Language: Amharic

Book: Genesis

Genesis

Chapter 1

1 እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማይንና ምድርን ፈጠረ። 2 ምድርም ቅርፅ የሌላትና ባዶ ነበረች። ጥልቅ የሆነው ስፍራዋም በጨለማ ተውጦ ነበር።
የእግዚአብሔርም መንፈስ በውሃው ላይ ሰፍፎ ነበር። 3 እግዚአብሔርም፦ “ብርሃን ይሁን” አለ፤ ብርሃንም ሆነ። 4 እግዚአብሔርም ብርሃኑ መልካም እንደሆነ
አየ፤ ብርሃንኑም ከጨለማ ለየው። 5 እግዚአብሔርም ብርሃኑን ‘ቀን’ ጨለማውን ደግሞ ‘ሌሊት’ ብሎ ጠራው። ቀኑ መሸ ሌሊቱም ነጋ አንድ ቀን ሆነ። 6
እግዚአብሔርም፦ “በውሆች መካከል ጠፈር ይሁን፣ ውሆችንም ይለያዩ” አለ። 7 እግዚአብሔር ጠፈርን አደረገና ከጠፈር በላይና ከጠፈር በታች ያሉትን
ውሆች ለየ። እንደዚያም ሆነ። 8 እግዚአብሔር ጠፈሩን ‘ሰማይ’ብሎ ጠራው። ቀኑ መሸ ሌሊቱም ነጋ ሁለተኛ ቀን። 9 እግዚአብሔር፦ “ከሰማይ በታች ያለው
ውሃ ወደ አንድ ስፍራ ይሰብሰብ፣ ምድሩም ይገለጥ” አለ። እንደዚያም ሆነ። 10 እግዚአብሔርም ምድሩን ‘የብስ’፣ ወደአንድ ስፍራ የተሰበሰበውንም ውሃ
‘ባሕር’ ብሎ ጠራው። ይህም መልካም መሆኑን ተመለከተ። 11 እግዚአብሔር፦ እንደ ዓይነታቸው ዘርን የሚያፈሩ ተክሎችን፣ በውስጣቸው ዘርን ያዘሉ የፍራፍሬ
ዛፎችን እንደዓይነታቸው የሚያፈሩ አዝርዕትን ታብቅል” አለ። እንደዚያም ሆነ። 12 ምድር እንደአይነታቸው የሚያፈሩ አዝርዕትን አበቀለች። ይህም መልካም
እንደሆነ እግዚአብሔር ተመለከተ። 13 ቀኑ መሸ፣ ሌሊቱም ነጋ ሶስተኛ ቀን ሆነ። 14 እግዚአብሔር፦ “ቀኑን ከሌሊቱ ይለዩ ዘንድ በሰማይ ብርሃናት ይሁኑ።
እነዚህ ብርሃናት የዓመት ወቅቶችን፣ ቀናትንና ዓመታትን የሚለዩ ምልክቶች ይሁኑ። 15 ለምድርም ብርሃን ይሰጡ ዘንድ በሰማይ ላይ የሚገኙ ብርሃናት ይሁኑ”
አለ። እንደዚያም ሆነ። 16 እግዚአብሔር ታላቁ ብርሃን በቀን፣ ታናሹ ብርሃን በሌሊት ይሠለጥኑ ዘንድ ሁለት ታላላቅ ብርሃናትን አደረገ። ከዋክብትንም ደግሞ
አደረገ። 17 ለምድርም ብርሃን ይሰጡ ዘንድና 18 በቀንና በሌሊት ላይ እንዲሠለጥኑ እንደዚሁም ብርሃንን ከጨለማ እንዲለዩ በሰማይ አኖራቸው።
እግዚአብሔር ይህ መልካም እንደሆነ ተመለከተ። 19 ቀኑ መሸ፣ ሌሊቱም ነጋ አራተኛ ቀን ሆነ። 20 እግዚአብሔር፦ “ውሆች በሕያዋን ፍጡራን የተሞሉ ይሁኑ፣
ወፎችም ከምድር በላይ ባለው በሰማይ ጠፈር ይብረሩ” አለ። 21 እግዚአብሔር ታላላቅ የባሕር ፍጥረታትን እንደዚሁም በምድር የሚንቀሳቀሱ፣ በውሆች
ውስጥ የሚርመሰመሱና በክንፎቻቸው የሚበሩ ወፎችን እንደዓይነታቸው ፈጠረ። እግዚአብሔር ይህ መልካም እንደሆነ ተመለከተ። 22 እግዚአብሔርም፦
“ብዙ ተባዙ የባሕርን ውሆች ሙሉአቸው፣ ወፎችም በምድር ላይ ይብዙ” ብሎ ባረካቸው። 23 ቀኑ መሸ፣ ሌሊቱም ነጋ አምስተኛ ቀን ሆነ። 24
እግዚአብሔርም፦ “ምድር እንደወገናቸው ሕያው ፍጥረታትን ማለትም ከብቶችን፣ በምድር ላይ የሚሳቡትንና የምድር አራዊትን ታስገኝ” አለ። እንደዚያም ሆነ።
25 እግዚአብሔር በየዓይነታቸው የምድር አራዊትን፣ በየዓይነታቸው ማናቸውንም በምድር የሚሳቡትን ፈጠረ። 26 እግዚአብሔርም፦ “ሰውን በመልካችን እንደ
አምሳላችን እንፍጠር፣ ሰዎችም በባሕር ዓሣዎች፣ በሰማይ በሚበሩ ወፎችና በምድር ላይ በሚሳቡ ማናቸውም ተሳቢ ፍጥረቶች ላይ ሥልጣን ይኑራቸው” አለ።
27 እግዚአብሔር ሰውን በራሱ መልክ፣ በራሱም አምሳል ፈጠረው። ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። 28 እግዚአብሔር ባረካቸው እንደዚህም አላቸው፦ “ብዙ
ተባዙ፣ ምድርንም ሙሉአት ግዟትም። በባሕር ውስጥ ባሉት ዓሣዎች፣ በሰማይ ላይ በሚበሩት ወፎችና በምድር ላይ በሚንቀሳቀሱት ማናቸውም ሕያዋን
ፍጥረቶች ሁሉ ላይ ሥልጣን ይኑራችሁ” 29 እግዚአብሔርም፦ “እነሆ፣ ምግብ ይሆኑላችሁ ዘንድ በምድር ሁሉ ላይ በውስጣቸው ዘርን ያዘሉ ማናቸውንም
ተክሎችና በውስጣቸው ፍሬ ያላቸውን ማናቸውንም የፍራፍሬ ዛፎች ሰጥቻችኋለሁ። 30 በምድር ላይ ለሚገኙ እንስሳት ሁሉ፣ በሰማይ ለሚበሩ ወፎች ሁሉ፣
እንዲሁም በምድር ላይ ለሚሳቡ ፍጥረታት ሁሉ ማለትም የሕይወት እስትንፋስ ላለበት ማንኛውም ፍጡር ማንኛውም ለምለም ተክል ምግብ እንዲሆናቸው
ሰጥቻለሁ። እንደዚሁም ሆነ። 31 እግዚአብሔር የፈጠረውን ማንኛውንም ነገር ተመለከተ። እነሆ፣ እጅግ መልካም ነበረ። ቀኑ መሸ፣ ሌሊቱም ነጋ ስድስተኛ ቀን
ሆነ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 የምድር በውስጣቸው ያሉትም ሕያዋን ፍጡራን አፈጣጠር በዚህ ሁኔታ ተከናወነ። **2** እግዚአብሔር ይሠራ የነበረውን ሥራ በሰባተኛው ቀን ፈጽሞ በዚሁ ቀን
ከሥራው ሁሉ አረፈ። **3** እግዚአብሔር የመፍጠር ሥራውን ሁሉ ፈጽሞ ያረፈው በዚህ ቀን ስለሆነ ሰባተኛውን ቀን ባረከው ቀደሰውም። **4** እግዚአብሔር አምላክ
ሰማይንና ምድርን በፈጠረበት ወቅት የሰማይና የምድር የአፈጣጠራቸው ታሪክ እንደዚህ ነበር። **5** እግዚአብሔር አምላክ በምድር ላይ ዝናብ እንዲዘንብ
ስላደረገና ምድርንም የሚያለማ ሰው ባለመኖሩ በምድር ላይ ምንም ቡቃያ አልነበረም፣ በምድር ላይ የሚበቅል ተክልም ገና አልበቀለም። **6** ነገር ግን ውሃ
ከመሬት እየመነጨ የምድርን ገጽ ያረሰርስ ነበር። **7** እግዚአብሔር አምላክም ከምድር አፈር ሰውን አበጀው፤ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት፤
ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ። **8** እግዚአብሔር አምላክም በስተምሥራቅ በኩል በዔደን የአትክልት ስፍራ አዘጋጀ፣ የአበጀውንም ሰው በዚያ አኖረው። **9**
ከምድር ውስጥም እግዚአብሔር አምላክ ለዓይን የሚያስደስቱና ለምግብነት የሚጠቅሙ ልዩ ልዩ ዛፎች እንዲበቅሉ አደረገ። በአትክልት ስፍራው መካከልም
የሕይወት ዛፍ ነበር፣ መልካሙንና ክፉውን የሚያሳውቀውም ዛፍ በዚያ ነበር። **10** የአትክልት ስፍራውንም የሚያጠጣ ወንዝ ከኤደን ይፈስ ነበር። ወንዙም
ከኤደን ከወጣ በኋላ አራት ወንዞች ሆኖ ይከፋፈል ነበር። **11** የመጀመሪያው ፊሶን የተባለው ወንዝ ነበር፣ ይህም ወርቅ ይገኝበት የነበረውን መላውን የሐዊላ
ምድር አቋርጦ የሚፈሰው ወንዝ ነበር። **12** የዚያ አገር ወርቅ የጠራ ወርቅ ነበር፤ በተጨማሪም በዚያ አገር ሽቶና የከበሩ ድንጋዮች ነበሩ። **13** የሁለተኛው ወንዝ
ስም ግዮን ይባል ነበር፣ እርሱም መላውን የኢትዮጵያ ምድር አቋርጦ ይፈስ ነበር። **14** የሶስተኛው ወንዝ ስም ጤግሮስ ይባል ነበር፣ እርሱም በአሦር
በስተምሥራቅ ይፈሳል። አራተኛው ወንዝ ኤፍራጥስ ነበር። **15** እግዚአብሔር አምላክም የኤደንን የአትክልት ስፍራ ያለማና ይንከባከብ ዘንድ ሰውን ወስዶ በዚያ
አኖረው። **16** እግዚአብሔር አምላክም እንዲህ በማለት አዘዘው፣ “በአትክልቱ ስፍራ ካለው ከማንኛውም የፍሬ ዛፍ መብላት ትችላልህ። **17** ነገር ግን
መልካሙንና ክፉውን ከሚያሳውቀው ዛፍ አትብላ፣ ምክንያቱም ከእርሱ በበላህ ቀን በእርግጥ ትሞታለህ።” **18** ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር አምላክ፦ “ሰው
ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም። ስለዚህ የምትመቸውን ረዳት እፈጥርለታለሁ” አለ። **19** እግዚአብሔር አምላክም ከምድር አፈር የምድር እንስሶችንና
የሰማይ ወፎችን አበጀ። ምን ስም እንደሚያወጣላቸው ይመለከት ዘንድ ወደ አዳም አመጣቸው። ለእያንዳንዱ ሕያው ፍጡር አዳም ያወጣለት ስም ያ ስሙ ሆነ።
20 አዳም ለሁሉም ከብቶች፣ ለሁሉም የሰማይ ወፎችና ለምድር አራዊት ሁሉ ስም አወጣላቸው። ነገር ግን ለአዳም ለራሱ የምትመች ረዳት አልተገኘለትም። **21**
እግዚአብሔር አምላክ በአዳም ላይ ከባድ እንቅልፍ እንዲወስደው አደረገ፣ ስለሆነም አዳም አንቀላፋ። እግዚአብሔር አምላክ አዳም አንቀላፍቶ ሳለ ከጎድን
አጥንቶቹ አንዱን ወስዶ አጥንቱን የወሰደበትን ስፍራ በሥጋ ዘጋው። **22** እግዚአብሔር አምላክ ከአዳም ከወሰደው የጎድን አጥንት ሴት አድርጎ ሠራት። ወደ
አዳምም አመጣት። **23** አዳምም፦ “አሁን ይህቺ ከአጥንቴ የተገኘች አጥንት ከሥጋዬ የተገኘች ሥጋ ናት። ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል” አለ። **24** ስለዚህ
ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይጣመራል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። **25** አዳምና ሚስቱ ሁለቱም ራቁታቸውን ነበሩ፤ ይሁን እንጂ
አይተፋፈሩም ነበር።

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 እግዚአብሔር በምድር ላይ ከፈጠራቸው ማናቸውም ሌሎች አራዊቶች ሁሉ ይልቅ እባብ ተንኮለኛ ነበር። እርሱም ሴቲቱን፦ “በእርግጥ እግዚአብሔር ‘በአትክልቱ ስፍራ ካለው ከማንኛውም ዛፍ አትብሉ’ ብሎአልን?” ብሎ ጠየቃት። **2** ሴቲቱም ለእባቡ፦ “በአትክልቱ ስፍራ ካሉት የዛፎች ፍሬዎች መብላት እንችላለን፤ **3** ነገር ግን በአትክልቱ ስፍራ መካከል ስለሚገኘው ዛፍ እግዚአብሔር “እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ አትንኩትም” ብሎአል። **4** እባብም ለሴቲቱ፦ “በፍጹም አትሞቱም። **5** ከእርሱ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንደሚከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም መልካሙንና ክፉውን የምታውቁ እንደምትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው አላት።” **6** ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት መልካም፣ ሲያዩት ደስ የሚያሰኝና ጥበብንም ለማግኘት የሚያጓጓ እንደሆነ ተመልክታ ከፍሬው ወስዳ በላች፤ ከእርሷ ጋር ለነበረውም ለባሏ ከፍሬው ሰጠችው፣ እርሱም በላ። **7** የሁለቱም ዓይኖች ተከፈቱ፣ ራቁታቸውን እንደነበሩም አወቁ። የበለስ ቅጠሎችንም በማጋጠም ከሰፉ በኋላ ለራሳቸው መሸፈኛ ግልድም ሠሩ። **8** ቀኑ ወደ ምሽት ሲቃረብ በአትክልት ስፍራው ሲመላለስ የእግዚአብሔር አምላክን ድምፅ ሰሙ፤ ስለዚህ አዳምና ሚስቱ ከእግዚአብሔር አምላክ ፊት በመሸሸግ በአትክልቱ ስፍራ በነበሩት ዛፎች መካከል ተሸሸጉ። **9** እግዚአብሔር አምላክ አዳምን ጠራውና፣ “የት ነህ?” አለው። **10** አዳምም፣ “በአትክልቱ ስፍራ ውስጥ ድምፅህን ሰማሁና ራቁቴን ስለነበርሁ ፈራሁ፤ በዚህም ምክንያት ተሸሸግሁ።” **11** እግዚአብሔርም፦ “ራቁትህን እንደሆንክ ማን ነገረህ? ከእርሱ እንዳትበላ ብዬ ካዘዝኩህ ከዛፉ ፍሬ በላህን?” አለው። **12** አዳምም፦ “አብራኝ እንድትሆን የሰጠኸኝ ሴት ከዛፉ ፍሬ ሰጠችኝ፣ እኔም በላሁት” አለ። **13** እግዚአብሔር አምላክም ሴቲቱን፦ “ምንድነው ያደረግሽው?” አላት። ሴቲቱም፦ “እባቡ አታለለኝና በላሁ” አለች። **14** እግዚአብሔር አምላክም ለእባቡ፦ “ይህንን በማድረግህ ከእንስሳት ሁሉና ከምድር አራዊት ሁሉ ተለይተህ የተረገምህ ትሆናለህ። በደረትህ እየተሳብክ ትሄዳለህ፣ በሕይወት ዘመንህም ሁሉ አፈር ትበላለህ። **15** በአንተና በሴቲቱ፣ በዘርህና በዘሯ መካካል ጠላትነትን አደርጋለሁ። የእርሷ ዘር ራስህን ይቀጠቅጣል፣ አንተም ተረከዙን ትነክሳለህ” አለው። **16** ለሴቲቱም እንዲህ አላት፦ “በምጥ ጊዜ ጭንቅሽን አበዛለሁ፤ በስቃይም ትወልጃለሽ። ፈቃድሽ ወደ ባልሽ ይሆናል፣ እርሱም ገዢሽ ይሆናል።” **17** ለአዳምም እንደዚህ አለው፦ “የሚስትህን ቃል ሰምተህ ‘ከእርሱ እንዳትበላ’ ብዬ ካዘዝሁህ ከዛፉ ፍሬ ስለበላህ ከአንተ የተነሳ ምድር የተረገመች ትሁን፤ በሕይወትህ ዘመን ሁሉ በከባድ ድካም ምግብህን ከእርሷ ታገኛለህ። **18** ምድር እሾህና አሜኬላ ታበቅልብሃለች፤ የምድርንም ቡቃያ ትበላለህ። **19** ከተገኘህበት አፈር እስክትመለስ ድረስ በላብህ እንጀራን ትበላለህ። አፈር ነህና ወደ አፈር ተመልሰህ ትሄዳለህ”። **20** የሕያዋን ሁሉ እናት በመሆኗ አዳም ለሚስቱ ‘ሔዋን’ የሚል ስም አወጣላት። **21** እግዚአብሔር አምላክ ከቆዳ ልብስ አዘጋጅቶ አዳምንና ሚስቱን አለበሳቸው። **22** እግዚአብሔር አምላክ፦ “መልካምንና ክፉውን ለይቶ በማውቅ ረገድ አሁን ሰው ከእኛ እንደ አንዱ ሆኖአል። ስለዚህ አሁን እጁን ዘርግቶ ከሕይወት ዛፍ ፍሬ ቀጥፎ እንዳይበላ ለዘላለምም እንዳይኖር ሊፈቀድለት አይገባም” አለ። **23** በዚህም ምክንያት የተገኘባትን ምድር እንዲያለማ እግዚአብሔር አዳምን ከኤደን የአትክልት ስፍራ አስወጣው። **24** ስለዚህ እግዚአብሔር አዳምን ከአትክልት ስፍራው አባረረው፣ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውንም መንገድ ይጠብቁ ዘንድ ከኤደን የአትክልት ስፍራ በስተቀኝ በኩል ኪሩቤልን እንደዚሁም በየአቅጣጫው የምትገለባበጥ ነበልባላዊ ሰይፍ አኖረ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 አዳምም ከሚስቱ ከሔዋን ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጸመ። እርሷም ፀነሰች። ቃየንንም ወለደች። “በእግዚአብሔር ዕርዳታ ወንድ ልጅ ወለድሁ” አለች። **2** ከዚያ በኋላም ወንድሙን አቤልን ወለደች። አቤል የበግ እረኛ ሲሆን ቃየን ግን ገበሬ ሆነ። **3** ከዕለታት አንድ ቀን ቃየን ከምድር ፍሬ ለእግዚአብሔር መባ አቀረበ። **4** አቤል ደግሞ መጀመሪያ ከተወለዱ በጎች መካከል ስባቸውን መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ። እግዚአብሔር በአቤልና በመሥዋዕቱ ደስ ተሰኘ፣ **5** በቃየንና በመሥዋዕቱ ግን ደስ አልተሰኘም። ስለዚህ ቃየን በጣም ተቆጣ፣ ፊቱም ተኮሳተረ። **6** እግዚአብሔር አምላክ ቃየንን፦ “ለምን ተቆጣህ፣ ፊትህስ ለምን ተኮሳተረ? **7** መልካም ብታደርግ ፊትህ ያበራ አልነበረምን? ያደረግኸው መልካም ካልሆን ግን ኃጢአት በደጅህ እያደባች ናት፣ ልትቆጣጠርህም ትፈልጋለች፣ አንተ ግን በቁጥጥርህ ሥር አድርጋት” አለው። **8** ቃየን ወንድሙን አቤልን፦ “ወደ ሜዳ እንውጣ” አለው፣ በዚያም ቃየን በወንድሙ በአቤል ላይ በቁጣ ተነሳበት፣ ገደለውም። **9** ከዚያ በኋላም እግዚአብሔር ቃየንን፦ “ወንድምህ አቤል ወዴት ነው?” አለው። እርሱም፦ “አላውቅም፣ እኔ የወንድሜ ጠባቂ ነኝን?” አለ። **10** እግዚአብሔርም፦ “ያደረግኸው ምንድን ነው? የወንድምህ ደም ከምድር ወደ እኔ ይጮኻል” አለው። **11** “አሁንም የወንድምህን ደም ከእጅህ ለመቀበል አፍዋን በከፈተች በምድር ላይ አንተ የተረገምህ ነህ። **12** ምድርንም በምታርስበት ጊዜ ፍሬዋን በሙላት አትሰጥህም። በምድር ላይ ኮብላይና ተንከራታች ትሆናለህ” አለው። **13** ቃየንም ለእግዚአብሔር፦ ቅጣቴ ከምችለው በላይ ነው። **14** በእርግጥም ዛሬ ከምድሪቱ አባርረኸኛል፣ እኔም ከፊትህ እሸሸጋለሁ። በምድር ላይ ኮብላይና ተንከራታች እሆናለሁ፣ የሚያገኘኝም ሁሉ ይገድለኛል” አለው። **15** እግዚአብሔርም፦ “ቃየንን የሚገድል ማንኛውም ሰው ሰባት እጥፍ የበቀል እርምጃ ይወሰድበታል” አለ። ከዚያ በኋላም የሚያገኘው ማንኛውም ሰው እንዳይገድለው እግዚአብሔር በቃየን ላይ ምልክት አደረገበት። **16** ቃየንም ከእግዚአብሔር ፊት ወጥቶ ሄደ፣ ከኤደን በስተምሥራቅ በነበረው ኖድ በተባለው ምድር ኖረ። **17** ቃየንም ከሚስቱ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጸመ፣ እርሷም ፀነሰች፣ ሄኖክንም ወለደች። ቃየን ከተማን መሠረተ፣ የመሠረታትንም ከተማ በልጁ ስም ሄኖክ ብሎ ጠራት። **18** ሄኖክም አራድን ወለደ። አራድም መሑያኤልን ወለደ። መሑያኤልም መቱሳኤልን ወለደ። መቱሳኤልም ላሜክን ወለደ። **19** ላሜክም ዓዳና ጲላ የተባሉ ሁለት ሚስቶችን አገባ። **20** ዓዳ ያባልን ወለደች፣ እርሱም በድንኳን ለሚኖሩ ለከብት አርቢዎች አባት ነበር። **21** የእርሱ ወንድም ዩባልም የበገና ደርዳሪዎችና የዋሽንት ነፊዎች አባት ነበር። **22** ጲላም ከነሐስና ከብረት መሣሪያዎችን የሚሠራውን ቱባልቃይንን ወለደች። የቱባልቃይንም እህት ናዕማ ትባል ነበር። **23** ላሜክ ለሚስቶቹ፦ “አዳና ጲላ ስሙኝ፣ እናንተ የላሜክ ሚስቶች የምላችሁን ስሙኝ ስለጎዳኝና ስላቆሰለኝ አንድ ሰው ገድያለሁ። **24** ቃየንን የሚገድል ሰባት እጥፍ የበቀል እርምጃ የሚወሰድበት ከሆነ የላሜክ ገዳይማ ሰባ ሰባት እጥፍ የበቀል እርምጃ ይወሰድበታል” አላቸው። **25** አዳም ከሚስቱ ጋር እንደገና የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጸመ፣ እርሷም ወንድ ልጅ ወለደች። “ቃየን በገደለው በአቤል ፈንታ እግዚአብሔር ምትክ ሰጠኝ” በማለት ስሙን ሤት ብላ ጠራችው። **26** ለሤትም ወንድ ልጅ ተወለደለት፣ ስሙንም ሄኖስ አለው። በዚያም ዘመን ሰዎች የእግዚአብሔርን ስም መጥራት ጀመሩ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 5

1 የአዳም የትውልድ ሐረግ እንደሚከተለው ነው። እግዚአብሔር ሰውን በፈጠረው ጊዜ በራሱ አምሳያ ፈጠራቸው፤ **2** ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፣ ባረካቸውም። በተፈጠሩም ጊዜ ‘ሰው’ ብሎ ጠራቸው። **3** አዳም ዕድሜው 130 ዓመት በሆነ ጊዜ፣ እርሱን የሚመስል ወንድ ልጅ ወለደ፣ ስሙንም ‘ሄት’ ብሎ ጠራው። **4** አዳም ሄትን ከወለደ በኋላ 800 ዓመታት ኖረ። ሌሎችን ወንዶችንና ሴቶች ልጆችን ወለደ፤ **5** 930 ዓመት ሲሆነውም ሞተ። **6** ሄት ዕድሜው 105 ሲሆን ሄኖስን ወለደ። **7** ሄኖስን ከወለደ በኋላ ሄት 807 ዓመት ኖረ። ሌሎች ወንዶችንና ሴቶች ልጆችን ወለደ። **8** ሄት 912 ዓመታት ከኖረ በኋላ ሞተ። **9** ሄኖስ 90 ዓመት ሲሆነው ቃይናንን ወለደ። **10** ሄኖስ ቃይናንን ከወለደ በኋላ 815 ዓመታት ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችንና ሴቶች ልጆችን ወለደ። **11** ሄኖስ 905 ዓመታት ከኖረ በኋላ ሞተ። **12** ቃይናን 70 ዓመት ሲሆነው መላልኤልን ወለደ። **13** ቃይናን መላልኤልን ከወለደ በኋላ 840 ዓመታት ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችንና ሴቶች ልጆችን ወለደ። **14** ቃይናን 910 ዓመታት ከኖረ በኋላ ሞተ። **15** መላልኤል 65 ዓመት ሲሆነው ያሬድን ወለደ። **16** መላልኤል ያሬድን ከወለደ በኋላ 800 ዓመታት ኖረ። ሌሎች ወንዶችንና ሴቶች ልጆችን ወለደ። **17** መላልኤል 895 ዓመታት ከኖረ በኋላ ሞተ። **18** ያሬድ 162 ዓመት ሲሆነው ሄኖክን ወለደ። **19** ያሬድ ሄኖክን ከወለደ በኋላ 800 ዓመታት ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችንና ሴቶች ልጆችን ወለደ። **20** ያሬድ 962 ዓመታት ከኖረ በኋላ ሞተ። **21** ሄኖክ 65 ዓመት ሲሆነው ማቱሳላን ወለደ። **22** ሄኖክ ማቱሳላን ከወለደ በኋላ የእግዚአብሔርን መንገድ በመከተል 300 ዓመታት ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችንና ሴቶች ልጆችን ወለደ። **23** ሄኖክ 365 ዓመታት ኖረ። **24** ሄኖክ የእግዚአብሔርን መንገድ በመከተል ኖረ፣ ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር ስለወሰደው አልተገኘም። **25** ማቱሳላ 187 ዓመት ሲሆነው ላሜሕን ወለደ። **26** ማቱሳላ ላሜሕን ከወለደ በኋላ 782 ዓመታት ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችንና ሴቶች ልጆችን ወለደ። **27** ማቱሳላ 969 ዓመታት ከኖረ በኋላ ሞተ። **28** ላሜሕ 182 ዓመት ሲሆነው አንድ ወንድ ልጅ ወለደ። **29** “ይህ ልጅ እግዚአብሔር በረገማት ምድር ከልፋታችንና ከብርቱ ሥራችን ያሳርፈናል” ሲል ስሙን ‘ኖህ’ ብሎ ጠራው። **30** ላሜሕ ኖህን ከወለደ በኋላ 595 ዓመታት ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችንና ሴቶች ልጆችን ወለደ። **31** ላሜሕ 777 ዓመታት ከኖረ በኋላ ሞተ። **32** ኖህ 500 ዓመታት ሲሆነው ሴም፣ ካምንና ያፌትን ወለደ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 6

1 የሰው ልጆች በምድር ላይ እየበዙ ሲሄዱ ሴቶች ልጆች ተወለዱላቸው። **2** የእግዚአብሔር ልጆችም የሰዎች ሴቶች ልጆች የሚስብ ውበት እንዳላቸው ተመለከቱ። ከእነርሱ መካከልም የመረጧቸውን ሚስቶች አድርገው ወሰዱ። **3** እግዚአብሔርም፦ “እርሱ ሥጋ ስለሆነ መንፈሴ በሰው ላይ ለዘላለም አይኖርም፤ ዕድሜውም 120 ዓመት ይሆናል” አለ። **4** የእግዚአብሔር ልጆች ከሰዎች ሴቶች ልጆች ጋብቻ በፈጸሙና ልጆችን በወለዱበት በዚያን ጊዜ ከዚያም በኋላ ኔፊሊም የተባሉ ግዙፍ ሰዎች በምድር ላይ ነበሩ። እነርሱም በጥንት ዘመን ዝናን ያተረፉ ኀያላን ነበሩ። **5** እግዚአብሔር የሰው ልጆች ክፋት በምድር ላይ እየበዛ እንደሆነና የልቡም ሃሳብ ዘወትር ወደ ክፋት ብቻ ያዘነበለ መሆኑን ተመለከተ። **6** እግዚአብሔር የሰው ልጆችን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ ልቡም አዘነ። **7** በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር፦ “የፈጠርሁትን የሰው ልጅ ከምድር ገጽ አጠፋለሁ፤ ስለፈጠርኋቸው ተጸጽቻለሁና ከእነርሱም ጋር እንስሳትን፣ በደረታቸው የሚሳቡትን ፍጥረታትና የሰማይ ወፎችን ሁሉ አጠፋለሁ” አለ። **8** ኖኅ ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ አገኘ። **9** የኖኅ ታሪክ እንደሚከተለው ነው። ኖኅ በዘመኑ ከነበሩት ሰዎች ሁሉ ይልቅ ጻድቅና ከበደል የራቀ ሰው ነበር፤ የእግዚአብሔርንም መንገድ የሚከተል ሰው ነበር። **10** ኖኅ ሴም፣ ካምና ያፌት የተባሉትን ሶስት ወንዶች ልጆች ወለደ። **11** በእግዚአብሔር ፊት በክፉ ሥራ ረከሰች በዓመፅም ተሞላች። **12** እግዚአብሔር ምድርን ተመለከተ፣ የተበላሸች እንደሆነችና በምድር የሚኖሩትም ሰዎች ሁሉ በክፋት እንደሚኖሩ አየ። **13** እግዚአብሔርም ኖኅን፦ “ሥጋን የለበሰ ሁሉ ፍጻሜ ደርሶአል፣ ከእነርሱ የተነሳ ምድር በግፍ ተሞልታለችና። እኔም በእርግጥ ከምድር ጋር አጠፋቸዋለሁ። **14** አንተ ግን ከጥሩ እንጨት መርከብ ሥራ፤ መርከቧም ክፍሎች እንዲኖራት አድርግ፤ ውስጧንና ውጭዋንም በቅጥራን ለቅልቀው። **15** እንደዚህ አድርገህ ሥራት፦ ርዝመቷ 140 ሜትር፣ ወርዷ 23 ሜትር፣ ከፍታዋ 13. 5 ሜትር ይሁን። **16** ለመርከቧ ጣራ አብጅላት፣ ጣራና ግድግዳው በሚጋጠምበት ቦታ ግማሽ ሜትር ክፍተት ተው፤ ከጎኗ በር አውጣላት፤ ባለ ሦስት ፎቅ አድርገህ ሥራት። **17** እኔም ከሰማይ በታች የሕይወት እስትንፋስ ያለባችውን ፍጡራን ሁሉ ለማጥፋት እነሆ በምድር ላይ የጥፋት ውሃ አወርዳለሁ፤ በምድር ላይ ያለ ሁሉ ይጠፋል። **18** ከአንተ ጋር ግን ቃል ኪዳን እገባለሁ፤ አንተና ሚስትህ፣ ልጆችህና የልጆችህ ሚስቶች ከአንተ ጋር ወደ መርከቧ ትገባላችሁ። **19** ከአንተ ጋር በሕይወት እንዲቆዩ ከሕያዋን ፍጡራን ሁሉ ወንድና ሴት እያደረግህ ሁለት ሁለቱን ወደ መርከቧ ታስገባለህ። **20** ከእያንዳንዱ የወፍ ወገን፣ ከእያንዳንዱ የእንስሳ ወገን፣ በምድር ላይ ከሚሳቡ ፍጥረት ሁሉ በየወገናቸው በሕይወት ይቆዩ ዘንድ ወደ አንተ ይምጡ። **21** ለአንተና ለእነዚህ ፍጥረቶች ሁሉ የሚበቃ ልዩ ልዩ ዓይነት ምግብ በመርከቡ ውስጥ አከማች።” **22** ኖኅም እግዚአብሔር ያዘዘውን ሁሉ አደረገ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 7

1 እግዚአብሔር ኖኅን እንዲህ አለው፦ “በዚህ ትውልድ መካከል አንተን ጻድቅ ሆነህ አግኝቼሃለሁና ቤተሰብህን በሙሉ ይዘህ ወደ መርከቧ ግባ። **2** ከንፁህ እንስሳት ሁሉ ሰባት ሰባት ወንድና ሴት፣ ንፁሕ ካልሆኑት እንስሳት ደግሞ ሁለት ሁለት ወንድና ሴት ከአንተ ጋር አስገባ። **3** እንዲሁም ከሰማይ ወፎች ወገን ሰባት ወንዶችና ሰባት ሴቶች በምድር ላይ ለዘር እንዲተርፉ ከአንተ ጋር ታስገባለህ። **4** ከሰባት ቀን በኋላ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት በመድር ላይ ዝናብ አዘንባለሁ፤ የፈጠርሁትንም ሕያው ፍጡር ሁሉ ከምድር ላይ አጠፋለሁ።” **5** ኖኅም እግዚአብሔር ያዘዘውን ሁሉ አደረገ። **6** የጥፋት ውሃ በምድር ላይ በወረደ ጊዜ ኖኅ የ600 ዓመት ሰው ነበር። **7** ኖኅና ወንዶች ልጆቹ ሚስቱና የልጆቹ ሚስቶች ከጥፋት ውሃ ለማምለጥ ወደ መርከቡ ገቡ። **8** ንፁሕ ከሆኑትና ንፁሕ ካልሆኑት እንስሳት ከወፎችና በምድር ላይ ከሚሳቡ ፍጡራን ሁሉ **9** ጥንድ ጥንድ ወንድና ሴት ሆነው ወደ ኖኅ መጡ፤ እግዚአብሄር ኖኅን ባዘዘው መሠረትም ወደ መርከቧ ገቡ። **10** ከሰባት ቀንም በኋላ የጠፋት ውሃ በምድር ላይ መጣ። **11** ኖኅ በተወለደ በ600ኛው ዓመት በሁለተኛው ወር ከወሩም በአሥራ ሰባተኛው ቀን የታላቁ ጥልቅ ምንጮች በሙሉ ተነደሉ፤ የሰማይ መስኮቶችም ተከፈቱ። **12** ዝናቡም መዝነብ ጀመረ፣ አርባ ቀንና አርባ ሌሊትም ባለማቋረጥ በምድር ላይ ዘነበ። **13** ዝናቡ መዝነብ በጀመረበት ቀን ኖኅና ሚስቱ ከልጆቻቸው ጋር ከሴም ከካም ከያፌትና ከሶስቱም ልጆቻቸው ሚስቶች ጋር ወደ መርከቡ ገቡ። **14** ከአራዊት ከእንስሳት በደረታቸው እየተሳቡ ከሚንቀሳቀሱ ፍጥረቶችና በሰማይ ከሚበሩ ወፎች ከእያንዳንዱ ዓይነት አብረዋቸው ገቡ። **15** የሕይወት እስትንፋስ ያለባቸው ፍጡራን በሙሉ ጥንድ ጥንድ እየሆኑ ከኖኅ ጋር ወደ መርከቡ ገቡ። **16** ከሕያዋንም ፍጡራን ሁሉ እግዚአብሔር ኖኅን ባዘዘው መሠረት ወንድና ሴት እየሆኑ ገቡ፤ ከዚያም እግዚአብሔር የመርከቡን በር ከውጭ ዘጋ። **17** የጥፋት ውሃም ለአርባ ቀናት ያለመቋረጥ በምድር ላይ ዘነበ ውሃው እየጨመረ በሄድ መጠን መርከቧን ከምድር ወደ ላይ አነሳት። **18** ውሃው በምድር ላይ በጣም እየጨመረና ከፍ እያለ ሲሄድ፣ መርከቧ በውሃ ላይ ተንሳፈፈች። **19** ውሃው በጣም ከፍ በማለቱ፣ ከሰማይ በታች ያሉትን ታላላቅ ተራሮች ሁሉ ሸፈናቸው። **20** ውሃው ከተራሮች ጫፍ በላይ 7ሜትር ያህል ከፍ አለ። **21** በምድር ላይ የነበሩ ሕያዋን ፍጡራን ሁሉ፦ ወፎች፣ የቤት እንስሳት፣ አራዊት፣ በምድር የሚርመሰመሱ ፍጡራን ሰዎችም በሙሉ ጠፉ። **22** የሕይወት እስትንፋስ ያላቸው በምድር የነበሩ ፍጡራን ሁሉ ሞቱ። **23** ሕይወት ያላቸው ፍጡራን ሁሉ ከሰዎች ጀምሮ እንስሳት፣ በምድር ላይ የሚሳቡ ፍጡራንና የሰማይ ወፎች ሁሉም ከምድር ገጽ ጠፉ። ኖኅና ከእርሱ ጋር በመርከቧ ውስጥ የነበሩት ብቻ ተረፉ። **24** ውሃውም ምድርን ሸፍኖ መቶ አምሳ ቀን ቆየ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 8

1 እግዚአብሔር ኖኅንና ከእርሱ ጋር በመርከቧ ውስጥ የነበሩትን አራዊትና እንስሳት ሁሉ አሰበ። በምድር ላይ ነፋስ እንዲነፍስ አደረገ ውሃውም ጎደለ። **2** የጥልቁ ምንጮችና የሰማይ መስኮቶች ተዘጉ፣ ዝናቡም መዝነቡን አቆመ። **3** ውሃው ከምድር ላይ ቀስ በቀስ እየቀነሰ መጣ፤ ከመቶ ሃምሳ ቀን በኋላም የውሃው ከፍታ እጅግ ቀነሰ። **4** በሰባተኛው ወር፤ በአሥራ ሰባተኛው ቀን መርከቧ በአራራት ተራሮች ላይ አረፈች። **5** ውሃው እስከ አሥረኛው ወር ድረስ ቀስ በቀስ እየጎደለ ሄደ። በአሥረኛው ወር መጀመሪያው ቀን የተራሮች ጫፎች ታዩ። **6** ከአርባ ቀን በኋላ ኖኅ የሠራውን የመርከቧን መስኮት ከፍቶ፣ **7** ቁራን ወደ ውጭ ላከ፤ ቁራውም ውሃው ከምድር ላይ እስኪደርቅ ድረስ ወዲያና ወዲህ ይበር ነበር። **8** ከዚያም በኋላ ኖኅ ውሃው ከምድር ላይ ገጽ ጎድሎ እንደሆነ ለማወቅ ርግብን ላከ፤ **9** ነገር ግን ውሃው ገና ምድርን ሁሉ ሸፍኖ ስለነበር ርግቢቱ የምታርፍበት ቦታ አላገኘችም፤ ስለዚህ ኖኅ ወዳለበት መርከብ ተመልሳ መጣች፤ ኖኅም እጁን ዘርግቶ ወደ መርከቡ ውስጥ አስገባት። **10** ሰባት ቀን ከቆየ በኋላ ኖኅ ርግቧን እንደገና ላካት። **11** እርሷም ወደ ማታ ተመለሰች፤ እነሆም የለመለመ የወይራ ቅጠል በአፏ ይዛ ነበር፤ ከዚህም የተነሣ ኖኅ ውሃው ከምድር ላይ መጉደሉን አወቀ። **12** ደግሞም ሰባት ቀን ከቆየ በኋላ ኖኅ ርግቢቱን እንደገና አውጥቶ ላካት፤ በዚህ ጊዜ ግን ርግቢቱ ወደ እርሱ አልተመለሰችም። **13** ኖኅ በተወለደ 601ኛው ዓመት፣ በመጀመሪያው ወር፣ ከወሩም በመጀመሪያው ቀን ውሃው ከምድር ላይ ደረቀ። ኖኅ የመርከቡን ክዳን አንሥቶ ዙሪያውን ተመለከተ፣ ምድሪቱም እንደደረቀች አየ። **14** በሁለተኛው ወር፣ በሃያ ሰባተኛው ቀን ምድሪቱ ሙሉ በሙሉ ደረቀች። **15** ከዚያም እግዚአብሔር ኖኅን እንዲህ አለው። **16** “አንተና ሚስትህ፣ ልጆችህና የልጆችህ ሚስቶች ከመርከቧ ውጡ። **17** እንዲዋለዱ፣ እንዲራቡና በምድር ላይ እንዲበዙ ከአንተ ጋር ያሉትን ወፎች፣ እንስሳትና በምድር ላይ የሚሳቡ ሕያዋን ፍጡራንን ሁሉ ይዘሃቸው ውጣ።” **18** ስለዚህ ኖኅ ከልጆቹ፣ ከሚስቱና ከልጆቹ ሚስቶች ጋር ወጣ። **19** እንስሳቱ ሁሉ፣ ወፎችም፣ በምድር የሚሳቡት፣ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱ ሕያዋን ፍጥረታት ሁሉ በየወገናቸው ከመርከቧ ወጡ። **20** ኖኅም ለእግዚአብሔር መሠዊያን ሠራ። ንፁሕ ከሆኑት እንስሳትና ንፁሕ ከሆኑት ወፎች አንዳንዶቹን ወስዶ የሚቃጠል መሥዋዕት አቀረበ። **21** እግዚአብሔርም ደስ የሚያሰኘውን መዓዛ አሸተተ፣ በልቡም እንዲህ አለ፦ “ምንም እንኳ ሰው ገና ከልጅነቱ ጀምሮ ሐሳቡ ወደ ክፋት ያዘነበለ ቢሆንም በእርሱ ምክንያት ሁለተኛ ምድርን አልረግማትም፤ አሁን እንዳደረግሁት ሕያዋን ፍጡራንን ዳግመኛ አላጠፋም። **22** ምድር እስካለች ድረስ የዘር ወቅትና መከር፣ ሙቀትና ቅዝቃዜ፣ በጋና ክረምት፣ ቀንና ሌሊት አይቋረጡም።”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 9

1 ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ኖኅንና ልጆቹን እንዲህ ሲል ባረካቸው፦ “ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት፤ **2** አስፈሪነታችሁና አስደንጋጭነታችሁ በእንስሳት፣ በሰማይ ወፎች፣ በደረት በሚሳቡ ተንቀሳቃሽ ፍጡሮችና በባሕር ዓሦች፣ በምድር ላይ በሚገኙ ሕያዋን ፍጡራን ሁሉ ላይ ይሁን። ሁሉም በሥልጣናችሁ ሥር ይሁኑ። **3** ሕያውና ተንቀሳቃሽ ፍጡር ሁሉ ምግብ ይሁናችሁ፣ ለምለሙን ዕፅዋት እንደሰጠኋችሁ፣ አሁን ደግሞ ሁሉን ሰጠኋችሁ። **4** ነገር ግን ሕይወቱ ማለት ደሙ ገና በውስጡ ያለበትን ሥጋ አትብሉ። **5** ሰውን የገደለ ሁሉ ስለሟቹ ደም ተጠያቂ ነው፤ የሟቹን ሰው ደም ከገዳዩ ከእንስሳም ይሁን ከሰው እሻለሁ። **6** የሰውን ደም የሚያፈስ ሁሉ ደሙ በሰው እጅ ይፈሳል፤ በእግዚአብሔር አምሳል እግዚአብሔር ሰውን ሠርቶታልና። **7** እናንተ ግን ብዙ ተባዙ፣ ዘራችሁ በምድር ላይ ይብዛ ይንሠራፋም።” **8** ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ለኖኅና ለልጆቹ እንዲህ አላቸው፦ **9** “እነሆ ከእናንተና ከእናንተ በኋላ ከሚመጣው ዘራችሁ ጋር ኪዳኔን እመሠርታለሁ፤ **10** እንዲሁም ከእናንተ ጋር ከነበሩት ሕያዋን ፍጡራን ሁሉ ከወፎች፣ ከእንስሳት ከእናንተ ጋር ከመርከቧ ከወጡት በምድር ላይ ካሉት ሕያዋን ፍጡራን ሁሉ ጋር ኪዳን እገባለሁ። **11** ከእንግዲህ ሕይወት ያለው ፍጡር ሁሉ በጥፋት ውሃ እንደማይጠፋ፣ ዳግመኛም ምድርን የሚያጠፋ ውሃ ከቶ እንደማይመጣ ከእናንተ ጋር ኪዳን እገባለሁ።” **12** እግዚአብሔርም እንዲህ አለ፦ “በእኔና በእናንተ መካከል ከእናንተም ጋር ካሉ ሕያዋን ፍጡራን ሁሉ፣ ከሚመጣው ትውልድ ሁሉ ጋር፣ የማደርገው የኪዳኑ ምልክት ይህ ነው፤ **13** ቀስተ ደመናዬን በደመና ላይ አድርጋለሁ፤ ይህም በእኔና በምድር መካከል ለገባሁት ኪዳን ምልክት ይሆናል። **14** ደመናን በምድር ላይ በጋረድሁና ቀስቴም በደመና ላይ በሚታይበት ጊዜ ሁሉ **15** ከእናንተና ከሕያዋን ፍጡራን ሁሉ ጋር የገባሁትን ኪዳን አስባለሁ፤ ሕይወት ያለውንም ሁሉ ያጠፋ ዘንድ፣ ከእንግዲህ የጥፋት ውሃ ከቶ አይመጣም። **16** ቀስቱ በደመና ላይ ተገልጦ በማይበት ጊዜ ሁሉ በእኔና በምድር ላይ ባሉ ሕያዋን ፍጡራን መካከል ያለውን ዘላለማዊ ኪዳን አስባለሁ።” **17** ከዚያ በኋላም እግዚአብሔር ለኖኅ፦ “ይህ በእኔና በምድር ላይ በሚኖሩ ሕያዋን ሁሉ መካከል የገባሁት ኪዳን ምልክት ነው።” አለው። **18** ከመርከቧ የወጡትም የኖኅ ልጆች ሴም፣ ካምና ያፌት ነበር፤ ካም የከነዓን አባት ነው። **19** እነዚህ ሶስቱ የኖኅ ልጆች ሲሆኑ፣ በምድር ላይ የሚኖሩ ሕዝቦች ሁሉ የተገኙት ከነዚሁ ነው። **20** ኖኅ ገበሬ መሆን ጀመረ፣ ወይንንም ተከለ። **21** ከወይኑም ጠጅ ጠጥቶ ሰከረና በድንኳኑ ውስጥ እርቃኑን ተኛ። **22** የከንዓን አባት ካም የአባቱን ዕርቃነ ሥጋ አየ፤ ወደ ውጭም ወጥቶ ለሁለቱ ወንድሞቹ ነገራቸው። **23** ሴምና ያፌት ግን ልብስ ወስደው በትከሻቸው ላይ አደረጉና የአባታቸውን ዕርቃነ ሥጋ እንዳያዩ ፊታቸውን አዙረው የኋሊት በመሄድ የአባታቸውን ዕርቃነ ሥጋ ሸፈኑ። **24** ኖኅ ከወይን ጠጁ ስካር ሲነቃ ታናሽ ልጁ ያደረገበትን አወቀ። **25** ከዚህም የተነሣ፦ “ከነዓን የተረገመ ይሁን፤ ለወንድሞቹም አገልጋይ ይሁን።” አለ። **26** ደግሞም፦ “የሴም አምላክ የሆነው እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን፣ ከነዓንም የሴም አገልጋይ ይሁን። **27** እግዚአብሔር የያፌትን ግዛት ያስፋ፤ ያፌት በሴም ድንኳኖች ይኑር፤ ከነዓን የያፌት አገልጋይ ይሁን።” አለ። **28** ኖኅ ከጥፋት ውሃ በኋላ 350 ዓመት ኖረ። **29** ኖኅ በአጠቃላይ 950 ዓመት ኖሮ ሞተ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 10

1 የኖኅ ልጆች የሴም፣ የካምና የያፌት ዝርያዎች የሚከተሉት ናቸው። ከጥፋት ውሃም በኋላ ልጆች ተወለዱላቸው። **2** የያፌት ልጆች፦ ጋሜር፣ ማጎግ፣ ማዴ፣ ያዋን፣ ቶቤል፣ ሞሳሕና ቴራስ ነበሩ። **3** የጋሜር ልጆች፦ አስከናዝ፣ ሪፋትና ቴርጋማ ነበሩ። **4** የያዋን ልጆች፦ ኤሊሳ፣ ተርሴስ፣ ኪቲምና ሮዳኢ ነበሩ። **5** ከእነዚህም በየነገዳቸው በየጎሳቸውና በየቋንቋቸው ተከፋፍለው በባሕር ዳርና በደሴቶች በየምድራቸው የሚኖሩ ሕዝቦች ወጡ። **6** የካም ልጆች፦ ኩሽ፣ ምጽራይም፣ ፉጥና ከነዓን ነበሩ። **7** የኩሽ ልጆች፦ ሳባ፣ ኤውላጥ፣ ሰብታ፣ ራዕማና ሰበቀታ ነበሩ። የራዕማ ልጆች፦ ሳባና ድዳን ነበሩ። **8** ኩሽ በምድር ላይ የመጀመሪያው ታላቅ ጦረኛ የነበረው የናምሩድ አባት ነበር። **9** እርሱም በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ አዳኝ ነበር። ስለዚህም፣ “በእግዚአብሔር ፊት እንደ ናምሩድ ብርቱ አዳኝ” ይባል ነበር። **10** የግዛቱም የመጀመሪያ ከተሞች በሰናዖር ምድር የነበሩት፦ ባቢሎን፣ አሬክ፣ አርካድና ካልኔ ነበሩ። **11** ከዚያም ወደ አሦር ምድር ሄደና ነነዌን፣ ርሆቦትን፣ ካላሕን **12** እንዲሁም በነነዌና በካላሕ መካከል የነበረውን ታላቅ ከተማ ሬሴን የተባሉትን ከተሞች መሠረተ። **13** ምጽራይም የሎዳማውያን፣የዐናሚማውያን፣ የላህሚማውያን፣ የነፍታሌማውያን፣ **14** የፈተሩሲማውያንና ፍልስጥኤማውያን የተገኙባቸው የካስሎሂማውያንና የቀፍቶርማውያን አባት ነበር። **15** የከነዓንም የበኩር ልጅ ሲዶን ተከታዩም ሔት ይባሉ ነበር። **16** ሌሎቹም የከነዓን ዝርያዎች ኢያቡሳውያን፣ አሞራውያን፣ ጌርጌሳውያን፣ **17** ኤውያውያንን፣ ዓርቃውያን፣ ሲናውያን፣ **18** ኤርዋዳውያን፣ አርዋዳውያን፣ ደማራውያን፣ ሐማታውያን የሚባሉ ነበሩ። ከጊዜ በኋላ የከነዓን ጎሣዎች በየስፍራው ተሠራጩ። **19** የከነዓን ወሰን ከሲዶና አንሥቶ በጌራራ በኩል ገሞራን አዳማንና ሰቦይን ይዞ እስከ ላሣ ይዘልቃል። **20** እነዚህም በየጎሣቸውና በየቋንቋቸው በየምድራቸውና በየነገዳቸው ይኖሩ የነበሩ የካም ዝርያዎች ነበሩ። **21** ለያፌት ታላቅ ወንድም ለሴም ደግሞ ወንዶች ልጆች ተወለዱለት፤ እርሱም የዔቦር ልጆች ሁሉ ቅድመ አያት ነበር። **22** የሴም ልጆች ኤላም፣ አሦር፣ አርፋክስድ፣ ሉድ፣ አራም ነበሩ። **23** የአራም ልጆች ዑፅ፣ ሁል፣ ጌቴር፣ ሞሶሕ ነበሩ። **24** አርፋክስድ ሳላን ወለደ፤ ሳላም ኤቦርን ወለደ። **25** ዔቦርም ሁለት ወንዶች ልጆችን ወለደ። በዘመኑ ምድር ተከፍላ ስለነበር የአንደኛው ልጅ ስም ፍሌቅ ተባለ፤ ወንድሙም ዮቅጣን ተባለ። **26** ዮቅጣንም የአልሞዳድ፣ የሼሌፍ፣ የሐጸርማዌት፣ የዮራሕ፣ **27** የዐዶራም፣ የኢዛል፣ የዲቅላ፣ **28** የዖባል፣ የአቢማኤል፣ የሳባ፣ **29** የኦፊር፣ የሐዊላና የዮባብ አባት ነበር። እነዚህ ሁሉ የዮቅጣን ዝርያዎች ነበሩ። **30** መኖርያ ስፍራቸውም በስተምሥራቅ ባለው በተራራማው አገር ከሜሻ እስከ ስፋር ይደርስ ነበር። **31** እነዚህም በየጎሣቸውና በየቋንቋቸው በየምድራቸውና በየነገዳቸው ይኖሩ የነበሩ የሴም ዝርያዎች ነበሩ። **32** የኖኅ ወንዶች ልጆች ጎሣዎች እንደ ትውልዳቸው በየነገዳቸው እነዚህ ነበሩ። ከጥፋት ውሃ በኋላ ሕዝቦች በምድር ላይ የተሠራጩት ከእነዚሁ ነበር።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 11

1 በዚያ ዘመን መላው ዓለም የሚናገረውና የሚግባባው በአንድ ቋንቋ ነበር። **2** ወደ ምሥራቅ ሲጓዙ፣ በሰናዖር አንድ ሜዳማ ቦታ አግኝተው በዚያ ሰፈሩ። **3** እርስ በርሳቸውም፣ “ኑ፣ ጡብ እንሥራና እስከበቃው ድረስ በእሳት እንተኩሰው” ተባባሉ። በድንጋይ ፈንታ ጡብ ተጠቀሙ፤ ጡቡን እርስ በርስ ለማያያዝም ቅጥራን ተጠቀሙ። **4** ከዚያም፣ “ለስማችን መጠሪያ እንዲሆን ጫፉ ሰማይ የሚደርስ ግንብ እንሥራ። ያንን ካላደረግን በምድር ሁሉ ፊት መበታተናችን ነው” አሉ። **5** የአዳም ልጆች የሠሩትን ለማየት ያህዌ ወደ ከተማውና ወደ ግንቡ ወረደ። **6** ያህዌም፣ “አንድ ቋንቋ የሚናገሩ አንድ ሕዝብ በመሆናቸው ይህን ማድረግ ችለዋል! ከእንግዲህ ማድረግ የፈለጉትን ለማድረግ ምንም የሚያቅታቸው አይኖርም። **7** ኑ እንውረድ፤ አርስ በርስ እንዳይግባቡም ቋንቋቸውን እንደበላልቀው” አለ። **8** ስለዚህ ያህዌ ከዚያ ቦታ ወደ መላው ዓለም በታተናቸው፣ እነርሱም ከተማዋን መሥራት አቋረጡ። **9** በዚያ የዓለምን ቋንቋ ስለ ደበላለቀ የከተማዋ ስም ባቤል ተባለ። ከዚያም ያህዌ በመላው ዓለም በተናቸው። **10** የሴም ትውልድ ይህ ነው። የጥፋት ውሃ ከመጣ ሁለት ዓመት በኋላ ሴም መቶ ዓመት ሲሆነው አርፋድሰድን ወለደ። **11** አርፋድሰድን ከወለደ በኋላ ሴም አምስት መቶ ዓመት ኖረ። ሌሎች ወንዶች እና ሴቶች ልጆችንም ወለደ። **12** አርፋክሰድ በሰለሣ አምስት ዓመቱ ሰላን ወለደ፤ **13** ሰላን ከወለደ በኋላ አርፋክሰድ አራት መቶ ሦስት ዓመት ኖረ፤ እርሱም ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለደ። **14** ሳላ ሰላሣ ዓመት ሲሆነው ዔቦርን ወለደ፤ **15** ዔቦርን ከወለደ በኋላ ሳላ አራት መቶ ሦስት ዓመት ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችንም ወለደ። **16** ዔቦር አራት ዓመት ሲሆነው ፋሌቅን ወለደ፤ **17** ፋሌቅን ከወለደ በኋላ ዔቦር አራት መቶ ሰላሣ ዓመት ኖረ፤ እርሱም እንዲሁ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለደ። **18** ፋሌቅ ሰለሣ ዓመት ሲሆነው፣ ሪግውን ወለደ፤ **19** ሪግውን ከወለደ በኋላ ፋሌቅ ሁለት መቶ ዘጠኝ ዓመት ኖረ፤ እርሱም እንዲሁ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለደ። **20** ሪግው ሰለሣ ሁለት ዓመት ሲሆነው፣ ሴሮሕን ወለደ፤ **21** ሴሮሕን ከወለደ በኋላ ሪግው ሁለት ሞት ሰባት ዓመት ኖረ፤ እርሱም እንዲሁ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለደ። **22** ሴሮሕ ሰለሣ ዓመት ሲሆነው፣ ናኮርን ወለደ፤ **23** ናኮርን ከወለደ በኋላ ሴሮሕ ሁለት መቶ ዓመት ኖረ፤ እርሱም እንዲሁ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለደ። **24** ናኮር ሃያ ዘጠኝ ዓመት ሲሆነው ታራን ወለደ፤ **25** ታራን ከወለደ በኋላ ናኮር አንድ መቶ አሥራ ዘጠኝ ዓመት ኖረ፤ እርሱም እንዲሁ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆች ወለደ። **26** ታራ ሰባ ዓመት ሲሆነው አብራምን፣ ናኮርንና ሐራንን ወለደ። **27** የታራ ትውልድ ይህ ነው። ታራ፣ አብራምን፣ ናኮርንና ሐራን ወለደ። ሐራን ሎጥን ወለደ። **28** ሐራን አባቱ ታራ በሕይወት እያለ በተወለደበት ከተማ በከለዳውያን ዑር ሞተ። **29** አብራምና ናኮር ሁለቱም ሚስት አገቡ። የአብራም ሚስት ሦራ ስትባል፣ የናኮር ሚስት ደግሞ ሚልካ ትባል ነበር፤ ሚልካ የሐራን ልጅ ስትሆን፣ ሐራን የሚልካና የዮሳካ አባት ነበር። **30** ሦራ ምንም ልጅ ያልነበራት መካን ነበረች። **31** ታራ ልጁ አብራምን፣ የልጅ ልጁን ሎጥንና የአብራምን ሚስት ምራቱን ሦራን ይዞ ወደ ከነዓን ለመሄድ በከለዳውያን ምድር ከምትገኘው ዑር አብረው ወጡ። ሆኖም፣ ካራን በደረሱ ጊዜ በዚያ ተቀመጡ። **32** ታራ ሁለት መቶ አምስት ዓመት ኖሮ በካራን ሞተ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 12

1 በዚህ ጊዜ ያህዌ አብራምን እንዲህ አለው፤ “አገርህን፣ ወገንህንና የአባትህን ቤተ ሰብ ትተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ሂድ፤ **2** ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ፤
እባርክሃለሁ፤ ስምህን ገናና አደርገዋለሁ፤ ለሌሎችም በረከት አደርግሃለሁ። **3** የሚባርኩህን እባርካለሁ፤ የሚረግሙህንና የሚያዋርዱህን እረግማለሁ። በአንተ
አማካይነት በምድር የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ይባረካሉ።” **4** ስለዚህ አብራም ያህዌ እንዳዘዘው ወጣ፤ ሎጥም አብሮት ሄደ። አብራም ከካራን ተነሥቶ ሲሄድ፣ የሰባ
አምስት ዓመት ሰው ነበር። **5** አብራም ሚስቱ ሦራን፣ የውንድሙ ልጅ ሎጥን አስከትሎ በካራን ያፈሩትን ሀብትና የነበራቸውን አገልጋዮች ይዞ በመጓዝ፣ ከነዓን
ምድር ገቡ። **6** አብራም በሞሬ ያለው ግዙፍ የወርካ ዛፍ እስካለበት እስከ ሴኬም ዘልቆ ሄደ። በዚያ ዘመን ከነሻናውያን በዚህ ምድር ይኖሩ ነበር። **7** ያህዌ
ለአብራም ተገልጦ፣ “ይህችን ምድር ለዘርህ እሰጣለሁ” አለው። ስለዚህ አብራም ለተገለጠለት ለያህዌ በዚያ መሠዊያ ሠራ። **8** ከዚያ በመነሣት ከቤቴል
በስተ ምሥራቅ ወዳለው ተራራማ አገር ሄደ፤ ቤቴል በስተ ምዕራብ፣ ጋይ በስተ ምዕራብ ባለችበት ቦታ ድንኳኑን ተከለ። እዚያ ለያህዌ መሠዊያ ሠራ፤ የያህዌንም
ስም ጠርቶ ጸለየ። **9** አብራም ከዚያ ተነሥቶ ወደ ኔጌብ መጓዙን ቀጠለ። **10** በዚያ ምድር ጽኑ ራብ ስለ ነበር አብራም እዚያ ጥቂት ጊዜ ለመቆየት ወደ ግብፅ
ሄደ። **11** ግብፅ በመግባት ላይ እያለ አብራም ሚስቱ ሦራን እንዲህ አላት፤ “መቼም አንቺ ቆንጆ ሴት መሆንሽን አውቃለሁ። **12** ግብፃውያን ሲያዩሽ ‘ይህች
ሚስቱ ናት’ ይላሉ፤ እኔን ይገድሉኛል፤ አንቺን ግን ይተዉሻል። **13** ስለዚህ በአንቺ ምክንያት ለእኔ መልካም እንዲሆልኝ ሕይወቴም እንዲተርፍ እኅቱ ነኝ’ በዪ
አላት። **14** አብራም ወደ ግብፅ ሲገባ፣ ሦራ ምን ያህል ቆንጆ እንደ ሆነች ግብፃውያኑ አዩ። **15** የፈርኦን ሹማምንት ባዩአት ጊዜ እርሷን እያደነቁ ለፈርዖን ነገሩት፤
ወደ ቤተ መንግሥትም ተወሰደች። **16** በእርሷ ምክንያት ፈርኦን አብራምን በክብር አስተናገደው፤ በጎች፣ በሬዎች፣ ወንድ አህዮች ወንድና ሴት ባሪያዎች፣ ሴት
አህዮችና ግመሎች ሰጠው። **17** በአብራም ሚስት በሦራ ምክንያት ያህዌ ፈርዖንና ቤተ ሰቡን በታላቅ መቅሠፍት መታ። **18** ፈርዖን አብራምን አስጠርቶ እንዲህ
አለው፤ “ለመሆኑ ምን እያደረግህብኝ ነው? ሚስትህ መሆንዋን ለምን አልነገርከኝም? **19** ለምን እኅቴ ናት አልከኝ? እኅቴ ናት ስላልከኝ ሚስቴ ላደርጋት ነበር።
አሁንም ሚስትህ እቻት፤ ይዘሃት ሂድ” **20** ከዚያም ፈርዖን አብራምን በተመለከተ ለባለሟሎቹ ትእዛዝ ሰጠ፤ እነርሱም አብራምን ከሚስቱና ከንብረቱ ሁሉ ጋር
አሰናበቱት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 13

1 ስለዚህ አብራም ሚስቱንና ያለውን ንብረት ሁሉ ይዞ ከግብፅ ወደ ኔጌብ ሄደ። ሎጥም ከእነርሱ ጋር ነበረ። **2** በዚህ ጊዜ አብራም በከብት፣ በብርና በወርቅ በልጽጎ ነበር። **3** ከኔጌብ ተነሥቶ እስከ ቤቴል ተጓዘ፤ ቀድሞ ድንኳን ተክሎበት ወደ ነበረው በቤቴልና በጋይ መካከል ወደ ነበረው ቦታ ደረሰ። **4** ይህ ቀድሞ መሠዊያ የሠራበት ቦታ ሲሆን በዚያ ያህዌን ጠራ። **5** ከአብራም ጋር ይጓዝ የነበረው ሎጥ የራሱ በጎች፣ ከብቶችና ድንኳኖች ነበሩት። **6** ሁለቱ አንድ ላይ ይኖሩ ስለ ነበር ስፍራው አልበቃቸውም፤ በዚህ ላይ ንብረታቸውም በጣም ብዙ ስለ ነበር አብረው መኖር አልቻሉም። **7** ይህም በመሆኑ በአብራምና በሎጥ እረኞች መካከል ጠብ ተፈጠረ። በዚያ ዘመን ከነኣናውያንና ፌርዛውያን በዚያው አገር ይኖሩ ነበር። **8** አብራም ሎጥን እንዲህ አልው፤ “በእኔና በአንተ፣ በእኔ እረኞችና በአንተ እረኞች መካከል ግጭት መኖር የለበትም፤ በዚህ ላይ ደግሞ ቤተ ሰብ ነን። **9** ይኸው እንደምታየው ምድሩ ሰፊ ነው፤ ብንለያይ ይሻላል። አንተ ግራውን ብትመርጥ፣ እኔ ወደ ቀኝ እሄዳለሁ፤ ወይም አንተ ቀኙን ብትመርጥ እኔ ወደ ግራ እሄዳለሁ። **10** ስለዚህ ሎጥ ዙሪያውን ሲመለከት እስከ ዞዓር ድረስ ያለው የዮርዳኖስ ረባዳ ሜዳ ሁሉ እንደ ያህዌ ገነት እንደ የግብፅ ምድር በጣም ለም ሆኖ አገኘው። እንዲህ የነበረው እግዚአብሔር ሰዶምና ገሞራን ከማጥፋቱ በፊት ነበር። **11** ሎጥ የዮርዳኖስን ረባዳ ሜዳ ሁሉ መርቶ ወደ ምሥራቅ ተጓዘ፤ በዚህ ሁኔታ ዘመዳሞቹ ተለያዩ። **12** አብራም መኖሪያውን በከነዓን ምድር አደረገ፤ ሎጥ ግን በረባዳው ሜዳ ባሉት ከተሞች መካከል ኖረ። እስከ ሰዶም ድረስ ባለው ቦታ ድንኳኖቹን ተከለ። **13** የሰዶም ሰዎች በጣም ዐመፀኞችና በያህዌም ፊት እጅግ ኀጢአተኞች ነበሩ። **14** ሎጥ ከእርሱ ከተለየው በኋላ ያህዌ አብራምን እንዲህ አለው፤ “ካለህበት ቦታ ወደ ሰሜን፣ ወደ ደቡብ፣ ወደ ምሥራቅና ምዕራብ ተመልከት። **15** ይህን የምታየውን ምድር ሁሉ ለአንተና ለዘርህ ለዘላለም እሰጣለሁ። **16** ዘርህን እንደ ምድር ትቢያ አበዛዋለሁ፤ የምድር ትቢያ ሊቆጠር እንደማይቻል ሁሉ የአንተም ዘር ሊቆጠር አይችልም። **17** እንግዲህ ምድሪቱን ስለምስጥህ ተነሣና በርዝመትና በስፋቱ ተመላለሰባት።” **18** ስለዚህ አብራም ድንኳኑን ነቀለና በኬብሮን ወዳሉት የመምሬ ወርካ ዛፎች መጥቶ ኖረ፤ እዚያም ለያህዌ መሠዊያ ሠራ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 14

1 አምራፌል የሰናዖር ንጉሥ፣ አርዮክ የአላሳር ንጉሥ፣ ከሎደጎምር የኤላም ንጉሥ፣ ተድዓል የጎይም ንጉሥ፣ **2** በነበሩበት ዘመን፤ ከሰዶም ንጉሥ በላ፣ ከጎሞራ ንጉሥ ከብርሳ፣ ከአዳማ ንጉሥ ከሰነአብ፣ ከሰቦይ ንጉሥ ከሰሜበር፣ እንዲሁም ዞዓር ከተባለች ከቤላ ንጉሥ ጋር ለመዋጋት ወጡ። **3** እነዚህ የኋለኞቹ አምስት ነገሥታት የጨው ባሕር እየተባለች በምትጠራው በሲዶም ሸለቆ ተሰበሰቡ። **4** እነርሱም አሥራ ሁለት ዓመት ለኮሎዶጎምር ተገዙ፤ በአሥራ ሦስተኛው ዓመት ግን ዐመፁ። **5** በአሥራ አራተኛው ዓመት ከሎዶጎምርና ከእርሱም ጋር የነበሩት ነገሥታት መጥተው ራፋይምን፣ በአስታሮት ቃርናይምን፣ በካም ዙዚምን፣ በሴዊ ኑሚምን፣ በሸቨት ኢምንን፣ **6** የሖር ሰዎችንም በተራራማው አገር በሴይ በረሐማ አጠገብ እስካለው እስከ አልፋራን ድረስ ድል አደረጋቸው። **7** ከዚያም ተመልሰው ዓይንሚስፓጥ ወደሚባለው ወደ ቃዴስ መጡ፤ የአማሌዋውያንና በሐሴስ ታማር ይኖሩ የነበሩትን የአሞራውያን ግዛት በሙሉ ድል አድርገው ያዙ። **8** ከዚያም የሶዶም፣ የገሞራ፣ የአዳማ፣ የሰቦይ እንዲሁም ዞዓር የተባለችው የቤላ ነገሥታት ወደ ሲዶም ሸለቆ ሄደው ለጦርነት ተዘጋጁ። **9** እነዚህ አምስቱ በኤላም ንጉሥ በኮሎዶጎምር፣ በጎይም ንጉስ በቲድዓል፣ በሰናዖር ንጉሥ በአምራፌል፣ በአላሶር ንጉሥ በአርዮክ በእነዚህ ላይ ዘመቱባቸው። **10** በሲዲም ሸለቆ ብዙ የቅጥራን ጉድጓዶች ነበሩ፤ የሰዶምና የጎመራ ነገሥታት ሲሸሹ ከሰዎቻቸው አንዳንዶቹ በእነዚህ ጉድጓዶች ውስጥ ወደቁ። የተረፉትም ወደ ተራሮች ሸሹ። **11** አራቱ ነገሥታትም በሰዶምና በጎሞራ ያገኙትን ሀብትና ምግብ ሁሉ ዘርፈው ሄዱ። **12** በሰዶም ይኖር የነበረውን የአብርሃምን ወንድም ልጅ ሎጥንና የነበረውን ንብረት ሁሉ ይዘው ሄዱ። **13** ከዚያ ያመለጠ አንድ ሰው መጥቶ ለዕብራዊው ለአብራም ነገረው። በዚያ ጊዜ ይኖር የነበረው የአስኮና የእውናን ወንድም በነበረው በአሞራዊው መምሬ ዋርካ ዛፎች አጠገብ ነበር፤ እነዚህ ሁሉ የአብራም አጋሮች ነበር። **14** ጠላት ዘመዶቹን ማርኮ መውሰዱን አብራም ሲሰማ በቤቱ ተወልደው ያደጉ ሦስት መቶ አሥራ ስምንት ሰዎች ይዞ እስከ ዳን ድረስ ተከታተላቸው። **15** አብራም ጠላቶቹን ለማጥቃት ሰራዊቱን ሌሊቱን በቡድን በቡድን ከፋፍሎ ከደማስቆ በስተ ሰሜን እስከሚገኘው እስከ ሖባ ድረስ አሳደዳቸው። **16** ጠላት የማረከውን በሙሉ አስጣለ፤ ዘመዱ ሎጥንና ንብረቱን፣ እንዲሁም ሴቶቹንና ሌሎች ሰዎችን አስመለሰ። **17** አብራም የኮሎዶጎምርንና ከእርሱ ጋር የነበሩ ነገሥታትን ድል አድርጎ ሲመለስ የሰዶም ንጉሥ የንጉሥ ሸለቆ ተብሎ በሚጠራው በሴዊ ሸለቆ ሊቀበለው ወጣ። **18** የሰሌም ንጉሥ መልከጼዴቅ እንጀራና ወይን ጠጅ ይዞ መጣ። እርሱ የልዑል አምላክ ካህን ነበር። **19** አብራምም እንዲህ በማለት ባረከው፣ “ሰማይና ምድርን የፈጠረ ልዑል እግዚአብሔር አብራምን ይባርክ። **20** ጠላቶችህን በእጅህ አሳልፎ የሰጠ ልዑል እግዚአብሔር ይባረክ።” አብራምም ይዞት ከነበረው ሁሉ አንድ አሥረኛውን ሰጠው። **21** የሰዶም ንጉሥ አብራምን፣ “ሰዎቹን ለእኔ ስጠኝ፤ ንብረቱን ግን ለራስህ አስቀር” አለው። **22** አብራምም ለሰዶም ንጉሥ እንዲህ አለው፤ “ከአንተ ብጣሽ ክርም ሆነ የጫማ ማሰሪያ እንኳ ቢሆን፣ **23** ደግሞም ‘አብራምን ባለጸጋ አደረግሁት’ እንዳትል የአንተ ከሆነ ምንም ነገር እንዳልወስድ ሰማይና ምድርን ወደ ፈጠረ አምላክ ወደ ያህዌ እጄን አንሥቻለሁ። **24** አብረውኝ ያሉት ሰዎች ከበሉትና የእነርሱ ድርሻ ከሆነው በቀር ምንም ነገር አልወስድም። አውናን፣ ኤስኩልና መምሬ ድርሻቸውን ይውሰዱ።”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 15

1 ከዚህ በኋላ የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል ወደ አብራም መጣ፤ “አብራም ሆይ፣ አትፍራ፤ እኔ ለአንተ ጋሻህ ነኝ፤ ታላቅ ሽልማትህም እኔው ነን።” 2 አብራምም፣
“ጌታ ያህዌ ሆይ፣ እኔ ልጅ የለኝም፤ የቤት ወራሽ የሚሆነው የደማስቆው ሰው ኤሊዔዘር ነው፤ ታዲያ አንተ ለእኔ የምትሰጠኝ ምንድን ነው?” አለ። 3
በመቀጠልም አብራም “አንተ ልጅ እስካልሰጠኸኝ ድረስ፣ ከቤቴ አገልጋይ አንዱ ወራሼ መሆኑ አይቀርም” አለ። 4 በዚህ ጊዜ የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል ወደ
እርሱ መጣ፤ “ይህ ሰው ወራሽህ አይሆንም፤ ይልቁንም ወራሽህ የሚሆነው ከአብራክህ የሚከፈል የራስህ ልጅ ይሆናል።” 5 ከዚያም ወደ ውጭ አወጣውና
እንዲህ አለው፤ “ቀና ብለህ ወደ ሰማይ ተመልከት፤ መቍጠር ከቻልህ ከዋክብቱን ቍጠር። ዘርህም እንዲሁ ይበዛል።” 6 አብራም ያህዌን አመነ፤ እርሱም
ጽድቅ አድርጎ ቆጠረለት። 7 እንዲህም አለው፤ “ይህችን ምድር እንድትወርስ ልሰጥህ ከከለዳውያን ምድር ከዑር ያወጣሁህ እኔ ያህዌ ነኝ።” 8 አብራምም፣
“ጌታ ያህዌ ሆይ፣ ይህችን ምድር እንደምወርስ እንዴት አውቃለሁ?” አለ። 9 በዚህ ጊዜ፣ “እያንዳንዳቸው ሦስት ዓመት የሆናቸው አንዲት ጊደር፣ አንዲት ፍየልና
አንድ በግ እንዲሁም ዋኖስና አንድ ርግብ አቅርብልኝ” አለው። 10 እርሱም እነዚህን ሁሉ አቀረበለት፤ ቆርጦም ሁለት ቦታ ከከፈለቸው በኋላ እያንዳንዱን ክፍል
በሌላው ወገን ትይዩ አስቀመጣቸው፤ ወፎቹን ግን አልከፈለቸውም። 11 አሞሮች ሥጋውን ለመብላት ወረዱ፤ አብራምም አባረራቸው። 12 ፀሓይ ልትጠልቅ
ስትል አብራም ከባድ እንቅልፍ ወሰደው፤ የሚያስፈራም ድቅድቅ ጨለማም መጣበት። 13 በዚህ ጊዜ ያህዌ አብራምን እንዲህ አለው፤ “ዘሮችህ የራሳቸው
ባልሆነ ምድር ባዕድ እንደሚሆኑና እዚያ ለአራቶ መቶ ዓመት በባርነት እንደሚኖሩ በእርግጥ ዕወቅ። 14 እኔም ባሪያዎች ባደረጓቸው ሕዝብ እፈርዳለሁ፤ በኋላም
ብዙ ሀብት ይዘው ይወጣሉ። 15 አንተ ግን በሰላም ወደ አባቶችህ ትሄዳለህ፤ ዕድሜም ጠግበህ ትቀበራለህ። 16 በአራተኛውም ትውልድ እንደ ገና ወደዚህ
ይመጣሉ፤ ምክንያቱም የአሞራውያን ኀጢአት ጽዋው ገና አልሞላም።” 17 ፀሓይ ገብታ ከጨለመ በኋላ የምድጃ ጢስና የሚንበለበል ፋና በተቆራረጡት
ሥጋዎች መካከል አለፈ። 18 በዚያን ቀን ያህዌ እንዲህ በማለት ከአብራም ጋር ኪዳን አደረገ፤ “ከግብፅ ወንዝ ጀምሮ እስከ ታላቁ ወንዝ ኤፍራጥስ ድረስ
ያለውን ምድር ለዘርህ እሰጣለሁ፤ 19 የምሰጣቸውም የቄናውያንን፣ የቄንፌዛውያንን፣ የቃድሞናውያንን፣ 20 የኬጢያውያንን፣ የፌርዛውያንን፣ የራፋይምን፣ 21
የአሞራውያንን፣ የከነዓናውያን፣ የጌርሳውያንንና የኢያቡሳውያን ምድር ነው።”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 16

1 የአብራም ሚስት ሦራ ልጅ አልወለደችለትም ነበር፤ ነገር ግን አጋር የምትባል ግብፃዊት አገልጋይ ነበረቻት። **2** አብራምንም፣ "ያህዌ ልጅ እንዳልወደልድ አድርጎኛል። ምናልባት በእርሷ በኩል ልጅ አገኝ ይሆናልና ክአገልጋዬ ጋር ተኛ" አለችው። አብራም ሦራ በነገረችው ተስማማ። **3** የአብራም ሚስት ሦራ ግብፃዊት አገልጋይዋ ሚስት እንድትሆነው ለአብራም የሰጠችው አብራም በከነዓን ምድር አሥር ዓመት ከኖረ በኋላ ነበር። **4** አብራም ክአጋር ግን'ኡንት አደረገ እርሷም ፀነሰች። አጋር መፅነሷን ባወቀች ጊዜ እመቤቷን በንቀት ማየት ጀመረች። **5** በዚህ ጊዜ ሦራ አብራምን፣ "ይህ በደል የደረሰብኝ በአንተ ምክንያት ነው። ጎቅፍህ ውስጥ እንድትሆን አገልጋዬን ሰጠሁ፤ እርሷ ግን መፅነሷን ስታውቅ እኔን መናቅ ጀመረች። ያህዌ በእኔና በአንተ መካከ ይፍረድ" አለችው። **6** አብራምም መልሶ ሦራን፣ "አገልጋይሽ እኮ በእጅሽ ውስጥ ናት እርሷ ላይ የፈለግሽውን ማድረግ ትችያልለሽ" አላት። ስለዚህ ሦራ ስላሠቃየቻት፣ አጋር ከቤት ጠፍታ ሄደች። **7** የያህዌ መልአክ አጋርን ምድረ በዳ ውስጥ በነበረ አንድ ምንጭ አጠገብ አገኛት፤ ያ ምንጭ ወደ ሱር በሚወስደው መንገድ ላይ ነበር። **8** መልአኩም፣ "የሦራ አገልጋይ አጋር ሆይ፣ ከየት መጣሽ ወዴትስ እየሄድሽ ነው?" አላት። እርሷም፣ "ከእመቤቴ ከሦራ ኮብልዬ እየሄድሁ ነው" አለችው። **9** የያህዌ መልአክ፣ "ወደ እመቤትሽ ተመለሺ፤ ራስሽንም ለሥልጣንዋ አስገዢ" አላት። **10** ከዚያም የያህዌ መልአክ፣ "ዘርሽን እጅግ አበዛዋለሁ፤ ከበምዛቱም የተነሣ ሊቆጠር አይቻልም" አላት። **11** የያህዌም መልአክ በተጨማሪ እንዲህ አላት፤ "እነሆ ፀንሰሻል ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፤ ያህዌ ችግርሽን ሰምቷልና ስሙን እስማኤል ትዪዋለሽ። **12** እርሱ እንደ ዱር አህያ ይሆናል። ከሰው ሁሉ ጋር ይጣላል፤ ሰው ሁሉም ከእርሱ ጋር ይጣላል፤ ከወንድሞቹ ሁሉ ተነጥሎ ይኖራል።" **13** እርሷም ይሚያናግራትን ያህዌን፣ "አንተኮ እኔን የምታይ አምላክ ነህ"በማለት ጠራችው፤ ምክንያቱም፥ "እርሱ እኔን እንዳየ ሁሉ እኔም እርሱን አየው ይሆን?" ብላ ነበር። **14** ስለዚህ ያ ምንጭ ብኤርልያህሮኢ ተባለ፤ የሚገኘው በቃዴስና በባሬድ መካከ ልነው። **15** አጋር ለአብራም ወድን ልጅ ወለደችለው፤ አብራምም አጋር የወለደችለትን ልጅ እስማኤል ብሎ ጠራው። **16** አጋር እስማኤልን በወለደች ጊዜ አብራም ሰማንያ ስድስት ዓመት ሆኖት ነበር።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 17

1 አብራም የዘጠና ዘጠኝ ዓመት ሰው እያለ ያህዌ ተገለጠለትና እንዲህ አለው፤ "እኔ ሁሉን ቻይ አምላክ ነኝ፤ በፊቴ ተመላለስ ነቀፋም አይኑርብህ። **2** በእኔና በአንተ መካከል የተደረገውን ኪዳን አጸናለሁ፤ አንተንም እጅግ አበዛሃለሁ።" **3** አብራም በግንባሩ መሬት ላይ ተደፋ፤ እግዚአበሔርም እንዲ አለው፤ **4** "እነሆ ኪዳኔ ክአንተ ጋር ነው። የብዙ ሕዝብ አባት አደርግሃለሁ። **5** ከእንግዲህ ስምህ አብራም መባል የለበትም፤ ስምህ አብርሃም መባል እለበት፤ ምክንያቱም የብዙ ሕዝብ አባት አድርጌሃለሁ። **6** እጅግ አበዛሃለሁ፣ ሕዝቦች ክአንተ ይገኛሉ፤ ነገሥታትም ክአንተ ይወጣሉ። **7** በእኔና በአንተ፣ ክአንተም በኋላ ከዘርህ ጋር ኪዳኔን እመሠርታለሁ፤ ለአንተ ከአንተም በኋላ ለዘርህ በዘላለም ኪዳን አምላክ እሆናችኋለሁ። **8** ለአንተና ከአንተም በኋላ ለዘርህ ይህች አሁን የምትኖርባትን የከነዓንን ምድር በሙሉ ለዘላለም ርስት አድርጌ እሰጣላለሁ፤ አምላካቸውም እሆናለሁ።" **9** ከዚያም እግዚአብሔር አብርሃምን፣ "በአንተም በኩል፣ አንተና ከአንተ በኋላ የሚመጣው ዘርህ ከትውልድ እስከ ትውልድ ኪዳኔን መጠበቅ አለባችሁ። **10** በእኔና በአንተ መካከል ከአንተም በኋላ በእኔና በዘርህ መካከል መጠበቅ ያለባችሁ ኪዳኔ ይህ ነው፤ በመካከላችሁ ያለ ወንድ ሁሉ ይገረዝ። **11** እናንተ ሸለፈታችሁን ትገረዛላችሁ፤ ይህም በእናንተ መካከል ያለው ኪዳን ምልክት ይሆናል። **12** በመካከላችሁ ያለው ማንኛውም ስምንት ዓመት የሞላው ወንድ የሚመጣው ትውልድ ሁሉ ይገረዝ። ይህ በቤትህ የተወለደውን በገንዘብህ የተገዛውን ሁሉ ይጨምራል። **13** ቤትህ ውስጥ የተወለደና በገንዘብህ የገዛኸው መገረዝ አለባቸው። ስለሆነም ኪዳኔ በዘላለም ኪዳን ሥጋችሁ ላይ ይሆናል። **14** ሸለፈቱን ያልተገረዘ ማንኛውም ወንድ ኪዳኔን አፍርሷልና ከወገኖቹ ይወገድ።" **15** እግዚአብሔር አብርሃምን እንዲህ አለው፤ "ሚስትህ ሦራን ክአንግዲህ ሥራ እንጂ ሦራ ብለህ አትጥራት። **16** እባርክሃለሁ፤ ከእርሷ ወንድ ልጅ እሰጥሃለሁ። እባርካታለሁ። እርሷም የብዙ ሕዝብ እናት ትሆናልች፤ የሕዝቦችም ነገሥታት ክአርሷ ይወጣሉ። **17** በዚህ ጊዜ አብርሃም በግንባሩ መሬት ላይ ተደፍቶ እየሳቀ በሉ እንዲህ አለ፤ "ለመሆኑ የመቶ ዓመት ሽማግሌ ልጅ መውልደድ ይችላል? የዘጠና ዓመቷ አሮጊት ሥራስ ብትሆን ልጅ መውለድ ይሆንላታል?" **18** አብርሃም እግዚአብሔርን፣ "ይልቅ፣ እስማኤልን ብቻ ባኖርህልኝ!" አለ። **19** እግዚአብሔርም፣ "እንደዚያ አይደለም፤ ሚስትህ ሥራ ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች፤ ስሙንም ይስሐቅ ብለህ ትጠራዋለህ። የዘላለም ኪዳኔን ከእርሱ ጋር፣ ከእርሱም በኋላ ከዘሩ ጋር እመጸርታለሁ። **20** እስማኤልን በተመለከተም ልምናህን ሰምቻለሁ። እነሆ እርሱንም እባርከዋለሁ፤ ፍሬያማም አደርገዋለሁ፤ እጅግም አበዛዋለሁ። የአሥራ ሁለት ነገዶች አባት ይሆናል፤ ታላቅ ሕዝብ እንዲሆንም አደርጋለሁ። **21** ኪዳኔን ግን፣ የዛሬ ዓመት በዚህ ጊዜ ሣራ ከምትወልድህል ከይስሐቅ ጋር እመሠርታለሁ።" **22** ከእርሱ ጋር መነጋገሩን ከጨረሰ በኋላ እግዚአብሔር ወደ ላይ ወጣ። **23** በዚያኑ ዕለት አብርሃም ልጁ ይስሐቅን፣ በቤቱ ውስጥ የተወለዱትን በሙሉ፣ በገንዘቡ የገዛቸውን ሁሉ፣ ቤቱ ውስጥ ያለ ማንኛውንም ወንድ ሁሉ እግዚአብሔር በነገረው መሠረት ገረዛቸው። **24** አብርሃም በተገረዘ ጊዜ እድሜው ዘጠና ዘጠኝ ዓመት ነበር። **25** ልጁም እስማኤል በተገረዘ ጊዜ እድሜው አሥራ ሦስት ነበር። **26** በዚያው ቀን አብርሃምና ልጁ እስማኤልም ተገረዙ። **27** ቤቱ ውስጥ የተወለዱትን፣ ከውጭ በገንዘብ የተገዙትን ጨምሮ ቤቱ ውስጥ የነበሩ ወንዶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ተገረዙ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 18

1 ቀኑ በጣም ሞቃት በሆነ ጊዜ አብርሃም በመምሬ ወርካ ዛፎች አቅራቢይ ኣድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ እያለ ያህዌ ተገለጥለት። **2** እርሱም ቀና ብሎ ሦስት ሰዎች ፊት ለፊቱ ቆመው አየ። ባያቸውም ጊዜ ከድንኳኑ ደጃፍ ተነሥቶ ፈጥኖ ወደ እነርሱ ሄዶ፣ ወደ መሬት ዝቅ ብሎም እጅ ነሣ። **3** አብርሃም እንዲህ አለ፤ "ጌታዬ፣ በፊትህ ሞገስ አግኝቼ ከሆነ፣ ባሪያህን አልፈህ አትሂድ። **4** ጥቂት ውሃ ትምጣላችሁና እግራችሁን ታጠቡ፤ ከዚያም ዛፉ ሥር ዐረፍ በሉ። **5** ወደ እኔ ወዳገልጋያችሁ ከመጣችሁ የደከመ ሰውነታችሁ እንዲበረታ እስቲ ጥቂት እህል ላምጣላችሁና ብሉ፤ ከዚያ ጕዞአችሁን ትቀጥላላችሁ።" እነርሱም. "እንዳልኸው አድርግ" አሉት። **6** ያኔውኑ አብርሃም በፍጥነት ሣራ ወደ ነበረችበት ድንኳን ገብቶ፣ "ቶሎ ብለሽ ሦስት መስፈሪያ ስልቅ ዱቄት አቡኪና ቂጣ ጋግሪ" አላት። **7** ከዚያም ወደ መንጋው በፍጥነት ሄዶ አንድ ፍርጥም ያለ ሥጋው ግን ገር የሆነ ጥጃ መረጠና ለአገልጋዩ ሰጠው፤ እርሱም በአስቸኳይ አደረሰው። **8** አብርሃምም እግሮ፣ ወተትና የተዘጋጀውን የጥጃ ሥጋ አቀበላቸው፤ እነርሱ እየበሉ እያለ እርሱ ዛፉ ሥር አጠገባቸው ቆሞ ነበር። **9** እነርሱም እንዲህ አሉት፤ "ሚስትህ ሥራ የታለች?" እርሱም፣ "ድንኳን ውስጥ ናት" አለ። **10** እነርሱም፣ "የዛሬ ዓመት በፀደይ ወቅት ልክ በዚሁ ጊዜ በእርግጥ ተመልሼ እመጣለሁ፤ ሚስትህ ሥራ ልጅ ትወልዳለች" አለ። ሥራ ከጀርባ በነበረው ድንኳን ደጃፍ ሆና ታዳምጥ ነበር። **11** በዚህ ጊዜ አብርሃምና ሥራ በጣም አርጅተው ነበር፤ ሥራማ ልጅ የመውለጃ ጊዜ አልፎባት ነበር። **12** ስለዚህ ሣራ በልቧ፣ "ይህን ያህል ካረጀሁና ጌታዬም ከደከመ በኋላ በዚህ ነገር መደሰት ይሆንልኛልን?" ብላ ሳቀች። **13** ያህዌ አብርሃምን እንዲህ አለው፤ "ካረጀሁ በኋላ እንዴት አድርጌ ልጅ እወልዳለሁ ስትል ሣራ የሳቀችው ለምንድን ነው? **14** ለመሆኑ ለያህዌ የሚሳነው ነገር አለ? እኔ በወሰንሁት የፀደይ ወቅት ወደ እናንተ እመለሳለህ፤ በሚመጣው ዓመት በዚህ ጊዜ ሥራ ወንድ ልጅ ትወልዳለች።" **15** ሣራ ግን ፈርታ ስል ነበር፣ "ኧረ እልሳቅሁም" በማለት ካደች። እርሱም፣ "የለም፤ ስቀሻል እንጂ" አላት። **16** ሰዎቹ ለመሄድ ሲነሡ ቁልቁል ወደ ሰዶም ተመለከቱ። አብርሃምም ሊሸኛቸው ከእነርሱ ጋር ሄደ። **17** በዚህ ጊዜ ያህዌ እንዲህ አለ፤ "እኔ የማደርገውን ክአብርሃም መደበቅ አለብኝን? **18** አብርሃም በእርግጥ ታላቅና ብርቱ ሕዝብ ይህሆናል፤ የምድር ሕዝቦችም ሁሉ በእርሱ ይባረካሉ። **19** ትክክለኛና ቀና የሆነውን በማድረግ የያህዌን መንገድ እንዲጠብቁ ልጆቹንና ከእርሱ በኋላ ቤተ ሰቡን እንዲያስተምር እኔ አብርሃምን መርጬዋለሁ፤ ይኸውም ለአብርሃም የነገረውን ሁሉ ያህዌ እንዲፈጽምለት ነው።" **20** ደግሞም እግዚአብሔር እንዲህ አለ፤ "በሰዶምና በገሞራ ላይ የሚሰማው ክስ በጣም ስለ በዛ፣ ኀጢአታቸውም በጣም ትልቅ ስል ሆነ፤ **21** ወደ እኔ የመጡ ክሶች ምን ያህል እውነት መሆናቸውን ለማየት ወደዚያ እወርዳለሁ፤ እንደዚይ ካልሆነም አውቃለሁ።" **22** ሰዎቹም ፊታቸውን ወደ ሰዶም አቅንተው ሄዱ፤ አብርሃም ግን ያህዌ ፊት እንደ ቆመ ነበር። **23** አብርሃም ወደ እርሱ ቀረብ ብሎ፣ "በእርግጥ ጻድቁን ከኀጢአተኛው ጋር ታጠፋለህን? **24** ምናልባት በከተማዋ ሃምሳ ጻድቃን ቢገኙስ? እዚያ ባሉ ጻድቃን ስትል ከተማዋን ሳታድን ታጠፋታለህን? **25** ጻድቁን ከኀጢአተኛው ጋር በመግደል፣ ኀጢአተኛ ላይ የደረሰው በእርሱም እንዲደርስ ማድረግን የመሰለ ንገር ከአንተ ይራቅ! እንዲህ ያለው ከአንተ ይራቅ! የምድር ሁሉ ዳኛ እውነተኛ ጻድቅ የሆነውን አያደርግምን? **26** ያህዌም እንዲህ አለ፤ "በሰዶም ከተማ ውስጥ ሃምሳ ጻድቃን ካገኘሁ ፣ ለእነርሱ ስል ያንን ቦታ እምራለሁ።" **27** አብርሃምም መልሶ እንዲህ አለ፤ "እኔ ትቢያና ዐመድ ሆኜ ሳለሁ ከጌታዬ ጋር ለመናገር አንዴ ደፍሬአለሁ፤ **28** ለመሆኑ ከአምሳዎቹ ጻድቃን አምስት ቢጎድሉ፣ በጎደሉት አምስቱ ምክንያት ከተማዋን በሙሉ ታጠፋለህን?" እርሱም፣ "እዚያ አርባ አምስ ጻድቃንካገኘሁ አላጠፋትም" አለ። **29** አብርሃምም እንደ ገና፣ "ምናልባት አርባ ጻድቃን ቢገኙስ?" እለ፤ እርሱም፣ "ለአርባዎቹ ስል አላደርገውም" እለ። **30** አብርሃምም፣ "እባክህን ጌታዬ ይህን ያህል በመናገሬ አትቆጣኝ። እንደው ምናልባት ሰለሣ ቢገኙስ" አለ። እርሱም መልሶ፣ "ሰላሣ ጻድቃን ካገኘሁ አላደርገውም" በማለት መለሰ። **31** አብርሃምም፣ "መቼም አንዴ ከጌታዬ ጋር መናገር ጀምሬአለሁ! እንደው ምናልባት ሃያ ቢገኙስ" አለ። እርሱም መልሶ፥ "ለሃያዎቹ ስል አላደርገውም" አለ። **32** በመጨረሻም እንዲህ አለ፤ "እባክህ ጌታዬ አትቆጣኝ፤ አንዴ ብቻ ልናገር፤ ምናልባት አሥር ቢገኙስ። እርሱም፣ "ለአሥሩ፣ ሲል አላጠፋትም" አለ። **33** ከአብርሃም ጋር መነጋገሩን እንደ ጨረሰ ያህዌ ሄደ፤ አብርሃምም ወደ ቤቱ ተመለሰ።

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 19

1 ሁለቱ መላእክት ምሽት ላይ ወደ ሰዶም መጡ፤ በሰዶም ከተማ መግቢያበር ላይ ተቀምጦ ነበር። ሎጥ ሲያያቸው ሊቀበላቸው ተነሣ፤ በግንባሩም መሬት ላይ
ተደፋ። 2 እርሱም፣ "እባካችሁ ጌቶቼ ወደ እኔ ወደ ባሪያችሁ ቤት ጎራ በሉ፤ እግራችሁን ታጠቡ፤ ሌሊቱንም ከእኛ ጋር አሳልፉ፤ ከዚያ ጧት በማለዳ ተነሥታችሁ
ጕዞአችሁን ትቀጥላላችሁ።" እነርሱም፣ "የለም፤ እዚሁ አደባባዩ ላይ እናድራለን" አሉት። 3 ሎጥ ግን አጥብቆ ስለ ለመናቸው እርሱ ቤት ለማደር አብረውት
ገቡ። ከዚያም ቂጣ ጋግሮ አቀረበላቸው፤ እነርሱም በሉ። 4 ሆኖም፣ ገና ከመተኛታቸው በፊት የሰዶም ከተማ ነዋሪዎች የሆኑ ወጣቶችና ሽማግሌዎች
ከየአካባቢው መጥተው ቤቱን ከበቡት። 5 ሎጥን በመጣራት፣ "በዚህ ምሽት ወደ ቤትህ የመጡ ሰዎች የታሉ? ሩካቤ ሥጋ እንድንፈጽምባቸው ወደ ውጭ
አውጣልን" አሉት። 6 ሎጥ ሊያነጋግራቸው ወደ ውጭ ወጣ መዝጊያውን ከበስተ ኋላው ዘጋ። 7 እንዲህም አለ፤ "ወንድሞቼ እንዲህ ያለ ክፉ ነገር እንዳታደርጉ
እለምናችኋለሁ። 8 ከወንድ ጋር ተኝተው የማያውቁ ሁለት ሴቶች ልጆች አሉኝ፤ እነርሱን ላውጣላችሁና የወደዳችሁትን አድርጉባቸው። በእነዚህ ሰዎች ላይ ግን
ምንም ነገር አታድርጉባቸው፤ እኔን ብለው ወደ ቤቴ ተብተዋልና።" 9 እነርሱ ግን፣ "ዞር በል!" ይኸ ሰውዬ ስደተኛ ሆኖ እዚህ ለመኖር መጣ፤ ደግሞ ዳኛ
ሆነብን! ይልቁ በእነርሱ ላይ ካሰብነው የከፋ እንዳይደርስብህ ዘወር በልልን" አሉት ሎጥንም እየገፈታተሩ የበሩን መዝጊያ ለመስበር ተቃርበው ነበር። 10
ሰዎቹ እጃቸውን ዘርግተው ሎጥን ወደ ቤት አስገቡትና በሩን ዘጉ። 11 ከቤቱ ውጪ የነበሩትን ውጣቶችንም ሆን ሽማግሌዎችን ግን የሎጥ እንግዶች
ዐይናቸውን አሳወሩአቸው፤ እነርሱም በሩን ለማግኘት ይደነባበሩ ጀመር። 12 ከዚያም ሰዎቹ ሎጥን እንዲህ አሉት፤ "በከተማዋ የሚኖሩ የአንተ የሆኑ ሰዎች
አሉህ? ወንዶችና ሴቶች ልጆችህን፣ የወንዶች ልጆችህን ሚስቶች፣ የሴቶች ልጆችህን ባሎችና ሌሎች ዘመዶችህን ሁሉ ከዚህ አውጣ። 13 ምክንያቱም ይህን
ቦታ ልናጠፋ ነው፤ በያህዌ ፊት ከተማዋ ላይ የሚቀርቡ ክሶች በጣም እየጮኹ በመሆናቸው እንድናጠፋት እርሱ ልኮናል።" 14 ሎጥ ከቤቱ ወጥቶ የሴት
ልጆቹን ባሎች፣ የሴት ልጆቹን እጮኞች፣ "ቶሎ ከዚህ ቦታ ውጡ፤ ያህዌ ከተማዋን ሊያጠፋ ነው" አላቸው። የሴት ልጆቹ ባሎች ግን የሚቀልድ መሰላቸው። 15
ሲነጋጋም መላእክቱ ሎጥኝ፣ "ከተተማዋ ላይ በሚመጣው ቅጣት አብራችሁ እንዳትጠፉ ሚስትህንና ሁለቱ ሴት ልጆችህን ይዘህ ከዚህ ቦታ በፍጥነት ውጣ"
እያሉ አቻኮሉት። 16 ሎጥ አመነታ፤ ያህዌ ምሕረት ስላደረገላቸው ሰዎቹ የእርሱ፣ የሚስቱንና የሁለት ሴት ልጆቹን እጅ ይዘው ከከተማዋ አወጣቸው። 17
ከከተማው ካወጧቸው በኋላ ከሰዎቹ አንዱ፣ "ሕይወታችሁን ለማዳን ሩጡ! ወደ ኋላችሁ አትመልከቱ፤ ወይም ረባዳው ስፍራ ላይ አትቆዩ። ወደ ተራሮች ሸሹ፤
አለበለዚያ ትጠፋላችሁ።" 18 ሎጥም እንዲህ አላቸው፤ "ጌቶቼ ሆይ፣ 19 እኔ ባሪያችሁ በፊታችሁ ሞገስ አግኝቻለሁ፤ ሕይወቴን ለማዳን ታላቅ ርኅራኄ
አድርጋችሁልኛል፤ እኔ እንደ ሆንኩ ወደ ተራሮቹ ሸሽቼ ማምለጥ ስለማልችል የሚወርደው መዓት ደርሶ ያጠፋኛል። 20 ወደዚያ ሸሽቶ ለማምለጥ ቅርብ ቦታ ያለች
ትንሽ ከተማ አለች ሸሽቼ ወደዚያ ብሄድ ሕይወቴን ማዳን እችላለሁ።" 21 እርሱም፣ "ይሁን እሺ፤ ልመናህን ተቀብብያለሁ፤ ያክካትንም ከተማ አላጠፋትም። 22
አንተ እዚያ እስክትደርስ ምንም ማድረግ ስለማልችል በል ቶሎ ፍጠንና ወደዚያ ሽሽ" አለው። ስለዚህ ያቺ ከተማ ዞዓር ተባለች። 23 ሎጥ ዞዓር ሲደርስ ፀሓይ
በምድሩ ወጥታ ነበር። 24 ከዚያ ያህዌ ሰዶምና ጎሞራ ላይ ድኝና እሳት አዘነበ። 25 እነዚያን ከተሞችና ረባዳ ቦታዎቹን፣ የከተሞቹ ነዋሪዎችንና እዚይ ኣያሉ
ለምለም ነገሮችን ሁሉ አጠፋ። 26 ከኋላው የነበረችው የሎጥሚስት ግን ወደ ኋላዋ ስለ ተመለከተች የጨው ዐምድ ሆና ቀረች። 27 አብርሃም ጠዋት ማለዳ
ተነሥቶ ያህዌ ፊት ቆሞ ወደ ነበረበት ቦታ ሄደ። 28 ቁልቁል ሰዶምና ጎሞራን፣ እንዲሁም በረባዳው ስፍራ የነበረውን ምድር ተመለከተ። ከምድጃ የሚወጣ
የመሰለ ጢስ ከምድሩ እየወጣ ነበር። 29 እግዚአብሔር በረባዳው ቦታ የነበሩ ከተሞችን ባጠፋ ጊዜ አብርሃምን አሰበው። ሎጥ የነበረበትን ከተሞች
ቢያጠፋም፣ እርሱ ግን ከጥፋት መሐል አወጣው። 30 ሎጥ ግን በዞዓር መኖር ስለ ፈራ ከሁለት ሴቶች ልጆቹ ጋር ተራሮቹ ላይ ለመኖር ከዞዓር ወደ ላይ ወጣ።
ስለዚህ እርሱና ሁለት ሴቶች ልጆቹ ዋሻ ውስጥኖሩ። 31 ታላቋ ልጅ ታናሿን እንዲህ አለቻት፣ "አባታችን አርጅቷል፤ በምድር ሁሉ እንደሚኖሩ ሰዎች ወግ ከእኛ
ጋር የሚተኛ ወንድ በአካባቢያችን የለም። 32 ስለዚህ አባታችንን የወይን ጠጅ እናጠጣውና ከእርሱ ጋር እንተኛ፤ የትውልድ ሐረጋችን እንዳይቋረጥ ከአባታችን
ዘር እናትርፍ።" 33 ስለዚህ በዚያ ምሽት አባታቸውን የወይን ጠጅ አጠጡት። ታላቂቱ ልጅ ሄዳ ክአባቷ ጋር ተኛች፤ እርሷ ስትተኛም ሆነ ስትነሣ አላወቅም። 34
በሚቀጥለው ቀን ታላቂቱ ታናሺቱን እንዲህ አለቻት፤ "ትናንት ሌሊት እኔ ከእባቴ ጋር ተኛሁ። ዛሬም እንደ ገና የወይን ጠጅ እናጠጣው፣ ከዚያ አንቺ ሄደሽ ከእርሱ
ጋር ትተኛለሽ፣ የአባታችንንም ዘር እናተርፋለን።" 35 ስለዚህ በዚያም ምሽት አባታቸውን ወይን ጠጅ አጠጡት፤ ታናሺቱ ልጅ ሄዳ ከእርሱ ጋር ተኛች፤ እርሷ
ስትተኛም ሆነ ስትነሣ አላወቀም። 36 ሁለቱ የሎጥ ልጆች ክአባታቸው አረገዙ። 37 ታላቂቱ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ስሙንም ሞዓብ አለችው። እርሱም ዛሬ ያሉት
ሞዓባውያን አባት ሆነ። 38 ታናሺቱም እንዲሁ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ስሙንም ቤንአሚ አለችው። እርሱም ዛሬ ያሉት አሞናውያን አባት ሆነ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 20

1 አብርሃም ከዚያ ተነሥቶ ወደ ኔጌብ አካብቢ ሄደ፤ በቃዴስና በሱር መካከልም መኖር ጀመረ። ለጥቂት ጊዜ በጌራራ ተቀመጠ። **2** አብርሃም ሚስቱ ሥራራን፣ "እኅቴ ናት" ይል ነበር፤ ስለዚህ ይጌራራ ንጉሥ አቢሜሌክ ሰዎች ልኮ ሣራን ወሰዳት። **3** እግዚአብሔር ግን በሕልም ወደ አቢሜሌክ መጥቶ፣ "እነሆ በወሰድካት ሴት ምክንያት አንተ ምውት ነህ፤ ምክንያቱም እርሷ ባለ ባል ናት" አለው። **4** አቢሜሌክ ገና አልሰረሰባትም ነበርና እንዲህ አለ፤ "ጌታ ሆይ፣ በደል ያልተገኘበትን ሕዝብ ልታጠፋ ነውን? **5** 'እኅቴ ናት' ያለኝ እርሱ ራሱ አይደለምን? እርሷም ብትሆን 'ወንድሜ ነው' ብላኛለች። እኔ እንዲህ ያደረግሁት በቅን ልቦናና በንጹሕ እጅ ነው።" **6** በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር በሕልም እንዲህ አለው፤ "አዎን፣ ይህን ያደረግኸው በልብ ቅንነት እንደ ነበር እኔም አውቃለሁ፤ እኔ ላይ ኀጢአት እንዳትፈጽም የጠበቅሁህና እንዳትነካትም ያደረግሁት በዚህ ምክንያት ነው፤ **7** ስለዚህ የሰውየውን ሚስት መልስለት፤ እርሱ ነቢይ ስለ ሆነ ይጸልይልሃል አንትም ትድናለህ። እርሷን ካልመለስህ፣ እንተና የአንተ የሆነው ሁሉ በእርግጥ እንደምትጠፉ ዐውቃለሁ።" **8** አቤሜሊክ ጧት በማለዳ ተነሥቶ ሹማምንቶቹን ሁሉ ጠራ። የሆነውን ሁሉ ሲነግራቸው በጣም ፈሩ። **9** ከዚያም አቤሜሌ አብርሃምን አስጠርቶ፣ "ለመሆኑ፣ ምን እያደረግህብን ነው? በእኔና በግዛቴ ላይ እንዲህ ያለውን ትልቅ መዘዝ ያመጣህብኝ ምን ብበድልህ ነው? መደረግ ያልነበረትን አድርገህብኛል" አለው። **10** በመቀጠልም፣ አብርሃምን፣ "እንዲህ እንድታደርግ ያነሣሣህ ምንድን ነው?" ሲል ጠየቀው። **11** አብርሃምም፣ "በዚህ ቦታ እግዚአብሔርን መፍራት የለም፤ ለሚስቴ ሲሉ ይገድሉኛል በማለት ስላሰብሁ ነው። **12** በዚህ ላይ ደግሞ ከእናቴ ባትወለድም የአባቴ ልጅ እኅቴ ናት፤ በኋላም ሚስቴ ሆነች። **13** የአባቴን ቤት ትቼ በየአገሩ እንድዞር እግዚአብሔር ሲያዝዘኝ፣ "ለእኔ ለባልሽ ያለሽን ታማኝነት በዚህ አሳዪኝ፤ በምንሄድበት ቦታ ሁሉ 'ወንድሜ ነው' በዪ አልኳት።" **14** ከዚያ አቤሜሊክ በጎችና በሬዎች፣ ወንዶችና ሴቶች ባሪያዎች ለአብርሃም ሰጠው። ሚስቱ ሣራንም ለአብርሃም መለሰለት። **15** አቤሜሌክ እንዲህ አለ፤ "አገሬ አገርህ ነው፤ ደስ በሚያሰኝህ ቦታ ተቀመጥ።" **16** ሣራንም፣ "ለወንድምሽ አንድ ሺህ ጥሬ ብር እሰጠዋለሁ። ይህም፣ በአንቺ ላይ ለተፈጸመው በደል ካሣ እንዲሆንና አብረውሽ ያሉ ሁሉ አንቺ ንጹሕ ሴት መሆንሽን እንዲያውቁ ነው።" **17** ከዚያም አብርሃም ለአቤሜሌክ ጸለየ፤ እግዚአብሔርም አቤሜሌክን፣ ሚስቱንና ሴት አገልጋዮቹን ፈወሳቸው፤ ልጅ ለመውለድም በቁ። **18** ከአብርሃም ሚስት ከሣራ የተነሣ በአቢሜሌክ ቤት የሚገኙ ሴቶችን ሁሉ ያህዌ ማኅፀናቸውን ዘግቶ ነበር።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 21

1 ለአብርሃም በሰጠው የተስፋ ቃል መሰረት እግዚአብሔር ሳራን አሰባት፤ እንደገባላት የተስፋ ቃልም አደረገ ፤ **2** ስለዚህም ሳራ አርግዛ በእርጅናው ጊዜ
ለአብርሃም ወንድ ልጅ ወለደችለት፤ ልጁም የተወለደው «በዚህ ጊዜ ይወለዳል» ብሎ እግዚአብሔር በተናገረበት ጊዜ ነው። **3** አብርሃም ሚስቱ ሳራ
የወለደችለትን ልጅ «ይስሐቅ» ብሎ ስም አወጣለት። **4** ይስሐቅ ከተወለደ ከስምንት ቀን በኋላ እግዚአብሔር ባዘዘው መሰረት አብርሃም ገረዘው። **5** ልጁ
ይስሐቅ በተወለደለት ጊዜ አብርሃም መቶ ዓመት ሆኖት ነበር። **6** ሳራም «እግዚአብሔር ሳቅ አደረገልኝ ስለዚህ ይህንን ነገር የሚሰማ ሁሉ ከእኔ ጋር
ይስቃል»አለች። **7** ቀጥላም «ሳራ ለአብርሃም ልጆችን ወልዳ ታጠባለች» ብሎ የሚናገር ከቶ ማን ነበር አሁን ግን እነሆ በእርጅናው ዘመን ወንድ ልጅ
ወለድሁለት» አለች። **8** ልጇም አድጎ ጡት መጥባት ተወ፤ ጡት ባስጣሉበትም ቀን አብርሃም ታላቅ ግብዣ አደረገ። **9** ግብጻዊትዋ አጋር ለአብርሃም
የወለደችለት እስማኤል ከዕለታት አንድ ቀን በሳራ ልጅ በይስሐቅ ላይ ሲያሾፍበት ሳራ አየች። **10** ስለዚህ ሳራ አብርሃምን«ይህችን አገልጋይ ከነ ልጅዋ ወዲያ
አባርልኝ የዚህች አገልጋይ ልጅ ከልጄ ከይስሐቅ ጋር አብሮ መውረስ አይገባውም» አለችው። **11** እስማኤልም ልጁ ስለሆነ ይህ ጉዳይ አብርሃምን በብርቱ
አስጨነቀው **12** እግዚአብሔር ግን አብርሃምን «ስለ ልጁና ስለ አገልጋይቱ ስለ አጋር አትጨነቅ። ዘር የሚወጣልህ በይስሃቅ በኩል ስለሆን እርሳ የምትልህን
ሁሉ አድርግ። **13** የአገልጋይቱም ልጅ የአንተ ዘርያ ስልሆን ታላቅ ሕዝብ አደርገዋለሁ» አለው **14** አብርሃም በማለዳ ተነሳ ጥቂት ምግብ ውሃም በአቁማዳ
ለአጋር በትከሻዋ አደረገላት። ልጁንም በጀርባዋ አሳዝሎ ከቤት አስወጣት፤ እርስዋም በቤርሳቤህ በረሃ ትንከራተት ጀመር። **15** በአቁማዳ የነበረው ውሃ ባለቀ
ጊዜ ልጁን በቁጥቋጦ ስር አስቀምችጠችው። **16** እርስዋም «ልጄ ሲሞት ማየት አልፈልግም» በማለት ጥቂት ከልጅዋ ርቃ ተቀመጠች፤ እዚያም ሆና ድምጻን
ከፍ አድርጋ ታለቅስ ጀመር። **17** እግዚአብሔሬም ልሉ ምርር ብሎ ሲያለቅስ ሰማ የእግዚአብሔርም መልአክ ከሰማይ አጋርን «አጋር ሆይ የምትጨነቂበት ነገር
ምንድር ነው? እግዚአብሔር የልጂን ለቅሶ ሰምቶአልና አትፍሪ። **18** ተነሺ ሂንና ልጁን አንስተስ አባብይው፤ የእርሱንም ዘር አበዛለሁ ታላቅ ሕዝብም
አደርገዋለሁ። **19** በዚህም ጊዜ እግዚአብሔር ዓይኖችዋን ከፈተላትና አንድ የውኃ ጉድጋድ አየች፤ ሄዳም በአቁማዳ ውሃ ሞላች ለልጅዋም አጠጣችው። **20** ልጁ
እያደገ በሚሄድበት ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበር። **21** በፋራንም በረሓ ኖረ፤ ቀስት በመወርወርም የታወቀ አዳኝ ሆነ። እናቱም ከአንዲት ግብጻዊት
ጋር አጋባችው። **22** በዚያን ጊዜ አቤሜሌክ ከሰራዊቱ አለቃ ከፊኮል ጋር ሄደና አብርሃምን «በምታደርገው ሁሉ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነው፤ **23** እኔንም ሆነ
ልጆቼን ወይም ዝርያዎቼን እንዳትዋሸኝ አሁን በእግዚአብሔር ስም ማልልኝ። እኔ ለአንተ ታማኝነትን አሳይቻለሁ፤ አንተም ለእኔና ለዚህች ለምትኖርባትአገር
ታማኝንትን እንደምታሳይ ማልልኝ» አለው። **24** አብርሃምም «እሺ እምላለሁ» አለ። **25** አብርሃም የአቢሜሌክ አገልጋዮች ስለ ወሰዱበት የውሃ ጉድጋድ
ለአቤሜሌክ አቤቱታ አቀረበ፤ **26** አቤሜሌክም «ይህን ያደረገ ማን እንደሆን አላውቅም። አንተም አልነገርኸኝም ይህንን ነገር ገና ዛሬ መስማቴ ነው» አለው።
27 ከዚህ በኋላ አብርሃም ብዙ በጎችና ከብቶች አምጥቶ ለአቢሜሌክ ሰጠው፤ በዚያን ቀን ሁለቱም የስምምነት መሀላ አደረጉ። **28** በዚያን ጊዜ አብርሃም
ሰባት እንስት የበግ ጠቦቶችን ከመንጋው ለየ፤ **29** አቤሜሌክም «እንዚህን ሰባት ጠቦቶች ለይተህ ያቆምሃቸው ለምንድር ነው?» አለው። **30** አብርሃምም
«እነዚህን ሰባት እንስት ጠቦቶች ተቀበለኝ እነርሱን ከተቀበልከኝ ይህን ጉድጋድ የቆፈርሁ እኔ መሆኔን ምስክር እንዲሆን ነው» አለው፤ **31** ሁለቱ ተማምለው
የተስማሙበት ስፍራ በመሆኑ የዚያ ቦታ ስም ቤርሳቤህ ተባል፤ **32** ይህን ስምምንት በቤርሳቤህ ተስማምተው ካደረጉ በኋላ አቤሜሌክና የሰራዊቱ አለቃ ፊኮል
ወደ ፍልስጥኤም ምድር ተመለሱ **33** ከዚህ ብኃላ አብርሃም በቤርሳቤህ የታማሪስክ ዛፍ ተከልና የዘላለም አምላክ ለሆነው ሰገደ፤ **34** አብርሃም
በፍልስጥኤም ምድር በእንግድነት ለረዥም ጊዜ ኖረ።

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 22

1 ሁሉ ነገር በኋላ እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው፤ እግዚአብሔርም «አብርሃም»ብሎ ጠራው፤ «እነሆ አለሁኝ» ብሎ መለሰ። **2** እግዚአብሔርም «የምትወደውን አንድ ልጅህን ወደ ሞሪያ ምድር ሂድ። እዚያ በማሳይህ አንድ ኮረብታ ላይ እርሱን የሚቃጠል መስዋዕት አድርገህ አቅርብልኝ» አለው፤ **3** አብርሃም በማለዳ ተነስቶ ለመስዋዕት የሚሆን እንጨት ቆረጠና በአህያው ላይ ጫነው፤ከእርሱ ጋር ልጁን ይስሐቅን ና ሁለት ወጣት ሰዎችን ይዞ እግዚአብሔር ወደ ነገረው ቦታ ለመሄድ ጉዞ ጀመረ። **4** በሦስተኛው ቀን አብርሃም ቀና ብሎ ሲመለከት ቦታውን በሩቅ አየ። **5** ከዚህ በኋላ አብርሃም የርሱን ወጣቶች «እናንተ ከአህያው ጋር በዚህ ቆዩ እኔና ልጄ ወደዚያ ሄደን ከሰገድን በኋላ እንመለሳለን፤ **6** አብርሃምም የሚቃጠለውን መስዋዕቱን ማቃጠያ እንጨት አንስቶ ለልጁ ለይስአቅ አሸከመው፤ እርሱ ግን ቢላዋውንና እሳቱን ያዘ ሁለቱም አብረው ሄዱ። **7** ይስሐቅ አብርሃምን «አባባ» አለው፤ እርሱም «እነሆ አለሁ ልጄ» አለው፤ ይስሐቅም «እነሆ እሳትና እንጨት ይዘናል ታዲያ ለመስዋዕት የሚሆነው በግ የት አለ?» በማለት አብርሃምን ጠየቀው። **8** አብርሃምም «ልጄ ሆይ ለመስዋዕት የሚሆነውን በግ እግዚአብሔር እራሱ ያዘጋጃል» አለው። ሁለቱም አብረው መንገዳቸውን ቀጠሉ። **9** እግዚአብሔር ነገረው ቦታ በደረሱ ጊዜ አብርሃም መሰዊያ ሰርቶ እንጨቱን ረበረበው፤ ልጁን ይስሐቅንም አስሮ ከእንጨቱ በላይ በመሰዊያው ላይ አጋደመው። **10** ልጁን ለማረድ ቢላዋ አንስቶ እጁን ዘረጋ። **11** ነገር ግን የእግዚአብሔር መልአክ ከሰማይ «አብርሃም! አብርሃም!» ብሎ ጠራው። እርሱም «እነሆኝ አለሁኝ» አለ። **12** እርሱም «በልጁ ላይ እጅህን አትጫንበት፣ ምንም ዓይነት ጉዳትም አታድርስበት፣ እነሆ እግዚአብሔርን የምትፈራ መሆንህን ተረድቻለሁ፤ አንድ ልጅህን እንኳ ለእኔ ከመስጠት አልተቆጠብህም» አለው። **13** አብርሃም ዙሪያውን በተመለከት ጊዜ ከበስተጀርባው ቀንዶቹ በቁጥቋጥ ዛፍ የተያዙ አንድ በግ አየ፤ አብርሃምም ሄዶ በጉን አመጣና በልጁ ፋንታ የሚቃጠል መስዋዕት አድርጎ አቀረበው። **14** አብርሃምም ያን ቦታ «እግዚአብሔር ያዘጋጃል» ብሎ ጠራው። ዛሬም ቢሆን ሠዎች «እግዚአብሔር በተራራው ላይ ያዘጋጃል» ይላሉ። **15** የእግዚአብሔር መልአክ ለሁለተኛ ጊዜ አብርሃምን ከሰማይ ጠራውና፤ **16** እንዲህ አለው፤ «እግዚአብሔር ብዙ በረከት እንድምሰጥህ በራሴ ስም እምላለሁ» ይላል፤ ይህን ስላደረግህና አንድ ልጅህንም ለእኔ ለመስጠት ስላልተቆጠብህ፤ **17** እኔም ዘርህን እንደ ሰማይ ከዋክብትና እንደ ባህር ዳር አሸዋ አበዛዋለሁ፤ ዝርያዎችህም ጠላቶቻቸውን ድል ነስተው፤ ከተሞቻቸውን ይይዛሉ። **18** ትዕዛዜን ስለ ፈጸምህ የዓለም ህዝቦች ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ»፤ **19** ከዚህ በኋላ አብርሃም ወደ ወጣቶችሁ ተመለሰና በአንድነት ሆነው ወደ ቤርሳቤህ ሄዱ፤ አብርሃምም በቤርሳቤህ ተቀመጠ። **20** ከዚህ ሁሉ በኋላ እንዲህ ተብሎ ለአብርሃም ተነገረው «ሚልካ ልጆችን ለወንድምህ ለናኮር ወልዳለች፤ **21** እነርሱም የመጀመሪያው ልጅ ዑፅ ወንድሙም ቡዝ የአራም አባት ቀሙኤል፤ **22** ኬሰድ፣ ሐዞ፣ ፊልዳሽ፤ ይድላፍና በቱኤል ናቸው። **23** በቱኤል ርብቃን ወለደ። ሚልካ እነዚህን ስምንት ልጆች ለአብርሃም ወንድም ለንኮር ወለደችለት፤ **24** ረኡማ የተባለች የናኮር ቁባት ደግሞ ጤባሕን፣ ገሐምን፣ ተሐሽና ማዕካን ወለደችለት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 23

1 ሣራ መቶ ሃያ ሰባት ዓመት ኖረች። እነዚህን ዓመታት ነበር ሳራ የኖረችው። **2** በከነዓን ምድር ባለችው ቂርያት አርባ ተብላ በምትጠራው በኬብሮን ከተማ
ሞተች፤ አብርሃም በሣራ ሞት ምክንያት እጅግ ሃዘነ አለቀሰም። **3** ከዚያም አብርሃም ከተቀመጠበት ከሚስቱ ሬሳ አጠገብ ተነሳ፣ ኬጢያውያንን እንዲህ
አላቸው፤ **4** «እኔ በመካከላችሁ በእንግድነት የምኖር ነኝ። እባካችሁ የመቃብር ቦታ ስጡኝ፤ የሚስቴንም ሬሳ ልቅበርበት።» **5** የኬጢ ልጆችም ለአብርሃም
እንዲህ ሲሉ መለሱለት፤ **6** «ጌታ ሆይ ስማን፣ አንተ በእኛ መካከል ከእግዚአብሔር አለቃ ነህ። ከመቃብር ቦታችን በመረጥከው ስፍራ ሬሳህን መቅበር
ትችላለህ፣ ማናችንም ብንሆን የሞተብህን ሰው እንዳትቀብርበት የምቃብር ቦታችንን አንከለክልህም።» **7** አብርሃም ተነሣ በኬጢያውያን ልጆች ፊት እጅ ነስቶ
እንዲህ አለ። **8** የሚስቴን አስከሬን እዚህ እንድቀብር ከፈቀዳችሁልኝ የጾሐር ልጅ ዔፍሮምን ስለ እኔ ሆናችሁ ልምኑልኝ፤ **9** በእርሻው ዳር ያለችውን መክፈል
የተባለችውን ዋሻውን እንዲሸጥልኝ ጠይቁልኝ፣ ይህ ስፍራ የመቃብር ቦታ እንዲሆንልኝ በእናንት ፊት ሙሉ ዋጋ ከፍዬ እንድገዛው አድርጉልኝ።» **10** ኤፍሮንም
በኬጢ ልጆች መካከል ተቀምጦ ነበር፤ የኬጢም ሰው ኤፍሮንም የኪጥ ልጆችና ወደ ከተማ የሚገቡ ሲስሙ ለአብርሃም እንዲህ ሲል መለሰለት፤ **11**
«አይደለም ጌታዬ፣ ስማኝ። እርሻውን፣ በርሱም ዳር ያለውን ዋሻ፤ በወገኔ ልጆች ፊት ሰጥቼአለሁ። ሬሳህን ቅበር።» **12** አብርሃምም በአገሩ ሰዎች ፊት ሰገደ።
13 የአገሩ ሰዎችም እየሰሙ ለኤፍሮን እንዲህ ሲል ተናገረ፤ «እባክህ ፈቃደኛ ብትሆን አድምጠኝ፤ የእርሻውን ዋጋ እሰጥሃለሁ። አንተም ከእኔ ዘንድ ውሰድ፤
ሬሳዬንም በዚያ እቀብራለሁ **14** ኤፍሮንም ለአብርሃም እንዲህ ሲል መለሰለት፤ **15** «ጌታዬ ሆይ እኔን ስማኝ፤ የመሬቱ ዋጋ እራት መቶ ሰቅል ቢሆን ነው፤ ታዲያ
ይሄ በእኔና በአንተ መካከል ምንድር ነው? ሬሳህንም ቅበር» **16** አብርሃምም የኤፍሮንን ነገር ሰማ፤ አብርሃምም በኬት ልጆች ፊት የነገረውን አራት መቶ ሰቅል
መዝኖ ለኤፍሮን ሰጠው፤ ብሩንም በወቅቱ የንግድ መለኪያ መሰረት መዘነለት። **17** በዚህም ሁኔታ በመምሬ አጠገብ በመክፈላ ያለውን የኤፍሮንን እርሻ ቦታ
ከነዋሻው በከልሉ ካሉት ዛፎች ሁሉ ጭምር ለአብርሃም በርስትነት ተላለፈ፤ **18** እርሻው በእርሱ ያለውን ዋሻው በእርሻውም ውስጥ በዙሪያውም ያለው እንጨት
ሁሉ በኬጢ ልጆችና በከተማይቱ በር በሚገቡ ሁሉ ፊት ለአብርሃም ርስቱ ሆነ። **19** ከዚያም በኋላ ኬብሮን በምትባል በምምሬ ፊት በከነአን ፊት ባለው እርሻ
ባለ ድርብ ክፍሌ በሆነው ዋሻ ውስጥ ሚስቱን ሳራን ቀበረ። **20** እርሻውና በርሱ ያለው ዋሻው በኪጥ ልጆች ዘንድ ለአብርሃም የመቃብር ርስት ሆኖ ጸና።

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 24

1 በዚህ ጊዜ አብርሃም ሸመገለ፤ ዕድሜውም ገፋ፤ እግዚአብሔርም አብርሃምን በሁሉ ነገር ባረከው። 2 አብርሃምም የንብረቱ ሁሉ ጎላፊ የቤቱ ሁሉ አዛዥ
የሆነውን አገልጋይ እንዲህ አለው፤ እጅህን ከጭኔ በታች አድርግ 3 እኔም በመካከላቸው ከምኖረው ከከነዓናዊያን ለልጄ ሚስት እንዳታጭለት በሰማይና በምድር
አምላክ እግዚአብሔር አስምልሃለሁ። 4 ነገር ግን ወደ ገዛ ሀገሬ እና ወደ ወገኖቼ ሄደህ ለልጄ ለይስሐቅ ሚስትን ታጭለታለህ። 5 አገልጋዩም «ምናልባት
የምመርጥለት እጮኛ ከእንይ ጋሬ ወደዚህ አገር ለመምጣት እምቢ ብትልስ? ልጅህን ቀድሞ አንተ ወደ ነበርክበት አገር እንዲመለስ ላድርገው?» ብሎ ጠየቀ።
6 አብርሃም ግን እንዲህ አለው፤ «በምንም ዓይነት ምክንያት ቢሆን ልጄን ወደዚያ አገር መልሰህ እንዳትወስድ ተጠንቀቅ፤ 7 የሰማይ አምክክ እግዚአብሔር
ከአባቴ ቤትና ከትውልድ አገሬ አውጥቶ አምጥቶኛል፤ ይህንንም ምድር ለዝርያዎቼ እንደሚሰጥ በመሃላ ቃል ገብቶልኛል፤ ከዚያ ለልጄ ሚስት ማግኘት
እንድትችል እግዚአብሔር መልአኩን በፊትህ ይልካል። 8 ልጅትዋ ከአንተ ጋር ለመምጣት ፈቃደኛ ባትሆንከዚህ መሓላ ነፃ ትሆናለህ፤ ልጄን ግን በምንም ዓይነት
ሁኔታ ወደዚያ አትመልሰው።» 9 ከዚህ በኋላ አገልጋዩ እጁን በጌታው በአብርሃም ጉልበት ላይ አድርጎ አብርሃም ያዘዘውን ሁሉ እንደሚፈፅም በመሐላ ቃል
ገባ። 10 የአብርሃም ንብረት ጎላፊ የነበረው መጋቢ ከጌታው ቤት ምርጥ የሆኑ የስጦታ ዕቃዎችን በዕሥር ግመሎች ጭኖ በሰሜን መስጴጦምያ ናኮር
ወደሚኖርበት ከተማ ሄደ። 11 እዚያ በደረሰ ጊዜ ከከተማው ውጭ ባለ የውሃ ጉድጓድ አጠገብ ግመሎቹ ተንበርክከው እንዲያርፉ አደረገ፤ ሰዓቱም ሊመሸ
ተቃርቦ፣ ሴቶች ውሃ ለመቅዳት የሚወጡበትን ጊዜ ነበር፤ 12 አገልጋዩ እንዲህ ብሎ ጸለየ፣ "የጌታዬ የአብርሃም አምላክ እግዚአብሔር ሆይ! ዛሬ የእኔን አሳብ
በመፈፀም ለጌታዬ ለአብርሃም ዘላለምዊ ፍቅርህን ግለጥ። 13 እነሆ፣ እኔ በዚህ የውሃ ጉድጓድ አጠገብ ቆሜአለሁ፤ የከተማይቱም ልጃገረዶች ውሃ ሊቀዱ
ወደዚህ ይመጣሉ፤ 14 ከእነሱም አንድዋ ልጃገረድ 'እንስራሽን ዘንበል አድርገሽ ውሃ አጠጪኝ' እላታለሁ፤ 'አንተም ጠጣ፤ ግመሎችህም እንዲጠጡ ውጃ
ቀድቼ አመጣለሁ' ካለችኝ ለአገልጋይህ ለይስሐቅ ፍቅርህን እንዳሳየኸው ዐውቃለሁ።" 15 ገና ጸሎቱን ሳፅቸርስ ርብቃ እንስራ ተሸክማ መጣች፤ የዚህችም
ልጅ አባት ባቱኤል ይባል ነበር፤ እርሱም የአብርሃም ወንድም ናኮር ከሚስቱ ከሚልካ የወለደው ነው። 16 ርብቃ ገና ወንድ ያልደረሰባት በጣም ቆንጆ ልጃገረድ
ነበረች፤ እርስዋ ወደ ውሃው ጉድጓድ ወርዳ በእንስራዋ ውሃ ከቀዳች በኋላ ተመለሰች። 17 አገልጋዩም ወደ እርስዋ ሮጦ ሄዳና "እባክሽ ከእንስራሽ ከእንስራሽ
ጥቂት ውሃ አጠጪኝ"አላት። 18 እርስዋም "እሺ ጌታዬ ጠጣ" አለችና እንስራዋን ከትከሻዋ አውርዳ ዘንበል አድርጋ ያዘችለት። 19 ጠጥቶም ከረካ በኋላ
"ለግመሎችህም ውሃ እቀዳላቸዋለሁ፤ እስኪበቃቸውም ድረስ ይጠጡ" አለችው። 20 ወዲያውኑ፤ በእንስራዋ የያዘችውን ውሃ ግመሎቹ በሚጠጡበት ገዳን ላይ
ገልብጣ ግመሎቹ ሁሉ ጠጥተው እስከሚረኩ ድረስ እየተጣደፈች ከጉድጓድ ውሃ መቅዳት ቀጠለች። 21 ሰውየውም እግዚአብሔር የሄደበትን ተልእኮ
አቃንቶለት እንደሆን ለማረጋገጥ የምታደርገውን ሁሉ ዝም ብሎ ይመለከት ነበር። 22 ግመሎቹ ጠጥተው በኋላ ሰውየው አምስት ግራም ያህል የሚመዝን
የወርቅ ጎታቻ አውጥቶ በጆሮዋ ላይ አደረገላት፤ መቶ ዐሥር ግራም ያህል የሚመዝን ሁለት የወርቅ አምባሮችንም አውጥቶ በእጆችዋ ላይ አደረገላትና፤ 23
"የማን ልጅ ነሽ? እስቲ እባክሽ ንገሪኝ፤ ለእኔና አብረውኝ ቤት ይገኛልን?" ብሎ ጠየቃት። 24 እርስዋም "የባቱኤል ልጅ ነኝ፤ የባቱኤል አባት ናኮር፣ እናቱም
ሚልካ ይባላሉ፤ 25 በቤታችን ብዙ ገለባና ድርቆሽ አለ፤ ለእናንተም ማደሪያ ቦታ ይገኛል" አለችው። 26 ሰውየምውም በመንበርከክ ለእግዚአብሔር ሰግዶ፣ 27
"ለጌታዬ የገባውን ቃል ኪዳንና ዘላለማዊ ፍቅሩን የጠበቀ የጌታዬ የአብርሃም አምላክ እግዚአብሔር ይመስገን፤ በቀጥታ መርቶ ወደ ጌታዬ ወንድሞች ቤት
ያመጣኝ እርሱ ነው" አለ። 28 ልጅትዋ ወደ ቤት ሮጣ ሄደችና የሆነውን ሁሉ ለእናትዋና ለእርስዋ ጋር ላሉት ሁሉ ነገረቻቸው። 29 ርብቃ ላባ የተባለ ወንድም
ነበራት፤ እርሱ የአብርሃም አገልጋይ ወዳለበት ውሃ ጉድጓድ እየሮጠ ሄደ። 30 ላባ ወደ ሰውየው የሄደው እኅቱ በጆሮዋ ላይ ያደረገችውን ጉትቻና በእጆችዋ ላይ
ያደረገቻቸውን አንባሮች ስላየና ርብቃ ሰውየው ጉድጓድ አጠገብ ከግመሎቹ ጋር ቆሞ አገኘው። 31 ስለዚህ ላባ "አንተ እግዚአብሔር የባረከህ ሰው! ና ወደ ቤት
እንሂድ፤ በውጭ የቆምኸው ለምንድን ነው? በቤታችን ለአንተ ማደሪያ የተዘጋጀ ቦታ አለ" አለው። 32 ከዚህ በኋላ ሰውየው ወደ ቤት ሄደ፤ ላባም በግመሎቹ
ላይ የነበረውን ጭነት አረግፎ ገለባና ድርቆሽ አቀረበላቸው፤ ቀጥሎም የአብርሃም አገልጋይና አብረውት የነበሩት ሰዎች እግራቸውን የሚታጠቡበትን
አመጣላቸው። 33 ገበታ በቀረበው ጊዜ ጊዜ ሰውየው "የተላክሁበትን ጎዳይ ከመናገሬ በፊት እህል አልቀምስም" አለ። ላባም "ይሁን ተናገር" አለው። 34
እርሱም "እኔ የአብርሃም አገልጋይ ነን፤ 35 እግዚአብሔር ጌታዬ እጅግ ባርኮል፤ ባለጸጋም አድርጎታል፤ ብዙ የበግ፣ የፍየልና የከብት መንጋ፣ ብርና ወርቅ፣
ወንዶችና ሴቶች አገልጋዮች ግመሎችና አህዮች ሰጥቶታል። 36 የጌታዬ ሚስት ሣራ በእርጅናዋ ዘምን ወንድ ልጅ ወልዳለታለች፤ ጌታዬም ያለውን ሀብት ሁሉ
ለዚሁ ልጅ አውርሶታል። 37 ጌታዬ አብርሃም 'እኔ በመካከላቸው ከምኖረው ከከነዓናዊያን ሴቶች ልጆች መካከል ለልጄ ሚስት እንዳላጭለት፤ 38 ነገር ግን ወደ
አባቴ ቤተሰብና ወደ ዘመዶቼ ሄደህ ለልጄ ሚስት እጭለት' ሲል በመሐላ ቃል ኪዳን አስገብቶኛል።' 39 እኔም ጌታዬን 'ልጅቷ ከእኔ ጋር ለመምጣት ፈቃደኛ
ባትሆንስ ምን ላድርግ?' ብዬ ጠየኩት። 40 እርሱም እንዲህ አለኝ 'ዘውትር የማገለግለው እግዚአብሔር መልአኩን ከአንተ ጋር ይልካል፤ ጉዞህም የተቃና
እንዲሆን ያደርጋል፤ በዚህ ሁኔታ አንተም ከአባትቴ ቤተሰብና ከዘመዶቼ መካከል ለልጄ ሚስት ልታጭለት ትችላለህ፤ 41 ከመሐላህ ነፃ የምትሆነው ወደ
ዘመዶቼ ሄደህ እነርሱ ልጅትዋን አንሰጥም ብለው የከለከሉህ እንደሆነ ብቻ ነው።' 42 "ከዚያም በኋላ ዛሬ ወደ ውሃው ጉድጓድ ስመጣ እንዲህ ብዬ ጸለይሁ
'የጌታዬ የአብርሃም አምላክ እግዚአብሔር ሆይ! እባክህ የመጣሁበት ጉዳይ እንዲቃና አድርግልኝ፣ 43 እነሆ በዚህ ውሃ ጉድጓድ አጠገብ ቆሜአለሁ፤ አንዲት
ልጃገረድን ውሃ ልትቀዳ ስትመጣ፣ 'እባክሽ ከእንስራሽ ጥቂት ውሃ አጠጪኝ' ብዬ እጠይቃታለሁ፤ 44 እርስዋም 'እሺ ጠጣ፤ ለግመሎችህም
እቀዳቸዋለሁ'የምትለኝ ብትሆን፣ ለጌታዬ ልጅ ሚስት እንድትሆን አንተ የመረጥሃት እርስዋ ትሁን። 45 የኅሊና ጸሎትን ገና ሳልጨርስ ርብቃ እንስራ ተሸክማ ብቅ
አለች፤ ወደ ጉድጓዱም ሄዳ ውሃ ቀዳች፤ እኔም 'እባክሽ ጥቂት ውሃ አጠጪኝ አልኋት። 46 እርስዋም እንስራዋን በፍጥነት ከጀርባዋ አወረደችና ዘንበል አድርጋ
'እሺ ጠጣ፤ ግመሎችህንም አጠጣልሃለሁ' አለችኝ፤ ስለዚህ እኔም ጠጣሁ፤ ግመሎቼንም አጠጣችልኝ። 47 እኔም 'የማን ልጅ ነሽ?' ብዬ ጠየቅኋት።
እርስዋም 'የባቱኤል ልጅ ነኝ፤ የባቱኤል አባት ናኮር እናቱም ሚልካ ይባላሉ' አለችኝ። ከዚህ በኋላ ጉትቻ በጆሮዋ ላይ፣ አንባሮቹንም በእጅዎችዋ ላይ
አደረግሁላት፤ 48 ከዚህ በኋላ በጉልበቴ ተንበርክኬ ለእግዚአብሔር ሰገድሁ፤ የጌታዬን የአብርሃም አምላክ እግዚአብሔር አመሰገንሁ፤ ምክንያቱም ለጌታዬ ልጅ
ሚስት የምትሆነዋን ሴት ወዳገኘሁበት ወደ ጌታዬ ወንድም ቤት በቀና መንገድ የመራኝ እርሱ ነው። 49 እንግዲህ የጌታዬን ዐደራ በእውነት ተቀብላችሁ እርሱን
ደስ ለማሰኘት የምትፈቅዱ እንደሆነ ንገሩኝ፤ የማትፈቅዱም እንደሆነ ቁርጡን ነገሩኝ፤ እኔም እግዚአብሔር ወደሚመራኝ እሄዳለሁ።" 50 ላባና ባቱኤልም "ይህ
ነገር ከእግዚአብሔር የመጣ ስለሆነ፣ መከልከል አልችልም፤ 51 ርብቃ ይችውልህ፤ እነሆ ይዘሃት ሂድ፤ እግዚአብሔር ራሱ እንደተናገረው ለጌታዬ ልጅ ሚስት
ትሁን" አሉት። 52 የአብርሃም አገልጋይ ይህን በሰማ ጊዜ በጉልበቱ ተንበርክኮ ለእግዚአብሔር ሰገደ፤ 53 ከውርቅና ከብር የተሠሩ ጌጣጌጦችን፣ እንዲሁም
ልብስ አውጥቶ ለርብቃ ሰጣት፤ ለወንድምዋና ለእናትዋም በጣም ውድ የሆኑ ስጦታዎችን አውጥቶ ሰጣቸው። 54 ከዚህ በኋላ የአብርሃም አገልጋይና
አብረውት የነበሩ ሰዎች በልተው ጠጥተው እዚያው አደሩ፤ ጠዋት በተነሡ ጊዜ የአብርሃም አገልጋይ "እንግዲህ ወደ ጌታዬ እንድመለስ ፍቀዱልኝ" አለ። 55
ነገር ግን የርብቃ ወንድምና እናትዋ "ልጅትዋ ዐሥር ቀን ያህል ከእኛ ጋር ትቆይ፤ ከዚህ በኋላ ከአንተ ጋር ልትሄድ ትችላለች" አሉት። 56 እርሱ ግን "እባካችሁ
አታቆዩኝ፤ እግዚአብሔር የመጣሁበትን ጉዳይ ስላቃናልኝ ቶሎ ብዬ ወደ ጌታዬ ልመለስ" አላቸው። 57 እነርሱም "እስቲ ልጅቷን እንጥራትና እርስዋ የምትለውን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንስማ" አሉ። **58** ስለዚህ ርብቃን ጠሩና "ከዚህ ሰው ጋር መሄድ ትፈልጊያለሽ?" ብለው ጠየቅዋት። እርስዋም "አዎ እሄዳለሁ"አለች። **59** ስለዚህ ርብቃ ሞግዚትዋን አስከትላ፣ ከአብርሃም አገልጋይና ከእርሱ ሰዎች ጋር እንድትሄድ ፈቀዱላት። **60** "አንቺ እኅታችን የብዙ ሺ ሕዝብ እናት ሁኚ፤ ዝርያዎችሽም የጠላቶችሽን ከተሞች ይውረሱ" ብለው ርብቃን መረቁአት። **61** ከዚህ በኋላ ርብቃ ከተከታዮችዋ ጋር ለመሄድ ተነሣች፤ በግመሎቹ ላይ ተቀምጠው ከአብርሃም አገልጋይ ጋር ለመሄድ ተዘጋጁ። በዚህ ዐይነት የአብርሃም አገልጋይ ርብቃን ይዞ ሄደ። **62** በዚህ ጊዜ ይስሐቅ "ብኤር ላሐይ ሮኤ ወይም የሚያየኝን ሕያው አምላክ"የተባለው ኩሬ ወዳለበት በረሓ መጥቶ በኔጌብ ተቀምጦ ነበር። **63** ከለዕታት አንድ ቀን ወደ ማታ ጊዜ እያሰላሰለ በመስክ ውስጥ ሲዘዋወር ሳለ ግመሎች ሲመጡ በሩቅ አየ። **64** ርብቃ ይስሐቅ ባየች ጊዜ ከግመሏ ወረደችና፣ **65** "ያ በመስክ ውስጥ ወደ እኛ የሚመጣው ሰው ማን ነው?" ስትል የአብርሃምን አገልጋይ ጠየቀችው። አገልጋዩም "እርሱ ጌታዬ ነው!" አላት። ስለዚህ በጥፍነት በሻሽ ፊትዋን ሸፈነች። **66** አገልጋዩም ያደረገውም ነግር ሁሉ ለይስሐቅ ነገረው። **67** ከዚህ በኋላ ይስሐቅ እናቱ ሣራ ትኖርበት ወደነበረው ድንኳን ርብቃን ይዞአት ገባ፤ ሚስትም ሆነችው፤ ይስሐቅ ርብቃን ወደዳት፤ በእናቱ ሞት ምክንያት ከደረሰበትም ሐዘን በዚህ ሁኔታ ተጽናና።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 25

1 አብርሃም ቀጡራ የምትባል ሌላ ሚስት አገባ፤ **2** እርስዋም ዚምራንን፣ ዮቅሻንን፣ መዳንን፣ ምድያምን፣ ዩሽባቅንና ሹሐን ወለደችለት። **3** ዮቅሻንም ሳባንና ደዳንን ወለደ፤ የዳደንም ዝርያዎች አሹራውያን፣ ሌጡሻውያንና ሌአማውያን ናቸው። **4** የምድያም ልጆች ዔፋ፣ ዔፈር፣ ሐኖክ፣ አቢዳዕና ኤልዳዓ ናቸው፤ እነዚሁ ሁሉ የቁጠራ ዝርያዎች ናቸው። **5** አብርሃም ያለው ሀብት ሁሉ ለይስሐቅ አወረሰው፤ **6** ከሌሎች ሴቶች ለተወለዱትም ልጆች ገና በሕይወት ሳለ ስጦታ ሰጣቸው፤ ከዚህ በኋላ እነዚህ ሌሎች ልጆች ከይስሐቅ ርቀው ወደ ምሥራቅ አገር እንዲሄዱ አደረጋቸው። **7** የአብርሃም ዕድሜ በአጠቃላይ መቶ ሰባ አምስት ዓመት ነበር፤ **8** በዚህም ዐይነት አብርሃም በቂ ዕድሜ አግኝቶ ካረጀ በኋላ ሞተ፤ **9** ልጆቹ ይሰሐቅና እስማኤል ማክፌላ በተባለ ዋሻ ቀበሩት፤ ይህም ዋሻ ከመምሬ በስተምሥራቅ በሒታዊ በጾሐር ልጅ በዔፍሮን እርሻ ውስጥ የሚገኘው ነው። **10** እነሱም አብርሃም ከሒታዊያን ላይ የገዛው የመቃብር ቦታ ነው፤ በዚህ ዐይነት አብርሃም ሚስቱ ሣራ በተቀበረችበት ዋሻ ተቀበረ። **11** አብርሃም ከሞተ በኋላ ልጁን ይስሐቅን እግዚአብሔር ባረከው፤ ይስሐቅ "ብኤርላሐይሮኢ ወይም የሚያየኝ ሕያው አምላክ" ተብሎ በመጠራት ኩሬ አጠገብ ይኖር ነበር። **12** የሣራ አገልጋይ ግብፃዊትዋ አጋር ለአብርሃም የወለደችለትን እስማኤል፤ **13** ከዚህ በታች በዕድሜአቸው ቅደም ተከተል ተራ የተዘረዘሩትን ልጆች ወለደ፤ እነርሱም፦ ነባዮት፣ ቄዳር፣ አድብኤል፣ ሚብሣም፣ **14** ሚሽማዕ፣ ዱማ፣ ማሣ፣ **15** ሐዳድ፣ ቴማ፣ ይጡር፣ ናፊሽና ቄድማ ናቸው። **16** እነዚህ የእስማኤል ልጆች ለአሥራ ሁለት ነገዶች ቅድመ አያቶች ነበሩ፤ ስማቸውም በኖሩባቸው ከተሞችና ሰፍራዎች ሲጠራ ይኖራል። **17** እስማኤል መቶ ሠላሳ ሰባት ዓመት ሲሆነው ሞተ። **18** የእስማኤል ዝርያዎች ከግብፅ በስተምጅራቅ ወደ አሦር በምትወስደው መንገድ በሐዊላና በሹር መካከል ይኖሩ ነበር። የኖሩበትም ከሌሎቹ የአብርሃም ዝርያዎች ጋር በጥላቻ ተራርቀው ነበር። **19** የአብርሃም ልጅ ይስሐቅ ታሪክ ይህ ነው። አብርሃም ይስሐቅን ወለደ። **20** ይስሐቅ የባቱኤልን ልጅ ርብቃን ሲያገባ አርባ ዓመት ሆኖት ነበር፤ የርብቃ አባት ባቱኤልና ወንድምዋ ላባ በመስጴጦምያ የሞኖሩ ሶሪያውያን ነበሩ። **21** ርብቃ መካን ስለ ነበረች ይስሐቅ ስለ እርስዋ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤ እግዚአብሔርም ጸሎቱን ስለ ሰማ ርብቃ ፀነሰች፤ **22** የተፀነሱትም መንትያዎች ስለነበሩ እርስ በርሳቸው በማሕፀንዋ ውስጥ ይገፋ ነበር፤ እርስዋም "ይህን ዐይነት በገር ለምን ደረሰብኝ?" በማለት ወደ እግዚአብሔር ለመጸለይ ተነሣሣች። **23** እግዚአብሔርም ያሉት ሁለት ሕዝቦች ናቸው፤ እርስ በርሳቸው የማይስማሙ ሁለት ወገኖች ትወልጃለሽ፤ አንዱም ከሌላው የበረታ ይሆናል፤ ታላቁም ታናሹ አገልጋይ ይሆናል" አላት። **24** የመውለጃዋም ሰዓት በደረሰ ጊዜ ሁለት ወንዶች ልጆች ወለደ። **25** የመጀመሪያው ልጅ መልኩ ቀይ፣ ሰውነቱ ጠጉራም ነበር፤ ስለዚህ ዔሳው ተባለ። **26** ሁለተኛው ልጅ ሲወለድ የዔሳውን ተገረዝ ይዞ በመውጣቱ ያዕቆብ ተባለ፤ ልጆቹ በተወለዱ ጊዜ ይስሐቅ ስልሳ ዓመት ሆኖት ነበር። **27** ሁለቱም ልጆች አደጉ፤ ዔሳው በዱር መዋል የሚወደ ብልኅ አዳኝ ሆነ፤ ያዕቆብ ግን በቤት መዋል የሚወድ ጭምት ሰው ነበር። **28** ይስሐቅ ዔሳውን ይወድ ነበር። ምክንያቱም ዔሳው እያደነ ሥጋ ያበላው ነበር።ርብቃ ግን ያዕቆብን ትንን ነበር። **29** ለዕለታት አንድ ቀን ያዕቆብ ቀይ የምስር ወጥ በመሥራት ላይ እንዳለ ዔሳው ከአደን መጣ፤ በጣም እርቦት ነበር፤ **30** ስለዚህም ያዕቆብ "ከዚህ ከቀይ ወጥ ሰጠኝ" አለው። ኤዶም የተባለውም ነዚሁ ምክንያት ነበር። **31** ያዕቆብም "በመጀመሪያ ብኩርናህን ሸጥልኝ" አለው። **32** ዔሳውም "እኔ በረሀብ መሞቴ ነው፤ ታዲያ ብኩርና ምን ያደርግልኛል?" አለው። **33** ያዕቆብም "እንግዲያውስ ብኩርናህን እንደምትሸጥልኝ መጀመሪያ ማልልኝ" አለው። ስለዚህ ዔሳው ምሎ ብኩርናውን ለያዕቆብ ሸጠ። **34** ከዚህ በኋላ ያዕቆብ የምስሩን ወጥ በእንጀራ አድርጎ ሰጠው፤ ዔሳውም ከበላና ከጠጣ በኋላ ተነሥቶ ሄደ፤ በዚህ ዐይነት ዔሳው ብኩርናውን በመናቅ አቃለላት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 26

1 በአብርሃም ዘመን ከደረሰው ረሀብ ሌላ ዳግመኛ ረሀብ በምድር ላይ መጣ፤ በዚህ ምክንያት ይስሐቅ የፍልስጥኤማዋን ንጉሥ አቢሜሌክ ወዳለበት ወደ ገራር ሄደ፤ 2 በዚህም እግዚአብሔር ለይስሐቅ ተገለጠለትና እንዲህ አለው፣ "ወደ ግብፅ አገር አትሂድ፤ እንድትኖርበትም በምነግርህ በዚህ ምድር ተቀመጥ፤ 3 እዚሁ ኑር፤ እኔም ከአንተ ጋር እሆናለሁ፤ እባርክሃለሁ፤ ይህም ምድር ለአንተና ለዘርይዎችህ እሰጣለሁ፤ በዚህ ዐይነት ለአባትህ ለአብርሃም የገባሁትን ቃል ኪዳን እፈፅማለሁ፤ 4 ዘርህን አንደ ሰማይ ክዋክብት አበዛዋልለሁ፤ ይህንንም ሁሉ ምድር አወርሳቸዋለሁ፤ ይህንንም ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ። 5 አንተን የምባርክበትንም ምክንያት አባትህ አብርሃም ለእኔ ታዛዥ በመሆን የሰጠሁት ሕግና ሥርዓት ሁሉ ስለ ጠበወ ነው። 6 ስለዚህ ይስሐቅ መኖሪያውን በገራር አደረገ፤ 7 በዚያ አገር ስሰዎችም ስለ ርብቃ "ምንህናት" ብለው በጠየቁት ጊዜ "እኅቴ ናት" አላቸው፤ ይህንንም ያለበት ምክንያት ርብቃ በጣም ቆንጆ ስለ ነበረች የዚያ አገር ሰዎች በእርስዋ ሰበብ እንዳይገድሉት በመፍራት ነው። 8 ይስሐቅ እዚያ አገር ብዙ ጊዜ ከቆያ በኋላ የፍልስጥኤም ንጉሥ አቢሜሌክ በመስኮት ወደ ውጪ ሲመለከት ይስሐቅና ርብቃ እንደባልና ሚስት በመዳራት ሲጫወቱ አየ። 9 ስለዚህ አቢሜሌክ ይስሐቅን አስጠርቶ "ለካስ ርብቃ ሚስትህ ናት! ታዲያ "እኅቴ ናት' ያልከው ለምንድን ነው?" ሲል ጠየቀው። እርሱም "ሚስቴ ነች ያልኩ እንደሆን ሰዎች ይገድሉኝል ብዬ አስፈራሁ ነው" ብሎ መለሰ። 10 አቢሜሌክ "ይህ በእኛ ላይ ያደረግኸው ነገር ምንድን ነው? ከእኛ ሰዎች አንዱ በቀላሉ ሚስትህን ለመድፈር በቻለ ነበር፤" 11 ቀጥሎም አቢሜሌክ "ይህን ሰው ወይም ሚስቱን የሚነካ ሰው በሞቱ ይቀጣል"የሚል ማስጠንቀቂያ ለሕዝቡ ሰጠ። 12 ይስሐቅ በዚያች ምድር ዘርን ዘራ፤ እግዚአብሔር ስለባረከውም በዚያኑ ዓመት መቶ እጥፍ አመረተ፤ 13 ሀብት በሀብት ላይ እየተጨመረበት ዘመን የእርሱ አገልጋዮች ቁፍረዋቸው የነበሩትን የውሃ ጉድጓዶች ሁሉ ዐፈር ሞልተው ደፈኑአቸው። 14 ብዙ የበግና የከብት መንጋ፤ እንዲሁም ብዙ አገልጋዮች ስለ ነበሩት ፍልስጥኤማውያን ቀኑበት። 15 ስለዚህ የይስሐቅ አባት አብርሃም በሕይወት በነበረበት ዘመን የእሱን አገልጋዮች ቁፍረዋቸው የነበሩትን ውሃ ጉድጓዶች ሁሉ ዐፈር ሞልተው ደፈኑአቸው። 16 በዚያን ጊዜ አቢሜሌክ ይስሐቅን "ኅይልህ ከእኛ ይልቅ እየበረታ ስለሄደ፤ አገራችንን ለቀህ ውጣ" አለው። 17 በዚህ ምክንያት ይስሐቅ ያንን ቦታ ለቆ በገራር ሸለቆ ውስጥ ሰፈረ፤ እዚያም ተቀመጠ። 18 አብርሃም በሕይወት ሳለ አስቆፍሮአቸው የነበሩትን አብርሃም ከሞተ በኋላ ግን ፍልስጥኤማውያን የደፈኑአቸውን የውሃ ጉድጓዶች ይስሐቅ እንደገና እንዲቆፍሩ አደረገ፤ አባቱ ባወጣላቸ ስሞችም ጠራቸው። 19 የይስሐቅ አገልጋዮች በሸለቆው ውስጥ የውሃ ጉድጓድ ቁፍሩና ጥሩ የምንጭ ውሃ አገኙ፤ 20 የገራር እረኞች ግን "ይህ ውሃ የእኛ ነው" በማለት ከይስሐቅ እረኞች ጋር ተጣሉ።በዚህ ምክንያት ይስሐቅ ጉድጓዱን "ዔሤቅ" ብሎ ሰየመው። 21 የይስሐቅ አገልጋዮች ሌላ የውሃ ጉድጓድ ቁፈሩ፤ በዚህኛውም ጉድጓድ ምክንያት ሌላ ጠብ ተነሣ፤ ስለዚህ ይስሐቅ ይህን ጉድጓድ "ስጥና" ብሎ ሰየመው። 22 ከዚያም እልፍ ብሎ ሌላ የውሃ ጉድጓድ ምክንያት ምንም ጠብ ስላልተናሳ "እነሆ አሁን እግዚአብሔር ሰፊ ቦታ ሰጠን፤ በምድር ላይም እንበዛለን ሲል ያንን ቦታ 'ረሖቦት" ብሎ ሰየመው። 23 ከዚያ በኋላ ይስሐቅ ወደ ቤርሳቤህ ወጣ፤ 24 በዚያን ሌሊት እግዚአብሔር ተገለጠለትና "እኔ የአባትህ አምላክ ነኝ፤እኔ ከአንተ ጋር ስለሆንኩ አትፍራ! ለአገልጋዬ ለአብርሃም በገባሁት ቃል ኪዳን መሠረት እባርክሃለሁ፤ ዘርህንም አበዛዋለሁ" አለው። 25 ይስሐቅ በዚያ መሠዊያ መሠዊያ ሠራና ለእግዚአብሔር ሰገደ፤ መኖሪያውንም እዚያ አደረገ፤ አገልጋዮቹም ሌላ ጉድጓድ ቆፈሩ። 26 አቢሜሌክ ከአማካሪው ከአሑዘትና ከሠራዊቱ ኣዥ ኮፊኮል ጋር ይስሐቅን ለመጎብኘት ከገራር ወት፤ 27 ስለዚህ ይስሐቅ "ከዚህ በፊት ጠልታችሁን አገራችሁ እንድወጣ አድርጋችሁኛል፤ ታዲያ አሁን ልትጎበኝ የመጣችሁት ለምንድን ነው?" አላቸው። 28 እነርሱም እንዲህ ሲሉ መለሱለት፣ "እግዚአብሔር ከአንተ ጋር መሆኑን በግልጥ ዐውቀናል፤ ስለዚህ በእኛና በአንተ መካከል በሰላም ለመኖር የሚያስችል ስምምነት በመሐላ ለመፈፀም አስበናል፤ በዚህም መጀረት ቃል ኮዳን እንድትገባልን የሚንፈለገው፣ 29 በእኛ ላይ ምንም ዐይነት በደል እንዳታደርስብን ነው፤ ምክንያቱም እኛ በአንተ ላይ ምንም ግፍ አልሠራንም፤ ዘውትር መልካም ነገር አደረግንልህ እንጂ ክፉ አላደረግብህም፤ ከአገራችንም የወጣኸው በሰላም ነው፤ አሁንም እግዚአብሔር ባርኮሃል።" 30 ከዚህ በኋላ፣ ይስሐቅ ግብዣ አደረገላቸው፤ እነሱም በሉ፣ ጠጡ። 31 በማግሥቱ ጠዋት በማለዳ ተነሡና ተማማሉ፤ ይስሐቅ ካሰናበታቸው በኋላም በሰላም ሄዱ። 32 ከዚያኑ ቀን የይስሐቅ አገልጋዮች መጥተው ስለ ቁፈሩት ጉድጓድ ለይስሐቅ ነገሩት፤ "ውሃ አገኘን" ብለውም አበሠሩት። 33 እርሱም የውሃን ጉድጓድ "ሳቤህ"ብሎ ጠራው፤ ስለዚህም የከተማይቱ ስም እስከ ዛሬ "ቤርሳቤህ" እየተባለ ይጠራል። 34 ዔሳው አርባ ዓመት ሲሆንው የብኤሪን ልጅ ዮዲትንና የኤሎንን ልጅ ባሴማትን አገባ፤ ሁለቱም ሒታውያን ነበሩ። 35 ይህም ጋብቻ ይስሐቅንና ርብቃን ሲያዝናቸው ይኖር ነበር።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 27

1 ይስሐቅ አርጅቶ ዐይኖቹም ታውረው ነበር፤ ታላቁ ልጁን ዔሳውን፤ "ልጄ ሆይ!" ብሎ ጠራው፤ ልጁም "እነሆ አለሁ" አለ። 2 ይስሐቅም እንዲህ አለው፣
"እንደምታየኝ አርጅቻለሁ፤ የምሞትበትንም ቀን አላውቅም፤ 3 ስለዚህ የምታድንበትን ቀስትና ፍላጻ ያዝ፤ ወደ ዱር ሂድና አውሬ አድነህ ሥጋ አምጣልኝ፤ 4 ልክ
እንደምወደው አድርገህ ምግብ ሥራልኝ ከበላሁም በኋላ ከመሞቴ በፊት የመጨረሻ ምርቃቴን እሰጥሃለሁ።" 5 ይስሐቅ ለልጁ ለዔሳው ወደ አደን ከሄደ በኋላ፣
6 ርብቃ ልጅዋን ያዕቆብን "አባትህ ዔሳውን እንዲህ ሲለው ሰማሁ፣ 7 አውሬ አድነህ ሥጋ አምጣልኝ፤ ልክ እንደምወደው አድርገህ የጣፈጠ ምግብ ሥራልኝ፤
ሳልሞትም በእግዚአብሔር ፊት እነርቅሃለሁ፤ 8 አሁንም ልጄ ሆይ! የምነግርህን አድምጥ፤ የማዝህንም አድርግ፤ 9 አባትህ እንደሚወደው አጣፋጩ ጥሩ
ምግብ እንድሠራለት፣ ወደ መንጋዎች ሂድና ሁለት የሰቡ የፍየል ጥቦቶች አምጣልኝ፤ 10 አንተም ያዘጋጀሁትን ምግብ እንዲበላ ለአባትህ ወስደህ
ታቀርብለታለህ፤ በዚህ ዐይነት አባትህ ከመሞቱ በፊት ይመርቅሃል።" 11 ያዕቆብ ግን እናቱን ርብቃን "የወንድሜ የዔሳው ገላ ጠጉራም ነው፤ የ እኔ ገላ ግን
ምንም ጠጉር የሌለው ለስላሳ ነው፤ 12 ምናልባት አባቴ ቢዳስሰኝና እንዳታለልኩህ ቢያውቅ በምርቃት ፈንታ እርግማን እንደማተርፍ ታውቂ የለምን?" አላት።
13 እናቱም "ልጄ ሆይ! የአንተ እርግማን በእኔ ላይ ይሁን፤ አሁንም እንደነገርሁህ አድርግ፤ ሄድህ ጥቦቶቹን አምጣልኝ" አለችው። 14 ስለዚህ ሄዶ ጥቦቶቹን
አመጣለት እርስዋም ልክ አባቱ እንደሚወደው እድርጋ ጥሩ ወጥ ሠራች፤ 15 የታላቁ ልጅዋን የዔሳውን የክት ልብስ ከተቀመጠበት ቦታ አውጥታ ለያዕቆብ
አለበሰችው። 16 የፍየሎቹንም ቆዳ በክንዶቹ ላይና ጠጉር በሌለበት በአንገቱ ላይ አለበሰችው። 17 ያዘጋጀውንም ጥሩ ወጥ ከጋገረችው እንጀራ ጋር ልልጅዋ
ለያዕቆብ ሰጠችው። 18 ያዕቆብ ወደ አባቱ ሄደና "አባባ!" አለው፤ እርሱም "እነሆ አለሁ! ለመሆኑ አንተ የትኛው ልጄ ነህ!" አለ። 19 ያዕቆብም "የበኩር
ልጅህ ዔሳው ነኝ፤ እነሆ እንዳዘዝከኝ አድርጌአለሁ፤ እንድትመርቀኝ እስቲ ቀና በልና ያመጣሁልህን የአደን ሥጋ ተመገብ" አለው። 20 ይስሐቅም "ልጄ ሆይ!
እንዴት ቶሎ ልታገኝ ቻልህ?" አለው። ያዕቆብም "አምላክህ እግዚአብሔር ስለረዳኝ በቶሎ ለማግኘት ቻልሁ" አለው። 21 ይስሐቅም "እስቲ ወደ እኔ ቀረብ በልና
ልዳብስህ፤ በእርግጥ አንተ ዔሳው ነህን?" አለው። 22 ያዕቆብም ወደ አባቱ ተጠጋ፤ አባቱም ዳሰሰውና "ድምፅህ የያዕቆብ ድምፅ ይመስላል፤ ክንድህ ግን
የዔሳውን ክንድ ይመስላል" አለው። 23 ክንዶቹ እንደ ዔሳው ክንዶች ጠጉራም ስለ ነበሩ ይስሐቅ ያዕቆብን ለይቶ ማውቅ አልቻለም፤ ሊመርቀው ከዝዘጋጀ
በኋላ፣ 24 "እርግጥ አንተ ልጄ ዔሳው ነህን?" ሲል እንደገና ጠየቀው፤ እርሱም "አዎ ነን" አለ። 25 ይስሐቅም "ልጄ! በል ከአደንከው ሥጋ አቅርብልኝ፤
ከበላሁም በኋላ እመርቅህለሁ" አለው። ያዕቆብም ምግቡን አቀረበለት፤ የወይን ጠጅም እንዲጠጣ አመጣለት። 26 ከዚህ በኋላ አባቱ ይስሐቅ "ልጄ ሆይ!
ቀረብ በልና ሳመኝ" አለው፤ 27 ያዕቆብም ቀርቦ ሳመው። ይስሐቅ የያዕቆብ ልብስ ባሸተተ ጊዜ እንዲህ ሲል መረቀው፣ "እነሆ የልጄ መልካም ሽታ
እግዚአብሔር እንደባረከው የእርሻ ሽታ ነው፤ 28 እግዚአብሔር ከሰማይ የሚያረሰርሰው ተል ይስጥህ፤ ምድርህን ያለምልምልህ፤ እህልንና የወይን ጠጅህን
ያብዛልህ፤ 29 መንግሥታት ይገዙልህ፤ ሕዝቦችህም ያገልግሉህ፤ በወንድሞችህ ሁሉ ላይ አለቃ ሁን፤ የእናትህም ልጆች ይስገዱልህ፤ የሚረግሙህ የተረገሙ
ይሁኑ፤ የሚመርቁህ የተመረቁ ይሁኑ።" 30 ይስሐቅ ያዕቆብን መርቆ እንዳበቃና ያዕቆብም አባቱን ፊት እንደወጣ ወዲያውኑ ዔሳው ከአደን ተመልሶ መጣ። 31
እርሱም በበኩሉ የጣፈጠ ወጥ ሠርቶ ለአባቱ አቀረበለትና "አባቴ ሆይ እንድትመርቀኝ፣ እስቲ ቀና ብለህ ካመጣሁልህ የአደን ሥጋ ብላ" አለው። 32 ይስሐቅም
'አንተ ማን ነህ?" አለው፤ እርሱም "እኔ የበኩር ልጅ ዔሳው ነኝ" አለ። 33 ይስሐቅም እጅግ ደንግጦ እየተነቀጠቀጠ "ታዲያ አውሬ አድኖ ያመጣልኝ ማን
ነበረ? ልክ አንተ ከመምጣትህ በፊት ተመገብሁ የመጨረሻ ምርቃቴንም ሰጠሁት፤ ምርቃቱም ተእርሱ ሆኖ ይኖራል"አለው። 34 ዔሳው ይህን በሰማ ጊዜ
ድምፁን ከፍ በማድረግ ምርር ብሎ እያለቀሰ "አባቴ ሆይ! እኔንም መርቀኝ!" አለ። 35 ይስሐቅም "ወንድምህ መጥቶ እኔን በማታለል የአንተን ምርቃት
ወስዶብሃል"አለው። 36 ዔሳውም "እርሱ እኔን ሲያሰናክለኝ ይህ ሁለተኛው ነው፤ ያዕቆብ መባሉ ተገቢ ነው፤ ከዚህ በፊት ብኩርናዬን ወሰደብኝ፤ አሁን ደግሞ
ምርቃቴን ቀማኝ፤ ታዲያ ለእኔ ያስቀረከው ምንም ምርቃት የለምን? አለው። 37 ይስሐቅም "ቀድሞ ብዬ እርሱን የአንተ ጌታ አድርጌዋለሁ፤ ወንድሞቹ ሁሉ
የእርሱ አገልጋዮች እንዲሆኑ አድርጌአለሁ፤ እህልና የወይን ጠጅ እንዲበዛለት አድርጌአለሁ፤ ልጄ ሆይ! እንግዲህ ለአንተ ምን ላደርግልህ እችላለሁ?" አለው።
38 ዔሳውም "አባቴ ሆይ! ምርቃትህ እንዲት ብቻ ናትን? እባክህ እኔንም መርቀኝ" እያለ ለማልቀስ አባቱን ነዘነዘው። 39 ይስሐቅም አንዲህ አለው። "በረከት
ከሞላበት ለምለም ምድር ርቀህ ትኖራለህ፤ የሰማይ ጠልም አታገኝም፤ 40 በሰይፍም ኅይል ትኖራለህ፤ የወንድምህም አገልጋይ ትሆናለህ፤ በተቃወምከውም
ጊዜ ግን ከእርሱ ጭቁና ትላቀቃለህ።" 41 አባቱ ስለመረቀው ዔሳው ያዕቆብን አጥብቆ ጠላው፤ በልቡም "አባቴ በቅርብ ቀን ይሞታል፤ ከዚህ በኋላ ወንድሜን
ያዕቆብን እገድለዋለሁ"ብሎ አሰበ። 42 ነገር ግን ርብቃ የዔሳውን ዕቅድ ስለ ሰማች፣ ያዕቆብን ጠርታ እንዲህ አለችው፣ "አድምጠኝ፤ ወንድምህ ዔሳው አንተን
በመግደል ሊበቀልህ አስቦአል፤ 43 አሁንም ልጄ ሆይ! የምልህን አድርግ፤ ተነሥተህ በካራን ወደሚገኘው ወደ ወንድሜ ወደ ላባ ሸሽ፤ 44 የወንድምህ ቁጣ
እስኪበርድ ድረስ ለጥቂት ጊዜ እዚያው ቆይ፤ 45 ቁጣውም ሲበርድ ያደረግህበትን ነገር ይረሳል፤ ከዚያ በኋላ ሰው ልኬ አስመጣሃለሁ፤ ሁለታችሁም በአንድ
ቀን ማጣት አልፈልግም። 46 ርብቃ ይስሐቅን "ዔሳው ባገባቸው በእነዚህ በሖታውያን ሴቶች ምክንያት መኖሬን ጠላሁት፤ ያዕቆብ ደግሞ ከነዚህ ከሒታውያን
ሴቶች አንዲቱ ከገባ ለመኖር ይልቅ ሞቴን እመርጣለሁ"አለችው።

Genesis 27:1

ዓይኖቹ ደክመው
ይህ የሚናገረው ዓይኖች እንደ መብራት ብርሃን እየቀነሱ እንደሄዱ እና ማየት ወደ መሳን ደረጃ እንደደረሱ ነው:: አት: “ዓይኖቹ ማየት ተስኖአቸው” ወይም “ዓይኖቹ ወደ መታወር ደርሰው” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)::

እርሱም እርሱን አለው
“ዔሣው መለሰለት”“ዔሣው መለሰለት”

እነሆ አለው
“እነሆ አለሁ” ወይም “እየሰማሁ ነኝ” በዘፍጥረት 22:1 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

እርሱም አለው
“ከዚያም ይሥሐቅም አለ”

ይሄው ተመልከት
“ይኼው ተመልከት” የሚለው ሀረግ ለሚቀጥለው ሃሳብ አጽንዖት የሚሰጥ ነው:: አት: “በጥንቃቄ ስማ ግምታዊ እውቀት” ወይም “ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ”

የምሞትበትን ቀን አላውቅም
ይህ ይስሐቅ ቅርብ ጊዜ እንደሚሞት የሚያመለክት ነው:: አት: “ከማንኛውም ጊዜ ሊሞት ይሆናል”:: (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሞት
አካላዊ ሞትን ይገልጻል

Genesis 27:3

አጠቃላይ መረጃ
“ይስሐቅ ለታላቅ ልጁ ለዔሣው መመሪያልችን ይሰጣል”

የአደን መሣሪያህን
“የአደን መሣሪያዎችህን”

የፍላጻ ኩሮጆ
የፍላጻ ኩሮጆ የቀስቶች መሸከሚያ ነው:: አት: “የቀስቶች መሸከሚያ ኩሮጆ” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

አድነህም አምጣልኝ
“የዱር እንስሳት አድነህ አምጣልኝ”

የምወደው ዓይነት ጣዕም ያለው ምግብ አዘጋጅተህ
“ጣዕም ያለው” የሚለው ቃል እጅግ በጣም ጣፋጭ የሆነውን ነገር ያመለክታል:: አት: “የምወደው ዓይነት የሥጋ ምግብ አዘጋጅልኝ” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

እንዲመርቅህ
በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን አባት መደበኛ የሆነ መንገድ ልጆችን ይመርቃል

Genesis 27:5

“በወቅቱ”
በወቅቱ የሚለው ቃል ትኩረቱ ወደ ርብቃና ያዕቆብ መዞሩን ያሳያል:: (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ርብቃም ይስሐቅ ለልጁ ለዔሣው ሲነግር ትሰማ ነበር
“ይስሐቅ ለልጁ የተናገረውን ርብቃ ትሰማ ነበር”

ዔሣው ... ለማምጣት ሄደ:: ርብቃም ያዕቆብን እንዲህ አለችው
ዔሣው ከወጣ በኋላ ርብቃ የሰማችውን ለያዕቆብ ተናገረች:: አት: “ዔሣው ለማምጣት በወጣ ጊዜ ርብቃም ለያዕቆብ ተናገረች” (አያየዥ ቃላት ይመልከቱ)

ለዔሣው ለልጁ .... ለያዕቆብ ልጅዋን
ዔሣውና ያዕቆብ ሁለቱም የይስሐቅና የርብቃ ልጆች ናቸው አንድ ወላጅ አንዱን ልጅ ከሌላኛው ልጅ አብልጦ እንደሚወድ ተደርገው የእርሱ ልጅ እና የእርስዋ ልጅ ተብለው ተጠርተዋል::

ይሄው ተመልከት
“ይኼው ተመልከት” የሚለው ሀረግ ለሚቀጥለው ሃሳብ አጽንዖት የሚሰጥ ነው:: አት: “በጥሞና ስማ ግምታዊ እውቀት” ወይም “ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ”

እርሱም አለ ከመሞቴ በፊት በእግዚአብሔር ፊት እንዲመርቅህ ጥሩ ጣዕም ያለው ምግብ እንድበላ አዘጅልኝ
ይህ በጥቅስ ውስጥ የሚገኝ ጥቅስ ነው:: እንደተዘዋዋሪ ጥቅስ ለገለጽ ይችላል አት: “ለዔሣውም ነገረው; ‘የዱር እንስሳ እንዲያድንና የሚወደውን ጣዕም የሥጋ ምግብ እንዲያዘጋጅለት’ ከዚያም ከመሞቱ በፊት በእግዚአብሔር ፊት የስሐቅ ዔሣውን እንዲባርከው” (በጥቅስ ውስጥ ጥቅሶችንና ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)::

አድነህም አምጣልኝ
“የዱር እንስሳት አድነህ ገድለህ አምጣልኝ”

የምወደው ዓይነት ጣዕም ያለው ምግብ አዘጋጅተህ
“የምወደው ዓይነት የሥጋ ምግብ አዘጋጅልኝ” ይህን በዘፍጥረት 27:4 እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

በእግዚአብሔር መገኘት እንዲመርቅህ
“በእግዚአብሔር ፊት እንዲመርቅህ”

Genesis 27:8

አጠቃላይ መረጃ
ርብቃ ለሁለተኛ ልጅዋ ለያዕቆብ መናገርዋን ቀጠለች

አሁንም
ይህ በዚያ ወቅት የሚለውን የሚናገር አይደለም ነገር ግን ለሚቀጥለው ዋና ነጥብ ትኩረት እንዲሰጥበት ነው::

እኔ በማዝዝህን ድምጼን ስማኝ
ርብቃ “ድምጼን” ያለችው የምትናገረውን ነገር ለማመልከት ነው:: አት: “ታዘዘኝ የምናገረውንም ነገር አድርግ” (ተዛማጅ ባሕሪይ የሚገልጽ ምትክ ቃል የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

እነርሱንም አባትህ እንደሚወደው ዓይነት ጣፋጭ ምግብ አዘጋጅለታለሁ
ጣፋጭ የሚለው ቃል በጣም ጥሩ ጣዕም ያለውን ነገር ያመለክታል:: በዘፍጥረት 27:4 ተመሳሳይ ቃል እንዴት እንደተተረጐመ ይመልከቱ::

ወደ አባትህም ይዘህ ግባለት
“ከዚያም ወደ አባትህ ይዘህ ግባ”

እንዲበላ እንዲመርቅህ
ከበላ በኋላ ይመርቅሃል

ይመርቅህ ይሆናል
ምርቃት የሚለው ቃል አባት ልጆቹን የሚናገረው መደበኛ ምርቃት ነው

ከሞቱ በፊት
ከመመቱ በፊት

Genesis 27:11

እኔ ለስላሣ ነኝ
“የእኔ ገላ ለስላሣ ነው” ወይም “እኔ ጸጉራም አይደለሁም”

በምርቃት ፈንታ ርግማን አተርፋለሁ
መረገም ወይም መባረክ ምርቃት ወይም በረከት በአንድ ሰው ላይ እንደሚሆን ዕቃ ተደርገው ተነግረዋል አት ከዚያም ከዚህም የተነሣ ይረግመኛል ወይም አይባርከኝም (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

Genesis 27:13

ልጄ ሆይ ማንኛውም ርግማን በእኔ ላይ ይድረስ
“ልጄ ሆይ መርገምህ በእኔ ላይ ይሁን” መረገም ርግማን በአንድ ሰው ጫንቃ ላይ እንደሚሆን ዕቃ ተደርጐ ተገለጸአል:: አት “ልጄ ሆይ አባትህ አንተን ከመርገም እኔን ይርገመኝ” (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

ድምጼን ታዘዝ
ርብቃ “ድምጼን” ያለችው የምትናገረውን ነገር ለማመልከት ነው:: አት: “የሚናገርህን ታዘዝ” ወይም “ታዘዘኝ” (ተዛማጅ ባሕሪይ የሚገልጽ ምትክ ቃል የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

እነርሱን አምጣልኝ
“ጠቦቶቹን አምጣልኝ”

ልክ አባቱ እንደሚወደው ዓይነት ጣፋጭ ምግብ አዘጋጅችለት::
ጣፋጭ የሚለው ቃል በጣም ጥሩ ጣዕም ያለውን ነገር ያመለክታል:: በዘፍጥረት 27:4 ተመሳሳይ ቃል እንዴት እንደተተረጐመ ይመልከቱ::

Genesis 27:15

ጠቦቶቹን ቆዳ በእጆቹ ላይ አለበሰችው
የጠቦቶች ቆዳዎች ጸጉር ነበረባቸው

የሠራችውን ጣፋጭ መብልና እንጀራውን ለልጅዋ ለያዕቆብ በእጁ ሰጠችው
“የሠራችውን ጣፋጭ መብልና እንጀራውን ለልጅዋ ለይዕቆብ ሰጠችው”

Genesis 27:18

እርሱም አለው
“እናም አባቱ መለሰው” ወይም “ይስሐቅም መለሰው”

አነሆኝ
“አዎን እየሰማሁ ነኝ” ወይም “አዎን ምንድነው?” በዘፍጥረት 22 1 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ

የተናገርከኝ ወይም ያዘዝከኝን አድርጌአለሁ
እንዳደርገው የነገርከኝን አድርጌአለሁ

አደን አድኜ ካመጣሁት ከፊሉ
“የታደነ” የምለው ቃል አንድ ሰው የዱር እንሰሳትን አድኖና ገድሎ የሚያቀርበውን ያመለክታል:: በዘፍጥረት 27:3 “የታደነ” የሚለው እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

Genesis 27:20

እርሱም አለው
ያዕቆብም መለሰው

አሳካልኝ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር እግዚአብሔር ለሁኔታው ምክንያን እንደሆነ ይገልጻል:: አት: “በማድንበት ጊዜ እንዲሳካልኝ ረድቶኛል” (ፈሊጣዊ አነጋገሮች ይመልከቱ)::

በእርግጥ እውነተኛው ልጄ ዔሣው መሆንህን
“በእርግጥ ልጄ ዔሣው መሆንህን”

Genesis 27:22

ያዕቆብ ወደ አባቱ ወደ ይስሐቅ ቀረበ
“ያዕቆብ ወደ አባቱ ወደ ይስሐቅ ተጠጋ”

ይህ ድምጽ የያዕቆብ ድምጽ ነው
እዚህ ይስሐቅ የያዕቆብ ድምጽ ያዕቆብን እንደሚወክል ይናገራል። አት: “ድምጽህ የያዕቆብ ይመስላል” (ክፍልን እንደ ሙሉ ወይም ሙሉውን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

እጆቹ ግን የዔሣው እጆች ናቸው
እዚህ ይስሐቅ የዔሣው እጆች ዔሣውን እንደሚወከሉ ይናገራል። አት: እጆች ግን የኤሣው እጆች እንደሆኑ ይሰሙኛል። (ክፍልን እንደ ሙሉ ወይም ሙሉውን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

Genesis 27:24

እርሱም አለ
ይስሐቅ ልጁን ከመባረኩ በፊት ይህን ጥቃቄ ይጠይቀዋል:: አት: “ነገር ግን መጀመሪያ ይስሐቅ ጠየቀው” (የክስተቶች ቅደም ተከተል ይመልከቱ)

አድነህ ካቀረብክልኝ ልብላ
የታደነ የሚለው ቃል ሰዎች አድነውና ገድለው የሚያቀርቡትን የዱር እንሰሳ ያመለክታል:: በዘፍጥ 27:7 የታደነ እንዴት አንደተተረጐመ ይመልከቱ::

ጠጣም
“ይስሐቅ ጠጣ”

Genesis 27:26

እርሱም ልብሶቹን ካሸተተ በኋላ መረቀው
ልብሶች የኤሣው ልብሶች ሽታ እንዳሸቱ ግልጽ ነው:: አት: “እርሱም ልብሶቹን አሸተተ እናም ሽታው እንደ ዔሣው ልብሶች ሽታ ስለሆነ ባረከው” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

አሸተተ
ይስሐቅ አሸተተ

ሽታ
ጠረን

ባረከው
“ከዚያም ባረከው” ይህ አባት ልጆቹን የሚባረከውን መደበኛ በረከት ያመለክታል::

እነሆ የልጄ ጠረን
“እነሆ” የሚለው ቃል ይህ እውነት ነው የሚለውን ለመግለጽ የተጠቀመ አበክሮአዊ ሥዕላዊ አገላለጽ ነው:: አት: “በእውነት የልጄ ጠረን”

እግዚአብሔር እንደባረከው
እዚህ በረከት የሚለው ቃል እግዚአብሔር በእርሻው መልካም ነገሮች እንዲሆኑና ፍሬያማ እንዲሆን እንዲያደርግ ነው:: አት: “ያም እግዚአብሔር ፍሬያማ እንዲያደርግ” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 27:28

አጠቃላይ መረጃ
ይህ የይስሐቅ ባረኮት ነው ለኤሳው የተናገረው መሰለሙ ነገር ግን የተናገረው ለያዕቆብ ነው

ይስጥህ
እዚህ “ይስጥህ” ነጠላና ያዕቆብን የሚያመለክት ነው በረከቱ ግን ለያዕቆብ ትውልድም የሚሆን ነው:: (ሁለተኛ ሰው አጠቃቀምንና ክፍልን እንደ ሙሉ እና ሙሉን የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

የሰማይን ጠል
ጠል በሌሊት በተክሎች ላይ የሚሆን የውሃ ጠብታ ነው:: በትርጉም ይህን ግልጽ ማድረግ ይቻላል:: አት: “ተክሎችዎን ለማጠጣት የሌሊት ጠል” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

የምድርንም በረከት
ለም መሬት የመኖር መሬት ስብና ሀብታም እንደሆነች ተደርጐ ተገለጾአል:: አት: “እህልን የሚያመርት መልካም መሬት ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የተትረፈረፈ እህልና አዲስ የወይን ጠጅ
“እህል”ና “ወይን” ያልተገለጹ እስከሆነ ድረስ ጠቅለል ባለ መልክ መግለጽ ይቻላል:: አት: “የተትረፈረፈ መብልና መጠጥ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 27:29

አንተ.... ያንተ
እዚህ እነዚህ ተውላጤ ስሞች በነጠላ የተገለጹና የዕቆብን ያመለክታሉ በረከቱ ግን ለያዕቆብ ትውልድም ነው (ሁለተኛ ሰው አገላለጽንና ክፍልን እንደ ሙሉ እና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ሕዝቦች ተደፍተው እጅ ይንሠህ ወይም ይስገዱልህ
እዚህ ሕዝቦች ሰዎችን ያመለክታል አት የሁሉም ሕዝቦች ሰዎች ተደፍተው እጅ ይንሠህ:: (ተዛማጅ ተመሣሣይ ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

ይስገዱልህ
ይህ ጐንበሥ በማለት አንድ ሰው አክብሮት መስጠትን ይገልጻል ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ

የወንድሞችህ ጌታ ሁን
በወንድምችህ ላይ ጌታ ወይም ገዢ ሁን

ወንድሞችህ ...የእናትህም ልጆች
ይስሐቅ ይህን በረከት በቀጥታ ለያዕቆብ ይናገራል ነገር ግን ይህ የያዕቆብ ትውልድ በኤሣው ትውልድና በሌሎች ማናቸውም የያዕቆብ ወንድሞች ትውልድ ላይ ገዢዎች እንደሚሆኑ ለእነርሱም ይሆናል። (ክፍል ለሙሉና ሙሉን ለክፍል የመጠቀም አገላለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

የእናትህም ልጆች ይስገዱልህ
የእናትህም ልጆች የሰግዱልሃል

የምረግሙህ የተረገሙ ይሁኑ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “እግዚአብሔር የሚረግሙህን ሁሉ ይርገማቸው“ (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

የሚባርኩህ የተባረኩ ይሁኑ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “እግዚአብሔር የሚባርኩህን ሁሉ ይባርካቸው“ (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Genesis 27:30

ያዕቆብም ገና ከአባቱ ዘንድ ሳይወጣ ወዲያውኑ
“ከአባቱን ከይስሐቅን ድንኳን እንደወጣ”

ጣፋጭ ምግብ
የምወደው ጣፋጭ ሥጋ በዘፍጥረት 27:3 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ።

ልጅህ ካደንሁት
እዚህ “ልጅህ” ኤሣው ካደነው ያዘጋጀውን ምግብ በትህትና ያቀረበበት መንገድ ነው:: (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

ልጅህ ካደነው
የታደነ የሚለው ቃል ሰዎች አድነውና ገድለው የሚያቀርቡትን የዱር እንሰሳ ያመለክታል:: በዘፍጥ 27:7 የታደነ እንዴት አንደተተረጐመ ይመልከቱ::

ባርከኝ
ይህ አንድ አባት ልጆቹን የሚባርክበት መደበኛ መንገድ ያመለክታል

Genesis 27:32

ለእርሱም አለው
ዔሣውን አለው

ይስሐቅም ተንቀጠቀጠ
ይስሐቅም መንቀጥቀጥ ጀመረ

በአደን የታደነ
የታደነ የሚለው ቃል ሰዎች አድነውና ገድለው የሚያቀርቡትን የዱር እንሰሳ ያመለክታል:: በዘፍጥ 27:7 የታደነ እንዴት አንደተተረጐመ ይመልከቱ::

Genesis 27:34

ድምጹን ከፍ በማድረግ ምርር ብሎ አለቀሰ
የዔሣው ምሬት አንድ መራራ ጣዕም ካለው ነገር ጋር የሚመሳሰል ነበር:: አት: “በከፍተኛ ድምጽ አለቀሰ” (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

ምርቃትህን ወስዶብሃል
ይህ ያዕቆብ የዔሣውን በረከት እንደወሰደ የሚገልጽ ምሳሌያዊ አገላለጽ ነው አት በአንተ ፈንታ እርሱን ባርከአለሁ (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

Genesis 27:36

ያዕቆብ መባሉ የሚታወቅ አይደለምን?
ዔሣው በያዕቆብ ላይ ያለውን ቁጣ ለመጨመር ጥያቄ ይጠቀማል:: አት ያዕቆብ በእርግጥ ለወንድሜ ትክክለኛ ስም ነው:: (ቅኔያዊ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

ያዕቆብ
ተርጓሚዎች እንዲህ የሚለውን የግርጌ ማስታወሻ ይጠቀማሉ ያዕቆብ የሚለው ስም ተረከዙን ያዘ የሚል ትርጉም አለው በመሠረታዊው ቋንቋ ቃሉ አታላይ የሚል አንድምታ አለው::

ብኩርናዬን ወሰደብኝ
ይህ ብኩርና እንደ አንድ ዕቃ ከሰው እንደሚወሰድ አድርጐ ይናገራል:: አት: “የእኔ የሆነው ብኩርና በማታለሉ ምክንያት የእርሱ ሆኖአል” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)::

አሁን ደግሞ ምርቃቴን ቀማኝ
ይህ ምርቃት እንደ አንድ ዕቃ ከሰው እንደሚቀማ አድርጐ ይናገራል:: አት : “አታልሎህ በእኔ ፈንታ እርሱን እንዲትመርቅ አድረጐሃል” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)::

ለእኔ ያስቀረኼው ምንም ምርቃት የለም?
ያዕቆብን የባረከውን ዓይነት በረከት አባቱ እንደማይባርከው ዔሣው ያውቃል ይስሐቅ ያዕቆብን በሚባርክበት ጊዜ ሳይናገር የቀረው ካለ ዔሣው ይጠይቀዋል

ልጄ ለአንተ ምን ላደርግልህ እችላለሁ?
ይስሐቅ ጥያቄ በመጠቀም ምንም ሊያደርገው የሚችለው ነገር እንደሌለ በአጽንዖት ይናገራል:: አት “ለአንተ የማደርገው የቀረ ነገር የለም” (ቅኔ አዘል ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

Genesis 27:38

አባቴ ሆይ በረከትህ አንዲት ብቻ ናትን?
ይህ በአዎንታዊ መንገድ ሊነገር ይችላል:: አባቴ ሆይ አንድ የቀረ መረከት ለእኔ የሚሆን አለህን?

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Genesis 27:39

እርሱን አለው
ዔሣውን አለው

ቦታውን ተመልከት
ትኩረት አድርግ ስለቦታው የሚናገረው እውነትና ጠቃሚ ነው

ከምድር በረከት የራቀ
ይህ ስለምድር ለምነት የሚናገር ምሳለያዊ አነጋገር ነው አት ለም ያልሆነ መሬት

ለአንተ.... አንተ
በ27:39-40 እነዚህ ተውላጤ ስሞች ነጠላና ዔሣውን ያመለክታሉ:: ነገር ግን ይስሐቅ የሚናገረው ለዔሣው ትውልድም የሚሆን ነው:: ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ::

ከላይም ከሰማይ ጠል
ጠል በሌሊት በተክሎች ላይ የሚሆን የውሃ ጠብታ ነው:: በትርጉም ይህን ግልጽ ማድረግ ይቻላል:: አት: “ተክሎችዎን ለማጠጣት የሌሊት ጠል” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

በሰይፍ ትኖራለህ
ሰይፍ ለአመጽ የሚቆም ነው:: አት: “ለመኖር የሚያስፈልግህን ለማግኘት ሰዎችን ትዘርፋለህ ትገድላለህ” (ተዛማጅ ተመሣሣይ ምትክ ቃል ስለመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

ቀንበሩ ከጫንቃህ ላይ ወዲያው ትጥላለህ
ይህ አንድ ጌታ እንዳለውና የጌታውም የበላይ አገዛዝ አንደሚሸከምበት ቀንበር እንደተጫነበት ተደርጐ ተነግሮአል አት ከግዛቱ ራስህን ነጻ ታወጣለህ:: (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 27:41

ዔሣውም በልቡ እንዲህ ብሎ አሰበ
“ልብ” ራሱ ዔሣውን ያመለክታል:: አት: “ዔሣው ለራሱ እንዲህ አለ” (ተዛማጅ ተመሣሣይ ምትክ ቃል የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ) የአባቴ የለቅሶ ቀን ቀርቦአልና ይህ የቤተሰብ አባል ሲሞት አንድ ሰው የሚያዝንበት ቀናት ያመለክታል

የታላቅ ልጇ የኤሣው ሀሳብ ለርብቃ ተረገራት
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “አንድ ሰው የዔሣውን ዕቅድ ለርብቃ ነገራት“ (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

እይ
“ተመልከት” “አዳምጥ” “ለምናገረው ነገር ትኩረት ስጥ”

ራሱን እያረጋጋ ነው
ራሱን ጥሩ ስሜት እንዲሰማው እያደረገ ነው

Genesis 27:43

አሁንም
ይህ “አሁን ጊዜ” ማለት አይደለም:: ነገር ግን የሚቀጥለው አስፈላጊ ነጥብ ትኩረት እንዲሰጥበት ተጠቅሞአል::

ወደ ላባን ቶሎ ሽሽ
ቶሎ ከዚህ ሽሽ እናም ወደ ላባን ሂድ

ለጊዜ
ለተወሰነ ጊዜ

የወንድምህ ቁጣ እስኪበርድ
ወንድምህ እስኪበርድ

የወንድምህ ቁጣ ከአንተ እስኪመለስ
ያለ መቆጣት ቁጣ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ አቅጣጫ እንደሚዞር ተደርጐ ተነግሮአል:: አት: “በአንተ ላይ መቆጣቱን እስኪተው ድረስ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ሁለታችሁን በአንድ ቀን ለምን ሊጣ?
ርብቃ ሥጋትዋን ለመግለጽ ጥያቄ ትጠቀማለች አት ሁለታችሁን በአንድ ቀን ማጣት አልፈልግም! (ቅኔ አዘል ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

ሁለታችሁን በአንድ ቀን አጣለሁ
ይህ የሚገልጸው ኤሣው ያዕቆብን ከገደለ እርሱ ደግሞ ገዳይ በመሆኑ ስለሚገድሉት ነው:: (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

አጣለሁ
ልጆቹዋ እንደሚሞቱባት የሚያመላክት ለዛ ያለ አገላለጽ ነው (ንጎብነት ወይም ለዛ ባለ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ አንድን ነገር የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

Genesis 27:46

መኖር አስጠልቶኛል
ኤሣው የኬጢያውያን ሴት በማግባቱ ርብቃ መንኛ እንደተናደደች በማግነን ትኩረት መስጠትዋ ነው:: አት: “በማምረር ጠልቸዋለሁ” (hyperbole and Generalization/

የኬጢያውያን ሴት ልጆች
“እነዚህ የኬጢያውያን ሴቶች” ወይም “የኬጢያውያን ትውልጆች”

እንደነዚህ ሴቶች ከዚህ አገር ሴቶች ልጆች
“የአገሩ ሴቶች ልጆች” የአገሩ ሴቶች ማለት ነው:: አት: “በአገሩ የሚኖሩ እንደ እነዚህ ሴቶች” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይጠቀሙ)

በሕይወት መኖር ለምኔ ነው?
ያዕቆብ ከኬጢያውያን ሴት ልጆች የሚያገባ ከሆነ ርብቃን ማነኛ እንደሚያስከፋት በማግነን ጥያቄ ትጠቀማለች:: አት: “ሕይወቴ የከፋ ይሆናል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 28

1 ይስሐቅ ያዕቆብን ጠርቶ መረቀው፤ እንዲህም ሲል አዘዘው፣ "ከነዓናዊት ሴት እንድታገባ፤ **2** ይልቅስ ተነሥተህ በመስጴጦምያ ወዳለው ወደ እናትህ አባት ወደ ባቱኤል ቤት ሂድ፤ እዚያም ከአጎትህ ከገባ ሴቶች ልጆች አንዷን አግባ፤ **3** ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር ይባርክህ፤ ብዙ ልጆችም ይስጥህ፤ የብዙ ሕዝቦችም አባት ያድርግህ፤ **4** አብርሃምን እንደባረከ አንተንና ዘርህን ይባርክ፤ ይህንንም ለአብርሃም ሰጥቶት የነበረውንና አንተም ደስተኛ ሆነህ የኖርክበት ምድር ርስት አድርጎ ይስጥህ።" **5** በዚህ ሁኔታ ይስሐቅ ያዕቆብን አሰናበተው፤ ያዕቆብም በመስጴጦምያ ወደሚያኖረው ወደ ላባ ሄደ፤ ላባ የያዕቆብና የዔሳው እናት የርብቃ ወንድም ነበረ፤ አባቱም ሶርያዊው ባቱኤል **6** ይስሐቅ ያዕቆብን እንደመረቀና ሚስት እንደሚፈልግ ወደ መስጴጦምያ እንደላከው ዔሳው ተረዳ፤ ይስሐቅ ያዕቆብን ሲመርቀው "ከነዓናዊት ሴት እንዳታገባ" ብሎ ያዘዘው መሆኑንም ሰማ፤ **7** ያዕቆብ ለአባቱና ለእናቱ በመታዘዝ ወደ መስጴጦምያ መሄዱንም ተረዳ፤ **8** በዚህም አባቱ ይስሐቅ የከነዓንያውያንን ሴቶች እንደማይወድ ዔሳው ተገነዘበ፤ **9** ስለዚህ ከዚህ በፊት ከገባቸው ሌላ በተጨማሪ ወደ አብርሃም ልጅ ወደ እስማኤል ሄዶ ልጁን ማሕላትን አገባ፤ እርስዋም የነባዮት እኅት ናት። **10** ያዕቆብ ቤርሳቤህን ትቶ ወደ ካራን ለመሄድ ተነሣ፤ **11** ፀሐይ በጠለቀች ጊዜ ወደ አንድ ስፍራ መጥቶ ዐረፈ፤ በዚያም አንድ ድንጋይ ተንተርሶ ተኛ፤ **12** በሕልሙም ከመሬት እስከ ሰማይ የሚደርሰው መሰላል አየ፤ በመሰላሉም የእግዚአብሔር መላእክት ወደ ላይ ይውጡና ወደ ታች ይውረዱ ነበር። **13** እግዚአብሔር በአጠገቡ ቆሞ እንዲህ አለው፣ "እኔ የአባትህ የአብርሃምና የይስሐቅ አምላክ እግዚአብሔር ነኝ፤ ለአንተና ለዝርያዎችህ እንዲሆን ይህን የተገኘህበት ምድር እሰጥሃለሁ። **14** ዘርህን እንደ ምድር አሸዋ አበዛዋለሁ፤ እነርሱ በሁሉ አቅጣጫ ይዞታቸውን ያስፋፋሉ፤ በአንተና በዘርህ የዓለም ሕዝቦች ሁሉ ይባረካሉ። **15** አይዞህ! እኔ ከአንተ ጋር ነኝ፤ በምትሄድበት ስፍራ ሁሉ እጠብቅሃለሁ፤ ወደዚያም ምድር በደህና እመልስሃለሁ፤ የገባሁልህን ቃል ኪዳን ሁሉ እፈፅምልሃለሁ፤ ከቶም አልተውህም።" **16** ያዕቆብም ከእንቅልፉ ነቃና "በእርግጥ እግዚአብሔር በዚህ ስፍራ አለ፤ እኔ ግን ይህን አላወቅሁም ነበር"አለ። **17** በጣም ፈርቶም ስለነበር "ይህ እንዴት የሚያስፈራ ቦታ ነው፤ ይህ የእግዚአብሔር ቤት መሆን አለበት፤ ወደ ሰማይ የሚያስገባው በር ይህ ነው"አለ። **18** ያዕቆብ በማግሥቱም ጠዋት በማለዳ ተነሣ፤ ተንተርሶት የነበረውንም ድንጋይ መታሰቢያ እንዲሆን እንደ ሐውልት አቆመው፤በላዩ ላይም የወይራ ዘይት አፈሰሰበት። **19** ይህንንም ስፍራ "ቤትኤል"ብሎ ሰየመው፤ ይህ ስፍራ ከዚያ በኋላ ሎዛ እየተባለ ይጠራ ነበር። **20** ከዚህ በኋላ ያዕቆብ እንዲህ ብሎ ለእግዚአብሔር ተሳለ "ከእኔ ጋር ሆነህ በምትሄድበት መንገድ ብትጠብቀኝ፣ የሚያስፈልገኝን ምግብና ልብስ ብትሰጠኝ፣ **21** ወደ አባቴም ቤት በሰላም ብትመልሰኝ፤ አንተ አምላኬ ትሆናለህ፤ **22** ይህ ለመታሰቢያነት ያቆምሁት ድንጋይ ወደ ፊት የእግዚአብሔር ቤት ይሆናል፤ ከምትሰጠኝም ሁሉ ከዐሥር አንዱን እጅ ለአንተ እሰጣለሁ።"

Genesis 28:1

አታግቡ
አታግባ

ተነሣ ሂድ
ወዲያውኑ ሂድ

ጳዳን አራም
ይህ የመስጴጦምያ ግዛት ሌላ ስሙ ሲሆን የአሁኑ ራቅ የሚገኝበት ቦታ ነው:: በዘፍጥረት 25:20 ይህ እንዴት አንደተተረጐመ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)

ቤት
የሰውየው ትውልድ ወይም ሌሎች ዘመዶች: አት: “ቤተሰብ” (ተዛማጅ ተመሣሣይ ምትክ ቃል የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

ባቱኤል
ባቱኤል የርብቃ አባት ነው በዘፍጥረት 22:22 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ። (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)

የእናትህ አባት
ወንድ አያትህ

ሴት ልጆች መካከል
ከሴት ልጆች

የእናትህ ወንድም
አጐትህ

Genesis 28:3

አጠቃላይ መረጃ
ይስሐቅ ለያዕቆብ መናገሩን ቀጠለ

ልጆች አፍራ ዘርህን ያብዛው
ያብዛው የሚለው ቃል እግዚአብሔር ያዕቆብን እንዴት ፍሬያማ እንደሚያደርገው ይገልጻል:: አት: “ብዙ ልጆችንና ትውልድ ይሰጥሃል” (ድርብ ቃላት ይመልከቱ)

ለአብርሃም የሰጠውን በረከት ለአንተና ለዘሪህ ይስጥ
ይህ የሚናገረው አንድን ሰው ስለመባረክ ሲሆን በረከት አንድ ሰው ሊሰጥ እንደሚችል ዕቃ ተደርጐ ተገልጾአል ረቂቅ ስም “በረከት” “ይባርክ” በሚለው ሊገለጽ ይችላል:: አት: “አብርሃምን እንደባረከ አንተንና ዘርህን እግዚአብሔር ይባርክ” ወይም “ለአብርሃም የገባውን ተስፋ ለአንተና ለዘርህ እግዚአብሔር ይስጥ”:: (ዜይቤያዊ አነጋገርና ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ)

ምድሪቱን ያወርስህ ዘንድ
እግዚአብሔር የከነዓንን ምድር ለያዕቆብና ለዘሩ መስጠቱ ልጅ ከአባቱ ገንዘብ ወይም ሀብት እንደሚወርስ ተደርጐ ተገልጾአል (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

የሚትኖርበትን ይህችን ምድር
“እስከአሁን ያለህበትን ምድር”

እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን
እግዚአብሔር ለአብርሃም ተሰፋ የሰጠውን

Genesis 28:5

ጳዳን አራም
ይህ የመስጴጦምያ ግዛት ሌላ ስሙ ሲሆን የአሁኑ ራቅ የሚገኝበት ቦታ ነው:: በዘፍጥረት 25:20 ይህ እንዴት አንደተተረጐመ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)

ባቱኤል
ባቱኤል የርብቃ አባት ነው በዘፍጥረት 22:22 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ። (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Genesis 28:6

አጠቃላይ መረጃ
ታሪኩ ከያዕቆብ ወደ ዔሣው ይዞራል

አሁንም
ይህ ቃል እዚህ የተጠቀመው ከተነገረው ታሪክ ወደ ዔሣው የሕይወት መረጃ ፍሰቱ መቀየሩን ለማመልከት ነው (ታሪካዊ ዳራ መረጃ ይመልከቱ)

ጳዳን አራም
ይህ የመስጴጦምያ ግዛት ሌላ ስሙ ሲሆን የአሁኑ ራቅ የሚገኝበት ቦታ ነው:: በዘፍጥረት 25:20 ይህ እንዴት አንደተተረጐመ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)

ሚስት ያግባ
ሚስትን ያግባ

እንዲሁም ደግሞ ይስሐቅም እንደባረከው አየ
እንዲሁም ይስሐቅ ያዕቆብን እንደባረከው ኤሣው አየ

የከነዓን ሴቶች
የከነዓን ሴት ልጆች ወይም የከነዓናዊያን ሴቶች

Genesis 28:8

አጠቃላይ መረጃ
የዔሣውን ታሪካዊ ዳራ ይቀጥላል

ዔሣው አየ
ዔሣው ተገነዘበ

ከነዓናውያን ሴቶች በአባቱ በይስሐቅ ዘንድ ተጠልተዋል
አባቱ ይስሐቅ የከነዓናውያንን ሴቶች አልተቀበለም

የከነዓን ሴቶች
የከነዓን ሴት ልጆች ወይም የከነዓናዉያን ሴቶች

ስለዚህም ሄዴ
በዚህ ምክንያት ሄዴ

በሚስቶቹ ተጨማሪ
ከነበሩ ሚስቶች ተጨማሪ

ማዕሌት
የእስማኤል ሴት ልጆች አንዷ ነች (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ነባዮት
ከእስማኤል ወንድ ልጆች አንዱ ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 28:10

አጠቃላይ መረጃ
ታሪኩ እንደገና ወደ ያዕቆብ ይመለሳል

ወደ አንድ ሥፍራም ደረሰ ጸሐይም ጠልቃ ነበርና ከዚያ አደረ
ወደ አንድ ሥፍራ ደረሰ ጸሐይም ጠልታ ስለነበር አዳሩን ከዚያ ለማድረግ ወሰነ

Genesis 28:12

እርሱም ሕልም ዐለመ
ያዕቆብ ሕልም ዐለመ

በምድር ላይ ቆሞ
ታችኛው አካል መሬትን በነካ መንገድ ቆሞ

ጫፉ ሰማይ የሚደርስ
ይህ እግዚአብሔር የሚኖርበትን ቦታ ያመለክታል

እነሆም
እነሆም የሚለው ቃል ለሚቀጥለው አስደናቂ መረጃ ትኩረት ለመስጠት ነው

እግዚአብሔር በጫፉ ላይ ቆሞ
ተገቢ ትርጉሞች 1 እግዚአብሔር በመሰላሉ ጫፍ ላይ ቆሞ 2 እግዚአብሔር በያዕቆብ ጐን ቆሞ

ለአብርሃም ለአባትህ
እዚህ “አባት” ቅድመ ዘር ማለት ነው:: አት: “አብርሃም ለዘርህ” ወይም “አብርሃም ለቅድመ አያትህ”

Genesis 28:14

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለያዕቆብ በሕልም መናገሩን ቀጠለ

ዘርህ እንደምድር አሸዋ ይሆናል
በቁጥር መብዛትን አግንኖ ለማሳየት እግዚአብሔር የያዕቆብን ዘር ከምድር አሸዋ ጋር ያነጻጽራል:: አት: “መቁጠር ከምትችሉት በላይ ብዙ ዘር ይሆንላችኋል” ተመሣሣይ አባባል/simile ይመልከቱ

እስከ ምዕራብ ትስፋፋለህ
ትስፋፋለህ በነጠላ የተቀመጠና ያዕቆብን ያመለክታል እዚህ ያዕቆብ ዘሩን ይወክላል:: አት: “መቁጠር ከሚትችለው በላይ ብዙ ዘር ይሆንልሃል” (ተዛማጅ ተመሣሣይ ምትክ ቃል የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

ትስፋፋለህ
ይህም ሕዝቡ የምድራቸውን ድንበር የሰፋሉ እናም ብዙ ምድር ይወርሳሉ ማለት ነው

ወደ ምዕራብ ወደ ምሥራቅ ወደ ሰሜን ወደ ደቡብ
እንዚህ ሀረጐች በጣምራ “ወደ ሁሉም አቅጣጫዎች” የሚል ትርጉም ለመስጠት ተጠቅመዋል:: (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

የምድርም ሕዝቦች ሁሉ በአንተና በዘርህ አማካይነት ይባረካሉ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት: “በአንተና በዘርህ በምድር ያሉ ሕዝቦችን እባርካለሁ” (ተሻጋረ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተነገር ይመልከቱ)

እነሆ እኔ
ትኩረት ስጥ እኔ የሚናገረው እውነትና ጠቃሚ ነው፤ እኔ

አልተውህም ሁሉንም እፈጽምልሃለሁ
ሁሉንም እስከሚፈጽምልህ ድረስ አልተውህም

እጠብቅሃለሁ
“ደኅንነትህን እጠብቃለሁ” ወይም “እከላከልልሃለሁ”

እንደገና ወደዚችም ምድር እመልስሃለሁ
ወደዚህች ምድር እመልስሃለሁ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Genesis 28:16

ከእንቅልፉ ሲነሣ
ከእንቅልፉ ሲነቃ

የእግዚአብሔር ቤት ... የሰማይ ደጅ
የሰማይ ደጅ የሚለው ሀረግ የሚገልጸው የእግዚአብሔር ቤት እና የእግዚአብሔር መኖሪያ መግቢያ ቦታ እንደሆነ ነው (ድርብ ቃላትና አባባሎች ይመልከቱ)

ይህ የሰማይ ደጅ ነው
ይህ ስለ እግዚአብሔር መኖሪያ ቦታ መግቢያ የሚናገረው በአካል እንደሚታይ አንድ ሰው በር ከፍቶ ሰዎችን እንደሚያስገባው የመንግሥት ቤት ተደረጐ ተገልጾአል:: (ዘይቤያዊ አባባል ይመልቱ)

Genesis 28:18

ሐውልት
ትልቅ ድንጋይ ወይም በጫፉ ቅርጽ ያለበት ለማስታወሻነት የቆመ ሐውልት ነው

በላዩ ላይ የወይራ ዘይት አፈሰሰበት
ያዕቆብ ሐውልቱን ለእግዚአብሔር መቀደሱን የሚያመለክት ድርጊት ነው:: የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት: “ሐውልቱን ለእግዚአብሔር ለመቀደስ ዘይት በላዩ ላይ አፈሰሰበት” (ምልክታዊ ድርጊት ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ቤተል
ቤተል ማለት የእግዚአብሔር ቤት የሚለውን ተረጓሚዎች እንደ ግርጌ ማስታወሻ ያስቀምጣሉ

ሎዛ
ይህ የከተማይቱ ስም ነው

Genesis 28:20

ስእለት ተሳለ
“ስእለት አደረገ” ወይም “በተለይ ለእግዚአብሔር ቃል ገባ”

እግዚአብሔር እንዲህ.... እግዚአብሔር አምላኬ ይሆናል
ያዕቆብ እግዚአብሔርን በሶስተኛ ሰው አገላለጽ ያናግረዋል ይህ በሁለተኛ ሰው አገላለጽ ሊገለጽ ይችላል:: አት: አንተ እንዲህ...የማመልከው አምላኬ ትሆናለህ” (ተዛማጅና ተመሣሣይ ምትክ ቃል የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

የሚበላውን እንጀራ ቢትሰጠኝ
እዚህ “እንጀራ” አጠቃላይ ምግብ ይገልጻል (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ወደ አባቴ ቤት
“ቤት” ለያዕቆብ ቤተሰብን ይገልጻል አት ወደ አባቴና ወደሌሎች የቤተሰብ አባላት (ተዛማጅና ተመሣሣይ ምትክ ቃል የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

የተቀደሰ ድንጋይ
ድንጋዩ እግዚአብሔር የተገለጠበትን ቦታ ያመለክታልና ሰዎች እግዚአብሔርን የሚያመልኩበት ቦታ ይሆናል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 29

1 ያዕቆብ ጉዞውን ቀጥሎ በስተ ምሥራቅ ወዳለው አገር ደረሰ፤ **2** እዚያም በሜዳ ላይ አንድ የውሃ ጉድጓድ አየ፤ በሦስት የተከፈሉ የበግ መንጋዎች በጉድጓድ ዙሪያ ነበሩ፤ መንጋዎቹ ውሃ የሚጠጡት ከዚሁ ጉድጓድ ነበር፤ ጉድጓዱም የሚዘጋበት ድንጋይ ትልቅ ነበር፤ **3** መንጋዎቹ ሁሉ እዚያ ከተሰበሰቡ በኋላ እረኞቹ ድንጋዩን አንከባለው ከጉድጓዱ ውሃ ያጠቱአቸው ነበር፤ መንጋዎቻቸውን ካጠጡ በኋላ ግን ድንጋዩንም መልሰው በጉድጓዱ አፍ ላይ ይከዱኑታል። **4** ያዕቆብም እረኞቹን "ወዳጆቼ ሆይ! ከየት ነው የመጣችሁት?" ብሎ ጠየቃቸው። እነሱም "እኛ የመጣነው ከካራን ነው" አሉት። **5** እርሱም "የናኮርን የልጅ ልጅ ላባን ታውቁታላችሁን?" ብሎ ጠየቃቸው። እነሱም "አዎ እናውቀዋለን" አሉት። **6** እርሱም "ለመሆኑ እርሱ ደኅና ነውን?" አላቸው። እነርሱም "አዎ፣ ደኅና ነው፤ እንዲያውም ልጁ ራሔል ያችውልህ! በጎች እየነዳች በመምጣት ላይ ነች" አሉት። **7** ያዕቆብም "ጊዜው ገና ቀን ነው፤ መንጋዎቻቸውንም ወደ ቤት የምታስገቡበት ሰዓት ገና አልደረሰም፤ ታዲያ ለምን ውሃ አጠጥታችሁ አታሰማሩአቸውም? ፤ አለ። **8** እነርሱም "እረኞች ሁሉ መንጋዎቻቸውን ይዘው እዚህ ከመሰብሰባቸው በፊት ምንም ማድረግ አንችልም፤ ሁሉም እዚህ ከመጡ በኋላ ግን ድንጋዩን በኅብረት አንከባለን በጎቹን እናጠጣቸዋለን" አሉት። **9** ያዕቆብም ከእረኞቹ ጋር በመነጋገር ላይ ሳለ ራሔል የአባትዋን በጎች ይዛ ወደዚያ መጣች፤ ምክንያቱም እርስዋ የበጎች እረኛ ነበረች። **10** ያዕቆብ ያጉቱን የላባን በጎች እየነዳች ስትመጣ ራሔልን አይቶ ወደ ጉድጓድ ሄደ፤ ጉድጓዱ የተከደነበትንም ድንጋይ አንከባሎ በጎቹን አጠጣቸው። **11** ከዚያ በኋላ ራሔልን ሳማት። ከደስታውም ብዛት የተነሣ አለቀሰ፤ **12** "እኔ የአባትሽ እኅት የሆነችው የርብቃ ልጅ ሄደች። **13** ላባም የእኅቱ ልጅ ያዕቆብ መምጣቱን በሰማ ጊዜ ሊቀበለው ፈጥኖ ሄደ፤ አቅፎ ከሳመውም በኋላ ወደ ቤት አመጣው፤ ያዕቆብ የሆነውን ሁሉ ለላባ ነገረው፤ **14** ላባም "በእርግጥ አንተ ቅርብ የሥጋ ዘመዴ ነህ" አለው፤ ያዕቆብም አንድ ወር ያህል ከአጎቱ ጋር ተቀመጠ። **15** ላባ ያዕቆብን "ዘመዴ በመሆንህ ብቻ በነፃ ልታገለግለኝ አይገባህም፤ ስለዚህ ምን ያህል ደመወዝ ላስብልህ? አለው። **16** ላባ ሁለት ሴቶች ልጆች ነበሩት፤ ታላቂቱ ልያ፤ ታናሽቱ ራሔል ይባሉ ነበር። **17** ልያ ዐይነ ልም ስትሆን፣ ራሔል ግን ቁመናዋ የሚያምር የደስ ደስ ያላት ነበረች። **18** ያዕቆብ ራሔልን እጅግ ስለወደዳት "ራሔልን ብትድርልኝ ሰባት ዓመት አገለግልሃለሁ" አለ። **19** ላባም "ለሌላ ሰው ከምሰጣት ይልቅ ለአንተ ብሰጥህ ይሻለኛል፤ እሺ ተስማምቼአለሁ፤ እዚሁ ከእኔ ጋር ኑር" አለው። **20** ያዕቆብ ራሔልን ለማግባት ሰባት ዓመት አገለገለ፤ ይሁን እንጂ ራሔልን በጣም ይወዳት ስለነበር የቆየበት ጊዜ ጥቂት ቀን ብቻ መስሎ ታየው። **21** ከዚያ በኋላ ያዕቆብ ላባን "እነሆ የአገልግሎት ዘመኔ ተፈፅሞአል፤ ሚስት እንድትሆነኝ ልጅህን ስጠኝ" አለው። **22** ላባም የሠርግ ድግስ አዘጋጅቶ በአቅራቢያው የሚገኙትን ሰዎች ሁሉ ጠራ። **23** ነገር ግን ላባ በራሔል ምትክ ልያን ለያዕቆብ ሰጠው፤ ያዕቆብም ከልያ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት አደረገ። **24** ላባ ሴት አገልጋዩን ዚልፋን አገልጋያዋን እንድትሆን ለልጁ ለልያ ሰጣት። **25** በማግስቱ ጠዋት ያዕቆብ አብራው ያደረችው ልያ መሆንዋን ባወቀ ጊዜ ወደ ላባ ሄዶ "ይህ ያደረግህብኝ ነገር ምንድን ነው? ያገለገልሁህ ራሔልን ለማግኘት አልነበረም? ታዲያ ለምን አታለልከኝ"አለው። **26** ላባም "ታላቂቱ ሳትዳር፤ ታናሺቱን መዳር የአገራችን ልማድ አይደለም፤ **27** የልያ ሠርግ ሰባት ቀን እስኪሞላው ድረስ ጠብቅ፤ ከእንግዲህ ወዲይ ሰባት ዓመት የምታገለግለኝ ከሆነ ራሔልን እሰጥሃለሁ" አለው። **28** ያዕቆብም ነገሩ ተስማማ፤ ከልያ ጋር ሰባት ቀን ተሞሽሮ ከቆየ በኋላ፤ ላባ ልጁን ራሔልን ለያዕቆብ ሳረለት። **29** ላባ ሴት አገልጋዩን ባላን አገልጋይዋ እንድትሆን ለልጁ ለራሔል ሰጣት። **30** ያዕቆብ ከራሔልም ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት አደረገ፤ ከልያም አብልጦ ወደዳት፤ ከዚያ በኋላ ላባን ሰባት ዓመት አገለገለው። **31** ልያ የራሔልን ያህል እንዳልተወደደች እግዚአብሔር ባየ ጊዜ መውለድ እንድትችል ማሕፀንዋን ከፈተላት፤ ራሔል ግን መኻን ሆነች፤ **32** ልያ ርግዝ ወንድ ልጅ ወለደች፤ "እግዚአብሔር መከራዬን ተመለከተ፤ ከእንግዲህስ ወዲያ ባሌ ይወደኛል" ስትል ስሙን ሮቤል አለችው። **33** እንደገና አረገዘችና ሌላ ወንድ ልጅ ወደች፤ "እግዚአብሔር እንዳልተወደድሁ ሰማ፤ ይህንንም ልጅ ደግሞ ሰጠኝ' ስትል ስሙን ስምዖን አለችው። **34** እንደገና 'አረገዘችና ሌላ ወንድ ልጅ ወለደች፤ "እንግዲህ ሦስት ወንዶች ልጆች ስለ ወለድሁለት ባሌ ከእኔ ጋር በፍቅር ይጠመዳል" ስትል ስሙን ሌዊ አለችው፤ **35** እንደገና አረገዘችና ውንድ ልጅ ወለደች፤ "አሁንስ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ" ስትል ስሙን ይሁዳ አለችው፤ ከዚህ በኋላ መውለድ አቋረጠች።

Genesis 29:1

የምሥራቅ ሰዎች
ከከነዓን ምድር በስተምሥራቅ የሚገኙ የጻዳን አራም ሰዎች ማለት ነው::

እነሆ በአንድ ሜዳ ላይ ሶስት የበግ መንጋዎች ተኝተው በነበሩበት
እነሆ የሚለው ቃል በትልቁ ታሪክ ውስጥ አንድ ሌላ ክስተት መጀመሩን ያመለክታል:: በሚትተረጉሙበት ቋንቋ ይህን የመግለጽ መንገድ ሊኖሮት ይችላል::

ከዚያ ጉድጓድ
ከዚሁ ጉድጓድ ይህ ሀረግ ታሪኩን ወደ ዳራው መረጃ ይመልስና እንዴት እረኞች በጎችን ውሃ እንደሚያጠጡ ይናገራል

እነርሱ ውሃ ያጠጣሉ
“እረኞች ውሃ ያጠጣሉ” ወይም “በጎችን የሚጠብቁ ውሃ ያጠጣሉ”

የጉድጓዱ አፍ
አፍ ጉድጓዱ የተከፈተበትን ቦታ ያሳያል:: አት: “ጉድጓዱ የተከፈተበት ቦታ”

Genesis 29:4

ያዕቆብም እነርሱን አለ
ያዕቆብም እረኞቹን አለ

ወንድምቼ
ይህ ለእንግዶች በትህትና ሰላምታ የማቅረብ መንገድ ነው

የናኮር ወንድ ልጅ ላባ
አዚህ ወንድ ልጅ ወንድ ዘርን ያመለክታል ሌላ ተገቢ ትርጉም የናኮር የልጅ ልጅ ላባ

እነሆ ተመልከት ራሔል በጎችን እየነዳች በመምጣት ላይ ነች
አሁን ተመልከት የእርሱ ሴት ልጅ ራሔል ከበጎች ጋር በመምጣት ላይ ነች

Genesis 29:7

ገና ቀትር ነው
“ገና ጸሐይ በሰማይ ላይ ነች/ጊዜው ገና ነው” ወይም “ጸሐይ ገና በማብራት ላይ ነች”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መንጎች እስኪሰበሰቡ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት: “መንጐችን እስኪሰበስቡ” (ተሻጋረ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተነገር ይመልከቱ)

መሰብሰብ
ይህም ሌሊቱን እንዲያሳልፉ በቅጥር ውስጥ መሰብሰብ ማለት ነው:: የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: (ግምታዊ እውቀት እና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ወደ ግጦሽ ይመለሱ
በሜዳ ያለውን ሣር ይመገቡ

ውሃ ሊናጠጣቸው አንችልም
ውሃ ሊናጠጣቸው መጠበቅ አለብን ይህ ፈቃደኝነት ሳይሆን ጊዜን በሚመለከት ነው

መንጐቹ ሁሉ እስኪሰበሰቡ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት: “ሌሎች እረኞች መንጐቻቸውን እስኪሰበስቡ” (ተሻጋረ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተነገር ይመልከቱ)

ከጉድጓዱ አፍ
እዚህ አፍ ጉድጓዱ የተከፈተውን ቀዳዳ ያመለክታል አት ከጉድጓዱ ወይም ጉድጓዱ በተከፈተበት (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 29:9

የእናቱ ወንድም
አጐቱ

የጉድጓዱ አፍ
እዚህ “አፍ” የተከፈተበትን ቦታ ያመለክታል:: አት: “ጉድጓዱ” ወይም “ጉድጓዱ የተከፈተበትን ቦታ” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 29:11

ያዕቆብም ራሔልን ሳማት
በጥንታዊቷ ቅርብ ምሥራቅ በመሳም ሰላምታ መለዋወጥ የተለመደ ነው:: ነገር ግን በወንዶች ዘንድ እምብዛም የታወቀ ነው:: በሚትተረጉሙበት ቋንቋ ባህል እንዲህ ዓይነቱ ስሜትን በመግለጽ ዘመዳሞች ሰላምታ የመለዋወጥ ነገር ካለ ይህን ይጠቀሙ:: ከሌለ ግን ሌላ ተገቢ አባባል ይጠቀሙ::

ድምጹን ከፍ አድርጐ አለቀሰ
ያዕቆብ የሚያለቅሰው ደስተኛ በመሆኑ ነው የዚህ ዐረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉሙ ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

የአባትዋ ዘመድ
ለአባትዋ የሚዛመድ

Genesis 29:13

የእርሱ እኅት ልጅ
የእኅቱ ልጅ

አቀፈው
አቀፈው

ሳመው
በጥንታዊቷ ቅርብ ምሥራቅ በመሳም ለዘመድ ሰላምታ ማቅረብ የተለመደ ነው:: ነገር ግን ይህ በወንዶች መካከል የታወቀ ነው:: በሚተረጉሙት ቋንቋ ለዘመድ የሚቀርብ ሰላምታ ስሜትን የሚገልጽ ከሆነ ይህን ይጠቀሙበት:: ካለሆነ ግን ሌላ ተገቢ አባባል ይጠቀሙ::

ያዕቆብም ሁኔታውን ሁሉ ለላባ ነገረው
“ከዚያም ያዕቆብ ለራሔል የነገረውን ሁሉ ለላባ ነገረው”

የአጥንቴ ፍላጭ የሥጋዬ ቁራጭ
እነዚህ ሀረጐች በቀጥታ የሚዛመዱ ናቸው:: አት: “የእኔ ዘመድ” ወይም “የቤተሰቤ አባል” (ተዛማጅ ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

Genesis 29:15

ዘመዴ በመሆንህ ብቻ በነጻ ሊታገለግለኝ አይገባምና...?
ስለሚሠራለት ሥራ ለያዕቆብ መክፈል ስለአለበት ላባን ይህንን አግንኖ ለመናገር ጥያቄ ይጠቀማል:: ይህ በአዎንታዊ መንገድ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “ዘመዴ ቢትሆንም ለሚትሠራልኝ መክፈል በእርግጥ ትክክል ነው” See:RhetoricalQuestionandLitotes

የልያ ዐይን ልም ነው
ተገቢ ትርጉሞች 1 የልያ ዓይኖች ልም ነበሩ 2 የልያ ዐይኖች ታማሚ ነበሩ

ያዕቆብ ራሔልን ወደደ
እዚህ ወደደ የሚለው ቃል በአንድ ወንድና ሴት መካከል የሚሆን ስሜታዊ ወዋደድን ያመለክታል

Genesis 29:19

ለሌላ ወንድ ከሚሰጣት ይልቅ
ለሌላ ወንድ ከሚድራት ይልቅ

እነዚያ ጥቂት ቀናት ብቻ ሆኖ ታየው
“ነገር ግን ጊዜው ጥቂት ቀናት ሆኖ ታየው”

ለእርስዋ ካለው ፍቅር
“ለእርስዋ ያለውን ፍቅር ስመዝን” ወይም “ለእርስዋ ካለው ፍቅር የተነሣ”

Genesis 29:21

እንዳገባት ዘንድ ሚስቴን ስጠኝ ቀኔ ተፈጽሞአልና
ቀኔ ተፈጽሞአል የሚለው ሀረግ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: ይህ emphatic ዐረፍተ ነገር ነው:: አት: “ለአንተ መሥራት የሚገባኝን ጊዜ ስለፈጸምሁ እንዳገባት ሚስቴን ስጠኝ” ወይም “ለሰባት ዓመታት ስላገለገልሁ እንዳገባት ራሔልን ስጠኝ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ሠርግ አዘጋጀ
የጋብቻ ሠርግ አዘጋጀ ምናልባት ላባን ሌሎች ሰዎች እንዲያዘጋጁ አደረገ:: አት: “ሌሎች የጋብቻ ሠርግ እንዲያዘጋጁ አደረገ”:: (ተዛማጅ ምትክ ቃላት አጠቃቀም ዘይቤ ይመልከቱ)::

Genesis 29:23

አብሮአት ተኛ
ይህ የሚገልጸው ምሽት ስለነበረና ስላላያት ከልያ ጋር መሆኑን ያዕቆብ አላወቀም ነበር:: የዐረፍተ ነገሩ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ላባን ዘለፋ የተባለች አገልጋዩን ለልጁ ለልያ ደንገጡር እንድትሆን ሰጣት
እዚህ ጸሐፊው ላባን ዘለፋን ለልያ እንደሰጠ መረጃ ይሰጣል። ዘለፋን ለልያ ከሠርግ በፊት ሳይሰጣት አይቀርም:: (ታሪካዊ ዳራ መረጃ ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እነሆ ልያ ሆና ተገኘች
ያዕቆብም ልያ በአልጋ አብሮአት በማየቱ ተገረመ:: “እነሆ” የሚለው ቃል ያዕቆብ ባየው ነገር እንዴት እንደተደነቀ የሚያሳይ ነው።

ምነው እንደዚህ አደረግህብኝ?
ያዕቆብ ቁጣውንና መገረሙን ለመግለጽ ጥያቄ ይጠቀማል ይህ ቅኔ አዘልጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት: “ይህን ለእኔ ታደርጋለና ብዬ አላምንህም” (See: RhetoricalQuestion)

ያገለገልሁህ ለራሔል ብዬ አልነበረምን?
ያዕቆብ እነዚህን ጥያቄዎች የሚጠቀመው ላባን ያታለለውን ጉዳቱን ለመግለጽ ነው ይህ ቅኔ አዘል ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጽ ይችላል ራሔልን ለማግባት ሰባት ዓመት አገልግየሃለሁ (See: Rhetorical Question)

Genesis 29:26

እንሰጥ ዘንድ ወግ አይደለም
በቤተሰባችን አንሰጥም

ለዚህች ሴት ልጅ ይህን የጫጉላ ሳምንት ፈጽም
የልያን ጫጉላ ሳምንት ፈጽም

ሌላኛይቱን ደግሞ እንሰጣለን
የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል አት በሚቀጥለው ሳምንት ደግሞ ራሔልን እንሰጥሃለን (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 29:28

ያዕቆብም እንዲሁ አደረገ እናም የልያን ሳምንት ፈጸመ
ያዕቆብ ላባን የጠየቀውን አደረገ እናም የልያን ጫጉላ ሳምንት ማክበርን ፈጸመ

ባላ
ይህ የራሔል ሴት አገልጋይ ስም ነው:: (ስሞችን ስለመተርጎም ይመልከቱ)

ያዕቆብም ከራሔል ጋር ተኛ
ጋብቻዊ ግንኙነት እንደፈጸሙ የሚገልጽ አክብሮታዊ ወይም ለዛ አባባል ነው

ራሔልን ወደዳት
በአንድ ወንድና በአንድ ሴት መካከል የሚሆን ስሜታዊ ፍቅር ያመለክታል

Genesis 29:31

ልያ አልተወደደችም
ይህ ተሻሪ ግሥ በያዘ መልክ ወይም በገቢር ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል:: አት: “ያዕቆብ ልያን አልወደዳትም” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

እንዳልተወደደች
ያዕቆብ ራሔልን ከልያ ይልቅ እንደወደዳት በማተኮር አግንኖ የሚናገር ነው አት ከራሔል አሳንሶ ወደዳት (አግንኖና በገሃድ የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ማሕጸንዋን ከፈተላት
እግዚአብሔር ልያ እንዲትጸንስ ማድረጉ እግዚአብሔር ማሕጸንዋን እንደከፈተ ተደርጐ ተነግሮአል:: (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

መካን ነበረች
ሊትጸንስ አልቻለችም

ልያ ጸነሰች ልጅም ወለደች
ልያ ጸነሰች ወንድ ልጅም ወለደች

ስሙን ሮበል አለችው
ተረጓሚዎች የሚከተለውን አንደ ግርጌ ማስታወሻ ተጨማሪ አድርገው ሊያቀርቡ ይችላሉ:: ሮበል የሚለው ስም ‘ወንድ ልጅ አየሁ’ ማለት ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

እግዚአብሔር መከራዬን ስለተመለከተልኝ
ልያ ያዕቆብ ስላልተቀበላት በስሜታዊ ሕመም ነበራት:: “መከራ” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግሥ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “እግዚአብሔር እንደተሰቃየሁ አየኝ” (ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ)

Genesis 29:33

እንደገናም ጸነሰች
እንደገናም ልያ ጸነሰች

ልጅ ወለደች
ወንድ ልጅ ወለደች

ስሙን ስምዖን ብላ ጠራችው
ተረጓሚዎች የሚከተለውን አንደ ግርጌ ማስታወሻ ተጨማሪ አድርገው ሊያቀርቡ ይችላሉ:: “ስምዖን የሚለው ስም ‘ተሰማ’ ማለት ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ባሌ ያቀርበኛል
ባሌ ያቅፈኛል

ሶስት ወንዶች ልጆች ስለወለድሁለት
ለእርሱ ሶስት ወንጆ ልጆች ወለድሁለት

ስው ሌዊ ይባላል
ተረጓሚዎች የሚከተለውን አንደ ግርጌ ማስታወሻ ተጨማሪ አድርገው ሊያቀርቡ ይችላሉ:: “ሌዊ የሚለው ስም ‘የተጠጋ’ ማለት ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 29:35

እንደገናም ጸነሰች
ልያ እንደገና አረገዘች

ወንድ ልጅ ወለደች
ወንድ ልጅን ወለደች

ስሙንም ይሁዳ ብላ ጠራችው
ተረጓሚዎች የሚከተለውን አንደ ግርጌ ማስታወሻ ተጨማሪ አድርገው ሊያቀርቡ ይችላሉ:: “ይሁዳ የሚለው ስም ‘ምሥጋና’ ማለት ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 30

1 ራሔል ለያዕቆብ አንድም ልጅ እንዳልወለደችለት ባየች ጊዜ በእኅቷ ቀናች። ያዕቆብንም፣ “ልጅ ስጠኝ አለበለዚያ እሞታለሁ” አለችው። **2** ያዕቆብም ራሔልን ተቆጥቶ፤ “እኔ የሆድሽን ፍሬ በነሳሽ በእግዚአብሔር ቦታ ነኝን?” አላት። **3** እርሷም፣ “እነሆ፣ አገልጋዬ ባላ አለችልህ፣ ልጆች እንድትወልድልኝና እኔም ደግሞ በእርሷ አማካይነት ልጆች እንዳገኝ ከእርሷ ጋር ተኛ” አለችው። **4** ስለዚህ ባላን እንደሚስት አድርጋ ሰጠችው፤ ያዕቆብም ከእርሷ ጋር የግብረ-ሥጋ ግንኙነት አደረገ። **5** ባላም አረገዘችና ወንድ ልጅ ወለደችለት። **6** ራሔልም፦ “እግዚአብሔር ፈረደልኝ፣ ልመናዬንም ሰምቶ ወንድ ልጅ ሰጥቶኛል” አለች። ስለዚህ ስሙን ዳን ብላ ጠራችው። **7** የራሔል አገልጋይ ባላ ዳግመኛ አረገዘችና ለያዕቆብ ሁለተኛ ወንድ ልጅ ወለደች። **8** ከእኅቴ ጋር ብርቱ ትግል ታግዬ አሸነፍኋት” አለች። ስለዚህ ስሙን ንፍታሌም ብላ ጠራችው። **9** ልያም ልጅ መውለድ ማቆሟን እንደተረዳች፣ አገልጋይዋን ዘለፋን ሚስት እንድትሆነው ለያዕቆብ ሰጠችው። **10** የልያ አገልጋይ ዘለፋም ለያዕቆብ ወንድ ልጅ ወለደችለት፣ **11** ልያም፣ “እንዴት የታደልሁ ነኝ!” ስትል ስሙን ጋድ ብላ ጠራችው። **12** የልያም አገልጋይ ዘለፋ ለያዕቆብ ሁለተኛ ልጅ ወለደችለት፤ **13** ልያም፣ “እጅግ ደስ ብሎኛል፣ ከእንግዲህ ወዲያ ሴቶች ‘ደስተኛዋ’ ይሉኛል አለች፤ ስሙንም ‘አሴር’ ብላ ጠራችው። **14** በስንዴ መከር ወራት ሮቤል ወደ ዱር ሄዶ እንኮይ አገኘ፤ ለእናቱ ለልያም አመጣላት፤ ራሔልም ልያን፣ “እባክሽን ልጅሽ ካመጣልሽ እንኮይ ስጪኝ” አለቻት። **15** ልያም፦ “ባሌን የቀማሽኝ አነሰና የልጄን እንኮይ ደግሞ ልትወስጂ አማረሽ?” አለቻት። ራሔልም፣ “ስለልጅሽ እንኮይ ዛሬ ያዕቆብ ከአንቺ ጋር ይደር” አለቻት። **16** በዚያ ምሽት ያዕቆብ ከእርሻ ሲመለስ፣ ልያ ወጥታ ተቀበለችውና፣ “በልጄ እንኮይ ስለተከራየሁህ የዛሬው አዳርህ ከእኔ ጋር ነው” አለችው። ያዕቆብም በዚያች ሌሊት ከእርሷ ጋር አደረ። **17** እግዚአብሔር የልያን ጸሎት ሰማ፣ ስለዚህ አረገዘችና ለያዕቆብ አምስተኛውን ወንድ ልጅ ወለደችለት። **18** ልያም፦ “አገልጋዬን ለባሌ በመስጠቴ እግዚአብሔር ደመወዜን ከፈለኝ” አለች። ስሙንም ይሳኮር አለችው። **19** ልያ አሁንም ደግማ ፀነሰች፤ ለያዕቆብም ስድስተኛውን ወንድ ልጅ ወለደች። **20** እርሷም፣ “እግዚአብሔር በከበረ ስጦታ አድሎኛል፣ ስድስት ወንዶች ልጆች ስለወለድሁለት ከእንግዲህ ባሌ አክብሮ ይይዘኛል” አለች፤ ስሙንም ዛብሎን አለችው። **21** ከዚያም በኋላ ሴት ልጅ ወለደች ስምዋንም ዲና አለቻት። **22** እግዚአብሔርም ራሔልን አሰበ፤ ጸሎትዋንም ሰምቶ ልጅ እንድትወልድ አደረጋት፤ **23** አርግዛም ወንድ ልጅ ወለደችና፣ “እግዚአብሔር ዕፍረቴን አስወገደልኝ” አለች፤ **24** ደግሞም ሌላ ወንድ ልጅ ይጨምርልኝ ስትል ስሙን ዮሴፍ ብላ ጠራችው። **25** ራሔል ዮሴፍን ከወለደች በኋላ ያዕቆብ ላባን እንዲህ አለው፦ “ወደ ተወለድሁበት አገር እንድመለስ አሰናብተኝ፤ **26** አንተን በማገልገል ያገኘኋቸውን ሚስቶቼንና ልጆቼን ስጠኝና ልሂድ፤ ምን ያህል አገልግሎት እንዳበረከትኩልህ ታውቃለህ።” **27** ላባም፣ “በአንተ ምክንያት እግዚአብሔር እንደባረከኝ በንግርት መረዳቴን ልነግርህ እወዳለሁ፤ **28** የምትፈልገውን ደመወዝ ንገረኝና እከፍልሃለሁ” አለው። **29** ያዕቆብም እንዲህ አለው፦ “እንዴት እንዳገለገልሁህና የከብትህም መንጋ በእኔ ጠባቂነት እንዴት እንደረባልህ አንተ ታውቃለህ፤ **30** እኔ ከመምጣቴ በፊት ጥቂት የነበሩት መንጋዎችህ አሁን እጅግ በዝተዋል፤ በተሰማራሁበት ሁሉ እግዚአብሔር በረከቱን አብዝቶልሃል። ታዲያ፣ ለራሴ ቤት የሚያስፈልገኝን የማቀርበው መቼ ነው?” **31** ላባም፣ “ታዲያ ምን ያህል ልክፈልህ?” ብሎ ጠየቀው። ያዕቆብም እንዲህ ሲል መለሰ፦ “እኔ የምልህን አንድ ነገር ብቻ ብታደርግልኝ መንጋህን ማሰማራቴንና መጠበቄን እቀጥላልሁ፤ **32** ዛሬ በመንጋዎችህ መካከል ልለፍና ዝንጉርጉርና ነቁጣ ጥቁርም የሆኑትን በጎች ሁሉ ልለይ፤ እንዲሁም ነቁጣና ዝንጉርጉር የሆኑትን ፍየሎች እመርጣለሁ፤ እነርሱም ደመወዜ ይሆናሉ፤ **33** ወደፊት ደመወዜን ለመቆጣጠር በምትመጣበት ጊዜ ታማኝነቴ ይታወቃል፤ ደመወዜን ለመቆጣጠር ስትመጣ ዝንጉርጉር ያልሆነ ወይም ነቁጣ የሌለበት ፍየል ብታገኝ፣ እንዲሁም ጥቁር ያልሆነ በግ ብታገኝ የተሰረቀ መሆኑን መረዳት ትችላልህ” አለው። **34** ላባም፣ “እሺ አንተ ባልከው እስማማለሁ” አለ። **35** ነገር ግን በዚያኑ ዕለት ከተባት ፍየሎች ሸመልመሌ የሆኑትን ወይም ነቁጣ ያለባቸውን ሁሉ እንዲሁም ከእንስት ፍየሎች ነቁጣ ያለባቸውን ዝንጉርጉር የሆኑትን ሁሉ መረጠ፤ ደግሞም ጥቋቁር የሆኑትንም በጎች ሁሉ ለየና ወንዶች ልጆቹን አስጠበቃቸው። **36** ከዚህ በኋላ ላባ መንጋውን ነድቶ የሦስት ቀን መንገድ ያህል ከያዕቆብ ርቆ ሄደ፤ ያዕቆብም የቀሩትን የላባን መንጋዎች መጠበቁን ቀጠለ። **37** ያዕቆብም ልብን፣ ለውዝና ኤርሞን ከሚባሉ ዛፎች እርጥብ በትሮችን ወሰደ፤ በበትሮቹ ያለው ነጭ እንዲታይ ሸመልመሌ አድርጎ ላጣቸው፤ **38** መንጋዎቹ ውሃ ለመጠጣት ሲመጡ ከፊት ለፊት እንዲያዩአቸው የተላጡትን በትሮች በውሃ ማጠጫዎቹ ውስጥ አደረጋቸው። መንጎቹም ስሜታቸው ሲነሣሣና ውሃ ለመጠጣት ሲመጡ፣ **39** በትሮቹን ፊት ለፊት እያዩ ይሳረሩ ነበር፤ ሸመልመሌ፣ ዝንጉርጉርና ነቁጣ የጣለባቸውንም ግልገሎች ወለዱ። **40** ያዕቆብ እነዚህን ግልገሎች ለብቻ ለየ፤ የቀሩትን ግን ዝንጉርጉርና ጥቁር በሆኑት በላባ መጋዎች ፊት ለፊት አቆማቸው፤ በዚህ ዓይነት የራሱን መንጋ ከላባ መንጋ ጋር ሳይቀላቅል ለብቻ አቆማቸው። **41** ያዕቆብም ብርቱ እንስቶች አውራ ፈልገው በሚቅበጠበጡበት ጊዜ በትሮቹ አቅራቢያ እንዲጠቁ በትሮቹን በውሃ ገንዳዎች ውስጥ ፊት ለፊታቸው ያስቀምጥ ነበር፤ **42** ደካማ በሆኑት እንስቶች ፊት ግን በትሮቹን አያስቀምጥም ነበር፤ ስለዚህ ደካሞቹ ለላባ ሲሆኑ፣ ብርቱዎቹ ለያዕቆብ ሆኑ። **43** በዚህም ሁኔታ ያዕቆብ እጅግ ባለጸጋ ሆነ፤ ብዙ መንጋዎች፤ ሴቶችና ወንዶች አገልጋዮች፣ ብዙ ግመሎችና አህዮችም ነበሩት።

Genesis 30:1

ራሔል ለያዕቆብ ልጅን እንዳልወለደች ባየች ጊዜ
ራሔል ማርገዝ እንዳልቻለች ባወቀች ጊዜ

እሞታለሁ
ራሔል ልጅ ባለመኖርዋ ምነኛ እንደተከፋች ማጋነንዋ ነው:: አት: ምንም እንደማልጠቅም ይሰማኛል:: (በማጋነንና በገሃድ የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ልጅ ስጠኝ
እንዳረግዝ አድርገኝ

ያዕቆብም ቁጣ በራሔል ላይ ነደደ
የያዕቆብ ቁጣ እንደ እሳት ተደርጐ ተገልጾአል። አት፡ “ያዕቆብ ራሔልን በጣም ተቆጣት” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

እኔ እንዳትወልጂ ያደረግሽን እግዚአብሔርን መሰልኩሽን?
ይህ ያዕቆብ ራሔልን ለመቆጣት የተጠቀመው ቅኔያዊ ጥያቄ ነው:: ይህም እንደ ዐረፍተ ነገር ልተረጐም ይችላል። አት፡ “እኔ እግዚአብሔር አይደለሁም! ልጅ እንዳትወልጂ የሚከለክለው እኔ አይደለሁም” (ቅኔ አዘል ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

Genesis 30:3

እርስዋም አለች
ራሔል አለች

እነሆ
“ተመልከት” ወይም “ስማ” ወይም “ሊናገር ስላለሁ ነገር ትኩረት ስጥ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አገልጋዬ ባላ አለችልህ ..... ከእርስዋ ልጆች እንዳገኝ
በዚያን ጊዜ መካን ሴት በሕጋዊነት ልጅ የሚታገኝበት ተቀባይነት ያለው መንገድ ይህ ነው:: የዚህ ዐረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ባላ
የራሔል ሴት ባሪያ ስም ነው። በዘፍጥረት 29:29 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ።

በጉልበቶቼ ወይም በጭኖቼ
ይህ ባላ የሚትወልደው ልጅ ለራሔል እንደሚሆን የሚገልጽ አባባል ነው:: አት: “ለእኔ” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

በእርሷ አማካኝነት ልጅ ይኖረኛል
በዚህ መንገድ ልጅ እንዲኖረኝ ታደርጋለች

Genesis 30:5

ባላ
የራሔል ሴት ባሪያ ስም ነው። በዘፍጥረት 29:29 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ።

ለያዕቆብ ወንድ ልጅ ወለደች
ለያዕቆብ ወንድ ልጅም ወለደችለት

ስሙንም አወጣችለት
ራሔል ስም አወጣችለት

ዳን ብላ ጠራችው
ተረጓሚዎች የሚከተለውን አንደ ግርጌ ማስታወሻ ተጨማሪ አድርገው ሊያቀርቡ ይችላሉ:: “ዳን የሚለው ስም ‘እርሱ ይፈርዳል’ ማለት ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 30:7

ባላ እንደገና ጸነሰች
ባላ እንደገና አረገዘች

ለያዕቆብ ሁለተኛ ወንድ ልጅ ወለደች
ለያዕቆብ ሁለተኛ ወንድ ልጅን ወለደችለት

ከእኅቴ ጋር ብርቱ ትግልን ታገልሁ
ትግልን ታገልሁ የሚለው ሀረግ አጽንዖትን የሚሰጥ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው ራሔል እንደ እኅትዋ አንድን ልጅ ለማግኘት ያደረገችው ከልያጋር አካላዊ ትግል እንዳደረገች የሚገልጽ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው:: አት: “እንደ ታላቅ እኅቴ ልያ ልጅን ለማግኘት ትልቅ ተጋድሎ አድርጌያለሁ:: (ፈሊጣዊና ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ቻልኩኝ
አሸነፍሁ ወይም ተሳክቶልኛል

ስሙንም ንፍታለም ብላ አወጣችለት
ተረጓሚዎች የሚከተለውን አንደ ግርጌ ማስታወሻ ተጨማሪ አድርገው ሊያቀርቡ ይችላሉ:: “ንፍታለም የሚለው ስም ‘ትግሌ’ ማለት ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 30:9

ልያም ባየች ጊዜ
ልያም በተረዳች ጊዜ

አገልጋይዋን ዘለፋን ወሰደች ሚስት ትሆነውም ዘንድ ለያዕቆብ ሰጠችው
አገልጋይዋን ዘለፋን ሚስት እንዲትሆነው ለያዕቆብ ሰጠችው

ዘለፋ
የልያ ሴት አገልጋይ ስም ነው:: በዘፍጥረት 29:24 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

ለያዕቆብ ወንድ ልጅ ወለደች
ለያዕቆብ ወንድ ልጅን ወለደችለት

ምን ዓይነት መታደል ነው!
እንዴት ያለ መታደል ነው! ወይም ምን ዓይነት ዕድል ነው!

ስሙንም ጋድ ብላ አወጣችው
ተረጓሚዎች የሚከተለውን አንደ ግርጌ ማስታወሻ ተጨማሪ አድርገው ሊያቀርቡ ይችላሉ:: “ጋድ የሚለው ስም ‘እድለኛ’ ማለት ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 30:12

ዘለፋ
የልያ ሴት አገልጋይ ስም ነው:: በዘፍጥረት 29:24 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

ለያዕቆብ ሁለተኛ ወንድ ልጅ ወለደች
ለያዕቆብ ሁለተኛ ወንድ ልጅ ወለደችለት

ምነኛ ደስተኛ ሆንሁ!
እንዴት የተባረኩ ነኝ! ወይም እንዴት ደስተኛ ነኝ !

ሴቶች ልጆች
ሴቶች ወይም ልጃገረዶች/ወጣት ሴቶች

ስሙንም አሴር ብላ አወጣችለት
ተረጓሚዎች የሚከተለውን አንደ ግርጌ ማስታወሻ ተጨማሪ አድርገው ሊያቀርቡ ይችላሉ:: “አሴር የሚለው ስም ‘ደስታ’ ማለት ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 30:14

ሮቤል ወደ ሜዳ ወጣ
ሮቤልም ወጣ

ስንዴ በሚታጨድበት ቀናት
ቀናት የሚለው አባባል በዓመት ውስጥ ያለ ወቅት ወይም ጊዜ የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው:: አት “በዓመት ስንዴ በሚታጨድበት ጊዜ” ወይም “ስንዴ በሚታጨድበት ወቅት” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

እንኮይ
ከፍቅረኛ ጋር ለመተኛት ስሜት የሚያነሣሣና ፍሬን የሚጨምር የአትክልት ፍሬ ነው:: አት: “የፍቅር ፍሬ” (ያልታወቁትን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ባሌን....ጥቂት ነገር ነውን?
ባሌን .... አይሰማሽምን? ይህ ራሔልን ለመቆጣት የተጠቀመችው ቅኔያዊ ጥያቄ ነው ይህ ጥያቄ በስድ ዐረፍት ነገር ሊገለጽ ይችላል:: ባሌን የማያስከፋ ነው:: (ቅኔ አዘል ጥያቄዎችን ይመልከቱ) ...ደግሞ ሊትወስጂ አማረሽ? ይህንም ቅኔ አዘል ጥያቄ የተጠቀመችው ራሔልን ለመቆጣት ነው ይህ ጥያቄ በስድ ዐረፍት ነገር ሊገለጽ ይችላል:: አት: አሁን ደግሞ... አማረሽ! (ቅኔ አዘል ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

ከዚያም ይተኛ
“ከዚያም ያዕቆብ ይተኛ” ወይም “ያዕቆብ እንዲተኛ እፈቅዳለሁ”

Genesis 30:16

በልጄ እንኮይ
ለልጄ “እንኮይ” ዋጋ በዘፍጥረት 30;14 እንኮይ እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

ጸነሰች
አረገዘች

ለያዕቆብ አምስተኛ ወንድ ልጅ ወለደች
አምስተኛ ወንድ ልጅንም ለያዕቆብ ወለደች

እግዚአብሔር ዋጋዬን ከፈለልኝ
እግዚአብሔር ልያን መካሡ ለሚሠራው ሠራተኛ አንድ አለቃ ድርጐውን እንደሚከፍል እንደከፈለላት ተደርጐ ተገልጾአል “እግዚአብሔር የድርሻዬን ሰጠኝ” ወይም “እግዚአብሔር ካሠኝ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ስሙንም ይሳኮር ብላ አወጣችለት
ተረጓሚዎች የሚከተለውን አንደ ግርጌ ማስታወሻ ተጨማሪ አድርገው ሊያቀርቡ ይችላሉ:: “ይሳኮር የሚለው ስም ‘ካሣ አለ’ ማለት ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 30:19

ልያ አሁንም ደግሞ ጸነሰች
ልያ እንደገና አረገዘች

ለያዕቆብ ስድስተኛ ወንድ ልጅ ወለደች
ስድስተኛ ወንድ ልጅም ለያዕቆብ ወለደች

ስሙንም ዛብሎን አለችው
ተረጓሚዎች የሚከተለውን አንደ ግርጌ ማስታወሻ ተጨማሪ አድርገው ሊያቀርቡ ይችላሉ:: “ዛብሎን የሚለው ስም ‘ክብር’ ማለት ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ስምዋንም ዲና አለቻት
ይህ የልያ ሴት ልጅ ስምዋ ነው::(ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 30:22

እግዚአብሔርም ራሔልን አሰባት ልመናዋንም ሰማ
አሰባት የሚለው አባባል አስተዋላት ማለት ነው:: ይህ እግዚአብሔር ራሔልን ረስቶአታል ማለት አይደለም:: ጥያቄዋን አሰበ ማለት ነው:: አት: “እግዚአብሔርም ራሔልን አሰበ የፈለገችውንም ሰጣት” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ኀፍረተን አስወገደልኝ
እግዚአብሔር ራሔል እንዳታፍር ያደረገው ሐፍረት አንድ ሰው ከአንድ ሰው ወስዶ እንደሚያስወግድ ዕቃ ተደርጐ ተነገሮአል:: ረቂቅ ስም ሐፍረት እንደ እፍረት ሊገለጽ ይችላል::

አት: እግዚአብሔር ከእንግዲህ ወዲህ እንዳላፍር አድርጐኛል። (ዘይቤያዊ አነጋገር ወይም ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ) ስሙንም ዮሴፍ አለችው
ተረጓሚዎች የሚከተለውን አንደ ግርጌ ማስታወሻ ተጨማሪ አድርገው ሊያቀርቡ ይችላሉ:: “ዮሴፍ” የሚለው ስም ‘እርሱ ይጨምር’ ማለት ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ሌላ ወንድ ልጅ ጨምሮ ይስጠኝ
የራሔል የመጀመሪያዎቹ ወንድ ልጆች ከሴት አገልጋይዋ ከባላ ነበር

Genesis 30:25

ራሔል ዮሴፍን ከወለደች በኋላ
ራሔልም ዮሴፍን ከወለደች በኋላ

እናም እመለስ ዘንድ
እንዲመለስ

እንዳገለገልሁህ ታውቃለህ
ያዕቆብ ላባንን የተስማሙበትን ኮንትራት ያስታውሳል (ዘፍጥረት 29 :27) ረቂቅ ስም “አገልግሎት” እንደ “አገለገለ” ሊገለጽ ይችላል:: አት: ለረጅም ጊዜያት እንዳገለገልሁህ ታውቃለህ:: (ረቂቅ ስሞች ይጠቀሙ)

Genesis 30:27

ላባንም እንዲህ አለው
ላባንም ያዕቆብን እንዲህ አለው

በአይንህ ፊት ሞገስን የማገኝ ቢሆን
አይኖች ማየትን ይወክላሉ እናም ማየት ሃሳብን ወይም ውሳኔን ይወክላል:: አት: “በአንተ ፊት ሞገስ ካገኘሁ” ወይም “በእኔ የተደሰትህ ከሆንህ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ሞገስ ማግኘት
አንድ ሰው በሌላኛው ሰው ዘንድ ሞገስ ማግኘቱን የሚገልጽ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው:: (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ቆይ ምክንያቱም
ተቀመጥ ምክንያቱም

በንግርት ተረድቸአለሁ
በመንፈሳዊና ማጅካዊ ልምምዶቼ ተረድቸአለሁና

በአንተ የተነሣ
በአንተ ምክንያት

ደመወዝህን ንገረኝ
ይህ ግልጽ ሊደረግ ይችላል አት እዚሁ ላቆይህ ምን ያህል መክፈል እንዳለብኝ ንገረኝ። (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 30:29

ያዕቆብም አለው
ያዕቆብ ላባንን አለው

ከብቶችህ በእኔ ጥበቃ ምን ያህል እንደተመቻቸው
ጥበቃ ከጀመርኩባቸው ጊዜ ከብቶች እንዴት እንደተመቻቸው

እኔ ከመምጣቴ በፊት ጥቂት ነበሩ
ለአንተ ሥራ ከመጀመረ በፊት መንጐችህ ጥቂት ነበሩ

እናም ይህ በመጨመር ተትረፍርፎአል
ነገር ግን አሁን ሀብትህ በጣም ጨምሮአል

አሁንም እኔ ደግሞ ለቤቴ የሚሆነውን የማቀርበው መቼ ነው?
አሁንም እኔ ደግም ለቤተሰቤ የምሠራው መቼ ነው? ያዕቆብ ለቤተሰቡ የሚሆነውን ማቅረብ እንዳለበት ለማጽናት ጥያቄ ይጠቀማል ይህም ጥያቄ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በዐረፍተነገር መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “አሁን ለቤተሰበ የሚሆነውን ማሰብ አለብኝ” (ቅኔ አዘል ጥያቄችን ይመልከቱ)

Genesis 30:31

ታዲያ ምን ልስጥህ?
“ታዲያ ምን መክፈል እችላለሁ?” ወይም “ታዲያ ምን መስጠት እችላለሁ?” ይህ የበለጠውኑ ግልጽ ሊደረግ ይችላል አት እንዲትቆይና እንዲትሠራልኝ ዘንድ ምን መክፈል እችላለሁ?(ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይጠቀሙ)

ይህንም ነገር ቢታደርግልኝ
ያዕቆብ ሊናገር ያለው እርሱ ከተናገረው ጋር እንደሚጻረር ለማሳየት አገናኝ ቃል “ነገር ግን” በመግቢያው ሊጠቀም ይቻላል:: አት: “ነገር ግን ይህንም ነገር ቢታደርግልኝ” (አገናኝ ቃላት ይመልከቱ)

ይህ ነገር
“ይህ ነገር” የሚለው ሀረግ ያዕቆብ በቁጥር 32 የሚያቀርበውን ያመለክታል::

መንጎችህን እመግባለሁ/አሠማራለሁ እጠብቃለሁ
መንጎችህን እመግባለሁ እጠብቃለሁ

ከበጎቹ መካከል ዝንጉርጉር የሆኑትን ነቁጣ ያለባቸውንና ጥቋቁሮቹን እንዲሁም ከፍዬሎች ነቁጣ ያለበቸውንና ዥንጉርጉሮቹን እለያለሁ
ማንኛውንም ዥንጉርጉርና ጥቁር የሆነውን በግና ዝንጉርጉር የሆነውን ፍዬል እለያለሁ

እነዚህ ደመወዜ ይሁኑ
እንዚህ እዚሁ ለሚቆየው ዋጋዬ ይሁኑ

Genesis 30:33

ታማኝነቴ ይታወቃል
ታማኝነት የሚለው ቃል አማንነት ማለት ነው ይህም ታማኝነት አንድ ሰው ሰለሌላኛው ሰው በመደገፍ ወይም በመቃወም የሚሰጠው ምሥክርነት እንደሆነ ይናገራል:: አት: “ለአንተ ታማኝ መሆነንና አለመሆነን በኋላ ታውቀዋለህ”:: (ሰውኛ አገላለጽ ይመልከቱ)

በመንጋቼ መካከል ዥንጉርጉር ወይም ነቁጣ የሌለበት ፍዬል ወይም ጥቁር ያልሆነ ቢገኝ ያ እንደተሰረቀ ይቆጠር
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ ገቢራዊ መንገድ ሊገለጽ ይችላል አት ማንኛውም ዥንጉርጉር ያለሆነ ፍዬልና ጥቁር ያልሆነ በግ ቢታገኘው እንደተሰረቀ መቁጠር ትችላለህ:: (ተሻጋሪና የማይሻገር ግሥ የያዙ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

እነሆ እንደቃልህ ይሁን
“እንደተናገርከው ይሁን” ወይም “አንተ እደተናገርከው እናደርጋለን”

Genesis 30:35

ሸመልመሌ የሆኑትን ወይም ነቁጣ ያለባቸውን
ሸመልመሌና ነቁጣ ያለባቸውን

ነቁጣ ያለባቸውንና ዥንጉርጉር የሆኑትን
ነቁጣ ያለባቸውን

ማንኛውንም ነጭ ያለበትን
ማንኛውም ነጭ ያለበት በግ

ከበጎች ሁሉ ጥቋቁር የሆኑትን
ጥቁር በጎችን ሁሉ

በእነርሱ እጅ ሰጣቸው
እዚህ “እጅ” “ቁጥጥር” ወይም “ጥበቃ” የሚተካ ነው:: አት: “ልጆቹ እንዲጠብቁ አደረጋቸው” (ተመሣሣይ ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

Genesis 30:37

እርጥብ የልብን የለውዝንና የኤርሞን
እነዚህ ሁሉ ነጭ ዛፎች ናቸው:: (ያልታወቁትን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ቅርፊታቸውን ልጦ የበትሮቹ ውስጠኛው ነጩ አካል እንዲታይ አደረገ
የቅርፊታቸውን አንዳንድ ክፍሎችን በመላጥ የበትሮቹ ውስጠኛው ነጭ አካል እንዲታይ አደረገ

በማጠጫ ገንዳዎች
ከብቶችን ለማጠጣት ውሃን የሚይዙ ረጅምና ክፍት የሆኑ ገንዳዎች

Genesis 30:39

መንጋዎች ይሳረሩ ነበር
“የመንዎች እንስሳት ይጸልሱ ነበር” ወይም “ይጠቃቁ ነበር”

ሸመልመሌ ዝንጉርጉርና ነቁጣ የጣለባቸውን ግልገሎች ወለዱ
ዝንጉርጉርና ነቁጣ ያለባቸውን ግልገሎት ወለዱ

ያዕቆብም ለያቸው
ይህ ለብዙ ዓመታት እንደተረገ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “ለሚቀጥሉት ብዙ ዓመታት ያዕቆብ ለያቸው” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ፊታቸውን መልሰው
ፊት ለፊት እያዩ

ከመንጋዎቹ ለራሰ ለያቸው
የራሱን መንጋ ለየ

Genesis 30:41

በመንጋዎች ዐይን ፊት
እዚህ የመንጋዎች ዐይን በጎችን ወይም መንጋዎችን የሚያመለክትና የሚያዩትን እንደሚያተኩር ነው:: አት: (መንጋው እንዲያየው ዘንድ (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉውን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

በበትሮቹ መካከል
በበትሮቹ ፊትለፊት

በከሱ እንስሳት
በደካማዎች እንስሳት

ስለዚህ ደካማ ደካማዎቹ ለላባን ሲሆኑ ብርቱ ብርቱዎቹ ለያዕቆብ ሆኑ
ይህን ይበልጥኑ ግልጽ ማድረግ ይቻላል:: አት: “ደካማ ደካማዎቹ ዝንጉርጉርና ነቁጣ ስለሌላቸው ለላባን ሲሆኑ ብርቱ ብርቱዎች ዝንጉርጉርና ነቁጣ ስላላቸው ለያዕቆብ ሆኑ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 30:43

ይህ ሰው
ያዕቆብ

እጅግ ባለጠጋ ሆነ
“እጅግ በለጸገ” ወይም “ሀብታም ሆነ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 31

1 የላባ ወንዶች ልጆች፣ “ያዕቆብ የአባታችንን ሀብት እንዳለ ወስዶታል፤ ይህ ሁሉ እርሱ ያከማቸውም ሀብት ከአባታችን የተገኘ ነው” እያሉ ሲያወሩ ያዕቆብ
ሰማ። 2 በላባም ዘንድ እንደቀድሞ ተወዳጅ አለመሆኑን ተረዳ። 3 እግዚአብሔርም ያዕቆብን፣ “ወደ አባቶችህ ወደ ዘመዶችህ አገር ተመለስ፤ እኔም ከአንተ ጋር
እሆናለሁ” አለው። 4 ስለዚህ ያዕቆብ መንጋዎቹ ወደ ተሰማሩበት መስክ እንዲመጡ ራሔልንና ልያን አስጠራቸው፤ 5 እንዲህም አላቸው፤ “አባታችሁ ስለ እኔ
ያለው አመለካከት እንደ ቀድሞ አለመሆኑን ተረድቻለሁ፤ ቢሆንም የአባቴ አምላክ አልተለየኝም፤ 6 መቼም ባለኝ አቅም አባታችሁን ማገልገሌን እናንተ
ታውቃላችሁ። 7 አባታችሁ ደመወዜን ዐሥር ጊዜ እየለዋወጠ አታልሎኛል፣ ሆኖም እንዲጎዳኝ እግዚአብሔር አልፈቀደለትም። 8 እርሱ፣ ‘ደመወዝህ ዝንጉርጉሮቹ
ይሆናሉ ሲለኝ፣ መንጎቹ ሁሉ ዝንጉርጉር ወለዱ’፤ ደግሞም፣ ‘ደመወዝህ ሽመልመሌዎቹ ይሆናሉ ሲለኝ፣ መንጎቹ ሁሉ ሽመልመሌ መልክ ያላቸውን ወለዱ፤ 9
ስለዚህ እግዚአብሔር የአባታችሁን ከብቶች ወስዶ ለእኔ ሰጠኝ። 10 እንስሳቱ በሚጠቁበት ወራት የሚያጠቋቸው አውራ ፍየሎች ሽመልመሌ፣ ዝንጉርጉርና
ነቁጣ መሆናቸውን በሕልም አየሁ። 11 በዚያው ሕልም የእግዚአብሔር መልአክ፦ ‘ያዕቆብ’ ብሎ ጠራኝ፣ እኔም ‘እነሆ አለሁ’ አልሁ። 12 እርሱም እንዲህ
አለኝ፦ ‘መንጋዎቹን የሚያጠቋቸው አውራ ፍየሎች ሽመልመሌ፣ ዝንጉርጉርና ነቁጣ ያለባቸው መሆናቸውን ተመልከት፣ ላባ የፈጸመብህን በደል አይቻለሁ። 13
የድንጋይ ሐውልት በማቆም ዘይት ቀብተህ የተሳልህባት የቤቴል አምላክ እኔ ነኝ፤ አሁንም ይህን አገር ፈጥነህ ልቀቅ ወደ ተወለድህበትም ምድር ተመልሰህ ሂድ’
አለኝ።” 14 ራሔልና ልያም እንዲህ ብለው መለሱለት፦ “ከአባታችን የምንወርሰው ድርሻ አለን? 15 እርሱ እኛን የሚያየን እንደ ባዕዳን አይደለምን? ደግሞም
እኮ እኛን ሸጦናል፣ የተሸጥንበትንም ዋጋ ራሱ በልቶታል። 16 እግዚአብሔር ከአባታችን ወስዶ ለአንተ የሰጠው ሀብት ሁሉ የእኛና የልጆቻችን ነው፤ ስለዚህ
እግዚአብሔር የነገረህን ሁሉ አድርግ።” 17 ከዚያም ያዕቆብ ተነሥቶ ልጆቹንና ሚስቶቹን በግመሎች ላይ አስቀመጠ፤ 18 በመስጴጦምያ ካፈራው ሀብት ሁሉ
ጋር ከብቶቹን በሙሉ ወደፊት አስቀደመ፣ ወደ አባቱም ወደ ይስሐቅ አገር፣ ወደ ከነዓን ምድር ጉዞውን ቀጠለ። 19 ላባ በጎቹን ሊሸልት ሄዶ ስለነበር፣ እርሱ
በሌለበት ራሔል ከቤት የነበሩትን የአባቷን ጣዖቶች ሰርቃ ሄደች። 20 ያዕቆብ መሄዱን ለላባ ሳይገልጥለት አታሎት ሄደ፣ 21 የራሱ የሆነውን ሀብት ይዞ
በፍጥነት ታጓዘ፤ የኤፍራጥስንም ወንዝ ተሻግሮ ወደ ኮረብታማው አገር ወደ ገለዓድ ሄደ። 22 ያዕቆብ መኮብለሉን ለላባ በሦስተኛው ቀን ተነገረው። 23
ከዘመዶቹ ጋር ሆኖ ያዕቆብን ተከታተለው፤ ሰባት ቀን ከተጓዙ በኋላ ገለዓድ በተባለው ተራራማ አገር ላይ ሊደርስበት ተቃረበ። 24 በዚያን ሌሊት እግዚአብሔር
ለላባ በሕልም ተገለጠለትና “ያዕቆብን ክፉም ሆን ደግ እንዳትናገረው ተጠንቀቅ” አለው። 25 ያዕቆብ ገለዓድ በተባለው ኮረብታማ ስፍራ ድንኳኑን በመትከትል
ሰፍሮ ሳለ ላባ ደረሰበት፤ ላባና ዘመዶቹም እዚያው ድንኳናቸውን ተክለው ሰፈሩ። 26 ከዚህ በኋላ ላባ ያዕቆብን እንዲህ አለው፦ “ስለምን እንዲህ አድርገህ
አታለልኸኝ፤ ሴቶች ልጆቼንስ በጦርነት እንደተማረኩ ያህል ይዘሃቸው ለምን ሄድህ? 27 ሳትነግረኝ ተሰውረህ በመሄድ ለምን አታለልኽኝ? ነግረኸኝ ቢሆን
በከበሮና በመስንቆ እየተዘፈነ በደስታ በሸኘሁህ ነበር። 28 ልጆቼንና የልጅ ልጆቼን በመሳም እንድሰናበታቸው ባለማድረግህ የሞኝነት ተግባር ፈጽመሃል። 29
ጉዳት ሳደርስብህ እችል ነበር፣ ነገር ግን ባለፈው ሌሊት የአባትህ አምላክ፣ ‘ያዕቆብን ክፉም ሆነ ደግ አንድ ቃል እንዳትናገረው’ ብሎ አስጠነቀቀኝ፣ 30 ወደ
ትውልድ አገርህ ለመመለስ ባለህ ብርቱ ፍላጎት እንደተለየኸኝ አውቃለሁ፣ ታዲያ የቤቴን ጣዖቶች የሰረቅኽብኝ ለምንድነው?” 31 ለላባ እንዲህ ሲል መለሰለት፦
“ሴቶች ልጆችህን በኃይል ነጥቀህ ታስቀርብኛለህ ብዬ ስለ ፈራሁ ነው በድብቅ የሄድኩት። 32 ነገር ግን ከእኛ መካከል የአንተን የጣዖት ምስል የሰረቀ ሰው
ካለ ይሙት። የአንተ የሆነ አንዳች ነገር ከኔ ዘንድ ቢገኝ፣ አንተው ራስህ ዘመዶቻችን ባሉበት ፈልግና ውሰድ።” እንደዚህ ሲል ራሔል የጣዖታቱን ምስል መስረቋን
ያዕቆብ አያውቅም ነበር። 33 ላባም ወደ ያዕቆብ ድንኳንና ወደ ልያ ድንኳን እንዲሁም ወደ ሁለቱ ደንገጡሮቹ ድንኳን ገባ፤ ነገር ግን ምንም አላገኘም። ከልያ
ድንኳን ከወጣ በኋላ ወደ ራሔል ድንኳን ገባ። 34 ራሔል ግን ጣዖቱቹን ወስዳ በግመሉ ኮርቻ ሥር በመሰወር በላያቸው ተቀምጣባቸው ነበር። ላባ በድንኳኑ
ውስጥ ያለውን ጓዝ ሁሉ በርብሮ ምንም ነገር አላገኘም። 35 ራሔልም አባቷን፦ “በፊትህ ተነሥቼ መቆም ስላልቻልሁ፣ ጌታዬ አትቆጣ የወር አበባዬ መጥቶ
ነው” አለችው፤ ስለዚህ በረበረ፤ የጣዖቱን ምስል ግን ማግኘት አልቻለም። 36 በዚህ ጊዜ ያዕቆብ ተቆጣ፤ ላባንም እንዲህ ሲል ወቀሰው፦ “እስቲ ወንጀሌ
ምንድን ነው? ይህን ያህል የምታሳድደኝ ኃጢአቴ ምን ቢሆን ነው? 37 ዕቃዬን አንድ በአንድ በርብረሃል፤ ታዲያ የአንተ ሆኖ ያገኘኸው ዕቃ የትኛው ነው? ካለ፣
እስቲ በአንተም በእኔም ዘመዶች ፊት አቅርብና እነርሱ ያፋርዱን። 38 ሃያ ዓመት አብሬህ ኖሬአለሁ፤ በጎችህና ፍየሎችህ አልጨነገፉም፤ ከመንጋህም አንድ ጠቦት
እንኳ አልበላሁም። 39 አውሬ የሰበረውንም ቢሆን እተካ ነበር፣ በቀንም ሆነ በሌሊት የተሰረቁትን ሁሉ ስታስከፍለኝ ኖረሃል። 40 ብዙ ጊዜ በቀን ሐሩርና በሌሊት
ቁር እሠቃይ ነበር፤ በቂ እንቅልፍ ያገኘሁበት ጊዜ አልነበረም። 41 ሃያ ዓመት በቤትህ የኖርሁት በዚህ ሁኔታ ነበር፤ ዐሥራ አራት ዓመት ለሁለቱ ልጆችህ ብዬ
አገለገልሁ፤ ስድስት ዓመት ስለመንጋዎችህ ስል አገለገልሁ፤ ይህም ሆኖ ደመወዜን ዐሥር ጊዜ ለዋውጠኽብኛል። 42 የአባቴ አምላክና እርሱም የሚፈራው
የአብርሃም አምላክ ከእኔ ጋር ባይሆን ኖሮ ባዶ እጄን ሰድደኽኝ ነበር፤ እግዚአብሔር ግን መከራዬን ዐይቶ፣ ልፋቴን ትመልክቶ ትናንት ሌሊት ገሠጸህ።” 43
ላባም ለያዕቆብ እንዲህ ሲል መለሰ፤ “እነዚህ ሴቶች የእኔው ልጆች ናቸው፤ ልጆቻቸውም የእኔ ናቸው፤ እነዚህም መንጋዎች የእኔ ናቸው፤ ይህ የምታየው ሁሉ
የራሴ ነው፤ ታዲያ በእነዚህ ሴቶች ልጆቼና በወለዷቸው ልጆቻቸው ላይ ዛሬ ምን ማድረግ እችላለሁ? 44 በል አሁን ቃል ኪዳን እንጋባ፤ ኪዳኑም በአንተና በእኔ
መካከል ምስክር ይሁን።” 45 ያዕቆብም ድንጋይ ውስዶ ሐውልት አድርጎ አቆመው፤ 46 ከዚያም ዘመዶቹን “ድንጋይ ሰብስቡ” አላቸው። እነርሱም ድንጋይ
እያመጡ ከመሩ፤ በክምሩም አጠገብ ምግብ በሉ። 47 ላባም ክምር ድንጋዩን ይጋርሠሀዱታ ብሎ ጠራው፤ ያዕቆብ ደግሞ ገለዓድ አለው። 48 ላባም “ይህ
ክምር ድንጋይ በእኔና በአንተ መካከል ዛሬ ምስክር ነው” አለው። ገለዓድ ተብሎ የተጠራውም በዚሁ ምክንያት ነው፤ 49 ደግሞም ምጽጳ ተባለ ምክንያቱም ላባ
እንዲህ ብሎአልና፤ “እንግዲህ ከዚህ በምንለያይበት ጊዜ እግዚአብሔር እኔንና አንተን ይጠብቀን፤ 50 ልጆቼን ብትበድላቸው ወይም ሌሎችን በላያቸው ብታገባ፣
ማንም ከእኛ ጋር ባይኖርም እንኳ እግዚአብሔር በአንተና በእኔ መካከል ምስክር መሆኑን አትርሳ።” 51 ላባም ያዕቆብን እንዲህ አለው፦ “ክምር ድንጋዩ እነሆ፤
በአንተና በእኔ መካካል ያቆምሁትም ሐውልት እነሆ፤ 52 ይህን ክምር ድንጋይ አልፌ አንተን ለማጥቃት ላልመጣ፣ አንተም ይህን ክምር ድንጋይና ይህን ሐውልት
አልፈህ እኔን ለማጥቃት ላትመጣ፤ ይህ ክምር ድንጋይ ምስክር ነው፤ ይህም ሐውልት ምስክር ነው። 53 የአብርሃም አምላክ፣ የናኮር አምላክ፣ የአባታቸውም
አምላክ በመካከላችን ይፍረድ።” ስለዚህ ያዕቆብ አባቱ ይስሐቅ በሚፈራው በእግዚአብሔር ማለ። 54 ያዕቆብ በኮረብታማው አገር ላይ መሥዋዕት አቀረበ፤
ዘመዶቹንም ምግብ እንዲበሉ ጋበዛቸው፤ እነርሱም ከበሉ በኋላ እዚያው አደሩ። 55 በማግስቱም ማለዳ ላባ የልጅ ልጆቹን እንዲሁም ሴቶች ልጆችን ስሞ
መረቃቸው፤ ከዚያም ወደ አገሩ ተመለሰ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Genesis 31:1

ይህን
ይህ ቃል የታሪኩን ትረካ መሥመር ለማቋረጥ ተጠቅሞአል በዚህ ጸሐፊው አዲስ ታሪክ ይጀምራል

ያዕቆብ የላባን ወንዶች ልጆች ያሉትን ነገር ሰማ
ያዕቆብ የላባን ወንዳች ልጆች የሚሉትነ ሰማ

ያዕቆብ የአባታችን የሆነውን ሁሉ ወስዶታል
የላባን ወንዶች ልጆች ከመቆጣታቸው የተነሣ አጋንነው ይናገራሉ አት ያዕቆብ የወሰደው ነገር ሁሉ የአባታችን ነበር:: (ማጋነንና ገሃዳዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

ያዕቆብም የላባን ፊት አየ አመለካከቱም እንደተለወጠበት ተገናዘበ
እነዚህ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች በመሠረት አንድ ናቸው:: ሁለተኛው ያዕቆብ በላባን ፊት ያየውን ይገልጻል:: አት: “ያዕቆብም ላባን እንዳለተደሰተበት ተረዳ” (ተጓዳኝ ንጽጽር ይመልከቱ)

አባቶችህ
አባትህ ይስሐቅና አያትህ አብርሃም

Genesis 31:4

ያዕቆብም ልኮ ራሔልንና ልያን ወደ በጎቹ ሥፍራ ወደ ሜዳ ጠራቸው
ያዕቆብ መንጎቹ ወደተሠማሩበት መስክ እንዲመጡ ራሔልንና ልያን አስጠራቸው

ለመንጋው እናም እንዲህ አላቸው
እነዚህ ሁለት አጫጭር ዐረፍተ ነገሮች ናቸው:: አት “ለመንጋው:: እንዲህም አላቸው” (የዐረፍተ ነገር ውቅር ይመልከቱ)

አባታችሁ ስለእኔ ያለው አመለካከት እንደቀድሞው አለመሆኑን ተረድቻለሁ
አባታችሁ በእኔ ደስተኛ እንዳልሆነ ተረድቻለሁ

ባለኝ ጉልቤቴ ሁሉ አባታችሁን እንዳገለገልሁ እናንተ ታውቃላችሁ
እናንተ የሚለው ቃል ራሔልንና ልያን ያመለክታል እንዲሁም ደግሞ ትኩረትን ይጨምራል። አት: “አባታችሁን ባለኝ ጉልበት ሁሉ እንዳገለገልሁ እናንተው ራሳችሁ ታውቃላችሁ” (ሁለተኛ ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

Genesis 31:7

አታልሎኛል
ዋሽቶኛል ወይም በፍትሃዊነት አላስተናገደኝም

ደመወዜ
ሊከፍለኝ የተናገረውን

ሊጐዳኝ
ተገቢ ትርጉሞች 1 አካላዊ ጥቃት በማንኛውም መንገድ ለያዕቆብ መከራ መንስሄ በመሆን

ነቁጣ እንስሳት
ነጭ ምልክት ያላቸው እንስሳት

መንጎቹ ወለዱ
በጎቹ ወለዱ

ዝንጉርጉር
ዝንጉርጉር ቀለም ያላቸው እንስሳት

በዚህ መንገድ እግዚአብሔር የአባታችሁን ከብቶች ወስዶ ለእኔ ሰጠኝ
ይህም እንዴት እግዚአብሔር የአባታችሁን እንስሳት ለእኔ እንደሰጠኝ ነው

Genesis 31:10

አጠቃላይ መረጃ
ያዕቆብ ታሪኩን ለሚስቶቹ ለልያና ለራሔል መናገሩን ይቀጥላል

የሚጠቁበት ወራት በሚሆንበት ጊዜ
በሚጠቁበት ወራት

መንጋው በሚጠቃበት
እዚህ “መንጋው” ሴት ፍዬሎችን ያመለክታል:: አት: “ሴት ፍዬሎች በሚጠቁበት” (ክፍልን ለሙሉና ሙሉውን ለክፍል የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

ሸመልመሌ ዝንጉርጉርና ነቁጣ
ዝንጉርጉር ትንሽ ነቁጣና ትልቅነቁጣ ያላቸው

የእግዚአብሔር መልአክ
ተገቢ ትርጉሞች 1) እግዚአብሔር በሰው መልክ ሲገለጥ 2) ከእግዚአብሔር መልእክተኞች አንዱሲገለጥ ሀረጉ በተክክል እስካልተገለጸ ለ”መልአክ” የሚንጠቀመውን መደበኛ ቃል በመጠቀም በቀላሉ እንደ “እግዚአብሔር መልእክተኛ” መተረጐም ተገቢ ነው::

እኔም አልሁ
እኔም መለስሁ

እነሆኝ
አዎን እየሰማሁ ነኝ ወይም አዎን ምንድነው? በዘፍጥረት 22: 1 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ።

Genesis 31:12

አጠቃላይ መረጃ
የእግዚአብሔርም መልአክ ያዕቆብን መናገር ቀጠለ:: (ዘፍጥረት 31:10 ይመልከቱ)

ዐይኖችህን ቀና አድርግ
ይህ ቀና ብለህ ተመልከት ማለት ነው (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

መንጎቹን የሚያጠቋቸውን
እዚህ “መንጋ” እንስት ፍዬሎች ብቻ ያመለክታል:: አት “የመንጋው እንስት ፍዬሎችን የሚያጠቋቸውን” (ክፍል ለሁሉና ሁሉን ለክፍል የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

ሸመልመሌ ዝንጉርጉርና ነቁጣ
ዝንጉርጉርና ነቁጣ ያለባቸው

ዘይት የቀባሄው ሐውልት
ያዕቆብም ሐውልቱን ዘይፍ በመቀባት ለእግዚአብሔር የቀደሰው (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

የትውልድህ ምድር
የተወለድህበት ምድር

Genesis 31:14

ራሔልና ልያም እንዲህ ብለው መለሱ
ይህ በተመሣሣይ ጊዜ ተናግረዋል ማለት አይደለም እንተስማሙ ያጸናል

ከአባታችን ሀብት የሚናገኘው ምን ድርሻ ወይም ውርስ አለን?
ራሔልና ልያ በጥያቄ መልክ አባታቸው ሊሰጣቸው ምንም እንዳልቀረ አጥብቀው ይናገራሉ። አት፡ “ከአባታችን ልንወርሰው በፍጹም የቀረ ምንም ነገር የለም!” (ቅኔ አዘል ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

እኛን የሚያየን እንደባዕድ አይደለምን?
አባታቸው እንዴት እንደሚያያዩአቸው ያላቸውን ቁጣ በጥያቄ ይገልጸሉ:: አት: ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ገቢራዊ ዓረፍተ ነገር ለገለጽ ይችላል አት አባታችን እንደ ሴት ልጆቹ ሳይሆን እንደባዕድ ሴቶች ያየናል:: (ቅኔ አዘል ጥያቄዎችና ተሻጋሪ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዙ ዐረፍተ ነገሮች ይመልከቱ)

ሸጦናል
ይህ ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት: ለራሱ ጥቅም ሸጦናል:: (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ደግሞም ዋጋችንን በፍጹም በልቶታልና
ላባን ለሴት ልጆቹ መስጠት የነበረበትን ገንዘብ በፍጹም ለራሱ መጠቀሙ የዱር አራዊት እንደ ምግብ ገንዘቡን እንደበሉት ተደርጐ ተነግሮአል:: አት: “በፍጹም ገንዘባችንን ተጠቅሞአል” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይጠቀሙ)

ሁሉ የእኛና የልጆቻችን ነው
ለእኛና ለልጆቻችን ይገባል

አሁንም
እዚህ አሁን የአሁን ጊዜ አይደለም ነገር ግን ለሚከተለውን አስፈላጊ ነጥብ ትኩረት ለመስጠት ነው።

እግዚአብሔር ያለህን ሁሉ አድርግ
እግዚአብሔር የነገረህን ሁሉ አድርግ

Genesis 31:17

ወንዶች ልጆቹ
ያዕቆብ ልጆቹን ሁሉ ወሰደ:: ወራሾች ስለሆኑ ወንዶች ልጆቹን ብቻ የጠቀሳል:: አት: “ልጆቹን” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ከብቶቹን ሁሉ ነዳ
ሁሉን ከብቶች ነዳ:: እዚህ “ከብቶች” ሁሉን የቤት እንስሳትን ይወክላል።

በጳዳን አራም ካፈራው ሀብት ሁሉ ጋር
በጳዳን አራም እያለ ያፈራቸውን ሌሎች ከብቶችንም

ከዚያም ወደ አባቱም አገር ወደ ይስሐቅ ወደ ከነዓን ጉዞውን ቀጠለ
አባቱ ይስሐቅ ወደሚኖርበት አገር ወደ ከነዓን ሄዴ

Genesis 31:19

ላባን በጐቹን ሊሸልት ሄዶ ሳለ
ላባን የበጐቹን ጸጉር ሊያስቆርጥ በሄደበት ጊዜ

ወንዙን
የኤፍራጥሰ ወንዝ ያመለክታል

አመራ
ተጓዘ

ወደ ኮረብታማው አገር ወደ ገለአድ
ወደ ገለአድ ተራራዎች ወይም ወደ ገለአድ ተራራ

Genesis 31:22

በሶስተኛው ቀን
የወጡበትን ቀን እንደ አንድ ቀን መቁጠር የአይሁድ ለማድ ነው:: አት: “ከወጡበት ሁለት ቀናት በኋላ”

ለላባን ተነገረው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አት አንድ ሰው ለላባን ነገረው ተሻጋሪ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዙ ዐረፍተ ነገሮች ይመልከቱ

ያዕቆብም ኮበለለ
የቤተሰቡ መሪ ስለሆነ ያዕቆብ ብቻ ተጠቅሶአል ቤተሰቡ ከእርሱ ጋር እንደተጓዙ ግልጽ ማድረግ ይቻላል:: አት: “ያዕቆብ ከሚስቶቹና የልጆቹ ጋር ኮበለለ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ይዞ ተነሣ
ላባን ይዞ ተነሣ

ተከታተለው
አሳደደው

ለሰባት ቀናት ጉዞ
ያዕቆብን ደርሶ ለመያዝ ላባን ሰባት ቀናት ተጓዘ

ደረሰበት
ያዘው

Genesis 31:24

ከዚያም እግዚአብሔር ለሶሪያዊው ለላባን በሕልም ተገልጦ
“ከዚያም” የሚለው ቃል የተጠቀመው ታሪኩን ወደ ላባን የሕይወት ዳራ መረጃ ለመቀየር ነው አት: “በዚያ ሌሊት እግዚአብሔር ለላባን ተገልጦ” (የዳራ መረጃዎች ይመልከቱ)

ያዕቆብን ክፉም ሆነ ደግ እንዳትናገረው ተጠንቀቅ አለው
“ክፉ ሆነ ደግ” የሚለው ሀረግ የተጠቀመው “ምንም” ለማለት ነው። አት: ያዕቆብን ከመሄድ ለማቋረጥ ለመሞከር ምንም ነገር እንዳትናገር (See: Merism)

ከዚያም ያዕቆብ ገለዓድ በተባለው ኰረብታማ አገር ድንኳን ተክሎ ሳለ ላባ ደረሰበት ላባና ዘመዶቹ በዚያው ሠፈሩ::
“ከዚያም” የሚለው ቃል የተጠቀመው ታሪኩን ወደ ያዕቆብናላባን የሕይወት ዳራ መረጃ ለመቀየር ነው:: አት: “ላባን ያዕቆብን በደረሰበት ጊዜ ያዕቆብ በኰረብታማው አገር ድንኳን ተክሎ ነበር: ከዚያም ላባንና ዘመዶቹ ደግሞ በኰረብታማው ገለዓድ አገር ድንኳን ተከሉ” (የዳራ መረጃዎች ይመልከቱ)

Genesis 31:26

ልጆቼን የጦር ምርኮኛ ይመስል አካልበህ ወሰድናቸው
ያዕቆብ ቤተሰቡን ከራሱ ጋር ወደ ከነዓን ምድር መውሰዱ ልክ ያዕቆብ እንደ የጦር ምርኮኞችን እናም አሰገድዶአቸው እየወሰደ እንዳለ ላባን ይናገራል ላባን ስለተቆጣና ያዕቆብ ስላደረገው ነገር ጸጸት እንዲሰማው አግንኖ ይናገራል:: (ተመሣሣይ ንጽጽር የማጋነንና ገሃዳዊ አገላለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ተደብቀህ ሄድህ
በድብቅ ሸሸህ

ፍስሐ በማድረግ
በደስታ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በከበሮ/ ታምቡርና በበገና
እነዚህ መሣሪያዎች ሙዝቃን የሚገልጹ ናቸው። አት: “እናም በሙዝቃ” (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ታምቡር
የከበሮ ዓይነት ለምት የሚሆን አናት ያለው ዙሪያሙ ከብረት የተሠራና መሣሪያው በሚመታበት ጊዜ የሚርገበገብ የሙዝቃ መሣሪያ ነው ያልታወቁትን ስለመተርጐም ይመልከቱ

ወንዶች የልጅ ልጆቼን እንዲስማቸው
እዚህ ወንዶች የልጅ ልጆች ወንድ ሆነ ሴት ሁሉን የልጅ ልጆችን ይወክላሉ:: አት: “የልጅ ልጆቼን እንዲስማቸው” (በወንዴ ጾታ የተጠቀሱ ሴት ጾታንም የመግለጽ አባባል ይመልከቱ)

አሁን የሠራሄው የጅል ሥራ ነው
በጅልነት አድርገሄዋል

አሁንም
ይህ የዚያን ጊዜ ማለተ አይደለም ነገር ግን ለሚከተለውን ጠቃሚ ነገር ትኩረት እንደሰጥበት ነው

Genesis 31:29

እናንተን ልጐዳችሁ ነበር
እዚህ “እናንተ” ብዙና ከያዕቆብ ጋር ያሉትን ሁሉ ያመለክታል:: አት: “ሊጐዳችሁ የሚያስችለኝ ከእኔ ጋር ብዙ ሰዎች ነበሩ” (የሁለተኛ ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

ያዕቆብን ክፉም ሆነ ደግ እንዳትናገረው ተጠንቀቅ አለኝ
“ክፉ ሆነ ደግ” የሚለው ሀረግ የተጠቀመው “ምንም” ለማለት ነው። በዘፍጥረት 31:24 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: አት: “ያዕቆብን ከመሄድ ለማቋረጥ ለመሞከር ምንም ነገር እንዳትናገር” (See: Merism)

አንተም ሄደሃል
አንተ የሚለው ነጠላና ያዕቆብን ያመለክታል:: (የሁለተኛ ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

ወደ አባትህም ቤት
እዚህ ቤት ቤተሰብን ይወክላል:: አት: “ወደ አባትህና ሌሎች ቤተሰብህ ቤት ለመመለስ” (ክፍልን ሙሉና ሙሉውን ክፍል አድርጐ የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

አምላኮቼን
ጣዖቶቼን

Genesis 31:31

ልጆችህን ከእኔ የምትቀማ ስለመሰለኝና ስለፈራሁ በድብቅ ወጣሁ።
በድብቅ የወጣሁት ልጆችህን ከእኔ ነጥቀህ ታስቀርብኛለህ ብዬ ስለፈራሁ ነው።

ከእኛ መካከል የአንተን የጣዖታት ምስል ደብቆ የተገኘ ሰው ካለ ይሙት
ይህ በአዎንታዊ መንገድ መገለጽ ይችላል አት ጣዖቶችህን የሰረቀ ማንም ቢገኝ እንገድላለን (ምጸት ይመልከቱ)

ዘመዶቻችን/የእኛ ዘመዶች ባሉበት
የእኛ የሚለው ቃል የያዕቆብ ዘመዶችንና የላባን ዘመዶች ያመለክታል:: ሁሉም ዘመዶች ፍትሃዊና ግልጽ መሆኑን ለማረጋገጥ ያዩታል (ሁሉ አቀፍ አንደኛ ወገን አገላለጽ ይመልከቱ)

ያንተ የሆነ አንዳች ነገር ከኔ ዘንድ ቢገኝ ውሰድ
በእኛ ዘንድ ካለው ያንተ የሆነውን ፈልግና ውሰድ

ያዕቆብ ራሔል እነዚያን/ጣዖታቱን መስረቋን አያውቅም ነበር
ይህም ታሪኩን ወደ ያዕቆብ ሕይወት ዳራ መረጃ ይቀይራል (የዳራ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 31:33

ሁለቱ ደንገጡሮቿ
ዘለፋንና ባላን ያመለክታል

አላገኛቸውም
ጣዖታቱን አላገኘም

Genesis 31:34

ከዚያም ራሔል በላያቸው ተቀምጣ ነበር
ከዚያም የሚለው ቃል ታሪኩን ወደ ራሔል ሕይወት ዳራ መረጃ የቀይራል (የዳራ መረጃ ይመልከቱ)

ኮርቻ
ሰው እንዲቀመጥበት በጋማ እንስሳት ጀርባ የሚደረግ መቀመጫ ነው

ጌታዬ
አንድን ሰው “ጌታዬ” ብሎ መጥራት የማክበር መንገድ ነው

በፊትህ ተነስቼ መቆም ስላልቻልሁ
ይህ ከማሕጸንዋ ወራዊ ደም የሚፈስበት ጊዜ ውስጥ እንዳለች ያለመክታል:: (ንጎብነት ወይም ለዛ ባለ መንገድ በተዘዋዋሪ አንድን ነገር ስለመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

Genesis 31:36

እርሱም እንዲህ አለው
ያዕቆብ ላባንን እንዲህ አለ

ወንጄሌ ምንድነው? ይህን ያህል የምታሳድደኝ ኃጢአቴ ምን ቢሆን ነው?
ወንጄሌ ምንድነው እና ኃጢአቴ ምን ሆን የሚሉ ሀረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው ያዕቆብ ላባንን ምን ስህተት እንደሠራ ይጠይቀዋል አት ይህን ያህል በጽኑ የምታሳድደኝ ምን ስህተት ቢፈጽም ነው? (ተጓዳኝ ተነጻጻሪ አባባል ይመልከቱ)

በጽኑ
እዚህ “ጽኑ” የሚለው ቃል ላባን በማጣደፍ ያዕቆብን ለመያዝ ባለው ተነሣሽነት እንዳሳደደው ይገልጻል (ፈሊጣዊ አባባል ይመልከቱ)

ከቤትህስ ዕቃ ሁሉ ምን አገኘህ?
ያንተ ሆኖ ያገኘሄው ዕቃ የትኛው ነው?

በእኛ ዘመዶች ፊት አቅርብ
እዚህ እኛ የሚለውቃል የያዕቆብ ዘመዶችና የላባንን ዘመዶች ያመለክታል:: አት: ያገኘሄውን ማንኛውንም ነገር በዘመዶቻችን ፊተ አቅርብ (አካታች አንደኛ ወገን አገላለጽ ይመልከቱ)

እነርሱ ሁለታችንን ይፍረዱ ወይም እነርሱ ይፍረዱን
እዚህ “ሁለታችን” ያዕቆብንና ላባን ያመለክታል:: “ይፍረዱን” የሚለው አባባል ከክርክሩ የትኛው ትክክል እንደሆነ ይወስኑ ማለት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Genesis 31:38

አጠቃላይ መረጃ
ያዕቆብ ለላባን መናገሩን ቀጠለ

ሃያ ዓመታት
20 ዓመታት (ቁጥሮች ይመልከቱ)

ሴት በግ
እንስት የበግ ጠቦት

አልጨነገፉም
በእርግዝና ወቅት የተቀጨ ወይም ሞቶ የተወለደ ጠቦት አልነበረም ማለት ነው

በአውሬ የተሰበረውን አምጥቼ አላውቅም
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊገለጽ ይችላል አት አውሬ ከእንሰሳትህ አንዱን በገደለ ጊዜ በድኑን ለአንተ አምጥቼ አላውቅም (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ያጣሄውን እተካ ነበር
ያዕቆብ ከመንጋው የላባንን ሙት እንስሳት ምትክ መቁጠር በጫንቃው እንደተሸከመው ሸክም እንደነበር ተደርጐ ተገልጾአል:: አት: “ከመንጋህ እንደጠፋ ከመቁጠር ከመንጋዬ እንደጠፋ ቆጥረዋለሁ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

በቀን በሐሩር ሌሊት በቁር ይበላኝ ነበር
በሞቃትና ቀዝቃዛ የአየር ሁኔታ መሠቃየት የአየር ሁኔታዎች ያዕቆብ እንደ አውሬዎች እንደበሉ ተደርጐ ተገልጾአል:: አት በቀን ሐሩርና በሌሊት ቁር ከመንጋዎችህ ጋር ነበርሁ (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 31:41

አጠቃላይ መረጃ
ያዕቆብ ለላባን መናገሩን ቀጠለ

እነዚህ ሃያ ዓመታት
እነዚህ 20 ዓመታት (ቁጥሮች ይመልከቱ)

አሥራ አራት ዓመታት
14 ዓመታት (ቁጥሮች ይመልከቱ)

ደመወዘን አሥር ጊዜ ለዋውጠህብኛል
መክፈል ያለበትን አሥር ጊዜ ለዋውጦብኛል:: በዘፍጥረት 31:7 ደመወዜን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

የአባቴ አምላክ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም ፍርሃት ከእኔ ጋር ባይሆን ኖሮ
የአብርሃምና የአባቴ የይስሐቅ አምላክ ከእኔ ጋር ባይሆን ኖሮ

የአባቴ አምላክ
እዚህ “አባቴ” የሚለው ቃል አባቱን ይሰሐቅን ያመለክታል::

ይስሐቅ የሚፈራው
እዚህ “ፍርሃት” ለእግዚአብሔር ያለውን ፍርሃት ያመለክታል።

ባዶ እጄን
ይህ ምንም አለመኖር ማለት ነው:: አት: “ፍጹም ባዶ” (ተመሣሣይ ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

እግዚአብሔር መከራዬን አይቶ ልፋቴን ተመልክቶ
መከራ የሚለው ረቂቅ ስም መከራ አየ በሚቶል ሊገለጽ ይችላል:: አት: “እግዚአብሔር ልፋቴን አይቶ እንዴት መከራ እንዳሳየሄኝ ተመልክቶ” (ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ)

Genesis 31:43

ነገር ግን በእነዚህ ሴቶች ልጆቼና በወለዷቸው ልጆቻቸው ላይ ዛሬ ምን ማድረግ እችላለሁ?
ላባን ምንም ማድረግ እንደማይችል አግንኖ ለመቅለጽ ጥያቄ ይጠቀማል ይህ አጋናኝ ጥያቄ በዐረፍተነገር መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት: “ነገር ግን ከእኔ ጋር ወደ ኋላ ለመመለስ በልጆቼና በልጅ ልጆቼ ምንም ላደርግ አልችልም” (አግናኝ ጥቃቄዎች ይመልከቱ)

ምስክር ይሁን
እዚህ “ምስክር” የሚለው ቃል ሰውን አያመለክትም ነገር ግን ያዕቆብና ላባ የሚገቡትን ቃልኪዳን የሚያመለክትና በምሳለያዊነት የተጠቀመ ነው:: ምስክሩ ሁለቱ በሰላማዊ መንገድ ስስማሙ እንደተገኘ ሰው ተደርጐ ተነግሮአል (ሰውኛ አገላለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

Genesis 31:45

ሐውልት
ይህ በክስተቱ ማብቂያ ያቆመው ትልቅ ድንጋይ ሲሆን አስፈላጊ ክስተት እንደተከናወነ ለማመለከት ነው

ድንጋይ ከመሩ
ድንጋዩን አንዱን በአንዱ ላይ በማድረግ ከመሩ

ከዚያም በድንጋዩ ክምር አጠገብ በሉ
አብሮ ምግብን መመገብ ቃል ኪዳን መፈጸሚያ አካል አንዱ ነው የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ይጋርሠሀዱታ
ተርጓሚዎች የማከተውን እንደግርጌ ማስናታወሻ ሊጠቀሙ ይችላሉ:: “ይጋርሠሀዱታ” የሚለው ስም በላባን ቋንቋ “ክምር ምስክርነት” ማለት ነው:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ገለዓድ
ተርጓሚዎች የማከተውን እንደግርጌ ማስናታወሻ ሊጠቀሙ ይችላሉ:: “ገለዓድ” የሚለው ስም በላባን ቋንቋ “ክምር ምስክርነት” ማለት ነው:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 31:48

ይህ ክምር በእኔና በአንተ መካከል ምስክር ነው
ድንጋዮች በእርግጥ እንደሰው ምስክር ሊሆኑ አይችሉም:: አት: “ይህ ክምር በእኔና በአንተ መካከል ማስታወሻ ይሆናል” (በሰውኛ አገላለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ገለዓድ
ተርጓሚዎች የማከተውን እንደግርጌ ማስናታወሻ ሊጠቀሙ ይችላሉ:: “ገለዓድ” የሚለው ስም በላባን ቋንቋ “ክምር ምስክርነት” ማለት ነው:: በዘፍጥረት 31:47 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ምጽጳ
ተርጓሚዎች የማከተውን እንደግርጌ ማስናታወሻ ሊጠቀሙ ይችላሉ:: “ምጽጳ” የሚለው “የመጠበቂያ ማማ” ማለት ነው:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እኛ በማንተያይበት ጊዜ
እዚህ “አለመተያየት” በተለያየን ይወክላል:: አት “በተለያየን ጊዜ” (ተመሣሣይ ምትክ ቃላት ስለመጠቀም ይመልከቱ)

ማንም ከእኛ ጋር ባይኖር
እዚህ “እኛ” ያዕቆብንና ላባን ያመለክታል:: አት: “ማንም የሚያየን ባይኖር”

እይ
“ተመልከት” “አስተውል” “ለሚናገረው ነገር ትኩረት ስጥ”

Genesis 31:51

ይህ ክምር መሥክር ነው... ይህም ሐውልት ምሥክር ነው
የሰላም ስምምነታቸውን በሚመለከት እነዚህ የድንጋይ ክምሮች ለላባና ለያዕቆብ የማስታወሻና ድንበር ምልክቶች ናቸው:: እነዚህ እንደሰው ምሰክሮች እንደሆኑ ተደርጐ ተነግሮአል (በሰውኛ አገላለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

የአባቱ የይስሐቅ ፍርሃት
እዚህ “ፍርሃት” ይስሐቅ ለእግዚአብሔር ያለውን አክብሮትና ያንንም በመታዘዝ መግለጹን ያመለክታል።

Genesis 31:54

ዘመዶቹንም ምግብ እንዲበሉ ጋበዛቸው
አብሮ ምግብ መብላት አብሮ ቃል ኪዳን የመግባት አካል ነው የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

በማግስቱም ማለዳ...ወደ አገሩ ተመለሰ
ቁጥር 55 በመጀመሪያው የዕብራይስጡ መጽሐፍ የምዕራፍ 32 የመጀመሪያ ቁጥር ነው ነገር ግን በአብዛኛዎቹ ዘመናዊ መጽሐፍ ቅዱሶች የምዕራፍ 31 የመጨረሻ ቁጥር ነው በዘመናዊ መጽሐፍ ቅዱሶች የተጠቀመውን የቁጥር አቀማመጥ በቋንቋዎ እንዲጠቀሙ ይመከራል

የተባረከ
አዎንታዊና ጠቃሚ ነገሮች ለአንድ ሰው እንዲደረጉ መሻትን የሚገልጽ ማለት ነው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 32

1 ያዕቆብ በጉዞ ላይ ሳለ የእግዚአብሔር መላእክት በመንገድ ተገናኙት። **2** ባያቸውም ጊዜ፤ “ይህ የእግዚአብሔር ሰፈር ነው” አለ፤ የዚያንም ቦት ስም መሃናይም አለው። **3** ያዕቆብም በኤዶም አገር ሴይር በተባለው ምድር ወደሚኖረው ወንድሙ ወደ ዔሳው መልእክተኞችን አስቀድሞ ላከ፤ **4** እንዲህም ብሎ አዘዛቸው፤ “ጌታዬን ዔሳውን እንዲህ ትሉታላችሁ፤ ‘አገልጋይህ ያዕቆብ እንዲህ ብሎአል በሉት፤ ከላባ ዘንድ ተቀምጬ እስካሁን ድረስ እዚያው ኖርሁ፤ **5** ከብቶች፣ አህዮች፣ የበግና የፍየል መንጎች እንደዚሁም የወንድን የሴት አገልጋዮች አሉኝ፤ አሁንም ይህን መልእክት ለጌታዬ መላኬ በአንተ ዘንድ ሞግስ አገኛለሁ በሚል ተስፋ ነው።’” **6** የተላኩትም ሰዎች ወደ ያዕቆብ ተመልሰው፣ “ወደ ወንድምህ ወደ ዔሳው ሄደን ነበር፤ እርሱም ከአንት ጋር ለመገናኘት በመምጣት ላይ ነው፤ ከእርሱም ጋር አራት መቶ ሰዎች አሉ” አሉት። **7** በዚህ ጊዜ ያዕቆብ እጅግ በመፍራት ተጨነቀ፤ አብረውት የነበሩትንም ሰዎች በሁለት ክፍል መደባቸው፤ እንዲሁም በጎቹን፣ ፍየሎቹን፣ ከብቶቹንና ግመሎቹን በሁለት በሁለት መደባቸው። **8** ይህንንም ያደረገው፦ “ዔሳው የመጀመሪያውን ክፍል ቢያጠቃ፣ ሌላው ክፍል ሊያመልጥ ይችላል” ብሎ በማሰብ ነው። **9** ያዕቆብ እንዲህ ሲል ጸለየ፤ “የአባቴ የአብርሃም አምላክ፣ የአባቴ የይስሐቅ አምላክ ሆይ፣ ‘ወደ አገርህና ወደ ዘመዶችህ ተመልስ፣ እኔም በጎ ነገር አደርግልሃለሁ’ ያልኸኝ እግዚአብሔር ሆይ፣ **10** እኔ ባሪይህ እስካሁን ላደረግህልኝ ቸርነትና ታማኝነት ብቁ አይደለሁም፤ ዮርዳኖስን ስሻገር በእጄ ላይ ከነበረው በትር በስተቀር ምንም አልነበረኝም፤ አሁን ግን ይኸው ሁለት ሠራዊት ሆኛለሁ። **11** ከወንድሜ ከዔሳው እጅ እንድታድነኝ እለምንሃለሁ፤ መጥቶ እኔንም ሆነ እነዚህን እናቶች ከነልጆቻቸው ያጠፋናል ብዬ ፈርቻለሁኝ፤ **12** ነገር ግን አንተ ራስህ፣ ‘አበለጽግሃለሁ፤ ዘርህንም ሊቆጠር እንደማይችል እንደ ባሕር አሸዋ አበዛዋለሁ’ ብለኸኛል።” **13** በዚያችም ሌሊት ያዕቆብ እዚያው አደረ፤ ካለው ሀብት ለወንድሙ ለዔሳው እጅ መንሻ እንዲሆኑ እነዚህን መረጠ፦ **14** ሁለት መቶ እንስት ፍየሎችና ሃያ አውራ ፍየሎች፣ ሁለት መቶ እንስት በጎችና ሃያ አውራ በጎች፣ **15** ሠላሳ የሚያጠቡ ግመሎች ከነግልገሎቻቸው፣ አርባ ላሞችና ዐሥር ኮርማዎች፣ ሃያ እንስት አህዮችና ዐሥር ተባት አህዮች። **16** እነዚህንም በየመንጋው ለይቶ፣ የሚነዱአቸውን ጠባቂዎች መደበላቸው፤ ጠባቂዎችንም እናንተ ቀድማችሁ ሂዱ፣ መንጋዎቹንም አራርቃችሁ ንዱአቸው” አላቸው። **17** ቀድሞ የሚሄደውንም እንዲህ ሲል አዘዘው፤ ዔሳው አግኝቶህ ‘የማን ነህ? ወዴትስ ትሄዳለህ? የምትነዳውስ ይህ ሁሉ ከብት የማን ነው?’ ብሎ ቢጠይቅህ፣ **18** ‘የአገልጋይህ የያዕቆብ ናቸው፤ ለጌታዬ ለዔሳው እጅ መንሻ የሰደዳቸው ናቸው፤ እርሱም ከበስተኋላችን እየመጣ ነው’ ብለህ ንገረው **19** እንዲሁም ሁለተኛውን፣ ሦስተኛውንና መንጎቹን የሚነዱትን ሌሎቹንም ሁሉ እንዲህ ሲል አዘዛቸው፤ ‘ዔሳውን ስታገኙት ይህንኑ ትነግሩታላችሁ፤ **20** በተጨማሪም ‘አገልጋይህ ያዕቆብ ከኋላችን እየመጣ ነው’ በሉት። ይህንንም ያዘዘው፣ ‘ዔሳው ከእኔ ጋር ከመገናኘቱ በፊት እጅ መንሻዬ አስቀድሞ ቢደርሰው ምናልባት ልቡ ይራራና በሰላም ይቀበለኛል’ ብሎ ስላሰበ ነበር። **21** ስለዚህ የያዕቆብ እጅ መንሻ ከእርሱ አስቀድሞ ተላከ፤ እርሱ ራሱ ግን እዚያው በሰፈሩ ቦታ አደረ። **22** በዚያኑ ሌሊት ያዕቆብ ተነሣ ሁለቱን ሚስቶቹን፣ ሁለቱን ሴት አገልጋዮቹንና ዐሥራ አንዱን ልጆቹን ይዞ የያቦቅን ወንዝ ተሻገረ። **23** ወንዙን አሻግሮ ከሸኛቸው በኋላ፣ ጓዙን ሁሉ ሰደደ። **24** ያዕቆብም ብቻውን እዚያ ቀረ፤ አንድ ሰውም እስኪነጋ ድረስ ሲታገለው አደረ። **25** ያም ሰው ያዕቆብን ታግሎ ማሸነፍ እንዳቃተው በተረዳ ጊዜ፣ የጭኑን ሹልዳ መታው፣ ያዕቆብም በሚታገልበት ጊዜ ጭኑ ከመገጣጠሚያው ላይ ተለያየ፤ **26** በዚያን ጊዜ ሰውዬው፣ “እንግዲህ መንጋቱ ስለሆን ልቀቀኝና ልሂድ” አለው። ያዕቆብም፣ “ካልባረክኸኝ አልለቅህም” አለው። **27** ሰውዬውም፣ “ስምህ ማን ነው?” አለው። እርሱም፣ “ያዕቆብ ነው” አለ። **28** ሰውዬውም፣ “ከእግዚአብሔርም ከሰዎችም ጋር ታግለህ አሸንፈሃልና ከእንግዲህ ስምህ እስራኤል እንጂ ያዕቆብ አይባልም” አለው። **29** ያዕቆብም፣ “እባክህ ስምህን ንገረኝ” ብሎ ጠየቀው። ሰውዬውም፣ “ስሜን ለማወቅ ለምን ፈለግህ?” አለው፤ በዚያም ስፍራ ባረከው። **30** ስለዚህ ያዕቆብ “እግዚአብሔርን ፊት ለፊት ዐይቼ እንኳ ሕይወቴ ተርፋለች” ሲል የዚያን ቦታ ስም ጵኒኤል አለው። **31** ጵኒኤልንም እንዳለፈ ፀሐይ ወጣችበት፣ እርሱም በጭኑ ምክንያት ያነክስ ነበር። **32** ከዚህም የተነሣ የእስራኤል ልጆች ሹልዳን ከጭኑ ጋር የሚያገናኘውን ሥጋ አይበሉም፤ ምክንያቱም ያዕቆብ ከሰውዬው ጋር ሲታገል ሰውዬው ሹልዳውን መትቶት ስለነበር ነው።

Genesis 32:1

መሃናይም
ተርጓሚዎች በግርጌ ማስታወሻዎች ሊጨምሩ ይችላሉ:: መሃናይም የሚለው ስም “ሁለት ሰፈሮች” ማለት ነው

Genesis 32:3

ሴይር
ይህ በኤዶምያስ ግዛት ተራራማው ቦታ ነው:: ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ::

ጌታዬን ዔሣውን እንዲህ ትሉታላችሁ “አገልጋይህ ያዕቆብ እንዲህ ብሎአል በሉት “እስካሁን .... በፊትህ’”
ይህ በጥቅስ ውስጥ የሚገኝ ጥቅስ አለው:: ቀጥታው ጥቅስ እንደ ተዘዋዋሪ ጥቅስ ለገለጽ ይችላል:: አት: “ ‘ይህ ለጌታዬ ለዔሣው ሊነግር የሚወደው ነው:: እስከዚህ እንዳለሁት ……በፊቱ’” (ጥቅስን በጥቅስ ውቅጥና ቀጥታና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

ጌታዬ ዔሣው
ያዕቆብ ወንድሙን ጌታው አድርጐ በማቅረብ የትህትና ቃል ይጠቀማል

አገልጋይህ ያዕቆብ
ያዕቆብ ራሱን እንደአገልጋዩ በማድረግ የትህትና ቃል ይጠቀማል

በአንተ ፊት ሞገስ ባገኝ
ሞገስ ማግኘት የሚለው ሀረግ በሌሎች ሰዎች ዘንድ ተቀባይነትን ማትረፍን የሚገልጽ ፈሊጣዊ አባባል ነው አት “መቀበልህን እንዲታረጋግጥልኝ” (ፈሊጣዊ አነጋገር ተመሣሣይ ምትክ ቃላትና ዘይቤያዊ አባባሎች ይመልከቱ)

Genesis 32:6

አራት መቶ ሰዎች
400 ሰዎች ቁጥሮች ይመልከቱ

ፍርሃት
አንድ ሰው በራሱ ወይም ከሌሎች ሥጋት የሚፈጥር ጉዳት ሲደረስበት የማሰማው ስሜት ነው

ጭንቀት
ተስፋ መቁረጥ ወይም መረበሽ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በአንደኛው ሠፈር ላይ አደጋ ቢጥል ሌላው ሠፈር ሊያመልጥ ይችላል
እዚህ ሠፈር ሰዎችን ይወክላል አት በአንዱ ሠፈር ባለው ሰው አደጋ ቢጣል በሌላው ሠፈር ያለው ሰው ያመልጣል። (ተመሣሣይ ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

Genesis 32:9

የአባቴ የአብርሃም አምላክ የአባቴ የይስሐቅ አምላክ ሆይ
ይህ ለተላያዩ አማልክት ሳይሆን ሁሉም ያመለኩትን አንድ እግዚአብሔርን ያመለክታል አት የአያተ የአብርሃምና የአባተ የይስሐቅ አምላክ እግዚአብሔር (ግምታዊ እውቀትና ጥብቅ መረጃ ይመልከቱ)

ወደ አገርህና ወደ ዘመዶችህ ተመለስ እኔም በጐ ነገርን አደርግልሃለሁ ያልከኝ እግዚአብሔር ሆይ
ይህ በጥቅ ውስጥ የሚገኝ ጥቅሰ ነው:: በተዘዋዋሪ ጥቅስ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “ወደ አገረና ወደ ሕዝቤ እንድመለስና በጐ ነገርንም አደርግልሃለሁ ያልከው እግዚአብሔር”

ወደ ዘመዶችህ
ወደ ቤተሰብህ

በጐ ነገር አደርግልሃለሁ
መልካም ነገር አደርግልሃለሁ ወይም በመልካምነት እንከባከብሃለሁ

እኔ ባሪያህ እስካሁን ላደረክልኝ የቃልኪዳን ቸርነትና ታማኝነት ብቁ አይደለሁም
ረቂቅ ስሞች ቸርነትና ታማኝነት እንደ ቸር እና ታዛዥ ሊገለጹ ይችላሉ አት እኔ ባሪያህ እስካሁን ላደረክልኝ የቃልኪዳን ታማኝ አይደለሁም ወይም ታዛዥ አይደለሁም (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተነገር ይመልከቱ)

ባሪያህ
“እኔ” የሚለው በትህትና ቃል ሲገለጽ ነው

አሁን ግን የሁለት ክፍል ሠራዊት ሆንሁ
ሆንሁ የሚለው ሐረግ ያለውን ሀብት የሚገልጽ ፈሊጣዊ አባባል ነው:: አት: “አሁን ግን ከእኔ ጋር በሁለት ክፍል ሠራዊት በቂ ሰዎች መንጋዎችና ሀብት አሉኝ” ፈሊጣዊ አባባል ይመልከቱ

Genesis 32:11

አድነኝ
አትርፈኝ

ከወንድሜ እጅ ከዔሣው እጅ
እዚህ “እጅ” ጉልበትን ያመለክታል ሁለቱም ሀረጐች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው ሁለተኛው የሚገልጸው ያዕቆብ የሚያስበው ወንድመ ዔሣው እንደሆነ ነው። አት: ከወንድሜ ከዔሣው ጉልበት ወይም ከወንድሜ ከዔሣው (ተመሣሣይ ምትክ ቃል ወይም ተጓዳኝ ንጽጽር ይመልከቱ)

እንዳያጠፋ እኔ እፈራለሁና
እንደሚያጠፋ ፈርቼያለሁና

ነገር ግን አንተ ራስህ አበለጽግሃለሁ ዘርህን ሊቈጠር....
ይህ በጥቅስ ውስጥ ያለ ጥቅስ ነው እንደተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “ነገር ግን አንተ ራስህ አብለጽግሃለሁ እናም የዘረንም ቁጥር..” (ጥቅሶችን በጥቅስ ውስጥና ቀጥተኛና በዘዋዋሪ ጥቅችን ይመልከቱ)

አበለጽግሃለሁ
መልካም ነገርን አደርግልሃለሁ ወይም በመልካምነቴ አሳይሃለሁ

ዘርህን እንደ ባህር አሸዋ አበዛዋለሁ
የያዕቆብን ዘር ቁጥር እጅግ ብዙ ማድረጉ ቁጥሩ እንደ ባህር አሸዋ ቁጥር እንደሚሆን ተደርጐ ተነግሮአል (ተመሣሣይ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

ሊቆጠር እንደማይችል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አት: “ያም ከቁጥራቸው የተነሣ ማንም መቁጠር እስከማይችል” (ተሻጋሪ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Genesis 32:13

ሁለት መቶ
200 (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

ሃያ .... ሠላሣ .... አርባ ... አሥር
20 .... 30 .... 40 ....10 (ቁጥሮች ይመልከቱ)

ግልገሎች
እየጠቡ ያሉ ለጋ እንስሳት

እነዚህንም መንጐች በየወገኑ ከፍሎ በባሪያዎች እጅ አደረጋቸው
እዚህ “በእነሱ እጅ” በእነሱ ቁጥጥር ሥር አደረገ ማለት ነው:: አት በየወገኑ ከፈለቸው እናም እያንዳንዱን መንጋ በእያንዳንዱ ባሪያ ቁጥጥር ሥር አደረገ (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

መንጋውንና መንጋውን አራርቁት
አንዱ መንጋ ከሌላው መንጋ በርቀት እንዲጓዝ አድረጉ

Genesis 32:17

መመሪያ ሰጠው
አዘዘው

በፊትህ ያለው... የማን ነው? ብሎ የጠየቀህ እነደሆነ
ይህ በጥቅስ ውስጥ ያለ ጥቅስ ነው እንደ ተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “የማን ነህ? ወዴትስ ተሄዳለህ? የምትነዳውስ ይህ ሁሉ ከብት የማን ነው? ብሎ ቢጠይቅህ” (ጥቅስ በጥቅስ ውስጥ እና ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅሶች ይመልከቱ)

የማን ነህ?
ጌታህ ማን ነው?

በፊትህ ያለው ይህ ሁሉ ከብት የማን ነው?
በፊትህ ያለው የዚህ ሁለ ከብት ባለቤት ማን ነው?

በዚያን ጊዜ አንተ ለጌታዬ ለዔሣው እጅ መንሻ የሰደደው የባሪያህ የያዕቆብ ነው እርሱም ደግሞ ከኋላችን እየመጣ ነው፤ በለው
ይህ በጥቅስ ውስጥ የሚገኝ ጥቅስ ነው በተዘዋዋሪ ጥቅስ መልክ ሊገለጽ ይችላል፤ አት፤ “በዚያን ጊዜ እነዚህ ሁሉ የአገልጋይህ የያዕቆብ ናቸው፤ ለጌታዬ ለዔሣው እጅ መንሻ የሰደዳቸው ናቸው፤ እርሱም ሊገናኝህ ከበስተኋላችን እየመጣ ነው፤ ብለህ እንዲትነግረው እፈልጋለሁ::” (ጥቅስ በጥቅስ ውስጥ እና ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅሶች ይመልከቱ)

የአገልጋይህ የያዕቆብ ናቸው
የዕቆብ ራሱን ትህትናን በተሞላ መንገድ የዔሣው ባሪያ አድርጐ ያቀርባል

ለጌታዬ ለዔሣው
ያዕቆብ በትህትና ዔሣውን እንደ ጌታው መቁጠሩን ያመለክታል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከእኛ ኋላችን እየመጣ ነው
እኛ የሚናገረውን ባሪያ ያመለክታል እናም ሌሎች ባሪያዎችም ለዔሣው እጅ መንሻ ይዘው እየመጡ እንዳለ ይገለጻል (ብዙና ነጠላ “እኛ” ይመልከቱ)

Genesis 32:19

ለሁለተኛው ቡድን መመሪያ ሰጠ
ሁለተኛውን ቡድን አዘዘ

ይህኑን ትነግሩታላችሁ ባሪያህ ያዕቆብ
አማራጭ ተገቢ ትርጉሞች 1) “ደግሞም እንዲህ ትነግሩታላችሁ ባሪያህ ያዕቆብ” 2) “ደግሞም እንዲህ ትላላችሁ ባሪያህ ያዕቆብ”

አስደስት ይሆናል
አረጋጋው ይሆናል ወይም ቁጣው እንዲርቅ አደርግ ይሆናል

ይቀበለኛል
በርኀራኄ ይቀበለኛል

የያዕቆብ እጅ መንሻ ከእርሱ አስቀድሞ ተላከ
እዚህ እጅ መንሻ እጅ መንሻውን ይዘው የሄዱ ባሪያዎች ይወክላል (ምትክ አባባሎችን የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

እርሱ ራሱ ግን እዚያው አደረ
እዚህ “ራሱ” ያዕቆብ ከባሪያዎቹ ጋር እንዳለሄደ አበክሮ ይናገራል (ተጣቃሽ ተውላጤ ስም ይመልከቱ)

Genesis 32:22

ሁለት ሴት ባሪያዎቹ/አገልጋዮቹ
ሁለት ባሪያ/አገልጋይ ሚስቶቹ፤ ዘለፋና ባላ ማለት ነው

የወንዝ መልካ
በወንዝ ጥልቅ ያልሆነ በቀላሉ የሚያሻግር ቦታ

ያቦቅ
ይህ የወንዝ ስም ነው ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ይመልከቱ

ንብረቱን ሁሉ
ያለውን ነገር ሁሉ

Genesis 32:24

እስኪነጋ
ንጋት ድረስ

የጭኑ ሹልዳ ሲታገለው ደነዘዘ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ልገለጽ ይችላል፤ አት: “በሚታገልበት ጊዜ የሚታገለው ሰው የያዕቆብን ሹልዳ ጐዳው” (ተሻጋሪ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ጭን
ከዳሌ ጋር የተያያዘ ላይኛው የእግር አካል ነው

ሊነጋ ሲል
ጸሐይ ከመውጣትዋ በፊት

መባረክ
በአንድ ሰው ላይ በረከትን ማዘዝና ለዚያ ሰው መልካም ነገር እንዲሆኑለት ማድረግ ነው

ካልባረክሄኝ አልለቅህም
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ልገለጽ ይችላል፤ አት: “በእርግጥ አልለቅህም መጀመሪያ ባርከኝና ከዚያም እለቅሃለሁ” (ተሻጋሪ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ) (ድርብ አሉታዊ አባባሎች ይመልከቱ)

Genesis 32:27

እስራኤል
ተርጓሚዎች የግርጌ መስታወሻ እንደሚከተለው ሊጨምሩ ይችላሉ እስራኤል የሚለው ስም ከእግዚአብሔር ጋር ይታገላል ማለት ነው ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ

ሰዎች
ሰዎችን በገሃድ የሚገልጽ ነው

Genesis 32:29

እርሱም ስሜን ለምን ትጠይቃለህ? አለው
እርሱም ስለ ስሜ ለምን ተቀጠይቃለህ አለው ይህ አግናኝ ጥያቄ ያዕቆብን የሚያደነግጠው የሚገሥጸውና በእርሱና ከእርሱ ጋር ሲታገል በቆየው ሰው መካከል ምን እንደተከሰተ እንዲያስብ የሚያደርገው ነው:: አት: “ስሜን አትጠይቅ” (አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

ጵንኤል
ተርጓሚዎች የግርጌ መስታወሻ እንደሚከተለው ሊጨምሩ ይችላሉ:: “ጵንኤል” የሚለው ስም “የእግዚአብሔር ፊት” ማለት ነው:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)።

ፊት ለፊት
“ፊት ለፊት” ሁለት ሰዎች በቅርበት በአካል የሚተያዩበት ማለት ነው::

ሕይወቴ ተርፋለች
ይህ በሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አት ሕይወቴን አትርፎአታል:: (ተሻጋሪ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Genesis 32:31

ከዚህም የተነሣ እስከ ዛሬ ድረስ
ይህ ታሪኩ ወደ እስራኤል ዘር ዳራ ትረካ እንተለወጠ አመላካች ነው (የዳራ መረጃ ይመልከቱ)

የጭኑ ሹልዳ
ሹልዳን ከጭኑ ጋር የሚያገናኝ የጡንቻ ሥጋ ያመለክታል

ተነክቶ ነበር
ሲታገል ተነክቶ ነበር

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 33

1 ያዕቆብ አሻግሮ ተመለከተ፤ እነሆ፣ ዔሳው አራት መቶ ሰዎች አስከትሎ እየመጣ ነበር። ስለዚህ ያዕቆብ ልጆቹን ለልያ ለራሔልና ለሁለቱ አገልጋዮቹ አከፋፈላቸው። **2** ከዚያም ሁለቱን አገልጋዮች ከነልጆቻቸው አስቀደመ፤ ልያንና ልጆቿንም አስከተለ፤ ራሔልንና ዮሴፍን ግን ከሁሉ ኋላ እንዲሆኑ አደረገ። **3** እርሱ ራሱም ቀድሞአቸው ሄደ፤ ወንድሙም ዘንድ እስኪደርስ ድረስ ሰባት ጊዜ ወደ መሬት ለጥ ብሎ እጅ ነሣ። **4** ዔሳው ግን ሊገናኘው ወደ እርሱ ሮጦ ሄዶ አቀፈው፤ በአንገቱም ላይ ተጠምጥሞ ሳመው፤ ሁለቱም ተላቀሱ። **5** ከዚያም ዔሳው ቀና ብሎ ሲመለከት ሴቶቹንና ልጆቹን ዐየ፤ እርሱም፣ “እነዚህ አብረውህ ያሉ እነማን ናቸው?” ብሎ ጠየቀው። ያዕቆብም መልሶ፣ “እነዚህማ እግዚአብሔር በቸርነቱ ለእኔ ለአገልጋይህ የሰጠኝ ልጆች ናቸው” አለው። **6** በዚህ ጊዜ ሁለቱ ሴት አገልጋዮችና ልጆቻቸው ቀርበው እጅ ነሡ፤ **7** ከዚያም ልያና ልጆቿ መጥተው እጅ ነሡ፤ በመጨረሻም ዮሴፍና ራሔል መጡ፤ እነርሱም ቀርበው እጅ ነሡ። **8** ዔሳውም፣ “ወደ እኔ ተነድቶ የመጣው ይህ ሁሉ መንጋ ምንድነው?” አለው። ያዕቆብም፣ “ጌታዬ ሆይ፣ በአንተ ዘንድ ሞገስ ባገኝ ብዬ ነው” አለው። **9** ዔሳው ግን፣ “ወንድሜ ሆይ፤ እኔ በቂ አለኝ፤ የራስህን ለራስህ አድርገው” አለው። **10** ያዕቆብም፣ “የለም፣ እንዲህ አይደለም፤ በአንተ ዘንድ ሞገስ አግኝቼ እንደሆነ፣ እጅ መንሻዬን ተቀበል፤ በመልካም ሁኔታ ተቀብለኸኝ ፊትህን ማየት መቻሌ ራሱ፣ የእግዚአብሔርን ፊት የማየት ያህል እቆጥረዋለሁ። **11** እግዚአብሔር በቸርነቱ አሟልቶ ስለ ሰጠኝ የሚያስፈልገኝ ሁሉ አለኝና ያቀረብሁልህን እጅ መንሻ እባክህ ተቀበለኝ” አለው። ያዕቆብ አጥብቆ ስለለመነው፣ ዔሳው እጅ መንሻውን ተቀበለ። **12** ዔሳውም፣ “እንግዲህ እንሂድ፤ እኔም ከአንተ ቀድሜ እሄዳለሁ” አለው። **13** ያዕቆብ ግን እንዲህ አለው፤ “ጌታዬ እንደምታየው ልጆቹ ይህን ያህል የጠኑ አይደሉም፣ ለሚያጠቡት በጎችና ጥጎቶች እንክብካቤ ማድረግ አለብኝ፤ እንስሳቱ ለአንዲት ቀን እንኳ በጥድፊያ ቢነዱ በሙሉ ያልቃሉ። **14** ስለዚህ ጌታዬ፣ አንተ ቀድመኸኝ ሂድ፤ እኔም በምነዳቸው እንስሳትና በልጆቹ ጉዞ አቅም ልክ እያዘገምሁ ሴይር ላይ እንገናኛለን” **15** ዔሳው፣ “እንግዲያስ ከሰዎቼ ጥቂቶቹን ልተውልህ” አለው። ያዕቆብ ግን፣ “ለምን ብለህ? በአንተ ዘንድ ሞገስ ማግኘቴ ይበቃኛል” አለው። **16** ስለዚህ ዔሳው በዚሁ ዕለት ወደ ሴይር ለመመለስ ተነሣ። **17** ያዕቆብ ግን ወደ ሱኮት ሄደ፤ እዚያም ለራሱ መጠለያ፣ ለከብቶቹም በረት ሠራ፤ ከዚህም የተነሣ የቦታው ስም ሱኮት ተባለ። **18** ያዕቆብ ከመስጴጦምያ በተመለሰ ጊዜ በከነዓን ምድር ወዳለችው ወደ ሴኬም በሰላም ደረሰ፤ በከተማይቱም ፊት ለፊት ሰፈረ። **19** ድንኳኑን የተከለበትንም ቦታ የሴኬም አባት ከነበረው ከኤሞር በመቶ ጥሬ ብር ገዛው፤ **20** በዚያም መሠዊያ አቁሞ፤ ኤል ኤሎሄ እስራኤል ብሎ ጠራው።

Genesis 33:1

እነሆ
“እነሆ” የሚለው ቃል ለሚያስደንቀው ለታሪኩ አድስ ክፍል ትኩረት እንዲንስጥ ያደርጋል

አራት መቶ ሰዎች
400 ሰዎች (ቁጥሮች ይመልከቱ)

ያዕቆብ ልጆቹን ..... ለሴት አገልጋዮች አከፋፈላቸው
ይህ እያንዳንዷ ሴት ተመሣሣይ ቁጥር ልጆች እንዲኖራት ያዕቆብ ልጆቹን አከፈላቸው ማለት አይደለም እያንዳንዱ ልጅ ከእናቱ ወይም ከእናትዋ ጋር የሆን ዘንድ ያዕቆብ ለጆቹን አከፋፈላቸው (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ሴት አገልጋዮች
“አገልጋይ ሚስቶች” ዘለፋንና ባላን ያመለክታል

እርሱ ራሱ ቀድሞአቸው ሄደ
እዚህ ራሱ የሚለው ያዕቆብ ራሱ በሌሎች ፊት ቀድሞ እንደሄደ ትኩረት ይሰጣል (ተጣቃሽ ተውላጤ ስም ይመልከቱ)

ጐንበስ ብሎ እጅ ነሣ
ጐንበስ ማለት አንድን ሰው በትህትና መቀበልንና ማክበርን ይገልጻል (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

Genesis 33:4

ሊገናኘው
ያዕቆብን ሊገናኝ

ዐቀፈው በአንገቱም ላይ ተጠምጥሞ ሳመው
ይህ እንደ አዲስ ዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል:: አት: “ዔሣው በያዕቆብ ላይ እጆቹን ጠምጥሞ አቀፈው እናም ሳመው”

ከዚያም ሁለቱ አለቀሱ
ይህ በግልጽ ሊተረጐም ይችላል:: አት: “ከዚያም እንደገና በመተያየታቸው ተደስተው ዔሣው ያዕቆብ አለቀሱ” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ሴቶቹንና ልጆቹን አየ
ከያዕቆብ ጋር ያሉ ሴቶቹንና ልጆቹን አየ

እነዚህማ እግዚአብሔር በቸርነቱ ለእኔ ለአገልጋይህ የሰጠኝ ልጆች ናቸው
የአንተ አገልጋይ የሚለው ሀረግ ያዕቆብ ራሱን በትህትና ያቀረበው መንገድ ነው:: አት: “እነዚህ እግዚአብሔር በቸርነቱ ለአገልጋይህ የሰጠኝ ልጆች ናቸው” (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

Genesis 33:6

አገልጋይ ሴቶች
ሴት አገልጋዮች:: ባላንና ዘለፋን ያመለክታል::

ጐንበስ አለ
በሌላ ሰው ፊት ትህትናንና አክብሮትን የሚያሳይ ምልክት ነው:: (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

ወደ እኔ ተነድቶ የመጣው ይህ ሁሉ መንጋ ምንድን ነው?
“ይህ ሁሉ” የሚለው ሀረግ ያዕቆብ በየቡድኑ በባሪያዎች ለዔሣው የላከውን ስጦታዎች ያመለክታል:: አት: “እነኛ የተለያዩ ቡድኖች ሁሉ እንዲገናኙኝ ለምን ላክሃቸው?”

በጌታዬ ፊት ሞገስ ባገኝ ብዬ ነው
ሞገስ ማግኘት የሚለው ሀረግ በአንድ ሰው ተቀባይነትን ማረጋገጥ የሚል ትረጉም የያዘ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው እንዲሁም ደግሞ ፊት ፍርድን ወይም ግማገማን ይወክላል አት አንተ ጌታዬ እንዲትደሰትብኝ ነው (ፈሊጣዊና ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ጌታዬ
ጌታዬ ዔሣው በትህት መንገድ ዔሣው የተገለጸበት ነው:: (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Genesis 33:9

እኔ በቂ አለኝ
እንስሳት ወይም ንብረት የታወቁ ቃላት ናቸው:: አት: “በቂ እንስሳት አለኝ ወይም በቂ ንብረት አለኝ” (ድብቅ አገላለጽ ይመልከቱ)

በአንተ ዘንድ ሞገስ አግኝቼ እንደሆነ
ሞገስ ማግኘት የሚለው ሀረግ በአንድ ሰው ተቀባይነትን ሰለማኘት የሚገልጽ ፈሊጣዊ አባባል ነው እዚህ ዓይን የማየት ምትክ ቃል ሲሆን ማየት ግምገማውን የሚገልጽ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው:: አት: “በእኔ የተደሰትህ እንደሆነ” (ተመሣሣይ ምትክ ቃላት የሊጣዊና ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

እጅ መንሻዬ
“እጅ” ያዕቆብን ያመለክታል አት ይህ ለአንተ የሚሰጠው እጅ መንሻዬ ነው (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

በውኑ እጅ መንሻዬ
እንደ አድስ ዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል። አት፡ “በእርግጥም እጅ መንሻዬ”

የእግዚአብሔርን ፊት እንደሚያይ ፊትህን አይቼአለሁና
ይህ ተመሣሣይ አባባል ግልጽ አይደለም ተገቢ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው 1 እግዚአብሔር ይቅር እንዳለለት ዔሣውም ይቅር እንዳለው ያዕቆብ ደስተኛ ነው ወይም 2 ያዕቆብ እግዚአብሔርን በመገናኘቱ እንደተደነቀው ሁሉ ዔሳውን በመገናኘቱ ተደንቆአል 3 ያዕቆብ በእግዚአብሔር መገኘት ራሱን እንዳዋረደው ሁሉ በዔሣው ፊት ራሱን ያዋርዳል (ተመሣሣይ አባባሎችን ይመልከቱ)

ፊትህን አይቻለሁ
እዚህ ፊት ዔሣውን ያመለክታል ይህ ፊት በመባል ሊተረጐም ይችላል፤ ምክንያቱም “ፊት” የሚለው ቃል በዘፍጥረት 32:30 “የእግዚአብሔር ፊት” እና “ፊት ለፊት” ለመግለጽ ተጠቅሞአል (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ይህችንም ያመጣሁልህ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “ይህም አገልጋዮቼ ያመጡልህ” (ተሻጋሪና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

እግዚአብሔር በቸርነቱ አሟልቶ ስለሰጠኝ
እግዚአብሔር በቸርነቱ ስለመለከተኝ ወይም እግዚአብሔር እጅግ በጣም ስለባረከኝ

ያዕቆብም አጥብቆ ስለለመነው ዔሣው እጅ መንሻውን ተቀበለ
አንድን ሥጦታ ላለመቀበል መገዳደር ነገር ግን ከዚያ በኋላ ሰጪው እንዳያዝን መቀበል የተለመደ ባህላዊ መንገድ ነው

Genesis 33:12

ጌታዬ ያውቃል
ይህ በትህትናና በመደበኛ መንገድ ዔሣውን ማመልከት ነው:: አት: “አንተ ጌታዬ ታውቃለህ” (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

ልጆች የጠኑ አይደሉም
ትርጉሙም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አት፡ “በፍጥነት ለመጓዝ ልጆች ገና የጠኑ አይደሉም”:: (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይጠቀሙ)

አንዲት ቀን እንኳ በጥድፍያ ቢነዱ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “ለአንድ ቀን እንኳ በፍጥነት እንዲጓዙ ቢናጣድፋቸው” (ተሻጋሪና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ጌታዬ ከባሪያው ቀድሞ ይሂድ
ይህ ያዕቆብ ራሱን በመደበኛና በትህትና መንገድ የሚገልጸው ነው:: አት: “ጌታዬ እኔ ባሪያህ ነኝ” (ከፊቴ ቀድመህ ሂድ አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

በሚነዱአቸው እንስሳት እርምጃ ልክ
“በሚነዱአቸው እንስሳት እርምጃ ፍጥነት መጠን”

ሴይር
በኤዶም ግዛት የሚገኝ ተራራማ ሥፍራ ነው። በዘፍጥረት 32 3 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ። (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)

Genesis 33:15

ለምንድር ነው?
ዔሣው ሰዎቹን መተው እንደሌለበት ለማጽናት ያዕቆብ ጥያቄን ይጠቀማል:: አት: “ይህን አታድርገው” ወይም “ይህን ማድረግ አይገባህም” (አግናኝ ጥያቄዎች ይመልከቱ)

ጌታዬ
ይህ በመደበኛና በትህትና ዔሣውን የሚግለጽ ነው:: አት: “አንተ ጌታዬ” (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

ሱኮት
ተርጓሚዎች እንደግርጌ ማስታወሻ ሊጨምሩ ይችላሉ ሱኮት የሚለው ስም መጠለያዎች ማለት ነው ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ

ለራሱ ቤትን ወይም መጠለያን ሠራ
ይህ የተሠራው ቤት ለቤተሰቡም እንደሆነ ያመለክታል። አት: “ለራሱና ለቤተሰቡ ቤት ሠራ” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ለመንጋው
ለሚጠብቁአቸው እንስሳት

Genesis 33:18

አጠቃላይ መረጃ
ይህ አድስ የታሪኩን አካል ይጀምራል በሱኮት ካረፈ በኋላ ያዕቆብ ምን እንዳደረገ ጸሓፊው ይገልጻል

ያዕቆብ ወደ ጳዳን አራም በመጣ ጊዜ
ያዕቆብ ..... ደረሰ ..... ሠፈረ

ይህ ያዕቆብ የቤሰቡ መሪ ስለሆነ እርሱን ብቻ ይጠቅሳል::
የእርሱም ቤተሰብ ከእርሱ ጋር እንደነበር ግልጽ ነው (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

አጠገብ ሠፈረ
በቅርበት ሠፈረ

ከፊል መሬት
ከፊል ቦታ

ኤሞር
የአንድ ሰው ስም ነው

የሴኬም አባት
ሴኬም የሰውዬውና የከተማይቱ ስም ነው

አንድ መቶ
100 (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ኤል ኤሎሄ እስራኤል
ተርጓሚዎች የግርጌ ማስታወሻ እንደሚከተለው ሊጨምሩ ይችላሉ አት ኤል
ኤሎሄ የሚለው ቃል እግዚአብሔር የእስራኤል አምላክ ማለት ነው (ስሞችን
ስለመተርጎም ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 34

1 ልያ ለያዕቆብ የወለደችለት ሴት ልጅ ዲና፤ አንድ ቀን የዚያን አገር ሴቶች ለማየት ወጣች። 2 የአገሩ ገዥ የኤዊያዊ የኤሞር ልጅ ሴኬም ባያት ጊዜ ያዛት
በማስገደድም ክብረ ንጽሕናዋን ደፈረ። 3 ልቡ በያዕቆብ ልጅ በዲና ተማረከ፤ ልጅቷንም በጣም ወደዳት፤ በጣፈጠም አንደበት አናገራት። 4 ሴኬምም አባቱን
ኤሞርን፣ “ይህችን ልጅ አጋባኝ” አለው። 5 ያዕቆብ የልጁን የዲናን ክብረ-ንጽሕና ሴኬም እንደደፈረ ሰማ፤ ነገር ግን ወንዶች ልጆቹ የከብት መንጋ ይዘው
ተሰማርተው ስለነበር፣ እነርሱ እስኪመጡ ዝም ብሎ ቆየ፤ 6 ከዚያም የሴኬም አባት ኤሞር፣ ያዕቆብን ሊያነጋግረው ወጣ። 7 የያዕቆብ ወንዶች ልጆችም
የተፈጸመውን ድርጊት እንደሰሙ ወዲያውኑ ከመስክ መጡ፤ ሴኬም መደረግ የማይገባውን አስነዋሪ ነገር በእስራኤል ላይ በመፈጸም የያዕቆብን ልጅ ስለደፈረ
አዘኑ እጅግም ተቆጡ። 8 ኤሞር ግን እንዲህ አላቸው፤ “ልጄ ሴኬም ልጃችሁን በጣም ወዶአታል፤ ስለዚህ እንዲያገባት ፍቀዱለት፤ 9 በጋብቻ እንተሳሰር፣ ሴት
ልጃችህን ስጡን፣ የእኛንም ሴቶች አግቡ። 10 አብራችሁንም መኖት ትችላላችሁ፤ አገራችን አገራችሁ ናት፣ ኑሩባት፤ ነግዱባት፣ ሀብት ንብረትም አፍሩባት። 11
ሴኬም ደግሞ የዲናን አባትን ወንድሞች እንዲህ አላቸው። “በእናንተ ዘንድ ሞገስ ላግኝ እንጂ የተጠየቅሁትን ሁሉ እሰጣለሁ፤ 12 ለሙሽራዋም ጥሎሽ
የፈለጋችሁትን ያህል ጠይቁኝ፤ እርሷን እንዳገባ ፍቀዱልኝ እንጂ፣ የፈለጋችሁትን ሁሉ ለመጠት ዝግጁ ነኝ።” 13 ሴኬም እኅታቸውን ዲናን አስነውሮ ስለነበር
የያዕቆብ ልጆች ለእርሱና ለአባቱ በተንኮል እንዲህ ሲሉ መለሱላቸው፣ 14 እንዲህ አሉአቸው፤ “እኅታችንን ላልተገረዘ ሰው ብንሰጥ ውርደት ስለሚሆንብን፣
እንዲህ ያለውን ነገር አናደርገውም። 15 ሆኖም የምንስማማበት አንድ መንገድ ብቻ አለ፤ ይኸውም አንተና በእናንተ ዘንድ ያሉት ወንዶች ሁሉ እንደኛ የተገረዛችሁ
እንደሆነ ነው። 16 እንዲህ ከሆነ እናንተ የእኛን ሴቶች ልጆች ታገባላችሁ፣ እኛም የእናንተን ሴቶች ልጆች እናገባለን፣ አንድ ሕዝብ ሆነንም አብረን እንኖራለን። 17
ዐሳባችንን ባትቀበሉና ባትገረዙ ግን እኅታችንን ይዘን እንሄዳለን። 18 ያቀረቡትም ዐሳብ ለኤሞርና ለልጁ ለሴኬም መልካም መስሎ ታያቸው። 19 ከአባቱ
ቤተሰብ ሁሉ እጅግ የተከበረው ይህ ወጣት የያዕቆብን ልጅ እጅግ ወዶአት ስለነበር፣ ያሉትን ለማድረግ ጊዜ አልወሰደበትም። 20 ስለዚህ ኤሞርና ልጁ ሴኬም
ይህንኑ ለወገኖቻቸው ለመንገር ወደ ከተማቸው በር ሄዱ፤ 21 እንዲህም አሏቸው፤ “እነዚህ ሰዎች ከእኛ ጋር የሚኖሩት በሰላም ነው፣ በምድሪቱ ላይ አብረው
ይቀመጡ፣ ተዘዋውረውም እንዲነግዱ እንፍቀድላቸው፤ ምድሪቱ እንደሆን ለእኛም ለእነርሱም ትበቃለች። ሴቶች ልጆቻቸውን እናገባለን፤ እነርሱም የእኛን ሴቶች
ልጆች ያገባሉ፤ 22 ሆኖም ሰዎቹ ከእኛ ጋር እንደ አንድ ሕዝብ ሆነው አብረውን ለምኖር ፈቃደኞች የሚሆኑት፣ የእኛ ወንዶች እንደ እነርሱ የተገረዙ እንደሆነ ብቻ
ነው። 23 ታዲያ እንዲህ ብናደርግ ከብታቸው ንብረታቸው፣ እንስሶቻቸውም ሁሉ የእኛው ይሆኑ የለምን? ስለዚህ ባሉት እንስማማ፣ እነርሱም አብረውን ይኑሩ።”
24 የከተማይቱ ነዋሪዎች ሁሉ ኤሞርና ሴኬም ባቀረቡት ዐሳብ ተስማምተው ወንዶቹ ሁሉ ተገረዙ። 25 በሦስተኛውም ቀን የሁሉም ቁስል ገና ትኩስ ሳለ
ከያዕቆብ ልጆች ሁለቱ፣ የዲና ወንድሞች ስምዖንና ሌዊ፣ ሰይፋቸውን መዘው ሳይታሰብ ወደ ከተማይቱ ገብተው ወንዶቹን በሙሉ ገደሏቸው። 26 ኤሞርንና
ሴኬምንም በሰይፍ ገድለው፣ እኅታቸውን ዲናን ከሴኬም ቤት አውጥተው ይዘዋት ተመለሱ። 27 የቀሩትም የያዕቆብ ልጆች እኅታቸውን ስለደፈሩባቸው ወደ
ሞቱት ሰዎች ቤት እየገቡ ከተማይቱን በሙሉ ዘረፉ። 28 የበግና የፍየል መንጎቻቸውን፣ ከብቶቻቸውንና አህዮቻቸውን እንዲሁም በከተማይቱና በአካባቢው
የሚገኘውን ንብረታቸውን ሁሉ ወሰዱባቸው፤ 29 ሀብታቸውን ሁሉ ዘርፈው ሴቶቻቸውንና ሕፃናቶቻቸውን ሁሉ ማርከው በየቤቱ ያገኙትን ሁሉ ይዘው ሄዱ። 30
ያዕቆብ ስምዖንና ሌዊን እንዲህ አላቸው፤ “በእኔ ላይ ከባድ ችግር አመጣችሁብኝ፤ እነሆ፣ በዚህ ድርጊት የተነሣ በዚህች ምድር የሚኖሩ ከነዓናውያንና
ፌርዛውያን ይጠሉኛል፤ እኛ በቁጥር አነስተኞች ነን፣ እነርሱ ተባብረው ቢያጠቁን እኔና ቤተሰቤ እንጠፋለን።” 31 ስምዖንና ሌዊ ግን፣ “ታዲያ ሴኬም እኅታችንን
እንደዝሙት አዳሪ ይድፈራትን?” አሉት።

Genesis 34:1

አሁንም
በዚህ ይህ ቃል የታሪኩን አድስ ክፍል ለማመልከት ተጠቅሞአል።

ዲና
የልያ ሴት ልጅ ነች በዘፍጥረት 30:21 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ኤዊያዊ
ይህ የብሔር ስም ነው:: በዘፍጥረት 10:17 ኤዊያዊያን የሚለውን ቃል እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

የአገሩ ገዢ
ይህ ሴኬምን ሳይሆን ኤምርን ያመለክታል በዚህ ቦታ ገዢ የንጉሥ ልጅ ማለት አይደለም ይህም ኤሞር በዚያ ለሚኖሩ ሰዎች መሪ እንደነበር ነው

አስነወራት ከእርስዋም ጋር ተኛ
ሴኬም ዲናን ደፈራት (ንኅብነት ወይም ለዛ ባለ ቃል ወይም በተዘዋዋሪ አንድን ነገር የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ወደ ዲና ተሳበ
“በዲና ተማረከ” ዲናን እንደወደዳትና ከእርስዋ ጋር ለመሆን አንድ ነገር ወደ ዲና እንዲመጣ እንዳስገደደው ስለ ሴኬም ይናገራል ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “ከዲና ጋር ለመሆን እጅግ በጣም ፈልጐአል” (ዘይቤያዊ አነጋገር ወይም ተሻጋሪ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

በጣፈጠ አንደበት አናገራት
እንደሚወዳትና እንዲትወደው ለማድረግ ሊያሳምናት በሚስብ መንገድ አናገራት ማለት ነው

Genesis 34:4

አሁንም ያዕቆብ
“አሁን” የተጠቀመው ከታሪኩ ወደ ያዕቆብ ዳራ መረጃ ለውጥ ማድረግን ለማመልከት ነው

ያዕቆብም ... እርሱ ... ሰማ
“እርሱ” የሚለው ቃል ሴኬምን ያመለክታል

አስነወራት
ሰኬም በጉልበት ከእርስዋ ጋር በመተኛት ዲናን እጅግ በጣም አዋረዳት ክብርዋን ነፈጋት ማለት ነው

ታግሶ ቆዬ
ያዕቆብ ስለ ጉዳዩ ምንም አላደረገም ወይም አልተናገረም ማለት ነው:: (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Genesis 34:6

ኤሞር ያዕቆብን ሊያነጋግረው ወጣ
ኤሞር ያዕቆብን ሊያነግረው ሄደ

የያዕቆብ ወንዶች ልጆች አዘኑ
ወንዶች ልጆች እጅግም ተቆጡ ወይም ደነገጡ

እስራኤልን አስነወረ
እዚህ እስራኤል የሚለው ቃል እያንዳንዱን የእስራኤል ቤተሰብ አባል ያመለክታል እስራኤል እንደብሔር ተደፍሮአል:: አት: “የእስራኤልን ቤት አዋርዶአል” ወይም “የእስራኤልን ስዎች አሳፍሮአል” (ክፍልን እንደሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘጥቤ ይመልከቱ)

የያዕቆብን ሴት ልጅ ስለደፈረ
የያዕቆብን ልጅ ስለደፈራት

ይህ ዓይነት ተግባር መደረግ አይገባውም
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “እንደዚህ አስነዋሪ ነገር ማድረግ አይገባውም ነበር” (ተሻጋሪ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Genesis 34:8

ኤሞርም እንዲህ ብሎ ነገራቸው
ኤሞር ለያዕቆብና ለልጆቹ እንዲህ ብሎ ነገራቸው

በልጃችሁ ፍቅር ተነድፎአል
ፍቅር የሚለው ቃል በአንድ ወንድና ሴት መካከል የሚሆን ስሜታዊ ፍቅር ነው አት ወድዶአታልና ሊያገባት ይፈልጋል

ሚስት እንዲትሆነው እርሷን ስጡት
በአንዳንድ ባህሎች ልጆች ማግባት ያለባቸውን ወላጆች ይወስናሉ

በጋብቻ እንተሳሰር
በጋብቻ መተሣሠር ከሌላ ዘር ብሔር ባህልና ጐሣ ሰዎች ጋር መጋባት ማለት ነው:: አት: “በአናንተና በእኛ ሰዎች መጋባትን እንፍቀድ”

ምድሪቱ በእናንተ ፊት ናት
ምድሪቱ የእናንም ናት

Genesis 34:11

ሴኬም ደግሞ አባትዋን እንዲህ አለ
ሴኬም የዲናን አባት ያዕቆብን እንዲህ አለ

በእናንት ፊት ሞገስ ላግኝ እንጂ የጠየቅሁትን ሁሉ እሰጣለሁ
“ሞገስ ማግኘት” የሚለው ሀረግ በአንድ ሰው ተቀባይነትን ማረጋገጥ የሚናገር ዘይቤያዊ አነጋገር ነው ደግሞም ዓይኖች ማየትን ሲወክሉ ማየት ሀሳብን ወይም ፍረጃን ያመለክታሉ:: አት: “እንደተቀበላችሁን ካረጋገጥሁ የሚትጠይቁኝን ሁሉ እሰጣለሁ”:: (ፈሊጣዊና ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ጥሎሽ
በአንዳንድ ባህሎች በጋብቻ ጊዜ ለሙሽሪቱ ቤተሰብ ሙሽራው በገንዘብ በንብረት በእንስሳትና በሌላም መልክ ስጦታ መስጠት የተለመደ ነው

የያዕቆብ ወንዶች ልጆችም ለሴኬምና ለኤሞር የሚያታልል መልስ ሰጡ
ማታለል የሚለው ረቂቅ ስም መዋሸት እንደሚለው ግሥ ሊገለጽ ይችላል:: ነገር ግን የያዕቆብ ወንዶች ልጆች ለሴኬምና ለኤሞር በመለሱአቸው ጊዜ ዋሹአቸው (ረቂቅ ስሞችን ይመልከቱ)

ሴኬም ዲናን አስነውሮአታል
ከእርሱ ጋር እንዲትተኛ በመድፈሩ ሴኬም ዲናን እጅግ በጣም አዋርዶአታል አስነውሮአታል ማለት ነው:: በዘፍጥረት 34:5 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

Genesis 34:14

እነርሱም እንዲህ አሉአቸው
የያዕቆብ ወንድ ልጆች ለሴኬምና ለኤሞር እንዲህ አሉ

እኅታችንን ብንሰጥ እንዲህ ያለውን ነገር አናደርገውም
ዲናን በጋብቻ ሊንሰጥ አንስማማም

ይህም ለእኛ ውርዴት ነው
ይህም እኛን ያሳፍረናል:: እዚህ “እኛ” የያዕቆብን ወንዶች ልጆችንና የእስራኤልን ልጆች በአጠቃላይ ያመለክታል (የሚያካትትና የማያካትት እኛን ይመልከቱ)

ሴቶች ልጆቻችንን እንሰጣችኋለን የእናንተን ሴቶች ልጆች እንወስዳለን
ይህም ከያዕቆብ ቤተሰብ የሆነ ሰው በኤሞር ምድር የሚኖረውን ሰው ያገባል ማለት ነው

Genesis 34:18

ያቀረቡትም ሃሳብ ለኤሞርና ለልጁ ለሴኬም መልካም መስሎ ታየቸው
ኤሞርና ልጁ ሴኬም የያዕቆብ ወንዶች ልጆች ባቀረቡት ሃሳብ ተስማሙ

ያሉትን ለማድረግ
ለመገረዝ

የያዕቆብ ሴት ልጅ
የያዕቆብ ሴት ልጅ ዲና

ከአባቱ ቤተሰብ ሁሉ እጅግ የተከበረው
ይህ እንደ አዲስ ዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል:: እጅግ ስለሚያከብሩት ሌሎች ሰዎች ለመገረዝ እንደሚስማሙ ሴኬም እንደተረዳ ግልጽ ማድረግ ይቻላል:: አት: “እርሱ በእነርሱ ዘንድ የተከበረ በመሆኑ የአባቱ ቤተሰብ ወንዶች ሰዎች ሁሉ ለመገረዝ እንደሚስማሙ ሴኬም ያውቅ ነበር” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)::

Genesis 34:20

ወደ ከተማቸው በር
ሕጋዊ ውሳኔ ለመወሰን በከተሞች በር መሰባሰብ በመሪዎች የተለመደ ነው

እነዚህ ሰዎች
ያዕቆብ ወንዶች ልጆቹና የእስራኤል ሰዎች

በእኛ ዘንድ የሰላም ሰዎች
እዚህ “እኛ” ኤሞር ልጁንና የተናገሩአቸው በከተማው በር ያሉ ሰዎችን ሁሉ ያቀፈ ነው (ሁሉን ያቀፈ “እኛ” ይመልከቱ)

በምድራችን ይኑሩ ይነግዱበትም
በምድሪቱ ይኑሩ ይነግዱበትም

እነሆ ምድሪቱ በእርግጥ ሰፊ ናት
ለዐረፍተ ነገሩ ትኩረት ለመስጠት ሴኬም “በእርግጥ” የሚለውን ቃል ይጠቀማል:: “እነሆ ምድሪቱ በእርግጥ ለእነርሱም ሰፊ ናት” ወይም “እነሆ ለእነርሱ የሚበቃ በቂ መሬት አለ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሴት ልጆቻቸውን እንውሰድ ለእነርሱም ሴት ልጆቻችንን እንስጥ
ይህ በአንዱ ቡድን ሴቶች በሌላው ቡድን ወንዶች መካከል የሚፈጸሙ ጋብቻዎችን ያመለክታል። በዘፍጥረት 34:9 ተመሣሣይ ሀረጐችን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ።

Genesis 34:22

አጠቃላይ መረጃ
ኤሞርና ልጁ ሴኬም ለከተማዋ ሸማግሌዎች መናገራቸውን ቀጠሉ

አንድ ሕዝብ ሆነን ከእኛ ጋር ይቀመጡ ዘንድ በዚህ ነገር ብቻ እሺ ይሉናል እነርሱ እንደተገረዙ ወንዶቻችንን ሁሉ ብንገርዝ
ሰዎቹ ከእኛ ጋር እንደ አንድ ሕዝብ ሆነው አብረውን ለመኖር ፈቃደኞች የሚሆኑት የእኛ ወንዶች እንደ እነርሱ የተገረዙ እንደሆነ ብቻ ነው

ታዲያ እንዲህ ብናደርግ ከብቶቻቸው ንብረታቸው እንስሶቻቸው ሁሉ የእኛው ይሆኑ የለምን?
የያዕቆብ እንስሶችና ንብረቶች ለሴኬም ሰዎች እንደሚሆን ሴኬም ጥያቄ ምልክት በመጠቀም አበክሮ ይናገራል:: ይህ እንደዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል:: አት: “የእነርሱ እንስሳትና ንብረት ሁሉ ለእኛ ይሆናል” አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ::

Genesis 34:24

ወንዶች ሁሉ ተገረዙ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አት ስለዚህ ኤሞርና ሴኬም ወንዶችን ሁሉ የሚገርዙ ነበሩአቸው (ተሻጋሪና የማይሻገር ግሥ የያዘበት ዐረፍት ነገር ይመልከቱ)

በሶስተኛውም ቀን
ሶስት ተራ ቁጥር ሶስት ነው:: ያለ ተራ ቁጥር ሊነገር ይችላል:: አት: “ከሁለት ቀን በኋላ”

ሁሉም ቆስለው ሳሉ
የከተማው ወንዶች ቆስለው ሳሉ

እያንዳንዱ ሰይፉን መዝዘ
ሰይፋቸውን መዘው

ከተማዋን ወጉት
ከተማ ሰዎችን ይወክላል አት እነርሱ የከተማይቱን ሰዎች ተዋጉ (ተመሣሣይ ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

ጥበቃ፤ እናም ወንዶችን ሁሉ ገደሉ
ይህ እንደአዲስ ዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል:: አት: “ጥበቃ: ስምዖንና ሌዊ የከተማይቱን ወንዶች ሁሉ ገደሉ።”

Genesis 34:27

ሬሳዎች
የኤሞር የሴኬምና ወንዶች ስዎቻቸው ሬሳ

ከተማዋን ዘረፉ
በከተማይቱ ያለውን ጠቃሚ ነገር ሁሉ ወሰዱ

ሰዎች እህታቸውን ስላረከሱአት
ሴኬም ብቻውን ዲናን አርክሶአት ነበር ነገር ግን የያዕቆብ ልጆች የሴኬም መላው ቤተሰብና በከተማው ያለው ሁሉ ሰው ለዚህ ድርጊት ተጠያቂ አድርገው ቆጥረዋል

አረከሳት
ከእርሱ ጋር እንዲትተኛ በመድፈር ሴኬም ዲናን አዋረዳት ወይም ክብርዋን ነፈጋት/አሳፈራት ማለት ነው:: በዘፍጥረት 34: 5 አረከሳት እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ

መንጎቻቸውን ወሰዱ
የያዕቆብ ልጆች የሰዎችን መንጋ ወሰዱ

ሀብቶቻቸውን ሁሉ
ንብረታቸውንና ገንዘባቸውን ሁሉ ሕጻናቶቻቸውንና ሴቶቻቸውን ሁሉ ማረኩ

Genesis 34:30

አስጨነቃችሁኝ
ለአንድ ሰው የጭንቀት ምክንያት መሆን ጭንቀት በአንድ ሰው ላይ እንደሚመጣና እንደሚቀመጥ ዕቃ ተደርጐ ተገልጾአል አት: “ትልቅ ችግሮችን ፈጥራችሁብኛል” (ዜይቤያዊ አነጋገር ይጠቀሙ)

በዚህ አገር በሚኖሩ ዘንድ እንደጥንብ አስቆጠራችሁኝ
ያዕቆብ በዙሪያው በሚኖሩ ሰዎች ዘንድ እንዲጠላ ማድረግ የያዕቆብ ልጆች እርሱን እንደ መጥፎ ሽታ እንዳደረጉ ተገልጾአል ይህ እንደ አዲስ ዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል:: አት: “በምድሪቱ በሚኖሩ ዘንድ የተጠላሁ እንዲሆን አድርጋችሁኛል” (ዜይቤያዊ አነጋገር ይጠቀሙ)

እኔ በቁጥር አነስተኞች ነኝ ቢያጠቁኝ እኔንና ቤተሰቤን ያጠፋሉ
እዚህ “እኔ” እና “እኔን” የሚሉ ቃላት ያዕቆብን ቤተሰብ በአጠቃላይ ይወክላሉ:: ያዕቆብ የቤተሰቡ መሪ ከመሆኑ የተነሳ “እኔ” ወይም “እኔን” ይጠቀማል:: አት: “ቤተሰብ አነስተኛ ነው ... ተባብረው ቢነሡብኝና ቢያጠቁኝ ሁላችንንም ያጠፋሉ::” (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ተባብረ ይነሡና ያጠቁኛል
ሠራዊት ይፈጥሩና ያጠቁኛል ወይም ሠራዊት ይፈጥሩና ያጠቁናል

እኔም እጠፋለሁ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “ያጠፉኛል ወይም ያጠፉናል ተሻጋሪ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ”

ሴኬም በሴተኛ አዳሪ/በጋለሞታ እንደሚደረግ በእኅታችን ያደርግባትን?
ሴኬም ያደረገው ጥፋትና ሞት እንደሚገባው አበክረው ለመግለጽ ሌዊና ስምዖን ጥያቄ ይጠቀማሉ:: አት: “ሴኬም እህታችንን እንደ ሴተኛ አዳሪ/ጋለሞታ አድርጐ ባልቆጠረ ነበር!” (አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 35

1 እግዚአብሔር ያዕቆብን፣ “ተነሣና ወደ ቤቴል ሂድ፣ እዚያም ኑር። ከወንድምህ ከዔሳው ሸሽተህ በሄድህ ጊዜ ለተገለጠልህ አምላክ በዚያ መሠዊያ ሥራ አለው። **2** ስለዚህም ያዕቆብ ለቤቱ ሰዎችና አብረውት ለነበሩት ሁሉ እንዲህ አላቸው፤ “በእናንተ ዘንድ ያሉትን ባዕዳን አማልክት አስወግዱ፤ ሰውነታችሁን አንጹ፤ ልብሳችሁንም ለውጡ። **3** ተነሥተን ወደ ቤቴል እንሂድ፤ እዚያም በመከራዬ ጊዜ ለሰማኝ በሄድሁበትም ስፍራ ሁሉ ላልተለየኝ አምላክ መሠዊያ እሠራለሁ። **4** ስለዚህ በእነርሱ ዘንድ የነበሩትን ባዕዳን አማልክት ሰብስበው፣ የጆሮ ጉትቻቻቸውን አውልቀው ለያዕቆብ ሰጡት። ያዕቆብም ወስዶ ሴኬም አጠገብ ካለው ዋርካ ዛፍ ሥር ቀበራቸው። **5** ያንንም ቦታ ለቀው ሄዱ፤ እግዚአብሔርም በዙሪያቸው በነበሩት ከተሞች ሁሉ ላይ ፍርሃትና ድንጋጤ ስለለቀቀባቸው ያሳደዳቸው አልነበረም። **6** ያዕቆብና አብረውት የነበሩት ሰዎች ሁሉ በከነዓን ወደምትገኘው፣ ቤቴል ወደተባለችው ወደ ሎዛ ደረሱ። **7** ያዕቆብም በዚያ ስፍራ መሠዊያ ሠርቶ፣ ስሙን ኤል ቤቴል አለው፤ ምክንያቱም ከወንድሙ ሸሽቶ በሄደ ጊዜ እግዚአብሔር የተገለጠለት በዚህ ቦታ ነበር። **8** በዚህ ጊዜ የርብቃ ሞግዚት ዲቦራ ሞተች፣ ከቤቴል ዝቅ ብሎ በሚገኘው የዋርካ ዛፍ ሥር ተቀበረች። ከዚህ የተነሣም ያ ቦታ አሎንባኩት ተባለ። **9** ያዕቆብ ከመስጴጦምያ በተመለሰ ጊዜ እግዚአብሔር ዳግመኛ ተገለጠለትና ባረከው። **10** እግዚአብሔርም፣ “እስካሁን ስምህ ያዕቆብ ነበር፤ ከእንግዲህ ያዕቆብ ተብለህ አትጠራም፤ ነገር ግን ስምህ እስራኤል ይባላል” አለው። ስለዚህም እስራኤል ብሎ ጠራው። **11** ደግሞም እግዚአብሔር ያዕቆብን እንዲህ አለው፤ “እኔ ሁሉም ማድረግ የሚችል አምላክ ነኝ፤ ብዙ ልጆች ይኑሩህ፤ ዘርህም ይብዛ፤ የብዙ ሕዝብ አባት ሁን፤ ነገሥታትም ከአንተ ይወለዱ። **12** ለአብርሃምና ለይስሐቅ የሰጠኋትን ምድር ለአንተ እሰጣለሁ፤ ከአንተም በኋላ ይህችን ምድር ለዘርህ አሰጣለሁ።” **13** እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከተነጋገረ በኋላ ከዚያ ስፍራ ወደ ላይ ወጣ። **14** ያዕቆብ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር በተነጋገረበት ስፍራ የድንጋይ ሐውልት አቆመ፣ በሐውልቱ ላይ የመጠጥ ቁርባን አፈሰሰ፤ ዘይትም አፈሰሰበት። **15** ያዕቆብም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የተነጋገረበትን ስፍራ ቤቴል ብሎ ጠራው። **16** ከዚያም ከቤቴል ተነሥተው ሄዱ፤ ኤፍራታ ለመድረስ ጥቂት ሲቀራቸው ራሔልን ምጥ ያዛት፣ ምጡም ጠናባት። **17** ምጧ እየበረታ በሄደ ጊዜ አዋላጅቱ፣ “አይዞሽ አትፍሪ፤ ሌላ ወንድ ልጅ ልትወልጂ ነው” አለቻት። **18** እርስዋ ግን ልትሞት ታጣጥር ስለነበር ከመሞቷ በፊት ልጅዋን ‘ቤንኦኒ’ አለችው፤ አባቱ ግን ‘ብንያም’ አለው። **19** ራሔል ሞተች፤ ወደ ኤፍራታ በሚወስደው መንገድ በቤተልሔም ተቀበረች። **20** ያዕቆብም በራሔል መቃብር ላይ ሐውልት አቆመ፤ እስከዛሬም የራሔል መቃብር ምልክት ይኸው ሐውልት ነው። **21** ያዕቆብ ጉዞውን ቀጥሎ በዔዴር ግንብ ባሻገር ድንኳን ተክሎ ሰፈረ። **22** ያዕቆብ በዚያ ምድር ሲኖር ሳለ፣ ሮቤል ከአባቱ ቁባት ከባላ ጋር የግብረሥጋ ግንኙነት አደረገ፤ ያዕቆብም ይህን ነገር ሰማ ያዕቆብ ዐሥራ ሁለት ወንዶች ልጆች ነበሩት፣ እነርሱም፦ **23** የልያ ልጆች፦ የያዕቆብ የበኩር ልጅ ሮቤል፣ ስምዖን፣ ሌዊ፣ ይሁዳ፣ ይሳኮር፣ ዛብሎን፤ **24** የራሔል ልጆች፦ ዮሴፍ፣ ብንያም፤ **25** የራሔል አገልጋይ የባላ ልጆች፦ ዳን፣ ንፍታሌም፤ **26** የልያ አገልጋይ የዘለፋ ልጆች፦ ጋድ፣ አሴር፣ ናቸው። እነዚህ ወንዶች ልጆች ያዕቆብ በመስጴጦምያ ሳለ የተወለዱለት ናቸው። **27** ያዕቆብ በቂርያት አርባቅ (በኬብሮን) አጠገብ መምሬ በምትባል ስፍራ ወደሚኖረው አባቱ ወደ ይስሐቅ ሄደ፤ ይህም ስፍራ አብርሃምና ይስሐቅ የኖሩበት ነው። **28** ይስሐቅ መቶ ሰማንያ ዓመት ኖረ፤ **29** አርጅቶ ዕድሜ ጠግቦ ሞተ፤ ወደ ወገኖቹ ተሰበሰበ፤ ልጆቹም ዔሳውና ያዕቆብ ቀበሩት።

Genesis 35:1

ወደ ቤተል ውጣ
ውጣ የሚለው ቃል የተጠቀመው ቤቴል ከሴኬም በከፍታ ላይ ስለሚገኝ ነው

በዚያ መሠዊያ ሥራ
እግዚአብሔር ስለራሱ በሶስተኛ ሰው መንገድ ይናገራል:: አት: “ለእኔ ለአምላክህ መሠዊያ ሥራ” (እንደ አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ሰው መግለጽን ይመልከቱ)

ለቤቱ ሰዎች እንዲህ አላቸው
ለቤተሰቡ እንዲህ አላቸው

በእናንተ ዘንድ ያሉትን ባዕዳን አማልእክት አስወግዱ
“ጣዖታትን አስወግዱ” ወይም “ሐሰተኞች አማልእክትን አስወግዱ”

ራሳችሁን አንጹ ልብሳችሁን ለውጡ
ይህ እግዚአብሔርን ለማምለክ ከመቅረብ በፊት በአካላዊና ሥነምግባራዊ ሕይወት ራስን የማንጻት ልምድ ነበር

ልብሳችሁን ለውጡ
አድስ ልብሶችን መልበስ ወደ እግዚአብሔር ከመቀረባቸው በፊት ራሳቸውን ንጹህ የማድረጋቸው ምልክት ነበር (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

በመከራዬ ቀን
በመከራዬ ጊዜ ወይም በጭንቀተ ጊዜ

Genesis 35:4

ስለዚህ ሰጡት
“ሁሉም የያዕቆብ ቤት ሰጠ” ወይም “የያዕቆብ ቤተሰብና አገልጋዮቻቸው ሰጡት”

በእጃቸው ያሉትን
እዚህ “በእጃቸው ያሉት” የእነርሱ የሆኑትን ይወክላል:: አት: “ሀብታቸው የሆኑትን ወይም ያላቸውን” (ተመሣሣይ ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

የጆሮ ጉትቻቻቸውን
ጉትቻቻቸውን ተገቢ ትርጉሞች እነሆ 1 የጆሮቻቸውን ወርቅ ብዙ ጣዖታትን ሊሠሩ ሊጠቀሙ ይችላሉ 2 እነዚህ ጉትቻች የሴኬም ከተማ ሰዎችን በተዋጉና ሁሉን ሰዎች በገደሉ ጊዜ የበዘበዙአቸው ናቸው:: ጉትቻች ስለጋጢአታቸው የሚያውሱ ይሆናሉና::

በዙሪያው ባሉ ከተሞች ሁሉ እግዚአብሔር ድንጋጤ ለቀቀባቸው
ያዕቆብንና ቤተሰቡን የከተሞች ሰዎች እንዲደነግጡ እግዚአብሔር ያደረገው ድንጋጤ እንደ አንድ ነገር በከተሞች እንደወደቀ ተደርጐ ተገልጾአል:: “ድንጋጤ” የተባለው ረቂቅ ስም እንደ “ፍርሃት” ሊገለጽ ይችላል:: አት: “እግዚአብሔር በዙሪያው ያሉ የከተሞች ሰዎች ያዕቆብንና በቤተሰቡን እንዲፈሩ አደረገ” ዘይቤያዊ አነጋገርና ረቂቅ ስሞችን ይመልከቱ

በከተሞች ላይ
“ከተሞች” በከተሞች የሚኖሩ ሰዎችን ይወክላሉ::

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የያዕቆብ ወንዶች ልጆች
ከያዕቆብ ቤተሰብ ማንም እንዳልተጠቃ ይገልጻል ነገር ግን የያዕቆብ ሴት ልጅ ከተደፈረች በኋላ ስምዖንና ሌዊ የሴኬምን ከነዓናዊያን ዘመዶችን አጠቁአቸው በዘፍረት 34:30 ያዕቆብ ሊበቀሉ ይፈልጉ ይሆናል ብሎ ፈርቶአል አት የያዕቆብ ቤት ወይም የያዕቆብ ቤተሰብ (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 35:6

ሎዛ
ይህ የከተማ ስም ነው:: በዘፍጥረት 28 19 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ኤል ቤቴል
ተርጓሚዎች የሚከተለውን የግርጌ ማስታወሻ ሊጨምሩ ይችላሉ። “ኤል ቤተል የሚለው ስም የቤተል አምላክ ማለት ነው” (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

እግዚአብሔር የተገለጠለት በዚህ ቦታ ነበር
እግዚአብሔር ራሱን ለያዕቆብ ያስታወቀበት በዚህ ቦታ ነበር

ዲቦራ
ይህ የአንዲት ሴት ስም ነው ስምችን ስለመተርጐም ይመልከቱ

የርብቃ ሞግዚት
ሞግዚት የሌላ ሴት ልጅን የሚትንከባከብ ሴት ማለት ነው ሞግዚት እጅግ የተከበረችና በቤተሰብ ዘንድ ተቀባይነት ያላት ነች

ከቤተል ዝቅ ብሎ .... ተቀበረች
“ዝቅ ብሎ” የሚለው ሀረግ የተጠቀመው እርስዋ የተቀበረችው ቦታ ከፍታ ከቤተል ዝቅ ብሎ ስለሚገኝ ነው::

አሎንባኩት
ተርጓሚዎች የሚከተለውን የግርጌ ማስታወሻ ሊጨምሩ ይችላሉ። “አሎንባኩት የሚለው ስም ለቅሶ ያለበት ዋርካ ዛፍ ማለት ነው” (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 35:9

ያዕቆብ ከጳዳን አራም በተመለሰ ጊዜ
በቤተል እንደነበሩ ግልጽ ማድረግ ይቻላል አት ያዕቆብም ከጳዳን አራም ከተመለሰ በኋላ በቤተል በነበረበት ጊዜ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ባረከውም
በረከት ለአንድ ሰው መልካም ነገር እንዲደረግለትና በዚያው ሰው ላይ የረከት ቃል መናገር ነው

ከእንግዲህ ያዕቆብ ተብለህ አትጠራም
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት: “ስምህ ያዕቆብ አይባልም” (ተሻጋሪ ወይም የማይሻገር የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Genesis 35:11

እግዚአብሔር እርሱን እንዲህ አለው
እግዚአብሔር ያዕቆብን እንዲህ አለው

ብዛ ተባዛ
ብዙ ልጆች እንዲኖሩት ያዕቆብ ብዙ ልጆችን እንዲወልድ እግዚአብሔር ተናገረው ብዛ የሚለው እንዴት መባዛት እዳለበት ይገልጻል በዘፍጥረት 1:22 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ድርብ ቃላትና ፈሊጣዊ ንግግር ይመልከቱ)

ሕዝብና የሕዝቦች ማኅበር ከአንተ ይወጣሉ
እዚህ ሕዝብ እና ሕዝቦች የያዕቆብ ዘሮች እነዚህን ሕዝቦች እንደሚመሠርቱ ነው:: (ተመሣሣይ ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ከእርሱ.... ወደ ላይ ወጣ
ወደ ላይ ወጣ የተጠቀመው ከምድር ከፍ ብሎ እግዚአብሔር እንደምኖር ለመግለጽ ነው:: አት: “እግዚአብሔር ተለየው”

Genesis 35:14

ሐውልት
ይህ በጫፉ መከሎ/ቅርጽ ያለው ትልቅ ድንጋይ ለመታሰቢያነት የቆመ ሐውልት ነው

የመጠጥ መስዋዕትንም በእርሱ ላይ አፈሰሰ ዘይትንም አፈሰሰበት
ይህም ሐውልቱን ለእግዚአብሔር የመሰደስ ምልክት ነው (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

በቴል
ተርጓሚዎች የሚከተለውን የግርጌ ማስታወሻ ሊጨምሩ ይችላሉ። “በቴል የሚለው ስም የእግዚአብሔር ቤት ማለት ነው” (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 35:16

ኤፍራታ
ይህ የቤተልሔም ከተማ ሌላው ስም ነው

በከባድ ምጥ ውስጥ ሳለች
ምጡ አስጨንቆአት ሳለ

አዋላጅ
አንድ ሴት ልጅን በሚትወልድበት ጊዜ የሚታገዝ ሴት

ስትሞት ነፍስዋ በሚትወጣበት ጊዜ
“ነፍስ መውጣት” አንድ ሰው በሚሞትበት ጊዜ የመጨረሻ እስትንፋስ ማለት ነው። አት “ከመሞትዋ በፊት በመጨረሻዋ እስትንፋስ ጊዜ” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ቤንኦኒ
ተርጓሚዎች የሚከተለውን የግርጌ ማስታወሻ ሊጨምሩ ይችላሉ። “ቤንኦኒ የምለው ስም የጭንቀቴ ልጅ ማለት ነው” (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ብንያምን
ተርጓሚዎች የሚከተለውን የግርጌ ማስታወሻ ሊጨምሩ ይችላሉ። “ብንያምን የምለው ስም የቀኝ እጄ ልጅ ማለት ነው” የቀኝ እጅ የሚለው ሀረግ ልዩ የሚወደድ ቦታ ማለት ነው::

ተቀበረች
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት “እነርሱ ቀበሩአት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

በሚወስድ መንገድ
በሚወስደው መንገድ

እስከዛሬም የራሔል መቃብር ምልክት ይሄው ሐውልት ነው
ይህ እስከዛሬም የራሔል መቃብር ምልክት ነው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እስከዛሬ
እስካሁን ጊዜ ይህ ጸሐፊው፤ ይህ መልእክት የጻፈበትን ጊዜ ያመለክታል።

Genesis 35:21

እስራኤልም ጉዞውን በመቀጠል
የእስራኤል ቤተሰብና አገልጋዮቹ ከእርሱ ጋር እንደነበሩ ይገልጻል የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ባላ
የራሔል ሴት አገልጋይ ስም ነው:: በዘፍጥረት 29:29 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ::

ያዕቆብ አሥራ ሁለት ወንዶች ልጆች ነበሩት
ይህ ዐረፍተ ነገር በሚከተሉት ቁጥሮች የሚቀጥለውን አድስ አንቀጽ ይጀምራል

አሥራ ሁለት ወንዶች ልጆች
12 ወንዶች ልጆች

Genesis 35:23

ባላ
የራሔል ሴት አገልጋይ ስም ነው:: በዘፍጥረት 29:29 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 35:26

ዘለፋ
የልያ ሴት አገልጋይ ስም ነው:: በዘፍጥረት 29:24 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

በጳዳን አራም የተወለዱ ነበሩ
ይህ በከነዓን ምድር በቤተልሔም አጠገብ የተወለደውን ብንያምን እንደማያካትት ይናገራል:: አብዛኛዎቹ የተወለዱት በጳዳን አራም ስለሆነ ይህንኑን ይጠቅሳል:: የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት: “በከነዓን ምድር ከተወለደው ከብንያምን በስተቀር በጳዳን አራም የተወለዱለት” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ያዕቆብ ወደ ይስሐቅ መጣ
መጣ የተባለው ሄዴ በሚለው ሊተካ ይችላል (ሄዴ እና መጣ ይመልከቱ)

መምሬ
የሔብሮን ከተማ ሌላ ስምዋ ነው የአብርሃም ወዳጆች በኖሩበት በመምሬ ስም ተጠርቶ ይሆናል በዘፍጥረት 13 18 ይህን እንዴት አንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ቅርያትአርባቅ
ይህ የከተማ ስም ነው በዘፍጥረት 23 2 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 35:28

መቶ ሰማንያ ዓመት
180 ዓመት (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

ይስሐቅም ነፍሱን ሰጠ ሞተም
ይስሐቅም የመጨረሻውን እስትንፋስ ሰጠ ሞተም እንትንፋሱን ሰጠ/ነፍሱን ሰጠ ወይም ሞተ የሚሉ ሀረጐች በመሠረቱ አንድ ትርጉም አላቸው:: በዘፍጥረት 25:8 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: አት: “ይሥሐቅም ሞተ” (ድርብ ቃላት ይመልከቱ)

ነፍሱን ሰጠ
ይህ አንድ ሰው መሞቱን ትሁትና መንገድ የሚገልጽ ነው:: በዘፍጥረት 25:8 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ንጎብነት ለዛ ባለ ወይም በተዘዋዋሪ አንድን ነገር የመግለጽ ዘይቤያዊ አባባል ይመልከቱ)

ወደ ወገኖቹ ተከማቸ/ተሰበሰበ
ይስሐቅ ከሞተ በኋላ ከዚህ በፊት የሞቱ ወገኖች ነፍስ ወዳለበት ቦታ ነፍሱ ሄደች ማለት ነው ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል አት የሞቱትን የቤተሰብ አባላትን ተቀለቀለ ማለት ነው:: (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ተሻጋሪና የማይሻገር ግሥ የያዙ ዐረፍተ ነገሮችን ይመልከቱ)

አርጅቶ እድሜ ጠግቦ
አረጅቶ እና እድሜ ጠግቦ የሚሉ ሀረጐች በመሠረቱ ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው:: አበክረው የሚናገሩት ይስሐቅ ብዙ ዓመታትን እንደኖረ ነው:: አት: “ብዙ ዓመታትን ኖሮ ከአረጀ በኋላ” (ድርብ አባባል ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 36

1 ኤዶም የተባለው የዔሳው የትውልድ ታሪክ የሚከተለው ነው፤ **2** ዔሳው ከነዓናውያን ሴቶችን አገባ፤ እነርሱም የኬጢያዊው የዔሎን ልጅ ዓዳን፣ የኤውያዊው የፅብዖን ልጅ ዓና የወለዳት አህሊባማ፣ **3** እንዲሁም የነባዮት እኅት የሆነችውን የእስማኤል ልጅ ቤስሞት ነበሩ። **4** ዓዳ ለዔሳው ኤልፋዝን ወለደችለት። **5** እንደዚሁም አህሊባማ የዑስን፣ የዕላምንና ቆሬን ወለደችለት፤ እነዚህ ዔሳው በከነዓን አገር የወለዳቸው ልጆቹ ናቸው። **6** ዔሳው ሚስቶቹንና ወንዶችና ሴቶች ልጆቹን፣ ቤተ ሰቦቹን በሙሉ እንደዚሁም የቀንድ ከብቶቹንና ሌሎቹንም እንስሳት ሁሉ በከነዓን ምድር ያፈራውን ሀብት እንዳለ ይዞ ከወንድሙ ከያዕቆብ ራቅ ወዳለ ቦታ ሄደ። **7** ብዙ ሀብት ስለነበራቸው አብረው መኖር አልቻሉም፣ የነበሩበትም ስፍራ ከከብቶቻቸው ብዛት የተነሣ ሊበቃቸው አልቻለም። **8** ስለዚህ ዔዶም የተባለው ዔሳው መኖሪያውን በተራራማው አገር በሴይር አደረገ። **9** በተራራማው አገር በሴይር የሚኖሩ የኤዶማውያን አባት፣ የዔሳው ዝርያዎች እነዚህ ናቸው፤ **10** የዔሳው ልጆች ስም፦ የዔሳው ሚስት የዓዳ ልጅ ኤልፋዝና የዔሳው ሚስት የቤሴሞት ልጅ ራጉኤል፤ **11** የኤልፋዝ ልጆች፦ ቴማን፣ ኦማር፣ ስፎ፣ ጎቶም ቄኔዝ፤ **12** የዔሳው ልጅ ኤልፋዝ ትምናዕ የምትባል ቁባት ነበረችው፤ እርሷም አማሌቅን ወለደችለት፤ የዔሳው ሚስት የዓዳ የልጅ ልጆች እነዚህ ናቸው። **13** የራጉኤል ልጆች፦ ናሖት፣ ዛራ፣ ሻማና ሚዛህ፤ እነዚህም ደግሞ የዔሳው ሚስት የቤሴሞት የልጅ ልጆች ናቸው። **14** የፅብዖን የልጅ ልጅ፤ የዓና ልጅ የዔሳው ሚስት አህሊባማ ለዔሳው የወለደቻቸው ልጆች፦ የዑስ፣ የዕላማና ቆሬ፤ **15** ከዔሳው ዝርያዎች እነዚህ የነገድ አለቆች ነበሩ፤ የዔሳው የበኩር ልጅ የኤልፋዝ ልጆች፦ ቴማን፣ ኦማር፣ ስፎ፣ ቄኔዝ **16** ቆሬ፣ ጎቶምና አማሌቅ፤ እነዚህ በኤዶም ምድር ከኤልፋዝ የተገኙ የነገድ አለቆች፣ የዓዳ የልጅ ልጆች ነበሩ። **17** የዔሳው ልጅ የራጉኤል ልጆች፦ ናሖት፣ ዛራ፣ ሃማና፣ ሚዛህ፤ እነዚህ በኤዶም ምድር ከራጉኤል የተገኙ የነገድ አለቆች፣ የዔሳው ሚስት የቤሴሞት የልጅ ልጆች ነበሩ። **18** የዔሳው ሚስት የአሕሊባማ ልጆች፦የዑስ፣ የዕላማና ቆሬ፤ እነዚህ ከዓና ልጅ ከዔሳው ሚስት አሕሊባማ የተገኙ የነገድ አለቆች ነበሩ። **19** እነዚህም ኤዶም የተባለው የዔሳው ልጆችና የነገድ አለቆቻቸው ነበሩ። **20** በኤዶም ምድር ነዋሪዎች የነበሩት የሴይር ልጆች የነበሩ የሖራውያን አለቆች፦ ሎጣን፣ ሦባል፣ ፅብዖን፣ ዓና፣ **21** ዲሶን፣ ኤድርና ዲሳን፤ እነዚህ በኤዶም የነበረው የሴይር ልጆች፣ በሖራውያን የነገድ አለቆች ነበሩ። **22** የሎጣን ልጆች፦ ሖሪና ሔማም የሎጣንም እኅት ቲምናዕ ትባል ነበር። **23** የሦባል ልጆች፦ ዓልዋን፣ ማኔሐት፣ ዔባልና ስፎና አውናንም፤ **24** የፅብዖን ልጆች፦ አያና፣ ዓና፤ ይህ ዓና የአባቱን የፅባዖንን አህዮች ሲጠብቅ፣ የፍልውሃ ምንጮችን በምድረበዳ ያገኘ ሰው ነው። **25** የዓና ልጆች፦ዲሶንና የዓና የሴት ልጅ አህሊባማ፤ **26** የዲሶን ልጆች፦ ሔምዳን፣ ሴስባን፣ ይትራንና ክራን፤ **27** የኤድር ልጆች፦ ቢልሐን፣ ዛዕዋንና ዓቃን፤ **28** የዲሳን ልጆች፦ዑፅና አራን። **29** የሖራውያን የነገድ አለቆች እነዚህ ነበሩ፦ሎጣን፣ ሦባል፣ፅዖን፥ ዓና፣ **30** ዶሶን፣ ኤድርና ዲሳን፤ እነዚህ በሴይር ምድር እንደየነገዳቸው የሖራውያን የነገድ አለቆች ነበሩ። **31** ንጉሥ በእስራኤል ከመንገሡ በፊት፣ በኤዶም የነገሡ ነገሥታት እነዚህ ነበሩ፦ **32** የቢዖር ልጅ ባላቅ በኤዶም ነግሦ ነበር፤ የከተማውም ስም ዲንሃባ ይባል ነበር። **33** ባላቅ ሲሞት፣ በስፍራውም የባሶራው የዛራ ልጅ ኢዮባብ ነገሠ። **34** የባሶራው የዛራ ልጅ ኢዮባብ ሲሞት የቴማኒው ሑሳም ነገሠ። **35** ሑሳም ሲሞት፣ የምድያምን ሰዎች በሞዓብ ምድር ድል ያደረጋቸው የባዳድ ልጅ ሃዳድ በምትኩ ነገሠ፤ የከተማውም ስም ዓዊት ይባል ነበር። **36** ሃዳድ ሲሞት፣ የመሥሬቃው ሠምላ በምትኩ ነገሠ። **37** ሠምላ ሲሞት፣ በወንዙ አጠገብ ያለው የርሆቦቱ ሳኦል በምትኩ ነገሠ። **38** ሳኦል ሲሞት፣ የዓክቦር ልጅ በልሐናን በምትኩ ነገሠ። **39** የዓክቦር ልጅ በልሐናን ሲሞት፣ ሃዳር በምትኩ ነገሠ፤ የከተማውም ስም ፋው ይባል ነበር፤ የሚስቱም ስም መሄጣብዔል ሲሆን፣ እርሷም መጥሬድ የወለደቻት የሜዛሃብ ልጅ ነበረች። **40** ከዔሳው የተገኙት የነገድ አለቆች ስም፣ እንደየነገዳቸውና እንደየአገራቸው ይህ ነው፦ ቲምናዕ፣ ዓለዋ፣ የቴት፣ **41** አህሊባማ፣ ኤላ፣ ፌኖን፣ **42** ቄኔዝ፣ ቴማን፣ ሚብሳር፣ **43** መግዲኤልና ዒራም፣ እነዚህ በያዙት ምድር እንደየይዞታቸው ከኤዶም የተገኙ የነገድ አለቆች ነበሩ። ይህም ዔሳው የኤዶማውያን አባት ነበር።

Genesis 36:1

የዔሣው ትውልድ ይህ ነው እርሱም ኤዶም ነው
ኤዶም የተባለው የዔሣው ትውልድ ይህ ነው ይህ በዘፍጥረት 36:1-8 የተጠቀሰውን የዔሣው ትውልድን ያስታውቃል:: አት “ይህ ኤዶም የተባለው የዔሣው ትውልድ ነው” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ዓዳ አህሊባማ
እነዚህ የዔሣው ሚስቶች ስም ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ዔሎን ኬጢያዊው
“ዔሎን የኬጥ ትውልድ” ወይም “ዔሎን የኬጥ ልጅ” ይህ የአንድ ሰው ስም ነው:: በዘፍጥረት 26:34 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ዓና ... ጽብዖን .... ነባዮት
እነዚህ የመንዶች ሰዎች ስም ናቸው

ኤዋዊ
ይህ ትልቅ ሕዝብ ቡድንን ያመለክታል። በዘፍጥረት 10:17 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

ቤሴሞት
ከዔሣው ሚስቶች የአንዷ ስም ነው:: ዘፍጥረት 26:34 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ነባዮት
ከእስማኤል ወንዶች ልጆች የአንዱ ስም ነው:: ዘፍጥረት 28:9 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:4

ዓዳ ... ቤሴሞት ... አህሊባማ
እነዚህ የዔሣው ሚስቶች ስሞች ናቸው:: በዘፍጥረት 36:2-3 እነዚህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ኤልፋዝ ራጉኤል የዑስ የዕላም ቆሬ
እነዚህ የዔሣው ወንድ ልጆች ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:6

በከነዓን ምድር ያፈራውን ሀብት
ይህ በከነዓን ምድር በሚኖርበት ጊዜ የሰበሰበውን ወይም ያፈራውን ሁሉን ነገር ያመለክታል አት በከነዓን ምድር በሚኖርበት ጊዜ ያፈራውን ሀብት (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ወዳለ ቦታ ሄደ
ወደ ሌላ ቦታ ሂዶ በዚው ኖረ ማለት ነው:: አት: “በሌላ ቦታ ለመኖር ሄደ” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሀብቶቻቸው
የዔሣውና የያዕቆብ ሀብቶች

ከከብቶቻቸው ብዛት የተነሣ ሊበቃቸው አልቻለም
ያዕቆብና ዔሣው ያሉአቸውን ከብቶቻቸውን ለማሠማራት ምድሪቱ በቂ አልነበረችም:: አት “ከብቶቻቸውን ለማሠማራት አልበቃቸውም” ወይም “ለያዕቆብ ከብቶችና ለዔሣው ከብቶች በቂ አልነበረም” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

የነበሩበት ሥፍራ
የነበሩበት የሚለው ቃል ወደ አንድ ቦታ የመሄድና በዚያ መኖር ያመለክታል:: አት: “የሄዱበት ሥፍራ ወይም ቦታ” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 36:9

ይህ የዔሣው ትውልድ ነው
ይህ ዐረፍተ ነገር በዘፍጥረት 36: 9-43 ያለውን የዔሣው ትውልድ ዝርዝር ያስታውቃል (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

በሴይር ተራራማ አገር
በሴይር ተራራ ኖረዋል ማለት ነው:: የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት: “በተራራማው በሴይር አገር የኖሩ” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ኤልፋዝ ... ራጉኤል
እነዚህ የዔሣው ወንዶች ልጆች ስሞች ናቸው:: በዘፍጥረት 36:4 እነዚህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ዓዳ ... ቤሴሞት
እነዚህ የዔሣው ሚስቶች ስሞች ናቸው:: በዘፍጥረት 36:2-3 እነዚህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ቴማን ... ኦማር... ስፎ... ጎቶም... ቄኔዝ
እነዚህ የኤልፋዝ መንዶች ልጆች ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ትምናዕ
የኤልፋዝ ቁባት ስም ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:13

ራጉኤል ... ጽብያን ... የዑስ ... የዕላም ... ቆሬ
እነዚህ የዔሣው ወንዶች ልጆች ስሞች ናቸው:: በዘፍጥረት 36:4-5 እነዚህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ናሖት ዛራ ሣማ ሚዛህ
እነዚህ የራጉኤል ወንዶች ልጆች ስሞች ናቸው:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ዓና ... ጽብዮን
የወንድ ሰዎች ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

በሴሞት ... አህሊባማ
እነዚህ የዔሣው ሚስቶች ስሞች ናቸው:: በዘፍጥረት 36 2 3 እነዚህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:15

ኤልፋዝ
ይህ ከዔሣው ወንዶች ልጆች የአንዱ ስም ነው በዘፍጥረት 36: 4 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ቴማን ... ኦማር ... ስፎ ... ቄኔዝ ... ቆሬ ... ጎቶም ... አማሌቅ
የኤልፋዝ ወንዶች ልጆች ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ዓዳ
ከዔሣው ሚስቶች የአንዷ ስም ነው በዘፍጥረት 36: 2-3 ስምዋን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:17

ራጉኤል ... የዑስ ... የዕላም ... ቆሬ
እነዚህ የዔሣው ወንዶች ልጆች ስሞች ናቸው:: በዘፍጥረት 36:4-5 እነዚህን ስሞች እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ናሖት ዛራ ሣማ ሚዛህ
እነዚህ የራጉኤል ወንዶች ልጆች ስሞች ናቸው:: በዘፍጥረት 36:13 እነዚህን ስሞች እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

በኤዶም ምድር
ይህም በኤዶም ምድር ኖረዋል ማለት ነው:: አት: “በኤዶም ምድር የኖሩ” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

በሴሞት ... አህሊባማ
እነዚህ የዔሣው ሚስቶች ስሞች ናቸው:: በዘፍጥረት 36 :2-3 እነዚህን ስሞች እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ዓና
ይህ የወንድ ሰው ስም ነው በዘፍጥረት 36፡2 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:20

ሴይር
ሴይር የሚለው ቃል የአንድ ወንድ ሰውና የአንድ አገር ስም ነው

ሖሪውያን
“ሖሪውያን” የሚለው ቃል የአንድ ሕዝብ ቡድን ስም ነው:: በዘፍረት 14:6 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ(ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

በምድሪቱ ነዋሪዎች
ኤዶም በተባለው በሴይር የሚኖሩ

ሎጣን ሶባል ጽብያን ዓና ዲሶን ኤጽር ዲሳን
እነዚህ የወንዶች ሰዎች ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ቲምናዕ
ይህ የሴት ስም ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:23

ሶባል... ጽብያን
እነዚህ የወንድ ሰው ስሞች ናቸው:: በዘፍረት 36:20 እነዚህን ስሞች እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ዓልዋን ...ማኔሐት... ዔባል... ስፎና አውናም ... አያና ዓና
እነዚህ የወንድ ሰው ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Genesis 36:25

ዓና ዲሶን ኤጽር ዲሳን
እነዚህ የወንድ ሰው ስሞች ናቸው:: በዘፍረት 36: 20-21 እነዚህን ስሞች እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

አሊህባማ
ይህ የአንዲት ሴት ስም ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ሔምዳን ኤስባን ይትራንና ክራን ቢልሐን ዛዕዋንና ዓቃን
እነዚህ የወንድ ሰው ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:29

ሖሪውያን
የአንድ ሕዝበ ወገን ስም ነው:: በዘፍጥረት 14:6 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ሎጣን ሶባል ጽብዖን ዓና ዲሶን ኤጽር ዲሳን
እነዚህ የወንድ ስዎች ስሞች ናቸው በዘፍረት 36:20-21 እነዚህን ስሞች እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

በሴይር ምድር
ይህም በሴይር ምድር ኖረዋል ማለት ነው:: አት “በሴይር ምድር የኖሩ” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 36:31

ቢዖር ባላቅ ኢዮባብ ዛራ
እነዚህ የወንድ ሰው ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

የከተማውም ስም
ይህ እርሱ የኖረበት ከተማ ነበር ማለት ነው:: አት: “እርሱ የኖረበት ከተማ ስም” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ዲንሃባ ባሶራ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:34

ኢዮባብ
ይህ የወንድ ሰው ስም ነው በዘፍጥረት 36 33 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ሐሳም ሃዳድ ባዳድ ሠምላ
እነዚህ የወንድ ሰው ስሞች ናቸው:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

የቴማኒው ምድር ሐሳም
ይህም ሐሳም በቴማኒ ምድር ኖሮአል ማለት ነው:: አት “በቴማኒ ምድር የኖረ ሐሳም” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ዓዊት ምሥሬቃ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ቴማኒው
ቴማኒ የተባለው ሰው ትውልድ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

የከተማው ስም
ይህ እርሱ የኖረበት ከተማ ነበር ማለት ነው:: አት: “እርሱ የኖረበት ከተማ ስም” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

የመሥሬቃው ሠምላ
ከመሥሬቃ የሆነው ሠምላ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:37

ሠምላ
ይህ የወንድ ሰው ስም ነው:: በዘፍጥረት 36:36 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

በወንዙ አጠገብ ያለው የርሆቦቱ ሳኦል በምትኩ ነገሠ
ሳኦል በርሆቦት ይኖር ነበር:: ርሆቦት በኤፍራጥስ ወንዝ አጠገብ ነው:: ይህ መረጃ ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት: “ከዚያም ሳኦል በምትኩ ነገሠ:: እርሱም ከኤፍራጥስ ወንዝ አጠገብ ከነበረችው ከርሆቦት ነው (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ርሆቦት ፋዑ
የቦታዎች ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

የከተማው ስም
ይህ እርሱ የኖረበት ከተማ ነበር ማለት ነው:: አት: “እርሱ የኖረበት ከተማ ስም” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

የሜዛሃብ ልጅ መጥሬድ የወለደቻት
እርሷም የሜዛሃብ ልጅ መጥሬት የወለደቻት ነበረች

መሄጣብኤል
የሴት ስም ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:40

የነገድ አለቆች
የነገድ መሪዎች

እንደየስማቸው እንደየነገዳቸውና እንደየአገራቸው
ነገዳቸውና አገራቸው በአለቆቻው ወይም በመሪዎቻቸው ስም ተሰይሞአል:: አት: “የነገዶቻቸውና የሚኖሩባቸው አገራቸው በመሪዎቻቸው ስም ተሠይሞአል” የእነርሱ ስሞች እነሆ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ቲምናዕ ዓልዋ የቴት አህሊባማ ኤላ ፋኖን ቄኔዝ ቴማን ሚብሳር መግዲኤልና ዒራም
እነዚህ የህዝብ ወገኖች ወይም የነገዶች ስም ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

በግዛታቸው ወይም በሠፈሩባቸው ምድር
“በሚኖሩባቸው ቦታዎች” ወይም “በኖሩባቸው ቦታዎች”

ይህም ዔሣው ነው
ይህ የስም ዝርዝር ዔሣው ነው የተባለው ይህ የትውልዱ አጠቃላይ ዝርዝር ነው ማለት ነው:: አት: “ይህ የዔሣው ትውልድ ዝርዝር ነው” (ተዛማጅ ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 37

1 የዕቆብ አባቱ በኖረበት በከነዓን ምድር ተቀመጠ። 2 የያዕቆብ ትውልድ ታሪክ ይህ ነው። ዮሴፍ የዐሥራ ሰባት ዓመት ወጣት በነበረ ጊዜ፣ ከአባቱ ሚስቶች
ከባላቅና ከዘለፋ ከተወለዱት ወንድሞቹ ጋር የአባቱን በጎችና ፍየሎች ይጠብቅ ነበር። እርሱም ስለወንድሞቹ ድርጊት ለአባቱ መጥፎ ወሬ ይዞለት መጣ። 3
እስራኤል ዮሴፍን በስተርጅናው ስለወለደው፣ ከልጆቹ ሁሉ አብልጦ ይወደው ነበር፣ በኅብረ ቀለማት ያጌጠ እጀ ጠባብም ሰፋለት። 4 ወንድሞቹም አባታቸው
ከእነርሱ አብልጦ የሚወደው መሆኑን ሲያዩ ዮሴፍን ጠሉት፤ በቅን አንደበት ሊያናግሩት አልቻሉም። 5 ዮሴፍ ሕልም አለመ፤ ሕልሙንም ለወንድሞቹ
ሲነግራቸው የባሰ ጠሉት፤ 6 እርሱም እንዲህ አላቸው፤ “ያየሁትን ሕልም ልንገራችሁ አድምጡኝ” 7 ‘እኛ ሁላችን በእርሻ ውስጥ ነዶ እናስር ነበር፤ የእኔ ነዶ
ተነሣና ቀጥ ብሎ ቆመ፤ የእናንተ ነዶዎች ዙሪያውን ተሰብስበው ለእኔ ነዶ ሰገዱለት’” 8 ወንድሞቹም፣ “ታዲያ በእኛ ላይ ንጉሥ ሆነህ ልትገዛን ታስባለህን?”
ብለው ጠየቁት። ስለ ሕልሙና ስለተናገረው ቃል ከፊት ይልቅ ጠሉት። 9 እንደ ገናም ሌላ ሕልም አለመ፤ ለወንድሞቹም እነሆ፣ ሌላ ሕልም አለምሁ፣ ፀሐይና
ጨረቃ፣ ዐሥራ አንድ ክዋክብትም ሲሰግዱልኝ ዐየሁ” ብሎ ነገራቸው። 10 ይህንኑ ለወንድሞቹ የነገራቸውን ሕልም ለአባቱም በነገረው ጊዜ፣ አባቱ፣ “ይህ ምን
ዐይነት ሕልም ነው? እኔና እናትህ ወንድሞችህም በፊትህ ወደ ምድር ተጎንብሰን በርግጥ ልንሰግድልህ ነው?” ሲል ገሠጸው። 11 ወንድሞቹ ቀኑበት፤ አባቱ ግን
ነገሩን በልቡ ያዘው። 12 አንድ ቀን የዮሴፍ ወንድሞች የአባታቸውን መንጋዎች ይዘው ወደ ሴኬም ተሰማሩ፤ 13 እስራኤልም ዮሴፍን፣ “እንደምታውቀው
ወንድሞችህ መንጎቹን በሴኬም አካባቢ አሰማርተዋል፤ በል ተነሥ፣ ወደ እነርሱ ልላክህ” አለው። ዮሴፍም፣ “እሺ እሄዳለሁ” አለ። 14 አባቱም፣ “በል
እንግዲህ ሄድና የወንድሞችህንና የመንጋዎቹን ደኅንነት አይተህ ንገረኝ” አለው። በዚህ ዓይነት እስራኤል ዮሴፍን ከኬብሮን ሸለቆ ላከው። ዮሴፍም ሴኬም
በደረሰ ጊዜ፣ 15 ሜዳ ላይ ወዲያ ወዲህ ሲባዝን አንድ ሰው አግኝቶት፣ “ምን እየፈለግህ ነው?” ሲል ጠየቀው። 16 ዮሴፍም፣ “ወንድሞቼን እየፈለግኋቸው
ነው፤ መንጎቻቸውን የት እንዳሰማሩ ልትነግረኝ ትችላለህ?” አለው። 17 ሰውዬውም፣ “ከዚህ ሄደዋል፤ ደግሞም ‘ወደ ዶታይን እንሂድ’ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ”
አለው። ከዚያም ዮሴፍ ወንድሞቹን ፍለጋ ሄደ፣ በዶታይን አቅራቢያም አገኛቸው። 18 ወንድሞቹም ዮሴፍ ወደ እነርሱ ሲመጣ በሩቅ ዐዩት፣ ወደ ነበሩበትም
ስፍራ ከመድረሱ በፊት ሊገድሉት ተማከሩ። 19 እነርሱ እንዲህ ተባባሉ፦ “ያ ሕልም አላሚ መጣ፤ 20 ኑ እንግደለውና ከጉድጓዶቹ በአንዱ ውስጥ እንጣለው፤
ከዚያም፣ ‘ክፉ አውሬ ነጥቆ በላው’ እንላለን፤ እስቲ ሕልሞቹ ሲፈጸሙ እናያለን።” 21 ሮቤል ግን ይህን ምክር ሲሰማ ከእጆቹው ሊያድነው ፈለገ እንዲህም
አለ፤ “አንግደለው፤ 22 የሰው ደም አታፍስሱ፣ ከምትገድሉት ይልቅ በዚህ በበረሃ ባለው ጉድጓድ ውስጥ ጣሉት” አላቸው። ሮቤል ይህን ያለው ሕይወቱን
ከእጆቹው አትርፎ ወደ አባቱ ሊመልሰው ዐስቦ ነበር። 23 ዮሴፍ ወደ ወንድሞቹ እንደደረሰ፣ የለበሳትን በኅብረ ቀለማት የጌጠች እጀ ጠባቡን ገፈፉት፤ 24
ይዘውም ወደ ጉድጓድ ጣሉት፤ ጉድጓዱም ውሃ የሌለበት ደረቅ ነበር። 25 ምግባቸውን ለመብላት ተቀመጡ፤ አሻግረው ሲመለከቱም ከገለዓድ የሚመጡ
እስማኤላውያን ነጋዴዎች ጓዛቸውን በግመሎች ላይ ጭነው ተመለከቱ። ነጋዴዎቹ ሽቶ፣ በለሳን፣ ከርቤ በግመሎቻቸው ጭነው ወደ ግብፅ የሚወርዱ ነበሩ። 26
ይሁዳም ወንድሞቹን እንዲህ አላቸው፤ “ወንድማችንን መግደልና አሟሟቱን መደበቅ ምን ይጠቅመናል? 27 ከዚህ ይልቅ ለእስማኤላውያን ነጋዴዎች
እንሸጠው፤ እጃችንን ግን በእርሱ ላይ አናንሳ። ምንም ቢሆን የሥጋ ወንድማችን ነው” ወንድሞቹም በሃሳቡ ተስማሙ። 28 የምድያም ነጋዴዎች የሆኑ
እስማኤላውያን በዚያ በኩል ያልፉ ነበር፤ ስለዚህ ወንድሞቹ ዮሴፍን ከጉድጓድ ጎትተው በማውጣት ለእነዚህ እስማኤላውያን በሃያ ብር ሸጡላቸው፣ እነርሱም
ወደ ግብፅ ይዘውት ሄዱ። 29 ሮቤል ወደ ጉድጓዱ ተመልሶ ሲያይ፣ ዮሴፍን በማጣቱ ልብሱን በሐዘን ቀደደ። 30 ወደ ወንድሞቹም ተመልሶ፣ “እነሆ፣ ልጁ
እዚያ የለም! እንግዲህ እኔ ወዴት ብሄድ ይሻለኛል?” አለ። 31 ከዚህ በኋላ አንድ ፍየል አረዱና የዮሴፍን ልብስ በደም ነከሩት። 32 በኅብረ ቀለማት
ያጌጠችውን እጀ ጠባብ ወደ አባታቸው ወስደው፣ “ይህን ወድቆ አገኘነው፤ የልጅህ እጀ ጠባብ መሆን አለመሆኑን እስቲ እየው” አሉት። 33 እርሱ የልጁ ልብስ
መሆኑን ተረድቶ፣ “ይህማ የልጄ እጀ ጠባብ ነው! ፤ ክፉ አውሬ በልቶታል፣ በእርግጥም ዮሴፍ ተቦጫጭቆአል” አለ። 34 ከዚህ በኋላ ያዕቆብ ልብሱን ቀደደ፤
ማቅም ለብሶ ስለ ልጁ ብዙ ቀን አለቀሰ፤ 35 ወንዶችና ሴቶች ልጆቹም ሁሉ ሊያጽናኑት መጡ፤ እርሱ ግን ሊጽናና አልቻለም፣ “በሐዘን እንደተኮራመትሁ ልጄ
ወዳለበት መቃብር እወርዳለሁ” አለ። ስለ ልጁም አለቀሰ። 36 በዚህ ጊዜ የምድያም ነጋዴዎች ዮሴፍን ወደ ግብፅ ወስደው፣ ከፈርዖን ሹማምንት አንዱ
ለነበረው ለዘበኞች አለቃ፣ ለጲጥፋራ ሸጡት።

Genesis 37:1

አባቱ በቆየበት አገር በከነዓን ምድር ተቀመጠ
አባቱ በኖረበት በከነዓን ምድር ተቀመጠ

የያዕቆብ ትውልድ ታሪክ ይህ ነው
ይህ ዐረፍተ ነገር በዘፍጥረት 37: 1-50:26 ያለውን የያዕቆብን ትውልድ ያስታውቃል። እዚህ ያዕቆብ መላው በተሰቡን ይወክላል። አት “ይህ የያዕቆብ ቤተሰብ ታሪክ ነው” (ክፍልን እንደሙሉና ሙሉን እንደክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

አሥራ ሰባት ዓመት ዕድሜ
17 ዓመት ዕድሜ

ባላ
ይህ የራሔል ሴት አገልጋይ ስም ነው:: በዘፍጥረት 29: 29 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ዘለፋ
ይህ የልያ ሴት አገልጋይ ስም ነው:: በዘፍጥረት 29: 24 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ሚስቶች
እነዚህ ሴቶች ልጅ እንዲወልዱ ዘንድ ለያዕቆብ የተሰጡ የልያና የራሔል አገልጋዮች ናቸው

ስለእነርሱ መጥፎ ወሬ
ስለወንድሞቹ መጥፎ ወሬ

Genesis 37:3

አሁንም
ይህ ቃል ታሪኩ ስለ እስራኤልና ዮሴፍ ዳራ መረጃ መቀየሩን የሚያመለክት ነው (ዳራ መረጃ ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ስለወደደው
ይህ ወንድማማች ፍቅር ወይም ጓደኛ ፍቅር ወይም ቤተሰብ ፍቅር ያመለክታል ይህ በጓደኛሞችና በቤተሰብ መካከል የሚገለጽ ተፈጥሮአዊ የሰው ልጅ ፍቅር ነው

በስተርጅናው
እስራኤል በአረጀ ጊዜ ዮሴፍን ወልዶአል ማለት ነው:: አት: “እስራኤል በአረጀ ጊዜ የተወለደው” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

እርሱ ለእርሱ .....አደረገለት
እስራኤል ለዮሴፍ ..አደረገለት

በጎብረቀለማት ያገጤ እጄ ጠባብ
እጅግ የሚያምር እጄ ጠባብ

በቅን አንደበት ሊያናግሩት አልቻሉም
በሰላም ሊያናግሩት ዘንድ አልቻሉም

Genesis 37:5

ዮሴፍም ሕልምን አለመ ሕልሙንም ለወንድምቹ ሲነግራቸው የባሰ ጠሉት
ይህ በዘፍጥረት 37:6-11 የተቀመጠው ታሪክ ማጠቃለያ ሀሳብ ነው::

የበለጠውኑ ጠሉት
የዮሴፍ ወንድሞች ከዚህ በፊት ከሚጠሉት በላይ ጠሉት

ያየሁትን ይህን ሕልም ልንገራችሁ አድምጡኝ
ሕልሜን ልንገራችሁ አድምጡኝ

Genesis 37:7

አጠቃላይ መረጃ
ስለሕልሙ ዮሴፍ ለወንድሞቹ ይናገራል

እነሆ
“እነሆ” የሚለው ቃል ለሚቀጥለው አስደናቂ ሃሳብ ትኩረት እንዲሰጠው ያነቃል

እኛ ሁላችን
“እኛ” የሚለው ቃል ዮሴፍና ወንድሞቹን ሁሉ ያጠቃልላል (ሁሉን ያቀፈ እኛ ይመልከቱ)

ነዶ እናሥር ነበር
እህል ከታጨደ በኋላ ፍሬው ከገለባው እስኪበጠር ድረስ በየነዶው ታሥሮና ተከምሮ ይጠበቃል

እንሆ
“እነሆ” የሚለው ቃል ዮሴፍ ባየው እንደተደነቀ ይገልጻል

የእኔ ነዶ በድንገት ተነሥታ ቀጥ ብላ ቆመች የእናንተ ነዶዎች ዙሪያዋን ከበው ለእኔ ነዶ ሰገዱላት
እዚህ እንደሰው ነዶዎች ሲቆሙና ሲሰግዱ ይታያል እነዚህ ነዶዎች ዮሴፍንና ወንድምቹን ይወክላሉ (በሰውኛ መንገድ አገላለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

በላያችን ልትነግሥብን ይሆን? ልትገዛ ይሆን?
እነዚህ ሁለቱም ሀረጐች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው የዮሴፍ ወንድሞች ጥያቄዎችን በመጠቀም ዮሴፍን ማላገድ ጀመሩ እነዚህ በዐረፍተ ነገሮች መልክ ለገለጹ ይችላሉ አት ንጉሣችን አትሆንም እኛም ለአንተ አንሠገድም (አግናኝ ጥያቄዎችንና ተዛማጅ ተመሣሣይ አባባል ይመልከቱ)

እኛን ልትገዛ
እኛ የሚለው ቃል ዮሴፍን ሳይሆን ወንድሞቹን ያመለክታል (ሁሉን አቀፍና ሁሉን የማያቅፍ “እኛ” ይመልከቱ)

ለሕልሙና ለተናገረው ቃል
ስለ ሕልሙና ልሰተናገረው ቃል

Genesis 37:9

ሌላ ሕልም አለመ
ዮሴፍ ሌላ ሕልም አለመ

አሥራ አንድ ከዋክብት
11 ከዋክብት ቁጥሮች ይመልከቱ

አባቱ ገሠጸው እንዲህም አለው
እስራኤልም ገሠጸው አለውም

ይህ ያየሄው ሕልም ምንድን ነው? እኔና እናትህ ወደ ምድር ተጐንብሰን ልንሰግድል ነው?
እስራኤል ዮሴፍን ለማረም ጥያቄዎችን ይጠቀማል:: ይህ እንደ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል:: አት: “ይህ ያየሄው ሕልም ትክክል አይደለም:: እኔ እናትህና ወንድሞችህ በፊትህ አንሰግድልህም!” (አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

ቀኑበት
አንድ ሰው ስኬታማና እጅግ ታዋቂ ከመሆኑ የተነሣ በቁጣ መሞላት ማለት ነው

ነገሩን በልቡ ያዘው
ስለዮሴፍ ሕልም ትርጉም ማሰቡን ቀጠለ ማለት ነው:: አት: “የሕልሙ ትርጉም ምን እንደሆን ማሰቡን ቀጠለ” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 37:12

ወንድሞችህ በሰኬም በጎችን ይጠብቁ አይደለምን?
እስራኤል በንግግሩ ውስጥ ጥያቄ ይጠቀማል:: ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ለገለጽ ይችላል:: አት “ወንድሞችህ በሰኬም በጎችን ይጠብቃሉ” (አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

ና
ለመሄድና ወንድሞቹን ለማየት ዮሴፍ እንዲዘጋጅ እስራኤል መጠየቁን የሚገልጽ ነው:: አት “ተዘጋጅ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

እነሆኝ
ለመሄድ ተዘጅቸአለሁ(ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

እርሱም እርሱን አለው
እስራኤል ዮሴፍን አለው

ወሬያቸውን አምጣልኝ
ወንድሞቹና በጎቹ እንዴት እንደሆኑ ዮሴፍ ተመልሶ እንዲነግረው እስራኤል ይፈልጋል አት ተመልሰው ያገኘሄውን ንገረኝ ወይም ርፖርት አቅርብልኝ (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

በሸለቆው
ከሸለቆው

Genesis 37:15

እነሆ ዮሴፍ ሜዳ ላይ ወዲያና ወዲህ ሲባዝን ነበር አንድ ሰውም ዮሴፍን አገኘው
ዮሴፍ ወዲያና ወዲህ ሲባዝን አንድ ሰው ዮሴፍን አገኘው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እነሆ
በትልቁ ታሪክ ስለሌላ ክስተት መጀመሩን የሚያመለክት ነው በቀደሙ ክስተቶች ከነበሩ ሌሎች ሰዎች የሚያሳትፍ ነው በእርስዎ ቋንቋ ይህ የሚገለጽበት መንገድ ሊኖር ይችላል

ምን እያየህ ነው ?
ምን እየፈለግህ ነው?

ወዴት ነው እባክህ ንገረኝ
ወዴት እንደሆነ እባክህ ንገረኝ

ዶታይን
ከሰኬም 22 ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት ያለ ቦታ ስም ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 37:18

በሩቅ አዩት
በሩቅ እያለ የዮሴፍ ወንድሞች አዩት

ይገድሉት ዘንድ በእርሱ ላይ ተማከሩ
እርሱን ለመግደል አቀዱ

ያ ሕልም ዐላሚ መጣ
ያ ባለ ሕልም ይሄው መጣ

ስለዚህ አሁንም ኑ
ይህ አባባል ወንድሞቹ ዕቅዳቸውን መተግበር መጀመራቸውን ያሳያል:: አት: (ስለዚህ አሁን ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ክፉ አውሬ
አደገኛ አውሬ ወይም ሰው ጨካኝ አውሬ

ቦጫጭቆ በላው
ንጥቆ በላው

ከሕልሞቹም የሚሆነውን እናያለን
ወንድሞቹ ለገድሉት አቅደዋልና ስለዚህ እስከሞተ ድረስ ሕልሞቹ ይፈጸሙ እንደሆን መናገራቸው አሽሙራዊ/ሽሙጣዊ አባባል ነው:: አት “እስቲ ሕልሞቹ ሲፈጸሙ እናያለን” (በአሽሙር/ሽሙጥ መንገድ የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

Genesis 37:21

ይህን ሰማ
እነርሱ የመከሩትን ሰማ

ከእጃቸው
ከእጃቸው የሚለው አባባል ለገድሉት ያቀዱትን የወንድሞቹን እቅድ ያመለክታል:: አት “ከእነርሱ” ወይም “ከእቅዳቸው” (ተዛማጅ ምትክ ቃላት አጠቃቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

ሕይወቱን አናጥፋ
ሕይወት ማጥፋት የሚለው ሀረግ አንድን ሰው ስለመግደል በንኀብነት ወይም ለዛ ባለ ቃል በተዘዋዋሪ የሚገልጽ ነው። አት: “ዮሴፍን አንግደለው” (ንኀብነት ወይም ለዛ ባለ ቃል በተዘዋዋሪ መንገድ የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ደም አታፍስሱ
በግሡ አሉታዊነት ተጨምሮበታል ደግሞም ደምን ማፍሰስ አንድን ሰው ስለመግደል በንኀብነት ወይም ለዛ ባለ ቃል በተዘዋዋሪ የሚገልጽ ነው። አት የማንኛውንም ሰው ደም አታፍስሱ ወይም አትግደሉት (በአሉታዊነት አዎንታዊነትን የመግለጽ ዘይቤና ንኀብነት ወይም ለዛ ባለ ቃል በተዘዋዋሪ መንገድ የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

እጃችሁን አታንሡበት
አታቆስሉት ወይም አትጉዱት ማለት ነው አት አትጉዱት (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ከእጃቸው ሊያተርፈው
ይህ እንደ አዲስ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል:: “ሮቤል ይህ ያለው ዮሴፍን ሊታርፈው ዘንድ ነው”

ከእጃቸው
ከእጃቸው የሚለው አባባል ለገድሉት ያቀዱትን የወንድሞቹን እቅድ ያመለክታል:: አት “ከእነርሱ” ወይም “ከእቅዳቸው” (ተዛማጅ ምትክ ቃላት አጠቃቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

ሊመልሰው
እናም ሊመልሰው

Genesis 37:23

እንደ ደረሰ
ይህ ሐረግ በታሪኩ ተፈለጊ ክስተት ለመጠቆም ተጠቅሞአል በቋንቋህ እንዲህ ዓይነት ካለ በዚህ ቦታ ሊጠቀሙ ይችላሉ

በኀብረ ቀለማት ያገጠች እጀ ጠባቡን ገፈፉት
በኀብረ ቀለማት ያገጠች እጀ ጠባቡን ከላዩ ላይ ቀደዱት

ያገጠች ልብስ
ያገጠች እጀ ጠባብ፤ በዘፍጥረት 37:3 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ

Genesis 37:25

እንጀራም ሊበሉ ተቀመጡ
እንጀራ በአጠቃላይ መግብን ያመለክታል አት ምግባቸውን ለመብላት ተቀመጡ ወይም የያዕቆብ ወንድሞች ምግባቸውን ሊበሉ ተቀመጡ (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ዐይኖቻቸውንም አንስተው አዩ እነሆም... የግመል ጓዝ
እዚህ አንስተው አዩ አንድሰው በውኑ አይኑን እንሰቶ እንደሚያይ ተደርጐ ተነግሮአል ደግሞም እነሆ የሚለው ቃል ሰዎች ላዩት ትኩረት ለመስጠት ተጠቅሞአል:: አት: “አይኖቻቸውን አነሡ እናም ወዲያውም የግመል ጓዝ አዩ” (ዘይቤያዊ አባባል ይመልከቱ)

ተሸክመው
ጭነው

ኬርቤ
ቅመማቅመም

በለሳን
የቆዳ ቁስለትን የሚፈውስና የሚከለክል ጣፋጭ ጣዕም ያለው ቅባታማ ነገር “መድኃኒት”

ጭነው ወደ ግብጽ የሚወርዱ
ወደ ግብጽ የሚያመጡ ይህ ግለጽ ሊደረግ ይችላል አት ለመሸጥ ወደ ግብጽ የሚወርዱ ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወንድማችንን መግደልና ደሙን መሸሸግ ምን ይጠቅማናል?
ይህ እንደዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል:: አት “ወንድማችንን በመግደልና አሟሟቱን በመደበቅ እንጠቀምም” (አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

ደሙን መሸሸግ
የዮሴፍን ሞት በደበቅን የሚገልጽ ምሳሌዊ አነጋገር ነው:: አት “አሟሟቱን መደበቅ” (ዘይቤያዊ አባባል ይመልከቱ)

Genesis 37:27

ለእስማኤላዊያን
የእስማኤል ዘር ለሆኑ ለእነዚህ ሰዎች

እጃችንን በእርሱ ላይ አናንሳ
ይህም “አናቆስለው” ወይም “አንጉዳው” ማለት ነው አት: “አንጉዳው” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ወንድማችን ሥጋችን ነው
ሥጋ የሚለው ዘመድ ለሚለው ቃለ የሚቆም ምትክ ቃል ነው:: አት: “እርሱ የሥጋ ዘመዳችን ነው” (ተዛማጅ ምትክ ቃላትን የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

ወንድሞቹም የእርሱን ነገር ሰሙት
የይሁዳ ወንድሞች ሰሙት ወይም የይሁዳ ወንድሞች በሐሳቡ ተስማሙ

ምድያማዊያን ..... እስማኤላዊያን
ሁለቱም ስሞች የዮሴፍ ወንድሞች ያገኙአቸው ተመሣሣይ ነጋዴዎችን ያመለክታል

ለሃያ ጥሬ ብር
ለሃያ ጥሬ ብር ዋጋ (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

ዮሴፍን ወደ ግብጽ የዘውት ሄዱ
ዮሴፍን ወደ ግብጽ ወሰዱት

Genesis 37:29

ሮቤል ወደ ጉድጓዱ ተመልሶ ሲያይ ዮሴፍን በማጣቱ
ሮቤል ወደ ጉድጓዱ ተመልሶ ዮሴፍን በማጣቱ እነሆ ተገረመ:: “እነሆ” የሚለው ቃል ሮቤል ዮሴፍ በሄዱን ባወቀ ጊዜ መገረሙን ያሳያል::

ልብሱን ቀደደ
ይህ የጥልቅ ጭንቀትና ሀዘን ምልክት ነው:: ይህ በግልጽ ሊገለጽ ይችላል:: አት: እጅግም ስላዘነ ልብሱን ቀደደ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ብላቴናው የለም እንግዲህ እኔ ወዴት እሄዳለሁ?
የዮሴፍ መጥፋቱን ችግር ትኩረት ለመስጠት ሮቤል ጥያቄ ይጠቀማል:: አት: “ብላቴናው ሄዶአል እንግዲህ ወደ ቤት መመለስ አልችልም” (አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

Genesis 37:31

የዮሴፍ እጀ ጠባብ
አባቱ ያዘጋጀለት ያጌጠችውን እጀ ጠባብ ያመለክታል

ደም
የፍዬል ደም

አምጥተው
እጀ በባቡን አምጥተው

ቦጫጭቆ በልቶታል
በልቶታል

በእርግጥም ዮሴፍ ተቦጫጭቆአል
ያዕቆብ የዮሴፍን አካል ክፉ አውሬ እንደገነጣጠለ አሰበ:: አት: “በእርግጥም ዮሴፍን ቦጫጭቆታል” (ተሻጋሪና የማይሻገር ግሥ ይመልከቱ)

Genesis 37:34

ያዕቆብ ልብሱን ቀደደ
ይህ ጥልቅ መጨነቅንና ሀዘንን የሚያመለክት ነው ይህ በግልጽ ሊገለጽ ይችላል አት ያዕቆብ እጅግ ስላዘነ ልብሱን ቀደደ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

በወገቡም ማቅ ታጥቆ
ወገብ የሰውነት መሀከለኛው አካል ነው አት ማቅ ለብሶ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ተነሡ
እዚህ አባታቸውን ለማጽናናት የልጆች መጥጣት እንደ መነሣት ተደርጐ ተገልጾአል:: አት: “ወደ እርሱ መጡ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

እርሱ ግን ሊጽናና ባለመቻሉ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “ነገር ግን እንዲያጽናኑት አልፈቀደም” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ወደ ሙታን ሥፍራ እያዘንሁ እወርዳለሁ
ከዛሬ ጀምሮ እስከሚሞት ድረስ እንደሚያዝን ይገልጻል:: አት: “በሚሞትበትና ወደ ሙትን ሥፍራ በሚወርድበትም ጊዜም በእርግጥ እያዘንኩ ይሆናል” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ምድያማዊያን ሸጡት
ምድያማዊያን ዮሴፍን ሸጡት

ለዘበኞች አለቃ
ንጉሡን ለሚጠብቁ ዘበኞች መሪ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 38

1 በዚያም ወራት ይሁዳ ከወንድሞቹ ተለይቶ ሒራ ወደተባለ ዐዲላማዊ ሰው ዘንድ ሄደ፣ መኖሪያውንም **2** እዚያም ሳለ፣ ይሁዳ የከነዓናዊውን የሴዋን ሴት ልጅ ዐየ፤ እርሷንም አግብቶ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጸመ። **3** እርሷም አርግዛ ወንድ ልጅ ወለደችለት፤ ስሙንም ዔር ብላ ጠራችው። **4** እንደገናም አረገዘችና ወንድ ልጅ ወለደችለት፤ ስሙንም አውናን አለችው። **5** አሁንም ደግማ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ስሙንም ሴሎም ብላ ጠራችው፣ እርሱንም የወለደችው ክዚብ በተባለ ቦታ ነበር። **6** ይሁዳ የመጀመሪያ ልጁን ዔርን ትዕማር ከምትባል ልጃገረድ ጋር አጋባው። **7** የይሁዳ የበኩር ልጅ ዔር ግን በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነበር፤ እግዚአብሔርም ቀሠፈው። **8** ይሁዳ አውናንን፣ “ዋርሳዋ እንደመሆንህ ከወንድምህ ሚስት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት በመፈጸም የወንድምህን ስም የሚያስጠራለት ዘር ተካለት አለው። **9** አውናን ግን የሚወለደው ልጅ የእርሱን ስም የሚያስጠራ እንደማይሆን ስላወቀ፣ ከወንድሙ ሚስት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት በፈጸመ ቁጥር የወንድሙን ስም የሚያስጠራ ልጅ እንዳይወለድ ዘሩን በምድር ላይ ያፈስ ነበር። **10** ይህም በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሆኖ ስለተገኘ፣ እርሱንም እግዚአብሔር በሞት ቀሠፈው። **11** ከዚያም ይሁዳ ምራቱን ትዕማርን፣ “ልጄ ሴሎም ለአካለ መጠን እስኪደርስ ድረስ ወደ አባትሽ ቤት ሄደሽ መበለት ሆነሽ ብትኖሪ ይሻላል” አላት፤ ይህን ያለውም፤ ሴሎም እንደወንድሞቹ ተቀሥፎ ይሞትብኛል ብሎ ስለፈራ ነበር። ትዕማርም እንዳላት ሄደች፤ በአባቷም ቤት ተቀመጠች። **12** ከብዙ ጊዜ በኋላ የሹዓ ልጅ፣ የይሁዳ ሚስት ሞተች። ይሁዳ ከሐዘኑ ከተጽናና በኋላ ከዓዶላማዊው ከሒራ ጋር የበጎቹን ጠጉር የሚሸልቱ ሰዎች ወዳሉበት ወደተምና ሄደ። **13** ሰዎቹም ለትዕማር፣ “አማትሽ የበጎቹን ጠጉር ወደሚሸልቱ ሰዎች ዘንድ ወደተምና እየሄዱ ነው” አሏት። ይህን እንድሰማች **14** የመበለትነት ልብሷን አውልቃ፣ ማንነቷ እንዳይታወቅ ፊቷን በሻሽ ተከናንባ ወደ ተምና በሚወስደው መንገድ ዳር ባለች ኤናይም በተባለች ከተማ መግቢያ በር ላይ ተቀመጠች፤ ይህን ያደረገችው፣ ሴሎም ለአካለ መጠን ቢደርስም፣ እርሷን እንዲያገባ አባቱ አለመፈለጉን ስላወቀች ነው። **15** ፊቷ በሻሽ ተሸፋፍኖ ሲያያት፣ ይሁዳ ዝሙት አዳሪ መሰለችው። **16** ምራቱ መሆኗን ባለማወቁ፣ እርሷ ወዳለችበት ወደ መንደሩ ዳር ጠጋ ብሎ፣ “እባክሽን አብሬሽ ልተኛ” አላት። እርሷም፣ “አብሬህ ብተኛ ምን ትሰጠኛለህ?” ብላ ጠየቀችው። **17** “ከመንጋዬ መካከል አንድ የፍየል ጠቦት እልክልሻለሁ” አላት። እርሷም “ጠቦቱን እስክትልክልኝ ድረስ ምን መያዣ ትሰጠኛለህ?” ብላ ጠየቀችው። **18** “ታዲያ ምን መያዣ ልስጥሽ?” አላት። እርሷም፣ “የማኅተም ቀለበትህን ከነማሰሪያው፣ እንደዚሁም ይህን በትርህን ስጠኝ” አለችው። የጠየቀችውን ሁሉ ሰጣትና አብሯት ተኛ፤ እርሷም አረገዘችለት። **19** ከዚያም ወደ መኖሪያዋ ተመልሳ፣ ሻሽዋን አውልቃ እንደወትሮዋ የመበለት ለብሷን ለበሰች። **20** ይሁዳ በመያዣ ስም የሰጣትን ዕቃዎች ለማስመለስ የፍየሉን ጠቦት በዓዶሎማዊ ወዳጁ እጅ ላከላት፣ እርሱ ግን ሊያገኛት አልቻለም። **21** “በኤናይም ከተማ መግቢያ ከመንገዱ ዳር የነበረች ያቺ ዝሙት አዳሪ የት ደረሰች?” ብሎ ዓዶሎማዊው ሰውዬ ጠየቀ። ሰዎቹም፣ “በዚህ አካባቢ እንደዚህ ያለች ዝሙት አዳሪ የለችም” አሉት። **22** ስለዚህ ወደ ይሁዳ ተመልሶ ሄደና፣ “ላገኛት አልቻልሁም፤ በዚያ የሚኖሩትም ሰዎች፥ ‘እንደዚህ ያለች ዝሙት አዳሪ እዚህ የለችም’ አሉኝ” ብሎ ነገረው። **23** ይሁዳም፣ “እንግዲህ መያዣውን እንደያዘች ትቅር አለዚያ መሳቂያ እንሆናለን። ለነገሩማ ይህን ፍየል ላክሁ፣ አንተም ፈልገህ አላገኘሃትም” አለ። **24** ከሦስት ወር ያህል በኋላ፣ “ምራትህ ትዕማር ዘማዊ ሆናለች፤ ከዚህም የተነሣ አርግዛለች” ተብሎ ለይሁዳ ተነገረው። ይሁዳም፣ “አውጧትና በእሳት ተቃጥላ ትሙት” አለ። **25** እርሷም ተይዛ በምትወሰድበት ጊዜ ለአማትዋ፣ “እኔ ያረገዝሁት የእነዚህ ዕቃዎች ባለቤት ከሆነ ሰው ነው” ስትል ላከችበት፤ ደግሞም፣ “የማኅተሙ ቀለበት ከነማንጠልጠያውና በትሩ የማን እንደሆነ እስቲ ተመልከት” አለችው። **26** ይሁዳም ዕቃዎቹን አውቆ፣ “ልጄ ሴሎም እንዲያገባት ባለማድረጌ፣ እርሷ ከእኔ ይልቅ ትክክል ናት” አለ። ከዚያም በኋላ ከእርሷ ጋር አልተኛም። **27** የመውለጃዋ ጊዜ እንደደረሰም ፅንሷ መንታ መሆኑ ታወቀ። **28** በምትወልድበትም ጊዜ አንደኛው እጁን አወጣ፤ አዋላጂቱም፣ “ይህኛው መጀመሪያ ወጣ” ስትል በእጁ ላይ ቀይ ክር አሰረችለት፤ **29** ነገር ግን፣ እጁን መልሶ ሲያስገባ ወንድሙ ተወለደ። አዋላጂቱም፣ “አንተ እንዴት ጥሰህ ወጣህ!” አለች፣ ከዚያም ስሙ ፋሬስ ተባለ። **30** ከዚያ በኋላ እጁ ላይ ቀይ ክር የታሰረለት ወንድሙ ተወለደ፣ ስሙም ዛራ ተባለ።

Genesis 38:1

በዚያም ወራት ይሁዳ
ይህ ስለ ይሁዳ የሚናገረውን አድስ የታሪኩን ክፍል ያስታውቃል (አድስ ክስተት መጀመር ስለማስታወቅ ይመልከቱ)

ኤራስ ወደተባለ ዓዶሎማዊ
ኤራስ በዓዶሎም የሚኖር ወንድ ሰው ስም ነው (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)

ሴዋ
ሴዋ ይሁዳን ያገባች ከነዓናዊ ሴት ነች (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)

Genesis 38:3

እርስዋም ጸንሣ
የይሁዳ ሚስት ጸንሣ

ዔር ተብሎ ተሠየመ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት: “አባቱ ዔር ብሎ ሰየመው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ስሙንም ... ጠራው
ሰየመው

ክዚብ
የቦታ ወይም የሀገር ስም ነው (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)

Genesis 38:6

ዔር
ይህ የይሁዳ ወንድ ልጅ ስም ነው:: በዘፍጥረት 38:3 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነበር
በእግዚአብሔር ፊት የሚለው ሀረግ እግዚአብሔር የዔርን ክፋት እንደአየው ያመለክታል:: አት: “ክፉ ነበርና እግዚአብሔር አየው” (ፊሊጣው አነጋገር ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ቀሠፈው
ክፉ ከመሆኑ የተነሣ እግዚአብሔር ቀሠፈው:: ይህ ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት “ስለዚህ እግዚአብሔር ቀሠፈው” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Genesis 38:8

አውናን
ይህ ከይሁዳ ወንድ ልጆች የአንዱ ስም ነው በዘፍጥረት 38:4 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)

ወደ ወንድምህ ሚስት ግባ
ይህ ታላቅ ወንድም አግብቶ ሳለ ልጅ ሳይወልድ ቢሞት ተከታይ ወንድሙ ወደ መበለትዋ በመግባት ሩካቤ ሥጋ በመፈጸም ዘርን የማስቀጠል ባህል እንደሆነ ያመለክታል መበለትዋ የመጀመሪያ ወንድ ከወለደች ያ ወንድ ልጅ የሞተው ወንድም ልጅ እንደሆነ በመቆጠር የሟቹን ሀብት ይወርሳል::

በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነበር
በእግዚአብሔር ፊት የሚለው ሀረግ እግዚአብሔር የአውናን ክፋት እንደአየው ያመለክታል:: አት: “ክፉ ነበርና እግዚአብሔር አየው” (ፊሊጣው አነጋገር ይመልከቱ)

እንዲሁም ደግሞ እግዚአብሔር ቀሠፈው
ያደረገው ነገር ክፉ ከመሆኑ የተነሣ እግዚአብሔር ቀሠፈው:: ይህ ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት “ስለዚህ እንዲሁ ደግሞ እግዚአብሔር ቀሠፈው” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 38:11

ምራቱ
የታላቅ ወንድ ልጁ ሚስት

ወደ አባትሽ ቤት
ይህም ማለት በዚህ በአባትዋ ቤት እንዲትኖር ነው:: አት “እናም በአባትሽ ቤት... ቢትኖሪ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ልጄ ሴሎም ለአካለ መጠን እስኪደርስ ድረስ
ይሁዳ ትዕማር ሴሎም ለአካለመጠን በደረሰ ጊዜ እንዲታገባው ያስባል:: አት “ልጄ ሴሎም ለአካለ መጠን በደረሰ ጊዜ ሊያገባሽ ይችላል” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ሴሎም
ይህ ከይሁዳ ወንድ ልጆች የአንዱ ስም ነው በዘፍጥረት 38:5 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)

እንደ ወንድሞቹ ተቀሥፎ ይሞትብኛል ብሎ ስለ ሠጋ
ሴሎም ትዕማርን ቢያገባ እንደ ወንድሞቹ ይሞትብኛል ብሎ ይሁዳ ሠግቶአል:: አት “እርሱ እርስዋን ካገባ እንደወንድሞቹ ይሞትብኛል ብሎ ስለሠጋ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 38:12

ሹዓ
ይህ የወንድ ሰው ስም ነው በዘፍጥረት 38:2 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)

ይሁዳ ከሀዘኑ ተጽናና
ይሁዳም ሀዘኑን ባቆመ ጊዜ

የበጎቹን ጸጉር ወደሚሸልቱት ሰዎች ወደ ተምና
ተምና የበጎቹንነ ጸጉም የሚሸልቱ ስዎች ወዳሉበት ሥፍራ

ተምና ... ኤናይም
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

እርሱና የእርሱ ጓደኛ ዓዶላማዊው ሒራ
ከዓዶላም ጓደኛው ሒራ አብሮት ሄደ

ሒራ ዓዶላማዊው
ሒራ የወንድ ሰው ስም ነው እናም ዓዶላም እርሱ የሚኖርበት ቀበሌ ስም ነው:: በዘፍጥረት 38:1 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ትዕማር ተነገራት
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት “አንድ ሰው ለትዕማር ነገራት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

እይው አማትሽ
ስሚ ፤ እዚህ “እይው” የሚለው ቃል የትዕማርን ትኩረት ለመሳብ ተጠቅሞአል::

አማትሽ
የባልሽ አባት

የመበለትነት ልብስ
መበለቶች የሚለብሱት ልብስ

ሻሸ
ሴቶች ፊታቸውንና ጭንቅላታቸውን ለመሸፈን የሚጠቀሙት ከስስ ጨርስ የተሰራ ልብስ

ራስዋን ተከናንባ
ይህም ሰዎች እንዳያውቃት ራስዋን በልብስ በመከናነብ ሸፈነች ማለት ነው ሴቶች ራሳቸውን መከናነብ የሚያስችላቸው ሰፋፊ ልብሶች በባህሉ የተለመዱ ናቸው አት ሰዎች እንዳያውቃት በሰፋፊ ልብሶች ተከናነበች (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

መንገድ ዳር
በመንገድ ዳር ወይም በመንገድ

ለእርሱ ሚስት ሆና አልተሰጠችም ነበር
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ይሁዳ ለሴሎም ሚስት አድርጐ አልሰጣትም ነበር” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Genesis 38:15

ፊትዋን ስለሸፈነች
ይሁዳ እንደ ጋለሞታ ያሰባት ፊትዋን ስለሸፈነች ብቻ ሳይሆን በከተማው መግቢያም ስለተቀመጠች ነው አት ጭንቅላትዋን ስለሸፈነችና ጋለሞቶች በሚቀመጡበት ቦታ ስለተቀመጠች ነበር (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ወደ እርስዋም አዘነበለ
ትዕማር በመንገዱ ዳር ነበረች አት እርስዋም ወደተቀመጠችበት ወደ መንገዱ ዳር ሄደ ወይም አዘነበለ(ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

እባክሽ ነዪ
እባክሽ ወደ እኔ ነዪ ወይም እባክሽ አሁነ ነዪ

ምራቱ
የልጁ ሚስት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Genesis 38:17

ከመንጋዬ
ከፍዬሎች መንጋዬ

ማኅተም ቀለበት ከነማሰሪያው .... በትር
ማኅተም ብር መሣይ በላዩ ላይ ቅርጽ የተቀረጸበት የቀለጠ ሰም ለመቅረጽ የሚጠቀምበት ነው ቀለበት ማኅተም ያለበትና ባለቤቱ በአንገት የሚያደረገው ነው በትር ከረጅም እንጨት የተሠራና በአዳጋች በመንገድ የሚጠቀሙበት ነው

ለእርሱም ጸነሰች
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት “እርሱም እርሷን አስረገዛት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Genesis 38:19

ሻሸ
ሴቶች ፊታቸውንና ጭንቅላታቸውን ለመሸፈን የሚጠቀሙት ከስስ ጨርስ የተሰራ ልብስ ነበር:: በዘፍጥረት 38: 14 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ

የመበለት ልብስዋን ለበሰች
መበለቶች የሚለብሱትን ልብስ ለበሰች:: በዘፍጥረት 38: 14 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

አዶሎማዊ
በአዶሎም ቀበለ የሚኖር ሰው በዘፍጥረት 38፡ 1 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

መያዣ የሰጣትን
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት “መያዣውን ለማስመለስ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ከሴቲቱ እጅ
እዚህ እጅ የሚለው ቃል በእርስዋ ቁጥጥር ሥር እንደሆነ አበክሮት ይሰጣል:: የሴቲቱ እጅ ሴቲቱን ይወክላል:: አት “ከሴቲቱ” (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

Genesis 38:21

አዶሎማዊ
በአዶሎም ቀበለ የሚኖር ሰው በዘፍጥረት 38 1 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

የአገሩ ሰዎች
በዚያ ከሚኖሩ ሰዎች እንዳንዶች

ቤተ ጣዖት ዝሙት አደሪዋ
በቤተ ጣዖት የሚታገለግል ዝሙት አዳሪ

ኤናይም
ይህ የቦታ ስም ነው በዘፍጥረት 38፡14 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ፡፡ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

አለዚያ መሳቂያ እንሆናለን
የሆነውን ነገር ሰዎች ከሰሙ በይሁዳ ይስቁበታል ይሣለቁበታል:: ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ወይም ደግሞ የሆነውን ሰዎች ካወቁ ይስቁብናል” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ እና ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Genesis 38:24

እንዲህም ሆነ
ይህ ሀረግ የታሪኩን አድስ አካል ጅማሬ ያመለክታል (አድስ ክስተት ስለማስታወቅ ይመልከቱ)

ለይሁዳ ተነገረው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “አንድ ሰው ለይሁዳ ነገረው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ምራትህ ትዕማር
ትዕማር የታላቅ ልጅህ ሚስት

ከዚህም የተነሣ ጸነሰች
ከዚህ የሚለው ቃል ከዝሙት ከፈጸመችው ዝሙት ማለት ነው ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ከዚህም አረገዘች” ወይም “አረገዘች” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

አምጡአት
አውጡአት

በእሳት ትቃጠል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “እንዲትሞት እናቃጥላታለን” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

እርስዋም ባወጡአት ጊዜ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “እነርሱ ባወጡአት ጊዜ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

አማትዋ
የባልዋ አባት

ማኅተም ቀለበት ከነማሰሪያው .... በትር
ማኅተም ብር መሣይ በላዩ ላይ ቅርጽ የተቀረጸበት የቀለጠ ሰም ለመቅረጽ የሚጠቀምበት ነው:: ቀለበት ማኅተም ያለበትና ባለቤቱ በአንገት የሚያደረገው ነው በትር ከረጅም እንጨት የተሠራና በአዳጋች በመንገድ የሚጠቀሙበት ነው:: (በዘፍጥረት 38: 18 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ)

ሴሎም
ይህ ከይሁዳ ወንድ ልጆች የአንዱ ስም ነው:: በዘፍጥረት 38፡5 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)

Genesis 38:27

በዚያን ጊዜ
ይህ ሀረግ የታሪኩ አድስ ክፍል መጀመሩን ያመለክታል (አድስ ክስተት ስለማታወቅ ይመልከቱ)

እነሆ
እነሆ የሚለው ከዚህ በፊት ያልታወቀው ትዕማር መንታ ልጆችን እንደተሸከመች እንድንገረም ለማድረግ ተጠቅሞአል

ስትወልድም እንዲህ ሆነ
እንዲህ ሆነ የሚለው ሀረግ በታሪኩ ዋና ክስተት ያመለክታል በቋንቋዎ ይህን የመሰለውን የመግለጽ አባባል ካለ ይጠቀሙ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አንደኛው እጁን አወጣ
ከሕጻኖች አንደኛው እጁን አወጣ

አዋላጅ
አንድ ሴት በሚትወልድበት ጊዜ የሚረዳት ሰው ነው በዘፍረት 35:17 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ

ቀይ ክር
ደማቅ ቀይ ክር

በእጁ
በአምባሩ ዙሪያ

Genesis 38:29

እነሆ
እነሆ የሚለው ቃል ለሚከተለው የሚያስገርም መረጃ ትኩረት እንድንሰጠው ነው

እንዴት ጥሰህ መጣህ!
ይህ ሁለተኛው ሕጻን ቀድም ሲወጣ አዋላጅዋ በማየት የተደነቀችውን የሚያሳይ ነው:: አት “እንዴት የራስህን መንገድ ጥሰህ ወጣህ!” ወይም “ሰንጥቀህ ቀድመህ ወጣህ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመለከቱ)

ስም ተሰጠው ወይም ተሰየመ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት “እርስዋ ስም ሰጠችው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ፋሬስ
የወንድ ልጅ ስም ነው ተርጓሚዎች እንደሚከተለው የግርጌ ማስታወሻ ሊጨምሩ ይችላሉ:: ፋሬስ የሚለው ስም ጥሶ መውጣት ማለት ነው:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ዛራ
ይህ የወንድ ልጅ ስም ነው ተርጓሚዎች እንደሚከተለው የግርጌ ማስታወሻ ሊጨምሩ ይችላሉ:: ዛራ የሚለው ስም ቀይ ክር ወይም ደማቅ ቀይ ክር ማለት ነው:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 39

1 ዮሴፍ ወደ ግብፅ ተወስዶ ነበር፤ ከፈርዖንም ሹማምንት አንዱ የነበረውም የዘበኞች አለቃ፣ ግብፃዊው ጴጥፋራ ወደዚያ ከወሰዱት ከእስማኤላውያን
ነጋዴዎች እጅ ገዛው። **2** እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ስለነበረ ኑሮው ተቃናለት፤ እርሱም በግብፃዊው አሳዳሪው ቤት ኖረ። **3** አሳዳሪው እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር
እንዳለና ሥራውንም ሁሉ እንዳከናወነለት ባየ ጊዜ፣ **4** ዮሴፍ በእርሱ ዘንድ ሞገስ አገኘ፣ የቅርብ አገልጋዩም ሆነ። ጲጥፋራ በቤቱ ላይ ሾመው፣ ያለውንም ሀብት
ሁሉ በኃፊነት ሰጠው። **5** ዮሴፍ በጲጥፋራ ቤትና ባለው ሀብት ሁሉ ላይ ከተሾመበት ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔር የግብፅዊውን ቤት ባረከ፣ የእግዚአብሔርም
በረከት በግቢም በውጭም ባለው የጲጥፋራ ሀብት ንብረት ሁሉ ላይ ሆነ። **6** ስለዚህ ጲጥፋራ ባለው ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጠው፣ የቀረበለትንም ከመመገብ
በስተቀር፣ ማናቸውንም ጉዳይ በዮሴፍ ላይ ጥሎ ነበር። ዮሴፍ ጥሩ ቁመና ያለውና መልከ-መልካም ነበር፤ **7** ከጊዜ በኋላ የጌታው ሚስት ዮሴፍን ተመልክታ
ስላፈቀረችው፣ “ና ከእኔ ጋር አብረን እንተኛ” አለችው። **8** እርሱ ግን ይህን ለመፈጸም ፈቃደኛ አልሆነም፤ እንዲህም አላት፤ “ጌታዬ ያለውን ሁሉ በኃላፊነት
ስለሰጠኝ፣ በቤቱ ውስጥ ስላልው ሁሉ ምንም የሚያውቀው ነገር የለም። **9** በዚህ ቤት ላይ ከእኔ የበለጠ ኃላፊነት ያለው ማንም የለም፣ ከአንቺ በቀር በእኔ
ቁጥጥር ሥር ያላደረገው ምንም ነገር የለም፤ ይኸውም ሚስቱ ስለሆንሽ ነው፤ ታዲያ፣ እኔ ይህን ክፉ ድርጊት በእግዚአብሔር ፊት እንዴት እፈጽማለሁ?” **10**
ይህንም ነገር በየዕለቱ ለዮሴፍ ትነግረው ነበር፤ እርሱም ከእርሷ ጋር ይተኛ ዘንድ ከእርስዋም ጋር ይሆን ዘንድ አልሰማትም። **11** አንድ ቀን ዮሴፍ ለሥራ ጉዳይ
ወደ ቤት ሲገባ በቤት ውስጥ አንድም ሠራተኛ አልነበረም፤ **12** እርሷም ልብሱን ጨምድዳ ይዛ፣ “በል አብረኸኝ ተኛ” አለችው። እርሱ ግን ልብሱን እጅዋ ላይ
ትቶላት ከቤት ሸሽቶ ወጣ። **13** እርሷም ልብሱን በእጅዋ ላይ ትቶ ከቤት ሸሽቶ መውጣቱን በተመለከተች ጊዜ፣ **14** አገልጋዮችዋን ጠርታ እንዲህ አለቻቸው፣
“እነሆ፣ ባለቤቴ ያመጣው ይህ ዕብራዊ ሊያዋርደኝ ነበር፤ ወዳለሁበት ክፍል ገብቶ ሊደፍረኝ ሞከረ፤ እኔ ግን ድምፄን ከፍ አድርጌ ጮኽሁ። **15** ዕርዳታ
ለማግኘትም መጮኼን በሰማ ጊዜ ልብሱን በአጠገቤ ትቶ ከቤት ሸሽቶ ወጣ።” **16** የዮሴፍ አሳዳሪ እስኪመጣ ድረስ ልብሱን በእርስዋ ዘንድ አቆየችው። **17**
በመጣም ጊዜ የሆነውን ታሪክ እንዲህ ስትል ዘርዝራ ነገረችው፤ “አንተ ወደዚህ የመጣኸው ዕብራዊ አገልጋይ ወዳለሁበት ክፍል ገብቶ ሊያዋርደኝ ነበር። **18**
ነገር ግን ድምፄን ከፍ አድርጌ በጮኽሁ ጊዜ ልብሱን በአጠገቤ ትቶ ከቤት ሸሽቶ ወጣ።” **19** “የአንተ አገልጋይ እንዲህ አደረገኝ” ብላ የነገረችውን ታሪክ
በሰማ ጊዜ የዮሴፍ አሳዳሪ እጅግ ተቆጣ። **20** ዮሴፍንም ወስዶ፣ የንጉሥ እስረኞች ወደታሠሩበት እስር ቤት አስገባው። **21** እግዚአብሔር ዘላለማዊ ፍቅሩን
ዐሳየው፣ በእስር ቤት አዛዡም ዘንድ ሞገስን ሰጠው። **22** ስለዚህ የእስር ቤቱ አዛዥ ዮሴፍን የእስረኞች ሁሉ አለቃ አደረገው፤ በእስር ቤት ላለውም ነገር ሁሉ
ኃላፊ ሆነ። **23** እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ሆኖ የሚያደርገው ነገር ሁሉ እንዲቃናለት ስላደረገ የእስር ቤት አዛዥ በዮሴፍ ቁጥጥር ሥር በነበረው ነገር ምንም
ዐሳብ አልነበረበትም።

Genesis 39:1

ዮሴፍ ወደ ግብጽ ወርዶ ነበር
ወደ ግብጽ መጓዝ ወደ ላይ ወደ ተስፋይቱ ምድር የመጓዝ ተጻራሪ ወደ ታች መውረድ ተደርጐ ይቆጠራል ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊገለጽ ይችላል:: አት “እስማኤላዊያን ዮሴፍን ወደ ግብጽ ወሰዱት” (ፈሊጣዊ አነጋገርና ተሻጋሪ ግሥ እና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

እግዚአብሔር የዮሴፍ ጋር ነበረ
ይህ እግዚአብሔር ዮሴፍን ረድቶታል ሁልጊዜም ከእርሱ ጋር ነበር ማለት ነው:: አት “እግዚአብሔር ዮሴፍን መራው አገዘውም” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

አሳዳሪው ቤት ኖረ
እዚህ ጸሓፊው በአሳዳሪው ቤት መሥራቱን በአሳዳሪው ቤት እንደመኖር ይናገራል:: በአሳዳሪዎቻቸው ቤት መሥራት የሚችሉት በጣም ታማኝ የሆኑ ሎሌዎች ብቻ ናቸው:: አት እርሱም በቤት ውስጥ ይሠራ ነበር (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 39:3

አሳዳሪው እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንዳለ አየ
አሳዳሪው እግዚአብሔር እርሱን እየረዳ እንደሆነ አየ ማለት ነው አት እግዚአብሔር እየረዳው እንደሆነ አሳዳሪው አየ (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ሥራውን ሁሉ እንዳከናወነለት
እግዚአብሔር የሚሠራው ሁሉ መከናወንለት አደረገ

ዮሴፍ በእርሱ ዘንድ ሞገስ አገኘ
ሞገስ ማግኘት በአንድ ሰው ተቀባይነትን ማስረገጥ ማለት ነው በእርሱ ዘንድ የሚለው ፈሊጣዊ አባባል በሰውዬው አመለካከት እንደሆነ ያመለክታል:: ተገቢ ትርጉሞች እነሆ 1) ጲጥፋራ በዮሴፍ ተደስቶአል 2) እግዚአብሔር በዮሴፍ ተደስቶአል (ፈሊጣዊ አባባል ይመልከቱ)

ጲጥፋራን አገለገለ
የጲጥፋራ የግል ሎሌው ነበር ማለት ነው

ጲጥፋራ ዮሴፍን በቤቱ ላይ ሾመው ያለውን ሀብት ሁሉ በኃላፊነት ሰጠው
ጲጥፋራ በቤቱና የጲጥፋራ በሆነው ሁሉ ላይ ለዮሴፍ በኃላፊነት ሰጠው

በእርሱ ኃላፊነት ሥር አደረገ
አንድ ነገር በአንድ ሰው ኃላፊነት ሥር ሲሆን ያ ሰው ያንን ነገር ለመንከባከብና ደኅንነቱን ለመጠበቅ ኃላፊነት አለው ማለት ነው:: አት “ዮሴፍ እንዲንከባከብ ሰጠው” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 39:5

ዮሴፍ በጲጥፋራ ቤትና ባለው ሀብት ሁሉ ላይ ከተሾመበት ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔር የግብጻዊውን ቤት ባረከ
ተውላጤ ስሞችን ከመጠቀምዎ በፊት “ዮሴፍ” እና “ግብጻዊው” የሚሉ ቃላትን መጠቀም ይችላሉ:: ግብጻዊው ዮሴፍን በቤቱና ባለው ሀብት ሁሉ ላይ ኃላፊነት ሰጠው እናም ከጊዜ ወደ ጊዜ በዮሴፍ ምክንያት እግዚአብሔር የግብጻዊውን ቤት ባረከ::

እንዲህም ሆነ
እነዚህ ሁለቱ ጥቅሶች ለሚቀጥለው ክስተት ዳራ መረጃ እንደሆኑ ለአንባቢያን ለመናገር ይህ ሀረግ ተጠቅሞአል

እርሱም እርሱን በቤቱና ባለው ሀብት ሁሉ ላይ ሾመው
ጲጥፋራ ዮሴፍን በቤቱና ባለው ተብት ሁሉ ላይ ሾመው

ባረከው
በሚባረከው ነገር ወይም ሰው መልካም ወይም ጠቃሚ ነገር እንዲደረግ ምክንያት መሆን ማለት ነው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የእግዚአብሔር በረከት ሆነ
እዚህ ጸሐፊው እግዚአብሔር የሰጠውን በረከት በአንድ ነገር ላይ እንደተቀመጠ መሸፈኛ አድርጐ ይናገራል:: አት: “እግዚአብሔር ባረከ” ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ

በግቢም በውጭም ባለው የጲጥፋራ ሀብት ንብረት ሁሉ
ይህ ቤት እረሻውንና ከብቶችን ያለመክታል የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት “በጲጥፋራ ቤትና በከብቶችና እርሻው ሁሉ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቀ መረጃ ይመልከቱ)

ጲጥፋራ ማንኛውንም ጉዳይ በዮሴፍ ቁጥጥር ሥር አድርጐ/በዮሴፍ ላይ ጥሎ ነበር
አንድ ነገር በአንድ ሰው ቁጥጥር ሥር ሲሆን ያ ሰው ሊጠብቀውና ሊንከባከበው ኃላፊነት አለው ማለት ነው አት: “ስለዚህ ጲጥፋራ ባለው ሁሉ ላይ ለዮሴፍ ስልጣን ሰጠው”

ከሚበላው እንጀራ በቀም ምንም የሚያውቀው አልነበረም
ምን ምግብ መመገብ እንዳለበት ከመወሰን በቀር በቤቱ ስላለው ማንኛውም ነገር አይጨነቅም ነበር ይህ በአዎንታዊ መንገድ ሊገለጽ ይችላል አት ጲጥፋራ ምን መመገብ እንደሚፈልግ ብቻ ማሰብ ነበረበት በቤቱ ስላለው ማንኛውም ነገር መጨነቅ የለበትም (ግምታዊ እውቀትና ጥልቀ መረጃ ይመልከቱ)

አሁንም
“አሁንም” የሚለው ቃል ስለ ዮሴፍ ዳራ መረጃ ለመስጠት በታሪኩ መስመር ውስጥ ጣልቃ ማስገባቱን ያመለክታል (ዳራ መረጃ ይመልከቱ)

ዮሴፍ መልከ መልካምና ውብ ነበር
ሁለቱም ቃላት ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው ዮሴፍ የሚያስደስት ቁመና እንዳለው ያመለክታሉ:: ጠንካራና ጥሩ ቁመና ነበረው:: አት: “ጠንካራና መልከመልካም ነበር”

Genesis 39:7

ከዚህ በኋላ እንደዚህ ሆነ
እናም ደግሞ ይህ ሀረግ አድስ ክስተት መጀመሩን ሊያመለክት ተጠቅሞአል (አዲስ ክስተት ማታወቅ ይመልከቱ)

እይው
ስሚው ዮሴፍ የጲጥፋራን ሚስት መስብ/ትኩረት ለማግኘት ይህን ቃል ተጠቅሞአል

ጌታዬ በቤቱ ውስጥ ስላለው ሁሉ ምንም የሚያውቀው ነገር የለም
“ጌታዬ በኃላፊነቴ ሥር ስላለው ስለቤቱ ሁሉ ምንም የሚያውቀው ነገር የለም”:: ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ጌታዬ ስለቤቱ ያምነኛል” (ድርብ አሉታዊነት ይመልከቱ)

ጌታዬ ያለውን ሁሉ በኃላፊነት ለእኔ ስለሰጠኝ
አንድ ነገር “በአንድ ሰው ኃላፊነት ሥር” ሲሆን ያ ሰው እንዲንከባከበውና እንዲጠብቀው ኃላፊነት አለው ማለት ነው:: አት: “ያለውን ሁሉ በኃላፊነት ስለሰጠኝ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ለዚህ ቤት ከእኔ የሚበልጥ ሰው የለም
እዚህ ጸሓፊው ኃላፊነትን እንደ ትልቅነት ይናገራል አት: “ከማንም ሰው የበለጠ ለዚህ ቤት ኃላፊነት አለኝ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ከአንቺ በቀር ያልሰጠኝ ነገር የለም
ይህ በአዎንታዊ መንገድ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “እርሱ ያለሰጠኝ ነገር ቢኖር አንቺን ብቻ ነው” (አሉታዊነትን በአዎንታዊነት የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

እንዴት ይህን ክፉ ድርጊት ፈጽሜ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት እሠራለሁ
ዮሴፍ ትኩረት ለመስጠት ጥያቄ ይጠቀማል ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጽ ይችላል አት ይህን ክፉ ድርጊት ፈጽሜ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት አልሠራም (አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

Genesis 39:10

በየዕለቱ ለዮሴፍ ትነግረው ነበር
ከእርስዋ ጋር እንዲተኛ በተደጋጋሚ ትጠይቀው ነበር ማለት ነው:: የዚህ ጥቅስ ሙሉ ትርጉሙ ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት: “ዮሴፍ ከእርስዋ ጋር እንዲተኛ ትጐተጉተው ነበር” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ከእርስዋም ጋር እንዲሆን
እንዲቀርባት

እንዲህም ሆነ
“እንዲሁም ደግሞ” የሚለው ሀረግ በታሪኩ አድስ ክስተት መጀመሩን ለማመልከት ነው (አዲስ ክስተት ስለማታወቅ ይመልከቱ)

ከቤቱ አገልጋዮችም አንድም ሰው
በቤቱ ከሚያገለግሉ ሰዎች ማንም

ሸሽቶ ከቤት ወጣ
“እናም ወዲያው ሮጦ ወደ ውጪ ወጣ” ወይም “እናም ወዲያው ሮጦ ከቤት ወጣ”

Genesis 39:13

እንዲህም ሆነ .... ጠራች
ከዚያም .... ጠራች እንዲህም ሆነ የሚለው ሀረግ በታሪኩ ሁለተኛውን ክስተት ለማመልከት ተጠቅሞአል (አዲስ ክስተት ስለማስታወቅ ይመልከቱ)

ሸሽቶ ወደ ውጭ ወጣ
ወዲያው ሮጦ ከቤት ወጣ

የቤትዋን ሰዎች
በቤትዋ የሚሠሩ ሰዎች

አያችሁ
“ተመልከቱ” ወይም “ሰማችሁ” ወይም “ስለሚናገረው ነገር ትኩረት አድርጉ”

ከእኔ ጋር ሊተኛ ወደ እኔ ገባ
እዚህ የጲጥፋራ ሚስት ዮሴፍ ሊይዛትና ከእርስዋ ጋር ሊተኛ እንደሞከረ ትከሳለች

እንዲህም ሆነ መጮሄን ሲሰማ
ድምጼን ከፍ አድርጌ መጮሄን ሲሰማ እንዲህም ሆነ የሚለው ሀረግ የተጠቀመው በታሪኩ ሁለተኛውን ክስተት ለማመልከት ነው (አዲስ ክስተት ስለማስታወቅ ይመልከቱ)

Genesis 39:16

ጌታውም
የዮሴፍ ጌታ ይህ ጲጥፋራን ያመለክታል::

እንዲህ ስትል ነገረችው
ይህን ነገር እንዲህ ብላ ነገረችው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወደ እኛ ያመጣሄው
“እኛ” የሚለው ቃል ጲጥፋራን ሚስቱንና ሌሎች በቤት ውስጥ ያሉትን ጠቃልላል (ሁሉ አቀፍ እኛን ይመልከቱ)

መሣለቂያ ሊያደርገኝ ወደ እኔ ገባ
መሣቂያ ሊያደርገኝ ወደ እኔ ገባ መሣለቂያ የሚለው ቃል ሊይዘኝና ከእኔ ጋር ሊተኛ የሚለውን አባባል በንኀብነት ወይም አንድን ነገር ለዘብ ባለ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚገለጽ ነው:: አት “ወዳለሁበት ገባ አስገድዶ ከእኔ ጋር ሊተኛ ሞከረ” (ንኀብነት ወይም አንድን ነገር ለዘብ ባለ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚገለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

እንዲህም ሆነ
“ከዚያም” የጲጥፋራ ሚስት ይህን ሀረግ የተጠቀመችው ዮሴፍ ከእርስዋ ጋር ለመተኛት መሞከሩን ለእርሱ የሚትነግረውን የታሪኩን ሁለተኛውን ክስተት ለማመልከት ነው::(አዲስ ክስተት ስለማታወቅ ይመልከቱ)

ሸሸቶ ወደ ውጭ ወጣ
ወዲያው ሮጦ ከቤት ወጣ

Genesis 39:19

እንዲህም ሆነ
“እንዲህም ሆነ” የሚለው ሀረግ በታሪኩ አዲስ ክስተት መጀመሩን ለማመልከት ተጠቅሞአል (አዲስ ክስተት ስለማስታወቅ ይመልከቱ)

ጌታውም
የዮሴፍ ጌታ ይህ ጲጥፋራን ያመለክታል ይህ መረጃ ግልጽ ሊደረግ ይችላል አት የዮሴፍ ጌታ ጲጥፋራ

እጅግ ተቈጣ
ጲጥፋራ እጅግ ተቈጣ

የንጉሡ እስረኞች ወደ ተጋዙበት እስር ቤት
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አተ ንጉሡ እስረኞችን ያኖረበት ቦታ ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ

በዚያ ነበረ
ዮሴፍ በዚያ ቆየ

Genesis 39:21

ነገር ግን እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ነበረ
እግዚአብሔር ለዮሴፍ ተጠነቀቀለት እናም ቸር ነበረ:: “ነገር ግን እግዚአብሔር ለዮሴፍ ቸር ነበር” ወይም “እግዚአብሔር ዮሴፍን ተንከባከበ” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

የቃል ኪዳን ታማኝነቱን ገለጸለት
“ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም “ታማኝ” ወይም “በታማኝነት” ሊገለጽ ይችላል:: አት ከእርሱ ጋር ለገባው ቃል ኪዳን ታማኝ ነበር ወይም በታማኝነት ወደደው (ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ)

በወህኑ ቤት አዛዡም ዘንድ ሞገስን ሰጠው
ይህም እግዚአብሔር የወህኑ ቤት አዛዥ ዮሴፍን እንዲቀበለውና እንዲንከባከበው አደረገው አት እግዚአብሔር የእስር ቤቱ አዛዥ በዮሴፍ እንዲደሰት አደረገው (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

የእስር ቤቱ አዛዥ
“የእስረኞች አስተዳደር” ወይም “በእስር ቤቱ ኃላፊነት የተሰጠው”

በዮሴፍ እጅ አሳልፎ ሰጣቸው
እዚህ “እጅ” የሚለው የዮሴፍን ኃይል/አቅም ወይም ታማኝ ኃላፊነት ይወክላል”” አት “ዮሴፍን አለቃ አደረገው” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

በዚያ ለሚደረገው ማንኛውም ነገር ዮሴፍ ኃላፊ ነበር
“ዮሴፍ በዚያ ለሚደረገው ነገር ሁሉ ኃላፊ ነበር”

እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለነበረ
ይህ እግዚአብሔር እንዴት እንደረዳውና እንደመራው የሚያመለክት ነው። አት “እግዚአብሔር ዮሴፍን ስለመራው” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

የሚያደርገውን ሁሉ እግዚአብሔር ያሳካለት ነበር
ዮሴፍ የሚያደርገውን ሁሉ እግዚአብሔር ያሳካለት ነበር

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 40

1 ከዚህም በኋላ የግብፅ ንጉሥ የመጠጥ አሳላፊውና የእንጀራ ቤት ኃላፊው ንጉሡን የሚያሳዝን በደል ፈጸሙ። **2** ፈርዖንም በመጠጥ አሳላፊዎቹ አለቃና በእንጀራ ቤቱ አዛዡ፣ በሁለቱም ሹማምንቱ ላይ እጅግ ተቆጣ፤ **3** በዘበኞቹ አለቃ ቤት ወዳለው ዮሴፍ ወደታሠረበት እስር ቤት አስገባቸው። **4** የዘበኞቹም አለቃ እስረኞቹን ለዮሴፍ አስረከባቸው፤ በእስር ቤትም ለጥቂት ጊዜ ቆዩ። **5** ታስረው የነበሩት የግብፅ ንጉሥ የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃና የእንጀራ ቤቱ አዛዥ፣ በአንድ ሌሊት የየራሳቸውን ሕልም ዐዩ፤ የሁለቱም ሕልም ለየራሱ የተለየ ፍቺ ነበረው። **6** በማግስቱ ጥዋት ዮሴፍ እነርሱ ወዳሉበት ክፍል በገባ ጊዜ ተክዘው አገኛቸውና፤ **7** “ዛሬ በፊታችሁ ላይ ሐዘን የሚታየው ለምንድን ነው?” አላቸው። **8** እነርሱም፣ “ሁለታችንም ሕልም ዐየን፤ ነገር ግን የሚተረጕመልን ሰው አጣን” ሲሉ መለሱለት። ዮሴፍም፣ “ሕልም የመተርጎም ችሎታ የሚሰጥ እግዝአብሔር ነው፣ ስለዚህ የእያንዳንዳችሁን ሕልም ንገሩኝ” አላቸው። **9** ስለዚህ የመጠጥ አሳላፊዎቹ አለቃ እንዲህ ሲል ሕልሙን ለዮሴፍ ነገረው፤ “ከፊት ለፊቴ አንዲት የወይን ተክል ዐየሁ፤ **10** ተክሏም ሦስት ሐረጎች ነበሯት፤ ወዲያው እቆጥቁጣ አበበች፤ የወይን ዘለላውም ወዲያው በሰለ። **11** የፈርዖንንም ጽዋ ይዤ ነበር፣ የወይኑን ፍሬ ለቅሜ በጽዋው ውስጥ ጨምቄ ጽዋውን በእጁ ሰጠሁት።” **12** ዮሴፍም እንዲህ አለው፤ “እንግዲህ የሕልሙ ትርጓሜ ይህ ነው፤ ሦስቱ ሐረግ ሦስት ቀን ነው፤ **13** በሦስት ቀን ውስጥ ፈርዖን ከእስር ቤት ያወጣሃል፣ ወደ ቀድሞ ሹመትህም ይመልስሃል፤ በፊት የመጠጥ አሳላፊ በነበርህበት ጊዜ ታደርግ እንደነበረው ኡሉ የፈርዖንን ጽዋ በእጁ ትሰጠዋለህ። **14** እንግዲህ፣ በጎ ነገር በገጠመህ ጊዜ፣ እኔን አስበህ ቸርነት አድርግልኝ፣ ስለ እኔም ለፈርዖን ንገርልኝ፤ ከዚህም እስር ቤት አስወጣኝ፤ **15** ከዕብራውያን ምድር ወደዚህ የመጣሁት በአፈና ነው፤ አሁንም ቢሆን እዚህ እስር ቤት የተጣልሁት አንዳች ጥፋት ኖሮብኝ አይደለም።” **16** የእንጀራ ቤት አዛዡም፣ ለመጠጥ አሳላፊዎቹ አለቃ ሕልም የተሰጠው ፍቺ ደስ የሚያሰኝ መሆኑን ሲሰማ፣ የራሱን ሕልም ለዮሴፍ እንዲህ ሲል ነገረው፤ “እኔም ደግሞ ሕልም አይቻለሁ፣ ሦስት መሶቦች በራሴ ላይ ተሸክሜ ነበር፤ **17** በላይኛው መሶብ ውስጥ ለፈርዖን የተዘጋጀ የተለያየ ምግብ ነበረበት፣ ነገር ግን ወፎች ምግቡን ከመሶቡ እያነሱ የበሉት ነበር።” **18** ዮሴፍም እንዲህ ሲል መለሰለት፤ “የሕልሙ ፍቺ ይህ ነው፤ ሦስቱ መሶብ ሦስት ቀን ነው፤ **19** በሦስት ቀን ውስጥ ፈርዖን ራስህን ካስቆረጠ በኋላ በእንጨት ላይ ይሰቅልሃል፤ ወፎችም ሥጋህን የበሉታል።” **20** በሦስተኛው ቀን የፈርዖን ልደት በዓል ስለነበር ለመኳንንቱ ሁሉ ግብዣ አደረገ፤ በዚያኑ ዕለትም የመጠጥ አሳላፊዎቹን አለቃና የእንጀራ ቤት አዛዡን ሹማምንቱ ካሉበት ከእስር ቤት አወጣቸው። **21** የመጠጥ አሳላፊዎቹን አለቃ ወደ ቀድሞ ሹመቱ መለሰው፤ እርሱም እንደ ቀድሞው ጽዋውን ለፈርዖን በእጁ ይሰጠው ጀመር፤ **22** የእንጀራ ቤት አዛዡን ግን ልክ ዮሴፍ እንደተረጎመላቸው ሰቀለው። **23** የሆነው ሆኖ፣ የመጠጥ አሳላፊዎቹ አለቃ ዮሴፍን አላስታወሰውም፤ ረሳው።

Genesis 40:1

ከዚህም በኋላ
ይህ ሀረግ የተጠቀመው በታሪኩ አዲስ ክስተት መጀመሩን ለማመልከት ነው። (አዲስ ክስተት ስለማስታወቅ ይመልከቱ)

የመጠጥ አሳላፊ
ይህ ለንጉሡ መጠጥ የሚያቀርብ ሰው ነው

እንጀራ ቤቱ
ይህ ለንጉሡ ምግብ የሚያዘጋጅ ሰው ነው

ጌታቸውን በደሉት
ጌታቸውን አስቆጡት

የመጠጥ አሳላፊዎቹ አለቃና የእንጀራ ቤቱ አዛዥ
ዋና የመጠጥ አሳላፊና ዋና እንጀራ አቅራቢ

በዘበኞቹ አለቃ ቤት ወዳለው እስር ቤት አስገባቸው
በዘበኞቹ አለቃ በሚተዳደረው የቤት ውስጥ እስር ቤት አስገባቸው

አስገባቸው
ንጉሡ ወደ እሥር ቤት አላስገባቸውም ነገር ግን እንዲታሠሩ አዘዛቸው። አት “እነርሱ እንዲያስገቡ አደረጋቸው” ወይም “ዘበኛው እንዲያስገባቸው አዘዘ” (ተዛማጅ ምትክ አባባሎችን የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

ዮሴፍ ወደጋዘበት እስር ቤት
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አት ይህ ዮሴፍ የነበረበት ተመሣሣይ እስር ቤት ነው ወይም ይህ ጲጥፋራ ዮሴፍን ያስገባበት ተመሣሣይ እስር ቤት ነው (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Genesis 40:4

በእስር ቤት ጥቂት ጊዜ ቆዩ
በእስር ቤት አያለ ጊዜያት ቀን ተቀመጡ

Genesis 40:6

ዮሴፍ ወደእነርሱ ገባ
ዮሴፍ ወደ መጠጥ አሳላፊውና እንጀራ አቅራቢው ገባ

እነሆም አዝነው አያቸው
እነሆም የሚለው ቃል ባየው ነገር ዮሴፍ እንዴት እንደተገረመ የሚያሳይ ነው:: አት “እነርሱን አዝነው በማየቱ ተገረመ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

አብረውት የነበሩ የፈርዖን ሹማምንት
ይህ የጠጅ አሳላፊዎች አለቃና የእንጀራ አቅራቢዎች አዛዥ ያመለክታል

በጌታው ግቢ በግዞት
በጌታው ግቢ በእስር ቤት፤ ጌታው የዮሴፍ ጌታ፤ የዘበኞች አለቃ የሚያመለክት ነው

ትርጓሜ ከእግዚአብሔር የማገኝ አይደለምን?
አጽንዖት ለመስጠት ዮሴፍ ጥያቄ ይመለከታል:: ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ትርጓሜ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው! ወይም ለሕልሞች ትርጉምን መስጠት የሚችል እግዚአብሔር ነው” (አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

እስቲ ንገሩኝ
ሕልማቸውን እንዲነግሩት ዮሴፍ ይጠይቃቸዋል:: አት “ሕልሞቻችሁን እባካችሁ ንገሩኝ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Genesis 40:9

የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ
ለንጉሡ መጠጦችን የሚያቀርብ ዋና ሰው ነው"" በዘፍጥረት 40: 2 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

በሕልሜ እንሆ የወይን ዛፍ በፊቴ ሆና አየሁ
"በሕልሜ የወይን ጣፍ በፋቴ ሆና አየሁ!" የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ ባየው ነገር እንደተደነቀና ዮሴፍ ትኩረት እንዲሰጠው ለማሳየት "እነሆ" የሚለውን ቃል ይጠቀማል::

ዘለላዎችዋም በሰሉ
ዘለላዎችዋም ተንዠርግገው በሰሉ

ጨመቅሁአቸው
ከእነዚያ የጁስ ጭማቂ አወጣሁ ማለት ነው አት ከእነዚያ ጁስ ጨምቄ አወጣሁ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 40:12

የዚህ ትርጓሜ ይህ ነው
የሕልሙ ትርጓሜ ይህ ነው

ሶስቱ ሐረግ ሶስት ቀን ነው
ሶስት ሐረጐች ሶስት ቀኖች ያመለክታሉ

በሶስት ቀኖች ውስጥ
እስከ ሶስት ቀኖች

ራስህን ከፍ ከፍ ያደርጋል
እዚህ ፊርዖን ከእስር ቤት የመጠጥ አሳላፊዎችን አለቃ የሚያወጣው ፈርዖን ከፍ ከፍ እንደሚያደርገው ተደርጐ ተነግሮአል:: አት "ከእስር ቤት ያወጣሃል" (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ወደ ቀድሞ ሹመትህ ይመልስሃል
ወደ ሥራህ ይመልስሃል

በነበርህበት ጊዜ
በነበርህበት ጊዜ ታደርግ እንደነበረው

Genesis 40:14

ቸርነት አድርግልኝ
ቸር ሁንልኝ

ስለእኔም ለፈርዖን ንገርልኝና ከዚህም እስር ቤት አስወጣኝ
ዮሴፍም የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ ስለእርሱ ለፈርዖን እንዲነግረው ከዚህም የተነሣ ፈርዖን ከእስር ቤት እንዲያስወጣው ማለት ነው:: አት: "ስለእኔ ለፈርዖን በመንገር ከእስር ቤት እንዲወጣ እርዳኝ" (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

በእርግጥ በአፈና ውስጥ ነኝ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት: "በእርግጥ ሰዎች አፍነው እምጥተውኛል" ወይም "በእርግጥ እስማኤላዊያን ይዘው አምጥተውኛል" (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ከዕብራዊያን ምድር
ዕብራዊ ሰዎች ከሚኖሩበት ምድር

አሁንም ቢሆን እዚህ እስር ቤት የተጣልሁት አንዳች ጥፋት ኖሮብኝ አይደለም
እናም ደግሞ እዚህ በግብጽ በሚርበት ጊዜ በእስር ቤት እንዲጣል የሚያደርገኝን ምንም ነገር አላደረግሁም

Genesis 40:16

የእንጀራ ቤት አዛዡም
ይህ ለንጉሡ ምግብ የሚያቀርብ መሪ ሰው እንደሆነ ያመለክታል:: በዘፍጥረት 40:2 ይህ እንዴት እንደተተረጐመ ይመልከቱ::

እኔም ደግሞ ሕልም አይቻለሁ እናም
እኔም ደግሞ ሕልም አይቻለሁ እናም በሕልሜ

እነሆም ሶስት መሶብ እንጀራ በራሴ ላይ ተሸክሜ ነበር
ሶስተ መሶብ እንጀራ በራሴ ላይ ተሸክሜ ነበር! እዚህ የእንጀራ ቤቱ አዛዥ "እነሆ" የሚለውን ቃል የሚጠቀመው ባየው ሕልም መገረሙንና ዮሴፍም ትኩረት እንዲሰጠው ለማሳየት ነው::

ለፈርዖን ከተዘጋጀው እንጀራ
ለፈርዖን ከተዘጋጀው ምግብ

Genesis 40:18

ፍቺው ይህ ነው
የሕልሙ ትርጉም ይህ ነው

ሶስቱ መሶቦች ሶስት ቀኖች ናቸው
ሶስት መሶቦች ሶስት ቀኖችን ይወክላሉ

ራስህን ከፍ ያደርጋል
ዮሴፍ በዘፍረት 40:13 ለመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ በሚናገርበት ጊዜ ደግሞ ራስህን ከፍ ያደርጋል የሚለውን ሀረግ ተጠቅሞአል እዚህ ግን የተለየ ትርጉም አለው አማራጭ ተገቢ ትርጉሞች: (1) በአንገትህ ገመድ በማሠር ራስህን ከፍ ያደርጋል ወይም (2) ራስህን በመቁረጥ ከፍ ያደርግሃል::

ሥጋ
የ "ሥጋ" ቀጥታ ትርጉሙ የአንድ ሰው አካል ክፍል ማለት ነው

Genesis 40:20

እንዲህም ሆነ በሶስተኛውም ቀን
ከዚያም በኋላ በሶስተኛውም ቀን እዚህ እንዲህም ሆነ የሚለው ሀረግ የተጠቀመው አዲስ ክስተትን ለማመልከት ነው (አዲስ ክስተት ስለማስታወቅ ይመልከቱ)

ግብር አበላ
ግብዣ ነበረው

የመጠጥ አሳላፊዎችን አለቃ
ይህ ለንጉሡ መጠጥን የሚያዘጋጅና የሚያቀርብ መሪ ሰው ነበር። በዘፍጥረት 40:2 እነዚህ ቃላት እንዴት እንደተተረጐሙ ይመልከቱ፡

የእንጀራ ቤት አዛዡን
ይህ ለንጉሡ ምግብን የሚያዘጋጅ መሪ ሰው እንደሆነ ያመለክታል:: በዘፍጥረት 40:2 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ

የመጠጥ አሳላፊዎቹን አለቃ ወደ ቀድሞ ሹመቱ መለሰው
የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ ሹመት ወይም ኃላፊነት እንደመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ ሥራው እንደሆነ ያመለክታል አት ለመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ ሥራውን መልሶ ሰጠው (ተዛማጅ ምትክ ቃላትን ስለመጠቀም ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ነገር ግን የእንጀራ ቤት አዛዡን ሰቀለው
ፈርዖን ራሱ አልሰቀለውም ይሁን እንጂ እንዲሰቀል አዘዘ አት የእንጀራ ቤት አዛዥ እንዲሰቀል አዘዘ ወይም ዘበኞቹ ወይም ጥበቃዎቹ የእንጀራ ቤት አዛዡን እንዲሰቅሉ አዘዘ (ተዛማጅ ምትክ ቃላትን ስለመጠቀም ይመልከቱ)

ልክ ዮሴፍ እንደተረጐመላቸው
ይህ ዮሴፍ ሕልማቸውን እንደተረጐመላቸው የሚለውን ያመለክታል አት የሁለቱን ሰዎች ሕልም ዮሴፍ እንደተረጐመላቸው እንዲሁ ሆነ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 41

1 ድፍን ሁለት ዓመት ካለፈ በኋላ ፈርዖን ሕልም ዐለም፤ ሕልሙም በዓባይ ወንዝ ዳር ቆሞ ነበር፤ 2 እነሆ፣ መልካቸው ያማረ፣ ሥጋቸው የወፈረ ሰባት ላሞች
ከወንዙ ወጥተው በወንዙ ዳር የበቀለውን ሣር ይበሉ ጀመር። 3 ቀጥሎም መልካቸው የከፋ አጥንታቸው የወጣ ሌሎች ሰባት ላሞች ከወንዙ ወጥተው
አስቀድመው ከወጡት ላሞች አጠገብ ቆሙ። 4 እነዚህ መልካቸው የከፋና አጥንታቸው የወጣ ላሞች፥ እነዚያን ያማሩና የወፈሩ ላሞች ሲውጡአቸው ዐየ፤
ከዚያም ፈርዖን ከእንቅልፉ ነቃ። 5 ፈርዖንም እንደገና እንቅልፍ ወስዶት ሳለ ሌላ ሕልም ዐየ። በሕልሙም በአንድ የእህል አገዳ ላይ ሰባት የዳበሩና ያማሩ የእሸት
ዛላዎች ዐየ፤ 6 ቀጥሎም የቀጨጩና ከበረሐ በተነሣ የምሥራቅ ነፋስ ተመትተው የደረቁ ሰባት የእሸት ዛላዎች ወጡ። 7 የቀጨጩት የእሸት ዛላዎች፤ ሰባቱን
የዳበሩና ያማሩ የእሸት ዛላዎች ዋጡአቸው፤ በዚህ ጊዜ ፈርዖን ከእንቅልፉ ነቃ፣ ነገሩ ሕልም ነበር። 8 በነጋታውም ፈርዖን መንፈሱ ታወከበት፣ ስለዚህ በግብፅ
አገር ያሉትን አስማተኞችና ጥበበኞች በሙሉ አስጠርቶ ሕልሞቹን ነገራቸው፣ ይሁን እንጂ፣ ሕልሞቹን ሊተረጕምለት የቻለ አንድም ሰው አልተገኘም። 9 በዚያን
ጊዜ የመጠጥ አሳላፊዎቹ አለቃ ፈርዖንን እንዲህ አለው፤ “የሠራሁት በደል ዛሬ ታወሰኝ። 10 ፈርዖን ሆይ! አንተ በእኔና በእንጀራ ቤት ኃላፊው ላይ ተቆጥተህ
በዘበኞች አለቃ ቤት እንድንታሰር አድርገህ ነበር፤ 11 በዚያ ሳለን በአንድ ሌሊት ሁለታችንም የተለያየ ሕልም ዐየን፤ የእያንዳንዳችንም ሕልም የተለያየ ትርጉም
ነበረው። 12 በዚያን ጊዜ የዘበኞች አለቃ አገልጋይ የሆን አንድ ዕብራዊ ወጣት ከእኛ ጋር እስር ቤት ነበር። ሕልማችንን በነገርነው ጊዜ፣ ፍቺውን ነገረን፤
ለእያንዳንዳችንም እንደ ሕልማችን ተረጎመልን፤ 13 ነገሩም ልክ እርሱ እንደተረጎመልን፤ እኔ ወደ ቀድሞ ሹመቴ ተመለስሁ፤ የእንጀራ ቤት አዛዡም ተሰቀለ። 14
ፈርዖን ዮሴፍን እንዲያመጡት ትዕዛዝ ሰጠ፤ ከእስር ቤትም በጥድፊያ ይዘውት መጡ፤ ጠጉሩንም ከተላጨና ልብሱን ከለወጠ በኋላ ፈርዖን ፊት ቀረበ 15
ፈርዖንም ዮሴፍን፣ “ሕልም ዐይቼ ነበር፣ ሕልሜን ሊተረጕምልኝ የቻለ አንድም ሰው አልተገኘም፣ አንተ ግን ሕልም ሲነገርህ የመተርጎም ችሎታ እንዳለህ ሰማሁ”
አለው። 16 ዮሴፍም ለፈርዖን እንዲህ ብሎ መለሰ፦ “ይህ በእኔ አይደለም፤ እግዚአብሔር ግን ለፈርዖን በበጎነት ይመልስለታል” 17 ፈርዖን ዮሴፍን እንዲህ
አለው፤ “ሕልሜ በዓባይ ወንዝ ዳር ቆሜ ነበር። 18 ሥጋቸው የወፈረና መልካቸው የማረ ሰባት ላሞች ከወንዙ ወጥተው በወንዙ ዳር የበቀለውን ሣር ሲበሉ
ዐየሁ። 19 ከእነርሱም በኋላ ዐቅመ ደካማ፣ መልካቸው እጅግ የከፋና አጥንታቸው የወጣ ሌሎች ሰባት ላሞች ወጡ፤ እነዚያን የመሰሉ የሚያስከፋ መልክ
ያላቸው ላሞች በግብፅ ምድር ከቶ ዐይቼ አላውቅም። 20 አጥንታቸው የወጣና አስከፊ መልክ ያላቸው ላሞች መጀመሪያ የወጡትን፣ ሥጋቸው የወፈረውን
ሰባቱን ላሞች ዋጧቸው። 21 ከዋጧቸውም በኋላ፣ ያው የበፊቱ መልካቸው ስላልተለወጠ እንደዋጧቸው ማንም ሊያውቅ አይችልም ነበር፤ ከዚያም ከእንቅልፌ
ነቃሁ 22 ደግሞም በአንድ የእህል አገዳ ላይ ሰባት የዳበሩና ያማሩ የእሸት ዛላዎች ዐየሁ፤ 23 ቀጥሎም የቀጨጩና የደረቁ ሌሎች ሰባት ዛላዎች ወጡ። 24
የቀጨጩት የእሸት ዛላዎችም ሰባቱን ያማሩ የእሸት ዛላዎች ዋጧቸው፤ ያየኋቸውንም ሕልሞች ለአስማተኞች ነገርሁ፣ ነገር ግን ሕልሞቹን ማንም ሊተረጕምልኝ
አልቻለም።” 25 ዮሴፍም ለፈርዖን እንዲህ አለው፤ “ሁለቱም የፈርዖን ሕልሞች ተመሳሳይና አንድ ዓይነት ናቸው፤ እግዚአብሔር ወደፊት የሚያደርገውን ለፈርዖን
ገልጦለታል። 26 ሰባቱ የሚያምሩ ላሞች ሰባት ዓመታት ናቸው፣ ሰባቱም የሚያማምሩ የእሸት ዛላዎች ሰባት ዓመታት ናቸው፤ ሕልሙም አንድና ተመሳሳይ ነው።
27 ከእነርሱም በኋላ አጥንታቸው የወጣ አስከፊ መልክ ያላቸው ሰባት ላሞች፣ ሰባት ዓመታት ናቸው፤ እንደዚሁም ፍሬ አልባ የሆኑትና በምሥራቅ ነፋስ
ተመትተው የደረቁት ሰባት የእሸት ዛላዎች ሰባት የራብ ዓመታት ናቸው። 28 አስቀድሜ ለፈርዖን እንደተናገርሁት እግዚአብሔር ወደፊት የሚያደርገውን ነገር
ለፈርዖን ገልጦለታል። 29 በመላው የግብፅ ምድር እጅግ የተትረፈረፈ ጥጋብ የሚሆንባቸው ሰባት ዓመታት ይመጣሉ። 30 በዚህ በኋላ ግን በተከታታይ ሰባት
የራብ ዓመታት ይሆናሉ። የራቡ ዘመን አገሪቱን እጅግ ስለሚጎዳት በግብፅ የነበረው ያለፈው የጥጋብ ዘመን ሁሉ ጨርሶ አይታወስም። 31 ከጥጋብ ዓመታት
በኋላ የሚመጣው የራብ ዘመን እጅግ ጽኑ ከመሆኑ የተነሣ፣ ቀደም ሲል የነበረው የጥጋብ ዘመን ፈጽሞ ይረሳል። 32 ሕልሙ ለፈርዖን በድጋሚ መታየቱ፣ ነገሩ
ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቆረጠ ስለሆነ ነው፤ ይህንንም እግዚአብሔር በቅርብ ጊዜ ይፈጽመዋል፤ 33 እንግዲህ ፈርዖን ብልኅና አስተዋይ ሰው ፈልጎ፣ በመላው
የግብፅ ምድር ላይ አሁኑኑ ይሹም። 34 እንደዚሁም በሰባቱ የጥጋብ ዓመታት ከሚገኘው ምርት፣ አንድ አምስተኛው እንዲሰበሰብ የሚያደርጉ ኃላፊዎችን
ይሹም። 35 እነርሱም በሚመጡት የጥጋብ ዓመታት ከሚገኘው ምርት ሁሉ ይሰብስቡ፤ በፈርዖንም ሥልጣን ሥር ያከማቹ፤ ለምግብ እንዲሆኑም በየከተማው
ይጠበቁ። 36 የሚከማቸው እህል፣ ወደፊት በግብፅ አገር ላይ ለሚመጣው የሰባት ዓመት ራብ መጠባበቂያ ይሁን፤ በዚህም ሁኔታ አገሪቱ በራብ አትጠፋም።
37 ዕቅዱም ፈርዖንና ሹማምንቱ ሁሉ መልካም ሆኖ አገኙት። 38 ፈርዖንም፣ “የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት እንደዚህ ያለ ሰው ልናገኝ እንችላለን?” ብሎ
ጠየቃቸው። 39 ፈርዖን ዮሴፍን እንዲህ አለው፣ “እግዚአብሔር ይህን ሁል ገለጠለህ እንዳንተ ያለ አስተዋይና ብልህ ሰው የለም። 40 አንተ በቤተ መንግሥቴ
የበላይ ትሆናለህ፤ ሕዝቤም ሁሉ ለሥልጣንህ ይገዛል፤ እኔ ከአንተ የምበልጠው በዙፋኔ ብቻ ይሆናል።” 41 ከዚያም፣ ፈርዖን ዮሴፍን፣ “በመላይቱ የግብፅ
ምድር ላይ ኃላፊ አድርጌሃለሁ” አለው። 42 ፈርዖንም ባለማኅተሙን ቀለበት ከጣቱ አውልቆ በዮሴፍ ጣት ላይ አደረገው፤ እንዲሁም ከጥሩ የተልባ እግር
የተሠራ ልብስ አለበሰው፤ በአንገቱም የወርቅ ሐብል አጠለቀለት። 43 በማዕረግ ከእርሱ ሁለተኛ ሰው አድርጎ በሠረገላ ላይ አስቀመጠው። ሰዎችም በፊቱ፣
“እጅ ንሡ” እያሉ ይጮኹ ነበር፤ በዚህ ሁኔታም በግብፅ ምድር ሁሉ ላይ ሾመው። 44 ከዝህ በኋላ ፈርዖን ዮሴፍን፣ “እኔ ፈርዖን ነኝ፤ ሆኖም በመላይቱ ግብፅ
ያለ አንተ ፈቃድ ማንም ሰው እጁን ወይም እግሩን ማንቀሳቀስ አይችልም” አለው። 45 ፈርዖን ዮሴፍን ጸፍናት ፐዕናህ ብሎ ስም አወጣለት። እንዲሁም አስናት
ተብላ የምትጠራውን ኦን ተብሎ የሚጠራው ከተማ ካህን የጶጢፌራ ልጅ በሚስትነት ሰጠው። 46 ዮሴፍ የግብፅ ንጉሥ ፈርዖንን ማገልገል ሲጀምር፣
ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ነበር። ዮሴፍም ከፈርዖን ፊት ወጥቶ የግብፅን ምድር በሙሉ ዞረ። 47 በሰባቱም የጥጋብ ዓመታት ምድሪቱ የተትረፈረፈ ሰብል ሰጠች።
48 በእነዚያ ሰባት የጥጋብ ዓመታት፣ ዮሴፍ በግብፅ አገር የተገኘውን ምርት ሰብስቦ በየከተሞቹ አከማቸ፣ በእያንዳንዱ ከተማ ከየአቅራቢያው የተመረተውን
እህል እንዲከማች አደረገ። 49 ዮሴፍ ብዛቱ እንደ ባሕር አሸዋ የሚሆን የእህል ሰብል አከማቸ፤ ሰብሉ እጅግ ከመብዛቱ የተነሣ ልኩን መስፈርና መመዝገብ
አልቻለም ነበር። 50 ሰባቱ የራብ ዓመታት ከመምጣታቸው በፊት የኦን ከተማ ካህን የጶጢፌራ ልጅ አስናት ለዮሴፍ ሁለት ወንድ ልጆች ወለደችለት። 51
ዮሴፍም፣ “እግዚአብሔር መከራዬን ሁሉ የአባቴንም ቤት እንድረሳ አድርጎኛል” በማለት የመጀመሪያ ልጁን ስም ምናሴ አለው። 52 እንደዚሁም “መከራ
በተቀበልሁበት ምድር እግዚአብሔር ፍሬያማ አደረገኝ” ሲል ሁለተኛ ልጁን ኤፍሬም አለው። 53 በግብፅ ምድር የነበረው ሰባቱ የጥጋብ ዘመን አለፈና 54
ዮሴፍ አስቀድሞ እንደተናገረው የሰባቱ ዓመት የራብ ዘመን ጀመረ። ሌሎች አገሮች ሁሉ ሲራቡ፣ በመላው የግብፅ ምድር መስፋፋት ሲጀመር፣ 55 ሕዝቡ ምግብ
ይሰጠን በማለት ወደ ፈርዖን ጮኸ። ፍርዖንም ግብፃውያኑን፣ “ወደ ዮሴፍ ሂዱና የሚላችሁን አድርጉ” አላቸው። 56 ራቡ በአገሩ ላይ እየተስፋፋ ስለሄደ፣ ዮሴፍ
ጎተራዎቹን ከፍቶ እህሉ ለግብፃውያን እንዲሸጥ አደረገ፤ ምክንያቱም ራቡ በመላይቱ ግብፅ ጸንቶ ነበር። 57 ራቡ በመላው ዓለም ጸንቶ ስለነበር፣ የየአገሩ ሰዎች
ሁሉ ከዮሴፍ ዘንድ እህል ለመሸመት ወደ ግብፅ ምድር መጡ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Genesis 41:1

እንዲህም ሆነ
ይህ ሀረግ የታሪኩ አድስ ክፍል መጀመሩን ያመለክታል በቋንቋዎ ይህን የሚገልጹበት መንገድ ካለ ያን ሊጠቀሙ ይችላሉ (አዲስ ክስተትን ማስታወቅ ይመልከቱ)

ድፍን ሁለት ዓመታት ካለፈ በኋላ
በእስር ቤት ከዮሴፍ አብረውት ስለነበሩት የፈርዖን መጠጥ አሳላፊዎች አለቃና እንጀራ ቤት አዛዥ ሕልሞችን ዮሴፍ ከተረጐመላቸው ሁለት ዓመታት ካለፈ በኋላ

እነሆም ቆሞ ነበር
እዚህ እነሆ የሚለው ቃል በሰፊው ታሪክ ሌላ ክስተት መጀመሩን ያመለክታል በቋንቋዎ ይህን የሚገልጹበት መንገድ ሊኖር ይችላል። አት “ቆሞ በመገኘቱ ገርሞት ነበር”

ቆሞ ነበር
ፈርዖ ቆሞ ነበር

መልካምና የወፈሩ
ጤናማና የወፈሩ

በውሃውም ዳር ባለው ቀጠማ ተሰማርተው ነበር
በወንዙ ዳር የበቀለውን ሣር ይበሉ ነበር

ቀጤማ
በረግረጋማ ቦታ የሚበቅል ቀጭንና ረጅም ሣር ነው

እነሆ ሌሎች ሰባት ላሞች
እዚህ እነሆ የሚለው ቃል ፈረዖን እንደገና ባየው ነገር እንደተገረመ ያሳያል

የከፉና የከሱ
ታማሚና የከሱ

ወንዝ ዳር
“በወንዝ ዳር” ወይም “ወንዝ ዳረቻ ላይ” ይህ በአንድ ወንዝ ዳር ጠርዝ የሚገኝ ከፍታ ያለው መሬት ማለት ነው::

Genesis 41:4

የከፉና የከሱ
“ደካማና የከሱ” በዘፍጥረት 41:3 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

መልካምና የወፈሩ
“ጤናማና የደለቡ ወይም በደንብ የበሉ” በዘፍጥረት 41:2 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

ነቃ
ከእንቅልፉ ነቃ

ሁለተኛ ጊዜ
“ሁለት” የሚለው ቃል ተራ ቁጥር ሁለት ነው:: አት “እንደገና” (ተራ ቁጥሮችን ይመልከቱ)

እነሆ ዛላዎች
እዚህ እነሆ የሚለው ቃል ፈርዖን ባየው ነገር እንደተገረመ የሚያሳይ ነው

የእሸት ዛላዎች
ዛላዎች ፍሬዎች የሚንዠረግጉበት የበቆሎ ተክል አካል ነው

በአንድ የእህል አገዳ ላይ
“በአንድ አገዳ ላይ ያፌራውን ወይም የተንዠረገገውን” አገዳ ወፍራምና ረጅም የተክል ክፍል ነው::

በአንዱ አገዳ ላይ የተንዠረገገና ያማረ
በአንድ አገዳ ጤናማና ያማረ

የቀጨጩና በምሥራቅ ንፋስ የተመቱ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት: “ያም ከምሥራቅ ደረቅ አየር የትነሳ የቀጨጩና በዋግ የተመቱ” (ተሻጋሪ ግሥና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

የምሥራቅ ንፋስ
የምሥራቅ ንፋስ ከረሃማ ተነሥቶ የሚነፍስ ነው። የምስራቅ ንፋስ ሙቀት እጅግ ጐጂ ነው።

ዛላዎች ወጡ
ዛላዎች አደጉ ወይም ተንዠረገጉ

Genesis 41:7

የቀጨጩ የእሸት ወይም የእህል ዛላዎች
እህል የተባለው ቃል የታወቀ ነው:: አት “የቀጨጩ የእህል ዛላዎች” (የተደበቁ ቃላትን የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ዋጡአቸው
በሉአቸው ሰው ምግብን እንደሚበላ የቀጨጩ የእሸት ዛላዎች ጤናማ የእሸት ዛላዎች ሲውጡ ፈርዖን በሕልሙ አየ

ሙሉና ፍሬያቸው የተንዠረገገውን የእሸት ዛላዎች
ጤናማና መልካም የእሸት ዛላዎች

በዘፍጥረት **41:5** የዚህ ተመሣሣይ ሀረግ እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ ነቃ
ከእንቅልፉ ነቃ

እነሆ
እዚህ እነሆ የሚለው ቃል ፈርዖ ባየው ነገር እንደተገረመ ያሳያል

ሕልም ነበር
ሕልም ሲያልም ነበር

እንዲህም ሆነ
ይህ ሀረግ የተጠቀመው የታሪኩ አድስ ክፍል መጀመሩን ለማመልከት ነው:: በቋንቋዎ ይህን የሚገልጹበት መንገድ ካለ ይጠቀሙ:: (አድስ ክስተት ስለማስታወቅ ይጠቀሙ)

መንፈሱ ታወከበት
እዚህ መንፈሱ የሚለው ቃለ የውስጥ ማንነቱን ወይም ስሜቱን ያመለክታል አት “በውስጥ ማንነቱ ታወከ” ወይም “ታወከ” (ተመሣሣይ ምትክ ቃል ስለመጠቀም ይመልከቱ)

ልኮና አስጠርቶ
አገልጋዮቹን እንደላካቸው መረዳት ይቻላል:: አት “እንዲጠሩ አገልጋዮቹን ላካቸው ወይም አገልጋዮቹ እንደጠሩ አዘዛቸው” (የተደበቁ ቃላትን የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

የግብጽ አስማተኞችንና ጥበበኞች
የጥንት ነገሥታት አስማተኞችንና ጥበበኞችን እንደአማካሪዎች ይጠቀሙ ነበር

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Genesis 41:9

የመጠጥ አሳላፊዎችን አለቃ
ይህ ለንጉሡ መጠጥን የሚያዘጋጅና የሚያቀርብ መሪ ሰው ነበር። በዘፍጥረት 40:2 እነዚህ ቃላት እንዴት እንደተተረጐሙ ይመልከቱ፡

የሠራሁት በደል ዛሬ ታወሰኝ
ዛሬ የሚለው ቃል የተጠቀመው አስንዎት ለመስጠት ነው በደሉ ቀደም ብሎ ለፈርዖን መናገር የነበረበት አንድ ነገር ነገር ግን ያልተናገረበት ነው:: አት “ለአንተ መናገር የረሳሁትን አሁን አስታወስኩ”

ፈረዖን ተቆጥቶ ነበር
የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ ፈርዖንን አንደ ሶስተኛ ወገን ሰው ያመለክታል ይህም አነስተኛ ኃላፊነት ያለው ከፍተኛ ኃላፊነት ያለው የሚያስቀምጥበት የተለመደ መንገድ ነው እርስዎ ፈርዖን ተቆጥተው ነበር (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

ከእርሱ አገልጋዮች ጋር
እዚህ እርሱ ፈርዖንን ያመለክታል አገልጋዮች የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃና የእንጀራ ቤት አዛዥ ያመለክታል:: አት “እኛ አገልጋዮችህ” (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

እኔንና የእንጀራ ቤት አዛዡን በዘበኞች አለቃ ግቢ አስሮን ነበር
እኔንና የእንጀራ ቤት አዛዡን በዘበኞች አለቃ ኃላፊነት በተሰጠው እስር ቤት እስሮን ነበር:: እዚህ “ቤት” እስር ቤትን ያመለክታል::

የዘበኞች አለቃ
ንጉሡ ጠባቂዎች ላይ ኃላፊነት የተሰጠው ወታደር ነው በዘፍጥረት 20:2-3 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

የእንጀራ ቤት አዛዥ
ለንጉሡ ምንብን የሚያዘጋጅ ዋና አስፈላጊ ሰው ነው። በዘፍጥረት 20:2-3 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

እርሱና እኔ በአንዲት ሌሊት ሕልም አየን
“እኛ ሁለታችን በአንድ ሌሊት ሕልም አለምን” እዚህ እኛ የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃንና እንጀራ ቤት አዛዡን ያመለክታል (ነጠላና ብዙ እኛ ይመልከቱ)

የእያንዳንዳችን ሕልም የራሱ የሆነ ትርጉም ነበረው
ሕልሞቻችን የተለያየ ትርጉም ነበራቸው

Genesis 41:12

አጠቃላይ መረጃ
የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ ለፈርዖ መናገሩን ቀጠለ

ከእኛ ጋር ነበር
በእስር ቤት ከእንጀራ ቤት አዛዥና ከእኔ ጋር ነበር

የዘበኞች አለቃ
ንጉሡ ጠባቂዎች ላይ ኃላፊነት የተሰጠው ወታደር ነው በዘፍጥረት 20:2-3 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

ሕልሞቻችንን በነገርነው ጊዜ ፊቺውን ነገረን
ሕልሞቻችንን ነገርነው እናም እርሱ ትርጉምቻቸውን ነገረን

ለእያንዳንዳችን እንደሕልማችን ተረጐመልን
እዚህ እርሱ ወይም እያንዳንዱ የሕልሙ ተርጓሚውን ሳይሆን የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃንና የእንጀራ ቤት አዛዥ በግል የሚያመለክት ነው አት ለእያንዳንዳችን ምን ሊሆን እንዳለ አስረዳን (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ወገን ሰው አጠቃቀም ይመልከቱ)

በዚያን ጊዜ
ይህ ሀረግ የተጠቀመው በታሪኩ አስፈላጊ ክስተት ለማመልከት ነው በቋንቋዎ ይህን መግለጽ የሚችሉበት መንገድ ካለ ይጠቀሙ

እርሱ እንደተረጐመልን ሆነ
ስለሕልሞቻችን እንደነገረን ሆነ

ፈርዖን ወደ ሹሜቴ መለሰኝ
እዚህ የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ ማከበሩን ለመግለጽ የፈርዖን የማዕረግ ስም ይጠቀማል:: አት ወደ ሥራዬ እንዲመለስ ፈቀድክልኝ (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

እርሱን ወይም ሌላኛውን
የእንጀራ ቤት አዛዡን

እርሱ ሰቀለው
እዚህ እርሱ ፈርዖንን ያመለክታል እና ይህም የእንጀራ ቤት አዛዡን እንዲሰቅሉት ፈርዖን ወታደሮቹን ማዘዙን ይወክላል አት እንዲሰቀል እርስዎ ወታደረችዎን አዝዘዋል:: (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽና ተዛማጅ ምትክ ቃላትን ስለመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ

Genesis 41:14

ፈርዖንም ሊኮ አስጠራ
ፈርዖን አገልጋዮቹን እንደላከ ይታወቃል አት ዮሴፍን እንዲያመጡት አገልጋዮችን ላከ (የተደበቁ ቃሎችን የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ከግዞት ቤት
“ከእስር ቤት” ወይም “ከወህኒ”

ጸጉሩን ከተላጨ
በፈርዖን ፊት ለመቅረብ በመዘጋጀት ጊዜ የፊትና የራስ ጸጉርን መላጨት የተለመደ ተግባር ነበር

ፈርዖን ፊት መጣ
እዚህ መጣ የሚለው ገባ በሚለው ሊገለጽ ይችላል አት ፈርዖን ፊት ገባ (መጣ እና ገባ ይመልከቱ)

የሚተረጉመውም አልተገኘም
ሊተረጉምልኝ የቻለ አንድም ሰው አልተገኘም

አንተ የመተርጐም ችሎታ አለህ
አንተ ትርጉሙን ሊትነግረኝ ትችላለህ

ይህ በእኔ አይደለም
እኔ የመተርጐም ችሎታ የለኝም

እግዚአብሔር በደኅንነት ለፈርዖን ይመልስለታል
እግዚአብሔር ለፈርዖን የሚሻውን ትርጉም ይሰጠዋል

Genesis 41:17

እነሆ ቆሜ ነበር
ስለሚያስገርመው መረጃ ዮሴፍ ትኩረት እንዲሰጠው ፈርዖን “እነሆ” የሚለውን ቃል ይጠቀማል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በዐባይ ወንዝ ዳር
በዐባይ ወንዝ ዳርቻ የለውን ከፍታ የለውን መሬት ያመለክታል:: በዘፍጥረት 41:3 የዚህ ተመሣሣይ ሀረግ እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: አት “በዐባይ ወንዝ ዳር”

እነሆ ሰባት ላሞች
ስለሚያስገርመው መረጃ ዮሴፍ ትኩረት እንዲሰጠው ፈርዖን “እነሆ” የሚለውን ቃል ይጠቀማል

የወፈሩና ያማሩ
“የተቀለቡ/የደለቡና ጤናማ” በዘፍጥረት 41:2 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

በቀጠማዎች ውስጥ ወይም በመስኩ ይሰማሩ ነበር
በወንዙም ዳር ያለውን ሣር ይመገቡ ነበር:: በዘፍጥረት 41:2 የዚህ ተመሣሣይ ሀረግ እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ።

Genesis 41:19

እነሆ ሰባት ሌሎች ላሞች
ስለሚያስገርመው መረጃ ዮሴፍ ትኩረት እንዲሰጠው ፈርዖን “እነሆ” የሚለውን ቃል ይጠቀማል

የከፉና የከሱ
አቅሜ ደካሞችና የከሱ ወይም የቀጨጨ በዘፍጥረት 41:3 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ

እንደዚህ የሚያስከፉ
“አስከፊ” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ቅጽል ሊተረጐም ይችላል:: አት “የሚያስከፉ ላሞች” ወይም “የማይጠቅሙ የሚመስሉ ላሞች” (ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ)

የወፈሩ ላሞች
“የደለቡ ወይም የተቀለቡ ላሞች” በዘፍጥረት 41:2 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

እንደዋጧቸው ምንም ሊታወቅ አይችልም ነበር
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “የከሱ ላሞች የወፈሩትን መዋጣቸውን ማንም ሊነግረው እስከማይችል ነበር:: (ተሻጋሪ ግሥና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Genesis 41:22

አጠቃላይ መረጃ
ፈርዖን ሕልሙን ለዮሴፍ መናገሩን ቀጠለ

በሕልሜ አየሁ
ይህ ፈርዖን ከነቃና ተመልሶ ከተኛ በኋላ ያየውን ሕልም ይጀምራል። አት “እንደገናም ሕልም አለምሁ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

እነሆ ሰባት የእሸት ዛላዎች
ስለሚያስገርመው መረጃ ዮሴፍ ትኩረት እንዲሰጠው ፈርዖን “እነሆ” የሚለውን ቃል ይጠቀማል::

ሰባት የእሸት ዛላዎች
የእሸት ወይም የእህል የሚለው አባባል የታወቀ ነው:: አት “ሰባት የእህል ዛላዎች” (ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

በአንድ አገዳ ሲወጡ
“በአንድ አገዳ ሲንዝረግጉ” አገዳ ወፍራምና ረጅም የተክል አካል ነው:: በዘፍጥረት 41:5 ይህን ሀረግ እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

እነሆ ሰባት ሌሎች የእሸት ዛላዎች
ስለሚያስገርመው መረጃ ዮሴፍ ትኩረት እንዲሰጠው ፈርዖን “እነሆ” የሚለውን ቃል ይጠቀማል::

የጠወለጉ
የደረቁና ፍሬ አልባ የሆኑ

በምሥራቅ ነፋስ
“ከበረሃማ ቦታ የሚነፍሰው የምሥራቅ ንፋስ” የምሥራቁ ንፋስ ሙቄት አብዛኛውን ጊዜ ለእህሎች እጅግ አደገኛ ነበር::

ተንዝረገገ
አደገ ወይም ፍሬ ሰጠ

የቀጨጩ የእሸት ወይም የእህል ዛላዎች
የእህል የሚለው ቃል የታወቀ ነው በዘፍጥረት 41:7 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ አት የቀጨጩ የእህል ዛላዎች (የተደበቁ ቃላትን የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ዋጧቸው
“በሉ” ፈርዖን ያለመው ሕልም ሰው ምግብን እንደሚበላ ጤናማ ያልሆኑ የበቆሎ እህሎች ጤናማ ያልሆኑትን እንደበሉ ነው:: በዘፍጥረት 41:7 የዚህ ተመሣሣይ ሀረግ እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

የሚችል ማንም አልተገኘም
የሚችል አንድም አልተገኘም ወይም ማንም አልቻለም

Genesis 41:25

የፈርዖን ሕልሞች ተመሣሣይ ናቸው
ትርጉሞችም ተመሣሣይ ናቸው የሚል አንድምታ አለው:: አት “ሁለቱም ሕልሞች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ሊያደርግ ያለውን ለፈርዖን አስታወቀው
ዮሴፍ ፈርዖንን እንደሳስተኛ ወገን ሰው ያናግረዋል ይህ አክብሮትን መግለጫ መንገድ ነው:: እንደ ሁለተኛ ወገን ሰው መግለጽ ይቻላል:: አት “ቶሎ ሊያደርግ ያለውን እያሳየህ ነው” (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

Genesis 41:27

አጠቃላይ መረጃ
ዮሴፍ የፈርዖንን ሕልም መተርጐም ይቀጥላል።

የከሱና አስከፊ መልክ ያላቸው ላሞች
የቀጨጩና ዐቅሜ ደካማ ላሞች በዘፍጥረት 41:3 የዚህ ተመሳሳይ ሀረግ እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ

በምሥራቅ ነፋስ የተመቱ ሰባት የቀጨጩ የእሸት ዛላዎች
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ከምሥራቁ ሙቀት አዘል ነፋስ የተነሣ የቀጨጩ ሰባት የእህል ዛላዎች” (ተሻጋሪ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ይህን ለፈርዖን የተናገርኩትን ... ለፈርዖን ገልጦለታል
ዮሴፍ ፈርዖንን እንደ ሶስተኛ ወገን ሰው ያናግረዋል ይህም አክብሮች መግለጫ መንገድ ነው:: በሁለተኛ ወገን ሰው መልክ ልገለጽ ይችላል:: “እንደተናገርኩህ እነዚህ ይደረጋሉ..... ፈርዖን ለአንተ ገልጦልሃል” (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እይ ሰባት
“እኔ የሚናገረው እውነትና ጠቃሚ ነውና ትኩረት ስጥ፤ ሰባት”

በመላው የግብጸ ምድር እጅግ የተትረፈረፈ ጥጋብ የሚሆንባቸው ሰባት ዓመታት ይመጣሉ
ጊዜ እንደሚመጣና በወቅቱ በአንድ ቦታ እንደሚሆን ይህ ስለጥጋብ ዓመታት ይናገራል:: አት “የተትረፈረፈ ምግብ በግብጽ በመላው የግብጽ ምድር የሚሆንበት ሰባት ዓመታት ይመጣሉ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 41:30

አጠቃላይ መረጃ
ዮሴፍ የፈርዖንን ሕልምች መተርጐም ቀጠለ

ከዚህ በኃላ ሰባት የራብ ዓመታት ይሆናሉ
ወደ አንድ ቦታው ተንቀሳቅሶ እንደሚመጣ ነገር ተደርጐ ስለ ሰባት ዓመታት ራስ ተነግሮአል አት ከዚም በኋላ እጅግ ጥቂት ምግብ የሚሆንበት ሰባት ዓመታት ይሆናሉ (ዘይቤይዊ አነጋገር ይመልከቱ)

የራቡ ዘመን አገሪቱን እጅግ ስለሚጐዳት ... የጥጋቡ ዘመን ሁለ ጨርሶ አይታወስም::
....የሚመጣው የራብ ዘመን እጅግ ጽኑ ከመሆኑ የተነሣ የጥጋብ ዘመን ፈጽም ይረሳል:: ዮሴፍ ለጉዳዩ አጽንዖት ለመስጠት አንድን ሀሳብ በሁለት መንገድ ይገልጻል (ተመሣሣይ ተጓዳኝ አባባሎችን ይመልከቱ)

በግብጽ ምድር የጥጋብ ዘመን ሁሉ ይረሳል
ምድር ሰዎችን ያመለክታል ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “የግብጽ ሰዎች የተትረፈረፈ ምግብ የነበረበትን ዓመታት ሁሉ ይረሳሉ” (ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤና ተሻጋሪ ግሥና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

አገሪቱን ይጐዳሉ
አገር የሚለው የአገሪቷን መሬት ሰዎችና መላውን የአገሪቷን አካል ያመለክታል (ምትክ ቃላትን የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

ከሚመጣው ራብ የተነሣ
ይህ ተከትሎ እንደሚመጣ እንደ አንድ ነገር ስለሚመጣው ራብ ወይም ድርቅ ይናገራል። አት “ከዚያ በኋላ በሚሆነው ራብ ወይም ድርቅ የተነሣ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ሕልሙ ለፈርዖን በሁለት መልክ በድጋሚ መታየቱ ነገሩ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቈረጠ ስለሆነ ነው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “እግዚአብሔር ሁለት ሕልሞችን የሰጠህ ነገሮች በእርግጥ እንደሚከሰቱ ለማሣየት ነው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Genesis 41:33

አጠቃላይ መረጃ
ዮሴፍ ለፈርዖን መናገሩን ቀጠለ

አሁንም
ይህ በዚህን ጊዜ ማለት አይደለም ነገር ግን ስለሚቀጥለው ጠቃሚ ነጥብ ትኩረት እንዲሰጥበት ነው

እንግዲህ ፈርዖን ... ይፈልግ
ዮሴፍ ለፈርዖን እንደ ሶስተኛ ወገን ሰው ይናገራል ይህ አክብሮትን የመግለጫ መንገድ ነው በሁለተኛ ወገን ሰው መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “አንተ ፈርዖን ፈልግ” (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

በግብጽ ምድር ላይም ይሹመው
ይሹመው ማለት ኃላፊነት ይስጠው ማለት ነው። አት “በግብጽ ግዛት ላይ ኃላፊነት ይስጠው ወይም በግብጽ ግዛት ላይ ይሹመው (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

የግብጽ ምድር
እዚህ ምድር በግብጽ ምድር ያሉ ሰዎችንና ሁሉን ነገር ይወክላል (ተመሣሣይ ተዛማጅ ምትክ ቃላት አጠቃቀም ዘይቤ ይመልቱ)

በግብጽ ምድር ከሚገኘው የእህል ምርት አንድ አምስተኛውን ይውሰዱ
አምስተኛ የሚለው ቃል ክፍልፋይ ነው:: የግብጽን ምድር እህል ምርት በአምስት መደብ ይክፈሉ፤ ከዚያም አንዱን እጅ ወይም መደብ ይውሰዱ (ክፍልፋዮችን ይመልከቱ)

በሰባት የጥጋብ ዓመታት
የተትረፈረፈ ምግብ ባለባቸው ሰባት ዓመታት

Genesis 41:35

አጠቃላይ መረጃ
ፈርዖንን መምከሩን ቀጠለ

እነርሱም ይሰብስቡ
ሹማምንት ወይም ኃላፊዎች እንዲሰበስቡ ይደረግ

በእነዚህ በሚመጡት ጥጋብ ዓመታት
እነዚህ ዓመታት አንድ ነገር ተጉዞ ወደ አንድ ቦታ እንደማመጣ እንደሚመጡ ይናገራል:: አት “ቶሎ ሊመጡ ያሉ የጥጋብ ዓመታት” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

በፈርዖን ሥልጣን ሥር ያከማቹ
በፈርዖን ሥልጣን ሥር የሚለው ሀረግ ፈርዖን ሥልጣን ይስጣቸው ማለት ነው አት እህሉን ለመሰብሰብ የፈርዖንን ሥልጣን ይጠቀም ፈሊጣዊ አነገጋር ይመልከቱ

እነርሱም ይህን ይጠብቁ
እነርሱ የሚለው ቃል እህሉ እንዲጠበቅ የሚያዝዙ ሹማምንቶችንና ወታደሮች ያመለክታል አት ሹማምቶች እህሉ እንዲጠበቅ በዚያው ወታደሮችን ይመድቡ ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ

እህሉ ለምድሪቱ ምግብ ይሆናል
ምድሪቱ ሰዎችን ትወክላለች አት እህሉም ለሰዎች ምግብነት ይሆናል (ምትክ ቃላት ስለመጠቀም ይመልከቱ)

በዚህ ሁኔታ ምድሪቱ በራብ አትጠፋም
እዚህ “ምድር” ሰዎችን ይወክላል:: ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አት “በዚህ መንገድ በራብ ጊዜ ሰዎች አይራቡም” (ምትክ ቃላት አጠቃቀም ዘይቤ ወይም ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Genesis 41:37

ይህ ምክር ለፈርዖንና በሎለዎቹ ፊት መልካም ሆነ
ፊት ማየትን የሚያመለክት ሲሆን ማየት ማሰብን ወይም ብያኔን ያመለክታል አት ፈርዖንና ሎሌዎቹ ይህ መልካም እቅድ ሆኖ አገኙት

ሎሌዎች
የፈርዖ ሹማምንት

እንደዚህ ያለ ሰው
ዮሴፍ የገለጸው ዓይነት ሰው

የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት
የእግዚአብሔር መንፈስ የሚኖርበት

Genesis 41:39

እንዳንተ ያለ ብልህ የለም
እንዳንተ ያለ ውሳኔ አቅራቢ የለም:: በዘፍጥረት 41:33 ብልህ እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

አንተ የቤተመንግሥቴ የበላይ ትሆናለህ
እዚህ “ቤት” የፈርዖን ቤተመንግሥትና በቤተመንግሥቱ ያሉ ሰዎችን ይወክላል:: የበላይ የሚለው ሀረግ ዮሴፍ የበላይ ኃላፊነት ይሰጠዋል ማለት ነው:: አት በቤተመንግሥቴ በሁሉም ላይ ሥልጣን ይሰጥሃል:: (ምትክ ቃላት ስለመጠቀም ዘይቤና ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ሕዝቤ ሁሉ ለሥልጣኔ ይገዛል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል በሕዝቤ ላይ ገዥ ትሆናለህና አንተ የሚታዝዘውን ያደርጋሉ:: (ተሻጋሪ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

በዙፋኔ ብቻ
እዚህ ዙፋን ፈርዖን እንደንጉሥ ገዥ እንደሆነ ይገልጻል:: አት “በንጉሥነት ሚናዬ ብቻ”

እየው አድርጌሃለሁ
“እየው” የሚለው ቃል ፈርዖን በሚቀጥለው ለሚናገረው አጽንዖት ይሰጣል:: አት “እየው አድርጌሃለሁ”

በመላይቱ የግብጽ ምድር ላይ ኃላፊ አድርጌሃለሁ
የበላይ አድርጌሃለሁ ማለት ሥልጣን ሰጥቼሃለሁ ማለት ነው እዚህ ምድር ሰዎችን ያመለክታል አት በግብጽ ምድር ባለው በማንኛውም ላይ ኃላፊነት ሰጥቼሃለሁ (ምትክ ቃል የመጠቀም ዘይቤና ፈሊጣዊ አነጋገር ይጠቀሙ)

Genesis 41:42

ፈርዖንም ባለማኅተሙን ቀለበት አውልቆ .... የወርቅ ሐብል አጠለቀለት
እነዚህ ሁሉ ድርጊቶች የሚያመለክቱት ዮሴፍ ያቀደውን ሁሉ እንዲያደርግ ፈርዖን ለዮሴፍ ሥልጣን መስጠቱን ነው (ምልክታዊ ድርጊት የመልከቱ)

ባለማኅተሙ ቀለበት
ይህ ቀለበት የፈርዖን ማኅተም የተቀረጸበት ነው:: ይህም ያቀደውን እንዲያከናውን ለዮሴፍ ገንዘብና ሥልጣንን ሰጠው::

ከጥሩ የተልባ እግር የተሠራ ልብስ
የተልባ እግር የተሠራ ልብስ ሰማያዊ አበባ ካለው የተልባ እግር የተሠራ ለስላሳ ጠንካራ ልብስ ነው::

የእርሱም በሆነው ሁለተኛው ሠረገላ ላይ አስቀመጠው
ይህ ድርጊት ለሰዎች ግልጽ የሚያደርገው የፈርዖን ሁለተኛ ሰው ዮሴፍ ብቻ መሆኑን ነው (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

ስገዱ ወይም እጅ ንሡ
ስገዱና ዮሴፍን አክብሩ እጅ መንሣትና መስገድ ክብርንና አክብሮትን የመስጠት ምልክት ነው (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

ፈርዖን በምድሪቱ ባለው ማንኛውም ላይ ሾመው
ማንኛውም ላይ ሾመው የሚለው ሀረግ ሁሉ ላይ ስልጣን ሰጠው ማለት ነው:: እዚህ ምድር ሰዎችን ያመለክታል በዘፍጥረት 41:41 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: አት “በግብጽ ባለው ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጠሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገርና ምትክ ቃላት አጠቃቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

Genesis 41:44

እኔ ፈርዖን ነኝ ... ያለ አንተ
ፈርዖን የራሱን ሥልጣን አጽንቶ ይናገራል። አት “እንደ ፈርዖን እኔ የማዝዘው ያለአንተ”

ያላንተ ማንም እጁንም እግሩንም አያንሣ
እዚህ “እጅና እግር” የሰዎችን ድርጊቶች ይወክላሉ:: አት “ማንኛውም ሰው ምንም ነገር ያለፈቃድህ በግብጽ አያድርግ ወይም ማንኛውም ሰው ምንም ነገር በግብጽ ከማድረጉ በፊት ያንተን ፈቃድ ይጠይቅ” (ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

ማንም ሰው
እዚህ “ሰው” ወንድም ሆነ ሴት በአጠቃላይ ማንንም ሰው ያመለክታል:: (በወንድ ጾታ የተገለጹ ቃላት ለሴት ጾታም መሆናቸውን ይመልከቱ)

ጸፍናት ፐዕናህ
የእስራኤል ቤተሰብ አባላት ሄኖኅ ፌሉሶ አስሮንና ከርሚ...ይሙኤል ያሚን ኦሃድ ያኪን ጾሐርና ሳኡል ...ጌድሶን ቀዓትና ሜራሪ፤ እነዚህ ሁሉ የወንድ ሰው ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጎም ይመልከቱ)

Genesis 46:12

ዔር አውናን ሴሎም
እነዚህ ይሁዳ ከሚስቱ ከሰዋ የወለዳቸው ወንዶች ልጆች ነበሩ:: በዘፍጥረት 38:3-5 እነዚህን ስሞች እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ::

ፋሬስና ዛራ
እነዚህ ይሁዳ ከምራቱ ከታማር የወለዳቸው ወንዶች ልጆች ነበሩ:: በዘፍጥረት 38:29-30 እነዚህን ስሞች እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ::

ኤስሮም ሐሙል ... ቶላ ፋዋ ዮብ ... ሺምሮን... ሴሬድ ኤሎን... ያሕልኤል
እነዚህ ሁሉ የወንድ ሰው ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጎም ይመልከቱ)

ዲና
ይህ የልያ ሴት ልጅ ስም ነው በዘፍጥረት 30:21 ይህን ስም እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ::(ስሞችን ስለመተርጎም ይመልከቱ)

የወንዶችና የሴቶች ልጆች ቁጥር ሠላሣ ሶስት ነበር
እዚህ ወንዶች ልጆችና ሴቶች ልጆች የያዕቆብ ወንዶችና ሴቶች ልጆች እና የልያ የልጅ ልጆች ያመለክታል አት በአንድነት 33 ወንዶችና ሴቶች ልጆችና የልጅ ልጆች ነበረው (ቁጥሮች ይመልከቱ)

Genesis 46:16

ጽፎን... ሐጊ ሹኒ... ኤስቦን ዔሪ አሮዲና... አርኤሊ....የምና ...የሱዋ የሱዊና... በሪዓ ... ሐቤር... መልኪኤል
እነዚህ ሁሉ የወንድ ሰው ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጎም ይመልከቱ)

ሤራሕ
ይህ የሴት ስም ነው (ስሞችን ስለመተርጎም ይመልከቱ)

ዘለፋ
የልያ ሴት አገልጋይ ስም ነው:: በዘፍጥረት 29:24 ይህን እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጎም ይመልከቱ)

ለያዕቆብ የወለደቻቸው እነዚህ ወንዶች ልጆች በአንድነት አሥራ ስድስት ናቸው
ይህ ከዘለፋ የተወለዱ አሥራ ስድስት ልጆች የልጅ ልጆችና የልጁ ልጅ ልጆች ናቸው (ቁጥሮች ይመልከቱ)

Genesis 46:19

አስናት
የሴት ስም ነው:: በዘፍጥረት 41:45 ይህን እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጎም ይመልከቱ)

ጾጥፌራ
የወንድ ሰው ስም ነው:: በዘፍጥረት 41:45 ይህን እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጎም ይመልከቱ)

የኦን ካህን
ኦን የጸሐይ አምላክ ረሐ አምልዕኮ ማዕከል ያለባትና የጸሐይ ከተማ ደግሞም ሄልዮቱ የተባለች ከተማ ነች:: በዘፍጥረት 41:45 ይህን እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጎም ይመልከቱ)

ቤላ ቤኬር አስቤል ጌራ ናዕማን አኪ ሮስ ማንፌን ሑፊምና አርድ
እነዚህ የወንድ ሰዎች ስሞች ናቸው:: (ስሞችን ስለመተርጎም ይመልከቱ)

በአጠቀላይ አሥራ አራት ናቸው
ራሔል የወለደቻቸው 14 ወንዶችና የልጅ ልጆች ናቸው

Genesis 46:23

ሑሺም ያሕጽኤል ጉኒ ዬጽርና ሺሌም
እነዚህ የወንድ ሰዎች ስሞች ናቸው:: (ስሞችን ስለመተርጎም ይመልከቱ)

ባላ
የራሔል ሴት ባሪያ ወይም አገልጋይ ስም ነው:: በዘፍጥረት 29:29 ይህን እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጎም ይመልከቱ)

በአጠቃላይ ሰባት ነበሩ
ይህ ባላ የወለደቻቸው 7 ልጆችና የልጅ ልጆች እንደሆኑ ያመለክታል (ቁጥሮች ይመልከቱ)

Genesis 46:26

ስድሳ ስድስት
66 (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

ሰባ
70 (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

Genesis 46:28

በፊቱ የጌሤምን መንገድ እንዲያሳየው
የጌሜምን መንገድ እንዲያሳያቸው

ዮሴፍ ሰረገላውን አዘጋጀና ... ወጣ
እዚህ “ዮሴፍ” አገልጋዮቹን ወይም ባሪያዎቹን ይወክላል:: አት “የዮሴፍ አገልጋዮች ሠረገላውን አዘጋጁለትና ዮሴፍም ....ወጣ” (ምትክ ቃላት ይጠቀሙ)

እስራኤልን ሊገናኘው .....ወጣ
“ወደ ላይ ወጣ” የሚለው ሀረግ የተጠቀመው ዮሴፍ አባቱን ሊገናኘው ወደ ከፍታማ ሥፍራ ስለተጓዘ ነው:: አት “እስራኤልን ሊገናኘው ሄዴ”

አንገቱን አቀፈና ረጅም ጊዜ አለቀሰ
እንገቱ ላይ ተጠመጠመና ረጅም ጊዜ አለቀሰ

አሁን ቢሞት እይቆጨኝ
“አሁን ለሞት ተዘጋጅቻለሁ” ወይም “አሁን እንግዲ የሚሞተው በደስታ ነው”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አንተ ገና በሕይወት ሳለህ ፊትህን አይቻለሁና
እዚህ “ፊት” ሙሉ ሰው ይወክላል”” ያዕቆብ ዮሴፍን በማየቱ የተሰማውን ደስታ ይገልጻል:: አት “አንተን እንደገና በሕይወት ስላየሁህ” (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

Genesis 46:31

የአባቱን ቤት
እዚህ ቤት ቤተሰቡን ይወክላል:: አት “የአባቱን ቤተሰብ” ወይም “የአባቱን ቤተሰዎች” (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

ወደ ፈርዖን ወጥቼ እናገረዋለሁ
ወደ አንድ ትልቅ ባለሥልጣን ሄዶ መናገር ወደ ላይ ወጣ የሚለውን ሀረግ መጠቀም የተለመደ ነበር አት ለፈርዖን ለመናገር እሄዳለሁ

ለፈርዖን እነግረዋለሁ፡ ወንድምቼ ... ያላቸውን ሁሉ
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስን ይዞአል ይህ በተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ወንድሞቼ ...ያላቸውን ሁሉ... ለፈርዖን እነግረዋለሁ” (ጥቅሶችን በጥቅስ ውስጥና ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

Genesis 46:33

እንዲህም ሆነ
ይህ ሀረግ የተጠቀመው በታሪኩ ስለተከሰተው ዋና ክስተት ለማመልከት ነው። በቋንቋዎ ይህንን የሚገልጹበት መንገድ ካለ የጠቀሙ

ሥራችሁ ምንደነው ብሎ ቢጠይቃችሁ
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስን ይዞአል:: ይህ በተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ምን ሥራ ታከናውናላችሁ ብሎ ቢጠይቃችሁ” (ጥቅሶችን በጥቅስ ውስጥና ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

እንዲህ በሉት እኛ ባሪያዎችህ.... እኛም አባቶቻችንም...
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስን ይዞአል:: ይህ በተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት “እንዲህ በሉት....እኛና አባቶቻችን ሁላችን...” (ጥቅሶችን በጥቅስ ውስጥና ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

የአንተ ባሪያዎች
የዮሴፍ ቤተሰቦች ለፈርዖን ሲናገሩ ራሳቸውን ባሪያዎችህ ብለው ማቅረብ አለባቸው:: ይህ ለአንድ ታላቅ ባለሥልጣን የሚነገርለት መንገድ ነው:: ይህም እንደ አንደኛ ወገን ሰው ሊገለጽ ይችላል:: አት “እኛ አገልጋዮችህ” (አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

በግ ጠባቂ ሁሉ ለግብጻዊያን ርኩስ/ ጸያፍ ነውና
“ጸያፍ” የሚለው ረቂቅ ስም “የሚያስጠላ” በሚለው ቅጽል ስም ሊተረጐም ይችላል:: አት “ግብጻዊያን የከብት ጠባቂዎችን እንደ ጸያፍ ይቆጥሩ ነበር” (ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 47

1 ዮሴፍም ወደ ፈርዖን ሄዶ፣ “አባቴና ወንድሞቼ በጎቻቸውን፣ ፍየሎቻቸውን እንዲሁም ያላቸውን ሁሉ ይዘው ከከነዓን አገር መጥተው በጌሤም ሰፍረዋል” አለው። 2 ከወንድሞቹም መካከል አምስቱን መርጦ፣ ፈርዖን ፊት አቀረባቸው። 3 ፈርዖን የዮሴፍን ወንድሞች፣ “ሥራችሁን ምንድነው?” ሲል ጠየቃቸው። እነርሱም ፈርዖንን፣ “እኛ አገልጋዮችህ ልክ እንደአባቶቻችን ከብት አርቢዎች ነን” አሉት። 4 ደግሞም፣ “በከነዓን ምድር ራቡ እጅግ የጸና በመሆኑ በጎችና ፍየሎች የሚሰማሩበት በማጣታቸው፣ ለጊዜው እዚህ ለመኖር መጥተናል፤ አሁንም ባሮችህ በጌሤም ምድር እንድንኖር እንድትፈቅድልን እንለምንሃለን” አሉት። 5 ፈርዖንም ዮሴፍን እንዲህ አለው፤ “አባትንህና ወንድሞችህ ወደ አንተ መጥተዋል፤ 6 የግብፅ ምድር እንደሆነ በእጅህ ነው፤ አባትህንና ወንድሞችህን ምርጥ በሆነው ምድር አስፍራቸው፤ በጌሤም ይኑሩ። ከመካከላቸው ልዩ ችሎታ ያላቸው መኖራቸውን የምታውቅ ከሆነ፣ የከብቶቼ ጎላፊዎች አድርጋቸው።” 7 ከዚህ በኋላ ዮሴፍ አባቱን ያዕቆብን ቤተ መንግሥት አግብቶ በፈርዖን ፊት አቀረበው፤ ያዕቆብ ፈርዖንን ከመረቀው በኋላ 8 ፈርዖን፣ “ለመሆኑ ዕድሜህ ምን ያህል ነው?” ሲል ያዕቆብን ጠየቀው። 9 ያዕቆብም ለፈርዖን፣ “በምድር ላይ በእንግድነት ያሳለፍሁት ዘመን 130 ዓመት ነው፤ ይህም አባቶቼ በእንግድነት ከኖሩበት ዘመን ጋር ሲነጻጸር አጭር ነው፤ ችግር የበዛበትም ነበር” ሲል መለሰለት። 10 ከዚያም ያዕቆብ ፈርዖንን መርቆ፣ ተሰናብቶት ወጣ። 11 ዮሴፍም አባቱንና ወንድሞቹን በግብፅ እንዲኖሩ አደረገ፤ ፈርዖን በሰጠውም ትእዛዝ መሠረት ምርጥ ከሆነው ምድር ራምሴን በርስትነት ሰጣቸው። 12 ዮሴፍም ለአባቱ፣ ለወንድሞቹና ለመላው የአባቱ ቤተ ሰዎች በልጆቻቸው ቁጥር ልክ ቀለብ እንዲሰፈርላቸው አደረገ። 13 በመላው ምድር እህል ባለመኖሩ ራቡ እየጸና ሄደ፤ ከዚህ የተነሣም ግብፅና ከነዓን በራብ እጅግ ተጎዱ፤ 14 ዮሴፍ የግብፅና የከነዓን ሰዎች እህል በመሸመት የከፈሉትን ገንዘብ ሁሉ ሰብስቦ ወደ ፈርዖን ቤተ መንግሥት አስገባ። 15 የግብፅና የከነዓን ሕዝቦችም ገንዘባቸው ባለቀ ጊዜ፣ ግብፃውያን ሁሉ ወደ ዮሴፍ ቀርበው፣ “የምንበላው እህል ስጠን፣ ገንዘባችን አልቆብናል፤ ዓይንህ እያየ እንዴት በራብ እንለቅ?” አሉት። 16 ዮሴፍም ከብቶቻችሁን አምጡ፣ ገንዘባችሁ ካለቀ በከብቶቻችሁ ለውጥ እህል እሰጣችኋለሁ አለ። 17 ስለዚህ ከብቶቻቸውን ወደ ዮሴፍ አምጡ፤ እርሱም በፈረሶቻቸው፣ በበጎቻቸው፣ በፍየሎቻቸው፣ በከብቶቻቸውና በአህዮቻቸው ለውጥ እህል ሰጣቸው። በከብቶቻቸው ልዋጭ ባገኙት ምግብ በዚያ ዓመት ሳይራቡ እንዲያልፉ አደረጋቸው። 18 ያም ዓመት ካለፈ በኋላ ሕዝቡ በሚቀጥለው ዓመት ወደ ዮሴፍ መጥተው እንዲህ አሉት፣ “እንግዲህ ከጌታችን የምንሰውረው ምንም ነገር የለም፤ ገንዘባችን አልቆአል፤ ከብቶቻችንንም አስረክበንሃል፤ እንግዲህ ለጌታችን የምንሰጠው፣ ከሰውነታችንና ከመሬታችን በቀር ሌላ ምንም ነገር የለንም። 19 ታዲያ እያየኸን እንዴት እንለቅ? መሬታችንም ለምን ጠፍ ሆኖ ይቅር? እኛንና መሬታችንን ውሰድና በለውጡ እህል ስጠን፤ እኛ የፈርዓን አገልጋዮች እንሆናለን፤ መሬታችንም የእርሱ ይሁን፣ እኛም እንዳንሞት መሬታችንም ጠፍ ሆኖ እንዳይቀር የምንዘራው ዘር ስጠን። 20 ስለዚህ ዮሴፍ የግብፅን ምድር ሁሉ ለፈርዖን ገዛለት፤ ራቡም እጅግ ስለጸናባቸው ግብፃውያን ሁሉ መሬታቸውን ሸጡ፣ ምድሪቱም የፈርዖን ርስት ሆነች። 21 ዮሴፍ በግብፅ አገር ዳር እስከ ዳር ያሉት ሰዎች ሁሉ የንጉሡ አገልጋዮች እንዲሆኑ አደረገ። 22 ሆኖም ዮሴፍ የካህናቱን መሬት አልገዛም፤ ምክንያቱም ካህናቱ ከፈርዖን ቋሚ አበል ስለሚያገኙ እርሱም ከሚሰጣቸው አበል ምግብ ያገኙ ስለነበረ መሬታቸውን አልሸጡም። 23 ዮሴፍ ሕዝቡን እንዲህ አላቸው፣ “እነሆ፣ ዛሬ እናንተንም መሬታችሁንም ለፈርዖን ገዝቻችኋለሁና ይህን ዘር ወስዳችሁ በመሬት ላይ ዝሩ። 24 መከሩ በሚሰበሰብበት ጊዜ ግን ከአምስት እጅ አንዱን ለፈርዖን ታስገባላችሁ፣ ከአምስት እጅ አራቱን ደግሞ ለመሬታችሁ ዘር፣ እንዲሁም ለራሳችሁ፣ ለቤተ ሰቦቻችሁና ለልጆቻችሁ ምግብ ታደርጉታላችሁ።” 25 እነርሱም፣ “እንግዲህ ሕይወታችንን አትርፈህልናል፤ በጌታችን ፊት ሞገስ ካገኘን ለፈርዖን ገባሮች እንሆናለን” አሉት። 26 ስለዚህ ዮሴፍ የምርቱ አንድ አምስተኛ ለፈርዖን እንዲገባ የሚያዝ የመሬት ሕግ አወጣ፤ ይህም ሕግ እስከ ዛሬ ይሠራበታል። በፈርዖን እጅ ያልገባው መሬት የካህናቱ ብቻ ነው። 27 በዚህ ጊዜ እስራኤላውያን በግብፅ አገር በጌሤም ይኖሩ ነበር፣ በዚያም ሀብት ንብረት አፈሩ፤ ቁጥራቸውም እጅግ እየበዛ ይሄድ ጀመር። 28 ያዕቆብ በግብፅ ዐሥራ ሰባት ዓመት ኖረ፣ ዕድሜውም አንድ መቶ አርባ ሰባት ዓመት ነበር። 29 እስራኤልም የሚሞትበት ጊዜ መቃረቡን እንደተረዳ ልጁን ዮሴፍን አስጠርቶ እንዲህ አለው፤ “በአንተ ዘንድ ሞገስ ካገኘሁ እጅህን በጭኔ ላይ አኑረህ፣ በጎነትንና ታማኝነትን ልታደርግልኝ ቃል ግባልኝ፤ በምሞትበት ጊዜ በግብፅ አትቅበረኝ፤ 30 እኔም ከአባቶቼ ጋር ሳንቀላፋ ከግብፅ አውጥተህ እነርሱ በተቀበሩበት ቦት ቅበረኝ” ዮሴፍም፣ “እሺ፣ እንዳልኸኝ አደርጋለሁ” አለ። 31 ያዕቆብ፤ “በል ማልልኝ” አለው። ዮሴፍም ማለለት፣ እስራኤልም በአልጋው ራስጌ ላይ ሆኖ ጎንበስ አለ።

Genesis 47:1

ዮሴፍ ሄዶ ለፈርዖን ነገረው ....ከወንድምቹም አምስት ሰዎችን ወስዶ በፈርዖን ፊት አቀረባቸው
UDB ክስተቶች በቅደም ተከተል ሲያስቀምጥ ULB ጸሐፊው እንዳስቀመጠ ይዘረዝራል (የክስተቶች ቅደም ተከተል ይመልከቱ)

Genesis 47:3

እኛ ባሪያዎችህ የበግ አርቢዎች ነን
ባሪያዎችህ በጎችን እናረባለን

ባሪያዎችህ
የዮሴፍ ወንድሞች ራሳቸውን እንደ “ባሪያዎችህ” ያቀርቡታል:: ይህ ብዙ ኃላፊነት ላለው ሰው የሚነገርለት መደበኛ መንገድ ነው:: ይህም እንደ አንደኛ ወገን ሰው ሊገለጽ ይችላል:: አት “እኛ ባሪያዎችህ ወይም እኛ” (አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

እንደ አባቶቻችን
“እኛና ቅድመ አባቶቻችን ሁላችን” ወይም “እኛና አባቶቻችን ሁሉ”

በዚህ ምድር ለጊዜው ለመኖር መጥተናል
በግብጽ ለጊዜው ለመኖር መጥተናል

በጎች የሚሠማሩበት ሥፍራ የለምና
በጎች የሚሠሩበት ሣር የለምና

አሁንም
ይህ በዚህን ጊዜ ማለት አይደለም ነገር ግን ለሚቀጥለው ዋና ነገር ትኩረት ለመስጠት ነው::

Genesis 47:5

የግብጽ ምድር በፊትህ ናት
“የግብጽ ምድር ለአንተ ክፍት ነው” ወይም “መላው የግብጽ ምድር በአንተ እጅ ነው”

በመልካም ምድር አባትህንና ወንድሞችህን አኑራቸው በጌሤም ምድር
አባትህንና ወንድሞችህን ምርጥ በሆነው በጌሤም ምድር አኑራቸው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከመካከላቸው ልዩ ችሎታ ያላቸው መኖራቸውን የምታውቅ ከሆነ
ይህ የሚገለጸው ከብት የማርባት ችሎታ እንዳላቸው ነው:: አት “ከመካከላቸው ከብት በማርባት ትልቅ ችሎታ ያላቸውን የሚቃውቅ ከሆነ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 47:7

ያዕቆብ ፈርዖንን ባረከው
እዚህ “ባረከው” የሚለው ለዚያ ሰው አዎንታዊና ጠቃሚ ነገሮች እንዲሆኑለት መሻቱን ገለጸ ማለት ነው

እድሜህ ምን ያህል ነው?
እድሜህ ስንት ዓመት ነው?

የእንግድነቴ ዘመን መቶ ሠላሳ ዓመት ነው
የእንግድነቴ ዘመን የሚለው ሀረግ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በመዘዋወር በምድር ላይ ምን ያህል እንደኖረ ያመለክታል:: አት “በምድር ላይ በእንግድነት ያሳለፍኩት ዘመን 130 ዓመት ነው” (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

የሕይወቴ ዘመኖች አባቶቼ በእንግድነት ከኖሩበት ዘመን ጋር ሲነጻጸር ጥቂት ናቸው
ከአብርሃምና ከይስሐቅ የሕይወት ዘመን ጋር ስነጻጸር ዮሴፍ የሕይወቱ ዘመን አጭር እንደሆነ ይናገራል

ችግር የበዛበት
ያዕቆብ በሕይወቱ ብዙ ሥቃይና ችግር ተለማምዶአል

Genesis 47:11

ዮሴፍም አባቱንና ወንደሞቹን አኖረ
ከዚያም ዮሴፍ አባቱንና ወንድሙን ተንከባከባቸው በሚኖሩበት ሥፍራ እንዲመሠረቱ አደረገ

ራሚሴ ምድር
ይህ የጐሼም ምድር ሌላው ስም ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

በየልጆቻቸው ቁጥር
እዚህ “ልጆች” በቤተሰብ ጥገኝነት ያሉ ትናንሽ ልጆች ማለት ነው:: አት “በየቤተሰቡ በሚገኙ ትናንሽ ልጆች ቁጥር”

Genesis 47:13

አሁንም
ይህ ቃል ዋናው ታሪክ በመሃል የሚቋረጥበትን ለማመልከት ተጠቅሞአል:: በዚህ ጸሐፊው የታሪኩን አድስ ክፍለ መናገር ይጀምራል::

የግብጽ ምድርና የከነዓን ምድር
ይህ በእነዚህ አገሮች የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታል አት የግብጽ ሰዎችና የከነዓን ሰዎች (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

ተጐዳ
ተቀጨ ወይም ደከመ

ዮሴፍም በግብጽ ምድርና በከነዓን ምድር በእህል ሸመት የተገኘውን ገንዘብ ሰበሰበ
ዮሴፍም የግብጽና የከነዓን ሰዎች ገንዘባቸውን ሁሉ ከዮሴፍ እህል ለመሸመት አውለዋል

ዮሴፍም ሰበሰበ... ዮሴፍም አመጣ
ገንዘቡን እንዲሰበስቡና እንዲያመጡ ዮሴፍ አገልጋዮቹን እንዳዘዘ ይገመታል (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

Genesis 47:15

የግብጽና የከነዓን ምድር ገንዘብ ባለቀ ጊዜ
እዚህ ምድር በዚያ ምድር የሚኖሩ ሰዎችን ይወክላል:: ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት “የግብጽና የከነዓን ሕዝቦችም ገንዘባቸው ባለቀ ጊዜ” (ምትከ ቃላት አጠቃቀምና ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

የግብጽና የከነዓን ምድሮች
ከግብጽ ምድር እና ከከነዓን ምድር

ብሩ አልቆብናልና በፊትህ ስለምን እንሞታለን?
ሰዎች እህል ለመሸመት እንዴት እንደጓጉ ትኩረት ለመሰጠት ጥቃቄ ይጠቀማሉ። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጐም ይችላል፡ አት “ገንዘባችን ስላለቀብን እባካችሁ እንድንሞት አታድርጉ!” (ሽንገላ አዘል አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

እህልን መገባቸው
እህል ምግብን በአጠቃላይ ይወክላል:: አት “እህልን ሰጣቸው” ወይም “እህልን አደላቸው” (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

Genesis 47:18

እነርሱም ወደ እርሱ መጡ
ሰዎች ወደ ዮሴፍ መጡ

እኛ ከጌታችን አንሰውርም
ሰዎችን ዮሴፍን እንደ” ጌታችን” ያመለክታሉ ይህ ትልቅ ሥልጣን ላሌው ሰው የሚነገርለት መደበኛ መንገድ ነው:: ይህ እንደ ሁለተኛ ወገን ሰው ሊገለጽ ይችላል:: አት” ከጌታችን የምንሰውረው የለም” ወይም “ከአንተ የምንሰውረው የለም” (አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

በጌታችን ፊት አንዳች የቀረ የለም
እዚህ ፊት ዮሴፍን ያመለክታል:: አት “ለጌታችን የምንሰጠው የቀረ የለንም” (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

እኛ በዐይኖችህ ፊት ስለምን እንሞታለን? ምድራችንስ ስለምን ትጠፋለች?
እዚህ ዐይኖች የዮሴፍን እይታ ያመለክታሉ ሰዎች እህልን ለመግዛት ምንኛ እንደጓጉ ለማተኮር ጥያቄ ይጠቀማሉ ይህ ጥያቄ እንደ ዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል:: አት “እኛ ስንሞት ምድራችም ስትጐዳ እባክህን እንዲሁ ዝም ብለህ አትመለከተን” (ምትክ ቃላት አጠቃቀምና ሽንገላ አዘል አግናኝ ጥያቄዎችን ይጠቀሙ)

እኛ ለምን እንሞታለን እኛና ምድራችን
የተዘራበት ዘር ስለሌለባት ምድሪቱ የተጐዳችና ጥቅም የሌላት መሆንዋ ምድሪቱ እንደሚትሞት ተደርጐ ተነግሮአል (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 47:20

በዚህ መንገድ የግብጽ ምድር ሁሉ ለፈርዖን ገዛለት
ስለዚህ ምድሪቱ የፈርዖን ሆነች

ዮሴፍ ያልገዛው የካህናቱን መሬት ብቻ ነበር
ነገር ግን የካህናቱን መሬት አልገዛም

ካህናቱ ድርጐ ያግኙ ነበር
ድርጐ በቋሚነት አንድ ሰው ለሌላ ሰው የሚሰጠው የገንዘብ ወይም የመግብ መጠን ነው:: ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ፈርዖን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በየዕለቱ ለካህናት የተወሰነ ምግብ ይሰጥ ነበር” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

እነርሱም ፈርዖን ከመደበላቸው ይመገቡ ነበር
ፈርዖን ከሰጣቸው ይመገቡ ነበር

Genesis 47:23

በመሬት ላይ ዝሩ
ሊትዘሩ ትችላላችሁ

በመከርም ጊዜ ፍሬውን ከአምስቱ እጅ አንዱን እጅ ለፈርዖን ስጡ አራቱም እጅ ለእናንተ ለራሳችሁ ይሆናል
አምስት እጅ የሚለው ቃል ክፍልፋይ ነው። አት “በመከር ጊዜ እህላችሁን በአምስት መደብ ትከፍላላችሁ አንዱን መደብ እንደክፍያ ለፈርዖን ትሰጡታላችሁ እናም አራቱ መደቦች ለእናንተ ይሆናሉ” (ክፍልፋዮችን ይመልከቱ) ለቤተሰቦቻችሁና ለልጆቻችሁ ምግብ ታደርጉታላችሁ (የተደበቁትን ስለመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

Genesis 47:25

በዐይኖችህ ፊት ሞገስ ካገኘን
ሞገስ ማግኘት የሚለው ሀረግ በአንድ ሰው ተቀባይነትን ማግኘት የሚገልጽ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው:: ደግሞም ዐይኖች ማየትንና ማየት ሃሳብንና በየናን ይወክላል:: አት “በእኛ ከተደሰትክ” (ፈሊጣዊና ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

በግብጽ ምድር
“በግብጸ ምድር ላይ” ወይም “በመላው የግብጽ ምድር”

እስክ ዛሬ ድረስ
ጸሐፊው እስከጻፈበት ጊዜ ድረስ

አንድ አምስተኛ
በዘፍጥረት 47:24 አንድ እምስተኛ እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ

Genesis 47:27

ንብረትንም አፈሩ እጅግም በዙ
በዙ የሚለው ቃል እንዴት እንደአፈሩ ይገልጻል እነርሱም ብዙ ልጆች ነበሩአቸው (ድርብ ቃላት ይመልከቱ)

ፍሬያማ ነበሩ
እዚህ ፍሬያማ መበልጸግ ወይም ብዙ ልጆች መኖር ማለት ነው

አሥራ ሰባት ዓመታት
17 ዓመታት (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

የያዕቆብም የሕይወቱ ዘመን አንድ መቶ አርባ ሰባት ዓመት ነበር
ያዕቆብ የኖረው 147 ዓመት ነው (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

Genesis 47:29

እስራኤልም የሚሞትበት ጊዜ መቃረቡን
ይህ ጊዜ እንደሚጓዝና አንድ ቦታ እንደሚመጣ ይናገራል:: አት “እስራኤል የሚሞትበት ጊዜ እንደደረሰ” (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

በዓይኖችህ ፊተ ሞገስን ካገኘሁ
እዚህ ዓይኖች የማየት ምትክ ቃል ነው እናም ማየት ሃሳብን ወይም አመለካከትን ይወክላል:: አት “በአንተ ፊት ሞገስ ካገኘሁ ወይም ካስደሰትኩህ” (ምትክ ቃላትና ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

አሁን
ይህ በዚህን ጊዜ ማለት አይደለም ለሚቀጥለው ጠቃሚ ነጥብ ትኩረት እንዲሰጥበት ነው

ሞገስ ማግኘት
አንድ ሰው በአንድ ሰው ተቀባይነቱን ማረጋገጥ ማለት ነው ፈሊጣሊ አነጋገር ይመልከቱ

እጅህን ከጭኔ በታች አድርግ
ለጠንቃቃ ቃል መግባት የሚደረግ ምልክት ነው በዘፍጥረት 24:2 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

በጐነትንና ታማኝነትን ሊታደርግልኝ
በጐነት እና ታማኝነት የተባሉ ረቂቅ ስሞች እንደ ቅጽል ስሞች ሊተረጐሙ ይችላሉ አት በበጐነትና በታማኝነት አድርግልኝ ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ

እባክህን በግብጽ አትቅበረኝ
እባክህን የሚለው ለዚህ ጥያቄ እጽንዖት ይሰጣል

ከአባቶቼ ጋር ሳንቀላፋ
ማንቀላፋት መሞትን ለዘብ ባለ ቃል የሚገልጽ ነውፀፀ አት “በሚሞትበትና ከዚህ ቀደም የሞቱ ቤተሰቦቼን በሚገናኝበት ጊዜ” (ንኀብነት ወይም ለዘብ ባለና በተዘዋዋሪ መንገድ አንድን ነገር የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ቃል ግባልኝ
“ተስፋ ስጠኝ” ወይም “ማልልኝ”

ማለለት
“ተስፋ ሰጠው” ወይም “ቃል ገባለት”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 48

1 ከጥቂት ጊዜ በኋላም፣ “አባትህ ታሞአል” ተብሎ ለዮሴፍ ስለተነገረው ሁለቱን ልጆቹን ምናሴንና ኤፍሬምን ይዞ ሄደ። **2** ለያዕቆብ፣ “ልጅህ ዮሴፍ ወደ አንተ መጥቶአል” ተብሎ በተነገረው ጊዜ፣ እስራኤል ተበረታትቶ አልጋው ላይ ተቀመጠ። **3** ያዕቆብም ዮሴፍን እንዲህ አለው፤ “ሁሉን የሚችል አምላክ በከነዓን ምድር ሎዛ በምትባል ቦታ ተገለጠልኝ፤ ባረከኝም፤ **4** እንዲህም አለኝ፤ ‘ፍሬያማ አደርግሃለሁ፣ ዝርያዎችህም ብዙ ሕዝቦች ይሆናሉ፣ ይህችንም ምድር ለዝርያዎችህ ለዘላለም ርስት አድርጌ እሰጣቸዋለሁ’ አለኝ።” **5** ወደዚህ ከመምጣቴ በፊት በግብፅ የወለድሃቸው ሁለቱ ልጆችህ ከእንግዲህ የእኔ ልጆች ሆነው ይቆጠራሉ፤ ሮቤልና ስምዖን ልጆቼ እንደሆኑ ሁሉ፣ ኤፍሬምና ምናሴም ልጆቼ ይሆናሉ። **6** ከእነርሱ በኋላ የሚወለዱልህ ልጆች ግን፣ የአንተ ይሁኑ፤ በርስት ድልድላችው ግን በወንድሞቻቸው ስም ይቆጠራሉ። **7** ከሰሜን ምዕራብ መስጴጦምያ ስመለስ ኤፍራታ ለመድረስ ጥቂት ሲቀረኝ፤ እናትህ ራሔል በከነዓን ምድር ሞታብኝ አዘንሁ። እኔም ወደ ኤፍራታ ማለት ወደ ቤተ ልሔም በሚወስደው መንገድ ዳር ቀበርኋት።” **8** እስራኤልም የዮሴፍን ልጆች ባየ ጊዜ፣ “እነዚህ እነማን ናቸው?” ሲል ጠየቀ፤ **9** ዮሴፍም፣ “እነዚህ እግዚአብሔር የሰጠኝ ልጆች ናቸው” ብሎ መለሰለት፤ እስራኤልም “አቅርባቸውና ልመርቃቸው” አለ። **10** በዚህ ጊዜ እስራኤል ዓይኖቹ በእርጅና ምክንያት በመድከማቸው አጥርቶ ማየት ይሳነው ነበር፤ ስለዚህ ዮሴፍ ልጆቹን አባቱ ዘንድ አቀረባቸው፤ አባቱም ስሞ አቀፋቸው። **11** እስራኤልም ዮሴፍን፣ “ዓይንህን እንደገና ዐያለሁ ብዬ አላሰብኩም ነበር፤ እግዚአብሔር ግን ልጆችህን ጭምር ለማየት አበቃኝ” አለው። **12** ዮሴፍም ልጆቹን ከእስራኤል ጉልበት ፈቀቅ በማድረግ አጎንብሶ በግንባሩ መሬት ላይ ተደፋ። **13** ከዚያም ዮሴፍ ሁለቱን ልጆቹን ይዞ ኤፍሬምን ከራሱ በስተቀኝ ከእስራኤል በስተግራ፣ ምናሴን ደግሞ ከራሱ በስተግራ ከእስራኤል በስተቀኝ በኩል አቀረባቸው። **14** እስራኤል ግን ቀኝ እጁን በታናሹ በኤፍሬም ራስ ላይ አኖረ፣ ግራ እጁንም በቀኝ እጁ ላይ አስተላልፎ በበኩሩ በምናሴ ላይ አኖረ። **15** ከዚህ በኋላ ዮሴፍን ባረከ፤ እንዲህም አለው፤ “አባቶቼ አብርሃምና ይስሐቅ መንገዱን በመከተል ያገለገሉትና ለእኔም እስከ ዛሬ ድረስ በዘመኔ ሁሉ እረኛ የሆነኝ አምላክ፣ **16** ከጉዳትም ሁሉ የታደገኝ ምልአክ፣ እርሱ እነዚህን ልጆች ይባርክ፤ እነርሱም በስሜ፣ በአባቶቼ በአብርሃምና በይስሐቅ ስም ይጠሩ፣ በምድር ላይ እጅግ ይብዙ። **17** ዮሴፍ አባቱ ቀኝ እጁን በኤፍሬም ራስ ላይ ማድረጉን ሲያይ ቅር ተሰኘ፤ ከኤፍሬም ራስ ላይ አንስቶ በምናሴ ራስ ላይ ለማኖር የአባቱን እጅ ያዘ፤ **18** ዮሴፍም፣ “አባቴ ሆይ፣ እንዲህ አይደለም በኩሩ ይህኛው ስለሆነ፣ ቀኝ እጅህን እርሱ ራስ ላይ አድርግ” አለው። **19** አባቱ ግን፣ “ዐውቃለሁ፣ ልጄ ዐውቃለሁ፣ እርሱም እኮ ሕዝብ ይሆናል፤ ታላቅም ይሆናል፤ ይሁን እንጂ፣ ታናሽ ወንድሙ ከእርሱ ይበልጣል፤ ዘሮቹም ታላቅ ሕዝቦች ይሆናሉ” ብሎ እምቢ አለው። **20** በዚያን ዕለት ባረካቸው፣ እንዲህም አላቸው፤ “እስራኤላውያን በሚመርቁበት ጊዜ የእናንተን ስም በማስታወስ፤ ‘እግዚአብሔር እንደ ኤፍሬምና እንደ ምናሴ ያድርጋችሁ’ ይላሉ” በዚህ ሁኔታም ኤፍሬምን ከምናሴ አስቀደመው። **21** ከዚህ በኋላ እስራኤል ዮሴፍን እንዲህ አለው፣ እኔ የምሞትበት ጊዜ ተቃርቦአል፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሆናል፤ ወደ አባቶቻችሁም ምድር መልሶ ያገባችኋል። **22** እነሆ በሰይፌና በቀስቴ ከአሞራውያን እጅ የወሰድኋትን ምድር ከወንድሞችህ ድርሻ አብልጬ ለአንተ ሰጥቼሃለሁ።”

Genesis 48:1

እንዲህም ሆነ
ይህ ሀረግ የታሪኩ አድስ ክፍል መጀመሩን ለማመልከቱ ተጠቅሞአል (አድስ ክስተት ስለማስታወቅ ይመልከቱ)

አንድ ሰው ለዮሴፍ ተናገረው
አደ ሰው ለዮሴፍ ነገረው

እየው፤ አባትህ
ስማ ፤አባትህ፤ እዚህ “እየው” የሚለው ቃል የዮሴፍን ትኩረት ለማግኘት ተጠቅሞአል::

ስለዚህ ይዞ
ስለዚህ ዮሴፍ ይዞ

ለያዕቆብ ... በተነገረው ጊዜ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “አንድ ሰው ለያዕቆብ በነገረው ጊዜ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ልጅህ ዮሴፍ ልያይህ ወደ አንተ መጥቶአል
ልጅህ ዮሴፍ መጥቶአል

እስራኤል ተበረታትቶ በአልጋው ላይ ተቀመጠ
እዚህ እስራኤል ተነሥቶ በአልጋው ሊቀመጥ የታገለውን አንድ ሰው አንድን ዕቃ እንደሚሰበስብ ብርታትን እንደሰበሰበ አድርጐ ጸሐፊው ይናገራል:: አት “በአልጋው ተነሥቶ ሊቀመጥ እስራኤል ከፍተኛ ጥረት አድርጐአል ወይም በአልጋው ተነሥቶ ሊቀመጥ እስራኤል ታግሎአል” (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይጠቀሙ)

Genesis 48:3

ሎዛ
ይህ የከተማ ስም ነው:: በዘፍጥረት 28:19 የዚህን ከተማ ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

በከነዓን ምድር ... ባረከኝም እንዲህም አለኝ
ይህ በሌላ ሀረግ እንደሚጀምር እንደ አዲስ ዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል:: “በከነዓን ምድር ባረከኝ እናም እንዲህ አለኝ”

ባረከኝ
እግዚአብሔር መደበኛ በረከትን በአንድ ሰው ላይ እንዳደረገ ያመለክታል

እንዲህም አለኝ እነሆ ፍሬያማ አደርግሃለሁ አበዛሃለሁ ለብዙ ሕዝብም ጉባዔ አደርግሃለሁ ይህችንም ምድር ከአንተ በኋላ ለዘላለም ርስት ለዘርህ እሰጣታለሁ
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስን ይዞአል እንደተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል አት ፍሬያማ እንደሚያደርገኝና እንደሚያበዛች ተናግሮኛል:: እናም ለብዙ ሕዝብም ጉባዔ እንደሚያደርገኝና ይህችንም ምድር ከእኔ በኋላ ለዘላለም ርስት አድርጐ ለዘሬ እንደሚሰጠኝ ነግሮኛል (ጥቅሶችን በጥቅስ ውስጥና ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

እነሆ
እዚህ ቦታ እነሆ የተጠቀመው እግዚአብሔር ሊናገር ስላለው ነገር ያዕቆብ ትኩረት እንዲሰጥ ለማንቃት ነው

ፍሬያማ አደርግሃለሁ አበዛሃለሁ
አበዛሃለሁ የሚለው ሀረግ እግዚአብሔር እንዴት ያዕቆብን ፍሬያማ እንደሚያደርገው ይገልጻል:: አት “ብዙ ዘር/ትውልድ እሰጥሃለሁ” (ድርብ ቃላትና ፈሊጣዊ አነጋገር ይጠቀሙ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አንተን ለብዙ ሕዝብ ጉባዔ አደርግሃለሁ
እዚህ አንተ ያዕቆብን ቢያመለክትም የያዕቆብን ትውልድ ይወክላል አት “ትውልድህን ብዙ ሕዝቦች አደርጋለሁ” (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

የዘላለም ርስት
ቋሚ ርስት

Genesis 48:5

አሁን
ይህ በዚህን ጊዜ ማለት አይደለም ነገር ግን ለሚቀጥለው ዋና ነጥብ ትኩረት እንዲሰጥበት ተጠቅሞአል

ኤፍሬምና ሚናሴ ለእኔ ናቸው
እንደ ዮሴፍ ወንድሞች ኤፍሬምና ሚናሴ ከምድሪቱ ክፍል የየራሳቸውን ርስት ይቀበላሉ

በርስታቸው በወንድሞቻቸው ስም ይጠራሉ
ተገቢ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው 1 እንደ ሚናሴና ኤፍሬም ነገዶች ሌሎች የዮሴፍ ልጆች ምድሪቱን ይወርሳሉ 2 ዮሴፍ ከኤፍሬምና ሚናሴ የተለየ ምድር የሰጠዋል እናም የዮሴፍ ሌሎች ልጆች ያን ምድር ይወርሳሉ አት በርስት ድልደላቸው በወንድሞቻቸው ስም ይቆጠራሉ

ኤፍራታ
ይህ የቤተልሔም ከተማ ስም ነው:: በዘፍጥረት 35:16 የዚህን ከተማ ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

ያም ቤተልሔም ነው
ጸሐፊው የዳራ መረጃ ይሰጣል (የዳራ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 48:8

እነዚህ እነማን ናቸው?
እነዚህ የማን ወንዶች ልጆች ናቸው?

ባረካቸው
አባት ልጆቹንና የልጅ ልጆቹን እብዛኛውን ጊዜ መደበኛ በረከት ይባርካል

በዚህን ጊዜ የእስራኤል ዐይኖች .... ማየት ተስኖአቸው
በዚህን ጊዜ የሚለው ቃል የተጠቀመው ታሪኩ ወደ እስራኤል ዳራ መረጃ እንደተቀየረ ለማመልከት ነው (ዳራ መረጃ ይመልከቱ)

እርሱም ሳማቸው
እስራኤል ሳማቸው

Genesis 48:11

ፊትህን እንደገና አያለሁ
እዚህ “ፊት” ሙሉ ሰው ይወክላል:: አት እንደገና አይሃለሁ (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን አንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

በእስራኤል ጉልበቶች መካከል
ዮሴፍ ልጆቹን በእስራኤል ጭን ወይም ጉልበት ላይ ማስቀመጡ እስራኤል እንደራሱ ልጆች እንደተቀበላው የሚገልጽ ምልክት ነው:: ይህም ለልጆች የወራሽነት መብት ከያዕቆብ ያስገኛል (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

በግምባሩም ወደ ምድር አጐንብሶ ሰገደ
ዮሴፍ ለአባቱ ክብርን ለመስጠት ወደ ምድር አጐንበሶ ሰገደ (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

ሚናሴንም በግራው በእስራኤል ቀኝ
እስራኤል ቀኝ እጁን በሚናሴ ላይ እንዲያደርግ ዮሴፍ ልጆቹን ያስቀምጣቸዋል ሚናሴ ታላቅ ወንድም ነው እናም ቀኝ እጅ ትልቅ በረከት የመቀበል ምልክት ነው (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

Genesis 48:14

ቀኝ እጁን ዘርግቶ በኤፍሬም ራስ ላይ አኖረ
ቀኝ እጁን በኤፍሬም ራስ ላይ ማኖር እርሱ ትልቅ በረከት እንዲቀበል ምልክት ነበር (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

እስራኤል ዮሴፍን ባረከው
ዮሴፍ ደግሞ ኤፍሬምንና ሚናሴን ይወክላል:: ዮሴፍ አባት ስለሆነ እርሱ ብቻውን ተጠቅሶአል (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

አባቶቼ አብርሃምና ይስሐቅ በፊቱ የሄዱለት እግዚአብሔር
እግዚአብሔርን ማገልገል በእግዚአብሔር ፊት እንደመሄድ ተደርጐ ተነግሮአል አት አያቴ አብርሃምና አባቴ ይስሐቅ ያገለገሉት እግዚአብሔር (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

እረኛ የሆነኝ
እረኛ በጐቹን እንደምንከባከብ እግዚአብሔር እስራኤልን ተንከባክቦታል አት እረኛ እንስሳትን እንደሚንከባከብ የተንከባከበኝ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

መልአክ
ተገቢ ትርጉሞች አት እግዚአብሔር ያዕቆብን ለመጠበቅ የላከውን መልአክ ያመለክታል 2 ይህ እግዚአብሔር ያዕቆብን ለመጠበቅ በመልአክ መልክ የተገለጸውን ያመለክታል

ጠበቀኝ
አዳነኝ

ስሜም የአባቶቼ የአብርሃምና የይስሐቅ ስም በእነርሱ ይጠራ
እዚህ ስም ሰውን ይወክላል ስሜ በእነርሱ ይጠራ የሚለው ሀረግ አንድ ሰው ከሌላ ሰው የተነሣ እንዲታወስ የሚገልጽ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው:: ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ከኤፍሬምና ሚናሴ የተነሣ ሰዎች አብርሃም ይስሐቅንና እኔን ያስታውሱ” (ምትክ ቃል : ፈሊጣዊ አነጋገርና ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

በምድርም ላይ ይብዙ
እዚህ እነርሱ ኤፍሬምንና ሚናሴን ቢያመለክትም የእነርሱ ትውልድንም ይወክላል:: አት “በምድር ሁሉ ላይ የሚኖር ብዙ ትውልድ ይኑራቸው” (ምትክ ቃል እጠቃቀም ይመልከቱ)

Genesis 48:17

ቀኝ እጅህን እርሱ ራስ ላይ አድርግ
ቀኝ እጅ በኩር ወንድ ልጅ የሚያገኘው ትልቅ በረከት ምልከት ነበር (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

Genesis 48:19

እርሱ ደግሞ ሕዝብ ይሆናል ታላቅም ይሆናል
እዚህ እርሱ ሚናሴን ቢያመለክትም የእርሱን ትውልድ ይወክላል አት ታላቅ ልጅህ ብዙ ትውልድ ይኖረዋል እናም ታላቅ ሕዝብ ይሆናል (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

በዚያን ቀን በእነዚህ ቃላት
በዚያ ዕለት እንዲህ ብሎ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በእናንተ ስም እስራኤል እንዲህ ብሎ ይባርካል
የእስራኤልም ሰዎች ሌሎችን በሚባርኩበት ጊዜ በስማችሁ ይባርካሉ

በእናንተ ስም እንዲህ ብለው እግዚአብሔር እንደ ኤፍሬምና እንደሚናሴ ያድርጋችሁ
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስን ይዞአል ይህም እንደ ተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት “በእናንተ ስም እግዚአብሔር ሌሎችን ሰዎች እንደ ኤፍሬምና እንደ ሚናሴ እንዲያደርግ ይጠይቁታል” (ጥቅሶችን በጥቅስ ውስጥ ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

እንደ ኤፍሬምና እንደ ሚናሴ
እስራኤል ኤፍሬምን አስቀድሞ መጥራቱ ኤፍሬም ከሚናሴ ታላቅ እንደሚሆን የሚገልጽ ነው

እስራኤል ኤፍሬምን ከሚናሴ አስቀድሞታል
ለኤፍሬም ትልቁን በረከት መስጠትና ኤፍሬም ከሚናሴ የተሻለ አድርጐ መውሰድ እስራኤል በአካል ኤፍሬምን ከሚናሴ በፊት እንዳስቀመጠው ተደርጐ ተገልጾአል (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 48:21

ከእናንተ ጋር ይሆናል ወደ አባቶቻችሁም ምድር መልሶ ያገባችኋል
እዚህ “እናንተ” “የእናንተ” ብዙና የእስራኤልን ሕዝብ ሁሉ ያመለክታል (“እናንተ” አጠቃቀም ይመልከቱ)

ከእናንተ ጋር ይሆናል
እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ እንደሚረዳና እንደሚባረካቸው የሚገልጽ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው አት እግዚአብሔር ይረዳችኋል ወይም እግዚአብሔር ይባርካችኋል (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ወደ አባቶቻችሁም ምድር
ወደ ዘራችሁም ወይም ትውልዳችሁም ምድር

ለአንተ ከወንድሞችህ አንድ እጅ እብልጩ ዐምባ ሰጠሁህ
ተገቢ ትርጉሞች 1 ከወንድሞቹ ይበልጥ ብዙ ክብርና ሥልጣን ለዮሴፍ መሰጠቱ እርሱ በአካል ከሌሎች የበላይ ተደርጐ ተገልጾአል:: አት “ለአንተ ከሌሎች ለሚትበልጠው የተራራውን ዐምባ ሰጠሁህ” ወይም 2)ያዕቆብ ለዮሴፍ ወንድሞች ከሚሰጠው መሬት በላይ ለዮሴፍ እንደሚሰጠው ይገልጻል:: አት “ለአንተ ለወንድሞችህ ከሰጠሁት በላይ ridge ሰጠሁህ የተራራውን ዐምባ ሰጠሁህ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ለአንተ
እዚህ አንተ በነጠላ የተገለጸና ዮሴፍን ያመለክታል (አንተ አጠቃቀም ይመልከቱ)

በሰይፌና በቀስቴ ከአሞራዊያን እጅ የወሰድኳትን ዐምባ
እዚህ ሰይፍ እና ቀስት በጦርነት መዋጋትን ያመለክታሉ:: አት “የተዋጋሁትና ከአሞራዊያን እጅ የወሰድሁት ምድር” (ምትክ ቃላት አጠቃቀም ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 49

1 ያዕቆብ ልጆቹን ጠርቶ እንዲህ አላቸው፤ “በአንድነት ተሰብሰቡና ወደፊት የሚገጥማችሁን ነገር ልንገራችሁ፣ 2 እናንተ የያዕቆብ ልጆች፣ በአንድነት
ተሰብስባችሁ ስሙ፣ አባታችሁ እስራኤል የሚነግራችሁንም አድምጡ። 3 ሮቤል፣ ኃይልና የጎልማሳነት ብርታት በነበረኝ ጊዜ የወለድሁህ የበኩር ልጄ ነህ።
ከልጆቼ ሁሉ በክብርና በኃይል የምትበልጥ አንተ ነህ። 4 ይሁን እንጂ እንደ ውሃ የምትዋልል ስለሆንህ የበላይ አለቅነት ለአንተ አይገባም፣ ምክያንቱም የአባትህን
መኝታ ደፍረሃል ምንጣፌንም አርክሰሃል። 5 “ስምዖንና ሌዊ ወንድማማቾች ናቸው፣ ዓመፅ ለመፈጸም የጦር መሣሪያዎቻቸውን ያነሳሉ። 6 ወደ ሸንጎአቸው
አልግባ፣ ጉባኤያቸው ውስጥ አልገኝ፣ በቁጣ ተነሣስተው ወንዶችን ገድለዋል፣ የበሬዎችንም ቋንጃ እንደፈለጉ ቆራርጠዋል። 7 እጅግ አስፈሪ የሆነ ቁጣቸው፣
ጭከና የተሞላ ንዴታቸው የተረገመ ይሁን፤ በያዕቆብ እበትናቸዋለሁ፣ በመላው እስራኤልም አሠራጫቸዋለሁ። 8 ይሁዳ ወንድሞችህ ያመሰግኑሃል፣ እጅህም
የጠላቶችህን አንገት አንቆ ይይዛል፣ የአባትህ ልጆች በፊትህ ተደፍተው ይስግዱልሃል። 9 ይሁዳ እንደ ደቦል አንበሳ ነው፣ ከዐደንህ የምትመለስ ልጄ፣ እንደ
አንበሳ ያደፍጣል በምድርም ላይ ይተኛል፤ እንደ እንስት እንበሳም ያደባል፣ ታዲያ ማን ሊቀሰቅሰው ይደፍራል? 10 በትረ መንግስሥት ከይሁዳ እጅ አይወጣም፤
የገዥነት ምርኩዝም ከእግሮቹ መካከል፣ ሕዝቦች ሁሉ የሚታዘዙለት ‘ሴሎ’ እስኪመጣ ድረስ፣ ሕዝቦች ሁሉ ይታዘዙለታል። 11 አህያውን በወይን ግንድ፣
ውርንጫውንም በምርጡ የወይን ሐረግ ቅርንጫፍ ላይ ያስራል፣ ልብሱን በወይን ጠጅ፣ መጎናጸፊያውንም በወይን ጭማቂ ያጥባል። 12 ዓይኖቹ ከወይን ጠጅ
የቀሉ፣ ጥርሶቹም ከወተት ይልቅ የነጡ ይሆናሉ። 13 ዛብሎን በባሕር ዳርቻ ይኖራል፣ የመርከቦቹ መጠጊያም ይሆናል፣ ወሰኑም እስከ ሲዶና ይደርሳል። 14
ይሳኮር፣ አጥንተ ብርቱ አህያ በጭነት መካከል የሚተኛ፣ ማረፊያ ቦታው መልካም፣ 15 ምድሪቱም አስደሳች መሆኗን ሲያይ፣ ትከሻውን ለሸክም ዝቅ ያደርጋል
ከባድ የጉልበት ሥራም ይሠራል። 16 ዳን ከእስራኤል ነገዶች እንደ አንዱ ሆኖ በራሱ ሕዝብ ላይ ይፈርዳል። 17 ዳን የመንገድ ዳር እባብ፣ የመተላለፊያም
መንገድ እፉኝት ነው፤ ጋላቢው የኋሊት እንዲወድቅ፣ የፈረሱን ሰኮና ይነክሳል። 18 እግዚአብሔር ሆይ፣ ማዳንህን እጠባበቃለሁ። 19 ጋድን ወራሪዎች አደጋ
ይጥሉበታል፣ እርሱ ግን ዱካቸውን ተከታትሎ ብድሩን ይመልሳል። 20 አሴር ማዕደ ሰፊ ይሆናል፤ ለነገሥታትም የሚስማማ ምግብ ያቀርባል። 21 ነጻ
እንደተለቀቀች ሚዳቋ ነው፣ የሚያማምሩ ግልገሎች ይኖሩታል። 22 ዮሴፍ፤ ፍሬያማ የወይን ተክል፣ በምንጭ ዳር የተተከለ ወይን ነው። ሐረጎቹ ቅጥርን
ያለብሳሉ። 23 ቀስተኞች በብርቱ ያጠቁታል፤ በቀስታቸውም እየነደፉ ያሳድዱታል፤ 24 ነገር ግን በያዕቆብ ኃያል አምላክ ክንድ፣ እረኛም በሆነው በእስራኤል
አለት ቀስቱ ጸና ጠንካራ ክንዱም ቀልጣፋ ሆነ። 25 አንተን በሚረዳህ በአባትህ አምላክ፣ በሚባርክህ ሁሉን በሚችል አምላክ፣ ከላይ ከሰማይ በሚገኝ ረድኤት፣
ከምድር ጥልቅ በሚገኝ በረከት፣ ከማኅፀንና ከጡት በሚገኝ ምርቃት ይባርክሃል። 26 ከጥንት ተራሮች በረከት፣ ከዘላለም ኮረብቶች ምርቃት ይልቅ፣ የአባትይ
በረከት ይበልጣል፤ ይህ ሁሉ በዮሴፍ ራስ ላይ ይውረድ፤ በወንድሞቹ መካከል አለቃ በሆነውም ግንባር ላይ ይረፍ። 27 ብንያም ነጣቂ ተኩላ ነው፤ ያደነውን
ማለዳ ይበላል፤ የማረከውን ማታ ያከፋፍላል። 28 እነዚህ ሁሉ ዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች ናቸው። ይህም እያንዳንዳቸውን ተገቢ በሆነው በረከት አባታቸው
ሲባርካቸው የተናገረው ቃል ነው። 29 ከዚህ በኋላ ያዕቆብ እንዲህ ሲል አዘዛቸው፤ “እኔ የምሞትበትና ወደ ወገኖቼ የምሰበሰብበት ጊዜ ደርሶአል፤ ስለዚህ
በኬጢያዊው በኤፍሮን እርሻ ውስጥ ባለችው ዋሻ ከአባቶቼ ዘንድ ቅበሩኝ፤ 30 ይህንን በከነዓን ምድር በመምሬ አጠገብ በማክፌል እርሻ ውስጥ ያለውን ዋሻ
የመቃብር ቦታ እንዲሆን ከኬጢያዊው ኤፍሮን ላይ የገዛው አብርሃም ነው። 31 በዚያ አብርሃምና ሚስቱ ሣራ ተቀብረዋል፤ በዚያ ይስሐቅና ሚስቱ ርብቃ
ተቀብረዋል፤ እኔም ልያን የቀበርኋት እዚያው ነው፤ 32 እርሻውና ዋሻው የተገዙት ከኬጢያውያን ላይ ነው።” 33 ያዕቆብ እነዚህን ቃላት ለልጆቹ ተናግሮ እንዳበቃ
እግሮቹን በአልጋው ላይ ሰብስቦ የመጨረሻ ትንፋሹን ተንፍሶ ሞተ፣ ወደ ወገኖቹም ተሰበሰበ።

Genesis 49:1

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ያዕቆብ ልጆቹን የሚባርከውን መጨረሻውን በረከት የጀምራል:: ይህም እስከ ዘፍጥረት 49:27 ይቀጥላል የያዕቆብ ምርቃቶች በግጥም መልክ ተጽፈዋል (ሥነ ግጥሞችን ይመልከቱ)

እናንተ የያዕቆብ ልጆች ሆይ ተሰብሰቡና ስሙ፤ አባታችሁ እስራኤልንም አድምጡ
ሁለቱ ዐረፍተ ነገሮች ትኩረት ለመስጠት ተመሣሣይ ሃሳብ ይናገራሉ አት ወደ አባታችሁ ኑና በጥንቃቄ አድምጡ (ተመሣሣይ ተነጻጻሪ ይመልከቱ)

እናንተ የያዕቆብ ልጆች አባታችሁን እስራኤልን አድምጡ
ያዕቆብ ራሱን እንደሶስተኛ ወገን ሰው ያቀርባል እንደአንደኛ ወገን ሰው ሊገለጽ ይችላል አት ልጆች ሆይ እኔን አባታችሁን ስሙ (አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን ሰው አጠቃቀም ይመልከቱ)

Genesis 49:3

የበኩር ልጄ ኃይሌና የጉብዝናዬ መጀመሪያ
የበኩር ልጄ ኃይሌ የጉብዝናዬ መጀመሪያ የሚሉ ሀረጐች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው ኃይል እና ጉብዝና የሚሉ ቃሎች የያዕቆብ ልጅ የመውለድ አቅሙን ያመለክታሉ በኩር እና መጀመሪያ የሚሉ ቃላት ሮቤል በኩር ልጁ እንደሆነ ይገልጻሉ (ተመሣሣይ ተነጻጻሪ ይመልከቱ)

በክብር ትልቃለህ በኃይልም ትበልጣለህ
ይህ እንደ አድስ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል አት በክብርና በኃይል የመጀመሪያ ትሆናለህ ወይም በክብርና በኃይል ማንኛውንም ሰው ትበልጣለህ

እንደ ውሃ የምትዋልል ነህ
ያዕቆብ ሮቤል ቁጣውን እንደማይችል ለማተኮር በከባድ ማዕበል እንደሚዋልል ውሃ አድርጐ ያቀርበዋልና እርሱ የተረጋጋ አይደለም (ተመሣሣይ አባባል ይመልከቱ)

እልቅና አይኖርህም
በወንድሞችህ መካከል የመጀመሪያ ወይም አለቃ አትሆንም

ወደ አባትህ መኝታ ወጥተሃልና ከዚያም አርክሰሄዋል ወደ አልጋዬም ወጥተሃል
እዚህ መኝታና አልጋ የያዕቆብን ቁባት ባላን ያመለክታሉ ያዕቆብ ሮቤል ከባላ ጋር የተኛበትን ያመለክታል (ዘፍጥረት 35:22 ይመልከቱ) አት “ወደ አልጋዬ ስለወጣህና በቁባቴ ከባላ ጋር ስለተኛህ አዋርደህኛልና” (ምትክ ቃላት አጠቃቀም ይመልከቱ)

ወደ አባትህ አልጋ ወጥተሃል ወደ አልጋዬም ወጥተሃል
ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው (ተመሣሣይ ተነጻጻሪ ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Genesis 49:5

ስምዖንና ሌዊ ወንድማማቾች ናቸው
ይህ በትውልድ ወንድሞች መሆናቸውን አይገልጽም ያዕቆብ የሴኬም ሰዎችን ለመግደል አብረው መሥራታቸውን ለማተኮር ነው።

ሰይፎቻቸው የዐመጽ መሣሪያ ናቸው
ሰዎችን ለመጉዳትና ለመግደል ሰይፎቻቸውን ይጠቀማሉ

ነፍሴ .... ልቤ
ያዕቆብ ራሱን ለመግለጽ ነፍሴ እና ልቤ የሚሉ ቃሎችን ይጠቀማልና ክፋን ለማድረግ ከሚያቅዱት ጋር ባለመተባበሩ ሌሎች ሰዎችና እግዚአብሔርም ደግሞ እጅግ እንዳከበሩት ይናገራል (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ወደ ሸንጐአቸው አልግባ
ጉባዔያቸው ውስጥ አልገኝ እነዚህ ሁለቱ ሀረጐች በመሠረቱ ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው ያዕቆብ ሁለቱን በማገናኘት በክፉ እቅዳቸው እንደማይሳተፍ አበክሮ ይገልጻል አት ማንኛውንም እቅድ ለማዘጋጀት ከእነርሱ ጋር አልተባበርም (ተመሣሣይ ተነጻጻሪ ይመልከቱ)

የቤሬዎችን ቋንጃ ቈራርጠዋል
ስምዖንና ለዊ ለዕይታ ብለው ቤሬዎችን አስነክሰዋል

ቋንጃ መቈረጥ ወይም ማስነከስ
ይህ የእንስሳትን ቋንጃ በመቁረጥ እንዳይራመዱ ማድረግ ነው

Genesis 49:7

ቁጣቸው ርጉም ይሁን ጽኑ ነበርና ንዴታቸው ጭከና የተሞላ ነበርና
እግዚአብሔር ስምዖንና ሌዊን የሚረግመው እግዚአብሔር ቁጣቸውንና ንዴታቸውን እንደሚረግም ተደርጐ የገልጾአል:: (ዘይቤያዊ አነጋገርና ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ቁጣቸው የተረገመ ይሁን
አብዛኛውን ጊዜ ነብይ ትንቢትን ሲናገር የሚናገረው ቃል እግዚአብሔር እንደሚናገር ይቆጠራል:: ይህም የሚናገረው ነበዩና እግዚአብሔር እንዴት እንደተቆራኙ ነው::

ንዴታቸው ጭከና የተሞላ ስለነበር
እረግማለሁ የሚለው ቃል የታወቀ ነው አት ንዴታቸው ጭከናን የተሞላ ስለሆነ እረግማለሁ (የተደበቁትን የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

እኔም በያዕቆብ እከፋፍላቸዋለሁ በእስራኤልም እበትናቸዋለሁ
“እኔ” እግዚአብሔርን ያመለክታል:: “እነርሱ” ስምዖንንና ለዊን ቢሆንም ምትክ ቃል ስለሆነ ለትውልዳቸውም ይሆናል:: “ያዕቆብ”ና “እስራኤል” ተወራራሽ ስሞችና የእስራእል ሕዝብ የሚተኩ ናቸው:: አት ትውልዳቸውን እበትናለሁ በእስራኤልም ሰዎች መካከል አሠራጫለሁ (ምትክ ቃላትና ተመሣሣይ ተነጻጻሪ አባባል ይመልከቱ)

Genesis 49:8

ወንድሞችህ አንተን ያመሰግኑሃል የአባትህ ልጆች በፊትህ ይሰግዳሉ
ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው (ተመሣሣይ ተነጻጻሪ ይመልከቱ)

ያመሰግኑሃል፤ እጅህ
ሁለተኛው ዐረፍተ ነገር ለአንደኛው ምክንያት ነው ይህ “ስለ” ወይም “ምክንያቱም/የተነሣ” አገናኝ ቃላትን በመጠቀም ግልጽ ሊሆን ይችላል:: አት “ስለ እጅህ ያመሰግኑሃል” ወይም “ከእጅህ የተነሣ ያመሠግኑሃል” (አገናኝ ቃላት ይመልከቱ)

እጅህ በጠላቶችህ አንገት ላይ ነው
“ጠላቶችህን ታሸንፋለህ” የሚል አባባል ነው:: (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ይሰግዳሉ
ለአንድ ሰው እጅ መንሣት ወይም አክብሮት በትህትና ለመግለጽ ጐንበስ ማለትን ይገልጻል (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

Genesis 49:9

ይሁዳ የአንበሳ ደቦል ነው
የአንበሳ ደቦል እንደሆነ ስለ ይሁዳ ያዕቆብ ይናገራል:: ያዕቆብ የይሁዳን ጥንካሬ በአትኩሮት ይገልጻል:: አት “ይሁዳ እንደ አንበሳ ደቦል ነው” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ልጄ ሆይ ከአደንህ ወጣህ
“አንተ ልጄ ከአደንህ ተመለስህ”

እንደ እንስት አንበሳ
ያዕቆብ ይሁዳን ከእንስት አንበሳ ጋር ያነጻጽራል አት እንስት አንበሳ በአደን ቀዳማይና ቡድንዋን የሚትከላከል ነች (ተመሣሣይ አባባል ይመልከቱ)

ያስነሣውስ ዘንድ ማን ይችላል?
ያዕቆብ ይሁዳ ለሌሎች ሰዎች ምንኛ አስፈሪ እንደሆነ ትኩረት ለመሰጠቅ ጥያቄ ይጠቀማል። አት “ማንም ሊቀሰቅሰው አይችልም” (አግናኝ ጥያቄ ይመልከቱ)

Genesis 49:10

በትሬ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም የገዥም ዘንግ ከእግሮቹ መካከል
በትርና ዘንግ ንጉሥ የሚይዛቸው ያገጡ ረጃጅም በትሮች ናቸው የሥልጣን አገዛዝ የሚተኩ ምልክቶች ናቸው እናም ይሁዳ የእርሱን ዘር ይወክላል:: አት “የአገዛዝ ሥልጣን ሁልጊዜም ለይሁዳ ዘር ይሆናል” (ምትክ ቃላትና ተመሣሣይ ተነጻጻሪ አባባል ይመልከቱ)

ገዥነት የሚገባው ወይም ሰሎ እስኪመጣ ድረስ
ተገቢ ትርጉሞች 1 ሰሎ ማለት ክብር ወይም አድናቆት ማለት ነው አት ሕዝቦች እስኪታዘዙለትና እስክያከብሩት ድረስ ወይም 2 ሰሎ የሴሎ ከተማን ይወክላል አት ገዥ ወደ ሰሎ እስኪመጣና ሕዝቦች እስኪታዘዙለት ድረስ ብዙ ሰዎች እንደሚናገሩት ይህ ትንቢት ከዳዊት ዘር ስለሚመጣው መስህ ነው ዳዊት ከይሁዳ ዘር ነውና

ሕዝቦች ይታዘዙለታል
ሕዝቦች ሰዎችን ያመለክታሉ አት ሕዝቦች ሁሉ ይታዘዙለታል (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

Genesis 49:11

አህያውን ያስራል... በወይን ግንድ
ሁለቱም አረፍተ ነገሮች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው የወይኑ ፍሬ ብዙ ሰለሆነ አህያው ፍሬዎችን ቢበላ ጌታው እንደማይገደው ተደረጐ ተገልጾአል:: (ተመሣሣይ ተነጻጻሪ እና ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

የእርሱ ... እርሱ
የእርሱ ወይም እርሱ በተጠቀሱባቸው ሁሉ ተገቢ ትርጉማቸው 1 የይሁዳን ዘር ያመለክታሉ:: “የእነርሱ” “እነርሱ” ወይም 2) እነርሱ በዘፍጥረት 49:10 ምናልባት ሚናሴን የሚያመለክተውን ገዥ ያመለክታሉ::

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ልበሱን ያጥባል... በወይን ጭማቂ
ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው ይህም በጭማቂዎቻቸው ልብሶቻቸውን ማጠብ እንኳ የሚያስችል ብዙ ወይን ፍሬዎች ይኖራሉ ማለት ነው (ተመሣሣይ ተነጻጻሪ እና ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

አጠበ
አብዛኛውን ጊዜ ወደፊት የሚፈጸሙ ትንብቶች እንደተፈጸመ ተደርጐ ይገለጻል ይህ በአትኩሮት የሚናገረው ክስተቱ በእርግጥ እንደሚፈጸም ነው አት እነርሱ ያጥባሉ ወይም እርሱ ያጥባል (ወደፊት አመለካች ኃላፊ ክስተት ይመልከቱ)

የወይን ደም ወይም ጭማቂ
የወይን ጭማቂን እንደ ወይን ደም ያቀርባል ይህም ጭማቂው ምንኛ ቀይ ቀለም እንዳለው ይገልጻል (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ዐይኖቹ እንደ ወይን የቀሉ
ይህ እንደ ቀይ ቀለም ወይን የሰውን ዐይን ቀለም ቅላት ያመለክታል:: ተገቡ አማራጭ ትርጉሞች እነሆ አት 1)ጥቁር ቀለም ያላቸው ዐይኖች ጤናማ ዐይኖች ናቸው ወይም 2) ብዙ የወይን ጠጅ ከመጠጣት የተነሣ የሰዎች ዐይኖች ይቀላሉ (ተመሣሣይ አባባል እና ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ጥርሶቹ ከወተት ይልቅ የነጡ
ይህ የሰውን ነጭ ጥርስ ከወተት ንጣት ጋር ያነጻጽራል። ይህም ወተትን የሚጠጡበት ብዙ የሚታለቡ ላሞች እንደሚኖሩ ነው (ተመሣሣይ አባባል እና ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 49:13

ዛብሎን በበሕር ዳር ይኖራል
ይህ የዛብሎንን ነገድ ያመለክታል:: የዛብሎት ነገድ ወይም ትውልድ በበሕር ዳር ይኖራል (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

እርሱም ወደብ ይሆናል
እዚህ እርሱ የዛብሎን ሰዎች የሚወርሱት ወይም የሚገነቡት የባሕር ዳር ከተሞችን ይወክላል እነዚህ የወደብ ከተሞች ለመረከበኞች መጠለያ ይሆናሉ (ምትክ ቃል አጠቃቀም ይመልከቱ)

ወደብ
በባህር ዳር ያለ መሬትና ለመርከቦች መቆሚያ ደኅንነት ያለው ቦታ ማለት ነው

Genesis 49:14

ይሳኮር አጥንተ ብርቱ አህያ ነው
ያዕቆብ ስለይሳኮርና ነገድ ወይም ትውልድ ሲናገር እንደ አህያ ይቆጥራቸዋል ይህም እጅግ የሚሠሩ እንደሚሆኑ በአትኩሮት ይገልጻል የይሳኮር ትውልድ አንደ አጥንተ ብርቱ አህያ ነው (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ይሳኮርም
አብዛኛውን ጊዜ ወደፊት የሚፈጸሙ ትንቢቶች እንደተፈጸመ ተደርጐ ይገለጻል ይህ በአትኩሮት የሚናገረው ክስተቱ በእርግጥ እንደሚፈጸም ነው ይህም በወደፊት ጊዜ ሊገለጽ ይችላል አት “ይሳኮር... ይሆናል” ወይም “የይሳኮር ትውልድ... ይሆናል” (ወደፊት አመለካች ኃላፊ ክስተት ይመልከቱ)

ይሳኮር ...ያያል... ይሆናል
እዚህ ይሳኮር ለነገዱ ምትክ ሆኖ የሚቆም ስም ነው አት “የይሳኮር ትውልዶች... ያያሉ ...ይሆናሉ” (ምትክ ቃላት ይጠቀሙ)

በበጐች ጉሬኖ መካከል ያርፋል
ተገቢ ትርጉሞች 1 በጭነት መካከል ይተኛል ወይም 2 በሁለት በጐች አጥር መካከል ይተኛል ደግሞም በሌላ መንገድ ያዕቆብ ስለይሳኮር ልጆች እጅግ እንደሚሠሩና ከዚያም ለእረፍት እንደሚተኙ ይናገራል (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

መልካም የእረፍት ቦታና የለማች ምድር
መልካም እረፍት የሚያገኙበት ቦታና የለማች ምድር

ትከሻውን ለሸክም ያመቻቻል
ትከሻውን ለሸክም ያመቻቻል ማለት ሸክምን በመሸከም እጅግ ይሠራል ማለት ነው (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ለሥራ ባሪያ ይሆናል
ለሌሎች እንደባሪያ ያገለግላል

Genesis 49:16

ዳን በወገኑ ይፈርዳል
እዚህ ዳን ነገዱን ይወክላል የዳን ልጆች በራሱ ሕዝብ ላይ ይፈርዳል ምትክ ቃላት አጠቃቀም ይመልከቱ

የራሱ ሕዝብ
ተገቢ ትርጉሞች የራሱ ሕዝብ፤ 1) በዳን ሕዝብ 2) በእስራኤል ሕዝብ

ዳን የመንገድ ዳር እባብ ይሆናል
ያዕቆብ ስለዳንና የእርሱ ትውልድ እንደ እባብ አድርጐ ይናገራቸዋል እባብ ምንም ትንሽ ቢሆን መንገደኛውን ከፈረስ ላይ ማውረድ ይችላል እንዲሁ ዳን ትንሽ ነገድ ሲሆን በጠላቶቹ ላይ አደገኛ ነው አት የዳን ልጆች በመንገድ ዳር እንዳለ እባብ ናቸው (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ሆይ ማዳንህን እጠባበቃለሁ
ረቂቅ ስም “ማዳን” እንደ “መዳን” ሊተረጐም ይችላል። አት “እግዚአብሔር ሆይ እንዲታድነኝ እጠባብቃለሁ”

እኔ እጠባበቃለሁ
“እኔ” ያዕቆብን ያመለክታል

Genesis 49:19

ጋድ ...ይዘምቱበታል እርሱ ግን
ጋድ ትውልዱን ይወክላል:: አት “የጋድ ልጆች ..ይጠቃሉ ነገር ግን እነርሱ” (ምትክ ቃል ይጠቀሙ)

አሴር ማእደ ሰፊ ይሆናል ...እርሱም
አሴር የአሴር ልጆችን ይወክላል:: እት “የአሴር ልጆች ማእደ ሰፊ... እናም እነርሱ” ምትክ ቃል ይጠቀሙ

ንፍታሌም ...እርሱም
ንፍታሌም የንፍታሌምን ትውልድ ይወክላል:: አት “የንፍታሌም ልጆች.. እነርሱ... ይሆናሉ”

በተራሮች
ከዳን ልጆች በመሸሸ በተራራማው የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታል

ምግቡ የተረከተ
እዚህ የበረከተ የሚለው ምግቡ ጣፋጭ ማለት ነው ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ

ንፍታለም ነጻ እንደተለቀቀች ሚዳቋ ነው
ያዕቆብ ስለንፍታሌም ልጆች ለመሮጥ እንደተለቀቀች እንደ እንስት ሚዳቋ እንደሆነ ይናገራል:: ይህም እነርሱ ፈጣን መልእክተኞች እንደሆኑ ነው:: አት “የንፍታሌም ዘሮች እንደተለቀቀች ሚዳቋ ይሆናሉ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የሚያማምሩ ግልገሎች
ግልገሎች ትናንሽ የሚዳቋ ግልገሎች ናቸው የዕብራይስጡ ቃል ትርጉም ግልጽ አይደለም አንዳንድ ትርጉሞች መልካም ቃል ይሰጣል ወይም መልካም ነገር ይናገራል የሚለውን ተጠቅመዋል (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 49:22

ዮሴፍ ፍሬያማ ዛፍ ነው
ዮሴፍ ትውልዱን/ዘሩን ይወክላል ያዕቆብ እነርሱን ብዙ ፍሬ እንደሚያፈራ የዛፍ ቅርንጫፍ አድርጐ ይናገራል:: አት “የዮሴፍ ዘር ፍሬያማ የዛፍ ቅርንጫፍ ነው”

የዛፍ ቅርንጫፍ
የዛፍ ዋና ቅርንጫፍ

ሐረጐቹ ቅጥርን ያለብሳሉ
ቅርንጫፎች አድገው ቅጥርን ማልበሳቸው እነዚያ በቅጥር ላይ እንደሚወጡ ተደርጐ ተገልጾአል (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 49:24

አጠቃላይ መረጃ
ያዕቆብ ዮሴፍንና ዘሩን መባረክ ይቀጥላል

ቀስቱ ጸና
ቀስቱን የያዘው ሰው መጽናቱ ቀስቱ ራሱ እንደጸና ተደርጐ ተግልጾአል ወደ ጠላቱ በሚያልምበት ጊዜ ቀስቱ እንደሚጸና ይገልጻል አት ወደ ጠላቱ በሚያልምበት ጊዜ ቀስቱን አጽንቶ ይይዛል (ምትክ ቃላት አጠቃቀም እና ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ቀስቱ....እጆቹ
እዚህ “እርሱ” ዘሩን የሚወክለውን ዮሴፍን ነው አት “ቀስቶቻቸውና እጆቻቸው” (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

እጆቹ ቀልጣፋ ይሆናሉ
ቀስትን መያዘ የለመዱ እጆች ስለሆኑ ሙሉ ሰው እንደ እጆች ተገልጾአል:: (ክፍልን እንደሙሉና ሙሉን እንደክፍል የመግልጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ኃያል አምላክ እጆች
እጆች የእግዚአብሔርን ኃይል ይገልጻሉ:: አት “የሁሉን ቻይ አምላክ ኃይል” (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

ከእረኛው ስም የተነሣ
እዚህ ስም ሙሉ ሰው ይወክላል አት ከእረኛው የተነሣ (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

እረኛው
ያዕቆብ እግዚአብሔር እረኛ እንደሆነ ይናገራል አት ይህም እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚመራና እንደሚጠብቅ ይናገራል (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ዐለት
ያዕቆብ እግዚአብሔር ሰዎች የሚወጡበትና ከጠላቶቻቸው የምድኑበት አለት እንደሆነ ይናገራል ይህ የሚያጐላው እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚጠብቅ ነው (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 49:25

አጠቃላይ መረጃ
ያዕቆብ ዮሴፍንና ዘሩን መባረክ ይቀጥላል (ዘፍጥረት 49:22-23 ይመልከቱ)

አንተን በሚረዳህ ...በሚባርክህ
እዚህ “አንተ” ዘሩን የሚወክለውን ዮሴፍን ያመለክታል አት “የአንተን ዘር በሚረዳ ....በሚባርክህ” (ምትክ ቃላት አጠቃቀም ይመልከቱ)

በሰማይ በረከቶች
ሰማይ ተክልን ወይም ሰብልን የሚያሳድገው ዝናብን ይወክላል (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

ከምድር ጥልቅ ከሚገኝ በረከት
ጥልቅ ለወንዞችና ለኩሬዎች የሚሆን ውሃ የሚወጣበትን ይወክላል (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

በጡትና በማህጸን በረከት
እዚህ ጡቶችና ማህጸን እናቶች የመውለድና ጡት የማጥባት አቅም ያመለክታል (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

Genesis 49:26

አጠቃላይ መረጃ
ያዕቆብ ዮሴፍንና ልጆቹን መባረክ ይቀጥላል።

ከጥንት ተራሮች
የመሠረታዊው ቋንቋ ትርጉም ግልጽ አይደለም:: አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች በጥንት ተራሮች ፈንታ ጥንት አባቶች ይጠቀማሉ::

እነርሱ በዮሴፍ ራስ ላይ ይሁኑ
እዚህ “እነርሱ” የአባቱ በረከቶች ናቸው::

በወንድሞች መካከል አለቃ በሆነው ራስ አናት ላይ
ያዕቆብ እነዚህ በረከቶች ልጆቹ እጅግ በበለጡት ላይ እንዲሆን ይሻል:: አት “እጅግ በበለጡ በዮሴፍ ልጆች ራስ አናት ላይ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

በወንድሞቹ መካከል አለቃ በሆነው
ከወንድሞቹ ዋና በሆነው

Genesis 49:27

ብንያም ነጣቂ ተኩላ ነው
ብንያም ዘሩን የሚወክል ምትክ ስም ነው:: ያዕቆብ የብያም ልጆችን እንደ ተራበ ተኩላ ይናገራል:: ይህም አጉልቶ የሚናገረው አጥቂ ተዋጊዎች እንደሆኑ ነው:: የብንያም ነገድ ሰዎች እንደተራቡ ተኩላ ናቸው:: (ምትክ ቃልና ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 49:28

እነዚህ አሥራ ሁሉቱ የእስራኤል ነገዶች ናቸው
እነዚህም በዘፍጥረት 49: 1- 27 የተዘረዘሩትን ይመለከታል እያንዳንዱ ልጅ የነገድ አባት ሆኖአል።

በባረካቸው ጊዜ
እዚህ “ባረካቸው” የሚለው መደበኛ በረከቶችን እንደተናገረ ነው

እያንዳንዱን በተገቢ መንገድ ባረካቸው
ለእያንዳንዱ የሚገባውን በረከት ባረከ

መመሪያ ሰጣቸው
አዘዛቸው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወደ ወገኖቼ የምሄድበት ጊዜ ደርሶአል
ይህ ለመሞት መድረሱን በትህትና የሚገለጸበት መንገድ ነው። አት “ለመሞት ቀርበአለሁ ወይም ልሞት ነኝ” (ንኀብነት ወይም ለዛ ባለ መንገድ መግለጽንና ፈሊጣዊ አነጋገርን ይመልከቱ)

ወደ ወገኖቼ የምሄድበት
ያዕቆብ በሚሞትበት ጊዜ የራሱ ውስጠኛው ሰው/ ነፍሱ ወደየት እንደሚሄድ ያመለክታል:: ከሞት በኋላ አብርሃምንና ይስሐቅን እንደሚገናኝ ይጠብቃል (ንኀብነት ወይም ለዛ ባለ መንገድ መግለጽንና ፈሊጣዊ አነጋገርን ይመልከቱ)

ኬጢያዊው ኤፍሮን
ይህ ወንድ ሰው ስም ነው። “ኬጢያዊ” የኬጥ ዘር ነው:: በዘፍጥረት 23:8 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ማክፌላ
የአንድ ቦታ ወይም ግዛት ስም ነው። በዘፍጥረት 23:9 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ። (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

መምሬ
ይህ የሔብሮን ከተማ ሌላ ስምዋ ነው:: ምናልባት መምሬ የተባለው የአብርሃም ወዳጅ ስም የተሰየመ ሳይሆን አይቀርም:: በዘፍጥረት 13:18 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ(ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

በዚያ የተገዛው
ግዥው ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት “በዚያ አብርሃም የገዛውን” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ከኬጥ ሰዎች
ከኬጢያዊያን

እነዚህን መመሪያዎች ለልጆች ተናግሮ እንዳበቃ
“ለልጆቹ መመሪያ መሰጠቱን እንዳበቃ” ወይም “ልጆቹን አዝዞ እንዳበቃ”

እግሮቹን በአልጋው ላይ ሰብስቦ
ያዕቆብ በአልጋው ላይ ተቀምጦ ነበር አሁን ግን ሊሞት መልሶ እግሮቹን በአልጋ ላይ የሰበሰባል

የመጨረሻ አስትንፋሱን ተነፈሰ/ሰጠ
ይህ አንድ ሰው መሞቱን ለዛ ባለ ቋንቋ የሚገለጽበት መንገድ ነው (ንኀብነት ወይም ለዛ ባለ መንገድ መግለጽን ይመልከቱ)

ወደ ወገኖቹ ተሰበሰበ
ያዕቆብ በሞተ ጊዜ ውስጠኛው ሰው ወይም ነፍሱ ከእርሱ በፊት የሞቱ ወገኖች ወደሄዱበት ቦታ ተሰብስቦአል (ንኀብነት ወይም ለዛ ባለ መንገድ መግለጽንና ፈሊጣዊ አነጋገርን ይመልከቱ)

Genesis 49:31

አጠቃላይ መረጃ
ያዕቆብ ለልጆቹ መናገሩን ይቀጥላል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 50

1 ዮሴፍ እጅግ ከማዘኑ የተነሣ በአባቱ ፊት ተደፍቶ አለቀሰ ሳመውም። **2** ከዚያም የአባቱ የእስራኤል አስከሬን እንዳይፈርስ ባለ መድኃኒት የሆኑ አገለጋዮች በመድኃኒት እንዲያሹት አዘዘ። ባለ መድኃኒቶቹም አስከሬኑ እንዳይፈርስ በመድኃኒት አሹት። **3** በአገሩ ልማድ መሠረት አስከሬኑ እንዳይፈርስ ማሸቱ አርባ ቀን ወሰደባቸው፤ ገብፃውያንም ሰባ ቀን አለቀሱለት። **4** የለቅሶው ወራት በተፈጸመ ጊዜ ዮሴፍ የፈርዖንን ባለሥልጣኖች እንዲህ አላቸው፤ “መልካም ፈቃዳችሁ ቢሆን እባካችሁ ለፈርዖን፣ **5** ‘አባቴ ለመሞት ሲቃረብ በከነዓን ምድር ባዘጋጀው መቃብር እንድቀብረው በመሐላ ቃል አስገብቶኛል፤ ስለዚህ ወደዚያ ሄጄ አባቴን ቀብሬ እንድመለስ ይፈቀድልኝ ሲል ጠይቆአል’ ብላችሁ ንገሩልኝ” አላቸው። **6** ፈርዖንም፣ “ባስማለህ መሠረት ሄደህ አባትህን ቅበር” አለው። **7** ስለዚህ ዮሴፍ አባቱን ለመቅበር ሄደ፣ የፈርዖን ሹማምንት በሙሉ፣ የቤተ መንግሥቱ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች እንዲሁም የግብፅ ከፍተኛ ባለ ሥልጣኖች ሁሉ ተከተሉት። **8** እንደዚሁም የዮሴፍ ቤተ ሰቦች ወንድሞቹና ሌሎችም የአባቱ ቤተ ሰቦች ሁሉ ከዮሴር ጋር ሄዱ፣ በጌሤም የቀሩት ሕፃናት ልጆቻቸው፣ የበግ፣ የፍየልና የከብት መንጋዎቻቸው ብቻ ነበሩ። **9** እንዲሁም ሠረገሎች፣ ፈረሰኞች አብረውት ወጡ፤ አጀቡም እጅግ ብዙ ነበር። **10** እነርሱም በዮርዳኖስ ማዶ ካለው አጣድ ከተባለው ዐውድማ ሲደርሱ ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ ምርር ብለው አለቀሱ፤ ዮሴፍም በዚያ ለአባቱ ሰባት ቀን ለቅሶ ተቀመጠ። **11** በዚያ የሚኖሩ ከነዓናውያን በአጣድ ዐውድማ የተደረገውን ልቅሶ ባዩ ጊዜ፣ “ይህ ለግብፃውያን መራራ ልቅሶአቸው ነው” አሉ። በዮርዳኖስ አጠገብ ያለው የዚያ ቦታ ስም አቤል ምጽራይም ተብሎ መጠራቱም ከዚሁ የተነሣ ነበር። **12** በዚህ ሁኔታ የያዕቆብ ልጆች አባታቸው እንዳዘዛቸው አደረጉ፤ **13** አስከሬኑን ወደ ከነዓን ወስደው ከመምሬ በስተምሥራቅ በምትገኘው በማክፌላ ዋሻ ቀበሩት፤ ይህም ዋሻ አብርሃም ለመቃብር ቦት እንዲሆን ከኬጢያዊው ከኤፍሮን በገዛው እርሻ ውስጥ የሚገኝ ነው። **14** ዮሴፍ አባቱን ከቀበረ በኋላ ከወንድሞቹና ለቀብር አጅበውት ከሄዱት ሰዎች ሁሉ ጋር ሆኖ ወደ ግብፅ ተመለሰ። **15** የዮሴፍ ወንድሞች ከአባታቸው ሞት በኋላ፣ “ከፈጸምንበት በደል የተነሣ ዮሴፍ ቂም ይዞ በበቀልን ምን እናደርጋለን ተባባሉ። **16** ስለዚህ እንዲህ የሚል መልእክት ላኩ፣ አባትህ ከመሞቱ በፊት፣ **17** ‘ለዮሴፍ ወንድሞችህ በአንተ ላይ የፈጸሙትን ኃጢአትና ክፉ በደል ይቅር በላቸው’ ብላችሁ ንገሩት የሚል ትእዛዝ አስተላልፎ ነበር። አሁንም የአባትህን አምላክ አገልጋዮች ኃጢአት ይቅር በለን።” ዮሴፍ ይህን በሰማ ጊዜ አለቀሰ። **18** ከዚያም ወንድሞቹ መጡና በፊቱ ተደፍተው፣ “እኛ የአንተ አገልጋዮች ነን” አሉት። **19** ዮሴፍ ግን እንዲህ አላቸው፤ “አትፍሩ፣ እኔ በእግዚአብሔር ምትክ የተቀመጥሁ አይደለሁም፣ **20** እናንተ እኔን ለመጉዳት አስባችሁ አድርጋችሁት ነበር፤ እግዚአብሔር ግን ዛሬ እንደሚታየው ሁሉ የብዙዎችን ሕይወት ለማዳን ለበጎ ነገር አዋለው። **21** አሁንም ቢሆን አትፍሩ፤ ለእናንተና ለልጆቻችሁ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ አደርግላችኋለሁ” በማለት በመልካም ንግግር አረጋጋቸው። **22** ዮሴፍ ከአባቱ ቤተ ሰቦች ጋር በግብፅ ተቀመጠ፤ አንድ መቶ ዐሥር ዓመትም ኖረ፤ **23** የኤፍሬምንም የልጅ ልጆች እስከ ሦስት ትውልድ ድረስ ዐየ። ከምናሴ የተወለደውንም የማኪርንም ልጆች በጭኑ ላይ አድርጎ አቀፋቸው። **24** ከዚህ በኋላ ዮሴፍ ወንድሞቹን እንዲህ አላቸው፤ “እነሆ፣ እኔ የምሞትበት ጊዜ ተቃርቦአል፤ እናንተ ግን እግዚአብሔር በረድኤት ይጎበኛችኋል፤ ከዚህም አገር አውጥቶ ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ ለመስጠት በመሐላ ቃል ወደገባላቸው ምድር ይመልሳችኋል። **25** እግዚአብሔር በሚጎበኛችሁና ወደዚያች ምድር በሚመልሳችሁ ጊዜ ዐጽሜን ከዚህ ይዛችሁ የምትወጡ መሆናችሁን በማረጋገጥ ቃል ግቡልኝ” ብሎ አስማላቸው። **26** ዮሴፍም ዕድሜው መቶ ዐሥር ዓመት ሲሞላው ሞተ፣ አስከሬኑንም መድኃኒት ቀብተው በሬሳ ሳጥን ካስገቡት በኋላ በግብፅ ምድር አስቀመጡት።

Genesis 50:1

በአባቱ ፊት ተደፍቶ
እዚህ ተደፍቶ የሚለው ፈሊጣዊ አባባል ተመስጦ ማለት ነው። አት “በአባቱ ላይ ተደፍቶ በሀዘን” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ባለመድኃኒት የሆኑ አገልጋዮቹ
አስከሬንን የሚያስተካክሉ አገልጋዮቹ

የአባቱን አስከሬን እንዲቀቡት
መቀባት ከቀብር በፊት አስከሬኑ እንዳይፈርስ የሚያቆዩበት ልዩ መንገድ ነው (ንጎብነት ወይም ለዛ ባለ መንገድ መግለጽን ይመልከቱ)

አርባ ቀን ወሰደባቸው
40 ቀናት ወሰደባቸው (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

ሰባ ቀናት
70 ቀናት (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

Genesis 50:4

የሐዘኑ ጊዜ እንዳበቃ
“የማዘኑ ቀናት” ወይም “ለእርሱ የማልቀስ ቀናት”

ዮሴፍ ለፈርዖን ቤት ተናገረ
እዚህ የፈርዖን ቤት የፈርዖን ንጉሣዊ ፍርድ ቤት ወክል ባለሥልጣናት ያመለክታል ዮሴፍ ለፈርዖን ባለሥልጣናት ተናገረ (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

በፊታችሁ ሞገስ አግኝቼ እንደሆነ
ሞገስ ማግኘት የሚለው ሐረግ በአንድ ሰው ፊት ተቀባይነትን ማትረፍ የሚናገር ፈሊጣዊ አባባል ነው:: አት “በእናንተ ፊት ሞገስ ካገኘሁ ወይም በእኔ ደስተኞች ከሆናችሁ” (ፈሊጣዊ አባባልና ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ለፈርዖን እንዲህ ብላችሁ ንገሩልኝ ፤አባቴ አምሎኛል፤ እንዲህ ስል፤ እነሆ እኔ እሞታለሁ፤ በቆፈርሁትም መቃብር በከነዓን ምድር ከዚያ ቅበረኝ ። አሁንም ወጥቼ አባቴን ሊቅበርና ሊመለስ።
ይህ ሁለት ደረጃና ሶስት ደረጃ ጥቅስ ይዞአል እነዚህ በተዘዋዋሪ ጥቅስ ለገለጹ ይችላሉ:: አት “በከነዓን ምድር በቆፈረው መቃብር እንዲቀብረው አባቴ በሚሞትበት ጊዜ እንዳመለኝ ለፈርዖን ንገሩልኝ:: አባተን እንዲቀብረውና ከዚያም ተመልሸ እንዲመጣ ፈርዖንን ጠይቁልኝ” (ጥቅሶችን በጥቅስ ውስጥና ቀጥታና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

እኔ ልሞት ቀርቦአለሁ
ሊሞት ነኝ

ልውጣ
ከግብጽ ወደ ከነዓን መጓዝ በሚነገርበት ጊዜ “ወደ ላይ መውጣት” የሚለውን ሀረግ መጠቀም የተለመደ ነው።

ፈርዖንም መለሰ
የመንግሥት ምክር ቤት አባላት ለፈርዖን ነገሩትና ከዚያም ፈርዖን ለዮሴፍ መለሰ (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

አባትህ እንዳማለህ
ለእርሱ እንደማልህለት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Genesis 50:7

ዮሴፍም... ወጣ
ከግብጽ ወደ ከነዓን መጓዝ በሚነገርበት ጊዜ “ወደ ላይ መውጣት” የሚለውን ሀረግ መጠቀም የተለመደ ነው።

የፈርዖን ሹማምንት በሙሉ የቤቱ ሽማግሌዎች/የቤተመንግሥቱ ከፍተኛ ባለሥልጣናትና የግብጽ ምድር ከፍተኛ ባለሥልጣናት
የፈርዖን ከፍተኛ መሪዎች ሁሉ የቀብሩን ሥነሥርዓት ተካፈሉ (የሁኔቶች ሥርዓት ይመልከቱ)

የቤቱ ሽማግሌዎች
የፈሪዖን ቤተምንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣናትን ያመለክታል

ከግብጽ ምድር ፤የዮሴፍ ቤተ ሰዎች ወንድሞቹና የአባቱ ቤተ ሰዎች
ይህ እንደ አዲስ ዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል:: አት “የግብጽ ምድር ፤ እንዲሁም የዮሴፍ ቤተ ሰዎች ወንድሞቹና የአባቱ ቤተ ሰዎች ከእርሱ ጋር አብረውት ሄዱ” (የሁኔቶች ቅደም ተከተል ይመልከቱ)

ሰረገላዎች
እዚህ በሠረገላዎች የተቀመጡ ሰዎችን ያመለክታል (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ
እጅግ ብዙ ሰዎች ጉባኤ ነበር

Genesis 50:10

እነርሱም በመጡ ጊዜ
“እነርሱ” የሚለው ቃል በቀብር ሥነሥርዓቱን ይካፈሉ የነበሩ ሰዎችን ያመለክታል

የአጣድ አውድማ
ተገቢ ትርጉሞች 1) “አጣድ” የሚለው ቃል እሾህ ማለት ነው፤ አናም እጅግ ብዙ እሾሆች የሚበቅሉበት መሬት ሊባል ይችላል ወይም 2) “የአውድማው ባለቤት ስም ሊሆን ሊችላል:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ከፍተኛና መራራ ለቅሶ አለቀሱ
እጅግ መራራና ከፍተኛ ልቅሶ አልቅሰው ነበር

ሰባት ቀን
7 ቀን (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

በአጣድ አውድማ
ተገቢ ትርጉሞች 1) አጣድ የተባለው ሰው አውድማ ውስጥ ወይም 2) አጣድ በተባለው አውድማ ውስጥ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ይህ ግብጻዊያን እጅግ ያዘኑበት ጊዜ ነበር
የግብጻዊያን ልቅሶ መራራ ነበር

አቤል ምጽራይም
ተርጓሚዎች የሚከተለውን እንደ ግርጌ ማስታወሻ ሊጠቀሙ ይችላሉ አቤል ምጽራይም የሚለው ስም የግብጻዊያን ሐዘን ማለት ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 50:12

ልጆቹም
የያዕቆብ ልጆችም

ልክ እንዳዘዛቸው
ልክ መመሪያ እንደሰጣቸው

ልጆቹም ተሸክመውት
ልጆቹም አስከሬኑን ተሸክመውት

ማክፌላ
ማክፌላ የቦታ ወይም የግዛት ስም ነው በዘፍጥረት 23:9 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

መምሬ
የሔብሮን ከተማ ሌላ ስምዋ ነው በዚያ ይኖር በነበረው በአብርሃም ወዳጅ መምሬ ስም ሳትሰየም አትቀርም። በዘፍጥረት 13: 18 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ኬጢያዊው ኤፍሮን
ይህ የወንድ ሰው ስም ነው ኬጢያዊ የኬጥ ዘር ነው በዘፍጥረት 23:8 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ወደ ግብጽ ዮሴፍ ተመለሰ
ዮሴፍ ወደ ግብጽ ተመለሰ

አብረውት የነበሩ ሁሉ
አብረውት የሄዱት ሁሉ

Genesis 50:15

ምናልባት ዮሴፍ ቂም ሊበቀለን ይሆናል
እዚህ ቂም ዮሴፍ በእጁ እንደምይዝ ዕቃ ተደርጐ ተገልጾአል አት ምናልባት ዮሴፍ የጠላን ይሆናል (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ባደረግንበት ክፋት ሁሉ ብድራት ይመልስብን ይሆናል
እርሱን የበደለውን ሰው መበቀል አንድ ሰው ከሌላ ሰው የተበደረውን እንደመመለስ ተደርጐ ተገልጾአል:: አት “ባደረግንበት ክፋት ምናልባት ልበቀለን ይችላል” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

አባትህ ገና ሳይምት እንዲህ ብሎ አዘዞአል ዮሴፍን እንዲህ በሉት እባክህ የወንድምችን በደል ኃጢአታቸውንም ይቅር በል እነርሱ በአንተ ከፍተውብሃልና
ይህ ሁለት ደረጃና ሶስት ደረጃ ጥቅስ ይዞአል እንደተዘዋዋሪ ጥቅስም ሊገለጹ ይችላሉ:: አት “አባትህ ከመሞቱ በፊት እኛ የበደልንህን ይቅር እንዲትለን እንድንነግርህ አዝዞናል” (ጥቅስን በጥቅስ ውስጥ እና ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

አባትህ ከመሞቱ በፊት አዝዞናል እንዲህ ስል
ያዕቆብ ለወንድማማቾች ሁሉ አባት ነው:: እዚህ ዮሴፍ አባቱ ለተናገረው ትኩረት እንዲሰጥ “አባትህ” ብለው ይናገራሉ:: አት “አባታችን ከመሞቱ በፊት”

በበደሉህ ጊዜ ያደረጉትን ኃጢአታቸውን
በአንተ ላይ ስላደረጉት ክፉ ነገሮች

አሁንም
ይህ በዚህን ጊዜ ማለት አይደለም ነገር ግን ለሚቀጥለው ዋና ነጥብ ትኩረት እንዲሰጥበት ነው

የአባትህ አምላክ ባሪያዎች የበደሉህን ይቅር በል
ወንድሞቹ ራሳቸውን “የአባትህ አምላክ ባሪያዎች” ብለው ይገልጻሉ:: (አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

ዮሴፍ ይህን ስሉት አለቀሰ
የሴፍ ይህን መልእክት በሰማ ጊዜ አለቀሰ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Genesis 50:18

በፊቱ ሰግደው
በፊቱ ወደ መሬት ጐንበስ በማለት ሰግደው፤ ይህ የትህትና እና ለዮሴፍ ክብርን የመስጠት ምልክት ነው። (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

እኔ በእግዚአብሔር ፋንታ ነኝን?
ዮሴፍ ወንድሞቹን ለማደፋፈር ጥያቄ ይጠቀማል:: አት “እኔ በእግዚአብሔር ፋንታ አይደለሁም” ወይም “እኔ እግዚአብሔር አይደለሁም” (አግናኝ ወይም ሸንገላ አዘል ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

እናንተ ክፉ ነገር አስባችሁብኝ
እናንተ ክፉ ነገር አድርጋችሁብኝ

እግዚአብሔር ለመልካም አሰበው
እግዚአብሔር ለመልካም አደረገው

ስለዚህ አሁንም አተፍሩ
ስለዚህ እኔን አተፍሩ

እናንተንና ልጆቻችሁን እመግባችኋለሁ
ሁል ጊዜ እናንተና ልጆቻችሁ በቂ ምግብ እንዲኖራችሁ አረጋግጣለሁ

አጽናናቸውም ልባቸውን ደስ አሰኛቸው
እዚህ ልቦች ወንድሞቹን ያመለክታሉ:: አት “አጽናናቸውም ደስም አሰኛቸው” (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

Genesis 50:22

መቶ አሥር ዓመት
110 ዓመት (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

የኤፍሬም ልጆች እስከ ሶስት ትውልድ
የኤፍሬም ልጆችና የልጅ ልጆች

ማኪር
ይህ የዮሴፍ ወንድ የልጅ ልጅ ስም ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

በዮሴፍ ጭን ላይ ተወለዱ
ይህ አባበል ዮሴፍ እነዚህን የማኪርን ልጆች የራሱ የልጅ ልጆች አድርጐ ተቀበላቸው ማለት ነው:: ይህም ዮሴፍን ለመውረስ ልዩ መብት አላቸው ማለት ነው (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 50:24

በእርግጥ እናንተን ይጐበኛችኋል
በዘፍጥረት 50: 24./26 “እናንተ” የሚለው ቃል የዮሴፍን ወንድሞች ነገር ግን ደግሞ የእነርሱን ልጆች ያመለክታል፡: (ምትክ ቃላት አጠቃቀም ይመልከቱ)

ወደ ምድራችሁ ከዚህ ምድር ያወጣችኋል
ከግብጽ ወደ ከነዓን መጓዝ በሚነገርበት ጊዜ “ወደ ላይ መውጣት” የሚለውን ቃለ መጠቀም የተለመደ ነው:: አት “ከዚህ ምድር ያወጣችኋል ወደ ምድራችሁ ይወስዳችኋል” (የክስተቶች ቅደም ተከተል ይመልከቱ)

110 ዓመታት
መቶ አሥር ዓመታት

እነርሱም በመድሃኒት ቀቡት
አንድን አስከሬን ከመቀበሩ በፊት እንዳይፈርስ ለማቆየት መድሃኒት መቀባት ልዩ የሆነ መንገድ ነበር በዘፍጥረት 50 1 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ

ኖረ ወይም ተቀመጠ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት “አኖሩት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

በአስከሬን ሳጥን ውስጥ
“በሬሳ ሳጥን” ወይም “በሳጥን” ይህ ሳጥን የሞተ ሰው የሚቀመጥበት ነው::

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Exodus

Exodus

Chapter 1

1 እያንዳንዳቸው ቤተ ሰባቸውን በመያዝ፣ ከያዕቆብ ጋር ወደ ግብፅ የገቡት የእስራኤል ልጆች ስሞች እነዚህ ናቸው፦ **2** ሮሜል፣ ስምዖን፣ ሌዊ፣ ይሁዳ፣ **3** ይሳኮር፣ ዛብሎን፣ ብንያም፣ **4** ዳን፣ ንፍታሌም፣ ጋድና አሴር። **5** ከያዕቆብ ዘር የተገኙት ሰዎች ሰባ ነበር። ዮሴፍ ቀድሞውኑ በግብፅ ውስጥ ነበረ። **6** ከጊዜ በኋላ ዮሴፍ፣ ወንድሞቹ ሁሉና ያ ትውልድ በሙሉ ሞቱ። **7** ነገር ግን እስራኤላውያን እየተዋለዱ ሄዱ፤ ቊጥራቸውም እጅግ ጨምሮ በጣም ብርቱዎች ሆኑ፤ ምድሪቱንም ሞሏት። **8** በግብፅ ስለ ዮሴፍ የማያውቅ ዐዲስ ንጉሥ ተነሣ። **9** ለሕዝቡም እንደዚህ አለ፤ “እስራኤላውያንን ተመልከቷቸው፤ ከእኛ ይልቅ በቊጥር በዝተዋል፤ እጅግም በርትተዋል። **10** በቊጥር እየበዙ እንዳይሄዱ፣ ጦርነት ቢነሣም ከጠላቶቻችን ጋር ዐብረው እንዳይወጉንና ምድሪቱ ጥለው እንዳይሄዱ ኑ በዘዴ እርምጃ እንውሰድባቸው።” **11** በከባድ ሥራ የሚያስጨንቋቸው አሠሪ አለቆችን በላያቸው ሾሙ። እስራኤላውያን ለፈርዖን ፊቶምና ራምሴ የተባሉ የንብረት ማከማቻ ከተሞችን ሠሩ። **12** ግን ግብፃውያን እስራኤላውያንን ባስጨነቋቸው ቊጥር፣ እስራኤላውያን በቊጥር እየበዙና በምድሪቱ እየተስፋፉ ሄዱ። ስለዚህ ግብፃውያን እስራኤላውያን መፍራት ጀመሩ። **13** ግብፃውያን እስራኤላውያንን በጥብቅ እንዲሠሩ አደረጓቸው። **14** በሸክላ ሥራና ጭቃ በማስቦካት፣ በዕርሻ ውስጥም ሁሉን ዐይነት ከባድ ሥራ በማሠራት አስመረሯቸው (ሕይወታቸውን መራራ አደረጉባቸው) ። የሚጠበቅባቸው ሥራ ሁሉ ከባድ ነበር። **15** ከዚያም በኋላ የግብፅ ንጉሥ ሲፓራና ፉሐ የሚባሉ ዕብራውያት አዋላጆችን እንዲህ አላቸው፤ **16** “ዕብራውያት ሴቶችን በማማጫው ላይ ስታዋልዱ፣ በሚወልዱበት ጊዜ ተመልከቱ። ወንድ ከተወለደ ግደሉት፤ ሴት ከሆነች ግን በሕይወት ትኑር።” **17** ነገር ግን አዋላጆቹ እግዚአብሔርን ፈሩ፣ ንጉሡ ያዘዛቸውንም አልፈጸኩም፤ ትእዛዙን በመፈጸም ፈንታ ሕፃናት ወንዶችን በሕይወት እንዲኖሩ አደረጉ። **18** የግብፅ ንጉሥ አዋላጆቹን ጠርቶ፣ “ለምን ይህን አደረጋችሁ፣ ሕፃናት ወንዶችንስ ለምን አልገደላችኋቸውም?” አላቸው። **19** አዋላጆቹም ለፈርዖን፣ “ዕብራውያት ሴቶች እንደ ግብፃውያት ሴቶች አይደሉም። እነርሱ ብርቱዎች ናቸው፣ የሚወልዱትም አዋላጅ ወደ እነርሱ ከመምጣቱ በፊት ነው” በማለት መለሱለት፥ **20** እግዚአብሔር እነዚህን አዋላጆች ጠበቃቸው። ሕዝቡ በቊጥር በዙ፣ እጅግ ብርቱዎችም ሆኑ። **21** አዋላጆቹ እግዚአብሔርን ስለ ፈሩ፣ እግዚአብሔር ቤተ ሰቦችን ሰጣቸው። **22** ፈርዖን፣ “የተወለደውን ወንድ ልጅ ሁሉ ወንዝ ውስጥ ጣሉ፣ ሴትን ልጅ ግን በሕይወት እንድትኖር ታደርጋላችሁ” በማለት ሕዝቡን ሁሉ አዘዘ።

Exodus 1:1

ቤተሰብ
በአንድ ቤት አብረው የሚኖሩ ሰዎች ስብስብና ከቤተሰብ አባላት ውጭ ሌሎች አገልጋዮችም ጭምር ያሉበት ቤተሰብ ይባላል።

ሰባ ነፍሶች
በቁጥር ሰባ የሚያህሉ ሰዎች ማለት ነው

• ዮሴፍም አስቀድሞ በግብፅ ነበረ
የዮሴፍ ወንድሞች ወደ ግብጽ ከመምጣታቸው በፊት ዮሴፍ በግብጽ ይኖር ነበር

Exodus 1:6

• ወንድሞቹ
ወንድሞቹ የተባሉት የዮሴፍ አስር ታላቅ ወንድሞቹና አንድ ታናሽ ወንድሙ ስብስብ ነው

• ልጆች አፈሩ
ልጆችን አፈሩ የሚለው ሀረግ በተለዋጭ ዘይቤ የተጻፈ ነው። በእስራኤላውያን ዘንድ ልጅ መውልድ ከዛፍ ፍሬ ማፍራት ጋር ተነጻጽሮ ቀርቧል። የዚህ አማራጭ ትርጉም “ብዙ ልጆች ወለዱ” ወይም “ብዙ ልጆችን አገኙ” የሚል ነው።

• ምድሪቱም በእነርሱ ሞላች
ይህ በተደራጊ ግስ የተጻፈ ሲሆን በአድራጊ ግስ “እነርሱ ምድርቱን ሞሉ” ማለት ነው።

• እነርሱ
በሶስተኛ መደብ የተጠራው “እነርሱ” የሚለው ቃል “እስራኤላውያንን” ያመለክታል።

Exodus 1:8

• በግብጽ... ተነሳ
ግብጽ የሚለው ቃል የግብጽ ህዝብን የሚያመለክት ነው። የዚህ አማራጭ ትርጉም “የግብጽ ህዝብን የሚገዛ አዲስ ንጉስ ነገሰ” የሚል ነው።

• እርሱም ህዝቡን
የግብጽ ንጉስ ለህዝቡ እንዲህ ብሎ ተናገረ።

• ህዝቡን
በግብጽ ምድር የሚኖሩ ህዝቦች ወይም ግብጻውያንን ማለት ነው።

• ኑ
ይህ አባባል ንጉሱንና እርሱ የሚመራውን ህዝብ ወይም ግብጻውያንን የሚያጠቃላል ነው። “እኛ” የሚለው መደብ መገለጫ ነው።

• ሰልፍም በተነሳብን ጊዜ
“ሰልፍ” የሚለው ጠላት በእኛ ጦርነት ባወጀ ጊዜ ወይም ጠላት ልወጋን በሚመጣበት ጊዜ የሚለውን ሀሳብ ይገልጻል። “ሰልፍ በተነሳብን” ጊዜ የሚለው በሰውኛ ዘይቤ የተገለጸ ነው፤ ምክንያቱም ሰልፍ እንደ ሰው ተነሳ የሚል አገላለጽ የያዘ ነው።

• ከምድሪቱም እንዳይወጡ
እስራኤላውያን ግብጽን ለቀው እንዳይሄዱ ማለት ነው።

Exodus 1:11

• በብርቱ ሥራም ያስጨንቁአቸው ዘንድ
ግብጻውያን እስራኤላውያንን ከባድ ወይም አስቸጋሪ ሥራ እንዲሰሩ ያስጨንቋቸው ነበር ማለት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• ግብር አስገባሪዎች
እስራኤላውያን ከባድ ሥራ እንዲሰሩ የሚያስገድዱ የግብጽ “አሰሪ አለቆች” ማለት ነው።

• ጽኑ ከተሞች ... ሠሩ
ንጉሱና ሌሎች መሪዎች ወይም ሹማምንት ምግብና ሌሎች ተፈለጊ የሆኑ ንብረቶችን የሚያኖሩበት “ንብረት ማከማቻ ከተሞች” ማለት ነው።

Exodus 1:13

• በመከራ ገዙአቸው
ጭካኔ በተሞላበትና ርህራሄ በለሌው ስሜት ግፍ ይፈጽሙባቸው ነበር።

• ሕይወታቸውን ያስመርሩአቸው ነበር
የአንድ ዛፍ ፍሬ መራራ ከሆነ እንደማይበላና ደስ እንደማይል ሁሉ የእስራኤላውያን ህይወት እለት ተዕለት በሚደርስባቸው ጭካነ መራራ በመሆኑ ደስተኞች አልነበሩም ማለት ነው። አባባሉ በተለዋጭ ዘይቤ የተገለጸ ነው።

• በጡብ ሥራ
ለቤት ሥራ የሚውል ከጭቃና ከሸክላ አፈር እንዲሁም በዘመናዊ መንገድ ከሲሚንቶ የሚሰራ ብሎኬት መሳይ ነገር ማለት ነው

• በመከራም በሚያሠሩአቸው ሥራ ሁሉ
ግብጻውያን እስራኤላውያንን የተለያዩና በጣም ከባድ የሆነ የጉልበት ሥራዎችን ያሰሩአቸው ነበር።

Exodus 1:15

• የግብፅም ንጉሥ
የግብጽ ንጉስ በወል ወይም በጋራ ስም “ፈርዖን” ተብሎ ይጠራል።

• አዋላጆች
ሴቶች በሚወልዱበት ጊዜ የማዋለድ ሥራ የሚሰሩ ወይም አገልግሎት የሚሰጡ ሴቶች ማለት ነው

• ሲፓራና ፉሐ
የዕብራውያን ሴቶች ስም ነው (ስሞችን የመተርጎም ዘዴ ተመልከት)

• የማማጫ ድንጋይ **(**መቀመጫ**)**
ሴቶች በሚወልዱበት ጊዜ የሚቀመጥቡት ድንጋይ ወይም መቀመጫ ማለት ነው። እስራኤላውያን ሴቶች ለመውለድ በዚህ ድንጋይ ላይ ሲቀመጡ ወይም ሴቶቹ በሚወልዱበት ጊዜ ማለት ነው።

Exodus 1:18

• ለምን እንዲህ አደረጋችሁ? ወንዶቹን ሕፃናትንስ ለምን አዳናችሁ?፦
ፈርዖን ይህንን ጥያቄ አዋላጆችን የጠየቀው ወንድ ህጻናትን ባለመግደላቸው ምክንያት ልገስጻቸው ፈልጎ ነው። ይህ ጥያቄ በመደበኛ ዓረፍተ ነገር ሲተረጎም “ወንድ ህጽናትን ባለመግደላችሁ ትዕዛዜን ተላልፋችሁኋል” የሚል ይሆናል። ጥያቄው በባህርዩ አጋናኝ ጥያቄ ነው።

• የዕብራውያን ሴቶች እንደ ግብፃውያን ሴቶች አይደሉም
አዋላጆች የንጉሱን ቁጣ ለማብረድ በጥበብና በምክንያታዊነት የተናገሩት ንግግር ዓይነት ነው።

Exodus 1:20

• ለአዋላጆቹ መልካም ሆነላቸው
ፈረዖን እነዚህን ሴቶች እንዳይገድላቸው እግዚአብሔር ጠበቃቸው፥ ተከላከላቸው፥ ለክፉ አሳልፎ አልሰጣቸውም ማለት ነው።

• እግዚአብሔርን ስለ ፈሩ
እግዚአብሔር ከሁሉ በላይ ገዥ እንደሆነ አምነው ከፈረዖን ይልቅ እግብቻ ሰሙ ማለት ነውዚአብሄርን ፈሩ፥ ለእርሱ ብቻ ታዘዙ፥ እርሱን

• ለያንዳንዳቸውም ቤተሰብ ሰጣቸው
እግዚአብሔር ለእነዚህ አዋላጆች ቤተሰብ ወይም ልጅ ወይም ዘር ሰጣቸው ማለት ነው።

• የሚወለደውን ወንድ ልጅ ሁሉ እያነሣችሁ ዓባይ ወንዝ ውስጥ ጣሉ
ወንዶች ልጆች ውሃው ውስጥ ሰጥመው እንድሞቱ ህዝቡ እያንዳንዱን ወንድ ልጅ ወደ አባይ ወንዝ እንድጥል ጥብቅ ትዕዛዝ ንጉሱ ሰጣቸው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 ከሌዊ ወገን የሆነ አንድ ሰው ሌዋዊት ሴት አገባ። **2** ሴትዮዋ ፀነሰች ወንድ ልጅም ወለደች። ሕፃኑ መልከ መልካም መሆኑን ስታይ፣ ሦስት ወር ሸሸገችው። **3** ከዚያ በላይ ልትሸሸገው ባልቻለች ጊዜ፣ የደንገል ቅርጫት ወስዳ በዝፍትና በቅጥራን ለቀለቀችው። ከዚያም ልጁን በውስጡ አስተኝታ ውሃው ውስጥ በቄጠማው መካከል በወንዙ ዳርቻ አስቀመጠችው። **4** የሚያጋጥመውን ለማየት የሕፃኑ እኅት በርቀት ቆማ ነበር። **5** ጠባቂዎቿ በወንዙ ዳር እየሄዱ ሳለ፣ የፈርዖን ልጅ በወንዙ ለመታጠብ ወረደች። ልዕቲቱ ቅርጫቱን በቄጠማዎች መካከል አየችው። ቅርጫቱን እንዲያመጣላት ጠባቂዋን ላከች። **6** ቅርጫቱን ስትከፍተው፣ ሕፃኑን አየች። እነሆ፣ ሕፃኑ ያለቅስ ነበር። ራራችለትና፣ «ይህ በእርግጥ ከዕብራውያን ልጆች አንዱ ነው» አለች። **7** ከዚያም በኋላ የሕፃኑን እኅት የፈርዖንን ልጅ፣ «ልሂድና ሕፃኑን የምታሳድግልሽ ዕብራዊት ሴት ልፈልግልሽ?» አለቻት። **8** የፈርዖንም ልጅ «ሂጂ» አለቻት። ወጣቷም ልጅ ሄዳ የሕፃኑን እናት አመጣች። **9** የፈርዖን ልጅ የሕፃኑን እናት፣ «ይህ ሕፃን ውሰጅና አሳድጊልኝ፤ ደሞዝ እከፍልሻለሁ» አለቻት። ሴትዮዋም ሕፃኑን ወስዳ አሳደገችው። **10** ሕፃኑ ባደገ ጊዜም ወደ ፈርዖን ልጅ አመጣችው፤ የልዕልቲቱም ልጅ ሆነ። «ከውሃ አውጥቼዋለሁና» ብላም ስሙን ሙሴ አለችው። **11** ሙሴ ባደገ ጊዜ ወደ ወገኖቹ ሄዶ የሚሠሩትን ከባድ ሥራ ተመለከተ። ከገዛ ወገኖቹ መካከል አንዱን ዕብራዊ አንድ ግብፃዊ ሲደበድበው አየ። **12** ግራና ቀኙን ተመልክቶ ማንም አለመኖሩን ሲያረጋግጥ፣ ግብፃዊውን ገድሎ በአሸዋ ውስጥ ደበቀው። **13** ቀን ሙሴ ወደ ውጭ ወጣ፤ እነሆም ሁለት ዕብራውያን ወንዶች እየተጣሉ ነበር።በደለኛ የነበረውን ሰውየ፣ «ባልንጀራህ ለምን ትደበድበዋለህ?» አለው። **14** ሰውየው ግን፣ «አንተን በእኛ ላይ አለቃና ዳኛ ማን አደረገህ? ያን ግብፃዊ እንድ ገደልኸው እኔንም ልትገድለኝ ታስባለህ?» አለ። ሙሴም ፈራና፣ «ያደረግሁት በሌሎች ሰዎች ዘንድ በእርግጥ ታውቋል» አለ። **15** ስለ ጉዳዩ ሲሰማ ሙሴን ሊገድለው ፈለገ። ነገር ግን ከፈርዖን ሸሽቶ በምድያም አገር ኖረ። እዚያም በአንድ የውሀ ጉድጓድ አጠገብ ተቀመጠ። **16** ካህን ሰባት ሴት ልጆች ነበሩት። እነርሱም ወደ ጉድጓዱ መጥተው ውሀ ቀዱ፣ የአባታቸውን መንጋ ለማጠጣትም ገንዳውን ሞሉት። **17** መጥተው ሊያባርሯቸው ሞከሩ፣ ነገር ግን ሙሴ ሄዶ ዐገዛቸው። መንጋቸውንም አጠጣላቸው፤ **18** ወደ አባታቸው ወደ ራጉኤል ሲሄዱም፣ አባታቸው፣ «ዛሬ እንዴት ቶሎ ወደ ቤት መጣችሁ?» አለ። **19** «አንድ ግብፃዊ ከእረኞች አዳነን፤ ውሀም ቀድቶ መንጋውን አጠጣልን» አሉ። **20** ልጆቹን፣ «ታዲያ የት አለ?» ሰውየውን ለምን ተዋችሁት? ምግብ ከእኛ ጋር እንዲበላ ጥሩት» አላቸው። **21** ሲፓራን እንዲያገባትም እንኳ ከሰጠው ሰውየ ጋር ለመኖር ሙሴ ተስማማ። **22** ወንድ ልጅ ወለደች፤ ሙሴም፣ «የባዕድ ምድር ኗሪ ነኝ» ሲልም ስሙን ጌርሳም አለው። **23** ከረጅም ጊዜ በኋላ፣ የግብፅ ንጉሥ ሞተ። እስራኤላውያን ከባርነት ሥራ የተነሣ አለቀሱ፣ ለርዳትም ጮኹ፤ ከባርነት ቀበራቸው የተነሣም ያሰሙት ጩኸት ወደ እግዚአብሔር ወጣ። **24** እግዚአብሔር ልቅሶአቸውን ሲሰማ ከአብርሃም፣ ከይስሐቅና ከያዕቆብ ጋር የገባውን ቃል ኪዳኑን ዐሰበ። **25** እግዚአብሔር እስራኤላውያንን አየ፤ ሁኔታቸውንም ተረዳ።

Exodus 2:1

• በዚያን ጊዜ
በዕብራይስጡና በቀድሞ አማርኛ ትርጉም (በ1954 ትርጉም) ይህ አገናኝ ሀረግ የለም። ነገር ግን በአንዳንድ እንግሊዘኛና በሌሎች አማርኛ ትርጉሞች እንደ አገናኝ ሀረግ የገባ ነው። ይህ አገናኝ ሀረግ አዲስ ሀሳብ ሲጀመር ወይም አንድ ታሪክ አልቆ ሌላ ታሪክ ሲጀመር የሚያሳይ ነው። ንጉሱ የዕብራውያን ወንድ ልጆች እንዲገደሉ ባዘዘበት ጊዜ ሌላ ታሪክ ሲከሰት ያሳየናል። ተርጓሚዎች በቋንቋቸው እንደዚህ ያሉ አገናኝ ሀረጎች ወይም ቃላት መኖሩን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል።

Exodus 2:3

• የደንገል ሣጥን
በናይል ወንዝ ዳር የሚበቅልና የሚያድግ ከቀጤማ፥ ከመቃ፥ ወይም ከሸምበቆ የተሰራ ቅርጫት መሳይ ነገር ነው።

• ዝፍትና ቅጥራን
ለአስፋልት መንገድ ሥራ የሚጠቅም ቃጥራሜ ወይም ሬንጅ ዓይነት ነገር ነው። ውሃ ወደ ቅርጫቱ እንዳይገባ ወይም እንዳይሰርግ የሚያደርግ ነገር ነው። ጥቁር ወይም ቡናማ ቀለም ያለው ድፍድፍ ነዳጅ ዘይት እና ከዛፍ ላይ የሚገኝ ሲሆን በተፈጥሮ የማጣበቅ ባህርይ ያለው ነው።

• ለቀለቀችው
ውሃ ወደ ውስጥ እንዳይገባ ለጠፈችው ወይም አሸገችው ማለት ነው።

• ቄጠማ
በወንዝ ዳር ወይም ደግሞ እርጥበት ባለበት አከባቢ የሚበቅል ረጅም ሳር መሳይ ነገር ነው፥ ምናልባት ሸምበቆ በሌለበት ወይም በማይታወቅበት ማህበረሰብ ውስጥ ሸምበቆ ወይም ቀርከሃ በምትክነት መጠቀም ይቻላል።

• ራቅ ብላ ቆማ ታይ ነበር
ሌሎች አይተዋት ማን እንደሆነች እንዳይጠቋትና እንዲሁም ህጻኑን ማየትና መከታተል በምትችልበት ርቀት ላይ ቆማ ሁኔታውን እየተከታተለች ነበር ማለት ነው።

Exodus 2:5

• ደንገጥሮችዋም
አገልጋዮቹዋ እንደ ማለት ነው። በተለይ በንጉሱ ሴት ልጅ ላይ ምንም ጉዳት እንዳይደርስባትና ብቸኛ እንዳትሆን የሚጠብቋት አገልጋዮቿ ናቸው።

• በዚህ ጊዜ
በታሪኩ መካከል ላይ ሌላ ጣልቃ ገብ ታሪክ ሲከሰት “በዚህን ጊዜ” በማለት የአንባቢን ትኩረት ይስባል። ይህ አገናኝ ሀረግ በቀድሞና በአዲሱ አማርኛ ትርጉም ላይ እንዲሁም በዕብራይስጡ ላይ አልተጠቀሰም።

Exodus 2:7

• ታጠባልሽ ዘንድ
ሕፃኑን እያጠባች የምታሳድግ ሴት ማለት ነው።

Exodus 2:9

• ሕፃን ወስደሽ አጥቢልኝ
ይህን ሕፃን ወስደሽ እያጠባሽ አሳድጊልኝ

• ለእርስዋም ልጅ ሆነላት
ልጁም የፈርዖን ሴት ልጅ የማደጎ ልጅ ሆነላት ማለት ነው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• ከውኃ አውጥቼዋለሁና
ሙሴ የሚለው የስሙ ትርጉም በዕብራይስጥ ቋንቋ “ማውጣት” የሚል ፍቺ ስላለው ተርጓሚዎች የግርጌ ማስታወሻ በመስጠት የስሙን ፍቺ ግልጽ ሊያደርጉ ይችላሉ።

Exodus 2:11

• የዕብራውያንን ሰው ሲመታ አየ
አንድ ግብፃዊ ሰው ዕብራዊ ወገኑን ሲደበድበው ማየቱን የሚገልጽ ነው

• ወዲህና ወዲያም ተመለከተ
ይህ ሁለት ተቃራኒ አቅጣጫዎች ጠቋሚ አገላለጽ አካባቢውን ቃኝቶ ሰው አለመኖሩን ለማጣራት ሁሉንም አቅጣጫ ተመለከተ የሚል አጠቃላይ ፍቺ ይዟል

Exodus 2:13

• በሁለተኛውም ቀን ወጣ
ሙሴ በማግስቱ እየሆነ ያለውን ነገር ለማየትና ለማጣራት መውጣቱን ለመግለጽ ነው

• በዳዩንም
ጥላቻውን የጀመረውን ወይም ጥፋተኛውን ወይም ጓደኛውን ቀድሞ መምታት የጀመረውን ዕብራዊ ወገኑን ማለት ነው። ይህ አባባል በዕብራውያን ዘንድ የታወቀና በባህሉ የተለመደ አባባል ነው።

• በእኛ ላይ አንተን አለቃ ወይስ ዳኛ ማን አደረገህ?
ይህ ጥያቄ የሚያሳየው ሙሴ በሁለቱ ሰዎች መካከል ጣልቃ በመግባቱ ነገሩን ሳታጣራ ወይም በትክክል ሳትረዳ ለምን አለቃ ትሆናለህ ብሎ ለመገሰጽ የተጠቀመበት አባባል ነው። ይህ አጋናኝ ጥያቄ በመደበኛ ዐረፍተ ነገር ሲተረጎም “አንተ በእኛ ላይ ለመፍረድና መሪ ለመሆን አልተጠራህም” እንደ ማለት ነው።

• ግብፃዊውን እንደገደልኸው ልትገድለኝ ትሻለህን?
ይህ አጋናኝ ጥያቄ የሚያመለክተው ውስጠ ወይራ ወይም አሽሙር ነው። አማራጭ ትርጉሙ፦ ትናንትና አንድ ግብጻዊ እንደገደልክ እናውቃለን፥ እኔን ግን አትገድለኝም” ሊሆን ይችላል።

Exodus 2:15

• ፈርዖንም ይህን ነገር በሰማ ጊዜ
በታሪኩ ውስጥ ፀሐፊው ሌላ ሀሳብ ሲያስገባ ወይም አዲስ የታሪክ ክፍል ሲጨምር እንመለከታለን። ሙሴ ያደርገውን ነገር ፈርዖን ሰምቶታል ማለት ነው ወይም ወሬው ወደ ፈርዖን ደረሰ ማለት ነው።

• ለምድያምም ካህን ሰባት ሴቶች ልጆች ነበሩት
ጸሐፊው በታሪኩ ውስጥ አዳዲስ ሰዎችን ወይም ተዋንያንን ሲጨምር እናያለን፥

• እነርሱም መጥተው ውኃ ቀዱ
በጊዜው ዕብራውያን ውሃ የሚቀዱት ከጉድጓድ ነበርና ውሃ ለመቅዳት ወደ ጉድጓዱ እንደመጡ ያሳያል።

• ገንዳ
ከእንጨት ወይም ከድንጋይ ወይም ከሌሎች ነገሮች የሚሰራ ከብቶችን ውሃ ለማጠጣት ወይም መኖ ለመስጠት የሚያገለግል ነው።

• እረኞችም መጥተው ገፉአቸው
እረኞችም መጥተው እነዚያን ሴቶች አባረሩአቸው፥ ከለከሉአቸው፥ አሳደዱአቸው እንደማለት ነው።

• ሙሴ ግን ተነሥቶ ረዳቸው
እረኞችም መጥተው ሴቶቹን ሲያባርሯቸው ሙሴ ከተቀመጠበት ተነሥቶ ተከላከለላቸው፥ ከእረኞችም እጅ አዳናቸው ወይም አስጣላቸው ማለት ነው።

Exodus 2:18

• ለምንስ ያንን ሰው ተዋችሁት?
ይህ ጥይቄ አነስተኛ የሆነ ቁጣ አዘል ንግግር ወይም ጥያቄ ነው። እንደ ዕብራውያን ባህል እነዚህ ሴቶች ልጆች ይህን ሰው በእንግድነት ወደ ቤታቸው መጋበዝ ነበረባቸው። በቀጥታ ዐረፍተ ነገር ሲነገር “ይህን ሰው በጉድጓድ ውሃው አጠገብ ትታችሁ መምጣት አልነበረባችሁም”

Exodus 2:21

• ሙሴም ከዚያ ሰው ጋር ሊቀመጥ ወደደ
ሙሴም ከሰውየው ወይም ከራጉኤል ጋር ለመኖር ተስማማ ወይም ፈቃደኛ ሆነ ማለት ነው።

• ጺጳራን
የራጉኤል ሴት ልጁ ነች

• ጌርሳም
የሙሴ ታላቅ ልጁ ነው

• በሌላ ምድር መጻተኛ ነኝ
በሰው አገር መጤ ወይም እንግዳ ነኝ ማለት ነው

Exodus 2:23

• አለቀሱ
ከመከራቸውና ከጭንቃቸው የተነሳ ማልቀሳቸውን የሚያሳይ ነው

• ጩኸታቸው ወደ እግዚአብሔር ወጣ
የእስራኤላውያን ጩኸት እግር እንዳለው ሰው ወደ እግዚአብሔር እንደተጓዘ ወይም እንደሄደ በሰውኛ ዘይቤ የተነገረ ነው። በቀጥተኛ ዐረፍተ ነገር ሲነገር “እግዚአብሔር ጩኸታቸውን ሰማ” የሚል ነው።

• እግዚአብሔር . . . ቃል ኪዳኑን አሰበ
ይህ አባባል በዕብራውያን ዘንድ የተለመደ ነው። ሰው አንድን ነገር ረስቶ እንደገና እንደሚያስብ የተነገረ ዘይቤያዊ ንግግር ነው። በሌላ አገላለጽ፦ “እግዚአብሔር የገባውን ቃል ኪዳን አሰበ”።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 ሙሴ የምድያምን ካህን፣ የዐማቱን የየቶርን በጎች ጠብቅ ነበር። በጎቹን ወደ ምድረ በዳው ዳርቻ ነድቶ ወደ እግዚአብሔር ተራራ ወደ ኮሬብ ደረሰ። 2 በዚያም
የእግዚአብሔር መልአክ በቍጥቋጦ ውስጥ በእሳት ነበልባል ተገለጠለት። ሙሴ ተመለከተ፣ እነሆም ቍጥቋጦው እየተቀጣጠለ ነበር፤ ነገር ግን
ቍጥቋጦው አልተቃጠለም። 3 ሙሴም፣ «ልቅረብና ቍጥቋጦው ለምን እንዳልተቃጠለ ይህን አስደናቂ ነገር ልይ» አለ። 4 ሊመለከት እንደ ቀረበ
እግዚአብሔር ሲያየው፣ ከቍጥቋጦው ውስጥ ጠራው፤ «ሙሴ፣ ሙሴ» አለውመ። ሙሴም፣ «እነሆኝ» አለ። 5 እግዚአብሔር፣ «አትቅረብ! የቆምህበት
ምድር ለእኔ ተቀድሶአልና ጫማህን አውልቅ» አለው። 6 ደግሞም፣ «እኔ የአባትህ አምላክ፣ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅ አምላክ፣ የያዕቆብ አምላክ ነኝ»
አለው። ከዚያም በኋላ ሙሴ እግዚአብሔርን ማየት ስለ ፈራ ፊቱን ሸፈነ። 7 እንዲህ አለ፤ «በግብፅ የሚኖሩትን የሕዝቤን ሥቃይ በእርግጥ አይቻለሁ። አሠሪ
አለቆቻቸው ከሚያደርሱባቸው ጭቈና የተነሣ ጩኸታቸውን ሰምቻለሁ፤ ስለ ሥቃያቸው ዐውቃለሁና። 8 ከግብፃውያን አገዛዝ ነጻ ላወጣቸውና ከዚያም ጋር
አውጥቼ ማርና ወተት ወደምታፈሰው መልካምና ለም ወደሆነችው፤ ወደ ከነዓናውያን፣ ኬጢያውያን፣ አሞራውያንን፣ ፌርዛውያን፣ ኤውያውያንና ኢያቡሳውያን
ምድር ላሰገባቸው ወርጃለሁ አለ። 9 የእስራል ሕዝብ ጩኸት ወደ እኔ ደርሶአል። ይልቁንም ግብፃውያን ያደረሱባቸውን ጭቈና አይቻለሁ። 10 ስለዚህ ሕዝቤን፣
እስራኤላውያንን ከግብፅ እንድታወጣ ወደ ፈርዖን እልክልሃለሁ።» 11 ግን፣ እግዚአብሔርን «ወደ ፈርዖን የምሄድና እስራኤላውያንን ከግብፅ የማወጣቸው እኔ
ማን ነኝ?» አለው። 12 ሙሴን መልሶ፣ «እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ። ይህ እኔ እንደ ላክሁህ ምልክት ይሆናል። ሕዝቡን ከግብፅ ስታወጣቸው፣ በዚህ ተራራ ላይ
ታመልኩኛላችሁ» አለው። 13 ሙሴም እግዚአብሔርን፣ «ወደ እስራኤላውያን ስሄድና ‹የአባቶቻችሁ አምላክ ወደ እናንተ ልኮኛል› ብዬ ስነግራቸው፣ እነርሱም፣
«ስሙ ማን ነው? ሲሉኝ ምን እነግራቸዋሉ? አለው። 14 እግዚአብሔርም ሙሴን፣ «እኔ ያለሁ የምኖርም ነኝ። ያለና የሚኖር ወደ እናንተ ልኮኛል ብለህ
ለእስራኤላውያን ንገራቸው» አለው። 15 ደግሞም እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ አለ፤ እግዚአብሔር የአባቶቻችሁ አምላክ፣ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅ
አምላክ፣ የያዕቆብ አምላክ ወደ እናንተ ልኮኛል። ስሜ ለዘለዓለም ይህ ነው፤ ለትውልዶች ሁሉ የታስበውም በዚህ ነው ብለህ ለእስራኤላውያን ንገራቸው።» 16
ሂድና የእስራኤልን ሽማግሌዎች ሰብስብ፤ እንዲህም ብለህ ንገራቸው፤ የአባቶቻችሁ አምላክ፣ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅ አምላክ፣ የያዕቆብ አምላክ
እግዚአብሔር ለእኔ ተገለጠልኝ፤ እንዲህም አለኝ፣ «ጐብኝቻችኋለሁ፤ በግብፅ ውስጥ የደረሰባችሁንም አይቻለሁ። 17 በግብፅ ከደረሰባችሁ ጭቈና ነጻ
ላወጣችሁና ማርና ወተት ወደምታፈሰው ወደ ከነዓናውያን፣ ወደ ኬጢያውያን፣ ወደ አሞራውያን፣ ወደ ፌርዛውያን፣ ወደኤዊያውያንና ወደ ኢያቡሳውያን ምድር
ላገባችሁ ቃል ገብቻለሁ።» 18 ሽማግሌዎቹም ይሰሙሃል። አንተና የእስራኤል ሽማግሌዎች ወደ ግብፅ ንጉሥ ሂዱና፣ የዕብራውያን አምላክ እግዚአብሔር
ተገለጠልን። ስለዚህም ለአምላካችን ለእግዚአብሔር መሠዋት እንድንችል በምድረ በዳው ውስጥ የሦስት ቀን ጕዞ እንሂድ በሉት። 19 ነገር ግን የግብፅ ንጉሥ
እጁ ካልተገደደ በቀር ለመሄድ እንደማይፈቅድላችሁ ዐውቃለሁ። 20 በመካከላቸው በማድረጋቸው ተአምራት ሁሉ ግብፃውያንን እመታቸዋለሁ። ከዚያ በኋላ፣
እንድትሄዱ ይፈቅድላችኋል። 21 ሕዝብ ከግብፃውያን ዘንድ መወደድን እንዲያገኝ አደርጋለሁ፣ ስለዚህ ስትወጡ፣ ባዶ እጃችሁን አትወጡም። 22 ሴት
ከግብፃውያት ጎረቤቶቿና በጎረቤቶቿ ቤቶች ውስጥ ከምትኖር ማንኛውም ሴት የብርና የወርቅ ጌጣጌጦች፣ ልብስም እንዲሰጣት ትጠይቃለች። እነርሱንም
በወንዶችና በሴቶች ልጆቻችሁ ላይ ታደርጓቸዋላችሁ። ግብፃውያንን በዚህ መንገድ ትበዘብዟቸዋላችሁ።

Exodus 3:1

• የእግዚአብሔር መልአክ
አንድ የተለየ የእግዚአብሔር መልዓክ ወይም መልዕክተኛ ማለት ነው።

• እግዚአብሔር
በዕብራይስጡ ያህዌ ተብሎ የሚጠራው ስም ነው። አንዳንድ የእንግሊዘኛ ትርጉሞች ይህን “YHWH” የሚለውን ስም “LORD” ይላሉ፤ ይህ ስም
አዶናይ “ጌታ” ከሚለው ስም ይለያል። የእንግሊዘኛ ትርጉሞች ይህንን ስም ለመለየት “Lord” ብለዋል። በአማርኛችን “ያህዌ” እና “ኤሎሂም”
የሚለው ስም “እግዚአብሔር” በሚለው ስም ተጠቅሶ እናገኛለን።

• እነሆም
ይህ ገላጭ ቃል ለሰው ወይም ለግዑዝ ነገር ሊውል ይችላል። በዕብራይስጡ አዲስ ሀሳብ ለመግለጽ ወይም አዲስ ሀሳብ መኖሩን ለማሳየት ወይም ዕውቅና
ለመስጠት የሚጠቀሙበት ነው።

Exodus 3:4

• ጫማህን ከእግርህ አውጣ
“ራስህን ቀድስ” ወይም “ራስህን ለእግዚአብሔር ለይ” የሚል ነው

• እኔ የአባትህ አምላክ
ይህ አባባል ሁለት ትርጉሞች ይኖሩታል፦ 1) የአባትህ 2) ቅድሜ አያትህ
የሚል ሊሆን ይችላል። በዚህ ክፍል ትርጉሙ “ቅድሜ አያትህ” የሚል ከሆነ
የአብርሃም፥ የይስሃቅ እና የያዕቆብ አምላክ የሚለው ትክክለኛ ትርጉም መሆኑ
ነው። “አባትህ” የሚለው ከሆነ “የሙሴ አባት” መሆኑ ነው።

Exodus 3:7

• ከአስገባሪዎቻቸውም የተነሣ
እስራኤላውያን ከባድ ሥራ እንዲሰሩ የሚያስገድዱ የግብጽ “አሰሪ አለቆች”
ወይም “አሠሪዎቻቸው” ማለት ነው። ከምዕራፍ 1፡11 ጋር ተመሳሳይነት
አለው።

• ወተትና ማር ወደምታፈሰሰው
ይህ ሐረግ በግነታዊ እና በተለዋጭ ዘይቤ የተገለጸ ነው። ይህ አገላለጽ
ከምድሪቱ ወተትና ማር ይፈልቃል ማለት ሳይሆን ለከብት ርባታና ለእርሻ
በጣም ምቹ የሆነ ምድር እንደሆነ ለማሳየት ነው። እንዲሁም “የምታፈስ”
አገር የሚለው ቃልም ሁሉም ነገር የሞላባት ምድር የሚል ፍቺ ያለው ነው።

• ወተት
በእንስሳት ምርትና ተዋጽኦ የዳበረች አገር መሆኑዋን ለማመልከት ነው

• ማር
በእስራኤል ምድር ማር በሁለት መንገዶች ይመረታል። አንደኛው ከከብት
እርባታ የሚገኘው ሲሆን ሁለተኛው ከተምር ዛፍና ከሌሎች ዕጽዋት የሚገኘው
ነው።

Exodus 3:9

• የሕዝቤ የእስራኤል ጩኸት ወደ እኔ ደርሶአል
እዚህ ጋር ጩኸታቸው ወደ እኔ ደርሷል ሲል ጩኸት እጅና እግር አውጥቶ
እንደተራመደ አድርጎ ያቀርባል። ይህ በሰውኛ ዘይቤ የቀረበ ሲሆን
“እግዚአብሔር የእስራኤል ሰዎች ጩኸት ሰምቷል” የሚል ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Exodus 3:11

• ወደ ፈርዖን የምሄድ የእስራኤልንም ልጆች ከግብፅ የማወጣ እኔ ማን ነኝ?
ሙሴ ይህን ጥያቄ እግዚአብሔርን ሲጠይቅ እርሱ ደካማ ሰው መሆኑንና ማንም ሰው እርሱ የሚለውን አይሰማም ብሎ በማሰቡ ነበር። በመደበኛ ንግግር “እኔ ወደ ፈርዖን ለመሄድና የእስራኤልን ልጆች ከግብጽ ለማውጣት በቁ ሰው አይደለሁም” ማለቱ ነው።

Exodus 3:13

• ያለና የሚኖር እኔ ነኝ
ስሙ ማን እንደሆነ ሙሴ ለጠየቀው ጥያቄ እግዚአብሔር ሲመልስ እኔ “ያለሁና የምኖር ነኝ” ስለሆንኩ ስሙ “ ‘እኔ ነኝ’ የሆነ እግዚአብሔር ወደ እናንተ ልኮኛል” ብለህ ንገራቸው አለው።

• ያለና የሚኖር
የዚህ ሀረግ አገላለጽ በሁለት መንገድ ልተረጎም ይችላል። 1) “ያለና የሚኖር ነኝ” የሚለው ሀረግ ስሙ ሊሆን ይችላል፤ 2) እግዚአብሔር ስሙን ሳይሆን ማንነቱን ለሙሴ እየነገረው ሊሆን ይችላል። ስለሆነም እግዚአብሔር ዘላለማዊ ስለሆነ ትናንት የነበረ፥ ዛሬም ያለና ነገም የሚኖር አምላክ ነው።

• እኔ ነኝ
ይህ ስም ለትርጉም አስቸጋሪ ሊሆን ስለሚችል “እኔ ሕያው ነኝ” በሚል ልተረጎም ይችላል።

Exodus 3:16

አጠቃላይ ዕይታ፦ እግዚአብሔር ለሙሴ መናገሩን ቀጥሏል • የአባቶቻችሁ አምላክ የአብርሃም የይስሐቅም የያዕቆብም አምላክ
እነዚህ ሶስቱ ሰዎች የሙሴ ቅድሜ አያቶች ናቸው፥ እንዲሁም የእስራኤላውያንም ቅድሜ አያቶች ናቸው።

• መጎብኘትን ጎበኘኋችሁ
እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ቀድሞ እንዳያቸውና እንደተመለከታቸው እንዲሁም እንደጎበኘቸው ይሳያል።

• እነርሱም ቃልህን ይሰማሉ
“እነርሱ” የተባለው የእስራኤል ሽማግሌዎች ሲሆኑ “ቃልህን” የተባለው ደግሞ ሙሴ የሚናገረውን ቃል እንደሚሰሙ ለማመልከት ነው።

Exodus 3:19

አጠቃላይ ዕይታ፦ እግዚአብሔር ለሙሴ መናገሩን ቀጥሏል • በጽኑ እጅ ካልሆነ በቀር
“በጽኑ እጅ” ምትካዊ ዘይቤ ሲሆን የሀይል ምንጭ የሆነውንና የእጁን ባለቤት አመልካች ነው። የዚህ ሀረግ ሁለቱ ፍቺዎች፦ 1) ፈርዖን ምንም ለማድረግ አቅም እንደለሌው 2) ፈርዖን እንዲለቅ እግዚአብሔር ሲፈቅድ ብቻ መሆኑን ለማመልከት ነው።

• እኔም እጄን እዘረጋለሁ
እግዚአብሔር በታላቅ ሀይሉ ሲያጠቃው ወይም ሲያስገድደው እንደ ማለት ነው። እኔ እጄን እዘረጋለሁ ሲል “ሀይሌን እገልጣለሁ” ማለቱ ነው።

• ባዶ እጃችሁን አትሄዱም
የዚህ ሀረግ ተቃራኒ ሀሳቡ ብዙ ነገሮችን ይዛችሁ፤ ውድና ያጌጡ ነገሮችን አግኝታችሁ በሙላት ትሄዳላችሁ ማለት ነው። የአገላለጹ ምክንያት ትኩረት ለመስጠት ነው።

• ከጎረቤትዋ በቤትዋም ካለችው ሴት
ይህ አባባል 1) በእስራኤላዊት ጎረበት ከምትገኘው ከግብጻዊት ሴት፤ 2) በእስራኤላዊት ጎረበት የምትገኘው ቤት ከምትኖር ሴት ማለት ሊሆን ይችላል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 ሙሴም መልሶ፣ «ባያምኑኝስ ወይም ባይሰሙኝ ነገር ግን በምትኩ፣ እግዚአብሔር አልተገለጠልህም» ቢሉኝስ? 2 እግዚአብሔር ሙሴን፣ «በእጅህ ያለው
ምንድን ነው?» አለው። ሙሴም «በትር» አለ። 3 እግዚአብሔር፣ «መሬት ላይ ጣለው» አለው። ሙሴም በትሩን መሬት ላይ ጣለው፤ በትሩም እባብ ሆነ።
ሙሴ ከእባቡ ሸሸ። 4 እግዚአብሔር ሙሴን፣ «እጅህን ዘርግተህ የእባቡን ጅራት ያዝ» አለው። ሙሴም እጁን ዘረገና እባቡን ያዘው። እባቡ በእጁ ላይ እንደ ገና
በትር ሆነ። 5 «ይህ የሆነው የአባቶቻቸው አምላክ፣ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅ አምላክ፣ የያዕቆብ አምላክ እግዚአብሔር የተገለጠልህ መሆኑን እነዲያምኑ
ነው።» 6 ደግሞም እግዚአብሔር ሙሴን፣ «እጅህን በብትህ ውስጥ አግባ» አለው። እጁን ሲያወጣው እነሆ፣ እንደ በረዶ ነጽቶ ለምጽ ሆኖአል። 7
እግዚአብሔር፣ «እጅህን እንደ ገና በብብትህ ውስጥ አግባ» አለው። ሙሴም እጁን በብብቱ ውስጥ አገባ፣ ከብብቱ ሲወጣውም እንደ ሌላው ሰውነቱ ጤናማ
ሆኖ አየው። 8 እግዚአብሔርም እንዲህ አለ፤ «ባያምኑህ፣ የመጀመሪያውን የተአምር ምልክት ባይቀበሉ ወይም ባያምኑበት፣ ሁለተኛውን ያምናሉ። 9 እነዚህን ሁለት
የተአምር ምልክቶች ባያምኑም እንኳ፣ ወይም ባይሰሙህ፣ ከወንዙ ጥቂት ውሀ ወስደህ በደረቁ መሬት ላይ አፍስሰው። ያፈሰስኸውም ውሀ በደረቁ መሬት ላይ
ደም ይሆናል።» 10 እግዚአብሔርን፣ «ጌታ ሆይ፣ በፊትም፣ አንተ ለባሪያህ ከተናገርህ ወዲህም ርቱዕ አንደበት ያለኝ አይደለሁም። ኮልታፋና ንግግር የማልችል
ሰው ነኝ» አለው። 11 እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው፤ «የሰውን አንደበት የፈጠረ ማን ነው? ሰውን ዲዳ ወይም ደንቈሮ ወይም እንዲያይ ወይም
እንዲታወር የሚያደርግስ ማን ነው? እኔ እግዚአብሔር አይደለምን? 12 አሁን ሂድ፤ እኔም ከአፍህ ጋር እሆናለሁ፤ ምን እንደምትናገርም አስተምርሃለሁ።» 13
ሙሴ ግን፣ «ጌታ ሆይ፣ እባክህ ልትልከው የምትፈልገውን ሌላ ሰው ላክ» አለ። 14 በኋላ እግዚአብሔር ሙሴን ተቈጣው። እንዲህም አለው፤ «ሌዋዊው
ወንድምህ አሮንስ? እርሱ በሚገባ መናገር እንደሚችል ዐውቃለሁ። እንዲያውም ከአንተ ጋር ለመገናኘት እየመጣ ነውና ሲያይህ በልቡ ደስ ይሰኛል። 15 አንተ
ለእርሱ ትናገራለህ፤ የሚናገራቸውንም ቃላት በአፉ ውስጥ ታስቀምጣለህ። እኔ በአፍህና በአፉ እሆናለሁ፣ ምን እነደምታደርጉም አሳያችኋለሁ። 16 ለሕዝቡ
ይናገርልሃል። እርሱ የአንተ አፍ ይሆናል፤ አንተም ለእርሱ እንደ እኔ፣ አምላክ ትሆነዋህ። 17 ይህን በትር በእጅህ ትይዛለህ፣ በእርሱም ተአምራትን ታደርጋለህ።»
18 ሙሴም ወደ ዐማቱ ወደ የቶር ተመልሶ ሄደ፤ «ግብፅ ውስጥ ወዳሉት ዘመዶቼ ተመልሼ እንድሄድና አሁንም ድረስ በሕይወት መኖራቸውን እንዳይ
ፍቀድልኝ» አለው። ዮቶርም ሙሴን፣ «በሰላም ሂድ» አለው። 19 ምድያም ውስጥ እያለ እግዚአብሔር «ሂድ፣ ወደ ግብፅ ተመለስ፤ ሊገድሉህ የሚፈልጉ ሰዎች
ሁሉ ሞተዋል» አለው። 20 መሴም ሚስቱንና ልጆቹን ይዞ፣ በአህያ ላይም አስቀምጦ ወደ ግብፅ ተመለሰ፤ የእግዚአብሔርን በትርም በእጁ ይዞ ነበር። 21
ሙሴን እንዲህ አለው፤ «ወደ ግብፅ ተመልሰህ ስትሄድ፣ በእጅህ ያስቀመጥኋቸውን ተአምራት ሁሉ በፈርዖን ፊት እንደምታደርግ ዐስብ። ነገር ግን እኔ ልቡን
አደነድነዋለሁ፤ ሕዝቡ እንዲሄዱም አይፈቅድም። 22 እንዲህ ብለህ ንገረው፤ «እግዚአብሔር እየተናገረ ያለው ይህን ነው፤ እስራኤል ልጄ፣ በኩሬ ነው፤ 23
«እንዲያመልከኝ ልጄን ልቀቅ ብዬ እነግርሃለሁ።» ነገር ግን ለመልቀቅ እምቢ ስላለህ፣ በኵር ልጅህን እገድላለሁ።» 24 ላይ ለምሽቱ ዐርፈው ሳለ፣
እግዚአብሔር ሙሴን አግንኝቶ ሊገድለው ነበር። 25 ግን ስለታም ቢላዋ ይዛ የልጇን ሸለፈት ገረዘች፤ እግሩንም አስነካችው። ከዚያም በኋላ «አንተ ለእኔ
በእውነት የደም ሙሽራዬ ነህ» አለች። 26 እግዚአብሔር ሙሴን ተወው። «አንተ የደም ሙሽራ ነህ» ብላ የተናገረችው በግርዘቱ ምክንያት ነው። 27 አሮንን፣
«ወደ ምድረ በዳ ሂድና ከሙሴ ጋር ተገናኝ» አለው። አሮን ሄደ፣ ሙሴንም በእግዚአብሔር ተራራ ላይ አግኝቶ ሳመው። 28 እንዲናገር የላከለትን የእግዚአብሔር
ቃሎች ሁሉና እንዲፈጽማቸው ያዘዘውን ተአምራት በሙሉ ለአሮን ነገረው። 29 በኋላ ሙሴና አሮን ሄደው የእስራኤልን ሽማግሌዎች ሁሉ በአንድነት ሰበሰቡ። 30
እግዚአብሔር ተአምራትም በሕዝቡ ፊት አሳየ። 31 አመኑ። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን የጐበኛቸውና የደረሰባቸውን ጭቈና የተመለከተ መሆኑን ሲሰሙም
ሰገዱ፣ አመለኩትም።

Exodus 4:1

• እነሆ አያምኑኝም ቃሌንም አይሰሙም
ምንም እንኳን ሙሴ በእግዚአብሔር (በያህዌ) ብያምንም በእርሱ አልታመነም። ይህ የሚያሳየው ሙሴ የእግዚአብሔርን ማንነት ያለመረዳቱን ያሳያል። ሙሴ የተረዳው እርሱ እንዲያደርግ የተጠየቃቸው ነገሮች በእርሱ ሀይል የሚሆኑ መስሎት ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር እየጠየቀ ያለው “በእርሱ እንዲታመንና ሀይሉን እንዲያስተውል ነው።

Exodus 4:4

• እጅህን ዘርግተህ ጅራትዋን ያዝ
እጅህን ዘርጋና ጅራቷን ይዘህ አንሣት

• በእጁም ውስጥ በትር ሆነች
ሙሴም እጁን ዘርግቶ ሲይዛት እባቧ ተለውጣ በእጁ ላይ እንደ ገና በትር ሆነች ማለት ነው

Exodus 4:6

• እነሆ
በዚህ ክፍል የዚህ ቃል ጥቅም ቃለ አጋኖ ለመፍጠር እና መደነቅን ለማሳየት ነው

• እንደ በረዶ ለምጽ ሆነች
እንደ በረዶ ነጭ ሆነ የሚል ሲሆን ተነጻጻሪ ዘይቤ ነው

Exodus 4:8

• ከወንዙ ውኃን ውሰድ
ይህ ወንዝ የአባይ ወንዝ ወይም በእንግሊዘኛው ናይል ወንዝ የሚንለው ነው።

Exodus 4:10

• አፌ ኮልታፋ
ደህና አድርጎ መናገር የማይችል ወይም አንደበቴ ርቱዕ ያልሆነ ሰው ማለት ነው

• ምላሴም ጸያፍ የሆነ ሰው ነኝ
አንደበቱ የሚኮላተፍና አጥርቶ መናገር የማይችል ሰው ማለት ነው። ሙሴ ይህን የተናገረው አጥርቶ መናገር የማይችል ሰው መሆኑን ለመግለጽ ሲፈልግ ነው።

• ምላሴም ጸያፍ
ኮልታፋና ተናግሮ ለማሳመን አቅም የሚያንሰው መሆኑን ያሳያል (ምትካዊ ዘይቤ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• የሰውን አፍ የፈጠረ ማን ነው?
እግዚአብሔር (ያህዌ) ይህን ጥያቄ ሲጠይቅ ሰዎች መናገር እንዲችሉ አድርጎ የፈጠረውና ለመናገርም አፍ የፈጠረው እርሱ ራሱ መሆኑን ለማጽናት ፈልጎ ነው (አጋናኝ ዘይቤ)

• ዲዳስ ደንቆሮስ የሚያይስ ዕውርስ ያደረገ ማን ነው?
እግዚአብሔር (ያህዌ) ይህን ጥያቄ የጠየቀው ሰዎች መናገርና መስማት እንዲችሉ የሚያደርገው ራሱ እንደሆነ ለማሳየት ነው (አጋናኝ ጥያቄ)

• እኔ እግዚአብሔር አይደለሁምን?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ ሲጠይቅ ሁሉን ነገር የሚወስነው ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን ለማጽናት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ ይህን ሁሉ የማደርግ እኔ እግዚአብሔር አይደለሁምን? (አጋናኝ ጥያቄ) ወይም ይህን ሁሉ የማደርግ እኔ እግዚአብሔር ነኝ።

• እኔም ከአፍህ ጋር እሆናለሁ
“አፍ” የሚለው ቃል የሙሴ የመናገር ችሎታውን ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የመናገር ችሎታ ለአንተ እሰጣለሁኝ” ወይም “መናገር እንድትችል አደርጋለሁ”

Exodus 4:14

• የእግዚአብሔርም ቁጣ በሙሴ ላይ ነደደ
“ቁጣ” እንደ እሳት የመንደድ ባህርይ እንዳለው ተደርጎ የቀረበው ተለዋጭ ዘይቤ ነው። እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ ላይ እጅግ ተቆጣ።

• ሌዋዊው ወንድምህ አሮን
ሌዋዊ የሆነው ወንድምህ አሮን/ከሌዊ ነገድ የሆነው ወንድምህ አሮን

• ባየህም ጊዜ በልቡ ደስ ይለዋል
“በልቡ” የሚለው ቃል የአንድ ሰው ውስጣዊ ሀሳቡንና ስሜቱን የሚመለከት ነው። አማራጭ ትርጉም፡ አንተን በሚያይበት ጊዜ በጣም ደስ ይለዋል (ምትካዊ ዘይቤ)

• ቃሉንም በአፉ ታደርገዋለህ
ቃሉን በአፉ ታደርገዋል የሚለው ሀረግ አንድን ነገር በአንድ ሰው አፍ ውስጥ እንደማኖር/እንደማስቀመጥ ይታይ ይሆናል። አማራጭ ትርጉም፦ “እርሱ መናገር ያለበትን መልዕክት ይሰጠዋል/ያቀርብለታል”

• እኔ ከአፍህና ከአፉ ጋር እሆናለሁ
ከ “አፍህና ከአፉ” ጋር የሚሉ ቃላት የሚያሳዩት ሁለቱም የሚጠቀሙትን የቃላት ምርጫና አጠቃቀም ይመለከታል። ሙሴና አሮን መልዕክታቸውን ለማስተላለፍ ተገቢ የሆነ ቃላት ይመርጣሉ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ እኔ መልዕክታችሁን ለማስተላለፍ የሚያስችላችሁን ተገቢ ቃል እሰጣችኋለሁ (ምትካዊ ዘይቤ)

• እርሱ አፍ ይሆንልሃል (ምትካዊ ዘይቤ)
ይህ አባባል የሚያሳየን አሮን የሚናገረው ሙሴ የተናገረውን መልዕክት መሆኑን ነው።

• አንተም በእግዚአብሔር ፈንታ ትሆንለታለህ
እግዚአብሔር በሙሴ ላይ እንዳለው ዓይነት ሥልጣን ሙሴ በአሮን ላይ ይኖረዋል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እንተ ለአሮን ሲትናገር እኔ እግዚአብሔር ለአንተ (ለሙሴ) በተናገረው ስልጣን ለአሮን ትናገራለህ”

Exodus 4:18

• ወደ አማቱ ወደ ዮቶር ተመለሰ
ሙሴ ወደ ሚስቱ አባት ወይም ወደ አማቹ ወደ ዮቶር ተመለሰ ማለት ነው

Exodus 4:21

• እኔ ግን ልቡን አጸናዋለሁ
እኔ ልቡን አጸናዋለሁ ማለት አበረታታዋለሁ ወይም ድፍረት እሰጠዋለሁ ማለት ሳይሆን ልቡን አደነድነዋለሁ፥ አመጸኛ አደርገዋለሁ፥ እንዳይታዘዝና እንዳይሰማ አደርገዋለሁ ማለት ነው (ምትካዊና ንጽጽራዊ ዘይቤ)።

• እስራኤል የበኩር ልጄ ነው
እስራኤል የሚለው ቃል መላውን የእስራኤል ህዝብ የሚወክል ቃል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የእስራኤል ህዝብ የእኔ ልጆች” ናቸው።

• የበኩር ልጄ ነው
የእስራኤል ህዝብ የእግዚአብሔር ልጅ ብቻ ሳይሆን ደስታና ኩራት የሆነ የእግዚአብሔር ልጅ ነው (ተለዋጭ ዘይቤ)።

Exodus 4:24

• በመንገድ ላይ ባደረበት ስፍራ እግዚአብሔር ተገናኘው፥ ሊገድለውም ፈለገ
የዚህ ትርጉም በትክክል ባይታወቅም ምናልባት ሙሴ ልጁን ባለመገረዙ ምክንያት ሊሆን ይችላል።

• ሲፓራም ሚስቱ
የሙሴ ሚስት ስሟ ሲፖራ ወይም በዕብራይስጡ ጽፖራ ነው።

• ባልጩት
የተፈጥሮ ስለት ያለው ለመቁረጥ የሚያገለግል የባልጩት ድንጋይ

• ወደ እግሩም ጣለችው
ይህ “ወደ እግሩም ጣለችው” የሚለው ሀረግ ሁለት ዋና ዋና የትርጉም አመለካከቶች አሉት። 1) ልጁ መገረዙን ለማመልከት በእግሩ ላይ የደም ምልክት እንድኖር ስትፈልግ እናቱ የቆረጠችውን ሸለፈት በልጁ እግር ላይ መጣሏን፤ 2) “እግር” የሚለው ቃል በእስራኤላውያን ዘንድ የአይነኬ ዘይቤ አገላለጽ በመሆኑ ወደ ሙሴ የመዋለጃ ብልት ላይ ጣለችው የሚል አመለካከትም አለው።

• አንተ ለእኔ የደም ሙሽራ ነህ
የዚህ ሀረግ ፍቺው ወይም መልዕክት ግልጽ አይደለም። እንደዚህ ዓይነት ንግግር በጊዜው በእስራኤል ታሪክ የሚታወቅ ልሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በዚህ ደም ምክንያት አንተ ከእኔ ጋር ግንኙነት አለ” ወይም “በዚህ ደም ምክንያት አንተ ለእኔ ባሌ ነህ”

Exodus 4:27

• እግዚአብሔርም አሮንን
በዚህ ክፍል የታሪኩን አዲስ ጀማሮ ለማመልከት የሚረዳ አንድ አገናኝ ቃል መጠቀም ጥሩ ነው። ለምሳሌ፦ “በዚህን ጊዜ” ብሎ መቀጠል ይቻላል።

• በእግዚአብሔር ተራራ ተገናኘው
ይህ በሲና የሚገኘው ተራራ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን በትክክል የትኛው ተራራ እንደሆነ አይናገርም።

• እግዚአብሔር በእርሱ ዘንድ የላከውን ቃል ሁሉ
በእርሱ ዘንድ የሚለው ቃል በሙሴ በኩል የሚለውን ፍቺ ይይዛል።

Exodus 4:29

• ጭንቀታቸውንም አየ
እግዚአብሔር እስርኤላውያንን አየ ወይም ለእነርሱ አሰበ የሚል ነው።

• አነነበሱ ሰገዱም
ተንበርክከው ሰገዱ የሚል ነው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 5

1 እነዚህ ነገሮች ከሆኑ በኋላ፣ ሙሴና አሮን ወደ ፈርዖን ሄደው፣ እንደዚህ አሉ፤ «የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር የሚለው ይህ ነው፦ ‹በምድረ በዳው ለእኔ በዓል እንዲያደርጉ ሕዝቤን ልቀቅ።›» **2** ፈርዖንም፣ «እግዚአብሔር ማን ነው? ቃሉን የምሰማው፣ እስራኤልንስ የምለቅ ለምንድን ነው? እግዚአብሔርን አላውቀውም፤ እስራኤልንም አልለቅም» አለ። **3** ሙሴና አሮንም፣ «የዕብራውያን አምላክ ከእኛ ጋር ተገናኝቶአል። በመቅሠፍትና በሰይፍ እንዳይመታን፣ ወደ ምድረ በዳው የሦስት ቀን ጕዞ እንድናደርግና ለእግዚአብሔር እንድንሠዋ ፍቀድልን» አሉት። **4** የግብፅ ንጉሥ ግን፣ «አንተ ሙሴ አንተም አሮን! ሕዝቡን ሥራቸውን አስፈትታችሁ የምትወስዷቸው ለምንድን ነው? ወደ ሥራችሁ ሂዱ» አላቸው። **5** እንዲህ አላቸው፤ «በምድራችን አሁን ብዙ ዕብራውያን አሉ፤ እናንተም ሥራ ታስፈቷቸዋላችሁ።» **6** በዚያው ቀን ፈርዖን ለሕዝቡ አሠሪዎችና ተቈጣጣሪዎች ትእዛዝ ሰጠ። እንዲህም አለ፤ **7** «እንደ ቀድሞው፣ ከእንግዲህ ወዲያ ለሸክላ ሥራ ጭድ አታቅርቡ። እነርሱ ራሳቸው ይሂዱና ጭድ ይሰብስቡ። **8** ሆኖም በፊት የሚሠሩትን አንድ ዐይነት የሸክላ ቊጥር አሁንም ሠርተው እንዲያቀርቡ ማድረግ አለባችሁ። ከዚያ ያነሰ አትቀበሉ፤ ምክንያቱም ሰነፎች ናቸው። ‹እንሂድ ፍቀድልንና ለአምላካችን እንሠዋ› እያሉ የሚጮኹትም ለዚህ ነው። **9** እንዲተጉና ለማይረባ ንግግር ትኵረት እንዳይሰጡ ሥራውን ጨምራችሁ አክብዱባቸው።» **10** ስለዚህ የሕዝቡ አሠሪ አለቆችና ተቈጣጣሪዎች ወጥተው ሄዱ፤ ለሕዝቡም ነገሯቸው። እንዲህም አሉ፤ «ፈርዖን የሚለው ይህ ነው፦ ‹ከእንግዲህ ወዲያ ምንም ጭድ አልሰጣችሁም። **11** ሂዱና ማግኘት ከምትችሉበት ፈልጋችሁ አምጡ፤ የሥራችሁ መጠንም አይቀላለም።» **12** ሕዝቡ በጭድ ፈንታ ገለባ ለመሰብሰብ በግብፅ ምድር ሁሉ ተሠራጩ። **13** አለቆቹ፣ «ጭድ በሚቀርብላችሁ ጊዜ የምትሠሩትን ሥራችሁን ጨርሱ» ይሏቸውና ያስጠነቅቋቸው ነበር።» **14** ፈርዖን የመደባቸው አሠሪ አለቆች የሠራተኞች ተቈጣጣሪ ያደረጓቸውን እስራኤላውያን ጎላፊዎች ገረፏቸው። አሠሪ አለቆቹ፣ «በፊት ታደርጉት እንደ ነበረው፣ ትናንትናም ዛሬም የሚጠበቅባችሁን ሸክላ በሙሉ ሠርታችሁ ያላቀረባችሁ ለምንድን ነው?» እያሉ ይጠይቋቸው ነበር። **15** እስራኤላውያን ተቈጣጣሪዎቹም ወደ ፈርዖን መጥተው አቤቱታ አቀረቡ። እንደዚህም አሉት፤ «ባሪያዎችህን በዚህ መንገድ ለምን እንድንኖር ታደርጋለህ? **16** ጭድ አይሰጡንም፤ ነገር ግን አሁንም ‹ሸክላ ሥሩ!› ይሉናል። እኛ ባሪያዎችህ ተገርፈናልም፤ ስሕተቱ ግን የገዛ ሕዝብህ ነው።» **17** ግን እንዲህ አለ፤ «እናንተ ሰነፎች! እናንተ ሰነፎች! ‹ለእግዚአብሔር እንድንሠዋ ፍቀድልን› ትላላችሁ። **18** ወደ ሥራ ተመለሱ። አንዳችም ጭድ አይሰጣችሁም፤ ነገር ግን አሁንም ያንኑ የሸክላ ቊጥር መሥራት አለባችሁ።» **19** «የየቀኑን የሸክላ ቊጥር መቀነስ የለባችሁም» የሚለው ሲነገራቸው፣ እስራኤላውያን ተቈጣጣሪዎች ችግር ውስጥ እንደ ነበሩ አስተዋሉ። **20** ከፈርዖን ዘንድ ሲወጡ፣ ከቤተ መንግሥቱ ውጭ ቆመው ከነበሩት ከሙሴና ከአሮን ጋር ተገናኙ። **21** ለሙሴና ለአሮንም እንዲህ አሏቸው፣ «እግዚአብሔር ይይላችሁ፣ ይፍረድባችሁም፤ ምክንያቱም በፈርዖንና በአገልጋዮቹ ፊት አስጸያፊዎች እንድንሆን አድርጋችሁናል።» **22** ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ፣ «ጌታ ሆይ፣ በዚህ ሕዝብ ላይ መከራ እንዲደርስበት ያደረግህ ለምንድን ነው? እኔንስ ቀድሞውኑ ለምን ላክኸኝ? **23** ስም ልነግረው ወደ ፈርዖን ከመጣሁበት ጊዜ ጀምሮ፣ በዚህ ሕዝብ ላይ መከራ አምጥቶአል፤ አንተም ሕዝብህን ከቶ ነጻ አላወጣኸውም» አለው።

Exodus 5:1

• ከዚህም በኋላ
በትረካ ውስጥ “ከዚህ በኋላ” የሚለው አገናኝ ሀረግ አንድ ዋና ሀሳብ ከተነገረ በኋላ ቀጣይ የትረካው አካል መከተሉን ያመለክታል። ይሁን እንጂ ሙሴና አሮን ወደ ፈርዖን ተመልሰው ለመሄድ ምን ያህል ጊዜ እንደወሰደባቸው ግልጽ አይደለም።

• በዓል ያደርግልኝ ዘንድ
እግዚአብሔርን በማምለክ የአግዚአብሔር በዓል እንዲያደርጉ ወይም እንዲያከብሩ ማለት ነው

• እግዚአብሔር ማን ነው?
ይህ አጋናኝ ጥያቄ የሚያሳየው ፈርዖን እግዚአብሔር እውነተኛ እና ልታወቅ የሚገባ አምላክ መሆኑን ለማወቅ አለመፈለጉን ወይም አለማወቁን አመልካች ነው። በመደበኛ ዐረፍተ ነገር ሲጻፍ፦ እግዚአብሔር (ያህዌ) ማን እንደሆነ አላውቅም ማለቱ ነው።

• የእርሱን ትእዛዝ ሰምቼ
የእርሱን ድምጽ/ትዕዛዝ ሰምቼ የሚለው እግዚአብሔር የሚናገረውን ቃል ሰምቼ የሚል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ እርሱ/እግዚአብሔር የሚለውን ሰምቼ

Exodus 5:3

• የዕብራውያን አምላክ
ይህ ቃል “የእስራኤላውያን አምላክ ወይም ያህዌ” የሚለውን የሚገልጽ ነው

• ቸነፈር ወይም ሰይፍ እንዳይጥልብን
ይህ ሀረግ እግዚአብሔር በሽታ ሲልክብን ወይም ጦርነት ሲያስነሳብን ወይም ጠላት ሲልክብን ማለት ነው።

• ሕዝቡን ለምን ሥራቸውን ታስተዋላችሁ?
ፈርዖን ይህን አጋናኝ ጥያቄ ሙሴንና አሮንን ሲጠይቅ እስራኤላውያን ሥራ እንዳይሰሩ እያደረጉ ነው ብሎ ስላሰበና በእነርሱ ላይ መቆጣቱን ለመግለጽ ነው። እማራጭ ትርጉም፦ “ህዝቡ ሥራ እንዳይሰራ አታደርጉ ወይም ሥራ አትከለክሉ ወይም ሥራ አታስፈቱ”

Exodus 5:6

• አስገባሪዎች ሹማምቶቹንም
ግብጻውያን አሠሪዎችና የእስራኤላውያን ሠራተኞች አለቆችን የሚመለከት ነው

• ለጡብ ሥራ ገለባ ለሕዝቡ አትስጡ
ይህን እንዳያደርጉ የተነገራቸው አስገባሪዎችና ሹማምቶችን ነው። “አትስጡ” የሚለው የወል ስም ስለሆነ አሰሪ አለቆችን ይመለከታል።

Exodus 5:10

• አስገባሪዎች ሹማምቶቹንም
ግብጻውያን አሠሪዎችና የእስራኤላውያን ሠራተኞች አለቆችን የሚመለከት ነው (ዘጸአት 1:11 ተመለከት)

• ገለባ አልሰጣችሁም
“አልሰጣችሁም” ሲል ለእናንተ የሚለውን የወል ስም የሚገልጽ ሲሆን እስራኤላውያንን የሚመለከት ነው።

• እናንተ ሂዱ
ግብጻውያን ገለባ በመሰብሰብ ሥራ እስራኤላውያንን አያግዙአችሁም ማለት ነው። ራሳቸው ለገለባ ፍለጋ ይሄዳሉ ማለት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• ከሥራችሁ ግን ምንም አይጎድልም
ይህን አገላለጽ በሌላ መልክ ሲገለጽ፦ ከዚህ በፊት በምትሰሩት ጡብ ልክ ሥራችሁን ሰርታችሁ ታቀርባላችሁ ማለት ነው።

Exodus 5:12

• በግብፅ ምድር ሁሉ ተበተኑ
የተሰጣቸውን ወይም የተጣለባቸውን ሥራ ለመስራት እስራኤላውያን በግብጽ ምድር መሰራጨታቸውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ በግብጽ ምድር በሁሉም አከባቢዎች እስራኤላውያን ተበተኑ። (ግነታዊና ጥቅል ዘይቤያዊ አነጋገር ተመልከት)

• ገለባ
የስንዴ፥ የገብስ፥ የጤፍ፥ እና የመሳሰሉት የሰብል ዓይነቶች ከአጨዳ ወይም ከውቂያ በኋላ የቀረው ክፍል ነው።

አስገባሪዎች
ግብጻውያን አሠሪዎችና የእስራኤላውያን ሠራተኞች አለቆችን የሚመለከት ነው (ዘጸአት 1:11 ተመለከት)

• ቀድሞ ታደርጉ እንደ ነበራችሁ ትናንትናና ዛሬ የተቆጠረውን ጡብ ስለ ምን አትጨርሱም?
ግብጻውያን አሰሪዎቻቸው ይህን ጥያቄ እስራኤላውያንን የጠየቁት የምጠበቅባቸውን ጡብ ሰርተው ለማቅረብ ባለመቻላቸው ተቆጥተውባቸው ነው። አማራጭ ትርጉም፦ ከዚህ ከደም እንደምታደርጉት ትናንትም ይሁን ዛሬ የሚጠበቅባችሁን ጡብ ሰርታችሁ ማቅረብ አልቻላችሁም (አጋናኝ ጥያቄ)።

Exodus 5:15

• ግድፈቱ ግን በአንተ ሕዝብ ላይ ነው ብለው ጮሁ
ጥፋቱ ወይም ስህተቱ የገዛ ሰዎችህ ነው እንጂ የእኛ አይደለም ብለው አቤቱታ አቀረቡ

• የጡቡንም ሥራ እንድንሠራ ያዝዙናል
“ያዝዙናል” የሚለው ቃል ግብጻውያን አሰሪዎችን የሚመለከት ነው

Exodus 5:19

• በፈርዖንና በባሪያዎቹ ፊት ሽታችንን አግምታችሁታልና
ምክንያቱም እናንተ (ሙሴና አሮን) በንጉሠ በፈርዖንና በመኳንንቱ ዘንድ እጅግ እንድንጠላ አድርጋችሁናል (ተለዋጭ ዘይቤ)

• ይገድሉንም ዘንድ ሰይፍን በእጃቸው ሰጥታችኋቸዋልና
ምክንያቱም እነርሱ እኛን እንዲገድሉ ምክንያት በመሆናችሁ ሰይፍን በእጃቸው ሰጥታችኋቸዋል። ሰይፍ የሚወከለው ያጠፉአቸው ዘንድ ምቹ አጋጣሚ መፈጠሩን ለማመልከት ነው።

Exodus 5:22

• ስለ ምን ይህን ሕዝብ አስከፋህ? (አጋናኝ ጥያቄ)
ይህ አጋናኝ ጥያቄ የሚመለከተው ሙሴ በእስራሴላውያን መበደልና ርህራሄ የለሽ ተግባራቸው የተከፋ መሆኑን ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፦ እግዚአብሔር ሆይ በእስራኤላውያን ላይ በደረሰው ነገር በጣም አዝናለሁ

• ስለ ምንስ ላክኸኝ? (አጋናኝ ጥያቄ)
ሙሴ እስራኤላውያንን ነጻ እንዲያወጣ በመላኩ ማዘኑን የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ ወደዚህ ስፍራ ባትልከኝ እመርጥ ነበር።

• በስምህ እናገር ዘንድ
“በስምህ” የሚለው የእግዚአብሔር መልዕክት ለማማመልከት ነው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 6

1 ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ሙሴን፣ «በፈርዖን ላይ የማደርገውን አሁን ታያለህ፡፡ ከጽኑዕ እጄ የተነሣ ሕዝቡን ይለቃቸዋልና፣ ይህን ታያለህ፡፡ ከጽኑዕ እጄ የተነሣ
ሕዝቡን ከምድሩ ያስወጣቸዋል» አለው፡፡ 2 ለሙሴ እንዲህ አለው፤ «እኔ እግዚአብሔር ነኝ፡፡ 3 እኔ ለአብርሃም፣ ለይስሐቅ፣ ለያዕቆብ ሁሉን እንደሚችል አምላክ
ተገለጥሁላቸው፤ ነገር ግን በስሜ፣ በእግዚአብሔር ለእነርሱ አልታወቅሁላቸውም ነበር፡፡ 4 የተሰደዱባትን፣ በእንግድነት የኖሩባትን የከነዓንን ምድር ልሰጣቸው፣
ከእነርሱ ጋር ኪዳን አጽንቻለሁ፡፡ 5 ደግሞም ግብፃውያን ባሪያ ያደረጓቸውን የአስራኤላውያንን ጩኸት ሰምቻለሁ፤ ኪዳኔንም አስታውሻለሁ፡፡ 6 ስለዚህ
ለእስራኤላውያን እንዲህ በላቸው፤ ‹እኔ እግዚአብሔር ነኝ፡፡ በግብፃውያን ሥር ከምትኖሩባት ባርነት እታደጋችኋለሁ፤ ከአገዛዛቸውም ነፃ አወጣችኋለሁ፡፡ በታላቅ
ፍርድና ኀይሌን በማሳየት እታደጋችኋለሁ፡፡ 7 አድርጌ ወደ ራሴ እወስዳችኋለሁ፤ እኔም አምላካችሁ እሆናለሁ፡፡ ግብፃውያን ከጫኑባችሁ ባርነት ነፃ ያወጣኋችሁ
አምላካችሁ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ፡፡ 8 ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ ልሰጥ ቃል ወደገባሁባት ምድር አስገባችኋለሁ፡፡ ምድሪቱን ርስት
አድርጌ እሰጣችኋለሁ፡፡ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፡፡› 9 ይህን ለእስራኤላውያን በነገራቸው ጊዜ፣ በአስከፊው ባርነታቸው ተስፋ ከመቊረጣቸው የተነሣ
አላደመጡትም፡፡ 10 ሙሴን እንዲህ አለው፤ 11 ሂድና ለግብፅ ንጉሥ ለፈርዖን የእስራኤልን ሕዝብ ከምድሩ እንዲለቅ ንገረው፡፡ 12 ሙሴም እግዚአብሔርን፣
«ተብታባ በመሆኔ እስራኤላውያን ካልሰሙኝ፣ ፈርዖን እንዴት ይሰማኛል? 13 እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን አናገራቸው፡፡ እስራኤላውያን ከግብፅ ምድር
እንዲያስወጡ ስለ ግብፅ ንጉሥ ስለ ፈርዖንና ስለ እስራኤላውያንም ትእዛዝ ሰጣቸው፡፡ 14 የአባቶቻቸውም ቤት አለቆች እነዚህ ነበሩ፤ የእስራኤል በኵር ልጅ
የሮቤል ልጆች ሄኖኅ፣ ፈሉስ፣ አስሮንና ከርሚ ነበሩ፡፡ እነዚህ የሮቤል ነገድ ናቸው፡፡ 15 የስምዖን ልጆች ይሙኤል፣ ያሚን፣ ኦሃድ፣ ያኪን፣ ዱሐርና የከነዓናዊቷ ሴት
ልጅ ሳኡል ነበሩ፡፡ እነዚህ የስምዖን ነገድ አባቶች ናቸው፡፡ 16 የሌዊ ልጆች ስሞች ከትውልዶቻቸው ጋር እነዚህ ናቸው፤ ጌድሶን፣ ቀዓትና ሜራሪ ነበሩ፡፡ ሌዊ መቶ
ሠላሳ ዓመት ኖረ፡፡ 17 የጌድሶን ልጆች ሉቤኒና ሰሜኢ ነበሩ፡፡ 18 የቀዓት ልጆች እንበረም፣ ይሰዓር፣ ኬብሮንና ዑዝኤል ነበሩ፡፡ ቀዓት መቶ ሠላሳ ሦስት ዓመት
ኖረ፡፡ 19 የሜራሪ ልጆች ሞሖሊና ሙሲ ነበሩ፡፡ እነዚህ በትውልዶቻቸው መሠረት፣ የሌዋውያን የነገድ አባቶች ሆኑ፡፡ 20 የአባቱን አጎት ዮካብድን አገባ፤
እርሷምአሮንንና ሙሴን ወለደችለት፡፡ እንበረም መቶ ሠላሳ ሰባት ዓመት ኖሮ ሞተ፡፡ 21 የይስዓር ልጆች ቆሬ፣ ናፌግና ዝክሪ ነበሩ፡፡ 22 ልጆች ሚሳኤል፣
ኤልዳፋንና ሥትሪ ነበሩ፡፡ 23 የአሚካዳብን ልጅ፣ የነኦሶንን እኅት ኤልሳቤጥን አገባ፡፡ እርሷም ናዳብንና አብዩድን፣ አልዓዛርንና ኢታምርን ወለደችለት፡፡ 24 የቆሬ
ልጆች አሴር፣ ሕልቃናና አብያሳፍ ነበሩ፡፡ እነዚህ የቆሬ ነገድ አባቶች ናቸው፡፡ 25 ልጅ አልዓር ከፏትኤል ልጆች አንዲቱን አገባ፡፡ እርሷም ፊንሐስን ወለደችለት፡፡
እነዚህ በየትውልዶቻቸው የሌዋውያን አባቶች ቤቶች አለቆች ናቸው፡፡ 26 ሁለት ሰዎች፣ «እስራኤላውያንን በየተዋጊ ሰራዊታቸው ከግብፅ ምድር አውጡ» ብሎ
እግዚአብሔር ያዘዛቸው አሮንና ሙሴ ነበሩ፡፡ 27 ሙሴ እስራኤላውያንን ከግብፅ ለማውጣት እንዲፈቅድላቸው ለግብፅ ንጉሥ ለፈርዖን ተናገሩ፡፡ እነዚህ ሙሴና
አሮን እነዚያው ራሳቸው ነበሩ፡፡ 28 እግዚአብሔር በግብፅ ውስጥ ሙሴን ባናገረው ጊዜ፣ 29 «እኔ እግዚአብሔር ነኝ፡፡ የምነግርህን ሁሉ ለግብፅ ንጉሥ
ለፈርዖን ንገረው» አለው፡፡ 30 ግን እግዚአብሔርን፣ «እኔ ተብታባ ነኝ፤ ፈርዖን ታዲያ እንዴት ይሰማኛል? አለው፡፡

Exodus 6:1

• በጸናች እጅ ይለቅቃትኋልና፥ በጸናችም እጅ ከምድሩ አስወጥቶ ይሰድዳቸዋልና (ምትካዊ ዘይቤ)
“የጸናች እጅ” የፈርዖን እጅ ሳይሆን የእግዚአብሔር ሀይል ለማመልከት ነው። “እጅ” ምትካዊ ዘይቤ ስለሆነ የእግዚአብሔርን ሀይል ይመለከታል። አማራጭ ትርጉም፦ “በእግዚአብሔር ሀይል ይለቃቸዋል፤ በሀይሌም ከምድርቱ አስወጥቶ ይሰዳቸዋል”

Exodus 6:2

• ለአብርሃምም ለይስሐቅም ለያዕቆብም ሁሉን እንደሚችል አምላክ ተገለጥሁ
እኔ ራሴን ለአብርሃም፥ ለይስሃቅና ለያዕቆብ አሳየሁ

• ነገር ግን ስሜ እግዚአብሔር አልታወቀላቸውም
ነገር ግን ያህዌ በሚለው ስሜ አላወቁኝም

• የእስራኤልን ልጆች ልቅሶ ሰማሁ
በአማርኛው ቅጅ “ለቅሶ” የሚለው ቃል በዕብራይስጡ ለቅሶ ሳይሆን “ጭንቀትን፥ ሰቆቃን፥ ማቃሰትን፥ መቃተትን” የሚመለከት ነው።

Exodus 6:6

• ለእስራኤል ልጆች እንዲህ በላቸው
ትዕዛዛዊ ንግግር ነው፤ ሙሴ ለእስራኤላውያን እንድነግራቸው ያህዌ ሙሴን ሲያዘው ያሳየናል።

• በተዘረጋ ክንድ በታላቅ ፍርድም እታደጋችኋለሁ
ግብጻውያንን በመቅጣት ወይም በመምታትና ለእስራኤላውያን እውነተኛ ፍርድ በማምጣት ነጻ አወጣችኋለሁ። “የተዘረጋች ክንድ” የሚለው ሀረግ ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን ግብጻውያንን እቀጣለሁ ወይም እፈርድባቸዋለሁ” ማለት ነው።

Exodus 6:8

• ወደ ማልሁባት ምድር አገባችኋለሁ
ተስፋ ወደ ገባሁላቸው ምድር አስገባቸዋለሁ ወይም እሰጣችኋለሁ ብዬ ወደነገርኳቸው ምድር እወስዳችኋለሁ ማለት ነው።

Exodus 6:10

እነሆ የእስራኤል ልጆች አልሰሙኝም፣ እንዴትስ ፈርዖን ይሰማኛል? ይልቁንም እኔ ከንፈረ ቈላፍ ነኝ ብሎ ተናገረ (አጋናኝ ጥያቄ)
ሙሴ ይህን ጥያቄ ሲጠይቅ ሁለት ነገሮችን ተስፋ ያደረገ ይመስላል። 1) ፈርዖን እንደማይሰማኝ ታውቃለህና አታስቸግረኝ ማለቱ ነው 2) እግዚአብሔር የቀድሞ ሀሳቡን ቀይሮ ሙሴን እንዲለቀውና በሙሴ በኩል ልፈጽም ያሰበውን ሀሳብ እንድተው መጠየቁ ነበር። ለዚህ ምክንያት አድርጎ ያቀረበው “እኔ አጥርቼ መናገር የማልችል ኮልታፋ ነኝ” በማለት ነበር። አማራጭ ትርጉም፦ “እስራኤላውያን እስካላመኑ ድረስ ፈርዖንም አያምነኝም”

Exodus 6:14

ዘጸአት 6:14-25 • የአባታቸውም ቤት አለቆች
የየቤተሰቡ ወይም የየነገድ አለቆች። አማራጭ ትርጉም፦ “የአያቶቻቸው አለቆች ወይም መሪዎች”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• ሄኖክ፥ ፋሉ፥ ሔጽሮን፥ ...
የወንዶች ስም ሲሆን የየነገድ ወይም ቅድመ አያቶቻቸው ስም ዝርዝር ነው። ከቁጥር 14-25 ድረስ ባለው ከፍል የተጠቀሱትን የዕብራይስጥ ስሞችንና ቁጥሮችን የመተርጎም ዘዴዎችን አስተውል።

Exodus 6:26

• ከግብፅ ምድር በየሠራዊቶቻቸው የእስራኤልን ልጆች አውጡ
“አንድን ነገድ” ወይም “አንድን ቤተሰብ” በሰልፍ ተራ በተራ መምራትን ያመለክታል። የእስራኤል ሰዎች “ሠራዊት” የተባሉት የጦር ሠራዊት ሆነው ሳይሆን “በየነገዳቸው እንደ ሠራዊት” በሰልፍ መውጣታቸውን ለማመልከት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የእስራኤልን ሕዝብ በየነገዳቸው ከግብጽ ምድር መርታችሁ አውጡ”

Exodus 6:28

• እነሆ እኔ ከንፈረ ቈላፍ ነኝ፣ እንዴትስ ፈርዖን ይሰማኛል?
በዚህ አጋናኝ ጥያቄ ሙሴ የእግዚአብሔርን ሀሳብ ለማስቀየር ያሰበ ይመስላል። እንዲሁም ወደ ፈርዖን ለመሄድ ካለመፈለጉም ሌላ በፈርዖን ድርጊትም ተስፋ የቆረጠ ይመስላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔ የንግግር ችሎታ ስለሌለኝ ፈርዖን በርግጥ አይሰማኝም”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 7

1 ሙሴን እንዲህ አለው፤ «ልብ በል፤ አንተን ለፈርዖን እንደ አምላክ አድርጌሃለሁ። ወንድምህ አሮን ነቢይህ ይሆናል። **2** እንድትናገር ያዘዝሁህን ሁሉ ትናራለህ። የእስራኤል ሕዝብ ከምድሩ እንዲለቀ፣ ወንድምህ አሮን ለፈርዖን ይናገራል። **3** ነገር ግን እኔ የፈርዖንን ለብ አደነድነዋሁ፤ የተአምራቴን ብዙ ምልክቶች፣ ብዙ ድንቆችም በግብፅ ምድር አሳያለሁ። **4** ነገር ግን ፈርዖን አይሰማችሁም፤ ስለዚህ እጄን በግብፅ ላይ አደርጋሁ፤ ሰራዊቱን፣ ሕዝቤን፣ የእስራኤልን ልጆች በታላቅ ፍርድ ከግብፅ ምድር አወጣለሁ። **5** በግብፅ ላይ ስዘረጋና እስራኤላውያንን ከመካከላቸው ሳወጣ፣ ግብፃውያን እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ።» **6** አሮን እንዲሁ አደረጉ፤ እግዚአብሔር ያዘዛቸውን ፈጸሙ። **7** ባጋገሩት ጊዜ፣ የሙሴ ዕድሜ ሰማንያ፣ የአሮን ደግሞ ሰማንያ ሦስት ነበር። **8** ሙሴንና አሮንን እንዲህ አላቸው፤ **9** ‹ተአምር አሳዩ› ሲላችሁ፣ አሮንን እንዲህ በለው፤ ‹በትርህን ውሰድና በፈርዖን ፊት ጣለው፤ እባብም ይሆናል።›› **10** ሙሴ አሮን ወደ ፈርዖን ሄደው፣ እግዚአብሔር አዝዞአቸው የነበረውን አደረጉ። አሮን በትሩን በፈርዖንና በአገልጋዮቹ ፊት ጣለው፤ እባብም ሆነ። **11** ደግሞ ለጥበበኛ ሰዎቹና ለጠንቋዮቹ ጥሪ አደረገ። እነርሱም በምትሀታቸው ያንኑ አደረጉ። **12** እያንዳንዱ ሰው በትሩን ጣለ፤ በትሮቹም እባብ ሆኑ፣ ነገር ግን የአሮን በትር የእነርሱን እባቦች ዋጣቸው። **13** አስቀድሞ እንደ ተናገረው፣ የፈርዖን ልብ ደነደነ፤ አልሰማምም። **14** እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፤ «የፈርዖን ልብ ደንድኖአል፤ ሕዝቡም እንዲሄዱ አይፈቅድም። **15** ወደ ውሃው በሚሄድበት ጊዜ፣ በጠዋት ወደ ፈርዖን ሂድ። እንዳገኘውም በወንዙ ዳር ቁም፤ ወደ እባብነት ተለውጦ የነበረውን በትርህን ውሰድ። **16** እንዲህ በለው፤ ‹የዕብራውያን አምላክ እግዚአብሔር ይህን እንድናገር ወደ አንተ ላከኝ፤ «በምድረ በዳ እንዲያመልኩኝ ሕዝቤን ልቀቅ፤ እስካሁን ድረስ አልሰማህም።» **17** የሚናገረው ይህ ነው፤ «እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ በዚህ ታውቃለህ። የአባይን ወንዝ ውሀ በእጄ በያዝሁት በትር እመታዋለሁ፣ ወንዙም ወደ ደምነት ይለወጣል። **18** ውስጥ የሚገኙት ዓሦች ይሞታሉ፤ ወንዙ ይከረፋል።ግብፃውያኑም ከወንዙ ውሀ መጠጣት አይችሉም።» **19** ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ አለ፤ አሮንን፣ ‹በትርህን ውሰድና ውሀቸው ደም እንዲሆን፣ በግብፅ ውሀዎች ላይ፣ በወንዞቻቸውም፣ በምንጮቻቸውም፣ በውሀ ማጠራቀሚያዎቻቸውና በኩሬዎቻቸው ሁሉ ላይ እጅህን ዘርጋ ብለህ ንገረው። በመላው የግብፅ ምድር፣ ከዕንጨትና ከድንጋይ በተሠሩ ውሀ መያዣዎች ያለው ውሀም እንኳ ደም እንዲሆን ይህን አድርግ።›› **20** ሙሴና አሮን እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው አደረጉ። አሮን በትሩን አንሥቶ በፈርዖንና በአገልጋዮቹ ፊት የወንዙን ውሀ መታው። የወንዙ ውሀ በሙሉ ወደ ደምነት ተለወጠ። **21** ውስጥ ያለው ዓሣ ሞተ ወንዙም መከርፋት ጀመረ። ግብፃውያኑ ከወንዙ ውሀ መጠጣት አልቻሉም፤ ደሙም በግብፅ ምድር በየትኛውም ስፍራ ነበረ። **22** የግብፅ ጠንቋዮችም በምትሀታቸው ያንኑ ዐይነት ነገር አደረጉ። ስለዚህ የፈርዖን ልብ ደነደነ፤ እግዚአብሔር ይሆናለ ብሎ ተናግሮት እንደ ተናገረውም ሙሴንና አሮንን ለመስማት እምቢ አለ። **23** ወደ ቤቱ ተመለሰ። ለዚህ ጉዳይ ትኩረትም እንኳ አልሰጠም። **24** ግብፃውያኑ ሁሉ በወንዙ ዙሪያ የሚጠጣ ውሀ ለማግኘት ቈፈሩ፤ ነገ ርግን የወንዙን ውሀ መጠጣት አልቻሉም። **25** እግዚአብሔር ወንዙን ከመታው በኋላ ሰባት ቀን ዐለፈ።

Exodus 7:1

• እይ፥ እኔ ለፈርዖን አምላክ አድርጌሃለሁ
አስተውል፤ ወይም ልብ በል፤ እኔ አንተን ለፈርኦን እንደ አምላክ አድርገሃለሁ።

Exodus 7:3

• እኔም የፈርዖንን ልብ አጸናለሁ
“ልብ” ተብሎ በወካይ ዘይቤ የተገለጠው ራሱን ፈርዖንን ለመግለጽ ነው። የፈርዖንን ልብ ያደነደነው እግዚአብሔር ራሱ እንደሆነ ልብ ይሏል። ስለሆነም ልቡን እግዚአብሔር ስላደነደነው ፈርዖን ለመስማት አልፈለገም ወይም እምብተኛ ሆነ ማለት ነው። (ምዕራፍ 3:21 ተመልከት)

• ድንቄንና ተአምራቴን አበዛለሁ
“ድንቅና ታአምር” ሁለቱም ተመሳሳይ ወይም ቅርብ ፍቺ ያላችው ቃላት ናቸው። ታአምር ድርጊቱን ወይም ክስተቱን ሲገልጽ ድንቅ ምልክትን ወይም የክስተቱ ማረጋገጫ የሚመለከት ነው። ሁለቱም ከተፈጥሮ ክስተት ውጪ የሆኑ የእግዚአብሔር አሰራሮች ናቸው።

• እጄንም በግብፅ ላይ አደርጋለሁ
“እጄን” ሲል ለፍርድና ለቅጣት የተዘረጋውን የእግዚአብሔር እጅ እንጂ የማደፋፈር ወይም የማነቃቃት እጅ ማለት አይደለም። አማራጭ ትርጉም፡- ግብጻውያንን በመፍረድ ወይም በመቅጣት ታላቁን ሀይሌን አሳያቸዋለሁ”

Exodus 7:6

• ሙሴ የሰማንያ ዓመት ሰው ነበር፥ አሮንም የሰማኒያ ሦስት ዓመት ሰው ነበር **(**የተተወ ሀሳብና ቁጥሮችን የመተርጎም ዘዴ ተመልከት**)**
ለሙሴ ዕድሜው ሰማንያ ዓመት ሲሆን የአሮን ዕድሜው ሰማንያ ሦስት ዓመት ነበር።

Exodus 7:8

• ፈርዖን፡- ተአምራትን አሳዩኝ ሲላችሁ፥ አሮንን፡- በትርህን ወስደህ እባብ እንድትሆን በፈርዖን ፊት ጣላት በለው።
ፈርዖን እስቲ ተአምራት በማድረግ ማንነታችሁን ግለጡልኝ’ ቢላችሁ ለአሮን ንገረውና በትሩን ወስዶ በንጉሡ ፊት ይጣለው፤ በዚያን ጊዜ በትሩ ተለውጦ እባብ ይሆናል። (ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪ ንግግር ዕይነቶችን የመተርጎም ዘዴ ተመልከት)

Exodus 7:11

• የአሮን በትር ግን በትራቸውን ዋጠች
ነገር ግን የአሮን በትር የእነርሱን በትሮች ሁሉ ዋጠች።

• የፈርዖን ልብ ጸና **(**ምትካዊ ዘይቤ ተመልከት**)**
ፈርዖን ድፍረት አገኘ ማለት ሳይሆን ፈርዖን እምቢ አለ ወይም እልከኛ ማለት ነው።

Exodus 7:14

• የፈርዖን ልብ ደነደነ
ፈርዖን ለመስማት አልፈለገም፥ እምቢተኛ ሆነ ማለት ነው

• እነሆ ወደ ውኃ ይወጣል **(**ግልጽ ያለሆነ ሀሳብ/ግምታዊ ዕውቀት/ ተመልከት**)**
ወደ አባይ (ናይል) ወንዝ በሚወርድበት/በሚሄድበት ጊዜ

Exodus 7:16

• እንዲህም ትለዋለህ
ለፈርዖን እንዲህ ብለህ ትነግረዋለህ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• እነሆ እኔ የወንዙን ውኃ በእጄ ባለችው በትር እመታለሁ
እነሆ፥ እኔ በዚህ በትር የአባይን ወንዝ ውሃ እመታለሁ

Exodus 7:19

• በግብፅም አገር ሁሉ
በግብፅ ምድር ደም በየቦታው ይሆናል

Exodus 7:20

• የፈርዖን ልብ ጸና **(**ምትካዊ ዘይቤ ተመልከት**)**
ፈርዖን ድፍረት አገኘ ማለት ሳይሆን ፈርዖን እምቢ አለ ማለት ነው።

• በወንዙ የነበሩ ዓሶች
ግልጽ ለማድረግ ከተፈለገ “በአባይ ወንዝ ውስጥ የነበሩ ዓሶች”

Exodus 7:23

• ግብፃውያንም ሁሉ
ብዙ ግብጻውያን ወይም የግብጽ ሰዎች ሁሉ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 8

1 ከዚያም እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፤ «ወደ ፈርዖን ሂድና እንዲህ በለው፤ ‹እግዚአብሔር የሚለው ይህ ነው፤ «እንዲያመልኩኝ ሕዝቤን ልቀቅ። 2 ካልህ፣ አገርህን በሙሉ በጓጒንቸው መቅሠፍት እመታዋለሁ። 3 ጓጒንቸር ይርመሰመሳል። ጓጒንቸሮቹ ከወንዙ ይወጡና ወደ ቤትህ፣ ወደ መኝታ ክፍልህና ወደ ዐልጋህ ውስጥ ይገባሉ። ወደ አገልጋዮችህም ቤቶች ውስጥ ይገባሉ። ወደ ሕዝብህ፣ ወደ ምድጆችህና ወደ ቡሃቆችም ይዛመታሉ። 4 ጓጒንቸሮቹ አንተን፣ ሕዝብህንና አገልጋዮችህን ሁሉ ይመታሉ።› 5 ለሙሴ እንዲህ አለ፤ «አሮንን፣ እጅህንና በትርህን በወንዞች፣ በምንጮችና በቦዮች ላይ ዘርጋና በግብፅ ምድር ላይ ጓጒንቸሮች እንዲወጡ አድርግ» በለው። 6 በግብፅ ውሆች ላይ እጁን ዘረጋ፤ ጓጒንቸዎቹም ወጥተው የግብፅን ምድር ሸፈኑት። 7 ጠንቋዮቹም በምትሃቸው ያንኑ አደረጉ፤ ጓጒንቸሮቹ በግብፅ ምድር ላይ እንዲወጡ አደረጉ። 8 ሙሴንና አሮንን አስጠርቶ፣ «ጓጒንቸሮቹን ከእኔና ከሕዝቤ ላይ አንዲያስወግድ ወደ እግዚአብሔር ጸልዩ። ከዚያም ለእግዚአብሔር እንዲሠዉ ሕዝቡን እለቃቸዋለሁ» አላቸው። 9 ፈርዖንን እንዲህ አለው፤ «ጓጒንቸሮቹ ከአንተና ከቤቶችህ እንዲወገዱ፣ በወንዙ ውስጥ ብቻ ግን እንዲቈዩ፣ ለአንተ፣ ለአገልጋዮችህና ለሕዝብህ የምጸልይበትን ጊዜ ለእኔ መንገሩ የአንተ ድርሻ ነው።» 10 «ነገ» አለው። ሙሴም ፈርዖንን መልሶ፣ «እንደ አምላካችን እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም እንደሌለ እንድታውቅ አንተ እንደምትለው ይሁን። 11 ጓጒንቸሮቹ ከአንተ፣ ከቤቶችህ ከአገልጋዮችህና ከሕዝብህ ይወገዳሉ። በወንዙ ውስጥ ብቻ ግን ይቈያሉ» አለው። 12 አሮን ከፈርዖን ወጥተው ሄዱ። ሙሴም እግዚአብሔር በፈርዖን ላይ ስላመጣቸው ጓጒንቸሮች ወደ እግዚአብሔር ጮኸ። 13 ሙሴ እንደ ለመነው አደረገ፦ ጓጒንቸሮቹ በየቤቱ፣ በየግቢውና በየሜዳው ሞቱ። 14 ሕዝቡ የሞቱትን ሰብስበው ከመሯቸው፤ ምድሩም ከረፋ። 15 ነገር ግን ፈርዖን ፋታ መገኘቱን ሲያይ፣ ልቡን አደነደነ፤ እንደዚህ ያደርጋል ብሎ እግዚአብሔር ተናግሮ እንድ ነበረ፣ ሙሴንና አሮንንም አልሰማቸውም። 16 ለሙሴ እንዲህ አለ፤ «አሮንን እንዲህ በለው ‹በመላው የግብፅ ምድር ተባይ እንዲሆን የምድሩን ትቢያ በበትርህ ምታ።›» 17 እነርሱም እንዲሁ አደረጉ፦ አሮን እጁን ዘርግቶ በበትሩ የምድሩን ትቢያ መታው። በሰውና በእንስሳ ላይ ተባይ መጣ። የምድሩ ትቢያ ሁሉ በመላው የግብፅ ምድር ተባይ ሆነ። 18 በምትሃቸው ተባይ እንዲመጣ ሙከራ አደረጉ፤ ነገር ግን አልቻሉም። በሰውና በእንስሳ ላይ ተባዮች ነበሩ። 19 ጠንቋዮቹ ታዲያ ፈርዖንን፣ «ይህ የእግዚአብሔር ጣት ነው» አሉት። ነገር ግን የፈርዖን ልብ ደነደነ፤ እነርሱንም ለማድመጥ እምቢ አለ። ይህም የሆነው ፈርዖን እንዲህ እንደሚያደርግ እግዚአብሔር ተናግሮት በነበረው መሠረት ነው። 20 እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፤ «በማለዳ ተነሣና ፈርዖን ወደ ወንዙ ሲወጣ በፊት ለፊቱ ቁም። እንደዚህም ብለህ ንገረው፤ ‹እግዚአብሔር የሚለው ይህ ነው፦ «እንዲያመልኩኝ ሕዝቤን ልቀቅ። 21 የማትለቅ ከሆነ ግን፣ በአንተ፣ በአገልጋዮችህና በሕዝብህ ላይ፣ ወደ ቤቶችህም ውስጥ የዝንብ መንጋ እልካለሁ። የግብፃውያን ቤቶች በዝንብ መንጋ ይሞላሉ፤ የሚቆሙበት ምድርም እንኳ ዝንብ ብቻ ይሆናል። 22 ግን በዚያ ቀን የዝንብ መንጋ እንዳይገኝባ፣ ሕዝቤ የሚኖርባትን የጌሤምን ምድር በተለየ ሁኔታ እይዛታለሁ። እኔ እግዚአብሔር በዚህ ምድር እንዳለሁ እንድታውቅ ይህ ይሆናል። 23 በሕዝቤና በሕዝብህ መካከል ልዩነት እንዲኖር አደርጋለሁ። ይህ ተአምራዊ ምልክት ነገ ነው የሚሆነው።» 24 እግዚአብሔር እንዲሁ አደረገ፤ ጥቅጥቅ ያለ የዝንብ መንጋም ወደ ፈርዖን ቤትና ወደ አገልጋዮቹ ቤቶች መጣ። በመላው የግብፅ ውስጥ ምድሩ ከዝንቡ መንጋ የተነሣ ተበላሽቶ ነበር። 25 ሙሴንና አሮንን አስጠርቶ፣ «ሂዱና በምድራችሁ ለአምላካችሁ ሠዉ» አላቸው። 26 እንዲህ ለማድረግ ለእኛ ትክክል አይደለም፤ ለአምላካችን በእግዚአብሔር የምንሠዋቸው መሥዋዕቶች ለግብፃውያን አስጸያፊዎች ናቸውና። ለግብፃውያን አስጸያፊ የሆኑትን መሥዋዕቶች እያን በፊታቸው ብንሠዋ፣ በድንጋይ አይወግሩንም? 27 ባዘዘን መሠረት፣ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር መሠዋት ያለብን ወደ ምድረ በዳው የሦስት ቀን ጒዞ ሄደን ነው» አለ። 28 «እንድትሄዱና በምድረ በዳው ለአምላካችሁ ለእግዚአብሔር እንድትሠዉ እፈቅድላችኋለሁ። ርቃችሁ መሄድ ግን የለባችሁም። ለእኔም ጸልዩልኝ» አለ። 29 «ከአንተ ወጥቼ እንደ ሄድሁ፣ የዝንቦቹ መንጋ አንተን ፈርዖንን፣ አገልጋዮችህንና ሕዝብህን ነገ ለቀው እንዲሄዱ ወደ እግዚአብሔር እጸልይልሃለሁ። ነገር ግን ለእግዚአብሔር ለመሠዋት ሕዝባችን እንዲሄድ ባለመፍቀድ ከእንግዲህ ወዲያ ልታታልለን አይገባም» አለ። 30 ከፈርዖን ወጥቶ ሄደና ወደ እግዚአብሔር ጸለየ። 31 እግዚአብሔር ሙሴ እንደ ለመነው አደረገ፦ የዝንቡን መንጋ ከፈርዖን፣ ከአገልጋዮቹና ከሕዝቡ ላይ አስወገደ። አንድም አልቀረም። 32 ነገር ግን ፈርዖን በዚህም ጊዜ ልቡ አደነደነ፤ ሕዝቡም እንዲሄድ አልፈቀደም።

Exodus 8:1

• ወንዙም ጓጒንቸሮችን ያፈላል
የአባይ ወንዝ በጓጒንቸሮች በእንቁራሪቶች የተሞላ ይሆናል ወይም በአባይ ወንዝ እንቁራሪቶች ይሞላሉ

• በውኃ ማከማቻዎቹም
የዚህ ሀረግ ትርጉም ሁለት ነው። 1) በኩሬዎች ሁሉ ላይ 2) የጓጒንቸሮች መራቢያ ሥፍራዎች ሁሉ

Exodus 8:5

• አሮንን፦ በትርህን ይዘህ በወንዞቹና በመስኖቹ በውኃ ማከማቻዎቹም ላይ እጅህን ዘርጋ
በወንዞች፥ በቦይ ውሃዎችና በኩሬ ውሃዎች ላይ በእጁ ያለውን በትር እንዲያነሳ ለአሮን ንገረው

• የግብፅንም አገር ሸፈኑ
እንቁራሪቶች ወጥተው የግብጽን ምድር ሞሉ ወይም ምድሪቱን አለበሱአት

Exodus 8:8

• ፈርዖንም ሙሴንና አሮንን ጠርቶ
ፈርዖንም ሙሴንና አሮንን አስጠርቶ ወይም ሙሴና ፈርዖን እንዲመጡ አድርጎ

• ለአንተ ለባሪያዎችህም ለሕዝብህም መቼ እንድጸልይ አስታውቀኝ
ለሹማምቶችህና ለሕዝብህ የምንፀልይበትን ጊዜ አንተው ወስን ወይም ለአንተና ለመኳንንትህና ለሕዝብህ የምጸልይበትን ሰዓት ብቻ ወስንልኝ ወይም ንገረን።

Exodus 8:10

• አምላካችንን እግዚአብሔርን የሚመስል እንደሌለ ታውቅ ዘንድ
አንተም እንደ አምላካችን እንደ እግዚአብሔር ያለ ሌላ አምላክ እንደሌለ እንዲታውቅ

• እንደ ቃልህ ይሁን
እንዳልከው አደርጋለሁ ወይም እንደ ነገርከኝ እፈጽማለሁ

• ከአንተ ከቤቶችህም ከባርያዎችህም ከሕዝብህም ይሄዳሉ
ሙሴ እያንዳንዱ ሰውና ሥፍራ በእንቁራሪቶች እንደ ተወረረ እና ጭንቅ ውስጥ እንደገባ በመግለጽ መቅሰፍቱ እንደሚቆም አጽንኦት ሰጥቶ ይናገራል። በሌላ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አገላለጽ፦ ከአንተ፥ ከቤትህ፥ ከሹማምንትህና ከሕዝብህ ሁሉ ዘንድ እንቁራርቶች ይወገዳሉ

Exodus 8:13

• ፈርዖንም ጸጥታ እንደሆነ ባየ ጊዜ ልቡን አደነደነ
ፈርዖን ችግሩ ካለፈና መረጋጋት ከሆን በኋላ እምቢ አለ።

• እግዚአብሔርም እንደተናገረ አልሰማቸውም
እግዚአብሔር (ያህዌ) እንዳለው ፈርዖን ሙሴንና አሮንን አልሰማቸው።

Exodus 8:16

• የምድሩን ትቢያ
የምድሩን ትቢያ ወይም አቧራ ወይም አፈር

• በግብፅ አገር ሁሉ የምድር ትቢያ ሁሉ ቅማል ሆነ
“ቅማል” የሚለው አንዳንደ ትንኝ ተብሎ ተተርጉሟል። በአማራጭነት ሁለቱንም ትርጉሞች መጠቀም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ በግብጽ አገር ያለውም ትቢያ ወይም አፈር ወይም አቧራ ሁሉ ወደ ተናካሽ ትንኝነት ወይም ወደ ቅማልነት ተለወጠ

Exodus 8:18

• የእግዚአብሔር ጣት ነው **(**ወካይ ዘይቤ**)**
“የእግዚአብሔር ጣት” የእግዚአብሔርን ሀይል ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ይህ የእግዚአብሔር ሥራ ነው”

• የፈርዖን ልብ ግን ጸና **(**ምትካዊ ዘይቤ ተመልከት**)**
ፈርዖን ድፍረት አገኘ ማለት ሳይሆን ፈርዖን እምቢ አለ ማለት ነው።

Exodus 8:20

• በፈርዖንም ፊት ቁም
ንጉሱን ፈርዖንን አግኘው/በፊቱ ቅረብ

• ሕዝቤን ልቀቅ
ህዝቤ እንዲሄዱ ፈቃድ ስጣቸው

Exodus 8:22

አጠቃላይ ምልከታ፦ እግዚአብሔር **(**ያህዌ**)** በሙሴ በኩል ለፈርዖን መናገሩን ቀጥሏል • በግብፅም አገር ሁሉ ላይ ከዝንቡ መንጋ የተነሣ ምድር ጠፋች
በተደራጊ ግስ የተጻፈው በአድራጊ ግስ ሲጸፍ፦ የዝንብ መንጋ የግብጽን ምድር ሁሉ ጎዳው።

Exodus 8:25

• በፊታቸው ብንሠዋ አይወግሩንምን**?**
በዕብራይስጡ “በዓይናቸው ፊት ብንሰዋ አይወግሩንም” ይላል። ይህ የተለመደ የዕብራውያንን አባባል ነው። ትርጉሙም አንድ ሰው በሚገኝበት ቦታ ወይም እርሱ ባለበት ሥፍራ እንደማለት ነው። አማርኛው በፊታቸው የሚለው የተፈጥሮ ፊታቸው ላይ ማለት ሳይሆን “እነርሱ ባሉበት ሥፍራ” ማለት ነው።

Exodus 8:28

• ነገር ግን ለእግዚአብሔር ይሠዋ ዘንድ ሕዝቡን እንዳይለቅቅ ፈርዖን እንደገና አያታልለን
ይህን ዐረፍተ ነገር በአዎንታዊ ሲንተረጉም፤ “ከእንግዲህ በኋላ አንተ እውነት ልትነግረንና ህዝባችንንም እንዲሄዱ መፍቀድ አለብህ”

• ፈርዖን እንደገና አያታልለን
ፈርዖን አንተ እንዲህ መናገር የለብህም ወይም ፈርዖን አንተ አታታልለን

Exodus 8:30

• ፈርዖንም . . . ልቡን አደነደነ
በዚህ ሀረግ አባባል ልቡን ያደነደነው እግዚአብሔር ሳይሆን ፈርዖን ራሱ አመጸኛ ሆነ፥ አልሰማም አለ። (ዘጸአት 7:13 ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 9

1 ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ አለ፤ «ወደ ፈርዖን ሂድና እንዲህ ብለህ ንገረው፤ ‹የዕብራውያን አምላክ እግዚአብሔር ይህን ይናገራል። «እንዲያመልኩኝ ሕዝቤን ልቀቅ።» 2 ብትልና አሁንም ከልክለህ ብታስቀራቸው፣ 3 የእግዚአብሔር እጅ መስክ ላይ ባለው ከብትህ፣ በፈረሶችህ፣ በአህዮችህ፣ በግመሎችህ፣ በፍየሎችህና በበጎችህ ላይ ይሆናል፤ አስከፊ በሽታም ያመጣል። 4 እግዚአብሔር በእስራኤል ከብትና በግብፅ ከብት መካከል ልዩነት አድርጓል፦ የእስራኤል ከብት አይሞትም። 5 ጊዜ ወስኖአል፤ «በምድሪቱ ላይ ይህን የማደርገው ነገ ነው» ብሎአል። 6 ይህን በሚቀጥለው ቀን አደረገው፦ የግብፅ ከብት ሁሉ ሞተ። ከእስራኤል ከብት ግን አንድም አልሞተም። 7 ተከታትሎ አጣራ፣ ከእስራኤል ከብት አንድም እንኳ አለመሞቱን ተረዳ። ነገር ግን ልቡ ደንድኖ ነበር፤ ስለዚህ ሕዝቡ እንዲሄድ አልፈቀደም። 8 እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን አላቸው፤ «ከምድጃ ላይ እፍኝ ዐመድ ውሰዱና አንተ ሙሴ ወደ ሰማይ ፈርዖን እያየ ዐመዱን በትነው። 9 በግብፅ ምድር ሁሉ ላይ ትቢያ ይሆናል። ይህም በመላው የግብፅ ምድር በሰውና በእንስሳት ላይ ዕባጭና ቍስል ያመጣል።» 10 ስለዚህ ሙሴና አሮን ከምድጃ ዐመድ ወስደው ከፈርዖን ፊት ለፊት ቆሙ። ከዚያም ሙሴ ዐመዱን ወደ ሰማይ በተነው። ዐመዱ በሰውና በእንስሳ ላይ የሚወጣ ዕባጭና ቍስልን አመጣ። 11 በእነርሱና በሌች ግብፃውያን ሁሉ ላይ ወጥቶ በነበረው ዕባጭ ምክንያት ጠንቋዮቹ በሙሴ ፊት መቆም አልቻሉም። 12 እግዚአብሔር የፈርዖንን ልብ ስለ አደነደነው፣ ፈርዖን ሙሴንና አሮንን አልሰማቸውም። ይህም የሆነው ፈርዖን እንደዚህ እንደሚደርግ እግዚአብሔር ለሙሴ ነግሮት እንድ ነበረው ነው። 13 እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፤ «በጠዋት ተነሣና ከፈርዖን ፊት ለፊት ቁም፤ እንደዚህ ብለህም ንገረው፤ ‹የዕብራውያን አምላክ እግዚአብሔር ይህን ተናገሯል፦ «እንዲያመልኩኝ ሕዝቤን ልቀቅ። 14 ጊዜ በአንተ በራስህ፣ በአገልጋዮችህና በሕዝብህ ላይ መቅሠፍቴን ሁሉ እልካለሁ። ይህን የማየደርገውም በድምር ሁሉ እንደ እኔ ያለ እንደሌለ እንድታውቅ ነው። 15 ጊዜ እጄን ዘርግቼ አንተንና ሕዝብህን በበሽታ በመምታት ከምድር ባጠፋኋችሁ ነበር። 16 ግን በሕይወት እንድትቈይ ያደረግሁህ፣ ኀይሌን እንድገልጥብህና ስሜም በምድር ሁሉ እንዲታወቅ ነው። 17 ሕዝቤን እንዳይሄድ በማድረግ በሕዝቤ ላይ ራስህን እያሳበይህ ነው። 18 ነገ በዚህ ጊዜ ከተመሠረተችበት ቀን ጀምሮ እስካሁን ድረስ በግብፅ ታይቶ የማይታወቅ ከባድ የበረዶ ማዕበል አመጣለሁ። 19 አሁን ሰው ላክና ከብትህን፣ በመስክ ላይ ያለህን ማንኛውንም ነገር ወደ ጠለያ ስፍራ ሰብስብ። መስክ ላይ የቀረና ወደ ቤት ያልመጣ ማንኛውም ከብትና ሰው ሁሉ በረዶው ይወርድባቸውና ይሞታሉ።» 20 አገልጋዮች የእግዚአብሔር ቃል የተቀበሉት ባሮቻቸውንና ከብቶቻቸውን ወደ ቤት ለማምጣት ተጣደፉ። 21 የእግዚአብሔርን ቃል ከምር ያልተቀበሉት ግን ባሮቻቸውንና ከብታቸውን መስክ ላይ ተዉ። 22 ሙሴን እንዲህ አለው፤ «በሁሉም የግብፅ ምድር፣ በሕዝብ፣ በእንስሳትና በመላው የግብፅ ምድር መስክ ላይ ባሉ ተክሎች ሁሉ ላይ በረዶ እንዲወርድ እጅህን ወደ ሰማይ ዘርጋ።» 23 በትሩን ወደ ሰማይ ዘረጋ፤ እግዚአብሔርም ነጐድጓድ፣ በረዶና መብረቅ ወደ ምድር ላከ።በግብፅም ምድር ላይ በረዶ አዘነበ። 24 ግብፅ አገር ከሆነችበት ጊዜ ጀምሮ በምድሪቱ ሁሉ ያልታየ እጅግ ከባድ የበረዶና የመብረቅ ቅልቅል ነበር የዘነበው። 25 የግብፅ ምድር፣ በረዶው መስክ ላይ ያለውን ማንኛውንም ነገር፣ ሰውንም እንስሳቱንም መታ። በመስክ ያለውን ተክል ሁሉ መታው፣ ዛፉንም ሁሉ ሰባበረው። 26 እስራኤላውያን በሚኖሩበት በጌሤም ምድር ብቻ በረዶ አልነበረም። 27 በኋላ ፈርዖን ሙሴንና አሮንን እንዲጠሩ ሰዎችን ላከ። እንዲህም አላቸው፤ «በዚህ ጊዜ ኀጢአት ፈጽሜአለሁ። እግዚአብሔር ጻድቅ ነው፤ እኔና ሕዝቤ ግን ኀጢአተኞች ነን። 28 እግዚአብሔር ጸልዩ፤ ምክንያቱም ከባዱ ነጐድጓድና በረዶ እጅግ በዝቶብናል። እለቅቃችኋለሁ፤ ከእንግዲህ ወዲያ እዚህ አትቆዩም። 29 ፈርዖንን እንዲህ አለው፤ «ከከተማዪቱ እንደ ወጣሁ፣ እጆቼን ወደ እግዚአብሔር እዘረጋለሁ። ነጐድጓዱ ያቆማል፣ በረዶም አይኖርም። በዚህ መንገድ አንተ ምድር የእግዚአብሔር መሆኗን ታውቃለህ። 30 ግን አንተንና አገልጋዮችህን በሚመለከት እግዚአብሔር አምላክን ገና በእውነት እንደማታከብሩ ዐውቃለሁ።» 31 ጊዜ ተልባው አብቦ፣ ገብሱም ፍሬ በመያዝ ላይ ነበረ፣ ተልባውና ገብሱ ከጥቅም ውጭ ሆነዋል። 32 አጃው ግን ቄይተው የሚደርሱ ሰብሎች በመሆናቸው አልተጐዱም። 33 ሙሴ ከፈርዖንና ከከተማዪቱ ሲወጣ፣ እጆቹን ወደ እግዚአብሔር ዘረጋ፤ ነጐድጓዱና በረዶው ቆሙ፤ ዝናብም አልዘነበም። 34 ፈርዖን ዝናቡ፣ በረዶውና ነጐድጓዱ መቆሙን ሲያይ፣ እንደ ገና ኀጢአት አደረገ፤ ከአገልጋዮቹ ጋርም በአንድነት ልቡን አደነደነ። 35 የፈርዖን ልብ ስለ ደነደነ፣ የእስራኤል ሕዝብ እንዲሄዱ አልፈቀደም። ይህም የሆነው ፈርዖን ልቡን እንድሚያደነድን እግዚአብሔር ለሙሴ ነግሮት የነበረው መንገድ ነው።

Exodus 9:1

ጠቅላላ ምልከታ፦ እግዚአብሔር (ያህዌ) ከሙሴ ጋር መነጋገሩንና ፈርዖን የእስራኤልን ህዝብ ከግብጽ ምድር አውጥቶ እንድለቃቸው የተለያዩ ምልክቶችን ሲያደርግ እንመለከታለን። • ልትለቅቃቸውም እንቢ ብትል ብትይዛቸውም
“ልትለቅቃቸውም እንቢ ብትል ብትይዛቸውም” ሁለቱም አባባሎች ተመሳሳይ ናቸው። ፈርዖን ህዝቡን ለመልቀቅ እምቢ ብል ልደርስበት ያለውን ነገር ለማሳየትና ትኩረት ለመስጠት ሲፈለግ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ እስራኤላውያንን ለመልቀቅ ባትፈልግና እምቢ ብትል

• እነሆ የእግዚአብሔር እጅ በሜዳ ውስጥ ባሉት ከብቶች ላይ ይሆናል
“የእግዚአብሔር እጅ” የሚለው ሀረግ እግዚአብሔር ከብቶችን በበሽታ ለመጉዳት ሀይል እንዳለው የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የእግዚአብሔር (ያህዌ) ሀይል ከብቶችህን ይቀስፋል ወይም ይገድላል”

• በከብቶችህ
በፈርዖን ከብቶች ላይ የሚመጣ መቅሰፍት መሆኑን ያሳያል፤ ነገር ግን ፈርዖን የግብጽን ህዝብ ሁሉ በመወከል የቀረበ አነጋገር ነው።

• በእስራኤል ከብቶች
“በእስራኤል ከብቶች” የተባለው የእስራኤላውያንን ከብቶች የሚመለከት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ የእስራኤላውያን የሆኑ ከብቶች

• በግብጽ ከብቶች
“በግብጽ ከብቶች” የተባለው የግብጻውያንን ከብቶች የሚመለከት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ የግብጻውያን የሆኑ ከብቶች

Exodus 9:5

• ጊዜን ወሰነ
ጊዜ ቀጠረ ወይም ጊዜ ለየ ወይም ጊዜ ወሰነ

• የግብፅም ከብት ሁሉ ሞተ
ይህ ግነታዊ ዘይቤ ዓይነት ነው። በርግጥ በዚህን ጊዜ የግብጻውያን ከብቶች ሁሉ አልሞቱም፤ ምክንያቱም በኋለኛው መቅሰፍት የሞቱ ሌሎች ከብቶች አሉ። በትርጉም ሥራ ወቅት “ሁሉ” የሚለው ቃል መቅረት የለበትም።

• የግብጽም ከብት ሁሉ
“ግብጽ” የሚለው ምድሪቱን ለማመልከት ሳይሆን የግብጽ ሰዎችንና ከብቶቻቸው ማለት ነው።

• ፈርዖንም ላከ
ንጉሡ የሆነውን ሁሉ ለማጣራት ሰዎችን በላከ ጊዜ ወይም ፈርዖን ያጣሩ ዘንድ ሰዎች ልኮ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• እነሆም
ይህ ቃል የሚያመለክተው ፈርዖን በሆነው ነገር እጅግ መገረሙን የሚያሳይ ነው።

• የፈርዖን ልብ ግን ደነደነ
በዚህኛ ክፍል “ፈርዖን ልቡን አደነደነ” ወይም “እግዚአብሔር የፈርዖንን ልብ አጸና” ሳይሆን “የፈርዖን ልብ ግን ደነደነ” የሚለው ትኩረቱ ልቡ እንደ ሰው ለመታዘዝ ፈቃደኛ አልሆነም ማለት ነው።

Exodus 9:8

• ከምድጃ አመድ ውሰዱ
እሳት ከሚነድበት ቦታ እፍኝ ዐመድ ውሰዱ

• ሻህኝ የሚያወጣ ቊስል ሆነ
መግል የሚቋጥር ቁስል ወይም ቡጉንጅ ወይም እባጭ ዓይነት ቁስል ሆነ ማለት ነው

Exodus 9:11

• እግዚአብሔርም የፈርዖንን ልብ አጸና **(ዘጸአት 7:13)**
የፈርዖን ልብ የተባለው ራሱ ፈርዖን ማለት ነው። ፈርዖን ለመስማት አልፈለገም ወይም እምብ አለ ማለት ነው። (ወካይ ወይም ተለዋጭ ዘይቤ ተመልከት)። በዚህኛ ክፍል የፈርዖንን ልብ ያደነደነው ወይም ፈርዖን እንዳይሰማ ያደረገው እግዚአብሔር እንደሆነ ይገልጻል።

Exodus 9:13

• በሰውነትህ
በአንተ ላይ ወይም አንተን ራስህን መቅሰፍቱ ይጎዳሃል ማለት ነው።

Exodus 9:15

• እጄን ዘርግቼ
እግዚአብሔር በታላቅ ሀይሉ ለማጥቃት ወይም ለመጉዳት ሲነሳ ማለት ነው። “እኔ እጄን ዘርግቼ” ሲል ሀይሌን ለመግለጥ ሲነሳ ወይም ሀይሌን ሲገልጥ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “አንተን ለመቅጣት ሀይሌን ሲጠቀም”

• ስሜም በምድር ሁሉ ላይ ይነገር ዘንድ
“ስሜ” የሚለው የእግዚአብሔር (ያህዌ) ዝና የሚመለከት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ እኔ ትልቅ እንደሆንኩ ሰዎች እስኪያውቁ ድረስ

• ስለዚህ አስነሥቼሃለሁ
ፈርዖን እስራኤላውያን እንዳይሄዱ ሲያደርግና እንቅፋት ሲሆንባቸው ምክንያቱ እግዚአብሔር ያንን እንዲያደርግ ስለፈቀደ ነው።

Exodus 9:18

• ከተመሰረተች ጀምሮ
በሌላ አገላለጽ፦ ግብጽ እንደ አገር ከታወቀችበት ወይም ከተቋቋመች ጊዜ ጀምሮ ማለት ነው

• አሁን እንግዲህ ላክ፥ ከብቶችህንም በሜዳም ያለህን ሁሉ አስቸኩል
በመስክ የተሰማሩ ከብቶችህና ከቤት ውጪ ያለ ማንኛውንም የአንተ ንብረት ሁሉ በፍጥነት ወደ መጠለያ እንዲያስገቡ ለአገልጋዮችህ አሁን ትእዛዝ ስጥ።

Exodus 9:20

• ከፈርዖንም ባሪያዎች የእግዚአብሔርን ቃል የፈራ
እግዚአብሔር (ያህዌ) ስለተናገረው ነገር የፈሩት የፈርዖን ሹማምት ወይም እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር ሰምተው የታዘዙት የፈርዖን ሹማምት

• የእግዚአብሔርንም ቃል ያላሰበ
እግዚአብሔር የተናገረውን ቃል ያልታዘዘ ወይም ችላ ያለ ወይም ለመስማት ፈቃደኛ ያልሆነ

Exodus 9:22

• እጅህን ወደ ሰማይ ዘርጋ
x

Exodus 9:25

• ሰውንና እንስሳን መታ
ሕዝቡንና ከብቶችን ጭምር ገደለ ወይም በህዝብና በከብቶች ላይ አደጋ አደረሰ

• የእስራኤል ልጆች ተቀምጠው በነበሩባት
እስራኤላውያን ወይም የእስራኤል ህዝብ በሚኖሩባት

Exodus 9:27

• እጄን ወደ እግዚአብሔር እዘረጋለሁ
እጅን ወደ ላይ ማንሳት በሌላ መልኩ ለጸሎት መዘርጋት የሚያመለክት ተምሳሌት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እጄን ዘርግቼ ወደ እግዚአብሔር እጸልያለሁ”

• አምላክን እግዚአብሔርን ገና እንደማትፈሩ
ለእግዚአብሔር ክብር እንደምትሰጡ፥ እግዚአብሔርን እንደማትታዘዙ

Exodus 9:31

• ተልባ
የእህል ዓይነት በተለይ የጥራጥሬ ዓይነት ነው።

• ገብስ
የእህል ዓይነት ለሰዎችና ለከብቶች ምግብነት የሚውል

• አጃ
የስንዴና የገብስ ዘር የሆነ የእህል ዓይነት

• እጁንም ወደ እግዚአብሔር ዘረጋ
እጁን ወደ ላይ አንስቶ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ

Exodus 9:34

• ኃጢያትን ጨመረ
እንደገና ኃጢአት ሠራ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 10

1 እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፤ «የፈርዖንና የአገልጋዮቹን ልብ አደነድናለሁና ወደ ፈርዖን ሂድ። እነዚህን የተአምራቴን ምልክቶች ለማሳየት ይህን
2 አድርጌአለሁ። ይህን ያደረግሁት ግብፃውያንን እንዴት በከባድ አያያዝ እንደያዝኋቸውና በመካከላቸውም የተአምራትን ልዩ ልዩ ምልክቶች እንዳሳየሁ
ለልጆቻችሁና ለልጅ ልጆቻችሁ እንድትነግሯቸው ነው። በዚህ መንገድ እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ።» **3** አሮንም ወደ ፈርዖን ሄደው እንዲህ አሉት፤
«የዕብራውያን አምላክ እግዚአብሔር የሚለው ይህ ነው፦ ‹ራስህን በፊቴ ለማዋረድ እምቢ የምትለው እስከ መቼ ነው? እንዲያመልኩኝ ሕዝቤን ልቀቅ። **4** ግን
ሕዝቤን አልለቅም ብትል፣ እነሆ፣ በነገው ቀን በአገርህ ላይ አንበጣዎችን አመጣለሁ። **5** ማንም ሰው መድሩን ማየት እስከማይችል ድረስ የምድሩን ገጽ
ይሸፍኑታል። ከበረዶው አምልጦ የቀረውን ሁሉ ይበሉታል። መስክ ላይ የሚያድግላችሁንም ዛፍ ሁሉ ይበሉታል። **6** አንበጣዎቹ የአንተን፣ የአገልጋዮችህን ቤቶች
ሁሉ ይሞሏቸዋል፤ ይህም፣ አባትህም አያትህም በዚህ ምድር ላይ መኖር ከጀመሩበት ቀን አነሥቶ እስከዚህ ጊዜ ድረስ ታይቶ የማይታወቅ ነው።› ሙሴም
ከፈርዖን ዘንድ ወጥቶ ሄደ። **7** ፈርዖንን፣ «ይህ ሰው ወጥመድ የሚሆንብን እስከ መቼ ነው? አምላካቸውን እግዚአብሔርን እንዲያመልኩት እስራኤላውያን
ይሂዱ። ግብፅ መጥፋቷን ገና አልተገነዘብህምን?» አሉት። **8** ሙሴና አሮን፣ «ሂዱ አምላካችሁን እግዚአብሔርን አምልኩ። ነገር ግን የሚሄዱት የትኞቹ
ናቸው?» ወዳላቸው ወደ ፈርዖን እንደገና እንዲመጡ ተደረገ። **9** የምንሄደው ከወጣቶቻችንና ከሽማግሌዎቻችን፣ ከወንድና ከሴት ልጆችን ጋር ነው።
ለእግዚአብሔር በዓል ማክበር ስለሚገባን፣ የበግና የፍየል መንጎቻችንን፣ የቀንድ ከብቶቻችንንም ይዘን እንሄዳለን» አለ። **10** ፈርዖንም እንዲህ አላቸው፤
«እናንተንና ታናናሽ ልጆቻችሁን ስለችሁ፣ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን። ነገር ግን ተመልከቱ፣ ክፉ ነገር ዐስባችኋል። **11** ከመካከላችሁ ወንዶች ብቻ
ይሂዱና እግዚአብሔርን ያምልኩ፤ የምትፈልጉት ያንን ነውና።» ከዚያም በኋላ ሙሴና አሮን ከፈርዖን ዘንድ እንዲወጡ ተደረገ። **12** እግዚአብሔርም ሙሴን፣
«አንበጣዎች የግብፅን ምድር እንዲወርሩትና ከበረዶው ተርፎ የቀረውን፣ በምድሩ ያለውን ተክል ሁሉ እንዲበሉት እጅህን በግብፅ ምድር ላይ ዘርጋ» አለው። **13**
ሙሴም በትሩን በግብፅ ምድር ላይ ዘረጋ፤ እግዚአብሔርም በዚያ ቀንና ሌሊት ሁሉ የምሥራቅ ነፋስ በምድሩ ላይ እንዲነፍስ አደረገ። ማለዳ ላይ የምሥራቁ ነፋስ
አንበጣዎቹን አምጥቶ ነበር። **14** በግብፅ ምድር ሁሉ ተሠራጩ፤ አገሩንም ሁሉ ወረሩት። እንደዚህ እጅግ የበዙ አንበጣዎች በምድሩ ውስጥ ከዚህ በፊት
አልነበሩም፤ ወደፊትም አይኖሩም። **15** ጨለማ እስኪሆን ድረስ የምድሩን ሁሉ ገጽ ሸፈኑት። በምድሩ ላይ ያለውን ማንኛውንም ተክልና ከበረዶው ተርፎ የቀረውን
የዛፍ ፍሬ ሁሉ በሉት። በግብፅ ምድር ሁሉ ለምለም ቅጠል ያለው ተክል አልቀረም፤ በመስክም ላይ ምንም ዛፍ አልነበረም። **16** ሙሴንና አሮንን በፍጥነት
አስጠርቶ እንዲህ አላቸው፤ “በአምላካችሁ በእግዚአብሔርና በእናንተ ላይ ኀጢአት ሠርቻለሁ። **17** እንግዲህ አሁን ኀጢአቴን ይቅር በሉኝና ይህን ሞት ከእኔ
እንዲያስወግድልኝ ወደ አምላካችሁ ወደ እግዚአብሔር ጸልዩልኝ።” **18** ስለዚህ ሙሴ ከፈርዖን ዘንድ ወጥቶ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ። **19** አንበጣዎቹን ለቃቅሞ
ወደ ቀይ ባሕር የሚከትታቸውን ብርቱ የምዕራብ ነፋስ አመጣ፤ በግብፅ ግዛት ሁሉ የቀረ አንድም አንበጣ አልነበረም። **20** ነገር ግን እግዚአብሔር የፈርዖንን ልብ
ስላደነደነው፣ ፈርዖን እስራኤላውያንን አልለቀቃቸውም። **21** ሙሴን፣ “በግብፅ ምድር ላይ የሚዳሰስ ከባድ ጨለማ እንዲሆን እጅህን ወደ ሰማይ ዘርጋ”
አለው። **22** እጁን ወደ ሰማይ ዘረጋ፤ በግብፅም ምድር ሁሉ ለሦስት ቀን ድቅድቅ ጨለማ ሆነ። **23** ቀኖች አንዱ ሌላውን ማየት አልቻለም፤ ከቤቱም የወጣ
ማንም የለም። ለእስራኤላውያን ግን በሚኖሩበት ስፍራ ብርሃን ነበራቸው። **24** ፈርዖን ሙሴን አስጠርቶ፣ “ሂዱ እግዚአብሔርን አምልኩ። ቤተ ሰቦቻችሁም እንኳ
ዐብረዋችሁ መሄድ ይችላሉ፤ በጎቻችሁና ከብቶቻችሁ ግን እዚህ መቅረት አለባቸው” አለው። **25** እንዲህ አለው፤ “ለአምላካችን ለእግዚአብሔር እንድንሠዋቸው
ለመሥዋዕትና ለሚቃጠል መሥዋዕት እንስሳቱንም ልትሰጠን ይገባል። **26** ከብቶቻችንም ከእኛ ጋር መሄድ አለባቸው፤ አምላካችንን እግዚአብሔርን ለማምለክ
ልንወስዳቸው ይገባልና ከእነርሱ ሰኮናም እንኳ እዚህ አይቀርም። ምክንያቱም እግዚአብሔርን በምን እንደምናመልከው እዚያ እስክንደርስ ድረስ አናውቅም።” **27**
ግን የፈርዖንን ልብ ስላደነደነው ፈርዖን ሕዝቡን አልለቀቃቸውም። **28** ሙሴን፣ “ሂድ ከእኔ ዘንድ! ፊቴን እንዳታይ ተጠንቀቅ፤ ፊቴን ባየህበት ቀን ትሞታለህና”
አለው። **29** ሙሴም፣ “አንተ ራስህ ተናግረሃል። ፊትህን እንደ ገና አላየውም” አለው።

Exodus 10:1

• የእርሱን የባሪያዎቹንም ልብ አደንድኜአለሁና **(ተለዋጭ ዘይቤ)**
እግዚአብሔር ፈርዖንና ሹማምንቱን የማይሰሙና የማይታዘዙ መሆናቸውን ለመግለጽ ልባቸውን አደንድኛለሁ ይላል። (ዘጸአት 9፡12 እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት)።

• ይህችንም ተአምራቴን
የዕብራይስጡ ቅጂ “እነዚህን ታአምራት” ይላል። አንድ ታአምር ሳይሆን ብዙ ታአምራትና ምልክቶችን አድርጓል ማለት ነው። አዲሱ መደበኛ አማርኛ ቅጂም እንደ ዕብራይስጡ “እነዚህን ታአምራት” ይላልና ተርጓሚዎች ትኩረት ሊሰጡት ይገባል።

Exodus 10:3

• እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
ሙሴና አሮን የሚናገሩት ቃል የራሳቸው ሳይሆን የእግዚአብሔር መሆኑን ያሳያል። እነርሱም ተልከው የሄዱት በእግዚአብሔር ነውና።

Exodus 10:5

• በረዶ
ከዝናብ ጋር አብሮ የሚወርድ እህልና ቡቃያ የሚያጠፋ ነው

Exodus 10:7

• ዕንቅፋት ይሆንብናል
ዕንቅፋት መሆን ማለት ችግር ፈጣሪ፥ ፀብ ጫሪ ሰው እንደማለት ነው።

• ይህ ሰው እስከ መቼ ዕንቅፋት ይሆንብናል? **(አጋናኝ ጥያቄ)**
የፈርዖን ሹማምት ይህን ጥያቄ የጠየቁት በዚህ ሰው ምክንያት በግብጽ ምድር ጥፋት መምጣቱን ለማመልከት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ይህ ሰው በእኛ ላይ ጥፋት እንዲያመጣ አንፈቅድለትም”

• ግብፅስ እንደ ጠፋች ገና አታውቅምን?
የፈርዖን ሹማምት ንጉሱን ይህን ጥያቄ የጠየቁት ግብጽ በጥፋት ላይ መሆኗን ፈርዖን ማየት ወይም ማስተዋል ባለመቻሉ ነበር። አማራጭ ትርጉም፦ “ግብጽ በጥፋት ላይ መሆኗን አስተውል”። እነዚህ መቅሰፍቶች ግብጽን አጥፍተዋል ወይም “የሙሴና አሮን አምላክ ግብጽን አውድሟታል” እንደማለት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• ከፈርዖንም ፊት አባረሩአቸው
ፈርዖን ሙሴንና አሮንን ከፊቱ አባረራቸው ወይም ፈርዖን ሙሴንና አሮንን እንዲያባርሩዋቸው እንዲያስወጧቸው አገልጋዮቹን አዘዘ ማለት ነው

Exodus 10:9

• እናንተን ከልጆቻችሁ ጋር ስለቀቅ
ፈርዖን ይህን ያለው እስራኤላውያንና ልጆቻቸውን ለመልቀቅ እንደማይፈልግ ለማሳየት ነው።

• ከፈርዖንም ፊት አባረሩአቸው
ሙሴና አሮን ከፈርዖን ፊት እንዲወጡ ተደረገ ወይም ሙሴና አሮን የግድ ከፈርዖን ፊት እንዲወጡ አደረጓቸው

Exodus 10:12

• የምሥራቅን ነፋስ
“የምስራቅ ነፋስ” ማለት ከምስራቅ በኩል የሚነፍስ ነፋስ ወይም ከምስራቅ በኩል የሚነሳ ነፋስ ማለት ነው።

• በግብፅ አገር ላይ እንዲወጡ
አንበጦች በግብጽ ምድር ላይ እንዲመጡ ወይም አንበጦች የግብጽን ምድር እንዲወሩ እንደማለት ነው።

Exodus 10:14

• የምድሩንም ፊት ፈጽመው ሸፈኑት አገሪቱም ጨለመች
ከአንበጣው ብዛት የተነሳ አገሪቱ ጠቁራ ጨለማ እስክትመስል ድረስ የአንበጣ መንጋ ሸፈናት ማለት ነው።

Exodus 10:16

• አንድ ጊዜ ብቻ
በተጨማሪ ወይም አንድ ዕድል ስጡኝና እንደ ማለት ነው።

• ይህም ሞት ብቻ ከእኔ ያነሣልኝ ዘንድ
በዚህ ቦታ “ሞት” የተባለው በአንበጦች ምክንያት የመጣውን መቅሰፍት ወይም ጥፋት ለማመልከት ነው። ይህ ጥፋት እየከፋ ሲሄድ ሞት እንደሚያስከትል ለመግለጽም ጭምር ነው።

Exodus 10:19

• እግዚአብሔርም ከምዕራብ ዐውሎ ነፋሱን አስወገደ
የዚህ ዐረፍተ ነገር ትክክለኛ ትርጉም እግዚአብሔርም አንበጦቹንም ጠራርጎ ወደ ቀይ ባሕር የሚነዳ ብርቱ ነፋስ ከምዕራብ በኩል አስነሣ ወይም ያህዌ ነፋሱን ወደ ብርቱ የምዕራብ ነፋስ ለወጠው ያም ነፋስ አንበጣዎቹን እየነዳ ወደ ቀይ ባህር ከተታቸው ማለት ነው።

• እግዚአብሔርም የፈርዖንን ልብ አጸና
የፈርዖን ልብ የተባለው ራሱ ፈርዖን ማለት ነው። ፈርዖን ለመስማት አልፈለገም ወይም እምቢ አለ ማለት ነው። (ዘጸአት 9:12 ተመልከት)።

Exodus 10:21

• ፅኑ ጨለማ ይሁን
ድቅድቅ ጨለማ ወይም በእጅ እንደምዳሰስ ዓይነት ጨለማ

Exodus 10:24

• አንድ ሰኮናም አይቀርም **(**ወካይ ዘይቤ**)**
አንድ ሰኮናም የሚለው “ሙሉ ከብቱን” ለማመልከት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ አንድ ከብት እንኳን አናስቀርም

Exodus 10:27

• እግዚአብሔርም የፈርዖንን ልብ አጸና
የፈርዖን ልብ የተባለው ራሱ ፈርዖን ማለት ነው። ፈርዖን ለመስማት አልፈለገም ወይም እምብ አለ/እምብተኛ/ ሆነ ማለት ነው። ዘጸአት 9:12 ተመልከት።

• ሊለቅቃቸው አልወደደም
በሌላ አገላለጽ፦ ፈርዖንም ሕዝቡን መልቀቅ አልፈለገም

• ፊቴን እንዳታይ ተጠንቀቅ **(**ወካይ ዘይቤ**)**
“ፊት” የሚለው “ሰውዬውን” ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ እኔን እንዳታይ ተጠንቀቅ

• እንደ ተናገረህ ይሁን
በዚህ አባባል ሙሴ የፈርዖንን ንግግር ሲያጸናው እንመለከታለን። አንተ የተናገርከው እውነት ነው እንደማለት ነው። (ፈሊጣዊ ንግግር)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 11

1 ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ አለ፤ “በፈርዖንና በግብፅ ላይ የማመጣው ገና አንድ መቅሠፍት አለ። ከዚያ በኋላ ከዚህ እንድትሄዱ
ይፈቅድላችኋል። በመጨረሻ እንድሄድ ሲያደርግም፣ ሙሉ በሙሉ ያባርራችኋል። **2** ወንድና እያንዳንዱ ሴት ከጎረቤቱ ወይም ከጎረቤቱ የብርና የወርቅ ዕቃዎችን
ስጡን ብለው እንዲጠይቁ ለሕዝቡ ተናገር።” **3** እስራኤላውያንን ደስ ለማሰኘት ግብፃውያን እንዲነሣሡ አደረገ። ሙሴም በፈርዖን አገልጋዮችና በግብፅ ሕዝብ
ዘንድ እጅግ የሚደነቅ ሰው ሆነ። **4** እንዲህ አለ፤ “እግዚአብሔር ይህን ተናግሯል፦ ‘እኩለ ሌሊት ላይ በመላው ግብፅ ዐልፋለሁ። **5** ላይ ከሚቀመጠው
ከፈርዖን በኵር ልጅ ጀምሮ፣ ወፍጮ ላይ እስከምትፈጨዋ እስከ ባሪያዪቱ በኵር ልጅና እስከ እንስሳቱ በኵር ሁሉ ድረስ በግብፅ ምድር ያሉ በኵር በሙሉ
ይሞታል። **6** በቀድሞው ጊዜ ያልነበረ እንደገናም የማይደገም ታላቅ ዋይታ በግብፅ ምድር ሁሉ ይሆናል። **7** ሕዝብ ላይ ግን፣ በሰውም ሆነ በእንስሳ ላይ ውሻ
እንኳ አይጮኽም። በዚህም ግብፃውያንንና እስራኤላውያንን የማስተናግድበት መንገድ የተለያየ እንደ ሆነ ታውቃላችሁ።’ **8** እነዚህ አገልጋዮችህ ሁሉ ወደ እኔ
ይመጣሉ፤ ለእኔም ይሰግዳሉ። ‘አንተና ተከታዮችህ ሁሉ ሂዱ!’ ብለውም ይናገራሉ። ከዚያ በኋላ እወጣለሁ።” ከዚያም ሙሉ ከፈርዖን ዘንድ በትልቅ ቊጣ
ወጥቶ ሄደ። **9** ሙሴን፣ “ፈርዖን እናንተን አይሰማችሁም። ይህም የሆነው ብዙ አስደናቂ ነገሮችን በግብፅ ምድር ላይ እንዳደርግ ነው” አለው። **10** አሮን
እነዚህን ድንቆች ሁሉ በፈርዖን ፊት አደረጉ። ነገር ግን እግዚአብሔር የፈርዖንን ልብ ስላደነደነው፣ ፈርዖን የእስራኤል ሕዝብ ከምድሩ እንዲወጡ አልፈቀደም።

Exodus 11:1

• ሲለቅቃችሁም አባርሮ ይሰድዳችኋል
አንድ ሰው እንዳይቀር ሁላችሁንም በማባረር ያስወጣችኋል

• በሕዝቡ ጆሮ ተናገር
ለህዝብ መናገርን በወካይ ዘይቤ ተጠቅሞ ለጆሮአቸው ተናገር ይላል። በሌላ
አገላለጽ፦ ለህዝቡ ተናገር

• ሙሴም በፈርዖን ባሪያዎችና በሕዝቡ ፊት በግብፅ አገር እጅግ የከበረ ሰው ነበረ
የግብጽ ንጉስ ፈርዖን፤ ሹማምቱና ሕዝቡ ሁሉ ሙሴ ታላቅ ወይም የከበረ ሰው
አድርገው ይቀበላሉ

Exodus 11:4

• በግብፅም አገር ያለ በኵር ሁሉ
በኩር የሚለው ቃል ሁል ጊዜ መጀመሪያ የተወለደን ወንድ (ሰውና እንስሳ)
የሚመለከት ነው።

• በዙፋኑ ከሚቀመጠው
ይህ በንግስና ዙፋን ላይ የተቀመጠውን ፈርዖንን የመለከታል

• በወፍጮ እግር እስካለችው (ፈሊጣዊ አነጋገር)
የወፍጮ መጅ ገፊ እስከ ሆነችው ወይም በድንጋይ መፍጫ እህል በመፍጨት
እስከምታገለግል

Exodus 11:6

• ከዚያም በኋላ እወጣለሁ
ሙሴ የእስራኤልን ህዝብ አስከትሎ ከግብጽ እንደሚሄድ መናገሩ ነው።
አማራጭ ትርጉም፦ “ከዚያም በኋላ እሄዳለሁ” ወይም “እኔም ከዚያ በኋላ
እሄዳለሁ”

Exodus 11:9

• ተአምራቴ በግብፅ አገር ብዙ እንዲሆን
በግብጽ ምድር ላይ ብዙ ተአምራት አደርግ ዘንድ ወይም በግብጽ ምድር ድንቅ
ሥራዎቼ በብዛት እንዲታዩ

• እግዚአብሔር የፈርዖንን ልብ አጸና
የፈርዖን ልብ የተባለው ራሱ ፈርዖን ማለት ነው። ፈርዖን ለመስማት አልፈለገም
ወይም እምብ አለ ማለት ነው። (ወካይ ወይም ተለዋጭ ዘይቤ ተመልከት)።
በዚህኛ ክፍል የፈርዖንን ልብ ያደነደነው ወይም ፈርዖን እንዳይሰማ ያደረገው
እግዚአብሔር (ያህዌ) ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 12

1 በግብፅ ምድር ለሙሴና ለአሮን እንዲህ ብሎ ነገራቸው፤ 2 ወር ለእናንተ የወሮች መጀመሪያ፣ የዓመቱም የመጀመሪያ ወር ይሁናችሁ። 3 ጉባኤ ይህን ንገሩ፤ ‘በዚህ ወር ዐሥረኛ ቀን ላይ እያንዳንዳቸው ለራሳቸው አንድ ጠቦት የሚያንስ ከሆነ፣ 4 የቅርብ ጎረቤቱ ከቍጥራቸው ጋር የሚመጣጠን ጠቦት ያዘጋጁ። የሚመገቡትን በቂ ሥጋ መውሰድ እንዲችሉ፣ ጠቦቱ ለሁሉም የሚበቃ መሆን አለበት። 5 ወይም የፍየል ጠቦታችሁ እንከን የሌለበት የአንድ ዓመት ተባት ጠቦት ሊሆን ይገባል። ከበጎቹ ወይም ከፍየሎቹ አንዱን ልትወስዱ ትችላላችሁ። 6 እስከ ወሩ ዐሥራ አራተኛ ወር ድረስ አቆዩአቸው። ከዚያም መላው የእስራኤል ጉባኤ እነዚህን እንስሳት ፀሐይ ስትጠልቅ ይረዷቸው። 7 ከዚያም ከደሙ ጥቂት ውሰዱና ሥጋውን በምትበሉበት ቤት በር መቃንና ጉበን ላይ አድርጉት። 8 በእሳት ከጠበሳችሁት በኋላ፣ በዚያው ሌሊት ከቂጣና ከመራራ ቅጠል ጋር ብሉት። 9 ወይም ቅቅሉን አትብሉት። ይልቁን ከጭንቅላቱ፣ ከእግሮቹና ከሆድ ዕቃው ጋር በእሳት ጠብሳችሁ ብሉት። 10 ድረስ ከሥጋው አንዳችም አታስቀሩ። የተራረፈ ነገር ቢኖር፣ በእሳት ይቃጠል። 11 ወገባችሁን ታጥቃችሁ፣ ጫማችሁን አጥልቃችሁና በትራችሁን በእጃችሁ ይዛችሁ ነው። ተጣድፋችሁ ልትበሉት ይገባል። የእግዚአብሔር ፋሲካ ነው። 12 በዚያ ሌሊት በግብፅ ምድር ሁሉ ዐልፋለሁ፤ በግብፅ ምድርም የሰውንና የእንስሳትን በኵር በሙሉ እመታለሁ። በግብፅ አማልክት ሁሉ ላይ እፈርድባቸዋለሁ። እኔ እግዚአብሔር ነኝ። 13 ደሙ እኔ ወደ እናንተ በቤቶቻችሁ ላይ ምልክት ይሆናል። ደሙንም በማይበት ጊዜ የግብፅን ምድር ስመታ እናንተን ዐልፌአችሁ እሄዳለሁ። ይህ መቅሠፍት በእናንተ ላይ አይመጣም፤ አያጠፋችሁምም። 14 ቀን የእግዚአብሔር በዓል ቀን አድርጋችሁ የምታከብሩት የመታሰቢያ ቀን ይሆንላችኋል። ቀኑን እንድታከብሩት ለእናንተ፣ ለትውልዶቻችሁም ሁሉ ቋሚ ሥርዐት ይሆናችኋል። 15 ቀን ቂጣ ትበላላችሁ። በመጀመሪያው ቀን እርሾውን ከቤታችሁ ታስወግዳላችሁ። ከመጀመሪያው ቀን እስከ ሰባተኛው ቀን እርሾ ያለበትን እንጀራ የበላ ሰው ሁሉ ከእስራኤል ይወገድ። 16 በመጀመሪያው ቀን ለእኔ የተቀደሰ ጉባኤ ይደረጋል፤ በሰባተኛውም ቀን እንደዚሁ ያለ ሌላ ጉባኤ ይሆናል። ሁሉም የሚበላውን ከመቀቀል በቀር፣ በእነዚህ ቀኖች ሥራ አይሠራም። የምትሠሩት የምግብ ዝግጅቱን ሥራ ብቻ ነው። 17 በዓልን አክብሩት ምክንያቱም ሕዝባችሁን ሰራዊት በሰራዊት አድርጌ ከግብፅ ምድር ያወጣሁት በዚህ ቀን ነው። ስለዚህ ይህን ቀን በትውልዶቻችሁ ሁሉ አክብሩት፤ ለእናንተ ቋሚ ሥርዓት ይሆናችኋል። 18 የመጀመሪያ ወር ዐሥራ አራተኛ ቀን ፀሐይ መጥለቅ አንሥቶ፣ እስከ ወሩ ሃያ አንደኛ ቀን ፀሐይ መጥለቅ ድረስ ቂጣ ትበላላችሁ። 19 በሰባቱ ቀኖች በቤታችሁ ውስጥ እርሾ መገኘት የለበትም። እርሾ ያለበት እንጀራ የሚበላ እንግዳም ሆነ በምድራችሁ የተወለደ ሰው ከእስራኤል ማኅበረ ሰ ይወገዳል። 20 የተጋገረ አንዳችም መብላት የለባችሁም። የትም ብትኖሩ፣ መብላት የሚገባችሁ እርሾ የሌለበትን ነው።” 21 በኋላ ሙሴ የእስራኤልን ሽማግሌዎች ሁሉ ጠርቶ እንዲህ አላቸው፤ “ሂዱና ቤተ ሰቦቻችሁን ለመመገብ የሚበቁ ጠቦቶችን ወይም ግልገሎችን መርጣችሁ የፋሲካን በግ ዕረዱ። 22 ጭብጥ የሂሶጵ ቅጠል ያዙና በሳሕን ውስጥ በሚቀመጠው ደም ውስጥ በመንከር፣ የቤታችሁን ጉበን ዐናትና ሁለቱን መቃኖች እርጩ። እስኪነጋ ድረስ ከእናንተ አንድም ከቤቱ አይወጣ። 23 ለመቅሠፍት እግዚአብሔር ስለሚያልፍ፣ ደሙን በጉበኑ ዐናትና በሁለቱ መቃኖች ላይ ሲያይ፣ በበራፋችሁ ላይ ያልፋል፣ ቀሣፊውም ወደ ቤታችሁ እንዲገባና እናንተን እንዲቀሥፋችሁ አይፈቅድም። 24 ይህ ሥርዐት ለእናንተም ለልጆቻችሁም የሁልጊዜ ሥርዐት ስለ ሆነ ልታከብሩት ይገባል። 25 ቃል በገባላችሁ መሠረት፣ እግዚአብሔር ወደሚሰጣችሁ ምድር ስትገቡ፣ ይህን የአምልኮ ሥርዐት ጠብቁት። 26 ‘ይህ የአምልኮ ሥርዐት ምን ትርጕም አለው?’ ብለው በሚጠይቋችሁ ጊዜ፣ 27 እንደዚህ ብላችሁ ልትነግሯቸው ይገባል፤ ‘ይህ የእግዚአብሔር ፋሲካ መሥዋዕት ነው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ግብፃውያንን ሲቀሥፍ፣ በግብፅ ውስጥ በእስራኤላውያን ቤቶች ዐልፎ ሄዶአል። ቤተ ሰቦቻችንን ነጻ አውጥቷቸዋል።” ከዚያም ሕዝቡ ሰገዱ፣ እግዚአብሔርንም አመለኩት። 28 ሄደው እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን እንዳዝዛቸው አደረጉ። 29 እኩለ ሌሊት ላይ በዙፋኑ ላይ ከሚቀመጠው ከፈርዖን በኵር ልጅ ጀምሮ፣ በእስር ቤት ውስጥ እስካለው ሰው በኵር ልጅና እስከ እንስሳት በኵር ሁሉ ድረስ፣ እግዚአብሔር በግብፅ ምድር የሚገኝን በኵር በሙሉ ቀሠፈ። 30 አገልጋዮቹ ሁሉና ግብፃውያን በሙሉ ሌሊት ላይ ተነሡ። በግብፅ ውስጥ ጕልሕ የልቅሶ ጩኸት ነበረ፤ ሰው ያልሞተበት እንደም ቤት አልነበረምና። 31 ሙሴንና አሮንን በሌሊት አስጠርቶ እንዲህ አላቸው፤ “ተነሡ፤ እናንተና እስራኤላውያን ከሕዝቤ መካከል ውጡ። ማድረግ የምትፈልጉትን እንደ ተናገራችሁ ሂዱ፣ እግዚአብሔርን አምልኩ። 32 እንደ ተናገራችሁት፣ የበግና የፍየል መንጎቻችሁን፣ የቀንድና የጋማ ከብቶቻችሁንም ይዛችሁ ሂዱ፤ እኔንም ባርኩኝ።” 33 እስራኤላውያንን ከአገራቸው ለማባረር በትልቅ ጥድፊያ ላይ ነበሩ፤ “ሁላችንም ማለቃችን ነው” ብለው ነበርና። 34 ሕዝቡ እርሾ ያልተጨመረበትን ሊጣቸውን ያዙ። የቡሆ እቃዎቻቸውን ቀድሞውኑ በጨርቃቸው አስረው በትከሻቸው ተሸክመዋቸዋል። 35 ሕዝብ ሙሴ እንደ ነገራቸው አደረጉ። የወርቅና የብር ዕቃዎችን፣ ልብስም እንዲሰጧቸው ግብፃውያንን ጠየቁ። 36 ደስ ለማሰኘት እግዚአብሔር ግብፃውያንን አነሣሣ። ስለዚህ እስራኤላውያን የጠየቋቸውን ሁሉ ግብፃውያን ሰጧቸው። በዚህ መንገድ፣ እስራኤላውያን ግብፃውያንን በዘበዟቸው። 37 ከራምሴ በመነሣት ወደ ሱኮት ተጓዙ። ቍጥራቸው ከሕፃናቱና ከሴቶቹ ሌላ ስድስት መቶ ሺሕ ያህል እግረኛ ነበር። 38 እስራኤላዊ ያልሆነ ድብልቅ ሕዝቤም፣ ከበግና ከፍየል፣ እጅግ ብዙ ከሆነ የከብት መንጋ ጋር ዐብሯቸው ሄደ። 39 ከግብፅ ያመጡትን እርሾ ተባርረው ስለ ወጡና ምግብ ማዘጋጀት ስላልቻሉ ነው። 40 እስራኤላውያን በግብፅ ውስጥ የኖሩት አራት መቶ ሠላሳ ዓመት ነበር። 41 መቶ ሠላሳው ዓመት ፍጻሜ፣ በዚያው ቀን፣ ሁሉም የእግዚአብሔር ሰራዊት ከግብፅ ምድር ወጣ። 42 ሌሊት እግዚአብሔር ከግብፅ ምድር እንዲያወጣቸው ለእስራኤላውያን ነቅቶ የመቆያ ሌሊት ነበር። ይህ ሌሊት እስራኤላውያን ሁሉ፣ መላ ትውልዶቻቸው ሊያከብሩት የሚገባ ሌሊት ነው። 43 እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን እንዲህ አላቸው፤ “የፋሲካ ሕግ እነሆ፦ ባዕድ ሰው ፋሲካን አይበላውም። 44 የተገዛ እያንዳንዱ የእስራኤል ባሪያ ግን ከገረዛችሁት በኋላ መብላት ይችላል። 45 ቅጥር አገልጋዮች መብላት አይገባቸውም። 46 ምግቡ በአንድ ቤት ውስጥ መበላት አለበት። ሥጋ ከቤት ማውጣት፣ ዐጥንትም መስበር የለባችሁም። 47 የእስራኤል ማኅበረ ሰብ በዓሉን ሊያከብር ይገባል። 48 ባዕድ ሰው ከእናንተ ጋር ቢኖርና ፋሲካን ለእግዚአብሔር ለማክበር ቢፈልግ፣ ወንድ ዘመዶቹ ሁሉ መገረዝ አለባቸው። ከዚያም በኋላ፣ ሰውየው መምጣትና በዓሉን ማክበር ይችላል። በምድሩ እንደ ተወለዱት ሰዎች ይሆናል። ይሁን እንጂ፣ ያልተገረዘ ሰው የፋሲካን ምግብ አይበላም። 49 አንድ ዐይነት ሕግ ተግባራዊ የሚሆነው በሁለቱም ማለት በአገሬው ተወላጅና በመካከላችሁ በሚኖረው ባዕድ ሰውም ላይ ነው።” 50 እስራኤላውያን ሁሉ እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን እንዳዘዛቸው አደረጉ። 51 በዚያው ቀን እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በየሰራዊታቸው ከግብፅ ምድር አወጣቸው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Exodus 12:1

• ይህ ወር የወሮች መጀመሪያ ይሁናችሁ፣ የዓመቱም መጀመሪያ ወር ይሁናችሁ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ አንድ ትርጉም ወይም ፍቺ ያላቸው ሲሆን አጽንዖት ለመስጠት የገባ በመሆኑ እስራኤላውያን ከግብጽ የወጡበትንና አዲስ ታሪክ የጀመረበት ስለሆነ ወሩ የአመቱ መጀመሪያ ወር እንዲሆንላቸው የተነገረ ወይም የተሰጠ ነው። ይህ ወር የሚጀምረው በአመዛኙ በሚያዚያ ወር አከባቢ ነው።

Exodus 12:3

• የቤቱ ሰዎች ቁጥርም ለጠቦቱ የማይበቃ ቢሆን
በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ያሉ ሰዎች ቁጥር አንድን የበግ ጠቦት በልቶ ለመጨረስ የማይበቃ ከሆነ

• እርሱና ለቤቱ የቀረበው ጎረቤቱ
“እርሱ” የተባለው የዚያ ቤተሰብ መሪ የሆነው ሰው ማለት ነው

Exodus 12:5

• ሲመሸ
“ምሽት” የሚለው ቃል ሙሉ በሙሉ ሲመሸ ሳይሆን ፀሐይ መጥለቂያ እና ማምሻ መካከል ያለው ሰዓት ሲሆን ከመጨለሙ በፊት ብርሃን ያለ መሆኑን አመልካቺ ነው።

• መቃን ጉበኑን ይቅቡት
የበሩን ወይም የደጃፉን ጎንና ጎን እንዲሁም የላኛውን ጉበን ማለት ነው።

• ቂጣውን እንጀራ
በአማርኛ “ቂጣ እንጀራ” ወይም “እንጀራ ቂጣ” ምን ማለት እንደሆነ ግልጽ ላይሆን ይችላል። ቂጣውን እንጀራ ማለት እርሾ ያልገባበት ደረቅ ቂጣ ሲሆን እንደ ህብረተሰቡ አጠቃቀም “ቂጣ፥ ያልቦካ ቂጣ፥ ደረቅ ቂጣ” ሊሆን ይችላል።

• ከመራራ ቅጠል ጋር ይበሉታል
መራራ ቅጠል የተባለው ምን ዓይነት ተክል እንደሆነ በስም አልተገለጸም። በአይሁዳውያን ባህል ሥጋ ለማድረቅ ወይም ለመቀመም የሚጠቀሙበት ተክል ዓይነት ነው።

Exodus 12:9

• ጥሬውን በውኃም የበሰለውን አትብሉ
የፍየሉን ወይም የበጉን ጥሬ ሥጋ ወይም በውሃ ተቀቅሎ የበሰለውን አትብሉ

• ከእርሱም እስከ ጥዋት አንዳች አታስቀሩ
ከሥጋው እስከ ጧት ድረስ ምንም አታስቀሩ

• ወገቦቻችሁን ታጥቃችሁ
የወገብ መታጠቂያ ከቆዳ ወይም ከጥጥ የተሰራ የወገብ መታጠቂያ ወይም በእያንዳንዱ ባህል ማህበረሰቡ የሚጠቀመው የወገብ መታጠቂያ ሊሆን ይችላል።

• ፈጥናችሁም ትበሉታላችሁ
በጥድፊያ ወይም በችኮላ ብሉት

• እርሱ የእግዚአብሔር ፋሲካ ነው
“እርሱ” የሚለው በአስራ አራተኛው ቀን የበግ ወይም ፍዬል ጥቦት እረድና የመብላት ሥርዓቱን ማለት ነው።

Exodus 12:12

• በግብፅም አማልክት ሁሉ ላይ እፈርድባቸዋለሁ
የግብጽን አማልክት ወይም እግዚአብሔሮች ሁሉ እቀጣለሁ

• ደሙም ባላችሁበት ቤቶች ምልክት ይሆንላችኋል
እኔ ወደ እናንተ በሚመጣበት ጊዜ ደሙ የእስስራኤላውያን ቤት ስለመሆኑ ምልክት ይሆንልኛል።

• ደሙንም ባየሁ ጊዜ ከእናንተ አልፋለሁ
እኔም ደሙን በማይበት ጊዜ አልፌአችሁ እሄዳለሁ ወይም ወደ ቤታችሁ ሳልገባ/ሳልጎበኛችሁ አልፌ እሄዳለሁ (ዘይቤያዊ ንግግር)

• ለልጅ ልጃችሁ ሥርዓት ሆኖ ለዘላለም ታደርጉታላችሁ
በሚቀጥሉት ትውልዶች ወይም ዘመናት ሁሉ ቋሚ ሥርዐት ሆኖ የእግዚአብሔር (ያህዌ) በዓል አድርጋችሁ ታከብሩታላችሁ።

Exodus 12:15

• ማንኛውም ሰው ከእስራኤል ይጥፋ
“ይጥፋ” የሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር ሶስት አማራጭ ፍቾች ይኖሩታል። 1) የእስራኤል ሰዎች ይህን ሰው ከመካከላቸው አውጥተው ማስወገድ አለባቸው 2) ይህ ሰው ከእስራኤላውያን እንደ አንዱ መታየት የለበትም 3) እስራኤላውያን ይህን ሰው መግደል ወይም ማጥፋት አለባቸው።

• በመጀመሪያውም ቀን የተቀደሰ ጉባኤ እንዲሁም በሰባተኛውም ቀን የተቀደሰ ጉባኤ ይሆንላችኋል
በመጀመሪያውና በሰባተኛው ቀን የተቀደሰ ጉባኤ ታደርጋላችሁ

• ከሚበላ በቀር በእነርሱም ምንም አትሠሩም
በእነዚያም ቀኖች ምግባችሁን ከማዘጋጀት በቀር ምንም ሥራ አትሠሩም

• ይህንም ብቻ ታደርጉታላችሁ
የምትሠሩት ሥራ ቢኖር ለእያንዳንዱ ምግብ ማዘጋጀት ብቻ ይሆናል።

Exodus 12:17

• ሠራዊታችሁን ከግብፅ አገር አውጥቼአለሁና
ይህ አገላለጽ ለጦር ሠራዊት የተሰጠ ስም ሲሆን በዚህ ክፍል የተገለጸው “ክፍል ለክፍል ወይም ቡድን ለቡድን” በሰልፍ የሚወጣውን የእስራኤልን ህዝብ የሚመለከት ነው።

• ሲመሸ
“ምሽት” የሚለው ቃል ሙሉ በሙሉ ሲመሸ ሳይሆን ፀሐይ መጥለቂያ እና ማምሻ መካከል ያለው ሰዓት ሲሆን ከመጨለሙ በፊት ብርሃን ያለ ማለት ነው።

• በመጀመሪያውም ወር በአሥራ አራተኛው ቀን
ይህ ወር በእስራኤላውያን ዘመን አቆጣጠር የአመቱ የመጀመሪያ ወር ነው። በአውሮጳውያን አቆጣጠር የመጋቢት መጨረሻ ሳምንት እና የሚያዚያ የመጀመሪያ ሳምንት አከባቢ የሚጀምር ወር ነው።

• ከወሩም እስከ ሀያ አንድ ቀን በመሸ ጊዜ
የመጀመሪያ ወር በገባ በ21ኛው ቀን ማለት ነው

Exodus 12:19

• ሰባት ቀን በቤታችሁ እርሾ አይገኝ
እስከ ሰባት ቀን ድረስ ምንም ዓይነት እርሾ በቤታችሁ መገኘት የለበትም

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• ከእስራኤል ማኅበር ተለይቶ ይጥፋ
ዘጸአት 12፡15 ተመልከት

• እርሾ ያለበትን ምንም አትብሉ
ዘጸአት 12፡5-8 ያለውን ማብራሪያ ተመልከት

Exodus 12:21

• ሂሶጵ
ሸካራ የሆነ ትናንሽ ቅጠሎች ያሉት በተለይ ፈሳሽ ነገሮችን ለመርጨት የሚያገለግል የዛፍ ዓይነት ነው

• መቃኖችና ጉበኑን እርጩ
የበሩን ወይም የደጃፉን ጎንና ጎን እንዲሁም የላኛውን ጉበን ማለት ነው።

Exodus 12:23

• እግዚአብሔር በደጁ ላይ ያልፋል
“በደጁ” ላይ ያልፋል የሚለው ጠቅላላውን ቤተሰብ ወይም ቤት የሚመለከት ነው። ደም በመቃኖቻቸውና በጉበኖቻቸው ላይ የተገኘባቸው ቤቶችን እግዚአብሔር ሳይነካቸው ያልፋል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- እግዚአብሔር ቤታችሁን ትቶ ያልፋል

Exodus 12:24

• ይህችን ነገር ጠብቁ
“ይህችን ነገር” የተባለው “የፋሲካ በዓል” ወይም “የቂጣ በዓል” ማለት ነው። የፋሲካ በዓል ማክበር እግዚአብሔርን (ያህዌን” ማክበር ነው።

Exodus 12:26

• ቤቶቻችንን ያዳነ የእግዚአብሔር የማለፉ
በሌላ አገላለጽ፡- እግዚአብሔር የእስራኤላውያንን መኖሪያ ቤቶች አልፎ በመሄድ ቤታቸውን ስላተረፈ ወይም በእስራኤላውያን ቤት የሚገኙትን በኩር ወንድ ልጆችን ባለመግደሉ”

• እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን እንዳዘዘ እንዲሁ አደረጉ
ሄደውም በሙሴና በአሮን አማካይነት እግዚአብሔር ያዘዛቸውን ሁሉ አደረጉ

Exodus 12:29

• በዙፋን ከተቀመጠው ከፈርዖን በኩር ጀምሮ በግዞት እስካሉት እስከ ምርኮኞቹ በኩር ድረስ
በኩር የሚለው ቃል ሁል ጊዜ መጀመሪያ የተወለደን ወንድ (ሰውና እንስሳ) የሚመለከት ነው። (ዘጸአት 11፡5 ተመልከት)

• በዙፋን ከተቀመጠው ከፈርዖን በኩር ጀምሮ
በዙፋን ላይ ከተቀመጠው ከፈርዖን የበኩር ልጅ ጀምሮ

• በግዞት እስካሉት እስከ ምርኮኞቹ በኩር ድረስ
በጨለማ እስር ቤት ውስጥ እስካለው እስረኛ የበኩር ልጅ ድረስ ያለውን ማለት ነው። ምርኮኛ የተባለው አንድ እስረኛ ሳይሆን ሁሉንም እስረኛ ሲሆን አንደ አንድ ሰው የተጠቀሰው ለሁሉም ያገለግላል ማለት ነው።

• የሞተ የሌለበት ቤት አልነበረምና
በኩር የሆነ ወንድ ልጅ ያልሞተበት አንድ ቤት እንኳ አልነበረም

• በግብፅ ምድር ታላቅ ልቅሶ ሆነ
በግብጽ ምድር ሁሉ ታላቅ የለቅሶ ጩኸትና ዋይታ ሆነ

Exodus 12:31

• ሁላችን እንሞታለን ብለዋልና
እስራኤላውያን ግብጽን ለቀው ካልወጡ ሁላችን እናልቃለን ብለው ግብጻውያን ስለፈሩ ---። አማራጭ ትርጉም፡- “እናንተ ለቃችሁ የማትሄዱ ከሆነ እኛም መሞታችን ነው”

Exodus 12:34

• ሕዝቡም ሊጡን ሳይቦካ ተሸከሙ፥ ቡሃቃውንም በልብሳቸው ጠቅልለው በትከሻቸው ተሸከሙት
በሌላ አገላለጽ፡- ሕዝቡ ያልቦካውን ሊጥ በየቡሆ ዕቃው አድርገው በጨርቅ ጠቅልለው በትከሻቸው ተሸከሙ

Exodus 12:37

• ከራምሴ
ራምሴ ግብጻውያን እህል ከሚያከማቹባቸው ከተሞች አንዱ ነው። (ዘጸአት 1፡11 ተመልከት)

• ከሕፃናቱም ሌላ ስድስት መቶ ሺህ ሰው የሚያህል እግረኛ ነበረ
“ህጻናት” የተባሉት ድጋፍ የሚፈልጉ ወንድና ሴት ልጆችን የሚመለከት ወይም ህጻናትና ሴቶችን የሚመለከት ሊሆን ይችላል። ጠቅላላ መዋጋት የሚችሉ ወንዶች ብዛት ስድስት መቶ ሺህ ያህል ነበር።

• ከግብፅም ከእነርሱ ጋር ያወጡትን ሊጥ ጋገሩ
ከግብፅ ይዘው ከወጡት ሊጥ ያልቦካ ቂጣ ጋገሩ

• ግብፃውያን በመውጣት ስላስቸኮሉአቸው ይቆዩ ዘንድ አልተቻላቸውም
ከግብፅ በጥድፊያ ወይም በችኮላ እንዲወጡ ስለተደረጉ ለራሳቸው ምግብ ለማዘጋጀት ጊዜ አልነበራቸውም

Exodus 12:41

• የእስራኤልም ልጆች በግብፅ ምድር የተቀመጡት ዘመን አራት መቶ ሠላሳ ዓመት ነው
እስራኤላውያን በግብጽ ምድር የኖሩት አራት መቶ ሠላሳ ዓመት ነበር

• የእግዚአብሔር ሠራዊት ሁሉ ከግብፅ ምድር ወጣ
እዚህ ጋር ሠራዊት የተባለው የእስራኤልን ህዝብ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ የግብጽን ምድር ለቆ ወጣ” (ዘጸአት 12፡17 ተመልከት)

• በእስራኤል ልጆች ሁሉ ዘንድ እስከ ልጅ ልጃቸው ድረስ ለእግዚአብሔር የተጠበቀች ናት
ይህ ሌሊት እስራኤላውያን በመጠባበቅ ተግተው የሚያድሩበትና ለሚመጣው ትውልድ ወይም ዘመን ሁሉ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ሌሊት ነው

Exodus 12:43

• ከእርሱ እንግዳ ሰው አይብላ
“እርሱ” የተባለው የፋሲክን ምግብ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- የባዕድ አገር ሰው የሆነ የፋሲካን ራት ወይም ምግብ አይብላ

• በብር የተገዛ ባሪያ ቢኖር
በገንዘብ የገዛችሁት ማንኛውም ባሪያ ቢሆን

Exodus 12:45

• በአንድ ቤትም ይበላ
ምግቡ በሙሉ በዚያው በተዘጋጀበት ቤት ውስጥ መበላት አለበት ማለት ነው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• አጥንትም አትስበሩት
የሚታረደው ጠቦት አጥንቶቹን አትስበሩ

Exodus 12:47

• አስቀድሞ ወንድ ሁሉ ይገረዝ
አስቀድማችሁ በቤተሰቡ ያሉትን ወንዶች ሁሉ ግረዙ

• ያልተገረዘ ሁሉ ግን ከእርሱ አይብላ
በሌላ አባባል የተገረዘ ሁሉ ከፋሲካው ምግብ መብላት ይችላል ማለት ነው

Exodus 12:49

• እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን እንዳዘዘ እንዲሁ አደረጉ
እግዚአብሔር በሙሴና በአሮን አማካይነት ያዘዘውን ሁሉ ፈጸሙ

• የእስራኤልን ልጆች ከሠራዊታቸው ጋር **(**ዘጸአት **12**:**17** ተመልከት**)**
አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር መላውን የእስራኤል ሕዝብ በክፍል በክፍል ከግብጽ ምድር መርቶ አወጣ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 13

1 ሙሴን እንዲህ አለው፤ **2** ‘በእስራኤላውያን ዘንድ ከሰውም ሆነ ከእንስሳት በመጀመሪያ የተወለደውን ወንድ ሁሉ ለእኔ ቀድስልኝ። በኵር የእኔ ነው።” **3** ለሕዝቡ እንዲህ አለ፤ “ከባርነት ቤት ከግብፅ የወጣችሁበትን ይህን ቀን አስታውሱት፤ በዚህ ቀን እግዚአብሔር በብርቱ እጁ ከዚህ ስፍራ አውጥቶአችኋልና። እርሾ ያለበት ምግብ አይበላም። **4** በዚህ ቀን፣ በአቢብ ወር ከግብፅ ወጥቷችኋል። **5** ለእናንተ ለመስጠት ለአባቶቻችሁ ወደ ማለላቸው፣ ማርና ወተት ወደምታፈስሰው፣ ወደ ከነዓናውያን፣ ኬጢያውያን፣ አሞራውያን፣ ኤውያውያን፣ ኢያቡሳውያን ምድር እግዚአብሔር ሲያስገባችሁ፣ ይህን አምልኮ በዚህ ወር ትፈጽማላችሁ። **6** ቀን ቂጣ ትበላላችሁ፤ በሰባተኛውም ቀን እግዚአብሔርን የምታከብሩበት በዓል ይሆናል። **7** ቀን ሁሉ መበላት ያለበት ቂጣ ነው፤ እርሾ ያለበት እንጀራ በእናንተ ዘንድ መታየት የለበትም። በአዋሳኞቻችሁም ዘንድ እርሾ አይኑር። **8** ቀን፣ ‘ይህ እንዲህ የሚሆነው ከግብፅ ስወጣ እግዚአብሔር ለእኔ ካደረገው የተነሣ ነው’ ብላችሁ ለልጆቻችሁ ትነግሯቸዋላችሁ።’ **9** ይህም በእጃችሁና በግንባራችሁ ላይ መታሰቢያ ይሆናል። ይኸውም እግዚአብሔር በብርቱ እጁ ከግብፅ ስላወጣችሁ፣ የእግዚአብሔር ሕግ በአፋችሁ እንዲሆን ነው። **10** ይህን ሕግ በየዓመቱ በተወሰነለት ጊዜ ልትጠብቁት ይገባል። **11** ለእናንተና ለአባቶቻችሁ በማለው መሠረት፣ እግዚአብሔር ወደ ከነዓናውያን ምድር ሲያስገባችሁ፣ **12** በመጀመሪያ የተወሰደውን፣ የእንስሶቻችሁንም በኵር ሁሉ ለእግዚአብሔር ቀድሱ። ወንዶች የእግዚአብሔር ናቸው። **13** ከአህያ በመጀመሪያ የተወለደውን ሁሉ በጠቦት ትዋጁታላችሁ። ካልዋጃችሁት፣ ዐንገቱን ስበሩት። ከወንድ ልጆቻችሁ መካከል በኵር የሆኑትን ሁሉ ዋጇቸው። **14** ልጅህ፣ ‘ይህ ምን ማለት ነው? ብሎ ወደፊት ቢጠይቅህ፣ እንደዚህ ትነግረዋለህ ‘ከባርነት ቤት፣ ከግብፅ እግዚአብሔር ያወጣን በብርቱ እጅ ነበር። **15** እኛን ለመልቀቅ በግትርነት እንቢ ባለ ጊዜ፣ እግዚአብሔር በግብፅ ምድር ያለውን በኵር ሁሉ፣ የሰውንም ሆነ የእንስሳትን በኵር በሙሉ ገደለ። ከእንስሳት ሁሉ በመጀመሪያ የተወለደውን ለእግዚአብሔር የምሠዋውና ከወንድ ልጆችም በኵር የሆነውን የምዋጀውን በዚህ ምክንያት ነው።’ **16** ከግብፅ ያወጣን በብርቱ እጅ ነውና፣ ይህ በእጅህና በግንባር ላይ ማስታወሻ ይሆናል።” **17** ሕዝቡን ሲለቅቃቸው፣ እግዚአብሔር ምንም እንኳ ቅርብ ቢሆንም፣ በፍልስጥኤማውያን ምድር ባለው መንገድ አልመራቸውም። እግዚአብሔር፣ “ሕዝብ ጦርነት ቢያጋጥማቸው፥ ምናልባት ሐሳባቸውን ይለውጣሉ፣ ወደ ግብፅም ይመለሳሉ” ብሎ ነበርና። **18** እግዚአብሔር ሕዝቡን በምድረ በዳው ዙሪያ ውደ ቀይ ባሕር መራቸው። እስራኤላውያን ለውጊያ ተዘጋጅተው ከግብፅ ምድር ወጥተው ሄዱ፣ **19** ሙሴ የዮሴፍን ዐፅም ይዞ ሄደ፤ ምክንያቱም ዮሴፍ፣ “እግዚአብሔር በእርግጥ ይታደጋችኋልና ዐፅሜን ይዛችሁ እንድትሄዱ” በማለት እስራኤላውያንን አስምሎአቸው ነበር። **20** ከሱኮት በመጓዝ ምድረ በዳው ዳር ላይ በሚገኘው በአታም ሰፈሩ። **21** እግዚአብሔር ሕዝቡን በመንገድ ላይ ሊመራቸው ቀን ቀን በደመና ዐምድ በፊታቸው ሄደ። ሌሊት ሌሊት ደግሞ ብርሃን ሊሰጣቸው በእሳት ዐምድ ሄደ። በዚህ ዐይነት ሕዝቡ በቀንም በሌሊትም መጓዝ ቻሉ። **22** እግዚአብሔር የቀኑን የደመና ዐምድ ወይም የሌሊቱን የብርሃን ዐምድ ከሕዝቡ ፊት አላነሣም።

Exodus 13:1

• ማሕፀንን የሚከፈት በኵር ሁሉ ለእኔ ቀድስልኝ
በኵር ሆኖ የተወለደ ሁሉ ለእግዚአብሔር የተለየ እንዲሆን እግዚአብሔር ይፈልገዋል

Exodus 13:3

• ይህን ቀን አስቡ
“ይህን ቀን አስቡ” የሚለው አንድ ሰው ያለፈውን ነገር ወደ ኋላ እንዲያስታውስ መናገር የተለመደ አባባል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ ይህን ቀን አስታውሱ ወይም ይህን ቀን አትርሱ።

• የባርነት ቤት
ህዝቡ በአንድ ቤት ታጉሮ እንደነበር ዓይነት አነጋገር የያዘ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በባርነት የነበራችሁበት ዘመን ወይም ሁኔታ”

• እግዚአብሔር . . . በብርቱ እጅ አውጥቶአችኋልና
ምክንያቱም እግዚአብሔር በታላቅ ኀይሉ በመታደግ አውጥቷችኋል

• የቦካ እንጀራ አትብሉ
እርሾ የገባበትን ዳቦ ወይም ምግብ አትብሉ

• በአቢብ ወር ወጥታችኋል
የአቢብ ወር ለእብራውያን የአመቱ መጀመሪያ ወር ነው። እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር አቢብ ወር የሚጀምረው ከመጋቢት መጨረሻ ሳምንት እስከ ሚያዝያ መጀመሪያ ሳምንት ባለው ጊዜ ውስጥ ነው።

• ወተትና ማር ወደምታፈስስ ምድር
ይህ ሐረግ በግነታዊ እና በተለዋጭ ዘይቤ የተገለጸ ነው። ይህ አገላለጽ ከምድሪቱ ወተትና ማር ይፈልቃል ማለት ሳይሆን ለከብት ርባታና ለእርሻ በጣም ምቹ የሆነ ምድር እንደሆነ ለማሳየት ነው። እንዲሁም “የምታፈስ” አገር የሚለው ቃልም ሁሉም ነገር የሞላባት ምድር የሚል ፍቺ ያለው ነው።

• ይህችን አምልኮ በዚህ ወር ታደርጋለህ
እስራኤላውያን በከነዓን ሲኖሩ በዓመቱ መጀመሪያ ወር ላይ ይህን በዓል (የፋሲካ በዓል) ማክበር አለባቸው (ዘጸአት 12፡25)

Exodus 13:6

አጠቃላይ ምልከታ፦ ሙሴ ለእስራኤል ሰዎች አሁንም ቀጥሎ ይናገራል • ሰባት ቀን ቂጣ እንጀራ ትበላለህ
እስከ ሰባት ቀን ወይም ለሰባት ቀን ሙሉ እርሾ ያልገባበትን ምግብ ትበላላችሁ

• በአንተም ዘንድ እርሾ ያለበት እንጀራ አይታይ
እርሾም ሆነ እርሾ የገባበት ምግብ በፍጹም በምድራችሁ አይገኝ

• በድንበርህም ሁሉ እርሾ አይታይ
እርሾ በአገርህ ውስጥ በየትኛውም ሥፍራ/ቦታ/ አይገኝ

Exodus 13:8

• በዚያም ቀን፦ ከግብፅ በወጣሁ ጊዜ እግዚአብሔር ስላደረገልኝ ነው ስትል ለልጅህ ትነግረዋለህ
ይህ አነጋገር በቀጥታ አነጋገር ሲገለጽ፦ “በዓሉን በምታከብርበት ወቅት ይህን የምታደርገው ከግብጽ በወጣህበት ጊዜ እግዚአብሔር ያደረገልህን መልካም ነገር ለማስታወስ መሆኑን ለልጆችህ ንገራቸው”

• በብርቱ እጅ ከግብፅ አውጥቶሃልና
ምክንያቱም እግዚአብሔር በታላቅ ኀይሉ ከግብጽ አውጥቷችኋል

• በእጅህ እንደ ምልክት በዓይኖችህም መካከል እንደ መታሰቢያ ይሁንልህ
እስራኤላውያን በዓሉን ወይም የፋሲካን በዓል ሲያከብሩ እነዚህን ሁለት የሚታዩ ምልክቶችን እንድያደርጉ ሙሴ ያሳስባቸዋል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• በእጅህ እንደ ምልክት
ሙሴ ሲናገር እስራኤላውያን በዓሉን ሲያከብሩ በእጃቸው የሆነ ነገር አስረው እንደምያከብሩ አድርጎ ይገልጻል። አማራጭ ትርጉም፦ ለምልከነት በእጅህ ላይ የሆነ ነገር እንደምታስረው ይሁን።

• በዓይኖችህም መካከል እንደ መታሰቢያ ይሁንልህ
ሙሴ ሲናገር እስራኤላውያን በዓሉን ሲያከብሩ በግንባራቸው የሆነ ነገር አስረው እንደምያከብሩ አድርጎ ይገልጻል። አማራጭ ትርጉም፦ ለምልክትነት በግንባርህ ላይ የሆነ ነገር እንደምታስረው ይሁን።

• በብርቱ እጅ ከግብፅ አውጥቶሃልና
ምክንያቱም እግዚአብሔር በታላቅ ኀይሉ ከግብጽ አውጥቷችኋል

Exodus 13:11

• እርስዋንም በሰጠህ ጊዜ
እግዚአብሔር የከነዓናውያንን ምድር ለአንተ በሰጠህ ጊዜ

• የአህያውን በኩር በጠቦት ትዋጀዋለህ፥ ባትዋጀውም አንገቱን ትሰብረዋለህ
በኩር የተወለደ አህያ ለእግዚአብሔር አይለይም ወይም አይቀደስም። አማራጭ ትርጉም፦ በኩር የተወለደ አህያ የበግ ጠቦት በመተካት ከእግዚአብሔር ትዋጃለህ /መልሰህ ተገዛለህ/፤ ነገር ግን አህያውን መዋጀት ካልፈለግህ አንገቱን ስበረው።

• የሰውንም በኩር ሁሉ ከልጆችህ መካከል ትዋጀዋለህ
በኩር ሆኖ የተወለደን ወንድ ልጅ ሁሉ መዋጀት /መልሰህ መግዛት/ ይገባሃል

Exodus 13:14

• በሚመጣው ጊዜ ልጅህ፦ ይህ ምንድር ነው? ብሎ በጠየቀህ ጊዜ እንዲህ ትለዋለህ
በሌላ አገላለጽ፦ “በሚመጡት ዘመናት ልጆችህ የዚህ ሥርዓት ትርጉም ምንድን ነው” ብለው ቢጠይቁህ፥ እንዲህ ብለህ ታስረዳቸዋለህ

• እግዚአብሔር በብርቱ እጅ
ምክንያቱም እግዚአብሔር በታላቅ ኀይሉ

• የባርነት ቤት
ህዝቡ በአንድ ቤት ታጉሮ እንደነበር ዓይነት አነጋገር የያዘ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በባርነት የነበራችሁበትን ሁኔታ ወይም ሕይወት”

• በእጅህ እንደ ምልክት፥ በዓይኖችህም መካከል እንደ ተንጠለጠለ ነገር ይሁንልህ
እስራኤላውያን በዓሉን ወይም የፋሲካ በዓል ሲያከብሩ እነዚህን ሁለት የሚታዩ ምልክቶችን እንድያደርጉ ሙሴ ያሳስባቸዋል (ተነጻጻሪ ዘይቤ፤ ለተመሳሳይ አገላለጽ 13:8-10 ተመልከት)

Exodus 13:17

• ምንም ቅርብ ቢሆን
ቅርብ በሆነው መንገድ

• ሕዝቡ ሰልፉን ባየ ጊዜ እንዳይጸጽተው ወደ ግብፅም እንዳይመለስ ብሎአልና
እስራኤላውያን ረጅሙን ዕድሜያቸውን በባርነት ስላሳለፉ ከጦርነት ይልቅ ሰላምን ስለሚፈልጉ ከመዋጋት ይልቅ ወደ ባርነት መመለስ ይፈልጋሉ

Exodus 13:19

• በምድረ በዳውም ዳር በኤታም ሰፈሩ
ኤታም ወደ ፍልስጥኤም በሚወስደው መንገድ ላይ በምድረ በዳው ዳር ላይ ወይም ድንበር ላይ ይገኛል

• መንገድ ሊያሳያቸው ቀን በደመና ዓምድ፥ ሊያበራላቸውም ሌሊት በእሳት ዓምድ
እግዚአብሔር ቀን በደመና ዐምድ /ምሶሶ መሳይ/፥ ሌሊት ብርሃን በሚሰጥ በእሳት ዐምድ /ምሶሶ መሳይ/ ይመራቸው ነበር

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 14

1 ለሙሴ እንዲህ ብሎ ተናገር፤ 2 በሚግዶልና በባሕሩ መካከል ባለው በፊሀሒሮት ፊት፣ በበኣልዛፎንም አንጻር እንዲሰፍሩ ለእስራኤላውያን ንገር። በፊሀሒሮት
ትይዩ በባሕሩ አጠገብ ትሰፍራላችሁ። 3 ፈርዖን ስለ እስራኤላውያን፣ ‘በምድሪቱ እየተንከራተቱ ነው፤ ምድረ በዳውም ዘግቶባቸዋል’ ይላል። 4 የፈርዖንን ልብ እኔ
አደነድነዋለሁ፤ እርሱም እስራኤላውያንን ይከታተላቸዋል። በፈርዖንና በመላው ሰራዊቱ ምክንያት እኔ እከብራለሁ። ግብፃውያን እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ
ያውቃሉ።” ስለዚህ እስራኤላውያን በተነገራቸው መሠረት ሰፈሩ። 5 ንጉሥ እስራኤላውያን እንደ ሄዱ ሲነገረው፣ ፈርዖንና አገልጋዮቹ ሐሳባቸውን በመለወጥ፣
እስራኤላውያን ለእኛ ከመሥራት ነጻ ሆነው እንዲሄዱ መፍቀዳችን ምን ማድረጋችን ነው? አሉ። 6 ሠረገላዎቹ እንዲዘጋጁለት አደረገ፤ ሰራዊቱንም ከእርሱ ጋር
ይዞ ሄደ። 7 መቶ ምርጥ ሠረገሎችንና የግብፅን ሌሎች ሠረገሎች በሙሉ፣ በያንዳንዳቸው ላይ መኮንኖች ያሉባቸውን ይዞ ተንቀሳቀሰ። 8 እግዚአብሔር
የግብፅን ንጉሥ፣ የፈርዖንን ልብ ስላደነደነው፣ ንጉሡ እስራኤላውያንን ተከታተላቸው። አሁን እስራኤላውያን በድል ወጥተው ሄደዋል። 9 ነገር ግን ግብፃውያን፣
ሁሉም የፈርዖን ፈረሶችና ሠረገሎች፣ የፈርዖን ፈረሰኞችና ሰራዊቱ እስራኤላውያንን አሳደዷቸው። በበኣልዛፎን አንጻር በባሕሩ አጠገብ ፊሀሒሮት ጥግ ሰፍረው
እንዳሉ ደረሱባቸው። 10 ፈርዖን በቀረ ጊዜ፣ እስራኤላውያን ወደ ላይ ተመለከቱ፣ ተደነቁም። ግብፃውያን ከኋላ እየተከተሏቸው ነበርና ፈሩ። እስራኤላውያን ወደ
እግዚአብሔር ጮኹ። 11 እንዲህ አሉት፤ “እዚህ ያመጣኸንና በምድረ በዳ እንድንሞት ያደረግኸው በግብፅ መቃብር ታጥቶ ይህን ነግረንህ አልነበረምን? 12
ሠራተኞች እንድንሆን ተወን’ ብለንህ ነበር። በምድረ በዳ ከምንሞት፣ ለእነርሱ ሠራተኞች ሆነን ብንቀር ይሻል ነበር።’” 13 እንዲህ አላቸው፤ “አትፍሩ። ጸንታችሁ
ቁሙና ዛሬ እግዚአብሔር ለእናንተ የሚያደርግላችሁን ትድግና ታያላችሁ። ዛሬ የምታዩአቸውን ግብፃውያንን ዳግም አታዩአቸውም። 14 እግዚአብሔር ለእናንተ
ይዋጋል፤ እናንተ መታገሥ ብቻ ነው ያለባችሁ።” 15 እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፤ “አንተ ሙሴ ለምን ትጮኽብኛለህ? እስራኤላውያን ወደ ፊት
እንዲሄዱ ንገራቸው። 16 የእስራኤል ስዎች በባሕሩ ውስጥ በደረቅ መሬት እንዲሻገሩ በትርህን አንሣና እጅህን በባሕሩ ላይ ዘርግተህ ለሁለት ክፈለው። 17
ተከትለዋቸው እንዲገቡ እኔ የግብፃውያንን ልብ የማደነድን መሆኔን ዕወቅ። ከፈርዖንና ከሰራዊቱ ሁሉ፣ ከሠረገሎቹና ከፈረሰኞቹ የተነሣ እኔ እከብራለሁ። 18
በፈርዖን፣ ሠረገሎቹና በፈረሰኞቹ ምክንያት ክብርን ሳገኝ፣ ግብፃውያኑ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ያውቃሉ።” 19 ፊት ይሄድ የነበረው የእግዚአብሔር መልአክ
በስተ ኋላቸው ሄደ። የደመናውም ዐምድ ከፊታቸው ተንቀሳቅሶ በስተኋላቸው ሄዶ ቆመ። 20 በግብፅ ሰራዊትና በእስራኤል መካከል መጣ። ለግብፃውያን
የጨለማ ደመና ሲሆን፣ ለእስራኤላውያን ግን ሌሊቱን ብሩህ ያደረገ ደመና ነበር፤ ይህም ሌሊቱን ሙሉ አንደኛው ወገን ወደ ሌላው እንዳይጠጋ አደረገ። 21
እጁን በባሕሩ ላይ ዘረጋ። እግዚአብሔርም በዚያ ሌሊት ባሕሩን በብርቱ የምሥራቅ ነፋስ ወደ ኋላ እንዲሄድ በማድረግ ባሕሩን ደረቅ መሬት አደረገው። በዚህ
መንገድ ውሃው ተከፈለ። 22 እስራኤላውያን በባሕሩ መካከል ገብተው በደረቅ መሬት ዐለፉ። ውሃው በቀኛቸውና በግራቸውና በኩል ግድግዳ ሆነላቸው። 23
ተከታትለዋቸው መጡ። እነርሱ፣ የፈርዖን ፈረሶች ሠረገሎችና ፈረሰኞች ሁሉ እስራኤላውያኑ ተከትለው በባሕሩ መካከል ገቡ። 24 ላይ እግዚአብሔር በእሳቱና
በደመናው ዐምድ ውስጥ የግብፃውያንን ሰራዊት ወደ ታች ተመለከተ። በግብፃውያን መካከልም ሽብር እንዲፈጠር አደረገ። 25 የሠረገሎቻቸው መንኮራኩሮች
ተቆላለፉ፤ ፈረሰኞችም ለመንቀሳቀስ እጅግ ተቸገሩ። ስለዚህ ግብፃውያኑ፣ እግዚአብሔር እኛን እየወጋላቸው ነውና፣ ከእስራኤል እንሸሽ” አሉ። 26 ሙሴን፣
“ውሃው በግብፃውያኑ፣ በሠረገሎቻቸውና በፈረሰኞቻቸው ላይ ተመልሶ እንዲመጣባቸው እጅህን በባሕሩ ላይ ዘርጋ” አለው። 27 እጁን በባሕሩ ላይ ዘረጋ፤
ንጋት ላይም ባሕሩ ወደ ተለመደ ስፍራው ተመለሰ። ግብፃውያኑ ከባሕሩ ሸሹ፤ እግዚአብሔር ግን ወደ ባሕሩ መካከል አስገባቸው። 28 ውሃው ተመስሎ
በመምጣት የፈረዖንን ሠረገሎች፣ ፈረሰኞችን ሠረገሎቹን ተከትለው ወደ ባሕሩ የገቡትን ጠቅላላ ሰራዊቱን ሸፈናቸው። አንድም ሳይሰምጥ የቀረ አልነበረም።
29 ግን በባሕሩ መካከል በደረቅ መሬት ላይ ተራምደው ሄዱ። ውሃው በቀኛቸውም በግራቸውም በኩል ለእነርሱ ግድግዳ ሆናላቸዋል። 30 እግዚአብሔር በዚያ
ቀን እስራኤላውያንን ከግብፃውያን እጅ ታደጋቸው፤ እስራኤላውያኑም የግብፃውያኑን ሬሳ በባሕሩ ዳር አዩ። 31 እግዚአብሔር በግብፃውያኑ ላይ የገለጠውን ታላቅ
ኀይል ሲያዩ፣ ሕዝቡ እግዚአብሔርን አከበሩ፣ በእግዚአብሔርና በአገልጋዩ በሙሴም ታመኑ።

Exodus 14:1

• በሚግዶልና በባሕር መካከል፣ በበኣልዛፎንም
እነዚህ በምስራቃዊው ግብጽ ላይ ያሉ ከተሞች ናቸው

• ፈርዖንም ስለ እስራኤል ልጆች፦ በምድር ይቅበዘበዛሉ፣ ምድረ በዳም ዘጋቻቸው፣ ይላል
ይህ ቀጥተኛ ንግግር ቀጥታ ባልሆነ ሲጻፍ፦ “ንጉሡ ፈርዖን የእስራኤል
ህዝብ በበረሓ ተዘግተው ወይም መንገድ አጥተው በአገሪቱ ዙሪያ
የሚንከራተቱ ይመስለኛ” ብሎ አሰበ።

• ምድረ በዳም ዘጋቻቸው
ምድረ በዳው እስራኤላውያንን እንደጠለፋቸውና በአንድ ቤት ዘግቶ
እንዳስቀመጣቸው አድርጎ ፈርዖን ይናገራል። ነገር ግን ሀሳቡ “እስራኤላውያን
በምድረ በዳ መንገድ አጥተው” ማለት ነው።

Exodus 14:4

አጠቃላይ ምልከታ፦ እግዚአብሔር(ያህዌ) ሙሴ ወዴት መሄድ እንዳለበትና እግዚአብሔር (ያህዌ) ምን ሊያደርግ እንዳለ አመራር ሲሰጥ እናያለን። • እኔ የፈርዖንን ልብ አጸናለሁ
የፈርዖን ልብ የተባለው ራሱ ፈርዖን ማለት ነው። ፈርዖን ለመስማት አልፈለገም
ወይም እምብ አለ ማለት ነው። (ወካይ ወይም ተለዋጭ ዘይቤ ተመልከት)።
በዚህኛ ክፍል የፈርዖንን ልብ ያደነደነው ወይም ፈርዖን እንዳይሰማ ያደረገው
እግዚአብሔር እንደሆነ ነው። (ዘጸአት 9፡12 ተመልከት)

• እርሱም ያባርራቸዋል
በሌላ አገላለጽ፦ ፈርዖን እስራኤላውያንን ያብርራቸዋል ማለት ነው

• ክብር አገኛለሁ
ሰዎች እኔን ያከብሩኛል

• ግብፃውያንም እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ
በዚያን ጊዜ እኔ እግዚአብሔር እውነተኛ አምላክ እንደ ሆንኩ ግብጻውያን
ያውቃሉ

• እነርሱም እንዲሁ አደረጉ
እስራኤላውያን እንደ ተነገራቸው አደረጉ ወይም እስራኤላውያን እግዚአብሔር
እንደ ነገራቸው ፈጸሙ

• ለግብፅ ንጉሥ
ለግብጽ ንጉስ ፈርዖን

• ሕዝቡም እንደ ኮበለሉ
እስራኤላውያን እንዳመለጡ

• የፈርዖንና የባሪያዎቹም ልብ በሕዝቡ ላይ ተለወጠና
ፈርዖንና አገልጋዮቹ/መኳንንቱ/ ሀሳባቸውን ቀይረው ወይም ለውጠው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• እንዳይገዛልን እስራኤልን የለቀቅነው ምን አድርገናል?
ፈርዖንና መኳንንቱ ይህን ጥያቄ የጠየቁት የሞኝነት ተግባር እንደፈጸሙ ስላሰቡ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ ይህ የሠራነው ነገር ምንድን ነው? እስራኤላውያንን እንዲሄዱ ፈቅደን አገልጋዮችን ማጣታችን አይደለምን? (አጋናኝ ጥያቄ የመተርግም ዘዴ ተመልከት)

Exodus 14:6

• ስድስት መቶ የተመረጡ ሰረገሎችን . . . ወሰደ
ስድስት መቶ (600) ምርጥ ሠረገሎችን . . . አሰለፈ

• እግዚአብሔር . . . የፈርዖንን ልብ አጸና
የፈርዖን ልብ የተባለው ራሱ ፈርዖን ማለት ነው። ፈርዖን ለመስማት አልፈለገም ወይም እምብ አለ ማለት ነው። (ወካይ ወይም ተለዋጭ ዘይቤ ተመልከት)። በዚህኛ ክፍል የፈርዖንን ልብ ያደነደነው ወይም ፈርዖን እንዳይሰማ ያደረገው እግዚአብሔር እንደሆነ ነው። (ዘጸአት 9:12 ተመልከት)

• በኣልዛፎን . . . ፊሀሒሮት
በግብጽ ምስራቃዊው ክፍል የሚገኙ ከተሞች ነበሩ (ስሞችን የመተርጎም ዘዴ ተመልከት)

Exodus 14:10

• ፈርዖንም በቀረበ ጊዜ
በዚህ ክፍል “ፈርዖን” የተባለው መላውን የፈርዖን ሠራዊት የሚመለከት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ ንጉሡ “ፈርዖንና ሠራዊቱ እየቀረቡ መምጣታቸውን”

• በግብፅ መቃብር ስላልኖረ በምድረ በዳ እንሞት ዘንድ አወጣኸንን?
እስራኤላውያን ይህንን ጥያቄ የጠየቁት እንዳይሞቱ ከመፍራታቸው እና ከመደንገጣቸው የተነሳ ነው። ይህን አጋናኝ ጥያቄ በመደበኛ ዐረፍተ ነገር ሲንተረጉም፦ በግብጽ ምድር በቂ የመቃብር ቦታ አለ፤ ለመቀበር ወይም መቃብር ፍለጋ እዚህ ምድረ በዳ መምጣት አልነበረብንም።

• ከግብፅ ታወጣን ዘንድ ይህ ያደረግህብን ምንድር ነው?
እስራኤላውያን ይህን ጥያቄ ሙሴን የጠየቁት በምድረ በዳ እንድሞቱ በማምጣቱ ለመገሰጽ ወይም ለመተቸት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ አንተ እኛን ከግብጽ አውጥተኸን እንዲህ ሊታሰቃየን አይገባህም ነበር።

• በግብፅ ሳለን ያልንህ ቃል ይህ አይደለምን?
ይህ አጋናኝ ጥያቄ የሚያሳየው ከዚህ በፊት በግብጽ እያሉ ለእርሱ የነገሩትን ለማስታወስ ወይም አትኩሮት ለመስጠት ነበር። አማራጭ ትርጉም፦ ይህ ሁሉ እንደሚሆን ገና ከዚያ ሳንወጣ ወይም በግብጽ ሳለን ነግረንህ አልነበረምን?

• ተወን፥ ለግብፃውያን እንገዛ ብለን
በሌላ አገላለጽ፦ “እባክህ ተወን ወይም ይቅርብን ለግብጻውያን ባርያዎች ሆነን እናገልግል” ብለን ነግረንህ ነበር

Exodus 14:13

• ሙሴም ለሕዝቡ
ሙሴ ለህዝቡ/ለእስራኤላውያን/ እንዲህ ብሎ መልስ ሰጣቸው

• ዛሬ ለእናንተ የሚያደርጋትን
እግዚአብሔር ዛሬ እናንተን እንዴት እንደምያድን/ለእናንተ እንዴት እንደሚሰራ/

• ዛሬ የምታዩአቸውን ግብፃውያንን ለዘላለም አታዩአቸውምና
ሙሴ እስራኤላውያንን በትህትና በማናገር እግዚአብሔር የግብጻውያንን ሰራዊት እንደሚደመስስ ይነግራቸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ እግዚአብሔር ዛሬ የግብጻውያንን ሰራዊት ይገድላል። (በአይነኬ ዘይቤ የተነገረ)

Exodus 14:15

• ለምን ትጮኽብኛለህ?
ሙሴ እርዳታ ፍለጋ ወደ እግዚአብሔር ይጸልይ ነበረና እግዚአብሔር ይህንን ጥያቄ ሙሴን ለማስገደድ ሲጠቀምበት እናያለን። ይህን አጋናኝ ጥያቄ በሁለት መንገድ በአጋናኝ ጥያቄ ወይም በመደበኛ ዐረፍተ ነገር መተርጎም ይቻላል። 1) “ሙሴ አንተ ወደ እኔ የምትጮኸው ለምንድን ነው?” 2) ሙሴ ከእንግዲህ ወዲህ ወደ እኔ አትጩህ ወይም ከእንግዲህ ወዲህ እኔን አትጥራ”

• ክፈለውም
ውሃውን ለሁለት ክፈለው ወይም ውሃው ለሁለት ይከፈለል

• እኔ የግብፃውያንን ልብ አጸናለሁ
“የግብጻውያንን ልብ” የተባለው ግብጻውያንን የሚመለከት ሲሆን “ገታራነታቸው ወይም እልከኝነታቸው” ልባቸው ጠንካራ እንደሆነ ተመስሎ ተነገረ። አማራጭ ትርጉም፦ እኔ ግብጻውያን እንብተኞች ወይም እልከኞች አደርጋቸዋለሁ።

• በኋላቸውም ይገባሉ
ግብጻውያን እስራኤላውያንን ተከትለው ባህሩ ውስጥ ይገባሉ

Exodus 14:19

• በግብፃውያን ሰፈርና በእስራኤል ሰፈር መካከልም ገባ
በግብጻውያን ሠራዊት መካከል እና በእስራኤላውያን ሠራዊት መካከል

• ሌሊቱንም ሁሉ እርስ በእርሳቸው አልተቃረቡም
የግብጽ ሠራዊት ሌሊቱን ሙሉ ወደ እስራኤላውያን ሠራዊት መጠጋት አልቻለም ወይም የግብጽ ሠራዊትና የእስራኤል ሠራዊት አንዱ ሌላው ጋር መጠጋት አልቻሉም

Exodus 14:21

• የምሥራቅ ነፋስ አምጥቶ
ይህ ነፋስ ከምስራቅ በኩል ይነሳና ወደ ምዕራብ ይነፍሳል

• ምስራቅ
ፀሐይ የሚወጣበት አቅጣጫ

• ውኃውም ተከፈለ
በሌላ አገላለጽ፦ “እግዚአብሔር ውሃውን ከፈለው”

Exodus 14:23

• የግብፃውያንንም ሠራዊት አወከ
አንድ ሰው ከፍርሃት የተነሳ ሲታወክ በትክክል ማሰብ አይችልምና ከልክ በላይ ደነገጡ ወይም ፈሩ ወይም የሚሆኑትን አጡ ማለት ነው።

• የሰረገሎቹንም መንኮራኩር አሰረ
የሠረገላዎቻቸውን ብረት ጎማ ወይም መንኩራኮር ከመሬት ወይም ከጭቃ ጋር አጣበቀባቸው

Exodus 14:26

• እግዚአብሔርም ሙሴን፦ እጅህን በባሕሩ ላይ ዘርጋ፥ በግብፃውያን በሰረገሎቻቸውም በፈረሰኞቻቸውም
አማራጭ ትርጉም፦ እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ ብሎ አዘዘው፦ “ውሃው በግብጻውያን ላይ፥ በሰረገላዎቻቸው ላይና በፈረሰኞቻቸው ላይ እንዲመለስ እጅህን በባህሩ ላይ ዘርጋ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• ግብፃውያንም ከእርሱ ሸሹ
የእብራይስጡ ትርጉም ከባህሩ ሸሹ ሳይሆን ወደ ባህሩ ሮጡ የሚል ፍቺ አለው። ይህ ማለት ግብጻውያን ከውሃው መሸሸ ሲገባቸው እየዋጣቸው ወዳለው ውሃ ይሮጡ ነበር።

• እግዚአብሔርም ግብፃውያንን በባህሩ መካከል ጣላቸው
እግዚአብሔር (ያህዌ) ግብጻውያንን በባህሩ ውስጥ አሰጠማቸው

• ከግብፃውያን እጅ አዳነ
“እጅ” የሚለው ቃል “ሀይልን” የሚመለከት ሲሆን እግዚአብሔር ከግብጻውያን ሀይል/ጥቃት/ጉልበት/ ማለት ይቻላል (ወካይ ዘይቤ ተመልከት)

• በባሕር ዳር አዩ
በባህሩ አጠገብ አዩ

Exodus 14:29

• እስራኤልን
በተለያዩ ቦታዎች “እስራኤል” ተብሎ የተጠቀሰው “የእስራኤል ህዝብን” የሚመለከት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ የእስራኤል ህዝብ ወይም እስራኤላውያን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 15

1 ጊዜ ሙሴና የእስራኤል ሕዝብ ይህን መዝሙር ለእግዚአብሔር እንዲህ እያሉ ዘመሩ፦ “በክብር ከፍ ከፍ ብሎአልና ለእግዚአብሔር እዘምራለሁ፤ ፈረሱንና
ፈረሰኛውን በባሕር ውስጥ ጥሎአል። 2 ብርታቴና ዝማሬዬ ነው፤ ድነቴም ሆኖልኛል። እርሱ አምላኬ ነው፣ አመሰግነዋለሁ፤ የአባቴ አምላክ ነው፣ ከፍ ከፍ
አደርገዋለሁ። 3 ተዋጊ ነው፤ ስሙም እግዚአብሔር ነው። 4 ሠረገሎችና ሠራዊት በባሕር ውስጥ ጥሎአል። የፈርዖን ምርጥ መኮንኖች በቀይ ባሕር ውስጥ
ሰመጡ። 5 ማዕበሎቹ ሸፈናቸው፤ እንደ ድንጋይ ወደ ጥልቆቹ ወረዱ። 6 እግዚአብሔር ሆይ፣ ቀኝ እጅህ ጠላትን ሰባበረ። 7 ላይ የተነሡትን በታላቅ ግርማ
ገለበጥሃቸው። ቍጣህን ላክህ፤ እንደ ገለባም አርጎ በላቸው። 8 በአፍንጫህ እስትንፋስ ውሆች ተከመሩ፤ ፈሳሾች እንደ ክምር ቆሙ፤ የጥልቁ ውሃ በባሕሩ
ውስጥ ረጋ። 9 ጠላት፣ ‘አሳድዳቸዋለሁ፣ እይዛቸዋለሁ፣ ምርኮም እካፈለለሁ፤ ፍላጎቴ በእነርሱ ርዳታ ያገኛል፤ ሰይፌን እመዝዛለሁ፤ እጄም ታጠፋቸዋለች’ አለ።
10 ግን በነፋስህ እፍ አልህ፣ ባሕሩም ሸፈናቸው፤ በጎይለኛ ውሆች ውስጥ እንደ ብረት ሰመጡ። 11 ሆይ፣ ክአማልክት መካከል እንደ አንተ ያለ ማን ነው?
በቅድስና የከበረ፣ ተአምራትን በማድረግ በምስጋና ከፍ ያለ፣ እንደ አንተ ያለ ማን ነው? 12 እጅህን ዘረጋህ፤ ምድርም ዋጠቻቸው። 13 ፍቅርህ የታደግሃቸውን
ሕዝብህን መራህ። በብርታትህ ወደ ቅዱስ ማደሪያህ መራሃቸው። 14 ይሰማሉ፣ ይንቀጠቀጣሉም፤ የፍልስጥኤምን ኗሪዎች ሽብር ይይዛቸዋል። 15 ጊዜ
የኤዶም እለቆች ይደነግጣሉ፤ የሞዓብ መሪዎች ይርበደበዳሉ፤ የከነዓን ኗሪዎች ሁሉ ይቀልጣሉ። 16 ሆይ፣ ሕዝብህ እስከሚያልፉ፣ የታደግሃቸው ሕዝብህ
ዐልፈው እስከሚሄዱ ድረስ፣ ሽብርና ድንጋቴ ይወድቅባቸዋል፤ ከክንድህ ብርታት የተነሣ፣ እንደ ድንጋይ የማይንቀሳቀሱ ይሆናሉ። 17 ሆይ፣ ማደሪያህ
ባደረግኸው ስፍራ፣ ጌታችን ሆይ፣ እጆችህ በሠሩት መቅደስ፣ በርስትህ ተራራ ላይ ሕዝብህን ታመጣቸዋለህ፣ ትተክላቸዋለህም። 18 ከዘለዓለም እስከ
ዘለዓለም ይነግሣል።” 19 ፈረሶች ከሠረገሎቹና ከፈረሰኞቹ ጋር ወደ ባሕሩ ውስጥ ሲገቡ፣ እግዚአብሔር የባሕሩን ውሀ መልሶ በላያቸው አመጣባቸው።
እስራኤላውያን ግን በባሕሩ መካከል በደረቅ መሬት ሄዱ። 20 ይአሮን እኅት፣ ነቢይቱ ማርያም ከበሮ አነሣች፤ ሌሎቹ ሴቶችም በሙሉ ከበሮ ይዘው ከእርሷ ጋር
እያሸበሸቡ ወጡ። 21 “ፈረሱንና ፈረሰኛውን በባሕር ውስጥ ጥሎአል፤ በክብር ከፍ ከፍ ብሎአልና፣ ለእግዚአብሔር ዘምሩ” እያለች ዘመረችላቸው። 22 ሙሴ
እስራኤላውያንን ከቀይ ባሕር እየመራቸው ወደ ሱር ምድረ በዳ ሄዱ። በምድረ በዳው ውስጥ ሦስት ቀን ሲጓዙ ውሀ አላገኙም። 23 ማራም ደረሱ፤ ነገር ግን እዚያ
የሚገኘው ውሀ መራራ ስለ ነበረ ሊጠጡት አልቻሉም። ቦታውን ማራ ያሉት ከዚህ የተነሣ ነው። 24 ሕዝቡ፣ “ምን እንጠጣ?” ብለው በሙሴ ላይ አጒረመረሙ።
25 ወደ እግዚአብሔር ጮኸ፣ እግዚአብሔርም አንድ ዛፍ አሳየው። ሙሴም የዛፉን ዕንጨት ወደ ውሀው ውስጥ ጣለው፣ ውሀውም ጣፋጭ ሆነ። እግዚአብሔር
ለሕዝቡ ሕግና ሥርዐት የሰጣቸውና የፈተናቸው በዚያ ስፍራ ነበር። 26 እንዲህ አለ፤ “የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ድምፅ በጥንቃቄ ብትሰሙ፥ ትክክለኛ
የሆነውንም በፊቱ ብታደርጉ፣ ትእዛዛቱንም ብታስተውሉና ሕግጋቱን ሁሉ ብትጠብቁ፣ ግብፃውያን ላይ ካመጣኋቸው በሽታዎች አንዱንም በእናንተ ላይ
አላመጣም፤ እኔ ፈዋሻችሁ እግዚአብሔር ነኝና።” 27 በኋላ ሕዝቡ ዐሥራ ሁለት ምንጮችና ሰባ የዘንባባ ዛፎች ወደ ነበሩበት ወደ ኤሊም መጡ። በዚያም
በውሀው አጠገብ ሰፈሩ።

Exodus 15:1

አጠቃላይ ምልከታ፦ ይህ መዝሙር ወይም ምዕራፍ **15** በምዕራፍ **14:26-28** በተከሰተው ከስተት ምክንያት የተዘመረ መዝሙር ነው • በክብር ከፍ ከፍ ብሎአልና
ይህ ለእግዚአብሔር (ያህዌ) ለድል አድራጊነቱ የተዘመረ መዝሙር ነው። በሌላ አገላለጽ፦ “እርሱ በግብጻውያን ላይ በታላቅ አሸናፊነት ተገለጸ” ወይም “እርሱ
በግብጻውያን ታላቅ ድል ተጎናጸፈ”

• ፈረሱንና ፈረሰኛውን በባሕር ጣለ
እግዚአብሔር በግብጻውያን ላይ ባህሩን መመለሱንና እነርሱን በባህር ማስጠመን ሙሴ በሌላ አገላለጽ እግዚአብሔር በባህር ውስጥ እንደጣላቸው ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “እርሱ በፈረሱና በፈረሰኛው ላይ ባህሩን መለሰባቸው” ወይም “እርሱ ፈረሱንና ፈረሰኛውን በባህር አሰጠማቸው”

• ፈረሱንና ፈረሰኛውን
እስራኤላውያንን የሚያሳድዱ ብዙ ፈረሶችንና ፈረስ ጋላቢዎችን የሚገልጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ ፈረሶችንና ፈረስ ጋላቢዎችን

Exodus 15:2

• እግዚአብሔር ጉልበቴ ነው **(**ወካይ ዘይቤ**)**
አማራጭ ትርጎሞች፦ 1) ሀይልን የሚሰጠኝ እግዚአብሔር ነው 2) እኔን የሚጠብቀኝ ወይም የሚከላከለኝ እግዚአብሔር ነው

• ዝማሬዬ እግዚአብሔር ነው **(**ወካይ ዘይቤ**)**
ሙሴ እግዚአብሔርን የዝማሬዬ ምንጭ ነው ወይም እግዚአብሔር እኔ የሚዘምርለት እርሱ ነው

• መድኃኒቴም ሆነልኝ **(**ወካይ ዘይቤ**)**
ሙሴ እግዚአብሔር መድሀኒቴ ብሎ ይጠራዋል ምክንያቱም እርሱ ከግብጻውያን እጅ አድኖአቸዋልና። አማራጭ ትርጉም፦ የሚያድነኝ እግዚአብሔር ነው

• እግዚአብሔር ተዋጊ ነው
ሙሴ እግዚአብሔርን ተዋጊ ብሎ ይጠራል ምክንያቱም እርሱ በሀይሉ ግብጻውያንን ተዋግቶ አሸንፏል። አማራጭ ትርጉም፦ እግዚአብሔር እንደ ብርቱ ተዋጊ ነው (ተለዋጭ ዘይቤ)

Exodus 15:4

• የፈርዖንን ሰረገሎች ሠራዊቱንም በባሕር ጣላቸው
ሙሴ ስለእግዚአብሔር ሲዘምር እግዚአብሔር ባህሩን በፈርዖን፥ ሰረገሎችና በሠራዊቱ ላይ መመለሱን በባህር ውስጥ እንደመጣል ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ እርሱ በፈርዖን ሰረገላዎችንና በሠራዊቱ ላይ ባህሩን መልሷል ወይም እርሱ የፈርዖን ሰረገላዎችንና ሠራዊቱን በባህር አስጥሟል

• ወደ ባሕር ጥልቀት እንደ ድንጋይ ሰጠሙ
ድንጋይ በባህር እስከ ውስጥ እንደሚሰጥም የጠላት ሠራዊት እስከ ባህሩ ጥልቅ ድረስ መስጠማቸውን ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ ድንጋይ በባህር ውስጥ እንደሚሰጥም እነርሱ በብሃር ውስጥ ሰጠሙ (ተነጻጻር ዘይቤ)

Exodus 15:6

• ቀኝህ በኃይል ከበረ
ሙሴ እግዚአብሔር እጅ እንዳለው አድርጎ ይናገራል፤ “ቀኝ እጅ” የእግዚአብሔርን ሀይል ወይም እግዚአብሔር በሀይሉ የሚሰራቸውን ነገሮች ይገልጻል። አማራጭ ትርጉም፦ እግዚአብሔር ሀይልህ የከበረ ነው፤

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እግዚአብሔር ሆይ አንተ በሀይልህ የምትሰራቸው ነገሮች ክቡር ናቸው (ወካይ ዘይቤ)።

• ቀኝህ ጠላቱን አደቀቀ
ሙሴ እግዚአብሔር እጅ እንዳለው አድርጎ ይናገራል፤ “ቀኝ እጅ” የእግዚአብሔርን ሀይል ይገልጻል። አማራጭ ትርጉም፦ እግዚአብሔር ሆይ ሀይልህ ጠላቶችን አደቀቀ ወይም እግዚአብሔር ሆይ በሀይልህ ጠላቶችን አደቀቅህ

• የተነሡብህን አጠፋህ
በእግዚአብሔር ላይ ማመጽ በእግዚአብሔር ላይ እንደመነሳት ተቆጥሯል፤ አማራጭ ትርጉም፦ በአንተ ላይ ያመጹ ወይም ጠላቶችህን

• ቍጣህን ሰድደህ
የእግዚአብሔርን ቁጣ ሙሴ ሲገልጽ አንድ ነገር ለመሥራት እንደ ተላከ አገልጋይ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ አንተ ቁጣህን አሳየህ ወይም አንተ እንደ ቁጣ ሥራህን ፈጸምክ

• እንደ ገለባም በላቸው
x

Exodus 15:9

• ነፍሴም ትጠግባቸዋለች
በሌላ አገላለጽ፦ እኔ ፍላጎቴን አሟላለሁ ወይም እኔ የፈለግሁትን ከእነርሱ እወስዳለሁ

• እጄም ታጠፋቸዋለች
ጠላቶች እስራኤላውያንን በእጃቸው ሀይል እንደሚያጠፉ ሲናገሩ እጃቸው እያጠፋቸው እንደሆነ አስመስለው ይናገራሉ። አማራጭ ትርጉም፦ እኔ በእጄ አጠፋቸዋለሁ

• ነፋስህን አነፈስህ
ሙሴ እግዚአብሔር በአፉ ወይም በአፍንጫው ነፋሱን እንደነፈሰባቸው አድርጎ ይገልጻል። አማራጭ ትርጉም፦ አንተ ነፈሱ እንዲነፍስ አድርገሃል

• እንደ አረር ሰጠሙ
አረር ከባድ የብረት ዘር ሲሆን ነገሮች በውሃ ወይም በባህር ውስጥ እንድሰምጡ ሲፈለግ አረር ይጠቀማሉ። እዚህ ቦታ “አረር” የተጠቀሰበት ምክንያት ጠላቶች ምን ያህል ፈጥነው እንደ ጠፉ ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ እንደ አረር ወይም ከባድ ብረት በሚናወጠው ውሃ ውስጥ ሰጥመው ቀሩ

• በአማልክት መካከል እንደ አንተ ያለ ማን ነው? (አጋናኝ ጥያቄ)
ሙሴ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው የእግዚአብሔርን ትልቅነት ለመግለጽ ሲፈልግ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ እግዚአብሔር ሆይ፥ ከአማልክት መካከል አንተን የሚመስል ማን ነው?

• ድንቅንም የምታደርግ፥ እንደ አንተ ያለ ማን ነው? (አጋናኝ ጥያቄ)
ሙሴ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው የእግዚአብሔርን ትልቅነት ለመግለጽ ሲፈልግ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ ታአምራትን የምታደርግ አንደ አንተ ያለ ማን ነው? ወይም ድንቅ ሥራዎችን የምትሰራ አንተን የሚመስል ማን ነው።

Exodus 15:12

• ቀኝህን ዘረጋህ
“ቀኝ እጅ” የእግዚአብሔርን ታላቅ ሀይል የሚገልጽ አባባል ሲሆን “በታላቅ ሀይልህ” የሚል ፍቺ አለው። “ዘረጋህ” የሚለው እግዚአብሔር እጅ እንዳለውና እጁን እንደዘረጋው አድርጎ ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፦ በታላቅ ሀይልህ ይህን አደርግኸው

• ምድርም ዋጠቻቸው
ሙሴ በሰውኛ ዘይቤ ምድር አፍ እንዳላትና ነገሮችን መዋጥ ወይም መብላት እንደምትችል አድርጎ ያቀርባል። አማራጭ ትርጉም፦ ምድር በላቻቸው ወይም አጠፋቻቸው

Exodus 15:14

• ተንቀጠቀጡም
ይህ በፍርሃት ምክንያት መንቀጥቀጣቸውን የሚገልጽ ነው።

• በፍልስጥኤም የሚኖሩትን ምጥ ያዛቸው
ፍልስጥኤማውያን ወይም በፍልስጥኤም የሚኖሩ ሰዎች ተሸበሩ/ታወኩ/

• በከነዓን የሚኖሩ ሁሉ ቀለጡ
ሰዎች ከፍርሃት የተነሳ መድከማቸውን ሙሴ እንደ ቀለጡ አድርጎ ያሳያል። በሌላ አገላለጽ፦ የከነዓን ሕዝብ ወኔ ከዳቸው ወይም ድፍረት አጡ

Exodus 15:16

አያያዥ ዐረፍተ ነገር፦ ለሎች ህዝቦች የእግዚአብሔርን ህዝብ ሲያዩ ምን እንደሚሰማቸው ሙሴ በመዝሙር ይገልጻል። • ፍርሃትና ድንጋጤ ወደቀባቸው
እነዚህ ሁለቱ ቃላት የሚያሳዩት በእነርሱ ላይ ፍርሃት ሊመጣ እንደሆነ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ፍርሃት በእነርሱ ላይ ይመጣል”

• በክንድህ ብርታት
የእግዚአብሔር ክንድ የእርሱን ትልቅ ሀይል የሚመለከት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ ከሀይልህ ትልቅነት የተነሳ”

• እንደ ድንጋይ ዝም አሉ
አማራጭ ትርጉሞች፦ 1) እነርሱ እንደ ድንጋይ ዝም ይላሉ 2) እነርሱ እንደ ድንጋይ እንቅስቃሴ አልባ ይሆናሉ

Exodus 15:17

• አንተ ታስገባቸዋለህ
“አንተ ታስገባቸዋለህ” የሚለው በሌላ አገላለጽ፦ አንተ ህዝብህን ወደ ከነዓን ታመጣቸዋለህ ወይም ትወስዳቸዋለህ የሚል ነው።

• በርስትህ ተራራም ትተክላቸዋለህ
እግዚአብሔር የከነዓንን ምድር ለእስራኤላውያን ርስት አድርጎ መስጠቱን ሙሴ ተክል ከመትከል ጋር ሲያነጻጽር ይታያል። “የርስት ተራራ” የተባለው በከነዓን ምድር ያለው “የጽዮን ተራራ ነው”። እግዚአብሔር ምድርቱን እንደ ርስት አድርጎ ይሰጣቸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ አንተ እነርሱን በርስት ተራራቸው ታኖራቸዋለህ ወይም እነርሱ በርስት ተራራቸው ይኑሩ።

Exodus 15:19

• ማርያም . . . አሮን
ማርያም የሙሴና የአሮን ታላቅ እህት ነበረች።

• ከበሮ
ከሙዚቃ መሳሪያዎች አንዱ ሲሆን ከተለያዩ ቁሳቁሶች ይሰራል፤ ለምሳሌ ከብረት፥ ከእንጨትና ከቆዳ ወዘተ።

• በክብር ከፍ ከፍ ብሎአል
ይህ ለእግዚአብሔር (ያህዌ) ለድል አድራጊነቱ የተዘመረ መዝሙር ነው። በሌላ አገላለጽ፦ “እርሱ በግብጻውያን ላይ በታላቅ አሸናፊነት ተገለጸ ወይም እርሱ በግብጻውያን ታላቅ ድል ተጎናጸፈ (15:1 ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• ፈረሱንና ፈረሰኛውን በባሕር ጣለ
እግዚአብሔር በግብጻውያን ላይ ባህሩን መመለሱንና እነርሱን በባህር ማስጠመን ሙሴ በሌላ አገላለጽ እግዚአብሔር በባህር ውስጥ እንደ አንድ ነገር እንደ ጣላቸው ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- እርሱ በፈረሱና በፈረሰኛው ላይ ባህሩን መለሰባቸው ወይም እርሱ ፈረሱንና ፈረሰኛውን በባህር አሰጠማቸው (15:1 ተመልከት)

Exodus 15:22

• ሙሴም እስራኤልን ከኤርትራ ባሕር አስጓዘ
“እስራኤል” የሚለው የእስራኤልን ህዝብ የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- ሙሴ የእስራኤልን ህዝብ መራቸው

• ወደ ሱር ምድረ በዳ ወጡ . . . ወደ ማራም መጡ
እነዚህ ቦታዎች በትክክል የት ጋር እንደሆኑ በትክክል ማሳየት አይቻለም። ነገር ግን ቦታዎች ወይም መንደሮች ነበሩ፤ ምናልባት በከነዓን ምድር በደቡባዊ ምስራቅ የሚገኙ አከባቢዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

Exodus 15:24

• በሙሴ ላይ አንጎራጎሩ
ህዝቡ በሙሴ ላይ ደስተኞች አለመሆናቸውን የሚገልጽ ነው፤ አማራጭ ትርጉም፡- በሙሴ ላይ አጉረመረሙ ወይም በሙሴ ላይ በቁጣ ተናገሩ

• የእግዚአብሔርን ቃል አጥብቀህ ብትሰማ
እግዚአብሔር ስለራሱ ድምጽ ይናገራል፤ ድምጹ እርሱን ይገልጻል ወይም ይወክላል። በሌላ አገላለጽ፡- ድምጼን ወይም እኔ የሚለውን (ወካይ ዘይቤ)

• በፊቱም የሚበጀውን ብታደርግ
“በፊቱ” የሚለው በእግዚአብሔር ፊት ሲሆን አንድ ሰው በእግዚአብሔር በዓይኑ ፊት ቆሞ አንድ ነገር እንደምፈጽም የሚናገር ነው። አማራጭ ትርጉም፡- እግዚአብሔር የሚቀበለውን መልካም ነገር አድርጉ ወይም እግዚአብሔር የሚፈልገውን ነገር አድርጉ

Exodus 15:27

• ወደ ኤሊም መጡ
ውሃና መልካም አየር እንዲህም ትላልቅ ዛፎች ያሉበት ቦታ ነው።

• ሰባ የዘንባባ ዛፎች
“ዘንባባ” የተባለው በርግጥ ዘንባባ ሳይሆን ተምር ነው። ተምር በመልኩ ከዘንባባ ጋር ስለሚመሳሰል አማርኛው ትርጉም ዘንባባ ብሎታል። በሌላ አገላለጽ፡- ሰባ የተምር ዛፎች

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 16

1 የእስራኤል ማኅበር አባላት ከኤሊም ተንሥተው፣ ከግብፅ ምድር ከወጡ በኋላ በሁለተኛው ወር ዐሥራ አምስተኛ ቀን በኤሊምና በሲና መካከል ወዳለው ወደ
ሲን ምድረ በዳ መጡ። 2 በዳው ውስጥም ጠቅላላ የማኅበሩ አባላት በሙሴና በአሮን ላይ አጒረመረሙ። 3 ሙሴንና አሮንንም፣ “በሥጋ ምንቸቶች ዙሪያ
ተቀምጠን እስክንጠግብ ምግብ በምንበላበት በግብፅ ምድር በእግዚአብሔር እጅ ምነው በሞትን ኖሮ፤ ከዚያ አውጥታችሁ ወደዚህ ምድረ በዳ ያመጣችሁን
መላውን ማኅበራችንን በረኃብ ልትጨርሱ ነውና” አሏቸው። 4 ሙሴን እንዲህ አለው፤ “እንጀራ ከሰማይ አዘንብላችኋለሁ። በሕጌ የሚመሩ ወይም የማይመሩ
መሆናቸውን እንድፈትናቸው፣ ሕዝቡ ይውጡና በየቀኑ ለአንድ ቀን የሚሆነውን ይሰብስቡ። 5 ቀን በየቀኑ ከሚሰበስቡት ዕጥፍ ይሰብስቡ፤ ያመጡትንም
ያዘጋጁ።” 6 ከዚያም ሙሴና አሮን ለእስራኤል ሕዝቡ ሁሉ እንዲህ አሉ፤ “ከግብፅም ምድር ያወጣችሁ እግዚአብሔር እንደ ሆነ ማታ ታውቃላችሁ። 7 በእርሱ
ላይ ያጒረመረማችሁትን ሰምቶአልና፣ የእግዚአብሔርንም ክብር ጠዋት ታያላችሁ። በእኛ ላይ ልታጒረመርሙ እኛ ለእናንተ ምንድን ነን?” 8 ደግሞ እንዲህ አለ፤
በእርሱ ላይ ያጒረመረማችሁትን ሰምቶታልና፣ እግዚአብሔር ማታ ሥጋ፣ ጠዋትም ምግብ እስክትጠግቡ ሲሰጣችሁ፣ ይህን ታውቁታላችሁ። አሮንና እኔ ምንድን
ነን? የምታጒረመርሙት በእኛ ላይ ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ላይ ነው።” 9 ሙሴ አሮንን፣ “‘ጒርምርምታችሁን ሰምቶታልና ወደ እግዚአብሔር ፊት ቅረቡ’ በልህ
ለእስራኤል ሕዝብ ማኅበር ሁሉ ተናገር’” አለው። 10 አሮን ለእስራኤል ሕዝብ ማኅበር ሁሉ እንደ ተናገረ፣ ወደ ምድረ በዳው ተመለከቱ፤ እነሆም፣
የእግዚአብሔር ክብር በደመናው ውስጥ ታየ። 11 እግዚአብሔርም ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው፤ 12 “የእስራኤልን ሕዝብ ጒርምርምታ ሰምቻለሁ። እንዲህ
ብለህ ንገራቸው፤ ‘ማታ ሥጋ ትበላላችሁ፤ ጠዋት ደግሞ እንጀራ ትበሉና ትጠግባላችሁ። ከዚያም በኋላ እኔ አምላካችሁ እግዚአብሔር መሆኔን ታውቃላችሁ።
13 ላይ ድርጭቶች መጡና ሰፈሩን ሸፈኑት። በጠዋቱም የሰፈሩን ዙሪያ ጤዛ ተኝቶበታል። 14 ሲጠፋ፣ እንደ ዐመዳይ ያለ ስስ ቅርፊት በምድረ በዳው ላይ ታየ።
15 ሰዎች ሲያዩት፣ አንዳቸው ለአንዳቸው፣ “ምንድን ነው?” ተባባሉ። ምን እንደ ነበረ አላወቁምና። ሙሴም እንዲህ አላቸው፤ “ይህ እንድትበሉት እግዚአብሔር
የሰጣችሁ እንጀራ ነው። 16 እግዚአብሔር ይህን ትእዛዝ ሰጥቶአል፦ ‘ለመብላት የምትፈልጉትን መጠን በሕዝባችሁ ቊጥር ለያንዳንዱ ሰው አንድ ጎሞር
ሰብስቡ። የምትሰበስቡት እንደዚህ ነው፦ በድንኳናችሁ ውስጥ ለሚኖር ለእያንዳንዱ ሰው ለመብላት የሚበቃውን ሰብስቡ።’” 17 የተነገራቸውን አደረጉ።
አንዳንዶች የበለጠ፣ አንዳንዶችም ያነሰ ሰበሰቡ። 18 በጎሞር መጠን ሲለኩት፣ ብዙ የሰበሰቡት የተረፈ አላገኙም፤ ትንሽ የሰበሰቡትም ያጡትና የጎደለባቸው
አልነበረም። እያንዳንዱ ሰው የሰበሰበው ለፍላጎቱ የሚበቃውን ያህል ነበር። 19 “ማንም ሰው ለነገ ከእርሱ ምንም ማስተረፍ የለበትም” አላቸው። 20 ግን
ሕዝቡ ሙሴን አልሰሙትም። አንዳንዶቻቸው ከሰበሰቡት እስከሚቀጥለው ጠዋት የተወሰነ አስቀሩ፤ ያስቀሩት ምግብ ግን ተላ፣ ሸተተም። ሙሴ ተቆጣቸው።
21 የሰበሰቡት ጠዋት ጠዋት ነበር። እያንዳንዱ ሰው ለቀኑ የሚበቃውን ሰበሰበ። ፀሐይ ስትሞቅ ቀለጠ። 22 ቀን ለያንዳንዱ ሰው ሁለት ሁለት ጎሞር እንጀራ
አድርገው ዕጥፍ ሰበሰቡ። የማኅበረ ሰቡ አለቆችም በሙሉ መጥተው ለሙሴ ነገሩት። 23 “እግዚአብሔር ይህን ተናግሮአል፦ ‘ነገ ፍጹም ዕረፍት፣
ለእግዚአብሔር ክብር የተቀደሰ ሰንበት ነው። መጋገር የምትፈልጉትን ጋግሩ፤ መቀቀል የምትፈልጉትንም ቀቅሉ። ተርፎ የሚቀረውን ሁሉ እስከ ጠዋት ለራሳችሁ
አስቀምጡት’” አላቸው። 24 የተረፈውን ሙሴ በነገራቸው መሠረት እስከ ጠዋት አቆዩት። አልሸተተም፤ ትልም አልነበረበትም። 25 እንዲህ አለ፤ “ዛሬ
እግዚአብሔርን ለማክበር የተቀደሰ ሰንበት ነውና፣ ያስተረፋችሁትን ያን ምግብ ዛሬ ብሉት። ዛሬ ሜዳ ላይ አታገኙትም። 26 ቀኖች ትሰበስቡታላችሁ፤ ሰባተኛው
ቀን ግን የሰንበት ቀን ነው። በሰንበት ቀን መና የለም።” 27 ቀን አንዳንዶች መና ሊሰበስቡ ወጡ፣ ነገር ግን ምንም አላገኙም። 28 ሙሴን እንዲህ አለው፤
“ትእዛዛቴንና ሕገጋቴን ለመጠበቅ እንቢ የምትሉት እስከ መቼ ነው? 29 በሉ፤ እግዚአብሔር ሰንበትን ሰጥቶአችኋል። ስለዚህ በስድስተኛው ቀን የሰጣችሁ
ለሁለት ቀን የሚሆን እንጀራ ነው። ከእናንተ እያንዳንዱ በገዛ ስፍራው ይቆይ፤ በሰባተኛው ቀን ማንም ሰው ከስፍራው መውጣት የለበትም።” 30 በሰባተኛው ቀን
ዐረፉ። 31 ምግቡን “መና” ብለው ጠሩት። ምግቡም እንደ ድንብላል ዘር ነጭ፣ ጣዕሙም በማር በስሱ እንደ ተጋገረ ቂጣ ነበረ። 32 ሙሴም፣ “እግዚአብሔር
ያዘዘው ይህ ነው፦ ‘ከግብፅ ምድር ካወጣኋችሁ በኋላ በምድረ በዳ ያበላኋችሁን እንጀራ ልጆቻችሁ ማየት እንዲችሉ፣ አንድ ጎመር መና ለትውልዶቻችሁ ሁሉ
ይቀመጥ’ አለ። 33 አሮንን፣ “አንድ ማሰሮ ውሰድና አንድ ጎሞር መና አስቀምጥበት፤ ለትውልዶች ሁሉ ተጠብቆ እንዲቆይም በእግዚአብሔር ፊት
አስቀምጠው” አለው። 34 ሙሴን ባዘዘው መሠረት፣ አሮን መናውን በምስክሩ ፊት አስቀመጠው። 35 ወደሚኖሩበት ምድር እስከሚመጡ ድረስ አርባ ዓመት
መና በሉ። ወደ ከነዓን ምድር ድንበር እስከሚመጡ ድረስ የተመገቡት እርሱን ነው። 36 አንድ ጎመር የኢፍ አንድ ዐሥረኛ ነው።

Exodus 16:1

• ሲን ምድረ በዳ መጡ
“ሲን” የምድረ በዳው ስም ነው፤

• በሁለተኛው ወር ከወሩም በአሥራ አምስተኛው ቀን
በሁለተኛው ወር በአስራ አምስተኛ ቀን

• የእስራኤልም ልጆች ማኅበር ሁሉ
ይህ ግነታዊ ዘይቤ አገላለጽ ሲሆን “እስራኤላውያን ሁሉ” (ጠቅላይ እና ግነታዊ ዘይቤ)

• አንጎራጎሩ
አጒረመረሙ ወይም ተቆጡ ወይም ተናደዱ

• ምነው በሞትን
ይህ አገላለጽ አሁን ባለንበት ሁኔታ ውስጥ ከመጨናነቅ እዚያው ሞተን ቢሆን ይሻለን ነበር ብለው ተናገሩ። አማራጭ ትርጒም፦ ምነው በእግዚአብሔር (ያህዌ) እጅ ሞተን ባረፍነው ኖሮ ወይም ምነው በግብጽ ሳለን እግዚአብሔር በገደለን ኖሮ

• በእግዚአብሔር እጅ
“በእግዚአብሔር እጅ” የሚለው በእግዚአብሔር አሰራር ወይም እርምጃ የሚል ፍች አለው።

Exodus 16:4

• እነሆ ከሰማይ እንጀራን አዘንብላችኋለሁ
እግዚአብሔር ከሰማይ የሚልከውን ምግብ ከመዝነብ ጋር አነጻጽሯል። በሌላ አገላለጽ፦ ከሰማይ ምግብ እንደ ዝናብ እልክላችኋለሁ /እሰጣችኋለሁ/። “እንጀራ” የሚለው አንድ የተወሰነ የምግብ ዓይነት ይገልጻልና በአከባቢው የተለመደ ማንኛውንም የምግብ ዓይነት መጠቀም ይቻላል።

• በሕጌ ይሄዱ ወይም አይሄዱ እንደሆነ
ህጌን ይታዘዙ ወይም አይታዘዙ እንደሆነ ማለት ነው

• ህጌን
ትዕዛዜን ማለት ነው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Exodus 16:6

• በእኛም ላይ የምታንጎራጉሩ እኛ ምንድር ነን?
ሙሴና አሮን ይህን አጋናኝ ጥያቄ የጠየቁት ህዝቡ በእነርሱ ላይ ማጉረምረማቸው ስንፍና ወይም ሞኝነት እንደሆነ ለማሳየት ነው። በአጋናኝ ጥያቄ ወይም በመደበኛ ዐረፍተ ነገር መተርጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- በእኛ ላይ የምታጉረመርሙት እኛ ምን ስለሆንን ነው? ወይም በእኛ ለማጉረምረም እኛ ብቁ ሰዎች አይደለንም

• እንጀራን እግዚአብሔር ይሰጣችኋል
ሙሴ “ምግብ” በማለት ፋንታ “እንጀራ ወይም ዳቦ” ይላል። ይህን ከሰማይ የሚሰጣቸውን ምግብ እንደ ሌሎቹ የምግብ ዓይነት ሁልጊዜ ይበሉታል።

• እኛም ምንድር ነን?
ሙሴ ይህን አጋናኝ ጥያቄ የጠየቃቸው እርሱና አሮን ህዝቡ የፈለጉትን ነገር ለመስጠት እንደማይችሉ ለመግለጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- እኔና አሮን እናንተ የምትፈልጉን ነገር መስጠት አንችልም

• ማንጎራጎራችሁ በእግዚአብሔር ላይ ነው እንጂ በእኛ አይደለም
ህዝቡ ያጉረመረሙት የእግዚአብሔር አገልጋዮች በሆኑት በሙሴና በአሮን ላይ ነበር። በሙሴና በአሮን ላይ ማጉረምረም በተዘዋዋሪ በእግዚአብሔር ላይ እንደማጉረምረም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- በእኛ ላይ ስታጉረመርሙ በእግዚአብሔር ላይ ማጉረምረማችሁ እንደሆነ እወቁ ወይም ማጉረምረማችሁ በእኛ ላይ ሳይሆን በርግጥ በእግዚአብሔር ላይ ነው

Exodus 16:9

• እነሆም
ይህ “እኔሆ” የሚለው ቃለ ህዝብ አንድ አስደናቂ ነገር እንዳየ ለማመልከት ወይም ትኩረት ለመሳብ ነው

• ማለዳም እንጀራን ትጠግባላችሁ
ሙሴ “ምግብ” በማለት ፋንታ “እንጀራ ወይም ዳቦ” ይላል። ይህን ከሰማይ የሚሰጣቸውን ምግብ እንደ ሌሎቹ የምግብ ዓይነት ሁልጊዜ ይበሉታል። አማራጭ ትርጉም፡- በማለዳ/ጧት/ የምትፈልጉትን ያህል ምግብ ትጠግባላችሁ

Exodus 16:13

• እንዲህም ሆነ
ይህ አገናኝ ሀረግ በታሪኩ ውስጥ ያለውን በጣም አስፈላጊውን ክፍል ለይቶ ያሳያል። በአንተ ቋንቋ እንዲህ ባለሁ ጉዳይ ላይ አገልግሎት የሚሰጥ ቃል ካለ መጠቀም ይችላል።

• ድርጭቶች
ትናንሽ የሆኑ የወፍ ዝሪያዎች ናቸው፤

• ደቃቅ ውርጭ
በጊዜው ለነበሩ ሰዎች “ውርጭ” ማለት ምን ማለት እንደሆነ ግልጽ ነው። በአማርኛ ውርጭ የሚለው ቃል ወደ ከባድ ብርድ ያደላል። ነገር ግን “ውርጭ” እንደ በረዶ የመጋገር ባህርይ ያለው ስለሆነ አመዳይ ወይም እንደ ቅርፍት የተጋገረ ነገር ነው። አማራጭ ትርጉም፡- ዐመዳይ ይመስል ነበር ወይም አመዳይ የሚመስል የተጋገረ ነገር

• እግዚአብሔር የሰጣችሁ እንጀራ
ሙሴ “ምግብ” በማለት ፋንታ “እንጀራ ወይም ዳቦ” ይላል። ይህ ከሰማይ የሚሰጣቸው ምግብ እንደ ሌሎቹ የምግብ ዓይነቶች ሁልጊዜ ይበሉታል። አማራጭ ትርጉም፡- እግዚአብሔር የሰጣችሁ እንጀራ ወይም ዳቦ፥ ምግብ

Exodus 16:16

አገናኝ ዐረፍተ ነገር፡- ሙሴ እግዚአብሔር ስለምሰጠው ምግብ ለህዝቡ መናገሩን ቀጥሏል።• አንድ ጎሞር
አንድ ጎሞር ወደ ሁለት ሊትር ያህል ነው

Exodus 16:22

• እንዲህም ሆነ
ይህ ሀረግ በታሪኩ ውስጥ አዲስ ሀሳብ እየገባ ወይም እየጀመረ ስለመሆኑ ለማሳየት ነው። በቁጥር 22-23 ድረስ ባለው ክፍል በስድስተኛውና በሰባተኛ ቀን ህዝቡ መናውን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ያሳያል። በአንተ ቋንቋ እንዲህ ያለ አገናኝ ሀረግ ካለ መጠቀም ጥሩ ነው።

• ነገ ዕረፍት ነው
ሥራ የማይሰራበትና እረፍት የሚደረግበት ቀን

Exodus 16:24

• አልሸተተም
በስብሶ መሽተት አልጀመረም

• የእግዚአብሔር ሰንበት ዛሬ ነውና ብሉት
ዛሬ ሰንበት ስለሆነ እግዚአብሔርን ለማከበር ብቻ ይውላል

Exodus 16:26

• ሰባተኛው ቀን ግን
ነገር ግን በቀን ሰባት

• መና
እግዚአብሔር በየቀኑ ወይም በየማለደኣ ለሰጣቸው ምግብ እስራኤላውያን የሰጡት ስም ነው።

• በእርሱ አይገኝም
ምንም ምግብ አይኖርም ወይም ምንም ነገር አይኖርም

Exodus 16:28

አጠቃላይ ዕይታ፡- እግዚአብሔር ለሙሴ መናገሩን ቀጥሏል።• ትእዛዞቼንና ሕጎቼን ለመጠበቅ እስከ መቼ እንቢ ትላላችሁ?
እግዚአብሔር ይህን አጋናኝ ጥያቄ የጠየቀ ህዝቡ የእግዚአብሔርን ትዕዛዞች ስላልታዘዙ እነርሱን ለመተቸት ወይም ለመገሰጽ ነው። ይህን አጋናኝ ጥያቄ በመደበኛ ዐረፍተ ነገር ስንተረጉም፡- እናንተ እስራኤላውያን ትዕዛዞቼንና ህጎቼን ለመታዘዝ ፈቃደኛ አይደላችሁም

• እግዚአብሔር ሰንበትን እንደ ሰጣችሁ እዩ
እግዚአብሔር (ያህዌ) ሰንበትን የሰጣችሁ እንድታርፉ መሆኑን ልብ በሉ/ አስተውል/

• በስድስተኛው ቀን የሁለት ቀን እንጀራ ሰጣችሁ
በስድስተኛው ቀን ለሁለት ቀን የሚበቃ ወይም የሚሆን ምግብ ስለምሰጣችሁ

Exodus 16:31

• እንደ ድንብላል ዘር ነጭ ነው
የድንብላል ዘር ከቅመም ዘሮች አንዱ ሲሆን ምግብ ጣዕም እንዲኖረው የሚያደርግ ነው

• እንደ ማር ቂጣ ነው
በጣም ቀጭን ቂጣ ወይም እንደ እንጀራ በቀጭኑ የተጋገረ ነገር ነው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• ጎሞር
አንድ ጎሞር ወደ ሁለት ሊትር ያህል ነው

Exodus 16:33

• ጎሞርም የእፍ መስፈሪያ አሥረኛ ክፍል ነው
ጎሞርና እፍ ሁለቱም መለኪያዎች ናቸው። እፍ ወደ ሀያ ኪሎ ግራም ሲመዝን ጎሞር ሁለት ኪሎ ግራም ይመዝናል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 17

1 የእስራኤል ማኅበር የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመከተል ከሲን ምድረ በዳ ተነሡ፤ በራፊዲምም ሰፈሩ፤ ነገር ግን ሕዝቡ የሚጠጡት ውሀ አልነበረም። 2
ሕዝቡ ሙሴን ወቀሡት፤ “የምንጠጣው ውሀ ስጠን” ብለውም ተናገሩት። ሙሴም፣ “ለምን እኔን ትጣሉኛላችሁ? እግዚአብሔርንስ ለምን ትፈታተኑታላችሁ?”
አላቸው። 3 ያ ሕዝቡ ውሀ በጣም ጠምቷቸው ስለ ነበር በሙሴ ላይ አጕረመረሙ። እንዲህም አሉት፤ “እኛንና ልጆቻችንን፣ ከብቶቻችንንም በውሀ ጥም
ለመፍጀት ከግብፅ ለምን አወጣኸን?” 4 እነዚህን ሰዎች ምንድን ነው ማድረግ ያለብኝ? በድንጋይ ሊወግሩኝ ተዘጋጅተዋል” በማለት ወደ እግዚአብሔር ጮኸ።
5 እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፤ “ከእስራኤል ሽማግሌዎች አንዳንዶችን፣ ወንዙን የመታህበትንም በትር ያዝና ከሕዝቡ ፊት ቀድመህ ሂድ። 6 ኮሬብ
ባለው ዐለት ላይ እኔ ከፊትህ እቆማለሁ፤ ዐለቱንም ትመታዋለህ። ከእርሱም ሕዝቡ የሚጠቱት ውሀ ይወጣል።” ሙሴም በእስራኤል ሽማግሌዎች ፊት
የታዘዘውን አደረገ። 7 ስላጕረመረሙና “እግዚአብሔር በመካከላችን አለ ወይስ የለም?” በማለት እግዚአብሔርን ስለ ተፈታተኑት ያን ስፍራ ማሳህና መሪባ ብሎ
ጠራው። 8 መጥተው እስራኤልን ራፊዲም ላይ ወጉ። 9 ስለዚህም ሙሴ ኢያሱን፣ “ጥቂት ሰዎችን ምረጥና ውጣ፤ ከአማሌቃውያን ጋርም ተዋጋ። ነገ እኔ
የእግዚአብሔን በትር ይዤ በኮረብታው ዐናት ላይ እቆማለሁ” አለው። 10 ሙሴ ባዘዘው መሠረት አማሌቃውያን ተዋጋቸው፤ ሙሴ፣ አሮንና ሖርም ወደ ኮረብታው
ዐናት ወጡ። 11 እጁን ወደ ላይ ሲያነሣ፣ እስራኤላውያን ድል ያደርጉ ነበር፤ እጁን ሲያወርድ ግን አማሌቃውያን ለማሸነፍ ይጀምሩ ነበር። 12 የሙሴ እጆች
እየደከሙ ሲሄዱ፣ አሮንና ሖር ድንጋይ ወስደው እንዲቀመጥበት ከእርሱ ሥር አስቀመጡለት። በዚያውም ጊዜ አሮንና ሖር አንዳቸው በአንድ ጎኑ፣ የቀረውም
በሌላው ጎኑ በኩል በመሆን የሙሴን እጆች ወደ ላይ ደግፈው ያዙ። የሙሴ እጆችም ፀሐይ እስክትገባ ድረስ ጠንክረው ቆዩ። 13 ስለዚህም ኢያሱ
አማሌቃውያንን በሰይፍ ድል አደረጋቸው። 14 እግዚአብሔር ሙሴን፣ “የአማሌቃውያንን መታሰቢያ ከሰማይ በታች ሙሉ በሙሉ ስለምደመስስ፣ ይህን
በመጽሐፍ ጽፈህ ኢያሱ እየሰማ አንብበው” አለው። 15 ሙሴም መሠዊያ ሠርቶ፣ “እግዚአብሔር አርማዬ ነው” ብሎ ሰየመው። 16 “እጅ ወደ እግዚአብሔር
ዙፋን ተነሥቶአልና፣ እግዚአብሔር በአማሌቃውያን ላይ ከትውልድ እስከ ትውልድ ጦርነት ያደርጋል” አለ።

Exodus 17:1

• ሲን ምድረ በዳ
“ሲን” የምድረ በዳው ስም ነው፤ (ዘጸአት 16፡1 ተመልከት)

• በራፊዲምም ሰፈሩ
በጉዞ ላይ ሰዎች የሚያርፉበት ወይም የሚቀመጡበት ሥፍራ ነው፤

• ለምን ትጣሉኛላችሁ? እግዚአብሔርንስ ለምን ትፈታተናላችሁ?
ሙሴ እነዚህን ጥያቄዎች የጠየቃቸው ህዝቡን ለመገሰጽ ወይም ለመኮነን ነው። ይህ አጋናኝ ጥያቄ በመደበኛ ዐረፍተ ነገር ምተርጎምም ይቻላል፤ ከእኔ ጋር ልትጣሉ አይገባችሁም፤ እግዚአብሔርንም (ያህዌን) ልትፈታተኑ አያስፈልጋችሁም

• እኛንና ልጆቻችንን ከብቶቻችንንም በጥማት ልትገድል ለምን ከግብፅ አወጣኸን?
እስራኤላውያን ይህንን እአጋናኝ ጥያቄ የጠየቁት በምድረ በዳ ልገድላቸው እንዳመጣቸው አድርገው ሙሴን ለመክሰስ ነው። ይህን አጋናኝ ጥያቄ በመደበኛ ዐረፍተ ነገር መተርጎምም ይቻላል፦ አንተ ከግብጽ ምድር ያወጣኸን እኛን፥ ልጆቻችንን እና ከብቶቻችንን በውሃ ጥም ለመፍጀት ወይም ለመግደል ነው

Exodus 17:4

• በሕዝቡ ፊት አለፍ
ከሕዝቡ ቀድም ብለህ ወደ ፊት ሂድ ወይም ከህዝቡ ፊት አልፈህ ሂድ

• ማሳህ . . . መሪባ ብሎ ጠራው
በምድረ በዳ ያለ ቦታ ሲሆን የስሙ ትርጉም “መፈታተን” ማለት ነው፤ “መሪባ” በምድረ በዳ ያለ ሥፍራ ሲሆን የስሙ ትርጉም “ማጉረምረም” ማለት ነው።

Exodus 17:8

• ራፊዲምም
በምድረ በዳ ያለ ሥፍራ ሲሆን ሰዎች በጉዞ ላይ ሲሆኑ የሚያርፉበት ወይም የሚቀመጡበት ሥፍራ ነው፤

• ኢያሱም . . . ከአማሌቅም ጋር ተዋጋ
ኢያሱ ራሱንና ለውጊያ የመረጣቸውን እስራኤላውያንን ወክሎ ቀርቧል። አማራጭ ትርጉም፦ ኢያሱና እርሱ የመረጣቸው ሰዎች አማሌቃውያንን ወጉት

• ሖር
የሙሴና የአሮን ጓደኛ

Exodus 17:11

• እስራኤል ድል ያደርግ ነበር . . . አማሌቅ ድል ያደርግ ነበር
እስራኤልና አማሌቅ ከሁለቱም ወገን ለውጊያ የተሰለፉ ሰዎችን የሚመለከት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ እስራኤላውያን ድል ያደርጉ ነበር . . . አማሌቃውያን ያሸንፉ ነበር

• የሙሴ እጆች ግን ከብደው ነበር
ፀሐፊው የሙሴ እጆች መድከማቸውን ለማሳየት ሲፈልግ እንደ ከበዱ አድርጎ ይገልጻል፤ በሌላ አገላለጽ፦ የሙሴ እጆች ደክመው ወይም ዝለው ነበር

• በሰይፍ ስለት አሸነፈ
በሰይፍ ተዋግቶ ድል አደረገ

Exodus 17:14

• የአማሌቅን ዝክር ከሰማይ በታች ጨርሼ እደመስሳለሁና
እግዚአብሔር የአማሌቅን መደምሰስ ሲገልጽ የአንድን ሰው የማሰብ አቅምን ከማጥፋት ጋር ሲያነጻጽር ይታያል። አንድ ሰው ወይም ቡድን ወይም ማህበረሰብ ፈጽሞ ሲጠፋ የምያስታውሳቸው ወይም መታሰቢያ ይጠፋል። በሌላ አገላለጽ፦ እኔ አማሌቃውያንን ፈጽሞ አጠፋለሁ ወይም እደመስሳለሁ (ተለዋጭ ዘይቤ)

• እጁን በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ ስለጫነ
እጅ የማንሳት ልምምድ የሚታወቀው ሰዎች መሀላ ሲፈጽሙ ወይም ቃል ኪዳን ሲገቡ እጃቸውን ሲያነሱ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ ምክንያቱም እጆች ወደ እግዚአብሔር (ያህዌ) ዙፋን ተዘርግተዋል ወይም ምክንያቱም ሙሴ እጁን ወደ እግዚአብሔር (ያህዌ) ስላነሳ

• በአማሌቅ
በአማሌቃውያን ላይ ወይም በአማሌቅ ሰዎች ላይ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 18

1 ካህን፣ የሙሴ ዐማት ዮቶር ለሙሴና ለሕዝቡ ለእስራኤላውያን እግዚአብሔር ያደረገውን ሁሉ ሰማ። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ ያወጣቸው
መሆኑን ዮቶር ሰምቶ ነበር። 2 ሙሴ ወደ ቤት ከመለሳት በኋላ፣ የሙሴ ዐማት ዮቶር የሙሴን ሚስት ሲፓራን፣ 3 ምድር ባዕድ ነበርሁ” ሲል ጌርሳም ብሎ
የጠራውንና ሌላውንም ልጅ ተቀብሏቸው ነበር። 4 “የአባቶቼ አምላክ ረድቶኛል፤ ከፈርዖንም ሰይፍ አድኖኛል” ብሎ ነበርና፣ የሌላው ልጁ ስም አልዓዛር ነው። 5
ዐማት ዮቶር ከሙሴ ልጆችና ከሚስቱ ጋር በምድረ በዳው ውስጥ በእግዚአብሔር ተራራ አጠገብ ሰፍሮ ወደ ነበረው ወደ ሙሴ መጣ። 6 ሙሴን፣ “እኔ
ዐማትህ፣ ዮቶር ከሚስትህና ከልጆችህ ጋር ወደ አንተ እየመጣሁ ነው” አለው። 7 ዐማቱን ሊቀበለው ወጣ፤ ሰገደ፤ ሳመውም። ስለ እያንዳንዳቸው ደኅንነት
ተጠያይቀው ወደ ድንኳኑ ውስጥ ገቡ። 8 ሙሴም እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ሲል በፈርዖንና በግብፃውያን ላይ ያደረገውን በሙሉ፣ በመንገድም በእነርሱ
ላይ የደረሰባቸውን ችግር ሁሉና እግዚአብሔር እንዴት እንደታደጋቸው ለዐማቱ ነገረው። 9 ዮቶር እስራኤላውያንን ከግብፃውያን እጅ በመታደግ እግዚአብሔር
ባደረገው መልካም ነገር ሁሉ ተደሰተ። 10 እንዲህ አለ፤ “ከግብፃውያን እጅና ከፈርዖን እጅ አድኖአችኋል፤ ሕዝቡንም ከግብፃውያን እጅ ታድጎአቸዋልና
እግዚአብሔር ይመስገን። 11 እግዚአብሔር ከአማልክት ሁሉ ታላቅ እንደ ሆነ አሁን ዐውቃለሁ፤ ምክንያቱም ግብፃውያን እስራኤላውያንን በትዕቢት ይዘዋቸው
በነበረ ጊዜ፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን ታድጎአል።” 12 ዐማት ዮቶር የሚቃጠል መሥዋዕቶችን ለእግዚአብሔር አቀረበ። አሮንና የእስራኤል አለቆች ሁሉ ከሙሴ
ዐማት ጋር በእግዚአብሔር ለመብላት መጡ። 13 በሚቀጥለው ቀን ሙሉ ሕዝቡን ሊዳኝ ተቀመጠ። ሕዝቡ ከጠዋት እስከ ማታ ድረስ በእርሱ ዙሪያ ቆሙ። 14
የሙሴ ዐማት ሙሴ ለሕዝቡ ያደረገውን ሁሉ ተመልክቶ፣ “ምን እያደረግህ ነው? ብቻህን ለምን ትቀመጣለህ? ሰዎችስ ሁሉ ከጧት እስከ ማታ ድረስ ለምን
በአንተ ዙሪያ ይቆማሉ?” አለው። 15 ዐማቱን እንዲህ አለው፤ “ሰዎቹ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመጠየቅ ወደ እኔ ይመጣሉ። 16 ሲኖራቸው፣ ወደ እኔ ይመጡና
በመካከላቸው ላለው ችግር ውሳኔ እሰጣለሁ፤ የእግዚአብሔርን ሕገጋትና ሥርዐትም አስተምራቸዋለሁ።” 17 ዐማቱም ሙሴን መልሶ እንዲህ አለው፤
“የምታደርገው ተገቢ አይደለም። 18 ዐብረውህ ያሉ ሰዎች በእውነት ራሳችሁን ታደክማላችሁ። ይህ ለአንተ ከባድ ሸክም ነው። ይህን ተግባር ብቻህን ማከናወን
አትችልም። 19 ስማኝ። ምክር እሰጥሃለሁ፤ እግዚአብሔርም ከአንተ ጋር ይሆናል፤ ምክንያቱም አንተ በእግዚአብሔር ፊት የሕዝቡ ወኪል ነህ፤ አቤቱታቸውንም
ወደ እግዚአብሔር ታቀርባለህ። 20 ሥርዐታትና ሕገጋት ልታስተምራቸው፣ የሚሄዱበትን መንገድና የሚሠሩትን ሥራም ልታሳያቸው ይገባል። 21 እግዚአብሔርን
የሚፈሩ ችሎታቸውን፣ ኢፍትሓዊ ጥቅምን የሚጠሉ የእውነት ሰዎችንከሕዝቡ ሁሉ ምረጥ። ዕነርሱን መሪዎች እንዲሆኑ በሕዝቡ ላይ ሸለቆች፣ መቶ አለቆች፣
ዐምሳ አለቆችና ዐሥር አለቆች አድርገህ ሹማቸው። 22 ጉዳዮችን ሁሉ በሚመለከት ሕዝቡን የሚዳኙት እነርሱ ይሆናሉ፤ ከባድ ከባድ ጉዳዮችን ግን ወደ አንተ
ያቀርባሉ። አነስተኛ ጉዳዮችን ሁሉ በሚመለከት፣ እነርሱ ራሳቸው ውሳኔ ሊሰጡባቸው ይችላሉ። በዚህ መንገድ ሥራው ለአንተ ይቀልልሃል፤ እነርሱም ሸክሙን
ከአንተ ጋር ይሸከማሉ። 23 ይህን ብታደርግና እግዚአብሔርም እንደዚሁ እንድታደርግ ቢያዝዝህ፣ በርትተህ መሥራት ትችላለህ፤ መላው ሕዝብም ረክቶ ወደ ቤት
መሄድ ይችላል።” 24 የዐማቱን ምክር በመስማት የነገረውን ሁሉ አደረገ። 25 ሙሴ ከእስራኤል ሁሉ ችሎታ ያላቸውን ሰዎች መረጠ፤ ሸለቆች፣ መቶ አለቆች፣
ዐምሳ አለቆችና ዐሥር አለቆች አድርጎም የሕዝቡ መሪዎች እንዲሆኑ ሾማቸው። 26 በቀላል ጉዳዮች ሕዝቡን ይዳኙ ነበር። ከበባድ ጉዳዮችን ለሙሴ አቀረቡ፤
ትንንሽ ጉዳዮችን ሁሉ ግን እነርሱ ለራሳቸው ብያኔ ሰጡባቸው። 27 በኋላ ሙሴ ዐማቱን አሰናበተው፤ ዮቶርም ወደ ገዛ ምድሩ ተመልሶ ሄደ።

Exodus 18:1

• የሙሴ አማት
የሙሴ የሚስቱ አባት

• የሙሴን ሚስት ሲፓራን ሁለቱንም ልጆቿን ወሰደ
ይህ ሀረግ ሁለት ፍችዎችን ይዟል፦ 1) ዮቶር ሲፖራንና ሁለቱን ልጆቹን ወደ ሙሴ አመጣቸው 2) ዮቶር ሲፖራንና ሁለቱን ልጆች ወደ ቤት መልሶአቸው ነበር

• ዮቶር መልሶአት የነበረውን
ይህ አባባል ቀደም ብሎ ሙሴ የሰራውን ወይም ዮቶር ያደረገውን የሚያሳይ ነው። በሌላ አገላለጽ፦ ሙሴ ሚስቱን ወደ አማቾቹ ቤት ከላከ በኋላ

• ጌርሳም
የሙሴና የሲፖራ ልጅ ሲሆን የስሙ ትርጉም እንግዳ ወይም መጻተኛ ማለት ነው

• አልዓዛር
የሙሴና የሲፖራ ልጅ ሲሆን የስሙ ትርጉም እግዚአብሔር ረዳቴ ማለት ነው

• ከፈርዖንም ሰይፍ አዳነኝ
በፈርዖን ወይም በፈርዖን ሠራዊት ከመገደል መትረፉን ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ በፈርዖን ወይም በፈርዖን ሠራዊት ከመገደል/ከመሞት/ አዳነኝ።

Exodus 18:5

• በምድረ በዳ ወደ ሰፈረ
እርሱ ከእስራኤላውያን ጋር ወደ ሰፈረበት ወደ ምድረ በዳ

Exodus 18:7

• ሰገደም፥ ሳመውም
ሰዎች ታላቅ አክብሮትና ትህትናን እየሰጡ ስለመሆናቸው የሚያሳዩት እንደ ባህሉ በመሳምና እጅ በመንሳት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ ራሱን ዝቅ አድርጎ እጅ በመንሣት ሳመው

• ስለ እስራኤል ያደረገውን ሁሉ
እግዚአብሔር ለእስራኤል ሲል ያደረጋቸውን ነገሮች ሁሉ

• በመንገድም ያገኛቸውን ድካም ሁሉ
በመንገድ ላይ ስላጋጠማቸው መከራ ሁሉ ወይም የደረሰባቸውን ፈተና ሁሉ

Exodus 18:9

• ከግብፃውያንና ከፈርዖን እጅ ያዳናችሁ
“እጅ” አንድ ሰው አንድን ነገር ለማድረግ የሚያስችል ሀይል እንዳለው የሚገልጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ ከሀያላን ግብጻውያንና ከሀያሉ ፈርዖን ያተረፋችሁ/ያስመለጣችሁ/ያዳናችሁ/ (ወካይ ዘይቤ)

Exodus 18:13

• ይህ በሕዝቡ የምታደርገው ምንድር ነው?
ዮቶር ይህንን አጋናኝ ጥያቄ የጠየቀው ሙሴ የሚያደርገው ነገር ጥሩ ወይም ትክክል እንዳለሆነ ለማሳየት ነው። በትርጉም ውስጥ አጋናኝ ጥያቄውን እንዳለ ማምጣጥ ይቻላል ወይም ወደ መደበኛ ዐረረፍተ ነገር መቀየር ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ አንተ በህዝቡ ላይ ይህን ሁሉ ነገር ማድረግ አልነበረብህም ወይም ለህዝቡ የምታደርገው ይህ ሁሉ ነገር ምንድን ነው?

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• አንተ ብቻህን ስለ ምን ተቀምጠሃል?
“ተቀምጠሃል” የሚለው ቃል ወካይ ዘይቤ ሲሆን “ለፍርድ” ወይም “ለህዝቡ ፍርድ ለመስጠት” መቀመጡን ለማሳየት ነው። ዳኞች የሰዎችን ጉዳይ ለመስማት እና ለመዳኘት መቀመጣቸውን ሲገልጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ አንተ ብቻህን ትፈርዳለህ” ወይም “ህዝቡ ላይ እየፈረድክ ያለኸው አንተ ብቻ ነህ (ወካይ ዘይቤ)

• ሕዝቡ ሁሉ ከጥዋት ጀምሮ እስከ ማታ ድረስ በዙሪያህ ቆመው ሳሉ አንተ ብቻህን ስለ ምን ተቀምጠሃል?
ዮቶር ይህን አጋናኝ ጥያቄ የጠየቀው ሙሴ ብዙ ሥራ ብቻውን እየሰራ መሆኑን አጽንዖት ሰጥቶ ለመናገር ፈልጎ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ ይህ ሁሉ ሰው ከጧት እስከ ማታ ድረስ በአንተ በዙሪያ ቆሞ ሳለ አንተ ብቻህን በፍርድ ወንበር ላይ ለምን ትቀመጣለህ? ወይም ይህ ሁሉ ሰው ከጧት እስከ ማታ ድረስ በአንተ ዙሪያ ቆሞ ሳለ አንተ ብቻህን ለፍርድ መቀመጥ አይገባህም

Exodus 18:15

• ሕዝቡ እግዚአብሔርን ለመጠየቅ
ሕዝቡ /ሰዎች/ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ወይም ለመፈለግ/ለመረዳት/

Exodus 18:17

• ይህ ነገር ይከብድብሃል
ዮቶር ሙሴ የሚሰራው ሥራ ከባድ መሆኑ ለማመልከት አንድን ነገር ከመሸከም ጋር ያነጻጽራል። አማራጭ ትርጉም፦ ሥራው ከአቅምህ በላይ ነው (ተለዋጭ ዘይቤ)

• አንተ ከአንተም ጋር ያለው ሕዝብ ትደክማላችሁ
አንተ ራስህንም ሆነ ሕዝቡን በከንቱ ታደክማለህ

• አሁንም እመክርሃለሁ
“ምክር እሰጥሃለሁ” ወይም “አቅጣጫ እጠቅምሃለሁ”

• እግዚአብሔርም ከአንተ ጋር ይሆናል
“ከአንተ ጋር ይሆናል” የሚለው የእግዚአብሔር እርዳታ ወይም እግዚአብሔር እንደምረዳው ለመግለጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ እግዚአብሔር ይረዳሃል ወይም እግዚአብሔር ለሥራው ጥበብ ይሰጥሃል

• ነገራቸውንም ወደ እግዚአብሔር አድርስ
ዮቶር ሲናገር ሙሴ የህዝቡን ጥያቄ ወይም አቤቱታ ወደ እግዚአብሔር ለማድረስ ይዞ እንደምመጣ አድርጎ ይገልጻል። አማራጭ ትርጉም፦ አንተ ጥያቄአችውን ለእግዚአብሔር ተናገር/አሳውቅ/

• የሚሄዱበትን መንገድ የሚያደርጉትንም ሥራ ሁሉ አሳያቸው
ህዝቡ እንዴት መኖር እንዳለባቸውና ምን ማድረግ እንደሚገባቸውም መናገር ወይም ማሳየት አለብህ እንደማለት ነው

Exodus 18:21

አያያዥ ዐረፍተ ነገር፦ ዮቶር ንግግሩን ይቀጥላል •አንተም . . . ሰዎች ምረጥ
በተጨማሪ/ነገር ግን/ አንተ . . . ሰዎችን ምረጥ

• የሺህ አለቆችን፥ የመቶ አለቆችን፥ የአምሳ አለቆችን፥ የአሥርም አለቆችን
ይህ አባባል ሁለት ዓይነት ፍቺዎች ይኖሩታል፦ 1) እነዚህ ቁጥሮች በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ ያሉትን የሰዎች ቁጥር ወይም ብዛት አመልካች ናቸው፤ አማራጭ ትርጉም፦ “1000 ሰው ያለበት ቡድን፥ 100 ሰው ያለበት ቡድን፥ 50 ሰው ያለበት ቡድን እና 10 ሰው ያለበት ቡድን”፤ 2) እነዚህ ቁጥሮች በትክክል የሚታዩ ቁጥሮች ሳይሆኑ ምሳሌያዊ ናቸው፤ አማራጭ ትርጉም፦ “በጣም ትንሽ ሰው ቡድን መሪ፤ የትንሽ ሰው ቡድን መሪ፤ የብዙ ሰው ቡድን መሪ፤ በጣም ብዙ ሰው ቡድን መሪ”

• ሹምላቸው
በህዝቡ ላይ መፍረድ እንዲችሉ ሰይማቸው ወይም ሥልጣን ስጣቸው

• ታናሹንም ነገር ሁሉ እነርሱ ይፍረዱ
ከባድ ያልሆኑ ወይም ቀላል በሆኑ ነገሮች ላይ እነርሱ ይፍረዱ/ይወስኑ/

• አውራውን ነገር ሁሉ ወደ አንተ ያምጡት (ተለዋጭ ዘይቤ)
አስቸጋሪ የሆነውን ጉዳይ ሁሉ ለአንተ እንዲያቀርቡ /ለአንተ እንድነግሩ/
አድርግ ወይም ከአቅማቸው በላይ የሆነውን ከባድ ጉዳይ ወደ አንተ ያምጡት

• ከአንተ ጋር ሸክሙን ይሸከማሉ
ዮቶር ይህንን ሲናገር እነዚህ ሰዎች ከሙሴ ጋር አብረው አንድን ነገር ለመሸከምና እርሱን ለመርዳት የመጡ አስመሎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ ሥራውን በመሥራት ስለሚያግዙህ ሥራው ቀላል ይሆናል ወይም ከአንተ ጋር አብረው ስለሚሰሩ ሥራው ቀላል ይሆንልሃል

• ለአንተም ይቀልልልሃል
የሥራ ክብደቱ ለአንተ ቀላል ይሆናል ወይም የሥራ ጫና ይቀንስልሃል

Exodus 18:24

• ከእስራኤል ሁሉ አዋቂዎችን መረጠ
ፀሐፊው የሚናገረው አንድን ነገር ለማድረግ የሚያስችል አቅም ወይም ችሎታ እንጂ ዕውቀት አይደለም። ከእስራኤላውያን መካከል ችሎታ ያላቸውን ሰዎች መረጠ ወይም ከእስራኤላውያን መካከል ነገር የመለየት ችሎታ ያላቸውን መረጠ

• የሺህ አለቆችን፥ የመቶ አለቆችን፥ የአምሳ አለቆችን፥ የአሥርም አለቆችን
ኡህ አባባል ሁለት ዓይነት ፍቺዎች ይኖሩታል፦ 1) እነዚህ ቁጥሮች በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ ያሉትን የሰዎች ቁጥር አመልካች ናቸው፤ አማራጭ ትርጉም፦ “1000 ሰው ያለበት ቡድን፥ 100 ሰው ይለበት ቡድን፥ 50 ሰው ያለበት ቡድን እና 10 ሰው ያለበት ቡድን”፤ 2) እነዚህ ቁጥሮች በትክክል የሚታዩ ቁጥሮች ሳይሆኑ ምሳሌያዊ ናቸው፤ አማራጭ ትርጉም፦ “በጣም ትንሽ ሰው ቡድን መሪ፤ የትንሽ ሰው ቡድን መሪ፤ የብዙ ሰው ቡድን መሪ፤ በጣም ብዙ ሰው ቡድን መሪ”

• በሕዝቡም ላይ ሁልጊዜ ፈረዱ
እነርሱ ሁልጊዜ የሕዝብ ዳኞች ሆነው አገለገሉ/ያገለግሉ ነበር/

• የከበደባቸውንም ነገር ወደ ሙሴ አመጡ
አስቸጋሪ የሆኑትን ጉዳዮች ብቻ ወደ ሙሴ ያቀርቡ ነበር ወይም አስቸጋሪ በሆኑ ነገሮች ላይ ሙሴ እንዲፈርድ ወደ እርሱ ያመጡ ነበር

• ታናሹን ነገር ሁሉ ግን እነርሱ ፈረዱ
ቀላል በሆነው ነገር ላይ እነርሱ ራሳቸው ይወስኑ ነበር

• የህጉ መገለጥ
በዚህ ምዕራፍ የተገለጹ ነገሮች የሙሴን ህግ እንዲቀበሉ ህዝቡን የሚያዘጋጅ ነበር። ህጉን ለመቀበል ህዝቡ ህጉ የሚጠይቀውን እያንዳንዱን ነገር ለመማርና ለማድረግ ራሳቸውን ማዘጋጀት አለባቸው። የዚህ ምዕራፍ ክስተት ለእስራኤል አስፈላጊና ዋናው አካል ነበር።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 19

1 ወር፣ እስራኤላውያን ከግብፅ ምድር በወጡበት በዚያው ቀን ወደ ሲና ምድረ በዳ መጡ። **2** ከራፊዲም ከተነሡ በኋላ፣ ወደ ሲና ምድረ በዳ መጥተው በምድረ በዳው ውስጥ ከተራራው ፊት ለፊት ሰፈሩ። **3** ወደ እግዚአብሔር ወጣ። እግዚአብሔርም ከተራራው ጠርቶት እንዲህ አለው፤ **4** “ለያዕቆብ ቤት፣ ለእስራኤል ሕዝብ እንደዚህ ብለህ ተናገር፦ በግብፃውያን ላይ ምን እንዳደረግሁ ፣ እናንተንም በርግም ክንፎች እንዴት እንደ ተከከምኋችሁና ወደ ራሴ እንዴት እንዳመጣኋችሁ አይታችኋል። **5** ቃሌን በታዛዥነት ብትሰሙና ኪዳኔንም ብትጠብቁ፣ ከሕዝብ ሁሉ መካከል የእኔ ርስት ትሆናላችሁ፤ ምድር ሁሉ የእኔ ነውና። **6** እናንተ ለእኔ የካህናት መንግሥትና ቅዱስ ሕዝብ ትሆናላችሁ። ለእስራኤላውያን የምትነግራቸው ቃሎች እነዚህ ናቸው። **7** መጣ፤ የሕዝቡንም ሽማግሌዎች ጠርቶ እግዚአብሔር ያዘዘውን እነዚህን ቃሎች ሁሉ በፊታቸው ተናገረ። **8** ሁሉ በአንድነት፣ “እግዚአብሔር የተናገረውን ሁሉ እናደርጋለን” በማለት መልስ ሰጡ። ሙሴ ሕዝቡ የተናገሩትን ወደ እግዚአብሔር ለማቅረብ መጣ። **9** ሙሴንም፤ “እኔ ከአንተ ጋር ስነጋገር፣ መስማት እንዲችሉና አንተንም ሁልጊዜ እንዲያምኑህ፣ ወደ አንተ በከባድ ደመና እመጣለሁ” አለው። ሙሴም ሕዝቡ የተናገሯቸውን ቃሎች ለእግዚአብሔር ነገረው። **10** ሙሴን፣ “ወደ ሕዝቡ ሂድ። ዛሬና ነገ ለእኔ ቀድሳቸው፤ ልብሳቸውንም እንዲያጥቡ አድርግ። **11** ቀንም ይዘጋጁ፤ በሦስተኛው ቀን እኔ እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ እወርዳለሁና። **12** ዙሪያ ሁሉ ለሕዝቡ ወሰን አብጅና ለሕዝቡ እንዲህ በላቸው፤ ‘ወደ ተራራው እንዳትወጡ ወይም የተራራውን ግርጌ ጫፍ እንዳትነኩ ተጠንቀቁ። ተራራውን የነካ ይሞታል።’ **13** ዐይነቱን ሰው ማንም አይንካው። እንዲያውም የነካው በድንጋይ ይወገራል ወይም በቀስታ ይወጋል። ሰውም ሆነ እንስሳ ይሞታል። መለከቱ የማያቋርጥ ድምፅ ሲያሰማ፣ ሕዝቡ ወደ ተራራው መውጣት ይችላሉ” አለው። **14** ሙሴም ከተራራው ወደ ሕዝቡ ወረደ። ሕዝቡን ለእግዚአብሔር ቀደሳቸው፤ ልብሳቸውንም አጠቡ። **15** “በሦስተኛው ቀን ተዘጋጁ፤ ወደ ሚስቶቻችሁም አትጠጉ” አላቸው። **16** ቀን ጠዋት ላይ ነጋድጓድና የመብረቅ ብልጭታ፣ ከባድ ደመና እና ጉሉሕ የመለከት ድምፅ በተራራው ላይ ነበሩ። በሰፈሩ ውስጥ የነበሩ ሰዎች ሁሉ ተንቀጠቀጡ። **17** ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር እንዲገናኙ ሕዝቡን ከሰፈር አወጣቸው፤ በተራራው ግርጌም ቆሙ። **18** እግዚአብሔር በእሳትና በጢስ ወርዶበት ስለ ነበረ፣ የሲና ተራራ ሙሉ በሙሉ በጢስ ተሸፈነ። ጢሱ እንደ ምድጃ ጢስ ይወጣ ነበር፤ ጠቅላላ ተራራውም በኀይል ተናወጠ። **19** ድምፅ እየጨመረና እየጎላ ሲሄድ፣ ሙሴ ተናገረ፤ እግዚአብሔርም በድምፅ መለሰለት። **20** እግዚአብሔር በሲና ተራራ ጫፍ ላይ ወርዶ፣ ሙሴን ወደ ተራራው ጫፍ እንዲወጣ ጠራው። ሙሴም ወጣ። **21** ሙሴን እንዲህ አለው፤ “ለማየት ዐልፈው ወደ እኔ እንድይመጡ፣ ሂድና ሕዝቡን አስጠንቅቃቸው፤ አለዚያ ብዙዎች ይሞታሉ። **22** ወደ እኔ የሚቀርቡ ካህናትም ራሳቸውን ይቀድሱ፤ እንዳላጠፋቸውም ለእኔ መምጣት ራሳቸውን ያዘጋጁ።” **23** እግዚአብሔርን፣ “ሕዝቡ ወደ ተራራው መውጣት አይችሉም፤ ምክንያቱም ‘በተራራው ዙሪያ ወሰን አብጅና ለእግዚአብሔር ቀድሰው’ ብለህ አዝዘኸናል” አለው። **24** ሙሴን፣ “ከተራራው ወርደህ ሂድና አሮንን ክአንተ ጋር ይዘኸው ና፤ ካህናቱና ሕዝቡ ግን ወሰን ዐልፈው ወደ እኔ እንዲመጡ አትፍቀድላቸው፤ አለዚያ አጠፋቸዋለሁ” አለው። **25** ስለዚህ ሙሴ ወደ ሕዝቡ ሄዶ ይህንኑ ነገራቸው።

Exodus 19:1

• በሦስተኛውም ወር የእስራኤል ልጆች ከግብፅ ምድር ከወጡ በኋላ በዚያ ቀን . . .
እስራኤላውይ ወደ ሲና ምድረ በዳ የደረሱት በሶስተኛው ወር በመጀመሪያው ቀን ልክ ከግብጽ በወጡበት በዚያች ቀን ነበር። ይህ ማለት ከግብጽ የወጡበትና ወደ ምድረ በዳ የደረሱበት ቀን ተመሳሳይ ነበር ማለአት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ "በሶስተኛው ወር እስራኤላውያን ግብፅን ለቀው በወጡበት በዚያችው በተመሳሳይ ዕለት . . .

• ራፊድም
ይህ ሥፍራ የሚገኘው በሲና ምድረ በዳ ጫፍ አከባቢ እስራኤላውያን የሰፈሩበት ሥፍራ ነው (ዘጸአት 17፡1 ተመልከት)

Exodus 19:3

• የያቆብ ቤት
“የያዕቆብ ቤት” የሚለው የያዕቆብን ቤተሰብ እና ትውልዱን የሚመለከት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ የያዕቆብ ተወላጆች ለሆኑት

• ለያቆብ ቤት . . . ለእስራኤልም ልጆች
“የእስራኤል ልጆች” የሚለው ሀረግ የሚገልጸው “የያዕቆብ ቤት” የሚለውን የሚያብራራ ነው።

• በንስርም ክንፍ እንደ ተሸከምኋችሁ
እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ያደረገውን ጥበቃና ጥንቃቄ ሲገልጽ እርሱ ንስር እንደ ሆነና እነርሱን በክንፉ እንደ ተሸከማቸው አድርጎ ይገልጻል። አማራጭ ትርጉም፦ ንስር ጫጩቶችዋን በክንፎችዋ እንደምትሸከም እኔም እናንተን እንዴት እንደተሸከምኳችሁ

• ቃሌን በእውነት ብትሰሙ
“ቃሌን ብትሰሙ” የሚለው እንዲሁ መስማት ብቻ ሳይሆን መታዘዝንም ይጨምራል። በሌላ አገላለጽ፦ ቃሌን ብትሰሙና ለእኔም ብትታዘዙ

• ኪዳኔንም ብትጠብቁ
ቃል ኪዳኔ የምጠይቃችሁን ነገር ብትፈጽሙ

• ርስት ትሆኑልኛላችሁ
የእኔ ርስት ወይም ሀብት ትሆናላችሁ

• የካህናት መንግስት . . . ትሆኑልኛላችሁ **(ተለዋጭ ዘይቤ)**
እግዚአብሔር ህዝቡ ካህናት እንደሆኑ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ የመንግስት ህዝብ የሆናችሁ ለእኔ እንደ ካህናት ናችሁ ወይም የመንግስት ህዝብ የሆናችሁ እናንተ ለእኔ ካህናት የሚሰሩትን የምትሰሩ ናችሁ

Exodus 19:7

• ይህን ቃል ሁሉ በፊታቸው ተናገረ
ይህ ሀረግ የሚያሳየን ሙሴ ለህዝቡ ሲናገር ቃሉን ለፊታቸው እንደተናገረ አድርጎ ያቀርባል። አማራጭ ትርጉም፦ እነዚህን ቃሎች ሁለ ለእነርሱ ተናገረ

• እግዚአብሔር ያዘዘውን
እግዚአብሔር ለእርሱ የሰጠውን ትዕዛዝ

• ሙሴም የሕዝቡን ቃል ወደ እግዚአብሔር አደረሰ
ሙሴ እነርሱ ያሉትን መልሶ ወደ እግዚአብሔር (ያህዌ) ወሰደ ወይም ለእግዚአብሔር ሪፖርት አደረገ

• የሕዝቡን ቃል
“የህዝቡ ቃል” ህዝቡ የተናገሩትን የሚገልጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ ህዝቡ ያሉትን ወይም የተናገሩትን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Exodus 19:10

• ዛሬና ነገም ቀድሳቸው
የዚህ ሀረግ ትርጉም:- ራሳቸውን ቅዱስ እንዲያደርጉ ወይም እንዲለዩ ለህዝቡ ንገራቸው

• ለሦስተኛው ቀን ይዘጋጁ
ይህ ትዕዛዛዊ ሀረግ ሲሆን በሌላ አገላለጽ:- ህዝቡ ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ ትዕዛዝ ተሰጣቸው

Exodus 19:12

አጠቃላይ ዕይታ:- እግዚአብሔር ለሙሴ መናገሩን ቀጥሏል። •ለሕዝቡ በዙሪያው ወሰን አድርግላቸው
በህዝቡ ዙሪያ ደንበር ወይም ገደብ አድርግ ወይም ህዝቡ እንዳያልፉ ድንበር ወይም ገደብ አበጅላቸው

• ተራራውንም የነካ ፈጽሞ ይሞታል
ማንም ሰው ተራራውን ቢነካ በርግጥ ይሞታል ወይም ተራራውን የሚነካ ማንም ቢሆን ግደሉት

• የሚነካው ሁሉ ይወገራል ወይም በፍላጻ ይወጋል
ተራራውን የሚነካ በድንጋይ ተወግሮ ወይም በቀስት ተወግቶ ይሙት

• ሳያቋርጥ የመለከት ድምፅ ሲነፋ
ከፍ ባለ ድምፅ ወይም ለረጅም ጊዜ ጥሩንባ በተነፋ ጊዜ

Exodus 19:14

• ወደ ሴቶቻችሁ አትቅረቡ
ይህ በትህትና የተገለጸው ወደ ሌላ ሴት ሳይሆን ወደ ሚስቶቻቸው እንዳይቀርቡ ነው። አማራጭ ትርጉም:- ከሚስቶቻችሁ ጋር አትተኙ ወይም ከሚስቶቻችሁ ጋር ግብረ ሥጋ ግንኙነት አታድርጉ

Exodus 19:16

• እግዚአብሔር . . . ስለ ወረደበት
እግዚኢአብሔር ከተራራው ስለመጣ ወይም ስለወረደ

• እንደ እቶን ጢስ ያለ ጢስ ይወጣ ነበር
ጪሱ ከትልቅ የእሳት ምድጃ ወይም ከትልቅ የእሳት ቃጠሎ እንደሚወጣ ጪስ ነበር

• የእቶን ጢስ
በጣም ትልቅና የሚያቃጥል የእሳት ምድጃ

Exodus 19:19

• የቀንደ መለከቱም ድምፅ እጅግ በበረታና በጸና ጊዜ
የእምቢልታው ወይም የጥሩንባው ድምጽ እየበረታ ወይም እያየለ በመጣ ጊዜ

• እግዚአብሔርም በድምፅ መለሰለት **(**ወካይ ዘይቤ**)**
እዚህ ቦታ “ድምጽ” እግዚአብሔር የሚያሰማውን ድምጽ የሚመለከት ነው። የዚህ ሀረግ ፍቺው 1) እንደ መብረቅ እግዚአብሔር በትልቅ ድምጽ ተናግሯል 2) መብረቅ ድምጽ እንዲያወጣ በማድረግ 3) እግዚአብሔር ራሱ በከፍተኛ ድምጽ ተናገረ

• ሙሴን ወደ ተራራው ራስ ጠራው
ሙሴ ተራራው ላይ እንዲወጣ ጠየቀው/አዘዘው/

• ዳርቻውን እንዳያልፉ
የተወሰነውን ክልል ወይም ድንበር አልፈው እንዳይመጡ

Exodus 19:23

• ውረድ
ከተራራው ላይ ውረድ/ሂድ/

• አይተላለፉ
የተወሰነውን ክልል ወይም ድንበር አልፈው እንዳይመጡ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 20

1 እነዚህን ቃሎች እንዲህ በማለት ተናገረ፦ 2 ከግብፅ ምድር፣ ከባርነት ምድር ያወጣሁህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ። 3 ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት
አይኑሩህ። 4 በላይ በሰማይ ያለውን፣ ወይም በታች በምድር ያለውን፣ ከምድርም በታች በውሀ ውስጥ ያለውን የማንኛውንም ነገር የተቀረጸ ምስልና ሥዕል ለራስህ
ጣዖት አታብጅ። 5 አትስገድላቸው፤ አታምልካቸውም፤ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና። የሚጠሉኝን ሦስትና አራት ትውልድ በልጆች ላይ
ቅጣት በማምጣት የአባቶችን ኀጢአት እቀጣለሁ። 6 በሚወዱኝና ትእዛዛቴን በሚጠብቁት በሺዎች ላይ ግን የኪዳን ታማኝነት አሳያለሁ። 7 የአምላክህን
የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ አታንሣ፤ ስሜን በከንቱ የሚያነሣውን በደል ዐልባ አላደርገውምና። 8 እንድትቀድሰው፣ የሰንበትን ቀን ዐስብ። 9 ቀን ሥራ፤
ተግባርህንም ሁሉ አከናውን። 10 ቀን ለእኔ ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ሰንበት ነው። በሰንበት ቀን አንተም ወንድ ልጅህም፣ ሴት ልጅህም፣ ወንድ አገልጋይህም፣
ሴት አገልጋይህም፣ እንስሳትህም፣ በግቢህ ያለ እንግዳም ሥራ አትሠሩም። 11 እግዚአብሔር ሰማያትን፣ ምድርንና ባሕርን፣ በእነርሱ ውስጥ ያለውንም ሁሉ
በስድስት ቀን ፈጥሬ በሰባተኛው ቀን ዐርፌአለሁና። ስለዚህ እኔ እግዚአብሔር የሰንበትን ቀን ባረክሁት፤ ለራሴም ቀደስሁት። 12 እኔ እግዚአብሔር አምላክህ
በምሰጥህ ምድር ብዙ ጊዜ እንድትቆይ፣ አባትህንና እናትህን አክብር። 13 አትግደል። 14 አታመንዝር። 15 አትስረቅ። 16 በባልንጀራህ ላይ በሐሰት
አትመስክር። 17 የባልንጀራህን ቤት አትመኝ፤ የባልንጀራህን ሚስት፣ ወንድ አገልጋዩን፣ ሴት አገልጋዩን፣ በሬውን፣ አህያውን፣ ወይም የባልንጀራህ የሆነውን
ማንኛውንም ነገር አትመኝ።” 18 ሰዎች ሁሉ ነጎድጓዱንና መብረቁን አዩ፤ የመለከቱን ድምፅም ሰሙ፤ የሚጨሰውንም ተራራ ተመለከቱ። ሕዝቡ ይህን ሲያዩ፣
ተንቀጠቀጡ፤ ርቀውም ቆሙ። 19 ሙሴን፣ “አንተ ተናገረን፤ እኛም እንሰማሃለን፤ ነገር ግን እግዚአብሔር እንዲናገረን አታድርግ፤ አለዚያ እንሞታለን” አሉት።
20 ሙሴም ሕዝቡን፣ “አትፍሩ፤ ፈሪሀ እግዚአብሔር በእናንተ ዘንድ እንዲገኝና ኀጢአት እንዳትሠሩ ሊፈትናችሁ እግዚአብሔር መጥቶአልና” አላቸው። 21
ስለዚህ ሕዝቡ ርቀው ቆሙ፤ ሙሴም እግዚአብሔር ወዳለበት ወደ ጨለማው ተጠጋ። 22 ሙሴን እንዲህ አለው፤ “ለእስራኤላውያን የምትነግራቸው ይህ ነው፦
‘እኔ ከሰማይ ከእናንተ ጋር እንደ ተነጋገርሁ እናንተ ራሳችሁ አይታችኋል። 23 በቀር ሌሎች አማልክትን፣ የብር ወይም የወርቅ አማልክትን ለራሳችሁ አታብጁ። 24
የጭቃ መሠዊያ ሥራልኝ፣ በእርሱም ላይ የሚቃጠሉትን መሥዋዕቶችህን፣ የኅብረት መሥዋዕቶችህን፣ በጎችህንና በሬዎችህን ሠዋበት። ስሜ እንዲከበር
በማደርግበት ስፍራ ሁሉ፣ ወዳንተ እመጣለሁ፤ እባርክሃለሁም። 25 መሠዊያ የምትሠራልኝ ከሆነ፣ በተጠረበ በድንጋይ አትሥራው፤ ለመጥረብ ስትል
መሣሪያህን በላዩ ካሳረፍህበት ታረክሰዋለህና። 26 ሆነህ እንዳትጋለጥ፣ በመሠዊያዬ ላይ በደረጃ አትውጣ።”

Exodus 20:1

• ከባርነት ቤት
በባርነት የነበራችሁበት ቦታ

• ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ
ከእኔ በስተቀር ሌሎችን አማልክት አታምልክ

Exodus 20:4

• የማናቸውንም ምሳሌ፣ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ
የማንኛውንም ዐይነት ምስል ተጠቅመህ ለራስህ ጣዖት አድርገህ አትሥራ

• አትስገድላቸው፣ አታምልካቸውምም
ማንኛውንም ጣዖት አታምልክ ለእርሱም እጅ ነስተህ አትስገድለት

• እኔ . . . ቀናተኛ አምላክ ነኝ
እግዚአብሔር ህዝቡ እርሱን ብቻ እንዲያመልኩት ይፈልጋል

• የአባቶችን ኃጢያት በልጆች ላይ የማመጣ
እግዚአብሔር ስለአባቶቻቸው ሀጢአት ልጆችን ወይም የሚቀጥለውን ትውልድ የሚቀጣ መሆኑን ይገልጻል

• እስከ ሦስተኛና እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ
እስከ የልጅ ልጅ ድረስ

• እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ
“ምህረት” የሚለው ቃል በዕብራይስጡ እግዚአብሔር ለቃል ኪዳኑ ታማኝ መሆኑን የሚመለከት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ እኔን ለሚወዱ ቃል ኪዳኔን እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ የሚጠብቅ ታማኝ አምላክ ነኝ

• እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ
“ሺህ” የሚለው ቃል በወካይ ዘይቤ የተጠቀሰ ሲሆን የብዙ አመታትን ቁጥር የሚገልጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ እስከ ዘላለም ድረስ

Exodus 20:7

• የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ
የአምላክህን ስም በከንቱ ወይም በግድየለሽነት ወይም በንቀት አታንሣ ወይም አትጠቀም

• ከበደል አያነጻውም
ይህ ድርብ አሉታዊ አገላለጽ እግዚአብሔር ሳይቀጣ እንደማያልፍ ለማመልከት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ እኔ በደለኛውን በርግጥ እቀጣለሁ

Exodus 20:8

• ተግባርህንም ሁሉ አድርግ
በየቀኑ የምታደርጋቸውን ተግባራት በየዕለቱ ፈጽም

• በደጆችህም ውስጥ ያለ እንግዳ
በአይሁዶች በቀድሞ ልምድ ከተሞች ዙሪያቸው የታጠረና ሰዎች እንድገቡና እንድወጡ በርም ነበራቸው። አማራጭ ትርጉም፦ በአገርህ ውስጥ የሚኖሩ መጻተኞችም ወይም በአጥርህ ውስጥ የሚኖሩ የሌሎች አገሮች ሰዎች

• የሰንበትን ቀን ባርኮታል
ሁለት አማራጭ ትርጉሞች፦ 1) እግዚአብሔር የሰንበት ቀን መልካም ነገር እንዲያመጣ/እንዲያፈራ/ አድርጎታል 2) እግዚአብሔር የሰንበት ቀን መልካም ነው ብሏል

• የሰንበትን ቀን ቀድሶታል
የሰንበትን ቀን ለራሱ ለይቶታል

Exodus 20:12

• አታመንዝር
ከሚስት ወይም ከባል ጋር ካልሆነ በቀር ከማንም ጋር ግብረ ሥጋ ግንኙነት አታድርግ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Exodus 20:15

• በሐሰት አትመስክር
በማንም ሰው ላይ በሐሰት አትመስክር ወይም ስለአንድ ሰው በውሸት አትናገር

• አትመኝ
አንድን ነገር ለማግኘት ከልክ በላይ አትፈልግ ወይም ለራሴ ይሁንልኝ ብለህ አትመኝ

Exodus 20:18

• የቀንደ መለከቱን ድምፅ
ከቀንድ የተሰራ ድምጽ ማውጫ። ይህን ድምጽ ማውጫ መሳሪያ ለማያውቁ በስዕል ማሳየት ይቻላል።

• ተራራውንም ሲጤስ
ከተራራው ላይ ጭስ ሲወጣ ወይም በተራራው ቃጠሎ ምክንያት ጭስ ሲወጣ

• ተርበደበዱ
በፍርሃት ተንቀጠቀጠቀጡ

• ርቀውም ቆሙ
“ራቅ ብለው ቆሙ” ወይም “በርቀትም ቆሙ”

• ኃጢያትንም እንዳትሠሩ እርሱን መፍራት በልባችሁ ይሆን ዘንድ
እግዚአብሔርን በመፍራት ወይም በማክበር ኃጢአት ከመሥራት ተቆጥባችሁ እንድትኖሩ ነው”

• ሙሴም . . . ወደ ጨለማው ቀረበ
ሙሴ . . . ጥቅጥቅ ወደ ሆነው ደመና ተጠጋ/ሄደ/

Exodus 20:22

• ለእስራኤል ልጆች እንዲህ በል
ለእስራኤላውያን እንዲህ ብለህ ንገራቸው

• እኔ ከሰማይ እንደ ተናገርኋችሁ እናንተ አይታችኋል
ከሰማይ ሆኜ እንደ ተናገርኋችሁ እናንተ ራሳችሁ አይታችኋል

• በአጠገቤ ምንም አታድርጉ
እኔን ትታችሁ ሌሎችን አማልክት በጣኦት መልክ አትሥሩ

• የብር አማልክት የወርቅም አማልክት ለእናንተ አታድርጉ
ከብርና ከወርቅ የተሰሩ ጣኦታት ወይም ከብርና ከወርቅ የተሰሩ አማልክት

Exodus 20:24

• የጭቃ መሰዊያ ሥራልኝ
ከአፈር፥ ከድንጋይ ወይም ከሸክላ የተሰራ መሰዊያ

• ስሜን በማሳስብበት ስፍራ ሁሉ
“ስም” የእግዚአብሔርን ማንነት የሚገልጽ አባባል ነው (ወካይ ዘይቤ)። ስሜ እንዲታሰብበት እንዲከብርበት በወሰንኩት ስፍራ ወይም ስሜን እንዲታከብሩ በመረጥኩት ሥፍራ

• ወደ መሠዊያዬ በደረጃ አትውጣ
ወደ ላይ ለመውጣት ደረጃ ያለውን መሰዊያ ለእኔ አትሥራ

• ኃፍረተ ሥጋህ በእርሱ እንዳይገለጥ
ራቁትህን እንዳትሆን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 21

1 የምትመሠርታቸው ድንጋጌዎች እነዚህ ናቸው፦ **2** አገልጋይ ብትገዛ፣ ስድስት ዓመት ያገልግልህና በሰባተኛው ዓመት ያለ ክፍያ ነጻ ይውጣ። **3** ከመጣ፣ ብቻውን ነጻ ይውጣ፤ ሚስት ያገባ ከሆነ፣ ሚስቱም ዐብራው ነጻ ትውጣ። **4** ጌታው ሚስት አጋብቶት ከሆነና እርሷም ወንዶች ወይም ሴቶች ልጆችን ከወለደችለት፣ ሚስቲቱና ልጆቿ የጌታዋ ይሆናሉ፤ ባልዮው ግን ብቻውን በነጻ ይሂድ። **5** ግን አገልጋይ፣ “ጌታዬን፣ ሚስቴንና ልጆቼን እወድዳለሁ፤ ነጻ ወጥቼ አልሄድም” ቢል፣ **6** ወደ ዳኞች ይውሰደው፥ ወደ በሩ ወይም ወደ መቃኑ ወስዶም ጆሮውን በወስፌ ይብሳው፤ ከዚያም አገልጋይ ጌታውን ለዘለዓለም ያገለግለዋል። **7** ሰው ሴቶ ልጁን በአገልጋይነት ቢሸጣት፣ እንደ ወንዶቹ አገልጋዮች በነጻ መሄድ የለባትም። **8** ለራሱ የመረጣትን ጌታዋን ደስ ባታሰኝ፣ በዎጆ ይልቀቃት። ለባዕዳን እንዲሸጣት መብት የለውም፤ ምክንያቱም አታልሎአታል። **9** ለልጁ አያያዝ ያድርግለት። **10** ሌላ ሚስት ቢያጋባውም፣ የመጀመሪያዋን ሚስቱን ምግብ፥ ልብስ፣ ወይም ቊሳዊ መብት ማጕደል የለበትም። **11** ነገር ግን እነዚህን ሦስት ነገሮች የማይሰጣት ቢሆን፣ ያለ ምንም የገንዘብ ክፍያ በነጻ መሄድ ትችላለች። **12** ሰው ሰውን ቢደበድብና ቢገድል፣ ለሞት ይገባዋል። **13** ሰውየው ዐስቦ ሳይሆን ድንገት አድርጎት ከሆነ፣ የሚሸሽበት ስፍራ አዘጋጃለሁ። **14** አንድ ሰው ባልንጀራውን ሆነ ብሎ በተንኮል ቢያጠቃውና ቢገድለው፣ ከእግዚአብሔር መሠዊያም እንኳ ተወስዶ ይገደል። **15** ወይም እናቱን የሚመጣ ይገደል። **16** የሚጠልፍና የሚሸጥ፣ ወይም የተጠለፈው ሰው በእጁየሚገኝበት ይገደል። **17** ወይም እናቱን የሚሳደብ ይገደል። **18** ቢጣሉና እንደኛው ሌላውን በድንጋይ ወይም በቡጢ ቢመታው፣ የተመታው ሰውም ባይሞትና ዐልጋው ላይ ቢቀር፤ **19** በኋላም ቢያገግምና በትሩን ተደግፎ በአካባቢው መንቀሳቀስ ቢችል፣ ለባከነበት ጊዜ የመታው ሰውን ይክፈል፤ ያገገመበትንም በሙሉ ይክፈል። ነገር ግን ያ ሰው የነፍስ ተጠያቂ አይደለም። **20** አንድ ሰው ወንድ ወይም የሴት አገልጋዩን በበትር ሲመታና አገልጋዩም ከድብደባው የተነሣ ቢሞት፥ ያ ሰው መቀጣት አለበት። **21** ነገር ግን አገልጋዩ አንድ ወይም ሁለት ቀን በሕይወት ቢቆይ፣ ጌታው መቀጣት የለበትም፤ አገልጋዩ የግል ንብረቱ ነውና። **22** ሰዎች ቢጣሉና ነፍሰ ጡር ሴት ቢጎዱ፣ እርሷም ብትጨነግፍ፣ ሆኖም ሌላ ጕዳት ባይደርስባት፣ በደለኛው ሰውዬ የሴትዮዋ ባል የሚጠብቅበትንና ዳኞቹ የሚወስኑትን መክፈል አለበት። **23** ጕዳት ካደረሰ ግን፣ ሕይወትን ለሕይወት፣ **24** ዐይንን ለዐይን፣ ጥርስን ለጥርስ፣ እጅን ለእጅ፣ እግርን ለእግር፣ **25** ቃጠሎን ለቃተሎ፣ ቊስልን ለቊስል፣ ወይም ግርፋትን ለግርፋት በቅጣት ታስከፍላለህ። **26** አንድ ሰው የወንድ ወይም የሴት አገልጋዩን ዐይን ቢመታና ቢያጠፋው፣ አገልጋዩን ስለ ዐይኑ ካሣ ነጻ ሊያደርገው ይገባል። **27** የወንድ ወይም የሴት አገልጋዩን ጥርስ ቢያወልቅ፣ አገልጋዩን ለጥርሱ ካሣ ነጻ ሆኖ እንዲሄድ ማድረግ አለበት። **28** በሬ አንድን ሰው ወይም ሴት ቢወጋና የሞት አደጋ ቢያደርስ፣ በሬው በድንጋይ ይወገር፣ ሥጋውም አይበላ፤ የበሬው ባለቤት ግን ከተጠያቂነት ነጻ ይሁን። **29** ግን በሬው የመዋጋት ልማድ ከቀድሞ ጀምሮ ካለበትና ባለቤቱ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት በሬውን ሳይጠብቀው ቀርቶ፣ በሬው አንድ ወንድ ወይም ሴት ወግቶ ቢገድል፣ ያ በሬ በድንጋይ ይወገር፤ ባለቤቱም በሞት ይቀጣ። **30** ለሕይወቱ ካሣ እንዲከፍል ካስፈለገ፣ የተጠየቀውን ይክፈል። **31** በሬው የአንድን ሰው ወንድ ወይም ሴት ልጅ ቢወጋ፣ የበሬው ባለቤት ይህ ሕግ የሚጠብቅበትን ያድርግ። **32** ወንድ ወይም ሴት አገልጋይን ቢወጋ፣ የበሬው ባለቤት ሠላሳ የብር ሰቅል ለአገልጋዩ ጌታ መክፈልና በሬውም በድንጋይ መወገር አለበት። **33** ሰው ጕድጓድ ቢከፍት ወይም ቢቆፍርና ሳይደፍነው ቀርቶ በሬ ወይም አህያ ቢገባበት፣ **34** ባለቤት ለጠፋው መክፈል ይኖርበታል። ለሞተው እንስሳ ባለቤት ገንዘብ መክፈል አለበት፤ የሞተው እንስሳም የእርሱ ይሆናል። **35** የአንድ ሰው በሬ የሌላ ሰውን በሬ ቢወጋና ቢሞት፣ የበሬዎቹ ባለቤቶች በሕይወት ያለውን በሬ ሸጠው የተሸጠበትንና የሞተውንም በሬ ይካፈሉ። **36** ነገር ግን በሬው ከቀድሞ ጀምሮ የመውጋት ልማድ ያለበት መሆኑ ከታወቀና ባለቤቱም ያልጠበቀው ከሆነ፣ በበሬው ፈንታ በሬውን መክፈል አለበት፤ የሞተው እንስሳም የእርሱ ይሆናል።

Exodus 21:1

አጠቃላይ ምልከታ፦ እግዚአብሔር (ያህዌ) ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል • በፊታቸው
የምታደርገው ሥርዓት
ለእስራኤላውያን የምትሰጣቸው ህግ ወይም ለእስራኤላውያን የምትነግራቸው ደንብ

Exodus 21:2

አጠቃላይ ምልከታ፦ እግዚአብሔር (ያህዌ) እስራኤላውያን ማድረግ ያለባቸውን ነገር በሙሴ በኩል ይናገራል •ብቻውን መጥቶ እንደሆነ ብቻውን ይውጣ
ብቻውን የሚለው ሀረግ በአንዳንድ ቋንቋዎች ግልጽ ላይሆን ይችላል። ስለሆነም ገላጭ ሊያስፈልገው ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ ባሪያ እንዲሆንህ አንተ በገዛኸው ጊዜ ሚስት ያላገባ ከሆነ ወይም እርሱን ባርያ ስታደርገው ሚስት ያላገባ ከሆነ ወይም ሚስት ያገባው አንተ ባርያ አድርገህ ከገዛኸው በኋላ ከሆነ።

• ብቻውን
“ያለ ሚስት” ወይም “ሚስት ሳያገባ”

• ከሚስቱ ጋር መጥቶ እንደሆነ
ባርያ ከመሆኑ በፊት አግብቶ ከሆነ ወይም በባርነት ከመገዛቱ በፊት ባለትዳር ከሆነ

Exodus 21:5

• አርነት አልወጣም ብሎ ቢናገር ብሎ ቢናገር
ብሎ ነጻ መውጣት ባይፈልግ ወይም ብሎ አለመፈለጉን በግልጽ ብናገር

• ጆሮውን በወስፌ ይብሳው
“ወስፌ” በጊዜው በእስራኤላውያን ባህል የተለመደው ጆር መብሻ መሳሪያ ነበር። ዛሬም እንደየህብረተሰቡ የመብሻ መሳሪያ መተካት ይቻላል። ስለሆነም በአማራጭ ጆሮውን በመብሻ ይብሳው ማለት ይቻላል።

• ለዘላለምም ባሪያው ይሁን
እስከ ዕድሜ ልክ ወይም እስኪ ሞት ድረስ

Exodus 21:7

• በዎጆ ይስደዳት
ተመልሳ በሕዝብዋ ትዋጅ ወይም አባቷ መልሶ እርሷን እንዲገዛት መፍቀድ አለበት

• ይሸጣት ዘንድ አይገባውም
ለባዕድ ሊሸጣት አይችልም ወይም ለባዕድ የመሸጥ ሥልጣን የለውም

• ስለ ናቃት
የማይገባ ነገር ስላደረገባት ወይም ስላታለላት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Exodus 21:9

• ለልጃም ብድራት
ሚስት ትሆንለት ዘንድ ለልጁ ቢሰጣት ወይም ልጁ እንዲያገባት ቢፈልግ

• መኖዋን ልብስዋንም ለምንጣፍዋም ተገቢውን አያጕድልባት
ለመጀመሪያ ሚስቱ ምግብ፥ ልብስ እና ቀድሞ የነበራትንም የጋብቻ መብት አይከልክላት

• መኖዋን . . . አያጕድልባት
የሚገባትን የምግብ አቅርቦት አያቋርጥባት

• ለምንጣፍዋም ተገቢውን አያጕድልባት (አይነኬ ዘይቤ)
በባልና ሚስት መካከል ያለውን የተራክቦ ግንኙነት አያቋርጥ ወይም አይከልክላት

Exodus 21:12

• ሰው ሰውን ቢመታ
ሰው ሰውን ቢገድል ወይም ሰውን ደብድቦ የሚገድል

• እርሱ ፈጽሞ ይገደል
ይህንን ተደራጊ ግስ በአድራጊ ግስ መተርጎም ይቻላል፦ ይህን ሰው በርግጥ መግደል አለብህ ወይም ይህ ሰው መሞት አለበት

• ባይሸምቅበትም
ሆን ብሎ ደፈጣ በማድረግ ሳይሆን ወይም ጉዳት ለማድረስ በልቡ ባያስብ ወይም ባያቅድ

• የሚሸሸበት ስፍራ እኔ አደርግልሃለሁ
ሸሽቶ በማምለጥ በሰላም የሚኖርበትን ስፍራ እኔ አዘጋጅለታለሁ

• ባልጀራውን በተንኮል ቢገድለው
ሆን ብሎ ወይም አውቆ ሌላ ሰው ቢገድል

• እንዲሞት ከመሠዊያዬ አውጥተህ ውሰደው
ሕይወቱን ለማዳን ወደ መሠዊያዬ ሸሽቶ ቢሄድ በሞት ይቀጣ

Exodus 21:15

• አባቱን ወይም እናቱን የሚመታ ፈጽሞ ይገደል
ይህን ዐረፍተ ነገር በአድራጊ ግስ ሲንተረጉም፦ ማንም አባቱን ወይም እናቱን ቢመታ አንተ እርሱን መግደል አለብህ

• ፈጽሞ ይገደል
ፈጽሞ መሞት አለበት

• በእጁ ቢገኝ
“እጅ” በወካይ ዘይቤነት የቀረበ ስለሆነ የአንድን ሰው ሙሉ ማንነቱን የሚመለከት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ በአንተ ቁጥጥር ሥር

• እርሱ ፈጽሞ ይገደል
በሞት ይቀጣ ወይም ፈጽሞ ይገደል

• አባቱን ወይም እናቱን የሚሰድብ ፈጽሞ ይገደል
አባቱን ወይም እናቱን የሚረገም ወይም በአባቱና በእናቱ ላይ ክፉ ቃል የሚናገር

Exodus 21:18

• ታምሞ በአልጋው ላይ ቢተኛ
የተመታው ሰው ታሞ በአልጋ ላይ ቢውል ወይም አልጋ ላይ ተኝቶ ቢቀር

• ተነሥቶም በምርኩዝ
በኋላም ተነስቶ ወይም ህመሙ ሲሻለው ወይም በትር እየተመረኰዘ መራመድ ቢችል

• ምርኩዝ
ከእንጨት ወይም ከብረት የተሰራ የጉዞ መደገፊያ

• ተግባሩን ስላስፈታው
ሰውዬው በመታመሙ ምክንያት የባከነውን የሥራ ጊዜ ወይም ሥራ ያልሰራበትን ቀናት የሚመለከት ነው።አማራጭ ትርጉም፦ ሥራ ሳይሰራ ከንቱ ያሳለፈው ጊዜ

• ገንዘብ ይከፍለው ዘንድ
“የመታው ሰው ካሣ ይክፈለው” ወይም “የመታው ሰው የህክምና ወጪ ሊከፍለው ይገባል”

Exodus 21:20

• ቢሞትበትም
አንድ ሰው በምቱ ምክንያት ቢሞትበት” ወይም “ጌታው ባርያውን ቢመታና ቢሞትበት”

• ፈጽሞ ይቀጣ
ያ ሰው መቀጣት ይገባዋል ወይም ያንን ሰው መቅጣት አለብህ

• ገንዘቡ ነውና አይቀጣ
በትርጉሙ ውስጥ ባርያው ለባለቤቱ ንብረቱ ወይም ሀብቱ እንደሆነ መገለጽ አለበት። አማራጭ ትርጉም፦ ምክንያቱም ጌታው ውድ የሆነውን ባርያውን በማጣቱ ተጎቷል

Exodus 21:22

• ልጁን እስክትጨነግፍ ቢገፉአት ባትጎዳ
ህጻኑን ቢያስወርዳት ወይም ያለጊዜው ተወልዶ ቢሞትና በሴትዮዋ ላይ ሌላ ምንም ጉዳት ሳይደርስ ቢቀር

• የሴቲቱ ባል የጫነበትን ያህል ካሳ ይስጥ
በሌላ አገላለጽ፦ አጥፊው ሰው መቀጣት አለበት ወይም ያጠፋው ሰው ተገቢውን ካሳ መክፈል አለበት

• ፈራጆቹም እንደ ፈረዱበት ይክፈል
ዳኞች የፈረዱበትን ወይም የወሰኑበትን ካሳ መክፈል አለበት

• ጕዳት ግን ቢያገኛት ሕይወት በሕይወት ዓይን በዓይን . . .
ሴትዮዋ ብትጎዳ የጎዳትም ሰው በተመሳሳይ መልኩ መጎዳት አለበት። አማራጭ ትርጉም፦ ሰውዬው ለሕይወቷ ሕይወቱን፥ ለዓይኗ ዓይኑን መክፈል ወይም መጎዳት አለበት

Exodus 21:26

• ሰውም
የባርያ ጌታው ወይም አሳዳሪው

• አርነት ያውጣው
ለበደለው በደል ካሣ እንዲሆን ባሪያውን ነጻ ይልቀቅ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Exodus 21:28

• በሬ ወንድን ወይም ሴትን . . . ቢወጋ
የአንድ ሰው በሬ አንድን ሰው በቀንዱ ወግቶ ቢገድል

• በሬው ይወገር
በሬው በድንጋይ ተወግሮ ይሙት ወይም በሬውን በድንጋይ ወግራችሁ ግደሉት

• ሥጋውም አይበላ
በሌላ አገላለጽ፦ የበሬውን ሥጋ አትብሉ ወይም የበሬው ሥጋ አይበላ

• የበሬው ባለቤት ግን ንጹሕ ነው
በሌላ አገላለጽ፦ የበሬው ባለቤት በነጻ ይለቀቅ ወይም የበሬውን ባለቤት በነጻ ልቀቁት አይጠየቅ

• ባለቤቱ ደግሞ ይገደል
የበሬው ባለቤት ወይም ባለ ንብረቱ በሞት ይቀጣ ወይም የበሬውን ባለቤት ወይም ባለ ንብረቱን ግደሉት

• ከእርሱ ግን ካሳ ቢፈልጉ
ተጎጂዎች ካሳ ክፊያ ቢፈልጉ የበሬው ባለቤት ሕይወቱን ለማዳን ቢፈልግ ዳኞች የወሰኑበትን መክፈል አለበት። በትርጉሙ ውስጥ ይህ ግልጽ ሆኖ መታየት አለበት። አማራጭ ትርጉም፦ የበሬው ባለቤት ሕይወቱን ለመዋጀት ወይም ከሞት ለመትረፍ ካሣ እንዲከፍል ከተፈቀደለት ወይም ከተስማሙ ካሣውን በሙሉ መክፈል አለበት።

Exodus 21:31

• ወንድን ልጅ ቢወጋ ሴትንም ልጅ ቢወጋ
ያ በሬ ወይም የዚያ ሰው በሬ ወንድ ወይም ሴት ልጅ ወግቶ ቢገድል

• ሠላሳ የብር ሰቅል
330 ግራም ብር ይስጥ፤ አንድ ሰቅል 11 ግራም ብር ይመዝናል።

• በሬውም ይወገር
በሬውን በድንጋይ ወግራችሁ ግደሉት ወይም በሬው በድንጋይ ተግሮ ይሙት

Exodus 21:33

• ሰውም ጉድጓድ ቢከፍት
አንድ ሰው የጉድጓድ መክደኛ ቢያነሣ ወይም ጉድጓድ ቆፍሮ ሳይከድነው ቢተው

• ዋጋቸውን ለባለቤታቸው ይክፈል
የበሬው ባለቤት ይጉዳቱን ካሳ ማግኘት አለበት። አማራጭ ትርጉም፦ ለበሬው ባለቤት ለሞተው እንስሳ ምትክ ካሳ ይከፈለው

• የሞተውም ለእርሱ ይሁን
ለሞተው እንስሳ ምትኩን የከፈለው ሰው የሞተውን እንሳሳ ለራሱ ወስዶ የፈለገውን ማድረግ ይችላል። የዚህ ክፍል የመልዕክቱ ዋና ሀሳብ ግልጽ ሆኖ መውጣት አለበት። አማራጭ ትርጉም፦ የሞተው እንስሳ ለጉድጓዱ ባለቤት ይሆናል ወይም የሞተውን እንስሳ ለራሱ ማስቀረት አለበት

Exodus 21:35

• ዋጋውንም በትክክል ይካፈሉ
የበሬውን ዋጋ በጋራ ይክፋፈሉ ወይም ገዘቡን አብረው ይካፈሉ”

• ተዋጊ መሆኑ ቢታወቅ
በሌላ አገላለጽ፦ በሬው ተዋጊ መሆኑን ሰዎች የሚያውቁ ከሆነ ወይም የበሬው ባለቤት በሬው ተዋጊ መሆኑን የሚያውቅ ከሆነ

• ባለቤቱም ባይጠብቀው
የበሬው ባለቤት በሬው በአግባቡ ባይጠብቀው ወይም ከአጥር ውስጥ እንዳይወጣ ባያደርግ

• በሬውን በበሬው ፈንታ ይስጥ
የገደለው በሬ ባለቤት በሬው ለሞተበት ሰው በሬ መካስ አለበት። ስለሆነም በትርጉም ውስጥ ይህ ሀሳብ በግልጽ መታየት አለበት። አማራጭ ትርጉም፦ በሬው ለሞተበት ሰው አንድ በሕይወት ያለ በሬ ካሣ መክፈል አለበት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 22

1 ሰው በሬ ወይም በግ ቢሰርቅና ቢያርደው ወይም ቢሸጠው፣ ለአንድ በሬ ዐምስት በሬ፣ ለአንድ በግም ዐምስት በግ መክፈል አለበት፥ 2 ሌባ በር ሰብሮ ሲገባ
ቢገኝና ተደብድቦ ቢሞት፣ በማንም ሰው ላይ የደም ዕዳ አይኖርም። 3 ነገር ግን ሰብሮ ከመግባቱ በፊት ፀሐይ ከወጣ፣ በገደለው ሰው ላይ የደም ተጠያቂነት
ይኖራል። ሌባ የሰረቀውን መመለስ አለበት። ምንም ነገር ከሌለው፣ የሰረቀውን እንዲከፍል እርሱ ራሱ መሸጥ ይኖርበታል። 4 ሆነ አህያ ወይም በግ ቢሆን
የተሰረቀው እንስሳ በሕይወት እርሱ ዘንድ ከተገኘ፣ ዕጥፉን መልሶ መክፈል አለበት። 5 ሰው ከብቱን መስክ ላይ ወይም የወይን ዕርሻ ውስጥ አሰማርቶ
ቢለቅቀውና በሌላ ሰው ዕርሻ ውስጥ ገብቶ ቢግጥ፣ ምርጥ ከሆነው ከራሱ መስክና የወይን ዕርሻ መካስ ይኖርበታል። 6 እሳት ቢነሣና በእሾኾችም ውስጥ
ቢዛመት፣ ክምሩም፣ ያልታጨደውም እህል ወይም ዕርሻው ቢቃጠል፣ እሳቱን ያቀጣጠለው ሰው ካሣ ይካሥ። 7 ሰው እንዲጠበቅለት ገንዘቡን ወይም ዕቃውን
ለጎረቤቱ ቢሰጥ፣ በዐደራ ያስቀመጠውንም ከሰውዬው ቤት ሌባ ቢሰርቀውና ሌባውም ቢገኝ፣ ያ ሌባ ዕጥፍ መክፈል አለበት፤ 8 ባይገኝ ግን፣ የቤቱ ባለቤት
እጁን በጎረቤቱ ንብረት ላይ መዘርጋቱንና አለመዘርጋቱን ለማየት፣ በዳኞች ፊት ሊቀርብ ይገባል። 9 ስለ በሬ፣ ስለ አህያ፣ ስለ በግ፣ ስለ ልብስ ወይም አንድ ሰው፣
“ይህ የእኔ ነው” ስለሚለው ስለ ማንኛውም የጠፋ ነገር የሚነሣ ክርክር ሁሉ፣ የሁለቱም ወገን አቤቱታ በዳኞች ፊት መቅረብ አለበት። ዳኞች በደለኛ ሆኖ
ያገኙት ሰው ለጎረቤቱ ዕጥፍ መክፈል ይኖርበታል። 10 አንድ ሰው አህያ፣ በሬ፣ በግ፣ ወይም ማንኛውም እንስሳ እንዲጠበቅለት ለጎረቤቱ በዐደራ ቢሰጥና
እንስሳው ቢሞት፣ ወይም ጕዳይ ቢደርስበት፣ ወይም ማንም ሳያይ ቢወሰድ፣ 11 ሰው የጎረቤቱ ንብረት ላይ እጁን መዘርጋቱን ወይም አለመዘርጋቱን ለመለየት፣
ሁለቱም በእግዚአብሔር ፊት መማል አለባቸው። ባለቤቱ ይህን ሊቀበል ይገባል፤ ሌላውም ሰው ካሣ አይክሥም። 12 ነገር ግን እንስሳው ከእርፍሱ ተሰርቆ
ከሆነ፣ ሌላው ሰው ለባለቤቱ ካሣ መካሥ አለበት። 13 አንድን እንስሳ አውሬ ቢዘነጥለው፣ ሌላው ሰውዬ እንስሳውን ማስረጃ አድርጎ ያቅርብ። ለተዘነጣጠለው
እንስሳ ካሣ መክፈል የለበትም። 14 አንድ ሰው ከጎረቤቱ እንስሳ ቢዋስና እንስሳው ባለቤቱ በሌለበት ቢጎዳ ወይም ቢሞት፣ ሌላው ሰውዬ ካሣ መካሥ አለበት።
15 ባለቤቱ ካለበት ከሆነ ግን፣ ሌላው ሰውዬ ካሣ መክፈል የለበትም፤ እንስሳ ተከራይቶ የነበረ ከሆነ፣ በተከራየበት ዋጋ ይከፈለል። 16 አንድ ሰው ያልታጨች
ልጃገረድን ቢያታልልና ዐብሯት ቢተኛ፣ ለዚህ ተገቢ የሆነውን ማጫ ከፍሎ ሚስቱ ሊያደርጋት ይገባል። 17 አባቷ በሚስትነት አልሰጥህም ካለው፣ ልጃገረዶች
ማጫ ከሚከፈለው ጋር እኩል የሆነ ገንዘብ መክፈል አለበት። 18 መተተኛ ሴት በሕይወት እንድትኖር አትፍቀድ። 19 ከእንስሳት ጋር የወሲብ ግንኙነት
የሚያደርግ መምት አለበት። 20 ከእግዚአብሔር በቀር ለማንኛውም ባዕድ አምላክ መሥዋዕት የሚሠዋ ፈጽሞ መጥፋት ይኖርበታል። 21 መጻተኛውን
አትበድሉት ወይም አታስጨንቁት፤ እናንተም በግብፅ ምድር መጻተኞች ነበራችሁና። 22 ማንኛዋንም መበለት ወይም አባትና እናት የሌለውን ልጁ ማስጨነቅ
የለባችሁም። 23 የምታስጨንቋቸው ከሆነና እነርሱም ወደ እኔ ከጮኹ፤ እኔ እግዚአብሔር ጩኸታቸውን እሰማለሁ። 24 ቊጣዬ ይቀጣጠላል፤ በሰይፍም
እገድላችኋለሁ፤ ሚስቶቻችሁ መበለታት፣ ልጆቻችሁም አባት ዐልባዎች ይሆናሉ። 25 ከሕዝቤ መካከል ድኻ ከሆኑት ለአንዱ ገንዘብ ብታበድሩ፣ እንደ አራጣ
አበዳሪ አትሁኑበት ወይም ወለድ አታስከፍሉት። 26 የጎረቤትህን ልብስ በመያዣነት ብትወስድ፣ ፀሐይ ከመግባቷ በፊት ልትመልስለት ይገባል። 27 ሰውነቱን
የሚሸፍንበት ልብሱ እርሱ ብቻ ነውና። ምን ሌላ ልብስ ለብሶ መተኛት ይችላል? ወደ እኔ ሲጮኽ፣ ርኅሩኅ ነኝና እሰማዋለሁ። 28 ፈራጆችንም አትስደብ፤
የሕዝብህን አለቃም አትርገም። 29 ወይም ከወይን ጭማቂዎችህ የምታቀርባቸውን ስጦታዎች ማዘግየት የለብህም። የወንድ ልጆችህንም በኵር ለእኔ መስጠት
አለብህ። 30 በበጎችህ ላይም ይህንኑ ማድረግ ይኖርብሃል። ልጆቹ ሰባት ቀን ክአእናቶቻቸው ጋር መቆየት ይችላሉ፤ በስምንተኛው ቀን ግን ለእኔ መስጠት
አለብህ። 31 ለእኔ ቅዱስ ሕዝብ ትሆናላችሁ። ስለዚህ መስክ ላይ አውሬ የዘነጣጠለውን ሥጋ ለውሾች ጣሉት፣ ልትበሉት አይገባም።

Exodus 22:1

አጠቃላይ ዕይታ፦
እግዚአብሔር (ያህዌ) ህጉን በሙሴ በኩል ለእስራኤላውያን መናገሩን
ሲቀጥል እናያለን

• ቢሰርቅ
በሌላ አገላለጽ፦ አንድ ሰው ሌባ ሆኖ ቢገኝ ወይም አንድ ሰው ሰርቆ ቢገኝ

• ሌባው ቤት ሲምስ ቢገኝ
በሌላ አገላለጽ፦ አንድ ሌባ የአንድ ሰው ቤት ሰብሮ ቢገባ

• እርሱም እስኪሞት ቢመታ
በሌላ አገላለጽ፦ አንድ ሰው ቢመታውና ሌባው ቢሞት

• በመታው ሰው ላይ የደም ዕዳ አይሆንበትም
በሌላ አገላለጽ፦ ተከላካዩ ወይም ሌባውን መቶ የገደለው ሰው ለፈሰሰው ደም
ወይም በመግደሉ ተጠያቂ አይሆንም

• ፀሐይ ግን ከወጣችበት የደም ዕዳ አለበት
በሌላ አባባል፦ ፀሐይ ከወጣ በኋላ ወይም ብርሃን እያለ ሌባው ተመትቶ
ቢገደል ግን ተከላካዩ በግድያው ተጠያቂ ይሆናል

• ሌባው የሰረቀውን ይመልስ
ሌባው የሰረቀውን መክፈል አለበት ወይም ሌባው በሰረቀው ንብረት ምትክ
ክፊያ መስጠት አለበት

• የሚከፍለውም ቢያጣ ስለ ሰረቀው ይሸጥ
ምንም ከሌለው ግን የሰረቀውን ይከፍል ዘንድ ራሱ በባርነት ይሸጥ

• የሰረቀው ደኅና ሆኖ በእጁ ቢገኝ
ሌባው የሰረቀው እንስሳ ሕያው ሆኖ ቢገኝ ወይም በሕይወት ቢገኝ

• የሰረቀውን ያህል ሁለት እጥፍ ይክፈል
ለያንዳንዱ እንስሳ ዕጥፍ ዋጋ ወይም ሁለት እንስሳ ይክፈል

Exodus 22:5

• ማንም ሰው ወደ እርሻ ወይም ወደ ወይን ስፍራ ከብቱን ቢነዳው
አንድ ሰው እንስሶቹ በእርሻው ወይም በመስክ ወይም በወይን ተክል ቦታ
አሰማርቶ እያለ

• የሌላውንም እርሻ ቢያስበላ
እንስሶቹ ወደ ሌላ ሰው እርሻ ገብተው ሰብሉን ቢበሉት

• ከተመረጠ እርሻው ከማለፊያውም ወይኑ ይካስ
ከራሱ እርሻ ሰብል ወይም የወይን ቦታ ምርጡን መክፈል አለበት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Exodus 22:6

• እሳት ቢነሣ፥ እሾኽንም ቢይዝ
አንድ ሰው በእርሻው ውስጥ እሳት ቢያቀጣጥልና እሳቱ ወደ ቊጥቋጦ ተዛምቶ ቢሰራጭ

• ክምሩንም ወይም ያልታጨደውን እህል ወይም እርሻውን ቢያቃጥል
ወደ ሌላው ሰው እርሻ በመዛመት ያልታጨደውን ወይም ታጭዶ የተቀመጠውን ወይም የተከመረውን እህል ቢያቃጥል

• እሳቱን ያነደደው ይካስ
እሳቱን ያቀጣጠለው ሰው ካሣ ይክፈል

Exodus 22:7

• አደራ ቢያኖር
እንዳይጠፋበት ወይም እንዳይሰረቅበት በአደራ ቢያስቀምጥ

• ከቤቱም ቢሰረቅ
በሌላ አገላለጽ፦ አንድ ሰው ወይም ሌባ ቢሰርቀው

• ሌባው ቢገኝ
በሌላ አገላለጽ፦ የሰረቀውን ሰው ብታገኘው ወይም ብታገኘው

• ሌባውም ባይገኝ ባለቤቱ ወደ ፈራጆች ይቅረብ
ሌባው ካልተገኘ ግን ዕቃውን በዐደራ የተቀበለው ሰው ዳኞች ፊት ይቅረብ / ይምጣ/

• እጁንም በባልንጀራው ከብት ላይ እንዳልዘረጋ ይማል
“እጁን . . . እንዳልዘረጋ” የሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። ይህን ዘይቤያዊ እነጋገር በተመሳሳይ ዘይቤያዊ ንግግር መትርጎም የሚቻል ከሆነ መተረጎም ጥሩ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ የዚያን ሰው ንብረት ራሱ አለመስረቁን በመሐላ ያረጋግጥ

• ክርክራቸው ወደ ፈራጆች ይድረስ
በሁለቱ መካከል ክርክር ቢነሣ ባለ ጉዳዮቹ ነገሩን ለዳኞች ያቅርቡት

Exodus 22:10

• የእግዚአብሔር መሐላ በሁለታቸው መካከል ይሁን
እንስሳውን ሰርቀሃል ተብሎ የተከሰሰው ሰው አለመስረቁን በመሀላ ያረጋግጥ። የእንሳሳው ባለቤት ደግሞ የሰውየውን መሀላ መቀበል አለበት። በሌላ አገላልጽ፦ እንስሳውን በአደራ የተቀበለው ሰው በእግዚአብሔር ፊት ይማል እንዲሁም የእንስሳው ባለቤት መሀላውን ይቀበል

• ከእርሱም ዘንድ ቢሰረቅ
በሌላ አገላለጽ፦ እንስሳው ከባለአደራው የተሰረቀ ከሆነ

• ተቧጭሮም ቢገኝ
በሌላ አገላለጽ፦ እንስሳው በአውሬ ተሰብሮን ተበልቶ ከሆነ

• በመቧጨሩም ምክንያት አይክፈል
አውሬ ስለ ገደለውም ወይም ስለበላው ካሳ አይክፈል።

Exodus 22:14

• ፈጽሞ ይክፈለው
በውሰት ለሰጠው ሰው ካሳ መክፈል አለበት ወይም በውሰት ለሰጠው ሰው ሌላ እንስሳ በምትክ መስጠት አለበት

• ባለቤቱ ግን ከእርሱ ጋር ቢኖር አይክፈል
ባለቤቱ ከእንስሳው ጋር ከሆነ ግን ተበዳሪው መክፈል የለበትም

• ቢከራየው በክራዩ ይግባ
እንስሳውን የተከራየው ሰው ከክራይ ገንዘብ ይልቅ ምንም ዓይነት ካሳ መክፈል የለበትም። የክራዩ ገንዘብ ክሳርውን ይሸፍንለትታል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ ለኪራይ የተከፈለው ገንዘብ ጕዳቱን ወይም ኪሳራውን ያካክስለታል።

Exodus 22:16

• ሰው ያልታጨችውን ድንግል ቢያስታት
አንድ ሰው ያልታጨችን ልጃገረድ ከእርሱ ጋር እንድትተኛ ቢያታልላት

• ያልታጨች
ለጋብቻ ያልታጨች ወይም ቃል ኪዳን ይላደረገች

• ከእርስዋም ጋር ቢተኛ (አይነኬ ዘይቤ)
ከእርሷ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ቢፈጽም

• ማጫዋን ሰጥቶ
የሞራል ካሳ ከፍሎ ወይም የማጫ ዋጋ ከፍሎ

• ሚስት ያድርጋት
የሞራል ካሳ ከፍሎ ወይም የማጫ ዋጋ ከፍሎ

• ሚስት ያድርጋት
“ሚስት ያድርጋት” የተባለው አታሏት የደፈራት ወይም ክብረ ንጽህናዋን የወሰዳት”

Exodus 22:18

• ከእንስሳ ጋር የሚረክስ ፈጽሞ ይገደል
እዚህ ጋር “የሚረክስ” የሚለው በአይነኬ ዘይቤ የተገለጸ ሲሆን አንድ ሰው ከእንስሳ የሚፈጽመውን የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚመለከት ነው። በሌላ አገላለጽ፦ “ከእንስሳ ጋር ግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚፈጽምን ሰው ፈጽማችሁ ግደሉ”

Exodus 22:20

• ከእግዚአብሔር በቀር ለአንዳች አምላክ የሚሠዋ ፈጽሞ ይጥፋ
ከእግዚአብሔር ሌላ ለማንኛውም አምላክ መሥዋዕት የሚያቀርብ በሞት ይቀጣ ወይም ግደሉት

• ስደተኛውን አትበድለው
መጻተኛውን ወይም እንግዳ ሰው አትበድል ወይም አታስጨንቅ

Exodus 22:22

• መበለቲቱንና ድሀ አደጎቹን አታስጨንቁአቸው
በሌላ አገላለጽ፦ ባል የሞተባትን ሴት እና አባትና እናት የሞቱበትን ድኻ ዐደግ አታጉላሉ” ወይም “ባል የሞተባትን ሴት እና ወላጅ አጥ ድኻ ዐደጉን እኩል አስተናግድ”

• መበለት
ባሏ የሞተባት ሴት

• ድሀ አደጎቹን
አባትና እናት የሞተበት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• በሰይፍም አስገድላችኋለሁ
በጦርነት ወይም በተለየ አደጋ እንድትሞቱ አደርጋችኋለሁ

Exodus 22:25

• ገንዘብ ብታበድረው
ለአንድ ሰው ገንዘብ ብታበድር

• እንደ ባለ አራጣ አትሁን
እንደ ገንዘብ አበዳሪ ወለድ ጨምሮ እንዲከፍልህ አትጠይቀው

• የባልንጀራህን ልብስ ለመያዣ ብትወስድ
የባልንጀራህን ወይም የጓደኛህን ልብስ መያዣ አድርገህ ብትይዝ

• ሥጋውን የሚከድንበት እርሱ ብቻ ነውና
ምክንያቱም ለሰውነቱ መሸፈኛ ወይም ለብርድ መከላከያነት ያለው ልብስ ያ ብቻ ነው

• የሚተኛበትም ሌላ የለውምና
ምክንያቱም ሌላ ለብሶ የሚተኛበት ወይም የሚያድረበት የለውም

Exodus 22:28

• ፈራጆችን አትስደብ
በእግዚአብሔር (ያህዌ) ላይ የስድብ ቃል አትናገር ወይም አታሰማ

• የሕዝብንም አለቃ አትርገመው
የሕዝብንም አለቃ አትርገመው” ወይም “የህዝብህን መሪ እንድረግመው እግዚአብሔርን አትጠይቅ

Exodus 22:29

• ነዶህንም የወይንህንም ጭማቂ ለማቅረብ አትዘግይ
በሌላ አገላለጽ፦ “የእህልህን ወይም የወይን ጠጅህን መስዋዕት ለእኔ ከማቅረብ ወደ ኋላ አትበል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 23

1 ማንም ሰው የሐሰት ወሬ አትናገር። ሐሰተኛ ምስክር ለመሆን ከክፉ ሰው ጋር አትተባበር። 2 ክፋት ለመፈጸም ሕዝብን አትከተል፤ ወይም ፍትሕን ለማጣመም
ከሰዎች ጋር ተባብረህ ምስክርነት አትስጥ። 3 ድኻውን በሙግቱ አታድላለት። 4 በሬ ወይም አህያ ጠፍቶ ብታገኘው መልስለት። 5 የሚጠላህን ሰው አህያ እንደ
ተጫነ ከጭነቱ ሥር ወድቆ ብታየው፣ ያን ሰው ትተኸው አትሂድ። አህያውን ለማንሣት ልታግዘው ይገባል። 6 ጊዜ ለድኻው ወገንህ የሚሰጠውን ፍትሕ
አታጣምም። 7 በሐሰት ክስ ከሌሎች ጋር አትተ ባበር፤ ንጹሑንም ወይም ጻድቁንም አትግደል፤ እኔ ኀጢአተኛውን ንጹሕ አላደርግምና። 8 አትቀበል፤ ጕቦ የሚያዩ
ሰዎችን ያሳውራል፤ የታማኝ ሰዎችን ቃልም ያጣምማልና። 9 የመጻተኛነትን ስለምታውቁት፣ መጻተኛን አታስጨንቁ፤ እናንተም በግብፅ ምድር መጻተኞች
ነበራችሁና። 10 ስድስት ዓመት በመሬትህ ላይ ዘር ዝራ፤ መከሩንም ሰብስብ። 11 በሰባተኛው ዓመት ግን በሕዝብህ መካከል ያሉ ድኾች መብላት እንዲችሉ
ሳታርሰው ዕዳሪውን ተወው። ከድኾች የሚተርፈውንም የዱር እንስሳት ይበሉታል። በወይን ቦታዎችህና በወይራ ዛፎችህም ይህንኑ ታደርጋለህ። 12 ቀን ሥራህን
ትሠራለህ፤ በሰባተኛው ቀን ግን ታርፋለህ። ይህን የምታደርገውም፦ በሬህ፣ አህያህ፣ የሴት አገልጋይህ ወንድ ልጅና መጻተኛው ሁሉ ዕረፍት እንዲያገኙና እንዲዝናኑ
ነው። 13 የነገርኋችሁን ሁሉ ጠብቁ። የሌሎች አማልክትን ስም አትጥሩ፤ ወይም ስማቸው ከአፋችሁ አይሰማ። 14 በየዓመቱ ሦስት ጊዜ ልአእኔ በዓል
ታከብራላችሁ። 15 በዓልን አክብር። ባዘዝሁህ መሠረት ሰባት ቀን ቂጣ ትበላለህ። በዚያ ጊዜ፣ ለዚህ በተወሰነው በአቢብ ወር በፊቴ ትቀርባለህ። ከግብፅ
የወጣኸው በዚህ ወር ነበር። ነገር ግን በፊቴ ባዶ እጅህን መቅረብ የለብህም። 16 ላይ የዘራኸውን የእህልህን በኵራት፣ የመከርን በዓል አክብር። በዓመቱ
መጨረሻ ምርትህን ከማሳ ስትሰበስብ፣ የመክተቻውን በዓል አክብር። 17 ዘንድ ያለ ወንድ ሁሉ በዓመት ሦስት ጊዜ በእኔ በእግዚአብሔር ፊት ይቅረብ። 18
የመሥዋዕቱን ደም እርሾ ካለበት ዳቦ ጋር ለእኔ አታቅርብ። በበዓሎቼ የሚቀርበው የመሥዋዕቴ ሥብ እስከ ንጋት ድረስ መቆየት የለበትም። 19 የመሬትህን
ምርጥ ፍሬ በኵራት ወደ እኔ፣ ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ቤት አምጣ። የፍየልን ግልገል በእናቱ ወተት አትቀቅል። 20 በመንገድ የሚጠብቅህንና
ወዳዘጋጀሁልህ ስፍራ መርቶ የሚያስገባህን መልአክ በፊትህ እልካለሁ። 21 ተከተለው፤ ታዘዝለትም። ኀጢአትህን ይቅር አይልህምና አታስቆጣው። ስሜ
በእርሱ ላይ ነው። 22 ድምፁን በእውነት ብትሰማና የምነግርህን ሁሉ ብታደርግ፣ ለጠላቶችህ ጠላት እሆናለሁ፤ የሚቃወሙህንም እቃወማለሁ። 23 መልአክ
በፊትህ ይሄዳል፤ አንተንም ወደ አሞራውያንና ወደ ኢያቡሳውያን ምድር ያስገባሃል። እኔ እነርሱን አጠፋቸዋለሁ። 24 ለአማልክታቸው አትስገድ፤ አታምልካቸውም፤
ወይም ሕዝቡ እንደሚያደርጉት አታድርግ፤ ይልቁን ፈጽመህ ልታፈራርሳቸው፣ የድንጋይ ዐምዶቻቸውንም ልትሰባብራቸው ይገባል። 25 እኔን አምላክህን
እግዚአብሔርን አምልክ። ይህን ካደረግህ፣ የምትባውንና የምትጠጣውን እባርካለሁ። በሽታንም ከመካከልህ አጠፋለሁ። 26 የምትጨነግፍ ወይም የምትመክን
ሴት አትምርም። ለአንተ ረጅም ዕድሜ እሰጥሃለሁ። 27 ምድር ሕዝብ ላይ ማስፈራቴን እልካለሁ። የሚያጋጥሙህን ሰዎች ሁሉ እገድላለሁ። ጠላቶችህን ሁሉ
ከፍርሀት የተነሣ ጀርባቸውን ወደ አንተ እንዲያዞሩ አደርጋለሁ። 28 ከነዓናውያንን ኬጤያውያንን ከፊትህ እንዲያበሯቸው ተርቦችን በፊትህ እሰድዳለሁ። 29 ወና
እንዳትሆንና የዱር አራዊትም እጅግ እንዳበዙብህ፣ የምድሪቱን ኗሪዎች በአንድ ዓመት ውስጥ ከፊትህ አላባርራቸውም። 30 ነገር ግን አንተ እስክትበዛና ምድሪቱን
እስክትወርሳት ድረስ በትንሽ በትንሹ አስወጣቸዋለሁ። 31 ከቀይ ባሕር እስከ ፍልስጥኤም ባሕር፣ ከምድር በዳውም እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ
አደርገዋለሁ። በምድሪቱ ኗሪዎች ላይ ድል እንድትጎናጸፍ አደርጋለሁ፤ ከፊትህም ታባርራቸዋለህ። 32 ወይም ከአማልክታቸው ጋር ኪዳን አታድርግ። 33 እነርሱ
በምድርህ ውስጥ መኖር አይገባቸውም፤ አልዚያ በእኔ ላይ ኀጢአት እንድትሠራ ያደርጉሃል። አማልክታቸውን ብታመልክ፣ ይህ በእውነት ወጥመድ ይሆንብሃል።”

Exodus 23:1

አጠቃላይ ዕይታ፦
እግዚአብሔር (ያህዌ) ህጉን በሙሴ በኩል ለእስራኤላውያን መናገሩን ሲቀጥል እናያለን

• ሐሰተኛ ምስክርም ትሆን ዘንድ
ተንኰል ያለበትን ምስክርነት በመስጠት ወይም በሀሰት በመመስከር

• ብዙ ሰዎችን አትከተል
ይህ ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን አንድ ሰው ከብዙ ሰው ጋር በመስማማት ፍለጋቸውን መከተልን የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ ክፉ ለማድረግ የተሰባሰቡ ሰዎችን አትከተል ወይም ብዙ ሰዎች የሚፈልጉትን ለማድረግ ከእነርሱ ጋር አትተባበር

• ፍርድንም ለማጥመም
ፍትህን ወይም እውነተኛ ፍርድን ለማዛባት ወይም የህሊና ዳኝነት ለመካድ ወይም ላለመስማት

Exodus 23:4

አጠቃላይ ዕይታ፦
እግዚአብሔር (ያህዌ) ህጉን በሙሴ በኩል ለእስራኤላውያን መናገሩን ሲቀጥል እናያለን

Exodus 23:6

አጠቃላይ ዕይታ፦
እግዚአብሔር (ያህዌ) ህጉን በሙሴ በኩል ለእስራኤላውያን መናገሩን ሲቀጥል እናያለን

• በሚምዋገትበት ጊዜ የድሀህን ፍርድ አታጥምም
በፍርድ አደባባይ ወይም በዳኝነት አድልዎ በማድረግ የድኻውን ፍርድ አታጣምበትብ ወይም አታዛባ

Exodus 23:10

አጠቃላይ ዕይታ፦
እግዚአብሔር (ያህዌ) ህጉን በሙሴ በኩል ለእስራኤላውያን መናገሩን ሲቀጥል እናያለን

• ፍሬዋንም አግባ
ከእርሻ የምታገኘውን ምርት ሰብስብ

• ተዋት አሳርፋትም
ሳትርሳት እንዲሁ ተዋት፤ ምድርቱን አሳርፋት

• የሕዝብህም ድሆች ይበሉታል
ድሆች በእርሻው ውስጥ ራሱ የበሰለውን ምርት ይበሉ ዘንድ ምድርቱን ሳታርስ ተው። አማራጭ ትርጉም፦ በሕዝብህ መካከል የሚገኙ ድኾች ምግብ ያገኙ ዘንድ ወይም በወገንህ መካከል ያሉት ድኾች ከእርሷ ምግብ ያገኛሉ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Exodus 23:12

አጠቃላይ ዕይታ፡-
እግዚአብሔር (ያህዌ) ህጉን በሙሴ በኩል ለእስራኤላውያን መናገሩን ሲቀጥል እናያለን

• ያልኋችሁንም ነገር ሁሉ ጠብቁ
የነገርኳችሁን ሁሉ በጥንቃቄ አድምጡ

• በሬህና አህያህ ያርፉ ዘንድ
የሥራ እንስሳት እንዲያርፉ

• ለባሪያህም ልጅ ለመጻተኛውም ዕረፍት ይሆን ዘንድ
በሌላ አገላለጽ፡- በቤትህ የተወለደው ባሪያና መጻተኛው ወይም የሌላ አገር ሰው ያርፉ ዘንድ

• የሌሎችንም አማልክት ስም አትጥሩ
ሌሎችን አማልክት ስም መጥራት ፀሎትን የሚመለከት ነውና “ወደ ሌሎች አማልክት አትጸልዩ”

Exodus 23:14

አጠቃላይ ዕይታ፡-
እግዚአብሔር (ያህዌ) ህጉን በሙሴ በኩል ለእስራኤላውያን መናገሩን ሲቀጥል እናያለን

• በአቢብ ወር
የአቢብ ወር ለእብራውያን የአመቱ መጀመሪያ ወር ነው። እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር አቢብ ወር የሚጀምረው ከመጋቢት መጨረሻ ሳምንት እስከ ሚያዝያ መጀመሪያ ሳምንት ድረስ ነው። (ዘጸአት 13:4 ተመልከት)

• በፊቴም ባዶ እጃችሁን አትታዩ
ይህ አነጋገር እግዚአብሔር ማንም ሰው ወደ ፊቱ ሲመጣ የሆነ ነገር ተሸክሞ እንድመጣ የሚጠይቅ ይመስላል። ነገር ግን ይህ ወካይ ዘይቤ የሚያሳየው “ወደ እኔ የሚመጣ ማንም ቢሆን መስዋዕት ሳይዝ አይምጣ” ወይም “ወደ እኔ የሚመጣ ማንም ቢሆን መስዋዕት ማምጣት አለበት” የሚል ነው።

Exodus 23:16

አጠቃላይ ዕይታ፡-
እግዚአብሔር (ያህዌ) ህጉን በሙሴ በኩል ለእስራኤላውያን መናገሩን ሲቀጥል እናያለን

• የመክተቻውን በዓል ጠብቅ
ይህ በዓል የዳስ በመባል ይታወቃል። ይህ ልምምድ የመጣው እርሻቸውን በዳስ ወይም በጊዜያዊ ጎጆ ውስጥ ሆነው ያረሱና እህሉ እስኪደርስ ድረስ በዚያ ዳስ ሆነው ከአውሬ ሲጠብቁ የነበሩ አርሶ አደሮች ልምምድ ነው። “መክተቻ” የተባለው የእህል ማከማቻ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በዓመቱ መጨረሻ የዳስ በዓል አክብሩ”

• ወንድ ሁሉ በጌታ በእግዚአብሔር ፊት ይታይ
እዚህ ቦታ “ይታይ” የሚለው ለአምልኮ መሰብሰብን የሚመለከት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- ወንድ ሁሉ እግዚአብሔርን (ያህዌን) ለማምለክ በአንድ ላይ መሰብሰብ አለበት።

Exodus 23:18

አጠቃላይ ዕይታ፡-
እግዚአብሔር (ያህዌ) ህጉን በሙሴ በኩል ለእስራኤላውያን መናገሩን ሲቀጥል እናያለን

• የበዓሌም ስብ እስኪነጋ አይደር
ስቡ የሚበላ ሳይሆን ለእግዚአብሔር የሚቃጠል መስዋዕት ሆኖ መቅረብ አለበት። ስለሆነም “ለነገ እንዲያድር አይፈቀድም ወይም እስከ ነገ መቆየት የለበትም”

• የተመረጠውን
ከእርሻ ምርቱ የተሻለውን ወይም መጀመሪያ የደረሰውን”

• ጠቦትን በእናቱ ወተት አትቀቅል
ይህ ድርጊት የከነዓናውያን ልምምድ ሲሆን ምርታማነትን ይጭምራል ተብሎ ስለሚታሰብ የሚደረግ ነው። ስለሆነም እስራኤላውያን ይህንን ድርጊት እንዳያደርጉ ተከልክለዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “የበግ ወይም የፍየል ግልገል በእናቱ ወተት አትቀቅል”

Exodus 23:20

አጠቃላይ ዕይታ፡
እግዚአብሔር (ያህዌ) ህጉን በሙሴ በኩል ለእስራኤላውያን መናገሩን ሲቀጥል እናያለን

• በፊቱ ተጠንቀቁ
በጥንቃቄ ተከተለው ወይም አዳምጠህ እግዚአብሔርን (ያህዌን) ታዘዝ

• አታስመርሩ
እርሱን የምታስመርር (ለቁጣ የምታነሳሳ) ከሆነ ይቅር አይልህም

• ስሜም በእርሱ ስለ ሆነ
በዚህ ቦታ “ስም” የእግዚአብሔርን ስልጣንን የሚመለከት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- ለእርሱ ስልጣን ስለሰጠሁ

• አንተ ግን ቃሉን ብትሰማ
እግዚአብሔር (ያህዌ) የሚናገረውን በጥንቃቄ ብታደምጥ

• ጠላቶችህን እጣላቸዋለሁ፥ የሚያስጨንቁህንም አስጨንቃቸዋልሁ (ተነጻጻሪ ዘይቤ)
እንዚህ ሁለት ነገሮች ተመሳሳይ ነገር የሚገልጹና አጽንኦት ለመስጠት የገቡ ናቸው።

Exodus 23:23

አጠቃላይ ዕይታ፡-
እግዚአብሔር (ያህዌ) ህጉን በሙሴ በኩል ለእስራኤላውያን መናገሩን ሲቀጥል እናያለን

• እንደ ሥራቸውም አትሥራ
እስራኤላውያን ጣኦትን እንደምያመልኩ እንደ ሌሎች ህዝቦች መኖር የለባቸውም። አማራጭ ትርጉም፡- የሌሎችን ህዝቦች ሃይማኖታዊ ልማዶቻቸውን ወይም ሥርዓታቸውን አትከተል

• እርሱም እህልህንና ውኃህን ይባርካል (ጠቅላይ ዘይቤ)
ይህ አባባል አጠቃላይ የኑሮ ሁኔታ ለውጥ የሚመለከት ነው። ዘማራጭ ትርጉም፡- እርሱ የምትበላውን እህል እና የምትጠጣውን ውሃ ይባርክልሃል ወይም የምትበላውን እህልና የምትጠጣውን ውሃ ይባርክሃል

Exodus 23:26

አጠቃላይ ዕይታ፡-
እግዚአብሔር (ያህዌ) ህጉን በሙሴ በኩል ለእስራኤላውያን መናገሩን ሲቀጥል እናያለን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• በምድርህም መካን ወይም የምትጨነግፍ አትሆንም
በሌላ አገላለጽ፦ በምድርህ ጽንስ የሚያስወርዳት ወይም መካን ሴት አትኖርም ወይም በምድርህ ያሉ ሴቶች ያረግዛሉ እንዲሁም ይወልዳሉ

• የምትጨነግፍ
ጊዜው ሳይደርስ የምትወልድ እና ልጇ የሚሞትባት ሴት

• በፊትህም ተርብ እሰድዳለሁ
“ተርብ” ሰዎችን በመንደፍ ስቃይ የሚያስከትሉ በራሪ ነፍሳት

• ምድር ባድማ እንዳትሆን
ምድርቱ ሰው የማይኖርባት ምድር እንዳትሆን

Exodus 23:30

አጠቃላይ ዕይታ፦
እግዚአብሔር (ያህዌ) ህጉን በሙሴ በኩል ለእስራኤላውያን መናገሩን ሲቀጥል እናያለን

• ወጥመድ ይሆኑብሃልና (ዘይቤያዊ አነጋገር)
“ወጥመድ” ሰዎች አውሬዎችን፥ ወፎችን፥ እና ሌሎች ነገሮችን ለማጥመድ ወይም ለመያዝ የሚጠቀሙት መሳሪያ ነው። በተመሳሳይ መልኩ እስራኤላውያን ሌሎች አማልክትን ብያመልኩ ወደ ጥፋት እንደምወስዳቸው ያመለክታል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 24

1 እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፤ “አንተ፣ ናዳብ፣ አብድዩና ሰባው የእስራኤል ሽማግሌዎች ወደ እኔ ኑ፤ በርቀት ሆናችሁም ስገዱልኝ። 2 ሙሴ ብቻ ወደ እኔ መቅረብ ይችላል። ሌሎች መቅረብ የለባቸውም፤ ወይም ሕዝቡ ከሙሴ ጋር መምጣት አይችሉም።” 3 ሙሴ ወደ ሕዝቡ ሄዶ እግዚአብሔር የተናገራቸውን ቃሎችና ሕጎቹን ሁሉ ነገራቸው። ሕዝቡም ሁሉ በአንድ ድምፅ፣ “እግዚአብሔር የተናገራቸውን ቃሎች ሁሉ እናደርጋለን” ብለው መለሱ። 4 ሙሴም የእግዚአብሔርን ቃሎች ሁሉ ጻፈ። ማለዳ ላይም በተራራው ግርጌ መሠዊያ ሠራ፤ ዐሥራ ሁለቱን የእስራኤል ነገዶች እንዲወክሉም፣ ዐሥራ ሁለት የድንጋይ ዐምዶችን አቆመ። 5 የሚቃጠልና የኅብረት መሥዋዕቶችን ከበሬዎች ለእግዚአብሔር እንዲያቀርቡም፣ ጥቂት የእስራኤል ወጣት ወንዶችን ላከ። 6 ሙሴ የደሙን እኩሌታ በሣህን አደረገው፣ የቀረውንም እኩሌታ በመሠዊያው ላይ ረጨው። 7 መጽሐፍ ወስዶ ለሕዝቡ ጮኽ ብሎ አነበበላቸው። ሕዝቡም፣ “እግዚአብሔር የተናገረውን ሁሉእናደርጋለን፤ እንታዘዛለንም” ብለው ተናገር። 8 ሙሴ ደሙን ወስዶ በሕዝቡ ላይ ረጨው። “ይህ፣ ይህን የተስፋ ቃል ከእነዚህ ቃሎች ጋር ለእናንተ በመስጠት፣ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር የገባው የኪዳኑ ደም ነው” በማለትም ተናገረ። 9 ከዚያም በኋላ ሙሴ፣ አሮን፣ ናዳብ፣ አብድዩና ሰባው የእስራኤል ሽማግሌዎች ወደ ተራራው ወጡ። 10 የእስራኤልን አምላክ አዩት። ከእግሮቹ ሥርም እንደ ንጹሕ ሰማይ ከጠራ የሰንፔር ድንጋይ የተሠራ ወለል ነበረ። 11 በእስራኤላውያን ሽማግሌዎች ላይ ተቆጥሮ እጅ አላሳረፈባቸውም። እነርሱ እግዚአብሔርን አዩ፤ በሉ፣ ጠጡም። 12 እግዚአብሔር ሙሴን፣ “ተራራው ላይ ወደ እኔ ና፤ በዚያም ቆይ። የድንጋይ ጽላቱን ሕዝቡን እንድታስተምራቸውም የፋጽሏቸውን ሕጉንና ትእዛዛቱን እሰጥሃለሁ” አለው። 13 ስለዚህ ሙሴ ከረዳቱ ከኢያሱ ጋር ወደ እግዚአብሔር ተራራ ሄደ። 14 ሙሴ ሽማግሌዎቹን፣ “ተመልሰን ወደ እናንተ እስክንመጣ ድረስ እዚህ ቆዩን። አሮንና ሖር ከእናንተ ጋር ናቸው። ክርክር የሚኖርበት ሰው ካለ፣ ወደ እነርሱ ይቅረብ” አላቸው። 15 ወደ ተራራው ወጣ፤ ደመናውም ተራራውን ሸፈነው። 16 የእግዚአብሔር ክብር በሲና ተራራ ላይ ወረደ፤ ደመናውም ተራራውን ስድስት ቀን ሸፈነው። በሰባተኛው ቀን እግዚአብሔር ከደመናው ውስጥ ሙሴን ጠራው። 17 የእግዚአብሔርን ክብር እስራኤላውያን ሲያዩት እንደሚያጋይ እሳት ነበር። 18 ሙሴ ደመናው ውስጥ ገብቶ ወደ ተራራው ወጣ። በተራራውም ላይ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ቆየ።

Exodus 24:1

• ናዳብም አብዩድም
እነዚህ የወንዶች ስም ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ስሞችን የመተርግሞ ዘዴ የሚለውን ተመልከት፤ ከዘጸአት 6:23 ጋር አነጻጽር።

• ከእስራኤልም ሰባ ሽማግሌዎች
ከእስራኤል ሰዎች ወይም መሪዎች ሰባ የሚሆኑ

Exodus 24:3

• በአንድ ድምፅ
ይህ ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን ህዝቡ በፍጹም መስማማት መሆናቸውን ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፦ በአንድነት ወይም በመስማማት

• ከተራራውም በታች
በተራራው ሥር ወይም ከተራራው ግርጌ ማለት ነው

Exodus 24:5

• የደሙን እኩሌታ ወስዶ በቆሬ ውስጥ አደረገው
ሙሴ ሰዎችን ለመርጨት ከደሙ ግማሹን ወስዶ በገበቴ ወይም በባዝ ውስጥ አኖረው። ይህ የሚያሳየው የእስራኤል ህዝብ ከእግዚአብሔር ጋር ለሚያደርገው ቃል ኪዳን ማጽኛ ይሆን ዘንድ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ሙሴም ከእንስሶቹ ደም ግማሹን ወስዶ በገበቴ ውስጥ አኖረው”

• የደሙንም እኩሌታ በመሠዊያው ረጨው
“መሰዊያው” እግዚአብሔርን የሚወክል ነው። ይህ የሚያሳየው እግዚአብሔር በቃል ኪዳን ተሳታፊ መሆኑ የሚያረጋግጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ከእንስሳው ደም ግማሹን በመሠዊያው ፊት ረጨው”

Exodus 24:7

• እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እናደርጋለን
በሌላ አገላለጽ፦ ለእግዚአብሔር በሁሉ ነገር እንታዘዛለን

• ሙሴም ደሙን ውስዶ
ይህ ደም ሙሴ በገበቴው ውስጥ የጨመረው ደም እንጂ ሌላ ደም አይደለም። አማራጭ ትርጉም፦ “ሙሴ በገበቴ ያለውን ደም ወስዶ

Exodus 24:9

• ናዳብም አብዩድም
እነዚህ የወንዶች ስም ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ስሞችን የመተርግሞ ዘዴ የሚለውን ተመልከት፤ ከዘጸአት 6:23 ጋር አነጻጽር።

• ከእግሩም በታች
ይህ አባባል እግዚአብሔር እግር እንዳለው አድርጎ የሚያቀርብ ሰውኛ ዘይቤ ነው።

• እንደ ሰማይ መልክ የሚያበራ እንደ ብሩህ ሰንፔር ድንጋይ የሚመስል ወለል
ሰንፔር ከሚመባል ከሰማያዊ ድንጋይ የተሰራ የሚያንጸባርቅ ወለል

• ወለል
ጠንካራ የሆነ ለመራመድ ወይም ለመንዳት የሚያገልግል

• እንደ ሰማይ መልክ
ሰማያዊ ቀለም ያለው (የማይታወቁ ነገሮችን የመተርጎም ዘዴ የሚለውን ተመልከት)

• ሰንፔር ድንጋይ
የከበረ (ውድ) ድንጋይ ሲሆን ቀለሙ ሰማያዊ ነው

• እንደ ሰማይ መልክ የሚያበራ
ይህ ተነጻጻሪ ዘይቤ ሲሆን “እንደ ጠራ ሰማይ የሚያበራ ወይም ደመና እንደሌለው ሰማይ የጠራ”

• እጁንም በእስራኤል አዛውንቶች ላይ አልዘረጋም
ይህ ማለት እግዚአብሔር የእስራኤል ሽማግሌዎችን አልጎዳቸውም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ እግዚአብሔር የእስራኤል መሪዎች የሆኑ ሰዎችን አልቀሠፈም”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Exodus 24:12

• ሕግና ትእዛዝ የድንጋይም ጽላት እሰጥሃለሁ
በጠፍጣፋ ድንጋዮች ላይ እግዚአብሔር ህጉንና ትዕዛዛቱን ጻፈ። በሌላ አባባል፦ “እኔ በእነርሱ ላይ ትዕዛዛቱን የጻፍኩባቸውን ሁለቱን የድንጋይ ጽላቶች”

• ሙሴና ሎሌው ኢያሱ ተነሡ
ሙሴ ከረዳቱ ወይም ከአገልጋዩ ኢያሱ ጋር ተነሱ

Exodus 24:14

• በዚህ ቆዩን
እኔንና ኢያሱን ጠብቁ

• ሖር
ይህ ሰው የሙሴና የአሮን ቅርብ ጓደኛቸው ነው፤ ዘጸአት 17፡10 እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት

Exodus 24:16

• የእግዚአብሔርም ክብር
የእግዚአብሔርን ህልዎት የሚወክለው አንጸባራቂ ብርሃን

• እንደሚያቃጥል እሳት ነበረ (ተነጻጻሪ ዘይቤ)
የእግዚአብሔር (የያህዌ) ክብር ትልቅና እንደ እሳት የሚያቃጥል ሆኖ ቀርቧል። አማራጭ ትርጉም፦ እንደ ትልቅ እሳት የሚያቃጥል ነበር

• በእስራኤል ልጆች ፊት
ዓይኖቻቸው ማየትን፥ ማየታቸው ደግም ሀሳባቸውን ወይም የሚያዩትን ነገር እንዴት እንደሚፈርጁ አመልካቺ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ በእስራኤል ሕዝብ ዘንድ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 25

1 ሙሴን እንዲህ አለው፤ 2 “እያንዳንዱ ሰው ልቡ በፈቀደለት መሠረት ስጦታ ለእኔ እንዲያመጣ ለእስራኤላውያን ንገር። እነዚህን ስጦታዎች ተቀበልልኝ። 3 ከእነርሱ የምትቀበላቸውም ስጦታዎች እነዚህ ናቸው፦ ወርቅ፣ ብርና ነሐስ፤ 4 ሰማያዊ፣ ሐምራዊ፣ ቀይ ማግና የበፍታ ድር ልብስ፣ የፍየል ጠጕር፣ 5 ቀለም የተነከረ የአውራ በግ ቆዳና የአቆስጣ ቁርበት፣ የግራር ዕንጨት፤ 6 ለመቅደሱ መብራቶች ዘይት፣ ለመቅቢያው ዘይት ቅመሞችና ጣፋጭ መዐዛ ያለው ዕጣን፤ 7 ለኤፉድና ለደረት ኪሱ የሚሆኑ መረግዶችና ሌሎች ዕንቆች። 8 እንዳድር ሕዝቡ መቅደስ ይሥሩልኝ። 9 ለመገናኛው ድንኳንና ለዕቃዎቹ ሁሉ እኔ ባሳየሁህ ምሳሌ መሠረት ሥሩት። 10 ሁለት ክንድ ተኩል፣ ስፋቱ አንድ ክንድ ተኩል፣ ቁመቱም አንድ ክንድ ተኩል የሆነ ታቦት ከግራር ዕንጨት ይሠሩ። 11 ውስጡንም ውጭውንም በንጹሕ ወርቅ ለብጠው፤ በዙሪያውም የወርቅ ክፈፍ አድርግለት። 12 የወርቅ ቀለበቶችን ሠርተህለት በታቦቱ አራት እግሮች ላይ፣ ሁለቱን በአንድ ጎኑ፣ ሁለቱን ደግሞ በሌላው ጎኑ አስቀምጣቸው። 13 መሎጎያዎችን ከግራር ዕንጨት ሥራና አወርቅ ለብጣቸው። 14 ታቦቱን ለመሸከም መሎጊያዎቹን በታቦቱ ጎን ባሉ ቀለበቶች ውስጥ አስገባ። 15 መሎጊያዎቹ ምንጊዜም በታቦቱ ቀለበቶች ውስጥ ይቀመጣሉ እንጂ ከዚያ አይወጡም። 16 የኪዳኑን ምስክሮች በታቦቱ ውስጥ ታስቀምጣለህ። 17 ሁለት ክንድ ተኩል፣ ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል የሆነ የስርየት መክደኛ ከንጹሕ ወርቅ ሥራ። 18 ለሁለቱ የስርየት መክደኛ ጫፎች ሁለት ኪሩቤልን ከተቀጠቀጠ ወርቅ ትሠራለህ። 19 ኪሩብ ለስርየት መክደኛው አንድ ጫፍ፣ ሌላውን ኪሩብ ደግሞ ለሌላው ጫፍ በማድረግ ከስርየት መክደኛው ጋር ወጥ ሆነው መሠራት አለባቸው። 20 ክንፎቻቸውን ወደ ላይ መዘርጋትና የስርየት መክደኛውን በክንፎቻቸው መጋረድ ይኖርባቸዋል። እርስ በርሳቸው መተያየትና ወደ ስርየት መክደኛውም መመልከት አለባቸው። 21 መክደኛውን በታቦቱ ላይ ታደርገዋለህ፤ በታቦቱ ውስጥም የምሰጥህን የኪዳኑን ምስክሮች ታስቀምጣለህ። 22 እኔ ከአንተ ጋር የምገናኘው በታቦቱ ነው። በስርየት መክደኛው ላይ ሆኜ ከአንተ በተናገርሁበት በምስክሩ ታቦት ላይ ባሉት በሁለቱ ኪሩቤል መካከል ነው። 23 እርዝመቱ ሁለት ክንድ፣ ወርዱ አንድ ክንድ፣ ቁመቱም አንድ ክንድ ተኩል የሆነ ጠረጴዛ ከግራር ዕንጨት ሥራ። 24 ወርቅ ለብጠው፤ በዙሪያውም የወርቅ ክፈፍ አድርግለት። 25 አንድ ስንዝር ስፋት ያለው ጠርዝ ለጠርዙ በዙሪያው ከሚኖረው የወርቅ ክፈፍ ጋር አብጅለት። 26 አራት የወርቅ ቀለበቶችን ሥራለትና ቀለበቶችን አራቱ እግሮቹ ባሉበት ከሚገኙት አራት ማዕዘኖች ጋር አያይዛቸው። 27 ለማስቀመጥና ጠረጴዛውን መሸከም እንዲቻል፣ ቀለበቶቹ ከክፈፉ ጋር መያያዝ አለባቸው። 28 የጠረጴዛው መሸከሚያ እንዲሆኑም መሎጊያዎችን ከግራር ዕንጨት ሥራና በወርቅ ለብጣቸው። 29 ቊርባኑን ለማፍሰስ ጥቅም እንዲሰጡ ወጭቶችን፣ ጭልፋዎችን፣ ማንቆርቆሪያዎችንና ጎድጓዳ ሣህኖችን ከንጹህ ወርቅ ሥራ። 30 በጠረጴዛውም ላይ የገጽ ኅብስት ሁልጊዜ በፊቴ ታደርጋለህ። 31 መቆሚያና ዘንግ አበጅተህበት ከተቀጠቀጠ ንጹሕ ወርቅ መቅረዝ። ጽዋዎቹ፣ ቀንበጦቹና አበባዎቹ ሁሉ ወጥ ሆነው ከመቅረዙ ጋር ይሠራሉ። 32 ሦስት ቅርንጫፎች በአንድ ጎን፣ ሦስት ቅርንጫፍ ደግሞ በሌላው ጎን፣ ስድስት ቅርንጫፎች ለመቅረዙ ይውጡለት። 33 የመጀመሪያው ቅርንጫፍ የለውዝ አበቦችን መስለው የተሠሩ ሦስት ጽዋዎች ከቀንበጥና ክአበባ ጋር፣ በሌላው ቅርንጫፍም እንደዚሁ የለውዝ አበቦችን የሚመስሉ ሦስት ጽዋዎች የተቀረጹበት ከቀንበጥና ከአበባ ጋር ሊኖሩት ይገባል። ከመቅረዙ በሚወጡት በስድስት ቅርንጫፎች ሁሉ ላይ የሚሆነውም እንደዚሁ አንድ ዐይነት ነው። 34 ላይ የለውዝ አበባ መስለው የተቀረጹ አራት ጽዋዎች ከቀንበጦቹና ከአበባዎቹ ጋር ሊኖሩበት ይገባል። 35 በመጀመሪያዎቹ ቅርንጫፎች ጥንድ ሥር ወጥ ሆኖ ዐብሮ የተሠራ ቀንበጥ፣ በሁለተኛው የቅርንጫፎች ጥንድ ሥርም እንደዚሁ ወጥ ሆኖ ዐብሮ የተሠራ ቀንበጥ ይኖረዋል። በሦስተኛው የቅርንጫፎቹ ጥንድ ሥርም ወጥ ሆኖ ዐብሮ የተሠራ ቀንበጥ ይበጅለታል። ከመቅረዙ በሚወጡ በስድስቱ ቅርንጫፎች ሁሉ የሚሆነውም ይኸው አንድ ዐይነት ነው። 36 ቀንበጦቻቸውና ቅርንጫፎቻቸው ሁሉ አንድ ወጥና ከተቀጠቀጠ ንጹሕ ወርቅ የተሠሩ መሆን አለባቸው። 37 መቅረዙንና ሰባት መብራቶችን ሠርተህ ፊት ለፊት ላለው ስፍራ ብርሃን እንዲሰጥ አድርግ። 38 የኰስታሪ መሰብሰቢያ ሣህኖቻቸው ከንጹሕ ወርቅ መሠራት አለባቸው። 39 መቅረዙንና የመቅረዙን ዕቃ ሁሉ ለመሥራት አንድ መክሊት ንጹሕ ወርቅ ተጠቀም። 40 ላይ ባሳየሁህ ምሳሌ መሠረት የሠራሃቸው ስለ መሆንህ እርግጠኛ ሁን።

Exodus 25:1

• በልቡ ከሚያምረው ሰው ሁሉ
ይህ ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን ስጦታ ለመስጠት የተነሳሳን አንድ ሰው ፍልጎት ወይም በጎ ፈቃድ ያሳያል አማራጭ ትርጉም፦ ስጦታ ለመስጠት የሚፈልግ ሰው

• መባ ተቀበሉ
“ተቀበሉ” ተብሎ የተነገራቸው ሙሴንና የእስራኤል መሪዎችን/ ሽማግሌዎችን/ ነው። የሚቀበሉትም ህዝቡ የሚያመጣውን ስጦታ ወይም መስዋዕት ወይም ቁርባን ነው።

Exodus 25:3

አጠቃላይ ዕይታ፦
እስራኤላውያን ማድረግ ያለባቸውን ነገር እግዚአብሔር(ያህዌ) በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል።

• ሰማያዊ፥ ሐምራዊና ቀይ ግምጃ
አማራጭ ትርጉሞች፦ 1) በሰማያዊ፥ ሀምራዊና ቀይ ቀለም የተቀቡ ልብሶች/ ሶፎች/ ወይም 2) ላይነኖችን ለመቀባት የሚረዱ ሰማያዊ፥ ሐምራዊና ሰማያዊ ቀለም

• ቀይ ግምጃ
ነጣ ያለ ቀይ ቀለም ወይም በቀይ ቀለም የተቀለመ ጨርቅ

• የአስቆጣ ቁርበት
ግዙፍና ሳር በል የሆነ የባህር እንስሳ

• ለጣፋጭ ዕጣን ቅመም
የደረቁ የእጽዋት ተዋጽኦ ሲሆን ሰዎች ፈጭተው ጥሩ ሽታ እንድኖረው ዘይት ወይም ምግብ በዚያ ላይ ጨምረው የሚሰሩት ነው።

• መረግድ
በላዩ ላይ ሁለት ቅርፍት ያለው ማለትም ነጭ ወይም ጥቁር፥ ቀይ ያለው የድንጋይ ዓይነት

Exodus 25:8

አጠቃላይ ዕይታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• ቤተ መቅደስ . . . ድንኳን
“ቤተ መቅደስ” የሚለው “ቅዱስ ስፍራ” የሚገልጽ ሲሆን “ድንኳን” ደግሞ “ቅዱስ ድንኳን” ወይም ጊዜያዊ ቤት/መቆያ/ዳስ/ የሚል ፍቺ አለው። ሁለቱም ተመሳሳይ ፍቺ የሚሰጡ ተወራራሽ ቃላት ናቸው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• እኔ እንደማሳይህ ሁሉ . . . እንዲሁ ሥሩት
“እኔ በማሳይህ” የሚለው ሀረግ ሙሴን የሚመለከት ሲሆን “ሥሩት” ሙሴንና የእስራኤልን ህዝብ የሚመለከት ነው።

• እኔ እንደማሳይህ ሁሉ
ሁሉንም እኔ በማሳይህ ዕቅድ መሠረት

Exodus 25:10

አጠቃላይ ዕይታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል፥ ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል፤ ቁመቱም አንድ ክንድ ተኩል
ርዝመቱ አንድ ሜትር ከአስራ አምስት ሴንቲ ሜትር ስፋቱና ከፍታው ሥልሳ ዘጠኝ ሳንቲ ሜትር። አንድ ክንድ 46 ሴንቲ ሜትር ያክል ነው።

Exodus 25:12

አጠቃላይ ዕይታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• አራት የወርቅ ቀለበቶችም አድርግለት
“የወርቅ ቀለበቶችን አድርግለት” የሚለው ወርቆችን በማቅለጥ በቀለበት መልክ ማውጣቱን ወይም ማድረቁን የሚመለከት ነው። በሌላ አገላለጽ፦ አራት የወርቅ ዋልታዎችንም ወይም ቀለበቶችን ሠርተህ

• ለታቦቱ መሸከሚያ
ታቦቱን ለመሸከም እንዲያገለግል

Exodus 25:15

አጠቃላይ ዕይታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• የስርየት መክደኛ
በምስክሩ ታቦት ላይ የሚቀመጥና የስርየት መስዋዕቱን የሚሸፍን መክደኛ ነው

• ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል፥ ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል፤ ቁመቱም አንድ ክንድ ተኩል
ርዝመቱ አንድ ሜትር ከአስራ አምስት ሴንቲ ሜትር ስፋቱና ከፍታው ሥልሳ ዘጠኝ ሳንቲ ሜትር። አንድ ክንድ 46 ሴንቲ ሜትር ያክል ነው።

• የተቀጠቀጠ ወርቅ
ተቀጥቅጦ የተሰራ ወርቅ

Exodus 25:19

አጠቃላይ ዕይታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• የስርየት መክደኛ
በምስክሩ ታቦት ላይ የሚቀመጥና የስርየት መስዋዕቱን የሚሸፍን መክደኛ ነው

• በአንድ ላይ ትሠራዋለህ
እነርሱም ከክዳኑ ጋር አብረው/ተያይዘው/ የተሠሩ ይሁኑ

Exodus 25:22

አጠቃላይ ዕይታ፦
እግዚአብሔር ለሙሴ መናገሩን ቀጥሏል

• በዚያም ከአንተ ጋር እገናኛለሁ
እኔ በታቦቱ መክደኛ ላይ ባሉ በሁለቱ ክሩቤሎች ውስጥ ሆኜ ለአንተ እገለጥልሃለሁ

• የስርየት መክደኛ
በምስክሩ ታቦት ላይ የሚቀመጥና የስርየት መስዋዕቱን የሚሸፍን መክደኛ ነው

Exodus 25:23

አጠቃላይ ዕይታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል፥ ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል፤ ቁመቱም አንድ ክንድ ተኩል
ርዝመቱ አንድ ሜትር ከአስራ አምስት ሴንቲ ሜትር ስፋቱና ከፍታው ሥልሳ ዘጠኝ ሳንቲ ሜትር። አንድ ክንድ 46 ሴንቲ ሜትር ያክል ነው።

Exodus 25:25

አጠቃላይ ዕይታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• አንድ ጋት የሚያህል ክፈፍ
በባህላዊው ልከት አንድ ጋት የአራት ጣቶች ጥምር ማለት ሲሆን ከ8-10 ሳንቲ ሜትር ያህል ነው።

• ክፈፍ አድርግለት
ጠርዝ ሥራለት/አብጅለት/

• የወርቅ ቀለበቶች አድርግለት
የወርቅ ቀለበቶችን በጠርዙ ላይ አያይዝ

• ገበታውንም ለመሸከም
ጠረጴዛውን ለመሸከም እንዲያገለግል

Exodus 25:28

አጠቃላይ ዕይታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• ገበታውን ይሸከሙባቸው ዘንድ
በሌላ አገላለጽ፦ አንተ እነርሱን አስገብተህ ጠረጴዛውን መሸከም እንድትችል

• ለማፍሰሻም ይሆኑ ዘንድ
በሌላ አገላለጽ፦ አንተ እነርሱን ለወይን ጠጅ መቅጃ እንድትጠቀም

• በገበታም ላይ የገጽ ኅብስት
በጠረጴዛው ላይ ሆኖ ለእኔ የሚቀርበው የተቀደሰ ኅብስት/ዳቦ/

Exodus 25:31

• መቅረዝንም ከጥሩ ወርቅ አድርግ
መብራት ማስቀመጫ ባላ መሳይ ነገር

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• ጽዋዎቹም ጉብጉቦቹም አበቦቹም አንድነት በእርሱ ይደረጉበት
ለጌጥ ወይም የውበት አበባዎች፥ እንቡጦችና ቀንበጦች ከእርሱ ጋር አንድ ሆነው ይሠሩ

Exodus 25:33

አጠቃላይ ዕይታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል። በሚቀጥሉት ክፍሎች እግዚአብሔር (ያህዌ) የመብራት ማስቀመጫውን (የመቅረዙን) አሰራር ዝርዝር ይናገራል (ዘጸአት 25፡31-32 ተመልከት)

• የለውዝ አበባ የሚመስሉትን ጽዋዎች
ነጭ ወይም ሮዝ ቀለም/ቀላ ያለ አምራዊ/ መልክ ያለው አበባ የሚያወጣና አምስት ቀነበጦች ያሉት

Exodus 25:35

አጠቃላይ ዕይታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል። በሚቀጥሉት ክፍሎች እግዚአብሔር (ያህዌ) የመብራት ማስቀመጫውን (የመቅረዙን) አሰራር ዝርዝር ይናገራል (ዘጸአት 25፡31-32 ተመልከት)

• ጉብጉቦቹና ቅርንጫፎቹ ሁሉ ከእርሱ ጋር አንድ ይሁኑ
እንቡጦቹ፥ ቅርንጫፎቹና መቅረዙ ሁሉም አንድ ወጥ ሆነው ይሰሩ

Exodus 25:37

አጠቃላይ ዕይታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል።

• በፊቱ ያበሩ ዘንድ
ከፊት ለፊት በኩል ወይም ወደ ፊት እንዲያበሩ

• መኮስተሪያዎችዋን የኩስታሪ ማድረጊያዎችዋንም ከጥሩ ወርቅ አድርግ
መለኮሻዎችንና የአመድ ማስቀመጫ ሳሕኖችን ከንጹሕ ወርቅ ሥራ

• መቅረዙም ዕቃውም ሁሉ ከአንድ መክሊት ጥሩ ወርቅ ይሠሩ
አንድ መክሊት ወደ ከ33-35 ኪሎ ግራም ያህል ነው። በሌላ አገላለጽ፦ መብራት ማስቀመጫውን (መቅረዙን) እና እነዚህን ሁሉ ዕቃዎች ሠላሳ አምስት ኪሎ ግራም ከሆነ ንጹሕ ወርቅ ሥራ።

• በተራራ ላይ እንዳሳየሁህ ምሳሌ እንድትሠራ ተጠንቀቅ
አማራጭ ትርጉም፦ “እኔ አንተን በተራራው ላይ ያሳየሁትን ምሳሌ ተከትለህ በጥንቃቄ ሥራ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 26

1 ከተፈተለ በፍታ ድር፣ ከሰማያዊ፣ ከሐምራዊና ከቀይ ማግ ከተሠሩና ኪሩቤል ከተጠለፉባቸው ዐሥር መጋረጃዎች ጋር ማደሪያ ድንኳኑን ሥራ። ይህም ብልኅ
ሠራተኛ የሚሠራው ሥራ ነው። 2 የያንዳንዱ መጋረሣ እርዝመት ሃያ ስምንት ክንድ፣ ወርዱ አራት ክንድ ይሁን። መጋረጃዎቹ ሁሉ እኩል መጠን ይኑራቸው። 3
ዐምስቱ መጋረጃዎች እርስ በርስ መያያዝ አለባቸው፤ ሌሎቹ ዐምስት መጋረጃዎችም እንደዚሁ እርስ በርሳቸው መገጣጠም ይኖርባቸዋል። 4 በአንደኛው ወገን
የመጨረሻ መጋረጃ የውጭ ጠርዝ ላይ የሰማያዊ ግምጃ ቀለበቶችን አድርግ። ለሁለተኛው ወገን የመጨረሻ መጋረጃ የውጭ ጠርዝም ይህንኑ አበጅለት። 5
ዐምሳ ቀለበቶችን በአንደኛው የመጋረጃ ወገን፣ ዐምሳ ቀለበቶችን በሌላው የመጨረሻ መጋረጃ ላይ አድርግ። ይህን የምትሠራውም ቀለበቶቹ እርስ በርስ
እንዲተያዩ በማድረግ ነው። 6 ዐምሳ የወርቅ ማያያዣዊችብ ሠርተህ ማደሪያ ድንኳኑ አንድ እንዲሆን፣ መጋረጃዎቹን በእነርሱ አያይዛቸው። 7 ከማደሪያው በላይ
ለድንኳን የሚሆኑ ዐሥራ አንድ የፍየል ጠጕር መጋረጃዎችን ሥራ። 8 መጋረጃ እርዝመት ሠላሳ ክንድ፣ ወርዱ አራት ክንድ ይሁን። ዐሥራ አንዱም መጋረጃዎች
እኩል መጠን ይኑራቸው። 9 ዐምስት መጋረጃዎችን በአንድነት፣ ስድስት መጋረጃውችንም እንዲሁ እርስ በርስ አያይዛቸው። ስድስተኛውን መጋረጃ በድንኳኑ ፊት
ዕጠፈው። 10 በመጀመሪያ ተገጣጣሚ የመጨረሻ መጋረጃ ጠርዝ ላይ ዐምሳ ቀለበቶችን፣ ሁለተኛውን የመጋረጃ አካል በሚያገጣጥመው የመጨረሻ መጋረጃ
ጠርዝ ላይም እንደዚሁ ዐምሳ ቀለበቶችን አድርግ። 11 ዐምሳ የነሐስ ማያያዣዎችን ሥራና በቀለበቶቹ ውስጥ አስገ ባቸው። ከዚያም አንድ ወጥ እንዲሆን
ድንኳኑን አገጣጥመው። 12 መጋረጃዎች ተንጠልጥሎ ያለው ቀሪ ግማሽ መጋረጃ ከማደሪያ ድንኳኑ ጀርባ ይንጠልጠል። 13 ከመጋረጃዎቹ እርዝመት የተረፈው
በአንድ በኩል አንድ ክንድ ምጋረጃ፣ 14 በሌላው ጎንም አንድ ክንድ መጋረጃ ማደሪያው ድንኳን መሸፈኛ በቀይ ቀለም የተነከረ የአውራ በግ ቆዳና ከዚያም በላይ
የሚሆን የአስቆጣ ቁርበት አዘጋጅ። 15 ለማደሪያው ድንኳን የሚሆኑ ወጋግራዎችን ከግራር ዕንጨት አብጅ። 16 ወጋግራ እርዝመት ዐሥር ክንድ፣ ወርዱም አንድ
ክንድ ተኩል ይሁን። 17 በርስ የሚያገናኟቸው ሁለት ጕጣጕጦች በያንዳንዱ ወጋግራ ላይ ይኑር። የመገናኛ ድንኳኑን ወጋግራዎች ሁሉ በዚህ መንገድ ሥራ። 18
ድንኳን ወጋግራዎችን ስታበጅ፣ በደቡብ መኩል ላለው ሃያ ወጋግራዎችን አብጅ። 19 ወጋግራዎች የሚሆኑ አርባ የብር መቆሚያዎችን አብጅ። ከመጀመሪያው
ወጋግራ ሥር ሁለት መጋጠሚያዎች እንዲሆኑ ሁለት መቆሚያዎች ይኑሩ። በሌሎች ወጋግራዎች በያንዳንዳቸው ሥርም ለሁለት መጋጠሚያዎቻቸው ሁለት
መቆሚያዎች ይዘጋጁ። 20 በሰሜን በኩል ላለው ለሁለተኛው የመገናኛው ድንኳን ጎን ሃያ ወጋግራዎችንና አርባ የብር መቆሚያዎቻቸውን ሥራ። 21
በመጀመሪያው ወጋግራ ሥር ሁለት መቆሚያዎች፣ በሚቀጥለው ወጋግራ ሥርም እንደዚሁ ሁለት መቆሚያዎች. በእያንዳንዱ ሥር ይሁኑ። 22 በምዕራብ በኩል
ላለው ለመገናኛው ድንኳኑ የኋላ ጎን ስድስት ወጋግራዎችን አብጅ። 23 ለኋላ ማእዘኖቹም ሁለት ወጋግራዎችን አብጅ። 24 እነዚህ ወጋግራዎች ከታች ጥንድ፣
ከላይ ደግሞ በአንድ ቀለበት የተያያዙ መሆን አለባቸው። ለሁለቱም የኋላ ማእዘኖች የሚሆነው በዚህ መንገድ ነው። 25 ወጋግራዎች ከብር መቆሚያዎቻቸው
ጋር ሊኖሩ ይገባል። በሁሉም ዐሥራ ስድስት መቆሚያዎች ናቸው ያሉት፤ በመጀመሪያው ወጋግራ ሥር ሁለት መቆሚያዎች፣ በሚቀጥለው ወጋራ ሥርም ሁለት
መቆሚያዎችና በእያንዳንዱም ሥር እንዲሁ። 26 ድንኳኑ አንደኛ ጎን ወጋግራዎች ዐምስት አግዳሚዎችን ከግራር ዕንጨት አዘጋጅ፤ 27 ለማደሪያ ድንኳኑ ሌላ
ጎንም ወጋግራዎች ዐምስት አግዳሚዎችን፣ በምዕራብ በኩል ላለው ለመገናኛ ድንኳኑ የኋላ ጎን ወጋግራዎችም ዐምስት አግዳሚዎችን እንዲሁ አብጅ። 28
በወጋግራዎቹ መካከል ላይ ያለው አግዳሚ ከዳር እስከ ዳር መድረስ አለበት። 29 ወጋግራዎቹን በወርቅ ለብጣቸው። አግዳሞዎችን ደግፍ በመያዝ
እንዲያገለግሉም የወርቅ ቀለበቶቻቸውን ሥራላቸው፤ አግዳሚዎችንም በወርቅ ለብጣቸው። 30 ድንኳኑን መትከል ያለብህ በተራራው ላይ ያየኸውን ምሳሌ
በመተከትል ነው። 31 ብልኅ ሠራተኛ ኪሩቤልን የጠለፈበት፣ የሰማያዊ፣ የሐምራዊ፣ የቀይ ግምጃና አምሮ የተፈተለ በፍታ መጋረጃ አብጅ። 32 በወርቅ በተለበጡ
የግራር ዕንጨት አራት ዐምዶች ላይ ልትሰቅለው ይገባል። እነዚህ ዐምዶች በአራት የብር መቆሚያዎች ላይ የተቀመጡ የወርቅ ኩላቦች ይኖሯቸዋል። 33
መጋረጃውን በማያያዣዎቹ አንጠልጥለው፤ የምስክሩንም ታቦት አግባው። መጋረጃው ቅድስቱን ከቅድስተ ቅዱሳን ይለየዋል። 34 በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ ባለ
ውበምስክሩ ታቦት ላይ የስርየት መክደኛውን አስቀምጥ። 35 ከመጋረጃው ውጭ፣ መቅረዙንም ከመገናኛው ድንኳን ደቡባዊ ጎን ከጠረጴዛው ትይዩ
አስቀምጥ። ጠረጴዛው በሰሜናዊ ጎኑ በኩል መቀመጥ ይኖርበታል። 36 መግቢያ ከሰማያዊ፣ ከሐምራዊ፣ ከቀይ ማግና አምሮ ከተፈተለ በፍታ በጥልፍ
ብሚያስጌጥ ሠራተኛ የተሠራ መጋረጃ አብጅለት። 37 ዐምስት ምሰሶዎችን ከግራር ዕንጨት አብጅና በወርቅ ለብጣቸው። ኩላቦቻቸውም የውርቅ መሆን
እላቸው፤ ዐምስት የነሐስ መቆሚያዎችንም ሥራላቸው።

Exodus 26:1

አጠቃላይ ምልከታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል።

• ማደሪያ ሥራ
በዚህ ክፍል “ሥራ” ተብሎ የታዘዘው ሙሴ ነው። ሙሴ ሥራውን ለሚሰራው ሰው የሥራውን ዝርዝር እንዲያሳየውና በሀላፊነት እንዲቆጣጠረው መታዘዙን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ለሠራተኛው ንገረው”

• መጋረጃ
ክብደት ያለው እና ትልቅ የተሰፋ ጨርቅ ሲሆን መገናኛውን ድንኳን ለመሸፈንና የድንኳኑን ውስጠኛውን ክፍል ለመከፋፈል የሚያገለግል ነው።

• ከቀይም ግምጃ የተሠሩ
በቀይ ቀለም የተቀባ ወይም የተነከረ ሱፍ ጨርቅ

• ብልህ ሠራተኛ
የተውቡና ያገጡ ነገሮችን በእጅ የሚሰራ “እደ ጥበብ” ሰራተኛ

• ርዝመት ሀያ ስምንት ክንድ፣ ወርዱም አራት ክንድ ይሁን
ርዝመቱ 12 ሜትር ከ88 ሳ.ሜት እንዲሁም ወርዱ 1.ሜትር ከ82 ሳንት ሜትር

• አምስቱ መጋረጆች እርስ በርሳቸው የተጋጠሙ ይሁኑ፣ አምስቱም መጋረጆች እንዲሁ እርስ በርሳቸው የተጋጠሙ ይሁኑ
በአድራጊ ግስ ሲጻፍ፦ አምስቱን መጋረጃዎችን በአንድ ላይ ስፏቸው እንዲሁም ሌሎችን አምስት መጋረጃዎችን በአንድ ሰፏቸው

Exodus 26:4

• ቀለበቶች አድርግ
መጋረጃዎችን ለማያያዝ የሚጠቅሙ/የሚያገለግሉ/ ከሰማያዊ ጨርቅ የተሰሩ ቀለበቶች ናቸው።

Exodus 26:7

አጠቃላይ ምልከታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• አስራ አንድ . . . ሠላሳ . . . አራት
የመጋረጃዎችን ርዝመት፥ ስፋትና ከፍታ የሚያሳዩ ቁጥሮች ናቸው።

• ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሴንት ሜትር ያህል ነው

Exodus 26:10

አጠቃላይ ምልከታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• ቀለበቶች
መጋረጃዎችን ለማያያዝ የሚጠቅሙ/የሚያገለግሉ/ ከሰማያዊ ጨርቅ የተሰሩ ቀለበቶች ናቸው

Exodus 26:12

አጠቃላይ ምልከታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሴንት ሜትር ያህል ነው

• ከቀይ አውራ በግ ቁርበት
በቀይ ቀለም የተነከረ የበግ ቁርበት

Exodus 26:15

አጠቃላይ ምልከታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• ለማደሪያውም የሚቆሙትን ሳንቆች
ድንኳኑን የሚደግፉ ቋሚዎችን ወይም ለማደሪያው ድንኳን ወጋግራዎችን አብጅ”

• አንድ ክንድ ተኩል
ወደ ሰባ (70) ሴንት ሜትር ያህል ነው

Exodus 26:19

አጠቃላይ ምልከታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• የብር እግሮችን አድርግ
የብር መቆሚያዎችን አብጅ

• ከእያንዳንዱም ሳንቃ በታች ሁለት እግሮች ይሁኑ
በእያንዳንዱ ወጋግራ/ተራዳ ሥር ሁለት ሁለት መቆሚያ አድርግ

Exodus 26:22

አጠቃላይ ምልከታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• ከታችም እስከ ላይ እስከ አንደኛው ቀለበት ድረስ አንዱ ሳንቃ ድርብ ይሁን
ከታች በኩል ተጣምረው እስከ ላይ አንደኛው ዋልታ መያያዝ አለባቸው

• የብር እግሮቻቸው ይሁኑ
የብር መቆሚያዎች ይኑሩ/ይሰሩ/

Exodus 26:26

አጠቃላይ ምልከታ፦
የመገናኛውን ድንኳን እንዴት መገንባት እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴ መናገሩን ቀጥሏል

• መወርወሪያዎች
አግዳሚዎች/ አግዳሚ ብረቶች/አግዳሚ እንጨቶች/

• በማደሪያውም በስተ ኋላ በምዕራብ ወገን ላሉት ሳንቆች
የመገናኛው ድንኳን ፊቱ ወደ ምስራቅ የተመለሰ ነው

Exodus 26:31

አጠቃላይ ምልከታ፦
የመገናኛውን ድንኳን እንዴት መገንባት እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴ መናገሩን ቀጥሏል

አድርግ
በዚህ ክፍል “አድርግ” ተብሎ የታዘዘው ሙሴ ነው። ሙሴ ሥራውን ለሚሰራው ሰው የሥራውን ዝርዝር እንዲያሳየውና በሀላፊነት እንዲቆጣጠረው መታዘዙን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “እንዲሠራ ለሠራተኛው ንገረው”

• የምስክርን ታቦት አግባው
የቃል ኪዳን ታቦት ከመጋረጃው በስተኋላ በኩል አኑረው/አስቀምጠው

• መጋረጃውም በቅድስቱና በቅድስተ ቅዱሳኑ መካከል መለያ ይሁናችሁ
መጋረጃው ቅድስት የተባለውን ስፍራ ቅድስተ ቅዱሳኑ ከተባለው ሥፍራ የሚለይ ይሁን

Exodus 26:34

አጠቃላይ ምልከታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• የስርየት መክደኛውን
በታቦቱ ላይ የሚቀመጠው የማስተሰሪያ መስዋዕት የተሰራበት መክደኛ ወይም መሸፈኛ (ዘጸአት 25:17 ተመልከት)

• በምስክሩ ታቦት ላይ አድርግ
የቃል ኪዳን ታቦት እንደማለት ነው። በድንጋይ ጽላት ላይ የተጻፉት ቃላት እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ለገባው ቃል ኪዳን ምስክር እንዲሆን ነው።

• ገበታውንም በሰሜን ወገን አድርገው
ይህ ገበታ የህሊዎተ እግዚአብሔር መገኛ ምሳሌ የሆነው ዳቦ ያለበት ነው። በሌላ አገላለጽ፦ ጠረጴዛውን/የዳቦ ማስቀመጫውን/ ከቅድስተ ቅዱሳኑ ክፍል ውጪ ከማደሪያ ድንኳን በስተ ሰሜን በኩል አኑር/አስቀምጥ/

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Exodus 26:36

አጠቃላይ ምልከታ፦
የመገናኛውን ድንኳን እንዴት መገንባት እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴ መናገሩን ቀጥሏል

• ከሰማያዊ ከሐምራዊም ከቀይም ግምጃ
ይህ አገላለጽ ሁለት ፍቺዎች አሉት፤ 1) በቀይ ቀለም የተቀባ ወይም የተነከረ ክር ወይም የሱፍ ጨርቅ 2) ሰማያዊ፥ ሐምራዊና ቀይ የሆነ ክር ወይም የሱፍ ጨርቅ።

• ከተፈተለ ከጥሩ በፍታ
በእጅ የተፈተለ ወይም የተሰራ የሱፍ ክርም ማግም ሊሆን ይችላል

• በጥልፍ አሠራር የተሠራ መጋረጃ
በጥልፍ ያጌጠ መጋረጃ ወይም በጥልፍ ዐዋቂ የተጠለፈ መጋረጃ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 27

1 ዐምስት ክንድ ወርዱም ዐምስት ክንድ የሆነ መሠዊያ ከግራር ዕንጨት ሥራ። መሠዊያው አራት ማእዘንና ሦስት ክንድ ከፍታ ይኑረው። 2 ማእዘኖች የበሬ
ቀንድ ቅርጽ እንዲኖራቸው ታደርጋለህ። ቀንዶቹ ከመሠዊያው ጋር አንድ ወጥና በነሐስ የተለበጡ ይሆናሉ። 3 የመሠዊያውን ዕቃዎች፦ የዐመድ ማስወገጃ
ምንቸቶችን፣ መጫሪያዎችን፣ ጎድጓዳ ሳሕኖችን፣ የሥጋ ሜንጦዎችንና የፍም መያዣዎችን ሁሉ ከነሐስ አብጃቸው። 4 ለመሠዊያው ከነሐስ እንደ መረብ የተሠራ
ፍርግርግ አብጅለት። በፍርግርጉ አራት ማእዘኖች በያንዳንዳቸው ላይም የነሐስ ቀለበት አድርግ። 5 አጋማሽ ወገብ እስከ ታች እንዲደርስ ፍርግርጉን
ከመሠዊያው እርከን ሥር አድርገው። 6 ለመሠዊያው መሎጊያዎችን ከግራር ዕንጨት አበጅተህ በነሐስ ለብጣቸው። 7 በቀለበቶቹ ውስጥ መግባትና
መሠዊያውን ለመሸከም በሁለቱ ጎኖቹ ላይ መቀመጥ አለባቸው። 8 ባዶ እንዲሆን ከሳንቃዎች አብጀው። በተራራው ላይ ባየኸው መሠረት ልትሠራው ይገባል።
9 ድንኳን አደባባይ ሥራለት። በአደባባዩ ደቡብ ጎንም አንድ መቶ ክንድ እርዝመት ያላቸው የአማረ በፍታ መጋረጃዎች ይደረጉ። 10 መጋረጃዎቹ ከሃያ የነሐስ
መቆሚያዎች ጋር ሃያ ምሰሶዎች ይኑሯቸው። ከምስሶዎቹ ጋር የተያያዙ የብር ኩላቦችና ዘንጎችም መኖር አለባቸው። 11 በሰሜን በኩልም እንደዚሁ አንድ መቶ
ክንድ ርዝመት ያላቸው መጋረጃዎች ከሃያ ምሰሶዎች፣ ከሃያ የነሐስ መቆሚያዎችም ጋር ከምሰሶዎቹ ጋር የተያያዙ የብር ኩላቦችና ዘንጎች ሊኖሩ ይገባል። 12
በአደባባዩ ምዕራብ ጎንም ዐምሳ ክንድ ርዝመት ያለው መጋረጃ ይደረግ። ዐሥር ምሰሶዎችና ዐሥር መቆሚያዎችም ይኑሩት። 13 በምሥራቅም በኩል አደባባዩ
ዐምሳ ክንድ እርዝመት ይኑረው። 14 የመግቢያው አንድ ጎን መጋረጃዎች ዐሥራ ዐምስት ክንድ እርዝመት ሊኖራቸው ይገባል። ሦስት ምሰዎችም ከሦስት
መቆሚያዎች ጋር ይኖሯቸዋል። 15 ሌላው ጎንም ዐሥራ ዐምስት ክንድ እርዝመት ያላቸው መጋረጃዎች ይኖሩታል። የራሳቸው ሦስት ምሰሶዎችና ሦስት
መቆሚያዎች ይኖሯቸዋል። 16 መግቢያ መጋረጃ ሃያ ክንድ እርዝመት ያለው፣ ከሰማያዊ፣ ከሐምራዊ፣ ከቀይ ማግና አምሮ ከተፈተለ በፍታ ጠላፊ ጠልፎበት
የተሠራ ይሁን። አራት ምሰሶዎች ከአራት መቆሚያዎች ጋር ሊኖሩት ይገባል። 17 የአደባባዩ ምሰሶዎች ሁሉ የብር ዘንጎችና ኩላቦች፣ የነሐስ መቆሚያዎችም
ይኑሯቸው። 18 የአደባባዩ እርዝመት አንድ መቶ ክንድ፣ ወርዱ ዐምሳ ክንድ፣ ቁመቱ ዐምስት ክንድ ይሁን፤ የበፍታ መጋረጃዎችና የነሐስ መቆሚያዎችም
ይኑሩት። 19 በመገናኛው ድንኳን ውስጥ አገልግሎት የሚሰጥ ዕቃ ሁሉ፣ የድንኳኑ ካስማዎችም በሙሉ፣ አደባባዩም ከነሐስ መሠራት አለባቸው። 20 ሁልጊዜ
እንዲበሩ ለመብራቶቹ የወይራ ጭማቂ ንጹሕ ዘይት እንዲያመጡ እስራኤላውያንን እዘዛቸው። 21 በመገናኛው ድንኳን ውስጥ፣ ከመጋረጃው ውጭ በምስክሩ
ታቦት ፊት፣ አሮንና ልጆቹ መብራቶቹን ከማታ እስከ ንጋት ድረስ በእግዚአብሔር ፊት እንዲበሩ ያድርጉ። ይህም ለእስራኤል ትውልድ ሁሉ የዘለዓለም ሥርዐት
ይሆናል።

Exodus 27:1

አጠቃላይ ምልከታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል።

• ርዝመቱ አምስት ክንድ፥ ወርዱም አምስት ክንድ
ዝርመቱ 2.3 ሜትር፥ የጉኑ ስፋት 2.3 ሜትር ያህል ነው

• ክንድ
አንድ ክንድ ወደ 46 ሴንት ሜትር ያህል ነው

• በአራቱም ማዕዘን ቀንዶችን ታደርጋለህ
በመሰዊያው አራቱም ማእዘን ጫፍ ላይ ቀንድ መሳይ ጉጦች /ነገር/ አውጣ

• ቀንዶቹም ከእርሱ ጋር በአንድ የተሠሩ ይሁኑ
ቀንዶቹም ከመሠዊያው ጋር አብሮ የተሠሩ ይሁን

Exodus 27:3

አጠቃላይ ምልከታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል።

• አመድ የሚሆንባቸውን ምንቸቶች
ለዐመድ ማጠራቀሚያነት የሚያገለግሉ ድስቶች /ድስት መሳይ ነገሮች/

• መጫሪያዎች
የእሳት መጫሪያዎች ወይም የእሳት መለኮሻዎች

• ዕቃውንም ሁሉ
በመሰዊያው ላይ ለመጠቀም የሚያገለግሉ ማንኛውንም ቁሳቁስ

• እንደ መረብ ሆኖ የተሠራ የናስ መከታ አድርግለት
እንደ መረብ ሆኖ የተሠራ የነሐስ መከላከያ አብጅለት/ሥራለት/

• የናስ መከታ
እንጨት በእሳት ሲቃጠል ለመያዝ የሚያገለግል ከነሐስ ብረት የተሰራ መያዣ

Exodus 27:5

አጠቃላይ ምልከታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል።

• መከታውም እስከ መሠዊያው እኩሌታ ይደርስ ዘንድ መሰዊያው በሚዞረው በእርከኑ ታች አድርገው
መከላከያው እስከ መሠዊያው እኩሌታ/ግማሽ/ ድረስ እንዲዘልቅ ከመሠዊያው ክፈፍ/ጫፍ በታች አድርገው/አስቀምጠው

• የናስ መከታ
እንጨት በእሳት ሲቃጠል ለመያዝ የሚያገለግል ከነሐስ ብረት የተሰራ መያዣ (ዘጸአት 27፡4 ተመልከት)

• መሎጊያዎች
መሠዊያውን ለመሸከም የሚያገለግሉ አግዳሚ እንጨቶች/ብረቶች/

Exodus 27:7

አጠቃላይ ምልከታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል።

• መሎጊያዎቹ በቀለበቶች ውስጥ ይግቡ፣ መሠዊያውን ስትሸከሙ መሎጊያዎቹ በሁለቱ ወገኖች ይሁኑ
በሌላ አገላለጽ፦ መሠዊያውን ለመሸከም አግዳሚ እንጨቶችን/ብረቶችን/ ከመሠዊያው በእያንዳንዱ ጐን ባሉት ቀለበቶች ውስጥ አግባ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• ከሳንቆች ሠርተህ ባዶ አድርገው
ሳንቃ ከእንጨት ወይም ከብረት የተሰራ ጠፍጣፋ ነገር ነው። አማራጭ ትርጉም፦ መሠዊያው ውስጡ ባዶ ሆኖ ከሳንቃዎች መስራት አለብህ

• በተራራው ላይ ባሳየሁህ ዕቅድ መሠረት
ይህ ሀረግ ወይም ዓረፍተ ነገር በቀድሞ አማርኛ ትርጉም (በ1954/62) ላይ የተዘለለ/የተተወ ሀሳብ ነው። በዕብራይስጡና በሌሎች አማርኛና እንግሊዘኛ ትርጉሞች ይገኛል።

Exodus 27:9

• የማደሪያውን አደባባይ . . . የጥሩ በፍታ መጋረጆች ይሁኑለት
ለድንኳኑ አደባባይ ክልል የሚሆን ከቀጭን የሐር ክር (የጨርቅ ዓይነት) መጋረጃዎችን ሥራ

• የጥሩ በፍታ መጋረጆች
ቀጭን የሐር ክር ወይም ጨርቅ

• ርዝመት መቶ ክንድ ይሁን
ይህ ወደ 46 ሜትር የምያህል ርዝመት ያለው ነው።

• ለምሶሶቹ ኩላቦችና ዘንጎች የብር ይሁኑ
በምሶሶዎች ላይ ከብር ዘንጎችንና/ቋሚዎችንና/ መስቀያዎችን አድርግላቸው/ ሥራላቸው/

Exodus 27:11

አጠቃላይ ምልከታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል።

• እንዲሁም . . . ከናስ የተሠሩ
ቁጥር 10 ለመተርጎም ቁጥር 9-10 ያለውን እንዴት እንደተረጎምክ ማየቱ የተሻለ ነው። ምክንያቱም ብዙ ተመሳሳይ ነገሮች ተጠቅሰዋል።

• የብር ኩላቦችና ዘንጎች ይሁኑ
ከብር የተሰሩ መስቀያዎችና ቋሚዎች አድርግ ወይም ከብር መስቀያዎችንና ቋሚዎችን ሥራ

• አምሳ ክንድ ርዝመት ያላቸው መጋረጆች
ሃያ ሶስት (23) ሜትር የሆነ መጋረጃዎችን ሥራ

• አሥር ምሰሶች
አስር ምሶሶዎችን ሥራ

• የአደባባዩ ስፋት አምሳ ክንድ
የአደባባዩ ስፋት 23 ሜትር አድርግ

Exodus 27:14

አጠቃላይ ምልከታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል።

• ሰማያዊ፥ ሐምራዊና ቀይ ግምጃ
አማራጭ ትርጉሞች፦ 1) በሰማያዊ፥ ሀምራዊና ቀይ ቀለም የተቀቡ ልብሶች/ የሱፍ ጨርቆች/ ወይም 2) ላይነኖችን ለመቀባት የሚረዱ ሰማያዊ፥ ሐምራዊና ሰማያዊ ቀለም

• ለአደባባዩም ደጅ . . . ሃያ ክንድ መጋረጃ ይሆናል
ለአደባባዩ በር ወይም መግቢያ 9 ሜትር የሆነ መጋረጃ ሥራ

• ከጥሩ በፍታም በጥልፍ አሠራር የተሠራ ሀያ ክንድ መጋረጃ
ከጥሩ የሐር ክር የተሠራና የተፈተለ በጥልፍ ያጌጠ መጋረጃ

• በጥልፍ አሠራር የተሠራ
በጥልፍ ያጌጠና ያማረ መጋረጃ

Exodus 27:17

አጠቃላይ ምልከታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል።

• የአደባባዩ ርዝመት መቶ ክንድ ስፋቱም አምሳ ክንድ ይሁን
የድንኳኑ አደባባይ ርዝመቱ አርባ ስድስት ሜትር የጐኑ ስፋት ሃያ ሶስት ሜትር ሆኖ ይሰራ

• መጋረጃውም ከጥሩ በፍታ
መጋረጃው ከጥሩ /ከቀጭን/ የሐር ጨርቅ/ክር/ የተሰራ ይሁን ወይም መጋረጃውን ከጥሩ/ከቀጭን/ የሐር ጨርቅ/ክር/ ሥራ

• ለማገልገል ሁሉ የማደሪያው ዕቃ ሁሉ፥ ካስማዎቹም ሁሉ የአደባባዩም ካስማዎች ሁሉ፥ የናስ ይሁኑ
በድንኳኑ ውስጥ የሚገኙት ለማናቸውም አገልግሎት የሚውሉ የመገልገያ ዕቃዎችን ሁሉ፥ የድንኳኑንና የአደባባዩ ካስማዎችን ሁሉ ከነሐስ ብረት ሥራቸው።

• ካስማዎች
ከብረት ወይም ከእንጨት የተሰሩ በአንድ በኩል ሹል የሆኑ ድንኳን ለመወጠር የሚያገለግሉ ናቸው

Exodus 27:20

አጠቃላይ ምልከታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• መገናኛው ድንኳን
በሌላ ስሙ የማደሪያ ድንኳን ተብሎ ይታወቃል

• የምስክር ታቦት
የቃል ኪዳን ታቦት ሲሆን በድንጋይ ጽላት ላይ የተጻፉት ቃላት እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ለገባው ቃል ኪዳን ምስክር እንዲሆን ነው።

• በእስራኤል ልጆች ዘንድ ለልጅ ልጆቹው የዘላለም ሥርዓት ይሁን
ይህ በእስራኤል ሕዝብና ወደፊት በሚነሣው ወይም በሚመጣው ትውልድ ዘንድ ቋሚ/የፀና/ ሥርዓት ሆኖ ይኑር/ይቀጥል/

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 28

1 ሆነው እንዲያገለግሉኝ ወንድምህን ዘሮንንና ልጆቹን ናዳብን፣ አብድዩን፣ አልዓዛርንና ኢታምርን ከእስራኤል መካከል ወደ አንተ ጥራ። 2 ለወንድምህ ለአሮን
ለእኔ የተቀደሱ ልብሶችን አዘጋጅ። እነዚህ ልብሶች ለአሮን ክብርና ማዕርግ የሚሆኑ ናቸው። 3 ካህኔ ሆኖ እንዲያገለግለኝ የአሮንን ልብሶች የሚሠሩለትን፣
በልባቸው ጥበበኛ የሆኑትን፣ የጥበብን መንፈስም የሞላሁባቸውን ሰዎች ሁሉ አነጋግር። 4 የሚሠሯቸው ልብሶችም የደረት ኪስ፣ ኤፉድ፣ ቀሚስ፣ ጥልፍ
የተጠለፈበት ሸሚዝ፣ መጠምጠሚያና መታጠቂያ ናቸው። ለእኔ የተቀደሱትን እነዚህን ልብሶች መሥራት አለባቸው። ልብሶቹ ካህናት ሆነው እንዲያግለግሉኝ
ለወንድምህ ለአሮንና ለልጆቹ ይሆናሉ። 5 ወርቅ፣ ሰማያዊ፣ ሐምራዊ፣ ቀይ ማግና የአማረ በፍታ ይጠቀሙ። 6 ከወርቅ፣ ከሰማያዊ፣ ከሐምራዊ፣ ከቀይ ማግን
ኣአምሮ ከተፈተለ በፍታ ይሥሩት። ሥራው የብልኀተኛ ሙያተኝ ሥራ ሊሆን ይገባል። 7 ኤፉዱ ከሁለቱ ጠርዞቹ ጋር የሚያያዙ ሁለት የትከሻ ንጣዮች ይኑሩት። 8
በብልኀት የተጠለፈው የወገብ መታጠቂያም እንደ ኤፉድ መሆን አለበት፦ ከወርቅ፣ ከሰማያዊ፣ ከሐምራዊ፣ ከቀይ ማግና አምሮ ከተፈተለ በፍታ ወጥ ሆኖ
የተሠራ ይሁን። 9 ሁለት የመረግድ ድንጋዮችን ወስደህ የዐሥራ ሁለቱን የእስራኤል ልጆች ስሞች ቅረጽባቸው። 10 ስድስቱ ስሞቻቸው በአንድ ድንጋይ፣ ስድስቱ
ሌሎች ደግሞ በሌላው ድንጋይ ላይ እንደየልጁ ልደት ቀደም ተከተል ይቀረጹ። 11 ሠራተኛ ማኅተም እንደሚቀርጽ የእስራኤልን ዐሥራ ሁለት ልጆች ስሞች
በሁለቱ ድንጋዮች ላይ ቅረጽ። ድንጋዮቹንም በወርቅ ክፈፋቸው። 12 ሁለቱን ድንጋዮች የእስራኤልን ልጆች አምላክ የሚያስታውሱ ድንጋዮች እንዲሆኑ በኤፉዱ
የትከሻ ንጣዮች ላይ አስቀምጥ። መታሰቢያ እንዲሆኑ አሮን ስሞቻቸውን በሁለቱ ትከሻዎቹ ላይ በእግዚአብሔር ፊት ይሸከማል። 13 ፈርጦችንና 14 እንደ
ገመድ የተጎነጎኑ የንጹሕ ወርቅ ድሪዎችን አበጅተህ ከፈርጦቹ ጋር አያይዛቸው። 15 ብልኀ ሠራተኛ እንደሚሠራው፣ ኤፉዱ በተሠራበት መንገድ ፍርድ
የሚሰጥበትን የደረት ኪስ አብጅ። ከወርቅ፣ ከሰማያዊ፣ ከሐምራዊ፣ ከቀይ ማግና ከምሮ ከተፈተለ በፍታ ሥራው። 16 አራት ማእዘን ያለ ውይሁን። የደረት ኪሱን
ዐጥፈህ ድርብ አድርገው። አንድ ስንዝር እርዝመት፣ አንድ ስንዝር ስፋትም ይኑረው። 17 ዕንቆችን በአራት ረድፍ አስቀምጥ። የመጀመሪያው ረድፍ ሰርድዮን፣
ቶነዝዮንና አብረቅራቂ ዕንቊ ሊኖሩት ይገባል። 18 ሁለተኛው ረድፍ በሉር፣ ሰንፔርና አልማዝ ይኑሩት። 19 ሦስተኛው ረድፍ ያክንት፣ ኬልቄዶንና አማቴስጢኖስ
ይገኙበታል። 20 አራተኛው ረድፍ ቢረሌ፣ መረግድና ኢያስጲድ ይኑሩት። በወርቅ ፈርጥ ክፈፍ ሊደረግላቸው ይገባል። 21 ድንጋዮቹ በዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል
ልጆች ስሞች ቅደም ተከተል መሠረት መቀመጥ፣ ከእስራኤል ነገዶች አንዱን በመወከልም በቀለበት ማተሚያ እንደሚቀረጽ እያንዳንዱ ስም የተቀረጸባቸው
መሆን አለባቸው። 22 ኪሱ ከንጹሕ ወርቅ እንደ ገመድ የተጎነጎኑ ድሪዎችን አብጅለት። 23 ሁለት የወርቅ ቀለበቶችን ሥራና ከደረት ኪሱ ሁለት ጎኖች ጋር
አያይዛቸው። 24 የወርቅ ድሪዎች ከደረት ኪሱ ሁለት ማእዘኖች ጋር አያይዛቸው። 25 ጕንጕን ድሪዎች ሌሎች ጎኖች ከሁለቱ የወርቅ ፈርጦች ጋር አገናኛቸው።
ከኤፉዱ የትከሻ ንጣዮች ጋርም በፊቱ በኩል አያይዛቸው። 26 የወርቅ ቀለበቶችን ሥራና ከውስጠኛው የኤፉዱ ጎን ቀጥሎ ባለው ጠርዝ ላይ፣ በደረት ኪሱ
ሌሎች ሁለት ጎኖች ላይ አድርጋቸው። 27 ሁለት ተጨማሪ የወርቅ ቀለበቶችን አብጅና በብልኀት ከተጠለፈው ከሴፉዱ መታጠቂያ በላይ፣ መጋጠሚያው
አጠገብ ከኤፉዱ ፊት ሁለት የትከሻ ንጣዮች ግርጌ ጋር አያይዛቸው። 28 ከኤፉዱ መታጠቂያ በላይ መያያዝ እንዲችሉ፣ የደረት ኪሱን ቀለበቶቹ ከኤፉዱ
ቀለበቶች ጋር በሰማያዊ ገመድ ማሰር አለባቸው። ይህም የሚሆነው የደረት ኪሱ ከኤፉዱ ጋር ሳይያያዝ እንዳይቀር ነው። 29 አሮን ወደ መቅደሱ በገባ ጊዜ፣
የዐሥራ ሁለቱን የእስራኤል ልጆች ስሞች በደረት ኪሱ ላይ ለፍርድ በልቡ ላይ ይሸከም። ይህም በእግዚአብሔር ፊት የዘለዓለም መታሰቢያ ሆኖ ያገለግላል። 30
በፍርድ መስጫው የደረት ኪስ ውስጥ ኡሪምንና ቱሚምን አስቀምጥ። አሮን ወደ እግዚአብሔር ፊት ሲቀርብ፣ ኡሪምና ቱሚም በደረቱ ላይ መኖር አለባቸው፤
አሮንም ለእስራኤል ፍርድ መስጫውን በእግዚአብሔር ፊት ሲቀርብ ሁልጊዜ መሸከም ይኖርበታል። 31 ቀሚስ ሙሉ በሙሉ ሰማያዊ ይሁን። 32 ለራስ
ማስገቢያ ክፍተት ይኑረው፤ ክፍተቱም እንዳይቀደድ ዙሪያውን የተዘመዘመ ጠርዝ ይኑረው። ይህ ሥራ የሸማኔ ሥራ መሆን አለበት። 33 የግርጌ ጠርዝ ላይ
የሰማያዊ፣ የሐምራዊና የቀይ ማግ ሮማኖችን በዙሪያው አድርግ። በመካከላቸውም ዙሪያውን የወርቅ ኻኩራዎችን አብጅ። 34 የወርቅ ኻኩራዎቹና ሮማኖቹ
በቀሚሱ ጠርዝ ዙሪያ እየተፈራረቁ መቀመጥ አለባቸው። 35 ወደ መቅደሱ ሲገባና በእግዚአብሔር ፊት ሲሆን፣ ከመቅደስ ሲወጣም፣ ድምፁ እንዲሰማ
ቀሚሱን አሮን ሲያገለግል ይልበሰው። ይህም የሚደረገው አሮን እንዳይሞት ነው። 36 ከንጹሕ ወርቅ ሳሕን አብጅና በቀለበት ላይ ማኅተም እንደሚቀረጽ፣
“ቅዱስ ለእግዚአብሔር” ብለህ በላዩ ቅርጽበት። 37 ሳሕን ከመጠምጠሚያው ፊት ጋር በሰማያዊ ገመድ አያይዘው። 38 ሁልጊዜም በአሮን ግንባር ላይ ይሁን፤
አሮን እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር ለይተው ከሚያቀርቧቸው የተቀደሱ ስጦታዎች ጋር የሚያያዝ ማንኛውንም በደል ይሸከማል። እግዚአብሔር ስጦታዎቻቸውን
እንዲቀበል፣ መጠምጠሚያ ሁልጊዜ በአሮን ግንባር ላይ መሆን አለበት። 39 ሸሚዙንም፣ መጠምጠሚያውንም ከአማረ በፍታ ትሠራለህ። መታጠቂያውም
በጥልፍ ጠላፊ እንዲሠራ ታደርጋለህ። 40 ለአሮን ልጆችም ሸሚዞቹን፣ መታጠቂያዎችንና የራስ ማሰሪያዎችን ለክብራቸውና ለማዕረጋቸው ታደርጋለህ። 41
ለወንድምህ ለአሮንና ለልጆቹ አልብሳቸው። ቅባቸው፣ ሹማቸውም፤ ካህናት ሆነው እንዲያገለግሉኝም ለእኔ ቀድሳቸው። 42 እስከ ጭን የውስጥ ሰውነታቸውን
የሚሸፍን የውስጥ ልብሶችን ከበፍታ ሥራ። 43 ልጆቹ ውደ መገናኛው ድንኳን ሲገቡ፣ ወይም መቅደሱ ውስጥ ለማገልገል ወደ መሠዊያው ሲቀርቡ እነዚህን
የውስጥ ልብሶች መልበስ አልባቸው። በደል እንዳይገኝባቸውና እንዳይሞቱ ይህን ማድረግ ይገባቸዋል። ይህ ለአሮንና ከእርሱም በኋላ ለሚመጡት ዘሮቹ
የዘለዓለም ሥርዓት ይሆናል።

Exodus 28:1

• ወደ አንተ አቅርብ
“ወደ አንተ” የተባለው ሙሴ ነው። በሌላ አገላለጽ፦ ወደ አንተ ጥራቸው

• ናዳብን አብዩድንም አልዓዛርንም ኢታምርንም
የወንዶች ስም ዝርዝር ነው (ስሞችን የመተርጎም ዘዴ ተመልከት)

• ልብስ እንዲሠሩለት
ይህ በወል ስም የተጠቀሰው “የእስራኤላውያንን” የሚመለከት ነው

• ቅዱስ ይሆን ዘንድ
ለእኔ የተለየ እንዲሆን

Exodus 28:4

አጠቃላይ ምልከታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• ዝንጕርጕር ሸሚዝም
ባጌጠ ጥልፍ የተሰራና በእፉዱ ላይ በውጭ በኩል የሚለበስ ልብስ ወይም ኮት። ነገር ግን እንደ ዛሬው የሸሚዝ ዓይነት ከጃኬት ወይም ከኮት ሥር የሚለበስ አይደለም

• መጠምጠሚያ
ረዘም ያለ ከልብስ/ከጨርቅ/ የተሰራ በራስ ላይ የሚጠመጠም ነው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• መታጠቂያ
ከልብስ/ከጨርቅ/ የተሰራ በወገብ ላይ ወይም በደረት ላይ የሚለበስ

Exodus 28:6

አጠቃላይ ምልከታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• ከተፈተለ ከጥሩ በፍታም
በቀጭኑ ከተፈተለ ከተጠመዘዘ ሐር ጨርቅ/ክር/ ወይም ከላይነን ጨርቅ ሥሩ

• ብልህ ሠራተኛ እንደሚሠራ (ዘጸአት 26፡36 ተመልከት)
የጥልፍ ዐዋቂዎች በጥልፍ አስጊጠው ይሥሩ

• ሁለቱ ወገን አንድ እንዲሆን
መተሳሰር ወይም መያያዝ እንዲችል ሆኖ

• የመረግድ ድንጋይ
ይህ የተመረጠ ወይም የከበረ ድንጋይ የሚባለው ድንጋይ ዘር ሲሆን የተለያየ ቀለም ያለው የድንጋይ ዓይነት ለምሳሌ ነጭ፥ ጥቁር፥ ቀይ ወይም ሰማያዊ ቀለም አለው።

Exodus 28:10

አጠቃላይ ምልከታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• በቅርጽ ሠራተኛ ሥራ እንደ ማኅተም ቅርጽ
የቅርጽ ሠራተኛ ማኅተም እንደሚቀርጽ አደርገህ

• የቅርጽ ሠራተኛ
የቅርጽ ሠራተኛ በጠንካራ ነገር ላይ ለምሳሌ በድንጋይ፥ በብረት ወይም በእንጨት ላይ በመቅረጽ የሚሰራ ማለት ነው።

• በኤፉዱ ጫንቃዎች ላይ ታደርጋለህ
በኤፉዱ ትከሻ ላይ ካሉት ንጣዮች ጋር አያይዛቸው

Exodus 28:13

አጠቃላይ ምልከታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• በኤፉዱ ጫንቃዎች ላይ ታደርጋለህ
በኤፉዱ ትከሻ ላይ ካሉት ንጣዮች ጋር አያይዛቸው (28፡11 ተመልከት)

• የወርቅም ፈርጦች ሁለትም ድሪዎች ሥራ
ሁለት የወርቅ ፈርጦች ሥራ

Exodus 28:15

አጠቃላይ ምልከታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• ብልህ ሠራተኛም እንደሚሠራ የፍርዱን የደረት ኪስ ሥራው
የፍርድ መስጫውን ወይም የእግዚአብሔር ፈቃድ መጠየቂያውን የደረት ኪስ ብልኅ ሠራተኛ እንደሚሠራው አድርገህ ሥርው

• ስንዝር
አንድ ስንዝር ወደ ሃያ ሁለት ሴንት ሜትር ያህል ነው።

Exodus 28:17

አጠቃላይ ዕይታ፦
ዕይታ፦ በዚህ ሥፍራ አስራ ሁለት የድንጋይ ዓይነቶች ተዘርዝረዋል። በዕብራይስጥ የትኛው ቃል የትኛውን የድንጋይ ዓይነት እንደሚገልጽ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን እርግጠኛ አይደሉም። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጅዎች የተለያየ የድንጋይ ዓይነት ዝርዝር ያቀርባሉ።

• የከበረ ድንጋይ
በአማርኛ ቅጅዎች የከበሩ ድንጋዮች ወይም ዕንቁዎች ተብለው ይታወቃሉ።

• የመረግድ ድንጋይ
ይህ የተመረጠ ወይም የከበረ ድንጋይ የሚባለው ድንጋይ ዘር ሲሆን የተለያየ ቀለም ያለው የድንጋይ ዓይነት ለምሳሌ ነጭ፥ ጥቁር፥ ቀይ ወይም ሰማያዊ ቀለም አለው።

• ሰርድዮን፥ ቶጳዝዮን . . . ኢያስጵድ
እነዚህ የከበሩ ድንጋዮች ወይም ዕንቁዎች ናቸው

• ሰንፔር
የከበረ ድንጋይ ወይም ዕንቁ ሲሆን ቀለሙ ሰማያዊ ነው።

• በወርቅ ፈርጥ ይደረጋሉ
በወርቅ ፈርጥ ላይ ይቀመጣሉ

Exodus 28:21

አጠቃላይ ምልከታ፦
ምልከታ፦ እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• የዕንቆቹም ድንጋዮች እንደ እስራኤል ልጆች ስሞች አሥራ ሁለት ይሆናሉ
ለእያንዳንዱ የእስራኤል ልጆች ስም ዐሥራ ሁለት ድንጋዮች ይሁኑ/ይሰሩ/

• በየስማቸውም ማተሚያ እንደሚቀረጽ ይቀረጹ
የዐሥራ ሁለቱ ነገዶች ስሞች እንደ ማኅተም የተቀረጸባቸው (ዘጸአት 28፡11 ተመልከት)

• የተጎነጎኑትን ድሪዎች እንደ ገመድ አድርገህ ከጥሩ ወርቅ ሥራቸው
እንደ ገመድ የተጐነጐነ ወይም እንደ ገመድ ሆኖ የተጌጠ የወርቅ ድሪ ከንጹሕ ወርቅ ሥራ (ዘጸአት 28፡14 ተመልከት)

Exodus 28:25

አጠቃላይ ምልከታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• የወርቅ ፈርጦች
እንደ ገመድ የተገመዱ የወርቅ ፈርጦች

• ሁለት የወርቅ ቀለበቶችም ሥራ፥ እነርሱንም በኤፉዱ ፊት ለፊት ባለው በደረቱ ኪስ በሁለቱ ጫፎች ላይ ታደርጋቸዋለህ
እነዚህ ሁለት የወርቅ ከበቶች ኤፉዱን በሁለት በኩል የሚያቅፉ ናቸው (ዘጸአት 28፡14)። አማራጭ ትርጉም፦ ሁለት የወርቅ ቀለበቶች ሠርተህ በውስጥ በኩል ከኤፉዱ ቀጥሎ ባለው የደረት ኪስ ከታችኛዎቹ ማእዘኖች ጋር እንዲያያዙ አድርገህ ሥራ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Exodus 28:27

አጠቃላይ ምልከታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• በብልሃት የተጠለፈ የኤፉዱ ቋድ
በብልኀት ከተጠለፈው ወይም በጥልፍ ያጌጠው የኤፉድ መታጠቂያ

• ከኤፉዱም እንዳይለይ፥ የደረቱን ኪስ ከቀለበቶቹ ወደ ኤፉዱ ቀለበቶች በሰማያዊ ፈትል ያስሩታል
ከኤፉዱ ጋር እንዳይላቀቅ፣ ከኤፉድ መታጠቂያ ጋር በማገናኘት በሰማያዊ ገመድ ከኤፉዱ ቀለበቶች ጋር መያያዝ አለበት

Exodus 28:29

አጠቃላይ ምልከታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• በእግዚአብሔር ፊት ለዘላለም መታሰቢያ የእስራኤልን ልጆች ስሞች በፍርዱ በደረት ኪስ ውስጥ በልቡ ላይ ይሸከም
በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት ለዘላለም መታሰቢያ ይሆን ዘንድ የእስራኤልን ልጆች ስሞች በፍርድ መስጫው ደረት ኪስ በልቡ ላይ ይሸከም (ዘጸአት 28፡ 17-21 ተመልከት)

• በልቡ ላይ ይሸከም
አሮን በልቡ ላይ ወይም በደረቱ ላይ ይሸከም

• በፍርዱ በደረት ኪስም ውስጥ ኡሪምንና ቱሚምን ታደርጋለህ፣
ወደ እግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት በሚገባበት ጊዜ በአሮን ልብ ላይ ይሆኑ ዘንድ ኡሪሙንና ቱሚሙን በደረት ኪሱ አድርግ

• ኡሪምና ቱሚም
እነዚህ ነገሮች ምን እንደሆኑ አይታወቅም ነገር ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ የሚረዱ ድንጋዮች ሳይሆኑ አይቀሩም።

Exodus 28:31

አጠቃላይ ምልከታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• የኤፉዱን ቀሚስ
በኤፉዱ መደረቢያ ቀሚስ ወይም ረጅም ልብስ

Exodus 28:33

አጠቃላይ ምልከታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• ሮማን
የፍራፍሬ ዛፍ ሲሆን ክብ የሆነ የፍሬው ውጫዊ ክፍሉ ቀይ ነው።

• ወርቅ ሻኩራ ሮማን
ሮማን የሚመስለው የወርቅ መርገፍ ወይም ጸናጽል

• በማገልገል ጊዜም በአሮን ላይ ይሆናል
አሮን በክህነት በሚያገለግልበት ጊዜ ይህን ቀሚስ መልበስ አለበት

• በእግዚአብሔር ፊት ሲገባና ሲወጣ ድምፁ ይሰማል
በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት ወደ መቅደሱ ሲገባና ከመቅደሱ ሲወጣ የጸናጸሎች ድምፅ ይሰማል

• እርሱም እንዳይሞት
ይህ የሚያሳየን አሮን በትክክል እግዚአብሔርን ካልታዘዘ እንደሚሞት ነው። በሌላ አገላለጽ፦ ምክንያቱም አሮን እንዳይሞት

Exodus 28:36

አጠቃላይ ምልከታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• በእርሱም እንደ ማኅተም ቅርጽ አድርገህ
በማኅተም ላይ እንደሚቀረጽ ቅረጸው (ዘጸአት 28፡11 ተመልከት)

• መጠምጠሚያ
ረዘም ያለ ከልብስ/አጨርቅ/ የተሰራ በራስ ላይ የሚጠመጠም

• በአሮንም ግምባር ላይ ይሆናል
አሮንም በግንባሩ ላይ ያድርገው ወይም ይልበሰው

Exodus 28:39

አጠቃላይ ምልከታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• መጠምጠሚያ
ረዘም ያለ ከልብስ/አጨርቅ/ የተሰራ በራስ ላይ የሚጠመጠም

• መታጠቂያ
ከልብስ/ከጨርቅ/ የተሰራ በወገብ ላይ ወይም በደረት ላይ የሚለበስ (ዘጸአት 28፡4)

• በጥልፍ አሠራር
በጥልፍ ጥበብ ወይም በጥልፍ ጠላፊ ያጌጠ ይሁን

Exodus 28:40

አጠቃላይ ምልከታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• መታጠቂያ
ከልብስ/ከጨርቅ/ የተሰራ በወገብ ላይ ወይም በደረት ላይ የሚለበስ (ዘጸአት 28፡4 ተመልከት)

• ቆቦች
ከጨርቅ የተሰሩ ጠበብ ያሉ የራስ ማሰሪያዎችን

• አሮንን ከእርሱም ጋር ልጆቹን ታለብሳቸዋለህ
በሌላ አገላለጽ፦ እነዚህን ልብሶች አሮንና ወንድ ልጆቹን ታለብሳቸዋለህ

Exodus 28:42

አጠቃላይ ምልከታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• የበፍታ ሱሪ ታደርግላቸዋለህ፣ ከወገባቸውም እስከ ጭናቸው ይደርሳል
ከጥሩ በፍታ (ሐር ጨርቅ/ክር/ የተሰራ ከወገባቸው እስከ ጭናቸው የሚደርስ ቀሚጣ ሱሪ ወይም የውስጥ ሱሪ ሥራላቸው

• ለእርሱ ከእርሱም በኋላ ለዘሩ ለዘላለም ሥርዓት ይሆናል
ይህ እንግዲህ ለአሮንና ለትውልዱ ሁሉ ጸንቶ የሚኖር (የማይለወጥ) ሥርዓት ይሆናል

• መገናኛው ድንኳን
ማደሪያው ድንኳን ሌላ ስሙ ነው (27:1 ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 29

1 ሆነው እንዲያገለግሉኝ እነርሱን ለእኔ ለመቀደስ አሁን የምታደርገው ይህ ነው። ነውር የሌለባቸውን አንድ ወይፈንና ሁለት አውራ በጎች፣ **2** የሌለበትን እንጀራና
ዘይት የተቀላቀለበትን እንጎቻ ውሰድ፤ ዘይት የተቀባ ስስ ቂጣም አድርግ። **3** በአንድ ሌማት አድርጋቸውና ከወይፈኑና ከአውራ በጎቹ ጋር አቅርባቸው። **4** አሮንንና
ልጆቹንም ወደ መገናኛ ድንኳኑ መግቢያ አቅርባቸው። በውሀም እጠባቸው። **5** ውሰድና፦ ሸሚዙን፣ የኤፉዱን ቀሚስ፣ ኤፉዱን፣ የደረት ኪሱን፣ በብልኀት
የተጠለፈውን የኤፉዱን መታጠቂያ በወገቡ ዙሪያ በማስታጠቅ አሮን አልብሰው። **6** ቅዱሱን አክሊል በላዩ አስቀምጠህ መጠምጠሚያውን በአሮን ራስ
አድርግ። **7** ዘይቱንም ወስደህ በራሱ ላይ በማፍሰስ ቅባው። **8** አምጥተህ ሸሚዞችን አልብሳቸው። **9** መታጠቂያዎችን ለአሮንና ለልጆቹ ታስታጥቃቸዋለህ፤
የራስ ማሰሪያዎችንም ታደርግላቸዋለህ። የክህነቱ ሥራ በዘለዓለማዊ ሕግ የእነርሱ ይሆናል። እኔን እንዲያገለግሉኝ አሮንና ልጆቹን ትክናቸዋለህ። **10** በመገናኛው
ድንኳን ፊት አቅርብ፤ አሮንና ልጆቹም በወይፈኑ ራስ ላይ እጆቻቸውን ይጫኑ። **11** በእኔ በእግዚአብሔር ፊት በመገናኛው ድንኳን መግቢያ ዕረደው። **12**
ከወይፈኑ ደም ጥቂት በጣትህ ወስደህ በመሠዊያው ቀንዶች ላይ ታደርጋለህ፤ **13** የሆድ እቃዎችን የሚሸፍነውን ስብ ሁሉ ጉበቱን የሚሸፍነውንና ሁለቱን
ኩላሊቶች በላያቸው ካለው ስብ ጋር ወስደህ ሁሉንም በመሰዊያው ላይ ታቃጥላቸዋለህ። **14** ነገር ግን የወይፈኑን ሥጋ ግን ቁርበቱንና ፈርሱን ጭምር ከሰፈር
ውጭ አውጥተህ ታቃጥላለህ። ያ የኀጢአት መሥዋዕት ይሆናል። **15** የአውራ በግም ውሰድና አሮንና ልጆቹ እጆቻቸውን ይጫኑበት። **16** በጉን ዕረደው፤
ደሙንም ወስደህ በመሠዊያው ላይ ዙሪያውን እርጨው። **17** በጉን ለሁለት ክፈልና የሆድ ዕቃውንና እግሮቹን እጠብ፤ የሆድ ዕቃውንም ከተቆራተጡ ብልቶችና
ከራሱ ጋር **18** ላይ አስቀምጥ። ከዚያም እውራ በጉን ሙሉ በሙሉ አቃጥለው። ለእኔ ለእግዚአብሔር የሚቃጠል መሥዋዕት ይሆናል። ይህም ለእኔ ጣፋጭ
መዐዛ ያለው፣ በእሳት የቀረበልኝ መሥዋዕት ይሆናል። **19** ሌላውንም አውራ በግ ወስደህ አሮንና ልጆቹ እጆቻቸውን በራሱ ላይ ይጫኑበት። **20** በኋላ አውራ
በጉን ዕረደው፤ ከደሙም ጥቂት ውሰድና በአሮን ቀኝ ጆሮ ጫፍና በልጆቹ ቀኝ ጆሮዎች ጫፍ ላይ፣ በቀኝ እጆቻቸውና በቀኝ እግሮቻቸው አውራ ጣቶች ላይ
አድርግ። ደሙን በመሠዊያው ላይ ዙሪያውን እርጨው። **21** ካለው ደም፣ ከመቅቢያው ዘይትም ጥቂት ውሰድና በአሮንና በልብሶቹ፣ በልጆቹና በልብሶቻቸውም
ላይ እርጨው። አሮንና ልብሶቹ፣ ልጆቹና ልብሶቻቸው ከእርሱ ጋር ይቀደሱልኛል። **22** በጉን ሥብ፣ ላቱን፣ ሆድ ዕቃውን የሚሸፍነውን ሥብ፣ የጉበቱን መሸፈኛ፣
ሁለቱን ኩላሊቶችና በላያቸው የሚገኘውን ሥብ፣ የቀኙን ወርችም ውሰድ፤ ይህ አውራ በግ ካህኑ ለእኔ የሚቀደስበት ነውና። **23** እንጀራ፣ አንድ በዘይት የተጋገረ
እንጎቻና አንድ ስስ ቂጣ በእኔ በእግዚአብሔር ፊት ከሚሆነው ያለ እርሾ ከተጋገረው ኅብስት ሌማት ትወስዳለህ። **24** እነዚህን በአሮን እጆችና በልጆቹ እጆች
ታስቀምጣለህ። እነርሱ በእኔ በእግዚአብሔር ፊት ይወዝውዟቸው፤ መሥዋዕት አድርገውም ለእኔ ያቅርቧቸው። **25** ከእጆቻቸው ወስደህ ከሚቃጠለው
መሥዋዕት ጋር በመሠዊያው ላይ አቃጥለው። ለእኔ ጣፋጭ መዐዛ ያለው፣ በእሳት የቀረበልኝ መሥዋዕት ይሆናል። **26** የአሮንን የክህነት አውራ በግ ፍርምባ
ወስደህ ወዝውዘውና መሥዋዕት አድርገህ ለእኔ ለእግዚአብሔር አቅርበው። ይህም አንተ የምትበላው የአንተ ድርሻ ይሆናል። **27** የመሥዋዕቱን ፍርምባና
የቀረበውን የመሥዋዕቱን ወርች ለእኔ ቀድስልኝ፤ ሁለቱም አሮንና ልጆቹ ለእኔ ካህናት መሆናቸውን ለማረጋገጥ ከአውራ በጉ የሚገኙ ናቸው። **28** የሚሰጧቸው
እነዚህ የሥጋ ክፍሎች ምንጊዜም የአሮንና የልጆቹ ናቸው። በኅብረቱ መሥዋዕቶች ሥርዐት፣ ከእስራኤላውያን ለካህናቱ፣ ለእኔ ለእግዚአብሔር የሚቀርቡ
መሥዋዕቶች ይሆናሉ። **29** የአሮን የተቀደሱ ልብሶች ከእርሱ በኋላ ለልጆቹም ይሆናሉ። በልብሶቹ የአሮን ልጆች ለእኔ መቀባትና መካን አለባቸው። **30**
በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ እኔን ለማገልገል ወደ መገናኛው ድንኳን የሚገባ፣ አሮንን ከልጆቹ መካከል የሚተካ እነዚያን ልብሶች ሰባት ቀን ይልበስ። **31**
የክህነቱን አውራ በግ ውሰድና ሥጋውን በተቀደሰ ስፍራ ቀቅለው። **32** ልጆቹ የአውራ በጉን ሥጋና በመገናኛው ድንኳን መግቢያ በር ባለው ሌማት የተቀመጠውን
ኅብስት ይብሉት። **33** ለማስተስረይና ለእኔ እንዲቀደሱ የቀረቡትን ሥጋውንና ኅብስቱን መብላት አለባቸው። ሌላ ሰው መብላት አይችልም፤ ምክንያቱም ምግቡን
ለእኔ የተቀደሰ አድርገው ሊይዙት ይገባል። **34** መሥዋዕቱ ሥጋ፣ ወይም ከኅብስቱ እስከሚቀጥለው ጠዋት ድረስ አንዳች የሚተርፍ ከሆነ፣ አቃጥለው። ለእኔ
የተቀደሰ ስለ ሆነ መበላት የለበትም። **35** በዚህ መንገድ እንድታደርገው ያዘዝሁህን ሁሉ በመከተል ለአሮንና ለልጆቹ ትፈጽምላቸዋለህ። እነርሱን ሰባት ፍቀን
ቀድስልኝ። **36** ለስርየት የሚሆን የኀጢአት መሥዋዕት በየቀኑ አንድ ወይፈን አቅርብ። ማስተሰረያውን በማድረግም መሠዊያውን አንጻ፤ ለእኔ ለመቀደስም
ቅባው። **37** ሰባት ቀን ማስተሰረያ አድርግለትና ለእግዚአብሔር ቀድሰው። ከዚያ በኋላ መሠዊያው ሙሉ በሙሉ የተቀደሰ ይሆናል፤ መሠዊያውን የሚነካውም
ሁሉ ይቀደሳል። **38** የአንድ ዓመት ጠቦቶችን ዘወትር በየቀኑ በመሠዊያው ላይ አቅርብ። **39** ጠቦት ማለዳ፣ ሌላውን ደግሞ ምሽት ላይ ታቀርበዋህ። **40**
ከመጀመሪያው ጠቦታ ጋር የኢፍ አንድ ዐሥረኛ ያማረ ዱቄት ተወቅጦ ከተጠለለ ሩብ ኢፍ ዘይት ጋር በመለወስ፣ ሩብ ወይንንም የመጠጥ ቍርባን በማድረግ
አቅርብ። **41** ሁለተኛውን ጠቦት በምሽት ሠዋው። በማለዳ እንደ ተሠዋው ጠቦት ተመሳሳይ የእህልና የመጠት ቍርባን ማቅረብ አለብህ። እነዚህ መሥዋዕቶች
ለእኔ ጣፋጭ መዐዛ ያላቸው በእሳት የቀረቡልኝ መሥዋዕቶች ናቸው። **42** ትውልዶች ሁሉ ዘወትር የሚቀርቡ የሚቃጠሉ መሥዋዕቶች ናቸው። ለናግራችሁ
ከእናንተ ጋር በምገናኝበት በመገናኛው ድንኳን መግቢያ በር በእኔ በእግዚአብሔር ፊት መሥዋዕቶቹን አቅርቧቸው። **43** ከእስራኤላውያን ጋር የምገናኝበት ቦታ ያ
ነው፤ ድንኳኑ በክብሬ ይቀደስልኛል። **44** የመገናኛውን ድንኳንና መሠዊያውን የእኔ ብቻ እንዲሆኑ እቀድሳቸዋለሁ። ካህናት ሆነው እንዲያገለግሉኝ አሮንንና ልጆቹን
እለያቸዋለሁ። **45** በእስራኤላውያን መካከል እኖራለሁ፤ አምላካችውም እሆናለሁ። **46** በመካከላቸው እንድኖር፣ ከግብፅ ምድር ያወጣኋቸው እኔ እግዚአብሔር
አምላካችው እንደ ሆንሁ ያውቃሉ።

Exodus 29:1

• የምታደርግባቸው ነገር ይህ ነው
እግዚአብሔር የካህናት ልብስ ዝግጅትና አሰራር ላይ የሰጠውን መመሪያ ጨርሶ ወደ ካህናትን ወደ መቀደስ ሥርዓት ሲሻገር እናያለን።

• የምታደርግባቸው ነገር ይህ ነው
ይህን የሚሰራው ሙሴ እንደ ሆነ ማመልከቱ ነው።

• ትቀድሳቸው ዘንድ
አሮንና ልጆቹ ካህናት ሆነው በፊቴ ወይም እኔን እንዲያገለግሉኝ የምትለያቸው

• እንዲያገለግሉኝ
በአንደኛ መደብ የተገለጸው እግዚአብሔር /ያህዌ/ ነው። በሌላ አገላለጽ፦ “እኔን እንዲያገለግሉ”

• አንድ ወይፈን
ቀንበር ያልተቀመጠበት ወጣት በሬ ማለት ነው

• ቂጣ እንጀራ፥ በዘይትም የተለወሰ የቂጣ እንጎቻ
እርሾ ያልነካው በወይራ ዘይት የታሸ ወይም ወይራ ዘይት የመጨመረበት ቂጣ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• በዘይትም የተቀባ ስስ ቂጣ ከመልካም ስንዴ
ምርጥ የሆነ የስንዴ ዱቄት ወስደህ ስስ/ቀጭን/ ቂጣ ጋግረህ ዘይት ቀባው

Exodus 29:3

አጠቃላይ ዕይታ፦
እግዚአብሔር (ያህዌ) ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል

• በአንድ ሌማትም ታደርጋቸዋለህ
“ሌማት” የተባለው የዳቦ/የቂጣ/የእንጀራ/ ወይም ሌላ ምግብ ማስቀመጫ የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ ሁሉንም በመሶብ ወይም በቅርጫት መሳይ ነገር ታስቀምጣቸዋለህ/ ታኖራቸዋለህ/

• ከወይፈኑና ከሁለቱ አውራ በጎች ጋር በሌማቱ ታቀርባቸዋለህ
በዚህ ክፍል “ታቀርባቸዋለህ” የሚለው መስዋዕት ማቅረብን የሚመለከት ነው። በሌላ አገላለጽ፦ አንድ ኰርማ/ወይፈን/ እና ሁለቱን አውራ በጎች በምትሠዋበት ጊዜ ለእኔ መባ/መስዋዕት/ አድርገህ አቅርብልኝ/ሰዋልኝ/

• መገናኛው ድንኳን
በሌላ ስሙ የማደሪያ ድንኳን ተብሎ ይታወቃል (ዘጸአት 27፡21 ተመልከት)

Exodus 29:5

አጠቃላይ ዕይታ፦
እግዚአብሔር (ያህዌ) ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል

• ሸሚዝ
ባጌጠ ጥልፍ የተሰራና በእጁዱ ላይ በውጭ በኩል የሚለበስ ልብስ ወይም ኮት። ነገር ግን እንደ ዛሬው የሸሚዝ ዓይነት ከጃኬት ወይም ከኮት ሥር የሚለበስ አይደለም (ዘጸአት 28፡4 ተመልከት)

• በብልሃትም በተጠለፈ ቋድ
ይህ ከቀጭን የሐር ልብስ/ጨርቅ/ክር/ ተገምዶ የተሰራ የወገብ ወይም በደረት አከባቢ የሚያደርጉት መታጠቂያ ነው (ዘጸአት 28፡8 ተመልከት)

• መጠምጠሚያ
አንድ ሰው ወይም ካህኑ በራሱ ላይ ዙሪያውን የሚጠመጥመው ራስ መሸፈኛ ነው (ዘጸአት 28፡4 ተመልከት)

• የተቀደሰ አክሊል
በዚህ ክፍል የተጠቀሰው “አክሊል” በጠፍጣፋ/ዝርግ/ ወርቅ ላይ “ቅድስና ለእግዚአብሔር” ወይም “ለእግዚአብሔር የተለየ” ተብሎ የተቀረጸውን የሚመለከት ነው። ይህ ጠፍጣፋ/ዝርግ/ ወርቅ ከራስ መጠምጠሚያው ላይ የተሰፋ ወይም የተያያዘ ነበር።

Exodus 29:8

አጠቃላይ ዕይታ፦
እግዚአብሔር (ያህዌ) ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል

• ልጆቹንም ታቀርባቸዋለህ
የአሮን ልጆች ወደ አንተ ታመጣቸዋል/ታቀርባቸዋለህ/

• ሸሚዞቹንም ታለብሳቸዋለህ
ባጌጠ ጥልፍ የተሰራና በእጁዱ ላይ በውጭ በኩል የሚለበስ ልብስ ወይም ኮት። ነገር ግን እንደ ዛሬው የሸሚዝ ዓይነት ከጃኬት ወይም ከኮት ሥር የሚለበስ አይደለም። በሌላ አገላለጽ፦ ሸሚዝ/ኮት/ አልብሳቸው (ዘጸአት 28፡4)

• መታጠቂያ
ይህ ከቀጭን የሐር ልብስ/ጨርቅ/ክር/ ተገምዶ የተሰራ የወገብ ወይም በደረት አከባቢ የሚያደርጉት መታጠቂያ ነው (ዘጸአት 28፡4 ተመልከት)

• ቆብንም ታለብሳቸዋለህ
በራስ/በጭንቅላት/ ላይ የሚደረግ/የሚለበስ/ ውበት ያለው ከልብስ/ከጨርቅ/ የተሰራ ጥብቅ ጥምጥም

• ክህነት ይሆንላቸዋል
የክህነት አገልግሎታቸው/ሥራቸው/ተግባራቸው/

• ለዘላለም ሥርዓትም
ለዘለዓለም ቋሚ ሥርዓት ይሆናል (ዘጸአት 28፡43 ተመልከት)

Exodus 29:10

አጠቃላይ ዕይታ፦
እግዚአብሔር (ያህዌ) ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል

• መገናኛው ድንኳን
በሌላ ስሙ የማደሪያ ድንኳን ተብሎ ይታወቃል (ዘጸአት 27፡21 ተመልከት)

• ወይፈኑን . . . ታርደዋለህ
ወይፈኑን/ወጣት በሬውን/ የሚያርደው ሙሴ እንጂ አሮን ወይም ካህናቱ አይደሉም። ወይፈኑ የሚታረደው በድንኳኑ በራፍ/ደጃፍ/ ላይ እንጂ ውስጥ አይደለም።

• ከወይፈኑም ደም ወስደህ
ከታረደው ወይፈን ደም ወስደህ

Exodus 29:12

አጠቃላይ ዕይታ፦
እግዚአብሔር(ያህዌ) ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል

• መሠዊያው ቀንዶች ላይ
በመሰዊያው አራቱም ማእዘን ጫፍ ላይ ቀንድ መሳይ ጕጦች ላይ (ዘጸአት 27፡2)

• ደሙንም ሁሉ ከመሠዊያው በታች ታፈስሰዋለህ
የቀረውን /የተረፈውን/ ደም በመሠዊያው ሥር አፍስሰው

• የሆድ ዕቃውንም የሚሸፍነውን ስብ
የሆድ ዕቃውን /ውስጠኛውን ሆድ ዕቃ/ የሚሸፍነውን ሞራ/ስብ/

• የወይፈኑን ሥጋ ግን፥ ቁርበቱንም፥ ፈርሱንም ከሰፈር ውጭ በእሳት ታቃጥለዋለህ፣ የኃጢአት መሥዋዕት ነው
ነገር ግን የተረፈውን የኰርማውን ሥጋ፥ ቆዳውን፥ አንጀቱን ሁሉ ወስደህ ከሰፈር ውጪ አቃጥለው፤ ይህ የኃጢአት መሥዋዕት ነው

Exodus 29:15

• አውራውንም በግ ታርደዋለህ
ይህ አውራ በግ የሚታረደው ካህናትን ለማንጻት ነው፤ በጉን የሚያርደው አሮን ወይም የእርሱ ልጆች ሳይሆኑ ሙሴ ነው።

• አውራውን በግ በመሠዊያው ላይ ታቃጥላለህ
የወይፈኑ መስዋዕት ከሰፈር ውጪ ወይም ከመገናኛው ድንኳን ደጅ ላይ ታርዷል ነገር ግን አውራ በጉ በሰፈር ውስጥ ወይም በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ይታረዳል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Exodus 29:19

አጠቃላይ ዕይታ፦
እግዚአብሔር (ያህዌ) ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል

Exodus 29:21

አጠቃላይ ዕይታ፦
እግዚአብሔር (ያህዌ) ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል

• እርሱም ልብሶቹም፥ ከእርሱም ጋር ልጆቹ ልብሶቻቸውም ይቀደሳሉ
በዚህ ዐይነት እርሱ፥ ልጆቹ እና ልብሶቻቸው ጭምር ለእኔ የተለዩ ይሆናሉ

• የውስጥ ዕቃውን . . . ጉበቱን. . . ኩላሊቱን
እነዚህ የበግ፥ የፍየል፥ የከብት፥ ወዘተ ውስጠኛው የሰውነት ክፍል አካላት ናቸው

• በእግዚአብሔር ፊት በሌማት ካለው ቂጣ እንጀራ ትወስዳለህ
በመሶብ/በቅርጫት/ ካለው ለእኔ ለእግዚአብሔር ከቀረበው ቂጣ ከየአንዳንዱ ዐይነት አንድ ሙልሙል/ክብ/ ዳቦ ውሰድ (ዘጸአት 29፡2)

• በእግዚአብሔር ፊት
አንተ በእግዚአብሔር ፊት ካስቀምጥከው

Exodus 29:22

አጠቃላይ ዕይታ፦
ዕይታ፦ እግዚአብሔር (ያህዌ) ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል

Exodus 29:24

አጠቃላይ ዕይታ፦
እግዚአብሔር (ያህዌ) ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል

• ሁሉንም በአሮን እጆችና በልጆቹ እጆች ታኖረዋለህ
“ሁሉንም” የተባለው ቀደም ባሉት ቁጥሮች የተዘረዘሩትን የመስዋዕት ዓይነቶችን ማለቱ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ይህን ሁሉ ምግብ በአሮንና በልጆቹ እጅ ላይ አኑር/አስቀምጥ/

• እርሱ ለእግዚአብሔር የእሳት ቍርባን ነው
ይህም በእሳት የሚቃጠል መስዋዕት ሆኖ ለእግዚአብሔር ይቀርባል/ይሰዋል/

Exodus 29:26

አጠቃላይ ዕይታ፦
እግዚአብሔር (ያህዌ) ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል

• ለአሮንም ክህነት የታረደውን በግ
አሮንን ለክህነት አገልግሎት ለመሾም ከታረደው የበግ ጠቦት

• ከሚካኑበትም አውራ በግ
አሮንና ልጆቹ ከሚካኑበት /ለእግዚአብሔር ከሚለዩበት/ የበግ ጠቦት

• ለዘላለም የአሮንና የልጆቹ ወግ ይሁን
ለአሮንና ለልጆቹ ቋሚ ሥርዓት ይሁን

Exodus 29:29

አጠቃላይ ዕይታ፦
እግዚአብሔር (ያህዌ) ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል

• የተቀደሰውም የአሮን ልብስ ይቀቡበትና ይካኑበት ዘንድ
እነርሱም (ልጆቹ) ተቀብተው የክህነት ሹመት/ሥልጣን/ በሚቀበሉበት ጊዜ ይልበሱት

• ከእርሱ በኋላ ለልጆቹ ይሁን
እነዚህ ልብሶች ተራ ልብሶች ወይም ደግሞ የአሮን የግሉ ልብሶች ሳይሆኑ የክህነት ልብሶች ናቸው። አማራጭ ትርጉም፦ አሮን በሚሞትበት ጊዜ የክህነት ልብሶቹ ለልጆቹ መተላለፍ አለባቸው፤

• መገናኛው ድንኳን
በሌላ ስሙ የማደሪያ ድንኳን ተብሎ ይታወቃል (ዘጸአት 27፡21 ተመልከት)

Exodus 29:31

አጠቃላይ ዕይታ፦
እግዚአብሔር (ያህዌ) ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል

• የሚካንበትንም አውራ
ለካህናት የአገልግሎት ሹመት/ሥልጣን/ በምትሰጥበት ጊዜ የታረደው የበግ ጠቦት

• በተቀደሰ ስፍራ ትቀቅለዋለህ
ይህ ቦታ ከቅድስተ ቅዱሳን ወጭ ያለው ቅዱስ ስፍራ የሚመለከት አይደለም። ነገር ግን በመገናኛው ደንኳን አደባባይ ላይ ያለውን ሥፍራ የሚመለከት ነው።

• መገናኛው ድንኳን
በሌላ ስሙ የማደሪያ ድንኳን ተብሎ ይታወቃል (ዘጸአት 27፡21 ተመልከት)

• ሌላ ሰው ግን አይብላው
በሌላ አገላለጽ፦ ከካህናት ሌላ ማንም ሰው አይብላው

• የተቀደሰ ነውና
በሌላ አገላለጽ፦ ምክንያቱም የተቀደሰ ወይም ለእግዚአብሔር የተለየ ነው

Exodus 29:35

አጠቃላይ ዕይታ፦
እግዚአብሔር (ያህዌ) ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል

• እንዳዘዝሁህም ሁሉ በአሮንና በልጆቹ እንዲህ አድርግ
አሮንና ልጆቹ ለክህነት አገልግሎት ስትሾም ወይም ሥልጣን ስትሰጥ ልክ እኔ ባዘዝኩህ ሥርዓት መሠረት ፈጽም

• መሠዊያውም ቅድስተ ቅዱሳን ይሆናል
በዚህም ዐይነት መሠዊያው ፍጹም የተቀደሰ ወይም ለእግዚአብሔር የተለየ ይሆናል

Exodus 29:38

አጠቃላይ ዕይታ፦
እግዚአብሔር (ያህዌ) ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል

• በቀን በቀን ዘወትር ሁለት የዓመት ጠቦቶች ታቀርባለህ
በየዕለቱ አንድ ዓመት የሆናቸውን ሁለት ጠቦቶች መሥዋዕት አድርገህ በመሠዊያው ላይ አቅርብ፤

Exodus 29:40

አጠቃላይ ዕይታ፦
እግዚአብሔር (ያህዌ) ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• አራተኛ እጅ (መጽሐፍ ቅዱሳዊ መለኪያዎች)
አንድ አራተኛ (¼) ማለት ነው

• አሥረኛ እጅ (መጽሐፍ ቅዱሳዊ መለኪያዎች)
አንድ አስረኛ (1/10) ማለት ነው

• የኢን መስፈሪያ (መጽሐፍ ቅዱሳዊ መለኪያዎች)
አንድ ኢን ወደ 3.7 ሊትር ያህል ነው

• የኢፍ መስፈሪያ (መጽሐፍ ቅዱሳዊ መለኪያዎች)
አንድ ኢፍ ወደ 22 ሊትር ያህል የሚመዝን ነው

Exodus 29:41

አጠቃላይ ዕይታ፦
እግዚአብሔር (ያህዌ) ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል

• ለእግዚአብሔር ጣፋጭ ሽቱ እንዲሆን የእሳት ቍርባን ይሆናል
ይህ ለእኔ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ መዓዛው ደስ የሚያሰኝ የምግብ መባ/ መስዋዕት/ ነው፤

• ለሚመጡት ዘመናት ሁሉ
ይህ ዘወትር ለልጅ ልጃችሁ ወይም በየዓመቱ የሚፈጸም

• መገናኛው ድንኳን
በሌላ ስሙ የማደሪያ ድንኳን ተብሎ ይታወቃል

Exodus 29:43

አጠቃላይ ዕይታ፦
እግዚአብሔር (ያህዌ) ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል

• ድንኳኑም በክብሬ ይቀደሳል
በሌላ አገላለጽ፦ ክብሬ ወይም ሕሊዎቴ ይህን ስፍራ የተቀደሰ ወይም የተለየ ያደርገዋል

Exodus 29:45

አጠቃላይ ዕይታ፦
እግዚአብሔር (ያህዌ) ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 30

1 ዕጣን የሚጤስበት መሠዊያ ከግራር ዕንጨት ሥራ። 2 እርዝመቱ አንድ ክንድ፣ ወርዱም አንድ ክንድ ይሁን። አራት ማእዘንና ሁለት ክንድ ከፍታ ይኑረው። ቀንዶቹ ከመሠዊያው ጋር ወጥ ይሁኑ። 3 የዕጣን መሠዊያውን ላይኛ ክፍል፣ ጎኖቹንና ቀንዶቹን በንጹሕ ወርቅ ለብጣቸው። የመሠዊያውን ዙሪያ በወርቅ ክፈፈው። 4 ከክፈፉ በታች በሁለቱ ትይዩ ጎኖቹ ላይ እንዲያያዙ ሁለት የወርቅ ቀለበቶችን አብጅ። ቀለበቶቹ መሠዊያውን ለመሸከም መሎጊያዎችን ደግፈው የሚይዙ ናቸው። 5 ከግራር ዕንጨት ሥራና በወርቅ ለብጣቸው። 6 የዕጣን መሠዊያውን ከመጋረጃው ፊት በምስክሩ ታቦታ አጠገብ አስቀምጠው። ይህም እኔ ከአንተ ጋር በምገናኝበት፣ በምስክሩ ታቦታ ላይ ካለው ከስርየት መክደኛው ፊት ይሆናል። 7 ደስ የሚያሰኝ መዐዛ ያለውን ዕጣን ሁልጊዜ ጧት ቷት ያጢስ። ማጤስ ያለበትም መብራቶቹን በሚያዘጋጅበት ጊዜ ነው። 8 መብራቶቹን በምሸት ሲያበራም፣ በዕጣን መሠዊያው ላይ ዕጣን ማጤስ አለበት። ይህ በእኔ በእግዚአብሔር ፊት ዘወትር በትውልዶች ሁሉ የሚጤስ ዕጣን ይሆናል። 9 ነገር ግን ሌላ ዕጣን፣ አንዳችም የሚቃጠል መሥዋዕት ወይም የእህል ቊርባን በዕጣን መሠዊያው ላይ አታቅርብ፤ ምንም ዐይነት የመጠጥ ቊርባንም አታፍስስበት። 10 መሠዊያው ቀንዶች ላይ አሮን በዓመት አንድ ጊዜ ማስተስረያ ያድርግ ይህንም የሚያደርገው የኀጢአት ስርየት ደሙን በመጠቀም ነው። ሊቀ ካህናቱ በትውልዶቻችሁ ሁሉ ይህን ያድርገው። ይህ መሥዋዕት ሙሉ በሙሉ ለእኔ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ይሆናል።” 11 ሙሴን እንዲህ አለው፤ 12 ስትቆጥራቸው፣ እያንዳንዱ ሰው ለራሱ ሕይወት ቤዛ ለእግዚአብሔር መክፈል አለበት። ስትቆጥራቸውና ከቆጠርሃቸውም በኋላ በመካከላቸው መቅሠፍት እንዳይኖር ይህን አድርግ። 13 የተመዘገበ እያንዳንዱ ሰው በመቅደሱ ሰቅል ክብደት መሠረት የብር ግማሽ ሰቅል ይክፈል። ይህ ግማሽ ሰቅልም ለእኔ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ መሥዋዕት ይሆናል። 14 ከሃያ እና ከዚያ በላይ ዕድሜ ያለው የተቆጠረ ሁሉ ይህን መሥዋዕት ለእኔ ማቅረብ አለበት። 15 ለሕይወታቸው ማስተስረያ ለማድረግ ይህን መሥዋዕት ለእኔ ሲያቀርቡ፣ ባለጠጋው ከግማሽ ሰቅል የበለጠ፣ ድኻውም ከዚያ ያነሰ መስጠት የለባቸውም። 16 የማስተስረያ ገንዘብ ከእስራኤላውያን ተቀበልና ለመገናኛ ድንኳኑ ሥራ አውለው። ለሕይወታችሁ ማስተስረያ ማድረግ በፊቴ ለእስራኤላውያን መታሰቢያ ይሁን።” 17 ሙሴን እንዲህ አለው፤ 18 ትልቅ የናስ ሳሕን ከናስ መቆሚያ ጋር አብጅ። በመገናኛው ድንኳንና በመሠዊያው መካከል አስቀምጠውና ውሀ አድርግበት። 19 ልጆቹ እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን ውስጡ ባለው ውሀ ይታጠቡ። 20 መገናኛው ድንኳን ሲገቡ ወይም የሚቃጠል መሥዋዕት በማቅረብ እኔን ለማገልገል ወደ መሠዊያው ሲቀርቡ፣ እንዳይሞቱ በውሀ መታጠብ አለባቸው። 21 እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን ሊታጠቡ ይገባል። ይህ ለአሮንና ለዘሮቹ በትውልዶቻቸው ሁሉ የሁልጊዜ ሕግ ይሁን።” 22 ሙሴን እንዲህ አለው፤ 23 ምርጥ ቅመሞች፦ ዐምስት መቶ ሰቅል ፈሳሽ ከርቤ፣ ሁለት መቶ ዐምሳ ሰቅል ጣፋጭ ሽታ ያለው ቀረፋ፣ ሁለት መቶ ዐምሳ ሰቅል ጠጅ ሣር፣ 24 ዐምስት መቶ ሰቅል ብርጕድ በመቅደሱ ሰቅል ክብደት ተለክቶ፣ አንድ የኢን መስፈሪያ ወይራ ዘይትም ውሰድ። 25 ቅመሞች በሽቶ ቀማሚ ሥራ የተቀደሰ መቅቢያ ዘይት አዘጋጅ። ይህ ለእኔ የተቀደሰ መቅቢያ ዘይት ይሆናል። 26 ዘይት የመገናኛውን ድንኳን፣ የምስክሩን ታቦትም፣ 27 ጠረጴዛውንና ዕቃውንም ሁሉ፣ መቅረዙንና ዕቃውን፣ የዕጣን መሠዊያውንም፣ 28 የሚቃጠል መሥዋዕት ማቅረቢያ መሠዊያውን ከዕቃው ሁሉ ጋር፣ መታጠቢያ ሳሕኑንም ከመቆኘሚያው ጋር ቅባ። 29 ለእኔ የተቀደሱ እንዲሆኑ እነርሱን ለይልኝ። እነርሱን የሚነካ ማንኛውም ነገርም የተቀደሰ ይሆናል። 30 ሆነው እንዲያገለግሉኝ አሮንንና ልጆቹን ቅባቸው፣ ለእኔም ለያቸው። 31 እንዲህ በላቸው፤ ‘ይህ በትውልዶቻችሁ ሁሉ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ መቅቢያ ዘይት መሆን አለበት። 32 የሰው ቆዳ ሊቀባበት አይገባም፤ እንደዚህ ያለ አንዳችም ዘይት በአንድ ዐይነት ቀመር መሥራት የለባችሁም ምክንያቱም ይህ ዘይት ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ዘይት ነው። እናንተም ቅዱስ መሆኑን ዐስቡ። 33 እንደዚህ የሚሠራ ሁሉ፣ ወይም ከዚህ ዘይት ጥቂት በሰው ላይ የሚያፈስስ ሁሉ፣ ከወገኑ ይወገድ።’” 34 ሙሴን እንዲህ አለው፤ “የጣፋጭ ሽቶ ቅመሞችን፦ የሚንጠባጠብ ሙጫ፣ በዛጎል ውስጥ ያለ ሽቶ፣ የሚሸት ሙጫ ከንጹሕ ዕጣን ጋር፣ እያንዳንዱን በእኩል መጠን ውሰድ፥ 35 በሽቶ ቀማሚ እንደ ተሠራ፣ በጨው የተቀመመ፣ ንጹሕና ለእኔ የተቀደሰ ዕጣን አድርገው። 36 አድቅቀህ ትወቅጠዋለህ። ከፊሉን ከአንተ ጋር በምገናኝበት፣ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ባለው በምስክሩ ታቦት ፊት ለፊት አስቀምጥ። ለእኔ የተቄደሰ መሆኑንም ዐስብ። 37 እንደምትዘጋጀው ዕጣን በአንድ ዐይነት ቀመር ለራስህ ምንም አታድርግ። ለአንተ እጅግ ቅዱስ ይሁን። 38 እንደ ሽቶ ለመጠቀም እንደዚህ አድርጎ የሚሠራ ሁሉ ከገዛ ወገኑ ይወገድ።”

Exodus 30:1

አጠቃላይ ምልከታ፦
የአምልኮ ዕቃዎችን እንዴት መሥራት እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴ ይነግረዋል።

• ቀንዶቹም ከእርሱ ጋር በአንድነት የተሠሩ ይሁኑ
በመሰዊያው አራቱም ማእዘን ጫፍ ላይ ቀንድ መሳይ ጒጦች ከመሰዊያው ጋር አንድ ወጥ ሆነው ይሰሩ

Exodus 30:3

አጠቃላይ ዕይታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል።

• ለመሸከምም የመሎጊያዎች ስፍራ ይሁኑ
ለመሸከም የሚያገለግሉት መሎጊያዎች እንዲገቡበት ከክፈፉ ሥር አያይዛቸው

Exodus 30:5

አጠቃላይ ዕይታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል።

• በምስክሩ ታቦት
የቃል ኪዳን ታቦት ሲሆን በድንጋይ ጽላት ላይ የተጻፉት ቃላት እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ለገባው ቃል ኪዳን ምስክር እንዲሆን ነው (ዘጸአት 26:33 ተመልከት)።

• የስርየት መክደኛ
በምስክሩ ታቦት ላይ የሚቀመጥና የስርየት መስዋዕቱን የሚሸፍን መክደኛ ነው

• ይህንም አንተን በምገናኝበት
እኔም በዚያ ለአንተ እገለጥልሃለሁ ወይም እኔም ከአንተ ጋር እዚያ እገናኛለሁ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Exodus 30:7

አጠቃላይ ዕይታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል።

• በእግዚአብሔር ፊት ለልጅ ልጃችሁ
በእግዚአብሔር ፊት በሚመጡት ዘመናት ሁሉ ወይም በህሊዎተ እግዚአብሔር ፊት በሚመጡት ዘመናት

• አሮን በማታ ጊዜ መብራቶቹን ሲያበራ ያጥነዋል
ይህ ትዕዛዝ በሙሴ በኩል ለአሮን የተሰጠ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ አሮን በየምሽቱ መብራቶቹን ሲያበራ እንዲሁ ያድርገዋል።

Exodus 30:10

እግዚአብሔር (ያህዌ) ለሙሴ መናገሩን ቀጥሏል።
እግዚአብሔር (ያህዌ) ለሙሴ መናገሩን ቀጥሏል።

• በቀንዶቹ ላይ
በመሰዊያው አራቱም ማእዘን ጫፍ ላይ ቀንድ መሳይ ጉጦች ላይ

• ለልጅ ልጃችሁ
በሚመጡት ዘመናት ወይም ጊዜያት ሁሉ

Exodus 30:11

• አንተ የእስራኤልን ልጆች ቍጥር ተቀብለህ
አንተ የእስራኤልን ሕዝብ በምትቈጥርበት ጊዜና በቆጠራው ወቅት

• ግማሽ ሰቅል እንደ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን ይሰጣል
እያንዳንዱ ሰው በተቀደሰው ድንኳን በታወቀው ሚዛን ልክ ስድስት ግራም ብር ይክፈል፤ ግማሽ ሰቅል (½) ከ5.5 – 6 ግራም ይመዝናል።

• እንደ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን
በጊዜው ወይም በዚያን ጊዜ ሁለት ዓይነት ሚዛን እንዳለ ይታወቃል፤ አንደኛ መደበኛ የሆነ መገበያያ ሰቅል ሲሆን ሌላኛው በቤተመቅደስ አገልግሎት የሚሰጥ ሰቅል ነው።

• ሰቅሉ ሀያ ኦቦሊ ነው
አንድ ሰቅል ሃያ ኦቦሊ ያህል ሲሆን በዘመናዊ ሚዛን ወደ 0.6 ግራም የሚመዝን ነው፤ ኦቦሊ ከሁሉም ትንሹ የክብደት መለኪያ ነው።

• ከሀያ አመት ጀምሮ ከዚያም ከፍ ያለ
ሃያ ዓመት የሞላውና ከዚያም በላይ የሆነ ሁሉ

Exodus 30:15

አጠቃላይ ዕይታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል።

• ከእስራኤል ልጆች
ከወንድ እስራኤላውያን ብቻ

• ግማሽ ሰቅል
ተርጓሚዎች የክብደት፥ የርዝመት፥ የፈሳሽና ሌሎችን መለኪያችን ስተረጉሙ ህብረተሰቡ በሚረዳው መለኪያ ብጠቀሙ መልካም ነው። ግማሽ ሰቅል ወደ 6 ግራም የሚመዝን ነው።

• በእግዚአብሔርም ፊት ለነፍሳችሁ ቤዛ እንዲሆን ለእስራኤል ልጆች መታሰቢያ ይሁን
ይህ አባባል የተለያየ ትርጉም ሊኖረው ይችላል፦ 1) እስራኤላውያን ለነፍሳቸው ወይም ለሕይወታቸው ቤዛ እንዲያቀርቡ ይህ ያሳስባቸዋል 2) እስራኤላውያን ለነፍሳቸው ወይም ለሕይወታቸው ቤዛ እንዳቀረቡ ያስገነዝባቸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ ይህም መባ ለሕይወታቸው ቤዛ ስለሚሆን እኔ እነርሱን እያስታወስኩ እጠብቃቸዋለሁ”

Exodus 30:17

• የመታጠቢያ ሰን
የመታጠቢያ ገንዳ ወይም ገበቴ። ይህ የመታጠቢያ ገንዳ ካህናት የሚታጠቡበትን ውሃ የሚያኖሩበት ነው

• መቀመጫውን
የመታጠቢያ ገንዳው መቀመጫ ወይም ማስቀመጫ

• መሠዊያው
የእንስሳት መስዋዕት ማቅረቢያ ቦታ

Exodus 30:19

አጠቃላይ ዕይታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• አሮንና ልጆቹም እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን ይታጠቡበታል
በዚህ ውሃ አሮንና ልጆቹ እጃቸውንና እግራቸውን ለመታጠብ ይገለገሉበታል

• ይህም ለእርሱ ከእርሱም በኋላ ለዘሩ የዘላለም ሥርዓት ይሆንላቸዋል
ይህም ለእነርሱና ከእነርሱ በኋላ ለሚመጡ ዘሮቻቸው/ትውልዶቻቸው/ የዘለዓለም ሥርዓት ሆኖ ይኖራል

Exodus 30:22

አጠቃላይ ዕይታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• ቅመም
ጥሩ ሽታና ጣዕም እንዲኖረው ከደረቀ ዕጽዋትና ዘር ተፈጭቶ የተሰራና ዘይት ወይም ምግብ የገባበት ዱቀት ነክ ነገር ነው (ዘጸአት 25:6 ተመልከት)

• አምስት መቶ ሰቅል . . . ሁለት መቶ አምሳ ሰቅል . . . ሁለት መቶ አምሳ ሰቅል፥
አንድ ሰቅል 11 ግራም ሲሆን ተርጓሚዎች ማህበረሰቡ በየዕለቱ አገልግሎቱ የምጠቀምበትን መለኪያ መጠቀም የተሻለ ነው። 500 ሰቅል ----- 5.5 ኪሎ ግራም፤ 250 ሰቅል ---- 2.75 ኪሎ ግራም፤ 250 ሰቅል ---- 2.75 ኪሎ ግራም ሲሆን በጠቅላላው 11 ኪሎ ግራም ያህል ነው።

• ጣፋጭ ቀረፋ
ጣፋጭ ሽታ ያለው ቀረፋ (የቅመም ዓይነት)

• እንደ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን
በጊዜው ወይም በዚያን ጊዜ ሁለት ዓይነት ሚዛን እንዳለ ይታወቃል፤ አንደኛው መደበኛ የሆነ መገበያያ ሰቅል ሲሆን ሌላኛው ለቤተመቅደስ አገልግሎት የሚሰጥ ሰቅል ነው።

Exodus 30:26

እግዚአብሔር (ያህዌ) ለሙሴ መናገሩን ቀጥሏል
እግዚአብሔር (ያህዌ) ለሙሴ መናገሩን ቀጥሏል

• የምስክር ታቦት
የቃል ኪዳን ታቦት ሲሆን በድንጋይ ጽላት ላይ የተጻፉት ቃላት እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ለገባው ቃል ኪዳን ምስክር እንዲሆን ነው።

• ለሚቃጠል መሥዋዕት የሚሆነውን መሠዊያ
ለሚቃጠል መሥዋዕት የሚያገለግለውን መሠዊያ ወይም የሚቃጠል መስዋዕት የሚቀርብበት መሰዊያ

Exodus 30:29

አጠቃላይ ዕይታ፦
እግዚአብሔር (ያህዌ) ለሙሴ መናገሩን ቀጥሏል

• ሁሉንም ትቀድሳቸዋለህ
ሁሉንም ለእግዚአብሔር የተለየ አድርገህ ታስቀምጣቸዋለህ

• ይህ ለልጅ ልጃችሁ የተቀደሰ የቅብዓት ዘይት ይሁንልኝ
ይህ የተቀደሰ ወይም ለእግዚአብሔር የተለየው የቅባት ዘይት ለሚመጡት ዘመናት ሁሉ ለእኔ አገልግሎት ይሁን፤

Exodus 30:32

አጠቃላይ ዕይታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• በሰው ሥጋ ላይ አይፍሰስ
ለእግዚአብሔር የተለየው ዘይት በማንኛውም ተራ ሰው ላይ አይፍሰስ ወይም የማንኛውንም ተራ ሰው ቆዳ//ሥጋ/ አይንካ፤

• እንደ እርሱ ያለውን የሚያደርግ ሰው
ይህን የመሰለ ቅባት የሚሠራ ወይም ከዚህ ቅባት ወስዶ ካህን ያልሆነውን ሰው የሚቀባ

• ከሕዝቡ ተለይቶ ይጥፋ (ዘይቤያዊ አነጋገር)
ይህ ሀረግ ወደ ሶስት የተለያዩ ፍቺዎች አሉት፤ 1) እኔ ይህን ሰው ከእስራኤላውያን እንደ አንዱ አድርጌ እቀበላቸዋለሁ 2) እስራኤላውያን ይህ ሰው ከመካከላቸው ያውጡ/ይለዩ/ 3) እስራኤላውያን ይህን ሰው መግደል አለበት

Exodus 30:34

• ጣፋጭ ሽቱ፥ የሚንጠባጠብ ሙጫ፥ በዛጎል ውስጥ የሚገኝ ሽቱ
ጣፋጭ ቅመሞች፥ የሚንጠባጠብ ፈሳሽነት ያለው ሙጫ፥ በዛጎል ውስጥ የሚገኝ ሽቱ

• የሚሸትትም ሙጫ፥ ጥሩም እጣን ውሰድ
ይህ አባባል ሁለት ፍቺዎች አሉት፦ 1) ሙሴ ጣፋጭ ሽቶ ለመስራት ሌላ ሰው እንደቀጠረ 2) ጣፋጭ ሽቶ እንደሚሰራ ሰው ሙሴ ራሱ ሽቶዎችን እንደሰራ፤ አማራጭ ትርጉም፦ “የሚሸት ሙጫና ጣፋጭ ሽታ ያለው ዕጣን ወስደህ”

• ከእርሱም ጥቂት ትወቅጣለህ
ከእርሱም ጥቂቱን ወስደህ በመውቀጥ

Exodus 30:37

አጠቃላይ ዕይታ፦
እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ በኩል መናገሩን ቀጥሏል

• እንደ እርሱ የተሠራ ዕጣን ለእናንተ አታድርጉ
በዚህ ዐይነት የምታደባልቁትን ዕጣን ለራሳችሁ መጠቀሚያ አታድርጉት

•በእናንተ ዘንድም ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ይሁን
በዚህ ዐይነት የምታደባልቁትን ዕጣን ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ወይም የተለየ አድርገህ አቅርብ

• እንደ እርሱ የሚያደርግ ሰው ከሕዝቡ ተለይቶ ይጥፋ
ይህ ሀረግ ወደ ሶስት የተለያዩ ፍቺዎች አሉት፤ 1) እኔ ይህን ሰው ከእስራኤላውያን እንደ አንዱ አድርጌ እቀበላቸዋለሁ 2) እስራኤላውያን ይህ ሰው ከመካከላቸው ያውጡ/ይለዩ/ 3) እስራኤላውያን ይህንን ሰው መግደል አለበት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 31

1 እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፤ 2 “የሖር የልጅ ልጅ የሆነውን የኡሪን ልጅ ባስልኤልን ከይሁዳ ነገድ በስሙ ጠርቼዋለሁ። 3 ለሁሉም ዐይነት የእጅ ሞያ ጥበብን፣ ማስተዋልንንና ዕውቀትን እንዲሰጠው፣ ባስልኤልን በመንፈስ ሞልቼዋለሁ፤ 4 ይኸውም ጥበባዊ ሥራዎችን በወርቅ፣ በብርና በነሐስ እንዲሠራ፣ 5 ዐይነት የእጅ ሞያ ለማከናወንም ድንጋይ እንዲጠርብና ዕንጨትም እንዲቀርጽ ነው። 6 ከእርሱም በተጨማሪ የአሂሳሚክን ልጅ ኤልያብን ከዳን ነገድ መርጬዋለሁ። ያዘዝሁህንም ሁሉ እንዲሠሩ የእጅ ሞያ ዐዋቂዎች በሆኑት ልብ ውስጥ ብልኀትን አስቀምጫለሁ። 7 የመገናኛውን ድንኳን፣ የምስክሩን ታቦት፣ በታቦቱ ላይ ያለውን የስርየት መክደኛና የድንኳኑን ዕቃ ሁሉ፦ 8 ጠረጴዛውንና ዕቃውን፣ ንጹሑን መቅረዝ ከዕቃዎቹ ሁሉ ጋር፣ የዕጣኑን መሠዊያ፤ 9 የሚቃጠለውን መሥዋዕት መሠዊያ ከዕቃዎቹ ሁሉ ጋርና ትልቁን ሰን ከነመቆሚያው የሚያካትት ይሆናል። 10 የተሠሩትን ልብሶች፦ ካህናት ሆነው እንዲያገለግሉኝ ለእኔ የተለዩትን የካህኑን የአሮንንና የልጆቹን የተቀደሱ ልብሶችም ይጨምራል። 11 ዘይቱንና የመቅደሱን ጣፋጭ ዕጣንም ያካትታል። እነዚህ የእሥ ሞያ ዐዋቂዎች እነዚህን ሁሉ እኔ ባዘዝሁህ መሠረት ይሥሯችው።” 12 ሙሴን እንዲህ አለው፤ 13 “ለእስራኤላውያን እንዲህ ብለህ ንገራቸው፦ ‘የእግዚአብሔርን የሰንበት ቀኖች ጠብቁ፤ እናንተን ለራሱ የለያችሁ እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን እንድታውቁ፣ ይህ በእርሱና በእናንተ መካከል በትውልዶቻችሁ ሁሉ ምልክት ነውና። 14 ስለዚህ ለእናንተ የተቀደሰ የእግዚአብሔር ሰንበት ነውና አክብሩት። ሰንበትን የሚያረክስ ሁሉ ይሞታል። በሰንበት የሚሠራም ከወገኑ ተነጥሎ ይጥፋ። 15 ስድስት ቀን ይሠራል፤ ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር ክብር የተጠበቀና የተቀደሰ የፍጹም ዕረፍት ሰንበትን ያክብሩ። 16 በትውልዶቻቸው ሁሉ ቋሚ ሕግ አድረገው ሰንበትን ሊያከብሩት ይገባል። 17 እግዚአብሔር በስድስት ቀን ሰማይንና ምድርን ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን ዐርፎአልና፣ ሰንበት በእግዚአብሔርና በእስራኤላውያን መካከል ሁልጊዜ ምልክት ይሆናል።” 18 እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ከሙሴ ጋር የሚያደርገውን ንግግር ከጨረሰ በኋላ፣ በገዛ እጁ የጻፈባቸውን የምስክሩን ሁለት የድጋይ ጽላት ለሙሴ ሰጠው።

Exodus 31:1

• ባስልኤልን በስሙ ጠርቼዋለሁ
ይህ “በስሙ ጠርቼዋለሁ” የሚለው ስሙን መጥራት ሳይሆን “ለሥራው ለይቼዋለው ወይም መርጬዋለሁ” ማለት ነው። የእብራይስጥ ስሙ “ብጻልኤል” ሲሆን አማርኛ ትርጉሞች “ባስልኤል” ብለውታል። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔ ባስልኤን መርጬዋለሁ”

• የሆር የልጅ ልጅ፥ የኡሪ ልጅ----
የወንዶች ስም ሲሆን የባስልኤል አባትና አያት የሚመለክቱ ናቸው

Exodus 31:3

• የእዚአብሔርን መንፈስ ሞላሁበት (ዘይቤያዊ)
እግዚአብሔር (ያህዌ) በአንድ ፈሳሽ መያዣ ውስጥ መንፈሱን እንደሚሞላ ባስልኤልን እሞላዋለሁ እያለ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ እኔ መንፈሴን ለባስልኤል ሰጥቼዋለሁ

• በሁሉም ዐይነት የእጅ ጥበብ ሥራ
ማንኛውም ዓይነት ሥራ የመሥራት ችሎታና ጥበብ

Exodus 31:6

• ለእጅ ጥበብ ዐዋቂዎች ሁሉ ብልሃትን ሰጥቻቸዋለሁ
የእጅ ጥበብ ሥራዎችን ሁሉ መስራት እንዲችሉ ታላቅ ችሎታ እንዲኖራቸው አድርጌአለሁ

• የመገናኛውን ድንኳን
እግዚአብሔር በሙሴ አማካይነት ከህዝቡ ጋር የሚገናኝበት ድንኳን ማለት ነው

• የምስክሩንም ታቦት
የቃል ኪዳኑ ታቦት

• የስርየት መክደኛ
በምስክሩ ታቦት ላይ የሚቀመጥና የስርየት መስዋዕቱን የሚሸፍን መክደኛ ነው

• የዕጣን መሠዊያውን
ዕጣን የሚሰዋበት ቦታ ወይም የሚቀርብበት ቦታ

• ለሚቃጠል መሥዋት የሚሆነውንም መሠዊያ
የሚቃጠል መስዋዕት ለእግዚአብሔር የሚቀርብበት ቦታ ወይም የሚሰዋበት ቦታ

• የነጻውን መቅረዝ
ከንጹህ ወርቅ የተሰራውን የወርቅ መቅረዝ ወይም የብርሃን ማስቀመጫ

Exodus 31:10

• ልብሰ ተክህኖ
በጥብቅ የተሰራ የሊኖ ልብስ ሲሆን ካህናት በክህነት አገልግሎት ወቅት የሚለብሱት ልብስ ነው

Exodus 31:12

• ሰንበቶቼን ፈጽሞ ጠብቁ
እግዚአብሔር በሙሴ በኩል ለእስራኤላውያን የሚነግራቸው የሰንበት ቀን በማክበር እርሱን እንድታዘዙ ነው።አማራጭ ትርጉም፦ “የሰንበት ቀን በማክበር እኔን መታዘዝ አለባችሁ”

• በእኔና በእናንተ ዘንድ ለልጅ ልጃችሁ ምልክት ነው
ከትውልድ እስከ ትውልድ ድረስ ወይም እስከ ልጅ ልጃችሁ ድረስ ምልክት ይሆናል

• እኔ የምቀድሳችሁ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቁ
እግዚአብሔር ለራሱ የለያችሁ ወይም የመረጣችሁ ሰዎች ናችሁ

• ለእናንተ ቅዱስ ነውና ሰንበትን ጠብቁ
የሰንበት ቀን ማክበር ቅዱስ ተግባር ስለሆነ ሰንበቴን አክብሩ

• የሚያረክሰውም ሰው
ሰንበትን ማክበር የማይፈልግ ወይም የሰንበት ቀን አክብሮት የሚሸር ሰው ወይም ትኩረት የማይሰጥና የሚንቅ ሰው

• ሁሉ ፈጽሞ ይገደል
በአድራጊ ግስ፦ ይህን ሰው ግደሉ ወይም ከመካከላችሁ አስወግዱ ወይም ይህ ሰው በሞት ይቀጣ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከሕዝቡ መካከል ተለይቶ ይጥፋ
ይህ አባባል በተለያዩ መንገዶች ልተረጎም ይችላል

1. እግዚአብሔር ይህን ሰው ከህዝቡ መካከል ይለየዋል ወይም እንደራሱ ህዝብ አይቆጥረውም
2. እናንተ እስራኤላውያን ይህን ሰው ከመካከላችሁ ለዩ ወይም አስወግዱ
3. እናንተ እስራኤላውያን ይህን ሰው ያለ ርህራሄ ግደሉት

• ሰባተኛው ቀን
ቀን 7 ወይም የሳምንቱ 7ኛ ቀን

Exodus 31:16

• ሰንበትን ይጠብቁ
እግዚአብሔር በሙሴ በኩል ለእስራኤላውያን የሚነግራቸው የሰንበት ቀን በማክበር እርሱን እንድታዘዙ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ የሰንበት ቀን በማክበር እኔን መታዘዝ አለባችሁ

Exodus 31:18

• በእግዚአብሔር ጣት የተጻፈባቸውን
እግዚአብሔር ራሱ የጻፋቸው ወይም እግዚአብሔር ራሱ በራሱ እጅ የጻፋቸው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 32

1 ከተራራው ሳይወርድ እንደ ዘገየ ሕዝቡ ሲመለከቱ፣ በአሮን ዙሪያ ተሰብስበው እንዲህ አሉት፤ “በፊታችን የሚሄድ ጣዖት ሥራልን። ከግብፅ ያወጣን ሙሴ ምን
እንዳጋጠመው አናውቅም።” 2 እንዲህ አላቸው፤ “በሚስቶቻችሁ ጆሮዎች፣ በወንድና በሴት ልጆቻችሁ ጆሮዎችም ላይ ያሉ የወርቅ ቀለበቶችን አውልቁና ወደ እኔ
አምጧቸው።” 3 ሁሉም በጆሮዎቻቸው ላይ ያሉ የወርቅ ቀለበቶችን አውልቀው ወደ አሮን አመጧቸው። 4 ወርቁን ከእነርሱ ተቀብሎ በማቅለጥ ቅርጽ ሰጠው፤
የጥጃ ምስልም አደረገው። ሕዝቡም፣ “እስራኤል፣ ይህ ከግብፅ ምድር ያወጣህ አምላክህ ነው” አሉ። 5 ይህን ባየው ጊዜ፣ በጥጃው ምስል ፊት መሠዊያ
ሠራ፤ “ነገ ለእግዚአብሔር ክብር በዐል ይሆናል” ብሎም ዐወጀ። 6 ሕዝቡ በማግስቱ ማልደው በመነሣት የሚቃጠሉ መሥዋዕቶችንና የኅብረት መሥዋዕቶችን
አቀረቡ። ሊበሉና ሊጠጡም ተቀመጡ፤ ለመዝፈንም ተነሡ። 7 ሙሴን እንዲህ አለው፤ “ከግብፅ ያወጣሃቸው ሕዝብህ ራሳቸውን በክለዋልና ቶሎ ሂድ። 8
መንገድ ፈጥነው ወጥተዋል። ለራሳቸው የጥጃ ምስል ሠርተው ሰግደውለታል፤ መሥዋዕትም አቅርበውለታል። ‘እስራኤል፣ ከግብፅ ያወጣህ አምላክህ ይህ ነው
ብለውም ተናግረዋል።’” 9 እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፤ “ይህን ሕዝብ አይቼዋለሁ። ተመልከት፣ ዐንገተ ደንዳናዎች ናቸው። 10 በእነርሱ ላይ
እንዲቀጣጠልና እንዳጠፋቸው ተወኝ። ከአንተም ታላቅ ሕዝብ አደርጋለሁ (አንተንም ለታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ) ።” 11 ግን አምላኩ እግዚአብሔር ዝም
እንዲልለት ፈለገ፤ እንዲህም አለ፤ “እግዚአብሔር ሆይ፣ በታላቁ ኀይልና በኀያል እጅ ከግብፅ ባወጣሃው ሕዝብህ ላይ ቊጣህ ለምን ይቀጣጠላል? 12
‘እግዚአብሔር በተራሮች ላይ ሊገድላቸውና ከገጸ ምድር ሊያጠፋቸው ዐስቦ ነው ያወጣቸው’ ለምን ይበሉ? ከሚነድደው ቊጣህ ተመለስ፤ በሕዝብህ ላይ ይህን
ቊጣ ከማምጣትም ታገሥ። 13 ‘ዘራችሁን እንደ ሰማይ ከዋክብት አበዛዋለሁ፣ የተናገርሁትን ይህንም ምድር ሁሉ ለዘራችሁ እሰጠዋለሁ፤ የዘለዓለም ርስታቸው
ይሆናል’ ያልሃቸውንና በራስህ የማልህላቸውን ባሪያዎችህ አብርሃምን፣ ይስሐቅንና እስራኤልን ዐስብ።” 14 ከዚያም እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ
አመጣባቸዋለሁ ካለው ቊጣ ታገሠ። 15 ተመለሰ፤ የምስክሩን ሁለት ጽላት በእጁ ይዞ ከተራራው ወረደ። ጽላቱ በሁለቱም ጎኖቻቸው፣ በፊትም በኋላም
ተጽፎባቸው ነበር። 16 የእግዚአብሔር ሥራ ነበር፤ በጽላቱ ላይ የተቀረጸው ጽሕፈትም የእግዚአብሔር ጽሕፈት ነበር። 17 ላይ የተቀረጸው ጽሕፈትም
የእግዚአብሔር ጽሕፈት ነበር። 17 ኢያሱ የሕዝቡን ጫጫታ ሲሰማ፣ ሙሴን፣ “በሰፈር ውስጥ የጦርነት ድምፅ አለ” አለው። 18 ሙሴም “የድል አድራጊ ድምፅ
አይደለም፤ ድል የተደረገ ሕዝብ ድምፅም አይደለም፤ የምሰማው የዘፈን ድምፅ ነው” ብሎ መለሰለት። 19 ወደ ሰፈሩ ሲቀርብ፣ ጥጃውንና የሚጨፍረውን ሕዝብ
አይቶ በጣም ተናደደ። ጽላቱን ከእጁ ወርውሮ በተራራው ግርጌ ሰበራቸው። 20 ሠርተውት የነበረውን ጥጃም ወስዶ አቃጠለው፤ ዱቄት እስከሚሆን ድረስ
በመፍጨትም በውሀ ውስጥ በተነው። ከዚያም የእስራኤል ሕዝብ እንዲጠጣው አደረገ። 21 “እንደዚህ ያለ ታላቅ ኀጢአት ያመጣህበት ይህ ሕዝብ ምን
አድርጎህ ነው?” አለው። 22 እንዲህ ብሎ መለሰለት፤ “ጌታዬ ሆይ ቊጣህ አይንደድ። እነዚህ ሰዎች ለክፋት የተዘጋጁ እንደ ሆኑ ታውቃለህ። 23 እንደዚህ
ብለውኛል፤ ‘በፊታችን የሚሄድ አምላክ አብጅልን። ከግብፅ ያወጣን ሰውየ ይህ ሙሴ ምን እንዳጋጠመው አናውቅም።’ 24 እኔም፣ ‘ወርቅ ያለው ሰው ሁሉ
ያውልቀው’ አልኋቸው። እነርሱም ወርቁን ሰጡኝ። በእሳት ውስጥም ጣልሁትና ይህ ጥጃ ወጣ።” 25 መዘባበቻ እንዲሆኑ አሮን መረን ስለ ለቀቃቸው፣ ሕዝቡ
ከቊጥጥር ውጭ መሆናቸውን ሙሴ አስተዋለ። 26 በሰፈሩ መግቢያ ቆሞ፣ “የእግዚአብሔር የሆነ ሁሉ ወደ እኔ ይምጣ” አለ። ሌዋውያን ሁሉ በሙሴ ዙሪያ
ተሰበሰቡ። 27 ሌዋውያኑን እንዲህ አላቸው፤ “የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይህን ተናግሮአል፦ ‘እያንዳንዱ ሰይፉን በወገቡ ይታጠቅና በሰፈሩ ሁሉ ከበር
እስከ በር ወደ ኋላና ወደ ፊት እየተመላለሰ ወንድሙን፣ ጓደኛውንና ጎረቤቱን ይግደል።’” 28 ሌዋውያኑ ሙሴ ያዘዘውን ፈጸሙ። በዚያ ቀን ከሕዝቡ ሦስት ሺሕ
ያህል ሰዎች ሞቱ። 29 ሌዋውያኑን፣ “ዛሬ ከእናንተ እያንዳንዱ በልጁና በወንድሙ ላይ እርምጃ ስለ ወሰደ፣ ለእግዚአብሔር አገልግሎት ተቀድሳችኋል።
ስለዚህም እግዚአብሔር ዛሬ ባርኳችኋል” አላቸው። 30 በማግስቱም ሙሴ ሕዝቡን፣ “ታላቅ ኀጢአት ሠርታችኋል። አሁን ወደ እግዚአብሔር እወጣለሁ።
ምናልባት ለኀጢአታችሁ ማስተሰረያ ማድረግ እችል ይህናል” አላቸው። 31 ሙሴ ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ ሄደ፤ እንዲህም አለ፤ “ወዮ! እነዚህ ሰዎች ታላቅ
ኀጢአት ሠርተዋል፤ ለራሳቸውም ከወርቅ ጣዖት አበጅተዋል። 32 ግን እባክህ ኀጢአታቸውን ይቅር በል፤ ይቅር የማትላቸው ከሆነ ግን ከጻፍኸው መጽሐፍ እኔን
ደምስሰልኝ።” 33 ሙሴን እንዲህ አለው፤ እኔን የበደለኝን ሁሉ ከመጽሐፌ እደመስሰዋለሁ። 34 ሂድ፤ ሕዝቡን ወደ ነገርኋችሁ ስፍራ ምራው። እነሆ፣ የእኔ
መልአክ በፊትህ ይሄዳል። ሕዝቡን በምቀጣበት ቀን ግን ስለ ኀጢአታቸው እቀጣቸዋለሁ።” 35 አሮን በሠራው ጥጃ ስላደረጉት፣ እግዚአብሔር በሕቡ ላይ
መቅሠፍት ላከባቸው።

Exodus 32:1

• እንደ ዘገየ ባዩ ጊዜ
ይህ በዘይቤያዊ አነጋገር የተገለጸ ሲሆን አንድ ሰው ወይም አንድ ነገር እንደተገለጠ ወይም እንደታዬ አድርጎ ተገልጿል። አማራጭ ትርጉም፦ “እንደ ዘገየ በተረዱ ወይም ባስተዋሉ ጊዜ”

• ወደ አሮን ተሰብስበው
አሮንን አንድ ጥያቄ ለመጠየቅና ለማስገደድ እንደ መጡ ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፦ ወደ አሮን መጥተው ወይም ቀርበው

• በፊታችን የሚሄዱ
እኛን የሚመሩን ወይም መሪ ልሆኑን የሚችሉ

Exodus 32:3

• ሕዝቡም ሁሉ
ሙሴንና የሙሴን እግዚአብሔር የተቃወሙ ሰዎች ሁሉና እግዚአብሔር አምላካቸው እንዳይሆን ሙሴ መሪያቸው እንዳይሆን ያልፈለጉ ሰዎች ሁሉ ማለት ነው

• የወርቅ ቀለበቶች ሰብራችሁ አምጡልኝ
“ሰብራችሁ” የሚለውን ቃል አዲሱ መደበኛ ትርጉም “አውልቃችሁ” ብሎ ተርጉሟል። ነገር ግን ይህ ትርጉም ልል ነው። በዕብራይስጡ ለማለት የተፈለገው “የወርቅ ጉትቻዎቻችሁን ከጆሮአችሁ ሰብራችሁ አውጥታችሁ” የሚል ጠንካራ ቃል ወይም ግስ ይጠቀማል።

• በመቅረጫ ቀረጸው፥ ቀልጦ የተሠራ ጥጃም አደረገው
አሮን ወርቆችን በማቅለጫ አቅልጦ፥ በጥጃም መልክ ቀርጾ ጣኦት ሰራላቸው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Exodus 32:5

• አሮንም ባየው ጊዜ
ይህ ግልጽ ያልሆነ አባባል ነውና ግልጽ ማድረግ አስፈላጊ ነው። አሮን የእስራኤል ህዝብ ያደረገውን ባየ ጊዜ ወይም አሮን የሰራውን የወርቅ ጥጃ ባየ ጊዜ በሚል መተርጎም ይቻላል።

• ሊዘፍኑም ተነሡ
በአማርኛችን የዚህ ሀረግ ትርጉም በጣም ተደብቋል። “ሊዘፍኑም ተነሡ” የሚለው ተራ ዘፈን ሳይሆን ከሰው ባህርይ የወጣ ተግባር ሲፈጽሙ ነበር። ከበሉና ከጠጡ በኋላ ራሳቸውን መቆጣጠር አቅቷቸው በሜዳ ላይ ይሰስኑ፥ ይዳሩና ይዘሙቱ ነበር። የእንስሳነት ባህርይ ተላብሰው ልቅ ወሲብ ይፈጽሙ ነበር ማለት ነው።

Exodus 32:7

• ካዘዝኋቸው መንገድ ፈጥነው ፈቀቅ አሉ
እግዚአብሔር ሙሴን ሲናገር እስራላውያን ካሳየኋቸው መንገድ ፈቀቅ ብለዋል ሲል አንድ መንገድ እግዚአብሔር አሳይቷቸው እነርሱ ግን ያንን መንገድ ትተው በሌላ መንገድ እንደሄዱ አድርጎ ያቀርባል። አማራጭ ትርጉም፦ እንድያደርጉ ያዘዝኳቸውን ትዕዛዛት አላደረጉም ወይም ትዕዛዜን ለምድረግ ፈቃደኛ አይደሉም

• ቀልጦ የተሠራ የጥጃ ምስል ለራሳቸው አደረጉ
ለራሳቸውም በጥጃ ምስል የተቀረጸ ጣዖትን ሠርተው ለእርሱ ሰገዱለት

Exodus 32:9

• እኔ ይህን ሕዝብ አየሁት (ዘይቤያዊ ንግግር)
እግዚአብሔር (ያህዌ) ይህን ህዝብ አውቃለሁ በማለት ፋንታ ይህን ህዝብ አየሁ ይላል። አማራጭ ትርጉም፦ ይህን ህዝብ አውቃለሁ

• አንገተ ደንዳና ሕዝብ ነው (ዘይቤያዊ ንግግር)
“አንገተ ደንዳና” የሚለው ሀረግ “ልቤ ደነዳና ወይም የማይታዘዝ ልብ” የሚለውን ትርጉም ይይዛል። ነገር ግን አማርኛው የልብን እልከኝነት በአንገተ ደንዳናነት ሲተካው እናያለን።

• አሁንም
እግዚአብሔር (ያህዌ) ከሙሴ ጋር ሲያደርግ የነበረው ንግግር ላይ ሌላ አዲስ የንግግር ምዕራፍ ሲከፍት እናያለን፥ ስለሆነም ያህዌ ሊያደርግ ያለውን ነገር ለሙሴ ሲናገር እናያለን።

• ቁጣዬ እንዲቃጠልባቸው እንዳጠፋቸውም ተወኝ
እግዚአብሔር (ያህዌ) ቁጣው እንደ እሳት ትኩስና የሚያቃጥል እንደሆነ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ በእነርሱ ላይ እጅግ ተቈጥቼ ላጠፋቸው ስለ ተዘጋጀሁ ተወኝ

• አንተንም ለታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ
“አንተን” የተባለው ሙሴ ሲሆን በተውላጠ ስም ተጠቅሷል።

• ቁጣህ በታላቅ ኃይልና በጽኑ እጅ ከግብፅ ምድር ባወጣኸው በሕዝብህ ላይ ስለ ምን ተቃጠለ? (አጋናኝ ጥያቄ)
ሙሴ ይህን ጥያቄ እግዚአብሔርን (ያህዌን) የጠየቀው እግዚአብሔር በህዝቡ ላይ እንዳይቆጣ ለመለመን ወይም ለማሳመን ነው። ይህ አጋናኝ ጥያቄ በመደበኛ ዐረፍተ ነገር ሲተረጎም፦ እግዚአብሔር ሆይ፥ በሥልጣንህና በታላቅ ኀይልህ ከግብጽ ምድር ያወጣኸውን ሕዝብህን አትቆጣ

• በታላቅ ኃይልና በጽኑ እጅ
ሁለቱ ሀረጎች ተመሳሳይ ፍቺ የሚጋሩ ሲሆን ለንግግሩ አጽንኦት ለመስጠት የገቡ ናቸው።

• በጽኑ እጅ
“ጽኑ እጅ” የሚያመለክተው ከዚህ በፊት እስራኤላውያንን ከግብጽ ለማውጣት እግዚአብሔር የሰራቸውን ሥራዎች የሚያመለክት ነው።

Exodus 32:12

እግዚአብሔር እስራኤላውያንን እንዳያጠፋቸው እግዚአብሔር ምክንያት እየሰጠ ንግግሩን ይቀጥላል።
እግዚአብሔር እስራኤላውያንን እንዳያጠፋቸው እግዚአብሔር ምክንያት እየሰጠ ንግግሩን ይቀጥላል።

• ግብፃውያንስ፦ በተራራ መካከል ለገድላቸው፥ ከምድርም ፊት ሊያጠፋቸው ለክፋት አወጣቸው ብለው ስለ ምን ይናገራሉ? (አጋናኝ ጥያቄ)
ይህ አጋናኝ ጥያቄ የሚያመለክተው እስራኤላውያንን እንዳያጠፋቸው ሙሴ እግዚአብሔርን ሲለምን የሚያሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም ግብጻውያን ‘እግዚአብሔር ከግብጽ ምድር መርቶ ያወጣቸው በተራራዎች ላይ ለገድላቸውና ፈጽሞ ሊያጠፋቸውና ለክፉ ነግር ነው’

• ከምድር ፊት
ከምድር ላይ

• ከመዓትህ ተመለስ
ከክፉ ቊጣህ ተመለስ ወይም ሀይለኛ ቁጣህን ተው

• አብርሃምንና ይስሐቅን እስራኤልንም፥ አስብ
አብርሃምን፥ ይስሃቅንና ያዕቆብን (እስራኤልን) አስታውስ

• የማልህላቸውን
ቃል ኪዳን የገባህላቸውን

• ለዘላለምም ይወርሱአታል
ለዘላለምም ይወርሱአታል ወይም የራሳቸው አድርገው ይይዟታል

Exodus 32:15

• ሁለቱንም የምስክር ጽላቶች
በሁለት ጠፍጣፋ ድንጋዮች ላይ የተጻፉ የእግዚአብሔር ትዕዛዛት /ትዕዛዞች/

• እርሱም
ሙሴም

Exodus 32:19

• ጽላቶቹንም
እግዚአብሔር የጻፈባቸውን ሁለቱን ጠፍጣፋ ድንጋዮች

Exodus 32:21

• ይህን ታላቅ ኃጢአት ታመጣበት ዘንድ ይህ ሕዝብ ምን አደረገህ? (ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ጥያቄ)
“ይህ ሕዝብ ምን አድርጎህ ወይም በድሎህ ነው ይህን የመሰለ ክፉ ኃጢአት እንዲሠራ ያደረግኸው?”

• ይህን ታላቅ ኃጢአት ታመጣበት ዘንድ
ሀጢአት እንደ አንድ ግዑዝ ነገር ሆኖ አሮን በህዝቡ ላይ እንዳመጣበት በዘይቤያዊ አነጋገር ሙሴ ይገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ ይህን ክፉ ሀጢአት እንዲሰሩ ምክንያት የሆንከው አሮን አንተ ነህ

• ጌታዬ ሆይ፥ ቁጣህ አይቃጠል (ዘይቤያዊ አነጋገር)
ጌታዬ በእኔ ላይ እንዲህ በሀይል አትቈጣ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• ይህ ሕዝብ ክፋትን እንዲወድድ አንተ ታውቃለህ (ዘይቤያዊ ንግግር)
ይህ ሕዝብ ምን ያህል የክፋት ዝንባሌ እንዳለው ወይም ክፉ የማድረግ ፍላጎት እንዳለው አንተ ታውቃለህ

• ይህ ከግብፅ ምድር ያወጣን ሰው ሙሴ
“ይህ ሙሴ” የሚለው ሀረግ ህዝቡ ለሙሴ ያለው አክብሮት እንደ ወረደባቸው የሚገልጽ ነው። ከዚህ በፊት ሙሴን እንደማያውቁና እርሱም የማይታመን ሰው እንደሆነ “ይህ ሙሴ” በሚለው ሀረግ አርቀው ይናገራሉ።

• እኔም፦ ከእናንተ ወርቅ ያለው ሰው ከእርሱ ሰብሮ ያምጣልኝ
እኔ የወርቅ ጉትቻዎቻቸውን ወይም ጌጣጌጦቻቸውን አውልቀው ወይም ሰብረው እንዲያመጡልኝ ነገርኳቸው

• በእሳትም ላይ ጣልሁት፥ ይህም ጥጃ ወጣ
አሮን ሀላፊነት የወርቅ ጥጃውን ስለመስራቱ ላለመውሰድ ሲፈልግ እኔ ወርቆቹን ወደ እሳት ጣልኩኝ ነገር ግን ይህ ጥጃ ወጣ ብሎ ሲያስተባብል እናያለን።

Exodus 32:25

• በጠላቶቻቸው ፊት እንዲነወሩ
ህዝቡ ነውረኛ ነገር በማድረግና ራሳቸውም ነውረኛ በመሆን ልቅ ተግባር ፈጽመዋል።

• በሰፈሩ ደጅ ቆሞ፦ የእግዚአብሔር ወገን የሆነ ወደ እኔ ይምጣ! (ቀጥተኛ ያልሆነ ንግግር)
ሙሴ ወደ ሰፈሩ መግቢያ በር/ደጅ/ ቆሞ የእግዚአብሔር ወገን የሆነ ሁሉ ወደ እርሱ እንድመጣ ለእስራኤላውያን ተናገረ።

• የእግዚአብሔር ወገን የሆነ
ለእግዚአብሔር ታማኝ የሆነ ሰው የእግዚአብሔር ወገን እንደሆነ በዘይቤያዊ ንግግር ቀርቧል። በሰፈሩም ውስጥ በዚህና በዚያ ከበር እስከ በር ተመላለሱ፤ የእናንተም ሰው ሁሉ ወንድሙን ወዳጁንም ጎረቤቱንም ይግደል በሰፈር ውስጥ ከአንዱ በር/ደጅ/ ወደ ሌላው በር/ደጅ/ እያለፈ ወይም እየዞረ እያንዳንዱ ሰው ወንድሙን፣ ጓደኛውንና ጎረቤቱን ይግደል።

Exodus 32:28

• ከሕዝቡ ሦስት ሺህ ሰዎች ሞቱ (መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቁጥሮች)
“3000 ሰው ሞተ”

• እጃችሁን ለእግዚአብሔር ቅዱስ አድርጉ
እግዚአብሔርን የምታገለግሉ ካህናት ሆናችሁ ራሳችሁን ቀድሳችኋል

• እያንዳንዳችሁ በልጃችሁና በወንድማችሁ ላይ
እግዚአብሔርን (ያህዌ) በመታዘዝ እያንዳንዳችሁ ልጆቻችሁንና ወንድሞቻችሁን ገድላችኋል

Exodus 32:30

• እናንተ ታላቅ ኃጢአት ሠርታችኋል
እናንተ ጣዖት በማምለክ እጅግ የከፋ ሀጢአት ሰርታችኋል

• ምናልባት ኃጢአታችሁን አስተሰርይላችኋለሁ
ሙሴ ወደ እግዚአብሔር በመለመን እግዚአብሔር ይቅር እንዲላቸው ልመና ለማቅረብ ሲዘጋጅ ይታያል። አማራጭ ትርጉም፦ ምናልባት ስለ ኃጢአታችሁ ይቅርታ አስገኝላችሁ ይሆናል

• እባክህ ደምስሰኝ
“እባክህ ደምስሰኝ” የሚለው ሙሴ ስለራሱ ሲናገር ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፦ ይህ የማይሆን ከሆነ ወይም ይቅር የማትላቸው ከሆነ የእኔን ስም ሰርዝ

• ከጻፍኸው መጽሐፍህ
የሕዝብህ ስሞች ከተጻፉበት መዝገብ

Exodus 32:33

• እርሱን ከመጽሐፌ እደመስሰዋለሁ
“እርሱን” የሚለው ያንን ሀጢአት የሰራውን ሰው ስም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ እኔን የበደለኝን ሰው ስም ከመጽሐፌ እሰርዛለሁ

• ከመጽሐፌ
ይህ መጽሐፍ ሙሴ የሚናገረው የእግዚአብሔር (ያህዌ) መጽሐፍ ነው። የመጽሐፉ ባለበት እግዚአብሔር (ያህዌ) ነው።

• ነገር ግን በምጐበኝበት ቀን ኃጢአታቸውን አመጣባቸዋለሁ አለው
ነገር ግን እኔ እነርሱን የምቀጣበት ጊዜ ሲደርስ ስለ ኀጢአታቸው የምቀጣው እኔ እግዚአብሔር ነኝ

• እግዚአብሔር ሕዝቡን ቀሠፈ
በምን ዓይነት ሁኔታ ህዝቡን እንደቀሰፈ አልተገለጸም ነገር ግን በበሽታ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ከባድ በሽታ ላከ

• አሮን የሠራውን ጥጃ ስለ ሠሩ
የጥጃ ምስል ጣኦት የሰራው አሮን ቢሆንም ያንን የጥጃ ምስል ጣኦት አሮን እንዲሰራው ያስገደዱት ህዝቡ ነበሩ። አማራጭ ትርጉም፦ አሮን የጥጃ ምስል ጣኦት እንዲሰራ ህዝቡ በማስገደዳቸው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 33

1 እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፤ “አንተና ከግብፅ ያወጣሃው ሕዝብ ከዚህ ሂድ። ‘ለዘርህ እሰጠዋለሁ’ ባልሁ ጊዜ፣ ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ
ወደማልሁበት ምድር ሂድ። 2 በፊትህ መልአክ እሰድዳለሁ፤ ከነዓናውያንን፣ አሞራውያንን፣ ኬጤያውያንን፣ ፌርዛውያንን፣ ኤዊያውያንና ኢያቡሳውያንንም
አስወጣቸዋለሁ። 3 ማርና ወተት ወደምታፈስሰዉ ምድር ሂዱ፤ ነግር ግን እናንተ ግትሮች ስለ ሆናችሁ፣ እኔ ከእናንተ ጋር አልወጣም። በመንገድ ላይ ላጠፋችሁ
እችላለሁ።” 4 እነዚህን አስጨናቂ ቃሎች ሲሰሙ፣ አለቀሱ፤ ምንም ዐይነት ጌጥ ያደረገ ሰውም አልነበረም። 5 ሙሴን እንዲህ ብሎት ነበር፤ “ለእስራኤላውያን
እንዲህ ብለህ ንገራቸው፤ ‘እናንተ ግትር ሰዎች ናችሁ። ለአፍታ እንኳ ዐብሬአችሁ ብሄድ፣ አጠፋችኋለሁ። ስለዚህ ምን እንደማደርግባችሁ ለመወሰን
ጌጣጌጦቻችሁን አውልቁ።” 6 እስራኤላውያንም ከኮሬብ ተራራ ጀምረው ጌጦቻቸውን አወለቁ። 7 አንድ ድንኳን ወሰደና በተወሰነ ርቀት ላይ ከሰፈር ውጭ
ተከለው። የመገናኛ ድንኳን ብሎ ጠራው። ስለ ማንኛውም ጕዳይ እግዚአብሔርን የሚጠይቅ ሰው ሁሉ ከሰፈሩ ውጭ ወደሚገኘው የመገናኛ ድንኳን ይሄድ
ነበር። 8 ወደ ድንኳኑ ሲሄድ፣ ሕዝቡ ሁሉ በየድንኳኑ መግቢያ ላይ ቆሞ ወደ ድንኳኑ ሲገባ ሙሴን ይመለከት ነበር። 9 ወደ ድንኳኑ በሚገባበት ጊዜ ሁሉ፣
የደመና ዐምድ ይወርድና በድንኳኑ መግቢያ ላይ ይቆማል። እግዚአብሔርም ከሙሴ ጋር ይነጋገራል። 10 ሕዝቡ በድንኳኑ መግቢያ ላይ የደመናውን ዐምድ ቆሞ
ሲያዩት፣ እያንዳንዱ ሰው በራሱ ድንኳን መግቢያ ላይ ይነሣና ይሰግዳል። 11 እግዚአብሔር አንድ ሰው ጓደኛውን እንደሚያነጋግር፣ ሙሴን ፊት ለፊት
ያነጋግረዋል። ከዚያም በኋላ ሙሴ ወደ ሰፈሩ ይመለሳል፤ አገልጋዩና ወጣት የነበረው የነዌ ልጅ ኢያሱ ግን ከድንኳኑ አይለይም ነበር። 12 ሙሴ እግዚአብሔርን
እንዲህ አለው፤ “ይህን ሕዝብ ምራው ብለኸኝ ነበር፤ ከእኔ ጋር ማንን እንደምትልክ ግን አላሳወቅኸኝም። ‘በስም ዐውቅሃለሁ፤ በፊቴም ሞገስ አግኝተሃል’
ብለሃል። 13 በፊትህ ሞገስ ካገኘሁ፣ እንዳውቅህና በፊትህ ሞገስን በማግኘት እንድቀጥል መንገዶችህን አሳየኝ። ይህ ሕዝብ የአንተ ሕዝብ እንደ ሆነም
አስታውስ።” 14 እግዚአብሔርም መልሶ፣ “የእኔ ሀልዎት ከአንተ ጋር ዐብቶ ይሄዳል፤ ዕረፍትም እሰጥሃለሁ” አለው። 15 እግዚአብሔርን እንዲህ አለው፤
“የአንተ ሀልዎት ዐብሮን የማይሄድ ከሆነ፣ ከዚህ አታውጣን። 16 ከእኛ ጋር ካልሄድህ፣ እኔና ሕዝብህ በፊትህ ሞገስ ያገኘን መሆናችን እንዴት ሊታወቅ ይችላል?
እኔና ሕዝብህ በምድር ገጽ ካለው ሕዝብ ሁሉ የተለየን የምንሆነው አንተ ከእኛ ጋር ብትሄድ ብቻ አይደለምን?” 17 ሙሴን፣ “በፊቴ ሞገስን ስላገኘህና በስምም
ስለማውቅህ፣ የጠየቅኸውን አድረጋለሁ” አለው። 18 “እባክህ ክብርህን አሳየኝ” አለ። 19 እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው፤ “መልካምነቴ ሁሉ በፊትህ
እንዲያልፍ አደርጋለሁ፤ ስሜን እግዚአብሔርንም በፊትህ ዐውጃለሁ። የምምረውን እምረዋለሁ፤ የምራራለትንም እራራለታለሁ።” 20 ነገር ግን እግዚአብሔር፣
ፊቴን ማየትና በሕይወት መኖር የሚችል ሰው ስለሌለ፣ አንተ የእኔን ፊት ማየት አትችልም” ብሎ መለሰለት። 21 እንዲህ አለ፤ “እነሆ፣ በእኔ ዘንድ ስፍራ አለ፤
አንተ በዚህ ዐለት ላይ ትቆማለህ። 22 ክብሬ በዚያ ሲያልፍ፣ እኔ እስከማልፍ ድረስ አንተን በዐለቱ ስንጥቅ ውስጥ በእጄ እሸፍንያለሁ። 23 ከዚያም እጁን
አነሣውና ጀርባዬን ታያለህ፤ ፊቴ ግን አይታይም።”

Exodus 33:1

አጠቃላይ ምልከታ፦
ምልከታ፦ እግዚአብሔር (ያህዌ) በህዝቡ ላይ መቆጣቱን ቀጥሎ ይናገራል።

• ወተትና ማርም ወደምታፈስሰው ምድር
ይህ ሐረግ በግነታዊ እና በተለዋጭ ዘይቤ የተገለጸ ነው። ይህ አገላለጽ ከምድሪቱ ወተትና ማር ይፈልቃል ማለት ሳይሆን ለከብት እርባታና ለእርሻ በጣም ምቹ የሆነ ምድር እንደሆነ ለማሳየት ነው። እንዲሁም “የምታፈስ” አገር የሚለው ቃልም ሁሉም ነገር የሞላባት ምድር የሚል ፍቺ ያለው ነው። አማራጭ ትርጉም፦ ለከብት እርባታና ለእርሻ ምቹ የሆነ ምድር

• ወተት
በእንስሳት ምርትና ተዋጽኦ የዳበረች አገር መሆኑዋን ለማመልከት ነው

• ማር
በእስራኤል ምድር ማር በሁለት መንገዶች ይመረታል። አንደኛው ከንብ እርባታ የሚገኘው ሲሆን ሁለተኛው ከተምር ዛፍና ከሌሎች ዕጽዋት የሚገኘው ነው።

• አንገተ ደንዳና ሕዝብ
ጸሐፊው የማይታዘዝ ህዝብ መሆኑን ለማሳየት በዘይቤያዊ አነጋገር ይገልጸል። የልባቸው እልከኝነት ከአንገት ደንዳናነት ጋር ተነጻጽሯል። አንገተ ዳንዳና ማለት ገታራና የማይመለስ ወይም መታጠፍ የማይችል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ የማይሰማና የማይታዘዝ ህዝብ፤ ለለውጥ ያልተዘጋጀ ህዝብ ወይም ከገታራ አቋሙ የማይመለስ ማለት ነው።

Exodus 33:4

• ከእነርሱም ማንም ጌጡን አልለበሰም
ምንም ዐይነት ጌጣጌጥ (የጆሮ ጌጥ፥ የአንገት ሀብል፤ እና ሌሎች ጌጣጌጦች) ማድረግ አልፈለጉም

• እናንተ አንገተ ደንዳና ሕዝብ ናችሁ
እናንተ የማትታዘዙና የማትሰሙ ለለውጥም ያልተዘጋጃጀችሁ ሰዎች ናችሁ

Exodus 33:7

• የደመና ዓምድ
ደመናው እንደ አምድ ይታይ ነበር ወይም የአምድ ቅርጽ ነበረው ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ደመናው በአምድ ቅርጽ ይወርድ ነበር”

• ይወርድ ነበር
የጋራ መረዳት ከለሌው ከየት እንደሚወርድ አይገልጽም። አማራጭ ትርጉም፦ “ከሰማይ ይመጣ ነበር”

Exodus 33:10

• እግዚአብሔር --- ፊት ለፊት ከሙሴ ጋር ይነጋገር (ዘይቤያዊ ንግግር)
በራዕይና በህልም ሳይሆን እግዚአብሔር በቀጥታ አንድ ሰው ከሌላ ሰው ጋር ፊት ለፊት ወይም አንዱ ሌላውን እያየ እንደምነጋገር ከሙሴ ጋር ይነጋገር። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር (ያህዌ) ከሙሴ ጋር በቀጥታ ይነጋገር ነበር”

• ሎሌው ብላቴና
ኢያሱ ከሙሴ ይልቅ ወጥት ሲሆን “ብላቴና” የተባለው ወጣት መሆኑን ያሳያል፥ ሎሌው የተባለው “ረዳት” መሆኑን ይገልጻል። አማራጭ ትርጉም፦ “ረዳቱ ወጣት”

Exodus 33:12

• እነሆ
“እይ” ወይም “ስማ” ወይም “አድምጠኝ” እንደማለት ነው። ቃሉ በዕብራይስጥ ትኩረት ለመሳብ ወይም የሀሳብ አንድነት መኖሩን ለማመልከት የገባ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• በስምህ አወቅሁህ
አንድን ሰው በስም ማወቅ ያንን ሰው በሚገባ ወይም በትክክል እናውቄዋለን ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔ አንተን በደንብ አውቅሃለሁ”

• በእኔ ፊት ሞገስን አገኘህ **(**ዘይቤያዊ አነጋገር**)**
በዚህ ሀረግ “ሞገስ አገኘህ” የሚለው የሚያመለክተው ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን ዕውቅና ያገኘ ወይም እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ ደስ ተሰኘ ማለት ነው። “እኔ ፊት” የተባለው በእግዚአብሔር እይታ ወይም የእግዚአብሔርን ግምገማ የሚመለከት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ እኔ አንተን ገምግሜ ዕውቅና ሰጥቼሃለሁ ወይም በአንተ ተደስቻለሁ/በአንተ ደስ ይለኛል/

• መንገድህን እባክህ አሳየኝ
ይህን ሀረግ በሁለት መልኩ መተርጎም ይቻላል፦ ወደፊት ማድረግ የምትፈልገውን ነገር እባክህ ንገረኝ ወይም ወደፊት ህዝቡ ማድረግ የሚገባቸውን ነገር እባክህ አሳያቸው

Exodus 33:14

• አሳርፍህማለሁ
ዕረፍት እሰጥሃለሁ

• በምን ይታወቃል**?** **(**አጋናኝ ጥያቄ**)**
ሰዎች ሁሉ እንዴት ሊያውቁ ይችላሉ?

Exodus 33:17

አጠቃላይ ምልከታ፦
እግዚአብሔር “አንተ’ እያለ በነጠላ ቁጥር የሚናገረው “ሙሴን” የሚመለከት ነው።

• በፊቴ ሞገስ ስላገኘህ
በዚህ ሀረግ “ሞገስ ስላገኘህ” የሚለው የሚያመለክተው ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን ዕውቅና ያገኘ ወይም እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ ደስ ተሰኘ ማለት ነው። “በፊቴ” የተባለው በእግዚአብሔር እይታ ወይም የእግዚአብሔርን ግምገማ የሚመለከት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ እኔ አንተን ገምግሜ ዕውቅና ሰጥቼሃለሁ ወይም በአንተ ተደስቻለሁ/በአንተ ደስ ይለኛል/

• በስምህም ስላወቅሁህ **(**ዘይቤያዊ ንግግር**)**
አንድን ሰው በስም ማወቅ ያንን ሰው በሚገባ ወይም በትክክል እንደማወቅ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ እኔ አንተን በደንብ ወይም በሚገባ አውቅሃለሁ

Exodus 33:19

• እኔ መልካምነቴን ሁሉ በፊትህ አሳልፋለሁ
እግዚአብሔር (ያህዌ) ከሙሴ ፊት መልካምንቱን አሳልፎ የእግዚአብሔር መልካምነት በፊቱ እንደሚሄድ ዓይነት አቀራረብ አለው። አማራጭ ትርጉም፦ አንተ የእኔን መልካምነት እንዲታይ መልካምነቴን በፊት አሳልፋለሁ

Exodus 33:21

• እነሆ
“እይ” ወይም “ስማ” ወይም “አድምጠኝ” እንደማለት ነው። ቃሉ በዕብራይስጥ ትኩረት ለመሳብ ወይም የሀሳብ አንድነት መኖሩን ለማመልከት የገባ ነው።

• ጀርባዬንም ታያለህ
እግዚአብሔር ከሙሴ ፊት ለፊት ስለሚሄድ ሙሴ ማየት የሚችለው የእግዚአብሔርን (ያህዌ) ጀርባ ነው

• ፊቴ ግን አይታይም
እግዚአብሔር በሙሴ ፊት ስለሚሄድ ጀርባውን እንጂ ፊቱን ማየት አይሆንለትም። አማራጭ ትርጉም፦ አንተ ፊቴን ማየት አትችልም

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 34

1 እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፤ “ሁለት የድንጋይ ጽላትን እንደ መጀመሪያዎቹ ጽላት አድርገህ ጥረብ። በሰበርሃቸው በመጀመሪያዎቹ ጽላት ላይ ተጽፈው
የነበሩ ቃሎችን በእነዚህ ጽላት ላይ እጽፍባቸዋለሁ። 2 ማለዳ ላይ ተዘጋጅተህ ወደ ሲና ተራራ ውጣና በዚያ በተራራው ዐናት ላይ በፊቴ ቁም። 3 ከአንተ ጋር
ማንም ሰው አይምጣ። በተራራው ላይ በየትኛውም ስፍራ ማንም እንዲታይ አታድርግ። የበግና የፍየል መንጋዎች፣ የቀንድ ከብቶችም እንኳ በተራራው ፊት ለፊት
ሣር መጋጥ የለባቸውም።” 4 ሁለት የድንጋይ ጽላትን እንድ መጀመሪያዎቹ አድርጎ ጠረበ፤ እግዚአብሔር እንዳዘዘውም በማለዳ ተነሥቶ ወደ ሲና ተራራ ወጣ።
ሙሴ ሁለቱን የድንጋይ ጽላት በእጁ ይዞ ነበር። 5 እግዚአብሔር በደመና ወርዶ ከሙሴ ጋር በእዚያ ቆመ፤ ስሙን እግዚአብሔርንም ዐወጀ። 6 በሙሴ ፊትም
እንዲህ እያለ በማወጅ ዐለፈ፤ “እግዚአብሔር፣ ርኅሩኅም ቸርም አምላክ እግዚአብሔር፣ ለቍጣ የዘገየ፣ በጽኑዕ ፍቅርና በታማኝነት ባለ ጸጋ፣ 7 ጽኑዕ ፍቅሩን
ለሺሕ ትውልድ የሚጠብቅ፣ ክፋትን፣ ዐመፅንና ኀጢአትን ይቅር የሚል፤ በደለኛውን ግን ከቶ ንጹሕ አያደርገውም። ለአባቶች ኀጢአት ልጆቻቸውንና የልጅ
ልጆቻቸውን እስከ ሦስትና እስከ አራት ትውልድ ድረስ ይቀጣል።” 8 ሙሴ ወዲያውኑ ወደ መሬት ዝቅ ብሎ ሰገደ። 9 አለ፤ “ጌታዬ ሆይ በፊትህ ሞገስ አግኝቼ
ከሆነ፣ እባክህ ዐብረኸን ሂድ፤ ይህ ሕዝብ ግትር ሕዝብ ቢሆንም፣ ክፋታችንና ኀጢአታችንን ይቅር በለን፤ ርስትህም አድርገህ ውሰደን።” 10 እንዲህ አለ፤
“እነሆ፣ ኪዳን እገባለሁ። በምድር ሁሉ አየትኛውም ሕዝብ ዘንድ ተደርገው የማያውቁ ድንቆችን በሕዝብህ ሁሉ ፊት አደርጋለሁ። በአንተ ዘንድ የማደርገው
የሚያስፈራ ነውና፣ ዐብሮህ ያለው ሕዝብ ሁሉ ሥራዬን ያያል። 11 የማዝዝህን ፈጽም። አሞራውያንን፣ ከነዓናውያንን፣ ኬጤያውያንን፣ ፌርዛውያንን፣ አሞያውያንንና
ኢያቡሳውያንን በፊትህ አስወጣቸዋለሁ። 12 አገር ኗሪዎች ጋር ኪዳን እንዳታደርግ ተጠንቀቅ፤ አለዚያ በመካከልህ ወጥመድ ይሆኑብሃል። 13 ሰባብሩ፤
የማምለኪያ ዐምዶቻቸውን አድቅቋቸው፤ የአሼራ ዐፀዶቻቸውንም ቍረጡ። 14 ስሜ ‘ቀናተኛ’ የሆነ እኔ እግዚአብሔር ቀናተኛ አምላክ ነኝና ሌላ አምላክ
አታምልክ። 15 ስለዚህም ከምድሪቱ ኗሪዎች ጋር ኪዳን እንዳታደርግ ተጠንቀቅ፤ ምክንያቱም አማልክታቸውን በመከተልያመነዝራሉና፣ መሥዋዕትም
ያቀርቡላቸዋልና አንተንም አንዱ ስለሚጋብዝህና ከመሥዋዕቱም ጥቂት ስለምትበላ፣ 16 ከዚያም ከሴቶች ልጆቹ የተወሰኑትን ለወንዶች ልጆችህ ትወስዳለህ፤
ሴት ልጆቹም አማልክታቸውን በመከተል ያመነዝራሉ፤ ወንዶች ልጆችህንም ለአማልክታቸው እንዲያመነዝሩ ያደርጓቸዋል። 17 የተሠሩ አማልክትን ለራስህ
አታብጅ። 18 የቂጣ በዓልን አክብር። ባዘዝሁህ መሠረት እርሾ ያልገባበትን ዳቦ በተወሰነው ጊዜ በአቢብ ወር ሰባት ቀን ብላ፤ ከግብፅ የወጣሃው በአቢብ ወር
ነበርና። 19 በኵር ሁሉ፣ የከብትህም እንኳ ተባዕት በኵር በሙሉ፣ የበሬዎችህም የበጎችም በኵር የእኔ ነው። 20 የአህያውን በኵር በጠቦት ዋጀው፤
ካልዋጀኸው ግን ዐንገቱን ስበረው። በኵር ወንድ ልጆችህን ሁሉ ዋጃቸው። ባዶ እጁን በፊቴ የሚቀርብ ማንም እይኑር። 21 ቀን ሥራ፤ በሰባተኛው ቀን ግን
ዕረፍ። በዕርሻና በመከር ጊዜም እንኳ ዕረፍ። 22 ሱባዔ በዓል ከስንዴው በኵራት ጋር፣ የመክተቻውንም በዓል በዓመቱ መጨረሻ አክብር። 23 በአንተ ዘንድ ያለ
ወንድ ሁሉ በዓመት ሦስት ጊዜ በእኔ በእስራኤል አምላክ ፊት ይቅረብ። 24 በፊትህ አስወጣቸዋለሁ፤ ወሰንህንም አሰፋዋለሁ። በዓመት ሦስት ጊዜ በእኔ
በአምላክህ በእግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ ስትወጣ፣ ምድርህን ለመውረርና ለመቆጣጠር ማንም አይመኝም። 25 ደም ከእርሾ ጋር አታቅርብ፤ ወይም በፋሲካ
በዓል የቀረበው መሥዋዕት ሥጋ እስከ ማለዳ ተርፎ አይቆይ። 26 የዕርሻህ ምርጥ በኵራት ወደ ቤቴ አምጣ። የፍየልን ግልገል በእናቱ ወተት አትቀቅል።” 27
እግዚአብሔር ሙሴን፣ “እነዚህን ቃሎች ጻፋቸው፤ በተናገርሷቸው በእነዚህ ቃሎች ክአንተና ከእስራኤል ጋር ኪዳን አድርጌአለሁና አለው። 28 አርባ ቀንና አርባ
ሌሊት ከእግዚአብሔር ጋር እዚያው ነበረ። ምግብም አልበላም፤ ውሃም አልጠጣም። 29 ሁለቱን የምስክሩን ጽላት በእጁ ይዞ ከሲና ተራራ ወረደ።
ከእግዚአብሔር ጋር እየተነጋገረ ሳለ፣ ፊቱ የሚያበራ ምሆኑን አላወቀም። 30 እስራኤላውያን ሙሴን ሲያዩት፣ ፊቱ ይበራ ነበር፤ ስለዚህም ወደ እርሱ ለመጠጋት
ፈሩ። 31 ግን ጠራቸው፤ አሮንና የሕዝቡ መሪዎችም ወደ እርሱ መቱ፣ ሙሴም ከእነርሱ ጋር ተነጋገረ። 32 ከዚያ በኋላም፣ የእስራኤል ሰዎች ሁሉ ወደ ሙሴ
መጡ፤ እርሱም በሲና ተራራ ላይ እግዚአብሔር ሰጥቶት የነበረውን ትእዛዝ ሁሉ ነገራቸው። 33 ንግግሩን ከጨረሰ በኋላ፣ በፊቱ ላይ መሸፈኛ አደረገ። 34
ከእግዚአብሔር ጋር ለመነጋገር በፊቱ በሚቀርብበት ጊዜ ሁሉ፣ እስከሚወጣበት ጊዜ ድረስ መሸፈኛውን ያወልቀው ነበር። ሲወጣ ምን እንዲል እንደታዘዘ
ለእስራኤላይዋን ይነግራቸዋል። 35 እስራኤላውያን የሚያበራውን ፊቱን ሲያዩ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ለመነጋገር ተመልሶ እስኪሄድ ድረስ መሸፈኛውን እንደ ገና
በፊቱ ላይ ያደርገዋል።

Exodus 34:1

• የድንጋይ ጽላቶች
ጠፍጣፋ ድንጋዮች (ዘጸአት 31:18 ተመልከት)

Exodus 34:3

• ከአንተም ጋር ማንም ሰው አይውጣ፥ በተራራውም ሁሉ ማንም አይታይ
በተራራው ላይ መታየት በተራራው ላይ አንድ ሥራ እንደ መሥራት ይቆጠራል። አማራጭ ትርጉም፦ ከአንተ ጋር ማንም ሰው አይምጣ፤ በተራራው በማንኛውም በኩል ወይም ቦታ ማንም ሰው አይታይ

• መንጎችና ከብቶችም በዚያ ተራራ ፊት አይሰማሩ
በግ ወይም ከብት ማንኛውም እንስሳ በተራራው ግርጌ ወይም አጠገብ አይሰማራ

Exodus 34:5

• በዚያም ከእርሱ ጋር ቆመ
“እግዚአብሔር በተራራው ላይ ከሙሴ ጋር ቆመ”

• የእግዚአብሔርንም ስም አወጀ
የዚህ ዐረፍተ ነገር ፍቺ 1) እርሱ ስሙን እግዚአብሔር (ያህዌ) ብሎ ተናገረ 2) እርሱ እግዚአብሔር (ያህዌ) ማን እንደሆነ ተናገረ። ስሙ እግዚአብሔር ማን እንደሆነ አመልካች ነውና።

• እግዚአብሔር፥ እግዚአብሔር መሐሪ፥ ሞገስ ያለው
እግዚአብሔር ስለራሱ ይናገራል፤ አማራጭ ትርጉም፦ እኔ እግዚአብሔር (ያህዌ) ርህሩህና መሐሪ አምላክ ነኝ

• ታጋሽም፥ ባለ ብዙ ቸርነትና እውነት
ይህ አባባል በተለያዩ ቅጂዎች በሁለት መንገድ ይታያል። አንዳንድ ቅጂዎች በአንደኛ መደብ ሲንገሩ ሌሎች በ3ኛ መደብ ይናገራል። ስለዚህ በሁለቱም ትክክል ናቸው፤ 1) እኔ ለቍጣ የዘገየሁ፤ ዘለዓለማዊ ፍቅሬና ታማኝነቴ የበዛ ነው 2) እግዚአብሔር (ያህዌ) ለቍጣ የዘገየ፣ ፍቅሩና ታማኝነቱ የበዛ ነው

• እስከ ሺህ ትውልድም ቸርነትን የሚጠብቅ
ቃል ኪዳኔን እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ እጠብቃለሁ ወይም ዘለዓለማዊ ፍቅሬንም እስከ ብዙ ሺህ ትውልድ እጠብቃለሁ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• በደለኛውን ግን ሳይቀጣ ዝም ብሎ አይተውም
በሶስተኛ መደብ የተነገረው እግዚአብሔር ራሱን በሶስተኛ መደብ ሲናገር ይታያል። አማራጭ ትርጉም፦ እኔ እግዚአብሔር ሀጢአተኛውን/በደለኛውን ሳልቀጣ አልተውም

• በአባቶች ጎጢአት ልጆችን የልጅ ልጆቻቸውን እስከ ሦስትና አራት ትውልድ ይቀጣል
በአባቶች ሀጢአት ምክንያት ልጆቻችሁንና ልጅ ልጆቻችሁን እስከ ሶስትና አራት ትውልድ ድረስ እቀጣለሁ

Exodus 34:8

• በፊትህ ሞገስ አግኝቼ ከሆነ
በዚህ ሀረግ “ሞገስ አግኝቼ” የሚለው የሚያመለክተው ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን ዕውቅና ያገኘ ወይም እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ ደስ ተሰኘ ማለት ነው። “በፊትህ” የተባለው በእግዚአብሔር እይታ ወይም የእግዚአብሔርን ግምገማ የሚመለከት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ እኔ አንተን ገምግሜ ዕውቅና ሰጥቼሃለሁ፤ ወይም በአንተ ተደስቻለሁ/በአንተ ደስ ይለኛል/

• ክፋታችንንና ጎጢአታችንን ይቅር በል
ሁለቱ ቃላት የፍች ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም ልዩነት በመካከላቸው እንዳለ እሙን ነው። እዚህ ጋር በአንድ ላይ የመጡበት ምክንያት አጽንኦት ለመስጠት ነው። ሁለቱን ቃላት ለየብቻ ለመተርጎም የማይቻል ከሆነ ሀጢአታችንን ሁሉ ይቅር በለን ማለት ይቻላል።

• እንደ ርስትህም አድርገህ ውሰደን
ይህ አነጋገር አንድ ሰው አንድን ንብረት ካለበት ቦታ እንደሚወስድ ዓይነት አነጋገር ርስትህ አድርገህ ውሰደን ይላል። አማራጭ ትርጉም፦ የራስህ ሕዝብ አድርገህ ተቀበለን ወይም እኛን ህዝብህን እንደ ርስትህ የራስህ አድርገህ ተቀበለን

Exodus 34:10

• በሕዝብህ ሁሉ ፊት ድንቅ አደርጋለሁ
“በህዝብህ” የተባለው አንተ በምትመራው ህዝብ ፊት ወይም አንተ የምትመራው ህዝብ ሁሉ እያየ

• እኔም በአንተ ዘንድ የምሠራው ነገር የሚያስፈራ ነውና (ዘይቤያዊ ንግግር)
ይህ የሚያስፈራው ነገር ህዝቡ እንዲፈራ የሚያደርግ ነገር ይሆናል። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር የሚያደርገውን ነገር አይቶ ህዝቡ ይፈራል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ እኔ ለአንተ የማደርገው ነገር ህዝቡ እኔን እንዲፈራ የሚያደርግ ነው

• በአንተ ዘንድ የምሠራው
“በአንተ ዘንድ” የተባለው ሙሴንና የእስራኤልን ህዝብ የሚመለከት ነው

Exodus 34:12

አጠቃልይ ዕይታ፦
እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴና እስራኤላውያን ማድረግ ያለባቸውን ነገር እየቀጠለ ይናገራል።

• በመካከልህ ወጥመድ እንዳይሆኑብህ
ሌሎችን ሀጢአት እንዲሰሩ የሚያደርጉ እንደ ወጥመድ ተቆጥረዋል። አማራጭ ትርጉም፦ እነርሱ ሀጢአት እንድትሰሩ ያደርጓችኋል

• ስሙ ቀናተኛ የሆነ እግዚአብሔር (ምትካዊ ዘይቤ)
“ቀናተኛ” የተባለው እግዚአብሔር ክብሩን ለማንም እንደማያጋራና የራሱን ክብር እንደሚጠብቅ የሚያሳይ ነው። የእግዚአብሔር ህዝብ ሌሎች አማልክት ቢያመልኩ እግዚአብሔር ክብሩ ይነካል፤ ምክንያቱም የእርሱ የሆኑት እርሱን የማያመልኩ ከሆነ ሌሎችም አያመልኩትም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ እኔ እግዚአብሔር ሁልጊዜ ክብሬን እጠብቃለሁ

• ቅንዓት ያለው አምላክ ነውና
ይህ የእግዚአብሔርን ባህርይ የሚመለከት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ እኔ እግዚአብሔር ቀናተኛ አምላክ ስለ ሆንኩ

Exodus 34:15

ቀጥሎ እግዚአብሔር የሚናገረው እስራኤላውያን ከሌሎች ህዝቦች ጋር ያላቸው ግንኙነት ምን መምሰል እንዳለበት ያሳያቸዋል።
ቀጥሎ እግዚአብሔር የሚናገረው እስራኤላውያን ከሌሎች ህዝቦች ጋር ያላቸው ግንኙነት ምን መምሰል እንዳለበት ያሳያቸዋል።

• ባመነዘሩና በሠዉላቸው ጊዜ እንዳይጠሩህ
እግዚአብሔር (ያህዌ) ሌሎች አማልክትን ማምለክ ከሌላ ወንድ ጋር እንደማመንዘር እንደሆነ ይነግራቸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ “እነርሱ ሌሎች አማልክት አመለኩ” ወይም “ምክንያቱም እነርሱ ወደ ሌላ ወንድ እንደሚሄዱ አመንዝራዎች ሌሎች አማልክትን አምልከዋል”

• ከመሥዋዕታቸውም እንዳትበላ
ለሌሎች አማልክት የተሰዋን ምግብ መብላት ምን ያህል ክፉ እንደሆነ በግልጽ ያትታል። አማራጭ ትርጉም፦ አንተ (እናንተ) እነርሱ ለአማልክታቸው የሚያቀርቡትን (የሚሰውትን) ምግብ በመብላት አማልክቶቻቸውን ለማምለክ ትፈተናላችሁ ወይም እነርሱ ለአማልክቶቻቸው የሰውትን ምግብ በመብላት ራሳችሁን አመንዝራ ታደርጋላችሁ

Exodus 34:18

አጠቃላይ ምልከታ፦
እግዚአብሔር (ያህዌ) እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው በሙሴ በኩል ያሳስባቸዋል።

• ሰባት ቀን
ለሰባት ቀን ወይም እስከ ሰባት ቀን

• በአቢብ ወር ከግብፅ ወጥተሃልና
እስራኤላውያን ከግብጽ የወጡት በአቢብ ወር ስለሆነ ለእነርሱ የአመቱ መጀመሪያ ወር ነው። እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር አቢብ ወር የሚጀምረው ከመጋቢት መጨረሻ ሳምንት እስከ ሚያዝያ መጀመሪያ ሳምንት ድረስ ነው። (ዘጸአት 13:4 ተመልከት)።

Exodus 34:19

አጠቃላይ ምልከታ፦
እግዚአብሔር (ያህዌ) እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው በሙሴ በኩል ያሳስባቸዋል።

• ማኅፀንንም የሚከፍት (ዘይቤያዊ አነጋገር)
በኩር ሆኖ የሚወለድ ወይም የሚወጣ

• ትዋጀዋለህ
በኩር ሆኖ የሚወለድ ወንድ እና አህያ የእግዚአብሔር (የያህዌ) ነው፤ ነገር ግን መስዋእት ሆነው እንዲቀርቡለት ያህዌ አይፈልግም። በእነርሱ ፋንታ እስራኤላውያን በጎችን እንዲሰዉለት ተጠይቀዋል። ስለሆነም እስራኤላውያን በኩር ሆኖ የተወለደን አህያ ወይም ወንድ ልጅ ከእግዚአብሔር መልሰው እንዲገዙ ተፈቅዶላቸዋል። የምይዋጁ ከሆነ አንገቱን ቆልምመው ለመስዋዕት እንዳይቀርብ እንድያደርጉ ተጠይቀዋል።

• በፊቴም አንድ ሰው ባዶ እጁን አይታይ
ይህ አነጋገር እግዚአብሔር ማንም ሰው ወደ ፊቱ ሲመጣ የሆነ ነገር ተሸክሞ እንድመጣ የሚጠይቅ ይመስላል። ነገር ግን ይህ ወካይ ዘይቤ የሚያሳየው ወደ እኔ የሚመጣ ማንም ቢሆን መስዋዕት ሳይዝ አይምጣ ወይም ወደ እኔ የሚመጣ ማንም ቢሆን መስዋዕት ማምጣት አለበት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Exodus 34:21

አጠቃላይ ምልከታ፦
እግዚአብሔር (ያህዌ) እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው በሙሴ በኩል ያሳስባቸዋል።

• በምታርስበትና በምታጭድበት ዘመን ታርፋለህ
“በእርሻም ወቅትም ሆነ በመከር ወቅት በሰባተኛው ቀን ምንም ሥራ አትሥሩ” ወይም “በእርሻና በመከር ጊዜ እንኳ ቢሆን ማረፍ አለብህ”

• የመክተቻ በዓል
ይህ በዓል የዳስ በመባል ይታወቃል። ይህ ልምምድ የመጣው እርሻቸውን በዳስ ወይም በጊዜያዊ ጎጆ ውስጥ ሆነው ያረሱና እህሉ እስኪደርስ ድረስ በዚያ ዳስ ሆነው ከአውሬ ሲጠብቁ የነበሩ አርሶ አደሮች ልምምድ ነው። “መክተቻ” የተባለው የእህል ማከማቻ ማለት ነው።

Exodus 34:23

አጠቃላይ ምልከታ፦
እግዚአብሔር (ያህዌ) እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው በሙሴ በኩል ያሳስባቸዋል

Exodus 34:25

አጠቃላይ ምልከታ፦
እግዚአብሔር (ያህዌ) እስራኤላውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው በሙሴ በኩል ያሳስባቸዋል

• የመሥዋዕቴን ደም
ደሙ መስዋዕት ከሚቀርበው እንስሳ የተገኘ ሲሆን የተሰዋው ለእግዚአብሔር ነበር። አማራጭ ትርጉም፦ የእንስሳ ደም ለእኔ በምታቀርብበት ጊዜ

• ከቦካ እንጀራ ጋር
እርሾ ካለው ወይም ከገባበት ከማንኛውም ነገር ጋር

Exodus 34:27

• በዚያም አርባ ቀንና አርባ ሌሊት
በተራራው ላይ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት

• በጽላቶቹም አሥሩን የቃል ኪዳን ቃሎች ጻፈ
በጽላቶቹ ላይ የቃል ኪዳን ቃላት የሆኑትን ዐሥሩን ትእዛዞች የጻፈው ሙሴ ይሁን ወይስ እግዚአብሔር ግልጽ አይደለም። እንደዚህኛው አባባል የጻፈው ሙሴ እንደሆነ ያሳይል ነገር ግን ከሌሎች አውድ ስንመለከት የጻፈው እግዚአብሔር (ያህዌ) ነው። “እርሱ” የሚለው ተውላጠ ስም ስለማን እንደሆነ አጠያያቂ ነው

Exodus 34:29

• የፊቱ ቁርበት እንዳንጸባረቀ
በሌላ አገላለጽ፦ “የግንባሩ ቆዳ” ማለት ሲሆን ጠቅላላ “ፊቱን” የሚመለከት ነው። ፊቱ እንደሚያበራ ወይም እንደሚያንጸባርቅ ሆነ ወይም ፊቱ አበራ ወይም አንጸባረቀ

• ወደ እርሱም ይቀርቡ ዘንድ ፈሩ
ወደ ሙሴ ለመቅረብ ፈሩ ወይም ፈርተው ነበር

• ወደ እርሱ ተመለሱ
ወደ ሙሴ ተመልሰው መጡ

Exodus 34:32

• እግዚአብሔርም በሲና ተራራ የተናገረውን ነገር ሁሉ አዘዛቸው
ሙሴም እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ የገለጠለትን ሕግ ሁሉ ለእስራኤላውያን ሰጣቸው ወይም እንዲያደርጉ አዘዛቸው

Exodus 34:34

• መሸፈኛውን ከፊቱ አነሣ
መሸፈኛውን ወይም ሻሹን ከፊቱ ላይ ያነሳ ነበር

• የታዘዘውን ነገር ነገረ
እግዚአብሔር (ያህዌ) እርሱን (ሙሴን) ያዘዘውን ነገር እርሱ ለእስራኤላውያን ነገራቸው ማለት ነው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 35

1 የእስራኤልን ማኅበረ ሰብ ሁሉ ሰብስቦ እንዲህ አላቸው፤ “እንድትፈጽሟቸው እግዚአብሔር የሰጣችሁ ትእዛዝት እነዚህ ናቸው። 2 ስድስት ቀን ሥራ
ትሠራላችሁ፤ ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር የተቀደሰ የፍጹም ዕረፍት የሰንበት ቀን ይሁንላችሁ። በዚያ ቀን ሥራ የሚሠዐራ ሁሉ ይሞታል። 3 በሰንበት ቀን
በማንኛችሁም ቤት ውስጥ እሳት አይንደድ።” 4 ሁሉን የእስራኤል ማኅበረ ሰብ እንዲህ አላቸው፤ “እግዚአብሔር ያዘዘው ይህ ነው። 5 ከልብ ፈቃደኛ የሆናችሁ
ሁሉ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቅርቡ። ሁሉም ለእግዚአብሔር የወርቅ፣ የብር፣ የነሐስ መባያምጣ፤ 6 ሐምራዊና ቀይ ማግ፣ ቀጭን በፍታ፣ የፍየል ጠጕር፣ 7
በቀይ ቀለም የተነከረ የአውራ በግ ቆዳና የአቆስጣ ቆዳ፣ የግራር ዕንጨት፣ 8 መብራቶች ዘይት፣ ለመቅቢያ ዘይቱ ቅመምና ጣፋጭ መዐዛ ያለው ዕጣን፣ 9
መረግዶችና ለኤፉዱና ለደረት ኪሱ የሚሆኑ ሌሎች ዕንጨቶችንም መባ አድርጎ ያቅርብ። 10 በመካከላችሁ ያሉ ብልኀተኛ ሰዎች ሁሉ ይምጡና እግዚአብሔር
ያዘዘውን ሁሉ ይሥሩ፦ 11 ከድንኳኑ ጋር፣ መደረያውን፣ ማያያዣዎቹን፣ ክፈፎቹን፣ አግዳሚዎቹን፣ ቋሚዎቹንና መሠረቶቹን፤ 12 ታቦቱንም ከነመሎጊያዎቹ፣
የስርየት መክደኛውንና የሚሸፍነውን መጋረጃ፤ 13 ከመሎጊያዎቹ ጋር፣ ዕቃዎቹንም ሁሉን ኣየገጽ ኅብስቱን፤ 14 የመብራቶቹን መቅረዝ ከዐባሪ ዕቃዎቹ ጋር፣
መብራቶቹንና የመብራቶቹን ዘይት፤ 15 የዕጣኑን መሠዊያ ከመሎጊያዎቹ ጋር፣ መቅቢያ ዘይቱንና ጣፋጭ መዓዛ ያለውን ዕጣን፣ የመገናኛ ድንኳኑን መግቢያ
መጋረጃ፣ 16 የሚቃጠሉ መሥዋዕቶችን መሠዊያ ከነሐስ መጫሪያው፣ ከመሎጊያዎቹና ከዕቃዎቹ ጋር፤ ትልቁን የመታጠቢያ ሰን እስከ ማስቀመጫው፤ 17
የአድደባባዩን መጋረጃዎች ከምሰሶዎቹና ከመሠረቶቹ ጋር፣ የአደባባዩን መግቢይ ኣመጋረጃ፤ 18 የማደሪያውን ድንኳን ካስማዎች ከነገመዶቻቸው፤ 19 ውስጥ
ለማገልገል በብልኀት የተሠሩ ልብሶችን፣ ካህናት ሆነው ለማገልገል ለካህኑ ለአሮንና ለልጆቹ የሚሆኑ የተቀደሱ ልብሶችን ያምጡ።” 20 ከዚያም ሁሉም
የእስራኤል ነገዶች ሁሉ ከሙሴ ፊት ወጥተው ሄዱ። 21 ልቡ የተነሣሣና ፈቃደኛ የሆነ ሁሉ በመምጣት ለመገናኛው ድንኳን ሥራ፣ ለውስጡም ለሚደረገው
አገልግሎትና ለተቀደሱ ልብሶች የሚሆን ስጦታን ሰጡ። 22 ፈቃደኛ የነበሩ ወንዶችም ሴቶችም መጥተው የአፍንጫ ጌጦችን፣ የጆሮ ጌጦችን፣ ቀለበቶችን፣
ድሪዎችንና ሁሉንም ዓይነት የወርቅ ጌጣጌጦች አመጡ። 23 ሐምራዊ፣ ቀይም ቀይ ማግ፣ ያማረ በፍታ፣ የፍየል ጠጕር፣ በቀይ ቀለም የተነከረ የአውራ በግ ቆዳ፣
ወይም የአስቆጣ ቆዳ የነበራቸውም አመጡ። 24 ለማንኛውም ተግባር የሚጠቅም የግራር ዕንጨት የነራቸው፣ የብርና የነሐስ ስጦታ ማድረግ የሚፈልጉ ሁሉ
በስጦታነት ለእግዚአብሔር አቀረቡ። 25 ብልኀተኛ ሴቶችም ሁሉ ማግ ፈትለው፣ የፈተሉትን ሰማያዊ፣ ሕዐምራዊ፣ ወይም ቀይ ማግ አመጡ። 26 ያነሣሣቸውና
ብልኀተኛ የሆኑ ሴቶች ሁሉ የፍየል ጠጕር ፈተሉ። 27 ለአፉዱና ለደረት ኪሱ የሚሆኑ መረግዶችንና ሌሎች ዕንቆችን አመጡ፤ 28 ለመቅቢያው ዘይትና ጣፋጭ
መዐዛ ላለው ዕጣን ዘይትና ቅመምም አመጡ። 29 የነጻ ፈቃድ ስጦታ ለእግዚአብሔር በሙሴ በኩል እንዲፈጸም አዝዞት ለነበረው ሥራ ሁሉ ቍሳቍሶችን
አመጡ። 30 እስራኤላውያንን እንዲህ አላቸው፤ “እነሆ፣ እግዚአብሔር የሖር የልጅ ልጅ የሆነውን የኡሪን ልጅ ባስልኤልን ከይሁዳ ነገድ በስም ጠርቶታል። 31
ለሁሉም ዐይነት የጥበብ ሥራ ጥበብን፣ ማስተዋልንና ዕውቀትን ሊሰጠው ባስልኤልን በመንፈሱ ሞልቶታል፤ 32 የወርቅ፣ የብርና የነሐስ ጥበባዊ ሥራዎችን
ለመሥራት፣ 33 የጥበባዊ ሥራ ዐይነቶችን ሁሉ ለመሥራት ድንጋዮችን እንዲጠርብና ዕንጨትም እንዲቀርጽ ነው። 34 እግዚአብሔር በባስልኤልና ከዳን ነገድ
በሆነው በአሂሳሚክ ልጅ በኤልያብ ልብ ይህን ችሎታ አስቀመጠ። 35 ጥበበኛ ሰዎች፣ እንደ ቀራጺዎች፣ በሰማያዊ፣ በሐምራዊና በቀይ ማግ፣ ባማረ በፍታም
እንደ ጥልፍ ጠላፊዎችና እንደ ሸመና ሠራተኞች እንዲሠሩም ብልኀትን ሞላባቸው። እነርሱ በሥራ ዐይነቶች ሁሉ ጥበበኞች የሆኑ የጥበብ ባለሙያዎች ናቸው።

Exodus 35:1

• ሰባተኛው ቀን
የሳምንቱ ሰባተኛ ቀን ወይም በአይሁዶች አቆጣጠር ቅዳሜ ማለት ነው

• የሚሰራበትም ሁሉ ይገደል
ይህ በተደራጊ ግስ የተጻፈው በአድራጊ ግስ ሲጻፍ፦ በዚህ ቀን ሥራ
የሚሠራበት ማንኛውም ሰው ግደሉት

Exodus 35:4

አጠቃላይ ምልከታ፦
እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን ያዘዛቸው ነገሮች እርሱ እስራኤላውያን
እንዲያደርጉ ይነግራቸዋል።

• ለእግዚአብሔር ቁርባንን አቅርቡ
ለእግዚአብሔር መባ ወይም መስዋዕት አቅርቡ

• የልብ ፈቃድ ያለው
“ልብ” መባውን የሚያቀርበውን ሰው ማመልከቱ ነው። አማራጭ ትርጉም፦
እያንዳንዱ ሰው ልቡ የፈቀደውን ወይም ፈቃደኛ የሆነ ማንም ሰው”

Exodus 35:10

አጠቃላይ ምልከታ፦
እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን ያዘዛቸው ነገሮች እርሱ እስራኤላውያን
እንዲያደርጉ ቀጥሎ ይነግራቸዋል።

• በልባቸው ጥበበኞች ሁሉ
የእጅ ጥበብ ዐዋቂዎች ሁሉ ወይም ጥበብ ያለው እያንዳንዱ ሰው

• መያዣዎቹንም
መጋረጃዎችን ለማገናኘት የሚያገለግሉ ቀለበቶች ናቸው (ዘጸአት 26፡4-6
ተመልከት)

• እግሮቹንም
በመሬት ላይ የተሰኩና ሌሎችን ከመሬት ጋር ለማገናኘትና እንዳይንቀሳቀሱ
ለማድረግ የሚያገልግሉ እንደመሰረት የሚያገለግሉ ናቸው (ዘጸአት 26:31)

• የስርየት መክደኛውንም
በታቦቱ ላይ የሚቀመጠው የማስተሰሪያ መስዋዕት የተሰራበት መክደኛ
ወይም መሸፈኛ

Exodus 35:13

• የገጹንም ኅብስት
ይህ ዳቦ ወይም ህብስት የእግዚአብሔርን ህልዎት የሚወክል ነው። (ዘጸአት
25:30 ተመልከት)

• የናሱንም መከታ
እንጨት ሲቃጠል ለመያዣነት የሚያገለግል የነሐስ መከላከያ ብረት

Exodus 35:17

• ምሰሶቹንም
ቀጥ ብለው የቆሙና ድጋፍ የሚሰጡ እንጨቶች ናቸው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• እግሮቻቸውንም
በመሬት ላይ የተሰኩና ሌሎችን ከመሬት ጋር ለማገናኘትና እንዳይንቀሳቀሱ ለማድረግ የሚያገልግሉ እንደመሰረት የሚያገለግሉ ናቸው (ዘጸአት 26፡19)

• ካስማዎች
ከእንጨት ወይም ከብረት የተሰሩ የድንኳን ጠርዞችን ወይም ማዕዘኖችን ለመወጠር የሚያገለግሉ ናቸው (ዘጸአት 27፡19 ተመልከት)

• በብልሃት የተሠሩትን ልብሶች
በጥበብ ያጌጡ ወይም የተቀደሱ ልብሶች

Exodus 35:20

• የእስራኤልም ልጆች ማኅበር ሁሉ
እያንዳንዱን ነገር የሚመለከት ነው። ከእያንዳንዱ ነገድ የሆኑ የእስራኤል ህዝቦች

• ሰው ሁሉ ልቡ እንዳነሣሣው
“ልብ” የሰውየው ማንነት የሚመለከት ሲሆን ልቡ ለእግዚአብሔር ነገር ክፍት የሆነ ለመስጠት ልቡ የፈቀደው ወይም ያነሳሳው

• መንፈሱም እሺ እንዳሰኘው
“መንፈስ” የሰው ማንነት መግለጫ ሲሆን የሰው መንፈስ ወይም ፈቃድ አመልካች ነው። መንፈሱ የፈቀደው ወይም ፈቃደኛ የሆነ ማለት ነው።

• ልባቸው እንደ ፈቀደ
ፈቃደኛ የነበሩ ወይም የሆኑ

Exodus 35:23

ለቁጥር **23** ዘጸአት **25**፡**4**-**5** ትርጉም ተመልከት
ለቁጥር 23 ዘጸአት 25፡4-5 ትርጉም ተመልከት

Exodus 35:25

• የፈተሉትንም ሰማያዊውን ሐምራዊውንም ቀዩንም ግምጃ
በእጃቸው የሠሩትን ጥሩ በፍታ ወይም ማግ በሰማያዊ፥ በሐምራዊና በቀይ ቀለም ቀለሙት

• ልባቸውም በጥበብ ያስነሣቸው
“ልብ” ሴቶችን የሚመለከት ሲሆን ፈቃደኛ የነበሩና ጥበብ ያላቸው ሴቶች ማለት ነው

Exodus 35:27

አለቆችም . . . ሙሴ ይሠራ ዘንድ እግዚአብሔር ላዘዘው ሥራ . . . አመጡ
ከቁጥር 27-29 ያለውን ክፍል ከምዕራፍ 25፡1-2 እና ቁጥር 3-7 በማነጻጸር ተርጉም።

Exodus 35:30

• የእግዚአብሔርን መንፈስ ሞላበት
የመንፈስ መሞላት አንድ ባዶ ነገር ውስጥ እንድን ነገር እንደመሙላት ይቆጠራል። የእግዚአብሔር መንፈስ ችሎታ ሰጠው።

• በሥራ ሁሉ ብልሃት
ማናቸውንም የጥበብ ሥራ መሥራት እንዲችል (ዘጸአት 31፡1-2 እና 31፡3-5)

Exodus 35:34

አጠቃላይ ምልከታ፦
ሙሴ ለህዝቡ ንግግሩን ይቀጥላል

• ያስተምሩ ዘንድ በልባቸው አሳደረባቸው
“በልባቸው” የሚለው ባስልኤልና የእርሱን የሥራ ጓደኞችን የሚመለከት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ ዕውቀታቸውን ለሌሎች የማስተማርን ችሎታ ሰጥቶአቸዋል

• በብልሃት የሚሠራውን ሁሉ ያደርጉ ዘንድ
ማናቸውንም የጥበብ ሥራ ለመሥራት እንዲችሉ

• በእነርሱ ልብ ጥበብን ሞላ
ማንኛውንም ዐይነት ሥራ ያከናውኑ ዘንድ ጥበብን ሰጣቸው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 36

1 ስለዚህ ባስልኤልና ኤልያብ፣ የልብ ጥበበኞች የነበሩና እንዲፈጽሙት እግዚአብሔር ያዘዘውን በመከተል መቅደሱ እንዴት እንደሚሠራ ለማወቅ ብልኀትንና
ማስተዋልን ያስቀመጠባቸውም ሁሉ ይሠራሉ። 2 ባስልኤልንና ኤልያብን፣ እግዚአብሔር በልቡ ብልኀትን አስቀምጦበት የነበረ ጥበበኛ ስውን ሁሉ፣ መጥቶ
ሥራውን ለመሥራት ልቡ ያነሣሣውንም ጠራ። 3 የጠራቸውም ለመቅደሱ ሥራ እስራኤላውያን አምጥተውት የነበረውን ስጦታ ሁሉ ከሙሴ ተቀበሉ። ሕዝቡ የነጻ
ፈቃድ ስጦታዎችን ጠዋት ጠዋት ወደ ሙሴ ማምጣት አላቋረጡም ነበር። 4 ስለዚህ በመቅደሱ ሥራ ላይ የተሰማሩ ብልኀተኛ ሰዎች ሁሉ ከሚሠሩት ሥራ
ተነሥተው መጡ። 5 ሙሴን፣ “እግዚአብሔር እንድንሠራው ላዘዘን ሥራ ከሚበቃው በጣም የሚበልጥ ሕዝቡ እያመጡ ነው” አሉት። 6 ሙሴም በሰፈሩ
ውስጥ ያለ ማንም ሰው ለመቅደሱ ሥራ ሌላ ስጦታ እንዳያመጣ ትእዛዝ ሰጠ። ከዚያም በኋላ ሕዝቡ ስጦታ ማምጣቱን አቆሙ። 7 ለሥራው ሁሉ ከሚበቃው
በላይ ቍሳቍሶች ነበሯቸው። 8 ያሉ ጥበበኞችም ሁሉ ከአማረ በፍታና ከሰማያዊ፣ ከሐምራዊ፣ ከቀይ ማግም ከተሠሩትና ኪሩቤልም ከተጠለፉባቸው ዕሥር
መጋረጃዎች ጋር የመገናኛውን ድንኳን ሠሩት። ይህም እጅግ ጥበበኛ የነበረው የባስልኤል ሥራ ነው። 9 መጋረጃ እርዝመት ሃያ ስምንት ክንድ፣ ወርዱም አራት
ክንድ ነበረ። ሁሉም መጋረጃዎች እኩል መጠን ነበራቸው። 10 ባስልኤል ዐምስት ዐምስቱን መጋረጃዎች በአንድ ላይ አድርጎ እርስ በርስ አገጣጠማቸው። 11
መጋረጃዎች የመጨረሻ የውጭ ጠርዝ ላይና በሁለተኛውም ተገጣጣሚ መጋረጃ የመጨረሻ የውጭ ጠርዝ ላይ ሰማያዊ ቀለበቶችን አደረገ። 12 በሁለተኛው
መጋረጃ ጠርዞች ዐምሳ ዐምሳ ቀለበቶችን አበጀ። ስለሆነም ቀለበቶቹ እርስ በርስ ትይዩ ሆነው የተደረጉ ነበር። 13 ባስልኤል ዐምሳ የወርቅ ማያያዣዎችን ሠርቶ
የመገናኛው ድንኳን ወጥ እንዲሆን መጋረጃዎቹን አያያዛቸው። 14 ባስልኤል በማደሪያው ላይ ላለው ድንኳን ዐሥራ አንድ የፍየል ጠጕር መጋረጃዎችን ሠራ። 15
የእያንዳንዱ መጋረጃ እርዝመት ሠላሳ ክንድ፣ ወርዱም አራት ክንድ ነበረ። ዐሥራ አንድ መጋረጃዎች እያንዳንዳቸው እኩል መጠን ነበራቸው። 16 መጋረጃዎች
እርስ በርሳቸው፣ ስድስቱንም መጋረጃዎች እንደዚሁ እርስ በርሳቸው አያያዛቸው። 17 ተገጣጣሚ መጋረጃዎች የመጨረሻ መጋረጃ ጠርዝ ላይ ዐምሳ ቀለበቶችን
በሁለተኛዎቹ ተገጣጣሚ መጋረጃዎች የመጨረሻ መጋረጃ ጠርዝ ላይም እንደዚሁ ዐምሳ ቀለበቶችን አበጀ። 18 ባስልኤል ወጥ እንዲሆን ድንኳኑን
ለማገጣጠም ዐምሳ የነሐስ ማያያዣዎችን ሠራ። 19 ለድንኳኑ መሸፈኛ በቀይ ቅለም የተነከረ የአውራ በግ ቆዳ፣ ከበላዩም የሚህን የአቆስጣ ቆዳ ሠራ። 20
ባስልኤል ከግራር ዕንጨት ወጋግራዎችን ለመገናኛው ድንኳን ሠራ። 21 ወጋግራ እርዝመት ዐሥር ክንድ፣ ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል ነበር። 22 እርስ በርስ
ለማያያዝ በያንዳንዱ ወጋግራ ሁለት ማያያዣዎች ነበር። የመገናኛውን ድንኳን ወጋግራዎች ሁሉ በዚህ መንገድ ሠራ። 23 ባስልኤል በዚህ መንገድ ወጋግራዎችን
ለመገናኛው ድንኳን ሠራ። ለደቡቡ ጎንም ሃያ ወጋግራዎችን አበጀ። 24 ባስልኤል ከሃያዎቹ ወጋግራዎች ሥር የሚሆኑ አራ የብር መቆሚያዎችን አበጀ።
ማያያዣዎች ለመሆን ከመጀመሪያው ወጋግራ ሥር ሁለት መቆሚያዎች ከያንዳንዱ ሌላ ወጋግራ በታችም እንደዚሁ ሁለት መቆሚያዎች ነበሩ። 25 ጎን ላለው
ለመገናኛው ድንኳን ሁለተኛ ጎን ሃያ ወጋግራዎችንና 26 የብር መቆሚያዎቻቸውን አበጀ። በመጀመሪያው ወጋግራ ሥር ሁለት መቆሚያዎች፣ በሚቀጥለው
ወጋግራ ሥርም እንዲሁ ሁለት ሁለት መቆሚያ አበጅቶአል። 27 በስተ ምዕራብ ላለው ለመገናኛው ድንኳን ጀርባ ባስልኤል ስድስት ወጋግራዎችን ሠራ። 28
ድንኳን የኋላ ማእዘኖች ሁለት ወጋግራዎችን አበጀ። 29 እነዚህ ወጋግራዎች ከታች የተነጣጠሉ፣ ከላይ ደግሞ በአንድ ቀለበት የየያያዙ ነበር። ለሁለቱም የኋላ
ማእዘኖች የተደረገው በዚህ መንገድ ነበር። 30 ከብር መቆሚያዎቻቸው ጋር ስምንት ወጋግራዎች ነበሩ። በመጀመሪያው ወጋግራ ሥር ሁለት መቆሚያዎች፣
በሚቀጥለውም ወጋግራ ሥር ሁለት መቆሚያዎች ለያንዳንዱ ወጋግራ ሁለት ሁለት በመሆን ዐሥራ ስድስት መቆሚያዎች ነበሩ። 31 ባስልኤል የግራር ዕንጨት
አግዳሚዎችን አበጀ፦ ለመገናኛው ድንኳን አንድ ጎን ወጋግራዎች ዐምስት፣ አግዳሚዎችን፣ 32 የመገናኛው ድንኳን ጎን ወጋግራዎች አምስት አግዳሚዎችን፣
በምዕራብ በኩል ላለው ለመገናኛው ድንኳን የኋላ ጎን ወጋግራዎችም ዐምስት አግዳሚዎችን ሠራ። 33 አግዳሚዎቹን የሥራቸውም በወጋግራዎች መካከል ላይ
ከዳር እስከ ዳር እንዲደርሱ አድርጎ ነው። 34 ወጋግራዎቹን በወርቅ ለበጣቸው። አግዳሚዎችን ለማያያዝ የወርቅ ቀለበቶችን ሠራ፣ አግዳሚዎችንም በወርቅ
ለበጣቸው። 35 በብልኀተኛ ሠራተኛ ሥራ ኪሩቤል የተጠለፉበትን መጋረጃ ከሰማያዊ፣ ከሐምራዊና ከቀይ ማግ፣ ካማረ በፍታም ሠራው። 36 አራት የግራር
ዕንጨት ምሰሶዎችን አበጅቶ በውርቅ ለበጣቸው። ለምሰሶዎችም የወርቅ ኲላቦችን ሠርቶ አራት የብር መቆሚያዎችን አደረገላቸው። 37 ለድንኳኑ መግቢያ
ከሰማያዊ፣ ከሐምራዊና ከቀይ ማግ፣ ካማረ በፍታም በጥልፍ ጠላፊ ሥራ የተዘጋጀ መጋረጃ አበጀለት። 38 የመጋረጃውን ዐምስት ምሰሶዎች ከኲላቦች ጋር
ሠራ። የምሰሶዎችን ዐናትና ዘንግ በወርቅ ለበጣቸው። ዐምስት መቆሚያዎቻቸውም ከነሐስ የተሰሩ ነበሩ።

Exodus 36:1

• ባስልኤልና ኤልያብ
ሁለቱም ወንዶች ሲሆኑ እግዚአብሔር ለመገናኛው ድንኳን ሥራ የጠራቸው ናቸው (ዘጸአት 31፡1-2፤ 31፡6)

• በልባቸው ጥበበኞችም ሁሉ
እግዚአብሔር ጥበብን በውስጡ እንዳስቀመጠለት የሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን እግዚአብሔር ጥበብ የሰጠው ማለት ነው።

• እግዚአብሔር እንዳዘዘው ነገር ሁሉ አደረጉ
እንዲያደርጉ /እንዲሰሩ/ እግዚአብሔር ባዘዘው መንገድ ወይም ልክ እግዚአብሔር እንዳዘዘው

Exodus 36:2

• ባስልኤልና ኤልያብ
ሁለቱም ወንዶች ሲሆኑ እግዚአብሔር ለመገናኛው ድንኳን ሥራ የጠራቸው ናቸው (ዘጸአት 31፡1-2፤ 31፡6)

• እግዚአብሔርም በልቡ ጥበብን ያደረገለትን
እግዚአብሔር ችሎታ የሰጣቸውንና ሥራውን ለመሥራት ፈቃደኛ የሆኑትን ሰዎች ሁሉ

• ልቡ ያስነሣውን ሁሉ
“ልብ” የሰውዬውን ማንነት የሚመለከት ሲሆን ለእግዚአብሔር ሥራ ውስጡ/ልቡ/ፈቃደኛ የሆነ ወይም ለእግዚአብሔር ሥራ ራሱን ያዘጋጀ ወይም ምላሽ የሰጠ ማለት ነው

Exodus 36:5

• የመቅደሱንም ሥራ የሚሠሩ ጠቢባን ሁሉ የሚያደርጉትን ሥራ ትተው መጡ
የመቅደሱን ሥራ የሚሰሩ ጥበበኞች የሆኑ ባለሙያዎች ሥራ ትተው ወደ ሙሴ መጥተው እግዚአብሔር ያዘዘን ሥራ ለመሥራት የሚያስችል በቂና ከበቂ በላይ ስጦታ ህዝቡ እያመጡ ነው ብለው ተናገሩ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Exodus 36:8

ምዕራፍ **38**:**8**-**10** ካለው ክፍል ጋር አነጻጽር እንዲሁም ምዕራፍ **26**:**1**-**3** ተመልከት።
ምዕራፍ 38:8-10 ካለው ክፍል ጋር አነጻጽር እንዲሁም ምዕራፍ 26:1-3 ተመልከት።

• ማደሪያውን ከአሥር መጋረጆች ሠሩ
የማደሪያው ድንኳን መጋረጃዎች በቁጥር አስር ሲሆኑ የተሰሩት ከልብስ ሆኖ አንዱ ከሌላው ጋር በስፌት ተያይዘው በግድግዳው ላይ ይሰቀላሉ።

Exodus 36:11

• የሰማያዊውን ግምጃ ቀለበቶች አደረጉ
ከሰማያዊ ጨርቅ የተሰሩ ቀለበቶች

• መጋረጆች
እነዚህ መጋረጃዎች የመገናኛውን ድንኳን ለመከፋፈልና ለመሸፈን የሚረዱ ሰፊና ከባድ የጨርቅ መጋረጃዎች ናቸው

• አደረጉ
በወል ስም የተጠቀሰው “አደረጉ” የሚለው የሚያመለክተው ባስልኤልና ከእርሱ ጋር የመገናኛውን ድንኳን ሥራ የሚሰሩ ሰዎች ሁሉ የሚዳስስ ነው።

• አምሳ ቀለበቶችንችን
ሀምሳ የወርቅ ቀለበቶችን (ክብ ነገሮችን)

Exodus 36:14

• አሥራ አንድ መጋረጆች አደረጉ
የመጋረጃው ቁጥር 11 መሆኑን ያመለክታል

• ርዝመቱ ሠላሳ ክንድ
ይህ የልከት ዘዴ ባህላዊ ሲሆን የአንድ ሰው ከክንድ መጋጠሚያ እስከ መካከለኛው ጣት ደረስ ያለው ክፍል ነው።

Exodus 36:18

ተመሳሳይ ክፍሎችን ምዕራፍ **26**:**11** እና **26**:**14** ተመልከት።
ተመሳሳይ ክፍሎችን ምዕራፍ 26:11 እና 26:14 ተመልከት።

Exodus 36:20

ምዕራፍ **26**:**15**-**18** እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከትና ከዚህኛ ክፍል ትርጉም ጋር አነጻጽር።
ምዕራፍ 26:15-18 እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከትና ከዚህኛ ክፍል ትርጉም ጋር አነጻጽር።

• ለማደሪያውም በደቡብ ወገን ሀያ ሳንቆችን አደረጉ
በደቡብ በኩል ላለው የማደሪያ ድንኳን ሃያ ወጋግራ (ቋሚዎችን) አደረጉ ወም ሰሩ

Exodus 36:24

ከዚህ ክፍል ጋር ተመሳሳይ የሆነውን ዘጸአት **26**:**19**-**21** ተመልከት።
ከዚህ ክፍል ጋር ተመሳሳይ የሆነውን ዘጸአት 26:19-21 ተመልከት።

• ለሁለተኛው ወገን በሰሜን በኩል ሀያ ሳንቆች
ለሁለተኛው ክፍል በሰሜን በኩል ወጋግራዎች ነበሩ

Exodus 36:27

• በስተ ኋላ ስድስት ሳንቆች አደረጉ
ምዕራፍ 26:22-23 ያለውን ክፍል እንዴት እንደተረጎምክ እይ

• በምዕራቡ ወገን
በምዕራብ በኩል ባለው

• ለሁለቱ ማዕዘን
ከኋላ በኩል ባለው ለሁለቱ ማዕዘናት

Exodus 36:29

ምዕራፍ **26**:**24**-**25** ተመልከትና ማስተካከያ አድርግ
ምዕራፍ 26:24-25 ተመልከትና ማስተካከያ አድርግ

Exodus 36:31

ዘጸአት **26**:**26**-**28** እና **26**:**29** ተመልከት
ዘጸአት 26:26-28 እና 26:29 ተመልከት

• ከዳር እስከ ዳር አሳለፉ
ለመገናኛው ድንኳን ከአንድ ጫፍ ወደ ሌላ ጫፍ መውሰድ ወይም ማሳለፍ

Exodus 36:37

• አምስቱም እግሮቻቸው የናስ ነበሩ
መቆሚያዎች ከነሐስ ብረት የተሰሩ ስለመሆናቸው የሚናገር ነው። ምዕራፍ 26:36-37 አነጻጽር።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 37

1 ባስልኤል እርዝመቱ ሁለት ተኩል ክንድ፣ ወርዱ አንድ ተኩል ክንድ፣ ቁመቱም አንድ ክንድ ተኩል የሆነ ታቦታ ከግራር ዕንጨት ሠራ። 2 ውስጡንና ውጩንም በንጹሕ ወርቅ ለበጠው፤ በዙሪያውም የወርቅ ክፈፍ አበጀለት። 3 ለአራት እግሮቹም አራት የወርቅ ቀለበቶችን፣ በአንዱ ጎኑ ላይ ሁለት ቀለበቶችን፣ በሌላውም ጎኑ ላይ ሁለት ቀለበቶችን ጨምሮ ሠራ። 4 ዕንጨት መሎጊያዎችን ሠርቶ በወርቅ ለበጣቸው። 5 ታቦቱን ለመሸከም በታቦቱ ጎኖች ላይ ባሉት ቀለበቶች ውስጥ መሎጊያዎቹን አስገባቸው። 6 ሁለት ተኩል ክንድ፣ ወርዱም አንድ ተኩል ክንድ የሆነ የስርየት መክደኛ ከንጹሕ ወርቅ ሠራ። 7 ባስልኤል ለስርየት መክደኛው ሁለት ጫፎች ሁለት ኪሩቤልን ከተቀጠቀጠ ወርቅ አበጀ። 8 አንዱ ኪሩብ ለአንዱ የስርየት መክደኛ፣ ሌላውም ለሌላው የስርየት መክደኛ ጫፍ ነበረ። ኪሩቤል ከስርየት መክደኛው ጋር ወጥ ሆነው ተበጅተው ነበር። 9 ኪሩቤል ክንፎቻቸውን ወደ ላይ በመዘርጋት የስርየት መክደኛውን በድንፎቻቸው ጋረዱት። እርስ በርስ ትይዩ ሆነውም ወደ ስርየት መክደኛው መካከል ይመለከቱ ነበር። 10 ባስልኤል እርዝመቱ ሁለት ክንድ፣ ቁመቱም አንድ ተኩል ክንድ የሆነ ጠረጴዛ ከግራር ዕንጨት ሠራ። 11 ወርቅ ለበጠው፤ ዙሪያውንም በንጹሕ ወርቅ ከፈፈው። 12 አንድ ስንዝር ጠርዝ ከወርቅ ክፈፍ ጋር አበጀለት። 13 የወርቅ ቀለበቶችንም ሠርቶ የጠረጴዛው እግሮች ካሉበት ማእዘኖች ጋር አያያዛቸው። 14 ለመሸከም መሎጊያዎችን ማስገባት እንዲቻል ቀለበቶቹ ከጠርዙ ጋር ተያይዘው ነበር። 15 ጠረጴዛውን መሸከም እንዲቻል መሎጊያዎቹን ከግራር ዕንጨት ሠርቶ በወርቅ ለበጣቸው። 16 በጠረጴዛው ላይ የሚቀመጡ ዕቃዎችን፦ ድስቶችን፣ ዝርግና ጎድጓዳ ሳሕኖችን ጭልፋዎችን፣ ወጭቶችንና የመጠጥ መሥዋዕቱን ማፍሰሻ ማንቆርቆሪያዎች ከንጹሕ ወርቅ ሠራ። 17 ከነማቆሚያውና ከነዘንጉ ከተቀጠቀጠ ንጹሕ ወርቅ ሠራ። ጽዋዎቹ፣ ቀንበጦቹና አበባዎቹ በሙሉ ከመቅረዙ ጋር ወጥ ሆነው ነበር የተሠሩት። 18 ቅርንጫፎች በመቅረዙ አንድ ጎን፣ ሦስት ቅርንጫፎች ደግሞ በሌላው የመቅረዙ ጎን ተሠርተው ስድስት ቅርንጫፎች ነበር። 19 ቅርንጫፍ ከቀንበጥና ክአበባ ጋር የለውዝ አበባ የሚመስሉ ሦስት ጽዋዎች ነበሩት፤ በሌላውም ቅርንጫፍ እንደዚሁ የለውዝ አበባ የሚመስሉ ሦስት ጽዋዎች ከቀንበጥና ከአበባ ጋር ነበር። ከመቅረዙ ለሚወጡ ስድስት ቅርንጫፎች ሁሉ የተደረገው አንድ ዐይነት ነበር። 20 በመቅረዙ መካከል ላይ ባለው ዘንግ ላይ የለውዝ አበቦችን የሚመስሉ እራት ጽዋዎች ከቀንበጦቻቸውና ከአበቦቻቸው ጋር ተሠርተዋል። 21 በመጀመሪያ የቅርንጫፎች ጥንድ ሥር ወጥ ሆኖ ዐብሮት የተሠሩ ቀንበጦች ነበር። ከመቅረዙ በሚወጡ ስድስት ቅርንጫፎች ሁሉ የተደረገው አንድ ዐይነት ነበር። 22 ቅርንጫፎቻቸው ከመቅረዙ ጋር ወጥ ሆነው ከተቀጠቀጠ ንጹሕ ወርቅ የተሠሩ ነበር። 23 መቅረዙንና ሰባቱን መብራቶች፣ መኮስተሪያዎቹንና የኰስታሪ ማስቀመጫዎቻቸውን ከንጹሕ ወርቅ ሠራ። 24 መቅረዙንና ዐባሪ ዕቃዎቹን ከአንድ መክሊት ንጹሕ ወርቅ ሠራቸው። 25 እርዝመቱ አንድ ክንድ፣ ወርዱም አንድ ክንድ የሆነውን የዕጣኑን መሠዊያ ከግራር ዕንጨት ሠራ። አራት ማእዘንና ቁመቱም ሁለት ክንድ ነበር። ቀንዶቹም ከእርሱ ጋር ወጥ ሆነው የተሠሩ ነበር። 26 የዕጣኑን መሠዊያ፦ ዐናቱን፣ ጎኖቹንና ቀንዶቹን በንጹሕ ወርቅ ለበጣቸው። ለዙሪያውም የወርቅ ክፈፍ አበጀለት። 27 በሁለቱ ተነጻጻሪ ጎኖቹ ላይ ከክፈፉ ሥር እንዲያያይዙት ሁለት የወርቅ ቀለበቶችን ሠራ። ቀለበቶቹ መሠዊያውን ለመሸከም መሎጊያዎችን ለመያዝ የሚያገለግሉ ናቸው። 28 ከግራር ዕንጨት ሠርቶ በወርቅ ለበጣቸው። 29 የተቀሰውን የመቅቢያ ዘይትና የሸቶ ቀማሚ ሥራ የሆነውን፣ ንጹሕና ጣፋጭ መዐዛ ያለውን ዕጣን ሠራ።

Exodus 37:1

• ርዝመቱም ሁለት ክንድ ተኩል፥ ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል፥ ቁመቱም አንድ ክንድ ተኩል
ርዝመቱ 1.1 ሜትር፤ ስፋቱና ከፍታው 0.7 ሜትር ያህል ነው

• በአራቱ እግሮቹ ላይ አኖረ
እነዚህ እግሮች እንደሰው ወይም እንስሳ እግር የተቆጠሩ ሲሆን ታቦቱን የሚሸከሙ ወይም የሚደግፉ ናቸው።

Exodus 37:4

አጠቃላይ ምልከታ፦
ባስልኤልና የሥራ ጓደኞቹ የማደሪያውን ድንኳንና በውስጡ የሚገኙ ሥራዎችን ስለመሥራታቸው በማደሪያ ድንኳኑ ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶችንና ሌሎችን በሚመለከት ዘጸአት 25፡13-14፥ 17 ተመልከት።

• ከጥሩ ወርቅም . . . ሠራ
የሠራው መሪ ባስልኤል በመሆኑ ሥራውን ብቻውን እንደሠራ አድርጎ ያቀርባል ነገር ግን ሥራው የተከናወነው ከሥራ ባልደረቦቹ ጭምር ነብር።

• ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል፥ ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል የሆነ የስርየት መክደኛ ሠራ
አንድ ክንድ በሜትር ሲለካ ከ46-50 ሳንቲ ሜትር ሲሆን ወደ ሜትር ሲቀየር 115 ሴ.ሜትር እና 70 ሳ.ሜ ያህል ነው።

Exodus 37:7

አጠቃላይ ምልከታ፦
ባስልኤልና የሥራ ጓደኞቹ የማደሪያውን ድንኳንና በውስጡ የሚገኙ ሥራዎችን ስለመሥራታቸው የሥርየት መክደኛው አሠራር በሚመለከት (37:7-9) ዘጸአት 25፡18-20 ያለውን ክፍል እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት።

• በአንድ ላይ ሠራቸው
እርሱ እነዚህን አንድ አድርጎ ሠራቸው

• ኪሩቤልም ክንፎቻቸውን ወደ ላይ የዘረጉ ሆኑ፥ የስርየት መክደኛውንም በክንፎቻቸው ሸፈኑ
የክሩቤል ምስሎችን እውነተኛ ክሩቤል በማስመሰል ክንፎቻቸውን ዘርግተው አንዱ ከሌላው ጋር ተገናኝተውና የስርየት መደኛውን ሸፍነው እንዲቀመጡ አደረጋቸው። አማራጭ ትርጉም፦ ባስልኤል እነዚህን ክንፍ ያላቸውን ፍጥረታት የአንዱ ክንፍ ከሌላው ጋር እንድገናኙ አድርጎና ክንፎቻቸውን የዘረጉ እንዲሆኑ አድርጎ ሠራቸው።

• እርስ በርሳቸውም ተያዩ
የክሩቤል ዓይኖች አንዱ ሌላውን እንዲመለከቱ ተደርገው የተሰሩ ናቸው

Exodus 37:10

አጠቃላይ ምልከታ፦
ባስልኤልና የሥራ ጓደኞቹ የማደሪያውን ድንኳንና በውስጡ የሚገኙ ሥራዎችን ስለመሥራታቸው ምዕራፍ 37፡10-13 ያለውን ክፍል ከምዕራፍ 25፡23-26 ካለው ክፍል ጋር በማነጻጸር በተገቢው መንገድ ለመተርጎም ሞክር።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• ርዝመቱ ሁለት ክንድ፥ ወርዱም አንድ ክንድ፥ ቁመቱም አንድ ክንድ ተኩል
ርዝመቱ 92 ሴ.ሜትር፤ ወርዱ 46 ሴ.ሜትር እና ቁመቱ 69 ሴ.ሜትር ያህል ነበር

• አንድ ጋት
በባህላዊው ልኪት አንድ ጋት የአራት ጣቶች ጥምር ማለት ሲሆን ከ8-10 ሳ.ሜትር ነው።

• አራቱ እግሮቹ
እነዚህ እግሮች እንደሰው ወይም እንስሳ እግር የተቆጠሩ ሲሆን ታቦቱን የሚሸከሙ ወይም የሚደግፉ ናቸው።

Exodus 37:14

አጠቃላይ ምልከታ፦
ባስልኤልና የሥራ ጓደኞቹ የማደሪያውን ድንኳንና በውስጡ የሚገኙ ሥራዎችን ስለመሥራታቸው ምዕራፍ 37፡14-16 ያለውን ክፍል ከምዕራፍ 25፡27-29 ካለው ጋር በማነጻጸር ተገቢውን የትርጉም ሂደት በመከተል መልዕክቱን ተርጉም።

• ቀለበቶች በክፈፉ አቅራቢያ ነበሩ
“ቀለበቶች ከክፈፉ ጋር ተያይዘው ተሰሩ ወይም ቀለበቶችን ከክፈፉ ጋር አያይዘው ሰሩ”

• ወጭቶቹንና ጭልፋዎቹን ጽዋዎቹንም መቅጃዎቹንም
ዝርግ ሳህኖችን፥ ድስቶችን፥ ጎድጓዳ ሳህኖችን (ውሃ መያዣዎችን) እና ማንቆርቆሪያዎችን . . .

Exodus 37:17

አጠቃላይ ምልከታ፦
ባስልኤልና የሥራ ጓደኞቹ የማደሪያውን ድንኳንና በውስጡ የሚገኙ ሥራዎችን ስለመሥራታቸው ምዕራፍ 37፡17-19 ያለውን ክፍል ከምዕራፍ 25፡31-33 ካለው ጋር በማነጻጸር ተገቢውን የትርጉም ሂደት በመከተል መልዕክቱን ለመተርጉም ሞክር።

• ጽዋዎቹን፥ ጉብጉቦቹን፥ አበቦቹን ከዚያው በአንድነት አደረገ
የአበባ ቅርጽ ያላቸው ጽዋዎችን፥ እንቡጦችንና የፈኩ አበቦችን አንድ ወጥ አድርጎ ሠራቸው

• ጉብጉቡንና አበባውን ሦስትም የለውዝ አበባ የሚመስሉትን ጽዋዎች
ከእንቡጦችና ከፈኩ አበቦች ጋር የለውዝ አበባ የሚመስሉ ሶስት ጽዋዎች

• የለውዝ አበባ
ነጭ ወይም ሮዝ መልክ ያለው የለውዝ አበባ በለውዝ ዘፍ ላይ ያደገ የሚመስል ነበር

Exodus 37:20

በዚህ ክፍል ያሉ ቃላትና ዕቃዎችን እንዴት እንደተርጎምክ በምዕራፍ **25**፡**34**-**36** ተመልከት።
በዚህ ክፍል ያሉ ቃላትና ዕቃዎችን እንዴት እንደተርጎምክ በምዕራፍ 25፡34-36 ተመልከት።

• በመቅረዙም ጉብጉቦቹንና አበቦቹን
በመቅረዙ ላይ እንቡጦችና አበቦች አደረገ

• አራትም የለውዝ አበባ የሚመስሉትን ጽዋዎች አደረገ
የለውዝ አበባ የሚመስሉ አራት ጽዋዎች ወይም ስኒዎች አደርገ ወይም ሰራ

• አንድ ሆኖ የተሠራ አንድ ጉብጉብ
ከመቅረዙ ጋር አንድ ወጥ ሆነው የተሰሩ እንቡጦች

Exodus 37:23

አጠቃላይ ምልከታ፦
ባስልኤልና የሥራ ጓደኞቹ የማደሪያውን ድንኳንና በውስጡ የሚገኙ ሥራዎችን ስለመሥራታቸው በዚህ ክፍል የተጠቀሱ ቃላትና ቁሶችን እንዴት እንደተረጎምክ በ25፡37-39 ላይ ተመልከት

• መኰስተሪያዎቹንም፥ የኩስታሪ ማድረጊያዎቹንም
እነዚህ መኮስተሪያዎች ሁለት ሆነው ከብረት ወይም ከእንጨት የተሰሩ ሲሆን በአንድ በኩል የተያያዙ ናቸው፥ ዕቃዎችን ቆንጥጦ ለመያዝና ለማውጣት የሚያገለግሉ እንደ መቆንጠጫ ያሉ ናቸው።

• ከአንድ መክሊት ጥሩ ወርቅ አደረገ
x

Exodus 37:25

አጠቃላይ ምልከታ፦
ባስልኤልና የሥራ ጓደኞቹ የማደሪያውን ድንኳንና በውስጡ የሚገኙ ሥራዎችን ስለመሥራታቸው የዚህን ክፍል (37፡25-26) ትርጉም ከምዕራፍ 30፡1-3 ካለው ጋር አነጻጽር

• ቀንዶቹም ከእርሱ ጋር በአንድነት የተሠሩ ነበሩ
ቀንዶቹ ከመሰዊያው ጋር በአንድ ላይ ተያይዘው የተሰሩ ናቸው

Exodus 37:27

አጠቃላይ ምልከታ፦
ባስልኤልና የሥራ ጓደኞቹ የማደሪያውን ድንኳንና በውስጡ የሚገኙ ሥራዎችን ስለመሥራታቸው የዚህን ክፍል (37፡27-28) ትርጉም ከምዕራፍ 30፡4-5 ካለው ጋር አነጻጽር

• ጥሩውንም የጣፋጭ ሽቱ ዕጣን በቀማሚ ብልሃት
የሽቱ ቀማሚ ሥራ የሆነውን ንጹህና መልካም መዓዛያለውን ዕጣን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 38

1 የሚቃጠለውን መሥዋዕት መሠዊያ ከግራር ዕንጨት ሠራ። ዐምስት ክንድ እርዝመትና ዐምስት ክንድ ስፋት፣ አራት ማእዘንና ሦስት ክንድ ቁመት ነበረው። 2 ማእዘኖችም የበሬ ቀንዶችን የሚመስሉ ቅርጾችን በመሥራት አስረዘማቸው። ቀንዶቹ ከመሠዊያው ጋር ወጥ ሆነው የተሠሩ ነበሩ፤ መሠዊያውንም በነሐስ ለበጠው። 3 ለመሠዊያው የሚያስፈልገውን ዕቃ ሁሉ፦ ለዐመድ ምንቸቶችን፣ መጫሪያዎችን፣ ጎድጓዳ ሳሕኖችን፣ ሜንጦዎችንና ማንደጃዎችን በሙሉ ከነሐስ ሠራ። 4 ከደረጃው ሥር ከመሠዊያው እኩሌታ እስከ ታች የሚደርስ እንደ መረብ የተሠራ የነሐስ ፍርግርግ ለመሠዊያው አበጀ። 5 ፍርግርግ አራት ማእዘኖች ለመሎጊያዎቹ መያዣ አራት ቀለበቶችን ሠራላቸው። 6 ዕንጨት መሎጊያዎችን ሠርቶ በነሐስ ለበጣቸው። 7 መሎጊያዎቹን መሠዊያውን ለመሸከም በመሠዊያው ጎኖች ላይ ባሉት ቀለበቶች ውስጥ አስገባቸው። መሠዊያውን ክፍት አድርጎ በሳንቃዎች ሠራው። 8 ባስልኤል ትልቁን የመታጠቢያ ሳሕን ከነሐስ መቆሚያ ጋር ሠራ። ሳሕኑን የሠራውም በመገናኛው ድንኳን መግቢያ ላይ የሚያገለግሉት ሴቶች ይጠቀሙባቸው ከነበሩ መስተዋቶች ነው። 9 ሠራው። በአደባባዩ ደቡብ ጎን ላይ የነበሩት መጋረጃዎች ከአማረ በፍታ የተሠሩና አንድ መቶ ክንድ እርዝመት ያላቸው ነበሩ። 10 መጋረጃዎቹ ሃያ ምሰሶዎችና ሃያ መቆሚያዎች ነበሯቸው። ከምሰሶዎቹና ከብር ዘንጎቹ ጋር የተያያዙ ኲላቦችም ነበሩ። 11 ጎን በኩልም እንደዚሁ አንድ መቶ ክንድ እርዝመት ያላቸው መጋረጃዎች ከሃያ ምሰሶዎችና ከሃያ የነሐስ መቆሚያዎች፣ ከምሰሶዎቹ ጋር ከተያያዙ ኲላቦችና ከብር ዘንጎች ጋር ነበር። 12 የምዕራቡ ጎን መጋረጃዎች ዐምሳ ክንድ የሚረዝሙ፣ ዐሥር ምሰሶችና መቆሚያዎች ያሏቸው ነበሩ። የምሰሶዎቹ ኲላቦችና ዘንጎች ብር ነበሩ። 13 አደባባዩም በምሥራቁ ጎን ላይ ዐምሳ ክንድ ይረዝም ነበር። 14 የመግቢያው አንድ ጎን መጋረጃዎች እርዝመት ዐሥራ ዐምስት ክንድ ነበረ። ሦስት ምሰሶዎች ከሦስት መቆሚያዎች ጋር ነበሯቸው። 15 በአደባባዩ መግቢያ ሌላ ጎን ላይም ዐሥራ ዐምስት ክንድ የሚረዝሙና ሦስት ምሰሶዎችና ሦስት መቆሚያዎች ያሏቸው መጋረጃዎች ነበሩ። 16 በአደባባዩ ዙሪያ ያሉት መጋረጃዎች ሁሉ አምሮ ከተፈተለ በፍታ የተሠሩ ነበሩ። 17 የምሰሶዎቹ መቆሚያዎች ከነሐስ፣ የምሰሶዎቹ ኲላቦችና ዘንጎቻቸው፣ የዐናታቸውም መሸፈኛ ከብር የተሠሩ ነበሩ። የአደባባዩ ምሰሶዎች ሁሉ በብር የተለበጡ ነበር። 18 የአደባባዩ በር መጋረጃቅ እርዝመት ሃያ ክንድ ነበረ። ከሰማያዊ፣ ከሐምራዊ፣ ከቀይ ማግና አምሮ ከተፈተለ በፍታ የተሠራ ነበረ። እንደ አደባባዩ መጋረጃዎች ሃያ ክንድ እርዝመትና ዐምስት ክንድ ቁመት ነበረው። 19 የነሐስ መቆሚያዎችና የብር ኲላቦች ነበሩት። የዐናታቸው መሸፈኛና ዘንጎቹ ከብር የተሠሩ ነበሩ። 20 የመገናኛው ድንኳን ካስማዎች ሁሉ የተሠሩት ከነሐስ ነበር። 21 የሙሴን ትእዛዝ በመከተል በተመዘገበው መሠረት የመገናኛው ድንኳን፣ ይኸውም የምስክሩ ድንኳኝ ቆጠራ ይህ ነው። በካህኑ በአሮን ልጅ በኢታማር መሪነት ይህ የሌዋውያኑ ሥራ ነበረ። 22 ከይሁዳ ነገድ የሆነው፣ የሑር የልጅ ልጅ፣ የኡሪ ልጅ ባስልኤል እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠውን ትእዛዝ ሁሉ ፈጸመ። 23 ከባስልኤልም ጋር ከዳን ነገድ የሆነው የአሂሳሚክ ልጅ ኤልያብ ቅርጽ አውጪ ሠራተኛ፣ የእጅ ጥበብ ሙያተኛ፣ በሰማያዊ፣ በሐምራዊ፣ በቀይ ግምጃና በአማረ በፍታ ጥልፍ ጠላፊም ሆኖ ዐብሮት ሠራ። 24 ከመቅደሱ ሥራ ጋር ለተያያዘው ተግባር ሁሉ ጥቅም ላይ የዋለው ወርቅ ማለትም፣ ከስጦታው የተገኘው ወርቅ ሁሉ በመቅደሱ ሰቅል መጠን መሠረት ሃያ ዘጠኝ መክሊትና ሰባት መቶ ሠላሳ ሰቅል ነበረ። 25 ማኅበረ ሰቡ የሰጠው ብር በመቅደሱ ሰቅል መጠን ተመዝኖ አንድ መቶ መክሊትና አንድ ሺሕ ሰባት መቶ ሰባ ዐምስት ሰቅል፣ 26 በአንድ ሰው አንድ ቤካ ይኸውም በመቅደሱ ሰቅል መጠን ግማሽ ሰቅል ነበረ። ይህ ቍጥር የተደረሰበት በሕዝብ ቆጠራው ሃያ ዓመትና ከዚያም በላይ የሆናቸው ተቆጥረው በተገኘው ስድስት መቶ ሦስት ሺሕ ዐምስት መቶ ዐምሳ ወንዶች ቍጥር በያንዳንዱ ሰው ተሰልቶ ነው። 27 የመቅደሱንና የመጋረጃዎችን መቆሚያዎች ለመሥራት አንድ መቶ የብር መክሊት ወጪ ሆኖአል፦ መቆሚያዎቹ በጠቅላላ አንድ መቶ ሆነው፣ ለያንዳንዱ መቆሚያ አንድ መክሊት ተከፍሎአል ማለት ነው። 28 በቀሩት አንድ ሺሕ ሰባቶ መቶ ሰባ ዐምስት የብር ሰቅሎች ባስልኤል የምሰሶዎቹን ኲላቦች ሠርቶ ዐናታቸውን ሸፈነባቸው፤ ዘንጎችንም ለምሰሶዎቹ ሠራባቸው። 29 ከስጦታ የተገኘው ነሐስ ተመዝኖ ሰባ ታለንትና ሁለት ሺሕ አራት መቶ ሰቅል ሆነ። 30 በዚህም የመገናኛውን ድንኳን መግቢያ መቆሚያዎች፣ የነሐስ መሠዊያውን፣ የእርሱንም የነሐስ ፍርግርግ፣ የመሠዊያውን ዕቃ ሁሉ፣ 31 የአደባባዩን መቆሚያዎች፣ የአደባባዩን መግቢያ መቆሚያዎች፣ የመገናኛውን ድንኳንና የአደባባዩን ድንኳን ካስሞች ሁሉ ሠራበት።

Exodus 38:1

አጠቃላይ ምልከታ፦
ባስልኤልና የሥራ ጓደኞቹ የመገናኛውን ድንኳንና የውስጡን ቁሳቁስ ሥራ ይቀጥላሉ።

• ዕቃውንም ሁሉ ከናስ አደረገ
የእነዚህ ዕቃዎች ዝርዝርና ፍቺያቸውን እንዴት እንደተረጎምክ ዘጸአት 27፡1-3 ካለው ክፍል ጋር አነጻጽር።

• ርዝመቱ አምስት ክንድ፥ ወርዱም አምስት ክንድ . . . ከፍታው ሦስት ክንድ ነበረ
ርዝመቱ 2.30 ሜትር፥ ስፋቱ 2.30 ሜትር እና ቁመቱ 1.38 ሜትር ነበር

• ቀንዶቹም ከእርሱ ጋር በአንድ የተሠሩ ነበሩ
ቀንዶቹ ከመሠዊያው ጋር አንድ ወጥ ሆነው የተሠሩ ነበሩ

Exodus 38:4

አጠቃላይ ምልከታ፦
ባስልኤልና የሥራ ጓደኞቹ የመገናኛውን ድንኳንና የውስጡን ቁሳቁስ ሥራ ይቀጥላሉ። ምዕራፍ 38፡4-5 ያለውን ክፍል ለመተርጎም ምዕራፍ 27፡4-5 ያለውን ክፍል እንዴት እንደተረጎምክ አነጻጽር።

Exodus 38:6

አጠቃላይ ምልከታ፦
ባስልኤልና የሥራ ጓደኞቹ የመገናኛውን ድንኳንና የውስጡን ቁሳቁስ ሥራ ይቀጥላሉ

• ከሳንቆቹም ሠርቶ ባዶ አደረገው
መሠዊያው ከሳንቃ (ጠፍጣፋ የሆነ) የተሠራ ሆኖ ውስጡ ክፍት ነበር (ዘጸአት 27፡7-8 ተመልከት)

Exodus 38:8

አጠቃላይ ምልከታ፦
ባስልኤልና የሥራ ጓደኞቹ የመገናኛውን ድንኳንና የውስጡን ቁሳቁስ ሥራ ይቀጥላሉ

• የመታጠቢያውን ሰንና መቀመጫውንም
“መቀመጫው” የመታጠቢያው ሳህን የሚቀመጥበት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የመታጠቢያውን ሳሕንና ማስቀመጫውን ጭምር ከነሐስ ሠራ” ዘጸአት 30፡18 ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• ከሴቶች መስተዋት ከናስ አደረገ
የነሐስ ብረቱ ከመስተዋት የተገኘ (የመጣ) ነበር። የመታጠቢያ ሳህኑ የተሰራው ከመስተዋት ነበር። ይህ መስተዋት ሴቶች ካመጡት የነሐስ መስተዋቶች የተሰራ ነበር።

• መስተዋት
አንጸባራቂና ሰዎች ፊታቸውን ወይም ሌሎችን ነገሮች ለማየት የሚጠቀሙት የብረት ቁራጭ ነው

Exodus 38:9

አጠቃላይ ምልከታ፦
ባስልኤልና የሥራ ጓደኞቹ የመገናኛውን ድንኳንና የውስጡን ቁሳቁስ ሥራ ይቀጥላሉ

• የተፈተለ የጥሩ በፍታ መጋረጆች ነበሩ
ይህን ክፍል ለመተርጎም ይረዳህ ዘንድ ዘጸአት ምዕራፍ 27:9-10 እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት

• ርዝመቱ መቶ ክንድ የሆነ
ርዝመቱ 46 ሜትር ወይም 4600 ሴ. ሜትር የሆነ

Exodus 38:11

ይህን ክፍል ለመተርጎም ይረዳህ ዘንድ ዘጸአት ምዕራፍ **27:11-12** እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት
ይህን ክፍል ለመተርጎም ይረዳህ ዘንድ ዘጸአት ምዕራፍ 27:11-12 እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት

• መቶ ክንድ ርዝመት . . . አምሳ ክንድ ርዝመት . . .
46 ሜትር ርዝመት . . . 23 ሜትር ርዝመት

Exodus 38:13

• በምሥራቅም ወገን . . . ዙሪያ
ይህን ክፍል ለመተርጎም ይረዳህ ዘንድ ዘጸአት ምዕራፍ 27:13-16 እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት። የመግቢያው ደጅ ባለበት በምሥራቅ በኩልና በድንኳኑ መግቢያ ዙሪያ ያሉት መጋረጃዎች።

• መጋረጆች ሁሉ ከተፈተለ ከጥሩ በፍታ ተሠርተው ነበር
ባስልኤልና ሌሎች የሥራ ባልደረቦቹ መጋረጃዎችን ከጥሩ በፍታ (ሐር) ሰርተውት ነበር።

Exodus 38:17

ይህን ክፍል ለመተርጎም ይረዳህ ዘንድ ዘጸአት ምዕራፍ **27:16-19** እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት።
ይህን ክፍል ለመተርጎም ይረዳህ ዘንድ ዘጸአት ምዕራፍ 27:16-19 እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት።

• የምሰሶቹም እግሮች የናስ
ባስልኤልና የሥራ ባልደረቦቹ የምሰሶዎቹ እግሮች የሠረኤትከነሐስ ብረት ነበር።

• ጉልላቶቹና ዘንጎቹም በብር ተለብጠው ነበር
ባስልኤልና የሥራ ባልደረቦቹ /ጓደኞቹ/ ጫፎቻቸውንና ዘንጎቻቸውን ከብር ሠርተውት ነበሩ

Exodus 38:21

አገናኝ ሀረግ፦
ባስልኤልና የሥራ ባልደረቦቹ የማደሪያ ድንኳኑንና በውስጡ ያሉ ቁሶችን ቀጥለው ሠሩ

• በኢታማር እጅ እንደ ተቈጠረው የማደሪያው፥ የምስክሩ ማደሪያ፥ ዕቃ ድምር ይህ ነው
በኢታማር መሪነት በሌዋውያን ሀላፊነት የተቆጠረሩ የመገናኛው ድንኳን ዕቃዎች ዝርዝር ቈጠራ ይህ ነው

• እግዚአብሔር ለሙሴ ያዘዘውን ሁሉ አደረገ
እግዚአብሔር በሙሴ በኩል ያዘዛቸውን ነገሮች ሁሉ ሠሩ።

• ኢታማር፥ ባስልኤል፥ ሆር፥ ኡር
እነዚህ የወንዶች ስም ዝርዝር ነው

• የአሂሳሚክ ልጅ ኤልያብ ነበረ
እነዚህ የወንዶች ስም ዝርዝር ነው

• የቅርጽ ሠራተኛና ብልህ ሠራተኛ
አንጥረኛ (የእጅ ጥበብ ባለሙያ) እና ፕላን (ዕቅድ) አውጪ ባለሞያ

Exodus 38:24

• የተሰጠው ወርቅ ሁሉ
ሰዎች ለሥራው የሠጡት ወርቅ በሙሉ

• ሀያ ዘጠኝ መክሊት ሰባት መቶ ሠላሳ ሰቅል ነበረ
አንድ መክሊት 33 ኪሎ ግራም ሲሆን 29 መክሊት 960 ኪሎ ግራም ወርቅ እና አንድ ሰቅል 3.3 ክሎ ግራም ሲሆን 100 ሰቅል 330 ኪሎ ግራም ይሆናል። በጠቅላላው የወርቁ ቁጥር 1290 ኪሎ ግራም ወርቅ ነበር።

• መቶ መክሊትና አንድ ሺህ ሰባት መቶ ከሰባ አምስት ሰቅል ብር
በጠቅልላው 1775 ሰቅል ወይም 5858 ኪሎ ግራም ብር ነበር

• የሰቅል ግማሽ **(**አንድ ቤካ**)**
አንድ ሰቅል 11 ግራም ሲሆን የሰቅል ግማሽ 5.5 ግራም ይሆናል።

• ከተቈጠረው ከእያንዳንዱ ሰው የተሰጠ ነው
ይህ የሰቅል ግማሽ የተሰበሰበው ዕድሜያቸው 20 አመት የሆናቸው፥ በቆጠራው የተካተቱና ግማሽ ሰቅል (አንድ ቤካ) መስጠት የሚገባቸው ሰዎች ቁጥር ማለት ነው።

• እንደ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን
የቤተመቅደስ የሰቅል ሚዛን ደረጃውን የጠበቀ ስለሆነ “በተቀደሰ ሚዛን፤ በታወቀው ሚዛን” ይባላል።

Exodus 38:27

• መቶውም የብር መክሊት
3300 ኪሎ ግራም የሚመዝን ብር

• ሺህ ሰባት መቶ ሰባ አምስት ሰቅል
ወደ 20 ኪሎ ግራም የሚመዝን

• ሰባ መክሊትና ሁለት ሺህ አራት መቶ ሰቅል
በጠቅላላው 2300 ክሎ ግራም የሚመዝን የነሐስ ብረት ነበር

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Exodus 38:30

• የናሱን መከታ
ከነሐስ ብረት የተሰራ ሲሆን እንጨት በእሳት ሲቃጠል ለመያዝ የሚያገለግል (ዘጸአት 27:4 ተመልከት)

• የማደሪያውንም ካስማዎች
ከእንጨት ወይም ከብረት የተሰሩ የድንኳን ጠርዞችን ወይም ማዕዘኖችን ለመወጠር የሚያገለግሉ ናቸው (ዘጸአት 27:19 ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 39

1 በመቅደሱ ውስጥ ለሚከናወነው አገልግሎት ከሰማያዊ፣ ከሐምራዊና ከቀይ ማግ የተሠሩ ልብሶችን አበጁ። እግዚአብሔር ሙሴን ባዘዘው መሠረት ለቤተ
መቅደሱ የሚሆኑ የአሮንን ልብሶች ሠሩ። 2 ኤፉዱን ከወርቅ፣ ከሰማያዊ፣ ከሐምራዊ፣ ከቀይ ማግና አምሮ ከተፈተለ በፍታ ሠራ። 3 ሠራተኛ እንደሚሠራው፣
በሰማያዊ፣ በሐምራዊ፣ በቀይ ማግና በአማረ በፍታ ለመ|ሥራት ወርቁን ቀጥቅጠው ወደ ሽቦነት ቆራረጡት። 4 የትከሻ ንጣዮችን ሠርተው ከላይኛዎቹ ጠርዞቹ
ጋር አያያዙት። 5 በብልኀት የተጠለፈው የወገብ መታጠቂያም እንደ ኤፉዱ ሲሆን፣ እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው፣ አምሮ ከተፈተለ በፍታ ይኸውም ከወርቅ፣
ከሰማያዊ፣ ከሐምራዊና ከቀይ ማግ ከኤፉድ ጋር ወጥ ሆኖ የተሠራ ነበረ። 6 የመረግድ ድንጋዮችን በወርቅ ፈርጥ ክፈፍ አበጁለቸው፤ እንደ ማኅተምም የዐሥራ
ሁለቱን የእስራኤል ልጆች ስሞች ቀረጹባቸው። 7 እግዚአብሔር ሙሴን ባዘዘው መሠረት፣ ባስልኤል በሴፉዱ የትከሻ ንጣዮች ላይ ለዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል
ልጆች የመታሰቢያ ድንጋዮች አድርጎ አስቀመጣቸው። 8 ኪሱንም ብልኀ ሠራተኛ እንደሚሠራው፣ እንደ ኤፉዱ አበጀው። ከወርቅ፣ ከሰማያዊ፣ ከሐምራዊ፣ ከቀይ
ማግና ከአማረ በፍታ ሠራው። 9 ኪሱ አራት ማእዘን ነበረ። ርዝመቱም ወርዱም አንድ ስንዝር ሆኖ የተደረበ ዕጥፍ ነበረ። 10 በውስጡም አራት የዕንቊ
ድንጋዮች ፈድፎች አበጅተዋል። በመጀመሪያው ረድፍ ሰርድዮን፣ ቶጳዝዮንና አብራቅራቂ ዕንቊ ነበሩት። 11 ረድፍ በሉር፣ ሰንፔር፣ አልማዝ፤ 12 በሦስተኛው
ረድፍ ያክንት፣ ኬልቄዶን፣ አሜቴስጢኖስ፤ 13 በአራተኛውም ረድፍ ቢረሌ፣ መረግድና ኢያስጲድ ነበሩ። ድንጋዮቹ በወርቅ ፈርጥ ዙሪያቸውን የተከፈፉ ነበር። 14
እያንዳንዳቸው በዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ልጆች ስሞች ቅደም ተከተል መሠረት የተቀመጡ ነበር። እያንዳንዱ ስም ከዐሥራ ሁለቱ ነገዶች አንዱን በመወከል
በማተሚያ ቀለበት ላይ እንደሚቀረጽ የተቀረጸባቸው ነበሩ። 15 ኪሱ ላይ ከንጹሕ ወርቅ እንደ ገመድ የተጎነጎኑ ድሪዎችን አበጁ። 16 ሁለት የወርቅ ፈርጦችንና
ሁለት የወርቅ ቀለበቶችን ሠርተው ሁለቱን ቀለበቶች ከደረት ኪሱ ሁለት ጠርዞች ጋር አያያዟቸው። 17 ሁለቱን የተጎነጎኑ የወርቅ ድሪዎች በደረት ኪሱ ጠርዞች
ሁለት ቀለበቶች ውስጥ አስቀመጧቸው። 18 ሌሎች ሁለት ጫፎች ከሁለት ፈርጦች ጋር አያያዟቸው። ከኤፉዱ የትከሻ ንጣዮች ጋር በኤፉዱ ፊት አገናኟቸው።
19 የወርቅ ቀለበቶችን ሠርተው ከውስጠኛው ጠርዝ ቀጥሎ በሚገኘው ጎን በደረት ኪሱ ሌሎች ሁለት ጠርዞች ላይ አስቀመጧቸው። 20 ተጨማሪ የወርቅ
ቀለበቶችን ሠርተው፣ በመያዣው አጠገብ በብልኀት ከተሠራው የወገብ መታጠቂያ በላይ፣ ከአፉዱ ፊት ሁለት የትከሻ ንጣዮች ግርጌ ጋር አያያዟቸው። 21
በብልኀት ከተሠራው ከኤፉዱ የወገብ መታጠቂያ በላይ መያያዝ እንዲችል፣ የደረት ኪሱን በራሱ ቀለበቶች ከኤፉዱ ቀለበቶች ጋር በሰማያዊ ፈትል አሰሩት። ይህ
የሆነው የደረት ኪሱ ከኤፉዱ የተነጠለ እንዳይሆን ነው። የተደረገውም እግዚአብሔር ሙሴን አዝዞት በነበረው መሠረት ነው። 22 የኤፉዱን ቀሚስ ሙሉ በሙሉ
የሸማኔ ሥራ ከሆነው ከሐምራዊ ጨርቅ ሠራው። 23 መካከሉ ላይ ዐንገት ማስገቢያ ነበረው። እንዳይቀደድም ዙሪያውን የተዘመዘመ ጠርዝ ነበረው። 24
በታችኛው የቀሚሱ ዘርፍ ላይም የሰማያዊ፣ የሐምራዊ፣ የቀይ ማግና የአማረ በፍታ ሮማኖችን አበጁ። 25 ሻኩራዎችን ከንጹሕ ወርቅ ሠርተው በታችኛው የቀሚሱ
ጠርዝ ዙሪያ ላይ በሮማኖቹም መካከል፣ 26 አገልግሎት በቀሚሱ ጠርዝ ላይ ሻኩራን ሮማን፣ ሻኩራና ሮማን እያደረጉ አስቀመጧቸው። ይህም የሆነው
እግዚአብሔር ሙሴን አዝዞት በነበረው መሠረት ነው። 27 ለአሮንና ለልጆቹ ሸሚዞችን ከአማረ በፍታ ሠሩ። 28 የራስ መጠምጠሚያዎችን፣ ቆቦችንና ሱሪዎችን
ከአማረ በፍታ፣ 29 መታጠቂያዎችንም ከአማረ በፍታ፣ ከሰማያዊ፣ ከሐምራዊና ከቀይ ማግ ጥልፍ ጠላፊ እንደሚሠራው አድርገው አበጁቸው። ይህም የሆነው
እግዚአብሔር ሙሴን አዝዞት በነበረው መሠረት ነው። 30 አክሊል ሠሌዳ ከንጹሕ ወርቅ ሠርተው በቀለበት ላይ ማኅተም እንደሚቀረጽ በላዩ ቅዱስ
ለእግዚአብሔርን ቀረጹበት። 31 እግዚአብሔር ሙሴን አዝዞት እንደ ነበረው፣ በመጠምጠሚያው ዐናት ላይ ለማንጠልጠል ሰማያዊ ፈትል አሰሩበት። 32
ድንኳን፣ የማደሪያው ሥራ ተጠናቀቀ። የእስራኤል ሰዎች እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጣቸውን መመሪያዎች በመከተል ሁሉንም አደረጉ። 33 ድንኳኑንና ዕቃዎቹን
ሁሉ፣ ካስማዎቹን፣ ወጋግራዎቹን፣ አግዳሚዎቹን፣ ምሰሶዎቹንና መቆሚያዎቹን፣ 34 በቀይ ቀለም የተነከረውን የአውራ በግ ቆዳ መሸፈኛ፣ የአስቆጣ ቆዳዊን
መሸፈኛና የሚሸፍነውን መጋረጃ፣ 35 የምስክሩን ታቦት፣ መሎጊያዎቹንና የስርየት መክደኛውን ወደ ሙሴ አመጡ። 36 ጠረጴዛውን፣ የጠረጴዛውን ዕቃዎች
ሁሉና የገጽ ኅብስቱን፤ 37 የንጹሑን ወርቅ መቅረዝና የረድፍ መብራቶችን ከዐባሪ ዕቃዎቹና ከመብራቶቹ ዘይት ጋር፤ 38 መሥዐዊያውን፣ መቅቢያ ዘይቱንና
ጣፋጭ መዐዛ ያለን ዕጣን፣ የመገናኛውን ድንኳን መግቢያ መጋረጃ፤ 39 የነሐስ መሠዊያውን ከነሐስ ፍርግርጉና ከመሎጊያዎቹ፣ ከዕቃዎቹ፣ ከትልቁ
የመታጠቢያ ሳሕንና ከመቆሚያው ጋር አመጡ። 40 የአደባባዩን መጋረጃዎች ከምሰሶዎቹና ከመቆሚያዎቹ ጋር፣ የአደባባዩን መግቢያ መጋረጃም፣ ገመዶቹንና
የድንኳን ካስማዎችን፣ ለመገናኛው ድንኳን አገልግሎት ጥቅም ላይ የሚውለውን ዕቃ ሁሉ አመጡ። 41 አገልግሎት በጥበብ የተሠሩትን ልብሶች፣ ካህናት ሆነው
እንዲያገለግሉ የካህኑን የአሮንንና የልጆቹን የተቀደሱ ልብሶችም አመጡ። 42 ስለዚህም የእስራኤል ሰዎች እግዚአብሔር ሙሴን ባዘዘው መሠረት ሥራውን
በሙሉ አከናወኑ። 43 ሙሴ ሥራውን ሁሉ ሲፈትሽ፣ እነሆ ሁሉን አከናውነውታል። ያከናወኑትም እግዚአብሔር አዝዞት በነበረው በዚያው መንገድ ነው። ሙሴም
ሕዝቡን ባረካቸው።

Exodus 39:1

• የተቀደሰውን ልብስ አደረጉ
“አደረጉ” የሚለው ቃል ባስልኤል፥ ኤልያብና ማናቸውንም ሥራ ለመሥራት ችሎታንና ዕውቀትን የሰጣቸው ሌሎች ሰዎች ማለት ነው

• እግዚአብሔርም ሙሴን እንዳዘዘው
እነዚህ ሰዎች ሥራውን የሰሩት እግዚአብሔር ሙሴን ባዘዘው መሠረት ነው ማለት ነው።

Exodus 39:2

አጠቃላይ ምልከታ፦
በመገናኛው ድንኳን የሚያገለግሉ ካህናት ልብሶች ዝግጅት ይቀጥላል

• ባስልኤል
ይህ የሰው ስም ነው፤ ልንጽጽር ዘጸአት 31:1-2 እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት

Exodus 39:4

አጠቃላይ ምልከታ፦
በመገናኛው ድንኳን የሚያገለግሉ ካህናት ልብሶች ዝግጅት ይቀጥላል

• ሁለቱ ወገን እንዲጋጠም በሁለቱ ጫንቃዎች ላይ የሚጋጠም ልብስ አደረጉት
ለኤፉዱም ማንገቻ በትከሻ ላይ የሚወርዱ ሁለት ማንጠልጠያ ሠርተው ጐንና ጐኑ እንዲያያዙ አደረጉ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• እግዚአብሔርም ሙሴን እንዳዘዘው
እነዚህ ሰዎች ሥራውን የሰሩት እግዚአብሔር ሙሴን ባዘዘው መሠረት ነው ማለት ነው። ቁጥር 1 ተመልከት።

Exodus 39:6

አጠቃላይ ምልከታ፦
በመገናኛው ድንኳን የሚያገለግሉ ካህናት ልብሶች ዝግጅት ይቀጥላል

• የመረግድ ድንጋዮች ሠርተው
የመረግድ ድንጋዮችን ወስደው የወርቅ ፈርጥ ቅርጽ በድንጋዩ ላይ ቀርጸው እንደ ማለት ነው

• ለእስራኤል ልጆች የመታሰቢያ ድንጋዮች
በ12ቱ (በእስራ ሁለቱ) የእስራኤል ልጆች መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ከድንጋይ የተቀረጸ

Exodus 39:8

አጠቃላይ ምልከታ፦
በመገናኛው ድንኳን የሚያገለግሉ ካህናት ልብሶች ዝግጅት ይቀጥላል

• አደረገው
አዲሱ አማርኛ እና መደበኛው አማርኛው ትርጉም “ሠሩት” ብሎ በወል ስም ይጠቅሳሉ። የዕብራይስጡ ቅጅ፥ የቀድሞ አማርኛ ቅጅና ለሎች ተአማኒነት ያላቸው ቅጅዎች “አደረገው” ይላሉ። “ሠሩት” በሚል የተረጎሙት ትኩረታቸው ባስልኤል፥ ኤልያብና ሌሎች ሰዎችን ታሳቢ በማድረግ ነው። “አደረገው” በሚል የተረጎሙት ትኩረታቸው የሥራው ዋና መሪ ባስልኤል ስለሆነ ትኩረታቸው በእርሱ ላይ ነው። የዕብራይስጡ ቅጅ ትኩረቱ በባስልኤል ላይ ስለሆነ “እርሱ አደረገው” የሚል ነው። ስለሆነም አደረገው የሚለው ትክክለኛ ትርጉም ነው።

• አንድ ስንዝር
በዘመናዊ የርቀት መለኪያ ከ20-22 ሴንቲ ሜትር ያህል ነው።

Exodus 39:10

አጠቃላይ ምልከታ፦
በመገናኛው ድንኳን የሚያገለግሉ ካህናት ልብሶች ዝግጅት ይቀጥላል

• ዕንቁዎቹንም በአራት ተራ አደረጉበት
ሠራተኞች የከበሩ ድንጋዮችን በተነገራቸው መሰረት በአራት ረድፍ አደርገው ሰሩት

• ሰርድዮን፥ ቶጳዝዮን ...
የእነዚህን ድንጋዮች ስም ዝርዝር በየቋንቋው ለማግኘት አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን እነዚህ ዕንቁ የተባሉት “የከበሩ ወይም ውድ” የድንጋይ ዓይነቶች መሆናቸውና አንዱ ከሌላው የተለየ መሆኑን ማወቅ አስፈላጊ ነው። ስለሆነም በትርጉም ወቅት ተውሶ ወይም ባዕድ ቃላትን በመጠቀም ትርጉሙን ግልጽ ማድረግ ይቻላል።

• በወርቅ ፈርጥ ተደረጉ
እነዚህን የከበሩ ወይም ውድ ድንጋዮችን በወርቅ ፈርጥ ወይም በተቀረጸው ወርቅ ላይ አስቀመጡ

Exodus 39:14

አጠቃላይ ምልከታ፦
በመገናኛው ድንኳን የሚያገለግሉ ካህናት ልብሶች ዝግጅት ይቀጥላል

Exodus 39:17

• የተጐነጐኑ የወርቅ ድሪዎች
ከንጹህ ወረቅ የተሰሩ የወርቅ ሰንሰለት ወይም ገመድ መሳይ

Exodus 39:19

አጠቃላይ ምልከታ፦
በምዕራፍ 28፡26-27 በተጠቀሰው መሰረት በመገናኛው ድንኳን የሚያገለግሉ ካህናት ልብሶች ዝግጅት ይቀጥላል

• የወርቅ ቀለበቶች ሠሩ
ለማያያዣነት የሚያገለግሉ የወርቅ ቀለበቶች ወይም ክብ ነገር

• በብልሃት ከተጠለፈው ቋድ
ከጨርቅ ወይም ከጨርቅ ክር የተሰራ የወገብ መታጠቂያ ወይም ቀበቶ ሲሆን የእጄ ጥበብ ባለሙያ የሰራው ዓይነት ማለት ነው

Exodus 39:21

አጠቃላይ ምልከታ፦
በምዕራፍ 28፡28 በተጠቀሰው መሰረት በመገናኛው ድንኳን የሚያገለግሉ ካህናት ልብሶች ዝግጅት ይቀጥላል

• ከኤፉዱም እንዳይለይ
ከኤፉዱ እንዳይላቀቅ የሚያደርግ ወይም በጥብቅ እንዲተሳሰር የሚያደርግ

Exodus 39:22

አጠቃላይ ምልከታ፦
በምዕራፍ 28፡31-33 በተጠቀሰው መሰረት በመገናኛው ድንኳን የሚያገለግሉ ካህናት ልብሶች ዝግጅት ይቀጥላል

• ባስልኤል
ይህ የሰው ስም ነው፤ ልንጽጽር ዘጸአት 31፡1-2 ላይ ስሞችን እንዴት እንደምትተረጉም አስተውል

Exodus 39:25

አጠቃላይ ምልከታ፦
በምዕራፍ 28፡34-35 ላይ በተሰጠው መመሪያ መሰረት በመገናኛው ድንኳን የሚያገለግሉ ካህናት ልብሶች ዝግጅት ይቀጥላል

• ከጥሩ ወርቅም ሻኩራዎችን
ከጥሩ ወርቅ ጸናጽሎችን ወይም ትናንሽ ድምጽ የሚሰጡ ቁርጥራጭ ነገሮችን ማለት ነው።

• ሻኩራንና ሮማንን፥ ሻኩራንና ሮማንን ለማገልገል አደረጉ
በአገልግሎት ወቅት እንዲለብሱ ጸናጽሎችንና ሮማን ፍሬ መሳይ ስዕሎችን በቀሚሱ ጠርዝ ወይም ጫፍ ዙሪያ አደረጉ

Exodus 39:27

አጠቃላይ ምልከታ፦
በመገናኛው ድንኳን የሚያገለግሉ ካህናት ልብሶች ዝግጅት ይቀጥላል

• እግዚአብሔርም ሙሴን እንዳዘዘው ... አደረጉ
እንደነዚህ ያሉትን ክፍሎች በ28:39-40 እና 42 ላይ ያለውን እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• መጠምጠሚያ
ወንዶች ራሳቸውን የሚሸፍኑበት ከጨርቅ የተሰራ ራስ ጥምጥም

• የእግር ሱሪዎችን
ከሌሎች ልብሶች ቀደም ተብሎ የሚለበስ የውስጥ ሱሪ ማለት ነው፥ (የጋራ መረዳትና ያልተገለጹ ሀሳቦች እንዴት እንተረጉማለን የሚለውን ተመልከት)

• መታጠቂያ
በትከሻ ወይም አንገትጌ ላይ የሚለበስና እንዲሁም በወገብ ላይ የሚለበስ የወገብ መታጠቂያ ነው።

Exodus 39:30

አጠቃላይ ምልከታ፦
በምዕራፍ 28፡36-37 ላይ በተሰጠው መመሪያ መሰረት በመገናኛው ድንኳን የሚያገለግሉ ካህናት ልብሶች ዝግጅት ይቀጥላል

• የተቀደሰ የአክሊል
ከንጹህ ወርቅ በራስ ላይ የሚደረግ ቆብ መሳይ ነገር

Exodus 39:32

አጠቃላይ ምልከታ፦
በምዕራፍ 35፡4-9 እና 35፡10-12 ላይ በተሰጠው መመሪያ መሰረት እስራኤላውያን የተሰጣቸውን ሥራ ሲጨርሱ ያሳየናል።

• እንዲሁም የመገናኛው ድንኳን የማደሪያውም ሥራ ሁሉ ተጨረሰ
ይህ በተደራጊ ግስ የተገለጸው ዐረፍተ ነገር “የእስራኤል ልጆች የመገናኛውን ድንኳን ሥራውን ሁሉ ጨረሱ” በሚለው ልተረጎም ይችላል። “የመገናኛው ድንኳን የማደሪያውም” የሚሉ ቃላት ሁለቱም ስለአንድ ነገር የሚያወሩ ናቸው።

• የማደሪያውን ድንኳን ወደ ሙሴ አመጡት
የእስራኤል ሰዎች እግዚአብሔር ሙሴን ባዘዘው መሰረት የተሰራውን የመገናኛውን ድንኳን ወደ ሙሴ አመጡ ማለት ነው።

• መያዣዎች
መጋረጃዎችን በአንድ ለማያያዝ የሚጠቅሙ ነገሮች ወይም አቃፊዎች ናቸው። ዘጸአት 26፡4-6 እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት።

• እግሮቹንም
ምሶሶዎች የሚቆሙባቸው እግሮች ማለት ነው።

• የስርየት መክደኛውንም
ከታቦቱ ላይ የሚቀመጥ መሸፈኛ ወይም መክደኛ ሲሆን የስርየት መስዋዕት የሚቀርብበትም ጭምር ነው።

Exodus 39:36

አጠቃላይ ምልከታ፦
በባስልኤልና በሥሩ ያሉ የሥራ ቡድኖች ማደሪያውንና መገናኛ ድንኳኑን ለሙሴ ሲያቀርቡ እናያለን።

• የገጹንም ኅብስት
ህልዎተ እግዚአብሔር መገለጫ የሆነው ዳቦ ነው። በመገናኛው ድንኳን ወይም በማደሪያው ውስጥ የእግዚአብሔር መኖር ምልክት የሆነው ዳቦ ነው። ከተራ ዳቦ የተለየ መሆኑን ለማመልከት በአማርኛ ኅብስት ተብሏል። ዘጸአት 25፡30 ተመልከት

• ከናስ መጫሪያው
እንጨት በእሳት ሲነድ በአንድ በኩል እንጨቱን ለመያዝ የሚያገለግል ከነሐስ ብረት የተሰራ ዘንግ ማለት ነው።

Exodus 39:40

አጠቃላይ ምልከታ፦
በባስልኤልና በሥሩ ያሉ የሥራ ቡድኖች ማደሪያውንና መገናኛ ድንኳኑን ለሙሴ ሲያቀርቡ እናያለን።

• የእስራኤል ልጆች ሥራውን ሁሉ ሠሩ
ሥራውን በሀላፊነት የሚመራው ባስልኤልና የእርሱ ቡድን ይሁን እንጂ እስራኤላውያንም በሥራው ላይ ተሳታፊ ነበሩ።

• እነሆም አድርገውት ነበር
በትክክልና በታዘዙት መሰረት ሰርተውት ነበር።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 40

1 ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፤ 2 “በዐዲሱ ዓመት የመጀመሪያ ወር የመጀመሪያ ቀን ማደሪያውን፣ የመገናኛውን ድንኳን ትከለው። 3 ታቦት በውስጡ አስቀምጠው፤ ታቦቱንም በመጋረጃ ከልለው። 4 ጠረጴዛውንም ወደ ውስጥ አምጣና በላዩ የሚቀመጡትን ዕቃዎች በሥርዐት አስቀምጥ። ከዚያም መቅረዙን አስገብተህ መብራቶቹን አስተካክል። 5 የወርቅ የዕጣን መሠዊያውን በምስክሩ ታቦት ፊት አስቀምጥ፤ የመገናኛውን ድንኳን መግቢያ መጋረጃም አድርግ። 6 የሚቃጠሉ መሥዋዕቶችን መሠዊያ በማደሪያው፣ በመገናኛው ድንኳን ፊት ለፊት አስቀምጥ። 7 ትልቁን የመታጠቢያ ሳሕን በመገናኛው ድንኳንና በመሠዊያው መካከል አስቀምጠው፤ ውሀም አድርግበት። 8 በዙሪያውም አደባባይ ሥራለትን በአደባባዩ መግቢያ ላይ መጋረጃውን ስቀል። 9 መቅቢያ ዘይቱን ውሰድና መገናኛውን ድንኳንና አውስጡ ያለውን ዕቃ ሁሉ ቅባ። እርሱንና በውስጡ ያለውን ዕቃ ሁሉ ለእኔ ቀድስልኝ፤ ከዚያም የተቀደሰ ይሆናል። 10 የሚቃጠሉ መሥዋዕቶችን መሠዊያና የመሠዊያውን ዕቃዎች ሁሉ ቅባቸው። 11 መሠዊያውን ለእኔ ቀድስልኝ፤ ከዚያም ለእኔ እጅግ የተቀደሰ ይሆንልኛል። 12 ልጆቹን ወደ መገናኛው ድንኳን መግቢያ አምጣና በውሀ እጠባቸው። 13 ለእኔ የተቀደሱ ልብሶችን ለአሮን አልብሰው፤ ካህኔ ሆኖ እንዲያገለግልም ቅባው፤ ቀድሰውም። 14 ልጆቹንም አምጣና ሸሚዞችን አልብሳቸው። 15 ካህናቴ ሆነው እንዲያገለግሉኝ፣ አባታቸውን እንደ ቀባኸው እነርሱንም ቅጣቸው። የእነርሱ መቀባት በትውልዶች ሁሉ የዘለቄታ ካህንነትን ለእነርሱ ያስገኛል።” 16 ሙሴ ያደረገው ይህ ነው፦ እግዚአብሔር ያዘዘውን ሁሉ ተከተለ። እዚህንም ሁሉ አደረገ። 17 በሁለተኛው ዓመት የመጀመሪያ ወር አንደኛ ቀን ላይ የመገናኛው ድንኳን ተተከለ። 18 ሙሴ መገናኛውን ድንኳን ተከለ፤ መቆሚያዎቹንም በስፍራቸው አስቀመጠ፤ ወጋግራዎቹን አቁሞ አግዳሚዎቹን አያያዘ፤ ምሰሶዎቹንም አቆመ። 19 በማደሪያው ላይ መሸፈኛውን ዘረጋ፤ ድንኳኑንም እግዚአብሔር አዝዞት እንደ ነበረው ከበላዩ አስቀመጠው። 20 ምስክሩን ወስዶ በታቦቱ ውስጥ አስቀመጠው። 21 ወደ መገናኛው ድንኳን አመጣው። እግዚአብሔር ሙሴን አዝዞት እንደ ነበረው፣ የምስክሩን ታቦት ለመከለል መጋረጃውን አደረገ። 22 ሰሜን ጎን ከመጋረጃው ውጭ ጠረጴዛውን በመገናኛው ድንኳን ውስጥ አስቀመጠ። 23 እግዚአብሔር አዝዞት እንደ ነበረው፣ ኅብስቱን በጠረጴዛው ላይ በሥርዐት በእግዚአብሔር ፊት አስቀመጠው። 24 መቅረዙን በመገናኛው ድንኳን ደቡብ ጎን ከጠረጴዛው ትይዩ በማደሪያው ድንኳን ውስጥ አስቀመጠው። 25 መብራቶቹን እግዚአብሔር እንዳዘዘው በእግዚአብሔር ፊት አበራቸው። 26 የተሠራውን የዕጣን መሠዊያም በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ከመጋረጃው ፊት ለፊት አደረገው። 27 ላይም እግዚአብሔር አዝዞት እንደ ነበረው ጣፋጭ መዐዛ ያለውን ዕጣን አቀጣጠለ። 28 መጋረጃውን በመገናኛው ድንኳን መግቢያ ላይ ሰቀለ። 29 የሚቃጠለውን መሥዋዕት መሠዊያም በማደሪያው፣ በመገናኛው ድንኳን መግቢያ አስቀመጠ። በመሠዊያውም ላይ የሚቃጠለውን መሥዋዕትና የእህሉን ቊርባን እግዚአብሔር እንዳዘዘው አቀረበ። 30 የመታጠቢያ ሳሕኑን በመገናኛው ድንኳንና በመሠውያው መካከል አኖረው፤ የመታጠቢያ ውሀም በውስጡ አደረገ። 31 ሙሴ፣ አሮንና ልጆቹ እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን በመታጠቢያው ውሀ ይታጠቡ ነበር፤ 32 መገናኛው ድንኳን ውስጥ በሚገቡትና መሠዊያው ወዳለበት ወደ ላይ በሚወጡበት ጊዜ ሁሉ፣ እግዚአብሔር ሙሴን ባዘዘው መሠረት ታጥበውታል። 33 ሙሴ በመገናኛው ድንኳንና በመሠዊያው ዙሪያ አደባባዩን አቆመ። መጋረጃውንም በአደባባዩ መግቢያ ዘረጋ። ሙሴ በዚህ መንገድ ሥራውን ፈጸመ። 34 ደመናውም የመገናኛውን ድንኳን ሸፈነ፤ የእግዚአብሔር ክብርም ማደሪያውን ሞላው። 35 ደመናው በላዩ ስላረፈና የእግዚአብሔር ክብርም ማደሪያውን ስለ ሞላው፣ ሙሴ መገናኛው ድንኳን ውስጥ መግባት አልቻለም ነበር። 36 ከማደሪያው ድንኳን በተነሣ ጊዜ ሁሉ፣ የእስራኤል ሰዎች ይጓዛሉ። 37 ግን ደመናው ከማደሪያው ላይ ካልተነሣ፣ ሕዝቡ አይጓዙም። ደመናው እስከሚነሣበት ቀን ድረስ ይቆያሉ። 38 በሁሉም የእስራኤል ሕዝብ ፊት በጉዟቸው ሁሉ ቀን የእግዚአብሔር ደመና፣ ማታ ደግሞ እሳቱ በማደሪያው ላይ ነበረ።

Exodus 40:1

• ከመጀመሪያው ወር በፊተኛው ቀን
እስራኤላውያን ከግብጽ የወጡበት ቀን የዓመቱ የመጀመሪያ ወር ሆኖ ተቆጠረላቸው። ይህ ወር ለእስራኤላውያን ሚያዚያ ወር ነው። የመጽሐፍ ቅዱሱ የወር አቆጣጠር የሚጀምረው በዚሁ ወር ነው።

Exodus 40:3

• በእርሱም ውስጥ የምስክሩን ታቦት ታኖራለህ
በመገናኛው ድንኳን ውስጥ የምስክሩን ወይም የቃል ኪዳኑን ታቦት ታኖራለህ

• ታቦቱንም በመጋረጃ ትጋርዳለህ
ታቦቱን ከመጋረጃው በስተጀርባ ወይም ታቦቱን በመጋረጃ ትጋርዳለህ ማለት ነው

Exodus 40:5

• የምስክር ታቦት
በሌላ ስሙ የሚታወቀው የቃል ኪዳን ታቦት ተብሎ ነው። በድንጋይ ጽላት ላይ የተጻፉት ቃላት እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ለገባው ቃል ኪዳን ምስክር እንዲሆን ነው።

Exodus 40:8

• የቅብዓት ዘይት
ይህ የወይራ ዘይት ሲሆን ማደሪያ ድንኳኑንና ሌሎችንም ዕቃዎች ለእግዚአብሔር የተለየ ለማድረግ ወይም ቅዱስ ለማድረግ የሚቀቡት ነው።

Exodus 40:12

• ወደ መገናኛው ድንኳን ደጃፍ አቅርበህ
ሙሴ አሮንና ልጆቹን ወደ መገናኛው ድንኳን እንዲያመጣቸው ትእዛዝ ተሰጠው።

• በክህነትም ያገለግለኝ ዘንድ ቀብተህ ትቀድሰዋለህ
አሮንን ለእኔ የተለየ ካህን ሆኖ እንዲያገለግለኝ አድርገው

Exodus 40:14

• ለልጅ ልጃቸው ለዘላለም ክህነት ይሆንላቸዋል
በሚመጡት ዘመናት ወይም ትውልዶች ሁሉ ካህናት ሆነው ያገለግሉኛል

Exodus 40:17

• ማደሪያው ተተከለ
ሙሴ መገናኛውን ደንኳን ወይም ማደሪያውን ድንኳን ተከለ በሚል በአድራጊ ግስ መተርጎም ይቻላል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

• በሁለተኛው ዓመት በፊተኛው ወር በመጀመሪያው ቀን
ይህ የነገናኛው ድንኳን ተከላና አሰራር የተፈጸመው ልክ እስራኤላውያን ከግብጽ በወጡ በሁለተኛው ዓመት በሁለተኛው ወር በወሩም በመጀመሪያው ቀን ላይ ነበር።

• እግዚአብሔርም እንዳዘዘው ሙሴ ማደሪያውን ተከለ
ሙሴ የድንኳኑን ተከላ የሚመራ መሪ ይሁን እንጂ ህዝቡ ያግዙትና በሥራው ይተባበሩት ነበር።

• ወጋግራዎቹን አቆመ
እግሮቹንም አኖረ ወይም ምሰሶዎቹን አቆመ የሚል ነው።

Exodus 40:21

• ታቦቱን ወደ ማደሪያው አገባ
ታቦቱን ወደ መገናኛው ድንኳን ውስጥ አስገባው ወይም አስገብቶ አስቀመጠ የሚል ይሆናል

Exodus 40:24

• ቀንዲሎቹን በእግዚአብሔር ፊት ለኰሰ
በእግዚአብሔር ፊት መብራቶቹን አበራ

Exodus 40:26

• በመጋረጃው ፊት አኖረ
ይህ መጋረጃ ቅድስተ ቅዱሳንን ከቅዱስ ስፍራው የሚለየው ነው። ስለሆነም የወርቁን መሰዋያዊ ከመጋረጃው ፊት ለፊት ሲያስቀምጥ ቅድስተ ቅዱሳኑ ከበስተሁዋላው ነው ማለት ነው።

Exodus 40:28

• በእርሱም ሙሴና አሮን ልጆቹም እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን ታጠቡ
በመታጠቢያው ሳህን ባለው ውሃ ውስጥ አሮንና ልጆቹ እጆቻቸውንና እግራቸውን ታጠበ።

Exodus 40:31

• በእርሱም ሙሴና አሮን ልጆቹም እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን ታጠቡ
በመታጠቢያው ሳህን ባለው ውሃ ውስጥ አሮንና ልጆቹ እጆቻቸውንና እግራቸውን ታጠበ።

Exodus 40:34

• የእግዚአብሔርም ክብር ማደሪያውን ሞላ
የእግዚአብሔርም መገኘት የመገናኛ በድንኳኑ ውስጥ ይታይ ነበር።

Exodus 40:36

• ደመናውም ከማደሪያው በተነሣ ጊዜ
በጉዞአቸው ሁሉ እስራኤላውያን የሰፈሩበትን ቦታ ለቀው የሚንቀሳቀሱት ደመናው ከድንኳኑ ላይ በሚነሣበት ጊዜ ብቻ ነበር።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Leviticus

Leviticus

Chapter 1

1 ያህዌ ከመገናኛው ድንኳን ሆኖ ሙሴን ጠርቶ እንዲህ አለው፣ **2** “ለእስራኤላዊያን እንዲህ ብለህ ንገራቸው፣ ‘ከእናንተ መሃል ማንም ሰው ለያህዌ መባ በሚያቀርብበት ጊዜ ከከብቶቻችሁ ወይም ከመንጋው እንስሳት መሃል አንዱን ያቅርብ። **3** መባው ከመንጋው መሃል የሚቃጠል መስዋዕት ከሆነ፣ ነውር የሌለበት ወንድ መስዋዕት ያቅርብ። መስዋዕቱ በያህዌ ፊት ተቀባይነት ያለው ይሆን ዘንድ በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ያቅርበው። **4** በሚቃጠለው መስዋዕት ራስ ላይ እጁን ይጭናል፣ ይህም በእርሱ ምነትክ ያስተሰርይለት ዘንድ ተቀባይነት ያገኛል። **5** ከዚያ በያህዌ ፊት ወይፈኑን ይረድ። በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ካህናቱ የአሮን ልጆች ደሙን ያቀርቡና በመሰዊያው ላይ ይረጩታል። **6** ከዚያም ካህኑ የመስዋዕቱን ከብት ቆዳ መግፈፍና ብልቶችንም ማውጣት ይኖርበታል። **7** ከዚያም ካህናቱ የአሮን ልጆች በመሰዊያው ላይ ዕሳት ይለኩሱና እንጨት ይጨምሩበታል። **8** ካህናቱ የአሮን ልጆች የስጋውን ብልቶች፣ የከብቱን ጭንቅላትና ስቡን በመስዋዕቱ ምድጃ ላይ በሚገኘው እንጨት ላይ በስርዓት ይደረድሩታል። **9** ነገር ግን ካህኑ የመስዋዕቱን ሆድቃና እግሮቹን በውሃ ማጠብ ይኖርበታል። በመስዋዕቱ ላይ የሚገኘውን ሁሉ የሚቃጠል መስዋዕት አብርጎ ያቃጥለዋል። ይህም ለእኔ ጣፋጭ ሽታ ይሆናል፤ ይህም ለእኔ በዕሳት የቀረበ መስዋዕት ይሆናል። **10** ለመስዋዕት የሚያቀርበው የሚቃጠል መስዋዕት ከመንጋው ከሆነ፣ ከበጎች ወይም ከፍየሎች መሃል ነውር የሌለበት ተባዕት መስዋዕት ማቅረብ አለበት። **11** በያህዌ ፊት መስዋዕቱን ከመሰዊያው በስተቀኝ በኩል ይረደው። ካህናቱ የአሮን ልጆች የመስዋዕቱን ከብት ደም በመሰዊያው ዙሪያ ሁሉ ይርጩት። **12** ከዚያ ካህኑ የመስዋዕቱን ከብት ጭንቅላቱንና ስቡን እንዲሁም ብልቶቹን ይቆራርጥ። ከዚያም በመሰዊያው በሚገኘው የሚነድ እንጨት ላይ በስርዓት ይደርድረው። **13** ነገር ግን የመስዋዕቱን ሆድቃና እግሮቹን በውሃ ይጠብ። ከዚያ ካህኑ መባውን በሙሉ ያቅርብና በመሰዊያው ላይ ያቃጥለው። ይህም የሚቃጠል መስዋዕት ነው፣ ለያህዌ ጣፋጭ መዓዛ ይሆናል፤ ለእርሱ በዕሳት የተዘጋጀ መስዋዕት ይሆናል። **14** “ካህኑ ለያህዌ የሚያቀርበው የሚቃጠል የወፎች መስዋዕት ከሆነ፣አንድ ወፍ ወይም ዕርግብ ማቅረብ አለበት። **15** ካህኑ መስዋዕቱን ወደ መሰዊያው ያመጣና አንገቱን ይቆለምመዋል፣ ከዚያም በመሰዊያው ላይ ያቃጥለዋል። ደሙም በመሰዊያው ጎን ተንጠፍጥፎ ይፈሳል። **16** የወፉን ማንቁርትና በውስጡ ያሉትን ያስወግድ፣ ከዚያም አመድ በሚደፉበት ከመሰዊያው በስተ ምስራቅ ይወርውረው። **17** ክንፎቹን ይዞ ይሰንጥቀው፣ ነገር ግን ለሁለት አይክፈለው። ከዚያ ካህኑ በዕሳቱ ላይ ባለው እንጨት መሰዊያው ላይ ያቃጥለው። ይህ የሚቃጠል መስዋዕት ይሆናል፣ እናም ለያህዌ ጣፋጭ ማዕዛ ይሆናል፣ ይህ ለእርሱ በዕሳት የተዘጋጀ መስዋዕት ይሆናል።”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 ማንኛውም ሰው ለያህዌ የእህል ቁርባን ሲያቀርብ፣ መባው መልካም ዱቄት ይሁን፣ ዘይት ያፈስበታል ደግሞም ዕጣን ያድርግበት። **2** ቁርባኑን ወደ ካህናቱ ወደ አሮን ልጆች ይወስደዋል፣ ካህኑ ከዘይቱና በላዩ ካለው ዕጣን ጋር ከመልካሙ ዱቄት እፍኝ ይወስዳል። ከዚያም ካህኑ የያህዌን በጎነት ለማሰብ መስዋዕቱን በመሰዊያው ላይ ያቃጥለዋል። ይህም ለያህዌ ጣፋጭ መዓዛ ነው፣ ለእርሱ በዕሳት የቀረበ መስዋዕት ይሆናል። **3** ከእህል መስዋዕቱ የተረፈው ሁሉ ለአሮንና ለልጆቹ ይሆናል። ይህ ሙሉ ለሙሉ ለያህዌ በዕሳት ከተዘጋጀው መስዋዕት ለእርሱ የተለየ ነው። **4** በምድጃ የተጋገረ እርሾ የሌለበት የእህል ቁርባን ስታቀርብ፣ በዘይት የተለወሰ ከመልካም ዱቄት የተዘጋጀ ለስላሳ ዳቦ መሆን አለበት፣ ወይም እርሾ የሌለበት በዘይት የተቀባ ቂጣ መሆን አለበት። **5** የእህል ቁርባንህ በመጥበሻ ላይ የተጋገረ ከሆነ፣ እርሾ ያልገባበት በዘይት የተለወሰ ከመልካም ዱቄት የተዘጋጀ ይሁን። **6** ቆራርሰህ በላዩ ዘይት ጨምርበት። ይህ የእህል ቁርባን ነው። **7** የእህል ቁርባንህ በመጥበሻ የሚዘጋጅ ከሆነ ከመለካም ዱቄትና ዘይት ይዘጋጅ። **8** ከእነዚህ ነገሮች የተዘጋጀውን የእህል ቁርባን ወደ ያህዌ ማቅረብ አለብህ፣ እናም ይህ ወደ መሰዊያው ወደሚያመጣው ወደ ካህኑ ይቅረብ። **9** ከዚያም የያህዌን በጎነት ለማሰብ ካህኑ ከእህል ቁርባኑ ጥቂት ይወስዳል፣ ቀጥሎም በመሰዊያው ላይ ያቃጥለዋል። ይህ በዕሳት የተዘጋጀ መስዋዕት ይሆናል፣ እናም ለያህዌ ጣፋጭ መዓዛ ይሆናል። **10** ከእህል ቁርባኑ የሚተርፈው ለአሮንና ለልጆቹ ይሆናል። ይህ ለያህዌ በዕሳት ከሚዘጋጀው ቁርባን ሙሉ ለሙሉ ለእርሱ የተለየ ነው። **11** ለያህዌ በምታቀርቡት የእህል ቁርባን ውስጥ እርሾ አይግባበት፣ ለያህዌ በዕሳት በምታዘጋጁት ቁርባን ውስጥ ምንም እርሾ፣ ወይም ማር አታቃጥሉ። **12** እነዚህን እንደ በኩራት ፍሬዎች ለያህዌ ታቀርባላችሁ፣ ነገር ግን በመሰዊያው ላይ መልካም መዓዛ ለመስጠት አታቀርቧቸውም። **13** የእህል ቁርባንህን ሁሉ በጨው አጣፍጠው። ከእህል ቁርባንህ በፍጽም የአምላክህ የቃል ኪዳን ጨው አይታጣ። በመስዋዕቶችህ ሁሉ ጨው ማቅረብ አለብህ። **14** ለያህዌ ከፍሬህ በኩራት የእህል ቁርባን ስታቀርብ ከእሸቱ በእሳት የተጠበሰውንና የተፈተገውን አቅርብ። **15** ከዚያ በላዩ ላይ ዘይትና እጣን ጨምርበት። ይህ የእህል ቁርባን ነው። **16** ከዚያ ካህኑ የተፈተገውን እህል እና ዘይት እንዲሁም ዕጣን የያህዌን በጎነት በአንክሮ ለማሰብ ከፊሉን ያቃጥለዋል። ይህም ለያህዌ የሚቀርብ የዕሳት መስዋዕት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 ማንኛውም ሰው ከመንጋው መሃል ወንድም ሆነ ሴት እንስሳ የህብረት መስዋዕት እንስሳ ቢያቀርብ፣በያህዌ ፊት ነውር የሌለበት እንስሳ ያቅርብ። **2** እጁን በመስዋዕቱ እንስሳ ራስ ላይ ይጭናል፣ ከዚያም በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ላይ ያርደዋል። ከዚያ ካህናቱ የአሮን ልጆች በመሰዊያው ዙሪያ ደሙን ይረጩታል። **3** የህብረት መስዋዕቱን ለያህዌ በዕሳት ያቀርባል። ሆድቃውን የሸፈነውን ወይም ከዚያ ጋር የተያያዘውን ስብ፣ **4** እና ሁለቱን ኩላሊቶች እንዲሁም በጎድኑ አጠገብ የሚገኘውን ስብ፣ እና የጉበቱን መረብ ከኩላሊቶቹ ጋር እነዚህን ሁሉ አውጥቶ ያቀርባል። **5** የአሮን ልጆች ከሚቃጠለው መስዋዕት ጋር እነዚህን በዕሳቱ ላይ በሚገኘው እንጨት በመሰዊያው ላይ ያቃጥሉታል። ይህም ለያህዌ ጣፋጭ ማዕዛ ይሆናል፣ ይህ በእሳት ለያህዌ የሚቀርብ መስዋዕት ይሆናል። **6** ለያህዌ የሚያቀርበው የህብረት መስዋዕት ወንድም ይሁን ሴት እንስሳ ነውር የሌለበት ይሁን። **7** መስዋዕቱ የበግ ጠቦት ከሆነ፣ በያህዌ ፊት ያቅርበው። **8** እጁን በመስዋዕቱ ራስ ላይ ይጫንና በመገናኛው ድንኳን ፊት ለፊት ይረደው። ከዚያ አሮን ልጆች በመሰዊያው ጎንና ጎኖች ደሙን ይረጩታል። **9** የህብረት መስዋዕቱን በእሳት እንደሚቀርብ መስዋዕት አድርጎ ለያህዌ ያቀርባል። ስቡን፣ላቱን እስከ ጀርባ አጥንቱ ድረስ፣እንዲሁም የሆድ እቃውን የሸፈነውን ስብ ሁሉ፣በሆድ እቃው ዙሪያ የሚገኘውን ስብ ሁሉ፣ **10** እና ሁለቱን ኩላሊቶችና ከእነዚህ ጋር ያለውን ስብ፣ በጎድኑ አጠገብ የሚገኘውን እና የጉበቱን መሸፈኛ ከኩላሊቶቹ ጋር እነዚህን ሁሉ አውጥቶ ያቀርባል። **11** ከዚያም ካህኑ ሁሉንም ለያህዌ በመሰዊያው ላይ በእሳት የመበል ቁርባን አድርጎ ያቃጥላል። **12** የሚያቀርበው መስዋዕት ፍየል ከሆነ፣በያህዌ ፊት ያቅርበው። **13** እጁን በፍየሉ ራስ ላይ መጫንና በመገናኛው ድንኳን ፊት ለፊት ማረድ ይኖርበታል። ከዚያ አሮን ልጆች በመሰዊያው ጎንና ጎኖች ደሙን ይረጩታል። **14** በእሳት የተዘጋጀውን መስዋእቱን ለያህዌ ያቀርባል። የሆድ እቃውን የሸፈነውንና በሆድ እቃው ዙሪያ የሚገኘውን ስብ ሁሉ አውጥቶ ያቀርባል። **15** እንዲሁም ሁለቱን ኩላሊቶችና ከእነዚህ ጋር የሚገኘውን ስብ፣ በጎድኖች እና ከኩላሊቶቹ ጋር በጉበቱን መሸፈኛው ላይ የሚገኘውን ስብ እነዚህን ሁሉ አውጥቶ ያቀርባል። **16** ካህኑ እነዚህን ሁሉ በመሰዊያው ላይ መልካም መዓዛ እንዲሆን እንደ መብል መስዋዕት አድርጎ ሁሉንም ያቃጥለዋል። ስቡ ሁሉ የያህዌ ነው። **17** “‘ይህ ለእናንተ ከትውልድ እስከ ትውልድ በምትኖሩበት ስፍራ ሁሉ ቀዋሚ መታሰቢያ ነው፣ እናንተ ስብ ወይም ደም አትብሉ።’”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 ያህዌ ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው፣ **2** “ለእስራኤል ህዝብ እንዲህ ብለህ ንገራቸው፣ ‘ማንም ሰው ያህዌ እንዳይደረግ ያዘዘውን ማናቸውንም ነገር በማድረግ ኃጢአት መስራት ሳይፈልግ ኃጢአት ቢሰራ፣ ደግሞም የተከለከለ አንዳች ነገር ቢያደርግ፣ እንዲህ ይደረግ። **3** ኃጢአት የሰራው ሊቀ ካህኑ ቢሆንና በህዝቡ ላይ በደል የሚያስከትል ኃጢአት ቢሰራ ስለ ሰራው ኃጢአት ለያህዌ ነውር የሌለበት ወይፈን የኃጢአት መስዋእት አድርጎ ያቅርብ። **4** ወይፈኑን በያህዌ ፊት ወደ መገናኛው ድንኳን ያምጣ፤ ካህኑ እጆቹን በወይፈኑ ራስ ላይ ይጫንና በያህዌ ፊት ይረደው። **5** የተቀባው ካህን ከወይፈኑ ጥቂት ደም ይውድና ወደ መገናኛው ድንኳን ያምጣው። **6** ካህኑ ጣቱን ደሙ ውስጥ እየነከረ ሰባት ጊዜ በቅድስተ ቅዱሳኑ መጋረጃ ላይ ከደሙ ጥቂት በያህዌ ፊት ይረጫል። **7** ደግሞም ካህኑ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ በያህዌ ፊት ከደሙ ጥቂት ወስዶ መልካም መዓዛ ያለውን ዕጣን በመሰዊያው ቀንዶች ይጨምራል፤ የቀረውን ወይፈኑን ደም ሁሉ በመገናኛው ድንኳን መግቢያ ላይ ለሚቃጠል መስዋዕት በመሰዊያው ስር ያፈሰዋል። **8** የሆድ ዕቃውን የሸፈነውንና ከሆድ ዕቃው ጋር የተያያዘውን የበደል መስዋዕቱን የሆነውን ወይፈን ስብ ሁሉ አውጥቶ ያቀርባል። **9** (ቁጥር 9?) **10** ለህብረት መስዋዕት ከሚቀርበው ወይፈን አውጥቶ እንዳቀረበ ሁሉ ይንንም አውጥቶ ያቀርባል። ከዚያም ካህኑ እነዚህን ክፍሎች ለሚቃጠል መስዋዕት በመሰዊያው ላይ ያቃጥላል። **11** የወይፈኑን ቆዳና ማንኛውንም ስጋ ከጭንቅላቱና ከእግሮቹ እንዲሁም ከሆድዕቃው ክፍሎችና ከፈርሱ ጋር፣ **12** የቀረውን የወይፈኑን ክፍሎች ሁሉ ከእነዚህ ክፍሎች ሁሉ ከመንደር ተሸክሞ አመዱን ወደ ደፉበት ለእኔ ወደሚነጹበት ስፍራ ወስዶ እነዚያን ክፍሎች በእንጨት ላይ ያቃጥላቸው። እነዚያን የከብቱን ክፍሎች አመዱን በደፉበት ስፍራ ያቃጥለው። **13** መላው የእስራኤል ጉባኤ ኃጢአት መስራት ሳይፈልግ ኃጢአት ቢሰራ፣ ጉባኤውም ኃጢአት መስራቱን ባያውቅና ያህዌ እንዳይደረግ ያዘዘውን ማናቸውንም ነገር ፈጽሞ ቢገኝና በደለኛ ቢሆን፣ **14** ከዚያም፣ የፈጸሙት በደል በታወቀ ጊዜ፣ ጉባኤው ለኃጢአት መስዋዕት ወይፈን ይሰዋና ወደ መገናኛው ድንኳን ፊት ያምጣው። **15** የጉባኤው ሽማግሌዎች በያህዌ ፊት በወይፈኑ ላይ እጆቸውን ይጫኑና በያህዌ ፊት ይረዱት። **16** የተቀባው ካህን ከወይፈኑ ደም ወደ መገናኛው ድንኳን ያመጣል፣ **17** ከዚያ ካህኑ ጣቱን በደሙ ውስጥ ነክሮ በመጋረጃው ላይ በያህዌ ፊት ሰባት ጊዜ ይረጨዋል። **18** በመገናኛው ድንኳን ውስጥ፣በያህዌ ፊት በመሰዊያው ቀንዶች ውስጥ ከደሙ ጥቂት ይጨምርበታል፤ ደግሞም ለሚቃጠል መስዋዕት በመገናኛው ድንኳን መግቢያ ላይ በመሰዊያው ታች ደሙን በሙሉ ያፈሳል። **19** ስቡን ሁሉ ከእንስሳው ቆርጦ ያወጣና በመሰዊያው ላይ ያቃጥላል። **20** ወይፈኑን በዚህ መልክ ለመስዋዕት ያቀርባል። ለኃጢአት መስዋዕት እንዳቀረበው ወይፈን ሁሉ፣ በዚህኛውም ወይፈን ይህንኑ ያደርጋል፣ እናም ካህኑ ለህዝቡ ማስተስረያ ያደርጋል፣ እናም ጉባኤው ይቅር ይባላል። **21** ካህኑ ወይፈኑን ከመንደር ያወጣና የመጀመሪያውን ወይፈን እንዳቃጠለ ይህኛውንም ያቃጥለዋል። ይህ ለጉባኤው የኃጢአት መስዋዕት ነው። **22** የህዝቡ መሪ ኃጢአት ለመስራት ሳያስብ ኃጢአት ቢሰራ፣ አምላኩ ያህዌ እንዳይደረግ ካዘዘው ማናቸውም ነገሮች አንዱን አድርጎ ቢገኝና በደለኛ ቢሆን፣ **23** ከዚያም የሰራው ኃጢአት ቢታወቀው፣ ነውር የሌለበት ተባዕት ፍየል ለመስዋዕት ያቀርባል። **24** እጁን በፍየሉ ራስ ላይ ይጭንና የሚቃጠል መስዋዕት በሚያርዱበት ስፍራ በያህዌ ፊት ይረደው። ይህ የኃጢአት መስዋዕት ነው። **25** ካህኑ ያኃጢአት መስዋዕቱን ደም በጣቱ ይውሰድና ለሚቃጠል መስዋዕት በመሰዊያው ቀንዶች ውስጥ ይጨምረው፣ ደግሞም ደሙን ለሚቃጠል መስዋዕት በመሰዊያው ስር ያፍስሰው። **26** ልክ እንደ ሰላም መስዋዕት ሁሉ ስቡን በሙሉ በመሰዊያው ላይ ያቃጥለው። ካህኑ የህዝቡ መሪ ለሰራው ኃጢአት ማስተስረያ ያድርግለታል፣ መሪውም ይቅር ይባላል። **27** ከተራው ህዝብ መሃል አንድ ሰው ኃጢአት ለማድረግ ሳያስብ ኃጢአት ቢሰራ፣ያህዌ እንዳይደረግ ካዘዘው ከእነዚህ ነገሮች መሃል አንዱን ቢፈጽም፣ እናም በደለኛ ሆኖ ቢገኝ፣ **28** ከዚያም የፈጸመው በደል ቢታወቀው፣ ለበደሉ መስዋዕት ነውር የሌለበት ሴት ፍየል ያቅርብ። **29** በኃጢአት መስዋዕቱ ራስ ላይ እጁን ይጭናል ከዚያም በሚቃጠል መስዋዕቱ ስፍራ የኃጢአት መስዋዕቱን ያርዳል። **30** ካህኑ በጣቱ ጥቂት ደም ወስዶ ለሚቃጠል መስዋዕት በመሰዊያው ቀንዶች ውስጥ ይጨምረዋል። የተቀረውን ደም ሁሉ በመሰዊያው ስር ያፈሰዋል። **31** መስዋዕቱ በተወሰደበት ሁኔታ ከዚህኛውም ሁሉንም ስብ ይወስዳል። ካህኑ ለያህዌ ጣፋጭ መዓዛ ለማቅረብ በመሰዊያው ላይ ያቃጥለዋል፣የሰውየውንም ኃጢአት ያስተሰርያል። **32** ለኃጢአት መስዋዕቱ የበግ ጠቦት ቢያቀርብ ነውር የሌለባት ሴት ጠቦት ያምጣ። **33** በኃጢአት መስዋዕቱ ራስ ላይ እጁን ይጫንና የሚቃጠል መስዋዕት በሚያርድበት ስፍራ ለኃጢአት መስዋዕት ያርዳል። **34** ካህኑ ከኃጢአት መስዋዕቱ ጥቂት ደም ይወስድና ለሚቃጠል መስዋዕት በመሰዊያው ቀንዶች ውስጥ ይጨምረዋል። ከዚያም በመሰዊያው ስር ደሙን ሁሉ ያፈሰዋል። **35** ከሰላም መስዋዕቱ የጠቦቱ ስብ በወጣበት ሁኔታ፣ከዚህኛውም ሁሉንም ስብ ይወስዳል፣ከዚያ ካህኑ በያህዌ መስዋዕቶች ላይ በእሳት በሚቀርበው መሰዊያ ላይ ያቃጥለዋል። ካህኑ መስዋእት አቅራቢው የሰራውን ኃጢአት ያስተሰርይለታል፣ እናም ሰውየው ይቅር ይባላል።

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 5

1 ማንም ሰው ያየውንም ሆነ የሰማውን አንዳች ነገር መምስከር ሲገባው ባለመመስከር ኃጢአት ቢሰራ፣ ይጠየቅበታል። **2** ወይም ማንም ሰው እግዚአብሔር ንጹህ አይደለም ያለውን ማናቸውንም ነገር ቢነካ፣ ይህ ንጹህ ያልሆነ ነገር የዱር እንስሳ ስጋ ወይም የሞተ የቤት እንስሳ ቢሆን፣ ወይም ማናቸውንም ያልነጻ ሰው ቢነካ፣ ደግሞም ይህን ማድረጉን ባያውቅ፣ ስለ ነገሩ ባወቀ ጊዜ ኃጢአጠኛ ይሆናል። **3** ቁጥር 3 (?) **4** ወይም ማንም ሰው በችኮላ ክፉ ወይም በጎ ለማድረግ በከንፈሮቹ ቢምል፣በችኮላ የማለው መሀላ ምንም አይነት ይሁን፣ ስለ ነገሩ ባያውቅ እንኳን፣ ነገሩን ባወቀ ጊዜ ከእነዚህ በማናቸውም ነገር ኃጢአተኛ ይሆናል። **5** አንድ ሰው ከእነዚህ ነገሮች በማንኛውም በደለኛ ሆኖ ሲገኝ፣የሰራውን ማንኛውንም ኃጢአት መናዘዝ አለበት። **6** ከዚያም ለሰራው ኃጢአት የበደል መስዋዕቱን ወደ ያህዌ ማምጣት አለበት፣ ለኃጢአት መስዋዕት ሴት ጠቦት በግ ወይም ሴት ፍየል ያቀርባል፤ ካህኑም ስለ ሰራው ኃጢአት ያስተሰርይለታል። **7** ጠቦት መግዛት ካልቻለ፣ ለኃጢአቱ የበደል መስዋዕት ለያህዌ ሁለት ዋኖሶች ወይም ሁለት እርግቦች ማምጣት ይችላል፤ አንዱ ለኃጢአት መስዋዕት እና ሌላኛው ለሚቃጠል መስዋዕት ያመጣል። **8** እነዚህን ወደ ካህኑ ያመጣል፣ እርሱም በመጀመሪያ አንዱን ለኃጢአት መስዋዕት ያቀርባል - እርሱም የመስዋዕቱን ራስ ከአንገቱ ይቆለምማል ነገር ግን ሙሉ ለሙሉ አይለያየውም። **9** ከዚያ ከኃጢአት መስዋዕቱ ጥቂት ደም ወስዶ በመሰዊያው ጎን ይረጫል፣ ከዚያ የቀረውን ደም በመሰዊያው ስር ደሙን ያንጠፈጥፈዋል። ይህ የኃጢአት መስዋዕት ነው። **10** ከዚያ ሁለተኛውን ወፍ በህጉ መሰረት የሚቃጠል መስዋዕት አድርጎ ያቀርበዋል፣ እናም ካህኑ ሰውየው ለሰራው ኃጢአት ማስተስረያ ያደርገዋል፤ ይቅር ይባላል። **11** “ነገር ግን ሁለት ዋኖሶች ወይም ሁለት እርግቦች መግዛት ሳይችል ቢቀር፣ ለሰራው ኃጢአት የኢፍ መስፈሪያ አንድ አስረኛ መልካም ዱቄት መስዋዕት ያቅርብ። ያኃጢአት መስዋዕት ስለሆነ ዘይት ወይም ዕጣን አይጨምርበት። **12** መስዋዕቱን ወደ ካህኑ ያቅርበው፣ካህኑም ለያህዌ በጎነት ምስጋና ለማቅረብ ከዱቄቱ እፍኝ ይወስዳል፣ ከዚያም በመሰዊያው ላይ ለያህዌ በመስዋዕቱ ላይ በእሳት ያቃጥለዋል። ይህ የኃጢአት መስዋዕት ነው። **13** ካህኑ ሰውየው የሰራውን ማንኛውንም ኃጢአት ያስተሰርይለታል፤ይቅር ይባላል። ከመስዋዕት የተረፈው እንደ እህል ቁርባኑ ሁሉ የካህኑ ይሆናል።’” **14** ከዚያም ያህዌ እንዲህ ሲል ሙሴን ተናገረው፣ **15** “ማንም ሰው የያህዌን ትዕዛዝ በመጣስ እርሱ ካለው ውጭ ሆኖ ኃጢአት ቢሰራ፣ ነገር ግን ይህንን ሁን ብሎ ባያደርግ ለያህዌ የበደል መስዋዕት ያቅርብ። ይህ መስዋዕት ከመንጋው ውስጥ ነውር የሌለበት ዋጋውም ለኃጢአት መስዋዕት በቤተ መቅድስ ገንዘብ በጥሬ ብር መገመት አለበት። **16** ቅዱስ ከሆነው በማጉደል ለሰራው በደል ዕዳውን በመክፈል ያህዌን ደስ ማሰኘት አለበት፣ እናም አንድ አምስተኛውን በዚህ ላይ ጨምሮ ለካህኑ ይስጥ። ከዚያ ካህኑ ከበደል መስዋዕቱ ጠቦት ጋር ያስተሰርይለታል፤ እናም ይቅር ይባላል። **17** ማንም ሰው ኃጢአት ቢሰራና ያህዌ እንዳይደረግ ያዘዘውን ማናቸውንም ነገር ቢያደርግ፣ ምንም እንኳን ነገሩን ሳያውቅ ቢያደርገውም በደለኛ ነው፤ ስለዚህም በበደሉ ጥፋተኛ ነው። **18** ከመንጋው ውስጥ ነውር የሌለበት ጠቦት ያቅርብ ለካህኑ ለበደል መስዋዕት ተመጣጣኝ ዋጋ ያምጣ። ከዚያም ካህኑ ሳያውቅ ከሰራው ኃጢአት ያስተሰርይለታል፤ ይቅር ይባላል። **19** ይህ የበደል መስዋዕት ነው፣ በያህዌ ፊት በእርግጥ ኃጢአተኛ ነው።”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 6

1 ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው፣ 2 “ ማንም ሰው ኃጢአት ቢሰራና የያህዌን ትዕዛዝ ቢተላለፍ፣ ታማኝነቱን አፍርሶ ሃሰተኛ ቢሆን፣ ወይም ጎረቤቱ በአደራ
የሰጠውን ቢክድ፣ ወይም ቢያታልል ወይም ቢሰርቀው፣ወይም ጎረቤቱን ቢበድል 3 ወይም ከጎረቤቱ የጠፋ ነገር አግኝቶ ቢዋሸ፣ እናም በሃሰት ቢምል፣ ወይም
እነዚህን በመሰሉ ሰዎች በሚበድሉባቸው ጉዳዮች ኃጢአት ቢሰራና፣ 4 በደለኛ ሆኖ ቢገኝ፣ በስርቆት የወሰደውን ይመልስ ወይም የበደለውን ይካስ፣ ወይም
ታማኝነቱን አጉድሎ የወሰደውን ጠፍቶ ያገኘውን ነገር ይመልስ። 5 ወይም በማንኛውም ጉዳይ ላይ ቢዋሸ፣ ሙሉ ለሙሉ ይመልስ፤ እንዲሁም ጥፋተኛ ሆኖ
በተገኘ ጊዜ ለባለንብረቱ አንድ አምስተኛውን ጨምሮ ይክፈል። 6 ከዚያም የበደል መስዋዕቱን ዋጋው ተመጣጣኝ የሆነ ነውር የሌለበት ጠቦት ከመንጋው
የኃጢአት መስዋእት ለያህዌ ወደ ካህኑ ያምጣ። 7 ካህኑ የኃጢአት ማስተስረያ በያህዌ ፊት ያቀርባል፣ እናም በዳዩ ለሰራው በደል ሁሉ ይቅር ይባላል።” 8
ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ 9 “አሮንን እና ልጆቹን እንዲህ ብለህ እዘዛቸው፣ ‘የሚቃጠል መስዋዕት ህግ ይህ ነው፡ የሚቃጠለው መስዋዕት በመሰዊያው
ምድጃ ላይ ሌሊቱን ሁሉ እስከ ማለዳ ይገኝ፣ ደግሞም የመሰዊያው እሳት ሳያቋርጥ ይንደድ። 10 ካህኑ የበፍታ ልብሱን ይልበስ፣ እንዲሁም የበፍታ ቀሚን
ይልበስ። እሳቱ በመሰዊያው ላይ ያለውን የሚቃጠለውን መስዋዕት ከበላ በኋላ አመዱን ይፈስ፣ ከዚያም አመዱን ከመሰዊያው ጎን ይድፋው። 11 አመዱን
ከሰፈር ውጭ ንጹህ ወደ ሆነ ስፍራ ለመውሰድ የለበሰውን አውልቆ ሌላ ልብስ ይልበስ። 12 በመሰዊው ላይ ያለው እሳት ሳያቋርጥ ይንደድ። መጥፋት
የለበትም፣ እናም ካህኑ በየማለዳው እንጨት ይጨምርበት። እንደ አስፈላጊነቱ በላዩ የሚቃጠል መስዋዕት ያድርግበታል፣ ደግሞም የሰላም መስዋዕት ስብ በላዩ
ያቃጥልበታል። 13 እሳቱ ሳያቋርጥ በመሰዊያው ላይ ይንደድ፤መጥፋት የለበትም። 14 የእህል ቁርባን ህግ ይህ ነው። የአሮን ልጆች ከያህዌ ፊት በመሰዊያው
ላይ ያቀርቡታል። 15 ካህኑ የእህል ቁርባን አድርጎ እፍኝ መልካም የእህል ዱቄትና ዘይት እንዲሁም ዕጣን ለመስዋዕት ይውሰድና የያህዌን በጎነት ምስጋና
ለማቅረብ በመሰዊያው ላይ ያቃጥለው። 16 አሮንና ልጆቹ ከመስዋዕቱ የቀረውን ይመገቡት። ይህም እርሾ ሳይገባበት በተቀደሰው ስፍራ ይብላ። በመገናኛው
ድንኳን ቅጽረ ግቢ ይመገቡት። 17 በእርሾ መጋገር የለበትም። እኔ በእሳት የተዘጋጀ ድርሻ አድርጌ ሰጥቻቸዋለሁ። የኃጢአት መስዋዕትና የበደል መስዋዕት
እጅግ የተቀደሰ ነው። 18 ለሚመጣው ተውልድ ሁሉ ለዘመናት ሁሉ ወንድ የሆነ የአሮን ትውልድ ድርሻው አድርጎ ከያህዌ ከሚቀርበው የእሳት ቁርባን ሊበላው
ይችላል። ማናቸውም እርሱን የሚነካ ቅዱስ ይሆናል።” 19 ያህዌ ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው፣ 20 “ይህ አሮንና ልጆቹ የሚያቀርቡት መስዋዕት ነው፣
እያንዳንዳቸው የአሮን ልጆች በሚቀቡበት ቀን ለያህዌ የሚያቀርቡት መስዋዕት ነው። እንደ ተለመደው የእህል ቁርባን የአፍ አንድ አስረኛ ክፍል መልካም ዱቄት፤
በጠዋት ግማሹን የተቀረውን ግማሽ ደግሞ ምሽት ያቀርቡታል። 21 በመጥበሻ ላይ በዘይት ይጋገራል። በእርጥቡ ሳለ፣ለያህዌ ጣፋጭ መዓዛ እንዲሆን
ታቀርበዋለህ። የእህል ቁርባኑን ለያህዌ ጣፋጭ መዓዛ እንዲሆን ቆራርሰህ ታቀርበዋለህ። 22 ከሊቀ ካህኑ ልጆች መሃል ተተኪ ካህን የሚሆነው ወንድ ልጅ
መስዋዕቱን ያቀርባል። ለዘለዓለም እንደታዘዘው፣ መስዋዕቱ በሙሉ ለያህዌ ይቃጠላል። 23 ካህኑ የሚያቀርበው እያንዳንዱ የእህል ቁርባን ሙሉ ለሙሉ
ይቃጠላል፤አይበላም።” 24 ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ 25 “አሮንና ወንዶች ልጆቹን እንዲህ በላቸው፣ ‘የኃጢአት መስዋዕት ህግ ይህ ነው፡ የኃጢአት
መስዋዕት የሚታረደው የሚቃጠል መስዋዕት በሚታረድበት ስፍራ ያህዌ ፊት ነው። እጅግ ቅዱስ ነው። 26 የኃጢአት መስዋዕት የሚያቀርበው ካህን
ይመገበዋል። በመገናኛው ድንኳን ቅጽረግቢ በተቀደሰው ስፍራ ይበላ። 27 የመስዋዕቱን ስጋ የሚነካ ሁሉ ይቀደሳል፣ደሙ በየትኛውም ልብስ ላይ ቢረጭ ደሙ
የነካውን የጨርቁን ስፍራ በተቀደሰ ቦታ እጠበው። 28 የተቀቀለበት የሸክላ ማሰሮ ግን ይሰበር። 29 ከካህናቱ መሀል ማናቸውም ወንድ ከዚህ መብላት ይችላል
ምክንያቱም እጅግ ቅዱስ ነው። 30 በተቀደሰው ስፍራ ወደ መገናኛው ድንኳን ለማስተስረይ ደሙ ከቀረበው የኃጢአት መስዋዕት ምንም አይበላ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 7

1 የበደል መስዋዕት ህግ ይህ ነው። እጅግ ቅዱስ ነው። 2 የበደል መስዋዕቱን በሚታረድበት ስፍራ የበደሉንም መስዋዕ ይረዱት፣ ደሙን በመሰዊያው
እያንዳንዱ ጎን ይርጩት። 3 በመስዋዕቱ ከብት ውስጥ ያለው ስብ ሁሉ ይቃጠል፤ ላቱ፣የሆድ ዕቃውን ክፍሎች የሸፈነው ስብ በመሁሉ፣ 4 በጎድኑ አጠገብ
ያለው ስብ፣ ሁለቱ ኩላሊቶችና በላያቸው ያለው ስብ፣ ጉበቱን የሸፈነው ስብ፣ ከኩላሊቶቹ ጋር - እነዚህ ሁሉ ይቅረቡ። 5 ካህኑ እነዚህን ክፍሎች በእሳት የተዘጋጀ
መስዋዕት አድርጎ በመሰዊያው ላይ ለያህዌ ያቃጥል። ይህ የበደል መስዋዕት ነው። 6 እያንዳንዱ ካህን ከዚህ መስዋዕት መብላት ይችላል። በተቀደሰ ስፍራ
ይበላ ምክንያቱም እጅግ ቅዱስ ነው። 7 የኃጢአት መስዋዕት ልክ እንደ በደል መስዋዕት ነው። የሁለቱም ህግ ተመሳሳይ ነው። እነዚህ ህጎች የማስተስረይ
አገልግሎት ለሚሰጡ ካህናት ያገለግላሉ። 8 የየትኛውንም ሰው የሚቃጠል መስዋዕት የሚያቀርብ ካህን የመስዋዕቱን ቆዳ መውሰድ ይችላል። 9 በምድጃ
የሚዘጋጅ እያንዳንዱ የእህል ቁርባን፣ እና በመጥበሻ የሚዘጋጅ እንዲህ ያለው እያንዳንዱ መስዋዕት ወይም በመጋገሪያ መጥበሻ ላይ የሚዘጋጅን መስዋዕት፣
መስዋዕቱን የሚያሳርገው ካህን ይወስደዋል። 10 ደረቅም ሆነ በዘይት የተለወሰ እያንዳንዱ የእህል ቁርባን ለአሮን ትውልዶች እኩል የእነርሱ ነው። 11 ይህ
ሰዎች ለያህዌ የሚያቀርቡት የሰላም መስዋዕት ህግ ነው። 12 ማንም ሰው ምስጋና ለማቅረብ ይህን ቢያደርግ፣ እርሾ የሌለበት መስዋዕት አድርጎ ያቅርበው፣
ነገር ግን ቂጣውን በዘይት ይለውሰው፣ ቂጣው በመልካም ዱቄት የተዘጋጀ በዘይት የተለወሰ ይሁን። 13 ደግሞም ምስጋና ለማቅረብ፣ ከሰላም መስዋዕቱ ጋር
በእርሾ የተዘጋጀ ህብስት ያቅርብ። 14 ከእነዚህ መስዋዕቶች ከእያንዳንዳቸው አንድ አይነት መስዋዕት ለያህዌ ያቅርብ። ይህ የሰላም መስዋዕቱን ደም
በመሰዊያው ላይ ለሚረጩት ካህናት ይሰጥ፤ 15 ምስጋና ለማቅረብ የሰላም መስዋዕት የሚያቀርበው ሰው መስዋዕቱ በሚቀርብበት ዕለት የመስዋዕቱን ስጋ
ይብላ። ከስጋው እስከ ማግስቱ አይደር። 16 ነገር ግን መስዋዕቱ የሚያቀርበው ለስዕለት ከሆነ፣ ወይም በበጎ ፈቃድ የሚቀርብ መስዋዕት ከሆነ ስጋው
መስዋዕቱን ባቀረበበት ዕለት ባያልቅ በማግስቱ ሊበላ ይችላል። 17 ሆኖም፣ ከመስዋዕቱ የተረው ስጋ በሶስተኛው ቀን ይቃጠል። 18 አንድ ሰው ካቀረበው የበጎ
ፈቃድ መስዋዕት አንዳች ስጋ በሶስተኛው ቀን ቢበላ ይህ ተቀባይነት የለውም፤ መስዋዕቱን ላቀረበውም ዋጋ የለውም። ደስ የማያሰኝ ነገር ይሆናል፣ ስጋውን
ለሚበላውም ሰው የበደል ዕዳ ይሆንበታል። 19 ንጹህ ያልሆነ ነገር የነካ ከዚህ ስጋ አይበላም። ስጋው መቃጠል ይኖርበታል። የተረውን ስጋ፣ ማንኛውም ንጹህ
የሆነ ሰው ሊበላው ይችላል። 20 ሆኖም፣ ለያህዌ የሚቀርበውን የሰላም መስዋዕት ስጋ የበላ ንጹህ ያልሆነ ሰው ከህዝቡ ተለይቶ ይወገድ። 21 ማንኛውም ሰው
ንጹህ ያልሆነ ነገር ቢነካ - ንጹህ ያልሆነን ሰው፣ ወይም ንጹህ ያልሆነን አውሬ፣ ወይም ንጹህ ያልሆነ እና ደስ የማያሰኝ ነገር ቢነካ፣ እና ከዚያም ለያህዌ ከቀረበው
የሰላም መስዋዕት ስጋ ቢበላ ያሰው ከህዝቡ ተለይቶ ይወገድ። 22 ቀጥሎም ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ 23 “የእስራኤልን ሰዎች እንዲህ በላቸው፣ ‘የበሬ
ወይም የበግ ወይም የፍየል ስብ አትብሉ። 24 ሳይታረድ ሞቶ የተገኘ እንስሳ ስብ፣ ወይም በዱር አውሬ የተገደለ እንስሳ ስብ ለሌላ ተግባር ሊውል ይችላል፣ ነገር
ግን የዚያን እንስሳ ስብ በፍጹም አትብሉ። 25 ሰዎች በእሳት ለያህዌ መስዋዕት አድርገው ሊያቀርቡ የሚችሉትን እንስሳ ስብ የሚላ ማንኛውም ሰው፣ ከህዝቡ
ተለይቶ ይወገድ። 26 በቤቶቻችሁ የወፍም ሆነ የእንስሳ ማናቸውም ዐይነት ደም አትብሉ። 27 ማናቸውንም ደም የበላ ማንም ሰው፣ ከህዝቡ ተለይቶ
ይጥፋ።’” 28 ደግሞም ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ 29 “የእስራኤልን ሰዎች እንዲህ በላቸው፣ ‘ለያህዌ የሰላም መስዋዕት የሚያቀርብ ከመስዋዕቱ ላይ
ወስዶ ለያህዌ ያቅርብ። 30 ለያህዌ በእሳት የሚዘጋጀውን መስዋዕት፣ በእርሱ በራሱ እጅ ያቅረበው። ስቡን ከፍርምባው ጋር ያቅርበው፣ ስለዚህ ፍርምባውን
በያህዌ ፊት ለመስዋዕት ያቅርበው። 31 ካህኑ ስቡን በመሰዊያ ላይ ያቃጥለው፣ ነገር ግን ፍርምባው የአሮንና የትውልዱ ነው። 32 የቀኙን ወርች ከሳለም
መስዋዕታችሁ የቀረበ ስጦታ አድርጋችሁ ለካህኑ ስጡት። 33 የሰላም መስዋዕቱንና ስቡን ደም የሚያቀርበው ከአሮን ትውልድ ውስጥ የሆነው ካህን
ከመስዋዕቱ ውስጥ የቀኝ ወርቹ የእርሱ ድርሻ ነው። 34 ለእኔ የተወዘወዘውንና የቀረበውን የፍርምባውንና የወርቹን መስዋዕት እኔ ስለ ወሰድኩ፣ እነዚህን
ሊቀካህን ለሆነው ለአሮንና ለዘሩ ሰጥቻለሁ፣ ይህ ሁልጊዜም በእስራኤል ህዝብ ከሚዘጋጀው የሰላም መስዋዕት ድርሻቸው ይሆናል። 35 ሙሴ በካህናት
አገልግሎት ያህዌን እንዲያገለግሉ እነርሱን ባቀረበ ቀን ይህ ለአሮንና ለዘሮቹ በእሳት ለያህዌ ከሚቀርበው መስዋዕት ድርሻቸው ነው። 36 እርሱ ካህናትን በቀባ
ቀን ያህዌ ከእስራኤል ህዝብ ድርሻቸው ሆኖ ለእነርሱ እንዲሰጥ ያዘዘው ይህ ነው። ይህ ሁልጊዜም በትውልዶች ሁሉ ድርሻቸው ይሆናል። 37 ይህ የሚቃጠል
መስዋዕት፣ የእህል ቁርባን፣ የኃጢአት መስዋዕት፣ በደል መስዋዕት፣ የክህነት ሹመት መስዋዕት እና የሰላም መስዋዕት ስርዓት ነው፤ 38 ይህ ያህዌ ለሙሴ
በሲና ተራራ ላይ የእስራኤል ህዝብ መስዋዕታቸውን በሲና ምድረበዳ የሚያቀርቡበትን ህግጋት ለሙሴ በሰጠበት ቀን የተሰጠ ስርዓት ነው።

Leviticus 7:22

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፤ ለእስራኤላዊያን እንዲህ በላቸው፤ “...ሥብ አትብሉ”::
ይህ በጥቅስ ውስጥ የተጠቀሰ ጥቅስ ነው። ቀጥተኛው ጥቅስ እንደተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊወሰድ ይችላል። አት፤ ከዚያም እግዚአብሔር ለሙሴ ተናገረ እናም ለእግዚአብሔር ሕዝብ እንዲናገር እንዲህ አለው፤ “...ሥብ አትብሉ”:: (ጥቅሶችን በጥቅስ ውስጥና ቀጥታና ተዘዋዋሪ ጥቅሶች ይመልከቱ)

ሳይሠዋ ሞቶ የተገኘውን
“የሞተ ነገር ግን መሥዋዕት ያልሆነውን”

በአውሬዎች የተገደለ ከብት ሥብ
ይህ በተሻጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “አውሬዎች የገደሉት ከብት ሥብ”:: (ተሻጋሪ ግሥና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)::

ለሌላ ተግባር ይዋል
ይህ በተሻጋሪ ግሥ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ለሌላ ተግባር ያውሉት”:: (ተሻጋሪ ግሥና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ::)

Leviticus 7:25

በእሳት የሚቀርብ መሥዋዕት
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል አት “የሚቃጠል መሥዋዕት”

ያ ሰው ከሕዝቡ ይወገድ
ያ ሰው ከሕዝቡ ዘንድ መወገድ ብጣሽ ጨርቅ ወይም የዛፍ ቅርንጫፍ እንደሚቆረጥ ከሕዝቡ ዘንድ እንደተቆረጠ ተደርጐ ተገልጾአል:: ይህ በተሻጋሪ ግሥ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: በዘሌዋዊያን 7:20 ይህን እንዴት እንደተረጐመ ይመልከቱ:: (ተሻጋሪ ግሥና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ደም አትብሉ “ደምን አትመገቡ”
በማንኛውም ቤቶቻችሁ “በየትኛውም ቤቶቻችሁ” ወይም “በማንኛውም በሚትኖሩበት ቦታ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Leviticus 7:28

ስለዚህ እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው ለእስራኤላዊያን እንዲህ በላቸው መሥዋዕት የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው
ይህ በጥቅስ ውስጥ የተጠቀሰ ጥቅስ ነው። ቀጥተኛው ጥቅስ እንደተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊወሰድ ይችላል። አት “ከዚያም እግዚአብሔር ሙሴን ተናገረ፤ እናም ለእስራኤል ሕዝብ እንዲናገር እንዲህ አለው፤ መሥዋዕት የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው፤”(ጥቅሶችን በጥቅስ ውስጥና ቀጥታና ተዘዋዋሪ ጥቅሶች ይመልከቱ)

ለእግዚአብሔር የሚያቀርበውን መሥዋዕት በራሱ እጅ ያቅርበው
በራሱ እጅ ያቅርበው የሚለው አባባል በዐረፍተ ነገሩ መጀመሪያ ሊቀመጥ ይችላል በእሳት ያቅርበው የሚለው ሀረግ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አት ፤ እርሱ ራሱ መሥዋዕት አድርጐ ለማቃጠል ያቀደውን መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ያቅርበው፤ (ተሻጋሪ ግሥና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ::)

በራሱ እጅ ያቅርበው
እዚህ “እጅ” መላውን ሰው ያመለክታል:: አት “እርሱ ራሱ ያቅርበው” (see synecdoche/ክፍልን እንደ ሙሉ እናም ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዜይቤያዊ አነጋገር ወይም ሥዕላዊ መግለጫ ይመልከቱ)::

ፍርምባ
የአንድ እንስሳ ከአንገት በታች ፊተኛ የአካል ክፍል ነው

ፍርምባውን መሥዋዕት አድርጐ በእግዚአብሔር ፊት ይወዘውዘው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ ካህኑ ይህን ለእግዚአብሔር የሚወዘወዝ መሥዋዕት አድርጐ ሊያቀርብ ይችላል:: (ተሻጋሪ ግሥና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)።

በእግዚአብሔር ፊት የሚወዘወዝ መሥዋዕት ተደርጐ ሊወዘወዝ ይችላል፤
መሥዋዕቱን ከፍ አድርጐ መያዝ ሰውየው መሥዋዕቱን ለእግዚአብሔር ማቅረቡ የሚያመለክት ምልክት ነው። (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)::

Leviticus 7:31

ወርች
ከጉልበት በላይ ያለው የእንስሳ አካል ክፍል ነው

እንደ መሥዋዕት ይቀርባል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “እና ይህ መሣዋዕት ተደርጐ ይቅረብ”፤ (ተሻጋሪ ግሥና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)።

Leviticus 7:33

እኔ ወስጃለሁ
እዚህ “እኔ” እግዚአብሔርን ያመለክታል::

ይህ የሚሰጥ ድርሻ
“ያም እንደመሥዋዕት የሚሰጥ”

Leviticus 7:35

በእሳት ለእግዚአብሔር ከቀረበው መሥዋዕት
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ ለእግዚአብሔር የሚቃጠል መሥዋዕት ነው:: (ተሻጋሪ ግሥና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)።

እስራኤላዊያን እንዲሰጧቸው እግዚአብሔር አዘዘ።
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። ያም ለእነርሱ እንዲሰጡ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ አዘዘ:: (ተሻጋሪ ግሥና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)።

ካህናቱን በቀባበት
“ሙሴ ካህናቱን በቀባበት”

ከትውልድ እስከ ትውልድ
በዘሌዋዊያን 3:17 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ።

Leviticus 7:37

አገናኝ ዐረፍተነገር
ይህ በዘሌዋዊያን 7:29 የተጀመረው ንግግር ማብቂያ ነው::

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 8

1 ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ 2 “አሮንንና ልጆቹን፣ የክህነት ልብሶቹን፣ የቅባት ዘይቱን፣የኃጢአት መስዋዕቱን ወይፈኖች፣ ሁለቱን ጠቦቶች፣ እርሾ የሌለበትን
ህብስት መሶብ ከእርሱ ጋር ውሰድ። 3 በመገናኛው ድንኳን መግቢያ ላይ ሁሉንም ጉባኤ ሰብስብ።” 4 ስለዚህም ሙሴ ያህዌ እንዳዘዘው አደረገ፣ ጉባኤውም
በመገናኛው ድንኳን መግቢያ ላይ ተሰበሰበ። 5 ከዚያም ሙሴ ለጉባኤው እንዲህ አለ፣ “ያህዌ እንዲደረግ ያዘዘው ይህ ነው።” 6 ሙሴ አሮንንና ልጆቹን
አቀረበና በውሃ አጠባቸው። 7 አሮንን እጀ ጠባብ አለበሰውና በወገቡ ዙሪያ መቀነት አስታጠቀው፣ ቀሚ አጠለቀለትና ኤፉድ ደረበለት፣ ከዚያም ኤፉዱን
በጥበብ በተጠለፈ መቀነት አስታጠቀው። 8 በቀሚሱ ላይ ደረት ኪስ አደረገለት፣ በደረት ኪሱ ውስጥ ኡሪምና ቱሚም አደረገበት። 9 ሙሴ ያህዌ እንዳዘዘው
በራሱ ላይ ጥምጥሙን ጠመጠመለት፣ በጥምጥሙ ላይ ከፊት በኩል ወርቃማ ቅብና ቅዱስ አክሊል አደረገለት። 10 ሙሴ የቅባቱን ዘይት ወሰደ፣ ማደሪያ
ድንኳኑንና በውስጡ ያለውን ሁሉ ቀባው፤ እናም ለያህዌ ቀደሳቸው። 11 በመሰዊያው ላይ ዘይቱን ሰባት ጊዜ ረጨው፣ እናም መሰዊያውንና መገልገያዎቹን ሁሉ
ቀባቸው፣ እንዲሁም የመታጠቢያ ሳህኑንና ማስቀመጫውን፣ ለያህዌ ቀደሳቸው። 12 አሮንን ያህዌ ለመለየት ከቅባቱ ዘይት ጥቂቱን በአሮን ራስ ላይ አፈሰሰው።
13 ሙሴ ያህዌ እንዳዘዘው የአሮንን ወንድ ልጆች አቅርቦ እጀጠባብ አለበሳቸው፣ በወገባቸው ዙሪያ መታጠቂያ አሰረላቸው፣ በራሳቸው ላይ በፍታ ጨርቅ
ጠቀለለላቸው። 14 ሙሴ ለኃጢአት መስዋዕት በሬ አመጣ፣ አሮንና ልጆቹ ለኃጢአት መስዋዕት ባመጡት በሬ ላይ እጆቻቸውን ጫኑ። 15 በሬውን አርዶ ደሙን
በመሰዊያው ቀንዶች ውስጥ በጣቱ ጨመረ፣ በመሰዊያው ስር ደሙን አፈሰሰ፣ ለማስተስረይ ለእግዚአብሔር ለየው። 16 በመስዋዕቱ ሆድ ዕቃ ውስጥ ያለውን
ስብ ሁሉ አወጣ፣ በጉበቱ መሸፈኛና በሁለቱ ኩላሊቶች ላይ ያለውን ስብ ወስዶ በመሰዊያው ላይ ሁሉንም አቃጠለው፤ 17 ነገር ግን በሬውን፣ ቆዳውን፣ ስጋውን
እና ፈርሱን ያህዌ እንዳዘዘው ከሰፈር አውጥቶ አቃጠለው። 18 ሙሴ ለሚቃጠል መስዋዕት ጠቦቱን አቀረበ፣ አሮንና ልጆቹ በጠቦቱ ራስ ላይ እጃቸውን ጫኑ።
19 ሙሴም ጠቦቱን አርዶ በመሰዊያው ዙሪያ ደሙን ረጨ። 20 ጠቦቱን ቆራርጦ ራሱንና ቁርጥራጩን እንዲሁም ስቡን አቃጠለ። 21 የሆድ ዕቃውን ክፍሎችና
እግሮቹን በውሃ አጠበ፣ ከዚያም ጠቦቱን በሙሉ በመሰዊያው ላይ አቃጠለ። ያህዌ ሙሴን እንዳዘዘው ይህ የሚቃጠል መስዋዕት ነው፤ ደግሞም ለያህዌ
በእሳት የተዘጋጀ ጣፋጭ መዓዛ ነው። 22 ከዚያም ሙሴ ሌላውን ጠቦት ያቀርባል፣ ይህም የክህነት ሹመት መስዋዕት ነው፣ እናም አሮንና ልጆቹ በጠቦቱ ራስ
ላይ እጃቸውን ይጭናሉ። 23 አሮን ጠቦቱን ያርዳል፣ ሙሴም ከደሙ ጥቂት ወስዶ በአሮን ቀኝ ጆሮ ጫፍ ላይ፣ በቀኝ እጁ አውራ ጣት እና በቀኝ እግሩ አውራ
ጣት ላይ ያደርጋል። 24 የአሮንን ልጆች አቅርቦ፣ በቀኝ ጆሯቸው ጫፍ ላይ፣ በቀኝ እጃቸው አውራ ጣት ላይ እና በቀኛ እግራቸው አውራ ጣት ላይ ከደሙ ጥቂት
ወስዶ ያደርጋል። ከዚያ ሙሴ የበጉን ደም በመሰዊያው ጎኖች ሁሉ ይረጫል። 25 ስቡን፣ ላቱን፣ በሆድ ዕቃ ክፍሎች ውስጥ ሁሉ የሚገኘውን ስብ፣ የጉበቱን
መሸፈኛ፣ ሁለቱን ኩላሊቶች እና በላያቸው የሚገነውን ስብ እንዲሁም ቀኝ ወርቹን ወሰደ። 26 በያህዌ ፊት ከነበረው መሶብ እርሾ የሌለበት አንድ ህብስት
ይወስዳል፣ደግሞም በዘይት ተለውሶ ከተሰራው ዳቦ አንዱን እና አንድ ስስ ቂጣ ይውሰድና በስቡና በቀኝ ወርች ላይ ያኖረዋል። 27 ሁሉንም በአሮን እጆችና
በአሮን ወንድ ልጆች እጆች ላይ ያስቀምጠዋል፣ ይህንንም ለሚወዘወዝ መስዋዕት በያህዌ ት ያቀርባሉ። 28 ከዚያም ሙሴ ከእጃቸው ይወስድና የሚቃጠል
መስዋዕት አድርጎ ያቀርበው። እነዚህ የክህነት ሹመት መስዋዕት ናቸው፤ ጣፋጭ መዓዛ ሆነው ይቀርባሉ። ይህ በእሳት ለያህዌ የሚቀርብ መስዋዕት ነው። 29
ሙሴ ፍርምባውን ወስዶ ለያህዌ መስዋዕት አድርጎ ይወዝውዘው። ያህዌ እንዳዘዘው ይህ ከጠቦቱ የክህነት ሹመት የሙሴ ድርሻ ነው። 30 ሙሴ በመሰዊያው
ላይ ካለው ከቅባት ዘይቱና ከደሙ ጥቂት ወስዶ እነዚህን በአሮን ላይ፣ በልብሶ ላይ፣ በወንድ ልጆቹ ላይ እና ከእርሱ ጋር በልጆቹ ልብሶች ላይ ይረጫል። በዚህ
መንገድ አሮንና የክህነት ልብሱን እንዲሁም ልጆቹንና ልብሳቸውን ለያህዌ ይቀድሳል። 31 ደግሞም ሙሴ ለአሮንና ለልጆቹ እንዲህ አለ፣ “በመገናኛው ድንኳን
ደጃፍ ላይ ስጋውን ቀቅሉት፣ በዚያም ስፍራ በሹመት መስጫው መሶብ ውስጥ ያለውን ህብስትም ‘አሮንና ልጆቹ ይብሉት’ ብዬ እንዳዘዝኩት ብሉት። 32
ከስጋውና ከህብስቱ የተረፈውን በሙሉ አቃጥሉት። 33 የሹመት ስርዓቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ ለሰባት ቀናት ከመገናኛው ከመገናኛው ድንኳን መግቢያ አትለፉ።
ያህዌ በሰባት ቀናት ውስጥ ይሾማችኋል። 34 በዚህ ቀን የሚሆነው እናንተን ለማስተረይ ያህዌ እንዲደረግ ያዘዘው ነው። 35 ለሰባት ቀናት ቀንም ሆነ ሌሊት
በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ላይ ትቆያላችሁ፣ ደግሞም የያህዌን ትዕዛዝ ትጠብቃላችሁ፣ ይህን ካደረጋችሁ አትሞቱም፣ ምክንያቱም የታዘዝኩት ይህንን ነው።” 36
ስለዚህም አሮንና ልጆቹ ያህዌ በሙሴ በኩል እንዲያደርጉት ያዘዛቸውን ሁሉንም ነገር አደረጉ።

Leviticus 8:1

አጠቃላይ መረጃ
በዘጸአት መጽሐፍ በሙሴ በዘገበው የእግዚአብሔር ትዕዛዝ መሠረት በምዕራፍ 8 ሙሴ አሮንና ልጆቹን ካህናት አድርጐ ይሾማቸዋል።

ልብሰ ትክህኖ
“የካህናት ልብሶች” ወይም “ካህናት የሚለብሱት ልብሶች”

Leviticus 8:4

እግዚአብሔር እንዲደረግ ያዘዘው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል፤ አት፤ እግዚአብሔር እንድናደርገው ያዘዘን (ተሻጋሪ ግሥና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)።

Leviticus 8:6

በውሃም አጠባቸው
ይህ ምልክታዊ ድርጊት ነው:: ይህም ካህናት እንዲሆኑ የሚያዘጋጃቸው የመንጻት ሥርዓት ነው፤ (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)::

ቀሚስ ፤እጀ ጠባብ፤ መቀነት፤ ኤፋድ፤ በልዩ ጥበብ የተጠለፈ መታጠቂያ‹፤
እነዚህ ልዩ አልባሳት ሕዝቡ ለካህናት እንዲያዘጋጁ እግዚአብሔር ያዘዛቸው ናቸው:: (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃዎች ይመልከቱ)::

መቀነት
በወገብ ወይም በደረት የሚታሠር ቀጭን ረጅም ልብስ ነው።

አስታጠቀው
“በላዩም አሰረው”

Leviticus 8:8

የደረት ኪሱን በላዩ አደረገለት
“ሙሴ ለአሮን የደረት ኪስ በላዩ አደረገለት”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የደረት ኪስ፤ ጥምጥም፤ ወርቃማ ቆብ፤ ቅዱስ አክሊል
እነዚህ ልዩ አልባሳት ሕዝቡ ለካህናት እንዲያዘጋጁ እግኢብሔር ያዘዛቸው ናቸው:: (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃዎች ይመልከቱ)::

ኡሪም እና ቱሚም
እነዚህ ነገሮች ምን እንደሆኑ ግልጽ አይደሉምና መገለጽ አለባቸው ካህኑ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ የሚጠቀማቸው ዕቃዎች ናቸው። (ያልታወቁትን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ጥምጥም
የሰው ራስ የሚሸፍንና በዙሪያውን የሚጠመጠም በረጅም የተቆረጠ ጨርቅ ነው።

ወርቃማ ቆብና ቅዱስ አክልል
ሁለቱ ሀረጐች አንድን ነገር የሚገልጹ ናቸው ንጹህ የወርቅ ቆብ ከጥምጥሙ ጋር ተያይዞ ይገኛል::

Leviticus 8:10

የመሠዊያው መገልገያ ዕቃዎች ሁሉ
እነዚህም ማሠሮዎች ምጣዶች ወይም ሳህኖች መቆስቆሻዎችና ሹካዎች ሁሉ፤

የመታጠቢያ ሳህን
ይህ በመሠዊያውና በታቦቱ መካከል የሚገኝ የመዳብ ሳህን ነው።

ይህ በመሠዊያውና በታቦቱ መካከል የሚገኝ የመዳብ ሳህን ነው። የሳህኑ መቀመጫ
ይህ የመታጠቢያው ሳህን የሚቀመጥበት የመዳፍ መቆሚያ ነው።

Leviticus 8:12

አፈሰሰው
ሙሴ አፈሰሰው::

መታጠቂያዎች
ይህ መታጠቂያ በብዙነት ሲገለጽ ነው። በዘሌዋዊያን 8:7 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ።

Leviticus 8:14

በወይፈኑ ራስ ላይ እጆቸውን ጫኑ
አሮንና ልጆቹን መሥዋዕት ከሚያቀርቡት እንስሳ ጋር የሚያስመስል ምልክታዊ ድርጊት ነው:: በዚህ መንገድ በእንስሳው በኩል ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ያቀርባሉ:: በዘሌዋዊያን 1:4 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ምልክታዊ ድርጊቶችን ይመልከቱ)

የመሠዊያው ቀንዶች
ይህ የመሠዊያው ማዕዘኖችን ያመለክታል:: በበሬ ቀንድ መልክ የተቀረጹ ናቸው:: በዘሌዋዊያን 4:7 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመለከቱ::

ለእግዚአብሔር ይቀድሰው
“መሠዊያውን ለእግዚአብሔር ይለየው”

እንዲህ አድርጐ ያስተሠርይለት ዘንድ
እዚህ ማስተሠርየት ማለት ወሠዊያውን ለእግዚአብሔር አገልግሎት ጥቅም ብቁ ማድረግ ነው:: አት ለኃጠአት መሥዋዕቶች መቃጠል ቦታውን ምቹ ለማድረግ ነው::

Leviticus 8:16

የውስጥ የሆድ ዕቃዎች
ሆድንና ጨጓራዎችን ነው:: በዘሌዋዊያን 1:9 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

ጉበት.... ኩላልቶች
በዘሌዋዊያን 3:4 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ።

ቆዳ
ቁርበት ወይም የቤት እንስሳት ቆዳ፤

Leviticus 8:18

እጆቸውን በበጉ ላይ ጫኑ
ይህም አሮንና ልጆቹ መስዋዕት የሚያቀርቡት እንስሳ መመሰላቸውን የሚገልጽ ምልክታዊ ድርጊት ነው። በዚህ መንገድ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርገው ያቀርባሉ:: በዘለዋዊያን 1;4 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

Leviticus 8:20

እርሱ በጉን ቆራረጠ
ሙሴ በጉን ቆራረጠ

ሽታውም ደስ ሚያሰኝ
እግዚአብሔር መሥዋዕትን በማቅረብ በቅንነት በሚያመልከው ሰው እንደሚደሰት በሚቃጠል መሥዋዕት ሽታ እንደተደሰተ ተደርጐ ተገልጾአል:: በዘሌዋዊያን 1:9 የዚህ ተመሳሳይ ሀረግ እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ::

ለእግዚአብሔር በእሳት የሚቀርብ መሥዋዕት
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት፤ እርሱ ለእግዚአብሔር ያቃጠለው መሥዋዕት: ተሻጋሪ ግሥ የያዘ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ::

Leviticus 8:22

ለቅድስና የሚሆነው አውራ በግ
“ቅድስና” የሚለው ቃል ረቂቅ ስም ነው አት “አሮንና ለጆቹን ለእግዚአብሔር አገልግሎት ለይቶ የሚያቀርብ አውራ በግ” (ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ)

እጆቻቸውን በቤጉ ራስ ላይ የጫኑ
ይህም አሮንና ልጆቹ መስዋዕት በሚያቀርቡት እንስሳ መመሰላቸውን የሚገልጽ ምልክታዊ ድርጊት ነው። በዚህ መንገድ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርገው ያቀርባሉ:: በዘሌዋዊያን 1;4 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

ሙሴ ከደሙም ጥቂት ወስዶ
ደሙ ከእንስሳው እንደወጣ ሙሴ በሳህን እንደያዘው የሚያመለክት ነው የዚህ ዐረፍት ነገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ

Leviticus 8:25

ውስጠኛ ወይም ሆድ ዕቃዎች
ሆድና ጨጓራዎችን ነው። ይህን በዘሌዋዊያን 1:9 እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ።

ጉበት...ኩላሊቶች
በዘሌዋዊያን 3:4 እንዚህን ቃላት እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ቀኝ ወርች
ከጉልበት በላይ የሚገኝ የእግር አካል ክፍል፤ በዘሌዋዊያን 7:32 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ።

በእግዚአብሔር ፊት ካለው ያለ እርሾ የተጋገረ ዳቦ ካለበት መሶብ
ይህ በመሶብ ያለው ዳቦ ያለበትን ቦታ የሚያመለክት አይደለም። ይህ የሚናገረው ሙሴ ለእግዚአብሔር ያቀረበውን ዳቦ ነው።

እነዚህን ሁሉ ለአሮንና ለልጆቹ በአጃቸው ሰጣቸው
እዚህ" እጆች" መላውን ሰው ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም (አት)፤ "ሁሉንም ለአሮንና ለልጆቹ ሰጠው" (See Synecdoche/ክፍልን እንደ ሙሉ እናም ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዜይቤያዊ አነጋገር ወይም ሥዕላዊ መግለጫ ይመልከቱ)::

የሚወዘወዝ መሥዋዕት አድርገው በእግዚአብሔር ፊት ወዘወዙት
አሮንና ልጆቹ መሥዋዕት እንዳቀረቡ የሚናገር ነው። የዚህ ዐረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉሙ ግልጽ ሊሆን ይችላል:: አት ፤ "እነርሱም በእግዚአብሔር ፊት እንደመወዘወዝ መሥዋዕት ወዘወዙት":: (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ወዘወዙት
ይህ መሥዋዕቱ ለእግዚአብሔር የሚቀርብበት ምልክታዊ ድርጊት ነው። (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

Leviticus 8:28

ሙሴ እነዚህን ተቀበለ
እዚህ "እነዚህ" ሥቡን ወርቹንና ዳቦዎች በአጠቃላይ ያመለክታል::

ከእጆቹው
እዚህ "እጆች" መላውን ሰው ያመለክታሉ:: አት፤ "ከአሮንና ልጆቹ" (See Synecdoche/ክፍልን እንደ ሙሉ እናም ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዜይቤያዊ አነጋገር ወይም ሥዕላዊ መግለጫ ይመልከቱ):: የቅድስና ወይም የመለየት መሥዋዕት ናቸው:: አሮንና ልጆቹን ለእግዚአብሔር አገልግሎት የሚለዩ መሥዋዕቶች ናቸው::

ለእግዚአብሔር በእሳት የሚቀርብ መሥዋዕት
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ ለእግዚአብሔር የሚቃጠል መሥዋዕት (ተሻጋሪ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመለከቱ)::

ሽታው ደስ የሚያሰኝ
እግዚአብሔር መሥዋዕትን በማቅረብ በቅንነት በሚያመልከው ሰው እንደሚደሰት በሚቃጠል መሥዋዕት ሽታ እንደተደሰተ ተደርጐ ተገልጾአል:: በዘሌዋዊያን 1:9 የዚህ ተመሳሳይ ሀረግ እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ፍርምባ
ከአንገት በታች ያለ የእንስሳ የፊት አካል ነው::

ክህነት
አንድን ሰው ካህን የማድረግ ሥርዓታዊ በዓል ነው::

Leviticus 8:31

የመሥዋዕት መሶብ
አሮንና ልጆቹ በሚቀደሱበት ጊዜ መሥዋዕቶችን የያዘው መሶብ ማለት ነው። አት፤ "መሶቡ"

ብዬ በታዘዝሁት መሠረት "አሮንና ልጆቹ ይብሉት" ይህም ጥቅስ በጥቅስ ውስጥ ይዞአል ቀጥታ ጥቅስ እንደተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ
ይችላል:: አት: "እንዲታደርጉ እንዳዘዝሁት" (ጥቅሶችን በጥቅሶች ውስጥ እና ቀጥታና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

የክህነት መቀበያችሁ ሰዓት እስከሚፈጸምበት
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ የክህነት ቀናት እስኪፈጽሙ፤ (ድረስ ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዙ ዐረፍተ ነገሮች ይመልከቱ) ክህነት ይህ አንድን ሰው ካህን የማድረግ ሥርዓታዊ በዓል ነው በዘሌዋዊያን 8:29 ይህን እንዴት እንደተረጐው ይመልከቱ

Leviticus 8:34

መደረግ ያለበት
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ እኛ ማድረግ ያለብን (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ለእናንተ ማስተሠሪያ
"ሥርየት" የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግሥ ሊገለጽ ይችላል:: አት፤ "ኃጢአታችሁን ለማስተሠርየት" (ረቂቅ ስሞችን ይመልከቱ)

ያዘዝሁት ይህ ነው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ "እርሱ ያዘዘኝ ይህ ነው" (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 9

1 በስምንተኛው ቀን ሙሴ አሮንንና ልጆቹን እንዲሁም የእስራኤልን ሽማግሌዎች ጠራ። **2** አሮንን እንዲህ አለው፣ “ለኃጢአት መስዋዕት ከመንጋው እምቦሳ እና ነውር የሌለበትን አውራ በግ ወስደህ በያህዌ ፊት ሰዋቸው። **3** እስራኤል ሰዎች እንዲህ ባላቸው፣ ‘ለኃጢአት መስዋዕት ወንድ ፍየል ውሰድ እንደዚሁም ነውር የሌለባቸው የአንድ አመት እምቦሳና ጠቦት ለሚቃጠል መስዋዓት ውሰድ፤ **4** እንዲሁም በያህዌ ፊት የሰላም መስዋት ለመስዋዕት አንድ በሬና አንድ አውራ በግ ውሰድ፣ በዘይት የተለወሰ የእህል ቁርባንም አቅርብ፣ ምክንያቱም ዛሬ ያህዌ ይገለጥላችኋል።’” **5** ስለዚህም ሙሴ ያዘዘውን ሁሉ ወደ መገናኛው ድንኳን አመጡ፣ የእስራኤል ጉባኤም ሁሉ ቀርበው በያህዌ ፊት ቆሙ። **6** ከዚያም ሙሴ እንዲህ አለ፣ “ያህዌ እንድታደርጉት ያዘዘው ይህንን ነው፣ስለዚህም ክብሩ ይገለጥላችኋል።” **7** ሙሴ አሮንን እንዲህ አለው፣ “ወደ መዊያው ቀርበህ የኃጢአት መስዋዕትህንና የሚቃጠል መስዋዕትህን አቅርብ፣ ደግሞም ያህዌ እንዳዘዘው ለራስህና ለህዝቡ አስተስርይ፣ ለህዝቡ ማስተስረያ ለማቅረብ መስዋዕቱን ሰዋ።” 8ስለዚህም አሮን ወደ መሰዊያው ቀርቦ ለራሱ የሆነውን መስዋዕት ለኃጢአት መስዋዕት እምቦሳውን አረደ። **8** ስለዚህም አሮን ወደ መሰዊያው ቀርቦ ለራሱ የሆነውን መስዋዕት ለኃጢአት መስዋዕት እምቦሳውን አረደ። **9** የአሮን ልጆቸ ደሙን አቀረቡለት፣ እርሱም ጣቱን ደሙ ውስጥ እየነከረ በመሰዊያው ቀንዶች ውስጥ ጨመረ፤ ከዚያም በመሰዊያው ስር ደሙን አፈሰሰ። **10** ሆኖም ያህዌ ሙሴን እንዳዘዘው ስቡን፣ ኩላሊቶቹን እና በመሰዊያው ላይ የጉበቱን ሽፋን የኃጢአት መስዋዕት አድርጎ አቃጠላቸው። **11** ስጋውንና ቆዳውን ከሰፈር ውጭ አቃጠለው። **12** አሮን የሚቃጠለውን መስዋዕት አረደ፣ ልጆቹ በመሰዊያው ዙሪያ የሚረጨውን ደም ሰጡት። **13** ከዚያ የሚቃጠለውን መስዋዕት ከከብቱ ራስ ጋር እየቆራረጡ ሰጡት፣ እርሱም በመሰዊያው ላይ አቃጠለው። **14** የሆድ ዕቃዎቹንና እግሮቹን አጥቦ በመሰዊያው ላይ በሚቃጠል መስዋዕቱ ላይ አቃጠላቸው። **15** አሮን አንድ ፍየል የህዝቡን መስዋዕት አቀረበ፣ ከዚያ ለኃጢአታቸው መስዋዕት አድርጎ አረደው፤ በመጀመሪያው ፍየል ላይ እንዳደረገው ሁሉ ለኃጢአት መስዋዕትነት ሰዋው። **16** ያህዌ እንዳዘዘው የሚቃጠል መስዋዕቱን አቅርቦ ሰዋው። **17** የእህል ቁርባኑን፣ ከእህል ቁርባኑ እፍኝ ሙሉ ወስዶ ከማለዳው የሚቃጠል መስዋዕት ጋር በመሰዊያው ላይ አቃጠለው። **18** እንዲሁም ለህዝቡ የሰላም መስዋዕት የሆነውን መስዋዕት በሬውንና አውራ በጉን አረደ። የአሮን ልጆች በመሰዊያው ዙሪያ የሚረጨውን ደሙን ሰጡት። **19** ሆኖም፣ የበሬውንና የአውራ በጉን ስብ፣ ላቱን፣ ሆድ ዕቃውን ክፍሎች የሸፈነውን ስብ፣ ኩላሊቶቹን፣ የጉበቱን ሽፋን **20** እነዚህን በፍርምባው ላይ አደረጉ፣ ከዚያም አሮን ሙሴ ባዘዘው መሰረት ስቡን በመሰዊያው ላይ አቃጠለው። **21** አሮን ፍርምባውንና የቀኝ ወርቹን መስዋዕት አድርጎ በያህዌ ፊት ይወዝስዘውና እነዚህን ለያህዌ ያቅርብ። **22** ከዚያ አሮን አጆቹን ወደ ህዝቡ አንስቶ ይባርካቸው፤ ቀጥሎ የኃጢአት መስዋዕቱን፣ የሚቃጠል መስዋዕቱንና የሰላም መስዋዕቱን አቅርቦ ይወርዳል። **23** ሙሴና አሮን ወደ መገናኛው ድንኳን ይሂዱ፣ ከዚያ ተመልሰው ይውጡና ህዝቡን ይባርኩ፣ እናም የያህዌ ክብር ለህዝቡ ሁሉ ይገለጣል። **24** ከያህዌ ዘንድ እሳት ወጥቶ የሚቃጠል መስዋዕቱንና በመሰዊያው ላይ ያለውን ስብ ሁሉ በላ። ህዝቡ ሁሉ ይህንን ባዩ ጊዜ ጮኸው በፊታቸው ተደፉ።

Leviticus 9:1

በስምንተኛውም ቀን
ስምንተኛ የሚለው ቃል ተራ ቁጥር ስምንት ነው:: (ተራ ቁጥሮችን ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ፊት
“በእግዚአብሔር መገኘት”

Leviticus 9:3

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ለአሮን መናገሩን ይቀጥላል::

እስራኤላዊያንንም እንዲህ በላቸው አንድ አውራ ፍየል ውሰዱ ... ስለራሳችሁም ቁሙ
ሙሴ ለአሮን መናገር ቀጠለ:: ይህም በጥቅስ ውስጥ የሚገኝ ጥቅስ ነው:: ቀጥተኛ ጥቅስ እንደተዘዋዋሪ ጥቅስ ለገለጽ ይችላል:: አት “አንድ አውራ ፍየል ይዘው....ለሕዝቡ ሁሉ እንዲያቀርቡ እስራኤላዊያንን ንገራቸው:: (ጥቅሶችን በጥቅሶች እና ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

የአንድ ዓመት ዕድሜ
“የአሥራ ሁለት ወር ዕድሜ”

በእግዚአብሔር ፊት ለመሥዋዕት
“ለእግዚአብሔር ለመሠዋት”

Leviticus 9:6

እናንተ እንዲታደርጉት እግዚአብሔር ያዘዛችሁ
እዚህ እናንተ የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል (See forms of you/ ሁለተኛ ሰው አገላለጽ አይነቶችን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ክብር ይገለጥላችሁ ዘንድ
እዚህ “ክብር” የእግዚአብሔርን መገለጥ ያመለክታል:: አት “እርሱ የክብሩ መገኘት ይገልጥለችሁ/ያሳያችሁ ዘንድ” (See Mentonymy/ተመሣሣይ ትርጉም የያዙ አባባሎች ዜይቤያዊ ንግግር ይመልከቱ)

ለራስህና ለሕዝቡም አስተሰርይ...ሊታስተሰርይላቸው ለሕዝቡ መሥዋዕት አቅርብ
እነዚህ ሁለት የተለያዩ መሥዋዕቶች ናቸው:: የመጀመሪያው የልቀ ካህኑን ኃጢአቶች ለማስተሠርየት ነው:: ሊቀ ካህኑ ኃጢአቶችን ሲፈጽም ሕዝቡን በደለኛ ያደርጋል:: ዘሌዋዊያን 4:3 ይመልከቱ:: ሁለተኛው ሕዝቡ የሠራቸውን ኃጢአት ለማስተሠርየት ነው::

Leviticus 9:8

የአሮን ልጆች ደሙን አቀረቡለት
ይህ ከእንስሳው እንደወጣ ደሙን የአሮን ልጆች በሳህን እንደያዙት ይገልጻል። የዐረፍተ ነገሩ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል (ግምታዊ እውቀት እና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

የመሠዊያው ቀንዶች
ይህ የመሠዊያውን ማዕዘናት ያመለክታል እንደ በሬ ቀንዶች መልክ የተቀረጹ ናቸው። በዘሌዋዊያን 4:7 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ።

በመሠዊያው ግርጌ
“ከመሠዊያው በታች”

Leviticus 9:10

እርሱ በእሳት አቃጠለው
“አሮን በእሳት አቃጠለው”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ኩላልቶች ጉበት
በዘሌዋዊያን 3:4 እነዚህን ቃላት እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ

ቁርበቱን
ይህ የቤት እንስሳ ቆዳ ወይም ሽፋን ነው:: በዘሌዋዊያን 7: 8 ይህን እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ::

Leviticus 9:12

ልጆቹ ደሙን አቀበሉት
ከእንስሳው እንደወጣ ልጆቹ ደሙን እንደያዙት የሚያመለክት ነው:: የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: (ግምታዊ እውቀት እና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

የሆድ ዕቃዎች
የውስጥ ክፍሎች ሆድንና አንጀቶችን ነው። በዘሌዋዊያ 1:9 ይህን እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ።

Leviticus 9:15

የመጀመሪያው ፍየል
“መጀመሪያ” የሚለው ቃል ለተራ ቁጥር አንድ ነው:: አት “ለራሱ መሥዋዕት የሚያቀርበው ፍየል” (ተራ ቁጥሮችን ይመልከቱ)

ጧት ጧት ከሚቀርበው መሥዋዕት ተጨማሪ
ይህ የየዕለቱን የመጀመሪያ መሥዋዕት ያመለክታል። ካህኑ ከማንኛውም መሥዋዕት በፊት በማለዳ ይህን የሚቃጠል መሥዋዕት ማቅረብ አለበት። የዚህ ዐረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። (ግምታዊ እውቀት እና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Leviticus 9:18

እርሱ ዐረደ
“አሮን ዐረደ”

የአሮን ልጆችም ደሙን አመጡለት
ይህም ደሙ በሳህኑ እንደነገበር ያመለክታል፤ የዚህ ዐረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ::

የሆድ ዕቃዎች
ይህ ሆድና አንጀቶችን ነው። ይህን በዘሌዋዊያን 1:9 እንዴት እንደረጎሙ ይመልከቱ።

ኩላሊቶችና ጉበት
በዘሌዋዊያ 3:4 እነዚህን ቃላት አንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ።

Leviticus 9:20

እነርሱ ክፍሎችን ወሰዱ
የአሮን ልጆች ክፍሎችን ወሰዱ

እነዚህን አስቀመጡ
“እነዚህ” የሚለው ቃል ቀድም ተብለው የተገለጹ ሥብንና የሆድ ዕቃዎችን ያመለክታል::

ፍርምባዎች
ከአንገት በታች የሚገኝ የእንስሳ ፊተኛ አካል ነው። በዘሌዋዊያን 7:30 ይህን እንዴት አንደተረጎሙ ይመልከቱ።

ቀኝ ወርች
ከጉልበት በላይ የሚገኝ የእግር አካል ነው። በዘሌዋዊያን 7:32 ይህን እንዴት እንደተዘጎሙ ይመልከቱ።

በእግዚአብሔር ፊት
“ለእግዚአብሔር”

Leviticus 9:22

ካቀረበ በኋላ ወረደ
“ካቀረበ በኋላ ወረደ” የሚለው ሀረግ የተጠቀመበት መሠዊያው ሕዝቡ ከቆመበት ቦታ ከፍ ብሎ ስለሚገኝ ነው::

የእግዚአብሔርም ክብር ለሕዝቡ ተገለጠ
እዚህ “ክብር” የእግዚአብሔርን መገኘት ይወክላል:: አት፤ እግዚአብሔርም የመገኘቱን ክብር ለሁሉም ሕዝብ አሳየ:: (See Metonymy/ / ተመሣሣይ ትርጉም የያዙ አባባሎች ዜይቤያዊ ንግግር ይመልከቱ)

እሳት ከእግዚአብሔር ዘንድ ወጥቶ በላው
“የሚበላውን እሳት እግዚአብሔር ላከ”

የሚቃጠለውን መሥዋዕት በላ
እሳቱ መሥዋዕቱን ሙሉ በሙሉ ያቃጠለው እሳቱ የሚቃጠለውን መሥዋዕት እንደበላ ወይም እንዳቃጠለ ተነግሮአል። (ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

በግምባራቸው ተደፉ
“በግምባራቸው ወደ መሬት አጐነበሡ” ይህ የማክበርና ክብር መስጠት ምልክት ነው:: (ምልክታዊ ድርጊቶችን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 10

1 የአሮን ልጆች ናዳብና አብዩድ እያንዳንዳቸው ጥናዎቻቸውን ወስደው እሳት አደረጉበት ከዚያም ዕጣን ጨመሩበት። ከዚያ በያህዌ ፊት እርሱ እንዲያቀርቡ
ያላዘዛቸውን ያልተፈቀደ ዕሳት አቀረቡ። 2 ስለዚህም ከያህዌ ዘንድ እሳት ወጥታ በላቻቸው፣ እነርሱም በያህዌ ፊት ሞቱ። 3 ከዚያም ሙሴ አሮንን፣ “ያህዌ ‘ወደ
እኔ በሚቀርቡ ላይ ቅድስናዬን እገልጻለሁ። በሰዎች ሁሉ ፊት እከብራለሁ’ ሲል ይህን ማለቱ ነው” አለው። አሮንም ምንም አልመለሰም። 4 ሙሴ የአሮን አጎት
የሆነውን የዑዝኤልን ልጆች ሚሳኤልንና ኤልጻፋንን ጠርቶ እንዲህ አላቸው፣ “ወደዚህ ኑና ከመቅደሱ ደጃፍ ወንድሞቻችሁን ተሸክማችሁ ከሰፈር አውጣቸው።”
5 ስለዚህም ሙሴ እንዳዘዘው ቀርበው የክህነት ቀሚሳቸውን እንደለበሱ ተሸክመው ከሰፈር አወጧቸው። 6 ከዚያም ሙሴ ለአሮንና ለልጆቹ ለአልአዛርና
ለኢታምር እንዲህ አላቸው፣ “እንዳትቀሰፉ ፀጉራችሁን አትንጩ፣ ልብሳችሁንም አትቅደዱ፣ ያህዌ በህዝቡ ላይ ሁሉ እንዳይቆጣ ተጠንቀቁ። ነገር ግን
ቤተዘመዶቻችሁና መላው የእስራኤል ቤት የያህዌ እሳት ለበላቻቸው ያልቅሱ። 7 እናንተ ግን ከመገናኛው ድንኳን ደጃፍ አትለፉ፣ የያህዌ የቅባት ዘይት በእናንተ
ላይ ነውና ትሞታላችሁ። ስለዚህም ሙሴ እንዳዘዘው አደረጉ። 8 ያህዌ አሮንን እንዲህ አለው፣ 9 “አንተ፣ ወይም ከአንተ ጋር የሚሆኑ ልጆችህ ወደ መገናኛው
ድንኳን ስትገቡ እንዳትሞቱ ወይን ጠጅ ወይም የሚያሰክር መጠጥ አትጠጡ። ይህ በትውልዳችሁ ሁሉ ቋሚ ስርዓት ይሆናል፣ 10 ቅዱስ በሆነውና ተራ
በሆነው መሃል ለመለየት፣ ንጹህ በሆነውና ንጹህ ባልሆነው መሃል ለመለየት፣ 11 ለእስራኤል ህዝብ ሁሉ በሙሴ በኩል ያህዌ ያዘዘውን ስርዓት ሁሉ
አስተምሩ።” 12 ሙሴ ለአሮንና ለተረፉት ልጆቹ ለአልአዛርና ለኢታምርን እንዲህ አላቸው፣ “በእሳት ለያህዌ ከቀረበው የእህል ቁርባን የተረፈውን መስዋዕት
ውሰድ፣ እጅግ ቅዱስ ነውና እርሾ ሳይገባበት ከመሰዊያው አጠገብ ብሉት። 13 በተቀደሰው ስፍራ ብሉት፣ ምክንያቱም በእሳት ለያህዌ ከቀረበው መስዋዕት ይህ
የአንተና የልጆችህ ድርሻ ነው፣ እንድነግርህ የታዘዝኩት ይህንን ነው። 14 ለመስዋዕት የተወዘወዘውን ፍርምባና ለያህዌ የቀረበውን ወርች እግዚአብሔር ደስ
በሚሰኝበት በተቀደሰው ስፍራ ብሉት። እነዚህን ድርዎቻችሁን አንተ፣ እንዲሁም ወንዶችና ሴቶች ልጆች ብሉት፣ እነዚህ የእስራኤል ህዝብ ከሚያቀርበው
የህብረት መስዋዕት የአንተና የልጆችህ ድርሻ ሆነው ተሰጥተዋል። 15 ለያህዌ መስዋዕት ሆኖ የቀረበውን ወርች እና መስዋዕት ሆኖ የተወዘወዘውን ፍርምባ
በእሳት ከተዘጋጀው የስብ መስዋዕቶች ጋር ከፍ አድርገው ለመወዘወዝና ለያህዌ መስዋዕት ለማድረግ በአንድነት ያቅርቧቸው። ይህም ያህዌ እንዳዘዘው
ለዘለዓለም የአንተና የልጆችህ ድርሻ ይሆናል።” 16 ከዚያ ሙሴ ለኃጢአት መስዋዕት ስለሚሆነው ፍየል ጠየቀ፣እናም በእሳት እንደተቃጠለ አወቀ። ስለዚህም
በአልአዛርና በኢታምር በተቀሩትም የአሮን ልጆች ላይ ተቆጣ፤ እንዲህም አላቸው፣ 17 “ይህ የኃጢአት መስዋዕት እጅግ የተቀደሰ ሆኖ ሳለና የጉባኤውን በደል
በእረሱ ፊት እንድታስወግዱበትና ኃጢአታቸውንም እንድታስተረዩላቸው ሰጥቷችሁ ሳለ ስለምን በቤተ አምልኮው ስፍራ አልበላችሁትም? 18 ተመልከቱ፣ ደሙ
ወደ ቤተመቅደስ ውስጥ አልመጣም፤ እንዳዘዝኳችሁ በቤተ መቅደሱ አካባቢ ለትበሉት ይገባ ነበር።” 19 ከዚያም አሮን ለሙሴ እንደህ ሲል መለሰለት፣
“እነሆ፣ ዛሬ የኃጢአት መስዋዕታቸውን እና የሚቃጠል መስዋዕታቸውን በያህዌ ፊት አቀርቡ፣ እናም ይህ ነገር በእኔ ላይ ደርሷል። ዛሬ እኔ የኃጢአት መስዋዕቱን
ብበላ ኖሮ ይህ በያህዌ ፊት ደስ ያሰኝ ነበርን?” 20 ሙሴ ያንን ሲሰማ መልሱ አረካው።

Leviticus 10:1

ናዳብና አብዩድ
እንዚህ የአሮን ልጆች ስሞች ናቸው

ጥና
ካህናት ፍምን ወይም እጣንን የሚሸከሙበት ጐድጓዳ የብረት መያዣ ነው

እሳት ጨመሩ
“የሚያቃጥል ፍም ጨመሩ”

እርሱ ያለዘዛቸውን ያልተፈቀደውን እሳት በእግዚአብሔር ፊት አቀረቡ
“እርሱ እንዲያቀርቡ ባዘዛቸው መንገድ ስላልሆነ እግዚአብሔር መሥዋዕታቸውን አላጸናም/አለፈቀደም”

በእግዚአብሔር ፊት ያልተፈቀደ እሳት
“ያልተፈቀደ እሳት ለእግዝአብሔር”

ከዚህም የተነሣ እሳት ከእግዚአብሔር ዘንድ ወጥቶ
“ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔር እሳት ላከ”

ከእግዚአብሔር ፊት ወጥቶ
“ከእግዚአብሔር ወጥቶ”

በላቸው
ሙሉ በሙሉ እሳቱ ሰዎችን ያቃጠለው እሳቱ እንደበላቸው ወይም ሙሉ በሙሉ እንዳቃጠላቸው ተገልጾአል። (ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

በእግዚአብሔርም ፊት ሞቱ
“በእግዚአብሔር መገኘት ሞቱ”

Leviticus 10:3

እግዚአብሔርም ሲናገር ያለው ይህ ነው ፤ቅድስናዬን በሕዝቡም ሁሉ ፊት እገልጣለሁ።
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ ይዞአል ቀጥተኛ ጥቅስ እንደተዘዋዋሪ ጥቅስ ለገለጽ ይችላል። አት፤ “ወደ እኔ በሚቀርቡት …ቅድስናዬን አገልጣለሁ እናም በሕዝቡ.. እከብራለሁ ባለ ጊዜ እግዚአብሔር ይናገር የነበረው ይህ ነው” (ጥቅሶችን በጥቅሶች ውስጥ እናም ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

ወደ እኔ በሚቀርቡት መካከል ቅድስናዬን እገልጣለሁ
ወደ እኔ በሚቀርቡት የሚለው ሀረግ እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ ካህናትን ያመለክታል። ወደ እኔ ለሚቀርቡ ቅዱስ እንደሆንሁ እገልጣለሁ ወይም ሊያገለግሉት ወደ እኔ የሚቀርቡ ቅዱስ እንደሆንሁ ይወቁኝ

በሕዝቡም ሁሉ ፊት እከብራለሁ
እግዚአብሔር ከተናገረው ሁለተኛው ክፍል እግዚአብሔርን ለማገልገል ስለሚቀርቡ ካህናት ይመለከታል፡ ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “በሕዝብ ሁሉ ፊት ሊያከብሩኝ ይገባል” ወይም “በሕዝብ ሁሉ ፊት ከፍ ሊያደርጉኝ የገባል”።

ሚሳኤል… ኤልጻፋ… ዑዝኤል
እንዚህ የሰው ስሞች ናቸው:: (የሰው ስሞች ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ወንድሞቻችሁ
እነዚህ በሥጋ ወንድሞች ናቸው ማለት አይደለም። እዚህ “ወንድሞች” ዘመዳሞች; የአጐት ወይም የአክስት ልጆች

Leviticus 10:5

እነርሱም መጥተው
ሚሳኤልና ኤልጻፋን መጥተው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሟቾቹ የክህነት ልብሳቸውን እንደለበሱ ተሸክመው
የናዳብና አብዩድ ሙት አካል በክህነት ልብሶቻቸው እንዳለ ተሸክመው

አልአዛር...ኢታምር
እነዚህ የአሮን ልጆች ስሞች ናቸው። (ስሞችን ስለመተርጎም ይመልከቱ)

ጸጉሮቻችሁን አትንጩ ልብሶቻችሁን አትቅደዱ
አሮንና ልጆቹ ምንም ዓይነት ውጫዊ ሃዘን ወይም ትካዜ እንዳያሳዩ እግዚአብሔር ይናገራቸዋል። (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

ስለዚህ እንዳትሞቱ
ከዚህ የተነሣ እንዳትሞቱ

በእስራኤል ጉባኤ ላይ ቁጣ እንዳይመጣ
እዚህ “ጉባኤ” መላውን የእስራኤል ጉባዔ እንጂ የቡድን መሪዎችን አይደለም (See Synecdoche/ክፍልን እንደ ሙሉ እናም ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዜይቤያዊ አነጋገር ወይም ሥዕላዊ መግለጫ ይመልከቱ)::

መላው ቤተ እስራኤል
እዚህ “ቤት” ሰዎችን ይወክላል:: አት : “መላው የእስራኤል ሕዝብ”

እግዚአብሔር በእሳት ስላቃጠላቸው ሰዎች
“እግዚአብሔር በእሳት ስላጠፋቸው ሰዎች”

Leviticus 10:8

ይህም
እዚህ “ይህ” ወደ ኋላ መለስ ብሎ ካህናት ወደ መገናኛው ድንኳን በሚገቡበት ጊዜ ወይን ወይም ጠንካራ መጠጥ እንዳይጠጡ የታዘዙትን የሚያመለክት ነው::

በልጅ ልጆቻችሁ ዘንድ የሚጠበቅ ዘላለማዊ ሥርዓት ነው:: በዘሌዋዊያን 3:17 እነዚህን ቃላት እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ::ለመለየት
በዚህ አድስ ዐረፍተ ነገር መጀመር ይቻላል:: “መለየት ይችሉ ዘንድ ይህን ያድርጉ”

በተቀደሰውና ባልተቀደሰው መካከል
“የተቀደሰ” እና “ያልተቀደሰ” ቅጽል ሥሞች እንደ ቅጽል ግሥ ለገለጹ ይችላሉ:: አት: “ቅዱስ በሆነውና ቅዱስ ባልሆነው ወይም ለእግዚአብሔር በተለየውና በተራው” (ቅጽል ሥሞችን ይመልከቱ)

በርኩሱና ንጹሑ መካከል
“ርኩሱ” እና “ንጹሑ” ቅጽል ሥሞች እንደ ቅጽል ግሥ ለገለጹ ይችላሉ:: አት: “ርኩሰ በሆነውና ንጹህ በሆነው በካከል ወይም እግዚአብሔር በማይቀበለውና በሚቀበው መካከል” (ቅጽል ሥሞችን ይመልከቱ)

ርኩስ
እግዚአብሔር እንዲነካ ያልፈለገው ሰው ወይም አንድ ነገር በአካል ርኩስ ተደርጐ ተገልጾአል:: (ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ንጹህ
እግዚአብሔር እንዲነካ የፈለገው ሰው ወይም አንድ ነገር በአካል ንጹህ ተደርጐ ተገልጾአል:: (ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Leviticus 10:12

በእሳት ለእግዚአብሔር የሚቀርበው ቁርባን
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ለእግዚአብሔር የሚቀርብ የሚቃጠል መሥዋዕት”(ተሻጋሪ ግሥና የማይሻገር ግሥ የያዙ ዐረፍተ ነገሮች ይመልከቱ)

ይህ እጅግ ቅዱስ ስለሆነ
የእህል ቁርባኑ እጅግ ቅዱስ ስለሆነ ይህን እንዲትናገር ያዘዝሁት ነው:: ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት: “ይህም እንዲናገር እግዚአብሔር ያዘዘኝ ነው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዙ ዐረፍተ ነገሮችን ይመልከቱ)

Leviticus 10:14

የተወዘወዘውን ፍርምባና ለእግዚአብሔር የቀረበውን ወርች
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት: “ለእግዚአብሔር የተወዘወዘውና የቀረበው ፍርምባና ወርች” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዙ ዐረፍተ ነገሮችን ይመልከቱ)

ፍርምባ
ከአንገት በታች የሚገኝ የእንስሳ ፊት አካል ክፍል ነው።

ወርች
ከጉልበት በላይ የሚገኝ ላይኛ የእግር አካል ክፍል ነው።

ንጹህ በሆነ ሥፍራ
ለእግዚአብሔር ዓላማዎች ጥቅም ተገቢ ሥፍራ በአካል ንጹህ ተብሎ ተገልጾአል። (ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

እነዚህ ለእናንተ የተመደቡ ድርሻ ናቸው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት: “እግዚአብሔር እነዚህን ለእናንተ ድርሻ አድርጐ ስጥቶአችኋል” (ተሻጋሪ ግሥና የማይሻገር ግሥ የያዙ ዐረፍተ ነገሮች ይመልከቱ)

አንተ እና ወንዶችና ሴቶች ልጆችህ
እዚህ “አንተ” አሮንን ያመለክታል:: (ሁለተኛ ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

ለአንተና ለልጆችህ ለዘላለም የተመደበ ድርሻ ይሆናል
ድርሻው ለአሮንና ለልጆቹ ተደርጐ እንደተገለጸ ይተርጉሙ። አት: “ይህ ድርሻ ሁልጊዜ ለአንተና ለልጆችህ ይሆናል” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Leviticus 10:16

ተቃጥሎአል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት: “ካህናት ሁሉንም አቃጥለዋል”

አልዓዛርና ኢታምር
እነዚህን ስሞች በዘሌዋዊያን 10:6 እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ።

ለምን... በፊቱ አልበላችሁም?
ሙሴም በጥያቄ መልክ አልዓዛርንና ኢታምርን ይቆጣቸዋል። ይህ ጥያቄያዊ አገላለጽ በስድ ዐረፍተ ነገር ሊቀመጥ ይችላል። አት: በፊቱ መብላት የገባችሁ ነበር።

እጅግ የተቀደሰ ነው
የኃጢአት መስዋዕት እጅግ የተቀደሰ ነው።

የሕዝቡን ኃጢአት እንዲታስወግዱበት
እግዚአብሔር የእስራኤልን ኃጢአት ይቅር ማለቱ ኃጢአት እግዚአብሔር ከሕዝቡ ላይ የሚያስወግደው ነገር እንደሆነ ተገልጾአል። (ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

በፊቱ
በመገኘቱ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ደሙ አልገባም
ይህ በተሻጋሪ ግሥ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፡ “እነርሱ ደሙን አላመጡም” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዙ ዐረፍተ ነገሮችን ይመልከቱ)

Leviticus 10:19

እንዲህ ያለ ነገር ደረሰብኝ
አሮን ስለሞቱ ሁለት ልጆቹ ያውሳል

ይህ በእግዚአብሔር ፊት ደስ የሚያሰኝ ኖሮአልን?
እነዚህ መሥዋዕቶች በእግዚአብሔር ፊት በፍስሃና በደስታ መበላት አለባቸው። በልጆቹ ሞት ምክንያት ሀዘንተኛ ስለሆነ መሥዋዕቶችን ቢበላ እግዚአብሔር ደስተኛ እንደማይሆን ለማተኮር አሮን በጥያቄ መልክ ያስቀምጣል። ይህም ጥያቄ በስድ ዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጐም ይችላል። “በእርግጥ እግዚአብሔር አልተደሰተም ኖሮአል።” (See Rehtorical Question/ንግግራዊ ጥያቄ ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 11

1 ያህዌ ሙሴንና አሮንን እንዲህ አላቸው፣ 2 “ለእስራኤል ሰዎች እንዲህ በሏቸው፣ ‘በምድር ላይ ከሚገኙ እንስሳት ሁሉ የምትመገቧቸው ህያዋን ነገሮች እነዚህ
ናቸው። 3 የተሰነጠቀ ሰኮና ያላቸውንና የሚያመሰኩትን ትመገባላችሁ። 4 ሆኖም፣ የሚያመሰኩ ቢሆኑም ነገር ግን የተሰነጠቀ ሰኮና የሌላቸውን እንደ ግመል
ያሉትን አትብሉ፤ምክንያቱም ያመሰኳሉ ነገር ግን ሰኮናው አልተሰነጠቀም። ስለዚህ ግመል ለእናንተ ንጹህ አይደለም። 5 እንዲሁም ሽኮኮ ያመሰኳል ነገር ግን
የተሰነጠቀ ሰኮና የለውም፣ ይህም ለእናንተ ንጹህ አይደለም። 6 ጥንቸል ቢያመሰኳም የተሰነጠቀ ሰኮና ስለሌለው ለእናንተ ንጹህ አይደለም። 7 አሳማ
የተሰነጠቀ ሰኮና ቢኖረውም፣ አያመሰኳም ስለዚህ ለእናንተ ንጹህ አይደለም። 8 የእነዚህን ስጋ ፈጽሞ አትብሉ፣ ጥንባቸውንም አትንኩ። እነርሱ ለእናንተ ንጹህ
አይደሉም። 9 በውቂያኖስም ሆነ በባህር በውሃ ውስጥ ከሚኖሩ እንስሳት የምትበሏቸው ክንፍና ቅርፊት ያላቸው ናቸው። 10 ነገር ግን በውቂያኖስ ወይም
በባህር የሚኖሩ ክንፍና ቅርፊት የሌላቸው ህያዋን ፍጥረታት ሁሉ፣በውሃ ውስጥ የሚንቀሳቀሱትን ጨምሮ እንዲሁም በውሃ ውስጥ ያሉት እንዲህ ያሉ ህያዋን
ፍጥረታት በሙሉ በእናንተ ዘንድ ጸያፍ ናቸው። 11 ጸያፍ ሊሆኑ ስለሚገባቸውም፣ ስጋቸውን ልትበሉ አይገባም፣ እንደዚሁም በድናቸውም ጸያፍ ነው። 12 በውሃ
ውስጥ የሚኖሩ ቅርፊት የሌላቸው እንስሳት ሁሉ፣በእናንተ ዘንድ ጸያፍ ናቸው። 13 ልትጸየፏቸው የሚገቡና የማትበሏቸው ወፎች እነዚህ ናቸው፤ ንስር፣ ጥንብ
አንሳ፣ 14 ጭላት፣ ማንኛውም አይነት የሎስ 15 ማንኛውም አይነት ቁራ፣ 16 የተለያ አይነት ጉጉት፣ የባህር ወፍ እና ማንኛውም ዐይነት ጭልፊት። 17 ትናንሽና
ትላልቅ ጉጉቶችን ትጸየፋላችሁ፣ርኩምና ጋጋኖ፣ 18 የተለያዩ ጉጉቶች፣ ይብራ፣ 19 ሽመላ፣ ማናቸውም ዐይነት የውሃ ወፍ፣ ሳቢሳ፣ ጅንጁላቲ ወፍና የለሊት ወፍ።
20 በእግራቸው የሚራዱ ክንፍ ያላቸው በራሪ ነፍሳት በሙሉ በእናንተ ዘንድ አስጸያፊ ናቸው። 21 ሆኖም ግን ከእግራቸው በላይ በምድር ላይ የሚፈናጠሩበት
አንጓ ያላቸውን ማናቸውንም የሚበሩ ነፍሳት መብላት ትችላላችሁ። 22 እንደዚሁም ደግሞ ማናቸውንም ዐይነት አንበጣ፣ ትልቅ የአንበጣ ዝርያ፣ ፌንጣና ዝንቢት
መብላት ትችላላችሁ። 23 ነገር ግን አራት እግር ያላቸው የሚበሩ ነፍሳት ሁሉ በእናንተ ዘንድ የተጠሉ ናቸው። 24 ከእነዚህ እንስሳት ውስጥ የአንዱን በድን
ብትነኩ እስከ ማታ ድረስ የረደሳችሁ ናችሁ። 25 ከእነዚህ የአንዱን በድን ያነሳ ማንም ሰው ልብሱን ይጠብ፣ እስከ ማታ ድረስ እርኩስ ነው። 26 ማንኛውም
ሙሉ ለሙሉ ያልተሰነጠቀ ሰኮና ያለው እንስሳ ወይም የማያመሰኳ እንስሳ በእናንተ ዘንድ ጸያፍ ነው። እነዚህን የነካ ሁሉ ይረክሳል። 27 በአራት እግሩ
ከሚራመድ እንስሳ መሃል በመዳፋቸው የሚሄዱ ሁሉ በእናንተ ዘንድ እርሱስ ናቸው። እንደነዚህ ያሉትን በድናቸውን የነካ እስከ ማታ እርኩስ ነው። 28 እንደነዚህ
ያሉትን በድናቸውን ያነሳ ልብሱን ይጠብ እስከ ማታ ድረስ እርኩስ ይሆናል። እነዚህ እንስሳት በእናንተ ዘንድ እርኩስ ናቸው። 29 በምድር ላይ ከሚሳቡ እንስሳት
መሃል፣ በእናንተ ዘንድ እርኩስ የሆኑት እነዚህ ናቸው፡ አቄስጣ፣ አይጥ፣ ማናቸውም አይነት እንሽላሊት 30 ትንሽ የቤት ላይ እንሽላሊት እና እስስት 31 ከሚሳቡ
እንስሳት በእናንተ ዘንድ እርኩስ የሆኑት እነዚህ ናቸው። ከእነዚህ የሞቱትን አንዳቸውን የነካ ሰው እስከ ምሽት እርሱስ ይሆናል። 32 ከእነዚህ መሃል አንዱ ሞቶ
በማናቸውም ከእንጨት፣ ከጨርቅ፣ ከቆዳ ወይም ከበርኖስ በተሰራ ነገር ላይ ቢወድቀቅ ያዕቃ እርኩስ ይሆናል። ዕቃው ምንም ይሁን ለምንም አይነት ተግባር
ይዋል ውሃ ውስጥ ይነከር እስከ ምሽት ድረስ እርኩስ ነው። ከዚያ ንጹህ ይሆናል። 33 ንጹህ ያልሆነ እንስሳ የገባበት ወይም የነካው የሸክላ ማሰሮ እንዲሁም
በውስጡ ያለው ነገር ሁሉ እርኩስ ይሆናል፤ ያንን ማሰሮ ሰባብረው። 34 ማናቸውም ለመበላት የተፈቀደ ምግብ፣ ንጹህ ካልሆነ ማሰሮ ውሃ ቢገባበት እርኩስ
ይሆኖል። እንዲህ ካለው ማሰሮ ማንኛውም ነገር ቢጠጣ ያረክሳል። 35 እርኩስ ከሆነ እንስሳ በድን ማናቸውም አካሉ የወደቀበት ምድጃም ሆነ የማብሰያ ሸክላ
እንዲሁም ማንኛውም ነገር ይረክሳል። ይሰባበር። እርኩስ ነው፣ በእናንተም ዘንድ የተጠላ ይሁን። 36 የመጠጥ ውሃ የሚገኝበት ምንጭ ወይም የውሃ ጉድጓድ
እንዲህ ያሉ እንስሳት ቢገኙበትም ንጹህ ነው። ነገር ግን ማንም ሰው በውሃው ውስጥ የሚገኘውን እርኩስ የሆነውን በድን ቢነካ እርኩስ ይሆናል። 37 ንጹህ
ያልሆነ እንስሳ በድን በዘር ላይ ቢወድቅ፣ እነዚያ ዘሮች የረከሱ ይሆናሉ። 38 ነገር ግን በዘሮቹ ላይ ውሃ ቢፈስ ንጹህ ያልሆነው እንስሳ በድን ማንኛውም አካል
የተክል ዘሩ ላይ ቢወድቅ ዘሩ በእናንተ ዘንድ እርኩስ ይሆናል። 39 ለመበላት ከተፈቀደው እንስሳ አንዱ ቢሞት፣ በድኑን የነካው ሰው እስከ ምሽት እርኩስ
ይሆናል። 40 ደግሞም እንዲህ ያለውን በድን ያነሳ ሰው ልብሱን ያጥባል፣ እስከ ምሽት ድረስ እርኩስ ይሆናል። 41 ማንኛውም በምድር ላይ የሚሳብ እንስሳ
ጸያፍ ነው፤ አይበላም። 42 በሆዱ የሚሳብ እንስሳ ሁሉ፣ እና በአራቱም እግሮቹ የሚራመድ፣ወይም ማንኛውም ብዙ እግሮች ያሉት - በምድር የሚሳብ እንስሳን
ሁሉ፣ አትብሉ፤ እነዚህ ጸያፍ ናቸው። 43 በደረቱ በሚሳብ ማናቸውም ህያው ፍጥረት ራሳችሁን አታርክሱ፤ እነዚህ እናንተን ያረክሳሉ። 44 እኔ አምላካችሁ ያህዌ
ነኝ። በምድር በሚንቀሳቀስ በማናቸውም አይነት እንስሳ ራሳችሁን አታርክሱ። 45 እኔ አምላካችሁ እሆን ዘንድ ከግብጽ ምድር ያወጣኋችሁ ያህዌ ነኝ። ስለዚህ
እኔ ቅዱስ እንደሆንኩ እናንተም ቅዱስ መሆን አለባችሁ። 46 ስለ እንስሳት፣ ስለ ወፎች፣ በውሃ ውስጥ ስለሚንቀሳቀሱ ማናቸውም ህያዋን ፍጥረታት፣
እንዲሁም በምድር ላይ ስለሚሳቡ ፍጥረታት ህጉ ይህ ነው፤ 47 ንጹህ ባልሆኑና ንጹህ በሆኑት መካከል ልዩነት ለመፍጠር፣ እና በሚበሉ ህያዋን ነገሮችና
በማይበሉ ህያዋን ነገሮች መሃል ለመለየት ህጉ ይህ ነው።’”

Leviticus 11:1

እንስሳት ሁሉ መካከል
በየብስ ሚኖሩ እንስሳት ሁሉ

Leviticus 11:3

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቡ እንዲበሏቸው የተፈቀደላቸውንና ያልተፈቀደላቸውን እግዚአብሔር ለሙሴና ለአሮን ይናገራል::

ሰኮናው የተሰነጠቀው
ይህም ሰኮናው አንድ ከመሆን ይልቅ ለሁለት የተሰነጠቀውን ማለት ነው::

Leviticus 11:5

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቡ እንዲበሏቸው የተፈቀደላቸውንና ያልተፈቀደላቸውን እግዚአብሔር ለሙሴና ለአሮን መናገርን ቀጠለ::

ሽኮኮ
በድንጋማ ቦታዎች የሚኖር ትንሽ እንስሳ ነው። (ያልታወቁትን ስለመተርጎም ይመልከቱ)

በእናንተ ዘንድ ርኩስ ይሁን
እነዚህን እንስሳት ሕዝቡ እንዲበላ ተገቢ እንዳይደለ እግዚአብሔር ስለተናገረ በአካል ርኩስ ተብለው ተገልጸዋል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጥንቸል
ሁልጊዜ በጉዳጓድ በመሬት ውስጥ የሚኖር ጆሮው ረጅም የሆነ እንስሳ ነው።

ጥምባቸውንም አትንኩ
ሙት አካላቸውን/በድናቸውንም አትንኩ

Leviticus 11:9

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቡ እንዲበሏቸው የተፈቀደላቸውንና ያልተፈቀደላቸውን እግዚአብሔር ለሙሴና ለአሮን መናገርን ቀጠለ::

ክንፎች
በዉሃ ውስጥ እንዲንሣፈፍ የሚያደርጉ የዓሣ ስስና ጠፍጣፋ የአካል ክፍሎች ናቸው።

ቅርፊቶች
የዓሣን አካል ቆዳ የሚሸፍኑ ትናንሽ ቅርፊቶች ናቸው።

በባሕሮችና በወንዞች ውሃ ውስጥ የሚኖሩ ክንፍና ቅርፊት የሌላቸው ሕይወት ያላቸው ፍጡሮች
በባሕሮችና በወንዞች ውሃ ውስጥ ከሚኖሩት ፍጡሮች ክንፍና ቅርፊት የሌላቸው።

በእናንተ ዘንድ እስጸያፊ ይሁኑ
እግዚአብሔር ሕዝቡ እነዚህን ፍጡሮች መብት እንዳይቀበሉና እንዲንቁ ያዝዛቸዋል። ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል። አት፡ “እነዚህን ተጸየፉአቸው ወይም ሙሉ በሙሉ አትቀበሉአቸው:: (ተሻጋሪ ግሥና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 11:11

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቡ እንዲበሏቸው የተፈቀደላቸውንና ያልተፈቀደላቸውን እግዚአብሔር ለሙሴና ለአሮን መናገርን ቀጠለ::

በእናንተ ዘንድ አስጸያፊ ስለሆኑ
አስጸያፊ የተናቀ ወይም ያልተቀበለ ነገር ነው። ይህም ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፡ “በእናንተ ዘንድ ስለሚትጸየፉ” ወይም “እናንተ ሙሉ በሙሉ ስላተቀበላችሁ”:: (ተሻጋሪ ግሥና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

በድናቸውንም ትጸየፋላችሁ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፡ “የእነርሱን ሙት አካል ትጸየፋላችሁ” ወይም “የእነርሱን ሙት አካል አትንኩ” (ተሻጋሪ ግሥና የማይሻገር ግሥ ይመልከቱ)

በውሃ ውስጥ ማንኛውም ክንፍና ቅርፊት የሌለው
ክንፍና ቅርፊት የሌለው ማንኛውም በውሃ ውስጥ የሚኖር

በእናንተ ዘንድ አስጸያፊ ይሁን
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት: “ተጸየፉት” ወይም “ሙሉ በሙሉ አትቀበሉት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 11:13

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቡ እንዲበሏቸው የተፈቀደላቸውንና ያልተፈቀደላቸውን እግዚአብሔር ለሙሴና ለአሮን መናገርን ቀጠለ::

ንሥር; ጥንብ አንሣ; ግልገል አንሣ; ጭልፊት ቁራ ሰጐን ጠለቋ በቋል
እነዚህ አእፋት በሌሊት የሚንቀሳቀሱ ወይም የሞቱ እንስሳትንና ጥንብ የሚመገቡ ናቸው። (ያልታወቁትን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Leviticus 11:17

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቡ እንዲበሏቸው የተፈቀደላቸውንና ያልተፈቀደላቸውን እግዚአብሔር ለሙሴና ለአሮን መናገርን ቀጠለ::

ጉጉት ርኩም ጋጋኖ የውሃ ዶሮ ይብራ ስደተኛ አሞራ ሽመላ
እነዚህ አእዋፋት በተለይ በሌሊት የማይተኙና ጥንብና ትላትሎችን የሚመገቡ ናቸው የማይታወቁትን ስለመተርጐም ይመልከቱ::

ሰቢሳ
ትልቅ ወፍ

ጅንጅላቴ ወፍ
እነዚህ እንሽላሊቶችንና ጥንብ ነገር የሚመገቡ ወፎች ናቸው።

የሌሊት ወፍ
የሌሊት ወፍ ወፍ ባትሆንም ክንፍ ስላለውና ስለሚበርር በዝርዝሩ ውስጥ ተካትቶአል። ጸጉራማ አካል ያለውና በሌሊት የማይተኛ ነው። ጥምብንና ትላትሎችን የሚመገብ ነው::

Leviticus 11:20

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቡ እንዲበሏቸው የተፈቀደላቸውንና ያልተፈቀደላቸውን እግዚአብሔር ለሙሴና ለአሮን መናገርን ቀጠለ::

ክንፍ ኖሮአቸው በአራት እግር የሚንቀሳቀሱ ነፍሳት ሁሉ በእናንተ ዘንድ አስጸያፊዎች ይሁኑ
“አስጸያፊ” የሚለው ቃል በግሥ ሃረግ ሊተረጐም ይችላል አት ክንፍ ኖሮአቸው አራት እግር ያሉአቸውን ነፍሳት ይጸየፉ። (ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ)

በአራት እግር የሚንቀሳቀሱ ነፍሳት
እዚህ “አራት እግር” የሚለው ሀረግ በምድር የሚንቀሳቀሱ መሆናቸውንና እንደ አእዋፋት ከመሠሉ ሁለት እግር ካላቸው ከሚበርሩ ነፍሳት እንደሚለዩ የሚገልጽ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው:: አት፡ “በምድር የሚንቀሳቀሱ ነፍሳት” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

አንበጣ ፈንጣ ኩብኩባ
እነዚህ ዕጽዋት ተመጋቢና የሚፈናጠሩ ትናንሽ እንስሳት ናቸው። (ያልታወቁትን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ባለአራት እግር የሚበርሩ ፍጥረታት ወይም ነፍሳት
“አራት እግር ያሉአቸው የሚበርሩ ፍጥረታት”

Leviticus 11:24

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቡ ርኩስ አድርጐ መቁጠር ስላለባቸው እንስት እግዚአብሔር ለሙሴና ለአሮን ይናገራል::

ከእነዚህ እንስሳት የአንዳቸውን በድን ቢነኩ እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ይሆናሉ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል። አት፡ “የእነዚህን እንስሳት በድን አንዳቸውን ከነካችሁ ርኩስ ያደርጋችኋል” (ተሻጋሪ ግሥና የማይሻገር ግሥ የያዘውን ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ርኩስ ይሆናሉ
ከእነዚህ በድን እንስሳት አንዱን በመንካቱ ምክንያት ለእግዚአብሔር ዓላማዎች ተቀባይነት ያጣው ሰው በአካል ርኩስ ተብሎ ተገልጸአል:: (ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

እነዚህ እንስሳት
በሚቀጥሉት ጥቅሶች የተዘረዘሩ እንስሳትን ያመለክታል::

Leviticus 11:26

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቡ ርኩስ አድርጐ መቁጠር ስላለባቸው እንስሳት እግዚአብሔር ለሙሴና ለአሮን መናገር ይቀጥላል::

ማንኛውም እንስሳ....በእናንተ ዘንድ ርኩስ ይሁን
ሕዝቡ አንዲመገቡ ያልተገቡ እግዚአብሔር የተናገራቸው እነዚህ እንስሳት በአካል ርኩስ ተብለው ተገልጸዋል። (ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ሰኰናው የተሰነጠቀ
አንድ ድፍን በመሆን ፈንታ ሰኰናው ለሁለት የተሰነጠቀ ማለት ነው። በዘሌዋዊያን 11:3 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ።

የሚያመስኩ ወይም የሚያመነዥጉ
ይህ ምግብን ከሆድ እንደገና ወደ አፍ በማምጣት የሚያኝኩ እንስሳት ማለት ነው። በዘሌዋዊያን 11:3 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ።

እነዚህን የሚነካ ሰው ሁሉ ይረክሳል
እነዚህን እንስሳት በመንካቱ ምክንያት ለእግዚአብሔር ዓላማዎች ያልተገባ ሰው በአካል ርኩስ ተደርጐ ተገልጾአል። (ዜይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

መዳፍ
ሾህና ያላቸው እንስሳት መረገጫ አካል

እስከ ማታ
ጸሐይ እስክትጠልቅ

Leviticus 11:29

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቡ ርኩስ አድርጐ መቁጠር ስላለባቸው እንስሳት እግዚአብሔር ለሙሴና ለአሮን መናገር ይቀጥላል::

እነዚህ እንስሳት በእናንተ ዘንድ ርኩስ ናቸው
ሕዝቡ አንዲመገቡ ያልተገቡ እግዚአብሔር የተናገራቸው እነዚህ እንስሳት በአካል ርኩስ ተብለው ተገልጸዋል።

ሙጭልጭላ
ወፎችንና ትናንሽ እንስሳትን የሚመገብ ቡኒ ጸጉር ያለው ትንሽ እንስሳ ነው

ዐይጥ እንሽላሊት ዔሊ ዐዞ ገበሎ አርጃኖ ዕስስት
እነዚህ አራት እግር ያላቸው የተለያዩ ተሳቢ እንስሳት ናቸው:: ያልታወቁትን ስለመተርጐም ይመልከቱ::

አርጃኖ
በአሸዋ የማኖር እንሽላሊት ነው::

Leviticus 11:31

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቡ ርኩስ አድርጐ መቁጠር ስላለባቸው እንስሳት እግዚአብሔር ለሙሴና ለአሮን መናገር ይቀጥላል::

እነዚህ እንስሳት በእናንተ ዘንድ ርኩስ ናቸው
ሕዝቡ አንዲመገቡ ወይም እንዲነኩ ያልተገቡ እግዚአብሔር የተናገራቸው እነዚህ እንስሳት በአካል ርኩስ ተብለው ተገልጸዋል። (ዜይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

እነዚህን የሚነካ ሁሉ ርኩስ ይሆናል
ከነዚህ እንስሳት በድን አንዱን በመንካቱ ምክንያት ለእግዚአብሔር ዓላማዎች ያልተገባ ሰው በአካሉ ርኩስ ተደርጐ ተገልጾአል:: (ዜይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

እስከ ማታ
ጸሐይ እስክትጠልቅ

እነዚህ በእናንተ ዘንድ ርኩሳን ናቸው
ከነዚህ በድን እንስሳት አንዳቸው በመጣላቸው ምክንያት ሕዝቡ እንዲነኩአቸው ያልተገባ እግዚአብሔር የተናገረው ነገር በአካል ርኩስ ተደርጐ ተገልጾአል በውሃ ከታጠበ በኋላ ንጹህ ተደርጐ ተገልጾአል (ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ከዚያም በኋላ ንጹህ ይሆናል
ከታጠበ በኋላ ሕዝቡ አንድነካ የተገባ እግዚአብሔር የተናገረው ነገር በአካል ንጹህ ተደርጐ ተገልጾአል::

ማንኛውም የተጠቀመበት ዕቃ በውሃ ውስጥ ይደረግ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት: "የተጠቀሙ ቢሆን በውሃ ይደረግ ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ"

Leviticus 11:34

ርኩስ
ርኩስ የሆነ ውሃ በላዩ ላይ በመፍሰሱ ምክንያት ሕዝቡ መብላት ያልተገባው ምግብ ርኩስ ተደርጐ ተነግሮአል። (ዜይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

በድኖች
ሙት አካላት

ይሰበር
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት: ይህን ይሰባብሩት ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ።

Leviticus 11:36

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቡ ርኩስ አድርጐ መቁጠር ስላለባቸው እንስሳት እግዚአብሔር ለሙሴና ለአሮን መናገር ይቀጥላል::

ምንጭ ወይም የውሃ ማጠራቀሚያ
ከምንጭ ወይም ከውሃ ማጠራቀሚያ ሕዝቡ እንዲጠጣ የተፈቀደለት በአካል ንጹህ ተብሎ ተነግሮአል:: (ዜይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

በድን
እግዝአብሔር የተናገረው ሕዝቡ እንዲበላ ወይም እንዲነካ ያልተገባው የእንስሳ በድን በአካል ርኩስ ተብሎ ተገልጾአል:: (ዜይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

ርኩስ
የእነዚህን እንስሳት በድን በመንካቱ ለእግዚአብሔር ዓላማዎች ያልተገባ ሰው በአካል ርኩስ ተደርጐ ተነግሮአል:: (ዜይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

የሚዘራ ዘር
ለመዝራት የሚያስቡት ዘር

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ዘሩ ንጹህ እንደሆነ ይቆያል ....ዘሩ ርኩስ ይሆናል
ሕዝቡ እንዲዘራ የተገባው እግዚአብሔር የተናገረው ዘር ንጹህ ተደርጐ ሲገለጽ ያልተገባው ዘር ግን ርኩስ እንደሆነ ተነግሮአል። (ዜይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

ነገር ግን በዘሩ ላይ ውሃ ከፈሰሰበት
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል አት ነገር ግን በዘሩ ላይ ውሃ ከጨበሩበት ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ

Leviticus 11:39

በድኑን የሚነካ እስከማታ ድረስ ርኩስ ይሆናል
የእንስሳ በድን በመንካቱ ለእግዚአብሔር ዓላማዎች ያልተገባ ሰው በአካል ርኩስ ተብሎአል። (ዜይቤያል አነጋገር ይመልከቱ)

እስከ ማታ
ጸሐይ እስኪጠልቅ

Leviticus 11:41

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቡ ርኩስ አድርጐ መቁጠር ስላለባቸው እንስሳት እግዚአብሔር ለሙሴና ለአሮን መናገር ይቀጥላል::

ጸያፍ ነው
ተሻጋሪ ግሥ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: “ተጸየፉት” ወይም “አትቀበሉት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ ይመልከቱ)

ይህ አይበላ
ተሻጋሪ ግሥ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: “ይህን አይብሉ”:: (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ ይመልከቱ)

እነዚህ ጸያፍ ናቸው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: “እነዚህን ተጸየፉአቸው” ወይም “ እነዚህን አትቀበሉአቸው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 11:43

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቡ ርኩስ አድርጐ መቁጠር ስላለባቸው እንስሳት እግዚአብሔር ለሙሴና ለአሮን መናገር ይቀጥላል::

በእነዚህ...ራሳችሁን አስጸያፊ አታድርጉ፤ በእነርሱ ራሳችሁን በማጉደፍ አትርከሱ
ርኩስ እንስሳ እንዳይበሉ ያዘዛቸውን ትዕዛዝ ለማጠንከር እግዚአብሔር ሁለት ጊዜ ተመሣሣይ ሃሳብ ይደግማል:: (ተጓዳኝ ንጽጽር ይመልከቱ)

ራሳችሁን አታርክሱ
ለእግዚአብሔር ዓላማ ያልተገባ ሰው በአካል ርኩስ ተብሎአል። (ዜይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

እንግዲህ በእነርሱ ራሳችሁን ታጐድፋላችሁ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል አት እንግዲህ ከእነርሱ የተነሣ ንጹሃን አትሆኑም (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 11:46

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ሕዝቡ ምን እንዲበላ እንደፈቀደና ምን እንዳይበላ እንደከለከለ ለሙሴና ለአሮን በመናገር ያበቃል

መለየት ስላለባቸው ነገሮች
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል አት እናንተ መለየት ስለአለባችሁ ነገሮች (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

በእርኩሱና በንጹሑ መካከል
ሕዝቡ እንዲነካና እንዲበላ የተገባቸው እግዚአብሔር የተናገራቸው እንስሳት በአካል ርኩስ ተብለዋል እና ሕዝቡ እንዲነካና እንዲበላ የተነገራቸው በአካል ንጹህ ተብለዋል ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ

የሚበላውና የማይበላው
ይህ በተሻጋሪ ግሥ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፡ የሚትበሉትንና የማትበሉትን። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 12

1 ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ **2** “ለእስራኤል ሰዎች እንደህ በላቸው፣ ‘አንዲት ሴት ብታረግዝና ወንድ ልጅ ብትወልድ፣ ልክ እንደ ወር አበባዋ ወቅት ለሰባት ቀናት ንጹህ አይደለችም። **3** በስምንተኛው ቀን ህጻኑ ልጅ መገረዝ አለበት። **4** ከዚያ የእናቲቱ ከደሟ መንጻት ለሰላሳ ሶስት ቀናት ይቆያል። ምንም አይነት የተቀደሰ ነገር መንካት የለባትም ወይም የመንጻቷ ቀናት እስኪፈጸም ድረስ ወደ ቤተመቅደስ አትምጣ። **5** ሴት ልጅ ከወለደች፣ በወር አበባዋ ወቅት እንደነበረችው ለሁለት ሳምንታት ንጹህ አትሆንም። ከዚያ የእናትየው የመንጻት ስርዓት ለስድስት ቀናት ይቀጥላል። **6** ወንድ ልጅም ሆነ ሴት ልጅ ከወለደች በኋላ የመንጻቷ ቀናት ሲያበቃ ለካህኑ በመገናኛው ድንኳን መግቢያ የአንድ አመት ጠቦት ለሚቃጠል መስዋዕት እንዲሁም ለኃጢአት መስዋዕት ዋኖስ ወይም ዕርግብ ታቅርብ። **7** ከዚያ ካህኑ መስዋዕቱን በያህዌ ፊት ይሰዋና ያስተሰርይላታል፣ እናም ከደሟ መፍሰስ ንጹህ ትሆናለች። ወንድም ይሁን ሴት ልጅ ለወለደች ሴት ህጉ ይህ ነው። **8** ጠቦት ማቅረብ ባትችል፣ ሁለት ዋኖሶች ወይም ሁለት ርግቦች ትውሰድ፣ አንዱን ለሚቀጠል መስዋዕት ሌላውን ለኃጢአት መስዋዕት ታቅርብ እናም ካህኑ ያስተሰርይላታል፣ ከዚያም ንጹህ ትሆናለች።’”

Leviticus 12:1

ትረክሳለች
ከማዕጸንዋ ደም ስለሚፈስስ ሰዎች የማይነኩአት ሴት በአካል ርኩስ ተብላለች ዜይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ

በወር አበባዋ ጊዜ
ይህ በወር ከማዕጸንዋ ደም የሚፈስስበት ጊዜ ያመለክታል (See Euphemism/ንኣብነት ወይም ጸያፍ አባበሎችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

የወንድ ልጅ አካለ ብልት ቆዳ ይገረዝ
ካህኑ ብቻ ይህንን ድርጊት ይፈጽም ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል አት ካህኑ ወንድ ህጻን ልጅን ይገርዘው። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 12:4

አንድ እናት ከደሟ እንስኪትነጻ ድረስ ሠላሣ ሶስት ቀን ድረስ ትቆይ
ይህች እናት ለሠላሣ ሶስት ቀናት ርኩስ ትሆናለች ማለት ነው።

ሠላሣ ሶስት ቀናት
33 ቀናት (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

ለሁለት ሳምንታት ርኩስ ትሆናለች
ከማዕጸንዋ ደም ስለሚፈስሳት ሌሎች ሰዎች የማይነኳት ሴት በአካል ርኩስ ትብላለች። (ዜይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

ለሁለት ሣምንታት
14 ቀናት

ወር አበባዋ ጊዜ
ከማዕጸንዋ ደም የሚፈስስበት ወራዊ ጊዜ ያመለክታል በዘሌዋዊያን 12:2 እንዴት አንደተረጐሙ ይመልከቱ (See: Euphemism/ንኣብነት ወይም ጸያፍ/አሳፋሪ አባበሎችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ስድሳ ስድስት ቀናት
66 ቀናት

Leviticus 12:6

የመስጻትዋ ጊዜ ስፈጸም
የአንድ እናት የመንጻት ቀኖችዋ ሲፈጸም

ለወንድ ልጅ ወይም ለሴት ልጅ
ወንድ ልጅ ወይም ሴት ልጅ ወልዳ ከሆነ የአንዱ እናት የመንጻት ቀኖችዋ የተለያየ እንደሆነ ያመለክታል።

Leviticus 12:7

ሴትዬዋ ከደሟ ፊሳሽ ትነጻለች
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “ይህ በወሊድ ጊዜ ከሚፈስሳት ደም ያነጻታል”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ጠቦት ለማምጣት አቅምዋ ካልፈቀደ
የመስዋዕት እንስሳ የመግዛት አቅም ማነስ በሚገልጽ መንገድ ይተርጉሙ። አት፡ “ጠቦት ለመግዛት በቂ ገንዘብ ከሌላት”

እርስዋም ትነጻለች:
ሌሎች ሰዎች መንካት የማችሏት ሴት በአካል ንጹህ ተብላለች።

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 13

1 ያህዌ ሙሴንና አሮንን እንዲህ አላቸው፣ 2 “ማንኛውም ሰው በሰውነቱ ቆዳ ላይ እባጭ ወይም ችፍታ ወይም ቋቁቻ ቢወጣና ቢቆስል በሰውነቱ ላይ የቆዳ
በሽታ ይሆናል፣ በዚህ ጊዜ ወደ ሊቀካህኑ አሮን ይምጣ፣ አሊያም ካህናት ከሆኑት ልጆቹ ወደ አንዱ ይምጣ። 3 ከዚያ በሰውነቱ ቆዳ ላይ ያለውን በሽታ ካህኑ
ይመረምረዋል። በበሽታው ዙሪያ ያለው ጸጉር ወደ ነጭነት ከተለወጠ፣ እና በሽታው በቆዳው ላይ ከሚታየው ይልቅ የከፋ ሆኖ ከተገኘ ተላላፊ በሽታ ነው። ካህኑ
ከመረመረው በኋላ፣ ንጹህ አለመሆኑን ያሳውቅ። 4 በቆዳው ላይ የታየው ቋቁቻ ነጭ ከሆነ፣ እና ወደ ቆዳው ዘልቆ የገባ ካልሆነ፣ እንዲሁም በህመሙ አካባቢ
የሚገኘው ጸጉር ወደ ነጭነት ካልተለወጠ፣ ካህኑ በሽታው ያለበትን ሰው ለሰባት ቀናት ያገልግለው። 5 በሰባተኛው ቀን፣ ካህኑ በእርሱ እይታ በሽታው አየከፋ
በቆዳው ላይ እየሰፋ አለመሄዱን ለማየት ይመርምረው። በሽታው ለውጥ ካላሳየ፣ ካህኑ ለተጨማሪ ሰባት ቀናት ሰውየውን አግልሎ ያቆየው። 6 በሰባተኛው ቀን
በሽታው እየተሻለው እንደሆነና በቆዳው ላይ እየሰፋ እንደላሆነ ለማየት ካህኑ ሰውየውን ደግሞ ይመረምረዋል። በሽታው ለውጥ ካለው፣ ካህኑ ሰውየው ንጹህ
መሆነኑን ይገልጻል። ይህ ሽፍታ ነው። ሰውየው ልብሱን ይጠብ፣ እናም ከዚህ በኋላ ንጹህ ነው። 7 ነገር ግን ሰውየው ራሱን ለካህን ካሳየ በኋላ ሽፍታው በቆዳው
ላይ ከተስፋፋ፣ እንደገና ራሱን ለካህን ያሳይ። 8 ሽፍታው ይበልጥ በሰውየው ቆዳ ላይ እየሰፋ መሆኑን ለማየት ካህኑ ይመረምረዋል። ከተስፋፋ፣ ከዚያ ካህኑ
ሰውየው ንጹህ አይደለም ይላል። ይህ ተላላፊ የቆዳ በሽታ ነው። 9 ተላላፊ የቆዳ በሽታ በአንድ ሰው ላይ ሲገኝ፣ ይህ ሰው ወደ ካህን ይምጣ። 10 ካህኑ
በሰውየው ቆዳ ላይ ነጭ ዕብጠት መኖሩን ለማየት ይመረምረዋል፣ ጸጉሩ ወደ ነጭነት መቀየሩን፣ ወይም በዕብጠቱ ላይ የስጋ መላጥ መኖሩን ይመልከት። 11
እንዲህ ያለ ነገር ካለ፣ ይህ ጽኑ የቆዳ ህመም ነው፣ እናም ካህኑ ሰውየው ንጹህ አለመሆኑን ይግለጽ። ሰውየውን አያገለውም፣ ምክንያቱም ቀድሞውኑም ንጹህ
አይደለም። 12 በሽታው በቆዳው ላይ በሰፊው ጎልቶ ከታየና የሰውየውን ቆዳ ከአናቱ እስከ እግሩ ከሸፈነ፣ ካህኑ ይህ እስከ ታየው ድረስ፣ በሽታው የሰውየውን
አካል ሸፍኖት እንደሆነ ለማየት ይመርምረው። 13 እንዲህ ሆኖ ከተገኘ፣ በሽታው ያለበት ሰው ንጹህ አለመሆኑን ካህኑ ይግለጽ። ሁሉም ወደ ንጣት ተለውጦ
ከሆነ ንጹህ ነው። 14 ነገር ግን የስጋ መላጥ ከታየበት፣ ሰውየው ንጹህ አይደለም። 15 ካህኑ የስጋውን መላጥ ማየትና ንጹህ አለመሆኑን ይግለጽ፣ ምክንያቱም
የተላጠ ስጋ ንጹህ አይደለም። ይህ ተላላፊ በሽታ ነው። 16 ነገር ግን የተላጠው ስጋ መለልሶ ነጭ ቢሆን፣ ሰውየው ወደ ካህኑ ይሂድ። 17 ካህኑ ስጋው ወደ
ነጭነት ተመልሶ እንደሆነ ይመረምረዋል። እንዲህ ከሆነ ካህኑ ሰውየው ንጹህ መሆኑን ይገልጻል። 18 አንድ ሰው በቆዳው ላይ እባጭ ወጥቶ ሲድን፣ 19 እና
በዕባጩ ስፍራ እብጠት ወይም ቋቁቻ፣ ቀላ ያለ ንጣት፣ ሲኖር ይህን ካህኑ ሊያየው ይገባል። 20 ካህኑ ይህ ወደ ታማሚው ቆዳ ዘልቆ የገባ መሆኑን እና በዚያ
ዙሪያ ያለው ጸጉር ወደ ነጭነት መለወጡን ለማየት ይመረምራል። እንዲያ ከሆነ፣ ካህኑ ታማሚው ንጹህ አለመሆኑን ያሳውቃል። እብጠቱ በነበረበት ስፍራ
እየሰፋ ከሄደ ይህ ተላላፊ በሽታ ነው። 21 ነገር ግን ካህኑ ይህንን መርምሮ በውስጡ ነጭ ጸጉር አለመኖሩን ከተመለከተ፣ እና ይህም ከቆዳው ስር ካልሆነ
ሆኖም ከደበዘዘ ካህኑ ታማሚውን ለሰባት ቀናት ያግልለው። 22 በቆዳው ላይ በሰፊው ከተስፋፋ፣ ካህኑ ታማሚው ንጹህ አይደለም ይበል። ይህ የሚተላለፍ
በሽታ ነው። 23 ነገር ግን ቋቁቻው በቦታው ከሆነና ካልተስፋፋ፣ ይህ የእባጩ ጠባሳ ነው፣ እናም ካህኑ ንጹህ ነው ብሎ ያስታውቅ። 24 አንድ ሰው ቆዳው
ቃጠሎ ሲኖርበትና የስጋው መላጥ ቀላ ያለ ንጣት ወይም ነጭ ጠባሳ ሲሆን፣ 25 ካህኑ ያጠባሳ ስፍራ ወደ ንጣት መለወጡን እና ወደ ቆዳው ዘልቆ መግባቱን
ለማየት ይመረምራል። እንደዚህ ከሆነ፣ ተላላፊ በሽታ ነው። ከቃጠሎው አልፎ ከውስጥ የመጣ ነው፣ እናም ካህኑ ሰውየው ንጹህ አለመሆኑን ያሳውቅ። ተላላፊ
በሽታ ነው። 26 ነገር ግን ካህኑ በሚመረምርበት ጊዜ በስፍራው ነጭ ጸጉር አለመኖሩን ቢደርስበትና ቁስሉ ከቆዳው ስር ሳይሆን ቢቀር እየከሰመ ቢመጣ ካህኑ
ታማሚውን ለሰባት ቀናት ያግልለው። 27 ከዚያም ካህኑ በሰባተኛው ቀን ይመርምረው። ምልክቱ በሰፊው በቆዳው ላይ ቢስፋፋ፣ ካህኑ ንጹህ አይደለም ብሎ
ያሳውቅ። ይህ ተላላፊ በሽታ ነው። 28 ምልክቱ በስፍራው ከቆየና በቆዳው ላይ እየሰፋ ካልሄደ ነገር ግን ከከሰመ ይህ በቃጠሎው የመጣ እብጠት ነው፣ እናም
ካህኑ ሰውየው ንጹህ መሆኑን ያሳውቅ፣ ይህ ከቃጠሎው የመጣ ጠባሳ እንጂ ሌላ ነገር አይደለም። 29 በአንድ ወንድ ወይም ሴት ራስ ወይም አገጭ ላይ
ተላላፊ በሽታ ቢኖር፣ 30 ችግሩ ከቆዳው ስር የዘለቀ መሆኑና በላዩ ቢጫ ስስ ጸጉር እንዳለ ለማየት ካህኑ ካህኑ የተላላፊ በሽታ ምርመራ ያድርግለት። ይህ
ከተገኘ፣ ካህኑ ሰውየው ንጹህ አለመሆኑን ያሳውቅ። ይህ የሚያሳክክ በሽታ ነው፣ በራስ ወይም አገጭ ላይ የወጣ ተላላፊ በሽታ ነው። 31 የሚያሳክከውን በሽታ
መርምሮ ከቆዳ ስር ያልዘለቀ መሆኑን ቢያይ፣ ደግሞም በውስጡ ጥቁር ጸጉር ባይኖር፣ ካህኑ ሰውየውን በሚያሳክክ በሽታው ምክንያት ለሰባት ቀናት ያግልለው።
32 በሰባተኛው ቀን በሽታው ተስፋፍቶ እንደሆነ ለማየት ካህኑ ይመረምረዋል። ቢጫ ጸጉር ከሌለና፣ በሽታው ላይ ላዩን ብቻ ከታየ፣ 33 ሰውየው ይላጭ፣ ነገር
ግን በሽታው የሚገኝበት ዙሪያ መላጨት የለበትም፣ እናም ካህኑ የሚያሳክክ በሽታ ያለበትን ሰው ለሰባት ቀናት ያግልለው። 34 በሰባተኛው ቀን በሽታው በቆዳው
ላይ መስፋፋቱን ማቆሙን ለማየት ካህኑ ምርመራ ያደርጋል። በሽታው ቆዳውን ዘልቆ የገባ ካልሆነ፣ ካህኑ የሰውየውን ንጹህ መሆን ያሳውቅ። ሰውየው ልብሱን
ይጠብ፣ እናም ከዚያ ንጹህ ይሆናል። 35 ነገር ግን ካህኑ ንጹህ መሆኑን ካሳወቀ በኋላ የሚያሳክከው በሽታ እየሰፋ ከሄደ ፣ 36 ካህኑ ዳግም ይመርምረው።
በሽታው በሰውየው ቆዳ ላይ እየሰፋ ከሄደ፣ካህኑ ቢጫ ጸጉር መኖሩን መፈለግ አይኖርበትም። ሰውየው ንጹህ አይደለም። 37 ነገር ግን ካህኑ ሰውየውን
የሚያሳክከው በሽታ እየሰፋ መሄዱን እንዳቆመ ከተመለከተ ንጹህ መሆኑን ያሳውቅ። 38 አንድ ወንድ ወይም አንዲት ሴት በቆዳቸው ላይ ነጭ ምልክቶች
ቢወጣ 39 ምልክቱ ዳለቻ መልክ ያለው በቆዳ ላይ የወጣ ሽፍታ ብቻ መሆኑን ለማየት ካህኑ ምርመራ ያድርግ። ሰውየው ንጹህ ነው። 40 የሰውየው ጸጉር ከራሱ
ላይ ካለቀ፣መላጣ ነው፣ ነገር ግን ንጹህ ነው። 41 ደግሞም ከፊት ለፊት ጸጉሩ ተመልጦ ራሰ በራ ቢሆንም ንጹህ ነው። 42 ነገር ግን በህመም ምክንያት ፈዘዝ
ያለ ቅላት በተመለጠው ራሱ ላይ ወይም በግምባሩ ላይ ቢኖር፣ ይህ በተላላፊ በሽታ ምክንያት የመጣ ነው። 43 በቆዳ ላይ ተላላፊ በሽታ ሲኖር እንደሚታየው
በመላጣው ወይም በበራው ላይ በህመሙ ዙሪያ ፈዘዝ ያለ ቅላት መኖሩን ለማየት ካህኑ ምርመራ ያድርግለት። 44 ይህ ከሆነ፣ ተላላፊ በሽታ አለበት እናም ንጹህ
አይደለም። በእርግጥ ካህኑ ሰውየው በራሱ ላይ ካለበት በሽታ የተነሳ ንጹህ እንደልሆነ ያስታውቅ። 45 ተላላፊ በሽታ ያለበት ሰው የተቀደደ ልብስ ይልበስ፣
ጸጉሩን በከፊል ይሸፍን፣ እስከ አፍንጫው ይከናነብና ‘እርኩስ ነኝ፣ እርኩስ ነኝ’ እያለ ይጩህ። 46 ተላላፊው በሽታ ባለበት ቀናት ሁሉ እርኩስ ነው። እየሰፋ
ሊሄድ በሚችል በሽታ ምክንያት ንጹህ ስላልሆነ፣ ለብቻው ይኑር። ከሰፈር ውጭ ይኑር። 47 በማናቸውም ነገር የተበከለ የሱፍም ሆነ የተልባ ዕግር ጨርቅ፣ 48
ወይም ከሱፍም ሆነ ከተልባ ዕግር ጨርቅ የተፈተለ፣ ወይም ቆዳም ሆነ ከቆዳ በተሰራ ልብስ - 49 በልብሱ ላይ አረንጓዴ ወይም ቀላ ያለ ብክለት ቢገኝበት፤
በቆዳው፣ በተጠለፈው ወይም በተሰፋው ነገር፣ ወይም ማናቸውም ከቆዳ በተሰራው ነገር ላይ ብክለቱ እየሰፋ ቢሄድ ካህኑ ይህን ይመልከት። 50 ካህኑ
የሚበከለውን ዕቃ ይመርምር፣ የተበከለውን ማናቸውንም ነገር ለሰባት ቀናት ይለየው። 51 በሰባተኛው ቀን እንደገና ብክለቱን ይመርምር። በልብሱ ወይም ከሱፍ
ወይም ከተልባ ዕግር ጨርቅ በተሸመነው ወይም በተጠለፈው ማናቸውም ልብስ ላይ ብክለቱ እየሰፋ ቢሄድ ወይም በቆዳ ወይም ከቆዳ በተሰራ ማናቸውም ነገር
ላይ ብክለቱ ቢሰፋ ጎጂ ነው፣ እናም ዕቃው ንጹህ አይደለም። 52 ካህኑ ያንን ልብስ ያቃጥል፣ ወይም ማናቸውም ከሱፍ ወይም ከተልባ ዕግር ጨርቅ የተፈተለ
ወይም ቆዳ ወይም ከቆዳ የተሰራ ነገር፣ ማናቸውም ጎጂ ብክለት የተገኘበት ነገር በሽታ ያመጣልና ያቃጥለው። ዕቃው ሙሉ ለሙሉ ይቃጠል። 53 ካህኑ ዕቃውን
መርምሮ ብክለቱ በልብ ወይም በተሸመነው ወይም በተለጠፈው ልብስ ወይም በቆዳ ዕቃዎቹ ላይ እየሰፋ የሚሄድ አለመሆኑን ካወቀ፣ 54 ብክለቱ የተገኘባቸውን
ዕቃዎች እንዲያጥቡ ያዛቸዋል፤ ደግሞም ዕቃውን ለሰባት ቀናት ያግልል። 55 ከዚያ ካህኑ የተበከለውን ዕቃ ከታጠበ ከሰባት ቀናት በኋላ ይመረምረዋል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ብክለቱ ቀለሙን ካልቀየረውና እየሰፋ ባይሄድ እንኳን ንጹህ አይደለም። ብክለቱ የትም ላይ ይሁን ዕቃዎቹን አቃጥሏቸው። **56** ካህኑ ዕቃውን ከመረመረና ልብሱ ከታጠበ በኋላ ብክለቱ እየለቀቀ ከሄደ፣ ከተበከለው የልብሱ ወይም የቆዳው ክፍል ወይም ከተሸመነው ወይም ከተጠለፈው ዕቃ ቀድዶ ያውጣው። **57** እንዲህም ሆኖ ብክለቱ አሁንም በተሸመነው ወይም በተጠለፈው፣ ወይም በማናቸውም ከቆዳ በተሰራው ነገር ላይ ከተገኘ እየሰፋ በመሄድ ላይ ነው። ብክለት ያለበትን ማናቸውንም ነገር አቃጥለው። **58** ከሱፍ ወይም ከተልባ ዕግር ጨርቅ የተሰራ ወይም የተለጠፈ ልብስ ወይም ማናቸውም ነገር፣ ወይም ቆዳ ወይም ከቆዳ የተሰራ ማናቸውም ነገር - ስታጥበው ብክለቱ እየለቀቀ ከሄደ፣ ዕቃው ዳግመኛ ይታጠብ እናም ንጹህ ይሆናል። **59** ከሱፍ ወይም ከተልባ ዕግር ጨርቅ ለተሸመነ ወይም ለተጠለፈ፣ከሱፍ ወይም ከተልባ ዕግር ጨርቅ ወይም ቆዳ ወይም ከቆዳ ለተሰራ ማናቸውም ነገር ብክለት ህጉ ይህ ነው፣ ስለዚህ ንጹህ ነው ወይም እርኩስ ነው ብለህ ማሳወቅ ትችላለህ።”

Leviticus 13:1

ከዚያም ያምጡት
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “ከዚያም አንድ ሰው ያምጣው”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ከልጆቹ ወደ አንዱ
ከአሮን ልጆች ወደ አንዱ

Leviticus 13:3

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴና ለአሮን መናገር ቀጠለ

የእርሱ ሰውነት ቆዳ ወይም የሰውነቱ ቆዳ
እዚህ እርሱ የቆዳ በሽታ ያለበትን ሰው ያመለክታል

ተላላፊ በሽታ
ከአንድ ሰው በቀላሉ ወደ ሌላው መተላለፍ የሚችል በሽታ

እርሱም ሰውየው ርኩስ መሆኑን ይግለጽ
ካህኑም ሰውየው ርኩስ መሆኑን ይግለጽ። ሌሎች ሰዎች የማይነኩት ሰው በአካል ርኩስ ተብሎአል:: (ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ለሰባት ቀናት
“ለ 7 ቀናት ቁጥሮችን ይመልከቱ”

Leviticus 13:5

እርሱን ካህኑ ይመረምረው
እዚህ እርሱ የቆዳ በሽታ ያለበትን ሰው ያመለክታል

በቆዳውም ላይ ካልተስፋፋ
ይህም የቆዳው በሽታ መጠኑን ካልጨመረ ወይም ወደ ሌላው የሰውነት አካል ካልተላለፈ ማለት ነው

ሰባተኛው ቀን
“ቀን 7” (ተራ ቁጥሮችን ይመልከቱ)

ሰባት ቀናት
“7 ቀናት” (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

ካህኑ ንጹህ ስለመሆኑ ይግለጽ...ንጹህም የሆናል
ሌሎች ሰዎች መንካት የሚችሉት ሰው በአካል ንጹህ ተብሎአል ዜይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ

ችፍታ
ይህ የሚያስከፋ የቆዳ አካል ነው ፤ነገር ግን ወደ ሌላ ሰው የማይተላለፍ ነው።

Leviticus 13:7

ራሱ...ብቻውን
በሽታው ያለበትን ሰው ያመለክታል

ካህኑ ርኩስ ስለመሆኑ ይግለጽ
ሌሎች ሰዎች የማይነኩት ሰው በአካል ርኩስ ተብሎአል። (ዜይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

ተላላፊ በሽታዎች
በዘሌዋዊያን 13:3 እነዚህን ቃላት እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ

Leviticus 13:9

ወደ ካህኑ ያምጡት
በሽታው ተሠራጭቶ እንደሆነ ካህናት ይወስናሉ:: ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “አንድ ሰው ወደ ካህኑ ያምጣው”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

እብጠቱ ውስጥ ቀይ ሥጋ ቢታይ
እዚህ ቀይ ሥጋ በእባጩ ላይ የተከፈቱ ቁስሎችን ወይም አዲስ ቆዳ ያደገውን ነገር ግን ዙሪያው እንደቆሰለ እንዳለ የሚያመለክት ነው።

ሥር የሰደደ የቆዳ በሽታ
ይህ የተደገመ ወይም ለረጅ ጊዜ በተደጋጋሚ የሚከሰት ነው።

ሰውየው ርኩስ መሆኑን ካህኑ ያስታውቅ ... ርኩስ መሆኑም ግልጽ ይሆናል
ሌሎች ሰዎች ሊነኩት የማይችሉት ሰው በአካል ርኩስ ይባላል። (ዜይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

Leviticus 13:12

አጠቃላይ መረጃ
አንድ ሰው የቆዳ በሽታ ሲኖረው ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴና አሮን ይናገራል

ካህኑ ሰውየውን ያስታውቅ ... ንጹህ .... ርኩስ ይሆናል
ሌሎች ሰዎች ሊነኩት የሚችሉት ሰው በአካል ንጹህ ይባላል፤ እናም ሌሎች ሰዎች ሊነኩት የማይችሉት ሰው በአካል ርኩስ ይባላል። (ዜይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

Leviticus 13:15

ካህኑ...ርኩስ መሆኑን ያሰታውቅ ምክንያቱም ቀይ ሥጋ ርኩስ ስለሆነ
ሌሎች ሰዎች የማይነኩት ሰው በአካል ርኩስ ተብሎአል:: (ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

እርሱ ርኩስ መሆኑን ያሰታውቅ
እዚህ ርኩስ የቆዳ በሽታ ያለበትን ሰው ያመለክታል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ቀይ ሥጋ
በዘሌዋዊያን 13:10 ይህን እነዚህን ቃላት እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ።

ተላላፊ በሽታዎች
በዘሌዋዊያን 13:3 እነዚህን ቃላት እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ።

ሰውየው ንጹህ መሆኑን ካህኑ ያስታውቃል
ሌሎች ሰዎች የሚነኩት ሰው በአካል ንጹህ ተብሎአል:: (ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Leviticus 13:18

አጠቃላይ መረጃ
አንድ ሰው የቆዳ በሽታ ሲኖረው ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴና አሮን ይናገራል

ዕባጭ
የሚያምም እብጠት የያዘ የቆዳ አካል ነው

ካህኑ ዘንድ ቀርቦ መታየት አለበት
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጎም ይችላል። አት፤ “እርሱም ካህኑን ያሳየው”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ርኩስ መሆኑን ካህኑ ያስታውቅ
ሌሎች ሰዎች የማይነካው ሰው በአካል ርኩስ ተብሎአል:: (ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Leviticus 13:21

አጠቃላይ መረጃ
አንድ ሰው የቆዳ በሽታ ሲኖረው ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴና አሮን ይናገራል

ይህን ይመረምረው
እዚህ “ይህ” በቆዳው ላይ የሚታይ ነጭ እብጠት ቀላ ያለ ነገር ማለት ነው

ርኩስ መሆኑን ካህኑ ያስታውቅ
ሌሎች ሰዎች የማይነካው ሰው በአካል ርኩስ ተብሎአል:: (ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ካህኑም ንጹህ መሆኑን ያስታውቅ
ሌሎች ሰዎች የማነካው ሰው በአካል ንጹህ ተብሎአል:: (ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Leviticus 13:24

አጠቃላይ መግለጫ
አንድ ሰው የቆዳ በሽታ ሲኖረው ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴና አሮን ይናገራል።

ተላላፊ በሽታዎች
በዘሌዋዊያን 13:3 እነዚህን ቃላት እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ።

ርኩስ መሆኑን ካህኑ ያስታውቅ
ሌሎች ሰዎች የማይነካው ሰው በአካል ርኩስ ተብሎአል:: (ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Leviticus 13:26

አጠቃላይ መግለጫ
አንድ ሰው የቆዳ በሽታ ሲኖረው ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴና አሮን ይናገራል።

ይህን ይመረምረው
እዚህ “ይህ” በቆዳው ላይ የሚታይ ነጭ ጠባሳ ነገር ማለት ነው

ሰውየው ርኩስ መሆኑን ካህኑ ያስታውቅ
ሌሎች ሰዎች የማይነካው ሰው በአካል ርኩስ ተብሎአል:: (ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ተላላፊ በሽታዎች
በዘሌዋዊያን 13:3 እነዚህን ቃላት እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ።

ካህኑ ንጹህ መሆኑን ያስታውቅ
ሌሎች ሰዎች የሚነካው ሰው በአካል ንጹህ ተብሎአል:: (ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Leviticus 13:29

አጠቃላይ መግለጫ
አንድ ሰው የቆዳ በሽታ ሲኖረው ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴና አሮን ይናገራል።

ያ ሰው ርኩስ መሆኑን ካህኑ ያስታውቅ
ሌሎች ሰዎች መንካት የማይገባው ሰው በአካል ርኩስ ተብሎአል:: (ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Leviticus 13:31

አጠቃላይ መግለጫ
አንድ ሰው የቆዳ በሽታ ሲኖረው ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴና አሮን ይናገራል።

Leviticus 13:32

አጠቃላይ መግለጫ
አንድ ሰው የቆዳ በሽታ ሲኖረው ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴና አሮን ይናገራል።

ጸጉሩን ይላጭ ነገር ግን በቆሰለው ቦታ ያለውን አይላጭ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጎም ይችላል። አት፤ “ሰውየው በቁስሉ ላይ ያለውን ጸጉር ሳይሆን በቁስሉ ዙሪያ ያለውን ጸጉር ይላጭ”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 13:34

አጠቃላይ መግለጫ
አንድ ሰው የቆዳ በሽታ ሲኖረው ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴና አሮን ይናገራል።

የሚያሳክክ ቁስል
እዚህ የሚያሳክክ ቁስል በሰውየው ራስ ወይም ጉንጭ ላይ የሚታይ የሚያሳክክ ቁስል ያመለክታል ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ

ካህኑ ንጹህ መሆኑን ያስታውቅ
ሌሎች ሰዎች የሚነካው ሰው በአካል ንጹህ ተብሎአል:: (ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Leviticus 13:35

አጠቃላይ መግለጫ
አንድ ሰው የቆዳ በሽታ ሲኖረው ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴና አሮን ይናገራል።

ንጹህ መሆኑን ካህኑ ከተናገረ ... ሰውየው ነጽቶአል ካህኑም ንጹህ መሆኑን ያስታውቅ
ሌሎች ሰዎች መንካት የሚገባው ሰው በአካል ንጹህ ተብሎአል:: (ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ሰውየው ርኩስ ነው
ሌሎች ሰዎች መንካት የማይገባው ሰው በአካል ርኩስ ተብሎአል:: (ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Leviticus 13:38

አጠቃላይ መግለጫ
አንድ ሰው የቆዳ በሽታ ሲኖረው ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴና አሮን ይናገራል።

ቋቁቻ
ደለቻ/ደብዛዛ ነጭ ነገር

ሸፍታ
በዘሌዋዊያን 13:6 ይህን ቃል እንዴት አንደተረጐሙ ይመልከቱ::

ሰውየውም/እርሱ ንጹህ ነው
እዚህ “እርሱ” በአጠቃላይ ለወንዶችና ለሴቶች እንዴሚውል ያመለክታል: አት: “ያ ሰው ንጹህ ነው” (የወንድ ጾታ ቃላት ሴት ጾታን ስለማካተት ይመልከቱ)

ሰውየው ንጹህ ነው
ሌሎች ሰዎች መንካት የሚገባው ሰው በአካል ንጹህ ተብሎአል:: (ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Leviticus 13:40

አጠቃላይ መግለጫ
አንድ ሰው የቆዳ በሽታ ሲኖረው ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴና አሮን ይናገራል።

ሰውየው ንጹህ ነው
ሌሎች ሰዎች መንካት የሚገባው ሰው በአካል ንጹህ ተብሎአል:: (ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Leviticus 13:42

አጠቃላይ መግለጫ
አንድ ሰው የቆዳ በሽታ ሲኖረው ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴና አሮን ይናገራል።

ተላላፊ በሽታ
በዘሌዋዊያን 13:3 እነዚህን ቃላት እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ።

እርሱ ርኩስ ነው...ርኩስ መሆኑን ያስታውቅ
ሌሎች ሰዎች መንካት የማይገባው ሰው በአካል ርኩስ ተብሎአል:: (ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Leviticus 13:45

አጠቃላይ መግለጫ
አንድ ሰው የቆዳ በሽታ ሲኖረው ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴና አሮን ይናገራል።

ከሠፈር ውጪ
ሠፈር አብዛኛው እስራኤላዊያን የሚኖሩበት ቦታ ነው በሽታው ወደሌላ ሰው ስለሚዛመት ወይም ስለሚተላለፍ ንጹህ ያለሆነው ሰው በመካከላቸው እንደኖር አልተፈቀደም

ርኩስ ርኩስ
ሌሎች ሰዎች መንካት የማይገባው ሰው በአካል ርኩስ ተብሎአል:: (ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Leviticus 13:47

አረንጓዴ ወይም ቀይ መሣይ ደዌ የተበከለ ልብስ
አረንጓደ ወይም ቀይ መሣይ ደዌ በላይ ላዩ ያለው ልብስ ወይም በለምጽ ደዌ የተበከለ ልብስ

ተበከለ
በላዩ ላይ ጐጂ ነገር ስለታየበት ርኩስ ነው

ቀይ ወይም አረንጓዴ ደዌ
በርጥብና በተጣሉ ነገሮች ላይ የሚበቅል በአብዛኛው ነጭ ሻገታ ፋንገስ ነው

በሸማኔ ዕቃ በተሠራ ወይም በእጅ በተጠለፈ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “አንድ ሰው በሸማኔ ዕቃ ወይም በእጅ የሠራውን ማንኛው ነገር”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

በልብስ ላይ አረንጓዴ ወይም ቀይ መሣይ የተበከለ ነገረ ቢገኝ
“አረንጓዴ ወይም ቀይ መሣይ ዴዌ በልብስ ላይ ቢገኝ”

ከቆዳ የተሠራ ዕቃ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “አንድ ሰው ከቆዳ የሠራው ማንኛው ነገር”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ይህ ለካህኑ ይታይ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “የዕቃው ባለቤት ለካህኑ ያሣየው”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 13:50

ሰባት ቀናት
“7 ቀናት” (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

ሰባተኛ ቀን
“ሰባተኛ ለተራ ቁጥር 7 ነው”። (ተራ ቁጥሮች ይመልከቱ)

ማንኛውንም ቆዳ የተጠቀመበት ዕቃ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “አንድ ሰው ቆዳን የተጠቀመበቅ ማንኛውም ነገር”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጐጂ ደወው ያለበት ማንኛውም ነገር ቢገኝ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “ማንኛውንም ጐጂ ደወው ያለበትን ነገር ቢያገኝ”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ዕቃው ርኩስ ነው
ሕዝቡ እንዲነካ ያልተገባው ማንኛውም ነገር በአካል ርኩስ ተብሎአል:: (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

ይህ በሽታን ሊያስይዝ ይችላል
ክፉ ደወው ዕቃውን የሚነካውን ሰው በሽታ ሊያስይዝ ይችላል

ዕቃው ሙሉ በሙሉ ይቃጠል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “ዕቃውን ፈጽሞ ያቃጥለው”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)::

Leviticus 13:53

ይዘዝ
የዕቃው ባለቤቶችን ካህኑ ይዘዝ እዚህ ሕዝቡ የተበከሉ የቤት ዕቃዎችን ምን ማድረግ እንዳለባቸው ካህኑ ይናገራቸዋል

ክፉ ደዌ የተገኘበት ነገር
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “ክፉ ደዌውን ያገኙበት ነገር”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)::

ደዌው ያለበት ነገር ከታጠበ በኋላ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “ዴዌው ያለበትን ነገር ካጠቡ በኋላ”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)::

ርኩስ ነው
ሕዝቡ እንዲነካ ያልተገባው ማንኛውም ነገር በአካል ርኩስ ተብሎአል:: (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

እርሱ ዕቃው በእሳት ይቃጥል
እዚህ እርሱ ካህኑን አያመለክትም አንድ ሰው ዕቃውን ያቃጥል ማለት ነው።

Leviticus 13:56

ዕቃው ከታጠበ በኋላ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “ባለቤቱ ካጠበው በኋላ”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)::

እርሱም በእሳት ያቃጥል
እዚህ እርሱ በተለይ ካህኑን የሚያመለክት አይደለም አንድ ሰው ዕቃውን ማቃጠል አለበት ማለት ነው

ዕቃውን የሚያጥብ ከሆነ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “ባለቤቱ የሚያጥብ በኋላ”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)::

ንጹሕም ይሆናል
ሕዝቡ እንዲነካ የተገባው ማንኛውም ነገር በአካል ንጹህ ተብሎአል:: (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

Leviticus 13:59

ከቆዳ የተሠራው ማንኛውም ዕቃ በደዌ ቢበከል
በዘሌዋዊያን 13:47-48 እንነዚህን ቃላት እንዴት አንደተረጐሙ ይመልከቱ።

ስለሆነም ይህን ያስታውቀው
ስለሆነም ካህኑ ያስታውቀው

ንጹህ ወይም ርኩስ
ሕዝቡ እንዲነካ የተገባው ማንኛውም ነገር በአካል ንጹህ ተብሎአል:: እናም ሕዝቡ እንዲነካ ያልተገባው ማንኛውም ነገር በአካል ርኩስ ተብሎአል:: (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 14

1 ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ 2 “የታመመ ሰው በሚነጻበት ቀን ህጉ ይህ ነው። ወደ ካህኑ ይቅረብ። 3 ካህኑ የሰውየው ተላላፊ የቆዳ በሽታ መዳኑን
ለመመርመር ከሰፈር ይወጣል። 4 ከዚያም ካህኑ የሚነጻው ሰው ህይወት ያላቸው ሁለት ንጹህ ወፎችን፣ የጥድ ዕንጨት፣ ደማቅ ቀይ ድርና ሂሶጵ እንዲያመጣ
ያዘዋል። 5 ካህኑ የታመመው ሰው ከወፎቹ አንዱን አርዶ በሸክላ ማሰሮ ውስጥ እንዲጨምር ያደርጋል። 6 ከዚያ ካህኑ ህይወት ያለውን ወፍ፣የጥዱን እንጨትና፣
ደማቁን ቀይ ድርና ሂሶጵ ይቀበለውና ህይወት ያለውን ወፍ ጨምሮ እነዚህን ነገሮች በሙሉ ቀደም ሲል በታረደው ወፍ ደምና ንጹህ ውሃ ውስጥ ይከታቸዋል። 7
ከዚያ ካህኑ ይህንን ውሃ ከበሽታው በሚነጻው ሰው ላይ ሰባት ጊዜ ይረጫል፣ ከዚያ በኋላ ካህኑ ሰውየው ንጹህ መሆኑን ያሳውቃል። ከዚያ ካህኑ ህይወት ያለውን
ወፍ ወደ ሜዳ ይለቀዋል። 8 የነጻው ሰው ልብሱን ያጥባል፣ ፀጉሩን በሙሉ ይላጫል፣ገላውንም ይታጠባል፤ ከዚህ በኋላ ንጹህ ይሆናል። ከዚያ በኋላ ወደ ሰፈር
ይመለስ፣ ነገር ግን ከድንኳኑ ውጭ ለሰባት ቀናት ይቆያል። 9 በሰባተኛው ቀን የራሱን ፀጉር በሙሉ ይላጭ፣ ልብሶቹን ይጠብ፣ ገላውን በውሃ ይታጠብ፤ ከዚህ
በኋላ ንጹህ ይሆናል። 10 በስምንተኛው ቀን ነውር የሌለባቸው ሁለት ወንድ የበግ ጠቦቶች፣አንድ ነውር የሌለበት የአንድ አመት የበግ ጠቦት ያምጣ፣ በዘይት
የተለወሰ የአፍ ሶስት አስረኛ የላመ ዱቄት እና አንድ ሊትር ዘይት ለእህል ቁርባን ያቅርብ። 11 የመንጻት ስርዓቱን የሚያስፈጽመው ካህን የሚነጻውን ሰው ከእነዚህ
ነገሮች ጋር ይዞ፣ በያህዌ ፊት በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ላይ ይቆማል። 12 ካህኑ ወንዱን ጠቦት ወስዶ ለኃጢአት መስዋዕት ከአንዱ ሊትር ዘይት ጋር ያቀርባል፤
እነዚህንም በያህዌ ፊት ለመስዋዕት ይወዘውዘዋል፤ ለእርሱም ያቀርበዋል። 13 ወንዱን ጠቦት የኃጢአት መስዋዕቱንና የሚቃጠል መስዋዕቱን ባቀረቡበት
ስፍራ በቤተ መቅደስ ያርደዋል፤ እንደ በደል መስዋዕቱ ሁሉ የኃጢአት መስዋዕቱም ለካህኑ ይሰጥ፣ ምክንያቱም ይህ እጅግ ቅዱስ ነው። 14 ካህኑ ከበደል
መስዋዕቱ ጥቂት ደም ወስዶ በሚነጻው ሰው ቀኝ ጆሮ ጫፍ፣ በቀኝ እጁ አውራ ጣት ላይ እና በቀኝ እግሩ አውራ ጣት ላይ ይቀባ። 15 ከዚያ ካህኑ ከዘይቱ
ወስዶ በእርሱ በራሱ ግራ እጅ መዳፍ ላይ ያፈሳል፣ 16 ከዚያም በግራ እጁ መዳፍ ላይ በፈሰሰው ዘይት ውስጥ የቀኝ እጁን ጣት ያጠልቃል፣ በጣቱ ላይ
ካለው ዘይት በያህዌ ፊት ሰባት ጊዜ ይረጫል። 17 ካህኑ በእጁ ላይ የቀረውን ዘይት በሚነጻው ሰው ቀኝ ጆሮ ጫፍ፣ በቀኝ እጁ አውራ ጣት፣ እና በቀኝ እግሩ
አውራ ጣት ላይ ይቀባል። ይህንን ዘይት በበደል መስዋዕቱ ደም ላይ ያድርገው። 18 ካህኑ በእጁ የቀረውን ዘይት፣ በሚነጻው ሰው ራስ ላይ ያፍስስ፣ እናም ካህኑ
በያህዌ ፊት የሚነጻውን ሰው ያሰርይለታል። 19 ከዚያ ካህኑ የኃጢአት መስዋዕቱን ይሰዋል፤ ደግሞም ንጹህ ባለመሆኑ ምክንያት መንጻት ላለበት ሰው
ያሰርይለታል፣ እናም ከዚህ በኋላ የሚቃጠል መስዋዕቱን ይሰዋል። 20 ካህኑ የሚቃጠለውን መስዋዕትና የእህል ቁርባኑን በመሰዊያ ላይ ያቀርባል። ካሁኑ
ለሰውየው ማስተስረያ ያቀርብለታል። ከዚያ ንጹህ ይሆናል። 21 ሆኖም ሰውየው ደሃ ከሆነና እነዚህን መስዋዕቶች ማቅረብ ካልቻለ ለኃጢአቱ ማስተስረያ የበደል
መስዋዕት አንድ ወንድ ጠቦት፣ በዘይት የተለወሰ የአፍ አንድ አስረኛ መልካም ዱቄትና አንድ ሊትር ዘይት ያቅርብ፣ 22 ሰውየው በአቅሙ ከሁለት ርግቦች ወይም
ሁለት ዋኖሶች ጋር፣ አንደኛውን ወፍ የኃጢአት መስዋዕት ሌላኛው ደግሞ የሚቃጠል መስዋዕት ያቀርባል። 23 በስምንተኛው ቀን ስለ መንጻቱ ወደ መገናኛው
ድንኳን በያህዌ ፊት ያምጣቸው። 24 ከዚያ ካህኑ ጠቦቱን ለበደል መስዋዕት ደግሞም አንዱን ሊትር ዘይት፣ይወስድና ለያህዌ የበደል መስዋዕት ይወዘውዛል፣
እናም ለእርሱ እነዚህን ያቀርባቸዋል። 25 ለበደል መስዋዕት ጠቦቱን ያርዳል፣ እናም ከበደል መስዋዕቱ ጥቂት ደም ይወስድና በሚነጻው ሰው ቀኝ ጆሮ ጫፍ፣
በቀኝ እጁ አውራ ጣት ላይና በቀኝ እግሩ አውራ ጣት ላይ ይቀባል። 26 ከዚያ ካህኑ ከዘይቱ ጥቂቱን በገዛ ራሱ ግራ እጅ መዳፍ ላይ ያፈሳል፣ 27 በቀኝ ጣቱ
ከዘይቱ በግራ እጁ በያህዌ ፊት ሰባት ጊዜ ይረጫል። 28 ከዚያ ካህኑ በእጁ ካለው ዘይት ጥቂቱን በሚነጻው ሰው ቀኝ ጆሮ ጫፍ ላይ፣ በቀኝ እጁ አውራ ጣት
ላይና በቀኝ እግሩ አውራ ጣት ላይ የበደል መስዋዕቱን ደም ባደረገበት ተመሳሳይ ስፍራዎች ይቀባል። 29 የተረፈውን በእጁ ያለውን ዘይት ያስተሰርይለት ዘንድ
በያህዌ ፊት በሚነጻው ሰው ራስ ላይ ያፈሳል። 30 ሰውየው በአቅሙ ካቀረበው ከእርግቦቹ ወይም ከዋኖሶቹ አንዱን ይሰዋ - 31 ከእህል ቁርባኑ ጋር፣ አንዱን
ለኃጢአት መስዋዕት ሌላውን ለሚቃጠል መስዋዕት ያቅርብ። ከዚያም ካህኑ ለሚነጻው ሰው በያህዌ ፊት ያስተሰርይለታል። 32 ለመንጻት ዋናውን መስዋዕት
ማቅረብ ለማይችል ተላላፊ የቆዳ በሽታ ላለበት ሰው የመንጻት ህጉ ይህ ነው።” 33 ያህዌ ሙሴንና አሮንን እንዲህ ሲል ተናገራቸው፣ 34 “ርስት አድርጌ
ወደሰጠኋችሁ ወደ ከነዓን ምድር ስትመጡ፣ ርስት በሆናችሁ ምድር በቤታችሁ እየሰፋ የሚሄድ ብክለት ባደርግባችሁ፣ 35 የቤቱ ባለቤት ወደ ካህኑ መጥቶ
ይናገር። እንዲህም ይበል፣ “በቤቴ ብክለት ያለ ይመስለኛል።’ 36 ከዚያ ካህኑ በቤቱ ውስጥ የሚገኝ ማናቸውም ነገር እርኩስ እንዳይሆን ብክለት መኖሩን
ለማየት ወደዚያ ቤት ከመግባቱ አስቀድሞ ቤቱን ባዶ እንዲያደርጉ ያዛል፣ ከዚህ አስቀድሞ ካህኑ ያንን ቤት ለማየት ይገባል። 37 ሻጋታው በቤቱ ግድግዳዎች
ላይ መኖሩን፣ ደግሞም አረንጓዴ ሆኖ ወይም ቀላ ብሎ በግርግዳዎቹ ላይ መታየቱን ይመርምር። 38 ቤቱ ሻጋታ ካለው፣ ካህኑ ከዚያ ቤት ይወጣና ለሰባት ቀናት
በሩን ይዘጋዋል። 39 በሰባተኛው ቀን ካህኑ ተመልሶ ይመጣና ሻጋታው በቤቱ ግድግዳዎች ላይ መስፋፋቱን ለማየት ይመረምራል። 40 እንዲያ ከሆነ፣ ካህኑ
ሻጋታ የተገኘባቸውን ድንጋዮች ከግድግዳው ላይ እየፈነቀሉ እንዲያወጡና ከከተማ ውጭ ቆሻሻ ስፍራ መጣያ እንዲጥሏቸው ያዛል። 41 የቤቱ የውስጥ
ግድግዳዎች ሁሉ እንደዳፋቁ ይጠይቃል፣ እነርሱም እየተፋቁ የተነሱትን የተበከሉትን ቁሶች ከከተማ አውጥተው በቆሻሻ መጣያ ስፍራ ይጥላሉ። 42
ባስወገዷቸው ድንጋዮች ስፍራ ሌሎች ድንጋዮች ወስደው ያስቀምጡ፣ ቤቱን ለመምረግ አዲስ ጭቃ ይጠቀሙ። 43 ድንጋዮቹ ተነስተውና ግርግዳው ተፍቆ
እንዲሁም ተለስኖ ዳግም ብክለቱ ከወጣና ከታየ፣ 44 ካህኑ ብክለቱ መስፋፋቱን ለመመልከት ቤቱን ይመርምር። እንዲያ ከሆነ፣ ይህ ጎጂ ብክለት ነው፤ ቤቱ
ንጹህ አይደለም። 45 ቤቱ ይፍረስ። የቤቱ ድንጋዮች፣ በሮች፣ እና ፍርስራሾች ከከተማ ውስጥ በቆሻሻ መጣያ ይጣል። 46 በተጨማሪም፣ ቤቱ በተዘጋባቸው
ጊዜያት ወደዚያ ቤት የሄደ ሁሉ እስከ ምሽት ድረስ እርኩስ ነው። 47 ማንም በዚያ ቤት ውስጥ የተኛ ሰው ልብሱን ይጠብ፣ እንዲሁም በዚህ ቤት ውስጥ
የተመገበ ሰው ልብሱን ይጠብ። 48 ቤቱ ከተለሰነ በኋላ ብክለቱ ወዴት እንደተስፋፋ ለመመርመር ካህኑ ወደዚያ ቤት ቢገባ፣ እናም ብክለቱ ተወግዶ ቢሆን ቤቱ
ንጹህ መሆኑን ያሳውቃል። 49 ከዚያ ካህኑ ቤቱን ለማንጻት ሁለት ወፎች፣ የጥድ እንጨት፣ ደማቅ ቀይ ድር እና ሂሶጵ ይውሰድ። 50 ከወፎቹ አንዱ ንጹህ ውሃ
በያዘ በሸክላ ዕቃ ውስጥ ያርደዋል። 51 የጥድ እንጨት፣ሂሶጵደማቅ ቀይ ድር እና በህይወት ያለ ወፍ ይውድና በታረደው ወፍ ደም ውስጥ እና በንጹህ ውሃ
ውስት ይነክራቸዋል፣ከዚያም ቤቱን ሰባት ጊዜ ይርጨው። 52 ቤቱን በወፉ ደምና በንጹህ ውሃ፣ በህይወት በሚገኘው ወፍ፣ በጥድ እንጨት፣በሂሶጵና በደማቅ
ቀይ ድር ያነጻዋል። 53 በህይወት የሚገኘውን ወፍ ግን ከከተማ ውጭ ወደ ሜዳ ይለቀዋል። በዚህ መንገድ ቤቱን ያስተሰርያል፣ ቤቱም ንጹህ ይሆናል። 54
ለሁሉም አይነት ተላላፊ የቆዳ በሽታና እንዲህ ያለውን በሽታ ለሚያመጡ ነገሮች፣ እንዲሁም ለሚያሳክክ ህመም፣ 55 እንዲሁም ለልብስና ለቤት ብክለት፣ 56
ለእብጠት፣ ለሚያሳክክ ህመም፣ እና ለቋቁቻ፣ 57 በእነዚህ ሁኔታዎች እርኩስና ንጹህ የሚሆነውን ለመለየት ህጉ ይህ ነው።”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Leviticus 14:1

አጠቃላይ መግለጫ
አንድ ሰው ከቆዳ በሽታ ሲነጻ ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴና አሮን ይናገራል።

የመንጻቱ ቀን
ሰውየው በሥርዓቱ መሠረት ንጹህ እንደሆነ ካህኑ የሚያሳውቅበት ቀን ያመለክታል

እርሱም ወደ ካህኑ መወሰድ አለበት
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “አንድ ሰው ወደ ካህኑ እንዲወስደው ይገባል”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)::

Leviticus 14:3

አጠቃላይ መግለጫ
አንድ ሰው ከቆዳ በሽታ ሲነጻ ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴና አሮን ይናገራል።

ተላላፊ የቆዳ በሽታ
በዘሌዋዊያን 13:3 እነዚህን ቃላት እንዴት አንደተረጐሙ ይመልከቱ

የሚነጻው ሰው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “እርሱ የሚያነጻው ሰው”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)::

ንጹህ ወፎች
ሕዝቡ እንዲበላቸውና ለመሥዋዕትነት እንዲያቀርቡ የተፈቀዱ ወፎች በአካል ንጹህ ተብለዋል (ዜይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

ደመቅ ያለ ቀይ ድር
“ቀይ ድር”

ሂሶጵ
ለመድኃኒትነት የሚጠቀሙት መልካም በዓዛ ያለው ዕጽ ነው (ያልታወቁትን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Leviticus 14:6

አጠቃላይ መግለጫ
አንድ ሰው ከቆዳ በሽታ ሲነጻ ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴና አሮን ይናገራል።

የታረደው ወፍ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “ሰውየው ያረደው ወፍ”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)::

የሚነጻው ሰው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “እርሱ የሚያነጻው ሰው”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)::

ንጹህ እንደሆነ ካህኑ ያስታውቀው
ለእግዚአብሔር ዓላማዎች ተቀባይነት ያለውና ሌሎች ሰዎች ሊነኩት የሚችሉት ሰው በአካል ንጹህ ተብሎአል። ዜይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ

Leviticus 14:8

አጠቃላይ መግለጫ
አንድ ሰው ከቆዳ በሽታ ሲነጻ ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴና አሮን ይናገራል።

የሚነጻው ሰው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “ካህኑ የሚያነጻው ሰው”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)::

ንጹህም ይሆናል
ሌሎች ሰዎች ሊነኩት የሚችሉት ሰው በአካል ንጹህ ተብሎአል። (ዜይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

Leviticus 14:10

እርሱ ያቅርብ
እዚህ “እርሱ” የሚነጻውን ሰው ያመለክታል::

እፍ
አንድ እፍ 22 ሊትር ነው:: መጽሐፍ ቅዱሳዊ መለኪያዎች ይመልከቱ

ሎግ
አንድ ሎግ 0.31 ሊትር ነው::

የሚነጻው ሰው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “እርሱ የሚያነጻው ሰው”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)::

Leviticus 14:12

ሎግ
አንድ ሎግ 0.31 ሊትር ነው:: መጽሐፍ ቅዱሳዊ መለኪያዎችን ይመልከቱ

በመሠዊያው ቦታ
ይህ ሀረግ የቀደመውን ሀረግ የሚገልጽና ካህኑ ጠባቱን የሚያርድበት ቦታ የሚናገር ነው

Leviticus 14:14

የሚነጻው ሰው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “እርሱ የሚያነጻው ሰው”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)::

ሎግ
አንድ ሎግ 0.31 ሊትር ነው:: መጽሐፍ ቅዱሳዊ መለኪያዎችን ይመልከቱ

ጥቂት ዘይት በእግዚአብሔር ፊት ይርጭ
በእግዚአብሔር መገኘት ጥቂት ዘይት ይርጭ

Leviticus 14:17

በእጁ ውስጥ ከቀረው ዘይት
በመዳፉ ውስጥ ከቀረው ዘይት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የሚነጻው ሰው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “እርሱ የሚያነጻው ሰው”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)::

በእግዚአብሔር ፊት
በእግዚአብሔር መገኘት

Leviticus 14:19

የሚነጻውም ሰው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “እርሱ የሚያነጻው ሰው”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ):: ሰውየውም ንጹህ ይሆናል

ንጹህም ይሆናል
ሌሎች ሰዎች ሊነኩት የሚችሉት ሰው በአካል ንጹህ ተብሎአል። (ዜይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

Leviticus 14:21

አጠቃላይ መግለጫ
አንድ ሰው ከቆዳ በሽታ ሲነጻ ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴና አሮን ይናገራል።

አቅሙ ካልፈቀደለት
ለመግዛት ገንዘብ ከሌለው

ይወዘወዝ... ለእርሱ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “ካህኑ ለእርሱ... ይወዘውዘው”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)::

የእፍ አንድ አሥረኛ
የእፍ አንድ አሥረኛ 22 ሊትር ነው

ሎግ
አንድ ሎግ 0.31 ሊትር ነው:: (መጽሐፍ ቅዱሳዊ መለኪያዎችን ይመልከቱ)

Leviticus 14:24

ሎግ
አንድ ሎግ 0.31 ሊትር ነው:: (መጽሐፍ ቅዱሳዊ መለኪያዎችን ይመልከቱ)

የሚነጻው ሰው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “እርሱ የሚያነጻው ሰው”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)::

Leviticus 14:26

አጠቃላይ መግለጫ
አንድ ሰው ከቆዳ በሽታ ሲነጻ ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴና አሮን ይናገራል።

ጥቂት ዘይት... በእግዚአብሔር ፊት.. ይርጭ
ጥቂት ዘይት በእግዚአብሔር መገኘት ይርጭ:: በምን ላይ ካህኑ ዘይቱን እንደሚረጭ አልተገለጸም::

Leviticus 14:28

የሚነጻው ሰው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “እርሱ የሚያነጻው ሰው”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)::

Leviticus 14:30

ይሠዋል
“ካህኑ ይሠዋል”

የሚነጻው ሰው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “እርሱ የሚያነጻው ሰው”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)::

ተላላፊ የቆዳ በሽታ
በዘሌዋዊያን 13:3 እንዚህን ቃላት እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

ዐቅም ያነሰው
መደበኛ መሥዋዕት ለመግዛት በቂ ገንዘብ የሌለው ሰው እንዳሆነ ግልጽ በማድረግ ይተረጉሙ:: አት “በቂ ገንዘብ የሌለው ሰው” (ግምታዊ ዕውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Leviticus 14:33

እናንተ በገባችሁ ጊዜ
እዚህ እናንተ የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል (ሁለተኛ ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

አረንጓዴ ወይም ቀይ ምልክት ያለው ክፉ ደዌ
በዘሌዋዊያን 13:47 ይህን ቃል እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

ርስት አድርጌ የሚሰጣቸው ምድር
“ርስት አድርጌ የሚሰጣቸው” በግሥ መልክ ሊተረጐም ይችላል አት “የሚትወርሱት ምድር” (ረቂቅ ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Leviticus 14:36

በቤት ውስጥ ያለ ምንም ነገር ርኩስ አይሆንም
አንደ ካህኑ ቤቱ ርኩስ መሆኑን ካስታወቅ በቤቱ ውስጥ ያለው ሁሉም ነገር ርኩስ ይሆናል ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “በቤት ውስጥ የቀረው ምንም ነገር ርኩስ መሆኑን ማስታወቅ አይገባውም”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)::

ቤቱ ርኩስ ይሆናል
ሕዝቡ እንዲኖሩት ወይም እንዲነኩት ያለተገባ እንደሆነ እግዚአብሔር የተናገረው ቤት በአካል ርኩስ ተብሎአል:: (ዜይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

በግድግዳዎች አካል ክፍሎች
ክፉ ደዌው ከግድግዳዎች ላይኛው አካል ከፍል ባለፍ ሠርጾ የገባ እንደሆነ ካህኑ መርምሮ የሚወስንበት ማለት ነው

Leviticus 14:39

ክፉ ደዌው ከተገኘ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “ክፉ ደዌውን ካገኙ”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)::

ርኩስ ሥፍራ
ሕዝቡ እንዳይሠፍር ወይም ለእግዚአብሔር ዓላማዎች የማይጠቅም እግዚአብሔር የተናገረው ሥፍራ በአካል ርኩስ ተብሎአል ዜይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ

Leviticus 14:41

እርሱ ይፈልጋል
እዚህ እርሱ ካህኑን ያመለክታል

የተበከለው ውስጠኛው የቤቱ ግድግዳ በሙሉ ይፋቅ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “ባለቤቱ የቤቱን ውስጠኛ ግድግዳዎችን ይፍቃል”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)::

የተበከለው ዕቃ ይፋቅ
ይህም ክፉ ደዌ የነካው ዕቃ ማለት ነው ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “እነርሱ የሚፍቁት የተበከለው ዕቃ”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)::

ርኩስ ሥፍራ
ሕዝቡ እንዳይሠፍር ወይም ለእግዚአብሔር ዓላማዎች የማይጠቅም እግዚአብሔር የተናገረው ሥፍራ በአካል ርኩስ ተብሎአል ዜይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ

የተወገዱትም ድንጋዮች
ይህም ክፉ ደዌ የነካው ዕቃ ማለት ነው ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “እነርሱ ያስወገዱአቸው ድንጋዮች”። (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)::

ሌላ ጭቃ ወስደው ይመርጉ
ድንጋዮችን በአድስ ጭቃ ይሸፍኑ

Leviticus 14:43

ቤቱ ውስጥ... እንደና ይመረጋል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “ባለቤቱ ቤቱ ውስጥ ድንጋዮችንና የግድግዳዎችን ፍቅፋቂ ካስወገደ በኋላ አድስ ድንጋዮችን በጭቃ ይመርጋል።” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)::

ቤቱ ርኩስ ነው
ሰዎችን ለማኖር ያልተገባ ቤት በአካል ርኩስ ተብሎአል

Leviticus 14:45

ቤቱ ይፍረስ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “ቤቱን ይፍርሱት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)::

ድንጋዩ እንጨቱና ምርጊቱ በሙሉ ይወገድ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “ድንጋዩን እንጨቱንና ምርጊቱን ያስወጡት/ያስወግዱት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)::

ማንኛውም ሰው ቢገባበት ያ ሰው ርኩስ ይሆናል
ቤቱን በመግባቱ ምክንያት ለእግዚአብሔር ዓላማዎች ያልተገባውና ሰዎች የማይነኩት ሰው በአካል ርኩስ ተብሎአል። ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ።

እስከ ማታ
ጸሐይ እስኪጠልቅ

Leviticus 14:48

ቤቱ ከተመረገ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “ባለቤቱ በአዲስ ጭቃ ድንጋዮችን ከመረገ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)::

ቤቱ ንጹህ መሆኑን ያስታውቅ
ሰዎችን ለማኖር የተገባ ቤት በአካል ንጹህ ተብሎአል

Leviticus 14:49

ዝግባ እንጨት ቀይ ድርና ሂሶጵ
በዘሌዋዊያን 14:4 እነዚህን ቃላት እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

የታረደው ወፍ ደም
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “ያረደው ወፍ ደም” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)::

Leviticus 14:52

ቤቱንም ያንጻው
“ካህኑ በሥርዓቱ መሠረት ቤቱን ያንጻ”

ቤቱም ንጹህ ይሆናል
ሰዎችን ለማኖር የተገባ ቤት በአካል ንጹህ ተብሎአል:: (ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Leviticus 14:54

ተላላፊ የቆዳ በሽታ
በዘሌዋዊያን 13:3 እነዚህን ቃላት እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ

ክፉ ለምጽ ደዌ
በዘሌዋዊያን 13:47 ይህን ቃላት እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ

ችፍታ
በዘሌዋዊያን 13:6 ይህን ቃላት እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ

ርኩስ ወይም ንጹህ
ሌሎች ሰዎች የማይነኩት ሰውና ዕቃዎች በአካል ርኩስ ተብለዋል እናም ሰዎች መንካት የሚችሉአቸው በአካል ንጹህ ተብለዋል:: (ዜይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 15

1 ያህዌ ሙሴንና አሮንን እንዲህ ሲል ተናገራቸው፣ **2** ‹ለእስራኤል ሰዎች እንዲህ ብላችሁ ንገረቸው፣ ‹ማንም ሰው ከሰውነቱ የሚወጣ የሚመረቅዝ ፈሳሽ ሲኖርበት፣ ንጹኅ አይደለም። **3** ንጹኅ የማይሆነ ከሚመረቅዝ ፈሳሽ የተነሳ ነው። ከሰውነቱ የሚወጣ ፈሳሽ ቢቀጥል ወይም ቢቆም ንጹህ አይደለም። **4** የሚተኛበት አልጋ ሁሉ ንጹኅ አይሆንም፣ የሚቀመጥበት ነገር ሁሉ ንጹኅ አይሆንም። **5** አልጋን የነካ ሁሉ ልብሱን ይጠብ ሰውየውም በውሃ ይታጠብ፣ እስከ ምሽት ድረስ ንጹኅ አይደለም። **6** የሚመረቅዝ ፈሳሽ ያለበት ሰው በተቀመጠበት ማናቸውም ነገር ላይ የተቀመጠ ማንኛውም ሰው ልብሱን ይጠብ፣ እርሱም በውሃ ይታጠብ፣ እስከ ምሽት ንጹህ አይደለም። **7** የሚመረቅዝ ፈሳሽ ያለበትን ሰው አካል የነካ ማንኛውም ሰው ልብሱን ይጠብ፣ እርሱም በውሃ ይታጠብ። እስከ ምሽት ንጹህ አይደለም። **8** እንዲህ ያለ ፈሳሽ ያለበት ሰው ንጹኅ በሆነ ሰው ላይ ንጹኅ በሆነ ሰው ላይ ቢተፋ፣ ያ ሰው ልብሱን ማጠብና እርሱም በውሃ መታጠብ አለበት፣ እስከ ምሽት ንጹኅ አይደለም። **9** ፈሳሽ ያለበት ሰው የተቀመጠበት ማንኛውም ኮርቻ ንጹኅ አይደለም። **10** ከዚያ ሰው በታች ያለን ማንኛውንም ነገር የነካ እስከ ምሽት ንጹኅ አይደለም፣ እነዚያን ነገሮች የተሸከመ ማንም ሰው ልብሱን ይጠብ እርሱም በውሃ ይታጠብ፤ እስከ ምሽት ንጹኅ አይደለም። **11** እንዲህ ያለ ፈሳሽ ያለበት ማንም ቢሆን አስቀድሞ እጆቹን በውሃ ሳያጠራ ቢነካ፣ የተነካው ሰው ልብሱን ይጠብ እርሱም በውሃ ይታጠብ፣ እስከ ምሽት ንጹኅ አይደለም። **12** እንዲህ ያለ ፈሳሽ ያለበትን ሰው የነካ ማናቸውም አይነት የሸክላ ዕቃ ይሰበር፣ የእንጨት የተሰራ ማጠራቀሚያ ሁሉ በውሃ ይንጻ። **13** ፈሳሽ ያለበት ሰው ከፈሳሹ ሲነጻ ለመንጻቱ ለእራሱ ሰባት ቀናትን ይቁጠር፤ ከዚያ ልብሶቹን ይጠብ ሰውነቱን በምንጭ ውሃ ይታጠብ። ከዚያ ንጹህ ይሆናል። **14** በስምንተኛው ቀን ሁለት ርግቦች ወይም ሁለት ኖሶች ይውሰድና ወደ መገናኛ ድንኳን ያህዌ ፊት ይቅረብ፣ በዚያ ወፎቹን ለካህኑ ይስጥ። **15** ካህኑ አንዱን ለሀጢአት መስዋዕት እና ሌላውን የሚቃጠል መስዋዕት ያቅርባቸው፣ እናም ካህኑ ለሰውዬው ስለ ፈሳሹ ማስተሰርያ ያድርግ። **16** የማንንም ሰው የዘር ፈሳሽ ሳይታሰብ በድንገት ከእርሱ ቢወጣ፣ መላ ሰውነቱን በውሃ ይታጠብ፣ እስከ ምሽት ድረስ ንጹህ አይደለም። **17** ማናቸውም የዘር ፈሳሽ የነካ ልብስ ወይም ሌጦ በውሃ ይታጠብ፤ እስከ ምሽት ንጹኅ አይደለም። **18** አንዲት ሴትና አንድ ወንድ አብረ ቢተኙና ወደ እርሷ የዘር ፈሳሽ ቢተላለፍ ሁለቱም በውሃ ይታጠቡ፣ እስከ ምሽት ንጹኅ አይደሉም። **19** አንዲት ሴት የወር አበባ ሲፈሳት፣ ያለመንጻቷ ለሰባት ቀናት ይቀጥላል፣ እርሷን የነካ ሁሉ እስከ ምሽት ንጹህ አይደለም። **20** በወር አበባ ወቅት የምትተኛበት ማንኛውም ነገር ንጹህ አይደለም፤ እንደዚሁም የምትቀመጥበት ነገር ሁሉ ንጹኅ አይደለም። **21** አልጋውን የነካ ማንኛም ሰው ልብሱን ይጠብ እርሱም በውሃ ይታጠብ፣ ያሰው እስከ ምሽት ንጹህ አይደለም። **22** የተቀመጠችበትን ማናቸውንም ነገር የነካ ሁሉ ልብሱን ይጠብ እርሱም በውሃ ይታጠብ ያ ሰው እስከ ምሽት ንጹህ አይደለም። **23** በአልጋም ይሁን በማንኛም ነገር ላይ ብትቀመጥ የተቀመጠችበትን ነገር የነካ ሰው እስከ ምሽት ንጹህ አይደለም። **24** ከእርሷ ጋር የተኛ ንጹህ ያልሆነ ፈሳሽ ቢነካ፣ ለሰባት ቀናት ንጹህ አይደለም። የሚተኛበትም አልጋ ንጹህ አይደለም። **25** አንዲት ሴት ከወር አበባ ቀናት በኋላ ለብዙ ቀናት ደም መፍሰሱን ቢቀጥል፣ ይህም ከወር አበባ ጊዜያት በኋላ ፈሳሽ ቢኖርባት፣ ንጹኅ ባልሆነችባቸው ፈሳሽ ባለባት ጊዜያት ሁሉ፣ በወር አበባ ወቅት ላይ እንዳለች ሁሉ እርኩስ ይሆናል ንጹህ አይደለችም። **26** ደሟ በሚፈስባቸው ጊዜያት የምትተኛበት አልጋ ሁሉ በወር አበባ ወቅት እንደምትተኛበት እርኩስ ይሆናል፣ የምትቀመጥበት ነገር ሁሉ ልክ በወር አበባ ወቅት እንደሚሆነ ንጹህ አይደለም። **27** ደግሞም ከእነዚህ ነገሮች ማናቸንም የነካ ሁሉ ንጹህ አይደለም፤ ልብሶቹን ይጠብ እርሱም በውሃ ይታጠብ፤ እስከ ምሽት ድረስ ንጹህ አይደለም። **28** ነገር ግን ከደም መፍሰሳ ብትነጻ፣ ለራስዋ ሰባት ቀናትን ትቆጥራለች፣ እናም ከዚያ በኋላ ንጹኅ ናት። **29** በስምንተኛው ቀን ሁለት ርግቦች ወይም ሁለት ዋኖሶች ትወሰድና ወደ መገናኛው ድንኳን መግቢያ ለካህኑ ትስጥ። **30** ካህኑ አንዱን ወፍ ለሀጢአት መስዋእት ሌላውን ለሚቃጠል መስዋዕት ያቅርብ፣ ስለ ፈሳሽም እርኩሰት በያህዌ ፊት ያስተሰርይላታል። **31** የእስራኤል ሰዎች ከእርኩሰታቸው የምትይች እንደዚህ ነ፣ ይህ ከሆነ በመካከላቸ የምኖርበትን ቤተ መቅደሴን በማርከስ በእርኩሰታቸ አይሞቱም። **32** ከሰነቱ ፈሳሽ ለሚጣ፣ የዘረ ፈሳሹ ከእርሱ ለሚጣና ለሚያረክሰ ማንኛም ሰ ህግጋቱ እነዚህ ናቸ። **33** ለማንኛም በር አበባ ላይ ላለች ሴት፣ ከሰነቱ ፈሳሽ ለሚፈሰ ሰ ሁሉ፣ ንድም ይሁን ሴት፣ እንዲሁም ንጹህ ካልሆነች ሴት ጋር ለሚተኛ ንድ ህጉ ይህ ነ።”

Leviticus 15:1

ከሰውነቱ የሚወጣ
የሰው አካል ክፍሎች የሚወጣ (See Euphemism/ንኣብነት ወይም ጸያፍ/አሳፋሪ አባበሎችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ርኩስ ይሆናል
ሌሎች ሰዎች የማይነኩት ሰው በአካል ርኩስ ተብሎአል(ዜይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

ይህ ርኩስ ነው
“አካሉ ርኩስ ነው”

Leviticus 15:4

ርኩስ ነው
ሰውየው የተኛበት አልጋ ወይም የተቀመጠበት ማንኛውም ነገር ሌሎች ሰዎች የማይነኩት በአካል ርኩስ ተብሎአል። (ዜይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

አልጋውን የሚነካ ማንኛውም ሰው ርኩስ ይሆናል
ሌሎች ሰዎች የማይነካው ሰው በአካል ርኩስ ተብሎአል። (ዜይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

እስከማታ
“ጸሐይ እስኪጠልቅ”

Leviticus 15:6

ርኩስ ይሆናል
ሌሎች ሰዎች የማይነካው ሰው በአካል ርኩስ ተብሎአል። (ዜይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

እስከማታ
“ጸሐይ እስኪጠልቅ”

የሚነካ ሰው
ማንኛውንም የአካል ክፍል የሚነካ

Leviticus 15:8

ንጹህ የሆነ ሰው
ሌሎች ሰዎች መንካት የሚችሉት ሰው በአካል ንጹህ ተብሎአል። (ዜይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ርኩስ ይሆናል
ሌሎች ሰዎች የማይነካው ሰው በአካል ርኩስ ተብሎአል። (ዜይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

ኮርቻ
ኮረቻ በፈረስ ላይ ለመቀመጥ በጀርባው የሚቀመጥ ከቆዳ የተሥራ መቀመጫ ነው

ማንኛውም ኮሪቻ....ርኩስ ይሆናል
መንካት ያልተገባ እግዚአብሔር የተናገረው ማንኛውም ነገር በአካል ርኩስ ተብሎአል ዜይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ

Leviticus 15:10

አጠቃላይ መረጃ
ቁስልን ለማስወገድ ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴና አሮን መናገር ይቀጥላል

ያ ሰው
የቁስል ፈሳሽ ያለውን ሰው ያመለክታል

ርኩስ ነው
ሌሎች ሰዎች የማይነካው ሰው በአካል ርኩስ ተብሎአል። (ዜይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

እስከማታ
“ጸሐይ እስኪጠልቅ”

ፈሳሽ ነገር የሚወጣው የነካው
ፈሳሽ ነገር የሚወጣው ሰው የነካው

የተነካው ሰው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል። አት፤ “ፈሳሽ ነገር በሚወጣው ሰው የተነካው ሰው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)::

ፈሳሽ ነገር ያለበት ሰው የሚነካውን የሸክላ ዕቃ ይስበሩት
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ፈሳሽ ነገር ያለበት ሰው የሚነካውን ማንኛውንም የሸክላ ዕቃ ይስበሩት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

የእንጨቱም ዕቃ ሁሉ በውሃ ይታጠብ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “የእንጨቱንም ዕቃ ሁሉ አንድ ሰው በውሃ ይጠበው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 15:13

ከፈሳሹ ነገር ይነጻል
ከበሽታው እየገገመ ያለው ሰው በአካል ንጹህ እንደሆነ ተገልጾአል ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ከፈሳሽ ነገር ይፈወሳል” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር እና ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

ንጹህም ይሆናል
ሌሎች ሰዎች መንካት የሚችለው ሰው በአካል ንጹህ እንደሆነ ተነገሮአል:: (ዘይቤያዊ አጋገር ይመልከቱ)

Leviticus 15:16

እስከማታ ርኩስ ይሆናል
ሌሎች ሰዎች መንካት የሌለባቸው ሰዎችና ዕቃዎች በአካል ርኩስ ተብለዋል:: (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

እስከማታ ርኩስ
ጸሐይ እስኪትጠልቅ

ማንኛውም ልብስ በውሃ ይታጠብ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “አንድ ሰው ዘር የነካውን ልብስ ወይም ቁርበት ሁሉ በውሃ ማጠብ አለበት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 15:19

ሴት ፈሳሽ ነገር ቢኖርባት .... በወር አበባዊ ጊዜ
ሁለቱም ከሴት ማዕጸን ደም የሚፈስስበትን ጊዜ ያመለክታሉ

መርገምዋ ይቀጥላል
“ንጹህ እንዳልሆነች ይቀጥላል”

ርኩስ ነው
ሌሎች ሰዎች መንካት የሌለባቸው ሰዎችና ዕቃዎች በአካል ርኩስ ተብለዋል:: (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

Leviticus 15:21

መኝታዋ
ይህ የወር አበባ የሚፍስሳትን ሴት ያመለክታል

ያ ሰው ርኩስ ይሆናል
ሌሎች ሰዎች የማይነኩት ሰው በአካል ርኩስ ይባላል:: (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

Leviticus 15:24

የመርገምዋ ወር አበባዋ ፈሳሽ
ንጹህ ያልሆነው ፈሳሽዋ ወይም ከማዕጸንዋ የሚወጣው ፈሳሽ

ርኩስ ነው
ሌሎች ሰዎች መንካት የሌለባቸው ሰዎችና ዕቃዎች በአካል ርኩስ ተብለዋል:: (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

Leviticus 15:25

ልክ እንደወር አበባዋ ጊዜ ቢትሆን
ከመደበኛ የወር አበባዋ ጊዜ ውጪ ከማዕጸንዋ ደም የሚፈስሳት ከሆነ እንደወር አበባዋ ጊዜ ርኩስ ነች ማለት ነው::

እርስዋ ርኩስ ትሆናለች የሚነካትም ማንኛውም ሰው ርኩስ ይሆናል
ሌሎች ሰዎች መንካት የሌለባቸው ሰዎች በአካል ርኩስ ተብለዋል:: (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

የምትቀመጥበትም ማንኛውም ነገር ርኩስ ይሆናል::
ሌሎች ሰዎች የማይነኩት ዕቃዎች በአካል ርኩስ ተብለዋል:: (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)::

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Leviticus 15:28

ነገር ግን እርስዋ
እዚህ “እርስዋ” የሚለው የወር አበባ ያላትን ሴት ነው::

ከደምዋ ፍሳሽ ንጹህ ትሆናለች
ከፍሳሽዋ እየተሻላት ያለች ሴት በአካል ንጹህ ተብላለች ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ከደምዋ ፍሳሽ እየተሻላት ያለች” (ዘይቤያዊ አገላለጽ እና ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ንጹህ ትሆናለች
ሌሎች ሰዎች መንካት የሚችሉአት ሴት በአካል ንጹህ ተብላለች (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)::

ይዛ ትቀርባለች
ስለራስዋ ታቀርባለች

የደም ፈሳሽዋ ርኩሰት
ርኩስ የሚያደርጋት የደም ፍሳሽዋ

Leviticus 15:31

ይህም እስራኤላዊያንን ከሚያረክሱአቸው ነገር የሚትለዩበት ነው::
ሕዝቡን ከሚያረክሰው ነገር ስለመከላከል እግዚአብሔር የሚናገረው ሕዝቡን ከርኩሰት በርቀት እንደመጠበቅ ተገልጾአል:: “ርኩሰት” የተባለው ረቂቅ ስም እንደ “ርኩስ” ሊገለጽ ይችላል:: አት ይህ የእስራኤልን ሕዝብ ከርኩሰት ለመከላከሉበት ነው (ዘይቤያዊ አገላለጽ እና ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ)

ርኩስነታቸው
ሌሎች ሰዎች የማይነኩአቸውና ለእግዚአብሔር ዓላማ ተቀባይነት የሌላቸው ሰዎች በአካል ርኩስ ተብሎአል ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ

Leviticus 15:32

እነዚህ መመሪያዎች ናቸው
እነዚህ መደረግ የሚገባቸው ነገሮች ናቸው::

ርኩስ ያደርገዋል ... ርኩስ ሴት
ሌሎች ሰዎች የማይነኩአቸው ሰዎች በአካል ርኩስ ተብለው ተገልጸዋል::

በወር አበባ ላይ ያለች
የወር አበባ የሚፈስሳት ወይም ከማዕጸንዋ ደም የሚፈስሳት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 16

1 ያህ እንዲህ ሲል ሙሴን ተናገረ፡ - ይህ የሆነ የአሮን ሁለቱ ልጆች ¨ደ ያህ«ከቀረቡና ከሞቱ በሀላ ነበር፡፡ 2 ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለ፣ “ለ¨ንድምህ ለአሮን እንዲህ ብለህ ተናገረ፣ በፈለገ¬ ጊዜ ሁሉ በመጋረጃ ¬ስጠኛ ¨ዳለ ¨ደ ቅድስተ ቅዱሳኑ፣ በታቦቱ ላይ ወዳለ ወደ ማስተሰርያ ክዳን ፊት እንዳይቀርብ ንገረው፡፡ ይህንን ካደረገ፣ ይሞታል፣ ምክንያቱም እኔ በደመና በማስተሰርያ ክዳን ፊት እንዳይቀርብ ንገረው፡፡ ይህንን ካደረገ፣ ይሞታል፣ ምክንያቱም እኔ በደመና በማስተሰርያ ክዳን ላይ እገለጣለሁ፡፡ 3 ስለዚህም አሮን ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ መቅረብ ያለበት እንደዚህ ነው፡፡ ለሀጢአት መስዋዕት ወይፈን፣ ለሚቃጠል መስዋዕት አ¬ራ በግ ይዞ መግባት አለበት፡፡ 4 ቅዱሱን በፍታ ቀሚስ ይልበስ፣ እንዲሁም የበፍታ የስጥ ሱሪ ይልበስ፣ ደግሞም የበፍታ መጠምጠሚያ የበፍታ ቀሚስ ይልበስ፡፡ ቅዱሳኑ አልባሳት እነዚህ ናቸው፡፡ ሰውነቱን በውሃ ይታጠብና እነዚህን ልብሶች ይልበስ፡፡ 5 ከእስራኤል ሰዎች ጉባኤ ሁለት ወንድ ፍየሎችን ለሀጢአት መስዋዕት እንዲሁም አንድ አ¬ራ በግ ለሚቃጠል መስዋዕት ይውሰድ፡፡ 6 ከዚያም አሮን ለእራሱ ኮርማ¬ን ለኃጢአት መስዋዕት ያቅርብ፣ ይህም ለራሱና ለቤተሰቡ ማስተሰርያ ነው፡፡ 7 ቀጥሎም ሁለቱም ፍየሎች ወስዶ በመገናኛ¬ ድንኳን መግቢያ ላይ በያህዌ ፊት ያቁማቸው፡፡ 8 ከዚያ አሮን በሁለቱ ፍየሎች ላይ ዕጣ ይጣል፣ አንዱን ዕጣ ለያህዌ ሌላ¬ን ዕጣ ለሚለቀቀው ፍየል ይጣል፡፡ 9 ከዚያም አሮን ዕጣ ለያህ«የ¨ጣለትን ፍየል ያቀርባል፣ ያንን ፍየልም ለኃጢአት መስªዕት ያቀርበª፡፡ 10 ለመለቀቅ ዕጣ የጣትን ፍየል ግን ወደ ምድረበዳ በመልቀቅ ለስርየት ከነህይ¨ት ለያህዌ መቅረብ አለበት፡፡ 11 ከዚያም አሮን ለእራሱ ኮርማን ለሀጢአት መስዋዕት ያቀርባል፡፡ ለራሱና ለቤተሰቡ ማስተሰርያ ማድረግ አለበት፣ ስለዚህ ኮርማን ለራሱ የሀጢአት መስዋዕት አድርጎ ይረዳ፡፡ 12 አሮን በያህዌ ፊት ከመሰዊያ የከሰል እሳት የሞላውን ማጠንት ይውሰድ፣ በእጆቹ ሙሉ የላመ ጣፋጭ ዕጣን ይያዝና እዚህንም ነገሮች ¨ደ መጋረጃ ¬ስጥ ይዞ ይግባ፡፡ 13 በዚያም በያህ«ፊት ዕጣኑን በእሳቱ ላይ ይጨምር፣ ከእጣኑ የሚ¨ጣ ጢስ በምስክሩ ላይ ያለ የማስተሰርያን ክዳን ይሸፍናል፡፡ እንዳይሞት ይህንን ያድርግ፡፡ 14 ከዚያም ከወይፈኑ ጥቂት ደም ይውሰድና በጣቱ በማስተሰርያ ክዳን ፊት ይርጭ ከደሙ ጥቂት ¨ስዶ በጣቱ ሰባት ጊዜ በማስተሰርያ ክዳን ፊት ይርጭ፡፡ 15 ከዚያም ለህዝቡ ኃጢአት የኃጢአት መስªዕት ፍየሉን ይረድና ደሙን ¨ደ መጋረጃ ¬ስጥ ይዞ ይግባ፡፡ በዚያም በኮርማ ደም እንዳደረገ ሁሉ ያድርግ በማስተሰርያ¬ ክዳን ላይ ደሙን ይርጭ ከዚያም በማስተሰርያ¬ ክዳን ፊት ይርጭ፡፡ 16 በእስራኤል ህዝብ ያልተቀደሱ ተግባራት፣ በአመጻቸ¬ና በኃጢአቶቻቸ¬ ሁሉ ምክንያት ለተቀደሰ ስፍራ ማስተሰርያ ያድርግ፡፡ ንጹህ ያልሆኑ ተግባሮቻቸ¬ በታዩ ጊዜያት፣ ያህ በመካከላቸ¬ ለሚያድርበት ለመገናኛ¬ ድንኳንም ይህን ያድርግ፡፡ 17 አሮን ለማስተሰርይ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን በሚገባበት ሰዓትና እንዲሁም ለእርሱ፣ ለቤተሰቡና ለእስራኤል ጉባኤ ሁሉ ማስተሰርዩን እስከሚጨርስ ድረስ ማንም ሰው በመገናኛው ድንኳን ውስጥ አይገኝም፡፡ 18 በያህ«ፊት ወዳለ መሰዊያ ይሂድና መሰዊያን ያስተሰርይ፣ ከኮርማ ደም ጥቂት እንዲሁም ከፍየሉ ደም ጥቂት ይ¬ስድና በመሰዊያ ዙሪያ ባሉ ቀንዶች ሁሉ ¬ስጥ ያስነካ፡፡ 19 መሰዊያዉን ንጹህ ካልሆነ የእስራኤል ሰዎች ድርጊቶች ለማንጻትና ለያህዌ ለመለየት በላዩ ካለ ጥቂት ደም ወስዶ በጣቱ ሰባት ጊዜ ይርጭ፡፡ 20 ቅድስተ ቅዱሳኑን፣ የመገናኛን ድንኳንና መሰዊያን ማስተሰርያ¬ን ሲጨርስ በህይወት የሚገኘ¬ን ፍየል ያቅርብ፡፡ 21 አሮን ህይወት ባለው ፍየል ላይ ሁለቱንም እጆቹን ይጫንና የእስራኤልን ህዝብ በደልን ሁሉ፣ አመጻቸውን ሁሉ፣ እና ሀጢአታቸውን ሁሉ በላዩ ላይ ይናዘዝበት፡፡ ከዚያም ያንን ሃጢአተኛነት በፍየሉ ራስ ላይ አድርጎ ፍየሉን ወደ በረሃ ለመስደድ ኃላፊነት ባለበት ሰው አማካይነት ወደ በረሃ ያባው፡፡ 22 ፍየሉ የሰቹን በደል ሁሉ ይሸከምና ገለልተኛ ¨ደ ሆነ ስፍራ ይሄዳል፡፡ በበረሃ ስፍራም፣ ሰ¬ዬ¬ ፍየሉን ይለቀª፡፡ 23 ከዚያም አሮን ወደ መገናኛ ድንኳን ይመለስና ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ ከመሄዱ አስቀድሞ የለበሰን የበፍታ ልብሶች ያወልቃል፣ እነዚያን ልብሶችም በዚያ ስፍራ ያስቀምጣቸዋል፡፡ 24 በተቀደሰ ስፍራ ሰውነቱን በውሃ ይታጠብ፣ ከዚያም የዘወትር ልብሱን ይልበስ፣ ከዚያም ወጥቶ የራሱን የሚቃጠል መስዋዕቱን የህዝቡን የሚቃጠል መስዋዕት ያቅርብ፤ በዚህ መንገድ ለራሱና ለህዝቡ ማስተሰርያ ያቀርባል፡፡ 25 በመሰዊያ ላይ የኃጢአት መስዋዕቱን ስብ ያቃጥል፡፡ 26 የሚሰደደውን ፍየል የለቀቀው ሰው ልብሶቹንና ሰውነቱን ይታጠብ፣ ከዚያ በኋላ ወደ ሰፈር መመለስ ይችላል፡፡ 27 በተቀደሰው ስፍራ ለማስተሰርያው ደማቸው የቀረበው የኃጢአት መስªዕቱ ኮርማ እና የኃጢአት መስªዕቱ ፍየል ከሰፈር ውጭ ይውሰዳቸው፡፡ በዚያም ቆዳቸውን፣ ስጋቸውንና ፈርሳቸውን ያቃጥላFቸው፡፡ 28 እነዚህን የእንስሳውን ክፍሎች የሚያቃጥለው ሰው ልብሶቹንና ሰውነቱን በውሃ ይታጠብ፣ ከዚያ በኋላ፣ ወደ ሰፈር መመለስ ይችላል፡፡ 29 በሰባተኛው ወር፣ በወሩ በአስረኛው ቀን ራሳችሁን ትሁት ታደርጋላችሁ ስራም አትሰሩበትም ለእናንተም ሆነ ለመጻተኛው ይህ ሁልጊዜም መታሰቢያ ይሆናል፡፡ 30 ይህ የሚሆነው በዚህ ዕለት በያህዌ ፊት ቅዱስ ትሆኑ ዘንድ ከኃጢአቶቻችሁ ሁሉ እንድትነጹ ማስተሰርያ ስለሚደረግላችሁ ነው፡፡ 31 ይህ ለእናንተ ክቡር ሰንበት ዕረፍት ነው፣ ራሳችሁን ትሁት ማድረግ አለባችሁ ምንም ስራ አትስሩበት፡፡ይህ በእናንተ መሀል ሁልጊዜም መታሰቢያ ነው 32 ሊቀ ካህኑ፣ በአባቱ ስፍራ ሊቀካህን ሊሆን የሚቀባውና የሚሾመው፣ ይህን ማስተሰርያ ማስፈጸምና ቅዱስ የሆነውን የበፍታ ልብሶች መልበስ አለበት፡፡ 33 ለቅድስተ ቅዱሳኑ፣ ለመገናኛው ድንኳንና ለመስዋዕቱ፣ ማስተሰርያ ያደርጋል፤ እንደዚሁም ለካህናቱና ለጉባኤው ሰዎች በሙሉ ማስተሰርያ ያደርጋል፡፡ 34 "ይህ ለእናንተ ሁልጊዜም መታሰቢያ ይሆናል፣ ለእስራኤል ሰዎች ለኃጢአቶቻቸው ሁሉ ማስተሰርያ ለማቅረብ ይህ በየአመት አንድ ጊዜ ይደረግ፡፡” ያህዌ ሙሴን እንዳዘዘው እንዲሁ ተደረገ፡፡

Leviticus 16:1

የአሮን ሁለቱ ልጆች
ናዳብና እብዩድ ይመለከታል እግዚአብሔር ያልተቀበለውን እሳት በማቅረባቸው ምክንያት ሞተዋል ዘሌዋዊያን 10: 1-2 ይመልከቱ::

Leviticus 16:3

ስለዚህ እዚህ እንዲህ
“ይህም እንዲህ”

የውስጥ ልብስ ወይም የውስጥ ሱሪ
“ከውጨኛው ልብስ ውስጥ በሰውነት ላይ የሚያርፍ ከበፍታ የተሠራ ልብስ”

መቀነት
“በወገብ ወይም በደረት ዙሪያ የሚታጠቅ ከቀጭን ረጅም ጨርቅ የተሠራ”

መጠምጠሚያ
“ከጨርቅ ክፍልፋዮች የተሠራ ጭንቅላት መሸፈኛ ሻሽ”

ከእስራኤል ማኅበረሰብ
“ከእስራኤል ጉባዔ”

Leviticus 16:6

የኃጢአት መሥዋዕት ስለራሱ
ስለራሱ የኃጢአት መስዋዕት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Leviticus 16:8

የሚለቀቅ ፍዬል
የሚለቀቀው ፍዬል አሮንም አንድ ሰው ፍዬሉን ወደ ምድረ በዳ እንዲለቅቀው ያደርጋል

ዕጣው የሆነበት ወይም የወደቀበት
ዕጣው የመደበው

ነገር ግን ፍዬሉ በሕይወት በእግዚአብሔር ፊት መቅረብ አለበት
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ነገር ግን አሮን ፍዬሉን በሕይወት በእግዚአብሔር ፊት ማቅረብ አለበት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 16:11

አጠቃላይ መረጃ
በማስተሠረያ ቀን አሮን ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴ ይናገራል

ወይፈኑን ይረድ
በኋላ በመሠዊያው መክደኛ ላይ ለመርጨት አሮን የወይፈኑን ደም በሳጎን ይያዝ የዚህ ዐረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Leviticus 16:12

ጥና
ካህናት የሚጠቀሙት የእሳትና የዕጣን መያዣ

መልካም በዓዛ ያለው ዕጣን
መልካም በዓዛ የሚያሸት ዕጣን ይህ የዕጣኑን ሽታ ያመለክታል እንጂ ጣፋጭነት አይደለም

Leviticus 16:14

የወይፈኑ ደም
ይህ በዘሌዋዊያን 16:11 እንደተገለጸው አሮን በሳህን የያዘው ደም ነው::

በጣቱ ይርጭ
ደሙን ለመርጨት ጣቱን ይጠቀም

በሥርየቱ መክደኛ ትይዩ
በመክደኛው ላይ ደም ያድርግ ወይም ይርጭ እንዲሁ ደግሞ ወደ ቅዱሳነ ቅዱስ እንደገባ ከፊት ለፊቱ በመክደኛው ጐን ይርጨው

በሥርየቱ መክደኛ ፊት
ሁኔኛ ትርጉሞች: 1) ከሥርየቱ መክደኛ በታች በደረት አካባቢ 2) በሥርየቱ መክደኛ ፊት በመሬት

Leviticus 16:15

አጠቃላይ መረጃ
በማስተሠረያ ቀን አሮን ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴ ይናገራል

ደሙን በስርየቱ መክደኛ ላይ እንዲሁም በመክደኛው ትይዩ ይርጭ
አሮን በወይፈኑ ደም እንዳደረገው ሁሉ ደሙን ይርጨው የቀደሙ ሐጐችን በዘሌዋዊያን 16:14 እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

ከእስራኤል ሕዝብ ርኩሰታቸው የተነሣ ለቅድስተ ቅዱሳኑ ያስተሠርይለታል
የእስራኤል ኃጢአት ቅድስተ ቅዱሳኑን አርክሶአል

ርኩስ ድርጊቶች...አመጽ ...ኃጢአት
እነዚህ ቃላት በመሠረቱ አንድ ናቸው ሰዎች ሁሉ ዓይነት ኃጢአቶች እንደሠሩ አበክረው ያሳያሉ

ርኩስ ድርጊቶች
ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እንዳይኖር የሚያደርጉ ኃጢአታዊ ድርጊቶች ርኩስ ድርጊቶች ተብለዋል:: (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

በርኩሰት ድርጊቶቻቸው መካከል
“ርኩሰት ድርጊቶቻቸው” የሚለው ሀረግ ኃጢአታዊ ድርጊቶችን የሚፈጽሙ ሰዎችን ያመላክታል (See Metonymy/ምትክ ተመሳሳይ አባባሎች ይመልከቱ)

Leviticus 16:17

በእግዚአብሔር ፊት ወዳለው መሠዊያ ይምጣ
ይህ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ የሚገኝ የመሥዋዕት መሠዊያ ነው

ለመሠዊያው ያስተሠርይለት
እንደ ቅዱስ ቦታና መገናኛ ድንኳን መሠዊያው ከሰዎች ኃጢአት የተነሣ ርኩስ ይሆናል

የመሠዊያው ቀንዶች
በመሠዊያው ማዕዘናት ያሉ ቅርጾች ይህም የመሠዊያው ማዕዘናት ያመለክታል:: እንደ በሬ ቀንዶች የተቀረጹ ናቸው:: በዘሌዋዊያን 4:7 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

ለማንጻት
ለእግዚአብሔር ዓላማዎች መጠቀሚያ የሚገባው መሠዊያ ንጹህ እንደሆነ ተገልጾአል:: (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

ለእግዚአብሔርም ይለዩት ከእስራኤልም ሕዝብ ርኩስ ተግባራት ያርቁት
ለእግዚአብሔር የተለየው መሠዊያ ከሕዝቡም ኃጢአት እንደተለየ ተደርጐ ተነግሮአል:: (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

ርኩስ ድርጊቶች
በእግዚአብሔር ፊት ሰዎች ተቀባይነት እንዳይኖራቸው የሚያደርጉ ኃጢአታዊ ድርጊቶች ርኩስ ድርጊቶች ተብለው ተነግረዋል:: (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

Leviticus 16:20

በሕይወት ያለውን ፍዬል ያቅርበው
ይህ ፍዬል በዘለዋዊያን 16:10 ላይ የሚለቀቅ ፍዬል ተብሎአል::

በላዩ ላይ ይናዘዝበት
በፍዬሉ ላይ ይናዘዝበት

ኃጢአታቸውን በፍዬሉ ራስ ላይ ያድርግ
እዚህ የአሮን ድርጊቶች ያ ፍዬል የበደላቸውን ቅጣት እንደሚሸከም ዓይነት የሕዝቡን ኃጢአት ወደ ፍዬሉ የማስተላለፍ ምልክት ናቸው:: (ምልክታዊ ድርጊቶችን ይመልከቱ)

ክፋት.... አመጽ.... ኃጢአት
እነዚህ ሁሉ በመሠረቱ ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው:: ሕዝቡ የፈጸመውን ማንኛውንም ኃጢአት አሮን ይናዘዛል::

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Leviticus 16:23

የበፍታ ልብሶችን አውልቆ
እነዚህ አሮን ወደ ቅድስተ ቅዱሰኑ በሚገባበት ጊዜ የሚለብሱአቸው ልዩ ልብሶች ናቸው::

በተቀደሰውም ሥፍራ ሰውነቱን በውሃ ይታጠብ
እዚህ “ቅዱስ ሥፍራ” የመገናኛ ድንኳን አያመለክትም:: ይህ ሰውነቱን እንዲታጠብ የተለየ ልዩ ሥፍራ ነው::

የዘወትር ልብሱንም ይልበስ
እነዚህ ለመደበኛ ተግባራት አሮን የሚለብሱአቸው ልብሶች ናቸው::

Leviticus 16:25

ያቃጥል
“አሮን ያቅጥል”

የሚለቀቀውን ፍዬል የወሰደው ሰው ልብሱን ይጠብ ሰውነቱንም በውሃ ይታጠብ
የሕዝቡን ኃጢአት የተሸከመውን የሚለቀቀውን ፍዬል ስለነካ ሰውየው ርኩስ ነው

የሚለቀቀው ፍዬል
“ተለቅቆ የሚሄድ ፍዬል” በዘሌዋዊያን 16:8 ይህን እንዴት አንደተረጐሙ ይመልከቱ::

Leviticus 16:27

ደማቸው የገባው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “አሮን ያገባቸው ደማቸው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ተሸክመው ተወስደው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “አንድ ሰው ተሸክሞ ይውሰድ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ቁርበታቸው
ቈዳቸው ወይም የእነርሱ ቈዳ፤ እዚህ “እነርሱ” ወይፈኑንና ፍዬሉን ያመለክታል::

Leviticus 16:29

ለእናንተ
እናንተ የሚለው ቃል ብዙና የእስራኤልን ሕዝብ የሚያመለክት ነው:: (የሁለተኛ ሰው አገላለጾች ይመልከቱ)

በሰባተኛው ወር በአሥረኛው ቀን
ይህ በዕብራይጥ የቀን መቁጠሪያ ሰባተኛ ወር ነው አሥረኛው ቀን በምዕራባዊያን አቆጣጠር መስከረም ማገባደጃ ወይም መጨረሻ አካባቢ ነው:: (የዕብራይጥ ወራትንና መደበኛ ቁጥሮችን ይመልከቱ)

ሥርየት ይደረግላችኋል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “አሮን ሥርየት ያደርግላችኋል” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ያነጻችኋል ....ስለዚህ ትነጻላችሁ
ለእግዚአብሔር ዓላማዎች ተቀባይነት ያሉአቸው ሰዎች ንጹህ ተብለዋል::

ይህች የፍጹም ዕረፍት ሰንበት ናት
ይህ በየሳምንቱ የሚያከብሩት የሰንበት ቀን አይደለም:: በሥርየት ቀን የሚደረግ ልዩ ሰንበት ነው::

Leviticus 16:32

የተቀባና የተሾመ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “እነርሱ የሚቀቡትና የሚሾሙት ሰው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

በአባቱ ምትክ
ሊቀ ካህን ሲሞት ከልጆቹ አንዱ ይተካዋል::

የተቀደሰው በፍታ ልብስ
ቅድስተ ቅዱሳን በሚገባበት ጊዜ ሊቀ ካህኑ የሚለብሱአቸው ልዩ ልብሶች ናቸው

ለማኅበረሰቡ ሁሉ
“ለእስራኤል ሕዝብ ሁሉ”

Leviticus 16:34

አጠቃላይ መረጃ
በማስተሠረያ ቀን ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴ መናገሩን ይፈጽማል

እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘ እንዲሁ አደረገ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “እናም ሙሴ እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ” ወይም “እናም አሮን እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው አደረገ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 17

1 እንዲህ ሲል ሙሴን ተናገረው፣ 2 አሮንና ልጆቹን እንዲሁም የእስራኤል ህዝብ ሁሉ እንዲህ በላቸው። ያህዌ ያዘዘውን ንገራቸው። 3 “ከእስራኤል ሰዎች መሀል ማንም ለመስዋዕት በሰፈር ውስጥ ወይም ከሰፈር ውጭ በሬ፣ በግ፣ ወይም ፍየል ያረደ ሰው፣ 4 ወደ መገናኛው ድንኳን መግቢያ በመቅደሱ ፊት ለያህዌ መስዋዕት ለማድረግ ባመጣው ውሃ ያ ሰው ስላፈሰሰው ደም በደለኛ ነው” ደም አፍስሷልና ያ ሰው ከህዝቡ መሃል ተለይቶ ይጥፋ። 5 የዚህ ትእዛዝ ዓላማ የእስራኤል ሰዎች ለያህዌ በሜዳ ላይ የሚያቀርቧቸውን መስዋዕቶች ወደ ካህናት ለያህዌ የህብረት መስዋዕት አድርገው በመገናኛው ድንኳን መግቢያ እንዲያቀርቡ ነው። 6 ካህኑ የመስዋዕቱን ደም በመገናኛው ድንኳን መግቢያ ላይ በያህዌ መሰዊያ ላይ ይረጫል፤ ስቡን ለያህዌ ጣፋጭ ማዕዛ አድርጎ ያቃጥለዋል። 7 ሕዝቡ ከእንግዲህ መስዋዕቱን ለጣኦት አይሰዋ፣ እንዲህ ያለው ተግባር ምንዝርና ነው። ይህ በትውልዶቻቸው ሁሉ ቋሚ መታሰቢያ ይሆናል። 8 እንዲህ በላቸው፣ “ማንኛውም እስራኤላዊ፣ ወይም ማንኛውም በእነርሱ መሀል የሚኖር መጻተኛ፣ የሚቃጠል መስዋዕት የሚሰዋ ወይም መስዋዕት የሚያቀርብ 9 እና ለያህዌ ለመሰዋት ወደ መገናኛው ድንኳን ደጃፍ የማያመጣው ያ ሰው ከህዝቡ ተለይቶ ይጥፋ። 10 ደግሞም ከእስራኤል አንዱ፣ ወይም በእነርሱ መሀል ከሚኖር መጻተኛ አንዱ፣ ደም ቢበላ፣ ፊቴን ከዚያ ሰው አስቆጣለሁ፣ ማንንም ደም የሚበላን ሰው ከህዝቡ መሃል አጠፋዋለሁ። 11 የእንስሳ ህይወቱ በደሙ ውስጥ ነው። በመሰዊያ ላይ ማስተሰርያ ይሁናችሁ ዘንድ ደሙን ለሕይወታችሁ ሰትቻችኋለሁ፣ ምክንያቱም ማስተሰርያ የሚሆነው ደም ነው፣ ለሕይወት ስርየት የሚያስገኘው ደም ነው። 12 ስለዚህም ለእስራኤላውያን ከመሀላችሁ ማንም ደም አይብላ እላለሁ፣ በመሀላችሁ የሚኖር ማንም ሙያተኛም ቢሆን ደም አይብላ። 13 ከእስራኤል ሰዎች መሀል ማንም ቢሆን፣ ወይም በእነርሱ መሃል የሚኖር ማንኛውም መጻተኛ፣ የሚበላ እንስሳ ቢያርድ ወይም ወፍ ቢያጠምድ ደሙን ያፍስና በአፈር ይሸፍነው። 14 የእያንዳንዱ ፍጥረት ነፍስ ደሙ ነውና። ስለዚህም ነው ለእስራኤላውያን፣ የማንኛውም ፍጥረት ደም አትብሉ፣ የእያንዳንዱ ሕያው ፍጥረት ሕይወት ደሙ ነው። ማንም ይህን የሚበላ ተቆርጦ ይጥፋ” ብዬ የተናገርኩት። 15 እያንዳንዱ የሞተ፣ ወይም በዱር አውሬ የተዘነጠለ እንስሳ የበላ ሰው የአገር ተወላጅ ይሁን በመሀላችሁ የሚኖ መጻተኛ ልብሶቹን ይጠብ፣ እርሱም በውሃ ይታጠብ፣ እስ ምሽት ድረስ ንጹህ አይሆንም። ከዚያ ንጹህ ይሆናል። 16 ነገር ግን ልብሱን ባያጥብ ወይም ሰውነቱን ባይታጠብ፣ በበደሉ ተጠያቂ ነው።

Leviticus 17:1

በእግዚአብሔር ማደሪያ ፊት
በታቦቱ ፊት

ያ ሰው ከሕዝቡ ተቆርጦ ይወገድ ወይም ተለይቆ ይጥፋ
ከጎብረተሰቡ የሚገለል ሰው የልብስ ጨርቅ ወይም የዛፍ ቅርንጫፍ እንደሚቆረጥ ከሕዝቡ እንደሚቆረጥ ተደርጐ ተነግሮአል:: ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: በዘሌዋዊያን 7:20 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: አት፤ “በሕዝቡ ዘንድ ያ ሰው እንዲኖር አይገባም” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 17:5

ለመሠዋት ወደ ካህኑ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ካህኑም መሥዋዕት አድርጐ እንዲያቀርባቸው ወደ ካህኑ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 17:7

ላመነዘሩባቸው
ስህተት አማልዕክትን በማምለክ ለእግዚአብሔር ታማኝ ያልሆነው ሕዝብ በማመንዘር ባለቤቱን እንደካደ ሰው እንደሆነ ተገልአል አት: ለእግዚአብሔር ታማኝ ላልሆኑበት፤ (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

ለእነርሱና ከእነርሱ በኋላ ለሚነሣው ትውልድ ይህ የዘላለም ሥርዓት
በዘሌዋዊያን 3: 17 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

Leviticus 17:8

ያ ሰው ከሕዝቡ ተለይቶ ይጥፋ
የሰውየው ከማኅበረሰቡ መገለሉ አንድ ቢጣሽ ጨርቅ ከልብስ ወይም ቅርንጫፍ ከዛፍ እንደሚቆረጥ ከሕዝቡ እንደተቆረጠ ተደርጐ ተነግሮአል ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ያ ሰው በሕዝቡ መካከል መኖር የለበትም” ወይም “ያ ሰው ከሕዝቡ መለየት አለበት” (ዘይቤያዊ አገላለጽና ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 17:10

በዚያ ሰው ላይ ፊቴን አከብድበታለሁ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር “በጥብቅ እንደወሰነ” ይገልጻል:: አት: “ያን ሰው ለመቃወም በአእምሮዬ ወስኛለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ፊቴን ላከብድበት
“በቁጣ ሊገናኘው”

ከሕዝቡ ለይቼ እቆርጠዋለሁ/ አጠፋዋለሁ
የሰውየው ከማኅበረሰቡ መገለሉ አንድ ቢጣሽ ጨርቅ ከልብስ ወይም ቅርንጫፍ ከዛፍ እንደሚቆረጥ ከሕዝቡ እንደተቆረጠ ተደርጐ ተነግሮአል ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ያ ሰው በሕዝቡ መካከል መኖር የለበትም” ወይም “ያ ሰው ከሕዝቡ መለየት አለበት” (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

የፍጡር ሕይወት በደሙ ነውና ... ሕይወት ሥርየት የሚያስገኝ
ይህም ማለት ደም ሕይወት ስለሆነ እግዚአብሔር ደምን ተጠቅሞ የሰዎችን ኃጢአት ያስተሠርያል:: ይህ የተለየ ዓላማ ስላለው ሰዎች ደምን መብላት አይገባቸውም

Leviticus 17:12

“እኔ” እላለሁ
እዚህ “እኔ” ያህዌን ያመለክታል

ከእናንተ ማንም ደም አይብላ
“ከእናንተ ማንም ደም ያለበትን ሥጋ አይብላ”

ያ ሊበላ ይችላል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ያ እንዲበሉ እኔ የተናገርሁት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ደሙን አፈር ያልብሰው
“ደሙን የአፈር ብናኝ ያልብሰው”

Leviticus 17:14

የማንኛውም ፍጡር ሕይወት ደሙ ነውና
ይህም ማለት ደም ፍጡር በሕይወት እንዲኖር ያደርጋል የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል አት: “ከደሙ የተነሣ እያንዳንዱ ፍጡር በሕይወት ሊኖር ይችላሉ” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

የበላው ሰው ሁሉ ተለይቶ ይጥፋ
የሰውየው ከማኅበረሰቡ መገለሉ አንድ ቢጣሽ ጨርቅ ከልብስ ወይም ቅርንጫፍ ከዛፍ እንደሚቆረጥ ከሕዝቡ እንደተቆረጠ ተደርጐ ተነግሮአል ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ደምን የሚበላ ማንኛውም ሰው በሕዝቡ ዘንድ መኖር የሌበትም” ወይም “ደም የሚበላውን ሰው ከሕዝቡ መለየት አለባችሁ” (ዘይቤያዊ አገላለጽና ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 17:15

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል

አውሬ የዘነጠለውን
በአውሬ የተገደለው እንስሳ አውሬዎች አንሰሳውን ዘነጣጥለው እንደከፋፈሉት ተነግሮአል።ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “አውሬዎች የገደሉት” (ዘይቤያዊ አገላለጽና ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

የሀገር ተወላጅ
“እስራኤላዊ”

ርኩስ ይሆናል .... ከዚያም ርኩስ ይሆናል
ሌሎች ሰዎች ሊነኩት የማይችሉአቸው ሰው ርኩስ ተብሎአል እናም ሌሎች ሰዎች መንካት የሚችሉአቸው ሰው ንጹህ ተብሎአል::(ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

እስከማታ
“ጸሐይ እስኪጠልቅ”

በደሉን ይሸከማል
የሰውየው በደል አንድን ግዑዝ ዕቃ ሰው እንደተሸከመ ተደርጐ ተነግሮአል:: እዚህ “በደል” የሚለው ቃል ለበደሉ የሚሰጠውን ቅጣት ያመለክታል:: አት: ያም እርሱ ለበደሉ ተጠያቂ ነው ወይም ስለ ኃጢአቱ እቀጣዋለሁ:: (ዘይቤያዊ አነጋገር ወይም ምትክ ተመሳሳይ አባባሎችን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 18

1 ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ **2** “ለእስራኤል ሰዎች እንዲህ ብለህ ንገራቸው፣ “እኔ ያህዌ አምላካችሁ ነኝ። **3** እኔ በማስገባችሁ ምድር፤ ቀድሞ ትኖሩበት በነበረው በግብጽ የነበሩ ሰዎች ያደርጓቸው የነበሩ ነገሮችን አታድርጉ፣ ደግሞም በከነአን ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ያደርጓቸው የነበሩ ነገሮችን አታድርጉ። የእነርሱን ልምዶች አትከተሉ። **4** እናንተ መፈጸም ያለባችሁ የእኔን ህጎች ነው መጠበቅ ያለባችሁ የእኔን ትዕዛዛት ነው፣ ስለዚህም በእነርሱ ትኖራላችሁ፣ ምክንያቱም እኔ አምላካችሁ ያህዌ ነኝ። **5** ስለዚህም እኔን ትዕዛዛትና ህጎች ትጠብቀላችሁ። አንድ ሰው እነዚህን ቢጠብቅ፣ በእነርሱ ምክንያት በህይወት ይኖራል። እኔ ያህዌ ነኝ። **6** ማንም ሰው ከቅርብ ዘመዱ ጋር አይተኛ እኔ ያህዌ ነኝ። **7** ከእናትህ ጋር በመተኛት አባትህን አታዋርድ። እርሷ እናትህ ናት! እርሷን ማዋረድ የለብህም። **8** ከአባትህ ሚስት ከየትኛዋም ጋር አትተኛ፤ አባትህን በዚያን አይነት ማዋረድ የለብህም። **9** የአባትህ ልጅ ወይም የእናትህ ልጅ ብትሆን በቤት ውስጥ አብራህ ብታድግ ወይም ርቃ ብታድግም ከየትኛዋም እህትህ ጋር አትተኛ። **10** ከወንድ ልጅህ ሴት ልጅ ጋር ወይም ከሴት ልጅህ ሴት ልጅ ጋር አትተኛ። ይህ እፍረት ይሆንብሃል። **11** ከአባትህ ከተወለደች ከእንጀራ እናትህ ሴት ልጅ ጋር አትተኛ። እህትህ ናት፣ እናም ከእርሷ ጋር መተኛት የለብህም። **12** ከአባትህ እህት ጋር አትተኛ። ለአባትህ የቅርብ ዘመድ ናት። **13** ከእናትህ እህት ጋር አትተኛ። ለእናትህ የቅርብ ዘመድ ናት። **14** ወንድም ከሚስቱ ጋር በመተኛት አታዋርደው” ለዚያ ተግባር ወደ እርሷ አትቅረብ፣ አክስትህ ናት። **15** ከምራትህ ጋር አትተኛ። የወንድ ልጅህ ሚስት ናት፣ ከእርሷ ጋር አትተኛ። **16** ከወንድምህ ሚስት ጋር አትተኛ፣ በዚህ መንገድ አታዋርደው። **17** ከአንዲት ሴትና ከልጇ ጋር ወይም ከወንድ ልጇ ሴት ልጅ ጋር ወይም ከሴት ልጇ ሴት ልጅ ጋር አትተኛ። እነርሱ ለእርሷ የቅርብ ዘመዶች ናቸው፣ እናም ከእነርሱ ጋር መተኛት ጸያፍ ነው። **18** የሚስትህን እህት ሁለተኛ ሚስት አድርገህ አታግባ፤ ሚስትህ በህይወት ሳለች ከእህቷ ጋር አትተኛ። **19** አንዲት ሴት በወር አበባዋ ወቅት ላይ ሳለች አብረሃት አትተኛ። በዚያን ጊዜ ንጹኅ አይደለም። **20** ከጎረቤትህ ሚስት ጋር አትተኛ፣ በዚህ መንገድ ራስህን አታርክስ። **21** ከልጆችህ አንዳቸውንም በእሳት ውስጥ እንዲያልፉ አትስጥ፣ በዚህ ድርጊት ለሞሎክ መስዋዕት አድርህ ትሰጣቸዋለህ፣ የአምላክህን ስም ማቃለል የለብህም። እኔ ያህዌ ነኝ። **22** ከወንዶች ጋር ከሴት ጋር እንደምትተኛው አትተኛ። ይህ ጸያፍ ነው። **23** ከማናቸውም እንስሳ ጋር አትተኛ ራስህን አታርክስ። ማንም ሴት ከማናቸውም እንስሳ ጋር መተኛት የለባትም። ይህ አስጸያፊ ወሲብ ነው። **24** ከእነዚህ መንገዶች በየትኛውም ራስህን አታርክስ፣ ከአንተ አስቀድሞ ያባረርኳቸው ህዝቦች በእነዚህ ሁሉ መንገዶች ረክሰዋል። **25** ምድሪቱ ረከሰች፣ ስለዚህም በኃጢአታቸው ቀጣኋቸው፣ ምድሪቱም በላይዋ የሚኖሩትን ተፋቻቸው። **26** ስለዚህ እናንተ የእኔን ትዕዛዛትና ህግጋቴን መጠበቅ አለባችሁ፣ እናንተ ተወላጅ እስራኤላዊያንም ሆናችሁ በእንተ መሀል የሚኖሩ እንግዶች ከእነዚህ ያልተገቡ ነገሮች የትኞቹንም ማድረግ የለባችሁም። **27** ከእናንተ አስቀድሞ በዚህ ምድር የኖሩ ሰዎች የሰሩት ጸያፍነት ይህ ነው፣ እናም አሁን ምድሪቱ ረከሰች። **28** ስለዚህም ምድሪቱ ከእናንተ በፊት የነበሩትን ሰዎች እንደተፋች እናንተንም ካረከሳችኋት በኋላ እንዳትተፋችሁ ተጠንቀቁ። **29** ከእነዚህ አስነዋሪ ነገሮች መሀል የትኛውንም ነገር ያደረገ፣ እንዲህ ያለ ነገሮችን ያደረገው ሰው ከህዝቡ መሀል ተለይቶ ይጠፋል። **30** ስለዚህ በእነዚህ ነገሮች እንዳታረክሱ ከእናንተ አስቀድሞ በዚህ ስፍራ ይፈፀሙ የነበሩትን ጸያፍ ልምዶች ባለማድረግ ትዕዛዛቴን መጠበቅ አለባችሁ። እኔ ያህዌ አምላካችሁ ነኝ።

Leviticus 18:4

ሕጌን ያዘዙ ሥርዐቴንም በጥንቃቄ ጠብቁ
እነዚህ ሁለቱ ሐረጐች በመሠረቱ አንድ ትርጉም ያላቸውና ሕዝቡ እግዚአብሔር ያዘዛቸውን ሁሉ ማድረግ እንዳለበቸው የሚያተኩሩ ናቸው:: ይህን ተጓዳኝ ንጽጽር የእግዚአብሔርን ሕጐች ሁሉ መጠበቅ እንደሚገባቸው እንደ አንድ ዐረፍተ ነገር መተርጐም ይችላሉ አት ሕጐቼንና ሥርዓቶቼን ሁሉ ታዘዙ:: (ተጓዳኝ ንጽጽር ይመልከቱ)

በእነርሱም ኑሩ
የእግዚአብሔርን ሕጐች መታዘዝ አንድ ሰው የሚራመድበት ጐዳና ተደርገው ተነግረዋል:: አት: “ስለዚህ ባሕሪያችሁን በእነርሱ መሠረት ተለማመዱ” (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

Leviticus 18:6

ከአባትህ ሚስት ጋር
አንዳንዴ አንድ ወንድ ከአንድ በላይ ሚስቶች ይኖሩታል:: አባቱን ካገባች ከማንኛዋም ሴት ጋር ግብረ ሥጋ ግንኙት ማድረግን እግዚአብሔር አልፈቀደም::

Leviticus 18:9

ከአባትህ ወይም ከእናትህ ሴት ልጅ ጋር
ይህም አንድ ሰው ከተመሳሳይ ወላጅ ወይም የተለየ አባት ወይም እናት ቢኖራትም ከእህቱ ጋር በግብረ ሥጋ አይገናኝ ማለት ነው

በቤት ያደገች ወይም በውጭ የተወለደች ቢትሆን
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “በቤት ውስጥ ያደገች ወይም ከቤት ውጭ ያለች ቢትሆን” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

የአባትህ ሚስት ለአባትህ ከወለደቻት ሴት ልጅ ጋር ግብረ ሥጋ አትፈጽም
አማራጭ ትርጉሞች እነሆ ፤ (1)ከግማሽ እህትህ ጋር ግብረ ሥጋ አትፈጽም ፤(2)የእንጀራ እህት ጋር እዚህ ያ ሰው ተመሣሣይ አባት ወይ እናት ከሌላት እኅቱ ጋር ማለት ነው፤ወላጆቻቸው በተጋቡ ጊዜ ወንድምና እኅት ሆነዋልና፤

Leviticus 18:12

ለዚያ ዓላማ ወደ እርስዋ አትቅረብ
“የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም ወደ እርስዋ አትሂድ”

Leviticus 18:15

ከእርስዋ ጋር አትተኛ
እግዚአብሔር ደጋግሞ የሚናገረው ለትዕዛዙ አጽንዖት ለመስጠት ነው::

Leviticus 18:19

የወር አበባ
ይህ ከሴት ማዕጸን በወራዊ ጊዜ ደም የሚፈስስበት ነው

የባልንጀራህን ሚስት
የማንኛውንም ሰው ሚስት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Leviticus 18:22

ይህ አስጸያፊ ነው
እዚህ “አስጸያፊ” እግዚአብሔር እንዲሆኑ ያደረገውን የተፈጥሮአዊ ነገሮች ሥርዓት መተላለፍን ያመለክታል::

Leviticus 18:24

አሕዛብ...ሁሉ ረክሰዋልና
ይህ በከነዓን የሚኖሩ ሰዎች ያመለክታል:: “ሕዝብ” ወይም “አሕዛብ” የተባለው ሀሳብ “ሰዎች” በሚለው ግልጽ እንደሚሆን አድርገው ይተርጉሙ:: አት የአሕዛብ ሰዎች በእነዚህ ረክሰዋል:: (Metonymy/ምትክ አቻ ትርጉም ያላቸውን ተመሳሳይ አባባሎችን ይመልከቱ)

ምድሪቱም ... ረከሰች
“ሰዎች ምድሪቱን አርክሶአታል”

ምድሪቱ...የሚኖሩባትን ሰዎች ተፋቻቸው
እግዚአብሔር ሕዝቡን ከምድሪቱ በጉልበት ማስወጣቱ ምድሪቱ እንደሰው ሰዎችን እንደተፋች ተደርጐ ተነግሮአል (ዘይቤያዊ አነጋገርና በሰውኛ አገላለጽ ይመልከቱ)

Leviticus 18:26

ከእነኚህ የተጠሉ ድርጊቶች
“ከእነኚህ አስጸያፊ ድርጊቶች”

ይህ ርኩሰት ነው
ይህ “እነዚህን ጸያፍ ድርጊቶች” ያመለክታል

ስለዚህ ተጠንቀቁ
“ስለዚህ እኔን ለመታዘዝ ተጠንቀቁ”

በፊት የነበረውን ሕዝብ እንደተፋች እናንተን እንደትተፋችሁ
እግዚአብሔር ሕዝቡን ከምድሪቱ በጉልበት ማስወጣቱ ምድሪቱ እንደሰው ሰዎችን እንደተፋች ተደርጐ ተነግሮአል:: በዘሌዋዊያን 18:25 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: አት: “ከዚህም የተነሣ እነርሱን ከምድሪቱ በጉልበት እንዳወጣሁት እናንተንም ከምድሪቱ አወጣለሁ”(ዘይቤያዊ አነጋገርና በሰውኛ አገላለጽ ይመልከቱ)

Leviticus 18:29

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴ መናገሩ ያበቃል

ሰዎች...ከሕዝቡ ተለይተው ይጥፉ
ከማኅበረሰቡ መገለሉ ሰዎች አንድ ቢጣሽ ጨርቅ ከልብስ ወይም ቅርንጫፍ ከዛፍ እንደሚቆረጥ ከሕዝቡ እንደተቆረጠ ተደርጐ ተነግሮአል:: ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “እነዚህ ሰዎች በሕዝቡ ዘንድ እንዳይኖሩ ወይም እነዚህን ሰዎች ከሕዝቡ እንዲትለዩአቸው” (ዘይቤያዊ አገላለጽና ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ከእናንተ በፊት ካደረጓቸው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ከአናንተ በፊት የነበሩ ሰዎች ያደረጉት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

በእነዚህ
እዚህ “እነዚህ” ጸያፍ ልምዶችን ያመለክታል::

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 19

1 ሙሴን እንዲህ አለው 2 “ለእስራኤል ሰዎች ጉባኤ ሁሉ እንዲህ ብለህ ንገራቸው፣ “እኔ ያህዌ አምላካችሁ ቅዱስ እንደሆንኩ እናተም ቅዱሳን ሁኑ። 3
እያንዳንዱ እናቱንና አባቱን ያክብር፣ እናንተም ሰንበቴን ጠብቁ። እኔ አምላካች ያህዌ ነኝ። 4 ጥቅም ወደሌላቸው ጣኦታት ዘወር አትበሉ፣ ከቀለጠ ብረት
ለራሳችሁ አማልዕክትን አታብጁ። እኔ ያህዌ አምላካችሁ ነኝ። 5 ለያህዌ የህብረት መስዋእቶችን ስታቀርቡ፣ ተቀባይነት ልታገኙ በምትችሉበት መንገድ አቅርቡ።
6 መስዋዕቱ ባቀረባችሁበት ቀን አሊያም በማግስቱ ይበላ። አንዳች ነገር እስ ሶተኛው ቀን ቢተርፍመ ይቃጠል። 7 በሶስተኛው ቀን ቢበላ የረከሰ ነው።
ተቀባይነት አያገኝም፣ 8 ነገር ግን የበላው ሁሉ በበደለኛነቱ ይጠየቅበታል ምክንያቱም ለያህዌ የተለየውን አርክሷል። ያ ሰው ከህዝቡ ተለይቶ ይጥፋ። 9
የምድራችሁን ሰብል በምትሰበስቡበት ጊዜ፤ የእርሻችሁን ቀርጢያ ሁሉ አትልቀሙ፣ አሊያም የአዝመራችን ምርት ሁሉ አትሰብስቡ። 10 ከወይን ተክልህ
እያንዳንዱን ወይን ፍሬ አትሰብስብ፣ አሊያም በወይን ስፍራ የወዳደቁትን የወይን ፍሬዎች አትልቀም። ለድሆችና ለመጻተኞች እነዚህን ተዉላቸው። እኔ ያህዌ
አምላካችሁ ነኝ። 11 አትስረቁ። አትዋሹ። አንዳችሁ ሌላችሁን አታታሉ። 12 በሃሰት በስሜ አትማሉ የአምላካችን ስም አታርክሱ። እኔ ያህዌ ነኝ። 13 ጎረቤትህን
አትበድል ወይም አትዝረፈው። የቀን ሰራተኛውን ክፍያ በአንተ ዘንድ አታሳድር። 14 መስማት የተሳነውን ሰው አትርገመው ወይም ከእውሩ ፊት ማሰናከያ ድንጋይ
አታስቀምጥ ይልቁንም አምላክህን ፍራ። እኔ ያህዌ ነኝ። 15 ፍትህን አታጣም። አንድ ሰው ድሃ ስለሆነ ልታደላለት አይገባም፣ እንደዚሁም አንድ ሰው ባለጸጋ
ስለሆነ አታዳላለት። ይልቁንም ለጎረቤትህ በጽድቅ ፍረድ 16በሰዎች መሃል በሀሳት ሃሜትን አታሰራጭ 16 በሰዎች መሃል ሀሜትን እያሰራጨህ አትዙር፣
ይልቁንም የጎረቤትህን ሕይወት አቅና። እኔ ያህዌ ነኝ። 17 በልብህ ወንድምህን አትጥላ። በእርሱ ምክንያት የኃጢአቱ ተካፋይ እንዳትሆን ጎረቤትህን በቅንነት
ገስጸው። 18 ከህዝብህ ማንንም አትቀበል ወይም በማንም ላይ ቂም አይኑርህ፣ ነገር ግን በዚህ ፈንታ ጎረቤትህን እንደራስህ ውደድ። እኔ ያህዌ ነኝ። 19
ትዕዛዛቴን መጠበቅ አለብህ። እንስሳትህን ከሌሎች ልዩ ዝርያ ካላቸው እንስሳት ጋር አታዳቅል። በእርሻህ ላይ ስትዘራ የተለያየ የዘር ዐይነቶችን አትደባልቅ።
ከሁለት የተለያዩ አይነት ነገሮች ተደባልቆ የተሰራ ልብስ አትልበስ። 20 ቤዛ ካልተከፈለላት ወይም ነጻ ካልወጣች ለባል ከታጨች ባሪያ ከሆነች ልጃገረድ የተኛ
ሁሉ ይቀጡ። ሊገደሉ ግን አይገባም ምክንያቱም ነጻ አልወጣችም። 21 ሰውዬው ወደ መገናኛው ድንኳን መግቢያ ለበደል መስዋዕት ለያህዌ አውራ በግ
ያምጣ። 22 ከዚያ ካህኑ በያህዌ ፊት ሰውዬው ለሰራው ኃጢአት የበደል መስዋዕት አውራ በግ በማቅረብ ያስተሰርይለታል። ከዚያ የሠራው ኃጢአት ይቅር
ይባልለታል። 23 ወደምድሪቱ ስትገቡና ለምግብ የሚሆን ሁሉንም ዐይነት ዛፎች ስትተክሉ፣ ዛፎቹ ያፈሩትን ፍሬ ለመብላት እንደተከለከለ ቁጠሩት። ፍሬው
ለእናንተ ለሶስት ዓመታት የተከለከለ ነው። አይበላም። 24 ነገር ግን በአራተኛው አመት ፍሬው ሁሉ ለያህዌ ለምስጋና የሚሰዋ ቅዱስ ይሆናል። 25 አመት
ፍሬውን መብላት ትችላላችሁ። በመጠበቃችሁ ዛፎቹ ብዙ ያፈራሉ። እኔ ያህዌ አምላካችሁ ነኝ። 26 ደሙ በውስጡ ያለበትን ስጋ አትብሉ። ስለ ወደፊቱ
መናፍስትን አታማክሩ፣ ደግም ከተፈጥሮ በላይ በሆኑ ኃይላት ሌሎችን ለመቆጣጠር አትፈልጉ፤። 27 እንደ ጣኦት አምላኪዎች የጸጉራችሁን ዙሪያ አትላጩ
ወይም የጺማችሁን ዙሪያ አትቆረጡ። 28 ለሙታን ሰውነታችሁን በስለት አትቁረጡ ወይም በሰውነታችሁ ላይ ንቅሳት አታድርጉ። እኔ ያህዌ ነኝ። 29 ሴት ልጅህን
ሴተኛ አዳሪ በማድረግ አታወርዳት፣ በዚህ ነገር አገረ ወደ ግልሙትና ትገባለች ምድሪቱም በእርኩሰት ትሞላለች። 30 ጠብቁ የቤተመቅደሴን ቅድስና አክብሩ።
እኔ ያህዌ ነኝ። 31 ወደ ሙታን ጠሪዎችና መናፍስትን ወደሚያነጋግሩ ዘወር አትበሉ። እነዚህን አትፈልጉ፣ ካልሆነ ያረክሷችኋል። እኔ ያህዌ አምላካችሁ ነኝ። 32
ፀጉሩ ለሸበተ ሰው ተነስለት ደግሞም በዕድሜ የገፋውን ሰው አክብር። አምላክህን ፍራ። እኔ ያህዌ ነኝ። 33 በምድርህ በመካከልህ መጻተኛ ቢኖር፣ አትግፋው።
34 በመካከላችሁ የሚኖረው መጻተኛ እንደ ተወላጅ እስራኤላዊ ወገናችሁ ቁጠሩት ደግሞም እንደ ራሳችሁ ውደዱት፣ ምክንያቱም እናንተም በግብጽ ምድር
መጻተኞች ነበራችሁ። እኔ ያህዌ አምላካችሁ ነኝ። 35 ርዝመትን፣ ክብደትን፣ ወይም ብዛትን ስትለኩ። ሀሰተኛ መለኪያ አትጠቀሙ። 36 ትክክለኛ መስፈሪያን፣
ትክክለኛ ሚዛኖችን፣ ትክክለኛ የኢፍ እና የኢን መለኪያዎችን ተጠቀሙ። ከግብጽ ምድር ያወጣኋችሁ እኔ ያህዌ አምላካችሁ ነኝ። 37 ትዕዛዛቴንና ህግጋቴን ሁሉ
ጠብቁ፣ አድርጓቸውም። እኔ ያህዌ ነኝ።”

Leviticus 19:1

ሰንበታቴን ጠብቁ
“ሰንበታቴን አክብሩ” ወይም “ለአረፍኩት ቀን ክብር ስጡ”

ጥቅም ወደሌላቸው ጣዖታት ዘወር አትበሉ
ጣዖታትን ማምለክ ወደ እነሱ ዘወር እንደማለት ተደርጐ ተገልጾአል:: አት “የማይረቡ ጣዖታትን ማምለክ አትጀምሩ” (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

Leviticus 19:5

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴ መናገር ይቀጥላል

ተቀባይነት እንዲያገኝላችሁ አድርጋችሁ አቅርቡ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: ሁኔኛ ትርጉሞች እነሆ 1)እግዚአብሔር መስዋዕቱን የሚያቀርበውን ሰው ይቀበላል አት፤ “ እንዲቀበልህ በሥርዓት መሥዋዕትህን አቅርብ” ወይም 2) እግዚአብሔር የሚያቀርበውን ሰው መሥዋዕት ይቀበላል አት፤ “ መስዋዕትህን እንዲቀበል በሥርዓት አቅርብ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ እናም ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ይበላ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ይብሉት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ይቃጠል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ያቃጥሉት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ቢበላ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ቢበሉት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ተቀባይነት የለውም
የተመደበውን ጊዜ አሳልፎ የቀረበውን መሥዋዕት መብላት መስዋዕቱ የማሸፍነውን በደል መጨመርና እግዚአብሔርን መበደል ነው ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ለመብላት አይቀበሉ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

እያንዳንዱ...የራሱን በደል ይሸከማል
የሰውየው በደል አንድን ግዑዝ ዕቃ ሰው እንደተሸከመ ተደርጐ ተነግሮአል:: እዚህ “በደል” የሚለው ቃል ለዚያ በደሉ የሚሰጠውን ቅጣት ያመለክታል:: አት: ማንኛውም ለራሱ በደል ተጠያቂ ነው ወይም እግዚአብሔር ማንንም

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ስለኃጢአቱ ይቀጣል:: (ዘይቤያዊ አነጋገር ወይም ተመሳሳይ ትርጉም ያለቸው ምትክ አባባሎች ይመልከቱ)

ያ ሰው ከሕዝቡ ዘንድ ይወገድ
ሰውየው ከማኅበረሰቡ ዘንድ መገለሉ አንድ ቢጣሽ ጨርቅ ከልብስ ወይም ቅርንጫፍ ከዛፍ እንደሚቆረጥ ከሕዝቡ እንደተቆረጠ ተደርጐ ተነግሮአል:: ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: በዘሌዋዊያን 7:20 ይህን አንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: አት፤ “ሰውየው በሕዝቡ ዘንድ አይኑር ወይም ይህንን ሰው ከሕዝቡ ይለዩት” (ዘይቤያዊ አገላለጽና ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 19:9

የምድራችሁን መከር በምትሰበስቡበት ጊዜ በእርሻችሁ ዳርና ዳር ያለውን አትጨዱ
“እህሎቻችሁን በምትሰበስቡበት ጊዜ በእርሻችሁ ዳርና ዳር ያለውን ሙሉውን አትጨዱ”

ቃርሚያውንም አትልቀሙ
ይህ ሁለተኛ ጊዜ ወደኋላ በመመለስ ለመጀመሪያ ጊዜ ሳይሰበሰብ የቀረውን እንደገና መስብሰብን ያመለክታል:: የዚህ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት:: ወደኋላ ተመልሰው የቀረውን ሁሉ አይልቀሙ:: (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Leviticus 19:11

በስሜ በሐሰት አትማሉ
“እውነት ላልሆነው ነገር ስሜን በመጠቀም አትማሉ”

Leviticus 19:13

ባልጀራህን አቃጭበርብር ወይም አትቀማውም
እዚህ “ባልጀራ” “ማንኛውም ሰው” ማለት ነው ይህ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል አት “ባልጀራህን አትጉዳ ወይም አትቀማውም” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

የሙያተኛውን ደመወዝ ሳትከፍል አታሳድር
ሥራው በቀኑ በተፈጸመ ጊዜ አስሠሪው ለሠራተኛው ወዲያው መክፈል እንዳለበት እግዚአብሔር ያዝዛል የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉሙ ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Leviticus 19:15

በፍርድ ለማዛባት ምክንያት አትሁኑ
ድርብ አሉታዊ ቃላት ለአትኩሮት ተጠቅመዋል:: ይህ በአዎንታዊ መንገድ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “ሁልጊዜ ትክክለኛውን ፍርድ ይስጡ” (See Litotes/ በአሉታዊነት አዎንታዊነትን የመግለጽ አነጋገር ዘይቤ ይመልከቱ)

ለድሃ አታድላ ለባለጠጋ ልዩ አክብሮት አትስጥ
“ድሃ” እና “ባለጠጋ” የተባሉ ቃላት ሁለት ጫፍ የረገጡ አባባሎች ናቸውና ሲጣመሩ “ማንኛውም ሰው” የሚል ትርጉም ይሰጣሉ አነዚህን ጽንሰ ሀሳቦች ግልጽ ለማድረግ ይተርጉሙ:: አት: “ያለውን ገንዘብ ተመልክተህ ለማንኛውም ሰው አታድላ”:: (See Merism/ብዙውን በነጠላ መልቅ የመግለጽ አነጋገር ዘይቤ ይመልከቱ)

ለባልንጀራህ በትክክል ፍረድ
“ለማንኛውም ሰው በትክክለኛነት ፍረድ”

ሐሜት አታንዛ
“ስለሌሎች ሰዎች የሚጐዳውን እውነት ያልሆነውን መልእክቶች አታውራ”

Leviticus 19:17

ወንድምህን በልብህ አትጥላው
አንድን ሰው በቀጣይነት መጥላት ይህን ሰው ከልብ እንደመጥላት ተደርጐ ተነግሮአል:: አት: “ወንድምህን በቀጣይነት አትጥላው” (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

ባልንጀራህን በግልጽ ገሥጸው
“ኃጢአትን የሚሠራውን ሰው አርመው”

Leviticus 19:19

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል

ከሁለት ዓይነት ነገር የተሠራ ልብስ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “አንድ ሰው ከሁለት ዓይነት ነገሮች የሠራው ልብስ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 19:20

ለሌላ ከታጨች ሴት
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ሌላ ሰው ለማግባት ከተስማማች ሴት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ነገር ግን ያልተዋጀች ወይም ነጻ ያልወጣች ብትሆን
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ነገር ግን የወደፊት ባልዋ ያልዋጃትና ነጻነት ያልሰጣት ብትሆን” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ይቀጣሉ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ሴት ባሪያዋንና ከእርስዋ ጋር ያመነዘረውን ትቀጣላቸው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

አይገደሉም
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “አትግደሉአቸው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ሰውየው የበደሉን መሥዋዕት ወደ እግዚአብሔር ወደ መገናኛው ድንኳን ደጃፍ ያመጣል፡ ለበደል መሥዋዕት አውራ በግ ያመጣል
“ሰውየውም ለበደል መሥዋዕት የሚሆን አንድ አውራ በግ ወደ መገናኛው ድንኳን ደጃፍ ለእግዚአብሔር ያምጣ”

ኃጢአቱም ይቅር ይባልለታል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “የሠራውን ኃጢአት እግዚአብሔር ይቅር ይልለታል” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 19:23

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል

ከዚያም ፍሬው ለመብላት የተከለከለ መሆኑን እወቁ ለሶስት ዓመታትም የተከለከለ በመሆኑ አይበላ
እግዚአብሔር መከልከሉን ለማተኮር ደግሞ ይናገራል እናም ለመጀመሪያ ሶስት ዓመታት ፍሬ የሚሰጠውን ዛፍ ይገልጻል አት: “ከዚያም ለመጀመሪያ ሶስት ዓመታት የዛፎች ፍሬ አትብሉ” (ተዛማጅ ንጽጽር ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከዚያም ፍሬው ለመብላት የተከለከለ መሆኑን እወቁ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “እነርሱ የሚያፈሩትን ፍሬ እንዳትበሉ እኔ ከልክያችኋለሁ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ፍሬው ተከልክሎአችኋል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ፍሬውን ከልክያችኋለሁ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

አይበላ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “አትብሉ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 19:29

ሕዝብ በግልሙትና ምድሪቱ በርኩሰት እንዳትሞላ
እዚህ “ሕዝብ” እና “ምድር” የተባሉ ቃላት በዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታሉ:: አት፤ “ግልሙትናን ወይም ሌሎች ርኩሰቶችን የሚለማመዱ ሰዎች በዚያ ነገር እንደወደቁ ወይም እንደተሞሉ ተደርገው ተገልጸዋል” አት ሰዎች ግልሙትናንና ርኩስ ተግባራትን መለማመድ ጀመሩ(ተመሳሳይ ምትክ አባባሎችንና ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

Leviticus 19:31

ሙታን ወይም መናፍስት
ሁነኛ ትርጉሞች 1) ሙታንና መናፍስ የተለያዩ ናቸው 2) ይህ ድርብ ቃል ነው የሙታን መናፍስት (See Doublet/ ድርብ ቃላትንና አባባሎችን ይመልከቱ

አትፈልጉአቸው ወይም ያረክሱአችኋል
እንዚያን ሰዎች አትፈልጉአቸው፤ እንደዚያ ካደረጋችሁ ያረክሱአችኋል።

Leviticus 19:32

ተነሥለት
በአንድ ሰውፊት መነሣት የማክበር ምልክት ነው ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ::

ሽበታሙ ሰው
ከዕድሜ የተነሣ ጸጉሩ የሸበተውን ሰው ወይም ሽማግሌ ሰው ያመለክታል

Leviticus 19:35

ውሸተኛ መሥፈሪያ አትጠቀሙ
ይህ ነገሮች በሚትመዝኑበት ጊዜ በማወቅ ትክክለኛ ልከት የማይሰጡ መሣሪያዎችን የመጠቀም ልምምድን ይከለክላል::

አፍ
የእህል መለኪያ ነው (መጽሐፍ ቅዱሳዊ መለኪያዎች ይመልከቱ)

ኢን
የፈሳሽ መለኪያ ነው (መጽሐፍ ቅዱሳዊ መለኪያዎች ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 20

1 ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ **2** “ለእስራኤል ሰዎች እንዲህ በላቸው፣ ‹ከእስራኤል ሰዎች መሃል ማንም ሰው፣ ወይም ማንኛውም በእስራኤል የሚኖር መጻተኛ ከልጆቹ መሃል አንዱን ለሞሎክ ቢሰጥ በዕርግጥ ይገደል። በምድሪቱ የሚኖሩ ሰዎች በድንጋይ ይውገሩት። **3** እኔም በዚያ ሰው ላይ ፊቴን አዞርበታለሁ፣ ከህዝቡም መሃል እቆርጠዋለሁ ምክንያቱም የተቀደሰውን ስፍራዬን ለማርከስና ቅዱሱን ስሜን ለማቃለል ልጁን ለሞሎክ ሰጥቷል። **4** ያ ሰው ከልጆቹ አንዱን ለሞሎክ ሲሰጥ ዚያች ምድር ሰዎች እንዳላዩ ቢሆን፣ ባይገድሉት፣ **5** እኔ ራሴ በዚያ ሰውና በቤቱ ላይ ፊቴን አዞራለሁ፣ እኔ ቆርጬ እጥለዋለሁ እንደዚሁም ከሞሎክ ጋር በሚያመነዝረው በማንኛውም ላይ ይህን አደርጋለሁ። **6** ወደ ሙታን ጠሪዎች ዘወር የሚል፣ ወይም ከመናፍስት ጋር ከሚነጋገሩ ጋር የሚመነዝርን ሰው ፊቴን አዞርበታለሁ፤ ከህዝቡም መሃል አጠፋዋለሁ። **7** ስለዚህ ራሳችሁን ለያህዌ ስጡ ተቀደሱም፣ ምክንያቱም እኔ ያህዌ አምላካችሁ ነኝ። **8** ትዕዛዛቴን ጠብቁ አድርጓቸውም። ለራሴ የመረጥኳችሁ እኔ ያህዌ ነኝ። **9** ወይም እናቱን የሚረግም ሁሉ ይገደል። አባቱን ወይም እናቱን ረግሟልና በደለኛ ነው ሞት ይገባዋል። **10** ከሌላ ሰው ሚስት ጋር ዝሙት የፈጸመ ሰው፣ ከጎረቤቱ ሚስት፣ ጋር ያመነዘረ ይገደል አመንዝራውና አመንዝራይቱም ሁለቱም ይገደሉ። **11** ከአባቱ ሚስት ጋር ሊተኛት የወደቀ የገባ አባቱን ያዋርዳል። ልጅየውም የአባቱ ሚስትም ሁለቱም ይገደሉ። በደለኞች ናቸው ሞት ይገባቸዋል። **12** አንድ ሰው ከልጁ ሚስት ጋር ቢተኛ፣ ሁለቱም ሊገደሉ ይገባል ያልገባ ፍትወት ፈጽመዋል በደለኞች ናቸው ሞት ይገባቸዋል። **13** አንድ ወንድ ከሴት ጋር እንደሚተኛ ከሌላ ወንድ ጋር ቢተኛ፣ ሁለቱም ጸያፍ ነገር አድርገዋል። በእርግጥ ሞት ይገባቸዋል። ይገደሉ። በደለኞች ናቸው ሞት ይገባቸዋል። **14** አንድ ሰው አንዲትን ሴትና እናቲቱንም ቢያገባ፣ ይህ አሳፋሪ ነው። እርሱና ሴቲቱ ሁለቱም በእሳት ይቃጠሉ፣ ይህ ሲደረግ በመሀላችሁ ክፋት አይኖርም። **15** አንድ ሰው ከእንስሳ ጋር ቢተኛ፣ በእርግጥ ይገደል፣ እንስሳይቱንም ግደሏት። **16** አንዲት ሴት ለመገናኘት ወደ ማንኛውም አይነት እንስሳ ብተቀርብ ሴትየዋንም እንስሳውንም ግደሏቸው። በእርግጥ ሊገደሉ ይገባል። በደለኞች ናቸው ሞት ይገባቸዋል። **17** አንድ ሰው የአባቱ ልጅ ከሆነችውም ሆነ የእናቱ ልጅ ከሆነች እህቱ ጋር ቢተገኛ እህትም ከእርሱ ጋር ብትተኛ ይህ አሳፋሪ ነገር ነው። ከህዝባቸው መሃል ተለይተው ይውጡ፤ ምክንያቱም ከእህቱ ጋር ተኝቷል። በደሉን ይሸከማል። **18** አንድ ሰው አንዲትን ሴት በወር አበባዋ ወቅት አብሯት ቢተኛና ቢገናኛት፣ የደሟ ምንጭ የሆነውን የደም መፍሰሷን ገልጧል። ወንዱም ሴቷም ሁለቱም ከህዝባቸው መሃል ተለይተው ይውጡ። **19** ከእናትህ ወይም ከአባትህ እህት ጋር አትተኛ፣ ምከንያቱም የቅርብ ቤተ ዘመድህን ታዋርዳለህ። በደልህን ልትሸከም ይገባሃል። **20** አንድ ሰው ከአጎቱ ሚስት ጋር ቢተኛ አጎቱን አዋርዷል። በደላቸውን ሊሸከሙ ይገባል ያለ ልጅ ይቀራሉ። **21** አንድ ሰው የወንድሙን ሚስት ቢያገባ ይህ እርኩስ ነው ምክንያቱም ዘመዱ ሆኖ ሳለ የወንድሙን ትዳር አፍርሷል፣ ልጅ አልባ ይሆናሉ። **22** ስለዚህም ስርአቶቼንና ህግጋቶቼን ሁሉ መጠበቅ አለባችሁ፤ እንድትኖርባት ያመጣኋቸው ምድር እንዳትተፋችሁ ህግጋቴንና ሥርዓቶቼን ጠብቁ። **23** ከፊታችሁ በማባርራቸው ህዝቦች ልምዶች አትመላለሱ፣ እነርሱ እነዚህን ነገሮች ሁሉ አድርገዋል፣ እኔም እነርሱን ጠላሁ። **24** እኔ እንዲህ እላችኋለሁ፣ “ምድራቸውን ትወርሳላችሁ፣ ምድሪቱን እንድትወርሷት ለእናንተ እሰጣችኋለሁ፣ ወተትና ማር የምታፈስ ምድር ናት። ከሌላው ህዝብ የለየኋችሁ፣ እኔ ያህዌ አምላካችሁ ነኝ” **25** ስለዚህ እናንተ ንጹህ በሆኑና ንጹኅ በሆኑ እንስሳት መሃል፣ ንጹኅ በሆኑና ንጹህ ባልሆኑ ወፎች መሃል ልዩነት አድርጉ። ለእናንተ ርኩስ ናቸው ብዬ በለየኋቸው ንጹኅ ባልሆኑ እንስሳት ወይም ወፎች ወይም በማንኛውም በምድር ላይ በሚሳብ ፍጥረት ራሳችሁን አታርክሱ። **26** እኔ ያህዌ ቅዱስ እንደሆንኩ፣ ደግሞም ለእኔ ትሆኑ ዘንድ ከሌሎች ህዝቦች እንደለየኋችሁ ቅዱሳን ሁኑ። **27** ከሙታን ጋር የሚነጋገር አንድ ወንድ ወይም አንዲት ሴት ወይም ከመናፍስት ጋር የሚነጋገር በእርግጥ ይገደል። ህዝቡ በድንጋይ ወግፎ ይግደላቸው በደለኞች ናቸውና ሞት ይገባቸዋል።

Leviticus 20:1

ከልጆቹ አንዱን ለሞሎክ የሚሰጥ
ሞሎክን የሚያመልኩ ልጆቻቸውን በእሳት መሥዋዕት አድርገው ያቀርባሉ የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል አት: “ለሞሎክ እንደመስዋዕት ከልጆቹ ማንኛውን የሚገድል” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

በእርግጥ ይገደል፤እርሱንም የአገሬው ሰው በድንጋይ ይወገረው።
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “የአገረው ሕዝብ በድንጋይ ወግረው ይግደሉት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 20:3

እኔ ደግሞ በዚያ ሰው ላይ ጠላት እሆናለሁ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር የሚገልጸው “በጥብቅ መወሰኑን” ነው:: አት: “ይህን ሰው ሊጠላው በአእምሮዬ ወስኛለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ፊቴም ጠልቶታል
በቁጣ ተሞልቻለሁ

ልጁን ሰጠ
ልጁን መስዋዕት አደረገ

መቅደሴን አርክሶአልና ቅዱስ ስሜንም አቃልሎአልና
“እናም ይህን በማድረጉ መቅደሴን አርክሶአል ቅዱስ ስሜንም አቃልሎአል”

ቅዱስ ስሜንም አቃልሎአል
የእግዚአብሔር ስም እግዚአብሔርንና ምሥክርነቱን ይገልጻል:: አት: “ምሥክርነቴን አላከበራችሁም” ወይም “አላከበራችሁኝም” (ተመሣሣይ ምትክ አባባሎችና ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

አይተው ቸል ቢሉ
አይተው ቸል ቢሉ" የሚለው ሀረግ ማየት እንደተሳናቸው ይገልጻል ይህ የሚናገረው አንድን ነገር እንዳላዩ ቸል ማለትን ነው:: (ተመሳሳይ ምትክ አባባሎች ይመልከቱ)

ከሞሎክ ጋር በማመንዘር እርሱን የሚከተሉትን
ይህ ሀረግ ለእግዚአብሔር ታማኝ ያለሆኑትን ከአመንዝራዎች ጋር ያነጻጽራል:: አት: “ለእግዚአብሔር ታማኝ ያልሆኑት” (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

Leviticus 20:6

ከእነርሱም ጋር በሚያመነዝር ሰው
ይህ ሀረግ ታማኝ ያለሆኑ ሰዎችን ከአመንዝራዎች ጋር ያነጻጽራል:: አት: “ይህን በማድረጋቸው ከእኔ ሳይሆን ከመናፍስት ምክርን ይሻሉ” (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በዚያ ሰው ላይ ጠላት እሆንበታለሁ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር “በጥብቅ መወሰኑን” ይገልጻል:: አት: ያን ሰው ሊጠላው በአእምሮዬ/በሀሳቤ ወስኛለሁ:: (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ፊቴም ጠልቶታል
በቁጣ ተሞልቻለሁ

Leviticus 20:8

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል

ሥርዓተን ጠብቁ አድርጉትም
“ጠብቁ” “አድርጉ” የሚሉ ቃላት በመሠረቱ አንድ ናቸው:: እነዚህ ቃላት በአንድነት የተቀመጡት ሰዎች እግዚአብሔርን መታዘዝ እንዳለባቸው ትኩረት ለመስጠት ነው:: (Parallelism/ተመሣሣይ ተጓዳኝ ቃላት ይመልከቱ)

በእርግጥ ይገደል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ በእርግጥ ግደሉት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 20:10

አንድ ሰው ከባልንጀራው ሚስት ጋር ቢያመነዝር
የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: “ከማንም ሰው ሚስት ጋር የሚያመነዝር ሰው” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

በእርግጥ ይገደል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ በእርግጥ ሁለቱንም ግደሉት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ከአባቱ ሚስት ጋር የሚተኛ
ይህ አንድ ሰው ከአባቱ ሚስት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙት ማድረጉን ለዛ ባለ አባባል ይገልጻል:: አንዳንድ አባባሎች እንደ “አባቱ ሚስት ጋር ግብረ ሥጋ ግንኙነት አደረገ” የሚሉ በጣም ቀጥተኛ ሀረጐችን ይጠቀማሉ:: (See Euphmism/ንኣብነት ወይም ለዛ ያለ ወይም በተዘዋዋሪነት አንድን ነገር ስለሚገልጹ ቃላት ይመልከቱ)

ነውር አድርገዋል
እዚህ አንድ ሰው ከልጁ ሚስት ጋር ግብረ ሥጋ ግንኙት መፈጸም እግዚአብሔር ነውር የከፋ ኃጢአት ይለዋል:: በዘሌዋዊያን 18:23 ነውር እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

Leviticus 20:13

አንድ ሰው ወንድ ሰው ቢተኛ
ይህ ከሌላ ወንድ ጋር ግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸሙን ለዛ ባለ አባባል ይገልጻል አንዳንድ አባባሎች እንደ “አንድ ወንድ ሰው ግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጸመ” የሚሉ በጣም ቀጥተኛ ሀረጐችን ይጠቀማሉ:: (See Euphmism/ንኣብነት ወይም ለዛ ያለ ወይም በተዘዋዋሪነት አንድን ነገር ስለሚገልጹ ቃላት ይመልከቱ)

እንዲሁም ከሴት ጋር ቢተኛ
ከወንድ ጋር እንደፈጸመው ከሴት ጋር ቢፈጽም፤ አት: “እንዲሁ ከሴት ጋር ቢፈጽም” (See Simile/ተመሣሣይ አባባሎችን/ድርጊቶችን ይመልከቱ

ጸያፍ ነገር
“አሳፋሪ ነገር” ወይም “የሚዘገንን ነገር”

በእርግጥ ይገደሉ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ በእርግጥ ግደሉአቸው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ሰውየውና ሴቶቹ በእሳት ይቃጠሉ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ሰውየውንና ሴቶቹን ሁለቱንም በእሳት ይቃጥላችሁ ግደሉ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 20:15

በእርግጥ ይገደል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “በእርግጥ ግደሉት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ሴቲቱንና እንስሳውን ግደሉ በእርግጥ ይገደሉ
ሁለቱም ሀረጐች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው:: እንስሳውና ሴቲቱ እንዲሞቱ አጽንዖት የሰጣሉ:: (Parallelism/ተመሣሣይ ተጓዳኝ አባባሎች ይመልከቱ)

በእርግጥ ይገደሉ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “በእርግጥ ግደሉአቸው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 20:17

አንድ ሰው ቢተኛ
ይህ አንድ ሰው ከእህቱ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙት መፈጸሙን ለዛ ባለ አባባል ይገልጻል:: አንዳንድ አባባሎች እንደ “አንድ ሰው ግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጸመ” የሚሉ በጣም ቀጥተኛ ሀረጐችን ይጠቀማሉ:: (See Euphmism/ንኣብነት ወይም ለዛ ያለ ወይም በተዘዋዋሪነት አንድን ነገር ስለሚገልጹ ቃላት ይመልከቱ)

ከአባቱ ሴት ልጅ ወይም ከእናቱ ሴት ልጅ ጋር
ከተለየ አባት ወይም እናት ቢትሆንም ከእህቱ ጋር ግብረሥጋ ግንኙነት መፈጸም አይችልም የዚህ ዐረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት: “ሙሉ እህት ወይም ግማሽ እህት ብትሆንም” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ተቆርጦ ይወገድ ወይም ተለይቶ ይጥፋ
ከማኅበረሰቡ የተገለለው ሰው ብጣሽ ጨርቅ ከልብስ ወይም ቅርንጫፍ ከዛፍ እንደሚቆረጥ ከሕዝቡ ተቆርጦ እንደተወገደ ተደረጐ ተገልጾአል ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: ይህን ሃሳብ በዘልዋዊያን 7:20 እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ አት፤ “ያ ሰው በሕዝቡ ዘንድ አይኑር” ወይም “ያን ሰው ከሕዝቡ ለዩት” (ዘይቤያዊ አነጋገር ወይም ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

በደሉን ይሸከማል
ይህ ሀረግ ሰውየው በኃጢአቱ ይጠየቅበታል ማለት ነው:: አት: “በኃጢአቱ ተጠያቂ ነው” ወይም “ቅጡት” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

የወር አበባ ጊዜ
“ለአንድ ሴት በየወሩ ከማዕጸንዋ ደም የሚፈስስባት ጊዜ”

የፈሳሽዋን ምንጭ ገልጦአልና
በወር አበባዋ ጊዜ ከሴት ጋር ግንኙነት ማድረግን አንድ የተደበቀ ነገር ሸፋን መግለጥ ጋር ያነጻጸራል ይህ አሳፋሪ አድራጐት መሆኑ መገለጽ አለበት አት

የደምዋን ፍሳሽ በመግለጡ አሳፋሪ ነገር አድርጐአል:: (ዘይቤያዊ አገላለጽ ግምታዊ አውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ሰውየውና ሴቲቱ ሁለቱም ተለይተው ይጥፉ
ይህ ለምን መደረግ እንዳበት በግልጽ ይነገር:: ይህን አሳፋሪ ተግባር ስለፈጸሙ ሰውየው ሴቲቱም ሁለቱ ተለይተው ይጥፉ (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Leviticus 20:19

ቢተኛ
ይህ አንድ ሰው ከአባቱ እኅት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙት መፈጸሙን ለዛ ባለ አባባል ይገልጻል:: አንዳንድ አባባሎች እንደ “አንድ ሰው ግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጸመ” የሚሉ በጣም ቀጥተኛ ሀረጐችን ይጠቀማሉ:: (See Euphmism/ንኣብነት ወይም ለዛ ያለ ወይም በተዘዋዋሪነት አንድን ነገር ስለሚገልጹ ቃላት ይመልከቱ)

በደላችሁን ትሸከማላችሁ
“በደላችሁን ትሸከማላችሁ” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር “በኃጢአታችሁ ትጠየቃላችሁ” ማለት ነው:: አት: “በኃጢአታችሁ ትጠየቁታላችሁ” ወይም “እቀጣችኋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)::

ከወላጆቻቸው የወረሱትን ማንኛውንም ንብረት ከልጆቻቸው እወስዳለሁ
በብዙዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ሕተመቶች ይህ “ያለ ልጅ ይቀራሉ” ተብሎ ተተርጉሞአል::

Leviticus 20:22

እንዲትኖሩባት እናንተን የማስገባባት ምድር እንዳትተፋችሁ
ይህ ሀረግ መጥፎ ምግብን ባለመቀበል እንደሚተፋ ሰው ምድሪቱ እንደምትተፋቸው ይገልጻል ምግብን ካለመቀበል ፈንታ ምድሪቱ ሰዎችን አትቀበልም ታስወጣችኋለች:: በዘለዋዊያን 18 25 ይህን ፈሊጣዊ አባባል እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: አት “የማስገባባት ምድር እንዳትተፋችሁ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ሰውኛ አገላለጽ ይመልከቱ)

አትከተሉ
የጣዖት አድራጊዎች ተግባራት መለማመድ የእነርሱን መንገድ እንደመከተል ተደርጐ ተገልጾአል:: አት: “አትከተሉአቸው ዘይቤይዊ አነጋገር’ ይመልከቱ::

አስወጡ
አስወግዱ

Leviticus 20:24

ማርና ወተት የሚታፈሰውን አገር
ማርና ወተት መፍሰስ የሚለው ሀረግ ለሁሉ ሰው በቂ ምግብ የያዘ ባለጸጋና ፍሬያማ ማለት ነው:: አት: “ለእንስሳትና ለእርሻ እጅግ አመቺ አገር” ወይም “ፍሬያማ ምድር “ (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Leviticus 20:26

ለየኋችሁ
ለይቻችኋለሁ ወይም የራሴ አድጌአችኋለሁ

Leviticus 20:27

ጠሪ
መነጋገር የሚሞክር

በእርግጥ ይገደል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “በእርግጥ ግደሉት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 21

1 ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው “ለካህናቱ፣ ለአሮን ልጆች እንዲህ በላቸው፣ ‹ከእናንተ መሃል ማንም በመካከላችሁ በሞተ ሰው አይርከስ፣ **2** ለቅርብ ዘመድ ካልሆነ በስተቀር ማንም አይርከስ ለእናቱ እና አባቱ፣ ለወንድ ልጁና ለሴት ልጁ፣ ወይም ለወንድሙ **3** ወይም በቤቱ ከምትኖር ባል ካላገባች ልጃገረድ እህቱ በስተቀር አይርከስ። ለእርሷ ግን ራሱን ንጹህ ላያርግ ይችላል። **4** ለሌሎች ዘመዶቹ ግን እስኪረክስ ድረስ ራሱን ማርከስ የለበትም። **5** ካህናት ራሳቸውን አይላጩ ወይም የጺማቸውን ዳርቻ አይላጩ፣ አሊያም ሰውነታቸውን በስለት አይቁረጡ። **6** እነርሱ ለአምላካቸው የተለዩ ይሆኑ፣ የአምላካቸውን ስም አያቃሉ፣ ምክንያቱም ካህናቱ የአምላካቸውን “ምግብ” መስዋዕቱን ለያህዌ በእሳት ያቀርባሉ። ስለዚህም እነርሱ የተለዩ ይሁኑ። **7** ለአምላካቸው የተለዩ ስለሆኑ ማናቸውንም ጋለሞታ እና የረከሰች ሴት እንደዚሁም ከባሏ የተፋታችን ሴት ማግባት የለባቸውም። **8** የአምላክህን “ምግብ” የሚያቀርብ ነውና እርሱን መለየት አለብህ። በፊትህ ቅዱስ መሆን አለበት፣ ምክንያቱም ለራሴ የለየሁህ እኔ፣ ያህዌ ቅዱስ ነኝ። **9** ማንኛዋም የማንኛውም ካህን ሴት ልጅ ጋለሞታ ብትሆን አባቷን ታሳፍራለች። በእሳት ትቃጠል። **10** ከወንድሞቹ መሃል ሊቀ ካህን የሆነው፣ የሹመቱ ዘይት በራሱ ላይ የፈሰሰበት፣ ደግሞም የሊቀ ካህኑን ልዩ ልብሶች ለመልበስ የተጸመ ጸጉሩን ይሸፍን ልብሱን አይቅደድ። **11** ለአባቱ ወይም ለእናቱም ቢሆን እንኳን የሞተ ሰው በሚገኝበትና ራሱን በሚያረክስበት ማናቸውም ስፍራ አይሂድ። **12** ሊቀካህኑ የቤተ መቅደሱን የተቀደሰ ስፍራ ትቶ አይሂድ ወይም የአምላኩን ቅድስና አያቃል፣ ምክንያቱም በአምላኩ የቅባት ዘይት ሊቀ ካህን ሆኖ ተሾሞ ነበርና።እኔ ያህዌ ነኝ። **13** ካህኑ ድንግሊቱን ሚስቱ አድርጎ ያግባት። **14** ባሏ የሞተባትን ሴት፣ የተፋታችን ሴት፣ ወይም ጋለሞታን ሴት አያግባ፤ እንዲያ ካሉት ሴቶች መሃል አያግባ። ከራሱ ህዝብ መሃል ድንግሊቱን ብቻ ማግባት ይችላል። **15** እነዚህን ህጎች ይጠብቅ፣ በህዝቡ መሃል ልጆቹን እንዳያረክስ ህግጋቱን ይጠብቅ፣ እርሱን ለራሴ የለየሁት እኔ ያህዌ ነኝ። **16** ያህዌ እንደህ ሲል ሙሴን ተናገረው፣ **17** “አሮንን እንዲህ ብለህ ንገረው፣ ማናቸውም ከወገንህ መሀል በትወልዳቸው ውስጥ አካላዊ ጉድለት ያለበት፣ የአምላኩን ‹ምግብ› ለመሰዋት መቅረብ የለበትም። **18** ማናቸውም አካላዊ እንከን ያለበት ሰው ወደ ያህዌ መቅረብ የለበትም፣ እንደ ዐይነ ስውር፣ ሽባ የሆነ ሰው፣ አካሉ የጎደለ ወይም አካሉ የተወላገደ፣ **19** እጆቹ ወይም እግሮቹ ሽባ የሆነ፣ **20** መጻጉ ወይም ድንክ ሰው፣ ወይም በዐይኖቹ ላይ እንከን ያለበት ሰው፣ ወይም በሽታ የያዘው፣ ሞጭሟጫ፣ እከክ ያለበት ወይም ጃንደረባ ወደ ያህዌ አይቅረብ። **21** ከካህኑ ከአሮን መሃል ምንም አካላዊ ጉድለት ያለበት ሰው ለያህዌ የእሳት መስዋዕቶች ለመሰዋት አይቅረብ። አካላዊ ጉድለት ያለበት እንዲህ ያለው ሰው የአምላኩን ‹ምግብ ለማቅረብ መቅረብ የለበትም። **22** ከቅድስተ ቅዱሳኑም ሆነ ከቅዱሱ የአምላኩ ምግብ ሊበላ ግን ይችል፣ **23** ሆኖም፣ ወደ መጋረጃው መግባት የለበትም ወይም ወደ መሰዊያው አይቅረብ፣ ምክንያቱም አካላዊ ጉድለት ያለበት፣ ስለዚህም ቅዱሱን ስፍራዬን አያርክስ፣ ለራሴ የለየኋቸው እኔ ያህዌ ነኝ።” **24** ሙሴ እነዚህን ቃላት ለአሮን፣ ለልጆቹ፣ እና ለእስራኤል ሰዎች ሁሉ ተናገረ።

Leviticus 21:1

ራሱን ያረክሳል
ለእግዚአብሔር ዓላማዎች ያልተገባ ሰው ርኩስ ተብሎአል (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

በሕዝቡ ወይም በዘመዶቹ መካከል
በእራኤላዊያን መካከል

ድንግል
ያላገባች ወጣት ሴት

Leviticus 21:4

አይላጩ::
ካህናቶች የጢማቸውን ዙሪያ አይላጩ:: እዚህ ጸሐፊው ምን ለማለት እንደፈለገ ግልጽ ላይሆን ይችላል:: ሁኔኛ ትርጉሞች እነሆ 1) የጢማቸውን ከፊሉን ክፍል ይላጩ:: 2) ማንኛውንም የጢም ክፍል አይላጩ::

የተቀደሱ ይሁኑ
የተለዩ ይሁኑ

የአምላካቸውን ስም አያርክሱ
“ስም” የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ባህሪይ ያመለክታል:: አት: “የእግዚአብሔርን ምሥክርነት እታቃልሉ ወይም እግዚአብሔርን አያቃልሉ” (ተመሣሣይ ምትክ አባባሎችን ይመልከቱ)

የአምላካቸውን ምግብ
እዚህ ምግብ አጠቃላይ ምግብን ያመለክታል እግዚአብሔር እነዚህ የሚቀርቡ መሥዋዕቶችን አይመገብም:: እግዚአብሔርን የሚያስደስተውን የምግብ መሥዋዕት የሚያቀርቡ ሰዎች ቅንነትን ነው: (See Synecdoche/ክፍልን እንደ ሙሉ ሙሉን እንደክፍል የመግለጽ ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Leviticus 21:7

አያግቡ
ካህናት አያግቡ

የተቀደሱ ናቸው
ለተለዩ ናቸው

ቀድሰው
ካህኑን እንደቅዱስ ቁጠሩት

የአምላክህን ምግብ የሚያቀርብ ነውና
እዚህ ምግብ አጠቃላይ ምግብን ያመለክታል እግዚአብሔር እነዚህ የሚቀርቡ መሥዋዕቶችን አይመገብም:: እግዚአብሔር ምግብን እንደማይመገብ ግልጽ በማድረግ ይህን ይተርጉሙ (See Synecdoche/ክፍልን እንደ ሙሉ ሙሉን እንደክፍል የመግለጽ ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ቅዱስ ይሁንላችሁ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “እንደ ቅዱስ ቁጠሩት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

በእሳት ትቃጠል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “በእሳት አቃጥሉአት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 21:10

አጠቃላይ መረጃ
ካህናት ማድረግ ያለባቸው ምን እንደሆነ እግዚአብሔር ለሙሴ በናገሩ ይቀጥላል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የመቀብያ ዘይት
አዲስ ልቀካህን ለይቶ በመቀባት ሥርዓተ በዓል የሚጠቀሙበት የመቀብያ ዘይት ነው:: የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይጠቀሙ

የቅባቱ ዘይት በራሱ ላይ የሆነና የተለየ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “በራሱ ላይ የመቀብያ ዘይት ያፈሰሱበትና የለዩት ሰው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ጸጉሩ አይንጭ ልብሱን አይቅደድ
ራስ መንጨትና ልብስ መቀደድ የሀዘን ምልክቶች ናቸው:: የዚህ ዐረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Leviticus 21:13

ከወገኖቹ በካከል
ከራሱ ጐሣ ከሌዊ ጐሣ

ከወገኖቹ መካከል ዘሩን አያርክስ
የረከሰችውን ወይም ያልተገባችውን ሴት በማግባት ካህኑ የሚወልዱአቸው ልጆች ለእርሱ ያልተገቡ ይሆናሉ:: አት: “ያልተገባችውን ሴት በማግባት ያልተገቡ ልጆች አይኑሩት” (ፈሊጣዊ አነጋር ይመልከቱ)::

Leviticus 21:16

የአምላኩን ምግብ የሠዋ ዘንድ አይቅረብ
የዚህ ዐረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት: “በእግዚአብሔር መሠዊያ ላይ የሚቃጠለውን የእህል መሥዋዕት ለማቃጠል አይቅረብ” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Leviticus 21:18

ወደ እግዚአብሔር አይቅረብ
አንድ ካህን ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ዝርዝር አካላዊ መሥፈርቶችን ማሟላት አለበት:: ይህም የአካል ጐዶሎነት የኃጢአት ወጤት ወይም ማንኛውም የአካል ጐዶሎነት ያለው ሰው ወደ እግዚብሔር መቅረብ አይችልም ማለት አይደለም::

የፊቱ ገጽታ ወይም የሰውነቱ ቅርጽ የተበላሸ
“ፊቱና አካሉ የተበላሸ”

የአምላኩን ምግብ ለማቅረብ
“ምግብ” አጠቃላይ ምግብ ያመለክታል:: አት “በእግዚአብሔር መሠዊያ የሚቃጠል የእህል መሥዋዕት ለማቅረብ” (See Synecdoche/ክፍልን እንደ ሙሉ ሙሉን እንደክፍል የመግለጽ ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Leviticus 21:22

እርሱም
እዚህ “እርሱ” የአካል ጐዶሎነት ያለውን ካህን ያመለክታል

የአምላኩን ምግብ ይብላ
የአምላኩን ምግብ መሥዋዕቶች ይብላ ከመሥዋዕቶቹ ከፊሎች የካህናት ናቸውና ሊበሉ ይችላሉ

የተቀደሰውንና እጅግ ቅዱስ የሆነውን
ይህ ደግሞ መሥዋዕት ሆኖ ስለቀረበው ምግብ ነው የዚህ ዐረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል አት ከእነዚህ አንዳንድ መሥዋዕቶች በቅዱስ ሥፍራ ቀርበዋል ወይም ከእነዚህ አንዳንዶች በቅዱሳነ ቅዱሳን ቀርበዋል:: (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ለልጆቹ
“ለአሮን ልጆች”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 22

1 ያህዌ ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው፣ **2** “ለአሮንና ለልጆቹ እንዲህ በላቸው፣ የእስራኤል ሕዝብ ለእኔ ከለይዋቸው የተቀደሱ ነገሮች እንዲጠበቁ ንገራቸው። የተቀደሰው ስሜን አያርክሱ። እኔ ያህዌ ነኝ። **3** እንዲህ በላቸው፣ በዘመን ሁሉ ከትውልዳችሁ መሀል ማንም ንጹህ ያልሆነ ሰው የእስራኤል ህዝብ ለያህዌ ወደ ለየው ቅዱስ ነገሮች ቢቀርብ፣ ያ ሰው እኔ ፊት ከመቅረብ የተከለከለ ነው። እኔ ያህዌ ነኝ። **4** ከአሮን ትውልድ ውስጥ ተላላፊ የቆዳ በሽታ ያለበት፣ ወይም ከሰውቱ ፈሳሽ የሚወጣ ንጹኅ እስኪሆን ድረስ ለያህዌ ከሚቀርብ መስዋዕት አይብላ።ማንም ከሞተ ጋር በመነካካት ንጹህ ያልሆነውን ማንኛውንም ነገር የነካ፣ ወይም የዘር ፈሳሽ ካለበት ሰው ጋር በመነካካት፣ **5** ወይም የሚያረክሰውን ማናቸውንም በሆዱ የሚሳብ እንስሳ የነካ፣ ወይም ማናቸውንም የሚያረክሰውን ሰው የነካ፣ ማንኛውም አይነት እርኩሰት የሚያስከትል ነገር የነካ **6** ማናቸውንም እርኩስ ነገር የነካ ካህን እስከ ምሽት ንጹህ አይደለም። ሰውነቱን በውሃ ካልታጠበ በቀር ከተቀደሱት ነገሮች አንዳች አይብላ። **7** ፀሐይ ስትጠልቅ፣ በዚያን ሰዓት ንጹህ ይሆናል። ፀሐይ ከጠለቀች በኋላ ከተቀደሱት ነገሮች መብላት ይችላል፣ ምክንያቱም ለእርሱ የተፈቀዱ ምግብ ናቸው። **8** ሞቶ የተገኘን ማናቸውም ነገር አይብላ ወይም እርሱን የሚያረክሰውን በዱር እንስሳ የተገደለውን አይብላ። **9** ካህናት ትእዛዛቴን ይጠብቁ፣ ይህን ካላደረጉ በኃጢአት በደለኛ ይሆናሉ ደግም ስሜን በማቃለል ይሞታሉ። ለራሴ የለየኋቸው እኔ ያህዌ ነኝ፣ **10** ማንም የካህኑ ቤተሰብ ያልሆነ ሰው፣ የካህኑን እንግዶች ጨምሮ፣ ወይም ቅጥር አገልጋዮቹ ጭምር ቅዱስ ከሆነው አንዳች አይብሉ። **11** ነገር ግን ካህኑ በገንዘቡ ባሪያ ቢገዛ ያ ባሪያ ለያህዌ ከተለዩ ነገሮች መብላት ይችላል። የካህኑ ቤተሰብ አባላት እና በቤቱ የተወለዱ ባሪያዎች ከእርሱ ጋር ከእነዚህ የተቀደሱ ነገሮች መብላት ይችላሉ። **12** የካህኑ ሴት ልጅ ካህን ያልሆነ ሰው ብታገባ ለመስዋዕት ከመጣው ውስጥ አንዳች አትበላም። **13** ነገር ግን የካህኑ ሴት ልጅ ባሏ የሞተባት ከሆነች፣ ወይም ከባሏ ከተፋታች፣ እና ልጅ ያልወለደች ከሆነች እንደ ልጅነቷ ዘመን ለመኖር ወደ አባቷ ቤት ብትመለስ ከአባቷ ምግብ መብላት ትችላለች። ነገር ግን ማንም የካህን ቤተሰብ ያልሆነ ከካህናት ምግብ መብላት አይችልም። **14** አንድ ሰው ሳያውቅ ቅዱሱን ምግብ ቢበላ፣ ከወሰደው አንድ አምስተኛ ጨምሮ ለካህኑ ይመልስ። **15** የእስራኤል ህዝብ ለያህዌ የወዘወዙትንና ያቀረቡትን ቅዱስ ነገሮች ማቃለል የለባቸውም፣ **16** ያልተፈቀደላቸውን ቅዱሱን ምግብ በመብላት ራሳቸውን በደለኛ የሚያደርጋቸውን ኃጢአት እንዲሸከሙ ማድረግ የለባቸውም እነርሱን ለራሴ የለየሁት እኔ ያህዌ ነኝ” **17** ያህዌ እንዲህ አለው፣ **18** “ለአሮንና ልጆቹ እንዲሁም ለእስራኤል ሰዎች ሁሉ እንዲህ በላቸው፣ ‹ማንኛውም እስራኤላዊ፣ ወይም በእስራኤል የሚኖር ባይተዋር፣ ለስዕለትም ይሁን፣ ወይም ለበጎ ፈቃድ መስዋዕት ሲያቀርቡ፣ ወይም ለያህዌ የሚቃጠል መስዋዕት ሲያቀርቡ፣ **19** ተቀባይነትን እንዲያገኝ ከቀንድ ከብታቸው፣ ከበግ ወይም ፍየሎች ውስጥ ነውር የሌለበትን ተባዕት እንስሳ ያቅርቡ። **20** ነውር ያለበትን ግን አታቅርቡ። ይህን እኔ አልቀበልም። **21** ከከብቱ ወይም ከመንጋው ለስዕለት የህብረት መስዋዕት ለያህዌ የሚሰዋ ሁሉ፣ ወይም የበጎ ፍቃድ መስዋዕት የሚያቀርብ ተቀባይነት ያገኝ ዘንድ ነውር የሌለበትን መስዋዕት ያቅርብ። በእንስሳው ላይ እንከን አይኑርበት። **22** ዕውር፣ አንካሳ ወይም ሰንካላ፣ ወይም ኪንታሮት፣ ህመም፣ ወይም ቁስል ያለበትን እንስሳ አትሰዉ። እዚህን በእሳት መስዋዕት አድርጋችሁ በመሰዊያ ላይ ለያህዌ አታቅርቡ። **23** የበጎ ፈቃድ መስዋዕት አድርጋችሁ ጎደሎ ወይም ትንሽ በሬ ወይም በግ ማቅረብ ትችላላችሁ፣ እንዲህ ያለው መስዋዕት ግን ለስዕለት ተቀባይነት የለውም፣ **24** ለያህዌ ሰንበር ያለበት፣ የተሰበረ፣ የተዘነጠለ፣ ወይም የዘር ፍሬው የተቀጠቀጠ እንስሳ አታቅርቡ። እነዚህን በምድራችሁ አታቅርቡ፣ **25** ለእግዚአብሔር ለምግብ የሚቀርብ አድርጋችሁ ከመጻተኛው እጅ አትቀበሉ፣ ምክንያቱም በእነዚህ ላይ ጉድለቶች ወይም ነውሮች አሉባቸው እነዚህን ከእናንተ አልቀበለም።›” **26** ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ **27** “አንድ ጥጃ ወይም አንድ የበግ ወይም የፍየል ግልገል ሲወለድ፣ ከእናቱ ጋር ሰባት ቀናት ይቆይ። ከዚያም ከስምንተኛው ቀን አንስቶ፣ ለያህዌ በእሳት መስዋዕት ሆኖ መቅረብ ይችላል። **28** አንዲትን ላም ወይም ሴት በግ ከጥጃዋ ወይም ከግልገሏ ጋር በአንድ ቀን አትረዱ። **29** ለያህዌ የምስጋና መስዋዕት ስታቀርቡ፣ ተቀባይነት ባለው መንገድ አቅርቡ። **30** መስዋዕቱ በቀረበበት ቀን ይበላ። እስከ ማለዳው አንዳች አታስቀሩ። እኔ ያህዌ ነኝ። **31** ትዕዛዛቴን ጠብቁ አድርጓቸውም። እኔ ያህዌ ነኝ። **32** ቅዱስ ስሜን አታቃሉ። በቅድስናዬ በእስራኤል ህዝብ መታወቅ አለብኝ። እናንተን ለራሴ የለየሁት እኔ ያህዌ ነኝ፣ **33** አምላካችሁ እሆን ዘንድ ከግብጽ ምድር ያወጣኋችሁ እኔ ያህዌ ነኝ።”

Leviticus 22:1

ቅዱስ ከሆኑ ነገሮች እንደርቁ ንገራቸው
“ቅዱስ ከሆኑ ነገሮች ምን ጊዜ መራቅ እንዳለባቸው ንገራቸው” አንድ ካህን ርኩስ በሆነና ቅዱስ የሆኑ ነገሮች መንካት የሌለበት ሁኔታዎችን እግዚአብሔር ይገልጻል።

ቅዱስ ስሜን እንዳያረክሱ
እዚህ “ማርከስ” የሚለው ቃል አለማክበርን ይገልጻል። “ስም” የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ባህሪይ ያመለክታል:: አት “ምሥክርነቴን አላከበሩም” ወይም “አላከበሩኝም” (See Metonymy/ተዛማጅ ባህሪይ የሚቀልጽ ምትክ ቃላት የመጠቀም አነጋገር ዘይቤ ይመልከቱ)

በሚቀጥሉት ትውልዶች
“ከዛሬ/ከአሁን ጀምሮ”

ንጹህ ያልሆነ ሰው
ለእግዚአብሔር ዓላማዎች ያልተገባው ሰው ንጹህ ያልሆነ ወይም ርኩስ ተበሎአል:: (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ያ ሰው ከፊቴ ይወገድ
እግዚአብሔርን ማገልገል የማይችል ካህን ብጣሽ ጨርቅ ከልብሰ ወይም ቅርንጫፍ ከዛፍ ተቆርጦ እንደሚወገድ ከእግዚአብሔር መገኘት ተቆርጦ እንደተወገደ ተደርጐ ተገልጸአል። አት: “ያ ሰው ካህን ሆኖ ማገልገል አይችልም” (ዘይቤይዊ አገላለጽና ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 22:4

ተላላፊ የቆዳ በሽታ
ከአንድ ሰው ወደ ሌላው በቀላሉ ሊተላለፍ የሚችል የቆዳ በሽታ ነው

ከሰውነቱ የሚወጣው ፈሳሽ ነገር
“የሰውነት ፈሳሽ ነገር”

ከሰውነቱ
ይህ የሰውን ሀፍረተ አካላት ለዛነት በተሞላ አባባል ይገልጻል። በዘሌዋዊያን 15 1 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ አት ከሀፍረተ አካላቶች (see Euphemism/ንኣብነት ወይም ለዛ ያለ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ አንድን ነገር የመግለጽ ዘይቤያዊ አባባል ይመልከቱ)

እስኪነጻ ድረስ
ለእግዚአብሔር ዓላማዎች የተገባ ሰው ንጹህ ተበሎአል:: (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ማንኛውን የረከሰውን ነገር የነካ ሰው
እግዚአብሔር ለመንካ ወይም ለመብላት ያልተገባ ያለው አንድ ነገር በአካል ርኩስ ነው:: (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

አስከሬን በመንካት ደ
“ሙት አካል በመንካት”

ለእግዚአብሔር የቀረቡ መሥዋዕቶች
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “አንድ ሰው ለእግዚአብሔር ያቀረባቸው መሥዋዕቶች” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ርኩስ የሚያደርገውን በደረቱ የሚሳብ እንስሳ ወይም ርኩስ የሚያደርገውን ሰው ቢነካ
ይህ ግልጽ ሊደረግ ይችላል አት ወይም በደረት የሚሳብ እንስሳ በመንካት ወይም ርኩስ የሆነውን ሰው በመንካት የረከሰ ማንኛውም ሰው (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ካህኑ... ርኩስ ይሆናል
ለእግዚአብሔር ዓላማዎች ያልተገባው ሰው ርኩስ ተብሎአል (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

እስከ ማታ
ጸሐይ እስከሚትጠልቅ

Leviticus 22:7

ንጹህ ይሆናል
ከዚያም ካህኑ ንጹህ ይሆናል ለእግዚአብሔር ዓላማዎች የተገባው ሰው ንጹህ ተብሎአል (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

ሞቶ የተገኘ ወይም አውሬ የዘነጠለውን
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ሞቶ የተገኘውን ወይም አውሬ የገደለውን” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 22:10

አጠቃላይ መረጃ
አሮንና ልጆቹ ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር ለሙሴ ይናገራል

Leviticus 22:12

ቅዱስ የተዋጽኦ መሥዋዕቶች
“ተዋጽኦ” የሚለው ቃል እንደ ግሥ ሐረግ ሊተረጐም ይችላል:: አት: “ሰዎች ያዋጡት የተቀደሰው መሥዋዕት” (ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ)

Leviticus 22:14

የመሥዋዕቱን አንድ አምስተኛ ጨምሮ ለካህኑ ይተካ
ሁኔኛ ትርጉሞች 1)ምግቡን የበላ ሰው ተመሣሣይ ዓይነት ምግብ ይተካ 2) ስለበላው ምግብ ለካህኑ ገንዘብ ይክፈል አንድ አምስተኛ ከአምስት ተመሣሣይ ክፍሎች አንዱን ማለት ነው:: (ክፍልፋዮችን ይመልከቱ)

ወደ እግዚአብሔር ከፍ አድርገው ያቀረቡትን
እዚህ “ከፍ አድርገው” የሚለው ሀረግ ለእግዚአብሔር አንድን ነገር በአክብሮት የማቅረብ ድርጊታዊ ምልክት ነው:: “ማቅረብ” ከሚለው ጋር በመሠረቱ አንድ ነው :: አት: “አቅርበዋል” (ምልክታዊ ድርጊቶችንና ድርብ ቃላትን/doublet ይመልከቱ)

ቅጣት የሚያስከትል/በደለኛ የሚያደርጋቸውን ኃጢአት እንዳይሸከሙ
ኃጢአት ሰው እንደሚሸከመው ዕቃ ተደርጐ ተገልጾአል ሁኔኛ ትርጉሞች 1) ስለ ኃጢአታቸው ተጠያቂና በደለኛ ይሆናሉ አት ስለሠሩት ኃጢአት በደለኛ ይሆናሉ ወይም 2) ኃጢአት የሚለው ቃል ለሠሩት ኃጢአት ስለሚሰጥ ቅጣት ምትክ ቃል ነው አት በደለኞች ስለሆኑ ቅጣትን ይቀበላሉ:: (ዘይቤያዊ አነጋገርና ምትክ ተመሣሣይ ቃላት ይመልከቱ)

Leviticus 22:17

መጻተኛ
እንግዳ

ተቀባይነት እንዲኖረው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “እግዚአብሔር እንዲቀበለው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር እንዲቀበለው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 22:20

ተቀባይነት ይኖረው ዘንድ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “እኔ እንዲቀበለው” ወይም “እግዚአብሔር እንዲቀበለው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 22:22

ሰባራ ወይም ጉንድሽ
እነዚህ ቃላት በአደጋ ምክንያት የተከሰቱ የአካል ጐደሎነት ያመለክታሉ

እከክ ወይም ቋቁቻ ወይም የማመግል ቁስል
እነዚህ የቆዳ በሽታዎችን ያመለክታሉ

ተቀባይነት አይኖረውም
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “አልቀበለውም” ወይም “እግዚአብሔር አይቀበለውም” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

አካሉ ከመጠን በላይ የረዘመ ወይም ያጠረ
እነዚህ ቃላት በተፈጥሮ ችግር ያለባቸውን እንስሳት ያመለክታሉ

Leviticus 22:24

ለአምላካችሁ ምግብ አድርጋችሁ አታቅርቡ
እዚህ ምግብ አጠቃላይ ምግብ ይወክላል መሥዋዕት ሆነው የቀረቡትን እግዚአብሔር አይበላም:: ካህናት በእግዚአብሔር መሠዊያ መሥዋዕት ያቀርባሉ እናም ከሥጋው ይበላሉ:: አት: “ለእግዚአብሔር እንስሳን እንደምግብ መሥዋዕት አታቅርቡ” (See Synecdoche/ክፍልን እንደ ሙሉ ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ከባዕዳን እጅ
እጅ የሚለው ቃል መላውን ሰው ይወክላል ባእዳን እንስሳትን በማኮላሸት ለእግዚአብሔር ተቀባይነት እንዳይኖራቸው ስለሚያደርጉ እነርሱ መሥዋዕት አድርገው ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡትን እንስሳት እስራኤላዊያን እንዳይጠቀሙ ይገልጻል (see Synecdoche, ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ተቀባይነት አይኖራቸውም
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “እግዚአብሔር እነዚህን ከእናንት አይቀበልም” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Leviticus 22:26

ተቀባይነት ያለው ይሆናል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ሊትቀበሉት ትችላላችሁ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

በእሳት የሚቀርብ መሥዋዕት
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ለሚቃጠል መሥዋዕት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 22:28

ይበላ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ብሉት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

መሥዋዕት ሆኖ ቀርቦአል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “መሥዋዕት አድርጋችሁ አቅርባችኋል” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 22:31

ትእዛዛቴን ጠብቁ አድርጓቸውም
“ጠብቁ” እና “አድርጉ” የሚሉ ቃላት ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው:: ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ሕጐች እንዲታዘዙ ትኩረት የሚሰጡ ናቸው:: አት: “ሕጐቼን ታዘዙ” (See Doublet/ ተመሣሣይ ትርጉም ያላቸውን ድርብ ቃላትን ይመልከቱ)

ቅዱስ ስሜን አታርክሱ
እዚህ “ስም” የሚለው ቃል እግዚአብሔርንና ምሥክርነቱን ይወክላል፤ እናም “ማርከስ” ማለት እግዚአብሔር ፈጣሪና የዓለም ሁለ አምላክ በመሆኑ የሚገባውን ክብር አለመስጠት ነው:: (ተዛማጅ ባህርይ የሚገልጹ ምትክ ቃላት አጠቃቀም ዘይቤ ይመልከቱ/See Metonymy)

እኔ ቅዱስ መሆነ በእስራኤላዊያን ዘንድ ሊታወቅ ይገባል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “እስራኤላዊያን ቅዱስ መሆነን ማወቅ አለባቸው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 23

1 ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ 2 “ለእስራኤል ህዝብ እንዲህ በላቸው፣ ‹ለያህዌ የተለዩ የተቀደሱ ባዕሎቻችሁ፣ እንደ ቅዱስ ጉባኤዎቻችሁ የምታውጇቸው፣ የእኔ መደበኛ በዓላት ናቸው። 3 ስድስት ቀናት ትሰራላችሁ፣ ሰባተኛው ቀን ግን ሙሉ እረፍት የሚደረግበት ሰንበት ነው፣ የተቀደሰ ጉባኤ ዕለት ነው በምትኖሩበት ስፍራ ሁሉ ለያህዌ ሰንበት ስለሆነ ምንም ስራ አትስሩበት። 4 እነዚህ ለያህዌ የተመረጡ በዓላት ብላችሁ በተወሰነላቸው ጊዜ የምታውጇቸው የተቀደሱ ስብሰባዎች ናቸው። 5 በመጀመሪያው ወር በወሩ በአስራ አራተኛው ቀን ጸሀይ ስትጠልቅ የያህዌ ፋሲካ ነው። 6 በዚያው ወር በአስራ አምስተኛው ቀን የያህዌ የቂጣ በዓል ነው። ለሰባት ቀናት እርሾ ያልገባበት ቂጣ ትበላላችሁ። 7 በመጀመሪያው ቀን ለያህዌ የተለየ ጉባኤ ይኖራችኋል፣ የተለመደ ተግባራችሁን አትሰሩበትም። 8 ለሰባት ቀናት በእሳት የሚቀርብ መስዋዕት ለያህዌ ታቀርባላችሁ ሰባተኛው ቀን የተለመደ ተግባራችሁን የማታከናውኑበት ለያህዌ የተለየ ጉባኤ የሚደረግበት ነው›” 9 ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ 10 ”ለእስራኤል ሰዎች እንዲህ ብለህ ንገራቸው ‹ወደምሰጣችሁ ምድር ስትገቡ፣ እና የመጀመሪያውን አዝመራ ስትሰበስቡ፣ ከበኩራቱ ፍሬዎች ለካህኑ አንድ ነዶ ታመጣላችሁ። 11 ነዶው ተቀባይነትን እንዲያገኝ ካህኑ በያህዌ ፊት ይወዘውዘውና ለእርሱ ያቀርበዋል። ካህኑ ነዶውን የሚወዘውዘውና ለእኔ የሚያቀርበው በሰንበት ቀን ማግስት ነው። 12 ነዶውን በምትወዘውዙበትና ለእኔ በምታቀርቡበት ቀን ለያህዌ ነውር የሌለበት የአንድ አመት ወንድ ጠቦት የሚቃጠል መስዋዕት ታቀርባላችሁ። 13 የእህል ቁርባን ለያህዌ መልካም መዓዛ የሚሆን በዘይት የተለወሰ የኢፍ ሁለት አስረኛ መልካም ዱቄት፣ በእሳት የተዘጋጀ መስዋዕት፣ እና ከነዚህም ጋር የኢን አንድ አራተኛ ወይን የመጠጥ ቁርባን መቅረብ አለበት። 14 ለአምላካችሁ ይህን መስዋዕት እስከምታቀርቡበት ቀን ድረስ ምንም ዓይነት ዳቦ፣ አሊያም የተጠበሰ እሸት ወይም ለምለሙን እሸት አትብሉ። ይህ ለትወልዳችሁ ሁሉ በምትኖሩበት ስፍራ ሁሉ ቋሚ መታሰቢያ ይሆናል። 15 ከዚያ ሰንበት ቀን ማግስት አንስቶ ነዶውን ለመወዝወዝና ለያህዌ ለማቅረብ ካመጣችሁት ቀን ጀምራችሁ ሰባት ሙሉ ሳምንታት፣ ሰባት ሰንበት ትቆጥራላችሁ፣ 16 እስከ ሰባተኛው ሰንበት ማግስት ድረስ ትቆጥራላሁ። ያም ማለት ሀምሳ ቀናት ትቆጥራላችሁ። ከዚያ ለያህዌ የአዲስ አዝመራ መስዋዕት ታቀርባላችሁ። 17 ከየቤቶቻችሁ ከኢፍ ሁለት አስረኛ የተጋገሩ ሁለት ዳቦዎች ታመጣላችሁ። ከመልካም ዱቄት የሚዘጋጅና በእርሾ የተጋገሩ ይሁኑ፤ ከበኩራት ፍሬዎች የሚቀርቡ የሚወዘወዙና ለያህዌ የሚቀርቡ መስዋዕቶች ይሆናሉ። 18 ከዳቦው ጋር ነውር የሌለባቸው የአንድ ዓመት እድሜ ያላቸው ሰባት ጠቦቶች፣ አንድ ወይፈን በሬ፣ እና ሁለት አውራ በጎች ታቀርባላችሁ። እነርሱም ለያህዌ የሚቃጠል መስዋዕት ይሆናሉ፣ ከእህል ቁርባን ከመጠጥ ቁርባን ጋር፣ በእሳት የተዘጋጀ መስዋዕት እና ለያህዌ መልካም መዓዛ ያለው መስዋዕት ይሆናሉ። 19 ለኃጢአት መስዋዕት አንድ ወንድ ፍየል ታቀርባላሁ፣ እንዲሁም ለህብረት መስዋዕት የአንድ አመት ዕድሜ ያላቸው ሁለት ወንድ ጠቦቶች ለመስዋዕት ታቀርባላችሁ። 20 ካህኑ ከበኩራት ፍሬዎች ዳቦ ጋር በያህዌ ፊት ይወዘወዛቸው፣ እነርሱንም መስዋዕት አድርጎ ለእርሱ ከሁለት ጠቦቶች ጋር ያቅርብ። ለያህዌ ቅዱስ መስዋዕቶች ሲሆኑ የካህኑ ድርሻ ናቸው። 21 በዚያው ቀን ማወጅ አለባችሁ። የተቀደሰ ጉባኤ ይኖራል፣ እናም የተለመደ ስራችሁን አትሰሩም፤ ይህ የህዝባችሁ በትውልዶች ሁሉ በምትኖሩበት ሥፍራ ሁሉ ቋሚ መታሰቢያ ይሆናል። 22 የምድራችሁን ፍሬ ስትሰበስቡ፣ የእርሻችሁን ጥግጋት ሁሉ ሙሉ ለሙሉ አትሰብስቡ፣ የሰብላችን ቃርሚያ ሁሉ አትሰብስቡ። እነዚህን ለድሆችና ለመጻተኛው ተዉላቸው። እኔ ያህዌ አምላካችሁ ነኝ።” 23 ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ 24 ”ለእስራኤል ሰዎች እንዲህ በላቸው፣ ‹በሰባተኛው ወር፣ የወሩ የመጀመሪያው ቀን ለእናንተ ታላቅ እረፍት ይሆናል፣ በመለኮት ድምጽ መታሰቢያ የሚደረግበት፣ እና የተቀደሰ ጉባኤ ይሆናል። 25 የተለመደ ሥራ አትሰሩበትም፣ ለያህዌ የእሳት መስዋዕት አቅርቡበት።›” 26 ከዚያ ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ 27 “አሁን የዚህ የሰባተኛው ወር አስረኛ ቀን የስርየት ቀን ይሆናል። ለያህዌ የተለየ ጉባኤ መሆን አለበት፣ ራሳችሁን ማዋረድና ለያህዌ በእሳት መስዋዕት መሰዋት አለባችሁ። 28 በዚያን ቀን ምንም ሥራ አትስሩ ምክንያቱም በአምላካችሁ በያዌ ፊት ለራሳች ማስታሰርያ የምታቀርቡበት የስርየት ቀን ነው። 29 በዚያን ቀን ራሱን የማያዋርድ ማንም ቢሆን ከህዝቡ ተለይቶ ይጥፋ። 30 በዚያን ቀን ማናቸውንም ሥራ የሚሰራውን ማንንም ቢሆን፣ እኔ ያህዌ ከህዝቡ መሀል አጠፋዋለሁ። 31 በዚያ ቀን ማናቸውንም ዐይነት ሥራ አትሰሩም። ይህ በህዝባችሁና ትውልዶቻችሁ ሁሉ በምትኖሩባቸው ስፍራዎች ሁሉ ቋሚ መታሰቢያ ይሆናል። 32 ይህ ቀን ለእናንተ የከበረ የሰንበት ዕረፍት ይሁንላችሁ፣ እናንተም በወሩ በዘጠነኛው ቀን ራሳችን አዋርዱ። ከምሽት እስከ ምሽት ሰንበትን ጠብቁ።” 33 ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ 34 “ለእስራኤል ሰዎች እንዲህ በላቸው፣ ‹በሰባተኛው ወር አስራ አምስተኛው ቀን ለያህዌ የዳስ በዓል ይሆናል። ይህም ሰባት ቀናት ይወስዳል። 35 በመጀመሪያው ቀን ቅዱስ ጉባኤ ይኖራል። የተለመደውን ሥራ አትስሩበት። 36 ለሰባት ቀናት ለያህዌ የሚቃጠል መስዋዕት አቅርቡበት። በስምንተኛው ቀን ቅዱስ ጉባኤ ይሁን፣ እናንተም ለያህዌ የሚቃጠል መስዋዕት አቅርቡ። ይህ ክቡር ጉባኤ ነው፣ እናም አንዳች የተለመደ ሥራ አትስሩበት። 37 እነዚህ ለያህዌ የተለዩ በአላት ናቸው፣ ለያህዌ የሚቃጠል መስዋዕት ለማቅረብ ቅዱስ ጉባኤ የምታውጁበት፣ የሚቃጠል መስዋዕትና የእህል ቁርባን፣ የመስዋዕቶችና የመጠጥ ቁርባች እያንዳንዱን በየራሱ ቀን ለይታችሁ ለእግዚአብሔር የምታውጁባቸው በዓላት ናቸው። 38 እነዚህ በአላት ከያህዌ ሰንበታትና ከእናንተ ስጦታዎች ተጨማሪ ናቸው፣ ስጦቻችሁ ሁሉ፣ እና ለያህዌ የምትሰጧቸው የበጎ ፈቃድ መስዋዕቶቻችሁ ሁሉ ናቸው። 39 የዳስ በዓልን በሚመለከት፣ በሰባተኛው ወር በአስራ አምስተኛው ቀን፣ እናንተ የምድሪቱን ፍሬዎች ስትሰበስቡ ይህን የያህዌ በዓል ለሰባት ቀናት ማክበር አለባችሁ። የመጀመሪያው ቀን የፍፁም ዕረፍት ቀን ይሆናል፣ ስምንተኛው ቀንም እንደዚሁ የፍጹም ዕረፍት ቀን ይሆናል። 40 በመጀመሪያው ቀን ከዛፎቹ መልካሞቹን ፍሬዎች ውሰዱ፣ የዘንባባ ዛፎች ዝንጣፊዎች፣ እና የለምለሙ ዛፎች ቅርንጫፎች፣ ከወንዝ ዳርቻ ለምለም ዛፎች ቅርንጫፎች ወስዳችሁ በአምላካችሁ በያህዌ ፊት ለሰባት ቀናት ሃሴት ታደርጋላችሁ። 41 በየአመቱ ለሰባት ቀናት፣ ይህን በዓል ለያህዌ ታከብራላችሁ። ይህ በትውልዳችሁ ሁሉ በምትኖሩባቸው ስፍራዎች ሁሉ ቋሚ መታሰቢያ ይሆናል። ይህን በዓል በሰባተኛው ወር አክብሩ። 42 ለሰባት ቀናት በትንንሽ ዳሶች ውስጥ ትኖራላችሁ። እስራኤላዊ የሆነ ሁሉ ለሰባት ቀናት በትንንሽ ዳሶች ውስጥ ይቀመጥ፣ 43 ከእናንተ በኋላ የሚመጣው ትውልድ፣ የልጅ ልጆቻችሁ፣ እስራኤላውያንን ከግብጽ ምድር ሳወጣ በእንደዚህ ዐይነት ዳሶች ውስጥ እንዴት እንዲኖሩ እንዳደረግኩ ያውቃሉ። እኔ ያህዌ አምላካችሁ ነኝ።›” 44 በዚህ መንገድ፣ ሙሴ ለእስራኤል ህዝብ ለያህዌ የተለዩትን በዓላት አስታወቁ።

Leviticus 23:1

ለእግዚአብሔር የተቀደሱ በዓላት
እነዚህ እግዚአብሔር ቀን የመደበላቸው በዓላት ናቸው። በእነዚህ በዓላትሕዝቡ እርሱን ያመልካል። አት: “ለእግዚአብሔር የሆኑ በዓላት” ወይም “የእግዚአብሔር በዓላት”

Leviticus 23:3

አጠቃላይ መረጃ
በተለዩ ቀናትና ጊዜያት ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴ ይናገራል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሰባተኛው ቀን የዕረፍት ሰንበት ነው
ይህ ሕዝቡ መለማመድ ያለበት ነው ስድስት የሥራ ቀናት በኋላ በሰባተኛው ቀን ማረፍ አለባቸው

የተቀደሰ ጉባዔ
በዚያ ቀን እግዚአብሔርን ለማምለክ ሕዝቡ እንዲሰበሰብ የተፈለገው ያ ቀን የስብሰባ እንደሆነ ተደርጐ ተገልጾአል:: አት “የተቀደሰ ቀን፤ በአንድነት እኔን ለማምለክ የሚትሰባሰቡበት ጊዜ”

Leviticus 23:4

በተወሰነው ጊዜ
“በመደበኛው ጊዜ”

የመጀመሪያው ወር አሥራ አራተኛው ቀን በዚያ ወር በአሥራ አምስተኛው ቀን
በዕብራዊያን የቀን አቆጣጠር የመጀመሪያ ወር እግዚአብሔር እስራኤላዊያንን ከግብጽ ያመለክታል አሥራ አራተኛው ቀንና አሥራ አምስተኛው ቀን በምዕራባዊያን አቆጣጠር በሚያዝያ ወር መግቢያ ናቸው:: (የእብራይጥ ወራትና ተራ ቁጥሮችን ይመልከቱ)

ምሽት
ጸሐይ ስጠልቅ

Leviticus 23:7

በመጀመሪያው ቀን የተቀደሰ ጉባዔ አድርጉ
“መጀመሪያውን ቀን ጉባዔ ለማድረግ ለዩ” ወይም “የመጀመሪያውን ቀን እንደ ልዩና የጉባዔ ቀን ቁጠሩት”

የሚቃጠል መሥዋዕት አቅርቡ
በመሠዊያው በማቃጠል ለእግዚአብሔር ያቀርቡታል

ሰባተኛው ቀን ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ጉባዔ ነው
በዚያ ቀን እግዚአብሔርን ለማምለክ ሕዝቡ እንዲሰበሰብ የተፈለገው ያ ቀን የስብሰባ እንደሆነ ተደርጐ ተገልጾአል:: ለእግዚአብሔር የተቀደሰ/የተለየ ማለት በሚሰባሰቡበት ጊዜ እግዚአብሔርን ያመልኩታል ማለት ነው:: አት: “ሰባተኛው ቀን በአንድነት ተሰባስባችሁ እግዚአብሔርን የሚታመልኩበት ቀን ነው”

Leviticus 23:9

ተቀባይነት እንዲያገኝላችሁ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “እግዚአብሔር እንዲቀበልላችሁ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 23:12

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴ ይናገራል

ሁለት አሥረኛ የኢፍ መሥፈሪያ
አንድ ኢፍ 22 ሊትር ነው:: አት: አራት ከግማሽ ሊትር (መጽሐይ ቅዱሳዊ መለኪያዎችን ይመልከቱ)።

አንድ አራተኛ የኢን መሥፈሪያ
አንድ ኢን 3.7 ሊትር ነው:: አት: አንድ ሊትር መጽሐፍ ቅዱሳዊ መለኪያዎችን ይመልከቱ::

ቂሎ ወይም እሸት ጥራጥሬ አይሁን
የተቀቀለ ወይም ያልተቀቀለ ጥራጥሬ አይሁን ይህም ለሚመጡት ትውልዶች የዘላለም ሥርዓት ነው:: ይህም እነርሱ ሆነ ቀጣይ ትውልዳቸው ይህን ሥርዓት ለዘላለም መጠበቅ አለባቸው ማለት ነው በዘሌዋዊያን 3:17 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

Leviticus 23:15

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴ ይናገራል

ሃምሣ ቀናት
“50 ቀናት” ተራ ቁጥሮችን ይመልከቱ

ሰባተኛ
ይህ ቁጥር 7 መደበኛ ስያሜ ነው (መደበኛ ቁጥሮችን ይመልከቱ)

Leviticus 23:17

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴ ይናገራል

በሁለት አሥረኛ የኢፍ መሥፈሪያ የላመ ዱቄት በእርሾ የተጋገረ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ያም ሁለት አሥረኛ የኢፍ መሥፈሪያ የላመ ዱቄት ወስዳችሁ በእርሾ የጋገራችሁት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ሁለት አሥረኛ የኢፍ መሥፈሪያ
በግምት 4.5 ሊትር ያህላል:: አት: አራት ከግማሽ ሊትር (መጽሐፍ ቅዱሳዊ መለኪያዎች ይመልከቱ)

ለእግዚአብሔር መልካም መዓዛ ይሰጣል
በመልካም በዓዛው የእግዚአብሔር መደሰት መሥዋዕቱን በሚያቃጥለው ሰው መደሰትን ይወክላል:: አት: “እግዚአብሔር ይደሰትባችኋል” ወይም “እግዚአብሔርን ያስደስተዋል” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Leviticus 23:19

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴ ይናገራል

Leviticus 23:22

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴ ይናገራል

የምድራችሁን መከር በምትሰበስቡበት ጊዜ የእርሻችሁን ዳርና ዳር አትጨዱ
አት: “መከር በምትሰበስቡበት ጊዜ እስከ እርሻችሁ ዳርና ዳር ድረስ ያለውን ሁሉ አትሰብስቡ”

Leviticus 23:23

ሰባተኛው ወር በወሩም መጀመሪያው ቀን
ይህ በዕብራዊያን ቀን አቆጣጠር ሰባተኛ ወር ነው:: መጀመሪያው ቀን በምዕራባዊያን አቆጣጠር መስከረም ወር አጋማሽ አካባቢ ነው:: (የዕብራይስጥ ወራትንና መደበኛ ቁጥሮችን ይመልከቱ)

እረፍት ይሁንላችሁ
ለሥራ ሳይሆን ለአምልዕኮ ብቻ የተመደበ ጊዜ ማለት ነው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መሥዋዕትን በእሳት ለእግዚአብሔር አቅርቡ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን በእሳት አቅርቡ” ወይም “ለእግዚአብሔር በመሠዊያው መሥዋዕትን አቃጥሉ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 23:26

የሰባተኛው ወር አሥረኛ ቀን
ይህ በዕብራዊያን ቀን አቆጣጠር ሰባተኛ ወር ነው:: በምዕራባዊያን አቆጣጠር አሥረኛው ቀን መስከረም ወር መጨረሻ አካባቢ ነው:: (የዕብራይስጥ ወራትንና መደበኛ ቁጥሮችን ይመልከቱ)

የሥርየት ቀን
የእስራኤልን ሕዝብ ኃጢአት ሁሉ እግዚአብሔር ይቅር እንዲል በየዓመቱ በዚህ ቀን ሊቀ ካህኑ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ያቀርባል:: አት: “ለይቅርታ ወይም ለሥርየት መሥዋዕት የሚቀርብበት ቀን” (ያልታወቁትን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Leviticus 23:28

አገናኝ ዐረፍተ ነገር
በየዓመቱ ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴ ይናገራል

ከወገኖቹ መካከል ተለይቶ ይጥፋ
መገለል እንደ መቆረጥ ተነግሮአል በዘሌዋዊያ 7:20 ይህን ሀሳብ እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: አት: “ከሕዝቡ ዘንድ መወገዝ አለበት” ወይም “ሰውየውን ከሕዝቡ መለየት አለባችሁ” (ዘይቤያዊ አነጋገርና ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 23:30

አገናኝ ዐረፍተ ነገር
በየዓመቱ ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴ ይናገራል

በዚያ ዕለት
“በሥርየት ቀን”

ይህም ለሚመጡት ትውልዶች የዘላለም ሥርዓት ነው::
ይህም እነርሱ ሆነ ቀጣይ ትውልዳቸው ይህን ሥርዓት ለዘላለም መጠበቅ አለባቸው ማለት ነው። በዘሌዋዊያን 3:17 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

የዕረፍት ሰንበት
ይህ በየሳምንቱ በሰባተኛው ቀን እንደሚከበረው ሰንበት አይደለም። ይህ በሥርየት ቀን የሚከበር ልዩ ሰንበት ነው።

ራሳችሁን ዝቅ ዝቅ አድርጉ
በዚህ ዐውድ ራሳቸውን ዝቅ ማድረግ ማንኛውን ምግብ አለመብላታቸውን ያመለክታል ይህ ግልጽ ሆኖ ሊነገር ይችላል:: አት: “ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ ምግብንም አትብሉ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

በወሩም ዘጠነኛው ቀን
ይህ በዕብራይስጥ ቀን መቁጠሪያ ሰባተኛ ወር ነው በምዕራባዊያነ ቀን መቁጠሪያ ዘጠነኛው ቀን መስከረም ወር መጨረሻ አካባቢ ነው ይህም ግልጽ ሊደረግ ይችላል አት የሰባተኛው ወር ዘጠነኛ ቀን (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ከምሽት እስከ ምሽት
ከጸሐይ መግቢያ እስከሚቀጥለው ቀን ጸሐይ መግቢያ

Leviticus 23:33

ሰባተኛው ወር በገባ በአሥራ አምስተኛው ቀን
x

Leviticus 23:35

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ስለ ዳስ በዓል መመሪያዎችን ያስተላልፋል

Leviticus 23:37

አገናኝ ዐረፍተ ነገር
ሕዝቡ በየዓመቱ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴ ይናገራል

እነዚህ መደበኛ በዓላት ናቸው
በ23: 1-36 የተጠቀሱ በዓላትን ነው::

Leviticus 23:40

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር የዳስ በዓል መመሪያዎችን ያስተላልፋል

የዘንባባ ዝንጣፊ...የአኻያ ዛፍ ቅርንጫፍ
እነዚህ ቅርጫፎች የሚጠቅሙት 1) ጊዜያዊ ዳስ ለመሥራት 2) የበዓላቸውን ደስታ በማውለብለብ አንዳንድ ትርጉሞች እነዚህን ጥቅሞች ግለጽ አድርገው ሲገልጹ ሌሎች ግን ግልጽ ሳያደርጉ ይተዋሉ:: (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

የአኻያ ዛፎች
በውሃ አጠገብ የሚበቅሉ ረጅ ቀጭን ቅጠሎች ያሉአቸው ተክሎች ወይም ዛፎች ናቸው (ያልታወቁትን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Leviticus 23:42

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር የዳስ በዓል መመሪያዎችን ያስተላልፋል

ትውልዳችሁ... የልጅ ልጆቻችሁ ያውቃሉ
“የልጅ ልጆቻችሁ” ከአንድ ትውልድ ቀጥሎ የሚኖር እያንዳንዱን ትውልድ የሚገልጽ ፈሊጣዊ አባባል ነው: አት: “ትውልዳችሁ የሚመጣው ትውልድ ሁሉ ያውቃሉ ወይም ትውልዳችሁ ሁሉ ለዘላለም ያውቃል” (ፈሊጣዊ አባባሎች ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 24

1 ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ **2** “የእስራኤል ሰዎች መቅረዞች ሁልጊዜም እንዲነዱና ብርሃን እንዲሰጡ ከወይራ ፍሬ የተጠመቀ ንጹሳ ዘይት ለመቅረዞችህ ወደ አንተ እንዲያመጡ እዘዛቸው። **3** አሮን ያለማቋረጥ ከምሽት እስከ ማለዳ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ከመጋረጃው ውጭ በቃልኪዳኔ ድንጋጌ ፊት መቅረዙን በያህዌ ፊት ያለማቋረጥ ያብራ። ይህ በትውልዳች ሁሉ ቋሚ ስርዓት ይሆናል። **4** ሊቀ ካህኑ በንጹሳ ወርቅ በተሰራው የመቅረዝ መያዣ ላይ መቅረዞቹ ሁልጊዜም በያህዌ ፊት እንዲበሩ ያደርጋል። **5** መልካም ዱቄት ወስደህ አስራ ሁለት ዳቦዎች ጋግር። ለእያንዳንዱ ዳቦ የኢፍ ሁለት እስረኛ መጠን ተጠቀም። **6** ከዚያ በሁለት ረድፍ ደርድራቸው፣ በአንዱ መስመር ስድስቱን በንጹሳ ወርቅ በተሰራ ጠረጴዛ ላይ በያህዌ ፊት ደርድር። **7** በእያንዳንዱ የዳቦዎቹ ረድፍ እንደ ዳቦዎቹ ምልክት ንጹሳ ዕጣን አድርግበት። ይህ ዕጣን ለያህዌ በእሳት የሚቀርብ መስዋእት ይሆናል። **8** በእያንዳንዱ የሰንበት ዕለት ሊቀ ካህኑ የእስራኤልን ህዝብ ወክሎ የዘላለም ቃልኪዳን ምልክት አድርጎ ህብስቱን በመደበኛነት ለያህዌ ያቀርባል። **9** ይህ መስዋዕት የአሮንና የልጆቹ ድርሻ ይሆናል። ሙሉ ለሙሉ ለእርሱ የተለየና ለያህዌ በእሳት ከሚቀርበው መስዋዕት የተወሰደ ስለሆነ ቅዱስ በሆነው ስፍራ ይብሉት።” **10** እናቱ እስራኤላዊ የሆነች እና አባቱ ግብፃዊ የሆነ ልጅ በእስራኤል ህዝብ መሀል ወጣ። ይህ እስራኤላዊት ሴት ልጅ በሰፈር ውስጥ ከእስራኤላዊ ሰው ጋር ተጣላ። **11** የእስራኤላዊቷ ሴት ልጅ የያህዌን ስም ሰደበ እግዚአበሔርንም ረገመ፣ ስለዚህም ህዝቡ ወደ ሙሴ አመጡት። የእናቱ ስም ሰሎሚት ነበር፣ የደብራይ ልጅ ስትሆን ከዳን ወገን ነበረች። **12** ያህዌ ራሱ ፈቃዱን እስኪገልጽላቸው ድረስ በጥበቃ ስር አቆዩት። **13** ከዚያ ያህዌ ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው፣ **14** “እግዚአብሔርን የተሳደበውን ሰው ከሰፈር አውጡት የሰሙት ሁሉ እጆቻቸውን በላዩ ይጫኑ፣ ከዚያም መላው ጉባኤ በድንጋይ ይውገረው። **15** ለእስራኤል ሰዎች ብለህ ግለጽላቸው፣ ‹አምላኩን የተሳደበ ማንኛውም ሰው በደሉን ይሸከም። **16** ተወላጅ የሆነ እስራኤላዊም ቢሆን ወይም መጻተኛ የያህዌን ስም በስድብ ያቃለለ መላው ጉባኤ በድንጋይ ይውገሩትና ይገደል። ማንም ሰው የያህዌን ስም ቢሳደብ፣ ይገደል። **17** ሌላ ሰው የገደለ ይገደል። **18** የሌላውን ሰው እንስሳ የገደለ በገደለው ፈንታ ይክፈል፣ ህይወት ስለ ህይወት ነው። **19** አንድ ሰው ጎረቤቱን ቢጎዳ፣ እርሱ በጎረቤቱ ላይ ያደረገው ነገር ይደረግበት። **20** ስብራት ስለ ስብራት፣ አይን ስለ አይን፣ ጥርስ ስለ ጥርስ። በአንድ ሰው ላይ ጉዳት እንዳደረሰ፣ በእርሱም ላይ እንደዚያው ይደረግበት። **21** ማንም እንስሳ የገደለ ሰው መልሶ ይክፈል ማንም ሰው የገደለ ይገደል። **22** ለመጻተኛውም ይሁን ለተወላጅ እስራኤላዊው አንድ አይነት ህግ ይኑራችሁ፣ እኔ ያህዌ አምላካችሁ ነኝና።” **23** ሙሴ ለእስራኤል ሰዎች ይህን ነገራቸው፣ ሰዎቹም ያህዌን የተሳደበውን ሰው ከሰፈር ውጭ አመጡት። በድንጋይ ወገሩት። የእስራኤል ሰዎች የያህዌን ትዕዛዝ ሙሴ ባዘዘው መሠረት ፈጸሙ።

Leviticus 24:1

አጠቃላይ መረጃ
በመገናኛ ድንኳን ስላሉ ነገሮች እግዚአብሔር ለሙሴ መመሪያ ይሰጣል

ከወይራ ተጨምቆ የተጠለለ ዘይት
“ንጹህ የወይራ ዘይት”

መብራት
ለእግዚአብሔር በተቀደሰው መገናኛ ድንኳን ያለውን መብራት ያመለክታል:: ይህም ግልጽ መደረግ አለበት:: አት: “በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ያለው መብራት” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Leviticus 24:3

አገናኝ ዐረፍተ ነገር
በመገናኛ ድንኳን ስላሉ ነገሮች እግዚአብሔር ለሙሴ መመሪያ መስጠቱን ይቀጥላል

ከምስክሩ መጋረጃ ውጭ በእግዚአብሔር ፊት
“የኪዳን ምሥክር” የሚለው ሀረግ ሕግጋት የተጻፉባቸው ጽላቶች ወይም ጽላቶች የተቀመጡበት ሣጥን ያመለክታል:: እነዚህም በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ከመጋረጃው በስተጀርባ ባለው እጅግ የተቀደሰ ቦታ በሆነው ክፍል ይቀመጣሉ። አት: “ከመጋጃው ውጭ በምስክሩ ጽላቶች ፊት” ወይም “ከመጋረጃው ውጭ በኪዳኑ ሣጥን ፊት” (See Synecdoche/ ክፍል ሙሉን እንደሚወክል እናም ሙሉ ክፍልን እንደሚወክል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

መጋረጃው
በግድግዳ ላይ የሚንጠልጠል ወፍራም ጨርቅ ነው:: እንደመስኮት መጋረጃዎች ስስ አይደለም::

ከምሽት እስከ ጥዋት
“ከጸሐይ ጥልቀት እስከ ጸሐይ መውጣት” ወይም “ሌሊቱን ሙሉ”

ይህም ለሚመጡት ትውልዳችሁ የዘላለም ሥርዓት ነው::
ይህም እነርሱ ሆነ ቀጣይ ትውልዳቸው ይህን ሥርዓት ለዘላለም መጠበቅ አለባቸው ማለት ነው። በዘሌዋዊያን 3:17 ይህን እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ::

Leviticus 24:5

አገናኝ ዐረፍተ ነገር
በመገናኛ ድንኳን ስላሉ ነገሮች እግዚአብሔር ለሙሴ መመሪያ መስጠቱን ይቀጥላል

ሁለት አሥረኛ የኢፍ መስፈሪያ
4.5 ሊትር ያህላል:: አት አራት ከግማሽ ሊትር (መጽሐፍ ቅዱሳዊ መለኪያዎች ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ፊት ባለው ንጹህ ወርቅ ጠረጴዛ
ይህ ጠረጴዛ በቅዱስ ቦታ ነው ማለትም ከቅድስተ ቅዱሳኑ ፊት ነው

Leviticus 24:7

አገናኝ ዐረፍተ ነገር
በመገናኛ ድንኳን ስላሉ ነገሮች እግዚአብሔር ለሙሴ መመሪያ መስጠቱን ይቀጥላል

ንጹህ ዕጣን በጎብስቱ በእያንዳንዱ ረድፍ ላይ አኑር
ዕጣኑ በጎብስቱ ላይ ሳይሆን በየረድፉ በተቆራረሱ ጐን ሊሆን ይችላል አት ንጹህ ዕጣን በየረድፉ በተቆራረሱ አጠገብ አኑር (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

የመታሰቢያ ድርሻ ሆኖ የሚቀርብ መስዋዕት
ዕጣኑ ምን እንደሚወክል መገለጽ አለበት አት: “እያንዳንዱ የተቆራረሰው የጎብስቱ አካለ መስዋዕት እንደሆነ ይወክላል” ወይም “የተቆራረሱ አካላት መሥዋዕት መሆናቸውን ይወክላል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይህም ዕጣን በእግዚአብሔር ፊት ይጤስ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ለእግዚአብሔር ዕጣኑን አጢሱ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ይህ መሥዋዕት
“መሥዋዕት ሆኖ የቀረበው ይህ ኀብስት”

ከሚቀርበው መሥዋዕት ድርሻቸው ነው
“ከሚቀርበው መሥዋዕት ሊወስዱት የማችሉት”

ለእግዚአብሔር በእሳት የሚቀርቡ መሥዋዕቶች
“ለእግዚአብሔር የሚቃጠሉ መሥዋዕቶች” ወይም “ለእግዚአብሔር የሚታቃጥሉአቸው መሥዋዕቶች”

Leviticus 24:10

እንዲህ ሆነ
ይህ ሀረግ በመጽሐፉ አድስ ክፍል መጀመሩን ያመለክታል

የእግዚአብሔርን ስም አቃለለ ሰደበም
ሁለቱ ሀረጐች በመሠረቱ ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው:: አት: “እግዚአብሔርን በመስደብ አቃለለ” ወይም “ስለእግዚአብሔር ክፉ ነገር ተናገረ” ተመሣሣይ ንጽጽር ይመልከቱ::

ሰሎሚት
የሴትየዋ ስም ነው:: ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ::

ደብራይ
የሰውየው ስም ነው:: ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ::

Leviticus 24:13

የሰሙት ሁሉ እጆቸውን በራሱ ላይ ይጫኑበት
ሰውየው በደለኛ ሰለመሆኑ ለማሣወቅ እጆቸውን በራሱ ላይ ይጫኑበት:: (ምልክታዊ ድርጊቶችን ይመልከቱ)

Leviticus 24:15

አገናኝ ዐረፍተ ነገር
እግዚአብሔርን በረገመው ሰው ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለት እግዚአብሔር ለሙሴ መናገር ቀጠለ

የራሱን በደል ይሸከማል
ስለኃጢአቱ የሚሠቃየው በደሉን እንደተሸከመ ተደርጐ ተነግሮአል:: አት: “ስለኃጢአቱ ይሠቀይ” ወይም “ይቀጣ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

በእርግጥ ይገደል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ሕዝቡ ይግደለው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 24:17

አገናኝ ዐረፍተ ነገር
አንድ ሰው አንድን መጥፎ ነገር ቢያደርግ ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴ ይናገራል

እርሱ መገደል አለበት
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ሰውን የገደለ ሰው ግደሉት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ካሣውን ይክፈል
እንዴት ካሣውን መክፈል እንዳለበት ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት: “ሕይወት ያለውን ያንኑ ዓይነት እንስሳ በመስጠት ይተካ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ሕይወት ለሕይወት ፈንታ
የአንዱ ሕይወት የሌላኛውን እንደሚተካ የሚገልጽ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው አት የአንድ ሕይወት የሌላኛውን ይተካ (ፈሊጣዊ አገላለጽ ይጠቀሙ)

Leviticus 24:19

አገናኝ ዐረፍተ ነገር
አንድ ሰው አንድን መጥፎ ነገር ቢያደርግ ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴ ይናገራል

የዚያው ዓይነት ጉዳት ይፈጸምበት
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “የዚያው ዓይነት ጉዳት ፈጽሙበት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

በስብራት ፈንታ ስብራት በዐይን ፈንታ ዐይን በጥርስ ፈንታ ጥርስ
አነዚህ ሀረጐች አጽንዖት የሚሰጡት አንድ ሰው በሌላው ሰው ያደረሰበትን ጉዳት ተመሣሣይ ዓይነት ጉዳት በቅጣት እንዲቀበል ነው

በስብራት ፈንታ ስብራት
ይህ የተሠበሩ አጥንቶችን ያመለክታል:: አት: “በተሠበረው አጥንት ፈንታ የአጥንት ስብራት” ወይም “የአንድን ሰው አጥንት ሰብሮ እንደሆነ አጥንቱ ይሰበር” ወይም “የአንድን ሰው አጥንት ሠብሮ እንደሆን ከእርሱ አጥንቶች አንዱን ይስበሩ” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

በዓይን ፈንታ ዓይን
ይህ ዓይን እንዲጐዳ ወይም እንዲወገድ ያመለክታል:: “የአንድን ሰው አይን አጥፍቶ እንደሆነ ከአይኖቹ አንዱ ይወገድ” ወይም “የአንድን ሰው አይን አጥፍቶ እንደሆነ ከእርሱ ዓይኖች አንዱን ያጥፉ” (ፈሊጣዊ አባባል ይመልከቱ)

በጥርስ ፈንታ ጥርስ
ይህ የሚያመለክተው ጥርስን ከአገጭ መትቶ ማስወጣት ማለት ነው:: አት: “የአንድን ጥርስ አውልቆ ከሆነ ከጥርሶቹ አንድ ይውለቅ” ወይም “የአንድን ሰው ጥርስ አውልቆ ከሆነ ከጥርሶቹ አንዱን ያውልቁት” (ፈሊጣዊ አባባል ይመልከቱ)

ማንም አንድን ሰው የሚገድል ይገደል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ሰውን የሚገድለውን ሰው ግደሉት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 24:22

ሕጉን አደረጉ
“ሕጉን ታዘዙ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 25

1 ያህዌ በሲና ተራራ ላይ ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው፣ 2 “ለእስራኤላውያን እንዲህ ብለህ ንገራቸው፣ ‹እኔ ወደሰጠኋችሁ ምድር ስትገቡ፣ ምድሪቱ ለያህዌ
የሰንበት ዕረፍት ታክብር። 3 እርሻህን ለስድስት አመታት ታርሳለህ፣ ለስድስት አመታት የወይን ተክልህን እየገረዝህ ምርቱን ትሰበስባህ። 4 በሰባተኛው አመት
ግን፣ ለምድሪቱ የከበረ የሰንበት ረፍት ይሁንላት፣ ለያህዌ ሰንበት ነው። እርሻህን አታርስም። ወይም የወይን ተክልህን አትገርዝም። 5 ሳትዘራው የበቀለውን
አትጨደው፣ ያልገረዝከውን የወይን ተክል ፍሬ አትለቅመውም። ይህ ለምድሪቱ የከበረ የእረፍት አመት ነው። 6 ያልሰራህበት ምድር በሰባተኛው ዓመት ያፈራችው
ሁሉ ለአንተ ምግብ ይሆናል። አንተ፣ ወንድና ሴት ባሮችህ፣ ለቅጥረኛ አገልጋዮችህ እና ከአንተ ጋር ለሚኖሩ መጻተኞች ምግብ ይሁን። 7 ምድሪቱ ያፈራችውን ሁሉ
የቤት እንስሳትህና የዱር እንስሳት ይመገቡት። 8 ሰባት የሰንበት አመታትን ቁጠር፣ ይህም ማለት፣ ሰባት ጊዜ ሰባት አመታት ነው፣ ስለዚህ ሰባት የሰንበት
አመታት ይሆናሉ፣ ድምሩ አርባ ዘጠኝ አመታት ነው። 9 በሰባተኛው ወር በአስረኛው ቀን ከፍ ያለ የመለከት ድምጽ በሁሉም ስፍራ ንፉ። በማስተሰርያ ቀን
በምድራችሁ ላይ ሁሉ መለከት ንፉ። 10 አምሳኛውን አመት ለያህዌ ለዩና በምድሪቱ ላይ ለሚኖሩ ነዋሪዎች ሁሉ ነጻነትን አውጁ። ይህ ለእናንተ ንብረትና ባሮች
ወደየቤተሰቦቻቸው የሚመለሱበት ኢዩቤልዩ ይሆንላችኋል። 11 አምሳኛው አመት ለእናንተ ኢዮቤልዮ ይሆናል። አትተክሉም ወይም አዝመራ አትሰበስቡም።
ሳትዘሩ የበቀለውን ብሉ፣ ሳትገርዙት ወይናችሁ ያፈራውን ፍሬ ሰብስቡ። 12 ኢዮቤልዩ ነውና፣ ለእናንተ ቅዱስ ይሆናል። በሜዳ ሳትዘሩት የበቀለውን ምርት ብሉ።
13 በዚህ የኢዮቤልዩ አመት የእያንዳንዱን ሰው ንብረት መልሱለት። 14 ለጎረቤትህ ማናቸውንም መሬት ሸጠህለት ቢሆን ወይም ከጎረቤትህ ማንኛውንም መሬት
ገዝተህ ቢሆን አንዱ ሌላውን አያታል ወይም እርስ በእርሱ ያልተገባ ነገር አታድርጉ። 15 ከጎረቤትህ መሬት ብትገዛ፣ እስከ መጪው ኢዮቤልዩ ድረስ ያሉትን
አመታት እና ሊሰበሰብ የሚችለውን ሰብል ከግምት አስገባ። መሬቱን የሚሸጠው ጎረቤትህም እነዚህን ነገሮች ከግምት ያስገባል። 16 እስከ መጪው ኢዮቤልዩ
ለመድረስ ብዙ አመታት የሚቀር ከሆነ ይህ የመሬቱን ዋጋ ከፍ ያደርገዋል፣ እስከ መጪው ኢዮቤልዩ ለመድረስ ጥቂት አመታት የሚቀር ከሆነ ይህ የመሬቱን ዋጋ
ዝቅ ያደርገዋል፣ ምክንያቱም ለአዲሱ የመሬቱ ባለቤት መሬቱ የሚሰጠው አዝመራ መጠን ለሚቀጥለው ኢዮቤልዩ ለመድረስ ከቀረው አመታት ቁጥር ጋር
የተያያዘ ነው። 17 አንዳችሁ ሌላችሁን አታታሉ ወይም አንዳች ሌላችሁን አታሳስቱ፤ ይልቁንም አምላካችን አክብሩ፣ እኔ አምላካች ያህዌ ነኝ። 18 ስለዚህ
ትዕዛዛቴን ጠብቁ፣ ህግጋቴን ፈጽሙ እናም አድርጓቸው። ይህን ካደረጋችሁ በምድሪቱ ላይ በሰላም ትቀመጣላችሁ። 19 ምድሪቱ ምርቷን ትሰጣለች፣ እናንተም
ትጠግባላችሁ በዚያም በሰላም ትኖራላችሁ። 20 እንዲህ ልትሉ ትችላላችሁ “በሰባተኛው አመት ምን እንበላለን አንዘራም፣ ምርታችንንም አንሰበስብምና።” 21
በስድስተኛው አመት በረከቴ እንዲሆንላችሁ በእናንተ ላይ አዛለሁ፣ ምድሪቱ ለሶስት አመታት የሚሆን ምርት ትሰጣለች። 22 በስምንተኛው አመት ትተክላላችሁ፣
በቀደሙት አመታት ካመረታችሁትና ከሰበሰባችሁት ምግብ መብላት ትቀጥላላችሁ። 23 መሬት ለአዲስ ጊዜያዊ ባለቤቶች አይሸጥ፣ ምክንያቱም መሬቷ የእኔ
ናት። እናንተ ሁላችሁም በምድሬ ላይ እንግዶችና ጊዜያዊ ነዋሪዎች ናችሁ። 24 የያዛችሁትን ምድር ሁሉ የመቤዠት መብት እንዳላችሁ ማስተዋል አለባችሁ፤
በገዛችሁት ቤተሰብ መሬቱ ተመልሶ እንዲገዛ መፍቀድ አለባችሁ። 25 እስራኤላዊ ወገናችሁ ደሃ ቢሆንና በዚህም ምክንያት ከንብረቱ ቢሸጥ፣ የቅርብ ዘመዱ
ለአንተ የሸጠልህን ንብረት መልሶ ይግዛ። 26 ሰውዬው ንብረቱን የሚቤዥለት ምንም ዘመድ ባይኖረው፣ ነገር ግን ሀብት ቢያፈራና ንብረቱን መልሶ መቤዠት
ቢችል፣ 27 መሬቱ ከተሸጠበት ጊዜ አንስቶ ያሉትን አመታት ያሰላና ለሸጠለት ሰው ቀሪ ሂሳቡን ይክፈል። ከዚያ ወደ ራሱ ንብረት ይመለስ። 28 ነገር ግን መሬቱን
ለራሱ ማስመለስ ባይችል፣ የሸጠው መሬት እስከ ኢዮቤልዩ አመት ድረስ በገዛው ሰው ባለቤትነት ስር ይቆያል። በኢዮቤልዩ አመት፣ መሬቱ ለሸጠው ሰው
ይመለስለታል፣ ከመሰረቱ ባለቤት የነበረው ወደ ንብረቱ ይመለሳል። 29 አንድ ሰው በተቀጠረ ከተማ ውስጥ የሚገኝ ቤቱን ቢሸጥ፣ በተሸጠበት በአመት ጊዜ
ውስጥ መልሶ ሊገዛው ይችላል። 30 ለአንድ ሙሉ አመት ውስጥ ካልተቤዠ፣ በተቀጠረ ከተማ ውስጥ የሚገኘው ቤት፣ የገዛው ሰው ትውልድ የልጅ ልጅ ቋሚ
ንብረት ይሆናል። ያ ቤት በኢዮቤልዩ ተመላሽ አይሆንም። 31 ነገር ግን በዙሪያቸው ቅጥር የሌላቸው መንደሮች ቤቶች ከአገሩ የእርሻ መሬት ጋር የሚታዩ
ንብረቶች ይሆናሉ። ተመልሰው ለዋጁ ይችላሉ፣ በኢዮቤልዩ ተመላሽ ይሆናሉ። 32 ሆኖም፣ የሌዋውያን ንብረት የሆኑ ቤቶች በማንኛውም ጊዜ ለዋጁ ይችላሉ።
33 ከሌዋዊያን አንዱ የሸጠውን ቤት መልሶ ባይቤዥ፣ በከተማ ውስጥ የሚኘው የተሸጠው ቤት በኢዮቤልዩ ተመላሽ ይሆናል፣ በከተማ የሚገኝ የሌዋዊ ቤቶች
በእስራኤል ሰዎች መሀል የእነርሱ ንብረት ነው። 34 በከተማዎቻቸው ዙሪያ የሚገኙ እርሻዎች ግን አይሸጡም ምክንያቱም እነዚህ የሌዋዊያን ቋሚ ንብረት
ናቸው። 35 የአገራቸው ሰው ወገናችሁ ደሃ ቢሆን፣ ስለዚህም ራሱን መቻል ቢያቅተው፣ መጻተኛውን እንደምትረዱ እርዱት ወይም በመሀከላችሁ የሚኖርን ባዕድ
እንደምትረዱ ዕርዱት። 36 ወለድ አታስከፍሉት ወይም በማናቸውም መንገድ ከእርሱ ትርፍ ለማግኘት አትሞክሩ፣ ነገር ግን እግዚአብሔርን አክብሩ በመሆኑም
ወንድማችሁ ከእናንተ ጋር አብሮ መኖር ይችላል። 37 በወለድ ገንዘብ አታበድሩት፣ ወለድም አታስከፍሉት፣ ትርፍ ለማግኘት ምግባችሁን አትሸጡለት። 38
የከነዓንን ምድር እሰጣችሁና አምላካችሁ እሆን ዘንድ ከግብጽ ምድር ያወጣኋችሁ እኔ ያህዌ አምላካችሁ ነኝ። 39 የአገርህ ሰው ወገንህ ደሃ ቢሆንና ራሱን
ለአንተ ቢሸጥ፣ እንደ ባሪያ አታሰራው። 40 እንደ ተቀጣሪ አገልጋይ አስተናግደው። ከአንተ ጋር በጊዜያዊነት እንደሚኖር ሰው ይሁን። እስከ ኢዮቤልዩ አመት
ድረስ በአንተ ዘንድ ያገለግል። 41 ከዚያ ከአንተ ዘንድ ይሄዳል፣ እርሱና ከእርሱ ጋር ያሉ ልጆቹ፣ ወደ ራሱ ቤተሰቦችና ወደ አባቱ ይዞታ ይመለሳሉ። 42 እነርሱ
ከግብፅ ምድር ያወጣኋቸው አገልጋዮቼ ናቸውና፣ እንደ ባሪያዎች አይሸጡም። 43 በጭካኔ ልትገዛቸው አይገባም፣ ነገር ግን አምላክህን አክብር። 44 በዙሪያህ
ከሚኖሩ ህዝቦች ወንድና ሴት ባሪያዎችን ከእነርሱ መሀል መግዛት ትችላለህ። 45 በመሀልህ ከሚኖሩ መጻተኞችም ባሪያዎችን መግዛት ትችላለህ፣ ይህም
ማለት፣ ከአንተ ጋር ካሉ ቤተሰቦቻቸው፣ በምድርህ ከተወለዱ ልጆች ባሪያዎችን መግዛት ትችላለህ። እነርሱ የአንተ ሀብት ይሆናሉ። 46 እንዲህ ያሉትን ባሪያዎች
ንብረት አድርገው እንዳይዟቸው ከአንተ በኋላ ለልጆችህ ውርስ አድርገህ መስጠት ትችላለህ። ከእነርሱ ሁልጊዜም ባሪያዎችህን መግዛት ትችላለህ ነገር ግን
ከእስራኤላዊያን መሀል በወንድሞችህ ላይ በጭካኔ መግዛት የለብህም። 47 መጻተኛው ወይም ከአንተ ጋር በጊዜያዊነት ከሚኖረው እንግዳ መሃል አንዱ ባለጸጋ
ቢሆንና ከእስራኤላዊ ወገንህ መሃል አንዱ ደሃ ቢሆን፣ ለራሱም ለዚያ ባዕድ ቢሸጥ፣ ወይም ከባዕዳን ቤተሰብ መሃል ለአንዱ ቢሸት፣ 48 እስራኤላዊ ወገንህ
ከተገዛ በኋላ ተመልሶ ይገዛ። ከቤተሰቡ መሃል አንዱ ይቤዝው። 49 የሚቤዝው አጎቱ፣ የአጎቱ ልጅ፣ ሊሆን ይችላል፣ ወይም ከቤተሰቡ ውስጥ ማንኛውም
የቅርብ ዘመዱ ሊቤዝው ይችላል። ወይም፣ እርሱ ራሱ ባለፀጋ ቢሆን፣ ራሱን መቤዠት ይችላል። 50 ከገዛው ሰው ጋር ይደራደር፣ ለገዛው ሰው ራሱን ከሸጠበት
አመት ጀምረው እስከ ኢዮቤልዩ አመት ድረስ ይቁጠሩ። የመቤዣው ዋጋ ለገዛው ሰው መስራቱን መቀጠል በሚኖርበት አመታት ቁጥር ለተቀጣሪ አገልጋይ
በሚከፍለው ክፍያ ይሰላል። 51 እስከ ኢዮቤልዩ ለመድረስ ብዙ አመታት የሚኖር ከሆነ፣ ለቤዣው መልሶ የሚከፍለው የገንዘብ መጠን ከእነዚያ ቀሪ አመታት
ጋር የተመጣጠነ ይሁን። 52 ለኢዮቤልዩ አመት የቀሩት አመታት ጥቂት ከሆኑ፣ ከገዛው ሰው ጋር ለኢዮቤልዩ በቀሩት አመታት ልክ ይደራደር፣ ለመቤዣው
በቀሩት አመታት ውስጥ ይክፈለው። 53 በየዓመቱ እንደ ቅጥር ሰው ይኑር። በግፍ አለመስተናገዱን ማረጋገጥ ይገባሃል። 54 በእነዚህ መንገዶች ካልተዋጀ፣
እስከ ኢዮቤልዩ አመት ድረስ እርሱና ከእርሱ ጋር ልጆቹም አብረው ያገልግሉ። 55 እስራኤላውያን የእኔ አገልጋዮቼ ናቸው። ከግብጽ ምድር ያወጣኋቸው
አገልጋዮቼ ናቸው። እኔ ያህዌ አምላካችሁ ነኝ።”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Leviticus 25:1

ምድሪቱ ራሰዋ የእግዚአብሔርን ሰንበት ታብር
ምድር በሰንበት ማረፍን እንደሚታዘዝ ሰው ተደርጋ ተገልጻለች ሰዎች በየስንበቱ እንደሚያርፉ ሁሉ በሰባተኛው ዓመት ምድሪቱ ን ባለማረስ ሰዎች እግዚአብሔርን ያከብራሉ:: አት: “ምድሪቱ በሰባተኛው ቀን ለእግዚአብሔር እንዲትርፍ የሰንበትን ሕግ ጠብቁ” ወይም “በሰባተኛው ዓመት ምድሪቱን ባለማረስ የእግዚአብሔርን ሰንበት ጠበቁ” (ሰውኛ አገላለጽና ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

Leviticus 25:3

ወይንህን ግረዝ
ወይንን መገረዝ ጥሩ ፍሬ እንዲያፈራ የወይኑን ተክልና ቅርንጫፎቹን መቁረጥ ማለት ነው ::

ምድሪቱ የዕረፍት ሰንበት ታክብር ምድሪቱን አለማረስ ምድሪቱን እንደማሳረፍ ተነግሮአል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “የምድሪቱን የዕረፍት ሰንበት አክብሩ” ወይም “ምድሪቱን በሰባተኛው ዓመት ባለማረስ የሰንበትን ሕግ ጠብቁ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 25:5

አትሰብስብ....ከአንተ ጋር ለሚኖር ምግብ ይሁን
25: 5-6 እንደሚናገረው የእርሻው ባለቤት እንደመጀመሪያዎቹ ስድስት ዓመታት ሠራተኞችንና ምርቱን መቆጣጠር እግዚአብሔር አይፈቅድም ነገር ግን ግለሰቦች ወደ እርሻዎች በመውጣት ያገኙትን ፍሬ እንዲለቅሙና እንዲበሉ ይፈቅዳል።

ያልተገረዘው የወይን ተክል
ለስድስት ዓመታት እንደሚየደርጉት ማንም ያልተንከባከበውን ወይም ያልገረዘውን ወይን ማለት ነው ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ያልገረዙአቸው ወይኖቻችሁ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ማንኛውም ያልተሠራ እርሻ ያበቀለው
ባልተሠራ መሬት የሚበቅለው ማንኛውም

ያልተሠራ መሬት በስድስ ዓመታት እንደሚያደርጉት ማንም ያልተንከባከበው ማሣ ወይም እርሻ ማለት ነው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ያላረሳችሁት ማሣዎቻችሁ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ምድሪቱ የሚታስገኘው ማንኛውም
በምድሪቱ የሚበቅለው ማንኛውም

Leviticus 25:8

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴ መናገር ይቀጥላል

ሰባት የሰንበት ዓመታት ይሆናሉ
“ሰባት ምድብ ሰባት ዓመታት”

ዐርባ ዘጠኝ ዓመታት
“49 ዓመታት” (ቁጥሮች ይመልከቱ)

የሰባተኛው ወር አሥረኛው ቀን
በዕብራይስጥ የቀን መቁጠሪያ ሰባተኛ ወር ነው:: በምዕራባዊያን አቆጣጠር አሥሪኛው ቀን መስከረም ወር መጨረሻ አካባቢ ነው:: (የዕብራዊያን ወራትና መደበኛ ቁጥሮች ይመልከቱ)

የሥርየት ቀን
የእስራኤልን ሕዝብ ኃጢአት ሁሉ እግዚአብሔር ይቅር እንዲል በየዓመቱ በዚህ ቀን ሊቀካህኑ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ያቀርባል በዘሌዋዊያን 23:27 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

Leviticus 25:10

ሃምሳኛ ዓመት
ይህ መደበኛ ቁጥር ነው። አት: 50 ዓመት (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

ኢዩቤልዩ ይሁንላችሁ
ኢዩቤልዩ መሬትን ለርስቱ ባለቤት የሚመልሱበትና ለባሪያዎች ነጻነትን የሚያወጁበት ዓመት ነው አት: “ምርኮ የመመለስ ዓመት” ወይም “መሬት የመመለስና ለባሪያዎች የነጻነት ዓመት”

ንብረትና ባሪያዎች ይመለሳሉ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ንብረትንና ባሪያዎችን መልሱ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 25:11

ኢዩቤልዩ ይሁንላችሁ
“የምርኮ ዓመት” ወይም “መሬትን የመመለስ ዓመት” ለማን መሬትን እንደሚመልሱ ግልጽ ተደረግ አለበት:: አት: “ለእኔ መሬትን የሚትመልሱበት ዓመት” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ሳትዘሩ በሜዳ የበቀለውን ብሉ
የእርሻው ባለቤት እንደመጀመሪያዎቹ ስድስት ዓመታት ሠራተኞችንና ምርቱን መቆጣጠር እግዚአብሔር አልፈቀደም:: ነገር ግን ግለሰቦች ወደ እርሻዎች በመውጣት ያገኙትን ፍሬ እንዲለቅሙና እንዲበሉ ፈቅዶአል።

Leviticus 25:13

በዚህ በኢዩቤልዩ ዓመት
“በዚህ የመመለስ ዓመት” ወይም “በዚህ የመሬት መመለስና የባሪያ ነጻ መውጣት ዓመት”

Leviticus 25:15

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴ በናገሩን ቀጠለ

ሊሰበሰብ ይችላል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ሊትሰበሰቡ ትችላላችሁ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

የሚቀጥለው ኢዩቤልዩ
x

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Leviticus 25:18

ሥርዓቴን ጠብቁ ሕጌን ታዘዙ እናም አድርጉት
እነዚህ ሀረጐች ሁሉ በመሠረቱ ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው:: እግዚአብሔር የተናገረውን ማንኛውንም ነገር ሕዝብ እንዲታዘዝ ትኩረት ይሰጣሉ (ተመሣሣይ ተጓዳኝ ንጽጽር ይመለከቱ)

እስኪትጠግቡ ትበላላችሁ
ሆዳችሁ እስኪጠግብ በቂ ምግብ ትበላላችሁ:: አት: “እስኪትጠግቡ ትበላላችሁ” ወይም “ብዙ ምግብ ትበላላችሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Leviticus 25:20

እናንተም ትላላችሁ
እዚህ እናንተ የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል (ሁለተኛ ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

በረከተን እሰድድላችኋለሁ
እግዚአብሔር እንደሚታዘዝለት ሰው አድርጐ ስለ በረከቱ ይናገራል። አት: “በረከተን እልክላችኋለሁ ወይም እባርካችኋለሁ” (ሰውኛ አገላለጽ ይመልከቱ)

ቀድሞ ከሰበሰባችሁት
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ከሰበሰባችሁት ምግብ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 25:23

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል

መሬት ለዘለቄታው አይሸጥ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “መሬትን ለዘለቄታው ለአንድ ሰው አትሸጡ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

መሬት የሚዋጅበት እንዲኖር አድርጉ
መዋጀት የሚለው ስም “ሊዋጅ” ወይም “እንደገና ሊገዛ” በሚሉ ግሶች ሊገለጽ ይችላል:: አት: “የመሬቱ ባለቤት መሬቱን በፈለገበት ጊዜ መዋጀት እንደሚችል ይታወቅ” (ረቂቅ ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

የቅርብ ዘመዱ መጥቶ ወገኑ የሸጠውን ይዋጅለት
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “የቅርብ ዘመዱ ወገኑ የሸጠውን እንዲዋጅለት አድርጉ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 25:26

መሬት ከተሸጠ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “መሬቱን ከሸጠ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

የዋጋውን ልዩነት ለገዛው ሰው ይመልስ
ይህ ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት: “ገዢው የገዛውን ገንዘብ መጠን ይመልስልት” (ግምታም እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

የኢዩቤልዩ ዓመት
የመመለስ ዓመት መሬት የሚመለስበት ዓመት በዘሌዋዊያን 25: 10 ይህን እንዴት እንተረጐሙ ይመልከቱ::

መሬት ይመለሳል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “የገዛ ሰው መሬቱን ይመልሳል” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ወደ ርስቱ ይመለሳል
ወደ ራሱ መሬት ይመለሳል

Leviticus 25:29

ከተሸጠ በኋላ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “እርሱ ከሸጠ በኋላ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

የመዋጀት መብት
“መዋጀት” የሚለው ስም “ሊዋጅ” ወይም “እንደገና ሊገዛ” በሚሉ ግሶች ሊገለጽ ይችላል:: አት: “ሊዋጅ መብት አለው” (ረቂቅ ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ቤቱ ካልተዋጀ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “እርሱ ወይም ቤተሰቡ/ወገኑ ቤቱን ካልዋጀው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

አይወለስለትም
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “የገዛው ሰው ቤቱን አይመልስለትም” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

የኢዩቤልዩ ዓመት
“የመመለስ ዓመት” ወይም “መሬት የሚመለስበትና ባሪያዎች ነጻ የሚወጡበት ዓመት”

Leviticus 25:31

ቅጥር በዙሪያው ባልተሠራለት መንደር
አንዳንድ መንደሮች በዙሪያቸው ቅጥር የላቸውም

ለዋጁና ሊመለሱ ይችላሉ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “እነዚያን ቤቶች መዋጀት ይችላሉ እናም የገዙአቸውም ይመልሱ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

የኢዩቤልዩ ዓመት
“የመመለስ ዓመት” ወይም “መሬት የሚመለስበትና ባሪያዎች ነጻ የሚወጡበት ዓመት”

ሌዋዊያን የራሳቸው በሆኑት ከተሞች ውጥ የሚገኙትን ቤቶቻቸውን
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ሌዋዊያን በከተሞቻቸው ያሉ ቤቶቻቸውን” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ምን ጊዜም ለዋጁ ይችላሉ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ሌዋዊያን እነዚያን ምን ጊዜም ለዋጁ ይችላሉ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Leviticus 25:33

በከተማው ውስጥ የሚገኘው የተሸጠው ቤት ይመለሳል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “በከተማው ውስጥ ያለውን ቤት የገዛ ይመልሳል” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 25:35

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቡ ምን ማድረግ አንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴ ይናገራል

ወለድ አትቀበለው
ካበደርከው ተጨማሪ እንዲከፍል አታድርግ

Leviticus 25:39

እንደባሪያ አድርገህ አታስሠራው እንደ ቅጥር ሠራተኛ ቁጠረው
ባለቤቱ እስራኤላዊውን ባሪያ ሳይሆን እንደ ተከበረ ሰው ይቁጠረው ማለት ነው::

የኢዩቤልዩ ዓመት ነው
“የመመለስ ዓመት” ወይም “መሬት የሚመለስበትና ባሪያዎች ነጻ የሚወጡበት ዓመት”

Leviticus 25:42

አገናኝ ዐረፍተ ነገር
ለሕዝቡ ምን መናገር እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴ ይናገራል

አገልጋዮቼ ናቸው
የአገረው ሰዎች አገልጋዮቼ ናቸው

እንደባሪያዎች አይሸጡ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “እንደ ባሪያዎች አትሸጡአቸው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ከእነዚያ ባሪያዎችን ግዙ
“ከአሕዛብ መካከል ባሪያዎችን ግዙ”

Leviticus 25:47

አንድ እስራኤላዊ ወገን ቢሸጥ ከተሸጠ በኋላ ለዋጅ ይችላል፤ ከዘመዶቹ አንድ ይዋጀው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “መጻተኛ የእስራኤላዊውን ወገን ከገዛ በኋላ ከእስራኤላዊ ቤተሰብ አንድ ሰው ይህን ሰው ይዋጀው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 25:49

እስከ ኢዩበልዩ ዓመት
እስራኤላዊ ባሪያ ሊሆን የሚችለው እስከ ኢዩቤልዩ ዓመት ብቻ ነው እነዚህ መመሪያዎች ቢሆኑም ከኢዩቤልዩ ዓመት በፊት ነጻነቱን ለዋጅ ቢፈልግ ይችላል::

የኢዩቤልዩ ዓመት
“የመመለስ ዓመት” ወይም “መሬት የሚመለስበትና ባሪያዎች ነጻ የሚወጡበት ዓመት”

የመዋጀት ዋጋው ይተመናል
ይተመናል የሚለው ግሥ በተሻጋሪ ግሥ ሊገለጽ ይችላል አት፤ “የመዋጀቱን ወጋ ይተምናሉ ” ወይም እስራኤላዊውን ነጻ ለማውጣት ለመጻተኛው ምን ያህል መከፈል እንዳለበት ይተምናሉ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ለአንድ ቅጥር ሠራተኛ በሚከፈለው መሠረት
እስራኤላዊው ነጻነቱን ከተዋጀ እስራኤላዊው መሥራት የሚገባው ነገርግን ያልሠራውን ለማሥሠራት መጻተኛው አገልጋይ መቅጠር ይኖርበታል:: “ተከፈለ” እናም “ተቀጠረ” የሚሉ ግሶች በተሻጋሪ ግሥ መልክ ሊገለጹ ይችላሉ:: አት፤ “ለአንድ ቅጥር ሠራተኛ በሚከፈለው ተመን መሠረት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

በቀጣይ መሥራት የነበረባቸውን ዓመታት
“እስራኤላዊው መሥራት የሚገባቸው ነገርግን ያማይሠራባቸው እስከ ቀጣይ ኢዩቤልዩ ያሉ ዓመታት ቁጥር”

Leviticus 25:51

ይክፈል
እስራኤላዊው በሪያ ይክፈል

Leviticus 25:53

እንክብካቤ ይደረግለት
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “እንደባሪያ አድርጐ የገዛው መጻተኛ ይንከባከበው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

በጭካኔ አይግዛ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት፤ “ማንም አይጨክንበት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

በእነዚህ መንገዶች ካልተዋጀ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: እናም የሚዋጀው ሰው ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት፤ “ባሪያ አድርጐ ከገዛው ማንም በእነዚህ መንገዶች የማይዋጀው ከሆነ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር እና ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

በእነዚህ መንገዶች
በዚህ መንገድ

እስከ ኢዩቤልዩ ዓመት እርሱና ልጆቹ ያገልግሉ
እስራኤላዊው ባሪያና ልጆቹ እስከ ኢዩቤልዩ ዓመት መጻተኛውን ያገልግሉ እናም ከዚያ በኋላ መጻተኛው እስራኤላዊውንና ልጆቹን ነጻ ይልቀቅ

እስራኤላዊያን ለእኔ አገልጋዮቼ ናቸው
እስራኤላዊያን አገልጋዮቼ ናቸው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 26

1 “እኔ ያህዌ አምላካችሁ ነኝ፤ ጣኦታትን አታብጁ፣ የተቀረጸ ምስልንም አታቁሙ፣ ወይም ለአምልኮ የድንጋይ አምዶችን አታቁሙ፣ እንደዚሁም ልትሰግዱላቸው
ማናቸውንም የቀረፀ የድንጋይ ምስል በምድራችሁ አታድርጉ። 2 ሰንበቴን ጠብቁ የተቀደሰውን ስፍራዬን አክብሩ። እኔ ያህዌ ነኝ። 3 በህጌ ብትኖሩና ትዕዛዛቴን
ብትጠብቁ ብትታዘዟቸውም፣ 4 ዝናብን በወቅቱ እሰጣችኋለሁ፤ ምድር ምርቷን ትሰጣችኋለች፣ የሜዳ ዛፎችም ፍሬያቸውን ይሰጧችኋል። 5 የወቃችሁት እስከ
ወይን አዝመራችሁ ድረስ ይቆያል፣ የወይን ፍሬ አዝመራችሁም እስከምትዘሩበት ወቅት ድረስ ይቆያል። እንጀራችሁን በምድሪቱ ቤታችን በሰራችሁበት ጠግባችሁ
ትበላላችሁ በእረፍት ትኖራላችሁ። 6 በምድሪቱ ሰላምን እሰጣለሁ፣ ምንም ነገር ሳያስፈራችሁ ተዘልላችሁ ትቀመጣላችሁ። ከምድሪቱ አደገኛ እንስሳትን
አስወጣለሁ፣ በምድራች ሰይፍ አያልፍም። 7 ጠላቶቻችሁን ታሳድዳላችሁ፣ እነርሱም በፊታችሁ በሰይፍ ይወድቃሉ። 8 ከእናንተ አምስታችሁ መቶውን
ታሳድዳላችሁ፣ ከእናንተ መቶው አስር ሺህ ያሳድዳል፤ ጠላቶቻች በፊታችሁ በሰይፍ ይወድቃሉ። 9 ወደ እናንተ በሞገስ እመለከታለሁ፣ ፍሬያማም
አደርጋችኋለሁ፣ አበዛችሁማለሁ፤ ከእናንተ ጋር ቃል ኪዳኔን አደርጋለሁ። 10 ለረጅም ጊዜ የተከማቸ እህል ትበላላችሁ። ለአዲሱ ምርታችሁ ስፍራ
ስለሚያስፈልጋችሁ የተከማቸውን እህል ታወጣላችሁ። 11 ማደሪያዬን በመካከላችሁ አደርጋለሁ፣ እኔም እናንተን አልጣላችሁም። 12 በመካከላችሁ እሆናለሁ
አምላካችሁም እሆናለሁ፣ እናንተም የእኔ ህዝብ ትሆናላችሁ። 13 ከግብጽ ምድር ያወጣኋችው፣ እኔ ያህዌ አምላካችሁ ነኝ፣ ስለዚህም የእነርሱ ባሮች አትሆኑም።
የቀንበራችሁን ብረት ሰብሬያሁ፣ ቀና ብላችሁ እንድትሄዱ አድርጌያለሁ። 14 ነገር ግን እኔን ባትሰሙኝ፣ እነዚህን ትዕዛዛቴን ሁሉ ባትጠብቁ፣ 15 ትዕዛዛቴን
ብትተዉና ህግጋቴን ብትጠሉ፣ እናም ትዕዛዞቼን ሁሉ ሳትፈጽሙ ብትቀሩ፣ ነገር ግን ቃልኪዳኔን ብታፈርሱ 16 እነዚህን ነገሮች ብታደርጉ፣ እኔም ይህን
አደርግባችኋለሁ: ፍርሃትን እሰድባችኋለሁ፣ ዐይኖችንና ሕይወታችሁን የሚያጠፋ በሽታና ትሳት አደርስባችኋለሁ። በከንቱ ትዘራላችሁ፣ ምክንያቱም ፍሬያቸውን
ጠላቶቻችሁ ይበሉታል። 17 ፊቴን በጠላትነት ወደ እናንተ እመልሳለሁ፣ ከጠላቶቻችሁ ሀይል በታች ትወድቃላችሁ። የሚጠሏችሁ ሰዎች ይገዙዋችኋል፣ ማንም
ሳያሳድዳችሁ እንኳን ትሸሻላችሁ። 18 ትዕዛዛቴን ባትሰሙ፣ ከዚህ በኋላ ስለ ሀጢአታችሁ ሰባት እጥፍ እቀጣችኋለሁ። 19 የትእቢታችሁን ኃይል እሰብራለሁ።
ሰማይን በላያችሁ እንደ ብረት ምድራችሁንም እንደ ናስ አደርጋለሁ። 20 ብርታታችሁ ለአንዳች ነገር አይጠቅምም፣ ምክንያቱም ምድራችሁ አዝመራዋን
አትሰጥም፣ በምድራችሁ ዛፎቻችሁ ፍሬያቸውን አይሰጡም። 21 በእኔ ላይ ጠላት ሆናችሁ ብትመላለሱና ከኃጢአታችሁ በላይ እኔን ባትሰሙኝ፣ በእናንተ ላይ
ሰባት ዕጥፍ ድንጋጤ አመጣለሁ። 22 ልጆቻችን የሚነጥቁ፣ ከብቶቻችሁን የሚያጠፉ፣ እናንተን በቁጥር ጥቂት የሚያደርጉ አደገኛ አውሬዎችን
እሰድባችኋሉሁ። ስለዚህም ጎዳናዎቻችሁ በረሃ ይሆናሉ። 23 በእነዚህ ሁሉ ነገሮች ትምህርቶቼን ባትሰሙ ነገር ግን በእኔ ላይ ጠላት ሆናችሁ መመላለሳችሁን
ብትቀጥሉ፣ 24 እኔም በእናንተ ላይ ጠላት እሆናለሁ። እኔ ራሴ በሀጢአቶቻችሁ ሰባት እጥፍ እቀጣችኋለሁ። 25 ቃልኪዳን በማፍረሳችሁ በእናንተ ላይ የበቀል
ሰይፍ አመጣለሁ። በከተሞቻችሁ ውስጥ በአንድነት ትሰበሰባላችሁ፣ በዚያም በማህላችሁ በሽታን እልካለሁ፣ እናንተም በጠላቶቻችሁ ሀይል ትሸነፋላችሁ።
26 የምግብ አቅርቦታችሁን ስቆርጥ፣ አስር ሴቶች በአንድ ምድጃ እንጀራችሁን ይጋግራሉ፣ እንጀራችሁንም በሚዛን ያካፍሏችኋል። ትበላላችሁ ነገር ግን
አትጠግቡም። 27 እነዚህ ነገሮች ሁሉ ሆነው ባትሰሙት፣ ነገር ግን በእኔ ላይ በጠላትነት መመላሳችሁን ብትቀጥሉ፣ 28 እኔ በቁጣ እመጣባችኋለሁ፣
በኃጢአቶቻችሁ ሰባት እጥፍ እቀጣችኋለሁ። 29 ወንድ ልጆቻችሁን ስጋና የሴት ልጆቻችሁን ስጋ ትበላላችሁ። 30 የአምልኮ ሥፍራችሁን አጠፋለሁ፣ የእጣን
መሰዊያዎቻችሁን እቆርጣለሁ፣ በድኖቻችሁን በድን በሆኑ በጣኦቶቻችሁ ላይ እጥላለሁ፣ ደግሞም እኔ ራሴ እጸየፋችኋለሁ። 31 ከተሞቻችሁን ፍርስራሽ
አደርጋለሁ የተቀደሱ ቦታዎቻችሁን አጠፋለሁ። በመስዋዕቶቻችሁ መዓዛ ደስ አልሰንም። 32 ምድሪቱን አጠፋለሁ። በዚያ የሚኖሩ ጠላቶቻችሁ በጥፋቱ
ይደነግጣሉ። 33 በአገራት መሃል እበትናችኋለሁ፣ ሰይፌን መዝዤ አሳድዳችኋለሁ። ምድራችሁ ባድማ ትሆናለች፣ ከተሞቻችሁም ፍርስራሽ ይሆናሉ። 34
ከዚያም ምድሪቱ ባድማ ሆኖ እስከቆየች ድረስና እናንተ በጠላቶቻችሁ ምድር እስከቆያችሁ ድረስ የሰንበት ዕረፍቷን ታገኛለች። በነዚያ ጊዜያት፣ ምድሪቱ ታርፋለች
ሰንበቶቿንም ታገኛለች። 35 ፍርስራሽ ሆና እስከቆየች ድረስስ እረፍት ይሆንላታል፣ እናንተ በውስጧ ስትኖሩ በሰንበቶቻችሁ ያላገኘችውን ዕረፍት ታገኛች። 36
እናንተ በጠላቶቻችሁ ምድር በቀራችሁት ላይ በልቦቻችሁ ውስጥ ፍርሃት እሰዳለሁ፣ ስለዚህም የቅጠል ኮሰሸታ እንኳን ያስደነግጣችኋል፣ ከሰይፍ እንደሚሸሽ
ትሆናላች። ማንም ሳያሳድዳችሁ ትወድቃላች። 37 ማንም ባያሳድዳችሁም እንኳን ከሰይፍ እንደሚሸሽ ሰው አንዳችሁ በሌላችሁ ላይ ትደነቃቀፋላችሁ።
በጠላቶቻችሁ ፊት ለመቆም ምንም ሀይል አይኖራችሁም። 38 ከአገራት መሀል ተለይታችሁ ትጠፋላችሁ፣ የጠላቶቻችሁ ምድር ራሱ በፍርሃት ይሞላችኋል። 39
ከእናንተ መሃል የቀሩት በዚያ በጠላቶቻችሁ ምድር በሀጢአቶቻቸው ይጠፋሉ፣ እንዲሁም በአባቶቻቸው ሀጢአቶች ምክንያት ይጠፋሉ። 40 ሆኖም የእነርሱንና
የአባቶቻቸውን ሀጢአቶች ቢናዘዙ፣ ለእኔ ታማኝ ካልሆኑበት ክህደታቸው ቢመለሱ፣ ከእኔ ጋር ተላት ከሆኑበት አካሄዳቸው ቢመለሱ 41 እኔ በእነርሱ ላይ እንድነሳ
ካደረገንና ለጠላቶቸው ምድር አሳልፌ እንድሰጣቸው ካደረገ አካሄዳቸው ቢመለሱ ያልተገረዙ ልቦቻቸው ዝቅ ቢሉ፣ እናም በሀጢአቶቻቸው የደረሰባቸውን
ቅጣታቸውን ቢቀበሉ፣ 42 ከያዕቆብ ጋር የገባሁትን ኪዳኔን አስባለሁ፤ እንዲሁም፣ ምድሪቱን አስባለሁ። 43 ምድሪቱ ለቀዋት ስለሄዱ ባዶ ትቀራለች፣ ስለዚህ
ካለእነርሱ በተተወችበት ጊዜ በሰንበቶቿ ታርፋለች። እነርሱ በሀጢአታቸው ቅጣታቸውን ይቀበላሉ ምክንያቱም እነርሱ ራሳቸው ስርአቴን ትተዋል ህግጋቴንም
ጠልተዋል። 44 ሆኖም ከዚህ ሁሉ ባሻገር፣ በጠላቶቸው ምድር ውስጥ ሲሆኑ፣ እኔ አልተዋቸውም ሙሉ በሙሉ እስካጠፋቸውም ድረስ አልጠላቸውም፣
ደግሞም ከእነርሱ ጋር የገባሁትን ኪዳኔን አልረሳም፣ እኔ አምላካቸው ነኝ። 45 ነገር ግን ስለ እነርሱ ስል አምላካቸው እሆን ዘንድ አሕዛብ እያዩ ከግብጽ ምድር
ካወጣኋቸው ከአባቶቻቸው ጋር የገባሁትን ኪዳኔን አስባሁ። እኔ ያህዌ ነኝ።” 46 በሙሴ በኩል ያህዌ በሲና ተራራ ላይ በራሱና በእስራኤል ህዝብ መሃል
ያደረጋቸው ትዕዛዛት፣ ደንቦችና ህጎች እነዚህ ናቸው።

Leviticus 26:1

x
ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴ ይናገራል

ሰንቤታቴን ጠብቁ
የሰንቤታቴን ሕጐች ታዘዙ

Leviticus 26:3

በሥርዓቴ ብትሄዱ ትዕዛዜን ቢትጠብቁና ብትታዘዙ
ይህም አንድ አባባል በሶስት መንገዶች መግለጽ ነው እግዚአብሔር እንዲያደርጉ ያዘዙአቸውን ማንኛውም ነገር ሕዝቡ እንዲታዘዝ ትኩረት የሚሰጡ ናቸው:: አት ትዕዛዜንና ሥርዓተን በጥንቃቄ ብትጠብቁ (ተመሣሣይ ተጓዳኝ ንጽጽር ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በሥርዓቴ ቢትሄዱ
እንደሥርዓቱ መኖር በሥርዓቱ እንደመሄድ ተደርጐ ተነግሮአል አት በሥርዓቴ መሠረት ቢትመላለሱ ወይም በሥርዓቴ መሠረት ቢትኖሩ (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

Leviticus 26:5

ምግባችሁን እስኪትጠግቡ ትበላላችሁ
ምግብ የተባለው ሁሉን ምግብ ዓይነት ነው እስክትጠግቡ ሆዳችሁ እስክጠግብ ማለት ነው:: አት: እስክትጠግቡ ትበላላችሁ ወይም ብዙ ምግብ ትበላላችሁ (ፈሊጣዊ አነጋገርና Synecdoche/ ክፍል ሙሉውን ሙሉው ክፍልን እንደሚወክል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

በምድሪቱ ላይ ሰላምን እሰጣለሁ
በምድሪቱ ላይ ሰላም እንዲሆን ምክንያት አደርጋለሁ

ሰይፍም በምድራችሁ ላይ አያልፍም
እዚህ “ሰይፍ” የሚለው ቃል “የጠላት ሠራዊት” ወይም “የጠላት ጥቃት” ይወክላል:: አት “ምንም ሠራዊት አያጠቃህም” (See Metonymy/ ተዛማጅ ባሕሪይ የሚገልጹ ምትክ ቃላት ወይም አባባሎች ይመልከቱ)

Leviticus 26:9

ፊተን እመልሳለሁ
“መልካምነቴን አሳያለሁ” ወይም “እባርክሃለሁ”

እንድታፈሩና እንድትበዙ አደርጋለሁ
እነዚህ ሁለቱ ሀረጐች በትውልድ እንድበዙና ትልቅ ሕዝብ እንድሆኑ እግዚአብሔር እንደሚያደርጋቸው ያመለክታሉ (see doublet/ተመሣሣይ ትርጉም ያላቸውን ድርብ ቃላት ይመልከቱ)

ፍሬያማ አደርጋችኋለሁ
ዛፎች ብዙ ፍሬ እንደሚያፈሩ ብዙ ልጆች እንደሚኖራቸው እግዚአብሔር ይናገራል:: አት: ብዙ ልጆች እንድኖሩአችሁ አደርጋለሁ (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ለረጅም ጊዜ የተሰበሰበውን እህል ትበላላችሁ
“ለረጅም ጊዜ የምትመገቡት የተሰበሰበ ብዙ እህል ይኖራችኋል” ወይም “ለመሰብሰብና ለረጅም ጊዜ ለመብላት ብዙ እህል ይኖራችኋል”

Leviticus 26:11

ማደሪያዬን በመካከላችሁ አደርጋለሁ
መኖሪያዬን በአናንተ መካከል አደርጋለሁ

አልጸየፋችሁም
እቀበላችኋለሁ

በመካከላችሁ እመላለሳለሁ
በእነርሱ መካከል መመላለስ ከእነርሱ ጋር መኖርን ይወክላል አት ከእናንተ ጋር እኖራለሁ:: (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ቀንበራችሁን ሰብሬያለሁ
እግዚአብሔር ባርነታቸውን ከባድ ሥራን ለመሥራት በእንስሳት እንደሚደረግባቸው ቀንበር አድርጐ ይገልጻል:: ቀንበርን መስበር እነርሱን ነጻ ማውጣቱን ያመለክታል:: አት: ከባድ ሥራ እንድትሠሩ ከተደረጋችሁበት ምድር ነጻ አውጥቸአችኋለሁ:: (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Leviticus 26:14

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቡ ሕጉን ባይጠብቅ ምን እንደሚደርስበት እግዚአብሔር ለሙሴ ይናገራል

Leviticus 26:16

እነዚህን ነገሮች ቢያደርጉ
እነዚህ ነገሮች የሚለው ሀረግ በዘሌዋዊያን 26: 14-15 የተዘረዘሩ ነገሮችን ያመለክታል

የሚያስደነግጥ ትኩሳት አመጣባችኋለሁ
እዚህ ድንጋጤ እነርሱን ሊያስደነግጣቸው የሚችሉ ነገሮችን ያመለክታል:: አት: “የሚያስደነግጥ በሽታ አመጣባችኋለሁ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ሕይወታችሁን እንዲቀስፍ አሠቃያለሁ
ቀስ በቀስ ሕይወታችሁን እወስዳለሁ ወይም ቀሰ በቀስ እንዲትሞቱ አደርጋለሁ:: ይህንን የሚያደርጉት ትኩሳትና በሽታዎች ናቸው።

የሚትዘሩት በከንቱ ነው
በከንቱ ነው የሚለው ሀረግ ከሥራቸው ምንም አያገኙም ማለት ነው። አት፡ “ዘርን በከንቱ ትዘራላችሁ” ወይም “ዘርን ትዘራላችሁ ነገርግን ከዚያ ምንም አታገኙም” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ፊቴን በእናንተ ላይ አከብድባችኋለሁ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር እግዚአብሔር ለመጨከን እንደወሰነ ይናገራል:: አት: እናንተን ለመጥላት በሀሳቤ ወስኛለሁ:: (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

በጠላቶቻችሁ ድል እንዲትሁኑ አደርጋለሁ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: “ጠላቶቻችሁ ድል ያደርጓችኋል” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 26:18

ሰባት እጥፍ
እዚህ ሰባት እጥፍ በእርግጥ በቁጥሩ ልክ ማለት አይደለም እግዚአብሔር የቅጣቱን መጠን በፍጹም እንደሚጨምር ያመለክታል (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ትዕቢታችሁን እሠብራለሁ
እንዳይታበዩ ኃይልን መጠቀም ትዕቢታቸውን እንደመሥበር ተደርጐ ተነግሮአል:: አት: “ባላችሁ ጉልበት የማሰማችሁን ትዕቢት ለማቆም እቀጣችኋለሁ” ወይም “በጉልበታችሁ እንዳትታበዩ እቀጣችኋለሁ”:: (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ሰማያችሁን እንደብረት ምድራችሁንም እንደናስ አደርጋለሁ
ይህም እግዚአብሔር ዝናብ እንዳይዘንብ ያደርጋል ማለት ነው:: ይህም ሰዎች ዘርን እንዳይዘሩ ወይም እህልን እንዳያመርቱ ምድሪቱን ያደርቃል ማለት ነው:: (see Simile)

ኃይላችሁ በከንቱ ያልቃል
እጅግ ብዙ መሥራት ኃይል እስኪያልቅ ድረስ ሙሉ ጉልበትን ተጠቅሞ መሥራት ተደርጐ ተገልጾአል:: “በከንቱ ያልቃል” የሚለው ሀረግ እጅግ ብዙ ቢሠሩም ምንም አያገኙም ማለት ነው አት በከንቱ እጅግ ብዙ ትሠራላችሁ ወይም እጅግ ብዙ ትሠራላችሁ ነገርግን ብዙ በሠራችሁት ምንም አታገኙም ዘይቤያዊ አገላለጽ ወይም ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Leviticus 26:21

በእኔ ላይ ማመጽ ቢትቀጥሉ
“መቀጠል” ባሕሪይን ይገልጻል:: በእግዚአብሔር ላይ ማመጽ እግዚአብሔርን መቃወምን ወይም እርሱን አለመቀበልን ይወክላል አት: “በእኔ ላይ አታምጹ”

ሰባት እጥፍ መቅሠፍት እበትንባችኋለሁ
መበተን የሚለው ረቂቅ ስም መምታት በሚለው ግሥ ሊገለጽ ይችላል:: አት: ሳባት ጊዜ እመታችኋለሁ:: (ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ)

ሰባት እጥፍ መቅሠፍት እበትንባችኋለሁ
እግዚአብሔር በእስራኤላዊያን ላይ መቅሰፍትን ማምጣቱ በመቅሠፍት እንደሚመታቸው ወይም እንደሚጐዳቸው ተደርጐ ተገልጾአል አት: “በእናንተ ላይ ሰባት እጥፍ በላይ መቅሠፍት አመጣለሁ” ወይም “ሰባት ጊዜ በላይ በአሠቃቂነት እቀጣችኋለሁ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ሰባት እጥፍ
እዚህ ሰባት እጥፍ መደበኛ ሰባት ጊዜ አይደለም። እግዚአብሔር የቅጣቱን አሠቃቂነት ይጨምራል ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

እንደ ኃጢአታችሁ መጠን
“ኃጢአቶች” የሚለው ረቂቅ ስም “ኃጢአት” በሚለው ግሥ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “ምን ያህል ኃጢአት እንደሠራችሁ በዚያ መጠን” (ረቂቅ ስሞችን ይመልከቱ)

ልጆቻችሁን ይነጥቁአችኋል
“መንጠቅ” ማለት ማጥቃት ወይም አስገድዶ ማውጣት ነው ::አት: “ልጆቻችሁን የነጥቁአችኋል” ወይም “ልጆቻችሁን አስገድደው ይወስዱባችኋል” (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

መንገዶቻችሁም ሰው አልባ ይሆናሉ
“ማንም በመንገዶቻችሁ ላይ አይራመድም” አልባ ይሆናሉ ማለት ማንም በዚያ አይኖርም ማለት ነው

Leviticus 26:23

በዚህ ሁሉ ግን
“እንደዚህ በሚቀጣበት ጊዜ” ወይም “እንደዚህ ቢቀጣችሁ”

ቅጣቴን ባትቀበሉ
ቅጣቱን መቀበል ለዚያ ተገቢ ምላሽ መስጠት ነው:: እዚህ ተገቢ ምላሽ እግዚአብሔርን መታዘዝ ነው:: አት: “አሁንም ቅጣቴን አልተቀበላችሁም” ወይም “አሁንም አልታዘዛችሁኝም” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

በማመጽም ቢትሄዱ
መሄድ ባሕሪይን ይወክላል:: እርሱን በማመጽ መሄድ ማለት እርሱን ማመጽ ወይም እርሱን መቃወም ማለት ነው አት: “አምጸውብኛል” ወይም “ተቃውመውኛል” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

እኔም በማመጽ እሄዳለሁ
መሄድ ባሕሪይን ይወክላል:: እነርሱን በማመጽ መሄድ ማለት እነርሱን ማመጽ ወይም እርሱን መቃወም ማለት ነው አት: “ እኔም አምጽባችኋለሁ” ወይም “እቃወማቸዋለሁ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

እኔ ራሴ ሰባት ጊዜ እቀጣችኋለሁ
ቁጥር 7 ፍጹምነትን ይወክላል:: አት: “እኔ ራሴ ብዙ ጊዜ እቀጣችኋለሁ” ወይም “እኔው ራሴ እጅግ አሠቃቂ በሆነ መንገድ እቀጣችኋለሁ”

ስለ ኃጢአታችሁ
“ኃጢአቶች” የሚለው ረቂቅ ስም “ኃጢአት” በሚለው ግሥ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “በእኔ ላይ ኃጢአት መሥራታችሁን ስለቀጠላችሁ” (ረቂቅ ስሞችን ይመልከቱ)

Leviticus 26:25

በላያችሁ ሰይፍ አመጣባችኋለሁ
እዚህ “ሰይፍ” ሠራዊትን ወይም ከሠራዊት የሚደርስ ውጊያን ይወክላል:: አት: “የጠላት ሠራዊት አመጣበሃለሁ” ወይም “ጠላት እንዲዋጋህ አደርጋለሁ” (See Metonymy/ ተዛማጅ ባህሪይ የሚገልጹ ምትክ ቃላትና አባባሎች ይመልከቱ)

እበቀላችኋለሁ
እቀጣችኋለሁ

ቃል ኪዳኔን ስላፈረሳችሁ
“ቃልኪዳኔን ስላልታዘዛችሁ” ወይም “ቃል ኪዳኔን ስለማትታዘዙ”

በሚትሰበሰቡበት ጊዜ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: “ትሰበሰባላችሁ” ወይም “ትሸሻላችሁ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ለጠላትም እጅ አሳልፋችሁ ትሰጣላችሁ
እዚህ “እጅ” “ቁጥጥር ሥር” ማለት ሲሆን እናም በጠላት መሸነፍን ያመለክታል:: ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: “ለጠላቶቻችሁ እጅ አሳልፊ እሠጣችኋለሁ” ወይም “ጠላቶቻችሁ እንዲቆጣጠሯችሁ አደርጋለሁ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

የእንጀራችሁ እህል እንዲቋረጥ አደርጋለሁ
ሰዎች የሰበሰቡትን እህል ማጥፋት ወይም ሰዎች ይህን እንዳያገኙ ማድረግ የምግብ አቅርቦታቸውን ማቋረጥ ተደርጐ በተነግሮአል። አት: “የሰበሰባችሁትን እህል ባጠፋሁ ጊዜ” ወይም “ምግብን እንዳታገኙ ባደረግሁ ጊዜ” (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

ዐሥር ሴቶች በአንድ ምጣድ ላይ እንጀራ ይጋግራሉ
ይህም ጥቂት ዱቄት ከመኖር የተነሣ ብዙ ሴቶች የሚያመጡአቸው ለአንድ ምጣድ ብቻ እንደሚሆን ያመለክትል

Leviticus 26:27

ባትሰሙኝ
መስማት እርሱ ያለውን መታዘዝ ይወክላል አት ካለታዘዛችሁ (See Metonymy/ ተዛማጅ ባህሪይ የሚገልጹ ምትክ ቃላትና አባባሎች ይመልከቱ)

በአመጻችሁ ቢትሄዱ
መሄድ ባህሪይን ያመለክታል አንድን ሰው በማመጽ መሄድ እርሱን ማመጽ ወይም እርሱን መቃወም ነው። አት: ‘አመጻችሁብኝ” ወይም “ተቃወማችሁኝ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

እኔ ደግም በቁጣ እሄድባችኋለሁ
መሄድ ባህሪይን ያመለክታል አንድን ሰው በማመጽ መሄድ እርሱን ማመጽ ወይም እርሱን መቃወም ነው። አት: “እኔ አምጽባችኋለሁ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሰባት እጥፍ እቀጣችኋለሁ
እዚህ ሰባት እጥፍ መደበኛ ሰባት ጊዜን አያመለክትም እግዚአብሔር የቅጣቱን አሠቃነት መጠን ይጨምራል ማለት ነው (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Leviticus 26:29

አፈርሳለሁ ... እቆርጣለሁ... በድኖቻችሁን እጥላለሁ
እግዚአብሔር እነዚህን ለማድረግ ሠራዊትን ስለሚልክ ይህን ራሱ እንደሚያደርግ ተደርጐ ተናግሮአል አት “ለማፍረስ ... ለመቁረጥ... በድኖቻችሁን ለመጣል ሠራዊትን እልካለሁ” (See Metonymy/ ተዛማጅ ባህሪይ የሚገልጹ ምትክ ቃላትና አባባሎች ይመልከቱ)

በድኖቻችሁ
ሙት አካሎቻችሁ

በድን በሆነው ጣዖቶቻችሁ
በሕይወት ኖረው እንደሞቱ አስመስሎ እግዚአብሔር ጣዖቶቻቸው በድን እንደሆኑ ይናገራል:: አት: “ሕይወት የሌላቸው ጣዖቶቻችሁ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Leviticus 26:31

ከተሞቻችሁን አፈርሳለሁ መቅደሶቻችሁን ወና አደርጋለሁ
እነዚህ ሰዎች በእግዚአብሔር ፈንታ ጣዖቶቻቸውን ያመለኩባቸው ቦታዎች ናቸው

ጣፋጭ ሽታ ያለውን መሥዋዕቶቻችሁንም አልቀበልም
የእግዚአብሔር በመልካም መዓዛ ሽታ መደሰቱ መሥዋዕቱን በሚያቃጥሉ መደሰቱን ነው:: በዚህ ቦታ ግን ሰዎች መሥዋዕታቸውን ያቀጥላሉ ነገር ግን እግዚአብሔር በእነርሱ አልተደሰተም:: አት: “መሥዋዕቶችን ታቀርባላችሁ ወይም ታቃጥላላችሁ ነገር ግን እኔ አልደሰትባችሁም::” (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

ሰይፈን መዝዤ አሳድዳችኋለሁ
ይህ ጠላቶችን ሊኮ እንደሚዋጋቸው ያመለክታል አት ለዋጋችሁ የጠላት ሠራዊት እልክባችኋለሁ ወይም በሠይፎቻቸው ለመዋጋት የጠላት ሠራዊት እልክባችኋለሁ (See Metonymy/ ተዛማጅ ባህሪይ የሚገልጹ ምትክ ቃላትና አባባሎች ይመልከቱ)

ምድራችሁ ባድማ ከተሞቻችሁም ፍርስራሽ ይሆናሉ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: “ምድራችሁን ትተዋላችሁ እናም ጠላቶቻችሁ ከተሞቻችሁን ያፈርሳሉ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Leviticus 26:34

ከዚያም ምድሪቱ በሰንበት ዓመትዋ ትደሰታለች
ሕዝቡ በየሰባት ዓመቱ ምድሪቱን ባለማረስ የሰንበትን ሕግ መታዘዝ አለባቸው:: እግዚአብሔር ምድሪቱን የሰንበትን ሕግና እረፍት እንደታዘዘ ሰው አድረጐ ይናገራል:: አት: “ከዚያም በሰንበት ሕግ መሠረት ምድሪቱ ታርፋለች” ወይም “ከዚያም የሰንበት ሕግ እንደሚያዝዘው ምድሪቱ አትታረስም” (ሰውኛ አገላለጽ ይመልከቱ)

ምድሪቱ ታርፋለች
ያልተታረሰውን መሬት እረፍት እንዳገኘ ሰው አድርጐ እግዚአብሔር ይናገራል:: ምድሪቱ መታረስ የለባትም::

ድንጋጤ እሰድባቸዋለሁ
በእነርሱ ልብ ድንጋጤን መስደድ እነርሱን ማሳፈርን ይወክላል:: አት: “እጅግ እንዲታፍሩ አደርጋችኋለሁ”:: (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ከሰይፍ እንደሚሸሹ
ሰይፍ የሚወክለው ሰይፍን በመያዝ ሊገድል የተዘጋጀ ሰው ወይም ከጠላት ሠራዊት የሚሆን ውጊያን ነው:: አት: “በሰይፍ ከሚያሳድዳችሁ እንደሚትሸሹ” ወይም “ከጠላት ሠራዊት እንደሚትሸሹ” (See Metonymy/ ተዛማጅ ባህሪይ የሚገልጹ ምትክ ቃላትና አባባሎች ይመልከቱ)

Leviticus 26:37

ከሰይፍ እንደሚሸሹ
ሰይፍ የሚወክለው ሰይፍን በመያዝ ሊገድል የተዘጋጀ ሰው ወይም ከጠላት ሠራዊት የሚሆን ውጊያን ነው:: አት: “በሰይፍ ከሚያሳድዳችሁ እንደሚትሸሹ” ወይም “ከጠላት ሠራዊት እንደሚትሸሹ” (See Metonymy/ ተዛማጅ ባህሪይ የሚገልጹ ምትክ ቃላትና አባባሎች ይመልከቱ)

በጠላቶቻቸው ፊት መቆም
በጠላቶች ፊት መቆምበጠላቶች ጥቃትና ውጊያ አለመውደቅን ያመለክታል:: አት: “በሚዋጉአችሁ ጊዜ ጠላቶቻችሁን ለመቋቋም” ወይም “ጠላቶቻችሁን መልሳችሁ ለመዋጋት” (See Metonymy/ ተዛማጅ ባህሪይ የሚገልጹ ምትክ ቃላትና አባባሎች ይመልከቱ)

የጠላቶቻችሁም ምድር ትቦጫጭቃችኋለች
እግዚአብሔር የጠላቶቻቸውን ምድር እስራኤላዊያንን እንደሚበላ እንደ አውሬ አድርጐ ይናገራል መቦጫጨቅ የሚለው ቃል አብዛኛዎቹ እስራኤላዊያን በዚያ እንደሚሞቱ ትኩረትን ይሰጣል አት በጠላቶቻችሁ ሀገር ትሞታላችሁ (See Personification/ አንድ ነገር አካል እንዳለው የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ከእናንተ የተረፉት
ሳይሞቱ የቀሩት

በኃጢአታቸው መንምነው ያልቃሉ
በኃጢአታቸው መንመነው ማለቅ በኃጢአታቸው ምክንያት መንምነው ማለቅን ያመለክታል

የአባቶቻቸው ኃጢአት
እዚህ አባቶች የቀደሙ አባቶቻቸውን ያመለክታል (See Metonymy/ ተዛማጅ ባህሪይ የሚገልጹ ምትክ ቃላትና አባባሎች ይመልከቱ)

Leviticus 26:40

የአባቶቻቸው ኃጢአት
እዚህ አባቶች የቀደሙ አባቶቻቸውን ያመለክታል (See Metonymy/ ተዛማጅ ባህሪይ የሚገልጹ ምትክ ቃላትና አባባሎች ይመልከቱ)

ለእኔ ላይ ያልታመኑበትንና በእኔ ላይ ያመጹበትን
“ለእኔ ታማኝ ባልሆኑበት መንገድ እናም ለእነርሱ መልካም ሆኜ ሳለሁ በእኔ ላይ ያመጹበትን”

እኔን በማመጽ የሄዱበት
መሄድ ባህሪይን ያመለክታል አንድን ሰው በማመጽ መሄድ እርሱን ማመጽ ወይም እርሱን መቃወም ነው:: አት: ‘አመጹብኝ” ወይም “ተቃወሙኝ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እኔ ጠላት እሆንባቸዋለሁ
ይህ እቃወማችኋለሁ የሚለውን ይወክላል አት እቃወማቸዋሁ(ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ያልተገረዘው ልባቸው ቢዋረድ
እዚህ “ያልተገረዘ ልብ” ሙሉውን ሰው ያመለክታል:: አት: “በልቤ ደንዳናነት ካለመዘዝ ፈንታ ራሳቸውን ቢያዋርዱ” (See Synecdoche)

በዚያን ጊዜ ከያዕቆብ ጋር የገባሁትን ኪዳኔን ከይስሐቅም ጋር የገባሁትን ኪዳኔን ደግሞም ከአብርሃም ጋር የገባሁትን ኪዳኔን አስባለሁ
እዚህ “አስባለሁ” ሆን ብሎ ማሰብን የሚገልጽ ፈሊጣዊ አባባል ነው:: እዚህ ቦታ ቃል ኪዳኑን እንደሚፈጽም ያመለክታል:: አት: በዚያን ጊዜ ከያዕቆብ ከይስሐቅና ከአብርሃም ጋር የገባሁትን ቃል ኪዳኔን እፈጽማለሁ::

ምድሪቱን አስባታለሁ
እዚህ “አስባለሁ” ሆን ብሎ ማሰብን የሚገልጽ ፈሊጣዊ አባባል ነው:: እዚህ ስለምድሪቱ ያለውን ተስፋ ቃል እንደሚፈጽም ያመለክታል:: አት: “ስለምድሪቱ ያለውን ተስፋ ቃል እፈጽማለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገርና Metonymy/ ተዛማጅ ባህሪይ የሚገልጹ ምትክ ቃላትና አባባሎች ይመልከቱ)

Leviticus 26:43

ምድሪቱ ባዶ ተቀራለች
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: “የእስራኤል ሕዝብ ምድራቸውን ይተዋሉ/ይለቅቃሉ ወይም ባዶ ያደርጋሉ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

በሰንበትዋ ትደሰታለች
እግዚአብሔር ስለምድሪቷ አንድ ሰው በእረፍቱ እንደሚደሰት አድረጐ ይናገራል ምክንያቱም በእርስዋ ላይ ዘርን የሚዘራ ወይም ሰብልን የሚያሳድግ አይኖርም ይህም ምድሪቱ ለም እንዲትሆን ያደርጋታል:: አት: “ምድሪቱ በሰንበታት ትጠቀማለች” (ሰውኛ አገላለጽ ይመልከቱ)

Leviticus 26:44

አጠቃላይ መረጃ
ይህ የመታዘዝ በረከቶችና ያለታዘዝ ቅጣቶችን እግዚአብሔር በሲና ተራራ ለሙሴ የተናገረውን መልእክት ያጠቃልላል

ከቀደሙ አባቶቻችሁ ጋር የገባሁትን ቃል ኪዳን አስባለሁ
እዚህ “አስባለሁ” ሆን ብሎ ማሰብን የሚገልጽ ፈሊጣዊ አባባል ነው:: እዚህ ቦታ ቃል ኪዳኑን እንደሚፈጽም ያመለክታል:: አት: በዚያን ጊዜ ከአባቶቻችሁ ጋር የገባሁትን ቃል ኪዳኔን እፈጽማለሁ:: (ፈሊጣዊ አነጋገር እና Metonymy/ ተዛማጅ ባህሪይ የሚገልጹ ምትክ ቃላትና አባባሎች ይመልከቱ)

አሕዛብ እያዩ
ይህ የአሕዛብ ማወቅ ነው:: አት: “አሕዛብ እያወቁ” ወይም “አሕዛብ ይህን ያውቃሉ” (See Metonymy/ ተዛማጅ ባህሪይ የሚገልጹ ምትክ ቃላትና አባባሎች ይመልከቱ)

አሕዛብ
የአዛብ ሕዝብን ይወክላል:: አት:” የአሕዛብ ሕዝብ” (See Metonymy/ ተዛማጅ ባህሪይ የሚገልጹ ምትክ ቃላትና አባባሎች ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 27

1 ያህዌ ሙሴን ተናገረው እንዲህም አለ፣ **2** “ለእስራኤላውያን እንዲህ ብለህ ንገራቸው፣ ‹አንድ ሰው ለያህዌ ሰውን ለመስጠት የተለየ ስዕለት ቢሳል
ተመጣጣን ዋጋ ለመክፈል ተከታዮን ዋጋዎች ተጠቀም። **3** ከዚያ እስከ ስልሳ አመት ዕድሜ ላለው ወንድ መደበኛው ዋጋ በቤ መቅደሱ ሰቅል መለኪያ ሃምሳ
የብር ሰቅሎች ይሁን። **4** ለተመሳሳይ ዕድሜ ክልል ለሴቷ መደበኛው ዋጋ ሰላሳ ሰቅሎች ይሁን። **5** ከአምስት አመት እስከ ሀያ አመት ዕድሜ ለወንድ መደበኛው
ዋጋ ሀያ ሰቅሎች ይሁን፣ ለሴቷ አስር ሰቅሎች ነው። **6** ከአንድ ወር ዕድሜ እስከ አምስት አመት ለወንድ መደበኛው ዋጋ አምስት የብር ሰቅሎች ይሁን፣ ለሴት
ሶስት የብር ሰቅሎች ነው። **7** ከስልሳ አመት በላይ ለወንድ መደበኛው ዋጋ አስራ አምስት ሰቅሎች፣ ለሴት አስር ሰቅሎች ይሁን። **8** ነገር ግን ስዕለቱን የገባው
ሰው መደበኛውን ዋጋ መክፈል ባይችል፣ በስለት የተሰጠው ሰው ወደ ካህኑ ይቅረብ፣ ካህኑም ያንን ሰው የተሳለው ሰው ሊከፍል በሚችል ዋጋ ይተምነዋል። **9**
አንድ ሰው ለያህዌ እንስሳ መሰዋት ቢፈልግ፣ ያህዌ ያንን ቢቀበል፣ ከዚያ ያ እንስሳ ለእርሱ ይለያል። **10** ሰውዬው እንዲህ ያለውን እንስሳ መለወጥ ወይም
መቀየር የለበትም፣ መልካሙን በመጥፎው ወይም መጥፎውን በመልካሙ አይቀይርም። አንዱን እንስሳ በሌላው ቢለውጥ፣ ያ እንስሳና የተለወጠው ሁለቱም
ንጹህ ይሆናሉ። **11** ሆኖም፣ ሰውዬው ለያህዌ ሊሰጥ የተሳለው ንጹህ ካልሆነ ስለዚህ ምክንያት ያህዌ ያንን አይቀበልም፣ ከዚያ ሰውዬው እንስሳውን ወደ ካህኑ
ማምጣት አለበት። **12** ካህኑ በገበያው የእንስሳ ዋጋ ይተምነዋል። ማናቸውም ካህኑ ለእንስሳው የሰጠው ዋጋ፣ ያ የእንስሳው ዋጋ ይሆናል። **13** እናም ባለቤቱ
እንስሳውን ሊዋጅ ቢፈልግ፣ በሚዋጅበት ዋጋ ላይ አንድ አምስተኛውን ጨምሮ ይዋጀው። **14** አንድ ሰው ቤቱን ለያህዌ መቀደስ ሲፈልግ፣ ካህኑ የቤቱን ዋጋ
ይተምናል። ማናቸውም ካህኑ የተመነው ዋጋ ያ የዚያ ቤት ዋጋ ነው። **15** ነገር ግን ባለቤቱ ቤቱን ቢለይና በኋላ ሊዋጀው ቢፈልግግ በሚዋጅበት ዋጋ ላይ አንድ
አመስተና ይጨመር፣ እናም ከዚያ እንደገና የእርሱ ይሆናል። **16** አንድ ሰው ከመሬቱ ለያህዌ ለመለየት ቢፈልግ፣ የመሬቱ ዋጋ ግምት ለመዝራት በሚያስፈልገው
ፍሬ መጠን ይተመናል። አንድ ሆሜር መስፈሪያ ገብስ ሃምሳ የብር ሰቅሎች ያወጣል። **17** እርሻውን በኢዮቤልዩ አመት ቢለይ፣ የተገመተው ዋጋ ይፀናል። **18**
እርሻውን ከኢዮቤልዩ በኋላ ቢለይ ግን፣ ካህኑ የእርሻ መሬቱን ዋጋ እስከ ቀጣዩ የኢዮቤልዩ አመት ድረስ ባሉ አመታት ቁጥር ያሰላና የተገመተው ዋጋ ይቀነሳል።
19 እርሻውን የለየው ሰው ሊዋጀው ቢፈልግ፣ በተገመተው ዋጋ ላይ አንድ አምስተኛ ይጨምራ፣ እናም መሬቱ ተመልሶ የእርሱ ይሆናል። **20** እርሻውን ካልዋጀ
ወይም ለሌላ ሰው ሸጦት ከሆነ፣ ከዚያ በኋላ ተመልሶ ሊዋጅ አይችልም። **21** ይልቁንም፣ እርሻው፣ በኢዮቤልዩ ተመልሶ ሲለቀቅ ሙሉ ለሙሉ ለያህዌ እንደተሰተ
እርሻ ሁሉ ለያህዌ ቅዱስ ስጦታ ይሆናል። የካህናቱ ንብረት ይሆናል። **22** አንድ ሰው የገዛውን መሬት ለያዌ ቢለይ፣ ነገር ግን መሬቱ ከሰውዬው ቤተሰቦች መሬት
ውስጥ ባይሆን፣ **23** ካህኑ የእርሻውን ዋጋ እስ ኢዮቤልዩ አመት ድረስ ባለው ጊዜ መተን ይተምናል፣ ሰውዬውም ዋጋውን በዚያ ቀን ለያህዌ ቅዱስ ስጦታ
አድርጎ ይከፍላል። **24** በኢዮቤልዮ አመት፣ እርሻው ከገዛው ሰው ተወስዶ ወደ መሬቱ የቀድሞ ባለቤት ይመለሳል። **25** የሚተመኑ ዋጋዎች ሁሉ በመቅደሱ
ሰቅል ዋጋ ሊተመኑ ይገባል፡፤ ሃያ ጌራ ከአንድ ሰቅል ጋር እኩል ነው። **26** ከእንስሳት በመጀመሪያ የሚወለደው ግን አስቀድሞም ቢሆነ የያህዌ ነው፣ ማንም ሰው
ሊቀድሰው አይችልም በሬም ይሁን በግ የያህዌ ነው፣ ማንም ሰው ሊቀድሰው አይችልም በሬም ይሁን በግ የያህዌ ነው **27** ንጹህ ያልሆነ እንስሳ ከሆነ፣ ባለቤቱ
በተመገተው ዋጋ መልሶ ይግዛውው ደግሞም ከዋጋው በላይ አንድ አምስተኛ ይጨምርበት። እንስሳው ካልተዋጀ፣ በተተመነው ዋጋ ይሸጥ። **28** ሆኖም፣ አንድ
ሰው ለያህዌ ከለየው ሰውም ሆነ ወይም እንስሳ፣ ወይም የቤተሰቡ ርዕስት ምንም ነገር አይሸጥ ወይም አይዋጅ ማናቸውም የተለየ ነገር ለያህዌ ቅዱስ ነው። **29**
እንዲጠፋ ለተለየ ሰው ምንም መዋጃ አይከፈልለትም። ያ ሰው መገደል አለበት። **30** አስራት ሁሉ፣ በምድሪቱ ላይ የበቀለ ሰብልም ሆነ ወይም የዛፍ ፍሬ የያህዌ
ነው። ለያህዌ የተቀደሰ ነው። **31** አንድ ሰው ከአስራቱ አንዳች ቢዋጅ፣ በዋጋው ላይ አንድ አምስተኛ ይቸምር። **32** ከመንጋ ወይም ከከብት አስራት ሁሉ፣
ከእረኛው በትር ስር የሚያልፍ ሁሉ፣ ከአስር አንዱ ለያህዌ ይለይ። **33** እረኛው የተሸለውን ወይም የከፋውን እንስሳ አይፈልግም፣ ደግሞም አንዱን በሌላው
አይተካ። ቢለውጠው እኗን፣ የተለወጠውና የሚለወጠው ሁለቱም የተቀደሱ ይሆናሉ። ሊዋጅ አይችልም።” **34** ያህዌ በሲና ተራራ ለሙሴ የሰጣቸው
ለእስራኤላውያን የተሰጡ ትእዛዛት እነዚህ ናቸው።

Leviticus 27:1

ማንኛውም ሰው ለእግዚአብሔር ልይ ስእለት ቢሳል
በዚህ ዐውድ ስእለቱ ራሱን ወይም ሌላን ሰው ለእግዚአብሔር ለማቅረብ ይሆናል። ይህ ግልጽ ተደርጐ ሊነገር ይችላል። አት: “ማንም አንድን ሰው
ለእግዚአብሔር ለማቅረብ ቢሳል” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

የሚከተሉትን ተመጣጣኝ ዋጋ መክፈል
ለእግዚአብሔር ሰውን በመስጠት ፈንታ የተወሰነ ብር ይክፈል አት በሰው ፈንታ እንደሚከተሉት ተመጣጣኝ ዋጋ መሠረት ለእግዚአብሔር ስጦታ ያቅርብ
ወይም በሰው ፈንታ እንደሚከተሉት የነሐስ መጠን ይክፈል (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Leviticus 27:3

መደበኛ ዋጋ
“የሚከፈል የዋጋ መጠን” ወይም “መከፈል ያለበት”

ሃያ ስድሳ ሃምሳ ሠላሣ
20 60 50 30 ቁጥሮችን ይመልከቱ

ሃምሳ ሰቅል ብር
የዘመናዊ ሚዛኖች መለኪያ መጠቀም ካስፈለገ ሁለቱ መንገዶች እነሆ:: አት: “ሃምሳ ሰቅል ብር እያንዳንዳቸው አሥር ግራም የመዘናሉ” ወይም “500
ግራም ብር” (መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሚዛኖችን ይመልከቱ)

በቤተመቅደሱ ሰቅል ሚዛን መሠረት
የተለያየ ሚዛን ያላቸው ሰቅሎች አሉ:: በተቀደሰው የመገናኛው ድንኳን ውስጥ ሰዎች በመጠቀም ያለባቸው ይህን ሚዛን ነው:: ይህም 11 ግራም
ይመዝናል:: አት: “በመቅደሱ የሚጠቀሙበትን ዓይነት ሰቅል ይጠቀሙ” ወይም “ብርን ሲመዝኑ በመቅደሱ የሚጠቀሙበትን ሚዛን ይጠቀሙ”
(መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሚዛኖችን ይመልከቱ)

ሠላሣ ሰቅል
የዘመናዊ ሚዛኖች መለኪያ መጠቀም ካስፈለገ ሁለቱ መንገዶች እነሆ:: አት: “ሠላሣ ሰቅል ብር እያንዳንዳቸው አሥር ግራም የመዘናሉ” ወይም “300
ግራም ብር” (መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሚዛኖችን ይመልከቱ)

Leviticus 27:5

አምስት ሃያ አሥር ሶስት
5 20 10 3 ቁጥሮችን ይመልከቱ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መደበኛ ዋጋ
“የሚከፈል የዋጋ መጠን” ወይም “መከፈል ያለበት”

ሃያ ሰቅል
የዘመናዊ ሚዛኖች መለኪያ መጠቀም ካስፈለገ ሁለቱ መንገዶች እነሆ:: አት: “ሃያ ሰቅል ብር እያንዳንዳቸው አሥር ግራም የመዘናሉ” ወይም “ሁለት መቶ ግራም ብር” (መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሚዛኖችን ይመልከቱ)

ለሴት ከሆነ አሥር ሰቅል
እድሜ እና ግምቱ የሚሉ አዚህ ተዘለዋል:: ነገርግን ታሳቢ እንደሆኑ መረዳት ተገቢ ነው:: አት “ይህን እድሜ ለሆነ ሴት ግምቱ አሥር ሰቅል ነው”(መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሚዛኖችን ይመልከቱ)

አሥር ሰቅል
የዘመናዊ ሚዛኖች መለኪያ መጠቀም ካስፈለገ ሁለቱ መንገዶች እነሆ:: አት: “አሥር ሰቅል ብር እያንዳንዳቸው አሥር ግራም የመዘናሉ” ወይም “አንድ መቶ ግራም ብር” (መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሚዛኖችን ይመልከቱ)

አምስት ሰቅል
የዘመናዊ ሚዛኖች መለኪያ መጠቀም ካስፈለገ ሁለቱ መንገዶች እነሆ:: አት: “አምስት ሰቅል ብር እያንዳንዳቸው አሥር ግራም የመዘናሉ” ወይም “ሃምሳ ግራም ብር” (መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሚዛኖችን ይመልከቱ)

ሶስት ሰቅል
የዘመናዊ ሚዛኖች መለኪያ መጠቀም ካስፈለገ ሁለቱ መንገዶች እነሆ:: አት: “ሶስት ሰቅል ብር እያንዳንዳቸው አሥር ግራም የመዘናሉ” ወይም “ሠላሣ ግራም ብር” (መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሚዛኖችን ይመልከቱ)

Leviticus 27:7

ስድሳ አመት ዕድሜና ከዚያ በላይ
ስድሳ ዓመትና ከዚያ በላይ ዕድሜ

ስድሳ አሥራ አምስት አሥር
60 15 10 ቁጥሮችን ይመልከቱ

አሥራ አምስት ሰቅል
የዘመናዊ ሚዛኖች መለኪያ መጠቀም ካስፈለገ ሁለቱ መንገዶች እነሆ:: አት: “አሥራ አምስት ሰቅል ብር እያንዳንዳቸው አሥር ግራም የመዘናሉ” ወይም “ አንድ መቶ ሃምሳ ግራም ብር” (መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሚዛኖችን ይመልከቱ)

ለሴት ከሆነ አሥር ሰቅል
እድሜ እና ግምቱ የሚሉ አዚህ ተዘለዋል:: ነገርግን ታሳቢ እንደሆኑ መረዳት ተገቢ ነው:: አት “ይህን እድሜ ለሆነ ሴት ግምቱ አሥር ሰቅል ነው”(መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሚዛኖችን ይመልከቱ): Ellipsis/ ዐውዱ ሊገልጽ የሚችሉ ቃላትን ወይም አባባሎችን የመደበቅ ወይም የመዝለል ዘይቤ ይመልከቱ)

የተሰጠው ሰው ለካህኑ መቅረብ አለበት
በያህዌ ፊት ወደ መሰዊያው ያምጣው። **26** ካህኑ ከእህል ቁርባኑ እፍኝ ሙሉ ዘግኖ ይውሰድና በመሰዊያው ላይ ያቃጥለው። ከዚያ ለሴትየዋ መራራውን ውሃ
እንድትጠጣው ይስጣት። **27** ውሃውን እንድትጠጣው ሲሰጣት በባሏ ላይ በደል በመፈፀም ረክሳ ከሆነ፣ ዕርግማን የሚያስከትለው ውሃ ወደ ውስጧ ይገባና
መራራ ይሆናል። ሆዷ ያብጣል ጭኗ ይመነምናል። ሴትየዋ ከህዝቧ መሃል የተረገመች ትሆናለች። **28** ሴትየዋ የረከሰች ካልሆነችና ንጹህ ከሆነች፣ ነጻ
ትሆናለች። ልጆችን መጸነስ ትችላለች። **29** የቅናት ህግ ይህ ነው። ከባሏ ውጭ ለሄደች እና ለረከሰች ሴት ህጉ ይህ ነው። **30** የቅናት መንፈስ ለያዘውና በሚስቱ
ለቀና ሰው ህጉ ይህ ነው። ሴትየዋን በያህዌ ፊት ያምጣ፣ ካህኑም ይህ የቅናት ህግ የሚገልጸውን ሁሉ በእርሷ ላይ ያድርግ። **31** ሰውየው ሚስቱን ወደ ካህን
በማቅረቡ ከበደል ነጻ ይሆናለ። ሴትየዋ በድላ ከሆነ ማናቸውንም በደል ትሸከማለች።”

Numbers 5:1

ተላላፊ የቆዳ በሽታ
ይሄ የሚያመለክተው ቆዳን ለበሽታ የሚዳርገውንና ወደ ሌሎች ሰዎች በፍጥነት የሚዛመተውን የቆዳ በሽታ ነው።

ለሕመም የሚዳርግ ፈሳሽ
ይሄ የሚያመለክተው ከተከፈተ ነገር ውስጥ የሚወጣን ፈሳሽ ነው።

በሬሣም የረከሰውን ሁሉ
አንድ ሰው ሬሣ የሚነካ ከሆነ እንደረከሰ ነበር የሚቆጠረው።የእግዚአብሔርን ዓላማ ለማስፈፀም ተቀባይነት የሌለው ሰው አካሉ ንፁህ እንዳልሆነ ተደርጎ ነው የሚገለፀው።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ አውጧቸው
እዚህ ላይ “እናንተ”የሚለው ቃል የብዙ ቁጥር በመሆኑ የእሥራኤልን ሕዝብ የሚያመለክት ነው።

የእሥራኤልም ልጆች እንዲሁ አደረጉ
ይሄ ማለት የረከሱትን ሰዎች አስወጧቸው ማለት ነው።የዚህ ሙሉ ሃሣቡ የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“የእሥራኤል ሰዎች የረከሱትን ሰዎች ከሠፈራቸው ውጪ እንዲወጡ አደረጓቸው”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 5:5

ሰዎች እርስ በእርሳቸው የሚያደርጓቸው ኃጢአቶች
“ሰዎች እርስ በእርስ የሚያደርጓቸው ማንኛውም ዓይነት ኃጢአቶች”

ለእኔ ታማኝ ያልሆነ
አንድ ሰው በሌላ ሰው ላይ ኃጢአትን ቢሰራ በእግዚአብሔር ላይ እንዳመፀ ስለሚቆጠር እግዚአብሔር ይሄንን ሰው ታማኝ እንዳልሆነ ሰው ይቆጥረዋል ማለት ነው።“እኔንም በድለዋል”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 5:8

ነገር ግን ይመልስት ዘንድ ሰውዬው ዘመድ ባይኖረው
አብዛኛውን ጊዜ የተበደለው ሰው ገንዘቡን የሚወስድ ቢሆንም ሰውዬው በሕይወት ከሌለ ግን የገንዘቡ ክፍያ ለቅርብ ዘመዱ እንዲተላለፍ የሚደረግ ይሆናል።የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ሃሣብ የበለጠ ሊብረራ ይችላል።“የተበደለው ሰው በሕይወት ከሌለና ገንዘቡን የሚቀበልለት የቅርብ ዘመድ የማይኖረው ከሆነ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀት ወይም የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የተበደለው ሰው ግን ...
ይሄ በድርጊት መልኩ ሊገለፅ ይችላል።“ጥፋተኛ የተባለው ሰው የበደለ ከሆነ”

የበደሉን ዋጋ በካህኑ አማካይኝት ለእኔ ይስጥ
አንድ ሰው በበደለው በደል ምክኒያት ገንዘቡን ለካህኑ የሚሰጥ ከሆነ ለእግዚአብሔር እንደሰጠ ነው የሚቆጠረው።

ማስተሰረያው ለእርሱ ይሁን
ማስተሰረያ የሚደረገው ለሰውዬው ኃጢአት ነው።እዚህ ላይ እግዚአብሔር እያመለከተ ያለው ኃጢአቱን የፈፀመውን ሰው ነው።“ለኃጢአቱ ማስተሰረያ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ከእሥራኤል ሰዎች ለካህኑ የሚቀርቡ የተለዩ ነገሮች
ይሄ በድርጊት መልኩ ሊገለፅ ይችላል።“የእሥራኤል ሰዎች የተቀደሰውን ነገር ለይተው ወደ ካህኑ የሚያመጧቸው”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰው ሁሉ የሚሰጠው የተቀደሰ ነገር ለካህኑ ይሆናል፤ማንኛውም ሰው ማንኛውንም ነገር ለካህኑ ቢሰጥ የካህኑ ይሆናል
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን አንድ ላይ ሆነው እንዲቀርቡ የተፈለገበት ምክኒያት አንድ ሰው የሚሰጠው የተቀደሰ ነገር ለተሰጠው ለዚያ ካህን እንደሆነ አፅንኦት ለመሥጠት ተፈልጎ ነው። (ተመሣሣይነት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 5:11

የአንድ ሰው ሚስት ከእርሱ ፈቀቅ ብትል፤በእርሱም ላይ ብትበድል
ይሄ በመሠረቱ ሊሆን የሚችል ነገር ነው።

Numbers 5:16

አቅርበው በእግዚአብሔር ፊት ያስቀምጧት
ካህኑ “በእግዚአብሔር ፊት” መሠዊያው አጠገብ ያመጣታል።“በመሠዊያው አጠገብ በእግዚአብሔር ፊት ያስቀምጣታል” (በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 5:18

በእግዚአብሔር ፊት
“በእግዚአብሔር ሕልውና ፊት”

በሚቀርበው የእህሉ ቁርባን
ይህንን ሐረግ በኦሪት ዘኁልቁ 5፡15 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

የራሳችሁን መንገድ ካልተከተላችሁ
“የራስን መንገድ መከተል” ምሣሌያዊ አነጋገር ሲሆን “ታማኝ አለመሆን”ማለት ነው። “ለባለቤትሽ ታማኝ ካልሆንሽ” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኃጢአትን ፈፀማችሁ
“ኃጢአትን በመፈፀም” ይሄ ሐረግ የሚያመለክተው “ዝሙትን ስለመፈፀም ነው”

ከዚህ መራራ ውኃ ነፃ ትሆናላችሁ
ከሆነ ነገር “ነፃ ትሆናላችሁ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በእርሱ አለመጎዳትን ነው።“ሊጎዳችሁ የሚችል ውኃ ለጉዳት አይሰጣችሁም”(ምሣሌያዊ አነጋገርን የሚለውን ይመልከቱ)

መርገምን ሊያመጣ የሚችለው ይሄ መራራ ውኃ
እዚህ ላይ መራራው ውኃ መርገምን ሊያመጣ እንደሚችል ተደርጎ ተገልጿል። ይሄ ማለት አንዲት ሴት ኃጢአተኛ ከሆነች ውኃውን በምትጠጣበት ወቅት ልጅ እንዳትወልድ ምክኒያት ይሆንባታል ማለት ነው።“ይሄ መራራ ውኃ መርገም ሊሆንብህ ይችላል”(ግዑዝ ነገሮች ሕይወት እንዳላቸው ተደርገው ሲገለፁ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 5:20

በባሏ ሥር
ይሄ ሐረግ የሚያመለክተው በባሏ ሥልጣን ሥር መሆኗን ነው።“በባሏ ሥልጣን ሥር” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

የራሳችሁን መንገድ ካልተከተላችሁ
“የራስን መንገድ መከተል”የሚለው ሐረግ ምሣሌያዊ አነጋገር ሲሆን “ታማኝ አለመሆን”ማለት ነው።(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ረክሳችኋል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ራሣችሁን አርክሳችኋል” (ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

በላይዋ ላይ መርገምን ሊያወርድ የሚችል
“መርገምን ሊያወርድ”የሚለው ቃል ምሣሌያዊ አነጋገር ሲሆን በላይዋ ላይ መርገም ይመጣል የሚል ፍቺ ያለው ነው።“በላይዋ ላይ መርገም እንዲመጣ ሊያደርግ የሚችል”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ለእርግማን ይዳርግሻል...በሕዝብሽ መካከል
እዚህ ላይ ፀሐፊው የሚናገረው ሌሎች ሰዎች እንዲረግሟት መንስኤ የሚሆነውን እግዚአብሔር ለሴትዬዋ የሚሰጣትን መርገም በተመለከተ ልክ ሴትዬዋ ራስዋ መርገም እንደሆነች አድርጎ ነው የሚገልፀው።“እግዚአብሔር የረገመሽ በመሆኑ ሌሎች ሰዎችም ይረግሙሻል።እግዚአብሔርም በእውነት ስለመረገምሽ ሰዎች እንዲመለከቱ ያደርጋል”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በዚህ መልኩ ለሕዝብሽ የሚታይ ይሆናል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።”ይህንን ለሕዝብሽ እንደ እርግማን ያሣየዋል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ይሄ በሕዝብሽ መካከል የሚደረግ ይሆናል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።1)ሴትዬዋ ልጅ ለመውለድ አትችልም 2)እርግዝናው የሚጨናገፍ በመሆኑ ሕፃኑ ልጅ በሕይወት አይኖርም።

ጭንሽ ይሰለስላል
እዚህ ላይ “ጭን” የሚለው ቃል የሴትን ማሕፀን ወይም ሌላ የሰውነት አካሏን ለመጥራት የተጠቀሙበት ጨዋ የሆነ አገላለፅ ነው።“ማሕፀንሽ ጥቅም የማይሰጥ ይሆናል”(ሥርዓት የሌለውን ነገር በመልካም ነገር መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 5:23

የተፃፉትን መርገሞች በመራራም ውኃ ይደመስሰዋል
ይሄ ማለት ቀለሙን ከብራናው ላይ ያጥበዋል ማለት ነው።

የተፃፉ መርገሞች
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የፃፋቸው መርገሞች”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 5:24

አጠቃላይ መረጃ
ቁጥር 24 በአጠቃላይ የሚገልፀው ካህኑ ምን ማድረግ እንዳለበትና ሴትዬዋ ውኃውን በምትጠጣበት ወቅት ሊከሰት የሚችለውን ነገር አስመልክቶ ነው። ቁጥር 25 እና 26 ካህኑ ይህንን ሥራ እንዴት ማከናወን እንደሚኖርበት በዝርዝር ያብራራል።ካህኑ ውኃውን ለሴትዬዋ ከሰጣት በኋላ የምትጠጣው አንድ ጊዜ ብቻ ነው።

የውክልና ቁርባን
አንድ እፍኝ እህል አጠቃላዩን የእህል ቁርባን ይወክላል።ይሄ ማለት በጠቃላይ ቁርባኑ ለእግዚአብሔር ይሆናል ማለት ነው።

የቅንአት የእህል ቁርባን
“የቅንአት የእህል ቁርባን”ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 5፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

Numbers 5:27

ከፈፀመችው የተነሣ የረከሰች ከሆነ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል። “ድርጊቱን ከመፈፀሟ የተነሣ የረከሰች ከሆነ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ኃጠአትን ሠርታለች
እዚህ ላይ “ኃጢአት”የሚያመለክተው በተለይ ዝሙት መፈፀምን ነው።የዚህ ዓረፍተ ነገር ሃሣብ የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“ዝሙትን ሠርታለች” (በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሆድዋም ይነፋል፤ጭንዋም ይሰለስላል
ለዚህ ፍቺ ሊሆኑ የሚችሉት 1)ሴትዬዋ ልጅ ለመውለድ አትችልም 2)የሴትዋ ፅንስ ስለሚጨናገፍ ሕፃኑ ልጅ በሕይወት አይኖርም።እዚህ ላይ “ጭን”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሴትን ማሕፀን ወይም የአካሏን ክፍል ነው።(ሥርዓት የሌለውን ነገር በመልካም ነገር መተካት የሚለውን ይመልከቱ) ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 5፡21 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

ሴቲቱም በሕዝብዋ መካከል ለመርገም ትሆናለች
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሕዝቧ ይረግማታል”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ያልረከሰች
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“አላረከሳትም”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ንፁህ ከሆነች
እዚህ ላይ “ጥፋተኛ አለመሆን” “ንፁህ መሆን” በሚል ቃል ይገለፃል። (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ንፁህ ትሆናለች
ለዚህ ፍቺ ሊሆኑ የሚችሉት 1)“ከዚያ በኋላ የተረገመች አትሆንም”2)“ከዚያ በኋላ ከመርገም ነፃ ትሆናለች”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ልጅንም ታረግዛለች
“ታረግዛለች”

Numbers 5:29

የቅንአት ሕግ
“ቅንአትን የሚዳኝ ሕግ”

ከባልዋ ሸሽታ የምትሄድ
“መሸሸ”የሚለው ቃል ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙም “ታማኝ አለመሆን”ማለት ነው።“ለባልዋ ታማኝ ያልሆነች”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ረክሳለች
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ራስዋን ታረክሳለች”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

የቅንአት መንፈስ
ይሄ የሚያመለክተው የሰውን የቅንአት አስተሳሰብና ስሜቶችን ነው፡ይህንን በዘኁልቁ 5፡14 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡“ቅንአት ያለበት ሰው”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ ሚስቱም በቀና ጊዜ
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ሚስቱ ከሌላ ሰው ጋር በመተኛት ታማኝ አለመሆኗን መጠርጠር ማለት ነው።“ሚስቱ ለእርሱ ታማኝ እንዳልሆነች ይጠረጥራል” ወይም “ከሌላ ሰው ጋር እንደተኛች ይጠረጥራል”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ፊት
“በእግዚአብሔር ህልውና ፊት”

Numbers 5:31

ሚስቱን ወደ ካህኑ በማቅረቡ ከኃጢአቱ ንፁሕ ይሆናል
“ሚስቱን ወደ ካህኑ በማምጣቱ የተሳሳተ ነገር እንደፈፀመ ሰው በደለኛ አይባልም ”

መሸከም ግድ ነው
“መከራውን መቋቋም ያስፈልጋል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 6

1 ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ **2** “ለእስራኤል ሰዎች ተናገራቸው። እንዲህ በላቸው፣ ‘አንድ ወንድ ወይም አንዲት ሴት ናዝራዊ ሆኖ ራሱን ለያህዌ በተለየ
ስዕለት ሲለይ፣ **3** ከወይንና ከሚያሰክር መጠጥ ራሱን ይለይ። ከወይን ወይም ከሚያሰክር መጠጥ የተሰራ ኮምጣጤ አይጠጣ። ማናቸውንም የወይን ጭማቂ
አይጠጣ ወይም የወይን ፍሬ ወይም ዘቢብ አይብላ። **4** ለእኔ በተለየባቸው ቀናት ሁሉ፣ ከፍሬያቸው ግልፋፊ የተሰራ ማናቸውንም ነገር ጨምሮ ከወይን የተሰራ
ምንም ነገር አይብላ። **5** ለያህዌ ራሱን የለየባቸው ቀናት እስኪያበቁ ድረስ በስለቱ ጊዜያት ሁሉ ራሱን ምላጭ አይንካው። ለያህዌ የተለየ ይሁን። ፀጉሩ በራሱ
ላይ እንዲያድግ ይተወው። **6** ራሱን ለያህዌ በለየባቸው ጊዜያት ሁሉ፣ ወደ ሞተ ሰው አይቅረብ። **7** አባቱ፣ እናቱ፣ ወንድሙ ወይም እህቱ ቢሞቱ እንኳን ራሱን
ማርከስ የለበትም። ይህም የሚሆነው ማንም ሰው በረጅም ጠጉሩ እንደሚመለከተው፣ ለእግዚአብሔር የተለየ ነው። **8** በተለየበት ጊዜ ሁሉ ለያህዌ የተለየ
ቅዱስ ነው። **9** አንድ ሰው ድንገት አጠገቡ ቢሞት እና ማንነቱን የለየበትን ፀጉሩን ቢያረክስበት፣ መንጻት ባለበት ከሰባተኛው ቀን በኋላ ራሱን ይላጭ። ራሱን
መላጨት ያለበት በዚያን ጊዜ ነው። **10** በስምተኛው ቀን ሁለት ርግቦች ወይም ሁለት ዋኖሶች ወደ መገናኛው ድንኳን ደጃፍ ለካህኑ ያቅርብ። **11** ካህኑ አንዱን
ወፍ ለኃጢአት መስዋዕት ሌላውን የሚቃተል መስዋዕት አድርጎ ያቅርብ። ሬሳ አጠገብ በመሆን ኃጢአት ሰርቷልና እነዚህ ለእርሱ ስርየት ይቀርባሉ። በዚያው
ዕለት ራሱን መልሶ ለያህዌ ይስጥ። **12** ለተለየበት ጊዜ ራሱን ለያህዌ መልሶ ይስጥ። ለበደል መስዋዕት የአንድ አመት ወንድ ጠቦት ያምጣ። ራሱን ከማርከሱ
በፊት የነበሩ ቀናት አይቆጠሩም፣ ምክንያቱም ለእግዚአብሔር ተለይቶ ባለበት ጊዜ ረክሷል። **13** ናዝራዊ መለየቱ ስለሚያበቃበት ጊዜ የተሰጠው ህግ ይህ
ነው። ወደ መገናኛው ድንኳን ደጃፍ ያምጡት። **14** መስዋዕቱን ለያህዌ ያቅርቡ ነውር የሌለበት የአንድ አመት ወንድ ጠቦት የሚቃጠል መስዋዕት አድርጎ
ያቅርብ። ለህብረት መስዋዕት ነውር የሌለበት አውራ በግ ያምጣ። **15** እንደዚሁም እርሾ ያልገባበት አንድ መሶብ ዳቦ፣ በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት
ዳቦዎች፣ በዘይት የተቀባ እርሾ የሌለበት የገብስ ቂጣ፣ ከእህል ቁርባንና ከመጠጥ መስዋዕቶች ጋር ያምጣ። **16** ካህኑ እነዚህን በያህዌ ፊት ያቅርባቸው። እርሱ
የኃጢአት መስዋዕቱንና የሚቃጠል መስዋዕቱን ያቅርብ። **17** ለያህዌ የህብረት መስዋዕቱን፣ እርሾ ካልገባበት ከመሶቡ ዳቦ ጋር፣ አውራ በጉን መስዋዕት
አድርጎ ያቅርብ። እንዲሁም ካህኑ የእህል ቁርባኑን እና የመጠጥ መስዋዕቱን ጭምር ያቅርብ። **18** ናዝራዊው ለእግዚአብሔር መለየቱን የሚያሳየውን ፀጉሩን
በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ይላጭ። ፀጉሩን ከራሱ ወስዶ የህብረት መስዋዕቶቹ በሚቀርቡበት በሚነደው እሳት ውስጥ ይጨምረው። **19** ካህኑ የተቀቀለውን
አውራ በግ ወርች፣ ከመሶቡ ውስጥ እርሾ ያልገባበትን አንድ ዳቦ፣ እና አንድ እርሾ ያልገባበት የገብስ ቂጣ ይውሰድ። ናዝራዊው መለየቱን የሚያሳየውን ጸጉሩን
ከተላጨ በኋላ ካህኑ እነዚህን በእጆቹ ያስይዘው። **20** ካህኑ እነዚህን መስዋዕት አድርጎ በያህዌ ፊት ከፍ አድርጎ ያንሳቸውና ለእርሱ ያቅርባቸው። ይህ ከፍ
ተደርጎ ከተነሳው ፍርምባና ከቀረበው ወርች ጋር ለካህኑ ተለየ ቅዱስ ምግብ ነው። ከዚያ በኋላ ናዝራዊው ወይን ሊጠጣ ይችላል። **21** ለያህዌ ለመለየት
ስዕለቱን ያቀረበ ናዝራዊ ህጉ ይህ ነው። ማናቸውንም ሌሎች ነገሮች ቢሰጥ በናዝራዊነት ህግ መሠረት እንዲጠብቃቸው የተሰጡትን ቃል ኪዳኖች ለመጠበቅ
የገባውን የስዕለት ግዴታዎች መጠበቅ አለበት።” **22** ያህዌ እንደገና ሙሴን ተናገረው። እንዲህም አለው፣ **23** “ለአሮንና ለልጆቹ እንዲህ በላቸው፣
‘የእስራኤልን ሰዎች በዚህ መንገድ ባርኳቸው። እንደዚህ በሏቸው፣ **24** “ያህዌ ይባርኻሁ ይጠብቃችሁ። **25** ያህዌ ብርሃኑን በእናንተ ላይ ያብራራ ፊቱን
ይመልስለችሁ፣ ይራራላች። **26** ያህዌ በሞገስ ያጥግባችሁ፣ ሰላምንም ይስጣችሁ።’” **27** ለእስራኤል ሕዝብ ስሜን የሚያስተዋውቁት በዚህ መንገድ ነው።
እኔም እባርካቸዋለሁ።”

Numbers 6:1

ራሱን ይለያል...የተለየ ነው
“ራስን ለሆነ ሰው መለየት”ማለት ለዚያ ሰው “ራስን መስጠት”ማለት ነው።“ይሰጣል...ራሱን ይሰጣል”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ራሱን ከ...መለየት ይኖርበታል
የዚህ ፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉም ሊጠጣቸው ወይም ሊበላቸው አይገባም ማለት ነው።“መውሰድ አይገባውም”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከወይን የተገኘ ሆምጣጤ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሰዎች ከወይን የሚሰሩት ሆምጣጤ”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ሆምጣጤ
ይሄ ማለት ወይንና ሌላ ጠንካራ መጠጦች ለብዙ ጊዜ እንዲፈሉ ከተደረገ በኋላ መራራ የሚሆነው መጠጥ ነው።

ወይም ከጠንካራ መጠጥ
ግልፅ የተደረገውን መረጃ የበለጠ ልታብራሩት ትችላላችሁ። “ወይም ሰዎች ከጠንካራ መጠጥ የሚሰሩት ሆምጣጤ”(ምልክቶች እንጂ ቃላት ጥቅም ላይ የማይውሉበት የሚለውን ይመልከቱ)

ዘቢብ
የደረቁ ወይኖች

ለእኔ የተለየ ነው
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ራሱን ለእኔ የተለየ ያደርጋል”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ከወይን ያለተሰራ ነገር
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሰዎች ከወይን የማይሰሯቸው ነገሮች”(ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።)

ከውስጡ ፍሬ ጀምሮ እስከ ገረፎው ድረስ
እነዚህ ሁለት ፅንፍ የያዙ ነገሮች የቀረቡት በአጠቃላይ የወይን ፍሬ መበላት እንደሌለበት አፅንዖት ለመስጠት ነው።“ከየትኛውም የወይን ክፍል” (ሆን ብሎ አጋኖ መናገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 6:5

ራስን ለመለየት ስእለት ማድረግ
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው።“መለየት”ማለት“ራስን መስጠት”ማለት ነው።

በራሱ ላይ ምላጭ መድረስ አይኖርበትም
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ማንም ሰው ቢሆን በራሱ ላይ ምላጭ መጠቀም የለበትም”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእግዚአብሔር የተለየበት ወራት
“መለየት” የሚለው ቃል አሕፅሮተ ሥም ሲሆን በግሥ መልክ ሊገለፅ ይችላል።እዚህ ላይ “መለየት”ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን “ለአንድ ነገር ራስን መስጠት ማለት ነው”“ራሱን ለእግዚአብሔር የለየበት ወራት”ወይም “ራሱን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለእግዚአብሔር የሰጠበት ወራት”(አሕፅሮተ ሥምንና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለእግዚአብሔር የተለየበት ወራት እስኪፈፀም ድረስ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ለእግዚአብሔር የሚለይበት ወራት የመጠናቀቂያ ጊዜ አለው ”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእግዚአብሔር መለየት ይኖርበታል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ራሱን ለእግዚአብሔር መለየት አለበት”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 6:6

ይለያል...ተለይቷል...መለየት
እዚህ ላይ “መለየት”ማለት“ራስን መሥጠት”ማለት ነው።“ራሱን ይሰጣል..ራሱን ሰጥቷል...ራስን መሥጠት”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ንፁህ ያልሆነ
ለእግዚአብሔር ዓላማዎች ተቀባይነት የሌለው ሰው ልክ አካሉ ንፁህ እንዳልሆነ ዓይነት ተደርጎ ነው የሚገለፀው።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ተለይቷል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ራሱን ለይቷል”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ መለየት
“መለየት” የሚለው አሕፅሮተ ሥም በግሥ መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ራሱን የለየ በመሆኑ”

ራሱን ለእግዚአብሔር የተወ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ራሱን ለእግዚአብሔር አውሏል” ወይም “ራሱን ለእግዚአብሔር ለይቷል”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 6:9

የተለየውንም ራሱን ቢለጭ
እዚህ ላይ “ራስ”የሚለው ቃል የሚወክለው መሐላውን በተምሣሌትነት የሚገልፀውን የናዝራዊ ሰውን ፀጉር ነው።“ለእግዚአብሔር የተለየ መሆኑን ለሰዎች ሁሉ የሚያሳየውን ረዥሙን ፀጉር ይላጨዋል”ወይም “ራሱን ተላጨ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ በሚነፃበት ቀን
“መንፃት”የሚለው አሕፅሮተ ሥም እንደ ግሥ ሐረግ ሊገለፅ ይችላል።“ራሱን ለእግዚአብሔር በለየበት ወቅት”(አሕፅሮተ ሥምን የሚለውን ይመልከቱ)

በሰባተኛው ቀን
“ቀን 7”(ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 6:10

ስምንተኛው ቀን
“ቀን 8” (ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 6:12

ራሱን የተለየ ያደረገበት ወራት
“ራሱን እንደገና ሊለይ ባለበት ቀናት”

ተባት ጠቦት...ለመሥዋዕት ማምጣት ይኖርበታል
ሰውዬው ለመሥዋዕት ይቀርብ ዘንድ ጠቦቱን ወደ ካህኑ ማምጣት ይኖርበታል።የዚህ ዓረፍተ ነገር ትርጉም የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“ለበደል መሥዋዕት ይሆን ዘንድ የአንድ ዓመት ተባት ጠቦት ወደ ካህኑ ማምጣት ይኖርበታል።”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ራሱን ከመላጨቱ በፊት የነበሩት ወራት የማይቆጠሩ ይሆናል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ራሱን ከመላጨቱ በፊት የነበሩት ቀናት የማይቆጠሩ ይሆናሉ”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ቅድስናው ረክሷል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ራሱን አረከሰ”ወይም “ራሱን ተቀባይነት እንዳይኖረው አደረገ”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 6:13

መለየቱ
እዚህ ላይ “መለየት”ማለት “መሰጠት”ማለት ነው።ይሄ አሕፅሮተ ሥም በግሥ መልክም ሊገለፅ ይችላል። “መሠጠቱ”ወይም “ራሱን መሥጠቱ”ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውንና አሕፅሮተ ሥምን የሚለውን ይመልከቱ)

ይቅረብ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“አንድ ሰው ሊያቀርበው ይገባል”ወይም “መቅረብ ይኖርበታል”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

መሥዋዕቱን ለእግዚአብሔር ያቅርብ
ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ይሆን ዘንድ ቁርባኑን ወደ ካህኑ ማምጣት ይኖርበታል።የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ፍቺ የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“በካህኑ አማካይነት መሥዋዕት ይሆን ዘንድ መሥዋዕቱን ለካህኑ ማቅረብ ይኖርበታል።”ወይም “ቁርባኑን ለእግዚአብሔር ካቀረበ በኋላ ካህኑ ይሰዋዋል።”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሾ የሌለበት ቂጣ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ያለ እርሾ ያዘጋጀው ቂጣ”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት “
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በዘይት የለወሰው መልካም ዱቄት” (ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

በዘይትም የተቀባ እርሾ የሌለው ስስ ቂጣ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እርሾ የሌለው ቂጣ ሆኖ በዘይት የተለወሰ“(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሾ የሌለበት ቂጣ
የተቆራረጡ ጠፍጣፋ ቂጣዎች

የእነርሱን የእህል ቁርባንና የመጠጡን ቁርባን
“የእነርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ናዝራዊ ሰው እንዲያመጣ የተጠየቀውን ቁርባን ነው።አብዛኛውን ጊዜ የእህል ቁርባንና የመጠጥ ቁርባን ከሌሎች የመሥዋዕት ዓይነቶች ጋር እንዲቀርቡ ይጠየቁ ነበር።የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ፍቺ የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“ከሌሎች የመሥዋዕት ዓይነቶች ጋር እንዲቀርቡ እግዚአብሔር የሚጠይቀው”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Numbers 6:16

እርሱ የእርሱን የኃጢአት መሥዋዕት ያሳርጋል
“እርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ካህኑን ሲሆን “የእርሱ”የሚለው ቃል ደግሞ መሐላውን ያደረገውን ሰው ነው።

የወዳጅነት መሥዋዕት
“እንደ ሕብረት መፍጠሪያ መሥዋዕት”

ካህኑም ደግሞ .....የመጠጥ ቁርባን ማቅረብ ይኖርበታል
ግንዛቤ የተገኘበትን መረጃ የበለጠ ልታብራራሩት ትችላላችሁ።“ካህኑ የመጠጥ ቁርባኑን ....ለእግዚአብሔር ማቅረብ ይኖርበታል”(ምልክቶች እንጂ ቃላት ጥቅም ላይ የማይውሉበት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 6:18

መለየቱን የሚገልፀውን
እዚህ ላይ “መለየት”ማለት “መሠጠት”ማለት ነው።አሕፅሮተ ሥሙ በግሥ መልክ ሊፃፍ ይችላል።“መሠጠቱን የማሣወቅ”ወይም “ራሱን እንዴት እንደሰጠ ለማሣወቅ”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውንና አሕፅሮተ ሥምን የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 6:19

የተቀቀለውን የአውራ በግ ወርች
ይሄ እንግዲህ አውራውን በግ ቀቅሎታል ማለት ነው።ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የቀቀለው የአውራ በጉ ወርች”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

መለየትን ማሣወቅ
እዚህ ላይ “መለየት”ማለት “ራስን መሥጠት” ማለት ነው።ይሄ አሕፅሮተ ሥም “ተለየ” በሚል ግሥ መገለፅ ይችላል።“ራሱን መሥጠቱን ማመልከት”ወይም “ራሱን ለእግዚአብሔር መሥጠቱን ማሣወቅ”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውንና አሕፅሮተ ሥምን የሚለውን ይመልከቱ)

ካህኑ እነርሱን መወዝወዝ ይኖርበታል
ዕቃዎቹን ለናዝራዊው ከሰጠው በኋላ ካህኑ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ለማቅረብ እንደገና ከእርሱ ይቀበላቸዋል።የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“ከዚያ በኋላ ካህኑ እንደገና ወስዶ ሊወዘውዛቸው ይገባል”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከ..ጋር
“እርሱንም ጭምር”

ከተወዘወዘው
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ካህኑ የወዘወዘው”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

የቀረበውን
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እርሱ ያቀረበውን”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 6:21

የእርሱ መለየት
እዚህ ላይ “መለየት”ማለት “መሠጠት”ማለት ነው።አሕፅሮት ስሙ በግሥ መልክ ሊፃፍ ይችላል።“የእርሱ መሠጠት”ወይም “ራሱን ለእግዚአብሔር መለየቱ”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውንና አሕፅሮተ ሥምን የሚለውን ይመልከቱ)

እጁም ከሚያገኘው ሌላ
ይሄ የሚያመለክተው አንድ ናዝራዊ የሆነ ሰው እንዲሰጥ ከታዘዘው በላይ ለመሥጠት መወሰኑን ነው።የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ሃሣብ የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“ተጨማሪ የሚያቀርበው ቁርባን የሚኖር ከሆነ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ስእለቱን እንደተሳለ እንዲሁ ያደርጋል
“የተሳላቸውን የስእለት መሥፈርቶች ማሟላት ይጠበቅበታል”

ሕጎቹን መጠበቅ ይኖርበታል ...እንደ ናዝራዊ ሕግ መሠረት ቃሉን ለመጠበቅ
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሣሣይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን አንድ ላይ እንዲቀናጁ የተደረገው መታዘዝ እንደሚኖርበት አፅንኦት ለመስጠት ነው።(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

በናዝራዊ ሕግ በተጠቀሰው ተስፋ መሠረት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የናዝራዊ ሕግ የሚያመለክተው”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 6:22

እናንተ የእሥራኤልን ልጆች ልትባርኳቸው ይገባል
“እናንተ”የሚለው የብዙ ቁጥር ነው።(እናንተ በሚል በተለያዩ መልኮች የተገለፁትን ይመልከቱ)

ይጠብቅህ
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው።“መጠበቅ”ማለት“መከላከል”ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 6:25

ፊቱን ያብራልህ
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ለሆነ ሰው በጎ አስተሳሰብ አለው ማለት ነው። በፈገግታም ሊገለፅ ይችላል።አሕፅሮት ስሙ በግሥ መልክ ሊፃፍ ይችላል።“ፈገግ ሲልልህ”ወይም“ወደ አንተ በቅንነት ሲመለከት”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በርህራሄ ይመልከትህ
እዚህ ላይ “ይመልከትህ”የሚለው ቃል በዚያ ሰው ላይ በጎ የሆነ አስተያያት እንዳለው የሚገልፅ ነው።“አደላልህ”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ፊቱን ወደ አንተ ያንሳ ...ሰላምንም ይስጥህ
እዚህ ላይ “አንተ”የሚለው ቃል ነጠላ ነው።(አንተ በሚል በተለያዩ መልኮች የተገለፁትን ይመልከቱ)

ስሜን መሥጠት ይኖርባቸዋል
እዚህ ላይ እግዚአብሔር “ስሜን”ሰጥቻለሁ ብሎ በመናገሩ እሥራኤላውያን የራሱ እንደሆኑ ያውጃል።“የእሥራኤል ሕዝብ የእኔ መሆናቸውን ማሳወቅ ይኖርባቸዋል”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 7

1 ማደሪያ ድንኳኑን በጨረሰ ቀን፣ ከመገልገያ ዕቃዎቹ ጋር ቀብቶ ለያህዌ ለየው። በመሰዊያውና በዕቃዎቹ ላይ እንዲሁ አደረገ። ቀብቶ ለያህዌ ለያቸው። 2 በዚያ
ቀን፣ የእስራኤል መሪዎች፣ የአባቶቻቸው ቤተሰቦች አባቶች መስዋዕቶችን አቀረቡ። ጎሳዎቹን የሚመሩት እነዚህ ሰዎች ነበሩ። እነዚህ የህዝብ ቀጠራውን
ተቆጣጠሩ። 3 መስዋዕቶቻቸውን ያህዌ ፊት አመጡ። ስድስት የተሸፈኑ ሰረገሎችና አስራ ሁለት በሬዎች አመጡ። ለየሁለቱ መሪዎች አንድ ሰረገላ አመጡ፣
እያንዳንዱ መሪ አንድ በሬ አመጣ። እነርሱ እነዚህን ነገሮች በማደሪያው ድንኳን ፊት አቀረቡ። 4 ከዚያም ያህዌ ሙሴን ተናገረው። እንዲህም አለው፣ 5
“መስዋዕታቸውን ከእነርሱ ተቀበልና ለመገናኛው ድንኳን ሥራ አውላቸው። ለሥራው እንደሚያስፈልጋቸው ለእያንዳንዱ፣ መስዋዕቶቹን ለሌዋውያን ስጥ።” 6
ሙሴ ሰረገሎቹንና በሬዎቹን ወስዶ ለሌዋውያኑ ሰጣቸው። 7 ለጌድሶናውያን ተውልዶች ለስራቸው እንደሚያስፈልግ ሁለት ሰረገላዎችና አራት በሬዎች ሰጠ። 8
ለሜራሪ ትውልዶች በካህኑ በአሮን ልጅ በኢታምር በኩል አራት ሰረገሎችንና ስምንት በሬዎችን ሰጠ። ይህን ያደረገው ሥራቸው ይህን ስለሚጠይቅ ነው። 9
ለቀዓት ትውዶች ከእነዚህ ነገሮች ምንም አልሰጠም፣ ምክንያቱም የእነርሱ የሥራ ድርሻ የያህዌ የሆኑትን ነገሮች በገዛ ትከሻቸው ከመሸከም ጋር የተያያዘ ነው።
10 መሪዎቹ ሙሴ መሰዊያውን በቀባ ዕለት ስጦታዎቻቸውን ለመሰዊያው መቀደስ ሰጡ። መሪዎቹ መስዋዕቶቻቸውን በመሰዊያው ፊት አቀረቡ። 11 ያህዌ
ሙሴን እንዲህ አለው፣ “እያንዳንዱ መሪ ለመሰዊያው መቀደስ በራሱ ቀን መስዋዕቱን ማቅረብ አለበት።” 12 በመጀመሪያው ቀን፣ ከይሁዳ ጎሳ የሆነው፣
የአሚናዳብ ልጅ ነአሶን፣ መስዋዕቱነ አቀረበ። 13 መስዋዕቱ ይህ ነበር፣ በቤተ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን 130 ሰቅሎች የሚመዝን አንድ የብር ሳህን እና ሰባ
ሰቅሎች የሚዝን አንድ ጎድጓዳ የብር ሳህን ነበሩ። እነዚህ ሁለትም ዕቃዎች ለእህል ቁርባን የሚሆን በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት የተሞሉ ነበሩ። 14
በተጨማሪም በእጣን የተሞላ አስር ሰቅሎች የሚመዝን አንድ የወርቅ ሰሃን ሰጠ። 15 ለሚቃጠል መስዋዕት አንድ ኮርማ፣ አንድ አውራ በግ፣ እና የአንድ አመት
ወንድ ጠቦት በግ ሰጠ። 16 ለኃጢአት መስዋዕት አንድ ወንድ ፍየል ሰጠ። 17 ሁለት በሬዎች፣ አምስት አውራ በጎች፣ አምስት ወንድ ፍየሎች፣ እና አንድ አመት
የሆናቸው አምስት ወንድ የበግ ጠቦቶች፣ ለህብረት መስዋዕት እንዲቀርቡ ሰጠ። ይህ የአሚናዳብ ልጅ የነአሶን መስዋዕት ነበር። 18 በሁለተኛው ቀን፣ የይሳኮር
መሪ፣ የሶገር ልጅ ናትናኤል፣ መስዋዕቱን አቀረበ። 19 አንድ መቶ ሰላሳ ሰቅሎችን የሚመዝን አንድ ሳህን እና ሰባ ሰቅሎች የሚመዝን አንድ ጎድጓዳ የብር ሰሀን
በቤተ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን መስዋዕቱን አቀረበ። እነዚህ ሁለቱም ዕቃዎች ለእህል ቁርባን የሚሆን በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት የተሞሉ ነበሩ። 20
በተጨማሪም በዕጣን የተሞላ አስር ሰቅሎች የሚመዝን አንድ የወርቅ ሰሀን ሰጠ። 21 ለሚቃጠል መስዋዕት አንድ ኮርማ፣ አንድ አውራ በግ እና የአንድ አመት
ወንድ በግ ጠቦት ሰጠ። 22 ለኃጢአት መስዋዕት አንድ ወንድ ፍየል ሰጠ። 23 ሁለት በሬዎች አምስት አውራ በጎች፣ አምስት ወንድ ፍየሎች፣ እና አንድ አመት
የሆናቸው አምስት ወንድ በግ ጠቦቶች፣ ለህብረት መስዋዕት ሆነው እንዲቀርቡ ሰጠ። ይህ የሶገር ልጅ የናትናኤል መስዋዕት ነበር። 24 በሶስተኛው ቀን
የዛብሎን መሪ፣ የኬሎን ልጅ ኤልያብ፣ መስዋዕቱን አቀረበ። 25 አንድ መቶ ሰላሳ ሰቅሎችን የሚመዝን አንድ ሳህን እና ሰባ ሰቅሎች የሚመዝን አንድ ጎድጓዳ
የብር ሰሀን በቤተ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን መስዋዕቱን አቀረበ። እነዚህ ሁለቱም ዕቃዎች ለእህል ቁርባን የሚሆን በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት የተሞሉ ነበሩ።
26 በተጨማሪም በዕጣን የተሞላ አስር ሰቅሎች የሚመዝን አንድ የወርቅ ሰሀን ሰጠ። 27 ለሚቃጠል መስዋዕት አንድ ኮርማ፣ አንድ አውራ በግ እና የአንድ
አመት ወንድ በግ ጠቦት ሰጠ። 28 ለኃጢአት መስዋዕት አንድ ወንድ ፍየል ሰጠ። 29 ሁለት በሬዎች አምስት አውራ በጎች፣ አምስት ወንድ ፍየሎች፣ እና አንድ
አመት የሆናቸው አምስት ወንድ በግ ጠቦቶች፣ ለህብረት መስዋዕት ሆነው እንዲቀርቡ ሰጠ። ይህ የኬሎን ልጅ የኤልያብ መስዋዕት ነበር። 30 በአራተኛው ቀን፣
የሮቤል ትውልድ መሪ የሰዲዮር ልጅ ኤሊሱር መስዋዕቱን አቀረበ። 31 መስዋዕቱ ይህ ነበር፣ በቤተ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን 130 ሰቅሎችን የሚመዝን አንድ
ሳህን እና ሰባ ሰቅሎች የሚመዝን አንድ ጎድጓዳ የብር ሰሀን በቤተ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን መስዋዕቱን አቀረበ። እነዚህ ሁለቱም ዕቃዎች ለእህል ቁርባን የሚሆን
በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት የተሞሉ ነበሩ። 32 በተጨማሪም በዕጣን የተሞላ አስር ሰቅሎች የሚመዝን አንድ የወርቅ ሰሀን ሰጠ። 33 ለሚቃጠል
መስዋዕት አንድ ኮርማ፣ አንድ አውራ በግ እና የአንድ አመት ወንድ በግ ጠቦት ሰጠ። 34 ለኃጢአት መስዋዕት አንድ ወንድ ፍየል ሰጠ። 35 ሁለት በሬዎች
አምስት አውራ በጎች፣ አምስት ወንድ ፍየሎች፣ እና አንድ አመት የሆናቸው አምስት ወንድ በግ ጠቦቶች፣ ለህብረት መስዋዕት ሆነው እንዲቀርቡ ሰጠ። ይህ
የሰዲዮር ልጅ የአሌሊሱር መስዋዕት ነበር። 36 በአምስተኛው ቀን፣ የስምዖን ትውልድ መሪ፣ የሱሪሰዳይ ልጅ ስልሚኤል መስዋዕቱን አቀረበ። 37 መስዋዕቱ
ይህ ነበር፣ በቤተ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን 130 ሰቅሎችን የሚመዝን አንድ ሳህን እና ሰባ ሰቅሎች የሚመዝን አንድ ጎድጓዳ የብር ሰሀን በቤተ መቅደሱ ሰቅል
ሚዛን መስዋዕቱን አቀረበ። እነዚህ ሁለቱም ዕቃዎች ለእህል ቁርባን የሚሆን በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት የተሞሉ ነበሩ። 38 በተጨማሪም በዕጣን
የተሞላ አስር ሰቅሎች የሚመዝን አንድ የወርቅ ሰሀን ሰጠ። 39 ለሚቃጠል መስዋዕት አንድ ኮርማ፣ አንድ አውራ በግ እና የአንድ አመት ወንድ በግ ጠቦት
ሰጠ። 40 ለኃጢአት መስዋዕት አንድ ወንድ ፍየል ሰጠ። 41 ሁለት በሬዎች አምስት አውራ በጎች፣ አምስት ወንድ ፍየሎች፣ እና አንድ አመት የሆናቸው አምስት
ወንድ በግ ጠቦቶች፣ ለህብረት መስዋዕት ሆነው እንዲቀርቡ ሰጠ። ይህ የሱሪሰዳይ ልጅ የስልሚኤል መስዋዕት ነበር። 42 በስድስተኛው ቀን፣ የጋድ ትውልድ
መሪ፣ የራጉኤል ልጅ ኤሊሳፍ መስዋዕቱን አቀረበ። 43 መስዋዕቱ ይህ ነበር፣ በቤተ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን 130 ሰቅሎችን የሚመዝን አንድ ሳህን እና ሰባ
ሰቅሎች የሚመዝን አንድ ጎድጓዳ የብር ሰሀን በቤተ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን መስዋዕቱን አቀረበ። እነዚህ ሁለቱም ዕቃዎች ለእህል ቁርባን የሚሆን በዘይት
የተለወሰ መልካም ዱቄት የተሞሉ ነበሩ። 44 በተጨማሪም በዕጣን የተሞላ አስር ሰቅሎች የሚመዝን አንድ የወርቅ ሰሀን ሰጠ። 45 ለሚቃጠል መስዋዕት
አንድ ኮርማ፣ አንድ አውራ በግ እና የአንድ አመት ወንድ በግ ጠቦት ሰጠ። 46 ለኃጢአት መስዋዕት አንድ ወንድ ፍየል ሰጠ። 47 ሁለት በሬዎች አምስት አውራ
በጎች፣ አምስት ወንድ ፍየሎች፣ እና አንድ አመት የሆናቸው አምስት ወንድ በግ ጠቦቶች፣ ለህብረት መስዋዕት ሆነው እንዲቀርቡ ሰጠ። ይህ የራጉኤል ልጅ
የኤሊሳፍ መስዋዕት ነበር። 48 በሰባተኛው ቀን፣ የኤፍሬም ትውልድ መሪ፣ የዓመሁድ ልጅ ኤሊሳማ መስዋዕቱን አቀረበ። 49 መስዋዕቱ ይህ ነበር፣ በቤተ
መቅደሱ ሰቅል ሚዛን 130 ሰቅሎችን የሚመዝን አንድ ሳህን እና ሰባ ሰቅሎች የሚመዝን አንድ ጎድጓዳ የብር ሰሀን በቤተ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን መስዋዕቱን
አቀረበ። እነዚህ ሁለቱም ዕቃዎች ለእህል ቁርባን የሚሆን በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት የተሞሉ ነበሩ። 50 በተጨማሪም በዕጣን የተሞላ አስር ሰቅሎች
የሚመዝን አንድ የወርቅ ሰሀን ሰጠ። 51 ለሚቃጠል መስዋዕት አንድ ኮርማ፣ አንድ አውራ በግ እና የአንድ አመት ወንድ በግ ጠቦት ሰጠ። 52 ለኃጢአት
መስዋዕት አንድ ወንድ ፍየል ሰጠ። 53 ሁለት በሬዎች አምስት አውራ በጎች፣ አምስት ወንድ ፍየሎች፣ እና አንድ አመት የሆናቸው አምስት ወንድ በግ ጠቦቶች፣
ለህብረት መስዋዕት ሆነው እንዲቀርቡ ሰጠ። ይህ የራጉኤል ልጅ የኤሊሳፍ መስዋዕት ነበር። 54 በስምንተኛው ቀን፣ የምናሴ ትውልድ መሪ፣ የፍደሱር ልጅ
ገሚልኤል መስዋዕቱን አቀረበ። 55 መስዋዕቱ ይህ ነበር፣ በቤተ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን 130 ሰቅሎችን የሚመዝን አንድ ሳህን እና ሰባ ሰቅሎች የሚመዝን
አንድ ጎድጓዳ የብር ሰሀን በቤተ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን መስዋዕቱን አቀረበ። እነዚህ ሁለቱም ዕቃዎች ለእህል ቁርባን የሚሆን በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት
የተሞሉ ነበሩ። 56 በተጨማሪም በዕጣን የተሞላ አስር ሰቅሎች የሚመዝን አንድ የወርቅ ሰሀን ሰጠ። 57 ለሚቃጠል መስዋዕት አንድ ኮርማ፣ አንድ አውራ በግ
እና የአንድ አመት ወንድ በግ ጠቦት ሰጠ። 58 ለኃጢአት መስዋዕት አንድ ወንድ ፍየል ሰጠ። 59 ሁለት በሬዎች አምስት አውራ በጎች፣ አምስት ወንድ ፍየሎች፣
እና አንድ አመት የሆናቸው አምስት ወንድ በግ ጠቦቶች፣ ለህብረት መስዋዕት ሆነው እንዲቀርቡ ሰጠ። ይህ የፍደሱር ልጅ የገማልኤል መስዋዕት ነበር። 60
በዘጠነኛው ቀን፣ የብንያም ትውልድ መሪ፣ የጋዴዮን ልጅ አቢዳን መስዋዕቱን አቀረበ። 61 መስዋዕቱ ይህ ነበር፣ በቤተ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን 130 ሰቅሎችን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የሚመዝን አንድ ሳህን እና ሰባ ሰቅሎች የሚመዝን አንድ ጎድጓዳ የብር ሰሀን በቤተ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን መስዋዕቱን አቀረበ። እነዚህ ሁለቱም ዕቃዎች ለእህል ቁርባን የሚሆን በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት የተሞሉ ነበሩ። 62 በተጨማሪም በዕጣን የተሞላ አስር ሰቅሎች የሚመዝን አንድ የወርቅ ሰሀን ሰጠ። 63 ለሚቃጠል መስዋዕት አንድ ኮርማ፣ አንድ አውራ በግ እና የአንድ አመት ወንድ በግ ጠቦት ሰጠ። 64 ለኃጢአት መስዋዕት አንድ ወንድ ፍየል ሰጠ። 65 ሁለት በሬዎች አምስት አውራ በጎች፣ አምስት ወንድ ፍየሎች፣ እና አንድ አመት የሆናቸው አምስት ወንድ በግ ጠቦቶች፣ ለህብረት መስዋዕት ሆነው እንዲቀርቡ ሰጠ። ይህ የጋዲዮን ልጅ የአቢዳን. መስዋዕት ነበር። 66 በአስረኛው ቀን፣ የዳን ትውልድ መሪ፣ የአሚሳይ ልጅ አኪዔዘር መስዋዕቱን አቀረበ። 67 መስዋዕቱ ይህ ነበር፣ በቤተ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን 130 ሰቅሎችን የሚመዝን አንድ ሳህን እና ሰባ ሰቅሎች የሚመዝን አንድ ጎድጓዳ የብር ሰሀን በቤተ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን መስዋዕቱን አቀረበ። እነዚህ ሁለቱም ዕቃዎች ለእህል ቁርባን የሚሆን በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት የተሞሉ ነበሩ። 68 በተጨማሪም በዕጣን የተሞላ አስር ሰቅሎች የሚመዝን አንድ የወርቅ ሰሀን ሰጠ። 69 ለሚቃጠል መስዋዕት አንድ ኮርማ፣ አንድ አውራ በግ እና የአንድ አመት ወንድ በግ ጠቦት ሰጠ። 70 ለኃጢአት መስዋዕት አንድ ወንድ ፍየል ሰጠ። 71 ሁለት በሬዎች አምስት አውራ በጎች፣ አምስት ወንድ ፍየሎች፣ እና አንድ አመት የሆናቸው አምስት ወንድ በግ ጠቦቶች፣ ለህብረት መስዋዕት ሆነው እንዲቀርቡ ሰጠ። ይህ የፍደሱር ልጅ የገማልኤል መስዋዕት ነበር። 72 በአስራ አንደኛው ቀን፣ የአሴር ትውልድ መሪ፣ የኤክራን ልጅ ፋግኤል መስዋዕቱን አቀረበ። 73 መስዋዕቱ ይህ ነበር፣ በቤተ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን 130 ሰቅሎችን የሚመዝን አንድ ሳህን እና ሰባ ሰቅሎች የሚመዝን አንድ ጎድጓዳ የብር ሰሀን በቤተ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን መስዋዕቱን አቀረበ። እነዚህ ሁለቱም ዕቃዎች ለእህል ቁርባን የሚሆን በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት የተሞሉ ነበሩ። 74 በተጨማሪም በዕጣን የተሞላ አስር ሰቅሎች የሚመዝን አንድ የወርቅ ሰሀን ሰጠ። 75 ለሚቃጠል መስዋዕት አንድ ኮርማ፣ አንድ አውራ በግ እና የአንድ አመት ወንድ በግ ጠቦት ሰጠ። 76 ለኃጢአት መስዋዕት አንድ ወንድ ፍየል ሰጠ። 77 ሁለት በሬዎች አምስት አውራ በጎች፣ አምስት ወንድ ፍየሎች፣ እና አንድ አመት የሆናቸው አምስት ወንድ በግ ጠቦቶች፣ ለህብረት መስዋዕት ሆነው እንዲቀርቡ ሰጠ። ይህ የኤክራን ልጅ የፋግኤል መስዋእት ነበር። 78 በአስራ ሁለተኛው ቀን፣ የንፍታሌም ትውልድ መሪ፣ የዔናን ልጅ ኢኬሬ መስዋዕቱን አቀረበ። 79 መስዋዕቱ ይህ ነበር፣ በቤተ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን 130 ሰቅሎችን የሚመዝን አንድ ሳህን እና ሰባ ሰቅሎች የሚመዝን አንድ ጎድጓዳ የብር ሰሀን በቤተ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን መስዋዕቱን አቀረበ። እነዚህ ሁለቱም ዕቃዎች ለእህል ቁርባን የሚሆን በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት የተሞሉ ነበሩ። 80 በተጨማሪም በዕጣን የተሞላ አስር ሰቅሎች የሚመዝን አንድ የወርቅ ሰሀን ሰጠ። 81 ለሚቃጠል መስዋዕት አንድ ኮርማ፣ አንድ አውራ በግ እና የአንድ አመት ወንድ በግ ጠቦት ሰጠ። 82 ለኃጢአት መስዋዕት አንድ ወንድ ፍየል ሰጠ። 83 ሁለት በሬዎች አምስት አውራ በጎች፣ አምስት ወንድ ፍየሎች፣ እና አንድ አመት የሆናቸው አምስት ወንድ በግ ጠቦቶች፣ ለህብረት መስዋዕት ሆነው እንዲቀርቡ ሰጠ። ይህ የኤናን ልጅ የኤኪሬ መስዋዕት ነበር። 84 የእስራኤል መሪዎች ሙሴ መሰዊያውን በቀባበት ቀን እነዚህን ሁሉ ነገሮች አቀረቡ። አስራ ሁለት የብር ሳህኖች፣ አስራ ሁለት የብር ጎድጓዳ ሳህኖች እና አስራ ሁለት የወርቅ ሰሃኖች አቀረቡ። 85 እያንዳንዱ የብር ሳህን 130 ስቅሎች ሲመዝን እያንዳንዱ ጎድጓዳ ሰሀን ሰባ ሰቅሎች ይመዝናል። ሁሉም የውሃ መያዣዎች በቤተ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን 2400 ሰቅሎች ይመዝናሉ። 86 አስራ ሁለቱ ዕጣን የተሞሉ የወርቅ ሰሃኖች እያንዳንዳቸው በቤተ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን አስር ሰቅሎች ይመዝናሉ። ሁሉም የወርቅ ሳህኖች 120 ሰቅሎች ይመዝናሉ። 87 ለሚቃጠል መስዋዕት አስራ ሁለት በሬዎች፣ አስራ ሁለት አውራ በጎች፣ እና አስራ ሁለት የአንድ አመት ጠቦቶች አቀረቡ። የእህል ቁርባናቸውን ሰጡ። ለኃጢአት መስዋዕት አስራ ሁለት ወንድ ፍየሎች ሰጡ። 88 ከብቶቻቸው ሁሉ፣ ሀያ አራት በሬዎች፣ ስልሳ አውራ በጎች፣ ስልሳ ወንድ ፍየሎች እና አንድ አመት የሆናቸው ስልሳ ወንድ ጠቦት በጎች የህብረት መስዋዕት አድርገው አቀረቡ። እነዚህ ሁሉ መሰዊያውን ለመቀደስ በሚቀባበት ጊዜ የቀረቡ ስጦታዎች ናቸው። 89 ሙሴ ከያህዌ ጋር ለመነጋገር ወደ መገናኛው ድንኳን በገባ ጊዜ፣ ከእርሱ ጋር ሲነጋገር ድምጹን ሰማ። ያህዌ ከማስተሰርያ መክደኛ በላይ ሆኖ በቃል ኪዳን ታቦቱ ላይ፣ በሁለቱ ኪሩቤል መካከል ለእርሱ ተናገረ።

Numbers 7:1

ሙሴ ማደሪያውን ፈፀመ
“ሙሴ ማደሪያውን መሥራቱን አጠናቀቀ”

የእሥራኤል አለቆች ...አባቶቻቸው ቤቶች አለቆች
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በተለያዩ መንገዶች ሁለት ተመሳሳይ የሆኑ ቡድኖችን ነው የሚገልፁት።“የእሥራኤል አለቆች የሆኑትና በተመሳሳይ ሁኔታ አባቶች ቤቶች አለቆች የሆኑ” (ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

የአባቶች ቤቶች አለቆች
እዚህ ላይ የአባቶች ቤቶች መሪዎች “አለቆች”ተብለው ተጠርተዋል። “የአባቶቻቸው ቤቶች መሪዎች”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

የሚካሄደውን ቆጠራ ይከታተሉ ነበር
“ቆጠራ”የሚለው አሕፅሮተ ስም እንደ ግሥ ለገለፅ ይችላል።“አሮንንና ሙሴን በቆጠራ አግዘዋቸዋል”(አሕፅሮተ ሥምን የሚለውን ይመልከቱ)

መባቸውን በእግዚአብሔር ፊት አቀረቡ ...ይህንንም በመገናኛው ድንኳኑ ፊት አቀረቡት
ይሄ ማለት መባቸውን ከሰጡ በኋላ ወደ መገናኛ ድንኳኑ አመጡት ማለት ነው።ምናልባትም እነዚህ ሐረጎች ነገሩን የበለጠ ግልፅ ለማድረግ ሊቀናጁ ይችላሉ።“መባቸውን ለእግዚአብሔር ካመጡ በኋላ በመገናኛ ድንኳኑ ፊት አቀረቡት።”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ስድስት የተከደኑ ሠረገሎችና አሥራ ሁለት በሬዎች(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
6 የተከደኑ ሠረገሎችና 12 በሬዎች

Numbers 7:4

ለእያንዳንዱ እንደየገልግሎታቸው
“ለእንዳንዱ ለሥራው እንደሚያስፈልገው መጠን”

Numbers 7:6

ጌድሶን ... ሜራሪ
ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 3፡17 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

እንደ አገልገሎታቸው መጠን
“ምክኒያቱም ለሥራ የሚያስፈልጋቸውን ያህል ነበር”

ከካህኑም ከአሮን እጅ ከኢታምር በታች
“በካህኑ በአሮን ልጅ በኢታምር ተቆጣጣሪነት”ወይም “የካህኑ የአሮን ልጅ የሆነው ኢታምር ሥራቸውን ተመለከተ”

ኢታምር
ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 1:2 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

የሚያደርጉት አገልግሎት በሚጠይቀው አንፃር
“ምክኒያቱም ሥራውን ለማከናወን የሚያስፈልጋቸው ይሄ ስለነበር”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Numbers 7:9

ከእነዚያ ነገሮች አንዱ እንኳን
ይሄ የሚያመለክተው ሠረገሎቹንና በሬዎቹን ነው።

ቀአት
ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 3፡17 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

ማገልገል የእነርሱ ነውና
“ሥራቸው የሚሆነው”

ለእግዚአብሔር የሆኑት ዕቃዎች
ለእግዚአብሔር የሆኑት ነገሮች የሚለውንና በአግባቡ ያልተገለፀውን ነገር በሚገባ ልትገልፁት ትችላላችሁ።“ እግዚአብሔር ለመገናኛ ድንኳኑ እንዲሆን የመደበው”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 7:10

ዕቃዎቻቸውን አቀረቡ
“ሥጦታዎችን አቀረቡ”

እያንዳንዱ አለቃ መሥዋዕቱን በተመደበለት ቀን ማቅረብ ይጠበቅበታል
“አንድ መሪ በእያንዳንዱ ዕለት መሥዋዕቱን ማቅረብ ይኖርበታል”

Numbers 7:12

በመጀመሪያው ቀን
“ቀን 1”ወይም “ቀን ቁጥር 1” (ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

የአሚናዳብ ልጅ ነአሶን
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው።ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 1፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

130 ሰቅል የሚመዝን
“አንድ መቶ ሠላሣ ሰቅል የሚመዝን” “አስፈላጊ ሆኖ የሚገኝ ከሆነ እነዚህ ክብደቶች በዘመናዊ መለኪያ ሊፃፉ ይችላሉ።” “አንድ ኪሎ ግራም አካባቢ የሚመዝን”ወይም “አንድ ኪሎ ግራምና 430 ግራሞች” (ቁጥሮችንና የመፅሐፍ ቀዱስ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባ ሰቅል የሆነ አንድ የብር ድስት
“ሰባ ሰቅል የሚመዝን አንድ የብረት ድስት”አስፈላጊ የሚሆን ከሆነ እነዚህን መመዘኛዎች በዘመናዊ መለኪያ መለካት ይችላል።“አንድ አስረኛ ኪሎግራም አካባቢ የሚመዝን”ወይም “770 ግራም የሚመዝን አንድ የብረት ድስት”

በቤተመቅደሱ የሰቅል ሚዛን መሠረት
የተለያዩ ዓይነት የሰቅል ሚዛኖች ነበሩ።ይሄኛው ሰዎች በመቅደሱ ውስጥ ለሚገኘው የተቀደሰው ድንኳን የሚጠቀሙበት ነው።ሚዛኖቹን ወደ ዘመናዊ መለኪያ እየለወጣችሁ ከሆነ ይሄንን ሐረግ የመተርጎሚያ ሌላ መንገድ እነሆ።“በመቅደሱ ውስጥ በሚገኘው የሚዛን ደረጃ የተለካ”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለከያ የሚለውን ይመልከቱ) “እያንዳንዳቸው አንድ ዓመት የሆናቸው”

የአሚናዳብ ልጅ የነአሶን መባ ይሄ ነበረ
ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 1፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

Numbers 7:18

በሁለተኛውም ቀን
“ቀን 2”ወይም “ቀን ቁጥር 2” (ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

የሶገር ልጅ ናትናኤል
ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 1፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

130 ሰቅሎች የሚመዝን አንድ የብር ወጭት
አስፈላጊ ሆኖ የሚገኝ ከሆነ እነዚህ ሚዛኖች በዘመናዊ መለኪያዎች መፃፍ ይኖርባቸዋል።ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“አንድ የብር ወጭት አንድ ኪሎ ግራም ተኩል ገደማ ይመዝናል”ወይም “አንድ ብር ወጭት አንድ ኪሎ ግራም ከ430 ግራሞች ይመዝናሉል”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባ ሰቅል የሚመዝን አንድ የብር ድስት
“አንድ የብር ድስት 70 ሰቅል ይመዝናል”አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ እነዚህ ሚዛኖች በዘመናዊ መለኪያዎች ሊፃፉ ይችላል።ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 1፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።”አንድ የብር ሣህን አንድ አሥራ ስምንተኛ ኪሎግራም ገደማ የሚመዝን ነው”ወይም “አንድ የብር ሣህን 770 ግራም ይመዝናል።”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በቤተመቅደሱ የሰቅል ሚዛን መሠረት
የተለያዩ ዓይነት የሰቅል ሚዛኖች ነበሩ።ይሄኛው በመቅደሱ ውስጥ ለሚገኘው የተቀደሰው ድንኳን ሰዎች የሚጠቀሙበት ነው።ሚዛኖቹን ወደ ዘመናዊ መለኪያ እየለወጣችሁ ከሆነ ይሄንን ሐረግ የመተርጎሚያ ሌላ መንገድ እነሆ።“በመቅደሱ ውስጥ በሚገኘው ደረጃ ሚዛን የተለካ”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለከያ የሚለውን ይመልከቱ)

በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።” በዘይት የተለወሰው መልካም ዱቄት”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 7:20

አሥር ሰቅሎች የሚመዝን የወርቅ ሰሃን
አስፈላጊ ሆኖ የሚገኝ ከሆነ እነዚህ ሚዛኖች በዘመናዊ መለኪያዎች መፃፍ ይኖርባቸዋል።ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7፡14 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“አንድ የወርቅ ሳህን አንድ አሥረኛ ኪሎ ግራም ይመዝናል”ወይም “አንድ የወርቅ ሳህን 110 ግራሞች ይመዝናል”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ዓመት የሆነው
“እያንዳንዳቸው አንድ ዓመት የሆናቸው”

ይሄ የሶገር ልጅ የናትናኤል መሥዋዕት ነው
“ይሄ የሶገር ልጅ ናትናኤል ያቀረበው ነው”

የሶገር ልጅ ናትናኤል
የዚህን ሰው ስም በኦሪት ዘኁልቁ 1፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

Numbers 7:24

በሶስተኛውም ቀን
“ቀን 3”ወይም “ቀን ቁጥር 3” (ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

የኬሎን ልጅ ኤልያብ
የዚህን ሰው ሥም በኦሪት ዘኁልቁ 1:9 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

130 ሰቅሎች የሚመዝን አንድ የብር ወጭት
አስፈላጊ ሆኖ የሚገኝ ከሆነ እነዚህ ሚዛኖች በዘመናዊ መለኪያዎች መፃፍ ይኖርባቸዋል።ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።"አንድ የብር ወጭት አንድ ኪሎ ግራም ተኩል ገደማ ይመዝናል"ወይም "አንድ ብር ወጭት አንድ ኪሎ ግራም ከ430 ግራሞች ይመዝናሉ"(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባ ሰቅል የሚመዝን አንድ የብር ድስት
"አንድ የብር ድስት 70 ሰቅል ይመዝናል"አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ እነዚህ ሚዛኖች በዘመናዊ መለኪያዎች ሊፃፉ ይችላል።ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።"አንድ የብር ሣህን አንድ አሥራ ስምንተኛ ኪሎግራም ገደማ የሚመዝን ነው"ወይም "አንድ የብር ሣህን 770 ግራም ይመዝናል።"(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በቤተመቅደሱ የሰቅል ሚዛን መሠረት
የተለያዩ ዓይነት የሰቅል ሚዛኖች ነበሩ።ይሄኛው ሰዎች በመቅደሱ ውስጥ ለሚገኘው የተቀደሰው ድንኳን የሚጠቀሙበት ነው።"ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።በመቅደሱ ውስጥ በሚገኘው የጥራት ደረጃ መሠረት የተመዘነ"(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለከያ የሚለውን ይመልከቱ)

በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።" በዘይት የተለወሰው መልካም ዱቄት"(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

አሥር ሰቅል የሚመዝን አንድ የወርቅ ሣህን
አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ይሄ በዘመናዊ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል።እነዚህን ተመሳሳይ የሆኑ ሚዛኖችን በኦሪት ዘኁልቁ 7:14 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመለከቱ።"አንድ ወርቅ ሣህን አንድ አሥረኛ ኪሎግራም ይመዝናል"ወይም "አንድ የወርቅ ሣህን 110 ግራሞች ይመዝናል"(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለከያ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 7:27

አንድ ዓመት የሆነው
"እያንዳንዳቸው አንድ ዓመት የሆናቸው"

ይሄ የኬሎን ልጅ የኤልያብ መሥዋዕት ነው
"የኬሎን ልጅ ኤልያብ ያቀረበው መሥዋዕት ይሄ ነበር።"

የኬሎን ልጅ ኤልያብ
የዚህን ሰው ሥም በኦሪት ዘኁልቁ 1:19 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

Numbers 7:30

በአራተኛውም
"ቀን 4"ወይም "ቀን ቁጥር 4" (ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰዲዮር ልጅ ኤሊሱር
የዚህን ሰው ሥም በኦሪት ዘኁልቁ 1:5 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

130 ሰቅሎች የሚመዝን አንድ የብር ወጭት
አስፈላጊ ሆኖ የሚገኝ ከሆነ እነዚህ ሚዛኖች በዘመናዊ መለኪያዎች መፃፍ ይኖርባቸዋል።ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።"አንድ የብር ወጭት አንድ ኪሎ ግራም ተኩል ገደማ ይመዝናል"ወይም "አንድ ብር ወጭት አንድ ኪሎ ግራም ከ430 ግራሞች ይመዝናል"(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባ ሰቅል የሚመዝን አንድ የብር ድስት
"አንድ የብር ድስት 70 ሰቅል ይመዝናል"አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ እነዚህ ሚዛኖች በዘመናዊ መለኪያዎች ሊፃፉ ይችላሉ።ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።"አንድ የብር ሣህን አንድ አሥራ ስምንተኛ ኪሎግራም ገደማ የሚመዝን ነው"ወይም "አንድ የብር ሣህን 770 ግራም ይመዝናል።"(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በቤተመቅደሱ የሰቅል ሚዛን መሠረት
የተለያዩ ዓይነት የሰቅል ሚዛኖች ነበሩ።ይሄኛው ሰዎች በመቅደሱ ውስጥ ለሚገኘው የተቀደሰው ድንኳን የሚጠቀሙበት ነው።"ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።በመቅደሱ ውስጥ በሚገኘው የጥራት ደረጃ መሠረት የተመዘነ"(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለከያ የሚለውን ይመልከቱ)

በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።" በዘይት የተለወሰው መልካም ዱቄት"(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

አሥር ሰቅል የሚመዝን አንድ የወርቅ ሣህን
አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ይሄ በዘመናዊ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል።እነዚህን ተመሳሳይ የሆኑ ሚዛኖችን እንዴት በኦሪት ዘኁልቁ 7:14 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመለከቱ።"አንድ ወርቅ ሣህን አንድ አሥረኛ ኪሎ ግራም ይመዝናል"ወይም "አንድ የወርቅ ሣህን 110 ግራሞች ይመዝናል"(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለከያ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 7:33

አንድ ዓመት የሆነው
"እያንዳንዳቸው አንድ ዓመት የሆናቸው"

ይሄ የሰዲዮር ልጅ ኤሊሱር መሥዋዕት ነው
"የሰዲዮር ልጅ ኤሊሱር ያቀረበው መሥዋዕት ይሄ ነበር።"

የኬሎን ልጅ ኤልያብ
የዚህን ሰው ሥም በኦሪት ዘኁልቁ 1:5 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

Numbers 7:36

በአምስተኛውም ቀን
"ቀን 5"ወይም "ቀን ቁጥር 5" (ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

የሱሪሰዳይ ልጅ ሰለሚኤል
የዚህን ሰው ሥም በኦሪት ዘኁልቁ 1:6 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

130 ሰቅሎች የሚመዝን አንድ የብር ወጭት
አስፈላጊ ሆኖ የሚገኝ ከሆነ እነዚህ ሚዛኖች በዘመናዊ መለኪያዎች መፃፍ ይኖርባቸዋል።ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።"አንድ የብር ወጭት አንድ ኪሎ ግራም ተኩል ገደማ ይመዝናል"ወይም "አንድ ብር ወጭት አንድ ኪሎ ግራም ከ430 ግራሞች ይመዝናል"(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሰባ ሰቅል የሚመዝን አንድ የብር ድስት
“አንድ የብር ድስት 70 ሰቅል ይመዝናል”አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ እነዚህ ሚዛኖች በዘመናዊ መለኪያዎች ሊፃፉ ይችላሉ።ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።”አንድ የብር ሣህን አንድ አሥራ ስምንተኛ ኪሎግራም ገደማ የሚመዝን ነው”ወይም “አንድ የብር ሣህን 770 ግራም ይመዝናል።”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በቤተመቅደሱ የሰቅል ሚዛን መሠረት
የተለያዩ ዓይነት የሰቅል ሚዛኖች ነበሩ።ይሄኛው ሰዎች በመቅደሱ ውስጥ ለሚገኘው የተቀደሰው ድንኳን ሰዎች የሚጠቀሙበት ነው።“ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።በመቅደሱ ውስጥ በሚገኘው ደረጃ ሚዛን የተለካ”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለከያ የሚለውን ይመልከቱ)

በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።” በዘይት የተለወሰው መልካም ዱቄት”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

አሥር ሰቅል የሚመዝን አንድ የወርቅ ሣህን
አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ይሄ በዘመናዊ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል።እነዚህን ተመሳሳይ የሆኑ ሚዛኖችን እንዴት በኦሪት ዘኁልቁ 7:14 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመለከቱ።”አንድ ወርቅ ሣህን አንድ አሥረኛ ኪሎግራም ይመዝናል”ወይም “አንድ የወርቅ ሣህን 110 ግራሞች ይመዝናል”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለከያ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 7:39

አንድ ዓመት የሆነው
“እያንዳንዳቸው አንድ ዓመት የሆናቸው”

ይሄ የሱዲዮር ልጅ የሰለሚኤል መሥዋዕት ነው
“የሱዲዮር ልጅ ሰለሚኤል ያቀረበው መሥዋዕት ይሄ ነበር።”

የሱዲዮር ልጅ ሰለሚኤል
የዚህን ሰው ሥም በኦሪት ዘኁልቁ 1:6 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

Numbers 7:42

በስድስተኛውም ቀን
“ቀን 6”ወይም “ቀን ቁጥር 6” (ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

የራጉኤል ልጅ ኤሊሳፍ
የዚህን ሰው ሥም በኦሪት ዘኁልቁ 1:14 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

130 ሰቅሎች የሚመዝን አንድ የብር ወጭት
አስፈላጊ ሆኖ የሚገኝ ከሆነ እነዚህ ሚዛኖች በዘመናዊ መለኪያዎች መፃፍ ይኖርባቸዋል።ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“አንድ የብር ወጭት አንድ ኪሎ ግራም ተኩል ገደማ ይመዝናል”ወይም “አንድ ብር ወጭት አንድ ኪሎ ግራም ከ430 ግራሞች ይመዝናል”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባ ሰቅል የሚመዝን አንድ የብር ድስት
“አንድ የብር ድስት 70 ሰቅል ይመዝናል”አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ እነዚህ ሚዛኖች በዘመናዊ መለኪያዎች ሊፃፉ ይችላሉ።ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።”አንድ የብር ሣህን አንድ አሥራ ስምንተኛ ኪሎግራም ገደማ የሚመዝን ነው”ወይም “አንድ የብር ሣህን 770 ግራም ይመዝናል።”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በቤተመቅደሱ የሰቅል ሚዛን መሠረት
የተለያዩ ዓይነት የሰቅል ሚዛኖች ነበሩ።ይሄኛው ሰዎች በመቅደሱ ውስጥ ለሚገኘው የተቀደሰው ድንኳን የሚጠቀሙበት ነው።“ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።በመቅደሱ ውስጥ በሚገኘው ደረጃ ሚዛን የተለካ”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለከያ የሚለውን ይመልከቱ)

በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።” በዘይት የተለወሰው መልካም ዱቄት”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

አሥር ሰቅል የሚመዝን አንድ የወርቅ ሣህን
አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ይሄ በዘመናዊ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል።እነዚህን ተመሳሳይ የሆኑ ሚዛኖችን እንዴት በኦሪት ዘኁልቁ 7:14 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመለከቱ።”አንድ ወርቅ ሣህን አንድ አሥረኛ ኪሎግራም ይመዝናል”ወይም “አንድ የወርቅ ሣህን 110 ግራሞች ይመዝናል”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለከያ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 7:45

አንድ ዓመት የሆነው
“እያንዳንዳቸው አንድ ዓመት የሆናቸው”

ይሄ የራጉኤል ልጅ የኤሊሳፍ መሥዋዕት ነው
“የራጉኤል ልጅ ኤሊሳፍ ያቀረበው መሥዋዕት ይሄ ነበር።”

የራጉኤል ልጅ ኤሊሳፍ
የዚህን ሰው ሥም በኦሪት ዘኁልቁ 1:14 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

Numbers 7:48

በሰባተኛውም ቀን
“ቀን 7”ወይም “ቀን ቁጥር 7” (ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

የዓሚሁድ ልጅ ኤሊሳማ
የዚህን ሰው ሥም በኦሪት ዘኁልቁ 1:10 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

130 ሰቅሎች የሚመዝን አንድ የብር ወጭት
አስፈላጊ ሆኖ የሚገኝ ከሆነ እነዚህ ሚዛኖች በዘመናዊ መለኪያዎች መፃፍ ይኖርባቸዋል።ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“አንድ የብር ወጭት አንድ ኪሎ ግራም ተኩል ገደማ ይመዝናል”ወይም “አንድ ብር ወጭት አንድ ኪሎ ግራም ከ430 ግራሞች ይመዝናል”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባ ሰቅል የሚመዝን አንድ የብር ድስት
“አንድ የብር ድስት 70 ሰቅል ይመዝናል”አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ እነዚህ ሚዛኖች በዘመናዊ መለኪያዎች ሊፃፉ ይችላሉ።ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።”አንድ የብር ሣህን አንድ አሥራ ስምንተኛ ኪሎግራም ገደማ የሚመዝን ነው”ወይም “አንድ የብር ሣህን 770 ግራም ይመዝናል።”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በቤተመቅደሱ የሰቅል ሚዛን መሠረት
የተለያዩ ዓይነት የሰቅል ሚዛኖች ነበሩ።ይሄኛው ሰዎች በመቅደሱ ውስጥ ለሚገኘው የተቀደሰው ድንኳን የሚጠቀሙበት ነው።“ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።በመቅደሱ ውስጥ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በሚገኘው የጥራት ደረጃ መሠረት የተመዘነ”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።”በዘይት የተለወሰው መልካም ዱቄት”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

አሥር ሰቅል የሚመዝን አንድ የወርቅ ሣህን
አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ይሄ በዘመናዊ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል።እነዚህን ተመሳሳይ የሆኑ ሚዛኖችን በኦሪት ዘኁልቁ 7:14 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመለከቱ።”አንድ ወርቅ ሣህን አንድ አሥረኛ ኪሎግራም ይመዝናል”ወይም “አንድ የወርቅ ሣህን 110 ግራሞች ይመዝናል”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 7:51

አንድ ዓመት የሆነው
“እያንዳንዳቸው አንድ ዓመት የሆናቸው”

ይሄ የአሚሁድ ልጅ የኤሊሰማ መሥዋዕት ነው
“የአሚሁድ ልጅ ኤሊሰማ ያቀረበው መሥዋዕት ይሄ ነበር።”

Numbers 7:54

በስምንተኛውም ቀን
“ቀን 8”ወይም “ቀን ቁጥር 8” (ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

የፍዳሱር ልጅ ገማልኤል
የዚህን ሰው ሥም በኦሪት ዘኁልቁ 1:10 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

130 ሰቅሎች የሚመዝን አንድ የብር ወጭት
አስፈላጊ ሆኖ የሚገኝ ከሆነ እነዚህ ሚዛኖች በዘመናዊ መለኪያዎች መፃፍ ይኖርባቸዋል።ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“አንድ የብር ወጭት አንድ ኪሎ ግራም ተኩል ገደማ ይመዝናል”ወይም “አንድ ብር ወጭት አንድ ኪሎ ግራም ከ430 ግራሞች ይመዝናል”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባ ሰቅል የሚመዝን አንድ የብር ድስት
“አንድ የብር ድስት 70 ሰቅል ይመዝናል”አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ እነዚህ ሚዛኖች በዘመናዊ መለኪያዎች ሊፃፉ ይችላሉ።ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።”አንድ የብር ሣህን አንድ አሥራ ስምንተኛ ኪሎግራም ገደማ የሚመዝን ነው”ወይም “አንድ የብር ሣህን 770 ግራም ይመዝናል።”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በቤተመቅደሱ የሰቅል ሚዛን መሠረት
የተለያዩ ዓይነት የሰቅል ሚዛኖች ነበሩ።ይሄኛው ሰዎች በመቅደሱ ውስጥ ለሚገኘው የተቀደሰው ድንኳን የሚጠቀሙበት ነው።“ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።በመቅደሱ ውስጥ በሚገኘው ደረጃ ሚዛን የተለካ”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።”በዘይት የተለወሰው መልካም ዱቄት”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

አሥር ሰቅል የሚመዝን አንድ የወርቅ ሣህን
አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ይሄ በዘመናዊ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል።እነዚህን ተመሳሳይ የሆኑ ሚዛኖችን በኦሪት ዘኁልቁ 7:14 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመለከቱ።”አንድ ወርቅ ሣህን አንድ አሥረኛ ኪሎግራም ይመዝናል”ወይም “አንድ የወርቅ ሣህን 110 ግራሞች ይመዝናል”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 7:57

አንድ ዓመት የሆነው
“እያንዳንዳቸው አንድ ዓመት የሆናቸው”

ይሄ የፍሳዱል ልጅ የገማልኤል መሥዋዕት ነው
“የፍሳዱል ልጅ ገማልኤል ያቀረበው መሥዋዕት ይሄ ነበር።”

የፍሳዱል ልጅ ገማልኤል
የዚህን ሰው ሥም በኦሪት ዘኁልቁ 1:14 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

Numbers 7:60

በዘጠነኛውም ቀን
“ቀን 9”ወይም “ቀን ቁጥር 9” (ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

የጋዴዮን ልጅ አቢዳን
የዚህን ሰው ሥም በኦሪት ዘኁልቁ 1:11 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

130 ሰቅሎች የሚመዝን አንድ የብር ወጭት
አስፈላጊ ሆኖ የሚገኝ ከሆነ እነዚህ ሚዛኖች በዘመናዊ መለኪያዎች መፃፍ ይኖርባቸዋል።ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“አንድ የብር ወጭት አንድ ኪሎ ግራም ተኩል ገደማ ይመዝናል”ወይም “አንድ ብር ወጭት አንድ ኪሎ ግራም ከ430 ግራሞች ይመዝናል”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባ ሰቅል የሚመዝን አንድ የብር ድስት
“አንድ የብር ድስት 70 ሰቅል ይመዝናል”አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ እነዚህ ሚዛኖች በዘመናዊ መለኪያዎች ሊፃፉ ይችላሉ።ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።”አንድ የብር ሣህን አንድ አሥራ ስምንተኛ ኪሎግራም ገደማ የሚመዝን ነው”ወይም “አንድ የብር ሣህን 770 ግራም ይመዝናል።”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በቤተመቅደሱ የሰቅል ሚዛን መሠረት
የተለያዩ ዓይነት የሰቅል ሚዛኖች ነበሩ።ይሄኛው ሰዎች በመቅደሱ ውስጥ ለሚገኘው የተቀደሰው ድንኳን ሰዎች የሚጠቀሙበት ነው።“ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።በመቅደሱ ውስጥ በሚገኘው የጥራት ደረጃ መሠረት የተመዘነ”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።”በዘይት የተለወሰው መልካም ዱቄት”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

አሥር ሰቅል የሚመዝን አንድ የወርቅ ሣህን
አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ይሄ በዘመናዊ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል።እነዚህን ተመሳሳይ የሆኑ ሚዛኖችን በኦሪት ዘኁልቁ 7:14 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመለከቱ።”አንድ ወርቅ ሣህን አንድ አሥረኛ ኪሎ ግራም ይመዝናል”ወይም “አንድ የወርቅ ሣህን 110 ግራሞች ይመዝናል”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 7:63

አንድ ዓመት የሆነው
“እያንዳንዳቸው አንድ ዓመት የሆናቸው”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይሄ የአቢዳን ልጅ የጋዴዮን መሥዋዕት ነው
“የአቢዳን ልጅ ጋዴዮን ያቀረበው መሥዋዕት ይሄ ነበር።”

የአቢዳን ልጅ ጋዴዮን
የዚህን ሰው ሥም በኦሪት ዘኁልቁ 1:11 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

Numbers 7:66

በአስረኛውም ቀን
“ቀን 10”ወይም “ቀን ቁጥር 10” (ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

የአሚሳዳይ ልጅ አኪዔዘር
የዚህን ሰው ሥም በኦሪት ዘኁልቁ 1:12 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

130 ሰቅሎች የሚመዝን አንድ የብር ወጭት
አስፈላጊ ሆኖ የሚገኝ ከሆነ እነዚህ ሚዛኖች በዘመናዊ መለኪያዎች መፃፍ ይኖርባቸዋል።ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“አንድ የብር ወጭት አንድ ኪሎ ግራም ተኩል ገደማ ይመዝናል”ወይም “አንድ ብር ወጭት አንድ ኪሎ ግራም ከ430 ግራሞች ይመዝናል”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባ ሰቅል የሚመዝን አንድ የብር ድስት
“አንድ የብር ድስት 70 ሰቅል ይመዝናል”አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ እነዚህ ሚዛኖች በዘመናዊ መለኪያዎች ሊፃፉ ይችላሉ።ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።”አንድ የብር ሣህን አንድ አሥራ ስምንተኛ ኪሎግራም ገደማ የሚመዝን ነው”ወይም “አንድ የብር ሣህን 770 ግራም ይመዝናል።”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በቤተመቅደሱ የሰቅል ሚዛን መሠረት
የተለያዩ ዓይነት የሰቅል ሚዛኖች ነበሩ።ይሄኛው ሰዎች በመቅደሱ ውስጥ ለሚገኘው የተቀደሰው ድንኳን የሚጠቀሙበት ነው።“ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።በመቅደሱ ውስጥ በሚገኘው ደረጃ ሚዛን የተለካ”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።”በዘይት የተለወሰው መልካም ዱቄት”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

አሥር ሰቅል የሚመዝን አንድ የወርቅ ሣህን
አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ይሄ በዘመናዊ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል።እነዚህን ተመሳሳይ የሆኑ ሚዛኖችን እንዴት በኦሪት ዘኁልቁ 7:14 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመለከቱ።”አንድ የወርቅ ሣህን አንድ አሥረኛ ኪሎግራም ይመዝናል”ወይም “አንድ የወርቅ ሣህን 110 ግራሞች ይመዝናል”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 7:69

“እያንዳንዳቸው አንድ ዓመት የሆናቸው”
“እያንዳንዳቸው አንድ ዓመት የሆናቸው”

ይሄ የአሚሳዳይ ልጅ የአኪዔዜር መሥዋዕት ነው
“የአሚሳዳይ ልጅ አኪዔዜር ያቀረበው መሥዋዕት ይሄ ነበር።”

የአሚሳዳይ ልጅ አኪዔዜር
የዚህን ሰው ሥም በኦሪት ዘኁልቁ 1:12 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

Numbers 7:72

በአሥራ አንደኛውም ቀን
“ቀን 11”ወይም “ቀን ቁጥር 11” (ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

የኤክራን ልጅ ፋግኤል
የዚህን ሰው ሥም በኦሪት ዘኁልቁ 1:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

130 ሰቅሎች የሚመዝን አንድ የብር ወጭት
አስፈላጊ ሆኖ የሚገኝ ከሆነ እነዚህ ሚዛኖች በዘመናዊ መለኪያዎች መፃፍ ይኖርባቸዋል።ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“አንድ የብር ወጭት አንድ ኪሎ ግራም ተኩል ገደማ ይመዝናል”ወይም “አንድ ብር ወጭት አንድ ኪሎ ግራም ከ 430 ግራሞች ይመዝናል”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባ ሰቅል የሚመዝን አንድ የብር ድስት
“አንድ የብር ድስት 70 ሰቅል ይመዝናል”አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ እነዚህ ሚዛኖች በዘመናዊ መለኪያዎች ሊፃፉ ይችላሉ።ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።”አንድ የብር ሣህን አንድ አሥራ ስምንተኛ ኪሎግራም ገደማ የሚመዝን ነው”ወይም “አንድ የብር ሣህን 770 ግራም ይመዝናል።”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

በቤተመቅደሱ የሰቅል ሚዛን መሠረት
የተለያዩ ዓይነት የሰቅል ሚዛኖች ነበሩ።ይሄኛው ሰዎች በመቅደሱ ውስጥ ለሚገኘው የተቀደሰው ድንኳን ሰዎች የሚጠቀሙበት ነው።“ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።በመቅደሱ ውስጥ በሚገኘው የጥራት ደረጃ መሠረት የተመዘነ”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።”በዘይት የተለወሰው መልካም ዱቄት”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

አሥር ሰቅል የሚመዝን አንድ የወርቅ ሣህን
አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ይሄ በዘመናዊ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል።እነዚህን ተመሳሳይ የሆኑ ሚዛኖችን በኦሪት ዘኁልቁ 7:14 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመለከቱ።”አንድ ወርቅ ሣህን አንድ አሥረኛ ኪሎግራም ይመዝናል”ወይም “አንድ የወርቅ ሣህን 110 ግራሞች ይመዝናል”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 7:75

አንድ ዓመት የሆናቸው
“እያንዳንዳቸው አንድ ዓመት የሆናቸው”

ይሄ የኤክራን ልጅ የፋግኤል መሥዋዕት ነው
“የኤክራን ልጅ ፋግኤል ያቀረበው መሥዋዕት ይሄ ነበር።” ኤክራንና ፋግኤል የሰዎች ሥም ነው።ስማቸውን በኦሪት ዘኁልቁ 1:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 7:78

በአሥራ ሁለተኛውም ቀን
“ቀን 12”ወይም “ቀን ቁጥር 12” (ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የዔናን ልጅ አኪሬ
የዚህን ሰው ሥም በኦሪት ዘኁልቁ 1:15 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

130 ሰቅሎች የሚመዝን አንድ የብር ወጭት
አስፈላጊ ሆኖ የሚገኝ ከሆነ እነዚህ ሚዛኖች በዘመናዊ መለኪያዎች መፃፍ ይኖርባቸዋል።ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።"አንድ የብር ወጭት አንድ ኪሎ ግራም ተኩል ገደማ ይመዝናል"ወይም "አንድ ብር ወጭት አንድ ኪሎ ግራም ከ 430 ግራሞች ይመዝናል"(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባ ሰቅል የሚመዝን አንድ የብር ድስት
"አንድ የብር ድስት 70 ሰቅል ይመዝናል"አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ እነዚህ ሚዛኖች በዘመናዊ መለኪያዎች ሊፃፉ ይችላሉ።ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።"አንድ የብር ሣህን አንድ አሥራ ስምንተኛ ኪሎግራም ገደማ የሚመዝን ነው"ወይም "አንድ የብር ሣህን 770 ግራም ይመዝናል።"(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለከያ የሚለውን ይመልከቱ)

በቤተመቅደሱ የሰቅል ሚዛን መሠረት
የተለያዩ ዓይነት የሰቅል ሚዛኖች ነበሩ።ይሄኛው ሰዎች በመቅደሱ ውስጥ ለሚገኘው የተቀደሰው ድንኳን ሰዎች የሚጠቀሙበት ነው።"ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።በመቅደሱ ውስጥ በሚገኘው የጥራት ደረጃ መሠረት የተመዘነ"(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለከያ የሚለውን ይመልከቱ)

በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።"በዘይት የተለወሰው መልካም ዱቄት"(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

አሥር ሰቅል የሚመዝን አንድ የወርቅ ሣህን
አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ይሄ በዘመናዊ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል።እነዚህን ተመሳሳይ የሆኑ ሚዛኖችን እንዴት በኦሪት ዘኁልቁ 7:14 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመለከቱ።"አንድ ወርቅ ሣህን አንድ አሥረኛ ኪሎግራም ይመዝናል"ወይም "አንድ የወርቅ ሣህን 110 ግራሞች ይመዝናል"(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለከያ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 7:81

"እያንዳንዳቸው አንድ ዓመት የሆናቸው"
"እያንዳንዳቸው አንድ ዓመት የሆናቸው"

ይሄ የዔናን ልጅ የአኪሬ መሥዋዕት ነው
"የዔናን ልጅ አኪሬ ያቀረበው መሥዋዕት ይሄ ነበር።"

የዔናን ልጅ አኪሬ
የዚህን ሰው ሥም በኦሪት ዘኁልቁ 1:15 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

Numbers 7:84

እነዚህን ሁሉ ለዩልኝ
"መለየት"የሚለው ሐረግ ለአንድ ለተወሰነ ዓላማ ራስን መሥጠት ማለት ነው።በዚህ መሠረት ሥጦታዎቹ የሚሰጡት ለእግዚአብሔር ነበር።(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሙሴ መሠዊያውን በቀባበት ቀን
እዚህ ላይ"ቀን" የሚለው ቃል የሚያመለክተው በአጠቃላይ ዘመኑን ነው። የእሥራኤል አለቆች እነዚህን ነገሮች በአሥራ ሁለት ቀናት ነበር የሚሰውት። "ሙሴ መሠውያውን በቀባበት ወቅት"

130 ሰቅሎች የሚመዝን አንድ የብር ወጭት
አስፈላጊ ሆኖ የሚገኝ ከሆነ እነዚህ ሚዛኖች በዘመናዊ መለኪያዎች መፃፍ ይኖርባቸዋል።ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።"አንድ የብር ወጭት አንድ ኪሎ ግራም ተኩል ገደማ ይመዝናል"ወይም "አንድ ብር ወጭት አንድ ኪሎ ግራም ከ 430 ግራሞች ይመዝናል"(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

እያንዳንዱ የብር ድስት **70** ሰቅል ይመዝን ነበር
"እያንዳንዱ የብር ድስት 70 ሰቅል ይመዝን ነበርይመዝናል"አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ እነዚህ ሚዛኖች በዘመናዊ መለኪያዎች ሊፃፉ ይችላል።ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።"እያንዳንዱ የብር ድስት አንድ አሥራ ስምንተኛ ኪሎግራም ገደማ የሚመዝን ነው"ወይም "አንድ የብር ድስት 770 ግራም ይመዝናል።"(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

2,400 ሰቅል
"ሁለት ሺህ አራት መቶ ሰቅል"ወይም "ሃያ አራት መቶ ሰቅል"

በቤተመቅደሱ የሰቅል ሚዛን መሠረት
የተለያዩ ዓይነት የሰቅል ሚዛኖች ነበሩ።ይሄኛው ሰዎች በመቅደሱ ውስጥ ለሚገኘው የተቀደሰው ድንኳን የሚጠቀሙበት ነው።"ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።በመቅደሱ ውስጥ በሚገኘው የጥራት ደረጃ መሠረት የተመዘነ"(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለከያ የሚለውን ይመልከቱ)

የብር ዕቃዎቹ ሁሉ ተመዘኑ...የወርቅ ዕቃዎቹ ሁሉ ተመዘኑ
"የብር ዕቃዎቹ ሁሉ በአንድ ላይ ተመዘኑ...የወርቅ ዕቃዎቹ ሁሉ በአንድ ላይ ተመዘኑ"

የብር ዕቃዎቹ ሁሉ
እነዚህ የሚያመለክቱት ከብር የተሰሩትን በሳህንና በወጭት መልክ የመጡትን ሥጦታዎች ነው።

እንዳንዳቸው አሥራ ሁለቱ የወርቅ ሣህኖች ...አሥር ሰቅል ይመዝኑ ነበር
"እንዳንዳቸው አሥራ ሁለቱ የወርቅ ሣህኖች ...10 ሰቅል ይመዝኑ ነበር። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ እነዚህ ሚዛኖች በዘመናዊ መለኪያዎች ሊፃፉ ይችላሉ። ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 7:14 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።"እያንዳንዳቸው 12 የወርቅ ሣህኖች.... አንድ አሥረኛ ኪሎግራም ይመዝኑ ነበር"ወይም "እንዳንዳቸው 12ቱ የወርቅ ሣህኖች 110 ግራም ይመዝኑ ነበር"(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

120 ሰቅል
"አንድ መቶ ሃያ ሰቅል" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 7:87

አሥራ ሁለት...ሃያ አራት..ስድሳ
"12..24...60"እነዚህ ቁጥሮች ከፊደል ይልቅ በቁጥር ሊፃፉ ይችሉ ይሆናል።(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ዓመት
"አንድ ዓመት የሆነው"

ከተቀባ በኋላ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።"ሙሴ ከቀባው በኋላ"(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Numbers 7:89

የእርሱን ድምፅ ሲናገረው ሰማ
“የእርሱ”የሚለው የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ድምፅ ነው።“እግዚአብሔር ሲናገረው ሰማ” (ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)

ከሥርየት መክደኛ በላይ ...ከኪሩቤልም መካከል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚያመለክቱት ተመሳሳይ የሆነን ሥፍራ ነው። (ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

የምሥክሩ ታቦት
ይህንን ሐረግ በኦሪት ዘኁልቁ 4፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

እርሱ ተናገረው
“እግዚአብሔር ለሙሴ ተናገረው”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 8

1 ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ **2** “አሮንን እንዲህ በለው፣ ‘ሰባቱ መብራቶች በምትለኩሳቸው ጊዜ በመቅረዙ ፊት ለፊት ብርሃን ይስጡ።’” **3** አሮን ይህን አደረገ። ያህዌ ሙሴን እንዳዘዘው፣ ከመቅረዙ ፊት ለፊት ብርሃን እንዲሰጡ መብራቶቹን በመቅረዙ ላይ ለኮሳቸው። **4** መቅረዙ የተሰራው በዚህ መንገድ ነበር። ያህዌ አሰራሩን ለሙሴ አሳይቶት ነበር። ከመሰረቱ እስከ ጫፍ በአበባ መልክ የዋንጫ መልክ ቅርጽ አስይዘህ ወርቁን ቀጥቅጠህ አብጀው። **5** እንደገና፣ ያህዌ ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው፣ **6** “ከእስራኤል ሰዎች መሃል ሌዋውያንን ወስደህ አንጻቸው። **7** እነርሱን ለማንጻት ይህን አድርግ፣ የማንጻት ውሃ እርጫቸው። ፀጉራቸው በሙሉ እንዲላጩ፣ ልብሶቻቸውን እንዲያጥቡ፣ እና በዚህ መንገድ ራሳቸውን እንዲያነጹ አድርግ። **8** ከዚያ ጥጃና በዘይት የተለወሰ የመልካም ዱቄት የእህል ቁርባን ይውሰዱ። ሌላ ጥጃ ለኃጢአት መስዋዕት ያዘጋጁ። **9** ሌዋውያኑን ወደ መገናኛው ድንኳን ፊት ለፊት አቅርባቸውና መላውን የእስራኤል ማህበረሰብ ሰብስብ። **10** በእኔ በያህዌ ፊት ሌዋውያንን አቅርብ። የእስራኤል ሰዎች እጆቻውን በሌዋውያን ላይ ይጫኑ። **11** አሮን ሌዋውያኑን በእኔ ፊት ያቅርባቸው፣ የእስራኤልን ህዝብ ወክለው በእርሱ ፊት ከፍ አድርገው እንደሚያቀርቡ አቅርባቸው። ሌዋውያን እኔን እንደሚያገለግሉ እርሱ ይህን ያድርግ። **12** ሌዋውያኑ በበሬዎቹ ላይ እጆቻውን ይጫኑ። ሌዋውያኑን ለማስተሰርይ፣ ለኃጢአት መስዋዕት አንድ ኮርማ አቅርቡ፣ ደግሞም ሌላውን ኮርማ የሚቃጠል መስዋዕት አድርገህ ለእኔ አቅርብ። **13** ሌዋውያኑን በአሮንና በልጆቹ ፊት አቁማቸው፣ እናም እንደ ሚወዘወዝ መሥዋዕት ለእኔ ከፍ አድርገህ አቅርባቸው። **14** በዚህ መንገድ ሌዋውያኑን ከእስራኤል ሰዎች መሃል ለያቸው። ሌዋውያን ለእኔ ይለዩ። **15** ከዚያ በኋላ ሌዋውያኑ ወደ መገናኛው ድንኳን ለአገልግሎት ይግቡ። እነርሱን አንጻቸው። እንደ ስጦታ ለእኔ ከፍ አድርገህ አንሳቸው። **16** ከእስራኤል ህዝብ መሀል እነርሱ ሙሉ ለሙሉ የእኔ ናቸውና ይህን አድርግ። ከእስራኤል ወገን በኩር ሁሉ፣ ማህጸን ከከፈተው ከእያንዳንዱ ወንድ ልጅ ቦታውን ይወስዳሉ። እኔ ሌዋውያንን ለራሴ ለይቻለሁ። **17** ከሰውም ሆነ ከእንስሳው የእስራኤል ህዝብ በኩሩ ሁሉ የእኔ ነው። በግብፅ ምድር የበኩሩን ህይወት ሁሉ በወሰድኩ ቀን፣ እኔ እናንተን ለራሴ ለየኋችሁ። **18** በበኩሩ ሁሉ ምትክ፣ ከእስራኤል ሰዎች መሀል ሌዋውያንን ወሰድኩ። **19** ሌዋውያንን ለአሮንና ለልጆቹ እንደ ስጦታ ሰጠኋቸው። በመገናኛው ድንኳን የእስራኤልን ሰዎች ሥራ ይስሩ ዘንድ ከእስራኤል ሰዎች መሃል ወሰድኳቸው። ወደተቀደሰው ስፍራ ሲቀርብ ምንም ጥፋት እንዳይደርስባቸው ለእስራኤል ሰዎች እንዲያስተሰርዩ እነርሱን ሰጠኋቸው።” **20** ሙሴ፣ አሮንና መላው የእስራኤል ህዝብ ይህንን ከሌዋውያን ጋር አደረጉ። ሌዋውያንን በሚመለከት ያህዌ ሙሴን ያዘዘውን ነገር ሁሉ አደረጉ። የእስራኤል ሰዎች ከእነርሱ ጋር ይህን አደረጉ። **21** ሌዋውያን ልብሶቻቸውን በማጠብ ራሳቸውን ከኃጢአት አነጹ። አሮን ለያህዌ ስጦታ አድርጎ አቀረባቸው፤ ደግም ይነጹ ዘንድ የንስሃ ማስተስረያ አደረገላቸው። **22** ከዚያ በኋላ፣ ሌዋውያኑ በአሮንና በአሮን ልጆች ፊት አገልግሎታቸውን ይሰጡ ዘንድ ወደ መገናኛው ድንኳን ገቡ። ይህም ያህዌ ስለ ሌዋውያን ሙሴን ባዘዘው መሠረት ነበር። ሌዋውያንን በሙሉ በዚህ መንገድ ተቀበሉ። **23** ያህዌ እንደገና ለሙሴ ተናገረ። እንዲህም አለ፣ **24** “ይህ ሁሉ፤ ሃያ አምስት አመት እና ከዚያ በላይ ዕድሜ ላላቸው ሌዋውያን ነው። በመገናኛው ድንኳን ለማገልገል መምጣት አለባቸው። **25** አምሳ አመት ሲሞላቸው በዚህ መንገድ ማገልገላቸውን ያቁሙ። በዚያ ዕድሜ መደበኛ አገልግሎታቸውን ያቁሙ። **26** በመገናኛው ድንኳን የሚያገለግሉ ወንድሞቻቸውን ሊያግዙ ይችላሉ፣ ነገር ግን ዕድሜያቸው አምሳ ከሆነ በኋላ በዚህ መንገድ አያገለግሉ። ለሌዋውያን በእነዚህ ጉዳዮች ሁሉ መመሪያ ልትሰጣቸው ይገባል።

Numbers 8:1

በፊቱ መብራት ማብራት ያስፈልጋል
“በመቅረዙ ፊት ያበራሉ”

Numbers 8:3

ብርሃን መሥጠት
“ማብራት”

የመቅረዙ ማስቀመጫ ተሰራ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የመቅረዙን ማስቀመጫ ሰሩት”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

እስከ አበቦቹ ድረስ ከተቀጠቀጠ ሥራ
ከአፈራው አበባ ጋር እንዲመሳሰሉ የተቀጠቀጡ ፅዋዎችን እንዲቀርፁ ይታዘዙ ነበር።“ከአበቡት አበባዎች ጋር እንዲመሳሰሉ የተቀጠቀጡ ፅዋዎች”(ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 8:7

እነርሱን ሊቀድሳቸው
እዚህ ላይ “እነርሱን”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሌዋውያንን ነው።

ኃጢአትን የሚያነፃውን ውኃ እርጫቸው
ሙሴ በእነርሱ ላይ ውኃ መርጨቱ የድነታቸው ተምሣሌት ነው።“የደህንነት ተምሣሌት የሆነውን ውኃ በእነርሱ ላይ መርጨት”(ተምሳሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ልብሣቸውን ማጠብ
ሌዋውያን የራሣቸውን ልብስ ማጠብ ይጠበቅባቸዋል።ግንዛቤ የተገኘበትን ይህንን ሃሣብ የበለጠ ልታብራሩት ትችላላችሁ።“ልብሣቸውን እንዲያጥቡ አድርግ”(ምልክቶች እንጂ ቃላት ጥቅም ላይ የማይውሉበት የሚለውን ይመልከቱ)

ልብሣቸውን ማጠብ
ሌዋውያን የራሣቸውን ልብስ ማጠብ ይጠበቅባቸዋል።ግንዛቤ የተገኘበትን ይህንን ሃሣብ የበለጠ ልታብራሩት ትችላላችሁ።“ልብሣቸውን እንዲያጥቡ አድርግ”(ምልክቶች እንጂ ቃላት ጥቅም ላይ የማይውሉበት የሚለውን ይመልከቱ)

ወይፈንና የእህሉ ቁርባን
የወይፈን ሥጦታ በሚቀርብበት ወቅት አብዛኛውን ጊዜ የእህል ሥጦታም አብሮ ይሰጥ ነበር።

በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በዘይት የለወሱት መልካም ዱቄት”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 8:9

ማህበሩን ሁሉ ሰብስብ
“ማህበሩን ሁሉ አንድ ላይ አድርጋቸው”

በእግዚአብሔር ፊት
እዚህ ላይ እግዚአብሔር የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔር ራሱን የሚገልፅበት ሥሙን ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የእሥራኤል ልጆች በሌዋውያን ላይ እጆቸውን መጫን ይኖርባቸዋል
አብዛኛውን ጊዜ በአንድ ሰው ላይ“ እጅ የመጫን” ድርጊት የሚከናወነው አንድ ሰው ለእግዚአብሔር ቤት ሥራ ወይም አገልግሎት በሚለይበት ወቅት ነው። ለእኔ ይለዩ ዘንድ የእሥራኤል ሕዝብ በሌዋውያን ላይ እጆቸውን መጫን ይኖርባቸዋል።(ተምሳሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

እንደሚወዘወዝ ሥጦታ
አሮን ሌዋውያንን ለእግዚአብሔር የሚያቀርባቸው መሥዋዕቶችን በሚያቀርብበበት ስሜት ውስጥ ሆኖ ነው።“የሚወዝወዝ ሥጦታ እንደሆኑ”(ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 8:12

ሌዋውያኑም በወይፈኖቹ ራሶች ላይ እጆቸውን መጫን ይኖርባቸዋል
ይሄ ተምሣሌታዊ አነጋገር ሲሆን ለሌዋውያን የከብቶች ሥጦታ እንደሚሰጣቸው ለመግለፅ ነው።በዚህ መንገድ ሰውዬው በእንስሳው አማካይነት ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀርባል።(ተምሳሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

እንደሚወዘወዝ ሥጦታ አድርገህ ለእኔ አቅርባቸው
አሮን ቁርባንን እንደሚያነሳ እንዲሁ ሌዋውያንን በእግዚአብሔር ፊት ማቅረብ ነበረበት። “የሚወዘወዝ ቁርባንን እንደምታቀርብልኝ እንዲሁ እነርሱን ለእኔ ለይልኝ”

Numbers 8:14

ታነፃቸዋለህ።ሥጦታም አድርገህ ታቀርባቸዋለህ።
እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች የሚደጋግመው ለጉዳዩ አፅንዖትን ለመስጠት ነው።ይሄ መከናወን የሚኖርበት ሌዋውያኑ በመገናኛ ድንኳን ውስጥ አገልግሎትን ከመጀመራቸው አስቀድሞ ነው።የዚህ ዓረፍተ ነገር ሃሣብ የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“ነገር ግን በመጀመሪያ ልታነጿቸው ይገባል።እንደ ሥጦታ ልታቀርቧቸው ይገባችኋል (በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደሚወዘወዝ ሥጦታ አድርገህ ታቀርባቸዋለህ
የሚወዘወዙ ቁርባን ይመስል አሮን እነርሱን ለእግዚአብሔር ማቅረብ ነበረበት።“የሚወዘወዝ ቁርባን ለእኔ እንደሚቀርብ እንዲሁ እነርሱን ለእኔ ማቅረብ ይኖርብሃል።”(ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 8:16

በኩራት ሁሉ፤ማሕፀን የሚከፍት ሁሉ
በመሠረቱ እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን በጋራ እንዲነገሩ የተደረገው በኩር ልጆችን በተመለከተ የበለጠ አፅንዖት ለመስጠት ሲባል ነው። (ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

ማሕፀንን የሚከፍት ወንድ
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው።“ማሕፀንን የሚከፍት” ማለት ለመጀመሪያ ጊዜ ልጅን የሚወልድ ማለት ነው።ይሄ የሚያመለክተው እናት ለመጀመሪያ ጊዜ የምትወልደውን ወንድ ልጅን ነው።“ለእናቱ የመጀመሪያ ሆኖ የተወለደ ወንድ ልጅ”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሕይወታቸውን ነጠቅኩ
ይሄ አንድ ሰው ሌላ ሰውን በሚገድልበት ወቅት የሚገለፅበት የትህትና አነጋገር ነው።“ገደልኩ”(ሥርዓት የሌለውን ነገር በመልካም ነገር መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱን ለእኔ ለይቻቸዋለሁ
እዚህ ላይ “እነርሱን”የሚለው ቃል የሚያመለክተው “በእሥራኤል መካከል የተወለዱትን በኩሮች ነው”

Numbers 8:18

በበኩራቱ ፋንታ ...ሌዋውያንን ወስጃለሁ
“ወስጃለሁ” የሚለው ቃል በመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር ግልፅ ሲሆን በሁለተኛውም እንዲሁ ሊደገም ይችላል።“በኩሮቹን ከመውሰድ ይልቅ… ሌዋውያንን በሙሉ ወስጃለሁ”(ምልክቶች እንጂ ቃላት ጥቅም ላይ የማይውሉበት የሚለውን ይመልከቱ)

ሌዋውያንን ለአሮንና ለልጆቹ ሥጦታ አድርጌ ሰጥቻቸዋለሁ
እግዚአብሔር ሌዋውያን አሮንና ልጆቹን እንዲያግዟቸው የመደበበትን ሁኔታ ልክ እግዚአብሔር ለአሮንና ለልጆቹ እንደ ሥጦታ እንደሰጣቸው ተደርጎ ሲነገር እናያለን።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱን ወስጃቸዋለሁ...እነርሱን ሰጥቻቸዋለሁ
እዚህ ላይ “እነርሱን”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሌዋውያንን ነው።

እነርሱ በሚቀርቡበት ወቅት
እዚህ ላይ “እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእሥራኤልን ሕዝብ ነው።

Numbers 8:20

ሙሴና አሮን የእሥራኤልም ማህበር ሁሉ...የእሥራኤል ማህበር ይህንን ከእነርሱ ጋር አደረጉ
እዚህ ላይ ተመሳሳይ መረጃ የሚሰጡ ሶስት ተመሳሳይ ዓረፍተ ነገሮች አሉ። እንዲደጋገም የተፈለገበት ምክኒያት ሰዎቹ በሌዋውያን ላይ ያደረጉት ነገር በእግዚአብሔር ትዕዛዝ እንደሆነ አፅንዖት ለመሥጠት ነው።ሙሴና አሮን የእሥራኤልም ማህበር ሁሉ ሌዋውያንን በሚመለከት እግዚአብሔር የሰጠውን ትዕዛዝ ሁሉ ፈፀሙ። (ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 8:22

አገልግሎታቸውን ይሰሩ ዘንድ
“አገልግሎት”የሚለው አሕፅሮተ ሥም በግሥ መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ማገልገል”(አሕፅሮተ ሥምን የሚለውን ይመልከቱ)

በአሮንና በልጆቹ ፊት
x

Numbers 8:25

ዕድሜያቸው ሃምሳ ዓመት ሲሞላ
“በሃምሳ ዓመት ዕድሜ” ወይም “ሃምሳ ዓመት ሲሞላቸው”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 9

1 ከግብጽ ምድር ከወጡ በኋላ በሁለተኛው አመት በመጀመሪያው ወር፣ በሲና ምድረ በዳ ያህዌ ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው፣ **2** “የእስራኤል ሰዎች በተወሰነው የአመቱ ወቅት ፋሲካን ያድርጉ። **3** በዚህ ወር በእስራ አራተኛው ቀን፣ ምሽት ላይ፣ በተወሰነው በአመቱ ወቅት ፋሲካን አድርጉ። ፋሲካን አድርጉ፣ ደንቦቹን ጠብቁ፣ ከዚህ ጋር የተያያዙ ደንቦችን ሁሉ ታዘዙ።” **4** ስለዚህ፣ ሙሴ የፋሲካን በዓል እንዲያከብሩ ለእስራኤል ሰዎች ሁሉ ነገራቸው። **5** ስለዚህ በመጀመሪያው ወር በወሩ በአስራ አራተኛው ቀን፣ ምሽት ላይ፣ በሲና ምድረ በዳ ፋሲካን አከበሩ። የእስራኤል ሰዎች ያህዌ ለሙሴ እንዲያደርግ ያዘዘውን ሁሉ አደረጉ። **6** በሞተ ሰው በድን የረከሱ አንዳንድ ሰዎች ነበሩ። እነርሱ በዕለቱ ፋሲካን አላከበሩም። በዚያ ቀን እነዚህ ሰዎች ሙሴና አሮን ፊት ቀረቡ። **7** እነዚያ ሰዎች ሙሴን እንዲህ አሉት፣ “እኛ በሰው በድን አካል ምክንያት ንጹህ አይደለንም። ሆኖም በእስራኤል ሰዎች መሃል በተወሰነው የአመቱ ወቅት ለያህዌ መስዋዕት ከማቅረብ ለምን ትከለክለናለህ” **8** ሙሴ እንዲህ አላቸው፣ “ያህዌ ስለ እናንተ ምን ትዕዛዝ እንደሚሰጥ እስከምሰማ ጠብቁኝ።” **9** ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ **10** ”ለእስራኤል ሰዎች እንዲህ በላቸው፣ ‘ከእናንተ ማናችሁም ወይም ከትውልዳችሁ ማንም በበድን አካል ምክንያት እርኩስ ቢሆን፣ ወይም ሩቅ መንገድ ሄዶ ቢሆን፣ ለያህዌ ፋሲካን ማክበር ይችላል።’ **11** እነርሱ በሁለተኛው ወር በአስራ አራተኛው ቀን ፋሲካን ያክብሩ። እነርሱ ፋሲካን እርሾ ባስገባበት እንጀራ ከመራራ ቅጠል ጋር ይብሉ። **12** እስከ ማለዳ አንዳች አያስተርፉለት፣ አሊያም ከእንስሳቱ አጥንት አይስበሩ። የፋሲካን ህግጋት ሁሉ ይጠብቁ። **13** ነገር ግን ማናቸውም ንጹህ የሆነና ሩቅ መንገድ ያልሄደ ሰው፣ ነገር ግን ፋሲካን ሳያከብር የቀረ ሰው፣ ከህዝቡ ተለይቶ ይጥፋ፤ ምክንያቱም እርሱ በተወሰነው የአመቱ ወቅት የሚቀርበውን ያህዌ የሚጠይቀውን መስዋዕት አላቀረበም። ያሰው ኃጢአቱን ይሸከም። **14** እንግዳ በመሀላችሁ ቢኖርና ፋሲካን ለያህዌ ክብር ቢያብር፣ ፋሲካን መጠበቅና እርሱ ያዘዘውን ሁሉ ማድረግ አለበት፣ የፋሲካን ህግጋት ሁሉ መጠበቅ እንዲሁም የፋሲካን ህግነት መጠበቅ አለበት። ለመጻተኞች እና በምድሪቱ ለተወለዱ ሁሉ ተመሳሳይ ህግ ይኑርህ።” **15** የማደሪያው ድንኳን በተተከለበት ቀን፣ ደመና የማደሪያውን ድንኳን ፣ የቃል ኪዳኑን ምስክር ድንኳን ሸፈነው። በምሽት ደመናው በማደሪያ ድንኳኑ ላይ ነበር። እስከ ንጋት እሳት ይመስል ነበር። **16** በዚያ መልክ ቀጠለ። ደመናው የማደሪያ ድንኳኑን ሸፍኖ በምሽት እሳት ይመስል ነበር። **17** ደመናው ከድንኳኑ ላይ በተወሰደ ጊዜ ሁሉ፣ የእስራኤል ሰዎች ከመጓዝ ያቋርጡ ነበር። ደመናው በቆመ ጊዜ ሁሉ፣ ህዝቡ አንድ ቦታ ይሰፍራል። **18** የእስራኤል ሰዎች በያህዌ ትዕዛዝ ይጓዛሉ፣ በእርሱም ትእዛዝ በሰፈራቸው ይቆያሉ። ደመናው በማደሪያው ድንኳን ላይ ሲቆም፣ በሰፈራቸው ይቆያሉ። **19** ደመናው በማደሪያው ድንኳን ለብዙ ቀናት ሲቆይ፣ የእስራኤል ሰዎች የያህዌን ትዕዛዝ ተከትለው መጓዝ ያቆማሉ። **20** አንዳንድ ጊዜ ደመናው በማደሪያው ድንኳን ላይ ለጥቂት ቀናት ይቆያል። በዚህ ሁኔታ የያዌን ትእዛዝ ተከትለው በአንድ ቦታ ይሰፍራሉ፣ ከዚያ በእርሱ ትእዛዝ እንደገና ይጓዛሉ። **21** አንዳንድ ጊዜ ደመናው ከምሽት እስከ ማለዳ በሰፈር ይገኛል። ማለዳ ደመናው ሲነሳ፣ እነርሱ ይጓዛሉ። ቀንም ይሁን ሌሊት ጉዟቸውን የሚቀጥሉት ደመናው ከተነሳ ብቻ ነው። **22** ደመናው በማደሪያ ድንኳኑ ላይ ለሁለት ቀናት፣ ለወር ወይም ለአመት ቢቆይ በዚያ ስፍራ እስከ ቆየ ድረስ የእስራኤል ሰዎች በሰፈሮቻቸው ይቆያሉ አይጓዙም። ነገር ግን ደመናው ሲንቀሳቀስ እነርሱም ጉዟቸውን ይቀጥላሉ። **23** በያህዌ ትዕዛዝ ይሰፍራሉ፣ በእርሱ ትዕዛዝ ይጓዛሉ በሙሴ በኩል የተሰጣቸውን የያህዌን ትዕዛዝ ይፈጽማሉ።

Numbers 9:1

ከግብፅ ምድር በወጡ በሁለተኛው ዓመት በመጀመሪያው ወር
ይሄ ማለት ከግብፅ ምድር የወጡት ከአንድ ዓመት ቀደም ብሎ ነው ማለት ነው።ሁለተኛ ዓመታቸውን እየጀመሩ የነበሩት በበረሃ ውስጥ ሆነው ሳሉ ነው። (ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

በመጀመሪያው ወር
በዕብራውያን የዘመን አቆጣጠር መሠረት ይሄ የመጀመሪያው ወር ነው። እግዚአብሔር የእሥራኤልን ሕዝብ ከግብፅ ምድር ያወጣበትን ጊዜ የሚያመለክት ነው።(የዕብራውያን ወራትንና ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ከግብፅ ምድር ከወጡ በኋላ
“እነርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእሥራኤልን ሕዝብ ነው።“ወጡ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው መልቀቅን ነው።“የግብፅ ምድርን ከለቀቁ በኋላ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሕዝቡ...በተመደበው ዓመት ላይ ያድርጉት
“የተመደበው”የሚለው ቃል ቀደም ሲል መርሐ ግብር በተያዘለት መሠረት ማለት ነው።ይሄ ማለት በየዓመቱ ይህን ያደርጋሉ ማለት ነው።“ሕዝቡ… በዓመቱ በሚያከብሩት መሠረት” (በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በአሥራ አራተኛው ቀን...በተመደበው ዓመት
ይሄ ፋሲካን የሚያከብሩበት ዓመት ነው።የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ሃሣብ ሊብራራ የበለጠ ይችላል። “በአሥራ አራተኛው ቀን …አክብሩት።በየዓመቱ ማክበር የሚኖርባችሁ በዚህ ወቅት ነው ነው” (በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አሥራ አራተኛው ቀን
“ቀን 14” (ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ሥርዓቱ ሁሉ እንደ ፍርዱም ሁሉ አድርጉት
በመሠረቱ እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ሁለቱ እንዲቀናጁ የተደረጉት ትዕዛዙን መፈፀም የሚኖርባቸው ስለመሆኑ አፅንዖት ለመስጠት ነው።(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

ልትጠብቁት ይገባል
“ልትጠብቁት”የሚለው ቃል ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን አክብሩት ማለት ነው። “ልታከብሩት ይገባል”ወይም “ትኩረት ልትሰጡት ይገባል”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 9:4

የፋሲካን በዓል ጠብቁ
እዚህ ላይ “ጠብቁት” የሚለው ቃል ትርጉሙ አክብሩት ማለት ነው።“ለፋሲካ በዓል ትኩረት ስጡ”ወይም “የፋሲካን በዓል አክብሩ”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በመጀመሪያው ወር በአሥራ አራተኛው ቀን
“በመጀመሪያው ወር በ14ኛው ቀን” ይሄ የዕበራውያንን የዘመን አቆጣጠር ያሣያል።(የዕብራውያን ወራትንና ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 9:6

በሞተ ሰው ሬሣ የረከሱ
ይሄ የሚያሣየው የሞተ ሰው ሬሣን ከመንካታቸው የተነሣ የረከሱ መሆናቸውን ነው።የዚህን ዓረፍተ ነገር ሙሉ ሃሣብ የበለጠ ልታብራሩት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ትችላላችሁ።“የሞተ ሰው ሬሣ ከመንካታቸው የተነሣ ረከሱ” (በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ንፁሕ ያልሆነ
እግዚአብሔር አንድን ሰው በመንፈሣዊ ሕይወቱ ተቀባይነት እንደሌለውና ወይም የረከሰ እንደሆነ የሚቆጥረውን ሰው እዚህ ሥፍራ ላይ ልክ ሰውነቱ ንፁህ እንዳልሆነ ተደርጎ ይገለፃል።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ፋሲካን ጠብቁ
“ጠብቁ”የሚለው ቃል ትኩረት ስጡት ማለት ነው። “ፋሲካን በአግባቡ ትኩረት ስጡት”ወይም “ፋሲካን አክብሩት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከሞተ ሰው ሬሣ የተነሣ
ይሄ ማለት የሞተ ሰው ሬሣ ነክተዋል ማለት ነው።የዚህን ዓረፍተ ነገር ሙሉ ፍቺ ማብራራት ትችላላችሁ።“የሞተ ሰው ሬሣ ከመንካታችን የተነሣ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በእሥራኤል መካከል ....መሥዋዕትን ከማድረግ የምታግደን ለምንድነው?
ሰዎቹ ይሄንን ጥያቄ የሚጠይቁት በፋሲካ በዓል ላይ እንዳይሳተፉ የተደረጉበትን ሁኔታ ቅሬታ ለማቅረብ ነው።ይሄ ምላሽ የማያሻው ጥያቄ በዓረፍተ ነገር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በእሥራኤል ሕዝብ መካከል ....ከመሥዋዕቱ ሥጦታ እኛን ማግለላችሁ ተገቢ አይደለም”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

አቋም መያዝ
አቋም መያዝ ወይም አስቀድሞ መወሰን።

Numbers 9:9

ንፁሕ ያልሆነ
እዚህ ሥፍራ ላይ እግዚአብሔር አንድን ሰው በመንፈሣዊ ሕይወቱ ተቀባይነት እንደሌለውና ወይም የረከሰ እንደሆነ የሚቆጥረውን ሰው ልክ ሰውነቱ ንፁህ እንዳልሆነ ተደርጎ ይገለፃል።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከሞተ ሰው ሬሣ የተነሣ
ይሄ ማለት የሞተ ሰው ሬሣ ነክተዋል ማለት ነው።የዚህን ዓረፍተ ነገር ሙሉ ፍቺ የበለጠ ማብራራት ትችላላችሁ።“የሞተ ሰው ሬሣ ከመንካታችን የተነሣ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ፋሲካን ጠብቁ
“ጠብቁ”የሚለው ቃል በአግባቡ አስቡት ማለት ነው። “ፋሲካን በአግባቡ አስቡት”ወይም “ፋሲካን አክብሩት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 9:11

በፋሲካ ብሉ
እዚህ ላይ “መብላት”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ማክበርን ነው።“ለፋሲካ ትኩረት ሥጡ”ወይም “ፋሲካን አክብሩ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በሁለተኛው ወር በአሥራ አራተኛው ቀን
“14ኛ ቀን 2ተኛ ወር” ይሄ የአይሁዳውያንን የቀን አቆጣጠር የሚያመለክት ነው።(የዕብራውያን ወራትንና ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

በመሸ ጊዜ
“ፀሐይ ስትገባ”

እርሾ ከሌለበት ቂጣ ጋር
“እርሾ የሌለው ቂጣ”

መራራ ቅጠሎች
እነዚህ ቅጠሎች ትናንሾች ሲሆኑ አብዛኛውን ጊዜ ጠንካራና መራራ ጣዕም ያላቸው ናቸው።

ወይም ከእርሱም አጥንት አይስበሩ
“እና ከእርሱ ማንኛውንም እንት መስበር አይኖርባቸውም”

Numbers 9:13

ንፁህ የሆነ ማንኛውም ሰው
እዚህ ሥፍራ ላይ እግዚአብሔር አንድን ሰው በመንፈሣዊ ሕይወቱ ተቀባይነት እንዳለው የሚቆጥረውን ሰው ልክ ሰውነቱ ንፁህ እንደሆነ ተደርጎ ይገለፃል። (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ፋሲካን ጠብቁ
“ጠብቁ”የሚለው ቃል ትኩረት ስጡት ማለት ነው። “ፋሲካን በአግባቡ ትኩረት ስጡት”ወይም “ፋሲካን አክብሩት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሰውዬው መቆረጥ ይኖርበታል
እዚህ ላይ “መቆረጥ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ንብረቱን መንጠቅና ማባረርን ነው። “ያ ሰው መባረር ይኖርበታል”ወይም “ያንን ሰው ማባረር ይኖርባችኋል”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውንና ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

አቋም መያዝ
አቋም መያዝ ወይም አስቀድሞ መወሰን።

ያ ሰው ኃጢአቱን መሸከም ይኖርበታል
እዚህ ላይ አንድ ሰው የኃጢአትን ውጤቶች መሸከም እንዳለበት የሚገልፀውን ሃሣብ ኃጢአቱን እንደ ዕቃ እንደሚሸከመው ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል።“ያ ሰው የኃጢአቱን ቅጣት መሸከም ይኖርበታል”

በእናንተ መካከል ይኖራል
እዚህ ላይ “እናንተ”የሚለው ቃል የብዙ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተውም የእሥራኤልን ሕዝብ ነው።(እናንተ የሚለውን የተለያዩ አገላለፆች የሚለውንይመልከቱ)

ትዕዛዛቱን ሁሉ መጠበቅና ማድረግ ይኖርበታል
“ያ መፃተኛ ሰው እግዚአብሔር የሚያዝዘውን ትዕዛዛት መጠበቅና ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል”

የፋሲካን ሥርዓት ይጠብቅና ሕጉን ይታዘዝ ዘንድ
በመሠረቱ እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ሁለቱ ሐረጎች እንዲቀናጁ የተደረጉበት ምክኒያት መፃተኛው የፋሲካን ሕጎች በሙሉ መታዘዝ እንደሚኖርበት አፅንዖት ለመሥጠት ነው።(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

በምድሩ ውስጥ
“በእሥራኤል ምድር ውስጥ”

Numbers 9:15

ማደሪያው ተተከለ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሌዋውያን ማደሪያውን ተከሉ”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ለምሥክሩ ድንኳን የተቀመጡ ሥርዓቶች
ይሄ የመገናኛ ድንኳኑ ሌላ ሥም ነው።“የምሥክሩ ድንኳን ሥርዓቶች የሚለውን ሐረግ ”በኦሪት ዘኁልቁ 1:50 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

እስከ ማለዳ ድረስ እሣት ይመስል ነበር
ይሄ ደመናው በሌሊት የሚኖረውን ገፅታ የሚገልፅ ነው።እዚህ ላይ ደመናው ከእሣት ጋር ሲመሳሰል እንመለከታለን።“ሌሊት በሚሆንበት ወቅት ማለዳ እስኪነጋ ድረስ ደመናው ግዙፍ እሣት ይመስል ነበር” (ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚሁ ሥርዓት መሠረት ይቀጥል ነበር
ደመናው ከመገኛና ድንኳኑ በላይ ይውል እንደነበረ መግለፁ ተገቢ ሊሆን ይችላል።“ደመናው በዚህ መልኩ በመገናኛ ድንኳኑ ላይ ይቆይ ነበር” (በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በሌሊትም የእሣት አምሳል ይመስል ነበር
የደመናው አምሳል ከግዙፍ እሣት ጋር ተነፃፅሯል።(ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)

ደመናው ይነሳ ነበር
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ተንቀሳቀሰ” ወይም “እግዚአብሔር ደመናውን አነሳው”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ደመናው ቆመ
“ደመናው መጓዙን አቋረጠ” “

Numbers 9:18

በእግዚአብሔር ትዕዛዝ መሠረት
“ትዕዛዝ”የሚለው ቃል እንደ ሥም (ሰዋሰው)ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር በሚያዝበት ወቅት” (አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 9:20

በማደሪያው ላይ
“ከማደሪያው በላይ”

ሠፈር ይሰሩ ነበር
እዚህ ላይ “መሥራት” የሚለው ቃል ማቋቋም ማለት ነው።“ሠፈራቸውን ማቋቋም” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከማታ ጀምሮ እስከ ጥዋት ድረስ
ይሄ ማለት ደመናው በማደሪያው ላይ የሚቆየው ለአንድ ሊሊት ብቻ ነው ማለት ነው።የዚህን ዓረፍተ ነገር ትርጉም የበለጠ ልታብራሩት ትችላላችሁ። “ከማታ ጀምሮ እስከ ጥዋት ድረስ ብቻ”ወይም “በማደሪያው ላይ ለአንድ ሌሊት ብቻ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የሚቀጥል ከሆነ
የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ሃሣብ የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“ደመናው በማደሪያው ላይ የሚቆይ ከሆነ” (በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ጉዞ የሚጀምሩት ደመናው ሲንቀሳቀስ ብቻ ነው
“ደመናው ሲንቀሳቀስ ጉዞ ይጀምራሉ”

Numbers 9:22

ደመናው ይነሣ ነበር
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ደመናው ብድግ አለ”ወይም “እግዚአብሔር ደመናውን አነሳው”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ትዕዛዝ
“ትዕዛዝ”የሚለው ቃል እንደ ግሥ ሊገለፅ ይችላል። (አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

በሙሴ በኩል የተሰጠ የእግዚአብሔር ትዕዛዝ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር በሙሴ በኩል የሰጠው ትዕዛዝ”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 10

1 ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ 2 ”ሁለት የብር መለከቶች አብጁ። በብር ቀጥቅጠህ አብጃቸው። መለከቶቹን ማህበረሰቡን በጋራ ለመጥራትና ከመንደሮቸው
እንዲንቀሳቀሱ ጥሪ ለማሰማት ተጠቀምባቸው። 3 ካህናቱ ማህበረሰቡን በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ በፊትህ ለመሰብሰብ መለኮቶቹን ይንፉ። 4 ካህናቱ አንድ
መለከት ብቻ ከነፉ፣ የእስራኤል ነገድ መሪዎች ይሰበስቡ። 5 ከፍ ባለ ድምጽ ስትነፉ፣ በስተምስራቅ የሰፈሩት ጉዟቸውን ይጀምሩ። 6 ለሁለተኛ ጊዜ ከፍ ባለ
ድምጽ ስትነፋ በደቡብ በኩል የሰፈሩት ጉዟቸውን ይጀምሩ። ለጉዟቸው ከፍ ያለ የመለከት ድምጽ ያሰሙ። 7 ማህበረሰቡ በአንድነት ሲበሰበሰብ፣ መለከቶች
ይነፉ ነገር ግን ድምጹ ከፍ አይበል። 8 የካህኑ የአዘሮን ልጆች፣ መለኮቶቹን ይንፉ። በትውልዶቻችሁ ሁሉ ዘንድ ይህ ለእናንተ ሁልጊዜም ስርዓት ይሆናል። 9
በሚወሯችሁ ተቃዋሚዎቻች ላይ በምድራች ለጦርነት ስትወጡ፣ ለማንቂያ የመለከት ድምጽ ታሰማላችሁ። እኔ፣ አምላካችሁ ያህዌ፣ አስባችኋለሁ ደግሞም
ከጠላቶቻችሁ አድናችኋለሁ። 10 እንደዚሁም፣ በመደበኛ ባዕላቶቻችሁም ሆነ በወራቶች መጀመሪያ ላይ በክብረ በዓል ወቅት ለሚቃጠል መስዋዕቶቻችሁ
ክብርና በህብረት መስዋዕቶቻችሁ መስዋዕቶች ላይ መለኮቶችን መንፋት አለባች። እነዚህ እናንተ የእኔ የአምላካችሁ ለመሆናችሁ መታሰቢያ ሆነው ያገለግላሉ።
እኔ አምላካችሁ ያህዌ ነኝ።” 11 በሁለተኛው አመት፣ በሁለተኛው ወር፣ በወሩ ሀያኛ ቀን ደመናው ከቃል ኪዳኑ ምስክር ማደሪያ ላይ ተነሳ። 12 የእስራኤል ሰዎች
ከሲና ምድረበዳ ተነስተው ጉዟቸውን ቀጠሉ። ደመናው በፋራን ምድረ በዳ ውስጥ ቆመ። 13 የመጀመሪያ ጉዟቸው፣ በሙሴ በኩል የተሰጣቸውን የያህዌን
ትዕዛዝ ተከትለው አደረጉ። 14 በይሁዳ ትውልዶች ዓርማ ስር ያለው ሰፋሪዎች በመጀመሪያ ተንቀሳቀሱ። የይሁዳን ሠራዊት የሚመራው የአሚናዳብ ልጅ ነአሶን
ነበር። 15 የይሳኮርን ትውልዶች ሰራዊት የሚመራው የሶገር ልጅ ናትናኤል ነበር። 16 የዛብሎንን ትውልዶች ሰራዊት የሚመራው የኬሎን ልጅ ኤልያብ ነበር።
17 የማደሪያ ድንኳኑን የተሸከሙት የጌድሶን እና የሜራሪ ትውልዶች፣ ማደሪያ ድንኳኑን ነቅለው ጉዟቸውን ጀመሩ። 18 ቀጥሎ፣ በሮቤል ሰፈር ሰራዊት ዓርማ ስር
የነበሩት ጉዟቸውን ቀጠሉ። የሮቤልን ሰራዊት የሚመራው የሶዲዮር ልጅ ኤሊሱር ነበር። 19 የስምዖንን ትውልዶች ሰራዊት የሚመራዊ የሱሪስዓይ ልጅ
ስለሚኤል ነበር። 20 የጋድን ትውልዶች ሰራዊት የሚመራው የራጉኤል ልጅ ኤሊሳፍ ነበር። 21 ቀዓታውያን ተነሱ። እነርሱ የቅድስተ ቅዱሳኑን ቅዱስ ዕቃዎች
ተሸከሙ። ቀዓታውያን ቀጣዩ ሰፈር ከመድረሳቸው አስቀድሞ ሌሎች ማደሪያ ድንኳን ይተክላሉ። 22 የኤፍሬምን ሰራዊት የሚመራው የዓሚሁድ ልጅ ኤሊሳማ
ነበር። 23 የምናሴን ትውልዶች ሰራዊት የሚመራው የፍዳሱር ልጅ ገማልኤል ነበር። 24 የብንያምን ትውልዶች ሠራዊት የሚመራው የጋዴዮን ልጅ አቢዳን
ነበር። 25 በዳን ትውልዶች ዓርማ ስር የሰፈሩት ሠራዊቶች በመጨረሻ ይወጣሉ። የዳንን ሰራዊት የሚመራው የአሚሳዳይ ልጅ አኪዔዘር ነበር። 26 የአቤርን
ትውልዶች ሰራዊት የሚመራው የኤክራን ልጅ ፋግኤል ነበር። 27 የንፍታሌምን ትውልዶች ሰራዊት የሚመራው የዔናን ልጅ አኪሬ ነበር። 28 የእስራኤል ሰዎች
ሰራዊቶች ጉዟቸውን ያደረጉት በዚህ መልክ ነው። 29 ሙሴ ከምድያማዊው የራጉኤል ልጅ ከአባብ ጋር ተነጋገረ። ራጉኤል የሙሴ ሚስት አባት ነበር። ሙሴ
ከአባብ ጋር ተነጋገረ እንዲህም አለ፣ “ያህዌ እሰጣችኋለሁ ወዳለን ስፍራ እየተጓዝን ነው። ያህዌ እንዲህ ብሎን ነበር፣ ‘እኔ ለእናንተ የተናገርኩትን እርሷኑ ስፍራ
እሰጣችኋለሁ።’ አንተ ከእኛ ጋር አብረኸን ና እኛም መልካም እናደርግልሃለን። ያህዌ ለእስራኤል መልካም ለማድረግ ቃል ገብቷል።” 30 አባብ ግን ሙሴን
እንዲህ አለው፣ “እኔ ከአንተ ጋር አልሄድም። እኔ ወደ ገዛ ምድሬና ወደ ራሴ ህዝብ እሄዳለሁ።” 31 ከዚያም ሙሴ እንዲህ ሲል መለሰ፣ “እባክህን ከእኛ
አትለይ። በበረሃ እንዴት መስፈር እንደሚቻል ታውቃለህ። ስንሰፍር ልትመለከተን ይገባል። 32 ከእኛ ጋር ብትሄድ፣ ያህዌ ለእኛ የሚያደርግልንን በጎነት ያንኑ እኛም
ለአንተ እናደርግልሃለን።” 33 ከያህዌ ተራራ ተነስተው ለሶስት ቀናት ተጓዙ። የያህዌ የቃልዳኑ ታቦት የሚያርፍበትን ስፍራ እንዲያገኙ ለመፈለግ ለሶስት ቀናት
በፊታቸው ተጓዘ። 34 ሲጓዙ የያህዌ ደመና በቀን ብርሃን በላያቸው ነበር። 35 ታቦቱ በተነሳበት ጊዜ ሁሉ፣ ሙሴ እንዲህ ይላል፣ “ያህዌ ሆይ፣ ተነስ።
ጠላቶችህን በትን። የሚጠሉህ ከአንተ እንዲሸሹ አድርግ።” 36 ታቦቱ በቆመ ጊዜ ሁሉ፣ ሙሴ “ያህዌ ሆይ፣ ብዙ አስር ሺህ ወደሚሆኑት እስራኤላውያን
ተመለስ” ይል ነበር።

Numbers 10:1

ሁለት የብር መለከቶች
ይሄ ማለት እግዚአብሔር የሆነ ሰው መለከት እንዲሰራ ለሙሴ ትዕዛዝን ሰጥተታል ማለት ነው።ራሱ አይደለም የሰራቸው።“ለአንድ ሰው ሁለት መለከቶቸን እንዲሰራ ንገረው”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

መለከቶቹን ልትጠቀምባቸው ይገባሃል
ሙሴ መለከቶቹን የሚነፋው ራሱ ሳይሆን መለከቶቹን እንዲነፉ ካህናቱን ያዝዛቸዋል።(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 10:3

በፊትህ
“አንተ እዚያው እያለህ” ይሄ ማለት ካህኑ መለከቱን በሚነፋበት ወቅት ሙሴ እዚያው መገኘት አለበት ማለት ነው።

መሪዎች፤የእሥራኤል ነገድ አለቆች
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆኑ የነገድ ክፍሎችን የሚያመለክቱ ናቸው። እዚህ ላይ ሁለተኛው ሐረግ ጥቅም ላይ የዋለው የመጀመሪያውን ሐረግ ለማብራራት ሲባል ነው።“የእሥራኤል ነገድ አለቆች የሆኑ መሪዎች”(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ ከፍ ባለ ድምፅ መለከት ሰትነፉ
እዚህ ላይ“እናንተ”የሚለው ቃል የብዙ ቁጥር ነው።እግዚአብሔር ለሙሴ እየተናገረ ቢሆንም የሚያመለክተው ግን ካህናቱን ነው።ካህናቱ እንጂ ሙሴ መለከቱን አይነፋም።“ከፍ ባለ ድምፅ በሚነፉበት ወቅት”(እናንተ የሚለውን በተለያየ መልክ የሚገልፀውንና ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 10:6

እናንተ ከፍ ባለ ድምፅ ስትነፉ
እዚህ ላይ“እናንተ”የሚለው ቃል የብዙ ቁጥር ነው።እግዚአብሔር ለሙሴ እየተናገረ ቢሆንም የሚያመለክተው ግን ካህናቱን ነው።ካህናቱ እንጂ ሙሴ መለከቱን አይነፋም።“ከፍ ባለ ድምፅ በሚነፉበት ወቅት”(እናንተ የሚለውን በተለያየ መልክ የሚገልፀውንና ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ለሁለተኛ ጊዜ
“ቁጥር 2 ጊዜ”ወይም “እንደገና”(ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

ማሕበሩ በሚሰባሰብበት ወቅት
“ማሕበሩን በአንድነት መሰብሰብ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እነርሱ የእነርሱን ጉዞ ለማስጀመር ከፍ ባለ ድምፅ መንፋት ይኖርባቸዋል
“እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ካህናቱን ሲሆን “የእነርሱ”የሚለው ቃል ደግሞ የሚያመለክተው የእሥራኤልን ሕዝብ ነው።

ይሄ ለእናንተ ሥርዓት ይሁን
“ለእናንተ ሕግ ይሁን” እዚህ ላይ “እናንተ”የሚለው ቃል የብዙ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተው የእሥራኤልን ሕዝብ ነው።(እናንተ ለሚለው ቃል የተለያዩ አገላለፆች የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 10:9

አንተ ወደ ሠልፍ በምትወጣበት..በሚገፏችሁ ወቅት
እግዚአብሔር አንተ የሚለውን ቃል እየተጠቀመ ለሙሴ እየተናገረ ቢሆንም በመሠረቱ የሚናገረው ወደ ጦርነት ለሚወጣው ለእሥራኤል ሕዝብ ነው።“የእሥራኤል ሕዝብ ወደ ጦርነት በሚወጣበት ወቅት...እሥራኤል በምትገፋበት ወቅት”(ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)

ከፍ ባለ ድምፅ መለከቶቹን ይንፉ
እዚህ ላይ እግዚአብሔር ሙሴን አንተ እያለ እየተናገረው ቢሆንም በመሠረቱ ግን ሙሴ ካህናቱን መለከት እንዲያስነፋቸው ነበር ይናገረው የነበረው። (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ትታሰባላችሁ
“ትታሰባላችሁ”የሚለው ሐረግ “ትታወሳላችሁ ማለት ነው።“አስባችኋለሁ”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 10:10

በዓልን ማክበር
“መከበር”የሚለው ስም “ማክበር”በሚለው ግሥ ሊገለፅ ይችላል።“በምታከብሩበት ወቅት”(አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

መለከቱን መንፋት ይኖርባችኋል
እዚህ ላይ እግዚአብሔር ለሙሴ ቢናገርም በመሠረቱ ካህናቱ መለከቱን እንዲነፉ ነው የፈለገው።“ካህናቱ መለከቱን እንዲነፉ ትዕዛዝ መሥጠት ይኖርብሃል”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

በወሩ መጀመሪያ
በዕብራውያን የቀን አቆጣጠር መሠረት አሥራ ሁለት ወራት አሉ።በብርማ ቀለም የሚደምቀው የጨረቃ በርሃን የመጀመሪያው ምዕራፍ በቀን አቆጣጠሩ ላይ የመጀመሪያው ወር መሆኑን ያመለክታል።(የዕብራውያን ወራት የሚለውን ይመልከቱ)

የሚቃጠል መሥዋዕታችሁ...የደህንነት መሠሥዋዕታችሁ...እናንተ ለእኔ
በእነዚህ ሐረጎች ውስጥ “እናንተ”የሚለው ቃል የብዙ ቁጥር በመሆኑ የሚያመለክተው የእሥራኤልን ሕዝበ ነው።(እናንተ ለሚለው ቃል የተለያዩ አገላለፆች የሚለውን መልከቱ)

መሥዋዕታችሁ ላይ
“ለመሥዋዕቱ ከብር”

እነርሱም ለመታሰቢያ ይሆኑላቸኋል
“ለእኔ መታሰቢያ ይሆናችኋል” “መታሰቢያ”የሚለው ቃል “መታሰብ”በሚለው ግሥ ሊገለፅ ይችላል።“እኔን እንድታሰቡ ያደርጋችኋል”(አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱም ይሆኑላችኋል
“እነርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው መለከቶቹንና መሥዋዕቶቹን ነው።

Numbers 10:11

በሁለተኛውም ዓመት
“2ተኛ ዓመት”ይሄ የሚያመለክተው እግዚአብሔር እሥራኤላውያንን ከግብፅ ያወጣበትን ሁለተኛውን ወር ነው። (ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

በሁለተኛውም ወር ከወሩም በሃያኛው ቀን
“በ2ተኛውም ወር ከወሩም በ20ኛው ቀን”በዕብራውያን የቀን አቆጣጠር መሠረት ይሄ ሁለተኛው ወር ነው።”(የዕብራውያን ወራትንና ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

ደመናው ተነሳ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ደመናው ብድግ አለ”ወይም “እግዚአብሔር ደመናውን አነሳው”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይ መልከቱ)

የመገናኛ ድንኳኑ የምሥክር ሥርዓቶች
መገናኛ ድንኳኑ በዚህ ረዥም በሆነ ሥምም ጭምር የሚጠራበት ምክኒያት የእግዚአብሔር ሕግ ያለበት የቃል ኪዳኑ ሰነድ በውስጡ የሚቀመጥ በመሆኑ ነው።ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 1:50 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

በሙሴ በኩል የተሰጠው የእግዚአብሔር ትዕዛዝ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር በሙሴ አማካይነት የሰጣቸው ትዕዛዛት”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 10:14

በይሁዳ ልጆች ሠፈር ዓርማ ሥር
ይሄ ሠፈር በይሁዳ ሥር የሚገኙ የተለያዩ ነገዶችን የሚያካትት ነው። ይሁዳን፤ይሳኮርንና ዛብሎንን።

በመጀመሪያ ተጓዙ
ሌሎቹ ሁሉ ከሠፈራቸው ከመነሣታቸው በፊት እነርሱ ሠፈራቸውን በመጀመሪያ ለቀው ይሄዱ ነበር።

የአሚናዳብ ልጅ ነአሶን
የዚህን ሰው ሥም በኦሪት ዘኁልቁ 1:7 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

የሶገር ልጅ ናትናኤል
የዚህን ሰው ሥም በኦሪት ዘኁልቁ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

የኬሎን ልጅ ኤልያብ
የዚህን ሰው ሥም በኦሪት ዘኁልቁ 1:9 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

Numbers 10:17

ጌድሶን ...ሜራሪ
የእነዚህን ሰዎች ሥም በኦሪት ዘኁልቁ 3:17 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

በሮቤል ሠፈር ዓርማ ሥር የሚገኙ ሠራዊቶች
x

Numbers 10:21

ቀአታውያን
ይሄ የሚያመለክተው የቀአትን የትውልድ ሐረግ ነው።ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 3፡ 27 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

በኤፍሬምም ትውልድ ዓርማ ሥር ያሉ ሠራዊቶች
ይሄ የሚያመለክተው በኤፍሬም ክፍል ውስጥ ያሉትን የነገድ ሠራዊቶችን ነው።ሮቤል፤ስምዖንና ጋድ።ኤፍሬም፤ምናሴና ብንያም።

የአሚሁድ ልጅ ኤሊሳማ
የዚህን ሰው ሥም በኦሪት ዘኁልቁ 1:10 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

የፋዳሱር ልጅ ገማልኤል
የዚህን ሰው ሥም በኦሪት ዘኁልቁ 1:10 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

የጋዴዮን ልጅ አቢዳን
የዚህን ሰው ሥም በኦሪት ዘኁልቁ 1:11 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

Numbers 10:25

በዳን ትውልድ ዓርማ ሥር ያሉ ሠራዊቶች
ይሄ የሚያመለክተው በዳን ክፍል ውስጥ ያሉትን የነገድ ሠራዊቶችን ነው። ሮቤል፤ስምዖንና ጋድ።ኤፍሬም፤ምናሴና ብንያም።ዳን፤አሴርና ንፍታሌም።

የአሚሳዳይ ልጅ አኪዔዘር
የዚህን ሰው ሥም በኦሪት ዘኁልቁ 1:12 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

የኤክራን ልጅ ፋግኤል
የዚህን ሰው ሥም በኦሪት ዘኁልቁ 1:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

የዔናን ልጅ አኪሬ
የዚህን ሰው ሥም በኦሪት ዘኁልቁ 1:15 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

Numbers 10:29

የራጉኤል ልጅ ኦባብ
ይሄ የሰው ሥም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር የተናገረውን
“እግዚአብሔር ለእኛ የነገረንን”

መልካም እናደርግልሃለን
“ከመልካም አያያዝ ጋር እንንከባከብሃለን”

Numbers 10:31

ዓይን ትሆንልናለህ
“ዓይን ትሆንልናለህ”ማለት ምሪት መሥጠትና መንከባከብ ማለት ነው።“በበረሃ ውስጥ ምሪት ልትሰጠንና እንዴት መኖር እንደሚገባን ልታሣየን ትችላለህ”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 10:33

እነርሱ ተጓዙ
“እነርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእሥራኤልን ሕዝብ ነው።

የእግዚአብሔር ተራራ
ይሄ የሚያመለክተው የሲናን ተራራ ነው።የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ፍቺ የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“የሲና ተራራ፤የእግዚአብሔር ተራራ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔርም የኪዳኑ ታቦት በፊታቸው ይሄድ ነበር
የተወሰኑ ሌዋውያን የቃል ኪዳኑን ታቦት ተሸክመው በእሥራኤል ሕዝብ ፊት ይሄዱ ነበር።“እየተጓዙ እያሉ የተወሰኑ ሰዎች የቃል ኪዳኑን ታቦት ተሸክመው ፊት ለፊት ይሄዱ ነበር”(ግዑዝ ነገሮች ሕይወት እንዳላቸው ተደርገው ሲገለፁ የሚለውን ይመልከቱ)

በቀን ብርሃን
“በየዕለቱ”ወይም “ቀን ሣለ”

Numbers 10:35

ታቦቱ በተጓዘ ዘጊዜ
እዚህ ላይ ታቦቱ ልክ ሰው ይመስል ጉዞ እንደሚጓዝ ዓይነት ነው የሚገለፀው። ታቦቱን የሚሸከሙ ሰዎች ነበሩ።“ታቦቱ በተጓዘ ቁጥር ሰዎች ይሸከሙት ነበር።”(ግዑዝ ነገሮች ሕይወት እንዳላቸው ተደርገው ሲገለፁ የሚለውን ይመልከቱ)

አቤቱ ተነሳ
እዚህ ላይ “ተነሳ”የሚለው ሐረግ እግዚአብሔር ሥራውን እንዲጀምር የሚጠየቅበት ሲሆን በዚህ አውድ ግን ሙሴ ጠላቶቻቸውን እንዲበትንላቸው እየለመነ ነው።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሚጠሉህም ከፊትህ ይሸሹ
እዚህ ላይ ሙሴ ጠላቶቹ ከራሱ ከእግዚአብሔር የሚሸሹ ይመስል እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን ከእሥራኤል ሕዝብ እንዲሸሹ ምክኒያት እንዲሆንላቸው ነው የሚለምነው።“አንተን የሚጠሉህን ከታቦትህና ከሕዝብህ እንዲሸሹ አድርጋቸው”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ታቦቱ ባረፈ ጊዜ
እዚህ ላይ ታቦቱ ሰው ይመስል እንደሚጓዝ ዓይነት ተደርጎ ነው የሚገለፀው። ታቦቱን የሚሸከሙት ሰዎች ነበሩ።“ሰዎች እንደተሸከሙት ታቦቱ ያርፍ ነበር”(ግዑዝ ነገሮች ሕይወት እንዳላቸው ተደርገው ሲገለፁ የሚለውን ይመልከቱ)

እልፍ አዕላፋት
ይሄ የሚያመለክተው የሰዎቹን ቁጥር ነው።የዚህ ዓረፍተ ነገር ትርጉም የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“እልፍ አእላፋት ሕዝብ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 11

1 ህዝቡ ያህዌ እየሰማ ስለ ችግሮቻቸው አጉረመረሙ። ያህዌ ህዝቡን ሰምቶ ተቆጣ። ከያህዌ ዘንድ እሳት መጥታ በሰፈሩ ዙሪየ ከነበሩ ሰዎች አንዳንዶችን
በላች። 2 ከዚያም ህዝቡ ወደ ሙሴ ጮኸ፣ ስለዚህም ሙሴ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ እሳቱም ቆመ። 3 ስፍራው ተቤራ ተብሎ ተጠራ፣ ምክንያቱም የያህዌ
እሳት ከመሀላቸው ሰዎችን አቃጥላለች። 4 አንዳንድ ባዕዳን ከእስራኤላውያን ትውልዶች ጋር መስፈር ጀመሩ። እነርሱ የተሻለ ምግብ መብላት ፈለጉ። ከዚያ
የእስራኤል ሰዎች ማልቀስና “እንድንበላ ማን ስጋ ሊሰጠን ይችላል” ማለት ጀመሩ። 5 በግብጽ በነጻ እንበላ የነበረውን አሳውን፣ ዱባውን፣ በጢኹን፣ ባሮ
ሽንኩርቱን፣ ቀይ ሽንኩርቱንና ነጭ ሽንኩርቱን እናስታውሳለን። 6 አሁን ደካሞች ነን። ከመና በስተቀር ምንም የምንበላው የለም።” 7 መና እንደ ድንብላል ፍሬ
ያለ መልክ ነበረው። ሙጫ ይመስላል። 8 ሰዎቹ እየተዘዋወሩ ይሰበስቡታል። በወፍጮ ይፈጩታል፣ በሙጫ ያደቁታል፣ በገንቦዎቹ ይቀቅሉታል፣ ቂጣ
አድርገውም ይጋግሩታል። እንደ ንጹህ የወይራ ዘይት ይጣፍጣል። 9 ምሽት በሰፈር ውስጥ ጤዛ ሲወርድ፣ መናውም ይወርዳል። 10 ሙሴ ህዝቡ በየቤቱ
ሲያለቅስ አዳመጠ፣ ደግሞም እያንዳንዱ ሰው በእርሱ ድንኳን ደጃፍ ነበር። ያህዌ በጣም ተቆጥቶ ነበር፣ ደግም የእነርሱ ማጉረምረም በሙሴ እይታ ስህተት
ነበር። 11 ሙሴ ወደ ያህዌ እንዲህ ሲል ጮኸ፣ “ለምን ባሪያህን እንዲህ አስጨነከው? ስለምን በእኔ ደስ አልተሰኘህም? የዚህን ህዝብ ሁሉ ሸክም
እንድሸከም አደረግከኝ። 12 እኔ ይህን ህዝብ ሁሉ ፀንሼዋለሁን? ‘አባት ልጁን እነደሚያቅፍ ይህን ህዝብ ወደ ደረትህ አስጠግተህ ተሸከመው’ ትለኝ ዘንድ እኔ
ወልጃቸዋለሁን?’ ትሰጣቸው ዘንድ ለአባቶቻቸው ወደ ማልክላቸው ምድር እንዲገቡ እኔ ልሸከማቸውን? 13 ለእነዚህ ሁሉ ሰዎች የምሰጣቸውን ስጋ ከየት
አገኛለሁ? በእኔ ፊት እያለቀሱ እንዲህ ይላሉ ‘የምንበላው ስጋ ስጠን።’ 14 እኔ ብቻዬን ይህን ሁሉ ህዝብ ልሸከም አልችልም። እጅግ በዝተውብኛል። 15
እንዲህ እስካደረግኸኝ ድረስ፣ አሁኑኑ ግደለኝ፣ ለእኔ መልካም ከሆንክ፣ መከራዬን ከእኔ አርቅ።” 16 ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ “ከእስራኤል መሪዎች
ሰባዎቹን ወደ እኔ አምጣ። የህዝቡ መሪዎችና አለቃዎች መሆናቸውን እርግጠኛ ሁን። ከአንተ ጋር እንዲቆሙ ወደ መገናኛው ድንኳን አምጣው። 17 እኔ ወርጄ
በዚያ ከአንተ ጋር እነጋገራለሁ። ከአንተ ላይ ካለው መንፈስ ጥቂት ወስጄ በእነርሱ ላይ አደርገዋለሁ። እነርሱ ከአንተ ጋር የህዝቡን ሸክም ይሸከማሉ። አንተ
ብቻህን ሸክሙን አትሸከምም። 18 ለህዝቡ እንዲህ በል፣ ‘ነገ ራሳችሁን ለያህዌ ለዩ። ያህዌ እየሰማ አልቅሳችኋልና፣ በእርግጥ ስጋ ትበላላች። እንዲህ
ብላችኋል፣ “እንበላ ዘንድ ማን ስጋ ይሰጠናል? ለእኛስ በግብጽ መሆን መልካም ነበር።” ስለዚህ ያህዌ ስጋ ይሰጣችኋል፣ እናም ስጋ ትበላላችሁ። 19 ስጋ
የመትበሉት ለአንድ ቀን፣ ለሁለት ቀናት፣ ለአምስት ቀናት፣ ለአስር ቀናት ወይም ለሃያ ቀናት አይደለም፣ 20 ነገር ግን በአፍንጫችሁ እስኪወጣ ድረስ ወር ሙሉ
ስጋ ትበላላችሁ። ነገሩ ያስጸይፋችኋል፣ ምንያቱም በመሀላችሁ ያለውን ያህዌ እምቢ ብላችኋል። በፊቱ አልቅሳችኋል። እንዲህ ብላችኋል፣ “ለምን ከግብጽ
ወጣን?” 21 ከዚያ ሙሴ እንዲህ አለ፣ “እኔ ከ600000 ሰዎች ጋር ነኝ፣ አንተ ግን እንዲህ አልክ፣ ‘ወር ሙሉ እንዲበሉ ስጋ አበላቸዋለሁ።’ 22 እነርሱን
ለማጥገብ እኛ እንስሳትንና የከብት መንጋ ሁሉ እናርዳለን? እነርሱን ለማርካት የባህር አሶችን ሁሉ እናጠምዳን?” 23 ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ “እጄ አጭር
ናትን? አሁን ቃሌ እውነት መሆን አለመሆኑን ታያለህ።” 24 ሙሴ ወጥቶ ለህዝቡ የያህዌን ቃላት ነገራቸው። ሰባዎቹን የህዝብ መሪዎች ሰበሰበና በድንኳኑ
ዙሪያ አቆማቸው። 25 ያህዌ በደመና ውስጥ ወረዳና ሙሴን ተናገረው። ያህዌ በሙሴ ላይ ከነበረው መንፈስ ጥቂት ወሰደና በሰባዎቹ ሽማግሌዎች ላይ
አደረገው። መንፈሱ ሲያርፍባቸው፣ ትንቢት ተናገሩ፣ ነገር ግን በዚያ ወቅት እንጂ በሌላ ጊዜ ደግመው አልተነበዩም። 26 አልዳድና ሞድ የተባሉ ሁለት ሰዎች
በሰፈር ቀርተው ነበር። መንፈሱ በእነርሱ ላይም አረፈ። ስሞቻቸው በመዝገብ ተጽፎ ነበር፣ ነገር ግን ወደ ድንኳኑ አልሄዱም ነበር። ሆኖም ግን፣ እነርሱም በሰፈር
እያሉ ተነበዩ። 27 በሰፈር የነበረ አንድ ወጣት ሰው ወደ ሙሴ ሮጦ መጥቶ እንዲህ አለው፣ “ኤልዳድና ሞዳድ በሰፈር ውስጥ እየተነበዩ ነው።” 28 ከእርሱ
የተመረጡ ሰዎች አንዱ የሆነው የሙሴ ረዳት የነዌ ልጅ ኢያሱ ሙሴን እንዲህ አለው፣ “አለቃዬ ሙሴ ሆይ፣ ከልክላቸው።” 29 ሙሴ እያሱን እንዲህ አለው፣
“አንተ ለእኔ ተቆርቁረህ ነውን? እኔ መላው የያህዌ ህዝቦች ነቢያት ቢሆኑ እርሱ በሁሉም ላይ መንፈሱን ቢያደርግ እመኛለሁ!” 30 ከዚያ ሙሴና የእስራኤል
ሽማግሌዎች ወደ ሰፈር ተመለሱ። 31 ከዚያ ከያህዌ ዘንድ ነፋስ ወጥቶ ከባህር ድርጭቶችን አመጣ። ከሰፈሩ በአንድ በኩል የአንድ ቀን የእግር መንገድ ርቀት
ላይ፣ ደግሞም በሌላኛው በኩል በአንድ ቀን የእግር መንገድ ርቀት ድረስ ድርጭቶቹ ወደቁ። ድርጭቶቹ ሰፈሩን ከመሬት ሁለት ኪዩብ ከፍታ በሚሆን መጠን
ሞሉት። 32 ሰዎቹ ያን ዕለት ምሽቱን ጨምሮ እንዲሁም በማግስቱም ድርጭቶችን በመሰብሰብ ሥራ ተጠምደው ነበር። ማንም ከአስር የቆሮስ መስፈሪያ ያነሰ
ድርጭት አልሰበሰበም። በሰፈሩ ሁሉ ድርጭቶቹን ተከፋፈሉ። 33 ስጋው ገና በጥርሳቸው ውስጥ እያላመጡት ሳለ፣ ያህዌ በእነርሱ ላይ ተቆጣ። ህዝቡን
በታላቅ በሽታ መታው። 34 በዚያ ሥፍራ ስጋ ለማግኘት የጎመጁትን ሰዎች ስለቀበሯቸው የስፍራው ስም ቂብሮት ሃታአባ ተባለ። 35 ሰዎቹ ከቂብሮት ሃታአባ
ወደ ሰፈሩበት ወደ ሐጽሮት ተጓዙ።

Numbers 11:1

የእግዚአብሔርም እሣት በመካከላቸው ነደደች
“እግዚአብሔር የሚያነድን እሣት ላከ”

ለቦታው ሥም ተሰጠው
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ለዚያ ሥፍራ ሥም ሰጡት”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 11:4

የምንበላውን ሥጋ ማን ይሰጠናል?
እሥራኤላውያን ይህንን ጥያቄ ያቀረቡት ከመና ሌላ ተጨማሪ የሚበሉት ነገር እንደሚፈልጉ ለመጠየቅ ነበር።ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሥጋ የመብላት መሻት አለን”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የምግብ ፍላጎታቸን ጠፋ
“መብላት አንፈልግም” ወይም“” “መብላት አንችልም”

Numbers 11:7

የድንብላል ዘር
የዚህ ዕፅዋት ዘር በሚደርቅበት ጊዜ በቅመምነት ያገለግላል።

ድንብላል
ይሄ የሚያጣብቅ ነገር ያለው ሲሆን የገረጣ ቢጫ ቀለም አለው።

Numbers 11:9

በሙሴ ዓይን
ዓይኑ መመልከቱን የሚያመለክት ሲሆን መመልከቱ ደግሞ አስተሳሰቡን ወይም የፍርድ አሰጣጡን ይወክላል።“በሙሴ አስተሳሰብ”ወይም “በሙሴ ዳኝነት”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Numbers 11:11

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ምላሽ የማያሻቸውን ብዙ ጥያቄዎች ለእግዚአብሔር ያቀርባል።(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ለምን በባሪያህ ላይ ክፉ አደረግህ?ለምንስ በፊትህ ሞገስ አላገኘሁም?
ሙሴ እነዚህን ጥያቄዎች የጠየቀው እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ባለው ግንኙነት ላይ የተቃውሞ ጥያቄ ለማቅረብ ነበር።በድርጊት መልክ ሊገለፁ ይችላሉ። ሙሴ ስለራሱ በሶስተኛ አካልነት ነው የሚናገረው።“እኔ ባሪያህን በእንደዚህ ዓይነት መጥፎ ሁኔታ መያዝ አልነበረብህም።በእኔ ልትናደድ አይገባም”ወይም “እኔ ባሪያህ ያጠፋሁት ጥፋት ስለሌለ ጥሩ ባልሆነ ሁኔታ እኔን መያዝ አልነበረብህም!”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄንና የመጀመሪያ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ አካል የሚለውን ይመልከቱ)

የዚህን ሁሉ ሕዝብ ሸክም በእኔ ላይ አደረግህ
ሙሴ ሕዝቡን የመምራቱንና የሚያስፈልጋቸውን ነገር የመሥጠቱን ነገር ልክ ከባድ የሆነ ሸክምን ከመሸከም ጋር ያነፃፅረዋል።“ለእነዚህ ሰዎች ሁሉ ኃላፊነትን ሰጠኸኝ፤እኔ ግን ከብዶኛል”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህን ሁሉ ሕዝብ እኔ ፀነስኩትን?
ሙሴ ይህን ጥያቄ የሚጠይቀው አባታቸው እንዳልሆነ እግዚአብሔርን ለማሳሰብ ነው።“የእነዚህ ሰዎች ሁሉ አባት አይደለሁም”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በብብትህ እቀፋቸው የምትለኝ ...ይህን ሕዝብ ወለድኩትን?
ሙሴ እግዚአብሔር እንዲያስታውስለት የፈለገው ምንም እንኳን አባታቸው ባይሆንም እሥራኤላውያንን መንከባከብ እንደሚገባው መናገሩን ነበር።“እኔ ስላልወለድኳቸው እንደ ሕፃን ልጅ ተሸከማቸው ልትለኝ አትችልም”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በብብትህ እቀፋቸው
እሥራኤላውያንን መንከባከብ ልክ ዕርዳታ የሚያሻውን ሕፃን ልጅ ከመሸከም ጋር ተነፃፅሯል።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ልሸከማቸው ይገባል ...ምን ልስጣቸው?
የዚህ ዓረፍተ ነገር ትርጉም የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“እንድሸከማቸው እንድሰጣቸው መጠበቅ የለብህም!”ወይም “ልሸከማቸው አልችልም...ልሰጣቸው”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 11:13

ለዚህ ሁሉ ሕዝብ የምሰጠው ሥጋ ከወዴት አገኛለሁ?
ሙሴ ይሄንን ጥያቄ የሚያነሳው ለዚህ ሁሉ ሕዝብ ሥጋ መሥጠት የማይቻል መሆኑን ለመግለፅ ነው።“ለዚህ ሁሉ ሕዝብ የሚበቃ ሥጋ ለማግኘት የምችልበት ሁኔታ የለም”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህንን ሕዝብ ለብቻዬ ለመሸከም አልችልም
ሙሴ የመምራቱንና ለሕዝቡ የሚያስፈልጋቸውን ነገር የማቅረቡን ጉዳይ ልክ እነርሱን እንደሚሸከም ዓይነት አድርጎ ይገልፀዋል።“ለእነዚህ ሰዎች ሁሉ የሚያስፈልጋቸውን ነገር ለብቻዬ ለማቅረብ አልችልም”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ልሸከማቸው አልችልም
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው።“ይሄ ኃላፊነት ለእኔ አስቸግሮኛል”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 11:16

በአንተ ካለውም መንፈስ
“መንፈስ”የሚለው ቃል እግዚአብሔር ለሙሴ የተናገረውን ነገር እንዲያደርግ ኃይል የሚሰጠውን የእግዚአብሔርን መንፈስ ነው የሚያመለክተው።“እግዚአብሔር የሰጠህ በአንተ ያለው መንፈስ” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

የሕዝቡን ሸክም ከአንተ ጋር ይሸከማሉ
እግዚአብሔር የመምራቱንና አስፈላጊ ነገሮችን የማቅረቡን ጉዳይ ልክ ሙሴና ሌሎች መሪዎቹ እንደሚሸከሙት ነገር አድርጎ ነው የሚገልፀው።“የሕዝቡን ሸክም ከአንተ ጋር ይሸከማሉ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ብቻህን መሸከም አይጠበቅብህም
እግዚአብሔር የመምራቱንና ለሕዝቡ አስፈላጊ ነገሮችን የማቅረቡን ጉዳይ ልክ ሙሴና ሌሎች መሪዎቹ እንደሚሸከሙት ነገር አድርጎ ነው የሚገልፀው።“ብቻህን አትሸከማቸውም”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 11:18

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል።

የምንበላውን ሥጋ ማን ይሰጠናል?
እሥራኤላውያን ይህንን ጥያቄ ያቀረቡት ከመና ሌላ ተጨማሪ የሚበሉት ነገር እንደሚፈልጉ ለመጠየቅ ነበር።ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሥጋ የመብላት ፍላጎት አለን”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በአፍንጫችሁ እስኪወጣ
ለዚህ ፍቺ ሊሆኑ የሚችሉት 1/እግዚአብሔር ምግቡ በትውከት መልክ በአፍንጫቸው እንደሚወጣ ነው የሚናገረው።“ታምማችሁ እስክታስታውኩ ድረስ”ወይም “በአፍንጫው በሚወጣበት ሁኔታ እጅግ ብዙ ሥጋን ይበላሉ” “በአፍንጫቸው የሚወጣ እስኪመስል ድረስ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለምን ከግብፅ ወጣን?
ሕዝቡ ይሄንን ጥያቄ የጠየቀው ቅሬታውን ለመግለፅና አቤቱታን ለማቅረብ ነበር።“ከግብፅ ምድር መውጣት አልነበረብንም”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 11:21

600,000 ሕዝብ
“ስድስት መቶ ሺህ ሕዝብ” (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

“እነርሱን የሚያጠግብ የበሬና የበግ መንጋ ይታረድን?ወይስ የባህርን ዓሣ ሁሉ ያጠግባቸው ዘንድ ይሰብሰብላቸውን?”
ሙሴ እነዚህን ጥያቄዎች የሚያቀርበው ሕዝቡ እንዲጠግብ ለማድረግ በቂ ሥጋ ስለመኖሩ ጥርጣሬ ስለገባው ነው። “እነርሱን ለማጥገብ የበሬና የበግ መንጋ እንዲሁም የባህርን ዓሣ ሁሉ መግደል ይኖርብናል”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

መንጎችና ከብቶች
በመሠረቱ እነዚህ ቃላት ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው።በአንድነት የሚያመለክቱት ነገር ቢኖር ብዙ ከብቶች የመኖራቸውን ጉዳይ ነው።(ሁለት ተመሳሳይ ገፅታ ያላቸው የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የባህርን ዓሣ ሁሉ
“ሁሉ” የሚለው ቃል የተጋነነ ሲሆን ለእሥራኤል ሕዝብ ሁሉ ምግብ ለማቅረብ የማይቻል መሆኑን ለመግለፅ ነው።(የተጋነነ ንፅፅር እና አጠቃላይነት የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲጠግቡ ለማድረግ
“ረሃባቸውን ለማስታገስ”

እጁ አጠረችን?
እዚህ ላይ “እጅ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ኃይል ነው። እግዚአብሔር ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው እግዚአብሔር ለሕዝቡ በቂ ሥጋ ሊሰጥ አይችልም ብሎ በማሰቡ ለገስፀው ነው።“ይህንን የማድረግ በቂ ኃይል የለኝም ብለህ ታስባለህ?”ወይም “ይህንን ለማድረግ ከበቂ በላይ ኃይል እንዳለኝ ማወቅ ይኖርብሃል”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውንና ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 11:24

የእግዚአብሔር ቃላት
“እግዚአብሔር የተናገረው ነገር”

በሙሴ ላይ ከነበረው መንፈስ
“መንፈስ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ለሙሴ የተሰጠውን የእግዚአብሔርን መንፈስ ነው።ተመሳሳይ ሐረጎችን በኦሪት ዘኁልቁ 11:17 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“ለሙሴ የሰጠው የተወሰነ ኃይል”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

በሰባዎቹ ሽማግሌዎች ላይ አድርግ
ለሽማግሌዎቹ ኃይልን መሥጠት መንፈስን በእነርሱ ላይ ማድረግ በሚል መልኩ ነው የተገለፀው።ተመሣሣዩን ሐረግ በኦሪት ዘኁልቁ 11:17 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“ለሰባ ሽማግሌዎች ሰጠ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መንፈሱም በላያቸው ላይ ባደረ ጊዜ
ከመንፈሱ ኃይል ማግኘትን መንፈሱ እንደወረደባቸው ተደርጎ ተነግሯል።“ከመንፈሱ ኃይልን ባገኙበት ወቅት”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 11:26

መንፈሱም በላያቸው አደረ
ከመንፈሱ ኃይል ማግኘትን መንፈሱ እንደወረደባቸው ተደርጎ ተነግሯል።“መንፈሱ ኃይልን ሰጣቸው”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ስማቸው በዝርዝሩ ውስጥ ተፅፎ ነበረ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሙሴ ሥማቸውን በዝርዝሩ ውስጥ ፃፈው”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 11:28

ከልክላቸው
“መተንበዩን እንዲያቆሙ ንገራቸው”

ስለ እኔ አንተ ትቀናለህን?
ሙሴ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው እግዚአብሔርን ለመውቀስ ነበር።አስፈላፊ ሆኖ ከተገኘ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ለእኔ ስትል ልትቀና አይገባህም”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ እኔ አንተ ትቀናለህን?
አስፈላጊ ከሆነ እግዚአብሔር የሚቀናበት ነገር ምን እንደሆነ የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“ለእኔ የሆነውን ነገር ሊወስዱ ይችላሉ ብለህ ሰጋህን?”ወይም “ሰዎች ሥልጣኑን አያከብሩለትም ብለህ ተጨነቅክን?”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መንፈሱን በእነርሱ ላይ ያደርግ ዘንድ
ሙሴ ለሰዎች ኃይል የሚሰጠውን የእግዘአብሔርን መንፈስ ልክ እግዚአብሔር መንፈሱን በእነርሱ ላይ እንደሚያስቀምጥ አድርጎ ይገልፀዋል።“የእግዚአብሔር መንፈስ ኃይልን ሁሉ ይሰጣቸው ዘንድ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 11:31

ድርጭት
“ትንሽ ወፍ”(ያልታወቁትን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

የአንድ ቀንም መንገድ ያህል በዚህ የአንድ ቀንም ያህል መንገድ በዚያ
“በእያንዳንዱ አቅጣጫ አንድ ሰው ቀኑን ሙሉ የሚጓዝበትን መንገድ ያህል”

ሁለት ክንድ ያህል
ክንድ የመለኪያ ዓይነት ሲሆን 46 ሴንቲ ሜትር አካባቢ ይሆናል።“92 ሴንቲ ሜትር ያህል” ወይም “አንድ ሜትር ያህል” (መፅሐፍ ቅዱሣዊ ርቀትንና ቁጥሮችን ይመልከቱ)

ከአሥር የቆሮስ መስፈሪያ በታች የሰበሰበ አልነበረም
ይሄ ድርብ አሉታዊ ሲሆን በአዎንታዊ ዓረፍተ ነገር ሊገለፅም ይችላል።

አሥር የቆሮስ መስፈሪያ
የቆሮስ መሥፈሪያ የመለኪያ ዓይነት ሲሆን 220 ሊትር ያህል ይሆናል።“220 ሊትር”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ የመጠን መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 11:33

ሥጋውም ገና በጥርሳቸው መካከል ሳለ ሳያኝኩትም
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው።አንድ ላይ በመሆን አፅንዖት የሚሰጡት ሥጋውን ገና እየበሉ እያሉ ያኔውኑ እግዚአብሔር ቅጣቱን የላከባቸው መሆኑን ነው።“ገና ሥጋውን እየበሉ እያሉ”(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

የዚያ ሥፍራ ሥም የምኞት መቃብር ተብሎ ተጠራ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሥፍራውን የምኞት መቃብር ብለው ጠሩት”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውንና ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

ሐሢሮት
ይሄ በበረሃ ውስጥ የሚገኝ የአንድ ስፍራ ስም ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 12

1 “ከዚያ ማርያም እና አሮን ሙሴ ባገባት ኩሻዊ ሴት ምክንያት በሙሴ ላይ በተቃውሞ ተናገሩ። 2 እንዲህም አሉ፣ “ያህዌ የተናገረው ከሙሴ ጋር ብቻ ነውን? ከእኛስ ጋር አልተናገረምን?” ያህዌ እነርሱ የተናገሩትን ሰማ። 3 ሙሴ ፣ በምድር ላይ ከሚገኝ ከማንኛውም ሰው ይልቅ በጣም ትሁት ሰው ነበር። 4 ወዲያውኑ ያህዌ ከሙሴ፣ ከአሮንና ማርያም ጋር ተናገረ “እናንተ ሶስታችሁ ወደ መገናኛው ድንኳን ውጡና ኑ።” ስለዚህም ሶስቱም ወጥተው መጡ። 5 ከዚያም ያህዌ በደመና አምድ ወረደ። በድንኳኑ መግቢያ ቆሞ አሮንንና ማርያምን ጠራቸው። ሁለቱም ወደ ፊት ቀረቡ። 6 ያህዌ እንዲህ አለ፣ “አሁን ቃሎቼን ስሙ። አንድ የእኔ ነብይ በመካከላችሁ ሲሆን፣ ራሴን፣ በራዕይ እገልጥለታለሁ፣ በህልምም እናገረዋለሁ። 7 አገልጋዬ ሙሴ ግን እንደዚያ አይደለም። እርሱ በቤቴ ላይ ሁሉ የታመነ ነው። 8 እኔ ከመሴ ጋር በቀጥታ እናገራሁ፣ በራዕይ ወይም በዘይቤ አይደለም። እርሱ የእኔን መልክ ያያል። ስለዚህ በአገልጋዬ በሙሴ ላይ ስትናገሩ ለምን አልፈራችሁም?” 9 የያህዌ ቁጣ በእነርሱ ላይ ነደደ፣ ከዚያም ትቷቸው ሄደ። 10 ደመናው ከድንኳኑ ላይ ተነሳ፣ እናም ማርያም በድንገት በለምጽ ተመታች እንደ በረዶ ነጭ ሆነች። አሮን ወደ ማርያም ዞር ብሎ ሲመለከታት በልምጽ መመታቷን አየ። 11 አሮን ሙሴን እንዲህ አለው፣ “ጌታዬ ሆይ፣ እባክህን በአንተ ላይ የፈጸምነውን ይህን በደል አትቁጠርብን። በስንፍና ተናግረናል፣ ደግሞም በድለናል። 12 እባክህን ከእናቱ ማህጸን ሲወጣ ጭንጋፍ ሆኖ እንደ ተወለደ ከፊል አካሉ እንደተበላ ሆና አትተዋት።” 13 ስለዚህም ሙሴ ወደ ያህዌ ጮኸ። እንዲህም አለ፣ “እግዚአብሔር ሆይ፣ እባክህ፣ እባክህ ፈውሳት።” 14 ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ “አባቷ በፊቷ ላይ ቢተፋባት፣ ለሰባት ቀናት በሀፍረት ትቆያለች። ከሰፈር ውጭ ለሰባት ቀናት ዝጋባት። ከዚያ በኋላ መልሰህ አምጣት።” 15 ስለዚህም ማርያም ከሰፈር ውጭ ለሰባት ቀናት ተዘጋባት። እርሷ ወደ ሰፈር እስክትመለስ ድረስ ህዝቡ ጉዞ አላደረገም። 16 ከዚያ በኋላ፣ ህዝቡ ከሐዴሮት ተነስቶ ተጓዘና በፋራን ምድረበዳ ሰፈረ።

Numbers 12:1

በውኑ እግዚአብሔር በሙሴ ብቻ ተናግሯልን?በእኛስ ደግሞ የተናገረ አይደለምን?
ማርያምና ሙሴ ይሄንን ጥያቄ የጠየቁት ሙሴ ብዙ ሥልጣን ሲኖረው እኛ ግን የሚገባንን ያህል ሥልጣን የለንም በሚል ምክኒያት ነው።ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር የተናገረው ለሙሴ ብቻ አይደለም።ከእኛም ጋር ተነጋግሯል።”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

አሁን እግዚአብሔር ሰማ
እዚህ ላይ “አሁን”የሚለው ቃል ከዚህ ቀጥሎ ላለው አስፈላጊ ነጥብ ሰው የበለትኩረት እንዲሰጥ ያደርጋል።

አሁን ሰው የሆነው ሙሴ
“አሁን”የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው በዋናው ታሪክ ላይ እረፍት ለመሥጠት ነው።ተራኪው የሙሴን ባህርይ በሚመለከት የጀርባ ታሪኩን ይናገራል።(የጀርባ ታሪክ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 12:4

የደመና አምድ
የደመናው ቅርፅ አምድ እንደሆነ ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል።“የአምድ ቅርፅ ያለው ደመና”ወይም “ረዥም ደመና” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 12:6

ባሪያዬ ሙሴ ግን እንዲህ አይደለም
“ለሙሴ እንደዚያ አልናገርም”

በቤቴ ሁሉ የታመነ ነው
እዚህ ላይ ቤቴ የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእሥራኤልን አገር ነው። በእግዚአብሔር ቤት ታማኝ መሆን እሥራኤልን ለመምራት ታማኝ መሆንን ያመለክታል።“ሙሴ ሕዝቤን በታማኝነት ይመራል”ወይም“ሕዝቤን እሥራኤልን እንዲመራ እምነት የምጥልበት ሙሴን ነው” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

በባሪያዬ በሙሴ ላይ ትናገሩ ዘንድ ስለምን አልፈራችሁም?
እግዚአብሔር ይህንን ጥያቄ የጠየቀው ማርያምንና አሮንን ለመገሰፅ ነው። በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይቸላል።“ባሪያዬን ሙሴን በመቃወም ለመናገር መፍራት ነበረባችሁ።”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በባሪያዬ ላይ፤በሙሴ ላይ
“በሙሴ ላይ”የሚለው ሐረግ እግዚአብሔር የሚናገረው ባሪያው እርሱ ስለመሆኑ ግልፅ ይሆናል።“በባሪያዬ በሙሴ ላይ”(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 12:9

የእግዚአብሔርመ ቁጣ በእነርሱ ላይ ነደደ
የእግዚአብሔር ቁጣ እሣት እንደሆነ ዓይነት ተደርጎ ነው የተነገረው።“እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ በጣም ተቆጣ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ በረዶ ነጭ ሆነ
ለምፅ የማርያምን ሥጋ ወደ ነጭነት ቀየረው።“በጣም ነጭ ሆነ”(ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 12:11

እባክህ ኃጢአታችንን አትያዝብን
የሰዎችን ኃጢአት መያዝ ማለት ለፈፀሙት ኃጢአት ተጠያቂ ናቸው ማለት ነው።ይሄ የሚያመለክተው በኃጢአታቸው የመቀጣታቸውን ጉዳይ ነው። (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ከእናቱ ሆድ በወጣ ጊዜ ግማሽ ሥጋው ተበልቶ እንደሞተ አትሁን
በማርያም ላይ የተጣበቀባት ለምፅ ሕይወቷ እስኪያልፍ ድረስ ሥጋዋ እየበሰበሰ እንዲሄድ የሚያደርግ ነበር።እየበሰበሰ የሚሄደው ሥጋ ልክ እንደሚባላ ነገር ተደርጎ ተገልጿል።“ከእናቱ ሆድ በወጣ ጊዜ ግማሽ ሥጋው ተበልቶ እንደሞተ አትሁን”(ተነፃፃሪ የሚለውንና ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 12:13

እባክህ ፈውሳት፤እባክህ አግዚአብሔር
“እባክህ”የሚለው ቃል የተደገመው ለጉዳዩ አፅንዖት ለመሥጠት ነው።

አባትዋ ምራቁን በላይዋ ላይ ቢፋባት
ይሄ የሚያመለክተው ሊሆን ይችል የነበረ ነገር ተግባራዊ አለመደረጉን ነው። በአንድ ሰው ፊት ላይ ምራቅ መትፋት ትልቅ ስድብ ነበር።(በግምት ላይ የተመሠረቱ ሁኔታዎችንና ተምሣሌታዊ ድርጊቶች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ማርያምም ከሠፈር ውጪ ተዘግታ ተቀመጠች
ከሠፈር ውስጥ ከወጣች በኋላ ተመልሣ ለመምጣት ያለመቻሏን ሁኔታ ልክ ከጀርባዋ በር እንደተቆለፈባት ተደርጎ ተገልጿል።“ማርያም ከሠፈር ውጪ እንደትሄድ ተደረገ”ወይም “ማርያም ከሠፈር ውጪ እንድትሆን ተደረገ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ማርያም ከሠፈር ውጪ ነበረች
ይሄ በድርጊት መልከ ሊገለፅ ይችላል።“ሙሴ ማርያምን ከሠፈር ውጪ ዘጋባት”ወይም “ሙሴ ማርያምን ከሠፈር ውጪ ላካት”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 12:16

ሐጺሮት
ይሄ በበረሃ ውስጥ ያለ የአንድ ሥፍራ ሥም ነው።ይህንን በኦሪት ዘኁልቁ 11፡35 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 13

1 ዚያም ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ 2 ”ለእስራኤላውያን የሰጠኋቸውን የከነዐንን ምድር እንዲያዩ ጥቂት ሰዎችን ላክ። ከአባቶቻቸው ከእያንዳንዱ ነገድ አንድ
ሰው ላክ። ከመሀላቸው የሚላከው እያንዳንዱ ሰው መሪ መሆን አለበት።” 3 ሙሴ የያህዌን ትእዛዝ እንዲያደርጉ ከፋራን ምድረ በዳ ላካቸው። ሁሉም
ከእስራኤል ሰዎች መሃል የተመረጡ መሪዎች ነበሩ። 4 ስሞቻቸው እነዚህ ነበሩ፡ ከሮቤል ነገድ፣ የዘኩር ልጅ ሳሙኤል። 5 ከስምዖን ነገድ፣ የሱሬ ልጅ ሰፈጥ።
6 ከይሁዳ ነገድ፣ የዩፎኒ ልጅ ካልብ። 7 ከይሳኮር ነገድድ የዮሴፍ ልጅ ይግአል። 8 ከኤፍሬም ነገድ፣ የነዌ ልጅ አውሴ። 9 ከብንያም ነገድ፣ የራፋ ልጅ ፈልጢ።
10 ከዛብን ነገድ፣ የሰዲ ልጅ ጉዲኤል። 11 ከዮፍ ትውልዶች፣ ይህም፣ ከምናሴ ነገድ ነው፣ የሱሲን ልጅ ጋዲ። 12 ከዳን ነገድ፣ የገማሊ ልጅ ዓሚኤል። 13
ከአሴር ነገድ፣ የሚካኤል ልጅ ሰቱር። 14 ከንፍታሌም ነገድ፣ የያቢ ልጅ ናቢ። 15 ከጋድ ነገድ፣ የማኪ ልጅ ጉዲኤል ነበሩ። 16 ምድሪቱን እንዲያዩ ሙሴ
የላቸው ሰዎች ስሞች እነዚህ ነበሩ። ሙሴ የነዌ ልጅ አውሴን፣ ኢያሱ ብሎ ጠራው። 17 ሙሴ እነርሱ የከነዓንን ምድር እንዲያዩ ላካቸው። እንዲህ አላቸው፣
“ከነጌብ ጀምራችሁ እስከ ተራራማው አገር ድረስ ሂዱ። 18 ምድሪቱ ምን እንደምትመስል ተመልከቱ። በዚያ የሚኖሩ ሰዎችን እዩ፣ ጠንካሮች ወይም ደካሞች
መሆናቸውን፣ እና ጥቂት ወይም ብዙ መሆናቸውን ተመልከቱ። 19 የሚኖሩባት ምድር ምን እንደምትመስል እዩ። መልካም ናት ወይስ መጥፎ? በዚያ ምን
አይነት ከተሞች አሉ? ሰፈር አይነት ናቸው? የተቀጠሩ ከተሞችስ ናቸውን? 20 ምድሪቱ ምን እንደምትመስል እዩ፣ ለእርሻ የተመቸች ናት ወይስ አይደለችም፣
በዚያ ዛፎች አሉ ወይስ የሉም። ብርቱ ሁኑና ከምድሪቱ ምርት ከየአይነቱ ይዛችሁ ኑ።” ወቅቱ የወይን ፍሬ ማፍራት የጀመረበት ነበር። 21 ስለዚህ ሰዎቹ ወጥተው
በሌለቦ ሐማት አጠገብ፣ ከጺን ምድረበዳ እስከ ሌቦ ድረስ ምድሪቱን ተመለከቱ። 22 ከኔጌብ ወጥተው እስከ ኬብሮን ደረሱ። ከዔናቅ ነገድ ዝርያ የሆኑ
የአኪመን፣ የሴሲና፣ እና የተላሚ ነገዶች በዚያ ነበሩ። ኬብሮን ግብጽ ውስጥ የተመሰተረችው ከከጣኔዎስ ሰባት አመት ቀደም ብላ ነበር። 23 ኤሽኮል ሸለቆ
ሲደርሱ፣ የወይን ዘለላ የያዘ ቅርንጫፍ ቆረጡ። ከቡድናቸው በሁለቱ መሃል በበትር አድርገው የወይኑን ዘለላ ተሸከሙት። እንደዚሁም ሮማንና በለስም አመጡ።
24 የእስራኤል ሰዎች በዚያ ከቆረጡት የወይን ዘለላ የተነሳ፣ ያቺ ስፍራ የኤሽኮል ሸለቆ ተብላ ተጠራች። 25 ምድሪቱን መርምረው ከአርባ ቀናት በኋላ ተመለሱ።
26 የተላኩት ሰዎች፣ ሙሴና አሮን እንዲሁም መላው የእስራኤል ማህበረሰብ ወዳሉበት በፋራን ምድረበዳ ወደምትገኘው ወደ ቃዴስ መጡ። ወደ እነርሱና ወደ
መላው ማህበረሰብ ተመልሰው መጥተው፣ የምድሪቱን ፍሬ አሳይዋቸው። 27 ሙሴን እንዲህ አሉት፣ “ወደ ላከን ምድር ደረስን። በእርግጥም ወተትና ማር
ታፈሳለች። ከምድሪቱ ምርት እነሆ። 28 ሆኖም፣ በዚያ የሚኖሩ ሰዎች ብርቱዎች ናቸው፤¨ከተሞቹም የተመሸጉና ትላልቅ ናቸው። ደግሞም በዚያ የዔናቅን
ዝርያዎችም አይተናል። 29 አማሌቃውያን በነጌብ ይኖራሉ። ኬጢያውያን፣ ኢያቡሳዊያን፣ እና አሞራዊያን በተራራማው አገር ይኖራሉ። ከነዓናዊያን በባህሩ
አቅራቢያ በዮርዳኖስ ወንዝ ዳርቻ ይኖራሉ።” 30 ከዚያ ካሌብ በሙሴ ዙሪያ የተሰበሰቡበትን ሰዎች ሊያበረታታቸው ተነሳ፣ እንዲህም አለ፣ “በአንድ ጊዜ
ተነስተን እንውጣና ምድራቸውን እንውረስ፣ ምክንያቱም በሚገባ ልናሸንፍ እንችላለን።” 31 ግን ከእርሱ ጋር የሄዱት ሌሎች ሰዎች እንዲህ አሉ፣ “እኛ ሰዎቹን
ማጥቃት አንችልም ምክንያቱም እነርሱ ከእኛ ይልቅ ጠንካሮች ናቸው።” 32 ስለዚህም ስለተመለከቷት ምድር በእስራኤለ ሰዎች መሀል ተስፋ አስቆራጭ ወሬ
አሰራጩ። እንዲህም አሉ፣ “የተመለከትናት ምድር በላይዋ የሚኖሩትን የምትበላ ናት። በዚያ ያየናቸው ሰዎ ሁሉ ቁመተ ረጃጅም ሰዎች ናቸው። 33 በዚያ የኤናቅ
ዝርያዎችን አይተናል፣ ከግዙፋኑ ሰዎች የመጡትን ግዙፎቹን ሰዎች አይተናል። ከእነርሱ ጋር ስንተያይ፣ በእኛ በራሳችን ዐይን እንደ አንበጣ ነበርን፣ ደግሞም
በእነርሱም ዐይን እንደዚሁ ነበርን።”

Numbers 13:1

የምሰጣትን
እግዚአብሔር የከነዓንን ምድር ለእሥራኤል ሕዝብ ለመስጠት የወሰነ ቢሆንም ወደዚያ ግን አልገቡም ነበር።“ልሰጥ የወሰንኩትን”ወይም “በቅርቡ የምሰጠውን”(የቆየ ትንቢት የሚለውን ይመልከቱ)

እያንዳንዱ በመካከላቸው አለቃ ይሁን
“አንተ የላክኸው እያንዳንዱ ሰው በነራሱ ነገድ መካከል አለቃ መሆን ይኖርበታል።”

Numbers 13:3

የዘኩር ልጅ ሰሙኤል
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 13:5

ሰፈጥ...ኡሪ...ዮፎኒ...ይግአል...ዮሴፍ..ነዌ
እነዚህ ሁሉ የሰዎች ስሞች ናቸው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 13:9

ፈልጢ...ራፉ...ጉድኤል...ጋዲ...ሱሲ...አሚኤል...ገማሊ
እነዚህ ሁሉ የሰዎች ስሞች ናቸው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዮሴፍ ነገድ አርሱም የምናሴ ነገድ
በዮሴፍና በምናሴ መካከል ያለው ግንኙነት የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“ከዮሴፍ ልጅ ከምናሴ ነገድ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 13:13

ሰቱር...ሚካኤል...ናቢ ያቢ...ጉዲኤል...ማኪ
እነዚህ ሁሉ የሰዎች ስሞች ናቸው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

የነዌ ልጅ አውሴ
የእነዚህን ሰዎች ሥም በኦሪት ዘኁልቁ 13:8 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

Numbers 13:17

ምድሪቱ መልካም ወይም ክፉ፤የሚኖሩባቸው ከተሞች ሠፈሮች ወይም አምባዎች እንደሆኑ እዩ
ሙሴ ይህን ጥያቄ የሚጠይቀው የተላኩት ሰዎች በሚመለሱበት ወቅት ሊያቀርቡ የሚገባቸውን መረጃ በሚመለከት ግልፅ ለማድረግ በመፈለግ ነው። ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል። “ምድሪቱ መልካም ወይም ክፉ፤ምን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ዓይነት ከተሞች እንዳሉ፤ከተሞቹ ሰዎች የሚኖሩባቸው ሠፈሮች ብቻ እንደሆኑ ወይም የጦር ምሽግ መኖር አለመኖሩን አጣሩ” (ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ሠፈሮች ናቸው ወይስ የተመሸጉ ከተማዎች ናቸው?
የተመሸጉ ከተሞች ራሣቸውን ከጠላት ጦር ለመከላከል ሲሉ ጠንካራ ቅጥሮች ይኖሯቸዋል።ሠፈሮች ግን እንደዚህ ዓይነት ቅጥሮች የሏቸውም።

Numbers 13:21

ጺን...ሐማት..ረአብ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

የጺን ምድረ በዳ
እዚህ ላይ “ጺን” የሚለው ቃል በዕብራይስጥ ቋንቋ ምድረ በዳ ማለት ነው። (ቃላትን መዋስና መቅዳት የሚለውን ይመልከቱ)

ኬብሮንም በግብፅ ካለችው ከጣኔዎስ በፊት ሰባት ዓመት ተሠርታ ነበር
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ግብፃውያን ጺንን ከመገንባታቸው ሰባት ዓመታት በፊት ከነዓናውን ኬብሮንን ገንብተዋት ነበር” (ገቢራዊና ፍዝ የሚለውንና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

አኪመን...ሴሲ...ተላሚ
እነዚህ በየአባቶቻቸው ቤቶች የነገድ ስሞች አንፃር የተሰየሙ ናቸው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

ዔናቅ
ይሄ የሰው ሥም ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 13:23

ኤሽኮል
ይሄ የቦታ ስም ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

በሁለቱ ወገኖቻቸው መካከል
“በየወገኖቻቸው ባሉ ሁለት ሰዎች መካከል”

የዚያን ሥፍራ ሥም ...ብለው ጠሩት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ለዚያ ሥፍራ ሥም ሰጡት” (ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 13:25

ከአርባ ቀናት በኋላ
“ከ40 ቀናት በኋላ”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ቃል ይዘው ተመለሱ
“ቃል”የሚለው የሚያመለክተው መረጃን ነው።“መረጃቸውን ይዘው ተመለሱ” ወይም “የተመለከቱትን ነገር ዘገቡ” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 13:27

እርስዋም ወተትና ማር ታፈስሳለች
“በእርግጥም ወተትና ማር እዚያ ይፈስሳሉ”ምድሪቱ ለእንስሳትና ለዕፅዋት ተስማሚ መሆኗን ለመግለፅ ከእነዚያ እንስሳት የሚገኘው ወተትና ማር በምድሪቱ ላይ እንደሚፈስስ ነገር አድርገው ይገልፁታል።“ከብቶችን ለማሳደግና አህልን ለማግኘት ድንቅ የሆነ ሥፍራ ነው”ወይም “በእርግጥም ለምለም የሆነ አገር ነው”ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውንና ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ወተት
ወተት ከላምና ከፍየል የሚገኝ ነገር በመሆኑ ከብቶችንና ከከብቶች የሚገኘውን ምገብ ያመለክታል።“ከከብቶች የሚገኝ ምግብ” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ማር
ማር ከአበቦች የሚገኝ ነገር በመሆኑ ዕፅዋትንና ከዕፅዋት የሚገኘውን ምገብ ያመለክታል።“ከዕፅዋት የሚገኝ ምግብ” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 13:32

እነርሱ ስለ ሰለልዋትም ... እያወሩ
እዚህ ላይ “እነርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከካሌብና ከኢያሱ በስተቀር በጊዜው ለስለላ የሄዱትን ሰዎች ሁሉ ነው።

የሚኖሩባትን ምድር የምትበላ ምድር
ሰዎቹ ምድሪቱ ወይም በምድሪቱ የሚኖሩ ሰዎች እጅግ አደገኞች መሆናቸውን ለመግለፅ ምድሪቱ ሰዎችን የምትበላ እንደሆነች አድርገው ያቀርቡታል።“እጅግ አደገኛ ምድር”ወይም “ሰዎቹ ነፍሳችንን የሚያጠፉበት ምድር” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ዔናቅ
ይሄ የሰው ሥም ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ በዓይናችን ግምት ...እኛ በዓይናቸው ዘንድ
እዚህ ላይ “ማየት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ግምገማንና የፍርድ ውሳኔ መሥጠትን ነው።“በእኛ አስተሳሰብ...በእነርሱ አስተሳሰብ” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በዓይናችን ግምት እንደ አንበጣ ነበርን
ሰዎቹ ስለ አንበጣ የተናገሩት በዚያ ምድር ካሉት ሰዎች ጋር ራሣቸውን ሲያነፃፅሩ ምን ያህል ትንሽ መሆናቸው እንደተሰማቸው ለመግለፅ ብለው ነው።“እኛን ከእነርሱ ጋር ስናነፃፅረው የአንበጣ ያህል ትናንሾች ነን›።(ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 14

1 “በዚያን ምሽት ማህበረሰቡ በሙሉ ድምጹን ከፍ አድርጎ አለቀሰ። 2 እስራኤል ሰዎች ሁሉ ሙሴንና አሮንን ነቀፉ። መላው ማህበረሰብ እንዲህ አሏቸው፣ “በግብጽ ምድር ብንሞት ይሻለን ነበር። ውይም ምነው በዚህ በረሃ በሞትን ኖሮ! 3 ያህዌ ለምን በዚህ ምድረበዳ በሰይፍ እንድንሞት ወደዚህ ምድር አመጣን? ሚስቶቻችንና ትናንሽ ልጆቻችን የተጠቁ ይሆናሉ። ወደ ግብጽ መመለስ አይሻለንምን?” 4 እርስ በእርሳቸው እንዲህ ተባባሉ፣ “ሌላ መሪ እንምረጥ፣ እናም ወደ ግብጽ እንመለስ።” 5 ከዚያ ሙሴና አሮን በእስራኤል ህዝብ በማህበረሰቡ ጉባኤ ፊት በግምባራቸው ተደፉ። 6 ምድሪቱን ለማየት ከወጡት ውስጥ ከነበሩት የነዌ ልጅ ኢያሱና የዩፎኒ ልጅ ካሌብ ልብሳቸውን ቀደዱ። 7 እስራኤል ሰዎች መላው ማህበረሰብ እንዲህ ሲሉ ተናገሩ፣ “በውስጧ ያለፍነውና የተመለከትናት ምድር በጣም መልካም መድር ናት። 8 ያህዌ በእኛ ደስ ከተሰኘ፣ ወደዚህች ምድር ያስገባናል ደግሞም እርሷን ለእኛ ይሰጠናል። ምድሪቱ ወተትና ማር የምታፈስ ናት። 9 ነገር ግን በያህዌ ላይ አታምጹ፣ ደግሞም በምድሪቱ የሚኖሩትን ህዝቦች አትፍሩ። በቀላሉ እንደ ምግብ እንበላቸዋለን። ጥላቸው ከእነርሱ ተገፏል፣ ምንያቱም ያህዌ ከእኛ ጋር ነው። እነርሱን አትፍሯቸው”። 10 ነገር ግን መላው ማህበረሰብ እስከ ሞት ሊወግሯቸው ተነሰቡቸው። ከዚያ የያህዌ ክብር በመገናኛው ድንኳን ለመላው የእስራኤል ሰዎች ታየ። 11 ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ “ይህ ህዝብ እስከ መቼ እኔን ይንቀኛል በመካከላቸው በሃይሌ ያደረኳቸውን ምልክቶች እያዩ እንኳን እስከ መቼ በእኔ አያምኑም 12 በበሽታ እመታቸዋለሁ፣ ወደ ርስታቸው አላስገባቸውም፣ ሆኖም ከአንተ ከራስህ ነገድ ከእነርሱ ይልቅ ታላቅና ሃያል ህዝብ አበጃለሁ።” 13 ሙሴ ያህዌን እንዲህ አለው፣ “ይህን ብታደርግ፣ ግብጻዊያን ስለዚህ ነገር ይሰማሉ፣ ምክንያቱም አንተ ይህን ህዝብ በኃይልህ ከእነርሱ አድነሃቸዋል። 14 ለዚህች ምድር ነዋሪዎች ይህንን ይናገራሉ። አንተ ያህዌ፣ ከዚህ ህዝብ ጋር እንደሆንክ እነርሱ ሰምተዋል፣ ምክንያቱም አንተ ፊት ለፊት ታይተሃል። የአንተ ደመና በእኛ ህዝብ ላይ ሆኗል። አንተ በእነርሱ ፊት በቀን በደመና አምድ በምሽት በእሳት አምድ ሄደሃል። 15 አሁን ይህንን ህዝብ እንደ አንድ ሰው ብትገድል፣ ዝናህን የሰሙ ህዝቦች እንዲህ ይላሉ፣ 16 ‘ያህዌ ይህንን ህዝብ ሊሰጣቸው ወደ ማለላቸው ምድር ሊያስገባቸው ባለመቻሉ ምክንያት፣ በምድረበዳ ገደላቸው። 17 አሁን፣ እኔ እለምንሃለሁ፣ ታላቁን ሀይልህን ተጠቀም። አንተ እንዲህ ብለሃልና፣ 18 ‘ያህዌ ለቁጣ የዘገየ ነው፣ በቃል ኪዳን ታማኝነቱ የተትረፈረፈ ነው። እርሱ በደልና መተላለፍን ይቅር ይላል። የአባቶችን ኃጢአት ቅጣት እስከ ሁለትና ሶስት ትውልድ በልጆቻቸው ላይ ሲያመጣ በደላቸውን በምንም አይነት ሳይቀጣ አይቀርም።’ 19 የቃል ኪዳን ታማኝነነትህን ታላቅነት ስላልተረዳ ይህ ህዝብ ይበድላል፣ በግብጽ ከነበሩበት ጊዜ አንስቶ እስከ አሁን ሁልጊዜም ይቅር እንዳልካቸው ይቅር እንድትል እለምንሃለሁ።” 20 ያህዌ እንዲህ አለው፣ “ልመናህን ሰምቼ ይቅር ብያቸዋለሁ፣ 21 ነገር ግን፣ እኔ ሕያው ስለሆንኩና መላው ምድርም በእኔ ክብር የተሞላች ስለሆነች፣ 22 ክብሬን፣ በግብጽና በምድረበዳው ጉዟቸው ያደረኳቸውን የሀይሌን ምልክቶች አይተው እነዚያ ህዝቦች ሁሉ - እስከ አሁን ድረስ በእነዚህ አስር ጊዜ ተፈታተኑኝ እንጂ ድምጼን አልሰሙም። 23 ስለዚህ ለአባቶቻቸው የማልኩላቸውን ምድር በፍጹም አያዩም። እኔን ከናቁት ውስጥ አንዳቸውም ምድሪቱን አያዩም፣ 24 ከባሪያዬ ከካሌብ በስተቀር፣ ምክንያቱም እርሱ የተለየ መንፈስ አለው። እርሱ እኔን በሙሉ ልቡ ተከትሎኛል፣ ሊያያት ወደሄደበት ምድር እኔ እመጣዋለሁ። የእርሱ ትውልዶች ይወርሷታል። 25 (አሁን አማሌቃዊያንና ከነዓናውያን በሸለለቆው ይኖራሉ።) ነገ ተመልሳችሁ በሸምበቆው ባህር በኩል ወደ ምድረ በዳው ሂዱ።” 26 ህዋ ሙሴንና አሮንን እንዲህ አላቸው፣ 27 ”እኔን የሚነቅፈውን ይህን ክፉ ማህበረሰብ እስከ መቼ እታገሳለሁ የእስራኤል ሰዎች በእኔ ላይ ሲያጉረመርሙ ሰምቻለሁ። 28 እንዲህ በላቸው ‘እኔ ሕያው ነኝ’ ይላል ያህዌ፣ ‘እኔ እየሰማሁ፣ የተናገራችሁትን፣ ያንኑ አደርግባችኋለሁ። 29 በድናችሁ በዚህ ምድረ በዳ ይወድቃል፣ እናንተ በእኔ ላይ ያጉረመርማችሁ ሁላችሁም፣ በህዝብ ቆጠራው የተቆጠራችሁ ሃያ አመትና ከዚያ በላይ ዕድሜ ያላችሁ ሰዎች ሁሉ ትሞታላችሁ። 30 መኖሪያችሁ ትሆን ዘንድ እንደምሰጣችሁ ቃል ወደገባሁላችሁ ምድር ከዮፍኒ ልጅ ከካሌብና ከነዌ ልጅ ከኢያሱ በስተቀር ከእናንተ አንዳችሁም አትገቡም። 31 ነገር ግን ተጠቂ ይሆናሉ ያላችኋቸው ትንንሽ ልጆቻችሁን፣ እኔ ወደ ምድሪቱ አስገባቸዋለሁ። እናንተ የናቃችኋትን ምድር እነርሱ ይገቡባታል! 32 እናንተ ግን፣ በድናችሁ በዚህ ምድረ በዳ ይወድቃል። 33 ልጆቻችሁ ለአርባ አመታት በምድረዳ ይንከራተታሉ። በረሃው ሁላችሁንም እስኪገድላችሁ ድረስ፣ እነርሱ እናንተን የአመጽ ድርጊቶች ዋጋ ይከፍላሉ። 34 ምድሪቱን በተመለከታችሁባቸው አርባ ቀናት ልክ፣ ለአርባ አመታት ስኃጢአታችሁ መከራ ትቀበላላችሁ - ለእያንዳንዱ ቀን አንድ አመት፣ እናም የእኔ ጠላት መሆን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ታውቃላችሁ። 35 እኔ ያህዌ፣ ይህንን ተናግሬያለሁ። በእኔ ላይ በተነሱ በዚህ ክፉ ማህበረሰብ ላይ በእርግጥ ይህን አደርጋሁ። በዚህ ምድረ በዳ ይጠፋሉ። በዚህ ስፍራ ይሞታሉ።” 36-37 ስለዚህ ሙሴ ምድሪቱን እንዲያዩ የላካቸው ሰዎች ሁሉ በያህዌ ፊት በወረርሽኝ አለቁ። እነዚህ ሰዎች ስለምድሪቱ መጥፎ ወሬ ይዘው የተመለሱ ነበሩ። ይህም መላው ማህበረሰብ በሙሴ ላይ እንዲያጉረመርም አደረገ። 38 ምድሪቱን ለማየት ከሄዱት ሰዎች መሀል፣ የነዌ ልጅ ኢያሱና የዩፎኒ ልጅ ካሌብ ብቻ በህይወት ቀሩ። 39 ሙሴ እነዚህን ቃላት ሁሉ ለእስራኤል ሰዎች ሲናገር፣ በጥልቅ አዘኑ። 40 ማልደው ተነስተው ወደ ተራራው ጫፍ ወጥተው እንዲህ አሉ፣ “እነሆ፣ አሁን በዚህ አለን፣ ደግሞም ያህዌ ቃል ወደገባልን ስፍራ እንሄለን፣ እኛ በድለናል።” 41 ነገር ግን ሙሴ እንዲህ አለ፣ “ለምን አሁን የያህዌን ትእዛዝ ትሸራላችሁ ድል አይቀናችሁም። 42 አትውጡ፣ ምክንያቱም በጠላቶቻችሁ እንዳትሸነፉ ሊጠብቃችሁ ያህዌ ከእናንተ ጋር አይደለም። 43 በዚያ አማሌቃዊያንና ከነዓናዊያን አሉ፣ እናንተም በሰይፍ ታልቃላችሁ ምክንቱም ያህዌን ከመከተል ፊታችሁን መልሳችኋል። ስለዚህ እርሱ ከእናንተ ጋር አይሆንም።” 44 እነርሱ ግን ወደ ተራራማው አገር ለመሄድ በድፍረት ተነሱ፣ ሆኖም፣ ሙሴም ሆነ የያህዌ የቃል ኪዳኑ ታቦት ከሰፈር አብሯቸው አልወጣም። 45 ከዚያ አማሌቃዊያን ወርደው መጡ፣ እንደዚሁም በተራሮቹ የሚኖሩ ከነዓናዊያን መጡባቸው። እነርሱም እስራኤላውያንን አጠቋቸው እስከ ሔርማ መንገድ ድረስ አሳደዷቸው።

Numbers 14:1

እግዚአብሔር በሰይፍ እንሞት ዘንድ ወደዚች ምፍር ለምን ያገባናል?
እዚህ ላይ ሰዎቹ ጥያቄ የሚያነሱት እግዚአብሔር በአግባቡ እንዳልያዛቸው ለመግለፅ ነው።ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በሠይፍ እንድንገደል ለማድረግ ሲል ብቻ እግዚአብሔር ወደዚህ ሥፍራ ሊያመጣን አይገባም ነበር” (ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በሠይፍ ለመገደል
እዚህ ላይ“ሠይፍ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በሠይፍ መሞትን ወይም በጦርነት ውስጥ መሞትን ነው። “ሰዎች በሠይፍ ሲያጠቁን መሞት”ወይም “በጦርነት ውስጥ መሞት”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ግብፅ መመለስ አይሻለንምን?
ሰዎቹ ይሄንን ጥያቄ የሚጠይቁት ሌሎች ሰዎችም ወደ ግብፅ ብንመለስ ይሻለናል ብለው በሃሣባቸው እንዲስማሙላቸው ለማድረግ ነው።ይሄ በድርጊት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ከነዓንን ለማሸነፍ ከምንጥር ይልቅ ወደ ግብፅ ብንመለስ ይሻለናል”

Numbers 14:4

እርስ በእርሣቸው ተነጋገሩ
ይሄ የሚያመለክተው የእሥራኤልን ሕዝብ ነው።

በግምባራቸው ወደቁ
“ፊታቸው መሬቱን ነክቶ ሰገዱ”ሙሴና አሮን ይህንን ያደረጉት ራሣቸውን በእግዚአብሔር ፊት ማዋረዳቸውን ለማሣየት ነበር።ሕዝቡ በእግዚአብሔር ላይ ስላመፀ ሊቀጣቸው ይችል ይሆናል ብለው በመስጋታቸው ነበር።“በእግዚአብሔር ፊት ትህትናን ለማሣየት ፊትን ወደ መሬት መድፋት”ወይም “ወደ እግዚአብሔር ለመፀለይ ፊትን ወደ መሬት መድፋት”(ተምሣሌታዊ ደርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 14:6

ነዌ...ዮፎኒ
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

ከሰላዮቹ ጋር የነበሩት አንዳንድ ሰዎች
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሙሴ ከላካቸው መካከል አንዳንድ ሰዎች” (ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ልብሣቸውን ቀደዱ
ልብስን መቅደድ የሚመለክተው አንድ ሰው ችግር ላይ እንዳለና በርቱ ለቅሶ እያለቀሰ የሚገኝ መሆኑን ነው።(ተምሣሌታዊ ድርጊት)

ወተትና ማር ወደምታፈስሰው
ምድሪቱ ለእንስሳትና ለዕፅዋት ተስማሚ መሆኗን ለመግለፅ ከእነዚያ እንስሳት የሚገኘው ወተትና ማር ልክ በምድሪቱ ላይ እንደሚፈስስ ዓይነት ነገር አድርገው ይገልፁታል።ይህንን ሐረግ በኦሪት ዘኁልቁ 1:15 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“ከብቶችን ለማርባትና ለእህል ዕድገት እጅግ የሚያመች ሥፍራ ነው”ወይም “እጅግ ለም የሆነ መሬት ነው” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 14:9

የማያያዣ ዓረፍተ ነገር
ኢያሱና ካሌብ ለሕዝቡ መናገራቸውን ይቀጥላሉ።

እንደ አንጀራ ይሆኑልናል
ኢያሱና ካሌብ ጠላቶቻቸውን ማጥፋት እንጀራን እንደመብላት ያህል ቀላል እንደሆነ ይናገራሉ።“ምግብን የመብላት ያህል በቀላሉ እናጠፋቸዋለን”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውንና ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥላቸው ከላቸው ተግፍፏል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር ጥላቸውን ከላያቸው ላይ ይገፍፋል” (ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

መከላከያቸው
“መከላከያቸው” የሚለው አሕፅሮተ ሥም “መከላከል”በሚለው ሥም(ሰዋሰው)ሊገለፅ ይችላል። (አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 14:11

ይህ ሕዝብ እስከ መቼ ይንቀኛል?በፊቱስ ባደረግሁት ተአምራት ሁሉ እስከ መቼ አያምንብኝም?....እነርሱ?
እግዚአብሔር ይህንን ጥያቄ የጠየቀው መቆጣቱን ለመግለፅና ሕዝቡን በሚመለከት ትዕግሥቱ ማለቁን ለማሣየት ነው።እነዚህ በድርጊቶች ሊገለፁ ይችላሉ።“ይሄ ሕዝብ ለብዙ ጊዜ ጠልቶኛል።በፊቱ ባደረግሁት ተአምራት ሁሉ አላመነብኝም....እነርሱ።(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ከርስታቸው አጠፋቸው ዘንድ
“የእኔ ሕዝበ እንዳልሆኑ እቆጥራቸዋለሁ”በአንዳንድ ቅጂዎች ትርጓሜ መሠረት ደግሞ ሊያጠፋቸው እንደፈለገ የሚያመለክት ሊሆንም ይችላል።

የራስህን ነገድ ፍጠር
እዚህ ላይ “የራስህን የሚለው ቃል ነጠላ ስለሆነ የሚያመለክተው ሙሴን ነው።(አንተ የሚለው ቃል በተለያየ መንገድ የሚገለፅበት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 14:13

ፊት ለፊት ትተያያለህ
ለዚህ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት 1/ሙሴ እግዚአብሔር ራሱን ለሕዝቡ የሚገልፅበትን ሁኔታ ልክ ፊቱን እንዲያዩ እንደፈቀደላቸው አድርጎ ያቀርበዋል 2/ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን የጠበቀ ግንኙነት ለመግለፅ ልክ እግዚአብሔር ለሙሴ በሚናገርበት ወቅት ፊቱን እንደተመለከተ ዓይነት አድርጎ ተነግሯል።ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“አንተ ለእኔ የምትናገረው በቀጥታ ነው”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውንና ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 14:15

እንደ አንድ ሰው
ሁሉንም በአንድ ጊዘ መግደልን ልክ አንድን ሰው እንደመግደል ተደርጎ ተገልጿል።“ሁሉንም በአንድ ጊዜ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 14:17

የቃል ኪዳንህ ታማኝነት የተትረፈረፈ
“ታማኝነት”የሚለው አሕፅሮተ ቃል “ታማኝ”ወይም “በታማኝነት”ተብሎ ሊገለፅ ይችላል።“ዘወትር ለቃል ኪዳኑ ታማኝ የሆነ”ወይም “ሕዝቡን ዘወትር በታማኝነት ያፈቅራል” (አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

ኃጢአተኞችን ከቶ የማያነፃ
“እውነትም ኃጢአተኛ የሆኑ ሰዎችን ይቅር አይልም” የሰዎችን ኃጢአት ማስወገድ የሚለው ቃል ለመቀጣት ፈቃደኛ ላለመሆናቸው ምሣሌያዊ አነጋገር ነው።እግዚአብሔር የበደለኞችን ኃጢአት ይቅር አይልም።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የአባቶችን ቅጣት በልጆች ላይ የሚያመጣ
እዚህ ላይ መቅጣት የሚለው ሃሣብ የተገለፀው ልክ አንድ ቁሣቁስ መጥቶ በሕዝብ ላይ እንደሚቀመጥ ዓይነት ተደርጎ ነው።“በበደሉ ሰዎች ኃጢአት ምክኒያት የበደሉትን ሰዎች ትውልድ ሲቀጣ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 14:20

ምድር ሁሉ በእኔ ክብር ይሞላል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ክብሬ ምድርን ሁሉ ይሞላል”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ተፈታተኑኝ
“መፈታተኑን አላቋረጡም”

አሥር ጊዜ
እዚህ ላይ አሥር ጊዜ ሲባል ለብዙ ጊዜያት ለማለት ነው።“ለብዙ ጊዜ”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ድምፄን አልሰሙም
እዚህ ላይ “መስማት”የሚለው ቃል የሚመለክተው መታዘዝን ሲሆን የእግዚአብሔር ድምፅ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ደግሞ የእርሱን ንግግር ነው።“የተናገርኩትን ነገር አልታዘዛችሁም” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 14:23

ማያያዣ ዓረፍተ ነገር
እግዚአብሔር ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል።

ሌላ መንፈስ ከእርሱ ጋር ስላለ
እዚህ ላይ “መንፈስ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው አስተሳሰቡን ነው።ካሌብ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ፈቃደኛ ነበር።አስተሳሰቡ ምን እንደነበረ የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“የተለየ አስተሳሰብ የነበረው በመሆኑ”ወይም “እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ፈቃደኛ ስለነበረ” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውንና ግልፅ የሆነ ትግበራ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 14:26

የሚያጉረመርምብኝን ይህን ክፉ ሕዝብ እስከ መቼ እታገሰዋለሁ?
እግዚአብሔር ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው በሕዝቡ ላይ ያለው ትዕግሥት በመሟጠጡ ነው።ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ለብዙ ጊዜ ሲያጉረመርምብኝ የኖረውን ይህንን ማህበረሰብ ታግሼዋለሁ”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የእሥራኤልን ልጆች ማጉረምረም ሰማሁ
“ማጉረምረም”የሚለው አሕፅሮተ ሥም በሥም(ሰዋሰው) መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የእሥራኤል ሕዝብ ሲያጉረመርም ሰምቻለሁ”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 14:28

በጆሮዬ እንደተተናገራችሁት
“ስትናገሩ እንደሰማኋችሁ”

በድኖቻችሁ ይወድቃሉ
የበድኖቻቸው መውደቅ የሚያመለክተው የሚሞቱ መሆኑን ነው።“ትሞታላችሁ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

የተቆጠራችሁ ሁሉ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ቆጠራ በተካሄደበት ወቅት ሙሴ የቆጠራችሁ”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ከሃያ ዓመት ጀምሮ ከዚያም በላይ
“ሃያ ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑ”

Numbers 14:31

በድኖቻችሁ ይወድቃሉ
የበድኖቻቸው መውደቅ የሚያመለክተው የሚሞቱ መሆኑን ነው።“ትሞታላችሁ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ልጆቻችሁ በምድረ በዳ እረኞች ይሆናሉ
አንዳንድ የትርጉም ቅጂዎች “ልጆቻችሁ በምድረ በዳ ይቅበዘበዛሉ”የሚለውን ሃሣብ ይመርጡታል።ይሄ የሆነበት ምክኒያት ከብቶቹ የሚግጡት ሣር እስከሚያገኙ ድረስ እረኞቹ ከቦታ ቦታ ይዘዋወሩ ስለነበረ ነው።

የሥራችሁን ውጤት መሸከም ይኖርባቸዋል
“ከድርጊታችሁ ፍሬ የተነሣ ሊሰቃዩ ይገባል”ወይም “ከእናንተ ድርጊት የተነሣ እነርሱ ሊሰቃዩ ይገባል”

በድኖቻችሁ እስከጠፉ ድረስ
በድን ሬሣ ነው።በድኖቻችሁ እስኪጠፉ ድረስ የሚለው ቃል የሚያመለክተው አንድ ሰው ሣይቀር የሚሞት መሆኑን ነው።“ከእናንተ የመጨረሻው ሰው እስከሚሞት ድረስ”ወይም “ሁላችሁም እስክትሞቱ ድረስ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 14:34

ኃጢአታችሁን ትሸከማላችሁ
“በኃጢአታችሁ ፍሬ ተሰቃዩ”ወይም “ከኃጠአታችሁ የተነሣ ተሰቃዩ”

ፈፅመው ይቆረጣሉ
ይሄ ምናልባት በሕይወት አይኖሩም ለማለት ሊሆን ይችላል።“ፍፃሜያቸው ይሆናል”ወይም “ይጠፋሉ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውንና ግልፅ የሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 14:36

ክፉ ወሬ ያወሩ እነዚያ ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት በመቅሠፍት ሞቱ
“በእግዚአብሔር ፊት በመቅሠፍት”የሚለው ቃል የሚያመለከተው በእግዚአብሔር የተመቱ መሆኑን ነው።ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ስለምድሪቱ ከፉ ወሬ ያመጡትን ሰዎች በእግዚአብሔር ተቀስፈው ሞቱ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውንና ግልፅ የሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 14:39

እነሆ መጣን
ይህንን ነገር የተናገሩት ሃሣባቸውን መለወጣቸውንና ከአንድ ቀን በፊት ማድረግ የነበረባቸውን ነገር ለማድረግ መፈለጋቸውን አፅንኦት ለመሥጠት ነው።የእናንተ ቋንቋ ይህንን የማብራራት የራሱ መንገድ ሊኖረው ይችላል።

Numbers 14:41

የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ለምን ትተላለፋላችሁ?
ሙሴ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው የእሥራኤልን ሕዝብ ለመገሰፅ ነው።ይሄ አሕፅሮተ ሥም በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እንደገና መተላለፍ የለባችሁም”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር በእናንተ መካከል አይደለም
እነርሱን ማገዝ ከእነርሱ ጋር እንደመኖር ተደርጎ ተገልጿል።“እግዚአብሔር አይረዳችሁም”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በጠላቶቸችሁ ፊት እንዳትወድቁ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ጠላቶቻችሁ ድል እንዳይነሷችሁ ለመከላከል” ወይም “በጠላቶቻችሁ ላይ ድልን እንድታገኙ ለማድረግ” (ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰይፍ ትወድቃላችሁ
እዚህ ላይ “ሠይፍ”የሚያመለክተው ጦርነትን ነው።“በጦርነት ውስጥ ትሞታላችሁ”ወይም “ከእነርሱ ጋራ ስትዋጉ ይገድሏችኋል” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን ከመከተል ተመልሳችኋልና
እግዚአብሔርን መታዘዝ እርሱን እንደ መከተል ተደርጎ የተገለፀ ሲሆን የሚናገረውን ቃል አለመፈፀም ደግሞ ከእርሱ እንደመመለስ ተደርጎ ተገልጿል።“እግዚአብሔርን መታዘዝ አቁማችኋል”ወይም “እግዚአብሔርን ላለመታዘዝ ወስናችኋል” “(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)”

ከእናንተ ጋር አይሆንም
እነርሱን ማገዝ ከእነርሱ ጋር እንደመኖር ተደርጎ ነው የተገለፀው።“አይረዳችሁም”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 14:44

እነርሱ ግን ወደ ተራራው ራስ ሊወጡ ደፈሩ።“እግዚአብሔር ያልፈቀደው ነገር ቢሆንም እነርሱ ግን ወደ ተራራው ራስ ሊወጡ ደፈሩ።”
እነርሱ ግን ወደ ተራራው ራስ ሊወጡ ደፈሩ።“እግዚአብሔር ያልፈቀደው ነገር ቢሆንም እነርሱ ግን ወደ ተራራው ራስ ሊወጡ ደፈሩ።”

በተራራማው አገር
አብዛኛው የእሥራኤል ምድር ከፍታ ያለው ሥፍራ ነው።የእሥራኤል ልጆች ከነዓናውያንን ለመውጋት የዮርዳኖስን ወንዝ በተሻገሩበት ወቅት ወደ ከነዓን ምድር ውስጥ ዘልቀው ለመግባት መውጣት የሚኖርባቸው ተራራዎች ነበሩ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 15

1 ከዚያ ያህዌ ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው፣ **2** “ለእስራኤል ሰዎች እንዲህ በላቸው፣ ‘ያህዌ ለእናንተ ወደሚሰጣችሁ ወደ ምትኖሩባት ምድር ስትገቡ **3** ለእርሱ በእሳት መስዋዕት ስታቀርቡ፣ የሚቃጠል መስዋዕት ወይም ስዕለት ስታመጡ ወይም የበጎ ፈቃድ ስጦታ፣ ወይም በባዕላቶቻችሁ ለያህዌ ስጦታዎችን ከከብቶች ወይም ከመንጋችሁ ስታቀርቡ **4** ለያህዌ መስዋዕቱን የሚያቀርበው ሰው፣ በአንድ አራተኛ ኢን ዘይት የተለወሰ የኢፍ አንድ አስረኛ መልካም ዱቄት የእህል መስዋዕት ያቅርብ። **5** እንዲሁም የኢን አንድ አራተኛ ወይን ለመጠጥ መስዋዕት አቅርቡ። ይህን ከሚቃጠል መስዋዕት ጋር ወይም እያንዳንዱ ጠቦት ሲቀርብ አድርጉት **6** አውራ በግ የምታቀርቡ ከሆነ፣ የኢፍ ሁለት አስረኛ መልካም ዱቄት በአንድ ሶስተኛ ኢን ዘይት የተለወሰ የእህል ቁርባን አቅርቡ። **7** ለመጠጥ መስዕት፣ የኢን አንድ ሶስተኛ ወይን አቅርቡ። ይህ ለያዌ ጣፋጭ መዓዛ ይሆናል። **8** ለሚቃተል መስዋዕት በሬ፣ ወይም ስዕለት ለማድረስ መስዋዕት ወይም ለያህዌ የህብረት መስዋዕት ስታዘጋጁ **9** ከበሬው ጋር በግማሽ ኢን ዘይት የተለወሰ የኢፍ ሶስት አስረኛ መልካም ዱቄት የእህል ቁርባን አቅርቡ። **10** ለያዌ ጣፋጭ መዓዛ እንዲሆን ለመጠጥ ቁርባን የኢን ግማሽ ወይን፣ በእሳት የሚረብ መስዋዕት አቅርቡ። **11** እያንዳንዱ በሬ፣ እያንዳንዱ አውራ በግ፣ እና እያንዳንዱ ወንድ ጠቦት በግ ወይም ጠቦት ፍየል ሲቀርብ በዚህ አይት ይሁን። **12** እያንዳንዱ የምታዘጋጁት መስዋዕት እና ስጦታ እዚህ እንደተገለፀው ይቅረብ። **13** ማንም ሰው ለያህዌ ደስ የሚያሰኝ መዓዛ ለማቅረብ በእሳት የተዘጋጀ መስዋዕት ሲያመጣ፣ የአገር ተወላጅ የሆነ እስራኤላዊ ሁሉ እነዚህን ነገሮች በዚህ መንገድ ያድርግ። **14** መጻተኛው ከእናንተ ጋር ቢኖር፣ ወይም በእናንተ ትውልድ መሀል የሚኖር ማናቸውም ሰው፣ ለያህዌ መልካም መዓዛ ለማቅረብ በእሳት የተዘጋጀ መስወዕት ያድርግ። እርሱ እናንተ እንደምታደርጉት ያድርግ። **15** ለማህበረሰቡ እና ከእናንተ ጋር ለሚኖር መጻተኛ ተመሳሳይ ህግ ይሁን፣ ይህ በትውልዳች ሁሉ የፀና ህግ ይሁን። እናንተ እንደ ታያችሁት፣ ከእናንተ ጋር የሚኖሩ እንግዶች በአንድ አይነት ይታያሉ። **16** ለእናንተም ሆነ ከእናንተ ጋር ለሚኖሩ መጻተኞች ተመሳሳይ ህግና ደንቦች ተግባራዊ ይደረጋሉ።” **17** ያህዌ ዳግም ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው፣ **18** ”ለእስራኤል ሰዎች እንዲህ በላቸው፣ ‘ወደ ማስገባችሁ ምድር በመጣች ጊዜ፣ **19** በምድሪቱ የተመረተውን ምግብ በበላችሁ ጊዜ፣ መስዋዕት መሰዋትና ለእኔ ማቅረብ አለባችሁ። **20** ከመጀመሪያው ቡኬታችሁ ከአውድማው የማንሳት መስዋዕት ህብስት አቅርቡ። በዚህ መንገድ መስዋዕታችሁን አቅርቡ። **21** በትውልዶች ሁሉ ከመጀመሪያው ቡኬታችሁ የማንሳት መስዋዕት ለእኔ ትሰጣላችሁ። **22** አንዳንድ ጊዜ ለማድረግ ሳታስቡ ለሙሴ የነገርኩትን እነዚህን ህጎች ሁሉ በተመላለፍና **23** ትዕዛዛትን ለእናንተ መስጠት ከጀመርኩበት ቀን አንስቶ በትውልዳችሁ ቀጣይ ዘመናት በሙሴ በኩል ያዘዝኳችሁን ነገሮች በሙሉ ባታደርጉ ኃጢአት ትሰራላችሁ። **24** ማህበረሰቡ ሳያውቅ በደል ፈጽሞ ሲገኝ፣ መላው ህብረተሰብ ለያህዌ መልካም መዓዛ እንዲሆን አንድ ወይፈን ለሚቃጠል መስዋዕት ያቀርባል። ከዚሁ ጋር የእህል ቁርባን እና የመጠጥ ቁርባን እንዲሁም ለኃጢአት መስዋዕት አንድ ወንድ ፍየል በደንቡ መሠረት ያቅርብ። **25** ካህኑ ለመላው የእስራኤል ማህበረሰብ ማስተስረያ ያቀርባል። ኃጢአቱ የተፈፀመው፣ ባለማወቅ ስለሆነ ይቅር ይባላሉ። ለእኔ በእሳት የተዘጋጀውን መስዋዕታቸውን አቅርበዋልና ይቅር ይባላሉ። በእኔ ፊት ሳያውቁ ለፈጸሙት ስህተት የኃጢአት መስዋዕታቸውን አቅርበዋልና። **26** ከዚያ መላው የእስራኤል ማህበረሰብና ከእነርሱ ጋር የሚኖሩ መጻተኞች ይቅር ይባላሉ፣ ምክንያቱም ሁሉም ኃጢአቱን የፈፀሙት ሆን ብለው አይደለም። **27** አንድ ሰው ሳያውቅ ኃጢአት ቢሰራ ለኃጢአት መስዋዕት የአንድ አመት ሴት ፍየል ያቅርብ። **28** ካህኑ ሳያውቅ ኃጢአት ለሰራው ሰው በያህዌ ፊት ያስተሰርይለታል። ያ ሰው ማስተሰርያ ሲደረግ ይቅር ይባላል። **29** ማናቸውንም ነገር ሁን ብሎ ላላደረገ ተመሳሳይ ህግ ይኑራችሁ፣ በእስራኤል ሰዎች መሀል ለሚኖረው ተወላጅም ሆነ መጻተኛ ተመሳሳይ ህግ ይኑራቸው። **30** ነገር ግን ራሱን ለመከላከል አንዳች ነገር ያደረገ ሰው፣ የአገር ተወላጅም ይሁን መጻተኛ እኔን ያቃልላል። ስለዚህ ያ ሰው ከወገኖቹ ተለይቶ ይጥፋ። **31** ምክንቱም እርሱ ቃሌን ንቋል ደግሞም ትዕዛዛቴን ተላልፏል፣ ያ ሰው ሙሉ ለሙሉ ከህዝቡ ተለይቶ ይጥፋ። ኃጢአቱ በራሱ ላይ ይሆናል።” **32** የእስራኤል ህዝቦች በምድረ በዳ በነበሩበት ጊዜ፣ አንድ ሰው በሰንበት ቀን እንጨት ሲለቅም አገኙት። **33** ያገኙት ሰዎች ወደ ሙሴ፣ ወደ አሮንና ወደ መላው ማህበረሰብ አቀረቡት። **34** በእርሱ ላይ ምን መደረግ እንዳለበት የታወቀ ህግ ስላልበረ በጥበቃ ሥር አቆዩት። **35** ከዚያ ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ “በእርግጥ ሰውየው መገደል አለበት። መላው ማህበረሰብ ከሰፈር ውጭ በድንጋይ ይውገረው።” **36** ስለዚህም መላው ማህበረሰብ ሰውየውን ከሰፈር ውጭ አውጥተው ያህዌ ሙሴን እንዳዘዘው እስኪሞት ድረስ ወገሩት። **37** ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ **38** “ለእስራኤል ትውልዶች በየለብሳቸው ጠርዝ ዘርፍ እንዲያስሩ ንገራቸው፣ ዘርፎቹን በእያንዳንዱ ጠርዝ በሰማያዊ ገመድ እንዲያንጠለጥሉ እዘዛቸው። በሚቀጥሉት ትውልዶቻቸው ሁሉ ይህን ያድርጉ። **39** ይህንን ስትመለከቱ፣ በትዕዛዛት ሁሉ፣ እንድትሄዱ፣ የራሳችሁን ልቦናና እይታ ሳትከተሉ ቀድሞ ታደርጉት ከነበረው መንፈሳዊ አመንዝራነት ለመመለስ ይህ ለእናንተ ልዩ ማስታወሻ ይሆናችኋል። **40** ትዕዛዛቶቼን ሁሉ እንድትጠብቁና አስተዋዮች እንድትሆኑ ይህን አድርጉ፣ ደግሞም ቅዱሳንና ለእኔ ለአምላካችሁ የተለያችሁ ትሆናላች። **41** አምላካችሁ እሆን ዘንድ፣ ከግብጽ ምድር ያወጣኋችሁ እኔ ያህዌ አምላካችሁ ነኝ። እኔ ያህዌ አምላካችሁ ነኝ።”

Numbers 15:1

አጠቃላይ መረጃ
ዘኁልቁ 15፤1-32 ድረስ ያለው ክፍል ሙሴ ለእሥራኤላውያን እንዲናገራቸው እግዚአብሔር የተናገረውን የሚገልፅ ነው።

ለእግዚአብሔር ጣፋጭ ሽታ ታደርጉ ዘንደ ከበሬ ወይም ከበግ መንጋ
“ከበሬ ወይም ከበግ መንጋ ለእግዚአብሔር ጣፋጭ ሽታን ማቅረብ”እግዚአብሔር በጣፋጩ ሽታ ደስ መሰኘቱ የሚያመለክተው መሥዋዕቱን በሚያቀርበው ሰው መደሰቱን ነው።“ከበሬ ወይም ከበግ መንጋ ጣፋጭ ሽታን በማቅረብ እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 15:4

የሚቃጠል መሥዋዕት
ይሄ የሚያመለክተው በኦሪት ዘኁልቁ 15:3 የተጠቀሱትን መሥዋዕቶች ነው።

ከአሥር አንድ እጅ የሆነ መሥፈሪያ
መስፈሪያ የመለኪያ ዓይነት ሲሆን ከ22 ሊትር ጋር እኩል ነው።“2 ሊትር ያህል”ወይም “ሁለት ሊትር”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

የኢን መሥፈሪያ አራተኛ እጅ
ኢን የመለኪያ ዓይነት ሲሆን ከ3.7 ሊትር ጋር እኩል ነው።“1 ሊትር ያህል”ወይም “አንድ ሊትር”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Numbers 15:6

መሥፈሪያ ከአሥር እጅ ሁለት እጅ
መስፈሪያ የመለኪያ ዓይነት ሲሆን ከ22 ሊትር ጋር እኩል ነው።“4 ሊትር ያህል”ወይም “አራት ተኩል ሊትር”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

የኢን መሥፈሪያ ሲሶ
ኢን የመለኪያ ዓይነት ሲሆን ከ3.7 ሊትር ጋር እኩል ነው።“አንድ ሊትር”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእግዚአብሔር ጣፋጭ ሽታ ይሆናል
“እግዚአብሔርን የሚያስደስት ሽታ ይወጣዋል” እግዚአብሔር በጣፋጩ ሽታ ደስ መሰኘቱ የሚያመለክተው መሥዋዕቱን ባቀረበው ሰው ሐሴት ማድረጉን ነው።“እርሱን መሥዋዕት በማድረግ እግዚአብሔርን ታስደስታላችሁ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 15:8

ከመሥፈሪያው ከአሥር እጅ ሶስት እጅ
ይህንን ወደ ዘመናዊ መለኪያ ልትለውጡት ትችላላችሁ።“ስድስትና አንድ ከግማሽ ሊትር”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

ግማሽ ኢን
ይህንን ወደ ዘመናዊ መለኪያ ልትለውጡት ትችላላችሁ።“ሁለት ሊትር”(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

በእሣት የተደረገ
“በመሠዊያው ላይ የምታቃጥሉት”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእግዚአብሔር ጣፋጭ ሽታን ለማቅረብ
“እግዚአብሔርን የሚያስደስት ሽታ ማቅረብ” በቅን ልብ መሥዋዕትን በሚያቀርብ ሰው እግዚአብሔር መደሰቱን ለመግለፅ ልክ እግዚአብሔር በመልካም ሽቱ መሥዋዕት እንደሚደሰት ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል።“እርሱን በማቅረብ እግዚአብሔርን ማስደሰት።”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 15:11

ሊደረግ ይገባል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እናንተ ልታደርጉት ይገባል” (ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

በተገለፀው መሠረት እንዲሁ መደረግ ይኖርበታል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።በተናገርኩት መሠረት መፈፀም ይኖርባችኋል”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

በእሳት የተደረገ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በእሣት ላይ የሚያቀጥሉትን”

ለእግዚአብሔር ጣፋጭ ሽታ የሚሆንን ነገር ለማቅረብ
“ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ ሽታ ለማቅረብ” የሚለው ሐረግ እግዚአብሔር በቅን ልብ መሥዋዕትን በሚያቀርብ ሰው መደሰቱን ለመግለፅ ልክ እግዚአብሔር በመልካም ሽቱ መሥዋዕት እንደሚደሰት ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል።“እርሱን በማቅረብ እግዚአብሔርን ማስደሰት።”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 15:14

ቁርባንን በእሣት ማቅረብ ይኖርበታል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በመሠዊያው ላይ ቁርባንን ማቃጠል ይኖርበታል”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእግዚአብሔር ጣፋጭ ሽታ የሚሆንን ነገር ለማቅረብ
“እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሽታ ለማቅረብ”የሚለው ሐረግ እግዚአብሔር በቅን ልብ መሥዋዕትን በሚያቀርብ ሰው መደሰቱን ለመግለፅ ልክ እግዚአብሔር በመልካም ሽቱ መሥዋዕት እንደሚደሰት ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል።“እርሱን በማቅረብ እግዚአብሔርን ማስደሰት።”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእናንተም መካከል ለሚቀመጥ መፃተኛ አንድ ሥርዓት ይሆናል
ለዚህ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት1/ “እናንተና በመካከላችሁ ያሉት መፃተኞች በእግዚአብሔር ፊት እኩል ናችሁ”ወይም “እናንተንም ሆነ መፃተኛውን የሚገዛው ሕግ ተመሳሳይ ነው”

እናንተ እንደምታደርጉት እንዲሁ በእግዚአብሔር ፊት ያደርጋል
እናንተ እንደምታደርጉት እንዲሁ በእግዚአብሔር ፊት የሚያደርጉበት ምክኒያት በእግዚአብሔር ፊት እንደ እሥራኤላውያን መሆን ያለባቸው በመሆኑ ነው።ይሄ የሚያመለክተው ሕጎቹን ሁሉ እንደ እሥራኤላውያን መጠበቅ አለባቸው ማለት ነው።እናንተ እንደምታደርጉት ማድረግና ሕጎቹንም ሁሉ መጠበቅ ይኖርባቸዋል”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 15:17

በምድሪቱ ውስጥ ያለውን እንጀራ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ምድሪቱ የምታበቅለው እንጀራ”ወይም “እናንተ በምድሪቱ ውስጥ የምታመርቱት እንጀራ”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 15:20

መጀመሪያ ከምታደርጉት ሊጥ
ለዚህ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት 1/በመከር ወቅት የሚሰበስቡት የመጀመሪያው ሰብል ወይም 2/በመጀመሪያ ከሚያገኙት ሰብላቸው የሚሰሩት ሊጥ (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

እንጎቻ
እንጎቻ ተብሎ መጠራቱ የሚያመለክተው ሊጡን በመጀመሪያ መጋገር ያለባቸው መሆኑን ነው።

እንደ ማንሣት ቁርባን ማቅረብ
“ማንሣት”የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር የሚያመለክተው እንደ ሥጦታ መቅረቡን ነው።“እንደ ሥጦታ ማቅረብ”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከአውድማ እንደሚነሣ ቁርባን
ሥጦታው ከአውድማ ነው ተብሎ የተገለፀው የእህል ሥጦታቸውን ከሌላው ሰብል ለይተው የሚያስቀምጡበት ሥፍራ አውድማ በመሆኑ ነው።

Numbers 15:22

ማያያዣ ዓረፍተ ነገር
እግዚአብሔር ሙሴ ለእሥራኤል ሕዝብ መናገር ስላለበት ነገር መናገሩን ይቀጥላል።

አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ላይ “እናንተ” የሚለው ቃል የሚመለክተው እሥራኤላውያንን ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለእግዚአብሔር ጣፋጭ ሽታ የሚሆንን ነገር ለማቅረብ
“እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሽታ ለማቅረብ” የሚለው ሐረግ እግዚአብሔር በቅን ልብ መሥዋዕትን በሚያቀርብ ሰው መደሰቱን ለመግለፅ ልክ እግዚአብሔር በመልካም የሸቱ መሥዋዕት እንደሚደሰት ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል።“ እርሱን በማቅረብ እግዚአብሔርን ማስደሰት።”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእህል ቁርባንና የመጠጥ ቁርባን መደረግ ይኖርበታል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የእህል ቁርባንና የመጠጥ ቁርባን ማድረግ ይኖርባችኋል”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ሕጉ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሕጉ እንደሚያዘው”ወይም “ሕጉን ሳወጣ ባዘዝኩት መሠረት”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 15:25

ይሰረይላቸዋል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ይቅር እላቸዋለሁ”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

በእሣት የቀረበ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በእሣት የሰሩት”ወይም “በመሠዊያው ላይ ያቃጠሉት”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእሥራኤል ልጆች ማህበር ሁሉ ስርየት ይደረግላቸዋል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የእሥራኤልን ልጆች ማህበር ሁሉ ይቅር እላቸዋለሁ”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 15:27

የአንድ ዓመት እንስት ፍየል
“አንድ ዓመት የሞላው ፍየል”

መሥዋዕት በሚቀርብበት ወቅት የዚያ ሰው ኃጢአት ይሰረይለታል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ካህኑ መሥዋዕትን በሚያቀርብበት ወቅት የዚያን ሰው ኃጢአት ይቅር እላለሁ”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 15:30

ያም ሰው ከሕዝቡ መካከል ተለይቶ ይጥፋ
“ተለይቶ ይጥፋ” የሚለው ምሣሌያዊ አነጋገር ቢያንስ ሶስት ሃሣቦችን በውስጡ አዝሏል።1/“የራሱ ሕዝብ ሊያባርረው ይገባል”2/“ከእሥራኤል ሕዝብ እንደ አንዱ አልቆጥረውም” “የራሱ ሕዝብ ሊገድለው ይገባል”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውንና ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ትዕዛዜን ሰበረ
ትዕዛዝን አለመፈፀም አንድን ነገር እንደመስበር ተደርጎ ተገልጿል።“ትዕዛዜን ለመፈጸም ፈቃደኛ አልሆነም” ወይም “ያዘዝኩትን ነገር አልፈፀመም”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ኃጢአቱ በእርሱ ላይ ይሆናል
እዚህ ላይ “ኃጢአት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው 1/ለተሰራው ኃጢአት የሚፈረድበትን ቅጣት2/በዚያ ኃጢአት ምክኒያት የደረሰ በደል።ኃጢአት 1/ ለመቀጣትና 2/ለበደል ምሣሌያዊ አነጋገር ነው። “1/በሰራው ኃጢአቱ ምክኒያት እቀጣዋለሁ” ወይም 2/ “እንደ በደለኛ እቆጥረዋለሁ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውንና (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ))

Numbers 15:32

በእርሱ ላይ ሊወሰድ የሚገባው እርምጃ አልታወቀም ነበር
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር በእርሱ ላይ ስለሚወሰደው እርምጃ አልተናገረም ነበር”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 15:35

ሰውዬው ፈፅሞ ይገደል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሰውዬውን በእርግጥም መግደል ይኖርባችኋል”ወይም “ሰውዬው በእርግጥ መሞት ይኖርበታል”(ገቢራዊና ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 15:37

የእሥራኤል ትውልዶች
“የእሥራኤል ሕዝብ”

ተግባራዊ ለማድረግ
“እነርሱን ለመታዘዝ”

የልባችሁንና የዓይኖቻችሁን ፈቃድ እንዳትመለከቱ
እዚህ ላይ “መመልከት”የሚለው ቃል ማሰብ ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ልብ አንድ ሰው የሚሻውን ነገር የሚያመለክት ሲሆን ዓይን ደግሞ አንድ ሰው የሚያየውንና የሚፈልገውን ነገር ያመለክታል።“የምትፈልጉትን ነገር ሁሉ እንዳታስቡ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውንና ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

እርስዋን በመከተል ያመነዘራችሁበትን
ልባቸው ያሻውን ነገር እያደረጉ እግዚአብሔርን ያለመታዘዛቸውን ሁኔታ አንዲት ሴት ለባልዋ ታማኝ ካለመሆኗ የተነሣ ከሌላ ሰው ጋር ዝሙት እንደምትፈፅም ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል።ይሄ አሣፋሪ ድርጊት ስለመሆኑ የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“በሚያሣፍር ሁኔታ ለእኔ ታማኝ አልሆናችሁም”ወይም “ከመታዘዝ ይልቅ እነዚህን ነገሮች ታደርጋላችሁ” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን፤በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 15:40

ማያያዣ ዓረፍተ ነገር
እግዚአብሔር ሙሴ ለእሥራኤል ሕዝብ መናገር የሚኖርበትን ነገር መንገሩን ቀጥሏል። “እናንተ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእሥራኤልን ሕዝብ ነው።

በልባችሁ ላይ እንዲታይ
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው።“ማስታወስ”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ
ይሄ ሐረግ የተደጋገመው አፅንኦት ለመስጠት ሲባል ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 16

1 የይስዓር ልጅ ቆሬ የቀዓት ልጅ የሌዊ ልጅ፣ ከኤሊያብ ልጆች ከዳታንና አቤሮን ጋር፣ እንዲሁም የፍሬት ልጅ ኦን፣ የሮቤል ትውልዶች ሆነው ተሰበሰቡ። 2
እነርሱም ከእስራኤል ሌሎች ሰዎች ጋር ሆነው በሙሴ ላይ ተቃውመው ተነሱ፣ የማህበረሰቡ መሪዎች የሆኑ የታወቁ ሁለት መቶ ሀምሳ ሰዎች ተነሱበት። 3
ሙሴንና አሮንን ለመቃወም በአንድነት ተሰበሰቡ። ሙሴንና አሮንን እንደዚህ አሏቸው፣ “እናንተ ያለ ልክ አብዝታችሁታል። መላው ማህበረሰብ ቅዱስ ነው፣
ለያህዌ የተለየ ነው፣ እያንዳንዳቸው ንጹሃን ናቸው፣ ያህዌም በመሀከላቸው ነው። ለምን ራሳችሁን ከተቀረው የያህዌ ማህበረሰብ ከፍ ታደረጋላችሁ?” 4 ሙሴ
ይህንን ሲሰማ፣ በግምባሩ ተደፋ። 5 ለቆሬና ለእርሱ ወገኖች እንዲህ አላቸው፤ “ማለዳ ያህዌ የእርሱ የሆኑት እነማን እንደሆኑ ይለያል፣ ማን ለእርሱ እንደ ተለየ
ይታወቃል። የመረጠውን ሰው ወደ ራሱ ይለያል። የመረጠውን ወደ ራሱ ያመጣዋል። 6 ቆሬና የአንተ ቡድን ሁላች ይህን አድርጉ። ማጠንት ያዙ 7 ነገ በያህዌ
ፊት እሳትና እጣን በላያቸው ጨምሩ። ያህዌ የሚመርጠው ሰው እርሱ፣ ለያህዌ የተለየ ይሆናል። እናንተ የሌዊ ትውልዶች ከልክ አልፋችኋል።” 8 እንደገና፣
ሙሴ ቆሬን እንዲህ አለው፣ “አሁን ስማ፣ እናንተ የሌዊ ትውልዶች 9 የእስራኤል አምላክ ከእስራኤል ማህበረሰብ እናተን ለይቶ ወደራሱ ማቅረቡ፣ በያህዌ
የማደሪያ ድንኳን እንድታገለግሉ ማድረጉ፣ እነርሱን እንድታገለግሉ በማህበረሰቡ ፊት እናንተን ማቆሙ ለእናንተ ትንሽ ነገር ነውን? 10 እርሱ አንተን፣ የቅርብ
ዘመዶችህንና የሌዊ ትውልዶችን ከአንተ ጋር አቅርቧችኋል፣ እናንተ ግን ክህነቱንም እየፈለጋችሁ ነው! 11 አንተና የአንተ ተከታዮች ሁሉ በያህዌ ላይ በአንድ ላይ
ተነሳችሁ። ስለዚህ ለምን እግዚአብሔርን በሚታዘዘው በአሮን ላይ ታጉረመርማላችሁ?” 12 ከዚያ ሙሴ የኤልያብን ልጆች ዳታንንና አብሮንን ጠራቸው፣ እነርሱ
ግን እንዲህ አሉ፣ “እኛ ወደዚያ አንመጣም። 13 እኛን በምድረበዳ ልትገድለን ወተትና ማር ከሚፈስባት ምድር ያወጣኸን ትንሽ ነገር ሆኖ ነውን? አሁን ራስህን
በእኛ ላይ ገዢ ማድረግ ትፈልጋለህ! 14 በተጨማሪም፣ እኛን ወተትና ማር ወደምታፈስ ምድር አላመጣኸንም፣ ወይም እርሻዎችንና የወይን ተክሎችን ውርስ
አድርገህ አልሰጠኸንም። አሁን በባዶ ተስፋ ልታታልለን ትፈልጋህ? ወደ አንተ አንመጣም።” 15 ሙሴ እጅግ ተቆጥቶ ነበር፣ ወደ ያህዌ እንዲህ ሲል ጮኸ፣
“መስዋዕታቸውን አትቀበል። ከእነርሱ አንድ አህያ እንኳን አልወሰድኩም፣ ከእነርሱ አንዳቸውንም አልበደልኩም።” 16 ከዚያ ሙሴ ቆሬን እዲህ አለው፣ “ነገ
አንተና የአንተ የሆኑ በያህዌ ፊት ይቅረቡ፤ አንተ፣ እነርሱና አሮን በያህዌ ፊት ቁሙ። 17 እያንዳንዱ የራሱን ማጠኛ ይያዝና በውስጡ እጣን ይጨምርበት። ከዚያ
እያንዳንዱ ሰው ማጠኛውን በያዌ ፊት ያምጣ፣ ሁለት መቶ አምሳዎቹ ሰዎችህ ማጠኛዎቻቸውን ይዘው ይቅረቡ። አንተና አሮንም ደግሞ የየራሳቸችሁን ማጠኛ
አምጡ።” 18 ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው ማጠኛውን ወሰደ፣ በውስጡ እሳት አደረገ፣ እጣንም ጨመረበት ከሙሴና ከአሮን ጋር በመገናኛው ድንኳን መግቢያ ላይ
ቆሙ። 19 ቆሬ መላውን ማህበረሰብ በመገናኛው ድንኳን መግቢያ ላይ በሙሴና በአሮን ላይ በተቃውሞ ሰበሰበ፣ የያህዌ ክብር ደግሞ ለማህበረሰቡ ሁሉ ታየ።
20 ከዚያ ያህዌ ለሙሴና ለአሮን እንዲህ ሲል ተናገረ፣ 21 ”በቶሎ ከማጠፋው ከዚህ ማህበረሰብ መሀል ራሳችሁን ለዩ።” 22 ሙሴና አሮን በግንባራቸው
ተደፍተው እንዲህ አሉ፣ “ የሰው ልጆች ሁሉ መንፈስ አምላክ የሆንክ እግዚአብሔር ሆይ፣ አንድ ሰው ኃጢአት ቢሰራ ማህበረሰቡን በሙሉ ልትቆጣ ይገባልን?”
23 ያህዌ ለሙሴ እንዲህ ሲል መለሰለት፣ 24 ”ለማህበረሰቡ እንዲህ በል፣ ‘ከቆሬ፣ ከዳታንና ከኤብሮን ድንኳኖች ውጡ።’” 25 ከዚያ ሙሴ ተነስቶ ወደ ወደ
ዳታንና አብሮን ሄደ፤ የእስራኤል መሪዎች እርሱን ተከተሉት። 26 ለማህበረሰቡ እንዲህ ብሎ ተናገረ፣ “አሁን የእነዚህን ክፉ ሰዎች ድንኳኖች ልቀቁ፣ የእነርሱ
የሆነውን አንዳች ነገር አትንኩ፣ አለበለዚያ በእነርሱ ኃጢአቶች ሁሉ እናንተም ትጠፋላችሁ።” 27 ስለዚህ በቆሬ፣ በዳታንና በኤብሮን ድንኳኖች በእያንዳንዱ
አቅጣጫ የሚገኝ ማህበረሰብ ከእነርሱ ራቁ። ዳታንና አብሮን ወደ ውጭ ወጥተው ከሚስቶቻቸው፣ ከወንዶች ልጆቻቸውና ከህፃናቶቻቸው ጋር በድንኳኖቸው
ደጃፍ ላይ ቆሙ። 28 ከዚያ ሙሴ እንዲህ አለ፣ “በዚህም ያህዌ እነዚህን ስራዎች ሁሉ እንድሰራ እንደላከኝ ታውቃላችሁ፣ እኔ በራሴ ፈቃድ እነዚህን ነገሮች
አልሰራኋቸውም። 29 እነዚህ ሰዎች በተለመደው ሁኔታ ተፈጥሯዊ ሞት ቢሞቱ፣ ያህዌ እኔን አላኝም ማለት ነው። 30 ነገር ግን ያህዌ ምድሪቷን ቢከፍትና እርሷ
እንደ ተከፈተ አፍ ሆና፣ ከነቤተሰቦቻቸው ብትውጣቸው፣ ደግሞም በህይወታቸው ሳሉ ወደ ሲኦል ቢወርዱ፣ ያን ጊዜ እነዚህ ሰዎች ያህዌን እንደናቁ
ታውቃላችሁ።” 31 ሙሴ እነዚህን ቃላቶች ተናግሮ እንደጨረሰ፣ ምድሪቱ ከነዚህ ሰዎች በታች ተከፈተች። 32 መሬት አፏን ከፈተችና ዋጠቻቸው፣ ቤተሰቦቻቸው፣
እና የቆሬ ሰዎች ሁሉ እንዲሁም ያላቸው ሀብት ሁሉ ተዋጠ። 33 እነርሱና በየቤተሰባቸው እያንዳንዱ በሕይወት ሳሉ ወደ ሲኦል ወረዱ። መሬት በላያቸው
ተከደነች፣ እናም በዚህ መንገድ ከማህበረሰቡ መሀል ጠፉ። 34 በዙሪያቸው የነበሩ እስራኤላዊያን ሁሉ ከጩኸታቸው የተነሳ ሸሹ። እንዲህ እያሉም ጮኹ፣
“መሬት እኛንም ደግሞ ልትውጠን ነው!” 35 እሳት ከያህዌ ዘንድ ወጥታ የሚያጥኑትን 250 ሰዎች በላቻቸው። 36 ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ 37
”ጥናዎቹ ለእኔ የተለዩ ናቸውና ለካህኑ ለአሮን ልጅ ለአላዓዛር ከሚጤሱት የተረፉትን ጥናዎች እንዲወስድ ንገረው። ከዚያ ረመጡን ይበትኑት። 38
በኃጠአታቸው ምክንያት ሕይወታቸውን ያጡትን ሰዎች ጥናዎች ውሰድ። ጥናዎቹ የተቀጠቀጡ ሰሀኖች ተደርገው ለመሰዊያው መሸፈኛነት ይዋሉ። ለእኔ የተለዩ
ናቸውና፣ እነዚያ ሰዎች በእኔ ፊት ያቅርቧቸው። እነዚህም ለእስራኤል ሰዎች ለእኔ መገኘት ምልክት ይሆናሉ።” 39 ካህኑ አልዓዛር የተቃጠሉት ሰዎች
ይጠቀሙባቸው የነበሩትን የናስ ጥናዎች ይውሰድና ለመሰዊያው መሸፈኛነት ይቀጥቅጣቸው፣ 40 ይህም፤ ለእስራኤል ሰዎች ማስታወሻ እንዲሆን፣ ማንም
የአሮን ትውልድ ያልሆነ መጻተኛ በያህዌ ፊት ለማጠን እንዳያቀርብና እንደ ቆሬና እንደ እርሱ ተከታዮች እንዳይሆኑ ያህዌ በሙሴ በኩል እንዳዘዘው ልክ እንደዚያ
እንዳይሆንባቸው ነው። 41 ነገር ግን በማግስቱ የእስራኤል ማህበረሰብ በሙሉ በሙሴና በአሮን ላይ በማጉረምረም ተነሱባቸው። እነዲህም አሉ፣ “እናንተ
የያህዌን ሰዎች ገድላችኋል።” 42 ከዚያም እንዲህ ሆነ፣ ማህበረሰቡ በሙሴና በአሮን ላይ በተቃውሞ ሲሰበሰብ፣ ወደ መገናኛው ድንኳን አሻግሮ ሲመለከቱ፣
እነሆ ደመናው ድንኳኑን ሸፍኖት ነበር። የያህዌ ክብር ታየ፣ 43 እናም ሙሴና አሮን ወደ መገናኛው ድንኳን ወደፊት መጡ። 44 ከዚያ ያህዌ ሙሴን ተናገረው።
እንደህም አለው፣ 45 “ከዚህ ማህበረሰብ ፊት ራቅ፣ እኔ በቶሎ አጠፋቸዋለሁ።” ከዚያ ሙሴና አሮን በግምባራቸው ተደፉ። 46 ሙሴ አሮንን እንዲህ አለው፣
“ማጥንቱን ውሰድ፣ ከመሰዊያው እሳት ወስደህ አድርግበት፣ በውስጡ እጣን ጨምርበት፣ በቶሎ ወደ ማህበረሰቡ ውሰደው፣ እናም ለእነርሱ አስተሰርይ፣
ምክንያቱም ከያህዌ ዘንድ ቁጣ እየመጣ ነው። መቅሰፍቱ ጀምሯል።” 47 ስለዚህም አሮን ሙሴ እንደመራው አደረገ። ወደ ማህበረሰቡ መሃል ሮጠ።
መቅሰፍቱ በህዝቡ መካከል በፍጥነት መስፋፋት ጀመሮ ነበር፣ ስለዚህም እርሱ እጣኑን ጨምሮ ለህዝቡ ማስተሰርያ አደረገ። 48 አሮን በሙታኑና በህያዋኑ
መሀል ቆመ፣ በዚህ መንገድ መቅሰፍቱ ቆመ። 49 በመቅሰፍቱ የሞቱት ሰዎች ቁጥር 14700 ነበር፣ ይህም በቆሬ ምክንያት የሞቱትን ሳይጨምር ነው። 50
አሮን ወደ መገናኛው ድንኳን መግቢያ ወደ ሙሴ ተመለሰ፣ መቅሰፍቱም አበቃ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Numbers 16:1

ቀአት
የዚህን ሰው ሥም በኦሪት ዘኁልቁ 3:17 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።።

በሙሴ ላይ ተነሱ
በአንድ በኃላፊነት በሚገኝ ሰው ላይ ማመፅና መተቸት ልክ ለመጣላት እንደተነሱ ዓይነት ነገር ተደርጎ ተገልጿል።።“በሙሴ ላይ አመፁ” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሁለት መቶ ሃምሣ
“250”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ታዋቂ የሆኑ የማህበረሰቡ አባላት
“ዝነኛ የሆኑ የማህበረሰቡ አባላት” ወይም“በማህበረሰቡ ውስጥ ዋና የሆኑ ሰዎች”

እናንተ እጅግ አብዝታችኋል
ይሄ የሚያመለከተው አንድ ሰው ማድረግ ከሚገባው በላይ ማድረጉን ነው።።“ማድረግ ከሚገባችሁ በላይ አድርጋችኋል”ወይም “ሊኖራችሁ ከሚገባው በላይ የሆነ ሥልጣን ያላችሁ ይመሰላችኋል”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ጉባዔ ላይ ለምን ትታበያላችሁ?
ሰዎቹ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቁት ሙሴንና አሮንን ለመገሰፅ ብለው ነው።።ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል። “በተቀረው የእግዚአብሔር ጉባዔ ላይ ራሣችሁን ከፍ ማድረጋችሁ ትክክል አይደለም” (ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ከሌሎቹ በላይ ራሣችሁን ከፍ ማድረጋችሁ
አንድ ሰው አስፈላጊ ነኝ ብሎ የማመኑን ነገር ራስን ከፍ ከማድረግ ጋር ተነፃፅሯል።።“ራሣችሁን ከሌሎች የበለጠ አስፈላጊ ነን ብላችሁ ትገምታላችሁ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 16:4

በግምባሩ ወደቀ
ይሄ የሚያሣየው ሙሴ በእግዚአብሔር ፊት ራሱን ማዋረዱን ነው።። በእግዚአብሔርና በመረጣቸው ሰዎች ላይ በማመፃቸው እግዚአብሔር ሕዝቡን ሊቀጣ ይችላል ብሎ ፈራ።።(ተምሣሌታዊ ድርጊት)

ለእርሱ የሚሆነውን
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።።“እግዚአብሔር ለራሱ የለየውን”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 16:6

ማያያዣ ዓረፍተ ነገሮች
ሙሴ ለቀአትና ከቀአት ጋር ለነበሩት ሰዎች መናገሩን ይቀጥላል።።

ጥና
ዕጣንን ለማጤስ የሚያገለግል ዕቃ።።

በእግዚአብሔር ፊት
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው።።“በእግዚአብሔር ሕልውና ፊት”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ያ ሰው ለእግዚአብሔር የተለየ ይሆናል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።።“እግዚአብሔር ያንን ሰው ለራሱ የተለየ ያደርገዋል” (ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ እጅግ አብዝታችኋል
ይሄ የሚያመለከተው አንድ ሰው ማድረግ ከሚገባው በላይ አልፎ ማድረጉን ነው።።“ማድረግ ከሚገባችሁ በላይ አድርጋችኋል”ወይም “ሊኖራችሁ ከሚገባው በላይ የሆነ ሥልጣን ያላችሁ ይመሰላችኋል”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 16:8

አይበቃችሁምን..እነርሱን ለማገልገል
ሙሴ ይህንን ጥያቄ የሚያነሣው ቀአትንና ከእርሱ ጋር የነበሩትን ሰዎች ለመገሰፅ ብሎ ነው።።ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።።“እነርሱን ማገልገል ትንሽ ነገር መስሎ ይታያቸኋል”ወይም “እነርሱን ማገልገል እንደ ትንሽ ነገር መስሎ ሊታያችሁ አይገባም።።”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእናንተ ትንሽ ነገር
“ለእናንተ የማይበቃችሁ” ወይም “ለእናንተ ጠቃሚ ያልሆነ”

ክህነትንም ትፈልጋላችሁ
ክህነት መፈለግን ልክ በዓይናቸው እንደሚፈልጉት ዓይነት በሚመስል መልኩ ተገልጿል።።“ክህነትን ትፈልጋላችሁ” ወይም “እናንተም ካህናት መሆን ትፈልጋላችሁ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን በሚያገለግለው በአሮን ላይ ለምን ታጉረመረማላችሁ?
ሙሴ ይህንን ጥያቄ የሚያነሳበት ምክኒያት የአሮንን መልካም የሆነ ድርጊት በመጥቀስ ለመሞገት ነበር።።ምክኒያቱ ደግሞ አሮን እግዚአብሔር አድርግ የሚለውን ነገር የሚያደረግ ሰው ሰለነበረ ነው።።“የምታጉመርሙት በአሮን ላይ ሣይሆን አሮንን በሚያዝዘው በእግዚአብሔር ላይ ነው”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 16:12

በምድረ በዳ ትገድለን ዘንድ ...ያወጣኸን አይበቃህምን?
ዳታንና አቤሮን ይህንን ጥያቄ የሚጠይቁት ሙሴን ለመገሰፅ ነው።።ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።።“እኛን እዚህ ምድረ በዳ አምጥተህ በምድረ በዳ ልትገድለን ማሰብህን ምንም እንዳልሆነ ነገር ቆጥረኸዋል”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ትንሽ ነገር
“በቂ ያልሆነ”ወይም “ጠቃሚ ያልሆነ”

ወተትና ማር ወደምታፈስስ ምድር
ምድሪቱ ለከብቶችና ለዕፅዋት ተስማሚ መሆኗን ለመግለፅ ከእነዚያ እንስሳት የሚገኘው ወተትና ማር ልክ በምድሪቱ ላይ እንደሚፈስስ ነገር አድርገው ይገልፁታል።።ይህንን ሐረግ በኦሪት ዘኁልቁ 14:8 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።።“ከብቶችን ለማርባትና እህልን ለማብቀል እጅግ የያመች ሥፍራ ነው”ወይም “እጅግ ለም የሆነ መሬት ነው”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውንና ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ልትገድለን
ሰዎቹ ነገሩን አጋንነው የሚናገሩት ከአነርሱ ውስጥ አንድ ሰው ቢሞት ሙሴን ተጠያቂ ለማድረግ በማሰብ ነው።።(የተጋነነ ንፅፅር እና አጠቃላይነት የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ርስት
እግዚአብሔር ለዘላለም የሚሰጣቸውን ነገር በውርስ እንደሚያገኙት ነገር አድርገው ነው የሚናገሩት።።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በባዶ ተስፋ ዓይኖቻችንን ታሳውራለህን?
ሰዎቹ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቁት ሙሴን ለመቃወም ነው።ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በባዶ ተስፋ ልታሳውረን ትፈልጋለህ”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ልታሳውረን
ሰዎችን ማታለል ሰዎችን እንደ ማሳወር ተደርጎ ተገልጿል።“ልታታልለን”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በባዶ ተስፋ
ተስፋ የተሰጣቸው ነገሮች ያለመከናወናቸውን ለመግለፅ ባዶ ከሆነ ዕቃ ማስቀመጫ ጋር ያነፃፅሩታል።“የማትፈፅማቸው የተስፋ ቃሎችህ”ወይም “እነዚህ ነገሮች ይደረጋሉ እያልክ የማታከናውናቸው”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 16:15

ከእነርሱ አንድ አህያ ስንኳ አልወሰድኩም
እዚህ ላይ አንድ “አህያ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው አንድ ሰው ከሌላ ሰው ሊወስድ የሚችለውን ነገር ነው።“ከእነርሱ አንዲት ነገር አልወሰድኩም።አንድ አህያ እንኳን”(ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)

ጥና
ዕጣንን ለማጤስ የሚያገለግል ዕቃ።

Numbers 16:20

አጠፋቸው ዘንድ
እነርሱን ማጥፋት ልክ እግዚአብሔር እንደሚበላቸው ዓይነት ተደርጎ ነው የተገለፀው።“አጠፋቸው ዘንድ”ወይም “አጠፋቸዋለሁ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በግምባር መውደቅ
ይሄ የሚያሣየው ሙሴና አሮን በእግዚአብሔር ፊት ራሣቸውን ማዋረዳቸውን ነው።(ተምሣሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ሁሉ ነፍስ አምላክ
እዚህ ላይ “ነፍስ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ለመኖር ብቁ መሆንን ነው።“ለሰው ሁሉ ሕይወትን የሚሰጠው እግዚአብሔር” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ሰው ኃጢአት ቢሰራ በማህበሩ ሁሉ ትቆጣለህን?
ሙሴና አሮን ይህን ጥያቄ የሚጠይቁት ስለ ሕዝቡ ልመናን ለማቅረብ ብለው ነው።ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“አንድ ሰው ኃጢአትን በመሥራቱ እባክህን በማህበሩ ሁሉ ላይ አትቆጣ”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 16:25

ትጠፋላችሁ
መጥፋታቸው ልክ አንደ ምግብ እንደሚበሉ ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል።“ትጠፋላችሁ” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በኃጢአታቸውም ትጠፋላችሁ
ከኃጢአታቸው የተነሣ መጥፋታቸው ልክ ኃጢአት እንደሚያጠፋቸው ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል።“በኃጢአታቸውም ትጠፋላችሁ” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በኃጢአታቸውም ትጠፋላችሁ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የሰራችኋቸው ኃጢአቶቻችሁ ሁሉ ያጠፏችኋል”ወይም “ከኃጢአቶቸቻው ሁሉ የተነሣ እግዚአብሔር ያጠፋችኋል” (ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 16:28

በዚህ ታውቃላችሁ
እዚህ ላይ “በዚህ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሙሴ ቀጥሎ የሚናገረውን ነገር በሚመለከት ነው።

ምድር አፍዋን ከፍታ ትውጣቸዋለች
ሙሴ እዚህ ላይ የሚናገረው ልክ ምድር ሕይወት እንዳለው ነገር ሆኖ እነዚህ ሰዎች የሚወድቁበት የተከፈተ ጉድጓድ ደግሞ ሊበላቸው እንደተዘጋጀ ሠፊ አፍ አስመስሎ ነው።“ከበታቻቸው ያለው መሬት ተሰነጠቀ፤ምድርም አፍዋን ከፍታ ዋጠቻቸው”(ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 16:31

ምድርም አፍዋን ከፍታ ዋጠቻቸው
ሙሴ እዚህ ላይ የሚናገረው ልክ ምድር ሕይወት እንዳለው ነገር ሆኖ እነዚህ ሰዎች የሚወድቁበት የተከፈተው ጉድጓድ ደግሞ የምድርን አፍ አስመስሎ ነው።“ከበታቻቸው ያለው መሬት እንደ ሠፊ አፍ ተከፍቶ በዚያ ወደቁና በእርሱ ውስጥ ተቀበሩ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 16:33

ወደ ሲኦል ወረዱ
በኦሪት ዘኁልቁ 16:30 ላይ ተመሳሳይ የሆነ ሐረግ ይገኛል።እዚያ ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

እነርሱ ተደነቁ
“እነርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው “እሥራኤላውያንን ሁሉ”ነው።

ምድሪቱ እኛንም እንዳትውጠን
ሰዎቹ የሚናገሩት ልክ ምድር ሕይወት እንዳላት ነገር አድርገው ነው።“ምናልባት መሬት ተከፍታ እኛንም ልትውጠን ትችላለች”ወይም “ምድር እንደገና የምትከፈት ከሆነ እኛም እዚያ ውስጥ ወድቀን ልንቀበር እንችላለን” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እሳትም ከእግዚአብሔር ዘንድ ወጥታ ሁለት መቶ ሃምሳ ሰዎች በላች
በእሣት መጥፋታቸው ልክ በእሣት እንደተበሉ ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል። “እሳትም ከእግዚአብሔር ዘንድ ወጥቶ 250 ሰዎች አጠፋ” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

250 ሰዎች
“ሁለት መቶ ሃምሳ ሰዎች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 16:36

ከእሳቱ ውስጥ
ይሄ 250 ሰዎች ያቃጠለውን እሳት የሚያመለክት ነው።

ሕይወታቸውን ያጡት ሰዎች
ሕይወት ማጣት የሚያመለክተው መሞታቸውን ነው።“የሞቱት ሰዎች”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እነርሱ የተሰሩ ይሁኑ
“እነርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጥናዎቹን ነው።ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል። “ካህኑ አልዓዛር ይጠፍጥፋቸው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ የተቀደሱ ናቸው...እነርሱ ምልክት ይሆናሉ
“እነርሱ”እና“እነርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጥናዎቹን ነው።

Numbers 16:39

የተቃጠሉት ሰዎች ያቀረቧቸውን
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የተቀቃጠሉት ሰዎች የተጠቀሙባቸውን”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

በቆሬና በወገኑ
እንደ እነርሱ እንዴት ሊሆኑ እንደሚችሉ የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“ቆሬና ወገኑ እንደሞቱ መሞት”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 16:41

እንዲህም ሆነ
ይሄ ሐረግ ጥቅም ላይ እንዲውል የተደረገው በታሪኩ ውስጥ ጠቃሚ ክስተት መኖሩን ለማመልከት ነው።

በሙሴና በአሮን ላይ አጉረመረሙ
“በሙሴና በአሮን ላይ ለማጉረምረም ተሰባሰቡ”

እነሆም ከደመናው
“በድንገት ደመናው” እዚህ ላይ“እነሆም”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በተመለከቱት ነገር ሰዎቹ መደነቃቸውን ነው።

Numbers 16:44

አጠፋቸው ዘንድ
እግዚአብሔር እነርሱን የማጥፋቱን ነገር እንደሚበላቸው ዓይነት ተደርጎ ነው የተገለፀው።“አጠፋቸው ዘንድ”ወይም “አጠፋቸዋለሁ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በግምባራቸው ወደቁ
ይሄ የሚያመለክተው ሙሴና አሮን በእግዚአብሔር ፊት ራሣቸውን ማዋረዳቸውን ነው።(ተምሣሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ከእግዚአብሔር ፊት ቁጣ ወጥቶአልና
ቁጣ ከእግዚአብሔር ዘንደ ወጥቶአል የሚለው ቃል የሚያሣየው እግዚአብሔር መቆጣቱን ነው።“እግዚአብሔር መቆጣቱን እያሳየ ነው” ወይም “እግዚአብሔር በጣም ከመቆጣቱ የተነሣ ቁጣውን ወደ ተግባር እየለወጠው ነው”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 16:47

ዕጣንም ጨመረ
ዕጣኑን በጥናው ላይ ማድረጉ የሚያመለክተው ማቃጠሉን ነው።“ዕጣኑን አቃጠለው”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

መቅሰፍቱም ተከለከለ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“መቅሠፍቱ መስፋፋቱን አቆመ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 16:49

በቁጥር **14,700**
“በቁጥር አሥራ አራት ሺህ ሰባት መቶ”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 17

1 ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ **2** ”ለእስራኤል ሰዎች ተናገራቸው። ከእነርሱ በትሮችን ውሰድ፣ ከየነገዱ አባቶች አንድ በትር ውሰድ። ከእያንዱ መሪ አንድ በአጠቃላይ ከየነገድ የተመረጡ አስራ ሁለት በትሮችን ውሰድ። የእያንዳንዱን ሰው ስም በበትሩ ላይ ጻፍ። **3** የአሮንን ስም በሌዊ በትር ላይ ጻፍ። ለእያንዳንዱ መሪ ከየአባቶቹ ነገድ አንድ በትር ሊኖር ያስፈልጋል። **4** በትሮቹን ከአንተ ጋር በምገናኝበት በመገናኛው ድንኳን ከምስክሩ ኪዳን ፊት አስቀምጣቸው። **5** እንዲህ ይሆናል፣ እኔ የምመርጠው ሰው በትር ታቆጠቁጣለች። የእስራኤል ሰዎች በአንተ ላይ የሚያደርጉትን ማጉረምረማቸውን እንዲያቆሙ አደርጋለሁ።” **6** ሙሴ ለእስራኤል ሰዎች ተናገረ። ሁሉም የነገዱ መሪዎች በትሮቻቸውን ሰጡት፣ ከእያንዳንዱ መሪ አንድ በትር፣ ከየነገዱ አባቶች ተመረጠ፣ በአጠቃላይ አስራ ሁለት በትሮች ተመረጡ። የአሮን በትር ከእነዚህ መሀል ነበር። **7** ከዚያ ሙሴ እነዚህን በትሮች ወስዶ በያህዌ ፊት በምስክሩ ድንኳን ውስጥ አስቀመጣቸው። **8** በማግስቱ ሙሴ ወደ ምስክሩ ድንኳን ሄደ፣ እናም የሌዊ ነገድ የሆነችው የአሮን በትር አቆጥቁጣ አየ። እምቡጥ አብቅላ፣ አበባና ለውዝም አፍርታ ነበር! **9** ሙሴ በትሮቹን ሁሉ ከያህዌ ፊት ወደ እስራኤል ሰዎች ሁሉ አመጣቸው። እያንዳንዱ ሰው የራሱን በትር አግኝቶ ወሰደ። **10** ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ “የአሮንን በትር በምስክሩ ፊት አስቀምጣት። ባመፀት ሰዎች ላይ ለበደላቸው ምልክት ይሆን ዘንድ አስቀምጣት፣ ስለዚህም በእኔ ላይ የሚያሰሙትን ማጉረምረም ፍጻሜ ታደርግለታለህ፤ ይህ ካልሆነ ይሞታሉ።” **11** ሙሴ ልክ ያህዌ እንዳዘዘው አደረገ። **12** የእስራኤል ሰዎች ሙሴን፣ “እኛ ሁላችንም እዚህ መሞታችን ነው፣ ሁላችንም መጥፋታችን ነው! **13** ወደ ያህዌ ማደሪያ ድንኳን የቀረቡ፣ እያንዳንዳቸው ወደዚህ የመጡ ይሞታሉ። ሁላችንም መጥፋት ይኖርብናልን?” አሉት።

Numbers 17:1

አሥራ ሁለት
“12” (ቁጥሮች የሚለውን ይመለክቱ)

Numbers 17:3

የዓረፍተ ነገር ማያያዣ
እግዚአብሔር ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል።

የሌዊ ነገድ
እዚህ ላይ ሌዊ የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሌዊን ነገድ ነው።

ለአባቶቻቸው ቤቶች አለቃ
እዚህ ላይ “አለቃ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው “እያንዳንዱን”መሪ ነው።

የምሥክሩ ድንኳን
“የምሥክሩ ድንኳን”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ምሥክሩየተፃፉበት ሠሌዳ የሚቀመጥበትን ሣጥን ነው።“የምሥክሩ ድንኳን”ወይም “ምሥክሩን የሚይዘው ሣጥን”(ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)

የመረጥኩት ሰው በትር ታቆጠቁጣለች
“በመረጥኩት ሰው በትር ላይ የለመለመ ነገር ይወጣል”

በአንተ ላይ የሚናገሩትን የእሥራኤልን ልጆች ማጉረምረም አስቁም
እዚህ ላይ “ማጉረምረም”የሚለው አሕፅሮተ ሥም ሲሆን በግሥ መልክ ለገለፅ ይችላል። “የእሥራኤል ሕዝብ በአንተ ላይ ከማጉረምረም እንዲታቀቡ አድርጋቸው”(አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 17:6

እያንዳንዱ አለቃ ከየአባቶቹ ቤት የተመረጠ
ይሄ በድርጊት መልክ ለገለፅ ይችላል።“ከእያንዳንዱ ነገድ ሙሴ የመረጠው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

የምሥክሩ ድንኳን
“የምሥክሩ ድንኳን”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ምሥክሩ የተፃፉበት ሠሌዳ የሚቀመጥበትን ሣጥን ነው።“የምሥክሩ ድንኳን”ወይም “ምሥክሩን የሚይዘው ሣጥን”(ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 17:8

እንዲህም ሆነ
“እንዲህም ሆነ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው አንድ ልዩ የሆነ ነገር መከናወኑን ነው።በእናንተ ቋንቋ ተመሳሳይ የሆነ አገላለፅሊኖራችሁ ይችል ይሆናል።

Numbers 17:10

የምሥክሩ ድንኳን
“የምሥክሩ ድንኳን”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ምሥክሩ የተፃፉበት ሠሌዳ የሚቀመጥበትን ሣጥን ነው።“የምሥክሩ ድንኳን”ወይም “ምሥክሩን የሚይዘው ሣጥን”(ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)

በአንተ ላይ የሚናገሩትን የእሥራኤልን ልጆች ማጉረምረም አስቁም
እዚህ ላይ “ማጉረምረም”የሚለው አሕፅሮተ ሥም ሲሆን በግሥ መልክ ለገለፅ ይችላል። “የእሥራኤል ሕዝብ በአንተ ላይ ከማጉረምረም እንዲታቀቡ አድርጋቸው”(አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

አለበለዚያ ይሞታሉ
በማጉረምረማቸው የሚቀጥሉ ከሆነ የሚከሰተው ነገር ይሄ ነው። እግዚአብሔር ይሄ እንዳይሆን ነበር የሚሻው።“እንዳይሞቱ”(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 17:12

እንሞታለን፤ሁላችን እንጠፋለን
በመሠረቱ እነዚህ ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ተቀናጅተው የቀረቡበት ምክኒያት ለጉዳዩ አፅንኦት ለመስጠት ተፈልጎ ነው።(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 18

1 “ያህዌ አሮንን እንዲህ አለው፣ “አንተ፣ ወንዶች ልጆችህና የአባትህ ቤቶች በቤተ መቅደሱ ላይ ለሚሰራው በደል ተጠያቂ ትሆናላች። በክህነቱ ላይ ለሚፈፀሙ
በደሎች ሁሉ ግን አንተና ከአንተ ጋር ያሉ ወንዶች ልጆች ብቻ ተጠያቂ ትሆናላችሁ። 2 ከአባትህ ነገድ የሆኑት ሌዋዊያንን በሚመለከት ከአንተ ጋር ይሆኑና አንተና
ልጆችህ በምስክሩ ድንኳን ፊት ስታገለግሉ እንዲረዷችሁ አምጣቸው። 3 እነርሱ አንተንና መላውን ድንኳን ያገልግሉ። ሆኖም፣ ወደ ተቀደሰው ስፍራ ማናቸውም
ነገሮች አይቅረቡ ወይም ከመሰዊያው ጋር አይነካኩ፣ አለበለዚያ እነርሱና አንተም ጭምር ትሞታላችሁ። 4 እነርሱ ከአንተ ጋር ሆነው ለመገናኛው ድንኳንና
ከድንኳኑ ጋር ለተያያዙ ስራዎች ሁሉ እንክብካቤ ማድረግ አለባቸው። መጻተኛው ወደ አንተ አይጠጋ። 5 አንተ ለተቀደሰው ስፍራና ለመሰዊያው ሀላፊነት መውሰድ
አለብህ፣ እንደገና ቁጣዬ በእስራኤል ሰዎች ላይ እንዳይመጣ ይህን አድርግ። 6 ከእስራኤል ትውልዶች መሀል ሌዋውያንን የመረጥኩት እኔ ራሴ ነኝ። እነርሱ
ከመገናኛው ድንኳን ጋር የተያያዙ ሥራዎችን ለመስራት ለእኔ የተሰጡ ለእናንተ ስጦታዎች ናቸው። 7 ከመሰዊያውና በመጋረጃው ውስጥ ያሉትን አገልግሎቶች
ሁሉ በሚመለከት ግን የክህነቱን ስራ የምትሰሩት አንተና ወንዶች ልጆችህ ብቻ ናችሁ። አንተ ራስህ እነዚያን ሀላፊነቶች መወጣት አለብህ። እኔ ክህነቱን ስጦታ
አድርጌ ሰጥቼሃለሁ። ማናቸውም መጻተኛ ወደዚህ ቢጠጋ ይገደል።” 8 ከዚያ ያህዌ አሮንን እንዲህ አለው፣ “ለእኔ የሚወዘወዙትን መስዋዕቶችና የእስራኤል
ሰዎች ለእኔ የሰጧቸውን ቅዱስ መስዋዕቶች አያያዝ ሀላፊነቶች ሰጥቼሃለሁ። እነዚህን ስጦታዎች ቀጣይ ድርሻህ አድርጌ ለአንተና ለወንዶች ልጆችህ
ሰጥቻለሁ። 9 ለያህዌ ሙሉ ለሙሉ ከተለዩ ከእነዚህ ስጦታዎች ውስጥ ሙሉ ለሙሉ የማይቃጠሉት የአንተ ናቸው። ህዝቡ የሚያመጣው ማናቸውም
መስዋዕት፣ የእህል ቁርባኑን፣ የኃጢአት መስዋዕቱን፣ እና የበደል መስዋዕቱን ሁሉ ጨምሮ፣ እነዚህ እጅግ ቅዱስ የሆኑ ለእኔ የሚለይዋቸውና የሚያመጧቸው
ስጦታዎች የአንተና የወንዶች ልጆችህ ይሆናሉ። 10 አንተ የምትመገባቸው እነዚህ ስጦታዎች፣ ሙሉ ለሙሉ ለእኔ የተለዩ ናቸው። በመሀል የሚገኝ ማናቸውም
ወንድ እነዚህን ስጦዎች ይብላ። እነርሱ በእናንተ ዘንድ ለእኔ የተለዩ ተደርገው ይቆጠሩ። 11 እነዚህ የእናንተ ስጦታዎች ናቸው። ከእስራኤል ሰዎች ከሚሰበሰቡ
መስዋዕቶች ውስጥ የተለዩት ስጦታዎቻቸው ሁሉ፣ በእኔ ፊት የተወዘወዙና ለእኔ የቀረቡ ስጦዎች ሁሉ የእናንተ ናቸው። እነዚህን ለእናንተ፣ ለወንዶች ልጆቻችሁ፣
እና ለሴቶች ልጆቻችሁ፣ ቀጣይ ድርሻችሁ አድርጌ ሰጥቻለሁ። እያንዳንዱ በቤተሰብህ ውስጥ የመንጻት ሥርዓት የፈፀመ ሁሉ ከእነዚህ ስጦታዎች መመገብ
ይቻላል። 12 ከዘይቱ ምርጥ የሆነውን፣ ከአዲሱ ወይንና ሰብል ምርጡን፣ ህዝቡ ለእኔ ካቀረበው በኩራቱን፣ እነዚህን ሁሉ ለእናንተ ሰጥቻለሁ። 13 ለእኔ
የሚያመጡት፣ በምድራቸው ካለው በመጀመሪያ የደረሰው ፍሬ ሁሉ የአንተ ነው። በቤተሰብህ ውስጥ ያለ ንጹህ የሆነ ሁሉ እነዚህን ነገሮች መብላት ይችላል። 14
በእስራኤል ማናቸው ፈጽሞ የተሰጠ ነገር የአንተ ይሆናል። 15 እያንዳንዱ ማህጸን የሚከፍት ሁሉ፣ ሰዎች ለያህዌ የሰጡት በኩር ሁሉ፣ የሰውም ይሁን የእንስሳ
በኩር የአንተ ይሆናል። የሆነ ሆኖ፣ ሰዎቹ መጀመሪያ የተወለደውን ሁሉ መልሰው ይግዙ፣ ንጹህ ያልሆኑ እንስሳትን በኩራት መልሰው ይግዙ። 16 በሰዎች
ተመልሰው የሚገዙ አንድ ወር ከሞላቸው በኋላ መልሰው ይገዙ። ከዚያ ሰዎቹ በመቅደሱ ሰቅል ዋጋ መልሰው ከሀያ ጌራ ጋር እኩል ዋጋ ባለው በአምስት
ሰቅሎች ዋጋ ሊገዟቸው ይችላሉ። 17 ነገር ግን የላም በኩር፣ ወይም የበግ በኩር፣ ወይም የፍየል በኩር ከሆነ እነዚህን እንስሳት መልሰህ አትግዛ፤ እነዚህ ለእኔ
የተሰዉ ናቸው። ለእኔ ጣፋጭ መዓዛ ለማቅረብ፣ ደማቸውን በመሰዊያ ላይ እርጨው፣ ስባቸውን በእሳት የቀረበ መስዋዕት አድርገህ ኣቃጥለው። 18 ስጋቸው
ለአንተ ይሁን። ልክ እንደ ሚወዘወዘው ፍርምባና እንደ ቀኙ ወርች ስጋቸው የአንተ ይሆናል። 19 የእስራኤል ሰዎች ለእኔ ያቀረቧቸውን ቅዱስ የሆኑ መስዋዕቶች
ሁሉ እኔ፤ ለአንተ፣ ለወንድ ልጆችህ እና ለሴት ልጆችህ ቀጣይ ድርሻ አድርጌ ሰጥቻችኋለሁ። ለጨው ኪዳንና ለዘለዓም የአንድነት መስዋዕት ሆነው በፊቴ
ከአንተና ከትውልድህ ጋር ይኖራሉ።” 20 ያህዌ አሮንን እንዲህ አለው፣ “አንተ በህዝቡ ምድር ርስት አይኖርህም፣ ወይንም ደግሞ በህዝቡ መሀል የሀብት ድርሻ
አይኖርህም። በእስራኤል ህዝብ መሀል እኔ ድርሻህና ርስትህ ነኝ። 21 እስራኤላዊያን የሚያመጡትን አስራት ሁሉ፣ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ለሚሰጡት
አገልግሎት ድርሻቸው አድርጌ ለሌዊ ትውልድ ሰጥቻቸዋለሁ። 22 ከአሁን አንስቶ ከእስራኤል ህዝቡ ወደ መገናኛው ድንኳን አይቅረብ፣ ከቀረቡ በኃጢአታቸው
ሀላፊነትን ይወስዳሉ፤ እናም ይሞታሉ። 23 ከመገናኛው ድንኳን ጋር የተያያዙ ሥራዎችን ሌዋውያን ይስሩ። ይህን በሚመለከት ለማናቸውም ኃጢአት ተጠያቂ
ይሆናሉ። ይህ በእናተ ህዝብ ትውልዶች ሁሉ ቀዋሚ ህግ ይሆናል። በእስራኤል ህዝብ መሀል ሌዋውያን ርስት ሊኖቸው አይገባም። 24 እስራኤላዊያን መባ
አድርገው ለእኔ ያቀረቡትን አስራት እኔ ለሌዋውያን ርስታቸው አድርጌ የሰጠሁት እነዚህን ነው። ለዚህም ነው እንዲህ የምላቸው፣ ‘እነርሱ በእስራኤል ህዝብ
መሀል ርስት አይኖራቸውም።’” 25 ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ 26 ”ለሌዋውያን እንዲህ በላቸው፣ ‘ከእነርሱ የአንተ ርስት አድርጎ ያህዌ ለእናንተ የሰጣችሁን
አስራት ከእስራኤል ሰዎች ስትቀበሉ፣ ከዚያ አስራት ለእርሱ አንድ አስረኛውን መባ አድርጋችሁ ታቀርባላችሁ። 27 እናንተ የምታቀርቡት መስዋዕት በእናንተ ዘንድ
ከአውድማ እንደ ቀረበ የእህል አስራት ወይም ከወይን መጥመቂያ እንደ ቀረበ አስራት ሊቆጠር ይገባዋል። 28 እንደዚሁም ከእስራኤል ሰዎች ከተቀበላችሁት
አስራት ሁሉ ለያህዌ መባ ማቅረብ አለባችሁ። ከእነዚህም ለካህኑ ለአሮን ለእግዚአብሔር ከቀረበው ስጦታ መስጠት አለባች። 29 ከተቀበላችሁት ስጦታ ሁሉ፣
ከእያንዳንዱ ለያህዌ መባ መስጠት አለባችሁ። ይህንን ምርጥ ከሆነው ሁሉና ለእናንተ ከሰጠኋችሁ እጅግ ከተቀደሱት ነገሮች ማድረግ አለባችሁ።’ 30
ስለዚህም እንደዚህ በላቸው፣ ‘ከተቀበላችሁት ምርጡን ስታቀርቡ፣ ይህ በሌዋውያን ዘንድ ከአውድማ እንደቀረበ ምርትና ከወይን መጥመቂያ እንደቀረበ ሊቆጠር
ይገባል። 31 የተቀረውን ስጦታዎቻችሁን በማንኛውም ስፍራ ልትበሉ ትችላላችሁ፣ እናንተና ቤተሰቦቻችሁ ብሉት፣ ምክንያቱም በመገናኛው ድንኳን ለምትሰጡት
አገልግሎት ክፍያችሁ ነው። 32 ከተቀበላችሁት ምርጥ የሆነውን ለያህዌ ካቀረባችሁ፣ ያን በመብላታችሁና በመጠጣታችሁ ምንም አይት በደል በራሳችሁ ላይ
አታመጡም። ነገር ግን የተቀደሱ የእስራኤል ህዝቦች ስጦታዎች አታቃሉ፣ አሊያ ትሞታላች።

Numbers 18:1

በመቅደሱ ላይ የተሰራ ኃጢአት ሁሉ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ማንኛውም ሰው በመቅደሱ ላይ የሚሰራው ኃጢአት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

በማንኛውም ሰው በክህነት አገልግሎቱ ላይ የሚሰሩ ኃጢአቶች ሁሉ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ማንኛውም ሰው በክህነት አገልግሎቱ ላይ የሚሰራው ኃጢአት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

በክህነት አገልግሎት ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ሰው
“ማንኛውም ካህን”

Numbers 18:3

የዓረፍተ ነገር ማያያዣ
እግዚአብሔር ለአሮን መናገሩን ይቀጥላል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አንተን ማገልገል ይኖርባቸዋል..እነርሱበአንድነት ይሁኑ
“እነርሱ”የሚለው ቃል የሌዊ ነገድ አባላትን የሚያመለክት ሲሆን “አንተ”የሚለው ቃል ደግሞ የሚያመለክተው አሮንን ነው።(አንተ/እናንተ የሚለው ቃል በተለያየ መንገድ የሚገለፅበት የሚለውን ይመልከቱ)

ወይም አንተና እነርሱ ትሞታላችሁ
እዚህ ላይ “እነርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው“በቤተመቅደሱ ውስጥ ባሉት ሥፍራዎች ሁሉ”የመግባት መብት ያላቸውን ማንኛውንም የሌዊ ነገድ አባላትን ነው።“እነርሱ”የሚለው ቃል የብዙ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተውም አሮንንና በተፈቀደላቸው አገልግሎት ውስጥ የሚገኙትን ሌዋውያንን ነው።“(ተውላጠ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

ሌላ ሰው ወደ እናንተ አይቅረብ።ኃላፊነቱን መውሰድ ይኖርባችኋል።
እዚህ ላይ “እናንተ”የሚለው ቃል የብዙ ቁጥር በመሆኑ የሚያመለክተው አሮንንና የተቀሩትን ሌዋውያን ነው።(አንተ/እናንተ የሚለው ቃል በተለያየ መንገድ የሚገለፅበት የሚለውን ይመልከቱ)

ቁጣዬ በእሥራኤል ልጆች ላይ እንደገና እንዳይነድባቸው
ለዚህ ፍቺ ሊሆኑ የሚችሉት 1/እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ እጅግ እንደተቆጣ ያመለክታል።2/“በእሥራኤል ሕዝብ ላይ ዳግም በእጅጉ እንዳልቆጣ”2/ይሄ የሚያሣየው ከመቆጣቱ የተነሣ መቅጣቱን ያመለክታል።“የእሥራኤልን ሕዝብ ደግሜ እንዳልቀጣ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 18:6

የዓረፍተ ነገር ማያያዣ
እግዚአብሔር ለአሮን መናገሩን ይቀጥላል።

ለእናንተ ሥጦታ ናቸው
እግዚአብሔር ሌዋውያን አሮንን እንዲያግዙት የመደበበትን ሁኔታ እግዚአብሔር ለአሮን እንደተሰጠ ሥጦታ ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል።“ለአንተ እንደ ሥጦታ ናቸው”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለእኔ የተሰጡ
ለእግዚአብሔር “የተሰጡ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ለማገልገል መለየታቸውን ነው።ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ለራሴ የለየኋቸውን”ወይም“ለራሴ ለይቼያቸዋለሁ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውንና ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተና የአንተ ልጆችህ ብቻ
እዚህ ላይ“አንተ”እና “የአንተ”የሚሉት ቃላት የነጠላ ቁጥር በመሆናቸው የሚያመለክቱት አሮንን ነው።በሌሎች ሥፍራዎች ላይ “እናንተ”እና“የእናንተ”የሚሉት የብዙ ቁጥር በመሆናቸው የሚያመለክቱት አሮንንና ልጆቹን ነው።(አንተ/እናንተ የሚለው ቃል በተለያየ መንገድ የሚገለፅበት የሚለውን ይመልከቱ)

ክህነታችሁን ጠብቁ
“የካህናትን ተግባር አከናውኑ”

በመጋረጃው ውስጥ ያለውን ሁሉ
በመጋረጃው ውስጥ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከመጋረጃው ጀርባ የሚገኘውን የውስጥ ክፍል ነው።“ከመጋረጃው ጀርባ ባለው ከፍል ውስጥ የሚገኘውን ነገር ሁሉ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

እንግዳ የሆነ ሰው ቢቀርብ ይገደል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሌላ ሰው ቢቀርብ መገደል ይኖርበታል”ወይም “ሌላ ሰው ከቀረበ መግደል ይኖርባችኋል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ቢቀርብ
ሊቀርቡት የማይገባቸው ነገር ምን እንደሆነ በግልፅ ሊብራራ ይችላል።“ቅዱሱን ሥፍራ የሚቀርብ ሰው”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 18:8

ለእኔ የቀረበው የማንሣት ቁርባን
እዚህ ላይ “ማንሳት”የሚለው ቃል የሚያመለክተው አንድን ነገር ለእግዚአብሔር መሥጠትን ወይም ማቅረብን ነው።ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሰዎች ለእኔ የሚያቀርቧቸውመሥዋዕቶች”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውንና ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህን የማንሣት ቁርባኖች ለአንተ ሰጥቼሃለሁ
እግዚአብሔር ይህንን ውሳኔ ቀድሞ የወሰነ በመሆኑ ጉዳዩን እንደፈፀመው ዓይነት አድርጎ ይናገራል።“እነዚህን የማንሣት ቁርባኖች ለአንተ ሰጥቼሃለሁ”

ለልጆችህ ድርሻ እንዲሆን
ድርሻ ማለት አንድ ሰው የተወሰነውን የአንድ ነገር ክፍል ሲወስድ ማለት ነው።“በማይቋረጥ መልኩ የምትወስዱት ድርሻችሁ”

ከእሣቱ ከተረፈው
“በመሠዊያው ላይ ሙሉ በሙሉ የማታቃጥሉት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 18:10

ማያያዣ ዓረፍተ ነገር
እግዚአብሔር ለአሮን መናገሩን ይቀጥላል

Numbers 18:12

ማያያዣ ዓረፍተ ነገር
እግዚአብሔር ለአሮን መናገሩን ይቀጥላል

የፍሬ መጀመሪያ
ይሄ የሚያመለክተው ጥራት ያላቸውንና የሚያመርቷቸውን ዘይት፤ወይንና እህልን ነው።

በቤትህ ንፁሕ የሆነ ሁሉ
በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ማግኘትን ንፁሕ እንደመሆን አድርጎ አቅርቦታል።“በቤትህ ውስጥ በእኔ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ሰው ሁሉ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 18:14

ማያያዣ ዓረፍተ ነገር
እግዚአብሔር ለአሮን መናገሩን ይቀጥላል

ማሕፀንን የሚከፍት ሁሉ፤በኩራት የሆነ ሁሉ
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው።“ማሕፀንን የሚከፍት ወንድ ሁሉ”(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

ማሕፀንን የሚከፍት ሁሉ
“ማሕፀን መክፈት”የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገርእናት የምትወለደው የመጀመሪያ ወንድ ልጇ ማለት ነው።(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በመጀመሪያ የተወለደውን ሁሉ ሰዎች ሊቤዡት ይገባል
መጀመሪያ የተወለደውን ወንድ ልጆቸውን መሥዋዕት ከማድረግ ይልቅ ለልጆቻቸው ሲሉ ለካህኑ ገንዘብ መክፈል ነበረባቸው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሰዎች ከተተቤዟቸው ከአንድ ወር በኋላ ተመልሰው ሊቤዙ ይገባል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“አንድ ወር ከሞላቸው በኋላ ሰዎች መልሰው ሊቤዟቸው ይገባል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ዳግም ሊቤዙ የሚገባቸው ነገሮች
ይሄ ምናልባት የሚያመለከተው ሰዎችን እንጂ ንፁሕ ያልሆኑ እንስሳትን ለማመልከት አይመስልም።

አምስት ሰቅል ...ሃያ አቦሊ
በዘመናዊ የመለኪያ መንገድ መተቀም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ እነዚህን ተግባራዊ የማድረጊያ መንገዶች እነሆ።“አምስት ብር ቁርጥራጮች....እያንዳንዱ አምስት ግራም ያህል የሚመዝን”ወይም“በቤተመቅደሱ ውስጥ ጥቅም ላይ ባሉት የጥራት ደረጃዎች መሠረት የሚመዝን አምሳ ግራም ብር”(መፅሐፍ ቅዱሣዊመለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

አምስት ሰቅል
ሰቅል የክብደት መለኪያ ነው።የሚመዘነው ነገር ምን እንደሆነ የበለጠ ሊብራራ ይችላል።(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የቤተመቅደስሰቅል
የተለያየ ዓይነት የሰቅል ዓይነቶች ነበሩ።ይሄኛው በመገናኛ ድንኳኑ ውስጥ በሚገኘው የተቀደሰው ሥፍራ ላይ ሰዎች የሚጠቀሙበት ዓይነት ነበር።ሃያ አቦሊ ይመዝን ነበር።ይሄ 11 ግራም ገደማ ይሆናል።(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 18:17

ማያያዣ ዓረፍተ ነገር
እግዚአብሔር ለአሮን መናገሩን ይቀጥላል።

ደማቸውን መርጨት ይኖርብሃል
በመጀመሪያ እንስሣቱን መግደል በተመለከተየበለጠ ሊብራራ ይችላል።“እንስሳቱን ገድለህ ደማቸውን ልትረጭ ይገባሃል” (በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በእሣት የተቃጠለ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በእሣት የምትሰራውን”ወይም“በመሠዊያው ላይ በእሣት የምታቃጥለውን”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእግዚአብሔር ጣፋጭ ሽታ እንዲሆን
እግዚአብሔር በጣፋጭ ሽታ መደሰቱ የሚያመለክተው ቁርባኑን በሚሰዋው ሰው ደስ መሰኘቱን ነው።“እና እግዚአብሔር በአንተ ደስ ይለዋል”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ መወዘወወዝ ፍርምባ እንደ ቀኙም ወርች
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የመወዝወዝ ፍርምባውንና ቀኙን ወርች እንደ መሥዋዕት የምታቀርቡልኝ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 18:19

ማያያዣ ዓረፍተ ነገር
እግዚአብሔር ለአሮን መናገሩን ይቀጥላል።

ለአንተ ሰጥቼሃለሁ
እግዚአብሔር ይህንን ውሳኔ ቀድሞ የወሰነ በመሆኑ ጉዳዩን እንደፈፀመው ዓይነት አድርጎ ይናገራል።“ለአንተ ሰጠሁህ”

ለልጆችህ እንደሚቀጥል ድርሻ
ድርሻ ማለት አንድ ሰው የተወሰነውን የአንድ ነገር ክፍል ሲወስድ ማለት ነው።“በማይቋረጥ መልኩ እንደምትወስዱት ድርሻችሁ”

ከአንተም ጋር ለዘርህ የጨው ቃል ኪዳን ለዘለላም ነው
ሁለቱ ሐረጎች የሚያመለክቱት ተመሳሳይ የሆነ ነገርን ነው።“እነዚህ ሐረጎች በጋራ በመሆን አፅንዖት የሚሰጡት ኪዳኑ ለዘላለም የሚፀና መሆኑን ነው።”“ዘላለማዊ የሆነ ሥምምነት”(ተምሣሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

የዘላለም ጨው ቃል ኪዳን
“በጨው የተደረገ ቃል ኪዳን”ጨው ዘለቂነትን የሚያመለክት ሲሆን በመሥዋዕትና በቃል ኪዳን ወቅት በሚደረጉ ምግቦች ላይ ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረግ ነበር።”ዘላቂነት ያለው ኪዳን”ወይም “ዘላለማዊ ኪዳን”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በምድራቸው ርስት በመካከላቸውም ድርሻ አይሆንልህም
እግዚአብሔር ሌሎች ሰዎች የሚይዙትን ምድር እንደሚወርሱት ዓይነት አድርጎ ይናገራል።“ከሕዝቡ ምድር አንዱንም አትወርሱም” ወይም “እሥራኤላውያን ከሚይዟቸው መሬቶች ውስጥ አንዱንም አትወስዱም”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ድርሻህና ርስትህ ርስት እኔ ነኝ
እግዚአብሔር አሮንና ዘሩ እርሱን በክህነት በማገልገላቸው የሚጠብቃቸውን ታላቅ ክብር ሲገልፅላቸው ልክ እግዚአብሔር ራሱን እንደሚወርሱት አድርጎ ነው የሚናገረው።“በዚያ ምትክ የምኖራችሁ እኔ ነኝ”ወይም“በዚያ ምትክ እንድታገለግሉኝ እፈቅድላችኋለሁ፤በአገልግሎታችሁም ወቅት የሚያስፈልጋችሁን ነገር ሁሉ አዘጋጅላችኋለሁ” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 18:21

ማያያዣ ዓረፍተ ነገር
እግዚአብሔር ለአሮን መናገሩን ይቀጥላል።

ተመልከት ሰጥቼያለሁ
እዚህ ላይ“ተመልከት”የሚለው ቃል የሚቀጥለው ነገር ላይ የበለጠ አፅንኦት እንዲደረግ ያነሳሳል።“በእርግጥ እኔ ሰጥቼያለሁ”

እንደ ርስታቸው
እግዚአብሔር አሮንና ዘሩ የሚቀበሉትን ነገር እንደሚወርሱት ዓይነት አድርጎ ነው የሚናገረው።“ለእሥራኤል ሁሉ የምሰጠውን እንደ ድርሻቸው መጠን”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 18:23

ማያያዣ ዓረፍተ ነገር
እግዚአብሔር ለአሮን መናገሩን ይቀጥላል።

በእሥራኤል ልጆች መካከል ርስት አይወርሱም
እግዚአብሔር ሌሎች የእስራኤል ሰዎች የሚይዙትን ምድር እንደሚወርሱት ዓይነት አድርጎ ይናገራል።ሌዋውያን የትኛውንም ምድር አይቀበሉም”“ሌላው የእሥራኤል ሕዝብ የሚቀበለውን መሬት መቀበል አይኖርባቸውም”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ርስታቸው
እግዚአብሔር አሮንና ዘሩ የሚቀበሉትን ነገር እንደሚወርሱት ዓይነት አድርጎ ነው የሚናገረው።“ለእሥራኤል ሁሉ የምሰጠውን እንደ ድርሻቸው መጠን”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Numbers 18:25

ከእሥራኤል ልጆች ለእናንተ ርስት አድርጌ የሰጠኋችሁን አሥራት በተቀበላችሁ ጊዜ
የእሥራኤል ሕዝብ ከሰብሎቻቸውንና ከእንስሳቶቻቸው አንድ አሥረኛውን በሥጦታ መልክ ማቅረብ የሚጠበቅባቸው ሲሆን እግዚአብሔር ደግሞ ይሄንን ለሌዋውያን ይሰጣቸዋል።

ለእናንተ ርስት ይሆን ዘንድ
የሚወርሱት ነገር ይመስል እግዚአብሔር አሮንና ትውልዱ ስለሚቀበለው ነገር እግዚአብሔር ይናገራል።"ለእሥራኤል ሁሉ ከምሰጠው የእናንተ ድርሻ የሆነው"(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አሥራታችሁን ማቅረብ ይኖርባችኋል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።"አሥራታችሁን ለመሥጠት ማሰብ ይገባችኋል"(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 18:28

ማያያዣ ዓረፍተ ነገር
እግዚአብሔር ሙሴ ለሌዋውያን መናገር የሚኖርበትን ነገር መናገሩን ይቀጥላል።

የእርሱን የማንሣት ቁርባን ለካህኑ ለአሮን ትሰጣላችሁ
እዚህ ላይ"የእርሱ"የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው። በመሠረቱ የእግዚአብሔርን የማንሣት ቁርባንድርሻ መሥጠት የነበረባቸው ለእግዚአብሔር ነው።"ለእግዚአብሔር መሥጠት የሚገባችሁን ቁርባንለአሮን መሥጠት ይኖርባችኋል"

ለአንተ የተሰጠህን
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።"የእሥራኤል ሕዝብ የሰጠህን"(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 18:30

ማያያዣ ዓረፍተ ነገር
እግዚአብሔር ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል።

ከእርሱ የተመረጠውን
"ከእሥራኤል ሕዝብ ምርጥ የሆነውን ነገር የተቀበልከውን"

ሌሎች ሥጦታዎቻችሁ
"ሥጦታዎቹ"እሥራኤላውያን የሚያቀርቧቸው መሥዋዕቶች ሆነው ሌዋውያን የሚቀበሏቸው ነገሮች ናቸው።

በመብላታችሁና በመጠጣታችሁ ምንም ዓይነት ኃጢአት አትሸከሙም
"እርሱን በምትበሉበትና በምትጠጡበት ወቅት በደለኞች አትሆኑም"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 19

1 ያህዌ ለሙሴና ለአሮን ተናገረ፤ እንዲህም አለ፣ 2 ”ይህ እናንተን የማዛችሁ ትዕዛዝ መታሰቢያ ነው። የእስራኤል ሰዎች ወደ አንተ ቀንበር ተጭኗት የማታውቅ፣ እንከን ወይም ነውር የሌለባት ቀይ ጊደር እንዲያመጡ ንገራቸው። 3 ጊደሯን ለካህኑ ለአልዓዛር ስጠው። ከሰፈር ውጭ ያውጣት አንድ ሰው በፊቱ ይረዳት። 4 ካህኑ አልአዛር ከጊደሯ ደም በጣቱ ወስዶ በመገናኛው ድንኳን ፊት ባለው አቅጣጫ ሰባት ጊዜ ይርጨው። 5 ሌላ ካህን እርሱ እያየ ጊደሯን ያቃጥላት። ቆዳዋን፣ ስጋ እና ደሟን ከፈርሷ ጋር ያቃጥል። 6 ካህኑ የዝግባ እንጨት፣ ሂሶጵ፣ እና ደማቅ ሱፍ ይውሰድና ጊደሯ በምትቃጠልበት እሳት ውስጥ ይጨምር። 7 ከዚያ ልብሱን ይጠብ ሰውነቱንም በውሃ ይታጠብ። ከዚያ እስከ ምሽት እርኩስ ሆኖ ከቆየበት ወደ ሰፈር መመለስ ይችላል። 8 ጊደሯን ያቃጠለው ሰው ልብሱን በውሃ ይጠብ ገላውንም ይታጠብ። እስከ ምሽት እርኩስ ሆኖ ይቆያል። 9 ንጹህ የሆነ አንድ ሰው የጊደሯን አመድ አፍሶ ከሰፈር ውጭ ንጹህ በሆነ ስፍራ ይድፋው። ይህ አመድ ለእስራኤል ሰዎች ለማህበረሰቡ ይጠበቅ። አመዱ ከኃጢአት መስዋዕት የተገኘ እንደመሆኑ፣ ከኃጢአት ለመንጻት በውሃ ይበጠብጡታል። 10 የጊደሯን አመድ ያፈሰው ሰው ልብሱን ይጠብ። እስከ ምሽት እርኩስ ሆኖ ይቆያል። ይህ ለእስራኤላዊያንና ከእነርሱ ጋር ለሚኖሩ መጻተኞችም ቋሚ ህግ ይሆናል። 11 ማንም የሞተን ሰው አካል የነካ ሁሉ ለሰባት ቀናት እርኩስ ነው። 12 እንዲህ ያለው ሰው በሶስተኛውና በሰባተኛው ቀን ራሱን ያንጻ። ከዚያ ንጹህ ይናል። ነገር ግን በሶስተኛው ቀን ራሱን ካላነጻ፣ በሰባተኛው ቀን ንጹህ አይሆንም። 13 የሞተን ሰው የነካ ማንም ቢሆን፣ የሞተን ሰው የነካ ሁሉ፣ እናም ራሱን ያላነጻ ይህ ሰው የያህዌን ማደሪያ ያረክሳል። ያ ሰው ከእስራኤል ተለይቶ ይጥፋ፤ ምክንያቱም ከእርኩሰት የሚያነጻው ውሃ አልተረጨበትም። እርኩስ ሆኖ ይቆያል፣ ያለመንጻቱ በእርሱ ላይ ይቆያል። 14 አንድ ሰው በድንኳን ውስጥ በሚሞትበት ጊዜ ህጉ ይህ ነው። ወደ ድንኳኑ የገባ እያንዳንዱ ሰውና ቀድሞውኑም በድንኳኑ ውስጥ የነበረ ሰው ለሰባት ቀናት ንጹህ አይደለም። 15 ያልተከደነና ያልተሸፈነ ማናቸውም ዕቃ ይረክሳል። 16 በተመሳሳይ፣ በሰይፍ የተገደለንም ሰው ሆነ ማናቸውንም በሌላ ሁኔታ የሞተን ሰው፣ ወይም የሞተን ሰው አጽም፣ ወይም መቃብር የነካ ማናቸውም ከድንኳን ውጭ ያለ ሰው ለሰባት ቀናት ንጹህ አደለም። 17 ለረከሰ ሰው ይህን አድርግ፡ ከተቃጠለው የኃጢአት መስዋዕት ጥቂት አመድ ውሰድና በንጹህ ውሃ በዕቃ ውስጥ በጥብጠው። 18 ንጹህ የሆነ ሰው ሂሶጵ ይውሰድና ውሃው ውስጥ ይንከረው፤ ከዚያም በድንኳኑ ላይ፣ በድንኳኑ ውስጥ ባሉ ዕቃዎች ሁሉ ላይ፣ በዚያ በሚገኙ ሰዎች ላይ፣ እንዲሁም የሞተ ሰውን አጽም፣ የተገደለን ሰው፣ የሞተን ሰው ወይም መቃብር በነካ ሰው ላይ ይርጨው። 19 በሶስተኛው ቀንና በሰባተኛው ቀን፣ ንጹህ የሆነው ሰው ንጹህ ያልሆነውን ሰው ይርጨው። ያልነጻው ሰው በሰባተኛው ቀን ራሱን ያንጻ። ልብሱን ይጠብ ገላውንም በውሃ ይታጠብ። ምሽት ላይ ንጹህ ይሆናል። 20 ነገር ግን ሳይነጻ የሚቆይ ማናቸው ሰው፣ ራሱን ለማንጻት ያልፈቀደ ሰው ያ ሰው ከማህበረሰቡ ተለይቶ ይጥፋ፣ ምክንቱም የያህዌን መቅደስ አርክሷል። ከእርኩሰት የሚያነጻው ውሃ በእርሱ ላይ አልተረጨምና እርኩስ ሆኖ ይቆያል። 21 ለእነዚህ ሁኔታዎች ይህ ቀጣይ ህግ ይሆናል። ለመንጻት የሚሆንን ውሃ የሚረጨው ሰው ልብሶቹን ይጠብ። የሚያነጻውን ውሃ የሚነካ ሰው እስከ ምሽት ንጹህ አይደለም። 22 ማናቸውም ንጹህ ያልሆነ ሰው የነካው ነገር እርኩስ ይሆናል። ያንን የነካ ሰው እስከ ምሽት እርኩስ ይሆናል።”

Numbers 19:1

ሥርዓት/ደንብ
በመሠረቱ እነዚህ ቃላት ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው።“የሕግ ትዕዛዝ”ወይም “ሕጋዊነት ያለው ደንብ” (ሁለት ተመሳሳይ ገፅታ ያላቸው ነገሮች የሚለውን ይመልክቱ)

ለአንተ ያመጡልህ ዘንድ
እዚህ ላይ“ለአንተ”የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር በመሆኑ የሚያመለክተው ሙሴን ነው።

ቀንበር ያልተጫነች ወይም ነውርም የሌለባትን
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሣሣይ ዓይነት ትርጓሜ ያላቸው ሲሆኑ የሚያሳስበውም እንስሳው ምንም ዓይነት እንከን የማይገኝበት መሆን እንዳለበት አፅንኦት ለመሥጠት ነው።(ሁለት ተመሳሳይ ገፅታ ያላቸው የሚለውን ይመልክቱ)

Numbers 19:3

በእርሱ ፊት
“በእርሱ እይታ ሥር”ወይም“ይመለከተው ዘንድ”

ካህኑ የዝግባ እንጨት መውሰድ ይኖርበታል
“ካህኑ የሚለው ቃል የሚያመለክተው አልዓዛርን ነው።

ቀይ ግምጃ
“ደማቅ ቀይ ልብስ”

Numbers 19:7

ከዚያ በኋላ እርሱ ልብሱን ማጠብ ይኖርበታል
እዚህ ላይ“እርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው አልዓዛርን ነው።

ርኩስ ይሆናል
በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን አለማግኘት ወይም የተቀደሱ አገልግሎቶችን ለማከናወን ብቁ ያለመሆን ጉዳይ ሰውዬው ንፁሕ እንዳልሆነ ተደርጎ ነው የሚነገረው።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 19:9

ንፁሕ የሆነ ሰው
በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ማግኘትናወይም የተቀደሱ አገልግሎቶችን ለማከናወን ብቁ የመሆን ጉዳይ ሰውዬው ንፁሕ እንደሆነ ተደርጎ ነው የሚነገረው።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አመዱ መከማቸት ይኖርበታል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“አመዶቹ መከማቸት ይኖርባቸዋል።”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

በንፁሕ ሥፍራ ላይ
በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ማግኘት ንፁሕ እንደመሆን ተደርጎ ነው የሚነገረው።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ርኩስ ይሆናል
በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን አለማግኘት ወይም የተቀደሱ አገልግሎቶችን ለማከናወን ብቁ ያለመሆን ጉዳይ ሰውዬው ንፁሕ እንዳልሆነ ተደርጎ ነው የሚነገረው።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Numbers 19:11

አጠቃላይ መረጃ
“ንፁሕ መሆን”እና “መቀደስ” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ማግኘትን ነው።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ
“ንፁሕ ያልሆነ”“መርከስ”“ቅድሰና ማጣት” እና “በኃጢአት መበከል”የሚሉት ሃሣቦች የሚያመለክቱት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አለማግኘትን ነው።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሞተውን ሰው በድን
“የማንኛውም ሰው ሬሣ”

ራሱን ያጠራል
ይሄ ሰው አንድ ንፁሕ የሆነ ሰው ይጠራና ከውኃ ጋር የተደባለቀ የጊደር አመድ በመርጨት እንዲያጠራው ይጋብዘዋል።አንድን ሰው እንዲያጠራው በመጥራቱ ልክ ያ ሰው ራሱ እንደሚያጠራው ዓይነት ተደርጎ ነው የሚገለፀው።“አንድን ሰው እንዲያጠራው መጋበዝ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

በሶስተኛው ቀን ራሱን ካላጠራ በሰባተኛው ቀንም ንፁሕ አይሆንም
ይሄ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል።“በሰባተኛው ቀን ንፁሕ የሚሆነው በሶስተኛው ቀን ራሱን ያጠራ እንደሆነ ብቻ ነው”(ድርብ አሉታዎች)

ያ ሰው ተለይቶ መጥፋት አለበት
“መጥፋት”የሚል ቃል የሚያመለክተው ከማህበረሰቡ ጋር ያለው ማንኛውም ግንኙነት ተቋርጦ መባረሩን ነው።ይህንን በዘኁልቁ 9፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“ያ ሰው መባረር አለበት”ወይም “ያንን ሰው ማባረር አለባችሁ” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውንና ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ ላይ ባለው ርኩሰት ላይ ውኃ አልተረጨምና
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ማንም ሰው በርኩሰቱ ላይ ውኃን አልረጨም”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

በርኩሰት ላይ የሚረጭ ውኃ
“የረከሱ ነገሮች እንዲነፁ ለማድረግ የሚረጭ ውኃ”ወይም“ነገሮችን ለማንፃት የሚረጭ ውኃ”

ርኩስ ይሆናል፤ርኩሰቱ ከእርሱ ጋር ይቆያል
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን በአንድ ላይ እንዲነገሩ የተደረገው ለጉዳዩ አፅንኦት ለመስጠት ሲባል ነው። (ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 19:14

አጠቃላይ መረጃ
“ንፁሕ ያልሆነ”የሚለው ሃሣብ የሚያመለክተው በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት አለማግኘትን ወይም ለአገልግሎት ብቁ አለመሆንን ነው። (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መክደኛው ያልታሰረ የተከፈተ ዕቃ ሁሉ ርኩስ ይሆናል
ይሄ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል።“የተከፈቱ ዕቃዎች ንፁሕ የሚሆኑት መሸፈኛ የሚደረግላቸው ከሆነ ብቻ ነው።“ድርብ አሉታዊነት”

በሠይፍ የተገደለ ሰው
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሌላ ሰው በሠይፍ የገደለው ሰው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 19:17

አጠቃላይ መረጃ
“ንፁሕ ያልሆነ”የሚለው ሃሣብ የሚያመለክተው በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት አለማግኘትን ወይም ለአገልግሎት ብቁ አለመሆንን ነው። (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ
“ንፁሕ መሆን”እና “መቀደስ” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ማግኘትን ነው።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 19:20

አጠቃላይ መረጃ
“ንፁሕ መሆን”እና “መቀደስ” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት መኖሩን ነው።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ
“ንፁሕ ያልሆነ”የሚለው ሃሣብ የሚያመለክተው በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት አለማግኘትን ወይም ለአገልግሎት ብቁ አለመሆንን ነው። (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 20

1 የእስራኤል ሰዎች፣ መላው ማህበረሰብ በመጀመሪያው ወር ወደ ሲና ምድረ በዳ ሄደው በቃዴስ ሰፈሩ።ማርያም በዚያ ሞታ ተቀበረች። 2 ማህበረሰቡ ውሃ
ተጠማ፣ ስለዚህ በሙሴና በአሮን ላይ አምጸው ተሰበሰቡ። 3 ህዝቡ በሙሴ ላይ አጉረመረሙ። እንዲህም አሉ፣ “ወገኖቻችን እስራኤላውያን በያህዌ ፊት
በሞቱበት ጊዜ እኛም ብንሞት ኖሮ ይሻል ነበር! 4 እዚህ እንሞት ዘንድ የያህዌን ማህበረሰብ፣ እኛንና ከብቶቻችንን ለምን ወደዚህ ምድረበዳ አመጣችሁን? 5
ወደዚህ አስፈሪ ስፍራ ልታመጡን ለምን ከግብጽ እንድንወጣ አደረጋችሁን? እዚህ፤ እህል፣ በለስ፣ ወይም ወይም ሮማን የለም። የሚጠጣም ውሃ የለም።” 6
ስለዚህ ሙሴና አሮን ከጉባኤው ፊት ወጥተው ሄዱ። ወደ መገናኛው ድንኳን መግቢያ ሄደው በግምባራቸው ተደፉ። ከዚያ የያህዌ አንጸባራቂ ክብር ታያቸው። 7
ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ 8 “በትርህን ውሰድና አንተና ወንድምህ አሮን ማህበረሰቡን ሰብስቡ። በፊታቸው ለዓለቱ ተናገር፣ ውሃ እንዲያፈስም አለቱን
እዘዘው። ከዚያ ዓለት ውሃ አውጥተህ ትሰጣቸዋለህ፣ ማህበረሰቡና ከብቶቻቸው ይጠጡ ዘንድ ውሃ ስጣቸው።” 9 ሙሴ ያህዌ እንዳዘዘው ከያህዌ ፊት በትሩን
ወሰደ። 10 ከዚያ ሙሴና አሮን ጉባኤውን በአለቱ ፊት ሰበሰቡ። ሙሴ ጉባኤውን እንዲህ አለ፣ “እናንተ አመጸኞች፣ አሁን ስሙ። ከዚህ ዓለት ለእናንተ ውሃ
ማውጣት አለብን?” 11 ከዚያ ሙሴ እጁን አንስቶ በበትሩ አለቱን ሁለት ጊዜ መታው፣ እናም ብዙ ውሃ ወጣ። ማህበረሰቡ ጠጣ፣ እንዲሁም ከብቶቻቸው
ጠጡ። 12 ከዚያ ያህዌ ሙሴንና አሮንን እንዲህ አላቸው፣ “እኔን ስላላመናችሁ ወይም በእስራኤል ሰዎች ዐይኖች ፊት ቅዱስ አድርጋች ስላላያችሁኝ፣ ይህን
ጉባኤ ወደ ሰጠኋችሁ ምድር አታስገቧቸውም።” 13 ይህ ቦታ የመሪባ ውሃ ተብሎ ተጠራ፣ ምክንያቱም በዚያ የእስራኤል ሰዎች ከያህዌ ጋር ተጣልተው ነበር፣
እርሱም ራሱን በቅድስናው ገለፀላቸው። 14 ሙሴ ከቃዴስ መልዕክተኞችን ወደ ኤዶም ንጉስ ላከ፡ ወንድምህ እስራኤል ይህን ይላል፡ “በእኛ ላይ የደረሱትን
አስቸጋሪ ነገሮች ታውቃለህ። 15 አባቶቻችን ወደ ግብፅ ወርደው ለዘመናት በግብጽ መኖራቸውን ታውቃለህ። ግብጻውያን በእኛና በአባቶቻችን ላይ እጅግ
ከፉብን። 16 እኛ ወደ ያህዌ ስንጮህ፣ እርሱ ድምጻችንን ሰምቶ መልዓክ ልኮ ከግብጽ አወጣን። እነሆ፣ በምድርህ ዳርቻ በምትገኘው በቃዴስ እንገኛለን። 17
በምድርህ እንድናልፍ እንድትፈቅድልን እጠይቅሃለሁ። በእርሻዎች ወይም በወይን ሥፍራዎች ውስጥ አናልፍም፣ አሊያም ከጉድጓዶቻችሁ ውሃ አንጠጣም።
የንዱን አውራ ጎዳና ይዘን እንሄዳለን። ድንበርህን እስክናልፍ ድረስ ወደ ግራም ወደ ቀኝም አንልም።” 18 የኤዶም ንጉስ ግን እንዲህ ሲል መለሰለት፣ “በዚህ
በኩል ማለፍ አትችሉም። ይህን ብታደርጉ፣ ሰይፍ ይዤ እወጣባችኋለሁ።” 19 ከዚያ የእስራኤል ሰዎች እንዲህ አሉት፣ “እኛ በአውራ ጎዳናው እንሄዳለን። እኛም
ሆን ከብቶቻችን ውሃህን ብንጠጣ፣ ለዚያም እንከፍላለን። ሌላ ምንም ነገር ሳናደርግ በእግራችን እንለፍ።” 20 የኤዶም ንጉስ ግን እንዲህ ሲል መለሰ፣ “በዚህ
በኩል አታልፉም።” ስለዚህም የኤዶም ንጉስ በብርቱ ክንድ አያሌ ወታደሮች ይዞ በእስራኤላዊያን ላይ መጣባቸው። 21 የኤዶም ንጉስ እስራኤላውያን በድንበሩ
አቋርጠው እንዳያልፉ ተቃወመ። በዚህ ምክንያትና እስራኤል ከኤዶም ምድር ተመለሱ። 22 ስለዚህ ህዝቡ ከቃዴስ ተነስቶ ተጓዘ። የእስራኤል ህዝብ፣ መላው
ማህበረሰብ ወደ ሖር ተራራ መጣ። 23 ያህዌ በሖር ተራራ ለሙሴና አሮን ተናገራቸው። እንዲህም አለ፣ 24 ”አሮን ለእስራኤል ህዝብ ወደ ሰጠኋት ምድር
አይገባምና ወደ አባቶቹ ይሰበሰባል። ይህም የሚሆነው እናንተ ሁለታችሁም በመሪባ ውሃ በእኔ ቃሎች ላይ ስላመፃችሁ ነው። 25 አሮንንና ልጁን አልዓዛርን
ይዘህ ወደ ሖር ተራራ አምጣቸው። 26 የአሮንን የክህነት ልብስ ከእርሱ ላይ አውልቀህ ልጁን አልዓዛርን አልብሰው። አሮን በዚያ ይሞትና ወደ ወገኖቹ
ይሰበሰባል።” 27 ሙሴ ያህዌ እንዳዘዘው አደረገ። መላው ማህበረሰብ እያየ ወደ ሖር ተራራ ወጡ። 28 ሙሴ የአሮንን የክህነት ልብሶች ከእርሱ አውልቆ
ልጁን አልዓዛርን አለበሰው። አልዓዛር በተራራው አናት ላይ በዚያ ሞተ። ከዚያ ሙሴና አልዓዛር ከተራራው ወደ ታች ወረዱ። 29 መላው ማህበረሰብ አሮን እንደ
ሞተ ባየ ጊዜ፣ ጠቅላላው አገሩ ለሰላሳ ቀናት ለአሮን አለቀሰ።

Numbers 20:1

የዒን ምደረ በዳ
እዚህ ላይ “ዒን”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በዕብራይስጥምድረ በዳ የሚለውን ሥያሜ ነው።(ቃላትን መቅዳት ወይም መዋስ የሚለውን ይመልከቱ)

የመጀመሪያው ወር
በዕብራውያን የቀን አቆጣጠር መሠረት ይሄየመጀመሪያ ወራቸው ነው። እግዚአብሔር ከግብፃውያን ነፃ ያወጣቸውን ጊዜ የሚያመለክት ነው። በምዕራባውያን የቀን አቆጣጠር መሠረት የመጀመሪያ ወር የሚሆነው በመጋቢት የመጀመሪያዎቹ ቀናትና በየካቲት የመጀመሪያዎቹ ቀናት ወቅት ነው። (የዕብራውያን ወራት የሚለውን ይመልከቱ)

ተቀበረች
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ቀበሯት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 20:2

እነርሱ ተሰበሰቡ
እዚህ ላይ “እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ማህበረሰቡን ነው።

በአንድነት ተሰበሰቡ
“ለአመፅ ተሰባሰቡ”

በእግዚአብሔር ፊት
ይሄ የሚያመለክተው በእግዚአብሔር ድንኳን ፊት መሆናቸውን ነው።(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 20:4

ማያያዣ ዓረፍተ ነገር
የእሥራኤል ሕዝብ በሙሴና በአሮን ላይ ማጉረምረማቸውን ይቀጥላሉ።

የእግዚአብሔርን ሕዝብ ወደ ምድረ በዳ ለምን አመጣህ? እኛና ከብቶቻችን እንድንሞት ነውን?
ሕዝቡ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው በሙሴና በአሮን ላይ ለማጉረምርም ነው። እንደ መግለጫ ሊታይ ይችላል።“የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከከብቶቹ ጋር እንዲሞት ለማድረግ እዚህ በረሃ ውስጥ ማምጣት አልነበረብህም” (ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደዚህ አስከፊ ሥፍራ እንመጣ ዘንድ ከግብፅ ምድር ለምን አወጣኸን?
ሕዝቡ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው በሙሴና በአሮን ላይ ለማጉረምርም ነው።እንደ መግለጫ ሊታይ ይችላል።“እኛን ወደዚህ አስከፊ ሥፍራ ለማምጣት ከግብፅ ምድር ልታወጣን አይገባህም ነበር”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 20:6

በግምባራቸው ተደፉ
ይሄ የሚያመለክተው ሙሴና አሮን በእግዚአብሔር ፊት ራሣቸውን ማዋረዳቸውን ነው።(ተምሣሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Numbers 20:7

በዓይናቸው ፊት
እዚህ ላይ ሰዎቹ የሚያዩትን ነገር በሚመለከት“ዓይናቸው”እንደ ወኪል ሆኖ ቀርቧል።“አንተን በሚመለከቱበት ወቅት”(ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ፊት
ይሄ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ድንኳን ነው።“ከእግዚአብሔር ድንኳን”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 20:10

ከዚህ ድንጋይ ውኃ እናውጣላችሁን?
ሙሴ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ከብስጭት የተነሣ ሲሆን ሕዝቡ በማጉረምረማቸው ሊገስፃቸው ነበር።ይሄ እንደ መግለጫ ሊገለፅ ይችላል።“ውኃ የለም ብላችሁ አጉረምርማችኋል።እንደዚህ ከሆነ ከዚህ ዓለት ውኃ እናወጣላችኋለን”ወይም“ከዚህ ዓለት ውኃ ብናወጣላችሁ እንኳን ደስተኞች አትሆኑም።ቢሆንም ግን አደርገዋለሁ”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ ማውጣት አለብን?
እዚህ ላይ“እኛ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሙሴንና አሮንን ሲሆን እግዚአብሔርንም የሚያካትት ሊሆን ይችላል።ሆኖም ግን ሕዝቡን አያካትትም።(“እኛ”የሚለውንና አካታችና አካታች ያልሆነውን የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 20:12

በእሥራኤል ልጆች ዓይኖች ፊት ትቀድሱኝ ዘንድ በእኔ አላመናችሁም
እዚህ ላይ ሙሴ በእግዚአብሔር ላይ አለመታመኑና እግዚአብሔርን ያለማክበሩ ነገር በእርሱ ላይ መታየቱ በግልፅ ሊብራራ ይችላል።“በእሥራኤል ልጆች ዓይኖች ፊት ትቀድሱኝ ዘንድ በእኔ ባለማመናችሁምክንያት እኔ በተናገርኩት መንገድ ልታደርግ ሲገባህ በራስህ ሃሣብ ተመስርተህ ዓለቱን መታህ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በእሥራኤል ዓይኖች ፊት
እዚህ ላይ ሰዎቹ የሚያዩትን ነገር በሚመለከት “ዓይናቸው”እንደ ወኪል ሆኖ ቀርቧል።“አንተን በሚመለከቱበት ወቅት”(ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)

የዚህ ሥፍራ ሥም
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሰዎች ይሄንን ሥፍራ የሚጠሩት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 20:14

ወንድምህ እሥራኤል
ሙሴ ይሄንን ሐረግ የተጠቀመበት ምክኒያት ዘሮቻቸው የሆኑት ያዕቆበና ኤሳው ወንድማማቾች ስለሆኑ እሥራኤላውንና ኤዶማውያን ዘመዳሞች እንደሆኑ አፅንዖት ለመስጠት ፈልጎ ነው።

ወደ እግዚአብሔርም በጮህን ጊዜ
“ዕርዳታ ያደርግልን ዘንድ ወደ እግዚአብሔር በፀለይን ጊዜ”

ድምፃችንን ሰማ
እዚህ ላይ“ድምፅ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው መጮሃቸውንና ለእርሱ የተናገሩትን ነገር ነው።“ጩኸታችንን አዳመጠ”ወይም “የጠየቅነውን ነገር ሰማን”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ
“እነሆ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ስላለፈው ነገር ማውራት ማቆማቸውንና አሁን ስላሉበት ሁኔታ እየተናገሩ መሆኑን ይገልፃል።

Numbers 20:17

ማያያዣ ዓረፍተ ነገር
መልዕክተኞቹ ስለ ኤዶም ንጉሥ መናገራቸውን ይቀጥላሉ።

ወደ ቀኝም ወደ ግራም አንልም
“አንልም”የሚለው ቃል የሚያመለክተው መንገድ መልቀቅን ነው።“በየትኛውም አቅጣጫ ቢሆን መንገዱን አንለቅም”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

በንጉሡ ጎዳና
ይሄ ሰሜናዊውን የደማስቆ የሰሜኑን ክፍል ክፍል በደቡብ ከሚገኘው የአካባ ባህረ ሰላጤ ጋርየሚያገናኝ ዋና መንገድ ነው።

Numbers 20:18

በሠይፍ እንዳልገጥምህ አንተ በምድሬ ላይ አታልፍም
“አንተ”የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር በመሆኑ የሚያመለክተው የእሥራኤልን ሕዝብ የሚወክለውን ሙሴን ነው።“ሕዝብህን በሠይፍ እንዳልገጥም አንተ በምድሬ ላይ አታልፍም”(አንተ/እናንተ የሚለው ቃል በተለያየ መንገድ የሚገለፅበት የሚለውንና ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)

በሠይፍ እንዳልገጥም
እዚህ ላይ “ሠይፍ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የንጉሡን ሠራዊት ነው።“ሠራዊቴን እልካለሁ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

የእሥራኤል ሕዝብ
ይሄ ሐረግ የሚያመለክተው የእሥራኤልን መልዕክተኞች ነው።

በእግራችን እንለፍ
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር የሚያመለክተው በዚያ በኩል በእግራቸው ለማለፍ እንደፈለጉ ብቻ ነው።የኤዶምን ህዝብ ለማጥቃት በሠረገሎች አይመጡም ማለት ነው።(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 20:20

ኤዶምያስም በብዙ ሕዝብና በፅኑ እጅ ሊገጥመው ወጣ
እዚህ ላይ እጅ የሚለው ቃል የሚያመለከተው የንጉሡን ጠንካራ ሠራዊት ነው።“የኤዶም ንጉሥ እሥራኤልን ይዋጉ ዘንድ ብዙ ተዋጊዎች ያሉበትን ጠንካራ ሠራዊት ላከ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

በእነርሱ ድንበር ላይ ማለፍ
እዚህ ላይ “እነርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው አዶማውያንን ነው።

Numbers 20:22

የእሥራኤል ልጆች ማህበር ሁሉ
“ማህበር ሁሉ”የሚለው ቃል የሚሰጠው ያለምንም ልዩነት እዚያ የተገኘና “የእሥራኤል ሕዝብ”አካል የሆነ እያንዳንዱ ግለሰብ እዚያ ስለመገኘቱ አፅንኦት ይሰጣል። (ሁለት ተመሳሳይ ገፅታ ያላቸው የሚለውን ይመልክቱ)

አሮን ወደ ወገኑ ይከማች
ይሄ ጨዋ በሆነ አነጋገር አሮን መሞት አለበት ማለት ነው።ይሄ የሚያመለክተው አሮን መሞት ያለበት መሆኑንና መንፈሱም አባቶቹ ወዳሉበት ሥፍራ መሄድ ያለበት መሆኑን ነው ።“አሮን መሞተ አለበት”(ሥርዓት የሌለውን ነገር በመልካም ነገር መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

በቃሌ ስላመፃችሁ
“እኔ የተናገርኩትን ተግባራዊለማድረግ እምቢ አላችሁ”

Numbers 20:25

ማያያዣ ዓረፍተ ነገር
እግዚአብሔር ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል።

ወደ ወገኑ ይከማች፤በዚያም ይሙት
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው።ይሄ የሚያመለክተው አሮን መሞት ያለበት መሆኑንና መንፈሱም አባቶቹ ወዳሉበት ሥፍራ መሄድ ያለበት መሆኑን ነው።(ተመሳሳይነት የሚለውንና ሥርዓት የሌለውን ነገር በመልካም ነገር መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 20:27

ሠላሣ ቀናት
“30 ቀናት”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 21

1 በኔጌብ የሚኖረው ከነዓናዊው የዓረድ ንጉስ እስራኤል ወደ አታሪም እየመጣ በመንገድ ላይ መሆኑን ሲሰማ፣ ከእስራኤል ጋር ተዋግቶ አንዳንዶቹን በምርኮ ወሰደ። 2 እስራኤል ለያህዌ እንዲህ ብሎ ማለ፣ “በእነዚህ ህዝቦች ላይ ድል ብትሰጠን፣ ከዚያም ከተማቸውን ሙሉ ለሙሉ እናጠፋለን።” 3 ያህዌ የእስራኤልን ድምጽ ሰምቶ በከነዓናዊያን ላይ ድልን ሰጣቸው። ሙሉ ለሙሉ እነርሱንና ከተማቸውን አጠፉ። ያ ስፍራ ሖርማ ተብሎ ተጠራ። 4 ከሖር ተራራ ተነስተው ኤዶም ምድር ዙሪያ ለመድረስ በቀይ ባህር መንገድ ተጓዙ፤ ህዝቡ በመንገድ ሳለ እጅግ ተስፋ ቆረጡ። 5 በእግዚአብሔርና በሙሴ ላይ እንዲህ ሲሉ አጉረመረሙ። “በበረሃ እንሞት ዘንድ ለምን ከግብጽ አወጣችሁን በዚህ ዳቦ የለም፣ አንዳች ውሃ የለም፣ ደግሞም ይህን የማይረባ ምግብ ጠልተነዋል።” 6 ከዚያ ያህዌ በሰዎቹ መካከል መርዛም እባቦችን ሰደደ። እባቦቹ ሰዎችን ነደፉ፤ ብዙ ሰዎችም ሞቱ። 7 ሰዎች ወደ ሙሴ መጥተው እንዲህ አሉ፣ “እኛ በድለናል ምክንያቱም በያህዌና በአንተ ላይ በተቃውሞ ተናግረናል። እባቦቹን ከእኛ እንዲያርቅ ወደ ያህዌ ጸልይልን።” ስለዚህም ሙሴ ለህዝቡ ጸለየ። 8 ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ “እባብ አብጅና በምሰሶ ላይ አንጠለጠለው። እንዲህ ይሆናል፣ የተነደፈ ሁሉ ያንን ከተመለከተ ይድናል።” 9 ስለዚህም ሙሴ የናስ እባብ አበጅቶ በምሰሶ ላይ አንጠለጠለው። እባብ ማናቸውንም ሰው በነከሰ ጊዜ፣ ሰውየው ወደ ናሱ እባብ ከተመለከተ ይድናል። 10 ከዚያ የእስራኤል ሰዎች ተጉዘው በአቦት ሰፈሩ። 11 ከአቦት ተጉዘው በስተምስራቅ በሞአብ አንጻር በዒዮዓባሪም በምድረ በዳ ሰፈሩ። 12 ከዚያ ተጉዘው በዘሬድ ሸለቆ ሰፈሩ። 13 ከዚያ ተጉዘው እስከ አሞራዊያን ድንበር በሚዘልቀው በምድረበዳ ባለው በአሮን ወንዝ ሌላኛው ዳርቻ ሰፈሩ። የአርኖን ወንዝ በሞዐብና አሞራዊያን መሀል የሞአብን ወሰን ያበጃል። 14 በያህዌ የጦርነት መጽሐፍ ጥቅልል፣ በሱፋ ውስጥ የሚገኘው ዋሄብ እና የአርኖን ሸለቆዎች፣ 15 ወደ ዔር ከተማና ወደ ሞአብ ዳርቻ የሚወስዱ የሸለቆዎች ቁልቁለት” ተብሎ የተፃፈው ስለዚህ ነው። 16 ከዚያ ተነስተው ወደ ብኤር ተጓዙ፣ ይህም ስፍራ የውሃ ጉድጓድ የሚገኝበትና ያህዌ ሙሴን፡ - “ውሃ እሰጣቸው ዘንድ ሰዎቹን በአንድነት ሰብስባቸው” ብሎ የተናገረበት ነው። 17 ከዚያ እስራኤል ይህን መዝሙር ዘመረ። “አንተ ምንጭ ሆይ ፍለቅ። ስለዚህ እናንተም ዘምሩ። 18 መሪዎቻችን የቆፈሩት ጉድጓድ፣ የተከበሩ የህዝብ አለቆች በበትረ መንግስታቸውና በበትሮቻቸው የማሱት ጉድጓድ።” ከዚያ ከምድረበዳው ተነስተው ወደ መቴና ተጓዙ። 19 ከመቴና ተነስተው ወደ ነሃሊኤል፣ ከነሃሊኤል ወደ ባሞት እና ከባሞት በሞአብ ምድር ወደሚገኘው ሸለቆ ተጓዙ። 20 በፈስጋ ተራራ ጫፍ ሆኖ ምድረበዳው ቁልቁል የሚታይበት ይህ ስፍራ ነው። 21 ከዚያ እስራኤል ወደ አሞራዊያን ንጉስ ወደ ሴዎን እንዲህ ብለው መልእክተኞችን ላኩ፣ 22 ”በምድርህ እንለፍ። ወደ እርሻዎች ወይም ወደ ወይን አትክልቶች አንገባም። ከጉድጓዶችህ ውሃ አንጠጣም። ድንበርህን እስክናልፍ ድረስ በንጉሱ አውራ መንገድ እንጓዛለን።” 23 ንጉስ ሴዎን ግን እስራኤልን በድንበሩ እንዲያልፉ አልፈቀደም። ይልቁንም፣ ሴዎን ወታደሮቹን አሰባስቦ በምድረ በዳ እስራኤልን ለመውጋት ወጣ። 24 እስራኤል የሴዎንን ጦር በሰይፍ ወግቶ ከአርኖን እስከ ያቦቅ ወንዝና እስከ አሞን ሰዎች ወሰን ድረስ ምድሩን ወሰደ። የአሞን ሰዎች ድንበር ግን የተመሸገ ነበር። 25 እስራኤል የአሞራዊያንን ከተሞች ሁሉ፣ ሐስቦንንና መንደሮቹን ጭምር ይዞ በእነዚያ ውስጥ ተቀመጠ። 26 ሐስቦን ከሞአብ የቀድሞ ንጉስ ጋር የተዋጋው የአሞራዊያን ንጉስ የሴዎን ከተማ ነበረች። ሴዎን እስከ አርኖን ወንዝ ድረስ ያለውን ምድሩን ሁሉ ወሰደበት፡ 27 በምሳሌያዊ ንግግር የተናገሩ፣ “ወደ ሐሴቦን ኑ። የሴዎን ከተማ እንደ ገና ትገንባና ዳግም ትታነጽ። 28 እሳት ከሐሴቦን ተንቦገቦገ፣ ነበልባል ከሴዎን ከተማ የሞአብን ዔር አጠፉ፣ ደግሞም የአርን ተራሮች ባለቤቶችን በላ። 29 ሞአብ ዋይታ ሆነብህ! የከሞስ ህዝብ እናንተ ጠፋችሁ። ለአሞራውያን ንጉስ ለሴዎን ወንዶች ልጆቹን ለሸሸት ሴቶች ልጆቹን ለምርኮ አሳልፎ ሰጥቷል። 30 እኛ ግን ሴዎንን አሸንፈናል። ሐስቦን እስከ ዴናን ድረስ ወድማለች። ወደ ሜድባ እስከምታደርሰው ኖፋ ድረስ ሁሉንም አሸንፈናቸዋል።” 31 ስለዚህ እስራኤል በአሞራዊያን ምድር መኖር ጀመረ። 32 ከዚያ ሙሴ ሰዎችን ምድሪቱን እንደያዙ ወደ ኢያዜር ላከ። እነርሱ መንደሮቿን ማረኩ በዚያ የነበሩትንም አሞራዊያን አባረሩ። 33 ከዚያ ወደ ባሳን በሚስደው መንገድ ዞረው ሄዱ። የባሳን ንጉስ ዐግ በእነርሱ ላይ ዘመተ፣ እርሱና ሰራዊቱ ሁሉ በኤድራይ ለዋጓቸው ወጡ። 34 በዚያን ጊዜ ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ “እርሱን አትፈራው፣ ምክንያቱም እኔ በእርሱ፣ በሰራዊቱና በምድሩ ላይ ሁሉ ላይ ድል ሰጥቼሃለሁ። በሐስቦን እንደነበረው በአሞራዊያን ንጉስ በሴዎን ላይ እንዳደረከው በእርሱ ላይ አድርግበት።” 35 ስለዚህም እርሱን፣ ወንዶች ልጆቹን እና መላውን ሰራዊቱን አንድም ሰው በህይወት እስከ ማይተርፍለት ድረስ ፈጇቸው። ከዚያም ምድሩን ወረሱ።

Numbers 21:1

ከእሥራኤልም ጋር ሠልፍ አደረገ
“ሠልፍ አደረገ”ማለት ሠራዊቱ ተዋጋ ማለት ነው።“የእርሱ ሠራዊት ከእሥራኤል ሕዝብ ጋር ተዋጋ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ስእለት ተሳለ
ይሄ የሚያመለክተው የእሥራኤልን ሕዝብ ነው።“የእሥራኤል ሕዝብ ስእለትን ተሳለ”ወይም “እሥራኤላውያን ስእለትን ተሳሉ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

የእሥራኤልን ድምፅ ሰማ
“ሰማ”ማለት የጠየቁትን ነገር አደረገላቸው ማለት ነው።“እሥራኤል ጥያቄ ባቀረበለት መሠረት ተግባራዊ አደረገው”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

የእሥራኤል ድምፅ
እዚህ ላይ “ድምፅ”የሚለው ቃልከጥያቄያቸው ጋር የተያያዘ አባባል ነው።“እሥራኤል የጠየቀውን”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ከተሞቻቸውንም እርም ብለው አጠፉ
“የእሥራኤል ሕዝብ የከነዓናውያንን ሠራዊትና ከተሞቻቸውን ፈፅሞ አጠፉ”

የዚያን ሥፍራ ሥም ሔርማ ብለው ጠሩት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ያንን ሥፍራ ሔርማ ብለው ጠሩት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 21:4

በምድረ በዳ እንሞት ዘንድ ከግብፅ ለምን አወጣችሁን?
ሕዝቡ ይሄንን ጥያቄ የጠየቀው ሙሴን ለመገሰፅ ነበር።ይሄ በመግለጫ መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እኛን በምድረ በዳ ለመግደል ከግብፅ ልታወጣን አይገባህም ነበር”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 21:6

በእግዚአብሔርና በአንተ ላይ ተናግረናል።
“በእግዚአብሔርና በአንተ ላይ ክፉ ነገርን ተናግረናል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እኛ ተናግረናል...ከእኛ
“እኛ”እና “ከእኛ”የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ሙሴን ሣይሆን ሕዝቡን ነው።(“እኛ”የሚለውንና አካታች ሆነውንና ያልሆነውን የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 21:8

እባብን ሥራ
ሙሴ እውነተኛ የሆነ እባብን መሥራት የማይችል በመሆኑ የእባብ ናሙና እንዲሰራ ነበር የተፈለገው።ይሄ ተግባራዊ መሆን ያለበት መረጃ የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“የእባብ ምሳሌን ሥራ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የተነደፈውም ሁሉ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እባብ የሚነድፈው ሰው በሙሉ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

የናስ እባብ
“ከነሐስ የሰራ እባብ”

እባብም የነደፈችው ሁሉ የናሱን እባብ ባየ ጊዜ እርሱ ዳነ
እዚህ ላይ “እርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በእባብ የተነደፈውን “ማንኛውንም ሰው”ነው።

Numbers 21:10

በሞአብ ፊት ለፊት
እዚህ ላይ “ፊት ለፊት”የሚለው ቃል ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን “ከእነርሱ ማዶ”ወይም “ከእነርሱ አጠገብ”ማለት ነው።“ከሞአብ በመቀጠል”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 21:12

በሞአብና በአሞራውያን መካከል ያለ የሞአብ ዳርቻ ነው
ይሄ ማለት እነዚህ ሁለት ሕዝቦች እንደ ድንበር በሚያገለግላቸው በወንዙ አጠገብ ባሉ ክፍሎች ላይ ይኖሩ ነበር ማለት ነው።አሞራውን በወንዙ ደቡብ ክፍል ሲኖሩ አሞራውያን ደግሞ በወንዙ የሰሜኑ ክፍል ነበር የሚኖሩት።

Numbers 21:14

ዋሄብ በሱፋ
እነዚህ ሁለቱም የቦታ ሥሞች ናቸው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

የአርኖንም ሸለቆዎች ወደ ኤር ማደሪያ የሚወርድ በሞአብም ዳርቻ የሚጠጋ
“ወደ አርኖን ከተማ የሚያመራውና በሞአብ ድንበር ላይ ተንጣሎ የሚገኘው ሸለቆ“

Numbers 21:16

ብኤር፤ጉድጓዱ
እነዚህ እንደ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ሊገለፁ ይችላሉ።“ወደ ብኤር፤በዚያ ጉድጓድ ነበረ”

ይኸውም እግዚአብሔር ሙሴን “ሕዝቡን ሰብስብ ውኃንም እሰጣቸዋለሁ ብሎ የተናገረበት ነው”
ይሄ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ጥቅስ ሊገለፅ ይችላል።“ይኸውም እግዚአብሔር ሙሴን “ሕዝቡን ወደ እርሱ እንዲሰበስብ አድርጎ ውኃን ለመሥጠት የተናገረበት ነው”(ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ አባባሎች የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 21:17

አንተ ምንጭ ሆይ ፍለቅ
“ምንጭ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በጉድጓድ ውስጥ ያለውን ውኃ ነው። እሥራኤላውያን የሚያዳምጣቸው ሰው ይመስል ለውኃው የሚናገሩ ሲሆን ጉድጓዱን እንዲሞላላቸው ይጠይቁታል።“አንተ ውኃ ጉድጓዱን ሙላ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውንና ግዑዝ ነገሮች ሕይወት እንዳላቸው ተደርገው ሲገለፁ የሚለውን ይመልከቱ)

የሕዝብ አዛውንቶች ያጎደጎዱት፤አለቆችም የቆፈሩት
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ውኃውን በመቆፈር ረገድ መሪዎች ያላቸውን ሚና አፅንኦት በመሥጠት ይናገራል።(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

በበትረ መንግሥት፤በበትራቸውም
በትረመንግሥትየያዝየነበረውሥልጣንበነበራቸውሰዎችሲሆንበትርደግሞይያዝየነበረውበሁሉምሰው እነዚህሁለቱለቁፋሮአገልግሎትየሚውሉመሣሪያዎችአይደሉም። እነዚህሁለትቁሣቁሶች የሚያሣዩት በአካባቢያቸውየሚገኙትን ነገሮች ለመጠቀም ኩራት የሚባል ነገር የሌለባቸው ስለመሆኑ አፅንኦት ለመስጠት ነው።“በትረ መንግሥታቸውንና በትራቸውን እንኳን ሳይቀር ይጠቀማሉ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 21:19

ነሃልኤል...ባሞት
እነዚህ የቦታ ሥሞች ናቸው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

ፈስጋ ተራራ
ይሄ የተራራ ሥም ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

ምድረ በዳውን ከላይ ወደሚመለከተው
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው።ይሄ አነጋገር ተራራው ከፍ ያለ እንደሆነ ለመግለፅ ሲሆን ተራራው ከሥሩ የሚገኘውን ምድረ በዳ እንደሚመለከት ሕይወት እንዳለው ሰው አድርጎ ያቀርበዋል።“ከምድረ በዳው ይልቅ ከፍ ያለ ነው”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውንና ግዑዝ ነገሮች ሕይወት እንዳላቸው ተደርገው ሲገለፁ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 21:21

እሥራኤልም
እዚህ ላይ “እሥራኤል”የሚለው ቃል የሚያመለክተው እሥራኤልን ሕዝብና በተለይም መሪዎቿን ነው።“ከዚያ በኋላ እሥራኤላውያን”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እርሻና ወይን ቦታ አንገባም
“በየትኛውም እርሻና የወይን ቦታችሁ አንገባም”

በንጉሥ ጎዳና
ይሄ ደማስቆን በስተ ሰሜንንና የአካብን ባህረ ሠላጤ በደቡብ በኩል የሚያስተሳስር አውራ ጎዳና ነው።ይሄንን በዘኁልቁ 20፡17 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

በድንበራቸው ላይ ለማለፍ
“በእነርሱ ድንበር በኩል ለማለፍ” እዚህ ላይ “እነርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው አሞራውያንን ነው።

ያሃፅ
ይሄ የቦታ ሥም ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እርሱም ከእሥራኤልም ጋር ተዋጋ
እዚህ ላይ “እርሱም”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ራሱንና ሠራዊቱን የሚወክለው ንጉሥ ሴዎን ነው።“ከእሥራኤላውያን ጋር ተዋጉ”(ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 21:24

እሥራኤልም መታ
እዚህ ላይ “እሥራኤል” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእሥራኤልን ሕዝብ ነው።“እሥራኤላውን ጥቃት አደረሱ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

በሠይፍ ሥለት
“ስለታም በሆነው የሠይፉ ክፍል” “የሠይፍ ሥለት”የሚለው ቃል የሚያያዘው ከሞትና ፍፁም ከሆነ ጥፋት ጋር ነው።“ሙሉ በሙሉ ድል ነሷቸው”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

የእነርሱን ምድር ወረሱ
“የአሞራውያንን ምድር ድል አደረጉ” እዚህ ላይ “የእነርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው አሞራውያንን ነው።

የአሞን ሕዝብ...አሞራውያን
“አሞናውያን..አሞራውያን”ወይም “አሞን ሕዝብ ወይም የአሞር ሕዝብ” እነዚህ ስሞች ተመሳሳይ ቢሆኑም የሚያመለክቱት ግን ሁለት የተለያዩ ሕዝቦችን ነው።

የተመሸገ ነበረ
“ጠንካራ የሆነ መከላከያ ነበረው” እሥራኤላውያን አሞናውያንን አላጠቁም።

በሐሴቦንና በመንደሮቹ ሁሉ
እዚህ ላይ“ሁሉ”የሚለው ቃል አካታች ሲሆን የሐሴቦን ከተማ በቅርብ ካሉት መንደሮች ጋር ያለውን ግንኙነት ይገልፃል።“ሐሴቦንና የሚቆጣጠራቸው በቅርብ የሚገኙ ከተሞች”

ሴዎን እርሱን ከተማዎች ሁሉ ወስዶ ነበር
እዚህ ላይ“የእርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሞአብን ንጉሥ ነው።

Numbers 21:27

ሐሴቦን ... የሴዎን ከተማ
እነዚህ የሚያመለክቱትለአንድ ከተማ የተሰጡ ሁለት ስሞችን ነው። (ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

የሴዎን ከተማ ይሰራ፤ይመሥረት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“አንድ ሰው የሴዎንን ከተማ ይገንባና ይመሥርት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደገና ይገንባና ዳግም ይመሥርት
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሣሣይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ከተማዋ ሙሉ በመሉ የምትገነባ ስለመሆኗ አስረግጦ ለመናገር ነው።“ሙሉ በሙሉ ዳግም ይገነባል”(ሁለት ተመሳሳይ የሆነ ገፅታ ያላቸው የሚለውን ይመልክቱ)

እሣት ከሐሴቦን፤ነበልባልም ከሴዎን ወጣ
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሣሣይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆንውድመቱ ከሐሴቦን እንደሚጀምር አስረግጦ ይናገራል።እሣቱ የሚያመለክተው አጥፊ የሆነ ሠራዊትን ነው።“ንጉሥ ሴዎን ከሐሴቦን ከተማ ጠንካራ የሆነ ጦርን እየመራ መጣ” (ተመሳሳይነት የሚለውንናምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሞአብን ዔር፤የአርኖንን ተራራ አለቆች በላ
የሴዎን ሠራዊት የዔርን ከተማ እንደሚበላ አውሬ ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል።“በሞአብ ምድር ያለውን የኤርን ከተማ አጠፋ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 21:29

ሞአብ...የኮሞስ ሕዝብ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚያመለክቱት አንድ ዓይነት ሕዝብን ነው። (ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

የኮሞስ ሕዝብ
ኮሞስ ሞአባውያን ያመለኩት የነበረ ጣዖት ነው።“ኮሞስን የሚያመልክ ሕዝብ”

የራሱ ልጆችን እርሱ ሰጠ
“እርሱ”እና “የራሱ”የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ኮሞስን ነው።

እኛ ድል አድርገናል
እዚህ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ዲቦን ድል የነሱትን እሥራኤላውያንን ነው።

ሐሴቦን ፈራርሷል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሐሴቦንን ደምስሰናታል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ከሐሴቦን...እስከ ዴቦን ድረስ...ከኖፋም አስከ ሜድባ ድረስ
እነዚህ ሁሉ በሴዎን መንግሥት ውስጥ የነበሩ ቦታዎች ናቸው።ይሄ የሚያሳየው እሥራኤላውያን የሴዎንን አገር ሁሉ ሙሉ በሙሉ አጥፍተውታል ማለት ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውንና ሆን ብሎ አጋኖ መናገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 21:31

አባረሩ
“አሳደዷቸው”

Numbers 21:33

በእነርሱ ላይ ወጡ
“አጠቋቸው”

በአሞራውያን ንጉሥ በሴዎን እንዳደረግህ እንዲሁ ታደርግበታለህ
እሥራኤላውያን ሴዎንን ፈፅመው አጥፍተዋት ነበር።“የአሞራውያንን ንጉሥ ሴዎንን እንዳጠፋህ እንዲሁ አጥፋው”

ስለዚህ ገደሉት
“ስለዚህ የእሥራኤል ሠራዊት ዓግን ገደለው።

ሰውም አልቀረለትም
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የእርሱ የሆኑት ሰዎች ሁሉ ሞቱ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሩንም ወረሱ
“የእርሱን ምድር በቁጥጥራቸው ሥር አደረጉት”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 22

1 የእስራኤል ህዝብ ከከተማዋ ከዮርዳኖስ ወንዝ ሌላ ዳርቻ ኢያሪኮ አጠገብ ወደሚገኘው የሞአብ ሜዳ ደርሰው እስኪሰፍሩ ደረስ ተጓዙ። 2 የሴፎር ልጅ ባላቅ
እስራኤል በአሞራዊያን ላይ ያደረገውን ሁሉ አየ። 3 ሞአብ የእስራኤልን ህዝብ በጣም ፈርቶ ነበር ምክንያቱም ብዙ ነበሩ፣ እናም ሞአብ በእስራኤል ህዝብ
ተሸብሮ ነበር። 4 የሞብ ንጉስ ለምድያም ሽማግሌዎች፣ “ይህ ብዙ ህዝብ፣ በሬ በሜዳ ላይ ያለን ሳር በልቶ እንደሚጨርስ በዙሪያችን ያለውን ሁሉ በልቶ
ይጨርሳል።” አለ። በዚያን ጊዜ የሴፎር ልጅ ባላቅ የሞዓብ ንጉስ ነበር። 5 እርሱም በአገሩና በወገኖቹ መሀል በኤፍራጦስ ወንዝ አጠገብ በፋቱራ
ወደተቀመጠው የቢያር ልጅ በልዓም መልዕክተኞችን ላከ። አስጠርቶትም እንዲህ አለው፣ “እነሆ፣ ከግብጽ አንድ ህዝብ ወደዚህ መጥቷል። የምድርን ፊት
ሸፍነዋል፣ ደግሞም እዚሁ አጠገቤ ናቸው። 6 ስለዚህ አሁን መጥተህ ይህን ህዝብ ርገምልኝ፣ ምክንያቱም ከእኔ አቅም በላይ ናቸው። ምናልባት ከረገምክልኝ
በኋላ እነርሱን ለማጥቃትና ከምድሪቱ ለማባረር እችል ይሆናል። የባረከው ሁሉ እንደሚባረክ አውቃለሁ፣ የረገምከው ሁሉ እንደሚረገም አውቃለሁ።” 7 ስለዚህ
የሞአብ ሽማግሌዎችና የምድያም ሽማግሌዎች የምዋርቱን ዋጋ ይዘው ሄዱ። ወደ በለዓም መጥተው የባላቅን ቃል ነገሩት። 8 በለዓምም እንዲህ አላቸው፣ “ዛሬ
ምሽት እዚህ እደሩ። ያህዌ የሚለኝን አሳውቃችኋለሁ።” ስለዚህም የሞብ መሪዎች ያን ምሽት ከበለዓም ዘንድ ተቀመጡ። 9 እግዚአብሔር ወደ በለዓም መጥቶ
እንዲህ አለው፣ “ወደ አንተ የመጡት እነዚህ ሰዎች እነማን ናቸው” 10 በለዓም ለእግዚአብሔር እንዲህ ሲል መለሰለት፣ “የሞአብ ንጉስ የሴፎር ልጅ ባላቅ፣
እነርሱን ወደ እኔ ልኳቸዋል። እንዲህም አለ፣ 11 ‘እነሆ፣ ከግብጽ የመጡ ሰዎች የምድሬን ገጽ ሸፍነዋል። አሁን መጥተህ እነርሱን ርገምልኝ። ይህ ከሆነ ምናልባት
እነርሱን መዋጋትና ማባረር እችል ይሆናል።” 12 እግዚአብሔር ለበለዓም እንዲህ መለሰለት፣ “ከእነዚህ ሰዎች ጋር መሄድ የለብህም። የእስራኤልን ህዝብ
መርገም የለብህም ምክንያቱም እነርሱ የተባረኩ ናቸው።” 13 በለዓም በጠዋት ተነስቶ ለባላቅ መሪዎች እንዲህ አላቸው፣ “ወደ ምድራችሁ ተመልሳችሁ ሂዱ
ምክንያቱም ያህዌ ከእናንተ ጋር እሄድ ዘንድ አልፈቀደልኝም። 14 ስለዚህም የሞብ መሪዎች ተመልሰው ወደ ባላቅ ሂዱ። እንደህም አሉት፣ “በለዓም ከእኛ ጋር
ለመምጣት አልፈቀደም።” 15 ባላቅ እንደገና ከመጀመሪያዎቹ መልዕክተኞች የከበሩ ብዙ መሪዎችን ላከ። 16 እነርሱም ወደ በለዓም መጥተው እንዲህ አሉት፣
“የሴፎር ልጅ ባላቅ እንዲህ ብሏል፣ ‘እባክህ ወደ እኔ ለመምጣት አንዳች ነገር አያግድህ፣ 17 ምክንያቱም እጅግ ከፍ ያለ ክፍያ እከፍልሃለሁ፣ ታላቅ ክብርም
እሰጥሃለሁ፣ ደግሞም እንዳደርገው የምትነግረኝን ሁሉ አደርጋሁ። ስለዚህ እባክህ መጥተህ ይህን ህዝብ ርገምልኝ” 18 በለዓለም ለባላቅ ሰዎች እንዲህ ሲል
መለሰላቸው፣ “ባላቅ ብርና ወርቅ የሞላበትን ቤተ መንግስቱን ቢሰጠኝ እንኳን ከአምላኬ፣ ከያህዌ ቃል አልፌ መሄድ አልችልም፣ ደግሞም እርሱ ከነገረኝ አሳንሼ
ወይም ጨምሬ አላደርግም። 19 ስለዚህ አሁን፣ እባካችሁ ያህዌ የሚለኝን ተጨማሪ ነገር አውቅ ዘንድ ዛሬ ምሽትም ደግሞ በዚህ እደሩ።” 20 እግዚአብሔር
በምሽት ወደ በለዓም መጥቶ እንዲህ አለው፣ “እነዚህ ሰዎች ወደ አንተ እስከ መጡ ድረስ ተነስተህ ከእነርሱ ጋር ሂድ። ነገር ግን እንድታደርገው የምነግርህን
ብቻ አድርግ።” 21 በለዓም በጠዋት ተነስቶ አህያውን ጫንና ከሞአብ መሪዎች ጋር ሄደ። 22 ነገር ግን በመሄዱ፣ የእግዚአብሔር ቁጣ ነደደ። የያህዌ መልአክ፣
በአህያው ላይ ተቀምጦ የሚሄደውን በለዓምን ሊቃወመው በመንገድ ላይ ቆመ። የበለዓም ሁለቱ አገልጋዮቹም አብረውት ነበሩ። 23 አህያዋ የያህዌን መልአክ
የተመዘዘ ሰይፉን ይዞ በመንገድ ላይ ቆሞ አየችው። አህያዋ ከመንገድ ዘወር ብላ ወደ ሜዳው ሄደች። በለዓለም አህያይቱን ወደ መንገድ እንድትለስ መታት። 24
የያህዌ መልአክ በመንገዱ ጠባብ መተላፊያ ላይ በወይን እርሻው መሀል፣ በስተቀኙና በስተግራው ግድግዳ ባለበት ስፍራ ቆመ። 25 አህያይቶ የያህዌን
መልአክ አየች። ወደ ግድግዳው ተጠግታ የበለዓምን እግር አጣበቀችው። በለዓም እንደገና አህያይቱን መታት። 26 የያህዌ መልአክ እንደ ገና ራቅ ብሎ ሄዶ ወደ
የትኛውም አቅጣጫ መዞሪያ በሌለበት ሌላ ጠባብ መተላፊያ ስፍራ ቆመ። 27 አህያይቱ የያህዌን መልአክ አይታ ከበለዓም በታች ተኛች። የበለዓም ቁጣ ነደደ፣
በበትሩም አህያይቱን መታት። 28 ያህዌ የአህያይቱን አፍ ስለከፈተ መናገር ቻለች። በለዓምን እንዲህ አለችው፣ “እነዚህን ሶስት ጊዜያት እንድትመታኝ የሚያደርግ
ምን ነገር አደረግሁብህ” 29 በለዓም አህያይቱን፣ “በእኔ ላይ የማይረባ ድርጊት ስለፈጸምሽ ነው። በእጄ ላይ ሰይፍ ቢኖር እወድ ነበር። በእጄ ላይ ሰይፍ ቢኖር
ኖሮ፣ ይህን ጊዜ ገድዬሽ ነበር” አላት። 30 አህያይቱ በለዓምን እንዲህ አለችው፣ “እስከ ዛሬዋ ቀን ድረስ ስትቀመጥብኝ የኖርክብኝ አህያህ አይደለሁምን? ከዚህ
በፊት እንዲህ ያለ ነገር በአንተ ላይ የማድረግ ልማድ ነበረኝን?” በለዓም “እይ” አለ። 31 ከዚያ ያህዌ የበለዓምን ዐይኖች ከፈተ፣ እናም የያህዌ መልአክ በእጁ
ሰይፉን ይዞ በመንገዱ ላይ ቆሞ አየ። በለዓም ዝቅ ብሎ በግምባሩ ተደፋ። 32 የእግዚአብሔር መልአክ እንዲህ አለው፣ “አህያህን ለምን በእዚህ ሶስት ጊዜያት
መታሀት የምቃወምህ ሆኜ መጥቻለሁ ምክንያቱም ድርጊቶችህ በፊቴ መጥፎዎች ነበሩ። 33 አህያይቱ አይታኝ በእነዚህ ሶስት ጊዜያት ከእኔ ዞር አለች። እርሷ
ዞር ባትልልኝ ኖሮ፣ በእርግጥ አንተን እገድልህና የእርሷን ነፍስ አተው ነበር።” 34 በለዓም ለያህዌ መልአክ እንዲህ አለ፣ “እኔ በድያለሁ። እኔን ተቃውመህ በፊቴ
ቆመህ እንደነበር አላወቅሁም። አሁን እንግዲህ፣ ይህ ጉዞ አንተን ደስ ካላሰኘ፣ ወደመጣሁበት እመለሳለሁ።” 35 የያህዌ መልአክ ግን በለዓምን እንዲህ አለው፣
“ከሰዎቹ ጋር ጉዞህን ቀጥል። ነገር ግን እኔ የምነግርህን ብቻ መናገር አለብህ።” ስለዚህም በለዓም ከባላቅ መሪዎች ጋር ሄደ። 36 ባላቅ የበለዓምን መምጣት
ሲሰማ፣ ሞአብ ውስጥ ወዳለችው በድንበር ላይ ወደምትገኘው አርኖን ከተማ ሊቀበለው ወጣ። 37 ባላቅ በለዓምን እዲህ አለው፣ “እንዲጠሩህ ሰዎችን ወደ
አንተ አልላኩም ነበርን? ለምን ወደ እኔ አልመጣህም? እኔ ላከብርህ አልችልምን?” 38 ከዚያም በለዓም ለባላቅ መለሰለት፣ “በእርግጥ ወደ አንተ
መጥቻለሁ፤ አሁን አንዳች ነገር ለመናገር እኔ አንዳች ሀይል አለኝን? መናገር የምችለው እግዚአብሔር በአፌ ላይ ያስቀመጠውን ቃል ብቻ ነው።” 39 በለዓም
ከባላቅ ጋር ሄደ፣ እነርሱም ወደ ቂርያት ሐጾት ደረሱ። 40 ከዚያ ባላቅ በሬዎችንና በጎችን ሰዋ፣ ለበለዓምና ከእርሱ ጋር ለነበሩ መሪዎችም ሰጣቸው። 41 ማለዳ፣
ባላቅ በለዓምን ወደ ካሞት በኣል ይዞት ሄደ። በለዓም ከዚያ ሆኖ ማየት የሚችለው በሰፈሮቻቸው ካሉት እስኤላዊያን ጥቂቶቹን ብቻ ነበር።

Numbers 22:1

በኢያሪኮ ፊት ለፊት በዮርዳኖስ ማዶ ባለው
እሥራኤላውያን የሰፈሩት ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምሥራቅ በኩል ነበር።።ኢያሪኮ ደግሞ ከወንዙ በስተ ምዕራብ በኩል ነበር።

Numbers 22:2

የሴፎር ልጅ ባላቅ
ባላቅ የሞአብ ንጉሥ ነበር።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

ሴፎር
ሴፎር የባላቅ አባት ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሞአብ ከሕዝቡ የተነሣ እጅግ ፈራ...ከእሥራኤልም ልጆች የተነሣ ደነገጠ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ዓይነት ትርጉም ያላቸው ሲሆን ሞአብ ምን ያህል እንደፈራ አፅንዖት የሚሰጡ ናቸው።(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

ሞአብ እጅግ ፈራ
እዚህ ላይ “ሞአብ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሞአብን ሕዝብ ነው።“ሞአባውያን በሙሉ ከፍተኛ የሆነ ፍርሃት ይዟቸው ነበረ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ምክኒያቱም ብዙ ስለነበሩ
“ምከኒያቱም በቁጥር ብዙዎች ነበሩ”

የሞአብም ንጉሥ የምድያምን ሽማግሌዎች እንዲህ አላቸው
ሞአባውያንና ምድያማውያን የተለያዩ ሕዝቦች ቢሆኑም በዚያን ወቅት ምድያማውያን ይኖሩ የነበሩት በሞአብ ምድር ውስጥ ነበር።

በሬ የለመለመውን ሣር እንደሚጨርስ ይህ ጭፍራ በዙሪያችን ያለውን ሁሉ ይጨርሳል
እሥራኤላውያን ጠላቶቻቸውን የሚያጠፉበትን መንገድ በመስክ ላይ ሣርን እንደሚበሉ በሬዎች ተደርገው ተገልፀዋል።(ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚያን ወቅት የሴፎር ልጅ ባላቅ የሞአብ ንጉሥ ነበር
ይሄ ዋናውን ታሪክ ስለ ባላቅ የኋላ ታሪክ መረጃ ወደ መስጠት ያዞረዋል። (የጀርባ ታሪክ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 22:5

መልክተኞችን ላከ
“ባላቅ መልዕክተኞችን ላከ”

ቢኦር
ይሄ የበለዓም አባት ሥም ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

ፋቱራ
ይሄ የአንድ ከተማ ሥም ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

የራሱ አገርና የራሱ ሕዝብ
“የበለዓም አገርና ሕዝብ”

ጠራው
“ባላቅ በለዓምን ጠራው”ባላቅ በቀጥታ ከበለዓም ጋር አልተነጋገረም።ሆኖም ሃሣቡን ያስተላለፈው በላካቸው መልዕክተኞች አማካይነት ነው።

የምድሩን ፊት ሁሉ ሸፈኑ
ይሄ ብዛታቸውን ለመገለፅ ተጋንኖ የቀረበ አነጋገር ነው።“እጅግ ብዙዎች ናቸው”(የተጋነነ ንፅፅር እና አጠቃላይነት የሚለውን ይመልከቱ)

የምድሪቱን ፊት
ይሄ የሚያመለክተው የምድርን ገፅ ነው።(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ላሳድዳቸው
“ላባርራቸው”

አንተ የመረቅኸው ምሩቅ የረገምኸውም ርጉም እንደሆነ አውቃለሁና
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሰዎችን የመባረክም ሆነ የመርገም ኃይል እንዳለህ እኔ አውቃለሁ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 22:7

የምዋርቱን ዋጋ
“የምዋርቱን ዋጋ”የሚለው አሕፅሮተ ሥምበድርጊት መልከ ሊገለፅ ይችለላል።“እሥራኤልን እንዲረግም ለበለዓም የሚከፈል ገንዘብ”(አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ በለዓምም መጡ
“ወደ በለዓምም ሄዱ”የሚለውን አባባል ልትመርጡ ትችሉ ይሆናል።(መሄድና መምጣት የሚለውን ይመልከቱ)

የባላቅንም ቃል ነገሩት
“ከባላቅ የተላከውን መልዕከት ነገሩት”

ባላቅ
ይሄ የሰው ሥም ነው።ይህንን በዘኁልቁ 22:2 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

አመጣላችኋለሁ
የበለዓም መልዕክት ልክ አንድን ዕቃ ተሸክሞ እንደሚመጣ ዓይነት ተደርጎ ነው የተገለፀው።“እነግራችኋለሁ” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 22:9

እግዚአብሔርም ወደ በለዓም መጣ
“እግዚአብሔር ለበለዓም ተገለጠለት

እነዚህ በአንተ ዘንድ የመጡት ሰዎች እነማናቸው?
እግዚአብሔር ጥያቄውን ያነሳው በአዲስ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ውይይት ለመጀመር ነው።ይሄ አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ በመግለጫ መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ወደ አንተ ስለመጡት ሰዎች ማንነት ንገረኝ” (አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ባላቅ..ሴፎር
እነዚህየሰው ሥሞችናቸው።ይህንን በዘኁልቁ 22:2 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

ሕዝቡን ተመልከት...አሳድዳቸው
በለዓም ባላቅ ለእርሱ የላከውን መልዕክት መልሶ ይናገረዋል።እነዚህን ሐረጎች በዘኁልቁ 22:5-6 ያለውን ክፍል እንዴት እንደተረጎማችኋቸው ተመልከቱ።

አሳድዳቸው
“አባርራቸው”

Numbers 22:12

የተባረከ ነውና
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የባረክኋቸው በመሆኑ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ባላቅ
ይሄ ሰው ሥም ነው።ይህንን በዘኁልቁ 22:2 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

Numbers 22:15

ወደ በለዓምም መጡ
“ወደ በለዓምም ሄዱ”የሚለውን ልትመርጡ ትችሉ ይሆናል።(መሄድና መምጣት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ባላቅ
ይሄ ሰው ሥም ነው።ይህንን በዘኁልቁ 22፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

ይሄ ሕዝብ
ይሄ ነጠላ ሥም እሥራኤላውያንንየሚያየውልክ እንደ አንድ የህዝብ ስብስብ ነው።

Numbers 22:18

ባላቅ
ይሄ ሰው ሥም ነው።ይህንን በዘኁልቁ 22፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

ባላቅ በቤቱ የሞላውን ወርቅና ብር ቢሰጠኝ
በለዓም ፈፅሞ ሊሆን የማይችል ነገርን እየገለፀ ነው።እግዚአብሔርን እንዳይታዘዝ ሊያደርገው የሚችል ነገር ሊኖር እንደማይችል አስረግጦ እየተናገረ ነው።(ተግባራዊ ሊሆኑ የማይችሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በትንሹ ወይም በትልቁ የአምላኬን የእግዚአብሔርን ቃል አተላለፍ ዘንድ አይቻለኝም
ይሄ የሚያሣየው በምንም ሁኔታ ውስጥ ቢሆን በለዓም እግዚአብሔርን ከመታዘዝ ወደ ኋላ የማይል መሆኑን ነው።

Numbers 22:21

ኮርቻውን አህያው ላይ ጫነ
ኮርቻ እንስሳት ጀርባ ላይ ለግልቢያ ሲባል የሚደረግ መቀመጫ ነው።

የእግዚአብሔርም ቁጣ ነደደ
የእግዚአብሔር ቁጣ የመጨመሩ ነገር ልክ እሣት መንደድ እንደሚጀምር ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል።ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር በኃይል ተቆጣ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውንና ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

በበለዓም ላይ ጥላቻ እንዳለው ሰው
“እንደ በለዓም ጠላት” ወይም “በለዓምን ለማስቆም”

የተመዘዘም ሠይፍ
ሠይፍ ጥቅም ላይ ሊውል ከሰገባው ወጥቷል።“ጥቃት ለማድረስ ሠይፉን ዝግጁ አደረገ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አህያይቱም ከመንገድ ፈቀቅ ብላ ወደ እርሻው ውስጥ ገባች
አህያይቱ ይህንን ያደረገችው ከእግዚአብሔር መልአክ ለመሸሽ ብላ ነው።

እርሷን ይመልሳት ዘንድ
አንዳንድ ጊዜ እንስሳት“የእርሷ”ወይም “እርሷ”በመባል ይጠቀሳሉ።“ሊመልሰው”

Numbers 22:24

ወደ ቅጥሩ ተጠጋች
ይሄ ሙከራ በመንገድ ላይ ቆሞ ከነበረው መልአክ ለማምለጥ የተደረገ ነው።

እርሷ ሄደች
አንዳንድ ጊዜ እንስሳት“የእርሷ”ወይም “እርሷ”በመባል ይጠቀሳሉ።“ሄደ”

የበለዓምን እግር ከቅጥሩ ጋር አጣበቀች
“የበለዓምን እግር ከቅጥሩ ጋር አጋጨችው”ወይም “የበለዓምን እግር ከቅጥሩ ጋር ስታጣብቀው እግሩ ተጎዳ”

Numbers 22:26

በለዓምም እጅግ ተቆጣ
የበለዓም ቁጣ የመጨመሩ ነገር ልክ እሣት መንደድ እንደሚጀምር ዓይነት ተደርጎ ነው የተገለፀው።ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።በዘኁልቁ 22፡22 ላይ ያለውን ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“በለዓም በኃይል ተናደደ”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውንና ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 22:28

እግዚአብሔርም የአህያይቱን አፍ ከፈተ
የመናገር ችሎታ አፍ ከመክፈት ጋር ተነፃፅሯል።“ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ልክ እንደ ሰው እንደሚናገር ለአህያይቱ የመናገር ችሎታን ሰጣት”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

በለዓምን ተናገረችው
“አህያይቱ በለዓምን ተናገረችው”

ከብዙ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የምትቀመጥብኝ አህያህ አይደለሁምን?
ይሄ አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ የተጠየቀበት ምክኒያት በለዓም በአህያዋ ላይ የሰራው ጥፋት ተገቢነት የሌለው መሆኑን ለመግለፅ ነው።ይሄ በመግለጫ መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ከብዙ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የምትቀመጥብኝ አህያህ ነኝ”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በውኑ እንዲህ አደርግ ዘንድ ልማዴ ነውን?
ይሄ አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ የተጠየቀበት ምክኒያት በለዓም በአህያዋ ላይ የሰራው ጥፋት ተገቢነት የሌለው መሆኑን ለመግለፅ ነው።ይሄ በመግለጫ መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ለአንተ እንደዚህ ዓይነት ባህርይ የማሳየት ልማድ አልነበረኝም”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 22:31

እግዚአብሔርም የበለዓምን ዓይኖች ከፈተ፤የእግዚአብሔርንም መልአክ አየ
የአንድ ሰው“ዓይን መክፈት” “ከማየት ችሎታ”ጋር ተነፃፅሮ ቀርቧል።“ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ለበለዓም የማየት ችሎታን ሰጠው”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

የተመዘዘም ሠይፍ ይዞ
ሠይፍ ጥቅም ላይ ሊውል ከሰገባው ወጥቷል።ይህንን በዘኁልቁ 22፡23 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“ለማጥቃት ከተዘጋጀ ሠይፉ ጋር”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በለዓም ሰገደ፤በግንባሩም ወደቀ
ይሄ የሚያሣየው በዓለም ራሱን በመልአኩ ፊት ማዋረዱን ነው።(ተምሣሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

አህያህን ሦስት ጊዜ ለምን መታህ?
ይሄ አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ የተነሳበት ምክኒያት በለዓም የሰራው ሥራ ጥፋት መሆኑን ለማሳሰብ ነው።ይሄ በመገለጫ መልክ ሊተረጎም ይችለል።“አህያህን ሦስት ጊዜ መምታት አልነበረብህም”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥላቻ እንዳለው ሰው
“ጠላትህ እንደሆነ ሰው” ወይም “ተቃዋሚምህ እንደሆነ ሰው”

ከፊቴ ፈቀቅ ባላለች በእውነት አንተን በገደልሁህ እርስዋንም ባዳንኋት ነበር
ይሄ ግምታዊ አባባል የሚያሣየው ሊከሰት ይችል የነበረን ነገርና ከአህያይቱ ድርጊት የተነሣ የበለዓም ሕይወት መትረፉን ነው።(በግምት ላይ የተመሰረቱ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Numbers 22:34

አሁን አትወድድ እንደሆነ
“ጉዞዬን እንድቀጥል የማትፈልግ ከሆነ”

ከባላቅ አለቆች ጋር
“ባላቅ ከላካቸው አለቆች ጋር” “ባላቅን” በዘኁልቁ 22፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

Numbers 22:36

አርኖን
ይሄ የወንዝ ሥም ነው።ይህንን በዘኁልቁ 21፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

በውኑ አንተን ለመጥራት አልላኩህብምን?
ይሄ አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ የተጠየቀው በለዓም በመዘግየቱ ምክኒያት ለመገሰፅ ነበር።ይሄ በመግለጫ መልክ ሊረጎም ይችላል።“በእርግጥ ሰዎች እንዲጠሩህ ልኬብህ ነበር” (ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ለምንስ ወደ እኔ አልመጣህም?
ይሄ አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ የተጠየቀው በለዓም በመዘግየቱ ምክኒያት ለመገሰፅ ነበር።ይሄ በመግለጫ መልክ ሊረጎም ይችላል።“ወደ እኔ መምጣት ነበረብህ”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በውኑ እኔ አንተን ማክበር አልችልምን?
ይሄ አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ የተጠየቀው በለዓም በመዘግየቱ ምክኒያት ለመገሰፅ ነበር።ይሄ በመግለጫ መልክ ሊረጎም ይችላል።“በእርግጥም ወደ እኔ ዘንድ በመምጣትህ ገንዘብ ልከፍልህ እንደምችል አንተ ታውቃለህ”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 22:38

በውኑ አንዳች ነገር እናገር ዝንድ እችላለሁን?
በለዓም ይሄንን ጥያቄ የሚጠይቅበት አቢይ ምክኒያት ባላቅ እንዲያደርግ የሚፈልገውን ነገርሁሉ ለማድረግ የማይችል መሆኑን ለመናገር ነው።ይሄ በመግለጫ መልክ ሊረጎም ይችላል።“ነገር ግን የምፈልገውን ነገር ሁሉ የመናገር ሥልጣን የለኝም”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር በአፌ የሚያስቀምጠውን ቃል እርሱን እናገራለሁ
ይሄ መልዕክት የሚነገረው ልክ አንድን ነገር እግዚአብሔር በአፉ ውስጥ እንደሚያስቀምጥ ዓይነት ተደርጎ ነው።“እግዚአብሔር እንድናገረው የሚፈልገው መልዕክት”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ቂርያት ሐፆት
ይሄ የከተማ ሥም ነው።

ጥቂት ሥጋ
“ከመሥዋዕቱ ጥቂት ሥጋ”

Numbers 22:41

ወደ በአል ኮረብታ
ይህንን ሃሣብ ሊገልፁ የሚችሉት 1/ይሄ በዘኁልቁ 29፡11 ላይ ካለው የማሞዝሥፍራን ያመለክታል።ማሞዝ የሚለው ቃል ከፍታ የሆነ ሥፍራ ማለት ነው።ወይም 2/ሰዎች ለበአል መሥዋዕት የሚያቀርቡበት ሌላ ሥፍራ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 23

1 በለዓም ባላቅን እንዲህ አለው፣ “በዚህ ሰባት መሰዊያዎችንና ሰባት በሬዎችን እንዲሁም ሰባት አውራ በጎችን አዘጋጅልኝ።” 2 ስለዚህም ባላቅ በለዓም
እንደጠየቀው አደረገ። ከዚያም ባላቅና በለዓም በእያንዳንዱ መሰዊያ ላይ አንድ በሬና አንድ አውራ በግ አቀረቡ። 3 ከዚያ በለዓም ባላቅን እንዲህ አለው፣ “አንተ
በሚቃጠል መስዋዕትህ አጠገብ ቁም እኔ እሄዳለሁ። ምናልባት ያህዌ ሊገናኘኝ ይመጣ ይሆናል። እርሱ የሚያሳየኝን ሁሉ እነግርሀለሁ።” ስለዚህም በለዓም
ዛፎች ወደ ሌሉበት የተራራ ጫፍ ሄደ። 4 እግዚአብሔር እርሱን ተገናኘው፣ በለዓምም ለእግዚአብሔር እንዲህ አለ፣ “እኔ ሰባት መሰዊያዎችን አበጅቻለሁ፣
ደግሞም በእያንዳንዱ ላይ አንድ በሬና አንድ አውራ በግ አቅርቤያለሁ።” 5 ያህዌ በበለዓም አፍ ላይ መልዕክት አኑሮ እንዲህ አለ፣ “ወደ ባላቅ ተመለስና እንዲህ
በለው።” 6 ስለዚህ በለዓም በሚቃጠል መስዋዕቱ አጠገብ ወደቆመው ወደ ባላቅ ከእነርሱ ጋር ወደ ነበሩት የሞአብ መሪዎች ሁሉ ተመለሰ። 7 ከዚያ በለዓም
ትንቢቱን መናገር ጀመረ እንዲህም አለ፣ “ባላቅ እኔን ከአራም አመጣኝ፣ የሞአብ ንጉስ ከምስራቅ ተራሮች አመጣኝ። ‘ና፣ ያዕቆብን ዕርገምልኝ’ አለኝ። ‘ና፣
እስራኤልን ተፈታተንልኝ’ አለኝ። 8 እግዚአብሔር ያልረገመውን እኔ እንዴት መርገም እችላለሁ? ያህዌ ያልተቃወማቸውን እኔ እንዴት መቃወም እችላለሁ? 9
ከአለቶች በላይ ሆኜ አየዋለሁ፣ ከተራሮች ላይ ሆኜ ወደ እርሱ አያለሁ። ተመልከት፣ ብቻውን የሚኖር ራሱን እንደ ተራ ህዝብ አድርጎ የማይቆጥር ህዝብ አለ። 10
የያዕቆብን ትቢያ ማን መቁጠር ይችላል ወይም ከእስራኤል ሩቡን እንኳን ማን ይቆጥራል? የጻድቁነ ሞት እኔ ልሙት፣ ደግሞም የህይወቴ መጨረሻ እንደ እርሱ
ይሁን!” 11 ባላቅ በለዓምን እንዲህ አለው፣ “ምን እያደረግክብኝ ነው ጠላቶቼን እንድትረግምልኝ አመጣሁህ፣ ነገር ግን እነሆ አንተ እነርሱን ባረካቸው።” 12
በለዓም መለሰለት እንዲህም አለ፣ “ያህዌ በአፌ ላይ ያደረገውን ብቻ ለመናገር መጠንቀቅ የለብኝምን?” 13 ስለዚህም ባላቅ እንዲህ አለው፣ “እባክህ ከእኔ
ጋር ልታያቸው ወደ ምትችልበት ሌላ ቦታ ና። ከእነርሱ ሁሉንም ሳይሆን፣ በቅርብ ያሉትን ብቻ ታያለህ። በዚያ እነርሱን ትረግምልኛለህ።” 14 ስለዚህ በለዓምን ወደ
ጾፊም ሜዳ፣ ወደ ፊስጋ ተራራ ጫፍ ይዞት ሄደና ተጨማሪ ሰባት መሰዊያዎችን አበጀ። በእያንዳንዱ መሰዊያ አንድ በሬና አንድ አውራ ጠቦት ሰዋ። 15 ከዚያ
በለዓም ባላቅን እንዲህ አለው፣ “እኔ በዚያ ያህዌን ለመገናኘት ስሄድ፣ አንተ እዚህ በሚቃጠል መስዋዕትህ አጠገብ ቁም።” 16 ያህዌ በለዓምን ተገናኝቶ በአፉ
ምልክት አኖረ። እንዲህም አለው፣ “ወደ ባላቅ ተመለስና መልዕክቴን ንገረው።” 17 በለዓም ወደ ባላቅ ተመልሶ በሚቃጠል መስዋዕቱ አጠገብ አገኘው፣
የሞአብ መሪዎችም ከእርሱ ጋር ነበሩ። ባላቅ እንዲህ ሲል ጠየቅ፣ “ያህዌ ምን ነገረህ?” 18 በለዓም ትንቢቱን መናገር ጀመረ። እንዲህም አለ፣ “ባላቅ፣ ተነስና
አድምጥ። አንተ የሴፎር ልጅ እኔን አድምጠኝ። 19 እግዚአብሔር ይዋሽ ዘንድ ሰው አይደለም፣ ወይም ሀሳቡን ይቀየር ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም። ላያደርግ
አንዳች ነገር ቃል ይገባልን? ላይፈጽመውስ አንዳች ነገር አደርጋለሁ ይላልን? 20 እነሆ፣ ለመባረክ ታዝዣለሁ። እግዚአብሔር በረከትን ለቋል፣ እኔ ልከለክል
አልችልም። 21 እርሱ በያዕቆብ ላይ አንዳች ችግር ወይም በእስራኤል ላይ ድካም አላየም። ያህዌ አምላካቸው ከእነርሱ ጋር ነው፣ የንጉሳቸውም እልልታ ከእነርሱ
ጋር ነው። 22 እግዚአብሔር እንደ ጎሽ በሆነ ሀይል ከግብጽ አወጣቸው። 23 በያዕቆብ ላይ የሚሰራ ምንም አስማት የለም፣ የትኛውም ሟርት እስራኤልን
አይጎዳም። ይልቁንም ስለያዕቆብና ስለ እስራኤል እንዲህ ይባልላቸዋል፣ ‘እግዚአብሔር ያደረገውን እዩ!’ 24 እዩ፣ ህዝቡ እንደ እንስት አንበሳ ይነሳል፣ እንደ
አንበሳ ተነስቶ ያጠቃል። ያደነውን እስኪበላ የገደለውን ደም እስኪጠጣ አያርፍም።” 25 ከዚያ ባላቅ በለዓምን እንዲህ አለው፣ “እነርሱን ባትረግማቸው እንኳን
ጨርሰህ አትባርካቸው።” 26 በልዓም ግን ባላቅን መልሶ እንዲህ አለው፣ “እንድናገር ያህዌ የነገረኝን ሁሉ መናገር እንዳለብኝ አልነገርኩህምን?” 27 ስለዚህም
ባላቅ ለበለዓም እንዲህ ሲል መለሰለት፣ “አሁን ና፣ እኔ ወደ ሌላ ስፍራ እወስድሃለሁ። ምናልባት በዚያ እነርሱን እንድትረግምልኝ እግዚአብሔር ይፈቅድልህ
ይሆናል።” 28 ስለዚህም ባላቅ በለዓምን ምድረበዳውን ቁልቁል ወደሚያይበት ወደ ፌጎር ተራራ ጫፍ ወሰደው። 29 በለዓም ባላቅን እንዲህ አለው፣ “በዚህ
ስፍራ ሰባት መሰዊያዎችን አብጅና ሰባት በሬዎች እንዲሁም ሰባት አውራ በጎች አዘጋጅ።” 30 ስለዚህ ባላቅ ባለዓም እንደነገረው አደረገ፤ በእያንዳንዱ መሰዊያ
ላይ አንድ በሬና አንድ አውራ በግ ሰዋ።

Numbers 23:1

ባላቅ
ይሄ የሞአብ ንጉሥ ነው።ይህንን በዘኁልቁ 22፡2 ላይ እንዴት
እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

ሰባትም ወይፈን ሰባትም አውራ በግ በዚህ አዘጋጅልኝ
“ሰባትም ወይፈን ሰባትም አውራ በግ ለመሥዋዕት እረድልኝ”

በመሥዋትህ ዘንድ ቆይ እኔም እሄዳለሁ
“በዚህ በመሥዋትህ ዘንድ ቆይ እኔም ራቅ ወዳለ ሥፍራ እሄዳለሁ”

Numbers 23:4

አንድ ወይፈንና አንድ አውራ በግ አሳርጌያለሁ
እነዚህን አንስሳት እንደሚቃጠል መሥዋዕት አድርጎ ስለማቅረቡ ቀደም ብሎ
ተገልጿል።“አንድ ወይፈንና አንድ በግ አዘጋጅቼ በመሥዋዕት መልክ
አቃጥያቸዋለሁ” (በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ
የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔርም ቃልን በበለዓም አፍ አደረገ
እግዚአብሔር በለዓም እንዲናገር የሚሰጠውን መልዕክት ልክ በአፉ
እንደሚያስቀምጠው ዓይነት ተደርጎ ተነግሯል።“እግዚአብሔር ለባላቅ መነገር
የሚገባውን ነገር እንዲነግረው ለበለዓም ነገረው።(ምሣሌያዊ አነጋገር
የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 23:7

ባላቅ ከአራም አመጣኝ ...የሞአብምንጉሥ ከምሥራቅ ተራሮች
እነዚህ ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው።(ተመሳሳይነት
የሚለውን ይመልከቱ)

ና ያዕቆብን እርገምልኝ ...ና እሥራኤልን ተጣላልኝ ብሎ
እነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮችተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው።በለዓም
የእሥራኤልን ሕዝብ እንዲረግም ጫና የሚያደርጉ ናቸው። (ተመሳሳይነት
የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ያልረገመውን እንዴት እረግማለሁ?እግዚአብሔር ያልተቃወመውን እንዴት
እቃወማለሁ?
ይሄ አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ በለዓም እግዚአብሔርን አልታዘዝም ለማለት ፈቃደኛ
አለመሆኑን ያሣያል።ይሄ በመግለጫ መልክ ሊተረጎም ይችላል።“ነገር ግን
እግዚአብሔር ያልረገመውን ልረግም አልችልም።እግዚአብሔር ያልተጣላውን
ልጣላ አልችልም”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Numbers 23:9

በአምቦች ራስ ላይ ሆኜ አየዋለሁ...በኮረብቶችም ላይ ሆኜ እመለከተዋለሁ
እነዚህ ሁለት ሐረጎችተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው።በለዓምከኮረብታ አናት ላይ ሆኖ እሥራኤልን ተመለከተ።(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱን አየዋለሁ..እመለከተዋለሁ
እዚህ ላይ“እርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው እሥራኤልን ነው።

ሕዝብ አለ
“የተወሰነ የሕዝብ ክፍል አለ”

በአህዛብም መካከል አይቆጠርም
ይሄ አሉታዊ አነጋገር ጥቅም ላይ የዋለው ተቃራኒው ነገር እውነት መሆኑን አስረግጦ ለመናገር ነው።“ራሣቸውን የተለየ ሕዝብ አድርገው ይቆጥራሉ”(በተዘዋዋሪ መንገድ ሃሣብን መግለፅ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 23:10

የያዕቆብን ትቢያ ማን ይቆጥራል?የእሥራኤልንስ እርቦ ማን ይቆጠራል?
“የያዕቆብ ትቢያ”ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን የእሥራኤል ሕዝብ ቁጥር የትቢያን ያህል ብዛት እንዳለው አድርጎ ይናገራል።ይሄ አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ በዓረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል።“ለቁጥር የሚያዳግቱ እሥራኤላውያን አሉ። ብዙ ከመሆናቸው የተነሣ አንድ አራተኛውን እንኳን መቁጠር የሚችል ሰው አይኖርም”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውንና ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የፃድቅ ሰው ሞት
ይሄ ሰላማዊ የሆነ ሞት እንደሆነ ግልፅ ነው።ይሄ በዚህ መልክም ሊነገርም ይችላል።“ሠላም የሞላበት የፃድቅ ሰው ሞት”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ፃድቅ ሰው ... እንደ እርሱ
ይሄ የእሥራኤልን ሕዝብ እንደ አንድ ሰው አድርጎ የሚያመለክት ገላጭ ነው። (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 23:11

ባላቅ
ይሄ የሞአብ ንጉሥ ነው።ይህንን በዘኁልቁ 22:2 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

ያደረገህብኝ ምንድነው?
ባላቅ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው በለዓምን ለመውቀስ ነበር።ይሄንን ጥያቄ በዓረፍተ ነገር መልክም መተርጎም ይቻላል።“ይህንን በእኔ ላይ አድረገሃል ብዬ አላምንም”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ተመልከት
ይሄ የሚያመለክተው የሚመጣውን አስደንጋጭ ድርጊት ነው።

እግዚአብሔር በአፌ ያደረገውን እናገር ዘንድ አልጠነቀቅምን?
በለዓም ይሄንን አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ የሚጠይቀው ለድርጊቶቹ ምክኒያት ለመሥጠት ነው።ይሄ በመግለጫ መልክ ሊተረጎም ይችላል፡“እግዚአብሔር የተናገረኝን ነገር ብቻ ለመናገር መጠንቀቅ አለብኝ”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር በአፌ ያስቀመጠውን ነገር ብቻ እናገር ዘንድ
መልዕክቱ እግዚአብሔር በአፍ ውሰጥ እንደሚያስቀምጠው ዓይነት ነገር ተደርጎ ነው የተገለፀው።ይህንንተመሳሳይ ሐረግ በዘኁልቁ 22:38 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“እግዚአብሔር የሚናገረኝን ብቻ ለመናገር”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 23:13

እዚያ ሆነህ እርገምልኝ
“እዚያ ሆነህ እሥራኤላውያንን ትረግምልኛለህ”

ወደ ፆፊምም ሜዳ
“ፆፊም”የሚለው ቃል “አጥብቆ በዓይን መከታተል”ወይም “መሰለል” የሚገልፅ የግርጌ ማሰታወሻ ላይ ተርጓሚዎቹ ማስቀመጥ ሊኖርባቸው ይችል ይሆናል።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

የፈስጋ ተራራ
ይሄ የተራራ ሥም ነው።ይህንን በዘኁልቁ 21:20 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 23:16

ቃልንም በአፉ አደረገ
ይሄ መልዕክት ልክ እግዚአብሔር በአፉ ውስጥ እንዳደረገለት ዓይነት ተደርጎ ነው የተገለፀው።ተመሰሳዩን ሐረግ በዘኁልቁ 22:38 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“መናገር ያለበትን ነገር ነገረው”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህም አለ
“ከዚያ እግዚአብሔር ተናገረ”

ባላቅ ሆይ ስማ...የሴፎር ልጅ ሆይ እድምጠኝ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን የተደጋገሙበት ምክኒያት ባላቅ ለጉዳዩ ትኩረት መሥጠት እንደሚኖርበት አፅንዖት ለመሥጠት ነው።(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

የሴፎር ልጅ
ይሄ የሚያመለክተው ባላቅን ነው።ይህንን በዘኁልቁ 22:2 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

Numbers 23:19

እርሱ ያለውን አያደርገውምን?የተናገረውንስ አይፈፅመውምን?
እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች ተመሳሳይ ሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር የሚፈፅም ስለመሆኑ አፅንዖት ይሰጣሉ።እነዚህ ሁለት አስፈላጊ የሆኑ ጥያቄዎች በዓረፍተ ነገር መልክ ሊገለፁ ይችላሉ።“ቃል የገባውን ነገር ተግባራዊ ሳያደርግ የቀረበት ጊዜ የለም።ምን ጊዜም ቢሆን አደርገዋለሁ ያለውን ነገር በትክክል ተግባራዊ ያደርገዋል”(ተመሳሳይነት የሚለውንና ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ለመባረክ ትዕዛዝን ተቀብያለሁ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር እሥራኤላውያንን እንድባርክ አዝዞኛል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 23:21

በያዕቆብ ላይ ክፋትን....በእሥራኤልም ላይ ጠማማነትን
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው።ለዚህ ፍቺ ሊሆኑ የሚችሉት1/እግዚአብሔር ለእሥራኤል የሰጠው መልካም የሆኑ ነገሮችን ብቻ ነው።ወይም2/በእነርሱ ላይ ፍርድን ያመጣ ዘንድ በእሥራኤል ላይ ምንም ዓይነት ኃጢአት አላየም።(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

የንጉሥም እልልታ በመካከላቸው አለ
“እግዚአብሔር ንጉሣቸው በመሆኑ በደስታ እልል ይላሉ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጉልበቱ አንድ ቀንድ እንዳለው በሬ ነው
ይሄ ንፅፅር የእግዚአብሔር ኃያል ጉልበት ከበሬ ጋር የሚነፃፀር መሆኑን ነው የሚያመለክተው።(ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 23:23

በያዕቆብ ላይ አስማት የለም ...በእሥራኤልም ላይ ምዋርት የለም
እነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ተመሣሣይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ማንም ሰው በእሥራኤል ላይ መርገምን ቢደርገ ሊሰራለት አይችልም ለማለት ነው።“እዚህ ላይ ያዕቆብ የሚል ቃል የሚያመለክተው እሥራኤልን ነው” (ተመሳሳይነት የሚለውንና ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ይባላል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሰዎች ሊናገሩ ይችሉ ይሆናል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ያደረገውን ተመልከቱ
እግዚአብሔር ለእነርሱ ያደረገላቸው ነገር መልካም መሆኑን የሚያመለክት ነው።“እግዚአብሔር ለእነርሱ ያደረገላቸውን መልካም ነገር ተመልክቱ!”

Numbers 23:24

እነሆ ሕዝቡ እንደ እንሥት አንበሳ ይነሳል...ይገድላል
ይህ ጥቅስ ረዥም የሆነ ምሣሌያዊ አነጋገር ሲሆን እሥራኤል ጠላቷን ድል የማድረጓን ጉዳይ ልክ አንበሣ ያደነውን ነገር እንደሚበላ ዓይነት አድርጎ ያቀርበዋል።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 23:25

ባላቅ
ይሄ የሞአብ ንጉሥ ነው።ይህንን በዘኍልቁ 22:2 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር ሁሉ አደርጋለሁ ብዬ አልተናገርሁህምን?
በለዓም ይህንን እጅግ አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ የሚጠይቀው ወደ ባላቅ ከመምጣቱ በፊትም ቢሆን እግዚአብሔርን ላለመታዘዝ ፈቃደኛ እንዳልሆነ ለባላቅ ማሳሰቢያን ለመሥጠት ነው።ይሄ በዓረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል።“ከዚያ በፊት እግዚአብሔር የሚናገረኝን ነገር ብቻ እንደምናገር ነግሬሃለሁ”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 23:28

ምድረ በዳውን ከላይ ወደሚመለከተው
ይሄ ምድረ በዳ እሥራኤል ሰፍሮበት የነበረው ሥፍራ እንደሆነ ግልፅ ነው።“እሥራኤል በነበረበት ምድረ በዳውን ከላይ ወደሚመለከተው”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 24

1 በለዓምም ያህዌ እስራኤልን መባረክ እንደፈቀደ ባየ ጊዜ፣ በሌላ ጊዜ እንደሚያደርገው አስማት ለማድረግ አልወጣም። ይልቁንም፣ ወደ ምድረበዳው ቁልቁል ተመለከተ። **2** ዐይኖቹን አቅንቶ እስራኤልን በየነገዱ ሰፍሮ አየ፣ የእግዚአብሔር መንፈስም በእርሱ ላይ መጣ። **3** ይህን ትንቢት ተቀብሎ እንዲህ ሲል ተናገረ፣ “ዐይኖቹ እጅግ የተከፈቱለት የቢዖር ልጅ በለዓም እዲህ ይላል። **4** እርሱ የእግዚአብሔርን ቃላት ይናገራል ይሰማልም። እርሱ ሁሉን ቻይ ከሆነው ዘንድ ዐይኖቹ ተከፍተውለት በፊቱ ከሚሰግድለት ዘንድ የሆነውን ራእይን ይመለከታል። **5** ያዕቆብ ሆይ ድንኳኖችህ ምንኛ ያማሩ ናቸው፣ እስራኤል ሆይ መኖሪያዎችህ እንዴት ያምራሉ! **6** እንደ ሸለቆዎች ተዘርግተዋል፣ በወንዝ ዳር እንዳሉ መናፈሻ ስፍራዎች፣ በያህዌ እንደተተከሉ ሬቶች፣ በውሃ ዳርቻ እንዳሉ ዝግባዎች ናቸው። **7** ማድጋዎቻቸው በውሃ የተትረፈረፉ ናቸው፣ ሰብላቸው ውሃ አይታጣውም። ንጉሳቸው ከአጋግ ይበልጣል፣ መንግስታቸው የከበረ ነው። **8** እግዚአብሔር እርሱን ከግብጽ አውጥቶታል። እንደ ጎሽ ብርታት አለው። የሚዋጉትን መንግስታት ይፈጃቸዋል። አጥንቶቻቸውን ይሰባብራል። በቀስቶቹ ይወጋቸዋል። **9** እንደ አንበሳ ይሰባብራቸዋል፣ እንደ ሴት አንበሳ ያደቃቸዋል። ማን ሊቋቋመው ይችላል? የሚባርኩት ሁሉ ይባረኩ፤ የሚረግሙት ሁሉ የተረገሙ ይሁኑ።” **10** የባላቅ ቁጣ በበለዓም ላይ ነደደ፣ እጆቹን አጣፍቶ በለዓምን እንዲህ አለው፣ “እኔ ጠላቶቼን እንድትረግምልኝ ጠራሁህ፣ ነገር ግን አንተ ሶስት ጊዜም ባረካቸው። **11** ስለዚህ አሁኑኑ ከእኔ ተለይተህ ወደ ቤትህ ሂድልኝ። እጅግ አድርጌ አከብርሃለሁ ብዬ ነበር፣ ነገር ግን አንዳች ሽልማት እንዳታገኝ ያህዌ ከለከለህ።” **12** ከዚያ በለዓም ለባላቅ እንዲህ ሲል መለሰለት፣ “ወደ እኔ ለላካቸው መልዕክተኞች እንዲህ ብያቸው ነበር፣ **13** ‘ባላቅ በብርና ወርቅ የተሞላውን ቤተ መንግስቱን ቢሰጠኝ እንኳን፣ ያህዌ ከተናገረው ውጭ አንዳች መጥፎ ወይም መልካም፣ ወይም አንዳች እኔ ላደርግ የምፈልገውን አልናገርም። መናገር የምችለው ያህዌ ተናገር ያለንን ብቻ ነው።’ ይህን ለእነርሱ አልተናገርኩምን? **14** ስለዚህ እነሆ አሁን ወደ ህዝቤ እመለሳለሁ። ነገር ግን አሁን በቅድሚያ ይህ ህዝብ በሚመጡት ቀናት በአንተ ህዝብ ላይ ሊያደርግ ያለውን ላስጠንቅህ።” **15** በለዓም ይህን ትንቢት መናገር ጀመረ፣ “ዐይኖቹ እጅግ የተከፈቱለት የቢዖር ልጅ በልዓም ይህን ናገራል። **16** ይህ ከእግዚአብሔር ዘንድ ቃል የሚሰማ ሰው ትንቢት ነው፣ ከልዑል ዘንድ ዕውቀት ከተሰጠው፣ ሁሉን ቻይ ከሆነው አምላክ ራዕይ ከተቀበለው፣ በተከፈተ ዐይን በፊቱ ከሚሰግደው፣ ሰው የተነገረ ትንቢት ነው። **17** እኔ እርሱን አያለሁ፣ ነገር ግን እርሱ አሁን እዚህ አይደለም። እኔ እርሱን እመለከታለሁ፣ ነገር ግን እርሱ በቅርብ አይደለም። ኮከብ ከያዕቆብ ይወጣል፣ በትረ መንግስት ከእስራኤል ይነሳል። እርሱ የሞአብን መሪዎችን ይበታትናል፣ የሴትንም ትውልዶች ያጠፋል። **18** ከዚያ እስራኤል በሃይል ድል የሚነሳው ኤዶም፤ የእስራኤል ርስት ይሆናል፣ ደግሞም የእስራኤል ጠላት የሆነው ሴይር፣ የእነርሱ ርስት ይሆናል፣ **19** ከያዕቆብ ግዛት ያለው ንጉስ ይወጣል፣ እርሱም ከከተማቸው የተረፉትን ቅሬታዎች ያጠፋል።” **20** ከዚያ በለዓም አማሌቅን ተመልክቶ ትንቢት መናገር ጀመረ። እንዲህም አለ፣ “አማሌቅ ታላቅ ህዝብ ነበር፣ነገር ግን መጨረሻው ጥፋት ይሆናል።” **21** ከዚያ በለዓም ወደ ቄናውያን ተመልክቶ ትንቢቱን ጀመረ። እንዲህም አለ፣ “የምትኖርበት ስፍራ አስተማማኝ ነው፣ ጎጆችህም በአለቶች መሀል ነው። **22** ሆኖም ግን እናንተ ቄናውያን አሶር ምርኮ አድርጎ ሲወስዳችሁ ትደመሰሳላችሁ።” **23** ከዚያ በለዓም የመጨረሻውን ትንቢቱን መናገር ጀመረ። እንዲህም አለ፣ “አወይ! እግዚአብሔር ይህን ሲያደርግ ማን ይተርፋል? **24** መርከቦች ከኪቲም ዳርቻዎች ይመጣሉ፤ አሶርን ያጠቃሉ ዔቦርን ይይዛሉ፣ ነገር ግን እነርሱም ደግሞ መጨረሻቸው መደምሰስ ነው። **25** ከዚያ በለዓም ተነስቶ ሄደ። ወደ ቤቱ ተመለሰ፣ ባላቅም ተነስቶ ሄደ።

Numbers 24:2

ዓይኖቹን አነሳ
“ዓይኖቹን አነሳ”የሚለው ቃል ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ወደ ላይ መመልከት ማለት ነው።(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔርም መንፈስ በእርሱ ላይ መጣ
ይሄ ማለት ትንቢትን መናገር ይችል ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ሙሉ በሙሉ ተቆጣጠረው ማለት ነው።

ይህንን ትንቢት ተቀበለ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር ይህንን ትንቢት ሰጠው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

የቢዖር ልጅ በለዓም
ቢዖር የበለዓም አባት ነበር።ይህንን በዘኁልቁ 22፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

ዓይኖቹ የተከፈቱለት
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር የሚያሣየው በሚገባ ማየቱንና መገንዘቡን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 24:4

አጠቃላይ መረጃ
በለዓም በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ሆኖ ትንቢት መናገሩን ይቀጥላል።

እርሱ ይናገራል...እርሱ ያያል...እርሱ ይሰግዳል
እዚህ ላይ በለዓም ራሱን የሚጠራው“እርሱ” እያለ ነው።

እርሱ ይሰግዳል
ይሄ የትህትና ድርጊት ነው።(ተምሣሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ዓይኖቹ የተከፈቱለት
“ዓይኖቹ የተከፈቱለት”የሚለው ቃል ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን በለዓም እግዚአብሔር መናገር የፈለገውን ነገር የማወቅ ችሎታ ተሰጥቶታል ለማለት ነው።(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ያዕቆብ ሆይ ድንኳኖችህ፤እሥራኤል ሆይ ማደሪያዎችህ ምንኛ ያምራሉ?
እነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው።ለበለዓም የእሥራኤል ሰፈር ውብ እንደሆነበት አስረግጠው የሚናገሩ ናቸው። (ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 24:6

አጠቃላይ መረጃ
በለዓም በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ሆኖ ትንቢት መናገሩን ይቀጥላል።

በሸለቆዎች ተዘርግተዋል
በለዓም እሥራኤልን በሚመለከት ሸለቆዎቹን እንኳን መሸፈን እስኪችሉ ድረስ ዘንድ በቁጥር እጅግ ብዙ እንደሆኑ አድርጎ ነው የሚናገረው።(ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በወንዝ ዳር እንዳሉ አትክልቶች
በለዓም እሥራኤላውያንን በቂ ውኃ እንደሚጠጡና የተትረፈረፈ ምርትን እንደሚያስገኙ አትክልቶች አድርጎ ያቀርባቸዋል።(ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር እንደተከለው እሬት
የእሬት አትክልቶች መልካም የሆነ ሽታ ያላቸው በደረቅ የአየር ሁኔታ ውስጥ እንኳን በሚገባ ማደግ የሚችሉ ናቸው።በለዓም እሥራኤላውያን እንደ እሬት አትክልቶች እንደሚያድጉና መልካም እንደሚሆኑይናገራል።ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር የተከለው እሬት”(ያልታወቁ ነገሮችን መተርጎም፤ተነፃፃሪ የሚለውንና ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

በውኃም ዳር እንዳሉ ዘግባዎች
ዝግባ በእሥራኤል ውስጥ ከነበሩት ዛፎች ትልቁ ነው።በለዓም እሥራኤላውያን ልክ ውኃ እንደሚጠጣ ዝግባ ዛፍ ግዙፍ ሆነው እንዳደጉ ዓይነት አድርጎ ይናገራል።(ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 24:7

አጠቃላይ መረጃ
በለዓም በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ሆኖ ትንቢት መናገሩን ይቀጥላል።

ውኃ ይፈስሳል...በብዙ ውኖች ይሆናል
ብዛት ያለው ውኃ በምድር ላይ እንዳሉና እግዚአብሔር እንደባረካቸው ሰብሎች ተቆጥሯል።“እግዚአብሔር ለሰበሎቻቸው ይሆን ዘንድ ብዙ ውኃ በመሥጠት ይባርካቸዋል”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ዘሩም በብዙ ውሆች ይሆናል
በሚገባ ውኃ የጠጣ ዘር የሚለው ቃል የሚያመለክተው የተትረፈረፈ ሰብል ይኖራቸው ዘንድ የእግዚአብሔር በረከት በእነርሱ ላይ የሚመጣ መሆኑን ነው።“ጤናማ የሆኑ ሰብሎችን ያበቅሉ ዘንድ ለሚዘሩት ዘር ከበቂ በላይ የሆነ ውኃን ያገኛሉ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሡም ከፍ ከፍ ይላል...መንግሥቱም ይከበራል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ከሌሎች አገራት ይልቅ እጅግ እንደሚባርካቸው አፅንዖት የሚሰጥ ነው።(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሥም ከአጋግ ይልቅ ከፍ ከፍ ይላል
“ከፍ ከፍ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ታላቅ የሆነ ክብርና ሥልጣንን ነው። ይሄ የሚያመለክተው ወደፊት የሚነሣው የእሥራኤል ንጉሥ ከአጋግ ይልቅ የበለጠ ክብርና ሥልጣን የሚኖረው መሆኑን ነው።አጋግ የአማሌቃውያን ንጉሥ ነበር።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውንና (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ))

መንግሥቱም ይከበራል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሌሎች ሰዎች ለመንግሥታቸው ክብርን ይሰጣሉ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 24:8

አጠቃላይ መረጃ
በለዓም በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ሆኖ ትንቢት መናገሩን ይቀጥላል።

እግዚአብሔር አውጥቶታል
“እግዚአብሔር እሥራኤላውያንን አውጥቷቸዋል”

ጉልበቱ አንድ ቀንድ እንዳለው ነው
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር አፅንዖት የሚሰጠው እሥራኤላውያን ታላቅ የሆነ ጉልበት ያላቸው መሆኑን ነው።(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጠላቶቹን አህዛብን ይበላል
በለዓም እሥራኤላውያንን ልክ ዱር አውሬዎች ጠላቶቻቸውን ከሚበሉት አበላል ጋር አነፃፅሯቸዋል።ይሄ ማለት ጠላቶቻቸውን ያጠፏቸዋል ማለት ነው። (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 24:9

አጠቃላይ መረጃ
በለዓም በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ሆኖ ትንቢት መናገሩን ይቀጥላል።

እንደ አንበሳ አርፎ ተኝቷልእንደ እንስቲቱም አንበሳ ተጋድሟል
በዚህ ፈሊጣዊ አነጋገር ውስጥ በለዓም እሥራኤላውያንን ከሴትና ከወንድ አንበሳ ጋር መሳስላቸዋል።ይሄ ማለት አደገኞችና ሁልጊዜ ለማጥቃት ዝግጁ ናቸው ማለት ነው።(ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)

ማን ያስነሣዋል?
በለዓም ይህንን ጥያቄ የሚያነሳው ማንም ሰው ቢሆን እሥራኤልን እንዳያስቆጣ ለማስጠንቀቅ ነው።ይሄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል።“ማንም ቢሆን እርሱን ለመረበሽ ድፍረቱ አይኖረውም”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የሚመርቅህ ሁሉ የተመረቀ ይሁን፤የሚረግምህም ሁሉ የተረገመ ይሁን
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር እሥራኤላውያንን የሚባርኩትን ይባርክ፤የሚረግሙትንም ይርገም”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 24:10

የባላቅ ቁጣ ነደደ
የባላቅ ቁጣ የመንደዱ ጉዳይ ልክ ሊነድድ እነደጀመረ ዓይነት እሣትተደርጎ ተገልጿል።ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ባላቅ በኃይል ተናደደ”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውንገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

እጆቹንም አጨበጨበ
ይሄ የታላቅ ብስጭትና ንዴት ምልክት ነው።(ተምሣሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 24:12

ባላቅ በቤቱ የሞላውን ብርና ወርቅ ቢሰጠኝ
ባላቅ እየገለፀ ያለው ፈፅሞ ሊሆን የማይችልን ነገር ነው።ይሄ ዓረፍተ ነገር አስረግጦ የሚናገረው በምንም ዓይነት መንገድ በለዓም ለእግዚአብሔር እንዳይታዝ የሚያደርገው ነገር የማይኖር መሆኑን ነው።(ምናባዊ ሁኔታዎች)

ለላክሃቸው አልተናገርኩምን?
በለዓም ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ቀደም ሲል የተናገረውን ለባላቅ ለማሳሰብ ነው።ይሄ አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ በዓረፍተ ነገር መልክም ሊተረጎም ይችላል።“ይህንን ነግሬያቸዋለሁ”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ይሄ ሕዝብ
“እሥራኤላውያን”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Numbers 24:15

የቢዖር ልጅ በለዓም
ቢዖር በለዓም አባት ነበረ።ይህንን በዘኁልቁ 22፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

ዓይኖቹም የተከፈቱለት
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር የሚያመለክተው በሚገባ የሚያይና የሚረዳ መሆኑን ነው።ይህንን በዘኁልቁ 24፡3 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የልዑልንም ዕውቀት የሚያውቅ
“ዕውቀት”የሚለው ረቂቅ ሥም በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ታላቁ እግዚአብሔር የገለጠለትን ነገር የሚያውቅ ሰው”(አሕፅሮተ ሥሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ይሰግዳል
ይሄ ለእግዚአብሔር የመገዛት ምልክት ነው።(ተምሣሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 24:17

አጠቃላይ መረጃ
በለዓም ከአራቱ ትንቢቶች መካከል አንዱን መናገር ይጀምራል።

እርሱን አየዋለሁ አሁን ግን አይደለም፤እርሱን እመለከተዋለሁ በቅርብ ግን አይደለም
እነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው።በለዓም ወደፊት ስለሚከሰተው ነገር ራዕይ አየተመለከተ ነው።“እርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የወደፊቱን የእሥራኤል መሪ ነው።(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

ከያዕቆብ ኮከብ ይወጣል
እዚህ ላይ“ኮከብ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በእሥራኤል ላይ ሥልጣን የሚይዘውን ንጉሥ ነው።(ተምሣሌታዊ ቋንቋ የሚለውን ይመልከቱ)

ከያዕቆብ
እዚህ ላይ“ያዕቆብ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የያዕቆብን ትውልድ ነው።“ከያዕቆብ ትውልድ መካከል”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ከእሥራኤል በትር ይነሳል
ይሄ ከመጀመሪው ዓረፍተ ነገር ጋር ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያለው።እዚህ ላይ “በትር”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ብርቱ የሆነ ንጉሥን ነው። (ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

ከእሥራኤል
እዚህ ላይ“እሥራኤል”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የወደፊት እሥራኤላውያንን ነው።“ወደፊት ከሚወለዱት እሥራኤላውያን መካከል”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

የሞዓብንም ማዕዘኖች ይመታል
ለዚህ ፍቺ ሊሆኑ የሚችሉት 1/ሞዓብ መሪዎችን አናት ይመታል2/የሞዓብን መሪዎች ያጠፋል።

የሤትንም ልጆች
ይሄ የሤት ዝርያዎች የሆኑ ሞአባውያንን የሚመለከት ነው።

Numbers 24:18

አጠቃላይ መረጃ
በለዓም የመጀመሪዎቹን አራት ትንቢቶች መናገር ያበቃል።

ኤዶም ርስቱ ይሆናል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እሥራኤላውያን ኤዶምን በቁጥጥራቸው ሥር ያደርጓታል።”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 24:20

በለዓም አማሌቅን አይቶ
እዚህ ላይ“አማሌቅ የሚለው ቃል የሚያመለክተው የአማሌቅን ሕዝብ ነው። ራዕዩ የቀጠለው ወደ አሜሌቃውያን አቅጣጫ ከተመለከተ በኋላ ሲሆን ከዚያ በኋላ ስለ አማሌቃውያን መተንበዩን ይቀጥላል”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ ፍፃሜ ግን
ነጠላ ሥም ጥቅም ላይ የዋለበት ምክኒያት አማሌቃውያን እንደ አንድ ግለሰብ በመታየታቸው ነው።(የመጀመሪያ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ አካል የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 24:21

ቄናውያን
ይሄ ሥም የቃየን ትውልድ ሆነ ሕዝብ ሥም ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

ማደሪያህ የፀና ነው
“የምትኖርበት ሥፍራ ከባድ መከላከያ ያለው ነው”

ጎጆህም በአምባ ላይ ተሰርቷል
ይሄ ምሣሌያዊ አነጋገር ሲሆን ደህንነቱ በተጠበቀ ሥፍራ ላይ መኖር ማለት ነው።“የምትኖርበት ሥፍራ ዓለታማ በሆኑ ከፍታ ሥፍራዎች ላይ እንዳለ ወፍ ጎጆ ደህንነቱ የተጠበቀ ነው”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን አሦር እስኪማርክህ ድረስ ቄናዊው ለጥፋት ይሆናል
እዚህ ላይ የቄናውያን መጥፋት በእሣት እንደሚቃጠሉ ዓይነት ሆኖ ተገልጿል። ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ነገር ግን እናንተ ቄናዊያን አሦራውያን አንድ ነገር በእሣት እንደሚጠፋ ያጠፏችኋል፤በምርኮኝነትም ይወስዷችኋል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 24:23

እገዚአብሔር ይህንን ሲያደርግ አወይ ማን በይወት ይኖራል?
ይሄ አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ በዓረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል።“እግዚአብሔር ይህንን በሚያደርግበት ወቅት ማንም በሕይወት አይኖርም”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ኪቲም
ይሄ በሜዲተራንያን ባህር ውስጥ የሚገኝ የአንድ ደሴት ከተማ ሥም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱም ደግሞ ወደ ጥፋት ይመጣሉ
“ጥፋት”የሚለው ረቂቅ ሥም በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር እነርሱንም ያጠፋቸዋል”(አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

ባላቅ
ይሄ የሞአብ ንጉሥ ሥም ነው።ይህንን በዘኁልቁ 22፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 25

1 እስራኤል በሰጢም ተቀመጠ፣ ወንዶቹም ከሞዓብ ሴቶች ጋር ተኙ፣ **2** ይህም ሞአባዊያኑ ህዝቡን ለእነርሱ አማልዕክት የተሰዋውን ስለጋበዟቸው ነው። ስለዚህ ህዝቡ ለጣኦት የተሰዋውን በሉ ደግሞም ለሞአባውያን አማልዕክት ሰገዱ። **3** የእስራኤል ወንዶች የፌጎርን በኣል በማምለክ ተባበሩ፣ እናም የያህዌ ቁጣ በእስራኤል ላይ ነደደ። **4** ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ “ብርቱ ቁጣዬ ከእስራኤል ይርቅ ዘንድ የህዝቡን መሪዎች ሁሉ ግደልና እነርሱን በቀን ብርሃን ለማጋለጥ ስቀላቸው።” **5** ስለዚህም ሙሴ ለእስራኤል መሪዎች እንዲህ አለ፣ “እያንዳንዳችሁ የፌጎርን በኣል በማመልክ የተባበሩትን ሰዎቻችሁን ግደሉ።” **6** ከዚያ ከእስራኤል ወንዶች አንዱ ቀርቦ ከቤተሰቡ አባላት ጋር አንዲት ምድያማዊት ሴት አመጣ። ሙሴና መላው የእስራኤል ህዝብ እያዩ በመገናኛው ድንኳን መግቢያ ሆነው እያለቀሱ ሳለ ይህ ሆነ። **7** የአሮን ልጅ፣ የአልዓዛር ልጅ ካህኑ ፊንሀስ ይህን ሲመለከት፣ ከማህበሩ መሀል ጦሩን በእጁ ይዞ ተነሳ። **8** እርሱም ወደ ድንኳኑ እስራኤላዊውን ሰው ተከትሎ ገብቶ የእስራኤላዊውን ወንድና የምድያማዊቷን ሴት የሁለቱንም አካላት በአንድነት በጦሩ ወጋ። ስለዚህም እግዚአብሔር በእስራኤል ህዝብ ላይ የላከው መቅሰፍት አቆመ። **9** በመቅሰፍቱ የሞቱት በቁጥር ሃያ አራት ሺ ነበሩ። **10** ያህዌ ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው፣ **11** “ካህኑ፣ የአሮን ልጅ የአልአዛር ልጅ ፊንሀስ፣ ቁጣዬን ከእስራኤል ህዝብ አርቋል ምክንያቱም በእነርሱ መሃል የእኔን ቅንአት ቀንቷል። ስለዚህ የእስራኤልን ህዝብ በቁጣዬ ፈጽሞ አላጠፋኋቸውም። **12** ስለዚህ እንዲህ በል፣ ‘ያህዌ እንዲህ ይላል፣ “እነሆ፣ ለፊንሐስ የሰላሜን ኪዳን እሰጠዋለሁ። **13** ለእርሱና ከእርሱ በኋላ ለትውልዱ፣ ዘለዓለማዊ የክህነት ኪዳን ይሆናል፤ ምክንያቱም እርሱ ለእኔ ለአምላኩ ለእግዚአብሔር ቀንቷል። ለእስራኤል ህዝብ አስተሰርይዋል።” **14** ከምድያማዊቷ ሴት ጋር የተገደለው የእስራኤላዊ ሰው የሰሉ ልጅ ስም ዘንበሪ ሲባል፣ የስምኦናውያን አባቶች ቤተሰብ መሪ ነበር። **15** የተገደለችው የምድያም ሴት ስም ከስቢ ነበር፣ እርሷም ከምድያም ቤተሰብ የጎሳው መሪ የሱር ሴት ልጅ ነበረች። **16** ስለዚህም ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ **17** ”ምድያማዊያንን እንደ ጠላት ቆጥራችሁ አጥፏቸው፣ **18** እነርሱ በአታላይነታቸው እንደ ጠላት አስተናግደዋችኋልና። በፌጎር በሆነውና በእናታቸው በከስቢ ጉዳይ በፌጎር ምክንያት በመቅሰፍቱ ቀን በተገደለችው በምድያም አለቃ ልጅ ወደ ክፉ መርተዋችኋል።”

Numbers 25:1

ሰጢም
ይሄ በሞአብ ውስጥ የሚገኝ የቦታ ሥም ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰገዱ
ይሄ የአምልኮ ሥርዓት ድርጊት ነው።(ተምሣሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ብኤልፌጎር
ብኤልፌጎር የተራራ ሥም ነው።ይህንን በዘኁልቁ 23፡28 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

የእግዚአብሔርም ቁጣ ነደደ
የእግዚአብሔር ቁጣ መንደድ ከሚጀምር እሣት ጋር ተመሳስሎ ተነግሯል።ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።ይህንንሐረግ በዘኁልቁ 22፡20 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“እግዚአብሔር በጣም ተናደደ”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውንና ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 25:4

የእሥራኤል መሪዎች ሁሉ
ይሄ የሚያመለክተው ጣዖትን በማምለክ ጥፋተኛ የሆኑ መሪዎችን ነው።የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“ጣዖትን በማምለክ ጥፋተኛ የሆኑ የሕዝብ መሪዎች ሁሉ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በፀሐዩ ፊት ወስደህ
ይሄ ማለት የሕዝቡ መሪዎች እነዚህን ሰዎች ከገደሉ በኋላ ሬሣቸውን ሰዎች ሁሉ ሊያዩ በሚችሉበት ሥፍራ ላይ ይተውታል ማለት ነው።

የእሥራኤል መሪዎች
“በጣዖት አምልኮ ውስጥ ያልተሳተፉ የእሥራኤል መሪዎች”

ፌጎር
ፌጎር የተራራ ሥም ነው።ይህንን በዘኁልቁ 23፡28 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

Numbers 25:6

ምድያማዊቱን አንዲቱን ሴት ወደ ወንድሞቹ አመጣት
ይሄ የሚያመለክተው ወደ ሠፈሩ ከአርሷ ጋር ወሲባዊ ግንኙነት ለማድረግ ወደ ሠፈሩ ይዟት መምጣቱን ነው።የዚህ ሙሉ ትርጉም የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“ከምድያማዊቷ ሴት ጋር አብሮ ለመተኛት ወደ እሥራኤላውያን ሠፈር አመጣት”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በእሥራኤል ልጆች ማህበር ዓይን ፊት
“ዓይን ፊት” የሚለው ቃል ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ስለ ጉዳዩ ሰምተዋል ወይም ጉዳዩን አውቃውታል ማለት ነው።

አልዓዛር
ይሄ የአሮን ልጅ ሥም ነው።ይህንን በዘኁልቁ 3፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

Numbers 25:8

ተከትሎ ገባ
“ፊንሐስ ተከትሎ ገባ”

Numbers 25:10

ቁጣዬን ከእሥራኤል ልጆች መለሰ
የእግዚአበሔር ቁጣ ለመቆም እንዲችል ወደ አንድ ሥፍራ በአካል መገፋት እንዳለበት ዓይነት ነገር ተደርጎ ነው የሚነገረው።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔም የእሥራኤልን ልጆች በቅንዓቴ አላጠፋሁም
እግዚአብሔር እዚህ ላይ የተገለፀው ልክ የእሥራኤልን ሕዝብ እንደሚበላ ጨካኝ አውሬ ተደርጎ ነው።“በእጅጉ የተናደድኩ ቢሆንም የእሥራኤልን ሕዝብ ግን አላጠፋሁም”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Numbers 25:12

ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል።ለፊንሐስ እሰጠዋለሁ...የእሥራኤልን ሕዝብ
ይሄ የእግዚአብሔርን ንግገር ካለፈው ጥቅስ እንዲቀጥል ያደርገዋል።ይሄ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ አለው።ቀጥተኛ የሆኑት ጥቅሶች ቀጥተኛ እንዳልሆኑ ጥቅሶች ሊገለፁ ይችላሉ።(በጥቅሶች ውስጥ ጥቅሶችና ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ጥቅሶች የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 25:14

አሁን
ይሄ ዋናውን ታሪክ ወደ ጀርባ ታሪክ በመቀየር ስለ ዘንበሪና ስለ ከስቢ ያወሳል። (የጀርባ ታሪክ የሚለውን ይመልከቱ)

የተገደለው
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ፊንሐስ የገደለው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ዘንበሪ...ሰሉ...ሱር
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

ከስቢ
ይሄ የአንዲት ሴት ሥም ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 25:16

በሸነገሉት ሸንገላ
“መሸንገል”የሚለው ረቂቅ ሥም እንደ ሥም ሊገለፅ ይችላል።“እናንተን በማታለል”(አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ክፋት መሯችሁ
“ይህንን ክፉ ሥራ እንድትሰሩ አግቧቿችሁ”

በፌጎር ጉዳይ ..በፌጎር ነገር
እነዚህ ሁለቱም ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ሃሣብ ያላቸው ሲሆን እነዚህ ነገሮች የተከናወኑት በፌጎር ተራራ እንደሆነ ይገልፃሉ።

ፌጎር
ፌጎር የተራራ ሥም ነበር።ይህንን በዘኁልቁ 23፡28 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

የተገደለው
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ፊንሐስ የገደለው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 26

1 ከመቅሰፍቱ በኋላ እንዲህ ሆነ፣ ያህዌ ለሙሴና ለካህኑ ለአሮን ልጅ ለአልዓዛር እንዲህ አላቸው። **2** “የእስራኤልን ማህበረሰብ ሁሉ ቁጠሩ፣ ሀያ አመትና ከዚያ በላይ ዕድሜ ያላቸውን፣ ለእስራኤል ለመዋጋት ወደ ጦርነት መውጣት የሚችሉትን ሁሉ በየአባቶቻቸው ቤቶች ቁጠሯቸው።” **3** ስለዚህም ሙሴና ካህኑ አልዓዛር በሞአብ ሜዳ በዮርዳኖስ አጠገብ ኢያሪኮ ሳለ ለህዝቡ እንዲህ ሲሉ ተናገሩ፣ **4** “ከሃያ አመት ጀምሮ ከዚያ በላይ ዕድሜ ያላቸውን ከግብጽ ምድር የወጡትን ያህዌ ሙሴንና የእስራኤል ሰዎችን እንዳዘዘው ሁሉ ቁጠሯቸው።” **5** ሮቤል የእስራኤል በኩር ነበር። ከወንድ ልጁ ከሄኖክ የሄኖካውያን ጎሳዎች መጡ። ከፈለስ የፈለሳውያን ጎሳ መጡ። **6** ከአስሮን የአስሮናውያን ጎሳ መጡ። ከከርሚ የከርማውያን ጎሳ መጡ። **7** እነዚህ የሮቤል ጎሳ ትውልዶች ነበሩ፣ ቁጥራቸው 43730 ወንዶች ነበሩ። **8** ኤልያብ የፈሉስ ልጅ ነበር። **9** የኤልያብ ወንዶች ልጆች ነሙኤል፣ ዳታን፣ እና አቤሮን ነበሩ። እነዚህ ቆሬን ተከትለው ሙሴንና አሮንን በመቃወም በያህዌ ላይ ያመጹት እነዚያው ዳታንና ኤብሮን ነበሩ። **10** ሁሉም የእርሱ ተከታዮች ሲሞቱ፣ ምድር አፏን ከፍታ ከቆሬ ጋር ሁሉንም በአንድነት ዋጠቻቸው። በዚያ ጊዜ፣ በእሳት መቀጣጫ የሆኑትን 250 ወንዶችን በላች። **11** ነገር ግን የቆሬ የዘር ሀረግ አልጠፋም። **12** የስምዖን ትውልዶች እዚህ ነበሩ፡ በነሙኤል በኩል፣ የነሙኤላውያን ጎሳ፣ በያሚን በኩል፣ የያሚናውያን ጎሳ፣ በያኪን በኩል የያኪናውያን ጎሳ፣ **13** በዛራ በኩል የዛራውያን ጎሳ፣ በሳኡል በኩል የሳኡላውያን ጎሳ ነበሩ። **14** እነዚህ የስምዖን ጎሳ ትውልዶች ነበሩ፣ ቁጥራቸው 22200 ወንዶች ነበሩ። **15** የጋድ ጎሳ ትውልዶች እነዚህ ነበሩ፡ በጽፎን በኩል የጽፎናውያን ጎሳ፣ በሐጊ በኩል የሐጋውያን ጎሳ፣ በሺኒ በኩል፣ የሺናውያን ጎሳ፣ **16** በኤስና በኩል፣ የኤሶናውያን ጎሳ፣ በዔሪ በኩል የዔራውያን ጎሣ፣ **17** በአሮዲ በኩል የሮዳውያን ጎሳ፣ በአርኤሊ በኩል፣ የአርኤላውያን ጎሳ። **18** እነዚህ የጋድ ጎሳ ትውልድ ነበሩ፣ ቁጥራቸው 40500 ወንዶች ነበሩ። **19** የይሁዳ ልጆች ዔር እና አውናን ነበሩ፣ እነዚህ ወንዶች ግን በከነዓን ምድር ሞተዋል። **20** የይሁዳ ጎሳ ሌሎች ትውልዶች እነዚህ ነበሩ፣ በሴሎም በኩል፣ የሴሎማውያን ጎሳ፣ በፋሬስ በኩል፣ የፋሬሳውያን ጎሳ፣ እና በዛራ በኩል የዛራውያን ጎሳ ነበሩ። **21** የፋሬስ ትውልዶች እነዚህ ነበሩ በኤስሮም በኩል የኤስሮማውያን ጎሳ፣ በሐሙል በኩል፣ የሐሙላውያን ጎሳ። **22** እነዚህ የይሁዳ ጎሳ ትውልዶች ነበሩ፣ ቁጥራቸው 76500 ነበሩ። **23** የይሳኮር ጎሳዎች ትውልዶች እነዚህ ነበሩ። በቶላ በኩል የቶላውያን ጎሳ፣ በፋዋ በኩል ቦፋውያን ጎሳ፣ **24** በያሱብ በኩል፣ የያሱባውዩን ጎሳ፣ በሺምሮን በኩል፣ የሺምሮናውያን ጎሳ። **25** እነዚህ የይሳኮር ጎሳዎች ነበሩ፣ ቁጥራቸው 64300 ወንዶች ነበሩ። **26** የዛብሎን ጎሳዎች ትውልዶች እነዚህ ነበሩ። በሴሬድ በኩል የሴሬዳውያን ጎሳ፣ በኤሎን በኩል የኤሎናውያን ጎሳ፣ በያህልኤል በኩል የያህልኤላውያን ጎሳ። **27** እነዚህ የዛብሎን ጎሳዎች ነበሩ፣ ቁጥራቸው 60500 ወንዶች ነበሩ። **28** የዮሴፍ ጎሳ ትውልዶች ምናሴና ኤፍሬም ነበሩ። **29** የምናሴ ትውልዶች እነዚህ ነበሩ፡ በማኪር በኩል፣ የማኪራውያን ጎሳ (ማኪር የገለዓድ አባት ነበር) ፣ በገለዓድ በኩል፣ የገለዓዳውያን ጎሳ ነበሩ። **30** ትውልዶች እነዚህ ነበሩ፡ በኢዔዝር በኩል የኢዔዝራውያን ጎሳ፣ በኬለግ በኩል የኬሌጋውያን ጎሳ፣ **31** በእስራኤል በኩል የእስራኤላውያን ጎሳ፣ በሴኬም በኩል፣ የሴካማውያን ጎሳ፣ **32** በሸሚዳ በኩል፣ የሸሚዳውያን ጎሣ፣ በኦፌር በኩል የኦፌራውያን ጎሣ፣ **33** ልጅ ሰለጳዓድ ወንዶች ልጆች አልነበሩትም፣ ነገር ግን ሴቶች ልጆች ብቻ ነበሩት። የሴት ልጆቹ ስሞች እነዚህ ነበሩ፡ ማህለህ፣ ኑዓ፣ ዔግላ፣ ሚልካና ቲርዳ። **34** እነዚህ የምናሴ ጎሳዎች ነበሩ፣ ቁጥራቸው 52700 ወንዶች ነበሩ። **35** የኤፍሬም ጎሳዎች ትውልዶች እነዚህ ነበሩ፡ በሲቱላ በኩል፣ የሱቱላውያን ጎሣ፣ በቤኬር በኩል የቤኬራውያን ጎሣ፣ በታሐን በኩል፣ የታሐናውያን ጎሣ ነበሩ። **36** የሱቱላ ትውልዶች እነዚህ ነበሩ፡ በዔዴን በኩል፣ የዔዴናውያን ጎሣ ነበሩ። **37** እነዚህ የኤፍሬም ጎሣ ትውልዶች ነበሩ፡ ቁጥራቸው 32500 ወንዶች ነበሩ። እነዚህ የዮሴፍ ትውልዶች፣ በየጎሣቸው ተቆጠሩ። **38** የብንያም ጎሣ ትውልዶች እነዚህ ነበሩ፡ በቤላ በኩል፣ የቤላውያን ጎሣ፣ በአስቤል በኩል የአስቤላውያን ጎሣ፣ በኢኪራን በኩል፣ የኢኪራናውያን ጎሣ፣ **39** በሶፋን በኩል፣ የሶፋናውያን ጎሣ፣ በሑፋም በኩል፣ የሑፋፋማውያን ጎሣ ነበሩ። **40** የቤላ ወንዶች ልጆች አርድ እና ናዕመን ነበሩ። ከአርድ የአርዳውያን ጎሣ መጣ፣ ከናዕማን የናዕመናውያን ጎሣ መጣ። **41** የብንያም ጎሣ ትውልዶች እነዚህ ነበሩ። ቁጥቸው 45600 ወንዶች ነበሩ። **42** የዳን ትውልዶች እነዚህ ነበሩ፡ በስምዔ በኩል፣ የስምዔያናውያን ጎሣዎች ነበሩ። እነዚህ የዳን ትውልድ ጎሣዎች ነበሩ። **43** የስምዔያውያን ጎሣዎች በጠቅላላ 64400 ወንዶች ነበሩ። **44** የአሴር ትውልድ ጎሣዎች እነዚህ ነበሩ፡ በዩምና በኩል የዩምናውያን ጎሣ፣ በዩሱዋ በኩል፣ የየሱዋውያን ጎሣ፣ በበሪዓ በኩል፣ የበሪዓውያን ጎሣ ነበሩ። **45** የብንያም ትውልዶች እነዚህ ነበሩ፡ በሔቤር በኩል፣ የሔቤራውያን ጎሣ፣ በመልኪኤል በኩል የመልኪኤላውያን ጎሣ ነበሩ። **46** የአሴር ሴት ልጅ ስም ሤራህ ነበር። **47** እነዚህ የአሴር ጎሣ ትውልዶች ነበሩ፣ ቁጥራቸው 53400 ወንዶች ነበር። **48** የንፍታም ጎሣ ትውልዶች እነዚህ ነበሩ፡ በያሕድኤል በኩል፣ የያህጽኤላውያን ጎሣ፣ በጉኒ በኩል፣ የጉናውያን ጎሣ፣ **49** በሺሌም በኩል፣ የሺሌማውያን ጎሣ ነበሩ። **50** እነዚህ የንፍታሌም ጎሣ ትውልዶች ነበሩ፣ ቁጥራቸው 45400 ወንዶች ነበር። **51** ይህ በእስራኤል ህዝብ መሃል ጠቅላላው የወንዶች ቁጥር ነበር።በጠቅላላው 601730 ነበሩ። **52** ያህዌ ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፣ **53** “ምድሪቱ በእነዚህ ሰዎች መሃል ርስት ሆኖ እንደ ስሞቻቸው ቁጥር መሰረት ትከፋፈል። **54** ብዙ ቁጥር ላለው ጎሳ ሰፋ ያለውን ርስት ስጥ፣ አነስተኛ ቁጥር ላላቸው ጎሣዎች አነስ ያለውን ርስት ስጣቸው ለእያንዳንዱ ቤተሰብ እንደ ተቆጠረው ወንድ ብዛት ርስት ስጣቸው። **55** ሆኖም ምድሪቱ በዕጣ ትከፋፈል። ምድሪቱን በየአባቶቸው ጎሳዎች መሀል እንደምትከፋፈል ይወርሷት። **56** ርስታቸው በየጎሳው ብዛትና አነስተኛት መጠን ይከፋፈል፣ ክፍፍሉ በዕጣ ይሁን።” **57** በየነገዳቸው የተቆጠሩት የሌዋውያን ነገዶች እነዚህ ነበሩ፡ በጌድሶን በኩል፣ የጌድሶናውያን ጎሣ፣ በቀዓት በኩል፣ የቀዓታውያን ጎሣ፣ በሜራሪ በኩል፣ የሜራርያውን ጎሣ ነበሩ። **58** የሌዊ ጎሳዎች እነዚህ ነበሩ፡ የሊብናውያን ጎሣ፣ የኬብሮናውያን ጎሣ፣ የሞሐላውያን ጎሣ፣ የሙሳውያን ጎሣ፣ እና የቆሬያውያን ጎሳ ነበሩ። ቀዓት የእንበረም የዘር ሀረግ ነበር። **59** የእንበረም ሚስት ስሟ ዮካብድ ነበር፣ ከሌዋውያን ወገን ግብጽ ውስጥ የተወለደች ነበረች። ከእንበረም ልጆቻቸውን አሮንን፣ ሙሴን እና እህታቸውን ማርያምን ወለደች። **60** ለአሮን የተወለዱለት ናዳብ እና አብዩድ፣ ኤልዓዛር እና ኢታምር ነበሩ። **61** ናዳብና አብዩድ ያህዌ በፊቱ ተቀባይነት የሌለውን የእሳት መስዋዕት ሲያቀርቡ ሞቱ። **62** አንድ ወርና ከዚያ በላይ ዕድሜ ያቸው ሌዋውያን ወንዶች ቁጥር ሃያ ሶስት ሺ ነበር። ነገር ግን ከእስራኤል ትውልዶች ጋር አብረው አልተቆጠሩም። ምክንያቱም ለእነርሱ በእስራኤል ሕዝብ መሃል ምንም ርስት አልተሰጣቸውም ነበር። **63** በሙሴና በካህኑ አልዓዛር የተቆጠሩት እነዚህ ናቸው። በሞአብ ሜዳ በዮርዳኖስ ኢያሪኮ ውስጥ የእስራኤልን ህዝበ ቆጠሩ። **64** የእስራአል ትውልዶች በሲና ምድረ በዳ በተቆጠሩ ጊዜ በእነዚህ መሀል በሙሴና በካህኑ በአልዓዛር የተቆጠረ ሌላ ሰው ግን አልነበረም። **65** ያህዌ እነዚያ ሰዎች ሁሉ በእርግጥ በምድረበዳ እንደሚሞቱ ተናግሮ ነበር። ከዩፎኒ ልጅ ከካሌብና ከነዌ ልጅ ከኢያሱ በስተቀር ከመሀላቸው በህይወት የተረፈ አንድም ሰው አልነበረም።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Numbers 26:1

ማህበሩን ሁሉ ቁጠር
የሚቆጥሩት ሴቶችን ሣይሆን ወንዶችን ብቻ ነበር።የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“በማህበሩ ውሰጥ ያሉትን ወንዶች ሁሉ ቁጠሩ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከሃያ ዓመት ጀምሮ ከዚያ በላይ
“20 ዓመትና ከዚያ በላይ”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 26:3

“ተናገሯቸው”
ለእሥራኤል መሪዎች ተናገሩ።

ሜዳ
ሜዳ ሠፊና ለጥ ያለ መሬት ነው።

ሃያ ዓመትና ከዚያም በላይ
“20 ዓመትና ከዚያም በላይ”

Numbers 26:5

አጠቃላይ መረጃ
የእሥራኤል መሪዎች ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎችን ከትውልዳቸውና ከነገዳቸው አንፃር እየቆጠሩ ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውንና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

የእሥራኤል በኩር ነበረ
እዚህ ላይ እሥራኤል የሚለው ቃል የሚያመለክተው ያዕቆብ በመባል የሚታወቀውን ሰው ነው።

ከእርሱ ወንድ ልጁ
እዚህ ላይ“እርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሮቤልን ነው።

43,730
“አርባ ሶስት ሺህ ሰባት መቶ ሰላሣ”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 26:8

አጠቃላይ መረጃ
የእሥራኤል መሪዎች ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎችን ከትውልዳቸውና ከነገዳቸው አንፃር እየቆጠሩ ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

ኤልያብ... ዳታን... አቢሮን
የእነዚህን ሰዎች ሥም በዘኁልቁ 16፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

Numbers 26:10

ምድሪቱ አፍዋን ከፍታ ዋጠቻቸው
እዚህ ላይ ምድሪቱ የተቆጠረችው ልክ አንድ ሰው አፉን ከፍቶ አንድን ነገር እንደሚበላ ዓይነት ነው።“እግዚአብሔር ምድሪቱ እንድትከፈት ካደረገ በኋላ ሰዎቹ በዚያ ጉድጓድ ውስጥ ወደቁ”(ግዑዝ ነገሮች ሕይወት እንዳላቸው ተደርገው ሲገለፁ የሚለውን ይመልከቱ)

እሣቲቱም **250** ሰዎችን በላቻቸው
እዚህ ላይ እሣቱ የተገለፀው ልክ አንድ ትልቅ እንስሳ አንድን ነገር እንደሚውጥ ተደርጎ ነው። “እግዚአብሔር 250 ሰዎችን ለመግደል እሣትን ተጠቀመ”(ግዑዝ ነገሮች ሕይወት እንዳላቸው ተደርገው ሲገለፁ የሚለውን ይመልከቱ)

250 ሰዎች
“ሁለት መቶ ሃምሣ ሰዎች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

የቆሬ ወገኖች
“የቆሬ ቤተሰቦች በሙሉ”

ዋጠቻቸው
“መጨረሻቸው ሆነ”

Numbers 26:12

አጠቃላይ መረጃ
የእሥራኤል መሪዎች ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎችን ከትውልዳቸውና ከነገዳቸው አንፃር እየቆጠሩ ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

22,200 ሰዎች
“ሃያ ሁለት ሰሺህ ሁለት መቶ ሰዎች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 26:15

አጠቃላይ መረጃ
የእሥራኤል መሪዎች ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎችን ከትውልዳቸውና ከነገዳቸው አንፃር እየቆጠሩ ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውንና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

40,500 ሰዎች
“አርባ ሺህ አምስተ መቶ ሰዎች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 26:19

አጠቃላይ መረጃ
የእሥራኤል መሪዎች ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎችን ከትውልዳቸውና ከነገዳቸው አንፃር እየቆጠሩ ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውንና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

76,500 ሰዎች
“ሰባ ስድስት ሺህ አምስት መቶ ሰዎች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 26:23

አጠቃላይ መረጃ
የእሥራኤል መሪዎች ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎችን ከትውልዳቸውና ከነገዳቸው አንፃር እየቆጠሩ ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውንና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

64,300 ሰዎች
“ስድሳ አራት ሺህ ሶስት መቶ ሰዎች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 26:26

አጠቃላይ መረጃ
የእሥራኤል መሪዎች ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎችን ከትውልዳቸውና ከነገዳቸው አንፃር እየቆጠሩ ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውንና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

60,500 ሰዎች
“ስድሳ ሺህ አምስት መቶ ሰዎች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Numbers 26:28

አጠቃላይ መረጃ
የእሥራኤል መሪዎች ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎችን ከትውልዳቸውና ከነገዳቸው አንፃር እየቆጠሩ ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውንይመልከቱ)

Numbers 26:30

አጠቃላይ መረጃ
የእሥራኤል መሪዎች ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎችን ከትውልዳቸውና ከነገዳቸው አንፃር እየቆጠሩ ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 26:33

አጠቃላይ መረጃ
የእሥራኤል መሪዎች ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎችን ከትውልዳቸውና ከነገዳቸው አንፃር እየቆጠሩ ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውንና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

52,700 ሰዎች
“አምሳ ሁለት ሺህ ሰባት መቶ ሰዎች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 26:35

አጠቃላይ መረጃ
የእሥራኤል መሪዎች ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎችን ከትውልዳቸውና ከነገዳቸው አንፃር እየቆጠሩ ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውንና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

32,500 ሰዎች
“ሰላሳ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ሰዎች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ የተቆጠሩት የዮሴፍ ወገኖች ናቸው
“እነዚህ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የዮሴፍ ልጆች ከሆኑት ከኤፈሬምና ከምናሴ ልጆች የተወለዱትን ትውልድ ሁሉ ነው።የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ሃሣብ የበለጠ ሊበራራ ይችላል።“እነዚህ የያዕቆብ ልጆች ከሆኑት ከኤፍሬምና ከምናሴ ዘር የተገኙ ናቸው።እነርሱም ተቆጠሩ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በየወገናቸው ተቆጠሩ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በየወገናቸው ቆጠሯቸው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 26:38

አጠቃላይ መረጃ
የእሥራኤል መሪዎች ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎችን ከትውልዳቸውና ከነገዳቸው አንፃር እየቆጠሩ ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውንና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

45,600 ሰዎች
“አርባ አምስት ሺህ ስድስት መቶ ሰዎች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 26:42

አጠቃላይ መረጃ
የእሥራኤል መሪዎች ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎችን ከትውልዳቸውና ከነገዳቸው አንፃር እየቆጠሩ ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውንና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

64,400 ሰዎች
“ስድሳ አራት ሺህ አራት መቶ ሰዎች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 26:44

አጠቃላይ መረጃ
የእሥራኤል መሪዎች ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎችን ከትውልዳቸውና ከነገዳቸው አንፃር እየቆጠሩ ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውንና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 26:48

አጠቃላይ መረጃ
የእሥራኤል መሪዎች ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎችን ከትውልዳቸውና ከነገዳቸው አንፃር እየቆጠሩ ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውንና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

45,400 ሰዎች
“አርባ አምስት ሺህ አራት መቶ ሰዎች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 26:51

ሙሉ ቁጥሩ
“አጠቃላይ ቁጥሩ”

601,730
“ስድስት መቶ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሰላሣ”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 26:52

ምድሪቱ ትካፈለለች
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“መሬቱን ማከፋፈል አለባችሁ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ ሰዎች
ይሄ የሚያመለክተው ከኦሪት ዘኁልቁ 26:5 ጀምሮ በየወገናቸው የተቆጠሩትን ሁሉ ነው።

በስማቸው ቁጥር መሠረት
“በእያንዳንዱ ወገን ውስጥ ባለው የሕዝብ ቁጥር መሠረት”

Numbers 26:54

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል።

የበለጠ ርስት ሥጣቸው
በዚህ ምንባብ ወስጥ “ርስት”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የተወረሰውን መሬት ነው።የዓረፍተ ነገሩ ሙሉ ሃሣብ የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“እንደ ርስት አድርገህ የበለጠ ትሰጣቸዋለህ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የተቆጠሩት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የእሥራኤል መሪዎች የቆጠሯቸው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሪቱ መከፋፈል ይኖርባታል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ምድሪቱን ማከፋፈል አለባችሁ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በዕጣ
“ዕጣ በመጣል”

ይከፋፈላል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ታከፋፍሉታላችሁ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእነርሱ ማከፋፈል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“መሬቱን ለእነርሱ ማከፋፈል ይኖርባችኋል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 26:57

አጠቃላይ መረጃ
ይሄ የሌዋውያን ነገድ የሥም ዝርዝር ነው።ምንም መሬት ባለመቀበላቸው ምክኒያት ሙሴ ሌዋውያንን ለብቻቸው ቆጠራቸው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

በየነገዳቸው ተቆጠሩ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“መሪዎቹ በየነገዳቸው ቆጠሯቸው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ጌድሶን...ቀዓት...ሜራሪ..እንበረም
የእነዚህን ሰዎች ሥም በዘኁልቁ 3:17-19 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

ለእንበረም ልጆች ወለደችለት
“እርሷና እንበረም ልጆች ነበሯቸው”

Numbers 26:60

ናዳብ...አብዮድ...ኢታምር
የእነዚህን ሰዎች ሥም በዘኁልቁ 3:2 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት የሌለውን እሳት አቀረቡ
እዚህ ላይ“እሣት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው “የሚቃጠል መሥዋዕትን”ነው።ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ በዘኁልቁ 3:4 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“እርሱ ባልተቀበለው ሁኔታ የሚቃጠል መሥዋዕትን አቀረቡ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

የተቆጠሩት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“መሪዎቹ የቆጠሯቸው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ሃያ ሶስት ሺህ
“23,000”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ከአንድ ወር ጀምሮ ከዚያ በላይ ያሉ
“አንድ ወርና ከዚያ በላይ ዕድሜ ያለው”

ርሰት አልተሰጣቸውም ነበር
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።እዚህ ላይ “ርስት”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የተወረሰውን መሬት ነው።የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ሃሣብ የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“እግዚአብሔር ምንም ዓይነት መሬት በርስትነት እአይሰጣቸውም አለ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 26:63

በሙሴና በካህኑ አልዓዛር የተቆጠሩት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሙሴና ካህኑ አልዓዛር የቆጠሯቸው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

አንድም ሰው አልነበረም
“ሰዎች አልነበሩም”

በሙሴና በካህኑ አሮን የተቆጠሩት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሙሴና ካህኑ አሮን የቆጠሯቸው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

የእሥራኤልን ልጆች በቆጠሯቸው ጊዜ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የእሥራኤልን ትውልድ በቆጠሩበት ወቅት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 26:65

ከእነርሱ አንድ ሰው ስንኳ አልቀረም
“እነርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በሲና ምድረ በዳ ተቆጥረው የነበሩትን ሰዎች ሁሉ ነው።ይሄ በአዎንታዊ መለኩ ሊገለፅ ይችላል።“እስከ አሁን ድረስ በሕይወት ያሉት ሰዎች”(ድርብ አሉታውያን)

የዮፎኒ ልጅ
ዮፎኒየካሌብ አባት ነበር።ይህንን በዘኁልቁ 13:6 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

የነዌ ልጅ
ነዌ የኢያሱ አባት ነበር።ይህንን በዘኁልቁ 11:28 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 27

1 ከዚያ ከዮሴፍ ልጅ ለምናሴ ነገድ የአፌር ወንድ ልጅ የገለአድ ወንድ ልጅ የማኪር ወንድ ልጅ የምናሴ ወንድ ልጅ የሰለጰዓድ ሴት ልጆች ወደ ሙሴ መጡ
የሰለዓድ ሴት ልጆች ስሞች እነዚህ ነበሩ፡፡ ማህላህ፣ ኑዓ፣ ዔግላ፣ ሚልካና ቲርጻ፡፡ 2 እነርሱም በሙሴ፣ በካህኑ አልዓዛር፣ በመሪዋች፣ እና በመገናኛው ድንኳን
ደጃፍ በመላው ማህበረሰቡ ፊት ቆሙ፡፡ እንዲህም አሉ፣ 3 “አባታችን በምድረበዳው ሞተ፡፡ እርሱ በቆሬ አመጽ በያህዌ ፊት አምጸው በአንድነት ከተነሱት መሀል
አልነበረም፡፡ የሞተው በራሱ ኃጢአት ነበር፣ አባታችን የሞተው በራሱ ኃጢአት ምክንያት ነበር፡፡ 4 ስለምን ወንድ ልጅ ስለሌለው የአባታችን ስም ከጎሳው አባላት
ተለይቶ ይጠፋል? በአባታችን ቤተዘመዶች መሀል መሬት ስጠን፡፡” 5 ሙሴ ጉዳያቸውን ያህዌ ፊት አቀረበ፡፡ 6 ያህዌ ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው፣ 7
”የሰለጰዓድ ሴት ልጆች የተናገሩት ትክክል ነው፡፡ በአባታቸው ዘመዶች መሃል በእርግጥ ርስት አድርገህ መሬት ስጣቸው፣ ደግሞም የአባታቸው ርስት ወደ
እነርሱ መተላፉን አረጋግጥ፡፡ 8 ለእስራኤል ሰዎች እንዲህ በላቸው፣ ‘አንድ ሰው ወንድ ልጅ ሳይኖው ቢሞት፣ ርስቱ ወደ ሴት ልጁ እንዲተላፍ አድርጉ፡፡ 9 ሴት
ልጅ ባይኖረው፣ ርስቱን ለወንድሞቹ ስጡ፡፡ 10 ወንድሞች ባይኖት፣ ርስቱን ለአባቱ ወንድሞች ስጡ፡፡ 11 አባቱ ወንድሞች ባይኖሩት ርስቱን በጎሳው ውስጥ
ለቅርብ ዘመዱ ስጡ፣ ያም ሰው ይውሰደው፡፡ ይህም ያህዌ እንዳዘዘኝ፣ ለእስራኤል ህዝብ በአዋጅ የፀና ህግ ይሆናል፡፡’” 12 “ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣
“ወደ ዓባሪም ተራሮች ወጥተህ ለእስራኤል ህዝብ የሰጠሁትን ምድር ተመልከት፡፡ 13 ከተመለከትካት በኋላ፣ አንተም ደግሞ ወደ ሰዎችህ እንደ ወንድምህ
አሮን ሁሉ ትሰበሰባለህ፡፡ 14 ይህ ይሆናል፤ ምክንያቱም በጺን ምድረበዳ እናንተ ሁለታችሁ በትእዛዛቶቼ ላይ አምጻችኋል፡፡ በዚያ፣ ውሃው ከአለቱ ሲፈስስ
በቁጣህ ምክንያት በመላው ማህበረሰብ ዐይኖች ፊት እኔን በቅድስና ማክበር አልቻልክም፡፡” ይህ በጺን ምድረበዳ በቃዴስ የሚገኝ የመሪባ ውሃ ነው፡፡ 15
ከዚያ ሙሴ ለያህዌ እንዲህ አለ፣ 16 “የሰዎች ሁሉ መንፈስ አምላክ ያህዌ ሆይ፣ በዚህ ማህበረሰብ ላይ መሪ የሚሆን ሰው ሹም፣ 17 በፊታቸው የሚወጣና
የሚገባ ሰው፣ እየመራ የሚያስወጣቸውና የሚያስገባቸው፣ ህዝብህ እረኛ እንደሌላቸው በጎች እንዳይሆን ሰው ሹምለት፡፡” 18 ያህዌ ሙሴን፣ “የእኔ መንፈስ
የሚኖርበትን፣ የነዌን ልጅ ኢያሱን ውሰድና እጆችህን በእርሱ ላይ ጫን፡፡ 19 በካህኑ አልዓዛር ፊትና በመላው ማህበረሰብ ፊት አቁመህ እንዲመራቸው በፊታቸው
ሹመው፡፡ 20 ከአንተ ስልጣን በእርሱ ላይ አድርግ፣ ስለዚህም መላው የእስራኤል ማህበረሰብ እርሱን ይታዘዙታል፡፡ 21 እርሱም በኡሪም በመጠየቅ ፍቃዴን
ለማወቅ በካህኑ አልዓዛር ፊት ይሄዳል፡፡ ህዝቡ፣ እርሱና ከእርሱ ጋር መላው የእስራኤል ሰዎች፣ መላውም ማህበረሰብ የሚወጣውና የሚገባው በእርሱ ትዕዛዝ
ይሆናል፡፡ 22 ስለዚህም ሙሴ ያህዌ እርሱን እንዳዘዘው አደረገ፡፡ ኢያሱን ወስዶ በካህኑ አልዓዛርና በመላው ማህበር ፊት አቆመው፡፡ 23 ያህዌ እንዲያደርግ
እንዳዘዘው ሁሉ እጆቹን በላዩ ጫነና እንዲመራ ሾመው፡፡

Numbers 27:1

ከዚያም የሰለጰዓድ ሴቶች ልጆች ወደ ሙሴ ቀረቡ ....የዮሴፍ ልጅ
ከዚያም ከዮሴፍ ልጅ ከምናሴ ወገኖች፤የምናሴ ልጅ፤የማኪር ልጅ፤የገለዓድ ልጅ፤የኦፌር ልጅ የሰለጰዓድ ሴቶች ልጆች ወደ ሙሴ ቀረቡ፡፡ይሄ የትውልድን ሐረግ ይናገራል፡፡

ሰለጰዓድ የኦፌር ልጅ ...ማህለህ፤ኑዓ፤ዔግላ፤ሚልካ፤ቲርጻ
ይህንን በዘኁልቁ26፡33 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡

ገለዓድ....ማኪር
ይህንን በዘኁልቁ 26፡29 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡

Numbers 27:2

ቀረቡ
“የሰለጰዓድ ሴቶች ልጆች ቀረቡ”

በቆሬ ማህበር ውስጥ ሆኖ በእግዚአብሔር ላይ ያመፀ
በቆሬ ማህበር ውስጥ የነበሩት ሰዎች ተሰባሰበው በእግዚአብሔር ላይ አመፁ፡፡እግዚአብሔር ከኃጢአታቸው የተነሣ እንዲሞቱ አደረገ፡፡የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ሃሣብ የበለጠ ሊብራራ ይችላል፡፡“በእግዚአብሔር ላይ ያመፁ የቆሬ ማህበር ተከታዮች በመሆናቸው የሞቱ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በራሱ ኃጢአት
“ከራሱ ኃጢአት የተነሣ”

Numbers 27:4

ወንድ ልጅ ባይኖረው የአባታችን ስም ከወገኑ መካከል ለምን ይጠፋል?
በዚያን ዘመን መሬት የመውረስ ሥልጣን የነበረው ወንድ ልጅ ብቻ ነበር፡፡ሴቶቹ ይህንን ጥያቄ የጠየቁት ውርሱን በመውረስ የዘር ሐረጉ እንዲቀጥል ለማስቻል ነበር፡፡ይሄ እንደ መግለጫ ሊፃፍ ይችላል፡፡“አባታችን ወንድ ልጅ ስለሌለው ብቻ የአባታችንን ሥም ከነገድ አባልነቱ ልትፍቁት አይገባም”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በአባታችን ወንድሞች መካከል ርስትን ስጠን
ይሄ የአባታቸው ዘመዶች በወረሱት ርሰት አካባቢ የሚወርሱት ርስት ይሰጣቸው ዘንድ ያቀረቡት ጥያቄ ነው፡፡የዚህ ፍቺ የበለጠ ሊብራራ ይችላል፡፡“የአባታችን ዘመዶች ባሉበት ሥፍራ ላይ ርስትን ሥጠን”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 27:6

በአባታቸው ዘመዶች መካከል
ይሄ ማለት የአባታቸው ዘመዶች በወረሱት ርሰት አካባቢ የሚወርሱት ርስት ይሰጣቸዋልማለት ነው፡፡የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ሃሣብ የበለጠ ሊብራራ ይችላል፡፡“የአባታቸው ወንድሞች ወደሚኖሩበት”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 27:9

አጠቃላይ መረጃ
ይሄ ክስተት አንድ ሰው ወንድ ልጅ የማይኖረው ከሆነ መሬቱን ማን ሊወርስ እንደሚችል ለመወሰን የእግዚአብሔር ሕግ እንዲወጣ ምክኒያት ሆኗል፡፡

ለእሥራኤል ልጆች ሥርዓትና ፍርድ ይሁን
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“የእሥራኤል ሕዝብ ሁሉ የሚታዘዘው ሕግ ይሁን”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔን አዘዘኝ
እዚህ ላይ“እኔን”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሙሴን ነው፡፡

Numbers 27:12

ዓባሪም ተራራ
እነዚህ በሞአብ ውስጥ የሚገኙ የተያያዙ ተራራዎች ናቸው፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለእሥራኤል ልጆች የሰጠኋትን
እዚህ ላይ እግዚአብሔር ለእሥራኤላውያን እየሰጠ ያለውን ምድር ልክ ሰጥቶ እንደጨረሰ ዓይነት አድርጎ ይናገራል።በዚህ መልኩ የሚናገርበት ምክኒያት የሚሰጣቸው ስለመሆኑ አስረግጦ ለማሳሰብ ነው።“ለእሥራኤል ሕዝብ የምሰጠውን”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ደግሞ ወደ ወገኖችህ ትከማቻለህ
ይሄ ጨዋ የሆነ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙም ሙሴ እንደሚሞትና መንፈሱም አባቶቹ ወዳሉበት የሚሄድ መሆኑን ነው።“መሞት አለብህ”(የጨዋ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ወንድምህ እንደ አሮን
አሮን መሞቱ የታወቀ ነገር ቢሆንም የበለጠ ግን ልታብራሩት ትችላላችሁ።“ታላቅ ወንድምህ አሮን እንደሞተ”(ምልክቶች እንጂ ቃላት ጥቅም ላይ የማይውሉበት የሚለውን ይመልከቱ)

ሁለታችሁም አምፃችኋል
ይሄ የሚያመለክተው ሙሴና አሮንን ነው።

የጺን ምድረ በዳ
ይህንንዓረፍተ ነገርበዘኁልቁ 13፡21 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

በቁጣህ ውኃው ከዓለት ውስጥ በፈለቀበት ወቅት
ይሄ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ተአምራታዊ በሆነ መልኩ ውኃን ባወጣበት ወቅት ነበር።እግዚአብሔር ድንጋዩን እንዲናገረው ሙሴን አዘዘው።በዚህ ምትክ ግን በሕዝቡ ከመናደዱ የተነሣ ዓለቱን በበትሩ መታው።(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አልቀደሳችሁኝምና
“ቅዱስ እንደሆንኩ አላሰባችሁም”

በማህበሩ ሁሉ ፊት
እዚህ ላይ ያዩትን ነገር አፅንዖት ለመስጠት ሰዎች የሚወከሉት “በዓይኖቻቸው”ነው።“ማህበሩ ሁሉ ባለበት ፊት”(ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)

የመሪባ ውኃ
ይህንን ሐረግ በዘኁልቁ 20፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

Numbers 27:15

የሥጋ ሁሉ መንፈስ አምላክ እግዚአብሔር
ለዚህ ፍቺ ሊሆኑ የሚችሉት 1/እዚህ ላይ “መንፈስ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሕዝብን ሁሉ ነው።“የሰው ዘር ሁሉ የበላይ የሆነው እግዚአብሔር”ወይም 2/“መንፈስ”የሚለው ቃልየሚያመለክተው እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ ሕይወትንና ትንፋሽን መሥጠቱን ነው። “ለሰው ሁሉ ትንፋሽን የሚሰጠው እግዚአብሔር”ወይም“ለሰው ሁሉ ሕይወትን የሚሰጠው እግዚአብሔር”(ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)

በማህበሩ ላይ
በተወሰኑ ሰዎች “ላይ”መሆን ማለት እነርሱን ለመምራት ሥልጣን መያዝ ማለት ነው።“ማህበሩን የሚመራ ሰው”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በፊታቸው የሚወጣውን፤በፊታቸውም የሚገባውን፤የሚያስወጣቸውንም የሚያስገባቸውንም ሰው
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ሕዝቡን የሚመራና በጦርነትም ወቅት ሠራዊቱን የሚመራ ማለት ነው።(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር መንጋ እረኛ እንደሌለው መንጋ እንዳይሆን
ይሄ ንፅፅር ሲሆን የዚህ ሃሣብ ትርጉም ሕዝቡ መሪ የማይኖረው ከሆነ የተቅበዘበዘና ደካማ ይሆናል ማለት ነው።(ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 27:18

መንፈሴ የሚኖርበትን የነዌን ልጅ ኢያሱን ውሰድ
የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት ሲል ኢያሱ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የሚከተልና የሚታዘዝ ነው ማለቱ ነው።

እጅህን በላዩ ጫንበት
ይሄ አንድን ሰው ለእግዚአብሔር ለመለየት የሚካሄድ ሥርዓት ነው።“እርሱን ለመቀባት እጅህን በላዩ ላይ ጫንበት”(ተምሣሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

መሪያቸው ይሆን ዘንድ እነርሱ እያዩ እዘዘው
እዚህ ላይ ያዩትን ነገር አፅንዖት ለመስጠት ሰዎች የሚወከሉት “በዓይኖቻቸው”ነው።“የእሥራኤልን ሕዝብ ይመራ ዘንድ በሁሉ ፊት ኢያሱን እዘዘው”(ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 27:20

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለሙሴና ለኢያሱ መናገሩን ይቀጥላል።

ከክብርህ አኑርበት
እዚህ ላይ እግዚአብሔር ልክ በላዩ እንደሚደረግ ነገር ወይም አልባሳት ለኢያሱ ክብሩን እንዲያኖርበት ይናገረዋል።“ከሥልጣንህ የተወሰነውን ክፍል መሥጠት ይኖርብሃል”ወይም “ሰዎች ማድረግ የሚኖርባቸውን ነገር እርሱ ይወስን”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኡሪም
ይሄ የተቀደሰ ድንጋይ ሲሆን ሊቀ ካህኑ በደረቱ ላይ የሚያደርገው ነገር ነው፡ በእግዚአብሔር ነገር ላይ ውሳኔ ለመሥጠት የሚጠቀምበት ነገር ነበር። (የማይታወቁትን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

የእሥራኤል ማህበር ሁሉ በቃሉ ይውጡ በቃሉም ይግቡ
ይሄ ማለት ኢያሱ የእሥራኤልን ማህበር እንቅስቃሴዎች የማዘዝ ሥልጣን ይኖረዋል ማለት ነው።“መውታጣ”እና “መግባት”የሚሉት ቃላት በእንቅስቃሴያቸው ላይ ሙሉ ሥልጣን እንዳለው አፅንዖት የሚሰጡ ሁለት ተቃራኒ የሆኑ ትዕዛዛቶች ናቸው።“የማህበሩን እንቅስቃሴ ይመራል” (ሆን ብሎ አጋኖ መናገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ከእርሱም ጋር የእሥራኤል ልጆች ማህበር ሁሉ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን በጥምረት የቀረቡበት ምክኒያት ለጉዳዩ አፅንኦት ለመሥጠት ሲባል ነው።“እርሱና የእሥራኤል ሕዝብ ሁሉ”(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 27:22

ፊት አቆመው
“በማህበሩ ፊት እንዲቆም አዘዘው”

እርሱ እጁን በላዩ ላይ ጭኖ መሪ ይሆን ዘንድ እርሱን አዘዘው
“እርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሙሴን ሲሆን “እርሱ”የሚለው ቃል ደግሞ የሚያመለክተው ኢያሱን ነው።

እጁን በላዩ ላይ ጫነበት
እጅ መጫን አንድን ሰው ለተለየ የእግዚአብሔር አገልግሎት ለመለየት የሚደረግ ሥርዓት ነው።(ተምሣሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መምራት
ግልፅ የሆነውንና ሰዎችን የመምራትን ጉዳይ የበለጠ ልታብራሩት ትችላላችሁ።“ሰዎችን መምራት”ወይም“የእሥራኤላውያን መሪ መሆን”(ምልክቶች እንጂ ቃላት ጥቅም ላይ የማይውሉበት የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር እርሱን ባዘዘው መሠረት
እዚህ ላይ “እርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሙሴን ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 28

1 ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ **2** ”የእስራኤል ሰዎችን እንዲህ ብለህ እዘዛቸው፣ ‘በወቅቱ ለእኔ መስዋዕቶችን አቅርቡ፣ ለእኔ ጣፋጭ መዓዛ ያለው በእሳት የተበጀ መስዋዕት ለእኔ አቅርቡልኝ።’ **3** ደግሞም እንዲህ በላቸው፣ ‘ይህ ለያህዌ የምታቀርቡት የእሳት መስዋዕት ነው። ነውር የሌለበት የአንድ አመት ጠቦት፣ እንደ መደበኛ መስዋዕት በእያንዳንዱ ቀን ሁለት ጠቦቶች አቅርቡ። **4** አንዱን ጠቦት በማለዳ ታቀርባላችሁ፣ ሌላውን ጠቦት በምሽት ታቀርባላችሁ። **5** በተጠለለ የኢን አንድ አራተኛ ዘይት የተለወሰ የአፍ አንድ አስረኛ መልካም ዱቄት የእህል ቁርባን አድርጋችሁ አቅርቡ። **6** ይህ በሲና ተራራ የተደነገገ ለያህዌ የሚቀርብ በእሳት የተዘጋጀ መልካም መዓዛ ያለው መደበኛ የሚቃጠል መስዋዕት ነው። **7** ከዚህ ጋር የሚቀርበው የመጠጥ መስዋዕት ለአንዱ ጠቦት የኢን አንድ አራተኛ ይሁን። በተቀደሰው ስፍራ ለያህዌ የመጠጥ ስጦታ አፍስሱ። **8** ሌላውን ጠቦት ከሌላ የእህል ቁርባን ጋር በማለዳ ባቀረባችሁት መስዋዕት አይነት በምሽት አቅርቡ። ከዚህ ጋር ለያህዌ ጣፋጭ መዓዛ እንዲሆን በእሳት የተዘጋጀ ሌላ የመጠጥ መስዋዕትም አቅርቡ። **9** በሰንበት ቀን ነውር የሌላቸው ሁለት የአንድ አመት ጠቦቶች፣ እና በዘይት የተለወሰ የአፍ ሁለት አስረኛ መልካም ዱቄት የእህል ቁርባን አድርጋችሁ ከመጠጥ መስዋዕት ጋር አቅርቡ። **10** ይህ ከመደበኛው የሚቃጠል መስዋዕትና ከዚህ ጋር ከሚቀርበው የመጠጥ ቁርባን በተጨማሪ በየሰንበቱ የሚቃጠል መስዋዕት እንዲሆን ነው። **11** በየወሩ መጀመሪያ፣ ለያህዌ የሚቃጠል መስዋዕት አቅርቡ። ሁለት ወይፈኖች፣ አንድ አውራ በግ እና ነውር የሌለባቸው ሰባት ወንድ የበግ ጠቦት መስዋዕት አድርጋችሁ አቅረቡ። **12** ለእያንዳንዱ ወይፈን በዘይት የተለወሰ የኢፍ ሶስት አስረኛ መልካም ዱቄት የእህል ቁርባን አቅርቡ፣ ደግሞም ከአውራ በጉ ጋር በዘይት የተለወሰ የኢፍ ሁለት አስረኛ መልካም ዱቄት የእህል ቁርባን አቅርቡ። **13** እንደዚሁም ለእያንዳንዱ ጠቦት የኢፍ አንድ አስረኛ በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት የእህል ቁርባን አቅርቡ። ይህ ለያህዌ የሚቀርብ በእሳት የተዘጋጀ መልካም መዓዛ የሚሰጥ የሚቃጠል መስዋዕት የሚሆን ነው። **14** የሰዎች የመጠጥ ቁርባን ላንድ ኮርማ በሬ የኢን ግማሽ ወይን ጠጅ ይሁን፣ ከአውራ በጉ ጋር የኢን አንድ ሶስተኛ፣ ለአንድ ጠቦት በግ የኢን አንድ አራተኛ ወይን ጠጅ ይሁን። ይህ አመቱን በሙሉ በእያንዳንዱ ወር የሚቃጠል መስዋዕት ነው። **15** ለያህዌ አንድ ወንድ ፍየል የኃጢአት መስዋዕት መቅረብ አለበት። ይህ ከመደበኛው የሚቃጠል መስዋዕትና ከዚህ ጋር ከሚቀርብ የመጠጥ ቁርባን በተጨማሪ ነው። **16** በመጀመሪያው ወር፣ በወሩ በአስራ አራተኛው ቀን የያህዌ ፋሲካ ይውላል። **17** በዚህ ወር የአስራ አምስተኛው ቀን ክብረ በዓል ይሆናል። ለሰባት ቀናት እርሾ የሌለበት ቂጣ ይበላል። **18** በመጀመሪያው ቀን ያህዌን ለማክበር ቅዱስ ጉባኤ ይደረጋል። በዚያ ቀን የዘወትር ሥራችሁን አትሰሩም። **19** ሆኖም ለያህዌ በእሳት የተዘጋጀ የሚቃጠል መስዋዕት ስጦታ አድርጋችሁ ታቀርባላችሁ። ሁለት ወይፈኖች፣ አንድ አውራ በግ፣ እና ነውር የሌለባቸው የአንድ አመት ሰባት ወንድ የበግ ጠቦቶች ታቀርባላችሁ። **20** ከወይፈኑ ጋር በዘይት የተለወሰ የኢን ሶስት አስረኛ መልካም ዱቄት የእህል ቁርባን፣ ከአውራ በግ ጋር የኢን ሁለት አስረኛ መልካም ዱቄት የእህል ቁርባን አቅርቡ። **21** ከእያንዳንዳቸው ከሰባቱ ጠቦቶች ጋር፣ በዘይት የተለወሰ የኢፍ አንድ አስረኛ መልካም ዱቄት አቅርቡ፣ **22** እንዲሁም አንድ ወንድ ፍየል ለኃጢአት መስዋዕት ለማስተሰርያ አቅርቡ። **23** እነዚህን በየጠዋቱ ከሚያስፈልገው መደበኛው የሚቃጠል መስዋዕት በተጨማሪ አቅርቡ። **24** እዚህ እንደ ተገለፀው፣ እነዚህን መስዋዕቶች በየቀኑ ማቅረብ አለባችሁ፣ በፈሲካ ሳምንት፣ በእሳት የተዘጋጀው የምግብ መስዋዕት ለያህዌ ጣፋጭ መዓዛ ይቅረብ። ይህ ከመደበኛው የሚቃጠል መስዋዕትና ከዚህ ጋር ከሚቀርበው የመጠጥ ቁርባን በተጨማሪ መቅረብ አለበት። **25** በሰባተኛው ቀን ያህዌን ለማክበር የተቀደሰ ጉባኤ ይኑራችሁ፣ ደግሞም በዚያ ቀን የየዕለት ተግባራችሁን አታከናውኑ። **26** እንደዚሁም በበኩራት ፍሬ ቀን፣ በክብረ በዓላችሁ ሳምንታት የአዲስ እህል ስጦታ ለያህዌ ስታቀርቡ፣ ያህዌን ለማክበር የተቀደሰ ጉባኤ ይኑራችሁ፤ ደግሞም በዚያ ቀን የተለመደ የየዕለት ተግባራችሁን አትስሩ። **27** ለያህዌ ጣፋጭ መዓዛ የሚቃጠል መስዋዕት አቅርቡ። ሁለት ወይፈኖች፣ አንድ አውራ በግ፣ እና ሰባት የአንድ አመት ጠቦት በጎች አቅርቡ። **28** ከእነዚህ ጋር እነዚህን የእህል ቁርባን አቅርቡ በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት፣ ለእያንዳንዱ ወይፈን የኢፍ ሶስት አስረኛ በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት፣ እና ለአውራ በጉ ሁለት አስረኛ የእህለ ቁርባን አቅርቡ **29** የኢፍ አንድ አስረኛ በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት ለእያንዳንዳቸው ሰባት ጠቦቶች አቅርቡ፣ **30** ደግሞም አንድ ወንድ ፍየል ለኃጢአታችሁ ማስተሰርያ አቅርቡ። **31** ነውር የሌለባቸውን እነዚያን እንስሳት ከመጠጥ ቁርባናቸው ጋር ስታቀርቡ ይህ ከመደበኛ የሚቃጠል መስዋዕትና ከዚህ ጋር ከሚቀርበው የእህል ቁርባን በተጨማሪ መሆን አለበት።’”

Numbers 28:1

በየጊዜው
“እኔ በመረጥኩኩት ቀን”

በእሳት የተደረገውን ቁርባኔን
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በመሠዊያው ላይ የምታቀርቡት መብል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእኔ ጣፋጭ ሽታ
“የምወደውን ሽታ”

Numbers 28:3

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ህዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት ለሙሴ መንገሩን ይቀጥላል።

በእሣት የሚደረግ ቁርባን
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በእሳት የሚቃጠል ቁርባን”ወይም “በመሥዋዕቱ ላይ በእሣት ያቃጠላችሁት ቁርባን”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

የተለወሰ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ከ..ጋር የለወሳችሁት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

የኢፍ መሥፈሪያ አሥረኛ እጅ
“አሥረኛ እጅ”ማለት አሥር አኩል ከሆኑ ነገሮች ውስጥ አንዱ ክፍል ማለት ነው።ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል።“ሁለት ሊትሮች”ወይም “የኢፍ መስፈሪያ አንድ አሥረኛ”(ይሄ ሁለት ሊትር ያህል ይሆናል) (ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)

የኢን መሥፈሪያ አንድ አራተኛ እጅ
“አራተኛ እጅ”ማለት አራት አኩል ከሆኑ ነገሮች ውስጥ አንዱ ክፍል ማለት ነው።ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል።“አንድ ሊትር”ወይም “የኢን መስፈሪያ አንድ አራተኛ”(ይሄ አንድ ሊትር ያህል ይሆናል) (ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)

በተጠለለ ዘይት
“የተወቀጠ ዘይት”ወይም “ንፁህ ወይራ ዘይት”ይሄ የሚያመለክተው ከወይራ ተወቅጦ የወጣን ዘይት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Numbers 28:6

በሲና ተራራ ላይ የታዘዘ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ያዘዘው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

በእሣት የቀረበ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በእሣት ላይ ያቃጠላችሁት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

የኢን መሥፈሪያ አንድ አራተኛ እጅ
“አራተኛ እጅ”ማለት አራት አኩል ከሆኑ ነገሮች ውስጥ አንዱ ክፍል ማለት ነው።ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል።“አንድ ሊትር”ወይም “የኢን መስፈሪያ አንድ አራተኛ”(ይሄ አንድ ሊትር ያህል ይሆናል) (ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)

በመቅደሱ ውስጥ ለእግዚአብሔር ለመጠጥ ቁርባን መጠጥ ታፈስሳለህ
ይሄ ዓረፍተ ነገር የሚያሣየው ከበግ ጠቦቱ ጋር አብሮ የሚቀርበውን የመጠጥ ቁርባን ነው።የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ሃሣብ የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“ጠንካራ የሆነ የመጠጥ ቁርባን ሊሆን የሚገባው ሲሆን በእግዚአብሔር መቅደስ ውስጥ ልታፈስሱት ይገባል”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በፊት እንዳቀረብከው
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“አንተ ያቀረብከው ዓይነት”

Numbers 28:9

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ለሕዝቡ ማድረግ ያለበትን ነገር እግዚአብሔር መንገሩን እንደቀጠለ ነው።

ከመሥፈሪያው ከአሥር እጅ ሁለት እጅ
“ከአሥር እጅ ሁለት እጅ”ማለት አሥር እኩል ከሆኑ ክፍሎች ሁለቱ ማለት ነው።ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል።“አራት ሊትር ተኩል”ወይም “ከመሥፈሪያው ከአሥር እጅ ሁለት እጅ”(አራት ሊትር ተኩል ይሆናል) (ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)

በዘይት የተለወሰ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በዘይት የለወሳችሁት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእርሱ ጋር የመጠጥ ቁርባን
ብዙ ቁርባኖች አብሮ የመጠጥ ቁርባን እንዲቀርብ የሚጠይቁ ናቸው።የዚህ ሙሉ ሃሣብ የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“የመጠጥ ቁርባንም አብሮ ይቀርባል”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 28:11

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ለሕዝቡ ማድረግ ያለበትን ነገር እግዚአብሔር መንገሩን እንደቀጠለ ነው።

ከመሥፈሪያው አሥር እጅ ሶስት እጅ
“ከአሥር እጅ ሶስት እጅ”ማለት አሥር እኩል ከሆኑ ክፍሎች ሶስቱ ማለት ነው።ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል።“ስድስት ሊትር”ወይም “ከመሥፈሪያው ከአሥር እጅ ሶስት እጅ”(ስድስት ሊትር ያህል ይሆናል) (ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)

በዘይት የተለወሰ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በዘይት የለወሳችሁት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ከአሥር እጅ ሁለት እጅ መልካም ዱቄት
“ኢፍ”የሚለው ቃል ግልፅ ቢሆንም የበለጠ ሊብራራ ግን ይችላል።“ከአሥር እጅ ሁለት እጅ”ማለት እኩል ከሆኑ አሥር ክፍሎች ውስጥ ሁለቱ ማለት ነው።“አራት ተኩል ሊትር መልካም ዱቄት”ወይም “ሁለት አሥረኛ የአፍ መሥፈሪያ”(4.5 ያህል የሚሆን)(ምልክቶች እንጂ ቃላት ጥቅም ላይ የማይውሉበት የሚለውን፤ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)

ከመሥፈሪያው አንድ አሥረኛ እጅ
“አንድ አሥረኛ”ማለት አሥር እኩል ከሆኑ ክፍሎች አንዱ ማለት ነው።ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል።“ሁለት ሊትር”ወይም “ከመሥፈሪያው አሥረኛ እጅ”(ሁለት ሊትር ያህል ይሆናል)(ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)

በእሣት የቀረበ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በእሣት ላይ ያቃጠላችሁት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 28:14

የኢን ግማሽ
“ግማሽ”ማለት ሁለት እኩል ከሆኑ ክፍሎች ውስጥ አንደኛው ክፍል ማለት ነው።ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል።“ሁለት ሊትር”ወይም “የኢን ግማሽ”(ሁለት ሊትር)(ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)

የኢን ሢሶ
“የኢን አንድ ሶስተኛ”አንድ ሶስተኛ ማለት ሶስት እኩል ከሆኑ ክፍሎች ውስጥ አንደኛው ክፍል ማለት ነው።ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል።“1.2 ሊትር”ወይም “አንድ ሊትርና አንድ አምስተኛ ሊትር”(ሁለት ሊትር ማለት ነው) (ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)

የኢን አራተኛ እጅ
“አራተኛ እጅ”ማለት አራት እኩል ከሆኑ ክፍሎች ውስጥ አንደኛው ክፍል ማለት ነው።ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል።“አንድ ሊትር”ወይም “የኢን አራተኛ እጅ”(አንድ ሊትር ያህል የሆነ)(ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)

ለእግዚአብሔር አንድ አውራ ፍየል ይቀርባል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።ለኃጢአት መሥዋዕት አንድ አውራ ፍየል ለእግዚአብሔር ታቀርባላችሁ።(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 28:16

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ለሕዝቡ ማድረግ ያለበትን ነገር እግዚአብሔር መንገሩን እንደቀጠለ ነው።

በመጀመሪያው ወር ከወሩም በአሥራ አራተኛው ቀን....ከዚህም ወር በአሥራ አምስተኛው ቀን
“በመጀሪያው ወር በወሩ በ14ኛው ቀን...በዚሁ ወር በ15ኛው ቀን” “ይሄ የሚያመለክተው የመጀመሪያውን የዕብራውያንን ወር ነው” (የዕብራውያን ወራትና ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ፋሲካ ነው
“የእግዚአብሔርን ፋሲካ ልታከብሩት ይገባል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በዓል ይሆናል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በዓል ልታደርጉ ይገባል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሾ የሌለው ቂጣ መበላት ይኖርበታል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እርሾ የሌለው ቂጣ ልትበሉ ይገባል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

በመጀመሪያው ቀን
ይሄ የሚያመለክተው የበዓሉን የመጀመሪያ ዕለት ነው።ይሄ የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“በበዓሉ በ1ኛው ቀን” (ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን ለማክበር የተቀደሰ ጉባዔ መደረግ ይኖርበታል
“እግዚአብሔርን ለማምለክና ለማክበር መሰብሰብ ይኖርባችኋል።” “የተቀደሰ ጉባዔ”የሚለው ሐረግ ሰዎች ተሰብስበው እግዚአብሔርን ሲያመልኩ ማለት ነው።እግዚአብሔርን ማምለክ የተቀደሰ ክስተት ነው።

Numbers 28:19

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ለሕዝቡ ማድረግ ያለበትን ነገር እግዚአብሔር መንገሩን እንደቀጠለ ነው።

በእሣት የተደረገውን የሚቃጠለውን መሥዋዕት ታቀርባላችሁ
“የሚቃጠል”የሚለው ቃል በፍዝ መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በመሠዊያው ላይ የሚቃጠል መሥዋዕት ማቅረብ ይኖርባችኋል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ከመሥፈሪያው ከአሥር እጅ ሶስት እጅ
“ከአሥር እጅ ሶስት እጅ”ማለት አሥር እኩል ከሆኑ ክፍሎች ሶስቱ ማለት ነው።ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል።“ስድስት ሊትር”ወይም “ከመሥፈሪያው ከአሥር እጅ ሶስት እጅ”(ስድስት ሊትር ያህል ይሆናል) (ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)

በዘይት የተለወሰ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በዘይት የለወሳችሁት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ከአሥር እጅ ሁለት እጅ
“የኢፍ መሥፈሪያ መልካም ዱቄት”የሚለው ቃል በበፊቱ ሐረግ ግልፅ ተደርጓል።ይሄ ሊደገምም ይችላል።“ከአሥር እጅ ሁለት እጅ”ማለት እኩል ከሆኑ አሥር ክፍሎች ውስጥ ሁለቱ ማለት ነው።“አራት ተኩል ሊትር የሆነ መልካም ዱቄት”ወይም “ሁለት አሥረኛ የኢፍ መሥፈሪያ”(4.5 ያህል የሚሆን)(ምልክቶች እንጂ ቃላት ጥቅም ላይ የማይውሉበት የሚለውን፤ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)

ከመሥፈሪያው አንድ አሥረኛ እጅ
“አንድ አሥረኛ”ማለት አሥር እኩል ከሆኑ ክፍሎች አንዱ ማለት ነው።ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል።“ሁለት ሊትር”ወይም “ከመሥፈሪያውአንድ አሥረኛ እጅ”(ሁለት ሊትር ያህል ይሆናል)(ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)

መሥዋዕትን ማቅረብ
x

Numbers 28:23

ዘወትር ማልዶ ከሚቀርበው
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር በየማለዳው እንዲቀርብለት ከሚፈልገው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

እዚህ በተገለፀው መሠረት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እኔ እግዚአብሔር እዚህ በገለፅኩት መሠረት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

በእሣት የሚደረገውን የመብል ቁርባን
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የመብሉን ቁርባን በመሠዊያው ላይ ማቃጠል ይኖርባችኋል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእግዚአብሔር የሚሆን ጣፋጭ ሽታ
“ለእግዚአብሔር እንደ ጣፋጭ ሽታ”

መሥዋዕት መደረግ ይኖርበታል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ልትሰውት ይገባል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን ለማክበር የተቀደሰ ጉባዔ መደረግ ይኖርበታል
“እግዚአብሔርን ለማምለክና ለማክበር መሰብሰብ ይኖርባችኋል።” “የተቀደሰ ጉባዔ”የሚለው ሐረግ ሰዎች ተሰብስበው እግዚአብሔርን ሲያመልኩ ማለት ነው።እግዚአብሔርን ማምለክ የተቀደሰ ክስተት ነው።

Numbers 28:26

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ለሕዝቡ ማድረግ ያለበትን ነገር እግዚአብሔር መንገሩን እንደቀጠለ ነው።

በበኩራት ቀን
በበኩራት ቀንሲባልዕለቱን ነው።“ይሄ የሚያመለክተው በዓሉ በሚከበርበት ሣምንታት ውስጥ ለእግዚአብሔር የእህል ቁርባን የሚያቀርቡበትን ዕለት ነው።

እግዚአብሔርን ለማክበር የተቀደሰ ጉባዔ መደረግ ይኖርበታል
“እግዚአብሔርን ለማምለክና ለማክበር መሰብሰብ ይኖርባችኋል።” “የተቀደሰ ጉባዔ”የሚለው ሐረግ ሰዎች ተሰብስበው እግዚአብሔርን ሲያመልኩ ማለት ነው።እግዚአብሔርን ማምለክ የተቀደሰ ሁኔታ ነው።

በዘይት የተለወሰ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በዘይት የለወሳችሁት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ከአሥር እጅ ሁለት እጅ
“የኢፍ መሥፈሪያ መልካም ዱቄት”የሚለው ቃል በበፊቱ ሐረግ ግልፅ ተደርጓል።ይሄ ሊደገምም ይችላል።“ከአሥር እጅ ሁለት እጅ”ማለት እኩል ከሆኑ አሥር ክፍሎች ውስጥ ሁለቱ ማለት ነው።“አራት ተኩል ሊትር የሆነ መልካም ዱቄት”ወይም “ሁለት አሥረኛ የኢፍ መሥፈሪያ”(4.5 ያህል የሚሆን)(ምልክቶች እንጂ ቃላት ጥቅም ላይ የማይውሉበት የሚለውን፤ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)

ከመሥፈሪያው ሶስትአሥረኛ እጅ
“ሶስት አሥረኛ”ማለት አሥር እኩል ከሆኑ ክፍሎች ሶስቱ ማለት ነው።ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል።“ስድስት ሊትር”ወይም “የኢፍ መሥፈሪያሶስት አሥረኛ”(ስድስት ሊትር ያህል ይሆናል)(ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)

ከአሥር እጅ ሁለት እጅ
“የኢፍ መሥፈሪያ መልካም ዱቄት”የሚለው ቃል በበፊቱ ሐረግ ግልፅ ተደርጓል።ይሄ ሊደገምም ይችላል።“ከአሥር እጅ ሁለት እጅ”ማለት እኩል ከሆኑ አሥር ክፍሎች ውስጥ ሁለቱ ማለት ነው።“አራት ተኩል ሊትር የሆነ መልካም ዱቄት”ወይም “ሁለት አሥረኛ የኢፍ መሥፈሪያ”(4.5 ያህል የሚሆን)(ምልክቶች እንጂ ቃላት ጥቅም ላይ የማይውሉበት የሚለውን፤ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Numbers 28:29

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ለሕዝቡ ማድረግ ያለበትን ነገር እግዚአብሔር መንገሩን እንደቀጠለ ነው።

ከመሥፈሪያው አንድ አሥረኛ እጅ
“አንድ አሥረኛ”ማለት አሥር እኩል ከሆኑ ክፍሎች አንዱ ማለት ነው።ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል።“ሁለት ሊትር”ወይም “ከመሥፈሪያው አንድ አሥረኛ እጅ”(ሁለት ሊትር ያህል ይሆናል)(ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)

በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እናንተ በዘይት የምትለውሱት መልካም ዱቄት” (ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

መሥዋዕትን ማቅረብ
“መሥዋዕት ማቅረብ”የሚለው ሐረግ “መሰዋት”በሚለው ሥም ሊገለፅ ይችላል።(አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

የእነርሱን የመጠጥ ቁርባን
“የእነርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው እያንዳንዱ እንስሳ በሚሰዋበት ወቅት አብረው መቅረብ የሚገባቸውን የመጠጥ ቁርባኖችን ነው።“ከእነርሱ ጋር አብረው የሚቀርቡት የመጠጥ ቁርባኖች”ወይም “የሚያጅቧቸው የመጠጥ ቁርባኖች”(ንብረት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 29

1 ”በሰባተኛው ወር፣ በወሩ በመጀመሪያው ቀን፣ ያህዌን ለማክበር የተቀደሰ ጉባኤ አድርጉ። በዚያ ቀን የተለመደውን የዕለት ተግባራችሁን አታከናውኑ። ይህ ቀን መለከቶችን የምትነፉበት ቀን ይሆናል። 2 ለያህዌ መልካም መዓዛ የሚሆን የሚቃጠል መስዋዕት አቅርቡ። አንድ ወይፈን፣ አንድ አውራ በግ፣ እና እያንዳንዳቸው ነውር የሌለባቸው ሰባት የአንድ አመት ጠቦቶች አቅርቡ። 3 ከእነዚህ ጋር የእህል ቁርባናቸውን፣ በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት አቅርቡ፤ ለወይፈኑ የኢፍ ሶስት አራተኛ፣ ለአውራ በጉ የኢፍ ሁለት አስረኛ 4 እና ለሰባቱ ጠቦቶች ለእያንዳንዳቸው በዘይት የተለወሰ የኢፍ አንድ አስረኛ መልካም ዱቄት አቅርቡ። 5 ለኃጢአት ማስተስረያ አንድ ወንድ ፍየል አቅርቡ። 6 በየወሩ መጀመሪያ ከምታደርጉት የተለየ የሚቃጠል መስዋዕትና አብሮ ከሚቀርበው የእህል ቁርባን በተጨማሪ፣ እነዚህን መስዋዕቶች በሰባተኛው ወር አድርጉ። እነዚህ ከመደበኛው የሚቃጠል መስዋዕት ከእህል ቁርባኑና የመጠጥ ቁርባኖች በተጨማሪ የሚቀርቡ ናቸው። እነዚህን መስዋዕቶች ስታደርጉ፣ ለያህዌ በእሳት የሚዘጋጀውን መስዋዕት ጣፋጭ መዓዛ ለማቅረብ የተደነገገውን ትፈጽማላችሁ። 7 በሰባተኛ ወር በአስረኛው ቀን ያህዌን ለማክበር የተቀደሰ ጉባኤ ታደርጋላችሁ። ራሳችሁን በእግዚአብሔር ፊት ታዋርዳላችሁ በዕለቱ ሥራ አትሰሩም። 8 ለያህዌ ጣፋጭ ማዐዛ ያለው የሚቃጠል መስዋዕት ታቀርባላችሁ። አንድ ወይፈን፣ አንድ አውራ በግ፣ እና የአንድ አመት ሰባት ወንድ ጠቦት በጎች ታቀርባላችሁ። እያንዳንዳቸው ነውር የሌለባቸው ይሁኑ። 9 ከዚህ ጋር የእህል ቁርባን፤ በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት፣ ለወይፈኑ የኢፍ ሶስት አስረኛ፣ ለአውራ በጉ የኢፍ ሁለት አስረኛ፣ 10 እና ለሰባቱ ጠቦቶች ለእያንዳንዳቸው የኢፍ አንድ አስረኛ ታቀርባላችሁ። 11 አንድ ወንድ ፍየል ለኃጢአት መስዋዕት ማቅረብ አለባችሁ። ይህ ለኃጢአት ማስተስረያ፣ ለመደበኛ የሚቃጠል መስዋዕት፣ አብሮት ከሚቀርበው የእህል ቁርባን፣ እና ከእነዚህ ጋር በሚቀርበው የመጠጥ መስዋእቶች በተጨማሪ የሚቀርብ ነው። 12 በሰባተኛው ወር አስራ አምስተኛው ቀን ያህዌን ለማክበር የተቀደሰ ጉባኤ ታደርጋላችሁ። በዚያ ቀን የተለመደውን የዕለት ተግባራችሁን አታከናውኑም፣ ደግሞም ለሰባት ቀናት ክብረ በዓሉን ለእርሱ ታደርጋላችሁ። 13 በእሳት የተዘጋጀ ለያህዌ ጣፋጭ መዓዛ የሚሆን የሚቃጠል መስዋዕት ማቅረብ አለባችሁ። አስራ ሶስት ወይፈኖች፣ እና የአንድ አመት ዕድሜ ያላቸው አስራ አራት ወንድ ጠቦቶች ማቅረብ አለባችሁ። እያንዳንችው ነውር የሌለባቸው መሆን አለባቸው። 14 ከእነዚህ ጋር የእህል ቁርባን፣ ለአስራ ሶስቱም ወይፈኖች ለእያንዳንዳቸው የኢፍ ሶስት አስረኛ፣ ለሁለቱ አውራ በጎች ለእያንዳንዳቸው የኢፍ ሁለት አስረኛ 15 እና ለአስራ አራቱ ጠቦቶች ለእያንዳንዳቸው የኢፍ አንድ አስረኛ፤ በዘይትየተለወሰ መልካም ዱቄት አቅርቡ። 16 ከመደበኛው የሚቃጠል መስዋዕት፤ ከዚህ ጋር ከሚቀርበው የእህል ቁርባን እና የመጠጥ ቁርባን በተጨማሪ ለኃጢአት መስዋዕት አንድ ወንድ ፍየል ማቅረብ አለባችሁ። 17 በስብሰባው ሁለተኛ ቀን፣ አስራ ሁለት ወይፈኖች፣ ሁለት አውራ በጎች እና አስራ አራት ነውር የሌለባቸው የአንድ አመት ወንድ የበግ ጠቦቶች ማቅረብ አለባችሁ። 18 ከእነዚህ ጋር የእህል ቁርባን የመጠጥ ቁርባኖች ለኮርማዎቹ፣ ለአውራ በጎቹ እና ለጠቦቶቹ በተወሰነው ቁጥር መሠረት እንደ ትዕዛዙ ታቀርባላችሁ። 19 ከመደበኛ የሚቃጠል መስዋዕት፣ አብሮት ከሚቀርበው የእህል ቁርባንና የመጠጥ ቁርባን በተጨማሪ ለኃጢአት መስዋዕት አንድ ወንድ ፍየል ማቅረብ አለባችሁ። 20 በስብሰባው ሶስተኛ ቀን፣ አስራ አንድ ወይፈኖች ሁለት አውራ በጎች፣ እና አስራ አራት ነውር የሌለባቸው የአንድ አመት ወንድ የበግ ጠቦቶች ማቅረብ አለባችሁ። 21 ከእነዚህ ጋር የእህል ቁርባንና የመጠጥ ቁርባኖች ለኮርማዎቹ፣ ለአውራ በጎቹ፣ እና ለጠቦቶቹ በተወሰነው ቁጥር መሰረት እንደ ትዕዛዙ ታቀርባላችሁ። 22 ከመደበኛ የሚቃጠል መስዋዕት፣ አብሮ ከሚቀርበው የእህል ቁርባን፣ እና የመጠጥ ቁርባን በተጨማሪ ለኃጢአት መስዋዕት አንድ ወንድ ፍየል ማቅረብ አለባችሁ። 23 በስብሰባው አራተኛ ቀን፣ አስር ወይፈኖች፣ ሁለት አውራ በጎች እና አስራ አራት ነውር የሌለባቸው የአንድ አመት ወንድ የበግ ጠቦቶች ማቅረብ አለባችሁ። 24 ከእነዚህ ጋር የእህል ቁርባንና የመጠጥ ቁርባኖች፣ ለኮርማዎቹ፣ ለአውራ በጎቹ እና ለጠቦቶቹ በተወሰነው ቁጥር መሠረት እንደ ትዕዛዙ ታቀርባላችሁ። 25 ከመደበኛ የሚቃጠል መስዋዕት፣ አብሮት ከሚቀርበው የእህል ቁርባንና የመጠጥ ቁርባን በተጨማሪ ለኃጢአት መስዋዕት አንድ ወንድ ፍየል ማቅረብ አለባችሁ። 26 በስብሰባው አምስተኛ ቀን፣ ዘጠኝ ወይፈኖች፣ ሁለት አውራ በጎች፣ እና አስራ አራት ነውር የሌለባቸው የአንድ አመት ወንድ የበግ ጠቦቶች ማቅረብ አለባችሁ። 27 ከእነዚህም ጋር የእህል ቁርባንና የመጠጥ ቁርባኖች ለኮርማዎቹ፣ ለአውራ በጎቹ፣ እና ለጠቦቶቹ፣ በተወሰነው ቁጥር መሠረት እንደ ትዕዛዙ ታቀርባላችሁ። 28 ከመደበኛ የሚቃጠል መስዋዕት፣ አብሮት ከሚቀርበው የእህል ቁርባን፣ እና የመጠጥ ቁርባን በተጨማሪ ለኃጢአት መስዋዕት አንድ ወንድ ፍየል ማቅረብ አለባችሁ። 29 በስበሰባው ስድስተኛ ቀን ስምንት ወይፈኖች፣ ሁለት አውራ በጎች፣ እና አስራ አራት ነውር የሌለባቸው የአንድ አመት ወንድ የበግ ጠቦቶች ማቅረብ አለባችሁ። 30 ከእነዚህ ጋር የእህል ቁርባንና የመጠጥ ቁርባኖች ለኮርማዎቹ፣ ለአውራ በጎቹ፣ እና ለጠቦቶቹ በተወሰነው ቁጥር መሠረት እንደ ትዕዛዙ ታቀርባላችሁ። 31 ከመደበኛ የሚቃጠል መስዋዕት፣ አብሮት ከሚቀርበው እህል ቁርባን እና የመጠጥ ቁርባን በተጨማሪ ለኃጢአት መስዋዕት አንድ ወንድ ፍየል ማቅረብ አለባችሁ። 32 በስብሰባው ሰባተኛ ቀን፣ነውር የሌለባቸው፣ ሰባት ወይፈኖች፣ ሁለት አውራ በጎች እና አስራ አራት የአንድ አመት ወንድ የበግ ጠቦቶች ማቅረብ አለባችሁ። 33 ከወይፈኖች፣ከአውራ በጎች እና ጠቦቶች ጋር የእህል ቁርባንና የመጠጥ ቁርባኖች ታቀርባላችሁ። 34 ከመደበኛው የሚቃጠል መስዋዕትና አብሮት ከሚቀርበው የእህል ቁርባን፣ እንዲሁም ከመጠጥ ቁርባኑ በተጨማሪ ለኃጢአት መስዋዕት አንድ ወንድ ፍየል ማቅረብ አለባችሁ። 35 በስብሰባው ስምንተኛ ቀን፣ ሌላ የከበረ ጉባኤ ታደርጋላችሁ። በዚያን ቀን የተለመደ የዕለት ተግባራችሁን አታከናውኑም። 36 የሚቃጠል መስዋዕት ታደርጋላችሁ፣ ለያህዌ ጣፋጭ መዓዛ ያለው መስዋዕት ታቀርባላችሁ። አንድ ወይፈን፣ አንድ አውራ በግ፣ እና ነውር ሌለባቸው ሰባት የአንድ አመት ወንድ ጠቦት በጎች ታቀርባላችሁ። 37 ለወይፈኑ፣ ለአውራ በጉ፣ እና ለጠቦቶቹ የእህል ቁርባናቸውንና የመጠጥ ቀርባናቸውን በተወሰነው ቁጥር መሰረት እንደ ትእዛዙ ታቀርባላችሁ። 38 ከመደበኛ የሚቃጠል መስዋዕት፣ አብሮት ከሚቀርበው የእህል ቁርባን፣ እና የመጠጥ ቁርባን በተጨማሪ ለኃጢአት መስዋዕት አንድ ወንድ ፍየል ማቅረብ አለባችሁ። 39 በተወሰነ ክብረ በዓላቶቻችሁ ለያህዌ የምታቀርቧቸው እነዚህ ናቸው። እነዚህም ከስለቶቻችሁና የበጎ ፈቃድ ስጦታዎቻችሁ በተጨማሪ የምታቀርቧቸው ናቸው። እነዚህን የሚቃጠሉ መስዋዕቶቻችሁ፣ የእህል ቁርባኖች፣ የመጠጥ ቁርባኖች፣ እና የህብረት መስዋዕቶች አድርጋችሁ አቅርቧቸው።” 40 ሙሴ ያህዌ ለእስራኤል ሰዎች እንዲናገር ያዘዘውን ሁሉ ተናገረ።

Numbers 29:1

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ለሕዝቡ ማድረግ ያለበትን ነገር እግዚአብሔር መንገሩን እንደቀጠለ ነው።

በሰባተኛውም ወር ከወሩ በመጀመሪያ ቀን
ይሄ የሚያመለክተው የዕብራውያንን ሰባተኛ ወር ነው።“በ1ኛው ወር በ7ኛው ወር”(የዕብራውያን ወራትንናተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እግዚአብሔርን ለማክበር የተቀደሰ ጉባዔ ይሁንላችሁ
“እግዚአብሔርን ለማምለክና ለማክበር በአንድነት ተሰብሰቡ” “የተቀደሰ ጉባዔ”የሚለው ቃል ሰዎች እግዚአብሔርን ለማምለክ የሚሰበሰቡበት ሁኔታ ማለት ነው።እግዚአብሔርን ማምለክ የተቀደሰ ክስተት ነው።

እናንተ መለከቶችን የምትነፉበት ቀን ነው
“እናንተ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው እዚህ ላይ የእሥራኤልን ሕዝብ የሚወክሉትን ካህናትን ነው።ካህናት አምልኮው እንዲጀመር መለከትን ይነፋሉ ወይም ማህረሰቡ በአንድነት እንዲሰባሰብ ለማድረግ።“ካህናት መለከቶችን የሚነፉበት ቀን ይሆናል”(ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 29:2

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ለሕዝቡ ማድረግ ያለበትን ነገር እግዚአብሔር መንገሩን እንደቀጠለ ነው።

Numbers 29:3

የእህል ቁርባናቸውን
ይሄ የሚያመለክተው እያንዳንዱ እንስሳ በሚሰዋበት ወቅት አብረው መቅረብ የሚገባቸውን የእህል ቁርባኖችን ነው።“ከአነርሱ ጋር አብረው የሚቀርቡት የእህል ቁርባኖች”ወይም “የሚያጅቧቸው የእህል ቁርባኖች”(ንብረት የሚለውን ይመልከቱ)

በዘይት የተለወሰ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በዘይት የለወሳችሁት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ከአሥር እጅ ሁለት እጅ
“የኢፍ መሥፈሪያ መልካም ዱቄት”የሚለው ቃል በበፊቱ ሐረግ ግልፅ ተደርጓል።ይሄ ሊደገምም ይችላል።“ከአሥር እጅ ሁለት እጅ”ማለት እኩል ከሆኑ አሥር ክፍሎች ውስጥ ሁለቱ ማለት ነው።“አራት ተኩል ሊትር የሆነ መልካም ዱቄት”ወይም “ሁለት አሥረኛ የኢፍ መሥፈሪያ”(4.5 ያህል የሚሆን)(ምልክቶች እንጂ ቃላት ጥቅም ላይ የማይውሉበት የሚለውን፤ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)

ከመሥፈሪያው ሶስት አሥረኛ እጅ
“ሶስት አሥረኛ”ማለት አሥር እኩል ከሆኑ ክፍሎች ሶስቱ ማለት ነው።ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል።“ስድስት ሊትር”ወይም “የኢፍ መሥፈሪያ ሶስት አሥረኛ”(ስድስት ሊትር ያህል ይሆናል)(ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)

ከአሥር እጅ አንድ እጅ
“የኢፍ መሥፈሪያ መልካም ዱቄት”የሚለው ቃል በበፊቱ ሐረግ ግልፅ ተደርጓል።ይሄ ሊደገምም ይችላል።“ከአሥር እጅ አንድ እጅ”ማለት እኩል ከሆኑ አሥር ክፍሎች ውስጥ አንዱ ማለት ነው።“ሁለት ሊትር መልካም የሆነ ዱቄት”ወይም “አንድ አሥረኛ የኢፍ መሥፈሪያ”(4.5 ያህል የሚሆን)(ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)

መሥዋዕትን ማቅረብ
“መሥዋዕት ማቅረብ”የሚለው ሐረግ “መሰዋት”በሚለው ሥም ሊገለፅ ይችላል።(አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 29:6

በሰባተኛው ወር..በወራቶቹ የመጀመሪያው ቀን
“በ7ኛ ወር...በእያንዳንዱ ወር በ1ኛው ቀን”“ወር”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የዕብራውያንን የወር አቆጣጠር ነው።(የዕብራውያን ወራትንናተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

በየወሩ፤የተለየ የሚቃጠል መሥዋዕት ...ከእርሱ ጋር
“በየወሩ፤የተለየ የሚቃጠል መሥዋዕት ...ከእርሱ ጋር” ይሄ በየወሩ መጀመሪያ ላይ የሚደረግ መሥዋዕት ነው፡

በዘወትርም ከሚቃጠለው መሥዋዕትና ከእህሉ ቁርባን፤ከመጠጡም ቁርባን
ይሄ የሚያመለክተው ካህናቱ በየዕለቱ መሥጠት የሚገባቸውን መሥዋዕት ነው።የእህል ቁርባኑና የመጠጡቁርባን ዘወትር ከሚቃጠለው መሥዋዕት ጋር መቅረብ ይኖርባቸዋል።“ዘወትር የሚቀርበው የሚቃጠል መሥዋዕት አብረው ከሚቀርቡት ከእህል ቁርባንና ከመጠጥ ቁርባን ጋር”(ንብረት የሚለውን ይመልከቱ)

የተደነገገውን ትዕዛዝ ተግባራዊ ታደርጉታላችሁ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የእግዚብሔርን ትዕዛዝ ተግባራዊ ታደርጉታላችሁ”ወይም “እግዚአብሔር ያዘዘውን ትዕዛዝ ተግባራዊ ታደርጉታላችሁ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእግዚአብሔር በእሣት የሚቀርብ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ በመሠዊያው ላይ ለእግዚአብሔር ያቃጠላችሁት ቁርባን”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 29:7

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ለሕዝቡ ማድረግ ያለበትን ነገር እግዚአብሔር መንገሩን እንደቀጠለ ነው።

በሰባተኛው ወር..በወራቶቹ የመጀመሪያው ቀን
“በ7ኛ ወር...በእያንዳንዱ ወር በ1ኛው ቀን” “ወር”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የዕብራውያንን የወር አቆጣጠር ነው።(የዕብራውያን ወራትንናተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን ለማክበር የተቀደሰ ጉባዔ ይሁንላችሁ
“እግዚአብሔርን ለማምለክና ለማክበር በአንድነት ተሰብሰቡ” “የተቀደሰ ጉባዔ”የሚለው ቃል ሰዎች እግዚአብሔርን ለማምለክ የሚሰበሰቡበት ሁኔታ ማለት ነው።እግዚአብሔርን ማምለክ የተቀደሰ ክስተት ነው።

Numbers 29:9

በዘይት የተለወሰ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በዘይት የለወሳችሁት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ከመሥፈሪያው ሶስት አሥረኛ እጅ
“ሶስት አሥረኛ”ማለት አሥር እኩል ከሆኑ ክፍሎች ሶስቱ ማለት ነው።ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል።“ስድስት ሊትር”ወይም “የኢፍ መሥፈሪያ ሶስት አሥረኛ”(ስድስት ሊትር ያህል ይሆናል)(ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)

ከአሥር እጅ ሁለት እጅ
“የኢፍ መሥፈሪያ መልካም ዱቄት”የሚለው ቃል በበፊቱ ሐረግ ግልፅ ተደርጓል።ይሄ ሊደገምም ይችላል።“ከአሥር እጅ ሁለት እጅ”ማለት እኩል ከሆኑ አሥር ክፍሎች ውስጥ ሁለቱ ማለት ነው።“አራት ተኩል ሊትር የሆነ መልካም ዱቄት”ወይም “ሁለት አሥረኛ የኢፍ መሥፈሪያ”(4.5 ያህል የሚሆን)(ምልክቶች እንጂ ቃላት ጥቅም ላይ የማይውሉበት የሚለውን፤ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)

ከአሥር እጅ አንድ እጅ
“የኢፍ መሥፈሪያ መልካም ዱቄት”የሚለው ቃል በበፊቱ ሐረግ ግልፅ ተደርጓል።ይሄ ሊደገምም ይችላል።“ከአሥር እጅ አንድ እጅ”ማለት እኩል ከሆኑ አሥር ክፍሎች ውስጥ አንዱ ማለት ነው።“ሁለት ሊትር መልካም የሆነ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ዱቄት”ወይም “አንድ አሥረኛ የኢፍ መሥፈሪያ”(4.5 ያህል የሚሆን) (ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)

መሥዋዕትን ማቅረብ
“መሥዋዕት ማቅረብ”የሚለው ሐረግ “መሰዋት”በሚለው ሥም ሊገለፅ ይችላል።(አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

ከእህሉ ቁርባንና ከመጠጡ ቁርባን
የእህሉ ቁርባን ከሚቃጠለው ቁርባን ጋር መቅረብ ነበረበት።የመጠጥ ቁርባኑ ከኃጢአት መሥዋዕቱና ከሚቃጠለው መሥዋዕት ጋር አብሮ መቅረብ ነበረበት።“አብረው ከሚቀርቡት የእህል ቁርባንና የመጠጥ ቁርባን ጋር”(ንብረት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 29:12

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ለሕዝቡ ማድረግ ያለበትን ነገር እግዚአብሔር መንገሩን እንደቀጠለ ነው።

በሰባተኛውም ወር..በአስራ አምስተኛው ቀን
“በ7ኛ ወር...በ15ኛው ቀን” “ወር”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የዕብራውያንን የወር አቆጣጠር ነው።(የዕብራውያን ወራትንናተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን ለማክበር የተቀደሰ ጉባዔ ይሁንላችሁ
“እግዚአብሔርን ለማምለክና ለማክበር በአንድነት ተሰብሰቡ” “የተቀደሰ ጉባዔ”የሚለው ቃል ሰዎች እግዚአብሔርን ለማምለክ የሚሰበሰቡበት ሥርዓት ማለት ነው።እግዚአብሔርን ማምለክ የተቀደሰ ሁኔታ ነው።

በዓሉን ለእርሱ ልትጠብቁት ይገባል
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው።“መጠበቅ”የሚለው ቃል መከታተል ወይም ማክበር ማለት ነው።“እርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው።“በዓሉን ለእግዚአብሔር መጠበቅ ይኖርባችኋል”ወይም “በዐሉን ለእግዚአብሔር ልታከብሩት ይገባል”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእሳት የሚደረግ መሥዋዕት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በመሠዊያ ላይ ልታቃጥሉት ይገባል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

አሥራ አራት ወይፈኖች፤ሁለት አውራ በጎች፤አሥራ አራት የአንድ ዓመት ተባት ጠቦቶች
“14 ወይፈኖች፤2 አውራ በጎች፤14 የአንድ ዓመት ተባት ጠቦቶች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 29:14

በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በዘይት የለወሳችሁት መልካም ዱቄት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ከመሥፈሪያው ሶስት አሥረኛ እጅ
“ሶስት አሥረኛ”ማለት አሥር እኩል ከሆኑ ክፍሎች ሶስቱ ማለት ነው።ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል።“ስድስት ሊትር”ወይም “የኢፍ መሥፈሪያ ሶስት አሥረኛ”(ስድስት ሊትር ያህል ይሆናል)(ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)

ከአሥር እጅ ሁለት እጅ
“የኢፍ መሥፈሪያ መልካም ዱቄት”የሚለው ቃል በበፊቱ ሐረግ ግልፅ ተደርጓል።ይሄ ሊደገምም ይችላል።“ከአሥር እጅ ሁለት እጅ”ማለት እኩል ከሆኑ አሥር ክፍሎች ውስጥ ሁለቱ ማለት ነው።“አራት ተኩል ሊትር የሆነ መልካም ዱቄት”ወይም “ሁለት አሥረኛ የኢፍ መሥፈሪያ”(4.5 ያህል የሚሆን)(ምልክቶች እንጂ ቃላት ጥቅም ላይ የማይውሉበት የሚለውን፤ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)

ከአሥር እጅ አንድ እጅ
“የኢፍ መሥፈሪያ መልካም ዱቄት”የሚለው ቃል በበፊቱ ሐረግ ግልፅ ተደርጓል።ይሄ ሊደገምም ይችላል።“ከአሥር እጅ አንድ እጅ”ማለት እኩል ከሆኑ አሥር ክፍሎች ውስጥ አንዱ ማለት ነው።“ሁለት ሊትር መልካም የሆነ ዱቄት”ወይም “አንድ አሥረኛ የኢፍ መሥፈሪያ”(4.5 ያህል የሚሆን) (ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)

መሥዋዕትን ማቅረብ
“መሥዋዕት ማቅረብ”የሚለው ሐረግ “መሰዋት”በሚለው ሥም ሊገለፅ ይችላል።(አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

ከእህሉ ቁርባንና ከመጠጡ ቁርባን
የእህሉ ቁርባኑና የመጠጥ ቁርባኑ ዘወትር ከሚቀርበው የሚቃጠል መሥዋዕት ጋር አብሮ መቅረብ ነበረበት።

Numbers 29:17

በጉባዔው በሁለተኛው ቀን
“በበዓሉ 2ተኛ ቀን” እዚህ ላይ “ጉባዔ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በበዓሉ ወቅት ያሉትን ሣምንታት ነው።(ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

አሥራ አራት ወይፈኖች፤ሁለት አውራ በጎች፤አሥራ አራት የአንድ ዓመት ተባት ጠቦቶች
“14 ወይፈኖች፤2 አውራ በጎች፤14 የአንድ ዓመት ተባት ጠቦቶች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በታዘዙት መሠረት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእህሉ ቁርባንና ከመጠጡ ቁርባን
የእህሉ ቁርባን ከሚቃጠለው ቁርባን ጋር መቅረብ ነበረበት።የመጠጥ ቁርባኑ ከኃጢአት መሥዋዕቱና ከሚቃጠለው መሥዋዕት ጋር አብሮ መቅረብ ነበረበት።“አብረው ከሚቀርቡት የእህል ቁርባንና የመጠጥ ቁርባን ጋር”(ንብረት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 29:20

በጉባዔው በሶስተኛው ቀን
“በበዓሉ 3ተኛ ቀን” እዚህ ላይ “ጉባዔ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በበዓሉ ወቅት ያሉትን ሣምንታት ነው።(ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

አሥራ አንድ ወይፈኖች፤ሁለት አውራ በጎች፤አሥራ አራት የአንድ ዓመት ተባት ጠቦቶች
“11 ወይፈኖች፤2 አውራ በጎች፤14 የአንድ ዓመት ተባት ጠቦቶች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በታዘዙት መሠረት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእህሉ ቁርባንና ከመጠጡ ቁርባን
የእህሉ ቁርባን ከሚቃጠለው ቁርባን ጋር መቅረብ ነበረበት።የመጠጥ ቁርባኑ ከኃጢአት መሥዋዕቱና ከሚቃጠለው መሥዋዕት ጋር አብሮ መቅረብ ነበረበት።“አብረው ከሚቀርቡት የእህል ቁርባንና የመጠጥ ቁርባን ጋር”(ንብረት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Numbers 29:23

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ለሕዝቡ ማድረግ ያለበትን ነገር እግዚአብሔር መንገሩን እንደቀጠለ ነው።

በጉባዔው በአራተኛው ቀን
“በበዓሉ 4ተኛ ቀን” እዚህ ላይ “ጉባዔ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በበዓሉ ወቅት ያሉትን ሣምንታት ነው።(ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

አሥራ አራት ተባት ጠቦቶች
“14 ተባት ጠቦቶች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በታዘዙት መሠረት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእህሉ ቁርባንና ከመጠጡ ቁርባን
የእህሉ ቁርባን ከሚቃጠለው ቁርባን ጋር መቅረብ ነበረበት።የመጠጥ ቁርባኑ ከኃጢአት መሥዋዕቱና ከሚቃጠለው መሥዋዕት ጋር አብሮ መቅረብ ነበረበት።“አብረው ከሚቀርቡት የእህል ቁርባንና የመጠጥ ቁርባን ጋር”(ንብረት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 29:26

በጉባዔው በአምስተኛው ቀን
“በበዓሉ 5ተኛ ቀን” እዚህ ላይ “ጉባዔ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በበዓሉ ወቅት ያሉትን ሣምንታት ነው።(ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

አሥራ አራት ተባት ጠቦቶች
“14 ተባት ጠቦቶች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በታዘዙት መሠረት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእህሉ ቁርባንና ከመጠጡ ቁርባን
የእህሉ ቁርባን ከሚቃጠለው ቁርባን ጋር መቅረብ ነበረበት።የመጠጥ ቁርባኑ ከኃጢአት መሥዋዕቱና ከሚቃጠለው መሥዋዕት ጋር አብሮ መቅረብ ነበረበት።“አብረው ከሚቀርቡት የእህል ቁርባንና የመጠጥ ቁርባን ጋር”(ንብረት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 29:29

በጉባዔው በስድስተኛው ቀን
“በበዓሉ 6ተኛ ቀን” እዚህ ላይ “ጉባዔ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በበዓሉ ወቅት ያሉትን ሣምንታት ነው።(ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

አሥራ አራት ተባት ጠቦቶች
“14 ተባት ጠቦቶች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በታዘዙት መሠረት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእህሉ ቁርባንና ከመጠጡ ቁርባን
የእህሉ ቁርባን ከሚቃጠለው ቁርባን ጋር መቅረብ ነበረበት።የመጠጥ ቁርባኑ ከኃጢአት መሥዋዕቱና ከሚቃጠለው መሥዋዕት ጋር አብሮ መቅረብ ነበረበት።“አብረው ከሚቀርቡት የእህል ቁርባንና የመጠጥ ቁርባን ጋር”(ንብረት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 29:32

በጉባዔው በሰባተኛው ቀን
“በበዓሉ 7ተኛ ቀን” እዚህ ላይ “ጉባዔ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በበዓሉ ወቅት ያሉትን ሣምንታት ነው።(ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

አሥራ አራት ተባት ጠቦቶች
“14 ተባት ጠቦቶች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በትዕዛዙ መሠረት
“እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት”

ከእህሉ ቁርባንና ከመጠጡ ቁርባን
የእህሉ ቁርባን ከሚቃጠለው ቁርባን ጋር መቅረብ ነበረበት።የመጠጥ ቁርባኑ ከኃጢአት መሥዋዕቱና ከሚቃጠለው መሥዋዕት ጋር አብሮ መቅረብ ነበረበት።“አብረው ከሚቀርቡት የእህል ቁርባንና የመጠጥ ቁርባን ጋር”(ንብረት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 29:35

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ለሕዝቡ ማድረግ ያለበትን ነገር እግዚአብሔር መንገሩን እንደቀጠለ ነው።

በስምንተኛውም ቀን
“ስምንተኛው”የሚለው ቃል ስምንት ለሚለው ተከታታይ ቁጥር ነው።(ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

ሌላ የተቀደሰ ጉባዔ ይሁንላችሁ
“እግዚአብሔርን ለማምለክ እንደገና ተሰብሰቡ”ይሄ ከመጀመሪው ቀን በዓል ጋር የሚመሳሰል ሌላ ጉባዔ ነው።

በእሣት የሚደረግ መሥዋዕት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በመሠዊያው ላይ ማቃጠል ይኖርባችኋል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 29:37

የእህል ቁርባናቸውና የመጠጥ ቁርባናቸው
እነዚህ መሥዋዕቶች መቅረብ የሚኖርባቸው ከወይፈን፤ከበግ ጠቦትና ከአውራ በግ ጋር ነበር።”የእህል ቁርባንና የመጠጥ ቁርባን”(ንብረት የሚለውን ይመልከቱ)

በታዘዙት መሠረት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእህሉ ቁርባንና ከመጠጡ ቁርባን
የእህሉ ቁርባን ከሚቃጠለው ቁርባን ጋር መቅረብ ነበረበት።የመጠጥ ቁርባኑ ከኃጢአት መሥዋዕቱና ከሚቃጠለው መሥዋዕቱ ጋር አብሮ መቅረብ ነበረበት።“አብረው ከሚቀርቡት የእህል ቁርባንና የመጠጥ ቁርባን ጋር”(ንብረት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 29:39

የምታቀርቧቸው ነገሮች እነዚህ ናቸው
“የምታቀርቧቸው መሥዋዕቶች እነዚህ ናቸው”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ናቸው::“በተቆረጠላቸው”ማለት“በተመደበላቸው”ወይም“አስቀድሞ በተወሰነላቸው”ጊዜ ማለት ነው::

በተቆረጠላቸው ቀን የሚደረጉ በዓላት
“በዕቅድ የተያዙ በዓላት”እነዚህ በዓላት በተያዘላቸው የጊዜ ሠሌዳ መሠረት በቋሚነት የሚከናወኑ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 30

1 ሙሴ ለእስራኤል ህዝብ የጎሳ መሪዎች እንዲህ አላቸው፣ “ያህዌ ያዘዘው ይህን ነው። **2** ማንም ሰው ለያህዌ ስዕለት ሲሳል፣ ወይም በቃል ኪዳን ራሱን በመሀላ ሲያስር፣ ቃሉን ማፍረስ የለበትም። ከአፉ የወጣውን ማናቸውንም ነገር ለማድረግ ቃልኪዳኑን መጠበቅ አለበት። **3** አንዲት ወጣት ሴት በአባቷ ቤት እያለች ለያህዌ ብትሳልና በመሀላ ራሷን ብታስር፣ **4** አባቷም ስዕለቷንና ራሷን ያሰረችበትን መሀላ ቢሰማ፣ እርሱም እርሷን ለመመለስ አንዳች ነገር ባይናገር መሀላዎቿ ሁሉ መፈፀም አለባቸው። ራሷን ያሰረችባቸው ቃልኪዳኖች ሁሉ ተግባራዊ ይሆናሉ። **5** ነገር ግን አባቷ ስለ ስዕለቷና ስለገባችው ቃል ኪዳን ሰምቶ ምንም ነገር ባይነግራት በራሷ ላይ የወሰደቻቸው የገባቻቸው መሀላዎችና ቃል ኪዳኖች መፈጸም አለባቸው። **6** ሆኖም ግን፣ አባቷ የገባቻቸውን መሀላዎች ሁሉና የከበሩ ቃል ኪዳኖቿን ራሷን ግዴታ ውስጥ ያስገባችበትን ነገር ቢሰማ፣ ደግሞም በዚያው ቀን ማድረግ ያለበትን ቢነግራት መሀላዋን ለመፈጸም አትገደድም። ያህዌ ይቅር ይላታል ምክንያቱም አባቷ ማድረግ ያለባትን ነግሯታል። **7** እነዚያ መሀላዎች እያሉባት ባል ብታገባ ወይም በችኮላ መሀላ ብታደርግና ራሷን ግዴታ ውስጥ ብታስገባ እነዚያ ግዴታዎች መፈጸም አለባቸው። **8** ነገር ግን ባሏ በዚያው ቀን ሰምቶ ቢከለክላት የገባቸውን መሀላና በችኮላ ራሷን ያሰረችበትን መሀላዋን ያስቀራል። ያህዌ ከዚህ ነጻ ያደርጋታል። **9** ባሏ የሞተባት ወይም ከባሏ የተፋታች ሴት ግን ራሷን የሰራችባቸው ነገሮች ሁሉ ተፈፃሚ ይሆኑባታል። **10** ከባሏ ቤተሰቦች ጋር ያለች ሴት ብትሳል ራሷን በቃል ኪዳን መሀላ ብታስር፣ **11** እና ባልዋ ሰምቶ ምንም ነገር ባይነግራት ስእለቷን ባያስቀር፣ ስዕለቶቿ ሁሉ መፈጸም አለባቸው። ራሷን ያሰረችባቸው ቃልኪዳኖች ሁሉ መፈጸም አለባቸው። **12** ነገር ግን ባሏ ስለ ስዕለቶቿ በሰማ ቀን እንዲቀሩ ካደረገ፣ ስለ ስዕለቶቿ ወይም ቃልኪዳኖቿ ከከንፈሯ የወጡ ነገሮች ሁሉ የግዴታ መፈጸም አይኖርባቸውም። ባልዋ አስቀርቷቸዋል። ያህዌ ነጻ ያደርጋታል፣፤ **13** አንዲት ሴት የገባችውን እያንዳንዱን መሀላ ወይም ስእለት እንድታጥፍ የሚያደርጋትን አንዳች ነገር በባሏ ሊጸና ወይም ሊሻር ይችላል። **14** ነገር ግን ቀናት ሲያልፉ ባሏ አንዳች ካልነገራት፣ ስዕቶቿን ሁሉ እና ቃል የገባቻቸውን ነገሮች ያፀናባታል። ስዕቶቿንና መሀላዎቿን የሚያፀናባት ስለእነዚህ በሰማበት ጊዜ ምንም ስላልነገራት ነው። **15** ባሏ የሚስቱን ስዕለት ከሰማ ከረጅም ጊዜ በኋላ ሊሽር ቢሞክር፣ ስለእርሷ ኃጢአት ሀላፊነቱን ይወስዳል።” **16** ያህዌ ሙሴ እንዲያውጃቸው የሰጠው ቋሚ መመሪያዎች እነዚህ ናቸው። በአንድ ወንድና በሚስቱ መሀል፣ እንዲሁም በአባትና በወጣትነቷ በአባቷ ቤት ስለምትኖር ሴት ልጁ ያህዌ የሰጠው ቋሚ መመሪያ ይህ ነው።

Numbers 30:1

ሰው ለእግዚአብሔር ስእለት ቢሳል ወይም ራሱ በመሐላ ቢያስር
እነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን በጋራ እንዲቀርቡ የተደረጉት ስለ ስእለትና ስለ መሐላ አፅንኦት ለመስጠት ነው። (ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

ራሱ በመሐላ ቢያስር
ሙሴ እዚህ ላይ የሚናገረው አንድ ሰው አንድ ነገር ለማድረግ ቃል የመግባቱን ጉዳይ አስመልክቶ ቢሆንም የሚገባው ቃል ቁሣቁስ ይመስል ራሱ ላይ እንደሚያስረው ዓይነት አድርጎ ያቀርበዋል።“አንድ ነገር ለመፈፀም ራስን መሥጠት”ወይም “አንድን ነገር ለመፈፀም ቃል መግባት” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ቃሉን አይስበር፤ከአፉ እንደወጣው ሁሉ ያድርግ
እነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን በጋራ እንዲቀርቡ የተደረጉት የገባውን ቃል ተግባራዊ ማድረግ እንደሚኖርበት አፅንኦት ለመስጠት ነው።(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

ቃሉን አይስበር
“ቃሉን”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሰውዬውን መሐላና ቃል ኪዳን መግባት ነው።ሙሴ እነዚህን ነገሮች ተግባራዊ አለማድረግን ልክ አንድን ዕቃ ከመስበር ጋር አመሳስሎ ነው የሚናገረው።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውንና ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ከአፉ እንደወጣው ሁሉ
እዚህ ላይ“አፍ”የሚለው ቃል ሰውዬው የሚናገረውን ነገር ለመግለፅ የዋለ ነው።“አደርገዋለሁ የሚለውን ነገር ሁሉ ማድረግ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 30:3

ራሷን በስእለት ብታስር
እዚህ ላይ ሙሴ አንዲት ሴት ቃል የመግባቷን ጉዳይ ልክ ራሷን በአንድነገር እንደምታስረው ዓይነት አድርጎ ነው ያቀረበው።“የገባቸውን ቃል ለመፈፀም ራሷን ሰጠች”ወይም “አንድ ነገር ለመፈፀም ቃል ገባች”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መሐላውና ቃል መግባቱ
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ነው ያላቸው።አፅንኦት የሚሰጠው የገባችውን ቃል በሚመለከት ነው።“መሐላው”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ራሷን ባሰረችበት
እዚህ ላይ ሙሴ አንዲት ሴት ቃል የገባቸውን ነገር ለመፈፀም ስትል የምታደርገውን መሠጠት ልክ ከሰውነቷጋር እንዳሰረችው ቁሣቁስ አድርጎ ነው የሚያቀርበው።“የገባቸውን ቃል ለመፈፀም ራሷን ሰጠች”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ብታጥፍ
“ያለችውን ነገር ብትሰረዘው”

ስእለትዋ ሁሉ ይፀናል..መሐላ ሁሉ ይፀናል
እነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን መሐላዋን ሁሉ መጠበቅ እንዳለባት አፅነዖት የሚሰጥ ነው።(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

ይፀናል
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን መሐላዋ የፀና እንደሆነና ተግባራዊ ማድረግ እንደሚጠበቅባት የሚያስረዳ ነው።“ተግባራዊ እንድታደርገው ትገደዳለች”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 30:5

መሐላዋና ቃል መግባቷ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በጣም የተመሳሰለ ትርጉም ነው ያላቸው።ቃል የገባቸውን ነገር አጥብቀው የሚያሳስቡ ናቸው።“መሐላዋን”(ሁለት ተመሳሳይ የሆነ ገፅታ ያላቸው የሚለውን ይመልክቱ)

ራስዋ ላይ ያደረገችው
እዚህ ላይ ሴትዬዋ መሐላዋን ለመፈፀም ራሷን መሥጠቷን ልክ መሐላውን ሰውነቷ ላይ እንደምታደርገው ልብስ ተደርጎ ተገልጿል።“ራሷን

የሰጠችበት”ወይም “ቃል የገባችው”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይፀናል
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን መሐላዋ የፀና እንደሆነና ተግባራዊ ማድረግ እንደሚጠበቅባት የሚያስረዳ ነው።ይህንን ሐረግ በዘኁልቁ 30፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“ተግባራዊ እንድታደርገው ትገደዳለች”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 30:6

በተረጋጋ መንፈስ ውስጥ ሆና ራስዋን ያሰረችበት መሐላ
እዚህ ላይ ሙሴ አንዲት ሴት ቃል የገባቸውን ነገር ለመፈፀም ስትል የምታደርገውን መሠጠት ልክ ከሰውነቷጋር እንዳሰረችው ቁሣቁስ አድርጎ ነው የሚያቀርበው።“ ረጋ ባለ መንፈስ ቃል የገባችውን ነገር ለመፈፀም የምታደርገው መሠጠት”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ዝም ቢለት
እዚህ ላይ የሴትዋን ቃል ዝም ማለቱን ልክ አንድ ባለሥልጣን በሥልጣኑ እንደሚከለክላት ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል።(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

የፀና አይሆንም
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን መሐላዋ የፀና እንደማይሆንና ተግባራዊ ማድረግ እንደማይጠበቅባት የሚያስረዳ ነው።ይህንን ሐረግ በዘኁልቁ 30፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“ተግባራዊ እንድታደርገው አትገደድ”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔርም ይቅር ይላታል
ይሄ የሚያመለክተው መሐላዋን ባትፈፀምም እንኳን እግዚአብሔር ይቅር ያላት መሆኑን ነው።የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ሃሣብ የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“መሐላዋን ባትፈፅምም እግዚአብሔር ይቅር ይላታል”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በእነዚያ መሐላዎች ሥር ከሆነ
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው።መሐላዋ የፀና እንደማይሆንና ተግባራዊ ማድረግ እንደማይጠበቅባት የሚያስረዳ ነው።ይህንን ሐረግ በዘኁልቁ 30፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“ተግባራዊ እንድታደርገው አትገደድ”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በችኮላ
በአግባቡ ሳይታሰብ የሚደረግ ነገር።

እነዚያ ግዴታዎች
“ግዴታዎች”የሚለው ቃል “ማስገደድ”በሚለው ሥም ሊገለፅ ይችላል።“ራስዋን ግዴታዎች ውስጥ ያስገባችባቸው ነገሮች”(አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 30:8

ያደረገችው መሐላ...በችኮላ የተናገረችው ንግግር
“ያደረገችው መሐላ...ማለትም በችኮላ የተናገረችው ንግግር” እነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች የሚያመለክቱት አንድን ነገር ነው።ሁለተኛው ሐረግ ሴትዬዋ ያደረገችውን መሐላ የሚገልፅ ነው።(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

የአንደበቷ ችኩል አነጋገር
“ችኩል አነጋገር”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በችኮላ የገባችውን የተስፋ ቃል ነው።እዚህ ላይ “አንደበቷ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ራሷን ሴትዬዋን ነው።አንደበቷ ከምትናገረው ነገር ጋር የተያያዘ በመሆኑ “አንደበቷ”በሚለው ቃል ተወክላለች።“በችኮላ የተናገረቻቸው ነገሮች” ወይም“በችኮላ ቃል መግባቷ”(ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)

ራስዋን ያሰረችበትን
እዚህ ላይ ሙሴ አንዲት ሴት ቃል የገባቸውን ነገር ለመፈፀም ስትል የምታደርገውን መሠጠት ልክ ከሰውነቷ ጋር እንዳሰረችው ቁሣቁስ አድርጎ ነው የሚያቀርበው።“ ረጋ ባለ መንፈስ ቃል የገባችውን ነገር ለመፈፀም የምታደርገው መሠጠት”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ነፃ ያወጣታል
እዚህ ላይ ሙሴ አንዲት ሴት ቃል የገባችውን ነገር ባትፈፅምም እግዚአብሔር ይቅር እንደሚላት ለመግለፅ ከታሰረችበት ነገር እንደምትለቀቅ ዓይነት አድርጎ አቅርቦታል።የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ሃሣብ የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“እግዚአብሔር ይቅር ይላታል” “የገባችውን ቃል ባትፈፅምም እግዚአብሔር ይቅር ይላታል”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውንና (በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ))

Numbers 30:9

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ እግዚአብሔር ያዘዘውን ነገር ለነገድ መሪዎች መናገሩን ይቀጥላል።

የተፋታች ሴት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“አንድ ሰው የፈታት ሴት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ራስዋን ያሰረችበትን
እዚህ ላይ ሙሴ አንዲት ሴት ቃል የገባቸውን ነገር ለመፈፀም ስትል የምታደርገውን መሠጠት ልክ ከሰውነቷ ጋር እንዳሰረችው ቁሣቁስ አድርጎ ነው የሚያቀርበው።“ቃል የገባችውን ነገር ለመፈፀም የምታደርገው መሠጠት”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሷ ላይ የፀና ይሆናል
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን መሐላዋ የፀና እንደሆነና ተግባራዊ ማድረግ እንደሚጠበቅባት የሚያስረዳ ነው።ይህንን ሐረግ በዘኁልቁ 30፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“ተግባራዊ እንድታደርገው ትገደዳለች”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሴት በባሏ ቤት ውስጥ ሳለች ብትሳል
ይሄ የሚመለከተው ያገቡ ሴቶችን ነው።የዚህን ሃሣብ የበለጠ ልታብራሩት ትችላላችሁ።“ያገባች ሴት ስእለት ብትሳል”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያ በኋላ መሐላዋ ሁሉ የፀና ይሆናል...መተግበሩ ግዴታ ይሆናል
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው።“መተግበሩ ግዴታ ይሆናል”የሚለው ቃል የሚፀናና እርሱን ለመፈፀም ትገደዳለች ማለት ነው።የዚህን ተመሳሳይ ሐረግ በኦሪት ዘኁልቁ 30፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“ከዚያም መሐላዋን ሁሉ ተግበራዊ ማድረግ ይኖርባታል....መፈፀም ይኖርባታል”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ስእለትዋ ይፀናል...ራስዋንም ያሰረችበት መሐላ ሁሉ ይፀናል
በመሠረቱ እነዚህ ዓረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ተደጋገመው የቀረቡት ለጉዳዩ አፅንዖት ለመሥጠት ሲሆን ተቀናጅተውም ሊቀርቡ ይችላሉ።“ስእለቷና መሐላዋ ሁሉ የፀና መሆን ይኖርበታል” (ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 30:12

ከከንፈሯ የወጣ ማንኛውም ነገር
እዚህ ላይ ሴትዬዋ የተናገረችው ንግግር ከከንፈሯ እንደወጣ ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል።“ከዚያ በኋላ የተናገረችው ነገር ሁሉ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የፀና አይሆንም
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን መሐላዋ የፀና እንደማይሆንና ተግባራዊ ማድረግ እንደማይጠበቅባት የሚያስረዳ ነው።ይህንን ሐረግ በዘኁልቁ 30፡6 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“ተግባራዊ እንድታደርገው አትገደድ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ነፃ ያወጣታል
እዚህ ላይ ሙሴ አንዲት ሴት ቃል የገባችውን ነገር ባትፈፅምም እግዚአብሔር ይቅር እንደሚለት ለመግለፅ ከታሰረችበት ነገር እንደምትለቀቅ ዓይነት አድርጎ አቅርቦታል።የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ሃሣብ የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“እግዚአብሔር ይቅር ይላታል” “የገባችውን ቃል ባትፈፅምም እግዚአብሔር ይቅር ይላታል”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውንና (በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ))

Numbers 30:13

ስእለትዋን ሁሉ ...መሐላዋን ሁሉ በልዋ ያጸናዋል፤ባልዋም ከንቱ ያደርገዋል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የአንዲት ሴት ባል ራሰዋን ያሰረችበትን ማንኛውንም ነገር ማለትም ስእለት ወይም መሐላ ማጽናት ወይም ማፍረስ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

የታሰረችበትን
እዚህ ላይ ሙሴ አንዲት ሴት ቃል የገባችውን ነገር ለመፈፀም ስትል የምታደርገውን መሠጠት ልክ ከሰውነቷ ጋር እንዳሰረችው ቁሣቁስ አድርጎ ነው የሚያቀርበው።“ቃል የገባችውን ነገር ለመፈፀም የምታደርገው መሠጠት”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አሳሪ የሆኑ ቃል ኪዳኖች
ሙሴ አንዲት ሴት የምትገባቸው ቃል ኪዳኖች አካሏን እንደሚያስሩ ነገሮች አድርጎ አቅርቧቸዋል።“ግዴታዎች” “ቃል ኪዳኖች”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ዝም በሏታልና
ግልፅ የሆነውን ይህንን መረጃ የበለጠ ልታብራሩት ትችላላችሁ።“ጉዳዮቹን አስመልክቶ ምንም ነገር ስላልተናገረ”(ምልክቶች እንጂ ቃላት ጥቅም ላይ የማይውሉበት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 30:15

ስለ ኃጢአቷ ኃላፊነቱን እርሱ የሚወስድ ይሆናል
ስእለቷን የማትፈፀም ከሆነ በእርሷ ምትክ ኃጢአቷን ይሸከማል ማለት ነው። የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ሃሣብ የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“ስእለቷን ባትፈፀም በኃጢአቷ ጥፋተኛ አትባልም።እርሱ ግን በእርሷ ምትክ ጥፋተኛ የሚሆን ይሆናል።”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 31

1 ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ 2 “የእስራኤል ህዝብ ምድያማውያንን ይበቀሉ። ያን ካደረግህ በኋላ፣ ወደ ወገኖችህ ትከማቻለህ።” 3 ስለዚህም ሙሴ
ለህዝቡ እንዲህ አለ፣ “በምድያማውያን ላይ የያህዌን በቀል ይፈጽሙ ዘንድ ከወንዶቻችሁ አንዳንዶቹን ወደ ጦርነት እንዲወጡ አስታጥቋቸው። 4 እያንዳንዱ
በእስራኤል ውስጥ ያለ ጎሳ ለጦርነት አንድ ሺህ ወታደሮችን መላክ አለበት።” 5 ስለዚህ ከእስራኤል ብዙ ሺህ ወንዶች መሀል ከእያንዳንዱ ጎሳ አንድ ሺህ ሰው
ለጦርነት ቀረበ፣ በጠቅላላው አስራ ሁለት ሺህ ወንዶች ነበሩ። 6 ከዚያ ሙሴ ከየጎሳው አንድ ሺህ ሰዎችን ከካህኑ ከአልዓዛር ልጅ ከፊንሃስ ጋር እና ከተቀደሰው
ስፍራ ከጥቂት ቁሳቁሶችና እንዲሁም ምልክቶችን ለማሰማት በእጁ ያሉትን መለከቶች አስይዞ ወደ ጦርነት ላካቸው። 7 እነርሱም ያህዌ ሙሴን እንዳዘዘው
ከምድያማውያን ጋር ተዋጉ። ሰዎቹን ሁሉ ፈጇቸው። 8 የምድያምን ነገስታት ኤዊ፣ ሮቆም፣ ሱር ሑርን እና እና ሪባን ከተቀሩት ጋር በሰይፍ ገደሏቸው። 9
የእስራኤል ጦር፤ የምድያምን ሴቶች፣ ልጆቻቸውን ከብቶቻቸውን ሁሉ፣ መንጋዎቻቸውን እና ንብረቶቻቸውን ሁሉ ምርኮ አደረጉ። እዚህን ሁሉ ዘርፈው ወሰዱ። 10
የሚኖሩባቸውን ከተሞችና ሰፈሮች ሁሉ አቃጠሉ። 11 የሰውና እንስሳት ምርኮዎቻቸውንና እስረኞችን ወሰዱ። 12 እስረኞችን፣ የዘረፉትን፣ እና የያዙትን ነገሮች
ወደ ሙሴ፣ ወደ ካህኑ አልዓዛር፣ እና ወደ እስራኤል ማህበረሰብ አመጡ። እነርሱም እነዚህን ኢያሪኮ አጠገብ ዮርዳስ፣ በሞአብ ሜዳ ላይ ወደ ሚገኘው ሰፈር
አመጡ። 13 ሙሴ፣ ካህኑ አልዓዛር፣ እና የማህበረሰቡ መሪዎች በሙሉ ሊቀበሏቸው ከሰፈር ወጡ። 14 ሙሴ ግን ከጦርነት በተመለሱት በጦሩ መኮንኖች፣
በሻለቃዎችና በመቶ አለቆች ላይ ተቆጥቶ ነበር። 15 ሙሴ መኮንኖቹን እንዲህ አላቸው፣ “ሴቶቹ ሁሉ በህይወት እንዲኖሩ ተዋችኋቸውን?” 16 እነዚህ ሴቶች
በበለዓም ምክር፣ የእስራኤል ህዝብ በያህዌ ላይ በፌጎር ኃጢአት እንዲሰራና መቅሰፍት እንዲወርድበት ያደረጉ ናቸው። 17 ስለዚህ አሁን፣ ትናንሾቹን ወንዶች
ሁሉ ግደሉ፣ ከወንድ ጋር የተኙ ሴቶችን ሁሉ ግደሉ። 18 ከወንድ ጋር ተኝተው የማያውቁትን ወጣት ልጃገረዶች ግን ለራሳችሁ ውሰዱ። 19 ከእስራኤል ሰፈር
ውጭ ለሰባት ቀናት መቆየት አለባችሁ። ማንንም ሰው የገደላችሁ ሁሉና ወይም የሞተ ሰው የነካችሁ ሁሉ በሶስተኛው ቀንና በሰባተናው ቀን ራሳችሁን ማንጻት
አለባችሁ። እናንተና ምርኮኞቻችሁ መንጻት አለባችሁ። 20 ልብሶቻችሁን አንጹ፣ ከእንስሳት ቆዳ እና ከፍየል ፀጉር የተሰሩ ማናቸውንም ነገሮች፣ እንዲሁም
ከእንጨት የተሰሩ ነገሮችን ሁሉ አንጹ።” 21 ካህኑ አልዓዛር ወደ ጦርነት የሄዱትን ወታደሮች እንዲህ አላቸው፣ “ይህ ያህዌ ለሙሴ የሰጠው የተደገነገገ ህግ
ነው፡ 22 ወርቁ፣ ብሩ፣ ነሀሱ፣ ብረቱ፣ ቆርቆሮውና እርሳሱ 23 እና ማናቸውም እሳት የሚቋቋምን ነገር በእሳት ውስጥ አሳልፉት እናም የተቀደሰ ይሆናል። እነዚያን
ነገሮች በማንጻት ውሃ አንጹዋቸው። በእሳት ውስጥ ማለፍ የማይችለውን ማናቸውንም ነገር በውሃ አንጹ። 24 እናም ልብሶችሁን በሰባተኛው ቀን እጠቡ፣ ከዚያም
የተቀደሳችሁ ትሆናላች። ከዚህ በኋላ ወደ እስራኤል ሰፈር መግባት ትችላላችሁ።” 25 ከዚያም ያህዌ ሙሴን እንደዚህ አለው፣ 26 ”ሰዎችም ይሁኑ እንስሳት፣
የተማረኩትንና የተወሰዱትን ነገሮች ሁሉ ቁጠሩ። አንተ፣ ካህኑ አልዓዛር፣ እና የማህበረሰቡ መሪዎች እንዲሁም የጎሳ አባቶች 27 ምርኮዎቹን ለሁለት ክፍል
ክፈሏቸው። ለጦርነት በወጡ ወታደሮችና በተቀረው ማህበረሰብ መሃል ምርኮውን አከፋፍሉ። 28 ከዚያ ወደ ጦርነት ከወጡ ወታደሮች ለእኔ የሚሰጥ ግብር
ጣል። ይህ ግብር ከሰዎችም ይሁን፣ ከቀንድ ከብት፣ ከአህዮች፣ ከበጎች ወይም ከፍየሎች ከየአምስት መቶው አንዱ ይሁን። 29 ይህን ግብር የእነርሱ ከሆነው
ከከፊሉ ድርሻቸው ወስደህ ለእኔ የሚቀርብ ስጦታ እንዲሆን ለካህኑ አልዓዛር ስጠው። 30 ደግሞም ከከፊሉ የእስራኤል ህዝብ ድርሻ ከሆነው ሰዎች፣ ከቀንድ
ከብቶች፣ ከአህዮች፣ ከበጎች ከፍየሎች፣ ከየሀምሳው መሀል አንዱን ወሰድ። እነዚህን ማደሪያዬን ለሚያገለግሉት ለሌዋውያን ስጣቸው።” 31 ስለዚህ ሙሴና
ካህኑ አልዓዛር ያህዌ ሙሴን እንዳዘዘው አደረጉ። 32 ወታደሮቹ በዝብዘው የወሰዱት ምርኮ 675000 በጎች፣ 33 ሰባሁለት ሺህ በሬዎች፣ 34 ስልሳ አንድ ሺህ
አህዮች፣ 35 እና ሰላሳ ሁለት ሺህ ከወንድ ጋር ያልተኙ ሴቶች ነበሩ። 36 ለወታደሮች የተጠበቀላቸው ግማሹ 337000 በጎች ነበሩ። 37 ከዚህ ውስጥ የያህዌ
ድርሻ 675 በጎች ነበር። 38 በሬዎቹ ሰላሳ ስድስት ሺህ ሲሆኑ የያህዌ ግብር 72 ነበር። 39 አህዮች 30500 ነበሩ፣ ከዚህ ውስጥ የያህዌ ድርሻ 61 ነበር።
40 ሰዎቹ አስራ ስድስት ሺ ሴቶች ነበሩ፣ ከዚህ ውስጥ ለያህዌ የተሰጠው ግብር 32 ነበር። 41 ሙሴ ለያህዌ የሚቀርቡትን ስጦታዎች ግብር ወሰደ።
እርሱም ያህዌ ሙሴን እንዳዘዘው ለካህኑ አልዓዛር ይህንን ሰጠ። 42 ሙሴ ወደ ጦርት ከሄዱ ወታደሮች የወሰደውን የእስራኤል የሆነውን ግማሽ ምርኮ
በተመለከተ፤ 43 የማህበረሰቡ ከምርኮ ግማሹ 337500 በጎች፣ 44 ሰላሳ ስድስት ሺህ በሬዎች፣ 45 ሰላሳ ሺ አምስት መቶ አህዮች፣ 46 እና አስራ ስድስት
ሺ ሴቶች ነበሩ። 47 ከእስራኤል ህዝብ ግማሽ ከሆነ ድርሻው፣ ሙሴ ከሰውም ሆነ ከእንስሳት ከየአምሳው መሀል አንድ ወሰደ። እርሱም ያህዌ እንዲያደርገው
ባዘዘው መሠረት የያህዌን ማደሪያ ለሚያገለግሉ ለሌዋውያን እነዚህን ሰጠ። 48 ከዚያ የሰራዊቱ መኮንኖች፣ የሻለቃ አዛዦች እና የመቶ አለቆች ወደ ሙሴ
መጡ። 49 እንዲህም አሉ፣ “ባሮችህ በእኛ ስር ያሉትን ወታደሮች ቆጠርን፣ አንድ ሰው እንኳን አልጎደለም። 50 እኛ የያህዌን ስጦታ አምጥተናል፣ እያንዳንዱ
ሰው ያገኘውን፣ የወርቅ ዕቃዎች፣ አልቦዎችና አንባሮች፣ የጣት ቀለበቶች፣ የጆሮ ጉትቻዎች፣ እና የአንገት ሀብሎች ማስተስረያ እንደሆነን በያህዌ ፊት
አምጥተናል።” 51 ሙሴና ካህኑ አልዓዛር ወርቁንና የእጁ ጥበብ ውጤት የሆኑትን የጌጥ ዕቃዎች ሁሉ ከእነርሱ ተቀበሉ። 52 ለያህዌ ያቀረቧቸው የወርቅ
ስጦታዎች ሁሉ ከሻለቃዎችና ከመቶ አለቃዎች የተቀበሏቸው ስጦታዎች ክብደታቸው 16750 ሰቅሎቸ ነበር። 53 እያንዳንዱ ወታደርና እያንዳንዱ ሰው
ከምርኮው ለራሱ ወስዷል። 54 ሙሴና ካህኑ አልዓዛር ከሻለቆችና ከመቶ አለቆች ወርቁን ወሰዱ። ለያህዌ የእስራኤል ህዝብ ማስታወሻ አድርገው ወርቁን ወደ
መገናኛው ድንኳን አስገቡት።

Numbers 31:1

ስለ እሥራኤል ልጆች በቀል ምድያማውያንን ተበቀል
ምድያማውያን እሥራኤላውያን ጣኦት እንዲያመልኩ በመገፋፋታቸው ምክኒያት እግዚአብሔር ሊቀጣቸው ነው።

ከዚያም በኋላ ትሞታለህ ወደ ወገኖችህም ትከማቻለህ
በመሠረቱ እነዚህ ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው።ይሄ ጨዋ በሆነ አነገገር ቡሴ የመሞቻው ጊዜ መሆኑንና መንፈሱ አባቶቹ ወዳሉበት የሚሄድ መሆኑን የሚገልፅ ነው። (ተመሳሳይነት የሚለውንና ሥርዓት የሌለውን አነጋገር በመልካም ነገር መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 31:3

ከእናንተ መካከል ሰዎች ለጦርነት ይሰለፉ።
“ከሰዎችህ መካከል ለተወሰኑት ሰዎች መሣሪያ አስታጥቃቸው”

ስለ እግዚአብሔር በቀል ምድያማውያንን ይበቀሉ
“ሄደህ ከምድያማውያን ጋር በመዋጋት ላደረጉት ነገር ቅጣትን ሥጣቸው”

አንድ ሺህ...ሁለት ሺህ
“1000...2000”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የእሥራኤል አንድ ሺህ ሰዎች
“ከእሥራኤል አንድ ሺህ ወንዶች”

ከየነገዱ አንድ ሺህ ሰው ለጦርነት የሚሰለፉ ሰዎችተሰጡ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ከእያንዳንዱ ነገድ 1000 ሰዎች ለጦርነት ተላኩ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አሥራ ሁለት ሺህ ለጦርነት የተዘጋጁ ሰዎች
የሌዊን ነገድ ጨምሮ 12ቱም ነገዶች ሰዎችን ላኩ።እያንዳንዱ ነገድ 1000 ለጦርነት የሚሰለፉ ሰዎችን ላከ።(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 31:6

ኤዊ...ሮቆም...ሱር...ሑር...ሪባ
እነዚህ የምድያማውያን ነገሥታት ስሞች ናቸው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

የቢኦር ልጅ በለዓም
ቢኦር የበለዓም አባት ነበር።ይህንን በዘኁልቁ 22፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

Numbers 31:9

በዘበዙ
“የምድያማውያንን ንብረቶች የራሳችው አደረጉት”

ከተሞቻቸውን ሁሉ ሰፈሮቻቸውንም ሁሉ በእሣት አቃጠሉ
“እሥራኤላውያን ሠራዊቶች ምድያማውያን የሚኖሩባቸውን የምድያማውያንን ከተሞችና የምድያማውያንን ሠፈሮች ሁሉ አጠፉ”

Numbers 31:11

ወሰዱ
“የእሥራኤል ሠራዊት ወሰደው”

ብዝበዛው
ይሄ የሚያመለክተው ቁሳቁሶቹን ሁሉ በመውሰዳቸው ምክኒያት ምድያማውያንን ከሞት መታደጋቸውን ነው።

ሜዳ
ሠፊ ሆኖ ለጥ ያለ መሬት።

Numbers 31:13

ሻለቆችና የመቶ አለቆች
ለዚህ ፍቺ ሊሆኑ የሚችሉት 1/እነዚህ ቁጥሮች የሚያመለክቱት ሻለቆቹ ወይም የመቶ አለቆዎቹ የሚመሯቸው በሥራቸው የሚገኙ ሠራዊቶች ትክክለኛ ቁጥር ነው።“1000 ሰራዊት የሚመሩ ሻለቃዎችና 100 ሠራዊት የሚመሩ መቶ አለቃዎች”ወይም 2/“ሺዎችና መቶዎች የሚሉት ቃላት የታላላቅና የአነስተኛ የጦር ክፍሎች ስያሜዎች ናቸው እንጂ የሠራዊቱን ትክክለኛ ቁጥር የሚያመለክቱ አይደሉም” “ሠፊ የጦር ክፍል ያላቸው ሻለቃዎችና አነስተኛ የጦር ክፍል ያላቸው መቶ አለቃዎች”"(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በውኑ ሴቶችን ሁሉ አላዳናችኋቸውንም?
ማን ሊድን እንደሚገባና እንደፈሚቀድለት ሕጉ በግልፅ አስቀምጦታል። ሠራዊቱ ግን ሕጉን በመፃረር ሰቶችንና ልጆችን በሕይወት እንዲኖሩ አድርገዋቸዋል።ይሄ የሠራዊት መሪዎቹን ለመገሰፅ የቀረበ ጥያቄ ነው።(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 31:16

ተመልከቱ
ይሄ ቃል እዚህ ሥፍራ ላይ ጥቅም ላይ እንዲውል የተደረገው ከዚህ በመቀጠል የሚነገረውን ነገር ሕዝቡ በጥሞና እንዲያዳምጥ ታስቦ ነው።“አዳምጡ”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከወንድ ጋር የተኛ
“ከወንድ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ያደረገ”(ሥርዓት የሌለውን ነገር በመልካም ነገር መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 31:18

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ለእሥራኤል የጦር መሪዎች በእግዚአብሔር ፊት ንፁሕ መሆንን በተመለከተ ይነግራቸዋል።

ከወንድ ጋር ተኝተን አናውቅም
ይሄ የሚያመለክተው ድንግል ሴቶችን ነው።(ሥርዓት የሌለውን ነገር በመልካም ነገር መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

ሁላችሁም
ሙሴ እዚህ ላይ የሚናገረው የጦር አዛዦችን ብቻ ሣይሆን ማንኛውንም በጦርነቱ ላይ ተሣትፎ ያደረጉ ሰዎችን ሁሉ ነው።

ራሣችሁን ማንፃት ይኖርባችኋል
ወደ ሠፈሩ ውስጥ ከመግባታቸው በፊት በመንፈሣዊ ሕይወታቸው ዳግም ንፁሕ ሊሆኑ ይገባል።

ከቁርበት የተዘጋጀውን ሁሉ፤ከፍየልም ጠጉር፤ከእንጨትም የተሠራውን ሁሉ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“አንድ ሰው ከቁርበትከፍየልም ጠጉር፤ከእንጨትም የሠራውን ሁሉ” (ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 31:21

አጠቃላይ መረጃ
አልዓዛር ከሠልፍ የመጡትን ሰዎች ከጦርነት መልስ በኋላ በሕጉ ሥርዓት መሠረት እንዴት ንፁህ መሆን እንደሚገባቸው ያስተምራቸዋል፡

ወርቁን፤ብሩን፤ናሱን፤ብረቱን፤ቆርቆሮውን፤እረሩን
በዚያን ወቅት ጥቅም ላይ ይውሉ የነበሩ ብረቶች።

በእሣት ውስጥ ለማለፍ የሚችለውን
“የማይቃጠለውን”

በእሣት ውስጥ ታሳልፉታላችሁ
“እሣት ውስጥ አሰቀምጡት”

የማንፃት ውኃ
ይሄ የሚያመለክተው አንድ ሰው ከኃጢአት ቁርባን የወሰደውን ውኃ ከአመድ ጋር የመደባለቁን ሁኔታ ነው።(ኦሪት ዘኁልቁ 19፡17-19)

ከዚያ በኋላ ንፁህ ትሆናላችሁ
እነዚህ በሚከናወኑ ሥርዓቶች በእግዚአብሔር ፊት ንፁህ ሆኖ የመገኘት ልማዶች ናቸው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Numbers 31:25

የተማረኩትን ሁሉ ቁጠሩ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ወታደሮቹ የወሰዱትን ንብረት በሙሉ ቁጠሩ” (ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

የበዘበዛችሁት
ይሄ የሚያመለክተው እስራኤላውያን በጦርነት ውስጥ ከገደሏቸው ወይም ከማረኳቸው ሰዎች የወሰዷቸውን ንብረቶችን ነው።

የማህበሩም አባቶች አለቆች
“የየነገዶቹ መሪዎች”

Numbers 31:28

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል።

አጠቃላይ መረጃ
“እኔ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው።

ከእነዚያም ከተዋጉት ወደ ሠልፍም ከወጡት ለእኔ ያመጡ ዘንድ ቀረጥጣል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፦“ወታደሮቹ ከማረኳቸው ነገሮች ላይ ቀረጥ በመጣል ለእኔ አምጣው።(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ከአምስት መቶ አንድ
“በየአምስት መቶው”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ከድርሻቸው
“ከወታደሮቹ ድርሻ”

ለእኔ ይሰጥ ዘንድ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እርሱ ለእኔ የሚሰጠውን”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 31:30

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል።

ከእሥራኤልም ሕዝብ ድርሻ
“የእሥራኤል ሕዝብ ከበዘበዘው ከግማሹ”

ከየሃምሳው
“ከየ50”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

የሚጠብቁ
የመገናኛ ድንኳኑንና ለእግዚአብሔር የሚቀርቡትን መሥዋዕቶች በበላይነት የሚቆጣጠሩና የሚጠብቁ።

Numbers 31:32

አሁን
ይሄ ቃል ጥቅም ላይ እንዲውል የተደረገውበዋናነት በሚሰጠው ትምህርት ላይ የተወሰነ እረፍት እንዳለ ለማሣየት ነው።እዚህ ላይ ሙሴ ከተበዘበዙት ነገሮች ውስጥ ለወታደሮቹ፤ለሕዝቡና ለእግዚአብሔር ምን ያህል እንደተሰጠ ዝርዝራቸውን ያወጣል።

675,000 በጎች
“ስድስት መቶ ሰባ አምስት ሺህ በጎች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባ ሁለት ሺህ በሬዎች፤ስድሳ ሺህ አህዮች፤ሠላሳ ሁለት ሺህ ሴቶች
“72,000 በሬዎች፤60 ሺህ አህዮችና 32,000 ሴቶች” (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ወንድ የማያውቁ ሴቶች
ይሄ የሚያመለክተው ድንግል የሆኑ ሴቶችን ነው።(ሥርዓት የሌለውን ቃል በመልካም ነገር መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 31:36

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ከተበዘበዙት ነገሮች ውስጥ ለወታደሮቹ የሚሰጠውንና ተቀርጦ ለእግዚአብሔር የሚሰጠውን ዝርዝር ማውጣት ይጀምራል።(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ይሄ በድርጊት መበዘመቻ ለነበሩ ሰዎች ድርሻ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ለወታደሮቹ ከበጎቹ የሚደርሳቸው ድርሻ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

337,000 በጎች
“ሶስት መቶ ሰላሣ ሰባት ሺህ”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

675 ነበር
“ስድስት መቶ ሰባ አምስት”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰላሣ ስድስት ሺህ
“36,000”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባ ሁለት
72(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 31:39

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ከተበዘበዙት ነገሮች ውስጥ ለወታደሮቹ የሚሰጠውንና ተቀርጦ ለእግዚአብሔር የሚሰጠውን ዝርዝር ማውጣት ይጀምራል።(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

30,500 ነበሩ
“ሰላሣ ሺህ አምስት መቶ ነበሩ”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ስድሳ አንድ
61(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

አስራ ስድስት ሺህ
16,000(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰላሣ ሁለት
32 (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ለእግዚአብሔር ለግብርነት የሚሰጡ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ለእግዚአብሔር ቁርባን የሚሆነውን”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 31:42

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ከተበዘበዙት ነገሮች ውስጥ ለወታደሮቹ የሚሰጠውንና ተቀርጦ ለእግዚአብሔር የሚሰጠውን ዝርዝር ማውጣት ይጀምራል።(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

337,500 በጎች
“ሶስት መቶ ሰላሣ ሰባት ሺህ አምስት መቶ በጎች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰላሣ ስድስት ሺህ በሬዎች
“ሰላሣ ስድስት ሺህ በሬዎች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

አሥራ ስድስት ሺህ ሴቶች
“16,000 ሴቶች”ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የተማረኩ ወንዶቹና ያገቡ ሴቶች በሙሉ በሕይወት እንዳይኖሩ ተደርጓል።(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 31:47

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ከተበዘበዙት ነገሮች ውስጥ ለወታደሮቹ የሚሰጠውንና ተቀርጦ ለእግዚአብሔር የሚሰጠውን ዝርዝር ማውጣት ይጀምራል።(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ
በሕዝቡ ላይ የተጣለው ግብር በወታደሮቹ ላይ ከተጣለው ግብር ይልቅ ከፍ ያለ ነበር።

Numbers 31:48

ሻለቆችና የመቶ አለቆች
ለዚህ ፍቺ ሊሆኑ የሚችሉት 1/እነዚህ ቁጥሮች የሚያመለክቱት ሻለቆቹ ወይም የመቶ አለቆዎቹ የሚመሯቸው በሥራቸው የሚገኙ ሠራዊቶች ትክክለኛ ቁጥር ነው።“1000 ሰራዊት የሚመሩ ሻለቃዎችና 100 ሠራዊት የሚመሩ መቶ አለቃዎች”ወይም 2/ “ሺዎችና መቶዎች የሚሉት ቃላት የታላላቅና የአነስተኛ የጦር ክፍሎች ስያሜዎች ናቸው እንጂ የሠራዊቱን ትክክለኛ ቁጥር የሚያመለክቱ አይደሉም” “ሠፊ የጦር ክፍል ያላቸው ሻለቃዎችና አነስተኛ የጦር ክፍል ያላቸውመቶ አለቃዎች” ይህንንተመሳሳይ ሐረግ በዘኁልቁ 31፡ 14 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ባሪያዎችህ ቆጥረናል
የሠራዊት አዛዦቹ ራሣቸውን “ባሪያዎችህ” እያሉ የጠሩት ከፍተኛ ሥልጣን ካለው ሰው ጋር ንግግር በሚደረግበት ወቅት ጥቅም ላይ የሚውል ትህትና ያለበት አቀራረብ ስለሆነ ነው።

አንድ ሰው አልጎደለም
ይሄ በአዎንታዊ በሆነ አገላለፅ ሊገለፅ ይችላል።“ሁሉም ሰው እዚህ እንደሚገኝ እርግጠኞች ነን”(በተዘዋዋሪ መንገድ ሃሣብን መግለፅ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 31:50

አጠቃላይ መረጃ
የሠራዊቱ አዛዦች ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላሉ።

የእግር አልቦ፤አምባር፤ቀለበት፤ጉትቻ፤ድሪ
እነዚህ ሰዎች የሚያደርጓቸው ጌጣጌጦች ናቸው።

በእግዚአብሔር ፊት ያስተሰርይልን ዘንድ
“ሕይወታችንን ስላዳነን እግዚአብሔርን እናመሰግን ዘንድ”

ወርቆቹንና በልዩ ልዩ የተሰራውን ዕቃ ሁሉ
“የወርቅ ዕቃዎችን ሁሉ”ወይም “የወርቅ ጌጣጌጦችን ሁሉ”

Numbers 31:52

ሻለቆችም የመቶ አለቆችም ለእግዚአብሔር የማንሣት ቁርባን ያቀረቡት ወርቅ ሁሉ አሥራ ስድስት ሺህ ሰባት መቶ ሰቅል ይመዝናል
“የሻለቆችቹና የመቶ አለቆቹ ለእግዚአብሔር የሰጡት የወርቅ ሥጦታ ሁሉ የመዘነው…”

ሻለቆችና የመቶ አለቆች
ለዚህ ፍቺ ሊሆኑ የሚችሉት 1/እነዚህ ቁጥሮች የሚያመለክቱት ሻለቆቹ ወይም የመቶ አለቆዎቹ የሚመሯቸው በሥራቸው የሚገኙ ሠራዊቶች ትክክለኛ ቁጥር ነው።“1000 ሰራዊት የሚመሩ ሻለቃዎችና 100 ሠራዊት የሚመሩ መቶ አለቃዎች”ወይም 2/ “ሺዎችና መቶዎች የሚሉት ቃላት የታላላቅና የአነስተኛ የጦር ክፍሎች ስያሜዎች ናቸው እንጂ የሠራዊቱን ትክክለኛ ቁጥር የሚያመለክቱ አይደሉም” “ሠፊ የጦር ክፍል ያላቸው ሻለቃዎችና አነስተኛ የጦር ክፍል ያላቸው መቶ አለቃዎች” ይህንንተመሳሳይ ሐረግ በዘኁልቁ 31፡ 14 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

16,750
“አሥራ ስድስት ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰቅል
አንድ ሰቅል 11 ግራም ነው።(መፅሐፍ ቅዱሣዊ ገንዘብ የሚለውን ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ፊት ለእሥራኤላውያን መታሰቢያ ይሆን ዘንድ
ወርቆቹ መታሰቢያ የሚሆኑት እግዚአብሔር ድል የሰጣቸው መሆኑን ለማሳሰብ ነው።በሌላ በኩል ደግሞ በምድያማውያን ላይ ሕዝቡ የበቀል እርምጃ የወሰደ መሆኑን እግዚአብሔር ያስበው ዘንድ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 32

1 በዚህ ጊዜ የሮቤልና የጋድ ትውልዶች ብዙ የቀንድ ከብቶች ነበራቸው። የኢያዜርንና የገለዓድን ምድር ሲመለከቱ፣ ምድሪቱ ለከብቶቻቸው መልካም መሆኗን አዩ። 2 ስለዚህ የጋድና ሮቤል ትውልዶች ወደ ሙሴ፣ ወደ ካህኑ አልዓዛርና ወደማህበሩ መሪዎች መጥተው እንዲህ አሉ፣ 3 “ያህዌ በእስራኤል ህዝብ ፊት የመታው አጣሮት፣ ዲቦን ኢያዜር፣ ኒምራ፣ ሐሴናን፣ ኤልያሊ፣ ሴባማ፣ ናባውና ባያን 4 ምድሩ ለከብቶች መልካም ነው። እኛ፣ የአንተ አገልጋዮች ብዙ ከበቶች አሉን።” 5 ደግሞም እንዲህ አሉ፣ “በፊትህ ሞገስ አግኝተን ከሆነ፣ ይህች ምድር ለእኛ ለአገልጋዮችህ ርስት ሆና ትሰጠን። ዮርዳኖስን አቋርጠን እንድንሄድ አታድርግ።” 6 ሙሴ ለጋድና ሮቤል ትውልዶች እንዲህ ሲል መለሰላቸው፣ “እናንተ በዚህ ተቀምጣችሁ ወንድሞቻችሁ ወደ ጦርነት ሊሄዱ ይገባልን? 7 የእስራኤል ህዝብ ያህዌ ወደ ሰጣቸው ምድር እንዳይገቡ ለምን ልባቸውን ታደክማላችሁ? 8 አባቶቻችሁ ከቀዴስ በርኔ ምድሪቱን እንዲያዩ በላክኋቸው ጊዜ ያደረጉት ተመሳሳይ ነገር ነበር። 9 እነርሱ ወደ ኤሽኮል ሸለቆ ሄዱ። ምድሪቱን ካዩ በኋላ የእስራኤልን ልብ አደከሙ፤ ስለዚህም ያህዌ ወደ ሰጣቸው ምድር ለመግባት ተቃወሙ። 10 በዚያ ቀን የያህዌ ቁጣ ነደደ። በመሀላ እንዲህ አለ፣ 11 ‘ከግብጽ ምድር ከወጡ ሰዎች ሃያ አመትና ከዚያ በላይ ከሆናቸው፣ መሃል አንዳቸውም ለአብርሃም፣ ለይስሃቅ፣ እና ለያዕቆብ ልሰጣቸው በመሀላ ቃል የገባሁላቸውን ምድር አያዩም፣ ምክንያቱም እነርሱ በሙሉ ልባቸው አልተከተሉኝም፤ 12 ከቂኔዛዊው ከዩፎኒ ልጅ ከካሌብ፣ እና ከነዌ ልጅ ከኢያሱ በስተቀር። ካሌብና ኢያሱ ብቻ በሙሉ ልባቸው ተከትለውኛል።’ 13 ስለዚህም የያህዌ ቁጣ በእስራኤል ላይ ነደደ። በፊቱ ክፉ ያደረገው ትውልድ ሁሉ እስኪጠፋ ድረስ ለአርባ አመታት በምድረበዳ እንዲንከራተቱ አደረጋቸው። 14 እናንተ እንደ ሌሎች ኃጢአተኛ ሰዎች የያህዌን ቁጣ በእስራኤል ላይ ለመጨመር በአባቶቻችሁ እግር ተተካችሁ። 15 እርሱን ከመከተል ፊታችሁን ብታዞሩ፣ እርሱ እስራኤልን ዳግም በበረሃ ይተዋል እናንተም ይህን ሁሉ ህዝብ ታጠፋላችሁ።” 16 ስለዚህም ወደ ሙሴ መጥተው እንዲህ አሉ፣ “በዚህ ለከብቶቻችን አጥር እና ለቤተሰቦቻችን ከተማ እንድንገነባ ፍቀድልን። 17 ሆኖም፣ እኛ እራሳችን ወደ ስፍራቸው እስክናባርራቸው ድረስ ከእስራኤል ጦር ጋር ለመውጣት እንነሳለን እንታጠቃንም። ቤተሰቦችን ግን እስከ አሁን በዚህ ምድር ከሚኖሩ ሌሎች ሰዎች የተነሳ በተቀጠሩ ከተሞች ውስጥ ይኖራሉ። 18 የእስራኤል ህዝብ እያንዱ ሰው ርስቱን እስኪያገኝ ድረስ ወደ ቤቶቻችን አንመለስም። 19 እኛ ከእነርሱ ጋር ከዮርዳኖስ ማዶ ያለውን ምድር አንወርስም፣ ምክንያቱም የእኛ ርስት እዚህ በዮርዳኖስ ምስራቅ በኩል ያለው ነው።” 20 ስለዚህም ሙሴ እንዲህ ሲል መለሰላቸው፣ “የተናገራችሁትን ካደረጋችሁ፣ ወደ ጦርነት በያህዌ ፊት ለመውጣት ራሳችሁን ካስታጠቃችሁ፣ 21 ከዚያ በኋላ እያንዳንዳቸው የእናንተ የታጠቁ ወንዶች ጠላቶቹን ከፊቱ እስኪያባርራቸው ድረስ በያህዌ ፊት ዮርዳኖስን ማቋረጥ አለባቸው። 22 ደግሞም ምድሪቱ በእርሱ ፊት ጸጥ ብላ ትገዛለች። ከዚያ በኋላ መመለስ ትችላላችሁ። እናንተም በያህዌና በእስራኤል ፊት ጥፋተኛ አትሆኑም። ይህ ምድር በያህዌ ፊት ርስታችሁ ይሆናል። 23 እንዲህ ካላደረጋችሁ ግን፣ በያህዌ ፊት በደለኞች ትሆናላችሁ ኃጢአታችሁ እንደሚከተላችሁ እርግጠኞች ሁኑ። 24 ለቤተሰቦቻችሁ ከተሞችን ገንቡ ለበጎቻችሁም ጉረነዎች ስሩላቸው፤ ከዚያ ያላችሁትን አድርጉ።” 25 የጋድና ሮቤል ትውልዶች ሙሴን እንዲህ አሉት፣ “እኛ አገልጋዮችህ አንተ ጌታችን ያዘዝከንን እናደርጋለን። 26 ልጆቻችን፣ ሚስቶቻችን፣ መንጎችንና የቀን ከብቶቻችን በገለዓድ ከተሞች ይቆያሉ። 27 ሆኖም፣ እኛ፣ የአንተ አገልጋዮች ለጦርነት በያህዌ ፊት እንወጣን፤ ለጦርነት የታጠቀ እያንዳንዱ ሰው አንተ ጌታችን እንዳልከው ያደርጋል።” 28 ስለዚህም ሙሴ ለካህኑ አልዓዛር፣ ለነዌ ልጅ ለኢያሱና በእስራኤል ህዝብ መሃል የጎሳዎች አባቶች ለሆኑ መሪዎች እነርሱን በሚመለከት መመሪያዎቻችን ሰጠ። 29 ሙሴ እንዲህ አላቸው፣ “የጋድና የሮቤል ትውልዶች ከእናንተ ጋር ዮርዳስን ቢሻገሩና በያህዌ ፊት ለጦርነት የታጠቀ እያንዳንዱ ወንድ እና ምድሪቱ በፊታችሁ ቢገዙ፣ የገለዓድን ምድር ለእነርሱ ርስት አድርገህ ትሰጣቸዋለህ። 30 ነገር ግን ታጥቀው ከአንተ ጋር ዮርዳኖስን ባይሻገሩ፣ ርስታቸውን በከነአን ምድር ከአንተ ጋር ያገኛሉ።” 31 ስለዚህም የጋድና ሮቤል ትውልዶች እንዲህ ሲሉ መለሱ፣ “ያህዌ ለእኛ ለባሮችህ እንደተናገረው፣ የምናደርገው ነገር ይህ ነው። እንሻገራለን። 32 እኛ ታጥቀን በያህዌ ፊት ወደ ከነዓን ምድር እንሻገራለን፣ ነገር ግን የተወረሰው ርስታችን በዚህኛው የዮርዳስ ክፍል ከእኛ ጋር ይቀራል።” 33 ስለዚህ ሙሴ ለጋድና ለሮቤል ትውልዶች፣ እንዲሁም ለዮሴፍ ልጅ ለምናሴ ከፊል ነገድ፤ የአሞውያንን ንጉስ የሴዎንን ግዛት እና የባሳንን ንጉስ የዓግን ግዛቶች ሰጣቸው። ለእነርሱ ምድሪቱን ሰጣቸው፣ እንዲሁም ከተማዎቿን ከዳርቻዎቻቸው ጋር እና በዙሪያቸው ያሉ ከተሞችን አደላቸው። 34 የጋድ ትውልዶች ዲቦንን፣ አጣሮትን፣ አሮዔርን፣ 35 ዓጥሮት ሾፋንን፣ አያዜርን፣ ዮግብሃን፣ 36 ቤት ነምራንን እና ቤት ሃራንን የተቀጠሩ ከተሞችና ለበጎች ጉረኖዎች ያላቸው አድርገው እንደገና ገነቧቸው። 37 የሮቤል ትውልዶች ሐሴቦንንና፣ ኤልያሊንና ቂርያትይምን፣ 38 ናባውን፣ በአልሜዎንን (ስማቸው በኋላ ተቀይሯል) እና ሴባማንን እንደገና ገነቧቸው። እነርሱም ዳግም ለገነቧቸው ከተሞች ሌላ ስሞችን ሰጡ። 39 የምናሴ ልጅ የማኪር ትውልዶች ወደ ገለዓድ ሄደው በውስጧ ይኖሩ ከነበሩት ከአሞራውያን ከለአድን ወሰዱ። 40 ከዚያ ሙሴ ለምናሴ ልጅ ለማኪር ገለዓድን ሰጠው፣ የእርሱም ሰዎች መኖሪያችን በዚያ አደረጉ። 41 የምናሴ ልጅ ኢያዕር ሄዶ ከተማቸውን ይዞ የኢያዕር መንደሮች ብሎ ሰየማቸው። 42 ኖባህ ሄዶ ቄናትንና መንደሮቿን ይዞ፣ በራሱ ስም ኖባህ ብሎ ሰየማት።

Numbers 32:1

አሁን
ይሄ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው በዋናው የታሪክ ሂደት ላይ የተወሰነ እረፍት እንዳለ ለማሣየት ነው።እዚህ ላይ ሙሴ ስለ ሮቤልና ስለ ጋድ ነገዶች ስለጀርባ ታሪካቸው መረጃን ይሰጣል።(የኋላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አጣሮት፤ዲቦን፤ኢያዜር፤ነምራ፤ሐሴቦን፤ኤልያሊ፤ሴባማ፤ናባው፤ባያን
እነዚህ የከተማዎቹ ስሞች ናቸው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 32:4

አጠቃላይ መረጃ
ከሮቤልና ከጋድ የመጡ ሰዎች ለሙሴ፤ለአልዓዛርና ለሌሎቹ መሪዎች መናገራቸውን ይቀጥላሉ።

እግዚአብሔር በእሥራኤል ማህበር ፊት የመታው ምድር
በዚያ ምድር የነበሩትን ሰዎች ድል እንዲያደርጓቸው እግዚአብሔር ችሎታውን የሰጣቸው ቢሆንም ልክ እግዚአብሔር ራሱ በእሥራኤላውያን ፊት ወጥቶ ጥቃት እንዳደረሰ ዓይነት ተድርጎ ተገልጿል።“በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ድል እንደንነሳቸው እግዚአብሔር ችሎታውን ሰጠን” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ባሪያዎችህ
የሮቤልና የጋድ ሰዎች በዚህ መልክ ራሣቸውን የሚጠሩት ከፍ ያለ ሥልጣን ላለው ሰው አክበሮትን ለመሥጠት ነው።

በዓይኖችህ ዘንድ ሞገስን አግኝተን እንደሆነ
እዚህ ላይ“ሞገስ” የሚለው ቃል ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ተቀባይነትን ማግኘት ወይም መሪዎቹ በእነርሱ ደስ መሰኘታቸውን የሚያሣይ ነው።እዚህ ላይ “ዓይኖች”የሚለው ቃል እይታ ለሚለው ቃል ገላጭ ሲሆን እይታ ደግሞ የማመዛዘን ችሎታውን የሚያመለክት ምሣሌያዊ አነጋገር ነው።“በአንተ ዘንድ ሞገስን አግኝተን ከሆነ”ወይም “በእኛ ደስ የተሰኘህ ከሆነ”(ፈሊጣዊ አነጋገር፤ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃልንና ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ርስት አድርገህ ስጠን
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ይህንን ምድር ለእኛ ስጠን”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ዮርዳኖስም ማዶ አታሻግረን
የፈለጉት ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ተሻግረው መሬት መጠየቅ ሣይሆን ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምሥራቅ በኩል የሚገኘውን ሥፍራ ነበር የፈለጉት።“በዚያኛ በኩል ለእኛ መሬትን ለመሥጠት ብለህ የዮርዳኖስ ወንዝን እንድሻገር አታድርገን”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 32:6

ወንድሞቻችሁ ወደ ጦርነት ሲሄዱ እናንተ እዚህ ትቀመጣላችሁን?
ሙሴ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ሮቤልንና ጋድን ለመገሰፅ ብሎ ነው።“ወንድሞቸችሁ ጦርነት ላይ እያሉ እናንተ በዚህ ምድር መቀመጣችሁ ተገቢ አይደለም”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር የሰጣቸውን .....የሰውን ልብ ለምን ታደክማላችሁ?
ሙሴ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ከሮቤልና ከጋድ ሃሣብ ሕዝቡን ለመከላከል ነው።“እግዚአብሔር የሰጣቸውን ..... የሰውን ልብ አታድክሙ”ወይም “ድርጊታችሁ የሰዎችን ልብ ሊያደክሙ ይችላሉ....እግዚአብሔር የሰጣቸውን”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የእሥራኤልን ሕዝብ ልብ ከመሄድ ታደክሙታላችሁ
እዚህ ላይ“ልብ”የሚለው ቃል የሚወክለው ራሣቸው ሰዎቹን ሲሆን የሚያመለክተውም የስሜታቸው መሠረት የሆነውን ነገርነው።“የእሥራኤል ሕዝብ እንዳይሄድ ተስፋ ታስቆርጡታላችሁ”ወይም “የእሥራኤል ሕዝብ እንዳይሄድ ምክኒያት ትሆናላችሁ”(ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 32:8

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ለሮቤልና ለጋድ ሰዎች መናገሩን ይቀጥላል።

የኤሽኮል ሸለቆ
ይሄ የቦታ ሥም ነው።ይህንንበዘኁልቁ 13:23 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሪቱን አዩ
ይሄ የሚያመለክተው በምድሪቱ ውስጥ ያለውን ነገር መመልከታቸውን ነው።“በምድሪቱ ውስጥ የሚገኙትን ጠንካራ ሰዎችና ከተማዎቹን ተመለከቱ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የእሥራኤልን ልጆች ልብ አደከሙ
እዚህ ላይ“ልብ”የሚለው ቃል የሚወክለው ራሣቸው ሰዎቹን ሲሆን የሚያመለክተው የስሜታቸው መሠረት የሆነውን ነው።ይህንንበዘኁልቁ 32:7 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“የእሥራኤልን ሕዝብ ተስፋ አስቆረጡ”(ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 32:10

የእግዚአብሔር ቁጣ ነደደ
x

Numbers 32:13

የእግዚአብሔርም ቁጣ በእሥራኤል ላይ ነደደ
እግዚአብሔር መናደዱን ለመግለፅ ልክ እሣት መቀጣጠል ከመጀመር ጋር ተመሳስሎ ነው የተነገረው።ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር በእሥራኤል ላይ በጣም ተናደደ”(ምሣሌያዊ አነጋገርና ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

አርባ ዓመት
“40 ዓመት”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ትውልድ ሁሉ...ፊት እስኪጠፉ ድረስ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ትውልዱን ሁሉ አጠፋ...ፊት”ወይም “ትውልዱ ሁሉ...በእግዚአብሔር ፊት ጠፋ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

በፊቱ ክፉ ያደረጉትን
በአንድ ሰው ፊት ማለት ሰውዬው ሊያየው በሚችልበት ሁኔታ ውስጥ መሆን ማለት ነው።“በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ያደረገ”ወይም “የእግዚአብሔር ሕልውና ባለበት ክፉ ነገርን ያደረገ”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በአባቶቻችሁ ፋንታ ቆማችኋል
የሮቤልና የጋድ ሰዎች ልክ የአባቶቻቸውን ሥራ ማድረጋቸው አባቶቻቸው ባደረጉት ሥፍራ ላይ እንደቆሙ ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል።“እንደ አባቶቻችሁ ማድረግ ጀምራችኋል”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔርን መዓት በእሥራኤል ላይ ትጨምሩ ዘንድ
ሰዎች እግዚአብሔር የበለጠ እየተናደደ እንዲሄድ የሚያደርጉት ድርጊት ልክ ሰዎች በእሣቱ ላይ ነዳጅ እንደሚጨምሩ ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል።“እግዚአብሔር በእሥራኤል ላይ የበለጠ እንዲናደድ ምክኒያት መሆን”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህንን ሁሉ ሕዝብ
“ይሄ ሁሉ ሕዝብ”ወይም“ይሄ ሁሉ ትውልድ”

Numbers 32:16

እንዘጋጃለን፤እንታጠቃለን
“መሣሪያችንን ታጥቀን ዝግጁዎች እንሆናለን”ወይም “በጦርነት ለመሣተፍ ዝግጁ እንሆናለን”

በተመሸጉ ከተሞች
“ደህንነታቸው በተጠበቁ ከተማዎች ውስጥ”

Numbers 32:18

አጠቃላይ መረጃ
ሮቤልና ጋድ መናገራቸውን እንቀጠሉ ነው።

ርስቱን ወስዷል
ሰዎች እንደ ቋሚ ንብረት የሚቀበሉት ንብረት ልክ እንደሚወስዱት ንብረት ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል።“የሚደርሰውን የመሬት ድርሻ በንብረትነት ወስዷል”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 32:20

ራሣችሁን ብታስታጥቁ
“የጦር መሣሪያችሁን ብትወስዱ”

በእግዚአብሔር ፊት
የዚህ ትርጉም እግዚአብሔር በጦርነቱ ወቅት በፊታቸው በመሄድ ጠላቶቻቸውን ድል እንዲያደርጉ ጉልበትን በመሥጠት ምድራቸውን እንዲወርሱ ያደርጋል ማለት ነው።(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጠላቶቹን ከፊቱ እስኪያሳድድ ድረስ
እግዚአብሔር ጠላቶቹን ከፊቱ እስኪያሳድድ ድረስ።እዚህ ላይ የሚገኙት ተውላጠ ስሞች ሁሉ የሚያመለክቱት እግዚአብሔርን ነው።እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን ድል እንዲያደርጉ ያገዛቸውን ሁኔታ ልክ እግዚአበሔርየእነርሱን ጦርነት እየተዋጋ እንዳለ ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል።“እግዚአብሔር ሠራዊቶቻችን ድል እንዲደርጓቸውና ከእርሱ ፊት እስኪዲያሳድዷቸው ድረስ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሪቱም በፊቱ ድል እስክትሆን ድረስ
እዚህ ላይ “ምድሪቱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኑሯቸውን በዚያ ያደረጉትን ሰዎች ነው።ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እሥራኤላውያን በዚያ ምድር የሚኖሩትን ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት ድል አደረጓቸው”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃልና ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ልትመለሱ ትችሉ ይሆናል
ይሄ የሚያመለክተው ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ በኩል ወደሚገኘው ሥፍራ የሚመለሱ መሆናቸውን ነው።“ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ በኩል ወደሚገኘው ሥፍራ ልትመለሱ ትችሉ ይሆናል”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በእግዚአብሔርም ፊት በእሥራኤልም ዘንድ ንፁህ ትሆናላችሁ
ለዚህ ተስማሚ ፍቺ ሊሆኑ የሚችሉት 1/“የሚጠበቅባችሁን ግዴታ በእግዚአብሔርና በእራኤል ፊት ፈፅማችኋል”ወይም 2/“እግዚአብሔርም ሆነ የእሥራኤል ሕዝብ እናንተን የሚወቅሱበት ነገር የላቸውም”

Numbers 32:23

ኃጢአታእሁ እንዲያገኛችሁ እወቁ
ሙሴ በዚህ ሥፍራ ላይ ስለ ኃጢአት የሚናገረው ልክ አንድ ግለሰብ ጥፋተኛ የሆነን ሰው እንደሚኮንንዓይነት ነው።ይሄ ማለት ሰዎች በሰሩት ኃጢአት ልክ ከመቀጣት አይድኑም ማለት ነው።“እግዚአብሔር ስለ ኃጢአታችሁ እንደሚቀጣችሁ እርግጠኛ ሁኑ”(ግዑዝ ነገሮች ሕይወት እንዳላቸው ተደርገው ሲገለፁ የሚለውን ይመልከቱ)

ባሪያዎችህ
የጋድና የሮቤል ሰዎች ራሣቸውን “ባሪያዎችህ”እያሉ ነው የሚጠሩት።ይሄ ከፍ ያለ ሥልጣን ላለው ሰው አክበሮት ለመሥጠት የሚውል ቃል ነው።

Numbers 32:26

ይሻገራሉ
ዮርዳኖስን እንደሚሻገሩ ግልፅ ልታደርጉት ተችላላችሁ።“የዮርዳኖስን ወንዝ ይሻገራሉ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለጦርነት ዝግጁ የሆነ ሰው ሁሉ
“በጦርነት ውስጥ ለመሣተፍ የተዘጋጀ ሰው ሁሉ”

Numbers 32:28

የጦር መሣሪ የታጠቀ ሰው ሁሉ
“የጦር መሣሪያውን ዝግጁ ያደረገ ሰው ሁሉ”

ምድሪቱንም ድል ብትነሱ
እዚህ ላይ “ምድሪቱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ነው።ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በዚያ ምድር የሚኖሩትን ሰዎች እግዚአብሔርድል እንድትነሱ የሚያደርጋችሁ ከሆነ” ወይም “በምድሪቱ ውስጥ የሚኖሩትን ሰዎች ድል እንድታደርጓቸው እነርሱ የሚያግዟችሁ ከሆነ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

በከነዓን ምድር በእናንተ መካከል ርስታቸውን ይወርሳሉ
“የጋድና የሮቤል ትውልዶች በከነዓን ምድር ርታቸውን ይወርሳሉ”

Numbers 32:31

ትጥቃችንን እንደታጠቅን እንሻገራለን
ዮርዳኖስን እንደሚሻገሩ የበለጠ ግልፅ ልታደርጉት ትችላላችሁ።“ዮርዳኖስን የምንሻገረው ለጦርነት ዝግጁ ሆነን ነው”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የምንወስደው ርስታችን
ሕዝቡ እንደ ቋሚ ንብረትነት የሚወስደውን መሬት በውርስ እንደሚወስዱት ዓይነት ተደርጎ ነው የተገለፀው።“የራሣችን የምናደርገው የመሬት ድርሻችን”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእኛ ይሆናል
ይሄ ፈሊጣዊ አጋገር የሚያመለክተው የራስ ንብረት ማድረግን ነው።“የራሣችን ይሆናል”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 32:33

የሴዎን ግዛትና...የዐግ
እነዚህ ሁለት የተለያዩ ግዛቶችን የገዙ ነገሥታት ሥሞች ናቸው።“የሴዎን ግዛትና...የዐግ ግዛት”(ምልክቶች እንጂ ቃላት ጥቅም ላይ የማይውሉበት የሚለውንና ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 32:34

ዲቦን፤አጣሮት፤አሮኤል፤ዓጥሮትሓሸፋን፤ኢያዜር፤ዮግብሃን፤ቤትነምራና
እነዚህ የከተሞች ሰሞች ናቸው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 32:37

ሐሴቦን፤ኤልያሊ፤ቂርያታይም፤ናባው፤በኣልሜዎን..ሴባማ
እነዚህ የከተሞች ሰሞች ናቸው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

በኋላ ላይ ስማቸው ተለወጠ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በኋላ ላይ ሰዎች የእነዚህን ከተሞች ስሞች ለወጧቸው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ማኪር
ይሄ የሰው ሥም ነው።ይህንን ሐረግ በዘኁልቁ 26:29 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Numbers 32:40

ኢያዕር...ኖባህ
እነዚህ የሰዎች ሰሞች ናቸው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)አ

ኢያዕር...ቄናት
እነዚህ የከተሞች ሰሞች ናቸው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 33

1 የእስራኤል ህዝብ በሙሴና አሮን መሪነት በየታጣቂ በድኖቻቸው ሆነው ከግብጽ ምድር ከወጡ በኋላ ያደረጓቸው ጉዞዎች እነዚህ ነበሩ። **2** ሙሴ በያህዌ እንደታዘዘው፣ ከተነሰቡት አንስቶ እስሚሄዱበት ድረስ ያሉትን ስፍራዎች ጻፈ። ከስፍራ ስፍራ ያደረጓቸው እንቅስቃሴዎች እነዚህ ነበሩ። **3** በመጀመሪያው ወር፣ በወሩ በአስራ አምስተኛ ቀን ከራምሴ ተነስተው ተጓዙ። ከፋሲካው በኋላ በማለዳ፣ የእስራኤል ሕዝብ በግልጽ ግፃዊያን ሁሉ እያይዋቸው ወጡ። **4** ግብፃዊያን ያህዌ በመካከላቸው የገደላቸውን በኩሮቻቸውን እየቀበሩ ሳለና በአማልክቶቻቸው ላይ ጥፋት እያደረሰ ሳለ ይህ ሆነ። **5** የእስራኤል ሕዝብ ከራምሴ ወጥቶ በሱኮት ሰፈረ። **6** ከሱኮት ወጥተው በኤታሞ፣ በምድረ በዳው **7** ከኤታም ወጥተው ከበአልዛፎን በተቃራኒ ወደ ፊሀሔርት ተመልሰው በሚግዶል በተቃራኒ ሰፈሩ። **8** ከዚያም ከፈሀሔርት በተቃራኒ ተነስተው በባህሩ መሃል ወደ ምድረበዳው ሄዱ። ለሶስት ቀናት በኤታም ምድረ በዳ ተጉዞው በማራ ሰፈሩ። **9** ከማራ ተነስተው ኤሊም ደረሱ። በኤሊም አስራ ሁለት ምንጮችና ሰባ የቴምር ዛፎች ነበሩ። የሰፈሩት በዚያ ስፍራ ነው። **10** ከኤሊም ተነስተው ቀይ ባህር አጠገብ ሰፈሩ። **11** ከቀይ ባህር ተነስተው በሲን ምድረበዳ ሰፈሩ። **12** ከሲን ምድረበዳ ተነስተው በራፍቃ ሰፈሩ። **13** ከራፍቃ ተነስተው በኤሉስ ሰፈሩ። **14** ከኤሉስ ተነስተው የሚጠጣ ውሃ በሌለበት ሰራፊዲም ሰፈሩ። **15** ከራፊዲም ተነስተው በሲና ምድረበዳ ሰፈሩ። **16** ከሲና ምድረበዳ ተነስተው በቂብሮት ሃታቫ ሰፈሩ። **17** ከቂብሮት ሃታቫ ተነስተው በሐዴሮት ሰፈሩ። **18** ከሐዴሮት ተነስተው በሪትማ ሰፈሩ። **19** ከሪትማ ተነስተው በሬሞን ዘፋሬስ ሰፈሩ። **20** ከሬምን ዘፋሬስ ተነስተው በልብና ሰፈሩ። **21** ከልብና ተነስተው በሪሳ ሰፈሩ። **22** ከሪሳ ተነስተው በቀሄላታ ሰፈሩ። **23** ከቀሄላታ ተነስተው በሻፍር ተራራ ሰፈሩ። **24** ከሻፍር ተራራ ተነስተው በሐራዳ ሰፈሩ። **25** ከሐራዳ ተነስተው በመቅሄሎት ሰፈሩ። **26** ከመቅሄሎት ተነስተው በታሐት ሰፈሩ። **27** ከታሐት ተነስተው በታራ ሰፈሩ። **28** ከታራ ተነስተው በሚትቃ ሰፈሩ። **29** ከሚትቃ ተነስተው በሐሹምና ሰፈሩ። **30** ከሐሸምና ተነስተው በሞሴሮት ሰፈሩ። **31** ከሞሴሮት ተነስተው በብኔያዕቃን ሰፈሩ። **32** ከብኔያዕቃን ተነስተው በሖር ሃጊድጋድ ሰፈሩ። **33** ከሖር ሃጊድጋ ተነስተው በዮጥባታ ሰፈሩ። **34** ከዮጥባታ ተነስተው በዔብሮና ሰፈሩ። **35** ከዔብሮና ተነስተው በዔድዮን ጋብር ሰፈሩ። **36** ከዔድዮን ጋብር ተነስተው በቃዴስ በምትገኘው ጺን ምድረ በዳ ሰፈሩ። **37** ከቃዴስ ተነስተው በሖር ተራራ፣ በኤዶም ምድር ዳርቻ ሰፈሩ። **38** ካህኑ አሮን፤ በያህዌ ትዕዛዝ ወደ ሖር ተራራ ወጣ፣ የእስራኤል ህዝብ ከግብጽ ምድር በወጣበት በአርባኛው ዓመት፣ በአምስተኛው ወር፣ በወሩ በመጀመሪያው ቀን ካህኑ አሮን በዚያ ሞተ። **39** አሮን በሖር ተራራ ላይ ሲሞት ዕድሜው 123 ነበር። **40** በከነዓን ምድር በደቡባዊ በረሃ የሚኖረው ከነዓናዊው የዓራድ ንጉስ የእስራኤልን ህዝብ መምጣት ሰማ። **41** እነርሱ ከሖር ተራራ ተነስተው በሴልምና ሰፈሩ። **42** ከሴልምና ተነስተው በፋኖን ሰፈሩ። **43** ከፋኖን ተነስተው በአቦት ሰፈሩ። **44** ከአቦት ተነስተው በሞአብ ዳርቻ በኢያ አባሪም ሰፈሩ። **45** ከኢያ አባሪም ተነስተው በዲቦን ጋድ ሰፈሩ። **46** ከዲቦን ጋድ ተነስተው በዓልምን ዲብላታይም ሰፈሩ። 46ከዲቦን ጋድ ተነስተው በዓልምን ዲብላታይም ሰፈሩ። **47** ከዓልምን ዲብላታይም ተነስተው ከናባው ተራራ በተቃራኒ በዓብሪም ተራራ ሰፈሩ። **48** ከዓብሪም ተራራ ተነስተው በሞብ ሜዳዎች በዮርዳኖስ ኢያሪኮ ላይ ሰፈሩ። **49** በሞብ ሞአብ ዮርዳስ ላይ ከቤት የሺሞት እስከ አቤልስጢም ድረስ ሰፈሩ። **50** ያህዌ ሙሴን በሞአብ ሜዳዎች ዮርዳስ ውስጥ በኢያሪኮ ሳለ እንዲህ አለው፣ **51** “ለእስራኤላዊያን እንዲህ በላቸው፣ ‘ዮርዳኖስን አቋርጣችሁ ወደ ከነዓን ስትገቡ፣ **52** የምድሪቱን ነዋሪዎች በሙሉ ከፊታችሁ አስወጡ። የተቀረጹ ምስሎቻቸውን በሙሉ አጥፉ። የማምለኪያ ስፍራዎቻቸውንና የተቀረጹ ምስሎቻቸውን ሁሉ ደምስሱ። **53** የምድሪቱን ሀብት ውሰዱ በዚያም መኖር ጀምሩ፣ ምክንያቱም እኔ ምድሪቱን ለእናንተ ርስት አድርጌ ሰጥቻቸኋለሁ። **54** ምድሪቱን በእጣ እንደየ ጎሳው ብዛት ውረሱ። ብዙ ህዝብ ላለው ጎሳ ሰፊ መሬት ስጥ፣ አነስተኛ ቁጥር ላለው ጎሳ አነስ ያለ መሬት ስጥ። እያንዳንዱ ጎሳ እጣው በወደቀለት ስፍራ ያ መሬት ርስቱ ይናል። ምድሪቱን በአባቶችሁ ጎሳ መሰረት ትወርሳላችሁ። **55** የምድሪቱን ነዋሪዎች ከፊታችሁ ጨርሳችሁ ባታስወጡ ግን፣ እንዲቀሩ ያደረጋችኋቸው ሰዎች በዐይናችሁ ውስጥ እንደገባ ባዕድ አካል እና በጎናችሁ እንደገባ እሾህ ይሆኑባችኋል። በመትኖሩበት ምድር ሕይወታችሁን ከባድ ያደርጉባችኋል። **56** እኔ በእነዚህ ህዝቦች ላይ ላደርስባቸው ያቀድኩትን በእናንተም ላይ ደግሞ አደርገዋለሁ።’”

Numbers 33:1

ከታጠቁ ጭፍሮቻቸው በታች
“በየጦር ክፍሎቻቸው” “ይሄ የሚያሣየው እያንዳንዱ ነገድ የታጠቁና ከጠላት የሚከላከሉላቸው የራሣቸው ሰዎች ነበሯቸው ማለት ነው”“የታጠቀ ሠራዊት”የሚለውን ሐረግ በዘኁልቁ 1:3 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

በእግዚአብሔር ትዕዛዝ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ጉዟቸው፤እወጣጣቸው
“ከአንድ ሥፍራ ወደ ሌላ ሥፍራ”

Numbers 33:3

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ እሥራኤላውያን ከግብፅ ምድር ከወጡበት ጀምሮ የተጓዙባቸውን የቦታዎች የሥም ዝርዝር መፃፍ ይጀምራል።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

በመጀመሪያው ወር ከወሩም በአሥራ አምስተኛው ቀን ተጓዙ
“በመጀመሪያ”የሚለው ተከታታይ ቁጥር የሆነው አንድ ሲሆን “በአሥራ አምስተኛው”የሚለው ደግሞ ተከታታይ ቁጥር የሆነው አሥራ አምስት ነው። ይሄ ለዕብራውያን የመጀመሪያው ወራቸው ነው።በምዕራባውያን የቀን አቆጣጠር መሠረት አሥራ አምስተኛው ቀን የሚውለው በመጋቢት ወር መጀመሪያ ላይ ነው።(የዕብራውያን ቀን አቆጣጠርናተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

የእሥራኤል ልጆች ግብፃውያን ሁሉ እያዩ ከፍ ባለች እጅ ወጡ
“እሥራኤላውያን ከግብፃውያን ሳይደበቁ ፊት ለፊት እያይዋቸው ወጡ”

በኩሮቻቸው
ይሄ የሚያመለክተው በኩር የሆኑ ወንድ ልጆችን ነው።“በኩር ወንድ ልጆቻቸውን”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በአማልክቶቻቸውም ደግሞ ፈረደባቸው
እግዚአብሔር በግብፅ ከሚመለኩት ጣዖታት ይልቅ እጅግ ኃያል እንደሆነ የሚያረጋግጠውን ነገር ልክ እግዚአብሔር ጣዖቶቻቸውን እንደቀጣ ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል።“ከጣዖቶቻቸው ይልቅ ኃያል እንደሆነ አረጋገጠ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Numbers 33:5

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ እሥራኤላውያን ከግብፅ ምድር ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ የተጓዙባቸውን የቦታዎች የሥም ዝርዝር መፃፍ ይጀምራል።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

ከሆነ ሥፍራ ወጡ
“ከሆነ ቦታ ለቀቁ”

በምድረ በዳው ጫፍ
“በምድረው በዳ ድንበር”

Numbers 33:8

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ እሥራኤላውያን ከግብፅ ምድር ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ የተጓዙባቸውን የቦታዎች የሥም ዝርዝር መፃፍ ይጀምራል።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

በባህሩ ውስጥ አለፉ
ይሄ የሚያመለክተው እሥራኤላውያን ከግብፃውያን ሠራዊት ያመልጡ ዘንድ እግዚአብሔር ቀይ ባህርን የከፈለበትን ሁኔታ ነው።

አሥራ ሁለት የውኃ ምንጮች...ሰባ ዘንባቦች
“12 የውኃ ምንጮች...70 ዘንባቦች”(ቁጥሮች የሚለውን ተመልከቱ)

Numbers 33:11

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ እሥራኤላውያን ከግብፅ ምድር ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ የተጓዙባቸውን የቦታዎች የሥም ዝርዝር መፃፍ ይጀምራል።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

ሕዝቡ የሚጠጠው ውኃ አልነበረውም
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሰዎች ውኃ ለማግኘት የተቸገሩበት ሁኔታ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 33:15

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ እሥራኤላውያን ከግብፅ ምድር ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ የተጓዙባቸውን የቦታዎች የሥም ዝርዝር መፃፍ ይጀምራል።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 33:19

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ እሥራኤላውያን ከግብፅ ምድር ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ የተጓዙባቸውን የቦታዎች የሥም ዝርዝር መፃፍ ይጀምራል።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 33:23

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ እሥራኤላውያን ከግብፅ ምድር ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ የተጓዙባቸውን የቦታዎች የሥም ዝርዝር መፃፍ ይጀምራል።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 33:27

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ እሥራኤላውያን ከግብፅ ምድር ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ የተጓዙባቸውን የቦታዎች የሥም ዝርዝር መፃፍ ይጀምራል።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 33:31

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ እሥራኤላውያን ከግብፅ ምድር ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ የተጓዙባቸውን የቦታዎች የሥም ዝርዝር መፃፍ ይጀምራል።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 33:35

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ እሥራኤላውያን ከግብፅ ምድር ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ የተጓዙባቸውን የቦታዎች የሥም ዝርዝር መፃፍ ይጀምራል።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 33:38

ከአርባኛው ዓመት በኋላ
“ከአርባኛው”የሚለው ቃል አርባ ለሚለው ቁጥር ተከታታይነትን የሚያመለክት ነው።“ከ40 ዓመት በኋላ” (ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

በአምስተኛው ወር ከወሩም በመጀመሪያው ቀን
“አምስተኛው”የሚለው ቃል አምስት ለሚለው ቁጥር ተከታታይነትን የሚያመለክት ነው።“በዕብራውያን አቆጣጠር መሠረት ይሄ አምስተኛው ወር ነው”በምዕራባውያን የቀን አቆጣጠር መሠረት የመጀመሪያው ቀን የሚውለው ሐምሌ መሐል አካባቢ ነው።(የዕብራውያን ቀን አቆጣጠርንና ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

ዕድሜው **123** ዓመት
“መቶ ሃያ ሶስት ዓመት”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 33:40

ከነዓናዊው የዓራድ ንጉሥ
“የዓራድ ከነናዊ ንጉሥ”(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

አራድ
ይሄ የከነዓናውያን ከተማ ሥም ነበር።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

የእሥራኤል ልጆች እንደመጡ ሰማ
“የእሥራኤል ልጆች እየመጡ እንደሆነ ወሬ ሰማ”

Numbers 33:41

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ እሥራኤላውያን ከግብፅ ምድር ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ የተጓዙባቸውን የቦታዎች የሥም ዝርዝር መፃፍ ይጀምራል።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Numbers 33:44

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ እሥራኤላውያን ከግብፅ ምድር ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ የተጓዙባቸውን የቦታዎች የሥም ዝርዝር መፃፍ ይጀምራል።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 33:47

አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ እሥራኤላውያን ከግብፅ ምድር ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ የተጓዙባቸውን የቦታዎች የሥም ዝርዝር መፃፍ ይጀምራል።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

ሜዳ
ሠፊ የሆነና ለጥ ያለ መሬት

Numbers 33:50

ከፍ ያሉ ሥፈራዎቻቸውን ሁሉ ታፈርሳላችሁ
“ከፍ ያሉ ሥፈራዎቻቸውን ሁሉ ታፈርሳላችሁ”

Numbers 33:53

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ሕዝቡ ምን ማድረግ እንደሚኖርበት ለሙሴ እየተናገረ ነው።

ምድሪቱን መውረስ
ሕዝቡ እንደ ቋሚ ንብረትነት የሚወስደውን መሬት በውርስ እንደሚወስዱት ዓይነት ተደርጎ ነው የተገለፀው።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሪቱንም በየወገኖቻችሁ በዕጣ ትወርሳላቸሁ
“እያንዳንዱ ነገድ በሚወጣለት ዕጣ መሠረት መሬቱን ይረከባል”

Numbers 33:55

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ሕዝቡ ምን ማድረግ እንደሚኖርበት ለሙሴ እየተናገረ ነው።

ለዓይናችሁ እንደ እሾህ ለጎናችሁም እንደሚወጋ ነገር
በአንድ ሰው ወስጥ ትንሽ ነገር ዓይኑ ውስጥ ቢገባ ወይም ትንሽ እሾህ በሰው ቆዳ ውስጥ ቢገባ እንደሚያበሳጭ ሁሉ ከከነዓናውያን መካከል የተወሰኑ ሰዎች በምድሪቱ ላይ ቢቀሩ ለእሥራኤላውያን ትልቅ ችግርን ሊፈጥሩ ይችላሉ። (ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 34

1 ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ **2** “የእስራኤልን ሰዎች እንዲህ ብለህ እዘዛቸው፣ ‘የእናንተ ወደምትሆን የከነዓን ምድርና ወደ ድንበሮቿ ስትገቡ፣ **3** ደቡባዊ ድንበራችሁ ከሲና ምድረ በዳ እስከ ኤዶም ይደርሳል። የደቡባዊ ድንበር ምስራቃዊ ጫፍ በጨው ባህር ደቡባዊ ጫፍ ደረስ ይሆናል። **4** ከአቅራቢም ኮረብታ ድንበራችሁ ወደ ደቡብ ይዞርና በሲና ምድረበዳ በኩል ያልፋል። ከዚያ ተነስቶ፣ በቃዴስ በርኔ ደቡብ ያልፍና ወደ ሐጸር አዳር እና ርቆ ዓጽምን ይደርሳል። **5** ከዚያ ተነስቶ፣ ድንበሩ ከጽሞን ወደ ግብጽ ጅረት ዞሮ እስከ ባህሩ ይከተለዋል። **6** ምዕራባዊው ድንበር የታላቁ ባህር ዳርቻ ይሆናል። ይህ ምዕራባዊ ድንበራችሁ ይሆናል። **7** ሰሜናዊ ድንበራችሁ ከታላቁ ባህር እስከ ሆር ተራራ እስከ ምትይዙት ስፍራ ደረስ ይሰፋል፣ **8** ከዚያ ከሖር ተራራ እስከ ሌና ሐማት፣ ከዚያ እስከ ጽዳድ ይደርሳል። **9** ከዚያ ድንበሩ እስከ ዚፍሮን ይቀጥልና ሐጸር ዔርን ሲደርስ ይጨርሳል። ይህ ሰሜናዊ ድንበራችሁ ይሆናል። **10** ምስራቃዊ ድንበራችሁን ከሐጸር ዔናን በደቡብ እስከ ሴፋም ታደርጋላችሁ። **11** ምስራቃዊ ድንበራችሁ ታች እስከ ሴፋም ወርዶ በዓይን ምስራቅ በኩል ራብላ ይደርሳል። ድንበሩ እስከ ከኔሬት ባህር ምስራቅ ይዘልቃል። **12** ከዚያ ድንበሩ በደቡብ በዮርዳኖስ ወንዝ በኩል እስከ ጨው ባህር እና ታች የጨው ባህር ምስራቅ ዳርቻ ድረስ ይቀጥላል። ይህች ድንበሩን ተከትሎ ዙሪያውን በሙሉ የእናንተ ምድራችሁ ናት። **13** ሙሴ የእስራኤልን ሰዎች እንዲህ ሲል አዘዘ፣ “ያህዌ ለዘጠኙ ጎሳዎችና ለአንዱ ጎሳ እኩሌታ እንዲሰጣችሁ ያዘዘው፣ በዕጣ የምትካፈሏት ምድር ይህች ናት። **14** የሮቤል ጎሣ ትውልዶች እና የጋድ ጎሣ ትውልዶች እንዲሁም የምናሴ ነገድ እኩሌታ በየአባቶቻቸው ጎሣዎች የንብረት አከፋፈልን ስርዓት ተከትለው ርስታቸውን ተቀብለዋል። **15** ሁለቱ ጎሣዎችና የአንዱ ጎሣ እኩሌታ ከዮርዳኖስ ወዲያ በኢያሪኮ በስተ ምስራቅ በጸሀይ መውጫ የርስታቸውን ድርሻ ተቀብለዋል።” **16** ያህዌ ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፣ **17** “ምድሪቱን ርስታችሁ አድርገው የሚያካፍሏችሁ ሰዎች ስማቸው እነዚህ ናቸው፡ ካህኑ አልዓዛርና የነዌ ልጅ ኢያሱ ናቸው። **18** ለየጎሣቸው ምድሪቱን እንዲያካፍሉ ከየነገዱ አንድ መሪ ምረጡ። **19** የሰዎቹም ስሞች እነዚህ ናቸው፡ ከይሁዳ ነገድ የዩፎኒ ልጅ ካሌብ። **20** ከስምኦን ጎሣ ትውልዶች የዓሁድ ልጅ ሰላሚኤል። **21** ከቢኒያም ጎሣ፣ የኪስሎን ልጅ ኤልዳድ። **22** መሪ ከሆነው ከዳን ጎሣ ትውልዶች፣ የዩግሊ ልጅ ቡቂ። **23** ከዮሴፍ ትውልዶች፣ መሪ ከሆነው ከምናሴ ትውልዶች የሱፊድ ልጅ አኒኤል። **24** መሪ ከሆነው ከኤፍሬም ጎሣ ትውልዶች፣ የሺፍጣን ልጅ ቱሙኤል። **25** መሪ ከሆነው ከዛብሎን ጎሣ ትውልዶች የፈርናክ ልጅ ኤሊሳፈን። **26** መሪ ከሆነው ከይሳኮር ጎሣ ትውልዶች፣ የሖዛ ልጅ ፈልጢኤል። **27** መሪ ከሆነው ከኤሴር ጎሣ፣ የሴሌሚ ልጅ አሒሁድ። **28** መሪ ከሆነው ከንፍታሌም ጎሳ ትውልዶች፣ የዓሚሁድ ልጅ ፈዳሄል” ናቸው። **29** ያህዌ እነዚህን ሰዎች የከነዓንን ምድር እንዲያካፍሉና ለእያንዳንዱ የእስራኤል ጎሣዎች ድርሻቸውን እንዲሰጡ አዘዘ።

Numbers 34:1

የጺን ምድረ በዳ
ይህንን ሐረግ በዘኁልቁ 33፡12 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

Numbers 34:4

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ሙሴ ለእሥራኤላውያን የሚሰጠው መሬት ድንበሩ የት እንደሆነ ይነግረዋል።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 34:6

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ሙሴ ለእሥራኤላውያን የሚሰጠው መሬት ድንበሩ የት እንደሆነ ይነግረዋል።

Numbers 34:7

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ሙሴ ለእሥራኤላውያን የሚሰጠው መሬት ድንበሩ የት እንደሆነ ይነግረዋል።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

የሖር ተራራ
ይህንን ሐረግ በዘኁልቁ 20፡22 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

Numbers 34:10

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ሙሴ ለእሥራኤላውያን የሚሰጠው መሬት ድንበሩ የት እንደሆነ ይነግረዋል።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 34:13

ለዘጠኝ ነገድ ተኩል
ይሄ ማለት በከነዓን ምድር ከዮርዳኖስ በስተ ምዕራብ በኩል ወደፊት የሚኖሩት የእሥራኤል የቀሩት ነገዶች ናቸው።የሮቤል፤የጋድና ግማሹ የምናሴ ነገድ መሬታቸውን ከዮርዳኖሰ በስተ ምሥራቅ በኩል ተቀብለዋል።

በየአባቶቻቸው ቤት የርስት ምደባ መሠረት
“እግዚአብሔር ንብረቱን ለአባቶቻቸው ቤት በመደበው መሠረት”

ሁለቱ ነገድና የአንዱ ነገድ እኩሌታ
“የሮቤልና የጋድ ነገዶችና ግማሹ የምናሴ ነገድ”

Numbers 34:16

ለእናንተ ርስት እንዲሆን ምድሪቱን ክፈል
እዚህ ላይ “እናንተ”የሚለው ቃል የብዙ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተውም የእሥራኤልን ሕዝብ ነው።እነዚህ ሰዎች መሬቱን ለመከፋፈል ዕጣ ይጥላሉ። ከዚያ በኋላ በየነገዶቹ ያከፋፍሉታል።(እናንተ የሚለውን የተለያየ አገላለፆች ይመልከቱ)

Numbers 34:19

አጠቃላይ መረጃ
ለየነገዶቹ መሬቱን ለማከፋፈል እገዛ የሚያደርጉት ሰዎች የሥም ዝርዝር እነዚህ ናቸው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 34:21

አጠቃላይ መረጃ
ለየነገዶቹ መሬቱን ለማከፋፈል እገዛ የሚያደርጉት ሰዎች የሥም ዝርዝር እነዚህ ናቸው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Numbers 34:24

አጠቃላይ መረጃ
ለየነገዶቹ መሬቱን ለማከፋፈል እገዛ የሚያደርጉት ሰዎች የሥም ዝርዝር እነዚህ ናቸው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 34:27

አጠቃላይ መረጃ
ለየነገዶቹ መሬቱን ለማከፋፈል እገዛ የሚያደርጉት ሰዎች የሥም ዝርዝር እዚህ ላይ ይጠናቀቃል።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 35

1 ያህዌ ሙሴን በሞአብ ሜዳ ዮርዳኖስ አጠገብ በኢያሪኮ እንዲህ አለው፣ **2** ”የእስረኤል ሰዎችን ለሌዋውያን ርስታቸው ከሆነው ከድርሻቸው እንዲሰጧቸው እዘዝ። የሚኖሩባቸውን ከተሞችና በዙሪያቸውም የግጦሽ መሬት ይስጧቸው። **3** ሌዋውያን እነዚህን ከተሞች መኖሪያቸው ያድርጓቸው። የግጦሽ መሬቱ ለከብቶቻቸው ለመንጎቻቸው እና ለእንስሳቻቸው ይሁኑ። **4** ለሌዋውያኑ የምትሰጣቸው በከተሞቹ ዙሪያ የሚገኘው የግጦሽ መሬት ከከተማ ቅጥር በየአቅጣጫው ስፋቱ አንድ ሺህ ክንድ ይሆናል። **5** ከከተማዋ በምስራቅ አቅጣጫ ሁለት ሺህ ክንድ ለካ፣ በስተደቡብ በኩልም ሁለት ሺህ ክንድ ለካ፣ በምዕራብ በኩል ሁለት ሺህ ክንድ፣ እና በሰሜን በኩል ሁለት ሺህ ክንድ ለካ። ይህ በከተማቸው ዙሪያ የግጦሽ መሬት ይሆናል። ከተማይቱ በመሃል ትሆናለች። **6** ለሌዋውያን የምትሰጧቸው ስድስቱ ከተሞች የስደተኞች ከተሞች ሆነው ያገለግሉ። እነዚህን ከተሞች በነፍስ መግደል ለተከሰሱ መሸሻ ስፍራ እንዲሆኑ ስጣቸው። እንዲሁም ሌሎች አርባ ሁለት ከተሞችን ስጣቸው። **7** ለሌዋውያን የምትሰጣቸው ከተሞች በጠቅላላው አርባ ስምንት ይሆናሉ። ከከተሞቹ ጋር የግጦሽ መሬትም ትሰጣቸዋለህ። **8** ብዙ የሆኑ የእስራኤል ህዝብ ጎሳዎችና ብዙ መሬት ያላቸው ጎሣዎች ብዙ ከተሞች ይሰጣቸዋል። አነስተኛዎቹ ጎሣዎች ጥቂት ከተሞች ይሰጣቸዋል። እያንዳንዱ ነገድ እንደ ተቀበለው እንደ ድርሻው መጠን ለሌዋውያኑ መስጠት አለበት።” **9** ከዚያም ያህዌ ሙሴን እንዲህ አለው፣ **10** “ለእስራኤል ሰዎች እንዲህ በላቸው፣ ‘ዮርዳኖስን አቋርጣችሁ ወደ ከነዓን ስትገቡ፣ **11** ይሁነኝ ብሎ ሰው ያልገደለ ሰው ወደ እነዚያ ከተሞች መግባት እንዲችል የመሸሸጊያ ከተማ ሆነው የሚያገለግሉ ከተሞችን ምረጡ። **12** እነዚህ ከተሞች ከደመኞቻችሁ የምትሸሸጉባቸው ይሁኑ፣ ስለዚህም የተከሰሰው ሰው በቅድሚያ በማህበሩ ፊት ለፍርድ ሳይቀርብ አይገደልም። **13** የመሸሸጊያ ከተማ አድርጋችሁ ስድስት ከተሞችን ምረጡ። **14** ከዮርዳኖስ ወዲያ ሶስት ከተሞችን፣ በከነዓን ምድር ደግሞ ሶስት ከተሞችን ስጡ። እነዚህ የመሸሸጊያ ከተሞች ይሆናሉ። **15** እነዚህ ስድስት ከተሞች ለእስራኤል ሰዎች፣ ለመጻተኞች፣ እና ለማናቸውም በመሀላቸው ለሚኖር ሳያውቅ ሰውን ለገደለ መሸሸጊያ ሆነው ያገለግላሉ። **16** ነገር ግን የተከሰሰው ሰው ተበዳዩን በብረት መሳሪያ ቢመታውና ተጠቂው ቢሞት፣ ተከሰሹ ነፍሰ ገዳይ ነው። እርሱ በእርግጥ ይገደል። **17** የተከሰሰው ሰው በእጁ በያዘው ድንጋይ ተበዳዩን ቢመታና ተበዳዩ ቢሞት ተከሳሹ ነፍሰ ገዳይ ነው። በእርግጥ ይገደል። **18** የተከሰሰው ሰው ተበዳዩን ለገድል በሚችል የእንጨት መሳሪያ ቢመታውና ተበዳዩ ቢሞት ተከሳሹ በእርግጥ ነፍሰ ገዳይ ነው። ለገደል ይገባዋል። **19** ደም ተበቃዩ ራሱ ነፍሰ ገዳዩን ይገደለው። ሲያገኘው፣ ለገድለው ይችላል። **20** ተከሳሹ አንድን እየተደበቀ ወይም እየተሸሸገ ያለ ሰው በጥላቻ ቢገፈትረው ወይም አንዳች ነገር ቢወረውርበትና ከዚህም የተነሳ ተበዳዩ ቢሞት፣ **21** ወይም በጥላቻ መትቶ ቢጥለውና ከዚህም የተነሳ ተበዳዩ ቢሞት መትቶ የገደለው በእርግጥ ይገደል። ነብስ ገዳይ ነው። ደም ተበቃዩ ነብሰ ገዳዩን ሲያገኘው ይገደለው። **22** ነገር ግን ተከሳሹ ሰው ቀድሞ ባልታሰበበት ጥላቻ ተበዳዩን ቢመታው ወይም ሳያስበው አንዳች ነገር ወርውሮ ቢመታው፣ **23** ተበዳዩን ሳይመለከት ለገድለው የሚችል ድንጋይ ቢወረውርበት፣ ተከሳሹ የተበዳዩ ጠላት አይደለም፤ ተበዳዩን ለመጉዳት እየሞከረ አልነበረም። የሆነ ሆኖ ተበዳዩ ቢሞት፣ **24** በዚህ ሁኔታ፣ ማህበረሰቡ በተከሳሹና በደም ተበቃዩ መሀል በእነዚህ ህጎች መሠረት ይዳኝ **25** ማህበረሰቡ ተከሳሹን ከደም ተበቃዩ እጅ ያድነው። ማህበረሰቡ ተከሳሹን በመጀመሪያ ወዳሸሸበት መሸሸጊያ ከተማ ይመልሰው። ተከሳሹ፣ በቅዱሱ ዘይት የተቀባው በወቅቱ ያለው ሊቀካህን እስኪሞት ድረስ በዚያ ይኑር። **26** ነገር ግን የተከሰሰው ሰው በማንኛውም ጊዜ ከሸሸበት ከተማ ድንበር አልፎ ቢሄድ፣ **27** እና ደም ተበቃዩ ከመሸሸጊያ ከተማው ድንበር ውጭ ቢያገኘውና ቢገድለው፣ ደም ተበቃዩ በነብሰ ገዳይነት ጥፋተኛ አይሆንም። **28** ለዚህም ምክንያቱ ተከሳሹ ሰው እስከ ሊቀ ካህኑ ሞት ድረስ በመሸሸጊያ ከተማው መቆየት ስለነበረበት ነው። **29** እነዚህ ህጎች፤ በምትኖባቸው ቦታዎች ሁሉ፣ በትውልዳቸው ሁሉ ለእናንተ የጸኑ ናቸው። **30** ሰውን የገደለ ማንኛውም ሰው፣ በምስክሮች ቃል እየረጋገጠ መገደል አለበት። ነገር ግን የአንድ ምስክር ቃል ብቻውን ማንንም ሰው ለመግደል በቂ አይደለም። **31** ደግሞም፣ በነብስ ገዳይነት ጥፋተኛ ለሆነ ሰው ሕይወት የነፍስ ዋጋ አትቀበሉ። ያ ሰው በእርግጥ ይገደል። **32** ወደ መሸሸጊያ ከተማ ለሄደ የነፍስ ዋጋ አትቀበሉ። ሊቀ ካህኑ እስኪሞት ድረስ የነፍስ ዋጋ በመቀበል ወደ ራሱ ርስት ተመልሶ እንዲገባ አትፍቀዱለት። **33** በዚህ መንገድ የምትኖሩባትን ምድር አታርክሱ፣ ምክንቱም በነፍስ ግድያ የሚፈስ ደም ምድሪቱን ያረክሳል። ምድር በላይዋ ደም ሲፈስ፣ ደም ካፈሰሰው ሰው ደም በስተቀር ሌላ ምንም ማስተስረያ ማድረግ አይቻልም። **34** ስለዚህ የምትኖሩባትን ምድር አታርክሱ ምክንያቱም እኔ በውስጧ እኖራለሁ። እኔ፣ ያህዌ፣ በእስራኤል ሰዎች መሃል እኖራለሁ።”

Numbers 35:1

ሜዳ
ሠፊ ሆኖ ለጥ ያለ ሜዳ

ለሌዋውያን የሚደርሳቸውን የመሬት ድርሻ ስጧቸው
እግዚአብሔር የራሣቸው የሆነ መሬትለሌዋውያንያልሰጣቸው በመሆኑ በሌሎች ነገዶች ከተማዎች ውስጥ መቀመጥ ነበረባቸው።

የግጦሽ መሬት
እንስሳት ሣር የሚግጡባቸው የመሬት ክፍል

Numbers 35:3

አንድ ሺህ ክንድ
“1000 ክንድ”ዘመናዊ የርቀት መለኪያን መጠቀም ከፈለጋችሁ ከዚህ በሚከተለው መልኩ ለማድረግ ትችላላችሁ።“457 ሜትር”(ቁጥሮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ርቀት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 35:5

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ሰዎች ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል።

ሁለት ሺህ ክንድ
“2000 ክንድ”አንድ ክንድ 46 ሴንቲ ሜትር ነው።(ቁጥሮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ርቀት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 35:6

የሰው ነፍስ ያጠፋ ሰው
ይሄ የሚያመለክተው የሰው ነፍስ ያጠፉ ሰዎችን ሲሆን ነገር ግን ሰውዬውን የገደሉት ሆን ብለው ነው ወይስ ሳያስቡት ነው? የሚለውጥያቄ ግን ገና ውሳኔ ያላገኘ መሆኑን ነው።

አርባ ሁለት...አርባ ስምንት
“42...48” (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Numbers 35:8

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ሰዎች ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል።

Numbers 35:9

በስህተት
በድንገት ወይም ሳያደፍጡ ወይም ሆን ብለው ሳይጠብቁ

Numbers 35:12

ደም ተበቃይ
ጥፋተኛ የሆነውነ ሰው ለመበቀል የሚያደባ የቅርብ ዘመድን ነው።

በማህበሩ ፊት ለፊት እስኪቆም ድረስ እንዳይሞት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።"ጥፋተኛው ሰው ወደ ማህበሩ ፈርዶ ፍርዱን ለማግኘቱ በፊት አንድ ሰው እንዳይገድለው"(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 35:14

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ሰዎች ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል።

Numbers 35:16

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ሰዎች ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል።

ፈፅሞ ይገደል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።"በእርግጥም ልትገድሉት ይገባል"(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውንና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 35:19

ደም ተበቃዩ
እዚህ ላይ"ደም"የሚለው ቃል መግደል ለሚለው ሃሣብ ሌላ ገላጭ ቃል ነው።"የገደለውን ሰው የሚበቀል" ወይም "ለመበቀል የሚፈልግ የቅርብ ዘመድ"(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ደም ተበቃዩ ባገኘው ጊዜ ነፍሰ ገዳዩን ይግደለው
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።"የቅርብ ዘመድ የሆነ ሰው ጥፋተኛውን ሰው መግደል አለበት" ወይም "ጥፋተኛው ሰው መሞት አለበት"(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 35:22

ጥላቻ ሳይኖረው በድንገት
"ከጥላቻ የተነሣ ቀደም ሲል ጉዳዩን በተመለከተ ላይ ዕቅድ ሳይነድፍ"

ሳይሸምቅ
አንድ ሰው ሌላን ሰው ሆነ ብሎ ለመጉዳት የሚያደርገው ክትትል አንድ ሰው ለማጥቃት ደፈጣ የሚያደርግ አስመስሎ ነው የተገለፀው።"የሚጠቃውን ሰው ለመጉዳትት ሆነ ተብሎ ያልተደረገ" (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 35:24

ደም ተበቃዩ
እዚህ ላይ"ደም"የሚለው ቃል መግደል ለሚለው ሃሣብ ሌላ ገላጭ ቃል ነው።ይህንን ሐረግ በዘኁልቁ 35:19 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ማህበሩም ነፍሰ ገዳዩን ሰው ከደም ተበቃዩ እጅ ያድነዋል
ይሄ ማለት ማህበሩ ግድያው የተፈፀመው በአጋጣሚ ነው ብሎ የሚያስብ ከሆነ የተገደለው ሰው የቅርብ ዘመድ የሆነ ሰው እንዳይገድለው ያድኑታል።ነገር ግን ማህበሩ ግድያው የተፈፀመው ታስቦበት እንደሆነ ካመነ የሟች የቅርብ ዘመድ የሆነ ሰው ጥፋተኛውን ሰው መግደል ይኖርበታል።(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በቅዱስ ዘይትም የተቀባው
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።"በቅዱስ ዘይት የቀባኸው ሰው"(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 35:26

ደም ተበቃዩ
እዚህ ላይ"ደም"የሚለው ቃል መግደል ለሚለው ሃሣብ ሌላ ገላጭ ቃል ነው።ይህንን ሐረግ በዘኁልቁ 35:19 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 35:29

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ሰዎች ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል።

ለልጅ ልጃችሁ
"ከአንተ በኋላ ለሚመጡት ትውልዶቹ በሙሉ"

Numbers 35:31

እርሱ ፈፅሞ ይገድል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።"እርሱን ልትገድሉት ይገባቸኋል"(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውንና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በራሱ ንብረት ላይ እንዲቀመጥ አትፍቀዱለት
ይሄ የሚያመለክተው የመማፀኛ ከተማውን ለቅቆ ወደ ቤቱ ለመመለስ የፈለገን ሰው ነው።"የመማፀኛ ከተማውን ለቅቆ እንዲሄድ መደፍቀድ የለባችሁም።ወደ ቤቱ በመሄድ በራሱ ንብረት ላይ እንዲቀመጥ መፍቀድም የለባችሁም።"(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚህ ሁኔታ
"የነፍስ ዋጋን በመቀበል"

Numbers 35:33

የምትኖሩባትን ምድር አታርክሷት፤በደም አፍሳሹ ደም ካልሆነ በቀር ምድሪቱ ከፈሰሰባት ደም አትነፃም
በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ምድር አካሉ እንደተመረዘ ነገር ተገልጿል።ከሰው መግደል ጋር በተያያዘ የፈሰሰው ደም ምድሪቱ በእኔ ዘንድ ተቀባይነት እንዳይኖራት የሚያደርግ በመሆኑ በዚህ ዓይነትሁኔታ ምድራችሁ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በፊቴ ተቀባይነት እንዳይኖራት አታድርጉ።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በዚህ ሁኔታ
“የነፍስ ዋጋን በመቀበል”

በደም አፍሳሹ ደም ካልሆነ በቀር ምድሪቱ ከፈሰሰባት ደም አትነፃም
ይሄ የሚያመለክተው አንድ ሰው ሆነ ብሎ ሌላ ሰው የገደለ ሲሆን ነው።“አንድ ሰው በምድሪቱ ላይ ደም የሚያፈስስ ከሆነ ምድሪቱ የምትነፃው ያ ደም ያፈሰሰው ሰው ሲገደል ብቻ ነው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 36

1 ከዚያ ከዮሴፍ ትውልዶች ጎሣ የሆኑት፣ የአባቶቻቸው ቤተሰቦች መሪዎች፣ የምናሴ ልጅ በሆነው በሚኪር ልጅ ገለዓድ የተመሠረተው ጎሳ በሙሴና በእስራኤላዊያን አባቶች ቤተሰቦች አለቆች ፊት መጥተው ተናገሩ። **2** እንዲህም አሉ፣ “ጌታችን ሆይ፣ ያህዌ ለእስራኤል ህዝብ ርስታቸውን በዕጣ እንድታካፍላቸው አዞሃል። የወንድማችንን የሰለጰዓድን ድርሻ ለሴት ልጆቹ እንድትሰጥ ያህዌ አዝዞህ ነበር። **3** ነገር ግን ሴት ልጆቹ ከእስራኤል ሰዎች ከሌላ ጎሣ ወንዶችን ቢያገቡ፣ ድርሻቸው የሆነው መሬት ከአባቶቻችን ድርሻ ተነቅሎ ወደ ሌላ ጎሣ ይተላለፋል። መሬቱ የገቡበት የሌላ ጎሳ ድርሻ ይሆናል። በዚያ ሁኔታ፣ ከእኛ ርስትነት ይነቀላል። **4** ይህ ሲሆን፣ የእስራኤል ኢዮቤልዩ ሲመጣ፣ የእነርሱ ድርሻ የተጋቧቸው ጎሣዎች ርስት ይሆናል። በዚህ መንገድ የእነርሱ ድርሻ ከእኛ አባቶች ጎሣ ይወሰዳል። **5** ስለዚህም ሙሴ በያህዌ ቃል ለእስራኤል ሰዎች ትዕዛዝ ሰጠ። እንዲህም አለ፣ “የዮሴፍ ትውልዶች ጎሣ የተናገሩት ትክክል ነው። **6** ያህዌ ስለ ሰለጰዓድ፣ ሴት ልጆች ያዘዘው ይህ ነው። እንዲህም አለ፣ ‘የመረጡትን ያግቡ፣ ነገር ግን ማግባት ያለባቸው ከአባታቸው ጎሣ ብቻ ነው።’ **7** የእስራኤል ሰዎች ድርሻ ከአንድ ጎሣ ወደ ሌላው መሄድ የለበትም። እያንዳንዱ እስራኤላዊ የራሱን ጎሣ ድርሻ ይዞ መቀጠል አለበት። **8** ከጎሣዋ ርስት የወረሰች እያንዳንዷ የእስራኤል ሴት፣ ማግባት ያለባት ከአባቷ ጎሣ ውስጥ ብቻ ነው። ይህ የሚሆነው እያንዳንዱ እስራኤላዊ የአባቶቹን ርስት ይዞ እንዲኖር ነው። **9** ከአንዱ ጎሣ ወደ ሌላው ምንም ርስት መተላለፍ የለበትም። የእስራኤል ህዝብ እያንዳንዱ ጎሣ የራሱን ርስት ይዞ መቀጠል አለበት።” **10** ስለዚህ የሰለጰዓድ ሴት ልጆች ያህዌ ሙሴን እንዳዘዘው አደረጉ። **11** የሰለጰዓድ ሴት ልጆች ማህለህ፣ ቲርጻ፣ ጌግላ፣ ሚልካ፣ ኑዓ **12** ልጅ የምናሴትን ትውልዶች አገቡ። በዚህ መንገድ፣ ርስታቸው የአባታቸው ጎሣ ርስት ሆኖ ቀረ። **13** ያህዌ በሙሴ በኩል በሞአብ ሜዳዎች በዮርዳኖስ ኢያሪካ ላይ ለእስራኤል ሰዎች የሰጣቸው ትዕዛዛትና ድንጋጌዎች እነዚህ ናቸው።

Numbers 36:1

ማኪር
ይሄ የሰው ሥም ነው።የዚህን ሰው ሥም በዘኁልቁ 26፡29 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ታዝዘሃልና
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር አዝዞሃል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰለጰዓድ
ይሄ የሰው ሥም ነው።የዚህን ሰው ሥም በዘኁልቁ 26፡33 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 36:3

ከአባቶቻችን ነገድ ርስት ይጎድላል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በአባቶቻችን ርስት ውስጥ ድርሻ አይኖረውም”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ይጨመራል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ድርሻው የሚሆነው…”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ከአባቶቻችን ርስት ይነቀላል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የርስታችን አካል አይሆንም”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእሥራኤልም ልጆች ኢዩቤልዩ
ይሄ የሚያመለክተው በየሃምሣ ዓመቱ የሚደረገውን በዓል ነው።በዚህ የበዓል ወቅት አንድ ሰው የሸጠው መሬትም ሆነ ንግድ ወደ መጀመሪያ ባለቤቱ መመለስ ይኖርበታል።(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ድርሻቸው ይጨመራል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ድርሻቸው ….”

ርስታቸው ከአባቶቻችን ነገድ ርሰት ይጎድላል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የእኛን ነገድ የመሬት ድርሻ ይወስዱታል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 36:5

እንደ እግዚአብሔር ቃል
“እግዚአብሔር በተናገረው መሠረት”

የወደዱትን ያግቡ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ደስ ያላቸውን ሰው ያግቡ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን ከአባታቸው ነገድ ብቻ ያግቡ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የሚያገቡትን ሰው ግን ከአባታቸው ቤት ብቻ ነው ማግባት የሚኖርባቸው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 36:7

ድርሻ አይኖርም
“ድርሻ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው እንዳንዱ ነገድ በርስት መልክ የሚቀበለውን መሬት ነው።“ምንም ዓይነት የመሬት ድርሻ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 36:8

በአባቷ ቤት ርስት ያላት
“በነገዷ ውስጥ የመሬት ርስት ያላት”

ርስትንሊቀበል ይችላል
እያንዳንዱ ነገድ ንብረቱ የሚያደርገውን መሬት እንደሚቀበሉት ዓይነት ውርስ ተደርጎ ነው የሚነገረው። (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከአንድ ነገድ ወደ ሌላ ነገድ ምንም ርስት አይተላለፍ
ባለቤትነትን ከአንድ ነገድ ወደ ሌላ ማስተላለፍን በተመለከተ ልክ አንድ ንብረት ከአንድ ሰው እጅ ወደ ሌላ ሰው እጅ እንደተላለፈ ዓይነት ተደርጎ ነው የሚገለፀው።“ማንም ሰው ቢሆን የመሬት ድርሻ ባለቤትነትን ከአንድ ነገድ ወደ ሌላ ነገድ ማስተላለፍ አይኖርበትም”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Numbers 36:10

ማህለህ፤ቲርጻ፤ኤግላ፤ሚልካ፤ኑዓ
እነዚህን ስሞችበዘኁልቁ 26፡33 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

ርስታቸው
የሰለጰዓድ ሴቶች ልጆች በንብረትነት የወሰዱት መሬት ልክ እንደወረሱት ውርስ ተደርጎ ተገልጿል።“በውርስ መልክ የተቀበሉት መሬት”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 36:13

ሜዳዎች
ሰፊና ለጥ ያለ መሬት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Deuteronomy

Deuteronomy

Chapter 1

1 ሙሴ በዮርዳኖስ ማዶ በምድር በዳ በዮርዳኖስ ወንዝ ሸለቆ ሜዳ በዓረባ፥ በፋራን፥ በጦፌል፥ በላባን፥ በሐጼሮት፥ በዲዛሃብ መካከል ሳሉ፥ ለእስራኤል ሁሉ
የተናገራቸው እነዚህ ቃላት ናቸው። 2 በሴይር ተራራ መንገድ ከኮሬብ እስከ ቃዴስ በርኔ ድረስ የአሥራ አንድ ቀን ጉዞ ነው። 3 በአርባኛው ዓመት በአሥራ አንደኛው
ወር ከወሩም በመጀመሪያው ቀን ሙሴ እግዚአብሔር ስለ እነርሱ ያዘዘውውን ሁሉ ለእስራኤል ሕዝብ ነገራቸው። 4 ይህም እግዚአብሔር በሐሴቦን ይኖር
የነበረውን የአሞራውያንን ንጉሥ ሴዎንን፥ በአስታዎትና በኤድራይ ይኖር የነበረውንም የባሳንን ንጉሥ ዐግን ከመታ በኋላ ነበር። 5 በዮርዳኖስ ማዶ በሞዓብ ምድር
ሙሴ እንዲህ ብሎ እነዚህን መመሪያዎች ይናገር ጀመር፦ 6 እግዚአብሔር አምላካችን በኮሬብ እንዲህ ብሎ ተናገረን፦ በዚህ ተራራ የኖራችሁበት ይብቃችሁ። 7
ጉዞኣችሁን ወደ ኮረብታማው ወደ አሞራውያን አገር ወደ ድንበሮቹም፥ ሁሉ በዓረባም በደጋውና በቆላው፥ በደቡብና በባሕር ዳር ወዳሉ ወደ ከነዓናውያን ምድር፥
ወደ ሊባኖስ ወንዝ ሸለቆ እስከ ታላቁ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ ሄዱ። 8 እነሆ ምድሪቱን በፊታችሁ አድርጌአለሁ፤ እግዚአብሔር ለአባቶቻችሁ ለአብርሃም፥
ለይስሐቅና ለያዕቆብ፥ ከእነርሱም በኋላ ለዘራቸው ይሰጣቸው ዘንድ የማለላቸውን ምድር ሂዱና ውረሱ። 9 በዚያን ጊዜ እንዲህ ብዬ ተናግሬአችሁ ነበር፦ እኔ
በራሴ ብቻዬን ልሸከማችሁ አልችልም። 10 እግዚአብሔር አምላካችሁ አብዝቶአችኋል፥ እነሆም እናንተ ዛሬ እንደ ሰማይ ከዋክብት ብዙ ናችሁ። 11
የአባቶቻችሁ እግዚአብሔር አምላክ ሺህ ጊዜ ሺህ ያድርጋችሁ፤ ተስፋ እንደሰጣችሁም ይባርካችሁ። 12 ነገር ግን እኔ በራሴ ድካማችሁን፥ ሸክማችሁንና
ክርክራችሁን እሸከም ዘንድ ብቻዬን እንዴት እችላለሁ? 13 ከእናንተ መካከል ከየነገዶቻችሁ ጥበበኞች፥ አስተዋዮችና አዋቂዎች የሆኑትን ሰዎች ምረጡ፤ እኔም
እነርሱን የእናንተ አለቆች አደርጋቸዋለሁ ብዬኣችሁ ነበረ። 14 እናንተም እንዲህ ብላችሁ መለሳችሁ፦ የተናገርከንን ነገር ለማድረግ ለእኛ መልካም ነው። 15
ስለዚህም ጥበበኞችና አዋቂዎች የሆኑትን የነገዶቻችሁን ወሰድሁ፥ በእናንተም ላይ አለቆች እንዲሆኑ የሺህ አለቆች፥ የመቶ አለቆች፥ የአምሳ አለቆች፥ የአሥር
አለቆችና ሹማምንት በየገዶቻችሁ አደረግኋቸው። 16 በዚያን ጊዜም ፈራጆቻችሁን እንዲህ ብዬ አዘዝኳቸው፦ በወንድሞቻችሁ መካከል፤ በሰውና በወንድሙ
መካከልና በመጻተኛ ላይ በጽድቅ ፍረዱ። 17 በክርክርም ጊዜ ለማንም ፊት አድልዎ አታድርጉ፥ ታላቁን እንደምትሰሙ፥ ታናሹንም ስሙ። ፍርድ የእግዚአብሔር
ስለሆነ የሰው ፊት መፍራት አይገባችሁም። ከክርክርም አንድ ስንኳ ቢከብዳችሁ ወደ እኔ አምጡት እኔም እሰማዋለሁ። 18 በዚያን ጊዜም ልታደርጉት
የሚገባችሁን ነገር ሁሉ አዘዝኋችሁ። 19 ከኮሬብም ተነስተን፥እግዚአብሔር አምላካችን እንዳዘዘን እንዳያችሁትም በታላቁና እጅግ አስቸጋሪ በሆነ ምድረ በዳ
ሁሉ ተጉዘን በተራራማው በአሞራውን አገር ሄድን፥ ወደ ቃዴስ በርኔም መጣን። 20 እኔም እንዲህ አልኋችሁ፦ እግዚአብሔር አምላካችን ወደ ሚሰጠን ወደ
ተራራማው አሞራውያን አገር መጣችኋል። 21 እነሆ እግዚአብሔር አምላካችሁ ምድሪቱን በፊታችሁ አድርጎአል፤ የአባቶቻችሁ አምላክ እግዚአብሔር እንዳላችሁ
ውጡ፥ ውረሱአት፥ አትፍሩ አትደንግጡም። 22 ከእናንተም ሁላችሁ ወደ እኔ መጥታችሁ እንዲህ አላችሁ፦ ምድሪቱን እንዲሰልሉልንና እናጠቃቸው ዘንድ
የሚገባንን የመንገዱንና የምንገባባቸውን ከተሞች ሁኔታ ተመልሰው እንዲነግሩን ከፊታችን ሰዎችን እንድስደድ። 23 ነገሩም ደስ አሰኘኝ፤ ከእናንተም ከየነገዱ
ሁሉ አንድ አንድ ሰው፥ አሥራ ሁለት ሰዎችን መረጥሁ። 24 እነርሱም ወደ ተራራማው አገር ሄዱ፥ ወደ ኤሽኮልም ሸለቆ መጥተው ሰለሉአት። 25 እነርሱም
ከምድሪቱ ፍሬ በእጃቸው ወሰዱ፥ ወደ እኛም ይዘውት መጡ። እነርሱም ደግሞ፦ እግዚአብሔር አምላካችን የሚሰጠን ምድር መልካም ናት ብለውም አወሩልን።
26 ምድሪቷንም ማጥቃት እንቢ ብላችሁ፥ በአምላካችሁ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ላይ ዐመፃችሁ፥ ። 27 በድንኳናችሁም ውስጥ እንዲህ እያላችሁ
አጉረመረማችሁ፦ እግዚአብሔር ስለ ጠላን እንዲያጠፋን በአሞራውያን እጅ አሳልፎ ይሰጠን ዘንድ ከግብፅ ምድር አወጣን። 28 አሁን ወዴት መሄድ እንችላለን?
ሕዝቡ ብዙ ነው፥ ቁመቱም ከእኛ ይረዝማል ከተሞቹም ታላላቆች፥ የተመሸጉና እስከ ሰማይም የደረሱ ናችው፥ የዔናቅንም ልጆች ደግሞ በዚያ አየናቸው፤ ብለው
ወንድሞቻችን ልባችንን እንዲቀልጥ አደረጉ። 29 እኔም አልኋችሁ፦ አትደንግጡ፥ እነርሱንም አትፍሩአቸው። 30 በፊታችሁ የሚሄደው እግዚአብሔር አምላካችሁ
ስለ እናንተ ይዋጋል፥ በፊታችሁም በግብፅና በምድረ በዳ እንዳደረገላችሁ ሁሉ፤ 31 ወደዚህም ስፍራ እስክትመጡ ድረስ በሄድዳችሁበት መንገድ ሁሉ ሰው
ልጁን እንደሚሸከም እግዚአብሔር አምላካችሁ እንደ ተሸከማችሁ እናንተ አይታችኋል። 32 ዳሩ ግን እግዚአብሔር አምላካችሁን በዚህ ነገር አላመናችሁትም፤
33 በፊታችሁም ሆኖ በምትሄዱበት መንገድ ድንኳናችሁን እንድታቆሙ ቦታ እንድታገኙና በሌሊት በእሳት፥ በቀንም በደመና እንድትሄዱ መንገዱን ያሳታችሁ
እርሱ ነው። 34 እግዚአብሔርም የቃላችሁን ድምፅ ሰምቶ ተቆጣ፥ ምሎም፥ እንዲህ አለ፦ 35 በርግጥ ለአባቶቻችሁ እሰጣቸው ዘንድ የማልሁላቸውን
መልካሚቱን ምድር ከዮፎኒ ልጅ ከካሌብ በቀር ከእነዚህ ሰዎች ከዚህ ክፉ ትውልድ ማንም አያይም። 36 እርሱም እግዚአብህሔርን ፈጽሞ ተከትሎአልና
የረገጣትን ምድር ለእርሱና ለልጆቹ እሰጣለሁ ብሎ ማለ። 37 እግዚአብሔርም ደግሞ በእናንተ ምክንያት እኔን ተቆጣኝ እንዲህም አለ፦ አንተ ደግሞ ወደዚያ
አትገባም 38 በፊትህ የሚሄድ አገልጋይ የነዌ ልጅ ኢያሱ ወደዚያ ይገባል፥ እርሱም እስራኤላውያን ምድሪቱን እንዲወርሱ ይመራቸዋልና፤ አደፋፍረው። 39
ከዚህም በተጨማሪ፦ ለጉዳት ይዳረጋሉ፥ ዛሬም መልካሙንና ክፉውን መለየት የማይችሉ ናቸው ያላችኋችሁ ታናናሽ ሕፃናታችሁ ልጆቻችሁ እነርሱ ወደዚያ
ይገባሉ። ምድሪቱንም ለእነርሱ እሰጣለሁ ይወርሱታልም። 40 እናንተ ግን ተመልሳችሁ በኤርትራ ባሕር መንገድ ወደ ምድረ በዳ ሂዱ። 41 እናንተም፦
እግዚአብሔርን በድለናል፥ እግዚአብሔር አምላክችሁ እንዳዘዘን ሁሉ እንወጣለን፥ እንዋጋማለን ብላችሁ መለሳችሁልኝ። ከእናንተም ሰው ሁሉ የጦር መሣሪያውን
ያዘ፥ ወደ ተራራማውም አገር ለመውጣትና ለማጥቃት ተዘጋጀ። 42 እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ፦ እኔ በእናንተ መካከል ስለማልገኝ፥ በጠላቶቻችሁ ፊት
እንዳትሸነፉ አትውጡ፥ አትዋጉም በላቸው አለኝ። 43 እኔም ተናገርኋችሁ እናንተም አልሰማችሁም። በእግዚአብሔር ትእዛዝ ላይ ዐመፃችሁ፥ አልሰማችሁም
በትዕቢታችሁም ወደ ተራራማው አገር ለማጥቃት ወጣችሁ። 44 ነገር ግን በተራራማው አገር ይኖሩ የነበሩ አሞራውያን በእናንተ ላይ ወጥተው እንደ ንብ
አሳደዱአችሁ፥ እስከ ሔርማም ድረስ በሴይር መቱአችሁ። 45 ተመልሳችሁም በእግዚአብሔር ፊት አለቀሳችሁ፤ እግዚአብሔር ግን ድምፃችሁን አልሰማም፥ ወደ
እናንተም አላዳመጠም። 46 ሁሉም ቀናት በቆያችሁባችሁ ለብዙ ቀን በቃዴስ ተቀመጣችሁ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Deuteronomy 1:1

ከዮርዳኖስ ማዶ
ይህ የሚያመለክተው ከእስራኤል በስተምስራቅ የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻግሮ ያለውን ምድር ነው። ሙሴ ለእስራኤላውያን በሚናገርበት ጊዜ ከዮርዳኖስ በስተምስራቅ ነበር። አ.ት፡ ከዮርዳኖስ በስተምስራቅ

ሱፋ ... ፋራን ... ቶፌል ... ላባ ... ሐጼሮት ... ዘሀብ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ከኮሬብ እስከ ቃዴስ በርኔ የአሥራ አንድ ቀን መንገድ ነው
“ከኮሬብ ወደ ቃዴስ በርኔ ለመጓዝ አሥራ አንድ ቀን ይፈጃል”

የሴይር ተራራ
ይህ ከሙት ባህር በስተደቡብ ያለ ተራራማ አካባቢ ነው። አካባቢው “ኤዶም” በመባልም ይታወቃል። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

አሥራ አንድ
“11” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 1:3

ሙሴ በአርባኛው ዓመት፣ በአሥራ አንደኛው ወር፣ ከወሩም በመጀመሪያው ቀን ተናገረ
መቁጠሪያ ቁጥሮች ወደ ተራ ቁጥሮች ሊተረጎሙ ይችላሉ። አ.ት፡ “ሙሴ በተናገራቸው ጊዜ በምድረ በዳ የኖሩት ለ40 ዓመታት፣ ለ11 ወራትና ለ1 ቀን ነበር። (መቁጠሪያ ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

አርባኛ
40ኛ (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

በአሥራ አንደኛው ወር፣ ከወሩም በመጀመሪያው ቀን
ይህ በዕብራውያኑ የቀን አቆጣጠር አሥራ አንደኛው ወር ነው። የመጀመሪያው ቀን በምዕራባውያን አቆጣጠር ወደ ጥር ወር አጋማሽ ይቃረባል።(የዕብራውያን ወራት እና መቁጠሪያ ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

አሥራ አንደኛ
11ኛ (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ያህዌ
ይህ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ራሱን ለሕዝቡ የገለጠበት ስሙ ነው። ያህዌ እንዴት እንደሚተረጎም ለመረዳት የትርጉም ቃል ገጽን ተመልከት።

እግዚአብሔር ወግቷቸው ነበር
“እስራኤላውያን እንዲያሸንፉ እግዚአብሔር አስችሏቸው ነበር”

ሴዎን ... ዐግ
እነዚህ የነገሥታት ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ሐሴቦን ... አስታሮትን በኤድራይ
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 1:5

ከዮርዳኖስ በላይ
ይህ የሚያመለክተው ከእስራኤል በስተምስራቅ ከዮርዳኖስ ወንዝ ባሻገር ያለውን ምድር ነው። ሙሴ ይህንን በሚናገርበት ጊዜ ከዮርዳኖስ በስተምስራቅ ነበር። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 1:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። አ.ት፡ “ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምስራቅ”።

ለእኛ ተናገረን
“እኛ” የሚለው ቃል ሙሴንና ሌላውን የእስራኤል ሕዝብ ያመለክታል።

በዚህ ኮረብታማ አገር ብዙ ዓመት ኖራችኋል
ይህ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ከዚህ በኋላ በዚህ ተራራ አጠገብ መቆየት አይኖርባችሁም” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 1:7

ተመልሳችሁ ጉዞአችሁን ቀጥሉ
“ተመልሳችሁ” የሚለው ቃል አንድን ተግባር ለመጀመር ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “እንደገና ጉዞአችሁን ቀጥሉ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ኮረብታማ አገር -- ኤፍራጥስ
እግዚአብሔ ለእስራኤላውያን ለመስጠት ቃል በገባላቸው ምድር አካባቢዎቹን እያብራራላቸው ነው።

ኮረብታማ አገር
ይህ አሞራውያን ይኖሩ ከነበሩበት አቅራቢያ የሚገኝ ኮረብታማ አካባቢ ነው።

ቆላ
ዝቅና ለጥ ያለ የምድር አካባቢ

ተመልከት
“ለምናገረው ነገር ትኩረት ስጡ”

ምድሪቱን በፊታችሁ አስቀምጫለሁ
“አሁን ይህችን ምድር ሰጥቻችኋለሁ”

እግዚአብሔር የማለላችሁን ያንን
እግዚአብሔር ራሱን እንደ ሌላ አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “እኔ እግዚአብሔር ምያለሁ” (ተውላጠ ስም የሚለውን ተመልከት)

አባቶች
“አባቶች” የሚለው ቃል አያት፣ ቅድም አያቶችን ሁሉ የሚወክል ነው። አ.ት፡ “አያት፣ ቅድም አያቶች” (See: Synecdoche)

Deuteronomy 1:9

በዚያን ጊዜ ነገርኳችሁ
እዚህ ጋ “እኔ” የሚያመለክተው ሙሴን ነው። “በዚያን ጊዜ” የሚለው ሐረግ እስራኤላውያን በኮሬብ፣ ይኸውም የሲና ተራራ ራሱ ነው፣ በዚያ የነበሩበትን ጊዜ ነው። አ.ት፡ “በኮሬብ በነበርንበት ጊዜ ነገርኳችሁ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ለብቻዬ ልሸከማችሁ አልችልም
እዚህ ጋ “ልሸከማችሁ” ማለት “ልመራችሁ” ወይም “ላስተዳድራችሁ” ማለት ነው። አ.ት፡ “በራሴ ልመራችሁ ይከብደኛል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

እንደ ሰማይ ከዋክብት የበዛውን
ይህ ግነት ሲሆን ትርጉሙም እግዚአብሔር የእስራኤላውያንን ቁጥር እጅግ አብዝቶታል ማለት ነው። አ.ት፡ “እጅግ ብዙ ሕዝብ”(ግነት፣ ጥቅል አስተያየት እና Simile)

አንድ ሺህ ጊዜ
“አንድ ሺህ” የሚለው ሐረግ “በጣም ብዙ” የሚል ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “በጣም ብዙ ጊዜ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አንድ ሺህ
1000 (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 1:12

ይሁን እንጂ፣ ችግራችሁን፣ ሸክማችሁንና ክርክራችሁን ለብቻዬ እንዴት መሸከም እችላለሁ?
ሙሴ ችግሮቻቸውን በሙሉ ለብቻው መፍታት እንደማይችል አጽንዖት ለመስጠት ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ችግራችሁን፣ ሸክማችሁንና ክርክሮቻችሁን ለብቻዬ መሸከም አልችልም”። (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ችግራችሁን፣ ሸክማችሁን
ሙሴ የተሸከመውና ሊፈታቸው ያስፈልጉ የነበሩት የሕዝቡ ችግሮችና ቅሬታዎች ለእርሱ ልክ ቁስ አካል የመሸከም ያህል እንደከበዱት ይናገራል። አ.ት፡ “ችግሮቻችሁን፣ ቅሬታዎቻችሁን መፍታት” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ክርክራችሁን
“ሙግታችሁን” ወይም “አለመግባባቶቻችሁን”

ከየነገዱ መልካም ስም ያላቸውን ሰዎች
“ከእያንዳንዱ ነገድ እስራኤላውያን የሚያከብሯቸው ሰዎች”

Deuteronomy 1:15

መልካም ስም ያላቸውን ሰዎች
“ወገኖቻችሁ የሚያከብሯችሁን ሰዎች”። ይህ በዘዳግም 1፡13 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።

የሺዎች _ የመቶዎች _ የሃምሳዎች _ የአሥሮች
የ1000 ቡድን _ የ100 ቡድን _ የ50 ቡድን _ እና የ10 ቡድን (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ሻምበሎች _ መኮንኖች
እነዚህ በእስራኤል መንግሥት የተለያዩ መሪዎች የሚጠሩባቸው መጠሪያዎች ናቸው።

ነገድ በነገድ
“ከእያንዳንዳችሁ ነገድ”

በአንድ ሰውና በወንድሙ መካከል በጽድቅ ፍረዱ
“እስራኤላውያን እርስ በእርሳቸው በሚኖራቸው ክርክር ላይ ትክክለኛና ፍትሐዊ ውሳኔ ስጡ”

Deuteronomy 1:17

አድልዎ አታድርጉም
“አድልዎ አታድርጉ”

የታናሹንና የታላቁን እኩል ስሙ
“ታናሽ” እና “ታላቅ” የተባሉት እነዚህ ሁለት ጽንፎች ሕዝቡን ሁሉ ይወክላሉ። አ.ት፡ “ሕዝቡን ሁሉ በእኩል ትዳኙታላችሁ” (See: Merism)

የሰውን ፊት አትፈሩም
“ፊት” የሚለው ቃል የሰውን ሁለንተና የሚወክል ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። “አትፈሩም” ትዕዛዝ ነው። “ማንንም አትፍሩ” (See: Synecdoche)

በዚያን ጊዜ
ይህ ማለት በኮሬብ፣ በሲና ተራራ በነበሩበት ጊዜ ማለት ነው። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

Deuteronomy 1:19

ባያችሁት አስቸጋሪ ምድረ በዳ
“ያቋረጣችሁት ያ ሰፊና አደገኛ ምድረ በዳ

Deuteronomy 1:20

ተመልከቱ _ አምላካችሁ _ በፊታችሁ፤ ተነሡ፣ ውረሱ _ አባቶቻችሁ _ ለእናንተ፤ አትፍሩ፣ ተስፋም አትቁረጡ
ሙሴ ለአንድ ሰው የሚናገር ይመስል የሚናገረው ለእስራኤላውያን ነው፤ በመሆኑም እነዚህ ቅርጾች ብዙ ሳይሆኑ ነጠላ ቁጥር ናቸው። (ተውላጠ ስም የሚለውን ተመልከት)

ምድሪቱን በፊታችሁ አድርጓል
“አሁን ይህቺን ምድር ሊሰጣችሁ ነው”። ይህ በዘዳግም 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ተመልከት

Deuteronomy 1:22

አሥራ ሁለት ሰዎች
“12 ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ተመልሰው ሄዱ
መመለስ መመሪያውን ለመታዘዝ መጀመራቸውን የሚገልጽ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ያንን ስፍራ ትተው ሄዱ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የኤሽኮል ሸለቆ
ይህ ከኢየሩሳሌም በስተደቡብ የሚገኝ በኬብሮን አውራጃ የሚገኝ ሸለቆ ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ቃኙ
“መውጋት የሚችሉባቸውን አካባቢዎች ተመለከቱ”

Deuteronomy 1:25

ወሰዱ
“12ቱ ሰዎች ወሰዱ”

ከምድሪቱ ፍሬ ጥቂቱን በእጆቻቸው ወሰዱ
“ከምድሪቱ ፍሬ ጥቂቱን አነሡ”

ቃል አመጡልን፣ እንዲህም አሉን
ተናጋሪው “ቃል” አንድ ሰው ሊያመጣው የሚችለው ቁስ አካላዊ ነገር ይመስል ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

‘አምላካችን እግዚአብሔር የሚሰጠን ምድር ጥሩ ነው’ አሉ
ቀጥተኛው ትዕምርተ ጥቅስ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ተደርጎ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር አምላካችን የሚሰጠን ምድር ጥሩ እንደሆነ ተነግሯል”

Deuteronomy 1:26

እናንተ ግን ለመዋጋት እምቢ አላችሁ
እስራኤላውያን አሞራውያንን እንዲወጉና እንዲያጠፏቸው እግዚአብሔር አዘዛቸው፣ ነገር ግን እስራኤላውያን ፈሩ፣ ከእነርሱ ጋር ለመዋጋትም እምቢ አሉ”። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

በአሞራውያን እጅ
እዚህ ጋ “በ እጅ” ማለት ለአሞራውያን በእነርሱ ላይ የበላይ እንዲሆኑ መስጠት ማለት ነው። አ.ት፡ “ለአሞራውያን ኃይል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አሁን ወዴት መሄድ እንችላለን?
እዚህ ጋ ይህ ጥያቄ ምን ያህል እንደ ፈሩ አጽንዖት ይሰጣል። ይህ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ምንም መሄጃ የለንም”። (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ልባችን እንዲቀልጥ አደረጉ
ይህ ማለት ፈርተዋል ማለት ነው። አ.ት፡ “በጣም እንድንፈራ አደረጉን” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

እስከ ሰማይ ድረስ የታጠሩ ናቸው
ይህ ከተሞቹ ሰፊና ጠንካራ በመሆናቸው ምክንያት ሰዎቹ ምን ያህል እንደ ፈሩ አጽንዖት የሚሰጥ ግነት ነው። አ.ት፡ “ሰማይ የሚደርሱ የሚመስሉ ግንቦች አሏቸው” (ግነት እና ጥቅል አስተያየት የሚለውን ተመልከት)

የኤናቅን ልጆች
እነዚህ የኤናቅ ሕዝብ ተወላጆች ሲሆኑ በጣም ረጃጅምና ኃይለኞች ነበሩ። (See: Assumed Knowl- edge and Implicit Information and ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 1:29

አልኳችሁ
“ለአባቶቻችሁ ነገርኳቸው”

በዐይኖቻችሁ ፊት
እዚህ ጋ ሰዎቹ ስላዩት ነገር አጽንዖት ለመስጠት በ”ዐይኖቻቸው” ተወክለዋል። አ.ት፡ “እናንተ ራሳችሁ ያያችሁት” (See: Synecdoche)

ዐይታችኋል አምላካችሁ እግዚአብሔር ተሸከማችሁ ሄዳችሁ መጣችሁ
ሙሴ፣ እስራኤላውያን አንድ ሰው የሆኑ ይመስል “አንተ” እና “የአንተ” እያለ ይናገራል፤ እነዚህ አገባቦች ሁሉ ነጠላ ቁጥር ናቸው። (See: Forms of You)

አባት ልጁን እንደሚሸከም አምላካችሁ እግዚአብሔር እናንተን ተሸከማችሁ
እዚህ ጋ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚያደርግላቸው ክብካቤ ከአባት ጋር ተነጻጽሯል። አ.ት፡ “አባት ልጁን እንደሚንከባከብ አምላካችሁ እግዚአብሔር ተንከባክቧችኋል” (See: Simile)

ወደዚህ ስፍራ እስክተመጡ ድረስ
“እግዚአብሔር ሊሰጣችሁ ቃል ወደገባላችሁ ወደዚህ ምድር እስክትመጡ ድረስ”

Deuteronomy 1:32

በፊታችሁ የሄደ _ አምላካችሁ እግዚአብሔር
ባለፈው ዘመን በጉዞአቸው ሁሉ እግዚአብሔር በእስራኤል ፊት የሄደባቸውን መንገዶች በሙሉ ሙሴ ያስታውሳቸዋል።

ሥፈሩ
“ድንኳኖቻችሁን ትከሉ”

Deuteronomy 1:34

የቃላችሁን ድምፅ ሰማ
“ስትናገሩ የነበረውን ሰማ”

ማለና እንዲህ አለ
በእርሱ ላይ ያመጹት እግዚአብሔር ሊሰጣቸው ቃል ወደ ገባላቸው ምድር እንዳይገቡ ማለ።

ያያሉ
“ይገባሉ”

ካሌብ ብቻ
“ከካሌብ በቀር”

ዮፎኒ
ይህ የካሌብ አባት ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

እርሱ እግዚአብሔርን ፈጽሞ ተከትሏል
እግዚአብሔር ራሱን እንደ ሌላ አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “እርሱ ሙሉ በሙሉ ታዞኛል” (ተውላጠ ስም የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 1:37

እግዚአብሔር በእናንተ ምክንያት ተቆጣኝ
ይህ የሚያመለክተው ሙሴ በእስራኤል ሕዝብ ላይ በመቆጣቱ ምክንያት እግዚአብሔር እንዲያደርግ የነገረውን ያልታዘዘበትን ጊዜ ነው። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ነዌ
ይህ የኢያሱ አባት ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

በፊትህ የሚቆመው
ኢያሱ በሙሴ ፊት ለምን ይቆም እንደነበረ በግልጽ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እንደ አገልጋይህ በፊትህ የሚቆመው” ወይም “የሚረዳህ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

Deuteronomy 1:39

ክፉና ደጉን የማያውቁት
የትኛው ክፉ እና የትኛው ደግ እንደሆነ ገና የማያውቁ

ተመልሳችሁ ጉዞአችሁን ቀጥሉ
“ወደ ኋላችሁ ተመለሱና በመጣችሁበት መንገድ ተመልሳችሁ ሂዱ”

Deuteronomy 1:41

በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን ሠርተዋል
“እርሱን ባለመታዘዝ በእግዚአብሔር ላይ አምጸናል”

እንከተላለን
“እንታዘዛለን”

ኮረብታማውን አገር ለመውጋት
እዚህ ጋ “ኮረብታማው አገር” የተባለው ፈሊጣዊ አነጋገር የሚወክለው በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ነው። አ.ት፡ “በኮረብታማው አገር የሚኖሩትን ሰዎች ለመውጋት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከእናንተ ጋር አልሆንም፣ እናንተም በጠላቶቻችሁ ትሸነፋላችሁ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ከእናንተ ጋር ስለማልሆን ጠላቶቻችሁ ያሸንፏችኋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Deuteronomy 1:43

ኮረብታማውን አገር ወጉ
“ኮረብታማው አገር” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር የቆመው በዚያ ለሚኖሩ ሰዎች ነው። አ.ት፡ “በኮረብታማው አገር የሚኖሩትን ሰዎች ወጉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እንደ ንብ አባረሯችሁ
“ንብ” ትንሽ፣ በራሪ ነፍስ ሲሆን በመንጋ ሆኖ የሚበርና ስጋት የሚሆኑባቸውን ሰዎች የሚነድፍ ነው። ይህ ማለት በጣም ብዙ አሞራውያን የእስራኤል ወታደሮችን ከጦርነቱ እስኪሸሹ ድረስ ወግተዋቸዋል። (See: Simile and የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)

ሴይር
ይህ የአንድ አነስተኛ ምድር ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ሔርማ
ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

መቷችሁ
“ከወታደሮቻችሁ ብዙዎቹን ገደሉ”

Deuteronomy 1:45

ተመለሳችሁና አለቀሳችሁ
“ወደ ቃዴስ ተመለሳችሁና አለቀሳችሁ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 ከዚያም እግዚአብሔርም እንደተናገረኝ ተመልሰን በኤርትራ ባሕር መንገድ ጉዞአችንን በምድረ በዳ ውስጥ ተመለስን፤ 2 በሴይርም ተራራ ዙሪያ ለብዙ ቀናት
ተጓዝን። 3 እግዚአብሔርም እንዲህ ብሎ ተናገረኝ፦ ይህን ተራራ የዞራችሁበት ይበቃችኋል፤ ተመልሳችሁ ወደ ሰሜን ሄዱ። 4 ሕዝቡንም እንዲህ ብለህ
እዘዛቸው፦ በሴይር በሚኖሩ በወንድሞቻችሁ በዔሳው ልጆች ድንበር ታልፋላችሁ፤ እነርሱም ይፈሩአችኋል። 5 ስለዚህ የሴይርን ተራራ ለዔሳው ርስት አድርጌ
ስለ ሰጠሁ እኔ ከምድራቸው የጫማ መርገጫ ያህል እንኳ አልሰጣችሁም፥ ከእነርሱም ጋር እንዳትዋጉ እጅግ ተጠንቀቁ።። 6 የምትበሉትንም ምግብ ከእነርሱም
በገንዘብ ትገዛላችሁ፤ የምትጠጡትንም ውኃ ደግሞ በገንዘብ ትገዛላችሁ። 7 አምላካችሁ እግዚአብሔር ፤ በዚህ በታላቅ ምድረ በዳ መጓዛችሁን ስላወቀ
የእጃችሁን ሥራ ሁሉ ባርኮልሃልና። በእነዚህ አርባ ዓመት ውስጥ አምላካችሁ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ነበረ፥ አንዳችም አልጎደለባችሁም። 8 በሴይርም
ከሚኖሩት ከወንድሞቻችሁ ከዔሳው ልጆች በዓረባ መንገድ ከኤላትና ከዔጽዮን ጋብር አለፍን። ተመልሰንም በሞዓብ ምድረ በዳ መንገድ አለፍን። 9
እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ፦ ሞዓብን አታስጨንቁአቸው፤ አትውጋቸውም። ምክንያቱም የእነርሱን ምድር ርስት እንዲሆንላችሁ አልሰጣችሁም፤ ዔርን ለሎጥ
ልጆች ርስት አድርጌ ሰጠኋችሁ። 10 አስቀድሞ ታላቅና ብዙ ሕዝብ ሆነው እንደ ዔናቅምልጆች በቁመት የረዘሙ ኤሚማውያን በዚያ ይኖሩ ነበር፤ 11 እነርሱም
ደግሞ እንደ ዔናቅ ልጆች ራፋይም ይባሉ ነበር፤ ሞዓባውያን ግን ኤሚም ይሉአቸዋል። 12 ሖራውያንም ደግሞ አስቀድሞ በሴይር ላይ ይኖሩ ነበር፥ የዔሳው
ልጆች ግን አሳደዱአቸው። እግዚአብሔርም በሰጠው በርስቱ ምድር እስራኤል እንዳደረገ፥ ከፊታቸው አጠፉአቸው፥ በስፍራቸውም መኖር ጀመሩ። 13
እግዚአብሔርም፦ ተነሡ የዘሬድንም ወንዝ ተሻገሩ አለ። የዘሬድንም ወንዝ ተሻገርን። 14 ከቃዴስ በርኔ ከመጠንበት ዘሬድን ወንዝን እስከ ተሻገርንበት ቀኖች
ድረስ ሠላሳ ስምንት ዓመታት ነበሩ። እግዚአብሔር እንደ ማለላቸው ለመዋጋት ብቁ የሆኑ ሰዎች ትውልድ ሁሉ ከሕዝብ መካከል የጌድይት በዚያን ጊዜ ነበር።
15 ከዚህ በተጨማሪ፥ ከመሄዳቸው በፊት ከሕዝቡ መካከል ለማጥፋት የእግዚአብሔር እጅ በእነርሱ ላይ ከብዶ ነበረ። 16 ለመዋጋት ብቁ የሆኑት ሁሉ
ከሕዝቡ መካከል በሞቱና በጠፉ ጊዜ 17 እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ፦ 18 አንተ ዛሬ የሞዓብን ዳርቻ ዔርን ታልፋለህ። 19 ለሎጥም ልጆች ርስት አድርጌ ስለ
ሰጠሁ በአሞን ልጆች አቅረቢያ ስትደርስ አታስጨንቁአቸው አትውጋቸውም፤ ምክንያቱም ከአሞን ልጆች ምድር ርስት አልሰጥህምና ። 20 ያም ደግሞ የራፋይም
ምድር ተብሎ ተቆጠረ። ራፋይምም አስቀድሞ በዚያ ይኖሩ ነበር፤ 21 አሞናውያን ግን ዛምዙማውያን ብለው የሚጠሩአቸው እንደ ዔናቅም ልጆች ቁመታቸው
ረጅም ነበር። 22 እግዚአብሔር ከአሞራውያን ፊት አጠፋቸው፤ እነርሱንም አሳድደው በስፍራቸው ይኖሩ ነበር። ሖራውያንን ከፊታቸው አጥፍተው በሴይር
ለሚኖሩት ለዔሳው ልጆች እንዳደረገ እንዲሁ ለእነርሱ አደረገ፤እነርሱም አሳድደው በስፍራቸው እስከ ዛሬ ድረስ ተቀመጡ። 23 እስከ ጋዛ ድረስ ባሉ መንደሮች
ይኖሩ የነበሩትን ኤዋውያንን ከከፍቶር የወጡ ከፍቶራውያን አጠፉአቸው፥ በስፍራቸውም ኖሩ። 24 ደግሞም አለ፦ ተነሥታችሁ ሂዱ፥ የአርኖንንም ሸለቆ ተሻገሩ፤
እነሆ አሞራዊውን የሐሴቦንን ንጉሥ ሴዎንንና ምድሪቱን በእጅህ አሳልፌ ሰጥቻለሁ። እርስዋን ለመውረስ ጀምር፥ ከእርሱም ጋር ተዋጋ። 25 ከሰማይ በታች ባሉ
አሕዛብ ሁሉ ላይ ማስደንገጥህንና ማስፈራትህን እሰድድ ዘንድ ዛሬ እጀምራለሁ፤ ወሬህን በሰሙ ጊዜ በፊትህ ይንቀጠቀጣሉ፥ ድንጋጤም ይይዛቸዋል። 26
ከቅዴሞትም ምድረ በዳ የሰላምን ቃል ይነግሩት ዘንድ ወደ ሐሴቦን ንጉሥ ወደ ሴዎን እንዲህ ብዬ መልእክተኞችን ላክሁ፦ 27 ወደ ቀኝና ግራ ሳልል በአገርህ
ላይ በአውራ ጎዳና ልለፍ። 28 የምበላውን ምግብ በገንዘብ ሸጥልኝ፥ የምጠጣውንም ውኃ በገንዘብ እንድገዛ ስጠኝ፤ 29 በሴይር የሚኖሩ የዔሳው ልጆች፥
በዔርም የሚኖሩ ሞዓባውያን እንዳደረጉልኝ አምላካችን እግዚአብሔር ወደሚሰጠን ምድር ዮርዳኖስን እስክሻገር ድረስ ብቻ በእግሬ ልለፍ። 30 እግዚአብሔር
አምላካችሁ እንደ ዛሬው ሁሉ በእጃችሁ አሳልፎ ይሰጣችሁ ዘንድ ልቡን ስላደነደነና ስላጸና የሐሴቦን ንጉሥ ሴዎን ግን ያሳልፈን ዘንድ አልፈቀደም ። 31
እግዚአብሔርም፦ እነሆ ሴዎንንና ምድሩን በእጅህ አሳልፌ መስጠት ጀመርሁ ምድሩን ትገዛት ዘንድ መውረስ ጀምር አለኝ። 32 ሴዎንም ሕዝቡም ሁሉ
ሊጋጠሙን ወደ ያሀጽ ወጡ። 33 እግዚአብሔር አምላካችንም አሳልፎ ስለሰጠን አሸነፈነው፥እርሱንና ልጆቹን፥ ሕዝቡንም ሁሉ እስኪሞቱ ድረስ
አሸነፍን፤መታንም። 34 በዚያን ጊዜም ከተሞቹን ሁሉ ወሰድን የተቀመጡባቸውንም ሰዎች ሁሉ ሴቶችንና ሕፃናትን አንዳችም ሳናስቀር አጠፋን። 35
ከብቶቻቸውንና በከተሞቻቸው ያሉትን ብቻ ብዝበዛ ለራሳችን ወሰድን። 36 በአርኖን ቆላ ጫፍ ካለው ከአሮዔር ከሸለቆውም ውስጥ ካለው ከተማ ጀምረን እስከ
ገለዓድ ድረስ ማናቸውም ከተማ ከእኛ በላይ አልሆነም። እግዚአብሔር አምላካችን በፊታችን ባሉት ጠላቶቻችን ላይ ድልን ሰጠን። 37 ዳሩ ግን አምላካችን
እግዚአብሔር ወደ ከለከለን ወደ አሞን ልጆች ምድር በያቦቅም ወንዝ አጠገብ ወዳለው ስፍራ ሁሉ በተራራማው አገር ወዳሉት ከተሞች አልደረስንም።

Deuteronomy 2:1

ከዚያም ተመለስንና ጉዞአችንን ቀጠልን
“ከዚያም ተመለስንና ሄድን”

ለብዙ ቀናት በሴይር ተራራ አጠገብ ሄድን
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እስራኤላውያን ሴይር ተብሎ በሚጠራው ተራራ አቅራቢያ ለረጅም ጊዜ ተጉዘዋል ወይም 2) እስራኤላውያን ሴይር ተብሎ በሚጠራው ተራራ አካባቢ ለረጅም ጊዜ ተቅበዝብዘዋል።

የሴይር ተራራ
ይህ ከሙት ባህር በስተደቡብ የሚገኝ ተራራማ አካባቢ ነው። አካባቢው “ኤዶም” በመባልም ይጠራል። ይህንን በዘዳግም 1:2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ብዙ ቀናት
ይህንን አንዳንድ ቋንቋዎች “ብዙ ሌሊቶች” ብለው ይተረጉሙታል።

Deuteronomy 2:4

ወንድሞቻችሁ የኤሳው ተወላጆች
“ዘመዶቻችሁ የኤሳው ተወላጆች”

የሴይርን ተራራ ርስት አድርጌ ለኤሳው ሰጥቸዋለሁ
እግዚአብሔር ለኤሳው ተወላጆች ይህንን ክልል እንደ ሰጣቸው እስራኤላውያንን ያስታውሳቸዋል።

Deuteronomy 2:6

ከእነርሱ ምግብ ትገዛላችሁ
እግዚአብሔር የሚሰጣቸው ትዕዛዝ ሳይሆን ፈቃድ ወይም መመሪያ ነው፣ እንዳይሰርቁም ይነግራቸዋል። “ከእነርሱ ምግብ እንድትገዙ እፈቅድላችኋለሁ” ወይም “ምግብ ከፈለጋችሁ ከእነርሱ መግዛት ይኖርባችኋል”

ከእነርሱ
“ከኤሳው ተወላጆች”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በገንዘብ
ይህ ቃል የማያስፈልግ ወይም ትርጉሙን ግልጽ የማያደርግ ከሆነ መተው ይኖርብህ ይሆናል።

አምላክህ ባርኮሃል _ እጅህ _ አካሄድህ _ አምላክህ _ ከአንተ ጋር እና አላጣህም
ሙሴ እስራኤላውያንን አንድ ሰው እንደሆኑ ዓይነት አድርጎ ይናገራል፣ በመሆኑም “አንተ” እና “የአንተ” ተብለው የተነገሩት ሁሉ ነጠላ ቁጥር ናቸው። (See: Forms of You)

በእጅህ ሥራ ሁሉ
የ “እጅህ ሥራ” የሚያመለክተው ያደረጉትን ሥራ ሁሉ ነው። አ.ት፡ “ሥራህን ሁሉ” (See: Synec- doche)

በመንገዳችሁ ጠብቋችኋል
እዚህ ጋ ሕዝቡ ሲጓዙ የደረሰባቸው እንደ “መንገድ” ተነግሯል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አርባ ዓመታት
“40 ዓመታት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ምንም አላጣችሁም
ይህ “የምትፈልጉት ሁሉ ነበራችሁ” የተጋነነ አባባል ነው። (የተጋነነ አባባል የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 2:8

በወንድሞቻችን
“በዘመዶቻችን”

ኤላት _ ጽዮን ጋብር
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ተመለስን
ይህ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “መጓዛችንን ቀጠልን” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 2:9

ሞዓብን አታስቸግሩት
“ሞዓብ” የሚለው ቃል የሚወክለው የሞዓብን ሕዝብ ነው። አ.ት፡ “የሞዓብን ሕዝብ አታስቸግሯቸው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ዔር
ይህ በሞዓብ የሚገኝ የአንድ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የሎጥ ተወላጆች
የእስራኤል ሕዝብ ከሞዓብ ተወላጆች ጋር ዝምድና ነበራቸው። ሞዓብ የሎጥ ልጅ ነበር። ሎጥ ደግሞ የአብርሃም የወንድም ልጅ ነበር። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

Deuteronomy 2:10

ኤሚማውያን ይኖሩባት ነበር _ ኤሚም ብለው ይጠሯቸዋል
እነዚህ ቃላት ከሞዓባውያን በፊት በምድሪቱ ላይ ስለነበሩት ስለ ኤሚም ሕዝብ ዳራዊ መረጃ ይሰጣሉ። ቋንቋህ ዳራዊ መረጃን ለማመልከት የተለየ መንገድ ይኖረው ይሆናል። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ኤሚማውያን _ ራፋይም
እነዚህ ግዙፍ እንደሆኑ የሚታሰቡ የሕዝብ ወገን ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ዔናቅ
እነዚህ በጣም ረጃጅምና ኃይለኞች የነበሩ የዔናቅ ሕዝቦች ተወላጆች ናቸው። ይህንን በዘዳግም 1:28 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Deuteronomy 2:12

ሖራውያን
ይህ የአንድ የሕዝብ ወገን ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ከፊታቸው አጠፏቸው
“ከእነርሱ ጋር አንዱም በሕይወት እንዳይኖር ሁሉንም ገደሏቸው” ወይም “ሁሉንም በመግደል ከአጠገባቸው አስወገዷቸው”

Deuteronomy 2:13

ስለዚህ ‘አሁን ተነሡ _ ዜሬድ’
“ከዚያም እግዚአብሔር፣ “አሁን ተነሡ _ ዜሬድ’ ስለዚህ”። ይህ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ከዚያም እግዚአብሔር ተነሥተን _ ዜሬድ ተናገረን። ስለዚህ” (ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ የሚለውን ተመልከት)

ተነሡ
አንድ ነገር ለማድረግ ጀምሩ (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የዜሬድን ጅረት
ይህ ምንጭ ከደቡብ ምስራቅ ወደ ሙት ባህር በመፍሰስ በኤዶምና በሞዓብ መካከል ድንበር ያበጃል። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

አሁን ቀኖቹ
“አሁን” የሚለው ቃል ከትረካው የእስራኤል ሕዝብ ለምን ያህል ጊዜ እንደተጓዙና በዚያ ትውልድ ላይ እግዚአብሔር ወደተቆጣበት ዳራዊ መረጃ መቀየሩን ያመለክታል። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ሠላሳ ስምንት ዓመት
“38 ዓመት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ከሕዝቡ ተለይተው ሄደው ነበር
ይህ “ሞተው ነበር” የሚል የትህትና አነጋገር ነው። (See: Euphemism)

የእግዚአብሔር እጅ በእነርሱ ላይ
እዚህ ጋ “የእግዚአብሔር እጅ” የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ኃይል ነው። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ኃይሉን በእነርሱ ላይ ተጠቅሟል” ወይም “እግዚአብሔር ቀጣቸው” (See: Synecdoche)

Deuteronomy 2:16

እናንተ ናችሁ - መጣችሁ - አታስቸግሯቸው - አልሰጣችሁም
ሙሴ ለእስራኤላውያን አንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ በመሆኑም “አንተ” እና “አታስቸግሯቸው” የሚልበት ትዕዛዝ አገባብ ሁሉ ነጠላ ቁጥሮች ናቸው። (See: Forms of You)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ዔርን ታልፋላችሁ
ይህ በሞዓብ የሚገኝ የአንድ ከተማ ስም ነው። “ዔር”ን በዘዳግም 2:9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ለሎጥ ተወላጆች
የእስራኤል ሕዝብ ከአሞን ተወላጆች ጋር ዝምድና ነበራቸው። አሞን የሎጥ ልጅ ነበር። ሎጥ ደግሞ የአብርሃም የወንድሙ ልጅ ነበር። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

Deuteronomy 2:20

ያ ደግሞ ይቆጠር ነበር
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ሰዎች ያንን ደግሞ ይቆጥሩ ነበር”። (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ረፋይም
ይህ የአንድ ሕዝብ ወገን ስም ነው። ይህንን በዘዳግም 2:11 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ዘምዙማውያን
ይህ የረፋይም ሕዝብ ወገን ሌላው ስማቸው ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ዔናቅ
ይህ የአንድ ሕዝብ ወገን ስም ነው። ይህንን በዘዳግም 2:28 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

በአሞናውያን ፊት አጠፋቸው
“አሞናውያን እንዲያሸንፏቸው ፈቀደላቸው” ወይም “አሞናውያን ሁሉንም እንዲገድሏቸው ፈቀደላቸው”

እነርሱ ተኳቸው፣ በእነርሱ ስፍራም ኖሩ
“አሞናውያኑ ረፋይማውያን የነበራቸውን ሁሉ ወሰዱባቸው፣ ረፋይማውያን ይኖሩ በነበሩበትም ስፍራ ኖሩ”

ሖራውያን
ይህ የአንድ ሕዝብ ወገን ስም ነው። ይህንን በዘዳግም 2:12 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ተኳቸው፣ በእነርሱ ስፍራም ኖሩ
“ሖራውያን የነበራቸውን ሁሉ ወሰዱባቸው፣ ሖራውያን ይኖሩ በነበሩበትም ስፍራ ኖሩ”

Deuteronomy 2:23

ኤዋውያን - ከፍቶር
እነዚህ የሕዝብ ወገን ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ከፍቶር
x

Deuteronomy 2:24

አሁን ተነሡ
ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር ለሙሴ እየነገረው ነው። “አሁን ተነሡ” ወይም “አሁን ሂዱ”

መንገዳችሁን ሂዱ
“ጉዞአችሁን ቀጥሉ”

የአርኖን ሸለቆ
ይህ የአርኖን ወንዝ ሸለቆ ስም ነው። እርሱ በሞዓብና በአሞራውያን መካከል ድንበር ያበጃል። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

በእጃችሁ ሰጥቻችኋለሁ
“በእጃችሁ” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉም “በቁጥጥራችሁ ወይም በኃይላችሁ ሥር” ማለት ነው። አ.ት፡ “እንድታሸንፉ ኃይልን ሰጥቻችኋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እጃችሁ - ለመውረስ ጀምሩ - ተዋጉ - ማስፈራታችሁ - ዝናችሁ - በእናንተ ምክንያት
ሙሴ ለእስራኤላውያን አንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ በመሆኑም “አንተ” እና “የእናንተ” እንዲሁም ትዕዛዝ የሆኑት “ለመውረስ ጀምሩ” እና “ተዋጉ” ሁሉም አገባቦች ነጠላ ቁጥሮች ናቸው። (See: Forms of You)

ሴዎን
ይህ የአንድ ንጉሥ ስም ነው። ይህንን በዘዳግም 1:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ሐሴቦን
ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። ይህንን በዘዳግም 1:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ከእርሱ ጋር ተዋጋ
“ከእርሱና ከሰራዊቱ ጋር ተዋጋ”

አስፈሩ፣ አስደንግጡም
“ፍርሐት” እና “ድንጋጤ” የሚሉት ቃላት መሠረታዊ ትርጉማቸው አንድ ቢሆንም ፍርሐቱ ታላቅ መሆኑን አጽንዖት ይሰጣል። አ.ት፡ “ከባድ ፍርሐት ጣሉባቸው” (See: Doublet)

ከሰማይ በታች ያለ ሕዝብ ሁሉ
ይህ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “በየአገሩ ያሉ ሕዝቦች” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ይንቀጥቀጡና ይጨነቁ
ይህ ሕዝቡ በጭንቀት እንደሚንቀጠቀጡ አጽንዖት ይሰጣል። (See: Hendiadys)

Deuteronomy 2:26

እኔ ላክኋቸው
እዚህ ጋ “እኔ” የሚያመለክተው ሙሴን ነው።

ወደ ቄድሞት ምድረ በዳ
ይህ በአርኖን ሸለቆ አቅራቢያ የሚገኝ ቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ሴዎን -- ሐሴቦን
ይህ የሰውና የቦታ ስም ነው። እነዚህን በዘዳግም 1:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

በሰላም ቃል
“ሰላምን ባቀርብላቸው” ወይም “ስለ ሰላም ከሚጠይቅ መልዕክቴ ጋር”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወደ ቀኝም ሆነ ወደ ግራ ዘወር አልልም
ይህ ሐረግ ሁሌም በአንድ አቅጣጫ እንደሚሄዱ አጽንዖት ይሰጣል። ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። “አቅጣጫዬን አልቀይርም” ወይም “ሁሌም መስመሬን ጠብቄ እጓዛለሁ” (ምጸት የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 2:28

የምበላውን ምግብ በገንዘብ ትሸጥልኛለህ፤ የምጠጣውንም ውሃ በገንዘብ ስጠኝ
ሙሴ እስራኤላውያን ከአሞራውያን እንደማይሰርቁና ሴዎንና ሕዝቡ ምግብና ውሃ እንዲሸጡላቸው ሴዎንን ይጠይቀዋል እንጂ ትዕዛዝ አይሰጠውም። አ.ት፡ “ለምበላው ምግብና ለምጠጣው ውሃ መክፈል እንዳለብኝ አስባለሁ”

እንድበላ - ሸጥልኝ - እንድጠጣ - ስጠኝ
ሙሴ ስለራሱ አድርጎ የሚናገረው እስራኤላውያንን ሲያመለክት ነው። አ.ት፡ “እንበላው ዘንድ - ለእኔና ለሕዝቤ ሸጥልኝ - እንጠጣው ዘንድ - ስጠን” (See: Synecdoche)

በእግሬ እንዳልፍ ብቻ ፍቀድልኝ
“በምድርህ ተራምደን ብቻ እንለፍ”

ዔር
ይህ የቦታ ስም ነው። ይህንን በዘዳግም 2:9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 2:30

ሴዎን - ሐሴቦን
ይህ የሰውና የቦታ ስም ነው። እነዚህን በዘዳግም 1:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

አምላካችሁ -- ጉልበታችሁ
ሙሴ እስራኤላውያንን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራል፣ ስለዚህ በሁሉም አገባብ “ያንተ” የሚለው ነጠላ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)

አሳቡን አደነደን፣ ልቡንም ግትር አደረገ
ሁለቱም ሐረጎች ትርጉማቸው ተመሳሳይ ሲሆን አጽንዖት የሚሰጠው እግዚአብሔር “በጣም ግትር እንዲሆን አደረገው” ለማለት ነው። (See: Parallelism)

ሴዎንን እና ምድሩን በፊትህ አሳልፌ ልሰጥ
“ሴዎንን እና ምድሩን ለአንተ ልሰጥህ”

ምድሩ ለአንተ ይሆን ዘንድ ለመውረስ ጀምር
“ትወርሰው ዘንድ የእርሱን ምድር ለራስህ ውሰድ”

Deuteronomy 2:32

ሴዎን
ይህ የአንድ ንጉሥ ስም ነው። ይህንን በዘዳግም 1:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ያሀጽ
ይህ ሞዓብ ውስጥ የነበረ የአንድ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 2:34

የእርሱን ከተሞች ሁሉ ወሰድን
“የንጉሥ ሴዎንን ከተሞች በሙሉ ያዝን”

እያንዳንዱን ከተማ ፈጽሞ አጠፋን
“በየከተማው ይኖሩ የነበሩትን ሰዎች ሁሉ ገደልን”

Deuteronomy 2:36

አሮዔር
ይህ በአርኖን ወንዝ ሰሜናዊ ዳርቻ የሚገኝ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የአርኖን ሸለቆ
“አርኖን” የወንዝ ስም ነው። ይህንን በዘዳግም 2:24 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ለእኛ ከባድ የሆነ ከተማ አልነበረም
ይህ አሉታዊ አገላለጽ በጦርነት የነበራቸው ስኬት ላይ አጽንዖት ለመስጠት ጥቅም ላይ ውሏል። ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ምንም እንኳን ከተማው ዙሪያው በረጃጅም ቅጥር የታጠረ ቢሆንም በየከተማው ያሉትን ሕዝቦች ማሸነፍ ችለናል። (ምጸት የሚለውን ተመልከት)

አልሄዳችሁም
ሙሴ እስራኤላውያኑን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራል፣ ስለዚህ “አንተ” ነጠላ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)

የያቦቅ ወንዝ
ይህ በሴዎን እና በአሞናውያን ምድር መካከል ድንበር ያበጀ ወንዝ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 ተመልሰን በባሳን መንገድ ሄድን፥ የባሳን ንጉሥ ዐግና ሕዝቡ ሁሉ በኤድራይ ሊዋጉን መጡ። **2** እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ፦ እርሱንና ሕዝቡን ሁሉ ምድሩንም በእጅህ አሳልፌ ሰጥቼአለሁና አትፍራው። በሐሴቦን ይኖር በነበረው በአሞራውያን ንጉሥ በሴዎን ላይ እንዳደረግህ በእርሱም ታደርግበታለህ አለኝ። **3** እግዚአብሔር አምላካችንም በባሳን ንጉሥ በዐግ ሕዝቡንም ሁሉ በእጃችን ድልን ሰጠን። እኛም አንድ እንዳይቀር እስኪሞቱ ድረስ መታነው። **4** በዚያን ጊዜም አንድም ያልወሰድነው ሳይቀር ሁሉንም ስድሳ ከተሞችን፦ በባሳን ያለውን የዐግን መንግሥት፥ የአርጎብን አገር ሁሉ ከተሞችን ወሰድን። **5** እነዚህም ከተሞች ሁሉ ዙሪያቸው በረጅም ቅጥር፥ በበሮቻቸውና በመወርወሪያዎች የተመሸጉ ነበር፤ በአጠገባቸውም ብዙ ያልተመሸጉት ከተሞች ነበሩ። **6** በሐሴቦንም ንጉሥ በሴዎን እንዳደረግን ከወንዶችና ሴቶች ከሕፃናትም ጋር ፈጽሞ አጠፋናቸው። **7** ነገር ግን ከአጠፋናቸው ከተሞች ሁሉ ከብቶቹን ሁሉ ምርኮም ለራሳችን ወሰድን። **8** በዚያም ጊዜ ከአርኖን ሸለቆ ጀምሮ እስከ አርሞንዔም ተራራ ድረስ ምድሪቱን ከዮርዳኖስ ማዶ ከነበሩ ከሁለቱ ከአሞራውያን ነገሥታት እጅ ወሰድን፤ **9** (ሲዶናውያን አርሞንዔምን ሢርዮን ብለው ይጠሩታል፥ አሞራውያንም ሳኔር ብለው ይጠሩታል) ፤ **10** በሜዳውም ያሉትን ከተሞች ሁሉ፥ ገለዓድንም ሁሉ፥ በባሳንም ያሉትን የዐግን መንግሥት ከተሞች እስከ ስልካና፤እስከ ኤድራይ ድረስ ባሳንን ሁሉ ወሰድን። **11** ከራፋይም ወገን የባሳን ንጉሥ ዐግ ብቻውን ተርፎ ነበር፤ እነሆም አልጋው የብረት አልጋ ነበረ፤ እርሱ በአሞን ልጆች አገር በረባት አልኖረምን? ይህም በሰው ክንድ ልክ ርዝመቱ ዘጠኝ ክንድ፥ ወርዱም አራት ክንድ ነበረ። **12** በዚያን ጊዜ በአርሞን ሸለቆ ከአሮዔር ርስት አድርገን የወሰደነውን ይህን የገለዓድን ተራራማ ምድር እኩልታ ከተሞቹንም ለሮቤልና ለጋድ ነገድ ሰጠኋቸው። **13** ከገለዓድም የቀረውን የዐግንም መንግሥት ባሳንን ሁሉ የአጎብንም ምድር ሁሉ ለምናሴ ነገድ እኩሌታ ሰጠሁ። (ይህም ተመሳሳይ አገር የራፋይም ምድር ተብሎ ይቆጠራል።) **14** የምናሴ ነገድ አንዱ ኢያዕር እስከ ሄሸራውያንና እስከ ማዕካታውያን ዳርቻ ድረስ የአርጎብን አካባቢ ሁሉ ወሰደ። ይህንም የባሳንን ምድር እስከ ዛሬ ድረስ የሚጠራውን በስሙ የኢያዕር መንደሮች ብሎ ጠራ። **15** ለማኪርም ገለዓድን ሰጠሁት። **16** ለሮቤል ነገድና ለጋድም ነገድ ከገለዓድ ጀምሮ እስከ አርኖኖን ሸለቆ ድረስ የሸለቆውን እኩሌታ ዳርቻውንም እስከ አሞን ልጆች ዳርቻ እስከ ያቦቅ ወንዝ ድረስ ሰጠኋቸው። **17** ከኪኔሬት እስከ ዓርባ ባሕር (እርሱም የጨው ባሕር) ድረስ ከፈስጋ ተራራ በታች ወደ ምሥራቅ ያለውን የዮርዳኖስን ሸለቆ ዳቻውንም ሰጠኋቸው። **18** በዚያም ጊዜ እንዲህ ብዬ አዘዝኋችሁ፦ እግዚአብሔር አምላካችሁ ይህን ምድር ርስት አድርጎ ሰጥቶአችኋል፤ እናንተ የጦር ሰዎች መሣሪያችሁን ታጥቃችሁ በወንድሞቻችሁ ከእስራኤል ልጆች ፊት ታልፋላችሁ። **19** ነገር ግን ሚስቶቻችሁ፥ ልጆቻችሁና ከብቶቻችሁ (ብዙ ከብቶች እንዳሉአችሁ አውቃለሁ) በሰጠኋችሁ ከተሞች ይቀመጣሉ፤ **20** ይኸውም እግዚአብሔር እናንተን እንዳሳረፈም ወንድሞቻችሁን እስኪያሳርፍ ድረስ እነርሱም ደግሞ በዮርዳኖስ ማዶ እግዚአብሔር አምላካችሁ የሚሰጣቸውን ምድር እስኪወርሱ ድረስ ነው፤ ከዚያም በኋላ እናንተ ሁላችሁ ወደ ሰጠኋችሁ ርስት ትመለሳላችሁ። **21** በዚያም ጊዜ ኢያሱን እንዲህ ብዬ አዘዝሁት፦አምላካችሁ እግዚአብሔር በእነዚህ በሁለቱ ነገሥታት ያደረገውን ሁሉ ዓይኖችህ አይተዋል፤ እንዲሁ በምታልፍባቸው መንግሥታትም ሁሉ ላይ እግዚአብሔር ያደርጋል። **22** አምላካችሁ እግዚአብሔር እርሱ ስለ እናንት ስለሚዋጋ አትፈራቸውም ብዬ አዘዝሁት። **23** በዚያም ጊዜ እኔ ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ብዬ ለመንሁ፦ **24** ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፥ ታላቅነትህንና ብርቱ እጅህን ለእኔ ለባሪያህ ማሳየት ጀምረሃል፤ በሰማይ ወይም በምድር እንደ አንተ፥ እንደ ኃይልህ፥ ያደርግ ዘንድ የሚችል አምላክ ማን ነው? **25** እኔም ወደዚያ ልሂድና በዮርዳኖስም ማዶ ያለውን መልካሙን ምድርና መልካሙን ተራራማውን አገር ሊባኖስንም ለመየት እለምንሃለሁ። **26** እግዚአብሔር ግን እናንተ ባለመስማታችሁ ምክንያት ተቆጣኝ። እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ፦ ስለዚህም ነገር ደግመህ እንዳትናገረኝ ይበቃሃል። **27** ይህን ዮርዳኖስን ስለማትሻገር ወደ ፈስጋ ራስ ውጣና ዓይንህንም ወደ ምዕራብ፥ ወደ ሰሜን፥ ወደ ደቡብምና ወደ ምሥራቅ ዓይንህን አንሥተህ ተመልከት። **28** በዚህ ፈንታ ኢያሱን አስተምረው፥ አደፋፍረው እንዲሁም አጽናው፤ ምክንያቱም እርሱ በዚህ ሕዝብ ፊት ይሄዳል፥ አንተም የምታየውን ምድር ያወርሳቸዋል። **29** ስለዚህም በቤተ ፌጎርም በሸለቆው ውስጥ ቆየን።

Deuteronomy 3:1

ዐግ - ሴዎን
እነዚህ የነገሥታት ስሞች ናቸው። እነዚህን በዘዳግም 1:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ኤድራይ -- ሐሴቦን
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። እነዚህ በዘዳግም 1:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ፣ “አትፍራው -- ሰጥቼሃለሁ -- በቁጥጥርህ ስር -- በሐሴቦን -- እንዳደረግኸው
እግዚአብሔር ሙሴ እስራኤላውያንን እንደሆነ ያህል ይናገረዋል፣ ስለዚህ “አትፍራ” የሚለው ትዕዛዝና “አንተ” እና “የአንተ” የሚለው አገባብ ሁሉ ብዙ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)

አትፍራው -- በእርሱ ላይ -- ሕዝቡንና ምድሩን
እዚህ ጋ “እርሱን” እና “የእርሱ” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ዐግን ነው።

ድልን ሰጥቼሃለሁ
እግዚአብሔር ሊያደርግ ያለውን አስቀድሞ እንዳደረገው ቆጥሮ ይናገራል። (See: Predictive Past)

በሴዎን ላይ እንዳደረግኸው በእርሱ ላይ ታደርጋለህ
“በእርሱ” የሚለው ቃል”በእርሱ ሕዝብ ላይ” ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፦ “ሴዎንን እንዳደረግኸው ዐግንና ሕዝቡን ታጠፋቸዋለህ” (See: Synecdoche)

Deuteronomy 3:3

ሕዝቡ ሁሉ በቁጥጥራችን ሥር ሆነ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፦ “እግዚአብሔር የዐግን ሕዝብ በሙሉ በቁጥጥራችን ሥር አደረገ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የእርሱ ከሆነው ሕዝብ አንድም አልቀረለትም
አስራኤላውያን ማንንም በሕይወት እንዳላስቀሩ አጽንዖት ለመስጠት ይህ ምጸት ጥቅም ላይ ውሏል። አ.ት፦ “የእርሱ የሆነው ሕዝብ ሁሉ ሞተ” (ምጸት የሚለውን ተመልከት)

ከስልሳዎቹ ከተሞች ያልወሰድነው አንድም አልነበረም
ይህ 60ዎቹን ከተሞች በሙሉ ስለመውሰዳቸው አጽንዖት የተሰጠበት ድርብ አሉታ ነው። አ.ት፦ “እያንዳንዱን ስልሳ ከተማ ወሰድን” (ድርብ አሉታ የሚለውን ተመልከት)

ስልሳ ከተሞች
“60 ከተሞች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የአርጎብን አካባቢ
ይህ በባሳን ውስጥ ያለ የአንድ አካባቢ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 3:5

እነዚህ ከተሞች በሙሉ በግምብ የታጠሩ ነበሩ
“እነዚህ ከተሞች በሙሉ በ -- የተጠበቁ ነበሩ”

በጣም ብዙ ከሆኑት ጋር
“በጣም ብዙ ከሆኑት በተጨማሪ” ወይም “በጣም ብዙ የሆኑትን ሳይጨምር”

ሴዎን
ይህ የአንድ ንጉሥ ስም ነው። ይህንን በዘዳግም 1:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ሐሴቦን
ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። ይህንን በዘዳግም 1:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

እያንዳንዱን ከተማ በማጥፋት
“በየከተማው የሚኖሩትን ሰዎች በሙሉ በመግደል”

Deuteronomy 3:8

ከሁለቱ ነገሥታት እጅ
እዚህ ጋ “ከእጃቸው” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር “ከቁጥጥራቸው” ማለት ነው። አ.ት፡ “ከሁለት ነገሥታት ቁጥጥር” ወይም “ከሁለቱ ነገሥታት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አሞራውያን -- ባሳን -- ኤድራይ -- ዐግ
“የአሞራዊ ሕዝቦች -- የባሳን ምድር -- የኤድራይ ከተማ -- ንጉሥ ዐግ”። እነዚህን በዘዳግም 1:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

በዮርዳኖስ ማዶ
ይህ ከእስራኤል በስተምስራቅ ከዮርዳኖስ ወንዝ ባሻገር ያለውን ምድር ያመለክታል። ሙሴ ይህንን በሚናገርበት ጊዜ ከዮርዳኖስ በስተምስራቅ ነበር። ይህንን በዘዳግም 1:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምስራቅ”

በአርኖን ሸለቆ
እነዚህን ቃላት በዘዳግም 2:24 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

የአርሞንዔም ተራራ -- ሢርዮን -- ሳኔር
እነዚህ በሙሉ ከባሳን በስተሰሜን ዳርቻ ላይ ያለው የአንድ ተራራ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

በሜዳ
ይህ በአርኖን ወንዝና በገለዓድ ተራራ መካከል ያለ ረጅምና ሰፊ ስፍራ ነው።

ሰልካ
ይህ በኤድሪ አቅራቢያ የምትገኝ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 3:11

የትሩፉ -- ሰዎች በሚለኩበት
ይህ የንጉሥ ዐግ ዳራዊ መረጃ ነው። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ራፋይም
ይህንን በዘዳግም 2:11 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ተመልከት!
“ለምነግርህ ጠቃሚ ነገር ትኩረት ስጥ”።

የሚኖረው -- በረባት አልነበረም?
ጸሐፊው የእስራኤል ሕዝብ ወደ ረባት እንዲሄዱና ዐግ ምን ያህል ታላቅ እንደነበረ ያዩ ዘንድ ለማስታወስ ጥያቄ ያቀርባል። ይህ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች 1) “የሚኖረው -- በረባት ነበር” ወይም “በረባት -- ይኖራል” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሴንቲ ሜትር ይረዝማል። (መጽሐፍ ቅዱሳዊ የርቀት መለኪያ የሚለውን ተመልከት)

ሰዎች በሚለኩበት መንገድ
“አብዛኛው ሰው በሚጠቀምበት የክንድ መለኪያ”

Deuteronomy 3:12

አሮዔር
የዚህን ከተማ ስም በዘዳግም 2:36 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የአርኖን ሸለቆ
እነዚህን ቃላት በዘዳግም 2:24 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

የአርጎብን ክልል
እነዚህን ቃላት በዘዳግም 3:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

ያው ወሰን የራፋይም ምድር ተብሎ ይጠራል
ጸሐፊው የእስራኤል ሕዝብ ስለ ያዙት ምድር ዳራዊ መረጃ ማቅረብ ይጀምራል። የአንተ ቋንቋ ቀጥሎ የሚመጣው ዳራዊ መረጃ መሆኑን የሚያሳይበት መንገድ ካለ እርሱን እዚህ ጋ መጠቀም አለብህ። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ራፋይም
የዚህን ምድር ስም በዘዳግም 2:11 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Deuteronomy 3:14

ኢያዕር
ይህ የአንድ ሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ጌሹራውያን እና ማዕካታውያን
እነዚህ ከባሳን በስተምዕራብ የሚኖሩ የሕዝብ ወገን ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ሓቦት ኢያዕር
ተርጓሚዎች የሚከተለውን የግርጌ ማስታወሻ ያደርጉ ይሆናል፡ “ ‘ሓቦት ኢያዕር’ ማለት ‘የኢያዕር የድንኳን መንደሮች’ ወይም ‘የኢያዕር ግዛት’ ማለት ነው”።

Deuteronomy 3:15

ሰጠሁ
እዚህ ጋ “እኔ” የሚያመለክተው ሙሴን ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለማኪር
ማኪር የምናሴ ልጅ ነበር። እርሱ ሙሴ ይህንን ምድር ከመስጠቱ በፊት ሞቶ ነበር። ስሙ ለሰውየው ተወላጆች ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ለማኪር ተወላጆች” (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የአርኖን ሸለቆ
ይህ የአርኖን የወንዝ ሸለቆ ስም ነው። እርሱ በሞዓብና በአሞራውያን መካከል ድንበር ያበጃል። ይህንን በዘዳግም 2:24 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የያቦቅ ወንዝ
ይህ በሴዎን ምድር እና በአሞናውያን ምድር መካከል ድንበር ያበጀ ወንዝ ስም ነው። ይህንን በዘዳግም 2:37 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 3:17

ሌላው ወሰኑ ደግሞ
“የሮቤላውያን እና የጋዳውያን ድንበር ምዕራባዊ ወሰናቸው ነው”

ኪኔሬት
የኪኔሬት ባህር “የገሊላ ባህር” ወይም “የጌንሳሬጥ ሐይቅ” ተብሎም ይጠራል። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የፈስጋ ተራራ
ይህ ከአባሪም ሰንሰለታማ ተራራ በስተሰሜን የሚገኝ የተራራ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 3:18

በዚያን ጊዜ አዘዝኋችሁ
ሌሎች እስራኤላውያን እግዚአብሔር ተስፋ የሰጣቸውን የቀረውን ምድር ድል ያደርጉ ዘንድ የሮቤል ነገድ፣ የጋድ ነገድና ከፊሉ የምናሴ ነገድ እንዲያግዟቸው ሙሴ ያስታውሳቸዋል (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

መሣሪያችሁን ይዛችሁ በፊታቸው ታልፋላችሁ
“የጦር መሣሪያዎቻችሁን ትይዙና ቀድማችሁ የዮርዳኖስን ወንዝ ትሻገራላችሁ”

ወንድሞቻችሁ የእስራኤል ሰዎች
“እስራኤላውያን ባልንጀሮቻችሁ”

Deuteronomy 3:19

እግዚአብሔር ለወንድሞቻችሁ እረፍትን እስኪሰጥ
ጸሐፊው የማረፍን ችሎታ በስጦታ እንደሚሰጥ ቁሳዊ አካል አድርጎ ይናገራል። በተጨማሪም፣ “ማረፍ” የሚለው ቃል ጦርነት የሌለበትን ሰላማዊ ኑሮ የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ወድሞቻችሁ እንዲያርፉ እግዚአብሔር ይፈቅዳል” ወይም “በጦርነት መዋጋትን አቁመው በሰላም እንዲኖሩ እግዚአብሔር ለወንድሞቻችሁ ይፈቅዳል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከዮርዳኖስ ማዶ
ይህ ከእስራኤል በስተምስራቅ ከዮርዳኖስ ወንዝ ባሻገር ያለውን ምድር ያመለክታል። ሙሴ ይህንን በሚናገርበት ጊዜ ከዮርዳኖስ በስተምስራቅ ነበር። በዘዳግም 1:1 ላይ እነዚህን ቃላት እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። አ.ት፡ “ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምስራቅ”

ከዚያም ትመለሳላችሁ
እግዚአብሔር ለእነዚህ ሦስት ነገዶች ምድራቸውን እንዲወርሱ ከመፍቀዱ በፊት ሌሎቹ ነገዶች መሬታቸውን መውረስ እንዳለባቸው ሙሴ አጽንዖት ይሰጣል። “የምትመለሱት ከዚያ በኋላ ብቻ ነው”።

Deuteronomy 3:21

ዐይኖችህ ዓይተዋል
እዚህ ጋ “ዐይኖችህ” የሚያመለክተው ኢያሱን ነው። አ.ት፡ “አንተ ዐይተሃል” (See: Synecdoche)

Deuteronomy 3:23

ለመንሁ
እዚህ ጋ “እኔ” የሚያመለክተው ሙሴን ነው። ይህ ማለት በጣም ቅንና ስሜታዊ በሆነ መንገድ እግዚአብሔርን ጠይቆታል።

ለአገልጋይህ ለማሳየት
እዚህ ጋ “አገልጋይህ” የሚለው ቃል ለአንድ ታላቅ ሥልጣን ላለው በትህትና የመናገር መንገድ ነው። አ.ት፡ “ለአገልጋይህ ልታሳየኝ”

ብርቱ እጅህ
እዚህ ጋ ፈሊጣዊ የሆነው “እጅ” መቆጣጠር ወይም ኃይል ማለት ነው። አ.ት፡ “ኃይልህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ማድረግ የሚችል አምላክ ማነው?
ሙሴ እግዚአብሔር ያደረጋቸውን ሥራዎች ለማድረግ ኃይል ያለው ብቸኛው አምላክ እርሱ መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት በጥያቄ መልክ ያቀርባል። ይህ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “. . . የሚያደርግ ሌላ አምላክ የለም”። (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

በሰማይ ወይም በምድር ላይ
የእነዚህ ሁለት ጽንፎች ትርጉም በአንድነት “የትም ቦታ” ማለት ንው። (See: Merism)

ከዮርዳኖስ ማዶ
“ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምዕራብ”። ሙሴ ይህንን ቃል ለእግዚአብሔር በሚናገርበት ጊዜ ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምስራቅ ሞዓብ ውስጥ ነበረ።

Deuteronomy 3:26

እግዚአብሔር በእናንተ ምክንያት ተቆጥቶኝ ነበር
ይህ የሚያመለክተው ሙሴ በእስራኤል ሕዝብ ላይ በመቆጣቱ ምክንያት እግዚአብሔር እንዲያደርግ ያዘዘውን ያልታዘዘበትን ጊዜ ነው። ይህንን በዘዳግም 1:37 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ፈስጋ
ይህንን በዘዳግም 3:17 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ዐይኖችህን አንሣ
“ዐይኖችህን አንሣ” የሚሉት ቃላት ዘይቤአዊ አነጋገር ሲሆን ተመልከት ማለት ነው። አ.ት፡ “ተመልከት” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 3:28

ቤተ ፌጎር
ይህ በፈስጋ ተራራ አጠገብ በሞዓብ ውስጥ የሚገኝ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 አሁንም እስራኤል ሆይ እንድታደርጉአቸው፥ በሕይወት እንድትኖሩና የአባቶቻችሁ አምላክ እግዚአብሔር ወደሚሰጣችሁ ምድር ሄዳችሁ እንድትወርሱ
የማስተምራችሁን ሥርዓትንና ድንጋጌን ስሙ። 2 እኔ የማዛችሁን የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ትእዛዛትን ሁሉ ሳትጨምሩና ሳታጎሉ ትጠብቃላችሁ። 3
ከብዔልፌጎርም የተነሣ፥ ብዔልፌጎርን የተከተሉትን ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔር አምላካችሁ ከመካከላችሁ እንዳጠፋ ዓይኖቻችሁ አይተዋል። 4 እናንተ ግን
እግዚአብሔር አምላካችሁን የተከተላችሁ እስከ ዛሬ ድረስ በሕይወት አላችሁ። 5 እነሆ እናንተ ለመውረስ በምትሄዱባቸው ምድር ሰዎች መካከል ታደርጉ ዘንድ
እግዚአብሔር አምላኬ እንዳዘዘኝ ሥርዓትንና ድጋጌን አስተማርኋችሁ። 6 ስለዚህ ጠብቁአቸው፥ አድርጉአቸውም፤ ምክንያቱም ስለእነዚህ ሥርዓት ሰምተው፦
'በእውነት ይህ ታላቅ ሕዝብ ጠቢብና አስተዋይ ሕዝብ ነው' በሚሉ ሰዎች ሁሉ ፊት ይህ ጥበባችሁና ማስተዋላችሁ ነው። 7 በምንጠራው ጊዜ ሁሉ
እንደምቀርበን እንደ እግዚአሔር አምላካችን፥ ወደ እነርሱ የቀረበ አምላክ ያለው ሌላ ታላቅ ሕዝብ ማን ነው? 8 ዛሬ በፊታችሁ እንደማኖራው ሥርዓት ሁሉ ጽድቅ
የሆነው ሥርዓትና ድንጋጌ ያለው ሌላ ታላቅ ሕዝብ ማን ነው? 9 ዓይኖቻችሁ ያዩትን ነገር እንዳትረሱ በሕይወታችሁም ዘመን ሁሉ ከልባችሁ እንዳይጠፋ ብቻ
አስታውሉ፤በጥንቃቄም ራሳችሁን ጠብቁ። እግዚአብሔር፦ ሕዝቡን ወደ እኔ ሰብስብ በምድርም በሕይወት በሚኖሩበት ዘመን ሁሉ እኔን መፍራት ይማሩ ዘንድ
ልጆቻቸውንም ያስተምሩ ዘንድ ቃሌን አሰማቸዋለሁ ብሎ እንደተናገረኝ፥ 10 በእግዚአብሔር አምላካችሁ ፊት በኮሬብ በቆማችሁ ቀን እንደሰማችሁ፥ይህን
በልጆቻችሁና በልጅ ልጆቻችሁ ዘንድ እንዲታውቅ አድርጉ። 11 እናንተም ቀርባችሁ ከተራራው በታች ቆማችሁ ነበር። እስከ ሰማይም መካከል ድረስ እሳት
በተራራው ላይ ይነድድ ነበር፤ ጨለማና ደመና ድቅድቅ ጨለማ ነበረ። 12 እግዚአብሔርም በእሳት ውስጥ ሆኖ ተናገራችሁ፤ ድምፅን በቃል ሰማችሁ መልክን
ግን አላያችሁም፤ ድምፅን ብቻ ሰማችሁ። 13 ታደርጉትም ዘንድ ያዘዛችሁን ቃል ኪዳን አሥሪቱን ቃላት አስታወቃችሁ። በሁለቱም በድንጋይ ጽላቶች ላይ
ጻፋቸው። 14 በዚያን ጊዜ ትወርሱአት ዘንድ በምትሄዱባት ምድር የምታዳርጉትን ሥርዓትና ድንጋጌ አስተምራችሁ ዘንድ እግዚአብሔር አዘዘኝ። 15 እግዚአብሔር
በኮሬብ በእሳት መካከል ሆኖ በተናገራችሁ ጊዜ መልክን ከቶ እንዳላያችሁ፤ለራሳችሁ እጅግ ተጠንቀቁ። 16 የማናቸውንም ፍጥረት ምሳሌ የተቀረጸውን ምስል
በወንድ ወይም በሴት፥ 17 ወይም በማናቸውም በምድር ባለው በዱር እንስሳ መልክ፥ ወይም ከሰማይም በታች የሚበርረውን የወፍን ምሳሌ፥ 18 ወይም በምድር
ላይ የሚሳበውን ሁሉ ምሳሌ፥ ወይም ከምድርም በታች በውኃ ውስጥ የሚኖረውን የዓሣን ሁሉ ምሳሌ በማድረግ እንዳትረክሱ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። 19
ዓይኖቻችሁን ወደ ሰማይ አንሥታችሁ እግዚአብሔር አምላካችሁ ከሰማይ ሁሉ በታች ላሉት ሕዝብ ሁሉ የመደባቸውን ፀሐይንና ጨረቃን ከዋክብትንና የሰማይ
ሠራዊት ሁሉ ባያችሁ ጊዜ አምልኮና ስግደት በማቅረብ እንዳትስቱ ተጠንቀቁ። 20 እናንተን ግን እግዚአብሔር እንደ ዛሬው ሁሉ የርስቱ ሕዝብ ትሆኑለት ዘንድ
ወስዶ ከብረት እሳት ከግብፅ አወጣችሁ። 21 ከዚህም በተጨማሪ እግአብሔር በእናንተ ምክንያት ተቆጣኝ፣ ዮርዳኖስንም እንዳልሻገር ፣እግዚአብሔር
አምላካችሁም ርስት አድርጎ ወደሚሰጣችሁ ወደመልካሚቱ ምድር እንዳልገባ ማለ። 22 እኔ ግን በዚህች ምድር እሞታለሁ፥ ዮርዳኖስንም አልሻገርም፥ እናንተ
ግን ትሻገራላችሁ፥ ያችንም መልካሚቱን ምድር ትወርሳላችሁ። 23 እግዚአብሔር አምላካችሁም ከእናንተ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን እንዳትረሱ እግዚአብሔር
አምላካችሁም የከለከለውን በማናቸውም ቅርጽ የተቀረጸውን ምስል እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ። 24 እግዚአብሔር አምላካችሁ የሚበላ እሳት ቀናተኛም አምላክ
ነውና። 25 ልጆችን የልጅ ልጆችንም በወለዳችሁ ጊዜ፥ በምድሪቱም ብዙ ዘመን በተቀመጣችሁ ጊዜ፥ በማናቸውም ምስል የተቀረጸውን ምስል አድርጋችሁ
በረከሳችሁም ጊዜ፥ ታስቆጡትም ዘንድ በእግዚአብሔር በአምላካችሁ ፊት ክፉ የሆነውን ነገር በሠራችሁ ጊዜ ትወርሱአት ዘንድ ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ፤ 26
ከምትገቡባት ምድር እንደምትጠፉ እኔ ዛሬ ሰማይንና ምድርን በእናንተ ላይ ምስክር እንዲሆኑ እጠራለሁ፤ ዘመናችሁም አይረዝምም፥ ፈጽሞም ትጠፋላችሁም።
27 እግዚአብሔርም በአሕዛብ መካከል ይበትናችኋል፥ በአሕዛብም መካከል ጥቂት ትሆናላችሁ፥እግዚአብሔርም ያስወጣችሁኋል። 28 በዚያም የማያዩትን፥
የማይሰሙትን፥ የማይበሉትን፥ የማያሸቱትንም በሰው እጅ ከእንጨትና ከድንጋይ የተሠሩትን አማልክት ታመልካላችሁ። 29 ነገር ግን ከዚያ እግዚአብሔር
አምላካችሁን ትሻላችሁ፤ በፍጹም ልባችሁ፥ በፍጹም ነፍሳችሁም የፈለጋችሁት እንደ ሆነ ታገኛላችሁ። 30 በተጨነቃችሁና ይህም ሁሉ በደረሰባችሁ ጊዜ በዘመኑ
ፍጻሜ ወደ እግዚአብሔር አምላካችሁ ትመለሳላችሁ፥ ድምፁንም ትሰማላችሁ። 31 እግዚአብሔር አምላካችሁ መሓሪ አምላክ ነውና፥ አይተዋችሁም፥
አያጠፋችሁምም፤ ለአባቶቻችሁም የማለላቸውን ቃል ኪዳኑን አይረሳም። 32 እግዚአብሔር ሰውን በምድር ላይ ከፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ከሰማይ እስከ ዳርቻዋ
ድረስ ከቶ እንዲህ ያለ ታላቅ ነገር ወይም እንደ እርሱ ያለ ተሰምቶ እንደ ሆነ ከእናንተ በፊት የነበረውምን የቀደመውን ዘመን ጠይቁ። 33 እናንተ ከእሳት ውስጥ
ሆኖ ሲናገር የእግዚአብሔርን ድምፅ እንደሰማችሁት ሌላ ሕዝብ ሰምቶአልን? 34 ወይም እግዚአብሔር አምላካችሁ በዓይናችሁ ፊት በግብፅ ለእናንተ
እንዳደረገው ሁሉ በፈተናና በተአምራት በድንቅና በጦርነት በጸናች እጅና በተዘረጋ ክንድ በታላቅም ማስፈራት እግዚአብሔር ከሌላ ሕዝብ መካከል ለራሱ
ሕዝብን ይወስድ ዘንድ በዐይናችሁ ፊት አድርጎ ያውቃልን? 35 እግዚአብሔርም አምላክ እንደ ሆነ ታውቁ ዘንድ እነዚህ ነገሮች ለእናንተ የተገለጡ
ናቸው፤ከእርሱም ሌላ አምላክ የለም። 36 ያስተምራችሁ ዘንድ ከሰማይ ድምፁን አሰማችሁ፥ በምድርም ላይ ታላቁን እሳት አሳያችሁ፤ ድምፁንም ከእሳት መካከል
ሰማችሁ። 37 አባቶቻችሁን ስለወደደ ከእነሱም በኋላ ዘራቸውን መረጠ፥ ከግብፅም በታላቁ ኃይል በመገኘቱ አወጣችሁ፤ 38 ዛሬ እንደ ሆነ ከእናንተ የጸኑትን
ታላላቆችን አሕዛብ ከፊታችሁ ሊስያወጣቸውና ለእናንተም ምድራቸውንም ርስት አድርጎ ሊሰጣችሁ ነው። 39 እንግዲህ እግዚአብሔር በላይ በሰማይ በታችም
በምድር አምላክ እንደ ሆነ፥ ሌላም እንደሌለ ዛሬ እወቁ፤ በልባችሁም ያዙት። 40 ለእናንተ ከእናንተም በኋላ ለልጆቻችሁ መልካም ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር
አምላካችሁም ለዘላለም በሚሰጣችሁ ምድር ዕድሜአችሁ ይረዝም ዘንድ እኔ ዛሬ የማዝዛችሁን ሥርዓቱንና ትእዛዙን ጠብቁ። 41 በዚያን ጊዜ ሙሴ አስቀድሞ
ጠላት ያልነበረውን ሰው ሳያውቅ የገደለው ሰው 42 ወደ አንዲቱ ሸሽቶ በሕይወት ይኖር ዘንድ በምሥራቅ በኩል በዮርዳኖስ ማዶ ሦስት ከተሞች መረጠ። 43
ከተሞቹም ለሮቤል ነገድ በምድረ በዳ በደልዳላ ስፍራ ያለ ቦሶር፥ ለጋድም ነገድ በገለዓድ ያለ ራሞት፥ ለምናሴም ነገድ በባሳን ያለ ጎላን ነበሩ። 44 ሙሴ
በእስራኤል ልጆች ፊት ያኖራት ሕግ ይህች ናት። 45 ሙሴና የእስራኤል ልጆች ከግብፅ ከወጡ በኋላ እግዚአብሔር የተናገራቸው የቃል ኪዳን ድንጋጌዎች፥
ሥርዓቶች፥ ሌሎችም ድንጋጌዎች እነዚህ ናቸው፤ 46 በቤተ ፌጎር አንጻር ባለው ሸለቆ፥ በሴዎን ምድር፣ ከዮርዳኖስ በስትምሥራቅ፥ በነበሩበት ጊዜ፥ሙሴና
የእስራኤል ልጆች ከግብፅ በወጡበት ጊዜ ድል ያደረጉአቸው በሐሴቦን ተቀምጦ በነበረው በአራውያን ንጉሥ ነበር። 47 የእርሱንና የባሳንን ንጉሥ የዐግን ምድር
ወሰዱ፤ 48 በምሥራቅ በኩል በዮርዳኖስ ማዶ የነበሩትን የሁለቱ የአሞራያን ነገሥታት እነዚህ ናቸው። ይህም ምድር ከአርኖን በአሮዔር ዳርቻ እስከ ሴዎን ተራራ
እስከ አርሞንዔም ተራራ ድረስ፥ 49 በምሥራቅ በኩል የዮርዳኖስ ወንዝ ሸለቆ ሜዳ በሙሉ ጨምሮ በዮርዳኖስ ማዶ ከፈስጋ ተራራ በታች ያለውን ዓረባ ሁሉ
እስከ ዓረባ ባሕር ድረስ ያለው ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Deuteronomy 4:1

እኔ ላስተምራችሁ ነው
እግዚአብሔር እንዲያደርጉት የሚፈልግባቸውን ሙሴ ለእስራኤል ሕዝብ እየነገራቸው ነው።

እንድታደርጓቸው
“እና ታዘዟቸው”

በቃሉ ላይ አትጨምሩ -- ከእርሱም አትቀንሱ
እግዚአብሔር ሕዝቡ አዲስ ሕግ እንዲያዘጋጁ ወይም አስቀድሞ የሰጣቸውን ቸል እንዲሉ አይፈልግም።

Deuteronomy 4:3

ዐይኖቻችሁ ዐይተዋል
እዚህ ጋ “ዐይኖት” የሚያመለክቱት የእስራኤልን ሕዝብ ነው። አ.ት፡ “ዐይታችኋል” (See: Synecdoche)

በብዔልፌጎር ምክንያት
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “በብዔልፌጎር በሠራችሁት ኃጢአት ምክንያት” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ፌጎር
ይህንን በዘዳግም 3:29 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

አምላካችሁ እግዚአብሔር ከመካከላችሁ አጥፍቷቸዋል
ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “የአንተ” እና “አንተ” ነጠላ ቁጥር ናቸው። (ተውላጠ ስም የሚለውን ተመልከት)

ከእግዚአብሔር ጋር የተጣበቃችሁ እናንተ
ጸሐፊው በእግዚአብሔር መታመንና እርሱን መታዘዝን በአካላዊ ሁኔታ አንድን ሰው ከመያዝ ጋር አመሳስሎ ይናገራል። አ.ት፡ “እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ጠንቃቆች የነበራችሁ እናንተ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 4:5

ተመልከቱ
“ልብ በሉ”

በምድሪቱ መካከል እንደዚሁ ልታደርጉ ይገባል
“በምድሪቱ በምትኖሩበት ጊዜ ልትታዘዟቸው ይገባችኋል”

ጠብቋቸው፣ አድርጓቸውም
በመሠረቱ ሁለቱም ሐረጎች የሚሉት ተመሳሳይ ነገር ሲሆን እንዲታዘዟቸው አጽንዖት ይሰጣል። አ.ት፡ “በጥንቃቄ ታዘዟቸው” (See: Doublet)

ይህ በሕዝቦች ፊት ጥበባችሁና ማስተዋላችሁ ነው
የነገር ስም የሆኑት “ጥበብ” እና “ማስተዋል” እንደ ቅጽል ሐረግ ሊተርጎሙ ይችላሉ፣ የነገር ስም የሆነው “ፊት” ሰዎች የአንድን ነገር ዕሴት እንዴት እንደሚፈርዱ ወይም እንደሚወስኑ ያመለክታል። አ.ት፡ “ጥበበኞችና አስፈላጊ የሆነውን የምትረዱ መሆናችሁን ለሕዝቦች የሚያሳየው ይህ ነው” (See: የነገር ስም እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ይህ ታላቅ ሕዝብ ጥበበኛና አስተዋይ ሕዝብ ነው
“መንግሥት” የሚለው ቃል ለዚያ መንግሥት ሕዝብ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “የዚህ ታላቅ መንግስት ሕዝብ ጥበበኞችና አስተዋዮች ናቸው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 4:7

እንደ እርሱ ያለ ታላቅ ሕዝብ ማን አለ? ዛሬ በዚያ ማን ታላቅ ሕዝብ አለ?
እነዚህ ምላሽ የማይፈልጉ ጥያቄዎች እንደ መግለጫ ሆነው መተርጎም ይችላሉ። አ.ት፡ “እንደ እርሱ ያለ ታላቅ ሕዝብ የለም። ዛሬ ሌላ ታላቅ ሕዝብ የለም”። (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 4:9

ብቻ አስተውሉ -- ራሳችሁን ጠብቁ -- አትርሱ -- ዐይኖቻችሁ -- ልባችሁ -- ሕይወታችሁ -- ለልጆቻችሁና ለልጅ ልጆቻችሁ እንዲታወቁ አድርጉ -- በአምላካችሁ በእግዚአብሔር ፊት ቆማችኋል
ሙሴ እንደ አንድ ሰው አድርጎ ለእስራኤላውያን ይናገራል፣ ስለዚህ “አንተ”፣ “የአንተ” እና “ራሳችሁ” እንዲሁም “አስተውሉ”፣ “ጠብቁ” እና “አስታውቁ” የሚሉት ትዕዛዛት በሙሉ ነጠላ ቁጥር ናቸው። (ተውላጠ ስም እና Forms of You የሚለውን ተመልከት)

ብቻ አስተውሉ፣ ራሳችሁንም በጥንቃቄ ጠብቁ
“በጥንቃቄ አስተውሉ፣ እነዚህን ነገሮች ሁል ጊዜ ለማስታወስም እርግጠኞች ሁኑ”

አትርሱ -- ከልባችሁ አይራቁ
እነዚህ ሐረጎች የሚሉት ተመሳሳይ ነገር ሲሆን የእስራኤል ሕዝብ ያዩትን ማስታወስ እንዳለባቸው አጽንዖት ይሰጣሉ። (See: Parallelism)

ዐይኖቻችሁ ዐይተዋል
እዚህ ጋ “ዐይኖች” ሰውን ይወክላሉ። አ.ት፡ “ዐይታችኋል” (See: Synecdoche)

ሕዝቡን ሰብስብልኝ
“ሕዝቡን በአንድ ላይ ሰብስበህ ወደ እኔ አምጣልኝ”

Deuteronomy 4:11

ወደ ሰማይ ልብ በሚደርስ እሳት
ይህ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። “ልብ” የአንድ ነገር “መካከል” ወይም “ውስጠኛው ክፍል” ማለት ሲሆን “ሰማይ” ደግሞ የሚያመለክተው ጠፈርን ነው። አ.ት፡ “ወደ ጠፈር በሚደርስ እሳት” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በጨለማ፣ ደመና እና ድቅድቅ ጨለማ
እዚህ ጋ “ድቅድቅ ጨለማ” የሚገልጸው ደመናን ነው። አ.ት፡ “ጥቅጥቅ ባለ ጥቁር ደመና” (See: Hendiadys)

ድቅድቅ ጨለማ
ሌላው አማራጭ ትርጉም “ከባድ ደመና” የሚለው ነው።

Deuteronomy 4:13

ዐወጀ
“እግዚአብሔር ዐወጀ”

Deuteronomy 4:15

ስለዚህ ለራሳችሁ እጅግ ተጠንቀቁ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ስለዚህ በምታደርጉት ነገር በጣም መጠንቀቅ ይኖርባችኋል” ወይም 2) “ነፍሳችሁን በጥንቃቄ ጠብቁ”

ራሳችሁን አታርክሱ
“ትክክል ያልሆነውን ነገር አታድርጉ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በመሬት ላይ የሚሳብ
“በመሬት ላይ የሚጎተት”

Deuteronomy 4:19

ዐይኖችህን አንሥተህ -- ስትመለከት -- ስትቀርብ -- አምላክህ እግዚአብሔር
ሙሴ ለእስራኤላውያን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራል፣ ስለዚህ “አንተ” እና “የአንተ” የሚሉት አገባቦችና “ማንሣት”፣ “መመልከት” እና “መቅረብ” ነጠላ ቁጥሮች ናቸው። (See: Forms of You)

ለማምለክ አትቅረብ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ማንም ለማምለክ እንድትፈልግ እንዲያደርግህ አትፍቀድ” ወይም “ታመልክ ዘንድ ለራስህ ፈቃድን አትስጥ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የሰማይ ሰራዊትን ሁሉ
“በጠፈር ላይ ለማየት የምትችላቸውን ነገሮች ሁሉ”። ይህ በሌላ አባባል ፀሐይን፣ ጨረቃንና ከዋክብትን ያመለክታል።

አምላክህ እግዚአብሔር ለሕዝቦች ሁሉ ከሰጣቸው ድርሻ
ይህ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ሙሴ፣ ምግብን እንደመሳሰሉ ትናንሽ ነገሮች እግዚአብሔር ለሕዝብ ወገኖች አከፋፍሎ እንደሚሰጣቸው የሚናገረው ስለ ከዋክብት ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ከብረት ምድጃ አውጥቶ አመጣችሁ
የማብሰያው ብረት እንደሚግል ሙሴ የሚናገረው ስለ ግብፅና እስራኤላውያን እንደ ብረት ሆነው በዚያ ይሠሩ ስለነበረው ከባድ ሥራ ነው። አ.ት፡ “ሰዎች ከባድ ሥራ እንድትሠሩ ከሚያደርጉበት ምድር አውጥቶ አመጣችሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የርስቱ ሕዝብ እንድትሆኑለት
ይህ “የእርሱ ብቻ የሚሆንለት ሕዝብ” ተብሎ ሊተረጎም የሚችል ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 4:21

በእናንተ ምክንያት እግዚአብሔር ተቆጣኝ
ሙሴ በእስራኤል ሕዝብ ላይ በመቆጣቱ ምክያንት እግዚአብሔርን ሳይታዘዝ የቀረበትን ጊዜ ያመለክታል። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ይህንን በዘዳግም 1:37 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

አምላክህ እግዚአብሔር ወደሚሰጥህ
ሙሴ እንደ አንድ ሰው አድርጎ ለእስራኤላውያን ይናገራል፣ ስለዚህ “አንተ” እና “የአንተ” ነጠላ ቁጥሮች ናቸው። (See: Forms of You)

Deuteronomy 4:23

ለራሳችሁ ተጠንቀቁ
“በጥንቃቄ አስተውሉ”

አምላክህ እግዚአብሔር የከለከለውን -- አምላክህ እግዚአብሔር
ሙሴ እንደ አንድ ሰው አድርጎ ለእስራኤላውያን ይናገራል፣ ስለዚህ “አንተ” እና “የአንተ” ነጠላ ቁጥሮች ናቸው። (See: Forms of You)

አምላክህ እግዚአብሔር ቀናተኛና የሚባላ እሳት ነው
ሙሴ፣ እግዚአብሔር ሲቆጣ የሚያደርጋቸውን ነገሮችን እሳት ከሚያቃጥልበት መንገድ ጋር ያነጻጽራል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ሌሎች አማልክትን እንድታመልክ ስለማይፈልግ እሳት እንደሚያደርገው አምላክህ እግዚአብሔር በብርቱ ይቀጣሃል፣ ያጠፋሃልም”።(ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 4:25

በወለድህ -- አምላክህ እግዚአብሔር
እዚህ ጋ “አንተ” እና “የአንተ” የሚሉት ቃላት ነጠላ ቁጥሮች ናቸው።

መውለድ
የአንዱ አባት ወይም አያት መሆን

ራሳችሁን ብታረክሱ
“ትክክል ያልሆነውን ብታደርጉ”። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 4:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

እርሱን ታስቆጡት ዘንድ በአምላካችሁ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነውን ብታደርጉ
ይህ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “እርሱ ክፉ ያለውን በማድረግ አምላካችሁን እግዚአብሔርን ታስቆጡታላችሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ሰማይና ምድር ምስክር እንዲሆኑ እጠራቸዋለሁ
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች 1) ሙሴ ለሚናገረው በሰማይ የሚኖሩትን ሁሉና ምድርን ምስክር አድርጎ ይጠራል ወይም 2) ሙሴ፣ ሰዎችን የሆኑ ይመስል ሰማይና ምድር እርሱ ለሚናገረው ምስክር እንዲሆኑ ይጠራቸዋል። (See: (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት and Personification)

ረጅም ዘመን አትቀመጡበትም
ረጅም ቀናት የረጅም ዕድሜ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ረጅም ዘመን መኖር አትችሉም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ነገር ግን ፈጽሞ ትጠፋላችሁ
በ4:27 ላይ እንደተመለከተው እያንዳንዱ እስራኤላዊ አይገደልም። እዚህ ጋ “ፈጽሞ መጥፋት” በጥቅሉ ብዙ እስራኤላውያን እንደሚሞቱ አጽንዖት መስጫ ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ነገር ግን እግዚአብሔር ብዙዎቻችሁን ያጠፋችኋል” (ግነት እና ጥቅል አስተያየት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 4:27

እግዚአብሔር በሕዝቦች መካከል ይበትናችኋል
ሕዝቡ ዘር የሆነ ይመስል እግዚአብሔር እርሻ ላይ እንደሚበትናቸው ሙሴ ይናገራል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ወደተለያዩ አገሮች ይላካችኋል፣ በዚያ እንድትኖሩም ያስገድዳችኋል”።(ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አርቆ ይሰዳችኋል
“ይልካችኋል” ወይም “ጠላቶቻችሁ እንዲወስዷችሁ ያደርጋል”

የሰው የእጅ ሥራ፣ እንጨትና ድንጋይ
እዚህ ጋ “የሰው እጅ” የሚያመለክተው ሰውን ራሱን ሲሆን “ሥራ -- እንጨትና ድንጋይ” ደግሞ የቀረጿቸውን ጣዖታት ያመለክታሉ። አ.ት፡ “ሰዎች የሠሯቸው የእንጨትና የድንጋይ ጣዖታት” (See: Synecdoche)

Deuteronomy 4:29

ነገር ግን ከዚያ
“ነገር ግን በሌሎች አገሮች በምትኖሩበት ጊዜ”

ትፈልጉታላችሁ
እዚህ ጋ “እናንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)

እርሱን በምትፈልጉበት ጊዜ
“በእርግጥ እርሱን ለመፈለግ በምትሞክሩበት ጊዜ” ወይም “እርሱን በእርግጥ ለማወቅ በምትሞክሩበት ጊዜ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በፍጹም ልባችሁና በፍጹም ነፍሳችሁ
እዚህ ጋ “ልብ” እና “ነፍስ” የሰውን ውስጠኛ ማንነት የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። እነዚህ ሁለት ሐረጎች በአንድነት የተነገሩት “ሙሉ በሙሉ” ወይም “በቅንነት” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና Doublet የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 4:30

ይመጣብሃል
“ይደርስብሃል”

በእነዚያ በኋለኞቹ ቀናት
“ከዚያ በኋላ” ወይም “ከዚያም”

ድምፁን ትሰማለህ
እዚህ ጋ “መስማት” ዘይቤአዊ አነጋገር ሲሆን ትሩሙ ማድመጥና መታዘዝ ነው። በተጨማሪም፣ “ድምፁን” የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ሆኖ እርሱ በሚናገረው ላይ አጽንዖት ይሰጣል። አ.ት፡ “እርሱ የሚላችሁን ታዘዙት” (የአነጋገር ዘይቤ እና Synecdoche የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 4:32

እንደ እናንተ የእግዚአብሔር ድምፅ ከእሳት መካከል ሲናገር የሰማና በሕይወት የኖረ ሕዝብ አለ?
እዚህ ጋ፣ ባለፈው ጊዜ እግዚአብሔር እንዴት አስገራሚ በሆነ መንገድ እንደተናገራቸው የእስራኤል ሕዝብ እንዲያስታውሱ ተደርገዋል። ይህ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ከእናንተ በስተቀር እግዚአብሔር ከእሳት መካከል ተናግሮት በሕይወት የኖረ ሌላ ሕዝብ የለም”።(ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

የእግዚአብሔር ድምፅ ሲናገር የሰማ
እዚህ ጋ እግዚአብሔር በድምፁ ተወክሏል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ሲናገር ድምፁን ሰምታችኋል” (See: Synecdoche)

Deuteronomy 4:34

በጽኑ እጅና በተዘረጋች ክንድ
እዚህ ጋ “ጽኑ እጅ” እና “የተዘረጋች ክንድ” የእግዚአብሔርን ኃይል የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ጽኑ ኃይሉን በማሳየት” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በዐይኖቻችሁ ፊት
እዚህ ጋ “ዐይኖች” የሚያመለክቱት የሰውን ሁለንተናውን ነው። አ.ት፡ “በፊት ለፊታችሁ” (See: Synecdoche)

Deuteronomy 4:35

እነዚህ ነገሮች ለእናንተ ታይተዋል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች አሳይቶአችኋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እንድትሰሙ አድርጎችኋል -- እንድታዩ አድርጎችኋል
“እንደሰማችሁ አረጋግጧል . . . እንዳያችሁ አረጋግጧል”

አድርጎችኋል -- ሰምታችኋል
ሙሴ ከብዙ ዓመታት በፊት በሲና ተራራ የተናገራቸውን እነዚያኑ ሕዝቦች ይናገር ይመስል ለሕዝቡ ይናገራል። በመሠረቱ በሲና ተራራ የነበሩት ሰዎች እነዚህን ቃላት ለሚናገራቸው ሰዎች አባቶቻቸው ነበሩ። አ.ት፡ “አባቶቻችሁን … አድርጓል፣ አባቶቻችሁ ሰምተዋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 4:37

አባቶቻችሁ
ይህ የሚያመለክተው አብርሃምን፣ ይስሐቅን፣ ያዕቆብንና የያዕቆብን ወንዶች ልጆች ነው።

በሀልዎቱ፣ በታላቅ ኃይሉ
“ከሀልዎቱ በሚመጣ በታላቅ ኃይሉ” ወይም “በታላቅ ኃይሉ”

Deuteronomy 4:39

በልብህ አኑረው
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “አስታውሰው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በላይ በሰማይና በታች በምድር
“በሰማይ” እና “በምድር” የሚሉት ሁለት ሐረጎች ሁለት ጽንፎችን የሚያሳዩ ሲሆኑ ትርጉማቸው “በሁሉ ስፍራ” ማለት ነው። አ.ት፡ “በሁሉ ነገር ላይ” (See: Merism)

ዕድሜህ እንዲረዝም
ረጅም ቀናት ለረጅም ሕይወት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 4:26 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። አ.ት፡ “ረጅም ዕድሜ ለመኖር እንድትችል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 4:41

ቦሶር -- ራሞት -- ጎላን
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 4:44

ሕጉ ይህ ነው
ይህ በቀጣዮቹ ምዕራፎች ሙሴ የሚሰጣቸውን ሕግጋት ያመለክታል።

ቤተ ፈጎር
ይህ በሞዓብ ውስጥ ፈስጋ ተራራ አጠገብ የሚገኝ ከተማ ስም ነው። ይህንን በዘዳግም 3:29 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ሴዎን -- አሞራውያን -- ሐሴቦን
“ንጉሥ ሴዎን … አሞራውያን ሕዝቦች … የሐሴቦን ከተማ”። እነዚህን ስሞች በዘዳግም 1:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

Deuteronomy 4:47

ምድሩን
የንጉሥ ሴዎንን ምድር

የባሳን ንጉሥ ዐግ
ይህንን በዘዳግም 1:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ከዮርዳኖስ ማዶ በስተምስራቅ -- ከዮርዳኖስ በስተምስራቅ
ይህ ከእስራኤል በስተምስራቅ፣ ከዮርዳኖስ ወንዝ ባሻገር ያለውን ምድር ያመለክታል። ሙሴ ይህንን በሚናገርበት ጊዜ ከዮርዳኖስ በስተምስራቅ ነበር። አ.ት፡ “ከዮርዳኖስ ወንዝ አቅጣጫ በስተምስራቅ … ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምስራቅ በኩል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አሮዔር
ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። ይህንን በዘዳግም 2:36 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የአርኖን ሸለቆ
ይህ የአንድ ቦታ ስም ነው። ይህንን በዘዳግም 2:24 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሴዎን ተራራ -- የአርሞንዔም ተራራ
እነዚህ የተራራ ስሞች ናቸው። እነዚህን ስሞች በዘዳግም 3:8-9 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

የዓረባ ባህር -- ፈስጋ ተራራ
እነዚህን ስሞች በዘዳግም 3:17 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 5

1 ሙሴም የእስራኤል ልጆችን ሁሉ ጠርቶ እንዲህ አላቸው፦እስራኤል ሆይ፥ እንድትማሩአቸውና እንድትጠብቁአቸው ዛሬ በጆሮአችሁ የምናገራውን ሥርዓቶችንና ድንጋጌዎችን ስሙ። **2** እግዚአብሔር አምላካችን ከእኛ ጋር በኮሬብ ቃል ኪዳን አድርጎአል። **3** እግዚአብሔር ከአባቶቻችን ቃል ኪዳን አላደረገም ዛሬ በሕይወት ካለነው ከእኛ ጋር ነው። **4** እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ፊት ለፊት በተራራው ላይ በእሳት መካከል ተናገረ፥ **5** (በዚያን ጊዜ ከእሳቱም የተነሣ ፈርታችሁ ወደ ተራራው ባልቀረባችሁ ጊዜ ቃሉን ልገልጥላችሁ በእግዚአብሔርና በእናንተ መካከል ቆሜ ነበር) ። እግዚአብሔርም እንዲህ አለ፦ **6** ከባርነት ቤት፥ ከግብፅ ምድር ያወጣኋችሁ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ። **7** ከእኔ በቀር በፊቴ ሌሎች አማልክት አይኑራችሁ። **8** በላይ በሰማይ፥ወይም በታች በምድር፣ወይም ከምድርም በታች በውኃ፥ ማናቸውንም ምሳሌ የተቀረጸውን ምስል ለራሳችሁ አታድርጉ። **9** እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቀናተኛ ስለሆንኩ ለአማልክት አትስገዱላቸው፥ ወይም እነርሱን አታገልግሉአችሁ። በሚጠሉኝ ላይ እስከ ሦስተኛና አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ ቅጣትን ያመጣል፥ **10** ለቃል ኪዳኔም ታማኝነት ለሚያሳዩኝና ለሚወዱኝ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቀናተኛ አምላክ ነኝ። **11** የአምላካችሁን ስም በከንቱ አትጠቀሙ፥ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠቀመውን ከበደል አያነጻውምና። **12** እግዚአብሔር አምላካችሁ እንዳዘዛችሁ የሰንበትን ቀን ትቀድሱት ዘንድ ጠብቁ። **13** ስድስት ቀን ሥሩ ተግባራችሁንም ሁሉ አድርጉ፤ **14** ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር ለአምላካችሁ ሰንበት ነው። እናንተ እንደምታርፉ ሁሉ አገልጋያችሁና የቤት ሠራተኛችሁ ያርፉ ዘንድ እናንተ ወንድ ልጆቻችሁ፥ ሴት ልጆቻችሁም ፥ አገልጋዮቻችሁ፥ የቤት ሠራተኞቻችሁም በፊታችሁ፥ አህዮቻችሁም፥ ከብቶቻችሁም፥ ሁሉ በደጆቻችሁ ውስጥ ያለው እንግዳም ጭምር በሰንበት ምንም ሥራ አትሥሩ። **15** እናንተም በግብፅ በሪያ እንደ ነበራችሁ አስቡ፥ እብዚአብሔር አምላካችሁ በጸናች እጅና በተዘረጋች ክንድ ከዚያ አውጣችሁ። ስለዚህ እግዚአብሔር አምላካችሁ የሰንበትን ቀን ትጠብቁ ዘንድ አዘዛችሁ። **16** እግዚአብሔር አምላካችሁ እንዳዘዛችሁ ፤ እግዚአብሔር አምላካችሁ በሰጣችሁ ምድር ላይ ዕድሜአችሁ እንዲረዝምና መልካም እንዲሆንላችሁ አባታቸውንና እናታቸውን አክብሩ። **17** አትግደሉ። **18** አታመንዝሩ። **19** አትስረቁ። **20** በባልንጀራችሁ ላይ በሐሰት አትመስክሩ። **21** የባልንጀራችሁን ሚስት አትመኙ፤ የባልጀራችሁን ቤት፥ እርሻውንም፥ አገልጋዩንም፥ የባልጀራችሁንም በሬውንም፥ አህያውንም፥ ከባልጀራችሁ ገንዘብ ሁሉ ማናቸውንም አትመኙ። **22** እግዚአብሔር በተራራው ላይ በእሳትና በደመና በጨለማም ውስጥ ሆኖ በታላቅ ድምፅ፥ እነዚህን ቃሎች ለጉባኤአችሁ ሁሉ ከተናገረው ምንም አልጨመረም። በሁለቱም የድንጋይ ጽላቶቶች ላይ ጻፋቸው ለእኔም ሰጠኝ። **23** ተራራው በእሳት ሲነድድ ከጨለማው ውስጥ ድምፁን በሰማችሁ ጊዜ እናንተ የነገዶቻችሁ አለቆች ሽማግሌዎቻችሁም ወደ እኔ ቀረባችሁ። **24** አላችሁም፦ እነሆ አምላካችን እግዚአብሔር ክብሩንና ታላቅነቱን አሳይቶናል፥ ከእሳትም ውስጥ ድምፁን ሰምተናል፤ እግዚአብሔርም ከሰዎች ጋር ሲነጋገር ሰዎችም በሕይወት ሲኖር ዛሬ አይተናል። **25** አሁን እንግዲህ ይህች ታላቂቱ እሳት ታቃጥለናለችና ለምን እንሞታለን? እኛ የእግዚአብሔርን የአምላካችንን ድምፅ ደግሞ ብንሰማ እንሞታለን። **26** ከሥጋ ለባሽ ሁሉ እኛ እንደ ሰማን በእሳት ውስጥ ሆኖ ሲናገር የሕያው አምላክን ድምፅ ሰምቶ በሕይወቱ የኖረ ማን ንው? **27** አንተ ቅረብ፤ እግዚአብሔር አምላካችን የሚለውን ሁሉ ስማ፤ እግዚአብሔር አምላካችንም ለአንተ የሚናገረውን ሁሉ ለእኛ ንገረን፤ እኛም ሰምተን እናደርገዋለን አላችሁ። **28** በተናገራችሁኝም ጊዜ እግዚአብሔር የእናንተን ቃል ሰማ። እግዚአብሔርም አለኝ፦ይህ ሕዝብ የተናገሩህን ቃል ሰምቼአለሁ፤ የተናገሩትም ሁሉ መልካም ነው። **29** ለእነርሱ ለዘላለምም ለልጆቻቸው መልካም ይሆንላቸው ዘንድ፥ እንዲፈሩኝ፥ ሁልጊዜም ትእዘዜን ሁሉ እንዲጠብቁ፥ እንዲህ ያለ ልብ ምነው በነበራቸው! **30** ሄደህ እንዲህ በላቸው፦ ወደ ድንኳናችሁ ተመለሱ። **31** አንተ ግን በዚህ በእኔ ዘንድ ቁሙ፥ ርስት አድርጌ በምሰጣቸውም ምድር ላይ ያደርጉአት ዘንድ የምታስተምራቸውን ትእዛዜንና ሥርዓቴን፥ ድንጋጌንም ሁሉ እነግርሃለሁ። **32** ስለዚህ እግዚአብሔር አምላካችሁ እንዳዘዛችሁ ታደርጉ ዘንድ ጠብቁ፥ ከእርሱም ወደ ቀኝም ወደ ግራም ፈቀቅ አትበሉ። **33** በሕይወት እንድትኖሩ መልካምም እንዲሆንላችሁ፥ በምትወርሱአትም ምድር ዕድሜአችሁ እንዲረዝም፥ እግዚአብሔር አምላካችሁ ባዘዛችሁ መንገድ ሁሉ ሄዱ።

Deuteronomy 5:1

እስራኤልን ሁሉ ጠራ
እዚህ ጋ “ሁሉ” የሚለው ቃል ግነት ነው። ሙሴ በእስራኤል ያሉ ሁሉ ቃሉን እንዲሰሙና እንዲታዘዙ ፈልጓል፣ ይሁን እንጂ ሁሉ ይሰማው ዘንድ ምናልባት ድምፁ በጣም ከፍ ያለ አልነበረም። (ግነት እና ጥቅል አስተያየት የሚለውን ተመልከት)

ዛሬ በጆሮአችሁ የምናገረውን
እዚህ ጋ “ጆሮ” የሚያመለክተው የሰውን ሁለንተናውን ነው። ይህ ዘይቤአዊ አነጋገር አጽንዖት የሚሰጠው ሰዎቹ ኃጢአትን እንዳያደርጉ ሙሴ የነገራቸውን እንደሚያውቁና ኃጢአት መሥራታቸውን አለማወቃቸውን እንዳይናገሩ ነው። አ.ት፡ “ዛሬ የምነግራችሁን” (Synecdoche እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር ከአባቶቻችን ጋር ይህንን ቃል ኪዳን አላደረገም
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች 1) እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ያደረገው ከኋለኛው የእስራኤል ትውልድ ጋር ደግሞ እንጂ በኮሬብ ከነበሩት ጋር ብቻ አይደለም ወይም 2) እግዚአብሔር በሩቅ ከነበሩት አባቶቻቸው አብርሃምን፣ ይስሐቅንና ያዕቆብን ከመሳሰሉት ጋር ይህንን ቃል ኪዳን አላደረገም፤ ይልቁንም ይህ ቃል ኪዳን የጀመረው በኮሬብ ከነበሩት እስራኤላውያን ጋር ነው።

Deuteronomy 5:4

ፊት ለፊት
ለእርስ በርሳቸው ቅርበት ያላቸው ሁለት ሰዎች ሲነጋገሩ እርስ በርስ እንደሚተያዩ ለመግለጽ የቋንቋህን የአነጋገር ዘይቤ ተጠቀም። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 5:7

በፊቴ ሌሎች አማልክት አይኑሩህ
“እኔን እንጂ ሌሎች አማልክትን ማምለክ የለብህም”

ከምድር በታች ያለውን ወይም ከውሃ በታች ያለውን
ይህ በይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አ.ት፡ “ከእግሮቻችሁ በታች ባለው ምድር ላይ ያለ ወይም ከምድር በታች በውሃ ውስጥ ያለ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

Deuteronomy 5:9

አትስገዱላቸው ወይም አታገልግሏቸው
“የተቀረጹትን ምስሎች አታምልኩ ወይም እነርሱ የሚያዟችሁን አታድርጉ”

አታድርግ
“መቼም ቢሆን”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እኔ ቀናተኛ አምላክ ነኝ
“እኔን ብቻ እንድታመልኩኝ እፈልጋለሁ”

ለሚወዱኝ የቃል ኪዳን ታማኝነቴን ለሺዎች የማሳይ
“ታማኝነት” የሚለው የነገር ስም “በታማኝነት” ወይም “ታማኝ” ተብሎ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የሚወዱኝን ሺዎችን በታማኝነት እወዳቸዋለሁ” ወይም “ከሚወዱኝ ከሺዎች ጋር ለቃል ኪዳን ታማኝ እሆናለሁ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ለሚወዱኝ ለሺዎች
አንዳንድ ትርጓሜዎች “ለሚወዱኝ ለአንድ ሺህ ትውልዶች” በሚል ይነበባሉ። “ሺዎች” የሚለው ቃል ለመቁጠር የሚበዛውን ቁጥር ለማመልከት የሚውል ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ለሚወዱኝ ለእነርሱ እስከ ዘላለም” (Assumed Knowledge and Implicit Information፣ ፈሊጣዊ አነጋገር እና ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 5:11

የእግዚአብሔርን ስም አታንሣ
“በእግዚአብሔር ስም አትጠቀም”

አታድርግ
ይህንን በዘዳግም 5:9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

በከንቱ
“በግድየለሽነት” ወይም “ተገቢውን አክብሮት ባለመስጠት” ወይም “ለተሳሳቱ ዓላማዎች”

እግዚአብሔር ከበደል አያነጻውም
ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር በደለኛ አድርጎ ይቆጥረዋል” ወይም “እግዚአብሔር ይቀጣዋል” (ድርብ አሉታዎች የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 5:12

ቅዱስ አድርገህ እንድትጠብቀው
“ለእግዚአብሔር እንድትለየው”

ሥራህን ሁሉ ሥራ
“የተለመደውን ሥራህን ሁሉ ሥራ”

ሰባተኛው ቀን
“ቀን 7”። እዚህ ጋ “ሰባተኛው” ለሰባት ተራ ቁጥር ነው። (See: Ordinal Numbers)

በእርሱ አትሥራበት
“በዚያን ቀን ምንም አትሥራ”

በደጆችህ ውስጥ
እዚህ ጋ “ደጆች” ከተማን ራሱን የሚያመላክት ነው። አ.ት፡ “በማኅበረሰብህ መካከል” ወይም “በከተማህ ውስጥ” ወይም “ከአንተ ጋር የሚኖሩ” (See: Synecdoche)

Deuteronomy 5:15

አስታውስ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ማስታወስ አለብህ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በጽኑ እጅና በተዘረጋች ክንድ
እዚህ ጋ “ጽኑ እጅ” እና “የተዘረጋች ክንድ” የእግዚአብሔርን ኃይል የሚያሳይ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 4:34 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። አ.ት፡ “ጽኑ ኃይሉን በማሳየት” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 5:17

አታድርግ
ይህንን በዘዳግም 5:9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

አታመንዝር
“ከሚስትህ በቀር ከሌላ ከማንም ጋር አትተኛ”

በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር
“ስለ ሌላው ሰው ውሸትን አትናገር”

Deuteronomy 5:21

አታድርግ
ይህንን በዘዳግም 5:9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Deuteronomy 5:23

ድምፁን ሰምታችኋል
“ድምፅ” የሚለው ቃል የቃልን ድምፅ ወይም ተናጋሪውን ሰው የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “የቃሉን ድምፅ ሰምታችኋል” ወይም “እግዚአብሔር ሲናገር ሰምታችኋል” (See: Synecdoche)

Deuteronomy 5:25

ታዲያ ለምን እንሞታለን?
እግዚአብሔር ከተናገራቸው እንደሚሞቱ በማሰብ ፈርተው ነበር። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እንሞታለን ብለን ፈርተናል” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ያደረገ -- ከእኛ በቀር ማን አለ?
ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “… ያደረገ ከእኛ በቀር ሌላ አንድም ሕዝብ የለም”። (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ሥጋ ሁሉ
ይህ ሰዎችን ሁሉ ወይም ሕያዋን ፍጥረታትን ይወክላል። አ.ት፡ “ሰዎች ሁሉ” ወይም “ሕያዋን ፍጥረታት በሙሉ” (See: Synecdoche)

Deuteronomy 5:28

በነገራችሁኝ ጊዜ
እዚህ ጋ “እኔን” የሚያመለክተው ሙሴን ነው።

ምነው በኖራቸው
የአንተ ቋንቋ ለአንድ ነገር የሞኖርን ብርቱ ፍላጎት የሚገልጽ የአነጋገር ዘይቤ ካለው እዚህ ጋ ልትጠቀምበት ያስፈልግህ ይሆናል። አ.ት፡ “ቢኖሩ በጣም ደስ ይለኝ ነበር” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 5:31

ታስተምራቸዋለሁ
“የእስራኤልን ሕዝብ ታስተምራለህ”

Deuteronomy 5:32

ጠብቁ
ሙሴ ለእስራኤል ሕዝብ ትዕዛዝ እየሰጠ ነው።

ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበሉ
ይህ እግዚአብሔርን የማይታዘዘውን ሰው ከትክክለኛው መንገድ ከሚወጣው ሰው ጋር ያነጻጽረዋል። አ.ት፡ “በየትኛውም መንገድ ለእርሱ የማትታዘዝ መሆን የለብህም” ወይም “የሚላችሁን ሁሉ ማድረግ አለባችሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ዕድሜአችሁ እንዲረዝም
ረጅም ቀናት የረጅም ዕድሜ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ይህንን በዘዳግም 4:40 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ረጅም ዕድሜ መኖር እንድትችሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 6

1 ከዮርዳኖስ ማዶ በምትውርሱአት ምድር የምትጠብቃችሁ እግዚአብሔር አምላካችሁ እንዳስተምራችሁ ያዘዘኝ እነዚህ ትእዛዘት፥ ሥርዓትና ድንጋጌዎች እነዚህ ናቸው፤ **2** እኔ የማዛችሁን ሥርዓትንና ትእዛዘትን በመጠበቅ እናንተ፥ ልጆቻችሁ፥ የልጅ ልጆቻችሁም በዘመናችሁ ዕድሜአችሁ እንዲረዝም እግዚአብሔር አምላካችሁን አክብሩ። **3** እንግዲህ እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ መልካምም እንዲሆንላችሁ የአባቶቻችሁም አምላክ እግዚአብሔር ተስፋ እንደሰጣችሁ ወተትና ማር በምታፈስሰው ምድር እጅግ እንድትበዙ ነው። **4** እስራኤል ሆይ፥ ስማ፥ እግዚአብሔር አምላካችን አንድ እግዚአብሔር ነው። **5** እናንተም እግዚአብሔር አምላካችሁን በፍጹም ልባችሁ፥ በፍጹም ነፍሳችሁ፥ በፍጹም ኃይላችሁ ውደዱ። **6** እኔም ዛሬ እናንተን የማዝዘው ቃል በልባችሁ ይሁን፤ **7** በቤታችሁም ስትቀመጡ፥ በመንገድም ስትሄዱ፥ ስትተኙም፥ ስትነሡም፥ ልጆቻችሁን አስተምሩአቸው። **8** በእጃችሁም ምልክት አድርጋችሁ እሰሩት፥ በዓይኖቻችሁም መካከል እንደክታብ ይሁንላችሁ። **9** በቤታችሁም መቃኖች በደጃፋችሁም በሮች ላይ ጻፉት። **10** እግዚአብሔር አምላካችሁ ለእናንተ ሊሰጣችሁ ለአባቶቻችሁ ለአብርሃም፥ ለይስሐቅና ለያዕቆብ ወደ ማለላቸው ምድር ባገባችሁ ጊዜ፥ ያልሠራሃችኋቸውን ታላላቅና መልካም ከተሞች፥ **11** በመልካም ነገሮች ሁሉ የተሞሉ ቤቶች ያልማስሃችኋቸውን የተማሱ ጉድጓዶች፥ ያልተከልሃችኋቸውን ወይንና ወይራ በሰጣችሁ ጊዜ፥ **12** በበላችሁና በጠገባችሁ ጊዜ፥ በዚያን ጊዜ ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣችሁን እግዚአብሔርን እንዳትረሱ ተጠንቀቁ። **13** አምላካችሁን እግዚአብሔርን አክብሩ፤ እርሱንም አምልኩት በስሙም ማሉ። **14** በዙሪያችሁ ያሉትን አሕዛብ የሚያመልኩአቸውን ሌሎችን አማልክት ፍለጋ እንዳትሄዱ፥ እንዳከተከተሉ፤ **15** ምክንያቱም በመካከላችሁ ያለው እግዚአብሔር አምላካችሁ ቀናተኛ አምላክ ስለሆነ፥ ቁጣው እንዳይነድባችሁና ከምድር ገጽ እንዳያጠፋችሁ ተጠንቀቁ። **16** በማሳህ እንደተፈታተናችሁት እግዚአብሔር አምላካችሁን አትፈታተኑት። **17** ያዘዝኋችሁን የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ትእዛዘትንና ሥርዓቱን አጥብቃችሁ ጠይቁ። **18** መልካምም ይሆንላችሁ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት ቅኑንና መልካሙን ነገር አድርጉ፤ እግዚአብሔርም ለአባቶቻችሁ ወደ ማለላቸው ወደ መልካሚቱ ምድር ገብታችሁ እንድትወርሱ፥ **19** እግዚአብሔርም እንደተናገረ ጠላቶቻችሁን ሁሉ ከፊታችሁ ያወጣላችሁ ዘንድ። **20** በኋለኛው ዘመንም ልጆቻችሁ እንዲህ ብለው በጠየቃችሁ ጊዜ፦ እግዚአብሔር አምላካችን ያዘዛችሁ የቃል ኪዳን ድንጋጌዎች፥ ሥርዓትና ሌሎችስ ድንጋጌዎች እነዚህ ምንድን ናቸው? **21** እናንተም ለልጆቻችሁ እንዲህ በሉአቸው፦ በግብፅ አገር የንጉሥ ፈርዖን አገልጋዮች ነበርን፥ እግዚአብሔርም በጽኑ እጅ ከግብፅ አወጣን፥ **22** እግዚብብሔርም በግብፅና በፈርዖን፥ በቤቱም ሁሉ ላይ በዓይናችን ፊት ታላቅና ክፉ፥ ምልክትና ተአምራትን አደረገ። **23** ለአባቶቻችን ወደ ማለላቸው ምድር አምጥቶን እርስዋን ይሰጠን ዘንድ ከዚያ አወጣን። **24** እንደ ዛሬም በሕይወት እንዲያኖረን ሁልጊዜም መልካም እንዲሆንልን እግዚአብሔር አምላካችንን እንፈራ ዘንድ ይህችንም ሥርዓት ሁሉ እናደርግ ዘንድ እግዚአብሔር አዘዘን። **25** እርሱም እንዳዘዘን በእግዚአብሔር በአምላካችን ፊት እንፈጽመው ዘንድ ይህን ትእዛዝ ሁሉ ብንጠብቅ ለእኛ ጽድቅ ይሆንልናል።

Deuteronomy 6:1

ትጠብቁት ዘንድ -- ለመጠበቅ
“ትታዘዙ ዘንድ … ለመታዘዝ”

ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ
“ከዮርዳኖስ ወንዝ ወዲያ ማዶ ሄዳችሁ”

ዕድሜአችሁ እንዲረዝም
ረጅም ቀናት የረጅም ዕድሜ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ይህ በዘዳግም 4:26 እንዳለው በተመሳሳይ “ረጅም ዘመን እንድትኖሩ” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ዕድሜአችሁን እንዳረዝመው” ወይም “ረጅም ዕድሜ እንድትኖሩ አደርጋችሁ ዘንድ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 6:3

እነርሱን ስማ
እዚህ ጋ “ስማ” ማለት ታዘዝ ሲሆን “እነርሱን” የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ነው። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት፣ ሕግጋትና ሥርዓት ስማ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information

ጠብቃቸው
“ታዘዛቸው”

ወተትና ማር የምታፈሰውን ምድር
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “የተትረፈረፈ ወተትና ማር የሚፈስባት ምድር” ወይም “ከብት ለማርባትና ለእርሻ ምርጥ የሆነ ምድር” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 6:4

አምላካችን እግዚአብሔር አንድ ነው
“አምላካችን እግዚአብሔር አንድና ብቸኛ አምላክ ነው”

በሙሉ ልብህ፣ በሙሉ ነፍስህና በሙሉ ኃይልህ
እዚህ ጋ “ልብ” እና “ነፍስ” የአንድን ሰው ውስጣዊ ማንነት የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። እነዚህ ሦስቱ ሐረጎች በአንድነት ጥቅም ላይ የዋሉት “በፍጹም” ወይም “በቅንነት” ለማለት ነው። በዘዳግም 4:29 ላይ “በሙሉ ልብህ፣ በሙሉ ነፍስህ” የሚለውን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና Doublet የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 6:6

እኔ የማዝህን
ሙሴ ለእስራኤል ሕዝብ የሚናገረው የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ነው።

በልብህ ይኑር
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ሁል ጊዜ ማስታወስ አለብህ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በትጋት አስተምረው -- ተናገረው
“በትጋት እንድታስተምረው አዝሃለሁ … እንድትናገረው አዝሃለሁ”። አንባቢው እነዚህን እንደ ትዕዛዝ ሊረዳቸው ይገባዋል።

Deuteronomy 6:8

እሰራቸው
ይህ “እነዚህን ቃላት በብራና ላይ ጻፋቸው፣ ብራናውን በትንሽ ኪስ ውስጥ አድርገውና ኪሱን እሰረው” ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር በተራው “በአካል እዚያ ያሉ ያህል እነዚህን ቃሎች ታዘዛቸው”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለሚለው ዘይቤአዊ አነጋገር ሊሆን ይችላል። አ.ት፡ “እነዚህን ቃላት እሰራቸው”። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእጅህ ላይ እንደ ምልክት
“ሕጌን እንድታስታውስ እንደሚያደርግህ አንዳች ነገር”

እንደ ግንባር ጌጥ ያገለግሉሃል
ይህ “እነዚህን ቃላት በብራና ላይ ጻፋቸው፣ ብራናውን በትንሽ ኪስ ውስጥ አድርገውና በዚያ እንዲቀመጥ ትንሹን ኪስ በግምባርህ ላይ እሰረው” ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር በተራው “በአካል እዚያ ያሉ ያህል እነዚህን ቃሎች ታዘዛቸው” ለሚለው ዘይቤአዊ አነጋገር ሊሆን ይችላል። አ.ት፡ “ቃሎቼ እንደ ግምባር ጌጥ ያገለግላሉ”። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ክታብ
አንድ ሰው በግምባሩ ላይ የሚያደርጋቸው ጌጣ ጌጦች

ጻፍ
ይህ ትዕዛዝ ነው።

Deuteronomy 6:10

አንተ ያልሠራኻቸውን ሰፋፊና በጣም ያማሩ ከተሞች
የከነዓንን ሕዝቦች በሚያሸንፉበት ጊዜ እነዚህ ከተሞች በሙሉ የእስራኤል ሕዝብ ይሆናሉ።

ከባርነት ቤት ያወጣህ
እዚህ ጋ “የባርነት ቤት” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር የሚያመለክተው እስራኤላውያን ባሪያዎች የነበሩበትን ስፍራ፣ ግብፅን ነው። አ.ት፡ “ባሪያ ሆነህ ከኖርክበት ስፍራ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 6:13

አምላክህን እግዚአብሔርን ታከብራለህ፤ እርሱንም ታመልካለህ፣ በእርሱም ስም ትምላለህ
“ማክበር የሚኖርብህ አምላክህን እግዚአብሔርን እንጂ ሌላውን አይደለም፤ ማምለክ ያለብህ እርሱን ብቻ ነው፣ መማል የሚኖርብህም በእርሱ ስምና በእርሱ ስም ብቻ ነው”። እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ሌሎች አማልክቶችን እንዳያመልኩ ወይም እንዳያገለግሉ ስለመናገሩ ምናልባት የአንተ ቋንቋ አጽንዖት የሚሰጥበት ሌላ መንገድ ይኖር ይሆናል።

በስሙ ትምላለህ
በእግዚአብሔር ስም መማል ማለት እግዚአብሔርን የመሓላው መሠረት ወይም ኃይል ማድረግ ማለት ነው። “በስሙ” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ራሱን ነው። አ.ት፡ “ትምላለህ፣ እግዚአብሔር እንዲያጸናውም ትጠይቃለህ” ወይም “በምትምልበት ጊዜ ስሙን ትጠራለህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በመካከልህ
“በመካከልህ የሚኖር”

የአምላክህ የእግዚአብሔር ቁጣ በአንተ ላይ ይነዳል
ሙሴ የእግዚአብሔርን ቁጣ አንድን ነገር ለማቃጠል እሳት ከሚለኩስ ሰው ጋር ያነጻጽረዋል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ቁጣን መለኮስ በጣም የመቆጣት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “አምላክህ እግዚአብሔር ቁጣውን ያነዳል” ወይም “አምላክህ እግዚአብሔር በጣም ይቆጣል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከ -- ያጠፋሃል
“ምንህም እስከማይተርፍ ድረስ ያጠፋሃል”

Deuteronomy 6:16

እግዚአብሔርን አትፈታተነው
እዚህ ጋ “መፈተን” ማለት እግዚአብሔርን መገዳደርና ትክክለኛ መሆኑን እንዲያረጋግጥ ማስገደድ ማለት ነው።

ማሳህ
ይህ በምድረ በዳው ውስጥ ያለ የቦታ ስም ነው። ተርጓሚው ምናልባት፣ “‘ማሳህ’ የሚለው ስም ትርጉም ‘መፈተን’ ማለት ነው” የሚል የግርጌ ማስታወሻ መጨመር ይኖርበት ይሆናል። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 6:18

በእግዚአብሔር ፊት ትክክለኛና መልካም የሆነውን አድርግ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ትዕዛዝና በረከት ነው። እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ከታዘዙት ከእርሱ በረከትን ይቀበላሉ። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ትክክልና መልካም የሚለውን አድርግ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 6:20

ያዘዛችሁ የቃል ኪዳኑ ድንጋጌዎች ምንድናቸው
በዚህ ጥያቄ “የቃል ኪዳን ድንጋጌዎች” ትርጉማቸውንና ዓላማቸውን ይወክላሉ። አ.ት፡ “የታዘዙት የቃል ኪዳን ድንጋጌዎች ለአንተ ምን ትርጉም አላቸው” ወይም “የታዘዝከውን የቃል ኪዳን ድንጋጌዎች መታዘዝ የሚኖርብህ ለምንድነው”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ልጅህ
ይህ የሚያመለክተው ሙሴ የእግዚአብሔርን ቃል የሚነግራቸው የትልልቆቹ እስራኤላውያንን ልጆች ነው።

በጽኑ እጅ
እዚህ ጋ “ጽኑ እጅ” የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ኃይል ነው። ይህንን በዘዳግም 4:34 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት፡ አ.ት፡ “በጽኑ ኃይሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በቤቱ ሁሉ
እዚህ ጋ “ቤቱ” የሚለው ፈሊጣቂ አነጋገር የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ሕዝብ ነው። አ.ት፡ “በሕዝቡ ሁሉ ላይ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በዐይኖቻችን ፊት
እዚህ ጋ “ዐይኖቻችን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሰውን ሁለንተናውን ነው። አ.ት፡ “ልናያቸው በምንችልበት” (See: Synecdoche)

ሊያስገባን
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም መብራራት ይችላል። አ.ት፡ “ወደ ከነዓን ሊያስገባን” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

Deuteronomy 6:24

በእግዚአብሔር ፊት
“በእግዚአብሔር ሀልዎች” ወይም “እግዚአብሔር ሊያየን በሚችልበት”

ጠብቅ
ሁል ጊዜ፣ በየትኛውም ሁኔታ ታዘዝ

ይህ ጽድቃችን ይሆናል
“ይህ” የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት መጠበቅን ያመለክታል። ይህ እግዚአብሔር ጻድቅ አድርጎ እንደሚቆጥራቸው የሚያመለክት ፈሊጣዊ

አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ጻድቅ አድርጎ ይቆጥረናል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን
ተመልከት)

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 7

1 እግዚአብሔር አምላካችሁ እንድትወሱአት ወደምትገቡባት ምድር ባመጣችሁ ጊዜ፤ ከፊታችሁም ብዙ አሕዛብ ከእናንተ የበለጡትንና የበረቱትን ሰባቱን አሕዛብ ኬጢያዊውን፥ ጌርጌሳውያንን፥ አሞራውያንን፥ ከነዓናውያንን፥ፌርዛዊውን፥ ኤዊያዊውንና ኢያቡሳዊውን አወጣቸው። **2** እንዲሁም ጦርነት በገጠማችሁ ጊዜ እግዚአብሔር አምላካችሁ ድል በሰጣችሁ ጊዜ፥ እነርሱን ማጥቃት አለባችሁ፥ ከዚያም ፈጽሞ ማጥፋት ይኖርባችኋል። **3** ከእርሱም ጋር ቃል ኪዳን ማድረግ ወይም ምሕረት አለማድረግ፥ ከእነርሱም ጋር አትጋቡም፤ ሴት ልጆቻችሁን ለወንድ ልጆቻቸው አትስጡ፥ ሴት ልጃቸውንም ለወንድ ልጃችሁ አትውሰዱ። **4** ሌሎች አማልክትን እንዳያመልኩ፥ ልጆቻችሁን እኔን እንዳይከተሉ ይመልሳሉ፥ የእግዚአብሔርም ቁጣ ይነድድባችኋል ፈጥኖም ያጠፋችኋል። **5** በእነርሱ ላይ የምታደርጉባቸው እንደዚህ ነው፥ መሠዊያቸውን አፍርሱ፥ ሐውልቶቻቸውንም ሰባብሩ፤ የማምለኪያ ዐፀዶቻቸውንም ቁረጡ፥ የተቀረጸውን ምስላቸውንም በእሳት አቃጥሉ። **6** እናንተ ለእግዚአብሔር ለአምላካችሁ የተለያችሁ ሕዝብ ናችሁ። እግዚአብሔር አምላካችሁ በምድርም ገጽ ከሚኖሩ ሕዛብ ሁሉ ይልቅ ለእርሱ ሕዝብ ትሆንለት ዘንድ መረጣችሁ። **7** እግዚአብሔርም የወደዳችሁና የመረጣችሁ ከአሕዛብ ሁሉ በቁጥር ስለ ባዛችሁ አይደለም፤ እናንተ ከአሕዛብ ሁሉ በቁጥር ጥቂቶች ነበራችሁና፤ **8** ነገር ግን እግዚአብሔር ስለ ወደዳችሁ ለአባቶቻችሁም የማለላቸውን ቃል ኪዳን ስለ ጠበቀ ነው። እግዚአብሔር በጽኑ እጅ ያወጣችሁ፥ ከባሪነትም ቤት ከግብፅ ንጉሥ ከፈርዖን እጅ ያዳናችሁ ለዚህ ነው። **9** ስለዚህ እግዚአብሔር አምላካችሁ እርሱ አምላክ እንደ ሆነ ለሚወድዱትና ትእዛዘትንም ለሚጠብቁት፥ ቃል ኪዳኑንና ምሕረቱን እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ የሚጠብቅ የታመነ አምላክ እንደ ሆን እወቁ፥ **10** ነገር ግን የሚጠሉትን በፊታቸው ሊያጠፋቸው ብድራትን ይመልሳል፤እንዲሁም ብድራትን ለመመለስ አይዘገይም። **11** እንግዲህ ታደርጉት ዘንድ እኔ ዛሬ ለእናንተ የማዝዘውን ትእዛዘት፥ ሥርዓቶችና ድንጋጌዎችን ጠብቁ። **12** እነዚህን ድንጋጌዎችን ሰምታችሁ ብትጠብቁና ብታደርጉ፥ እግዚአብሔር አምላካችሁ ለአባቶቻችሁ የማለላችውን ቃል ኪዳን በታማኝነት ለእናንተ ይጠብቅላችኋል። **13** እርሱም ይወድዳችኋል፥ ይባርካችኋል፥ ያበዛላችኋል፤ እንዲሁም የሆዳችሁንና የምድራችሁን ፍሬ፥ እህላችሁን፥ ወይናችሁን፥ ዘይታችሁን፥ የከብቶቻችሁንና የበጎቻችሁን መንጋ ይባርካል። **14** ከአሕዛብም ሁሉ ይልቅ የተባረካችሁ ትሆናላችሁ፥ በሰዎቻችሁና በከብቶቻችሁ ዘንድ ወንድ ወይም ሴት ቢሆኑ መካን አይሆንባችሁም። **15** እግዚአብሔርም ሕመምን ሁሉ ከእናንተ ያርቃል፥ የምታውቁአችሁን ክፉውን የግብፅ በሽታ ሁሉ በእናንተ ላይ አያደርስባችሁም በሚጠሉባችሁም ሁሉ ላይ ያመጣባቸዋል። **16** እግዚአብሔር አምላካችሁም በእጃችሁ አሳልፎ የሚሰጣችሁን አሕዛብ ሁሉ ታጠፋቸዋላችሁ፥ ዓይናችሁም አያዝኑላቸውም። ወጥመድ እንዳይሆኑባችሁአማልክታቸውንም አታምልኩአችሁም። **17** በልብህም እንዲህ ብትሉ፦ እነዚህ አሕዛብ ከእኔ ይልቅ ይበዛሉና አወጣቸው ዘንድ እንዴት እችላለሁ? **18** እግዚአብሔር አምላካችሁ በፈዖንና በግብፅ ሁሉ ያደረገውን ትዝ ስለሚላችሁ እነሱን አትፍራቸው፤ **19** አምላካችሁ እግዚአብሔር ዓይናችሁ ፊት ታላቅን መቅሠፍት፥ ምልክትንና ተአምራትን በማድረግ በጸናችው እጅ፥ በተዘረጋውም ክንድ አወጣችሁ። እንዲሁ እግዚአብሔር አምላካችሁ እናንተ በምትፈሩአችሁ በአሕዛብ ሁሉ ላይ ያደርጋል። **20** በተጨማሪም እግዚአብሔር አምላካችሁ ራሳቸውን የተሸሸጉትን ከፊታችሁ እስኪጠፉ ድረስ በመካከላችው ተርብ ይሰድድባቸዋል። **21** እግዚአብሔር አምላካችሁ ታላቅና የተፈራ አምላክ በመካከላችሁ ስላለ፤ ከእነርሱ የተነሣ አትደንግጡ። **22** እግዚአብሔር አምላካችሁ እነዚህን አሕዛብ ጥቂት በጥቂት ከፊታችሁ ያወጣቸዋል። ሁሉንም አንድ ጊዜ አታጠፋቸውም፤ ወይም የዱር አራዊት በዙሪያችሁ በጣም ብዙ ይሆናሉ። **23** እግዚአብሔር አምላካችሁ እነርሱን በእጃችሁ አሳልፎ ይሰጣቸዋል፥ እስኪጠፉም ድረስ በታላቅ ድንጋጤ ያስደነግጣቸዋል። **24** ነገሥታታቸውንም በእጃችሁ አሳልፎ ይሰጣቸዋል፥ ስማቸውንም ከሰማይ በታች ታጠፋቸዋላችሁ። እስክታጠፏቸውም ድረስ ማንም በፊታችሁ ይቆም ዘንድ አይችልም። **25** የተቀረጸውንም የአማልክታቸውን ምስል በእሳት ታቃጥላላችሁ፤ ከብር ወይም ከወርቅ የተሠሩትንም ለራሳችሁ ለመውሰድ አትመኙ፥ በእግዚአብሔር በአምላካችሁም ዘንድ ርኩስ ነውና እንዳትጠመዱበት ከእርሱ ምንም አትውሰዱ። **26** እንደ እርሱም ርጉም እንዳትሆኑ ርኩስን ነገር ወደ ቤታችሁ አታግቡ ለማምለክም አትቃጡ፥ ለጥፋት የተለየ ስለ ሆነ ፈጽሞ ተጸየፉት፥ ጥሉትም።

Deuteronomy 7:2

አሳልፎ ይሰጥሃል
አንድ ሰው ለሌላው እንደሚሰጠው ቁሳዊ ነገር ሙሴ የሚናገረው ስለ ድል ነው። አ.ት፡ “እንድታሸንፋቸው ያስችልሃል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ስታሸንፋቸው
እዚህ ጋ “እነርሱን” የሚያመለክተው በዘዳግም 7:1 የተጠቀሱትን ሰባት አገሮች ነው።

Deuteronomy 7:4

እነርሱ
“ልጆችህ ከሌሎች አገሮች ሕዝቦች ጋር እንዲጋቡ ብትፈቅድ፣ የሌሎች አገሮች ሰዎች”

ስለዚህ የእግዚአብሔር ቁጣ በአንተ ላይ ይነድዳል
ሙሴ የእግዚአብሔርን ቁጣ እሳትን ከሚለኩስ ሰው ጋር ያነጻጽረዋል። ይህ የሚያስቆጣውን ስለሚያጠፋበት ስለ እግዚአብሔር ኃይል አጽንዖት ይሰጣል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በአንተ ላይ እግዚአብሔር ቁጣውን ያነዳል” ወይም “ከዚያም እግዚአብሔር በአንተ ላይ በጣም ይቆጣል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በአንተ ላይ
“አንተ” የሚለው ቃል እስራኤላውያንን ሁሉ ስለሚመለከት ብዙ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)

የምታደርጉት -- አፍርሱ -- ስበሩ -- ቁረጡ -- አቃጥሉ
እዚህ ጋ ሙሴ የሚናገረው ለእስራኤላውያን ሁሉ ነው፣ ስለዚህ እነዚህ ቃላት ብቁ ቁጥር ናቸው። (See: Forms of You)

Deuteronomy 7:6

የተለየ ሕዝብ ናችሁ
እግዚአብሔር ሕዝቡን እስራኤልን የእርሱ እንዲሆኑ በተለየ ሁኔታ መምረጡ ከሌሎች ሕዝቦች እንደለያቸው ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በምድር ፊት ከሚኖሩት
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት “በምድር ላይ ከሚኖሩት” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Deuteronomy 7:7

ፍቅሩን በእናንተ ላይ አላደረገም
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ሌሎችን ከወደደበት በላይ እናንተን አልወደዳችሁም” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በጽኑ እጅ
እዚህ ጋ “ጽኑ እጅ” የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ኃይል ነው። እነዚህ ቃላት በዘዳግም 4:34 ላይ ደግሞ ይታያሉ። አ.ት፡ “በጽኑ ኃይሉ”(ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 7:9

ለሺህ ትውልድ
“ለ1,000 ትውልድ” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ለሚጠሉት በፊታቸው ይበቀላቸዋል
የዚህ የአነጋገር ዘይቤ ትርጉም “እግዚአብሔር እንደቀጣቸው ያውቁ ዘንድ በግልጽና በፍጥነት ይበቀላቸዋል” የሚል ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በሚጠሉት በማናቸውም ላይ አይዘገይም
“አይዘገይም” የሚለው ቃል እግዚአብሔር በብርቱ ይቀጣል የሚለውን አጽንዖት ዝቅ አድርጎ የሚያሳይ ነው። አ.ት፡ “እግዚአብሔር የሚጠሉትን ሁሉ በብርቱ ይቀጣቸዋል” (ምጸት የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 7:12

ያበዛሃል
“የሕዝብህ ቁጥር እንዲበዛ ያደርጋል”

የማህፀንህን ፍሬ
ይህ “ልጆችህን” የሚል የአነጋገር ዘይቤ ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የመሬትህን ፍሬ
ይህ “ምርትህን” የሚል የአነጋገር ዘይቤ ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የከብትህን ብዛት
“ከብትህ እንዲበዛ”

Deuteronomy 7:14

ከሌሎች ሕዝቦች የበለጠ ትባረካለህ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሌሎች ሕዝቦችን ከምባርክበት በበለጠ እባርክሃለሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በመካከልህ ወይም በከብቶችህ መካከል የማይወልድ ወንድ ወይም መካን ሴት አይኖርም
ሙሴ ሁሉም ልጆች ሊኖሯቸው እንደሚችሉ አጽንዖት ለመስጠት አሉታዊ መግለጫዎችን ይጠቀማል። ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እናንተ ሁላችሁም ልጆች ይኖሯችኋል፣ ከብቶቻችሁም ይበዛሉ” (ምጸት የሚለውን ተመልከት)

በመካከልህ -- ከብቶችህ
“አንተ” እና “የአንተ” የሚሉት ቃላት ብዙ ቁጥር ናቸው። (See: Forms of You)

በሽታን ሁሉ ከአንተ አርቃለሁ
“እንደማትታመም እርግጠኛ ሁን” ወይም “ፍጹም ጤና እንድትሆን እጠብቅሃለሁ”

በአንተ ላይ -- ክፉ በሽታዎችን ሁሉ፣ ነገር ግን በሚጠሉህ ሁሉ ላይ ያመጣቸዋል
ሙሴ በሽታን እግዚአብሔር በሰዎች ጫንቃ ላይ እንደሚጭነው ከባድ ቁስ አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “እርሱ በየትኛውም ክፉ በሽታ እንድትታመም አያደርግህም … ነገር ግን ጠላቶችህ በእነርሱ እንዲታመሙ ያደርጋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 7:16

ሕዝቦችን ሁሉ ታጠፋቸዋለህ
“ሁሉንም የሕዝብ ወገኖች ፈጽመህ እንድታጠፋቸው አዝሃለሁ”

ዕይንህ አይራራላቸው
ይህ ትዕዛዝ ነው። ሙሴ ዐይን የሚያየው ራሱን ዐይንን እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “የምታየው እንድትራራላቸው እንዲያደርግህ አትፍቀድ” ወይም “የምታደርገው እንደሚጎዳቸው በማየትህ ምክንያት አትራራላቸው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አታምልክ
“በፍጹም አታምልክ”

ያ ለአንተ ወጥመድ ይሆንብሃል
ሕዝቡ ሌሎች አማልክትን ካመለኩ በወጥመድ እንደሚያዝ እንስሳ ይሆናሉ፣ ከዚያም ማምለጥ አይችሉም። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 7:17

በልብህ ---- ብትል -- አትፍራ
ሀገራቱ ከእነርሱ ይልቅ ብርቱዎች እንደሆኑ ቢያስተውሉም እንኳን ሕዝቡ መፍራት የለባቸውም። አ.ት፡ “ምንም እንኳን በልብህ -- ብትናገር” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በልብህ ብትናገር
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ብታስብ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

እንዴት ላስወጣቸው እችላለሁ?
ሕዝቡ ሌሎች አገራትን ስለ ፈሩበት ስሜት አጽንዖት ለመስጠት ሙሴ በጥያቄ መልክ ይጠቀማል። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል።አ.ት፡ “ላሸንፋቸው አልችልም” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

አስታውስ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ማስታወስ አለብህ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ዐይኖችህ ዐይተዋል
እዚህ ጋ “ዐይኖችህ” የሚወክለው የሰውን ሁለንተና ነው። አ.ት፡ “ያየኸው” (See: Synecdoche)

ጽኑውን እጅ፣ የተዘረጋችውንም ክንድ
እዚህ ጋ “ጽኑ እጅ” እና “የተዘረጋች ክንድ” የእግዚአብሔርን ኃይል የሚገልጹ ዘይቤአዊ አነጋገሮች ናቸው። ይህንን በዘዳግም 4:34 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እና በጽኑ ኃይሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 7:20

ከዚህም በላይ፣ እግዚአብሔር
“በተጨማሪም፣ እግዚአብሔር”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ተርብ ይልክባቸዋል
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች 1) ሰዎችን እንዲነድፉና እንዲያሳምሙ እግዚአብሔር ትክክለኛ በራሪ ነፍሳትን ይልክባቸዋል፣ ወይም 2) እግዚአብሔር ሕዝቡ እንዲፈሩና እንዲሸሹ ያደርጋቸዋል።

ከአጠገብህ ይጠፋሉ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ከዚህ በኋላ እንዳታያቸው ይሞታሉ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

አታያቸውም
“ከቶ”

ታላቅና የሚያስፈራ አምላክ
“ታላቅና ድንቅ አምላክ” ወይም “ሰዎቹን እንዲፈሩ የሚያደርግ ታላቅ አምላክ”

ጥቂት በጥቂት
“በዝግታ”

Deuteronomy 7:23

በእነርሱ ላይ ድልን ይሰጥሃል
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “እንድታሸንፍ ያስችልሃል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በእነርሱ ላይ ድልን
“ከሌሎች ሕዝቦች በሆኑት ሰራዊቶች ላይ ድልን”

በከፍተኛ ሁኔታ ያደናግራቸዋል
“በአግባቡ ማሰብ እንዳይችሉ ያደርጋቸዋል”

እስኪጠፉ ድረስ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እስክታጠፋቸው ድረስ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ከሰማይ በታች ስማቸው እንዲደመሰስ ታደርጋለህ
እስራኤላውያን የእነዚያን አገራት ሕዝቦች በሙሉ ፈጽመው ስለሚያጠፏቸው ወደፊት ማንም አያስታውሳቸውም። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በፊትህ የሚቆም
“አንተን በመቃወም የሚቆም” ወይም “አንተን በመቃወም ራሳቸውን መከላከል”

Deuteronomy 7:25

ታቃጥላለህ
ይህ ትዕዛዝ ነው።

አማልክቶቻቸውን
“የሌሎች ሕዝቦችን አማልክት”

አትቅና -- በእርሱ አትጠመድ
እነዚህ ቃላት አማልክቶቹን እንዲያቃጥሉ በተሰጣቸው መመሪያ ላይ ተጨማሪዎች ናቸው

በእርሱ ትጠመዳለህ
በጣዖታቱ ላይ ያለውን ወርቅ ወይም ብር መውሰድ እንኳን ሕዝቡ እንዲያመልኳቸው ሊያደርጋቸው ይችላል። ይህንን በማድረጋቸው በወጥመድ እንደተያዘ እንስሳ ይሆናሉ። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ወጥመድ ይሆንባችኋል” (See: (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት))

ይህ ለአምላክህ ለእግዚአብሔር አስጸያፊ ነው
እነዚህ ቃላት ሕዝቡ ጣዖታቱን እንዲያቃጥሉ እግዚአብሔር ለምን እንደፈለገ ይነግሩናል። “አምላካችሁ እግዚአብሔር በጣም ስለሚጠላው ይህንን አድርጉ”

ፈጽመህ ትጠላዋለህ፣ ትጸየፈዋለህም
“መጥላት” እና “መጸየፍ” የሚሉት ቃላት መሠረታዊ ትርጉማቸው አንድ ሆኖ ሳለ ለጥላቻው ጥልቅነት አጽንዖት ይሰጣሉ። አ.ት፡ “ፈጽመህ ትጠላዋለህ” (See: Doublet)

እርሱ ለጥፋት የተለየ ነው
እግዚአብሔር አንድን ነገር መርገሙና ሊያጠፋው መማሉ ነገሩን ከየትኛውም ነገር ለይቶ እንደሚያስቀምጠው ሆኖ ተነግሯል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እርሱን እግዚአብሔር ለጥፋት ለይቶ አስቀምጦታል” (See: (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊድምፅ የሚለውን ተመልከት))

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 8

1 በሕይወት እንድትኖሩና እንድትበዙ፥ እግዚአብሔርም ለአባቶቻችሁ ወደ ማለላቸው ምድር ገብታችሁ እንድትወርሱአት ዛሬ ለእናንተ የማዝዘውን ትእዛዘትን ሁሉ ጠብቁ። **2** እግዚአብሔር አምላካችሁ በልባችሁ ያለውን፥ ትእዛዘቱን መጠበቃችሁን ወይም አለመጠበቃችሁን ያውቅ ዘንድ ሊፈትናችሁና ትሁት እንድትሆኑ በእነዚህ በአርባ ዓመታት በምድረ በዳ የመራችሁን መንገድ ሁሉ አስቡ። **3** አስጨነቃችሁ፥ እንድትራቡም አደረጋችሁ፥ እንዲሁም እናንተና ልጆቻችሁ፥ አባቶቻችምሁ የማያውቁአቸውን መና መገባችሁ። ይህም ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው ነገር ሁሉ በሕይወት ይኖራል እንጂ በእንጀራ ብቻ እንደማይኖር ያስታውቃችሁ ዘንድ ነው። **4** በእነዚህ አርባ ዓመታት ውስጥ የለበሳችሁት ልብስ አላረጀም፥ እግራችሁም አላበጠም። **5** ሰውም ልጁን እንደሚገሥጽ እንዲሁም እግዚአብሔር አምላካችሁ እናንተን እንደሚገሥጽ በልባችሁ አስቡ። **6** በመንገዱም እንድትሄዱ እርሱንም እንድትፈሩ የእግዚአብሔ የአምላካችሁን ትእዛዝ ጠብቁ። **7** እግዚአብሔር አምላካችሁ ወደ መልካምና፥ ከሸለቆና ከኮረብታ የውኃ ጅረቶችና ፈሳሾች የሚመነጩ ምንጮች ወዳሉባት ምድር፤ ስንዴና ገብስ፤ **8** በለስና ሮማን፥ ወይራና ማር ወደ ሞሉባት፥ **9** ሳይጎድላችሁ እንጀራ ወደምትበሉባት ምድር፥ አንዳችም ወደማታጡባት፥ ድንጋይዋ ብረት ወደ ሆነ፥ ከተራራዋም መዳብ ወደሚማስባት ምድር አመጣችሁ። **10** እናንተም ትበላላችሁ፥ ትጠግባላችሁ፥ ስለ ሰጣችሁም ስለ መልካሚቱ ምድር እግዚአብሔር አምላካችሁን ትባርካላችሁ። **11** ዛሬ እኔ እናንተን የማዝዛውን ትእዛዘትን፥ ድንጋጌዎችንና ሥርዓቶችን ባለመጠበቅ እግዚአብሔር አምላካችሁን እንዳትረሱ ተጠንቀቁ። **12** ከበላችሁና ከጠገባችሁ ሙሉም ከሆናችሁ በኋላ መልካምም ቤት ሠርታችሁ በዚያ መኖር ከጀመራችሁ በኋላ እንዳትረሱ ተጠንቀቁ። **13** የላምና የበግ መንጋ ከበዛላችሁ በኋላ፥ ብራችሁና ወርቃችሁም፥ ያላችሁም ሁሉ ከበዛላችሁ በኋላ፥ **14** ልባችሁ እንዳይኮራ ከግብፅም ምድር ከባርነት ቤት ያወጣችሁን እግዚአብሔርን እንዳትረሱ ተጠንቀቁ። **15** መርዛማ እባብና ጊንጥ፥ውኃ በሌለባትና ጥማትም ባለባት በታላቂቱና በምታስፈራው ምድረ በዳ የመራችሁን፥ ከዐለት ድንጋይም ውኃን ያወጣላችሁን፥ **16** በመጨረሻም ዘመን መልካም ያደርግላችሁ ዘንድ ሊፈትናችሁ ሊያዋርዳችሁም አባቶቻችሁ ያላውቁትን መና በምድረ በዳ ያበላችሁን እግዚአብሔር አምላካችሁን እንዳትረሱ፥ **17** በልባችሁም፦ ጕልባታችን የእጃችን ብርታት ይህን ሀብት አመጣልን እንዳትሉ። **18** ነገር ግን ዛሬ እንደ ሆነ ለአባቶቻችሁ የማለላችሁን ቃል ኪዳን ያጸና ዘንድ ሀብት ለማከማቸት ጕልበት ሰጥቶአችኋል፥ እግዚአብሔር አምላካችሁን አስቡ። **19** አምላካችሁንም እግዚአብሔርን ብትረሳ ሌሎችንም አማልክት ብትከተል፥ ብታመልካቸውም፥ ብትሰግድላቸውም ፈጽሞ እንደምትጥፉ እኔ ዛሬውኑ እመሰክርባችኋልለሁ። **20** የእግዚአብሔር የአምላካችሁን ቃል ስላልሰማችሁ እግዚአብሔር ከፍታችሁ እንደሚያጠፋቸው እንደ አሕዛብ እንዲሁ እናንተ ትጠፋላችሁ።

Deuteronomy 8:1

በሕይወት እንድትኖሩና እንድትበዙ፣ አባቶቻችሁ -- ገብታችሁ እንድትወርሱ -- መጠበቅ አለብህ
“አንተ” እና “የአንተ” የሚሉት አገባቦች በሙሉ እንዲሁም ግሦቹ ብዙ ቁጥር ናቸው። (See: Forms of You)

አስታውስ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ማስታወስ አለብህ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

አርባ ዓመታት
“40 ዓመታት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ትሁት ሊያደርግህ
“ምን ያህል ደካማና ኃጢአተኛ እንደሆንክ ሊያሳይህ”

ለማወቅ
“ለመግለጥ” ወይም “ለማሳየት”

በልብህ የነበረውን
ልብ የሰው ባህርይ ምሳሌ ነው። አ.ት፡ “ምን ዓይነት ሕዝብ እንደሆንክ” ወይም “ባህሪህን እንዴት መግለጥ እንዳለብህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 8:3

ትሁት አደረገህ
“እግዚአብሔር ምን ያህል ደካማና ኃጢአተኛ መሆንህን አሳየህ”። በዘዳግም 8፡2 ላይ “ትሁት ሊያደርግህ” የሚለው ቃል እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።

መናን መገበህ
“እንድትበላው መናን ሰጠህ”

ሰዎች በሕይወት የሚኖሩት በእንጀራ ብቻ አይደለም
እዚህ ጋ “እንጀራ” የሚወክለው ሁሉንም የምግብ ዓይነት ነው። አ.ት፡ “ሰዎች በሕይወት ለመኖር እንዲችሉ የሚፈልጉት ምግብ ብቻ አይደለም” (See: Synecdoche)

ሰዎች በሕይወት የሚኖሩት ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ነገር ሁሉ ነው
እዚህ ጋ “የእግዚአብሔር አፍ” በፈሊጣዊ አነጋገር እግዚአብሔር የሚናገረው ቃል ማለት ነው። አ.ት፡ “ሰዎች በሕይወት መኖር እንዲችሉ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መታዘዝ አለባቸው” ወይም “ሰዎች በሕይወት መኖር እንዲችሉ እግዚአብሔር የሚነግራቸውን መፈጸም አለባቸው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 8:4

አርባ ዓመታት == ልብሳችሁ
ይህ “ማስታወስ” የሚገባቸው የመጨረሻው ንብረታቸው ነው (ዘዳግም 8፡2)

አርባ ዓመታት
“40 ዓመታት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

አስቡ == ጠብቁ == በመንገዱ ሂዱ፣ እርሱንም አክብሩት
ይህ በዘዳግም 8፡1-2 የሚጀምረውን የትዕዛዛቱን ዝርዝር የሚቀጥል ነው።

ስለዚህ ነገር በልብህ አስብ
እዚህ ጋ ፈሊጣዊ አነጋገር የሆነው “ልብ” የሚወክለው የአንድን ሰው አሳብና ማስተዋል ነው። አ.ት፡ “አስተውል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 8:7

የ == ምድር
“ከ -- ምድር” ወይም “ -- ያላትን ምድር”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Deuteronomy 8:9

የምትበላውን እንጀራ የማታጣባት ምድር
ይህ ምጸታዊ አነጋገር በአዎንታዊነት ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “የተትረፈረፈ ምግብ የምታገኝበትን ምድር” (ምጸት የሚለውን ተመልከት)

ምንም ነገር የማታጣበትን ሀገር
ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የምትፈልገውን ሁሉ የምታገኝበት” (ድርብ አሉታዊ የሚለውን ተመልከት)

ድንጋዮቹ ብረት የሆኑበት
ድንጋዮቹ በብረት ማዕድን የተሞሉ ናቸው። የብረት ማዕድን ሰይፍና ማረሻ ለመሥራት የሚያገለግል ጠንካራ ብረት ነው።

መዳብ ትቆፍራለህ
“የመዳብ ማዕድን ታወጣለህ”። መዳብ የቤት ውስጥ መገልገያዎችን ለመሥራት የሚያገለግል ለስለስ ያለ ብረት ነው።

ትበላለህ፣ ትጠግባለህም
“እስክትጠግብ ድረስ የምትበላው በቂ ምግብ ይኖርሃል”

ትባርካለህ
“ታመሰግናለህ” ወይም “ምስጋናን ታቀርባለህ”

Deuteronomy 8:11

ትዕዛዞቹን ቸል አትበል
“ትዕዛዞቹን መጠበቅህን አታቁም” ወይም “ትዕዛዛቱን መጠበቅህን ቀጥል”

በበላህና በጠገብህ ጊዜ
“የምትበላው በቂ ምግብ በሚኖርህ ጊዜ”

ልብህ ይነሣሣል
እዚህ ጋ “ልብ” የሚወክለው ውስጠኛውን ሰው ነው። መታበይና ከእንግዲህ እግዚአብሔርን ያለመታዘዝ እንደ ሰው ልብ መነሣሣት ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “ትታበያለህ፣ ከእንግዲህም እግዚአብሔርን አትታዘዝም” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 8:13

መንጋዎችህ
“የከብትህ፣ የበግና የፍየል መንጋህ”

መብዛት
በቁጥር እጅግ መጨመር

ያለህ ሁሉ ሲበዛልህ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በጣም ብዙ ነገሮች አሉህ” ወይም “በጣም ብዙ ንብረት አለህ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ልብህ ይነሣሣል
እዚህ ጋ “ልብ” የሚወክለው ውስጠኛውን ሰው ነው። መታበይና ከእንግዲህ እግዚአብሔርን ያለመታዘዝ እንደ ሰው ልብ መነሣሣት ሆኖ ተነግሯል። በዘዳግም 8:12 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ትታበያለህ፣ ከእንግዲህም እግዚአብሔርን አትታዘዝም” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ያወጣህን
ሙሴ ለእስራኤላውያን ስለ እግዚአብሔር የሚያውቁትን ማስታወስ ጀምሯል (ለይቶ ማሳወቅ ማሳወቅን ወይም ማስታወስን ሲቃረን የሚለውን ተመልከት)

ከባርነት ቤት ያወጣህ
ይህ በግብፅ በባርነት የነበሩበትን ጊዜ የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ባሪያዎች ከነበራችሁበት ስፍራ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 8:15

በመጨረሻ -- የመራህን
ሙሴ ለእስራኤላውያን ስለ እግዚአብሔር የሚያውቁትን ማስታወስ ቀጥሏል (ዘዳግም 8:14)። (ለይቶ ማሳወቅ ማሳወቅን ወይም ማስታወስን ሲቃረን የሚለውን ተመልከት)

የመራህ -- ያመጣህ -- መገበህ
“የመራህ እግዚአብሔር … ያመጣህ እግዚአብሔር … እግዚአብሔር መገበህ”

ተናዳፊ እባብ
“መርዘኛ እባብ”

የተጠማ ምድር
ይህ ሐረግ ልክ ሰው ውሃ በሚፈልግበት ጊዜ እንደሚጠማ ምድሪቱ መጠማቷን ይገልጻል። አ.ት፡ “ደረቅ ምድር” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

መልካም ሊያደርግልህ
“ሊረዳህ” ወይም “ለአንተ መልካም ስለነበረ”

ሆኖም በልብህ -- ትል ይሆናል
ይህ ምናልባት ሰዎች ልባቸው “በሚታበይበት” እና “እግዚአብሔርን በሚረሱበት” ጊዜ የሚያደርጉት ሦስተኛው ነገር ነው። (ዘዳግም 8:14)። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ኃይሌና የእጄ ብርታት ይህንን ሁሉ ሀብት አስገኘልኝ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚያመለክተው የአንድን ሰው ኃይል ወይም ችሎታ ነው። አ.ት፡ “እኔ በጣም ብርቱና ኃይለኛ ስለሆንኩኝ ይህንን ሀብት አግኝቻለሁ” ወይም “እነዚህን ነገሮች ሁሉ በራሴ ኃይልና ችሎታ አግኝቻለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 8:18

ነገር ግን ትዝ ይበልህ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ትዕዛዝ ነው። አ.ት፡ “ነገር ግን አስታውስ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ያጸና ዘንድ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “እርሱ በዚህ መንገድ ያጸናል” ወይም 2) “በዚህ መንገድ እርሱ ሊያጸና የታመነ ነው”

ያ -- ዘንድ
“ስለዚህ ይችላል”

ማጽናት
እንዲቆም ወይም እንዲኖር ማድረግ

ዛሬ እንደሆነው ሁሉ
“አሁን እንደሚያደርገው ሁሉ” ወይም “ቃል ኪዳኑን አሁን እንዳጸናው ሁሉ”

ሌሎች አማልክቶችን ብትከተል
መከተል የመታዘዝ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ሌሎች አማልክቶችን ማገልገል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በአንተ ላይ -- ብት -- በፊትህ -- ትጠፋላችሁ -- አትሆኑም -- አምላክህ
“አንተ” የሚሉት እነዚህ አገባቦች ሁሉ ብዙ ቁጥር ናቸው። (See: Forms of You)

በእናንተ ላይ እመሰክራለሁ
“አስጠነቅቃችኋለሁ” ወይም “በምስክሮች ፊት እነግራችኋለሁ”

በእርግጥ ትጠፋላችሁ
“ያለምንም ጥርጥር ትሞታላችሁ”

በፊታችሁ
“በፊት ለፊታችሁ”

የእግዚአብሔርን ድምፅ ስላልሰማችሁ
እዚህ ጋ “የእግዚአብሔር ድምፅ” ማለት እግዚአብሔር ያደርጉት ዘንድ ለሕዝቡ የሚነግራቸው ማለት ነው። አ.ት፡ “የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ስላልታዘዛችሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 9

1 እስራኤል ሆይ፥ ስሙ፥ ከእናንተ የበለጡትንና የበረቱትን አሕዛብ፥ እስከ ሰማይም ድረስ የተመሸጉትን ታላላቅ ከተሞች ለመውረስ ትገቡ ዘንድ ዛሬ ዮርዳኖስን
ልትሻገሩ ነው፤ **2** የኤናቅ ልጆች ፥ ታላቅና ረጅም ሕዝብ፥ እናንተም የምታውቃቸው ስለ እነርሱም እንዲህ ያላችኋቸው፦ በዔናቅ ልጆች ፊት ማን መቆም ይችላል?
3 ስለዚህ እግዚአብሔር አምላካችሁም እንደሚበላ እሳት ሆኖ በፊታችሁ ስለሚያልፍ፥ ዛሬ እርሱ ያጠፋቸዋል፥ በፊታችሁም ያዋርዳቸዋል፥ እግዚአብሔርም እንደ
ተናገራችሁ እናንተ ታሳድዳቸዋላችሁ ፈጥናችሁም ታጠፋቸዋላችሁ። **4** እግዚአብሔር አምላካችሁ ከፊታችሁ ካወጣቸው በኋላ ፦ እንወርሳት ዘንድ ወደዚህች
ምድር እግዚአሔር ያመጠን፥ ስለ ጽድቄ ነው፥ እነዚህንም አሕዛብ እግዚአብሔር ከፊታችን ያወጣቸው ኃጢአተኞች ስለ ሆኑ ነው፥ ብላችሁ በልባችሁ
እንዳትናገሩ። **5** ምድራቸውን ትወርሱአት ዘንድ የምትገቡት ስለ ጽድቃችሁ ወይም ስለ ልባችሁ ቅንነት አይደለም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር አምላካችሁ ከፊታችሁ
በሚያጠፋቸው በእነዚያ አሕዛብ ኃጢአት ምክንያትና ለአባቶቻችሁ ለአብርሃም፥ ለይስሐቅና ለያዕቆብ የማለላቸውን ቃል ይፈጽም ዘንድ ነው። **6** እንግዲህ
እናንተ አንገተ ደንዳና ሕዝብ ስለ ሆናችሁና እግዚአብሔር አምላካችሁ ይህን መልካም ምድር ርስት አድርጎ የሰጣችሁ ስለጽድቃችሁ እንዳይደለ እወቁ። **7**
እግዚአብሔር አምላካችሁን በምድረ በዳ እንዳስቁጣችሁት ከግብፅ አገር ከወጣችሁበት ቀን ጀምሮ ወደዚህ ስፍራ እስከ መጣችሁ ድረስ በእግዚአብሔር ላይ
እንዳመፃችሁ አስቡ። **8** በኮሬብ ደግሞ እግዚአብሔርን አስቆጣችሁ፤ እግዚአብሔርም ሊያጠፋችሁ ተቆጣባችሁ። **9** እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር የገባውን የቃል
ኪዳን፥ የድንጋዩን ጽላቶችን ከእግዚአብሔር ለመቀበል ወደ ተራራ ወጥቼ በተራራው ላይ ለአርባ ቀናትና አርባ ሌሊት በቆየሁበት ጊዜ እንጀራም አልበለሁም፥
ውኃም አልጠጠሁም። **10** እግዚአብሔርም በእርሱ ጣት የተጻፉትን ሁለቱን የድንጋይ ጽላቶችን ሰጠኝ፤ በጽላቶቹም ላይ በተራራው ሥር በነበረው ጉበዔ
እግዚአብሔር በእሳት መካከል ሆኖ የተናገራችሁ ቃል ሁሉ ተጽፎባቸው ነበር። **11** ከአርባ ቀንና ከእርባ ሌሊትም በኋላ እግዚአብሔር ሁለቱን የድግንጋይ
ጽላቶች፥ ያቃል ኪዳኑን ጽላቶች ሰጠኝ። **12** እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ፦ ተነሥተህ ከዚህ ፈጥነህ ውረድ ከግብፅ ያወጣሃቸው ሕዝብህ ረክሰዋል። ፈጥነው
ካዘዝኋቸውም መንገድ ፈቀቅ ብለዋል። ቀልጦ የተሠራ ምስልም ለራሰቸው አድርገዋል። **13** ከዚህም በተጨማሪ እግዚአብሔርም እንዲህ ብሎ ተናገረ፦ ይህ
ሕዝብ አንገተ ደንዳና መሆኑን አይቼአለሁ። **14** ስለዚህ አጠፋቸው፥ ስማቸውንም ከሰማይ በታች እደመስሳለሁ፥ አንተንም ከእነርሱ ለሚበረታና ለሚበዛ ሕዝብ
አደርግሃለሁ። **15** እኔም ተመልሼ ከተራራው ወረድሁ፥ ተራራውም በእሳት ይነድድ ነበር። ሁለቱም የቃል ኪንን ጽላቶች በእጆቼ ነበሩ። **16** እናንተም
እግዚአብሔር አምላካችሁን እንደበደላችሁ አየሁ። ለእናንተም ለራሳችሁ የጥጃ ምስል ሠርታችሁ ነበር። እግዚአብሔርም ካዘዛችሁ መንገድ ፈቀቅ ብላችሁ
ነበር። **17** ሁሉቱንም ጽላቶች ወስጄ፥ ከእጆቼ ጣልኋቸው። በዓይናችሁም ፊት ሰበርኋቸው። **18** ስለ ሠራችሁት ኃጢአት ሁሉ፥ እርሱንም ለማስቆጣት
በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነውን ነገር ከማድረጋችሁ የተነሣ እንደገና በእግዚአብሔር ፊት አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ወደቅሁ፥ እንጀራም አልበላሁም፥ ውኃም
አጠጣሁም ነበር። **19** ምክንያቱም እግዚአብሔር ሊያጠፋችሁ ከተቆጣባችሁ ከቁጣውና ከመዓቱ የተነሣ ስለ ፈራሁ ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር በዚያን
ጊዜም ሰማኝ። **20** እግዚአብሔርም አሮንን ሊያጠፋው እጅግ ተቆጣው፤ ስለ አሮንም ደግሞ በተመሳሳይ ሁኔታ ጸለይሁ። **21** ያደረጋችሁትንም ኃጢአት
ጥጃውን ወስድሁ በእሳትም አቃጠልሁት፥ አደቅዝቅሁትም፤ ዱቄትም እስኪሆን ድረስ ፈጨሁት። ዱቄቱንም ከተራራ በሚወርድ ወንዝ ጣልሁት። **22**
እግዚአብሔርንም በቀቤራ፥ በማሳህ፥ በምኞት መቃብርም አስቆጥታችሁት ነበር። **23** እግዚአብሔርም ውጡ የሰጠኋችሁንም ምድር ውረሱ ብሎ ከቃዴስ በርኔ
በላካችሁ ጊዜ በእግዚአብሔር በአምላካችሁ ትእዛዝ ላይ አመፃችሁ፥ በእርሱም አላመናችሁም፤ወይም ድምፁንም አልሰማችሁም። **24** እናንተን ካወቅሁበት ቀን
ጀምሮ በእግዚአብሔር ላይ ዓመፀኞች ነበራችሁ። **25** እግዚአብሔር ያጠፋችሁ ዘንድ ስለ ተናገረ በእነዚያ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት በእግዚአብሔር ፊት ወደቅሁ።
26 ጌታ በእግዚአብሔርም ፊት እንዲህ ብዬ ጸለይሁ፦ እግዚአብሔር ሆይ፥ በታላቅነትህና በኃያልነትህ ከግብፅ ያወጣቸውን፥ የተበዝሃቸውን ሕዝብህንና ርስትህን
አታጥፋ ። **27** አገልጋዮችህን አብርሃምንና ይስሐቅን ያዕቆብንም አስብ፤ የዚህን ሕዝብ ደንዳናነት፥ ክፋቱንና ኃጢአቱን አትመልከት፤ **28** እኛንም ያወጣህባት
ምድር ሰዎች እግዚአብሔር ተስፋ ወደ ሰጣቸው ምድር ያገባቸው ዘንድ ስላልቻለ፤ ስለጠላቸውም በምድረ በዳ ሊገድላቸው አወጣቸው ይላሉ። **29** እነርሱም
በታላቅ ኃይልህ በጸነችውም ክንድህ ያወጣሃቸው ሕዝብህና ርስትህ ናቸው።

Deuteronomy 9:1

እስራኤል ሆይ፣ ስማ
“እስራኤል” የሚለው ቃል የእስራኤልን ሕዝብ የሚመለከት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት: “የእስራኤል ሕዝብ ሆይ፣ ስማ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ለመውረስ
“መሬታቸውን ለመውሰድ”

እስከ ሰማይ ድረስ የተመሸጉትን
ይህ ከተሞቹ በጣም ሰፊና ጠንካራ በመሆናቸው ምክንያት ሕዝቡ መፍራታቸውን አጽንዖት ለመስጠት የተደረገ ግነት ነው። በዘዳግም 1:28 ላይ ተመሳሳዩን ቃላት እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። አ.ት: “ሰማይ የሚደርሱ የሚመስሉ ግንቦች ነበሯቸው” (ግነት እና ጥቅል አስተያየት የሚለውን ተመልከት)

የዔናቅ ልጆች
በጣም ረጃጅምና ኃያላን የነበሩ የዔናቅ ሕዝብ ተወላጆች ናቸው። ተመሳሳዮቹን ቃላት በዘዳግም 1:28 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።(See: Assumed Knowledge and Implicit Information እና ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

በዔናቅ ልጆች ፊት ማን መቆም ይችላል?
ይህ ማለት የዔናቅ ልጆች ኃያላን በመሆናቸው ሰዎች ይፈሯቸው ነበር። ይህ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት: “በዔናቅ ልጆች ፊት ራሱን መከላከል የሚችል አልነበረም” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 9:3

ዛሬ
ሙሴ ፀሐይ ከጠለቀችበት ጊዜ ጀምሮ ሳይሆን ቀናትና ሳምንታት ስለጀመሩባት ስለዚያች ቀን ማለቱ ነው።

እንደሚባላ እሳት
እግዚአብሔር የሌሎች ሕዝቦችን ሰራዊት ለማጥፋት የሚችል ኃያል ነው። (See: Simile)

በፊትህ ድል ያደርጋቸዋል
“ልትቆጣጠራቸው እንድትችል ደካማ ያደርጋቸዋል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Deuteronomy 9:4

በልብህ -- አትበል
እዚህ ጋ “በልብህ” ማለቱ “በአሳብህ” ለማለት ነው። አ.ት፡ “በራስህ አታስብ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ወግቶ ያስወጣቸዋል
“ሌሎች ሕዝቦችን አሳዶ ሲያስወጣቸው”

Deuteronomy 9:5

በልብህ ቅንነት
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። “ዘወትር የምታስበውና የምትመኘው ትክክለኛውን ነገር ስለሆነ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ቃሉ ይፈጸም ዘንድ
“ቃሉ” የሚለው ፈሊጣዊ በሆነ አነጋገር የሚያመለክተው እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ ነው። አ.ት፡ “ተስፋውን ይፈጽም ዘንድ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ለአባቶቻችሁ ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ
አብርሃም፣ ይስሐቅና ያዕቆብ ሙሴ ለሚናገራቸው ሰዎች “አባቶቻቸው” ናቸው።

Deuteronomy 9:7

አስታውስ፣ ከቶም አትርሳ
ሙሴ በማስታወስ አስፈላጊነት ላይ አጽንዖት ለመስጠት ተመሳሳዩን ትዕዛዝ በአዎንታዊና በአሉታዊ ቃላት ይደግማቸዋል። አ.ት፡ “ለማስታወስ ተጠንቀቅ” (See: Doublet)

እግዚአብሔርን እንዴት ለቁጣ እንዳነሣሣኸው
እዚህ ጋ “አንተ” የሚያመለክተው ከሙሴ ጋር ያሉትንና በተጨማሪም በቀደመው ትውልድ የነበሩትን እስራኤላውያንን ነው። (See: Forms of You)

ወደዚህ ስፍራ ከመጣህ፣ አመፀኛ ነበርክ -- ለቁጣ አነሣሣኸው -- ሊያጠፋህ
“አንተ” የሚሉት ሁሉም አገባቦች ብዙ ቁጥር ናቸው። (See: Forms of You)

ወደዚህ ስፍራ
ይህ የሚያመለክተው የዮርዳኖስ ወንዝ ሸለቆን ነው።

Deuteronomy 9:9

የድንጋይ ጽላቶች፣ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ያደረገው የኪዳኑን ጽላቶች
እዚህ ጋ “የድንጋይ ጽላቶች” ይኸውም እግዚአብሔር አሥሩን ትዕዛዛት የጻፈባቸውን መሆኑን ሁለተኛው ሐረግ ግልጽ ያደርጋል። (See: Parallelism)

አርባ ቀንና አርባ ሌሊት
“40 days and 40 nights” “40 ቀንና 40 ሌሊት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር የነገራችሁ ቃል ሁሉ በእነርሱ ላይ ተጽፈው ነበር
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ለእናንተ የነገራችሁን እነዚያኑ ቃላት በእነርሱ ላይ ጻፋቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ከእሳት መካከል -- እግዚአብሔር ተናገራችሁ
እግዚአብሔር እንደ ሰው በእሳት መካከል ቆሞ በታላቅ ድምፅ የተናገረ ይመስል ነበር።

በጉባዔ ቀን
የነገር ስም የሆነው “ጉባዔ” እንደ ግሥ “በአንድነት መሰብሰብ” ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። አ.ት፡ “እናንተ እስራኤላውያን ሁላችሁ መጥታችሁ በአንድ ስፍራ በተገናኛችሁበት ቀን” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 9:11

አርባ ቀና አርባ ሌሊት
“40 ቀንና 40 ሌሊት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ሁለቱን የድንጋይ ጽላቶች፣ የኪዳኑን ጽላቶች
እዚህ ጋ “ሁለቱን የድንጋይ ጽላቶች” የተባሉት እግዚአብሔር አሥሩን ትዕዛዛት የጻፈባቸውን መሆኑን ሁለተኛው ሐረግ ግልጽ ያደርጋል። (See: Parallelism)

ሕዝብህ -- ራሳቸውን አርክሰዋል
“ሕዝብህ … የተሳሳተ ነገር እያደረጉ ነው” እነዚህን ቃላት በዘዳግም 4:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

ካዘዝኳቸው መንገድ ዘወር ብለዋል
ሙሴ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት መጠበቅን በመንገድ ላይ ከመሄድ ጋር አመሳስሎ ይናገራል። አ.ት፡ “ትዕዛዘቼን እምቢ ማለት ጀምረዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 9:13

ስማቸውን ከሰማይ በታች እንድደመስሰው
“ስማቸው ፈጽሞ እንዲጠፋ አደርጋለሁ” ወይም “ማንም እንዳያስታውሳቸው ሁሉንም ጸድተላቸዋለሁ”። ተመሳሳዩን ሐረግ በዘዳግም 7:24 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

Deuteronomy 9:15

ተመለክትሁ
እዚህ ጋ “ተመለከትሁ” የሚለው ቃል ሙሴ ባየው ነገር መደነቁን ያሳያል።

ቀልጦ የተሠራ ጥጃን ለራሳችሁ አበጃችሁ
የእስራኤል የቀደመው ትውልድ ያመልኩት ዘንድ የብረት ጥጃ እንዲሠራላቸው አሮንን ጠየቁት። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

እግዚአብሔር ካዘዛችሁ መንገድ ፈጥናችሁ ወጣችሁ
ሙሴ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት መጠበቅ በመንገድ ላይ ከመሄድ ጋር አመሳስሎ ይናገራል። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 9:12 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

Deuteronomy 9:17

በዐይኖቻችሁ ፊት ሰባበርኳቸው
እዚህ ጋ “ዐይኖቻችሁ” የእስራኤልን ሕዝብ የሚወክል ምሳሌ ነው። አ.ት፡ “እዚያው በፊት ለፊታችሁ ሰባበርኳቸው” ወይም “ልታዩአቸው በምትችሉበት ስፍራ ሰባበርኳቸው” (See: Synecdoche)

በግምባሬ ተደፋሁ
“በመሬት ላይ በግምባሬ ወደቅሁ”። ይህ እግዚአብሔር ታላቅ እንደሆነና ሙሴ ምንም እንዳይደለ ማሳያ መንገድ ነው።

አርባ ቀንና አርባ ሌሊት
“40 ቀንና 40 ሌሊት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 9:19

እግዚአብሔር ሊያጠፋችሁ የተቆጣበትን ቁጣውንና ጽኑ ቅሬታውን ፈርቼ ነበር
“ቁጣና ጽኑ ቅሬታ” የሚሉት ቃላት እግዚአብሔር ስለ ተቆጣና ቅር ስለተሰኘ ሊያደርግ ያለውን የሚያመለክቱ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ናቸው። አ.ት፡ “እግዚአብሔር በእናንተ ተቆጥቶ ነበር -- በእናንተ ላይ እጅግ አዝኖ ነበር -- እስኪያጠፋችሁ ድረስ ተቆጥቶ ነበር፣ እኔም ስለሚያደርገው ነገር ፈርቼ ነበር”

Deuteronomy 9:21

ወሰድኩ -- አቃጠልኩት -- አድቅቄ -- መሬት -- በተንሁት
ሙሴ ምናልባት ሌሎች ሰዎች ሥራውን በቀጥታ እንዲሠሩት አዝዟቸው ይሆናል። አ.ት፡ “የሚወስዱ ... የሚያቃጥሉ ... የሚሰብሩ ... የሚፈጩ ... የሚበትኑ ሰዎች ነበሩኝ”

ኃጢአታችሁ፣ የሠራችሁት ጥጃ
እዚህ ጋ የሠሩት የወርቅ ጥጃ ራሱ የእነርሱ “ኃጢአት” መሆኑ ተመልክቷል። አ.ት፡ “በኃጥአተኝነት የሠራችሁት ጥጃ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 9:22

ተቤራ -- ማሳህ -- ቂብሮት ሐታአዋ
እነዚህ የእስራኤል ሕዝብ በምድረ በዳ በነበሩበት ጊዜ የሄዱባቸው የተለያዩ ቦታዎች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ውጡ
እግዚአብሔር ሊሰጣቸው የነገራቸው ምድር በኮረብታዎቹ ላይ ያለ ሲሆን እነርሱ የነበሩት ቆላው ላይ ነው፣ ስለዚህ ያገኙት ዘንድ ወደ ኮረብታዎቹ መውጣት ነበረባቸው።

በትዕዛዙ ላይ አመፃችሁ
“ትዕዛዝ” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ራሱን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “በእግዚአብሔር ላይ አመፃችሁ፤ ትዕዛዙንም አልጠበቃችሁም” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ድምፁን መስማት
እዚህ ጋ “ድምፁን” ማለት እግዚአብሔር ተናግሮችት የነበረውን ነው። አ.ት፡ “የተናገረውን ታዘዙት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ካወቅኧችሁ ጊዜ ጀምሮ
“ልመራችሁ ከጀመርኩበት ጊዜ አንሥቶ”። አንዳንድ ትርጉሞች “ካወቃችሁ ጊዜ ጀምሮ”፣ ለመጀመሪያ ጊዜ እግዚአብሔር እነርሱን ያወቀበት ቀን በሚል ይነበባሉ

Deuteronomy 9:25

በእግዚአብሔር ፊት በግምባር መደፋት
“በመሬት ላይ በግምባሬ ተደፋሁ”። ይህንን በዘዳግም 9፡18 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

አርባ ቀንና አርባ ሌሊት
“40 ቀንና 40 ሌሊት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

የተቤዠኸውን
እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ገንዘብ በመክፈል ከባርነት ነጻ እንዳደረጋቸው በሚመስል መልኩ ሙሴ ይናገራል። አ.ት፡ “አድነሃቸዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በታላቅነትህ
“ታላቅነት” የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ታላቅ ኃይል የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “በታላቅ ኃይልህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በብርቱ እጅ
እዚህ ጋ “ብርቱ እጅ” የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ኃይል ነው። ተመሳሳዮቹን ቃላት በዘዳግም 4:34 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። አ.ት፡ “በብርቱ ኃይልህ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 9:27

አስብ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “አስታውስ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

እኛን ከዚያ ያመጣህበት ያ ምድር
“ያ ምድር” የሚሉት ቃላት የግብፅን ሕዝብ የሚያመለክቱ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ናቸው። “ስለዚህ የግብፅ ሰዎች” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ይላሉ
“ሊሉ ይችላሉ”

በታላቅ ኃይልህና በተዘረጋች ጉልበትህ
እነዚህ ሐረጎች መሠረታዊ አሳባቸው አንድ ሆኖ ሕዝቡን ለማዳን እግዚአብሔር በተጠቀመበት ታላቅ ኃይሉ ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ። (See: Doublet)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 10

1 በዚያን ጊዜም እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ፦ እንደ መጀመሪያ ያሉትን ሁለት የድንጋይ ጽላቶች ጠርበህ ወደ እኔ ወደ ተራራ ውጣ፤ ለአንተም የእንጨት ታቦት ሥራ። **2** በሰበርሃቸው በመጀመሪያዎቹ ጽላቶች ላይ የነበሩትን ቃላት በእነዚህ ጽላቶች ላይ እጽፋለሁ፤ አንተም በታቦቱ ውስጥ ታደርጋቸዋለህ። **3** ከግራርም እንጨት ታቦትን ሠራሁ፥ እንደፊተኞቹም ሁለት የድንጋይ ጽላቶች ጠረብሁ፥ ሁለቱንም ጽላቶች በእጄ ይዤ ወደ ተራራው ወጣሁ። **4** በተራራው ሥር የጉባዔው ቀን እግዚአብሔር በተራራው ላይ በእሳት መካከል ሆኖ የተናገራችሁን አሥርቱን ቃላት በመጀመሪያ ተጽፈው እንደ ነበረ በጽላቶቹ ላይ ጻፈ፤ ከዚያም እግዚአብሔር እነርሱን ለእኔ ሰጠኝ። **5** ተመልሼም ከተራራው ወረድሁ፤ ጽላችቶችንም በሠረሁት ታቦት ውስጥ አደረግኋቸው፤እግዚአብሔርም እንዳዘዘኝ በዚያ ሆኑ። **6** የእስራኤልም ልጆች ከብኤሮት ብኔ ያዕቃን ወደ ሞሴራ ተጓዙ። በዚያ አሮን ሞተ፥ በዚያም ተቀበረ፥ በእርሱም ፋንታ ልጁ አልዓዛር ካህን ሆኖ አገለገለ። **7** ከዚያም ወደ ጉድጎዳ ተጓዙ፤ከጉድጎዳም ወደ ውኃ ምንጮች ምድር ወደ ዮጥባታ ተጓዙ። **8** በዚያን ጊዜም እግዚአብሔር የሌዊን ነገድ እግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ታቦት ይሸከሙና እርሱንም እንዲያገለግሉ፥ በፊቱም ይቆሙ ዘንድ በስሙም እንዲባርኩ መረጠ። **9** ስለዚህ ለሌዊ ከወንድሞቹ ጋር ክፍልና ርስት የለውም፤ አምላካችሁ እግዚአብሔር እንደ ተናገረው እግዚአብሔር ርስቱ ነው። **10** በተራራውም ላይ እንደ መጀመሪያውም አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ቆየሁ። እግዚአብሔርም እንደገናም ሰማኝ፤ እግዚአብሔርም ሊያጠፋችሁ አልፈለገም። **11** እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ፦ ተነሥተህ በሕዝቡ ፊት ሆነህ ሕዝቡን በጉዞው ምራው፤ ለአባቶቻቸው የማለሁላቸውን ምድር ሄደው ይገባሉ። **12** እስራኤል ሆይ፥ አሁንስ አምላክህን እግዚአብሔርን ትፈራ ዘንድ በመንገዱም ሁሉ ትሄድ ዘንድ፥ አምላክህንም እግዚአብሔርን ትውድድ ዘንድ፥ በፍጹም ልብህ፥ በፍጹምም ነፍስህ ታመልከው ዘንድ መልካምም እንዲሆንልህ **13** ዛሬ ለአንተ የማዘዘውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝና ሥርዓት ትጠብቅ ዘንድ ከሆነ በቀር እግዚአብሔር አምላክህ ከአንተ የሚፈልገው ምንድን ነው? **14** እነሆ፥ ሰማይና ሰማየ ሰማያትም፥ ምድርም በእርስዋም ያለው ሁሉ የእግዚአብሔር የአምላካችሁ ነው። **15** ብቻ እግዚአብሔር ስለ አባቶቻችሁ ደስ ተሰኝቶአል፥ እነርሱንም ወድዶቸዋል፤ ከእነርሱም በኋላ እናንተን ዘራችሁን እንደ ዛሬው ሁሉ ከአሕዝብ ሁሉ መካከል መረጣችሁ። **16** ስለዚህ እናንተ የልባችሁን ሸለፈት ግረዙ፥ አንገተ ደንዳኖች አትሁኑ። **17** እግዚአብሔር አምላካችሁ የአማልክት አምላክ የጌቶችም ጌታ፥ ታላቅ አምላክ ኃያልም የሚያስፈራም በፍርድ የማያደላ፥ መማለጃም የማይቀበል። **18** እግዚአብሔር ለድሃ አደጉና ባል ለሞተባት ይፈርዳል፥ ምግብና ልብስም የሚሰጥ ነው። **19** ስለዚህ እናንተም በግብፅ አገር ስደተኞች ስለ ነበራችሁ ስደተኛውን ውደዱ። **20** እግዚአብሔር አምላካችሁን ፍሩ፥ እርሱንም አምልኩት። በእርሱም ተጣበቁ፤ በስሙም ማሉ። **21** እርሱ ዓይኖቻችሁ ያዩትን እነዚህን ታላላቆችንና የሚያስፈሩትን ነገሮች ያደረገላችሁ ክብራችሁ ነው፤ አምላካችሁም ነው፤ ። **22** አባቶቻችሁ ሰባ ሰዎች ሆነው ወደ ግብፅ ሄዱ፤ አሁንም እግዚአብሔር አምላካችሁ ብዛታችሁን እንደ ሰማይ ክዋክብት አደረገ።

Deuteronomy 10:1

በዚያን ጊዜ
“ጸሎቴን ከጨረስኩ በኋላ”

የመጀመሪያው
ይህ የሚያመለክተው ሙሴ የሰበራቸውን የመጀመሪያዎቹን ጽላቶች ስብስብ ነው። አ.ት፡ “ቀድሞ በነበሩህ ጽላቶች” (See: Ellipsis እና ደረጃን አመልካች ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

በተራራው
ይህ የሲና ተራራን ያመለክታል።

Deuteronomy 10:3

የመጀመሪያው
ይህ የሚያመለክተው ሙሴ የሰበራቸውን የመጀመሪያዎቹን ጽላቶች ስብስብ ነው። አ.ት፡ “ቀድሞ በነበሩኝ ጽላቶች” (Ellipsis እና ደረጃን አመልካች ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ወደ ተራራው ወጣ
“ወደ ሲና ተራራ ወጣ”

ከእሳቱ መካከል
እግዚአብሔር እንደ ሰው በእሳት መካከል ቆሞ በታላቅ ድምፅ የሚናገር ይመስል ነበር። ይህንን በዘዳግም 9፡10 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

በጉባዔው ቀን
የነገር ስም የሆነው “ጉባዔ” “በአንድነት መሰብሰብ” በሚል ግሥ መነገር ይችላል። ይህንን በዘዳግም 9:10 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Deuteronomy 10:5

ተመለስኩኝ
እዚህ ጋ “እኔ” የሚያመለክተው ሙሴን ነው።

ከተራራው ወረድኩ
x

Deuteronomy 10:6

የእስራኤል ሕዝብ -- የውሃ ምንጮች ወዳሉባት ምድር
ይህ የእስራኤል ሕዝብ ወዴት እንደተጓዙ ዳራዊ መረጃ ይሰጣል። አሮንን በሞሴራ ተፈጥሮአዊ ሞት መሞቱን ደግሞ ያስታውቃል። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ከብኤሮት ብኔያዕቃን ወደ ሞሴራ -- ጉድጎዳ -- ዮጥባታ
እነዚህ የእስራኤል ሕዝብ በምድረ በዳ በነበሩበት ጊዜ የሄዱባቸው የተለያዩ ቦታዎች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ብኤሮት ብኔያዕቃን
ተርጎሚው፣ “’ብኤሮት ብኔያዕቃን’ የሚለው ስም ‘የያዕቃን ሰዎች የውሃ ጉድጓድ’ ማለት ነው” የሚል የግርጌ ማስታወሻ መጨመር ይኖርባቸው ይሆናል።

በዚያ ተቀበረ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እርሱን የቀበሩት በዚያ ነው” ወይም “እስራኤላውያን በዚያ ቀበሩት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

አልዓዛር
ይህ የአሮን ልጅ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Deuteronomy 10:8

ያገለግለው ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት እንዲቆም
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። “እግዚአብሔር የሚያዘውን መስዋዕት እንዲያቀርብ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በስሙ
እዚህ ጋ “ስም” ሥልጣንን ያመለክታል። አ.ት፡ “የእግዚአብሔር ተወካዮች ሆነው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እንደዛሬው
“ዛሬ እንደሚያደርጉት”

የመሬት ድርሻም ሆነ ርስት
የሌዊ ነገድ ወደዚያ በደረሱ ጊዜ ከተስፋይቱ ምድር ድርሻቸውን አልተቀበሉም። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም በይበልጥ ግልጽ መደረግ ይችል ይሆናል።(See: Assumed Knowledge and Implicit Informa- tion)

እግዚአብሔር ርስቱ ነው
እግዚአብሔር ሌዊና ተወላጆቹ ከእርሱ ጋር ስለሚኖራቸው የተለየ ዝምድና ሲናገር ራሱን ሊወርሱት እንደሚችሉ አንዳች ነገር አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “እነርሱ የሚኖራቸው እግዚአብሔር ነው” ወይም “እግዚአብሔር እርሱን እንዲያገለግሉት ይፈቅድላቸዋል፣ በዚያም አገልግሎት የሚያስፈልጋቸውን ያቀርብላቸዋል”

አምላክህ እግዚአብሔር
እዚህ ጋ፣ ሙሴ እስራኤላውያንን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “የአንተ” የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)

ነገረው
“ለሌዊ ነገድ ተናገራቸው”

Deuteronomy 10:10

እንደ መጀመሪያው ጊዜ
“አንደኛ” የአንድ መደበኛ ቁጥር ነው። እዚህ ጋ፣ ሙሴ ለመጀመሪያ ጊዜ የድንጋይ ጽላቶችን ከእግዚአብሔር ለመቀበል ወደ ሲና ተራራ የወጣበትን ያመለክታል” (መደበኛ ቁጥር የሚለውን ተመልከት)

አርባ ቀንና አርባ ሌሊት
“40 ቀንና 40 ሌሊት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ሊያጠፋህ
ሙሴ እስራኤላውያንን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “አንተ” የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)

ምድሪቱን እንዲወርሱ
“ምድሪቱን ውሰድ” ወይም “ምድሪቱን ተረከብ”

ለአባቶቻቸው
ይህ የሚያመለክተው አብርሃምን፣ ይስሐቅንና ያዕቆብን ነው።

ልሰጣቸው
“የምሰጥህን፣ ለአባቶቻቸው”

Deuteronomy 10:12

አሁንም እስራኤል
እዚህ ጋ “እስራኤል” የሚለው በፈሊጣዊ አነጋገር የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል። አ.ት፡ “አሁንም፣ የእስራኤል ሕዝብ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ የሚፈልገው ምንድነው? መልካም እንዲሆንልህ ትፈራው ዘንድ እንጂ
ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ ለማስተማር በጥያቄ ይጠቀማል። ይህ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “አምላክህ እግዚአብሔር እንድታደርገው የሚፈልገው ይህንን ነው፤ መልካም እንዲሆንልህ ትፈራው ዘንድ” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

በመንገዱም ሁሉ ትሄድ ዘንድ
እግዚአብሔርን መታዘዝ በመንገድ ላይ እንደመሄድ መሆኑን ሙሴ ይናገራል። አ.ት፡ “ትዕዛዙን ሁሉ ትጠብቅ ዘንድ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በሙሉ ልብህና በሙሉ ነፍስህ
እዚህ ጋ፣ “ልብ” እና “ነፍስ” የሰውን ውስጣዊ ማንነት የሚመለከት ፈሊጣዊ ንግግር ነው። እነዚህ ሁለት ሐረጎች “በፍጹም” ወይም “በቅንነት” ለማለት በአንድነት ጥቅም ላይ ውለዋል። እነዚህን ሐረጎች በዘዳግም 4፡29 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና Doublet የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 10:14

ተመልከት
“ልነግርህ ያለሁት እውነትና ጠቃሚ ስለሆነ ለ -- አስተውል”

ሰማይ -- ምድር
እነዚህ ቃላት ሁለት ጽንፎች ተጣምረው በሁሉም ቦታ ያሉ ሁሉም ነገሮች የእግዚአብሔር መሆናቸውን ያሳያሉ። (See: Merism)

የሰማይ ሰማያት
ይህ በሰማያት ያሉትን ከፍ ያሉ ስፍራዎች ያመለክታሉ። በሰማያት ያሉ ነገሮች በሙሉ የእግዚአብሔር ናቸው።

መርጧችኋል
እዚህ ጋ፣ “አንተ” የሚለው ቃል እስራኤላውያንን በሙሉ የሚመለከት በመሆኑ ብዙ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)

Deuteronomy 10:16

ስለሆነም
“በዚህ ምክንያት”

የልባችሁን ሸለፈት ግረዙት
“ሸለፈት” የሚለው ቃል በመገረዝ ጊዜ የሚወገደውን የወንድ አካል ሸፋን ያመለክታል። እዚህ ጋ፣ ሙሴ የሚያመለክተው መንፈሳዊ መገረዝን ነው። ይኸውም፣ ሕዝቡ ከሕይወታቸው ኃጢአትን ማስወገድ አለባቸው ማለት ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የአማልክት አምላክ
“ገናናው እግዚአብሔር” ወይም “ብቸኛው እውነተኛ አምላክ”

የጌቶች ጌታ
“ገናናው ጌታ” ወይም “ታላቁ ጌታ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የሚያስፈራው
“ሰዎች እንዲፈሩ የሚያደርጋቸው”

Deuteronomy 10:18

አባት ለሌላቸው በፍትሕ ይፈርዳል
“ሰዎች አባት የሌላቸውን በፍትሐዊነት እንዲይዙ እግዚአብሔር ያረጋግጣል”

አባት የሌላቸው
እነዚህ ወላጆቻቸው የሞቱባቸውና የሚንከባከባቸው ዘመድ የሌላቸው ልጆች ናቸው።

መበለት
እውነተኛ መበለት ባሏ የሞተባትና በእርጅና ዕድሜዋ የሚረዳት ልጅ የሌላት ሴት ናት።

ስለዚህ
“በዚህ ምክንያት”

Deuteronomy 10:20

እርሱን አምልከው
“ልታመልከው የሚገባህ እርሱን ነው”

ከእርሱ ጋር ተጣበቅ
ከእግዚአብሔር ጋር መልካም ግንኙነት መኖርና በእርሱ ላይ ሙሉ በሙሉ መታመን ከእግዚአብሔር ጋር መጣበቅ በሚል መልኩ ተነግሯል። አ.ት፡ “በእርሱ ላይ መታመን አለብህ” ወይም “ልትታመንበት የሚገባህ በእርሱ ላይ ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በስሙም ማል
በእግዚአብሔር ስም መማል ማለት እግዚአብሔርን የተደረገው መሐላ መሠረት ወይም ኃይል ማድረግ ማለት ነው። እዚህ ጋ፣ “ስም” የሚወክለው እግዚአብሔርን ራሱን ነው። በዘዳግም 6፡13 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ትምላለህ፣ እግዚአብሔር እንዲያጸናውም ትጠይቀዋለህ” ወይም “በምትምልበት ጊዜ ስሙን ትጠራለህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ዐይኖችህ ያዩትን
እዚህ ጋ፣ “ዐይኖች” የሚያመለክተው የሰውን ሁለንተና ነው። አ.ት፡ “አንተ ራስህ ያየኸውን” (See: Synecdoche)

እርሱ ምስጋናህ ነው
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች 1) “ልታመሰግን የሚገባህ እርሱን ነው” ወይም 2) “አንተ ስለምታመሰግነው ሌሎች ሕዝቦች ያመሰግኑሃል”

Deuteronomy 10:22

ወደ ግብፅ ወረዱ
“በስተደቡብ ወደ ግብፅ ወረዱ” ወይም “ወደ ግብፅ ሄዱ”

ሰባ ሰዎች
“70 ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

እንደ ሰማይ ከዋክብት አብዝቶሃል
ይህ ከሙሴ ጋር የነበሩት እስራኤላውያን ቁጥራቸው እጅግ ብዙ እንደነበር አጽንዖት ይሰጣል። አ.ት፡ “መቁጠር ከምትችለው በላይ” (See: Simile)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 11

1 ስለዚህ እግዚአብሔር አምላካችሁን ውዱዱት፥ ሁልጊዜም መመሪያዎቹን፥ ሥርዓቶቹን፥ ድንጋጌዎችንና ትእዛዛትን ጠብቁ። 2 የእግዚአብሔርን የአምላካችሁን
ቅጣት፥ታላቅነቱን፥ ኃያልነቱን፥ የተዘረጋውንም ክንዱን፥ ላላወቁት ወይም ላላዩት ልጆቻችሁ እየተናገርሁ እንዳልሆነ አስታውሉ፤ 3 በግብፅም መካከል በንጉሡ
በፈርዖንና በአገሩ ሁሉ ላይ ያደረጋውን ተአምራቱንና ሥራውን፥ 4 በተከተሉአችሁም ጊዜ በግብፅ ጭፍራ፥ በፈረሶቻቸውና በሰረገሎቻቸው ያደረገውን፥በኤርትራ
ባሕር ውኃ እንዳሰጠማቸው፥ እግዚአብሔርም እስከ ዛሬ ድረስ እንዳጠፋቸው፥ 5 ወደዚህ ስፍራ እስከትመጡ ድረስ በምድረ በዳ ያደረገላችሁን፥አይተዋል። 6
በእስራኤልም ሁሉ መካከል ምድር አፍዋን ከፍታ እነርሱንና ቤተ ሰቦቻቸውን ድንኳኖቻቸውንም ለእነርሱም የነበራቸውን ሁሉ በዋጠቻቸው በሮቤል ልጅ፥
በኤልያብ ልጆች፥ በዳታንና በአቤሮን እግዚአብሔር ያደረገውን አላዩም። 7 ነገር ግን እግዚአብሔር ያደረገውን ታላቁ ሥራ ሁሉ ዓይኖቻቸው አይተዋል። 8
እንግዲህ እንድትጠነክሩ ትወርሱአትም ዘንድ ወደምትሄዱባት ምድር እንድትሄዱ ዛሬ ለእናንተ የማዘዘውን ትእዛዝ ሁሉ ጠብቁ፤ 9 እግዚአብሔርም
ለአባቶቻችሁና ለዘራቸው ይሰጣቸው ዘንድ በማለላቸው ወተትና ማርም በምታፈስሰው ምድር ዕድሜአችሁ እንዲረዘም ትእዛዘትን ጠብቁ። 10 ትወሱአት ዘንድ
የምትሄዱባት ምድር በመጣችሁበት በግብፅ አገር ዘር እንደዘራችሁና ውኃ በእግራችሁ ታጠጡ እንደነበረ፥ እንደ አትክልት ቦታ አይደለችም፤ 11 ነገር ግን
ትወርሱአት ዘንድ ተሻግራችሁ የምትገቡባት ምድር ኮረብታና ሸለቆ ያለባት በሰማይ ዝናብ ውኃ የምትጠጣ አገር ናት፤ 12 አምላካችሁ እግዚአብሔር
የሚንከባከባት፤ ከዓመቱ መጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ የእግዚአብሔር የአምላካችሁ ዓይን ሁልጊዜ በእርስዋ ላይ የሆነ አገር ናት። 13 እንዲህም ይሆናል፤
እናንተ እግዚአብሔር አምላካችሁን ፥ በፍጹም ልባችሁ፥ በፍጹም ነፍሳችሁ፥ ትወድዱና ታገለግሉት ዘንድ ዛሬ የማዝዛችሁን ትእዛዘትን ፈጽማችሁ ብትሰሙ፥ 14
እህላችሁን፥ ወይናችሁን፥ ዘይታችሁን ትሰበስቡ ዘንድ በየዚዜው ለምድራችሁ የመጀመሪያውንና የኋለኛውን የወቅቱን ዝናብ ይሰጣችኋል። 15 በሜዳ
ለእንስሶቻችሁም ሣርን እሰጣለሁ፤ትበላላችሁ፣ ትጠግባላችሁም። 16 ልባችሁ እንዳይስት ፈቀቅ እንዳትሉ ሌሎችንም አማልክት እንዳታመልኩ፥
እንዳትሰግዱላቸውም፥ 17 የእግዚአብሔርም ቁጣ እንዳይነድድባችሁ ዝናብ እንዳይዘንብ ምድሪቱም ፍሬዋን እንዳትሰጥ ሰማይን እንዳይዘጋባችሁ፤
እግዚአብሔርም ከሚሰጣችሁ ከመልካሚቱ ምድር ፈጥናችሁ እንዳትጠፉ ተጠንቀቁ። 18 ስለዚህ እነዚህን ቃሎች በልባችሁና በነፍሳችሁ አኑሩ፤እነርሱንም
ለምልክት በእጃችሁ ላይ እሰሩአቸው፥ በዓይኖቻችሁም መካከል እንደ ክታብ ይሁኑላችሁ። ፥ 19 በቤታችሁም ስትቀመጡ፥ በመንገድ ላይም ስትሄዱ፥ ስትተኙ፥
ስትነሡም ልጆቻችሁንም አስተምሩአቸው። 20 በቤታችሁ መቃኖችና በከተሞቻችሁ በሮች ላይ ጻፈው፥ 21 እግዚአብሔርም እንዲሰጣቸው ለአባቶቻችሁ
በማለላቸው ምድር፥ እንደ ሰማይ ቀኖች በላይ በምድር ከፍ ያሉና የልጆቻችሁም ዘመን የረዘመ ይሁን ። 22 እግዚአብሔር አምላካችሁን ትወድዱ ዘንድ
በመንገዱም ሁሉ ትሄዱ ዘንድ፥ ከእርሱም ጋር ትጣበቁ ዘንድ፥ ዛሬ ለእናንተ የማዝዘውን ትእዛዘት ሁሉ ብትጠብቁ፥ ብታደርጉአቸውም፥ 23 እግዚአብሔር
እነዚህን አሕዛብ ሁሉ ከፊታችሁ ያወጣል፤ ከእናንተም የሚበልጡትን፥ የሚበረቱትንም አሕዛብ ትወርሳላችሁ። 24 የእግራችሁ ጫማ የሚረግጥበት ስፍራ ሁሉ
ለእናንተ ትሆናለች፤ ከምድረ በዳም ከሊባኖስ ወንዝ፥ ከኤፍራጥስ ወንዝ ጀምሮ እስከ ምዕራብ ባሕር ድረስ ዳርቻችሁ ይሆናል። 25 በእናንተም ፊት ማንም
መቆም አይችልም፤ አምላካችሁ እግዚአብሔር እርሱ እንደ ተናገራችሁ ማስፈራታችሁና ማስደንገጣችሁ በምትረግጡበት ምድር ሁሉ ላይ ያኖራል። 26 እነሆ፥
ዛሬ በፊታችሁ በረከትንና መርገምን አኖራለሁ፤ 27 በረከትም የሚሆነው፥ እኔ ዛሬ ለእናንተ የማዝዘውን የእግዚአብሔር የአምላካችሁን ትእዛዝ ብትሰሙ 28
እንዲሁም መርገም የሚሆነው የእግዚአብሔር የአምላካችሁን ትእዛዝ ባትሰሙ፥ ዛሬም ካዘዝኋችሁ መንገድ ፈቀቅ ብትሉ፥ ሌሎችንም የማታውቋቸውን አምልክት
ብትከተሉ ነው። 29 እግዚአብሔር አምላካችሁ ትወሱአት ዘንድ እናንተም ወደምትሄዱባት ምድር ባገባሃችሁ ጊዜ፥ በረከቱን በገሪዛን ተራራ፥ መርገሙንም
በጌባል ተራራ ይሆናል። 30 እነርሱም በዮርዳኖስ ማዶ ከምዕራብ ካለው መንገድ በኋላ በዓረባ በሚኖሩት በከነዓናውያን ምድር በጌልገላ ፊት ለፊት በሞሬ
የአድባር ዛፍ አጠገብ አይደለምን? 31 እግዚአብሔር አምላካችሁ የሚሰጣችሁን ምድር ትወርሱ ዘንድ ዮርዳኖስን ትሻገራላችሁ፥ ትወርሱአታላችሁ፥
ትቀመጡባታላችሁም። 32 እኔም ዛሬ በፊታችሁ የማኖራውን ሥርዓትና ድንጋጌዎች ሁሉ ታደርጉ ዘንድ ጠብቁ።

Deuteronomy 11:1

ሁልጊዜ ጠብቅ
“ሁልጊዜ ታዘዝ”

Deuteronomy 11:2

ያላወቁትም ሆኑ ያላዩት
“ያልተለማመዱት”

ጽኑ እጁን ወይም የተዘረጋች ክንዱን
እዚህ ጋ፣ “ጽኑ እጅ” እና “የተዘረጋች ክንድ” የተባሉት የእግዚአብሔርን ኃይል የሚያመለክቱ ዘይቤአዊ አነጋገሮች ናቸው። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 4:34 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። አ.ት፡ “ወይም ጽኑ ኃይሉን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በግብፅ መካከል
“በግብፅ ውስጥ”

በሀገሩ ሁሉ ላይ
እዚህ ጋ፣ “ሀገር” የሚወክለው ሕዝቡን ነው። አ.ት፡ “በሕዝቡ ሁሉ ላይ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 11:4

እርሱ ያደረገውን አላዩም
“እግዚአብሔር ያደረገውን ልጆቻችሁም ቢሆኑ አላዩም”

በግብፅ ሰራዊት
“በግብፅ ወታደሮች”

እናንተን አሳደዷችሁ
እዚህ ጋ “እናንተ” ማለት ከ40 ዓመታት በፊት የነበሩትን እስራኤላውያን ማለት ነው።

ወደዚህ ስፍራ
ይህ ማለት ሙሴ ወደ ከነዓን ከመሻገራቸው በፊት ሲናገራቸው የነበረበት ከዮርዳኖስ ሸለቆ አጠገብ ያለ ሜዳ ነው።

Deuteronomy 11:6

የኤልያብ ልጆች ዳታንና አቤሮን
ሙሴ የሚያመለክተው ዳታንና አቤሮን በሙሴና በአሮን ላይ ያመፁበትን ያለፈውን ጊዜ ሁነት ነው። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም በይበልጥ ግልጽ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መደረግ ይችላል። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ዳታን -- አቤሮን -- ኤልያብ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የሮቤል ልጅ
“የሮቤል ተወላጆች”

መሬት አፏን ከፍታ ዋጠቻቸው
እግዚአብሔር ምድሪቱ ተሰንጥቃ ሰዎች እንዲወድቁበት ማድረጉ ምድር አፍ እንዳላትና ሰዎችን የመዋጥ ችሎታ እንዳላት ተደርጎ ተነግሯል። (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

የተከተላቸው ሕይወት ያለው ሁሉ
ይህ የሚያመለክተው አገልጋዮቻቸውንና እንስሶቻቸውን ነው።

በእስራኤላውያን ሁሉ መካከል
ይህ ማለት በዳታን፣ በአቤሮን፣ በእንስሶቻቸውና በንብረታቸው ላይ ስለሆነው ነገር የእስራኤል ሕዝብ በሙሉ ምስክሮች ናችው።

ነገር ግን ዐይኖቻችሁ አይተዋል
እዚህ ጋ “ዐይኖች” የሚወክሉት የሰውን ሁለንተና ነው። አ.ት፡ “ነገር ግን እናንተ አይታችኋል” (See: Synecdoche)

Deuteronomy 11:8

ምድሪቱን መውረስ
“ምድሪቱን መውሰድ

ለመውረስ የምትገቡባት
የእስራኤል ሕዝብ የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻግረው ወደ ከነዓን መግባት ስለነበረባቸው “የምትገቡባት” የሚለው ሐረግ ጥቅም ላይ ውሏል።

ረጅም ቀናት
ረጅም ቀናት ረጅም ዕድሜን የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 4:26 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ረጅም ዘመን መኖር እንድትችል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ወተትና ማር የምታፈስ ምድር
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በዘዳግም 6:3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የተትረፈረፈ ወተትና ማር የሚፈስባት ምድር” ወይም “ለከብት ዕርባታና ለእርሻ ምርጥ የሆነ ምድር” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 11:10

በእግርህ ውሃ እንዳጠጣሃት
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች 1) “እግር” ወደ እርሻዎቹ ውሃ የመሸከምን ከባድ ሥራ የሚወክል ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ውሃ ለማጠጣት ምድከሙን” ወይም 2) ውሃ የጠጣውን እርሻ በእግሮቻቸው መገልበጥ ነበረባቸው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እጽዋት የሚበቅሉበት ስፍራ
“የአትክልት ስፍራ” ወይም “የልዩ ልዩ አትክልት ስፍራ”

ከሰማያት የዝናብን ውሃ የምትጠጣ
ምድሪቱ ብዙ ዝናብ መቀበሏና መምጠጧ ልክ ምድሪቱ ውሃውን እንደምትጠጣው ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “ከሰማይ የሚወርደው ዝናብ የተትረፈረፈ ውሃ ይሰጣታል” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

የአምላክህ የእግዚአብሔር ዐይን ዘወትር በእርሷ ላይ ነው
እዚህ ጋ “ዐይኖች” የሚወክሉት ትኩረትንና ክብካቤን ነው። አ.ት፡ “አምላክህ እግዚአብሔር ዘወትር ይመለከታታል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከዓመቱ መጀመሪያ እስከ ዓመቱ መጨረሻ ድረስ
እዚህ ጋ “መጀመሪያ” እና “መጨረሻ” የሚሉት ሁለት ጽንፎች በአንድነት ጥቅም ላይ የዋሉት ዓመቱን በሙሉ ለማለት ነው። አ.ት፡ “ሙሉውን ዓመት ባለማቋረጥ” (See: Merism)

Deuteronomy 11:13

ብታደርጉ ይሆናል
ይህ ማለት እስራኤላውያን እግዚአብሔር ያዘዛቸውን ከታዘዙ እርሱ የሰጣቸውን ተስፋ ይፈጽምላቸዋል።

እኔ የማዝህን
እዚህ ጋ “እኔ” የሚያመለክተው ሙሴን ነው።

በሙሉ ልብህና በሙሉ ነፍስህ
“በሙሉ ልብህ” የሚለው የአነጋገር ዘይቤ “በፍጹም” ማለት ሲሆን “በ . . . ነፍስህ” ማለት “በሁለንተናህ” ማለት ነው። እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ይህንን በዘዳግም 4:29 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። አ.ት፡ “በሁለንተናህ” ወይም “በሙሉ ኃይልህ” (የአነጋገር ዘይቤ እና Doublet የሚለውን ተመልከት)

ለምድርህ ዝናብን በወቅቱ እሰጣለሁ
“በተገቢው ወቅት በምድርህ ላይ ዝናብ እንዲዘንብ አደርጋለሁ”

እሰጣለሁ
እዚህ ጋ “እኔ” የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው። ይህ በሦስተኛ መደብ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ይሰጣችኋል” ወይም “እርሱ ይሰጣችኋል”

የመጀመሪያውንና የኋለኛውን ዝናብ
ይህ የሚያመለክተው በመጀመሪያ በዘር ወቅት የሚዘንበውን ዝናብና ሰብሉን ለምርትነት የሚያበቃውን ዝናብ ነው። አ.ት፡ “የመከርንና የፀደይን ዝናብ” ወይም “ዝናብን በወቅቱ”

Deuteronomy 11:16

ለራሳችሁ ተጠንቀቁ
“ተጠንቀቁ” ወይም “ልብ በሉ”

ልባችሁ እንዳይታለል
እዚህ ጋ “ልብ” የሚወክለው የአንድን ሰው ምኞት ወይም አሳብ ነው። ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ምኞታችሁ እንዳያታልላችሁ” ወይም “ራሳችሁን እንዳታታልሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ትመለሱና ሌሎች አማልክትን ታመልካላችሁ
እግዚአብሔርን መተውና ሌሎች አማልክትን ማምለክ ሰው በአካሉ ከእግዚአብሔር ተለይቶ በሌላ አቅጣጫ እንደሚሄድ ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ሌሎች አማልክትን ማምለክ ትጀምራላችሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የእግዚአብሔር ቁጣ በእናንተ ላይ እንዳይነድ
የእግዚአብሔር መቆጣት መንደድ እንደ ጀመረ እሳት ተደርጎ ተነግሯል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ስለዚህ እግዚአብሔር በእናንተ ላይ እንዳይቆጣ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምድር ፍሬዋን እንዳትሰጥና ዝናብን እንዳይሰጡ ሰማያትን እንዳይዘጋቸው
እግዚአብሔር ዝናብ ከሰማይ እንዳይወርድ ማድረጉ እርሱ ሰማይን እንደሚዘጋ ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “በምድሪቱ ላይ ሰብል እንዳይበቅል ዝናብ ከሰማይ እንዳይዘንብ እንዳያደርግ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 11:18

እነዚህን ቃሎቼን በልባችሁና በነፍሳችሁ ውስጥ አኑሩ
ሙሴ የሚያዝዘውን ዘወትር የሚያስብና የሚያመዛዝን ሰው ልቡና ነፍሱ መያዣ ዕቃ እንደሆኑና የሙሴ ቃላት መያዣውን እንደሚሞላ አንዳች ይዘት ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ አ.ት፡ “የምነግራችሁን እነዚህን ቃላት ለማስታወስ በጣም ተጠንቀቁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እነዚህን ቃሎቼን
“የሰጠኋችሁን እነዚህን ትዕዛዛት”

ልባችሁንና ነፍሳችሁን
እዚህ ጋ “ልብ” እና “ነፍስ” የሚወክሉት የአንድን ሰው አዕምሮ ወይም አሳብ ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እሰሯቸው
“እነዚህን ቃላት እሰሯቸው”። ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር በብራና ላይ የሚጽፍን፣ ብራናውን በትንሽ ኪስ መሰል ማስቀመጫ የሚከተውንና የሚያስረውን ሰው ይወክላል። ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር በሌላ መልኩ ሕዝቡ የሙሴን ትዕዛዛት ለመታዘዝ መጠንቀቅ አለበት የሚል ትርጉም ያለው ዘይቤአዊ አነጋገር ሊሆን ይችላል። ተመሳሳዮቹን ሐረጎች በዘዳግም 6:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእጅህ ላይ እንደ ምልክት
“ሕጌን እንድታስታውስ እንደሚያደርግህ አንዳች ነገር”

በዐይኖችህ መካከል እንደ ክታብ ይሁኑልህ
“ቃሎቼ በዐይኖችህ መካከል እንደ ክታብ ይሆኑልህ”። ይህ የሙሴን ቃላት በብራና ላይ የሚጽፍ፣ ብራናውን በትንሽ ኪስ መሰል ማስቀመጫ የሚከትና በዐይኖቹ መካከል የሚያስርን ሰው የሚወክል ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር በሌላ መልኩ ያ ሰው ሙሴ የሚያዘውን ትዕዛዝ ሁሉ ለመታዘዝ መጠንቀቅ አለበት የሚል ትርጉም ያለው ዘይቤአዊ አነጋገር ሊሆን ይችላል። በዘዳግም 6:8 ላይ ተመሳሳዮቹን ሐረጎች እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ክታቦች
አንድ ሰው በግምባሩ ላይ የሚያስራቸው ጌጣ ጌጦች

በቤትህ ስትቀመጥ፣ በመንገድ ስትሄድ፣ ስትተኛና ስትነሣ
“በቤትህ” እና “በመንገድ” የሚሉትን የተለያዩ ቦታዎች መጠቀምና ተቃራኒዎቹ “ስትተኛ” እና “ስትነሣ” ሁልጊዜ በሁሉ ቦታ ማለትን ይወክላሉ። የእስራኤል ሕዝቦች በየትኛውም ጊዜና በየትኛውም ቦታ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ማጥናትና ለልጆቻቸው ማስተማር ነበረባቸው። (See: Merism)

Deuteronomy 11:20

በቤትህ መቃኖችና በከተማህ መግቢያ በሮች ላይ ጻፋቸው
እነዚህን ቃላት በዘዳግም 6:9 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

የአንተ ዕድሜና የልጆችህ ዕድሜ እንዲረዝም
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር አንተንና ልጆችህን ረጅም ዕድሜ እንድትኖሩ እንዲያደርጋችሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ለአባቶችህ
ይህ አብርሃምን፣ ይስሐቅንና ያዕቆብን ያመለክታል።

ከምድር በላይ እስከ ሰማይ የሚደርስ ዕድሜ ይሰጣቸው ዘንድ
ሕዝቡ በምድሪቱ የሚኖሩበት ዘመን ሰማይ ከምድር በላይ ለምን ያህል ጊዜ ከመቆየቱ ጋር ተነጻጽሯል። ይህ “ለዘላለም” ብሎ የመናገር መንገድ ነው። አ.ት፡ “ለዘላለም የእነርሱ እንዲሆን ሊሰጣቸው” ወይም “በዚያ ለዘላለም እንዲኖሩ ለመፍቀድ” (See: Simile)

Deuteronomy 11:22

ታደርጓቸው ዘንድ እኔ የማዛችሁን እነዚህን ትዕዛዛት ሁሉ በትጋት ብትጠብቁ
“ያዘዝኳችሁን ሁሉ ለመፈጸም ብትጠነቀቁ”

በመንገዶቹ ሁሉ ትሄዱ
አንድ ሰው እንዴት መኖርና ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር መፈለጉ እንደ እግዚአብሔር መንገድ ወይም ጎዳና ተደርጎ ተነግሯል። አንድ ሰው እግዚአብሔርን ሲታዘዝ በእግዚአብሔር መንገድ ወይም ጎዳና እንደሄደ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከእርሱ ጋር ትጣበቁ
ከእግዚአብሔር ጋር የመልካም ግንኙነት መኖርና ሙሉ በሙሉ በእርሱ ላይ መታመን አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚጣበቅ ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “በእርሱ ለመታመን” ወይም “ከእርሱ ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖር”። ተመሳሳዮቹ ቃላት በዘዳግም 10:20 ላይ እንዴት እንደተተረጎሙ ተመልከት። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከአንተ በፊት የነበሩትን እነዚህን ሀገሮች ሁሉ፣ ሀገሮችን ታስለቅቃላችሁ
እዚህ ጋ “ሀገሮች” የሚወክሉት ቀድሞ በከነዓን ይኖሩ የነበሩትን የሕዝብ ወገኖች ነው። አ.ት፡ “ከእናንተ በፊት የነበሩትን እነዚህን የሕዝብ ወገኖች ሁሉ፣ ከሕዝብ ወገኖች ምድሪቱን ትወስዳላችሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከእናንተ ይልቅ ብዙና ኃያላን የሆኑትን
የእስራኤል ሰራዊት በከነዓን ከሚኖሩት የሕዝብ ወገኖች ይልቅ ጥቂትና ደካማ ቢሆኑም እንኳን የእስራኤል ሕዝብ ድል እንዲያደርጉ እግዚአብሔር ያስችላቸዋል።

Deuteronomy 11:24

የእግራችሁ ጫማ የሚረግጠውን ስፍራ ሁሉ
እዚህ ጋ “የእግራችሁ ጫማ” የሚወክለው የሰውን ሁለንተና ነው። አ.ት፡ “የምትሄዱበት ስፍራ ሁሉ” (See: Synec- doche)

ከወንዝ፣ የኤፍራጥስ ወንዝ
“ከኤፍራጥስ ወንዝ”

በፊታችሁ መቆም የሚችል ሰው አይኖርም
“በፊታችሁ መቆም” የሚለው ሐረግ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ማንም ሊያስቆማችሁ አይችልም” ወይም “ማንም ሊቃወማችሁ አይችልም”

አምላካችሁ እግዚአብሔር ማስፈራታችሁንና ማስደንገጣችሁን በምትረግጡት ምድር ሁሉ ላይ ያኖራል
እግዚአብሔር ሕዝቡ በጣም እንዲፈሩ ማድረጉ ፍርሐትና ድንጋጤን እርሱ እንደ ዕቃ በሕዝቡ ላይ እንደሚያኖራቸው በመሰለ መልኩ ተነግሯል። አ.ት፡ “አምላካችሁ እግዚአብሔር በምትሄዱበት ስፍራ ሁሉ ሕዝቡ እንዲፈሯችሁ ያደርጋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ማስፈራታችሁና ማስደንገጣችሁ
“ፍርሐት” እና “ድንጋጤ” የሚሉት ቃላት ትርጉማቸው ተመሳሳይ ሲሆን የፍርሐቱ መጠን ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ። አ.ት፡ “ከእናንተ የተነሣ ከባድ ፍርሐት” (See: Doublet)

በምትረግጡት ምድር ሁሉ ላይ
እዚህ ጋ “ምድሪቱ” የሚለው በምድሪቱ ላይ የሚኖሩትን ሰዎች በሙሉ የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “በምትሄዱበት ስፍራ ሁሉ በሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ላይ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 11:26

ተመልከቱ
“ልብ በሉ”

ዛሬ በረከትን እና መርገምን በፊታችሁ አኖራለሁ
እግዚአብሔር እንዲባርካቸው ወይም እንዲረግማቸው ይፈልጉ እንደሆነ ሕዝቡ እንዲመርጡ መፍቀዱ በረከትና መርገም ሙሴ በፊታቸው እንደሚያስቀምጣቸው ቁሶች ተደርገው ተነግሮላቸዋል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር እንዲባርካችሁ ወይም እንዲረግማችሁ ዛሬ መምረጥ አለባችሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በረከቱ -- መርገሙ --
የነገር ስም የሆነው “በረከት” እና “መርገም” በግሥነት ሊተረጎሙ ይችላሉ። አ.ት፡ “... ካደረጋችሁ እግዚአብሔር ይባርካችኋል፣ ... እግዚአብሔር ይረግማችኋል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ሌሎች አማልክትን ለመከተል እኔ ዛሬ ከማዛችሁ መንገድ ፈቀቅ ብትሉ ግን
ሙሴ ለሕዝቡ የሚነግራቸው የእግዚአብሔር ትዕዛዝ እንደ እግዚአብሔር መንገድ ወይም ጎዳና ሆነው ተነግረዋል። ለእግዚአብሔር ትዕዛዝ ያለመታዘዝ ሌሎች አማልክቶችን ለመከተል በሌላ አቅጣጫ ለመመለስ ከእግዚአብሔር በአካል እንደተለዩ ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “ሌሎች አማልክትን ለማምለክ ዛሬ እኔ የማዛችሁን ትዕዛዝ እምቢ ብትሉ ግን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የማታውቃቸውን ሌሎች አማልክት
ይህ የሚያመለክተው ሌሎች የሕዝብ ወገኖች የሚያመልኳቸውን አማልክት ነው። እስራኤላውያን ራሱን ስለገለጠላቸውና ኃይሉን ስለተለማመዱ እግዚአብሔርን ያውቁታል።

Deuteronomy 11:29

በረከቱን በገሪዛን ተራራ ላይ፣ መርገሙን በጌባል ተራራ ላይ ታስቀምጣላችሁ
በረከቱ እና መርገሙ አንድ ሰው በተራሮች ላይ እንደሚያስቀምጣቸው ቁሶች ተደርገው ተነግሮላቸዋል። አ.ት፡ “ከእናንተ ጥቂቱ በገሪዛን ተራራ አናት ላይ ቆማችሁ እግዚአብሔር እንዲባርካችሁ የሚያስደርገውን ቃል ታውጃላችሁ፣ ሌሎቹ በጌባል ተራራ አናት ላይ በመቆም እግዚአብሔር እንዲረግማችሁ የሚያስደርገውን ቃል ያውጃሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ገሪዛን ተራራ -- ጌባል ተራራ
እነዚህ ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምዕራብ የሚገኙ ተራሮች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

በሞሬ --- ከዮርዳኖስ ማዶ የሚገኙ አይደሉም?
እስራኤላውያን የሚገኙት ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምስራቅ ነው። ሙሴ እነዚህ ተራሮች የሚገኙባቸውን ስፍራዎች ለማስታወስ በጥያቄ መልክ ያቀርባል። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ተደርጎ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እንደምታውቁት ሞሬ የሚገኘው ከዮርዳኖስ ማዶ ነው” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ከዮርዳኖስ ማዶ
“ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምዕራብ”

ከምዕራቡ መንገድ በስተምዕራብ
“በምስራቅ”

በጌልገላ ትይዩ
“ጌልገላ አጠገብ” ይህ ምናልባት ኢያሪኮ ከተማ አጠገብ ያለው ስፍራ ላይሆን ይችላል። ምናልባት ሙሴ ሴኬም አቅራቢያ ያለውን ስፍራ እያመለከተ ይሆናል። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የሞሬ በሉጥ ዛፎች
እነዚህ በጌልገላ አቅራቢያ የሚገኙ የተቀደሱ ዛፎች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 11:31

ሥርዓቶችና ሕግጋት ሁሉ
እነዚህ ሙሴ በዘዳግም 12፡26 የሚሰጣቸው ሥርዓቶችና ሕግጋት ናቸው።

እኔ ዛሬ በፊታችሁ ያስቀመጥኋቸው
እነዚህ አዲስ ናቸው ማለት አይደለም። ሙሴ ከ40 ዓመታት በፊት የሰጣቸውን ሥርዓቶችና ሕግጋት እየከለሰላቸው ነው።

በፊታችሁ ያስቀመጥኋቸው
ሙሴ ለሕዝቡ የሚነግራቸው ሥርዓቶችና ሕግጋት በሕዝቡ ፊት እንደሚያስቀምጣችው ቁሶች ተደርጎ ተነግሮላቸዋል። አ.ት፡ “እኔ የምሰጣችሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 12

1 የአባቶቻችሁ አምላክ እግዚአብሔር እንድትወርሱ በሚሰጣችሁ ምድር፥ ሁልጊዜ በምድር እያላችሁ የምትጠብቁአችሁ ሥርዓትና ድንጋጌዎች እነዚህ ናቸው። 2 እናንተ የምትወርሱአቸው አሕዛብ አማልክታቸውን ያመለኩባቸውን በረጅም ተራሮች በኮረብቶችም ከለምለምም ዛፍ በታች ያለውን ስፍራ ሁሉ ፈጽማችሁ አጥፉአቸው። 3 መሠዊያቸውንም አፍርሱ፥ ሐውልቶቻቸውንም ሰባብሩ፥የማልመኪያ ዐፀዶቻችቸውንም በእሳት አቃጥሉ፥የአማልክታቸውንም የተቀረጹ ምስሎች ቆራርጡአቸው፥ ከዚያም ስፍራ ስማቸውን አጥፉ። 4 እግዚአብሔር አምላካችሁን እንዲህ ባለ ሁኔታ አታምልኩ። 5 ነገር ግን እግዚአብሔር አምላካችሁ ከነገዶቻችሁ ሁሉ ስሙን በዚያ ያኖር ዘንድ ወደዚያ ወደ መረጠው ስፍራ ትመጣላችሁ፥ ማደሪያውንም ትሻላችሁ። 6 ወደዚያም የሚቃጠለውን መሥዋዕታችሁን፥ ሌላም መሥዋዕታችሁንም፥ አሥራታችሁንም፥ በእጃችሁም ያነሣችሁትን ቁርባን፥ ስእለታችሁንም በፈቃዳችሁ የምታቀርቡትን፥ የላማችሁንና የበጋችሁንም በኩራት ውሰዱ። 7 በዚያም በእግዚአብሔር በአምላካችሁ ፊት ብሉ፥ እጃችሁንም በምትዘረጉበት እግዚአብሔር አምላካችሁ በባረካችሁ ነገር ሁሉ እናንተና ቤተ ሰባችሁ ደስ ይበላችሁ። 8 ሰው ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን፥ እኛ በዚህ ዛሬ የምናደርገውን ሁሉ አታደርጉም፥ 9 እግዚአብሔር አምላካችሁ ወደሚሰጣችሁ ዕረፍትና ርስት እስከ ዛሬ ድረስ አልገባችሁምና። 10 ነገር ግን ዮርዳኖስን በተሻገራችሁ ጊዜ እግዚአብሔር አምላካችሁም በሚያወርሳችሁ ምድር በተቀመጣችሁ ጊዜ ያለ ፍርሃትም እንድትኖሩ፥ ከከበቡአችሁ ጠላቶች ሁሉ ዕረፍት በሰጣችሁ ጊዜ በዚያ ጊዜ 11 እግዚአብሔር አምላካችሁ ፥ ስሙ ይጠራበት ዘንድ ወደዚያ ወደ መረጠው ስፍራ እኔ ያዘዝኋችሁን ሁሉ የሚቃጠለውን መሥዋዕታችሁን፥ ሌላም መሥዋዕታችሁን አሥራታችሁንም፥ በእጃችሁ ያነሣችሁትንም ቁርባን፥ ለእግዚአብሔርም ተስላችሁ የመረጣችሁትን ስእልታችሁን ሁሉ ውሰዱ። 12 እናንተም፥ወንዶች ልጆቻችሁና ሴቶች ልጆቻችሁ፥ አገልጋዮቻችሁና የቤት አገልጋዮቻችሁ፥ ከእናንተ ጋር ክፍልና ርስት ስለሌለው በደጆቻችሁ የተቀመጠው ሌዋዊም፥ በአምላካችሁ በእግዚአብሔር ፊት ደስ ይበላችሁ። 13 የሚቃጠለውን መሥዋዕታችሁን በሚታያችሁ ስፍራ ሁሉ እንዳታቀርቡ ተጠንቀቁ። 14 ነገር ግን እግዚአብሔር ከነገዶቻችሁ ከአንዱ ዘንድ በመረጠው ስፍራ በዚያ የሚቃጠለውን መሥዋዕታችሁን አቅርቡ፥ በዚያም የማዝዛችሁን ሁሉ አድርጉ። 15 ይሁን እንጂ እግዚአብሔር አምላካችሁ እንደሰጣችሁ በረከት ሰውነታችሁ እንደ ፈቀደ በደጆቻችሁ ሁሉ ውስጥ አርዳችሁ ብሉ፤ንጹሕም ያልሆነ ሰው እንደ ሚቋና እንደ ዋላ ያለውን ይብላው። 16 ደሙን ግን እንደ ውኃ በምድር ላይ ያፍስሰው፤ ደሙን አትብሉ። 17 የእህላችሁን፥ የወይናችሁን፥ የጠጃችሁን የዘይታችሁንም፥ አሥራት፥ የላማችሁንና የበጋችሁንም በኩራት የተሳላችሁትንም ስእለት ሁሉ በፈቃዳችሁም ያቀረባችሁትን፥ በእጃችሁም ያነሣችሁትን ቁርባን በደጆቻችሁ መብላት አትችሉም። 18 በዚህ ፈንታ እናንተ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም አገልጋዮቻችሁና የቤት አገልጋዮቻችሁ፥በአገራችሁ ደጅ ያለው ሌዋዊ እግዚአብሔር አምላካችሁ በመረጠው ስፍራ በእግዚአብሔር በአምላካችሁ ፊት ብሉት፥ እጃችሁንም በምትዘረጉባችሁ ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር በአምላካችሁ ፊት ደስ ይበላችሁ። 19 በምድራችሁ ላይ በምትኖሩባት ዘመን ሁሉ ሌዋዊውን ቸል እንዳትሉ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። 20 እግዚአብሔር አምላካችሁ እንደ ነገራችሁ አገራችሁን ባሰፋ ጊዜ፥ ሰውነታችሁም ሥጋ መብላት ስለ ወደደ፦ ሥጋ እንብላ፥ ስትሉ እንደ ሰውነታችሁ ፈቃድ ሥጋን ብሉ። 21 እግዚአብሔር አምላካችሁ በዚያ ስሙን ያኖር ዘንድ የመረጠው ስፍራ ከእናንተ ሩቅ ቢሆንም እግዚአብሔር ከሰጣችሁ ከላምና ከበግ መንጋችሁ እንዳዛዝኋችሁ እረዱ፥ እንደ ሰውነታችሁም ፈቃድ ሁሉ በአገራችሁ ደጅ ብሉ። 22 ሚዳቋና ዋላ እንደሚበሉ እንዲሁ ብሉ፥ ንጹሕ ሰው ንጹሕ ያልሆነም ይብለው። 23 ደሙ ሕይወት ነውና፥ ነፍሱንም ከሥጋው ጋር መብላት አይገባችሁምና፥ ደሙን እንዳትበሉ ተጠንቀቁ። 24 በምድር ላይ እንደ ውኃ አፍስሱት እንጂ አትብሉ። 25 በእግዚአብሔር ፊት መልካም የሆነውን ነገር ስታደርጉ ለእናንተ፥ ከእናንተም በኋላ ለልጆቻችሁ መልካም እንዲሆንላችሁ አትብሉ። 26 ነገር ግን የተቀደሰውን ነገራችሁን ስእለታችሁንም ይዛችሁ እግዚአብሔር ወደ መረጠው ስፍራ ሂዱ። 27 የሚቃጠለውንም መሥዋዕታችሁን ሥጋውንና ደሙን በአምላካችሁ በእግዚአብሔር መሠዊያ ላይ አቅርቡ፤ የመሥዋዕታችሁም ደም በእግዚአብሔር በአምላካችሁ መሠዊያ ላይ ይፍሰስ፥ ሥጋውንም ብሉ። 28 በእግዚአብሔር በአምላካችሁ ፊት መልካምና ቅን የሆነውን ነገር ስታደርጉ ለእናንተ፥ ከእናንተም በኋላ ለልጆቻችሁ ለዘላለም መልካም ይሆንላችሁ ዘንድ እኔ የማዝዛችሁን እነዚህን ቃሎች ሁሉ ሰምታችሁ ጠብቁ። 29 እግዚአብሔር አምላካችሁ ትወርሱአቸው ዘንድ የምትሄዱባቸውን አሕዛብን ፊታችሁ ባጠፋ ጊዜ፥ እናንተም በወረሳችሁ ጊዜ፥ በምድራቸውም በተቀመጣችሁ ጊዜ፥ 30 ከፊታችሁ ከጠፉ በኋላ እነርሱን ለመከተል እንዳትጠመዱ፦ እነዚህ አሕዛብ አማልክታቸውን የሚያመልኩት እንዴት ነው? እንዲሁ ደግሞ እኔም አደርጋለሁ ብላችሁ ስለ አማልክታቸው እንዳትጠይቁ ተጠንቀቁ። 31 እግዚአብሔር የሚጠላውን ርኩሰት ሁሉ እነዚህን ለአማልክታቸው አድርገዋል፥ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውንም ለአማልክታቸው በእሳት አቃጥሎአቸዋል፥ እናንተም ለእግዚአብሔር ለአምላካችሁ እንዲሁ አታድርጉ። 32 እኔ የማዝዛችሁን ነገር ሁሉ ታደርጉ ዘንድ ጠብቁ፤ ምንም በእርሱ ላይ አትጨምሩ ከእርሱም ምንም አታጉድሉ።

Deuteronomy 12:1

የምትጠብቃቸው
“መታዘዝ አለባችሁ”

በምድር ላይ በምትኖሩበት ዘመን ሁሉ
“በምድር ላይ በምትኖሩበት” የሚለው ሐረግ አንድ ሰው በሕይወት እስካለ ደረስ የሚል የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “በሕይወት እስካላችሁ ድረስ” (የአነጋገርዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ፈጽማችሁ አጥፉ
“ማጥፋት አለባችሁ”

የምታስለቅቋቸው ሕዝቦች
እዚህ ጋ “ሕዝቦች” የሚወክሉት በከነዓን የሚኖሩትን የሕዝብ ወገኖች ነው። አ.ት፡ “መሬታቸውን የምትወስዱባቸው የሕዝብ ወገኖች” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 12:3

መሠዊያዎቻቸውን ማፍረስ አለባችሁ
“የእነዚያን ሕዝቦች መሠዊያ ማፈራረስ አለባችሁ” ወይም “የእነዚያን ሕዝቦች መሠዊያዎች ማጥፋት አለባችሁ”

ከስክሳችሁ ጣሉ
“ሰባብራችሁ ጣሉ” ወይም “ብትንትናቸውን አውጡ”

ስማቸውን አጥፉ
እዚህ ጋ “ስማቸውን” የሚወክለው “መታሰቢያቸውን” ነው። አ.ት፡ “ማንም እንዳያስታውሳቸው ፈጽማችሁ አጥፏቸው” ወይም “እነዚህን ሐሰተና አማልክት የሚወክል የትኛውንም ነገር አጥፉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከዚያ ስፍራ
ይህ ሕዝቦች አማልክቶታቸውን የሚያመልኩባቸውን እያንዳንዱን ስፍራ ያመለክታል።

አምላካችሁን እግዚአብሔርን በዚያ መልኩ አታምልኩ
“እነዚያ ሕዝቦች አማልክቶቻቸውን እንዳመለኩ አምላካችሁን እግዚአብሔርን ማምለክ የለባችሁም”

Deuteronomy 12:5

አምላካችሁ እግዚአብሔር ስሙን ሊያስቀምጥበት ከነገዶቻችሁ ሁሉ የሚመርጠው ስፍራ
እዚህ ጋ “ስሙን” የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ራሱን ነው። እግዚአብሔር የሚኖርበትን አንድ ቦታ ይመርጣል፣ ሰዎች እርሱን ለማምለክ ወደዚያ ይመጣሉ። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መሄድ የሚኖርባችሁ ወደዚያ ነው
እግዚአብሔር ወደሚወስነው ስፍራ ለማምለክ ይሄዳሉ

በእጃችሁ የምታቀርቡት ስጦታ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው ሙሉ ሰውነትን ነው። አ.ት፡ “የምታቀርቡት ስጦታ” (See: Synecdoche)

የስእለቶቻችሁንና የፈቃደኝነት ስጦታዎቻችሁን
“ስእለታችሁን የምትፈጽሙበትን ስጦታዎቻችሁን፣ የበጎ ፈቃድ ስጦታዎቻችሁን”። እነዚህ የስጦታ ዓይነቶች ናቸው።

ከቀንድ ከብቶቻችሁና ከበግና ከፍየል መንጋዎቻችሁ በኩራቱን
ሕዝቡ ከእያንዳንዱ የቤት እንስሳው በመጀመሪያ የሚወለደውን ወንድ እንዲሰጡት እግዚአብሔር ይፈልጋል

Deuteronomy 12:7

በዚያ ነው
ይህ የሚያመለክተው የእስራኤል ልጆች እንዲያመልኩበት እግዚአብሔር የሚመርጥላቸውን ስፍራ ነው።

እጃችሁ በነካው ሁሉ ደስ ይበላችሁ
እዚህ ጋ “እጃችሁ በነካው” የሚወክለው ሙሉውን ሰውና እርሱ የሠራውን ነው። አ.ት፡ “በሠራችሁት ሥራ ሁሉ ደስ ይበላችሁ” (See: Synecdoche)

Deuteronomy 12:8

ዛሬ እዚህ የምናደርጋቸውን ነገሮች ሁሉ ማድረግ የለባችሁም
“ዛሬ እዚህ እንደምናደርገው ማድረግ የለባችሁም”። ይህ ማለት በዚያ ወቅት ከሚያመልኩበት በተለየ ሁኔታ በተስፋይቱ ምድር ማምለክ ይኖርባቸዋል።

አሁን እያንዳንዱ የሚያደርገው በዐይኑ መልካም መስሎ የታየውን ነው
ዐይን ማየትን፣ ማየትም ማሰብን ወይም መወሰንን ይወክላል። አ.ት፡ “እያንዳንዱ የሚያደርገው ልክ ነው ብሎ የሚያስበውን ነው” ወይም “አሁን እያንዳንዱ የሚያደርገው ልክ ነው ብሎ የሚወስነውን ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ወደ ማረፊያ
“ማረፊያ” የሚለው የነገር ስም እንደ ግሥ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ወደምታርፉበት ምድር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

አምላካችሁ እግዚአብሔር ወደሚሰጣችሁ ርስት
እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ የሚሰጣቸው ምድር አባት ለልጆቹ እንደሚተውላቸው ርስት ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “አምላካችሁ እግዚአብሔር እንደ ቋሚ ንብረት አድርጎ ወደሚሰጣችሁ ምድር” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 12:10

በምድሪቱ ስትኖሩ
ይህ የሚያመለክተው የከነዓንን ምድር ነው።

አምላካችሁ እግዚአብሔር እንድትወርሷት በሚያደርጋችሁ ምድር ላይ
እግዚአብሔር የከነዓንን ምድር ለእስራኤል ሕዝብ መስጠቱ እርሱ ለልጆቹ ርስት እንደሚሰጣቸው አባት ተደርጎ ተነግሮለታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በዙሪያችሁ ካሉ ከጠላቶቻችሁ ሁሉ ያሳርፋችኋል
“በዙሪያችሁ ካሉ ከጠላቶቻችሁ ሁሉ ሰላምን ይሰጣችኋል”

አምላካችሁ እግዚአብሔር ስሙ በዚያ እንዲቀመጥ በሚመርጠው ስፍራ ላይ
እዚህ ጋ “ስም” የሚወክለው እግዚአብሔርን ራሱን ነው። አ.ት፡ “አምላካችሁ እግዚአብሔር ለመኖር በሚመርጠው ስፍራ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእጃችሁ የምታቀርቡት ስጦታ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው ሙሉውን ሰው። አ.ት፡ “የምታቀርቡት ስጦታ” (See: Synecdoche)

ስለ ስእለቶቻችሁ የተመረጡትን ስጦታዎቻችሁን በሙሉ
“ስእለታችሁን ለመፈጸም የምታቀርቧቸውን የበጎ ፈቃድ ስጦታዎቻችሁን በሙሉ”

Deuteronomy 12:12

በእግዚአብሔር ፊት ደስ ይበላችሁ
“በእግዚአብሔር ሀልዎት ደስ ይበላችሁ”

በበራችሁ የሚኖሩ ሌዋውያን
እዚህ ጋ “በሮች” የሚያመለክተው ከተማውን ራሱን ነው። አ.ት፡ “በከተማችሁ ውስጥ የሚኖረው ሌዋዊ” ወይም “ከእናንተ ጋር የሚኖረው ሌዋዊ” (See: Synecdoche)

በመካከላችሁ ምንም ድርሻ ወይም ርስት ስለሌለው
እግዚአብሔር ለሌዋውያን ምንም መሬት ያለመስጠቱ እውነታ ለልጆቹ ርስት እንዳልሰጣቸው አባት ተደርጎ ተነግሮለታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ምንም ድርሻ የለውም
እዚህ ጋ “እርሱ” የሚያመለክተው ሌዊን ነው። ሌዊ ተወላጆቹን በሙሉ ይወክላል። አ.ት፡ “ምንም ድርሻ የላቸውም” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 12:13

ለራሳችሁ ትኩረት ስጡ
“ተጠንቀቁ”

በምታዩት ስፍራ ሁሉ
“ደስ በሚያሰኛችሁ ስፍራ ሁሉ” ወይም “በምትፈልጉት ስፍራ ሁሉ”

ነገር ግን እግዚአብሔር በሚመርጠው ስፍራ ነው
የሚቃጠል ስጦታ መቅረብ ያለበት በመገናኛው ድንኳን ነው። የመገናኛው ድንኳን የት መደረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ራሱ ይመርጣል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Deuteronomy 12:15

ይሁን እንጂ፣ በየበሮቻችሁ ውስጥ እንስሶችን አርዳችሁ መብላት ትችላላችሁ
ሕዝቡ ለመሥዋዕት እንስሶችን ማረድ የሚችለው እግዚአብሔር በሚመርጠው ስፍራ ብቻ ነው። ለምግብ የሚሆኑ እንስሶችን በፈለጉበት ሁሉ ማረድ ይችላሉ። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም በይበልጥ ግልጽ መደረግ ይችላል። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information

በየበሮቻችሁ ውስጥ
እዚህ ጋ “በሮች” ከተማውን በሙሉ ይወክላሉ። አ.ት፡ “በከተማችሁ ውስጥ” ወይም “በቤታችሁ” (See: Synecdoche)

ንጹሕ ያልሆኑ ሰዎች
ለእግዚአብሔር አገልግሎት ተቀባይነት የሌለው ሰው በአካሉ ንጹሕ እንዳልሆነ ተደርጎ ተነግሮለታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ንጹሕ የሆኑ ሰዎች
ለእግዚአብሔር አገልግሎት ተቀባይነት ያለው ሰው በአካሉ ንጹሕ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮለታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሚዳቋና ድኩላ
እነዚህ በፍጥነት መሮጥ የሚያስችል ቀጭንና ረጅም እግሮች ያሏቸው የዱር እንስሶች ናቸው። አ.ት፡ “አጋዘንና ድኩላ” (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)

ነገር ግን ደሙን አትብሉ
ደም ሕይወትን ስለሚወክል ሕዝቡ ደሙን ከምግባቸው ጋር እንዲበሉት እግዚአብሔር አልፈቀደላቸውም። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

Deuteronomy 12:17

በበሮችህ ውስጥ
እዚህ ጋ “በሮች” የሚወክሉት መላውን ከተማ ይወክላሉ። አ.ት፡ “በከተማህ ውስጥ” ወይም “በቤትህ ውስጥ” (See: Synecdoche)

በእጅህ የምታቀርበውን ስጦታ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው ሙሉውን ሰው። አ.ት፡ “ለእግዚአብሔር የምታቀርበውን የትኛውንም ስጦታ” (See: Synecdoche)

Deuteronomy 12:18

ትበሉታላችሁ
“ስጦታዎቻችሁን ትበላላችሁ”

በእግዚአብሔር ፊት
“በእግዚአብሔር ሀልዎት”

በበሮቻችሁ ውስጥ ያሉ ሌዋውያን
እዚህ ጋ “በር” የሚወክለውን መላውን ከተማ ነው። አ.ት፡ “በከተማችሁ ውስጥ የሚኖር ሌዋዊ ሁሉ” (See: Synecdoche)

እጅህን የምታኖርበት የትኛውም ነገር
እዚህ ጋ “እጅህን የምታኖርበት” የሚወክለው ሙሉውን ሰውና እርሱ የሚሠራውን ነው። አ.ት፡ “ስላሠራኸው ሥራ ሁሉ ደስ ይበልህ” (See: Synecdoche)

ለራስህ ትኩረት ስጥ
“ተጠንቀቅ”

እንዳትረሳ
ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በሚገባ ጠብቀው” (ድርብ አሉታ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 12:21

ስሙን ለማስቀመጥ የመረጠው
እዚህ ጋ “ስም” የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ራሱን ነው። እርሱ የሚኖርበትንና ሕዝቡ እርሱን ለማምለክ የሚመጣበትን ስፍራ እግዚአብሔር ይመርጣል። አ.ት፡ “መኖሪያውን ይመርጣል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በበሮችህ ውስጥ
እዚህ ጋ “በሮች” የሚወክሉት መላውን ከተማውን ነው። አ.ት፡ “በከተማህ ውስጥ” ወይም “በማኅበረሰብህ መካከል” (See: Synecdoche)

ነፍስህ እንደ ተመኘች
እዚህ ጋ “ነፍስ” የሚያመለክተው ሙሉውን ሰው ነው። አ.ት፡ “እንደምትመኘው” (See: Synecdoche)

ሚዳቋና ድኩላ የሚበሉ እንደሆኑ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ልክ ሚዳቋውን እና ድኩላውን እንደምትበላ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ሚዳቋና ድኩላውን
እነዚህ በፍጥነት መሮጥ የሚችሉ ቀጭንና ረጅም እግሮች ያሏቸው የዱር እንስሶች ናቸው። እነዚህን በዘዳግም 12:15 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

ንጹሕ ያልሆኑ ሰዎች
ለእግዚአብሔር አገልግሎት ተቀባይነት የሌለው ሰው በአካሉ ንጹሕ እንዳልሆነ ተደርጎ ተነግሮለታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ንጹሕ የሆኑ ሰዎች
ለእግዚአብሔር አገልግሎት ተቀባይነት ያለው ሰው በአካሉ ንጹሕ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮለታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 12:23

ደሙ ሕይወቱ ነው
እዚህ ጋ ደም ሕይወትን የሚያቆይበት መንገድ ደም ራሱ ሕይወት እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ደሙ ሕይወትን ያቆያል” ወይም “ሰዎችና እንስሳት በሕይወት እንዲኖሩ የሚያደርጋቸው ደም ነው።” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሕይወቱን ከሥጋው ጋር አትብላው
እዚህ ጋ፣ “ሕይወት” የሚለው ቃል የሚወክለው ሕይወትን የሚያቆየውን ደሙን ነው። አ.ት፡ “ሕይወትን የሚያቆየውን ከሥጋ ጋር አትብላው” ወይም “ሕይወትን የሚያቆየውን ደም ከሥጋ ጋር አትብላ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእግዚአብሔር ዐይን ትክክል የሆነውን
ዐይን ማየትን ይወክላል፣ ማየትም ማሰብን ወይም መወሰንን ይወክላል። አ.ት፡ “በእግዚአብሔር ውሳኔ ትክክል የሆነው” ወይም “እግዚአብሔር ትክክል ነው የሚለውን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 12:26

ስለ ስእለቶችህ የምታቀርባቸውን ስጦታዎች
“ስእለቶችህን ለመፈጸም ስጦታዎችን” ወይም “የስእለት ስጦታዎች”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የመሥዋዕትህ ደም መፍሰስ አለበት
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ካህኑ የመሥዋዕቱን ደም ያፈሰዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ሥጋውን ትበላለህ
የእግዚአብሔር ሕግ የእንስሳው የትኛው ክፍል የሚቃጠል መሥዋዕት፣ የትኛው ክፍል ለካህኑ እንደሚሆንና የትኛውን ክፍል አቅራቢው መብላት እንዳለበት ግልጽ ያደርጋል። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “ከሥጋው ጥቂቱን ትበላለህ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

Deuteronomy 12:28

እኔ የማዝህን እነዚህን ቃላት በሙሉ ስማ፣ በጥንቃቄም ጠብቃቸው
“የማዝህን ሁሉ በጥንቃቄ ስማና ታዘዘው”

ለአንተና ከአንተም በኋላ ለልጆችህ መልካም እንዲሆንልህ
እዚህ ጋ “ልጆች” ማለት ተወላጆቻቸው ሁሉ ማለት ነው። አ.ት፡ “አንተና ተወላጆችህ እንድትበለጽጉ” (See: Synecdoche)

መልካምና ትክክለኛውን ነገር በምታደርግበት ጊዜ
“መልካም” እና “ትክክለኛ” የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ ትክክለኛ ባህርይ አስፈላጊ በመሆኑ ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ። አ.ት፡ “ትክክል የሆነውን በምታደርግበት ጊዜ” (See: Doublet)

በእግዚአብሔር ዐይን መልካምና ትክክል
ዐይን ማየትን ይወክላል፣ ማየትም ማሰብን ወይም መወሰንን ይወክላል። አ.ት፡ “በእግዚአብሔር ውሳኔ መልካምና ትክክል የሆነው” ወይም “እግዚአብሔር መልካምና ትክክል ነው የሚለውን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 12:29

ሕዝቦችን ይቆርጣቸዋል
እግዚአብሔር በከነዓን የሚኖሩትን የሕዝብ ወገኖች ማጥፋቱ አንድ ሰው ቁራጭ ጨርቅ ወይም ከዛፍ ላይ ቅርንጫፍን እንደሚቆርጥ እንደሚቆርጣቸው ሆኖ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሕዝቦች
እዚህ ጋ “ሕዝቦች” የሚወክሉት በከነዓን የሚኖሩትን ሰዎች ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ታስወጧቸዋላችሁ፣ በምታስወጧቸው ጊዜ
“ሁሉንም ነገር በምትወስዱባቸው ጊዜ”

ለራሳችሁ ትኩረት ስጡ
“ተጠንቀቁ”

እነርሱን በመከተል እንዳትጠመዱ -- አማልክታቸውን ለመጠየቅ በመሞከር እንዳትጠመዱ
ስለ ሌሎች አማልክት የሚማርና የሚያመልክ ሰው በአዳኝ ወጥመድ እንደሚያዝ ሆኖ ተነግሮለታል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እንደ እነርሱ አታድርጉ … አማልክታቸውን የመጠየቅ ሙከራ ለማድረግ እንዳትማሩ” (See: (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት))

እነርሱን በመከተል አትጠመዱ
የከነዓን የሕዝብ ወገኖች ጣዖታትን እንደሚያመልኩ እስራኤላውያን ጣዖታትን ማምለካቸው ከሌሎች የሕዝብ ወገኖች በስተኋላ እንደ ተከተሉ ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከእናንተ አስቀድሞ ከጠፉ በኋላ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር በፊታችሁ ካጠፋቸው በኋላ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

‘እነዚህ ሕዝቦች አማልክታቸውን የሚያመልኩት እንዴት ነው? እኔም እንደዚያው አደርጋለሁ’ ብለህ ብትጠይቅ
ይህ በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ያለ ትዕምርተ ጥቅስ ነው። ቀጥተኛ የሆነው ትዕምርተ ጥቅስ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ተደርጎ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አንተም እንደዚያው ልታደርግ እነዚያ የሕዝብ ወገኖች አማልክታቸውን እንዴት እንዳመለኩ ብትጠይቅ” (በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ያለ ትዕምርተ ጥቅስ እና ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 12:31

በእርሱ ላይ አትጨምር፣ ከእርሱም አትቀንስ
ተጨማሪ ሕጎችን መፍጠርም ሆነ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ሕጎች ቸል ማለት አይኖርባቸውም።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 13

1 በመካከላችሁም፦ ነቢይ ወይም ሕልም አላሚ ቢነሣ፥ ምልክት ወይም ተአምራት ቢሰጣችሁ፥ እንደ ነገራችሁም **2** ምልክቱ ወይም ተአምራቱም ቢፈጸም፥ እርሱም፦ የማታውቃቸውን ሌሎች አማልክት ሄደን እንከተል እናምልካቸውም ቢላችሁ፥ **3** እግዚአብሔር አምላካችሁን በፍጹም ልባችሁ፥ በፍጹም ነፍሳችሁ ትወድዱት እንደሆነ ያውቅ ዘንድ እግዚአብሔር አምላካችሁ ሊፈትናችሁ ነውና፥ የዚያን ነቢይ ቃል ወይም ያን ሕልም አላሚ አትስሙ። **4** እግዚአብሔር አምላካችሁን ተከተሉ፥ እርሱንም አክብሩ፥ ትእዛዘትንም ጠብቁ፥ ድምፁንም ስሙ፥ እርሱንም አምልኩት፥ ከእርሱም ጋር ተጣበቁ። **5** ከግብፅ ምድር ካወጣችሁና ከባርነት ቤት ካዳናችሁ ከእግዚአብሔር ከአምላካችሁ ሊያስታችሁ ስለተናገረ ያ ነቢይ ወይም ያ ሕልም አላሚ ይገደል። ያም ነቢይ እግዚአብሔር አምላካችሁ እንድትሄዱበት ካዘዛችሁ መንገድ ሊያወጣችሁ ነው። ስለዚህ ክፉውን ነገር ከመካከላችሁ አርቁ። **6** የእናታችሁ ልጅ፥ ወንድማችሁ ወይም ወንድ ልጃችሁ ወይም ሴት ልጃችሁ ወይም በብብታችሁ ያለች ሚስታሁ ወይም እንደ ነፍሳችሁ የምትቆጥሩት ወዳጃችሁ በስውርም ሊፈትናችሁ፦ ኑ፥ እናንተ ወይም አባቶቻችሁ የማታውቁአችሁን አማልክት ሄደን እናምልክ ብሉአችሁ፥ **7** ከምድር ዳር ጀምሮ እስከ ሌላኛው ምድር ዳር ድረስ ወደ እናንተ የቀረቡት ከእናንተም የራቁት በዙሪያችሁ ያሉ አሕዛብ ከሚያመልኩአቸው አማልክት ቢያስታችሁ እሺ አትበሉ። **8** አትስማሙአቸው፤አትስማቸውም። ዓይናችሁም አይራራላቸው፥ አትምራቸውም፥ አትሸሽጋቸውም። **9** በዚህ ፈንታ ፈጽማችሁ ግደሉአቸው፤ እርሱን ለመግደል የእናንተ እጅ በእርሱ ላይ ይሁን፤ ከዚያም በኋላ የሕዝቡ ሁሉ እጅ በላዩ ይሁን። **10** ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ካወጣችሁ ከእግዚአብሔር ከአምላካችሁ ሊያርቃችሁ ወድዶአልና፥ እስኪሞት ድረስ በድንጋይ ወግሩት። **11** እስራኤልም ሁሉ ይህን ሰምተው ይፈራሉ፥ በመካከላችሁም እንዲህም ያለ ክፉ ሥራ ለማድረግ አይቀጥሉም። **12** እግዚአብሔር አምልካችሁ ልትኖሩባችሁ በሚሰጣችሁ በአንዲቱ ከተማችሁ እንዲህ ሲባል ብትሰሙ፦ **13** አንዳንድ ክፉ ሰዎች ከእናንተ መካከል ወጥተው፦ የማታውቋቸውን ሌሎችን አማልክት ሄደን እናምልክ ብለው የከተማቸውን ሰዎች አሳቱ፥ ሲሉ ብትሰሙ፤ **14** ታጣራላችሁ፥ ትመረምራላችሁ፥ በሚገባም ትጠይቃላችሁ። እነሆም፥ ይህም ክፉ ነገር በመካከላችሁ እንደ ተደረገ እውነት ሆኖ ቢገኝ። **15** የዚያችን ከተማ ሰዎች በሰይፍ ስለት ፈጽሞ ትመታቸዋላችሁ፤ ከተማይቱን በእርስዋም ያለውን ሁሉ እንስሳውንም በሰይፍ ስለት ታጠፉአቸዋላችሁ። **16** ዕቃዋንም ሁሉ ወደ አደባባይዋ ትሰበስባላችሁ፥ ከተማይቱንም ዕቃዋንም ሁሉ ለእግዚአብሔር ለአምላካችሁ በእሳት ፈጽማችሁ ታቃጥላላችሁ፤ እንደ ገና የማትሠራ ሆና ለዘላለም እንደ ፈረሰች ትቀራለች። **17** ለጥፋት ከተለዩ ነገሮች ምንም እርም ነገር በእጃችሁ አይገኙ። እግዚአብሔር ከቁጣ ትኩሳት ይመለስ ዘንድ፥ ለአባቶቻችሁም እንደማለላቸው ይምራችሁና ይራራላችሁ ዘንድ፥ ያበዛላችሁም ዘንድ ነው። **18** ዛሬ እኔ የማዝዛችሁን ትእዛዘት ሁሉ ትጠብቁ ዘንድ በአምላካችሁ በእግዚአብሔር ፊት ደስ የሚያሰኘውን ታደርጉ ዘንድ የእግዚአብሔር የአምላካችሁን ቃል ስሙ።

Deuteronomy 13:1

በመካከላችሁ ቢነሣ
“በመካከላችሁ ቢመጣ” ወይም “በመካከላችሁ ነኝ ቢል”

የሕልመኛው ሕልሞች
ይህ ከእግዚአብሔር በሕልም መልዕክት የሚቀበል ሰው ነው።

ምልክትን ወይም ድንቅን
እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ የተለያዩ ተአምራቶችን ያመለክታል። (See: Doublet)

ቢሆን
“ቢከናወን” ወይም “ቢመጣ”

ቢነግርሃና፣ ‘ሌሎች አማልክትን እንከተል፣ የማታውቃቸውን እናምልክ’ ቢልህ አትስማው
ይህ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ተደርጎ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “የማታውቃቸውን ሌሎች አማልክት እንድታመልክና እንድታገለግል ቢነግርህ አትስማው” (ቀጥተና እና ቀጥተኛ ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ የሚለውን ተመልከት)

ከሌሎች አማልክት ኋላ እንሂድ
ሌሎች አማልክትን ማምለክ ከሌሎች አማልክት ኋላ መሄድ ወይም መከተል ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “ሌሎች አማልክትን እንከተል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከማታውቃቸው ሌሎች አማልክት ኋላ ሂድ
“ከማታውቃቸው አማልክት” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ሌሎች የሕዝብ ወገኖች የሚያመልኳቸውን አማልክት ነው። ራሱን ስለገለጠላቸውና ኃይሉን ስለተለማመዱት እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ያውቁታል።

የዚያን ነቢይ ወይም ሕልም አላሚ ቃል አትስማ
“ያ ነቢይ የሚለውንም ሆነ ሕልም አላሚው የሚናገረውን አትስማው”

በሙሉ ልብህና በሙሉ ነፍስህ
እዚህ ጋ “ልብ” እና “ነፍስ” የአንድን ሰው ውስጣዊ ማንነት የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። እነዚህ ሁለት ሐረጎች “በፍጹም” ወይም “በቅንነት” የሚል ትርጉም እንዲሰጡ በአንድነት ጥቅም ላይ ውለዋል። ይህንን በዘዳግም 4፡29 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና Doublet የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 13:4

አምላካችሁን እግዚአብሔርን ተከተሉት
እግዚአብሔርን መታዘዝና ማምለክ ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ኋላ እንደ ሄዱ ወይም እንደተከተሉት ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “እግዚአብሔርን ታዘዙ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ድምፁን ታዘዙ
እዚህ ጋ “ድምፅ” የሚወክለው እግዚአብሔር የሚናገረውን ነው። አ.ት፡ “እርሱ የሚለውን ታዘዙ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከእርሱ ጋር ተጣበቁ
ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት መኖሩና ሙሉ በሙሉ በእርሱ ላይ መታመን ሰው ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚጣበቅ ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “በእርሱ ተማመን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ይገደል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “መግደል አለብህ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

አመፅን ተናግሯልና
የነገር ስም የሆነው “አመፅ” እንደ ግሥ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እንድታምፅ ሊያደርግህ ሞክሯል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ከባርነት ቤት የተቤዠህን
እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ባሪያ ከነበሩበት ከግብፅ ማዳኑ ሕዝቡን ከባርነት ለመቤዠት ገንዘብ እንደከፈለ በሚመስል መልኩ ተነግሯል። አ.ት፡ “

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ባሪያዎች ከነበራችሁበት ስፍራ ያዳናችሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የባርነት ቤት
እዚህ ጋ “የባርነት ቤት” የእግዚአብሔር ሕዝብ ባሪያዎች የነበሩበትን ግብፅን ይወክላል። አ.ት፡ “ባሪያዎች የነበራችሁበት ግብፅ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አምላካችሁ እግዚአብሔር እንድትሄዱበት ካዘዛችሁ መንገድ እንድትወጡ
እግዚአብሔር አንድ ሰው እንዴት መኖር ወይም ማድረግ እንዳለበት የሚፈልግበት ሁኔታ ሕዝቡ እንዲሄዱበት እንደሚፈልገው መንገድ ወይም ጎዳና ሆኖ ተነግሯል። አንድን ሰው እግዚአብሔርን ከመታዘዝ ለማስቆም የሚሞክር በእግዚአብሔር መንገድ ወይም ጎዳና ላይ እንዳይሄድ እንደተከላከል ሆኖ ተነግሮለታል። አ.ት፡ “አምላክህ እግዚአብሔር ያዘዘውን እንዳትፈጽም የሚያደርግህ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ስለዚህ ክፋትን ከመካከላችሁ አርቁ
እዚህ ጋ “ክፋትን” የሚያመለክተው ክፉ ሰውን ወይም ክፉ ባህርይን ነው። ይህ ስማዊ ቅጽል እንደ ቅጽል ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ስለዚህ ይህንን ክፉ ነገር የሚያደርገውን ሰው ከእስራኤል ሕዝብ መካከል ማስወገድ አለብህ” ወይም “ስለዚህ ይህንን ክፉ ሰው መግደል አለብህ” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 13:6

በእቅፍህ ያለች ሚስትህ
እቅፍ የሰው ድረት ነው። ይህ የአነጋገር ዘይቤ ወደ ደረቱ አስጠግቶ ይይዛታል፣ ይኸውም ይወዳታል፣ ይንከባከባታል ማለት ነው። አ.ት፡ “የምትወዳት ሚስትህ” ወይም “በፍቅር የምታቅፋት ሚስትህ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

እንደ ነፍስህ የሆነ ጓደኛህ
እዚህ ጋ “ነፍስ” የሚወክለው የሰውን ሕይወት ነው። ይህ ማለት ሰውየው ለራሱ ሕይወት የሚገደውን ያህል ስለ ጓደኛው ይገደዋል ማለት ነው። አ.ት፡ “ውድ ጓደኛህ” ወይም “ራስህን የምትወደውን ያህል የምትወደው ጓደኛህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በምስጢር ሊያስትህ፣ ‘በሌላው የምድር ጫፍ -- እንሂድና እናምልክ’ ቢልህ
ይህ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ወደ ሌላው የምድር ጫፍ ሄደህ እንድታመልክ ሊያሳምንህ በምስጢር ይሞክራል” (ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ የሚለውን ተመልከት)

በክበብህ ያሉ
“በዙሪያህ ያሉ”

ከአንዱ የምድር ጫፍ እስከ ሌላኛው የምድር ጫፍ
እዚህ ጋ ሁለቱ የምድር ጽንፍ ማጣቀሻዎች “በምድር ላይ በሁሉ ስፍራ” ማለት ነው። አ.ት፡ “በመላው ምድር ላይ” (See: Merism)

Deuteronomy 13:8

እሺ አትበለው
“እርሱ በሚፈልገው አትስማማ”

ዐይንህ አይራራለት
እዚህ ጋ “ዐይንህ” የሚያመለክተው ሙሉውን ሰው ነው። አ.ት፡ “በርኅራኄ አትመልከተው” ወይም “አትማረው” (See: Synecdoche)

አትተወው ወይም አትደብቀው
“ምህረት ልታሳየው ወይም እርሱ ያደረገውን ከሌሎች ልትደብቅ አይገባም”

እርሱን ለመግደል መጀመሪያ የአንተ እጅ ይሁንበት
ይህ ማለት በበደለኛው ሰው ላይ የመጀመሪያውን ድንጋይ እርሱ መወርወር ነበረበት። “እጅ” የሚለው ቃል የሚወክለው ሙሉውን ሰው ነው። አ.ት፡ “በመጀመሪያ እስኪሞት ድረስ የምትመታው አንተ መሆን አለብህ” (See: Synecdoche)

Deuteronomy 13:10

ከእግዚአብሔር ሊያርቅህ ሞክሯል
“ከእግዚአብሔር ሊመልስህ”። አንድ ሰው ሌላውን እግዚአብሔርን ከመታዘዝ ለጊታው መሞከሩ ያንን ሰው በአካሉ እግዚአብሔርን ትቶ እንዲመለስ ለማድረግ እንደሞከረ ተቆጥሮ ተነግሯል። አ.ት፡ “እግዚአብሔርን እንዳትታዘዝ ሊያደርግህ ሞክሯል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከባርነት ቤት
እዚህ ጋ፣ “የባርነት ቤት” የሚወክለው የእግዚአብሔር ሕዝብ ባሪያዎች የነበሩበትን ግብፅን ነው። አ.ት፡ “ባሪያዎች ከነበራችሁበት ስፍራ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እስራኤል ሁሉ ይሰሙና ይፈራሉ
ሕዝቡ ስለተገደለው ሰው በሚሰሙበት ጊዜ እርሱ እንዳደረገው ለማድረግ እንደሚፈሩ ያመለክታል። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

Deuteronomy 13:12

አንዳንድ ክፉ ሰዎች ከመካከልህ ሄደው
“ከመካከልህ” የሚለው ሐረግ እነዚህ ክፉ ሰዎች በማኅበረሰቡ መካከል የሚኖሩ እስራኤላውያን ነበሩ ማለት ነው።

የከተማቸውን ነዋሪዎች ሰብስበው፣ ‘ሄደን የማታውቋቸውን አማልክት እናምልክ’ ቢሉ
ይህ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “የማያውቋቸውን አማልክት ሄደው እንዲያመልኩ በከተማቸው የሚኖሩትን አስገድደዋል”። (ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ የሚለውን ተመልከት)

የከተማቸውን ነዋሪዎች ሰብስበው
አንድ ሰው ሌላውን እግዚአብሔርን እንዳይታዘዝ ቢያደርገው ያ ሰው በአካሉ ከእግዚአብሔር ተለይቶ እንዲመለስ እንዳደረገው ተቆጥሮ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መረጃውን አጣራ፣ ፈትሽ፣ በሚገባ መርምር
እነዚህ ሐረጎች ሁሉ በመሠረቱ የሚሉት አንድ ነገር ነው። ሙሴ በከተማይቱ ስለሆነው ነገር እውነቱን በጥንቃቄ እንዲያጣሩ አጽንዖት እየሰጠ ነው። (See: Doublet)

እንዲህ ያለ አስጸያፊ ነገር በመካከላችሁ ተደርጎ እንደሆን
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የከተማይቱ ሰዎች እንዲህ ያለ አስከፊ ነገር አድርገው እንደሆን (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 13:15

በሰይፍ ስለት
እዚህ ጋ “ስለት” የሚወክለው ሙሉውን ሰይፉን ነው። አ.ት፡ በሰይፎቻችሁ” (See: Synecdoche)

ምርኮውን ሁሉ
“ብዝበዛውን ሁሉ”። ይህ ሰራዊት በጦርነት ድል ካደረገ በኋላ የሚሰበስበውን ሀብትና ንብረት ያመለክታል።

የፍርስራሽ ክምር
“የፍርስራሽ ቁልል”

ፈጽሞ ዳግመኛ አትሠራ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ከተማይቱን ማንም ደግሞ አይሥራት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 13:17

ለመጥፋት ከተለዩ ከእነዚያ ነገሮች አንዱም እጅህ ላይ አይጣበቅ
እግዚአብሔር አንድን ነገር መርገሙና ሊያጠፋው መማሉ እርሱ ቁሱን ከሌሎች ነገሮች ለይቶ እንደሚያስቀምጠው ሆኖ ተነግሯል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር አጥፋው ብሎ ካዘዘህ ነገር ውስጥ የትኛውንም ማቆየት የለብህም” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እጅህ ላይ አይጣበቅ
ይህ አንድ ሰው የሆነ ነገርን ለራሱ የሚያቆይበት መንገድ ነው። አ.ት፡ “አታቆይ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር ከቁጣው መዓት ይመለሳል
እግዚአብሔር ከእንግዲህ ያለመቆጣቱ ቁጣው እንደ አንድ ቁስ ተቆጥሮ እግዚአብሔር በአካል ከእርሱ እንደሚመለስ ተነግሯል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር መቆጣቱን ይተዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ለአባቶችህ
እዚህ ጋ “አባቶችህ” ማለት አያቶችህ ወይም ቅድም አያቶችህ ማለት ነው።

የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰምተሃል
እዚህ ጋ “ድምፅ” እግዚአብሔር የሚናገረውን ይወክላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር የሚናገረውን ታዘሃል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በአምላክህ በእግዚአብሔር ዐይን ትክክል የሆነውን
ዐይን ማየትን ይወክላል፣ ማየትም ማሰብን ወይም መወሰንን ይወክላል። አ.ት፡ “በእግዚአብሔር ውሳኔ ትክክል የሆነውን” ወይም “አምላክህ እግዚአብሔር ትክክል እንደሆነ የሚቆጥረውን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 14

1 እናንተ የእግዚአብሔር የአምላካችሁ ሕዝብ ናችሁ። ስለ ሞተው ሰው አካላችሁን አታቆስሉ፥ የትኛውንም የፊታችሁን ክፍል አትላጩ። **2** ምክንያቱም እናንተ
ለእግዚአብሔር ለአምላካችሁ ቅዱስ ሕዝብ ናችሁ፤ በምድርም ላይ ከሚኖሩ አሕዛብ ሁሉ ይልቅ ለራሱ ሕዝብ ትሆኑ ዘንድ አምላካችሁ እግዚአብሔር እናንተን
መርጦአልና። **3** ርኩስን ነገር ሁሉ አትብሉ። **4** የምትበሉአቸው እንስሶች እነዚህ ናቸው፦ በሬ፥ በግ፥ ፍየል፥ **5** ዋላ፥ ሚዳቋ፥ የበረሃ አጋዘን፥ አጭ፥ አራይሌ፥
የተራራ በግ (ድኩላ)። **6** ከእንስሶች ሰኮናው የተሰነጠቀውን ጥፍሩም ከሁለት የተከፈለውን የሚያመነዥከውንም እንስሳ ሁሉ ትበላላችሁ። **7** ነገር ግን
ከማያመሰኩ ወይም ሰኮናቸው ካልተሰነጠቀ፥ እነዚህን አትበሉም፤ ግመል፥ ጥንቸል፥ ሽኮኮን፥ አትበሉም። የሚያመነዥኩና ነገር ግን ሰኮናቸው ያልተሰነጠቀም
እነዚህ ለእናንተ ርኩሶች ናቸው። **8** እርያም ሰኮናው ስለ ተሰነጠቀ ነገር ግን ስለማያመነዥክ፥ እርሱ ለእናንተ ርኩስ ነው፤ ሥጋውን አትብሉ በድኑንም አትንኩ። **9**
በውኃ ውስጥ ከሚኖሩት ሁሉ የምትበሉአቸው እነዚህ ናቸው፤ ክንፍና ቅርፊት ያላቸውን ትበላላችሁ። **10** ነገር ግን ክንፍና ቅርፊትም የሌላቸውን አትበሉም፥
ለእናንተ ርኩስ ናቸው። **11** ንጹሕ የሆኑትን ወፎችን ሁሉ ትበላላችሁ። **12** ነገር ግን ከወፎች ሊበሉ የማይገባቸው እነዚህ ናቸው። ንስር፥ ገዲ፥ ዓሣ አውጭ፥ **13**
ጭልፊት፥ ጭላት፥ በየወገኑ፥ **14** ቁራም ሁሉ በየወገኑ፥ **15** ሰጎን፥ ጠላቋ፥ ዝዪ፥ በቃል፥ በየወገኑ፥ **16** ጉጉት፥ ጋጋኖ፥ **17** የውኃ ዶሮ ይብራ፥ **18** ጥምብ አንሣ፥
አሞራ፥ እርኩም ሸመላ ሳቢሳ፥ በየወገኑ፥ ጅንጅላቴ ወፍ፥ የሌሊት ወፍ፥። **19** የሚበርርም ተንቀሳቃሽ ሁሉ ለእናንተ ርኩስ ነው፤ አይበሉም። **20** ንጹሕ የሆኑትን
ወፎች ሁሉ ብሉ። **21** የበከተውን ሁሉ አትብሉ፥ ይበላው ዘንድ በአገራችሁ ደጅ ለተቀመጠ፥ መጻተኛ ትሰጠዋላችሁ፥ ወይም ለእንግዳ ትሸጣላችሁ። ምክንያቱም
እናንተ ለእግዚአብሔር ለአምላካችሁ የተቀደሰ ሕዝብ ናችሁ። የፍየሉን፥ ጠቦት፥ በእናቱ ወተት አትቀቅሉ። **22** ከእርሻችሁ በየዓመቱ ከምታገኙት ከዘራችሁ ፍሬ
ሁሉ አሥራት ታወጣላችሁ። **23** ሁልጊዜ እግዚአብሔር አምላካችሁን መፍራት ትማሩ ዘንድ ስሙ፤ እንዲጠራበት በመረጠው ስፍራ በእግዚአብሔር
በአምላካችሁ ፊት የእህላችሁን የወይን ጠጃችሁንም የዘይታችሁንም አሥራት የላማችሁንና የበጋችሁንም በኩራት ብሉ። **24** እግዚአብሔር አምላካችሁ
በባረካችሁ ጊዜ መንገዱ ሩቅ ቢሆን፥ እግዚአብሔር አምላካችሁም ስሙን ያኖርበት ዘንድ የመረጠው ስፍራ ቢርቅባችሁ ግን ወደዚያ ለመሸከም ባትችሉ
ትሸጣላችሁ፥ **25** የዋጋውንም ገንዘቡ በእጃችሁ ይዛችሁ እግዚአብሔር አምላካችሁ ወደ መረጠው ስፍራ ትሄዳላችሁ። **26** በዚያም በገንዘቡ የፈለጋችሁትን በሬ
ወይም፥ በግ ወይም፥ የወይን ጠጅ፥ ወይም ብርቱ መጠጥ፥ ወይም የፈለጋችሁትን ሁሉ ትገዛላችሁ፤ በዚያም በእግዚአብሔር በአምላካችሁ ፊት ትበላላችሁ፥
እናንተና ቤተ ሰባችሁም ደስ ይላችኋል። **27** ድርሻና ርስት ከእናንተ ጋር ስለሌለው በአገራችሁ ደጅ ውስጥ ያለውን ሌዋዊውን ቸል አትበሉ። **28** በየሦስተኛው
ዓመት መጨረሻ በዚያ ዓመት ሌዋዊው ከእናንተ ጋር ክፍልና ርስት ስለሌለ የፍሬአችሁን አሥራት ሁሉ አምጥታችሁ በአገራችሁ ደጅ ታኖራላችሁ፤ **29**
በአገራችሁም ደጅ ያለ መጻተኛ፥ ድሀ አደግ፥ ባል የሞተባት መጥተው ይበላሉ፤ ይጠግባሉም። ይኸውም እግዚአብሔር አምላካችሁ በምታደርጉት በእጃችሁ
ሥራ ሁሉ ይባርካችሁ ዘንድ ነው።

Deuteronomy 14:1

እናንተ -- ሕዝብ ናችሁ -- እናንተ -- የተለየ ሕዝብ ናችሁ -- መርጧችኋል
“እናንተ” የሚለው አገባብ በሙሉ የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። ሙሴ የሕዝቡ አካል ሆኖ ተካቶአል። አ.ት፡ “እኛ… ሕዝብ ነን … እኛ የተለየን ሕዝብ ነን … መርጦናል”

ስለሞተው ራሳችሁን አትቁረጡ ወይም ከፊታችሁ የትኛውንም ክፍል አትላጩት
እነዚህ በከነዓን ይኖሩ የነበሩት የሕዝብ ወገኖች ለሞቱ ሰዎች ሐዘናቸውን የሚገልጹበት መንገድ ነበር። ሙሴ እንደዚያ እንዳያደርጉ ለእስራኤል ሕዝብ ይነግራቸዋል። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። (See: Symbolic Action and Assumed Knowledge and Implicit Information)

ከፊታችሁ የትኛውንም ክፍል አትላጩት
“ከራሳችሁ ጸጉር ላይ ከፊት ያለውን አትላጩት”

በምድር ፊት -- እናንተ የተለየ ሕዝብ ናችሁ
እነዚህን ቃላት በዘዳግም 7፡6 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

ለአምላካችሁ ለእግዚአብሔር የተለየ ሕዝብ ናችሁ
እግዚአብሔር በልዩ ሁኔታ የእርሱ እንዲሆኑ የእስራኤልን ሕዝብ መምረጡ እነርሱን ከሌሎች ሕዝቦች ሁሉ እንደለያቸው ተደርጎ ተነግሯል። ይህ በአድርጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አምላካችሁ እግዚአብሔር እናንተን ከሌሎች ሕዝቦች ለይቶአችኋል” (See: (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድርጊ ወይም ተደርጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት))

እግዚአብሔር የራሱ ንብረት የሆነ ሕዝብ እንድትሆኑ መርጧችኋል
ይህ ማለት በመሠረቱ ከዐረፍተ ነገሩ መጀመሪያ ጋር ተመሳሳይ ነገር ነው። ሁለቱም የሚሉት የእስራኤል ሕዝብ በልዩ ሁኔታ የእግዚአብሔር መሆኑን ነው። (See: Parallelism)

የራሱ ንብረት የሆነ ሕዝብ
“የግል ንብረቱ የሆነ ሕዝብ” ወይም “የእርሱ ሕዝብ”

በምድር ፊት ከሚኖሩ ሕዝቦች ሁሉ በላይ
“በዐለም ላይ ካሉ የሕዝብ ወገኖች ሁሉ”

Deuteronomy 14:3

የትኛውንም ንጹሕ ያልሆነ ነገር አትብላ
የእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔር መበላት የለባቸውም ያላቸውን የትኛውንም ነገር መብላት አይጠበቅባቸውም።

አጋዘን፣ ሚዳቋ፣ ሰስ
እነዚህ የተለያዩ ዓይነት አጋዘኖች ናቸው። የአንተ ቋንቋ እያንዳንዱን እንስሳ የሚወክል ቃል ከሌለው “ልዩ ልዩ ዓይነት አጋዘን” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል።

ሚዳቋ
ይህ በፍጥነት መሮጥ የሚችል ቀጭንና ረጅም እግር ያለው የዱር እንስሳ ነው። ይህንን በዘዳግም 12፡15 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሰስ
የአጋዘን ዓይነት (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)

ዋሊያ እና ድኩላ
እነዚህ ሁለቱም የድኩላ ዓይነቶች ናቸው። የአንተ ቋንቋ እያንዳንዱን እንስሳ የሚወክል ቃል ከሌለው “የተለያዩ የድኩላ ዓይነቶች” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል።

ዋሊያ
የድኩላ ዓይነት (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Deuteronomy 14:6

ሰኮናው የተከፈል
“የተሰነጠቀ ሰኮና ያለው”። ይህ ሰኮናው አንድ ሙሉ ከመሆን ይልቅ ሁለት ቦታ የተሰነጠቀ ነው።

የሚያመነዥክ
ይህ ማለት እንስሳው ምግቡን ከሆዱ ውስጥ እያመጣ እንደገና ያኝከዋል።

ጥንቸል
ይህ ረጃጅም ጆሮዎች ያሉት ትንሽ እንስሳ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ የሚኖረው ምድር ላይ በጉድጓዶች ውስጥ ነው። (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)

ሽኮኮ
ይህ ትንሽ እንስሳ ሲሆን የሚኖረው በዐለታማ አካባቢ ነው። (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)

እነርሱ ለእናንተ ንጹሕ አይደሉም
እግዚአብሔር ሕዝቡ ሊበላው አይገባውም የሚለው አንዳች ነገር በአካላዊነቱም ንጹሕ እንዳልሆነ ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 14:8

ዐሳማ ለእናንተ ንጹሕ አይደለም
እግዚአብሔር ሕዝቡ ሊበላው አይገባውም የሚለው አንዳች ነገር በአካላዊነቱም ንጹሕ እንዳልሆነ ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 14:9

በውሃ ውስጥ ከሚኖሩት እነዚህን መብላት ትችላላችሁ
“በውሃ ውስጥ ከሚኖሩት እነዚህን የመሳሰሉትን እንስሳት መብላት ትችላላችሁ”

ግልፋፊ
ዓሳ በውሃ ውስጥ ለመንቀሳቀስ የሚጠቀምበት ቀጭንና ሰፋ የሚል የአካል ክፍሉ

ቅርፊት
የዓሳውን አካል የሚሸፍኑ ትናንሽ ንብርብሮች

ለእናንተ ንጹሐን አይደሉም
እግዚአብሔር ሕዝቡ ሊበላው አይገባውም የሚለው አንዳች ነገር በአካላዊነቱም ንጹሕ እንዳልሆነ ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 14:11

ንጹሕ የሆነ ወፍ ሁሉ
እግዚአብሔር ሕዝቡ ሊበላው ይችላል የሚለው እንስሳ፣ ያ እንስሳ በአካላዊነቱም ንጹሕ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ንስር - ጥምብ አንሣ - ዓሳ አውጪ - ቀይ ጭልፊት - ጥቁር ጭልፊት - ገዴ
እነዚህ በሌሊት የሚንቀሳቀሱ ወይም ትናንሽ እንስሳትንና የሞቱ እንስሳትን የሚመገቡ የወፍ ዝርያዎች ናቸው። (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 14:14

ቁራ - የባህር ወፍ
እነዚህ በሌሊት የሚንቀሳቀሱ ወይም ትናንሽ እንስሳትንና የሞቱ እንስሳትን የሚመገቡ ሁሉም ዓይነት ወፎች ናቸው። (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 14:18

ሸመላ - የውሃ ወፍ፣ እርኩም
እነዚህ ትናንሽ እንስሶችንና እንሽላሊቶችን የሚመገቡ የወፍ ዓይነቶች ናቸው። (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)

የሌሊት ወፍ
በተለይ በምሽት የሚበር፣ ነፍሳትንና ዐይጦችን የሚመገብ፣ ክንፍና ጸጉራማ አካል ያለው እንስሳ

ክንፍ ያላቸው ጥቃቅን ነፍሳት ሁሉ
ይህ ማለት በመንጋ ሆነው የሚንቀሳቀሱ በራሪ ነፍሳት ሁሉ ማለት ነው።

ለእናንተ ንጹሕ አይደሉም
እግዚአብሔር ሕዝቡ ሊበላው አይገባውም የሚለው እንስሳ በአካላዊነቱም ንጹሕ እንዳልሆነ ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መበላት የለባቸውም
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ልትበሏቸው አይገባም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ንጹሕ ሆነው የሚበሩ ነገሮች
እግዚአብሔር ሕዝቡ ሊበላው ይችላል የሚለው እንስሳ፣ ያ እንስሳ በአካላዊነቱም ንጹሕ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 14:21

የትኛውንም የሞተ ነገር አትብላ
ይህ በተፈጥሮአዊ ሞት የሚሞተውን እንስሳ ማለት ነው።

እንተ ለአምላካችሁ ለእግዚአብሔር የተለየ ሕዝብ ናችሁና
እግዚአብሔር በልዩ ሁኔታ የእርሱ እንዲሆኑ የእስራኤልን ሕዝብ መምረጡ እነርሱን ከሌሎች ሕዝቦች ሁሉ እንደለያቸው ተደርጎ ተነግሯል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አምላካችሁ እግዚአብሔር እናንተን ከሌሎች ሕዝቦች ለይቶአችኋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 14:22

ከእርሻህ ከምታገኘው ምርት ሁሉ
ይህ ከምርታቸው ከየአሥሩ እጅ አንድ እጁን እንዲሰጡ ማለት ነው።

በዓመት በዓመቱ
“በየዓመቱ”

በእግዚአብሔር ፊት
“በእግዚአብሔር ሀልዎት ፊት”

Deuteronomy 14:24

እርሱን ይዘህ
እዚህ ጋ “እርሱ” የሚያመለክተው የምርቱንና የቀንድ ከብቱን አስራት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መባውን ወደ ገንዘብ ቀይረው
“መባህን በገንዘብ ትሸጠዋለህ”

ገንዘቡን በእጅህ ይዘህ ሂድ
“ገንዘቡን በቦርሳ አድርገህ ይዘኸው ሂድ”

Deuteronomy 14:26

ያሻህን ሁሉ
“የምትፈልገውን ሁሉ”

በእግዚአብሔር ፊት
“በእግዚአብሔር ሀልዎት ፊት”

በበርህ ውስጥ ያለ ሌዋዊ
እዚህ ጋ “በር” የሚወክለው ከተማውን ወይም መንደሩን በሙሉ ነው። አ.ት፡ “በከተማህ ውስጥ የሚኖረውን ሌዋዊ ሁሉ” (See: Synecdoche)

አትርሳው
ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ከአስራትህ ጥቂቱን ለሌዋዊው ስለመስጠትህ እርግጠኛ” (See: Double Negatives)

ከአንተ ጋር ድርሻም ሆነ ርስት የለውምና
የሌዊ ነገድ ርስት የሚሆናቸውን የመሬት ድርሻ አልወሰዱም። የእግዚአብሔር ካህናት ሆነው እርሱ ማገልገላቸው የእነርሱ የርስት ድርሻ ነው። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ድርሻም ሆነ ርስት የለውም
እግዚአብሔር ለሌዋውያን መሬት አለመስጠቱ ርስት እንዳልሰጣቸው ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 14:28

በየሦስተኛው ዓመት ከምርትህ ሁሉ አስራት አቅርብ
ለሌዋውያን፣ ወላጆቻቸውን ላጡ ልጆች፣ ለመበለቶችና መጻተኞች እንዲሰጣቸው እስራኤላውያን በ3 ዓመት አንድ ጊዜ አስራታቸውን በየከተማቸው ማከማቸት ነበረባቸው። (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

በበሮችህ ውስጥ
እዚህ ጋ “በሮች” የሚወክሉት ከተማውን ወይም መንደሩን በሙሉ ነው። አ.ት፡ “በከተማህ ውስጥ” (See: Synecdoche)

ከአንተ ጋር ድርሻም ሆነ ርስት የለውምና
እግዚአብሔር ለሌዋውያን ምንም መሬት አለመስጠቱ ርስት እንዳልሰጣቸው ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ወላጆቻቸውን ያጡ
እነዚህ ሁለቱም ወላጆቻቸው የሞቱባቸውና የሚንከባከባቸው ዘመድ የሌላቸው ልጆች ናቸው።

መበለት
ይህቺ ባል የሞተባትና በእርጅናዋ የሚረዳት ልጅ የሌላት ሴት ናት።

በምትሠራው የእጅህ ሥራ ሁሉ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው የሰውን ሁለንተናውን ነው። ይህ የሚያመለክተው አንድ ሰው የሚሠራውን ሥራ ነው። አ.ት፡ “በምትሠራው ሥራ ሁሉ” (See: Synecdoche)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 15

1 በየሰባት ዓመት የዕዳ ምሕረት ታደጋላችሁ። **2** ይህ ዕዳ ምሕረት አፈጻጸም እንከሚከተለው ነው፤ አበዳሪ ሁሉ ለባልንጀራው ላበደረው እንዲተውዋውና ከባልጀራው ወይም ወንድሙ መልሶ እንዳይጠይቅ እግዚአብሔር ያወጀው ይህ ነው። **3** ለእንግዳ ያበደራችሁትን መጠየቅ የምትችሉ ሲሆን፥ ለእስራኤላዊ ወንድማችሁ ያበደራችሁትን ግን ምሕረት አድርጉለት። **4** ይሁን እንጂ፥ አምላካችሁ እግዚአብሔር ትወርሱአት ዘንድ ርስት አድርጎ በሚሰጣችሁ ምድር ውስጥ አብዝቶ ስለሚባርካችሁ በመካከላችሁድኻ አይኖርም። **5** ይህ የሚሆነው የእግዚአብሔር የአምላካችሁን ድምፅ ፈጽማችሁ ስትሰሙና ዛሬ የማዛችሁን ትእዛዘትን ሁሉ ስትታዘዙ ብቻ ነው። **6** እግዚአብሔር አምላካችሁ በሚሰጣችሁ ተሰፋ መሠረት ስለሚባርካችሁ እናንተ ለብዙ አሕዛብ ታበድራላችሁ እንጂ እናንተ አትበደሩም፤ብዙ አሕዛብን ትገዛላችሁ እንጂ ማንም እናንተን አይገዛችሁም። **7** እግዚአብሔር አምላካችሁ በሚሰጣችሁ ምድር ላይ ደኻ ቢኖር፥ በደኻ ወንድማችሁ ላይ ልባችሁ አይጨክን፥ለደኻ ወንድማችሁ ላይም እጃችሁን ከመዘርጋት አትቆጥቡ፤ **8** ነገር ግን እጃችሁን በትክክል ፍቱለት ለማያስፈልገውም ቅር ሳትሉ አበድሩት። **9** ዕዳ የሚሠርዝበት ሰባተኛ ዓመት ቀርቦአል፥ በማለት ክፉ አሳብ አድሮባችሁ በችግረኛ ወንድማችሁ ላይ እንዳትጨክኑና ምንም ሳትሰጡት እንዳይቀር እርሱ በእናንተ ላይ ወደ እግዚአብሔር ጮኾ በደለኞች እንዳትሆኑ ተጠንቀቁ። **10** በቅን ልቦና ስጡት፥ ስትሰጡትም ልባችሁ አይጸጸት፥ከዚያም የተነሣ ግዚአብሔር አምላካችሁ ሥራችሁንና እጃችሁን ያረፈበትን ሁሉ ይባርክላችኋል። **11** በምድሪቱ ላይ ሁልጊዜ ድኾች አይጠፉም፥ስለዚህ በዚያ ለሚኖሩ ወንድሞቻችሁ ለድኾችና ለችግራኞች እጃችሁን እንድትዘረጉ አዛችኋለሁ። **12** እናንተም ወንድማችሁን ዕብራዊውን ወይም ዕብራዊቱን ብትገዙ ስድስት ዓመት ያገልግላችሁ በሰባተኛውም ዓመት ከእናንተ ዘንድ አርነት አውጡት። **13** ከእናንተም ዘንድ አርነት በሚታወጣበት ጊዜ ባዶውን አትስደዱት። **14** ነገር ግን ከመንጋህ፥ ከአውድማችሁም፥ ከወይራችሁም መጥመቂያም ትለግሱታላችሁ፥ እግዚአብሔር አምላካችሁ በባረካችሁ መጠን ትሰጡት ዘንድ ይገባል። **15** እናንተም በግብፅ አገር ባሮች እንደ ነበራችሁ እግዚአብሔር አምላካችሁም እንደ ነበራችሁ አስቡ፤ስለዚህ እኔ ዛሬ ይህን እንድታደርጉ አዛችሁኋለሁ። **16** ነገር ግን አገልጋያችሁ እናንተንና ቤተ ሰቦቻችሁን በመውደዱና ከእናንተ ጋር ደስተኛ ሆኖ ከመኖሩ የተነሣ፦ ከእናንተ መለየት አልፈልግም ቢለችሁ፦ **17** ጆሮውን ከቤታችሁ መዝጊያ ላይ በማስደግፍ በወስፌ ትበሳላችሁ፤ከዚያም ዕድሜ ልኩን አገልጋያችሁ ይሆናል። በቤት አገልጋዮችሁም ላይ እንዲሁ አድርግ። **18** አገልጋያችሁን አርነት ማውጣት ከባድ መስሎ አይታያችሁ፤ ምክንያቱም የስድስት ዓመት አገልግሎቱ አንድ የቅጥር ሠራተኛ ከሚሰጠው አገልግሎት እጥፍ ነውና። እግዚአብሔር አምላካችሁ በምታደጉት ነገር ሁሉ ይባርካችኋልና። **19** የቀንድ ከብት፥ የበግና የፍየል መንጋዎቻችሁን ተባዕት በኩር ሁሉ ለእግዚአብሔር ለአምላካችሁ ቀድሱ። የበሬአችሁን በኩር አትሥሩባቸው፥ የበጋችሁንም በኩር አትሸልቱ፥ **20** እርሱ በሚመርጠው ስፍራ እናንተና ቤተ ሰባችሁ በየዓመቱ በእግዚአብሔር በአምላካችሁ ፊት ትበሉታላችሁ። **21** አንድ እንስሳ እንከን ካለበት፤ አንካሳ ወይም ዕውር ወይም ደግሞ ማናቸውም ዓይነት ከባድ ጉድለት ያለበት ከሆነ፤ ለአምላካችሁ ለእግዚአብሔር አትሠዉ። **22** የከተሞቻችሁ ትበላላችሁ፤ በሥርዓቱ መሠረት ንጹሕ የሆነውም ሆነ ያልሆነው ሰው፥ እንደ ድኩላ እንደ ዋላ ያሉትን ይበላዋል። **23** ደሙን እንደ ውሃ መሬት ላይ አፍስሱት እንጂ አትብሉት።

Deuteronomy 15:1

ሰባት ዓመት
“7 ዓመት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ዕዳ ሰርዝ
“ሰዎች የተበደሩህን ሁሉ ተውላቸው”

ምሕረት የምታደርገው እንደዚህ ነው
“ዕዳውን የምትሰርዘው እንደዚህ ነው”

አበዳሪ
ለሌሎች ሰዎች ገንዘብ የሚያበድር ሰው

ጓደኛውን ወይም ወንድሙን
“ጓደኛ” እና “ወንድም” የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም የሚጋሩ ሲሆኑ ከሌላው እስራኤላዊ ወዳጆቸው ጋር ባላቸው የቅርብ ግንኙነት ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ። አ.ት፡ “እስራኤላዊ ጓደኛው” (See: Doublet)

እግዚአብሔር የዕዳ ምሕረት ዐውጆአልና
ይህ በአድርጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ዕዳን እንድትምር እግዚአብሔር አዞሃልና” (አድርጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እጅህ መተው አለበት
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “እንዲመለስልህ መጠየቅ የለብህም” ወይም “ተመልሶ እንዲከፈልህ መጠየቅ የለብህም” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 15:4

ድኻ አይኖርም
“ድኻ” የሚለው ስማዊ ቅጽል እንደ ቅጽል ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ድኻ ሕዝብ” ውይም “ድኻ የሚሆን አንድም ሰው” (See: Nominal Adjectives)

የሚሰጣችሁ ምድር
ይህ የከነዓንን ምድር ያመለክታል።

እንድትወርሰው ርስት አድርጎ በሚሰጥህ
እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚሰጣቸው ምድር ርስታቸው እንደሚሆን ተቆጥሮ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የአምላክህን የእግዚአብሔርን ድምፅ በጥንቃቄ የምትሰማ ከሆነ ብቻ
እዚህ ጋ “የእግዚአብሔር ድምፅ” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር የሚያመለክተው ራሱን እግዚአብሔርን ነው። አ.ት፡ “አምላክህ እግዚአብሔር የሚናገረውን ለመታዘዝ ከተጠነቀቅህ ብቻ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ታበድራለህ -- አትበደርም
“ገንዘብ” የሚለው ቃል የሚታወቅ ነው። የዚህን መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። አ.ት፡ “ገንዘብ ታበድራለህ … ገንዘብ አትበደርም” (See: Ellipsis)

ለብዙ ሕዝቦች -- በብዙ ሕዝቦች ላይ
እዚህ ጋ “ሕዝቦች” የሚወክሉት ሰዎችን ነው። አ.ት፡ “ለብዙ ሀገር ሰዎች … በብዙ ሀገር ሰዎች ላይ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በብዙ ሕዝቦች ላይ ትገዛለህ፣ እነርሱ ግን በአንተ ላይ አይገዙም
እዚህ ጋ “መግዛት” በገንዘብ ዐቅም መብለጥ ማለት ነው። ይህ ትርጉሙ በዐረፍተ ነገሩ የመጀመሪያ ክፍል ካለው ጋር ተመሳሳይ ነው። (See: Parallelism)

Deuteronomy 15:7

ድኻ የሆነ ሰው ቢኖር
እዚህ ጋ “ሰው” ማለት በጥቅሉ ሰው ነው። አ.ት፡ “ድኻ የሆነ ሰው ቢኖር”

ከወንድሞችህ አንዱ
“ከእስራኤላዊ ጓደኞችህ አንዱ”

ከበሮችህ በአንዱ
እዚህ ጋ “በሮች” የሚወክሉት ከተማን ወይም መንደርን በሙሉ ነው። አ.ት፡ “በየትኛውም ከተማህ” (See: Synecdoche)

ልብህን አታደንድን
ግትር መሆን ሰዎቹ ልባቸውን እንዳደነደኑ ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “ግትር አትሁን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከድኻው ወንድምህ እጅህን አትክደን
ለድኻው ሰው ለመስጠት የማይፈቅድ ሰው ድኻው ሰው ከእርሱ ምንም እንዳያገኝ እጁን እንደሚከድን ተደርጎ ተነግሮለታል። አ.ት፡ “ድኻ የሆነውን እስራኤላዊ ጓደኛህን ለመርዳት እምቢ አትበል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ነገር ግን እጅህን ልትዘረጋለት በእርግጥ ይገባል
ድኻውን ሰው የሚረዳ እጁን እንደ ከፈተለት ተደርጎ ተነግሮለታል። አ.ት፡ “ነገር ግን ልትረዳው በእርግጥ ይገባሃል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 15:9

የሚል ክፉ አሳብ በልብህ አይኑር
እዚህ ጋ “ልብ” የሚወክለው የሰውን አዕምሮ ነው። አ.ት፡ “ክፍ አሳብ አታስብ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሰባተኛው ዓመት፣ የምሕረት ዓመት ቀርቧል
ይህ የምሕረት ዓመት ስለቀረበ ይህንን የሚያስበው ሰው ድኻው ሰው ሊመልስለት እንደማይችል በማሰብ ድኻውን ለመርዳት እንደሚያመነታ ያመለክታል። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ሰባተኛው ዓመት
“ሰባተኛው” የሚለው ቃል የሰባት ደረጃ አመልካች ቁጥር ነው። (ደረጃን አመልካች ቁጥር የሚለውን ተመልከት)

የምሕረት ዓመት
“ዕዳን የመሰረዝ ዓመት”

ቀርቧል
በቅርብ የሚሆን አንድ ነገር በአካል የቀረበ በሚመስል መልኩ ተነግሯል። አ.ት፡ “በቅርቡ ይሆናል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ስስታም ሆነህ ለድኻው ወንድምህ ሳትሰጠው እንዳትቀር
“አትጨክን፣ ለእስራኤላዊ ጓደኛህ የትኛውንም ነገር ከመስጠት አትንፈገው”

ወደ እግዚአብሔር ያለቅሳል
“ዕርዳታ ለማግኘት ወደ እግዚአብሔር ይጮኻል”

ኃጢአት ይሆንብሃል
“አንተ ያደረግኸውን እግዚአብሔር ኃጢአት ይለዋል”

ልብህን አይጸጽተው
እዚህ ጋ “ልብ” ሙሉውን ሰው ይወክላል። አ.ት፡ “ቅር አይበልህ” ወይም “ደስ ይበልህ” (Synecdoche እና ምጸት የሚለውን ተመልከት)

እጅህን በምታኖርበት ሁሉ
እዚህ ጋ “እጅህን በምታኖርበት” የሚወክለው ሙሉውን ሰውና እርሱ የሚሠራውን ሥራ ነው። አ.ት፡ “በምትሠራው ሁሉ” (See: Synecdoche)

Deuteronomy 15:11

ድኻ ከምድር ላይ አይጠፋምና
ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በምድር ላይ ድኾች ሁሌም ይኖራሉና” (ድርብ አሉታ የሚለውን ተመልከት)

ድኾች
“ድኾች” የሚለው ስማዊ ቅጽል እንደ ቅጽል ሆኖ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ድኾች ሰዎች” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

‘በምድርህ ላይ -- እጅህን መክፈት አለብህ’ ብዬ አዝሃለሁ
ይህ በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ያለ ትዕምርተ ጥቅስ ነው። ቀጥተኛው ትዕምርተ ጥቅስ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ተደርጎ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በምድርህ ላይ -- እጅህን እንድትከፍት አዝሃለሁ” (በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ያለ ትዕምርተ ጥቅስ እና ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ)

ለወንድምህ፣ ለችግረኛና ለድኻው እጅህን ክፍት
አንድን ሰው ለመርዳት ፈቃደኛ የሚሆን ሰው እጁን እንደሚከፍት ተደርጎ ተነግሮለታል። አ.ት፡ “እስራኤላዊ ጓደኛህን፣ የተቸገሩትንና ድኾችን እርዳቸው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ለወንድምህ፣ ለችግረኛና ለድኻው
“ችግረኛ” እና “ድኻ” የሚሉት ቃላት መሠረታዊ ትርጉማቸው አንድ ሆኖ እነዚህ ራሳቸውን መርዳት የማችሉ ሰዎች መሆናቸው ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ። አ.ት፡ “ራሳቸውን መርዳት የማይችሉ እስራኤላውያን ጓደኞችህን እርዳቸው” (See: Doublet)

Deuteronomy 15:12

ወንድምህ
እዚህ ጋ “ወንድም” ማለት ወንድ ይሁን ሴት በአጠቃላይ እስራኤላዊ የሆነ ማለት ነው። አ.ት፡ “አንድ እስራኤላዊ ጓደኛህ” ወይም “አንድ ዕብራዊ ጓደኛህ” (ተባዕታዊ ቃል ሴቶችን ሲጨምር የሚለውን ቃል ተመልከት)

ለአንተ የተሸጠ
አንድ ሰው ዕዳውን መክፈል ባይችል አንዳንድ ጊዜ የተበደረውን ለመክፈል ራሱን ለባርነት ይሸጥ ነበር። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ራሳቸውን ለአንተ የሸጡ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ስድስት ዓመት
“6 ዓመት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ሰባተኛ ቁጥር
“7 ዓመት”። ይህ “ሰባተኛ” የሰባት ደረጃን አመልካች ቁጥር ነው። (ደረጃን አመልካች ቁጥር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ባዶ እጁን እንዲሄድ አታድርግ
ለራሱ ወይም ለቤተሰቡ የሚያቀርበው አስፈላጊ ነገር የሌለው ሰው እጆቹ ባዶ እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ለእርሱና ለቤተሰቡ የሚያቀርበው እንዲኖረው ሳትሰጠው እንዲሄድ አታድርገው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በልግስና ስጠው
“በደግነት ስጠው”

Deuteronomy 15:15

ባሪያ እንደነበርህ አስብ
እዚህ ጋ “አንተ” የሚለው ቃል ለብዙ ዓመታትባሪያዎች የነበሩትን ቅድም አያቶቹን ይጨምራል። አ.ት፡ “በአንድ ወቅት የአንተም ሕዝብ ባሪያዎች እንደነበሩ አስብ” (See: Forms of You)

አምላክህ እግዚአብሔር ተቤዥቶሃል
እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ በግብፅ ባሪያ ከነበረበት ማዳኑ ሕዝቡን ከባርነት ለመቤዠት ገንዘብ የከፈለ በሚመስል መልኩ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

‘ከአንተ አልለይም’ ቢልህ
ይህ በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ያለ ትዕምርተ ጥቅስ ነው። ቀጥተኛ የሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ከአንተ አልለይም ቢልህ” (በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ያለ ትዕምርተ ጥቅስ እና ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ

ቤትህ
እዚህ ጋ “ቤት” የሚወክለው የሰውየውን ቤተሰብ ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከዚያም ወስፌ ወስደህ በሩ ላይ አስደግፈህ ጆሮውን ትበሳዋለህ
“ከዚያም ራሱን በቤትህ የበር መቃን ላይ ታስደግፍና በጆሮው የጉትቻ ማንጠልጠያ ቦታ ላይ የወስፌው ጫፍ እንጨቱ ጋ እስኪደርስ ትበሳዋለህ”

ወስፌ
ቀዳዳ ለማበጀት የሚጠቅም ጫፉ የሾለና ቀጥ ያለ መሣሪያ (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)

ዕድሜ ልኩን
“እስከ ሕይወቱ መጨረሻ ድረስ” ወይም “እስኪሞት ድረስ”

Deuteronomy 15:18

በነጻ ማሰናበቱ አስቸጋሪ ሆኖ አይሰማህ
ይህ ማለት አንድን ሰው በነጻ በሚያሰናብቱበት ጊዜ ቅር መሰኘት የለባቸውም። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በነጻ በምታሰናብተው ጊዜ ደስ ይበልህ” (ምጸት የሚለውን ተመልከት)

የቅጥር ሠራተኛውን ዕጥፍ ዋጋ ተቀብለሃል
ይህ ማለት ባለቤቱ ሥራ ለማሠራት ከሚቀጥረው ሰው ባነሰ ዋጋ ብቻ ይህንን ባሪያ አሠርቶታል ማለት ነው።

የተቀጠረ ሰው
ይህ ተከፍሎት የሚሠራ ሰው ማለት ነው።

Deuteronomy 15:19

መሸለት
ሱፍ ወይም ጸጉር መቁረጥ

በእግዚአብሔር ፊት
“በእግዚአብሔር ሀልዎት ፊት”

ዓመት በዓመት
“በእያንዳንዱ ዓመት” ወይም “በየዓመቱ”

አንካሳ
ሽባ ወይም አካሉ የተጎዳ

Deuteronomy 15:22

በበሮችህ ውስጥ
እዚህ ጋ “በሮች” የሚወክሉት ከተማውን ወይም መንደሩን ነው። አ.ት፡ “በማኅበረሰብህ ውስጥ” ወይም “በከተማህ ውስጥ” (See: Synecdoche)

ንጹሕ ያልሆኑ -- ሰዎች
ለእግዚአብሔር አገልግሎት ተቀባይነት የሌለው ሰው በአካሉም ንጹሕ እንዳልሆነ ተደርጎ ተነግሮለታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ንጹህ የሆኑ ሰዎች
ለእግዚአብሔር አገልግሎት ተቀባይነት ያለው ሰው በአካሉም ንጹሕ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮለታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሚዳቋ ወይም ድኩላ
እነዚህ በፍጥነት መሮጥ የሚያስችል ረጅምና ቀጭን እግሮች ያሏቸው የዱር እንስሳት ናቸው። እነዚህን በዘዳግም 12:15 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

ደሙን አትብላ
“ደሙን አትመገበው”። ደም ሕይወትን ስለወከለ እስራኤላውያን ደም እንዲመገቡ እግዚአብሔር አልፈቀደላቸውም። (ዘዳግም 12:23ን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 16

1 እግዚአብሔር አምላካችሁ በአቢብ ወር ከግብፅ በሌሊት ስላወጣችሁ የአቢብ ወር ጠብቁ፥ የእግዚአብሔር የአምላካችሁን ፋሲካ አክብሩበት። **2** እግዚአብሔር ለሰሙ ማደሪያ ይሆን ዘንድ በሚመርጠው ስፍራ ከበግና ከፍየል ወይም ከመንጋችሁ አንዱን እንስሳ እግዚአብሔር በአምላካችሁ ፋሲካ አድርጋችሁ ሠዉ። **3** ከቦካ ቂጣ ጋር አትብሉ፤ ከግብፅ የወጣችሁ በችኮላ ነውና፥ ከግብፅ የወጣችሁበትን ጊዜ በሕይወታችሁ ዘመን ሁሉ ታስቡ ዘንድ ያልቦካ ቂጣ ሰባት ቀን ብሉ። **4** ከምድራችሁ ሁሉ ላይ በእናንተ ዘንድ ለሰባት ቀን እርሾ አይገኝ በመጀመሪያው ዕለት ምሽት ከምትሠዉም ላይ ማናቸውም ሥጋ እስከ ጧት ድረስ እንዲቆዩ አታድርጉ። **5** እግዚአብሔር አምላካችሁ በሚሰጣችሁ በማናቸውም ከተማ በሮች ላይ ፋሲካን መሠዋት አይገባችሁም። **6** በዚህ ፈንታ፥ ለስሙ ማደሪያ ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር አምላካችን በመረጠው ስፍራ ፀሐይ ስትጠልቅ በምሽት ላይ ከግብፅ ከወጣችሁበት ሰዓት ላይ በዚያ ፋሲካ ሰዉ። **7** ሥጋውንም ጠብሳችሁ እግዚአብሔር አምላካችሁ በሚመርጠው ስፍራ ብሉ፥ ሲነጋም ወደ ድንኳናችሁ ተመልሳችሁ ሂዱ። **8** ለስድስት ቀንም ያልቦካ ቂጣ ብሉ፤ በሰባተኛው ቀን በእግዚአብሔር በአምላካችሁ የተቀደሰ ጉባኤ አድርጉ፤ ሥራም አትሥሩበት። **9** እህላችሁን ማጨድ ከምትጀምሩበት ዕለት አንሥቶ ለራሰችሁም ሰባት ሳምንታትን ቁጠሩ። **10** ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር አምላካችሁ በባረካችሁ መጠን በፈቃዳችሁ የምታመጡትን ስጦታ በማቅረብ በመከሩ በዓል እግዚአብሔር አምላካችሁን አክብሩ። **11** እናንተ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ወንዶችና ሴቶች አጋልጋዮቻችሁ በከተሞቻችሁ ያለ ሌዋዊና መጻተኛ በመካከላችሁ የሚኖሩ አባት የሌላቸውና ባል የሞተባቸው እግዚአብሔር አምላካችሁ ለስሙ ማደሪያ እንዲሆን በሚመርጠው ስፍራ በእግዚአብሔር በአምላካችሁ ፊት ደስ ይበላችሁ። **12** እናንተም በግብፅ ባሪያዎች እንደ ነበራችሁ አስታውሱ፥ እነዚህንም ሥርዓቶች በጥንቃቄ ጠብቁ አድርጉም። **13** የእህላችሁን ምርት ከዐውድማችሁ ፤ ወይናችሁንም ከመጭመቂያችሁ ከሰበሰባችሁ በኋላ የዳስን በዓል ሰባት ቀን አክብሩ። **14** በበዓላችሁ እናንተና ወንድና ሴት ልጆቻችሁ፥ ወንድና ሴት አገልጋዮቻችሁ፥ በከተማው ያለ ሌዋዊ መጻተኛ፥ አባት አልባውና ባል የሞተባት ደስ ይበላችሁ። **15** እግዚአብሔር በመረጠው ስፍራ ለእግዚአብሔር ለአምላካችሁ በዓሉን ሰባት ቀን አክብሩ፥ እግዚአብሔር አምላካችሁ በእህል ምርታችሁና በእጆቻችሁ ሥራ ሁሉ ይበርካችኋልና፤ ደስታችሁም ፍጹም ይሆናል። **16** ወንዶቻችሁ ሁሉ በዓመት ሦስት ጊዜ በቂጣ በዓል፥ በመከር በዓልና በዳስ በዓል ላይ እርሱ በሚመርጠው ስፍራ በእግዚአብሔር በአምላካችሁ ፊት ይቅረቡ፥ ማንም ሰው በእግዚአብሔር ፊት ባዶ እጁን አይቅረብ፥ **17** በዚህ ፈንታ፥ እግዚአብሔር አምላካችሁ በባረካችሁ መጠን እያንዳንዱ እንደ ችሎታው ይስጥ። **18** እግዝዚአብሔር አምላካችሁ በሚሰጣችሁ ከተማ ሁሉ ለየነገዶቻችሁ ዳኞችንና አለቆችን ሹሙ፥ እነርሱም ሕዝቡን በቅን ፍርድ ይዳኙ፥ **19** ፍርድ አታዛቡ፥ አድልዎ አታደርጉ፥ ጉቦም አትቀበሉ፥ ጉቦ የጠቢባንን ዐይን ያሳውራልና፤ የጻድቃንንም ቃል ያጣምማልና። **20** በሕይወት እንድትኖሩና እግዚአብሔር አምላካችሁ የሚሰጣችሁን ምድር እንድትወርሱ ቅን ፍርድን ብቻ ተከተሉ። **21** ለእግዚአብሔር ለአምላካችሁ በምታደርጉት መሠዊያ አጠገብ የአሼራን ምስል የእንጨት ዐምድ አታቁሙ። **22** እግዚአብሔር አምላካችሁ የሚጠላውን ማምለኪያ ዐምድ ለእናንተ አታቁሙ።

Deuteronomy 16:1

የአቢብ ወር
ይህ በዕብራውያን የቀን አቆጣጠር የመጀመሪያው ወር ነው። እርሱ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ከግብፅ አውጥቶ ያመጣበትን ጊዜ ያስታውሳል። በምዕራባውያኑ አቆጣጠር በመጋቢት መጨረሻና በሚያዝያ መጀመሪያ አካባቢ ነው። (የዕብራውያን ወራት እና ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ፋሲካን ጠብቀው
“ፋሲካን ጠብቀው” በዓሉን ማክበርና የፋሲካን ምግብ መብላት እንዳለባቸው ያመለክታል። አ.ት፡ “የፋሲካን ምግብ አክብር” ወይም “የፋሲካን ምግብ ብላ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ፋሲካን ትሠዋለህ
እዚህ ጋ “ፋሲካ” የሚወክለው ለፋሲካ በዓል የሚሠዋውን እንስሳ ነው። አ.ት፡ “ለፋሲካ መሥዋዕት ታቀርባለህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 16:3

ከእርሱ ጋር
እዚህ ጋ “እርሱ” የሚያመለክተው የሚሠዉትንና የሚበሉትን እንስሳ ነው።

ሰባት ቀን
“7 ቀን” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

የመከራን እንጀራ
ይህ እርሾ የሌለበት እንጀራ ስም ነበር። ሙሉ ትርጉሙ በግልጽ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ይህ እንጀራ በግብፅ በነበራችሁበት ጊዜ ምን ያህል እንደተሰቃያችሁ ያስታውሳችኋል” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

በጥድፊያ ከግብፅ ምድር የወጣችሁበትን
ሕዝቡ በፍጥነት ግብፅን ለቀው መውጣት ስለነበረባቸው እርሾ ጨምረውበት እንጀራ ለመጋገር በቂ ጊዜ አልነበራቸውም። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግለጽ ሊደረግ ይችላል። አ.ት፡ “በችኮላ ከግብፅ በወጣችሁ ጊዜ እርሾ የገባበት እንጀራ ለማዘጋጀት ጊዜ አልነበራችሁም” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

በሕይወት ዘመናችሁ ሁሉ ይህንን አድርጉ
“በሕይወት እስካላችሁ ድረስ”

ልብ በሉ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “አስታውሱ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በመካከላችሁ ምንም እርሾ አይታይ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በመካከላችሁ ምንም እርሾ አይኑራችሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በግዛታችሁ ሁሉ
“በክልሎቻችሁ ሁሉ ውስጥ” ወይም “በምድራችሁ ሁሉ ላይ”

የመጀመሪያ ቀን
ይህ “የመጀመሪያ” አንድን የሚያመለክት የደረጃ አመልካች ቁጥር ነው። (ደረጃን አመልካች ቁጥር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 16:5

ፋሲካን መሠዋት አይኖርብህም
እዚህ ጋ “ፋሲካ” የሚወክለው የሚሠዋውን እንስሳ ነው። አ.ት፡ “ለፋሲካ እንስሳውን መሠዋት አይኖርባችሁም” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በየትኛውም የከተማችሁ በሮች
እዚህ ጋ “በሮች” የሚወክሉት ከተሞቹን ወይም መንደሮችን ነው። አ.ት፡ “በየትኛውም መንደሮችህ ውስጥ” (See: Synecdoche)

ፀሐይ በምትወርድበት
“ፀሐይ ስትጠልቅ”

Deuteronomy 16:7

መጥበስ ይኖርብሃል
“ማብስል ይኖርብሃል”

ስድስት ቀን
“6 ቀን” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ሰባት ቀን
“ሰባተኛ” የሰባት ደረጃን አመልካች ቁጥር ነው (ደረጃን አመልካች ቁጥር የሚለውን ተመልከት)

የተለየ ጉባዔ
“ልዩ ስብሰባ”

Deuteronomy 16:9

ሰባት ሳምንት ቁጠር
“7 ሳምንት ቁጠር” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

እህል ማጨድ ከምትጀምርበት ጊዜ ጀምሮ
“ማጨድ ከምትጀምርበት” የሚለው ሐረግ መከር መሰብሰብ የሚጀመርበትን ጊዜ ማመላከቻ መንገድ ነው። አ.ት፡ “እህል መሰብሰብ ከምትጀምርበት ጊዜ ጀምሮ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ማጭድ
ሣር፣ ሰብል፣ እና ወይን ለመቁረጥ የሚያገለግል ቆልማማ ምላጭ ያለው መሣሪያ ነው። (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)

በእጅህ በምትሰጠው የበጎ ፈቃድ ስጦታ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው ሙሉውን ሰው ነው። አ.ት፡ “የበጎ ፈቃድ ስጦታህን ትሰጣለህ” (See: Synecdoche)

አምላክህ እግዚአብሔር በባረከህ መጠን
“አምላክህ እግዚአብሔር እንደ ሰጠህ ምርት መጠን”። ይህ ማለት ሰዎቹ ምን ያህል መስጠት እንደሚኖርባቸው የሚወስኑት በዚያ ዓመት ባመረቱት ምርት መጠን ይሆናል።

Deuteronomy 16:11

ወንድ ልጅህ፣ ሴት ልጅህ፣ ወንድ ባሪያህ፣ ሴት ባሪያህ፣ ሌዋዊው
እነዚህ አንድን ተለይቶ የታወቀን ሰው አያመለክቱም። የሚያመለክተው እንዲህ ያሉትን ሰዎች በአጠቃላይ ነው። አ.ት፡ “ወንዶች ልጆቻችሁን፣ ሴቶች ልጆቻችሁን፣ ወንዶች ባሪያዎቻችሁን፣ ሴቶች ባሪያዎቻችሁን፣ የትኛውንም ሌዋዊ” (See: Generic Noun Phrases)

በከተማህ በሮች ውስጥ
እዚህ ጋ “በሮች” የሚወክሉት ከተሞችን ወይም መንደሮችን ነው። አ.ት፡ “በመንደሮችህ ውስጥ” (See: Synecdoche)

መጻተኛው፣ አባት የሌላቸውንና መበለቶችን
ይህ የሚያመለክተው እንዲህ ያሉትን የመሰሉ ሰዎችን በአጠቃላይ ነው። አ.ት፡ “መጻተኞችን ሁሉ፣ ወላጆቻቸውን ያጡትን፣ መበለቶችን” (See: Generic Noun Phrases)

አባት የሌላቸውን
እነዚህ አባትና እናት የሞቱባቸውና የሚንከባከባቸው ዘመድ የሌላቸው ልጆች ናቸው።

መበለት
ይህ ማለት ባል የሞተባትና በእርጅናዋ የሚረዳት ልጅ የሌላት ሴት ማለት ነው።

ልብ በል
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “አስታውስ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 16:13

የመጠለያ በዓል
የዚህ በዓል ሌሎች ስሞች፣ “የመገናኛው ድንኳን በዓል”፣ “የዳስ በዓል”፣ እና “የመሰብሰብ በዓል”። በመከር ጊዜ ገበሬዎች በመስኩ ላይ ጊዜያዊ መጠለያ ይሠሩ ነበር። ይህ በዓል የሚደረገው የዓመቱ መከር ከተሰበሰበ በኋላ ነበር።

ሰባት ቀን
“7 ቀን” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

በበሮችህ ውስጥ
እዚህ ጋ “በሮችህ” የሚለው ቃል የሚወክለው ከተሞችንና መንደሮችን ነው። “በመንደሮችህ ውስጥ” (See: Synecdoche)

Deuteronomy 16:15

በዓሉን
“የመጠለያ በዓሉን”

የእጆችህን ሥራ ሁሉ
እዚህ ጋ “እጆች” የሚወክሉት ሙሉውን ሰው ነው። አ.ት፡ “የምትሠራውን ሥራ ሁሉ” (See: Synecdoche)

Deuteronomy 16:16

ወንዶችህ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ይቅረቡ
እግዚአብሔር ሴቶቹ እንዲመጡ ባይጠይቅም ለእነርሱም ተፈቅዶላቸዋል። ወንዶቹ መላውን ቤተሰባቸውን መወከል ይችሉ ነበር።

በእግዚአብሔር ፊት ይቅረቡ
“ይምጡና በእግዚአብሔር ሀልዎት ፊት ይቁሙ”

ማንም በእግዚአብሔር ፊት ባዶ እጁን አይታይ
“በእግዚአብሔር ፊት ስጦታ ሳይዙ አይምጡ”። እነዚህ ሁለት አሉታዊ ሐረጎች በአንድ ላይ አዎንታዊ ትርጉም አላቸው። አ.ት፡ “ወደ እግዚአብሔር ፊት የሚመጣ ሁሉ ስጦታ ያምጣ” (ምጸት የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 16:18

ዳኞችን አድርግ
“ዳኞችን ሹም” ወይም “ዳኞችን ምረጥ”

በከተሞችህ በሮች ውስጥ
እዚህ ጋ “በሮች” የሚወክለው ከተማን ወይም መንደርን ነው። አ.ት፡ “በመንደሮችህ ሁሉ ውስጥ” (See: Synecdoche)

ይወሰዳሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ትመርጣቸዋለህ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በሕዝቡ ላይ በጽድቅ ፍርድ ዳኙ
“ሕዝቡን በፍትሐዊነት ዳኙ”

ፍትሕን በኃይል ምክንያት አታዛባ
ሙሴ ስለ ፍትሕ ሲናገር ብርቱው ሰው ከደካማው ሰው በጉልበት እንደሚቀማው አንዳች ቁሳዊ አካል አድርጎ ይናገራል። ይህ በአዎንታዊ መልኩ ሊነገር ይችላል። የአንተ ቋንቋ “ለመውሰድ ኃይል ተጠቀም” ለማለት አንድ ቃል ይኖረው ይሆናል። አ.ት፡ “በምትዳኝበት ጊዜ ኢፍትሐዊ አትሁን” ወይም “ትክክለኛ ውሳኔዎችን ስጥ” (See: (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት and Double Negatives))

አታድርግ
እዚህ ጋ “አንተ” የሚያመለክተው እነዚያን ዳኞችና አለቆች ተደርገው የተሾሙትን ነው። (See: Forms of You)

ጉቦ የጠቢቡን ዓይኖች ያሳውራልና የጻድቁንም ቃል ያጣምማልና
ጉቦ መቀበል ሰዎችን እንደሚያበላቸው ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ጉቦን የሚቀበል ጥበበኛ ሰው እንኳን ይታወራል፣ ጉቦን የሚቀበል ጻድቅ ሰውም እንኳን ሐሰትን ይናገራል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ጉቦ የጠቢቡን ዓይኖች ያሳውራል
ክፉ በሆነው ነገር ላይ እንዳይናገር ጉቦን የሚቀበል ጠቢብ ሰው የሚታወር ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ጠቢቡ
“ጠቢቡ” የሚለው ስማዊ ቅጽል እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ጠቢብ ሰው” ወይም “ጥበበኛ ሰዎች” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

የጻድቁን ቃል ያጣምማል
“ጻድቅ” የሚለው ስማዊ ቅጽል እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ጻድቁን ሰው እንዲዋሽ ያደርገዋል” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

ፍትሕን ተከተል፣ ፍትሕን ብቻ ተከተል
ፍትሕ በሚራመድ ሰው ተመስሎ ተነግሮለታል። ትክክለኛና ቅን የሆነውን ነገር የሚያደርግ ሰው ፍትሕን በቅርበት እንደተከተለ ተነግሮለታል። አ.ት፡ “አግባብነት ያለውን ብቻ አድርግ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አምላክህ እግዚአብሔር የሚሰጥህን ምድር ውረስ
እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚሰጣቸውን ምድር መቀበል ሕዝቡ ምድሪቱን ከእግዚአብሔር እንደሚወርስ ሆኖ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 16:21

ማድረግ የለብህም
እዚህ ጋ “አንተ” የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ በሙሉ ነው። (See: Forms of You)

አምላክህ እግዚአብሔር የሚጠላውን የትኛውንም የድንጋይ ማምለኪያ ዐምድ
“አምላክህ እግዚአብሔር የሚጠላውን” የሚለው ሐረግ ስለ ማምለኪያ የድንጋይ ዐምድ የበለጠ መረጃ ይሰጣል። አ.ት፡ “አምላክህ እግዚአብሔር ስለሚጠላቸው የትኛውንም የማምለኪያ የድንጋይ ዐምድ” (See: Distinguishing versus Informing or Reminding)

የማምለኪያ የድንጋ ዐምድ
ይህ የሚያመለክተው ሐሰተኞችን አማልክት ለማምለክ የሚጠቀሙባቸውን ጣዖታት የሆኑ ዐምዶችን ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 17

1 እንከን ወይም ጉድለት ያለበትን በሬ ወይም በግ እግዚአብሔር ለአምላክችሁ አትሠዉ በአምላካችሁ በእግዚአብሔር ፊት አስጸያፊ ነውና። **2** እግዚአብሔር በሚሰጣችሁ ከተሞች በሮች አብሮአችሁ የሚኖር ወንድ ወይም ሴት ኪዳኑን በማፍረስ በአምላካችሁ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ድርጊት ሲፈጽም ቢገኝ፥ **3** ትእዛዜንም በመተላለፍ ባዕዳን አማልክትን ያመለከ፥ ለእርሱም ማለትም ለፀሐይ ወይምለጨረቃ ወይም ለሰማይ ከዋክብት የሰገደ፥ **4** እናንተ ይህ መደረጉን ብትሰሙ ነገሩን በጥንቃቄ መርምሩ፥ የተባለውም እውነት ከሆንና እንዲህ ያለ አስጸያፊ ነገር በእስራኤል ዘንድ መፈጸሙ ከተረጋገጠ፥ **5** ይህን ክፉ ድርጊት የፈጸመውን ወንድ ወይም ሴት ወደ ከተማ ደጅ ወስዳችሁ ያን ሰው እስኪሞት ድረስ በድንጋይ ውገሩት። **6** ሞት የሚገባው ሰው በሁለት ወይም በሦስት ሰዎች ምስክርነት ይገደል፥ ነገር ግን በአንድ ሰው ምስክርነት ብቻ ማንም ሰው አይገደል። **7** ሲገደልም መጀመሪያ የምስክሮቹ እጅ ቀጥሎም የሕዝቡ ሁሉ እጅ ይረፍበት ክፉን ከመካከላችሁ አስወግዱ። **8** በአንድ የነፍስ ግድያ ዓይነትና በሌላ በአንድ ዓይነት ሕጋዊ ክርክርን በሌላ ወይም በአንድ የክስ ዓይነትና በሌላ መካከል ውሳኔ የሚጠይቅ ማንኛውም ጉዳይ ቢነሣ፥ ከአቅማችሁ በላይ የሆነ ጉዳይ በከተሞቻችሁ ውስጥ ቢያጋጥማችሁ፥ ተነሥታችሁ እግዚአብሔር አምላካችሁ ወደሚመርጠው ስፍራ ውጡ። **9** ካህናት ወደ ሆኑት ሌዋውያንና በዚያን ጊዜ ዳኛ ወደ ሆነው ሰው ሄዳችሁ ስለ ጉዳዩ ጠይቁአቸው፥ እነርሱም ውሳኔውን ይነግሩአችኋል። **10** እናንተም እግዚአብሔር በሚመርጠው ስፍራ እነርሱ በሚሰጡአችሁ ውሳኔ መሠረት ፈጽሙ። እንድፈጽሙ የሚሰጡአችሁን መመሪያ ሁሉ በጥንቃቄ አድርጉ፥ **11** በሚያስተምሩአችሁ ሕግና በሚሰጡአችሁ መመሪያዎች መሠረት ፈጽሙ፥ እነርሱ ከሚነግሩአችሁ ቀኝም ግራም አትበሉ። **12** እግዚአብሔር አምላካችሁን ለማገልገል በዚያ የሚቆመውን ካህን ወይም ዳኛ የሚንቅ ይገደል፥ ከእስራኤልም መካከል ክፉውን አስወግዱ። **13** ሕዝቡም ሁሉ ይህን ሲሰማ ይፈራል፤ ከዚያ ወዲያም እንዲህ ያለውን የንቀት ድርጊት አይደግመውም። **14** እግዚአብሔር አምላካችሁ ወደሚሰጣችሁ ምድር ስትገቡ፥ በምትወርሱአትና በምትቀመጡባት ምድር በዙሪያዬ እንዳሉት አሕዛብ ሁሉ፥ እኔም በላዬ ንጉሥ ላንግሥ ብትሉ፥ **15** ከዚያ፥ እግዚአብሔር አምላካችሁ የሚመርጠውን ንጉሥ በላይህ ታነግሣለህ፥ ከገዛ ወንድሞችህ መካከል እንጂ እስራኤላዊ ወንድምህ ያልሆነውን ባዕድ በላይህ አታንግሥ። **16** ንጉሡም ብዙ ፈረሶችን ለራሱ አያብዛ ወይም ደግሞ የፈረሰኞችን ቁጥር ለመጨመር ሕዝቡን ወደ ግብፅ አይመልስ፤ **17** እግዚአብሔር በዚያ መንገድ ፈጽሞ አትመለሱ፥ ብሎአችኋልና፤ ልቡ እንዳይስትም ብዙ ሚስቶችን አያግባ፥ ብዙ ብር ወይም ወርቅ ለራሱ አያብዛ። **18** በመንግሥቱ ዙፋን ላይ በሚቀመጥበትም ጊዜ የዚህን ሕግ ቅጅ ከሌዋውያን ካህናት ወስዶ በጥቅልል መጽሐፍ ለራሱ ይጻፍ። **19** እግዚአሔር አምላኩን ማክበር ይማር ዘንድ የዚህን ሕግ ቃል ሁሉና ይህን ሥርዓት በጥንቅቄ ይጠብቅ ዘንድ ከእርሱ ጋር ይሁን፤በሁሉም ቀኖች ያንብበው። **20** ይህን የሚያደርገው ከወንድሞቹ ላይ ልቡ እንዳይኮራ፥ ከትእዛዘትም ወደ ኋላ እንዳይመለስ፥ እርሱና ልጆቹም ረጅም ዘመን ይገዙ ዘንድ፥ ከሕጉ ቀኝ ወይም ግራም አበል።

Deuteronomy 17:1

የትኛውም እንከን ያለበት
“እንከን ያለበት” ወይም “አንዳች ጉድለት ያለበትን”። እንስሳው ሲታይ ጤነኛና እንከን የሌለበት

ያ ለእግዚአብሔር አስጸያፊ ይሆናል
“ያ ለእግዚአብሔር አስቀያሚ ይሆናል

Deuteronomy 17:2

ቢገኝ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አንድ ሰው ብታገኝ” ወይም “አንድ ሰው ቢኖር” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በየትኛውም የከተማህ በሮች ውስጥ
እዚህ ጋ “የከተማ በሮች” ከተሞችን ወይም መንደሮችን ይወክላሉ። አ.ት፡ “ከከተሞችህ በአንዱ ቢኖር” (See: Synecdoche)

በአምላክህ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነውን
የእግዚአብሔር ፊት የእግዚአብሔርን ውሳኔ ወይም ምዘና ይወክላል። አ.ት፡ “አምላክህ እግዚአብሔር ክፉ ነው ብሎ የሚያስበው ነገር” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ቃል ኪዳኑን ይተላለፋል
“ቃል ኪዳኑን አይታዘዝም”

የትኛውንም የሰማይ ሰራዊት
“የትኛውንም ኮከብ”

እኔ ያላዘዝኩትን
“እንዲያደርገው ለማንም ያላዘዝኩትን”

ስለዚህ ነገር ቢነገርህ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አንድ ሰው ስለዚህ የእምቢተኝነት ተግባር ቢነግርህ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በጥንቃቄ መርምር
የነገር ስም የሆነው “ምርመራ” እንደ ግሥ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የሆነውን ነገር በጥንቃቄ መርምር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

እንዲህ ያለ አስጸያፊ ነገር በእስራኤል ተደርጎ እንደሆን
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አንድ ሰው እንዲህ ያለውን አስከፊ ነገር በእስራኤል አድርጎ እንደሆነ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 17:5

ሞት የሚገባው ሰው በሁለት ወይም በሦስት ምስክሮች አፍ ይገደል
እዚህ ጋ “አፍ” የሚወክለው የመስካሪዎችን ምስክርነት ነው። ይህ ወደ አድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “በሰውየው ላይ ሁለት ወይም ሦስት ምስክሮች ከመሰከሩበት ከዚያ በኋላ ታስወግደዋለህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር፣ አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ እና ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ነገር ግን በአንድ ምስክር አፍ ብቻ መገደል የለበትም
እዚህ ጋ “አፍ” የሚወክለው የመስካሪውን ምስክርነት ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ነገር ግን በእርሱ ላይ የሚመሰክረው አንድ ሰው ብቻ ከሆነ ያንን ሰው ማስወገድ አይኖርብህም” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እርሱን ለመግደል በመጀመሪያ የምስክሮች እጅ፣ ከዚያም የሕዝቡ ሁሉ እጅ ይረፍበት
እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው ምስክሮችን በሙሉ ነው። አ.ት፡ “ድንጋዮቹን ለመወርወር ምስክሮቹ ራሳቸው የመጀመሪያ ይሁኑ፣ ከዚያም ሕዝቡ ሁሉ በእርሱ ላይ ድንጋይ በመወርወር ይግደሉት” (See: Synecdoche)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Deuteronomy 17:8

ጉዳይ ቢነሣ
“ጉዳይ ቢኖር” ወይም “ሁኔታ ቢኖር”

የአንዱ ሰው መብትና የሌላው ሰው መብት
“መብት” አንድ ሰው አንድን ነገር የሚያደርግበት ወይም አንድ ነገር እንዲኖረው የሚያስችለው ሕጋዊ ስልጣን ነው።

በከተማህ በሮች ውስጥ
እዚህ ጋ “የከተማ በሮች” ከተሞችን ወይም መንደሮችን ይወክላል። አ.ት፡ “በመንደርህ ውስጥ” (See: Synecdoche)

ምክራቸውን ጠይቅ
የነገር ስም የሆነው “ምክር” እንደ ግሥ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እንዲመክሩህ ጠይቃቸው” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ውሳኔውን ይሰጡሃል
የነገር ስም የሆነው “ውሳኔ” እንደ ግሥ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ይሰጣሉ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 17:10

የተሰጠህን ሕግ ተከተል
ካህናትና ዳኛው የሚወስኑትን የሚታዘዝ ሰው በአካሉ ከሕግ ኋላ እንደተከተለ ተደርጎ ተነግሯል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ስለ ጉዳዩ ዳኛውና ካህናት የሚወስኑትን ታዘዝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 17:12

ካህኑን የማይሰማ -- ወይም ዳኛውን የማይሰማ
“ካህኑን የማይታዘዝ … ወይም ዳኛውን የማይታዘዝ

ከእስራኤል ክፉን ታርቃለህ
ስማዊ ቅጽል የሆነው “ክፉን” እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ይህንን ክፉ ነገር ያደረገውን ሰው ከእስራኤል መካከል ታስወግደዋለህ” ወይም “ይህንን ክፉ ሰው ግደለው” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

ሕዝቡ ሁሉ ሰምተው ይፈራሉ፣ ከእንግዲህም የዕብሪትን ተግባር አይፈጽሙም
ሕዝቡ የዕብሪት ተግባር የፈጸመው ሰው ስለመገደሉ በሚሰሙበት ጊዜ ይፈራሉ እነርሱ ራሳቸው የዕብሪትን ተግባር አይፈጽሙም እንደ ማለት ነው። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

Deuteronomy 17:14

ወደ ምድሪቱ በምትመጡበት ጊዜ
“በምትመጡበት” የሚለው ቃል “በምትሄዱበት” ወይም “ስትገቡ” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። (ሂድ እና ና የሚለውን ተመልከት)

‘በዙሪያዬ እንዳሉት ሕዝቦች በራሴ ላይ ንጉሥ አነግሣለሁ’ በምትልበት ጊዜ፣ ያን ጊዜ
ይህ በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ያለ ትዕምርተ ጥቅስ ነው። ቀጥተኛ የሆነው ትዕምርተ ጥቅስ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ተደርጎ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ከዚያም በዙሪያህ ያሉ ሀገራት ሕዝቦች ንጉሥ እንዳላቸው አንተም እንዲኖርህ ትወስናለህ፣ ከዚያም” (በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ያለ ትዕምርተ ጥቅስ እና ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ የሚለውን ተመልከት)

በዙሪያዬ እንዳሉት -- በራሴ ላይ ንጉሥ አነግሣለሁ
ሙሴ እንደ አንድ ሰው ቆጥሮ የሚናገራቸው ሰዎች አሉት። ወደ ብዙ ቁጥር ተውላጠ ስም መተርጎም በይበልጥ የተለመደ ይሆናል። አ.ት፡ “በዙሪያችን … ለራሳችን እናነግሣለን” (ተውላጠ ስም የሚለውን ተመልከት)

ለራሴ ንጉሥ አነግሣለሁ
በእስራኤል ለአንድ ሰው እንደ ንጉሥ እንዲገዛቸው ሥልጣን መስጠታቸው ሕዝቡ ያንን ሰው ከእነርሱ በላይ ባለ ቦታ ላይ እንዳስቀመጡት ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በዙሪያዬ እንዳሉት ሕዝቦች ሁሉ
“በዙሪያዬ ያሉ ሕዝቦች”

ሀገራት ሁሉ
እዚህ ጋ “ሀገራት” የሚወክሉት በሀገራቱ ውስጥ የሚኖሩትን ሰዎች ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከወንድሞችህ መካከል አንዱን
“እንደ አንተው እስራኤላዊ ከሆኑት አንዱን”

በራስህ ላይ ወንድምህ ያልሆነውን መጻተኛ
የእነዚህ ሁለት ሐረጎች ትርጉም ተመሳሳይ ነው። ሁለቱም የሚያመለክቱት እስራኤላዊ ያልሆነውን ሰው ነው። የእስራኤል ሕዝብ መጻተኛው እንዲገዛቸው እንዳይፈቅዱ እግዚአብሔር አጽንዖት ሰጥቷል። አ.ት፡ “በራስህ ላይ መጻተኛውን” ወይም “እስራኤላዊ ያልሆነውን በራስህ ላይ” (See: Doublet)

Deuteronomy 17:16

እግዚአብሔር፣ ‘በዚያ መንገድ እንዳትመለስ’ ብሎአልና።
ይህ በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ሌላ ትዕምርተ ጥቅስ አለው። ቀጥተኛው ትዕምርተ ጥቅስ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ተደርጎ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ዳግመኛ ወደ ግብፅ እንዳትመለሱ ብሏልና” (በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ያለ ትዕምርተ ጥቅስ እና ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ የሚለውን ተመልከት)

ልቡ እንዳይስት
እዚህ ጋ “ልብ” የሚያመለክተው ሙሉውን ሰው ነው። ባዕዳን ሴቶችን የሚያገባና የእነርሱን ሐሰተኛ አማልክት ለማምለክ የሚጀምር እስራኤላዊ ንጉሥ ልቡ ከእግዚአብሔር እንደሚመለስ ተነግሯል። አ.ት፡ “እግዚአብሔርን ማክበሩን በማቆም ሐሰተኞች አማልክትን ማምለክ እንዲጀምር እንዳያደርጉት” (Synecdoche and ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 17:18

በመንግሥቱ ዙፋን ላይ በሚቀመጥበት ጊዜ
እዚህ ጋ “ዙፋን” የሚወክለው ሰውየው እንደ ንጉሥ የሚኖረውን ኃይልና ሥልጣን ነው። በዙፋን መቀመጥ ንጉሥ መሆን ማለት ነው። አ.ት፡ “ንጉሥ በሚሆንበት ጊዜ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የዚህን ሕግ ቅጅ ለራሱ በጥቅልል ላይ ይጻፈው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “በግሉ የዚህን ሕግ ቅጅ በጥቅልል ላይ ለራሱ ይጻፍ” ወይም 2) “የዚህን ሕግ ቅጅ የሚጽፍለትን ሰው ይሹም”

ሌዋውያን በሆኑት ካህናት ፊት ካለው ሕግ
“ሌዋውያን ካህናት ከሚጠብቁት ከሕጉ ቅጅ”

የዚህን ሕግ ቃል ሁሉ እና እነዚህን ሥርዓቶች እንዲጠብቅ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ የሚሉት ተመሳሳይ ነገር ሲሆን ንጉሡ የእግዚአብሔርን ሕግ በሙሉ መታዘዝ እንዳለበት አጽንዖት ይሰጣሉ። (See: Parallelism)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Deuteronomy 17:20

ልቡ በወንድሞቹ ላይ እንዳይታበይ
እዚህ ጋ “ልቡ” የሚያመለክተው ሙሉውን ሰው ነው። የአንድ ንጉሥ ዕብሪተኛ መሆን ልቡ እንደ ታበየ ሆኖ ተነግሮለታል። አ.ት፡ “ዕብሪተኛ እንዳይሆን” ወይም “እንደ እርሱ ካለው እስራኤላዊ ይልቅ የተሻለ እንደሆነ እንዳያስብ” (Synecdoche እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከትዕዛዛቱ ወደ ቀኝ ወይም ወደ ግራ እንዳይመለስ
አንድ ንጉሥ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት አለመታዘዙ አንድ ሰው ከትክክለኛው መንገድ እንደሚወጣ በሚመስል መልኩ ተነግሯል። ይህ በአዎንታዊ መልኩ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ከትዕዛዛቱ የትኛውንም ሳይታዘዝ እንዳይቀር” ወይም “ትዕዛዛቱን ሁሉ እንዲጠብቅ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ምጸት የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 18

1 ሌዋውን ካህናት፥ የሌዊ ነገድ ሁሉ ከእስራኤል ጋር የመሬት ድርሻ ወይም ርስት ስለማይኖራቸው ለእግዚአብሔር በእሳት የሚቀርበው ድርሻቸው ነውና ይብሉ። **2** እግዚአብሔር በሰጣቸው ተስፋ መሠረት እርሱ ራሱ ርስታቸው ስለሆነ በወንድሞቻቸው መካከል ርስት አይኖራቸውም። **3** ኮርማ ወይም በግ የሚሠዋው ሕዝብ ለካህኑ የሚሰጠው ድርሻ ወርቹን፥ ሁለት ጉንጮችንና የሆድ ዕቃውን ነው። **4** የእህላችሁን፥ የአዲሱን ወይናችሁንና የዘይታችሁን በኩራት እንዲሁም ከበጎቻችሁ በመጀመሪያ የተሸለተውን ጠጉር ትሰጣላችሁ። **5** በእግዚአብሔር ስም ቆሞ ለዘላለም ያገለግል ዘንድ እግዚአብሔር አምላክህ ከነገዶቻችሁ ሁሉ እርሱንና ዘሮቹን መርጦአል። **6** አንድ ሌዋዊ ከሚኖርበት ከየትኛውም በእስራኤል ካሉት ከተሞቻችሁ መካከል በፍጹም ፈቃድ እግዚአብሔር ወደሚመርጠው ስፍራ ቢመጣ፥ **7** በእግዚአብሔር ፊት ቆመው እንደሚያገለግሉት ሌዋውያን ወንድሞቹ፥ እርሱም በእዚግአብሔር በአምላኩ ስም ያገልግል። **8** ከቤተ ሰቡ ንብረት ሽያጭ ላይ ገንዘብ ቢቀበል እንኳ ባልንጀሮቹ ከሚያገኙት ጥቅም እኩል ይካፈላል። **9** እግዚአብሔር አምላካችሁ ወደሚሰጣችሁ ምድር በምትገቡበትጊዜ በዚያ የሚኖሩት አሕዛብ የሚፈጽሙትን አስጸያፊ መንገድ አትከተሉ። **10** በመካከላችሁ ወንድ ወይም ሴት ልጁን በእሳት የሚሥዋ ሟርተኛ፥ ወይም መተተኛ፥ ሞራ ገላጭ፥ ጠንቋይ፥ ወይም በድግምት የሚጠነቁል፥ **11** መናፍስት ጠሪ ወይም ሙት አነጋጋሪ በመካከላችሁ ከቶ አይገኝ። **12** እነዚህን የሚያደርግ ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊ ነው፥ ከእነዚህ አጸያፊ ልምዶች የተነሣ እግዚአብሔር አምላካችሁ እነዚያን አሕዛብ ከፊታችሁ ያስወጣቸዋል። **13** በእግዚአብሔር በአምላካችሁ ፊት ነውር የሌላው ይሁን። **14** ምድራቸውን የምታስለቅቃቸው አሕዛብ፥ መተተኞችን ወይም ሟርተኞችን ያዳምጣሉ፤ እናንተ ግን ይህን እንድታደርጉ እግዚአብሔር አምላካችሁ አልፈቀደላችሁም። **15** እግዚአብሔር አምላካችሁ ከገዛ ወንድሞቻችሁ መካከል እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣላችኋል። እርሱን አድምጡ። **16** በኮሬብ ጉባኤ በተደረገበት ዕለት እንዳልሞት የእግዚአብሔር የአምላካችሁን ድምፅ አንስማ፤እንዲህ ያለውንም አስፈሪ እሳት ደግመን አንይ ብላችሁ እግዚአብሔር አምላካችሁን የጠየቃችሁት ይህ ነውና። **17** እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ፥ የተናገሩት መልካም ነው። **18** ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለ ነቢይ አስነሣላቸዋለሁ። ቃሌን በአፉ አደርጋለሁ፤ የማዘውንም ሁሉ ይነግራቸዋል። **19** ማንም ሰው ነቢዩ በስሜ የሚናገረውን ቃሌን ባይሰማ፤ እኔ ራሴ ተጠያቂነት አደርገዋለሁ። **20** ነገር ግን እንዲናገር እኔ ያላዘዝሁትን ቃል በድፍረት በስሜና በሌሎች አማልክት ስም የሚናገር ነቢይ ይገደል። **21** እናንተም በልባችሁ እግዚአብሔር ያልተነገረውን መልእክት እንዴት ማወቅ እንችላለን? ብትሉ፥ **22** ነቢዩም በእግዚአብሔር ስም የተናገርው ካልተፈጸመ ወይም እውነት ሆኖ ካልተገኘ፤ መልእክቱ እግዚአብሔር የተናገርው አይደለም። ያ ነቢይ በድፍረት ተናግሮታልና እርሱን አትፍራው።

Deuteronomy 18:1

ከእስራኤል ጋር ድርሻም ሆነ ርስት አይኖራቸውም
ሌዋውያን የትኛውንም መሬት ከእግዚአብሔር አለመቀበላቸው ርስት እንዳልተቀበሉ ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “ከሕዝቡ መሬት የትኛውንም አይወስዱም” ወይም “እስራኤላውያን ከሚወስዱት መሬት የትኛውንም አይቀበሉም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ምንም ድርሻ
“ምንም ክፍል” ወይም “ምንም ድርሻ”

በወንድሞቻቸው መካከል
“በሌሎች የእስራኤል ነገዶች መካከል” ወይም “በሌሎች እስራኤላውያን መካከል”

ርስታቸው እግዚአብሔር ነው
አሮንና የእርሱ ተወላጆች እንደ ካህናት እግዚአብሔርን በማገልገላቸው ታላቅ ክብር እንደሚኖራቸው ሙሴ ሲናገር እግዚአብሔርን እንደሚወርሱት አንዳች ነገር አድርጎ ይናገራል። ተመሳሳዩን ሐረግ በዘዳግም 10፡9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ከዚያ ይልቅ እግዚአብሔር ይኖራቸዋል” ወይም “ከዚያ ይልቅ፣ እግዚአብሔር እርሱን እንዲያገለግሉት ይፈቅድላቸዋል፣ በዚያም አገልግሎት የሚያስፈልጋቸውን ያቀርብላቸዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 18:3

በውስጥ ያሉትን ክፍሎች
ይህ ጨጓራና አንጀት ነው።

ትሰጠዋለህ
“ለካህኑ ትሰጠዋለህ”

መርጦታል
እዚህ ጋ “እርሱን” ሌዋውያንን ሁሉ ይወክላል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእግዚአብሔር ስም ለማገልገል እንዲቆም
እዚህ ጋ “የእግዚአብሔር ስም” የቆመው ለራሱ ለእግዚአብሔርና ለሥልጣኑ ነው። አ.ት፡ “የእርሱ ልዩ አገልጋዮች እንዲሆኑ” ወይም “እንደ እግዚአብሔር ተወካዮች እንዲያገለግሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እርሱንና ወንዶች ልጆቹን ለዘላለም
እዚህ ጋ “እርሱን” የሚወክለው ሌዋውያንን ሁሉ ነው። አ.ት፡ “ሌዋውያንና ተወላጆቻቸው ለዘላለም” (See: Synec- doche)

Deuteronomy 18:6

በሙሉ ነፍሱ ቢፈልግ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “በብርቱ ቢፈልግ” ወይም “በእርግጠኝነት ቢፈልግ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ከዚያም በአምላኩ በእግዚአብሔር ስም ያገልግል
እዚህ ጋ “ስም” የሚወክለው እግዚአብሔርን እና የእርሱን ሥልጣን ነው። አ.ት፡ “ከዚያም አምላኩን እግዚአብሔርን በካህንነት ያገልግል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእግዚአብሔር ፊት በዚያ የሚቆሙት
“በእግዚአብሔር ሀልዎት ፊት በመቅደሱ የሚያገለግሉት”

የቤተሰቡን ርስት
ካህኑ ከአባቱ የሚወርሰው ይህ ነው

Deuteronomy 18:9

በምትመጣበት ጊዜ
(ሂድ እና ና የሚለውን ተመልከት)

የእነዚያን ሕዝቦች አስጸያፊ ተግባር ለመጠበቅ አትማር
በዙሪያቸው ያሉትን ሀገራት ሰዎች ሃይማኖታዊ ተግባራት እግዚአብሔር ይጠላል። እርሱ እጅግ ክፉዎች እንደሆኑ አድርጎ ይመለክታቸዋል። እዚህ ጋ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

“ሀገሮች” ሰዎቹን ይወክላሉ። አ.ት፡ “የሌሎች ሀገራት ሰዎች የሚያደርጓቸውን አስከፊ ነገሮች አታድርጉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በመካከልህ ማንም አይገኝ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በመካከልህ ማንም አይኑር” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ማንም የሚጠነቁል -- ከመናፍስት ጋር የሚነጋገር
እነዚህ አስማትን የሚለማመዱ የተለዩ ሰዎች ናቸው። የትኛውንም ዓይነት አስማት እግዚአብሔር ከልክሏል። ለእንደዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች ሁሉ የሚሆን ቃል ከሌለህ በይበልጥ ጥቅል በሆነ መልኩ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ወደፊት የሚሆነውን ለማወቅ በመሞከር፣ ዕጣ ለመጣል ወይም የሙታንን መናፍስት ለማነጋገር አስማት የሚጠቀም ማንም ቢሆን”

በሲኒ የሚገኙ ምልክቶችን የሚያነብ
በሲኒ ውስጥ ያሉ ቅርጾችንና ስዕሎችን የሚያነብና ከሚያየው ተነሥቶ ወደፊት የሚሆኑትን ሁነቶች የሚተነብይ

Deuteronomy 18:12

ያባርራቸዋል
እዚህ ጋ “እነርሱን” የሚያመለክተው አስቀድሞ በከነዓን የሚኖሩትን ሰዎች ነው።

ለእነዚህ ሕዝቦች
እዚህ ጋ “ሕዝቦች” የሚለው ቃል የቆመው በከነዓን ለሚኖሩ የሕዝብ ወገኖች ነው። አ.ት፡ “ለእነዚህ የሕዝብ ወገኖች” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የምታስወጧቸውን እነዚህን ሕዝቦች
“መሬታቸውን የምትወስድባቸው እነዚህ ሕዝቦች”

Deuteronomy 18:15

አምላክህ እግዚአብሔር ነቢይ ያስነሣልሃል
ነቢይ እንዲሆን እግዚአብሔር አንድን ሰው መሾሙ እግዚአብሔር ሰውየውን እንደሚያነሣው ወይም ብድግ እንደሚያደርገው ሆኖ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከወንድሞችህ አንዱ
“እንዳንተው እስራኤላዊ ከሆኑት አንዱ”

የጠየቅኸው ይህንን ነው
እዚህ ጋ “አንተ” የሚያመለክተው ከ40 ዓመታት በፊት በኮሬብ ተራራ የነበሩትን እስራኤላውያንን ነው።

በኮሬብ ጉባዔ በተደረገበት ቀን
“በኮሬብ በአንድ ላይ በተሰበሰባችሁበት ቀን”

ጉባዔ በተደረገበት ቀን፣ ‘የአምላካችንን የእግዚአብሔርን ድምፅ አንስማ፣ ይህንን ታላቅ እሳትም ከእንግዲህ አንይ፣ እንዲህ ካልሆነ እንሞታለን’ ስትል
ይህ በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ያለ ትዕምርተ ጥቅስ ነው። ቀጥተኛ የሆነው ትዕምርተ ጥቅስ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ተደርጎ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ጉባዔ በተደረገበት ቀን እንዳትሞት ፈርተህ ስለነበር የአምላካችንን የእግዚአብሔርን ድምፅ መስማትም ሆነ ከእንግዲህ የእርሱን ታላቅ እሳት ማየት እንደማትፈልግ በተናገርክ ጊዜ” (በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ያለ ትዕምርተ ጥቅስ እና ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ የሚለውን ተመልከት)

የአምላካችንን የእግዚአብሔርን ድምፅ እንደገና አንስማ
እዚህ ጋ እግዚአብሔር ለተናገረው አጽንዖት ለመስጠት የእርሱ በሆነ ”ድምፅ” ተወክሏል። አ.ት፡ “አምላካችን እግዚአብሔር እንደገና ሲናገር አንስማ” (See: Synecdoche)

Deuteronomy 18:17

ነቢይ አስነሣላቸዋለሁ
እግዚአብሔር፣ አንድን ሰው ነቢይ እንዲሆን መሾሙ፣ እግዚአብሔር ሰውየውን እንደሚያነሣው ወይም ብድግ እንደሚያደርገው ሆኖ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከወንድሞቻቸው መካከል
“እንደ እነርሱ እስራኤላዊ ከሆኑት መካከል”

ቃሌን በአፉ ላይ አኖራለሁ
ነቢዩ ምን ማለት እንዳለበት እግዚአብሔር ለእርሱ መንገሩ እግዚአብሔር በነቢዩ አፍ ውስጥ ቃልን እንደሚጨምርበት ሆኖ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ይነግራቸዋል
“ለእስራኤል ሕዝብ ይነግራቸዋል”

በስሜ የሚናገረውን ቃል የማይሰማ
እዚህ ጋ “ስሜ” የሚወክለው እግዚአብሔርን እና ሥልጣኑን ነው። አ.ት፡ “መልዕክቴን በሚናገርበት ጊዜ የማይሰማው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እጠይቀዋለሁ
“በኃላፊነት እጠይቀዋለሁ” ወይም “እቀጣዋለሁ”። እዚህ ጋ “እርሱን” የሚያመለክተው ነቢዩን የማይሰማውን ሰው ነው።

Deuteronomy 18:20

በትዕቢት ቃልን የሚናገር
“መልዕክት ለመናገር የሚደፍር” ወይም “በዕብሪተኝነት መልዕክት የሚናገር”

በስሜ
እዚህ ጋ “ስሜ” የሚያመለክተው ራሱን እግዚአብሔርንና ሥልጣኑን ነው። አ.ት፡ “ለእኔ” ወይም “በእኔ ሥልጣን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ቃልን
“መልዕክትን”

በሌሎች አማልክት ስም የሚናገር
እዚህ ጋ “ስም” የሚወክለው አማልክቱን ራሳቸውን ወይም ሥልጣናቸውን ነው። ይህ ማለት ሐሰተኞቹ አማልክት አንድን መልዕክት እንዲናገር እንደ ነገሩት ነቢዩ ያስታውቃል ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በልብህ እንዲህ ትላለህ
እዚህ ጋ “ልብ” የሚወክለው የሰውን አሳብ ነው። አ.ት፡ “ራስህን ትጠይቃለህ” ወይም “ለራስህ ትናገራለህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መልዕክቱን እግዚአብሔር እንዳልተናገረ እንዴት እንለያለን?
“ነቢዩ የሚናገረው መልዕክት ከእግዚአብሔር መሆኑን እንዴት እናውቃለን? እዚህ ጋ “እኛ” የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው።

Deuteronomy 18:22

ነቢይ የሚናገረው በእግዚአብሔር ስም ነው
እዚህ ጋ “የእግዚአብሔር ስም” የሚያመለክተው ራሱን እግዚአብሔርን እና ሥልጣኑን ነው። አ.ት፡ “ነቢይ እኔን ወክሎ እንደሚናገር ያስታውቃል” ወይም

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

“ነቢይ በእኔ ሥልጣን እንደሚናገር ያስታውቃል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ነቢዩ በማንአለብኝነት ተናግሮታል
“ነቢዩ ይህንን መልዕክት የተናገረው ያለ እኔ ሥልጣን ነው”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 19

1 እግዚአብሔር አምላካችሁ ምድራቸውን ለእናንተ የሚሰጥባቸውን አሕዛብ በሚደመስሳቸው ጊዜና እናንተም እነርሱን አስለቅቃችሁ በከተሞቻቸውና
በቤቶቻቸው በምትቀመጡበት ጊዜ፥ 2 እግዚአብሔር አምላካችሁ ርስት አድርጎ በሚሰጣችሁ ምድር አማካይ ስፍራ ሦስት ከተሞችን ለራሳችሁ ምረጡ፥ 3 ሰው
የገደለ ሁሉ እንዲሸሸባቸው እግዚአብሔር አምላካችሁ ርስት አድርጎ በሚሰጣችሁ ምድር መንገዶችን ሠርታችሁ በሦስት ክፈሉአቸው። 4 በተንኮል ሳይሆን
ድንገት ሳያስበው ባልንጀራውን ገድሎ ሕይወቱን ለማትረፍ ለሚሸሽ ሰው መመሪያው የሚከተለው ነው። 5 እነሆ፥ አንድ ሰው ከባልንጀራው ጋር እንጨት
ለመቁረጥ ወደ ጫካ ቢሄድ፥ ዛፉን ለመጣል መጥረቢያውን በሚሰነዝርበት ጊዜ ብረቱ ከእጀታው ወልቆ ባልንጀራውን በመምታት ቢገድለው፥ ያ ሰው ከእነዚህ
ከተሞች ወደ አንዱ በመሸሸ ሕይወቱን ማትረፍ ይችላል። 6 አለበለዚያ በተንኮል ሳይሆን ድንገት ሳያስበው ባልንጀራውን ቢገድል፥ መንገዱ ረጅም ከሆነ ደም
ተበቃዩ በንዴት ተከታትሎ ይደርስበትና መገደል የማይገባውን ሰው ሊገድል ይችላል። ይህ ከመሆኑ በፊት ባልንጀራውን ያልጠላ ከሆነ መሞት አይገባውም። 7
ሦስት ከተሞችን ለራሳችሁ እንድትመርጡ ያዘዙአችሁ በዚሁ ምክንያት ነው። 8 ለአባቶቻችሁ በመሐላ በገባላቸው ቃል መሠረት አምላካችሁ እግዚአብሔር
ወሰናችሁን ሲያሰፋውና ለእነርሱ በሰጣቸው መሠረት ምድሪቷን ሁሉ ሲሰጣችሁ፤ 9 እግዝክአብሔር አምላካችሁን እንድትወዱና ምን ጊዜም በመንገዱ
እንድትሄዱ ዛሬ የማዛችሁን እነዚህን ሕግጋት ሁሉ በጥንቃቄ የምትጠብቁ ከሆነ በእነዚህ ላይ ሌሎች ሦስት ከተሞችን ትጨምራላችሁ። 10 እግዚአብሔር
አምላካችሁ ርስት አድርጎ በሚሰጣችሁ ምድር የንጹሕ ሰው ደም እንዳይፈስና በሚፈሰውም ደም በደለኛ እንዳትሆኑ ይህን አድርጉ። 11 ነገር ግን አንድ ሰው
ባልንጀራውን ቢጠላው አድፍጦ ጥቃት ቢያደርስበት፥ ቢገድለውና ከእነዚህ ከተሞች ወደ አንዲቱ ቢሸሽ፥ 12 የሚኖርባት ከተማ ሽማግሌዎች ሰው ልከው
ከከተማው ያስመጡት፥ እንዲገድለውም ለደም ተበቃዩ አሳልፈው ይስጡት። 13 አትራራለት፥ ነገር ግን መልካም እንዲሆንላችሁ የንጹሑን ደም በደል
ከእስራኤል አስወግዱ። 14 እግዚአብሔር አምላካችሁ እንድትወርሱአት በሚሰጣችሁ ምድር ውስጥ ለእናንተ በሚተላለፍላችሁ ርስት ላይ የቀድሞ ሰዎች
ያስቀመጡትን የባልጀራችሁን የድንበር ምልክት አታንሡ። 15 በማንኛውም ወንጀል ወይም ሕግ በመተላለፍ ሰውን ጥፋተኛ ለማድረግ አንድ ምስክር
አይበቃም፥ጉዳዩ በሁለት ወይም በሦስት ሰዎች ምስክርነት መረጋገጥ አለበት። 16 ተንኮለኛ የሆነ ምስክር አንድን ሰው በሐሰት ለመመስከር ቢነሣ፤ 17 ክርክሩ
የሚመለከታቸው ሁለቱ ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት በዚያ ወቅት በሚያገለግሉት ካህናትና ፈራጆች ፊት ይቁሙ። 18 ፈፋጆችም ጉዳዩን በጥልቅ ይመርምሩት፥
19 ያም ምስክሩ በወንድሙ ላይ በሐሰት የመሰከረ መሆኑ ከተረጋገጠ በወንድሙ ላይ ለማድረግ ያሰበውን በእርሱ ላይ አድርጉበት ክፉውን ከመካከላችሁ
አስወግዱ። 20 የቀሩትም ሰዎች ይህን ሰምተው ይፈራሉ፤ እንዲህ ያለው ክፉ ነገርም ለወደፊቱ በመካከላችሁ ከቶ አይደገምም። 21 ርኅራኄ አታድርጉ ሕይወት
ለሕይወት፥ ዐይን ለዐይን፥ ጥርስ ለጥርስ፥ እጅ ለእጅ፥ እግር እግር ይመለስ።

Deuteronomy 19:1

አምላክህ እግዚአብሔር ሕዝቦችን በሚቆርጣቸው ጊዜ
እግዚአብሔር በከነዓን የሚኖሩትን ሰዎች ማጥፋቱ አንድ ሰው የጨርቅ ቁራጭ ወይም የዛፍ ቅርንጫፍ እንደሚቆርጥ እርሱም እንደሚቆርጣቸው ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሕዝቦችን
ይህ በከነዓን የሚኖሩትን የሕዝብ ወገኖች ይወክላል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አምላክህ እግዚአብሔር ምድራቸውን የሚሰጥህን የእነዚያን
“አምላክህ እግዚአብሔር በሚሰጥህ ምድር ላይ ይኖሩ የነበሩት እነዚያ ሕዝቦች”

በምትመጣባቸው
“ከነዚያ ሕዝቦች ምድሪቱን ስትወስድ” ወይም “እነዚያ ሕዝቦች ከለቀቁ በኋላ ምድሪቱን የራስህ ስታደርግ”

ሦስት ከተሞችን ምረጥ
“3 ከተሞችን ምረጥ” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

መንገድ ሥራ
ሰዎች ወደ እነዚህ ከተሞች ለመጓዝ እንዲቀላቸው መንገዶችን መሥራት ይኖርባቸዋል። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

የምድርህን ድንበሮች በሦስት ቦታ ክፈላቸው
ከሚመርጧቸው ከተሞች አንዱ በእያንዳንዱ የምድሪቱ ክፍል ውስጥ ይሁን። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

አምላክህ እግዚአብሔር በሚያወርስህ ምድር
እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ ምድሪቱን መስጠቱ ሕዝቡ ምድሪቱን እንደወረሱ ሆኖ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 19:4

ሕጉ ይህ ነው
“መመሪያዎቹ እነዚህ ናቸው” ወይም “አቅጣጫዎቹ እነዚህ ናቸው”

ሌላውን የገደለ
“ሰው” የሚለው ቃል እንዳለበት ይታወቃል። አ.ት፡ “ሌላውን ሰው የገደለ ሰው” (See: Ellipsis)

ወደዚያ የሚሸሸ
“ከእነዚህ ከተሞች ወደ አንዱ የሚያመልጥ” ወይም “ከእነዚህ ከተሞች ወደ አንዱ የሚሮጥ”

ለመኖር
“ሕይወቱን ለማዳን”። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “የሟች ቤተሰብ ተበቅለው እንዳይገድሉት” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ማንም ሳያውቅ ባልንጀራውን የሚገድል
እዚህ ጋ “ባልንጀራ” ማለት በአጠቃላይ የትኛውም ሰው ማለት ነው። አ.ት፡ “በድንገት ሌላውን ሰው የሚገድል የትኛውም ሰው”

አስቀድሞ ጥላቻ ሳይኖረው
“ነገር ግን ባልንጀራውን ከመግደሉ በፊት አልጠላው እንደሆነ”። ባልንጀራውን አስቦበት የሚገድልበት ምክንያት እንዳልነበረው ያመለክታል። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለምሳሌ፣ አንድ ሰው እንጨት ለመቁረጥ ወደ ጫካ ቢሄድ
ደራሲው አንድ ሰው ሌላውን በድንገት የሚገድልበትን መላ ምታዊ ሁኔታ ይሰጣል። (See: Hypothetical Situations)

ብረቱ ከእጀታው ወልቆ
የመጥረቢያው የብረት ክፍል ከእንጨቱ እጀታ ወልቆ

ባልንጀራውን መትቶ ቢገድለው
ይህ ማለት የመጥረቢያው ራስ ባልንጀራውን መትቶ ገድሎታል ማለት ነው።

ከእነዚህ ከተሞች ወደ አንዲቱ -- ሕይወቱን ያድን
የሟቹ ሰው ቤተሰብ ምናልባት ሊበቀሉት እንደሚሞክሩ ያመለክታል። በዚያ ያሉት ሰዎች ጥበቃ እንዲያደርጉለት እርሱን የገደለው ሰው ከእነዚህ ከተሞች ወደ አንዲቱ መሸሸ ይችላል (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

Deuteronomy 19:6

ደም ተበቃዩ
እዚህ ጋ “ደም” የሚወክለው የተገደለውን ሰው ነው። “ደም ተበቃዩ” ሰው የሟቹ የቅርብ ዘመድ ነው። ገዳዩን ለመቅጣት ኃላፊነቱ የዚህ ዘመድ ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሕይወትን የሚያጠፋ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ሌላውን ሰው የገደለ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በንዴት ግሎ
የአንድ ሰው በጣም መቆጣት ልክ ቁጣ እንደሚግል አንዳች ነገር ተቆጥሮ ተነግሯል። አ.ት፡ “በጣም ተቆጥቶ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ይመታውና ይገድለዋል
"ደም ተበቃዩ ሟችን የገደለውን ሰው ይመታና ይገድለዋል”

አስቀድሞ ባልንጀራውን አልጠላውምና ያ ሰው መሞት የሚገባው ባይሆንም
“ሌላውን ሰው የገደለው በድንገት ስለሆነና ጠላቱ ስላልነበረ፣ ሰውየውን ለመጉዳትም ስላላቀደ ያ ሰው መሞት የሚገባው ባይሆንም”

Deuteronomy 19:8

ድንበርህን ያሰፋል
“የምትወርሰውን ተጨማሪ መሬት ይሰጥሃል”

ለቅድም አያቶችህ እንደማለው
“እርሱ እንደሚያደርገው ለቅድም አያቶችህ ተስፋ የሰጠውን”

ታደርጋቸው ዘንድ እነዚህን ትዕዛዛት በሙሉ ብትጠብቅ
“እነዚህን ትዕዛዛት በሙሉ ብትታዘዝ”

ዘወትር በመንገዶቹ እንድትሄድ
እግዚአብሔር፣ አንድ ሰው እንዲኖረውና እንዲያደርገው የሚፈልግበት አግባብ እንደ እግዚአብሔር መንገድ ወይም ጎዳና ተቆጥሮ ተነግሯል። እግዚአብሔርን የሚታዘዝ ሰው በእግዚአብሔር መንገድ ወይም ጎዳና እንደ ሄደ ተቆጥሮ ተነግሮለታል። አ.ት፡ “ዘወትር እንድትታዘዘው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከዚያም ሦስት ተጨማሪ ከተሞችን ለራስህ ትጨምራለህ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “ከዚያም አንድ ሰው በድንገት ሌላውን ሰው ከገደለ እንዲያመልጥበት ተጨማሪ ሦስት ከተሞችን ትመርጣለህ” (ቁጥሮች እና Assumed Knowl- edge and Implicit Information የሚለውን ተመልከት)

ከእነዚህ ከሦስቱ በተጨማሪ
“አስቀድሞ ካዘጋጀኻቸው ከሦስቱ ከተሞች በተጨማሪ” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ንጹሕ ደም እንዳይፈስ ይህንን አድርግ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የቤተሰቡ አባላት ንጹሕ የሆነውን ሰው እንዳይገድሉ ይህንን አድርግ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ንጹሕ ደም እንዳይፈስ
እዚህ ጋ “ደም” የሚወክለው የሰውን ሕይወት ነው። ደም ማፍሰስ ማለት ሰው መግደል ማለት ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ማንም ንጹሕ የሆነውን ሰው አይግደል” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በምድሪቱ መካከል
“በምድሪቱ” ወይም “በግዛቱ”

አምላክህ እግዚአብሔር ርስት አድርጎ በሚሰጥህ
እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ የሚሰጣቸው ምድር ርስት እንደሆነ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የደም በደለኛ እንዳትሆን
የእስራኤል ሕዝብ “ከደም ተበቃዩ” የሚያመልጥበትን ከተማ ባለመሥራታቸው በሚሞተው ሰው ምክንያት በደለኛ መሆናቸው የሟቹ በደል በእነርሱ ላይ እንደሚሆን ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የደም በደል
እዚህ ጋ “ደም” የሚወክለው ሕይወትን ሲሆን “የደም በደለኛ” የሚያመለክተው አንድ ሰው ንጹሕ የሆነን ሰው ስለ መግደሉ የሚኖርበትን በደል ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በአንተ ላይ እንዳይሆን
ይህ ማለት አንድ የቤተሰብ አባል ንጽሕ የሆነን ሰው ቢገድል፣ ከዚያም ይህ እንዲሆን ዝም በማለታቸው የእስራኤል ሕዝብ በሙሉ በደለኛ ይሆናሉ።

Deuteronomy 19:11

ባልንጀራውን
እዚህ ጋ “ባልንጀራ” ማለት በአጠቃላይ ማንኛውም ሰው ማለት ነው።

አድፍጦ ቢጠብቀው
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አ.ት፡ “እርሱን ለመግደል ተደብቆ ይጠብቀዋል” ወይም “ሊገድለው ያቅዳል” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

በእርሱ ላይ ይነሣል
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ያጠቃዋል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

እስኪሞት ድረስ ክፉኛ ቢያቆስለው
“እስኪሞት ድረስ ቢጎዳው” ወይም “ቢገድለው”

ልከው ከዚያ መልሰው ያምጡት
“እንዲያመጡት ሰው ይላኩ፣ እርሱንም ከተከለለበት ከተማ መልሰው ያምጡት”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አሳልፈው ይስጡት
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “አሳልፈው ይስጡት” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ኃላፊነት ባለበት ዘመዱ እጅ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው የአንድን ሰው ሥልጣን ነው። አ.ት፡ “ኃላፊነት ላለበት ዘመዱ ሥልጣን” ወይም “ኃላፊነት ላለበት ዘመዱ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ኃላፊነት ያለበት ዘመድ
ይህ የተገደለው ሰው ዘመድ ነው። ይህ ዘመድ ገዳዩን ለመቅጣት ኃላፊ ነው።

እንዲሞት
“ገዳዩ እንዲሞት” ወይም “ኃላፊነት ያለበት ዘመድ ገዳዩን እንዲገድለው”

ዐይንህ አይራራለት
እዚህ ጋ “ዐይንህ” የሚወክለው ሙሉውን ሰው ነው። አ.ት፡ “ምሕረት አታድርግለት” ወይም “አትዘንለት” (See: Synecdoche)

የደምን በደል ከእስራኤል አስወግድ
እዚህ ጋ “የደም በደል” የሚወክለው ንጹሕ የሆነውን ሰው የመግደልን በደል ነው። አ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ በንጹሕ ሰው ሞት ምክንያት በደለኛ እንዳይሆን ነፍሰ ገዳዩን ግደለው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከእስራኤል
እዚህ ጋ “እስራኤል” የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 19:14

የባልንጀራህን የድንበር ምልክት አታንሣ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “በመሬቱ ድንበር ላይ ያለውን ምልክት በማንሣት ከባልንጀራህ መሬት አትውሰድበት” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ያስቀመጡትን
“የቀደሙት አባቶችህ ያስቀመጡትን”

ከብዙ ዓመታት በፊት
ሙሴ ይህንን የሚለው ሕዝቡ ለረጅም ዓመታት በምድሪቱ በተቀመጡ ጊዜ የቀደሙት አባቶቻቸው በመጀመሪያ ምድሪቱን በወሰዱ ጊዜ ያበጁትን ድንበር እንዳያነሡ ነው።

አምላክህ እግዚአብሔር እንድትወርሰው በሚሰጥህ ምድር፣ በምትወርሰው ርስትህ
እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ መሬት መስጠቱ ምድሪቱን እንደወረሱ ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “አምላክህ እግዚአብሔር እንድትወርሰው በሚሰጥህ ምድር” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 19:15

አንድ ብቸኛ ምስክር
“ አንድ ምስክር” ወይም “አንድ ምስክር ብቻ”

በሰው ላይ እንዳይነሣ
እዚህ ጋ “መነሣት” ማለት በፍርድ ቤት መቆምና አንድን ሰው በመቃወም ለዳኛው መናገር ማለት ነው። አ.ት፡ “አንድ ሰው ስላደረገው ክፉ ነገር ለዳኞች እንዳይናገር” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ኃጢአት በሚሠራበት በየትኛውም ጉዳይ
አንድ ሰው በየትኛውም ጊዜ ክፉ ነገር ሲያደርግ”

በሁለት ምስክሮች አፍ ወይም በሦስት ምስክሮች አፍ
እዚህ ጋ “አፍ” የሚወክለው ምስክሮች የሚናገሩትን ነው። ቢያንስ ሁለት ወይም ሦስት ምስክሮች መኖር እንዳለባቸው ያመለክታል። አ.ት፡ “በሁለት ወይም በሦስት ሰዎች ምስክርነት” ወይም “ቢያንስ ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች ተፈጽሟል ያሉትን መሠረት በማድረግ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና Assumed Knowledge and Implicit Information የሚለውን ተመልከት)

የትኛውም ጉዳይ መረጋገጥ አለበት
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሰውየው በደለኛ መሆኑን ታረጋግጣለህ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ቢሆን
“መቼ” ወይም “ከሆነ”

ሐሰተኛ ምስክር
“አንድን ሰው ለመጉዳት የሚሞክር ምስክር”

በማንም ላይ ክፉ ስለማድረጉ ሊመሰክርበት የሚነሣ
እዚህ ጋ “መነሣት” ማለት ፍርድ ቤት ውስጥ መቆምና አንድን ሰው በመቃወም ለዳኛው መናገር ማለት ነው። አ.ት፡ “ሰውየውን ችግር ላይ ለመጣል ኃጢአት ሠርቷል ብሎ ለዳኛው የሚናገር” ወይም “ዳኛው እንዲቀጣው አንድን ሰው ኃጢአት ሠርቷል ብሎ ለዳኛው የሚናገር” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 19:17

ክርክር በመካከላቸው ያለ
“እርስ በእርስ ያልተስማሙ”

በእግዚአብሔር ፊት ይቁሙ፣ በካህናቱና በዳኞቹ ፊት
ይህ ማለት ሁለቱ ሰዎች የእግዚአብሔር ሀልዎት ወደሚያድርበት ቅዱስ ስፍራ መሄድ አለባቸው ማለት ነው። ስለ እግዚአብሔር ሕጋዊ ውሳኔዎችን የመስጠት ሥልጣን ያላቸው ካህናትና ዳኞች በተቀደሰው ስፍራ አሉ። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

በእግዚአብሔር ፊት ይቁሙ፣ በካህናቱና በዳኞቹ ፊት
“ፊት ይቁሙ” የሚለው ሐረግ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህ ማለት ሥልጣን ወዳለው አካል መሄድና እርሱ ስለ ጉዳዩ ሕጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥ ማድረግ ማለት ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ዳኞቹ በጥንቃቄ ይመርምሩ
“ዳኞቹ የሆነውን ነገር ለማወቅ ጠንክረው መሥራት አለባቸው”

ከዚያም በወንድሙ ላይ ለማድረግ የተመኘውን በእርሱ ላይ ታደርግበታለህ
“ከዚያም ሐሰተኛውን ምስክር ሌላውን ሰው እንድትቀጣ በፈለገበት መንገድ ትቀጣዋለህ”

ክፉን ከመካከልህ ታስወግዳለህ
ስማዊ ቅጽል የሆነው “ክፉን” እንደ ቅጽል ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ክፉውን ልምምድ ከመካከልህ ታርቃለህ” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 19:20

ከዚያም የቀሩት
“ሐሰተኛውን ምስክር በምትቀጣበት ጊዜ የቀረው ሕዝብ”

ሰምተው ይፈራሉ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “ስለ ቅጣቱ ይሰሙና እነርሱም እንዳይቀጡ ይፈራሉ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንዲህ ያለውን ክፉ ከእንግዲህ አይፈጽሙም
“እንደዚህ ያለውን ክፉ ነገር ደግመው አያደርጉም”

ዐይኖችህ አይራሩለት
እዚህ ጋ “ዐይኖች” የሚያመለክቱት ሙሉውን ሰው ነው። አ.ት፡ “አትራራለት” ወይም “ምሕረት አታድርግለት” (See: Synecdoche)

ሕይወት ስለ ሕይወት ይከፈል -- እግር ስለ እግር
እዚህ ጋ ትርጉሙ ግልጽ ስለሆነ ሐረጎቹ አጥረዋል። ይኸውም አንድ ሰው ሌላውን ሰው በጎዳበት በዚያው መልኩ ሕዝቡ ይቀጣዋል ማለት ነው። (See: Ellipsis)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 20

1 ጠላቶቻችሁን ለመውጋት ወደ ጦርነት ስትሄዱ ሠርገሎችንና ፈረሶችን ከእናንተ የሚበልጥ ሰራዊትንም በምታዩበት ጊዜ፥ አትፍሩአቸው፥ ከግብፅ ያወጣችሁ እግዚአብሔር አምላካችሁ ከእናንተ ጋር ነውና። **2** ወደ ውጊያው ቦታ ስትቃረቡ፥ **3** ካህኑ ወደ ፊት ወጣ ብሎ ለሠራዊቱ ይናገር፥ እንዲህም ይበል እስራኤል ሆይ ስማ በዛሬው ቀን ጠላቶቻችሁን ለመግጠም ወደ ጦርነት ልትገቡ ነው። ልባችሁ አይባባ፤ አትፍሩ፤ አትደግጡ፤ በጠላቶቻችሁ ፊት አትሸበሩ። **4** ድልን ያቀዳጃችሁ ዘንድ ስለ እናንተ ጠላቶቻችሁን ሊወጋ አብሮአችሁ የሚወጣው አምላካችሁ እግዚአብሔር ነውና። **5** አለቆቹም ለሠራዊት እንዲህ ይበሉ፥ አዲስ ቤት ሠርቶ ያላስመረቀ አለን? ወደ ቤቱ ተመልሶ ይሂድ፥ ያለበለዚያ በጦርነቱ ላይ ሲሞት፥ ቤቱን የሚያስመርቀው ሌላ ሰው ይሆናል። **6** ወይን ተክሎ ገና ያልበላለት አለን? ወደ ቤቱ ይመለስ፣ ያለበለዚያ በጦርነቱ ሲሞት፥ ሌላ ሰው ይበለዋል። **7** ሚስት አጭቶ ያላገባት አለን? ወደ ቤቱ ይመለስ፥ ያለበለዚይ በጦርነቱ ሲሞት ሌላ ሰው ያገባታል። **8** በዚያም አለቆቹ፦ የሚፈራ ወይም ልቡ የሚባባ ሰው አለን? የወንድሞችም ልብ እንዳይባባ፥ ወደ ቤቱ ይመለስ፤ በማለት ጨምረው ይናገሩ። **9** አለቆቹ ለሰራዊቱ ተናግረው ሲያበቁ አዛዦችን በሰራዊቱ ላይ ይሹሙ። **10** አንድን ከተማ ለመውጋት በምትዘምቱበት ጊዜ አስቀድማችሁ ለሕዝቧ የሰላም ጥሪ አስተላልፉ፥ **11** ከተቀበሉአችሁና ደጃቸውን ከከፈቱላችሁ በከተማዋ ውስጥ ሕዝብ ሁሉ የጉልበት ሥራ ይሥሩ፥ ያገልግላችሁም። **12** ዕርቅ ሰላምን ባለመቀበል ውጊያ ከመረጡ፥ ከተማዪቱን ክበቡአት። **13** እግዚአብሔር አምላካችሁ አሳልፎ በእጃችሁ በሰጣችሁ ጊዜ በውስጧ ያሉትን ወዶች በሙሉ በሰይፍ ግደሉአቸው። **14** ነገር ግን ሴቶቹን ሕፃናትን እንስሳትንና በከተምዩቱ ውስጥ የሚገኘውን ማናቸውንም ነገር በምርኮ ለራሳችሁ አድርጉ፥ እግዚአብሔር አምላካችሁ ከጠላቶቻችሁ የሚሰጣችሁን ምርኮ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ። **15** እንግዲህ የአካባቢያችሁ አሕዛብ ከተሞች ባልሆኑትና ከእናንተ እጅግ ርቀው በሚገኙት ከተሞች ሁሉ ላይ የምታደርጉት ይኸው ነው። **16** እግዚአብሔር አምላካችሁ ርስት አድርጎ በሚሰጣችሁ በአሕዛብ ከተሞች ውስጥ እስትንፋስ ያለውን ነገር አታስተርፉ። **17** በዚህ ፈንታ፥ ኬጢያዊውን፥ አሞራዊውን፥ ከነዓናዊውን፥ ፌርዛዊውን፥ ኤዊያዊውን፥ ኢያቡሳዊውን እግዚአብሔር አምላካችሁ ባዘዛችሁ መሠረት ፈጽማችሁ ደምስሱአቸው። **18** አለበለዚያ አማልክታቸውን በሚያመልኩበት ጊዜ የሚፈጽሟቸውን አስጸያፊ ተግባራት ሁሉ ታደርግ ዘንድ ያስተምሩአችኋል፤ በእግዚአብሔር በአምላካችሁ ላይ ኃጢአት ትሠራላችሁ። **19** አንድን ከተማ ተዋገታችሁ ለመያዝ የረጅም ጊዜ ከበባ በምታድርጉበት ጊዜ፥ ዛፎቹን በመጥረቢያ ጨፍጭፋችሁ ማጥፋት የለባችሁም። የዛፎችን ፍሬ መብላት ስለምትችሉ አትቁረጡአቸው። ከባችሁ የምታጠፉአችሁ የሜዳ ዛፎች ሰዎች ናቸውን? **20** የሚበላ ፍሬ እንደማያፈራ የምታውቁትን ዛፍ ግን ልትቆርጡና ጦርነት የምታካሄዱባትን ከተማ በድል እስክትቆጣጠሩአት ድረስ ለከበባው ምሽግ መሥሪያ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ።

Deuteronomy 20:1

ለጦርነት በጠላቶችህ ላይ በምትወጣበት ጊዜ
“ከጠላቶችህ ጋር ለመዋጋት ወደ ጦርነት በምትወጣበት ጊዜ”

ፈረሶችን፣ ሠረገላዎችን ስታይ
ሰዎች ብዙ ፈረሶችና ሠረገላዎች ያሉትን ሰራዊት በጣም ጠንካራ እንደሆነ ይቆጥሩ ነበር። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ከግብፅ ምድር ያወጣህ
እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብፅ ወደ ከነዓን አምጥቷቸዋል። ከግብፅ ወደ ከነዓን የሚደረገውን ጉዞ ለማመልከት “ወደ ላይ” የሚለውን ቃል የተለመደ ነበር። አ.ት፡ “ከግብፅ ምድር መርቶ ያወጣችሁ እግዚአብሔር”

Deuteronomy 20:2

ለሕዝቡ ተናገር
“ለእስራኤል ወታደሮች ተናገር”

ልባችሁ አይሸበር። አትፍሩ ወይም አትደንግጡ። አትፍሯቸው
እነዚህ አራቱም አገላለጾች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ እንዳይፈሩ ጠንከር ያለ አጽንዖት ይሰጣሉ። የአንተ ቋንቋ ይህንን አሳብ የሚገልጹ አራት መንገዶች ከሌሉት ከአራት በሚያንሱ ቃላት መጠቀም ትችላለህ። (See: Parallelism)

ልባችሁ አይሸበር
እዚህ ጋ “ልባችሁ” የሕዝቡን የሕዝቡን ድፍረት ይወክላል። የልብ መሸበር የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን “አትፍሩ” ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ከጠላቶቻችሁ ጋር ለመዋጋት ከእናንተ ጋር የሚሄደው አምላካችሁ እግዚአብሔር ነው
እግዚአብሔር የእስራኤልን ጠላቶች ድል ማድረጉ ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ሆኖ እንደሚዋጋ ጦረኛ ተደርጎ ተነግሮለታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሊያድናችሁ
“ድል ሊሰጣችሁ”

Deuteronomy 20:5

አለቆቹ ይናገሩ
ከአለቆቹ ሥራ አንዱ ከሰራዊቱ ማን መሰናበት እንዳለበት መወሰን ነው። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

-- ማን አለ? ወደ ቤት ተመልሶ ይሂድ
“አዲስ ቤት ሠርቶ ያላስመረቀ ወታደር በዚህ ካለ ወደ ቤቱ ተመልሶ ይሂድ”

በጦርነት ላይ እንዳይሞትና ሌላ ሰው እንዳያስመርቀው
አለቃው አንድን ወታደር ሊያጋጥመው የሚችለውን ሁኔታ ይዘረዝራል። አ.ት፡ “እርሱ በጦርነት ላይ ቢሞት በእርሱ ፈንታ ሌላ ሰው ቤቱን እንዳያስመርቅ” (See: Hypothetical Situations)

Deuteronomy 20:6

- የተከለ አለ? ወደ ቤቱ ይሂድ
“እዚህ አዲስ ወይን ተክሎ ፍሬውን ያልሰበሰበ ወታደር ካለ ወደ ቤቱ ተመልሶ ይሂድ”

በጦርነት ላይ እንዳይሞትና ሌላ ሰው በፍሬው እንዳይደሰት
አለቃው አንድን ወታደር ሊያጋጥመው የሚችለውን ሁኔታ ይዘረዝራል። አ.ት፡ “እርሱ በጦርነት ላይ ቢሞት በእርሱ ፈንታ ሌላ ሰው ፍሬውን እንዳይሰበስብ” (See: Hypothetical Situations)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሚስት ለማግባት ያጨ አለ? -- ወደ ቤቱ ይሂድ
“ሚስት ለማግባት ቃል ኪዳን ያደረገ፣ ነገር ግን ያላገባት የትኛውም ወታደር እዚህ ቢኖር ወደ ቤቱ ተመልሶ ይሂድ”

በጦርነት ላይ እንዳይሞትና ሌላ ሰው እንዳያገባት
አለቃው አንድን ወታደር ሊያጋጥመው የሚችለውን ሁኔታ ይዘረዝራል። አ.ት፡ “እርሱ በጦርነት ላይ ቢሞት በእርሱ ፈንታ ሌላ ሰው እንዳያገባት” (See: Hypothetical Situations)

Deuteronomy 20:8

የሚፈራና ልቡ የሚሸበርበት ሰው ማነው? ወደ ቤቱ ተመልሶ ይሂድ
“እዚህ ያለ የትኛውም ወታደር ቢፈራና ልቡ ቢሸበር ወደ ቤቱ ተመልሶ ይሂድ”

የሚፈራ ወይም ልቡ የሚሸበርበት
ሁለቱም ቃላት መሠረታዊ ትርጉማቸው አንድ ነው። አ.ት፡ “በጦርነት ለመዋጋት የሚፈራ” (See: Doublet)

እንደ ራሱ ልብ የወንድሙም ልብ እንዳይቀልጥ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “እርሱ እንደፈራ ሌላውም እስራኤላዊ እንዳይፈራ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የወንድሙ ልብ -- እንደ ራሱ ልብ
እዚህ ጋ “ልብ” የሚወክለው የአንድን ሰው ድፍረት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእነርሱ ላይ አዛዦችን ይሹሙ
“የእስራኤልን ሕዝብ እንዲመሩ አለቆቹ አዛዦችን መሾም አለባቸው”

Deuteronomy 20:10

አንድን ከተማ ለመውጋት በምትዘምትበት ጊዜ
እዚህ ጋ “ከተማ” ሕዝቡን ይወክላል። አ.ት፡ “የአንድን ከተማ ሕዝብ ለመውጋት በምትሄድበት ጊዜ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ለእነዚያ ሰዎች የሰላም ጥሪ አቅርብላቸው
“በከተማው ለሚኖሩ ሰዎች እጅ እንዲሰጡ ዕድል ስጣቸው”

በሮቻቸውን ከከፈቱልህ
እዚህ ጋ “በሮች” የሚያመለክቱት የከተማይቱን በሮች ነው። “በሮቻቸውን ከከፈቱልህ” የሚለው ሐረግ የሚወክለው የሚማረኩትንና እስራኤላውያን ወደ ከተማቸው እንዲገቡ የሚፈቅዱትን ሰዎች ነው። አ.ት፡ “በሰላም ወደ ከተማቸው እንድትገባ ከፈቀዱልህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 20:12

ነገር ግን ያቀረብክለትን የሰላም ጥሪ ባይቀበል
እዚህ ጋ “እርሱ” የሚያመለክተው ሕዝቡን የሚወክለውን ከተማውን ነው። አ.ት፡ “ነገር ግን የከተማይቱ ሰዎች እጃቸውን ባይሰጡ” ወይም “ነገር ግን የከተማይቱ ሰዎች ያቀረብክላቸውን የሰላም ጥሪህን ባይቀበሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 20:14

ሕፃናቱን
“ልጆቹን”

ብዝበዛውን ሁሉ
“የሚጠቅሙትን ነገሮች በሙሉ”

ምርኮ
እነዚህ በጦርነት ድል ያደረጉ ሰዎች ከወጓቸው ሰዎች ላይ የሚወስዷቸው ጠቃሚ ነገሮች ናቸው።

ከተሞቹ ሁሉ
እዚህ ጋ “ከተሞች” የሚወክሉት ሕዝቡን ነው። አ.ት፡ “በከተሞች የሚኖሩት ሰዎች በሙሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 20:16

አምላክህ እግዚአብሔር ርስት አድርጎ በሚሰጥህ በእነዚህ ሰዎች ከተሞች ውስጥ
እግዚአብሔር ለሕዝቡ በከነዓን የሚሰጣቸው ከተሞች እነርሱ የሕዝቡ ርስት እንደሆኑ ተቆጥረው ተነግሮላቸዋል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እስትንፋስ ያለውን ምንም ነገር አታስቀር
“ሕይወት ያለበትን ሁሉ በሕይወት አታስቀር”። ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሕይወት ያለውን ሁሉ ግደል” (ምጸት የሚለውን ተመልከት)

ፈጽመህ አጥፋቸው
x

Deuteronomy 20:19

ጦርነት ዐውጅ
“በጦርነት ተዋጋ”

በመጥረቢያ ቁረጣቸው
“ዛፎቹን በመጥረቢያ ቁረጣቸው”

ልትከበው በሜዳ ላይ ያለ ዛፍ ሰው ነውን?
ይህ ሰዎቹ አስቀድመው የሚያውቁትን ለማስታወስ የቀረበ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ ነው። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “የፍሬ ዛፎች ሰዎች ስላልሆኑ ጠላቶችህ አይደሉም” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ለምግብነት የማይውሉ ዛፎች መሆናቸውን ስታውቅ
“የሚበላ ፍሬ የማይሰጡ ዛፎች መሆናቸውን ስታውቅ”

ከበባ ሥራባት
እነዚህ አንድን ከተማ ለመክበብ የሚያስፈልጉ መሰላሎችና ማማዎችን የመሳሰሉ መሣሪያዎችና መዋቅሮች ናቸው።

እስኪወድቅ ድረስ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “የከተማይቱ ሰዎች በጦርነቱ እስኪሸነፉ ድረስ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ይወድቃል
እዚህ ጋ “እርሱ” የሚወክለው የከተማይቱን ሕዝብ የሚወክለውን ከተማ ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 21

1 እግዚአብሔር አምላካችሁ እንድትወርሱአት በሚሰጣችሁ ምድር ላይ አንድ ሰው ተገድሎ ሜዳ ላይ ቢገኝና ገዳዩም ማን እንደ ሆነ ባይታወቁ፥ 2 ሽማግሌዎቻችሁና ዳኞቻችሁ ወጥተው የተገደለ ሰው ሬሳው ወድቆ ከተገኘበት አንሥቶ በአቅራቢያው እስካሉት ከተሞች ድረስ ያለውን ርቀት ይለኩ። 3 ከዚያም የተገደለ ሰው ሬሳው ወድቆ ከተገኘበት ስፍራ በጣም ቅርብ የሆነችው ከተማ ሽማግሌዎች ለሥራ ያልደረሰችና ቀንበር ያልተጫነባትን ጊደር ይዘው፥ 4 ከዚያ በፊት ታርሶ ወይም ተዘርቶበት ወደማይታወቅ ወራጅ ውሃ ወዳለበት ሸለቆ ያምጡት። በዚያ ሸለቆም የጊደሪቱን አንገት ይስበሩ፥ 5 እንዲያገለግሉና በእግዚአብሔር ስም እንዲባርኩ፥ በማንኛውም የክርክርና የጥቃት ጉዳዮች ሁሉ ላይ ውሳኔ እንዲሰጡ፥ እግዚአብሔር አምላካችሁ መርጦአቸዋልና የሌዊ ልጆች ካህናቱ ወደ ፊት ይቅረቡ። 6 ከዚያም ሬሳው በተገኘበት አቅራቢያ ከተማ የሚኖሩ ሽማግሌዎች ሁሉ፥ በሸለቆው ውስጥ፥ አንገቷ በተሰበረው ጊደር ላይ እጃቸውን ይታጠቡ፤ 7 እንዲህም ብለው ይናገሩ፥ እጆቻችን ደም አላፈሰሱም፤ ድርጊቱ ሲፈጸምም ዐይኖቻችን አላዩም። 8 እግዚአብሔር ሆይ፥ ስለ ተቤዠኸው ሕዝብህ ስለ እስራኤል ብለህ ይህን ስርየት ተቀበል፥ ሕዝብህንም በፈሰሰው ንጹሕ ደም በደለኛ አታድርግ። ስለ ፈሰሰውም ደም ስርየት ይደረግላቸዋል። 9 በዚህም መንገድ በእግዚአብሔር ፊት ቀና የሆነውን ስታደርጉ የንጹሑን ደም የማፍሰስ በደልን ከመካከላችሁ ታስወግዳላችሁ። 10 ከጠላቶቻችሁ ጋር ጦርነት ልትገጥሙ ወጥታችሁ አምላካችሁ እግዚአብሔር እነርሱን በእጃችሁ አሳልፎ ሰጥቶአችሁ በማረካችሁ ጊዜ፥ 11 ከምርኮኞቹ መካከል ቆንጆ ሴት አይታችሁ ብትማርኩ፥ ሚስታችሁ ልታደርጉአት ትችላላችሁ፤ 12 ወደ ቤታችሁ ውሰዱአት፥ ጠጉሯን ትላጭ፥ ጥፍሯንም ትቁረጥ። 13 ስትማርኩአት የለበሰችውንም ልብስ ታውልቅ፥ እቤታችሁ ተቀምጣ ለአባትና ለናቷ ወር ሙሉ ካለቀሰችላቸው በኋላ፥ ከእርሷ ጋር ለመተኛና ባል ልትሆለት፥ እርሷም ሚስት ልትሆናችሁ ትችላለች። 14 ነገር ግን በእርሷ ደስተኛ ባትሆን፥ ወደምትፈልገው እንድትሄድ ነጻነት ስጡአት፥ ውርደት ላይ ስለ ጠላችኋት በገንዘብ ልትሸጡአት ወይም እንደ ባሪያ ልትቆጥሩአት አይገባችሁም። 15 አንድ ሰው ሁለት ሚስቶች ቢኖሩት አንደኛዋን የሚወዳት፥ ሌላዋን ግን የሚጠላት ቢሆን፥ ሁለቱም ወንዶች ልጆችን ወልደውለት፥ በኩር ልጁ ግን የተወለደው ከማይወዳት ሚስቱ ቢሆን፥ 16 ንብረቱን ለልጆቹ በሚያወርስበት ጊዜ፥ የብኩርናን መብት ከማይወዳት ሚስቱ ከወለደው በኩር ልጅ ገፎ ከሚወዳት ሚስቱ ለተወለደው ልጁ በአድልዎ መስጠት አይገባውም፤ 17 በዚህ ፈንታ፥ ከተጠላችው ሚስቱ ለተወለደው ልጅ ካለው ሁብት ሁሉ ሁለት እጥፍ ድርሻውን በመስጠት ብኩርናውን ያስታውቅ ያ ልጅ የአባቱ ኃይል መጀመሪያ ነውና የብኩርና መብት የራሱ ነው። 18 አንድ ሰው የአባቱን ወይም የእናቱን ትእዛዝ የማይሰማ፥ ቢቀጡትም የማይታረም እልከኛና ዐመፀኛ ልጅ ቢኖረው፥ 19 አባትና እናቱ ይዘው በሚኖሩበት ከተማ በር ወዳሉት አለቆች ያምጡት፥ 20 ይህ ልጃችን እልከኛና ዐመፀኛ ነው፥ አይታዘዘንም አባካኝና ሰካራም ነው ብለው ለአለቆች ይንገሯቸው። 21 ከዚያም በኋላ የከተማዪቱ ሰዎች ሁሉ እስኪሞት ድረስ በድንጋይ ይወገሩት፥ ክፉውንም ከመካከላችሁ ታስወግዳላችሁ፥ እስራኤልም ሁሉ ይህን ሰምቶ ይፈራል። 22 አንድ ሰው ለሞት የሚያበቃ በደል ፈጽሞ ቢገደልና ሬሳው በእንጨት ላይ ቢሰቀል፥ 23 ሬሳውን በእንጨት ላይ እንደ ተሰቀለ አታሳድሩት ምክንያቱም በእንጨት ላይ የተሰቀለ በእግዚአብሔር ዘንድ የተረገመ ነውና፥ አምላካችሁ እግዚአብሔር ርስት አድርጎ የሚሰጣችሁን ምድር እንዳታረክሱ በዚያኑ ዕለት ቅበሩት።

Deuteronomy 21:1

አንድ ሰው ተገድሎ ቢገኝ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አንድ ሰው ማንነቱ ባልታወቀ ሰው የተገደለን ሰው ቢያገኝ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ሜዳ ላይ ወድቆ
የሞተው ሰው ሜዳ ላይ ወድቋል።

ማን እንደ ገደለው ባይታወቅ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ማን እንደ ገደለው ማንም አያውቅም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ወደ ከተሞቹ ይለኩ
“ለከተሞቹ ያለውን ርቅት ይለኩ”

የተገደለውን እርሱን
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ማንነቱ ያልታወቀ ሰው የገደለውን እርሱን” ወይም “ሬሳውን” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 21:3

ቀንበር ያልተሸከመ
x

Deuteronomy 21:5

ወደ ፊት ይቅረቡ
“ወደ ሸለቆው ይምጡ”

አምላክህ እግዚአብሔር እርሱን እንዲያገለግሉት መርጧቸዋልና
“ካህናቱ እርሱን እንዲያገለግሉት አምላክህ እግዚአብሔር ስለመረጣቸው”

አምላካችሁ እግዚአብሔር
ሙሴ ለአንድ ሰው እንደሚናገር አድርጎ ለእስራኤል ሕዝብ ስለሚናገር “የአንተ” የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)

ባርኮት እንዲሰጡ
“የእስራኤልን ሕዝብ እንዲባርኩ”

በእግዚአብሔር ስም
እዚህ ጋ “በ -- ስም” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ራሱንና የእርሱን ሥልጣን ነው። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ራሱ የሚለውንና የሚያደርገውን የሚልና የሚያደርግ እርሱ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር እና ማንኛውንም ዓይነት ክርክርና ጥቃት በቃላቸው እንዲወስኑ
“አለመግባባቶችንና የጸብ ምክንያቶችን ሁሉ የሚፈቱት እግዚአብሔር እና እነርሱ ይሆናሉ”

Deuteronomy 21:6

አንገቷ የተሰበረን ጊደር
x

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Deuteronomy 21:8

የዋጀኸውን
እግዚአብሔር በግብፅ ባሪያ የነበረውን የእስራኤልን ሕዝብ ማዳኑ ሕዝቡን ከባርነት ለመቤዠት ገንዘብ እንደከፈለላቸው በሚመስል መልኩ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በንጹሕ ደም ምክንያት በሕዝብህ በእስራኤል መካከል በደልን አታኑር
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ ንጹሕን ሰው እንደ ገደሉ በደለኞች አድርገህ አትቁጠራቸው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ከዚያም ስለ ፈሰሰው ደም ይቅር ይባላሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ከዚያም ስለ ንጹሑ ሰው ሞት እግዚአብሔር ሕዝቡን እስራኤልን ይቅር ይላቸዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ንጹሕን ደም ከመካከልህ ታስወግዳለህ
“ንጹሕን ሰው ስለ መግደልህ ከእንግዲህ በደለኛ አትሆንም”

በእግዚአብሔር ዐይን ትክክል የሆነውን
x

Deuteronomy 21:10

ውጣ
“እናንተ ወታደሮች የሆንችሁ ውጡ”

ብትመኛት
“ከእርሷ ጋር ለመተኛት ብትፈልግ” ለሚለው የትህትናን ሐረግ ተጠቀም።

ሚስትህ እንድትሆን ልትወስዳት ብትፈልግ
“ለታገባት ብትፈልግ”

ጸጉሯን ትላጨው
“ጸጉሯን ከራሷ ላይ ትመለጠው”

ጥፍሮቿን ትቆረጥ
“የጣቶቿን ጥፍር ትቁረጥ”

Deuteronomy 21:13

የለበሰችውን ልብስ ታውልቀው
ይህንን የምታደርገው በዘዳግም 21:12 እንደተጠቀሰው ሰውየው ወደ ቤቱ ካመጣትና ጸጉሯን ተቆርጣ፣ የእጅና የእግር ጣት ጥፍሮቿን ከተቆረጠች በኋላ ነው። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “የሕዝቧን ልብስ ታወልቅና የእስራኤላውያንን ልብስ ትለብሳለች” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ተማርካ በተወሰደች ጊዜ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እርሷን በማረክህ ጊዜ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

አንድ ሙሉ ወር
“ወሩን በሙሉ” ወይም “አንድ ወር ሙሉ”

ነገር ግን ባትደሰትባት
ሰውየው ከሴቲቱ ጋር ስለ መተኛቱ ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። አአ.ት፡ “ነገር ግን አብረሃት ከተኛህ በኋላ ሚስትህ እንዳትሆን ከወሰንክ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ወደፈለገችበት ትሂድ
“መሄድ ወደምትፈልግበት ትሂድ”

አዋርደሃታልና
“ከእርሷ ጋር ከተኛህ በኋላ ስለ ሰደድካት አሳፍረሃታልና”

Deuteronomy 21:15

አንዷ የተወደደችና ሌላይቱ የተጠላች
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፣ 1) “ሰውየው ከሚስቶቹ አንደኛዋን ይወዳል፣ ሌላይቱን ሚስቱን ይተላታል” ወይም 2) “ሰውየው ሌላይቱን ሚስቱን ከሚወድበት በበለጠ አንደኛውን ሚስቱን ይወዳታል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ሁለቱም ልጆችን ቢወልዱለት
“ሁለቱም ሚስቶቹ ልጆችን ወልደውለታል”

በኩሩ ከተጠላችው ከሆነ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በኩሩ ሰውየው ከሚጠላት ሚስቱ የተወለደ ከሆነ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ከዚያም ሰውየው በ-- ቀን
“ሰውየው በ-- ጊዜ”

ሰውየው ያለውን ልጆቹ እንዲወርሱ ያደርጋል
“ሰውየው ንብረቱን ለልጆቹ ርስት አድርጎ ይሰጣቸዋል”

ከተወደደች ሚስቱ የተወለደውን ልጅ ከተጠላችው ሚስቱ በተወለደው ልጅ ፊት በኩር አያድርገው
“ከተጠላችው ሚስቱ በተወለደው ልጅ ምትክ ከተወዳጅ ሚስቱ የተወለደውን ልጅ በኩር አያድርገው”

ዕጥፍ ድርሻ
“ሁለት ዕጥፍ”

ያ ልጅ የጉብዝናው ጅምሬ ነው
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ያ ልጅ ሰውየው የወንዶች ልጆች አባት መሆኑን የሚያሳይ ነው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 21:18

የአባቱን ቃል ወይም የእናቱን ቃል የማይታዘዝ
እዚህ ጋ “ድምፅ” አንድ ሰው የሚናገረውን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “አባቱ ወይም እናቱ የሚሉትን የማይታዘዝ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ያርሙት
“ስለ መጥፎ ተግባሩ ይቅጡት” ወይም “ያሰልጥኑትና ያስተምሩት”

ይዘው ያምጡት
“እንዲመጣ ያስገድዱት”

Deuteronomy 21:20

ይህ የእኛ ልጅ
“ልጃችን”

ድምፃችንን አይታዘዝም
እዚህ ጋ “ድምፅ” አንድ ሰው የሚናገረውን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ወይም የሙሉው ሰው ተምሳሌት ነው። አ.ት፡ “እንዲያደርግ የምንነግረውን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አያደርግም” ወይም “አይታዘዘንም” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና Synecdoche የሚለውን ተመልከት)

ሆዳም
ብዙ የሚበላና የሚጠጣ ሰው

ሰካራም
አስካሪ መጠጥ አብዝቶ የሚጠጣና ብዙ ጊዜ የሚሰክር ሰው

እስኪሞት ድረስ በድንጋይ ውገሩት
“እስኪሞት ድረስ ድንጋይ ወርውሩበት”

ክፉን ከመካከልህ ታርቃለህ
ቅጽሉ “ክፉ” ስማዊ ሐረግ ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ይህንን ክፉ ነገር የሚያደርገውን ሰው ከእስራኤላውያን መካከል ታርቃለህ” ወይም “ይህንን ክፉ ሰው ግደለው” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

እስራኤል ሁሉ
“እስራኤል” የሚለው ቃል የእስራኤልን ሕዝብ የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ በሙሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ስለ እርሱ ሰምተው ይፈራሉ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አ.ት፡ “በልጁ ላይ ስለሆነው ነገር ይሰማሉ፣ እነርሱንም ሕዝቡ እንዳይቀጣቸው ይፈራሉ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

Deuteronomy 21:22

አንድ ሰው ሞት የሚገባውን ኃጢአት ሠርቶ ከሆነ
“አንድ ሰው በሞት ልትቀጣው እስከሚያስፈልግህ ድረስ እጅግ የከፋ ነገር ካደረገ”

ይገደል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አስወግደው” ወይም “ግደለው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በዛፍ ላይ ስቀለው
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች 1) “ከሞተ በኋላ ዛፍ ላይ ስቀለው” ወይም 2) “ግደለውና በቋሚ እንጨት ላይ ስቀለው”

በዚያው ቀን ቅበረው
“በምታስወግደው ጊዜ በዚያው ቀን ቅበረው”

የተሰቀለ ሁሉ በእግዚአብሔር የተረገመ ነው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች 1) “ሰዎች የሚሰቅሉትን ሁሉ እግዚአብሔር ይረግማቸዋል” እና 2) “ሰዎች እግዚአብሔር የረገማቸውን በዛፍ ላይ ይስቀሏቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ምድሪቱን አታርክስ
እግዚአብሔር የረገመውን በዛፍ ላይ ሰቅለህ በመተው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 22

1 የእስራኤላዊ ወንድማችሁ በሬ ወይም በግ ጠፍቶ ሲባዝን ብታዩ ወደ እርሱ መልሳችሁ አምጡለት እንጂ ዝም ብላችሁ አትለፉት፥ 2 ወንድማችሁ በአቅራቢያ
ባይኖር፥ ወይም የማን መሆኑን የማታውቁ ከሆነ ባለቤቱ ፈልጎ እስኪ መጣ ድረስ ወደ ቤታችሁና ወስዳችሁ ከእናንተ ዘንድ አቆዩት፤ ከዚያም መልሳችሁ ስጡት።
3 የእስራኤላዊ ወንድማችሁን አህያ ወይም ልብስ ወይም የጠፋበትን ማናቸውንም ነገር ስታገኙ እንደዚህ አድርጉ፥ በቸልታ አትለፉት። 4 የወንድማሁ አህያ ወይም
በሬ መንገድ ላይ ወድቆ ብታዩት በእግሩ እንዲቆም ርዳው እንጂ አልፋችሁ አትሂዱ። 5 ሴት የወንድ ልብስ አትልበስ፤ ወንድም የሴት ልብስ አይልበስ፤ እንዲህ
የሚያደርገውን ሁሉ እግዚአብሔር አምላካችሁ ይጸየፈዋልና። 6 በመንገድ ስታልፉ አንዲት ወፍ ጫጩቶቿን ወይም ዕንቁላሎቿን የታቀፈችበትን ጎጆ በዛፍ ወይም
በመሬት ላይ ብታገኙም እናቲቱን ከነጫጩቶቿ አትውሰዱ፤ 7 ጫጩቶቿን መውሰድ ትችላላችሁ እናቲቱን ግን መልካም እንዲህንላችሁና ዕድሜአችሁም
እንዲርዝም ልቀቁት፤ 8 አዲስ ቤት በምትሠሩበት ጊዜ፥ ከጣራው ላይ ሰው ወድቆ ቤታችሁ ላይ የደም በደል እንዳታመጡ፥ በጣራው ዙሪያ መከታ አብጁለት።
9 በወይን ተክል ቦታችሁ ውስጥ ሁለት ዓይነት ዘር አትዝሩ ይህን ካደረጋችሁም የዘራችሁት ሰብል ብቻ ሳይሆን የወይን ፍሬአችሁ ይጠፋል። 10 በሬና አህያ
በአንድ ላይ ጠምዳችሁ አትረሱ። 11 ሱፍና ሐር አንድ ላይ ተፈትሎ የተሠራ ልብስ አትልበሱ። 12 በምትለብሱት ልብስ ላይ በአራቱ ማእዘኖች ዘርፍ አድርጉ።
13 አንድ ወንድ ሚስት አግብቶ አብሮአት ከተኛ በኋላ ቢጠላት፥ 14 ስሟንም በማጥፋት፥ ይህችን ሴት አገባኋት፥ዳሩ ግን በደረስሁባት ጊዜ ድንግልናዋን
አላገኘሁም ቢል፥ 15 የልጂቱ አባትና እናት ድንግልናዋን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ይዘው በከተማዪቱ በር ወዳሉት አለቆች ይምጡ። 16 የልጂቱም አባት ለአለቆቹ
እንዲህ ይበል፥ ልጄን ለዚህ ሰው ዳርሁለት፥ እርሱ ግን ጠላት፤ 17 ስሟንም በማጥፋት ልጅህን ከነድንግልናዋ አላገኘኋትም ብሎኛል፤ ነገር ግን የልጄ ድንግልና
ማረጋገጫ ይኸውላችሁ። ከዚያም ወላጆቿ የደሙን ሸማ በከተማዪቱ አለቆች ፊት ይዘርጉት። 18 ከዚያም በኋላ አለቆቹ ሰውየውን ይዘው ይቅጡት፥ 19 ይህ
ሰው የአንዲት እስራኤላዊት ድንግል ስም አጥፍቶአልና አንድ መቶ ሰቅል ብር ያስከፍሉት፥ ገንዘቡንም ለልጂቱ አባት ይስጡት፥ ሴቲቱም ሚስቱ ሆና ትኖራለች፤
በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ሊፈታት አይችልም። 20 ሆኖም ክሱ እውነት ሆኖ ሴቲቱ ድንግል ለመሆኗ ምንም ማረጋገጫ ማቅረብ ካልተቻለ፥ 21 በአባቷ ቤት ሳለች
በማመንዘር በእስራኤል ውስጥ አሳፋሪ ተግባር ፈጽማለችና ወደ አባቷ ቤት ደጃፍ ያምጣት፥ እዚያም የከተማዋ ሰዎች እስክትሞት ድረስ በድንጋይ ይውገሯት።
22 አንድ ሰው ከሌላ ሰው ሚስት ጋር ተኝቶ ቢገኝ፥ አብሮአት የተኛው ሰውና ሴቲቱ ሁለቱም ይገደሉ። ክፉውን ከእስራኤል ማስወገድ አለባችሁ። 23 አንድ ሰው
የታጨች ድንግል በከተማ ውስጥ አግኝቶ ከእርሷ ጋር ቢተኛ፥ ልጃገረዲቱ በከተማ ውስጥ እያለች አስጥሉኝ ብላ ስላልጮኸች፥ ሰውየውም የሌላን ሰው ሚስት
አስግድዶ ስለ ደፈረ፥ 24 ሁለቱንም ወደ ከተማ ደጃፍ ወስዳችሁ እስኪሞቱ ድረስ በድንጋይ ውገሯቸው። ክፉውን ከመካከላችሁ ማስወገድ አለባችሁ። 25 ነገር
ግን አንድ ሰው የታጨችውን ልጃገረድ ከከተማ ውጭ አግኝቶ በማስገደድ ቢደፍራት፥ ይህን ድርጊት የፈጸመው ሰው ብቻ ይገደል። 26 በልጃገረዲቱ ላይ ግን
ምንም አታድርጉባት፥ ለሞት የሚያበቃ ኃጢአት ምንም አልሠራችም፥ ይህ ዓይነቱ ጉዳይ አደጋ ጥሎ ባልንጀራውን ከሚገድል ሰው አድራጎት ጋር የሚመሳሰል
ነው። 27 ምክንያቱም ሰውየው የታጨችውን ልጃገረድ ከተማ ውጭ ስላገኛትና ብትጮኽም እንኳ ለርዳታ የደረሰላት ምንም ሰው ስላልነበር ነው። 28 አንድ ሰው
ያልታጨች ልጃገረድ አግኝቶ በማስገደድ ቢደርስባትና ቢጋለጡ 29 ሰውየው ለልጅቷ አባት አምሳ ስቅል ብር ይክፈል፥ ልጃገረዲቱን አስገድዶ ደፍሮአታልና
እርሷን ማግባት አለበት፥ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ሊፈታት አይችልም። 30 አንድ ሰው አባቱን ሚስት ማግባት የለበትም፥ የአባቱንም መኝታ አያርክስ።

Deuteronomy 22:1

ሲጠፋ
“ከባለቤቱ ርቆ ሲሄድ”

ራስህን ከእነርሱ አትደብቅ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “እንዳላየኻቸው አትሁን” ወይም “ምንም ነገር ሳታደርግ አትሂድ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

እስራኤላዊ ወንድምህ በአቅራቢያህ ባይኖር
“እስራኤላዊ ወንድምህ ከአንተ ርቆ የሚኖር ከሆነ”

ወይም የማታውቀው ከሆነ
“ወይም የእንስሳው ባለቤት ማን እንደሆነ ካላወቅህ”

እርሱ እስኪፈልገው ድረስ በአንተ ዘንድ ይቆይ
“ባለቤቱ ፈልጎት እስኪመጣ ድረስ እንስሳው በአንተ ዘንድ ይቆይ”

Deuteronomy 22:3

በአህያውም ላይ እንደዚሁ አድርግ
“አህያውንም በተመሳሳይ መንገድ መልስለት”

በልብሱም ላይ እንደዚሁ አድርግ
“በተመሳሳይ መንገድ ልብሱን መልስለት”

Deuteronomy 22:5

ለወንድ የሚገባውን
“የወንድ ልብስ”

Deuteronomy 22:6

የወፍ ጎጆ
ወፎች ከጭራሮ፣ ሣር፣ እጽዋትና ጭቃ ለራሳቸው የሚሠሩት ቤት

ከጫጩቶቿ ወይም በውስጧ ካሉ ዕንቁላሎች ጋር
“ከትናንሽ ወፎች ወይም በጎጆው ውስጥ ካሉ ዕንቁላሎች ጋር”

በትናንሾቹ ላይ የተቀመጠች እናት
“እናቲቱ ወፍ በጫጩት ወፎች ላይ ተቀምጣለት”

ቀኖችህ እንዲረዝሙ
ረጅም ቀናት የረጅም ዕድሜ ዘይቤአዊ አነጋገሮች ናቸው። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 4:26 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። አ.ት፡ “ረጅም ዓመት መኖር እንድትችል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 22:9

ምርትህ በሙሉ በተቀደሰው ስፍራ እንዳይወረስ
“ቅዱስ ስፍራ” የሚለው ቃል በተቀደው ስፍራ የሚሠሩትን ካህናት የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በእግዚአብሔር ቅዱስ ስፍራ ያሉ ካህናት ምርቱን ሁሉ እንዳይወስዱት” ወይም “ምርቱን ሁሉ እንዳታረክሰውና ካህናቱ ከመጠቀም

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንዳይከለክሉህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በወይን ተክል ቦታ የሚበቅለውን
“በወይን ተክል ቦታ የሚበቅለውን ፍሬ”

ሱፍ
በበጎች ላይ የሚበቅል ለስላሳና የሚጠቀለል ጸጉር

በፍታ
ከቃጫ ተክል የሚሠራ ክር (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 22:12

ጥለት
በአንድ ላይ ታስረው በእያንዳንዱ የካባው ማዕዘን ላይ የሚንጠለጠሉ ክሮች

ካባ
አንድ ሰው በሌሎች ልብሶቹ ላይ ደርቦ የሚለብሰው ረዘም ያለ ልብስ

Deuteronomy 22:13

ከዚያም አሳፋሪ ስለሆነ ነገር ቢከሳት
“ከዚያም ከጋብቻዋ በፊት ከሌላ ሰው ጋር ስለመተኛቷ ቢከሳት”

ምስክርነቷን ያበላሻል
የነገር ስም የሆነው “ምስክርነት” እንደ ግሥ ሐረግ ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ሰዎች መጥፎ ሰው እንደሆነች እንዲያስቡ ያደርጋል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 22:15

የድንግልናዋን ማረጋገጫ ይውሰዱ
የነገር ስም የሆኑት “ማረጋገጥ” እና “ድንግልና” እንደ ግሣዊ ሐረጎች ሊተረጎሙ ይችላሉ። አ.ት፡ “ቀደም ሲል የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዳልነበራት የሚያረጋግጥ አንዳች ነገር ውሰድ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 22:16

ስለ አሳፋሪ ነገር ከሷታል
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “ሳያገባት በፊት ከሌላ ሰው ጋር ስለመተኛቷ ከሷታል” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ከልጅህ የድንግልና ማረጋገጫ አላገኘሁኝም
የነገር ስም የሆኑት “ማረጋገጥ” እና “ድንግልና” እንደ ግሣዊ ሐረጎች ሊተረጎሙ ይችላሉ። አ.ት፡ “ልጅህ ቀደም ሲል የግብረ ሥጋ ግንኙነት ላለመፈጸሟ ማረጋገጫ ማቅረብ አልቻለችም” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ነገር ግን የልጄ ድንግልና ማስረጃው ይኸው
የነገር ስም የሆኑት “ማረጋገጥ” እና “ድንግልና” እንደ ግሣዊ ሐረጎች ሊተረጎሙ ይችላሉ። አ.ት፡ “ይሁን እንጂ ልጄ ቀደም ሲል የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዳልፈጸመች ይህ ያረጋግጣል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ከዚያም በከተማይቱ ሽማግሌዎች ፊት ጨርቁን ይዘረጉታል
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “ከዚያም ድንግል እንደነበረች ማስረጃ እንዲሆን እናትና አባቷ በደም የተነከረውን ጨርቅ ለሽማግሌዎቹ ያሳያሉ።(See: Assumed Knowledge and Implicit Information

Deuteronomy 22:18

ይቅጡት
“ቅጣት እንዲከፍል ያድርጉት”

አንድ መቶ ሰቅል
“100 ሰቅል” (ገንዘብ በመጽሐፍ ቅዱስ እና ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ለልጅቱ አባት ይስጡት
“ገንዘቡን ለልጅቱ አባት ስጡት”

የእስራኤል ድንግል ምስክርነቷ እንዲበላሽ አድርጓል
የነገር ስም የሆነው “ምስክርነት” እንደ ግሣዊ ሐረግ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ሰዎች የእስራኤልን ድንግል መጥፎ ሰው አድርገው እንዲያስቧት አድርጓል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

እንዳይሰዳት
“እንዲፈታት በፍጹም አትፍቀድለት”

በቀኖቹ ሁሉ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ሕይወቱን ሙሉ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 22:20

ሆኖም ይህ ነገር እውነት ቢሆን
“ሆኖም እውነት ቢሆን” ወይም “ሆኖም ሰውየው የተናገረው እውነት ቢሆን”

በልጅቱ ላይ የድንግልና ማስረጃ ባይገኝ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሰውየው ልጅቱ ድንግል ስለመሆኗ ማረጋገጫ አላገኘም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የድንግልና ማረጋገጫ
የነገር ስም የሆኑት “ማረጋገጫ” እና “ድንግልና” እንደ ግሣዊ ሐረጎች ሊተረጎሙ ይችላሉ። አ.ት፡ “ልጅቱ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጽማ እንደማታውቅ የሚያስረዳ አንዳች ነገር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ከዚያም ልጅቱን ያውጧት
“ከዚያም ሽማግሌዎቹ ልጅቱን ያውጧት”

በድንጋይ ወግረው ይግደሏት
“እስክትሞት ድረስ ድንጋይ ወርውሩባት”

በእስራኤል ውስጥ አሳፋሪ ተግባር ፈጽማለችና
“በእስራኤል ውስጥ አሳፋሪ ነገር አድርጋለችና”

በአባቷ ቤት ውስጥ እንደ ሴተኛ አዳሪ ለማድረግ
“በአባቷ ቤት ውስጥ እየኖረች እንደ ሴተኛ አዳሪ ማድረግ”

ክፉን አስወግድ
ቅጽል የሆነው “ክፉ” እንደ ስማዊ ሐረግ ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ይህንን ክፉ ነገር ያደረገውን ከእስራኤላውያን መካከል አስወግድ” ወይም “ይህንን ክፉ ሰው አስወግደው” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 22:22

አንድ ሰው --- ቢገኝ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አንድ ሰው ሌላውን ሰው ቢያገኝ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ታስወግዳለህ
“በዚህ መንገድ ታስወግዳለህ”

Deuteronomy 22:23

ለአንድ ሰው የታጨች
“አንድን ሰው እንድታገባ ቃል የተገባላት”

ውሰዱ -- እና ወገሩ
እነዚህ ትዕዛዛት ለእስራኤል እንደ ቡድን የተነገሩ ናቸው፣ በመሆኑም ብዙ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)

ሁለቱንም ውሰዷቸው
“ከዚያም ልጅቱንና ከእርሷ ጋር የተኛውን ሰው አምጧቸው”

ምክንያቱም አልጮኸችም
“ምክንያቱም ለእርዳታ አልተጣራችም”

የባልንጀራውን ሚስት አርክሷልና
በዚያን ዘመን እስራኤላውያን ለጋብቻ የተጫጨ ወንድና ሴትን እንደ ባልና ሚስት ይቆጥሯቸው ነበር። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “ምክንያቱም የእስራኤላዊ ወንድሙ ከምትሆን ልጅ ጋር ተኝቷል” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ክፉን ከመካከልህ አስወግድ
ቅጽሉ “ክፉ” እንደ ስማዊ ሐረግ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ይህንን ክፉ ነገር ያደረገውን ሰው ከእስራኤላውያን መካከል አስወግደው” ወይም “ይህንን ክፉ ሰው አስወግደው” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 22:25

የታጨችውን ልጅ
ይህ ማለት ወላጆቿ አንድን ሰው እንድታገባ የተስማሙባት፣ ሆኖም ገና ያላገባችው ልጅ ማለት ነው።

ከዚያም ከእርሷ ጋር የተኛው ሰው ብቻ ይገደል
“ከዚያም ከእርሷ ጋር የተኛውን ሰው ብቻ ግደሉ”

ልጅቱ ጋ ለሞት የሚያበቃት ኃጢአት የለም
“ስላደረገችው ነገር በሞት አትቅጧት”

ይህ ጉዳይ ባልንጀራውን ከሚያጠቃና ከሚገድለው ሰው ጋር ተመሳሳይ ነውና
“ምክንያቱም ይህ ሁኔታ አንድ ሰው ሌላውን ሰው አጥቅቶ ከሚገድልበት ሁኔታ ጋር ስለሚመሳሰል ነው”

ከሰፈር ውጪ አግኝቷታልና
“ምክንያቱም ሰውየው ልጅቱን ከሰፈር ውጪ ሥራ ላይ ሆና አግቷታል”

Deuteronomy 22:28

ሆኖም ያልታጨች
“ሆኖም ወላጆቿ ለሚያገባት ሰው እንደሚድሩለት ቃል ያልገቡለት”

ቢገኙ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አንድ ሰው ስለሆነው ነገር ቢያውቅ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ሃምሳ ሰቅል ጥሬ ብር
አንድ ሰቅል አሥራ አንድ ግራም ይመዝናል። አ.ት፡ “አምሳ የጥሬ ብር ዝርዝር” ወይም “550 ግራም ጥሬ ብር” (See: Biblical Money and Numbers)

በቀኖቹ ሁሉ አይስደዳት
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ዕድሜውን ሙሉ አይፍታት” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 22:30

የአባቱን ሚስት ለራሱ ሚስት አድርጎ አይውሰድ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “ምንም እንኳን እናቱ ባትሆንም የቀድሞ የአባቱን ሚስት ማግባት የለበትም” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 23

1 ብልቱ የተቀጠቀጠ ወይም የተቆረጠ ማናቸውም ሰው ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግባ። **2** ዲቃላም ይሁን፥ የዲቃላው ዘር የሆነ ሁሉ እስከ አሥር ትውልድ ድረስ እንኳን ቢሆን ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግባ። **3** አሞናዊም ሆነ ሞዓባዊ ወይም ማናቸውም የእርሱ ዘር፥ እስከ አሥር ትውልድ እንኳ ቢሆን ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግባ። **4** ምክንያቱም ከግብፅ ከወጣችሁ በኋላ በጉዞ ላይ በነበራችሁበት ጊዜ እህልና ውሃ ይዘው አልተቀበሏችሁም። በመስጴጦምያ በምትገኘው በፐቶር ይኖር የነበረውን የቢዖርን ልጅ በለዓምም እናንተን እንዲረግም በገንዘብ ገዙት። **5** ነገር ግን እግዚአብሔር አምላካችሁ በብዓምን አልሰማውም፤ አምላካችሁ እግዚአብሔር ስለሚወዳችሁ ርግማኑን ወደ በረከት አደረገላችሁ። **6** በሕይወት ዘመናችሁ ሁሉ ሰላምን ለእነርሱ አትመኙ። **7** ወንድማችሁ ስለ ሆነ ኤዶማዊውን አትጸየፈው፤ መጻተኛ ሆናችሁ በአገሩ ኖራችኋልና ግብፃዊውን አትጥሉት። **8** ለእነርሱ የተወለዳቸው የሦስተኛው ትውልድ ልጆች ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ መግባት ይችላሉ። **9** ጠላታችሁን ለመውጋት ወጥታችሁ በሰፈራችሁ ጊዜ ከማናቸውም ርኩሰት ራሳችሁን ጠብቁ። **10** ከመካከላችሁ ሌሊት ዘር በማፍሰስ የረከሰሰው ቢኖር፥ ከሰፈር ወጥቶ እዚያው ይቆይ። **11** እየመሸ ሲመጣ ግን ገላውን ይታጠብ ፀሐይ ስትጠልቅም ወደ ሰፈሩ ይመለስ። **12** ለመጸዳጃ የሚሆንህን ቦታ ከሰፈር ውጭ አዘጋጅ። ከትጥቅህም ጋር መቆፍሪያ ያዝ፥ **13** በምትጸዳዳበት ጊዜ አፈር ቆፍረህ በዐይነ ምድርህ ላይ መልስበት። **14** እግዚአብሔር አምላክህ ሊጠብቅህ ጠላቶህንም በእጅህ አሳልፎ ሊሰጥህ በሰፈር ውስጥ ስለሚዘዋወር በመካከልህ አንዳች ነውር አይቶ ከአንተ እንዳይመለስ፥ ሰፈርህ የተቀደሰ ይሁን። **15** አንድ ባሪያ ከአሳዳሪው ኮብልሎ ወደ እናንተ ቢመጣ፥ **16** ለአሳዳሪው አሳልፋችሁ አትስጡት፥ ደስ በሚያሰኘው ቦታን ራሱ በመረጠው ከተማ በመካከላችሁ ይኑር፤ እናንተም አታስጨንቁት። **17** ወንድ ወይም ሴት እስራኤላዊ የቤተ ጣዖት አመንዝራ አይኑራችሁ። **18** ለዝሙት አዳሪ ሴት ወይም ለወንድ ዝሙተኛ የተከፈለውን ዋጋ ለማናቸውም ስእለት አድርጋችሁ ለመስጠት ወደ እግዚአብሔር ወደ አምላካችሁ ቤት አታምጡ፤ እግዚአብሔር አምላካችሁ ሁለቱንም ይጸየፋቸዋልና። **19** የገንዘብ፥ የእህል ወይም የማንኛውንም ነገር ወለድ ለማግኘት ለወንድማችሁ በወለድ አታበድሩ። ባዕድ ለሆነ ሰው በወለድ ማበደር ትችላላችሁ። **20** ነገር ግን ልትወርሱአት በምትገቡባት ምድር እጃችሁ በሚነካው በማናቸውም ነገር እግዚአብሔር አምላካችሁ እንዲባርካችሁ ለእስራኤልዊ ወንድማችሁ በወለድ አታበድሩት። **21** ለእግዚአብሔር ለአምልካችሁ ስእለት ከተሳላችሁ እግዚአብሔር አምላካችሁ አጥብቆ ከእናንተ ይሻዋልና፤ ኃጢአት እንዳይሆንባችሁ ለመክፈል አትዘግዩ። **22** ሳትሳሉ ብትቀሩ ግን በደለኛ አትሆኑም። በአንደበታችሁ የተናገራችሁትን ሁሉ ለመፈጸም ጠንቃቃ ሁኑ፥ **23** ለአምላካችሁ ለእግዚአብሔር በገዛ አንደበታችሁ ፈቅዳችሁ ስእለት ተስላችኋልና። **24** ወደ ባልንጀራችሁ የወይን ተክል ቦታ በምትገቡበት ጊዜ ያሰኛችሁን ያህል መብላት ትችላላችሁ፤ ነገር ግን አንዳችም በዕቃችሁ አትያዙ። **25** ወደ ባልንጀራችሁ እርሻ በምትገቡበት ጊዜ እሸት መቅጠፍ ትችላላችሁ፤ በሰብሉ ላይ ግን ማጭድ አታሳርፉበት።

Deuteronomy 23:1

ተቀጥቅጦ የቆሰለ ወይም የተቆረጠ ሰው
“የወንድ አካሉ የተቀጠቀጠ ወይም የተቆረጠበት ሰው”

ወደ እግዚአብሔር ጉባዔ መግባት
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “የእስራኤል ማኅበረሰብ ሙሉ አባል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ዲቃላ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ወላጆቹ ዘመዳሞች ሆነው ወይም በዝሙት የወለዱት ልጅ ወይም 2) ከሴተኛ አዳሪ የተወለደ ልጅ።

ተወላጆቹ እስከ አሥረኛ ትውልድ ድረስ
ይህ “አሥረኛ” የአሥር ደረጃን አመልካች ቁጥር ነው። አ.ት፡ “ከዲቃላው ልጅ ተወላጆች አሥረኛ ትውልድ በኋላ እንኳን” (ደረጃን አመልካች ቁጥር የሚለውን ተመልከት)

ማናቸውም
“ከእነዚህ ተወላጆች ማናቸውም”

Deuteronomy 23:3

ወደ እግዚአብሔር ጉባዔ አይግቡ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “የእስራኤል ማኅበረሰብ ሙሉ አባል አይሁኑ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ተወላጆቹ እስከ አሥረኛ ትውልድ ድረስ
ይህ “አሥረኛ” የአሥር ደረጃን አመልካች ቁጥር ነው። አ.ት፡ “ከተወላጆቹ ከአሥር ትውልድ በኋላ እንኳን” (ደረጃን አመልካች ቁጥር የሚለውን ተመልከት)

በእንጀራና በውሃ አልተቀበሏችሁም
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “ምግብና መጠጥ በማቅረብ አልተቀበሏችሁም” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

በአንተ ላይ -- እንዲረግማችሁ
ሙሴ እስራኤላውያንን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “አንተ” የሚለው ቃል እዚህ ጋ ነጠላ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)

Deuteronomy 23:5

አልሰማም
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ትኩረት አልሰጠውም” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

እርግማኑን ወደ በረከት ለወጠልህ
“እንዲረግምህ ሳይሆን እንዲባርክህ አደረገው”

ሰላማቸውን ወይም ብልጽግናቸውን በፍጹም አትፈልግ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “ከአሞናውያንና ከሞዓባውያን ጋር የሰላም ስምምነት ከቶ ማድረግ የለብህም” ወይም 2) “ለእነዚያ 2 የሕዝብ ወገኖች መልካም እንዲሆንላቸውና ለመበልጸግ የሚያስችላቸውን ምንም ነገር አታድርግ”

በቀኖችህ ሁሉ
x

Deuteronomy 23:7

ኤዶማዊውን አትጸየፈው
“ኤዶማዊውን አትጥላው”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወንድምህ ነውና
“ዘመድህ ነውና”

ግብፃዊውን አትጸየፈው
“ግብፃዊውን አትጥላው”

የሚወለዱላቸው የተወላጆቻቸው ሦስተኛ ትውልድ ወደ እግዚአብሔር ጉባዔ እንዲገቡ
ይህ “ሦስተኛ” የሦስት ደረጃን አመልካች ቁጥር ነው። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “አንድ ኤዶማዊ ወይም ግብፃዊ በእስራኤላውያን ማኅበረሰብ ውስጥ ለመኖር ቢመጣ፣ የልጅ ልጆቹ የዚያ ማኅበረሰብ ሙሉ አባል ሊሆኑ ይችላሉ” (See: (ደረጃን አመልካች ቁጥር እና Assumed Knowledge and Implicit Information የሚለውን ተመልከት))

Deuteronomy 23:9

እንደ ሰራዊት በጠላቶችህ ላይ በምትወጣበት ጊዜ፣ ያን ጊዜ ራስህን ጠብቅ
ሙሴ ለእስራኤላውያን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “አንተ” እና “የአንተ” የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥሮች ናቸው። (See: Forms of You)

በጠላቶችህ ላይ
“ጠላቶችህን ለመውጋት”

ከክፉ ነገር ሁሉ ራስህን ጠብቅ
“መጥፎ ከሆኑ ነገሮች ሁሉ ራስህን አርቅ”

ሌሊት በሆነበት ነገር ምክንያት ንጹሕ ያልሆነ ማንኛውም ሰው
ይህ ዘር ማፍሰሱ የተነገረበት የትህትና አባባል ነው። አ.ት፡ “በእንቅልፍ ላይ እያለ ዘር ስለፈሰሰው ንጹሕ ያልሆነ ማንኛውም ሰው” (See: Euphemism)

Deuteronomy 23:12

የምትቆፍርበት መሣሪያ ይኑርህ
“ለመቆፈር የምትጠቀምበት መሣሪያ ይኑርህ”

Deuteronomy 23:15

ከጌታው ያመለጠ ባሪያ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “ከሌላ ሀገር ከጌታው አምልጦ ወደ እስራኤል የመጣ ባሪያ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ከአንተ ጋር ይኑር
“ባሪያው በሕዝብህ መካከል ይኑር”

Deuteronomy 23:17

የቤተ ጣዖት አመንዝራ -- የቤተ ጣዖት አመንዝራ -- ዝሙት አዳሪ -- ውሻ
እግዚአብሔር በማንኛውም ሰው በየትኛውም ምክንያት በወንድና በሴት የሚደረጉ የአመንዝራነት ዓይነቶችን የሚከለክል ዝርዝር ይሰጣቸዋል። (See: Merism)

በሴቶች ልጆች መካከል -- በወንዶች ልጆች መካከል -- የቤተ ጣዖት አመንዝራ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፤ ሙሴ፣ 1) ሴቶችና ወንዶች ወሲባዊ ተግባርን የመቅደስ አገልግሎት አካል እንዳያደርጉ ይከለክላቸዋል ወይም 2) ሴቶችና ወንዶች ገንዘብ ለማግኘት ወሲባዊ ተግባር እንዳይፈጽሙ ለመከልከል ሻል ባለ ቃል ይጠቀማል። (See: Euphemism)

የዝሙት አዳሪን ዋጋ ወደ -- ቤት አታምጣ
“በዝሙት ሥራ ገንዘብ የምታገኝ ሴት ያንን ገንዘብ ወደ -- ቤት አታምጣ”

ውሻ
ገንዘብ ለማግኘት ከእርሱ ጋር ወንዶች ወሲብ እንዲፈጽሙ የሚፈቅድ ወንድ

ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ቤት
“ወደ መቅደስ”

ለየትኛውም ስእለት
“ስእለት ለመፈጸም”

እነዚህን በሙሉ
የሴትና የወንድ ዝሙት አዳሪዎችን ዋጋ

Deuteronomy 23:19

ለእስራኤላዊ ወንድምህ በወለድ አታበድረው
“ለእስራኤላዊ ወንድምህ አንዳች ነገር ብታበድረው ካበደርከው በላይ እንዲመልስልህ አታድርገው”

በወለድ ማበደር
ለአንድ ሰው ማበደርና ያ ሰው ከተበደረው በላይ እንዲመልስ ማስገደድ

የገንዘብ ወለድ -- የትኛውም በወለድ የተሰጠ
“ለአንድ ሰው ገንዘብ፣ ምግብ ወይም የትኛውንም ነገር በምታበድርበት ጊዜ ወለድ አታስከፍለው”

እጅህን በምታሳርፍበት ሁሉ ላይ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “በምትሠራሁ ሁሉ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 23:21

ለመፈጸም አትዘግይ
“ስእለትህን ለመፈጸም ረጅም ጊዜ አትውሰድ”

አምላክህ እግዚአብሔር በእርግጥ ከአንተ ይፈልገዋልና
“ምክንያቱም ስእለትህን ካልፈጸምክ አምላክህ እግዚአብሔር ይነቅፍሃል፣ ይቀጣሃልም”

ሳትሳል ብትቀር ግን ኃጢአት አይሆንብህም
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “ካልተሳልክ ግን የምትፈጽመው ስእለት የለህምና ኃጢአት አትሠራም” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ከከንፈርህ የወጣውን
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “የተናገርከው ቃል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ለአምላክህ ለእግዚአብሔር እንደተሳልከው
“ታደርገው ዘንድ ለአምላክህ ለእግዚአብሔር የተሳልከውን ማንኛውንም ነገር”

በአንደበትህ ፈቅደህ ቃል የገባህበትን የትኛውንም ነገር
“ልታደርገው ስለፈለግህ ቃል ስትገባ ሰዎችህ የሰሙህን ነገር ሁሉ”

በአንደበትህ
“ስትናገር ሰዎች የሰሙህን”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Deuteronomy 23:24

የምትፈልገውን ያህል ወይን መብላት ትችላለህ
“ከዚያም እስክትጠግብ ድረስ ወይን በመብላት መደሰት ትችላለህ”

ሆኖም በቅርጫትህ ውስጥ ምንም እንዳትጨምር
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “ሆኖም ይዘህ ለመሄድ በከረጢትህ ውስጥ ምንም ወይን አትጨምር” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ወደ ባልንጀራህ የደረሰ ሰብል በምትገባበት ጊዜ
“ሰብሉ ባፈራበት የባልንጀራህ እርሻ መካከል በምታልፍበት ጊዜ”

እሸት መቅጠፍ ትችላለህ
“ከዚያም ከሰብሉ ፍሬ በእጅህ ወስደህ መብላት ትችላለህ”

ነገር ግን በደረሰው የባልንጀራህ ሰብል ላይ ማጭድ አታሳርፍበት
“ነገር ግን የባልንጀራህን የደረሰ ሰብል አጭደህ አትውሰድ”

ማጭድ
ገበሬዎች ስንዴ ለመሰብሰብ የሚጠቀሙበት ስለታም መሣሪያ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 24

1 አንድ ሰው አንዲት ሴት ካገባ በኋላ አሳፋሪ ነገር አግኝቶባት ባይደሰትባት የፍቺ ወረቀት ጽፎ በመስጠት ከቤቱ አስወጥቶ ይስደዳት። **2** ከቤቱ ከወጣች በኋላ ሌላ ባል ሊታገባ ትችላለች። **3** ሁለተኛ ባሏም እንደዚሁ ጠልቷት የፍቺ ወረቀት በመስጠት ከቤቱ አስወጥቶ ቢሰዳት፥ ወይም ቢሞት፥ **4** ከዚያ በኋላ ፈቶአት የነበረው የመጀመሪያ ባሏ፥ የረከሰች በመሆኗ እንደ ገና መልሶ ሊያገባት አይችልም፤ ይህ በእግዚአብሔር ፊት አስጸያፊ ነው። እግዚአብሔር አምላካችሁ ርስት አድርጎ በሚሰጣችሁ ምድር ላይ ኃጢአት አታምጡ። **5** አዲስ ሚስት በቅርብ ጊዜ ያገባ ሰው፥ ለጦርነት አይሂድ ወይም ሌላ ሥራ እንዲሥራ አይገደድ። ለአንድ ዓመት ነጻ ሆኖ እቤቱ ይቆይ፥ ያገባትን ሚስቱን ደስ ያሰኛት። **6** ወፍጮና መጁን ወይም መጁንም እንኳ ቢሆን፥ የብድር መያዣ አድርጋችሁ አትውሰዱ፤ የሰውን ነፍስ መያዣ አድርጎ መውሰድ ይሆናልና። **7** አንድ ሰው ከእስራኤላውያን ወንድሞቹ አንዱን ፈንግሎ በመውሰድ ባሪያ ሲያደርገው ወይም ሲሸጠው ቢገኝ፥ ፈንጋዩ ይሙት። ክፉውን ከመካከላችሁ አስወግድ። **8** የለምጽ ደዌን በተመለከተ ሌዋውያን ካህናት የሚሰጡአችሁን መመሪያ በትክክል ለመፈጸም ጥንቃቄ አድርጉ። እኔ ለእነርሱ የሰጠሁትን ትእዛዝ በጥንቃቄ ተከተሉ። **9** ከግብፅ ከወጣችሁ በኋላ በመንገድ ላይ ሳላችሁ እግዚአብሔር አምላካችሁ በሙሴ እህት በምርያም ላይ ያደረገባትን አስታውሱ። **10** ማናቸውንም ነገር ለባልንጀራችሁ ስታበድሩ መያዣ አድርጎ የሚሰጣችሁን ለመቀበል ወደ ቤቱ አትግቡ። **11** እንንተ ከውጭ ሆናችሁ ጠብቅ፥ ያበደራችሁም ሰው መያዣውን ከቤት ያምጣላችሁ። **12** ሰውየው ድኻ ከሆነ መያዣውን ከእናንተ ዘንድ አታሳድሩበት። **13** መደረቢያውን ለብሶት እንዲያድር ፀሐይ ሳትጠልቅ መልሱለት። ከዚያም ያመሰግናችኋል፤ እግዚአብሔር አምላካችሁ ፊትም የጽድቅ ሥራ ሆኖ ይቆጠርላችኋል። **14** ድኻና ችግረኛ የሆነውን የምንዳ ሠራተኛ እስራኤላዊ ወንድማችሁም ሆነ፥ከከተሞቻችሁ ባንዲቱ የሚኖረውን መጻተኛ አትበዝብዙት፤ **15** የሠራበትን ሒሳብ በዕለቱ ፀሐይ ሳትጠልቅ ክፈሉት፤ ድኻ በመሆኑ በጉጉት ይጠባበቀዋልና። ያለበለዚያ ወደ እግዚአብሔር ይጮኽና ኃጢአት ይሆንባችኋል። **16** አባቶች ስለ ልጆቻቸው፥ ልጆችም ስለ አባቶቻቸው አይገደሉ፤ እያንዳንዱ በራሱ ኃጢአት ይገደል። **17** መጻተኛው ወይም አባት ለሌለው ልጅ ፍትሕ አትንፈጉት፤ ባል የሞትባትንም መደረቢያ መያዣ አታድርጉ። **18** እናንተም በግብፅ ባሪያ እንደ ነበራችሁና እግዚአብሔር አምላካችሁ ከዚያ እንደ ተቤዣችሁ አስታውሱ፤ ይህን እንድታደርጉ ያዘዙአችሁ ለዚህ ነው። **19** የእርሻችሁን ሰብል በምታጭዱበት ጊዜ ተረስቶ የቀረ ነዶ ቢኖር፥ ያን ለመውሰድ ተመልሳችሁ አትሂዱ፤እግዚአብሔር አምላካችሁ በእጃችሁ ሥራ ሁሉ እንዲባርካችሁ ነዶውን ለመጻተኛው፥ አባት ለሌለውና ባል ለሞተባት ተዉ። **20** የወይራ ዛፋችሁን ፍሬ በምታራግፉበት ጊዜ በየቅርንጫፉ ላይ የቀረውን ለመቃረም ተመልሳችሁ አትሂዱ ለመጻተኛ፥ አባት ለሌለውና ባል ለሞተባት ተዉ። **21** የወይን ተክላችሁን ፍሬ ስትሰበስቡ ቃርሚያውን ለመሰብሰብ አትመለሱበት የቀረውን ለመጻተኛው፥ አባት ለሌለውና ባል ለሞተባት ተዉ። **22** በግብፅ ባሮች እንደነበራችሁ አስታውሱ፤ ይህን እንድታደርጉ ያዘዙአሁን ለዚህ ነው።

Deuteronomy 24:1

አንድ ሰው ሚስት ወስዶ በሚያገባበት ጊዜ
“ሚስት ወስዶ” እና “በሚያገባት” የሚሉት ሐረጎች ትርጉማቸው አንድ ነው። አ.ት፡ “አንድ ወንድ አንዲትን ሴት በሚያገባበት ጊዜ” (See: Doublet)

በዐይኖቹ ሞገስን ባታገኝ
እዚህ ጋ “ዐይኖች” የሚወክሉት ሙሉውን ሰው ነው። አ.ት፡ “እንደማይወዳት ከወሰነ” (See: Synecdoche)

አንዳች የሚመቸውን ነገር ስላላገኘባት
“በሆነ ምክንያት ከእርሱ ጋር ሊያቆያት ያለመፈለግ ውሳኔ አድርጓል”

የፍቺ ወረቀት ጽፎ ይስጣት
“ከዚህ በኋላ በጋብቻ ውስጥ እንደሌሉ የሚገልጽ ሕጋዊ ወረቀት ለሚስቱ ይስጣት”

ሄዳ የሌላ ሰው ሚስት እንድትሆን
“ሄዳ ሌላ ሰው እንድታገባ”

Deuteronomy 24:3

ሁለተኛው ባሏ ቢጠላት
“ሁለተኛው ባሏ እንደሚጠላት ቢወስን”

የፍቺ ወረቀት
ይህ ሰውየውና ሴቲቱ ከእንግዲህ በጋብቻ ውስጥ እንዳልሆኑ የሚናገር ሕጋዊ ወረቀት ነው። ይህንን በዘዳግም 24:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

በእጇ ያኑረው
“ለሴቲቱ ይስጣት”

ሚስት አድርጎ የወሰዳት ሰው
“ሴቲቱን ያገባት ሁለተኛው ሰው”

ከረከሰች በኋላ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “በፍቺውና እንደገና ሌላ ሰው በማግባቷ ከረከሰች በኋላ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ምድሪቱ በደለኛ እንድትሆን አታድርጋት
ምድር ኃጢአት ልትሠራ እንደምትችል ተደርጋ ተነግሮላታል። አ.ት፡ “በምድሪቱ ዙሪያ በደል እንዳታስፋፋ” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 24:5

አንድ ሰው አዲስ ሚስት በሚወስደበት ጊዜ
“አንድ ሰው በቅርቡ አንዲትን ሴት በሚያገባበት ጊዜ”

የጉልበት ሥራ ለመሥራት እንዲሄድም ቢሆን አይታዘዝ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ከቤቱ እንዲርቅና የትኛውንም ዓይነት ሥራ እንዲሠራ ማንም አያስገድደው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በቤቱ ለመሆን ነጻ ይሁን
“በቤቱ ለመኖር ነጻ ይሁን”

Deuteronomy 24:6

ወፍጮ
ክብደት ባላቸው ሁለት ክብ ድንጋዮች እህል በመፍጨት ዱቄት ለመሥራት የሚያስችል መሣሪያ

መጅ
ከወፍጮ ጋር ያለ የላይኛው ክብ ድንጋይ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ያ የሰውን ሕይወት በመያዣነት እንደመውሰድ ይሆናል
“ሕይወት” የሚለው ቃል አንድ ሰው ራሱን በሕይወት ለማቆየት የሚያስፈልገው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ሰውየው ለቤተሰቡ ምግብ ለማዘጋጀት የሚጠቀምበትን መውሰዱ ነውና” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 24:7

አንድ ሰው ተጠልፎ ቢገን
ይህ የአነጋገር ዘይቤ “አንድ ሰው ቢጠለፍ” እንደማለት ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አንድ ሰው ሲጠልፍ ብታገኘው” (የአነጋገር ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

መጥለፍ
አንድን ንጹሕ ሰው ኃይልን በመጠቀም ከቤቱ ወስዶ ማሰር ነው

በእስራኤል ሕዝብ መካከል ከወንድሞቹ አንዱን
“የትኛውንም እስራኤላዊ ወንድሙን”

ያ ሌባ ይሙት
“ከዚያም ሌሎች እስራኤላውያን ያንን ሌባ ስለድርጊቱ በመግደል ይቅጡት”

ክፉን ከመካከልህ ታስወግዳለህ
“ክፉ” የሚለው ቅጽል እንደ ስማዊ ሐረግ ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ይህንን ክፉ ነገር ያደረገውን ሰው ከእስራኤላውያን መካከል አስወግደው” ወይም “ይህንን ክፉ ሰው አስወግደው” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 24:8

አምላክህ እግዚአብሔር -- ትዝ ይበልህ -- ጥንቃቄ አድርግ -- በጥንቃቄ ጠብቅ
እዚህ ጋ ሙሴ እንደ አንድ ሰው አድርጎ ለእስራኤላውያን ይናገራል፣ ስለዚህ “አንተ” እና “የአንተ” የሚሉት ቃላትና “ጥንቃቄ አድርግ” እና “ትዝ ይበልህ” የሚሉት ትዕዛዛት ነጠላ ቁጥሮች ናቸው። (See: Forms of You)

የትኛውንም ለምጽ በሚመለከት ጥንቃቄ አድርግ
“የምትሠቃየው በለምጽ እንደሆነ ልብ በል” ወይም “ለምጽ ይኖርብህ እንደሆነ ልብ በል”

ካህናቱና ሌዋውያኑ የሚያስተምሩህን ለአንተ የተሰጠህን እያንዳንዱን መመሪያ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የሰጠሁህን መመሪያዎች በሙሉና ሌዋውያን የሆኑት ካህናቱ እንድታደርገው የሚያስተምሩህን” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የሚያስተምሩህን -- እንድታደርገው -- ከግብፅ ከወጣችሁ
እዚህ ጋ ሙሴ ለእስራኤላውያን የሚናገረው እንደ ቡድን ነው፣ ስለዚህ “አንተ” የሚሉት እነዚህ አገባቦች ብዙ ቁጥር ናቸው። (See: Forms of You)

እኔ እንዳዘዝኳቸው ታደርጋለህ
“እኔ እንዳዘዝኳቸው በትክክል ስለማድረግህ እርግጠኛ ሁን”

እንዳዘዝኳቸው
“እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሌዋውያን የሆኑትን ካህናት ነው።

ትዝ ይበልህ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “(የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ከግብፅ በመውጣት ላይ እያለህ
“ግብፅን ስትለቅ በነበረበት ጊዜ”

Deuteronomy 24:12

መያዣውን ለራስህ ወስደህ አታሳድርበት
“ኮቱን አታሳድርበት”

መያዣውን
ይህ የሚያመለክተው ብድሩን ባይመልስ በምትኩ ሊሰጥህ ቃል የገባውን ነገር ነው። ይህንን በዘዳግም 24:10 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

መያዣውን መልስለት
“ብድሩን እንደሚመልስልህ ለማሳየት የሰጠህን መልስለት”

Deuteronomy 24:14

የተቀጠረን አገልጋይ አትጨቁነው
“የተቀጠረን አገልጋይ አትበድለው”

የተቀጠረ አገልጋይ
በየቀኑ ለሥራው የሚከፈለው ሰው

ድኻና ችግረኛ
እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ ይህ ሰው ራሱን መርዳት የማይችል በመሆኑ ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ። (See: Doublet)

በከተማህ በሮች ውስጥ
እዚህ ጋ “የከተማ በሮች” ማለት መንደሮች ወይም ከተሞች ማለት ነው። አ.ት፡ “ከከተሞችህ በአንዱ” (See: Synecdoche)

ደሞዙን በየቀኑ ስጠው
“ሰውየው በየቀኑ ማግኘት የሚገባውን ገንዘብ ልትሰጠው ይገባል”

ይህንን ጉዳይ ሳትፈታ ፀሐይ አትጥለቅ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “እስራኤላውያኑ ፀሐይ ስትጠልቅ የአዲሱ ቀን ጅማሬ እንደሆነ ያስባሉ። አ.ት፡ “ሥራውን በሠራበት በዚያው ቀን ለሰውየው ልትከፍለው ይገባል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ድኻ በመሆኑ ይጠባበቀዋልና
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “ድኻ ስለሆነና ለቀጣይ ቀኑ ምግቡን ለመግዛት በደሞዙ ስለሚተማመን” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

በአንተ ላይ ወደ እግዚአብሔር እንዳይጮህ
“እግዚአብሔርን እንዳይጠራና እንዲቀጣህ እንዳይጠይቀው”

Deuteronomy 24:16

ወላጆች ስለ ልጆቻቸው አይገደሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ከልጆቻቸው አንዱ ባደረገው ክፉ ነገር ምክንያት ወላጆችን አትግደል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እንዲሁም ልጆች ስለ ወላጆቻቸው አይገደሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ወላጆቻቸው ባደረጉት ክፉ ነገር ምክንያት ልጆቻቸው አይገደሉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እያንዳንዱ ስለ ገዛ ራሱ ኃጢአት ይገደል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አንድን ሰው መግደል የሚኖርብህ እርሱ ራሱ ባደረገው ክፉ ነገር ምክንያት ብቻ ነው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Deuteronomy 24:17

ከመጻተኛው ወይም አባቱን ካጣው ላይ ኃይልን በመጠቀም ፍትሕን አታስቀርበት
ሙሴ ስለፍትሕ አንድ ጉልበተኛ የሆነ ሰው ከደካማው ላይ በኃይል እንደሚቀማው አካላዊ ቁስ አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “የመጻተኛውን ወይም አባቱን ያጣውን ልጅ ፍትሕ አታጓድል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አባቶቻቸውን ያጡ ልጆች
x

Deuteronomy 24:19

ከእርሻህ ላይ የደረሰውን ሰብል በምትሰበስብበት ጊዜ
“በእርሻህ ውስጥ ሰብል በምታጭድበት ጊዜ”

የእህል ነዶ
አንዳንድ ትርጉሞች ይህንን እንደ “እስር” ይተረጉሙታል። ትርጉሞቹ ሁሉ የሚያመለክቱት በቀላሉ ለመሸከም የሚቻል፣ በይበልጥም በአንድ ላይ የታሰሩ የአገዳ እህሎችን ነው።

እርሱ ለመጻተኞች፣ አባቶቻቸውን ላጡ ልጆች ወይም ለመበለቶች ይሁን
የሚታወቀውን መረጃ ግልጽ ልታደርገው ትችላለህ። አ.ት: “ነዶውን መጻተኛው፣ ወላጆቹን ያጣው ወይም መበለቲቱ እንዲወስዱት ተወው” (See: Ellipsis)

በእጆችህ ሥራ ሁሉ
እዚህ ጋ “እጆች” የሚያመለክቱት ሙሉውን ሰው ነው። አ.ት: “በምትሠራው ሥራ ሁሉ” (See: Synecdoche)

የወይራ ዛፍህን በምትነቀንቅበት ጊዜ
የሚታወቀውን መረጃ ግልጽ ልታደርገው ትችላለህ። አ.ት: “ፍሬው ሲረግፍ ለማንሣት የወይራ ዛፍህን ቅርንጫፎች በምትነቀንቅበት ጊዜ” (See: Ellipsis)

በድጋሚ ወደ ቅርንጫፎቹ አትመለስ
“ከወይራ ዛፉ ላይ እያንዳንዱን ፍሬ አትልቀም”

እርሱ ለመጻተኞች፣ አባቶቻቸውን ላጡ ልጆች ወይም ለመበለቶች ይሆናል
የሚታወቀውን መረጃ ግልጽ ልታደርገው ትችላለህ። አ.ት: “በቅርንጫፎቹ ላይ የሚቀሩት የወይራ ፍሬዎች መጻተኞች፣ ወላጆቻቸውን ያጡና መበለቶች ለቅመው የሚወስዷቸው ናቸው” (See: Ellipsis)

Deuteronomy 24:21

የቀረው ለመጻተኞች፣ አባቶቻቸውን ላጡ ልጆች እና ለመበለቶች ይሆናል
“የማትለቅመው የወይን ፍሬ ለመጻተኛው፣ አባቱን ላጣውና ለመበለቲቱ ይሆናል”

ለመጻተኞች፣ አባቶቻቸውን ላጡ ልጆች እና ለመበለቶች ይሆናል
እነዚህ የሚያመለክቱት የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ነው። አ.ት: “ለመጻተኞች፣ ወላጆቻቸውን ላጡና ለመበለቶች” (See: Generic Noun Phrases)

ትዝ ይበልህ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት: “አስታውስ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 25

1 በሰዎች መካከል ጠብ ቢነሣ ወደ ፍርድ አደባባይ ቢሄዱ፥ ዳኞች ተበዳይን ነጻ፥ በዳይን ግን ጥፋተኛ፥ በማድረግ የፍርድ ውሳኔ ይስጡ። **2** በደለኛው ሰው መገረፍ የሚገባው ሆኖ ከተገኘ፥ ዳኛው መሬት ላይ ያጋድመው፥ ለጥፋቱ ተመጣጣኝ የሆነ ግርፋት እርሱ ባለበት ይገረፍ። **3** ሆኖም ግርፋቱ ከአርባ የሚበልጥ አይሁን፥ ከዚህ ካለፈ ግን እስራኤላዊ ወንድማችሁ በፊታችሁ የተዋረደ ይሆናል። **4** እህል እያበራየ ያለውን በሬ አፉን አትሰሩ። **5** ወንድማማቾች በአንድነት ቢኖሩና፥ ከእነርሱ አንዱ ወንድ ልጅ ሳይወልድ ቢሞት፥የሟቹ ሚስት ከቤተ ሰቡ ውጭ ባል ማግባት የለባትም። የባሏ ወንድም ይውሰዳትና ያግባት፤ የዋርሳነት ግዴታውንም ይፈጽምላት። **6** በመጀመሪያ የምትወልደውም ልጅ ስሙ ከእስራኤል ፈጽሞ እንዳይጠፋ በሟች ወንድሙ ስም ይጠራ። **7** ሆኖም ግን አንድ ሰው የወንድሙን ሚስት ለማግባት ባይፈልግ ሴትዮዋ በከተማዋ በር ወዳሉት ሽማግሌዎች ሄዳ የባለቤቴ ወንድም የወንድሙን ስም በእስራኤል ለማስጠራት አልፈለገም፥ የዋርሳነት ግዴታውንም አልፈጸመልኝም ትበላቸው። **8** ከዚያም የከተማው ሽማግሌዎች ያን ሰው ጠርተው ያነጋግሩት እርሱም እርሷን ላገባት አልፈልግም ብሎ በሐሳቡ ቢጸና፥ **9** የወንድሙንም ሚስት በሽማግሌዎች ፊት ወደ እርሱ ቀርባ፥ የአንድ እግሩን ጫማ በማውለቅ በፊቱ ላይ ትትፋበትና የወንድሙን ቤት ማይሠራ ሰው ላይ እንዲህ ያለው ድርጊት ይፈጸምበታል ትበል። **10** የዚያም ሰው የዘር ሐረግ በእስራኤል ዘንድ ጫማው የወለቀበት ቤት ተብሎ ይታወቃል። **11** ሁለት ሰዎች ቢደባደቡ፥ የአንደኛው ሚስት ባሏን ከደብዳቢው እጅ ለማስጣል መጥታ እጇን ዘርግታ ብልቱን ብትይዘው **12** ፥እጇን ቁረጡ አትራሩላት። **13** በከረጢታችሁ ውስጥ ከባድና ቀላል የሆኑ ሁለት የተለያዩ ሚዛኖች አይኑሩአችሁ። **14** በቤታችሁም ውስጥ ትልቅና ትንሽ የሆኑ ሁለት የተለያዩ መስፈሪያዎች አይኑሩአችሁ። **15** እግዚአብሔር አምላካችሁ በሚሰጣችሁ ምድር ዕድሜአችሁ እንዲረዝም ትክክለኛና የታመነ ሚዛንና መስፈሪያ ይኑራችሁ። **16** እግዚአብሔር አምላካችሁ እንዲህ ያሉትን ጽድቅ ያልሆነ ነገሮች የሚፈጽመውንና የሚያምታታውን ሁሉ ይጸየፈዋልና። **17** ከግብፅ በወጣችሁ ጊዜ አማሌቅ በመንገድ በእናንተ ላይ ያደረጉባችሁን አስታውሱ፤ **18** ደክማችሁና ዝላችሁ በነበራችሁበት ጊዜ በጉዞ ላይ አግኝቶአሁ ከኋላ ያዘግሙ የነበሩትን ሁሉ ገደሉ፤ እግዚአቤርንም አልፈሩም። **19** እግዚአብሔር አምላካችሁ ርስት አድርጎ በሚሰጣችሁ ምድር ዙሪያ ካሉት ጠላቶቻችሁ ሁሉ ባሳረፋችሁ ጊዜ ከሰማይ በታች ያለውን የአማሌቅን መታሰቢያ ደምስሱ፤ ከቶ እንዳትረሱ!

Deuteronomy 25:1

በደለኛው ሰው መገረፍ የሚገባው ከሆነ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት: “ዳኛው በደለኛውን ሰው እንዲገርፉት ካዘዛቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በፊቱ ይገረፍ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት: “ሲገርፉት ያያቸዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ስለ ወንጀሉ የታዘዘውን የግርፋት ቁጥር
“ስላደረገው ክፉ ሥራ ባዘዘው ቁጥር ልክ”

Deuteronomy 25:3

ዳኛው አርባ ግርፋት ሊሰጠው ይችላል
“ዳኛው በደለኛውን ሰው 40 ጊዜ እንዲገርፉት ሊነግራቸው ይችላል” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ሆኖም ከዚያ ቁጥር መብለጥ አይኖርበትም
“ሆኖም ዳኛው ከ40 ጊዜ በላይ እንዲገረፍ ማዘዝ አይኖርበትም”

ከዚያ ቁጥር ካለፈና ተጨማሪ ግርፋት የሚገርፈው ከሆነ
“ዳኛው ከ40 ጊዜ በላይ እንዲገርፉት የሚያዛቸው ከሆነ”

ያን ጊዜ እስራኤላዊው ወንድምህ በዐይኖችህ ፊት የተዋረደ ይሆናል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት: “ያን ጊዜ በእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ፊት እስራኤላዊውን ወንድምህን ያዋርደዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በዐይኖችህ ፊት የተዋረደ ይሆናል
እዚህ ጋ ስለሚያዩት ነገር አጽንዖት ለመስጠት ሕዝቡ በ “ዐይኖቻቸው” ተወክለዋል። አ.ት: “ተዋርዷል፣ እናንተ ሁላችሁም አይታችሁታል” (See: Synecdoche)

Deuteronomy 25:5

ወንድማማቾች በአንድነት የሚኖሩ ከሆነ
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፣ 1) “ወንድማማቾች በአንድ ንብረት ላይ የሚኖሩ ከሆነ” ወይም 2) “ወንድማማቾች ተቀራርበው የሚኖሩ ከሆነ”

ያን ጊዜ የሟቹ ሰው ሚስት ሌላ ሰው ማግባት አይኖርባትም
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት: “ያን ጊዜ የሟች ቤተሰቦች መበለቲቱ ሌላ ሰው እንድታገባ መፍቀድ የለባቸውም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የዋርሳነቱን ተግባር ይፈጽምላት
“የሟች ወንድም እንዲያደርግ የሚጠበቅበትን ያድርግ”

በሟች ወንድሙ ስም ይጠራል
“ስም” የሚለው ቃል የሰውየውን የቤተሰብ ሐረግ የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት: “የሟች ወንድሙ የቤተሰብ ሐረግ ይቀጥላል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ስሙ ከእስራኤል እንዳይጠፋ
“ስም” የሚለው ቃል የሰውየውን የቤተሰብ ሐረግ የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት: “የቤተሰቡ ሐረግ ከእስራኤል እንዳይጠፋ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 25:7

ወደ በሩ ወደ ሽማግሌዎች ትሂድ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት: “ሽማግሌዎች በጉዳዮች ላይ ወደሚዳኙበት ወደ ከተማው በር ትሂድ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ለወንድሙ ስም ለማቆም እምቢ ቢል
እዚህ ጋ “ስም” የሚያመለክተው በተወላጆቹ አማካይነት የአንድን ሰው መታሰቢያ ነው። አ.ት: “ለወንድሙ ወንድ ልጅ ለመስጠት እምቢ ቢል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የዋርሳነቱን ተግባር አልፈጸመልኝም
“እኔን በማግባት ከዋርሳ የሚጠበቅበትን ተግባር አልፈጸመም”

ልወስዳት አልፈልግም
“ላገባት አልፈልግም”

Deuteronomy 25:9

በሽማግሌዎቹ ፊት ወደ እርሱ ትቅረብ
“በዚያ ያሉ ሽማግሌዎች እያዩአት ተራምዳ ትቅረበው”

የወንድሙን ቤት በማይሠራ
እዚህ ጋ “ቤት” የቤተሰብ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ለወንድሙ ወንድ ልጅ የማይሰጥና የወንድሙን የቤተሰብ ሐረግ የማያስቀጥል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ስሙ በእስራኤል ይጠራል
“በእስራኤል ያሉ ሰዎች ቤተሰቡን እንደ -- ያውቃሉ”

ጫማው እንዲወልቅ የተደረገበት ሰው ቤት
እዚህ ጋ ጫማ የማውለቁ ምሳሌ ወንድምየው ከሟች ወንድሙ ሀብት ምንም እንደማይወስድ ማሳያ ነው። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ደግሞም ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል. አ.ት፡ “የወንድሙ ሚስት ጫማውን ከእግሩ ያወለቀችበት ሰው ቤት” ወይም “የወንድሙን ሚስት ያላገባው ሰው ቤተሰብ” ወይም “ሁሉም ሰው የሚንቀው ቤተሰብ” ወይም “አሳፋሪው ቤተሰብ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 25:11

ከደብዳቢው እጅ
እዚህ ጋ “እጅ” ኃይልን ወይም ቁጥጥርን ያመለክታል። አ.ት፡ “ደብዳቢው እንደ ገና እንዳይደበድበው” ወይም “እርሱን ከሚመታው ሰው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ዐይንህ አይራራ
እዚህ ጋ “ዐይን” ማለት ሙሉውን ሰው ነው። አ.ት፡ “አትዘንላት” ወይም “ምሕረት አታድርግላት” (See: Synecdoche)

Deuteronomy 25:13

በቦርሳህ ውስጥ ትልቅና ትንሽ የሆኑ የተለያዩ ሚዛኖች አይኑሩህ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። በተጨማሪም የሚታወቀውን መረጃ ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። አ.ት፡ “ነገሮችን በምትገዛበት ጊዜ ከምትናገረው የሚበልጥን ሚዛን በመጠቀም፣ በምትሸጥበት ጊዜ ደግሞ ከምትናገረው ያነሰ ሚዛን በመጠቀም ሰዎችን አታጭበርብር” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information and Ellipsis)

ሚዛኖች
ሚዛኖች አንድ ነገር ምን ያህል እንደሚከብድ ለማወቅ መለኪያው ላይ የሚቀመጡ ድንጋዮች ነበሩ

በቤትህ ውስጥ ትልቅና ትንሽ የሆኑ የተለያዩ ሚዛኖች አይኑሩህ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ በተጨማሪም፣ የሚታወቀውን መረጃ ግልጽ ልታደርገው ትችላለህ። አ.ት፡ “ነገሮችን በምትገዛበት ጊዜ ከምትናገረው የሚበልጥ መለኪያ በመጠቀም፣ እንዲሁም በምትሸጥበት ጊዜ ከምትናገረው የሚያንስ መለኪያ በመጠቀም ሰዎችን ማጭበርበር የለብህም። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information and Ellipsis)

መለኪያዎች
መለኪያ አንድ ነገር ምን ያህል እንደሆነ የሚለካበት ቅርጫት ወይም ሌላ መያዣ ነበር።

Deuteronomy 25:15

ልክና ተገቢ
“ትክክል እና አግባብነት ያለው”

ሚዛን -- መለኪያ
እነዚህን ቃላት በዘዳግም 25:13 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

ቀኖችህ እንዲረዝሙ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ረጅም ዘመን እንድትኖር” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

እንደዚህ ያሉትን ነገሮች ለሚያደርጉ፣ በእምነት አጉዳይነት ለሚያደርጉ ሁሉ
“የተለያየ መጠን ያላቸውን ሚዛኖችና መለኪያዎችን በመጠቀም ሰዎችን የሚያጭበረብሩ ሁሉ”

Deuteronomy 25:17

አማሌቅ ያደረገብህ ትዝ ይበልህ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን “አማሌቅ” አማሌቃውያን ሰዎችን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “አማሌቃውያን ያደረጉብህን አስታውስ” (የአነጋገር ዘይቤ፣ ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በወጣህ ጊዜ
እዚህ ጋ “አንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)

በመንገድ ላይ እንዴት እንደተገናኘህ
“በጉዞ ላይ እያለህ እንዴት እንደተገናኙህ”

ከኋላ የነበራችሁትን አጠቋችሁ
“የኋላ መስመር ላይ የነበሩትን ሰዎችህን አጠቃ”

ከበስተኋላህ የደከሙትን ሁሉ
“በኋለኛው መስመር ላይ ደካሞች የነበሩትን ሰዎች በሙሉ”

ዝለትና ድካም
እነዚህ ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ ሕዝቡ ምን ያህል ደክመው እንደነበሩ አጽንዖት ይሰጣሉ። አ.ት፡ “ደክመውና ዝለው” (See: Doublet)

ለእግዚአብሔር ክብርን አልሰጠም
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “የእግዚአብሔርን ቅጣት አልፈራም” ወይም “እግዚአብሔርን አላከበረም” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

የአማሌቅን መታሰቢያ ከሰማይ በታች ደምስስ
“ከእንግዲህ ማንም እንዳያስታውሳቸው አማሌቃውያንን በሙሉ ግደላቸው”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 26

1 እግዚአብሔር አምላካችሁ ርስት አድርጎ ወደ ሚሰጣችሁ ምድር ስትገቡ፥ ስትወርሱአትና ስትኖሩባት፤ 2 እግዚአብሔር አምላካችሁ ከሚሰጣችሁ ምድር
ከሁሉም የመጀመሪያ ፍሬ ውሰዱት። ከዚያም በቅርጫት ውስጥ አድርጉትና እግዚአብሔር አምላካችሁ ለስሙ ማደሪያ እንዲሆን ወደሚመርጠው ስፍራ ሂዱ። 3
በዚያን ወቅት ወደ ሚያገለግለው ካህን ሄዳችሁ ፦ እግዚአብሔር ለእኛ ሊሰጠን ለአባቶቻችን ወደ ማለላቸው ምድር እንደ ገባሁ ዛሬ እግዚአብሔር አምላካችሁን
ለማምስገን እቀባለለሁ በለው። 4 ካህኑም ቅርጫቱን ከእጃችሁ ተቀብሎ በእግዚአብሔር በአምላካችሁ መሠዊያ ፊት ለፊት ያኖረዋል። 5 እናንተም
በእግዚአብሔር በአምላካችሁ ፊት እንዲህ ብላችሁ ትናገራላችሁ፦ አባቴ ዘላን ሶርያዊ ነበር፤ ከጥቂት ሰዎችም ጋር ወደ ግብፅ ወረደ፤ በዚያም ተቀመጠ፤ ታላቅ፥
ኃያልና ቁጥሩ የበዛ ሕዝብ ሆነ። 6 ግብፃውያንም በመጥፎ ሁኔታ እንገላቱን፥ አሠቃዩንም። እንደ ባሪያ ከባድ ሥራ እንድንሠራ አደረጉን። 7 ከዚያ በኋላ ወደ
አባቶቻችን አምላክ ወደ እግዚአብሔር ጮኽን፥ እርሱም ጩኸታችንን ሰማ፤ መከራችንን፣ ድካማችንንና የተፈጸመብንን ግፍ ተመለከተ። 8 ከዚህ የተነሣ
እግዚአብሔር በብርቱ እጅና በተዘረጋው ክንዱ፥ በታላቅ ድንጋጤና ታምራት በምልክትና በድንቅ ከግብፅ አወጣን፤ 9 ወደዚህም ስፍራ አመጣን፥ ማርና ወተት
የምታፈሰውን ይህችን ምድር ሰጠን። 10 እግዚአብሔር ሆይ እነሆ፥ አንተ ከሰጠኸኝ ከምድሪቱ የመጀመሪያ ፍሬ አምጥቻለሁ፤ ቅርጫቱንም በአምላክህ
በእግዚአብሔር ፊት አኑራሃው አምልከው፤ 11 ለአንተና ለቤትህ ባደረገው መልካም ነገር አንተ፥ ሌዋውያንና መጻተኞች በእግአብሔር በአምላክህ ፊት ደስ
ይበላችሁ። 12 የአሥራት ዓመት የሆነውን የሦስተኛውን ዓመት ፍሬ አንድ አሥረኛ ለይታችሁ ካወጣችሁ በኋላ በየከተሞቻችሁ ውስጥ በልተው እንዲጠግቡ፥
ለሌዋዊው፥ ለመጻተኛው፥አባት ለሌለውና ባል ለሞተባቸው ስጡአቸው። 13 ከዚያ በኋላ ለአምላካችሁ ለእግዚአብሔር እንዲህ በል፦ በሰጠኸኝ ትእዛዝ መሠረት
ለእግዚአብሔር የተቀደሰውን ከቤቴ አምጥቼ ለሌዋዊው፥ ለመጻተኛው፥ አባት ለሌለውና ባል ለሞተባት ሰጥቻለሁ። ከትእዛዝህ አልወጣሁም፤ አንዱንም
አልረሳሁም። 14 በሐዘን ላይ ሳለሁ፥ ከተቀደሰው ክፍል ላይ ምንም አልበላሁም ባልነጻሁበትም ጊዜ ከዚህ ላይ ያነሣሁትምና ለሙታን ያቀረብሁት ምንም ነገር
የለም። አምላኬን እግዚአብሔርን ታዝዣለሁ፥ ያዘዝኸኝንም ሁሉ ፈጽሜአለሁ። 15 ከቅዱስ ማደሪያ ሆነህ ከሰማይ ተመልከት፥ ሕዝብህን እስራኤልንና
ለአባቶቻችን በማለህላቸው መሠረት፥ ለእኛ የሰጠኸንን ይህችን ማርና ወተት የምታፈሰውን ምድር ባርክ። 16 እግዚአብሔር አምላካችሁ ይህን ሥርዓትንና ሕግን
ትጠብቁ ዘንድ ዛሬ ያዝዛችኋል፤ እናንተም በፍጹም ልባችሁ በፍጹምም ነፍሳችሁ ትፈጽሙት ዘንድ ተጠንቀቁ። 17 እግዚአብሔር አምላካችሁ እንደሆነ
በመንገዱም እንደምትሄዱ፥ ሥርዓቱን፥ ትእዛዙንና ሕጉን እንደምትጠብቁ እንደምትታዘዙለት በዛሬው ዕለት ተናግራችኋል። 18 እግዚአብሔር በሰጣችሁ ተስፋ
መሠረት እንንተ ሕዝቡና ርስቱ መሆናችሁን ትእዛዙንም ሁሉ እንደምትጠብቁ በዛሬው ዕለት ተናግሮአል፤ 19 ከፈጠራቸው ሕዝቦች ሁሉ በላይ ለማመስገን፥
ለማክበረና ከፍ ለማድረግና በሰጠውም ተስፋ መሠረት ለእግዚአብሔር ለአምላካችሁ ቅዱስ ሕዝብ እንደምትሆኑ ማረጋገጫ ሰጥቶአል።

Deuteronomy 26:1

ከመጀመሪያው ምርትህ ሁሉ ጥቂቱን
“ከምርትህ በኩራት ጥቂቱን” ወይም “ከመጀመሪያው የሰብል ምርትህ ጥቂቱን”። ይህ “መጀመሪያ” የአንድ ደረጃን ማሳያ ቁጥር ነው። (ደረጃን ማሳያ ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 26:5

ቅድመ ቅድም አያቴ ተቅበዝባዥ አራማዊ ነበር
ይህ እስራኤላዊ ወንድ ቅርጫቱን በሚያቀርብበት ጊዜ መናገር የሚኖርበት የዐረፍተ ነገሩ መጀመሪያ ነው።

ተቅበዝባዥ አራማዊ
ይህ የእስራኤላውያኑ ሁሉ ቅድመ ቅድም አያት የነበረውን ያዕቆብን ያመለክታል። እርሱ ለብዙ ዓመታት በሶሪያ በሚገኝ በአራም ናሃሪም ይኖር ነበር።

በዚያ ቆየ
“ቀሪ ሕይወቱን በዚያ ኖሯል”

በዚያ እርሱ -- ሆነ
“እርሱ” የሚለው ቃል “የያዕቆብን ተወላጆች” የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ታላቅ፣ ኃያል
በመሠረቱ እነዚህ ቃላት የሚሉት አንድ ነገር ነው። እስራኤል ብዙና ኃይለኛ ሕዝብ መሆኑ ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ። አ.ት፡ “በጣም ታላቅ” (See: Doublet)

Deuteronomy 26:6

ከፉብን፣ አሰቃዩንም
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚሉት አንድ ነገር ነው። ግብፃውያን የጭካኔ ተግባር እንደ ፈጸሙባቸው አጽንዖት ይሰጣሉ። (See: Doublet)

አደረገብን
እዚህ ጋ “እኛ” የሚያመለክተው በግብፅ ይኖሩ የነበሩትን የእስራኤል ሕዝብ ነው። ተናጋሪው በግብፅ ቢኖርም ባይኖርም ራሱን ከሕዝቡ አንዱ አድርጎ ይጨምራል። (See: Inclusive “We”)

ድምፃችንን ሰማ
እዚህ ጋ “ድምፅ” የሚያመለክተው ሙሉውን ሰው እና ጩኸቱን ወይም ጸሎቱን ነው። አ.ት፡ “ጩኸታችንን ሰማ” ወይም “ጸሎታችንን ሰማ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ስቃያችንን፣ ልፋታችንን እና መጨቆናችንን
“ግብፃውያን ያሰቃዩን የነበረውን፣ ስንሠራው የነበረውን በጣም ከባድ የሆነውን ሥራ እና ግብፃውያኑ ይጨቁኑን የነበረውን”

Deuteronomy 26:8

እግዚአብሔር አመጣን
እዚህ ጋ “እኛ” የሚያመለክተው በግብፅ ይኖሩ የነበሩትን የእስራኤል ሕዝብ ነው። ተናጋሪው በግብፅ ቢኖርም ባይኖርም ራሱን ከሕዝቡ አንዱ አድርጎ ይጨምራል። (See: Inclusive “We”)

በብርቱ እጅ፣ በተዘረጋች ክንድ
እዚህ ጋ “ብርቱ እጅ” እና “የተዘረጋች ክንድ” የእግዚአብሔርን ኃይል የሚያመለክቱ ዘይቤአዊ አነጋገሮች ናቸው። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 4:34 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። አ.ት፡ “ብርቱ ኃይሉን በማሳየት” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በታላቅ ማስደንገጥ
“ያዩአቸውን ሰዎች በሚያስፈሩ ድርጊቶች”

ወተትና ማር የምታፈስ ምድር
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በዘዳግም 6:3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት፡ አ.ት፡ “ብዙ ወተትና ማር የሚፈስባት ምድር” ወይም “ከብት ለማርባትና ለእርሻ ምርጥ የሆነች ምድር”

Deuteronomy 26:10

ከአዝመራው የመጀመሪያውን
“ከአዝመራው የመጀመሪያውን ፍሬ” ወይም “ከአዝመራው የመጀመሪያውን ሰብል”

አስቀምጠው
“ቅርጫቱን አስቀምጠው”

አምላክህ እግዚአብሔር ባደረገልህ መልካም ነገር ሁሉ ደስ ይበልህ
“አምላክህ እግዚአብሔር ስላደረገልህ መልካም ነገሮች ሁሉ ደስ ይበልህ፣ አመስግንም”

Deuteronomy 26:12

በሦስተኛው ዓመት
ይህ “ሦስተኛ” የሦስት ደረጃን አመልካች ቁጥር ነው። የእስራኤል ሕዝብ በየሦስት ዓመቱ ከአዝመራው አንድ አሥረኛውን ለድኾች ይሰጡ ነበር። (ደረጃን አመልካች ቁጥር የሚለውን ተመልከት)

አባቶቻቸውን ያጡ
እነዚህ ሁለቱም ወላጆቻቸው የሞቱባቸውና የሚንከባከባቸው ዘመድ የሌላቸው ልጆች ናቸው።

መበለት
ይህ ማለት ባል የሞተባትና በእርጅናዋ ጊዜ የሚንከባከብ ልጅ የሌላት ሴት ማለት ነው።

በከተማህ በሮች ውስጥ ብላ፣ ጥገብም
እዚህ ጋ “በሮች” ማለት መንደሮች ወይም ከተሞች ማለት ነው። አ.ት፡ “እነዚያ በመንደርህ ውስጥ የሚኖሩት የሚበሉት በቂ ምግብ እንዲኖራችው” (See: Synecdoche)

ከ -- አውጥቻችኋለሁ
እነዚህ እስራኤላዊው እንዲለው የሚጠበቅበት የሌላው አነጋገር የመጀመሪያ ቃላት ናቸው።

አልረሳኋቸውም
ይህ ማለት የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት በሙሉ ታዟል።

Deuteronomy 26:14

በለቅሶዬ ጊዜ ከእርሱ ምንም አልበላሁም
“ባለቀስኩበት ወቅት የትኛውንም አስራት አልበላሁም”

ባልነጻሁበት ጊዜ
እዚህ ጋ “ያልነጻ” ማለት በሕጉ መሠረት ንጹሕ ያልሆነ ሰው ማለት ነው። ንጹሕ ያልሆነ ሰው ለእግዚአብሔር የሚሰጠውን አስራት እንዲነካ እግዚአብሔር አይፈቅድለትም”። የዚህ አነጋገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “በሕጉ መሠረት ንጹሕ ባልነበርኩበት ጊዜ” ወይም “ልነካው እንደማልችል ሕጉ በሚናገርበት ጊዜ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

የአምላኬን የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰምቻለሁ፤ እንዳደርገው ያዘዝከኝን ሁሉንም ነገር ታዝዣለሁ
እዚህ ጋ “የእግዚአብሔር ድምፅ” እግዚአብሔር ለተናገረው የዋለ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ሁለቱም አነጋገሮች ተመሳሳይ ትርጉም ይጋራሉ። ሰውየው የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት በሙሉ ስለመታዘዙ አጽንዖት ይሰጣሉ። (See: (ፈሊጣዊ አነጋገር እና Parallelism የሚለውን ተመልከት))

ከምትኖርበት ከቅዱሱ ስፍራ፣ ከሰማይ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚሉት ተመሳሳይ ነገር ነው። አ.ት፡ “ከቅዱስ ማደሪያህ፣ ከሰማይ” (See: Dou- blet)

ወተትና ማር የምታፈስ ምድር
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በዘዳግም 6:3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ብዙ ወተትና ማር የሚፈስባት ምድር” ወይም “ከብት ለማርባትና ለእርሻ ምርጥ የሆነች ምድር”

Deuteronomy 26:16

በሙሉ ልብህና በሙሉ ነፍስህ
እዚህ ጋ “ልብ” እና “ነፍስ” የአንድን ሰው ውስጣዊ ማንነት የሚመለከቱ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ናቸው። እነዚህ ሁለት ሐረጎች በአንድ ላይ “ሙሉ በሙሉ” ወይም “በቅንነት” ለማለት ጥቅም ላይ ውለዋል። ይህንን በዘዳግም 4:29 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና Doublet የሚለውን ተመልከት)

በመንገዶቹ ትሄድና ሥርዓቱን፣ ትዕዛዛቱን እና ሕጉን ትጠብቅ ዘንድ፣ ድምፁንም ትሰማ ዘንድ
እዚህ ጋ “መሄድ”፣ “መጠበቅ” እና “መስማት” የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። እዚህ ጋ “ድምፅ” የሚያመለክተው እግዚአብሔር የተናገረውን ነው። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ያዘዘው ሁሉ ሙሉ በሙሉ እንድትጠብቅ” (See: Parallelism and Metonymy)

Deuteronomy 26:18

የራሱ ርስት የሆነን ሕዝብ
“የእርሱ የሚሆንን ሕዝብ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 27

1 ሙሴና የእስራኤል አለቆች ሕዝቡን እንዲህ ብለው አዘዙ፦ ዛሬ የማዛችሁን እነዚህን ትእዛዞች ሁሉ ጠብቁ። **2** አምላካችሁ እግዚአብሔር ወደሚሰጣችሁ ምድር ለመግባት ዮርዳኖስን በተሻገራችሁ ጊዜ ጥቂት ትልልቅ ድንጋዮችን አቁሙና በኖራ ለስኑአቸው። **3** የአባቶቻችሁ አምላክ እግዚአብሔር በሰጣችሁ ተስፋ መሠረት ማርና ወተት ወደምታፈሰው፥ አምላካችሁ እግዚአብሔር ወደሚሰጣችሁ ምድር ለመግባት ዮርዳኖስን ስትሻገሩ የዚህን ሕግ ቃላት ሁሉ ጻፉባቸው። **4** ዮርዳኖስን እንደ ተሻገራችሁም ዛሬ ባዘዙአችሁ መሠረት እነዚህን ድንጋዮች በጌባል ተራራ ላይ ትከሉአቸው በኖራም ለስኑአቸው። **5** እዚያም ለእግዚአብሔር ለአምላካችሁ የድንጋይ መሠዊያ ሥራ፥ በድንጋዮቹም ላይ ማናቸውንም የብረት መሣሪያ አታሳርፉባቸው። **6** የእግዚአብሔር የአምላካችሁን መሠዊያ ካልተጠረበ ድንጋይ ሥሩ፥ በላዩም ለእግዚአብሔር ለአምላካችሁ የሚቃጠል መሥዋዕት አቅርቡበት። **7** በላዩም የኅብረት መሥዋዕት ሠዉ፤ ብሉም፤ በእግዚአብሔር በአምላካችሁ ፊት ደስ ይበላችሁ። **8** በድንጋዮቹም ላይ የዚህ ሕግ ቃላት ሁሉ ግልጽ አድርጋችሁ ጻፉባቸው። **9** ሙሴና ሌዋውያን ካህናትም፥ ለእስራኤል ሁሉ እንዲህ ብላችሁ ተናገሩ፦ እስራኤል ሆይ፥ ጸጥ ብላችሁ አድምጡ! እናንተ ዛሬ የእግዚአብሔር የአላካችሁ ሕዝብ ሆናችኋል። **10** ስለዚይም እግዚአብሔር አምላካችሁን ታዘዙ፥ ዛሬ የሚሰጣችሁን ትእዛዙንና ሥርዓቱን ጠብቁ። **11** ሙሴ በዚያኑ ዕለት ሕዝቡን እንዲህ ብሎ አዘዘ፦ **12** ዮርዳኖስን በተሻገራችሁ ጊዜ ስምዖን ፥ ሌዊ፥ ይሁዳ፥ ይሳኮር፥ ዮሴፍና ብንያም ወገኖች ሕዝቡን ለመባረክ በገሪዛን ተራራ ላይ ይቁሙ። **13** ሮቤል፥ ጋድ፥ አሴር፥ ዛብሎን፥ ዳንና ንፍታሌምወገኖች በጌባል ተራራ ላይ ለመርገም ይቁሙ። **14** ሌዋውያን ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ለእስራኤል ሕዝብ ሁሉ እንዲህ ብለው ይናገሩ፦ **15** ጥበበኛ የሠራውን በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊ የሆነውን ምስል የሚቀርጽ ወይም ጣዖትን የሚያበጅ በስውርም የሚያቆም ሰው የተረገመ ይሁን። ሕዝብም ሁሉ፥ አሜን ይበል። **16** አባቱን ወይም እናቱን የሚያቃልል የተረገም ይሁን። ሕዝቡም ሁሉ፤ አሜን ይበል። **17** የባልንጀራውን የድንበር ድንጋይ ከቦታው የሚያንቀሳቅስ የተረገመ ይሁን። ሕዝቡም ሁሉ፤ አሜን ይበል። **18** ዕይነ ስዉርን በተሳሳተ መንገድ የሚመራ የተረገመ ይሁን። ሕዝቡም ሁሉ፤ አሜን ይበል። **19** በመጻተኛው፥ አባት በሌለውና ባል በሞተባት ላይ ፍትሕ የሚያዛባ የተረገመ ይሁን። ሕዝቡም ሁሉ፤ አሜን ይበል። **20** ከአባቱ ሚስት ጋር የሚተኛ የተረገመ ይሁን፤ የአባቱን መኝታ ያረክሳልና። ሕዝቡም ሁሉ፤ አሜን ይበል። **21** ከማናቸውም እንስሳ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚያደርግ የተረገመ ይሁን። ሕዝቡም ሁሉ፤ አሜን ይበል። **22** የአባቱ ወይም የእናቱ ልጅ ከሆነችው ከእኅቱ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚፈጽም የተረገመ ይሁን። **23** ሕዝቡም ሁሉ አሜን ይበል። ከሚስቱ እናት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚፈጽም የተረገመ ይሁን። ሕዝቡም ሁሉ አሜን ይበል። **24** በድብቅ ባልንጀራውን የሚገድል የተረገመ ይሁን። ሕዝቡም ሁሉ አሜን ይበል። **25** ንጹሕውን ሰው ለመግደል ጉቦ የሚቀበል የተረገመ ይሁን። ሕዝቡም ሁሉ አሜን ይበል። **26** የዚህን ሕግ ቃሎች በመፈጸም የማይጸና የተረገመ ይሁን። ሕዝቡም ሁሉ አሜን ይበል።

Deuteronomy 27:1

ዛሬ የማዛችሁን -- ትሻገራላችሁ
ሙሴ እንደ አንድ ቡድን አድርጎ የሚናገረው ለእስራኤላውያን ነው፣ ስለዚህ በሁለቱም አገባብ “አንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)

የማዛችሁን
እዚህ ጋ “እኔ” የሚያመለክተው ሙሴን ነው። ሽማግሌዎቹ ከሙሴ ጋር ተስማምተው በዚያ አሉ፣ ሆኖም ብቸኛው ተናጋሪ እርሱ ነው።

በኖራ ቅባው
ይህ ዓይነቱ በአብዛኛው የኖራ፣ አሸዋና ውሃ ድብልቅ ሲሆን በአንድ ነገር ላይ የሚቀባ ነው። ሲደርቅ አንድ ሰው በላዩ ላይ መጻፍ እንዲችል ጠንካራና ለስላሳ ገጽታ ይኖረዋል። አ.ት፡ “ቅባቸው” ወይም “ልትጽፍባቸው እንዲያስችሉህ አድርግ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ወተትና ማር የምታፈስ ምድር
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በዘዳግም 6፡3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ብዙ ወተትና ማር የሚፈስባት ምድር” ወይም “ለከብት እርባታና ለእርሻ ምርጥ የሆነች ምድር” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 27:4

እኔ የማዝህን -- ስትሻገር -- አስቀምጥ
ሙሴ ለእስራኤላውያን የሚናገረው እንደ ቡድን አድርጎ ነው፣ ስለዚህ “አንተ” የሚልበት አገባብና “አስቀምጥ” የሚለው ትዕዛዝ ብዙ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)

በኖራ ቅባው
“ቅባቸው” ወይም “ልትጽፍባቸው እንዲያስችሉህ አድርግ”። ይህንን በዘዳግም 27፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የጌባል ተራራ
ይህ በሴኬም አቅራቢያ የሚገኝ ተራራ ነው። እርሱን በዘዳግም 11፡29 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ድንጋዮቹን ለመጥረብ ምንም ዓይነት የብረት መሣሪያ አትጠቀም
ይህ ድንጋዮቹን በማለስለስ በተሻለ ሁኔታ በአንድ ላይ እንዲገጣጠሙ ለማድረግ የሚያገለግሉ መሮዎችን ያመለክታል። የዚህ አነጋገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “የመሠዊያውን ድንጋዮች በብረት መሣሪያ አትጥረባቸው” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

Deuteronomy 27:6

ባልተጠረቡ ድንጋዮች
ማንም በብረት መሣሪያ ያልጠረባቸው በተፈጥሮ ቅርጻቸው ያሉ ድንጋዮች

በድንጋዮቹ ላይ ጻፍባቸው
ይህ በኖራ ተቀብተው በጌባል ተራራ ላይ የሚቆሙትን ድንጋዮች ያመለክታል። ይህንን በዘዳግም 27፡12 እና 27፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Deuteronomy 27:9

የአምላክህን የእግዚአብሔርን ድምፅ ታዘዝ
እዚህ ጋ “የእግዚአብሔር ድምፅ” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር እርሱ የሚናገረውን ያመለክታል። አ.ት፡ “አምላክህ እግዚአብሔር የሚናገረውን ታዘዝ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እኔ የማዝህን
ሙሴ እያዘዘ ነው። ሌዋውያኑ ከሙሴ ጋር በመስማማት በዚያ ይገኛሉ፣ ሆኖም የሚናገረው እርሱ ብቻ ነው።

Deuteronomy 27:11

እነዚህ ነገዶች
እዚህ ጋ “ነገዶች” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር የሚያመለክተው የስምዖን፣ ሌዊ፣ ይሁዳ፣ ይሳኮር፣ ዮሴፍ፣ እና ብንያም ነገድ ሕዝቦችን ነው። አ.ት፡ “የእነዚህ ነገዶች ሕዝቦች” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የገሪዛን ተራራ
x

Deuteronomy 27:13

የጌባል ተራራ
ይህንን በዘዳግም 11:29 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

እርግማኖቹን ያውጁ
“እግዚአብሔር እስራኤልን እንዴት እንደሚረግማቸው በታላቅ ድምፅ ተናገር”

Deuteronomy 27:15

በድብቅ የሚያቆም ያ ሰው የተረገመ ይሁን
ይህ ሌዋዊው ለእስራኤል ሕዝብ በሙሉ ጮክ ብሎ የሚያደርገው ንግግር ነው። ይህ ንግግር በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በድብቅ የሚያቆመውን ሰው እግዚአብሔር ይርገመው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የባለሙያ እጅ የሠራውን
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ሰው የሠራው አንድ ነገር” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ባለሙያ
ነገሮችን ጥሩ አድርጎ መሥራት የሚያውቅ ሰው

Deuteronomy 27:16

ሰውየው የተረገመ ይሁን
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ሰውየውን ይርገመው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የባልንጀራውን የድንበር ምልክት የሚያስወግድ
የዚህ አነጋገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “በመሬቱ ድንበር ላይ ያሉትን ምልክቶች በማንሣት ከባልንጀራው መሬት የሚወስድ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

Deuteronomy 27:18

ሰውየው የተረገመ ይሁን
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ይህንን በዘዳግም 27:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ሰውየውን ይርገመው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ለመጻተኛው፣ -- ለመበለቲቱ የሚገባውን ፍትሕ ጉልበቱን ተጠቅሞ የሚነጥቅ
ሙሴ ስለ ፍትሕ የሚናገረው አንድ ጉልበተኛ የሆነ ሰው ደካማ ከሆነው ሰው ላይ በኃይል እንደሚቀማው አካላዊ ቁስ አድርጎ ነው። የአንተ ቋንቋ ምናልባት “ጉልበቱን ተጠቅሞ የሚነጥቅ” ለማለት የሚያስችል አንድ ቃል ይኖረው ይሆናል። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 24:17 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። አ.ት፡ “መጻተኛውን -- መበለቲቱን የሚበድል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አባቶቻቸውን ያጡ ልጆች
እነዚህ ሁለቱም ወላጆቻቸው የሞቱባቸውና የሚንከባከባቸው ዘመድ የሌላቸው ልጆች ናቸው።

Deuteronomy 27:20

ሰውየው የተረገመ ይሁን
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ይህንን በዘዳግም 27:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ሰውየውን ይርገመው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የአባቱን ሚስት
ይህ የአባቱን ሌላኛዋን ሚስት እንጂ የሰውየውን እናት አያመለክትም።

የአባቱን መብት ወስዷል
አንድ ሰው ሚስት በሚያገባበት ጊዜ እርሱ ብቻ ከእርሷ ጋር የመተኛት ሕጋዊ መብት ይኖረዋል። የዚህ አነጋገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “የአባቱን ሕጋዊ መብት ወስዶበታል” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ከየትኛውም ዓይነት እንስሳ ጋር የሚተኛ
የዚህ አነጋገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “ሰው ከሴት ጋር እንደሚተኛ ከየትኛውም ዓይነት እንስሳ ጋር የሚተኛ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

Deuteronomy 27:22

ሰውየው የተረገመ ይሁን
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ይህንን በዘዳግም 27:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ሰውየውን ይርገመው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ከአባቱ ሴት ልጅ ወይም ከእናቱ ሴት ልጅ ጋር
ይህ ማለት አንድ ሰው ከሌላ እናት ወይም አባት ብትወለድም እንኳን ከእህቱ ጋር ሊተኛ አይችልም።

Deuteronomy 27:24

ሰውየው የተረገመ ይሁን
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ይህንን በዘዳግም 27:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ሰውየውን ይርገመው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 27:26

ሰውየው የተረገመ ይሁን
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ይህንን በዘዳግም 27:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ሰውየውን ይርገመው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 28

1 ለእግዚአብሔር ለአምላካችሁ በፍጹም ብትታዘዙና እኔ ዛሬ የምሰጣችሁን ትእዛዘትን ሁሉ በጥንቃቄ ብትከተሉ አምላካችሁ እግዝአብሔር በምድር ላይ ከሚኖሩ
አሕዝብ ሁሉ በላይ ከፍ ያደርጋችኋል። 2 እግዚአብሔር አምላካችሁን ብትታዘዙ እነዚህ በረከቶች ሁሉ የእናንተ ይሆናሉ፤ አይለዩአችሁምም። 3 በከተማና በእርሻ
ትባረካላችሁ። 4 የማሕፀናችሁ ፍሬ፥ የምድራችሁ አዝመራ፥ የእንስሳታችሁ ግልገሎች፥ የክብታችሁ ጥጃ፥ የበግና የፍየል ግልገሎቻችሁም ይባረካሉ። 5
እንቅባችሁና ቡሓቃያችሁም ይባረካሉ። 6 ስትጓዙ ትበረካላችሁ፤ ስትወጡም ትባረካላችሁ። 7 እግዚአብሔር በእናንተ ላይ የሚነሡ ጠላቶቻችሁን በፊታችሁ
እንዲሸነፉ ያደርጋቸዋል፤በአንድ አቅጣጫ ቢመጡባችሁ በሰባት አቅጣጫም ከእናንተ ይሸሻሉ። 8 እግዚአብሔር በጎተራችሁና እጃችሁ በነካው ሁሉ በረከቱን
ይልካል። አምላካችሁ እግዚአብሔር በሚሰጣችሁ ምድር ላይ ይባርካችኋል። 9 የእግዚአብሔር የአምላካችሁ ትእዛዞች የምትጠብቁና በመንገዱ የምትሄዱ
ከሆነ በማለላቸው ተስፋ መሠረት የተቀደሰ ሕዝቡ አድርጎ ያቆማችኋል። 10 ከዚያ የምድር አሕዝብ ሁሉ በእግዚአብሔር ስም መጠራታችሁን ያያሉ፤
ይፈርሁማል። 11 እግዚአብሔርም ሊሰጣችሁ ለአባቶቻችሁ በማለላቸው ምድር የማሕፀናችሁ ፍሬ፥ በእንስሳታችሁ፥ ግልገል፥ በምድራችሁም ሰብል፥
የተትረፈረፈ ብልጽግና ይሰጣችኋል። 12 እግአብሔር ለምድራችሁ በወቅቱ ዝናብን ለመስጠትና የእጃችሁን ሥራ ሁሉ ለመባረክ መልካሙን መዝገብ ሰማዩን
ይከፍትላችኋል፤ እናንተም ለብዙ አሕዛብ ታበድራላችሁ እንጂ ከአንዳቸውም አትበደሩም። 13 እግዚአብሔም ራስ እንጂ ድራት አያደርጋችሁም፤ ዛሬ
የምሰጣችሁን የአምላካችሁ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በጥንቃቄ ብትጠብቁ መቼውንም ቢሆን በላይ እንጂ ፈጽሞ በታች አትሆኑም። 14 ሌሎች አማልክት
በመከተል እነርሱን በማገልገል ዛሬ ከምሰጣችሁ ትእዛዞች ቀኝም ግራም አትበሉ። 15 ነገር ግን ለእግዚአብሔር ለአምላካችሁ ባትታዘዙ በዛሬዋ ዕለት
የምሰጣችሁን ትእዛዙንና ሥርዓቱን ሁል በጥንቃቄ ባትከተሉአቸው እነዚህ ርግማኖች ሁሉ ይደርሱባችኋል፤ ያጥለቀልቁአችኋልም። 16 በከተማ ትረገማላችሁ፤
በእርሻም ትረገማላችሁ። 17 እንቅባችሁና ቡሓቃያችሁ የተረገሙ ይሆናሉ። 18 የማሕፀናችሁ ፍሬ፥ የእርሻህ ሰብል፥ የመንጋችሁ ጥጆች፥ የበግና የፍየል
ግልገሎቻችሁ ይረገማሉ። 19 ስትገቡ ትረገማላችሁ፤ ስትወጡም ትረገማላችሁ። 20 እርሱን በመተው ክፉ ድርጊት ከመፈለጋችሁ የተነሣ እስክትደመስሱ
ፈጥናችሁም እስክትጠፉ ድረስ እጃችሁ በነካው ሁሉ ላይ እግዚአብሔር ርግማንን መደናገርንና ተግሣጽን ይሰድባችኋል። 21 እግዚአብሔር ልትወርሱአት
ከምትገቡባት ምድር ላይ እስኪያጠፋችሁ ድረስም በደዌ ይቀሥፋችኋል። 22 እግዚአብሔር እስክትጠፉ ድረስ በሚቀሥፍ ደዌ ትኩሳትና ዕባጭ ኃይለኛ
ሙቀትና ድርቅ ዋግና አረማሞ ይመታችኋል። 23 ከራሳችሁ በላይ ያለው ሰማይ ናስ ከእግራችሁ በታች ያለው ምድርም ብረት ይሆናል። 24 እግዚአብሔር
የምድራችሁን ዝናብ ወደ አቧራነትና ወደ ትቢያነት ይለወጠዋል፤ ይህም እስክትጠፉ ድረስ ከሰማይ ይወርድባችኋል። 25 እግዚአብሔር በጠላቶቻችሁ ፊት
እንድትሸነፉ ያደርጋችኋል፤ በአንድ አቅጣጫ ትመጣበቸዋላችሁ ነገር ግን በሰባት አቅጣጫ ከፊታቸው ትሸሻላችሁ ለምድር መንግሥታትም ሁሉ መሸማቀያ
ትሆናላችሁ። 26 ሬሳችሁ ለሰማይ አሞሮችና ለምድር አራዊት ሲሳይ ይሆናል፤ በማስፈራራትም የሚያባርሩአቸው አይኖርም። 27 እግዚአብሔር በማትድኑበት
በግብፅ ብጉጅ፥ በእባጭ በሚመግል ቁስልና በእከክ ያሠቃያችኋል። 28 እግዚአብሔር በእብደት፥ በዕውርነትና ግራ በማጋባት ያስጨንኣቃችል። 29 በእኩለ
ቀን በጨለማ እንዳለ ዕውር በዳበሳ ትሄዳላችሁ። የምታደርጉት ሁሉ አይሳካላችሁም። በየዕለቱ ትጨቆናላችሁ፤ ትመዘበራላችሁም፤ የሚታደጋችሁም አይኖርም።
30 ሚስት ለማግባት ልጃገረድ ታጫላችሁ ሌላው ግን ወስዶ በኃይል ይደፍራታል። ቤት ትሠራላችሁ፤ ግን እናንተ አትኖሩበትም። ወይን ትተክላላችሁ ፍሬውን
ግን አትበሉም። 31 በሬህ ዐይናችሁ እያየ ይታረዳል፤ ከሥጋውም አንዳች አትቀምሱም። አህያችሁም በግድ ይወሰድባችኋል፤ አትበሉም። በጎቻችሁ
ለጠላቶቻችሁ ይሰጣሉ፤ የሚያሰጥላቸውም አይኖርም። 32 ወዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ለባዕድ ሕብብ ይሰጣሉ፤ እጃችሁንም ለማንሣት እቅም ታጣላችሁ፤
ይመጣሉ፤ በማለትም ዐይኖቻችሁ ሁልጊዜ እነርሱን በመጠባበቅ ይደክማሉ። 33 የምድራችሁንና የድካማሁን ፍሬ ሁሉ የማታውቁት ሕዝብ ይበላዋል፤ 34
ሁልጊዜ በጭቆናና በጫን ትኖራላችሁ፤ በምታዩት ሁሉ ትጃጀላላችሁ። 35 እግዚአብሔር ከእግራችሁ ጥፍር እስከ ራስህ ጠጉር በሚወርር ሊድን በማይችልና
በሚያሠቃይ ቁስል ጉልበታችሁንና እግራችሁን ይመታችኋል። 36 እግዚአብሔር እናንተንና በላያችሁ ያነገሣችሁትን ንጉሥ፥ እናንተና አባቶቻችሁ ወደ ማታውቁት
ሕዝብ ይወሰዳችኋል፤ ከዚያም ከእንጨትና ከድንጋይ የተሠሩ ሌሎች አማክልትን ታመልካላችሁ። 37 እግእብሔር እንድትገቡ በሚመራችሁ ምድር ለአሕዛብ
ሁሉ መሸማቀቂያ ማላገጫና መዘባበቻ ትሆናላችሁ። 38 በእርሻ ላይ ብዙ ዘር ትዘራላችሁ አንበጣ ስለሚበላው የምትሰበስቡ ጥቂት ይሆናል። ወይን
ትተክላላችሁ ትንከባከበዋላችሁ፤ 39 ነገር ግን የወይን ጠጁን አትጠጡም ዘለላውንም አትሰበስቡም። 40 በአገራችሁ ምድር ሁሉ የወይራ ዛፍ ይኖራችኋል፤
ፍሬው ስለሚረግፍባችሁ ግን ዘይቱን አትቀቡም። 41 ወንዶችንና ሴቶች ልጆቻችሁን ትወልዳላችሁ ነገር ግን በምርኮ ስለሚወሰዱ፤ አብረዋችሁ አይኖሩም። 42
ዛፋችሁንና የምድራችሁን ሰብል ሁሉ አንበጣ መንጋ ይወረዋል። 43 በመካከላችሁ የሚኖር መጻተኛ ከእናንተ በላይ ከፍ ከፍ ሲል እናንተ ግን ዝቅ ዝቅ ትላላችሁ።
44 እርሱ ያበድራችኋል እንጂ እናንተ አታበድሩም። እርሱ ራስ ይሆናል፤ እናንተ ግን ጅራት ትሆናላችሁ። 45 እነዚህ ርግማኖች እስክትጠፉ ድረስ ይከተሉአችኋል፤
ሁሉ በእናንተ ላይ ይመጣሉ፤ ይህም የሚሆነው አምላካችሁን እግዚአብሔርን ስላልታዘዛችሁና የሰጣኋችሁን ትእዛዝና ሥርዓት ስላልጠበቃችሁ
ይወርዱባችኋልም። 46 እነዚህ ርግማኖች እንደ ምልክትና ድንቅ ነገሮች ሆነው በእንንተና በዘራችሁ ለዘላለም ይሆናል። 47 በብልጽግና ጊዜ እግዚአብሔር
አምላካችሁን በደስታና በሐሤት ስላላገለገላችሁ በራብና በጥም በእርዛትና በከፋ ድኽነት 48 እግዚአብሔር የሚያስነሣባችሁን ጠላቶቻችሁን ታገለግላላችሁ፤
እስኪያጠፉአችም ድረስ በአንገታችሁ ላይ የብረት ቀንበር ይጭንባችኋል። 49 እግዚአብሔር እንደ ንስር በፈጣን የሚበሩና ቋንቋውን የማታውቁአችሁን ሕዝብ
እጅግ ሩቅ ከሆነ፥ ከምድርም ዳርቻ ያስነሣነሰባችኋል፤ 50 ሽማግሌ የማያከብር፥ ለወጣትም መልካም ያልሆኑና የሚያስፈራና ጨካኝ ሕዝብ ነው። 51
እስክትጠፉም ድረስ የእንስሳታችሁን ግልገልና የምድራችሁን ሰብል ይበላል፤ እስኪያጠፋችሁም ድረስ እህል፤አዲስ የወይን ጠጅና ዘይት የመንጋችሁን ጥጃና
የበግና ፍየል መንጋችሁን ግልገል አያስቀሩላችሁም። 52 የምትታመኑባቸውን ታላላቅ የተመሸጉ ቅጥሮች እስኪወድቁ ድረስ በመላው አገራችሁ ያሉትን
ከተሞቻችሁን ሁሉ ይከባል፤ አምላካችሁ እግዚአብሔር በሚሰጥጣችሁምድር ያሉትን ከተሞች በሙሉ ይወራቸዋል። 53 ጠላቶቻችሁ ከበው
በሚያስጨንቁአችሁ ጊዜ ከሥቃይ የተነሣ አምላካችሁ እግዚአብሔር የሰጣችህን የአብራካችሁ ፍሬ የሆኑትን የወንዶችና የሴቶች ልጆቻችሁን ሥጋ ትበላላችሁ።
54 ሌላው ይቅርና በመካከላችሁ በጣም ደግና ርኅሩኅ የሆነው ሰው እንኳ ለገዛ ወንድሙ ወይም ለሚወዳት ሚስቱ ወይም ለተረፉት ልጆቹ አይራራላቸውም። 55
ከሚበላው ከልጆቹ ሥጋ ላይም ቅንጣት ያህል እንኳ ከእነርሱ ለአንዱ አያቀምስም፤ ከተሞቻችሁ ሁሉ በመከበባቸው ጠላቶቻችሁ ከሚያደርሱባችሁ ሥቃይ
የተነሣ ለእርሱ የቀረለት ይህ ብቻ ነውና። 56 በመካከላችሁ ተመቻችታና ተቀማጥላ የምትኖር ከልስላሴና ከቅምጥልነት የተነሣ እግሯን አፈር ነክቶት የማያውቅ
ሴት የምትወደውን ባሏን፥ የገዛ ወንድና ሴት ልጆቿን ትንቃለች። 57 ከማሕፀኗ የወጣውን የምትወልዳቸውን ሕፃናት ትጠየፋለች፤ በመከራው ወቅት ጠላቶቻችሁ
ከተሞቻችሁን ከበው በሚያስጨንቁአችሁ ጊዜ ሌላ የሚበላ ስለማይኖር እነርሱን ደብቃ ትበላለች። 58 በዚህ መጽሐፍ የተጻፉትን የዚህን ሕግ ቃሎች ባትከተሉና
የተከበረውና አስፈሪ የሆነውን የአምላካችሁን 59 የእግዚአብሔርን ስም ባታከብሩ እግዚአብሔር አስፈሪ መቅሠፍት፥ አስጨናቂና ለብዙ ጊዜ የሚቋይ መዓት
አሠቃቂና በቀላሉ የማይወገድ ደዌ በእናንተና በዘሮቻችሁ ላይ ይልክባችኋል። 60 የምትፈሩአችሁንም የግብፅ በሽታዎች ሁሉ ያመጣባችኋል፤ በእናንተም ላይ
ይጣበቃሉ። 61 ደግሞም እግዚአብሔር በዚህ የሕግ መጽሐፍ ያልተጸፈውን ማንኛውንም ዓይነት ደዌና መከራ እስክትጠፉ ድረስ ያመጣባችኋል። 62

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለአምላካችሁ ለእግዚአብሔር ስላልታዘዝችሁ እንደ ሰማይ ከዋክብት በዝታችሁ ቢሆን እንኳ እናንተ ጥቂት ብቻ ትቀራላችሁ። **63** እግዚአብሔር ለእናንተ መልካም በማድረግና ቁጥራችሁን በማብዛት ደስ እንዳተሰኘ ሁሉ ፤ እናንተን በመደምሰስና በማጥፋት ደስ ይለዋል። ከምትወርሱዋት ምድር ትነቀላላችሁ። **64** ከዚያም እግዚአብሔር ከአንዱ የምድር ዳርቻ እስከ ሌላው ዳርቻ በሕዝቦች ሁሉ መካከል ይበትናችኋል። በዚያም አባቶአችሁ የማታውቋቸውን ከእንጨትና ከድንጋይ የተሠሩ ሌሎች አማልክትን ታመልካላችሁ። **65** በእነዚያ ሕዝቦች መካከል ዕረፍት አታገኙም፤ ለእግራችሁም ጫማ ማረገጫ አይኖርም፤ እዚያም እግዚአብሔር የሚጨነቅ አእምሮ፥ የሚደክም ዐይንና ተስፋ የሚቋርጥ ልብ ይሰጣችኋል። **66** ዘመናችሁን በሙሉ ቀንና ሌሊት በፍርሃት እንደ ተዋጣችሁ ሕይወትታችሁ ዘወትር በሥጋት ትኖራላችሁ። **67** ልባችሁ በፍርሃት ከመሞላቱና ዐይናችሁ ከሚያየው ነገር የተነሣ ሲነጋ ምነው አሁን ሲመሽ ፥ደግሞ ምነው አሁን በነጋ ትላላችሁ። **68** ዳግመኛ አትመለሱባትም ባልሁ መንገድም እግዚአብሔር በመርከብ ወደ ግብፅ ይመልሳችኋል። እዚያም እንደ ወንድና ሴት ባሪያ ለጠላቶቻችሁ ለመሸጥ ራሳችሁን ታቀርባላችሁ የሚገዛችሁ ግን አይኖርም።

Deuteronomy 28:1

ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ድምፅ

እዚህ ጋ “የእግዚአብሔር ድምፅ” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር የሚያመለክተው እርሱ የሚናገረውን ነው። አ.ት፡ “አምላክህ እግዚአብሔር ለሚናገረው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ትጠብቀው ዘንድ

“ትታዘዘው ዘንድ”

ከላይ ያደርግሃል

ሙሴ ከፍ ባለ ኮረብታ ላይ በአካል ከፍ እንደ ማለት አስፈላጊ ስለ መሆን ወይም ታላቅ ስለ መሆን ይናገራል። አ.ት፡ “ከ -- ይልቅ በጣም አስፈላጊ ያደርግሃል” ወይም “ከ-- ይልቅ ታላቅ ያደርግሃል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እነዚህ በረከቶች ሁሉ ይመጡብሃል፣ ይደርሱብሃልም

ሙሴ በረከቶችን የሚገልጻቸው በድንገት እንደሚያጠቃቸው ወይም አሳዶ እንደሚይዛቸው ሰው አድርጎ ነው። አ.ት፡ “ፈጽሞ በምትገረምበት እንዲህ ባለ መንገድ እግዚአብሔር ይባርክሃል፣ ይኸውም ልታመልጥ በማትችልበት መልኩ ይባርክሃል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 28:3

ትባረካለህ

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ይባርክሃል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በከተማ - በእርሻ

ይህ ቁንጽል፣ እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ ይባርካቸዋል የሚል ትርጉም አለው። (See: Merism)

የአካልህ ፍሬ፣ የመሬትህ ፍሬ፣ የእንስሳህ ፍሬ

“ልጆችህ፣ ሰብልህ፣ እና እንስሶችህ” እነዚህ የአነጋገር ዘይቤዎች እስራኤላውያን ዋጋ ለሚሰጧቸው ነገሮች በሙሉ በቁንጽል አመልካቾች ናቸው። (የአነጋገር ዘይቤ እና Merism የሚለውን ተመልከት)

የእንስሳህ ፍሬ፣ የከብቶችህ ፍሬ፣ እና የበግና የፍየል ጠቦቶችህ

ይህ ጥምረት እግዚአብሔር የእስራኤላውያንን እንስሶች እንደሚያበዛቸውና እንደሚያበረታቸው በሦስት መንገድ መናገሪያ ነው። አ.ት፡ “የከብቶቻችሁ ጥጃዎች እና የበግና የፍየል መንጋ ጠቦቶቻችሁ ከእንስሶቻችሁ ሁሉ ጋር” (See: Doublet)

Deuteronomy 28:5

ይባረካሉ

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ይባርካል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ቅርጫትህና ቡሓቃህ

እስራኤላውያን ቅርጫትን ጥራጥሬ ለመሸከም ይጠቀሙበት ነበር። “ቡሓቃ” እንጀራ ለመጋገር ዱቄቱን የሚያዋህዱበት ጎድጎድ ያለ ዕቃ ነው። አ.ት፡ “የምታበቅለው እህል እና የምትበላው ምግብ ሁሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በምትገባበት ጊዜ -- በምትወጣበት ጊዜ

ይህ ጥምረት በሚሄዱበት ቦታ ሁሉ የሚኖራቸውን የሕይወት ተግባራት በሙሉ ያመለክታል። (See: Merism)

Deuteronomy 28:7

በላይህ ላይ የተነሣውን ጠላትህን በፊትህ ተመትቶ እንዲወድቅ ያደርገዋል

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የሚዋጉህን ጠላቶችህን እንድታሸንፋቸው ያደርግሃል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ሆኖም በሰባት መንገድ ከአንተ ይሸሻሉ

“ሆኖም በሰባት አቅጣጫ ከአንተ በሩጫ ይሸሻሉ”

ሰባት መንገድ

ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ትክክለኛው ቁጥር ከሰባት ሊበልጥ ወይም ሊያንስ ይችላል። አ.ት፡ “በብዙ የተለያዩ አቅጣጫዎች” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በረከት በጎተራህ እንዲመጣ እግዚአብሔር ያዘዋል

እግዚአብሔር አንድ ሰው በድንገት እስራኤላውያንን እንዲያጠቃቸው የሚያዝ በሚመስል መልኩ እግዚአብሔር እንደሚባርካቸው ሙሴ ያብራራል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር በሚባርክህ ጊዜ በጎተራህ ባለው ጥራጥሬ ብዛት ትገረማለህ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

እጅህን በምታኖርበት ሁሉ ላይ

ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “በምትሠራው ነገር ሁሉ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 28:9

እግዚአብሔር ለራሱ የተለየ ሕዝብ አድርጎ ያቆምሃል

እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ የራሱ እንዲሆን በተለየ ሁኔታ መምረጡ ሌሎች ሕዝቦች በሙሉ ከሚኖሩበት ስፍራ ልዩ በሆነ ቦታ እግዚአብሔር እንዳስቀመጣቸው ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ለእርሱ የሚሆን ቅዱስ ሕዝብ ያደርግሃል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእግዚአብሔር ስም ተጠርተሃል

እዚህ ጋ “በእግዚአብሔር ስም ተጠርተሃል” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉም የእርሱ መሆን ማለት ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር የራሱ አድርጎ ጠርቶሃል” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Deuteronomy 28:11

በአካልህ ፍሬ፣ በከብቶችህ ፍሬ፣ በመሬትህ ፍሬ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 28፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። አ.ት፡ “በልጆች፣ እንስሳትና ሰብል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ከሰማይ መጋዘኑ
ሙሴ ዝናቡን የሚያስቀምጥባቸው ሕንጻዎች በሚመስሉበት መልኩ ዝናብ ስለሚያዘንቡ ደመናት ይናገራል። አ.ት፡ “ደመናት” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በትክክለኛው ጊዜ
“ሰብሎች በሚፈልጉት ጊዜ”

የእጆችህ ሥራ ሁሉ
“እጅ” የሚለው ቃል የሙሉው ሰው ተምሳሌት ነው። አ.ት፡ “የምትሠራው ሥራ ሁሉ” (See: Synec- doche)

Deuteronomy 28:13

ራስ እንጂ ጅራት አትሆንም
ይህ ዘይቤአዊ አነጋገር የእስራኤልን ሕዝብ እንደ እንስሳ ይገልጸዋል፣ ይኸውም እስራኤላውያን ሁልጊዜ የሌሎች ሕዝቦች መሪዎች ይሆናሉ እንጂ ከቶም አገልጋዮቻቸው ለመሆን ከኋላ አይከተሉም ማለት ነው። እስራኤላውያን በኃይል፣ በገንዘብና በክብር ብልጫ ያላቸው ይሆናሉ። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከላይ ብቻ ይሆናሉ -- ፈጽሞ ከበታች አይሆኑም
እስራኤላውያን በሌሎች ላይ ገዢዎች ይሆናሉ እንጂ ሌሎች አይገዟቸውም።

እኔ አዛችኋለሁ
ሙሴ የሚናገረው ለእስራኤላውያን በሙሉ ነው፣ ስለዚህ “አንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)

እኔ ዛሬ ከማዝህ ቃል ሁሉ ሌሎች አማልክትን ተከትለህ ለማገልገል ወደ ቀኝ ወይም ወደ ግራ ካልተከተልክ
እግዚአብሔርን አለመታዘዝና ሌሎች አማልክትን ማምለክ ልክ አንድ ሰው በአካሉ ከእግዚአብሔር ቃል ተመልሶ በሌላ አቅጣጫ እንደ ሄደ ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “ሌሎች አማልክትን በማገልገል ዛሬ እኔ የማዝህን ባትታዘዝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 28:15

ነገር ግን ባትታዘዝ
እዚህ ጋ ሙሴ ሕዝቡ ባይታዘዙ የሚደርስባቸውን እርግማን መዘርዘር ይጀምራል።

የአምላክህ የእግዚአብሔር ድምፅ
እዚህ ጋ “የእግዚአብሔር ድምፅ” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉሙ እግዚአብሔር የሚናገረው ማለት ነው። አ.ት፡ “አምላክህ እግዚአብሔር የሚናገረው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከዚያም እነዚህ እርግማኖች ሁሉ ይመጡብሃል፣ ይደርሱብሃል
ሙሴ እርግማኖቹን የሚገልጻቸው በድንገት እንደሚያጠቃቸው ወይም አሳዶ እንደሚይዛቸው ሰው አድርጎ ነው። አ.ት፡ “ፈጽሞ በምትደነቅበት ሁኔታ እግዚአብሔር ይረግምሃል፣ ይህም አንተን ከሚረግምበት ከእርግማኑ ማምለጥ በማትችሉበት ሁኔታ ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

ይመጡብሃል፣ ይደርሱብሃል
ይህንን በዘዳግም 28፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Deuteronomy 28:16

የተረገምክ ትሆናለህ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ይረግምሃል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በከተማ -- በእርሻ
የዚህ ጥምረት ትርጉም እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ ይባርካቸዋል የሚል ነው። ይህንን በዘዳግም 28፡3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (See: Merism)

ቅርጫትህና ቡሓቃህ
እስራኤላውያን ቅርጫትን ጥራጥሬ ለመሸከም ይጠቀሙበት ነበር። “ቡሓቃ” እንጀራ ለመጋገር ዱቄቱን የሚያዋህዱበት ጎድጎድ ያለ ዕቃ ነው። ይህንን በዘዳግም 28፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የምታበቅለው እህል እና የምትበላው ምግብ ሁሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 28:18

የተረገመ ይሆናል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ይረግማል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የአካልህን ፍሬ፣ የመሬትህን ፍሬ
ይህ “ልጆችህ፣ ሰብልህ” ለሚለው የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በዘዳግም 28፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የከብትህ፣ የበግና የፍየል ጠቦቶችህ ብዛት
ይህ ጥምረት እግዚአብሔር የእስራኤላውያንን እንስሳ ብዙና ብርቱ እንደሚያደርጋቸው በሁለት መንገድ የተነገረበት ነው። አ.ት፡ “የከብቶቹ ጥጃዎች፣ የበግና የፍየል መንጋው ጠቦቶች” (See: Doublet)

በምትገባበት ጊዜ -- በምትወጣበት ጊዜ
ይህ ጥምረት የሚያመለክተው በሚሄዱበት ቦታ ሁሉ የሚሆነውን የሕይወት ተግባራት በሙሉ ነው። ይህንን በዘዳግም 28፡6 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (See: Merism)

Deuteronomy 28:20

እርግማን፣ መደናገር፣ እና ተግሳጽ
“እልቂት፣ ፍርሀት እና መሳቀቅ”

እጅህን በምታኖርበት ሁሉ ላይ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “በምትሠራው ነገር ሁሉ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

እስክትጠፋ ድረስ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ጠላቶችህ እስኪያጠፉህ ድረስ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ይጣበቅብሃል
“በአንተ ላይ ይኖራል”

እኔን ትተኸኛል
እዚህ ጋ “እኔን” የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይጣበቅብሃል
“በአንተ ላይ ይኖራል”

Deuteronomy 28:22

ተላላፊ በሽታ፣ ትኩሳት፣ በሰውነት መመረዝ
“በሽታና የሚያቃጥል ትኩሳት ያደክምሃል”። እነዚህ ሁሉ የሚያመለክቱት ሰዎች እንዲዳከሙና እንዲሞቱ የሚያደርጋቸውን በሽታ ነው።

በድርቅ
“በዝናብ እጥረት”

ዋግ
በሰብል ላይ የሚበቅል ሻጋታ ሲሆን እንዲበሰብሱ ያደርጋቸዋል

እነዚህ ያሳድዱሃል
ሙሴ በእስራኤላውያን ላይ ስለሚደርስባቸው ክፉ ነገሮች ሲናገር ከእስራኤላውያን በስተኋላ ሆነው በሚያሳድዱ ሰዎች ወይም እንስሶች አስመስሎ ይናገራል። አ.ት፡ “በእነርሱ ምክንያት ትሰቃያለህ” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 28:23

ሰማይ ናስ ይሆናል
ሙሴ ዝናብ ስለማይኖር ሰማዩ እንደ ናስ እንደሚሆን ይናገራል። አ.ት፡ “ሰማይ -- ዝናብን አይሰጥም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ምድር -- ብረት ትሆናለች
ሙሴ ምድር ምንም ሰብል ስለማይበቅልባት እንደ ብረት እንደምትሆን ይናገራል። አ.ት፡ “መሬቱ ላይ ምንም ነገር አይበቅልም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የምድርህን ዝናብ እግዚአብሔር ወደ ትቢያና አቧራ ይለውጠዋል
“እግዚአብሔር በዝናብ ምትክ አሸዋ አዘል ውሽንፍር ይልካል”

እስክትጠፋ ድረስ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እስኪያጠፋህ ድረስ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 28:25

እግዚአብሔር በጠላቶችህ ፊት ተመትተህ እንድትወድቅ ያደርግሃል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ጠላቶችህን መትተው እንዲጥሉህ ያደርጋቸዋል”

በ -- ፊት ተመትተህ እንድትወድቅ
ይህንን በዘዳግም 28፡7 ላይ እንዴት እንደተረግምከው ተመልከት።

በሰባት መንገድ ከእነርሱ ትሸሻለህ
ይህ ማለት እስራኤላውያን ፈርተውና ደንግጠው ከጠላቶቻቸው ይሸሻሉ። የቃላቶቹን ተመሳሳይነት በዘዳግም 28፡7 ውስጥ ተመልከት። (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ሰባት መንገዶች
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “በብዙ የተለያዩ አቅጣጫዎች” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በመንግሥታት ሁሉ መካከል ትቅበዘበዛለህ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የሌሎች ሀገራት ሰዎች ከአንዱ ሕዝብ ወደ ሌላው ያባርሯችኋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 28:27

የግብፅን ዕባጭ
“ግብፃውያንን በረገምኩበት በዚያው የቆዳ በሽታ”

ዕባጭ -- የቆላ ቁስል፣ የደም በሽታና እከክ
እነዚህ ልዩ ልዩ ዓይነት የቆዳ በሽታዎች ናቸው።

ልትድን የማትችልበትን
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ማንም ሊፈውስህ የማይችለውን” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ዐይነ ሥውር በጨለማ በዳበሳ እንደሚሄድ በእኩለ ቀን በዳበሳ ትሄዳለህ
“በእኩለ ቀን እንኳን በዳበሳ እንደሚሄዱ እንደ ዐይነ ሥውራን ትሆናለህ”። እያንዳንዱ በሕይወቱ በሚደሰትበት ጊዜ እንኳን እስራኤላውያን አስቸጋሪ ሕይወት ይኖራቸዋል። (See: Simile)

ሁልጊዜ የተጨቆንክና የተዘረፍክ ትሆናለህ
“የበረቱ ሕዝቦች ሁልጊዜ ይጨቁኑሃል፣ ይዘርፉሃልም”

Deuteronomy 28:30

በዐይንህ ፊት በሬህ ይታረዳል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አንድ ሰው በሬህን ሲያርደው ታያለህ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በፊትህ አህያህ በግድ ይወሰድብሃል፣ አይመለስልህም
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አንድ ሰው አህያህን በጉልበት ይወስድብሃል፣ አይመልስልህምም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በጎችህ ለጠላቶችህ ይሰጣሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በጎችህን ለጠላቶችህ እሰጣቸዋለሁ” ወይም “ጠላቶችህ በጎችህን እንዲወስዱ እፈቅድላቸዋለሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 28:32

ወንዶችና ሴቶች ልጆች ለሌሎች ሕዝቦች ይሰጣሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ወንዶችና ሴቶች ልጆችህን ለሌሎች ሕዝቦች እሰጣቸዋለሁ” ወይም “ጠላቶችህ ወንዶችና ሴቶች ልጆችህን ይወስዷቸዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ዐይኖችህ ቀኑን ሙሉ እነርሱን ይጠባበቃሉ፣ ሆኖም እነርሱን በመናፈቅ ይዝላሉ
እዚህ ጋ “ዐይኖችህ” የሚያመለክተው ሙሉውን ሰው ነው። አ.ት፡ “እነርሱን በመጠባበቅና ዳግመኛ ልታያቸው በመናፈቅ ትደክማለህ” (See: Synecdoche)

ምንም ብርታት በእጅህ ላይ አይኖርህም
እዚህ ጋ “ብርታት በእጅህ ላይ” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር የሚያመለክተው ኃይልን ነው። አ.ት፡ “ስለጉዳዩ አንዳች ለማድረግ ኃይል አይኖርህም” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 28:33

ሀገር
እዚህ ጋ “ሀገር” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር የሀገሩ ሕዝብ ማለት ነው። አ.ት፡ “የሀገሩ ሕዝብ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሁልጊዜ የተጨቆንክና የተረገጥክ ትሆናለህ
“የተጨቆንክ” እና “የተረገጥክ” የሚሉት ቃላት መሠረታዊ ትርጉማቸው አንድ ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሁልጊዜ ይጨቁኗችኋል፣ ይረግጧችኋልም” ወይም “ባለማቋረጥ ይጨቁኗችኋል” (Doublet እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የሚሆነውን በማየት ታብዳለህ
“የምታየው እንድታብድ ያደርግሃል”

ልትድን በማትችልበት
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ማንም መፈወስ በማይችልበት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 28:36

እግዚአብሔር በሚወስድህ ሕዝቦች ሁሉ መካከል ጥላቻ፣ ምሳሌና መሳለቂያ
እዚህ ጋ “ምስሌ” እና “መሳለቂያ” የሚሉት ቃላት በመሠረቱ ትርጉማቸው አንድ ነው። ይህ እንደ አዲስ ዐረፍተ ነገር ተደርጎ መተርጎም ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር በሚልክህ ስፍራ ሕዝቡ የጥላቻ፣ ስለ አንተም ምሳሌና መሳለቂያን ያደርጋል” ወይም “እግዚአብሔር ከጥላቻ የተነሣ ወደሚስቁብህና ወደሚቀልዱብህ ሕዝቦች ይልክሃል” (See: Doublet)

መሳለቂያ
ሰዎች ሌሎችን ለማሳፈር የሚጠቀሙበት ቃል ወይም ሐረግ

Deuteronomy 28:38

ነገር ግን ጥቂት ዘር ትሰበስባለህ
“ነገር ግን በጣም ጥቂት ምግብ ታከማቻለህ”

Deuteronomy 28:40

ነገር ግን ምንም ዘይት በራስህ ላይ አትቀባም
ሰዎች የቆዳቸውን ጤና ለመጠበቅ የወይራ ዘይት ይቀቡ ነበር።

የወይራ ዛፎችህ ፍሬአቸውን ያረግፋሉ
ፍሬው ከመብሰሉ በፊት እንደሚረግፍ ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። አ.ት፡ “ፍሬው ከመብሰሉ በፊት የወይራ ዛፎችህ ፍሬአቸውን ያረግፋሉ” ወይም “የወይራው ፍሬዎች ከመብሰላቸው በፊት ከወይራ ዛፎችህ ላይ ይወድቃሉ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

Deuteronomy 28:42

መጻተኛው -- እርሱ -- ለእርሱ
ይህ ማንነቱ የታወቀ መጻተኛ አይደለም፣ ነገር ግን በጥቅሉ መጻተኞችን ያመለክታል። አ.ት፡ “መጻተኞች የሆኑ -- እነርሱ -- ለእነርሱ” (See: Generic Noun Phrases)

ከአንተ በላይ ከፍ ከፍ ይላል፤ አንተ ራስህ ዝቅ ዝቅ እያልክ ትመጣለህ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ የሚለው ከእስራኤላውያን የበለጠ ኃይል፣ ገንዘብና ክብር መጻተኞች ይኖራቸዋል ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

እርሱ ራስ ይሆናል፣ አንተ ጅራት ትሆናለህ
ይህ ማለት መጻተኞች ከእስራኤላውያን የበለጠ ኃይልና ሥልጣን ይኖራቸዋል። በዘዳግም 28:13 ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 28:45

እነዚህ እርግማኖች ሁሉ እስክትጠፋ ድረስ ይመጡብሃል፣ ያሳድዱሃል፣ ይደርሱብሃልም
ሙሴ እርግማኖችን በድንገት እንደሚያጠቃቸው ወይም አሳዶ እንደሚይዛቸው ሰው አድርጎ ይገልጻቸዋል። ተመሳሳዩን በዘዳግም 28:2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እግዚአብሔር እንደዚህ በሚያስገርምህ መንገድ ይረግምሃል፣ ይህም እንደሚያሳድድህና ሳይረግምህ በማታመልጠው ሁኔታ ይሆናል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ድምፅ
እዚህ ጋ “የእግዚአብሔር ድምፅ” የሚሉት ቃላት እግዚአብሔር ለሚናገረው ፈሊጣዊ አነጋገሮች ናቸው። አ.ት፡ “አምላክህ እግዚአብሔር ለተናገረው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ትዕዛዙንና ሥርዓቱን
“ትዕዛዝ” እና “ሥርዓት” የሚሉት ቃላት “እግዚአብሔር እንድታደርገው ያዘዘህን ሁሉ” ለሚለው ጥምረት ናቸው። (See: Doublet)

Deuteronomy 28:47

በደስታና በልብ ሐሴት
እዚህ ጋ “በደስታ” እና “በልብ ሐሴት” ማለት ትርጉማቸው አንድ ነው። ሕዝቡ እግዚአብሔርን ለማምለክ እጅግ ደስ ይላቸው እንደነበረ አጽንዖት ይሰጣሉ። (See: Doublet)

በአንገትህ ላይ የብረት ቀንበር ያደርጋል
x

Deuteronomy 28:49

ከሩቅ፣ ከምድር ጥግ
ሁለቱም ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ ጠላት ከእስራኤል እጅግ ሩቅ ከሆነ ሀገር እንደሚመጡ አጽንዖት ይሰጣሉ። (See: Doublet)

ከምድር ጥግ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ስለ እርሱ ከማታውቀው ስፍራ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ንስር ወደ ግዳዩ እንደሚበር
ይህ ማለት ጠላት በድንገት ስለሚመጣ እስራኤላውያን ሊያስቆሟቸው አይችሉም። (See: Simile)

አዛውንቶችን የማያከብርና ርኅራኄ የሌለው፣ ቁጡ ፊት ያለው ሀገር
“ሀገር” የሚለው ቃል የዚያን ሀገር ሕዝብ የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ቁጡ ፊት ያለው፣ አዛውንቶችን የማያከብርና ርኅራኄ የሌለው ሕዝብ ሀገር”

እስክትጠፋ ድረስ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እስኪያጠፉህ ድረስ” ወይም “ምንም ነገር እስከማያስቀሩልህ ድረስ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 28:52

አንተን በከተማህ በሮች ሁሉ
እዚህ ጋ “የከተማ በሮች” የሚወክሉት ከተማን ነው። አ.ት፡ “ከተሞችህን” (See: Synecdoche)

የገዛ ሰውነትህን ፍሬ፣ የወንድና የሴት ልጆችህን ሥጋ
እዚህ ጋ “የወንድና የሴት ልጆችህን ሥጋ” የሚለው “የገዛ ሰውነትህን ፍሬ” የሚለውን ዘይቤአዊ አነጋገር ያብራራል። የጠላት ሰራዊት ከተማቸውን ከከበበ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በኋላ ሕዝቡ የገዛ ልጆቻቸውን እስኪበሉ ድረስ ይራባሉ። (ዘይቤአዊ አነጋገር እና Parallelism የሚለውን ተመልከት)

የገዛ ሰውነትህን ፍሬ
ይህ የሚናገረው በወላጆቻቸው ሰውነት የተመረቱ ፍሬዎች በሚመስሉበት ሁኔታ ስለ ልጆች ነው። አ.ት፡ “የገዛ ራሳችሁ ልጆች” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 28:54

በመካከላችሁ ደግና በጣም ርኅሩኅ የሆነው እርሱ
“በመካከላችሁ ደግና በጣም ርኅሩኅ የሆነ ማነው? እርሱም እንኳን--”። ሙሴ የሚለው፣ አንድ ሰው ልጆቻቸውን ይበላሉ ብሎ የሚገምታቸው ብቻ ሳይሆኑ የመጨረሻዎቹ ይሆናሉ ብሎ የሚገምታቸውም እንኳን እነርሱ ልጆቻቸውን ይበላሉ።

የከተማህ በሮች ሁሉ
እዚህ ጋ “የከተማ በሮች” የሚወክሉት ከተሞቹን ራሳቸውን ነው። አ.ት፡ “ከተሞችህ በሙሉ” (See: Synecdoche)

Deuteronomy 28:56

በመካከላችሁ ደግና ርኅሩኅ የሆነች ሴት -- በደግነቷ -- እርሷ
x

Deuteronomy 28:58

የተጻፉትን
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እኔ የጻፍኩትን” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ይህ የአምላክህ የእግዚአብሔር ታላቅና አስፈሪ ስም
እዚህ ጋ “ስም” የተባለው ፈሊጣዊ አነጋገር ራሱን እግዚአብሔርን ያመለክታል። አ.ት፡ “ታላቅና አስፈሪ የሆነው አምላክህ እግዚአብሔር” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር በአንተና በዘርህ ላይ አስከፊ መቅሠፍት ያደርግብሃል
“እግዚአብሔር በአንተና በዘርህ ላይ አስከፊ መቅሰፍት ይልካል” ወይም “እግዚአብሔር አንተንና ዘሮችህን በአስከፊ መቅሰፍቶች እንድትሰቃዩ ያደርጋል”

Deuteronomy 28:60

የግብፅን በሽታዎች ሁሉ በአንተ ላይ ያመጣል
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “እንደገና በግብፅ በሽታዎች እንድትሰቃይ ያደርግሃል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በአንተ ላይ ይጣበቃሉ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “በሽታዎቹ አያቆሙም፣ ደግሞም ማንም ከእነርሱ ሊያድንህ አይችልም” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

እያንዳንዱ ሕመምና ያልተጻፈ መቅሰፍት
እዚህ ጋ “እያንዳንዱ” በአጠቃላይ ሲሆን “ብዙ” ማለት ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እኔ ያልጻፍኳቸው ሌሎች ህመሞችና መቅሰፍቶች እንኳን” (ግነት እና ጥቅል አስተያየት፣ አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እስክትጠፋ ድረስ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እስኪያጠፋህ ድረስ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ትቀራላችሁ -- እንደ -- የነበራችሁት -- አልሰማችሁም
ሙሴ ለእስራኤላውያን እንደ ቡድን አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “አንተ” የሚልበት አገባብ ሁሉ ብዙ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)

እንደ ሰማይ ከዋክበት ብዝታችሁ ነበር
ይህ ማለት ባለፈው ጊዜ ብዙ እስራኤላውያን ነበሩ። (See: Simile)

ለእግዚአብሔር ድምፅ
እዚህ ጋ “የእግዚአብሔር ድምፅ” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር የሚያመለክተው እግዚአብሔር የሚናገረውን ነው። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ለሚናገረው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 28:63

እግዚአብሔር በእናንተ ደስ ብሎት ነበር -- እናንተን በማብዛት -- እንድትደመሰሱና እንድትጠፉ በማድረግ በእናንተ ደስ ይለዋል። -- ትነቀላላችሁ።
ሙሴ ለእስራኤላውያን እንደ ቡድን አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “አንተ” የሚልበት አገባብ ሁሉ ብዙ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)

እግዚአብሔር ለእናንተ መልካም በማድረግና እናንተን በማብዛት ደስ ተሰኝቶባችሁ ነበር
“እግዚአብሔር ለእናንተ መልካም በማድረግና እንድትበዙ በማድረግ ተደስቶ ነበር"

እንድትደመሰሱ በማድረግ በእናንተ ደስ ይለዋል
“እንድትሞቱ በማድረግ ደስ ይለዋል”

ከምትወርሳት ምድር ትነቀላለህ
ሕዝቡ ፍራፍሬ የሆኑ ይመስል እግዚአብሔር እንደ ቁጥቋጦ እንደሚነቅላቸው ለመናገር ሙሴ ዘይቤአዊ አነጋገርን ይጠቀማል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ልትወርሱ ከምትገቡባት ምድር ያስወግዳችኋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በምትሄድበት -- ይበትንሃል -- ታመልካለህ -- የማታውቃቸውን -- አንተም ሆንክ አባቶችህ
ሙሴ ለእስራኤላውያን እንደ ቡድን አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ እዚህ ጋ “አንተ” እና “የአንተ” የሚሉት ቃላት ብዙ ቁጥር ናቸው። (See: Forms of You)

ከአንደኛው የምድር ጫፍ እስከ ሌላኛው የምድር ጫፍ
እነዚህ ሁለት ጽንፎች በአንድነት በምድር ላይ በሁሉም ስፍራ ማለት ነው። አ.ት፡ “በምድር ሁሉ” ወይም “በምድር ሁሉ ላይ” (See: Merism)

Deuteronomy 28:65

ለእግርህ መርገጫ እረፍት አይኖረውም
እዚህ ጋ “ለእግርህ መርገጫ” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ሙሉውን ሰው ነው። አ.ት፡ “የምታርፍበት ቋሚ ቤት ስለማይኖርህ ባለማቋረጥ ትቅበዘበዛለህ” (See: Synecdoche)

በዚያ እግዚአብሔር የሚንቀጠቀጥ ልብ፣ የሚደክም ዐይንና የሚያለቅስ ነፍስ ይሰጥሃል
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “እግዚአብሔር እንድትፈራ፣ ተስፋ እንዳይኖርህና እንድታዝን ያደርግሃል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ሕይወትህ በፊትህ በጥርጣሬ ይንጠለጠላል
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ትኖር ወይም ትሞት እንደሆነ አታውቅም” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 28:67

በልብህ ካለው ፍርሀት የተነሣ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ከሚሰማህ ፍርሀት የተነሣ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ዐይኖችህ ከሚያዩአቸው ነገሮች የተነሣ	ተናግሬ ነበር
እዚህ ጋ “ዐይኖች” የሚያመለክተው ሙሉውን ሰው ነው። አ.ት፡ “እንድታያቸው የማስገድድህን አስፈሪ ነገሮች” (See: Synecdoche and Assumed Knowledge and Implicit Information)	x

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 29

1 እግዚአብሔር በኮሬብ ከገባው ቃል ኪዳን በተጨማሪ በሞዓብ ምድር ከእስራኤላውያን ጋር እንዲያደርግ ሙሴን ያዘዘው የኪዳኑ ቃሎች እነዚህ ናቸው። **2** ሙሴ
እስራኤላውያንን ሁሉ ጠርቶ እንዲህ አላቸው፦ እግዚአብሔር በግብፅ በፈርዖን፥ በሹማምንቱ ሁሉና በመላ አገሩ ያደረተውን ሁሉ ዐይኖቻችሁ አይተዋል። **3**
እነዚያን ከባድ ፈተናዎች ታምራዊ ምልክቶችና ታላቅ ድንቆች በገዛ ዐኖቻችሁ አይታችኋል። **4** ነገር ግን እስከ ዛሬ ድረስ እግዚአብሔር የሚያስተውል አእምሮ
ወይም የሚያይ ዐይን ወይም የሚሰማ ጆሮ አልሰጣችሁም። **5** በምድረ በዳ በመራኋችሁ በእነዚያ አርባ ዓመታት ውስጥ ልብሳችሁ አላረጀም፥ የእግራችሁም
ጫማ አላለቀም፥ **6** ቂጣ አልበላችሁም፥ የወይን ጠጅ ወይም ሌላ የሚያሰክር መጠጥ አልጠጣችሁም፤ ይህን ያደረግሁት እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ
እንደሆንህ ታውቁ ዘንድ ነው። **7** ወደዚህ ስፍራ በደረሳችሁ ጊዜ የሐሴንቦን ንጉሥ ሴዎንና የባሳን ንጉሥ ዐግ ሊወጉን መጡ፤ ሆኖም ድል አደረግናቸው። **8**
ምድራቸውንም ወስደን ለሮቤላውያን ለጋዳውያንና ለምናሴ ነገድ እኩሌታ ርስት አድርገን ሰጠን። **9** እንግዲህ የምታደርጉት ሁሉ እንዲከናወንላችሁ፤ የዚህ ኪዳን
ቃሎች በጥንቃቄ ተከተሉ። **10** እናንተ ሁላችሁ መሪዎቻችሁና አለቆቻችሁ፥ ሽማግሌዎቻችሁና ሹሞቻችሁ እንዲሁም ሌሎች የእስራኤል ሰዎች ሁሉ ዛሬ
በአምላካችሁ በእግዚአብሔር ፊት ቆማችኋል፤ **11** ልጆቻችሁና ሚስቶቻችሁ እንጨታችሁን እየፈለጡ ውሃዎቻችሁንም እየቀዱ በሰፈራችሁ የሚኖሩ
መጻተኞችም አብረአችሁ ቆመዋል። **12** እዚህ የቆማችሁ፥ እግዚአብሔር ዛሬ ከእናንተ ጋር ወደ ሚያደርገውና በመሐላ ወደሚያጸናው ኪዳን፥ከእግዚአብሔር
ከአምላካችሁ ጋር ትገቡ ዘንድ ለእናንተ በሰጣችሁ ተስፋና፥ **13** ለአባቶቻችሁ ለአብርሃም፥ ለይስሐቅና ለያዕቆብ በማለላቸው መሠረት እርሱ አምላካችሁ ይሆን
ዘንድ እናንተም ሕዝቡ መሆናችሁን በዛሬው ዕለት ለማረጋገጥ ነው። **14** እኔም ይህ የቃል ኪዳን የማደርገው ከእናንተ ጋር ብቻ አይደለም፤ **15** አብራችሁን
በእግዚአብሔር በአምላካችን ፊት እዚህ ከቆማችሁት ጋር ብቻ ሳይሆን ዛሬ እዚህ ከሌሉትም ጋር ነው። **16** በግብፅ ምድር እንዴት እንደኖርንና ወደዚህ
ስንመጣም በየአገሮቹ ውስጥ እንዴት እንዳለፍን ራሳችሁ ታውቃላችሁ። **17** በመካከላቸውም አስጸያፊ ነገሮቻቸውን፦ የእንጨትና የድንጋይ፥ የብርና የወርቅ
ጣዖቶቻቸውን አይታችኋል፤ **18** የእነዚህን ሕዝቦች አማልክት ለማምለክ ልቡን ከእግዚአብሔር ከአምላካችን የሚመልስ ወንድ፥ ሴት፥ቤተ ሰብ፥ ወይም ጎሣና
ነገድ ዛሬ ከመካከላችሁ አይገኙ፤ ከመካከላችሁ እንዲህ ያለውን መራራ መርዝ የሚያወጣ ሥር እንዳይኖር ተጠንቀቁ። **19** እንዲህ ያለው ሰው የዚህን ቃል ኪዳን
በሚሰማበት ጊዜ በልቡ ራሱን በመባረክ፦ እንደ ልቤ ግትርነት ብመላለስም እንኳ ሰላም አለኝ ብሎ ያስባል። ይህም እርጥቡን ከደረቁ ጋር ያጠፋል። **20**
እግዚአብሔር ለዚህ ሰው ፈጽሞ ምሕረት አያደርግለትም፥ ቁጣውና ቅናቱ በእርሱ ላይ ይነድበታል፤ በዚህ መጽሐፍ የተጸፉት ርግማን ሁሉ ይወርድበታል፤
እግዚአብሔርም ስሙን ከሰማይ በታች ይደመስሰዋል። **21** በዚህ የሕግ መጽሐፍ በተጻፈው የኪዳኑ ርግማን መሠረት እግዚአብሔር እርሱን ከእስራኤል ነገዶች
ሁሉ ለጥፋት ይለየዋል። **22** የሚቀጥለው ትውልድ ከእናንተ በኋላ የሚተኩት ልጆቻችሁና ከሩቅ አገር የሚመጡ እንግዶች በምድሩቱ የደረሰውን ታላቅ
መቅሠፍትና እግዚአብሔር ያመጣባቸውን በሽታዎች ያያሉ፤ **23** ምድሩቱ በሙሉ የተቃጠለ ጨውና ዲን ዐመድ ትሆናለች፤ አንዳች ነገር አይተከልባት፤ ምንም
ነገር አያቆጠቁጥባትም። የሚያድግ ተክል አይገኝባትም። የምደርስባት ውድመት እግዝክአብሔር በታላቅ ቁጣ እንደ ገለባበጣቸው እንደሰዶምና ገሞራ እንደ
አዳማና ሊባዮ ጥፋት ይሆናል። **24** አሕዛብም ሁሉ፤ እግዚአብሔር በዚች ምድር ላይ ይህን ለምን አደረገባት? ይህ አስፈሪና የሚነድ ቁጣስ ለምን መጣባት?
ብለው ይጠይቃሉ። **25** ሕዝቡም እንዲህ ይላሉ፦ የአባቶቻቸው አምላክ እግዚአብሔር ከግብፅ ምድር ያወጣቸውንና ከእነርሱም ጋር ያደረጉትን ቃል ኪዳን ሕዝቡ
ስለ ተዉ ነው፤ **26** ወጥተውም የማያውቋቸውን እርሱም ያላዘዛቸውን ሌሎችን አማልክት ስለአመለኩአቸውና ስለሰገዱላቸውም ነው። **27** ስለዚህ በዚህ
መጽሐፍ የተጸፈውን ርግማን ሁሉ እስኪያመጣባት ድረስ የእግዚአብሔር ቁጣው በዚህች ምድር ላይ ነደደ። **28** እግዚአብሔር በታላቅ አስፈሪነት፥በቁጣና
በንዴት ከምድራቸው ነቀላቸው፤ ወደ ሌላም ምድር ጣላቸው የሚል ይሆናል። **29** ምስጢር የሆነው ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው፤ የተገለጠው ግን የዚህን
ሕግ ቃል ሁሉ ለዘላለም እንድንተገብረው ዘንድ የኛና የልጆቻችን ነው።

Deuteronomy 29:1

እነዚህ ሙሴ እንዲናገር እግዚአብሔር ያዘዘው ቃሎች ናቸው
ይህ ሙሴ የሚናገረውን ቃል ያመለክታል።

በሞዓብ ምድር
ይህ እስራኤላውያን ወደ ከነዓን ምድር ከመግባታቸው በፊት ከዮርዳኖስ በስተምስራቅ የቆዩበት ስፍራ ነው። “በሞዓብ ምድር እያሉ”

በኮሬብ -- በኪዳኑ ውስጥ ተጨምረው የነበሩት ቃላት
እነዚህ ተጨማሪ ትዕዛዛት በአዲሱ ምድራቸው በሚቀመጡበት ጊዜ ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ኪዳን በተሻለ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲያደርጉት የተሰጣቸው ነበር። እነዚህ አዲስ ትዕዛዛት የሌላ ቃል ኪዳን ሳይሆኑ በመጀመሪያው ኪዳን ላይ ተጨማሪዎች ነበሩ።

Deuteronomy 29:2

እግዚአብሔር በዐይኖቻችሁ ፊት ያደረገውን ሁሉ አይታችኋል
እግዚአብሔር ያደረገውንና እነርሱም ያዩትን እንዲያስታውሱ እግዚአብሔር ይጠብቅባቸዋል። እዚህ ጋ “ዐይኖች” ሙሉውን ሰው የሚወክሉ ሲሆኑ ሰውየው ባየው ነገር ላይ አጽንዖት ይሰጣል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ያደረገውን እንድታዩና እንድታስታውሱ እርሱ ያደረገውን ሁሉ አይታችኋል። (See: Synecdoche)

ዐይኖቻችሁ ያዩአቸው ታላላቅ መከራዎች
እዚህ ጋ “ዐይኖች” ያዩትን እንዲያስታውሱ እግዚአብሔር እንደሚጠብቅባቸው አጽንዖት ይሰጣል። አ.ት፡ “ሕዝቡ በከፍተኛ ሁኔታ መሰቃየቱን እራሳችሁ አይታችኋል” (See: Synecdoche)

ዐይኖቻችሁ
ሙሴ ለእስራኤላውያን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “የአንተ” የሚለው ቃል እዚህ ጋ ነጠላ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)

ምልክቶቹንና እነዚያን ታላላቅ ድንቆች
“ምልክቶች” እና “ድንቆች” የሚሉት ቃላት ሁለቱም የሚያመለክቱት እግዚአብሔር በግብፅ ላይ የላካቸውን መቅሰፍቶች ነው። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ያደረጋቸውን ኃይለኛ ነገሮች ሁሉ” (See: Doublet)

እግዚአብሔር የሚያውቅ ልቦና፣ የሚያይ ዐይን ወይም የሚሰማ ጆሮ አልሰጣችሁም ነበር
ሕዝቡ ልብ፣ ዐይንና ጆሮ አላቸው። ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ካዩትና ከሰሙት እግዚአብሔር ማን እንደሆነ፣ እንዴት እና ለምን እርሱን መታዘዝ እንደሚኖርባቸው እንዲያስተውሉ አላደረጋቸውም ይላል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እንድታውቁ ልብን ሰጥቷችኋል
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ማስተዋል እንድትችሉ አድርጎችኋል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Deuteronomy 29:7

የሐሴቦን ንጉሥ ሴዎን እና የባሳን ንጉሥ ዐግ
እነዚህን ስሞች በዘዳግም 1:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

በእኛ ላይ መጡብን
እዚህ ጋ “በእኛ ላይ” የሚያመለክተው ሙሴንና የእስራኤልን ሕዝብ ነው። (See: Inclusive “We”)

የዚህን ቃል ኪዳን ቃላት ጠብቁ፣ አድርጓቸውም
እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚሉት ተመሳሳይ ነገር ሲሆን ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት መታዘዝ እንዳለባቸው አጽንዖት ይሰጣሉ። አ.ት፡ “የዚህን ቃል ኪዳን ቃሎች ሁሉ ታዘዙ” (See: Parallelism)

Deuteronomy 29:10

በሰፈርህ ውስጥ በመካከልህ -- እንጨትህን -- ውሃህን
ሙሴ ለእስራኤላውያን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “አንተ’ እና “የአንተ” የሚሉት ቃላት እዚህ ጋ ነጠላ ቁጥር ናቸው። (See: Forms of You)

በሰፍርህ ያሉ መጻተኞች፣ ከእርሱም እንጨት የሚቆርጡልህና ውሃ የሚቀዱልህ
በእስራኤላውያን መካከል ብዙ መጻተኞች ነበሩ። አ.ት፡ “በሰፈርህ ውስጥ በመካከልህ የሚኖሩ መጻተኞች፣ ከእነርሱ እንጨት የሚቆርጡልህ ውሃ የሚቀዱልህ” (See: Generic Noun Phrases)

Deuteronomy 29:12

አምላክህ እግዚአብሔር ዛሬ ከአንተ ጋር በመሓላ ወደሚያደርገው ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ለመግባት
“በቃል ኪዳኑ ልትስማማ እና አምላክህ እግዚአብሔር የሚያዝህን ሁሉ ለመታዘዝ እንድትምል”

ለራሱ ሕዝብ
“ለእርሱ ብቻ የሚሆን የሕዝብ ወገን”

Deuteronomy 29:14

እኔ የማደርገውን
x

Deuteronomy 29:17

ዛሬ ከአምላካችን ከእግዚአብሔር ልቡ የሚመለስ
እዚህ ጋ “ልብ” የሚያመለክተው ሙሉውን ሰው ሲሆን “መመለስ” ማለት መታዘዝን ማቆም ነው። አ.ት፡ “ከእንግዲህ አምላካችንን እግዚአብሔርን የማይታዘዝ” (See: Synecdoche)

የትኛውም መራራ መርዝ የሚያበቅል ሥር
ሙሴ በድብቅ ሌላ አምላክ ስለሚያመልክ ሰው ሲናገር እርሱን እንደ ሥር እና ያንን አምላክ ለማገልገል የሚሠራውን ክፉ ሥራና ሌሎችም እንዲያደርጉት የሚያበረታታውን ሰዎችን እንደሚመርዝ መራራ እጽዋት ቆጥሮ ይናገራል።(ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ያ ሰው
በቁጥር 18 የተገለጸው ሰው ነው።

በልቡ ራሱን የሚባርክ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ራሱን እንኳን ደስ ያለህ የሚል” ወይም “ራሱን የሚያበረታታ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በልቤ ግትርነት ብመላለስም
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “እግዚአብሔርን ለመታዘዝ እምቢ እያልኩኝም እንኳን” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ይህ እርጥቡን ከደረቁ ጋር የሚያጠፋ ይሆናል
እዚህ ጋ “እርጥብ” እና “ደረቅ” የሚሉት ቃላት ጻድቅና ክፉ የሆኑትን ሰዎች የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገሮች ናቸው። ይህ “እያንዳንዱን” የሚል ጥምረት ይፈጥራል። አ.ት፡ “ይህ እግዚአብሔር በምድሪቱ የሚኖሩትን ጻድቅና ክፉ የሆኑትን ሁለቱንም ዓይነት ሰዎች እንዲያጠፋቸው ያደርገዋል” (See: (ዘይቤአዊ አነጋገር እና Merism የሚለውን ተመልከት))

እርጥብ -- ደረቅ
እነዚህ ስማዊ ቅጽሎች እንደ ስም ሊተረጎሙ ይችላሉ። አብዛኛውን ጊዜ ምድሪቱ ደረቅ ስለምትሆንና ሰዎች ሰብላቸው እንዲበቅል ዝናብ ስለሚፈልጉ እነዚህ ቃላት “ሕያው - ምውት” ወይም “ጥሩ -- መጥፎ” ለሚሉት ዘይቤአዊ አነጋገሮች ናቸው። አ.ት፡ “እርጥብ ነገሮች -- ደረቅ ነገሮች” ወይም “ጥሩ ሰዎች -- መጥፎ ሰዎች” (ስማዊ ቅጽል እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 29:20

የእግዚአብሔር ቁጣና ቅንዓት ይነዳል
ልክ እሳት በኃይል እንደሚነድ የእግዚአብሔር ቁጣና ቅንዓትም በኃይል ሊነድ ይችላል። አ.ት፡ “የእግዚአብሔር የቅንዓቱ ቁጣ እንደ እሳት ይግላል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የእግዚአብሔር ቁጣና ቅንዓቱ
እዚህ ጋ “ቅንዓት” የሚለው ቃል “የእግዚአብሔርን ቁጣ” ያብራራል። አ.ት፡ “የእግዚአብሔር የቅንዓቱ ቁጣ” (See: Hen- diadys)

የተጻፉትን
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እኔ የጻፍኩትን” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በዚህ መጽሐፍ የተጻፉት እርግማኖች ይመጡበታል
ሙሴ እርግማኖቹን በድንገት በሚያጠቃቸው ሰው መስሎ ይገልጻቸዋል። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 28:15 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር ስሙን ከሰማይ በታች ይደመስሰዋል
ይህ ማለት እግዚአብሔር ሰውየውንና ቤተሰቡን ፈጽሞ ያጠፋቸዋል። ወደፊት ሰዎች አያስታውሱትም። በዘዳግም 7:24 ላይ ተመሳሳይ ሐረግ ይታያል።

Deuteronomy 29:22

የሚመጣው ትውልድ፣ ከእናንተ በኋላ የሚነሡት ልጆቻችሁ
“ከእናንተ በኋላ -- ልጆቻችሁ” የሚሉት ቃላት “የሚመጣው ትውልድ” ማን መሆኑን ይናገራሉ።

በዚህች ምድር ላይ የሆኑት መቅሰፍቶችና እግዚአብሔር እንዲታመሙበት ያደረጋቸው በሽታዎች
“እግዚአብሔር የከነዓንን ምድር በመቅሰፍትና በበሽታ እንዴት እንደረገማት”

ምድሩ ሁሉ ዲንና የሚቃጠል ጨው ሆነው በሚያዩበት ጊዜ
ሰዎች መሬቱ ምንም ነገር እንዳያበቅል ዲንና ጨው ያደርጉበታል። “እግዚአብሔር ምድሪቱን በዲንና በጨው እንዳቃጠላት በሚያዩበት ጊዜ”

ምንም ነገር የማይዘራበት ወይም ፍሬ የማያፈራበት ስፍራ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ማንም ዘር ሊዘራበት የማይችልበትና ሰብሉ ፍሬ የማያፈራበት ስፍራ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሰዶምና ገሞራ እንደ ተገለበጡ
“ተገለበጡ” የሚለው የነገር ስም እንደ አንቀጽ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ሰዶምንና ገሞራን ፈጽሞ እንዳጠፋቸው ጊዜ”

አዳማ እና ሲባዮ
እነዚህ እግዚአብሔር ከሰዶምና ገሞራ ጋር ያጠፋቸው ከተሞች ስሞቻቸው ናቸው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

በንዴቱና በመዓቱ
የነገር ስም የሆኑት “ንዴት” እና “ቁጣ” በመሠረቱ ትርጉማቸው አንድ ነው፣ በመሆኑም እንደ ቅጽላዊ ሐረግ ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “በጣም በተቆጣ ጊዜ” (See: Doublet)

ከሌሎች ሀገሮች ሁሉ ጋር በመሆን --ምንድነው? በማለት ይናገራሉ
ይህ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ከሌሎች ሀገራት ሁሉ ጋር በመሆን እግዚአብሔር በምድሪቱ ላይ ይህንን ለምን እንዳደረገና ይህ የቁጣው ግለትስ ትርጉሙ ምንድነው በማለት ይጠይቃሉ” (ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ የሚለውን ተመልከት)

ከሌሎች ሀገሮች ሁሉ ጋር በመሆን -- ይናገራሉ
“ዘሮቻችሁና የሌሎች ሀገራ ሰዎች ሁሉ -- ይላሉ”

ይህ የታላቅ ቁጣ ግለት ትርጉሙ ምንድነው?
ጸሐፊው በሁለት ቃላት አማካይነት የሚያስተላልፈው አንድ አሳብ ነው። አ.ት፡ “የዚህ አስፈሪ ቁጣ ትርጉሙ ምንድነው?” (See: Hendiadys)

Deuteronomy 29:25

የአባቶቻቸውን አምላክ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ስለተዉ ነው
ይህ “እግዚአብሔር በዚህች ምድር ላይ ይህንን ያደረገው ለምንድነው?” ለሚለው መልስ ነው (ዘዳግም 29:24)። “እስራኤላውያን የቃል ኪዳኑን ተስፋና ሕግ ስላልተከተሉ እግዚአብሔር በምድሪቱ ላይ ይህንን አድርጓል”

ሌሎች አማልክትን አገለገሉ፣ ሰገዱላቸውም
“ሌሎች አማልክትን ታዘዙ፣ አመለኳቸውም”

Deuteronomy 29:27

የእግዚአብሔር ቁጣ በዚህች ምድር ላይ ነዷል
ሙሴ የእግዚአብሔርን መቆጣት ከአንድ እሳት ከሚለኩስ ሰው ጋር ያነጻጽራል። ይህ እግዚአብሔር እርሱን የሚያስቆጣውን የትኛውንም ነገር ስለሚያጠፋበት ኃይሉ አጽንዖት ይሰጣል፤ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር አይችልም። አ.ት፡ “እግዚአብሔር በዚህች ምድር ላይ በጣም ተቆጥቷል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በዚህች ምድር ላይ እንዲያመጣባት
እዚህ ጋ “ምድር” ሕዝቡን የሚወክል ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ያመጣባቸው ዘንድ የዚህ ምድር ሰዎች” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የተጻፉትን
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እኔ የጻፍኩትን” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር ከምድራቸው ነቅሏቸዋል -- ጥሎአቸዋል
እስራኤል እግዚአብሔር ከአትክልት ስፍራ ነቅሎ ከጣለው መጥፎ ተክል ጋር ተነጻጽሯል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ከምድራቸው አስወግዷቸዋል -- እንዲሄዱም አስገድዷቸዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በንዴት፣ በቁጣና በታላቅ መዓት
በመሠረቱ “ንዴት”፣ “ቁጣ” እና “መዓት” የሚሉት ቃላት ትርጉማቸው ተመሳሳይ ሲሆን በእግዚአብሔር ቁጣ ታላቅነት ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ። አ.ት፡ “እጅግ ታላቅ በሆነ ቁጣው” ወይም “እጅግ ስለተቆጣ” (See: Doublet)

Deuteronomy 29:29

ምስጢር የሆኑት ነገሮች የአምላካችን የእግዚአብሔር ብቻ ናቸው
“አምላካችን እግዚአብሔር ያልገለጣቸውና እርሱ ብቻ የሚያውቃቸው አንዳንድ ነገሮች”

የተገለጡት
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እርሱ የገለጣቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የዚህን ሕግ ቃሎች በሙሉ እንድናደርጋቸው
x

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 30

1 በፊታችሁ ያስቀመጥሁት ይህ በረከትና መርገም ሁሉ በእናንተ ላይ ሲመጣና አምላካችሁ እግዚአብሔር በትኖአችሁ ከምትኖሩበት አሕዛብ መካከል
ሆናችሁ፤ **2** ወደ ልባችሁ ተመልሳችሁ ነገሮቹን በምታስተውሉበት ጊዜ፥ እንዲሁም ዛሬ እኔ በማዝዛችሁ ሁሉ መሠረት እናንተና ልጆቻችሁ ወደ
አምላካችሁ ወደ እግዚአብሔር ተመልሳችሁ በፍጹም ልባችሁና በፍጹም ነፍሳችሁ እርሱን ስትታዘዙ፤ **3** እግዚአብሔር አምላካችሁ ምርኮአችሁን ይመልስላችኋል፤
ይራራላችሁማል፤ እናንተን ከበተነበት አሕዛብ መካከል እንደ ገና ይሰበስባችኋል። **4** ከሰማይ በታች እጅግ ሩቅ ወደ ሆነ ምድር ብትጋዙ እንኳ እግዚአብሔር
አምላካችሁ ከዚያ ይሰበስባችኋል፤ መልሶም ያመጣችኋል። **5** የአባቶቻችሁ ወደ ሆነችው ምድር ያመጣችኋል፤ እናንተም ትወርሱታላችሁ፤ ከአባቶቻችሁ
ይበልጥ ያበለጽጋችኋል፤ያበዛችሁማል። **6** እግዚአብሔር አምላካችሁን በፍጹም ልባችሁና በፍጹም ነፍሳችሁ እንድትወዱት፤በሕይወትም እንድትኖሩ
እግዚአብሔር አምላካችሁ የእናንተንና የዘራችሁን ልብ ይገርዛል። **7** አምላካችሁ እግዚአብሔር ይህን ርግማን ሁሉ በሚጠሉአችሁና በሚያሳድዱአችሁ
ጠላቶቻችሁ ላይ ያደርገዋል። **8** እናንተም ተመልሳችሁ ለእግዚአብሔር ትታዘዛላችሁ፥ ዛሬ እኔ የማዛችሁን ትእዛዝ ሁሉ ትጠብቃላችሁ። **9** በዚያም እግዚአብሔር
በእጃችሁ ሥራ ሁሉን በወገባችሁ ፍሬ በእንስሳታችሁ፥ ግልገሎችና በምድራችሁ ሰብል እጅግ ያበለጽጋችኋል። በአባቶቻችሁ ደስ እንደ ተሰኘ ሁሉ እግዚአብሔር
እናንተንም በማበልጸግ ደስ ይለዋልና። **10** ይህም የሚሆነው አምላካችሁን እግዚአብሔርን ከታዘዛችሁና በዚህ የሕግ መሕሐፍ የተጻፉትን ትእዛዙንና ሥርዓቱን
በመጠበቅ በፍጹም ልባችሁና በፍጹም ነፍሳችሁ ወደ አምላካችሁ ወደ እግዚአብሔር ስትመለሱ ነው። **11** ዛሬ የምሰጣችሁ ትእዛዝ ይህን ያህል አስቸጋሪ
ወይም ከእናንተ የራቀ አይደለም። **12** እንድንፈጽሙት አምጥቶ ይነግረን ዘንድ ማን ወደ ሰማይ ይወጣል? እንዳትሉ በሰማይ አይደለም። **13** ደግሞም
እንድናደርገው አምጥቶ ይነግረን ዘንድ ማን ባሕሩን ይሻገራል? እንዳትሉም ከባሕር ማዶ አይደለም። **14** ነገር ግን ቃሉ ለእናንተ በጣም ቅርብ ነው፤
ታደርጉትም ዘንድ በአፋችሁና በልባችሁ ውስጥ ነው። **15** እነሆ ዛሬ ሕይወትንና በረከትን፥ ሞትንና ጥፋትን በፊታችሁ አኑሬአለሁ። **16** እግዚአብሔር
አምላካችሁን እንድትወዱ በመንገዱም እንድትሄና ትእዛዙን፥ ሥርዓቱንና ሕጉን እንድትጠብቁ አዝዛችኋል፤ ከዚያም በሕይወት ትኖራላችሁ፥ ትበዛላችሁም፤
አምላካችሁም ትወርሱአት ዘንድ በምትገቡበት ምድር ይባርካችህኋል። **17** ዳሩ ግን ልባችሁን ወደ ኋላ በመለሰና ባትታዘዙ ለሌሎች አማልክት ለመስገድ
ብትታለሉና ብታመልኩአችሁ፤ **18** በርግጥ እንደምትጠፉ እኔ በዛሬው ዕለት እነግራችኋለሁ፤ ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ ትወርሱአት ዘንድ በምትገቡባት ምድር ብዙ
አትኖሩባትም። **19** ሕይወትንና ሞትን፥ በረከትንና ርግማንን በፊታችሁ እንዳስቀመጣችሁ ዛሬ ሰማይንና ምድርን ምስክር አድርጌ እጠራችኋለሁ። እንግዲህ
እናንተና ልጆቻችሁ በሕይወት እንድትኖሩ ሕይወትን ምረጡ፤ **20** ይኸውም እግዚአብሔር አምላካችሁን እንድትወዱ ቃሉን እንድታደምጥና ከእርሱ ጋር
እንድትጣበቁ ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር ሕይወታችሁ ነው፤ ለአባቶቻችሁ ለአብርሃም፥ ለሕስሐቅና ለያዕቆብ ሊሰጣቸው በማለላቸው ምድር ረጅም ዕድሜ
ይሰጣችኋል።

Deuteronomy 30:1

እነዚህ ነገሮች ሁሉ በመጡብህ ጊዜ
እዚህ ጋ “እነዚህ ነገሮች” የሚያመለክቱት በምዕራፍ 28 – 29 የተዘረዘሩትን በረከቶችና እርግማኖች ነው። “በመጡብህ” የሚለው ቃል የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ትርጉሙ ሲደርስብህ ማለት ነው። አ.ት፡ “እነዚህ ነገሮች ሁሉ በሚደርሱብህ ጊዜ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በፊትህ ያስቀመጥኩት
ይህ በፊት ለፊታቸው ያስቀመጠው ዕቃ ይመስል መልኩ ሙሴ ለሕዝቡ ስለ ነገራቸው በረከቶችና እርግማኖች ይናገራል። አ.ት፡ “አሁን ስለነገርኳችሁ ጉዳይ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ትዝ ይበሉህ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “አስታውሳቸው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በሌሎች ሕዝቦች ሁሉ መካከል
“በሌሎች ሕዝቦች ውስጥ በምትኖርበት ጊዜ”

አውጥቶሃል
“እንድትሄድ አስገድዶሃል”

ድምፁን ታዘዘው
እዚህ ጋ “ድምፅ” የሚያመለክተው እግዚአብሔር የሚናገረውን ነው። አ.ት፡ “እርሱ የሚለውን ታዘዝ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በሙሉ ልብህና በሙሉ ነፍስህ
እዚህ ጋ “ልብ” እና “ነፍስ” የአንድን ሰው ውስጣዊ ማንነት የሚያመለክቱ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ናቸው። እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች በአንድ ላይ “ፍጹም” ወይም “በቅንነት” ለማለት ጥቅም ላይ ውለዋል። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 4:29 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና Doublet የሚለውን ተመልከት)

ምርኮኛነትህን ይቀይረዋል
“ከምርኮኝነት ነጻ ያወጣሃል”። የነገር ስም የሆነው “ምርኮኝነት” እንደ ግሳዊ አንቀጽ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ከማረኩህ ከእነርሱ ነጻ ያወጣሃል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 30:4

ከተማረኩት ሰዎችህ ማናቸውም እጅግ ሩቅ ስፍራ ላይ ቢሆኑ
“እነዚያ የተማረኩት ሰዎችህ እጅግ ሩቅ በሆነ ስፍራ የሚኖሩ ቢሆኑም እንኳን”

ከሰማያት በታች
“ከጠፈር በታች” ወይም “በምድር ላይ”

Deuteronomy 30:6

ልብህን ይገርዛል
ይህ በቀጥታ ሥጋን ማስወገድ አይደለም። ይህ ማለት እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን ያስወግዳል፣ እርሱን እንዲወዱትና እንዲታዘዙትም ያስችላቸዋል ማለት ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በሙሉ ልብህና በሙሉ ነፍስህ
እዚህ ጋ “ልብ” እና “ነፍስ” የአንድን ሰው ውስጣዊ ማንነት የሚያመለክቱ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ናቸው። እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች በአንድ ላይ “ፍጹም” ወይም “በቅንነት” ለማለት ጥቅም ላይ ውለዋል። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 4:29 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና Doublet የሚለውን ተመልከት)

የእግዚአብሔርን ድምፅ ታዘዝ
እዚህ ጋ “ድምፅ” ማለት እግዚአብሔር የሚናገረውን ማለት ነው። አ.ት፡ “እግዚአብሔር የሚናገረውን ታዘዝ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እነዚህን እርግማኖች ሁሉ በጠላቶችህ ላይ ያደርጋል
ሙሴ እርግማኖቹን አንድ ሰው በሌላው አናት ላይ ሊያደርግ እንደሚችለው ሸክም ወይም መሸፈኛ አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “ጠላቶችህ በእነዚህ እርግማኖች ምክንያት እንዲሰቃዩ ያደርጋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 30:9

የእጅህን ሥራ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚያመለክተው ሙሉውን ሰው ነው። አ.ት፡ “በምትሠራው ሥራ ሁሉ” (See: Synecdoche)

በሰውነትህ ፍሬ -- በከብቶችህ ፍሬ -- በመሬትህ ፍሬ
እነዚህ ሦስት ሐረጎች “በልጆች -- በጥጆች -- በሰብሎች” ለሚለው የአነጋገር ዘይቤ ናቸው። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 28፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

Deuteronomy 30:11

ትደርስበት ዘንድ ለአንተ እጅግ ሩቅ አይደለም
አንድ ሰው ቁሳዊ አካል ላይ ሊደርስ እንደሚችል ሁሉ ትዕዛዛቱ አንድ ሰው እንዲያደርግ የሚፈልገውን ከትዕዛዛቱ መረዳት እንደሚቻል ሙሴ ይናገራል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር እንድታደርግ የሚፈልግብህን ለመረዳት በጣም አስቸጋሪ አይሆንብህም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እናደርገው ዘንድ እንድንሰማው ማን ወደ ሰማይ ወጥቶ ያወርድልናል?
እዚህ ጋ ሙሴ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄን በመጠቀም የእስራኤል ሕዝብ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ለማወቅ በጣም አስቸጋሪ እንደሚሆንባቸው ማሰባቸው ላይ አጽንዖት ይሰጣል። ይህ ጥያቄ እንደ ንግግር ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ለመማር ወደ ሰማይ መጓዝ አለበት፣ ከዚያም ልንታዘዛቸው እንችል ዘንድ ምን እንደ ሆኑ ሊነግረን መመለስ አለበት” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 30:13

እናደርገው ዘንድ ልንሰማው ማን ባህሩን ተሻግሮ ያምጣልን?
ይህ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የእስራኤል ሕዝብ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ማወቅ በጣም አስቸጋሪ ነው ብለው የሚያስቡበትን አሳብ ይቀጥላል። ይህ ጥያቄ እንደ ንግግር ሆኖ ሊተርጎም ይችላል። አ.ት፡ “የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ለመማር አንድ ሰው ባህሩን አቋርጦ መጓዝ ከዚያም ተመልሶ ምን እንደሆኑ ሊነግረን ያስፈልጋል” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

በአፍህና በልብህ
ይህ ማለት ሕዝቡ ቀደሞውኑ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ያውቃሉ፣ ለሌሎችም ሊነግሯቸው ይችላሉ። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 30:15

በፊትህ አስቀምጫለሁ
አንድን ነገር ሌላው ሰው ሊያይ በሚችልበት ማስቀመጥ ስለ አንድ ነገር ለአንድ ሰው የመንገር ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ስለ ጉዳዩ ነግሬሃለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሕይወትንና መልካምን፣ ሞትንና ክፉን
ግልጽ ያልሆነውን መረጃ ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። አ.ት፡ “መልካም የሆነውንና በሕይወት እንድትኖር የሚያደርግህን፣ ክፉ የሆነውንና እንድትሞት የሚያደርግህን” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

መብዛት
በቁጥር እጅግ መጨመር

Deuteronomy 30:17

ልብህ ቢመለስ -- ይልቱንም ቢማረክና ለሌሎች አማልክት ቢሰግድና ቢያመልካቸው
እዚህ ጋ “ልብ” የሚያመለክተው ሙሉውን ሰው ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ለእግዚአብሔር ያለህን ታማኝነት ብታቆም -- እና በምድሪቱ የሚኖሩ ሰዎች እንድትሰግድና ሌሎች አማልክትን እንድታመልክ ቢያባብሉህ” (Synecdoche እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ዛሬ ለአንተ -- ቀኖችህ እንደማይረዝሙ
x

Deuteronomy 30:19

ሰማይና ምድርን ምስክር እንዲሆኑ እጠራለሁ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሙሴ ለሚናገረው ምስክሮች እንዲሆኑ በሰማይና በምድር የሚኖሩትን ሁሉ ይጠራል ወይም 2) ሙሴ እንደ ሰዎች ቆጥሯቸው ለሰማይና ለምድር ይናገራል፣ እርሱ ለሚናገረው ምስክሮች እንዲሆኑም ይጠራቸዋል። (See: (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት and Personification and Apostrophe)

በአንተ ላይ ምስክር እንዲሆኑ
“ክፉ ነገሮችን ስለማድረግህ ለመናገር ፈቃደኛ እንዲሆን”

ዛሬ በአንተ ላይ
ሙሴ ለእስራኤላውያን እንደ ቡድን አድርጎ ይናገራል። (See: Forms of You)

ድምፁን ታዘዝ
እዚህ ጋ “ድምፅ” እግዚአብሔር የሚናገረውን ያመለክታል። አ.ት፡ “እርሱ የሚለውን ታዘዝ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከእርሱ ጋር እንድትጣበቅ
“በእርሱ ላይ እንድትተማመን”

እርሱ ሕይወትህና የቀኖችህ ርዝመት ነውና
እነዚህ ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸውና እግዚአብሔርን የሚገልጹ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ሲሆኑ ሕይወትን የሚሰጥና የሰዎችን የሕይወት ዘመን የሚወስን እርሱ መሆኑን አጽንዖት ይሰጣሉ። አ.ት፡ “ረጅም ሕይወት እንድትኖር የሚያስችልህ እግዚአብሔር ብቻ ነው” (Doublet እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ለአባቶቻችሁ የማለውን
ሞላላው ሊሞላ ይችላል። አ.ት፡ “ለአባቶቻችሁ ሊሰጣችሁ ምሏል” (See: Ellipsis)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 31

1 ሙሴም ወጥቶ እነዚህን ቃሎች ለእስራኤል በሙሉ ነገራቸው። 2 እንዲህም አላቸው፦ መቶ ሃያ ዓመት ሆኖኛል ከእንግዲህ መወጣትና መግባት አልችልም፤
እግዚአብሔርም ዮርዳኖስን አትሻገርም ብሎኛል፥ 3 እግዚአብሔር አምላካችሁ ራሱ በፊታችሁ ቀድሞ ይሄዳል፤ እነዚህንም አሕዛብ ከፊታችሁ ያጠፋቸዋል፤
እናንተም ምድራቸውን ትወርሳላችሁ፤ እግዚአብሔር እንደ ተናገረው፤ ኢያሱም እናንተን ቀድሞ ይሻገራል። 4 እግዚአብሔር የአሞራውያንን ነገሥታት ሴዎንንና ዐግን
ከነምድራቸው እንዳጠፋቸው እነዚህንም ያጠፋቸዋል። 5 እግዚአብሔር እነርሱን በፊታችሁ አሳልፎ ይሰጣችኋል፤ እናንተም ያዘዝኋችሁን ሁሉ በእነርሱ ላይ
ታደርጋላችሁ። 6 ብርቱና ደፋር ሁኑ፥ አትፍሯቸው ወይም አትደንግጡል አላቸው። እግዚአብሔር አምላካችሁ ከእናንት ጋር ይሄዳልና አይተዋችሁም
አይጥላችሁምም። 7 ከዚያም ሙሴ ኢያሱን ጠርቶ በእስራኤል ሁሉ ፊት እንዲህ አለው፦ እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው ሊሰጥ ወደ ማለላቸው ምድር ከዚህ
ሕዝብ ጋር አብረህ ስለምትገባ፤ ምድሪቱን ርስታቸው አድርገህ ስለምታከፋፍል በርታ፤ ደፋርም ሁን። 8 እግዚአብሔር ራሱ በፊትህ ይሄዳል፤ ከአንተም ጋር
ይሆናል፤ ፈጽሞ አይለይህም፤ አተውህምም አትፍራ ተስፋም አትቁረጥ። 9 ሙሴም ይህን ሕግ ጽፎ የእግዚአብሔርን የኪዳን ታቦት ለሚሸከሙ፥ ለሌዊ ልጆች፤
ለካህኑና ለእስራኤል አለቆች ሁሉ ሰጠ። 10 ከዚያም በኋላ ሙሴ እንዲህ ሲል አዘዛቸው፤ዕዳ በሚተውበት የዳስ በዓልም በሚከበርበት በየሰባቱ ዓመት
መጨረሻ 11 እስራኤል ሁሉ እርሱ በሚመርጠው ስፍራ በአምላካችሁ በእግዚአብሔር ፊት ሲታይ ይህ ሕግ በእነርሱ ፊት በጆሮአቸው ታነባቸዋላችሁ። 12
እነርሱም ይስሙና አምላካችሁን እግዚአብሔርን መፍራት ይማሩ ዘንድ የዚህን ሕግ ቃል ሁሉ በጥንቃቄ እንዲከተሉ ሕዝቡን ይኸውም ወንዶችን፥ ሴቶችንና
ልጆቻቸሁንና በከተሞቻችሁን የሚኖረውንም መጻተኛ ሰብስቡ። 13 ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ በምትወርሷት ምድር በምትኖሩበት ዘመን ሁሉ ይህን ሕግ
የማያውቁት ልጆቻቸሁም መስማትና አምላካችሁን እግዚአብሔርን መፍራት ለማሩ ይገባቸዋል። 14 እግዚአብሔር ሙሴን እነሆ የምትሞትበት ቀን ቀርቦአል፥
ትእዛዝ እንድሰጠው ኢያሱን ጥራውና ወደ መገናኛው ድንኳንም ቅረቡ። 15 እግዚአብሔር በድንኳኑ ላይ በደመና ዐምድ ተገለጠ፤ የደመናውም ዐምድ ከድንኳኑ
ደጃፍ ላይ ቆመ። 16 እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው፦ እነሆ ከአባቶቻችሁ ጋር ልታርፍ ነው፤ ይህም ሕዝብ በሚገባበት ምድር በሚገኙ አማልክት
ወዲያውኑ ያመነዝራል፤ እኔን ይተወኛል፤ ከእነርሱም ጋር የገባሁትን ኪዳን ያፈርሳሉ። 17 በዚያም ቀን ቁጣዬ በእነርሱ ላይ ይነዳል፤ እተዋቸዋለሁም። ፊቴንም
ከእነርሱ እሰውራለሁ፤ እነርሱም ይጠፋሉ። ብዙ ጥፋትና የከፋ ችግር ይደርስባቸዋል፤ በዚያም ቀን ይህ ጥፋት የደረሰሰብን አምላካችን ከእኛ ጋር ባለመሆኑ
አይደለምን? ይላሉ። 18 ወደ ባዕዳን አማልክት በመዞር በፈጸሙት ክፋታቸው የተነሣ በዚያን ቀን ፊቴን ከእነርሱ ፈጽሞ እሰውራለሁ። 19 እንግዲህ ይህን
መዝሙር ለራሳችሁ ጻፉና ለእስራኤል ልጆች አስተምሩ። ስለ እኔ ምስክር ይሆንባቸው ዘንድ እንዲዘምሩ አድርጉ። 20 ወተትና ማር ወደምታፈሰውና
ለአባቶቻቸው በመሐላ ቃል ወደ ገባህላቸው ምድር ባመጣሃቸው ጊዜ ከበሉና ከጠገቡ፥ ከበለጸጉም በኋላ እኔን ንቀው ኪዳኔንም አፍርሰው ወደ ባዕዳን
አማልክት ይዞራሉ፤ እነርሱንም ያመልካሉ። 21 ብዙ ጥፋትና የከፋ ችግር በደረሰባቸው ጊዜ ይህ መዛሙር ምስክር ይሆንባቸዋል። በዘራቸውም አፍ የሚረሳ
አይሆንም፤ ወደ ማልሁላቸው ምድር ሳላስገባቸው በፊት ምን ለማድረግ እንደሚያስቡ እንኳን አስቀድሜ አውቃለሁ። 22 ስለዚህም ሙሴ ይህን መዝሙር በዚያን
ቀን ጻፈና እስራኤላውያንን አስተማራቸው። 23 እግዚአብሔርም ለነዌ ልጅ ለኢያሱ በር ደፋር ሁን፤ የእስራኤልን ልጆች በመሐላ ቃል ወደ ገባሁላቸው ምድር
ታስገባቸዋለህና እኔም ከአንተ ጋር እሆናለሁ በማለት ትእዛዝ ሰጠው። 24 ሙሴ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የዚህን ሕግ ቃል በመጽሐፍ ጽፎ እንዳበቃ፤ 25
የእስራኤልን የኪዳን ታቦት የሚሸከሙ ሌዋውያንን እንዲህ ሲል አዘዛቸው፤ 26 ይህን የሕግ መጽሐፍ ውሰዱ፤ በዚያም በእናንተ ላይ ምስክር እንዲሆን
በእግዚአብሔር በአምላካችሁ ቃል ኪዳን ታቦት አጠገብ አኑሩት። 27 ዐመፀኞችና አንገተ ደንዳኖች እንደ ሆናችሁ አውቃለሁ፥ተመልከቱ እኔ ዛሬ በሕይወት
ከእናንተ ጋር እያለሁ እንኳን በእግዚአሔር ላይ እንደህ ካመፃችሁ ከሞትሁ በኋላማ እንዴት አታደርጉም? 28 ሰማይንና ምድርን ምስክር አድርጌ ጠርቼባቸው
ይህን ቃል ይሰሙ ዘንድ ብጆሮአቸው እንድናገር ፤ የነገድ አለቆቻችሁን በሙሉና ሹሞቻችሁን ሁሉ በፊቴ ሰብስቡ። 29 እኔ ከሞትሁ በኋላ ፈጽማችሁ
እንደምትረክሱ ካዘዝኋችሁም መንገድ ዘወር እንደምትሉ አውቃለሁና። በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ድርጊት ስለምትፈጽሙ፤ ይህ የሚሆነው እጆቻችሁ
በሠሯቸውም ነገሮች እርሱን ለቁጣ ስለምታነሣሡት በሚመጡት ዘመናት ጥፋት ይደርስባችኋል። 30 ሙሴ የዚህን መዝሙር ቃል ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ
ድረስ ለተሰበሰበው ለእስራኤል ሕዝብ ሁሉ በጆሮአቸው አሰማ።

Deuteronomy 31:1

የአንድ መቶ ሃያ ዓመት ዕድሜ
“120 ዓመት ዕድሜ” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ከእንግዲህ መውጣትና መግባት አልችልም
እዚህ ጋ “መውጣት” እና “መግባት” የተሰኙ ሁለት ጽንፎች በአንድ ላይ አንድ ጤነኛ ሰው ሊያደርግ የሚችለውን ሙሴ ከእንግዲህ ማድረግ አይችልም ማለት ነው። (See: Merism)

አምላክህ -- በፊትህ -- በፊትህ -- ታስወጣቸዋለህ -- በፊትህ
ሙሴ እስራኤላውያኑን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “አንተ” እና “የአንተ” የሚሉት ቃላት እዚህ ጋ ነጠላ ቁጥሮች ናቸው። (See: Forms of You)

ታስወጣቸዋለህ
“ምድራቸውን ትወስዳለህ”

እግዚአብሔር እንደተናገረው ኢያሱ በፊታችሁ ይሄዳል
“እግዚአብሔር ቃል እንደገባው ኢያሱ መርቶ ወንዙን ያሻግራችኋል”

Deuteronomy 31:4

በአሞራውያን ነገሥታት በሴዎንና በዐግ -- አደረገ
እዚህ ጋ “ሴዎን” እና “ዐግ” ሁለቱን የአሞራውያንን ነገሥታትና ሰራዊታቸውን ያመለክታል። እነዚህን ስሞች በዘዳግም 1:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። አ.ት፡ “በአሞራውያን ነገሥታት በሴዎን፣ በዐግና በሰራዊቶቻቸው ላይ -- አደረገ” (See: Synecdoche)

Deuteronomy 31:7

በእስራኤል ሁሉ ፊት
ይህ ማለት የእስራኤል ሕዝብ በሙሉ በዚያ ነበሩ ማለት ነው። አ.ት፡ “በእስራኤላውያን ሁሉ ፊት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ብርቱ ሁን፣ ድፍረትም ይኑርህ
“ብርቱና ደፋር ሁን”። ይህንን በዘዳግም 31:5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

እንዲወርሱት ታደርጋቸዋለህ
“ምድሪቱን እንዲወስዱ ትረዳቸዋለህ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Deuteronomy 31:9

ለሌዊ ልጆች ለካህናቱ ሰጣቸው
“ካህናት ለሆኑት ለሌዋውያኑ ሰጣቸው”

ሰባት ዓመት
“7 ዓመት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ዕዳን ለመተው የተወሰነበት
“ዕዳን ለመሰረዝ”

የመጠለያ በዓል
የዚህ በዓል ሌሎች ስሞች፣ “የመገናኛው ድንኳን በዓል”፣ “የዳስ በዓል”፣ እና “የመሰብሰብ በዓል”። በመከር ጊዜ ገበሬዎች በመስኩ ላይ ጊዜያዊ መጠለያ ይሠሩ ነበር። ይህ በዓል የሚደረገው የዓመቱ መከር ከተሰበሰበ በኋላ ነበር። ይህንን በዘዳግም 16፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

አምላክህ እግዚአብሔር -- ታነበዋለህ
ሙሴ እስራኤላውያኑን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “አንተ” እና “የአንተ” የሚለው ቃል እዚህ ጋ ነጠላ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)

በመስሚያቸው
“መስማት ይችሉ ዘንድ”

Deuteronomy 31:14

ተመልከት
“እኔ ለምነግርህ ትኩረት ስጥ”

የደመና ዓምድ
ይህ በላይኛው ክፍል ቅርጽ የያዘ ጥቅጥቅ ያለ የጢስ ደመና ነበር

Deuteronomy 31:16

ተመልከት
“እኔ ለምነግርህ ትኩረት ስጥ”

ከአባቶችህ ጋር ታንቀላፋለህ
ይህ “ትሞታለህ” የማለት የትህትና አገላለጽ ነው። አ.ት፡ “ትሞትና ከአንተ በፊት ከሞቱት ቅድመ ቅድም አያቶችህ ጋር አብረህ ትሆናለህ” (See: Euphemism)

ተነሥተው የአመንዝራን ተግባር ይፈጽማሉ
አመንዝራ መሆን ከእግዚአብሔር ሌላ ሌሎች አማልክትን ለማምለክ ማለት ነው። አ.ት፡ “ለእኔ አለመታመን ይጀምራሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 31:17

ቁጣዬ በእነርሱ ላይ ይነድዳል
እግዚአብሔር ቁጣውን እሳት ከሚለኩስ ሰው ጋር ያነጻጽራል። ይህ እርሱን የሚያስቆጣውን የትኛውንም ነገር በሚያጠፋ በእግዚአብሔር ኃይል ላይ አጽንዖት ይሰጣል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ቁጣዬን በእነርሱ ላይ አነድዳለሁ” ወይም “በእነርሱ ላይ እቆጣለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ፊቴን ከእነርሱ እደብቃለሁ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “አልረዳቸውም” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ይዋጣሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እውጣቸዋለሁ” ወይም “ጠላቶቻቸው እንዲውጡአቸው እፈቅድላቸዋለሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ተዋጡ
ይህ “ፈጽመው ጠፉ” ለሚለው ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ብዙ ጥፋትና መከራ ያገኛቸዋል
ይህ ጥፋቱንና መከራውን እንደ ሰው መስሎ ይገልጻቸዋል። አ.ት፡ “ብዙ ጥፋትና መከራ ይደርስባቸዋል” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

-- መካከል እነዚህ ጥፋቶች የመጡብን?
ይህ ጥፋቱንና መከራውን እንደ ሰው መስሎ ይገልጻቸዋል። ይህ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “-- መካከል እነዚህ ጥፋቶች እያጠፉኝ ነው” (ሰውኛ እና ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

አምላካችን በመካከላችን አይደለም
“ከእንግዲህ እግዚአብሔር እየጠበቀን አይደለም” ወይም “እግዚአብሔር ለብቻችን ትቶናል”

Deuteronomy 31:19

በአፋቸው አኑረው
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “እንዲያሰላስሉትና እንዲዘምሩት አድርጋቸው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ወተትና ማር የምታፈሰውን ምድር
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ብዙ ወተትና ማር የሚፈስባት ምድር” ወይም “ከብት ለማርባትና ለእርሻ ምርጥ የሆነች ምድር” ይህንን በዘዳግም 6፡3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Deuteronomy 31:21

በዚህ ሕዝብ ላይ ብዙ ክፋትና መከራ በመጣባቸው ጊዜ
እዚህ ጋ ክፋትና መከራ ሰብዓዊ ፍጥረት ሆነው ሰዎችን ሊያገኙ የሚችሉ መስለው ተገልጸዋል። አ.ት፡ “ይህ ሕዝብ ብዙ ክፋትና መከራ በሚገጥመው ጊዜ” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

ይህ መዝሙር በፊታቸው እንደ ምስክር ሆኖ ይመሰክርባቸዋል
መዝሙሩ እንደ ሰብዓዊ ፍጥረት ሆኖ በፍርድ ቤት ውስጥ በእስራኤል ላይ እንደሚመሰክር ይናገራል። (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

እርሱ በዘሮቻቸው አፍ የሚረሳ አይሆንም
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ዘሮቻቸው በአፋቸው ውስጥ መጠበቃቸውን አይረሱም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እርሱ በዘሮቻቸው አፍ የሚረሳ አይሆንም
ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ዘሮቻቸው በአፋቸው ውስጥ መጠበቅ እንዳለባቸው ያስታውሳሉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እርሱ በዘሮቻቸው አፍ የሚረሳ አይሆንም
“በአፋቸው መርሳት” የሚለው የአነጋገር ዘይቤ ስለ እርሱ መናገርን ማቆም ማለት ነው። አ.ት፡ “ዘሮቻቸው ለእርስ በእርሳቸው ስለ እርሱ ከመናገር አያቆሙም”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የሚሠሩትን ዕቅድ
ሰዎች ለማድረግ የሚያቅዱት እርሱ እንደ አካላዊ ቁስ ተደርጎ ተነግሮለታል። አ.ት፡ “ለማድረግ የሚያቅዱት” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ተስፋ የሰጠኋችሁ ምድር
እግዚአብሔር ስለምድሪቱ የሰጠው ተስፋ ለእስራኤል ሕዝብ እንደሚሰጣቸው ነበር። ይህ በግልጽ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እሰጣቸዋለሁ ብዬ ተስፋ የሰጠኋቸው ምድር” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

Deuteronomy 31:22

ብርቱ ሁን፣ ድፍረትም ይኑርህ
“ብርቱና ደፋር ሁን” ይህንን በዘዳግም 31:5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Deuteronomy 31:24

በአንተ ላይ ምስክር
ሙሴ እንደ አንድ ሰው አድርጎ ለሌዋውያን ይናገራል፣ ስለዚህ “አንተ” የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)

Deuteronomy 31:27

አመጸኛና አንገተ ደንዳና ሕዝብህ
ሙሴ እንደ አንድ ሰው አድርጎ ለሌዋውያን ይናገራል፣ ስለዚህ “አንተ” የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)

የአንተ አንገተ ደንዳና
በዘዳግም 9:6 ላይ “እልኸኛ” የሚለውን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ከሞትኩኝ በኋላ ይልቁን እንዴት?
ይህ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ ሕዝቡ እንዴት ያሉ አመጸኞች እንደነበሩ አጽንዖት ይሰጣል። ይህ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እኔ ከሞትኩኝ በኋላ እንኳን በይበልጥ አመጸኛ ትሆናላችሁ” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

እነዚህን ቃላት በጆሮአቸው እንድናገር
እዚህ ጋ “በጆሮአቸው” ማለት ሕዝቡን ራሳችውን ማለት ነው። አ.ት፡ “የዚህ መዝሙር ቃሎች እነግራችው ዘንድ” (See: Synecdoche)

በእነርሱ ላይ ምስክር እንዲሆኑ ሰማይና ምድርን እጠራለሁ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሙሴ ለሚናገረው ምስክሮች እንዲሆኑ በሰማይና በምድር የሚኖሩትን ሁሉ ይጠራል ወይም 2) ሙሴ እንደ ሰዎች ቆጥሯቸው ለሰማይና ለምድር ይናገራል፣ እርሱ ለሚናገረው ምስክሮች እንዲሆኑም ይጠራቸዋል። ተመሳሳይ ሐረግ በዘዳግም 30:19 ላይ ይታያል።

ፈጽሞ ራሳችሁን ታረክሳላችሁ
“ሙሉ በሙሉ ስሕተት የሆነውን ታደርጋላችሁ”። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 4፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት፡

እኔ ካዘዝኳችሁ መንገድ ዘወር ትላላችሁ
“የሰጠኋችሁን መመሪያ መከተል ታቆማላችሁ”። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 9፡12 እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነውን
የእግዚአብሔር ፊት የሚወክለው የእግዚአብሔርን ውሳኔ ወይም ምዘና ነው። አ.ት፡ “በእግዚአብሔር ውሳኔ ክፉ የሆነ” ወይም “እግዚአብሔር ክፉ ነው ብሎ የሚቆጥረውን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእጆቻችሁ ሥራ አማካይነት
እዚህ ጋ “እጆቻችሁ” ማለት ሕዝቡን ራሳቸውን ማለት ነው። አ.ት፡ “በሠራችሁት ሥራ ምክንያት” (See: Synec- doche)

Deuteronomy 31:30

ሙሴ በእስራኤል ጉባዔ ጆሮዎች ሁሉ አሰማ
እዚህ ጋ “ጆሮዎች” የሚያመለክቱት ሙሉውን ሰው ነው። አ.ት፡ “ሙሴ ለእስራኤል ሕዝብ ሁሉ አሰማቸው” (See: Synec- doche)

አሰማ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ዘመረ” ወይም 2) “ተናገረ”

የዚህን መዝሙር ቃላት
በውስጠ ታዋቂነት ያለውን መረጃ ግልጽ ልታደርገው ትችላለህ። አ.ት፡ “እግዚአብሔር እርሱን ያስተማረበትን የመዝሙሩን ቃላት” (See: Ellipsis)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 32

1 ሰማያት ሆይ፥ አድምጡ እኔም እናገራለሁ፤ ምድር ሆይ፥ አንቺም የአፌን ቃል ስሚ። 2 ትምህርቴም እንደ ዝናብ ይውረድ፤ ቃሌም እንደ ጤዛ ይንጠባጠብ፤ በቡቃያ ሣር ላይ እንደ ካፊያ፥ ለጋ ተክልም ላይ እንደ ከባድ ዝናብ ይውረድ። 3 እኔ የእግዚአብሔርን ስም አውጃለሁ፤ የአምላካችንን ታላቅነት አወድሱ። 4 እርሱ ዐለትና ሥራውም ፍጹም፥ መንገዱም ሁሉ ትክክል ነው። የማይሳሳት ታማኝ አምላክ፤ ቀጥተኛና ጻድቅ አምላክም እርሱ ነው። 5 በእርሱ ላይ ክፋት ፈጽመዋል። ከነውራቸው የተነሣ ከእንግዲህ ልጆቹ አይደሉም። ወልጋዳና ጠማማ ትውልዶች ናቸው። 6 እናንተ ተላላና ጥበብ የጎደላችሁ ሕዝብ፤ለእግዚአብሔር የምትመልሱለት በዚህ መንገድ ነውን? አባታችሁና ፈጣሪያችሁ የሠራችሁና ያበጃችሁእርሱ አይደለምን? 7 የጥንቱን ዘመን፥ የብዙ ዓመቶችን አስታውሱ፤ አባቶቻችሁን ጠይቁ ይነግሩማልም፥ ሽማግሌዎቻችንም ጠይቁ ያስረዱአችኋል። 8 ታላቁ አምላክ ለአሕዛብ ርስታቸውን በሰጠ ጊዜ የሰውንም ዘር በለያየ ጊዜ፤ በእስራኤል ልጆች ቁጥር ልክ፤ የአሕዛብን ርስት ድንበር ለየ። 9 የእግዚአብሔር ድርሻ የገዛ ሕዝቡ ያዕቆብ የተለየ ርስቱ ነውና። 10 እርሱን በምድረ በዳ፤ ባዶና ጭው ባለ በረሓ ውስጥ አግኘው፤እንደ ዐይኑ ብሌን ጠበቀው። 11 ንስር ጎጆዋን እንደትጠብቅ፤ በጫጩቶቿም ላይ እንደምትረብብ፥ እነርሱን ለመያዝ ክንፎቿን እንደምትዘረጋ በክንፎቿም እንደምትሸከማቸው፥ እግዚአብሔር ክንፎቹን ዘርግቶ፥ ተሸከሞ ወሰዳቸው። 12 እግዚአብሔር ብቻ መራው ምንም ባዕድ አምላክ ከእርሱ ጋር አልነበረም። 13 በምድር ከፍታ ላይ አስኬደው፤ የእርሻንም ፍሬ መገበው፤ ከዐለት ድንጋይ ማር አበላው፤ ከባልጩትም ድንጋይ ዘይት መገበው። በወንድና በሴት ልጆቹ ተቆጥቶአልና። 14 የላሙንና የበጉን መንጋ ቅቤና ወትት የሰቡትን በጎችና ፍየሎች፤ የባሳንን ሙኩት በግ፤ መልካም የሆነውንም ስንዴ ማለፈያውንም የወይን ጠጅ ጠጠህ። 15 ይሹሩን ወፈረ፥ ረገጠ፤ ስብ ጠገበ፥ ሰውነቱ ደነደነ፥ ለሰለሰም። የፈጠረውንም አምላክ ተወ፤ የመጠጊያ ዐለት የሆነውን አዳኙንም ናቀው። 16 በባዕዳን አማልክታቸው አስቀኑት፤ በአስፈያፊ ጣዖቶቻቸውም አስቆጡት። 17 አምላክ ላልሆኑ አጋንንት፥ ላላወቋቸው አማልክት፥ ከጊዜ በኋላ ለተነሡ አማልክት፥ አባቶቻችውም ላልፈሯቸው አማልክት ሠዉ። 18 አባት የሆናችሁን ዐለት ከዳችሁት፤ የወለዳችሁን አምላክ ረሳችሁ። 19 እግዚአብሔር ይህን አይቶ ተዋቸው፤ በወንድና በሴት ልጆቹ አስጥተውታልና። 20 እርሱም እንዲህ ብሎአል፦ ፊቴን ከእነርሱ እሰውራለሁ፤ መጨረሻቸው ምን እንደሚሆንም አያለሁ፤ ጠማማ ትውልድ፤ የማይታመኑም ልጆች ናቸውና። 21 አምላክ ላልሆነው አስቀኑኝ፤ በከንቱ ጣዖቶቻቸውም አስቆጡኝ። እኔም ሕዝብ ባልሆነው አስቀናቸዋል፤ በማያስተውልም ሕዝብ አስቆጣቸዋለሁ። 22 በቁጣዬ እሳት ተቀጣጥሎአልና፤እስከ ሲኦል ዘልቆ ይነዳል፤ ምድርን እስከ ሰብሏ ይበላል፤ የተራሮችንም መሠረት ያቀጣጥላል። 23 በመዓት ላይ መዓት አመጣባቸዋለሁ። ፍላጻዬንም በእነርሱ ላይ እተኩሳለሁ። 24 የሚያጠፋ ራብ፤በልቶ የሚጨርስ ቸነፈርና ከባድ መቅሠፍት እሰድባቸዋለሁ፤ የአራዊትን ሹል ጥርስ፥ በምድር የሚሳብ የእባብ መርዝም እሰድባቸዋለሁ። 25 ሰይፍ መንገድ ላይ ያስቀራቸዋል፤ በመኝታቸውም ድንጋጤ ይነግሣል፤ጎልማሳውና ልጃገረዷ፤ ሕፃኑና ሽማግሌው ይጠፋሉ። 26 ከሰዎችም መካከል መታሰቢያቸውን አጠፋለሁ፥ እበትናቸዋለሁም፤አልሁ፤ 27 ድል ያደረገው እጃችን ነው ብለው፥ ጠላቶቻቸው በስሕተት እንዳይታበዩ፥ የጠላት ማስቆጣት እንዳይሆን እሠጋለሁ። 28 እስራኤላውንም አእምሮ የጎደላቸው፤ ማስተዋልም የሌላቸው ናቸው። 29 አስተዋዮች ቢሆኑ ኖሮ ይህን በተገነዘቡና መጨረሻቸው ምን እንደሚሆን ባስተዋሉ ነብር። 30 መጠጊያ ዐለታቸው ካልሸጣቸው እግዚአብሔር ካልተዋቸው በቀር፥ አንድ ሰው እንዴት ሺሁን ያሳድዳል፥ ሁለቱስ እንዴት አሥር ሺሁን እንዲሸሹ ያደጋሉ? 31 የእነርሱ መጠጊያ ዐለታቸው እንደ እኛ መጠጊያ ዐለት አለመሆኑን፤ ጠላቶቻችንም እንኳ አይክዱም። 32 ወይናቸው ከሰዶም ወይን ከገሞራም እርሻ ይመጣል፤ የወይናቸው ፍሬ በመርዝ፥ ዘለላቸውም መራራ ነው። 33 ወይናቸው የእባብ መርዝ፤ መርዙም የጨካኝ እባብ ነው። 34 ይህስ በእኔ ዘንድ ተጠብቆ ያለ፤ በመዝገቤስ የታተመ አይደለምን? 35 በቀል የእኔ ነው፤ እኔ ብድራትን እመልሳለሁ፥ ጊዜው ሲደርስ እግራቸው ይሰናከላል፤ የመጥፊያቸው ቀን ቀርቦአል፤ የሚመጣባቸውም ነገሮች ይፈጥንባቸዋል። 36 ኃይላቸው መድከሙን ባሪያም ሆነ ነጻ ሰው አለመቅረቱን በሚያይበት ጊዜ፤ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ይፈርዳል፤ ለአገልጋዮቹም ይራራል። 37 እንዲህም ይላል፦ መጠጊያ ዐለት የሆኗቸው፤ አማልክታቸው ወዴት አሉ? 38 የመሥዋዕታቸውን ስብ የበሉ፤ የመጠጥ ቁርባናቸውንም የወይን ጠጅ የጠጡ አማልክት ወዴት ናቸው? እስቲ ይነሡና ይርዷችሁ! እስቲ መጠለያ ይስጧችሁ! 39 እኔ ራሴ እርሱ እንደ ሆንሁ እዩ፤ ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ የለም፤እገድላለሁ፤ አድናለሁ፤አቆስላለሁ፤ እፈውሳለሁም፤ ከእጄም የሚያስጥል ማንም የለም። 40 እጄን ወደ ሰማይ አነሣለሁ፤ ለዘላለምም ሕያው እንደ ሆንሁ እናገራለሁ።። 41 የሚያብራቀርቅ ሰይፌን ስዬ እጄ ለፍርድ ስይዘው፤ ባላጋራዎቼን እበቀላቸዋለሁ፤ ለሚጠሉኝም እንደሥራቸው እከፍላቸዋለሁ። 42 ሰይፌ ሥጋ በሚበላበት ጊዜ፥ ፍላጾቼ በደም እንዲሰክሩ አደርጋለሁ፤ ደሙ የታረዱትና የምርኮኞች የጠላት አለቆችም ራስ ደም ነው። 43 አሕዛብ ሆይ ከሕዝቡ ጋር ደስ ይበላችሁ፤ እርሱ የአገልጋዮቹን ደም ይመልሳል፤ጠላቶቹንም ይበቀላል። ምድሪቱንና ሕዝቡን ይቤዝቸዋል። 44 ሙሴም ከነዌ ልጅ ከኢያሱ ጋር መጥቶ የመዝሙር ቃሎችን በሕዝቡ ጆሮ ተናገረ። 45 ሙሴም እነዚህን ቃሎች ሁሉ ለመላው እስራኤል ተናገሮ ጨረሰ። 46 እርሱም እንዲህ አላቸው፦ የዚህን ሕግ ቃሎች ሁሉ በጥንቃቄ ይጠብቁ ዘንድ ልጆቻችሁን እንድታዟቸው እኔ ዛሬ በግልጥ የምነግራችሁን ቃሎች ሁሉ በልባችሁ አኑሩ። 47 ቃሎቹ ለእናንተ ሕይወታችሁ ናቸው፥ ባዶ ቃሎች አይደሉም፥ በእነርሱ ዮርዳንስን ተሻገራችሁ በምትወርሷትም ምድር ረጅም ዘመን ትኖራላችሁ። 48 በዚያችም ዕለት እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረ፦ 49 ከኢያሪኮ ማዶ ባለው የሞዓብ ምድር ከዓብሪም ተራሮች አንዱ ወደ ሆነው ወደ ናባው ተራራ ወጥተህ ለእስራኤላውያን ርስት አድርጌ የምሰጣትን የከነዓን ምድር አሻግረህ ተመልከት። 50 ወንድምህ አሮን በሖር ተራራ ላይ እንደ ሞተና ወደ ወገኖቹ እንደ ተሰበሰበ ሁሉ አንተም በወጣህበት በዚያ ተራራ ላይ ሙት፤ ወደ ወገኖችህም ተሰብሰብ። 51 ይህ የሚሆንበት ምክንያት ሁለታችሁም በሲን ምድረ በዳ በቃዴስ በሜሪባ ውሃ አጠገብ በእስራኤላውያን መካከል በእኔ ላይ ባለመታመናችሁ፤ እንዲሁም በእስራኤላውያን መካከል የሚገባውን አክብሮት ባለመስጠታችሁ ነው። 52 ስለዚህ ምድሪቱን ከሩቅ ሆነህ ታያታለህ እንጂ ለእስራኤል ሕዝብ ወደምሰጣት ምድር አትገባም።

Deuteronomy 32:1

እናንተ ሰማያት ጆሮአችሁን ስጡ -- ምድርም ትስማ
እዚያ ሆነው ይሰሙ ይመስል እግዚአብሔር ለሰማያትና ለምድር ይናገራል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እግዚአብሔር የሚናገረው በሰማይና በምድር ለሚኖሩት ነው፤ ወይም 2) እግዚአብሔር እንደ ሰው ቆጥሯቸው ለሰማይና ለምድር ይናገራል። (See: Apostrophe)

ትምህርቴ እንደ ዝናብ ይንጠባጠብ፣ በተክሎች ላይ እንደጎርፍ
ይህ ማለት የእርሱን ጠቃሚ ትምህርት ሕዝቡ በትጋት እንዲቀበሉ እግዚአብሔር ይፈልጋል። (See: Simile)

የተጣራ
ጤዛ የሚታይበትን ሂደት የሚገልጽ ቃል በራስህ ቋንቋ ተጠቀም።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጠል
ቅዝቃዜ ባለበት ጠዋት በቅጠሎችና በሣር ላይ የሚገኝ ውሃ

ለጋ ሣር
“አዲስ ተክሎች”

መጉረፍ
ከባድ ዝናብ

Deuteronomy 32:3

የእግዚአብሔርን ስም ዐውጅ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “እግዚአብሔር መልካም መሆኑን ተናገር” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የአምላካችንን ታላቅነት አሳስቡ
“አምላካችን ታላቅ መሆኑን ሰዎች ማወቃቸውን አረጋግጡ”

ዐለቱ
ይህ እንደ ዐለት ብርቱ እና ሕዝቡን መጠበቅ ለሚችለው ለእግዚአብሔር ሙሴ የሰጠው የተፀውዖ ስም ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሥራው
“እርሱ የሚያደርገው ሁሉ”

መንገዶቹ ሁሉ ትክክል ናቸው
መንገድ ላይ መራመድ አንድ ሰው ሕይወቱን እንዴት እንደሚኖረው የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ሁሉንም ነገር በትክክለኛ መንገድ አድርጓል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እርሱ ትክክለኛና ቀጥተኛ ነው
እነዚህ ሁለት ቃላት በመሠረቱ የሚሉት አንድ ነገር ሆኖ እግዚአብሔር ፍትሐዊና ትክክለኛውን ነገር እንዳደረገ አጽንዖት ይሰጣሉ። (See: Doublet)

Deuteronomy 32:5

በእርሱ ላይ በእርኩሰት አድርገዋል
“ትክክል ያልሆነን ነገር በማድረግ ተቃወሙት”። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 4፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

ወልጋዳና ጠማማ ትውልድ
“ወልጋዳ” እና “ጠማማ” የሚሉት ቃላት በመሠረቱ ትርጉማቸው አንድ ነው። ሙሴ ትውልዱ ምን ያህል ክፉ እንደሆነ አጽንዖት ለመስጠት ይጠቀምባቸዋል። አ.ት፡ “ፈጽሞ ክፉ የሆነ ትውልድ” (See: Doublet)

-ሕዝብ ለእግዚአብሔር በዚህ መንገድ ትመልስለታለህ?
ሙሴ ሕዝቡን ለመገሰጽ ይህንን ጥያቄ ይጠቀማል። አ.ት፡ “-ሕዝብ፣ ለእግዚአብሔር ተገቢውን ምስጋና ማቅረብ አለባችሁ” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

አንተ ሞኝና የማትረባ ሕዝብ
“ሞኝ” እና “የማትረባ” የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ ሕዝቡ እግዚአብሔርን ባለመታዘዛቸው ምን ያህል ሞኞች እንደሆኑ አጽንዖት ይሰጣሉ። አ.ት፡ “እጅግ ሞኞች የሆናችሁ ሰዎች” (See: Doublet)

አባትህ -- ፈጥሮሃል -- ሠርቶሃል፣ አጽንቶሃል
ሙሴ ለእስራኤላውያን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “አንተ” እና “የአንተ” የሚሉት ቃላት እዚህ ጋ ነጠላ ቁጥሮች ናቸው።

የፈጠረህ አባትህ አይደለምን?
ሙሴ ሕዝቡን ለመገሰጽ በጥያቄ መልክ ይጠቀማል። ይህ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር የፈጠረህ አባትህ ነው” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 32:7

ትዝ ይበልህ -- አስብ -- አባትህ -- ያሳዩሃል -- ሽማግሌዎችህ -- ይነግሩሃል
ሙሴ ለእስራኤላውያን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “አንተ” እና “የአንተ” የሚሉት ቃላት እዚህ ጋ ነጠላ ቁጥሮች ናቸው። (See: Forms of You)

ትዝ ይበልህ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “አስታውስ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የጥንቱን ዘመን
“ከረጅም ዓመታት በፊት”። ሙሴ፣ የእስራኤል ቅድመ ቅድም አያቶች ይኖሩ የነበሩበትን ጊዜ ያመለክታል።

ከብዙ ዓመታት በፊት ስለነበረው ጊዜ አስብ
ይህ ቀደም ሲል በነበረው ክፍል ሙሴ ተናግሮት የነበረው ድጋሚ ነው። ሙሴ የእስራኤል ሕዝብ እንደ ሕዝብ በታሪካቸው ላይ እንዲያተኩሩ ይፈልጋል። (See: Parallelism)

ያሳይሃል
“ግልጽ ያደርግልሃል” ወይም “እንድታስተውለው ያስችልሃል”

ለሕዝቡ ርስታቸውን ሰጣቸው
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ሕዝቡ ሊኖሩ በሚገባቸው ስፍራ ላይ አስቀመጣቸው”። “ርስት አድርጎ ወደሚሰጣችሁ” የሚሉ ተመሳሳይ ቃላት በዘዳግም 4፡21 ላይ ይታያሉ። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ደግሞም የአማልክታቸውን ቁጥር በሚወስኑበት ጊዜ ለሕዝቦች ድንበሮችን አደረገላቸው
እግዚአብሔር እያንዳንዱን የሕዝብ ወገን ከአማልክቱ ጋር በራሱ ግዛት እንዲኖር ወስኗል። በዚህ መንገድ የሕዝብ ወገኖችን ጣዖታት ተጽዕኖ ገድቧል።

Deuteronomy 32:9

የእግዚአብሔር ድርሻው ሕዝቡ ነውና፤ ያዕቆብ የርስቱ ዕድል ፈንታው ነው
እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚናገሩት በመሠረቱ አንድ ነገር ነው፣ ስለሆነም ሊጣመሩ ይችላሉ። አ.ት፡ “የያዕቆብ ዘሮች የእግዚአብሔር ርስት ናቸው” (See: Parallelism)

አገኘው -- ጋረደውና ተጠነቀቀለት -- ጠበቀው
“ያዕቆብን አገኘው -- ጋረደውና ተጠነቀቀለት -- ጠበቀው”። ይህንን ምናልባት ሙሴ እንደ ብዙ ሕዝብ አድርጎ የሚናገረው ስለ እስራኤላውያን እንደሆነ መተርጎም ያስፈልግህ ይሆናል። አ.ት፡ “ቅድመ ቅድም አያቶቻችንን አገኛቸው -- ጋረዳቸውና ተጠነቀቀላቸው -- ጠበቃቸው”

ጭው ባለ ምድረ በዳ
እዚህ ጋ “ጭው ያለ” የሚያመለክተው ባዶ መሬት ላይ ነፋሱ ሲነፍስ የሚያሰማውን ድምፅ ነው።

እንደ ዕይኑ ብሌን ጠበቀው
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። የዐይን ብሌን የሚያመለክተው አንድ ሰው ለማየት የሚያስችለውን በዐይኑ ኳስ ውስጥ ያለውን ጥቁሩን ክፍል ነው። ይህ በጣም አስፈላጊና ጥንቃቄ የሚፈልግ የሰውነት ክፍል ነው። ይህ ማለት የእስራኤል ሕዝብ ለእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊና እርሱ ጥበቃ የሚያደርግለትም ነው። አ.ት፡ “በጣም ዋጋ እንዳለውና ውድ ነገር ጠብቆታል”(የአነጋገር ዘይቤ እና Simile የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Deuteronomy 32:11

ንስር ጎጆዋን እንደምትጠብቅና በጫጩቶችዋ ላይ እንደምትሰፍፍ እግዚአብሔር ክንፎቹን ዘርግቶ ወሰዳቸው፣ በላባዎቹም ተሸከማቸው
ይህ ማለት እስራኤላውያን በበረሃ እያሉ እግዚአብሔር ጠብቋቸዋል፣ ተከላክሎላቸዋልም። (See: Simile)

ላባዎች
የወፍ የክንፉ ውጫዊ ጫፍ

መራው -- ከእርሱ ጋር
ሙሴ እንደገና እስራኤላውያንን “ያዕቆብ” በማለት ይናገራል (ዘዳግም 32፡9-10)። ሙሴ እስራኤላውያንን እንደ ብዙ ሕዝብ አድርጎ እንደተናገራቸው መተርጎም ያስፈልግህ ይሆናል። አ.ት፡ “መራቸው -- ከእነርሱ ጋር”

Deuteronomy 32:13

በምድሪቱ የከፍታ ስፍራ ላይ አስኬደው
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። “እርሱን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። አ.ት፡ “እግዚአብሔር በምድሪቱ የከፍታ ስፍራዎች ላይ አስኪዷቸዋል” ወይም “ምድሪቱን እንዲወስዱና እንዲሰፍሩባት እግዚአብሔር ረድቶአቸዋል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

አስኬደው -- መገበው -- አጠገበው
ሙሴ እስራኤላውያንን እንደ “ያዕቆብ” በመቁጠር መናገሩን ይቀጥላል (ዘዳግም 32:9-10)። ሙሴ እስራኤላውያንን እንደ ብዙ ሕዝብ አድርጎ እንደተናገራቸው መተርጎም ያስፈልግህ ይሆናል። “አባቶቻችንን እንዲሄዱ አደረጋቸው -- መገባቸው -- አጠገባቸው” (ተውላጠ ስም የሚለውን ተመልከት)

የእርሻውን ፍሬ መገባቸው
“የሚበላው ብዙ ሰብል ወዳለበት ምድር አመጣው”

ከዐለቱ በሚወጣ ማርና ከባልጩቴማ ቋጥኝ በሚገኝ ዘይት አጠገበው
ምድሪቱ በዐለት ቀዳዳዎች ውስጥ ማር የሚሠሩ ብዙ የጫካ ንቦች ነበሯት። በተጨማሪም፣ በዐለቶች፣ በኮረብቶችና በተራራዎች ላይ የሚበቅሉ ዘይት የሚሰጡ ብዙ የወይራ ዛፎች ነበሩ።

በማር አጠገበው
ይህ ልክ እናት ለሕፃን ልጇ ጡቷን እንደምትሰጠው ዓይነት ነው። “ማር እንዲጠባ ፈቀደለት” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 32:15

ይሹሩን
ሙሴ በሚገባ እንደ ተቀለበና ባለቤቱ ይሹሩን ብሎ እንደሰየመው እንስሳ ስለ እስራኤላውያን ይናገራል። “ ’ይሹሩን’ ማለት ‘ቀጥተኛ የሆነ’ ማለት ነው” የሚል የግርጌ ማስታወሻ ልትጨምርበት ትችላለህ። የአንተ ቋንቋ እስራኤላውያንን እንደ ይሹሩን የማይገልጻቸው ከሆነ የተከፈተው ተለዋዋጭ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም እንደሚያደርገው እስራኤላውያንን እንደ ብዙ ሕዝብ ማመልከት ትችላለህ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

መስባቱን ቀጠለ፣ ረገጠም
በሚገባ የተቀለበው እንስሳ፣ ገር ከመሆን ይልቅ የሚራገጠው ይሹሩን እግዚአብሔር ቢንከባከባቸውም እንኳን ያመጹትን እስራኤላውያንን የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መስባትህን ቀጠልክ፣ በጣም ሰብተህ ነበር፣ ፍጆታህን በልተህ ነበር
ሙሴ ለይሹሩን በሚዘምረው መዝሙር እስራኤላውያንን ይገስጻቸዋል። “ሰባችሁ፣ በጣምም ሰባችሁ፣ የሚቻላችሁን ያህልም ሰባችሁ”

የድነቱን ዐለት
ይህ ማለት እግዚአብሔር እንደ ዐለት ብርቱ ነው፣ ሕዝቡን ለመጠበቅም ይችላል ማለት ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ዐለቱ
ይህ ሙሴ ለእግዚአብሔር የሚሰጠው የተጸውዖ ስም እንደ ዐለት ብርቱና ሕዝቡን ለመጠበቅ የሚችል ነው። ይህንን በዘዳግም 32:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔርን አስቀኑት
እስራኤላውያን እግዚአብሔርን አስቀኑት።

Deuteronomy 32:17

ሠዉ
“የእስራኤል ሕዝብ ሠዉ”

በቅርቡ የመጡትን አማልክት
ይህ ማለት እስራኤላውያን ስለ እነዚህ አማልክት የተማሩት በቅርቡ ነው።

አባቶችህ
ሙሴ ለእስራኤላውያን እንደ ብዙ ሰው ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “የአንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)

አባትህን -- ትተሃል -- ረስተሃል -- ሰጥቶሃል
ሙሴ እስራኤላውያንን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “አንተ” እና “የአንተ” የሚልበት አገባብ ሁሉ ብዙ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)

ዐለቱን ትተሃል
እዚህ ጋ እግዚአብሔር ብርቱና መከላከያ ስለሆነ ዐለት ተብሎ ተጠርቷል። አ.ት፡ “የእግዚአብሔርን የመከላከል ክብካቤ ትተሃል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ዐለቱ
ይህ ሙሴ ለእግዚአብሔር የሚሰጠው የተጸውዖ ስም እንደ ዐለት ብርቱና ሕዝቡን ለመጠበቅ የሚችል ነው። ይህንን በዘዳግም 32:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አባትህ የሆነውን -- ልጅ የሰጠህን
ይህ እግዚአብሔርን ከአባትና ከእናት ጋር ያነጻጽራል። ይኸውም፣ እግዚአብሔር በሕይወት እንዲኖሩና ሕዝብ እንዲሆኑ አድርጎቸዋል ማለት ነው። አ.ት፡ “አባት ያደረጋችሁ ... ሕይወትን የሰጣችሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 32:19

ወንዶችና ሴቶች ልጆቹ
ይህ እግዚአብሔር ሕይወትን የሰጣቸውንና ሕዝብ ያደረጋቸውን የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ፊቴን ከእነርሱ እደብቃለሁ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ከእነርሱ እርቃለሁ” ወይም “እነርሱን መርዳቴን አቆማለሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

መጨረሻቸው ምን እንደሚሆን አያለሁ
“የሚደርስባቸውን አያለሁ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Deuteronomy 32:21

እኔን አስቀንተውኛል
እዚህ ጋ “እኔን” የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው።

አምላክ ያልሆነውን
“ሐሰተኞች አማልክትን”

የማይጠቅሙ ነገሮች
“ነገሮች” ምን እንደሆኑ ግልጽ ማድረግ ይኖርብህ ይሆናል። አ.ት፡ “የማይጠቅሙ ጣዖታት” (See: Assumed Knowl- edge and Implicit Information)

እነዚያን ሕዝብ ያልሆኑትን
“የአንድ ሕዝብ ወገን ያልሆኑ ሰዎች”

ሞኝ ሕዝብ
“ሞኝ” የሚለውን በዘዳግም 32፡6 እንዳለው አድርገህ ተርጉመው።

Deuteronomy 32:22

በቁጣዬ እሳት ተለኩሷልና -- የተራሮች መሠረቶች
እግዚአብሔር ቁጣውን ከእሳት ጋር ያነጻጽረዋል። ይህ የሚያስቆጣውን በሚያጠፋበት ኃይሉ ላይ አጽንዖት ያደርጋል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በቁጣዬ እሳት ተለኩሶ ነዶአል -- ይውጣል -- ተቀምጧል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ስለ ተቆጣሁ እሳት መለኮስ ጀምሬአለሁ፣ ይውጣል . . . የሚያጠፋ ነው . . . ተቀምጧል” ወይም “በምቆጣበት ጊዜ ጠላቶቼን እንደ እሳት አጠፋለሁ፣ በምድርና በ . . . ያለውን ሁሉ አጠፋለሁ . . . እውጣለሁ . . . አስቀምጣለሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እስከ ጥልቁ ሲዖል
“እስከ ሙታን ዓለም ድረስ”

Deuteronomy 32:23

ጥፋትን እከምርባቸዋለሁ
በእስራኤላውያን አናት ላይ የሚቆልላቸው ቆሻሻዎች የሆኑ በሚመስል መልኩ በእስራኤላውያን ላይ ስለሚደርስባቸው መጥፎ ነገሮች እግዚአብሔር ይናገራል። አ.ት፡ “ብዙ መጥፎ ነገሮች እንደሚደርሱባቸው አረጋግጣለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ፍላጻዎቼን ሁሉ በእነርሱ ላይ እወነጭፋቸዋለሁ
እዚህ ጋ እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ላይ በእርግጠኝነት እንዲደርስባቸው የሚያደርጋቸውን መጥፎ ነገሮች አንድ ሰው በቀስቱ ፍላጻዎችን ከማስወንጨፉ ጋር ያነጻጽራል። አ.ት፡ “እነርሱን ለመግደል ማድረግ የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በረሀብ ያልቃሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። የነገር ስም የሆነው “ረሀብ” “ይራባሉ” ወደሚል ግሥ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ይዝላሉ፣ በመራባቸው ምክንያትም ይሞታሉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ እና የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

እነርሱ -- ረሀብ እና በሚያቃጥል ሙቀትና በአሰቃቂ ጥፋት ይዋጣሉ
“የሚያቃጥል እሳት” ለሚለው ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እስራኤላውያን በንዳድ ይሰቃያሉ ወይም 2) በድርቅ ወይም በረሀብ ወቅት የአየሩ ሁኔታ ባለተለመደ መልኩ ሞቃት ይሆናል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እነርሱ . . . ረሀብ፣ የሚያቃጥል ሙቀትና አሰቃቂ ጥፋት ይውጣቸዋል” ወይም “እነርሱ . . . ረሀብ፣ በሚያቃጥል ሙቀትና በአሰቃቂ ጥፋት ይሞታሉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የዱር አራዊትን ጥርስ፣ አፈር ላይ ከሚሳቡ ነገሮች መርዝ ጋር እልክባቸዋለሁ
ጥርስና መርዝ እንስሳው እነዚህን ነገሮች በመጠቀም የሚገድልባቸው ናቸው። አ.ት፡ “እንዲነክሷቸው የዱር አራዊትን፣ ነክሰው እንዲመርዟቸው በአፈር ላይ የሚሳቡትን ነገሮች እልካለሁ” (See: Synecdoche)

Deuteronomy 32:25

ሰይፍ በውጭ ያስቀራቸዋል
እዚህ ጋ “ሰይፍ” የሚወክለው የጠላትን ሰራዊት ነው። አ.ት፡ “እስራኤላውያን ውጪ በሚሆኑበት ጊዜ የጠላት ሰራዊት ይገድላቸዋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ድንጋጤ ያደርጋል
x

Deuteronomy 32:27

የጠላትን ትንኮሳ ያልሰጋሁ ብሆን ኖሮ
“የጠላትን ትንኮሳ ሰግቼ ነበር”

የጠላት ትንኮሳ
ይህ የነገር ስም እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ጠላት እንዳይተነኩሰኝ” ወይም “ጠላት እንድቆጣ እንዳያደርገኝ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ጠላት
እግዚአብሔር የእርሱን ጠላቶች እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “ጠላቴን” ወይም “ጠላቶቼን” (ተውላጠ ስም የሚለውን ተመልከት)

በስሕተት መፍረድ
“አሳስቶ መረዳት”

እጃችን ከፍ ከፍ ብሏል
እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው የሰውን ጉልበት ወይም ኃይል ነው። ከፍ ከፍ ማለት ጠላትን የማሸነፍ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “እኛ ይበልጥ ኃይለኞች በመሆናችን አሸንፈናቸዋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 32:28

ምነው ጥበበኞች በሆኑ፣ ይህንን ያስተውሉ ዘንድ፣ የሚመጣባቸውን ፍርድ ያውቁ ዘንድ
ሙሴ እውነት እንዲሆኑ የሚመኛቸውን አንዳንድ ነገሮች ይናገራል፤ ይሁን እንጂ ጥበበኞች እንዳልሆኑና አለመታዘዛቸው እግዚአብሔር ይህንን ጥፋት እንዲያመጣባቸው እንደሚያደርገው እንዳልተገነዘቡ ያውቃል። (See: Hypothetical Situations)

የሚመጣባቸው ፍርድ
የነገር ስም የሆነው “ፍርድ” እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “በእነርሱ ላይ ሊደርስባቸው ያለ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 32:30

እግዚአብሔር አሳልፎ ካልሰጣቸው -- አንዱ አንድ ሺህ ማሳደድ እንዴት ይችላል
ሙሴ ጠላቶቻቸው ለምን እንዳሸነፏቸው ለማስተዋል ጥበበኞች ስላለመሆናቸው ጥያቄን በመጠቀም ሕዝቡን ይገስጻቸዋል። ይህ ጥያቄ ክፍት በሆነው ተለዋዋጭ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ውስጥ እንዳለው መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አንዱ አንድን ሺህ እንዴት ሊያሳድድ ይችላል፣ ሁለቱ አሥር ሺዎችን እንዲሸሹ ማድረግ እንዴ ይቻላቸዋል?
በውስጠ ታዋቂነት ያለውን መረጃ ግልጽ ልታደርገው ትችላለህ። አ.ት፡ “1 የጠላት ወታደር የእናንተን 1000 ሰዎች እንዴት ሊያሳድድ ቻለ፣ 2 የጠላት ወታደሮችስ የእናንተን 10000 ሰዎች እንዲሸሹ ለማድረግ እንዴት ቻሉ” (See: Numbers and Ellipsis)

Deuteronomy 32:32

ወይናቸው ከሰዶም ወይን ይመጣልና -- ዘለላቸው መራራ ናቸው
ሙሴ ሐሰተኛ አማልክት የሚያመልኩ ጠላቶችን በሰዶም ገሞራ ከኖሩት ክፉ ሕዝቦች እና መርዛማ ፍሬ ከሚያፈሩ የወይን ሐረጎች ጋር ያነጻጽራቸዋል። ይህ ማለት እስራኤላውያን በዙሪያቸው እንዳሉት ሕዝቦች ለማድረግ ከጀመሩ ጠላቶቻቸው ክፉዎች ስለሆኑ እስራኤላውያንን ለሞት ያበቋቸዋል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ወይናቸው ከሰዶም ወይን እና ከገሞራም እርሻ ይመጣል
ወይን ለሕዝብ ወገን ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። “ወይናቸው በሰዶምና ገሞራ ይበቅል የነበረው ወይን ቅርንጫፉ ነው” ወይም አ.ት፡ “በሰዶምና ገሞራ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች እንዳደረጉት በተመሳሳይ መንገድ ክፉ ያደርጋሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ዘለላዎቻቸው
“የወይን ዘለላዎቻቸው

Deuteronomy 32:33

ወይናቸው የእባብ መርዝና የትናንሽ መርዘኛ እባቦች ጨካኝ መርዝ ነው
ሙሴ የእስራኤል ሕዝብን ጠላቶች መርዘኛ ፍሬና ወይን ከሚያበቅል የወይን ሐረግ ጋር ማነጻጸሩን ይቀጥላል። ይህ ማለት ጠላቶቻቸው ክፉዎች ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ትናንሽ መርዘኛ እባቦች
መርዘኛ እባቦች

ይህ ዕቅድ በእኔ በምስጢርነት የተጠበቀ፣ በሀብቴም መካከል ታትሞበት የተቀመጠ አይደለምን?
ይህ ጥያቄ እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ ያለው ዕቅድ ዋጋ እንዳለው ሀብት በምስጢር እንደተጠበቀ አጽንዖት ይሰጣል። ምላሽ የማይፈልገው ጥያቄ እንደ ንግግር ተደርጎ ሊተረጎም ይችላል። ደግሞም፣ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ለእስራኤል ሕዝብና ለጠላቶቻቸው ለማድረግ ያቀድኩትን እኔ አውቃለሁ፣ አንድ ሰው ዋጋ ባላቸው ንብረቶቹ ላይ እንደሚቆልፍባቸው በእነዚያ ዕቅዶች ላይ ቆልፌባቸዋለሁ” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 32:35

በቀል እኔ የምሰጠው ነው፣ ብድራትንም
“በቀል” እና “ብድራትንም” የሚሉት ቃላት በመሠረቱ ትርጉማቸው ተመሳሳይ ነው። አ.ት፡ “እኔ እበቀላለሁ፣ የእስራኤልንም ጠላቶች እቀጣለሁ” (See: Doublet)

ብድራት
አንድ ሰው ስላደረገው ነገር ቅጣት ወይም ሽልማት

እግራቸው ይሰናከላል
መጥፎ የሆነ ነገር ደርሶባቸዋል። አ.ት፡ “ተስፋ የላቸውም” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ለእነርሱ የጥፋት ቀን
“እነርሱን የማጠፋበት ጊዜ”

በእነርሱ ላይ ሊመጡባቸው ያሉ ነገሮች በቶሎ ሊደርሱባቸው ይቸኩላሉ
ለቀጡአቸው በትጋት የሚሮጡ ሰዎችን በሚመስሉበት መልኩ እግዚአብሔር በጠላቶቹ ላይ ሊመጡ ስላሉት መጥፎ ነገሮች ይናገራል። አ.ት፡ “ፈጥኜ እቀጣቸዋለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 32:36

እግዚአብሔር ለሕዝቡ ፍትሕን ይሰጣልና
የነገር ስም የሆነው “ፍትሕ” እንደ ቅጽል ወይም ተውሳከ ግሥ ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ለሕዝቡ ፍትሐዊ የሆነውን ነገር ያደርግላቸዋል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ለአገልጋዮቹ ይራራል
“አገልጋዮቹን መርዳት እንዳለበት ይሰማዋል”

Deuteronomy 32:37

መጠጊያ ያደረጉ ዐለት፣ አማልክታቸው የት አሉ?
ከሌሎች አማልክት ከለላ ስለመፈለጋቸው የእስራኤልን ሕዝብ እግዚአብሔር ይገስጻቸዋል። ይህ ጥያቄ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ተመልከቱ፣ እስራኤላውያን እንደሚጠብቋቸው ያሰቧቸው አማልክት ሊረዷቸው አልመጡም” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የመሥዋዕቶቻቸውን ስብ የበሉ እና የመጠጥ ስጦታ የሆነውን ወይን የጠጡ አማልክት
እዚህ ጋ ለሌሎች አማልክት መሥዋዕት በማቅረባቸው የእስራኤልን ሕዝብ እግዚአብሔር ይገስጻቸዋል። ይህ ጥያቄ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እስራኤላውያን ሥጋና ወይን ያቀረቡላቸው አማልክት ሊረዷቸው አልመጡም” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ይነሡና ይርዷችሁ፤ ከለላ ይሁኗችሁ
በእስራኤላውያን ላይ ለማፌዝ እግዚአብሔር ይህንን ይናገራል። እነዚህ አማልክት ሊረዷቸው እንደማይችሉ ያውቃል። አ.ት፡ “እነዚህ ጣዖታት ሊነሡና ሊረዱ ወይም ሊጠብቋችሁ አይችሉም” (ምጸት የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 32:39

እኔ፣ እኔ እንኳን
“እኔ፣ እኔ ራሴ” ወይም “እኔ፣ እኔ ብቻዬን”። እግዚአብሔር እርሱ ብቻ አምላክ መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት “እኔ”ን ይደጋግማል።

እጄን ወደ ሰማይ አንሥቼ እናገራለሁ
“እጄን ወደ ሰማይ አንሥቼ እምላለሁ” ወይም “ምያለሁ”። እጅን ማንሣት የመማል ምልክት ነው።

ለዘላለም እንደምኖር
“ለዘላለም መኖሬ እርግጥ የመሆኑን ያህል” ወይም “ማለቂያ በሌለው ሕይወቴ እምላለሁ”። በዘዳግም 32:41-42 የተናገረው እንደሚፈጸም ይህ አነጋገር እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያረጋግጣል።

Deuteronomy 32:41

አብረቅራቂ ሰይፌን በምስልበት ጊዜ
“አንጸባራቂውን ሰይፌን በምስልበት ጊዜ”። ይህ ማለት እግዚአብሔር በጠላቶቹ ላይ ለመፍረድና ለመቅጣት ተዘጋጅቷል ማለት ነው። አ.ት፡ “በጠላቶቼ ላይ ለመፍረድ በምዘጋጅበት ጊዜ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እጄ ፍትሕን ማምጣት በሚጀምርበት ጊዜ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው ሙሉውን ሰው ነው (See: Synecdoche)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Deuteronomy 32:42

ፍላጻዎቼ በደም እንዲሰክሩ አደርጋቸዋለሁ፣ ሰይፌም ከደም ጋር ሥጋን ይበላል
ፍላጻዎች ሰው የሆኑና የሚያሰክር መጠጥ ይሰጣቸው ይመስል እግዚአብሔር ስለ ፍላጻዎቹ ይናገራል፣ ሰይፉም ስለ ራበው ደሙ ተንጠፍጥፎ ያልወጣለትን እንስሳ እንደሚበላ ሰው መስሎ ይናገራል። እነዚህ ዘይቤአዊ አነጋገሮች ብዙ ጠላቶችን ለመግደል ፍላጻዎችንና ሰይፍን የሚጠቀምን ወታደር የሚያመለክቱ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ናቸው። ይህ በተራው እግዚአብሔር በጦርነት ውስጥ ጠላቶቹን ስለመግደሉ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው።(ዘይቤአዊ አነጋገር፣ ፈሊጣዊ አነጋገር እና ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

የጠላት አለቆች ከሆኑት ራስ
ሊሆን የሚችለው ትርጉም “በራሳቸው ላይ ረጅም ጸጉር ካላቸው ጠላቶች” የሚለው ነው።

Deuteronomy 32:43

እናንተ ሕዝቦች ደስ ይበላችሁ
ሙሴ በዚያ ኖረው ይሰሙት ይመስል በየሀገራቱ ሁሉ ለሚኖሩ ሰዎች ይናገራል። (See: (ፈሊጣዊ አነጋገር እና Apostrophe የሚለውን ተመልከት))

የአገልጋዮቹን ደም ይበቀላልና፤ በጠላቶቹ ላይ በቀልን ይመልስባቸዋል
እዚህ ጋ “የአገልጋዮቹን ደም” የሚወክለው የተገደሉትን የእርሱን ንጹሕ አገልጋዮች ሕይወት ነው። አ.ት፡ “አገልጋዮቹን የገደሉትን ጠላቶቹን ይበቀላቸዋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 32:44

ነገራቸው -- መናገር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ተናገረ . . . መናገር” ወይም 2) “ዘመረ . . . መዘመር” ናቸው።

በሕዝቡ ጆሮ
x

Deuteronomy 32:46

ተናገራቸው
“ሙሴ ለእስራኤል ሕዝብ ተናገራቸው”

በልባችሁ አኑሩት
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ለ -- ትኩረት ስጡ” ወይም “ስለ -- አስቡ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

መስክሬላችኋለሁ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ባይታዘዙ እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ላይ ምን እንደሚያደርግባቸው የተናገረውን ለማመልከት “መስክሬላችኋለሁ” ማለቱን ያመለክታል ወይም 2) እንዲያደርጉት እግዚአብሔር ያዘዛቸውን ለማመልከት “አዝዣችኋለሁ” የሚሉት ናቸው

ልጆቻችሁ
“ልጆቻችሁና ተወላጆቻችሁ”

ይህ ነው
“ይህ ሕግ ነው”

አላስፈላጊ ነገር አይደለም
ይህ ምጸት በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በጣም ጠቃሚ የሆነ ነገር” (ምጸት የሚለውን ተመልከት)

እርሱ ሕይወትህ ስለሆነ
የነገር ስም የሆነው “ሕይወት” “መኖር” ወደሚል ግሥ ሊተረጎም ይችላል። ሕግን ራሱን የሚወክለውን የመታዘዝን ፈሊጣዊ አነጋገር ግልጽ ማድረግ ይኖርብህ ይሆናል። አ.ት፡ “ብትታዘዝው በሕይወት ትኖራለህና” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ቀኖችህ እንዲረዝሙ
ረጅም ቀናት የረጅም ሕይወት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 4:26 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። አ.ት፡ “ረጅም ጊዜ መኖር እንድትችል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 32:48

የአባሪም ተራሮች
ይህ ሞዓብ ውስጥ የሚገን የተራራ ሰንሰለት ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

በናባው ተራራ አናት አባሪም
“አባሪም እና ናባው ተራራ ላይ ውጣ”

የናባው ተራራ
ይህ ከአባሪም ተራሮች ከፍተኛው ስፍራ ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

በኢያሪኮ ትይዩ
“ከኢያሪኮ ከወንዙ በወዲያ ማዶ”

Deuteronomy 32:50

ወደ ሕዝብህ ተሰብሰብ
ይህ በሙታኑ ዓለም የሙሴ መንፈስ ከዘመዶቹ መንፈስ ጋር እንደሚገናኝ በትህትና የተነገረበት መንገድ ነው። አ.ት፡ “ከአንተ በፊት ከሞቱት አባቶችህ ጋር ተገናኝ” (See: Euphemism)

የሖር ተራራ
ይህ በኤዶም ዳርቻ የሚገኝ ተራራ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

መሪባ
ይህ በበረሃው ውስጥ ሙሴ እግዚአብሔርን ያልታዘዘበት ስፍራ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የጺን ምድረበዳ
ይህ በይሁዳ በስተደቡብ ዳርቻ የሚገኝ ምድረበዳ ስም ነው(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 33

1 የእግዚአብሔር ሰው ሙሴ ከመሞቱ በፊት ለእስራኤላውያን የሰው ቃለ ቡራኬ ይህ ነው። **2** እንዲህም አለ፦ እግዚአብሔር ከሲና መጣ፤ በእነርሱም ላይ ከሴይር እንደ ማለዳ ፀሐይ ወጣ፤ ከፋራን ተራራ አበራላቸው፤ከአእላፋት ቅዱሳኑ ጋር መጣ፤ በስተቀኙ የሚነድ እሳት ነበር። **3** በእርግጥ ሕዝቡን የምትወድ አንተ ነህ፤ ቅዱሳኑ ሁሉ በእጅህ ውስጥ ናቸው። ከእግርህ ሥር ሁሉ ይስገዳሉ፤ ከአንተ ትእዛዝ ይቀበላሉ፤ **4** ይህ ሙሴ የሰጠን ሕግ የያዕቆብ ጉባኤ ርስት ነው። **5** የሕዝቡ አለቆች ከእስራኤል ነገዶች ጋር ሆነው፤ በአንድነት በተሰበሰቡ ጊዜ፤ እግዚአብሔር በይሹሩን ላይ ንጉሥ ነበር። ሮቤል በሕይወት ይኑር፤ አይሙት። **6** የወገኖቹ ቁጥርም ጥቂት ይሁን። **7** ስለይሁዳ የተነገረው ባትኮት ይህ ነው። ሙሴም እንዲህ አለ፦ እግዚአብሔር ሆይ፥ የይዳን ጩኸት ስማ፤ ወደ ወገኖቹም እንደገና አምጣው። ስለእርሱ ተዋጋለት፤ አቤቱ ከጠላቶቹ ጋር ሲዋጋ ረዳቱ ሁን! **8** ስለ ሌዊም ሙሴ እንዲህ አለ፦ ቱሚምህና ኡሪምህ ለምትወደው ሰው ይሁን፤ ማሳህ በተባለው ቦታ ፈተንኸው፤ በመሪባም ውሃ ከእርሱ ጋር ተከራከርህ። **9** ስለ አባቱና ስለ እናቱ ሲናገርም፤ ስለ እነርሱ ግድ የለኝም አለ። ወንድሞቹን አልለያቸውም፤ ልጆቹንም አላወቃቸውም። ስለቃልህ ከለላ አደረገ፤ ኪዳንህንም ጠበቀ። **10** ሥርዓትህን ለያዕቆብ፤ ሕግህንም ለእስራኤል ያስተምራል። ዕጣን በፊትህ፤ ያሚቃጠለውን መሥዋዕት ሁሉ በምሠዊያህ ላይ ያቀርባል። **11** እግዚአብሔር ሆይ፥ ኃይሉን ሁሉ ባርክለት፤ በእጁ ሥራ ደስ ይበልህ፤ በእርሱ ላይ የሚነሡበትን ሸንጣቸውን ቁረጠው፤ ጠላቶቹንም እንደገና እንዳይነሡ አድርገህ ምታቸው። **12** ሙሴ ስለ ብንያም እንዲህ አለ፦ የእግዚአብሔር ወዳጅ የሆነ በእርሱ ተጠብቆ በሰላም ይረፍ፤ ቀኑን ሙሉ ይጋርደዋልና፤ እግዚአብሔር የሚወደውን ሰው በትክሻዎቹ መካከል ያርፋል። **13** መሴ ስለ ዮሴፍ ደግሞ እንዲህ አለው፦ እግአብሔር ምድሩን ይባርክ፤ ውድ በሆኑ ሰማያዊ ነገሮች፥ ጠል ከላይ በማውረድ፤ ከታች በጥልቅ በተንጣለለው ነገሮች ይባርክ። **14** ከፀሐይ በተሠሩ ምርጥ ፍሬ፤ ጨረቃም በምትሰጠው እጅግ መልካም ነገር፤ **15** ከጥንት ተራሮች በተገኘ ምርጥ ስጦታ፤ በዘላለማዊ ኮረብቶች ፍሬያማነት ይባርክ። **16** ምድር በምታስገኘው ውድ ስጦታና በብዛት በቁጥቋጦም ውስጥ በነበረው በእርሱ መልካም ሞገስ። እነዚህ ሁሉ በረከቶች በወንድሞቹ መካከል ገዥ በሆነው፤ በዮሴፍ ራስ ላይ ይውረድ። **17** በግርማው እንደ በኩር ኮርማ ነው፤ ዘንዶቹም የጎሽ ቀንዶች ናቸው። በእነርሱም ሕዝቦችን በምድር ዳርቻ ላይ ያሉትን እንኳ ሳይቀር ይወጋል፤ እነርሱም የኤፍሬም አሥር ሺዎቹ ናቸው። **18** ስለ ዛብሎንም ሙሴ እንዲህ አለ፦ ዛብሎን ሆይ፥ ወደ ውጭ በመውጣትህ፤ አንተም ይሳኮር በድንኳኖችህ ውስጥ ደስ ይበልህ። **19** እነርሱም አሕዛብን ወደ ተራራው ይጠራሉ፤ በዚያም የጽድቅን መሥዋዕት ያቀርባሉ። እነርሱም ከባሕሮች በአሸዋ ውስጥ የተደበቀውን ሀብት ያወጡበታል። **20** ስለ ጋድም ሙሴ እንዲህ አለ፦ የጋድን ግዛት የሚያሰፋ የተባረከ ይሁን! ክንድንና ራስን በመገነጣጠል፤ ጋድ እንደ አንበሳ በዚያ ይኖራል። **21** ለአለቃን ድርሻ ሆኖ የተጠበቀለትን ለም የሆነውን መሬት ለራሱ መረጠ። ከሕዝብ አለቆች ጋር መጣ። በእስራኤል ላይ የወሰነውን የእግዚአብሔርን ሥርዓትንና ፍርዱን ፈጸመ። **22** ስለ ዳንም ሙሴ እንዲህ አለ፦ ዳን ከባሳን ዘሎ የሚወጣ፤ የአንበሳ ደቦል ነው። **23** ስለ ንፍታሌምም ሙሴ እንዲህ አለ፦ ንፍታሌም በእግዚአብሔር ሞገስ ረክቶአል፤ በበረከቱም ተሞልቶአል፤ ባሕሩንና የደቡብን ምድር ይወርሳል። **24** ስለ አሴርም ሙሴ እንዲህ አለ፦ አሴር ከሌሎች ልጆች ይልቅ የተባረከ ይሁን፤ በወንሞቹ ዘንድ ተወዳጅ ይሁን፤ እግሩንም በዘይት ውስጥ ያጥልቅ። **25** በዘመንህና ደህንነትህ ሁሉ የደጃፍህ መቀርቀሪያ ብረትና ናስ ይሁን፤ ኃይልህም በዘመንህ ሁሉ ይኖራል። **26** አንተን ለመርዳት በሰማያት ላይ በግርማው በደመናትም የሚገሠግሥ፤ እንደ ይሽሩን አምላክ ያለ ማንም የለም። **27** ዘላለማዊ አምላክ መኖርያህ ነው፤ የዘላለም ክንዶቹም ከበታችህ ናቸው፤ እርሱን አጥፋው! በማለት፤ ጠላትህን ከፊትህ ያስወግደዋል። **28** ስለዚህ እስራኤል በሰላም ይሆራል:::: የሰማያት ጠል በሚወርድበት፤ እህልና የወይን ጠጅ ባለበት ምድር የያዕቆብን ምንጭ የሚነካው የለም። **29** እስራኤል ሆይ፥ አንተ ቡሩክ ነህ፤ እግዚአብሔር ያዳነው ሕዝብ፤ እንዳንተ ያለ ማን ነው? እርሱ ጋሻህና ረዳትህ፤ የክብርህም ሰይፍ ነው። ጠላቶችህ ተሸብራው በፍርሃት፤ ወደ አንተ ይመጣሉ። አንተም ከፍታቸውን መረማመጃ ታደርጋለህ።

Deuteronomy 33:1

እግዚአብሔር ከሲና መጣ፣ ከሴይርም በእነርሱ ላይ ተነሣ። ከፋራን ተራራ አበራ
ሙሴ እግዚአብሔርን ከንጋት ፀሐይ ጋር ያነጻጽራል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ከሲና በመጣ ጊዜ ከሴይር ወጥታ ከፋራን ተራራ የምታበራዋን ፀሐይ መስሎ ታይቷቸው ነበር” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእነርሱ ላይ
“በእስራኤል ሕዝብ ላይ”

አሥር ሺህ ቅዱሳኑ
“10000 መላእክት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

በቀኝ እጁ የሚያበራ መብረቅ ነበር
ሊሆኑ የሚችሉ ሌሎች ትርጉሞች 1) “በቀኝ እጁ የእሳት ነበልባል ነበር” ወይም 2) “የእሳትን ሕግ ሰጣቸው” ወይም 3) “ተራሮቹን ቁልቁል በመውረድ ከደቡብ መጣ”

Deuteronomy 33:3

ሕዝቡ
“የእስራኤል ሕዝብ”

ቅዱሳኑ ሁሉ በእጅህ ውስጥ ናቸው == እግርህ -- ቃሎችህ
የተጸውዖ ስሞች የሆኑት “የእርሱ” እና “የአንተ” የሚያመለክቱት እግዚአብሔርን ነው። አ.ት፡ “የእግዚአብሔር ቅዱሳን ሁሉ በእጁ ውስጥ ናቸው . . . እግሩ . . . ቃሎቹ” (ተውላጠ ስም የሚለውን ተመልከት)

ቅዱሳኑ ሁሉ በእጅህ ውስጥ ናቸው
እጅ የኃይል እና የጥበቃ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ቅዱስ ሕዝቡን ሁሉ አንተ ትጠብቃለህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ርስት
“ንብረት” ወይም “ዋጋው ውድ የሆነ ንብረት”

Deuteronomy 33:5

ንጉሥ ነበር
“እግዚአብሔር ነገሠ”

ይሹሩን
ይህ የእስራኤል ሌላው ስሙ ነው። ይህንን በዘዳግም 32፡15 እንዳለው አድርገህ ተርጉመው።

ሮቤል በሕይወት ይኑር
ሙሴ እያንዳንዱን የእስራኤል ነገዶች መባረኩን በዚህ ይጀምራል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሆኖም የእርሱ ሰዎት ጥቂቶች ይሁኑ
ሊሆኑ የሚችሉ ሌሎች ትርጉሞች 1) “የእርሱ ሰዎች ጥቂቶች አይሁኑ” ወይም 2) “የእርሱ ሰዎች ጥቂቶች ቢሆኑም እንኳን”

Deuteronomy 33:7

ለይሁዳ ድምፅ
እዚህ ጋ “የይሁዳ ድምፅ” የይሁዳን ሕዝብ ጩኸትና ጸሎት ያመለክታል። አ.ት፡ “የይሁዳ ሕዝብ ወደ አንተ በጸለየ ጊዜ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ረዳቱ ሁን
የነገር ስም የሆነው “ረዳት” እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እንዲዋጋ እርዳው” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 33:8

ቱሚምህና ኡሪምህ
እነዚህ ሊቀ ካህናቱ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ በሚፈልግበት ጊዜ በደረቱ ላይ የሚሸከማቸው ቅዱስ ድንጋዮች ነበሩ። እዚህ ጋ “የአንተ” የሚያመለክቱት እግዚአብሔርን ነው። (See: Forms of You እና የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)

ለአንተ ታማኝ የሆነ
“ለአንተ ቅዱስ የሆነ” ወይም “አንተን ደስ ለማሰኘት የሚፈልገው”። ይህ የሌዊን ነገድ ያመለክታል።

ማሳህ
ይህንን በዘዳግም 6:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ተርጓሚው፣ “ ‘ማሳህ’ ማለት ‘መፈተን’ ማለት ነው” የሚል የግርጌ ማስታወሻ መጨመር ይችላል።

መሪባ
ይህንን በዘዳግም 32:51 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ተርጓሚው፣ “ ‘መሪባ’ ማለት ‘መከራከር’ ወይም ‘መጣላት’ ማለት ነው” የሚል የግርጌ ማስታወሻ መጨመር ይችላል።

Deuteronomy 33:10

የአንተ == የአንተ == አንተ == የአንተ
ሙሴ ለእግዚአብሔር እየተናገረ ነው፣ ስለዚህ እነዚህ ቃላት ሁሉ ነጠላ ቁጥሮች ናቸው።

Deuteronomy 33:11

ተቀበል
በእርሱ ደስ ይበልህ

የእጆቹን ሥራ
እዚህ ጋ “እጆች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሙሉውን ሰው ነው። አ.ት፡ “እርሱ የሠራውን ሥራ ሁሉ” (See: Synecdoche)

ወገባቸውን ሰባብር
ወገብ የጉልበት ማዕከል እንደሆነ ይታሰባል፣ እዚህ ጋ የሚወክለውም ጉልበትን ነው። አ.ት፡ “ጉልበታቸውን ውሰድ” ወይም “ፈጽመህ አጥፋ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ተነሥ == ተነሥ
ይህ ሐረግ ዘይቤአዊ አነጋገር ሆኖ ሁለት ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል። አ.ት፡ “ለመዋጋት ተነሥ . . . እንዳያንሠራሩ አድርጋቸው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በ -- ላይ ተነሥ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ከ -- ጋር ተዋጋ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 33:12

በእግዚአብሔር የተወደደ -- ይኖራል
እዚህ ጋ ሙሴ የሚያመለክተው የብንያም ነገድ አባላትን ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር በሕይወት እንዲኖሩ የሚወድላቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በደኅንነት ይኖራል
የነገር ስም የሆነው “ደኅንነት” ግሣዊ ሐረግ በመጠቀም ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ማንም ሊጎዳው በማይችልበት ስፍራ ይኖራል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

በእግዚአብሔር ክንዶች መካከል ይኖራል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እግዚአብሔር የብንያምን ነገድ በኃይሉ ይከላከልላቸዋል ወይም 2) እግዚአብሔር በብንያም ነገድ ኮረብታማ አካባቢ ይኖራል። በሁለቱም ትርጉሞች፣ እግዚአብሔር ይንከባከባቸዋል የሚል አንድምታ አለው።

Deuteronomy 33:13

ስለ ዮሴፍ
ይህ የሚያመለክተው የኤፍሬምንና የምናሴን ነገዶች ነው። ሁለቱም ነገዶች የተገኙት ከዮሴፍ ነው።

የእርሱ ምድር በእግዚአብሔር ይባረክ
“የእርሱ” የሚለው ቃል የኤፍሬምንና የምናሴን ነገዶች የሚወክለውን ዮሴፍን ያመለክታል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ምድራቸውን ይባርክ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ከሰማይ በሆኑ የከበሩ ነገሮች፣ በጠል
“ከሰማይ በሆነ የከበረ ጠል” ወይም “ከሰማይ በሆነ የከበረ ዝናብ”

ጠል
ቅዝቃዜ ባለው ማለዳ ላይ በቅጠልና ሣር ላይ ውሃ የሚፈጥር። ይህንን በዘዳግም 32:2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ከታች በሚተኛ ጥልቅ
ይህ በከርሠ ምድር ውስጥ የሚገኘውን ውሃ ያመለክታል።

Deuteronomy 33:14

የእርሱ ምድር ይባረክ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ይህንን በዘዳግም 33:13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ምድሩን ይባርክ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ከፀሐይ በሚሆን የከበሩ ነገሮች መከር
“ፀሐይ እንዲበቅሉ በሚያደርጋቸው ምርጥ ሰብሎች”

ወራት በሚያስገኙት የከበሩ ነገሮች
“ከወር እስከ ወር በሚበቅሉ ምርጥ ሰብሎች”

ምርጥ ነገሮች -- የከበሩ ነገሮች
ሙሴ ምናልባት የምግብ ሰብሎችን ሳያመለክት አይቀርም። የዚህ አነጋገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አ.ት፡ “እጅግ ምርጥ የሆኑ ፍሬዎች

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

. . . የከበሩ ፍሬዎች” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

የጥንት ተራሮች
“ከረጅም ዘመን ጀምሮ የኖሩ ተራሮች”

የዘላለም ኮረብቶች
“ለዘላለም የሚኖሩ ኮረብቶች”

Deuteronomy 33:16

የእርሱ ምድር ይባረክ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ይህንን በዘዳግም 33፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእርሱን ምድር እግዚአብሔር ይባርክ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ብዛቱን
x

Deuteronomy 33:17

በግርማው እንደ በኩር በሬ ነው
በሬ በዘይቤአዊ አነጋገር ትልቅና ጉልበታም የሆነን ነገር ያመለክታል። “በኩር” የሚለው ቃል በዘይቤአዊ አነጋገር ክብር ማለት ነው። አ.ት፡ “ሰዎች ብዙና ኃያላን የሆኑትን የዮሴፍን ተወላጆች ያከብሯቸዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ቀንዶቹ የ -- ቀንዶች ናቸው
ቀንድ የብርታት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “እርሱ እንደ -- ብርቱ ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእነርሱ ይገፋል
በቀንዶቹ መግፋቱ ስለ ብርታቱ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “እርሱ በጣም ብርቱ ስለሆነ ይገፋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የኤፍሬም አሥር ሺዎች -- የምናሴ ሺዎች
ይህ ማለት የኤፍሬም ነገድ ከምናሴ ነገድ ይልቅ ይበረታል። አ.ት፡ “የኤፍሬም ሕዝብ ከ10000 ብዙ ዕጥፍ . . . (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 33:18

ዛብሎን በመውጣትህ፣ አንተም ይሳኮር በድንኳኖችህ ደስ ይበልህ
የዛብሎን ሕዝብ የሚገኙት በሜዴትራንያን ባህር አጠገብ ነበር። በባህር ላይ እየተጓዙ ከሌሎች ሕዝቦች ጋር ይገበያዩ ነበር። የይሳኮር ሕዝቦች በእርሻና ከብት በማርባት ሰላማዊ ኑሮን የሚመርጡ ነበሩ። በውስጠ ታዋቂነት ያሉ መረጃዎችን ግልጽ ልታደርጋቸው ትችላለህ። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

እነርሱ በዚያ ያቀርባሉ
“እነርሱ የሚያቀርቡት በዚያ ነው”

የጽድቅን መሥዋዕት
“ተቀባይነት ያላቸውን መሥዋዕቶች” ወይም “ተገቢነት ያላቸውን መሥዋዕቶች”

ከባህር የሚትረፈረፈውን ይጠባሉና፣ በባህር ዳር ካለው አሸዋም የሚገኘውን
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) በባህሩ ማዶ ካሉ ሕዝቦች ጋር ይገበያያሉ ወይም 2) አሸዋን በመጠቀም የሸክላ ሥራ መሥራት ጀምረው ነበር።

ከባህር የሚትረፈረፈውን ይጠባሉና
እዚህ ጋ “መጥባት” የሚለውን ቃል የዕብራይስጡ ትርጉም አንድ ሕፃን ልጅ የእናቱን ጡት እንዴት እንደሚመገብ ያመለክታል። ይህ ማለት አንድ ሕፃን ከእናቱ ወተት እንደሚያገኝ ሕዝቡ ከባህር ሀብት ያገኛሉ። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 33:20

ጋድን የሚያሰፋው የተባረከ ይሁን
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “እግዚአብሔር ጋድን ይባርከው፣ የሚኖርበትንም ብዙ መሬት ይስጠው” ወይም 2) ለጋድ የሚኖርበትን ብዙ ምድር ሰጥቶታልና ሰዎች እግዚአብሔር መልካም ነው ይበሉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እንደ ሴት አንበሳ በዚያ ይኖራል፣ ክንድንና ራስንም ይገነጣጥላል
ይህ ማለት የጋድ ሕዝብ ብርቱና ደህንነቱ የተጠበቀ ስለሆነ በጦርነት ጠላቶቻቸውን ያሸንፋሉ። (See: Simile)

Deuteronomy 33:22

ዳን ከባሳን ዘሎ የሚወጣ የአንበሳ ደቦል ነው
የዳን ሕዝብ እንደ አንበሳ ደቦል ብርቱዎች ናቸው፣ በባሳን የሚኖሩትን ጠላቶቻቸውን ወጉ። በውስጠ ታዋቂነት ያሉትን መረጃዎች ግልጽ ልታደርጋቸው ትችላለህ። (See: (ዘይቤአዊ አነጋገር እና Ellipsis የሚለውን ተመልከት))

Deuteronomy 33:23

ዳን ከባሳን ዘሎ የሚወጣ የአንበሳ ደቦል ነው
የዳን ሕዝብ እንደ አንበሳ ደቦል ብርቱዎች ናቸው፣ በባሳን የሚኖሩትን ጠላቶቻቸውን ወጉ። በውስጠ ታዋቂነት ያሉትን መረጃዎች ግልጽ ልታደርጋቸው ትችላለህ። (See: (ዘይቤአዊ አነጋገር እና Ellipsis የሚለውን ተመልከት))

በሞገስ ረክቷል
እግዚአብሔር በንፍታሌም መደሰቱ “ሞገስ” ምግብ ሆኖ ንፍታሌም ዳግመኛ እስከማይራብ ድረስ የበላው በሚመስል መልኩ ተነግሮለታል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር በእርሱ ስለ ተደሰተበት የሚፈልገው መልካም ነገሮች ሁሉ አሉት” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የእግዚአብሔር በረከት ሙላት
በረከቶች ምግብ ሆነው ንፍታሌም ተጨማሪ መያዝ እስከማይችል ድረስ የበላው በሚመስል መልኩ ተነግሯል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ስለ ባረከው የሚፈልገው ሁሉ አለው”

ሀብት ውሰድ
ሙሴ የንፍታሌምን ነገድ አንድ ሰው እንደ ሆኑ አድርጎ ይናገራል፣ ስለዚህ እነዚህ ቃላት ነጠላ ቁጥሮች ናቸው። (See: Forms of You)

በስተምዕራብና በስተደቡብ ያለ ምድር
ይህ በገሊላ ሐይቅ ዙሪያ ያለውን ምድር ያመለክታል። የዚህ ንግግር ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

Deuteronomy 33:24

እግሩን በወይራ ዘይት ውስጥ ያጠልቃል
የወይራ ዘይት ለምግብነትና ለፊትና ለክንድ ቆዳ ጥቅም ላይ ይውል ነበር። እግር ይቆሸሻል፣ ስለዚህ እግርን በወይራ ዘይት ውስጥ መጨመር ዋጋ ያለውን ዘይት ማበላሸት ይሆናል። የዚህ ንግግር ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አ.ት፡ “ማባከን እንዲቻለው ብዙ የወይራ ዘይት ይኑረው” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የከተማህ የበር መቀርቀሪያዎች - ቀኖችህ - ደህንነትህ
አንድ ሰው የሆኑ ይመስል ሙሴ የሚናገረው ለአሴር ነገድ ነው፣ ስለዚህ “የአንተ” የሚሉት አገባቦች ሁሉ ነጠላ ቁጥሮች ናቸው። (See: Forms of You)

የከተማህ በር መቀርቀሪያዎች ብረትና ነሐስ ይሁኑ
ከተሞች ጠላት እንዳይገባባቸው በበሮቻቸው አግድመት ላይ ረጃጅም መቀርቀሪያዎች ይኖራቸው ነበር። የዚህ ንግግር ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አ.ት፡ “በጠላቶችህ ከመጠቃት እንድትድን” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

Deuteronomy 33:26

ይሹሩን
ይህ የእስራኤል ሕዝብ ሌላው ስሙ ነው። ትርጉሙም “ቀጥተኛ የሆነ” የሚል ነው። ይህንን በዘዳግም 32:15 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

በሰማያት መካከል የሚራመድ -- በደመና ላይ
በጦር ሜዳ ላይ በሠረገላው እንደሚሄድ ንጉሥ በጠፈር መካከል በደመና ላይ የሚሄድ ይህ የእግዚአብሔር ምስል ነው። አ.ት፡ “ንጉሥ በጦር ሜዳ መካከል እንደሚሄድ በሰማያት መካከል ይሄዳል. . . በሠረገላው እንዳለ ንጉሥ በደመናት ላይ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሊረዳህ
“አንተን ለመርዳት” ሙሴ እስራኤላውያንን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “አንተ” የሚለው ቃል እዚህ ጋ ነጠላ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)

Deuteronomy 33:27

የዘላለም አምላክ መጠጊያ ነው
የነገር ስም የሆነው “መጠጊያ” መጠለያ ወይም ከአደጋ ማምለጫ ስፍራ ማለት ሲሆን እንደ ግሥ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የዘላለም አምላክ ሕዝቡን ይጠብቃል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

የዘላለም ክንዶች ከበታች ናቸው
“የዘላለም ክንዶች” የሚሉት ቃላት እግዚአብሔር ሕዝቡን ለዘላለም እንደሚጠብቃቸው ለሰጠው ተስፋ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ሕዝቡን ለዘላለም ይረዳቸዋል፣ ይንከባከባቸዋልም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

-በማለት ወግቶ ያስወጣቸዋል
ሙሴ እርሱ የሚናገረው የሚፈጸም ስለመሆኑ አጽንዖት ለመስጠት ወደፊት ሊሆን ያለውን ባለፈ ጊዜ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “እርሱ ወግቶ ያስወጣቸዋል. . . ይላል” (See: Predictive Past)

በፊትህ -- አጥፋው
ሙሴ እስራኤላውያንን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “አንተ” የሚለው ቃልና “አጥፋው” የሚለው ትዕዛዝ እዚህ ጋ ነጠላ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)

“አጥፋው!” ይላል
በአንተ ቋንቋ ይህ ቀጥተኛ ትዕምርተ ጥቅስ በሚገባ የማያገለግል ከሆነ ቀጥተኛ ወዳልሆነው ትዕምርተ ጥቅስ ልትለውጠው ትችላለህ። አ.ት፡ “እንድታጠፋቸው ይነግርሃል” (See: Direct and Indirect Quotations)

Deuteronomy 33:28

እስራኤል ይኖራል -- የያዕቆብ ምንጭ የተጠበቀ ነበር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሙሴ እርሱ የሚናገረው የሚፈጸም ስለመሆኑ አጽንዖት ለመስጠት ወደፊት ሊሆን ያለውን ባለፈ ጊዜ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። “እስራኤል ይኖራል . . . የያዕቆብ ምንጭ የተጠበቀ ይሆናል” ወይም 2) ሙሴ፣ “እስራኤል ይኑር . . . የያዕቆብ ምንጭም የተጠበቀ ይሁን” በማለት እስራኤልን እየባረከ ነው የሚሉት ናቸው። (See: Predictive Past)

የያዕቆብ ምንጭ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የያዕቆብ ቤት ወይም 2) የያዕቆብ ተወላጆች (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሰማያቱ ጠልን ያንጠባጥቡ
ጠል የዝናብን ያህል አስፈላጊ ስለመሆኑ ተነግሯል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሙሴ “እንደ ዝናብ ብዙ ጠል ምድሪቱን ይሸፍናት” በማለት እስራኤልን እየባረከ ነው ወይም 2) ሙሴ “ብዙ ጠል እንደ ዝናብ ምድሪቱን ይሸፍናታል” በማለት ወደ ፊት ምን ሊሆን እንዳለ ይነግራቸዋል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ጠል
ቅዝቃዜ ባለበት ጠዋት በቅጠሎችና በሣር ላይ የሚገኝ ውሃ። ይህንን በዘዳግም 32:2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Deuteronomy 33:29

በግርማ -- እንዳንተ ያለ፣ በእግዚአብሔር የዳነ ሕዝብ ማነው?
ይህ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እንደ ንግግር ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። ድግሞም በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እንደ አንተ ያለ እግዚአብሔር ያዳነው የሕዝብ ወገን የለም . . . በግርማ”። (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ጋሻ -- ሰይፍ
ይህ አገላለጽ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከጠላቶቻቸው እንደሚከላከልላቸውና ጠላቶቻቸውን እንዲወጉ እንደሚያስችላቸው ይናገራል። (See: Merism)

የረዳትህ ጋሻ
“ጋሻ” የሚለው ቃል እግዚአብሔር እስራኤላውያንን የመጠበቁና የመከላከሉ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። የነገር ስም የሆነው “ረዳት” እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “አንተን የሚጠብቅህና የሚረዳህ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

የግርማዊነትህ ሰይፍ
“ሰይፍ” የሚለው ቃል ጦርነቶችን ለማሸነፍ በሰይፍ ለመግደል ኃይል ማግኘትን የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ግርማ እንዲኖርህና ጦርነቶችን እንድታሸንፍ የሚያስችልህ እርሱን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የከፍታ ስፍራቸውን ትረግጣለህ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሌሎች ሕዝቦች ሐሰተኞች አማልክትን ያመለኩባቸውን ስፍራዎች እስራኤላውያን ይደመስሱታል ወይም 2) እስራኤላውያን ጠላቶቻቸውን ድል በሚያደርጉበት ጊዜ በጀርባቸው ላይ ይረማመዱባቸዋል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 34

1 ሙሴ ከሞዓብ ሜዳ ተነሥቶ ለኢያሪኮ ትይዩ ወደ ሆነው ፈስጋ ጫፍ ወደ ናባው ተራራ ሄደ። በዚያም እግዚአብሔር ከገለዓድ እስከ ዳን ያለውን ምድሪቱን ሁሉ፤ **2** ንፍታሌምን ሁሉ፥የኤፍሬምንና የምናሴን ግዛት እስከ ምዕራብ ባሕር ድረስ ያለውን የይሁዳን ምድር ሁሉ አሳየው፤ **3** ኔጌብንና የዘንባባ ከተማ ከሆነችው ከኢያሪኮ ሸለቆ እስከ ዞዓር ያለውን ምድር ሁሉ አሳየው። **4** ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር ለአብርሃም፥ ለይስሐንና ለያዕቆብ ለአባቶቻችሁ እሰጣለሁ ብዬ በመሐላ ቃል የገባሁላቸው ምድር፥ በዐይንህ እንድታያት አድርጌአለሁ፤ ነገር ግን ወደዚያ አትሻገርም አለው። **5** እግዚአብሔር እንደተናገረው የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴ በሞዓብ ምድር ሞተ። **6** በሞዓብ ምድር በቤተ ፌጎር ፊት ለፊት ባለው ሸለቆ እግዚአብሔር ቀበረው፤ ይሁን እንጂ መቃብሩ የት እንደ ሆን እስከ ዛሬ ማንም አያውቅም። **7** ሙሴ በሞተ ጊዜ ዕድሜው መቶ ሃያ ዓመት ነበር፤ ሆኖም ዐይኑ አልፈዘዘም፤ ጉልበቱም አልደከመም። **8** የልቅሶውና የሐዘኑ ጊዜ እስኪያበቃ ድረስ እስራኤላውያን በሞዓብ ሜዳ ሠላሳ ቀን አለቀሱለት። **9** ሙሴ እጆቹን ጭኖበት ስለ ነበር የነዌ ልጅ ኢያሱ በጥበብ መንፈስ ተሞላ። ስለዚህ እስራኤላውያን ሁሉ አደመጡት፤ እግዚአብሔር ሙሴን አዞት የነበረውንም ሁሉ አደረገ። **10** እግዚብሔር ፊት ለፊት ያወቀው እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ ከዚያ ወዲህ በእስራኤል አልተነሣም። **11** እግዚአብሔር ልኮት እነዚያን ታምራዊ ምልክቶችና ድንቆች ሁሉ በግብፅ በፈርዖን በሹማምንቱና በምድሪቱ ሁሉ ላይ እንዲያደርግ የላከውን ያደረገ ማንም ሰው አልነበረም። **12** ሙሴ በእስራኤል ሁሉ ፊት ያሳየውን ታላቅ ኃይል ያሳየ ወይም ያደረገውን አስደናቂ ተግባር የፈጸመ ማንም ነቢይ የለም።

Deuteronomy 34:1

የናባው ተራራ
ይህ ከአባሪም የተራራ ሰንሰለት በስተሰሜን የሚገኝ የፈስጋ ተራራ ጫፉ ነው። ይህንን በዘዳግም 32:49 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ፈስጋ
ይህንን በዘዳግም 3:17 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የዘንባባ ከተማ
x

Deuteronomy 34:4

ቤተ ፌጎር
ይህ በሞዓብ የነበረ መንደር ነው። ይህንን በዘዳግም 3:29 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

በዐይኖችህ ተመልከተው
“ለራስህ ተመልከተው”

እስከ ዛሬ ድረስ
ይህ የሚያመለክተው ይህ የተጻፈበትን ወይም የታረመበትን ጊዜ እንጂ በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ ያለውን የአሁኑን ጊዜ አይደለም።

Deuteronomy 34:7

የአንድ መቶ ሃያ ዓመት ዕድሜ -- ሠላሳ ቀን
“የ120 ዓመት ዕድሜ . . . 30 ቀን” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ዐይኑ አልፈዘዘም፣ የተፈጥሮ ጉልበቱም አልደከመም
ይህ ማለት ዐይኖቹና አካሉ ገና ብርቱና ጤናማ ነበሩ ማለት ነው።

Deuteronomy 34:9

የነዌ ልጅ
ይህንን በዘዳግም 1:38 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ኢያሱ -- በጥበብ መንፈስ ተሞልቶ ነበር
ጸሐፊው ኢያሱን አንድን ነገር እንደሚይዝ ዕቃ፣ መንፈስን ደግሞ በመያዣው ውስጥ እንደሚጨመር ቁሳዊ አካል አድርጎ ይናገራል። አ.ት: “ . . . በጣም ጥበበኛ እንዲሆን እግዚአብሔር ኢያሱን አስቻለው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሙሴ እጆቹን በእርሱ ላይ ጭኖበት ነበር
የዚህ ንግግር ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አ.ት: “ኢያሱ እግዚአብሔርን እንዲያገለግል ለመለየት ሙሴ እጆቹን በእርሱ ላይ ጭኖበት ነበር” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

Deuteronomy 34:10

እግዚአብሔር ፊት ለፊት ያወቀው
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህ ማለት እግዚአብሔርና ሙሴ በጣም የቀረበ ግንኙነት ነበራችው ማለት ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በታላላቆቹ ሁሉ
“ታላላቆቹን ሁሉ ያደረገ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Joshua

Joshua

Chapter 1

1 እንዲህም ሆነ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴ ከሞተ በኋላ እግዚአብሔር የሙሴ ዋና ረዳት የሆነውን የነዌ ልጅ ኢያሱን እንዲህ ብሎ ተናገረው፦ 2 አገልጋዬ ሙሴ ሞቶአል። ስለዚህም ለእስራኤል ልጆች ወደምሰጣቸው ምድር አንተና ይህ ሕዝብ ሁሉ ተነሥታችሁ ይህን ዮርዳኖስ ተሻገሩ። 3 የእግራችሁ ጫማ የሚረግጥውን ቦታ ሁሉ ለእናንተ ሰጥቼአለሁ።ለሙሴም ተስፋ እንደ ሰጠሁት ሰጥቻችኋለሁ። 4 ከምድረ በዳው ከዚህም ከሊባኖስ ጀምሮ እስከ ታላቁ ወንዝ እስከ ኤፍራጥስ ድረስ፤ የኪጢያውያን ምድር ሁሉ እስከ ፀሐይ መግቢያ እስከ ታላቁ ባሕር ድረስ ዳርቻአሁ ይሆናል። 5 በሕይወትህ ዘመን ሁሉ ማንም ሊቋቋምህ አይችልም። ከሙሴ ጋር እንደ ነበርሁ እንዲሁ ከአንተ ጋር እሆናለሁ። አልጥልህም አልትውህም። 6 ለአባቶቻቸው፦እሰጣችኋለሁ ብዬ ተስፋ የሰጠ'ኋችሁውን ምድር ይህ ሕዝብ እንዲወርስ ታደርጋለህና ጽና አይዞህ። 7 ስለዚህም ጽና እጅግ በርታ። አገልጋዬ ሙሴ ያዘዘህን ሕግን ሁሉ ትጠብቀው ዘንድ ተጠንቀቅ። በምትሄድበትም ሁሉ እንዲከናወንልህ ወደ ቀኝ ወይም ወደ ግራ አትበል። 8 ስለዚህ ሕግ መጽሐፍ ሁልጊዜ ተናገር። የተጻፈበትንም ሁሉ ትጠብቅ ዘንድ በቀንና በሌሊትም አሰላስለው። የዚያን ጊዜም የተከናወነልህና የተሳከልህ ትሆናለህ። 9 በምትሄድበት ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና፦ "ጽና፥ አይዞህ፥ አትፍራ፥ ተስፋ አትቁረጥ ብዬ አላዘዝሁህምን?" 10 ኢያሱም የሕዝቡን አለቆች እንዲህ ብሎ አዘዘ፦ 11 "በሰፈሩ መካከል እለፉ፤ ሕዝቡንም፦ ለራሳችሁ ስንቃችሁን አዘጋጁ ብላችሁ እዘዙአቸው። እግዚአብሔር አምላካችሁ እንዲትወርሱ ወደሚሰጣችሁ ምድር በሦስት ቀናት ውስጥ ይህን ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ ትወርሳላችሁ። 12 ኢያሱም የሮቤልን ልጆች የጋድንም ልጆች የምናሴንም ነገድ እኩሌታ እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፦ 13 የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴ እንዲህ ብሎ ያዘዛቸውን ቃል አስቡ፦አምላካችሁ እግዚአብሔር እረፍት ይሰጣችኋል፤ይህንንም ምድር ይሰጣችኋል። 14 ሚስቶቻችሁ፥ ልጆቻችሁና ከብቶቻችሁ ሙሴ በዮርዳኖስ ማዶ በሰጣችሁ ምድር ይቀመጣሉ። ነገር ግን ተዋጊ የሆኑ ሰዎቻችሁ እግዚአብሔር ለእናንተ እንደሰጣችሁ 15 ወንድሞቻችሁን እረፍት እስኪሰጥ ድረስ ከወንድሞቻችሁ ፊት በመሆን እነርሱንም ለመርዳት ይሄዳሉ ። እነርሱም ደግሞ አምላካችሁ እግዚአብሔር የሚሰጣቸውን ምድር ይወርሳሉ። ከዚያም በኋላ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴ ብዮርዳኖስ ማዶ በፀሐይ መውጫ ወደሰጣችሁ ወደ ርስታችሁ ትመለሳላችሁ፤ ትወርሳላችሁም። 16 እነርሱም ለኢያሱ እንዲህ ብለው መለሰለት፦ያዘዝኸንን ነገር ሁሉ እናደርጋለን፤ ወደምትልከንም ስፍራ ሁሉ እንሄዳለን። 17 ለሙሴ እንደ ታዘዝን ለአንተ ደግሞ እንታዘዛለን። ከሙሴ ጋር እንደ ነበረ እግዚአብሔር አምላክህ ብቻ ከአንተጋር ይሁን። 18 በትእዛዝህ ላይ የሚያምፅና ቃልህን የማይታዘዝ ማንም ቢሆን ይገደል። ብቻ ጽና፥ በርታ።

Joshua 1:1

ያህዌ
ይህ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለህዝቡ ራሱን የገለጸበት ስም ነው። ይህንን እንዴት እንደሚተረጉሙት ስለ ያህዌ የቃል ትርጉም ገጽ/ጽሁፍን ይመልከቱ።

ነዌ
የኢያሱ አባት (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህንን ዮርዳኖስን አቋርጡ
"ማቋረጥ" ማለት "ከወንዙ ማዶ መሄድ/ወንዙን ማቋረጥ" ማለት ነው። "ከዚህ ዳርቻ ወደ ዮርዳኖስ ወዲያኛው ዳርቻ መሄድ/ማቋረጥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ እና ይህ ህዝብ ሁሉ
"አንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢያሱን ነው። (አንተ የሚለውን ቃል መገለጫ መልኮች ይመልከቱ)

ሁሉንም ስፍራ ሰጥቼሃለሁ
እግዚአብሔር ምድሪቱን በመጭው ጊዜ ለእስራኤል መስጠቱ የተገለጸው አስቀድሞ እንደሰጣቸው ተደርጎ ነው። ይህ ምድሪቱን በእርግጥ እንደሚሰጣቸው አጉልቶ ያሳያል። "ለእናንተ ሁሉንም ስፍራ እሰጣችኋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የወደፊት ሃላፊ ጊዜ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእናንተ ሰጥቻለሁ
"እናንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢያሱን እና የእስራኤል ህዝብን ሁለቱንም ነው። (አንተ የሚለውን ቃል መገለጫ መልኮችን ይመልከቱ)

የእግራችሁ ጫማ የሚረግጠውን ስፍራ ሁሉ
ይህ የሚያመለክተው የዮርዳኖስን ወንዝ ሲያቋርጡ ኢያሱ እና እስራኤላውያን የሚጎዙበትን ስፍራ ሁሉ ነው። "በዚህ ምድር በምትሄዱበት ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 1:4

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ከኢያሱ ጋር ንግግሩን ቀጠለ

የአንተ ምድር
"የአንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢያሱን ብቻ ሳይሆን የእስራኤልን ነገዶች በሙሉ ነው። (አንተ የሚለውን ቃል መገለጫ መልኮችን ይመልከቱ)

በፊትህ ለመቆም
በቁጥር 5 "አንተ" እና "የአንተ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ኢያሱን ነው። (አንተ የሚለውን ቃል መገለጫ መልኮችን ይመልከቱ)

እኔ አንተን አልተውህም ወይም አልጥልህም
"መተው" እና "መጣል" የሚሉት ቃላት በመሰረታዊነት አንድ አይነት ነገሮች ናቸው። ያህዌ እነዚህን አንድ ላይ ያጣመራቸው እዘኒህን ነገሮች እንደማያደርግ ለማጉላት ነው። "በእርግጥ ሁልጊዜም ከአንተ ጋር እሆናለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም እና ጥንድ አሉታዎች የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Joshua 1:6

አጠቃላይ መረጃ ፡
ያህዌ ለኢያሱ ጥብቅ ትዕዛዛትን ሰጠው (ሃላፊነቶች -ሌሎች ጥቅሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በርታ ደግሞም ጽና
ያህዌ ኢያሱን በጽናት ፍርሃቶቹን እንዲያሸንፍ ያዘዋል። (ሃላፊነቶች -ሌሎች ጥቅሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚህ ወደ ቀኝ ወይም ወደ ግራ አትበል
ይህ በአዎንታዊ ትዕዛዝ ሊጻፍ ይችላል። "ይህንን በትክክል ተከተል" ወይም "በትክክል ተከተላቸው" (ሃላፊነቶች -ሌሎች ጥቅሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ፍሬያማ ሁን
"ግብህን ጨብጥ" ወይም "ግብህ ላይ ድረስ"

Joshua 1:8

አጠቃላይ መረጃ ፣
ያህዌ ከኢያሱ ጋር ንግግሩን ቀጠለ

ሁልጊዜም ትናገራለህ
"ሁልጊዜ" የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ መናገር ተጋኖ የተገለጸበት ነው። (ኩሸት እና ማጠቃለል የሚሉትን ይመልከቱ)

የበለጸገ እና ስኬታማ
እነዚህ ሁለት ቃላት በመሰረቱ አንድ ትረጉም ይዘዋል እናም ታላቅ ብልጽግናን ያጎላሉ። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ አላዘዝኩህምን?
ይህ ያህዌ ኢያሱን ማዘዙን ያመለክታል። "እኔ አዝዤሃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በርታ ደግሞም ጽና!
ያህዌ ኢያሱን እያዘዘው ነው። (ሃላፊነቶች -ሌሎች ጥቅሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 1:10

ወደ ሰፈር ገብታችሁ ‘ተዘጋጁ... ውረሱ' ብላችሁ ህዝቡን እዘዙ።'
በጥቅስ ውስጥ ቀረበው ቀጥተኛ ባለሆነ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል። "ወደ ሰፈር ግቡ ህዝቡ ለራሱ የሚሆነውን እንዲያዘጋጅ እዘዙ። በሶስት ቀናት ውስጥ ይህንን ዮርዳኖስን አቋርጠው ያህዌ አምላካቸው እንዲወርሷት የሰጣቸውን ምድር ይወርሳሉ።" (በጥቅስ ውስጥ የሚገኝ ጥቅስ የሚለውን ይጠቀሙ)

ህዝቡ
ይህ የእስራኤልን ህዝብ ያመለክታል። "የእስራኤል ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በሶስት ቀናት ውስጥ
እዚህ ስፍራ ያህዌ የሚገኝበትን ቀን እንደ መጀመሪያ ቀን እየቆጠረ ነበር። "ከአሁን በኋላ ሁለት ቀናት" ወይም "ከነገ በኋላ ባለው ቀን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ይህንን ዮርዳኖስን አቋርጡ
"አቋርጡ" የሚለው የሚያመለክተው ከወንዙ ወዲያ ማዶ መሻገርን ነው። "ከዮርዳኖስ ወንዝ ወዲያ ማዶ ተጓዙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 1:12

አጠቃላይ መረጃ:
የሮቤል፣ የጋድ እና የምናሴ ነገድ እኩሌታ ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምስራቅ መቀመጥ መረጡ። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የሮቤል ነገድ:/ሮቤላዊያን
እነዚህ የሮቤል ትውልዶች ነበሩ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የጋድ ነገድ/ጋድአዊያን
እነዚህ የጋድ ትውልዶች ነበሩ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 1:14

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሮቤላዊያን፣ ለጋድአዊያን እና ለምናሴ ነገድ እኩሌታ መናገሩን ቀጠለ

ልጆቻችሁ
"የእናንተ ትናንሽ ልጆች"

ከዮርዳኖስ ባሻገር
ይህ የሚያመለክተው ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ መስራቅ ያለውን ስፍራ ነው። ቆይቶ ብዙዎቹ እስራኤላውያን ከዮርዳኖስ በስተ ምስራቅ ይኖራሉ፣ ስለዚህም ምስራቁን "ከዮርዳኖስ ማዶ" ብለው ይጠሩታል። በዚህ ጊዜ ግን ሁሉም ገና በስተ ምስራቅ ናቸው። "ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምስራቅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ወንድሞቻችሁ እረፍት እስኪያገኙ
ይህ እስራኤላውያን የሚይዟቸውን በከነዓን የሚኖሩ ጠላቶቻቸውን ሁሉ እንደሚያሸንፉ ያመለክተል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ ... ትወርሳላችሁ
ይህ በዚያ በምድሪቱ በሰላም እንደሚኖሩ ያመለክታል።

ፀሐይ ከምትወጣበት፣ ከዮርዳኖስ ባሻገር
ይህ የዮርዳኖስን ምስራቃዊ ጎን ያመለክታል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 1:16

አጠቃላይ መረጃ:
ለኢያሱ የመለሱለት እነዚህ እስረኤላውያን፤ በተለይ ሮቤላዊያን፣ ጋድአዊያን እና ከምናሴ ነገድ እኩሌታዎቹ ነበሩ።

በትዕዛዛትህ ላይ አመጸ፣ ደግሞም ቃልህን አልታዘዙም
እነዚህ ሁለት ሀረጋት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ደግሞም ማናቸውንም አይነት መልክ የያዘ አለመታዘዝ እንደሚያስቀጣ አጉልተው ይገልጻሉ። (ትይዩ ንጽጽራ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይገደላል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሞት እንፈርድበታለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በርታ ደግሞም ጽና
እስራኤል እና እግዚአብሔር፤ ኢያሱ ለእስራኤል ህዝብ መሪ ሆኖ እንዲቀጥል ሁለቱም ባህርያት አስፈላጊው እንደሆኑ ይቆጥራሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 የነዌም ልጅ ኢያሱ፦ "ሄዳችሁ ምድሪቱን፥ በተለይም ኢያሪኮን ሰልሉ ብሎ ከሰጢም ሁለት ሰዎች በስውር ላከ። እነርሱም ሄደው ረዓብ ወደምትባል ሴተኛ አዳሪ ቤት ገቡ፥ በዚያም አደሩ። **2** ለኢያሪኮም ንጉሥ፦ እነሆ የእስራኤል ሰዎች አገሩን ሊሰልሉ ወደዚህ ገብተዋል ብለው ነገሩት። **3** የኢያሪኮም ንጉሥ፦አገሩን ሁሉ ሊሰልሉ ወደ አንቺ የመጡትንና ወደ ቤትሽ የገቡትን ሰዎች አውጪ ብሎ ወደ ረዓብ መልእክት ላከ። **4** ነገር ግን ሴቲቱም ሁለቱን ሰዎች ወስዳ ሸሸገቻቸው። እርስዋም፦አዎን ሰዎቹ ወደ እኔ መጥተዋል፥ ነገር ግን ከወዴት እንደ ሆኑ አላወቅሁም፤ **5** የከተማውም በር የሚዘጋበት ጊዜ ላይ ሰዎቹ ወጡ፤ ወዴት እንደ ሄዱ አላውቅም፤ፈጥናችሁ ከተከተላችሁ ምናልባት ልትይዙአቸው ትችላላችሁ አለች። **6** እርስዋ ግን ወደ ሰገነቱ አውጥታቸው፤ በዚያም በጣሪያ ውስጥ ባዘጋጀችው በተልባ እግር ውስጥ ሸሸጋቸው። **7** ሰዎቹ ወደ ዮርዳኖስ መሻገሪያ በሚወስደው መንገድ አሳደዱአቸው። አሳዳጆችም እንደወጡ በሮቹ ተቆለፉ። **8** ሰዎቹም ሳይተኙ ሴቲቱ ወደ እነርሱ ወደ ሰገነቱ ወጣች። **9** ሰዎቹንም እንዲህ አለቻቸው፦እግዚአብሔር ምድሪቱን አሳልፎ እንደሰጣችሁ እናንተንም መፍራት በላያችን እንደ ወደቀ፤ በምድሪቱም በሚኖሩት ሁሉ ከፊታችሁ እንደ ቀለጡ አውቃለሁ። **10** ከግብፅ ምድር በወጣችሁ ጊዜ እግዚአብሔር የኤርትራን ባሕር በፊታችሁ እንዳደረቀ፤ በዮርዳኖስም ማዶ በነበሩት እናንተም ፈጽማችሁ ባጠፋችኋቸው በሁለቱ በአሞራውያን ነገሥታት፥በሴዎንና በዐግ ያደረጋችሁትን ሰምተናል። **11** ይህን በሰማን ጊዜ ልባችን ቀለጠ፤ አምላካችሁም እግዚአብሔር በላይ በሰማይ በታችም በምድር እርሱ አምላክ ነውና ከእናንተ የተንሣ ከዚያ ወዲያ ለማንም ነፍስ አልቀርለትም። **12** እባክህም እባካችሁ እኔ ለእናንተ ቸርነት እንዳደረግሁ እናንተ **13** ደግሞ ለአባቴ ቤት ቸርነት እንድታደርጉ፥ አባቴንና እናቴን፥ ወንድሞቼንና እኅቶቼንና ቤተ ሰቦቻቸውን ሁሉ እንድታድኑ፤ እንዲሁም ከሞት እንድታድኑን በእግዚአብሔር ማሉልኝ እውነተኛ ምልክትም ስጡኝ። **14** ሰዎቹ፦ "ይህን ነገራችንን ባትገልጪ ነፍሳችን በነፍሳችሁ ፋንታ እስከሞት እንኳ ይሆናል፤ እግዚአብሔርም ምድሪቱን በሰጠን ጊዜ ምሕረትን እናደርጋለን እንዲሁም ታማኝ ሆነን እንገኛለን፤" አሉአት። **15** ቤትዋም በከተማ ቅጥር የተጠጋ ስለነበረ በመስኮቱ በገመድ አወረደቻቸው። **16** እርስዋም፦አሳዳጆቹ እንዳያገኙአችሁ ወደ ተራራው ሂዱ አሳዳጆቹም እስኪመለሱ ድረስ በዚያ ሦስት ቀን ተሰውራችሁ ተቀመጡ ኋላም መንገዳችሁን ትሄዳላችሁ አለቻቸው። **17** ሰዎቹም አሉአት፦ይህን የምንልሽን ካላደረግሽ እኛም ከዚህ ካማልሽን መሐላ የተነሣ የሰጠንሽን ተስፋ ከመጠበቅ ነፃ እንሆናለን። **18** እነሆ እኛ ወደ አገሩ በገባን ጊዜ ይህን ቀይ ክር እኛን ባወረድሽበት መስኮት በኩል እሰሪው ፤አባትሽንም እናትሽንም ወንድሞችሽንም የአባትሽንም ቤተ ሰብ ሁሉ ወደ አንቺ ቤት ሰብስቢ። **19** ከቤትሽም ደጅ ወደ ሜዳ የሚወጣ ሁሉ ደሙ በራሱ ላይ ይሆንበታል፤ እኛም ንጹሐን እንሆናለን። ነገር ግን ከአንቺ ጋር በቤቱ ውስጥ ያለውን አንድ ሰው ቢነካው ደሙ በእኛ ራስ ላይ ይሆናል። **20** ነገር ግን ይህንን ጉዳያችንን ብትገልጪ እኛም ከዚህ ካማልሽን መሐላ የተነሣ የሰጠንሽን ተስፋ ከመጠበቅ ነፃ እንሆናለን። **21** እርስዋም፦እንደቃላችሁ ይሁን አለች። ሰደደቻቸውም እነርሱም ሄዱ፤ ቀዩንም ክር በመስኮቱ በኩል አንጠለጠልችው። **22** እነርሱም ሄደው ወደ ተራራው ደረሱ፥ አሳዳጆቹም እስኪመለሱ ድረስ እዚያ ለሦስት ቀናት ቆዩ። በመንገዱ ሁሉ ፈልገው አላገኙአቸውም። **23** ሁለቱም ሰዎች ተመለሱ፤ ከተራራውም ወርደው ተሻገሩ ወደ ነዌም ልጅ ወደ ኢያሱ መጡ፤ የደረሰባቸውንም ሁሉ ነገሩት። **24** ለኢያሱም እንዲህ አሉት፦ በእውነት እግዚአብሔር ይህን አገር ሁሉ በእጃችን አሳልፎ ሰጥቶናል፤ በአገሩም ውስጥ ያሉ ሰዎች ሁሉ ከእኛ የተነሣ እየቀለጡ አሉት።

Joshua 2:1

ነዌ
ይህ የኢያሱ አባት ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰጢም
ይህ በዮርዳኖስ ወንዝ ምስራቅ አቅጣጫ የሚገኝ ስፍራ ስም ነው። ትርጉሙ "የግራር ዛፎች" ማለት ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰላዮች
እነዚህ ሰዎች እስራኤላውያን ምድሪቱን እንዴት እንደሚወሯት መረጃ ለማግኘት የሄዱ ነበሩ።

Joshua 2:4

አጠቃላይ መረጃ:
ጋለሞታይቱ ረዓብ ሁለቱን እስራኤላውያን ሰላዮች ከጉዳት ጠበቀች።

ነገር ግን ሴቲቱ ሁለቱን ሰዎች ወስዳ ደበቀቻቸው
ይህ የሆነው የንጉሡ መልዕክተኛ ከእርሷ ጋር ከመነጋገሩ አስቀድሞ ነው።

ሴቲቱ
ይህ ጋለሞታይቱን ረዓብን ያመለክታል

ማምሻ/ለዐይን ያዝ ሲያደርግ
ቀኑ ወደ ምሽቱ ጨለማ መግባት የሚጀምርበት ጊዜ ነው

Joshua 2:6

ነገር ግን እርሷ ... ወደ ሰገነቱ/ጣራ ላይ ወሰደቻቸው
ይህ ሰዎቹን እንዴት እንደ ደበቀቻቸው በኢያሱ 2:4 ላይ ሚገኝ የመረጃ ዳራ እና ማብራሪያ ነው። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰገነት/ጣራ
ጣራው ጠፍጣፋ ጠንካራ ነበር፣ በመሆኑም ሰዎች በዙሪያው ሊረማመዱ ይችሉ ነበር

የተልባ እግር
ልብስ ለመስራት የሚውል፣ ክር/ቃጫ ለማግኘት የሚተከል ተክል።

ሰዎቹ ተከተሏቸው
ሰዎቹ ሰላዮቹን የተከተሏቸው ረዓብ በኢያሱ 2:5 ላይ ከነገረቻቸው የተነሳ ነው።

መሻገሪያዎች/መልካ
የወንዝ ወይም ሌላ የውሃ አካል፣ በእርምጃ ወደ ሌላኛው ዳርቻ በእርምጃ ለመሻገር የሚቻልበት ጥልቀት የሌለው ስፍራ

Joshua 2:8

ገና ሳይጋደሙ
ይህ የሚያመለክተው በምሽቱ ወደ መኝታ መሄድን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ያህዌ ምድሪቱን ለእናንተ እንደሰጣችሁ አውቃለሁ
"እናንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክው መላውን የእስራኤል ሰዎች ነው። (እናንተ የሚለውን ቃል መገለጫ መልኮችን ይመልከቱ)

እናንተን መፍራት ወድቆብናል
ፈርተናል የሚለው የተገለጸው ፍርሃት ራሱ መጥቶ እንዳጠቃቸው ተደርጎ ነው። "እናንተን ፈራን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በፊታችሁ ቀለጥን
ይህ የፈራውን ህዝብ ከሚቀልጥና ከሚወርድ በረዶ ጋር ያነጻጽረዋል። አማራጭ ትርጉሞች ሊሆኑ የሚችሉት 1) በእስራኤላውያን ፊት ደካማ እንደሚሆኑ ወይም 2) እንደሚበታተኑ ነው። "እናንተን መቋቋም እስከማይችሉ ድረስ እጅግ ይፈራሉ" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 2:10

አጠቃላይ መረጃ:
ረዓብ ከእስራኤላውያን ሰላዮች ጋር መነጋገሯን ቀጠለች

የደንገል/ቄጤማ ባህር
ይህ የቀይባህር ሌላው ስም ነው

ሴዎን...ዐግ
እነዚህ የአሞራውያን ነገሥታት ስሞች ናቸው።(ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ልባችን ቀለጠ፣ አንዳች ድፍረት አልቀረልንም
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ በአንድ ላይ የቀረቡት ትኩረት ለመስጠት ነው። "ልባችን ቀለጠ" የሚለው ሃረግ የፈሩትን የኢያሪኮ ሰዎች ልብ እየቀለጠ ከሚወርድ በረዶ ጋር ነው ያነጻጽራል። (ጥንድ ትረጉም እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Joshua 2:12

አጠቃላይ መረጃ:
ረዓብ ከእስራኤላውያን ሰላዮች ጋር መነጋገሯን ቀጠለች

እባካችሁ ማሉልኝ... እርግጠኛ የሆነ ምልክት ስጡኝ
እነዚህ ረዓብ ከሰለዮቹ እርግጠኛ የሆነ ምልክት መፈለጓን የሚገልጹ ተመሳሳይ ሃሳቦች ናቸው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእናንተ መልካም ነበርኩ
"እናንተ" የሚለው ቃል ሁለቱን ሰላዮች ያመለክታል። (እናንተ የሚለውን ቃል መገለጫ መልኮችን ይመልከቱ)

ህይወታችንን አድኑ... ከሞት አድኑን
"አትግደሉን" የሚለውን ትሁት በሆነ መንገድ መግለጽ። (የፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 2:14

አጠቃላይ መረጃ:
እስራኤላውያን ሰላዮች ረዓብ የጠየቀችውን በኢያሱ 2:12 ቃል የገቡላትን ፈጸሙ

እስከ ሞት ድረስ እንኳን ቢሆን፣ ህይወታችንን ለእናንተ ህይወት ይህ ፈሊጥ ቃልኪዳናቸውን ካልጠበቁ እግዚአብሔር እርግማኑን በእነርሱ ላይ እንዲያመጣባቸው የሚምሉበት እና የሚጠይቁበት መንገድ ነው። "ቃል የገባነውን ሳናደርግ ብንቀር፣ ያህዌ እኛን ያጥፋን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 2:15

አጠቃላይ መረጃ:
እስራኤላውያኑ ሰላዮች ከረዓብ ጋር መነጋገራቸውን ቀጠሉ።

ይህንን ባታደርጊ
ይህ ሰላዮቹ ለረዓብ የገቡትን ቃል ኪዳን የሚፈጽሙበትን ሁኔታ ይገልጻል። "ይህ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው " ይህንን ደማቅ ቀይ ገመድ በመስኮቱ በኩል እሰሪው " የሚለውን በኢያሱ 2:18 የሚገኘውን ነው። (መላምታዊ ሁኔታ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 2:18

አያያዥ ሃሳብ:
እስራኤላውያኑ ሰላዮች በኢያሱ 2:15 የገለጹትን ሁኔታ ያብራራሉ።

አጠቃላይ መረጃ:
እስራኤላውያኑ ሰላዮች ከረዓብ ጋር መነጋገራቸውን ቀጠሉ።

ማናቸውም ከቤትሽ በር ውጭ የሄደ
ይህ ሃረግ መላምታዊ በመፍጠር አንድን ሁኔታ ይገልጻል። (መላምታዊ ሁኔታ የሚለውን ይመልከቱ)

ደሙ በራሳቸው ራስ ላይ ይሆናል
እዚህ ስፍራ "ደም" የሚለው የሚገልጸው የአንድ ሰውን መሞት ነው። ለራሳቸው ሞት ተጠያቂነቱ የተገለጸው ደም በራሳቸው ላይ እንደሚሆን ተደርጎ ነው። "ሞታቸው የገዛ ራሳቸው ጥፋት ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ በደለኞች አንሆንም
"ንጹሃን እንሆናለን"

በማንም ላይ እጅ ቢጫን
እዚህ ስፍራ "እጅ ቢጫን" የሚለው አንድ ሰው እንዲጎዳ ምክንያት መሆን በጨዋ አገላለጽ የተገለጸበት ነው። "በማንም ላይ ጉዳት እንዲደርስ ምክንያት ብንሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊሚዝም/የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 2:20

አጠቃላይ መረጃ:
ሁለቱ እስራኤላውያን ሰላዮች ከረዓብ ጋር መነጋገራቸውን ቀጠሉ።

አጠቃላይ መረጃ:
ሰላዮቹ ረዓብ ወደ እርሷ መምጣታቸውን እንዳትናገር ጠየቋት፣ ወይም ይህ ካልሆነ ቤተሰቧቿን ለማዳን ከገቡት መሃላ ነጻ ይሆናሉ።

ብትናገሪ
"አንቺ" የሚለው ረዓብን ያመለክታል። (አንቺ የሚለውን ቃል መገለጫ መልኮችን ይመልከቱ)

እናንተ ያላችሁት ይደረግ
ረዓብ ቤተሰቧችዋ እንዲጠበቁ ከእነርሱ የመሃላ ቃል ጋር ተስማማች

Joshua 2:22

አጠቃላይ መረጃ:
ሁለቱ እስራኤላውያን ኢያሪኮን ለቀው ወጡ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አሳዳጆቻቸው ተመለሱ
ወደ ኢያሪኮ ተመለሱ ማለቱ ሊረዳ ይችላል። "የእነርሱ አሳዳዶች ወደ ኢያሪኮ ከተማ ተመለሱ" በሚለው ውሰጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አንዳች አላገኙም
ይህ የሚያመለክተው ሰላዮቹን ያላገኟቸውን ሰዎች ነው

Joshua 2:23

ሁለቱ ሰዎች ተመለሱ
ሁለቱ ሰዎች ወደ እስራኤላውያን ሰፈር ተመለሱ። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ዞረው፣ አቋርጠው ተመልሰው መጡ
እነዚህ እስራኤላውያን ወዳረፉበት ስፍራ መመለሳቸውን የሚገልጹ ተመሳሳይ አባባሎች ናቸው

አቋርጠው
"አቋርጠው" ማለት ከወንዙ ተቃራኒ ዳርቻ መሄድ ማለት ነው። "ከዚህኛው ዳርቻ ወደ ተቃራኒው የዮርዳኖስ ዳርቻ መሄድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ነዌ
ይህ የወንድ ስም ነው፤ የኢያሱ አባት። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ
እዚህ ስፍራ "እኛ" የሚለው ቃል እስራኤልን ያመለክታል

የምድሪቱ ነዋሪዎች ቀለጡ
የምድሪቱ ነዋሪዎች ለእስራኤላዊያን ያላቸው አቋም ሲታይ በሙቀት እንደሚቀልጥ ነገር ይመስላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 ኢያሱም በጠዋት ተነሣ፥ እነርሱም ከሰጢም ተነሥተው ወደ ዮርዳኖስ መጡ፤ እርሱና የእስራኤልም ልጆች ሁሉ ሳይሻገሩም በዚም ሰፈሩ። **2** ከሦስት ቀንም በኋላ አለቆች በሰፈሩ መካከል ሄዱ። **3** ሕዝቡንም እንዲህ ብለው አዘዙ፦የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ታቦት ሌዋውያን ካህናት ተሸክመውት ባያችሁ ጊዜ ከሰፈራችሁ ተነሥታችሁ መከትል አለባችሁ። **4** በእናንተና በታቦቱ መካከል ያለው ርቀት ሁለት ሺህ ክንድ ያህል ይሁን። በዚህ መንገድ በከዚሄ በፊት አልሄዳችሁበትምና የምትሄዱበትን መንገድ እንድታውቁ ወደ ታቦቱ አትቅረቡ። **5** ኢያሱም ለሕዝቡ እንዲህ አለ፦ እግዚእአብሔር በመካከላችሁ ድንቅ ነገር ያደርጋልና ነገ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር ቀድሱ። **6** ከዚያም ኢያሱ ካህናቱን እንዲህ አለ፦ የቃል ኪዳኑን ታቦት ተሸክማችሁ በሕዝቡ ፊት እለፉ። ስለዚህ የቃል ኪዳኑን ታቦት ተሸክመው በሕዝቡ ፊት አለፉ። **7** እግዚአብሔርም ኢያሱን እንዲህ አለ፦ በዚህ ቀን በእስራኤል ሁሉ ፊት ከፍ ከፍ አደርጋለሁ። ከሙሴ ጋር እንደ ነበርሁ እንዲሁ ከእንተ ጋር መሆኔን ያውቃሉ። **8** አንተም የቃል ኪዳኑን ታቦት የሚሸከሙትን ካህናት፦ በዮርዳኖስ ውኃ ዳር ስትደርሱ በዮርዳኖስ ውስጥ ቁሙ ብለህ ታዛቸዋለህ። **9** ከዚያም ኢያሱ ለእስራኤል ሕዝብ እንዲህ አለ፦ ወደዚህ ቀርባችሁ የእግዚአብሔርን የአምላካችሁን ቃል ስሙ አለ። **10** ሕያው አምላክ በመካከላችሁ እንደ ሆነና እርሱም ኤዊያዊውንም ፈርዛዊውንም ጌርጌሳዊውንም አሞራዊውንም ኢያቡሳዊውንም ከፊታችሁ ፈጽሞ እንደሚያወጣ በዚህ ታውቃላችሁ። **11** እነሆ የምድር ሁሉ ጌታ የቃል ኪዳን ታቦት በፊታችሁ በዮርዳኖስ ውስጥ ያልፋል። **12** አሁንን ከእስራኤል ነገዶች አሥራ ሁለት ሰዎችን ምረጡ፤ ከየነገዱ አንድ አንድ ሰው ይሁን። **13** እንዲህም ይሆናል የምድርም ሁሉ ጌታ የእግዚአብሔርን ታቦት የተሸከሙ ካህናት የእግራቸው ጫማ በዮርዳኖስ ውኃ ሲቆም የዮርዳኖስም ውኃ ይቆማል፤ ከላይ የሚፈሰው ውኃ ሳይቀር መፍሰሱን ያቆማል፤ እንደ ክምርም ሆኖ ይቆማል። **14** ሕዝቡም ዮርዳኖስን ለመሻገር ከድንኳናቸው በወጡ ጊዜ የቃል ኪዳኑን ታቦት የተሸከሙ ካህናት በሕዝቡ ፊት ቀድመው ሄዱ። **15** የቃል ኪዳኑን ታቦት የተሸከሙ ወደ ዮርዳኖስ እንደመጡ፤ እግራቸውም የውኃውን ጫፍ በጠለቁ ጊዜ (በመከር ወራት ሁሉ ዮርዳኖስ እጅግ ሞልቶ እንደሚፈስ) **16** ከላይ የሚወርደው ውኃ ቆመ፤ በጻርታን አጠገብ ባለችው አዳም በምትባል ከተማ በሩቅ ቆሞ እንደ ክምርም ሆነ፤ ወደ ዓረባ ባሕር ወደ ጨው ባሕር የሚወርደውም ውኃ ፈጽሞ ተቋረጠ፤ ሕዝቡም በኢያሪኮ አጠገብ ተሻገሩ። **17** የእስራኤልም ሕዝቡ ሁሉ ዮርዳኖስን ፈጽመው አስኪሻሩ ድረስ የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦት የተሸከሙ ካህናት በዮርዳኖስ መካክል በደረቅ መሬት ጸንተው ቆመው ነበር።

Joshua 3:1

ተነሱ
"ተነሱ" የሚለው ሃረግ "መንቃት" ማለት ነው።

ሰጢም
እስራኤላውያን ወደ ተስፋ ምድራቸው ወደ ከነዓን ከመግባታቸው አስቀድሞ ከሰፈሩበት ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምዕራብ በሞአብ ምድር የሚገኝ ስፍራ

Joshua 3:2

አለቆች
እነዚህ የማዘዝ ወይም ስልጣን ደረጃን የያዙ ሰዎች ናቸው

ሰዎች
ይህ የእስራኤል ህዝብ ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሁለት ሺህ ክንድ
"2,000 ክንድ" ክንድ የሚለው ቃል ከክርን እስከ ጣት ጫፍ ድረስ ያለው እርቀት መለኪያ ነው። (መጽሐፍ ቅዱሳዊ ርቀት እና ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

Joshua 3:5

ራሳችሁን ቀደሱ
ይህ በያህዌ ፊት ንጹህ ለመሆን የሚደረግን ልዩ ዝግጅት ያመለክታል።

ያህዌ ተአምራት ያደርጋል
ያህዌ ሁሉም የሚያየው እና የሚዳስሰው ተአምራት ያደርጋል

ታቦቱን ያዙ
ይህ ሌዋውያን ታቦቱን ከአንድ ስፍራ ወደ ሌላ ይዘው መሄዳቸውን ያመለክታል

Joshua 3:7

አጠቃላይ መረጃ:
ካህናቱ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ያህዌ ለኢያሱ ነገረው።

በመላው እስራኤል ዐይኖች ፊት ታላቅ ሰው አደርግሃለሁ
ዐይኖች የሚለው ማየትን ሲወክል ፣ ማየት የሚለው ማሰብን ወይም ፍርድን ይገልጻል። "ህዝቡ የማደርገውን ያያል፣ ደግሞም አንተን ታላቅ ሰው እንዳደረግኩህ ያስተውላሉ" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የዮርዳኖስ ውሃ ዳርቻ
ኢያሱ ወደ ዳርቻ ወይም ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ዳርቻ ደረሰ

Joshua 3:9

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ምን ሊያደርግ እንደሆነ ኢያሱ ለእስራኤላውያን ነገራቸው።ከፊታችሁ ሊያጠፋቸው ያህዌ በምድሪቱ የሚኖሩ ሌሎች ህዝቦችን ከምድሪቱ ይወጡ ዘንድ ወይም እንዲገደሉ ያደርጋል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አቋርጠው
"አቋርጠው" ማለት ከወንዙ ተቃራኒ ዳርቻ መሄድ ማለት ነው። "ከዚህኛው ዳርቻ ወደ ተቃራኒው የዮርዳኖስ ዳርቻ መሄድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 3:12

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ምን ሊያደርግ እንደሆነ ኢያሱ ለእስራኤላውያን መናገሩን ቀጠለ።

አጠቃላይ መረጃ
የእስራኤል አባቶች ቀይ ባህርን እንዳቋረጡ፣ እነዚህ ሰዎች ዮርዳኖስን በደረቅ ምድር ያቋርጣሉ

የእግራቸው ኮቴ
ይህ የሚያመለክተው የእግራቸውን ስር ነው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከላይ የሚወርደው
ይህ ቃል የሚያመለክተው የዮርዳኖስ ወንዝ ውሃ ወደ እስራኤል የሚወርድበትን አቅጣጫ ነው

አንድ ክምር ሆኖ ቆመ
ውሃው በአንድ ነጥብ ወይም ስፍራ ላይ ይቆማል። ካህናቱ ዙሪያ አይፈስም

Joshua 3:14

የውሃ ዳርቻ፡
ይህ የውሃውን ገጽ እንዲሁም ውሃው ወደ ደረቅ ምድር የሚፈስበትን ዳርቻ ያመለክታል። (ስኔክቲኪ/ ዘይቤያዊ አነጋጋር- የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ፤ የሚለውን ይመልከቱ)አሁን ዮርዳኖስ ውሃ ሞልቶ እስከ መከር ጊዜ ድረስ ይፈስ ነበር ይህ የመረጃ ዳራ ያህዌ ሊያደርግ ያለውን አጉልቶ ያሳያል። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 3:17

አጠቃላይ መረጃ፡
ተአምራዊው የዮርዳኖስ ባህር መውረዱ ቀጠለ

ዮርዳኖስ
ይህ የዮርዳኖስ ወንዝ የሚፈስበትን ያመለክታል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አቋረጡ
ይህ ሃረግ ከወንዙ ተቃራኒ ዳርቻ መሄድ ማለት ነው። "ከዚህኛው ዳርቻ ወደ ተቃራኒው ዳርቻ መሄድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 ሕዝቡ ሁሉ ዮርዳኖስን ፈጽመው በተሻገሩ ጊዜ እግዚአብሔርም ኢያሱን እንዲህ አለ፦ **2** "ከሕዝቡ ከየነገዱ አንድ አንድ ሰው፥ አሥራ ሁለት ሰዎች ምረጥ። **3** እንዲህ ብለህ ትእዛዝ ስጣቸው፦"በዮርዳኖስ መካከል የካህናት እግር ከቆመበት ስፍራ አሥራ ሁለት ድንጋዮችን አንሡ፤ ተሸክማችሁም በዚህ ሌሊት በምታድሩበት ስፍራ አኑሩአቸው።" **4** ከዚያም ኢያሱ ከእያንዳንዱ የእስራኤል ነገድ አንድ አንድ ሰው የመረጣቸውን አሥራ ሁለት ሰዎች ጠራቸው። **5** ኢያሱም አላቸው፦"በአምላካችሁ በእግዚአብሔር ታቦት ፊት በዮርዳኖስ መካከል፤ እያንዳንዱም ሰው በጫንቃው ከአንዳንድ ድንጋይ ጋር በእስራኤል ልጆች ሁሉ ነገድ ቁጥር አሥራ ሁለት ድንጋዮችን ተሸክመው ይለፉ። **6** ፤ልጆቻችሁም በሚመጣው ዘመን፦ እነዚህ ድንጋዮች ለእናንተ ምን ትርጉም አላቸው? ብለው በሚጠይቁበት ጊዜ ይህ በመካከላችሁ ምልክት ይሆናል። **7** በዚያን ጊዜ እናንተም እንዲህ ብላችሁ ትመልሳላችሁ፦ "በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ታቦት ፊት የዮርዳኖስ ውኃ ስለተቋረጠ ነው። በተሻገሩም ጊዜ የዮርዳኖስ ውኃ ቆመ፤ እነዚህም ድንጋዮች ለእስራኤል ልጆች ለዘላለም መታሰቢያ ይሆናሉ።" **8** የእስራኤልም ልጆች ኢያሱ እንዳዘዛቸው አደረጉ፤ እግዚአብሔርም ኢያሱን እንደ ተናገረው በእስራኤል ነገድ ቁጥር ከዮርዳኖስ መካከል እንደ እስራኤል ነገድ ቁጥር አሥራ ሁለት ድንጋዮች አንሥተው ወደሚያድሩበት ስፍራ ወሰዱ። በዚያም በሚያድሩበት ስፍራ አኖሩአቸው። **9** ኢያሱም የቃል ኪዳኑን ታቦት የተሸከሙ ካህናት እግሮች በቆሙበት ስፍራ በዮርዳኖስ መካከል ሌሎችን አሥራ ሁለት ድንጋዮች ተከለ። እስከ ዛሬም ድረስ መታሰቢያ ሆነው በዚያ አሉ። **10** ሙሴም ኢያሱን እንዳዘዘው ሁሉ እግዚአብሔር ኢያሱን ለሕዝቡ እንዲነገር ያዘዘው ነገር ሁሉ እስክፈጸም ድረስ ታቦቱን የተሸከሙ ካህናት በዮርዳኖስ መካከል ቆመው ነበር። ሕዝቡም ፈጥነው ተሻገሩ። **11** ሕዝቡም ሁሉ ፈጽመው መሻገራቸውን በጨረሱ ጊዜ የእግዚአብሔር ታቦትና ካህናቱ በሕዝቡ ፊት ተሻገሩ። **12** ሙሴም እንዳዘዘቸው የሮቤል ልጆች፥ የጋድም ልጆች፥ የምናሴም ነገድ እኩሌታ ተሰልፈው በእስራኤል ልጆች ፊት ተሻገሩ። **13** አርባ ሺህ ያህል ሰዎች ጋሻና ጦራቸውን ይዘው ለጦርነት በእግዚአብሔር ፊት ወደ ኢያሪኮ ሜዳ ተሻገሩ። **14** በዚያም ቀን እግዚአብሔር ኢያሱን በእስራኤል ሁሉ ፊት ከፍ አደረገው። ሕዝቡም ሙሴን እንዳከበሩት በዕድሜው ሁሉ አከበሩት። **15** እግዚአብሔርም ኢያሱን እንዲህ ብሎ ተናገረው፦ **16** "የምስክርን ታቦት የሚሸከሙትን ካህናት ከዮርዳኖስ እንዲወጡ እዘዝ።" **17** ኢያሱም ካህናቱን፦ ከዮርዳኖስ ውጡ ብሎ አዘዛቸው። **18** የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳኑን ታቦት የተሸከሙ ካህናት ከዮርዳኖስ መካከል በወጡ ጊዜና የካህናቱም እግር ጫማ ደረቅ መሬት መርገጥ በጀመረ ጊዜ የዮርዳኖስ ውኃ ወደ ስፍራው ተመለሰ፤ ቀድሞም ከአራት ቀናት በፊት እንደ ነበረ በዳሩርቻው ሁሉ መፍሰስ ጀመረ። **19** ሕዝቡም በመጀመሪያው ወር በአሥረኛው ቀን ከዮርዳኖስ ወጡ። ከኢያሪኮ በስተ ምሥራቅ በኩል በጌልገላ ሰፈሩ። **20** ከዮርዳኖስም ውስጥ የወሰዱአቸውን አሥራ ሁለቱን ድንጋዮች ኢያሱ በጌልገላ አቆማቸው። **21** ለእስራኤልም ልጆች እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፦ "በሚመጣው ዘመን ልጆቻችሁ አባቶቻቸውን፦ እነዚህ ድንጋዮች ምንድን ናቸው? ብለው ሲጠይቁ፥ **22** ለልጆቻችሁ እንዲህ ብላችሁ ታስታውቃላችሁ፦ እስራኤል ይህን ዮርዳኖስን በደረቅ ተሻገረ። **23** እስክንሻገር ድረስ አምላካችሁ የኤርትራን ባሕር ከፊታችን እንዳደረቀ እንዲሁ እስክትሻገሩ ድረስ አምላካችሁ እግዚአብሔር የዮርዳኖስን ውኃ ከፊታችሁ አደረቀ። **24** የእግዚአብሔርም እጅ ጠንካራ እንደ ሆነች የምድር አሕዛብ ሁሉ እንዲያውቁ አምላካችሁንም እግዚአብሔርን ለዘላለሙ እንድታከብሩ ነው።

Joshua 4:1

አጠቃላይ መረጃ፡
ምንም እንኳን ያህዌ በቀጥታ ለኢያሱ ቢናገርም፣ አንተ የሚለው በተጠቀሰ ጊዜ ሁሉ እስራኤልን ያጠቃልላል። (ተውላጠ ስም/የስም ምትክ የሚለውን ይመልከቱ)

አቋረጠ
"አቋረጠ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከወንዙ ተቃራኒ ዳርቻ መሄድን ነው። "አቋርጦ ሄደ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የ ዮርዳኖስ
የዮርዳኖስ ወንዝ ። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእነርሱ ይህንን ተዕዛዝ ስጣቸው፡'...'
በጥቅስ ውስጥ የተቀመጠው ቀጥተኛ እንዳልሆነ ጥቅስ ሊቀርብ ይችላል። "ካህናቱ በደረቅ ምድር ቀመውበት ከነበረበት ስፍራ ከዮርዳኖስ መሃል አስራ ሁለት ድንጋዮችን እንዲያነሱ ይህንን ትዕዛዝ ስጣቸው፣ እነዚያንም ድንጋዮች ይዘህ መጥተህ ዛሬ ምሽት በምታድርበት ስፍራ አኑራቸው" (በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ እና ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅሶች የሚሉትን ይመልከቱ)

Joshua 4:4

አጠቃላይ መረጃ፡
ኢያሱ ለአስራ ሁለቱ ሰዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው ነገራቸው።ወደ ዮርዳኖስ መሃል እያንዳንዳችሁ በትከሻችሁ ድንጋይ ትሸከማላችሁ እያንዳንዳቸው አስራ ሁለቱ ሰዎች ከዮርዳኖስ ወንዝ ዳርቻ ትልልቅ ድንጋይ አንስተው መተሰቢያ ለማኖር ወደ ሌላው ዳር ተሸክመው ወሰዱ። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 4:6

አጠቃላይ መረጃ፡
ኢያሱ ለእስራኤላውያን የአስራ ሁለቱ ድንጋዮች ክምር ትርጉሙ ምን እንደሆነ ነገራቸው

የዮርዳኖስ ውሃ በያህዌ የቃል ኪዳኑ ታቦት ፊት ተቋረጠ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ያህዌ የዮርዳኖስን ውሃ በቃል ኪዳኑ ታቦት ፊት አቋረጠው" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የዮርዳኖስ ውሃዎች የነበሩት
"የዮርዳኖስ ወንዝ ነበር"

በታቦቱ ፊት ተቋርጠው ነበር
የዮርዳኖስ ወንዝ ካህናቱ ተሸክመውት እስከ ነበረው ታቦት ድረስ እንዳይፈስ እግዚአብሔር አግዶት ነበር

የዮርዳኖስ ውሃዎች ተቋርጠው ነበር
ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ቁልቁል ይፈስ የነበረው ውሃ በታቦቱ ፊት ቆመ፣ ስለዚህም ታቦቱን ጨምሮ ሁሉም በደረቀ የወንዝ መፋሰሻ ተጓዙ

Joshua 4:8

አጠቃላይ መረጃ፡
ኢያሱ እና መላው እስራኤል ያህዌ እንዳዘዘው መስራታቸውን ቀጠሉ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከዮርዳኖስ መሃል አስራ ሁለት ድንጋዮችን ተሸከሙ
ይህ የሚያመለክተው አስራ ሁለቱ ወንዶች ከዮርዳኖስ ወንዝ መፍሰሻ ድናጋዮችን መሸከማቸውን ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያ ኢያሱ በዮርዳኖስ መሃል አስራ ሁለት ድንጋዮች አስቀመጠ
እነዚህ አስራ ሁለቱ ሰዎች ከወንዙ መፋሰሻ የተሸከሟቸው ድንጋዮች ሳይሆኑ አስራ ሁለት ተጨማሪ ድንጋዮች ነበሩ። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መታሰቢያው እስከ ዛሬ ድረስ በዚያ አለ
ይህ ማለት ጸሐፊው ይህንን መጽሐፍ እስከሚጽፍበት ቀን ድረስ መታሰቢያው በዚያ ነበር

Joshua 4:10

የ ዮርዳኖስ
ይህ የዮርዳኖስን ወንዝ ያመለክታል።

ህዝቡ
ይህ የእስራኤልን ህዝብ ያመለክታል። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አቋረጡ
ይህ ማለት ከወንዙ ተቃራኒ ዳርቻ መሄድ ነው። "ከዚህኛው ዳርቻ ወደ ተቃራኒው ዳርቻ መሄድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በህዝቡ ፊት
ይህ የሚያመለክተው በህዝቡ ፊት መሆንን ወይም በሁሉም ህዝብ እይታ ውስጥ መሆንን ነው። እያንዳንዱ ካህናቱ ታቦቱን ተሸክመው አይቷል። (ፈሊጣው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 4:12

የሮቤል ነገድ፣ የጋድ ነገድ እና የምናሴ ነገድ እኩሌታ በወታደራዊ አሰላለፍ በእስራኤል ህዝብ ፊት አለፉ
እነዚህ እስራኤላውያንን በዮርዳኖስ ወንዝ ምስራቅ ለማስፈር እና ጦርነቱን በመምራት ግዴታቸውን የሚወጡ የሶስቱ ነገዶች ወታደሮች ነበሩ። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ልክ እነርሱ
"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእስራኤልን ህዝብ ነው

ሙሴን አከበሩት
ይህ ማክበርን ብቻ የሚያመለክት አይደለም፣ ነገር ግን ሙሴን ሲከተሉ ያደርጉት እንደነበረው ለእርሱ ትዕዛዛት መገዛትን እና እርሱን እንደ ሰራዊቱ አዛዥ መቀበልን ጭምር ያመለክታል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 4:17

አጠቃላይ መረጃ:
ጸሐፊው ለቀደመው ትውልድ የዮርዳኖስን ወንዝ መክፈል ቀይ ባህርን ከመክፈል ልዩነት እንደሌለው ግልጽ እያደረገ ነበር የዮርዳኖስ ውሃ ወደ ቦታው ተመልሶ በዳርቻዎቹ ሞልቶ ፈሰሰ የዮርዳኖስ ወንዝ እስራኤላውያን በደረቅ ምድር ከማለፋቸው በፊት እና በኋላም በዳርቻዎቹ ሞልቶ ይፈስና አካባቢውን ያጥለቀልቅ ነበር አራት ቀናት "4 ቀናት" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 4:19

ከዮርዳኖስ ወጡ
ይህ እስራኤል የዮርዳኖስ ወንዝን በደረቅ ምድር ማቋረጣቸውን ያመለክታል። በአራተኛው ወር በአስረኛው ቀን ይህ በዕብራውያን ቀን አቋጣጠር የመጀመሪያው ወር ነው። አስረኛው ቀን በምዕራባውያን ቀን አቋጣጣር በመጋት መጨረሻ አቅራቢያ ነው። (የዕብራውያን ወራት እና ተከታታይ ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

ከዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ ያወጧቸው አስራ ሁለቱ ድንጋዮች ኢያሱ በደረቅ ምድር የመሻገራቸውን መታሰቢያ መገንባት ይችል ዘንድ እያንዳንዱ ነገድ ከዮርዳኖስ ወንዝ አንድ ድንጋይ መውሰድ ነበረበት። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 4:22

አጠቃላይ መረጃ
ኢያሱ ለህዝቡ ስለ ድንጋይ ክምሩ ማስታወሱን ቀጠለ። ለልጆቻችሁ ንገሩ እስራኤላውያን ልጆቻቸው ያህዌን ለዘለዓለም ያከብሩ ዘንድ የእግዚአብሔርን ተአምራቶች ለእነርሱ ማስተማር ነበረባቸው። የያህዌ እጅ ታላቅ ነው ይህ የያህዌ ሃይል ታላቅ መሆኑን ያመለክታል። "ያህዌ ታላቅ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 5

1 በዮርዳኖስ ማዶ በምዕራብ በኩል የነበሩ የአሞራውያን ነገሥታት ሁሉ፥ በታላቁም ባሕር አጠገብ የነበሩ የከነዓናውያን ነገሥታት ሁሉ፥ የእስራኤል ሕዝብ
እስኪሻገሩ ድረስ የዮርዳኖስን ውኃ እግዚአብሔር እንዳደረቀ በሰሙ ጊዜ ልባቸው ቀለጠ፤ ከእስራኤልም ሕዝብ የተነሣ የአንድም ሕዝብ ነፍስ አልቀረላቸውም። **2**
በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር ኢያሱን እንዲህ አለው፦"የባልጩት ድንጋይ ስለት ሠርተህ የእስራኤልን ሕዝብ እንደገና ግርዛቸው።" **3** ኢያሱም የባልጩት ድንጋይ
ስለት ሠርቶ ግብት ሃራሎት (ትርጉሙም የግርዛት ኮረብታ) በተባለ ስፍራ የእስራኤልን ወንዶች ሁሉ ገረዛቸው። **4** ኢያሱም የገረዘበት ምክንያት ይህ ነው፤
ከግብፅ የወጡት ወንዶች ሁሉ ጦረኞችን ሁሉ ጭምር ከግብፅ ከወጡ በኋላ በመንገድ ላይ በምድረ በዳ ሞቱ። **5** የወጡት ሕዝብ ሁሉ ተገርዘው ነበር፤ ነገር
ግን ከግብፅ በወጡበት መንገድ በምድረ በዳ የተወለዱት ሕዝብ ሁሉ አልተገረዙም ነበር። **6** ከግብፅ የወጡ የእስራኤል ሕዝብና ጦረኞች ሁሉ
የእግዚአብሔርን ቃል ባለመስማታቸው እስኪሞቱ ድረስ አርባ ዓመት በምድረ በዳ ይጓዙ ነበር ። እግዚአብሔርም ወተትና ማር የምታፈስሰውን ምድር ለእኛ
ይሰጠን ዘንድ ለአባቶቻቸው የማለላቸውን ምድር እንደማያሳያቸው ማለላቸው። **7** እግዚአብሔር በእነርሱ ፋንታ ያስነሳቸው በመንገድ ሳሉ ሳይገረዙ የነበሩ
ኢያሱም ገረዛቸው እነዚህን ልጆቻቸው ነበሩ። **8** ሕዝቡም ሁሉ በተገዙ ጊዜ እስኪድኑ ድረስ በሰፈር ውስጥ በየስፍራቸው ነበሩ። **9** እግዚአብሔርም ኢያሱን
እንዲህ አለ፦ ዛሬ የግብፅን ነውር ከእናንተ ላይ አንከባልያለሁ አለው፤ ስለዚህ የዚያ ስፍራ ስም እስከ ዛሬ ድረስ ጌልገላ ተብሎ ይጠራል። **10** የእስራኤልም
ሕዝብ በጌልገላ ሰፈሩ። ከወሩም በአሥራ አራተኛው ቀን በመሸ ጊዜ በኢያሪኮ ሜዳ ፋሲካ አደረጉ። **11** ከፋሲካውም በዓል ቀን በኋላ በዚያው ዕለት የምድሪቱን
ፍሬ ቂጣና ቆሎ በሉ።. **12** ከምድሪቱም ፍሬ ከበሉበት ቀን በኋላ መና ተቋረጠ። ከዚያም ጊዜ ጀምሮ ለእስራኤል ልጆች መና አልነበራቸውም፤ ነገር ግን በዚያ
ዓመት የከነዓንን ምድር ፍሬ በሉ። **13** ኢያሱ ወደ ኢያሪኮ አጠገብ በነበረ ጊዜ ዓይኖቹን አንሥቶ ተመለከተ፥ እነሆም ሰይፍ በእጁ የያዘ ሰው በፊቱ ቆሞ ነበር፤
ኢያሱም ወደ እርሱ ቀርቦ፦ ከእኛ ወገን ወይስ ከጠላቶቻችን ወገን ነህን? አለው። **14** እርሱም፦ አይደለሁም እኔ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ሆኜ እዚህ
መጥቼአለሁ አለ። ኢያሱም ወደ ምድር በግምባሩ ተደፍቶ ሰገደና፦ ጌታዬ ለአገልጋዩ የሚነግረው ምንድን ነው? አለው። **15** የእግዚአብሔርም ሠራዊት አለቃ
ኢያሱን፦ አንተ የቆምህበት ስፍራ የተቀደሰ ነውና ጫማህን ከእግህ አውልቅ አለው። ኢያሱም እንዲሁ አደረገ።

Joshua 5:1

ልቦቻቸው ቀለጡ ... በውስጣቸው ነፍስ አልቀረም ነበር
እነዚህ ሁለት ሃረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው የፍርሃታቸውን ጥልቀት ያጎላሉ። (ትይዩ ተነጻጻሪ ዘይቤ/ፓራራሊዝም የሚለውን ይመልከቱ)

ልቦቻቸው ቀለጡ
እዚህ ስፍራ "ልቦች" የሚለው ድፍረትን ያመለክታል። ሰም በእሳት እንደሚቀልጥ ድፍረታቸው ቀልጦ ጠፍቶ እጅግ ፈርተው ነበር። "ድፍረታቸውን ሁሉ አጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)በውስጣቸው ነፍስ አልቀረም ነበር እዚህ ስፍራ "ነፍስ" የሚለው የሚያመለክተው ለመዋጋት ያላቸውን ፈቃድ ነው። "ለመዋጋት አንዳች ፈቃድ አልነበራቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 5:2

ኢያሱ የባልጩት ምላጭ አዘጋጀ... ወንዶቹን ሁሉ ገረዘ
ከ600,000 በላይ ወንዶች ነበሩ፣ ስለዚህም ኢያሱ በዚህ ተግባር ላይ በነበረበት ጊዜ ሌሎች ብዙ ሰዎች እንደረዱት ግልጽ ነው። ይህ አንባቢውን ግራ የሚያጋባው ከሆነ፣ ተርጓሚው ይህንን ግልጽ ማድረግ ሊያስፈልገው ይችላል። "ኢያሱ እና እስራኤላውያኑ ራሳቸው የባልጩት ምላጭ አዘጋጅተው... ወንዶችን ሁሉ ገረዙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ጊብዓዝ ዓረሎት
ይህ እስራኤል ራሳቸውን ለያህዌ ዳግም መስጠታቸውን የሚታወስበት ስፍራ ስም ነው። ትርጉሙ "የሸለፈት ኮረብታ" ማለት ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 5:4

አጠቃላይ መረጃ
የእስራኤል ወንዶች ሁሉ የሚገረዙበት ምክንያት ተገልጽዋል።

የጦር ሰዎች
ወታደር ለመሆን እድሜያቸው የደረሰ ወንዶች

Joshua 5:6

የያህዌን ድምጽ ታዘዙ
እዚህ ስፍራ "ድምጽ" የሚለው የሚያመለክተው ያህዌ የተናገራቸውን ነገሮች ነው። "ያህዌ ያዘዛቸውን ነገሮች ታዘዙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)ወተት እና ማር የምታፈስ ምድር ምድሪቱ ወተት እና ማር ከእነዚያ እንስሳት እና ተክሎች በምድሪቱ እንደሚፈስ፣ ለእንስሳት እና ተክሎች መልካም እንደሆነች እግዘአብሔር ተናገረ።"ከብቶችን ለማርባት እና እህል ለማብቀል እጅግ መልካም ሆነች ምድር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

Joshua 5:8

በዚህ ዕለት የግብጽን ውርደት ከላያችሁ አንከባልያለሁ
ውርደታቸው የተገለጸው መንገዳቸውን እንደዘጋ ትልቅ ድናጋይ/ቆጥኝ ተደርጎ ነው። እዚህ ስፍራ "አንከባልላለሁ" የሚለው "ማስወገድ" የሚል ትርጉም አለው። "በዚህ ዕለት የግብጽን ውርደት ከእናንተ ላይ አስወግጃለሁ" ወይም "በግብጽ ባሮች በነበራችሁ ጊዜ ተዋርዳችሁ ነበር። ዛሬ ግን፣ ከእንግዲህ የተዋረዳችሁ እንዳትሆኑ አድርጌያችኋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 5:10

በወሩ አስራ አራተኛ ቀን
ይህ በምዕራባውያን ቀን አቆጣጠር ወደ መጋቢት መጨረሻ ነው። "የመጀመሪያው ወር አስራ አራተኛ ቀን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የዕብራውያን ቀን አቆጣጠር እና ተከታታይ ቁጥር እንዲሁም ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Joshua 5:13

ዐይኖቹን አንስቶ ወደ ላይ ሲመለከት እነሆ፣ አንድ ሰው ቆሞ አየ
እዚህ ስፍራ ወደላይ አነሳ የሚለው የተነገረው ኢያሱ በቀጥታ ዐይኖቹን በእጆቹ እንዳነሳ ተደርጎ ነው። "አቅንቶ ሲመለከት አንድ ሰው ቆሞ አየ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር

እነሆ
"እነሆ" የሚለው ቃል ለአዲስ መረጃ ልዩ ትኩረት እንድንሰጥ ያነቃናል። እርስዎ የሚተረጉሙበት ቋንቋ ይህን የሚተረጉምበት የራሱ መንገድ ሊኖረው ይችላል።

ሰይፉን መዞ በእጆቹ ይዞ ነበር
እዚህ ስፍራ "እርሱ" እና "የእርሱ" የሚሉት ቃላት ሚያመለክቱት ከኢያሱ ፊት የቆመውን ሰው ነው።

Joshua 5:14

እርሱ አለ
"እርሱ" የሚለው ቃል ኢያሱ ያየውን ሰው ያመለክታል።

ከየትኛውም
ይህ ሰውየው ለኢያሱ ጥያቄ መልስ መስጠት የጀመረበት ነው፣ "አንተ ከእኛ ወይስ ከጠላቶቻችን ጋር ነህ?" ይህ አጭር መልስ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "እኔ ከእናንተም ሆነ ከጠላቶቻችሁ ከየትኛውም ወገን አይደለሁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ኢያሱ በአምልኮ ወደ ምድር ተደፋ ይህ የአምልኮ ድርት ነበር። (ትምዕርታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ) ጫማህን ከእግርህ አውልቅ ይህ የውዳሴ/አምልኮ ድርጊት ነበር። (ትምዕርታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 6

1 ከእስራኤልም ሠራዊት የተነሣ የኢያሪኮ በሮች መጽሞ ተዘግተው ነበር። ወደ እርስዋም የሚገባና የሚወጣ ማንም አልነበረም። 2 እግዚአብሔርም ኢያሱን
አለው፦ ተመልከት፥ ኢያሪኮንና ንጉሥዋን የሠለጠኑ ወታደሮችዋንም በእጅህ አሳልፌ ሰጥቼአለሁ። 3 ሠራዊቶቹቻችሁ ሁሉ ከተማይቱን አንድ ጊዜ መዞር
አለባቸው። ይህንንም ለስድስት ቀናት አድርጉት። 4 ሰባትም ካህናት ሰባት ቀንደ መለከት በታቦቱ ፊት ይሸከሙ፤ በሰባተኛውም ቀን ከተማይቱን ሰባት ጊዜ
ይዙሩ፥ ካህናቱም ቀንደ መለከቱን ይንፉ። 5 ቀንደ መለከቱም ባለማቋረጥ ሲነፋ የመለከቱንም ድምፅ በሰማችሁ ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ ታላቅ ጩኸት ይጩኽ፥
የከተማይቱም ቅጥር ይወድቃል። እያንዳንዱ ወታደር ወደፊት በመሄድ ማጥቃት አለባቸው። 6 ከዚያም የነዌ ልጅ ኢያሱ ካህናቱን ጠርቶ እንዲህ አላቸው፦ የቃል
ኪዳኑን ታቦት ተሸከሙ፥ ሰባትም ካህናት ሰባት ቀንደ መለከት ወስደው በእግዚአብሔር ታቦት ፊት ይሂዱ አላቸው። 7 ሕዝቡንም፦ ሂዱ፥ ከተማይቱንም
ዙሩ፥ሠራዊቱም በእግዚአብሔር ታቦት ፊት ይሂዱ አለ። 8 ኢያሱም ለሕዝቡ እንደተናገረው ሰባቱ ካህናት ሰባቱን ቀንደ መለከት በእግዚአብሔር ታቦት ፊት ይዘው
ወደፊት እያለፉ ቀንደ መለከቱንም ይነፉ ነበር። የእግዚአብሔርም ቃል ኪዳን ታቦት ከኋቸው ይከተላቸው ነበር። 9 ሠራዊቱም በካህናቱ ፊት ቀንደ መለከታቸውን
እየነፉ ይሄዱ ነበር፤ ከዚያም ከቃል ኪዳን ታቦት ኋላ ደጀን ጦር ይሄድ ነበር፤እንዲሁም ካህናቱ ቀንደ መለከታቸውን ያለማቋረጥ ይነፉ ነበር። 10 ኢያሱ ግን
ሕዝቡን እንዲህ ብሎ አዘዛቸው፦ እኔ ጩኹ እስከምልበት ቀን ድረስ አትጩኹ፥ ከአፋችሁም ድምፅ አይውጣ፤ በዚያን ጊዜ ብቻ ትጮኻላችሁ። 11 ስለዚህ
እግዚአብሔር የዚያን ቀን የቃል ኪዳን ታቦት አንድ ጊዜ ከተማይቱን እንዲዞር አደረገው፤ ከዚያም ወደ ማደሪያቸው ገቡ፤ ሌሊቱንም እዚያው አደሩ። 12 ከዚያም
ኢያሱ ማለዳ ተነሣ ካህናቱም የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ታቦት ተሸከሙ። 13 ሰባቱም ካህናት ሰባት ቀንደ መለከት ይዘው በእግዚአብሔር ታቦት ፊት በቀስታ
እየሄዱ ቀንደ መለከቱንም ይነፉ ነበር። ሠራዊቱም በፊታቸው ይሄዱ ነበር። የደጀን ጦር ከእግዚአብሔር ታቦት ኋላ በሚድበት ጊዜ የቀንደ መለከት ድምፅ
ያልማቋረጥ ይሰማ ነበር። 14 በሁለተኛውም ቀን ከተማይቱን አንድ ጊዜ ዞረው ወደ ሰፈር ተመለሱ፤ ስድስት ቀንም እንዲሁ አደረጉ። 15 በሰባተኛውም ቀን ሲነጋ
ማልደው ተነሡ፥ ከዚህ በፊት በተለመደው ሁኔታ ከተማይቱን ሰባት ጊዜ ዞሩ፤ ከተማይቱን ሰባት ጊዜ የዞሩት በዚያ ቀን ነው። 16 በሰባተኛውም ቀን ካህናቱ ቀንደ
መለከቱን ሲነፉ ኢያሱ ሕዝቡን አዘዘ፦ እግዚአብሔር ከተማይቱን ሰጥቶአችኋልና ጩኹ። 17 ከተማይቱና በእርስዋም ያለው ሁሉ ለእግዚአብሔር የተለየና
ለጥፋት ይሆናሉ። የላክናቸውን መልክተኞች ስለ ሸሸገች ሴተኛ አዳሪዋ ረዓብ ብቻና ከእርስዋም ጋር በቤትዋ ውስጥ ያሉት ሁሉ በሕይወት ይኖራሉ። 18 እናንተ
ግን ለጥፋት የተለዩ ነገሮችን ከለያችሁት በኋላ አንዳች እንዳትወስዱ ራሳችሁን ጠብቁ። ለጥፋትም ከሆነው ነገር አንዳች የወሰዳችሁ እንደ ሆነ የእስራኤልን
ሰፈር እንዲጠፋ ታደርጉታላችሁ፥ ችግርም ታመጣላችህ። 19 ብር፥ ወርቅ፥ ናስና ከብረት የተሠሩ ዕቃዎች ሁሉ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ይሁን። ወደ
እግዚአብሔርም ግምጃ ቤት ይግባ። 20 ሕዝቡም ጮኹ፥ ካህናቱም ቀንደ መለከቱን ነፉ። ሕዝቡም የቀንደ መለከቱን ድምፅ በሰሙ ጊዜ ታልቅ ጩኸት ጮኹ፥
ቅጥሩም ሲወድቅ፤ ሕዝቡም እያንዳንዱ አቅንቶ ወደ ፊቱ ወደ ከተማይቱ ወጣ፤ ከተማይቱንም ያዙ። 21 በከተማይቱም የነበሩትን ሁሉ ወንዱንና ሴቱን፥ ሕፃኑንና
ሸማግሌውን፥ በሬውንም ፥በጉንና አህያውን በሰይፍ ስለት ፈጽመው አጠፉ። 22 ኢያሱም ምድሪቱን የሰለሉትን ሁለቱን ሰዎች እንዲህ አላቸው፦ ወደ ሴተኛ
አዳሪዋ ቤት ግቡ ከዚያም ሴቲቱንና ከእርስዋ ጋር ያሉትን ሁሉ እንደ ማላችሁላት አውጡ። 23 ሰላዮቹም ወጣቶች ሄደው ረዓብን አውጧአት፤ አባትዋንና
እናትዋን፥ ወንድሞችዋንም፥ አብሯት የነበሩ ቤተ ዘምዶችዋንም ሁሉ አወጡ። ከእስራኤልም ሰፈር ውጭ ወዳለው ስፍራ አመጦአቸው። 24 ከተማይቱንም
በእርስዋም የነበረውን ሁሉ በእሳት አቃጠሉ። ብሩ፥ ወርቅ፥የናሱና የብረት ዕቃዎች ብቻ በእግዚአብሔር ግምጃ ቤት አስቀመጡአቸው። 25 ነገር ግን ኢያሪኮን
ሊሰልሉ ኢያሱ የሰደዳቸውን መልክተኞች የሸሸገች ሴተኛ አዳሪዋን ረዓብን፥ የአባትዋንም ቤተ ሰብ፥አብሯት የነበሩትንም ሁሉ ኢያሱ በሕይወት እንዲሆሩ
ፈቀደላቸው። እርስዋም ኢያሱ ኢያሪኮን እንዲሰልሉ የላካቸውን ሰዎች ስለሸሸገች በእስራኤል መካከል እስከ ዛሬ ድረስ ትኖራለች። 26 በዚያን ጊዜም ኢያሱ
እንዲህ ሲል አዘዛቸው፦ ይህችን ኢያሪኮ ከተማን ለመሥራት የሚነሣ ሰው በእግዚአብሔር ፊት የተረገመ ይሁን። መሠረትዋን ሲጀምር በኩር ልጁ ይሙት፥
እርዋንም ሲያቆም ታናሹ ልጁ ይሙት፥ ብሎ ማለ። 27 እግዚአብሔርም ከኢያሱ ጋር ነበር፤ ዝናውም በምድር ሁሉ ላይ ወጣ።

Joshua 6:1

አሁን
ይህ ቃል እዚህ ስፍራ ያገለገለው ዋናው የታሪክ መስመር ሌላ መስመር እንዲከተል ነው።እዚህ ላይ ተራኪው የኢያሪኮ በሮች ለምን እንደተዘጉ እና እንደተቆለፉ ይነግረናል።

ኢያሪኮን፣ ንጉሥዋን፣ እና የሰለጠኑ ወታደሮችዋን በእጃችሁ አሳላፌ ሰጥቻችኋለሁ
ያህዌ ለኢያሱ ይህንን በእርግጥ እንደሚያደርግ የሚነግረው አስቀድሞ ነገሩ ያደረገው መሆኑን በመግለጽ ነው። (ሃላፊ የትንቢት ጊዜ የሚለውን ይመልከቱ)

በእጃችህ
"እጅ" የሚለው ቃል እጅ የሚፈጽመውን ለመቆጣጠር የሚውል ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት/ ነው። "ስለዚህ አንተ ይህንን መፈጸም ትችላለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 6:3

አያያዥ ሃሳብ፡
እግዚአብሔር ለኢያሱ ህዝቡ ማድረግ ያለበትን መናገሩን ቀጠለ

ይህንን ለስድሰት ቀናት ማድረግ አለባችሁ
"ይህንን ለስድስት ቀናት በየዕለቱ በቀን አንዴ ማድረግ አለባችሁ"

ሰባት ካህናት በታቦት ፊት ሰባት ቀንደ መለከት መያዝ አለባቸው
ሰባቱ ካህናት ታቦቱን ከያዙና በከተማይቱ ዙሪያ ከሚጓዙ ሌሎች ካህናት ፊት ይሂዱ

Joshua 6:5

አያያዥ ሃሳብ፡
እግዚአብሔር ለኢያሱ ህዝቡ ማድረግ ያለበትን መናገሩን ቀጠለ

እነርሱ የመለከቱን... ድምጽ ከፍ አድርገው ይንፉት
"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰባቱን ካህናት ነው "ቀንደ መለከት" እና "መለከት" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት በኢያሱ 6:4 የተጠቀሰውን ካህናቱ የሚነፉትን ቀንደ መለከት ነው

የከተማይቱ ቅጥር
"የከተማይቱ ውጫዊ ቅጥር" ወይም "ከተማይቱ የታጠረችበት ገንብ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Joshua 6:6

ነዌ
የኢያሱ አባት ነው።(ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የቃል ኪዳኑን ታቦት ያዙ
"የቃል ኪዳኑን ታቦት ይዛችሁ ተጓዙ)

Joshua 6:8

በያህዌ ፊት
አማራጭ ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ያህዌን በመታዘዝ" ወይም 2) በያህዌ ታቦት ፊት ለፊት" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ድምጸ መለከቶቹን ከፍ አድርገው ነፉ
x

Joshua 6:10

ምንም ድምጽ ከአፋችሁ አይውጣ
ከአንድ ሰው አፍ የሚወጣ ድምጽ የሚያመለክተው የዚያን ሰው ንግግር ወይም ጩኸት ነው። "አትጩሁ ወይም አትናገሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ኢያሱ ግን ህዝቡን አዘዘ
ኢያሱ ህዝቡን ከተማዋን መዞር ከመጀመራቸው አስቀድሞ አዘዛቸው። "ኢያሱ ህዝቡን አዝዞ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የድርጊቶች ቅደም ተከተል የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 6:12

ሰባት ካህናት ... ሰባት ድምጸ መለከቶች
"7 ካህናት... 7 ድምጸ መለከቶች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በመለከቶቹ ከፍ ያለ ድምጽ አሰሙ
ይህ ማለት ድምጸመለከቶቻቸውን ከፍ ያለ ድምጽ እንዲያሰሙ አድርገው ደጋግመው ነፉ ማለት ነው። "ያለማቋረጥ ድምጸ መለከቶቹ ከፍ ያለ ድምጽ እንዲያሰሙ አደረጉ" ወይም "ያለ ማቋረጥ ድምጸ መለከቶቹን ነፉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

በሁለተኛው ቀን
በሚቀጥለው ዕለት (ተከታታይ ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ) እነርሱ ይህንን አደረጉ እስራኤል በኢያሪኮ ዙሪያ በእየለቱ አንድ ጊዜ ዞሩ

ስድስት ቀናት
"6 ቀናት" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 6:15

ህዝቡ
ይህ የእስራኤልን ህዝብ ያመለክታል

መለከቶቹን ከፍ ባለ ድምጽ ነፉ
"ድምጸ መለከቶቹን ከፍ አድርገው ነፉ" ወይም "ድምጸ መለከቶቹን ነፉ"

ያህዌ ለእናንተ ሰጥቷችኋል
ኢያሱ ያህዌ ከተማዋን በእርግጥ ለእነርሱ እንደሚሰጥ ነገሩ ከመሆኑ አስቀድሞ እንደተፈጸመ እየተናገረ ነው። (ኃላፊ የትንቢት ጊዜ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰጥቷችኋል
"እናንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው መላውን የእስራኤል ህዝብ ነው። (አንተ የሚለውን ቃል መገለጫ መልኮች ይመልከቱ)

Joshua 6:17

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢያሱ ለእስራኤል ህዝብ መናገሩን ቀጠለ

ከተማይቱ እና በውስጧ የሚኖሩ ሁሉ ይጠፉ ዘንድ ለያህዌ የተለዩ ይሆናሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ከተማይቱን እና በውስጣ የሚኖሩትን ሁሉ ይጠፉ ዘንድ ለያህዌ መለየት አለባችሁ" ወይም " ከተማቱን እና በውስጧ ሚኖሩትን ሁሉ በማጥፋት ለያህዌ መለየት አለባችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አንዳች ነገር እንዳትወስዱ ተጠንቀቁ
መጠንቀቅ የሚለው የተገለጸው ራሳቸውን መጠበቅ እንዳለባቸው ተደርጎ ነው። "ነገሮቹን አለመውሰዳችሁን ጥንቃቄ አድርጉ" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በዚያ ነገር ችግር ታመጣላችሁ
በከተማይቱ ላይመጥፎ ነገር እንዲፈጠር አንዳች ነገር ማድረግ የተገለጸው በላይዋ ላይ ችግር ማምጣት በሚል ነው። "በእርሷ ላይ መጥፎ ነገር እንዲደርስ ምክንያት ትሆናላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌ ሃብት
ያህዌን ለማምለክ የተለዩ ነገሮች ስብስብ

Joshua 6:20

ህዝቡ በታላቅ ድምጽ ጮኸ
"የእስራኤል ሰዎች ጮኹ"

በመለከቶች ታላቅ ድምጽ አሰሙ
"መለከቶቹን ከፍ አድረገው ነፉ" ወይም "ቀንደ መለከቶቹን ነፉ"

በሰይፍ ስለት በከተማይቱ ውስጥ የነገረውን ሁሉ ሙሉ ለሙሉ አጠፉ
"የሰይፍ ስለት" የሚለው የሚገልጸው ወታደሮች በጦርነት ውስጥ የሚጠቀሙባቸውን ሰይፎች እና ሌሎች መሳሪያዎች ነው። "በሰይፎቻቸው በከተማይቱ ውስጥ የሚገኙትን ሁሉ ሙሉ ለሙሉ አጠፉ" (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ ሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 6:23

ከተማይቱን አቃጠሉ
"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው እስራኤላውያን ወታደሮችን ነው። ረዓብን እና ቤተሰቧቿን ከከተማይቱ ያወጡትን ሁለት ወጣት ወንዶች ብቻ የሚያመለክት አይደለም።

Joshua 6:25

እርሷ በእስራኤል ውስጥ ትኖራለች
"እርሷ" የሚለው ቃል ረዓብን እና ትውልዷቿን ያመለክታል። "የእርሷ ትውልድ በእስራኤል ይኖራል" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እስከ ዛሬ ድረስ
"አሁን" ወይም "ዛሬ ድረስ።" የመጀመሪያው ጸሐፊ ይህንን ታሪክ እንደጻፈው የረዓብ ትውልዶች አሁንም በእስራኤል ይኖራሉ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Joshua 6:26

ዳግም የሚገነባት ሰው በያህዌ ዐይኖች ፊት የተረገመ ነው
በያህዌ አይኖች ፊት የተረገመ የሚለው የሚገልጸው በያህዌ የተረገመ ማለትን ነው። "ዳግም የሚገነባት ሰው ያህዌ የረገመው ይሁን" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መሰረቱን የሚጥለው/ የሚመሰርተው በመጀመሪያ ልጁ የህይወት ዋጋ ይሁን/መሰረቱን ሲጥል የበኩር ልጁ ይሙት
ለኢያሪኮ አዲስ መሰረትን የሚጀምር ሰው የሚከፍለው ዋጋ የመጀመሪያ ልጁ መሞት ነው። ይህ የተነገረው ሰውየው ለስራው እንደሚከፍለው ተመን/ዋጋ ተደርጎ ነው። "መሰረቱን ከጣለ፣ የመጀመሪያ ወንድ ልጁን ያጣል" ወይም "መሰረቱን ከጣለ፣ የመጀመሪያ ልጁ ይሞታል" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በታናሹ ልጁ የህይወት ዋጋ በሮቿን ያቆማል/በሮቿን ሲያቆም ታናሹ ልጁ ይሙት
የኢያሪኮን አዲስ በሮች የሚያቆም ሰው የሚከፍለው ዋጋ የታናሹ ልጁ መሞት ነው። ይህ የተነገረው ሰውየው ለስራው እንደሚከፍለው ተመን/ዋጋ ተደርጎ ነው። "በሮቿን ካቆመ፣ የመጨረሻ ልጁን ያጣል" ወይም " "በሮቿን ካቆመ፣ የመጨረሻ ልጁ ይሞታል" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ዝናው በምድሪቱ ሁሉ ተስፋፋ
ይህ የያህዌን ሳይሆን፣ የኢያሱን ዝና ያመለክታል። በምድሪቱ በሚኖሩ መሃል ታዋቂ ሆነ የሚለው የተገለጸው ዝናው እንደተስፋፋ ተደርጎ ነው። "ኢያሱ በምድሪቱ ሁሉ ዝነኛ ሆነ" ወይም "በምድሪቱ የሚኖሩ ሰዎች ስለ ኢያሱ አወቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 7

1 የእስራኤል ሕዝብ ግን እንዲጠፉ ከተለዩ ነገሮች በመውሰድ ታማኝነትን አጎደሉ። ከይሁዳ ነገድ የሆነ አካን፥ እርሱም የከርሚ ልጅ፥ የዘንበሪ ልጅ፥ የዛራ ልጅ፥ እንዲጠፉ ከተለዩት ነገሮች ወሰደ፤ የእግዚአብሔርም ቁጣ በእስራኤል ሕዝብ ላይ ነደደ። **2** ኢያሱም ከቤቴል በምሥራቅ በኩል በቤት አዌን አጠገብ ወዳለችው ወደ ጋይ ከኢያሪኮ ሰዎችን ላከ። እርሱም፦ ውጡ ምድሪቱንም ሰልሉ ብሎ ተናገራቸው። ሰዎቹም ወጡ፥ ጋይንም ሰለሉ። **3** እነርሱም ወደ ኢያሱ ተመልሰው፦ ሕዝብን ሁሉ ወደ ጋይ አትላክ። ጋይን እንዲመቱ ሁለት ወይም ሦስት ሺህ ያህል ሰዎች ብቻ ይላክ። የጋይ ሰዎች በቁጥር ጥቂቶች ስለሆኑ ሕዝብ ሁሉ በውጊያ እንዲደክም አታድርግ። **4** ከሠራዊቱ ሦስት ሺህ ያህል ሰዎች ብቻ ወደዚያ ወጡ፤ እነርሱም ከጋይ ሰዎች ፊት ሸሹ። **5** የጋይም ሰዎች ከእነርሱ ሠላሳ ስድስት ያህል ሰዎችን መቱ፥ ከበሩ እስከ ሸባሪም ድረስ አባረሩአቸው፤ በቁልቁለቱም መቱአቸው። የሕዝቡም ልብ ፈራ፤ ድፍረትንም አጡ። **6** ኢያሱም ልብሱን ቀደደ። እርሱና የእስራኤልም ሽማግሌዎች በእግዚአብሔር ታቦት ፊት እስከ ማታ ድርስ በግምባራቸው ተደፉ፤ በራሳቸውም ላይ ትቢያ ነሰነሱ። **7** ኢያሱም አለ፦ ወዮ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፦ ይህን ሕዝብ ቀድሞኑ ዮርዳኖስን ለምን አሻገርኸው? እንዲያጠፉን በአሞራውያን እጅ ለምን አሳልፈህ ሰጠሃን? ከዚህ የተለየ ምርጫ ማድረግ በቻልንና በዮርዳኖስም ማዶ በተመቀመጥን ይሻለን ነበር። **8** ጌታ ሆይ የእስራኤል ሕዝብ በጠላቶቻቸው ፊት ከሸሹ በኋላ ምን ማለት እችላለሁ? **9** ይህንን ከነዓናውያንና በምድሪቱም የሚኖሩ ሁሉ ይሰማሉ። እነርሱም ይከብቡናል፥ በምድር ያሉትም ሕዝብ ስማችን እንዲረሳ ያደርጋሉ። ለታላቁ ስምህስ የምታደርገው ምንድን ነው? **10** እግዚአብሔርም ኢያሱን አለው፦ተነስተህ ቁም! ለምን በግምባርህ ተደፍተሃል? **11** እስራኤል ኃጢአትን አድርጎአል። ያዘዝኋቸውንም ቃል ኪዳኔን አፍርሰዋል። ለጥፋት ከተለዩት ነገሮችን ሰርቀዋል፤ ሰርቀው የወሰዱትንም ኃጢአት በዕቃቸውም ውስጥ ሸሽገዋት። **12** በዚህም ምክንያት የእስራኤል ሕዝብ በጠላቶቻቸው ፊት መቆም አይችሉም። ራሳቸው ለጥፋት የተለዩ ሆነው በጠላቶቻቸው ፊት ሸሹ። በመካከላችሁ እስካሁን ያለውን መወገድ ያለበትን እርም ከመካከላችሁ ካላጠፋችሁ ከዚህ በኋላ ከእናንተ ጋር አልሆንም። **13** ተነሣና ሕዝቡን ቀድስልኝ፤ እንዲህም በላቸው፦ራሳችሁን ለነገ ለእግዚአብሔር ቀድሱ ይላል የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር፤ እስራኤል ሆይ ፥ሊጠፉ የሚገቡ ነገሮች እስካሁን በመካከላችሁ አለ። መጥፋት ያልባቸው ነገሮች ከመካከላችሁ እስክታጠፉ ድረስ በጠላቶቻችሁ ፊት መቆም አትችሉም። **14** ነገም ራሳችሁን በየነገዳችሁ ታቀርባላችሁ፤ እግዚአብሔርም በዕጣ የሚለየው ነገድ በየወገኖቹ ይቀርባል። እግዚአብሔርም የሚለየው ወገን በየቤተ ሰቦቹ ይቀርባል። እግዚአብሔርም የሚለየው ቤተ ሰብ አንድ በአንድ ይቀርባል። **15** ለጥፋትም የተለየ ነገር የተገኘበት ሰው የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን በማፍረሱና በእስራኤልም ላይ ክፉ ነገር እንዲመጣ በማድረጉ እርሱና ለእርሱም ያለው ነገር ሁሉ በእሳት ይቃጠላል። **16** ኢያሱም ማልዶ ተነሣ፥ እስራኤልንም በየነገዶቻቸው አቀረበ፤ የይሁዳም ነገድ ተለየ። **17** የይሁዳንም ወገን አቀረበ፥የዛራም ወገን ለየ። የዛራንም ወገን እያንዳንዱን አቀረበ፤ ዘንበሪም ተለየ። **18** የቤተ ሰቡንም እያንዳንዱን አቀረበ፤ ከይሁዳም ነገድ የሆነ የከርሚ ልጅ የዘንበሪ ልጅ የዛራ ልጅ አካን ተለየ። **19** ከዚያ ኢያሱ አካንን አለው፦ ልጄ ሆይ፥ በእስራኤልም አምላክ ፊት እውነቱን ተናገር፥ ለእርሱም ተናዘዝ። ያደረግኸውንም ንገረኝ፤ ከእኔም አትሸሸግ። **20** አካንም መልሶ ኢያሱን እንዲህ አለ፦ በእውነት የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን በድያለሁ። ያደረግሁትም ይህንን ነው፦ **21** በዘረፋ መካከል አንድ የሚያምር የባቢሎን ኮት፥ ሁለት መቶም ሰቅል ብር፥ ሚዛኑም አምሳ ሰቅል የሆነ ወርቅ አይቼ ተመኘኋቸው፥ ወሰድኋቸውም። እነሆም፥ በድንኳኔ ውስጥ በመሬት ተሸሽገዋል፥ ብሩም ከሁሉ በታች ነው አለው። **22** ኢያሱም መልእክተኞችን ሰደደ፥ ወደ ድንኳኑም ሮጡ፤ ዕቃዎቹም ነበሩ። በድንኳኑም ውስጥ ተሸሽጎ አገኙት ብሩም ከበታች ነበረ። **23** ከድንኳኑም መካከል ዕቃዎቹን ወስደው ወደ ኢያሱና ወደ እስራኤል ሕዝብ ሁሉ አመጡት። በእግዚአብሔርም ፊት አኖሩት። **24** ኢያሱና እስራኤል ሁሉ የዛራን ልጅ አካንን፥ ብሩንም፥ ኮቱንም፥ ወርቁንም፥ ወንዶችንና ሴቶች ልጆቹንም፥ በሬዎቹንም፥ አህያውንም፥ በጎቹንም፥ ድንኳኑንም፥ ያለውንም ሁሉ ወስደው ወደ አኮር ሸለቆ አመጡአቸው። **25** ኢያሱም እንዲህ አለው፦ ለምን አስጨነቅኸን? እግዚአብሔርም ዛሬ ያስጨንቅሃል። እስራኤልም ሁሉ በድንጋይ ወገሩት፤ሁሉንም በእሳትም አቃጠሉአቸው፥ በድንጋይም ወገሩአቸው። **26** በላዩም እስከ ዛሬ ድረስ ያለ ታላቅ የድንጋይ ክምር ሆነ። እግዚአብሔርም ከቁጣው ትኩሳት ተመለሰ። ስለዚህም የዚያ ስፍራ ስም እስከ ዛሬ ድረስ የአኮር ሸለቆ ነው።

Joshua 7:1

ለመደምሰስ/መጥፋት የተለዩ ነገሮች
"ያህዌ ፈጽማችሁ በማጥፋት/በመደምሰስ ለእኔ ለየልኝ ያላቸው ነገሮች"

አካን...ከርሚ...ዘንበሪ...ዛራ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌ ቁጣ ነደደ
"ቁጣ" እና "ነደደ" የሚሉት የሚገልጹት በአካል እሳት እንዳለ ሳይሆን የቁጣውን ከፍተኛነት ደረጃ ነው። "የያህዌ ቁጣ እንድ እሳት ነደደ" ወይም "ያህዌ እጅግ ተቆጥቶ ነበር" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 7:2

ህዝቡ ሁሉ
ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን ሰራዊት ነው።

እነርሱ በቁጥር ጥቂት ናቸው
"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የጋይን ሰዎች ነው።

Joshua 7:4

ከሰራዊቱ ሶስት ሺህ ወንዶች ተነስተው ወጡ
እነዚህ ወንዶች የሰራዊቱ ክፍል ነበሩ። "የሰራዊቱ ክፍል የሆኑ ሶስት ሺህ ወንዶች ወጡ"

ሶስት ሺህ ወንዶች...ሰላሳ ስድስት ወንዶች
"3,000 ወንዶች... 36 ወንዶች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

የህዝቡ ልብ ቀለጦ እንደ ውሃ ሆነ
"ቀለጠ" እና "እንደ ውሃ ሆነ" የሚሉት ሃረጋት ተመሳሳይ ትርጉምን ይጋራሉ፤ በአንድነት ተቀናጅተው የቀረቡት ሰዎቹ እጅግ ፈርተው እንደነበር አጉልቶ ለማሳየት ነው። (ትይዩ ንጽጽር ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የህዝቡ ልብ ቀለጠ
እዚህ ስፍራ ላይ ህዝቡ የተገለጸው በእነርሱ "ልቦች" ነው ይህም ስሜቶቻቸውን በትኩረት ለመግለጽ ነው። "ህዝቡ እጅግ ፈርቶ ነበር" (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ ሚለውን ይመልከቱ

የህዝቡ ልብ
"ህዝቡ" የሚለው ሃረግ የሚያመለክተው እስራኤላውያን ወታደሮችን ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Joshua 7:6

ልብሶቹን ቀደደ... በጭንቅላታቸው አብዋራ ነስንሰው በያህዌ ታቦት ፊት በግንባራቸው ተደፉ
እነዚህን ነገሮች ያደረጉት በእግዚአብሔር ፊት ምን ያህል እንዳዘኑ እና እንደተጨነቁ ለማሳየት ነው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ያጠፉን ዘንድ ለአሞራውያን እጆች አሳልፈህ ልትሰጠን ነውን?
ኢያሱ እግዚአብሔር ዮርዳኖስን አሻግሮ ያመጣቸው ምክንያቱ ይህ እንደሆነ እየጠየቀ ነበር። "ይህን የደረግከው አሞራውያን ያጠፉን ዘንድ ለእነርሱ እጆች አሳልፈህ ልትሰጠን ነውን?" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኢሊፕሰስ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

ያጠፉን ዘንድ ለአሞራውያን እጆች አሳልፈህ ልትሰጠን ነውን?
የአሞራውያን እጆች የሚለው የሚገልጸው አቅማቸውን እና ሃይላቸውን ነው። እነርሱን ለመደምሰስ እስራኤላውያንን ለእጆቻቸው መስጠት የሚለው የሚገልጸው አሞራውያን እስራኤላውያንን እንዲቆጣጠሩ እና እንዲያጠፏቸው መፍቀድን ነው። "አሞራውያን እንዲያጠፉን ትፈቅዳለህን?" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ምነው ሌላ ውሳኔ ባደረግን ኖሮ
"ባደረግን ኖሮ" የሚለው ቃል የሚያሳየው አንድ ነገር ምነው ባልሆነ ኖሮ የሚል ፍላጎትን መግለጫ ነው። "ምነው የተለየ ውሳኔ አድርገን ቢሆን ኖሮ"

Joshua 7:8

አጠቃላይ መረጃ:
ኢያሱ መጨነቁን ለያህዌ ይገልጻል

እስራኤል ጀርባውን ለጠላቶቹ ከሰጠ በኋላ ምን ማለት እችላለሁ?
ኢያሱ ይህን የሚናገረው ምን መናገር እንዳለበት እንኳን እስከሚረበሽ ድረስ ተስፋ መቁረጡን ለመግለጽ ነው። "ምን ማለት እንዳለብኝ አላውቅም። እስራኤል ጀርባውን ለጠላት ሰጥቷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እስራኤላውያን ጀርባቸውን በጠላቶቻቸው ፊት አዙረዋል
ይህንን ማድረግ የሚገልጸው ከጠላቶቻቸው ፊት መሸሻቸውን ነው። "እስራኤል ከጠላቶቻቸው ሸሽተዋል/ እስራኤላውያንን ጠላቶቻቸው አሳደዋቸል" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ እኛን ይከባሉ፣ ደግሞም በምድር የሚኖሩ ሰዎች ስማችንን እንዲረሱ ያደርጋሉ
ሰዎች የእስራኤልን ስም እንዲረሱ ማድረግ የሚገልጸው፤ እስራኤላውያንን እንዲረሱ ማድረግን ነው። በዚህ ሁኔታ ይህንን የሚያደርጉት እስራኤላውያንን በመግደል ነው። "ይከቡናል፣ ይገድሉንማል፤ ደግሞም የምድር ህዝብ ሁሉ ይረሳናል።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ለታላቁ ስምህ
"ታላቁ ስምህ" የሚለው ሃረግ እዚህ ስፍራ የሚገልጸው የእግዚአብሔርን ዝና እና ሃይል ነው። "እናም ስለዚህ አንተ ታላቅ መሆንህን ህዝቦች ያውቁ ዘንድ ምን ታደርጋለህ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ለታላቁ ስምህ ምን ታደርጋለህ?
ኢያሱ ይህንን ጥያቄ ያነሳው እስራኤላውያን ከተደመሰሱ፣ ሌሎች ህዝቦች እግዚአብሔር ታላቅ አይደለም ብለው ያስባሉ የሚለውን ለእግዚአብሔር ለማሳሰብ/ እግዚአብሔርን ለማስጠንቀቅ ነው። "ከዚያ ለስምህ ታላቅነት ልታደርገው የምትችለው ምንም ነገር አይኖርም" ወይም "ከዚያ ሰዎች አንተ ታላቅ መሆንህን አያውቁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

Joshua 7:10

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ እስራኤል ለምን እንደተረገመ ለኢያሱ መለሰለት።

ለምን በዚያ በፊትህ ተደፋህ?
እግዚአብሔር ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት ኢያሱ በዚያ በፊቱ መደፋቱን ለመገሰጽ ነው። "በአፍር ላይ በዚያ መደፋትህን አቁም!" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ)

ተለይተው ተቀምጠው የነበሩት ነገሮች
እነዚህ በኢያሱ 6:18-19 "እንዲጠፉ የተለዩ" ነገሮች ናቸው። "የተረገሙት ነገሮች" ወይም "እግዚአብሔር የረገማቸው ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ሰርቀዋል ከዚያም ደግሞ ኃጢአታቸውን ደብቀዋል
ኃጢአታቸውን መደበቅ የሚለው የሚገልጸው ኃጢአት መስራታቸውን ሌሎች እንዳያውቁ ለማድረግ መሞከራቸውን ይገልጻል። "እነዚያን ነገሮች ሰርቀዋል፣ ከዚያም ቀጥሎ ኃጢአት መስራታቸውን ሰዎች እንዳያውቁ ለማድረግ ሞክረዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በጠላቶቻቸው ፊት መቆም አይችሉም
በጠላቶቻቸው ፊት መቆም የሚለው የሚወክለው ጠላቶቻቸውን ውጤታማ ሆነው መውጋት አይችሉም የሚለውን ነው። "ጠላቶቻቸውን ውጤታማ ሆነው መውጋት አይችሉም" ወይም "ጠላቶቻቸውን ማሸነፍ አይችሉም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ለጠላቶቻቸው ጀርባቸውን አዞሩ/ጀርባቸውን አዙረው ሸሹ
ይህንን ማድረግ የሚወክለው ከጠላቶቻቸው መሸሻቸውን ነው። "ከጠላቶቻቸው ሸሹ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህ ከእናንተ ጋር አልሆንም
ከእስራኤል ጋር መሆን የሚወክለው እስራኤልን መርዳትን ነው። "ከእንግደህ በኋላ አልረዳችሁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 7:13

አያያዥ ሃሳብ:
ያህዌ ከኢያሱ ጋር መነጋገሩን ቀጠለ፤ ደግሞም ለህዝቡ መናገር ያለበትን ነገረው።(ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ህዝቡ
ይህ የእስራኤልን ህዝብ ያመለክታል

ጠላቶቻችሁን መቋቋም አትችሉም
ከጠላቶቻቸው ፊት መቆም የሚገልጸው ከጠላቶቻቸው ጋር ተዋግተው በስኬት ማሸነፍን ነው። "ከጠላቶቻችሁ ጋር በስኬት መዋጋት አትችሉም" ወይም "ጠላቶቻችሁን ማሸነፍ አትችሉም"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Joshua 7:14

አያያዥ ሃሳብ፡
ያህዌ ከኢያሱ ጋር መነጋገሩን ቀጠለ፤ ደግሞም ለህዝቡ መናገር ያለበትን ነገረው።

ራሳችሁን በየነገዳችሁ ማቅረብ አለባችሁ
የእስራኤልን ህዝብ የሚመሰርቱ አስራ ሁለት ነገዶች ነበሩ። "በየነገዶቻችሁ" የሚለው ሃረግ ትርጉሙ "በእያንዳንዱ ነገድ" ማለት ነው። "እያንዳንዳቸው ነገዶቻችሁ ራሳቸውን ለያህዌ ማቅረብ ይኖርባቸዋል " በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ የሚለየው ነገድ በየጎሳው ይቀርባል
ነገድ ከበርካታ ጎሳ የሚመሰረት ነው። "ያህዌ ከለየው ነገድ፣ እያንዳንዱ ጎሳ ወደፊት ይቀርባል" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ የሚለየው ነገድ
የእስራኤል መሪዎች እጣ ያወጣሉ፣ እናም ይህንን በማድረግ፣ ያህዌ የለየውን ነገድ ያውቃሉ። ይህ ይበልጥ በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "ያህዌ በእጣ የሚለየው ነገድ" ወይም "እጣ ስናወጣ ያህዌ የሚለየው ነገድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ያህዌ የሚለየው ጎሳ በእያንዳንዱ ቤተሰብ መቅረብ ይኖርበታል
ጎሳ በብዙ ቤተሰቦች የሚመሰረት ነበር። "ያህዌ ከሚለየው ጎሳ፣ እያንዳንዱ ቤተሰብ ወደፊት መቅረብ ይኖርበታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ የሚለየው ቤተሰብ በነፍስ ወከፍ መቅረብ ይኖርበታል
ቤተሰብ በርካታ ሰዎች በውስጡ ነበሩት። "ያህዌ ከለየው ቤተሰብ፣ እያንዳንዱ ሰው ወደፊት መቅረብ ይኖርበታል" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የተለየው ሰው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ያህዌ የለየው ሰው" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ የያህዌን ቃልኪዳን አፍርሷል
ቃልኪዳንን ማፍረስ የሚለው ያለመታዘዝን ያመለክታል። "እርሱ የያህዌን ቃል ኪዳን አፍርሷል" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 7:16

አጠቃላይ መረጃ፡
ኢያሱ እስራኤልን በያህዌ ፊት ለማቅረብ የያህዌን ትዕዛዝ ተከተለ

እስራኤልን በየነገዱ ወደፊት አቀረበ
"በየነገዱ/ነገድ በነገድ" የሚለው ሃረግ እያንዳንዱ ነገድ ማለት ነው። "እያንዳንዱን የእስራኤል ነገድ ወደፊት አቀረበ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳ ነገድ ተለየ
ይህ በዐድራጊ አረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ያህዌ የይሁዳን ነገድ ለየ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ።

የዛራውያንን ጎሳ በነፍስ ወከፍ አቀረበ
"በነፍስ ወከፍ/ በግለሰብ" የሚለው ሃረግ እያንዳንዱ ሰው የሚል ትርጉም የሚሰጥ ፈሊጥ ነው። በዚህ ዐረፍተ ነገር ውስጥ ግለሰቦች የተባሉት የቤተሰባቸው መሪዎች/አባወራ ነበሩ። "እርሱም የዛራውያንን ጎሳዎች እያንዳንዱን ሰው ወደፊት አቀረበ" ወይም "ከዛራውያን ጎሳ የቤተሰቡ መሪ የሆን እያንዳንዱን ሰው ወደፊት አቀረበ" (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

የዛራውያን ጎሳ
ጎሳው ስሙን ያገኘው ዛራ ከተባለው ሰው ስም በመነሳት ነው

ዘንበሪ...አካን...ከርሚ...ዛራ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። እነዚህን በኢያሱ 7:1 ላይ በተረጎሙበት መሰረት ይተርጉሙ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 7:19

ለእርሱ ኑዛዜያችሁን/ንስሃ አቅርቡ
"ንስሃ/ኑዛዜ" የሚለው ረቂቅ ስም "ተናዘዘ" በሚል ግስ ሊገለጽ ይችላል። "ለእርሱ ተናዘዝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ነገሩን ከእኔ አትደብቅ
መረጃን መደበቅ የሚወክለው አንድ ሰው ነገሩን እንዳያውቅ ጠብቆ ለመያዝ መሞከርን ነው። "ያደረግከውን እንዳላውቅ ልትሸሸገኝ አትሞክር" (ዘይቤያዊ አነጋገርየሚለውን ይመልከቱ)

ሁለት መቶ ሰቅል
ይህ ከሁለት ኪሎ ግራም በላይ ነው።(መጽሐፍ ቅዱሳዊ የክብደት መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

ሃምሳ ሰቅል
ይህ ከ500 ግራም በላይ ነው። (መጽሐፍ ቅዱሳዊ የክብደት መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

በመሬት ውስጥ ተደብቀዋል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እኔ በመሬት ውስጥ ደብቄያቸዋለሁ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 7:22

እነርሱ አዩ/አገኙ
"ኢያሱ የላካቸው ሰዎች አዩ/አገኙ"

እቃዎቹን አውጥተው ዘረገፉ
በእርስዎ ቋንቋ ውስጥ የሚገኝን በርካታ ትንንሽ እቃዎችን ከትልቅ ቦርሳ/ሻንጣ መሬት ላይ መድፋትን የሚገልጽ ቃል ይጠቀሙ

Joshua 7:24

የአኮር ሸለቆ
የስሙ ትርጉም "የችግር ሸለቆ" ማለት ነው፣ ነገር ግን አኮርን በተጻፈበት አጠራሩ እንዳለ አኮር ብሎ መተርጎሙ ይመረጣል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 7:25

ለምን አስጨነቅከን?
ኢያሱ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት አካንን ለመገሰጽ ነው። "አንተ አኛን አስጨነቅከን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሰሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚይም የቀሩትን በድንጋይ ወገሯቸው፤ ደግሞም በእሳት አቃጠሏቸው።
ሊሰጡ የሚችሉ አማራጭ ትርጉሞች 1)እስራኤላውያን የአካንን ቤተሰብ አቃጥለው ገደሉ፤ከዚያም ድንጋይ ከመሩባቸው ወይም 2) እስራኤላውያን የአካንን ቤተሰብ በድንጋይ ወግረው ገደሉ ከዚያም በድናቸውን አቃጠሉ ወይም 3) አካን እና ያለው ሁሉ በድንጋይ ተወገረ ከዚያም ተቃጠለ

ያህዌ የነድ ቁጣውን አራቀ
ቁጣውን አራቀ የሚለው የሚገልጸው ቁጣውን አቆመ ማለት ነው። የሚነድ ቁጣ የሚለው የሚወክለው ጠንካራ ቁጣን ነው። "ያህዌ ከቁጣው ተመለሰ/ መቆጣቱን አቆመ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እስከ ዛሬ ድረስ
ጸሐፊው ይህንን እስከጻፈበት ጊዜ ድረስ የአኮር ሸለቆ ተብሎ ይጠራ ነበር

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 8

1 እግዚአብሔርም ኢያሱን እንዲህ አለ፦ አትፍራ አትደንግጥ። ጦረኞችንም ሁሉ ከአንተ ጋር ውሰድ ተነሥተህም ወደ ጋይ ውጣ። ተመልከት፥ የጋይን ንጉሥ፥ ሕዝቡን፥ ከተማውንና ምድሩን በእጅህ ሰጥቼሃለሁ። **2** በኢያሪኮና በንጉሥዋም እንዳደረግህ እንዲሁ በጋይና በንጉሥዋ ታደርጋለህ፤ ምርኮውንና ከብቱን ግን ለራሳችሁ ትወስዳላችሁ። ከከተማይቱም በስተ ኋላ ድብቅ ጦር አዘጋዝጅ አለው። **3** ኢያሱም ተነሣና ጦረኞቹንም ሁሉ ወደ ጋይ ወሰዳቸው። ኢያሱም ጽኑዓን ኃያላን የሆኑትን ሠላሳ ሺህ ሰዎች መርጦ በሌሊትም ሰደዳቸው። **4** እንዲህም ብሎ አዘዘቸው፦ እነሆ፥ከከተማይቱ በስተ ኋላ ተደበቁ። ከከተማይቱ በጣም ርቃችሁ አትሂዱ፤ነገር ግን ሁላችሁም ተዘጋጁ። **5** እኔና ከእኔም ጋር ያለው ሕዝብ ሁሉ ወደ ከተማይቱ እንቀርባለን። እንደ በፊቱ ሊያጠቁን በሚመጡበት ጊዜ ከፊታቸው እንሸሻለን። **6** አስቀድመን እንደ ሸሸን፥ የምንሸሸ ይመስላቸዋል፥ ከከተማይቱ እስክናርቃቸው ድረስ ወጥተው ይከተሉናል። እንዲህም ይላሉ፦ባለፈው እንዳደረጉት ከፊታችን እየሸሹ ነው። እኛም ከእነርሱ እንሸሻለን። **7** እናንተም ከተደበቃችሁበት ስፍራ መጥታችሁ ከተማዋን ትይዛላችሁ። እግዚአብሔር አምላካችሁም እርስዋን በእጃችሁ አሳልፎ ይሰጣችኋል። **8** ከተማይቱንም በያዛችኋት ጊዜ በእሳት አቃጥሉአት። በእግዚአብሔርም ቃል እንደታዘዛሁ ታደርጋላችሁ። እነሆ፥ አዝዣችኋለሁ። **9** ኢያሱም ሰደዳቸው፤ እነርሱም ወደሚደበቁበት ስፍራ ሄደው፥ በጋይና በቤቴል መካከልም ከጋይ በስተምዕራብ ተደበቁ። ኢያሱ ግን በዚያች ሌሊት በሕዝቡ መካከል አደረ። **10** ኢያሱም ማልዶ ተነሣና ሕዝቡን አሰለፈ፤እርሱና የእስራኤልም ሽማግሌዎች የጋይን ሕዝብ አጠቁ ። **11** ከእርሱም ጋር የነበሩ ጦረኞች ሁሉ ሄደው፥ ወደ ከተማይቱ ደረሱ። ወደ ከተማይቱ አጠገብ መጡና በሰሜን በኩል በጋይ ሰፈሩ። በእነርሱና በጋይ መካከል ሸለቆ ነበረ። **12** አምስት ሺህ ያህል ሰዎችንም ወስዶ በቤቴልና በጋይ መካከል በከተማይቱም በምዕራብ በኩል በድብቅ አስቀመጣቸው። **13** በከተማይቱ የነበሩትን ሠራዊት ሁሉ፤ በከተማይቱ ሰሜን በኩል ዋና ጦርና በከተማይቱ ምዕራብ በኩል ደጀን ጦር ጠባቂዎችን አኖሩ። ኢያሱም በዚያች ሌሊት በሸለቆው አደረ። **14** የጋይም ንጉሥ ባየ ጊዜ ይህ ስለታወቀ፥እርሱና ሠራዊቱ በማለዳ ተነስተው እስራኤልን ለማጥቃት ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ሸለቆ ወዳለው ሰፍራ ቸኮሉ። ከከተማይቱ በስተ ኋላ ግን ድብቅ ጦር ለማጥቃት እንዳለ አያውቅም ነበር። **15** ኢያሱና እስራኤል ሁሉ ራሳቸው በፊታቸው ድል የተነሡ መስለው ወደ ምድረ በዳው መንገድ ሸሹ። **16** በከተማይቱም የነበሩ ሰዎች ሁሉ በአንድነት ከኋላቸው እንዲሄዱ ተጠሩ፤ ኢያሱንም አሳደዱት፥ ከከተማይቱም ርቀው ወጡ። **17** በጋይና በቤቴልም ውስጥ እስራኤልን ለማሳደድ ያልወጣ ሰው አልነበረም። ከተማይቱንም ክፍት አድርገው፥ እስራኤልን አሳደዱ። **18** እግዚአብሔርም ኢያሱን እንዲህ አለ፦ በእጅህ ያለውን ጦር በጋይ አነጣጥር፤ ጋይንም በእጅህ አሳልፌ እሰጥሃለሁ። ኢያሱም በእጁ ያለውን ጦር በከተማይቱ ላይ ዘረጋ። **19** የተደበቁትም ሠራዊት ፈጥነው ከስፍራቸው ወጥተው ኢያሱም እጁን እንደ ዘረጋ ሮጡ። ወደ ከተማይቱም ሮጡ፤ ገብተውም ያዙአት። ፈጥነውም ከተማይቱን በእሳት አቃጠሉአት። **20** የጋይም ሰዎች ወደ ኋላቸው ዞረው ተመለከቱ። ከከተማይቱ ወደ ሰማይ የሚወጣውን ጢስ አዩ፤ ወዲህ ወይም ወዲያም መንገድ ማምለጥ አልቻሉም። ወደ ምድረ በዳ ሸሽተው የነበሩ የእስራኤላውያን ጦር ሠራዊት ያሳድዱአቸው የነበሩትን ለመግጠም ተመለሱ። **21** ኢያሱና እስራኤል ሁሉ ድብቅ ጦር ከተማይቱን እንደ ያዙ ወደ ላይ ከሚወጣ ጢስ ጋር ባዩ ጊዜ፥ ወደ ኋላ ተመልሰው የጋይን ሰዎች ገደሉ። **22** ሌሎቹም ወደ ከተማይቱ ሄደው የነበሩ የእስራኤል ሠራዊት ለማጥቃት ወጡ። ስለዚህም የጋይ ሰዎች በእስራኤል ሠራዊት መካከል ሌሎቹ በዚህ በኩልና ሌሎቹ በዚያ በኩል ተያዙ። እስራኤልም የጋይን ሰዎች አጠቁአቸው፤ አንዳቸውም አልተረፉም፤ አላመለጡምም። **23** በሕይወት የያዙትን የጋይንም ንጉሥ ማርከው ወደ ኢያሱ አመጡት። **24** እንዲህም ሆነ፤ የጋይን ሰዎች ሁሉ በሜዳና በምድረ በዳ አጠገብ እስራኤልን ሲያሳድዱ በነበሩበት ቦታ ሁሉም የመጨረሻ በሰይፍ ስለት እስኪ ወድቁ ድረስ ጨርሰው ከገደሉአቸው በኋላ፥ እስራኤል ሁሉ ወደ ጋይ ተመለሱ። በሰይፍም ስለት መቱአቸው። **25** በዚያም ቀን በሰይፍ ስለት የወደቁት ወንዶችና ሴቶች የጋይ ሰዎች ሁሉ አሥራ ሁለት ሺህ ነበሩ። **26** ኢያሱም የጋይን ሰዎች ሁሉ ፈጽሞ እስኪያጠፋ ድረስ ጦር የዘረጋባትን እጁን አላጠፈም። **27** እስራኤላውያንም እግዚአብሔር ኢያሱን እንዳዘዘው የዚያችን ከተማ ከብትና ምርኮ ለራሳቸው ወሰዱ። **28** ኢያሱም ጋይን አቃጠላት፥ ለዘላለም የፍርስራሽ ክምር እንዲሆን አደረጋት። እስከ ዛሬም ድረስ ባዶ ስፍራ ሆነች። **29** የጋይንም ንጉሥ እስከ ማታ ድረስ በዛፍ ላይ ሰቀለው። ኢያሱም ፀሐይ በገባች ጊዜ የንጉሡን አስክሬን ከዛፍ አወርደው፥ በከተማይቱ በር አደባባይ እንዲጥሉት አዘዘ። በላዩም ታላቅ የድንጋይ ክምር አደረጉት። እስከ ዛሬ ድረስም ይህ የድንጋይ ክምር አለ። **30** ከዚያም ኢያሱ በጌበል ተራራ ላይ ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር መሠዊያን ሠራ። **31** የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ እንዳዘዘ፦ በሙሴም ሕግ መጽሐፍ እንደተጻፈው፥ መሠዊያው ካልተወቀረ ድንጋይና ብረት ካልነካው ነበረ። በእርሱም ላይ ለእግዚአብሔር የሚቃጠለውን መሥዋዕት አቀረቡ፥ የደኅንነትንም መሥዋዕት ሠዉ። **32** የእስራኤልም ሰዎች ፊት በድንጋዮቹ ላይ የሙሴን ሕግ ቅጂ ጻፈባቸው። **33** እስራኤል ሁሉ፥ ሽማግሌዎቻቸውም፥ አለቆቻቸውም፥ ፈራጆቻቸውም፥ በመጻተኞችና በአገሩ ልጆች ፥እኩሌቶቹ በገሪዛን ተራራ ፊት ለፊት እኩሌቶቹም በጌባል ተራራ ፊት ሆነው የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ታቦት በተሸከሙት በካህናትና በሌዋውያን ፊት ለፊት፥ በታቦቱም ፊት በወዲህና በወዲያ ቆመው ነበር። የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴ እንዳዘዘ፥የእስራኤልን ሕዝብ አስቀድሞ ባረኩ። **34** ከዚህም በኋላ ኢያሱ በሕጉ መጽሐፍ እንደ ተጻፉ የሕጉን ቃሎች ሁሉ በረከቱንና እርግማኑን አነበብ። **35** ኢያሱም በእስራኤል ጉባኤ ሁሉ ፊት በሴቶቹም፥ በሕፃናቱም፥ በመካከላቸውም በሚኖሩት መጻተኞች ፊት ሙሴ ካዘዘው አንዲት ቃል ሳያስቀር ሁሉን አነበበ ።

Joshua 8:1

አትፍሩ፣ ተስፋ አትቁረጡ
እነዚህ ሁለት ሃረጋት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ያህዌ ያቀናጃቸው ለፍርሃት አንዳች ምክንያት ስለሌለ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የጋይን ንጉሥ... እና ምድሩን በእጆችህ አሳልፌ ሰጥቼሃለሁ
እነርሱን ለእስራኤላውያን እጆች አሳልፎ መስጠት የሚወክለው ለእስራኤል ድልን እና የበላይነትን መስጠትን ነው። "በጋይ ንጉሥ እና በህዝቡ ላይ ደግሞም በእርሱ ከተማ እና በምድሩ ላይ ድልን ሰጥቼሃለሁ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ሰጥቼሃለሁ
እግዚአብሔር ሊያደርግ ቃል የገባውን ልክ እንዳደረገው ያህል ይናገራል፣ ምክንያቱ እርሱ በእርግጥ ስለሚያደርገው ነው። "እኔ በእርግጥ ሰጥቼሃለሁ" ወይም "እኔ እሰጣለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትንቢታዊ ኃላፊ ጊዜ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሷ ንጉሥ
"እርሷ" የሚለው ቃል የጋይን ከተማ ያመለክታል። ከተማዎች ብዙውን ጊዜ ሴት እንደሆኑ ተደርጎ ይነገሩ/ይገለጹ ነበር። "ንጉሥዋ" ወይም "የእነርሱ ንጉሥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Joshua 8:3

የጦርነት ሰዎች
"የእስራኤል ሰራዊት"

ሰላሳ ሺህ ወንዶች
"30,000 ወንዶች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 8:5

አጠቃላይ መረጃ
ኢያሱ ለወታደሮቹ የጦር ሜዳውን እቅድ መግለጹን ቀጠለ

በእጃችሁ ይሰጣችኋል
እዚህ ስፍራ "እጅ" ምሳሌነቱ እስራኤላውያን በጠላቶቻቸው ላይ ያላቸውን የበላይነት እና ሃይል የሚገልጽ ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 8:8

አጠቃላይ መረጃ
ኢያሱ ለወታደሮቹ የጦር ሜዳውን እቅድ መግለጹን አጠናቀቀ።

ኢያሱ ላካቸው
ይህ ሃረግ የሚያመለክተው ኢያሱ በጋይ እንዲያደፍጡ የተመረጡ ሰላሳ ሺህ ወንዶችን መላኩን ነው

የደፈጣው ስፍራ
"ጥቃት የማድረሻው ጊዜ እስኪደርስ ድረስ እነርሱ የሚደበቁበት ስፍራ ነው"

Joshua 8:10

አምስት ሺህ ወንዶች"**5,000** ወንዶች"
ይህ ቡድን ከ"ሰላሳ ሺህ ወንዶች" ውስጥ የተወሰደ ይመስላል (ኢያሱ 8፡ 9)። 25,000 የሚያህሉት ወንዶች ከተማዋን ሲያጠቁ ይህ አነስ ያለው ቡድን አድፍጦ ቆየ። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 8:13

አጠቃላይ መረጃ፡
እስራኤላውያን ጋይን ለመውጋት ተዘጋጁ

ዋናው ሰራዊት
ይህ በደፈጣ ላይ ከሆኑት ውጭ ያለውን ትልቁን የተዋጊ ቡድን ያመለክታል

ደጀን ጦር
እነዚህ "በከተማይቱ ምዕራብ አቅጣጫ አድፍጠው የተቀመጡ" ናቸው (ኢያሱ 8፡12 ይመልከቱ)

Joshua 8:15

ከእነርሱ አስቀድሞ ራሳቸው ይሸነፉ
"ከጋይ ሰዎች አስቀድሞ ራሳቸው ይሸነፉ" "ከእነርሱ አስቀድሞ" የሚለው ሃረግ የሚወክለው የጋይ ሶች የሚያዩትን እና የሚያስቡትን ነው። "የጋይ ሰዎች እስራኤላውያን እንደተሸነፉ ያስቡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከእነርሱ አስቀድሞ ራሳቸው ይሸነፉ
"ይሸነፉ" የሚለው ሃረግ በአድርጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የጋይ ሰዎች እስራኤላውያንን ያሸነፉ ይምሰላቸው" (አድርጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእነርሱ አስቀድሞ... ተከትለው ሄዱ... እነርሱ ተባረሩ
እዚህ ስፍራ "ከእነርሱ" እና "እነርሱ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት የጋይን ሰራዊት ነው።

እነርሱ ሸሹ ... ከእነርሱ በኋላ ተከተሉ
እዚህ ስፍራ "ከእነርሱ" እና "እነርሱ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት የእስራኤልን ሰራዊት ነው

በከተማይቱ የነበሩ ሰዎች ሁሉ በአንድነት ተጠሩ
ይህ በአድርጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የከተማይቱ መሪዎች የከተማይቱን ህዝብ በአንድነት ጠሩ" (አድርጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በከተማይቱ የነበሩ ሰዎች ሁሉ
ስለ ሁሉም ሰዎች አጠቃላይ በሆነ መንገድ ይጽፋል፣ ነገር ግን፣ "ሰዎች ሁሉ" የሚለው የሚያመለክተው መዋጋት የሚችሉትን ሰዎች ብቻ ነው። "በከተማይቱ የነበሩ የእስራኤልን ሰራዊት ማባረር የሚችሉ ሰዎች ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና ማጠቃለያ የሚሉትን ይመልከቱ።

ክፍት ትተው
"ከተማይቱን ክፍት ትተው"

Joshua 8:24

እስራኤላውያን ሁሉንም የምድሪቱን ነዋሪዎች አጥፍተው ሲጨርሱ... ሁሉም ... በሰይፍ ስለት በወደቁ ጊዜ
እዚህ ስፍራ "ወደቁ" የሚለው ሞቱ/ተገደሉ ለሚለው ኢፊሚዝም/የማያስደስትን ቃለ ሻል ባለ ቃል መጠቀም ነው። እንደዚሁም "የሰይፍ ስለት" የሚለው የሚወክለው ሰይፎችን በሙሉ ሲሆን ሰይፎች የሚለው የሚወክለው አንድም ጦርነትን ወይም የእስራኤልን ሰራዊት ነው። "በጦርነቱ ውስጥ ሞቱ" ወይም "የእስራኤል ወታደሮች በወጓቸው ጊዜ ሞቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኢፊሚዝም/የማያስደስትን ቃለ ሻል ባለ ቃል መጠቀም እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አስራ ሁለት ሺህ
"12,000" ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ

Joshua 8:27

የተተወ ስፍራ
ይህ በአንድ ወቅት ሰዎች የሚኖሩበት፣ አሁን ግን ማንም የማይኖርበት ስፍራ ነው

Joshua 8:29

እስከ ዛሬ ድረስ
"ዛሬ" ወይም "አሁን ድረስ"

Joshua 8:30

የጌባል ተራራ
በከነዓን የሚገኝ ተራራ (ስሞች እንዴት ይተጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Joshua 8:34

እስራኤል
ይህ የእስራኤልን መንግስት ያመለክታል

ሙሴ ካዘዘው ውስጥ ኢያሱ ያላነበበው አንዲትም ቃል እንኳን አልነበረም
ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊገለጽ ይችላል። "ኢያሱ ሙሴ ያዘዘውን ቃል ሁሉ አነበበ" ወይም "ኢያሱ የሙሴን ህግጋት ሁሉ አነበበ" (ድርብ አሉታዎች)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 9

1 ከዚያም በዮርዳኖስ ማዶ በተራራማውና በቆላማው በታላቁ ባሕር ዳርቻ በሊባኖስም ፊት ለፊት የነበሩ ነገሥታት ሁሉ፥ ኬጢያዊ አሞራዊም ከነዓናዊም
ፌርዛዊም ኤዊያዊም ኢያቡሳዊም **2** ኢያሱንና እስራኤልን ሊወጉ አንድ ሆነው ተሰበሰቡ። **3** የገባዖን ሰዎችም ኢያሱ በኢያሪኮና በጋይ ያደረገውን በሰሙ ጊዜ፥ **4**
እነርሱ ደግሞ የማታለል ዕቅድ አደረጉ። ራሳችውን እንደ መልእክተኛ አድርገው ቀረቡ። ያረጀና የተቀደደ ጆኒያ ወስደው በአህዮቻቸውም ላይ ጫኑ። ደግሞም
ያረጀ፥የተቀደደና የተሰፋ አሮጌ ወይን ጠጅ አቁማዳ ጫኑ። **5** ያረጀ የተሰፋም ጫማ በእግራቸው አደረጉ፤ አሮጌምና የተቀደድ ልብስም ለበሱ። ለስንቅም የያዙት
እንጀራ ሁሉ የደረቀና የሻገተ ነበረ። **6** ኢያሱም ወደ ሰፈረበት ወደ ጌልገላ ሄደው ለእርሱና ለእስራኤል ሕዝብ፦በጣም ሩቅ አገር ከሆነ ተጉዘን የመጠን ነን፥
ከእኛ ጋር ኪዳን አድርጉ አሉ። **7** የእስራኤልም ሰዎች ኤዊያውያንን፦ ምናልባት በመካከላችን የምትቀመጡ ትሆናላችሁ። እንዴትስ ከእናንተ ጋር ቃል ኪዳን
እናደርጋለን? አሉአቸው። **8** እነርሱም እንዲህ አሉት፦ እኛ የእናንተ አገልጋዮች ነን። ኢያሱም እንዲህ አላቸው፦ እናንተ እነማን ናችሁ? ከወዴትስ መጣችሁ? **9**
እነርሱም ለኢያሱ እንዲህ አሉት፦ እኛ አገልጋዮችህ ከእግዚአብሔር ከአምላክህ ስም የተነሣ እጅግ ከራቀ አገር እዚህ መጥተናል። ዝናውንም በግብፅም
ያደረገውን ሁሉ፥ **10** በዮርዳኖስ ማዶም በነበሩት በሁለቱ በአሞራውያን ነገሥታት በሐሴቦን በንጉሥ በሴዎን በአስታሮትም በነበረው በባሳን ንጉሥ በዐግ
ያደረገውን ሁሉ ሰምተናል። **11** ሽማግሌዎቻችንና በአገራችን የሚኖሩት ሁሉ፦ ለጉዞአችሁም ስንቅ በእጃችሁ ያዙ። ልትገናኙአቸውም ሂዱና እንዲህ በሉአቸው፦
እኛ አገልጋዮቻችሁ ነን፤ ከእኛም ጋር ቃል ኪዳን አድርጉ። **12** ወደ እናንተ ለመምጣት በተነሣንበት ቀን ይህን እንጀራ ትኩስን ለስንቅ ከቤታችን የወሰደነው ነው።
ነገር ግን ተመልከቱ፥ አሁንም ደረቅና የሻግብተ ነው። **13** እነዚህም የጠጅ አቁማዳዎች ስንሞላቸው አዲስ ነበሩ፤ እነሆም፥ ተቀድደዋል። ጉዞአችንም እጅግ ሩቅ
ስለ ነበረ ልብሶቻችንና ጫማዎቻችን አርጅተዋል። **14** እስራኤላውያንም ከስንቃቸው ወሰዱ፥ ነገር ግን ከእግዚአብሔርም ምክርን አልጠይቁም ነበር። **15**
ኢያሱም ከእነርሱ ጋር ስምምነት አደረገ፥ በሕይወት እንዲተዋቸውም ከእነርሱ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ። የማኅበሩም አለቆች ከእነርሱ ጋር ቃል ኪዳን አደረጉ። **16**
የእስራኤላውያንም ከገባዖን ሰዎች ጋር ቃል ኪዳኑን ካደረጉ ከሦስት ቀን በኋላ፥ ሰዎቹ እዚያው አጠገባቸው የሚኖሩ ጎረቤቶቻቸው መሆናቸውን ዐወቁ። **17**
ከዚያም እስራኤላውያን ተዘጋጅተው በሦስተኛው ቀን ወደ ከተሞቻቸው መጡ። የከተሞቻቸውም ስም ገባዖን፥ ክፈራ፥ ብኤሮትና ቂርያትይዓይሪም ናቸው። **18**
የሕዝቡም አለቆች በእስራኤል አምላክ በእግዚአብሔር ስም ቃል ኪዳን አድርገው ስለነበረ እስራኤላውያንም ጥቃት አልደረሱባቸውም። የእስራኤልም ሕዝብ
ሁሉ በመሪዎቹ ላይ አጉረመረሙ፥ **19** ነገር ግን መሪዎቹ ሁሉ ለማኅበሩ እንዲህ አሉ፦ በእስራኤል አምላክ በእግዚአብሔር ስም ቃል ኪዳን ስለገባንላቸው አሁን
ጉዳት ልናደርስባቸው አንችልም፥ **20** የምናደርግላቸው ነገር ቢኖር ይህ ነው፦ የገባንላቸውን የቃል ኪዳን ማሐላ ብናፈርስ ቁጣ እንዳይደርስብን በሕይወት
እንዲኖሩ ማድረግ ነው። የሕዝቡም አለቆች ለሕዝባቸው እንዲህ አሉ፦ በሕይወት ይኑሩ። **21** ስለዚህም የእስራኤል አለቆች ስለእነርሱ እንደ ተናገሩት ገባዖናውያን
ለእስራኤላውያን ሁሉ እንጨት ሰባሪና ውኃ ቀጂ ሆኑ። **22** ከዚያም ኢያሱ የገባዖንን ሰዎች ጠርቶ እንዲህ አላቸው፦ እናንተ እዚሁ በመካከላችን እየኖራችሁ፥
ከእናንተ ሩቅ ስፍራ ነው የመጠነው፥ ብላችሁ ያታለላችሁን ለምንድን ነው? **23** ስለዚህ በዚህ ምክንያት እናንተ የተረገማችሁ ናችሁ፥ አንዳንዶቻችሁም ለአምላኬ
ቤት ሁል ጊዜ እንጨት ሰባሪና ውኃ ቀጂ አገልጋዮች ትሆናላችሁ። **24** እነርሱም ለኢያሱ እንዲህ ብለው መለሱለት፥ እግዚአብሔር አምላክህ አገልጋዩን ሙሴን
እንዳዘዘው፥ ምድሪቱን በሙሉ ለእናንተ እንደሚሰጣችሁና ነዋሪዎቿንም ከፊታችሁ እንደሚያጠፋቸው በእርግጥ ለእኛ አገልጋዮችህ ተነግሮናል፥ ስለዚህ ከእናንተ
የተነሣ ለሕይወታችን በመሥጋት ይህን አድርገናል። **25** እነሆ አሁን በእጅህ ነን፥ መልካምና ትክክል መስሎ የታየህን ነገር ሁሉ አድርግብን። **26** ስለዚህ ኢያሱ
የገባዖንን ሰዎች ከእስራኤል ሰዎች እጅ አዳናቸ እስራኤላውያንም አልገደሏቸውም። **27** በዚያም ዕለት ኢያሱ የገባዖንን ሰዎች ለማኅበረ ሰቡና እግዚአብሔር
በመረጠው ስፍራ ለሚቆመው የእግዚአብሔር መሠዊያ እስከ ዛሬ ድረስ እንጨት ሰባሪችና ውኃ ቀጂዎች አደረጋቸው።

Joshua 9:1

የዮርዳኖስ
ለዮርዳኖስ ወንዝ አጭር ስያሜ ነው። (ስሞች እንዴት ይተጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)በአንድ እዝ ስር እዚህ ስፍራ "እዝ/አዛዥ" የሚለው የሚወክለው የሚያዛቸውን አዛዥ ነው። በእርሱ ስር መሆን የሚወክለው የእርሱን ትዕዛዞች መቀበልን ነው። "የአንድን መሪ ትዕዛዞች መቀበል" በሚለው ውሰጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 9:3

የማታለል እቅድ
ኢያሱን እና እስራኤላውያንን ለማታለል የተደረገ ማጭበርበር

ደረቅ እና የሻገተ
"ደረቅ እና በሻጋታ የተሞላ" ወይም "የሻገተ እና ያረጀ

Joshua 9:6

የእስራኤል ወንዶች
ይህ መላውን የእስራኤል መንግስት ያመለክታል። (ስነክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መወከል)

ሖራውያን
ይህ የገባዖናውያን ሌላ ስማቸው ነው። (ስሞች እንዴት ይተጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ምናልባት እናንተ በእኛ አቅራቢያ የምትኖሩ ልትሆኑ ትችላላችሁ። እንዴት ከእናንተ ጋር ቃል ኪዳን መግባት እንችላለን?
ኢያሱ የእስራኤል ህዝብ ከማናቸውም ነገር በላይ ለያህዌ ትእዛዝ ትኩረት ሰጥተው መከተል እንዳለባቸው ትኩረት ይሰጣል። "በእኛ አቅራቢያ የምትኖሩ ከሆናችሁ፣ ከእናንተ ጋር ቃል ኪዳን መግባት አንችልም" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 9:9

የዮርዳኖስ
ለዮርዳኖስ ወንዝ አጭር ስያሜ ነው። (ስሞች እንዴት ይተጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሴዎን
ይህ የተሸነፈው የአሞራውያን ንጉሥ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሔሴቦን
x

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Joshua 9:11

በእጃችሁ
የዚህ ሃረግ ትረጉም "ይዛችሁ ሂዱ" የሚል ነው። እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል የሚወክለው ከአቅርቦት ውስጥ ገባዖናውያን ያላቸውን ነው። (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር ወከል)አግኟቸውና እንዲህ በሏቸው "እነሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእስራኤልን ሰዎች ነው

Joshua 9:14

ኢያሱ አብረዋቸው ይኖሩ ዘንድ ከእነርሱ ጋር ሰላምን እና ቃልኪዳንን አደረገ። እንደዚሁም የህዝቡ መሪዎችም ለእነርሱ ቃለመሃላ አደረጉ።
እነዚህ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ነገር መደረጉን ይናገራሉ። የእስራኤል ህዝብ መሪ ኢያሱ፣ ገባዖናውያንን እንደማይገድል ቃል ገባ። የእስራኤል ህዝብ መሪዎችም በተመሳሳዩ ይህንኑ ቃል ኪዳን ገቡ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ህዝቡ
እዚህ ስፍራ ይህ ቃል የሚያመለክተው የእስራኤልን ህዝብ ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 9:16

ሶስተኛ ቀን
ይህ በቅደም ተከተል ቁጥር ሶስትን ያመለክታል (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ከፊራ
ይህ ከገባዖን ከተሞች አንዱ ነው። (ስሞች እንዴት ይተጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ብኤሮት
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ቂርያትይዓይሪም
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 9:18

ህዝቡ
እዚህ ስፍራ ይህ ቃል የሚያመለክተው የእስራኤልን ህዝብ ነው።

Joshua 9:20

"ገባዖናውያን እንጨት ቆራጮች እና ውሃ ቀጂዎች ሆኑ"
"ገባዖናውያን እንጨት ቆራጮች እና ውሃ ቀጂዎች ሆኑ"

Joshua 9:22

የአምላኬ ቤት
እዚህ ይህ ሃረግ የሚያመለክተው የማደሪያውን ድንኳን፣ የያህዌን ማደሪያ ስፍራ ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 9:24

መልካም እና ትክክል የሚመስለውን ሁሉ
"መልካም" እና "ትክክል" የሚሉት ቃላት በመሰረቱ አንድ አይነት ነገር ማለት ናቸው። "ተገቢ እና ትክክል የሚመስልህን ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 9:26

ለእነርሱ
እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ገባዖናውያንን ነው። እስከዚህ ቀን ድረስ "እስከ አሁን ድረስ እንኳን።" ይህ ማለት ህዝቡ እነዚህን ነገሮች ጸሐፊው ይኖር እስከ ነበረበት ጊዜ ድረስ ጭምር ማድረጋቸውን ቀጥለው ነበር ማለት ነው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 10

1 የኢየሩሳሌም ንጉሥ አዶንጼዴቅ ኢያሱ ጋይን ይዞ ፈጽሞ እንደ ደመሰሳት፤ እንደዚሁም በኢያሪኮና በንጉሥዋ ላይ ያደረገውን ሁሉ ሰማ። እንዲሁም የገባዖን
ሰዎች ከእስራኤል ጋር እንዴት የሰላም ውል አድርገው በመካከላቸው መኖራቸውን ሰማ። 2 የኢየሩሳሌም ሕዝብ ፈሩ፥ ምክንያቱም ገባዖን እንደ ነገሥታቱ ከተማ
ሁሉ ታላቅ ከተማ ነች። ገባዖንም ከጋይ ይልቅ ትልቅና ሰዎቿም ብርቱ ተዋጊዎች ነበሩ። 3 ስለዚህ የኢየሩሳሌም ንጉሥ አዶኒጼዴቅ፥ ወደ የኬብሮን ንገሥ ሆነም፥
ወደ የያርሙት ንጉሥ ጲርአም ፥ ወደ የለኪሶ ንጉሥ ያፈዓና ወደ የዔግሎን ንጉሥ ዳቤር ላከ። 4 ወደዚህ መጥታችሁ አግዙኝ። ገባዖን ከኢያሱና ከእስራኤላውያን
ጋር የሰላም ስምምነት ስላደረጉ ገባዖንን እንምታ። 5 ከዚያም አምስቱ የአሞራውያን ነገሥታት ማለት የኢየሩሳሌም ንጉሥ፥ የኬብሮን ንጉሥ፥ የያርሙት ንጉሥ፥
የለኪሶ ንጉሥና የዔግሎን ንጉሥ ያላቸውን ሠራዊታቸውን ሁሉ አስተባብረው፥ ገባዖንን ወጓት። 6 የገባዖንም ሰዎች ወደ ኢያሱና ወደ ጌልገላ ሠራዊት መልእክት
ላኩ። እንዲህም አሉ፦ ከአገልጋዮቻችሁ እጃችሁን አታውጡ ፍጠኑ። በፍጥነት መጥታችሁ አድኑን። በተራራማው አገር የሚኖሩ የአሞራውያን ነገሥታት ሁሉ
ኃይላቸውን አስተባብረው እኛን ለማጥቃት ተሰልፈውብናልና እርዱን። እኛን ባሮችህን አትተወን ርዳን ፈጥነህ በመድረስም አድነን ብለው ላኩበት። 7 ስለዚህ
ኢያሱ እርሱና ተዋጊዎች ሰዎች ሁሉ ከእርሱ ጋር ጨምሮ ከጌልገላ ወጣ። 8 እግዚአብሔርም ኢያሱን እንዲህ አለ፦ አትፍራቸው። በእጅህ አሳልፌ ሰጥቻለሁ፤
ማንም ሊቋቋመህ አይችልም። 9 ኢያሱም ከጌልገላ ሌሊቱን ሁሉ ሲገሠግሥ አድሮ ድንገት ደረሰባቸው። 10 እግዚአብሔም የጠላትን ሠራዊት በእስራኤል ፊት
ግራ አጋባቸው። እጅግ መታቸው። በገባዖንም ወደ ቤት ሖሮን በሚያስወጣው መንገድ እስከ ዓዜቅ መንገድ እስከ መቄዳም ድረስ ተከትሎአቸው አሳድዶ
መታቸው። 11 ከቤት ሖሮን ወደ ዓዜቃ ቁልቁል በሚወስደው መንገድ ላይ ከእስራኤላውያን ፊት በሚሸሹበት ጊዜ እግዚአብሔር ከሰማይ ትልልቅ ድንጋዮች
ወረወረባቸው ሞቱም። በእስራኤል ሰዎች ሰይፍ ከሞቱት ይልቅ በወረደው የበረዶ ድንጋዮች የሞቱት የበለጡ ነበሩ። 12 ከዚያም እግዚአብሔር ለእስራኤል
በአሞራውያን ላይ ድል በሰጠበት ዕለት ኢያሱ እግዚአብሔርን ተናገረ። ኢያሱም በእስራኤል ፊት እግዚአብሔርን እንዲህ አለው፦ "ፀሐይ፥ በኤሎን ሸለቆ
በገባዖን ላይ ይቁም።" 13 ሕዝቡ ጠላቶቹን እስኪ በቀል ድረስ፤ ፀሐይ ባለችበት ቆመች፥ ጨረቃም አልተንቀሳቀሰችም። ይህም በያሻር መጽሐፍ ላይ የተጻፈ
አይደለምን? ፀሐይ በሰማዩ መካከል ቆመች፥ ለሙሉ ቀን ያህል አልተንቀሳቀሰችም ነበር። 14 እግዚአብሔር የሰውን ቃል እንደዚያ የሰማበት ዕለት ከዚያ በፊት
ወይም ከዚያ በኋላ አልነበረም። እግዚእአብሔር ለእስራኤል ይዋጋ ነበር። 15 ኢያሱና መላው እስራኤል ወደ ጌልገላ ሰፈር ተመለሱ። 16 በዚህ ጊዜ አምስቱ
የአሞራውያን ገሥታት ሸሽተው በመቄዳ ዋሻ ራሳቸውን ደብቀው ነበር። 17 ኢያሱም አምስቱ ነገሥታት በመቄዳ ዋሻ ውስጥ ተደብቀው መገኘታቸውን ሰማ፤ 18
ኢያሱም እንዲህ አለ፦ ትልልቅ ድንጋዮች ወደ ዋሻው አፍ አንከባልሉ፤ወታደሮችንም እንዲጠብቁአቸው በዚያ አቁሙ። ቸልም አትበሉ። 19 ጠላቶቻችሁን
አሳዱአቸው፤ ከበስተ ኋላ ሆናችሁም ጥቃት አድርሱባቸው። እግዚአብሔር አምላካችሁ በእጃችሁ አሳልፎ ስለሰጣችሁ ወደ ከተሞቻቸው እንዳይገቡ
አድርጉአቸው። 20 ኢያሱና እስራኤል ልጆች ፈጽሞ እስኪያጠፉ ድረስ ከታላቅ ጭፍጨፋ ጋር ጨረሱ። የተረፉት ጥቂቶቹ ብቻ ወደ ተመሸጉት ከተሞቻቸው
ደረሱ። 21 ከዚያም ሠራዊቱ በሙሉ በደኅና ተመልሶ ኢያሱ ወደ ሰፈረበት ወደ መቄዳ ተመለሰ። በእስራኤላውያንም ላይ አንድት ቃል ለመናገር ማንም ሰው
የደፈረ አልነበረም። 22 ኢያሱም እንዲህ አላቸው፦ የዋሻውንም አፍ ክፈቱና ከዋሻው እነዚህን አምስቱን ነገሥታት አምጡልኝ። 23 እነርሱም እንዳለው አደረጉ።
እነዚህንም አምስቱን ነገሥታት፦ የኢየሩሳሌምን ንጉሥ፥ የኬብሮንን ንጉሥ፥ የያርሙትን ንጉሥ የለኪሶን ንጉሥና የዔግሎንን ንጉሥ አውጥተው አመጡለት። 24
እነዚህን ነገሥታት ወደ ኢያሱ ባማጡበት ጊዜ፥ እርሱም እያንዳንዱን የእስራኤል ሰዎች ጠራቸው፤ እንዲሁም ከእርሱ ጋር ወደ ጦርነት ሄደው የነበሩትን የጦር
አዛዦችን እንዲህ አላቸው፦ እግሮቻችሁን በእነዚህ ነገሥታት አንገት ላይ አድርጉ። እነርሱም ወደ ፊት ቀርበው እግሮቻቸውን በነገሥታቱ አንገት ላይ አሳረፉ። 25
ኢያሱም እንዲህ አላቸው፦ አትፍሩ፥ አትደንግጡም። በርቱ፥ ጽኑም። እግዚአብሔር አምላካችሁ በምትዋጉበት ጊዜ በጠላቶቻችሁ ሁሉ ላይ እንዲህ ያደርጋል። 26
ከዚያም ኢያሱ ነገሥታቱን መትቶ ገደላቸው። በአምስትም ዛፎች ላይ ሰቀላቸው። አስክሬናቸውም እስኪመሽ ድረስ ተሰቅለው ነበር። 27 የፀሐይ መጥለቂያ
በሆነ ጊዜ ኢያሱ ትእዛዝ ሰጠ፦ ከዚያም የነገሥታቱን አስክሬኖች ከዛፎቹ ላይ እንዲያወርዱ ቀድሞ ራሳቸውን ደብቀው ወደነበሩበት ዋሻ ውስጥ
እንዲጥሉአቸው አዘዛቸው። በዋሻውም አፍ ላይ ትልልቅ ድንጋዮች አኖሩ። እነዚያ ድንጋዮች እስከ ዛሬ ድረስ በዚያ ይገኛሉ። 28 በዚህ መንገድ በዚያች ዕለት
ኢያሱ መቄዳን ያዘ፤ ከንጉሥዋም ጭምር ሁሉንም በሰይፍ ገደለ። በሕይወት ያሉትንም ፍጥረት ሁሉ ምንም ሳያስቀር ፈጽሞ አጠፋቸው። በኢያሪኮ ንጉሥ ላይ
ያደረገውንም ሁሉ፥ በመቄዳ ንጉሥ ላይ አደረገ። 29 ኢያሱና እስራኤላውያን ከመቄዳ ወደ ልብና አለፉ። ወጓትም። 30 እንደገናም ከልብና ጋር ጦርነት ገጠሙ።
እግዚአብሔርም ከተማይቱንና ንጉሥዋን በእስራኤል እጅ አሳልፎ ሰጣቸው። ኢያሱም በተከማዪቱንና በውስጧ ያለውን ሕይወት ያለውን ፍጥረት ሁሉ በሰይፍ
ስለት አጠፋ። ሕይወት ያለውን ምንም አላስቀረም። በኢያሪኮ ንጉሥ ላይ ያደረገውንም በልብና ንጉሥ ላይ አደረገ። 31 ከዚያም ኢያሱና እስራኤላውያን ከእርሱ
ጋር ከልብና ወደ ለኪሶ አለፉ። በእርስዋም ሰፈሩ፤ ጦርነትም አደረጉ። 32 እግዚአብሔርም ለኪሶን በእስራኤል እጅ አሳልፎ ሰጠው። ኢያሱም በሁለተኛው ቀን
ያዛት። በልብና እንዳደርገው በሕይወት ያለውን ፍጥረት ሁሉ በሰይፍ ስለት አጠፋ። 33 ከዚያ የጌዝር ንጉሥ ሆራም ለኪሶን ለመርዳት መጣ። ኢያሱ ግን አንድ
እንኳ ሳያስተርፍ እርሱንና ሕዝቡን መታቸው። 34 ከዚያም ኢያሱና እስራኤላውያን በሙሉ ከለኪሶን ወደ ዔግሎን አለፉ። እዚያም ሰፈሩ፤ ወጓትም፤ 35 በዚያኑ
ዕለት ከተማዋንም ያዟት። ኢያሱም በለኪሶ እንዳደረገ ከተማይቱንና በውስጧ የሚገኙትን ፈጽመው በሰይፍ ስለት አጠፏት። 36 ከዚያም ኢያሱና እስራኤላውያን
ከዔግሎን ወደ ኬብሮን አለፉ። በከተማይቱም ጦርነት አደረጉ። 37 ከተማዪቱንም ከንጉሥዋ ከመንደሮቿና በውስጧ ካሉት ጭምር ሁሉ አንድም ሰው ሳያስቀሩ
በሰይፍ ስለት አጠፉአቸው። በዔግሎን እንዳደርጉት ሁሉ ከተማዪቱንና በውስጧ ያለውን ሁሉ ፈጽመው ደመሰሱ። ማንኛውንም ሕይወት ያለውን ፍጥረት ሁሉ
አጠፋ። 38 ከዚያ ኢያሱና እስራኤል ሠራዊት ከእርሱ ጋር ወደ ኋላ ተመልሰው በደቤርን አለፉ፤ ጦርነቱንም አደረጉ። 39 ከተማዪቱን ንጉሥዋንና በአካባቢ ያሉ
መንደሮቿን ሁሉ ያዙ። ከተማይቱንና በውስጧ ያለውንም ሁሉ አንድም ሰው ሳያስቀሩ፥ በሰይፍ ስለት አጠፉአቸው። ኢያሱ በኬብሮን ያደረጉትን ሁሉ በዳቤርና
በንጉሥዋ ላይ አደረጉት። 40 ኢያሱ ተራራማውን አገር ኔጌቭን ቆላና የተራራውን ሸንተረሮች ጨምሮ ምድሪቱን በሙሉ ከነገሥታቷ ጋር አሸነፈ። ከነገሥታቱንም
ያስቀረው ማንም የለም። የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረትሕይወት ያላቸውን ሁሉ ፈጽሞ አጠፋቸው። 41 ኢያሱም ከቃዴስ በርኔ እስከ ጋዛ፥
የጎሶምን ምድር ሁሉ እስከ ገባዖን ድረስ በሙሉ አጠፋ። 42 ኢያሱ እነዚህን ሁሉ ነገሥታትና ምድራቸውን የያዘው በአንድ ጊዜ፥ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር
ለእስራኤላውያን ስለተዋጋ ነው። 43 ኢያሱ ከመላው እስራኤላውያን ጋር ጌልገላ ወዳለው ሰፈር ተመለሰ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Joshua 10:3

የርሙት... ለኪሶ.. ዔግሎ
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው (ስሞች እንዴት ይተጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሆሃም... ጲርአም... ያፊዓ..ዳቤር
እነዚህ የንጉሦች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እኔ ና
"እኔ ወዳለሁበት ተጓዝ።" ኢየሩሳሌም በከነአን ለሚገኙ ከተሞች ሁሉ ከፍ ባለ ስፍራ ላይ የምትገኝ ከተማ ነበረች።

Joshua 10:5

አምስት ንጉሦች
"5 ንጉሦች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

የርሙት... ለኪሶ.. ዔግሎ
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው (ስሞች እንዴት ይተጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አሰፋፈራቸውን ከገባዖን በተቃራኒ አደረጉ
ይህ ማለት ሰፈራቸውን በከተማቸው ዙሪያ አደረጉ። ይህ በከተማይቱ የሚኖሩትን ማዳከሚያ መንገድ ነበር። ድርጊቱ ሰዎች ከከተማይቱ እንዳያመልጡ ያግዳል፣ እንደዚሁም ሌሎች ምግብ እና ውሃ ወደ ከተማይቱ እንዳያመጡላቸው ያግዳል።

Joshua 10:6

እነርሱ እንዲህ አሉ
"እነርሱ" የሚለው ቃል እዚህ ስፍራ የሚያመለክተው ገባዖናውያንን ነው።

እጆችህን ከባሪያዎችህ አታርቅ/አታንሳ
ይህ ትሁት ልመና በሁለት አሉታዎች ተገልጾዋል፣ ይህም አዎንታዊ ድርጊት/እርዳታ ማስፈለጉን በአጽንኦት ለመግለጽ ነው። "እባክህ መጥተህ በብርቱ እጆችህ ታደገን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምፀት/ላይዶክስ የሚለውን ይመልከቱ)

እጆችህ
እዚህ ስፍራ "እጆች" የሚለው ቃል የእስራኤልን ህዝብ ጥንካሬ ያመለክታል። "የአንተ ጥንካሬ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 10:8

እነርሱን በእጆችህ አሳልፌ ሰጥቼሃለሁ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው የሚወክለው የእስራኤልን ህዝብ ጥንካሬ እና ጠላቶቻቸውን የማሸነፍ አቅማቸውን ነው። "እነርሱ" የሚለው ቃል አጥቂ የሆነውን ሰራዊት ያመለክታል። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ለእነርሱ ሰጥቻቸዋለሁ
እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው ቃል ጥቃት የሚጥለውን ሰራዊት ያመለክታል።

Joshua 10:9

ኢያሱ መጣ
እዚህ ስፍራ መላው የእስራኤል ሰራዊት የተጠቀሱት በመሪያቸው በኢያሱ ነው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)ያህዌ በእስራኤል ፊት ጠላቶቻቸውን ግራ አጋባቸው እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚለው መላውን የእስራኤል ሰራዊት ያመለክታል። ቤትሖሮን... ዓዜቅ... መቄዳም እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው (ስሞች እንዴት ይተጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 10:11

ቤትሖሮን... ዓዜቅ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው (ስሞች እንዴት ይተጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ከላይ ከሰማይ ትላልቅ ድንጋይ አወረደባቸው
"ከሰማይ የበረዶ ድንጋይ አወረደባቸው"

Joshua 10:12

ፀሐይ በገባዖን ትቁም፣ ጨረቃም በኤሎን ሸለቆ ትቁም
ኢያሱ በዚህ ቀን ጊዜ ያህዌ ጊዜ መንቀሳቀሱን እንዲያቆም ጸለየ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን መልከቱ) ፀሐይ... ጨረቃ ኢያሱ ፀሐይን እና ጨረቃን እንደ ሰው አዘዛቸው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ) የኤሎን ሸለቆ ይህ የቦታ ስም ነው (ስሞች እንዴት ይተጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 10:13

ሃገሪቱ
ይህ የእስራኤልን ህዝብ ያመለክታል (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ በያሻር መጽሐፍ የተጻፈ አይደለምን?
ጸሐፊው ይህንን ጥያቄ ትዕይንቱ በሚገባ መመዝገቡን ለአንባቢው ለማስታወስ እንደ መረጃ ዳራ ተጠቅሞበታል። "ይህ በያሻር መጽሐፍ ተጽፏል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና የመረጃ ዳራ የሚሉትን ይመልከቱ)

Joshua 10:15

መቄዳ
ይህ የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ለኢያሱ ተነግሮት ነበር
መልዕክተኞች መጥተው ለኢያሱ ነገሩት። "አንድ ሰው ለኢያሱ ነገረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ተመልከቱ)

Joshua 10:18

በእናንተ እጅ
"በእጃችሁ" የሚለው ሀረግ ትርጉሙ "ማድረግ የምትችሉት" ማለት ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 10:20

መቄዳ
በኢያሱ 10:10 ውስጥ በተረጎሙት መሰረት ይተርጉሙ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በመቃወም አንድም ቃል ለመናገር የቻለ የለም
"ማንም አንዳች ነገር በመቃወም መናገር አልደፈረም" ወይም "ማንም ለማማረር ወይም ለመቃወም አልደፈረም"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Joshua 10:22

የዋሻውን አፍ ክፈቱ
እዚህ ስፍራ "አፍ" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ "መግቢያ" ማለት ነው። "የዋሻውን መግቢያ ክፈቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የርሙት... ለኪሶ.. ዔግሎ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው (ስሞች እንዴት ይተጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 10:24

እያንዳንዱ የእስራኤል ሰው
በዚህ ስፍራ የእስራኤል ሰዎች የሚለው የሚወክለው ወታደር የሆኑትን ብቻ ነው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ ማለውን ነገር መወከል የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 10:26

እስከ ዛሬ ድረስ
"ጸሐፊው ይህንን ታሪክ እስከጻፈ ድረስ"

Joshua 10:28

መቄዳ
ይህ የከተማ ስወም ነው። ይህንን በኢያሱ 10:10 ውስጥ እንዴት እንደ ተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)በውስጧ የሚገኙትን ሙሉ በሙሉ ደመሰሰ። አንድም ነገር በህይወት አላስቀረም። ኢያሱ አንድም ሰው ወይም እንስሳ በህይወት አለማስቀረቱን ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ፣ ሁለተኛው ዐረፍተ ነገር የመጀመሪያውን አረፍተ ነገር አጠቃሎ ያቀርባል።

Joshua 10:29

ልብና
ይህ የከተማ ስወም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በእስራኤል እጀ አሳልፎ ሰጣት
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው "መቆጣጠር" ማለት ነው። "ለእስራኤል አሳልፎ ሰጣት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 10:31

ልብና...ለኪሶ
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በእስራኤል እጀ
እዚህ ስፍራ የእነርሱ "እጅ" የሚለው የሚወክለው የእነርሱን የበላይነት/ መቆጣጠር ነው። "ያህዌ ለኪሶን ለእስራኤል መንግሥት አሳልፎ ሰጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 10:33

ሆራም
ይህ ታላቅ የሆነ ንጉሥ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ጌዝር... ለኪሶ
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 10:34

ለኪሶ...ዔግሎን
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰይፍ ስለት ምቷት... በውስጧ የሚኖሩትንም ሁሉ ሙሉ ለሙሉ አጥፉ
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። በአንድነት የዔግሎን ከተማ ሙሉ ለሙሉ መጥፋትን ይገልጻሉ። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 10:36

ዔግሎን
ይህ የከተማ ስወም ነው። ይህንን በኢያሱ 10:3 ውስጥ እንዴት እንደ ተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ከተማቱን ይዘው በሰይፍ ስለት ምቷት
ሰይፉ የሚወክለው የእስራኤልን ሰራዊት ነው፣ መምታት የሚለው የሚገልጸው የማረድ እና የመደምሰስ ሃሳብን ነው። "ያዙ፣ገደሉ፣ ደመሰሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 10:38

ዳቤር... ልብና
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱን በሰይፍ ስለት መቷቸው
ሰይፉ የሚወክለው የእስራኤልን ሰራዊት ነው፣ መምታት የሚለው የሚገልጸው የማረድ እና የመደምሰስ ሃሳብን ነው። "ገደሉ ደግሞም ደመሰሷቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 10:40

ከንጉሦቻቸው ውስጥ አንድ እንኳን በህይወት አላስቀረም። በህይወት ያለውን ነገር ሁሉ ሙሉ ለሙሉ ደመሰሰ
እነዚህ ሁለት ሃረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ሃረጎቹ የእስራኤል ህዝብ በያህዌ ትዕዛዝ የፈጸመውን ሙሉ ለሙሉ የመደምሰስ ተግባር ያጎላሉ። (ትይዩ ንጽጽር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 10:42

ኢያሱ እነዚህን ነገሥታት ሁሉ ማረከ እና አገራቸውንም ያዘ።
ይህ በኢያሱ 10:28 ጀምሮ የተዘረዘሩትን ነገሥታት እና ምድራቸውን ያመለክታል

ኢያሱ ማረከ
እዚህ ስፍራ ኢያሱ የሚወክለው ጠቅላላውን ሰራዊቱን ነው። "ኢያሱ እና ወታደሮቹ ማረኩ/ያዙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ)

በአንድ ጊዜ
ይህ በአንድ ቀን ማለት አይደለም። በርካታ ቀናት ወይም ሳምንታት ሊወስድ በሚችል በአንድ ወታደራዊ ዘመቻ ወቅት ማለት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 11

1 የአሦርም ንጉሥ ኢያቢስ ይህን በሰማ ጊዜ፥ ወደ ዮባብ ንጉሥ፥ ወደ ማዶን ንጉሥ፥ ወደ ሺምሮን ንጉሥና ወደ አዚፍ ንጉሥ መልእክት ላከ። 2 ደግሞም በሰሜናዊ በተራራማው አገር፥ በየርዳኖስ ወንዝ ሸለቆ ከኪኔሬት በስተ ደቡብ ፥ በምዕራቡ ቆላማ አገሮችና ከኮር ኮረብታማ በስተ ምዕራብ ወዳሉት ነገሥታት ላከ። 3 በምሥራቅና በምዕራብ ወደሚገኙት ወደ ከነዓናውያንም፥ ወደ አሞራውያን፥ ወደ ኬጢያውያን፥ ወደ ፌርዛውያንና በኮረብታማው አገር ወደሚኖሩት ወደ ኢያቡሳውያን እንዲሁም በምጽጳ ምድር በአርሞንዔም ተራራ ወዳሉት ወደ ኤዊያውያን ነገሥታት መልእክት ላከ። 4 እንዚህም ሠራዊቶቻቸው ሁሉ በቁጥርም በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ እጅግ ከብዙ ወታደሮች ጋር መጡ። ታላቅም ቁጥር ፈረሶችና ሠረገሎች ነበሩአቸው። 5 እነዚህ ሁሉ ነገሥታት እስራኤልን ለመውጋት ኃይላቸውን አስተባብረው በማሮን ውሃ አጠገብ በተቀጠረው ጊዜ ሰፈሩ። 6 እግዚአብሔርም ኢያሱን እንዲህ አለው፦ እነዚህን ሁሉ ነገ በዚች ሰዓት እንደ ሙት አድርጌ በእስራኤል እጅ አሳልፌ ስለምሰጣቸው አትፍራቸው። የፈረሶቻቸውንም ቋንጃ ትቆርጣለህ፥ ሠረገሎቻቸውንም ታቃጥላለህ። 7 ኢያሱና ሠራዊቱ ሁሉ መጡ። በድንገትም ወደ ማሮን ውሃ መጥተው ጠላቶቻቸውን አጠቁኣቸው። 8 እግዚአብሔርም ጠላትን በእስራኤል እጅ አሳልፎ ሰጣቸው። በሰይፍም ስለት አጠቁአቸው፥ ወደ ሲዶና፥ወደ ማስሮን፥ ምጽጳ ሸለቆ ድረስ በስተምሥራቅ አሳደዷቸው። ከእነርሱም በሕይወት አንድንም ሰው ሳያስቀሩ በሰይፍ ስለት አጠፉአቸው። 9 ኢያሱም እግዚአብሔር እንዳዘዘው በእነርሱ ላይ አደረጉ። የፈረሶቻቸውንም ቋንጃ ቆረጠ፥ ሠረገሎቻቸውንም አቃጠለ። 10 በዚያን ጊዜም ኢያሱ ወደ ኋላ ተመልሶ አጾርን ያዘ። ንጉሥዋንም በሰይፍ ገደለው። (አጾርም የእነዚህ መንግሥታት ሁሉ የበላይነት ነበራች።) 11 በውስጧ ያሉትን ሁሉ በሰይፍ ስለት ገደሉ፥ በሕይወት ካለው ፍጡር አንድ እንኳ ሳያስቀሩ ሁሉንም ደመሰሱ። አሦርንም በእሳት አቃጠሏት። 12 ኢያሱም የእነዚህን ነገሥታት ከተሞች በሙሉ ያዘ። ነገሥታታቸውን ሁሉ ማረካቸው፥ በሰይፍም ስለት አጠፋቸው። የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴ እንዳዘዘው በሰይፍ ስለት አጠፋቸው። 13 እስራኤልም በተራራው ላይ ከተሠሩ ከተሞች ከአጾር በስተቀር ሌሎችን አላቃጠሉም። ኢያሱ ይህችን ለብቻዋ አቃጠላት። 14 እስራኤላውያንም ምርኮውን በሙሉ ከእነዚህም ከተሞች የተገኙትን እንስሳት ለራሳቸው ወሰዱ። ሕዝቡን በሙሉ ሁሉም ሙት እስኪሆኑ ድረስ በሰይፍ ስለት ገደሉአቸው። በሕይወት ካለው ፍጡር አንድም አልቀሩም። 15 እግዚአብሔር አገልጋዩን ሙሴን እንዳዘዘው ሁሉ ሙሴም ኢያሱን አዘዘው። ኢያሱም እግዚአብሔር ሙሴን ካዘዘው ሁሉ እርሱ ያልፈጸመው አንዳች ነገር አልነበረም። 16 ኢያሱም ማለት ተራራማውን አገር፥ ኔጌቭን ሁሉ፥ የጎሶምን ምድር በሙሉ፥ የኮረብታ ግርጌ። የዮርዳኖስ ወንዝ ሸለቆ፥ የእስራኤልም ኮረብታማ አገርና ቆላማውን የምዕራቡን ቆላዎችን ሁሉ፥ያንን ምድር በሙሉ ወሰደ። 17 እንዲሁም እስከ ሴይር በሚደርሰው ከሐላቅ ተራራ አንሥቶ ከአርሞንዔም ተራራ በታች በሊባኖስ ሸለቆ ውስጥ እስካለው እስከ በዓል ጋድ ድረስ ያለውን ምድር በሙሉ ያዘ። ነገሥታታቸውንም ሁሉ ያዘ፥ መትቶም ገደላቸው። 18 ኢያሱ ከእነዚህ ነገሥታት ጋር ረጅም ጊዜ ጦርነት አደረገ። 19 በገባዖን ከሚኖሩ ከኤዊያውያን በስተቀር ከእስራኤላውያን ጋር የሰላም ስምምነት ያደረገ አንድም ከተማ አልነበረም። እስራኤል ሁሉንም ከተሞች የያዙት በጦርነት ነበር። 20 እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው ያለ አንዳች ርኅራኄ ፈጽሞ ይደመስሳቸው ዘንድ እስራኤልን እንዲወጉ ልባቸውን ያደነደናቸው ራሱ እግዚአብሔር ነበር። 21 በዚያንም ጊዜ ኢያሱ መጥቶ ዔናቅን አጠፋ። ይህንንም በተራራማው አገር በኬብሮን፥ በዳቤርና በአናብ እንዲሁም በመላው ይሁዳና የእስራኤል ተራራማ አገሮች ያሉትን ላይ አደረገ። እርሱም እነርሱንና ከተሞቻቸውን በሙሉ አጠፋቸው። 22 ከእነዚህም ጥቂቶቹ ብቻ በጋዛ፥ በጌትና በአሽዶድ ከቀሩት በስተቀር በእስራኤል አገር ከዓናቅ የቀሩት አልነበሩም። 23 ስለዚህ ኢያሱ እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው ምድሪቱን በሙሉ ያዘ። ኢያሱም እንደ ነገዳቸው አከፋፈል በመመደብም ርስት አድርጎ ለእስራኤላውያን ሰጣቸው። ከዚያም ምድሪቱ ከጦርነት ዐረፈች።

Joshua 11:1

ያቢን...ዮባብ
እነዚህ የንጉሦች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሃዞር.. ማዶን... ሺምሮን... አዚፍ... ኪኔሬት.. ናፎት ዶር ... ሄርሞን ተራራ
እነዚህ የስፍራ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 11:4

አጠቃላይ መረጃ፡
ሁሉም የከነዓን ንጉሦች በኢያሱና በእስራኤል ላይ ዘመቱ

ብዙ ቁጥር ያለው ሰራዊት ፣ በቁጥር እንደ ባህር ዳርቻ አሸዋ የበዛ
ማንም የባህር ዳርቻ አሸዋን መቁጠር አይችልም። ይህ ግነት የሚያገላው እነዚህ ነገሥታት የሰበሰቧቸውን ወታደሮች ብዛት ነው። "በወንዝ ዳርቻ እንደሚገኝ አሸዋ እንዲህ ያለ ታላቅ ቁጥር ያለው ወታደር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና ማጠቃለያ የሚሉትን ይመልከቱ)

ማሮም
ይህ የስፍራ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 11:6

እኔ ለእስራኤል ሁሉንም እንደ ሞተ ሰው አሳልፌ ሰጥቻቸዋለሁ
እስራኤ ጠላቶቹን ለመማረክ እና ሁሉንም ለመደምሰስ ያስቻለው ያህዌ የእስራኤል ጠላት የሆኑትን ወታደሮች በሙሉ ከገደለ በኋላ አሳልፎ እንደሰጣቸው ተደርጎ ተገልጽዋል። " እስራኤል ጠላቶቹን ሁሉ እንዲያጠፋ አሳልፌ እሰጠዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የፈረሶቻቸውን ቋንጃ ይቆርጣሉ
"እግሮቻቸውን በመቁረጥ ፈረሶቻቸውን ስንኩል ማድረግ" ይህ ከፈረሶቹ እግር በስተኋላ ያልን ጅማት በመቁረጥ ፈረሶቹ መራመድ እንዳይችሉ የማድረግ ልምምድ ነው።

ማሮም
ይህ የስፍራ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 11:8

ያህዌ ለእስራኤላዊያን ጠላቶቻቸውን በእጃቸው አሳልፎ ሰጣቸው
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል የሚወክለው ሃይልን ነው። ያህዌ የእስራኤል ሰራዊት ጠላቶቻቸውን እንዲማርኩ ማድረጉ የተገለጸው ልክ ጠላቶቻቸውን በእጃቸው ላይ እንዳስቀመጠ ተደርጎ ነው። "ያህዌ እስራኤል ጠላቶቹን እንዲማርክ አሳልፎ ሰጠው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምቷቸው.. ምቷቸው
"አጥቋቸው... አጥቋቸው"

ማስሪፎት/ማስሮን ሜም
ይህ የስፍራ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ቋንጃ መቁረጥ
ይህ ፈረሶቹ መሮጥ እንዳይችሉ ያኋላ እግራቸው ጅማት የተቆረጠበት ልምምድ ነው። ይህንን ቃል በኢያሱ 11:6 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

Joshua 11:10

ንጉሥዋን በሰይፍ መታ
"ኢያሱ የሐጾርን ንጉሥ በሰይፍ ገደለ"

ሐጾር የእነዚህ መንግሥታት ሁሉ ራስ ነበር
የሐጾር ከተማ ታላቅነት የተገለጸው ሐጾር የእነዚህ መንግሥታት ሁሉ ራስ ነበር በሚል ነው። "ሐጾር ከእነዚህ መንግሥታት ሁሉ ታላቅ ነበረች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያው አነጋገር እና ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚሉትን ይመልከቱ)

በዚያ የሚገኙትን ህይወት ያላቸውን ነገሮች ሁሉ በሰይፍ መቱ... ስለዚህም በህይወት የተረፈ አንዳችም ህይወት ያለው ነገር አልነበረም
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ ሙሉ ለሙሉ ጥፋት መፈጸሙን ያጎላሉ።(ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲደመሰሱ እርሱ ለይቶ አስቀመጣቸው
"እርሱ" የሚለው ቃል ኢያሱን ያመለክታል፤ ደግሞም እርሱን ራሱን እና ሰራቱን ይወክላል። በከተማይቱ ውስጥ የሚገኙ ህይወት ያላቸውን ነገሮች ሁሉ ሙሉ ለሙሉ መደምሰስ የሚለው የተነገረው እነዚያ ህይወት ያላቸው ነገሮች ሀሉ ለመጥፋት የተሰጡ እንደሆኑ ተደርጎ ነው። "ሰራዊቱ ሙሉ ለሙሉ ደመሰሳቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ዘይቤያው አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Joshua 11:12

እነርሱን በሰይፍ ስለት መታ
"እነርሱን ገደለ"

በጉብታዎች ላይ የተመሰረቱ ከተሞች
"በትንንሽ ኮረብቶች ላይ የተመሰረቱ ከተሞች"

Joshua 11:14

ለእነርሱ ለራሳቸው
ይህ ሃረግ የሚያመለክተው የእስራኤልን ሰራዊት ነው። (ደጋጋሚ ተውላጠ ስም/የስም ምትክ)

ሁሉም እስኪሞቱ በሰይፍ ስለት አንድም ሰው ሳይቀር ሁሉንም ገደሉ። እስትንፋስ ያለውን አንድም ፍጥረት በህይወት አልተዉም።
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ ሙሉ ለሙሉ ጥፋት መፈጸሙን ያጎላሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ ለሙሴ እንዲያደርግ ካዘዘው ውስጥ ሁሉ ሳያደርግ የተወው አንዳች ነገር የለም
ይህ አሉታዊ ሃረግ ኢያሱ ያህዌ ያዘዘውን ሁሉ እንዳደረገ አጉልቶ ይገልጻል። "ኢያሱ ያህዌ ያዘዘውን ነገር ሁሉ አደረገ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምፀት/ላይዶክስ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 11:16

ሐላቅ ተራራ... በኣልጋድ
እነዚህ የስፍራ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 11:18

ልባቸውን የጠነከረው ያህዌ ራሱ ነበር
ያህዌ የከተሞቹ ናሪዎች ልባቸው እንዲደነድን ያደረገበት ምክንያት የተገለጸው ልክ ያህዌ ልባቸው ጠንካራ እንዲሆን እንዳደረገ ሆኖ ነው። "በልበ ደንዳናነት ምላሽ እንዲሰጡ ያደረገው ያህዌ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 11:21

ዔናቃውያን
እነዚህ የዔናቅ ትውልዶች ነበሩ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ዳቤር...አናብ
እነዚህ የስፍራ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 11:23

ኢያሱ ለእስራኤል ርስት አድርጎ ሰጣት
ኢያሱ ምድሪቱን ለእስራኤላውያን የሰጠበት መንገድ የተገለጸው ለአስራኤላውያን ርስትን በቆሚነት እንደሰጣቸው ተደርጎ ነው። "ኢያሱ ለእስራኤላውያን ምድሪቱን ቋሚ ርስት አድርጎ ሰጣቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አሁን
ይህ ቃል እዚህ ስፍራ ያገለገለው በዋናው ታሪክ ፍሰት ቆም ለማለት ነው። እዚህ ላይ ጸሐፊው የመረጃ ዳራ መስጠት ይጀምራል። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሦቹ እነዚህ ናቸው
ይህ እስከ ቁጥር 24 የሚገኙትን የንጉሦች ስም ዝርዝር ያመለክታል።

ዓረባ...አርኖን
እነዚህ የስፍራ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሴዎን... ሔሴቦን
እነዚህን ቃላት በኢያሱ 9:10 እንዴት እንተረጎሟቸው ይመልከቱ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 12

1 የእስራኤልም ሰዎች ድል ያደረጉአቸው ነገሥታት እነዚህ ነበሩ። እስራኤላውያንም ከአዮርዳኖንም ሸለቆ በስተ ምሥራቅ ጀምሮ እስከ ፀሐይ መውጫ ድረስ፥ ከአርሞን ወንዝ ሸለቆ ወደ አርሞንዔም ተራራ ድረስ በምሥራቅ ያለውን ዓረባ ሁሉ ወሰዱ። የአሞራውያን ንጉሥ ሴዎን በሐሴቦን ተቀመጠ። 2 በአርኖንም ሸለቆ አጠገብ ካለችው ከአሮዔር ከሸለቆውም መካከል ጀምሮ የገለዓድን እኩሌታ እስከ ያቦቅ ወንዝ፥ እስከ አሞን ልጆች ዳርቻ ድረስ ገዛ። 3 ሴዎንም በምሥራቅም በኩል ያለውን ዓርባ እስከ ኪኔሬት ባሕር ድረስ፥በቤት የሺሞት መንገድ አጠገብ እስካለው እስከ ዓረባ ባሕር (እስከ ጨው ባሕር) ወደ ምሥራቅ ድረስ በደቡብም በኩል ከፍስጋ ተራራ አፋፍ በታች ያለውን ምድር ገዛ። 4 የባሳን ንጉሥ ዐግ ከራፋይምም ወገን የቀረ፥ በአስታሮትና በኤድራይ ተቀመጠ። 5 እርሱም የአርሞንዔምንም ተራራ፥ ስልካንና ባሳንንም ሁሉ እስከ ጌሹራውያንና እስከ ማዕካታውያን ዳርቻ፥ የገለዓድንም እኩሌታ፥ እስከ ንጉሥ ሀሴቦን ድረስ ገዛው ። 6 የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴና የእስራኤል ልጆች አሸነፉአቸው፤ የእግዚአብሔርም አገልጋይ ሙሴ ርስት አድርጎ ለሮቤል ልጆች፤ ለጋድም ልጆች ለምናሴም ነገድ እኩሌታ ምድሪቱን ሰጣቸው። 7 ኢያሱና የእስራኤል ሕዝብ ያሸነፉአቸ ነገሥታትና አገሮች እነዚህ ናቸው፦ በዮርዳኖስም ማዶ በምዕራብ በኩል፥ በሊባኖስ ሸለቆ አጠገብ ወደ ኤዶን አጠገብ ሃላክ ተራራ ድረስ ነው። ኢያሱም ለእስራኤል ነገዶች ሁሉ ምድሪቱን ርስት አድርጎ ሰጣቸው። 8 ተራራማውን አገር፥ በቆላውንም፥ በዓረባንም፥ የተራሮችን ቁልቁለት፥ ምድረ በዳውንም፥ የደቡቡም ያሉትን ኬጢያውያን፥ አሞራውያንም፥ ከነዓናውያንም፥ ፌርዛውያንም፥ ኤዊያውያንም፥ ኢያቡሳውያንም ሰጣቸው። 9 የኢያሪኮ ንጉሥ ጨምሮ፦ በቤቴል አጠገብ ያለው የጋይ ንጉሥ፥ 10 የኢየሩሳሌም ንጉሥ፥ የኬብሮን ንጉሥ፥ 11 የያርሙት ንጉሥ፥ የለኪሶ ንጉሥ፥ 12 የአግሎን ንጉሥ፥ የጌዝር ንጉሥ፥ 13 የዳቤር ንጉሥ፥ የጌድር ንጉሥ፥ 14 የሔርማ ንጉሥ፥ የዓራድ ንጉሥ፥ 15 የልብና ንጉሥ፥ የአዶላም ንጉሥ፥ 16 የመቄዳ ንጉሥ፥ የቤቴል ንጉሥ፥ 17 የታጹዋ ንጉሥ፥ ይአፌር ንጉሥ፥ 18 የአፌቅ ንጉሥ፥ የሸሮን ንጉሥ፥ 19 የማዶ ንጉንጉሥ፥የአሶር ንጉሥ፥ 20 የሺምሮን፥ ሚሮን ንጉሥ፥ የአዚፍ ንጉሥ፥ 21 የታዕናክ ንጉሥ፥የመጊዶ ንጉሥ፥ 22 የቃዴስ ንጉሥ፥ በቀርሜሎስ የነበረ የዮቅንዕም ንጉሥ፥ 23 በዶር ኮረብታ የነበረ የዶር ንጉሥ፥ የጌልገላ አሕዛብ ንጉሥ፥ 24 የቲርሳ ንጉሥ፥ ነገሥታቱ ሁሉ ሠላሳ አንድ ናቸው።

Joshua 12:1

አሁን
ይህ ቃል እዚህ ስፍራ ያገለገለው በዋናው ታሪክ ፍሰት ቆም ለማለት ነው። እዚህ ላይ ጸሐፊው የመረጃ ዳራ መስጠት ይጀምራል። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሦቹ እነዚህ ናቸው
ይህ እስከ ቁጥር 24 የሚገኙትን የንጉሦች ስም ዝርዝር ያመለክታል።

ዓረባ...አርኖን
እነዚህ የስፍራ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሴዎን... ሔሴቦን
እነዚህን ቃላት በኢያሱ 9:10 እንዴት እንተረጎሟቸው ይመልከቱ።

Joshua 12:6

ሮቤላውያን
እነዚህ የሮቤል ትውልዶች ናቸው።

ጋድአውያን
እነዚህ የጋድ ትውልዶች ናቸው።

የምናሴ ነገድ እኩሌታ
እኩሌታ ነገድ የሚባሉበት ምክንያት ሌላኛው የነገዱ እኩሌታ በከነዓን ምድር ርስታቸውን ስለተቀበሉ ነው።

Joshua 12:7

በኣል ጋድ... ሐላቅ ተራራ...ዓረባ
እነዚህ የስፍራ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 12:9

ጋይ...የርሙት...ለኪሶ...ዔግሎን... ጌድር
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። "የርሙት፣" "ለኪሶ፣" እና "ዔግሎን" የሚሉትን ስሞች በኢያሱ 10:3 በተረጎሙበት ተመሳሳይ መንገድ ይተርጉሙ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 12:13

ዳቤር...ጌድር...ሔርማ...ዓራድ...ልብና...ዓዶላም...መቄዳ
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 12:17

ታጹዋ... ኦፌር... አፌቅ...ለሸሮን... ማዶን... ሐጾር... ሺምሮን ሚሮን... አዚፍ
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 12:21

ታዕናክ... መጊዶ...ቃዴስ...ዮቅንዓም...ዶር...ጎይም...ቲርሳ
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በድምሩ ሰላሳ አንድ
"በድምሩ 31" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 13

1 ኢያሱም ሸመገለ በዕድሜም አረጀ፤ እግዚአብሔርም አለው፦ አንተ ሸመገልህ፥ በዕድሜህም አረጀህ ያልተወረሰ እጅግ ብዙ ምድር ገና ቀርቶአል። 2 የቀረውም
ምድር ይህ ነው፤ የፍልስጥኤማውያንና የጌሹራውያን አገር ሁሉ፥ 3 (በግብፅ ፊት ካለው ከሺሖር ወንዝ ጀምሮ በሰሜን በኩል አስካለው የከነዓናውያን ንብረት
ሆኖ ተቆጠረው እስከ አቃሮን ዳርቻ ድረስ፥ የጋዛ፥ የአዛጦን የአስቀሎና፥የጌትና የአቃሮን አምስቱ የፍልስጥኤማውያን መኳንንት።) 4 በደቡብም በኩል
የከነዓናውያንም ምድር ሁሉ፥ ለሲዶናውያንም የምትሆን መዓራ እስከ አሞራውያን ዳርቻ እስከ አፌቅ ድረስ፥ 5 የጌባላውያንም ምድር፥ በፀሐይ መውጫ በኩል
ሊባኖስ ሁሉ፥ ከኣል ጋድ ከአርሞንዔም ተራራ በታች እስከ ሐማት ድረስ ያለው ። 6 በተራራማውም አገር የሚኖሩትን ሁሉ ከሊባኖስ ጀምሮ እስከ ማሴሮን ድረስ
ሲዶናውያን ሁሉ። እነዚህን ከእስራኤል ፊት አባርራቸዋለሁ። እንዳዘዝሁም፤ምድራቸውን ለእስራኤል ርስት አድርገህ ለመመደብ እርግጠኛ ሁን። 7 አሁንም ይህን
ምድር ለዘጠኙ ነገድ ለምናሴም ነገድ እኩሌታ ርስት አድርገህ አከፋፍል። 8 የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴም እንደ ሰጣቸው ከሌላ እኩሌታ የምናሴ ነገድ ጋር
የሮብልና የጋድ ሰዎች በምሥራቅ በኩል በዮርዳኖስ ማዶ ሙሴ አዞአቸው የነበረውን ርስታቸውን ተቀበሉ። 9 በአርኖን ወንዝ ሸለቆ ዳር ካለው ከአሮዔር፥
(በሸለቆውም መካከል ካለው ከተማ ጀምሮ) የሜድባን ሜዳ ሁሉ እስከ ዲቦን ድረስ፥ 10 በሐሴቦንም የአሞርውያን ንጉሥ የሴዎን ከተሞች ሁሉ እስከ
አሞራውያን ዳርቻ ድረስ፥ 11 ገለዓድንም፥ የጌሹራውያንና የማዕካታውያንን አካባቢ ሁሉ፥ የአርሞንዔምንም ተራራ ሁሉ፥ባሳንንም ሁሉ እስከ ሰልካ ድረስ፥ 12
በባሳን የነበረውን በአስታሮትና በኤድራይ የነገሠውን የዐግን መንግሥት ሁሉ፥ እነርሱም ከራፋይም የቀረ ነበረ፤ እነዚህንም ሙሴ መታቸው አወጣቸውም። 13
ነገር ግን የእስራኤል ሰዎች ጌሹራውያንን ወይም ማዕካታውያንን አላወጡም ነበር። በዚህ ፈንታ ጌሹርና ማዕካት እስከ ዛሬም ድረስ በእስራኤል መካከል
ይኖራሉ። 14 ሙሴም ለሌዊ ነገድ ለብቻ ርስት አልሰጠም። እግዚአብሔር ለሙሴ እንደ ተናገረው ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር የሚቀረበው፥ በእሳት
የተደረገ መሥዋዕት ርስታቸው ነው። 15 ሙሴም ለሮቤል ልጆች ነገድ በየወገናቸው ርስትን ሰጥጣቸው። 16 ድንበራቸውም በአርኖን ሸለቆ ዳር ካለችው
ከአሮዔር ጀምሮ በሸለቆው መካከል ያለችው ከተማ፥ 17 ሐሴቦንና በሜዳውም ያሉት ከተሞችዋ ሁሉ፥ዲቦን፥ ባሞት በኣል፥ ቤት በኣልምዖን፥ 18 ያሀጽና
ቅዴሞት፥ ሜፍዓት፥ 19 ቂርያታይም፥ ሴባማ፥ ጼሬትሻሐር በሸለቆውም ተራራ ያለውና ሁሉ ሮቢን ተቀበለ። 20 ሮቤም ቤተ ፌጎርን፥ ከፈስጋ ተራራ በታች ያለው
ምድርን፥ ቤት የሺሞትን፥ 21 የሜዳውም ከተሞች ሁሉ፥ የአሞራውያን ንጉሥ የሴዎን መንግሥት፥ በሐሴቦንም የነገሠው፥ ሙሴም እርሱንና በምድሪቱ
የተቀመጡትን የምድያምን አለቆች፥ ኤዊን፥ ሮቆምን፥ ሱርን፥ ሑርንና ሪባን፥ የሴዎን መሳፍንት፥ መታቸው። 22 የእስራኤል ሰዎች ከገደሉአቸውም ሰዎች ጋር
ምዋርተኛውን የቢዖርን ልጅ በለዓምን በሰይፍ ገደሉ። 23 የሮቤልም ልጆች ድንበር የዮርዳኖስ ወንዝና ዳርቻው ነበረ። 23 የሮቤል ነገድ ድንበር የዮርዳኖስ ወንዝ
ነው፥ ይህም ድንበራቸው ነው። ይህም ከከተሞቻቸውና መንደሮቻቸው በየወገኖቻቸው ለሮቤል ነገድ የተሰጣቸው ርስት ነበረ። 24 ይህም መሴ ለጋድ ነገድ
በየወገኖቻቸው ርስት አድርጎ የሰጣቸው ነው። 25 ድንበራቸውም ኢያዜርና የገለዓድ ከተሞች ሁሉ፥ የአሞራውያንም ምድር እኩሌታ፥ 26 ከረባት በስተምሥራቅ፥
አስካለው እስከ አሮዔር ድረስ፥ ከሐሴቦን ጀምሮ እስከ ራማት ምጽጴ፥ እስከ ብጦኒም ድረስ፥ ከመሃናይም ጀምሮ እስከ ዳቤር ዳርቻ ድረስ ነበር። 27 ሙሴም
ቤትሀራምን፥ ቤትኒምራ፥ ሱኮትና ጻፎን፥ የቀሩትንም የሐሴቦን ንጉሥ የሴዎን መንግሥት ከዮርዳኖስን እንደ ድንበር በምሥራቅ በኩል ባለው በዩርዳኖስ ማዶ
የኪኔሬት ባሕር ወዲያኛው ዳርቻ ሰጣቸው። 28 ይህም የጋድ ነገድ ከከተሞቻቸውና ከመንደሮቻቸው ጋር በየወገኖቻቸው ርስት ነበረ። 29 ሙሴም ለምናሴ
እኩሌታ ነገድ ርስትን ሰጣቸው። ለምናሴም ነገድ እኩሌታ በየወገኖቻቸው መሠረት የተመመደበ ነበረ። 30 ድንበራቸውም ባሳን ሁሉ፥ ከመሃናይም ጀምሮ
የባሳን ንጉሥ የዐግ መንግሥት፥ በባሳንም ያሉት የኢያዕር መንደሮች ሁሉ ስድሳው ከተሞች፤ 31 የገለዓድም እኩሌታ፥ አስታሮትና ኤድራይ ነበር፤ (የ'ዐግ በባሳን
ያሉ የመንግሥት ከተሞች) ። እነዚህም ለምናሴ ልጅ ለማኪር ልጆች ሆኑ፤ ለማኪር ሰዎች እኩሌታ በየወገኖቻቸው ይህ ነበረ። 32 ይህም ሙሴ በምሥራቅ
በኩል በኢያሪኮ አንጻር በዮርዳኖስ ማዶ በሞዓብ ሜዳ ሳለ፥ የከፈለው ርስት ነው። 33 ሙሴም ለሌዊ ነገድ ርስት አልሰጣም ነበር። የእስራኤል አምላክ
እግዚአብሔር እንደ ተናገራቸው ርስታቸው ነው።

Joshua 13:2

አስከ አሁን ገና የቀረው ምድር ይህ ነው
እስራኤል ገና ሊይዘው የሚገባው ምድር ይህ ነው በማለት ማብራራት ይቻላል። "አስራኤላያን ገና ወዲፊት የሚይዙት ምድር ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሺሖር
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የከነዓናውያን ንብረት ነው ተብሎ የሚቆጠር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አሁን ከነዓናውያን ንብረታቸው አድርው የሚቆጥሩት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ኤዋውያን
ይህ የአንድ ቡድን ሰዎች የወል ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 13:4

ዓራ...አፌቅ...በኣልጋድ...ኤርሞንዔም ተራራ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ጌባላውያን
ይህ በገባኦን የሚኖሩ ሰዎች የወል ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 13:6

ማሴሮን
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ምድር...እርስት አድርጎ
እስራኤላውያን የእኔ ነው የሚሉት ምድር ቋሚ ሃብቸው አድርገው እንደሚቀበሉት ርስታቸው ተድረጎ ተገልጽዋል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Joshua 13:8

አርኖን... ሜድባ... ዲቦን
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሸለቆ
ወንዙ ከጎንና ጎኑ ከሚገኘው ስፍራ እጅግ ዝቅ ብሎ የሚገኝበት ነው

አንባ
ከወንዝ በላይ ከፍ ብሎ የሚገኝ ሜዳማ መሬት

Joshua 13:10

ሔሴቦን... ሰልካ... አስታሮት... ኤድራይ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የጌሹራውያን እና ማዕካታውያን ግዛት
" የጌሹራውያን እና ማዕካታውያን የሚኖሩበት ምድር"

ማዕካታውያን... ራፋይም
እነዚህ የህዝብ የወል ስም ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሙሴ መታቸው
እዚህ ስፍራ "ሙሴ" የሚወክለው ራሱን እና እርሱ የሚመራቸውን እስራኤላውያን ሰራዊት ነው። "ሙሴ አና እስራኤላውያን መቷቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 13:13

ጌሹራውያን ወይም ማዕካታውያን
ይህ የአንድ ቡድን ሰዎች የወል ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ጌሹራውያን እና ማዕካታውያን በእስራኤላውያን መሃል ይኖራሉ
"ጌሹራውያን" እና "ማዕካታውያን" አንድም "የጌሹራውያን" እና "የማዕካታውያን" አባቶች ናቸው ወይም የሚኖሩባቸው ከተሞች ስሞች ናቸው። "እነዚያ ህዝቦች በእስራኤላውያን መሃል ይኖራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እስከ ዛሬ ድረስ
ይህ ጸሐፊው ይህንን መጽሐፍ እሰከ ጻፈበት ጊዜ ድረስ ያለውን ጊዜ ያመለክታል

Joshua 13:14

ሙሴ ምንም ርስት አልሰጣቸውም
ሙሴ ለእስራኤል ነገድ የሰጠው ምድር ቋሚ ሃብት እንደተቀበሉ ተደርጎ ተገልጽዋል። (ዘይቤያው አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

ለያህዌ የሚቀርቡ መሥዋዕቶች ... ርስታቸው ነው
ጸሐፊው ሌዋውያን በክህነት ያህዌን በማገልገል ያላቸውን ታላቅ ክብር መስዋዕቶቹን እነርሱ እንደሚወርሷቸው ነገሮች አድርጎ ይገልጻል። "ለያህዌ የሚቀርቡ መሥዋዕቶች ... ለእነርሱ የሚሰጣቸው ይሆናል" (ዘይቤያው አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 13:15

አርኖን... ሜድባ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሸለቆ... አንባ
x

Joshua 13:17

ሔሴቦን... ዲቦን... ባሞትበኣል... ቤትበኣልምዖን... ያሀጽ... ቅዲሞት... ሜፍዓት... ቂርያታይም... ሴባማ... ጼሬትሻሓር
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 13:20

ቤት ፈጎር... ፊስጋ... ቤት የሺሞት... ሔሴቦን
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሴዎን... ኤዊ... ሮቆም... ሱር... ሑር... ሪባ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ከምድያም መሪዎች ጋር
"የምድያም መሪዎችን እንዳሸነፈ"

Joshua 13:22

ይህ ድንበራቸው ነው
የዮርዳኖስ ወንዝ የሮቤል ነገድ የተቀበለው ምዕራባዊ ዳርቻ ነው

ይህ የሮቤል ነገድ ርስት ነበር
ሙሴ ለሮቤል ነገድ የሰጠው ምድር የሮቤል ነገድ በቋሚነት እንደ ተቀበለው ርስት ተደርጎ ይገለጻል። (ዘይቤያው አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

ለእያንዳንዱ ጎሳቸው ተሰጠ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሙሴ ለእያንዳንዱ ጎሳቸው የሰጠው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 13:24

ኢያዜር...አሮዔር... ሐሴቦን... ራማት ምጽጴ.. ብጦኒም... መሃናይም... ዳቤር
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 13:27

ቤት ሀራም... ቤት ኒምራ... ጻፎን... ሐሴቦን
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የጋድ ነገድ ርስት ነው
ሙሴ ለጋድ ነገድ የሰጠው ምድር የጋድ ነገድ በቋሚነት እንደ ተቀበለው ርስት ተደርጎ ይገለጻል። (ዘይቤያው አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 13:29

ሙሴ ለምናሴ ነገድ እኩሌታ ርስት ሰጠ
ሙሴ ለምናሴ ነገድ እኩሌታ የሰጠው ርስት ለእነርሱ እንደ ሰጠው ቋሚ ርስት ተደርጎ ተገልጽዋል። (ዘይቤያው አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የምናሴ ነገድ እኩሌታ
የነገዱ እኩሌታ ብቻ ይህንን ምድር ተቀብሏል፣ ምክንያቱ የነገዱ ቀሪው እኩሌታ ከዮርዳኖስ ማዶ ባለው ምድር ርስቱን ተቀብሏል።

ተሰጥቷቸው ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሙሴ ርስታቸውን ሰጥቷቸው ነበር" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

መሃናይም... ኢያዕር... አስታሮት... ኤድራይ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የተሰጡት እነዚህ ነበሩ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሙሴ እነዚህን ሰጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ማኪር
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 13:32

ሙሴ የሰጣቸው ርስት ይህ ነው
ሙሴ ለእስራኤል ነገዶች የሰጣቸው ከዮርዳኖስ በስተምስራቅ የሚገኘው ምድር በቋሚነት እንደሰጣቸው ርስት ተደረጎ ተገልጽዋል። "ይህ ሙሴ ለእነርሱ ርስት አድርጎ የሰጣቸው ምድር ነው።" (ዘይቤያው አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል አምላክ ያህዌ፣ የእነርሱ ርስት ነው
ጸሐፊው ሌዋውያን በክህነት አገልግሎታቸው ያህዌን በማገልገል ያላቸውን ታላቅ ክብር የገለጸው የሚወርሱት ያህዌን እንደሆነ በመናገር ነው። "የእነርሱ ርስት የእስራኤል አምላክ ያህዌ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያው አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 14

1 የእስራኤልም ሕዝብ በካነዓን ምድር የወረሱት ካህኑ አልዓዛርና የነዌ ልጅ ኢያሱ በእስራኤልም ነገድ መካከል የአባቶቻቸው አለቆች ያካፈሉአቸው ርስት ይህ
ነው፤ 2 እግዚአብሔር በሙሴ እጅ እንዳዘዘ ለዘጠኙ ነገዶችና ለእኩሌታው በየርስታቸው በዕጣ አካፈሉአቸው፤ 3 ለሁለቱ ነገድና ለእኩሌታው ነገድ በዮዳኖስ
ማዶ ሙሴ ርስት ሰጥቶ ነበር፤ ነገር ግን በመካከላቸው ለሌዋውያን ርስት አልሰጣቸውም። 4 የዮሴፍ ነገድ፥ ምናሴና ኤፍሬም ሁለት ነገዶች ነበሩ።
ለሌዋውያንም ከሚቀመጡባቸው ከተወሰኑ ከተሞች፥ ለእንስሶቻቸውና ለከብቶቻቸውም ከሚሆን መሰምርያቸው በቀር በምድሩ ውስጥ ድርሻ
አልሰጡአቸውም። 5 እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው የእስራኤል ሕዝብ አደረጉ፥ ምድሩንም ተካፈሉ። 6 የይሁዳም ነገድ በጌልገላ ወደ ኢያሱ ቀረቡ።
ቄኔዛዊውም የዮፎኒ ልጅ ካሌብ እንዲህ አለው፦ ለእግዚአብሔር ሰው ለሙሴ ስለ እኔና ስለ አንተ እግዚአብሔር በቃዴስ በርኔ የተናገረውን ነገር ታውቃለህ። 7
የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴ ምድርን እሰልል ዘንድ ከቃዴስ በርኔ በላከኝ ጊዜ እኔ የአርባ ዓመት ሰው ነበርሁ፤ እኔም በልቤ እንደ ነበረ መረጃ አመጠሁለት። 8
ነገር ግን ከእኔ ጋር የሄዱ ወንድሞቼ የሕዝቡን ልብ በፍርሃት አቀለጡ። እኔ ግን አምላኬን እግዚአብሔርን ፈጽሜ ተከተልሁ። 9 ሙሴም በዚያ ቀን፦ አምላኬን
እግዚአብሔርን ፈጽመህ ተከትለሃልና እግርህ የረገጠው ምድር ለአንተና ለልጆችህ ለዘላለም በእርግጥ ርስት ይሆናል ብሎ ማለ። 10 አሁንም፥ እነሆ፥
እግዚአብሔር ለሙሴ ይህን ቃል ከተናገር በኋላ፥ እስራኤል በምድረ በዳ ሲጓዙ፥ እርሱ እንደ ተናገረኝ እግዚአብሔር እነዚህን አርባ አምስት ዓመት በሕይወት
አኖረኝ። እነሆ፥ ለእኔ ዛሬ ሰማንያ አምስት ዓመት ሆነኝ። 11 ሙሴም በላከኝ ጊዜ እንደ ነበርሁ፥ ዛሬ ጉልበታም ነኝ፥ ጉልበቴም በዚያን ጊዜ እንደ ነበር፥ እንዲሁ
ዛሬ ለመዋጋት፥ ለመውጣትና ለመግባትም ጉልበቴ ያው ነው። 12 እንግዲህ በዚያን ቀን እግዚአብሔር የተናገረውን ይህን ተራራማ አገር ስጠኝ። አንተም በዚያ
ቀን ታላላቅና በተመሸጉ ከተሞቻቸው ጋር ዔናቃውያን በዚያ እንደ ነበሩ ሰምተህ ነበር። እግዚአብሔርም እንደ ተናገረ እግዚአብሔርም ከእኔ ጋር ይሆናል፥
አሳድዳቸዋለሁ። 13 ኢያሱም ባረከው፤ ለዮፎኒም ልጅ ለካሌብ ኬብሮንን ርስት አድርጎ ሰጠው። 14 ስለዚህም የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን ፈጽሞ ስለ
ተከተለ ኬብሮን እስከ ዛሬ ለቄኔዛዊው ለዮፎኒ ልጅ ለካሌብ ርስት ሆንች። 15 የኬብሮንም ስም አስቀድሞ ቂርያት አርባቅ ትባል ነበር። (አርባቅም በዔናቅ ሰዎች
መካከል ከፍ ያለ ነበረ።) ምድሪቱም ከጦርነት ዐረፈች።

Joshua 14:1

የእስራኤል ህዝብ ርስት አድርጎ የተቀበላቸው ስፍራዎች
የእስራኤል ህዝብ ያገኘው ምድር የተገለጸው በቋሚነት እንደተቀበለው ሃብቱ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያው አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

የነገድ አለቆች
"የነገዶቹ አለቆች"

Joshua 14:2

ርስታቸው የተከመረጠላቸው በእጣ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አልዓዛር፣ ኢያሱ፣ እና የጎሳ አለቆች ርስታቸውን ለማከፋፈል እጣ ጣሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በሙሴ እጅ
እዚህ ስፍራ"እጅ" የሚለው ሙሴን ራሱን እና ያህዌ ሙሴን የእርሱን ትዕዛዝ ማስፈጸሚያ አድርጎ እንደ ተገለገለበት የሚገልተጽ ቃል ነው። "በሙሴ አማካይነት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልቱ)

ሙሴ የሁለቱን ነገዶች እና የአንዱን ነገድ እኩሌታ ርስት ከዮርዳኖስ ባሻገር ሰጠ፣ ለሌዋውያን ግን ምንም ርስት አልሰጣቸውም
ሙሴ ለነገዶቹ የሰጣቸው መሬት የተገለጸው በቋሚነት እንደ ተቀበሉት ርስት ተደርጎ ነው። (ዘይቤያው አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

ሌዋውያን ከምድሪቱ ርስት ተደርጎ ምንም ደርሻ አልተሰጣቸውም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሙሴ ለሌዋውያን ምንም ድርሻ ርስት አድርጎ አልሰጣቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ድርሻ
"ክፍል"

ነገር ግን አንዳንድ ከተሞች ብቻ ለመኖሪያነት
ግሱ የተወሰደው ከቀደመው ሀረግ ነው። "ነገር ግን እርሱ ለመኖሪያነት አንዳንድ ከተሞችን ብቻ ሰጣቸው" (ኢሊፕሲስ/የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

የግጦሽ መሬት
ለብቶች ግጦሽ የሚውል መስክ

ቁሳዊ ሃብት
ለቤተሰቦቻቸው ያቀርቧቸው ዘንድ የሚያስፈልጋቸው ቁሳዊ/አካላዊ ነገሮች

Joshua 14:6

ዮፎኒ
ይህ የወንድ ስም ነው (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ቄኔዛዊ
ይህ የአንድ ቡድን ሰዎች የወል ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእርሱ ዳግም በልቤ ማድረግ እንዳሰብኩት መረጃ ይዜ መጣሁ
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚለው ቃል የሚወክለው ሃሳብን ነው። ሀረጉ ፈሊጣው ሲሆን የሚያመለክተው በእውነተኛነት የቀረበን መረጃ ነው። "ለእርሱ ዳግም እውነተኛ መረጃ ይዜ መጣሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የህዝቡ ልብ በፍርሃት እንዲቀልጥ አደረጉ
ህዝቡ በጣም እንዲፈራ ማድረግ የተገለጸው የህዝቡ ልብ እንዲቀልጥ እንደተረገ ተደርጎ ነው። "ህዝቡ በጣም እንዲፈራ አደረጉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ሙሉ ለሙሉ ያህዌን ተከተልኩ
ለያህዌ ታማኝ መሆን የተገለጸው ያህዌን ሙሉ ለሙሉ እንደ መከተል ተደርጎ ነው። "ሁሌም ለያህዌ ታማኝ ነበርኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምድሪቱ... ለአንተ እና ለልጆችህ ለዘለዓለም ርስት ትሆናለች
ካሌብ እና የእርሱ ትውልድ የሚኖራቸው ምድር የተገለጸው በቋሚነት እንደ ተቀበሉት ርስት ተደርጎ ነው። (ዘይቤያው አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

እግርህ የረገጠውን ምድር
እዚህ ስፍራ "እግርህ" የሚለው የሚወክለው ካሌብን ነው። "የረገጥከው ምድር" (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልቱ)

Joshua 14:8

የህዝቡ ልብ በፍርሃት እንዲቀልጥ አደረጉ
ህዝቡ በጣም እንዲፈራ ማድረግ የተገለጸው የህዝቡ ልብ እንዲቀልጥ እንደተረገ ተደርጎ ነው። "ህዝቡ በጣም እንዲፈራ አደረጉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ሙሉ ለሙሉ ያህዌን ተከተልኩ
ለያህዌ ታማኝ መሆን የተገለጸው ያህዌን ሙሉ ለሙሉ እንደ መከተል ተደርጎ ነው። "ሁሌም ለያህዌ ታማኝ ነበርኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሪቱ... ለአንተ እና ለልጆችህ ለዘለዓለም ርስት ትሆናለች
ካሌብ እና የእርሱ ትውልድ የሚኖራቸው ምድር የተገለጸው በቋሚነት እንደ ተቀበሉት ርስት ተደርጎ ነው። (ዘይቤያው አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

እግርህ የረገጠውን ምድር
እዚህ ስፍራ "እግርህ" የሚለው የሚወክለው ካሌብን ነው። "የረገጥከው ምድር" (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልቱ)

Joshua 14:10

ተመልከት
"ትኩረት ስጥ፣ ምክንያቱም የምናገረው እውነትም ዋጋ ያለውም ነገር ነው"

እስራኤል በምድረ በዳ ሲጓዝ
"የእስራኤል ህዝብ በምድረ በዳ ሲጓዝ"

አሁንም ጥንካሬዬ በዚያን ጊዜ እንደነበረው ነው
"በዚያን ጊዜ ጠንካራ የነበርኩትን ያህል አሁንም ጠንካራ ነኝ"

ስገባና ስወጣ
ይህ የየዕለት ክንዋኔን የሚገልጽ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "በየዕለቱ ለማደርጋቸው ነገሮች" (ፈሊጣው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 14:12

ተራራማ አገር
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ብዙ ትላልቅ ኮረብቶች ወይም ትናንሽ ተራሮች 2) አንድ ተራራ

ዔናቅ
ይህ የአንድ ቡድን ሰዎች የወል ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 14:13

ኬብሮንን ለካሌብ ርስት አድርገህ ሰጠው
ኬብሮን ካሌብ በቋሚነት እንደተቀባለት ርስት ተደርጋ ተገልጻለች። (ዘይቤያው አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

እስከ ዛሬ ድረስ
ይህ ጸሐፊው ይህንን መጽሐፍ እሰከ ጻፈበት ጊዜ ድረስ ያለውን ጊዜ ያመለክታል።

እርሱ ሙሉ ለሙሉ ያህዌን ተከትሏል
ለያህዌ ታማኝ መሆን የተገለጸው ሙሉ ለሙሉ ያህዌን መከተል ተደርጎ ነው። "ሁሌም ለያህዌ ታማኝ ነበር" (ዘይቤያው አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

ቂርያት አርባቅ
ይህ የስፍራ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚህ በኋላ ምድሪቱ ከጦርነት አረፈች
ህዝቡ ከዚያ በኋላ ጦርነት ውስጥ አለመግባቱ የተገለጸው ምድሪቱ ራሷ ሰው እንደሆነች እና ከጦርነት እንዳረፈች ተደርጎ ነው። ይህንን ሀረግ በኢያሱ 11፡23 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። "ከዚህ በኋላ ህዝቡ በምድሪቱ ጦርነት አላደረገም" (ሰውኛ ዘይቤ እና ዘይቤያው አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 15

1 ለይሁዳም ልጆች ነገድ በየወገናቸው መሬትን ማከፋፈል እስከ ጺን ምድረ በዳ እስከ ደቡብም መጨረሻ እስከ ኤዶምያስ ዳርቻ ድረስ ዕጣ ሆነላቸው። 2 በደቡብም በኩል ያለው ድንበራቸው እስከ ጨው ባሕር መጨረሻ ወደ ደቡብ እስከሚያይ እስከ ባሕረ ልሳን ነበረ። 3 ከዚያም ቀጥሎ ከኮረብታ በስተደቡብ በኩል ወደ ጺንም አለፈ፤በቃዴስ በርኔ ወደ ደቡብ በኩል ይዘልቃል፤ በሐጽሮንም በኩል አልፎ ወደ አዳርም ደረሰ፥ ወደ ቀርቃ ዞረ፥ 4 ወደ አጽሞንም አለፈ፥ በግብፅም ወንዝ በኩል ወጣ፥ የድንባሩም መውጫ በባሕሩ አጠገብ ነበር፤ በደቡብ በኩል ያለው ድንበራቸው ይህ ነው። 5 በምሥራቅም በኩል ያለው ድንበር እስከ ጨው ባሕር እስከ ዮርዳኖስም መጨረሻ ነበረ። በሰሜንም በኩል ያለው ድንበር በዩርዳኖስ መጨረሻ እስካለው እስከ ባሕሩ ልሳን ድረስ ነበር። 6 ከዚያም ድንበሩ ወደ ቤት ሖግላ ወጣ፥ በቤት ዓርባ በሰሜን በኩል አለፈ። (ወደ ሮቤልም ልጅ ወደ ቦሀን) ድንጋይ ወጣ። 7 ድንበሩም ከአኮር ሸለቆ ወደ ዳቤር ወጣ፥ በሰሜን በኩል በአዱሚም ኮረብታ ፊት ለፊት፥በወንዙም በደቡብ በኩል ወዳለችው ወደ ጌልገላ ዞረ። ከዚያም ድንበሩ ወደ ቤት ሳሚስ ውኃ አለፈ፥ መውጫውም በዓይን ሮጌል አጠገብ ነበረ። 8 ከዚያ ድንበሩም በሄኖም ልጅ ሸለቆ አጠገብ (ኢየሩሳሌም) ወደምትባለው ወደ ኢያቡሳዊው ወደ ደቡብ ወገን ወጣ፤ ድንበሩም በራፋይም ሸለቆ ዳር በሰሜን በኩል ባለው በሄኖም ሸለቆ ፊት ለፊት በምዕራብ ወገን ወዳለው ተራራ ራስ ላይ ወጣ። 9 ድንበሩም ከተራራው ራስ ወደ ኔፍቶ ውኃ ምንጭ ደረሰ፥ ወደ ዔፍሮንም ተራራ ከተሞች ወጣ። ቂርያትይዓሪም ወደምትበል ወደ በኣላ ደረሰ። (ከዚያም ድንበሩ በባኣላ ዙሪያ እንደ ቂርያት በተመሳሳይ ታጠፈ) ። 10 ድንበሩም ከባአላ በምዕራብ በኩል ወደ ሴይር ተራራ ዞረ፤ክሳሎን ወደምትባል ወደ ይዓሪም ተራራ ወገን በሰሜን በኩል አለፈ፤ ወደ ቤት ሳሚስ ወረድ፥ በተምና በኩልም አለፈ። 11 ድንበሩም ወደ አቃሮን ወደ ሰሜን ወገን ወጣ፤ወደ ሽክሮን ደረሰ ወደ በኣላ ተራራ አለፈ፥ በየብኒኤል በኩልም ወጣ፤ የድንበሩም መውጫ በባሕሩ አጠገብ ነበረ። 12 በምዕራቡም በኩል ያለው ድንበር እስከ ታላቁ ባሕርና እስከ ዳርቻው ድረስ ነበረ።ለይሁዳ ልጆች በየወገናቸው በዙሪያው ያለ ድንበራቸው ይህ ነው። 13 እግዚአብሔርም ኢያሱን እንዳዘዘው ለዮፎኒ ልጅ ካሌብ በይሁዳ ልጆች መካከል ቂርያት አርበቅ የምትባለውን ከተማ ድርሻ አድርጎ ሰጠው፤ እርስዋም ኬብሮን ናት፥ ይህም ዘርባቅ የዔናቅ አባት ነበረ። 14 ካሌብም ሦስቱን የዔናቅን ልጆች ሴስን፥ አኪመንንና ተላሚን ከዚያ አሳደደ። 15 ከዚምም በዳቤር ሰዎች ላይ ወጣ፤ የዳቤርም ስም አስቀድሞ ቂርያት ሤፍር ትባል ነበር። 16 ካሌብም እንዲህ አለ፦ ቂርያት ሤፍርን ለሚመታ ለሚይዛትም ልጄን ዓክሳን አጋባዋለሁ አለ። 17 የካሌብ ወንድም የቄኔዝ ልጅ ጎቶንያል ያዛት። ስለዚህም ካሌብ ልጁን ዓክሳን አጋባው። 18 ዓክሳም ወደ እርሱ በመጣች ጊዜ ከአባትዋ እርሻ ለመለምን ገፋፈችው፤ እርስዋም ከአህያዋ ወረደች፤ካሌብም፦ ምን ፈለግሽ? አላት። 19 እርስዋም፦ ስጦታ ስጠኝ፤ የኔጌቭ ምድር ሰጥተኸኛል፥ አሁን ደግሞ የውኃውን ምንጭ ስጠኝ አለችው። እርሱም የላይኛውንና የታችኛውን ምንጭ ሰጣት። 20 በየወገኖቻቸውም የይሁዳ ልጆች ነገድ የተሰጠ ርስት ይህ ነው። 21 በድቡብም በኩል በምድራቸው ዳርቻ አጠገብ እስከ ኤዶምያስ ድንበር ያሉትን የይሁዳ ልጆች ነገድ ከተሞች እነዚህ ነበሩ ቀብስኤል፥ ዓዴር፥ ያጉር፥ 22 ቂና፥ ዲሞና፥ ዓድዓዳ፥ 23 ቃዴስ፥ ሐጾር፥ ዩትናን 24 ዚፍ፥ጠሌም፥በዓሎት። 25 ሐጾርሐ ዳታ፥ ሐጾር የምትባለውም ቂርታይሐጾር፥ 26 አማም ሽማዕ፥ ሞላዳ፥ 27 ሐጾርጋዳ፥ሐሽሞን፥ ቤትጳሌጥ፥ 28 ሐጾርሹዓል፥ ቤርሳቤህ፥ ቢዝዮትያ፥ 29 በኣላ፥ ዒዮም፥ ዓጼም፥ 30 ኤልቶላድ፥ ኪሲል፥ ሔርማ፥ 31 ጺቅላግ፥ ማድማና፥ ሳንሳና፥ 32 ልባዎት፥ ሺልሂም፥ ዓይን፥ ሪሞም፤ ሀያ ዘጠኝ ከተሞችና መንደሮቻቸው። 33 በቆላው ኤሽታኦል፥ ጾርዓ፥ አሽና፥ 34 ዛኖዋ፥ ጫይንገኒም፥ ያጹዋ፥ ዓይናም፥ 35 የሩት፥ ዓዶላም፥ ሰኮት፥ ዓዜቃ፥ 36 ሸዓራይም፥ ዓዲታይም፥ ግርራ፥ ግርሮታይም፤ አሥራ አራት ከተሞችና መንደሮቻቸው። 37 ጽናን፥ ሐዳሻ፥ ሚግዳልጋድ፥ 38 ዲልዓን፥ ምጽጳ፥ ዮቅትኤል፥ 39 ለኪሶ፥ በጽቃት፥ አግሎን 40 አዶላም፥ ከቦን፥ ለሕማስ፥ ኪትሊሽ፥ 41 ግዴሮት፥ ቤት ዳጎን፥ ናዕማ፥ መቄዳ፤አሥራ ስድስት ከተሞችና ቁጥር ስፍር የሌላቸው መንደሮቻቸው። 42 ልብና፥ ዔቴር፥ ዓሻን፥ 43 ይፍታሕ፥ አሽና፥ንጺብ፥ 44 ቅዒላ፥ አክዚብ፥ መሪሳ፤ ዘጠኝ ከተሞችና ቁጥር ስፍር የሌላቸው መንደሮቻቸው። 45 አቃሮን፥ ከተመሽጉና ካልተመሸጉ ከተሞችና መንደሮችዋ ጋር፤ 46 ከአቃሮንም ጀምሮ እስከ ባሕር ድረስ በአዛጦን አጠገብ ያሉት ሁሉ ከመንደሮቻቸው ጋር። 47 በአዛጦን የተመሸጉና መንደሮችዋም፥ ጋዛና የተመሸጉ ከተሞችና መንደሮችዋ፥ እስከ ግብፅ ወንዝና እስከ ታላቁ ባሕር ካርቻ ክረስ። 48 በተራራማውም አገር ሳምር፥ የቲር፥ ሶኮ፥ 49 ደና፥ ዳቤር የምትባለው ቂርያትሰና፥ 50 ዓባብ፥ኤሽትሞዓ፥ ዓኒም፥ 51 ጎሶም፥ ሖሎን፥ ጊሎ፤ አሥራ አንድ ከተሞችና ቁጥር ስፍር የሌላቸው መንደሮቻቸው። 52 አራብ፥ ዱማ፥ ኤሽዓን፥ 53 ያንም፥ ቤትታጹዋ፥ አፌቃ፥ 54 ሑምጣ፥ ኬብሮን የምትባል ቂርያትአርባቅ፥ ጺዖር ፤ ዘጠኝ ከተሞችና ቁጥር ስፍር የሌላቸው መንደሮቻቸው። 55 ማዖን፥ ቀርሜሎስ፥ ዚፍ፥ ዩጣም 56 ኢይዝራሴል፥ ዮቅድዓም፥ ዛኖዋሕ፥ 57 ቃይን፥ ጊብዓ፥ ተምና፤ አሥር ከተሞና ቁጥር ስፍር የሌላቸው መንደሮቻቸው። 58 ሐልሑል፥ ቤት ጹር፥ ጌዶር፥ 59 ማዕራት፥ ቤትዓኖት፥ ኤልትቆን፤ስድስት ከተሞችና ቁጥር ስፍር የሌላቸው መንደሮቻቸው። 60 ቂርያትይዓሪም የምትባለው ቂርያት በኣል፥ ረባት፤ ሁለት ከተሞችና መንደሮቻቸው። 61 በምድረ በዳ ቤትዓረባ፥ ሚዲን፥ ስካካ፥ 62 ኒብሻን፥ የጨው ከተማ፥ ዓይንጋዲ፤ ስድስት ከተሞችና ቁጥር ስፍር የሌላቸው መንደሮቻቸው። 63 በኢየሩሳሌም የተቀመጡትን ኢያቡሳውያንን ግን የይሁዳ ልጆች ሊያሳድዱአቸው አልተቻላቸውም፤ ኢያቡሳውያንም እስከ ዛሬ በይሁዳ ልጆች መካከል በኢየሩሳሌም ውስጥ ተቀምጠዋል።

Joshua 15:1

ጺን
ይህ በረሃማ ስፍራ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ከጨው ባህር መጨረሻ ፣ ፊቱን ወደ ደቡብ ከመለሰው ባህረ ሰላጤ
" ወደ ደቡብ ፊቱን ከመለሰው ባህረ ሰላጤ፣ በጨው ባህር መጨረሻ" እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ አቅጣጫን ያመለክታሉ። ሁለተኛው ሀረግ ደቡባዊው ዳርቻ የሚጀምርበትን ነጥብ ያብራራል

ወደ ደቡብ ፊቱን ከመለሰው ባህረ ሰላጤ
"እስከ ደቡብ ከሚደርሰው ባህረ ሰላጤ" ወይም "ከደቡባዊ ባህረ ሰላጤ"

ባህረ ሰላጤ
ወደ መሬት ክፍል ገባ የሚል አነስተኛ የባህር ክፍል

Joshua 15:3

ድንበራቸው
"የይሁዳ ነገድ ድንበር የሆነ ምድር"

አቅረቢም...ጺን... ሐጽሮን... አዳር... ቀርቃ... አጽሞን
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የግብጽ ጅረት
በግብጽ አጠገብ፣ በምድሪቱ ደቡባዊ ምዕራብ ዳርቻ የሚገኝ ትንሽ የወንዝ ውሃ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Joshua 15:5

ዮርዳኖስ ወንዝ በሚገባበት
ወንዙ ወደ ባህሩ ገብቶ የሚያበቃበት ነጥብ የወንዙ መግቢያ ተብሎ ይገለጻል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ዳርቻ... መውረጃ
"ዳርቻ... ነበር"

ቤት ሖግላ... ቤት ዓረባ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የቦሀን ድንጋይ
ይህ ምናልባት አንድ ሰው ለድንበር ምልክትነት ያስቀመጠው፣ በዚያ ቦሃን በተባለ ሰው ስም የተሰየመ ትልቅ ድንጋይ ሊሆን ይችላል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 15:7

ዳቤር... የአኮር ሸለቆ... የአዱሚም ኮረብታ... ዓይንሳሚስ... ዓይንሮጌል... የቤን ሄኖም ሸለቆ... የራፋይም ሸለቆ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 15:9

ኔፍቶ... የዔፍሮን ተራራ... በኣላ... ቂርያት ይዓሪም... ሴይር ተራራ... ይዓሪም ተራራ... ክሳሎን... ቤት ሳሚስ... ተምና
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 15:11

አቃሮን... በኣላ ተራራ... የብኒኤል
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 15:13

ቂርያት አባቅ... ዳቤር... ቂርያት ሣፍር
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አርባቅ...ዔናቅ... ሴሲን... አኪመን... ተላሚን
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የኤናቅ ሶስት ወንድ ልጆች፡ ሴሲን፣ አኪመን እና ተላሚን ናቸው፤ እነዚህ የአናቅ ትውልድ ናቸው
እነዚህ ስሞች የሴሲን፣ አኪመን እና ተላሚን ጎሳ የነበሩ ትውልዶችን ይወክላሉ። በዚህ ዐውድ "ልጆች" እና "ትውልዶች" የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ይሰጣሉ። "የኤናቅ ትውልድ የሆኑት ሶስቱ ጎሳዎች፣ ሴሲን፣ አኪመን እና ተላሚን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያ ተነስቶ ወጣባቸው
"ከዚያ ተነስቶ ሊወጋቸው ወጣ"

Joshua 15:16

ቂርያትሣፍር
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ዓክሳ
ይህ የሴት ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ጎቶንያል... ቄኔዝ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 15:18

ዓክሳ ወደ ጎቶንያል መጣች
ይህ ዓክሳ የጎቶንያ ሚስት እንደምትሆን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ዓክሳ የጎቶንያ ሚስት በሆነች ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አባቷ የእርሻ መሬት እንዲሰጠው ይጠይቅ ዘንድ ገፋፋችው
ይህ ቀጥተኛ ንግግር ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። " 'የእርሻ መሬት እንዲሰጠኝ አባቴን ለምነው' በማለት ገፋፋችው" (ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ትምህርተ ጥቅሶች

Joshua 15:19

የላይኛውን ምንጮች እና የታችኛውን ምንጮች
"የላይኛው" እና "የታችኛው" የሚሉት ቃላት በአመዛኙ የውሃ ምንጮቹን መልከዓ ምድራዊ ከፍታ የሚያመለክቱ ሊሆኑ ይችላሉ።

Joshua 15:20

ይህ የይሁዳ ነገድ ርስት ነበር
የይሁዳ ነገድ የተቀበለው ርስት የተገለጸው ቋሚ ሃብታቸው አድርገው እንደተቀበሉት ርስት ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 15:21

አያያዥ ሃሳብ፡
ጸሐፊው ይሁዳ የወረሰውን ደቡባዊ ከተሞች ይዘረዝራል። ይህ ዝርዝር እስከ ኢያሱ 15:32 ድረስ ይቀጥላል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 15:25

አያያዥ ሃሳብ፡
የከተሞቹ ስም ዝርዝር ይቀጥላል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 15:29

አያያዥ ሃሳብ፡
የከተሞቹ ስም ዝርዝር ይቀጥላል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 15:33

አጠቃላይ መረጃ፡
ጸሐፊው ይሁዳ የወረሰውን ሰሜናዊ ከተሞች ይዘረዝራል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 15:37

አያያዥ ሃሳብ፡
ጸሐፊው ይሁዳ የወረሳቸውን ከተሞች ይዘረዝራል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Joshua 15:40

አያያዥ ሃሳብ፡
ጸሐፊው ይሁዳ የወረሳቸውን ከተሞች ይዘረዝራል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 15:42

አያያዥ ሃሳብ፡
ጸሐፊው ይሁዳ የወረሳቸውን ከተሞች ይዘረዝራል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 15:45

አያያዥ ሃሳብ፡
ጸሐፊው ይሁዳ የወረሳቸውን ከተሞች ይዘረዝራል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰፈራዎች
መንደሮች

የግብጽ ጅረት
በግብጽ አጠገብ፣ በምድሪቱ ደቡባዊ ምዕራብ ዳርቻ የሚገኝ ትንሽ የወንዝ ውሃ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 15:48

አያያዥ ሃሳብ፡
ጸሐፊው ይሁዳ የወረሳቸውን ከተሞች ይዘረዝራል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 15:52

አያያዥ ሃሳብ፡
ጸሐፊው ይሁዳ የወረሳቸውን ከተሞች ይዘረዝራል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 15:55

አያያዥ ሃሳብ፡
ጸሐፊው ይሁዳ የወረሳቸውን ከተሞች ይዘረዝራል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 15:58

አያያዥ ሃሳብ፡
ጸሐፊው ይሁዳ የወረሳቸውን ከተሞች ይዘረዝራል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 15:60

አያያዥ ሃሳብ፡
ጸሐፊው ይሁዳ የወረሳቸውን ከተሞች ይዘረዝራል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 15:63

እስከ ዛሬ
ይህ የሚያመለክተው ጸሐፊው ይህንን መጽሐፍ እስከ ጻፈበት ጊዜ ድረስ ያለውን ወቅት ነው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 16

1 የዮሴፍም ልጆች የመሬት ድልድል በኢያሪኮ አጠገብ በምሥራቁ በኩል ካለው ከዮርዳኖስ አንሥቶ በምድረ በዳውና በተራራማው በኩል ከኢያሪኮ ወደ ቤቴል
ወጣ። 2 ከቤቴል ወደ ሎዛ ወጣ፥ በአርካውያንም ዳርቻ በኩል ወደ አጣሮት አለፈ። 3 ወደ ምዕራብም እስከ የፍርሌጣውያን ዳርቻ እስከ ታችኛው ቤት ሖሮን
ዳርቻ እስከ ጌዝር ድረስ ዘልቆ፥ መጨራሻውም በባሕሩ አጠገብ ነበር። 4 የዮሴፍም ነገድ ምናሴና ኤፍሬም ርስታቸውን የተቀበሉት በዚህ መንገድ ነበር። 5
የኤፍሬምም ነገድ ድንበር በየወገኖቻቸው እንደዚህ ነበረ፦ በምሥራቅ በኩል የርስታቸው ድንበር አጣሮት አዳር እስከ ላይኛው ቤት ሖሮን ድረስ ነበረ፤ 6 ከዚያ
ወደ ባሕሩ ቀጠለ። ድንበሩም ወደ ምዕራብ ወደ ሚክምታት በሰሜን በኩል ወደ ምሥራቅ ወደ ተአናት ሴሎ ዞረ፥ ከዚያም ወደ ኢያኖክ በምሥራቅ በኩል አለፈ።
7 ከኢያኖክም ወደ አጣሮትና ወደ ነዓራት ወረደ፤ ወደ ኢያሪኮም ደረሰ፥ ወደ ዮርዳኖስም ወጣ። 8 ድንበሩም ካታጹዋ ወደ ምዕራብ እስከ ቃና ወንዝ ድረስ አለፈ፥
መውጫውም በባሕሩ መጨራሻ ነበረ። የኤፍሬም ነገድ ርስት በየወገኖቻቸው ይህ ነበረ፤ 9 ይኸውም፥ በምናሴ ነገድ ርስት መካከል ለኤፍሬምም ልጆች ከተለዩ
ከተሞች ጋር፥ ከተሞች ሁሉ ከመንደሮቻቸው ጋር ነው። 10 በጌዝርም የተቀመጡትን ከነዓናውያንን አላሳደዱአቸውም ነበር፤እስከ ዛሬም ድረስ ከነዓናውያን
በኤፍሬም መካከል ተቀምጠዋል፤ሆኖም እነዚህ ሰዎች የጉልበት ሥራ እንዲሠሩ ተደርገው ነበር።

Joshua 16:1

የዮሴፍ ነገድ
"የዮሴፍ ነገድ" በውስጡ፣ የዮሴፍን ሁለት ልጆች ነገዶች ማለት የምናሴ እና ኤፍሬም ነገዶችን ይይዛል። የምናሴ ነገድ እኩሌታ አስቀድሞ በዮርዳኖስ ምስራቅ የሰፈረ በመሆኑ፣ ይህ ሀረግ የሚያመለክተው የኤፍሬምን ነገድ እና የምናሴን ነገድ እኩሌታ ነው። "የኤፍሬም ነገድ እና የቀረው ሌላው ግማሽ የምናሴ ነገድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሎዛ... አጣሮት
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አርካውያን
ይህ የአንድ ቡድን ሰዎች የወል ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 16:3

ፍሌጣውያን
ይህ የአንድ ቡድን ሰዎች የወል ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ታችኛው ቤትሖሮን... ጌዝር
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የዮሴፍ ነገዶች፣ ምናሴ እና ኤፍሬም
"የዮሴፍ ልጆች፣ የምናሴ እና ኤፍሬም ነገዶች"

ርስታቸውን ተቀበሉ
የምናሴ እና ኤፍሬም ነገዶች የያዙት ምድር የተገለጸው እንደ ቋሚ ሀብታቸው አድርገው እንደተቀበሉት ተደርጎ ነው። "ይህንን ምድር ርስታቸው አድርገው ተቀበሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 16:5

በየ ጎሳው የኤፍሬም ነገድ ድንበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ኢያሱ ለጎሳቸው የሰጠው ድንበር" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አጣሮት አዳር...የላይኛው ቤት ሖሮን... ሚክምታት...ተአናት ሴሎ ...ኢያኖክ...ነዓራት
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 16:8

ታጹዋ... ቃና
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የኤፍሬም ነገድ ርስት ነበር
ኤፍሬም የያዘው ምድር የተገለጸው ቋሚ ሀብታቸው አድርገው እንደተቀበሉት ተደርጎ ነበር። "የኤፍሬም ነገድ ርስቱ አድርጎ የተቀበለው ምድር ይህ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በየጎሳው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ኢያሱ ለጎሳቸው የሰጠው" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የተመረጡ ከተሞች
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ኢያሱ የመረጣቸው ከተሞች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በምናሴ ጎሳ ውርስ ውስጥ
የምናሴ ነገድ የያዙት ምድር የተገለጸው እንደ ቋሚ ሀብታቸው አድርገው እንደተቀበሉት ተደርጎ ነው። "የምናሴ ነገድ ርስቱ አድርጎ በተቀበለው ምድር ውስጥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 16:10

እስከ ዛሬ ድረስ
ይህ የሚያመለክተው ጸሐፊው ይህንን መጽሐፍ እስከ ጻፈበት ጊዜ ድረስ ያለውን ወቅት ነው

ይህ ህዝብ የጉልበት ስራ እንዲሰራ ይገደድ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እስራኤላውያን እነዚህን ሰዎች ባሪያ ሆነው እንዲያገለግሉ ያስገድዷቸው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 17

1 ለምናሴ ነገድ የተመደበው ይህ ነበር፤ እርሱም የዮሴፍ በኩር ነበር። የምናሴም በኩር የገለዓድ አባት ማኪር ራሱም የገለዓድ አባት ነበር። የማኪርም ወገኖች
የገለዓድና የባሳን ምድር ተሰጣቸው ምክንያቱም ማኪር የጦር ሰው ነበርና። 2 ለቀሩት ለምናሴ ልጆች በየወገኖቻቸው ለአቢዔዝር ልጆች፥ለኬሴግ ልጆች
ለአሥሪኤል ልጆች፥ ለሴኬም ልጆች፥ ለአፌር ልጆች፥ልሸሚዳ ልጆች ተሰጣቸው። የዮሴፍ ልጅ የምናሴ ወንዶች ልጆች በየወገኖቻቸው የተሰጣቸው እነዚህ
ናቸው። 3 ለምናሴ ልጅ፥ ለማኪር ልጅ፥ ለገለዓድ ልጅ፤ ለኦፌር ልጅ፥ ለሰለጰዓድግን ሴቶች ልጆች እንጂ ወንዶች ልጆች አልነበሩአቸውም የሴቶች ልጆቹም ስም
ማህለህ፥ ኑዓ፥ ዔግላ፥ ሚልካ፥ ቲርጻ ነበረ። 4 እነርሱም ወደ ካህኑ ወደ አልዓዛር፥ ወደ ነዌ ልጅ ወደ ኢያሱና ወደ አለቆች ቀርበው እንዲህ አሉ፦ እግዚአብሔርም
ሙሴን ከወንድሞቻችን ጋር ርስት እንዲሰጠን አዝዞ ነበር። ስለዚህ ትእዛዙን በመከተል በአባታቸው ወንድሞች መካከል ለእነዚያ ሴቶች ርስት ሰጣቸው። 5
በዮርዳኖስ ማዶ ካለው በገለዓድና በባሳን ምድር ለምናሴ አሥር የመሬት መደቦች ተመድቦ ነበር፤ 6 ምክንያቱም የምናሴ ሴቶች ልጆች ከወንዶቹ ጋር ርስት
ተቀብለዋል። የገለዓድም ምድር ለቀሩት ለምናሴ ነገድ ተመደበ። 7 የምናሴም የድንበር ክልል ከአሴር ጀምሮ በሴኬም ፊት ለፊት እስካለው እስከ ሚክምታት
ደረስ ደረሰ። ድንበሩም በምዕራብ በኩል ወደ ታጹዋ ምንጭ አጠገብ ወደሚኖሩ ሰዎች አለፈ። 8 (የታጹዋ ምድር ለምናሴ ነበረ፤ በምናሴ ዳርቻ ያለው ታጹዋ
ከተማ ግን ለኤፍሬም ነገድ ሆነ።) 9 ድንበሩም ወደ ቃና በኩል ወደ ታች ወረደ። እነዚህ ከወንዙ በስተደቡብ ያሉ ከተሞች በምናሴም ከተሞች መካከል
ለኤፍሬም ሆኑ። የምናሴም ድንበር በወንዙ በስተሰሜን በኩል ሆኖ በባሕሩ መጨራሻ ነበረ። 10 በደቡብ በኩል ያለው ለኤፍሬም ነበረ፥ በሰሜንም በኩል
ያለው ለምናሴ የነበረው ድንበሩ ባሕር ነበረ። በሰሜን በኩል ወደ አሴር፥ በምሥራቅ ም በኩል ወደ ይሳኮር ደረሰ። 11 በይሳኮርና በአሴር መካከል ቤት ሳንና
መንደሮችዋን፥ ይብልዓምንና መንደሮችዋን፥ ዶር ሰዎችንና መንደሮችዋን ፥ የዓይንዶር ሰዎችንና መንደሮችዋን፥ የታዕናክ ሰዎችንና መንደሮችዋን ፥ የመጊዶ
ሰዎችንና መደሮችዋን ፥ ሦስቱ ኮረብቶች ምናሴ ወረሳቸው። 12 ሆኖም የምናሴ ነገድ ግን እነዚህን ከተሞች ርስት አድርጎ ሊወስዳቸው አልቻሉም፤ ምክንያቱም
ከነዓናውያን በዚያ ምድር መኖራቸውን ቀጥለው ነበር። 13 የእስራኤልም ሕዝብ እየጠነከሩ በመጡ ጊዜ ከነዓናውያንን የጉልበት ሥራ እንዲሠሩ አደረጉአቸው፤
ነገር ግን ሙሉ በሙሉ ከምካከላቸው እንዲወጡ አላደረጉም ነበር። 14 ከዚያም የዮሴፍ ልጆች ኢያሱን እንዲህ ብለው ተናገሩ፦ እኛ ብዙ ሕዝብ ሆነን ሳለን፥
እግዚአብሔርም ባርኮን እያለ ለምን አንድ ክፍል፥ አንድም ዕጣ ብቻ ርስት አድርገህ ሰጠኸን? አሉት። 15 ኢያሱም እንዲህ አላቸው፦ በቁጥር ብዙ ሕዝብ
ከሆናችሁ፥ ወደ ዱር ወጥታችሁ በፌርዛውያንና በራፋይም ምድር ለራሳችሁ መንጥሩ። ተራራማውም የኤፍሬም አገር ጠብቦአችሁ እንደ ሆነ ይህንን አድርጉ።
16 የዮሴፍም ልጆች እንዲህ አሉ፦ '"ተራራማውም አገር አይበቃንም። ነገር ግን በሸለቆውም ውስጥ ለሚኖሩት፥ በቤት ሳንና በመንደሮችዋ በኢይዝራኤልም
ሸለቆ ለሚኖሩት ከነዓናውያን የብረት ሰርገሎች አላቸው።" 17 ከዚያም ኢያሱ ለዮሴፍ ልጆች መለሰላቸው፦ ለመሆኑ ለኤፍሬምና ለምናሴ እናንተ ብዙ ሕዝብ
ናችሁ፥ ጽኑም ኃይልም አላችሁ። አንድ ክፍል መሬት ብቻ ሊኖራችሁ አይገባም። 18 ተራራማውም አገር ለእናንተ ይሆናል። ዱር እንኳ ቢሆንም
ትመነጥሩአቸዋላችሁ፥ ለእናንተም እንዲሆኑ ታደርጋላችሁ። ከነዓናውያንም የብረት ሰረገሎች ያሉአቸውና ኃይለኞች ቢሆኑም ልታስለቅቁአቸው ትችላላችሁ።
ታሳድዳቸዋላችሁ አላቸው።

Joshua 17:1

በኩር እና እርሱ ራሱ ነበር
እዚህ ስፍራ "ራሱ" የሚለው የሚያጎላው ይንኑ ሰው ነው - ማኪር የምናሴ በኩር ነበር፣ እርሱ ራሱ የገለዓድም አባት ነበር። "እርሱ በኩርም ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ደጋጋሚ/ሪፍሌክቲቭ ተውላጠ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ማኪር...አቢዔዝር፣ ኬለግ፣ አሥሪኤል፣ ሴኬም፣ ኦፌር እና ሸሚዳ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ለማኪር ትውልዶች የገለዓድ እና ባሳን ምድር ተሰጣቸው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ኢያሱ የገለዓድን እና የባሳን ምድር ለማኪር ተውልዶች ሰጣቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሪቱ ተሰጠች... ለጎሳቸው ተሰጠች
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ኢያሱ ምድሪቱን አወረሰ... እናም ለጎሳቸው ሰጠ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 17:3

ሰለጰኣድ... ኦፌር... አልኣዛር
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ማህለህ፣ ኑዓ፣ ዔግላ፣ ሚልካ፣ እና ቲርጻ
እነዚህ የሴት ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእኛ ርስት ለመስጠት
ምድሪቱ የተገለጸችው ሰዎቹ በቋሚነት እንደሚወርሷት ተደርጎ ነው። "ለእኛ ጥቂት መሬት ርስት አድርጎ ለመስጠት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለእነዚያ ሴቶች ርስት ሰጣቸው
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ኢያሱ ለእነዚያ ሴቶች ርስት ሰጣቸው" ወይም 2) "አልዓዛር ለእነዚያ ሴቶች ርስት ሰጣቸው" የሚሉ ናቸው።

Joshua 17:5

አስር ቁራሽ መሬት ተሰጠ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ኢያሱ አስር ቁራሽ መሬት ሰጠ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አስር ቁራሽ
"አስር ክፍሎች/ድርሻ"

ርስት ተቀበሉ
ምድሪቱ የተገለጸችው እንደ ቋሚ ሀብት እንደተቀበሏት ተደርጎ ነው። "ምድሪቱን ርስት አድርገው ተቀበሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የገለዓደ ምድር ተሰጠች
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ኢያሱ የገለዓድን ምድር ሰጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Joshua 17:7

በስተ ደቡብ
በስተ ደቡብ በኩል

ሚክምታት... ታጸዋ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 17:9

ድንበሩ
"የምናሴ ምድር ድንበር"

ጅረት
በጣም ትንሽ ወንዝ

ቃና
የጅረት ስም (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በስተ ሰሜን አሴር ሊደረስ ይችላል
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) በስተ ሰሜን የምናሴ ምድር ዳርቻ እስከ አሴር ነገድ ምድር ሊደርስ ይችላል ወይም 2) አሴር ለመድረስ ወደ ሰሜን መጓዝ ይኖርበታል። "አሴር በስተ ሰሜን ይገኛል" ወይም "አሴር ለመድረስ ወደ ሰሜን መጓዝ ያስፈልጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ምስራቅ፣ ይሳኮር
ግሱ በፊተኛው ሀረግ ይገኛል። "በስተ ምስራቅ፣ ወደ ይሳኮር ሊደረስ ይቻላል" (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 17:11

ቤትሳን... ይብልዓም... ዶር... ታዕናክ... መጊዶ... ናፎት
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 17:14

የዮሴፍ ትውልዶች
ይህ የኤፍሬም እና ምናሴን ነገዶች ያመለክታል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ ባርኮን ሳለ...ለምን አንድ ብቻ ሰጠኸን?
የኤፍሬም እና የምናሴ ነገድ ሰዎች ይህንን ጥያቄ የጠየቁት ኢያሱ ለእነርሱ ተጨማሪ መሬት መስጠት እንደሚገባው አጽንኦት ለመስጠት ነው። "ያህዌ ባርኮናልና...ከአንድ በላይ ልትሰጠን ይገባ ነበር።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ እጅ መሬትና ርስት የሚሆን ድርሻ/አንድ ክፍል
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። በሁለተኛው ሀረግ፣ ምድሩ የተገለጸው ህዝቡ ቋሚ ሀብት አድርጎ እንደተቀበለው ነው። " አንድ እጅ መሬት የእኛ ርስት ተደርጎ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም እና ዘይቤያዊ አነጋጋር የሚሉትን ይመልከቱ)

ድርሻ
ክፍል

ህዝቡ በቁጥር ብዙ
"ብዙ ህዝብ"

እናንተ በቁጥር ብዙ ህዝብ ከሆናችሁ
"በቁጥር ብዙ ህዝብ እስከ ሆናችሁ ድረስ"

ራፋይም
የአንድ ቡድን ሰዎች የወል ስም። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 17:16

ቤት ሳን... ኢይዝራኤል
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የዮሴፍ ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ትውልዶችን ነው። "የዮሴፍ ትውልዶች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት)

ትመነጥሩታላችሁ
"የዱሩን ዛፎች ትመነጥራላችሁ" ወይም "ዛፎቹን ትቆርጣላችሁ/ ትመነጥራላችሁ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 18

1 የእስራኤል ልጆች ማኅበር ሁሉ በሴሎ ተሰበሰቡ። በዚያም የመገናኛውን ድንኳን ተከሉ፤ ምድሩም ጸጥ ብሎ ተገዛላቸው። 2 ከእስራኤልም ልጆች መካከል
ያልተካፈሉ ሰባት ነገዶች ቀርተው ነበር። 3 ኢያሱም ለእስራኤል ሰዎች አላቸው፦ የአባቶቻቸሁ እግዚአብሔር አምላክ የሰጣችሁን ምድር ትወርሱ ዘንድ እስከ
መቼ ድረስ ቸል ትላላችሁ? 4 ከየነገዱም ሦስት ሦስት ሰዎች ምረጡ፥ እኔም እልካቸዋለሁ። ተነሥተውም የምድሪቱን ላይና ታች ይለካሉ። እንደ ርስታቸውም
መጠን ይጽፉታል፤ ወደ እኔም ይመለሳሉ። 5 በሰባትም ክፍል ይከፍሉታል። ይሁዳም በደቡብ ድንበር ባሉበት ይጸናሉ፤ የዮሴፍ ወገኖች በሰሜን በኩል
በዳርቻው ውስጥ ይቀጥላሉ። 6 እናንተም ምድሪቱን በሰባት ክፍል ትጽፋላችሁ፥ የጻፋችሁትንም ወደ እኔ ታመጣላችሁ፤ በአምላካችንም በእግዚአብሔር ፊት
ዕጣ አጣጥላችኋለሁ። 7 ለሌዋውያንም ርስት የላቸውም፤ የእግዚአብሔር ክህነት ርስታቸው ነውና። የጋድም፥ የሮቤልም፥ የምናሴም ነገድ እኩሌታ ከዮርዳኖስ
ማዶ ተቀበሉ።ይህም የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴ የሰጣቸው ርስታቸው ይህ ነው። 8 ሰዎችም ተነሥተው ሄዱ፤ ኢያሱም ምድሩን ሊጽፉ የሄዱትን እንዲህ ብሎ
አዘዛቸው፦ ሂዱ፥ በምድሩም ላይና ታች ዞራችሁ ጻፉት፥ ከዚያም ወደ እኔ ተመለሱ። በዚህም በሴሎ በእግዚአብሔር ፊት ዕጣ አጣጥላችኋለሁ። 9 ሰዎቹም
ሄደው ምድሩን ላይና ታች ዞሩ። እንደ ከተሞችም በሰባት ክፍል ከፈሉት፥ ዝርዝራቸውንም ጻፉት። ከዚያም ኢያሱ ወደ ሰፈረበት ወደ ሴሎ ተመለሱ። 10 ኢያሱም
በእግዚአብሔር ፊት በሴሎ ዕጣ አጣጠላቸው። በዚያም ኢያሱ ለእስራኤል ልጆች እንደ ክፍሎቻቸው ምድሩን አካፈለቸው። 11 የምድሩም ዕጣ ለብንያምም
ነገድ በየወገኖቻቸው ተሰጠ። የዕጣቸውም ዳርቻ በይሁዳ ልጆችና በዮሴፍ ልጆች መካከል ነበረ። 12 በሰሜን በኩል ድንብራቸው ከዮርዳኖስ ይጀራል።
ድንበሩም ወደ ኢያሪኮ ወደ ሰሜን በኩል፥በተራራማው አገር ወደ ምዕራብ ደረሰ። መውጫውም በቤት አዌን ምድረ በዳ ነብረ። 13 ድንበሩም ከዚያ በደቡብ
በኩል ቤቴል ወደምትባል ወደ ሎዛ አለፈ። ድንበሩም በታችኛው ቤት ሖሮን በደቡብ በኩል ባለው ተራራ ወደ አጣሮት አዳር ወረደ። 14 ድንበሩም ወደ ምዕራብ
ዘለቀ፥ በቤቶሮንም ፊት ለፊት ካለው ተራራ ወደ ደቡብ ይዞራል፤ መውጫውም ቂርታትይዓሪም በትባል በይሁዳ ልጆች ከተማ በቂርያት በኣል ነበረ፤ ይህ
የምዕራቡ ዳርቻ ነበረ። 15 የደቡብም ዳርቻ ከቂርያት ይዓሪም ውጪ ይጀምራል። ድንበሩም በምዕራብ በኩል ወደ ነፍቶ ውኃ ምንጭ ሄደ። 16 ድንበሩም በበን
ሄኖም ሸለቆ ፊት ለፊት ወዳለው ተራራ መጨረሻ ወረደ፥ እርሱም በራፋይም ሸለቆ በሰንን በኩል ነው፤ ወደ ሄኖም ሸለቆ ወደ ኢያቡስ ዳር በደቡብ በኩል ወረደ፥
ወደ ዓይን ሮጌልም ወረደ። 17 ወደ ሰሜንም ዞረ፤ በኢን ሳሚስ አቅጣጫ በአዱሚም ዐቀበት ፊት ለፊት ወዳለው ወደ ጌሊሎትወጣ፤ ከዚያሜ ወደ ሮቤ ልጅ
ወደ ቦሀን ድንጋይ ወረደ፤ 18 በሰሜንም ወገን ወደ ዓረባ አጠገብ አለፈ፥ ወደ ዓረባም ወረደ። 19 ድንበሩም ወደ ቤት ሖግላ ወደ ሰሜን በኩል አለፈ።
መውጫውም በዮርዳንስ መጨረሻ በደቡብ በኩል ባለው በጨው ባሕር ልሳን አጠገብ ነበር፥ ይህም የደቡቡ ዳርቻ ነበረ። 20 በምሥራቅም በኩል ድንበሩ
ዮርዳኖስ ነበረ። ይህ በዙሪያቸው ዳርቻ በየወገኖቻቸው የብንያም ልጆች ርስት ነበረ። 21 የብንያምም ልጆች ነገድ ከተሞች በየወገኖቻችቸው እነዚህ ነበሩ፦
ኢያሪኮ፥ ቤት ሖግላ፥ ዓመቀጺጽ፥ 22 ቤት ዓረባ፥ ዘማራይም፥ ቤቴል፥ 23 ዓዊም፥ ፋራ፥ ኤፍራታ፥ 24 ክፊርዓሞናይ፥ ዖፍኒ፣ ጋባ፤ አሥራ ሁለት ከተሞችና
መንደሮቻቸው። 25 ገባዖን፥ ራማ፥ ብኤሮት፥ 26 ምጽጳ፥ ከፊራ፥አሞቂ፥ 27 ፍርቄም፥ይርጵኤል፥ ተርአላ፥ 28 ፅላ፥ ኤሌፍ፥ ኢየሩሳሌም የምትባልየኢያቡስ
ከተማ፥ ቂርያትጊብዓት፤ አሥራ ሦስት ከትሞችና መንደሮቸችው። የብንያም ልጆች ርስት በየወገኖቻቸው ይህ ነበረ።

Joshua 18:1

እነርሱም ምድሪቱን ያዙ
የመገናኛ ድንኳኑን ከመትከላቸው አስቀድሞ በምድሪቱ የሚኖሩ ሰዎችን ማረኩ። "ምድሪቱን ከማረኩ በኋላ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የትዕይንቶች ቅደም ተከተል የሚለውን ይመልከቱ)

ርስት ያልተሰጣቸው
ነገዶቹ የሚቀበሉት መሬት የተገለጸው በቋሚነት እንደተቀበሉት ሀብት ተደርጎ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ኢያሱ ርስት አድርጎ መሬት ላልሰጣቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

Joshua 18:3

የሰጣችሁን... እስከ መቼ ቸል ትላላችሁ
ኢያሱ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው እስራኤላውያን ምድሪቱን ለመውረስ እንዲነሳሱ ለማበረታታት ነው። "የሰጣችሁን ... ለረጅም ጊዜ፣ ቸል ብላችኋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የላይኛውን እና የታችኛውን ምድር
"ላይኛው እና ታችኛው" የሚሉት ቃላት በየአቅጣጫው የሚል ትርጉም አላቸው።ይህንን በኢያሱ 18፡4 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።"በምድሪቱ በሁሉም አቅጣጫ" ወይም "በምድሪቱ በሙሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይገባናል የሚሉትን የርስት ድርሻ ይጻፉ
ይህ ማለት እያንዳንዱ ነገድ የሚቀበለውን የርስት ድርሻ ይገልጻል ማለት ነው

ውርሳቸው
ሄደው የሚመለከቱት ምድር የተገለጸው እያንዳንዱ ነገድ እንደ ቋሚ ሀብት የሚወርሰው ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 18:5

አጠቃላይ መረጃ፡
ኢያሱ ለእስራኤል ልጆች የሚያደርገውን ንግግር ቀጠለ

እነርሱ ይከፋከሉታል
"እነርሱ ምድሩን ይከፋፈላሉ"

ይሁዳ ይቀራል
"የይሁዳ ነገድ ይቀራል"

የዮሴፍ ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የዮሴፍን ትውልዶችን ነው። ይህ ሀረግ የኤፍሬምን እና ምናሴን ነገዶች ያመለክታል። "የኤፍሬም እና የምናሴ ትውልዶች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

Joshua 18:7

አጠቃላይ መረጃ፡
ኢያሱ ለእስራኤል ልጆች የሚያደርገውን ንግግር ቀጠለ

ምንም ድርሻ
"አንዳች የመሬት ድርሻ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የያህዌ ካህን መሆናቸው የእነርሱ ርስት ነው
ኢያሱ ሌዋውያን ያህዌን በክህነት በማገልገል ያላቸውን ታላቅ ክብር ርስት አድርገው እንደሚወርሱት ነገር አድርጎ ይናገራል። "እነርሱ ያላቸው ድርሻ የያህዌ ካህን መሆን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የምናሴ ግማሽ ነገድ
"የምናሴ ነገድ ግማሹ"

ርስታቸውን ተቀበሉ
ነገዱ የተቀበለው መሬት የተገለጸው ቋሚ ሀብታቸው አድርገው እንደተቀበሉት ነው። "ምድሪቱን ርስታቸው አድርገው ተቀበሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 18:8

አጠቃላይ መረጃ:
ኢያሱ ወደ ምድሪቱ ለሚሄዱ ለሃያ አንዱ ሰዎች ተናገረ

በምድሪቱ ላይ እና ታች
"ላይኛው እና ታችኛው" የሚሉት ቃላት በየአቅጣጫው የሚል ትርጉም አላቸው።ይህንን በኢያሱ 18:4 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።"በምድሪቱ በሁሉም አቅጣጫ" ወይም "በምድሪቱ በሙሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 18:10

ለእያንዳንዱ ድርሻው የሆነው ርስት ተሰጠው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ኢያሱ ለእያንዳንዱ ነገድ ከምድሪቱ ድርሻ ድርሻውን ሰጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 18:11

በይሁዳ እና በየዮሴፍ ትውልዶች መሃል
"የይሁዳ ትውልዶች ርስት በሆነው ምድር እና የዮሴፍ ትውልዶች ርስት በሆነው ምድር መሃል"

የዮሴፍ ትውልዶች
ይህ የሚያመለክተው የኤፍሬምንና የምናሴን ትውልዶች ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ቤት አቄን
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 18:13

ድንበሩ... ዳርቻው
ይህ አንድ አይነት ነገርን ያመለክታል።

ሎዛ... አጣሮት አዳር... ቤት ሖሮን... ቂርያት በኣል... ቂርያት ይዓሪም
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 18:15

ቂርያት ይዓሪም...ኤፍሮን...ነፍቶ...ቤን ሄኖን... ራፋይም... ሂኖም... ዓይን ሮጌል
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 18:17

ኢን ሳሚስ... ጌሊሎት...አዱ ሚም...ቤት ዐረባ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የቦሀን ድንጋይ
ይህ ምናልባት አንድ ሰው ለድንበር ምልክትነት ያስቀመጠው፣ በዚያ ቦሃን በተባለ ሰው ስም የተሰየመ ትልቅ ድንጋይ ሊሆን ይችላል። ይህንን በኢያሱ 15:6 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የቤት ዓረባ ትከሻ
የመሬቱ አቀማመጥ በስላች መልክ ወይም በጉብታ በመሆኑ ትከሻ እንደሆነ ተደርጎ ተገጽዋል። "የቤተ ዓረባ ስላች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 18:19

የቤት ሓግላን ሰሜናዊ ትከሻ
የመሬቱ አቀማመጥ በስላች መልክ ወይም በጉብታ በመሆኑ ትከሻ እንደሆነ ተደርጎ ተገጽዋል። "የቤተ ሓግላን ስላች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ቤትሖግላ
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የብንያም ነገድ ርስት ነበር
የብንያም ነገድ የተቀበለው ምድር የተገለጸው ቋሚ ሀብታቸው አድርገው እንደተቀበሉት ተደርጎ ነው። "የብንያም ነገድ እንደ ርስት አድርጎ የተቀበለው ምድር ይህ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የተሰጠው በየጎሳው ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ኢያሱ ለእያንዳንዱ ጎሳ ይህን ሰጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 18:25

አጠቃላይ መረጃ:
ጸሐፊው በምድሪቱ የነበሩትን የብንያም ነገዶች ርስት አድርገው የተቀበሏቸውን ከተሞች መዘርዘሩን ቀጠለ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የብንያም ርስት ነበር
የብንያም ነገድ የተቀበለው ምድር የተገለጸው ቋሚ ሀብታቸው አድርገው እንደተቀበሉት ተደርጎ ነው። "የብንያም ነገድ እንደ ርስት አድርጎ የተቀበለው ምድር ይህ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 19

1 ሁለተኛውም ዕጣ ለስምዖን ልጆች ነገድ በየወገኖቻቸው ወጣ። ርስታቸውም በይሁዳ ልጆች ርስት መካከል ነበረ። **2** እነርዚህም ርስታቸው ሆኑላቸው፤ ቤርሳቤህም ሤባ፥ሞላዳ፥ **3** ሐጸርሹዕል፥ ባለ፥ዔጼም፥ **4** ኤልቶላድ፥ በቱል፥ ሔርማ፥ ጺቅላግ፥ **5** ቤትማርካቦት፥ ሐጸርሱሳ፥ **6** ቤተ ለባኦት፥ ሻሩሔን፤ አሥራ ሦስት ከተሞችና መንደሮቻቸው። **7** ዓይን፥ ሪሞን፥ ዔቴር፥ ዓሻን፤ አራት ከተሞችና መንደሮቻቸው፤ **8** እስከ ባዕላት ብኤርና እስከ ደቡቡ ራማት ድረስ በእነዚህ ከተሞችና ዙሪያ ያሉ መንደሮች ሁሉ። የስምዖን ልጆች ነገድ ርስት በየወገኖቻቸው ይህ ነበረ። **9** ከይሁዳ ልጆች ክፍል የስምዖን ልጆች ርስት ሆነ። የይሁዳም ልጆች ዕድል ፈንታ ስለ በዛባቸው የስምዖን ልጆች በርስታቸ መካከል ወረሱ። **10** ሦስተኛውም ዕጣ ለዛብሎን ልጆች በየወገኖቻቸው ወጣ። የርስታቸውም ድንበር ወደ ሣሪድ ደረሰ። **11** ድንበራቸውም በምዕራብ በኩል ወደ መርዓላ ወጣ፥ እስከ ደባሼትም ደረሰ፤ በዮቅንዓም ፊት ለፊት ወዳለው ወንዝ ደረሰ። **12** ከሣሪድም ወደ ፀሐይ መውጫ ወደ ምሥራቅ ወደ ኪስሎት ታቦር ዳርቻ ዞረ። ወደ ዳብራትም ወጣ፥ ወደ ያፊዓም ደረሰ። **13** ከዚያም በምሥራቅ በኩል ወደ ጋትሔፍርና ወደ ዒታቃጺን አለፈ፥ ወደ ሪሞንና ወደ ኒዓ ወጣ። **14** ድንበሩም በሰሜን በኩል ወደ ሐናቶን ዞረ፥ መውጫውም በይፍታሕኤል ሸለቆ ነበረ። **15** ቀጣት፥ ነህላል፥ ሺምሮን፥ ይዳላ፥ ቤተ ልሔም፤ አሥራ ሁለት ከተሞችና መንደሮቻቸው። **16** የዛብሎን ልጆች ርስት በየወገኖቻቸው እነዚህ ከተሞችና መንደሮቻቸው ናቸው። **17** አራተኛውም ዕጣ ለይሳኮር ልጆች በየወገኖቻቸው ወጣ። **18** ድንበራቸውም ወደ ኢይዝራኤል፥ወደ ከስሎት፥ወደ ሱነም፥ **19** ወደ ሐፍራይም፥ ወደ ሺአን፥ ወደ አናሐራት፥ **20** ወደ ረቢት፥ ወደ ቂሶን፥ ወደ አቤጽ፥ **21** ሬሜት፥ ወደ ዓይንጋቢም፥ ወደ ዓይንሐዳ፥ ወደ ቤት ጳጼጽ ደረሰ፤ ድንበሩም ወደ ብቦርና ወደ ሻሕጽይማ፥ ወደ ቤት ሳሚስ ደረሰ። **22** የድንበራቸውም መውጫ ዮርዳኖስ ነበረ፤ አሥራ ስድስት ከተሞችና መንደሮቻቸው። **23** የይሳኮር ልጆች ነገድ ርስት በየወገኖቻቸው እነዚህ ከተሞችና መንደሮቻቸው ናቸው። **24** አምስተኛውም ዕጣ ለአሴር ልጆች ነገድ በየወገኖቻቸው ወጣ። **25** ድንበራቸውም ሔልቃት፥ ሐሊ፥ ቤጤን፥ አዚፍ፥ አላሜሌክ፥ ዓምዓድ፥ ሚሸአል ነበረ፤ **26** በምዕራብ በኩል ወደ ቀርሜሎስና ወደ ሺሖርሊብናት ደረሰ። **27** ወደ ፀሐይም መውጫ ወደ ቤት ዳጎን ዞረ፥ወደ ዛብሎንም ወደ ይፍታሕኤል ሸለቆ፥ በሰሜን በኩል ወደ ቤት ዓሜቅና ወደ ንዒኤልም ደረሰ፤ በስተ ግራ ቡልም ወደ ካቡል ወጣ። **28** ከዚያም ወደ ዔብሮን፥ ወደ ረአብ፥ ወደ ሐሞን፥ ወደ ቃና እስከ ታላቁ ሲኖናም ደረሰ። **29** ድንበርም ወደ ራማ፥ ወደ ተመሸገውም ከተማ ወደ ጢሮስ ዞረ፤ ድንበሩም ወደ ሖሳ ዞረ፤ መውጫውም በአክዚብ በኩል ወደ ባሕሩ ነበረ፤ **30** ዑማ፥ አፌቅ፥ ረአብ ደግሞ ነበሩ። እነዚህም ሀያ ሁለት ከተሞችና መንደሮቻቸው። **31** የአሴር ልጆች ነገድ ርስት በየወገኖቻቸው ከተሞችና መንደሮቻቸው ናቸው። **32** ስድስተኛውም ዕጣ ለንፍታሌም ልጆች በየወገኖቻቸው ወጣ። **33** ድንበራቸውም ከሔሌፍ፥ ከጸዕነኒም ዛፍ፥ ከአዳሚኔቄብ፥ ከየብኒኤል እስከ ለቄም ድረስ ነበረ፤ መውጫውም በዮርዳኖስ ነበረ። **34** ድንበሩም ወደ ምዕራብ ወደ አዝኖት ታቦር ዞረ፥ ከዚያም ወደ ሑቆቅ ወጣ፤ከዚያም በደቡም በኩል ወደ ዛብሎን፥ በምዕራብ በኩል ወደ አሴር፥ በዮርዳስም ወንዝ በፀሐይ መውጫ ወደ ይሁዳ ደረሰ። **35** የተመሸጉትም ከትሞች እነዚህ፦ ነበሩ ጺዲም፥ ጼር፥ ሐማት፥ ረቃት፥ ኬኔሬት፥ **36** አዳማ፥ ራማ፥ አሶር፥ **37** ቃዴስ፥ኤድራይ፥ ዓይንሐጽር፥ ይርአን፥ **38** ሚግዳልኤል፥ ሖሬም፥ ቤት ዓናት፥ ቤት ሳሚስ፤ አሥራ ዘጠኝ ከተሞችና መንደሮቻቸው ያልተቆጠሩ። **39** የንፍታሌም ልጆች ነገድ ርስት በየወገኖቻቸው እነዚህ ከተሞችና መንደሮቻቸው ናቸው። **40** ሰባተኛውም ዕጣ ለዳን ልጆች ነገድ በየወገኖቻቸው ወጣ። **41** የርስታቸውም ዳርቻ ይህ ነበረ፤ ጾርዓ፥ ኤሽታኦል፥ ዒርሼሜሽ፥ **42** ሸዕለቢን፥ ኤሎን፥ ይትላ፥ ኤሎን፥ **43** ተምና፥አቃሮን፥ **44** ኢልተቄ። ገባቶን።ባዕላት፥ ይሁድ፥ **45** ብኔንርቅ፥ ጋትሪሞ፥ **46** ሜያርቆን፥ በኢዮጴ ፊት ለፊት ካለው ዳርቻ ጋር ራቆን። **47** የዳንም ልጆች ዳርቻ አልበቃቸውም፥ የዳንም ልጆች ከሌሼም ጋር ለዋጉ ወጡ፥ ያዙአትም፥ በሰይፍም ስለመቱአት፥ ወረሱአትም፥ ተቀመጡባትም። ስምዋንም በአባቶታቸው በዳን ስም ዳን ብለው ጠርአት። **48** የዳን ነገድ ርስት በየወገኖቻቸ እነዚህ ከትሞችና መንደሮቻቸው ናቸው። **49** ምድሩንም ሁሉ በየድንበሩ ርስት እንዲሆን ከፍለው ከጨረሱ በኋላ፥ የእስራኤል ልጆች ለነዌ ልጅ ለኢያሱ በመካከላቸው ርስት ሰጡት። **50** በኤፍሬም ተራራማ አገር ያለችውን ተምናሴራ የምትባለውን የፈለጋትን ከተማ እንደ እግዚአብሔር ትእዛዝ ሰጡት። ከተማውንም እንደ ገና ሠርቶ ተቀመጠበት። **51** ካህኑ አልዓዛር፥ የነዌም ልጅ ኢያሱ፥ የእስራኤልም ነገዶችና የአባቶች አለቆች በእግዚአብሔር ፊት በሴሎ በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ አጠገብ በዕጣ የተካፈሉት ርስት ይህ ነው። የምርሪቱንም ማከፋፈል ሥራ ጨረሱ።

Joshua 19:1

ሁለተኛው ዕጣ ሲጣል ለስምዖን ወጣ
"ኢያሱ ለሁለተኛ ጊዜ ዕጣ ሲጥል፣ ዕጣው የስምዖንን ነገድ አመለከተ"

ሁለተኛው
በዝርዝር ውስጥ ሁለተኛው ቁጥር (ተከታታይ ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

በየጎሳ በየጎሳው
"ኢያሱ ምድሪቱን ለእያንዳንዱ ጎሳ ሰጠ"

ውርሳቸው በይሁዳ ነገድ ርስት መሃል የሚገኝ ነበር።
ምድሪቱ የተገለጸችው ነገዶቹ በቋሚነት የተቀበሏት ሃብት ተደርጋ ነው። "ርስት አድርገው የተቀበሉት ምድር የይሁዳ ነገድ ርስት አድርገው በተቀበሉት ምድር መሃል ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 19:5

አጠቃላይ መረጃ:
ጸሐፊው በምድሪቱ የነበሩትን የስምዖን ነገዶች ርስት አድርገው የተቀበሏቸውን ከተሞች መዘርዘሩን ቀጠለ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ጺቅላግ
የዚህችን ከተማ ስም በኢያሱ 15:31 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ

Joshua 19:8

ይህ የስምዖን ነገድ ርስት ነበር
የስምዖን ነገድ የተቀበሏቸው ምድር እና ከተሞች የተገለጹት ቋሚ ርስታቸው አድርገው እንደ ተቀበሉት ሀብት ተደርጎ ነው። "የስምዖን ነገድ ርስታቸው አድርገው የተቀበሏቸው ምድር እና ከተሞች እነዚህ ነበሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በየጎሳ በየጎሳው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ኢያሱ ለጎሳቸው የሰጣቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ለይሁዳ ነገድ ድርሻ ተደርጎ የተሰጠ ምድር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ኢያሱ ለይሁዳ ነገድ ድርሻ አድርጎ የሰጠው ምድር " በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የድርሻቸው መሃል
"የይሁዳ ምድር ድርሻ መሃል"

Joshua 19:10

ሦስተኛውን ዕጣ መጣል
ይህንን ሀረግ በኢያሱ 19:1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ

ሦስተኛው
በዝርዝር ውስጥ ሦስተኛው ቁጥር (ተከታታይ ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

ሣሪድ... መርዓላ... ደባሼት... ዮቅንዓም ከቅንዓም በተቃራኒ
"ቅንዓምን አቋርጦ"

Joshua 19:12

ሣሪድ...ኪስሎት ታቦር... ዳብራት... ያፊዓ... ጋት ሔፍር... ዒታ ቃጺን... ሪሞን... ነዓ
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 19:17

አራተኛውን ዕጣ መጣል
ይህንን ሀረግ በኢያሱ 19:1 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ

አራተኛው
በዝርዝር ውስጥ አራተኛው ቁጥር (ተከታታይ ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

ከስሎት... ሱነም... ሐፍራይም... ሺኦን... አናሐራት
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 19:20

ረቢት... ቂሶን... አቤጽ...ሬማት...ዓይን ጋኒም... ዓይን ሐዳ... ቤት ጳጼጽ... ሻሕጸማ
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ታቦር
ይህ የተራራ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 19:23

ይህ የይሳኮር ነገድ ርስት ነበር
የይሳኮር ነገድ የተቀበለው ምድር እና ከተማ የተገለጹት ቋሚ ርስት አድረገው እንደተቀበሏቸው ተደርጎ ነው። "ይህ የይሳኮር ነገድ ወርስ አድርጎ የተቀበለው ምድር እና ከተማዎች ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 19:24

አምስተኛውን ዕጣ መጣል
ይህንን ሀረግ በኢያሱ 19:1 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ

አምስተኛው
በዝርዝር ውስጥ አምስተኛው ቁጥር (ተከታታይ ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

ሔልቃት፣ ሐሊ፣ ቤጤን፣ አዚፍ፣ አላሜሌክ፣ ዓምዓድ፣ እና ሚሸአል... ሺሖር ሊብናት
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 19:27

ቤት ዳጎን...የይፍታሕ ኤል ሸለቆ... ቤት ዔሜቅ... ንዒኤል... ካቡል... አብዶን...ረአብ... ሑሞን...ቃና
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 19:29

ሖሳ... አክዚብ...ዑማ... አፌቅ...ረአብ
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 19:31

ሖሳ... አክዚብ...ዑማ... አፌቅ...ረአብ
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 19:32

ስድስተኛውን ዕጣ መጣል
ይህንን ሀረግ በኢያሱ 19:1 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ

ስድስተኛው
በዝርዝር ውስጥ ስድስተኛው ቁጥር (ተከታታይ ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

ሔሌፍ...ጸዕነኒም...አዳሚ ኔቄብ... የብኒኤል...ለቄም...አዝኖት ታቦር...ሑቆቅ
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 19:35

ጺዲም...ጼር... ሐማት... ረቃት... ኪኔሬት... አዳማ... ራማ... ሀዞር... ኤድራይ..ዓይንሐጾር
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሐማት
ይህ የሚገኘው በተመሳሳይ "ሐማት" ባለበት ሳይሆን፣ በገሊላ ባህር ምዕራብ የባህር ዳርቻ ነው።

Joshua 19:38

ይርኦን... ሚግዳል ኤል... ሖሬም... ቤት ዓናት
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይህ የንፍታሌም ነገድ ርስት ነበር
የንፍታሌም ነገድ የተቀበለው ምድር እና ከተማ የተገለጹት ቋሚ ርስት አድረገው እንደተቀበሏቸው ተደርጎ ነው። "ይህ ንፍታሌም ነገድ ወርስ አድርጎ የተቀበለው ምድር እና ከተማዎች ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባተኛውን ዕጣ መጣል
ይህንን ሀረግ በኢያሱ 19:1 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ

ሰባተኛው
በዝርዝር ውስጥ ሰባተኛው ቁጥር (ተከታታይ ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

የርስታቸው ግዛት/ክልል
የዳን ነገድ የተቀበለው ምድር የተገለጸው ቋሚ ርስት አድርገው እንደተቀበሉት ተደርጎ ነው። "የዳን ነገድ ወርስ አድርጎ የተቀበለው ርስት ግዛት/ክልል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)ጾርዓ፣ ኤሽታኦል፣ ዒር ሼሜሽ፣ ሸዕለቢን፣ ኤሎን፣ እና ይትላ እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 19:40

ሰባተኛውን ዕጣ መጣል
ይህንን ሀረግ በኢያሱ 19:1 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ

ሰባተኛው
በዝርዝር ውስጥ ሰባተኛው ቁጥር (ተከታታይ ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

የርስታቸው ግዛት/ክልል
የዳን ነገድ የተቀበለው ምድር የተገለጸው ቋሚ ርስት አድርገው እንደተቀበሉት ተደርጎ ነው። "የዳን ነገድ ወርስ አድርጎ የተቀበለው ርስት ግዛት/ክልል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)ጾርዓ፣ ኤሽታኦል፣ ዒር ሼሜሽ፣ ሸዕለቢን፣ ኤሎን፣ እና ይትላ እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 19:43

ኤሎን፣ ተምና፣ አቃሮን፣ ኢልተቄ፣ ገባቶን፣ ባዕላት፣ ይሁድ፣ ብኔ ብረቅ፣ ጋት ሪሞን፣ ሜያርቆን፣ እና ራቆን
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ኢዮጴን ተሻግሮ
"ከኢዮጴ በተቃራኒ" ወይም "ከኢዮጴ አጠገብ

Joshua 19:47

ሌሼም
ይህ የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የዳን ነገድ ርስት ነበር
የዳን ነገድ የተቀበለው ምድር እና ከተማ የተገለጹት ቋሚ ርስት አድረገው እንደተቀበሏቸው ተደርጎ ነው። "ይህ የዳን ነገድ ወርስ አድርጎ የተቀበለው ምድር እና ከተማዎች ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 19:49

ለነዌ ልጅ ለኢያሱ በመሃላቸው ርስት ሰጡት
ኢያሱ የተቀበላት ከተማ የተገለጸችው ቋሚ ርስቱ አድርጎ እንደተቀበላት ርስቱ ተደርጎ ነው። "በምድራቸው ርስት አድርገው ለነዌ ልጅ ለኢያሱ ከተማ ሰጡት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ተምና ሴራ
ይህ የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 19:51

የተሰጧቸው... ርስቶች እነዚህ ናቸው
የተለያዩ ነገዶች የተቀበሏቸው መሬት እና ከተሞች የተገለጹት ቋሚ ሀብት አድርገው እንደተቀበሏቸው ተደርጎ ነው። "ውርስ ተደርጎ የተሰጣቸው... ምድርና ከተሞች ድርሻቸው እነዚህ ናቸው።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 20

1 ከዚያም እግዚአብሔር ኢያሱን እንዲህ ብሎ ተናገረው፦ **2** ለእስራኤልም ልጆች እንዲህ ብለህ ተናገራቸው፡ **3** ሳያውቅም ሰውን የገደለ እንዲሸሸባቸው በሙሴ እጅ የነገርኋችሁን የመማፀኛ ከተሞችን ለዩ። እነዚህም ከተሞች ከተገደለበት ከማንኛውም ከደም ተበቃይ የሚሸሹበት ቦታ ይሆኑላችኋል። **4** ከእነዚህም ከተሞች ወደ አንዲቱ ይሸሻል፥ በከተማይቱም በር አደባባይ ቆሞ ለከተማይቱ ሽማግሌዎች ጉዳዩን ያስረዳል። እነርሱም ወደ ከተማይቱ ይቀበሉታል፥ የሚኖርበትንም ስፍራ ይሰጡታል። **5** ሰው የሞተበትም ደም ተበቃዩ መጥቶ ለመበቀል ቢሞክር፥ የከተማውም ሰዎች ሰውየውን ለከተማው ባለሥልጣናት አሳልፈው መስጠት አይኖርባቸውም። ይህን ማድረግ የማይገባቸው እርሱ የገደለው ከዚህ በፊት ጥላቻ ሳይኖርና ሆነ ብሎ ባለመሆኑ ነው። **6** በማኅበሩ ፊት ለፍርድ እስኪቆም ድረስ፥ በዚያን ጊዜ ያለው በሊቀ ካህንነት የሚያገለግለው እስኪሞት ድረስ በዚያች ከተማ ይቀመጥ። ከዚያም ወዲያ ነፍሰ ገዳዩ ፥ ሸሽቶ ከነበረበት ከተማ ወደ ከተማውና ወደ ቤቱ ይመለሳል። **7** በንፍታሌም ባለው በተራራማው አገር በገሊላ ቃዴስን፥ በኤፍሬምም ባለው በተራራማው አገር ኬብሮን የምትባለውን ቂርያትአርባቅን ለዩ። **8** ከዮርዳኖስም ማዶ ከኢያሪኮ ወደ ምሥራቅ ከሮቤል ነገድ በምድረ በዳው በደልዳላው ስፍራ ቦሶርን፥ ከጋድም ነገድ በገለዓድ ራሞትን፥ ከምናሴም ነገድ በባሳን ቶላንን ለዩ። **9** ማንም ሰው ሳያውቅ ሰውን የገደለ ወደዚያ እንዲሸሸና በመካከላቸውም ለሚቀመጥ መጻተኛ ለእስራኤል ልጆች ሁሉ የተመረጡ ከተሞች እነዚህ ናቸው። ይህም ሰው በማኅብሩ ፊት ለፍርድ እስኪቆም ድረስ በደም ተበቃዩ እጅ እንዳይሞት ነው።

Joshua 20:1

በሙሴ እጅ
እዚህ ስፍራ "የሙሴ እጅ" የሚለው የሚያመለክተው ሙሴ የጻፋቸውን መጽሐፍት ነው። "ሙሴ በጻፋቸው ነገሮች አማካይነት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሳየስበው በድንገት የገደለ
x

Joshua 20:4

እርሱ ይሸሻል
እዚህ ስፍራ "እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሳያውቅ እንድን ሰው የገደለን ሰው ነው።

ለከተማይቱ ሽማግሌዎች ጉዳዩን ያስረዳል
"ሰውየውን ሳያወቅ በድንገት እንደገደለው የከተማይቱን ሽማግሌዎች ያሳምናል/ያስረዳል"

ከዚይም እነርሱ እርሱን ይወስዱታል
"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሽማግሌዎችን ሲሆን "እርሱን" የሚለው የሚያመለክተው ሳያውቅ አንድን ሰው የገደለን ሰው ነው።

በእነርሱ መሃል ይኖራል
ይህ ሽማግሌዎችን ብቻ ሳይሆን፣ ከተማይቱን በጭምር ያመለክታል።

Joshua 20:5

የሟችን ደም መበቀል
እዚህ ስፍራ የአንድ ሰው የፈሰሰ ደም የሚለው የሚገልጸው መሞትን ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። ይህንን በኢያሱ 20:3 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። "የሞተውን ሰው መበቀል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ወዳጁን/ጎረቤቱን ሳያውቅ የገደለ...በድንገት ሰውየውን የገደለ
እነዚህ ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው

በጉባኤው ፊት ይቁም
ይህ ሀረግ የሚገልጸው ፍትህን በመፈለግ አብረውት በሚኖሩ ወገኖቹ ችሎት ፊት መቆምን ነው

Joshua 20:7

አጠቃላይ መረጃ:
በዚህ ክፍል ውስጥ በርካታ ስሞች አሉ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የዮርዳኖስ
ይህ የዮርዳኖስ ወንዝ አጭር ስም ነው

Joshua 20:9

በሌላ ሰው መገደል የለበትም
እዚህ ስፍራ "በእጅ" የሚለው ለአንድ ነገር ልዩ ምክንያት መሆን የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "መገደል የለበትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የፈሰሰውን ደም መበቀል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። ይህንን ሀረግ በኢያሱ 20:3 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። "የአንድን ሰው ሞት መበቀል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 21

1 ከዚያም የሌዋውያን ወገኖች አለቆች ወደ ካህኑ አልዓዘር፥ ወደ ነዌ ልጅ ኢያሱና ወደ እስራኤል ነገዶች አለቆች ቀርቡ። **2** እነርሱም በከነዓን ምድር ባለችው በሴሎ እንዲህ አሉአቸው፦ እግዚአብሔር በሙሴ እጅ የምንቀመጥባቸውንና ለከብቶቻችንም መሰማሪያ የሚሆኑ ከተሞች እንድትሰጡን አዞአችኋል። **3** ስለዚህም የእስራኤልም ሕዝብ በእግዚአብሔር ትእዛዝ የሚከተሉትን ከተሞች ለከብቶቻቸውም መሰማሪያ ጭምር እንዲሆኑ ርስታቸውን ለሌዋውያን ሰጡአቸው። **4** ለቀዓትም ወገኖች የዕጣው ውጤት እንዲህ ሆነ፦ ሌዋውያንም ለነበሩ ለካህኑ ለአሮን ልጆች፥ ከይሁዳ ነገድ ከስምዖንም ነገድ ከብንያምም ነገድ አሥራ ሦስት ከተሞች ተሰጣቸው። **5** ለቀሩትም ለቀዓት ልጆች ከኤፍሬም ነገድ፥ ከዳንም ነገድና ከምናሴ ነገድ እኽኩሌታ አሥር ከተሞች በዕጣ ተቀበሉ። **6** ለጌድሶንም ልጆች ከይሳኮር ነገድ፥ ከአሴር ነገድ፥ ከንፍታሌምም ነገድ፥ በባሳን ካለው ከምናሴ ነገድ እኩሌታ አሥራ ሦስት ከተሞች በዕጣ ተሰጣቸው። **7** ለሜራሪም ልጆች በየወገኖቻቸው ከሮቤል ነገድ፥ከጋድ ነገድና ከዛብሎን ነገድአሥራ ሁለት ከተሞ ተቀበሉ። **8** እግዚአብሔርም በሙሴ እጅ እንዳዘዛቸው የእስራኤል ልጆች እነዚህን ከተሞችና መሰማሪያቸውን ለሌዋውያን በዕጣ ሰጡ። **9** ከይሁዳም ልጆች ነገድ ከስምዖንም ልጆች ነገድ በስማቸው እነዚህን ከተሞች ሰጡ። **10** እነዚህ ከተሞች ከሌዊ ልጆች ነገድ የቀዓት ወገን ለሆኑ ለአሮን ልጆች ተሰጥቶአቸው ነበር። የመጀመሪያው ዕጣ ለእነርሱ ወጥቶላቸው ነበር። **11** እንደ ኬብሮን ተመሳሳይ ቦታ በይሁዳ ተራራማ አገር ያለችውን ቂርያት አርባቅ (ይህም አርባቅ የዔናቅ አባት ነበረ) የምትባለውን ከተማ በዙሪያዋም ያለውን የከብቶች መሰማሪያዋን ሰጡአቸው። **12** የከተማይቱንም እርሻ ግን መንደሮችዋንም ለዮፎኒ ልጅ ለካሌብ ርስት አድርገው ሰጡት። **13** ለካህኑም ለአሮን ልጆች ሳያውቁ ነፍሰ ገዳይ ለሆኑት መማፀኛ ከተማ የሆነችውን ኬብሮንንና መሰማሪያዋን፥ ልብናን ከመሰማሪያዋን ጋር ሰጡ፤ **14** የቲርንና መሰማሪያዋን፥ ኤሽት ሞዓንና መሰማሪያዋን፥ **15** ሖሎንንና መሰማሪያዋን፥ ዳቤርንና መሰማሪያዋን፥ **16** ዓይንንና መሰማሪያዋን፥ ዮጣንና መሰማሪያዋን፥ ቤት ሳሚስንና መሰማሪያዋን ሰጡ። ከእነዚህ ከሁለቱ ነገዶች ዘጠኝ ከተሞችን ነበሩ። **17** ከብንያምም ነገድ ገባዖንንና መሰማሪያዋን፥ ናሲብንና መሰማሪያዋን፥ **18** ዓናቶትንና መሰማሪያዋን፥ አልሞንንና መሰማሪያዋን፤አራት ከተሞችን ሰጡ። **19** ለአሮን ልጆች ለካህናት የተሰጡ ከተሞች ከመሰማሪያቸው ባጠቃላይ አሥራ ሦስት ከተሞች ናቸው። **20** ለቀሩትም ለቀዓት ልጆች ወገኖች ሌዋውያን የተሰጣቸ ከተሞች ከኤፍሬም ነገድ ዕጣ ወጥቶላቸው ነበር። **21** ለእነርሱም በኤፍሬም ተራራማ አገር ሳያውቁ ነፍሰ ገዳይ ለሆኑት መማፀኛ ከተማ የሆነችውን ሴኬምንና መሰማሪያዋን፥ ጌዝርንና መሰማሪያዋን፥ **22** ቂብጻይምንና መሰማሪያዋን፥ ቤት ሖሮንንና መሰማሪያዋን፤ አራቱን ከተሞች ሰጡአቸው። **23** ከዳንም ነገድ ኤልተቄንና መሰማሪያዋን፥ ገባቶንንና መሰማሪያዋን፥ **24** ኤሎንንና መሰማሪያዋን፥ ጋትሪሞንንና መሰማሪያዋን፤ አራቱን ከተሞች ሰጡአቸው። **25** ከምናሴም ነገድ እኩሌታ ታዕናክንና መሰማሪያዋን፥ ጋትሪሞንንና መሰማሪያዋን፤ ሁለቱን ከተሞች ሰጡአቸው። **26** ለቀሩት የቀዓት ልጆች ወገኖች የተሰጡ ከተሞች ሁሉ ከመሰማሪያቸውን ጋር አሥር ከተሞችናቸው። **27** ለሌሎች ሌዋውያንም ወገኖች ለጌድሶን ልጆች ከምናሴ ነገድ እኩሌታ ሳያውቁ ነፍሰ ገዳይ ለሆኑት መማፀኛ ከተማ በባሳን ውስጥ የሆነችውን ጎላንንና መሰማሪያዋን፥ በኤሽትራንና መሰማይያዋን ሁለቱን ከተሞች ሰጡአቸው። **28** ከይሳኮርም ነገድ ቂሶንንና መሰማሪያዋን፥ ዳብራትንና መሰማሪያዋን፥ **29** የያርሙትንና መሰማሪያዋን፥ ዓይንጋኒምንና መሰማሪያዋን፤ አራቱን ከተሞች ለጋሪሶን ነገድ ሰጡአቸው። **30** ከአሴርም ነገድ ሚሸአልንና መሰማሪያዋን፥ ዓብዶንና መሰማሪያዋን፥ **31** ሔልቃትንና መሰማሪያዋን፥ ረአብንና መሰማሪያዋን፤ አራቱን ከተሞች ሰጡአቸው። **32** ከንፍታሌምም ነገድ ሳያውቁ ነፍሰ ገዳይ ለሆኑት መማፀኛ ከተማ የሆነችውን በገሊላ ውስጥ ቃዴስንና መሰማሪያዋን፥ ሐሞትዶርንና መሰማሪያዋን፥ ቀርታንንና መሰማሪያዋን፤ ሦስቱን ከተሞች ለጌድሶን ነገድ ሰጡአቸው። **33** የጌድሶን ልጆች ከተሞች ሁሉ በየወገኖቻቸው ከመሰማሪያቸው ጋር አሥራ ሦስት ከተሞች ናቸው። **34** ከሌዋውያንም ለቀሩት ለሜራሪ ልጆች ወገን ከዛብሎን ነገድ ዮቅንዓምንና መሰማሪያዋን፥ ቀርታንና መሰማሪያዋን፥ **35** ዲሞናንና መሰማሪያዋን፥ ነህላልንና መሰማሪያዋን፤ አራቱን ከተሞች ሰጡ። **36** ለሜራሪ ነገድ ከሮቤልም ነገድ ቦሶርንና መሰማሪያዋን፥ ያህጽንና መሰምሪያዋን፥ **37** ቅዴሞትንና መሰማሪያዋን፥ ሜፍዓትንና መሰማሪያዋን፤ አራቱን ከተሞች ሰጡ። **38** ሳያውቁ ነፍሰ ገዳይ ለሆኑት መማፀኛ ከተማ የሆነችውን ከጋድም ነገድ በገለዓድ ውስጥ ራሞትንና መሰማሪያዋን፥ መሃናይምንማ መሰማሪያዋን ሰጡ። **39** ሐሴቦንንና መሰማሪያዋን፥ ኢያዜርንና መሰማሪያዋን ሜራሪ ነገድ ደግሞ የተሰጡ ባጠቃላይ አራት ከተሞች ናቸው። **40** ከሌዋውያን ወገኖች የቀሩት የሜራሪ ልጆች ከተሞች ሁሉ በየወገኖቻቸው እነዚህ ነበሩ፤ ዕጣቸውም ባጠቃላይ አሥራ ሁለት ከተሞች ነበሩ። **41** በእስራኤል ልጆች ርስት መካከል የነበሩት የሌዋውያን ከተሞች ሁሉ አርባ ስምንት ከተሞችና መሰማሪያቸው ነበሩ። **42** እነዚህም ከተሞች እያንዳንዳቸው ከመሰማሪያቸው ጋር ነበሩ፤ እነዚህም ከተሞች ሁሉ በዚህ ዓይነት መንገድ ነበሩ። **43** እግዚአብሔርም ይሰጣቸው ዘንድ ለአባቶቻቸው የማለላቸውን ምድር ሁሉ ለእስራኤል ሰጠ። ወረሱአትም፥ ተቀመጡባትም። **44** እግዚአብሔርም ለአባቶቻቸው እንደ ማለላቸው በዙሪያቸው ካሉት አሳረፋቸው። ከጠላቶቻቸውም ሁሉ ይቋቋማቸው ዘንድ ማንም ሰው አልቻለም፤ እግዚአብሔርም ጠላቶቻቸውን ሁሉ በእጃቸው አሳልፎ ሰጣቸው። **45** እግዚአብሔር ለእስራኤል ቤት ከተናገረው መልካም ነገር ሁሉ ተፈጸመ እንጂ ምንም አልቀረም።

Joshua 21:1

አልዓዛር... ነዌ
እነዚህ ስሞች የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእነርሱ አሏቸው
"ሌዋውያን ለእነርሱ አሏቸው"

ያህዌ እናንተን በሙሴ እጅ አዘዛችሁ
"በእጅ" የሚለው ሀረግ ያህዌ ትዕዛዙን ለመስጠት/ማቅረብ ሙሴን እንደተጠቀመበት የሚገልጽ ፈሊጣ አነጋገር ነው። "ያህዌ ያዛችሁ ዘንድ ሙሴን ተናገረው/ አዘዘው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 21:3

ተከታዮቹ ከተሞች
ይህ የሚያመለክተው በተከታዮቹ ቁጥሮች የሚዘረዘሩትን/የሚጸፉትን ከተሞች ነው።

Joshua 21:4

እጣ መጣል
ከመሪዎች ፍላጎት ውጭ በዕጣ ምርጫ የማድረግ ዘዴ ብዙውን ጊዜ የሚካሄደው እግዚአብሔር ውጤቱን ይወስን በሚል ሃሳብ ነው። ይህንን እንዴት በኢያሱ 19፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ቀዓታውያን
በዚህ ቡድን ውስጥ እነዚህ ካህናት የሌዊ ትውልድ የሆኑ የቀዓት ልጆች ነበሩ። ከእነርሱ ከፊሎቹም የአሮን ትውልድ፣ የቀዓት የልጅ ልጆች ነበሩ።

አስራ ሶስት ከተሞች... አስር ከተሞች
የከተሞች ቁጥር (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ግማሽ ነገድ
የነገዱ ግማሽ የተባለበት ምክንያት ቀሪው ግማሽ ርስታቸውን ዮርዳኖስን ወንዝ ከማቋረጣቸው አስቀድሞ ስተቀበሉ ነው።

Joshua 21:6

ጌርሶን
ጌርሶን ከሌዊ ልጆች አንዱ ነበር። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እጣ መጣል
ከመሪዎች ፍላጎት ውጭ በዕጣ ምርጫ የማድረግ ዘዴ ብዙውን ጊዜ የሚካሄደው እግዚአብሔር ውጤቱን ይወስን በሚል ሃሳብ ነው። ይህንን እንዴት በኢያሱ 19:1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

ሜራሪ
ሜራሪ ከሌዊ ልጆች አንዱ ነበር። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 21:8

ያህዌ በሙሴ እጅ አዘዘ
"በእጅ" የሚለው ሀረግ ትርጉሙ ያህዌ ሙሴን ትዕዛዙን ለማቅረብ ተጠቀመበት ማለት ነው። "ያህዌ ሙሴ እንዲያዝ ነገረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የቀዓታውያን ነገዶች
በዚህ ቡድን ውስጥ እነዚህ ካህናት የሌዊ ትውልድ የሆኑ የቀዓት ልጆች ነበሩ። ከእነርሱ ከፊሎቹም የአሮን ትውልድ፣ የቀዓት የልጅ ልጆች ነበሩ። ይህንን እንዴት በኢያሱ 19:1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

Joshua 21:11

አርባቅ የኤናቅ አባት ነበር
ይህ መረጃ የቂርያት አርባቅን ከተማ ስለ መሰረታት ሰው ስም የቀረበ የመረጃ ዳራ ነው። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

ዔናቅ
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ተራራማ አገር
ከተራሮች አነስ ያለ ተፈጥሯዊ ከፍታ ያለው ምድር

የግጦሽ መሬት/ የከብቶች መሰማሪያ
በሳር ወይም ለከብቶች ግጦሽ ተስማሚ በሆነ ተክል የተሸፈነ አካባቢ

የከተማይቱ መሰማሪያ
ብዙውን ጊዜ ተክሎች የሚገኙበት በከተማ ዙሪያ ሚገኝና የከተማይቱ ይዞታ የሆነ መሬት

መንደሮች
ብዙውን ጊዜ ከከተማ የሚያንስ፣ አነስተኛ ማህበረሰብ።

Joshua 21:13

ልብናን... ቲርናን... ኤሽትሞዓን... ሖሎን... ዳቤር... ዓይን... ዮጣን
እነዚህ ሁሉ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ዘጠኝ ከተሞች... ሁለት ነገዶች
በክፍሉ/ምንባቡ ውስጥ የከተሞች እና የነገዶች ቁጥር

Joshua 21:17

ከብንያም ነገድ ገባዖን ተሰጠ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የብንያም ነገድ ገባዖንን ሰጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ገባዖን... አናቶት... አልሞን
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አስራ ሶስት ከተሞች
"13 ከተሞች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 21:20

የቀዓት ነገዶች
በዚህ ቡድን ውስጥ እነዚህ ካህናት የሌዊ ትውልድ የሆኑ የቀዓት ልጆች ነበሩ። ከእነርሱ ከፊሎቹም የአሮን ትውልድ፣ የቀዓት የልጅ ልጆች ነበሩ። ይህንን እንዴት በኢያሱ 19:1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

የተሰጧቸው ከተሞች ነበሯቸው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ከተሞችን ተቀበሉ/ተሰጧቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ዕጣ መጣል
ከመሪዎች ፍላጎት ውጭ በዕጣ ምርጫ የማድረግ ዘዴ ብዙውን ጊዜ የሚካሄደው እግዚአብሔር ውጤቱን ይወስን በሚል ሃሳብ ነው። ይህንን እንዴት በኢያሱ 19:1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

ጌዝር... ቂብጻይምን... ቤት ሖሮን
የከተሞች ስሞች (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በጠቅላላው አራት ከተሞች
ይህ የሚያመለክተው የከተሞቹን ቁጥር ዝርዝር በአጠቃላይ ነው (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 21:23

ከዳን ነገድ፣ የቀዓት ነገድ ኤልተቄን ሰጧቸው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የዳን ነገድ ለቀዓት ኤልተቄን ሰጧቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የቀዓት ነገድ
በዚህ ቡድን ውስጥ እነዚህ ካህናት የሌዊ ትውልድ የሆኑ የቀዓት ልጆች ነበሩ። ከእነርሱ ከፊሎቹም የአሮን ትውልድ፣ የቀዓት የልጅ ልጆች ነበሩ። ይህንን ተመሳሳይ ሀረግ በኢያሱ 21:20 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ኤልተቄን... ገባቶን... ኤሎን....ጋት ሪሞን
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አራት ከተሞች
ይህ የከተሞቹን ቁጥር ያመለክታል። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 21:25

ከምናሴ ግማሽ ነገድ፣ የቀዓት ነገድ ታዕናክን ሰጧቸው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የምናሴ ነገድ እኩሌታ ለቀዓት ነገድ ታዕናክን ሰጧቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ታዕናክ... ጋት ሪሞን
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሁለት ከተሞች... አስር ከተሞች
የተመዘገቡ ከተሞች ቁጥር (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

የቀዓት ነገድ...የቀዓታውያን ነገዶች
በዚህ ቡድን ውስጥ እነዚህ ካህናት የሌዊ ትውልድ የሆኑ የቀዓት ልጆች ነበሩ። ከእነርሱ ከፊሎቹም የአሮን ትውልድ፣ የቀዓት የልጅ ልጆች ነበሩ። ይህንን በኢያሱ 21:2 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 21:27

ከምናሴ ነገድ አንስቶ፣ እስከ ጌርሶን ጎሳ ድረስ እነዚህም ሌሎች የሌዊ ጎሳዎቸ ነበሩ እነርሱም ጎላንን ሰጡ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የምናሴ ነገድ እኩሌታ፣ ሌሎች የሌዊ ነገዶች ከምናሴ ነገድ እኩሌታ ጎላንን ተቀበሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ጎላን... በኤሽትራ
የከተሞች ስሞች (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሌላውን ሳያውቅ የገደለ
ይህ የሚያመለክተው ሰውን ለመግደል ታስቦ ያልተደረገን ግድያ ነው

ሁለት ከተሞች
የከተሞች ቁጥር (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 21:28

ለጌርሶን ነገድም ቂሶን ሰጡ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የጌርሶን ነገድ ደግሞ ቂሶንን ተቀበሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ቂሶን... ዳብራት... የርሙት...ዓይን ጋኒም... ሚሸአል...ዓብዶን... ሔልቃት... ረአብ
የከተሞች ስሞች (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ከአሴር ነገዶች፣ ሚሸአልን ሰጡ ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ከአሴር ነገድ ሚሸአልን ተቀበሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በአጠቃላይ አራት ከተሞች
ይህ የሚያመለክተው የተመዘገቡ/የተዘረዘሩ ከተሞችን ዝርዝር ነው (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 21:32

ከንፍታሌም ነገድ ለጌርሶን ነገዶች ቃዴስን ሰጡ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የጌርሶን ከንፍታሌም ነገድ ቃዴስን ተቀበሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ጌርሶን
ይህ የሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሐሞት ዶር... ቀርታን
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በጠቅላላው አስራ ሶስት ከተሞች
"በጠቅላላው 13 ከተሞች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 21:34

ለተቀሩት ሌዋውያን- የሜራሪ ነገድ- ከዛብሎን ነገድ ድርሻ ዮቅናምን ሰጡ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የተቀሩት ሌዋውያን- የሜራሪ ነገድ- ከዛብሎን ነገድ ዮቅናምን ተቀበሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ሜራሪ
ይህ የሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ዮቅናም... ቀርታ...ዲሞና... ነህላል
የከተሞች ስሞች (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በአጠቃላይ አራት ከተሞች
ከተሞቹ በጠቅላላው የተጠቀሱት እንደ ቁጥር ነው። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 21:36

ለሜራሪ ነገዶች ከሮቤል ነገዶች ቦሶር ተሰጣቸው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የሜራሪ ነገዶች ከሮቤል ነገዶች ቦሶርን ተቀበሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አራት ከተሞች
ይህ የከተሞቹን ቁጥር ያመለክታል። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ቦሶር...ያሀጽ... ቅዴሞት... ሜፍዓት...ራሞት
የከተሞች ስሞች (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ከጋድ ነገድ ውስጥ ራሞት ተሰጣቸው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ከጋድ ነገድ ራሞትን ተቀበሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

መሃናይም
ይህ የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 21:39

የሜራሪ ነገዶችም ደግሞ ሐሴቦን ተሰጣቸው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የሜራሪ ነገድ ደግሞ ሐሴቦንን ተቀበሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሐሴቦን...ኢያዜር
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በአጠቃላይ አስራ ሁለት ከተሞች
"በአጠቃላይ 12 ከተሞች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በአጠቃላይ በዕጣ አስራ ሁለት ከተሞች ተሰጧቸው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እነዚህን አስራ ሁለት ከተሞች በዕጣ መጣል ተቀበሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ዕጣ መጣል
ከመሪዎች ፍላጎት ውጭ በዕጣ ምርጫ የማድረግ ዘዴ ብዙውን ጊዜ የሚካሄደው እግዚአብሔር ውጤቱን ይወስን በሚል ሃሳብ ነው። ይህንን እንዴት በኢያሱ 19:1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

Joshua 21:41

የሌዋውያን ከተሞች ከምድሪቱ መሃል የተሰጡ ናቸው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሌዋውያኑ ከተሞቻቸውን ከምድሪቱ መሃል ተቀበሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አርባ-ስምንት ከተሞች
"48 ከተሞች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 21:43

ማለ
"መሃላ ሰጠ"

ከጠላቶቻቸው አንዳቸውም ሊያሸንፏቸው አይችሉም
ሃሳቡን ለማጉላት ይህ የተገለጸው በአሉታ ነው። "እነርሱ ጠላቶቻቸውን ሁሉ አሸነፉ" (ምፀት/ላይዶክስ የሚለውን ይመልከቱ)

ጠላቶቻቸውን ሁሉ በእጆቻቸው አሳልፎ ሰጣቸው
እዚህ ስፍራ "በእጆቻቸው" የሚለው "ከጉልበታቸው ስር አደረጋቸው/ አንበረከከላቸው" ማለት ነው። "ጠላቶቻቸውን ሁሉ እንዲያሸንፉ ሃይል ሰጣቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት)

ያህዌ ለእስራኤል ቤት ቃል ከገባው መልካም ነገር ሁለ አንድ ነገር እንኳን ሳይፈጸም አልቀረም።
ሃሳቡን ለማጉላት ይህ የተገለጸው በአሉታ ነው። "ያህዌ ለእስራኤል ቤት የተናገረው እያንዳንዱ መልካም ቃል ኪዳን ተፈጸመ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምፀት/ላይዶክስ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 22

1 በዚያን ጊዜም ኢያሱ የሮቤል ልጆችንና የጋድ ልጆችን የምናሴንም ነገድ እኩሌታ ጠራቸው። 2 እንዲህም አላቸው፦ የእግዚአአብሔር አገልጋይ ሙሴ
ያዘዛችሁን ሁሉ ጠብቃችኋል፥ እኔም ላዘዝኋችሁ ነገር ሁሉ ታዝዛችኋል። 3 ይህንም ያህል ብዙ ጊዜ እስከ ዛሬ ድረስ ወንድሞቻችሁን አልተዋችሁም፥
የአምላካችሁንም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጠብቃችኋል። 4 አሁንም እግዚአብሔር አምላካችሁ እንደ ተናገራቸው ወድሞቻችሁን አሳርፎአቸዋል። አሁን እንግዲህ
ተመለሱ፥ ወደ ቤታችሁና የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴ በዮርዳኖስ ማዶ ወደ ሰጣችሁ ወደ ርስታችሁ ምድር ሂዱ። 5 የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴ
ያዘዛችሁን ትእዛዙንና ሕጉን ታደርጉ ዘንድ እግዚአብሔር አምላካችሁን ትወድዱ ዘንድ መንገዱንም ሁሉ ትሄዱ ዘንድ፥ ትእዛዙንም ትጠብቁ ዘንድ፥ ወደ እርሱም
ትጠጉ ዘንድ፥ በፍጹምም ልባችሁ በፍጹምም ነፍሳችሁ ታመልኩ ዘንድ ብቻ እጅግ ተጠንቀቁ። 6 ኢያሱም መረቃቸው፥ ሰደዳቸውም፤ ወደ ቤታቸውም ሄዱ። 7
ለምናሴም ነገድ እኩሌታ ሙሴ በባሳን ውስጥ ርስት ሰጥቶአቸው ነበር፤ ለቀረው እኩሌታው ግን ኢያሱ በዮርዳኖስ ማዶ በምዕብብ ወንን በወንድሞቻቸው
መካከል ርስት ሰጣቸው። ኢያሱም ወደ ቤታቸው በሰደዳቸው ጊዜ 8 እንዲህ ብሎ መረቃቸው፦ በብዙ ብልጥግና በእጅግም ብዙ ከብት፥ በብርም፥ በወርቅም፥
በናስም፥ በብረትም፥ በእጅግም ብዙ ልብስ ወደ ቤታችሁ ተመለሱ፤ የጠላቶቻችሁንም ምርኮ ከወንድሞቻችሁ ጋር ተካፈሉ። 9 የሮቤልም ልጆች የጋድም ልጆች
የምናሴም ነገድ እኩሌታ የእስራኤል ሕዝብ በከነዓን በሴሎ ትተው ወደ ቤታቸው ተመለሱ። በሙሴም እጅ በተሰጠ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ወደ ተቀበሉአት ወደ
ርስታቸው ወደ ገለዓድ ምድር ይገቡ ዘንድ ሄዱ። 10 በከነዓን ምድር ወዳለው ወደ ዮርዳኖስ አቅራቢያም በመጡ ጊዜ የሮቤል ልጆችና የጋድ ልጆች የምናሴም
ነገድ እኩሌታ በዚያ በዩርዳኖስ አጠገብ ታላቅ መሠዊያ ሠሩ። 11 ለእስራኤልም ልጆች፦ እነሆ፥ በከነዓን ምድር ዳርቻ በዮርዳኖስ አጠገብ ባለው ግዛት፥
የእስራኤል ልጆች ባሉበት ወገን፥ የሮቤል ልጆችና የጋድ ልጆች የምናሴም ነገድ እኩሌታ መሠዊያ ሠርውዋል፤ የሚል ወሬ ደረሰላቸው። 12 የእስራኤል ሕዝብ
ይህን በሰሙ ጊዜ የእስራኤል ልጆች ማኅበር ሁሉ ወጥተው እነርሱን ለዋጉ በሴሎ ተሰበሰቡ። 13 የእስራኤልም ልጆች በገለዓድ ምድር ወዳሉት ወደ ሮቤል
ልጆችና ወደ ጋድ ልጆች ወደ ምናሴም ነገድ እኩሌታ መልእክት ላኩ። የካህኑን የአልዓዛርን ልጅ ፊንሐስን ደግሞ ላኩ፥ 14 ከእርሱም ጋር አሥር አለቆች ነበሩ፥
ከእስራኤል ከነገዱ ሁሉ አንድ አንድ የአባቶች ቤት አለቃ እያንዳንዱም በእስራኤል አእላፋት መካከል የእየአባቶቻቸው ቤት አለቃ ነበሩ። 15 በገለዓድም ምድር
ወዳሉት ወደ ሮቤል ልጆችና ወደ ግድ ልጆች ወደ ምናሴም ነገድ እኩሌታ መጡ፥ እንዲህም ብለው ተናገሩአቸው፦ 16 የእግዚአብሔር ማኅበር ሁሉ የሚለው
ይህ ነው፦ ይህ በእስራኤል አምላክ ላይ ያደረጋችሁት ኃጢአት ምንድን ነው? ዛሬ እግዚአአብሔርን ከመከተል ተመልሳችኋል ዛሬም በራሳችሁ መሠዊያ
በመሥራታችሁ በእግዚአብሔር ላይ ዐምፃችኋል። 17 በፌጎር ያደረገነው ኃጢአታችን አይበቃምን? እስከ ዛሬም ድረስ ከዚያ ኃጢአት ራሳችንን አላነጸንበትም።
ከዚያም ኃጢአት የተነሣ በእግዚአብሔር ማኅበር ላይ መቅሠፍት ወረደ። 18 እናንተ ዛሬ እግዚአብሔርን ከመከተል መመለስ ይገባችኋልን? ዛሬ በእግዚአሔር
ላይ ብታምፁ ነገ በእስራኤል ማኅበር ሁሉ ላይ ይቆጣል። 19 የርስታችሁም ምድር የረከሰ ቢመስላችሁ የእግዚአብሔር ማደሪያ ወደ ሚቀመጥበት ወደ
እግዚአብሔር ርስት ምድር አልፋችሁ በመካከላችን ውረሱ። ከአምላካችንም ከእግዚአብሔር መሠዊያ ሌላ ለእናንተ መሠዊያ በመሥራታችሁ በእግዚአብሔርና
በእኛ ላይ አታምፁ። 20 የዛራ ልጅ አካን እርም ነገር በመውሰድ ኃጢአትን ስለ ሠራ በእስራኤል ማኅበር ሁሉ ላይ ቁጣ አልወረደምን? እርሱም በኃጢአት
ብቻውን አልሞተም። 21 ከዚያም የሮቤል ልጆችና የጋድ ልጆች የምናሴም ነገድ እኩሌታ ለእስራኤል አለቆች እንዲህ ብለው መለሱላቸው፦ 22 ሁሉን የሚችል
አምላክ እግዚአብሔር ታላቁ አምላክ እግዚአብሔር እርሱ ያውቃል፥ እስራኤልም እንዲያውቅ ያደርጋል! በእግዚአብሔር ላይ ዐምፀንና ተላልፈን እንደ ሆነ ዛሬ
አታድነን እግዚአሔርን ከመከተል እንድንመለስ፥ የሚቃጠለውን 23 መሥዋዕትና የእህልን ቁርባን እንድናሳርግበት፥ የደኅነኝትንም መሥዋዕት እንድናቀርብበት
ብለን መሠዊያ ሠርተን እንደ ሆነ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ ይበቀለን። 24 ይልቁንም ከልባችን ፍርሃት የተነሣ፦ በሚመጣው ዘመን ልጆቻችንን፦ እናንተ የሮቤልና
የጋድ ልጆች፥ ከእስራኤል አምላክ ከእግዚአብሔር ጋር ምን አላችሁ? 25 እግዚአብሔር በእኛና በእናንተ መካከል ዮርዳኖስን ድንበር አድርጎአል። እናንተ
የሮቤልና የጋድ ልጆች በእግዚአብሔር ዘንድ እድል ፈንታ የላችሁም ይሉአቸዋል ብለን ይህን አደረግን። በዚህም ልጆቻችሁ ልጆቻችንን እግዚአብሔርን ከመፍራት
ያስተዋቸዋል። 26 ስለዚህ፦ መሠዊያ እንሥራ አልን፤ ነገር ግን ለሚቃጠል መሥዋዕት ወይም ለሌላ መሥዋዕት አይደለም፤ 27 ነገር ግን በእኛና በእናንተ
መካከል ከእኛም በኋላ በትውልዳችንና በትውልዳችሁ መካከል በሚቃጠል መሥዋዕትና በቁርባን በደኅንነትም መሥዋዕታችን እግዚአብሔርን እናመልክ ዘንድ
በሚመጣውም ዘመን ልጆቻችሁ ልጆቻችንን፦በእግዚአብሔር ዘንድ እድል ፈንት የላችሁም እንዳይሉ ምስክር ይሆናል። 28 ስለዚህም አልን፦ በሚመጣው
ዘመን ለእኛ ወይም ለትውልዳችን፥ ይህን እንላለን እኛ፦ እነሆም አባቶቻችን ያደረጉትን የእግዚአብሔርን መሠዊያ ምሳሌ እዩ በእኛና በእናንተ መካከል ምስክር
ነው እንጂ ስለሚቃጠል መሥዋዕታችን ስለሌላ መሥዋዕት አይደለም። በማደሪያው ፊት ካለው ከአምላካችን 29 ከእግዚአብሔር መሠዊያ ሌላ ለሚቃጠል
መሥዋዕትና ለእህል ቁርባን ለሌላ መሥዋዕትም የሚሆን መሠዊያን የሠራነው በእግዚአብሔር ላይ በማመፅ እግዚአብሔርንም ዛሬ መከተልን ለመተው በማለት
እንደ ሆነ ይህ ከእኛ ይራቅ። 30 ካህኑ ፊንሐና የማኅበሩ አለቆች፥ ከእርሱ ጋር ከነበሩት የእስራኤል አለቆች፥ የሮቤል ልጆችና የጋድ ልጆች የምናሴም ልጆች
የተናገሩትን ቃል በሰሙ ጊዜ ነገሩ እጅግ ደስ አሰኛቸው። 31 የካህኑም በአልዓዛር ልጅ ፊንሐስ ለሮቤል ልጆችና ለጋድ ልጆች ለምናሴም ልጆች፦ ይህን
መተላለፍ በእግዚአብሔር ላይ አላደረጋችሁምና እግዚአብሔር በመካከላችን እንዳለ ዛሬ እናውቃለን፤ አሁን የእስራኤልን ልጆች ከእግዚአብሔር እጅ አድናችኋል
አላቸው። 32 የካህኑም የአልዓዛር ልጅ ፊንሐስና አለቆቹ ከሮቤል ልጆችና ከጋድ ልጆች ዘንድ ከገለዓድ አገር ወደ ከነዓን አገር ወደ እስራኤል ልጆች ተመለሱ፥
ወሬም አመጡላቸው። 33 ነገሩም የእስራኤል ልጆችን ደስ አሰኘ፤ የእስራኤልም ልጆች እግዚአብሔርን አመሰገኑ፥ ከዚያም ወዲያ የሮቤል ልጆችና የጋድ ልጆች
የተቀመጡባትን ምድር ያጠፉ ዘንድ ወጥተው አንዲወጉአቸው አልተናገሩም። 34 የሮቤል ልጆችና የጋድ ልጆች፦ እግዚአብሔር አምላክ እንደ ሆነ ይህ
በመካከላችን ምስክር ነው ሲሉ መሠዊያውን ምስክር ብለው ጠሩት።

Joshua 22:1

ሮቤላውያን
የሮቤል ነገድ ሰዎች (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ጋዳውያን
የጋድ ነገድ ሰዎች (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ድምጼን ታዛችኋል
እዚህ ስፍራ "ድምጼ" የሚለው የሚያመለክተው ኢያሱ የተናገራቸውን ነገሮች ነው። "የተናገርኩትን ሁሉ ታዛችኋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት)

ወንድሞቻችሁን አልተዋችሁም
ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ከወንድሞቻችሁ ጋር ቆይታችኋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምፀት/ላይዶክስ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Joshua 22:4

በመንገዱ ሁሉ ለመሄድ
ያህዌን የሚታዘዝ ሰው በያህዌ መንገዶች ወይም ጎዳናዎች እንደሄደ ተደርጎ ይነገራል። "እርሱ ያለውን ነገር ሁሉ መታዘዝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በሙሉ ልባችሁ እና በሙሉ ነፍሳችሁ
"ልብ" እና "ነፍስ" የሚሉት ቃላት እዚህ ስፍራ ላይ ያገለገሉት የሰውን ሁለንተና ለመግለጽ ነው። "በሙሉ ሃሳባችሁ እና ስሜታችሁ" ወይም "በሁለንተናችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 22:7

የዮርዳኖስ
ይህ የዮርዳኖስ ወንዝ አጭር ስያሜ ነው

ብረት
ጠንካራ፣ ከባድ፣ ማግኔት የሚስበው ነገር

ምርኮ/ዘረፋ
ያሸነፈው ሰራዊት ካሸነፈው ህዝብ ዋጋ ያለውን ማናቸውንም ነገር ይወስዳል

Joshua 22:9

በሙሴ እጅ የያህዌ ትዕዛዝ
"በእጅ" የሚለው ሀረግ ያህዌ ትዕዛዙን ለመስጠት/ለማቅረብ ሙሴን እንደተጠቀመበት የሚገልጽ ፈሊጣ አነጋገር ነው። "ያህዌ ያዛችሁ ዘንድ ሙሴን ተናገረው/ አዘዘው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 22:10

የዮርዳኖስ
ይህ የዮርዳኖስ ወንዝ አጭር ስያሜ ነው

ከከነዓን ምድር ፊት
ከዮርዳኖስ ወንዝ ባሻገር የሚኖሩ እስራኤላውያን ነገዶች መሰዊያውን ወደ ገነቡበት ከነዓን ይገባሉ። ይህ ስፍራ የተገለጸው ሌሎች ነገዶች የሚኖሩበት የከነዓን "ፊት " ወይም "መግቢያ" እንደነበረ ተደርጎ ነው። "ወደ ከነዓን ምድር መግቢያ ላይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ገሊሎት
የከተማ ስም (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 22:12

ጦርነት
በሁለት አገራት ወይም ህዝቦች መሃል በጦር ትጥቅ የሚደረግ ግጭት

Joshua 22:13

አልዓዛር
የወንድ ስም (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 22:15

መላው የያህዌ ጉባኤ ይህንን ተናገረ
መላው የእስራኤል ህዝብ በአንድነት የተገለጸው በነጠላ ቁጥር አንድ ሰው እንደሆኑ ተደርጎ ነው። "ሌሎቹ እስራኤላውያን ሁሉ ይጠይቃሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

Joshua 22:17

በፌጎር የሰራነው ኃጢአት አይበቃንምን?
ይህ ጥያቄ የቀድሞ ኃጢአታቸው ምን ያህል የከፋ እንደሆነ አጉልቶ ያሳያል። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አስቀድመን በፌጎር እጅግ ክፉ ኃጢአት ሰርተናል!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ፌጎር
ይህ የቦታ ስም ነው። በኢያሱ 13:20 ላይ በተረጎሙት መንገድ ይተርጉሙት። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እስከ አሁን ድረስ እንኳን ራሳችንን ከዚያ አላነጻንም
ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊጻፍ ይችላል። "እስከ አሁን ድረስ በዚያ ኃጢአት ውስጥ እንገኛለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምፀት/ላይዶክስ የሚለውን ይመልከቱ)

እስከ ዛሬ ድረስ ያህዌን ከመከተልስ መራቅ ነበረባችሁን?
ይህ ጥያቄ ህዝቡን በኃጢአቱ ለመገሰጽ ውሏል። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ዛሬ ያህዌን ከመከተል መራቅ የለባችሁም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 22:19

አካን...ዛራ
የወንዶች ስሞች ናቸው (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የዛራ ልጅ አካን ለእግዚአብሔር የተለዩ ነገሮችን በመንካት/በመውሰድ እምነትን አላጎደለምን? በመላው የእስራኤል ህዝብ ላይ ቁጣ አልወረደምን?
እነዚህ ጥያቄዎች ህዝቡ ባለፊት ኃጢአቶች ስለደረሰበት ቅጣት ለማስታወስ ውለዋል። እነዚህ ጥያቄዎች በዐፍተ ነገር ሊገለጹ ይችላሉ። "የዛራ ልጅ አካን ለእግዚአብሔር የተለዩ ነገሮችን በመንካት ኃጢአት ሰርቷል። ደግሞም በዚያ ምክንያት እግዚአብሔር መላውን የእስራኤል ህዝብ ቀጥቷል!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 22:21

ይህ የሆነው በአመጽ ከሆነ.. ያህዌ ለዚህ ስራችን ይቅጣን
ሶስቱ ነገዶች የቀረበባቸው እውነት ላለመሆኑ ሁለት መላምታዊ ሃሳቦችን አቅርበዋል። ሌሎች አማልክትን ለማምለክ መሰዊያ አላበጁም። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 22:24

አጠቃላይ መረጃ:
የሮቤል ነገድ፣ የጋድ እና የምናሴ ነገድ እኩሌታ መልሳቸውን ሰጡ።

የእናንተ ልጆች ለልጆቻችን እንዲህ ሊሉ ይችላሉ ... ከእስራኤል አምላክ ጋር ምን አላችሁ?
ይህ ሶስቱ ነገዶች የሌሎች ነገዶች ልጆች ወደ ፊት ሊያደርጉት ይችላሉ ብለው ያሰቡት መላምታዊ ክስ ነው። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ከእስራኤል አምላክ ከያህዌ ጋር ምን አላችሁ?
ሶስቱ ነገዶች ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀሙት ሊያስወግዱት የሚፈልጉትን ሁኔታ አጉልተው ለማሳየት ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይችላል። "ከእስራኤል አምላክ ከያህዌ ጋር አንዳች የላችሁም!" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 22:25

አጠቃላይ መረጃ:
የሮቤል ነገድ፣ የጋድ እና የምናሴ ነገድ እኩሌታ መልሳቸውን መስጠት ቀጠሉ።

ያህዌ ዮርዳኖስን... አድርጓልና ከያህዌ ጋር አንዳች የላችሁም
ይህ ሶስቱ ነገዶች የሌሎቹ ነገዶች ልጆች ወደ ፊት ሊያደርጉት ይችላሉ ብለው ያሰቡት የመላምታዊ ክሱ ቀጣይ ነው። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የዮርዳኖስ
ይህ የዮርዳኖስ ወንዝ አጭር ስያሜ ነው ስለዚህ የእናንተ ልጆች የእኛን ልጆች ያህዌን ከማምለክ እንዲያቆሙ ሊያደርጉ ይችላሉና ሶስቱ ነገዶች መሰዊያ የገነቡት ለወደፊት ይህ መላምታዊ ሁኔታ እንዳይፈጠር ለማስወገድ ነው። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 22:26

አጠቃላይ መረጃ:
የሮቤል ነገድ፣ የጋድ እና የምናሴ ነገድ እኩሌታ አሁን መልሳቸውን ሰጡ።

በእናንተ እና በእኛ መሃል ምስክር እንዲሆን
መሰዊያው የተገለጸው ለሶስቱ ነገዶች መብቶች ማስረጃ መስጠት የሚችል ምስክር እንደሆነ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህም የእናንተ ልጆች በሚመጣው ዘመን ለእኛ ልጆች በፍጹም "ከያህዌ ዘንድ አንዳች ድርሻ የላችሁም" ሊሏቸው አይችሉም
ይህ ሶስቱ ነገዶች እንዲሆን የማይሹት መላምታዊ ሁኔታ ነው። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

አንዳች ድርሻ
"ምንም ክፍል" ወይም "ምንም ርስት"

Joshua 22:28

አጠቃላይ መረጃ:
የሮቤል ነገድ፣ የጋድ እና የምናሴ ነገድ እኩሌታ አሁን መልሳቸውን ሰጥተው አበቁ።

ይህ መነገር ካለበት... በእኛ እና በእናንተ መሃል ምስክሩ
ሶስቱ ነገዶች በቀረበባቸው ክስ በመጪው ዘመን ሊሆንም ላይሆንም ስለሚችለው ያላቸውን መልስ እየሰጡ ነው። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

አመጽ ከእኛ ይራቅ
የማመጽ ሃሳብ እንደሌላቸው ይህ ሃሳብ የተገለጸው፣ ከእነርሱ በጣም በሩቅ ስፍራ ላይ እንደሚገኝ ነገር ተደርጎ ነው። "እኛ በእርግጥ አናምጽም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱን ከመከተል ርቃችኋል
ያህዌን መከተልን ማቆም የተገለጸው እነርሱ ከእርሱ እንደዞሩ ተደርጎ ነው። "እርሱን መከተል አቆሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 22:30

ቃሎቹን ሰሙ
"መልዕክቱን ሰሙ" በዐይኖቻቸው ፊት መልካም ነበር እዚህ ስፍራ "በዐይኖቻቸው ፊት" የሚለው "በእነርሱ አስተያየት" ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ ላይ ይህንን ክህደት መፈጸም
"ለእርሱ የገባችሁትን ቃል ኪዳን ማፍረስ"

እናንተ የእስራኤልን ህዝብ ከያህዌ እጅ አድናችኋል
እዚህ ስፍራ "የያህዌ እጅ" የሚለው የሚያመለክተው ቅጣትን ነው። ህዝቡን መጠበቅ የተገለጸው ከእርሱ እጅ እንደ ማዳን ተደርጎ ነው። "ያህዌ እኛን እንዳይቀጣን ጠብቃችሁናል" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት)

Joshua 22:32

የተናገሩት በህዝቡ ዐይን ደስ የሚያሰኝ ሆነ
እዚህ ስፍራ "በዐይኖች ፊት ደስ የሚያሰኝ" የሚለው "ተቀባይነት አገኘ" ማለት ነው። "ህዝቡ የሽማግሌዎቹን ንግግር ተቀበለ"በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሪቱን ማጥፋት
"በምድሪቱ የሚገኘውን ማናቸውንም ነገር ማጥፋት"

Joshua 22:34

እንዲህ አሉ
ይህ የሚያመለክተው ሮቤላውያንን እና ጋዳውያንን ነው

ይህ በመሃላችን ምስክር ነው
መሰዊያው የተነገረው የሶስቱ ነገዶች ማረጋገጫ ምስክር እንደሆነ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 23

1 ከብዙ ቀናት በኋላ፥እግዚአብሔርም እስራኤልን በዙሪያቸው ካሉት ጠላቶቻቸው ሁሉ ካሳረፈ፥ ኢያሱ ሸምግሎ ነበር። 2 ኢያሱም እስራኤልን ሁሉ
ሸማግሌዎቻቸውን፥ አለቆቻቸውን፥ ፈራጆቻቸውንና ሹማምቶቻቸውን ጠርቶ እንዲህ አላቸው፦ እኔ በጣም ሸምግያለሁ። 3 እናንተም አምላካችሁ እግዚአብሔር
በእነዚህ አሕዛብ ሁሉ ስለ እናንተ ያደረገውን ሁሉ አይታችኋል፤ ስለ እናንተ የተዋጋ እርሱ አምላካችሁ እግዚአብሔር ነው። 4 ተመልከቱ! እኔ ካጠፋኋቸው
አሕዛብ ሁሉ ጋር ከዮርዳኖስ ጀምሮ እስካለው እስከ ታላቁ ባሕር ድረስ ለነገዶቻችሁ ርስት እንዲሆኑ መድቤላችኋለሁ። 5 እግዚአብሔር አምላካችሁም እርሱ
ከፊታችሁ በብርቱ ይበትናቸዋል፥ ከፊታችሁም ያሳድዳቸዋል። እግዚአብሔር አምላካችሁ እንደ ተናገራችሁም ምድራቸውን ትወርሳላችሁ። 6 ስለዚህም በሙሴ
ሕግ መጽሐፍ የተጻፈውን ሁሉ ለመጠበቅና ለማድረግ በጣም በርቱ፥ ከእርሱም ወደ ቀኝም ወደ ግራም ፈቀቅ አትበሉ። 7 በእናንተ መካከል ወደ ቀሩት ወደ
እነዚህ አሕዛብ አትግቡ፤ የአማልክታቸውንም ስም አትጥሩ፥ አትማሉባቸውም፥ አታምልኩአቸውም፥ አትስገዱላቸውም። 8 እስከ ዛሬ ድረስ እንዳደረጋችሁት
በእግዚአብሔር በአምላካችሁ ተጣበቁ። 9 እግዚአብሔርም ታላላቆችንና ኃይለኞችን መንግሥታት ከፊታችሁ አስወጣላችሁ። እስከ ዛሬም ድረስ ማንም
ሊቋቋማችሁ አልቻለም። 10 እግዚአብሔር አምላካችሁ እንደ ተጋገራችሁ ስለ እናንተ የሚዋጋ እርሱ ነውና፥ ከእናንተ አንድ ሰው ሺህ ሰውን ያሳድዳል። 11
እግዚእብሔር አምላካችሁን ትወድዱት ዘንድ ትኩረት አድርጉ። 12 እናንተ ግን ተመልሳችሁ በመካከላችሁ ከቀሩት ከእነዚህ አሕዛብ ጋር ብትጣበቁ፥ወይም
ከእነርሱም ጋር ብትጋቡ፥ ወይም እናንተ ወደ እነርሱም ወደ እናንተ ጎብረት ብታደርጉ፥ 13 ከዚያም እግዚአብሔር አምላካችሁ ከመካከላችሁ እነዚህን ሰዎች
እንደማያስወጣችሁ በርግጥ እወቁ። በዚህ ፈንታ ከዚህች እግዚአብሔር ከሰጣችሁ ከመልካሚቱ ምድር እስክትጠፉ ድረስ ለእናንተም መውደቂያና ወጥመድ፥
በጎናችሁም መግረፊያ፥ በዓይናችሁም እሾህ ይሆኑባችኋል። 14 እነሆም ዛሬ የምድርን መንገድ ሁሉ እሄዳለሁ፤ እናንተም እግዚአብሔር ስለ እናንተ ከተናገረው
ከመልካም ነገር ሁሉ አንድ ነገር እንዳልቀረ በልባችሁ ሁሉ በነፍሳችሁም ሁሉ እወቁ፥ ሁሉ ደርሶላችኋል፤ ከእርሱም አንድ ነገር አልቀረም። 15 እግዚአብሔ
አምላካችሁ የተናገረው መልካም ነገር ሁሉ እንደ ደረሰላችሁ፥ እግዚአብሔር አምላካችሁ ከሰጣችሁ ከዚህች ከመልካሚቱ ምድር እናንተን እስኪያጠፋችሁ ድረስ
እግዚአብሔር እንዲሁ ክፉን ነገር ሁሉ ያመጣባችኋል። 16 የእግዚአብሔር አምላካችሁን ቃል ኪዳን ብታፈርሱ፥ ሄዳችሁም ሌሎችን አማልክት ብታመልኩ፥
ብትሰግዱላቸውም፥ በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር ቁጣ ይነድድባችኋል፥ ከሰጣትችሁም ከመልካሚቱ ምድር ፈጥናችሁ ትጠፋላችሁ።

Joshua 23:1

በጣም አረጀ
ለብዙ አመታት የኖረ

Joshua 23:4

የዮርዳኖስ
ይህ የዮርዳኖስ ወንዝ አጭር ስያሜ ነው

በምዕራብ
ይህ የሚያመለክተው ፀሐይ የምትጠልቅበትን አቅጣጫ ነው

Joshua 23:6

ከዚህ ወደ ቀኝ ወይም ወደ ግራ ዞር ማለት
የሙሴን ትዕዛዛት አለመጠበቅ የተገለጸው ከዚህ መንገድ ወደ ቀኝ ወይም ወደ ግራ ዞር ማለት ተብሎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አትቀላቀሉም
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ከእነርሱ ጋር የቀረበ ወዳጅነት መመስረት 2) ከእነርሱ ጋር በጋብቻ መተሳሰር

መጥቀስ
መናገር

አማልዕክቶቻቸው
ይህ የሚያመለክተው የሌሎችን ህዝቦች አማልዕክት ነው

ያህዌን አጥብቆ መያዝ
"ያህዌን አጥብቆ መያዝ።" በያህዌ ማመን የተገለጸው እርሱን አጥብቆ እንደመያዝ ተደርጎ ነው። "በያህዌ ማመንን መቀጠል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እስከ ዛሬ ድረስ
"እስከ ዛሬ ዘመን ድረስ"

Joshua 23:9

በፊትህ ለመቆም
እዚህ ስፍራ "መቆም" የሚለው የሚወክለው በጦርነት ውስጥ ስፍራ/ምድር መያዝን ነው። "አንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእስራኤልን መላ ህዝብ ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት እና አንተ የሚለው ቃል ልዩ ልዩ መልኮች የሚሉትን ይመልከቱ)

ነጠላ
አንድ ብቻ

አንድ ሺህ
"1,000" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 23:12

ከእነዚህ ህዝቦች ትሩፋን ጋር የጠበቀ ግንኙነት መመስረት
የእነዚህን ህዝቦች እምነቶች መቀበል የተገለጸው እነርሱን ጋር አጥብቆ መያዝ ተደርጎ ነው። "የእነዚህን ህዝቦች እምነቶች መቀበል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መሰናክል/አሽክላ እና ወጥመድ
"መሰናክል" እና "ወጥመድ" የሚሉት ቃላት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ቃላቱ በአንድነት የሚናገሩት ሌሎች ህዝቦች ለእስራኤል ከፍተኛ ችግር እንደሚሆኑ ነው። (ጥንድ ትርጉም እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ለጀርባችሁ ጅራፍ እና ለዐይኖቻችሁ እሾህ
እነዚህ ሀረጋት የሚናገሩት እነዚህ ህዝቦች በእስራኤል ላይ የሚፈጥሩት ችግር የጅራፍ እና የእሾህ ያህል የሚያሰቃያቸው መሆኑን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Joshua 23:14

የምድርን ሁሉ መንገድ ልሄድ ነው
ኢያሱ ሞቱን ለመናገር ትሁት አገላለጽ ይጠቀማል። "መሞቴ ነው/ልሞት ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊሚዝም/ጸያፍ ወይም አስነዋሪ ቃልን ሻል ባለ ቃል መጠቀም)

በሙሉ ልባችሁ እና ነፍሳችሁ ታውቃላችሁ
እዚህ ስፍራ "ልቦች" እና "ነፍሶች" የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው።ቃላቱ በአንድነት ሆነው ጠለቅ ያለ ግላዊ እውቀትን ያጎላሉ። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ቃል እንኳን ሳይፈጸም አልቀረም
እነዚህ ቃላት የያህዌ ቃል ኪዳኖች ሁሉ መፈጸማቸውን ትኩረት ሰጥተው ይገልጻሉ። ይህ በአዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እያንዳንዱ ቃል ተፈጸመ/እውን ሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ድርብ አሉታ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

Joshua 23:16

ይህንን ያደርጋል
ይህ በቀደመው ቁጥር ውስጥ የተጠቀሰውን ቅጣት አስፈሪነት ያመለክታል

ሌሎችን አማልዕክት ማምለክ እና ለእነርሱ መስገድ
እነዚህ ሁለት ሀረጋት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ሁለተኛው ህዝቡ እንዴት "ሌሎችን አማልክት እንደሚያመልክ" ይገልጻል።" (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌ ቁጣ በእናንተ ላይ ይነዳል
በዚህ ስፍራ "ይነዳል" የሚለው ቃል፣ ልክ እሳት "እንደሚቀጣጠል" ወይም "በመቀጣጠል" እንደሚጀምር፣ ወይም ደረቅ ሳርን/ጭድን ወይም ጭራሮን ማቃጠል መጀመር ቀላል የሆነውን ያህል የያህዌ ቁጣ ለመጀመሩ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "ያህዌ በእናንተ መቆጣት ይጀምራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 24

1 ኢያሱም የእስራኤልን ነገድ ሁሉ ወደ ሴኬም ሰበሰበ፥ የእስራኤልንም ሽማግሌዎችን፥ አለቆቻቸውን፥ ፈራጆቻቸውንና ሹማምቶቻቸውን ጠራቸው፤ እነርሱም
በእግዚአብሔር ፊት ቆሙ። **2** ኢያሱም ለሕዝቡ ሁሉ እንዲህ አለ፦ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ አባቶቻችሁ፥ የአብርሃምና የናኮር አባት
ታራ፥ አስቀድመው በወንዝ ማዶ ተቀመጡ፤ ሌሎችንም አማልክት አመለኩ። **3** አባታችሁንም አብርሃምን ከኤፍራጥስ ወንዝ ማዶ ወስጄ በከነዓን ምድር ሁሉ
መራሁት፤ ዘሩንም በልጁ በይስሐቅ በኩል እንዲበዛ ሰጠሁት። **4** ለይስሐቅም ያዕቆብንና ዔሳውን ሰጠሁት። ለዔሳውም የሴይርን ተራራ ርስት አድርጌ
ሰጠሁት፥ ነገር ግን ያዕቆብና ልጆቹ ወደ ግብፅ ወረዱ። **5** ሙሴንና አሮንንም ላክሁ፥ ግብፃውያንን በመቅሠፍት መታሁ። ከዚያም በኋላ አወጣኋችሁ። **6**
አባቶቻችሁንም ከግብፅ አወጣኋችው፤ ወደ ባሕሩም መጣችሁ። ግብፃውያንም አባቶቻችሁን በሰረገሎችና በፈረሰኞች እስከ ኤርትራ ባሕር ድረስ
አሳደዱአቸው። **7** አባቶቻችሁም ወደ እግዚአብሔር በጮኹ ጊዜ በእናንተና በግብፃውያን መካከል ጨለማ አደረገ። ባሕሩንም በእነርሱ ላይ መለሰባቸው፥
አሰጠማቸውም። ዓናኖቻችሁም በግብፃውያን ላይ ያደረግሁትን አይታችኋል። ለረጅም ጊዜም በምድረ በዳ ተቀመጣችሁ። **8** እኔም በዮርዳኖስ ማዶ ወደ
ተቀመጡበት ወደ አሞራውያን ምድር አመጣኋችሁ። ከእናንም ጋር ተዋጉ፥ በእጃችሁ አሳልፌ ሰጠኋችሁ። ምድራቸውንም ወረሳችሁ፤ ከፊታችሁም
አጠፋኋቸው። **9-10** የሞዓብም ንጉሥ የሴፎር ልጅ ባላቅ ተንሥቶ ከእስራኤል ጋር ተዋጋ እንዲረግማችሁም የቢዖርን ልጅ በለዓምን ልኮ አስጠራው።እኔ ግን
በለዓምን አልሰማሁትም። እርሱም በዚህ ፈንታ ባረካችሁ፥ እኔም ከእጁ አዳንኋችሁ። **11** ዮርዳኖስንም ተሻግራችሁ፥ ወደ ኢያሪኮም መጣችሁ። የኢያሪኮም
ሰዎች፥ ከአሞራዊውያን፥ ከፌርዛዊውያን፥ ከከነዓናዊውያን፥ ከኬጢያዊውያን፥ ከጌርጌሳዊውያን፥ ከኤዊያዊውያንና ከኢያቡሳዊውያን፥ ጋር ተዋጉአችሁ። በእነርሱም
ላይ ድልን ሰጠኋችሁ፤አሳልፌም በእጃችሁ ሰጠኋችሁ። **12** በፊታችሁ ያሉትን ሁለቱን የአሞራውያንን ነገሥታት እንዲያስወጡአቸው በፊታችሁም ተርብን
ሰደድሁባቸው። ይህም በእናንተ ሰይፍና ቀሥት አይደለም። **13** ያልደከማችሁበትንም ምድር፥ ያልሠራችኋቸውንም ዛሬ የተቀመጣችሁባቸውን ከተሞች
ሰጠኋችሁ። ያልተከላችኋቸውን ወይንና ወይራ በላችሁ። **14** አሁንም እግዚአብሔርን ፍሩ፥ በፍጹም ቅንነትና ታማኝነት አምልኩት፤ አባቶቻችሁም በኤፍራጥስ
ወንዝ ማዶ በግብፅም ያመለኩአቸውን አማልክት ከእናንተ አርቁ፤ እግዚአብሔርንም አምልኩ። **15** እግዚአብሔርንም ማምለክ ክፉ መስሎ ቢታያችሁ፥
አባቶቻችሁ በኤፍራጥስ ወንዝ ማዶ ሳሉ ያመለኩአቸውን አማልክት ወይም በምድራቸው ያላችሁባቸውን የአሞራውያንን አማልክት ታመልኩ እንደ ሆነ፥
የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ። እኔና ቤተ ሰቦቼ ግን እግዚአብሔርን እናመካለን። **16** ሕዝቡም መልሰው እንዲህ አሉ፦ እግዚአብሔርን ትተን ሌሎች አማልክትን
ማምለክ ከእኛ ይራቅ፥ **17** እኛንና አባቶቻችንን ከባርነት ቤት ከግብፅ ምድር ያወጣን፥ በዓይናችንም ፊት እነዚያን ታላላቅ ተአምራት ያደረገ፥ በሄድንባትም
መንገድ ሁሉ ባለፍንባችውም አሕዛብ ሁሉ መካከል የጠበቀን፥ እርሱ አምላካችን እግዚአብሔር ነው። **18** እግዚአብሔር አሕዛብን ሁሉ በምድሪቱም
የተቀመጡትን አሞራውያን ከፊታችን አስወጣ። ስለዚህ እርሱ አምላካችን ነውና፤ እግዚአብሔርን እናመልካለን። **19** ኢያሱም ሕዝቡን እንዲህ አላቸው፦ እርሱ
ቅዱስና፥ ቀናተኛ አምላክ ነውና፥ እግዚአብሔርን ማምለክ አትችሉም፤ መተላለፋችሁንና ኃጢአታችሁን ይቅር አይልም። **20** እግዚአብሔርን ትታችሁ እንግዶችን
አማልክት ብታመልኩ፥ ተመልሶ ክፉ ነገር ያደርግባችኋል፥ መልካም ካደረገላችሁ በኋላ ያጠፋችኋል። **21** ሕዝቡም ኢያሱን፦ እንዲህ አይሁን እግዚአብሔርን
እናመልካለን አሉት። **22** ከዚያም ኢያሱ ሕዝቡን፦ እግዚአብሔርን እንድታመኩት እንደመረጣችሁ በራሳችሁ ላይ ምስክሮች ናችሁ አላቸው። እነርሱም፦
ምስክሮች ነን አሉ። **23** እርሱም፦ አሁን እንግዲህ በመካከላችሁ ያሉትን እንግዶችን አማልክት አርቁ፥ ልባችሁንም ወደ እስራኤል አምላክ ወደ እግዚአብሔር
አዘንብሉ አላቸው። **24** ሕዝቡም ኢያሱን፦ አምላካችንን እግዚአብሔርን እናመልካለን፥ ድምፁንም እንሰማለን፥ አሉ። **25** በዚያን ቀን ኢያሱ ከሕዝቡ ጋር ቃል ኪዳን
አደረገ። በሴምም አዋጅንና ሕግን አደረገላቸው። **26** ኢያሱም እነዚህን ቃላት ሁሉ በእግዚአብሔር ሕግ መጽሐፍ ጻፈ። ታላቁንም ድንጋይ ወስዶ በእግዚአብሔር
መቅደስ አጠገብ ከነበረችው ከአድባሩ ዛፍ በታች አቆመው። **27** ኢያሱም ለሕዝቡ፦ ተመልከቱ፥ የተናገረነውን ይህ ድንጋይ ይመሰክርብናል። እግዚአብሔር
የተናገርነውን ሁሉ ሰምቶአል። እንግዲህ አምላካችሁን እንዳትክዱ ይህ ምስክር ይሆንባችኋል አላቸው። **28** ስለዚህም ኢያሱ ሕዝቡን ወደ እያንዳንዱ ርስት
እንዲሄዱ አደረገ። **29** ከዚህ ነገር በኋላ የእግዚአብሔር አገልጋይ የነዌ ልጅ ኢያሱ ዕድሜው መቶ አሥር ዓመት ሞልቶት ሞተ። **30** በተራራማውም በኤፍሬም
አገር በገዓስ ተራራ በሰሜን ባለችው በራሱ ርስት በተምና ሴራ ቀበሩት። **31** ኢያሱ በነረበት ዘመን ሁሉ፤ከኢያሱም በኋላ በነበሩት ለእስራኤልም ያደረገውን
የእግዚአብሔርን ሥራ ሁሉ ባወቁት በሽማግሌዎች ዘመን ሁሉ እስራኤላውያን እግዚአብሔርን አመለኩ። **32** የእስራኤልም ልጆች ከግብፅ የወጡት የዮሴፍን
አጥንት ያዕቆብ ከሴም አባት ከኤሞር ልጆች በገዛው እርሻ በሴኬም ቀበሩት። እርሱም በአንድ መቶ ብር ገዛው፤እርሻውም ለዮሴፍ ልጆች ርስት ሆነ። **33**
የአሮንም ልጅ አልዓዛር ሞተ፤ በተራራውም በኤፍሬም አገር ለልጁ ለፊንሐስ በተሰጠችው በጊብዓ መሬት ቀበሩት።

Joshua 24:1

ኢያሱ ሁሉንም የእስራኤል ነገዶች ሰበሰበ
ኢያሱ ለነገዶቹ ያደረገው ስብሰባ የተገለጸው ሁሉንም በአንድ ቋት ውስጥ እንዳከማቻቸው ተደርጎ ነው። "ኢያሱ መላው የእስራኤል ነገድ ከእርሱ ጋር እንዲገኛኝ ጠየቀ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ራሳቸውን ከፊት አቀረቡ
"መጥተው ከፊት ለፊት ቆሙ" ወይም "ከፊት መጡ"

ከረጅም ጊዜ አስቀድሞ
"ከብዙ አመታት በፊት"

ይህ ነው
ኢያሱ ያህዌ አስቀድሞ የተናገረውን መናገር ጀመረ። ጥቅሱ እስከ ቁጥር 13 መጭሻ ድረስ ይቀጥላል።

ታራ... ናኮር
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 24:3

አጠቃላይ መረጃ፡
ኢያሱ ያህዌ እርሱ ከህዝቡ ጋር ስላለው ስምምነት የተናገረውን መጥቀሱን ቀጠለ

ሴይር
የቦት ወይም የስፍራ ስም (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ወረዱ
ግብጽ ከከነዓን ምድር በአቀማመጥ ዝቅ ያለ ነው። "ተጓዙ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Joshua 24:5

አጠቃላይ መረጃ:
ኢያሱ ያህዌ እርሱ ከህዝቡ ጋር ስላለው ስምምነት የተናገረውን መጥቀሱን ቀጠለ።

እናነተን አወጣችሁ... አባቶቻችሁን አወጣቸው
ያህዌ በቀጣይነት ስለ ቀደሙትና ስለ አሁኖቹ መላ እስራኤላውያን የሚናገሩትን እነዚህን ሁለት ሀረጎች በመለዋወጥ ይናገራል። "እናንተ" የሚለው ቃል በዚህ ንግግር ውስጥ ሁሉ ብዙ ቁጥር ሲሆን መላውን የእስራኤል ህዝብ ያመለክታል። (አንተ የሚለውን ቃል መልኮች/ቅርጾች ይመልከቱ)

Joshua 24:7

አጠቃላይ መረጃ:
ኢያሱ ያህዌ እርሱ ከህዝቡ ጋር ስላለው ስምምነት የተናገረውን መጥቀሱን ቀጠለ።

አባቶቻችሁ... እናንተ
ያህዌ በቀጣይነት ስለ ቀደሙትና ስለ አሁኖቹ መላ እስራኤላውያን የሚናገሩትን እነዚህን ሁለት ሀረጎች በመለዋወጥ ይናገራል። "እናንተ" የሚለው ቃል በዚህ ንግግር ውስጥ ሁሉ ብዙ ቁጥር ሲሆን መላውን የእስራኤል ህዝብ ያመለክታል። (አንተ የሚለውን ቃል መልኮች/ቅርጾች ይመልከቱ)

ባህሩ
ይህ የሚያመለክተው ቀይ ባህርን ነው

በምድረበዳ
ሰው የማይኖርበት አካባቢ፣ በረሃ

Joshua 24:8

አጠቃላይ መረጃ:
ኢያሱ ያህዌ እርሱ ከህዝቡ ጋር ስላለው ስምምነት የተናገረውን መጥቀሱን/ መናገሩን ቀጠለ።

እናንተ
"እናንተ" የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ሲሆን በእዚህ ንግግር ውስጥ ሁሉ መላውን የእስራኤል ህዝብ ይገልጻል። (አንተ የሚለውን ቃል መልኮች/ቅርጾች ይመልከቱ)

የዮርዳኖስ
ይህ የዮርዳኖስ ወንዝ አጭር ስያሜ ነው

በእጃችሁ አሳልፎ ሰጣቸው
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው የሚያመለክተው ሃይልን ነው። "እንድትማርኳቸው አቅም ሆናችሁ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 24:9

አጠቃላይ መረጃ:
ኢያሱ ያህዌ እርሱ ከህዝቡ ጋር ስላለው ስምምነት የተናገረውን መጥቀሱን/ መናገሩን ቀጠለ።

ባላቅ... ሴፎር
የወንዶች ስም (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ
"እናንተ" የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ሲሆን በእዚህ ንግግር ውስጥ ሁሉ መላውን የእስራኤል ህዝብ ይገልጻል። (አንተ የሚለውን ቃል መልኮች/ቅርጾች ይመልከቱ)

እናንተን ከእጁ አዳናችሁ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው የሚያመለክተው ሃይልን ነው። "እንድትማርኳቸው አቅም ሆናችሁ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 24:11

አጠቃላይ መረጃ:
ኢያሱ ያህዌ እርሱ ከህዝቡ ጋር ስላለው ስምምነት የተናገረውን መጥቀሱን/ መናገሩን ቀጠለ።

እናንተ
"እናንተ" የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ሲሆን በእዚህ ንግግር ውስጥ ሁሉ መላውን የእስራኤል ህዝብ ይገልጻል። (አንተ የሚለውን ቃል መልኮች/ቅርጾች ይመልከቱ)

የዮርዳኖስ
ይህ የዮርዳኖስ ወንዝ አጭር ስያሜ ነው

የተርብ
በአንድነት የምትኖርና በፍጥነት የምትበር ተናዳፊ ትንሽ ነፍሳት። እዚህ ስፍራ ብዙ "ተርቦች" እንደ አንድ ብቻ ተደርጎ ተገልጽዋል።

Joshua 24:13

አጠቃላይ መረጃ:
ኢያሱ ያህዌ እርሱ ከህዝቡ ጋር ስላለው ስምምነት የሚናገረውን/ የሚጠቅሰውን አጠናቀቀ።

Joshua 24:14

በዐይኖቻችሁ ፊት ስህተት ሆኖ ከታያችሁ
ዐይኖች የሚለው የሚወክለው ማየትን፣ ሲሆን ማየት ደግሞ ሃሳብን ወይም መሻትን ይገልጻል። "የማትፈልጉ ከሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ቤቴ
ይህ የሚገልጸው በቤቱ የሚኖሩ ቤተሰቦቹን ነው። "ቤቴ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 24:16

እኛ... እኛን እና አባቶቻችን
ህዝቡ ከአባቶቻቸው ጋር እንደነበሩ አድርገው ይናገራሉ፣ ደግሞም "እኛን" እና "እኛ" የሚሉት ቃላት "የእኛ አባቶች" ከሚለው ጋር ለዋውጠው ይጠቀማሉ። (ተውላጠ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ከባርነት ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው የባርነታቸውን ስፍራ የሚገልጽ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ባሮች በነበርንበት አገር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በውስጣቸው አቋርጠን ባለፍንባቸው አገራት
"እኛ በውስጣቸው ባለፍንባቸው አገሮች"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Joshua 24:19

ህዝቦች
ይህ የሚያመለክው እስራኤላውያንን ነው።

እርሱ ቀናተኛ አምላክ ነው
እግዚአብሔር ህዝቡ እርሱን ብቻ እንዲያመልከው ይፈልጋል

እርሱ ያጠፋችኋል
የያህዌ ቁጣ የተገለጸው እነርሱን እንደሚያጠፋ እስት ሆኖ ነው። "በእሳት እንደሚያጠፋ እርሱ እናንተን ያጠፋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 24:21

ህዝቦች
ይህ የሚያመለክው እስራኤላውያንን ነው።

ልባችሁን ወደ ያህዌ መልሱ
ያህዌን ብቻ ለመታዘዝ መወሰን የሚለው የተነገረው ልባቸውን ወደ እርሱ እንደ ማዞር ተደርጎ ነው። እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚለው የሚገልጸው መላ ማንነትን ነው። በዚህ ሁኔታ፣ "ልብ" ብዙ ቁጥር ነው፤ ምክንያቱም መላውን እስራኤል እንደ አንድ ቡድን ይገልጻል። የሆነ ሆኖ፣ "የእናንተ" የሚለው ብዙ ቁጥር እንደመሆኑ ይህንን በብዙ ቁጥር መተርጎሙ እጅግ የተሻለ ይሆናል። "ራሳችሁን ወደ ያህዌ መልሱ" ወይም "ያህዌን ለመታዘዝ ወስኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር፣ ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና አንተ የሚለው ቃል መልኮች/ቅርጾች የሚሉትን ይመልከቱ)

Joshua 24:24

ህዝቦች
ይህ የሚያመለክው እስራኤላውያንን ነው።

እኛ የእርሱን ድምጽ እንሰማለን
እዚህ ስፍራ "መስማት" የሚለው መታዘዝ ማለት ነው። "እርሱ እንድናደርገው የነገረንን ነገር ሁሉ እንታዘዛለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ህግ መጽሐፍ
ይህ የሙሴ መጽሐፍት ቀጣይ ሊሆን ይችላል።

በዚያ አስቀመጠው
"በዚያ አኖረው/አደረገው"

Joshua 24:27

ህዝቦች
ይህ የሚያመለክው እስራኤላውያንን ነው።

ይህ ድንጋይ ምስክር ይሆናል... ሁሉንም ቃላት ሰምቷል
ኢያሱ ያስቀመጠው ድንጋይ የተገለጸው የተባለውን ሁሉ እንደሰማ እና የተነገረውን ለመመስከር እንደሚችል ሰው ተደርጎ ነው። (ሰውኛ የሚለውን ዘይቤ ይመልከቱ)

ሆናችሁ አትገኙ
"ሆናችሁ ባትገኙ"

Joshua 24:29

የ**110** አመት ሽማግሌ
"የአንድ መቶ አስር አመት ሽማግሌ" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ተምና ሴራ... ገዓስ ተራራ
የቦታ ስሞች (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 24:31

ኢያሱ በሕይወት በነበረበት ዘመናት በሙሉ
ይህ የኢያሱን መላ ህይወት የሚያመለክት ፈሊጥ ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኢያሱ ከሞተ በኋላ የኖሩ
"ከኢያሱ በኋላ የኖሩ"

Joshua 24:32

የዮሴፍ አጽም ... በሴኬም ቀበሯቸው
የዚህን ዐረፍተ ነገር አጀማመር ስርአት መለወጥ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። "የእስራኤል ህዝብ የዮሴፍን አጽም ከግብጽ አውጥተው በሴኬም ቀበሯቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

አንድ መቶ ሰቅል/ገንዘብ
"100 ሰቅል/ገንዘብ" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

አልዓዛር
የወንድ ስም (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ጊብዓ
የቦታ ስም (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Judges

Judges

Chapter 1

1 ከኢያሱ ሞት በኋላ፣ የእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔርን እንዲህ ብለው ጠየቁ፦ “ከነዓናውያንን ለመዋጋት ወደላይ ስንሄድ ማን ይመራናል?” 2 እግዚአብሔርም አላቸው፦ “ይሁዳ ይመራችኋል፡ ተመልከቱ፣ ምድሪቱን ለእነርሱ አሳልፌ ሰጥቻለሁ።” 3 የይሁዳም ሰዎች ለወንድሞቻቸው ለስምዖን ሰዎች እንዲህ አሏቸው፦ “ከነዓናውያንን አብረን እንወጋቸው ዘንድ ከእኛ ጋር ለእኛ ወደተሰጠው ክልል ኑ። እኛም እንዲሁ ለእናንተ ወደተሰጠው ክልል እንመጣለን።” ስለዚህም የስምዖን ነገድ ከእነርሱ ጋር ሄዱ። 4 የይሁዳ ሰዎችም ወደ ላይ ወጡ፣ እግዚአብሔርም በከነዓናውያንና በፌርዛውያን ላይ ድልን ሰጣቸው። በቤዜቅም ከእነርሱ አስር ሺህ ሰዎችን ገደሉ። 5 አዶኒ ቤዜቅን በቤዜቅ አገኙት፣ ከእርሱም ጋር ተዋግተው ከነዓናውያንና ፌርዛውያንን አሸነፉ። 6 አዶኒ ቤዜቅ ግን ሸሸ፣ ተከታትለውም አገኙትና ያዙት፣ የእጁንና የእግሩን አውራጣቶች ቆረጡ። 7 አዶኒ ቤዜቅም እንዲህ አለ፦ “የእግርና የእጅ አውራ ጣቶቻቸው የተቆረጠባቸው ሰባ ነገስታት ከእኔ ማዕድ ስር መብላቸውን ሰበሰቡ። እኔ እንዳደረግሁት፣ እግዚአብሔር በእኔ ላይ አደረገብኝ።” እርሱንም ወደ ኢየሩሳሌም አመጡት፣ በዚያም ሞተ። 8 የይሁዳ ሰዎች ከኢየሩሳሌም ከተማ ጋር ተዋግተው ተቆጣጠሯት። በሰይፍ ስለት ወጓት፣ ከተማዋንም አቃጠሏት። 9 ከዚያም በኋላ የይሁዳ ሰዎች በኮረብታማው አገር ይኖሩ የነበሩትን ከነዓናውያንን ለመዋጋት፣ወደ ኔጌብና ወደ ምዕራቡ ኮረብታ ግርጌ ወረዱ። 10 ይሁዳም በኬብሮን (የኬብሮን ስም ቀድሞ ቂርያት አርባቅ ትባል ነበር) የሚኖሩትን ከነዓናውያንን ለመውጋት ሄደ፣ ሴሲን፣ አክመንና ቴላሚንም ድል አደረጉ። 11 ከዚያም የይሁዳ ሰዎች ወደ ዴብር (የዴብር ስም ቀድሞ ቅርያት ሤፍር ተብላ ትጠራ ነበር) ሄዱ። 12 ካሌብም አለ፣ “ቅርያት ሤፍርን የሚዋጋና የሚቆጣጠራትን ሰው፣ ሴት ልጄን ዓክሳን ሚስት ትሆነው ዘንድ እሰጠዋለሁ።” 13 የካሌብ ታናሽ ወንድም የቄናዝ ልጅ ጎቶንያልም ዴብርን ተቆጣጠረ፣ ስለዚህ ካሌብ ሴት ልጁን ዓክሳን ሚስት ትሆነው ዘንድ ሰጠው። 14 ዓክሳም ወዲያውኑ ወደ ጎቶንያል መጣች፣ ለእርሱም አባቷ እርሻ እንዲሰጣት እንዲለምነው ጠየቀችው። ከአሕያዋም በወረደች ጊዜ፣ ካሌብ እንዲህ ብሎ ጠየቃት፣ “ምን እንዳደርግልሽ ትፈልጊያለሽ?” 15 እርሷም እንዲህ አለችው፣ “በረከትን ስጠኝ። በኔጌብ ምድር ያለውን መሬት ሰጥተኸኛልና፣ የውሃ ምንጭንም ስጠኝ።” ካሌብም የላይኛውንና የታችኛውን ምንጭ ሰጣት። 16 የቄናዊው የሙሴ አማት ዘሮችም ከባለ ዘንባባዋ ከተማ ለቀው ከይሁዳ ሰዎች ጋር በኔጌብ ወዳለችው ወደ ይሁዳ ምድረ በዳ ከይሁዳ ሰዎች ጋር በዓራድ አጠገብ ለመኖር ሄዱ። 17 የይሁዳ ሰዎችም ከወንድሞቻቸው ከስምዖን ሰዎች ጋር ሄዱና በጽፋት ይኖሩ የነበሩትን ከነዓናውያንን ወጓቸው፣ፈጽሞም አጠፏት። የከተማይቱም ስም ሔርማ ይባል ነበር። 18 በተጨማሪ የይሁዳ ሰዎች ጋዛንና በዙርያዋ ያለውን አገር፣ አስቀሎናንና በዙርያዋ ያለውን አገር እንደዚሁም አቃሮንንና በዙርያዋ ያለውን አገር ሁሉ ተቆጣጠሩ። 19 እግዚአብሔርም ከይሁዳ ሰዎች ጋር ነበር፣ የኮረብታማውንም አገር ተቆጣጠሩ፣ ነገር ግን በረባዳው ምድር የሚኖሩትን ሰዎች ማስወጣት አልቻሉም ነበር ምክንያቱም ነዋሪዎቹ የብረት ሰረገሎች ነበሯቸው። 20 ሙሴም እንደተናገረ ኬብሮንን ለካሌብ ሰጡት፣ እርሱም የዔናቅን ሶስት ልጆች ከዚያ አስወጣቸው። 21 ነገር ግን የቢንያም ሰዎች በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ኢያቡሳውያንን አላስወጧቸውም። ስለዚህ ኢያቡሳውያን እስከዛሬ ድረስ ከቢንያም ሰዎች ጋር በኢየሩሳሌም ይኖራሉ። 22 የዮሴፍ ወገንም ቤቴልን ለመውጋት ተዘጋጁ፣ እግዚአብሔርም ከእነርሱ ጋር ነበር። 23 ቀድሞ ሎዛ ተብላ ትጠራ የነበረችውን ቤቴልን ለመሰለል ሰዎችን ላኩ። 24 ሰላዮቹም ከከተማው አንድ ሰው ሲወጣ አዩ፣ እንዲህም አሉት፣ “ወደ ከተማው እንዴት መግባት እንደምንችል እባክህ አሳየን፣ ለአንተም ቸርነት እናደርግልሃለን።” 25 እርሱም ወደ ከተማው መግቢያውን መንገድ አሳያቸው። እነርሱም በሰይፍ ስለት ከተማውን ወጉ፣ ያንን ሰውና ቤተሰቦቹንም እንዲያመልጡ አደረጓቻው። 26 ሰውየውም ወደ ኬጢያውያን ሐገር ሄደና ከተማ ገነባ ስሙንም ሎዛ አለው፣ የዚያ ቦታ ስምም እስከዛሬ ሎዛ ነው። 27 የምናሴ ሰዎች በቤትሳንና በመንደሮቿ፣ በታዕናክና በመንደሮቿ፣ በዶርና በመንደሮቿ፣ በይብለዓምና በመንደሮቿ፣ በመጊዶና በመንደሮቿ ይኖሩ የነበሩትን ሰዎች አላስወጡአቸውም፣ ምክንቱም ከነዓናውያን በዚያ ለመቀመጥ ወስነው ስለነበር ነው። 28 እስራኤልም በበረታ ጊዜ፣ ከነዓናውያንን የጉልበት ስራ እየሰሩ እንዲያገለግሉአቸው አስገደዷቸው፣ ነገር ግን ሙሉ በሙሉ አላስወጧቸውም። 29 ኤፍሬም በጌዝር ይኖሩ የነበሩትን ከነዓናውያን አላስወጣቸውም፣ ስለዚህ ከነዓናውያን በእነርሱ መካከል በጌዝር መኖር ቀጠሉ። 30 ዛብሎንም በቂድሮን የሚኖሩትን ሰዎች ወይም በነህሎል ይኖሩ የነበሩትንም ሰዎች አላስወጣቸውም፣ ስለዚህ ከነዓናውያን በእነርሱ መካከል መኖር ቀጠሉ፣ ነገር ግን ዛብሎን ከነዓናውያን የጉልበት ስራ እየሰሩ እንዲያገለግሉአቸው ያስገድዳቸው ነበር። 31 አሴር በዓኮ፣ በሲዶን፣ በአሕላብ፣ በአክዚብ፣ በሒልባን፣ በአፌቅ፣ በረአብም የሚኖሩትን ሰዎች አላስወጣቸውም። 32 ስለዚህ የአሴር ነገድ በምድሪቱ በሚኖሩት በከነዓናውያን መካከል ኖሩ፣ ምክንያቱም አላስወጧቸውም ነበር። 33 የንፍታሌም ነገድ በቤት ሳሚስና በቤት ዓናት ይኖሩ የነበሩትን ሰዎችን አላስወጧቸውም። ስለዚህ የንፍታሌም ነገድ በምድራቸው ይኖሩ በነበሩ በነዓናውያን ሰዎች መካከል አብረው ኖሩ። ይሁን እንጂ የቤት ሳሚስና የቤት ዓናት ነዋሪዎች ለንፍታሌም ሰዎች የጉልበት ስራ እንዲሰሩ ይገደዱ ነበር። 34 አሞራውያንም የዳን ነገድ በኮረብታማው አገር እንዲኖሩ አስገደዷቸው፣ ወደ ሜዳማ ስፍራ ወርደው እንዲኖሩ አልፈቀዱላቸውም ነበር። 35 ስለዚህ አሞራውያን በሔሬስ ተራራ፣ በኤሎን፣ በሸዓልቢምም ኖሩ፣ ነገር ግን የዮሴፍ ቤት ወታደራዊ ኃይል በእነርሱ ላይ በረቱባቸው፣ ከዚህ የተነሳ ከባድ የጉልበት ስራ እየሰሩ 36 የአሞራውያንም ድንበር በሴላ ካለው ከአቅረቢም ኮረብታ ጀምሮ እስከ ኮረብታማው አገር ድረስ ነው።

Judges 1:1

አያያዥ መግለጫ
መጽሐፈ መሳፍንት የኢያሱን ታሪክ የሚቀጥል ሲሆን በተጨማሪም የአዲሱ ታሪክ ክፍል ጅማሬም ነው።

ያህዌ
ይህ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለሕዝቡ የገለጠው ስሙ ነው። ያህዌን እንዴት መተርጎም እንደሚኖርብህ ለመገንዘብ የትርጉም ቃል ገጽን ተመልከት።

ከነዓናውያንን ማን ይወጋልናል
“እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ሳይሆን የእስራኤልን ሕዝብ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይሁዳ ይወጋቸዋል
እዚህ ጋ “ይሁዳ” የሚወክለው የይሁዳ ነገድ የሆነውን ሕዝብ ነው። በመጀመሪያ እንዲወጉ እግዚአብሔር እነዚህን ሰዎች ያዛቸዋል። አ.ት፡ “የይሁዳ ሰዎች በመጀመሪያ መውጋት አለባቸው”

ተመልከቱ
“እዩ” ወይም “ስሙ” ወይም “የምነግራችሁን ልብ በሉ”

ይህቺን ምድር
ይህ ከነዓናውያን ይኖሩበት የነበረውን ምድር ያመለክታል። አ.ት፡ “የከነዓናውያን ምድር”

ወንድሞቻቸው
“እስራኤላውያን ባልንጀሮቻቸውን” ወይም “ዘመዶቻቸውን”

ከእኛ ጋር ውጡ
የይሁዳና የስምዖን ነገድ ሰዎች ከተቀሩት እስራኤላውያን ሕዝቦች ጋር በዮርዳኖስ ወንዝ ሸለቆ ሰፍረው ነበር። ለይሁዳ ተሰጥቶት የነበረው ምድር ከሸለቆው በላይ በኩል፣ በኮረብታው ላይ ነበር። አንዳንድ ቋንቋዎች፣ አብዛኛውን ጊዜ ሰዎቹ ወደ ላይ መውጣታቸውን ወይም መውረዳቸውን አያመለክቱም። አ.ት፡ “ከእኛ ጋር ኑ” ወይም “ከእኛ ጋር ሂዱ”

ወደ ተመደበልን - ወደ ተመደበላችሁ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ወደ መደበልን … እግዚአብሔር ወደ መደበላችሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እኛም ከእናንተ ጋር እንሄዳለን
“እኛም ደግሞ ከእናንተ ጋር እንሄዳለን” ወይም “በተመሳሳይ እኛም ከእናንተ ጋር እንሄዳለን”

Judges 1:4

የይሁዳ ሰዎች ተዋጉ
በውስጠ ታዋቂ የስምዖን ሰዎችም ከይሁዳ ሰዎች ጋር ሆነው መዋጋታቸውን ያመለክታል።

አሥር ሺህ ገደሉ
“10,000 ያህሉን ገደሉ” ወይም “ብዙ ሕዝብ ገደሉ” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ከእነርሱ
“የከነዓናውያንና የፌርዛውያን ወታደሮች” ወይም “ጠላቶች”

ቤዜቅ
በከነዓን ተራራዎች ላይ ያለ አካባቢ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

አዶኒቤዜቅ
ይህ ሰው የከነዓናውያንና የፌርዛውያን ሰራዊት አለቃ ነበር። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

እርሱን ተዋጉት
እዚህ ጋ “እርሱን” የሚያመለክተው በመሠረቱ አዶኒቤዜቅንና ሰራዊቱን ነው። አ.ት፡ “እርሱንና ሰራዊቱን ተዋጓቸው”

Judges 1:6

አሳደዱት
“አባረሩት”

ሰባ ነገሥታት
“70 ነገሥታት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

የእጅና የእግሮቻቸው አውራ ጣት የተቆረጠባቸው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የእኔ ሰዎች የእጆቻቸውንና የእግሮቻቸውን አውራ ጣቶች እንዲቆርጡ ያዘዝኳቸው” ወይም “የእጅና የእግሮቻቸውን አውራ ጣት የቆረጥናቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ከጠረጴዛዬ ስር ምግባቸውን ይለቅሙ ነበር
እነዚህ ነገሥታት ፍርፋሪ እንዲለቅሙ መገደዳቸው አዶኒቤዜቅ እነዚህን ነገሥታት ምን ያህል እንዳዋረዳቸው ያሳያል። እዚህ ጋ ምግብ “መልቀም” ማለት እንደሚመገቡት ያመለክታል። አ.ት፡ “ከጠረጴዛዬ ስር ፍርፋሪ ይበሉ ነበር” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 1:8

የኢየሩሳሌምን ከተማ እና …ወሰዷት
እዚህ ጋ “ከተማ” የሚወክለው ሕዝብን ነው። አ.ት፡ “በኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩትን ሰዎች እና … አሸነፏቸው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ወጓት
እዚህ ጋ “እርሷ” የሚያመለክተው ከተማን፣ ይኸውም የሚኖሩባትን ሰዎች ነው። አ.ት፡ “የከተማይቱን ሰዎች ወጓቸው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በሰይፍ ስለት
“በሰይፋቸው ጫፍ”። እዚህ ጋ “ሰይፍ” የሚወክለው ወታደሮች በጦርነት ውስጥ የሚጠቀሙበትን ሰይፍና ሌሎች የጦር መሣሪያዎች ነው። አ.ት፡ “በሰይፎቻቸው” ወይም “በጦር መሣሪያዎቻቸው”

የይሁዳ ሰዎች ለመዋጋት ወረዱ
ከኢየሩሳሌም በሚጓዙበት ጊዜ “ወረዱ” የሚለውን ቃል መጠቀም የተለመደ ነበር። አ.ት፡ “የይሁዳ ሰዎች ለመዋጋት ሄዱ”

በኔጌብ ውስጥ
“በደቡባዊው የይሁዳ ምድረ በዳ”

የኮረብታ ግርጌ
ከተራራ በታች ያሉ ኮረብታዎች ወይም የተራራ ወገብ

የኬብሮን ስም ቀድሞ ቂርያት አርባቅ ነበር
ይህ ዳራዊ መረጃ ነው። ይህንን መጽሐፍ በመጀመሪያ ያነበቡ አንዳንድ ሰዎች ምናልባት ቂርያት አርባቅ የሚለውን ሰምተው ይሆናል፣ ነገር ግን እርሱኑ የኬብሮን ከተማ ብለው እንደሚጠሩት አያውቁም ነበር። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ሴሲን፣ አኪመንና ተላሚን
እነዚህ በኬብሮን የሚኖሩ የሦስቱ ከነዓናውያን አለቆች ስም ነው። እያንዳንዱ አለቃ ሰራዊቱን ይወክላል። አ.ት፡ “ሴሲን፣ አኪመን፣ ተላሚና ሰራዊታቸው” (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 1:11

የዳቤር ስም ቀድሞ ቅርያት ሤፍር ነበር
ደራሲው ምናልባት ይህንን የጻፈው አንባቢዎቹ ከተማይቱን በዳቤር ስም ስለሚያውቋት ይሆናል። እስራኤላውያን በወጓት ጊዜ ግን ቅርያት ሤፍር በመባል ትታወቅ ነበር። አ.ት፡ “ቂርያትሤፍር ተብላ የምትጠራውን” (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ቀድሞ
“ባለፈው ዘመን” ወይም “በድሮ ጊዜ”

ቂርያት ሤፍርን የሚወጋና የሚወስዳት
እዚህ ጋ “ቂርያት ሤፍር” የሚወክለው ሕዝቡን ነው። አ.ት፡ “የቂርያት ሤፍርን ሕዝብ የሚወጋና የሚያሸንፍ ከተማቸውንም የሚወስድ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ዓክሳ
ይህ የካሌብ ሴት ልጅ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የቄኔዝ ልጅ ጎቶንያል
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Judges 1:14

አጥብቃ ነገረችው
“ዓክሳ ለጎቶንያል አጥብቃ ነገረችው”

መሬቱን ሰጥተኸኛልና እርሻውን ስጣት
ይህ የሚያሳየው በቁጥር 14 ላይ በጠየቀችው ጊዜ እርሻውን እንደሰጣት ነው። በቁጥር 15 ደግሞ ከእርሻው በተጨማሪ የምንጩን ውሃ ትጠይቀዋለች።

በረከትን ስጠኝ
“ውለታ ዋልልኝ” ወይም “ይህንን አድርግልኝ”

የኔጌብን ምድር ሰጥተኸኛልና
ካሌብ ዓክሳን ለጎቶንያል ስለዳረለት ጎቶንያል በማረካት በኔጌብ ከተማ ከእርሱ ጋር ኖረች። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉሙ መብራራት መቻል አለበት። አ.ት፡ “በኔጌብ እንድኖር እስከዳርከኝ ድረስ”

Judges 1:16

የሙሴ አማት
“የሙሴ የሚስቱ አባት”

ቄናዊው አማቱ ወጣ
“ከቄናውያን ሰዎች አንዱ የሆነው አማቱ ወጣ”

ከዘንባባዎቹ ከተማ ወደ ምድረበዳው ወጣ
“የዘንባባዎቹን ከተማ ትቶ … ወደ ምድረበዳ ወጣ”

የዘንባባዎች ከተማ
ይህ የኢያሪኮ ሌላኛው ስም ነው።

አራድ
ይህ በከነዓን የሚገኝ የአንድ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የወንድሞቻቸው የስምዖን ሰዎች
እዚህ ጋ “ወንድሞች” ማለት በሌላው የእስራኤል ነገድ ውስጥ የሚኖሩ ዘመዶች ማለት ነው።

ጻፋት
ይህ በከነዓን የሚገኝ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የከተማይቱ ስም ሔርማ ተብሎ ተጠራ
እስራኤላውያን ጻፋትን ከደመሰሷት በኋላ ስሟን ሔርማ ብለው ቀየሩት። “ሔርማ” ማለት “ፈጽሞ መጥፋት” ማለት ነው። (እና ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Judges 1:18

እግዚአብሔር ከይሁዳ ሕዝብ ጋር ነበር
እዚህ ላይ “ከ. . . ጋር” ማለት እግዚአሔር የይሁዳን ሕዝብ ረድቶታል ማለት ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ሜዳ
ዛፍ የሌለበት፣ በጣም ሰፊ ለጥ ያለ መሬት

Judges 1:20

ኬብሮን ሙሴ እንዳለው ለካሌብ ተሰጥታ ነበር
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሙሴ ኬብሮንን ለካሌብ ሰጥቶት ነበር” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ሦስቱን የዔናቅ ወንዶች ልጆች
የሕዝብ ወገን መሪዎች የሆኑት መላውን ማኅበር ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል። አ.ት፡ “የዔናቅ ሦስቱ ወንዶች ልጆቹና ሰዎቻቸው”

ዔናቅ
ይህ የአንድ ሰው ስም ነው። ዔናቅና ተወላጆቹ በረጅም ቁመታቸው የታወቁ ነበሩ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

እስከ ዛሬ ድረስ
“እስካሁን ድረስ”። ይህ የሚያመለክተው መጽሐፈ መሳፍንት የተጻፈበትን ጊዜ ነው።

Judges 1:22

የዮሴፍ ቤት
እዚህ ጋ “ቤት” የሚወክለው ተወላጆችን ነው። ምናሴና ኤፍሬም የዮሴፍ ልጆች ሲሆኑ የ “ዮሴፍ ቤት” የምናሴንና የኤፍሬምን ተወላጆች ሊያመለክት ይችላል። አ.ት፡ “የምናሴና የኤፍሬም ተወላጆች” ወይም “የምናሴና የኤፍሬም ነገድ ሰዎች” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ቤቴልን ለመውጋት
እዚህ ጋ “ቤቴል” የሚያመለክተው በቤቴል የሚኖሩትን ሰዎች ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሰላይ
በምስጢር መረጃ ለማግኘት

ቀድሞ ሎዛ ተብላ ትጠራ የነበረችውን ከተማ
ይህ የዳራው መረጃ ነው። በመጀመሪያ ይህንን መጽሐፍ ያነበቡት ሰዎች ምናልባት ቤቴል ብለው የሚጠሯት ከተማ ሎዛ እንደነበረች አያውቁም ይሆናል። (ዳራዊ መረጃ እና ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ሰላዮች
በምስጢር መረጃ የሚያገኙ ሰዎች

Judges 1:25

ከተማይቱን ወጉ
እዚህ ጋ “ከተማ” የሚወክለው ሕዝቡን ነው። አ.ት፡ “የከተማይቱን ሰዎች ወጉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በሰይፍ ስለት
“በሰይፍ ጫፍ”። “ሰይፍ” እዚህ ጋ የሚወክለው ሰዎች በጦርነት ጊዜ የሚጠቀሙባቸውን ሰይፍና ሌሎች የጦር መሣሪያዎችን ነው። አ.ት፡ “በሰይፎቻቸው” ወይም “በጦር መሣሪያዎቻቸው”

ሂድ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “አምልጥ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ሎዛ
በቤቴል አቅራቢያ፣ በኬጢያውያን ምድር የምትገኘው፣ እንደ አዲስ የተቆረቆረችውና ሰውየው የተዋት ይህች ከተማ በሎዛ ስም ትጠራ ነበር።

ይህ እስከ ዛሬ ድረስ ስሟ ነው
“እስካሁን ስሟ ነው”። እዚህ ጋ “እስከ ዛሬ ድረስ” የሚያመለክተው መጽሐፈ መሳፍንት የተጻፈበትን ጊዜ ነው።

Judges 1:27

ቤትሳን፣ ታዕናክ፣ ዶር፣ ይብለዓም፣ መጊዶ
እነዚህ የከተሞች ስም ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ከነዓናውያን በዚያች ምድር ለመኖር ወስነው ስለነበር
“መወሰን” በአንድ ነገር ቁርጠኛ አቋም መያዝ ነው። አ.ት፡ “ከነዓናውያን ያችን ምድር ላለመተው ቁርጠኛ አቋም ይዘው ስለነበር”

እስራኤል በበረታ ጊዜ
እዚህ ጋ “እስራኤል” የሚወክለው ሕዝቡን ነው። አ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ በበረታ ጊዜ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከነዓናውያን በጉልበት ሥራ እንዲያገለግሏቸው አስገደዷቸው
“ከነዓናውያን ከባድ ሥራ እንዲሠሩላቸው አስገደዷቸው”

Judges 1:29

ኤፍሬም ... አልቻሉም
እዚህ ጋ “ኤፍሬም” ማለት የኤፍሬም ነገድ ሰዎች ወይም ወታደር ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ጌዝር
በኤፍሬም አካባቢ ከሚገኙ ከተሞች የአንዱ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Judges 1:30

ዛብሎን አላስወጣቸውም
እዚህ ጋ “ዛብሎን” የሚወክለው የዛብሎንን ነገድ ሰዎች ወይም ወታደሮችን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ቂድሮን - ነሀሎል
እነዚህ በከነዓን ምድር የሚገኙ ከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ዛብሎን ግን አስገደዳቸው
እዚህ ጋ “ዛብሎን” የሚወክለው የዛብሎንን ነገድ ሰዎች ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከባድ ሥራ
“አስቸጋሪ ሥራ”

Judges 1:31

አሴር አላስወጣቸውም
እዚህ ጋ “አሴር” የሚወክለው የአሴርን ነገድ ሰዎች ወይም ወታደሮች ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ዓኮ ... ሲዶን ... አሕላብ፣ አክዚብ፣ ሒልባ፣ አፌቅ ... ረአብ
እነዚህ በከነዓን ምድር የሚገኙ ከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Judges 1:33

ቤት ሳሚስ - ቤት ዓናት
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የቤት ሳሚስና የቤት ዓናት ነዋሪዎች ለንፍታሌም የጉልበት ሥራ ለመሥራት ተገደዱ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የንፍታሌም ሰዎች የቤት ሳሚስንና የቤት ዓናትን ሰዎች እንደ ባሪያ እንዲሠሩላቸው አስገደዷቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Judges 1:34

እንዲወርዱ አልፈቀዱላቸውም
“ከመውረድ አስቆሟቸው”

ሜዳ
ዛፍ የሌለበት በጣም ለጥ ያለ ሰፊ መሬት

የሔሬስ ተራራ
ይህ የኤሎን ከተማ የተሠራበት ረጅም ኮረብታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ኤሎን - ሸዓልቢም
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የዮሴፍ ቤት ወታደራዊ ኃይል ድል አደረጋቸው
“የዮሴፍ ተወላጅ የሆነው ነገድ ሕዝብ ብርቱ ሠራዊት ስለነበራቸው ድል ሊያደርጓቸው ችለዋል”

የዮሴፍ ቤት
እዚህ ጋ “ቤት” የሚወክለው ተወላጆችን ነው። ምናሴና ኤፍሬም የዮሴፍ ልጆች ሲሆኑ የ“ዮሴፍ ቤት” የምናሴንና የኤፍሬምን ተወላጆች ሊያመለክት ይችላል። አ.ት፡ “የምናሴና የኤፍሬም ተወላጆች” ወይም “የምናሴና የኤፍሬም ነገድ ሰዎች” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የአቅረበም ኮረብታ
ይህ ከሙት ባህር በደቡብ ምዕራብ በኩል የሚገኝ መተላለፊያ ነበር። “የጊንጥ መተላለፊያ” በመባልም ይጠራል። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ሴላዕ
ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 የእግዚአብሔር መልዓክም ከጌልጌላ ወደ ቦኪም ወጣ፣ እንዲህም አለ፣ “ከግብጽ አወጣኋችሁ፣ ለአባቶቻችሁ ወደማልሁላቸው ምድር አመጣኋችሁ።
እንዲህም አልሁ፣ ‘ከእናንተ ጋር ያለኝን ቃል ኪዳን አላፈርስም። **2** በዚህ ምድር ከሚኖሩ ሰዎች ጋር ቃል ኪዳን አትግቡ። መሰዊያቸውን ማፍረስ አለባችሁ።’
እናንተ ግን ቃሌን አልሰማችሁም። ይህ ያደረጋችሁት ምንድን ነው? **3** አሁንም እላለሁ፣ ‘ከነዓናውያንን ከእናንተ ፊት አላወጣም፣ ነገር ግን እነርሱ የጎን እሾህ
ይሆኑባችኋል፣ ጣዖቶቻቸውም ለእናንተ ወጥመድ ይሆናሉ።’” **4** የእግዚአብሔር መልዓክም እነዚህን ቃሎች ለእስራኤል ሕዝብ ሁሉ በተናገረ ጊዜ ሕዝቡ ጮሁ
አለቀሱም። **5** ያንንም ቦታ ቦኪም ብለው ጠሩት። በዚያም ለእግዚአብሔር መስዋዕትን አቀረቡ። **6** ኢያሱም ሰዎችን ወደ መንገዳቸው በላካቸው ጊዜ፣
የእስራኤል ሕዝብ ምድሩን ለመውሰድና የራሳቸው ለማድረግ ለእንዳንዳቸው ወደተመደበላቸው ቦታ ሄዱ። **7** ኢያሱ በሕይወት በነበረበት ዘመን፣ የእግዚአብሔርን
ታላቅ ስራንና ለእስራኤል ምን እንዳደረገም ያዩ ከእርሱ በኋላም በኖሩ ሽማግሌዎች ዘመን ሁሉ ሕዝቡ እግዚአብሔርን አገለገለ። **8** የእግዚአብሔር አገልጋይ፣
የነዌ ልጅ ኢያሱ፣ በመቶ አስር ዓመቱ ሞተ። **9** እነርሱም በኤፍሬም ኮረብታማው አገር በሰሜናዊው ገአስ ተራራ በምድሪቱ ድንበር በተዘጋጀለት ቦታ በተምናሔሬስ
ቀበሩት። **10** ያ ሁሉ ትውልድም ወደ አባቶቻቸው ተሰበሰቡ። ከእነርሱም በኋላ እግዚአብሔርንና እርሱ ለእስራኤል ያደረገውን ነገር የማያውቅ ሌላ ትውልድ
ተነሳ። **11** የእስራኤል ሕዝብም በእግዚአብሔር ዓይን ክፉ የሆነውን ነገር አደረጉ፣ የበኣል አማልክትንም አመለኩ። **12** ከግብጽ ምድር ያወጣቸውን
የአባቶቻቸውን አምላክ እግዚአብሔርን ተዉ። ሌሎች አማልክትን፣ በዙሪያቸው የነበሩ ሕዝቦች አማልክትን ተከተሉ፣ ለእነርሱም ሰገዱ። እግዚአብሔርንም
አስቆጡት ምከንያቱም **13** እግዚአብሔርን ትተዋልና፣ በኣልንና አስታሮትንም አምልከዋልና። **14** የእግዚአብሔርም ቁጣ በእስራኤል ላይ ነደደ፣ ንብረታቸውን
ለሰረቋቸው ወራሪዎች አሳልፎ ሰጣቸው። ከእንግዲህ ወዲህ ራሳቸውን ከጠላታቸው መከላከል እንዳይችሉ፣ በዙርያቸው በጠላቶቻቸው ብርታት ተይዘው እንደ
ነበሩት ባርያዎች አሳልፎ ሸጣቸው። **15** እስራኤል ለውጊያ በምትሄዱበት ስፍራ ሁሉ፣ ለእነርሱ እንደማለላቸው ይሸነፉ ዘንድ የእግዚአብሔር እጅ በእነርሱ ላይ
ይከፋ ነበር። ከዚህ የተነሳ እነርሱም በጣም ተጨነቁ። **16** ያን ጊዜ ንብረታቸውን ከሚሰርቋቸው ሰዎች ኃይል ያድናቸው ዘንድ እግዚአብሔር መሳፍንትን
አስነሳላቸው። **17** ይሁን እንጂ እነርሱ መሳፍንቶቻቸውን ሊሰሟቸው አልቻሉም። ለእግዚአብሔር አልታመኑም፣ ራሳቸውንም እንደ አመንዝራዎች ለሌሎች
አማልክት ሰጡ፣ አመለኳቸውም። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ይከተሉ ከነበሩት ከአባቶቻቸው መንገድ ወዲያውኑ ዘወር አሉ፣ እነርሱ ራሳቸው እንደ አባቶቻቸው
አላደረጉም። **18** እግዚአብሔር ለእነርሱ መሳፍንትን ባስነሳላቸው ጊዜ፣ መሳፍንቱ በኖሩበት ዘመን ሁሉ እግዚአብሔር መሳፍንቱን ረዳቸው፣ ከጠላቶቻቸውም
ጉልበት ሁሉ አዳናቸው። በጨቆኗቸውና መከራ ባሳዩአቸው ሰዎች ምክንያት ወደ እርሱ በጮኹ ጊዜ እግዚአብሔር ለእነርሱ አዘነላቸው። **19** ነገር ግን መስፍኑ
በሞተ ጊዜ፣ ተመልሰው አባቶቻው ያደርጉ ከነበረውም እጅግ የከፋ ነገር አደረጉ። ሌሎች አማልክትን በመከተል እነርሱን ያገለግሉና ያመልኩ ነበር። ክፉ
ድርጊታቸውንና እልኸኛ መንገዳቸውንም ለመተው ፈቃደኛ አልነበሩም። **20** የእግዚአብሔርም ቁጣ በእስራኤል ላይ ነደደ፣ እንዲህም አለ፣ “ይህ ሕዝብ
ለአባቶቻቸው የገባሁትን ቃል ኪዳኔን ስላፈረሱ፣ ድምጼንም ስላልሰሙ **21** ከአሁን በኋላ ኢያሱ ሲሞት ሳያወጣቸው የተዋቸውን አሕዛብ ከፊታቸው
አላወጣቸውም። **22** ይህን የማደርገው እስራኤል አባቶቻቸው እንዳደረጉት የእግዚአብሔርን መንገድ ይጠብቁና በዚያም ይሄዱ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ
እፈትናቸው ዘንድ ነው።” **23** እግዚአብሔርም እነዚያን አሕዛብ የተዋቸው፣ በፍጥነትም ያላስወጣቸው፣ ኢያሱም እንዲያሸንፋቸው ያልፈቀደለት ለዚህ ነው።

Judges 2:1

የእግዚአብሔር መልአክ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “እግዚአብሔርን የሚወክል መልአክ” ወይም 2) “እግዚአብሔርን የሚያገለግል መልዕከተኛ” ወይም 3) መልአክ መስሎ ከሰው ጋር የተነጋገረውን እግዚአብሔርን ራሱን ያመለክት ይሆናል የሚሉት ናቸው።

ከጌልገላ ወደ ቦኪም ወጣ
“ጌልገላን ትቶ ወደ ቦኪም ሄደ”

ቦኪም
መልአኩ ሕዝቡን ከገሰጻቸው በኋላ እስራኤላውያን ለዚህ ስፍራ በ2:5 ላይ የሰጡት ስም ይህ ነው። “ቦኪም” ማለት “ማልቀስ” ማለት ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

አላቸው
የእግዚአብሔር መልአክ ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩ ግልጽ ነው።

ከግብፅ አወጣችሁ
“ከግብፅ መራችሁ”

አባቶቻችሁ
“ቅድም አያቶቻችሁ” ወይም “የቀድሞ አባቶቻችሁ”

ከእናንተ ጋር የገባሁትን ቃል ኪዳኔን አፈረሱ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “አደርግላችኋለሁ ያልሁትን እንዳላደርግ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ድምፄን አልሰማችሁም
“ድምፅ” እዚህ ጋ የሚወክለው እግዚአብሔር የተናገረውን ነው። አ.ት፡ “ትዕዛዞቼን አልጠበቃችሁም” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ይህ ያደረጋችሁት ምንድነው?
ይህ ጥያቄ የተጠየቀው የእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔርን እንዳልታዘዙና በዚህም ምክንያት መከራ እንደሚደርስባቸው እንዲገነዘቡ ነው። አ.ት፡ “የከፋ ነገር አድርጋችኋል” (መልስ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

Judges 2:3

አሁን እናገራለሁ፣ ‘...ወጥመድ አልሆንባችሁም’
ይህ በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ያለ ትዕምርተ ጥቅስ ነው። ይህ ቀጥታ የሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ተቆጥሮ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “... ወጥመድ እንደማልሆንባችሁ አሁን እነግራችኋለሁ”

ለጎናችሁ እሾህ ይሆናሉ
ከነዓናውያን እስራኤላውያንን ማስቸገራቸው ለእስራኤላውያን የጎን ውጋት እንደሚሆኑባቸው ተነግሯል። አ.ት፡ “መከራ ያመጡባችኋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እሾክ
እስከ 7 ሴንቲ ሜትር የሚረዝምና ከአንዳንድ እጽዋት ጋር አብሮ የሚበቅል ትናንሽ የሚወጉ ነገሮች ያሉበት እንጨት

አማልክቶቻቸው ወጥመድ ይሆኑባችኋል
እስራኤላውያኑ የከነዓናውያንን አማልክት ማምለካቸው ልክ አደን የሚያድን ሰው ያጠመደው ወጥመድ እንስሳውን ይዞ ለሞት እንደሚዳርገው ሁሉ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሐሰተኞቹ አማልክት አጥፊዎቻቸው እንደሚሆኑ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ጮኹና አለቀሱ
“በብዙ ዕንባ አለቀሱ”

Judges 2:6

አሁን ኢያሱ በ ... ጊዜ
እዚህ ጋ “አሁን” የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው ዋነኛው ታሪክ የተገታበትን ለመለየት ነው። እዚህ ላይ ከኢያሱ በኋላ የነበረው ትውልድ እንዴት ኃጢአትን እንደ ሠሩና ሐሰተኞች አማልክትን እንዳመለኩ፣ እግዚአብሔር እንደቀጣቸው ሆኖም እንዲታደጓቸው መሳፍንትን እንደላከላቸው ተራኪው ጠቅለል ያለ ማብራሪያ መስጠት ይጀምራል። ይህ ማጠቃለያ የሚያበቃው በ2:23 ላይ ነው።

ኢያሱ **110** ዓመት ሆኖት በሞተ ጊዜ
በ1:1-2:5 ላይ ያለው ሁነት የተፈጸመው ከኢያሱ ሞት በኋላ ነው። ይህ በኢያሱ መጽሐፍ መጨረሻ የተፈጸሙት ሁነቶች በድጋሚ የታሰቡበት ነው።

ወደ ተመደበላቸው ስፍራ
ይህ አገላለጽ በይበልጥ ግልጽ መሆን ይችላል። አ.ት፡ “ እግዚአብሔር ወደ ሰጣቸው ስፍራ”

በሕይወት ዘመኑ
ይህ ማለት አንድ ሰው የኖረበት ጊዜ ማለት ነው። አ.ት፡ “ዕድሜውን ሙሉ”

ሽማግሌዎች
ይህ ማለት የሙሴን ሕግ ከማስጠበቅ አንጻር በማኅበራዊ ፍትሕና ሀይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ እስራኤላውያንን ሲረዱ የነበሩ ሰዎች ናቸው።

ከእርሱ የበለጠ ኖረዋል
ይህ ማለት ከሌላው የበለጠ ዓመት መኖር ነው። አ.ት፡ “እርሱ ከኖረው የበለጠ ኖረዋል”

ነዌ
ይህ የአንድ ሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

110 ዓመት ዕድሜው ላይ
“አንድ መቶ አሥር ዓመት ዕድሜው ላይ” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

Judges 2:9

ወደ ተመደበለት
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ወደ ሰጠው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ተምና ሔሬስ
ይህ በምድሪቱ ላይ የአንድ አካባቢ ስም ነው።

ገዓስ ተራራ
ይህ የአንድ ተራራ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ያ ትውልድ ሁሉ ደግሞ ወደ አባቶቻቸው ተሰብስቦው ነበር
“ደግሞም ወደ አባቶቻቸው ተሰብስበው ነበር” የሚለው ሐረግ የዚያ ትውልድ ሰዎች ሲሞቱ ከእነርሱ በፊት የሞቱት አባቶቻቸው ወዳሉበት ወደዚያው ስፍራ ነፍሶቻቸው ሄዷል ማለት ነው። መሞታቸውን በትህትና የመግለጽ መንገድ ነው።

አባቶች
ይህ ማለት የአንድ ሰው ወይም የአንድ ሕዝብ ወገን የሆኑ አያቶች ማለት ነው።

አረጀ
“ዕድሜው ገፋ” ወይም “ሸመገለ”

እግዚአብሔርን የማያውቅ
እዚህ ጋ “የማያውቅ” ማለት የቀደመው ትውልድ ያውቅ እንደ ነበረ እግዚአብሔር ወይም የእርሱ ኃይል በሕይወታቸው የሚሠራውን ያልተለማመዱ ማለት ነው።

Judges 2:11

በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነውን
የእግዚአብሔር ፊት የሚወክለው ፍርዱን ወይም ምዘናውን ነው። አ.ት፡ “በእግዚአብሔር ፍርድ ክፉ የሆነውን” ወይም “እግዚአብሔር ክፉ ነው ያለውን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የበኣል አማልክትን
ይህ የበኣል ብዙ ቁጥር ነው። “በኣል” የአንድ ሐሰተኛ አምላክ ስም ሆኖ ሳለ ቃሉ አብዛኛውን ጊዜ ከበኣል ጋር ለሚመለኩ ለሌሎች የተለያየዩ አማልክትም ጥቅም ላይ ውሏል። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ከእግዚአብሔር ተለዩ
ከእንግዲህ እግዚአብሔርን የማይታዘዙ እስራኤላውያን፣ በአካል ከእርሱ እንደተነጠሉና እንደተዉት ተቆጥሮ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አባቶቻቸው
“አያቶቻቸው” ወይም “የቀደሙት አባቶቻቸው”

ሌሎች አማልክትን ተከተሉ
የእስራኤላውያኑ ሐሰተኞች አማልክትን ማምለክ መጀመር እስራኤላውያን ሐሰተኞች አማልክትን ተከትለው እንደሄዱ ተቆጥሮ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሰገዱላቸው
ይህ የአምልኮትና ለአንድ ሰው አክብሮትን የመስጠት ተግባር ነው።

እግዚአብሔርን ለቁጣ አነሣሡት
“እግዚአብሔር እንዲቆጣ አስደረጉት”

አስታሮቶች
ይህ የአስታሮት ብዙ ቁጥር ሲሆን በተለያዩ ቅርጾች የምትመለክ እንስት አምላክ ናት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Judges 2:14

የእግዚአብሔር ቁጣ በእስራኤል ላይ ነደደ
የእግዚአብሔር ቁጣ እንደ እሳት እንደሚቃጠል ተገልጿል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር በእስራኤል ሕዝብ ላይ በጣም ተቆጣ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሀብታቸውን ለሚቀሟቸው ለወራሪዎች አሳልፎ ሰጣቸው
“ወራሪዎች ሀብታቸውን እንዲቀሟቸው ተዋቸው”

ከእንግዲህ ራሳቸውን ከጠላቶቻቸው መከላከል እንዳይችሉ፣ በዙሪያቸው ለተገዙላቸው ጠላቶቻቸው እንደ ባሪያ ሸጣቸው።
ጠላቶች እስራኤላውያኑን እንደ ባሪያ አድርገው እንዲወስዷቸው እግዚአብሔር መፍቀዱ ለባርነት ሸጣቸው ተብሎ ተነግሯል። “ለተገዙላቸው” የሚለው ቃል በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እርሱ፣ ጠላቶቻቸው ድል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንዲያደርጓቸውና ባሪያ አድርገው እንዲወስዷቸው፣ ከእንግዲህም ብርቱዎቹን ጠላቶቻቸውን መቋቋም እንዳይችሉ ፈቀደ”። (ዘይቤአዊ አነጋገር፣ አድራጊና ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ይሸነፉ ዘንድ የእግዚአብሔር እጅ በእነርሱ ላይ ነበረች
እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው የእግዚአብሔርን እጅ ነው። አ.ት፡ “ያሸንፏቸው ዘንድ እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን ረዳቸው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እጅግ ተጨንቀው ነበር
“እጅግ ተሠቃይተው ነበር”

ከዚያም እግዚአብሔር መሳፍንትን አስነሣላቸው
እግዚአብሔር እንዲፈርዱ ሰዎችን መሾሙ ሰዎችን እንዳነሣቸው ወይም ብድግ እንዳደረጋቸው ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከእነዚያ እጅ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚያመለክተው ኃይልን ነው። አ.ት፡ “ከጠላቶቻቸው ኃይል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መሳፍንታቸውን አልሰሙም
“መሳፍንታቸውን አልታዘዙም”

ራሳቸውን እንደ ሴተኛ አዳሪዎች ለሌሎች አማልክት ሰጡ፣ አመለኳቸውም
የሕዝቡ እግዚአብሔርን ከድቶ ሌሎች አማልክትን ማምለክ እንደ ሴተኛ አዳሪ እንዲቆጠሩ ማስደረጉ ተነግሯል። አ.ት፡ “ሐሰተኛ አማልክትን በማምለክ ከዱት”

አባቶቻቸው ከኖሩበት መንገድ ፈጥነው ተመለሱ
ሕዝቡ እግዚአብሔርን እንዳመለኩ እንደ ቀድሞ አባቶቻቸው ያለማድረጋቸው፣ ከአባቶቻቸው መንገድ ተመልሰው በሌላ አቅጣጫ እንደሄዱ እንዲነገርላቸው ሆኗል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አባቶቻቸው
“ቅድመ አያቶቻቸው” ወይም “የቀድሞ አባቶቻቸው”

Judges 2:18

እግዚአብሔር መሳፍንትን ባስነሣላቸው ጊዜ
እግዚአብሔር እንዲፈርዱ ሰዎችን መሾሙ ሰዎችን እንዳነሣቸው ወይም ብድግ እንዳደረጋቸው ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መሳፍንትን ለእነርሱ ... አዳኑአቸው
“እነርሱ” የሚለው ቃል እስራኤላውያንን ያመለክታል።

የጠላቶቻቸው እጅ
እዚህ ጋ “እጅ” እስራኤልን የሚጎዱበትን የጠላትን ኃይል ያመለክታል። አ.ት፡ “የጠላቶቻቸውን ኃይል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መስፍኑ በኖረበት ዘመን ሁሉ
“መስፍኑ በሕይወት እስከ ኖረ ድረስ”

ማዘን
ለአንድ ሰው ወይም ለአንድ ነገር የርኅራኄ መኖር

በጮኹ ጊዜ
አንድ ሰው ከመከራው የተነሣ የሚጮኸው ጩኸት፣ እስራኤላውያኑ በመከራቸው ጊዜ ስቃያቸውን ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሏል። አ.ት፡ “በተሠቃዩ ጊዜ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ተመለሱ
ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ከቶ ያለመታዘዛቸው በአካል ከእግዚአብሔር እንደ ተለዩ ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አባቶቻቸው
“ቅድመ አያቶቻቸው” ወይም “የቀድሞ አባቶቻቸው”

ሄደው ሌሎች አማልክቶችን አገለገሉ፣ አመለኳቸውም
የእስራኤላውያን ሌሎች አማልክትን ማምለክ ከሌሎች አማልክት ኋላ እየተራመዱ እንደሄዱ ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ሌሎች አማልክትን አገለገሉ፣ ሰገዱላቸውም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የትኛውንም ክፉ ሥራቸውን ወይም የእልኸኝነት መንገድ ለመተው እምቢ አሉ
“ክፉ ነገር ማድረጋቸውንና እልኸኛ መሆናቸውን ለማቆም እምቢ አሉ”። ይህ በአዎንታዊ አገላለጽ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ክፉ ነገር ማድረጋቸውንና እልኸኝነታቸውን ቀጠሉ”

Judges 2:20

የእግዚአብሔር ቁጣ በእስራኤል ላይ ነደደ
የእግዚአብሔር ቁጣ እንደ እሳት እንደ ነደደ ተገልጿል። ይህንን በመሳፍንት 2፡ 14 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።

ይህ ሕዝብ ተላልፏል
እዚህ ጋ “ሕዝብ” የሚወክለው ሰዎቹን ነው። አ.ት፡ “እነዚህ ሰዎች ተላልፈዋል” ወይም “እስራኤላውያኑ ተላልፈዋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አባቶች
እዚህ ጋ፣ ይህ የሚያመለክተው የአንድ ሰው ወይም የአንድ ሕዝብ ወገን የሆኑ አያቶችን ነው።

እነርሱ ድምፄን አልሰሙም
እዚህ ጋ “ድምፅ” የሚወክለው እግዚአብሔር የተናገረውን ነው። አ.ት፡ “እኔ ያዘዝኳቸውን አልታዘዙም” ወይም “አልታዘዙኝም”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የትኞቹም ሕዝቦች
እዚህ ጋ “ሕዝቦች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከእስራኤል በፊት በከነዓን ይኖሩ የነበሩትን የሕዝብ ወገን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እነርሱ የእግዚአብሔርን መንገድ ይጠብቃሉ፣ ይሄዱበታልም
ሰዎች እንዲኖሩት ወይም እንዲያደርጉት እግዚአብሔር የሚፈልገው ሕይወት እንደ መንገድ ወይም ጎዳና ተደርጎ ተነግሯል። እግዚአብሔርን የሚታዘዝ ሰው በመንገዱ ላይ እየሄደ እንዳለ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ፈጥኖ አስወጥቶ በኢያሱ እጅ አልሰጣቸውም
እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚሉት አንድ ነገር ስለሆነ መጣመር ይችላሉ። አ.ት፡ “ኢያሱ ፈጥኖ እንዲያሸንፋቸውና እንዲያስወጣቸው አላደረገም”

በኢያሱ እጅ
እዚህ ጋ “እጅ” ኃይልን የሚገልጽ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን “ኢያሱ” ራሱንና ሰራዊቱን ይወክላል። አ.ት፡ “በኢያሱና በሰራዊቱ ኃይል ሥር” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 እግዚአብሔር እነዚህን ሕዝቦች ሳያስወጣ ያስቀራቸው እስራኤልን ይልቁንም ደግሞ በከነዓን በተደረጉት ጦርነቶች ያልተዋጉትን በእስራኤል የሚገኙትን
እያንዳንዱ ሰው ይፈትን ዘንድ ነው። **2** (ይህንን ያደረገው ውጊያ የማያውቁትን አዲሱ የእስራኤል ትውልድ ውጊያን ለማስተማር ነው) ፦ **3** አምስቱ
የፍልስጤማውያን ነገስታት፣ ከነዓናውያንም ሁሉ፣ ሲዶናውያን እና ከበዓልኤርሞንየም ተራራ እስከ ሐማት መግቢያ ድረስ በሊባኖስ ተራራዎች ይኖሩ የነበሩትም
ኤውያውያን ነበሩ። **4** እነዚህ ሕዝቦች ሳይወጡ እንዲቀሩ የተደረጉት እግዚአብሔር እስራኤልን መፈተኛ እንዲሆኑ ነው፣ እነርሱ ለአባቶቻቸው በሙሴ በኩል
የሰጣቸውን ሕግ ይታዘዙና አይታዘዙ እንደሆነ ለማረጋገጥ ነው። **5** ስለዚህ የእስራኤል ሕዝብ በከነዓናውያን፣ ከኬጢያውያን፣ ከአሞራውያን፣ ከፌርዛውያን
ከኤውያውያንና ከኢያቡሳውያን ጋር አብረው ኖሩ። **6** ሴት ልጆቻቸውንም ሚስት እንዲሆኗቸው ወሰዷቸው፣ የራሳቸውን ሴት ልጆችም ለወንድ ልጆቻቸው
ሰጧቸው፣ አማልክቶቻቸውንም አመለኩ። **7** የእስራኤል ሕዝብ በእግዚአብሔር ዓይን ጸያፍ የነበረውን ነገር ፈጸሙ፣ አምላካቸው እግዚአብሔርንም ረሱ። የኣልንና
የአስታሮትን አማልክት አመለኩ። **8** ስለዚህም የእግዚአብሔር ቁጣ በእስራኤል ላይ ነደደ፣ ለመስጶጣምያ ንጉስ ለኩሰርሰቴም እጅ አሳልፎ ሰጣቸው።
የእስራኤል ሕዝብም ኩሰርሰቴን ለስምንት አመታት አገለገሉ። **9** የእስራኤል ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር በጮሁ ጊዜ፣ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ለመርዳት
የሚመጣና ካሉበት ሁኔታም የሚያድናቸው ሰው አስነሳ፦ ይህም ሰው የካሌብ ታናሽ ወንድም የቄኔዝ ልጅ ጎቶንያል ነበር። **10** የእግዚአብሔር መንፈስም
አበረታው፣ እስራኤላውያን ላይም ይፈርድ ነበር፣ ወደ ውጊያም ይወጣ ነበር። እግዚአብሔርም በመስጶጣምያ ንጉስ በኩሰርሰቴ ላይ ድልን ሰጠው።
ኩሰርሰቴንም ያሸነፈው የጎቶንያል እጅ ነበር። **11** ምድሪም ለአርባ ዓመት ሰላም አገኘች። የቄኔዝ ልጅ ጎቶንያልም ሞተ። **12** የእስራኤልም ሕዝብ ክፉ ነገሮችን
በማድረግ ደግመው እግዚአብሔርን ሳይታዘዙ ቀሩ፣ እርሱም ምን እንዳደረጉ ተመለከተ። ስለዚህ እስራኤል ክፉ ነገሮችን ስላደረጉና፣ እግዚአብሔርም ስላያቸው
የሞኣብ ንጉስ ኤግሎም እስራኤልን ለመውጋት በመጣ ጊዜ እግዚአብሔር ብርታትን ሰጠው። **13** ኤግሎምም ከአሞንና ከአማሌቃውያን ጋር ተባበረ፣ እነርሱም
ሄዱ እስራኤልንም አሸነፉ፣ ከዚያም የዘንባባ ከተማን ተቆጣጠሩ። **14** የእስራኤልም ሕዝብ የሞኣብን ንጉስ ኤግሎምን ለአስራ ስምንት አመታት አገለገሉ። **15**
ነገር ግን የእስራኤል ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር በጮሁ ጊዜ፣ እግዚአብሔር የሚረዳቸውን ሰው አስነሳ፣ ይህም ግራኝ የነበረው ብንያማዊው የጌራን ልጅ ናኦድ
ነው። የእስራኤልም ሕዝብ እርሱን ወደ ሞኣብ ንጉስ ወደ ኤግሎም የሚከፍሉትን ግብር አስይዘው ላኩት። **16** ናኦድ በሁለት በኩል የተሳለ ርዝመቱ አንድ ክንድ
የሆነ ሰይፍን ሰራ፤ ከልብሱም በታች በቀኝ ጭኑ አሰረው። **17** ግብሩንም ለሞኣብ ንጉስ ለኤግሎም ሰጠው። (ኤግሎም በዚያን ጊዜ እጅግ ወፍራም ሰው
ነበር።) **18** ናኦድም የግብሩን ክፍያ ካቀረበ በኋላ፣ ግብሩን ተሸክመው ገብተው ከነበሩ ሰዎች ጋር ወጣ። **19** ይሁን እንጂ ናኦድ በጌልጌላ አጠገብ የተቀረጹ
ምስሎች ተሰርተውበት ወደነበረው ስፍራ ሲደርስ ተመልሶ ሄደና እንዲህ አለ፦ “ንጉስ ሆይ፣ ለአንተ የሚስጥር መልዕክት አለኝ።” ኤግሎምም እንዲህ አለ፦
“ጸጥታ!” ስለዚህም አገልጋዮቹ ሁሉ ክፍሉን ትተው ወጡ። **20** ናኦድም ወደ እርሱ መጣ። ንጉሱም ቀዝቃዛ በሆነው ሰገነት ላይ ብቻውን ተቀምጦ ነበር።
ናኦድም እንዲህ አለ፣ “ለአንተ ከእግዚአብሔር የመጣ መልዕክት አለኝ።” ንጉሱም ከመቀመጫው ተነሳ። **21** ናኦድም ግራ እጁን ዘረጋና ሰይፉን ከቀኝ ጭኑ
አወጣ፣ ሰይፉንም በንጉሱ ሰውነት ውስጥ ሰካው። **22** የሰይፉም እጀታ ከስለቱ ጋር ወደ ሰውነቱ ገባ፣ ጫፉም በጀርባው ወጣ፣ ሞራም ስለቱን ሸፈነው፣ ናኦድም
ሰይፉን ከንጉሱ ሰውነት አላወጣውም። **23** ከዚያም ናኦድ ወደ በረንዳው ወጣና የሰገነቱን በር በንጉሱ ላይ ዘግቶ ቈለፈው። **24** ናኦድም ከሄደ በኋላ፣ የንጉሱ
ባሪያዎች መጡ፤ የሰገነቱም ደጅ ተቈልፎ አዩ፣ ስለዚህ እንዲህ ሲሉ አሰቡ፣ “ምናልባት በቀዝቃዛው ሰገነት ውስጥ እየተጸዳዳ ይሆናል።” **25** ንጉሱ የሰገነቱን
በር ሳይከፍት በቆየም ጊዜ ስራቸውን ችላ እንዳሉ እስኪሰማቸው ድረስ ስጋት እያደረባቸው ጠበቁ። ስለዚህ ቁልፉን ወሰዱና በሮቹን ከፈቱ፣ እነሆም ጌታቸው
ተጋድሞ፣ በወለሉም ላይ ወድቆ፣ ሞቶም አገኙት። **26** ባርያዎቹ ምን ማድረግ እንዳለባቸው እያሰቡ ሲጠባበቁ፣ ናዖድ አመለጠ፣ የጣኦታት ምስል በተቀረጸበት
ስፍራ በኩል አለፈ፣ ወደ ቤይሮታም አመለጠ። **27** በደረሰም ጊዜ፣ በኮረብታማው በኤፍሬም አገር ቀንደ መለከት ነፋ። ከዚያም የእስራኤል ሕዝብ ከእርሱ ጋር
ከኮረብታማው አገር ወረዱ፣ እርሱም ይመራቸው ነበር። **28** እርሱም እንዲህ አላቸው፣ “ተከተሉኝ፣ እግዚአብሔር ጠላቶቻችሁን፣ ሞዓባውያንን በእጃችሁ አሳልፎ
ሰጥቶአልና።” እነርሱም ተከትለውት ወረዱና የዮርዳኖስን መሻገርያ ከሞዓባውያን ቀምተው ያዙ፣ እነርሱም ማንም ሰው ወንዙን እንዳይሻገር ከለከሉ። **29**
በዚያን ጊዜም ከሞዓብ አሥር ሺህ የሚሆኑ ሰዎችን ገደሉ፣ የተገደሉትም ሁሉ ጠንካራና ኃይለኛ ሰዎች ነበሩ። አንድም እንኳ አላመለጠም። **30** በዚያም ቀን
ሞዓብ በእስራኤል ብርታት ድል ሆነች። ምድሪቱም ለሰማንያ ዓመት ዐረፈች። **31** ከናኦድ በኋላ የተነሳው መስፍን ስድስት መቶ የፍልስጥኤም ሰዎችን በበሬ
መንጃ የገደለው የዓናት ልጅ ሰሜጋር ነበር። እርሱም ደግሞ እስራኤልን ከአደጋ አዳነ።

Judges 3:1

አሁን እግዚአብሔር
እዚህ ጋ “አሁን” የሚለው ቃል የታሪኩን አዲስ ክፍል ይጀምራል።

እነዚህ ሕዝቦች
ይህ ተራኪው በ3:3 የሚዘረዝራቸውን የሕዝብ ወገኖች ያመለክታል።

በከነዓን በተደረጉት በየትኛውም ጦርነት ያልተሳተፉትን
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በከነዓን በየትኛውም ጦርነት ያልተዋጉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ካሁን በፊት ጦርነት የማያውቁትን አዲሱን የእስራኤል ትውልድ ውጊያ ለማስተማር ይህንን አደረገ
ይህ ከዋናው የታሪክ መስመር ይነጠላል። እግዚአብሔር አንዳንድ የሕዝብ ወገኖችን ለምን በከነዓን እንዳስቀራቸው ተራኪው ዳራዊ መረጃ ይሰጣል። አ.ት፡ “ቀድሞ በጦርነት ያልተዋጉ ወጣቶችን እንዴት መዋጋት እንዳለባቸው ለማስተማር እግዚአብሔር በእስራኤላውያን መካከል ሕዝቦች እንዲቀሩ አደረገ” (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

አምስቱ ነገሥታት
እነዚህ አምስት ነገሥታት ራሳቸውንና ሕዝባቸውን ይወክላሉ። አ.ት፡ “አምስቱ ነገሥታትና ሕዝቦቻቸው”

በኣል አርሞንኤም ተራራ
ይህ በእስራኤል ረጅሙ ተራራ ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ሐማትስ መተላለፊያ
ይህ በሰሜናዊ የከነዓን ወሰን የሚገኝ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Judges 3:4

እነዚህ ሕዝቦች ቀሩ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር እነዚህን ሕዝቦች በከነዓን አስቀራቸው” ወይም “እነዚህ ሕዝቦች በከነዓን መኖራቸውን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንዲቀጥሉ እግዚአብሔር ፈቀደላቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እንደ ዘዴ
“እንደ መንገድ”

እንደሆን - ለአባቶቻቸው ሰጣቸው
“እነርሱ” እና “የእነርሱ” የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው።

እርሱ የሰጣቸውን ትዕዛዝ
“እግዚአብሔር የሰጣቸውን ትዕዛዝ”

Judges 3:7

በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነውን
የእግዚአብሔር ፊት የሚወክለው የእግዚአብሔርን ፍርድ ወይም ምዘና ነው። ይህንን በመሳፍንት 2፡11 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “በእግዚአብሔር ፍርድ ክፉ የሆነውን” ወይም “እግዚአብሔር ክፉ ያለውን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አምላካቸውን እግዚአብሔርን ረሱ
እዚህ ጋ “ረሱ” ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ “መታዘዛቸውን አቆሙ” የሚል ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የእግዚአብሔር ቁጣ ነደደ
የእግዚአብሔር በጣም መቆጣት በሚቀጣጠል እሳት ተመስሎ ተነግሯል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር በጣም ተቆጣ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በኩስርስቴም እጅ ሸጣቸው
የእስራኤል ሕዝብ እንዲሸነፍ መፍቀዱ እግዚአብሔር ለኩስርስቴም እንደ ሸጣቸው ተቆጥሮ ተነግሯል። አ.ት፡ “ኩስርስቴምና ሰራዊቱ ድል እንዲያደርጋቸው ፈቀደላቸው”

በኩስርስቴም እጅ
እዚህ ጋ “እጅ” በፈሊጣዊ አነጋገር የሚወክለው ኃይልን ወይም መቆጣጠርን ነው። በተጨማሪም “ኩስርስቴም” ራሱንና ሰራዊቱን የሚወክል ተምሳሌት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና የሚለውን ተመልከት)

ኩስርስቴም
ይህ የአንድ ሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

አራም ነሃራይም
ይህ የአንድ ሀገር ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Judges 3:9

እግዚአብሔር አንድ ሰው አስነሣ
እግዚአብሔር አንድ የተለየ ሥራ እንዲሠራለት አንዱን መሾሙ ከተቀመጠበት እንዳስነሣው ወይም ብድግ እንዳደረገው ተቆጥሮ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ጎቶንያል - ቄኔዝ
የእነዚህን ሰዎች ስም በመሳፍንት 1፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

ሾመው
ይህ ማለት ታላቅ መሪ ለመሆን የሚያስፈልገው ብቃት እንዲኖረውና እንዲያጎለብተው እግዚአብሔር ጎቶንያልን ረዳው ማለት ነው።

በእስራኤል ላይ ፈረደ
እዚህ ጋ “ፈረደ” ማለት የእስራኤልን ሕዝብ መራቸው ማለት ነው።

ወደ ጦርነት ሄደ
በዚህ አባባል ውስጥ “እርሱ” የሚያመለክተው ጎቶንያልን ራሱንና የእስራኤልን ሰራዊት ነው። አ.ት፡ “ጎቶንያልና የእስራኤል ወታደሮች ከኩስርስቴም ሰራዊት ጋር ለመዋጋት ሄዱ”

እግዚአብሔር በአራም ንጉሥ በኩስርስቴም ላይ ድልን ሰጠው
እዚህ ጋ “ኩስርስቴም” የራሱን ሰራዊት ይወክላል። አ.ት፡ “የእስራኤል ሰራዊት የአራም ንጉሥ የኩስርስቴምን ሰራዊት ድል እንዲያደርግ እግዚአብሔር ረዳቸው”

የጎቶንያል እጅ
እዚህ ጋ “እጅ” ሰራዊትን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “የጎቶንያል ሰራዊት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ምድሪቱ ሰላም አገኘች
“ምድሪቱ” ጥቅም ላይ የዋለው በምድሪቱ የሚኖሩትን ሰዎች ለማመልከት ነው። አ.ት፡ “ሕዝቡ በሰላም ኖሩ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አርባ ዓመት
“40 ዓመት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

Judges 3:12

በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነውን
የእግዚአብሔር ፊት የሚወክለው የእግዚአብሔርን ፍርድ ወይም ምዘና ነው። ይህንን በመሳፍንት 2፡11 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “በእግዚአብሔር ፍርድ ክፉ የሆነውን” ወይም “እግዚአብሔር ክፉ ያለውን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር ለሞዓብ ንጉሥ ለዔግሎን ብርታትን ሰጠው
የነገር ስም የሆነው “ብርታት” እንደ ቅጽል ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር የሞዓብን ንጉሥ ዔግሎንን አበረታው” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

እስራኤላውያንን ድል እንዲያደርጋቸው ለሞዓብ ንጉሥ ለዔግሎን
እዚህ ጋ “የሞዓብ ንጉሥ ዔግሎን” የሚወክለው ራሱንና ሰራዊቱን ነው። አ.ት፡ “የእስራኤልን ሰራዊት በሚወጉበት ጊዜ ለሞዓብ ንጉሥ ለዔግሎንና ለወታደሮቹ”

ዔግሎን
ይህ የንጉሥ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የዘንባባ ከተማ
ይህ ሌላው የኢያሪኮ ስም ነው። ይህንን በመሳፍንት 1፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

አሥራ ስምንት ዓመት
“18 ዓመት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

Judges 3:15

ወደ እግዚአብሔር ጮኹ
ይህ ማለት በሩቅ ወዳለ ወደሌላው መጣራት ወይም ከፍ ባለ ድምፅ መናገር ማለት ነው። ደግሞም አንድ ሰው፣ በተለይም እግዚአብሔር እንዲረዳ መጠየቅ ሊሆንም ይችላል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አንድ ሰው አስነሣላቸው
እግዚአብሔር አንድ የተለየ ሥራ እንዲሠራለት አንዱን መሾሙ ሰውየውን ከተቀመጠበት እንዳስነሣው ወይም ብድግ እንዳደረገው ተቆጥሮ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ናዖድ = ጌራ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ግራኝ
ናዖድ በግራ እጁ በተሻለ ሁኔታ ሰይፍ መያዝ ይችል ነበር።

Judges 3:16

አንድ ክንድ
ዘመናዊ የርዝመት መለኪያ መጠቀም የሚያስፈልግ ከሆነ ይህንን ለማድረግ ሁለት መንገዶች አሉ። አ.ት፡ “46 ሴንቲ ሜትር” ወይም “ግማሽ ሜትር ገደማ” (ርቀት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚለውን ተመልከት)

በቀኝ ታፋው በኩል በልብሱ ውስጥ ታጠቀው
“በቀኝ መታጠቂያው በኩል በልብሱ ስር ታጠቀው”

ታፋ
በወገብና በጉልበት መካከል ያለ የእግር ክፍል

በዚህ ጊዜ ዔግሎን በጣም ወፍራም ሰው ነበር
እዚህ ጋ “በዚህ ጊዜ” ጥቅም ላይ የዋለው ዋናው የታሪኩ መስመር መቆሙን ምልክት ለማድረግ ነው። እዚህ ጋ ተራኪው ስለ ዔግሎን ዳራዊ መረጃ ይሰጣል። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

Judges 3:19

የተቀረጹ ምስሎች ወደተሠሩበት ቦታ ወደ ጌልጌላ አቅራቢያ በደረሰ ጊዜ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሰዎች የተቀረጹ ምስሎች ወደ ሠሩበት ወደ ጌልጌላ አቅራቢያ በደረሰ ጊዜ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በነፋሻማው የላይኛው ክፍል
ይህ ከዝቅተኛው ቀጥሎ ወደ ላይ ያለ ክፍል ሲሆን ለማረፊያነትና በቀኑ ሞቃታማ ሰዓት ቀዝቀዝ ብሎአቸው የሚቆዩበት ክፍል ነው።

ንጉሡ ከመቀመጫው ተነሣ
መቆም፣ የእርሱን መልዕክት በማድመጥ እግዚአብሔርን የማክበር ምልክት ነው።

Judges 3:21

የሰይፉ ጫፍ በጀርባው በኩል ወጣ
“የሰይፉ ስለት መጨረሻ በጀርባው በኩል ወጣ”

በረንዳ
ጣሪያው የተሸፈነና ግድግዳው አጠር ያለ ውጫዊ ክፍል

Judges 3:24

በርግጥ ራሱን እያስታገሰ ነው
ይህ ስለሚጸዳዳ ሰው የሚነገር የትህትና አነጋገር ነው።

ተግባራቸውን ቸል ያሉ ያህል እስኪሰማቸው ድረስ
አንዳች ችግር ተፈጥሮ እንደሆነና የንጉሡን የግል ክፍሉን መክፈትም ቢሆን የእነርሱ ተግባር እንደሚሆን በማሰብ ሲጨነቁ ቆዩ።

ቁልፍ ወስደው ከፈቷቸው
“ቁልፍ ወስደው በሮቹን ከፈቷቸው”

Judges 3:26

አገልጋዮቹ ሲጠባበቁት ሳሉ - ናዖድ አመለጠ
ይህ የሚነግረን አገልጋዮቹ የላይኛውን ክፍል በሮች በመክፈት ንጉሡ ሞቶ ሳያገኙት በፊት የሆነውን ነገር ነው። አ.ት፡ “አገልጋዮቹ ከላይኛው ክፍል ውጪ በመጠበቅ ላይ እያሉ … ናዖድ አመለጠ”

ሴርታይም
ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

በደረሰ ጊዜ
ይህ በይበልጥ ግልጽ መሆን ይችላል። አ.ት፡ “ወደ ሴርታይም በደረሰ ጊዜ”

Judges 3:28

እግዚአብሔር ጠላቶቻችሁን ድል ያደርጋቸዋል
እስራኤላውያን ጠላቶቻቸውን እንዲያሸንፉ እግዚአብሔር መርዳቱ እግዚአብሔር ከጠላቶቻቸው ጋር ተዋግቶ ድል እንደሚያደርግ ጦረኛ ተቆጥሮ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መሻገሪያዎቹን ያዙ
“መሻገሪያዎቹን መቆጣጠር ቻሉ”

መሻገሪያዎች
ጥልቀት የሌለውና በቀላሉ ሊሻገሩት የሚቻል የወንዝ አካባቢ

ማንም እንዲሻገር አልፈቀዱም
“ማንም እንዳይሻገር ከለከሉ”

አሥር ሺህ ሰዎች
“10,000 ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ብቁ የሆኑ ሰዎች
“የሚችሉ ሰዎች” ወይም “በሚገባ መዋጋት የሚችሉ ሰዎች”

ሞዓብ ለእስራኤል ጉልበት ተገዛ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የእስራኤል ወታደሮች ሞዓባውያንን ድል አደረጓቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የእስራኤል ጉልበት
እዚህ ጋ “ጉልበት” የሚወክለው የእስራኤልን ሰራዊት ነው።

ምድሪቱ ዐርፋ ነበር
እዚህ ጋ “ምድር” የሚወክለው ሕዝብን ነው። አ.ት፡ “እስራኤላውያን በሰላም ኖሩ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሰማንያ ዓመት
“80 ዓመት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

Judges 3:31

መስፍን
እስራኤላውያን ነገሥታት ሳይኖሯቸው በፊት፣ ወደ ተስፋይቱ ምድር ከገቡ በኋላ፣ በችግራቸው ጊዜ እንዲመሯቸው እግዚአብሔር መሳፍንትን ሾመላቸው። መሳፍንት አብዛኛውን ጊዜ እስራኤላውያንን ከጠላቶቻቸው ይታደጓቸው ነበር።

ሰሜጋር
የአንድ ሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ዓናት
የአንድ ሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

600 ሰዎች
“ስድስት መቶ ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

በሬዎችን ለመንዳት የሚያገለግል በትር
በበሬ የሚያርሱ ገበሬዎች በሬዎቹ ወደ ፊት እንዲሄዱላቸው ለመምታት ሹልነት ያለው በትር ይጠቀሙ ነበር። አ.ት፡ “በሬዎቹን ለመንዳት የሚጠቀሙበት በትር” ወይም “በሬዎችን መምሪያ በትር”

እርሱም ደግሞ እስራኤልን ከአደጋ አዳናቸው
“አደጋ” የሚለው ቃል የእስራኤልን ሕዝብ ለመጉዳት የሞከሩ ጠላቶቻቸውን ያመለክታል። አ.ት፡ “እርሱም ደግሞ የእስራኤልን ሕዝብ ከጠላቶቻቸው አዳናቸው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 ናዖድም ከሞተ በኋላ፣ የእስራኤል ሕዝብ ክፉ ነገሮችን በመስራት እንደገና እግዚአብሔርን አልታዘዙም፣ እርሱም ምን እንዳደረጉ ተመለከተ። **2** እግዚአብሔርም በሐጾር ሆኖ ይገዛ በነበረው፣ በከነዓን ንጉሥ በኢያቢስ እጅ አሳልፎ ሰጣቸው። የሠራዊቱም አለቃ ሲሣራ ተብሎ ይጠራ ነበር፣ እርሱም የአሕዛብ በሆነችው በአሪሶት ኖረ። **3** የእስራኤልም ሕዝብ ለእርዳታ ወደ እግዚአብሔር ጮኹ፣ ምክንያቱም ሲሳራ ዘጠኝ መቶ የብረት ሰረገሎች ነበሩት፣ እርሱም የእስራኤልን ሕዝብ ለሀያ ዓመት በኃይል አስጨንቆ ገዛቸው። **4** በዚያ ጊዜ ነቢይቱ የለፊዶት ሚስት ዲቦራ፣ በእስራኤል ላይ ዋነኛ ፈራጅ ነበረች። **5** እርስዋም በኮረብታማው በኤፍሬም አገር በራማና በቤቴል መካከል ካለው የዲቦራ ዘንባባ ዛፍ ስር ትቀመጥ ነበር፣ የእስራኤልም ሕዝብ ለክርክራቸው መፍትሔ ለማግኘት ወደ እርስዋ ይመጡ ነበር። **6** እርስዋም በንፍታሌም ውስጥ ካለው ከቃዴስ የአቢኒኤምን ልጅ ባርቅን ጠራች። እንዲህም አለችው፣ “የእስራኤል አምላክ፣ እግዚአብሔር፣ እንዲህ ይልሃል፣ ‘ወደ ታቦር ተራራ ሂድ፣ ከንፍታሌምና ከዛብሎን አሥር ሺህ ሰዎች ከአንተ ጋር ውሰድ። **7** እኔ የኢያቢስን ሠራዊት አዛዥ ሲሣራን በቂሶን ወንዝ አቅራቢያ ከሰረገሎቹና ከሰራዊቱ ጋር እንዲያገኝህ አስወጣዋለሁ፣ እኔም በእርሱ ላይ ድልን እሰጥሃለሁ።’” **8-9** ባርቅም እንዲህ አላት፣ “አንቺ ከእኔ ጋር ከሄድሽ እኔም እሄዳለሁ፣ ነገር ግን አንቺ ከእኔ ጋር ካልሄድሽ እኔም አልሄድም።” እርስዋም እንዲህ አለች፣ “በእውነት ከአንተ ጋር እሄዳለሁ። ይሁን እንጂ፣ አንተ የምትሄድበት መንገድ ወደ ክብር አያደርስህም፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር ሲሣራን በጥንካሬዋ ድል ታደርገው ዘንድ ለሴት አሳልፎ ይሰጣልና።” ከዚያም ዲቦራ ተነሥታ ከባርቅ ጋር ወደ ቃዴስ ሄደች። **10** ባርቅም የዛብሎንና የንፍታሌም ሰዎች በአንድነት ወደ ቃዴስ እንዲመጡ ጠራቸው። አሥር ሺህም ሰዎች ተከተሉት፣ ዲቦራም ከእርሱ ጋር ሄደች። **11** ቄናዊው ሔቤርም ከቄናውያን ራሱን ለየ፣ እነርሱም የሙሴ አማት የኦባብ ልጆች ነበሩ፣ እርሱም በቃዴስ አጠገብ በጻዕናይም በነበረው በበሉጥ ዛፍ ጥግ ድንኳኑን ተከለ። **12** ለሲሳራም የአቢኔኤም ልጅ ባርቅ ወደ ታቦር ተራራ እንደወጣ በነገሩት ጊዜ፣ **13** ሲሣራም ሰረገሎቹን ሁሉ፣ ዘጠኝ መቶ የብረት ሰረገሎች፣ ከእርሱም ጋር የነበሩትን ወታደሮቹን ሁሉ፣ የአሕዛብ ከሆነችው ከአሪሶት ወደ ቂሶን ወንዝ ሰበሰባቸው። **14** ዲቦራም ባርቅን እንዲህ አለችው፣ “ሂድ! ዛሬ እግዚአብሔር በሲሣራ ላይ ድል እንድታደርግ በእጅህ አሳልፎ የሚሰጥበት ቀን ነውና። እነሆ እግዚአብሔር ከፊትህ አልወጣምን?” ስለዚህ ባርቅ ከታቦር ተራራ አብረውት ከነበሩት አስር ሺህ ሰዎች ጋር ወረደ። **15** እግዚአብሔርም የሲሣራን ሰራዊት ግራ አጋባ፣ ሰረገሎቹንም ሁሉ፣ ሠራዊቱንም ሁሉ፣ የባርቅም ሰዎች የሲሳራን ሰዎች አጠቋቸው፣ ሲሳራም ከሰረገላው ወርዶ በእግሩ ሸሸ። **16** ባርቅ ግን ሰረገሎችንና ሠራዊቱን እስከ አሪሶት ድረስ አባረራቸው፣ የሲሣራም ሠራዊት ሁሉ በሰይፍ ስለት ተገደሉ፣ አንድ ሰው እንኳ አልቀረም። **17** ሲሳራ ግን በእግሩ ወደ ቄናዊው ሔቤር ሚስት፣ ወደ ኢያዔል ድንኳን ሸሸ፣ ምክንያቱም በሐሶር ንጉስ በኢያቢስና፣ በቄናዊው በሔቤር ቤት መካከል ሰላም ስለነበር ነው። **18** ኢያዔልም ሲሣራን ለመገናኘት ወጣች እንዲህም አለችው፣ “ግባ፣ ጌታዬ ሆይ፤ ወደ እኔ ግባ አትፍራም።” እርሱም ወደ እርስዋ ወደ ድንኳንዋ ገባ፣ በብርድ ልብስም ሸፈነችው። **19** እርሱም እንዲህ አላት፣ “ጠምቶኛልና፣ እባክሽ የምጠጣው ጥቂት ውኃ ስጭኝ።” እርስዋም ከቆዳ የተሰራ የወተቱን ማስቀመጫ ከፍታ የሚጠጣ ሰጠችው፣ ከዚያም እንደገና ሸፈነችው። **20** እርሱም አላት፣ “በድንኳኑ በር ላይ ቁሚ። ሰውም ቢመጣና ‘በዚህ ሰው አለን?’ ብሎ ቢጠይቅሽ ‘የለም’ በይ።” **21** ከዚያም የሔቤር ሚስት ኢያዔል የድንኳን ካስማ ወሰደች በእጅዋም መዶሻ ያዘች በቀስታ ወደ እርሱ ሄደች፣ እርሱም በከባድ እንቅልፍ ላይ ነበር፣ እርስዋም ካስማውን በጆሮ ግንዱ ላይ ሰካችው፣ ካስማውም ሰውነቱን ወግቶ አለፈና ወደ መሬት ጠለቀ። እርሱም ሞተ። **22** ባርቅም ሲሣራን ሲያባርር፣ ኢያዔል ልታገኘው ወጣችና እንዲህ አለችው፣ “ና፣ የምትፈልገውንም ሰው አሳይሃለሁ።” እርሱም ወደ ውስጥ ከእርስዋ ጋር ገባ፣ እነሆም በዚያ ሲሣራ ሞቶ ተጋድሞ ነበር፣ ካስማውም በጆሮ ግንዱ ውስጥ ተሰክቶ አገኘው። **23** ስለዚህ በዚያ ቀን እግዚአብሔር የከነዓንን ንገሥ ኢያቢስን በእስራኤል ሕዝብ ፊት አሸነፈው። **24** የእስራኤል ሕዝብ ጉልበት የከነዓን ንጉሥ ኢያቢስን እስከሚያጠፉ ድረስ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየበረታ መጣ።

Judges 4:1

ናዖድ
የዚህን ሰው ስም በመሳፍንት 3፡15 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነውን
የእግዚአብሔር ፊት የሚወክለው የእግዚአብሔርን ፍርድ ወይም ምዘና ነው። ይህንን በመሳፍንት 2፡11 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “በእግዚአብሔር ፍርድ ክፉ የሆነውን” ወይም “እግዚአብሔር ክፉ ያለውን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር በከነዓን ንጉሥ በኢያቢስ እጅ ሸጣቸው
እዚህ ጋ “እጅ” የሚያመለክተው በእስራኤል ላይ የበረታውን የኢያቢስን ኃይል ነው። እግዚአብሔር ለኢያቢስ ኃይል ለመስጠት መወሰኑ እርሱ ሕዝቡን ለኢያቢስ እንደሸጣቸው ተነግሯል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር በከነዓን ንጉሥ በኢያቢስ ኃይል እንዲሸነፉ ፈቀደ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ኢያቢስ - ሲሣራ
እነዚህ የወንዶቹ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ሐጾር = ሐሮሼትሐጎይም
እነዚህ የከተሞች ወይም የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ዘጠኝ መቶ የብረት ሠረገላዎች
“900 የብረት ሠረገላዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ሃያ ዓመት
“20 ዓመት”

Judges 4:4

አሁን
ይህ ቃል ዋነኛውን የታሪክ መስመር ለማቆም ምልክት ሆኖ ጥቅም ላይ ውሏል። እዚህ ጋ ተራኪው ስለ ዲቦራ ዳራዊ መረጃ ይናገራል። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ዲቦራ
ይህ የአንዲት ሴት ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ለፊዶት
ይህ የአንድ ሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መስፍን
እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በመከራቸው ጊዜ የሚመሯቸው መሳፍንትን ሾመላቸው። አብዛኛውን ጊዜ መሳፍንቱ ከጠላቶቻቸው ያድኗቸው ነበር።

የዲቦራ ዘንባባ
ይህ ዛፍ በዲቦራ ስም ተጠርቷል።

Judges 4:6

ባራቅ - አቢኒኤም
እነዚህ የወንዶቹ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የታቦር ተራራ
ይህ የአንድ ተራራ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

አሥር ሺህ ሰዎች
“10,000 ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

አወጣዋለሁ
እዚህ ጋ “እኔ” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ያመለክታል።

ሲሣራን አወጣዋለሁ
እዚህ ጋ “ሲሣራ” ራሱንና ሰራዊቱን ይወክላል። አ.ት፡ “ሲሣራንና ሰራዊቱን አወጣለሁ”

ማውጣት
ሰዎች ከምቹ ስፍራቸው ወጥተው እንዲመጡ ማድረግ

ሲሣራ - ኢያቢስ
የእነዚህን ወንዶች ስም በመሳፍንት 4፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት

ቂሶን
ይህ የወንዝ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Judges 4:8

ባርቅ
የዚህን ሰውዬ ስም በመሳፍንት 4፡6 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

እየሄድክበት ያለው መንገድ ወደ ክብር አያደርስህም
ባርቅ የሚያደርገው ምርጫ የሚጓዝበትን መንገድ እንደ መምረጥ ተቆጥሯል። “ክብር”ም ለአንድ ተጓዥ እንደ መዳረሻ ተቆጥሮለታል። አ.ት፡ “በምታደርገው ነገር ማንም አያከብርህም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር ሲሣራን በሴት እጅ ላይ አሳልፎ ይሰጠዋል
እዚህ ጋ “እጅ” የሚያመለክተው እርሱን ለመግደል ያላትን ኃይል ነው። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ሲሣራን ሴት እንድታሸንፈው ያደርጋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሲሣራ
የዚህን ሰውዬ ስም በመሳፍንት 4፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ዲቦራ
የዚህችን ሴት ስም በመሳፍንት 4፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Judges 4:11

አሁን
ይህ ቃል ዋነኛውን የታሪክ መስመር ለማቆም ምልክት ሆኖ ጥቅም ላይ ውሏል። እዚህ ጋ ተራኪው ስለ ቄናዊው ሔቤር ዳራዊ መረጃ ይናገራል። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ሔቤር - ኦባብ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ቄናዊ
ይህንን በመሳፍንት 1፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

የሙሴ አማች
“የሙሴ የሚስቱ አባት”

ጻዕናይም
ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Judges 4:12

ለሲሣራ በነገሩት ጊዜ
እዚህ ጋ “እነርሱ” የሚለው ቃል በተለየ ሁኔታ ማንንም አይገልጽም። አ.ት፡ “አንድ ሰው ለሲሣራ ሲነግረው”

ሲሣራ
የዚህን ሰውዬ ስም በመሳፍንት 4፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ባርቅ - አቢኒኤም - የታቦር ተራራ
እነዚህን ስሞች በመሳፍንት 4፡6 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

ሲሣራ ሠረገላዎቹን ሁሉ ሰበሰበ
እዚህ ጋ “ሠረገላዎች” የሚወክሉት ሠረገላዎቹን የሚነዱ ወታደሮችን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ዘጠኝ መቶ የብረት ሠረገላዎች
“900 የብረት ሠረገላዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

አሪሶት ሐጎይም
የዚህችን ከተማ ስም በመሳፍንት 4፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የቂሶን ወንዝ
ይህንን በመሳፍንት 4፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Judges 4:14

እግዚአብሔር ድልን ሰጥቶሃል
ዲቦራ ስለ ድሉ እርግጠኛ ስለ ነበረች ባርቅ አስቀድሞ ጦርነቱን እንዳሸነፈ አድርጋ ትናገራለች። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ድልን ይሰጥሃል”

የሚመራህ እግዚአብሔር አይደለምን?
የሚዋጉት ከእግዚአብሔር ጋር ወግነው መሆኑን ባርቅን ለማስታወስ ዲቦራ ይህንን ጥያቄ ትጠይቃለች። አ.ት፡ “እግዚአብሔር እንደሚመራህ አስታውስ” (መልስ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ከአሥር ሺህ ጋር
“ከ10,000 ጋር” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Judges 4:15

እግዚአብሔር ሲሣራን፣ ሠረገላዎቹንና ሰራዊቱን ሁሉ አደናገራቸው
“እግዚአብሔር፣ ሲሣራን፣ ሠረገላዎቹንና ሰራዊቱን ሁሉ በአግባቡ ማሰብ እንዳይችሉ አደረጋቸው” ወይም “እግዚአብሔር፣ ሲሣራ፣ ሠረገላዎቹና ሰራዊቱ ሁሉ እንዲደነግጡ አደረጋቸው”

ሠረገላዎቹ ሁሉ
እዚህ ጋ “ሠረገላዎቹ” የሚለው ቃል ሠረገላዎቹን የሚነዱትን ወታደሮች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ሠረገላዎቹን የሚነዱት ሰዎች ሁሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ባርቅ አሳደደ
እዚህ ጋ “ባርቅ” የሚወክለው ራሱንና ሰራዊቱን ነው። አ.ት፡ “ባርቅና ወታደሮቹ አሳደዱ”

አሪሶት
ይህንን በመሳፍንት 4፡2 ላይ በተረጎምክበት በዚያው መልክ ተርጉመው።

የሲሣራ ሰራዊት በሙሉ በሰይፍ ስለት ተገደሉ
እዚህ ጋ “ሰይፍ” የሚወክለው ወታደሮች በጦርነት ላይ የሚጠቀሙባቸውን ሰይፍና ሌሎች የጦር መሣሪያዎች ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ባርቅና ወታደሮቹ የሲሣራን ወታደሮች በሙሉ በሰይፍ ገደሏቸው”

Judges 4:17

ሲሣራ - ኢያቢስ - ሐጾር
እነዚህን ስሞች በመሳፍንት 4፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

በእግሩ ሸሸ
በፈረስ ወይም በሠረገላ ከመጋለብ ይልቅ በእግሩ መሮጡ ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ኢያዔል
ይህ የአንዲት ሴት ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ሔቤር
የዚህን ሰውዬ ስም በመሳፍንት 4፡11 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ቄናዊ
ይህንን በመሳፍንት 1፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ዘወር በል
ይህ ማለት ከሚደረገው ጉዞ ለማረፍ የሚደረግ የመንገድ ለውጥ ነው። አ.ት፡ “ወዲህ ና”

ብርድ ልብስ
ከሱፍ ወይም ከእንስሳት ቆዳ የሚሠራና በመኝታ ጊዜ ሙቀት እንዲሰጥ የሚለበስ ሰፊ የአካል መሸፈኛ ነው።

Judges 4:19

ተናገራት
“ሲሣራ ለኢያኤል ተናገራት”

Judges 4:21

የድንኳን ካስማ
የድንኳኑን ማዕዘን ከምድር ጋር እንዲያያይዝ እንደ ትልቅ መንጠቆ በመዶሻ የሚመታ የሾለ እንጨት ወይም ብረት

መዶሻ
የድንኳኑን ካስማ ወደ መሬት ለማጥለቅ ክብደት ካለው እንጨት የሚሠራ መሣሪያ

ጥልቅ እንቅልፍ
አንድ ሰው ጥልቀት ካለው ጉድጓድ ውስጥ በቀላሉ መውጣት እንደማይችል ሁሉ ጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ ያለ ሰውም በቀላሉ አይነቃም። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ባርቅ ያሳድደው ነበር
“ባርቅ ያባርረው ነበር” ወይም “ባርቅ ይከተለው ነበር”

Judges 4:23

እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ፊት የከነዓንን ንጉሥ ኢያቢስን ድል አደረገው
እግዚአብሔር እስራኤላውያኑ ኢያቢስንና ሰራዊቱን እንዲያሸንፏቸው ማድረጉ የእስራኤል ሕዝብ እያዩ እግዚአብሔር ራሱ ኢያቢስን ድል እንዳደረጋቸው ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ጉልበት
“ወታደራዊ ኃይል”

ደመሰሱት
እዚህ ጋ “እርሱ” የሚያመለክተው ራሱንና ሰራዊቱን የሚወክለውን ኢያቢስን ነው። አ.ት፡ “ኢያቢስንና ሰራዊቱን ደመሰሱ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 5

1 በዚያም ቀን ዲቦራና የአቢኒኤም ልጅ ባርቅ ይህንን መዝሙር ዘመሩ፦ 2 “በእስራኤል ውስጥ መሪዎች የመሪነት ስፍራውን ሲይዙ፣ ሕዝቡም በደስታና
በፈቃዳቸው ለጦርነት ሲወጡ፣ እግዚአብሔርን እናመሰግናለን! 3 ስሙ፣ እናንተ ነገሥታት! አድምጡ፣ እናንተም መኳንንት! እኔ፣ እኔ ለእግዚአብሔር
እዘምራለሁ፤ ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር ምስጋናን እዘምራለሁ። 4 እግዚአብሔር ሆይ፣ ከሴይር በወጣህ ጊዜ፣ ከኤዶምያስም በተነሳህ ጊዜ፣ ምድር
ተናወጠች፣ ሰማያት ደግሞ ተንቀጠቀጡ፤ ደመናትም ደግሞ ውኃን አንጠባጠቡ። 5 ተራሮች በእግዚአብሔር ፊት ተንቀጠቀጡ፤ ሲና ተራራም እንኳ በእስራኤል
አምላክ በእግዚአብሔር ፊት ተንቀጠቀጠ። 6 በዓናት ልጅ በሰሜጋር ዘመን፣ በኢያዔል ዘመን፣ መንገዶች ተተዉ፣ መንገደኞችም በጠመዝማዛ መንገድ ብቻ
ይጠቀሙ ነበር። 7 እኔ ዲቦራ አለቃ እስከሆንሁበት ጊዜ ድረስ፣ ለእስራኤል እናት ሆኜ አለቅነትን እስከወሰድሁበት ጊዜ ድረስ፣ በእስራኤል ውስጥ ገበሬዎች
አልነበሩም። 8 አዲስ አማልክትን መረጡ፣ በከተማዋ ደጆች ጦርነት ነበረ፤ በእስራኤል ውስጥ በአርባ ሺህ መካከል ጋሻ ወይም ጦር አልታየም። 9 ልቤ ወደ
እስራኤል አለቆች ሄደ፣ በሕዝቡ መካከል ራሳቸውን በደስታ ስለ ሰጡትም እግዚአብሔርን እናመሰግናለን። 10 እናንተ በነጫጭ አህዮች ላይ ትንሽ የምንጣፍ
ኮርቻ ላይ ተቀምጣችሁ የምትጓዙ፣ በመንገድም የምትሄዱ እናንተ ስለዚህ ነገር አስቡ። 11 በማጠጫው ስፍራ መካከል ሆነው በጎችን የሚከፋፍሉትን ሰዎች
ድምጽ ስሙ። የእግዚአብሔርን የጽድቅ ድርጊትና ተዋጊዎቹ በእስራኤል ውስጥ የሰሩትን የጽድቅ ተግባር በዚያ እንደገና እየተናገሩ ነው። ያን ጊዜ የእግዚአብሔር
ሕዝብ ወደ ከተማው በሮች ወረዱ። 12 ንቂ፣ ንቂ፣ ዲቦራ ሆይ! ንቂ፣ ንቂ፣ መዝሙርን ዘምሪ! ባርቅ ሆይ፣ ተነሣ፣ የአቢኒኤም ልጅ ሆይ፣ ምርኮኞችህን ማርከህ
ውሰድ። 13 የዚያን ጊዜ የተረፉት ወደ ኃያላኑ መጡ፣ ከተዋጊዎቹም መካከል የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደ እኔ መጡ። 14 መሰረታቸው ከአማሌቅ ወገን የሆኑ
ከኤፍሬም መጡ፤ የብንያም ሕዝብም ተከተሉህ። ከማኪርም አዛዦች ወረዱ፣ የስልጣን በትር የያዙ ከዛብሎን ወረዱ። 15 የይሳኮርም መሳፍንት ከዲቦራ ጋር
ነበሩ፤ ይሳኮርም ከባርቅ ጋር በትዕዛዙ መሰረት ከኋላው እየተከተለ ወደ ሸለቆው ሄደ። በሮቤል ጎሳ መካከል ታላቅ የልብ ምርምር ነበረ። 16 የበጎች እረኞች
ለመንጎቻቸው በፉጨት ሲጫወቱ እያዳመጥህ በእሳት ማንደጃ መካከል ለምን ተቀመጥህ? በሮቤል ጎሳ መካከል ታላቅ የልብ ምርምር ነበረ። 17 ገለዓድ
በዮርዳኖስ ማዶ ተቀመጠ፤ ዳን ለምን በመርከብ ውስጥ ቀረ? አሴርም በባሕሩ ዳርቻ ቀረ፣ በወንዞቹም ዳርቻ ኖረ። 18 ዛብሎን ነፍሱን ወደ ሞት አሳልፎ
የሚሰጥ ሕዝብ ነው፣ ንፍታሌምም በውጊያ ሜዳ ላይ ነው። 19 ነገሥታት መጡ ተዋጉም፣ የዚያን ጊዜ የከነዓን ነገስታትም በመጊዶ ውኆች አጠገብ በታዕናክ
ተዋጉ። ምንም የብር ምርኮ አልወሰዱም። 20 ከሰማይ ከዋክብት ተዋጉ፣ በሰማያት ላይ በአካሄዳቸውም ሲሣራን ተዋጉት። 21 ከዱሮ ጀምሮ የታወቀው፣
የቂሶን ወንዝም፣ ጠርጎ ወሰዳቸው። ነፍሴ ሆይ ገስግሺ፣ በርቺ! 22 የፈረሶች የግልብያ ኮቴዎች ድምጽ፣ የኃያላኑ ግልቢያ ድምጽም። 23 የእግዚአብሔር
መልአክ “ሜሮዝን እርገሙ!” ይላል። ‘ነዋሪዎቿን ፈጽማችሁ እርገሙ! ምክንያቱም እግዚአብሔርን ለመርዳት አልመጡም፣ ከኃያላን ጦረኞች ጋር በተደረገው
ውጊያ እግዚአብሔርን ለመርዳት አልመጡምና።' 24 የቄናዊው የሔቤር ሚስት፣ ኢያዔል፣ ከሴቶች ሁሉ ይልቅ የተባረከች ናት፣ በድንኳን ውስጥ ከሚኖሩ ሴቶች
ሁሉ ይልቅ የተባረከች ናት። 25 ሰውየው ውኃ ለመናት፣ እርስዋም ወተት ሰጠችው፤ ለመሳፍንት በሚሆን በተከበረ ሳህን ቅቤ አመጣችለት። 26 እጅዋን ወደ
ድንኳን ካስማ፣ ቀኝ እጅዋንም ወደ ሠራተኛ መዶሻ አደረገች፤ በመዶሻውም ሲሣራን መታች፣ ራሱንም ቀጠቀጠች። ጆሮ ግንዱን በወጋችው ጊዜ ጭንቅላቱንም
ፈረከሰችው። 27 በእግሮችዋ መካከል ተደፋ፣ ወደቀ ተኛም። በእግሮችዋ አጠገብ ተሰብሮ ወደቀ። የተደፋበት ስፍራ በክፉ ሁኔታ የሞተበት ነው። 28 ከመስኮት
ሆና ወደ ውጭ ተመለከተች፣ የሲሣራ እናት በርብራብ በኩል በኃዘን ወደ ውጭ ጮኸች፣ ‘ወደዚህ ለመምጣት ሰረገላው ረዥም ጊዜ ለምን ወሰደበት? ለምንስ
ሰረገላዎቹን የሚጎትቱት የፈረሶቹ ኮቴዎች ዘገየ?’ 29 ብልሃተኞች ልዕልቶቿም መለሱላት፣ ለራስዋም ተመሳሳይ መልስ መለሰች፦ 30 ምርኮውን አግኝተው
ተካፍለው የለምን? ለእያንዳንዱ ሰው ምርኮ አንዲት ወይም ሁለት ልጃገረድ፤ ለሲሣራ ምርኮ ልዩ ልዩ ቀለም ያለው ልብስ፣ የተጠለፈ ባለቀለም ጨርቅ ምርኮ፣
ለማረኩ ሰዎች ለአንገታቸው የሚሆን በሁለት እጥፍ የተጠለፈ ባለቀለም ጨርቆች ምርኮን አላገኙምን?’ 31 ስለዚህ፣ እግዚአብሔር ሆይ፣ ጠላቶችህ ሁሉ
እንዲሁ ይጥፉ! ነገር ግን እርሱን የሚወዱት በኃይል እንደሚወጣ ጸሐይ ይሁኑ።” ምድሪቱም ለአርባ ዓመት ያህል ዐረፈች።

Judges 5:1

በዚያች ቀን
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም በይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አ.ት፡ “እስራኤላውያን የንጉሥ ኢያቢስን ሰራዊት ድል ባደረጉበት ቀን”

ዲቦራ
ይህንን ስም በመሳፍንት 4፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ባርቅ - አቢኒኤም
እነዚህን ስሞች በመሳፍንት 4፡6 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

ሕዝቡ በፈቃዳቸው ራሳቸውን ለጦርነት በሰጡ ጊዜ
“ሰዎቹ ለመዋጋት በተስማሙ ጊዜ”

Judges 5:3

እናንተ ነገሥታት ስሙ! እናንት መሪዎች አድምጡ
ዲቦራና ባርቅ፣ ነገሥታትና መሪዎች እዚያ ተገኝተው መዝሙሩን ይሰሙ ይመስል ይናገራሉ።

እናንት ነገሥታቶች - እናንት መሪዎች
ይህ የሚያመለክተው በጥቅሉ ነገሥታትንና መሪዎችን እንጂ የተለዩ ነገሥታትን ወይም መሪዎችን አይደለም።

ከሴይር በወጣህ ጊዜ፣ ከኤዶም በተነሣህ ጊዜ
ይህ እስራኤላውያን በከነዓን የሚኖሩትን ድል ለማድረግ ኤዶምን ትተው የተነሡበትን ጊዜ ያመለክታል። እግዚአብሔር፣ ሕዝቡ የከነዓንን ሰዎች ድል እንዲያደርጓቸው ማብቃቱ እርሱ የእስራኤልን ሰራዊት እንደሚመራቸው ጦረኛ ተደርጎ እንዲነገርለት ሆኗል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሴይር
ሴይር በእስራኤልና በኤዶም ምድር ድንበር ላይ የሚገኝ ተራራ ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ምድር ተናወጠች፣ ሰማያትም ተንቀጠቀጡ፤ ደመናትም ደግሞ ውሃን አንጠባጠቡ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ የምድር መናወጥንና ማዕበልን እንደሚፈጥር በመግለጽ ለእግዚአብሔር ኃይል አጽንዖት የሚሰጥ ሥነ ግጥማዊ ቋንቋ ነው ወይም 2) እስራኤላውያኑ በሚወጓቸው ጊዜ የከነዓን ሰዎች መፍራታቸው ሰማይና ምድር እንደተንቀጠቀጡ ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Judges 5:5

ተራሮች ተንቀጠቀጡ
ይህ እግዚአብሔርን በጣም በመፍራታቸው ተራሮች መንቀጥቀጣቸውን ለማሳየት፣ ምናልባት የምድር መናወጥን ያመለክት ይሆናል። አ.ት፡ “ተራሮች በፍርሃት ተርበደበዱ”

በእግዚአብሔር ፊት
እዚህ ጋ “ፊት” የእግዚአብሔርን ሀልዎት ያመለክታል። አ.ት፡ “በእግዚአብሔር ሀልዎት ፊት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የሲና ተራራ እንኳን ተንቀጠቀጠ
ሙሴና እስራኤል በሲና ተራራ በነበሩ ጊዜ ተንቀጥቅጦ ነበር። አ.ት፡ “ከዓመታት በፊት የሲና ተራራ እንኳን ተንቀጥቅጧል”

በ... ቀናት
“በ... የሕይወት ዘመን”

ሰሜጋር = ዓናት = ኢያዔል
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። ሰሜጋርና ዓናትን በመሳፍንት 3:31 ላይ እንዲሁም ኢያዔልን በመሳፍንት 4:18 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የዓናት ልጅ
ሰሜጋርንና የኖረበትን ዘመን መለየት እንዲቻል ለመርዳት የሰሜጋር አባት ተጠቅሷል። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

አውራ ጎዳናዎቹ ተትተዋል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር የሚችል ሲሆን መንገዶቹ የተተዉበትን ምክንያት ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። አ.ት፡ “የእስራኤልን ጠላቶች ስለ ፈሩ ሰዎች አውራ ጎዳናዎቹን መጠቀም አቆሙ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ፣ የሚለውን ተመልከት)

Judges 5:7

እኔ ዲቦራ እነሣለሁ = በእስራኤል እንደ እናት ሆነሽ ተነሽ
ዲቦራ ለትናንሽ ልጆች እንክብካቤ እንደምታደርግ እናት በእስራኤል ላይ መሪ ስለ መሆኗ ትናገራለች። አ.ት፡ “እኔ ዲቦራ መምራት ጀምሬአለሁ - እናት ልጆችዋን እንደምትንከባከብ እስራኤላውያንን እንከባከባለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አዳዲስ አማልክትን መረጡ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ መቻል አለበት። አ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ አዳዲስ አማልክትን አመለኩ”

በከተማይቱ በሮች ጦርነት ነበር
እዚህ ጋ “በሮች” መላውን ከተማውን ይወክላሉ። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉሙ በበለጠ ግልጽ መደረግ መቻል አለበት። አ.ት፡ “በእስራኤል ከተሞች ውስጥ ጠላት ሕዝቡን አጠቃ”

በእስራኤል በአርባ ሺዎቹ መካከል ጦር ወይም ጋሻ አልታየም
ይህ መግለጫ ምናልባት እስራኤላውያን ስለ ነበራቸው ጥቂት የጦር መሣሪያ በግነት የቀረበ ይሆናል። አ.ት፡ “በእስራኤል ለጦርነት የቀረው ጥቂት የጦር መሣሪያ ነው” (ግነት እና ጥቅል አስተያየት የሚለውን ተመልከት)

በእስራኤል አርባ ሺህ
“40,000 በእስራኤል” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

Judges 5:9

ልቤ ወደ እስራኤል አዛዦች ይሄዳል
“ልብ” የሚለው ቃል የአንድን ሰው ስሜት ይወክላል። “ልቤ ይሄዳል” የሚለው ሐረግ ዲቦራ ያላትን አድናቆት ወይም ምስጋና የማመልከቻ መንገድ ነው። አ.ት፡ “የእስራኤልን አዛዦች አደንቃለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

እናንተ በነጫጭ አህዮች የምትቀመጡ - በመንገዱ ላይ የምትሄዱ
ይህ ንጽጽር የሚያመለክተው ምናልባት ባለጸጎችንና ድኾችን ይሆናል። አ.ት፡ “እናንት በነጫጭ አህዮች የምትቀመጡ ባለጸጎች ... እናንት በመንገዱ ላይ የምትሄዱ ድኾች”

ለኮርቻ በስጋጃዎች ላይ ተቀምጣችሁ
እነዚህ ስጋጃዎች ምናልባት ጋላቢው በይበልጥ እንዲመቸው በአህያው ጀርባ ላይ ለኮርቻነት የሚጠቀምባቸው ሳይሆኑ አይቀሩም።

Judges 5:11

የእነዚያን ድምፆች ስሙ
እዚህ ጋ “ድምፆች” የሚዘምሩትን ሰዎች ይወክላል። አ.ት፡ “ስሟቸው”

ወደ ከተማይቱ በሮች ወረዱ
እዚህ ጋ “በሮች” መላውን ከተማ ይወክላሉ። አ.ት፡ “ወደ ከተሞቻቸው ተመለሱ”

Judges 5:12

ንቂ፣ ንቂ
ተናጋሪዎች ሊሆኑ የሚችሉት 1) የእስራኤል ሕዝብ ወይም 2) ለራሷ የምትናገረው ዲቦራ ወይም 3) መዝሙሩን የጻፈው ገጣሚ ነው።

ዲቦራ
ይህንን ስም በመሳፍንት 4:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ባርቅ - አቢኒኤም
እነዚህን ስሞች በመሳፍንት 4:6 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

ከጦረኞች ጋር ወደ እኔ
“እኔ” የሚለው ቃል ዲቦራን ያመለክታል።

Judges 5:14

ሥሩ በአማሌቅ ከሆነው ከኤፍሬም
የኤፍሬም ሰዎች የሚኖሩበት ምድር በመጀመሪያ የአማሌቅ ተወላጆች ይኖሩበት ስለ ነበረ የኤፍሬም ሰዎች በምድሪቱ እንደ ተተከሉና ስር እንደ ሰደዱ ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “በአንድ ወቅት የአማሌቅ ተወላጆች ይኖሩ ከነበሩበት ከኤፍሬም ምድር” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ተከተሉህ
እዚህ ጋ “ተከተሉህ” የሚያመለክተው የኤፍሬምን ሕዝብ ነው። በሦስተኛ መደብ ሊነገር ይቻላል። አ.ት፡ “ተከተሏቸው” (የአንተ ቅርጾች እና አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

ማኪር
ይህ የማኪር ተወላጆች ይኖሩ የነበሩበት ስፍራ ነው። ማኪር የምናሴ ልጅና የዮሴፍ የልጅ ልጅ ነበር። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከዛብሎን፣ እነዚያ የአለቅነትን በትር የያዙ
ወታደራዊ አመራሮች የስልጣናቸው ምልክት በሆነው በትራቸው ይገለጻሉ። አ.ት፡ “የዛብሎን ወታደራዊ መሪዎች” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 5:15

በይሳኮር ያሉ መስፍኖቼ ከዲቦራ ጋር ነበሩ
እዚህ ጋ “የእኔ” የሚያመለክተው ዲቦራን ነው። ይህ መግለጫ በአጠቃላይ በአንደኛ መደብ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “በይሳኮር የሚገኙት መስፍኖቼ ከእኔ ጋር ነበሩ” (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

ዲቦራ
ይህንን ስም በመሳፍንት 4፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

ይሳኮር ከባርቅ ጋር ነበር
እዚህ ጋ “ይሳኮር” የይሳኮርን ነገድ ያመለክታል። አ.ት፡ “የይሳኮር ነገድ ከባርቅ ጋር ነበር” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ባርቅ
ይህንን ስም በመሳፍንት 4፡6 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

መመሪያውን በመከተል ከበስተኋላው ወደ ሸለቆው ሮጡ
“መመሪያውን በመታዘዝና ወደ ሸለቆው ከበስተኋላው በመሮጥ”

ከበስተኋላው በመሮጥ
“ከኋላው በመከተል” ወይም “ከኋላው በመሮጥ”

ታላቅ የልብ ምርምር ነበር
እዚህ ጋ “ልብ” አሳብን ይወክላል። የሰዎቹ እርስ በእርስ መነጋገርና ምን ማድረግ እንዳለባቸው መወሰን አለመቻላቸው ልባቸውን እንደመረመሩ ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ምን ማድረግ እንዳለባቸው ብዙ ውይይት ነበር” (ፈሊጣዊ እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 5:16

እረኞች ለመንጋዎቻቸው የሚጫወቱትን ዋሽንት እየሰማችሁ እሳት በሚነድባቸው ምድጃዎች መካከል የተቀመጣችሁት ለምንድነው?
ወደ ጦርነቱ በመምጣት ለመዋጋት አልወሰኑም ነበርና ይህ ጥያቄ የተጠየቀው የሮቤልን ሰዎች ለመውቀስ ነው። ይህ እንደ መግለጫ ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “በቤት ቀርታችሁ እረኞች ለመንጋዎቻቸው የሚጫወቱትን ዋሽንት ከምትሰሙ ይልቅ ስንዋጋ ልትረዱን ይገባ ነበር” (መልስ የማይሻ ጥያቄ እና የሚለውን ተመልከት)

እሳት የሚነድባቸው ምድጃዎች
አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ዕትሞች “የበጎች ጉረኖ” ወይም “የበግ ማሳደሪያ” ይሉታል

Judges 5:17

ገለዓድ ተቀምጧል
እዚህ ጋ “ገለዓድ” የሚያመለክተው በጦርነቱ ላይ ለመዋጋት መሄድ የነበረባቸውን የገለዓድ ወንዶች ነው። አ.ት፡ “የገለዓድ ሰዎች ተቀምጠዋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከዮርዳኖስ ማዶ
ይህ የዮርዳኖስን ምስራቅ ያመለክታል።

ዳን በመርከቦች ላይ ለምን ዘገየ
የዳን ነገድ ሰዎች ለእስራኤል ስላልተዋጉ ይህ ጥያቄ የተጠየቀው ቁጣን ለመግለጽ ነው። አ.ት፡ “የዳን ሰዎች በመርከቦቻቸው ውስጥ መቆየት አልነበረባቸውም” ወይም “በጦርነቱ የዳን ነገድ ሰዎች አልረዱንም። ይልቁንም በመርከቦቻቸው ውስጥ ሆነው ወዲያና ወዲህ ይቅበዘበዙ ነበር!” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እና የሚለውን ተመልከት)

ለምን ነበር ዳን
እዚህ ጋ “ዳን” ጦርነቱን ለመዋጋት መሄድ የነበረባቸውን የዳን ሰዎች ይወክላል። አ.ት፡ “ለምንድነው የዳን ሰዎች” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በመርከቦች የሚቅበዘበዙት
የዳን ነገድ የሚገኘው በሜዴትራንያን ባህር አጠገብ ነበር። በንግድና ዓሳ በማስገር ገንዘብ ለማግኘት በባህሩ ላይ በመርከብ ይጓዙ ነበር።

አሴር በጠረፉ ላይ ተቀመጠ፣ በወደቡም አቅራቢያ ኖረ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉሙ በይበልጥ ሊብራራ ይችላል። አ.ት፡ “የአሴር ነገድ ሰዎችም ደግሞ ሳይረዱን ቀሩ። በወደቦቻቸው አቅራቢያ ብቻ ተቀመጡ”

አሴር ተቀመጠ
እዚህ ጋ “አሴር” ጦርነቱን ለመዋጋት መሄድ የነበረባቸውን የአሴር ሰዎች ይወክላል። አ.ት፡ “የአሴር ሰዎች ተቀመጡ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ወደቦች
ጥልቅ ውሃ ያለባቸውና መርከቦች የሚቆሙባቸው የባህር ዳርቻ አካባቢዎች

ንፍታሌምም ደግሞ
የሚታወቀውን መረጃ ግልጽ ልታደርገው ትችላለህ። አ.ት፡ “ንፍታሌምም ደግሞ ነፍሳቸውን እስከ ሞት ድረስ አሳልፈው ከሰጡት ነገዶች አንዱ ነበር”

Judges 5:19

ነገሥታት መጡ፣ ተዋጉም - የከነዓን ነገሥታት ተዋጉ
ራሱንና የሚያዛቸውን ሰራዊት ለማመልከት የአንድ ሕዝብ ወገን ንጉሥ የሚለው ጥቅም ላይ ውሏል። አ.ት፡ “ነገሥታትና ሰራዊቶቻቸው መጥተው ተዋጉ - የከነዓን ነገሥታትና ሰራዊቶቻቸው ተዋጉ”

እነርሱ ተዋጉ -- ተዋጉ
“እኛ” የሚለው ቃል የሚታወቅ ነው። አ.ት፡ “ወጉን - ወጉን”

ታዕናክ - መጊዶ
የእነዚህን ቦታዎች ስም በመሳፍንት 1፡27 እንዳደረግኸው ተርጉማቸው።

ምንም ብር አልበዘበዙም
እዚህ ጋ “ብር” በጥቅሉ የትኛውንም ዓይነት ገንዘብ ይወክላል። አ.ት፡ “የሚበዘብዙት ብር ወይም ሌላ ሀብት አልነበረም”

ብዝበዛ
አብዛኛውን ጊዜ በጦርነት ወይም በሌቦች አማካይነት በማስገደድ የሚወሰዱ ነገሮች

ከዋክብት ከሰማይ ተዋጉ፣ ከሰማያት ጥጎቻቸው ሲሣራን ተዋጉት
እግዚአብሔር፣ እስራኤላውያን ሲሣራንና ሰራዊቱን ድል እንዲያደርጓቸው መርዳቱ ከዋክብት ራሳቸው ሲሣራንና ሰራዊቱን እንደተዋጓቸው ተደርጎ ተነግሯል። ይህ እግዚአብሔር ሲሣራን ድል ለማድረግ ተፈጥሮአዊ ግብዓቶችን በተለይም ነጎድጓድን መጠቀሙን ያመለክት ይሆናል። (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በሲሣራ ላይ
እዚህ ጋ “ሲሣራ” የሚወክለው ራሱንና መላውን ሰራዊቱን ነው። አ.ት፡ “ሲሣራና ሰራዊቱ”

ሲሣራ
ይህንን ስም በመሳፍንት 4፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Judges 5:21

የቂሶን ወንዝ ጠራርጎ ወሰዳቸው
በከባድ ዝናብ ምክንያት ወንዙ በፍጥነት ስለሞላ ሠረገላዎቹ በጭቃ ተይዘው ስለነበር ብዙ ወታደሮች ሰመጡ። አ.ት፡ “የቂሶን ወንዝ ጎረፈና የሲሣራን ወታደሮች ጠራርጎ ወሰዳቸው”

ቂሶን
ይህንን በመሳፍንት 4፡6 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ነፍሴ ሆይ፣ በርቺ፣ ተሰለፊ
እዚህ ጋ “ነፍስ” የሰውን ሁለንተና ያመለክታል። “የእኔ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ዲቦራን ነው። አ.ት፡ “እንድበረታና እንድሰለፍ ለራሴ እነግራለሁ”

ከዚያም የሚጋልቡ የፈረሶች ኮቴ ድምፅ ተሰማ፣ የኃያላኑ ግልቢያ
ይህ የሚገልጸው ከጦርነት የሚሸሹ የብዙ ፈረሶችን ድምፅ ነው። አ.ት፡ “ከዚያም በሸሽት ላይ ያሉ የፈረሶችን ድምፅ ሰማሁ። ብርቱዎቹ የሲሣራ ፈረሶች እየሸሹ ነበር”

መጋለብ
በፍጥነት መሮጥ

Judges 5:23

ሜሮዝን እርገሙ
እዚህ ጋ “ሜሮዝ” የምትወክለው በዚያ የኖሩትን ሰዎች ነው። አ.ት፡ “የሜሮዝን ሰዎች እርገሙ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሜሮዝ
ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ነዋሪዎች
በአንድ ስፍራ የሚኖሩ ሰዎች

Judges 5:24

ኢያዔል
ይህንን ስም በመሳፍንት 4፡18 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሔቤር
ይህንን ስም በመሳፍንት 4፡11 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ቄናዊ
የዚህን የሕዝብ ወገን ስም በመሳፍንት 1፡16 ላይ እንዳደረግኸው ተርጉመው።

ቅቤ አመጣችለት
እዚህ ጋ “ቅቤ” የሚያመለክተው የረጋውን ወተት ነው። ይህ በኢያዔል ሰዎች መካከል የተመረጠ ወተትና ተወዳጅ መጠጥ ነበር። አ.ት፡ “እርጎ አመጣችለት” ወይም “የረጋ ወተት አመጣችለት”

ለልዑላን የተገባውን ማዕድ
ለልዑላን ምርጥ የሆነው ነገር ይቀርብ ስለነበር ይህ ሐረግ የሚለው ማዕዱ እጅግ ምርጥ መሆኑን ነው።

Judges 5:26

እጇን ወደ ድንኳኑ ካስማ ሰደደች
“ኢያዔል በግራ እጇ የድንኳኑን ካስማ ያዘች”

የድንኳን ካስማ
ይህ ድንኳኑን ከመሬት ጋር አገናኝቶ እንዲይዝ በመዶሻ የሚመታ እንደ ትልቅ ሚስማር የሾለ እንጨት ወይም ብረት ነው። ይህንን በመሳፍንት 4፡21 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ቀኝ እጇን ሠራተኛ ወደሚጠቀምበት መዶሻ
ይህ ሙሉ ዐረፍተ ነገር ሆኖ መነገር ይችላል። አ.ት፡ “በቀኝ እጇ መዶሻ ያዘች”

መዶሻ
የድንኳኑን ካስማ ወደ መሬት ለማጥለቅ ክብደት ካለው እንጨት የሚሠራ መምቻ ነው። ይህንን በመሳፍንት 4፡21 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሲሣራ
የዚህን ሰውዬ ስም በመሳፍንት 4፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት፡

መዛል
ዐቅም ማጣት ወይም መንቀሳቀስ አለመቻል

በቁጣ ተገደለ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ገደለችው” ወይም “ሞተ”(አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Judges 5:28

ርብራብ
ይህ በመስቀልዮሽ እንጨት የተሠራ የመስኮቱ መደገፊያ ነው።

ሠረገላው ሳይመጣ ለምን ይህን ያህል ጊዜ ፈጀበት? ሠረገላዎቹን የሚጎትቱት ፈረሶች ኮቴ ድምፅ ለምን ዘገየ?
ሁለቱም ጥያቄዎች የሚሉት አንድ ነገር ነው። እነዚህ ሁለቱም መግለጫዎች መጣመር ይችላሉ። አ.ት፡ “ሲሣራ ወደ ቤት ሳይመለስ የቆየው ለምንድነው?”

ሠረገላው - ፈጀበት - ሠረገላዎቹን የሚጎትቱት ፈረሶች ኮቴ ድምፅ
ሁለቱም አነጋገሮች የሚወክሉት ሲሣራን ነው። አ.ት፡ “ሲሣራን የወሰዱት. . . እርሱ ለምን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 5:29

ጠቢብ ልዕልቶች
“ልዕልት” የንጉሥ ልጅ ናት፣ ነገር ግን “ልዕልቶች” ማለት ደግሞ ምናልባት የንጉሡን ቤተሰቦች የሚያማክሩ ሴት አማካሪዎች ማለት ሊሆን ይችላል። አ.ት፡ “ጠቢብ ሴቶች”

ለራሷ ተመሳሳይ ምላሽ ሰጠች
“ያንኑ ነገር ለራሷ ተናገረች”

ምርኮ አግኝተው ተከፋፍለው አልጨረሱ ይሆን?
ሴቶቹ በእርግጥ የሆነው ይኸው ነው ብለው ስላመኑበት ጉዳይ አጽንዖት ለመስጠት ጥያቄ ይጠቀማሉ። አ.ት፡ “ለመከፋፈል ጊዜ የፈጀባቸው ብዙ ምርኮ እግኝተው መሆን አለበት” (መልስ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከበዘበዟቸው ላይ - አንድ ማህፀን፣ እያንዳንዱ ሁለት ማህፀን
ሴቶቹ በእርግጥ የሆነው ይኸው ነው ብለው ስላመኑበት ጉዳይ አጽንዖት ለመስጠት ጥያቄ ይጠቀማሉ። አ.ት፡ “ከበዘበዟቸው ላይ ለእያንዳንዱ ወንድ አንድ ማህፀን፣ ሁለት ማህፀን ደርሷቸው መሆን አለበት” (መልስ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ለእያንዳንዱ ወንድ አንድ ማህፀን፣ ሁለት ማህፀን
እዚህ ጋ “ማህፀን” የሚያመለክተው ሴትን ነው። የሲሣራ ሰዎች ብዙ ሴቶችን እንደማረኩ የሲሣራ እናት ታምናለች። አ.ት፡ “እያንዳንዱ ወታደር አንድ ወይም ሁለት ሴት ይደርሰዋል”

የቀለመ ጨርቅ
“ልዩ ልዩ ቀለም ያለው ልብስ” ወይም “ልዩ ልዩ ቀለም ያላቸው ልብሶች”

ማቅለም
ልዩ ልዩ ቀለማት ካላቸው ክሮች የተሠሩ ንድፎች

ለሚበዘብዙት ለአንገታቸው
እዚህ ጋ “አንገታቸው” የሚወክለው የሲሣራን ወታደሮች ነው። አ.ት፡ “የበዘበዙት ወታደሮች ሊለብሱት”

Judges 5:31

በብርታቷ እንደምትወጣ ፀሐይ
የየትኛውም ሀገር ሰራዊት የፀሐይን መውጣት ማስቆም ስለማይችል የእስራኤል ሕዝብ እንደ ማለዳ ፀሐይ ለመሆን ይመኛሉ።

ምድሪቱ ሰላም ነበራት
እዚህ ጋ “ምድሪቱ” የሚወክለው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። አ.ት፡ “የእስራኤልም ሕዝብ በሰላም ኖሩ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ለአርባ ዓመታት
“ለ40 ዓመታት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 6

1 የእስራኤልም ሕዝብ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነውን ሥራ ሠሩ፤ እርሱም በምድያም ቁጥጥር ስር እንዲሆኑ ለሰባት ዓመት አሳልፎ ሰጣቸው። 2
የምድያምም ኃይል በእስራኤል ላይ በረታ። ከምድያምም የተነሣ የእስራኤል ሕዝብ በኮረብታዎች ላይ ጕድጓድ፣ ዋሻና ምሽግም ለራሳቸው መሸሸጊያ አበጁ።
3 እንዲህም ሆነ፣ እስራኤል ዘር በዘሩ ጊዜ ምድያማውያን፣ አማሌቃውያንና ከምሥራቅም የመጡ ሰዎች እስራኤላውያንን ያጠቁ ነበር። 4 ሰራዊታቸውን በምድሪቱ
ላይ ያሰፍሩና እስከ ጋዛ ድረስ ያለውን ሰብል ያጠፉ ነበር። በእስራኤልም ምንም መብል፣ በጎች፣ ከብቶችና አህያዎች አይተዉም ነበር። 5 እነርሱ እንስሶቻቸውና
ድንኳኖቻቸውን ይዘው ሲመጡ እንደ አንበጣ መንጋ ሆነው ይመጡ ነበር፤ እነርሱንና ግመሎቻቸውንም መቁጠር አይቻልም ነበር። ምድሪቱንም ያጠፉ ዘንድ
ይወርሩአት ነበር። 6 ምድያም እስራኤልን ክፉኛ ከማዳከማቸው የተነሣ የእስራኤል ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር ጮኹ። 7 የእስራኤል ሕዝብ በምድያም ምክንያት
ወደ እግዚአብሔር በጮኹ ጊዜ፣ 8 እግዚአብሔር ወደ እስራኤል ልጆች ነቢይ ላከ። ነቢዩም እንዲህ አለ፦ “የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦
‘እኔ ከግብፅ ምድር አወጣኋችሁ፤ ከባርነትም ቤት አወጣኋችሁ። 9 ከግብፃውያንም እጅ እንደዚሁም ይጨቁኑአችሁ ከነበሩ ኃይላት ሁሉ አዳንኋችሁ።
ከፊታችሁም አሳድጄ አወጣኋቸው፣ ምድራቸውንም ሰጠኋችሁ። 10 ለእናንተንም እንዲህ አልኋችሁ፣ “እኔ አምላካችሁ እግዚአብሔር ነኝ፤ በምድራቸው
የተቀመጣችሁባቸውን፣ የአሞራውያንን አማልክት እንዳታመልኩ አዘዝኋችሁ። ነገር ግን እናንተ ድምጼን አልታዘዛችሁም። 11 የእግዚአብሔርም መልአክ
መጣና በዖፍራ ባለችው ለአቢዔዝራዊው ለኢዮአስ በነበረችው ከበሉጥ ዛፍ በታች ተቀመጠ፤ የኢዮአስም ልጅ ጌዴዎን ከምድያማውያን ለመሸሸግ በወይን
መጥመቂያው ውስጥ ስንዴ ይወቃ ነበር። 12 የእግዚአብሔርም መልአክ ለእርሱ ተገልጠለትና እንዲህ አለው፣ “አንተ ብርቱ ተዋጊ ሰው፣ እግዚአብሔር ከአንተ
ጋር ነው አለው!” 13 ጌዴዎንም ለእርሱ እንዲህ አለው፣ “ጌታዬ ሆይ፣ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ፣ ይህ ነገር ሁሉ ለምን በእኛ ላይ ደረሰብን? አባቶቻችንስ
የነገሩን እርሱ የሰራቸው አስደናቂ ነገሮች ወዴት አሉ፣ እንዲህ ብለው የነገሩን፣ ‘እግዚአብሔር ከግብፅ አላወጣንምን?’ አሁን ግን እግዚአብሔር ትቶናል፣
ለምድያማውያንም ብርታት አሳልፎ ሰጥቶናል። 14 እግዚአብሔርም ወደ እርሱ ተመለከተና እንዲህ አለው፣ “በዚህ ባለህ ብርታት ሂድ። እስራኤልንም ከምድያም
ኃይል አድን፤ እነሆ እኔ አልላክሁህምን?” 15 ጌዴዎንም እንዲህ አለው፣ “ጌታ ሆይ፣ እባክህ፣ እኔ እስራኤልን እንዴት ማዳን እችላለሁ? ተመልከት፣ የእኔ
ቤተሰብ ከምናሴ ነገድ ከሁሉ ይልቅ ደካማ ነው፣ እኔም በአባቴ ቤት ውስጥ የመጨረሻ ነኝ። 16 እግዚአብሔርም፣ “እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፣ አንተም
የምድያምን ሰራዊት በሙሉ ታሸንፋለህ” አለው። 17 ጌዴዎንም እንዲህ አለው፣ “በእኔ ደስተኛ ከሆንህ፣ የምትናገረኝ አንተ እንደሆንህ እርግጠኛ እሆን ዘንድ
ምልክትን ስጠኝ። 18 ወደ አንተ እስክመጣና መስዋእቴን አምጥቼ በፊትህ እስካቀርብ ድረስ እባክህ ከዚህ አትሂድ።” እግዚአብሔርም “እስክትመለስ ድረስ
እቆያለሁ” አለ። 19 ጌዴዎን ሄደ የፍየሉንም ጠቦት አረደ፣ የኢፍ መስፈሪያም ዱቄት ወስዶ ያልቦካ ቂጣ አዘጋጀ። ሥጋውን በቅርጫት አኖረ፣ መረቁንም
በምንቸት ውስጥ አኖረ፣ ሁሉንም ይዞ በበሉጥ ዛፍ በታች አቀረበለት። 20 የእግዚአብሔርም መልአክ እንዲህ አለው፣ “ሥጋውንና ያልቦካውን ቂጣ ውሰድና
በዚህ ድንጋይ ላይ አኑረው፣ መረቁንም በላዩ ላይ አፍስሰው።” ጌዴዎንም እንዲሁ አደረገ። 21 የእግዚአብሔርም መልአክ በእጁ የያዘውን የበትሩን ጫፍ ወደዚያ
ዘረጋ። በበትሩም ሥጋውንና ያልቦካውን ቂጣ ነካው፤ እሳትም ከድንጋዩ ውስጥ ወጥቶ ሥጋውንና ያልቦካውን ቂጣ በላ። የእግዚአብሔርም መልአክ ሄደ፣
ጌዴዎንም ሊያየው አልቻለም። 22 ጌዴዎንም የእግዚአብሔር መልአክ እንደ ሆነ አወቀ። ጌዴዎንም፣ “አምላኬ እግዚአብሔር ሆይ፣ ወዮልኝ! የእግዚአብሔርን
መልአክ ፊት ለፊት አይቻለሁና” አለ። 23 እግዚአብሔርም እንዲህ አለው፣ “ሰላም ለአንተ ይሁን! አትፍራ፣ አትሞትም።” 24 ስለዚህ ጌዴዎን በዚያ
ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሠራ። ስሙንም፣ እግዚአብሔር ሰላም ብሎ ጠራው። እስከ ዛሬ ድረስ በአቢዔዝራውያን ጎሳ በምትሆነው በዖፍራ አለ። 25
እግዚአብሔርም በዚያች ሌሊት እንዲህ አለው፣ “የአባትህን በሬ፣ ሰባት ዓመት የሆነውን ሁለተኛውንም በሬ ውሰድ፣ የአባትህ የሆነውን የበኣል መሠዊያ አፍርስና
በአጠገቡ ያለውን አሼራን ሰባብረው። 26 በዚህ መሸሸጊያ ስፍራ ጫፍ ላይ ለአምላክህ ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሥራ፣ በትክክለኛው መንገድም ስራው።
ከአሼራ ሰባብረህ በጣልኸው እንጨት ሁለተኛውን በሬ የሚቃጠል መስዋእት አድርገህ አቅርበው።” 27 ስለዚህ ጌዴዎን ከባሪያዎቹ አሥር ሰዎችን ወሰደና
እግዚአብሔር እንደነገረው አደረገ። ነገር ግን በቀን ለማድረግ የአባቱን ቤተ ሰቦችና የከተማውንም ሰዎች እጅግ በጣም ስለፈራ፣ በሌሊት አደረገው። 28
በማለዳ የከተማው ሰዎች በተነሱ ጊዜ፣ የበኣል መሠዊያ ፈርሶ ነበር፣ በአጠገቡ የነበረውም አሼራ ተሰባብሮ ነበር፣ ሁለተኛውም በሬ አዲስ በተሰራው መሠዊያ
ላይ ተሠውቶ ነበር። 29 የከተማውም ሰዎች እርስ በርሳቸው፣ “ይህን ያደረገው ማን ነው?” ተባባሉ። ከሌሎች ጋር ሲነጋገሩና መልስ ሲፈልጉ ሳሉ፣ “ይህን
ያደረገው የኢዮአስ ልጅ ጌዴዎን ነው” አሉ። 30 የዚያን ጊዜ የከተማው ሰዎች ኢዮአስን እንዲህ አሉት፣ “የበኣልን መሠዊያ አፍርሶአልና፣ በአጠገቡ የነበረውንም
አሼራ ሰባብሮታልና እንዲሞት ልጅህን አውጣ።” 31 ኢዮአስም ለተቃወሙት በሙሉ እንዲህ አላቸው፣ “ለበኣል ትምዋገቱለታላችሁን? እርሱን ታድኑታላችሁን?
ለእርሱ የሚምዋገትለት ሁሉ እስከ ነገ ጠዋት ይገደል። በኣል አምላክ ከሆነ፣ መሠዊያውን ሲያፈርሱበት ራሱን ይከላከል። 32 ስለዚህም በዚያ ቀን ጌዴዎን
“ይሩበኣል” የሚል ስም ተሰጠው፣ ምክንያቱም እርሱ “በኣል ራሱን ይከላከል” ብሏልና፣ ጌዴዎን መሠዊያውን አፍርሶአልና። 33 ምድያማውያንና አማሌቃውያን
ሁሉ፣ የምሥራቅም ሰዎች አንድ ላይ ተሰበሰቡ። ዮርዳኖስን ተሻግረው በኢይዝራኤል ሸለቆ ውስጥ ሰፈሩ። 34 ነገር ግን የእግዚአብሔር መንፈስ ጌዴዎንን
ሊረዳው በእርሱ ላይ ወረደ። ጌዴዎንም ቀንደ መለከት ነፋ፣ የአቢዔዝር ጎሳ ሰዎች ይከተሉት ዘንድ ጠራቸው። 35 እርሱም ወደ ምናሴ ነገድ ሁሉ መልክተኞችን
ሰደደ፣ እነርሱም ደግሞ እንዲከተሉት ተጠርተው ነበር። መልክተኞችንም ወደ አሴር፣ ዛብሎንና ንፍታሌምም ላከ፣ እነርሱም እርሱን ሊዋጉት ሄዱ። 36 ጌዴዎንም
እግዚአብሔርን እንዲህ አለው፣ “እንደ ተናገርኸው እስራኤልን ለማዳን እኔን የምትጠቀምብኝ ከሆነ 37 ተመልከት፣ በአውድማው ላይ የበግ ጠጕር ባዘቶ
አኖራለሁ። በጠጕሩ ብቻ ላይ ጠል ቢሆንና በምድሩም ሁሉ ደረቅ ቢሆን፣ የዚያን ጊዜ እንደተናገርኸው አንተ እስራኤልን ለማዳን እንደምትጠቀምብኝ
አውቃለሁ።” 38 እንዲሁም ሆነ፣ ጌዴዎን በነጋው ማልዶ ተነሣ፣ ጠጕሩንም በአንድ ላይ ጨመቀው፣ ከጠጕሩም የተጨመቀው ጠል አንድ ቆሬ ለመሙላት በቂ
ሆነ። 39 ጌዴዎንም እግዚአብሔርን እንዲህ አለው፣ “አትቈጣኝ፣ አንድ ጊዜ እንደገና እናገራለሁ። እባክህ፣ የጠጕሩ ባዘቶ በመጠቀም አንድ ተጨማሪ ሙከራ
እንዳደርግ ፍቀድልኝ። በዚህ ጊዜ ጠጕሩ ብቻ ደረቅ ይሁን፣ በምድሩና በዙርያውም ሁሉ ላይ ደግሞ ጠል ይሁን።” 40 እግዚአብሔርም በዚያ ሌሊት የጠየቀውን
አደረገ። ጠጕሩ ደረቅ ነበረ፣ በምድሩም ሁሉ ላይ ጠል ነበረ።

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Judges 6:1

በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነውን
የእግዚአብሔር ፊት የሚወክለው ፍርዱን ወይም ምዘናውን ነው። አ.ት፡ “በእግዚአብሔር ፍርድ ክፉ የሆነውን” ወይም “እግዚአብሔር ክፉ ነው ያለውን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የምድያማውያን እጅ
እዚህ ጋ “ምድያማውያን” የሚወክለው የምድያምን ሰዎች ነው። በተጨማሪም፣ “እጅ” መቆጣጠርን ይወክላል። አ.ት፡ “የምድያም ሰዎች መቆጣጠራቸው” ወይም “የምድያማውያን መቆጣጠር” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የምድያም ኃይል እስራኤልን አስጨነቀ
እዚህ ጋ “የምድያም ኃይል” የሚያመለክተው የምድያም ሰዎችን ነው። አ.ት፡ “የምድያም ሰዎች ከእስራኤል ሰዎች ይልቅ እጅግ በርትተው ስለነበር አስጨነቋቸው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ዋሻ
ሊያስጠልል የሚችል በዐለታማ ሸንተረር ላይ የሚገኝ ስፍራ

Judges 6:3

ሰራዊታቸውን ያሰፍሩ ነበር
“ሰራዊቱ ይሰፍር ነበር” ወይም “ሰራዊቱ ድንኳኑን ይተክል ነበር”

Judges 6:5

እነርሱ ከከብቶቻቸውና ከድንኳኖቻቸው ጋር ወጥተው በሚመጡበት ጊዜ ሁሉ
የምድያም ምድር በቀይ ባህር አቅራቢያ ከእስራኤል ምድር በስተደቡብ ነበር። ከምድያም ወደ እስራኤል የሚደረግ ጉዞ በሚነገርበት ጊዜ “ወጥተው በሚመጡበት” የሚለውን ሐረግ መጠቀም የተለመደ ነበር። አ.ት፡ “ምድያማውያን ከብቶቻቸውንና ድንኳኖቻቸውን ወደ እስራኤል ምድር በሚያመጡበት ጊዜ ሁሉ”

እንደ አንበጣ መንጋ ይመጡ ነበር
ምድያማውያን እጅግ ብዙ ሆነው ይመጡ ስለነበርና ከብቶቻቸው የሚበቅለውን ነገር ሁሉ ይበሉት ስለነበር ከአንበጣ መንጋ ጋር ተነጻጽረዋል።

ለመቁጠር አይቻልም ነበር
ይህ ቁጥሩ በጣም ብዙ መሆኑን ለማሳየት የቀረበ ግነት ነው። (ግነት እና ጥቅል አስተያየት የሚለውን ተመልከት)

ምድያም አደከማቸው
እዚህ ጋ “ምድያም” የሚወክለው የምድያምን ሕዝብ ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ወደ እግዚአብሔር ጮኹ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “እንዲረዳቸው ወደ እግዚአብሔር ጸለዩ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Judges 6:7

ወደ እግዚአብሔር ጮኹ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “እንዲረዳቸው ወደ እግዚአብሔር ጸለዩ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በምድያም ምክንያት
እዚህ ጋ “ምድያም” የሚወክለው የምድያምን ሕዝብ ነው። አ.ት፡ “በምድያማውያን ምክንያት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከግብፅ አወጣኋችሁ
“ከግብፅ መርቼ አወጣኋችሁ”

ከባርነት ቤት
ሙሴ ስለ ግብፅ ሲናገር ሰዎች ባሪያዎችን እንደሚያቆዩበት ቤት ይቆጥረዋል። አ.ት፡ “ባሪያዎች የነበራችሁበት ስፍራ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 6:9

ከ... እጅ
በዚህ ሐረግ “እጅ” የሚወክለው ኃይልን ወይም ቁጥጥርን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ድምፄን አልታዘዛችሁም
እዚህ ጋ “ድምፄን” የሚወክለው እግዚአብሔር ያዘዘውን ትዕዛዝ ነው። አ.ት፡ “ትዕዛዜን አልጠበቁም” ወይም “አልታዘዙኝም”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 6:11

አሁን
ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው የታሪኩ መስመር የተገታበትን ለማመልከት ነው። ተራኪው እዚህ ጋ የታሪኩን አዲስ ክፍል መናገር ይጀምራል።

ዖፍራ
ይህ የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

አቢዔዝራዊ
ይህ በቀድሞ አባታቸው በአቢዔዝር ስም የሚጠሩ የሕዝብ ወገን ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ወለሉ ላይ ስንዴ ይወቃ ነበር
ይህ የ “መውቃት” ሂደት ነው። ጌዴዎን የስንዴውን ምርት ከገለባው ለመለየት ወለሉ ላይ ይወቃ ነበር”

ታየው
“ወደ እርሱ ሄደ”

Judges 6:13

ጌታዬ
ጌዴዎን “ጌታዬ” የሚለውን ቃል የሚጠቀመው እንግዳ የሆነን ሰው በትህትና ሰላምታ ለመስጠት ነው። እርሱ የሚናገረው በመልአክ ወይም በሰው መልክ ከታየው ከእግዚአብሔር ጋር እንደሆነ አልተገነዘበም።

‘እግዚአብሔር ከግብፅ ያወጣን አይደለምን?’ ብለው አባቶቻችን የነገሩን ተአምራቱ ሁሉ የት አለ?
እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንዳለ የነገረውን እንግዳ ለመገዳደር ጌዴዎን ጥያቄ ያቀርብለታል። ደግሞም፣ በቀጥታ የተጠቀሰው ትዕምርተ ጥቅስ ቀጥተኛ ባልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር አባቶቻችንን ከግብፅ ባወጣቸው ጊዜ ስላደረገላቸው የነገሩንን ዓይነት ተአምር አንድም አላየንም”። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ፣ ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ የሚለውን ተመልከት)

በምድያማውያን እጅ ሰጥቶናል
“በ... ሰጥቶናል” የሚለው ሐረግ እስራኤላውያን እንዲሸነፉ እግዚአብሔር ፈቅዷል ማለት ነው። አ.ት፡ “ምድያማውያን እንዲያሸንፉን ፈቅዷል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በ... እጅ ሰጥቶናል
እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው ኃይልን ወይም ቁጥጥርን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በምድያም
እዚህ ጋ “ምድያም” የሚወክለው የምድያምን ሕዝብ ነው። አ.ት፡ “በምድያማውያን”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 6:14

እግዚአብሔር ወደ እርሱ ተመልክቶ
“እግዚአብሔር ወደ ጌዴዎን ተመልክቶ”

ከ... እጅ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው ኃይልን ወይም ቁጥጥርን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የምድያም
እዚህ ጋ “ምድያም” የሚወክለው የምድያምን ሕዝብ ነው። አ.ት፡ “በምድያማውያን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አልላክሁህምን?
እግዚአብሔር ጌዴዎንን እንደ ላከው ለማስረገጥ በጥያቄ መልክ ይጠቀማል። እዚህ ጋ “መላክ” ማለት እግዚአብሔር ጌዴዎንን ለአንድ ግልጽ ለሆነ ሥራ ሾሞታል ማለት ነው። አ.ት፡ “የምልክህ እኔ እግዚአብሔር ነኝ!” (መልስ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ጌታው፣ እባክህን
አሁን ጌዴዎን ሰውየውን በመሳፍንት 6፡13 ላይ እንዳደረገው “ጌታዬ” ከማለት ይልቅ “ጌታው” ብሎ ይጠራዋል። እዚህ ጋ ጌዴዎን እየተነጋገረ ያለው ከእግዚአብሔር ጋር መሆኑን ያወቀ ወይም የጠረጠረ ይመስላል።

እንዴት እስራኤልን ነጻ ማውጣት እችላለሁ?
ጌዴዎን እስራኤላውያንን መታደግ እንደሚችል እንደማያስብ አጽንዖት ለመስጠት ጥያቄ ያቀርባል። አ.ት፡ “እስራኤላውያንን በፍጹም ልታደጋቸው አልችልም!” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ቤተሰቤን ተመልከት
“እኔንና ቤተሰቤን ተመልከትና ትክክል መሆኔን ታያለህ”

ከምናሴ
“ከምናሴ ነገድ ውስጥ”

በአባቴ ቤት ውስጥ
እዚህ ጋ “ቤት” የሚወክለው ቤተሰብን ነው። አ.ት፡ “በአባቴ ቤተሰብ ውስጥ“ ወይም “በቤተሰቤ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 6:16

እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ
እዚህ ጋ “ከአንተ ጋር” የሚለው ሐረግ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን እግዚአብሔር ጌዴዎንን ይረዳዋል፣ ይባርከዋልም ማለት ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

እንደ አንድ ሰው
ሙሉውን ትርጉም በይበልጥ ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። አ.ት፡ “ከአንድ ሰው ጋር የምትዋጋውን ያህል በቀላሉ”

በፊትህ አድርግ
“በፊት ለፊትህ አድርገው”

Judges 6:19

የኢፍ መስፈሪያ ዱቄት
ዘመናዊ መስፈሪያ መጠቀም ካስፈለገ ይህን ማድረግ የሚቻልበት አንድ መንገድ አለ። አ.ት፡ “ከ22 ሊትር ዱቄት ጋር”

መረቅ
እንደ ሥጋ ያለ የተቀቀለ ምግብ ያለበት ውሃ።

አቀረበለት
“ለእግዚአብሔር መልአክ አቀረበለት”

የእግዚአብሔር መልአክ
ይህ ከእግዚአብሔር መልአክ ጋር አንድ ነው። አ.ት፡ “በመልአክ መልክ የተገለጠ አግዚአብሔር” ወይም “እግዚአብሔር”

Judges 6:21

የእግዚአብሔር መልአክ
በ6፡11-24 እግዚአብሔር በመልአክ መልክ ለጌዴዎን ተገልጦለታል። ይህንን በመሳፍንት 6፡11 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ተለይቶት ሄደ
“ተሰወረበት”

Judges 6:22

የእግዚአብሔር መልአክ
በ6፡11-24 እግዚአብሔር በመልአክ መልክ ለጌዴዎን ተገልጦለታል። ይህንን በመሳፍንት 6፡11 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ጌታ እግዚአብሔር ሆይ!
እዚህ ጋ “ሆይ” የሚለው ቃል ጌዴዎን እጅግ መፍራቱን ያሳያል።

የእግዚአብሔርን መልአክ ፊት ለፊት አይቻለሁና
ይህ ሐረግ ለእርስ በእርሳቸው ቅርበት ያላቸውን ሁለት ሰዎች ያመለክታል። አ.ት፡ “በእርግጥ የእግዚአብሔርን መልአክ አይቻለሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር አለው
እግዚአብሔር ጌዴዎንን ከሰማይ ተናገረው።

እስከዚህ ቀን ድረስ
ይህ ማለት መጽሐፈ መሳፍንት የተጻፈበት ጊዜ ማለት ነው።

ዖፍራ
የዚህን ከተማ ስም በመሳፍንት 6፡11 እንዳደረግከው በተመሳሳይ ተርጉመው።

የአቢዔዝር ጎሳ
የዚህን የሕዝብ ወገን ስም በመሳፍንት 6፡11 እንዳደረግከው ተርጉመው።

Judges 6:25

ሁለተኛውን ወይፈን
“ሁለተኛው” የሚለው ቃል የመቁጠሪያ ቁጥር “ሁለት” ነው። አ.ት፡ “ሌላ ወይፈን”

በአጠገቡ ያለውን
“በበኣል መሠዊያ አጠገብ ያለውን”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በዚህ የመደበቂያ ቦታ አናት ላይ
የዖፍራ ከተማ በኮረብታ አናት ላይ ነበረች። እስራኤላውያን ከምድያማውያን ለመደበቅ ወደዚያ ሸሹ።

በትክክለኛው መንገድ ሥራው
“ድንጋዮቹን ሥርዓት ባለው መልኩ አስቀምጣቸው” ወይም “በአግባቡ አነባብረው”

Judges 6:27

እግዚአብሔር እንደነገረው አደረገ
ይህ እግዚአብሔር በመሳፍንት 6:25-26 ላይ የሰጠውን ትዕዛዝ ያመለክታል።

Judges 6:28

ተነሣ
“ከአልጋው ተነሣ” ወይም “ነቃ”

የበኣል መሠዊያ ፈርሶ፣ በአጠገቡ የነበረው የአሼራ ምስልም ተሰባብሮና ሁለተኛው ወይፈን በተሠራው መሠዊያ ላይ ተሠውቶ ነበር
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አንድ ሰው የበኣልን መሠዊያ እንዳፈረሰ፣ በአጠገቡ የነበረውን የአሼራን ምስል እንደሰባበረውና መሠዊያ ሠርቶ በእርሱ ላይ ሁለተኛውን ወይፈን እንደ ሠዋ አስተዋሉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Judges 6:30

መሞት አለበት
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በሞት ልንቀጣው ይገባናል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Judges 6:31

ለበኣል ትሟገቱለታላችሁ?
ኢዮአስ ሰው ለአምላክ ጠበቃ መሆን እንደማይኖርበት አጽንዖት ለመስጠት ጥያቄ ያቀርብላቸዋል። አ.ት፡ “ለበኣል ጠበቃ ልትሆኑት አይገባም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ትሟገቱለታላችሁ
“ትከላከሉለታላችሁ” ወይም “ሰበብ ትሰጡለታላችሁ”

ታድኑታላችሁ?
ኢዮአስ ሰው አምላክን መታደግ እንደማይኖርበት አጽንዖት ለመስጠት ጥያቄ ያቀርብላቸዋል። አ.ት፡ “በኣልን ማዳን የለባችሁም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ይሩበኣል
ይህ የጌዴዎን ሌላው ስሙ ነው። ትርጉሙም፣ “በኣል ራሱን ይከላከል” የሚል ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ብሏልና
“ኢዮአስ ብሏልና”

Judges 6:33

አሁን
ይህ ቃል እዚህ ጋ ጥቅም ላይ የዋለው የታሪኩ መስመር መገታቱን ለማመልከት ነው። እዚህ ጋ ተራኪው የታሪኩን አዲስ ክፍል መናገር ይጀምራል።

በአንድነት ተሰበሰቡ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉሙ በይበልጥ መብራራት ይችላል። አ.ት፡ “እንደ ሰራዊት በአንድ ላይ ተሰበሰቡ”

Judges 6:34

በጌዴዎን ላይ መጡበት
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ጌዴዎንን ተቆጣጠሩት” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የአቢዔዝር ጎሳ
የዚህን የሕዝብ ወገን ስም በመሳፍንት 6:11 ላይ በተረጎምከው መልኩ ተርጉመው።

እንዲከተሉት
“ወደ ጦርነት” የሚሉት ቃላት ግልጽ ናቸው። አ.ት፡ “ወደ ጦርነት እንዲከተሉት”

እነርሱም ደግሞ እንዲከተሉት ተጠሩ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እንዲከተሉት ይጠራቸዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ወደ አሴር፣ ዛብሎንና ንፍታሌም
እነዚህ ሁሉ የእያንዳንዱን ጎሳ ሕዝብ ይወክላሉ። አ.ት፡ “ወደ አሴር፣ ዛብሎንና ንፍታሌም ጎሳ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 6:36

የበግ ጠጉር ባዘቶ
ሱፍነት ያለው የበግ ጠጉር

ጠል
ሌሊት ላይ እጽዋት ላይ የሚቆይ ውሃ

ከዚያም እንደምታድን ዐውቃለሁ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉሙ በይበልጥ መብራራት ይችላል። አ.ት፡ “ይህ ከአንተ ዘንድ ምልክት ይሆናል፣ ከዚያም እንደምታድን ዐውቃለሁ”

Judges 6:38

ጌዴዎን ተነሣ
“ጌዴዎን ከአልጋው ተነሣ”

ጨመቀው
ውሃው እንዲወጣለት አንድን ነገር ጠምዝዞ መጭመቅ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 7

1 ከዚያም ጌዴዎን የተባለው ይሩበኣልና ከእርሱም ጋር የነበሩ ሕዝብ ሁሉ በጠዋት ተነሡ፣ በሐሮድ ምንጭ አጠገብም ሰፈሩ። የምድያምም ሰፈር ከእነርሱ ወደ ሰሜን በኩል በሞሬ ኮረብታ አጠገብ በሸለቆው ውስጥ ነበረ። **2** እግዚአብሔርም ጌዴዎንን እንዲህ አለው፣ “ምድያማውያንን እንድታሸንፍ የሚያደርጉህ እጅግ በጣም ብዙ ወታደሮች አሉኝ። ‘የራሳችን ኃይል አዳነን’ ብለው እስራኤል እንዳይታበዩብኝ እርግጠኛ ሁን። **3** ስለዚህም አሁን፣ በሕዝቡ ጆሮዎች እንዲህ ብለህ ተናገር፣ “ማንም የፈራ ቢኖር፣ ማንም የደነገጠ ቢኖር፣ የገለዓድን ተራራ ትቶ ይመለስ።” ስለዚህ 22, 000 ሰዎች ተመለሱ፣ 10, 000 ሰዎችም ቀሩ። **4** እግዚአብሔርም ጌዴዎንን እንዲህ አለው፣ “ሕዝቡ አሁንም ገና ብዙ ነው። ሕዝቡን ወደ ውኃ ውሰዳቸው፣ በዚያም ቁጥራቸውን ጥቂት አደርግልሃለሁ። እኔ ‘ይህ ከአንተ ጋር ይሄዳል’ ካልሁህ እርሱ ከአንተ ጋር ይሄዳል፤ ነገር ግን እኔ ‘ይህ ከአንተ ጋር አይሄድም’ ካልሁህ እርሱ ከአንተ ጋር አይሄድም።” **5** ስለዚህ ጌዴዎን ሕዝቡን ወደ ውኃ ወሰዳቸው፣ እግዚአብሔርም ጌዴዎንን እንዲህ አለው፣ “ውሻ እንደሚጠጣ ውኃ የሚጠጣውን ሁሉ፣ ውኃ ለመጠጣት በጕልበታቸው ከሚንበረከኩት ሰዎች መካከል ለይ።” **6** ሦስት መቶ ሰዎች ውኃ እንደ ውሻ ጠጡ። የቀሩት ሰዎች ግን ውኃ ለጠጡ በጕልበታቸው ተንበረከኩ። **7** እግዚአብሔርም ጌዴዎንን እንዲህ አለው፣ “ውኃን እንደ ውሻ በጠጡት በሦስት መቶ ሰዎች ከምድያማውያን አድንሃለሁ፣ በእነርሱም ላይ ድል እሰጥሃለሁ። ሌሎቹ ሰዎች በሙሉ ወደ ስፍራቸው ይመለሱ።” **8** ስለዚህ የተመረጡት ሰዎች ስንቃቸውንና ቀንደ መለከታቸውን ወሰዱ። ጌዴዎን የእስራኤልን ሰዎች ሁሉ፣ እያንዳንዱን ሰው ወደ ድንኳናቸው ሰደዳቸው፣ ነገር ግን ሦስቱን መቶ ሰዎች በእርሱ ዘንድ አቆያቸው። የምድያምም ሰፈር ከእርሱ በታች በሸለቆው ውስጥ ነበረ። **9** በዚያም ሌሊት እግዚአብሔር ለእርሱ እንዲህ አለው፣ “ተነስ! ሰፈራቸውን ምታ፣ በእነርሱ ላይ እኔ ድል እሰጥሃለሁና። **10** ነገር ግን አንተ ወደ ለመውረድ ከፈራህ፣ ከአገልጋይህ ከፉራ ጋር ወደ ሰፈሩ ውረድ፣ **11** የሚናገሩትንም አድምጥ፣ ከዚያም በኋላ ሰፈሩን ለመውጋት ድፍረት ታገኛለህ።” ስለዚህ ጌዴዎን ከአገልጋዩ ከፉራ ጋር በሰፈሩ ወደ ነበሩት ጠባቂዎች ወረዱ። **12** ብዛታቸውም እንደ አንበጣ መንጋ የሆነ ምድያማውያን፣ አማሌቃውያንና የምሥራቅም ሰዎች ሁሉ በሸለቆው ውስጥ ሰፍረው ነበር። የግመሎቻቸውም ብዛት መቁጠር አይቻልም ነበር፤ ቁጥራቸው በባህር ዳርቻ ካለው አሸዋ ይልቅ የሚበልጥ ነበር። **13** ጌዴዎን በዚያ በደረሰ ጊዜ አንድ ሰው ሕልምን ለጓደኛው ሲነግረው ነበር። ሰውየውም እንዲህ አለ፣ “ተመልከት! ሕልም አለምሁ፣ አንዲት ክብ የገብስ ቂጣ ወደ ምድያም ሰፈር ተንከባልላ ስትወርድ አየሁ። ወደ ድንኳኑም ደረሰች፣ እስኪወድቅ ድረስም በጣም መታችው ከዚህ የተነሳ ወደቀ፣ ደግሞም ተገለበጠ፣ ስለዚህም ድንኳኑ ተጋደመ።” **14** ሌላኛውም ሰው እንዲህ አለ፣ “ይህ ነገር ከእስራኤል ሰው ከኢዮአስ ልጅ ከጌዴዎን ሰይፍ በቀር ሌላ አይደለም። እግዚአብሔር በምድያምና በሠራዊቱ ሁሉ ላይ ድል ሰጥቶታል።” **15** ጌዴዎን የሕልሙን ዝርዝርና ትርጓሜውን በሰማ ጊዜ በጸሎት ተደፍቶ ሰገደ። እርሱም ወደ እስራኤል ሰፈር ሄደና እንዲህ አለ፣ “ተነሱ! እግዚአብሔር በምድያም ሠራዊት ላይ ድል ሰጥተአችኋል።” **16** እርሱም ሦስቱን መቶ ሰዎች በሦስት ቡድን ከፈላቸው፣ ለሁሉም ሰዎች ቀንደ መለከትና ባዶ ማሰሮ፣ በማሰሮውም ውስጥ ችቦ ሰጣቸው። **17** እርሱም እንዲህ አላቸው፣ “እኔን ተመልከቱ፣ የማደርገውንም አድርጉ። አስተውሉ! ወደ ሰፈሩ ዳርቻ በመጣሁ ጊዜ፣ እኔ የማደርገውን እናንተም ታደርጋላችሁ። **18** እኔና ከእኔም ጋር ያሉት ሁሉ ቀንደ መለከት ስንነፋ፣ እናንተ ደግሞ በሰፈሩ በሁሉም አቅጣጫ ቀንደ መለከታችሁን ንፉና “ለእግዚአብሔርና ለጌዴዎን” ብላችሁ ጩኹ። **19** ስለዚህ ጌዴዎንና ከእርሱ ጋር የነበሩት መቶ ሰዎች የመካከለኛው የጥበቃ ሰዓት በተጀመረ ጊዜ ወደ ሰፈሩ ዳርቻ መጡ። ምድያማውያን የጥበቃ ሰዎችን በሚቀይሩበት ጊዜ፣ ቀንደ መለከቶቹን ነፉ፣ በእጃቸውም የነበሩትንም ማሰሮች ሰባበሩ። **20** ሦስቱም ቡድኖች ቀንደ መለከቶቹን ነፉ፣ ማሰሮችንም ሰበሩ። በግራ እጃቸው ችቦችን ያዙ፣ በቀኝ እጃቸው ደግሞ ቀንደ መለከቶችን ይዘው ለመንፋት ተዘጋጁ። እነርሱም “የእግዚአብሔርና የጌዴዎን ሰይፍ” ብለው ጮኹ። **21** ሁሉም ሰው በሰፈሩ ዙሪያ በየቦታው ቆመ፣ የምድያማውያን ሠራዊት ሁሉ ሮጡ። እነርሱም ጮኹና ሸሹ። **22** ሦስት መቶውንም ቀንደ መለከቶች በነፉ ጊዜ፣ እግዚአብሔር የእያንዳንዱን ምድያማዊ ሰው ሰይፍ በጓደኛውና በራሳቸው ሰራዊት ሁሉ ላይ አዘጋጀ። ሠራዊቱም በጽሬራ በኩል እስከ ቤትሺጣ፣ በጠባት አጠገብ እስካለው እስከ አቤልምሖላ ዳርቻ ድረስ ሸሸ። **23** የእስራኤል ሰዎች ከንፍታሌም፣ ከአሴርና ከምናሴም ሁሉ ተሰብስበው ምድያምን ከኋላ እየተከተሉ አሳደዱ። **24** ጌዴዎን መልክተኞችን በኤፍሬም ወዳለው ኮረብታማ አገር ሁሉ በመስደድ እንዲህ አለ፣ “ምድያምን ለመዋጋት ውረዱና እነርሱን ለማስቆም የዮርዳኖስን ወንዝ እስከ ቤትባራም ድረስ ተቆጣጠሩ።” ስለዚህ የኤፍሬም ሰዎች ሁሉ በአንድ ላይ ተሰብስበው እስከ ቤትባራና የርዳኖስ ወንዝ ድረስ ውኃውን ተቆጣጠሩ። **25** የምድያምን ሁለቱን መሪዎች ሔሬብንና ዜብን ያዙ። ሔሬብንም በሔሬብ ዓለት ገደሉት፣ ዜብንም በዜብ ወይን መጥመቂያ ላይ ገደሉት። ምድያማውያንንም አሳደዱ፣ የሔሬብንና የዜብንም ራስ ይዘው በዮርዳኖስ ማዶ ወደነበረው ወደ ጌዴዎን አመጡ።

Judges 7:1

ይሩበአል
ይህ የጌዴዎን ሌላው ስሙ ነው። ስሙን በመሳፍንት 6፡32 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሰፈሩ
“የጦር ሰፈራቸውን አዘጋጁ”

የሐሮድ ምንጭ - የሞሬ ኮረብታ
እነዚህ የቦታዎች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የምድያም የጦር ሰፈር በስተሰሜናቸው ነበር
እዚህ ጋ “ምድያም” የሚወክለው የምድያማውያኑን ሰራዊት ነው። አ.ት፡ “የምድያማውያን ሰራዊት የጦር ሰፈራቸውን ከእስራኤላውያን ሰራዊት በስተሰሜን ባለ ስፍራ አደረጉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 7:2

በምድያማውያን ላይ ድል እንድሰጥህ
“ድል” የሚለው ቃል የነገር ስም ሲሆን እንደ ግሥ ወይም ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ምድያማውያንን ታሸንፋቸው ዘንድ እንድፈቅድልህ” ወይም “በምድያማውያን ላይ ባለ ድል ላደርግህ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት”

የገዛ ራሳችን ኃይል አድኖናል
እዚህ ጋ “ኃይል” የሚወክለው ሕዝቡን ራሳቸውን ነው። አ.ት፡ “ያለ እግዚአብሔር እርዳታ ራሳችንን አድነናል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አሁን
ይህ “በዚህ ሰዓት” ማለት አይደለም፣ ነገር ግን ትኩረትን ወደሚቀጥለው አስፈላጊ ጉዳይ ለመሳብ ጥቅም ላይ ውሏል።

በሕዝቡ ጆሮ ዐውጅ
እዚህ ጋ “ጆሮ” የሰውን ሁለንተና ያመለክታል። አ.ት፡ “ለሕዝቡ ዐውጅ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ማንም የሚፈራ፣ ማንም የሚንቀጠቀጥ
ሁለቱም ሐረጎች ያላቸው ትርጉም አንድ ነው። (ተመሳሳይነት የሚለውን ተመልከት)

የሚንቀጠቀጥ
ይህ ቃል የሚገልጸው አንድ ሰው ከፍርሐት የተነሣ ሊቆጣጠረው በማይችለው ሁኔታ መንቀጥቀጡን ነው። አ.ት፡ “በፍርሐት የሚንቀጠቀጥ”

ይመለስ
ወዴት እንደሚሄድ ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። አ.ት፡ “ወደ ቤቱ ይመለስ”

ገለዓድ ተራራ
ይህ በገለዓድ አውራጃ የሚገኝ ተራራ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ሃያ ሁለት ሺህ
“22,000” (ቁጥሮችን ተመልከት)

አሥር ሺህ ቀሩ
በውስጠ ታዋቂነት “ሰዎች” ወይም “ወንዶች” የሚል ቃል መኖሩን ይረዷል። አ.ት፡ “10,000 ሰዎች ቀሩ” ወይም “10,000 ወንዶች ቀሩ”

አሥር ሺህ
x

Judges 7:4

በዚያ ብዛታቸውን እቀንስልሃለሁ
እዚህ ጋ “ቁጥር” ሰራዊትን ይወክላል። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም በበለጠ ግልጽ መሆን ይችላል። አ.ት፡ “በዚያ የሰራዊቱ ቁጥር እንዲቀንስ ማንን ወደ ቤቱ እንደምትመልሰው አሳይሃለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና የሚለውን ተመልከት)

Judges 7:5

ጌዴዎን አመጣ
“አመጣ” የሚለው ቃል “ወሰደ” ወይም “መራ” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። (ሂድ እና ና የሚለውን ቃል ተመልከት)

በእጆቻቸው
በምላስ በመላስ መጠጣት

ሦስት መቶ ሰዎች
“300 ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

Judges 7:7

ሦስት መቶ ሰዎች
“300 ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

አድንሃለሁ፣ ድልንም እሰጥሃለሁ
እዚህ ጋ “አንተ” ብዙ ቁጥር ሲሆን ጌዴዎንና እስራኤላውያንን ያመለክታል።

ስለዚህ እነዚያ የተመረጡት
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ስለዚህ እነዚያ እግዚአብሔር የመረጣቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ስንቃቸውንና መለከታቸውን ወሰዱ
እዚህ ጋ “እነርሱ” የሚያመለክተው ሰራዊቱን ትተው የሚመለሱትን የእስራኤል ወታደሮች ነው።

አሁን
ይህ ቃል እዚህ ጋ ጥቅም ላይ የዋለው የታሪኩ መስመር ለአፍታ ቆም ማለቱን ለማመልከት ነው። እዚህ ጋ ተራኪው የታሪኩን አዲስ ክፍል መናገር ይጀምራል።

Judges 7:9

በእነርሱ ላይ ድል ስለምሰጥህ የጦር ሰፈሩን አጥቃ
እዚህ ጋ “የጦር ሰፈር” የሚያመለክተው የምድያማውያንን ሰራዊት በሙሉ ነው። “ድል” የሚለው ቃል የነገር ስም ሲሆን እንደ ግሥ ወይም ቅጽል ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እንድታሸንፋቸው ልረዳህ ስለሆነ ምድያማውያንን በጦር ሰፈራቸው አጥቃቸው” ወይም “በእነርሱ ላይ ድል አድራጊ እንድትሆን ስለማደርግ ምድያማውያንን በጦር ሰፈራቸው አጥቃቸው” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ለመውረድ ፈራ
የታወቀውን መረጃ ግልጽ ልታደርገው ትችላለህ። አ.ት፡ “ወርዶ ለማጥቃት ፈራ”

ፉራ
ይህ የአንድ ሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ድፍረትህ ይጨምራል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የምትሰማው ያበረታሃል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ኬላ
ወታደሮች የጠላትን ሰራዊት ለመቆጣጠር የሚቆሙበት አካባቢ ዳርቻ

Judges 7:12

የአንበጣው ብዛት እንደ ደመና የሚሸፍን
እዚህ ጋ “ደመና” ማለት መንጋ ነው። ደራሲው ምን ያህል ወታደሮች እንደነበሩ አጽንዖት ለመስጠት የአንበጣ መንጋ በማለት ስለ ሰራዊቱ ይናገራል።

ግመሎቻቸው በባህር ዳርቻ ከሚገኝ አሸዋ በቁጥር ይበልጥ ነበር
ደራሲው በጣም ብዙ ግመሎች መኖራቸውን በአጽንዖት ሲገልጽ ግነትን ይጠቀማል። (ግነትና ጥቅል አስተያየት የሚለውን ተመልከት)

ግመሎቻቸው ከቁጥር በላይ ነበሩ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ግመሎቻቸው ማንም ሊቆጥራቸው ከሚችለው በላይ ነበሩ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Judges 7:13

ይህ ከጌዴዎን ሰይፍ በስተቀር ሌላ አይደለም
እዚህ ጋ “የጌዴዎን ሰይፍ” የሚያመለክተው አጥቂውን የጌዴዎንን ሰራዊት ነው። አ.ት፡ “በሕልምህ ያየኸው የገብስ እንጎቻ የጌዴዎን ሰራዊት መሆን አለበት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር በምድያም ላይ ድልን ሰጠው
ይህ ወደፊታዊ ሁነት እንደ አላፊ ሁነት ሆኖ ተነግሯል። ይህ በእርግጠኝነት የሚፈጸም ስለመሆኑ አጽንዖት ይሰጣል። አ.ት፡ “በእርግጥ እስራኤላውያን ምድያማውያንን እንዲያሸንፉ እግዚአብሔር ይረዳቸዋል”

Judges 7:15

ሦስት መቶ ሰዎች
“300 ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Judges 7:17

ለእግዚአብሔርና ለጌዴዎን!
በውስጠ ታዋቂነት “እንዋጋለን” ማለት ነው። አ.ት፡ “ለእግዚአብሔርና ለጌዴዎን እንዋጋለን!”

Judges 7:19

አንድ መቶ ሰዎች
“100 ሰዎች” (ቁጥሮችን ተመልከት)

ልክ በእኩለ ሌሊት ጅማሬ ላይ
የእኩለ ሌሊት ጅማሬ ከምሽቱ 4 ሰዓት ገደማ ይሆናል።

Judges 7:20

የእግዚአብሔርና የጌዴዎን ሰይፍ
እዚህ ጋ “ሰይፍ” የሚያመለክተው ውጊያቸውን ነው። አ.ት፡ “ለእግዚአብሔርና ለጌዴዎን እንዋጋለን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 7:22

ሦስት መቶ መለከቶች
“300 መለከቶች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር የእያንዳንዱን ምድያማዊ ሰይፍ በባልንጀራው ላይ እንዲሆን አደረገ
እዚህ ጋ “ሰይፍ” የሚያመለክተው ሰይፍ በመጠቀም ማጥቃታቸውን ነው። አ.ት፡ “እያንዳንዱ ምድያማዊ ሰው ባልንጀራው ከሆነው ወታደር ጋር እንዲዋጋ እግዚአብሔር አደረገ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ቤት ሺጣ - ጽሬራ - አቤላሞሖላ - ጠባት
እነዚህ የመንደሮችና የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ከንፍታሌም፣ አሴርና ምናሴ ሁሉ የእስራኤል ሰዎች ተጠርተው ወጡ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ጌዴዎን እስራኤላውያንን ከንፍታሌም፣ አሴርና ከምናሴ ነገድ ሁሉ ጠራ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Judges 7:24

ቤት ባራ
ይህ የእነስተኛ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

እስከ ቤት ባራና ዮርዳኖስ ወንዝ ያሉትን ውሃዎች ተቆጣጠሩ
“የዮርዳኖስን ወንዝ አካባቢ እስከ ቤት ባራ ደቡብ ድረስ ተቆጣጠሩ”

በሔራብ ዐለት - በዜብ የወይን መጭመቂያ
እስራኤላውያን ሔራብና ዜብን በዚያ ከገደሉ በኋላ አካባቢዎቹ እነዚህ ስሞች ተሰጥተዋቸው ነበር።

ሔራብ - ዜብ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 8

1 የኤፍሬም ሰዎች ለጌዴዎን እንዲህ አሉት፣ “ይህ በእኛ ላይ ያደረግኸው ምንድር ነው? ምድያምን ለመዋጋት በሄድህ ጊዜ እኛን አልጠራኸንም?” ከእርሱም ጋር በኃይል ተጣሉ። **2** እርሱም እንዲህ አላቸው፣ “ከእናንተ ጋር ሲነጻጸር አሁን እኔ ያደረግት ምንድን ነው? ከኤፍሬም የወይን ቃርሚያ ይልቅ የአቢዔዝር ሙሉ የወይን መከር አይሻልምን? **3** እግዚአብሔር በምድያም መሪዎች በሔሬብና በዜብ ላይ ድልን ሰጥቶአችኋል! ከእናንተ ጋር ሲነጻጸር እኮ ምን ፈጸምሁ?” ይህን በተናገረ ጊዜ ቊጣቸው በረደ። **4** ጌዴዎን ከእርሱ ጋር ከነበሩት ከሦስቱ መቶ ሰዎች ጋር ወደ ዮርዳኖስ መጣና ተሻገረ። እጅግ በጣም ደክመው ነበር፣ ይሁን እንጂ ያሳድዱ ነበር። **5** እርሱም ለሱኮት ሰዎች እንዲህ አላቸው፣ “ደክመዋልና እባካችሁ ለተከተሉኝ ሰዎች እንጀራ ስጡአቸው፣ እኔም የምድያምን ነገሥታት ዛብሄልንና ስልማናን እያሳደድሁ ነው።” **6** የሱኮትም መሪዎች እንዲህ አሉ፣ “ዛብሄልንና ስልማናን በጉልበትህ አሸነፍኃቸውን?” እኛ ለሠራዊትህ እንጀራ ለምን እንደምንሰጥ አናውቅም? **7** ጌዴዎንም እንዲህ አለ፣ “እግዚአብሔር በዛብሄልና በስልማና ላይ ድል በሰጠኝ ጊዜ፣ እኔ በምድረ በዳ እሾህና በኵርንችት ሥጋችሁን እቦጫጭቀዋለሁ።” **8** ከዚያም ወደ ጵኒኤል ወጣና በተመሳሳይ መንገድ በዚያ ለሚገኙ ሰዎች ተናገራቸው፣ ነገር ግን የጵንኤልም ሰዎች የሱኮት ሰዎች እንደ መለሱ መለሱለት። **9** እርሱም የጵኒኤልን ሰዎች ደግሞ እንዲህ አላቸው፣ “በሰላም በተመለስሁ ጊዜ፣ ይህን ግንብ አፈርሰዋለሁ። **10** ዛብሄልና ስልማናም ከሠራዊቶቻቸው ጋር፣ ከምሥራቅም ሰዎች ሠራዊት ሁሉ የቀሩ 15, 000 ያህል ሰዎች በቀርቀር ነበሩ። በሰይፍ ለመዋጋት ስልጠና የወሰዱ መቶ ሀያ ሺህ ሰዎች ወድቀው ነበርና። **11** ጌዴዎንም ዘላኖች ባሉበት መንገድ በኖባህና በዮግብሃ አልፎ ወደ ጠላት ሰፈር ሄደ። እርሱም የጠላትን ሰራዊት አሸነፈ፣ ምክንያቱም እንዲህ ዓይነት አደጋ ይገጥመናል ብለው አላሰቡም ነበርና። **12** ዛብሄልና ስልማናም ሸሹ፣ ጌዴዎንም ባሳደዳቸው ጊዜ ሁለቱንም የምድያም ነገሥታት ዛብሄልንና ስልማናን ያዛቸው፣ ሠራዊታቸውንም ሁሉ ድንጋጤ ላይ ጣላቸው። **13** የኢዮአስ ልጅ ጌዴዎንም በሔሬስ ዳገት በኩል በማለፍ ከጦርነት ተመለሰ። **14** እርሱም ከሱኮት ሰዎች አንድ ወጣት ይዞ ጠየቀውና ከእርሱ ምክር ፈለገ። ወጣቱም የሱኮትን መሪዎችና ሽማግሌዎች ሰባ ሰባት ሰዎች እነማን እንደሆኑ ገለጸለት። **15** ጌዴዎንም ወደ ሱኮት ሰዎች መጣና እንዲህ አላቸው፣ “‘ዛብሄልንና ስልማናን በጉልበትህ አሸነፍኃቸውን? እኛ ለሠራዊትህ እንጀራ መስጠት እንዳለብን አናውቅም?’ ብላችሁ ያላገጣችሁብኝ ዛብሄልና ስልማና ተመልከቱአቸው።” **16** ጌዴዎንም የከተማይቱን ሽማግሌዎች ያዛቸው፣ የሱኮትንም ሰዎች በምድረ በዳ እሾህና በኵርንችት ገረፋቸው። **17** የጵኒኤልንም ግንብ አፈረሰ፣ የዚያችን ከተማ ሰዎችን ገደለ። **18** ጌዴዎንም ለዛብሄልና ለስልማና እንዲህ አላቸው፣ “በታቦር የገደላችኋቸው ሰዎች ምን ዓይነት ሰዎች ነበሩ?” እነርሱም፣ “እንደ አንተ ያሉ ነበሩ። እያንዳንዳቸው የንጉሥ ልጅ ይመስላሉ” አሉት። **19** ጌዴዎንም “እነርሱ የእናቴ ልጆች ወንድሞቼ ነበሩ። በሕይወት እንዲኖሩ አድናችኋቸው ቢሆን ኖሮ፣ ሕያው እግዚአብሔርን፣ እኔ አልገድላችሁም ነበር” አለ። **20** ለበኩር ልጁ ለዬቴር እንዲህ አለው፣ “ተነሳና ግደላቸው!” ነገር ግን ወጣቱ ልጅ ስለፈራ ሰይፉን አልመዘዘም፣ ምክንያቱም ገና ወጣት ልጅ ነበረና። **21** የዚያን ጊዜ ዛብሄልና ስልማና እንዲህ አሉ፣ “አንተ ተነሳና ግደለን! የሰው ኃይሉ እንደ ሰውነቱ ነውና።” ጌዴዎንም ተነሥቶ ዛብሄልንና ስልማናን ገደላቸው። በግመሎቻቸውም አንገት ላይ የነበሩትን ጌጦች ወሰደ። **22** የእስራኤልም ሰዎች ጌዴዎንን “አንተ ግዛን፣ አንተ፣ የአንተ ልጅና የልጅ ልጆችህ ግዙን፣ ምክንያቱም አንተ ከምድያም ብርታት አድነኸናልና።” **23** ጌዴዎንም ለእነርሱ እንዲህ አላቸው፣ “እኔ በእናንተ ላይ አልገዛም፣ ልጄም በእናንተ ላይ አይገዛም፣ እግዚአብሔር ይገዛችኋል አላቸው። **24** ጌዴዎን ለእነርሱ እንዲህ አላቸው፣ “አንድ የምጠይቃችሁ ነገር አለኝ፦ እያንዳንዳችሁ ከምርኮአችሁ ጕትቻችሁን እንድትሰጡኝ እለምናችኋለሁ።” (ምድያማውያን የወርቅ ጕትቻ ነበራቸው ምክንያቱም እነርሱ እስማኤላውያንም ነበሩና።) **25** እነርሱም፣ “ለአንተ ልንሰጥህ ደስተኞች ነን” አሉት። እነርሱም ልብስ አነጠፉና ሁሉም ሰው የምርኮውን ጕትቻ በዚያ ላይ ጣለ። **26** እርሱ የጠየቀው የወርቅ ጕትቻ ክብደት 1, 700 ሰቅል ወርቅ ነበር። ይህም ምርኮ ከጌጣ ጌጦቹ ሌላ የአንገት ጌጥ፣ የምድያምም ነገሥታት ከሚለብሱት ሐምራዊ ልብስ፣ እንደዚሁም በግመሎቻቸውም አንገት ከነበሩት ጌጦች ሌላ ነበረ። **27** ጌዴዎንም ከጕትቻዎቹ ባገኘው ወርቅ ኤፉድ ሠራና በከተማው፣ በዖፍራ አኖረው፣ እስራኤልም ሁሉ እርሱን በማምለክ አመነዘረበት። ለጌዴዎንና በቤቱም ላሉት ወጥመድ ሆነባቸው። **28** ስለዚህም ምድያም በእስራኤል ሕዝብ ፊት ተዋረደ፣ ራሳቸውንም እንደገና አላነሡም። በጌዴዎንም ዘመን ምድሪቱ ለአርባ ዓመት ሰላም ሆነች። **29** የኢዮአስም ልጅ ይሩበኣል ሄደና በራሱ ቤት ተቀመጠ። **30** ጌዴዎንም ብዙ ሚስቶች ነበሩትና ሰባ ወንዶች ልጆች ነበሩት። **31** በሴኬም የነበረችው ቁባቱም ወንድ ልጅ ወለደችለት፣ ጌዴዎንም ስሙን አቤሜሌክ ብሎ ጠራው። **32** የኢዮአስ ልጅ ጌዴዎን በመልካም የሸምግልና ዕድሜ ሞተ፣ በአቢዔዝራውያን ጎሳ በሆነው በዖፍራ በነበረው በአባቱ በኢዮአስ መቃብር ተቀበረ። **33** ጌዴዎን ከሞተ በኋላ ብዙ ሳይቆይ እንዲህ ሆነ፣ የእስራኤል ሕዝብ እንደገና ተመለሱ፣ የበኣልን አማልክት በማምለክ አመነዘሩ። በኣልብሪትንም አምላካቸው አደረጉ። **34** የእስራኤልም ሕዝብ በተለያዩ አቅጣጫዎች ከነበሩት ከጠላቶቻቸው ኃይል ያዳናቸውን አምላካቸውን እግዚአብሔርን አላሰቡትም። **35** እነርሱም ለእስራኤል ስላደረገው በጎ ነገር አስበው ለይሩበኣል (የጌዴዎን ሌላኛው ስም ነው) ውለታ ለመመለስ ቃል ኪዳናቸውን አልጠበቁም።

Judges 8:1

ይህ ያደረግህብን ምንድነው?
የኤፍሬም ነገድ ሰዎች በሰራዊቱ ውስጥ እነርሱን ባለማካተቱ በዚህ ምላሽ በማይፈልግ ጥያቄ ጌዴዎንን ሲወቅሱት ነበር። ይህ እንደ መግለጫ መነገር ይችላል። አ.ት፡ “በአግባቡ አላየኸንም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

በምድያም ላይ
እዚህ ጋ “ምድያም” የሚወክለው የምድያማውያንን ሰራዊት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በኃይል ተሟገቱት
“ከእርሱ ጋር በቁጣ ተከራከሩ” ወይም “ክፉኛ ወቀሱት”

Judges 8:2

ከእናንተ ጋር ሲነጻጸር እኔ አሁን ያደረግሁት ምንድነው?
ጌዴዎን ይህንን ጥያቄ የሚያቀርበው የኤፍሬምን ሰዎች ለማክበር ነው። አ.ት፡ “እናንተ ካደረጋችሁት ጋር ሲነጻጸር እኔ ያደረግሁት በጣም ጥቂት ነው” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ከአቢዔዝር ሙሉ የወይን ምርት የኤፍሬም የወይን ቃርሚያ የሚሻል አይደለምን?
ጌዴዎን በዚህ ምላሽ በማያስፈልገው ጥያቄ አማካይነት የኤፍሬምን ሰዎች ያበርዳቸው ነበር። አ.ት፡ “እኛ የአቢዔዝር ተወላጆች ከሰበሰብነው ምርት በሙሉ ያለ ምንም ጥርጥር እናንተ የኤፍሬም ሰዎች የለቀማችሁት ወይን የተሻለ ነው!” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ከአቢዔዝር ሙሉ የወይን ምርት የኤፍሬም ቃርሚያ የተሻለ አይደለምን?
የጌዴዎንና የሰራዊቱ ምድያማውያንን ማሸነፍ የወይን ምርት እንደመሰብሰብ ተቆጥሮ ተነግሯል። የኤፍሬም ሰዎች በጦርነቱ መጨረሻ ሔሬብና ዜብን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መግደላቸው ከመከር በኋላ የወይን ቃርሚያን እንደ ለቀሙ ተቆጥሮ ተነግሮላቸዋል። አ.ት፡ “እኛ የአቢዔዝር ተወላጆች በመጀመሪያ ካደረግነው ይልቅ እናንተ የኤፍሬም ሰዎች በጦርነቱ መጨረሻ ላይ ያደረጋችሁት ይበልጥ ታላቅ ነው” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

አቢዔዝር
ይህ ከጌዴዎን ቅድም አያቶች የአንዱ ስም ነው። ጌዴዎን ስሙን ያገኘው ከአቢዔዝር ተወላጆችና ከምድራቸው ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ሔሬብና ዜብ
እነዚህን ስሞች በመሳፍንት 7፡25 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

ከእናንተ ጋር ሲነጻጸር እኔ ያከናወንኩት ምንድነው?
ጌዴዎን ይህንን ጥያቄ የሚያቀርበው የኤፍሬምን ሰዎች ለማክበር ነው። ይህ እንደ መግለጫ ሊገለጽ ይችላል። አ.ት፡ “እኔ ካደረግሁት ይልቅ እናንተ ያደረጋችሁት ይበልጥ ታላቅ ነው” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

በረደ
“ቀነሰ”

Judges 8:4

ሦስት መቶው ሰዎች
“300 ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ማሳደዳቸውን ቀጠሉ
“ማሳደድ” የሚለው ቃል የነገር ስም ሲሆን እንደ ግሥ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ጠላቶቻቸውን ማባረራቸውን ቀጠሉ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ዛብሄልና ስልማና
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Judges 8:6

የዛብሄልና የስልማና እጆች አሁን በእጅህ ውስጥ አሉ?
መሪዎቹ ጥያቄ የሚያቀርቡት እስራኤላውያኑ ዛብሄልንና ስልማናን ገና ያለመማረካቸውን አጽንዖት ለመስጠት ነው። አ.ት፡ “እስካሁን ዛብሄልና ስልማናን አልማረክኻቸውም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

የዛብሄልና የስልማና እጆች
እዚህ ጋ “እጆች” የሚያመለክተው ሙሉ ሰውነትን ነው።

አሁን በእጅህ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው ኃይልን ወይም መቆጣጠርን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ለሰራዊትህ እንጀራ የምንሰጠው ለምንድነው?
መሪዎቹ የሚጠይቁት ለእስራኤላውያኑ እንጀራ የሚሰጡበት ምንም ምክንያት እንደሌለ አጽንዖት ለመስጠት ነው። አ.ት፡ “ለሰራዊትህ እንጀራ የምንሰጥበትን አንዳች ምክንያት አላገኘንም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ቆዳችሁን በበረሃ እሾህና አሜከላ እተለትለዋለሁ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም በይበልጥ መብራራት ይችላል። አ.ት፡ “በበረሃ እሾህና አሜከላ ጅራፍ በመሥራት እገርፋችኋለሁ፣ እቆራርጣችኋለሁ”

እሾህና አሜከላ
ስል፣ በሐረግ ወይም ዛፍ ቅርንጫፍ ላይ ጫፉ የሾለና ሰውና እንስሳን ለመቁረጥ የሚችል

Judges 8:8

ከዚያ ወጥቶ ሄደ
እዚህ ጋ በውስጠ ታዋቂነት የሚገኘው “እርሱ” የሚያመለክተው ጌዴዎንን ነው። ጌዴዎን የሚወክለው ራሱንና የሚከተሉትን ወታደሮች ነው። አ.ት፡ “ያንን ስፍራ ተዉ” ወይም “ጌዴዎንና 300 ሰዎቹ ያንን ስፍራ ተዉ”

ጵንኤል
የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

በዚያ ላሉ ሰዎች በተመሳሳይ መንገድ ተናገራቸው
በውስጠ ታዋቂነት ያለውን መረጃ ግልጽ ልታደርገው ትችላለህ። አ.ት፡ “እዚያም በተመሳሳይ መንገድ ምግብ እንዲሰጡት ጠየቀ” ወይም “እርሱም ደግሞ ምግብ እንዲሰጡት ጠየቃቸው”

በሰላም በምመለስበት ጊዜ
ይህ ጠላቶቹን ስለማሸነፉ የሚያመለክት የትህትና አነጋገር ነው። አ.ት፡ “የምድያማውያንን ሰራዊት ሙሉ በሙሉ ካሸነፍኩኝ በኋላ”

ይህንን ግምብ አፈርሰዋለሁ
እዚህ ጋ “እኔ” ጌዴዎንን የሚያመለክት ሲሆን ራሱንና ሰራዊቱን ይወክላል። አ.ት፡ “እኔና የእኔ ሰዎች ይህንን ግምብ እናፈርሰዋለን”

Judges 8:10

አሁን
ይህ ቃል እዚህ ጋ ጥቅም ላይ የዋለው የታሪኩ መስመር ለአፍታ ቆም ማለቱን ለማመልከት ነው። እዚህ ጋ ተራኪው የታሪኩን አዲስ ክፍል መናገር ይጀምራል።

ዛብሄልና ስልማና
እነዚህን ስሞች በመሳፍንት 8፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

ቀርቀር
ይህ የአንድ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

አስራ አምስት ሺህ ሰዎች
“15,000 ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ወደቁ
ይህ በጦርነት የሞቱትን ሰዎች በትህትና የማመላከት መንገድ ነው። አ.ት፡ “ተገድለው ነበር” ወይም “በጦርነት ሞተው ነበር”

120,000 ሰዎች
“አንድ መቶ ሃያ ሺህ ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ሰይፍ ይመዙ የነበሩ ሰዎች
እዚህ ጋ ሰይፍ መምዘዝ የሚወክለው በጦርነት ውስጥ በሰይፍ መጠቀምን ነው። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ ሐረግ የሚያመለክተው በጦርነት ውስጥ በሰይፍ የሚጠቀሙ ወታደሮችን ነው። አ.ት፡ “ሰይፍ የታጠቁ ሰዎች” ወይም “በሰይፍ የሚዋጉ ሰዎች” ወይም 2) ይህ ሐረግ የትኛውንም ወታደር ያመለክታል። አ.ት፡ “ወታደሮች” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 8:11

ጌዴዎን ወጥቶ ሄደ
እዚህ ጋ “ጌዴዎን” የሚወክለው ራሱንና ወታደሮቹን ሁሉ ነው። አ.ት፡ “ጌዴዎንና ወታደሮቹ ወጥተው ሄዱ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አሸነፈ
እዚህ ጋ በውስጠ ታዋቂነት ያለው “እርሱ” የሚያመለክተው ጌዴዎንን ራሱንና ወታደሮቹን ሁሉ ነው። አ.ት፡ “ጌዴዎንና ወታደሮቹ አሸነፉ”

ኖባህና ዮግብሃ
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ዛብሄልና ስልማና
እነዚህን ስሞች በመሳፍንት 8፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

ድንጋጤ
አንድ ሰው ማሰብ እንዳይችል ወይም በአግባቡ እንዳይሠራ የሚያስደርገው ታላቅ ፍርሃት ወይም ጭንቀት

Judges 8:13

የሐሬስ መተላለፊያ
ይህ በሁለት ተራራዎች መካከል የሚያልፍ መንገድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ጠየቀውጠየቀው
ጌዴዎን ታዳጊውን ወጣት የጠየቀው ጥያቄ በግልጽ መነገር ይችላል። አ.ት፡ “በከተማው ውስጥ ያሉትን መሪዎች በሙሉ ስማቸውን እንዲነግረው ጠየቀው”

ሰባ ሰባት አለቆች
“77 አለቆች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

Judges 8:15

ዛብሄልና ስልማና
እነዚህን ስሞች በመሳፍንት 8፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

አስቀድመህ ዛብሄልንና ስልማናን ድል አድርገሃቸዋል?
ጌዴዎን የሱኮት ሰዎች ሊሳለቁበት የጠየቁትን አባባል ይጠቅሳል። አ.ት፡ “ዛብሄልንና ስልማናን ገና ድል አላደረግሃቸውም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ጌዴዎን ወሰደ - ገረፋቸው - አፈረሰው
እዚህ ጋ “ጌዴዎን” የሚወክለው ራሱንና ወታደሮቹን ነው። አ.ት፡ “ጌዴዎንና ወታደሮቹ ወሰዱ - ገረፏቸው - አፈረሱት

እሾክና አሜከላ
ስል፣ በሐረግ ወይም ዛፍ ቅርንጫፍ ላይ የሚገኝ፣ ጫፉ የሾለና ሰውና እንስሳን ለመቁረጥ የሚችል። ይህንን በመሳፍንት 8፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ጵንኤል
የከተማይቱን ስም በመሳፍንት 8፡8 ላይ በተረጎምከው መልኩ ተርጉመው።

Judges 8:18

ዛብሄልና ስልማና
እነዚህን ስሞች በመሳፍንት 8፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

ታቦር
የዚህችን ከተማ ስም በመሳፍንት 4፡6 ላይ በተረጎምክበት መልክ ተርጉመው

አንተኑ የሚመስሉ ነበሩ
“ልክ አንተን ይመስሉ ነበር”

ሕያው እግዚአብሔርን
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሀይማኖታዊ መሓላ ሲሆን የሚናገረው እውነት መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት ጥቅም ላይ ውሏል። አ.ት፡ “ቃል እገባላችኋለሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Judges 8:20

ዮቴር
ይህ የጌዴዎን ልጅ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የሰው ኃይሉ እንደ ሰውነቱ ነው
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “አንድ ሰው ሊያደርገው የሚገባው ሥራው ነው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ግማሽ ክብ
ይህ ሁለት ጫፍ ያለው ግማሽ ክብ ቅርጽ ነው። አብዛኛውን ጊዜ ይህ ቅርጽ የሚሆነው ጨረቃ በጥላ ስትጋረድ ነው።

ጌጣ ጌጦች
ማስዋቢያዎች

Judges 8:22

አንተ፣ ልጅህና የልጅ ልጅህ
ይህ የሚያሳየው እርሱ ከሞተ በኋላ የጌዴዎን ተወላጆች እንዲገዟቸው ነው። አ.ት፡ “አንተና አንተ ከሞትክ በኋላም ተወላጆችህ”

ከምድያም እጅ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው በእስራኤል ላይ የሆነውን የምድያም ኃይል ነው። አ.ት፡ “ከምድያም ኃይል” ወይም “ከምድያም” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የምድያም
እዚህ ጋ “ምድያም” የሚወክለው የምድያምን ሰዎች ነው። አ.ት፡ “ከምድያማውያን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 8:24

ጌዴዎን ... አላቸው
“ጌዴዎን ለእስራኤል ሰዎች አላቸው”

ጉትቻዎች
በጆሮ ላይ የሚደረግ ጌጥ

ዘረፋ
በማስገደድ የተቀሙ ወይም በጦርነት ከተገደሉ ሰዎች የተወሰዱ ነገሮች

ምድያማውያን እስማኤላውያን ስለነበሩ የወርቅ ጉትቻዎች ነበሯቸው
እዚህ ጋ ተራኪው ስለ ምድያማውያን ዳራዊ መረጃ ይናገራል። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ካባ
ረዘም ካለ ክር የሚሠራና እንደ ኮት በትከሻ ላይ የሚለበስ ልብስ

Judges 8:26

1,700 ሰቅል ወርቅ
“አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሰቅል ወርቅ”። ዘመናዊውን የመጠን መለኪያ መጠቀም የሚያስፈልግ ከሆነ ይህንን ማድረግ የሚያስችሉ ሁለት መንገዶች

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አሉ። አ.ት፡ “18.7 ኪ.ግ ወርቅ” ወይም “ወደ 20 ኪ.ግ የሚጠጋ ወርቅ” (ቁጥሮች እና የመጽሐፍ ቅዱስ ክብደት መለኪያ የሚሉትን ተመልከት)

ግማሽ ክብ ቅርጽ ያላቸው ጌጣ ጌጦች
ይህንን በመሳፍንት 8፡21 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

በአንገት ጌጥ ላይ የሚንጠለጠሉ ድሪዎች
በአንገት ሀብል ወይም ክር ላይ የሚንጠለጠሉ ትናንሽ ጌጣጌጦች

የምድያም ነገሥታት ይለብሱት የነበረውን
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የምድያም ነገሥታት የለበሱት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Judges 8:27

ጌዴዎን በጉትቻዎቹ ኤፉድ ሠራ
“ጌዴዎን የወርቅ ጉትቻዎቹን ኤፉድ ለመስሪያነት ተጠቀመበት”

ዖፍራ
የከተማይቱን ስም በመሳፍንት 6፡11 እንዳደረግኸው ተርጉመው።

በዚያ እስራኤል ሁሉ አመነዘሩበት
ይህ አመንዝራነትን በሚመስል መልክ ሐሰተኛ አምላክን ስለ ማምለካቸው ይናገራል። አ.ት፡ “እስራኤላውያን በዚያ ኤፉዱን በማምለካቸው በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን ሠሩ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እስራኤል በሙሉ
እዚህ ጋ “በሙሉ” በጣም ብዙዎቹ ልብሱን ማምለካቸውን አጽንዖት ለመስጠት የተደረገ ግነት ነው። አ.ት፡ “በእስራኤል በጣም ብዙ ሰዎች ልብሱን አመለኩት” (ግነትና ጥቅል አስተያየት የሚለውን ተመልከት)

እርሱም ለጌዴዎንና በቤቱ ላሉት ወጥመድ ሆነባቸው
ይህ አደን የሚያድን ሰው የሚያጠምደው ወጥመድ ይመስል ጌዴዎንና ቤተሰቡ ኤፉዱን ሊያመልኩት እንደተፈተኑ ያሳያል። አ.ት፡ “ለጌዴዎንና ለቤተሰቡ ፈተና ሆነባቸው” ወይም “ጌዴዎንና ቤተሰቡ እርሱን በማምለክ ኃጢአትን ሠሩ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በቤቱ ላሉት
እዚህ ጋ “በቤቱ” የሚወክለው የጌዴዎንን ቤተሰብ ነው። አ.ት፡ “ለቤተሰቡ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ስለዚህ ምድያም ለእስራኤል ሕዝብ ተገዛላቸው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሰለዚህ እግዚአብሔር ምድያማውያን በእስራኤል ሕዝብ ፊት እንዲገዙ አደረጋቸው” ወይም “ስለዚህ እስራኤላውያን ምድያማውያንን እንዲያሸንፉ እረዳቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ራሳቸውን ቀና አላደረጉም
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “እንደገና እስራኤልን አላጠቁም” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ስለዚህ ምድሪቱ ዐርፋ ነበር
እዚህ ጋ “ምድሪቱ” የሚወክለው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። አ.ት፡ “ስለዚህ እስራኤላውያን በሰላም ኖሩ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አርባ ዓመት
x

Judges 8:29

ይሩበአል
ይህ የጌዴዎን ሌላው ስሙ ነው። ስሙን በመሳፍንት 6:32 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሰባ ወንዶች ልጆች
“70 ወንዶች ልጆች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

Judges 8:32

ረጅም ዕድሜ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “በጣም በሸመገለ ጊዜ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ተቀበረ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ቀበሩት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ዖፍራ
የዚህችን ከተማ ስም በመሳፍንት 6፡11 እንዳደረግኸው ተርጉመው።

ከአቢዔዝር ጎሳ
የዚህን የሕዝብ ወገን ስም በመሳፍንት 6፡11 እንዳደረግኸው ተርጉመው።

እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ ጥቅም ላይ የዋለው የታሪኩ አዲስ ክፍል መጀመሩን ለማመልከት ነው። በቋንቋህ ይህንን ማድረግ የሚያስችል መንገድ ካለ ልትጠቀምበት ትችላለህ።

እንደገና ተመለሱ
ሕዝቡ እግዚአብሔርን መተዋቸው በአካል ከእርሱ እንደተለዩ ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “እግዚአብሔርን ማምለካቸውን አቆሙ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በኣልን በማምለክ አመነዘሩ
ሐሰተኛ አማልክትን ማምለካቸው እንደ አመንዝራነት ተቆጥሮ ተነግሯል። አ.ት፡ “በኣልን በማምለክ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን ሠሩ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በኣልብሪት
ይህ የሐሰተኛ አምላክ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Judges 8:34

ከጠላቶቻቸው እጅ ሁሉ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው ኃይልን ወይም መቆጣጠርን ነው። አ.ት፡ “ከጠላቶቻቸው ኃይል ሁሉ” ወይም “ከጠላቶቻቸው ሁሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በየአቅጣጫው
“የከበቧቸውን “

የይሩበአል ቤት
እዚህ ጋ “የ…ቤት” የሚወክለው የአንድን ሰው ቤተሰብ ነው። አ.ት፡ “የይሩበአል ቤተሰብ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ይሩበአል
ይህ የጌዴዎን ሌላው ስሙ ነው። ይህንን በመሳፍንት 6:32 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 9

1 የይሩበኣል ልጅ አቤሜሌክ ወደ እናቱ ዘመዶች ወደ ሴኬም ሄደና ለእነርሱና ለእናቱ ቤተሰብ ጎሳ በሙሉ እንዲህ አላቸው፣ 2 “በሴኬም የሚገኙ መሪዎች
በሙሉ ይሰሙ ዘንድ ይህን ተናገሩ፣ ‘ለእናንተ የሚሻለው የትኛው ነው? የይሩበኣል ሰባ ልጆች ሁሉ ቢገዙአችሁ ወይስ አንድ ሰው ቢገዛችሁ?’ እኔ የአጥንታችሁ
ፍላጭ የሥጋችሁ ቍራጭ እንደ ሆንሁ አስቡ።” 3 የእናቱም ዘመዶች ስለ እርሱ ለሴኬም መሪዎች ተናገሩ፣ እነርሱም አቤሜሌክን ለመከተል ተስማሙ፣ “እርሱ
ወንድማችን ነው” ብለዋልና። 4 እነርሱም ከበኣልብሪትም ቤት ሰባ ብር ሰጡት፣ አቤሜሌክም እርሱን የተከተሉትን ስርዓት አልበኞችንና ወሮበሎችን ለመቅጠር
ተጠቀበመት። 5 እርሱም ወደ አባቱ ቤት ወደ ዖፍራ ሄደ፣ የይሩበኣልን ልጆች ሰባ ወንድሞቹን በአንድ ድንጋይ ላይ አረዳቸው። ትንሹ የይሩበኣል ልጅ ኢዮአታም
ግን ተሸሽጎ ስለነበር እርሱ ብቻ ተረፈ። 6 የሴኬምና የቤትሚሎ መሪዎች ሁሉ በአንድ ላይ ተሰበሰቡ፣ እነርሱም ሄደው በሴኬም በዓምዱ አጠገብ ባለው
በበሉጥ ዛፍ ስር አቤሜሌክን አነገሡት። 7 ለኢዮአታም ይህን ነገር በነገሩት ጊዜ፣ በገሪዛን ተራራ ራስ ላይ ሄደና ቆመ። ድምፁንም ከፍ አድርጎ ጮኸና እንዲህ
አላቸው፣ “እናንተ የሴኬም መሪዎች፣ እግዚአብሔርም እናንተን ይሰማ ዘንድ፣ እኔን ስሙኝ። 8 አንድ ጊዜ ዛፎች በእነርሱ ላይ የሚያነግሱት ለመቀባት ሄዱ።
እነርሱም ለወይራ ዛፍ ‘በእኛ ላይ ንገሥ’ አሉት። 9 የወይራ ዛፍ ግን ለእነርሱ እንዲህ አላቸው፣ ‘እግዚአብሔርና ሰዎችን ለማክበር የሚጠቅመውን ቅባቴን ትቼ
ተመልሼ በሌሎች ዛፎች ላይ ለመወዛወዝ ልሂድን?’ 10 ዛፎቹም ለበለስ ዛፍ እንዲህ አሉት፣ ‘መጥተህ በእኛ ላይ ንገሥ።’ 11 ነገር ግን የበለሱ ዛፍ፣
ጣፋጭነቴንና መልካሙን ፍሬዬን ትቼ ተመልሼ በሌሎች ዛፎች ላይ ለመወዛወዝ ልሂድን?’ አላቸው። 12 ዛፎችም ለወይኑ፣ ‘መጥተህ በእኛ ላይ ንገሥ’
አሉት። 13 ወይኑም፣ እግዚአብሔርንና ሰውን ደስ የሚያሰኘውን አዲስ የወይን ጠጄን ትቼ ተመልሼ በዛፎች ላይ ለመወዛወዝ ልሂድን? አላቸው። 14 ከዚያም
ዛፎች ሁሉ የእሾህ ቁጥቋጦን፣ ‘መጥተህ በእኛ ላይ ንገሥ’ አሉት። 15 የእሾህ ቁጥቋጦውም ዛፎቹን፣ ‘በእውነት እኔን በእናንተ ላይ እንድነግስ ልትቀቡኝ
የምትፈልጉ ከሆነ፣ ኑና በጥላዬ ስር ተጠለሉ። እንዲህ ካልሆነ ግን እሳት ከእሾህ ቁጥቋጦ ይውጣና የሊባኖስንም ዝግባ ያቃጥል’ አላቸው። 16 አሁን
እንግዲህ፣ አቤሜሌክን ባነገሳችሁት ጊዜ በእውነትና በቅንነት አድርጋችሁ ከሆነ፣ ለይሩበኣልና ለቤቱም በጎነት አስባችሁ አድርጋችሁ ከሆነ፣ እንዳደረገውም
መጠን ለእርሱ የተገባውን ቀጥታችሁት ከሆነ 17 አባቴ ስለ እናንተ ተዋግቶ እንደነበር፣ ሕይወቱን አሳልፎ በመስጠት፣ ከምድያምም እጅ እናንተን እንዳዳናችሁ
አሰባችሁ ማለት ነው 18 ነገር ግን ዛሬ እናንተ በአባቴ ቤት ላይ ተነሥታችኋል፣ በአንድ ድንጋይ ላይ ልጆቹን፣ ሰባ ሰዎችን፣ አረዳችኋቸው። ከዚያም የሴት
አገልጋዩን ልጅ አቤሜሌክን ዘመዳችሁ ስለ ሆነ በሴኬም መሪዎች ላይ እንዲነግስ አደረጋችሁት። 19 ያንጊዜ ለይሩበኣልና ለቤቱ በእውነትና በቅንነትን
አድርጋችሁ ከሆነ፣ እንግዲያው እናንተ በአቤሜሌክ ደስ ሊላችሁ ይገባል፣ እርሱም በእናንተ ደስ ይበለው። 20 ነገር ግን እንዲህ ባይሆን፣ ከአቤሜሌክ እሳት
ይውጣና የሴኬምንም ሰዎችና የቤትሚሎን ቤት ያቃጥል። ከሴኬምም ሰዎችና ከቤትሚሎ እሳት ይውጣና አቤሜሌክን ያቃጥል። 21 ኢዮአታምም ሸሽቶ
አመለጠ፣ ከዚያም ወደ ብኤር ሄደ። እርሱም በዚያ ተቀመጠ ምክንያቱም ከአቤሜሌክ ከወንድሙ በጣም ሩቅ ነበረ። 22 አቤሜሌክም በእስራኤል ላይ
ለሦስት ዓመት ገዛ። 23 እግዚአብሔር በአቤሜሌክና በሴኬም መሪዎች መካከል ክፉን መንፈስ ሰደደ። የሴኬም መሪዎችም በአቤሜሌክ ላይ የነበራቸውን
እምነት ጥለው ከዱት። 24 እግዚአብሔር ይህንን ያደረገው በሰባዎቹ የይሩበኣል ልጆች ላይ የተደረገውን ዓመፅ ለመበቀል ነው፣ ወንድማቸው አቤሜሌክም
እነርሱን በመግደሉ ተጠያቂ እንዲሆን ለማድረግ ነው፤ የሴኬም ሰዎችም እርሱ ወንድሞቹን እንዲገድላቸው ስለተባበሩት ተጠያቂ እንዲሆኑ ለማድረግ ነው። 25
ስለዚህ የሴኬም መሪዎች በኮረብቶች ራስ ላይ እርሱን አድፍጠው የሚጠብቁ ሰዎች መደቡ፣ እነርሱም በዚያ መንገድ በአጠገባቸው ያለፉትን ሰዎች በሙሉ
ዘረፉ። ይህም ወሬ ለአቤሜሌክ ደረሰው። 26 የአቤድም ልጅ ገዓል ከዘመዶቹ ጋር መጣና ወደ ሴኬም ሄዱ። የሴኬም መሪዎች በእርሱ ተማመኑበት። 27
እነርሱም ወደ እርሻው ወጥተው ሄዱና ከወይን አትክልት ቦታ ወይን ለቅመው ጨመቁት። በአምላካቸው ቤት የደስታ በዓል አደረጉ፣ በሉም ጠጡም፣
አቤሜሌክንም ሰደቡ። 28 የአቤድም ልጅ ገዓል እንዲህ አለ፣ “እናገለግለው ዘንድ አቤሜሌክ ማን ነው? ሴኬምስ ማን ነው? እርሱ የይሩበኣል ልጅ
አይደለምን? ዜቡልስ የእርሱ ሹም አይደለምን? ለኤሞር ሰዎች፣ ለሴኬም አባት አገልግሉ! ለምን እርሱን እናገለግላለን? 29 ይህ ሕዝብ በእኔ አዛዥነት ስር
ቢሆን እመኝ ነበር! የዚያን ጊዜ አቤሜሌክን አስወግደው ነበር። ለአቤሜሌክም ‘ሠራዊትህን ሁሉ ጥራ’ እለው ነበር።” 30 የከተማይቱ ሹም፣ ዜቡል የአቤድን
ልጅ የገዓልን ቃል በሰማ ጊዜ ቁጣው ነደደ። 31 ወደ አቤሜሌክም ያታልለው ዘንድ እንዲህ ብሎ መልክተኞች ላከ፣ “ተመልከት፣ የአቤድ ልጅ ገዓልና ዘመዶቹ
ወደ ሴኬም እየመጡ ነው፣ ከተማይቱን በአንተ ላይ እንድትሸፍት አነሳስተዋል። 32 አሁንም አንተና ከአንተ ጋር ያሉት ወታደሮች በሌሊት ተነሡ፣ ሜዳውም ላይ
አድፍጡ። 33 ከዚያም በጠዋት ፀሐይ በወጣች ጊዜ ማልደህ ተነሣና በከተማይቱ ላይ ድንገተኛ ጥቃት ፈጽምባት። እርሱና ከእርሱ ጋር ያሉት ሕዝብ በአንተ
ላይ በመጡ ጊዜ በእነርሱ ላይ ልታደርግ የምትችለውን ማንኛውንም ነገር አድርግባቸው።” 34 ስለዚህ አቤሜሌክ በሌሊት ተነሳ፣ እርሱና ከእርሱ ጋር የነበሩት
ሰዎች በሙሉ፣ በአራት ወገን ተከፋፍለው በሴኬም ላይ አደፈጡ። 35 የአቤድ ልጅ ገዓል ወጥቶ በከተማይቱ በር መግቢያ ቆመ። አቤሜሌክና ከእርሱ ጋር
የነበሩት ሰዎችም ከተደበቁበት ስፍራ ወጥተው መጡ። 36 ገዓልም ሰዎቹን ባየ ጊዜ ዜቡልን፣ “ተመልከት፣ ሰዎች ከኮረብቶች ራስ ወርደው እየመጡ ነው!”
አለው። ዜቡልም እንዲህ አለው፣ “አንተ የምታየው ሰዎች የሚመስለውን የኮረብቶች ጥላ ነው።” 37 ገዓልም እንደገና እንዲህ ሲል ተናገረ፣ “ተመልከት፣
በምድር መካከል ሰዎች ወርደው እየመጡ ነው፣ አንድም ወገን በቃላተኞች የበሉጥ ዛፍ መንገድ እየመጣ ነው። 38 የዚያን ጊዜ ዜቡል እንዲህ አለው፣
“‘እናገለግለው ዘንድ አቤሜሌክ ማን ነው?’ ብለህ የተናገርሃቸው እነዚያ የትዕቢት ቃላቶችህ አሁን የት አሉ? እነዚህ ሰዎች አንተ የናቅሃቸው አይደሉምን? አሁን
ውጣና ከእነርሱ ጋር ተዋጋ።” 39 ገዓል ወጣና የሴኬም ሰዎችን ይመራ ነበር፣ ከአቤሜሌክም ጋር ተዋጋ። 40 አቤሜሌክም አሳደደው፣ ገዓልም በፊቱ ሸሸ።
ብዙዎቹም በከተማይቱ በር መግቢያ ፊት ለፊት በከባድ ሁኔታ ቆስለው ወደቁ። 41 አቤሜሌክም በአሩማ ተቀመጠ። ዜቡልም ገዓልንና ዘመዶቹን ከሴኬም
እንዲወጡ አስገደዳቸው። 42 በሚቀጥለው ቀን የሴኬም ሕዝብ ወደ እርሻ ሄዱ፣ ይህም ወሬ ለአቤሜሌክ ደረሰው። 43 ሕዝቡንም ወሰደ፣ በሦስት ወገንም
ከፈላቸውና በእርሻዎቹ ውስጥ አደፈጡ። እርሱም ተመለከተ፣ ሕዝቡ ከከተማ ወጥተው ሲመጡ አየ። እርሱም ተዋጋቸውና ገደላቸው። 44 አቤሜሌክና
ከእርሱም ጋር የነበሩት ወገኖች ተዋጉና የከተማይቱን በር መግቢያ ዘጉ። ሌሎቹ ሁለት ወገኖች ደግሞ በእርሻው ውስጥ የነበሩትን ሁሉ ወጓቸውና ገደሉአቸው።
45 አቤሜሌክም ቀኑን ሙሉ ከከተማይቱ ጋር ተዋጋ። ከተማይቱንም ተቆጣጠረና በውስጧ የነበሩትን ሕዝብ ገደላቸው። የከተማይቱንም ቅጥር አፈራረሰው፣
በላይዋም ጨው በተነባት። 46 የሴኬም ግንብ መሪዎች በሙሉ ይህንን ወሬ በሰሙ ጊዜ፣ ወደ ኤልብሪት ቤት ምሽግ ውስጥ ገቡ። 47 አቤሜሌክም መሪዎቹ
በሙሉ በሴኬም ግንብ ውስጥ በአንድ ላይ እንደተሰበሰቡ ተነገረው። 48 አቤሜሌክ ወደ ሰልሞን ተራራ ወጣ፣ እርሱና ከእርሱ ጋር የነበሩት ሰዎች ሁሉ።
አቤሜሌክም በእጁ መጥረቢያ ወሰደና የዛፉን ቅርንጫፎች ቆረጠ። እርሱም አንሥቶ በትከሻው ላይ አደረገውና ከእርሱ ጋር የነበሩትን ሰዎች እንዲህ ብሎ
አዘዛቸው፣ “እኔ ሳደርግ ያያችሁትን፣ ፈጥናችሁ እኔ እንዳደረግሁ አድርጉ።” 49 ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው የዛፉን ቅርንጫፎች ቈረጠና አቤሜሌክን ተከተሉት።
እነርሱም ቅርንጫፎቹን በምሽጉ ላይ ከመሩአቸው፣ በላዩም ላይ እሳት አቀጣጠሉበት፣ ከዚህ የተነሳ የሴኬም ግንብ ሰዎች ሁሉ፣ አንድ ሺህ የሚያህሉ ወንድና
ሴት ሞቱ። 50 ከዚያ በኋላ አቤሜሌክ ወደ ቴቤስ ሄደ፣ ቴቤስንም ከበባትና ተቆጣጠራት። 51 ነገር ግን በከተማይቱ ጠንካራ ግንብ ነበረ፣ የከተማይቱም
ሰዎች ሁሉ፣ ወንዶችና ሴቶች ሁሉ፣ የከተማይቱም መሪዎች ሁሉ ወደዚያ ሸሹና በውስጥ ሆነው ደጁን ዘጉት። ከዚያም እስከ ግንቡ ሰገነት ድረስ ወደ ላይ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወጡ። **52** አቤሜሌክም ወደ ግንቡ መጣና ተዋጋ፣ በእሳትም ሊያቃጥለው ወደ ግንቡ በር አጠገብ መጣ። **53** ነገር ግን አንዲት ሴት በአቤሜሌክ ራስ ላይ የወፍጮ መጅ ጣለችበት፣ መጂም ጭንቅላቱን ሰባበረው። **54** ከዚያም እርሱ በአስቸኳይ ጋሻ ጃግሬውን ጠርቶ፣ “አንድም ሰው እኔን ‘ሴት ገደለችው’ እንዳይል ሰይፍህን መዝዘህ ግደለኝ” አለው። ስለዚህ ወጣቱ ሰው ወጋውና ሞተ። **55** የእስራኤልም ሰዎች አቤሜሌክ እንደ ሞተ ባዩ ጊዜ ወደ ቤታቸው ተመለሱ። **56** እግዚአብሔርም ሰባ ወንድሞቹን በመግደል አቤሜሌክ በአባቱ ላይ ያደረገውን ክፋት ተበቀለው። **57** እግዚአብሔርም የሴኬምን ሰዎች ክፋት ሁሉ በራሳቸው ላይ መለሰባቸው፣ የይሩበኣልም ልጅ የኢዮአታም እርግማን በእነርሱ ላይ መጣባቸው።

Judges 9:1

ይሩበአል
ይህ የጌዴዎን ሌላው ስሙ ነው። ይህንን በመሳፍንት 6:32 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

እባካችሁ፣ በሴኬም ያሉ መሪዎች ሁሉ እንዲሰሙ እንዲህ በሉ፣ ‘ሰባዎቹ የይሩበዓል ልጆች ቢገዟችሁ ወይስ አንዱ ብቻ ቢገዛችሁ ይሻላችኋል?’
ይህ በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ያለ ትዕምርተ ጥቅስ ነው። ቀጥተኛው ትዕምርተ ጥቅስ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ሆኖ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እባካችሁ፣ የይሩበዓል ሰባ ልጆች ሁሉ እንዲገዟቸው ይፈልጉ እንደሆን ወይም ከልጆቹ አንዱ ብቻ እንዲገዛቸው ይፈልጉ እንደሆን የሴኬምን መሪዎች ጠይቋቸው” (በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ የሚገኝ ትዕምርተ ጥቅስ እና ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ የሚለውን ተመልከት)

ሰባ
“70” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

እኔ አጥንታችሁና ሥጋችሁ ነኝ
እዚህ ጋ “አጥንታችሁና ሥጋችሁ” የሚወክለው የአንድ ሰው ዘመድ መሆንን ነው። አ.ት፡ “እኔ የቤተሰባችሁ አባል ነኝ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 9:3

የእናቱ ዘመዶች ስለ እርሱ ለመሪዎቹ ነገሯቸው
ይህ ማለት የአቤሜሌክ የእናቱ ዘመዶች አቤሜሌክን ንጉሣቸው እንዲያደርጉት አሳብ በማቅረብ ለመሪዎቹ ተናገሩ።

አቤሜሌክን ለመከተል ተስማሙ
“አቤሜሌክ መሪያቸው እንዲሆን ተስማሙ”

ቤቱ
እዚህ ጋ “ቤት” የሚወክለው መቅደስን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሰባ ጥሬ ብር
ይህ ማለት ሰባ ሰቅል ብር ነው። አንድ ሰቅል 11 ግራም ይመዝናል። ይህንን ወደ ዘመናዊ መለኪያ መተርጎም አስፈላጊ ከሆነ እንደዚህ አድርገህ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “አንድ ኪሎ የሚያህል ጥሬ ብር” (ገንዘብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚለውን ተመልከት)

ሰባ
“70” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

በኣልብሪት
ይህ የሐሰተኛ አምላክ ስም ነው። እርሱን በመሳፍንት 8:33 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሕገ ወጦችንና ግድ የለሾችን
“ቁጡና ሞኞች”

Judges 9:5

ዖፍራ
በመሳፍንት 6:11 ላይ እንዳደረግኸው የዚህችን ከተማ ስም ተርጉመው።

አንድ ድንጋይ
“1 ድንጋይ” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ሰባ
“70” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ይሩበኣል
ይህ የጌዴዎን ሌላው ስሙ ነው። ይህንን በመሳፍንት 6:32 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ቤት ሚሎ
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Judges 9:7

ለኢዮአታም ይህ በተነገረው ጊዜ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አቤሜሌክ ወንድሞቹን መግደሉን ኢዮአታም በሰማ ጊዜ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ገሪዛን ተራራ
ይህ ተራራ ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ዛፎች በላያቸው ላይ ንጉሥ ለማንገሥ ተሰበሰቡ። የወይራውን ዛፍ ‘በእኛ ላይ ንገሥ’ አሉት
ኢዮአታም ሰዎች የሚያደርጓቸውን ነገሮች በዛፎች በመመሰል ያብራራል። (ምሳሌዎች እና ሰውኛ የሚሉትን ተመልከት)

በላያቸው ላይ ንጉሥ ለመቀባት
እዚህ ጋ በዘይት መቀባት አንድን ሰው ንጉሥ እንዲሆን መሾምን የሚወክል ምሳሌአዊ ድርጊት ነው። አ.ት፡ “በሁላቸውም ላይ እንዲገዛ ንጉሥ ለመሾም”

በእኛ ላይ ንገሥ
“ንጉሣችን ሁን”

Judges 9:9

የወይራው ዛፍ እንዲህ አላቸው - የበለስ ዛፍ እንዲህ አላቸው
ኢዮአታም ሰዎች የሚያደርጓቸውን ነገሮች በዛፎች ምሳሌ አድርጎ ያብራራል። (ምሳሌዎች እና ሰውኛ የሚሉትን ተመልከት)

በሌሎች ዛፎች ላይ - ዘይት መስጠቴን መተው አለብኝ?
የወይራው ዛፍ ንጉሥ መሆንን እምቢ ለማለት ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ መነገር ይችላል። አ.ት፡ “በሌሎች ዛፎች ላይ … ዘይት መስጠቴን አላቆምም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

መወዛወዝ
“መወዛወዝ” ማለት በንፋስ ምክንያት ወደ ፊትና ወደ ኋላ ማለት ነው። ዛፉ ይህንን ሐረግ የሚጠቀመው “መግዛት” ለማለት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በሌሎች ዛፎች ላይ - ጣፋጭነቴን መተው አለብኝ?
የበለስ ዛፉ ንጉሥ መሆንን እምቢ ለማለት ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ መነገር ይችላል። አ.ት፡ “በሌሎች ዛፎች ላይ … ጣፋጭነቴን አላቆምም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ጣፋጭነቴንና መልካሙን ፍሬዬን
“ጣፋጭነት” የሚለው ቃል የነገር ስም ነው። በዛፉ ላይ የሚበቅለውን ፍሬ ለመግለጽ እንደ ቅጽል ሆኖ ሊነገር ይችላል። (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

Judges 9:12

ዛፎቹ የወይንን ተክል እንዲህ አሉት
በዚህ ምሳሌ ኢዮአታም ሰዎች የሚያደርጓቸውን ነገሮች ዛፎቹና የወይን ተክል እንደሚያደርጉት አድርጎ ያብራራል። (ምሳሌዎች እና ሰውኛ የሚሉትን ተመልከት)

በሌሎች ዛፎች ላይ -- አዲሱን ወይኔን ማቆም አለብኝ?
የወይን ተክሉ ንጉሥ መሆንን እምቢ ለማለት ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ መነገር ይችላል። አ.ት፡ “በሌሎች ዛፎች ላይ … አዲሱን ወይኔን አላቆምም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

የእሾህ ቁጥቋጦ
እሾህ የሚጎዳ የሾለ መውጊያ አለው። ይህ ቁጥቋጦ በየቅርንጫፎቹ ላይ በርካታ ሹል መውጊያዎች አሉት።

Judges 9:15

የእሾህ ቁጥቋጦው ለዛፎቹ እንዲህ አላቸው
በዚህ ምሳሌ ኢዮአታም የቁጥቋጦው እሾህና ዛፎቹ ሰዎች የሚያደርጓቸውን ነገሮች እንደሚያደርጉ ያብራራል። (ምሳሌዎች እና ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

በላያችሁ እንድነግሥ ልትቀቡኝ
አንድን ሰው በዘይት መቀባት ንጉሥ እንዲሆን የመሾም ምሳሌአዊ ድርጊት ነው። አ.ት፡ “ንጉሣችሁ አድርጋችሁ ልትቀቡኝ” (ምሳሌአዊ ድርጊት የሚለውን ተመልከት)

ደህንነት እንዲሆንላችሁ
“ደህንነት” የሚለው ቃል የነገር ስም ሲሆን እንደ ቅጽል ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ተጠበቁ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

እሳት ከእሾህ ቁጥቋጦው ይውጣ፣ የሊባኖስንም ዝግባዎች ያቃጥል
ይህ ማለት ዝግባዎቹን ለማቃጠል የእሾህ ቁጥቋጦው ይነዳል።

ከዚያም እሳት ከእሾህ ቁጥቋጦው ይውጣ
የእሾህ ቁጥቋጦው ራሱን እንደ “እሾህ ቁጥቋጦ” ያመለክታል። አ.ት፡ “ከዚያም እሳት ከእኔው ከእሾህ ቁጥቋጦው ይውጣ” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

አሁን
ይህ “በዚህ ሰዓት” ማለት አይደለም፣ ነገር ግን ትኩረትን ወደሚቀጥለው አስፈላጊ ጉዳይ ለመሳብ ጥቅም ላይ ውሏል።

ለይሩበአልና ለቤቱ መልካም አድርጋችሁ ከሆነና የሚገባውን ቅጣት ሰጥታችሁት ከሆነ
ኢዮአታም ያደረጉት መልካም ይሆን እንደሆነ ምርጫውን ያቀርብላቸዋል፤ ይሁን እንጂ ያደረጉት በመሠረቱ መልካም እንደሆነ ኢዮአታም አያምንም። አ.ት፡ “መልካም የሆነውን አድርጋችሁ ከሆነና ልጆቹን ሁሉ ትገድሉበት ዘንድ ለይሩበአል የሚገባው ከሆነ”

ይሩበአል
ይህ የጌዴዎን ሌላው ስሙ ነው። ይህንን በመሳፍንት 6:32 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተምልከት።

ቤቱ
እዚህ ጋ “ቤት” የጌዴዎንን ቤተሰብ ይወክላል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 9:17

ከምድያማውያን እጅ -- አባቴ እንደተዋጋላችሁ ለማሰብ
እዚህ ጋ ጌዴዎን የሴኬምን ሰዎች ለማዳን ከተዋጋ በኋላ የሴኬም ሰዎች ለጌዴዎንና ለቤተሰቡ በክፋት መመለሳቸውን ኢዮአታም ማመን እንደማይችል ይገልጻል።

ከምድያማውያን እጅ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው ኃይልን ወይም መቆጣጠርን ነው። አ.ት፡ “ከምድያማውያን ኃይል” ወይም “ከምድያማውያን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ተነሣችሁበት
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ተቃወማችሁ” ወይም “በእርሱ ላይ አምጻችኋል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የአባቴ ቤት
እዚህ ጋ “ቤት” የሚወክለው ቤተሰብን ነው። አ.ት፡ “የአባቴ ቤተሰብ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሰባ
“70” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

አንድ ድንጋይ
“1 ድንጋይ” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ሴት ባሪያው
እዚህ ጋ “የእርሱ” የሚያመለክተው ጌዴዎንን ነው።

Judges 9:19

ከጌዴዎንና ከቤቱ ጋር በታማኝነትና በቅንነት አድርጋችሁ ከሆነ
ኢዮአታም ያደረጉት መልካም ይሆን እንደሆነ ምርጫውን ያቀርብላቸዋል፣ ይሁን እንጂ ያደረጉት በመሠረቱ መልካም እንደሆነ ኢዮአታም አያምንም። አ.ት፡ “ለይሩበአልና ለቤተሰቡ ሊደረግላቸው የሚገባቸውን አድርጋችሁላቸው ከሆነ”

ይሩበአል
ይህ የጌዴዎን ሌላው ስሙ ነው። እንዲህ ማለትም፣ “በኣል ለራሱ ይሟገት” ማለት ነው። ይህንን በ6:32 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ለቤቱ
እዚህ ጋ “ቤት” የሚያመለክተው ቤተሰብን ነው። አ.ት፡ “ቤተሰቡን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ካልሆነ ግን
ኢዮአታም ያደረጉት ክፉ መሆኑን እና እርግማን እንደሚሆንባቸው ተቃራኒውን አማራጭ ያቀርብላቸዋል። ኢዮአታም ያደረጉት ክፉ መሆኑን ያምናል። አ.ት፡ “ለይሩበአልና ለቤተሰቡ ሊደረግ የማይገባቸውን አድርጋችሁ ከሆነ ግን”

ከአቤሜሌክ እሳት ይውጣ፣ የሴኬምንም ሰዎች ያንድድ
ኢዮአታም የሚናገረው እርግማንን ነው። አቤሜሌክ በእሳት ያቃጥላቸው ይመስል የሴኬምን ሰዎች እንደሚያጠፋቸው ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አቤሜሌክን ለማንደድ እሳት ከሴኬምና ከቤትሚሎ ሰዎች ይውጣ
ኢዮአታም የሚናገረው እርግማንን ነው። የሴኬምና የቤትሚሎ ሰዎች በእሳት ያቃጥሉት ይመስል አቤሜሌክን እንደሚያጠፉት ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ቤትሚሎ
ይህ የቦታ ስም ነው። ይህንን በመሳፍንት 9:6 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ብኤር
ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Judges 9:22

እግዚአብሔር በአቤሜሌክና በሴኬም መሪዎች መካከል ክፉ መንፈስን ላከ
ይህ ማለት ኢዮአታም በአቤሜሌክና በሴኬም መሪዎች መካከል አለመግባባትንና ጠላትነትን እንዲፈጥር ክፉ መንፈስን በመላክ ያደረገውን እርግማን እግዚአብሔር ተግባራዊ አድርጎታል ማለት ነው።

ወንድሞቹን እንዲገድል ስለረዱት -- ስላደረጉት ግፍ እግዚአብሔር ይህንን አደረገ
ተደራጊ ድምፅ ያላቸውን ሐረጎች በአድራጊ ድምፅ መናገር ይቻላል። አ.ት፡ “አቤሜሌክ ስለገደላቸው ሰባ ልጆችና የሴኬም ሰዎች በግድያው ስለረዱት እግዚአብሔር ለመበቀል ይህንን አደረገ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ሰባ
“70” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ይሩበአል
ይህ የጌዴዎን ሌላው ስሙ ነው። ይህንን በመሳፍንት 6:32 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Judges 9:25

አደጋ እንዲጥሉበት በኮረብታማው ስፍራ ሰዎች አድፍጠው እንዲጠብቁት አደረጉ
“ሰዎች በኮረብታው ጫፍ እንዲደበቁና አቤሜሌክን ለመግደል እንዲጠባበቁ ላካቸው”

ይህ ለአቤሜሌክ ተነገረው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሰዎች ሊያጠቁት እየተጠባበቁ እንዳሉ አንድ ሰው ለአቤሜሌክ ነገረው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Judges 9:26

ገዓል -- አቤድ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ተማምነውበት ነበር
“መተማመን” የሚለው ቃል የነገር ስም ሲሆን “መታመን” በሚል ግሥ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ታመኑበት” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ወደ ሜዳ ወጡ
እዚህ ጋ “እነርሱ” የሚያመለክተው ገዓልን፣ ዘመዶቹንና የሴኬምን ሰዎች ነው።

ረገጣቸው
ይህንን ያደረጉት የወይን ጭማቂ ለማዘጋጀት ነው።

ረገጡ
“ሰባበሩ” ወይም “ጨፈለቁ”

በቤቱ ውስጥ
እዚህ ጋ “ቤት” የሚወክለው መቅደስን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 9:28

ገዓል -- ኤቤድ
እነዚህን ስሞች በመሳፍንት 9:26 ላይ እንዴት እንደተርጎምከው ተመልከት።

እንድናገለግለው አቤሜሌክ ማነው? ሴኬምስ ማነው?
ገዓል የሰኬም ሰዎች አቤሜሌክን ማገልገል እንደሌለባቸው አጽንዖት ለመስጠት ጥያቄ ይጠይቃል። አ.ት፡ “አቤሜሌክን ማገልገል የለብንም!” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

እንድናገለግለው አቤሜሌክ ማነው? ሴኬምስ ማነው?
እነዚህ ሁለቱም ጥያቄዎች አንድ ናቸው። የአቤሜሌክ እናት ከሴኬም በመሆኗ ምክንያት ገዓል አቤሜሌክን ለማመልከት “ሴኬም” ይላል። አ.ት፡ “አቤሜሌክን ማገልገል የለብንም፣ እርሱም ሴኬም ነው!” (እና ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

እርሱ የይሩበአል ልጅ አይደለምን? ዜቡልስ የእርሱ ሹም አይደለምን?
ገዓል የሰኬም ሰዎች አቤሜሌክን ማገልገል እንደሌለባቸው አጽንዖት ለመስጠት ጥያቄ ይጠይቃል። አ.ት፡ “እርሱ የይሩበአል ልጅ ብቻ ነው፣ ዜቡልም የእርሱ ሹም ብቻ ነው” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ይሩበአል
ይህ የጌዴዎን ሌላው ስሙ ነው። ይህንን በመሳፍንት 6:32 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ዜቡል
ይህ የሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የሴኬምን አባት የኤሞርን ሰዎች አገልግሉ
ገዓል የሚለው፣ የሴኬም ሰዎች ማገልገል ያለባቸው እውነተኛ ከነዓናውያን የሆኑትን ከኤሞር የተወለዱትን እንጂ እስራኤላዊ አባት ያለውን ሰው ማገልገል የለባቸውም።

አቤሜሌክን የምናገለግለው ለምንድነው?
ገዓል የሰኬም ሰዎች አቤሜሌክን ማገልገል እንደሌለባቸው አጽንዖት ለመስጠት ጥያቄ ይጠይቃል። አ.ት፡ “አቤሜሌክን ማገልገል የለብንም!” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

እነዚህ ሰዎች ከትዕዛዜ ስር እንዲሆኑ እመኛለሁ
“የሴኬምን ሰዎች ባስተዳድር እመኛለሁ”

Judges 9:30

ዜቡል
ይህንን ስም በመሳፍንት 9:28 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

የኤቤድን ልጅ የገዓልን ቃል ሰሙ
“የኤቤድ ልጅ ገዓል የተናገረውን ሰሙ”

ገዓል -- ኤቤድ
እነዚህን ስሞች በመሳፍንት 9:26 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ቁጣው ነደደ
መቆጣቱ እንደ እሳት መንደድ ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “በጣም ተቆጣ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ለማታለል
ዜቡል ገዓልንና የሴኬምን ሰዎች እያታለላቸው ነው። አ.ት፡ “በምስጢር”

ከተማይቱን በአንተ ላይ እያነሣሡ ነው
ይህ የከተማው ሰዎች በድስት ውስጥ እንዳለ ፈሳሽ መንተክተካቸውን ያሳያል። አ.ት፡ “የከተማይቱ ሰዎች በአንተ ላይ እንዲያምጹ እያነሣሧቸው ነው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ከተማይቱ
እዚህ ጋ “ከተማ” የሚወክለው በከተማይቱ የሚኖሩትን ሰዎች ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 9:32

አሁን
ይህ “በዚህ ሰዓት” ማለት አይደለም፣ ነገር ግን ትኩረትን ወደሚቀጥለው አስፈላጊ ጉዳይ ለመሳብ ጥቅም ላይ ውሏል።

ደፈጣ
“ተደብቆ እነርሱን በድንገት ማጥቃት”

የምትችለውን አድርግባቸው
ይህ ማለት የገዓልን ተከታዮች ለማጥፋት የፈለጉትን ማድረግ ይችላሉ።

Judges 9:34

ከእርሱ ጋር የነበሩት ሰዎች ሁሉ
“አቤሜሌክን የተከተሉ ሰዎች ሁሉ” ወይም “ለአቤሜሌክ ይዋጉ የነበሩ ሰዎች ሁሉ”

በሴኬም ላይ የሚያደፍጡትን አስቀመጡ
እዚህ ጋ “ሴኬም” የሚወክለው የሴኬምን ሰዎች ነው። አ.ት፡ “የሴኬምን ሰዎች በድንገት ለማጥቃት ተደበቁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አራት ቦታ አካፍሎ
“በ4 ቡድኖች ለያይቶ” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ገዓል -- ኤቤድ
እነዚህን ስሞች በመሳፍንት 9፡26 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

Judges 9:36

ገዓል
ይህ የሰው ስም ነው። ይህንን በመሳፍንት 9፡26 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ዜቡል
ይህ የሰው ስም ነው። ይህንን በመሳፍንት 9፡28 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የምትመለከተው ሰዎችን የሚመስሉ የኮረብቶችን ጥላ ነው
ዜቡል ገዓልን እያደናገረውና ለጦርነት እንዳይዘጋጅ እያዘገየው ነው። አ.ት፡ “ያ ሰዎች ሳይሆኑ በኮረብቶቹ ላይ ጥላዎች ብቻ ናቸው”

አንድ ክፍል
“1 ቡድን” ወይም “1 ጓድ” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

Judges 9:38

ዜቡል
በመሳፍንት 9፡28 ላይ ይህንን ስም እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

አሁን የትዕቢት ቃልህ የት አለ?
ዜቡል በዚህ ምላሽ በማይፈልግ ጥያቄ በገዓል ላይ እየተሳለቀበት ነው። አ.ት፡ “አሁን በትዕቢት አትናገርም” ወይም “አሁን አትታበይም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

‘እናገለግለው ዘንድ አቤሜሌክ ማነው?’ ያልከው አንተ
ዜቡል የገዓልን የኩራት ንግግር መልሶ እየጠቀሰለት ነው። ይህ እንደ መግለጫና ቀጥተኛ እንዳልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ተደርጎ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “አቤሜሌክን ማገልገል የለብንም ብለህ የነበርከው አንተ” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እና ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ትዕምርተ ጥቅሶች የሚለውን ተመልከት)

እነዚህ አንተ የናቅኻቸው ሰዎች አይደሉምን?
ዜቡል በዚህ ምላሽ በማይፈልግ ጥያቄ ገዓልን እየተገዳደረው ነው። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “የናቅኻቸው ሰዎች እኝውልህ” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

የተናቁ
እጅግ ያልተወደዱ ወይም የተጠሉ

ገዓል
ይህንን ስም በመሳፍንት 9፡26 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ብዙዎች ክፉኛ ቆስለው ወደቁ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ብዙ ሰዎች ቆስለው ሞቱ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Judges 9:41

አሩማ
ይህ የአንድ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ዜቡል
ይህ የሰው ስም ነው። ይህንን በመሳፍንት 9፡28 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ገዓል
ይህ የሰው ስም ነው። ይህንን በመሳፍንት 9፡26 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ይህ ለአቤሜሌክ ተነገረው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አንድ ሰው ይህንን ለአቤሜሌክ ነገረው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በሦስት ክፍል ከፋፈለቸው
“በ3 ቡድኖች ለያያቸው” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

በእርሻው ውስጥ የሚያደፍጡትን አኖሩ
x

Judges 9:44

ቡድኖቹ
“የወታደሮቹ ቡድኖች”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሌሎች ሁለት
“ሌሎች 2” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

አቤሜሌክ ተዋጋ -- አጠፋ
እዚህ ጋ “አቤሜሌክ” የሚወክለው ራሱንና ወታደሮቹን ነው። አ.ት፡ “አቤሜሌክና ወታደሮቹ ተዋጉ ... አጠፉ”

በከተማይቱ ላይ
እዚህ ጋ “ከተማ” የሚወክለው ሰዎችን ነው። አ.ት፡ “በሴኬም ሰዎች ላይ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አጠፉ
“አወደሙ”

ጨው ዘራባት
“በምድሪቱ ላይ ጨው ዘራ”። በምድር ላይ ጨው መዝራት በዚያ ቦታ ምንም ነገር እንዳይበቅል ያደርጋል።

Judges 9:46

ቤቱ
እዚህ ጋ ይህ የሚወክለው መቅደስን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ኤልበሪት
“ኤል” የሚለው ቃል ትርጉም “አምላክ” ማለት ነው። ይህ በመሳፍንት 8:33 እንዳለው “በኣል በሪት” ሁሉ ያው ሐሰተኛ አምላክ ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ለአቤሜሌክ ተነገረው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አንድ ሰው ለአቤሜሌክ ነገረው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Judges 9:48

ሰልሞን ተራራ
ይህ የተራራ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ቆለለ
ይህ ማለት ቅርንጫፎቹን በብዙ መጠን እንደ ክምር መከመር ነው።

አንድ ሺህ የሚያህሉ ሰዎች
“1,000 ያህል ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

Judges 9:50

ቴመስ
ይህ የአንድ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ቴመስን ከበበ
“ከቴመስ ከተማ ውጪ ሰፈረ”

Judges 9:52

ተዋጋት
“አጠቃት”

የወፍጮ መጅ
ሁለት ትላልቅና ጠፍጣፋ ድንጋዮች ጥራጥሬ ለመፍጨት ያገለግሉ ነበር። በታችኛው ላይ በመንከባለል በመሐል ያለውን ጥራጥሬ የሚፈጨው ከላይ የሚሆነው መጅ ነው።

ጋሻ ጃግሬ
ይህ የአቤሜሌክን የጦር መሣሪያ የሚሸከመው ሰው ነው።

ወጋው
ይህ ማለት ወጣቱ አቤሜሌክን በሰይፍ ወጋው።

Judges 9:55

ሰባ
“70” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

የሴኬምን ሰዎች ክፋት ሁሉ በራሳቸው ላይ መለሰባቸው
እዚህ ጋ “ክፋት በራሳቸው ላይ ተመለሰ” የሚለው የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ስላደረጉት ክፋት ሁሉ የሴኬምን ሰዎች ቀጣቸው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የይሩበአል ልጅ የኢዮአታም እርግማን ደረሰባቸው
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “የይሩበአል ልጅ የኢዮአታም እርግማን መጣባቸው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ይሩበአል
ይህ የጌዴዎን ሌላው ስሙ ነው። ይህንን ስም በመሳፍንት 6:32 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 10

1 ከአቤሜሌክ በኋላ ከይሳኮር ነገድ የሆነውና በኮረብታማውም በኤፍሬም አገር ባለችው በሳምር ይኖር የነበረው የዱዲ ልጅ የፎሉ ልጅ ቶላ እስራኤልን ለማዳን
ተነሣ። 2 እርሱም በእስራኤል ላይ ሀያ ሦስት ዓመት ፈረደ። እርሱም ሞተ፣ በሳምርም ተቀበረ። 3 ከእርሱም በኋላ ገለዓዳዊው ኢያዕር ተነሣ። በእስራኤልም
ላይ ሀያ ሁለት ዓመት ፈረደ። 4 በሠላሳ አህያዎች የሚጋልቡ ሠላሳ ልጆች ነበሩት፣ እነርሱም በገለዓድ ምድር ያሉ እስከ ዛሬ ድረስ የኢያዕር መንደሮች ተብለው
የሚጠሩ ሠላሳ ከተሞች ነበሩአቸው። 5 ኢያዕርም ሞተ፣ በቃሞንም ተቀበረ። 6 የእስራኤል ሕዝብ ከዚህ በፊት ከሰሩት በላይ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ስራ
ጨምረው ሠሩ፣ በኣልን፣ አስታሮትን፣ እንደዚሁም የሶርያን አማልክት፣ የሲዶናን አማልክት፣ የሞዓብን አማልክት፣ የአሞንን ሕዝብ አማልክት፣ የፍልስጥኤማውያንን
አማልክት አመለኩ።እግዚአብሔርን ተዉ፣ እርሱንም አላመለኩትም። 7 የእግዚአብሔርም ቊጣ በእስራኤል ላይ ነደደ፣ እርሱም ፍልስጥኤማውያንና አሞናውያን
ያሸንፉአቸው ዘንድ ለእነርሱ አሳልፎ ሰጣቸው። 8 እነርሱም በዚያን ዓመት የእስራኤልን ሕዝብ አደቀቋቸው፣ አስጨነቋቸው፣ ለአሥራ ስምንት ዓመት በዮርዳኖስ
ማዶ በአሞራውያን ምድር በገለዓድ ውስጥ የነበሩትን የእስራኤልን ሕዝብ ሁሉ አስጨነቋቸው። 9 የአሞንም ሰዎች ከይሁዳ፣ ከብንያምና ከኤፍሬም ቤት ጋር
ለመዋጋት ዮርዳኖስን ተሻገሩ፣ ከዚህ የተነሳ እስራኤል እጅግ በጣም ተጨነቁ። 10 የዚያን ጊዜ የእስራኤልም ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር ጮሁ፣ እንዲህ በማለት፣
“በአንተ ላይ በድለናል፣ ምክንያቱም አምላካችንን ትተን የበኣል አማልክትን አምልከናልና።” 11 እግዚአብሔርም ለእስራኤል ልጆች እንዲህ አላቸው፣
“ከግብፃውያን፣ ከአሞራውያንም፣ ከአሞናውያን፣ ከፍልስጤማውያንና 12 ከሲዶናውያን አላዳንኋችሁምን? አማሌቃውያንና ማዖናውያን አስጨነቋችሁ፤ ወደ እኔም
ጮኻችሁ፣ እኔም ከእነርሱ ኃይል አዳንኋችሁ። 13 ይሁን እንጂ እናንተ እንደገና ተዋችሁኝና ሌሎችን አማልክት አመለካችሁ። ስለዚህ፣ እኔም ከእንግዲህ ወዲህ
አላድናችሁም። 14 ሂዱና ወደምታመልኳቸው አማልክት ጩኹ። በመከራችሁ ጊዜ እነርሱ ያድኑአችሁ። 15 የእስራኤልም ሕዝብ እግዚአብሔርን እንዲህ አሉት፣
“እኛ ኃጢአትን ሠርተናል። ለአንተ ደስ የሚያሰኝህን ማንኛውንም ነገር በእኛ ላይ አድርግብን። እባክህ፣ የዛሬን ብቻ አድነን።” 16 እነርሱም በመካከላቸው ካሉት
ባዕዳን አማልክት ዘወር አሉ፣ እግዚአብሔርንም አመለኩ።እርሱም የእስራኤልን ጕስቍልና ሊታገሰው የማይቻለው ሆነ። 17 ከዚያም አሞናውያን በአንድ ላይ
ተሰበሰቡና በገለዓድ ሰፈሩ። እስራኤላውያንም በአንድ ላይ ተሰበሰቡና ሰፈራቸውን በምጽጳ ላይ አደረጉ። 18 የገለዓድ ሕዝብ መሪዎችም እርስ በርሳቸው
እንዲህ ተባባሉ፣ “አሞናውያንን ለመዋጋት የሚጀምር ሰው ማን ነው? እርሱ በገለዓድ በሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ላይ መሪ ይሆናል።”

Judges 10:1

ቶላ -- ፎሐ -- ዱዲ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ሳምር
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

እስራኤልን ለማዳን ተነሣ
“እስራኤልን ለማዳን መጣ” ወይም “እስራኤልን ለማዳን መሪ ሆነ”

እስራኤልን ለማዳን
እዚህ ጋ “እስራኤል” የሚወክለው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእስራኤል ላይ ፈረደ
እዚህ ጋ “ፈረደ” ማለት የእስራኤልን ሕዝብ መራ ማለት ነው።

ሃያ ሦስት ዓመት
“23 ዓመት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ተቀበረ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ቀበሩት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Judges 10:3

ከእርሱ ቀጥሎ ገለዓዳዊው ኢያዕር
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ከቶላ በኋላ ገለዓዳዊው ኢያዕር መሪ ነበር” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ኢያዕር
ይህ የአንድ ሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ገለዓዳዊው
ኢያዕር ከገለዓድ ነገድ ነበር

በእስራኤል ላይ ፈረደ
እዚህ ጋ “ፈረደ” ማለት የእስራኤልን ሕዝብ መራ ማለት ነው።

እስራኤል
እዚህ ጋ “እስራኤል” የሚወክለው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሃያ ሁለት ዓመት
“22 ዓመት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ሠላሳ ወንዶች ልጆች
“30 ወንዶች ልጆች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ሐቮዝጃኤር
ይህ በአንድ ሰው ስም የሚጠራ የአውራጃ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

እስካሁን ድረስ
ይህ ማለት መጽሐፈ መሳፍንት እስከሚጻፍበት ጊዜ ድረስ ማለት ነው።

ተቀበረ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ቀበሩት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ቃሞን
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Judges 10:6

በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ማድረጋቸውን አበዙ
አንድ ሰው እየጨመረበት እንደሚያተልቀው አንዳች ነገር ይህ የተነገረው ስለ ክፋት ነው። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ክፉ ነው ያለውን ማድረጋቸውን ቀጠሉ”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በእግዚአብሔር ፊት
የእግዚአብሔር ፊት የሚወክለው የእርሱን ፍርድ ወይም ምዘና ነው። አ.ት፡ “እግዚአብሔር እንደሚለው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አስታሮቶች
ይህ የአስታሮት ብዙ ቁጥር ሲሆን በተለያየ ቅርጽ የምትመለክ እንስት አምላክ ነበረች። ይህንን በመሳፍንት 2፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

እግዚአብሔርን ተዉት፣ አላመለኩትምም
በመሠረቱ ደራሲው ሁለት ጊዜ የተናገረው ስለ አንድ ነገር አጽንዖት ለመስጠት ነው። እነዚህ ሊጣመሩ የሚችሉ ናቸው። አ.ት፡ “እግዚአብሔርን ማምለካቸውን ሙሉ በሙሉ አቆሙ”

እግዚአብሔርን ተዉት
ከዚያ በኋላ እግዚአብሔርን አለማምለካቸውና አለመታዘዛቸው ሰዎቹ እግዚአብሔርን ትተው ወደ አንድ የሆነ ቦታ እንደሄዱ ሆኖ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእስራኤል ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ነደደ
ቁጣ የሚነድ እሳት ይመስል እግዚአብሔር እንደ ተቆጣ ተነግሯል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ በጣም ተቆጣ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በፍልስጥኤማውያንና በአሞናውያን እጅ ሸጣቸው
እግዚአብሔር ፍልስጥኤማያንና አሞናውያን እስራኤላውያንን እንዲያሸንፉ መፍቀዱ እስራኤላውያንን ለእነርሱ እንደሸጠላቸው ሆኖ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በ... እጅ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው ኃይልን ወይም መቆጣጠርን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 10:8

አደቀቋቸውና አስጨነቋቸው
እነዚህ ሁለት ቃላት የሚሉት በመሠረቱ ስለ አንድ ነገር ሲሆን እስራኤላውያን ምን ያህል እንደተሰቃዩ አጽንዖት ለመስጠት ነው። አ.ት፡ “በከፋ ሁኔታ አስጨነቋቸው”

አሥራ ስምንት ዓመት
“18 ዓመት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ከዮርዳኖስ ማዶ የነበሩት
ይህ ማለት ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምስራቅ ማለት ነው።

በገለዓድ ያለው
“ይህ አውራጃም ደግሞ ገለዓድ ተብሎ ተጠርቷል”

ይሁዳ - ብንያም
“ይሁዳ” እና “ብንያም” የእነዚያን ነገዶች ሕዝቦች ያመለክታል። አ.ት፡ “የይሁዳ ነገድ ሕዝቦች ... የብንያም ነገድ ሕዝቦች”። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የኤፍሬም ቤት
እዚህ ጋ “ቤት” የሚያመለክተው የኤፍሬምን ነገድ ሕዝቦች ነው። አ.ት፡ “የኤፍሬም ነገድ ሕዝቦች”። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በመሆኑም እስራኤል እጅግ ተጨነቀ
“እስራኤል” የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። አ.ት፡ “በመሆኑም የእስራኤል ሕዝብ በጣም ተሰቃየ”። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 10:10

የእስራኤል ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር ጮኹ
ይህ ማለት የእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔር እንዲረዳቸው በፍጹም ልባቸው ጠየቁት።

አምላካችንን በመተዋችን ምክንያት
ከዚያ በኋላ እግዚአብሔርን አለማምለካቸውና አለመታዘዛቸው ሰዎቹ እግዚአብሔርን ትተው ወደ አንድ የሆነ ቦታ እንደሄዱ ሆኖ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አምላካችንን ትተነዋል
ሕዝቡ የሚናገሩት ስለ እግዚአብሔር ሲሆን “አምላካችን” ብለው ይጠሩታል። ይህ በሁለተኛ መደብ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አምላካችን ሆይ፣ አንተን ትተንሃል” (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

ሲዶናውያን -- አላዳንኋችሁምን?
ሌሎች አማልክትን ስለማምለካቸው እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ይገስጻቸዋል። ይህ መልስ የማይሻ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ከሲዶናውያን ... ያዳንኋችሁ እኔ ነኝ” (መልስ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ማዖናውያን
እነዚህ ከማዖን ቤተሰብ ወይም ጎሳ የሆኑ ሕዝቦች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ከኃይላቸው
እዚህ ጋ “ኃይል” የሚወክለው አማሌቃውያንን እና ማዖናውያንን ነው። አ.ት፡ “ከእነርሱ”። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 10:13

እንደ ገና ተዋችሁኝ
ከዚያ በኋላ እግዚአብሔርን አለማምለካቸውና አለመታዘዛቸው ሰዎቹ እግዚአብሔርን ትተው ወደ አንድ የሆነ ቦታ እንደሄዱ ሆኖ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከእንግዲህ ወዲህ አላድናችሁም
“ከእንግዲህ ወዲህ” የሚለው ሐረግ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ትርጉሙም አንድ ነገር በማድረግ መቀጠል ማለት ነው። በእግዚአብሔር አነጋገር ውስጥ ግልጽ ያልሆነውን ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። አ.ት፡ “በተደጋጋሚ እናንተን ማዳኔን አልቀጥልም” ወይም “እናንተን ማዳን ማቆሜን እርግጠኛ መሆን ትችላላችሁ”

Judges 10:15

በመካከላቸው ያሉትን እንግዶች አማልክት
የዚህን መግለጫ ግልጽ ያልሆነ ትርጉም ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። አ.ት፡ “የወረሷቸውን የእንግዶች አማልክት ምስሎች”

እግዚአብሔር የእስራኤልን ስቃይ ለመታገስ አልቻለም
እዚህ ጋ እስራኤል የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። አ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ ከእንግዲህ ወዲያ እንዲሰቃይ አልፈለገም”።(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 10:17

ከአሞናውያን ጋር በመዋጋት የሚጀምርልን ሰው ማነው?
“አሞናውያንን ለመዋጋት ሰራዊታችንን የሚመራው ማን ነው?”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 11

1 ገለዓዳዊውም ዮፍታሔ ኃያል ተዋጊ ነበር፣ ነገር ግን የጋለሞታ ሴት ልጅ ነበረ። አባቱም ገለዓድ ነበረ። **2** የገለዓድም ሚስት ደግሞ ሌሎች ወንዶች ልጆችን ወለደችለት። የሚስቱ ልጆች ባደጉ ጊዜ፣ ዮፍታሔን ቤቱን ለቅቆ እንዲወጣ አስገደዱት፣ እንዲህም አሉት፦ “አንተ ከቤተሰባችን ምንም ነገር አትወርስም። አንተ የሌላ ሴት ልጅ ነህ።” **3** ስለዚህ ዮፍታሔ ከወንድሞቹ ፊት ሸሽና በጦብ ምድር ተቀመጠ። ስርዓት አልበኛ ሰዎችም ተከተሉት፣ ተሰብስበውም ከእርሱ ጋር ሄዱ። **4** ከጥቂት ቀናት በኋላ፣ የአሞን ሰዎች ከእስራኤል ጋር ውጊያ አደረጉ። **5** የአሞንም ሰዎች ከእስራኤል ጋር ውጊያ ባደረጉ ጊዜ፣ የገለዓድ ሽማግሌዎች ዮፍታሔን ከጦብ ምድር ለማምጣት ሄዱ። **6** ዮፍታሔንም፣ “ና፣ ከአሞን ሰዎች ጋር እንድንዋጋ አለቃችን ሁን” አሉት። **7** ዮፍታሔም ለገለዓድ ሽማግሌዎች እንዲህ አላቸው፣ “እናንተ ጠልታችሁኛል፣ የአባቴንም ቤት ትቼ እንድሄድ አስገድዳችሁኛል። አሁን በተቸገራችሁ ጊዜ ለምን ወደ እኔ መጣችሁ?” **8** የገለዓድም ሽማግሌዎችም ለዮፍታሔ፣ “አሁን ወደ አንተ የተመለስነው ለዚህ ነው፤ ከእኛ ጋር ና፣ ከአሞንም ሰዎች ጋር ተዋጋ፣ ከዚያም በኋላ በገለዓድ በሚኖሩት ሰዎች ሁሉ ላይ መሪ ትሆናለህ” አሉት። **9** ዮፍታሔም ለገለዓድ ሽማግሌዎች፣ “ከአሞን ሰዎች ጋር እንድዋጋ እንደገና ወደ ቤቴ ከመለሳችሁኝ፣ እግዚአብሔርም በእነርሱ ላይ ድል ከሰጠን መሪያችሁ እሆናለሁ” አላቸው። **10** የገለዓድ ሽማግሌዎችም ለዮፍታሔ፣ “እንደተናገርነው የማናደርግ ከሆነ እግዚአብሔር በእኛ መካከል ምስክር ይሁን” አሉት። **11** ስለዚህ ዮፍታሔ ከገለዓድ ሽማግሌዎች ጋር ሄደ፣ ሕዝቡም በላያቸው ላይ መሪና የጦር አዛዥ አደረጉት። እርሱ በምጽጳ በእግዚአብሔር ፊት በነበረ ጊዜ፣ ዮፍታሔ የገባውን ቃል ኪዳን ሁሉ ደገመው። **12** ዮፍታሔም ወደ አሞን ሰዎች ንጉሥ እንዲህ በማለት መልእክተኞችን ላከ፦ “በእኛ መካከል ያለው ጠብ ምንድን ነው? ምድራችንን ለመውሰድ በጦር ለምን መጣህ?” **13** የአሞንም ሰዎች ንጉሥም ለዮፍታሔ መልክተኞች “እስራኤል ከግብፅ በወጣ ጊዜ ከአርኖን ጀምሮ እስከ ያቦቅና እስከ ዮርዳኖስ ድረስ ምድሬን ወስደዋል። አሁን እነዚህን መሬቶች በሰላም መልሱልኝ” ብሎ መለሰላቸው። **14** ዮፍታሔም ወደ አሞን ሰዎች ንጉሥ መልክተኞችን እንደ ገና ላከ፣ **15** እንዲህም አለው፣ “ዮፍታሔ የሚለው ይህንን ነው፦ እስራኤል የሞዓብን ምድር የአሞንንም ሰዎች ምድር አልወሰደም፣ **16** ነገር ግን ከግብፅ በወጡ ጊዜ፣ እስራኤል በምድረ በዳ በኩል ወደ ቀይ ባሕር ከዚያም ወደ ቃዴስ ሄዱ፣ **17** እስራኤል ወደ ኤዶምያስ ንጉሥ እንዲህ በማለት መልእክተኞችን ላኩ፣ ‘በምድርህ እንድናልፍ እባክህ ፍቀድልን፣’ ነገር ግን የኤዶምያስ ንጉሥ አልሰማም። እንዲሁም ወደ ሞዓብ ንጉሥ መልእክተኞች ላኩ፣ እርሱም አልፈቀደም። ስለዚህ እስራኤል በቃዴስ ተቀመጠ። **18** እነርሱም በምድረ በዳ በኩል ሄዱና ከኤዶምያስና ከሞዓብ ምድር ተመለሱ፣ በሞዓብም ምድር በምሥራቅ በኩል ሄዱ፣ በአርኖንም ማዶ ሰፈሩ። ነገር ግን ወደ ሞዓብ ክልል ውስጥ አልገቡም፣ አርኖን የሞዓብ ድንበር ነበረና። **19** እስራኤልም በሐሴቦን ውስጥ ገዥ ወደነበረው ወደ አሞራውያን ንጉሥ ወደ ሴዎን መልክተኞችን ላከ፤ እስራኤልም ‘እባክህ፣ በምድርህ በኩል ወደ ስፍራችን እንድናልፍ ፍቀድልን’ አለው። **20** ነገር ግን ሴዎን እስራኤል በድንበሩ እንዲያልፍ አላመነውም። ስለዚህ ሴዎን ሰራዊቱን ሁሉ ሰበሰበና ወደ ያሀጽ ተንቀሳቀሰ፣ በዚያም ከእስራኤል ጋር ተዋጋ። **21** የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔርም ለእስራኤል በሴዎን ላይ ድል ሰጠውና ሕዝቡን ሁሉ በቁጥጥራቸው ስር እንዲሆኑ አሳልፎ ሰጣቸው። ስለዚህም እስራኤል በዚያች አገር ተቀምጠው የነበሩትን የአሞራውያንን አገር ሁሉ ወሰዱ። **22** በአሞራውያን ክልል ውስጥ የነበረውን ሁሉንም ነገር ወሰዱ፣ ከአርኖንም እስከ ያቦቅ ድረስ፣ ከምድረ በዳውም እስከ ዮርዳኖስ ድረስ። **23** ያንጊዜ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር አሞራውያንን ከሕዝቡ ከእስራኤል ፊት አስወጣቸው፣ ታዲያ አንተ አሁን ምድራቸውን ልትወስድ ይገባልን? **24** አምላክህ ካሞሽ የሚሰጥህን ምድር አትወስድምን? ስለዚህ እግዚአብሔር አምላካችን የሰጠንን ምድር ሁሉ እንወስዳለን። **25** አሁን አንተ ከሞዓብ ንጉሥ ከሴፎር ልጅ ከባላቅ በእውነት ትሻላለህን? እርሱ ከእስራኤል ጋር ከቶ ክርክር ነበረውን? ከእነርሱ ጋር ጦርነት አካሂዷልን? **26** እስራኤል በሐሴቦንና በቀበሌዎችዋ፣ በአሮዔርና በቀበሌዎችዋ፣ በአርኖንም ዳርቻ ባሉት ከተሞች ሁሉ ለሦስት መቶ ዓመት ሲኖር በነበረበት ጊዜ፣ ለምን ታዲያ በዚያን ጊዜ መልሳችሁ አልወሰዳችኋቸውም ነበር? **27** እኔ አልበደልሁህም ነገር ግን አንተ እኔን በመውጋት እየበደልከኝ ነው። ፈራጅ የሆነው እግዚአብሔር በእስራኤል ሰዎችና በአሞን ሰዎች መካከል ዛሬ ይፈርዳል። **28** ነገር ግን የአሞን ሰዎች ንጉሥ ዮፍታሔ የላከበትን ማስጠንቀቂያ አልተቀበለም። **29** ያን ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ በዮፍታሔ ላይ መጣ፣ እርሱም በገለዓድና በምናሴ አለፈ፣ በገለዓድ ባለው ምጽጳም አለፈ፣ ከዚያም በገለዓድ ካለው ምጽጳ ወደ አሞን ሰዎች አለፈ። **30** ዮፍታሔም ለእግዚብሔር እንዲህ ሲል ስእለት ተሳለ፦ “በአሞንን ሰዎች ላይ ድልን ብትሰጠኝ፣ **31** ከአሞን ሰዎች በሰላም በተመለስሁ ጊዜ እኔን ሊያገኘኝ ከቤቴ በር የሚወጣው ማንኛውም ለእግዚአብሔር ይሆናል፣ እርሱንም ለሚቃጠል መሥዋዕት አቀርበዋለሁ። **32** ስለዚህ ዮፍታሔ እነርሱን ለመውጋት ወደ አሞን ሰዎች አለፈ፣ እግዚአብሔርም በእነርሱ ላይ ድል ሰጠው። **33** እርሱም ከአሮዔርም እስከ ሚኒት፣ እንደዚሁም እስከ አቤልክራሚም ድረስ ያሉ ሀያ ከተሞችን ወጋቸው፣ ታላቅ እልቂትም አደረሰባቸው። ስለዚህ የአሞን ሰዎች በእስራኤል ሰዎች ቁጥጥር ስር ሆኑ። **34** ዮፍታሄ ምጽጳ ወዳለው ቤቱ መጣ፣ በዚያም የእርሱ ልጅ ከበሮ ይዛ እያሸበሸበች ልታገኘው ወጣች። እርስዋም ብቸኛ ልጁ ነበረች፣ ከእርስዋ ሌላ ወንድ ልጅም ይሁን ሴት ልጅ አልነበረውም። **35** እርስዋንም ባየ ጊዜ፣ ልብሱን ቀደደ እንዲህም አለ፦ “ወይኔ! ልጄ ሆይ! በጎዘን አደቀቅሽኝ፣ በእኔ ላይ ጭንቅ ያመጣብኝ ሰው ሆንሽብኝ! ለእግዚአብሔር ስእለት ተስያለሁና፣ ቃሌን ማጠፍ በፍጹም አልችልም።” **36** እርስዋም እንዲህ አለችው፦ “አባቴ ሆይ፣ ለእግዚአብሔር ስእለት ተስለሃል፣ ቃል የገባኸውን ሁሉ በእኔ ላይ አድርግብኝ፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር በጠላቶችህ በአሞናውያን ላይ ተበቅሎልሃልና።” **37** አርስዋም ለአባትዋ እንዲህ አለች፦ “ይህ ቃል ለእኔ ይደረግልኝ። ይህንን አካባቢ እንድለቅና ወደ ታች ወደ ኮረብታዎቹ እንድወርድ፣ ከጓደኞቼም ጋር ስለ ድንግልናየ እንዳለቅስ ለሁለት ወራቶች ያህል ብቻየን እንድሆን ፍቀድልኝ። **38** እርሱም፣ “ሂጂ” አለ። ለሁለት ወራትም አሰናበታት። እርስዋም ትታው ሄደች፣ ከባልንጀሮችዋም ጋር ስለ ድንግልናዋ በኮረብታዎቹ ላይ አለቀሱ። **39** በሁለት ወር መጨረሻ ላይ ወደ አባትዋ ተመለሰች፣ እርሱም ቃል እንደገባው እንደ ስእለቱ አደረገባት። እርስዋም ከወንድ ጋር ተኝታ አታውቅም፣ ይህም በእስራኤል ዘንድ ልማድ ሆነ፣ **40** የእስራኤል ሴቶች ልጆች በየዓመቱ፣ ለአራት ቀናት፣ የገለዓዳዊውን የዮፍታሔን ሴት ልጅ ታሪክ እየተናገሩ ያስቡአታል።

Judges 11:1

ገለዓዳዊው
ይህ ከገለዓድ አውራጃ የሆነ ግለሰብ ነው። የእርሱም አባት ስም ገለዓድ መሆኑ የአጋጣሚ ጉዳይ ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የሚስቱ ወንዶች ልጆች ባደጉ ጊዜ
“የገለዓድ ሚስት የወለደቻቸው ወንዶች ልጆች በጎለመሱ ጊዜ”

በጦብ ምድር
ጦብ የአውራጃ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መጡና ከእርሱ ጋር ሄዱ
“ተከተሉት” ወይም “አብረው በየስፍራው ሄዱ”

Judges 11:4

ከጥቂት ቀናት በኋላ
“ከጥቂት ጊዜ በኋላ”

ከእስራኤል ጋር ተዋጉ
“ተዋጉ” የሚለው ቃል የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ትርጉሙም እስራኤልን ወጉ፣ በጦርነቱም ከእነርሱ ጋር ነበሩ። እዚህ ጋ “እስራኤል” የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። (የአነጋገር ዘይቤ እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከ ... ጋር እንድንዋጋ
“ከ -- ጋር መዋጋት እንድንችል”

Judges 11:7

ከአባቴ ቤት
እዚህ ጋ “ቤት” የሚያመለክተው በቤቱ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ነው። አ.ት፡ “ቤተሰቦቼ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አሁን ወደ አንተ የመጣነው ለዚህ ነው
“ለዚህ ነው” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ዮፍታሔ በችግር ውስጥ ስለመሆናቸው የተናገረውን ነው። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉሙ ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “አሁን ወደ አንተ የመጣነው በችግር ውስጥ ስለሆንን ነው”።

ከአሞን ሰዎች ጋር ተዋጋ
“የአሞንን ሰዎች ውጋቸው”

Judges 11:9

መሪና አዛዥ
እነዚህ ሁለት ቃላት መሰረታዊ ትርጉማቸው አንድ ሆኖ ሳለ የዮፍታሔን አስፈላጊነት አጽንዖት ለመስጠት ተደግመዋል። ሁለቱን ቃላት ልታጣምራቸው ትችላለህ። አ.ት፡ “አዛዥ”።

ዮፍታሔ በምጽጳ በእግዚአብሔር ፊት በነበረ ጊዜ የተናገረውን ቃል በሙሉ ደገመው
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። እዚህ ጋ “በእግዚአብሔር ፊት” የሚለው ሐረግ የተናገረውን ቃል በእግዚአብሔር ፊት እንደ መሓላ ደገመው ማለት ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የተናገረውን ቃል በሙሉ
ይህ የሚያመለክተው መሪያቸው ለመሆን ለገለዓድ መሪዎች የተናገረውን ቃል ነው።

Judges 11:12

በመሐከላችን ያለው ይህ ጸብ ምንድነው
“በመካከላችን ለምን ጸብ ይሆናል?” ዮፍታሔ ንጉሡ በእስራኤል ላይ ለምን እንደ ተቆጣ ይጠይቃል።

መሬታችንን ለመውሰድ በኃይል የመጣኸው ለምንድነው
“አንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የአሞንን ንጉሥ ሲሆን ራሱንና ወታደሮቹን ይወክላል። አ.ት፡ “ወታደሮችህ መሬታችንን ለመያዝ ለምን ይመጣሉ”

በኃይል ለመውሰድ የመጡት
“በጉልበት ለመውሰድ የመጡት”

አርኖን == ያቦቅ
እነዚህ የሁለት ወንዞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

እስከ ዮርዳኖስ
“ከዮርዳኖስ ወንዝ በወዲያ በኩል”

በሰላም
“በሰላማዊ መንገድ” ወይም “ልትከላከላቸው እንዳትሞክር”

Judges 11:14

እርሱም አለ
እዚህ ጋ “እርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ለንጉሡ የሚናገረውን መልዕክተኛ ነው። ይህ ምናልባት በቡድን የሆኑትን መልዕክተኞች በሚያመለክተውና በተከፈተው ተለዋዋጭ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም እንዳለው “እነርሱ” ተብሎ መጻፍ ይኖርበት ይሆናል። አ.ት፡ “መልዕክተኞቹ እንዲህ እንዲሉ ዮፍታሔ ነገራቸው” ወይም “እንዲህ አሉ”።

ከግብጽ ወጥተው በመጡ ጊዜ
ሰዎች ወደ ተስፋይቱ ምድር በሚጓዙበት ጊዜ ሁሉ ወደ ተስፋይቱ ምድር “ወደ ላይ” እንደ ሄዱ ይነገርላቸዋል። እስራኤላውያን ግብፅን ለቀው በወጡ ጊዜ ወደ ተስፋይቱ ምድር በመጓዝ ላይ ነበሩ። አ.ት፡ “ግብፅን ለቀው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Judges 11:17

እስራኤል መልዕክተኞችን በላኩ ጊዜ
መልዕክተኞቹ የተላኩት በእስራኤል መሪዎች ናበር። አ.ት፡ “የእስራኤል መሪዎች መልዕክተኞችን በላኩ ጊዜ”

በሚያልፉበት
“በመሐል ሲሄዱ” ወይም “ማቋረጥ”

አልሰማም
ይህ ቃል ዘይቤአዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙም “እምቢ” ማለት ነው። አ.ት፡ “እምቢ አለ” ወይም “ጥያቄአቸውን አልተቀበለም” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ደግሞም ወደ ሞዓብ ንጉሥ መልዕክተኞችን ላኩ
እስራኤል ወደ ሞዓብ ንጉሥ መልዕክተኞችን የላኩበት ምክንያት ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “ደግሞም ወደ ሞዓብ ንጉሥ ተመሳሳዩን ጥያቄ የሚያቀርቡ መልዕክተኞችን ላኩ”

እርሱ ግን እምቢ አለ
እስራኤል በሞዓብ መካከል ለማለፍ ያቀረበውን ጥያቄ የሞዓብ ንጉሥ አልተቀበለውም። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም በበለጠ ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “እርሱም ደግሞ እምቢ አለ፣ በሞዓብ ምድር መካከል እንዲያልፉም አልፈቀደላቸውም”።

አርኖን
ይህ የወንዝ ስም ነው። ይህንን በመሳፍንት 11፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Judges 11:19

እስራኤል ወደ ሴዎን መልዕክተኞችን ላኩ
መልዕክተኞቹ የተላኩት በእስራኤል መሪዎች ነው። አ.ት፡ “የእስራኤል መሪዎች መልዕክተኞችን በላኩ ጊዜ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሴዎን
ይህ የሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ሐሴቦን -- ያሃድ
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ሴዎን ግን እስራኤል በግዛቱ ውስጥ ያልፍ ዘንድ አላመነውም
ሴዎን በምድሩ በሰላም ያልፋል ብሎ እስራኤልን አላመነም። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም በይበልጥ ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “ይሁን እንጂ ሴዎን የእስራኤል ሕዝብ በግዛቱ በኩል በሰላም ያልፋል ብሎ አላመነም”።

በዚያ ተዋጋቸው
“እርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሴዎንን ሲሆን ይህም ራሱንና ሰራዊቱን ይወክላል። አ.ት፡ “በዚያ ተዋጉ” ወይም “በዚያ ሰራዊቱ ተዋጋ”

Judges 11:21

ሴዎን
የዚህን ሰው ስም በመሳፍንት 11፡19 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሴዎንና ሕዝቡን ሁሉ በእስራኤል እጅ ሰጠ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚያመለክተው በጦርነት የማሸነፍ ኃይልን ነው። አ.ት፡ “በሴዎንና በሕዝቡ ሁሉ ላይ ለእስራኤል ኃይልን ሰጠው”። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አርኖን -- ያቦቅ
የእነዚህን ወንዞች ስም በመሳፍንት 11፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

Judges 11:23

አሁን መሬታቸውን የራስህ አድርገህ ትወስዳለህ?
ዮፍታሔ ምላሽ በማይፈልግ በዚህ ጥያቄ የአሞናውያንን ንጉሥ ይገስጸዋል። “የእነርሱ” የሚለው ቃል እስራኤልን ያመለክታል። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “በመሆኑም፣ መሬታቸውን የራስህ አድርገህ መውሰድ አይኖርብህም”። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

አምላክህ ካሞሽ የሚሰጥህን ምድር አትወስድም?
ዮፍታሔ ምላሽ በማይሻ ጥያቄ የአሞናውያንን ንጉሥ እየገሰጸው ነው። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “አምላክህ ካሞሽ የሚሰጥህን ምድር ብቻ መውሰድ ይኖርብሃል”። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ውሰድ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ትርጉሙ አንድን ነገር በቁጥጥር ስር ማድረግ ማለት ነው። አ.ት፡ “በቁጥጥር ስር አድርግ” ወይም “የራስህ አድርግ”። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ካሞሽ
ይህ የሐሰተኛ አምላክ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

አሁን አንተ ከሞዓብ ንጉሥ ከሴፎር ልጅ ከባላቅ በእርግጥ ትበልጣለህ?
ዮፍታሔ ምላሽ በማይሻ ጥያቄ የአሞናውያንን ንጉሥ እየገሰጸው ነው። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “አንተ የሞዓብ ንጉሥ ከነበረው ከሴፎር ልጅ ከባላቅ አትሻልም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ባላቅ -- ሴፎር
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ከእስራኤል ጋር ለመከራከር ደፍሯል?
ዮፍታሔ ምላሽ በማይሻ ጥያቄ የአሞናውያንን ንጉሥ እየገሰጸው ነው። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ይሁን እንጂ ከእስራኤል ጋር ለመከራከር አልደፈረም”። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

በእነርሱስ ላይ ጦርነትን ዐውጇል?
ዮፍታሔ ምላሽ በማይሻ ጥያቄ የአሞናውያንን ንጉሥ እየገሰጸው ነው። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ከቶ በእነርሱ ላይ ጦርነትን አላወጀም”። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

Judges 11:26

ሦስት መቶ ዓመት
“300 ዓመት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ሐሴቦን
በመሳፍንት 11፡19 ላይ በተረጎምክበት መልኩ የዚህችን ከተማ ስም ተርጉም።

አሮዔር
ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

አርኖን
በመሳፍንት 11፡13 ላይ በተረጎምክበት መልኩ የዚህችን ከተማ ስም ተርጉም።

ታዲያ በዚያን ጊዜ ለምን አላስመለስካቸውም?
ዮፍታሔ ምላሽ በማይሻ ጥያቄ የአሞናውያንን ንጉሥ እየገሰጸው ነው። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “በዚያን ጊዜ ማስመለስ ነበረብህ” ወይም “ከአመታት በፊት ልታስመልሳቸው ይገባህ ነበር፤ አሁን ግን በጣም ዘግይተሃል” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

እኔ አልበደልኩህም፣ አንተ ግን እየወጋኸኝ በድለኸኛል
ዮፍታሔ የሚናገረው ሴዎንን ነው። እዚህ ጋ፣ ዮፍታሔ፣ ራሱን እንደ እስራኤላውያን፣ ንጉሣቸውን ሴዎንን እንደ አሞናውያን አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “እስራኤላውያን ሕዝብህን አልበደሉም፣ ይሁን እንጂ ሕዝብህ እየወጉን በድለውናል”።

አልበደልኩህም -- በድለኸኛል
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አንድን ሰው መበደል ማለት እነርሱን መበደል ነው። አ.ት፡ “የማይገባውን አላደረግሁብህም … የማይገባውን አድርገህብኛል” ወይም “ኢፍትሐዊ አልሆንኩብህም … ኢፍትሐዊ ሆነህብኛል”። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Judges 11:29

የእግዚአብሔር መንፈስ በዮፍታሔ ላይ መጣበት
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ትርጉሙም በዮፍታሔ ውሳኔዎች ላይ መንፈስ ቅዱስ ተጽዕኖ አሳድሯል ማለት ነው። አ.ት፡ “የእግዚአብሔር መንፈስ ዮፍታሔን ተቆጣጠረው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ከገለዓድ ምጽጳ -- በገለዓድና በምናሴ መሐል አለፈ
ዮፍታሔ በእነዚህ አካባቢዎች ከአሞን ሰዎች ጋር ለሚያደርገው ውጊያ ሰዎችን በሰራዊቱ ውስጥ ለማካተት እየመዘገባቸው አለፈ። የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “ከምጽጳ ገለዓድ … ሰዎችን ወደ ሰራዊቱ እየሰበሰበ በገለዓድና ምናሴ መካከል አለፈ”።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እሠዋዋለሁ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ትርጉሙ አንድን ነገር መሥዋዕት አድርጎ ማቅረብ ማለት ነው። አ.ት፡ “እርሱን እሠዋልሃለሁ” ወይም “መሥዋዕት አድርጌ አቀርብልሃለሁ”። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Judges 11:32

ስለዚህ ዮፍታሔ አለፈ -- ተዋጋ - እግዚአብሔር ድልን ሰጠው
ዮፍታሔ የሰራዊቱ መሪ በመሆኑ፣ እርሱና ሰራዊቱ በተደጋጋሚ ዮፍታሔን ራሱን ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ስለዚህ ዮፍታሔና ሰራዊቱ አለፉ -- ተዋጉ -- እግዚአብሔር ድልን ሰጣቸው”

አሮኤር
የዚህችን ከተማ ስም በመሳፍንት 11:26 ላይ በተረጎምክበት መልኩ ተርጉም።

ሚኒት -- አቤል ክራሚም
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ሃያ ከተሞች
“20 ከተሞችን ጨምሮ” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

Judges 11:34

አታሞ
እንደ ከበሮ የሚመታበት አናት ያለው፣ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ድምፅ እንዲያሰማ በዙሪያው ቁርጥራጭ ብረቶች የሚደረጉለት የሙዚቃ መሣሪያ።

ልብሶቹን ቀደደ
ይህ ለቅሶን ወይም ታላቅ ሐዘንን የሚያሳይ ድርጊት ነው። አ.ት፡ “ልብሱን በሐዘን ቀደደ” (ምሳሌአዊ ድርጊት የሚለውን ተመልከት)

በሐዘን ሰበርሽኝ -- ለህመም ዳረግሽኝ
ዮፍታሔ አንዱን አሳብ ሁለት ጊዜ መናገሩ እጅግ ስለ ማዘኑ አጽንዖት ለመስጠት ነው።

በሐዘን ሰበርሽኝ
እዚህ ጋ፣ ዮፍታሔ ጥልቅ ሐዘኑን እንደሚሰባብረው አንደ አንዳች ነገር ቆጥሮ ይናገራል። አ.ት፡ “ጥልቅ ሐዘን ላይ ጥለሽኛል” ወይም “በሐዘን እንድሞላ አደረግሽኝ”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ለህመም ዳረግሽኝ
እዚህ ጋ ዮፍታሔ የሚናገረው ጥልቅ ሐዘኑና ሥቃዩ እንደ ሕመም እንደሆነበት ነው። አ.ት፡ “አንቺ ሥቃይ እንደሚያመጣብኝ ዓይነት ሰው ሆነሻል” ወይም “ለጥልቅ ሐዘን ዳርገሽኛል”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ቃሌን ማጠፍ አልችልም
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ቃልን ማጠፍ ማለት ልታደርገው ቃል የገባህበትን ጉዳይ መተው ነው። አ.ት፡ “ቃል የገባሁበትን ጉዳይ መፈጸም አለብኝ” ወይም “ቃሌን ለማጠፍ አልችልም”። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Judges 11:36

ጠላቶችህን አሞናውያንን ተበቅሎልሃልና
ጠላቶቹን በማሸነፍ እግዚአብሔር ተበቅሎለታል። የዚህ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “በጠላቶችህ በአሞናውያን ላይ ተበቅሎልሃል”

ይህ ቃል ኪዳን ይጠበቅልኝ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ስለ እኔ ይህንን ቃል ኪዳን ጠብቅ” ወይም “እኔን በሚመለከት ይህንን ቃል ኪዳን ጠብቅ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ስለ ድንግልናዬ ላልቅስ
“ድንግል በመሆኔ ምክንያት ላልቅስ” ወይም “ከእንግዲህ ስለማላገባ ላልቅስ”

Judges 11:38

ገለዓዳዊው
ይህ አንድን ከገለዓድ የሆነን ሰው ያመለክታል። ይህንን በመሳፍንት 10:3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 12

1 ወደ ኤፍሬም ሰዎችም ጥሪ ደረሰ፤ በጻፎን በኩል ተሻግረው ዮፍታሔን፣ “ከአሞን ሕዝብ ጋር ለመዋጋት ስታልፍ ከአንተ ጋር እንድንሄድ ያልጠራኸን ለምድን
ነው? ቤትህን በአንተ ላይ እናቃጥለዋለን” አሉት። **2** ዮፍታሔም እንዲህ አላቸው፣ “እኔና ሕዝቤ ከአሞን ሕዝብ ጋር በታላቅ ጦርነት ውስጥ ነበርን።
በጠራኋችሁም ጊዜ ከእነርሱ አላዳናችሁኝም። **3** እናንተም እንዳላዳናችሁኝ ባየሁ ጊዜ፣ ሕይወቴን በራሴ ብርታት አስቀምጬ በአሞን ሕዝብ ላይ ለመዋጋት
አለፍሁ፣ እግዚአብሔርም በእነርሱ ላይ ድል ሰጠኝ። ዛሬ እኔን ለመውጋት ለምን መጣችሁ? **4** ዮፍታሔም የገለዓድን ሰዎች ሁሉ ሰበሰበና ከኤፍሬምም ጋር
ተዋጋ። የገለዓድም ሰዎች የኤፍሬምን ሰዎች ወጓቸው ምክንቱም፣ “እናንተ ገለዓዳውያን በኤፍሬም ውስጥ ሸሽታችሁ የተጠጋችሁ፣ በኤፍሬምና በምናሴ ውስጥ
ጥገኞች የሆናችሁ ናችሁ” ይሏቸው ነበርና። **5** ገለዓዳውያንም ወደ ኤፍሬም የሚወስደውን የዮርዳኖስን መሻገሪያ ያዙባቸው። አምልጦ የሚሸሽ የኤፍሬም ሰው፣
“ወንዙን ተሻግሬ ልለፍ” ባለ ጊዜ፣ የገለዓድ ሰዎች ደግሞ እንዲህ ይሉታል፣ “አንተ ኤፍሬማዊ ነህን?” እርሱም፣ “አይደለሁም” ቢል፣ **6** እነርሱም “ሺቦሌት
በል” ይሉታል። እርሱም “ሲቦሌት” ብሎ ከተናገረ (ምክንያቱም እርሱ ቃሉን አጥርቶ መናገር አይችልምና) ፣ ገለዓዳውያን እርሱን ይዘው በዮርዳኖስ መሻገሪያ
ላይ ይገድሉታል። በዚያም ጊዜ አርባ ሁለት ሺህ ኤፍሬማውያን ተገደሉ። **7** ዮፍታሔም በእስራኤል ላይ ለስድስት ዓመት እንደ ፈራጅ አገለገለ። ከዚያም
ገለዓዳዊውም ዮፍታሔ ሞተ፣ ከገለዓድ ከተሞችም በአንዱ ተቀበረ። **8** ከእርሱም በኋላ የቤተ ልሔሙ ኢብጻን በእስራኤል ላይ እንደ ፈራጅ አገለገለ። **9** እርሱም
ሠላሳ ወንዶች ልጆች ነበሩት። ሠላሳ ሴቶች ልጆችንም ወደ ውጭ በትዳር ለሌሎች ሰጠ፣ ሠላሳ ሴቶች ልጆችን ደግሞ ከሌሎች ሰዎች በትዳር ለወንድ ልጆቹ
አመጣ። በእስራኤልም ላይ ለሰባት ዓመት ፈረደ። **10** ኢብጻንም ሞተ፣ በቤተ ልሔምም ተቀበረ። **11** ከእርሱም በኋላ ዛብሎናዊው ኤሎም በእስራኤል ላይ
እንደ ፈራጅ አገለገለ። እርሱም በእስራኤል ላይ ለአሥር ዓመት ፈረደ። **12** ዛብሎናዊውም ኤሎም ሞተ፣ በዛብሎንም ምድር ባለችው በኤሎም ተቀበረ። **13**
ከእርሱም በኋላ የጲርዓቶናዊው የሂሌል ልጅ ዓብዶን በእስራኤል ላይ እንደ ፈራጅ አገለገለ። **14** እርሱም አርባ ወንዶች ልጆችና ሠላሳ ወንዶች የልጅ ልጆች
ነበሩት። በሰባ አህያዎች ላይ ይጋልቡ ነበር፣ እርሱም በእስራኤል ላይ ለስምንት ዓመት ፈረደ። **15** የጲርዓቶናዊውም የሂሌል ልጅ ዓብዶን ሞተ፣ በተራራማውም
በአማሌቃውያን አገር በኮረብታማው በኤፍሬም አገር ውስጥ ባለችው በጲርዓቶን ውስጥ ተቀበረ።

Judges 12:1

ለኤፍሬም ሰዎች ጥሪ ደረሳቸው
እዚህ ጋ “ጥሪ” የሚለው የነገር ስም እንደ ግሥ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የኤፍሬም ሰዎች በአንድ ላይ ተጠሩ” ወይም “የኤፍሬም ሰዎች ወታደሮቻቸውን በአንድ ላይ ሰበሰቧቸው”። (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ጻፎን
ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ተሻገሩ -- አለፉ
“መንገዳቸውን … አልፈው ሄዱ” ወይም “ጉዞአቸውን … አልፈው ተጓዙ”

ቤትህን በላይህ ላይ እናቃጥለዋለን
ይህ የአነጋገር ዘይቤ የሚያመለክተው ቤቱን በውስጡ ካሉት ሰዎች ጋር ስለ ማቃጠል ነው። አ.ት፡ “ቤትህን በውስጡ እንዳለህ እናቃጥለዋለን”። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

እናንተን በጠራኋችሁ ጊዜ
እዚህ ጋ “እናንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተው የኤፍሬምን ሰዎች ነው።

አላዳናችሁኝም
ዮፍታሔ “እኔ” የሚለውን ቃል የሚጠቀመው ራሱንና የገለዓድን ሰዎች በሙሉ ለማመልከት ነው። አ.ት፡ “አታድኑን”

Judges 12:3

እናንተ አላዳናችሁኝም
“እናንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ሲሆን የኤፍሬምን ሰዎች ያመለክታል። ዮፍታሔ “እኔ” በሚልበት ጊዜ የሚያመለክተው ራሱን ጨምሮ የገለዓድን ሰዎች ነው። አ.ት፡ “አላዳናችሁንም”።

ሕይወቴን በእጄ ጥዬ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ በራስ ጉልበት በመደገፍ ራስን ለአደጋ መስጠት ማለት ነው። ዮፍታሔ የገለዓድን ሰዎች እንደ ራሱ አድርጎ ማመልከቱን ይቀጥላል።
አ.ት፡ “በራሳችን በመተማመን ሕይወታችንን ለአደጋ ሰጥተናል”። (የአነጋገር ዘይቤ እና የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር ድልን ሰጥቶኛል
በአሞናውያን ላይ እግዚአብሔር ለገለዓድ ሰዎች ድልን እንደ ሰጣቸው ዮፍታሔ ያመላክታል። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም በይበልጥ መብራራት ይችላል። አ.ት፡ “በእነርሱ ላይ እግዚአብሔር ድልን ሰጥቶናል” ወይም “በጦርነት እንድናሸንፋቸው እግዚአብሔር ፈቅዶልናል”

ከኤፍሬም ጋር ተዋጋ
“እርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ዮፍታሔንና የገለዓድን ተዋጊዎች ሁሉ ነው። አ.ት፡ “ከኤፍሬም ጋር ተዋጉ”

ለምን ልትወጉኝ መጣችሁ
“እናንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተው የኤፍሬምን ሰዎች ነው። ዮፍታሔ “እኔ” በሚልበት ጊዜ የሚያመለክተው ራሱን ጨምሮ የገለዓድን ሰዎች ነው። አ.ት፡ “እኛን ልትወጉን ለምን መጣችሁ”

ገለዓዳውያን ኮብላዮች ናቸው
የዚህን ስድብ ትርጉም ግልጽ ልታደርገው ትችላለህ። አ.ት፡ “ይህ ቦታ ለእናንተ ለገለዓዳውያን አይገባችሁም። እናንተ በዚህ ለመኖር የመጣችሁ ሰዎች ብቻ ናችሁ”

በአሞን ሰዎች ላይ አልፈው ሄዱ
ይህ ማለት በአሞን በኩል ሲያልፉ ከአሞናውያን ጋር ተዋጉ። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “በግዛታቸው በኩል ስናልፍ ክአሞን ሰዎች ጋር ተዋጋን”

ገለዓዳውያን
የገለዓድ ሰዎች

በኤፍሬም -- በኤፍሬምና በምናሴ
“በኤፍሬምና በምናሴ አውራጃዎች” ወይም “በኤፍሬምና በምናሴ ምድር”። እዚህ ጋ “ኤፍሬም” እና “ምናሴ” የሚያመለክቱት አውራጃዎችን ሲሆን በዚያ በሚኖሩ ነገዶች ስም ተሰይመዋል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Judges 12:5

ለኤፍሬም
“ለኤፍሬም ምድር”

ገለዓዳውያን ያዙት
“ገለዓዳውያን ተቆጣጠሩት” ወይም “ገለዓዳውያን ያዙት”

መልካ
እነዚህ ውሃው ጥልቀት የሌለው በመሆኑ በእግር ልታቋርጥ የምትችለው ወንዝ ያሉባቸው አካባቢዎች ናቸው።

ኤፍሬማዊ
ከኤፍሬም ነገድ የሆነ ሰው

ሺቦሌት -- ሲቦሌት
እነዚህ ቃላት ምንም ትርጉም የላቸውም። እነዚህን ቃላት ወደ ራስህ ቋንቋ ቅዳቸውና በቃላቱ መጀመሪያ ላይ “ሺ” እና “ሲ” የሚሉ ፊደላት ለየብቻ መተርጎማቸውን እርግጠኛ ሁን። (ቃላትን መቅዳት ወይም መዋስ የሚለውን ተመልከት)

ቃሉን መናገር
“የቃላቱን ድምፅ ማውጣት”

አርባ ሁለት ሺህ
“42,000” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

አርባ ሁለት ሺህ ኤፍሬማውያን ተገደሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አርባ ሁለት ሺህ ኤፍሬማውያንን ገደሉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Judges 12:7

ገለዓዳዊው ዮፍታሔ ሞተና ተቀበረ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ገለዓዳዊው ዮፍታሔ ሞተና ቀበሩት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Judges 12:8

የቤተ ልሔሙ ኢብጻን
ይህ ከቤተ ልሔም የሆነ የአንድ ሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

እርሱ ሠላሳ ሴቶች ልጆቹን ዳረ
እዚህ ጋ “ዳረ” የሚለው ቃል የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ልጆቹ እንዲያገቡ ፈቅዷል ማለት ነው። አ.ት፡ “ሠላሳ ሴቶች ልጆች ነበሩትና እያንዳንዳቸው እንዲያገቡ ቅድመ ዝግጅት አደረገላቸው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ለወንዶች ልጆቹም ከውጭ ከሌሎች ሰዎች ሠላሳ ሴቶች ልጆችን አመጣላቸው
“ከውጭ አመጣላቸው” የሚለው የአነጋገር ዘይቤ ትርጉሙ ከሌላ ጎሳ የሆኑት ሴቶች ከወንዶች ልጆቹ ጋር ተጋቡ ማለት ነው። አ.ት፡ “ከራሱ ጎሳ ውጭ ካሉ ሰዎች ሠላሳ ሴቶች ልጆች የእርሱን ወንዶች ልጆች እንዲያገቡ አደረገ”። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Judges 12:10

በቤተ ልሔም ተቀበረ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በቤተ ልሔም ቀበሩት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ኤሎን
ይህ የሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ዛብሎናዊ
ከዛብሎን ነገድ የሆነ አንድ ሰው

ኢያሎን
የዚህን ቦታ ስም በመሳፍንት 1:35 ላይ እንደተረጎምከው ተርጉመው።

በኢያሎን ተቀበረ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በኢያሎን ቀበሩት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Judges 12:13

አብዶን --ሂሌል
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ጲርዓቶናዊው -- ጲርዓቶን
ጲርዓቶን የቦታ ስም ሲሆን ከዚያ አካባቢ የሆነ ሰው ደግሞ ጲርዓቶናዊ ይባላል። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

በሰባ አህዮች የሚቀመጡ
እነዚህ ሰዎች የሚቀመጡባቸውን ሰባ አህዮች የራሳቸው ማድረግ ችለዋል። እዚህ ጋ “መቀመጥ” የሚለው ቃል “የራስ ማድረግ” ከሚለው ይልቅ ጥቅም ላይ ውሏል። አ.ት፡ “ሰባ አህዮች ነበሯቸው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አርባ ወንዶች ልጆች -- ሠላሳ የልጅ ልጆች -- ሰባ አህዮች
“40 ወንዶች ልጆች -- 30 የልጅ ልጆች -- 70 አህዮች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 13

1 የእስራኤልም ሕዝብ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነውን ስራ እንደ ገና ሠሩ፣ እርሱም ፍልስጥኤማውያን በእነርሱ ላይ ለአርባ ዓመት እንዲገዙ ፈቀደላቸው። 2 ከዳን ቤተሰብ የሆነ ስሙም ማኑሄ የሚባል አንድ የጾርዓ ሰው ነበረ። ሚስቱም መካን ስለነበረች ልጅ አልወለደችም። 3 የእግዚአብሔርም መልአክ ለሴቲቱ ተገልጦ እንዲህ አላት፣ “ተመልከቺ፣ አንቺ መካን ነበርሽ፣ ልጅም አልወለድሽም፣ ነገር ግን ትፀንሻለሽ፣ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ። 4 አሁንም የወይን ጠጅ ወይም የሚያሰክር ጠንካራ መጠጥ እንዳትጠጪ ተጠንቀቂ፣ ሕጉ ርኩስ እንደሆነ የገለጸውን ማንኛውንም ምግብ አትብዪ። 5 ተመልከቺ፣ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ። ልጁ ከአንቺ ማኅፀን ጀምሮ ለእግዚአብሔር የተለየ ናዝራዊ ስለሚሆን በራሱ ላይ ምላጭ አይድረስበት። እርሱም እስራኤልን ከፍልስጥኤማውያን ጉልበት ማዳን ይጀምራል። 6 የዚያን ጊዜ ሴቲቱ ወደ ባልዋ መጥታ እንዲህ ብላ ነገረችው፣ “አንድ የእግዚአብሔር ሰው ወደ እኔ መጣ፣ መልኩም እንደ እግዚአብሔር መልአክ የሚመስል ነበረ፣ በጣምም አስደነገጠኝ። ከወዴት እንደ መጣ አልጠየቅሁትም፣ እርሱም ስሙን አልነገረኝም። 7 እርሱም እንዲህ አለኝ፣ ‘ተመልከቺ! ትፀንሻለሽ፣ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ። ስለዚህ ልጁ ከአንቺ ማኅፀን ጀምሮ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ ለእግዚአብሔር የተለየ ናዝራዊ ስለሚሆን የወይን ጠጅ ወይም የሚያሰክር ጠንካራ መጠጥ እንዳትጠጪ፣ ሕጉ ርኩስ እንደሆነ የገለጸውን ማንኛውንም ምግብ አትብዪ።’” 8 ከዚያም ማኑሄ ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ጸለየ፣ “ጌታ ሆይ፣ አሁን በቅርቡ ለሚወለደው ልጅ ምን ማድረግ እንዳለብን እንዲያስተምረን እባክህ የላክኸው የእግዚአብሔር ሰው እንደገና ወደ እኛ ይምጣ።” 9 እግዚአብሔርም የማኑሄን ጸሎት መለሰ፣ የእግዚአብሔርም መልአክ እንደ ገና ወደ ሴቲቱ በእርሻ ውስጥ ተቀምጣ ሳለች መጣ። ነገር ግን ባልዋ ማኑሄ ከእርስዋ ጋር አልነበረም። 10 ስለዚህ ሴቲቱም ፈጥና ሮጠችና ለባልዋ ነገረችው፣ “ተመልከት! በሌላኛው ቀን ወደ እኔ የመጣው ሰው እንደገና ተገለጠልኝ።” 11 ማኑሄም ተነሳና ሚስቱን ተከተላት። ወደ ሰውዮውም በመጣ ጊዜ እንዲህ አለው፣ “ከሚስቴ ጋር የተነጋገርህ ሰው አንተ ነህን?” ሰውየውም፣ “እኔ ነኝ” አለው። 12 ስለዚህ ማኑሄ እንዲህ አለ፣ “አሁንም ቃሎችህ እውነት ይሁኑ። ነገር ግን ልጁ የሚመራው በምንድን ነው፣ እኛስ ለእርሱ የምንሰራው ምንድን ነው?” 13 የእግዚአብሔርም መልአክ ለማኑሄ እንዲህ አለው፣ “እርስዋ የነገርኋትን ነገር ሁሉ በጥንቃቄ ማድረግ አለባት። 14 ከወይን ከሚወጣው ማንኛውንም ነገር አትብላ፣ የወይን ጠጅ ወይም የሚያሰክር ሌላ ጠንካራ መጠጥ አትጠጣ፤ ሕጉ ርኩስ ነው ብሎ የገለጸውን ማንኛውንም ምግብ አትብላ። እኔ እንድታደርገው ያዘዝኋትን ማንኛውንም ነገር መታዘዝ አለባት። 15 ማኑሄም ለእግዚአብሔር መልአክ እንዲህ አለው፣ “ለአንተ የፍየል ጠቦት ለማዘጋጀት ጊዜ እናገኝ ዘንድ፣ እባክህ ለአጭር ጊዜ ቆይ።” 16 የእግዚአብሔርም መልአክ ለማኑሄ እንዲህ አለው፣ “ብቆይም እንኳ፣ መብልህን አልበላም።ነገር ግን የሚቃጠል መሥዋዕት የምታዘጋጅ ከሆነ፣ ያንን ለእግዚአብሔር አቅርበው።” ማኑሄ የእግዚአብሔር መልአክ መሆኑን አላወቀም ነበር። 17 ማኑሄም ለእግዚአብሔር መልአክ እንዲህ አለው፣ “የተናገርሃቸው ቃሎች እውነት በሆኑ ጊዜ እናከብርህ ዘንድ ስምህ ማን ነው?” 18 የእግዚአብሔርም መልአክ እንዲህ አለው፣ “ስሜን ለምን ትጠይቃለህ? ስሜ ድንቅ ነው!” 19 ስለዚህ ማኑሄም የፍየሉን ጠቦት ከእህል ቍርባን ጋር ወሰደና በድንጋይ ላይ ለእግዚአብሔር አቀረበው። ማኑሄና ሚስቱ እያዩ እርሱ አስደናቂ ነገር አደረገ። 20 ነበልባሉም ከመሠዊያው ላይ ወደ ሰማይ በወጣ ጊዜ፣ የእግዚአብሔር መልአክ በመሠዊያው ነበልባል ውስጥ ወደ ላይ ዐረገ። ማኑሄና ሚስቱም ይህን ተመለከቱና በግምባራቸው ምድር ላይ ተደፉ። 21 የእግዚአብሔርም መልአክ ላማኑሄ ወይም ለሚስቱ እንደገና አልተገለጠም። ያን ጊዜም ማኑሄ የእግዚአብሔር መልአክ መሆኑን አወቀ። 22 ማኑሄም ለሚስቱ እንዲህ አላት፣ “እግዚአብሔርን ስላየን በእርግጠኝነት እንሞታለን።” 23 ነገር ግን ሚስቱ እንዲህ አለችው፣ “እግዚአብሔር ሊገድለን ቢፈልግ ኖሮ፣ ለእርሱ ያቀረብነውን የሚቃጠለውን መሥዋዕትና የእህሉን ቍርባን ባልተቀበለን ነበር። ይህንም ነገር ሁሉ ባላሳየን ነበር፣ በዚህ ጊዜ እንዲህ ያሉ ነገሮችንም እንድንሰማ ባላደረገን ነበር።” 24 ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ሴቲቱ ወንድ ልጅ ወለደች፣ ስሙንም ሳምሶን ብላ ጠራችው። ልጁም አደገ እግዚአብሔርም ባረከው። 25 የእግዚአብሔርም መንፈስ እርሱን በጾርዓና በኤሽታኦል መካከል ባለው በዳን ሰፈር ውስጥ ያነቃቃው ጀመር።

Judges 13:1

በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነውን
የእግዚአብሔር ፊት የእርሱን ፍርድ ወይም ምዘና ይወክላል። ይህንን በመሳፍንት 2፡11 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “በእግዚአብሔር ፍርድ ክፉ የሆነውን” ወይም “እግዚአብሔር ክፉ ነው ያለውን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በፍልስጥኤማውያን እጅ ሰጣቸው
እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው በጦርነት ድል ማድረጊያ ኃይልን ነው። አ.ት፡ “ፍልስጥኤማውያን እንዲያሸንፏቸው ፈቀደ” ወይም “በፍልስጥኤማውያን እንዲጨቆኑ ፈቀደ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አርባ ዓመት
“40 ዓመት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ጾርዓ
ይህ በእስራኤል የነበረ ከተማ ስም ነው። እርሱ በዳን ድንበር አቅራቢያ በይሁዳ አውራጃ ነበር። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ዳናውያን
የዳን ነገድ ሰዎች

ማኑሄ
ይህ የሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Judges 13:3

ወንድ ልጅ ትወልጃለሽ
ይህ የሕፃን ልጅን መወለድ ያመለክታል። አ.ት፡ “ወንድ ልጅ መውለድ” ወይም “ወንድ ሕፃን ልጅ ይኖርሻል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ንጹሕ ያልሆነ ምንም ነገር
እግዚአብሔር መበላት የለበትም ያለው ነገር በአካላዊነቱም ንጹሕ እንዳይደለ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እነሆ
“አስተውይ” ወይም “አድምጪ”

በራሱ ላይ ምላጭ አያርፍበትም
እዚህ ጋ “ራስ” የሚያመለክተው ጸጉሩን ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ማንም ጸጉሩን እንዳይቆርጠው”(አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ምላጭ
ጸጉርን ከቆዳ አጠገብ አድርሶ ለመቁረጥ የሚያገለግል ስል ቢለዋ ነው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለእግዚአብሔር ናዝራዊ
ይህ ማለት እንደ ናዝራዊ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ይሆናል ማለት ነው። አ.ት፡ “ለእግዚአብሔር የተሰጠ ናዝራዊ” ወይም “እንደ ናዝራዊ ለእግዚአብሔር የተሰጠ”

ከማህፀን
እዚህ ጋ “ማህፀን” የሚያመለክተው ሕፃን ከመወለዱ በፊት ያለውን ጊዜ ነው። አ.ት፡ “ከመወለዱ በፊት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከፍልስጥኤማውያን እጅ
እዚህ ጋ “እጅ” መቆጣጠር ማለት ነው። አ.ት፡ “ከፍልስጥኤማውያን ቁጥጥር” ወይም “በፍልስጥኤማውያን ቁጥጥር ስር ከመሆን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 13:6

አንድ የእግዚአብሔር ሰው
ይህ ማለት ሰውየው የተላከው በእግዚአብሔር ነው። ይህ ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር የላከው አንድ ሰው”

መልኩ በጣም የሚያስፈራ እንደ እግዚአብሔር መልአክ ነበር
እዚህ ጋ “በጣም የሚያስፈራ” ማለት “አስደንጋጭ” ማለት ነው። አ.ት፡ “የእግዚአብሔርን መልአክ ይመስል ስለ ነበረ በጣም ፈርቼ ነበር”

እነሆ
“አስተውል” ወይም “አድምጥ”

ወንድ ልጅ ትወልዳለች
ይህ የሕፃን ልጅ መወለድን ያመለክታል። አ.ት፡ “ወንድ ልጅ ትወልዳለች” ወይም “ወንድ ሕፃን ልጅ ይኖራታል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የትኛውንም በሕጉ ንጹህ ያልተባለውን ምግብ
እግዚአብሔር መበላት የለበትም ያለው ነገር በአካላዊነቱም ንጹሕ እንዳይደለ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ለእግዚአብሔር ናዝራዊ
ይህ ማለት እንደ ናዝራዊ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ይሆናል። ይህንን በመሳፍንት 3፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ለእግዚአብሔር የተሰጠ ናዝራዊ” ወይም “እንደ ናዝራዊ ለእግዚአብሔር የተሰጠ”

በማህፀንሽ ከተፀነሰበት እስከሚሞትበት ጊዜ ድረስ
ይህ አጽንዖት የሚሰጠው በሕይወት ዘመኑ ሁሉ መሆን እንዳለበት ነው። አ.ት፡ “ሕይወቱን ሙሉ”

Judges 13:8

ማኑሄ
የዚህን ሰውዬ ስም በመሳፍንት 13፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ወደ ሴቲቱ መጣ
ግልጽ ያልሆኑትን የዳራውን ቃላት ግልጽ ልታደርጋቸው ትችላለህ። አ.ት፡ “ወደ ማኑሄ ሚስት መጣ”

Judges 13:10

እነሆ
“ስማ” ወይም “የምነግርህን ልብ በል”

ሰውየው
ይህ በመሳፍንት 13፡3 የእግዚአብሔርን መልአክ ያመለክታል። ይህ ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “የእግዚአብሔር ሰው”

Judges 13:12

ቃሎችህ
“የተናገርከው ቃል”

የትኛውንም ከወይን የሚገኘውን
እዚህ ጋ መልአኩ ከወይን “የሚወጣ” ሲል የትኛውንም ከወይን የሚገኘውን ምግብ እንደሆነ ያመላክታል። አ.ት፡ “በወይን ላይ የሚበቅል ማንኛውም ነገር” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ንጹሕ ያልሆነ
እግዚአብሔር መበላት የለበትም ያለው ነገር በአካላዊነቱም ንጹሕ እንዳይደለ ተነግሯል። ይህንን ሐረግ በመሳፍንት 13፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 13:15

የፍየል ጠቦት ይዘጋጅልህ
ግልጽ ያልሆነውን የማኑሄን መግለጫ ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። አ.ት፡ “እንድትበላው የፍየል ጠቦት እናብስልልህ”

Judges 13:17

ቃሎችህ ሲፈጸሙ
“የተናገርከው ሲፈጸም”

ስሜን ለምን ትጠይቃለህ?
መልአኩ በተግሳጽ መልክ ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ስሜ ማን መሆኑን መጠየቅ የለብህም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ድንቅ ነው
ስሙን ለምን መጠየቅ እንደማይኖርባቸው በይበልጥ ግልጽ ማድረጉ ይጠቅም ይሆናል። አ.ት፡ “ለመረዳት እጅግ ያስቸግራችሁ ይሆናል”

Judges 13:19

ከእህል ቁርባኑ ጋር
ይህ ሕግ የሚቃጠል መሥዋዕት በሚቀርብበት ጊዜ የእህል ቁርባን እንዲቀርብ ያዛል። አ.ት፡ “ከእርሱም ጋር የታዘዘውን የእህል ቁርባን” ወይም “አብሮት እንዲሆን የእህል ቁርባን”

በዐለቱ ላይ
“በመሠዊያው ላይ”። ማኑሄ መሥዋዕቱን ያቀረበበት መሠዊያ ዐለት ነበር።

አንድ ነገር አደረገ
“መልአኩ አንድ ነገር አደረገ”

የእግዚአብሔር መልአክ በመሠዊያው ነበልባል ውስጥ ወደ ላይ ወጣ
“የእግዚአብሔር መልአክ በመሠዊያው ነበልባል ውስጥ ተመልሶ ወደ ሰማይ ሄደ”

በፊታቸው በመሬት ላይ ተደፉ
“በግምባራቸው ተደፉ” ይህ የአድናቆትና የአክብሮት ምልክት ነው፣ ሆኖም እግዚአብሔርን መፍራታቸውንም ያሳያል። (ምሳሌአዊ ድርጊት የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Judges 13:21

የእግዚአብሔር መልአክ እንደ ነበረ
“እርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ማኑሄና ሚስቱ ያዩትን ሰው ነው።

እግዚአብሔርን ስላየነው በእርግጥ መሞታችን ነው
እግዚአብሔር እንደሚገድላቸው ማሰባቸውን ያሳያል። ይህ ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ስላየነው ይገድለናል”

Judges 13:23

እነዚህን ነገሮች ሁሉ አያሳየንም ወይም በዚህ ጊዜ እንዲህ ያሉትን ነገሮች እንድንሰማ አያደርገንም ነበር
የማኑሄ ሚስት ስለ አንዱ ነገር ሁለት ጊዜ የምትናገረው አጽንዖት ለመስጠት ነው። እነዚህ ሁለት መግለጫዎች መጣመር ይችላሉ። አ.ት፡ “እንድናደርግ የፈለገውን አይነግረንም ነበር”

Judges 13:24

ሴቲቱ
“የማኑሄ ሚስት”

ወንድ ልጅ ወለደች
ይህ የልጅ መወለድን ያመለክታል። አ.ት፡ “ወንድ ልጅ ወለደች” ወይም “ወንድ ልጅ አገኘች” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

አደገ
“ዐዋቂ ሆነ” ወይም “ጎለመሰ”

የእግዚአብሔር መንፈስ ሊያነቃቃው ጀመረ
እዚህ ጋ የእግዚአብሔር መንፈስ ሳምሶንን ማነቃቃቱ በማሰሮ ውስጥ ያለ ምግብ ከሚማሰልበት መንገድ ጋር ተነጻጽሯል። አ.ት፡ “የእግዚአብሔር መንፈስ በሳምሶን ላይ ተጽዕኖ ማድረግ ጀመረ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ማህነህ ዳን -- ኤሽታኦል
ማህነህ ዳን ለዘለቄታቸው የሚኖሩበትን በሚፈልጉበት ወቅት የዳን ነገድ በጊዜያዊነት የሰፈሩበት ቦታ ስም ነው። ኤሽታኦል የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ጾርዓ
የዚህን ከተማ ስም በመሳፍንት 13፡2 በተረጎምክበት መልኩ ተርጉመው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 14

1 ሳምሶንም ወደ ተምና ወረደ፣ በዚያም ከፍልስጥኤማውያን ሴቶች ልጆች አንዲት ሴት አየ። 2 ከዚያ በተመለሰ ጊዜ፣ ለአባቱና ለእናቱ እንዲህ ሲል ነገራቸው፣ “በተምና ከፍልስጥኤማውያን ሴቶች ልጆች መካከል አንዲት ሴት አየሁ። ሚስቴ እንድትሆነኝ አሁን እርስዋን አምጡልኝና አጋቡኝ። 3 ነገር ግን እንዲህ አሉት፣ “ከዘመዶችህ ሴቶች ልጆች ወይም ከሕዝባችን ሁሉ መካከል ሴት የለምን? ካልተገረዙት ከፍልስጥኤማውያን ሚስት ለመውሰድ ትሄዳለህን?” ሳምሶንም ለአባቱ እንዲህ አለው፣ “እርስዋን አምጣልኝ፣ እርስዋን ባየኋት ጊዜ ደስ አሰኝታኛለችና።” 4 ነገር ግን አባቱና እናቱ ይህ ነገር የመጣው ከእግዚአብሔር እንደሆነ አላወቁም፣ እርሱ ከፍልስጥኤማውያን ጋር ግጭት ለመፍጠር ይፈልግ ነበርና። በዚያን ጊዜ ፍልስጥኤማውያን እስራኤልን ይገዙ ነበርና። 5 ከዚያም ሳምሶን ከአባቱና ከእናቱ ጋር ወደ ተምና ወረዱ፣ እነርሱም በተምና ወዳለው ወደ ወይኑ አትክልት ስፍራ መጡ። ከዚያም ከአንበሳ ደቦሎች መካከል አንዱ ተነስቶ መጣና በእርሱ ላይ አገሳበት። 6 የእግዚአብሔር መንፈስ በድንገት በእርሱ ላይ ወረደ፣ ትንሽ የፍየል ጠቦት እንደሚቆራርጥ እንዲሁ አንበሳውን በቀላሉ ቈራረጠው፣ በእጁም ምንም ነገር አልያዘም ነበር። ነገር ግን ያደረገውን ነገር ለአባቱ ወይም ለእናቱ አልነገራቸውም። 7 እርሱም ሄደና ከሴቲቱ ጋር ተነጋገረ፣ እርስዋንም ባያት ጊዜ ሳምሶንን ደስ አሰኘችው። 8 ከጥቂትም ቀን በኋላ ሊያገባት ተመለሰ፣ የአንበሳውንም በድን ያይ ዘንድ ከመንገድ ዘወር አለ። በአንበሳ በድን ትራፊ ውስጥ የንብ መንጋ ሰፍሮበት ነበር፣ ማርም ነበረበት። 9 ማሩንም በእጁ ወስዶ መንገድ ለመንገድ እየበላ ሄደ። ወደ አባቱና ወደ እናቱ በመጣ ጊዜ፣ ለእነርሱም ሰጣቸውና እነርሱም በሉ። ነገር ግን ማሩን የወሰደው ከአንበሳ በድን ትራፊ ውስጥ እንደ ሆነ አልነገራቸውም። 10 የሳምሶን አባትም ሴቲቱ ወደ ነበረችበት ወረደ፣ ሳምሶንም በዚያ ግብዣ አደረገ፣ ይህን ማድረግ የወጣት ወንዶች ወግ ነበርና። 11 የእርስዋ ዘመዶች ባዩት ጊዜ፣ ከእርሱ ጋር ይሆኑ ዘንድ ሌሎች ሠላሳ ጓደኞች አመጡለት። 12 ሳምሶንም ለእነርሱ እንዲህ አላቸው፣ “አሁን እንቆቅልሽ ልንገራችሁ። ከእናንተ ውስጥ አንዱ ሰው እንቆቅልሹን ማግኘት ቢችልና በሰባቱ የግብዣ ቀኖች ውስጥ መልሱን ቢነግረኝ፣ ሠላሳ የቀጭን በፍታ ቀሚስና ሠላሳ የክት ልብስ እሰጠዋለሁ። 13 ነገር ግን እናንተ መልሱን ልትነግሩኝ ካልቻላችሁ፣ ሠላሳ የቀጭን በፍታ ቀሚስና ሠላሳ የክት ልብስ ትሰጡኛላችሁ።” እነርሱም እንዲህ አሉት፣ “እንሰማው ዘንድ እንቆቅልሽህን ንገረን።” 14 እርሱም እንዲህ አላቸው፣ “ከበላተኛው ውስጥ መብል ወጣ፤ ከብርቱም ውስጥ ጣፋጭ ወጣ።” ነገር ግን የእርሱ እንግዶች በሦስት ቀን ውስጥ መልሱን ሊያገኙት አልቻሉም። 15 በአራተኛውም ቀን ለሳምሶን ሚስት እንዲህ አሏት፣ “የእንቈቅልሹን መልስ እንዲነግረን ባልሽን አግባቢልን፣ አለዚያ ግን እንቺንና የአባትሽን ቤት በእሳት እናቃጥላለን። ወደዚህ የጠራችሁን ድሃ ልታደርጉን ነውን።” 16 የሳምሶን ሚስት በፊቱ ማልቀስ ጀመረች፤ እንዲህም አለችው፣ “ይህን ሁሉ ያደረግኸው እኔን ስለምትጠላኝ ነው! አንተ አትወደኝም። ከሕዝቤ ውስጥ ለአንዳንዶቹ እንቈቅልሽ ነግረሃቸዋል፣ ነገር ግን መልሱን ለእኔ አልነገርኸኝም።” ሳምሶንም እንዲህ አላት፣ “ወደዚህ ተመልከቺ፣ ለአባቴና ለእናቴ ካልነገርኋቸው፣ ለአንቺ ልነግርሽ ይገባልን?” 17 ግብዣቸው በሚቆይበት በሰባቱም ቀናት ውስጥ በፊቱ አለቀሰች። መልሱንም በሰባተኛው ቀን ነገራት ምክንቱም እጅግ በጣም አጥብቃ ስለነዘነዘችው ነው። መልሱንም ለሕዝቧ ዘመዶች ነገረቻቸው። 18 በሰባተኛው ቀን ፀሐይ ከመግባትዋ በፊት የከተማይቱ ሰዎች እንዲህ አሉት፣ “ከማር የበለጠ የሚጣፍጥ ምንድን ነው? ከአንበሳስ የበለጠ የሚበረታ ምንድን ነው?” ሳምሶንም እንዲህ አላቸው፣ “በጊደሬ ባታርሱ ኖሮ፣ ለእንቈቅልሼ መልስ ባላገኛችሁ ነበር።” 19 በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ በድንገት በሳምሶን ላይ በኃይል ወረደ። ሳምሶንም ወደ አስቀሎና ወረደና ከሕዝቡ መካከል ሠላሳ ሰዎችን ገደለ። እርሱም የለበሱትን ሁሉ ከገፈፈ በኋላ ልብሳቸውን በሙሉ ወስዶ እንቈቅልሹን ለመለሱለት ሰዎች ሰጣቸው። እርሱም በጣም ተናደደና ወደ አባቱ ቤት ወጣ። 20 የሳምሶን ሚስት ግን በጣም ቅርብ ለሆነው ጓደኛው ተሰጠች።

Judges 14:1

ሳምሶን ወደ ተምና ወረደ

“ወረደ” የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው የአባቱ ቤት ካለበት ተምና ዝቅ ባለ ስፍራ ስለሚገኝ ነው። ተምና በሶሬቅ ሸለቆ የሚገኝ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ከፍልስጥኤማውያን ሴቶች ልጆች አንዷ

“ሴት ልጅ” የሚለው ቃል ያላገባችን ወጣት ሴት የሚያመለክት የትህትና አገላለጽ ነው። አ.ት፡ “በፍልስጥኤም ሰዎች መካከል አንዲት ያላገባች ሴት” ወይም “ፍልስጥኤማዊት ልጃገረድ”

አሁን ሚስት እንድትሆነኝ አምጡልኝ

ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ሳምሶን ወላጆቹ የፍስጥኤማዊቷ ሴት ወላጆችን ለጋብቻ እንዲጠይቁለት ግድ እያላቸው ነው። አ.ት፡ “ሚስት እንድትሆነኝ አሁን አጋቡኝ” ወይም “እርሷን እንዳገባት ቅድመ ዝግጅት አድርጉልኝ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Judges 14:3

በዘመዶችህ መካከል ወይም በሕዝባችን ሁሉ ሴት ልጆች መካከል ሴት ስለጠፋች ነው?

ይህንን ጥያቄ ሳምሶንን የሚጠይቁት ከገዛ ሕዝባቸው መካከል ሚስት ሊያገኙለት እንደሚችሉ አሳብ ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ በመግለጫነት ሊጻፍ ይችላል። አ.ት፡ “በርግጥ ማግባት እንድትችል በሕዝብህ መካከል ሴቶች አሉ” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

የዘመዶችህ ሴቶች ልጆች

“ሴት ልጅ” የሚለው ቃል ያላገባችን ወጣት ሴት የሚያመለክት የትህትና አገላለጽ ነው። አ.ት፡ “በዘመዶችህ መካከል ካላገቡት ሴቶች አንዷን”

ካልተገረዙት ከፍልስጥኤማውያን ሚስት ልታገባ ነው?

ይህ ጥያቄ የተጠየቀው ሳምሶንን ለመገሰጽ ነው። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊጻፍ ይችላል። ወላጆቹ ፍልስጥኤማዊት እንዲያገባ ያልፈለጉበትን ምክንያት ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። አ.ት፡ “የፍልስጥኤም ሰዎች እግዚአብሔርን ስለማያመልኩ በእርግጠኝነት ፍልስጥኤማዊት ማግባት አይኖርብህም”። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እና የሚለውን ተመልከት)

እርሷን አምጡልኝ

ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ሳምሶን ስለ ጋብቻው የፍልስጥኤማዊቷን ሴት ወላጆች እንዲያነጋግሩለት ወላጆቹን ግድ እያላቸው ነበር። አ.ት፡ “አሁን ሚስት እንድትሆነኝ አዘጋጁልኝ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ታስደስተኛለች

ይህ ማለት ሴቲቱ ቆንጆ እንደ ሆነች ሳምሶን ያስባል። “ቆንጆ በመሆኗ ደስ ብሎኛል” ወይም “እርሷ ቆንጆ ናት”

ይህ ጉዳይ

ይህ የሚያመለክተው ፍልስጥኤማዊቱን ሴት ለማግባት ሳምሶን ያቀረበውን ጥያቄ ነው።

ግጭት ለመፍጠር ፈልጓልና

“እርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Judges 14:5

ሳምሶን ወደ ተምና ወረደ
“ወረደ” የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው የአባቱ ቤት ካለበት ተምና ዝቅ ባለ ስፍራ ስለሚገኝ ነው። ተምና በሶሬቅ ሸለቆ የሚገኝ ከተማ ነበር። የዚህን ከተማ ስም በመሳፍንት 14፡1 እንዳደረግኸው በተመሳሳይ መንገድ ተርጉመው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

እነሆ፣ አንድ የአንበሳ ደቦል መጣበት
እዚህ ጋ “እነሆ” የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው የአንባቢዎችን ትኩረት በታሪኩ ውስጥ ወደሚመጣው አስደናቂ ሁነት ለመሳብ ነው። “መጣበት” የሚለው ቃል ትርጉሙ አንበሳው ወደ እርሱ ቀርቧል ማለት ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

እያገሳበት ነበር
“አስፈራራው”። ይህ አንበሳ አንድን እንስሳ ለማጥቃት በሚያስፈራራበት ጊዜ የሚያሰማው ዓይነት ድምፅ ነው።

የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ላይ በድንገት መጣበት
“መጣበት” የሚለው ቃል ትርጉሙ የእግዚአብሔር መንፈስ ሳምሶን ላይ ተጽዕኖ አሳደረበት ማለት ነው። በዚህ ጉዳይ፣ በኃይል አበረታው። አ.ት፡ “የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል አበረታው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ቆራረጠው
ለሁለት ቆራረጠው

በእጁ ምንም ነገር ሳይኖር
እዚህ ጋ፣ በእጁ ምንም ነገር ሳይኖር የሚለው መግለጫ የጦር መሣሪያ አልያዘም ነበር ለሚለው አጽንዖት ለመስጠት ነው። አ.ት፡ “የጦር መሣሪያ አልነበረውም”

Judges 14:7

ሳምሶንን አስደሰተችው
ይህ ማለት በጣም ቆንጆ እንደሆነች አስቧል። አ.ት፡ “በቁንጅናዋ ተደስቷል” ወይም “በጣም ቆንጆ እንደ ነበረች አስቧል”

ፈቀቅ አለ
ይህ ማለት፣ አንድ ነገር ለማድረግ መንገዱን ትቶ ወጣ አለ። አ.ት፡ “መንገዱን ትቶ ወጣ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ሬሳ
የሞተ አካል

እነሆ፣ ንቦች ወረዉት ነበር
እዚህ ጋ “እነሆ” የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው የአንባቢዎችን ትኩረት በታሪኩ ውስጥ ወደሚመጣው አስደናቂ ሁነት ለመሳብ ነው። አ.ት፡ “ንቦች ወረዉት አገኘው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

መውረር
እጅግ የበዙ ነፍሳት

አፍሶ
“ሰብስቦ”

Judges 14:10

የሳምሶን አባት ሴቲቱ ወደነበረችበት ወረደ
“ወረደ” የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው የሳምሶን አባት ከሚኖርበት ተምና ዝቅ ባለ ስፍራ የሚገኝ መሆኑን ለመግለጽ ነው። አ.ት፡ “የሳምሶን አባት ሴቲቱ ወደምትኖርበት ሄደ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የወጣቶቹ ልማድ
ይህ የጋብቻ ልማድ እንደ ነበረ መግለጹ ጠቃሚ ይሆን ይሆናል። አ.ት፡ “የሚያገቡ ወጣቶች ልማድ”

ሠላሳ ጓደኞቻቸው
“30 ጓደኞቻቸው” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

Judges 14:12

ዕንቆቅልሽ
ተጫዋቾቹ ለአስቸጋሪው ጥያቄ መልስ ማግኘት የሚኖርባቸው ውድድር

መፍታት የሚችል
ይህ ማለት የዕንቆቅልሹን ትርጉም መንገር የሚችል ማለት ነው። አ.ት፡ “ትርጉሙን መንገር የሚችል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ሠላሳ የላይነን ቀሚስና ሠላሳ ሙሉ ልብስ
“30 የላይነን ቀሚሶችንና 30 ሙሉ ልብስ” (ቁጥሮችን ተመልከት)

ልትነግሩኝ ካልቻላችሁ ግን
እዚህ ጋ “እናንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተው በግብዣው ላይ የነበሩትን እንግዶች ነው።

ላይነን
የልብስ ዓይነት

Judges 14:14

ከበላተኛው ውስጥ የሚበላ ነገር
“ከበላተኛው ውስጥ የሚበላ ነገር ተገኘ” ወይም “አንድ የሚበላ ነገር ከአንድ ከሚበላ ነገር ውስጥ ወጣ”

በላተኛው
“በላተኛው” የሚለው ስም ወደ ግሣዊ ሐረግ መነገር ይችላል። አ.ት፡ “የሚባላው ነገር”

ከብርቱው ውስጥ የሚጣፍጥ ነገር
“ከብርቱው ውስጥ የሚጣፍጥ ነገር ወጣ” ወይም “ብርቱ ከሆነው ነገር ውስጥ ጣፋጭ የሆነ ነገር ወጣ”

ብርቱው
ይህ የሚያመለክተው ብርቱ የሆነን ነገር ነው። አ.ት፡ “ብርቱው ነገር”

እንግዶቹ
“በግብዣው ላይ የነበሩት ሰዎች”

መልሱን ማግኘት አልቻሉም
እዚህ ጋ፣ የዕንቆቅልሹን መልስ መንገር እንደ አንዳች የተደበቀና እንግዶቹ ፈልገው ሊያገኙት እንደሚያስፈልጋቸው ነገር ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “መልሱን መንገር አልቻሉም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Judges 14:15

አራተኛው ቀን
“ቀን 4”

ማታለል
እነርሱ ሊያደርጉት የማይፈልጉትን ነገር እንዲያደርግ አንድን ሰው ማሳሳት ወይም ማሞኘት

የአባትሽን ቤት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ ትክክለኛውን ቤት ያመለክታል። አ.ት፡ “አባትሽና ቤተሰቡ የሚኖሩበትን ቤት” ወይም 2) “ቤት” የሚያመለክተው በውስጡ የሚኖሩትን ሰዎች ነው። አ.ት፡ “ቤተሰብሽ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እናቃጥለዋለን
“እናቃጥለዋለን” የሚለው ቃል ትርጉም አንድን ነገር ሙሉ በሙሉ ማቃጠል ማለት ነው። አንድ ሰው “ከተቃጠለ” ያ ሰው ተቃጥሎ ሞቷል ማለት ነው።

የጋበዛችሁን ልታደኸዩን ነው?
ክፉ ስለማድረጓ ለመክሰስ ይህንን ይጠይቋታል። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊጻፍ ይችላል። አ.ት፡ “እዚህ የጠራሽን ድኻ ልታደርጊን ነው!”

ድኻ ልታደርጊን
ዕንቆቅልሹን ካልፈቱና አዲስ ልብሶች ከገዙለት ድኻ ይሆናሉ። አ.ት፡ “አዲስ ልብሶች እንድንገዛለት በማስገደድ ድኻ ልታደርጊን ነው”

Judges 14:16

ፈጽሞ ጠልተኸኛል! አትወደኝም
የሳምሶን ሚስት አጽንዖት ለመስጠት ያህል ሁለት ጊዜ የምትናገረው በመሠረቱ አንድ ነው። አ.ት፡ “በእውነት ፈጽሞ አትወደኝም”

ዕንቆቅልሽ
ተጫዋቾቹ ለአስቸጋሪው ጥያቄ መልስ ማግኘት የሚኖርባቸው ውድድር

ወዲህ ተመልከቱ
ይህ ጥቅም ላይ የዋለው የአንድን ሰው ትኩረት ለማግኘት ነው። እዚህ ጋ “ተመልከቱ” ማለት “አድምጡ” ማለት ነው። አ.ት፡ “አድምጡኝ” ወይም “የምናገረውን ልብ በሉ”

ለአባቴ ወይም ለእናቴ ካልነገርኳቸው ላንቺ መንገር አለብኝ?
መልሱን እንዲነግራት ግድ ስላለችው ሳምሶን እየገሰጻት ነበር። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሆኖ ሊጻፍ ይችላል። አ.ት፡ “ለአባቴ ወይም ለእናቴ እንኳን አልነገርኳቸውም፤ አልነግርሽም” ወይም “ከአንቺ ይልቅ ቅርቤ ለሆኑት ለወላጆቼ እንኳን አልነገርኳቸውምና እንድነግርሽ ግድ ልትዪኝ አይገባም”

ግብዣቸው በሚቆይባቸው በሰባቱ ቀናት
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች 1) “በግብዣቸው በሰባቱ ቀናት” ወይም 2) “ከሰባቱ የግብዣቸው ቀናት በቀሩት”

ሰባተኛው ቀን
“ቀን 7”

በጣም ነዘነዘችው
እዚህ ጋ “ነዘነዘችው” የሚለው ቃል ትርጉም “ግድ አለችው” የሚል ይሆናል። አ.ት፡ “እንዲነግራት መጨቅጨቋን ቀጠለች” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Judges 14:18

የከተማዪቱ ሰዎች
ይህ የሚያመለክተው የሳምሶን ሚስት ዘመዶችን ነው። ይህ በግልጽ መነገር ይችላል። አ.ት፡ “ወጣቶቹ” ወይም “ዘመዶቿ”

ሰባተኛው ቀን
“ቀን 7”

ከማር ይልቅ የሚጣፍጥ ምንድነው? ከአንበሳስ ይልቅ የሚበረታ ምንድነው?
ይህ የዕንቆቅልሹ መልስ ነው። በጥያቄ ፈንታ እንደ መግለጫ ሆኖ መጻፍ ይኖርበት ይሆናል። አስፈላጊ ከሆነ ተጨማሪ መረጃ በማከል ይህ ከዕንቆቅልሹ ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አ.ት፡ “ማር ጣፋጭ ነው፣ አንበሳም ብርቱ ነው” ወይም “ማር ጣፋጭ ነው፣ እርሱም ከአንበሳ ውስጥ ወጣ” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እና የሚለውን ተመልከት)

በጥጃዬ ባታርሱ ኖሮ
ሳምሶን መልሱን ለማግኘት ሚስቱን መጠቀማቸውን አንድ ሰው የራሱን እርሻ ለማረስ የሌላውን ሰው ጥጃ ከመጠቀሙ ጋር ያነጻጽራል። አ.ት፡ “በሚስቴ ባትጠቀሙ ኖሮ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ማረስ
ማረስ ማለት ዐፈሩን ለዘር ለማዘጋጀት እንስሳን በመጠቀም ስለታማውን ብረት ዐፈር ውስጥ አስገብቶ መሳብ ነው።

Judges 14:19

በሳምሶን ላይ በኃይል መጣበት
“መጣበት” የሚለው ቃል ትርጉሙ የእግዚአብሔር መንፈስ ሳምሶን ላይ ተጽዕኖ አሳደረበት ማለት ነው። በዚህ ጉዳይ፣ በኃይል አበረታው። አ.ት፡ “የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል አበረታው” ወይም “ሳምሶንን በጣም ኃይለኛ አደረገው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ከሰዎቻቸው ሠላሳውን ገደለ
“ከሰዎቻቸው 30 ገደለ” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ከሰዎቻቸው
በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች”

ብዝበዛ
አብዛኛውን ጊዜ ከውጊያ ወይም ከጦርነት በኋላ በኃይል የሚወሰዱ ነገሮች

ልብሶቻቸውን
እነዚህ ከአስቀሎና የወሰዳቸው ብዝበዛዎቹ ነበሩ። አ.ት፡ “የወሰዳቸውን ሙሉ ልብሶች”

በቁጣ ነደ
“በጣም ተናደ”

ወደ አባቱ ቤት ወጣ
እዚህ ጋ የአባቱ ቤት ከሚገኝበት አካባቢ ሳምሶን የነበረበት ተምና የመሬት አቀማመጡ ዝቅ ያለ ስለነበረ “ወጣ” የሚለው ቃል ጥቅም ላይ ውሏል።

የሳምሶን ሚስት ለቅርብ ጓደኛው ተሰጠች
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የሚስቱ አባት እርሷን ለቅርብ ጓደኛው ሰጣት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የቅርብ ጓደኛ
“ከሌላው የቀረበ ጓደኛ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 15

1 ከጥቂት ቀናትም በኋላ በስንዴ መከር ጊዜ፣ ሳምሶን የፍየል ጠቦት ይዞ ሚስቱን ሊጠይቅ ሄደ። ለራሱም እንዲህ አለ፣ “ወደ ሚስቴ ወደ ጫጕላው ቤት
ልግባ።” ነገር ግን አባትዋ ወደ ውስጥ እንዳይገባ ከለከለው። **2** አባትዋም እንዲህ አለ፣ “እኔ በእርግጠኝነት የጠላሃት መሰለኝ፣ ስለዚህም ለጓደኛህ ሰጠኋት።
የእርስዋ ታናሽ እኅት ከርስዋ የበለጠች ቆንጆ ናት፣ አይደለችም እንዴ? በእርስዋ ፋንታ ታናሽዋን ውሰዳት።” **3** ሳምሶንም ለእነርሱ እንዲህ አላቸው፣ “ከእንግዲህ
ወዲህ በፍልስጥኤማውያን ላይ ጕዳት ባደረስሁባቸው ጊዜ እኔ ንጹሕ ነኝ።” **4** ሳምሶንም ሄደና ሦስት መቶ ቀበሮዎች ያዘ፣ ሁለት ሁለቱንም ቀበሮዎች በአንድ
ላይ በጅራታቸው አሰራቸው። ከዚያም ችቦዎችን ወስዶ በእያንዳንዱ ጥንድ በሁለቱም ጅራቶች መካከል አሰራቸው። **5** ችቦውንም በእሳት ባቀጣጠለው ጊዜ፣
ቀበሮዎቹን በቆመው በፍልስጥኤማውያን እህል መካከል እንዲሄዱ አደረጋቸው፣ የእህሉን ነዶና በእርሻ ውስጥ የቆመውንም እህል፣ ከወይኑ አትክልት ስፍራና
ከወይራውም ተክል ጋር አቃጠሉት። **6** ፍልስጥኤማውያንም እንዲህ በማለት ጠየቁ፣ “ይህን ያደረገው ማን ነው?” እነርሱም “ይህን ያደረገው የተምናዊው
አማች ሳምሶን ነው፣ ምክንያቱም ተምናዊው የሳምሶንን ሚስት ወስዶ ለጓደኛው ሰጥቶአታልና” አሉ። ፍልስጥኤማያንም ሄደው እርስዋንና አባትዋን በእሳት
አቃጠሉ። **7** ሳምሶንም “እናንተ ይህንን ካደረጋችሁ፣ እኔ እበቀላችኋለሁ፣ እኔ የማርፈው ይህን ካደረግሁ በኋላ ነው” አላቸው። **8** እርሱም ዳሌአቸውንና
ጭናቸውን ቆራረጣቸውና በታላቅ አገዳደል ገደላቸው። ከዚያም ወርዶ በኤጣም ዓለት ባለው ዋሻ ውስጥ ተቀመጠ። **9** የዚያን ጊዜ ፍልስጥኤማውያን ወጡና
በይሁዳ ጦርነት ለማካሄድ ተዘጋጁ፣ ሰራዊታቸውንም በሌሒ ውስጥ አሰፈሩ። **10** የይሁዳም ሰዎች እንዲህ አሉ፣ “እኛን ለመውጋት የመጣችሁት ለምንድን
ነው?” እነርሱም እንዲህ አሉ፣ “የምንወጋችሁ ሳምሶንን ለመያዝ ነው፣ እርሱ በእኛ ላይ እንዳደረገው እኛም በእርሱ ላይ ልናደርግበት ነው።” **11** ሦስት ሺህ
የይሁዳ ሰዎችም በኤጣም ዓለት ወዳለው ዋሻ ወረዱና፣ ለሳምሶን እንዲህ አሉት፣ “ፍልስጥኤማውያን በእኛ ላይ ገዢዎች እንደሆኑ አታውቅምን? ይህ በእኛ
ላይ ያደረግኸው ነገር ምንድን ነው?” ሳምሶንም ለእነርሱ እንዲህ አላቸው፣ “እነርሱ በእኔ ላይ አደረጉብኝ፣ እኔም በእነርሱ ላይ አደረግሁባቸው።” **12** እነርሱም
ለሳምሶን እንዲህ አሉት፣ “አንተን አስረን ለፍልስጥኤማውያን እጅ አሳልፈን ልንሰጥህ መጥተናል።” ሳምሶንም እንዲህ አላቸው፣ “እናንተ ራሳችሁ
እንደማትገድሉኝ ማሉልኝ።” **13** እነርሱም እንዲህ አሉት፣ “አንገድልህም፣ በገመድ አስረን ብቻ ለእነርሱ አሳልፈን እንሰጥሃለን። እንደማንገድልህ ቃል
እንገባልሃለን።” ከዚያም በሁለት አዲስ ገመዶች አሰሩትና ከዓለቱ ውስጥ አወጡት። **14** ወደ ሌሒ በመጣ ጊዜ፣ ፍልስጥኤማውያን እየጮሁ መጡ፣
አገኙትም። የዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ላይ በኃይል ወረደበት። ክንዶቹ የታሰሩበት ገመዶችም በእሳት እንደ ተቃጠለ የተልባ እግር ፈትል
ከእጆቹ ላይ ወደቁ። **15** ሳምሶንም አዲስ የአህያ መንጋጋ አገኘ፣ እጁንም ዘርግቶ አነሳውና በእርሱ አንድ ሺህ ሰዎች ገደለ። **16** ሳምሶንም እንዲህ አለ፣ “በአህያ
መንጋጋ ክምር በክምር ላይ አድርጌአቸዋለሁ፣ በአህያ መንጋጋ አንድ ሺህ ሰዎች ገድያለሁ።” **17** ሳምሶንም መናገሩን በፈጸመ ጊዜ፣ የአህያ መንጋጋውን ከእጁ
ጣለው፣ ያም ስፍራ ራማትሌሒ ተብሎ ተጠራ። **18** ሳምሶን በጣም ተጠምቶ ነበርና ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ጮኸ፣ “አንተ ይህን ታላቅ ድል
ለአገልጋይህ ሰጥተሃል፣ ነገር ግን አሁን በጥም እሞታለሁ፣ ባልተገረዙትም ሰዎች እጅ እወድቃለሁ።” **19** እግዚአብሔርም በሌሒ ያለውን ክፍት ስፍራ ሰንጥቆ
ከፈተው፣ ከእርሱም ውኃ ወጣ።እርሱም በጠጣ ጊዜ፣ ብርታቱ ተመለሰና ተጠናከረ። ስለዚህ የዚያ ቦታ ስም ዓይንሀቆሬ ተብሎ ተጠራ፣ እስከ ዛሬ ድረስ በሌሒ
ይገኛል። **20** ሳምሶን በፍልስጥኤማውያን ዘመን በእስራኤል ላይ ለሀያ ዓመት ፈረደ።

Judges 15:1

ራሱን ጠየቀ
ይህ ማሰብን ያመለክታል። አ.ት፡ “በራሱ አሰበ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ወደ ሚስቴ ክፍል እሄዳለሁ
ሳምሶን ከሚስቱ ጋር ለመተኛት አስቦ ነበር። ይህ በግልፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እብረን እንድንተኛ ወደ ሚስቴ ክፍል እሄዳለሁ”

እንዲገባ አልፈቀደለትም
ሳምሶን ለራሱ ከተናገረው ውስጥ “የእርሷ ክፍል” የሚለውን ሐረግ መረዳት ይቻላል። ይህ እዚህ ጋር መደገም ይችላል። አ.ት፡ “ወደ ክፍሏ እንዲገባ አልፈቀደለትም”

ስለዚህ ለጓደኛህ ሰጠኋት
ይህ ማለት ሚስት እንድትሆነው ለጓደኛው ሰጣት ማለት ነው። ይህ በግልፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ከእርሱ ጋር እንድትጋባ ለጓደኛህ ሰጠኋት”

አይደለችምን?
ይህን ጥያቄ የሚጠይቀው ሳምሶን ከእርሱ ጋር ሊስማማ እንደሚገባ ለማመልከት ነው። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊጻፍ ይችላል። አ.ት፡ “እንደምትስማማ ተስፋ አደርጋለው”። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

በምትኳ ውሰዳት
ሳምሶን እንደ ሚስቱ እንዲወስዳት አስተያየት እየሰጠ ነው። ይህ በግልፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በእርሷ ምትክ ሚስት እንድትሆንህ ውሰዳት”

Judges 15:3

ፍልስጥኤማውያንን በምጎዳቸው ጊዜ ንጹሕ እሆናለሁ
ሳምሶን፣ ፍልስጤማውያን ስለበደሉት ቢያጠቃቸው ንጹሕ እንደሚሆን ያስባል። ይህ በግልፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ስለበደሉኝ ፍልስጤማውያንን ብጎዳቸው ንጹሕ እሆናለሁ”

ሦስት መቶ ቀበርዎች
“300 ቀበርዎች”

ቀበሮዎች
ቀበሮዎች እንደ ውሻ ያሉ ረጃጅም ጭራ ያላቸው፣ በጎጆ የሚኖሩ ወፎችንና ሌሎች ትናንሽ እንስሶችን የሚመገቡ እንስሶች ናቸው።

እያንዳንዱ ጥንድ
ጥንድ ማለት የትኛውም ነገር ሁለት ሆኖ ሲገኝ ነው፤ እንደ ሁለት ቀበርዎች ወይም ሁለት ጭራዎች።

ጭራ ከጭራ ጋር
“በጭራዎቻቸው”

ችቦዎች
ችቦ በአንደኛው ጫፉ ተቀጣጣይ ነገር የተደረገበት የእንጨት ጭራሮ ነው፤ ችቦ በአብዛኛው ሊሎች ነገሮችን ለመለኮስ ወይም ብርሃን እንዲሰጥ የሚያዝ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Judges 15:5

የቆመ እህል
በእርሻ ውስጥ ገና በአገዳው ላይ እያደገ ያለ እህል

የተከመረ እህል
ከታጨደ በኋላ ተሰብስበው የተከመሩ የእህል ነዶዎች

ተክሎች
የፍራፍሬ ዛፎች የሚበቅሉበት ቦታ ነው።

የተምናዊው አማች
የአንድ ሰው የሴት ልጁ ባል ለሰውየው “አማች” ነው።

ተምናዊው
ይህ ከተምናህ የሆነ ሰው ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የሳምሶንን ሚስት ወስዶ ለጓደኛው ሰጠው
የሳምሶን ሚስት አባት እርሷን የሳምሶን ጓደኛ እንዲያገባት ሰጠው። ይህ በግልጽ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የሳምሶንን ሚስት ወስዶ የሳምሶንን ጓደኛ እንድታገባው ፈቀደለት”

ፈፅመው አቃጠሏቸው
“ፈፅመው አቃጠሏቸው” የሚለው ሐረግ አንድን ነገር ጨርሶ ማቃጠል ማለት ነው። አንድ ሰው “ፈፅሞ ተቃጠለ” ማለት ያ ሰው ተቃጥሎ ሞተ ማለት ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Judges 15:7

እነርሱን አላቸው
“ፍልስጤማውያኑን አላቸው”

እናንተ ይህንን ካደረጋችሁ
“ይህንን ስላደረጋችሁ”

ሸንጥና ታፋቸውን ቆራረጣቸው
እዚህ ጋ “ሸንጥና ታፋ” ሙሉ ሰውነትን ያመለክታል። ይህ ሳምሶን ፍልስጥኤማውያንን እንዴት እንደገደላቸው የሚያሳይ ጉልህ ገለጻ ነው። አ.ት፡ “ሰውነታቸውን ቆራረጠው”።

ወደ ታች ወረደ
እዚህ ጋ “ወደታች ወረደ” የሚለው ሐረግ ከከፍታ መውረዱን ማመልከቱ ላይሆን ይችላል፤ እንዲያውም አንድ ሰው ወደ ሌላ ቦታ መጓዙን መግለጫ መንገድ ነው። አ.ት፡ “ሄደ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ዋሻ
በኮረብታ ወይም ተራራ ውስጥ ያለ ክፍት ቦታ

ገደል
ከፍ ያለ ዐለታማ ኮረብታ ወይም የተራራ ጎን

ኢታም
ይህ በኢየሩሳሌም አቅራቢያ ያለ የዐለታማ ኮረብታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Judges 15:9

በይሁዳ - ፍልስጥኤማውያኑ ወደ ላይ ወጡ ...
እዚህ ጋ “ወደ ላይ ወጡ” የሚለው ሐረግ ጥቅም ላይ የዋለው ፍልስጥኤማውያኑ እነርሱ ይጓዙበት ከነበሩበት ቦታ በከፍታ ወደሚበልጠው ይሁዳ ስለመጡ ነው።

ለጦርነት ተዘጋጅተው
“ራሳቸውን ለጦርነት አዘጋጅተው”

ሌሒ
ይህ በይሁዳ ያለ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

እርሱ እንዳደረገብን ልናደርግበት ነው
ፍልስጥኤማውያኑ ሳምሶን ብዙዎቹን ፍልስጥኤማውያን እንደገደለ እንዴት እንደሚገሉት እያነጻጸሩ ነው። አ.ት፡ “ብዙ ሰዎቻችንን እንደገደለ ግደሉት”

Judges 15:11

የይሁዳ ሶስት ሺህ ወንዶች
“3000 የይሁዳ ወንዶች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

በኢታም ገደል ያለ ዋሻ
ይህንን ሐረግ በመሳፍንት 15:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ፍልስጥኤማውያን በእኛ ላይ ገዢዎች እንደሆኑ አታውቅም? በእኛ ላይ ያደረከው ይህ ምንድን ነው?
የይሁዳ ሰዎች እነዚህን ጥያቄዎች የሚጠይቁት ሳምሶንን ለመገሰጽ ነው። እነዚህ ጥያቄዎች እንደ መግለጫ ሊጻፉ ይችሉ ይሆናል። አ.ት፡ “ፍልስጤማውያን በኛ ላይ ገዢዎች እንደሆኑ ታውቃለህ ነገር ግን አንተ የምታደርገው እንዳልሆኑ ያህል ነው። ያደረከው ነገር ከባድ ጉዳት አምጥቶብናል።” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

አደረጉብኝ፥ ስለዚህ እኔም አደረግሁባቸው
ሳምሶን ሚስቱን እንዴት እንደገደሉበትና እርሱ በበቀል እንዴት እንደገደላቸው እያመለከተ ነው። ይህ በግልጽ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሚስቴን ገድለዋታል፤ ስለዚህ እኔም ገደልኳቸው።”

Judges 15:12

የፍልስጥኤማውያን እጅ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚያመለክተው ኃይልን ነው። አ.ት፡ “የፍልስጥኤማውያኑ መቆጣጠር” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእጃቸው አሳልፈን ልንሰጥህ
ይህ ማለት አንድን ሰው በሌላ ሰው ቁጥጥር ስር እንዲሆን ማድረግ ማለት ነው። አ.ት፡ “ለፍልስጥኤማውያኑ ልንሰጥህ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ከዐለቱ ወደላይ
ይህ ሳምሶን በመሳፍንት 15:8 ላይ ሄዶበት የነበረውን በኢታም ገደል የሚገኘውን ዋሻ ያመለክታል። እዚህ ጋ “ወደ ላይ” የሚለው ቃል ከዋሻው አውጥተው አምጥተውታል ማለት ነው። አ.ት፡ “በትልቁ ዐለት ውስጥ ካለው ዋሻ አውጥተው”።

Judges 15:14

በመጣ ጊዜ
ሳምሶን ብቻውን እልተጓዘም፤ በገመድ ባሰሩት ሰዎች እየተመራ ነበር። አ.ት፡ “በመጡ ጊዜ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሌሒ
ይህ በይሁዳ የሚገኝ ከተማ ስም ነው። ይህንን በመሳፍንት 15፡9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

በእርሱ ላይ በኃይል መጣበት
“በላዩ ላይ መጣበት” የሚለው ሐረግ የእግዚአብሔር መንፈስ ሳምሶን ላይ ተጽዕኖ አሳድሯል ማለት ነው። በዚህ ቦታ፤ በጣም ብርቱ አድርጎታል። አ.ት፡ “ሳምሶንን በጣም ብርቱ አደረገው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በክንዱ ላይ የነበሩት ገመዶች እንደ ተቃጠለ ፈትል ሆኑ
ሳምሶን እጁ የታሰረበትን ገመድ በቀላሉ በጣጥሶታል። ደራሲው ገመዱን እንዴት በቀላሉ እንደበጣጠሰው ለመግለጽ እንደተቃጠለ ፈትል ይለዋል። አ.ት፡ ”በክንዱ ላይ ያሉትን ገመዶች ፈትል በቀላሉ እንደሚቃጠል በጣጠሳቸው”

የተልባ ፈትል
ከተልባ ተክል የሚገኝ ቃጫና ክር ጨርቅ ለመስራት ይጠቅማል።

Judges 15:15

አዲስ መንጋጋ
ይህ ማለት አህያው በቅርብ የሞተና አጥንቶቹም ገና መበስበስ ያልጀመሩ ናቸው ማለት ነው። መንጋጋ የታችኛዎቹን ጥርሶች የሚይዝ አጥንት ነው።

አንድ ሺህ ሰዎች
“1000 ወንዶች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

የአህያው መንጋጋ
“የአህያ መንጋጋ”

ክምር በክምር
ይህ ሐረግ ሳምሶን ምን ያህል ሰዎችን እንደገደለ ይገልጻል። ትልቅ የሬሳ ክምር ለመሥራት የሚበቃ ሬሳ ነበር። አ.ት፡ “ሬሳዎች ከምሬአለሁ”

Judges 15:17

ራማት ሌሒ
ይህ የቦታ ስም ነው። ስሙም “የመንጋጋ ኮረብታ” ማለት ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

በጣም ተጠምቶ ነበር
“ውሃ መጠጣት በጣም አስፈለገው”

ነገር ግን አሁን በውሃ ጥም ሞቼ ባልተገረዙት. . . እወድቃለሁ?
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሳምሶን በጣም ከመጠማቱ የተነሳ የምር ሊሞት እንደሆነ። አ.ት፡ “ነገር ግን አሁን በጥም እሞታለሁ፣ ሰውነቴም ባልተገረዙት … ይወድቃል”። ወይም 2) ሳምሶን በጥም ይሞት እንደሆነ በመጠየቅ ምን ያህል እንደተጠማ ያጋንናል። አ.ት፡ “ነገር ግን አሁን በጥሜ ምክንያት እንድደክም፤ ባልተገረዙትም … እንድወድቅ ትፈቅዳለህ?” (ግነት እና ጥቅል አስተያየት የሚለውን ተመልከት)

በጥም መሞት
ይህ ማለት በቂ ውሃ ባለመጠጣትህ ምክንያት በሰውነትህ ውስጥ በቂ ውሃ አጥተህ መሞት ማለት ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በእነዚያ ባልተገረዙት እጅ መውደቅ
“በእጃቸው መውደቅ” የሚለው ሐረግ መማረክ ማለት ነው። “እነዚያ ያልተገረዙ” የሚለው ፍልስጤማውያንን ሲሆን “ያልተገረዘ” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን የማያመልኩ ስለመሆናቸው አጽንዖት የሚሰጥ ቃል ነው። አ.ት፡ “እግዚአብሔርን በማያውቁ ፍልስጥኤማውያን መማረክ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Judges 15:19

ተሰንጥቆ ጉድጓድ ተከፈተ
“መሬት ላይ ቀዳዳ ተከፈተ” ወይም “ዝቅ ያለው ስፍራ ተከፈተ”። ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ምንጭ እንዲፈልቅ ያደረገበትን ዝቅ ያለ ስፍራ ነው።

ሌሔ
ይህንን በመስፍንት 15፡9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

ብርታቱ ተመለሰለትና ተነቃቃ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ የሚናገሩት ስለ አንድ ነገር ሲሆን ሳምሶን እንደገና ስለ መበርታቱ አጽንዖት የሚሰጡ ናቸው። እነዚህ ሁለት መግለጫዎች መጣመር ይችላሉ። አ.ት፡ “እንደገና በረታ” ወይም “ተነቃቃ”

ዓይንሀቆሬ
ይህ የውሃ ምንጭ ስም ነው። ስሙ “የጸለየው የእርሱ ምንጭ” ማለት ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

እስካሁን ድረስ በሌሒ ይገኛል
ይህ ማለት ምንጩ ሳይደርቅ ቆይቷል ማለት ነው። “እስካሁን ድረስ” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው የ”አሁን ጊዜ”ን ነው። አ.ት፡ ዛሬም እንኳን ምንጩ በሌሒ ይገኛል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በፍልስጥኤማውያኑ ዘመን
ይህ ፍልስጥኤማውያን የእስራኤልን ምድር ይቆጣጠሩ የነበረበትን ወቅት ያመለክታል። አ.ት፡ “ፍልስጥኤማውያን እስራኤልን ይገዙ በነበረበት ጊዜ”

ለሃያ አመታት
“ለ 20 ዓመታት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 16

1 ሳምሶን ወደ ጋዛ ሄደና በዚያ ዝሙት አዳሪ ሴት አየ፣ ከእርስዋም ጋር ወደ አልጋ ሄደ። **2** የጋዛ ሰዎችም “ሳምሶን ወደዚህ መጥቶአል” የሚል ወሬ ሰሙ። የጋዛ ሰዎች ስፍራውን ከበቡትና ሌሊቱን ሁሉ ተደብቀው በከተማይቱ በር ጠበቁት። ሌሊቱን ሁሉ ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ አላደረጉም። እንዲህ ብለዋልና፣ “እስኪነጋ ድረስ እንጠብቀው፣ ከዚያም እንገድለዋለን።” **3** ሳምሶንም እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ በአልጋ ላይ ተኛ። እኩለ ሌሊትም በሆነ ጊዜ ተነሳና የከተማይቱን በር መዝጊያና ሁለቱን መቃኖች ያዘ። እነርሱንም ከመወርወሪያው ጋር ከመሬት ነቀላቸው፣ በትከሻውም ላይ አደረጋቸው፣ በኬብሮንም ፊት ለፊት ወዳለው ኮረብታ ራስ ላይ ተሸክሞት ወጣ። **4** ከዚህ በኋላ ሳምሶን በሶሬቅ ሸለቆ የምትኖር አንዲት ሴት ወደደ። ስምዋም ደሊላ ይባል ነበር። **5** የፍልስጥኤማውያንም አለቆች ወደ እርስዋ መጡና እንዲህ አሏት፣ “እርሱን ለማዋረድ እናስረው ዘንድ በእርሱ ያለው ታላቅ ኃይል የት እንደሆነና በምን መንገድ እርሱን ማሸነፍ እንደምንችል እንዲያሳይሽ ሳምሶንን አባብዪው። ይህንን አድርጊልን፣ እኛም እያንዳንዳችን 1, 100 ብር እንሰጥሻለን። **6** ደሊላም ለሳምሶን እንዲህ አለችው፣ “እባክህ፣ እንዲህ በጣም ብርቱ የሆንከው እንዴት እንደሆነ ንገረኝ፣ በቁጥጥር ስር መዋል እንድትችል ሰው ሊያስርህ የሚችለው እንዴት ነው? **7** ሳምሶንም እንዲህ አላት፣ “ባልደረቁ ሰባት እርጥብ ጠፍሮች ቢያስሩኝ፣ እደክማለሁ፣ እንደ ማንኛውም ሰውም እሆናለሁ።” **8** የፍልስጥኤማውያን አለቆችም ያልደረቁ ሰባት እርጥብ ጠፍሮች አመጡላት፣ እርስዋም ሳምሶንን በእነርሱ አሰረችው። **9** በዚህን ጊዜ በጓዳዋ ውስጥ ሰዎች በምስጢር ተደብቀው ይጠብቁ ነበር። እርስዋም፣ “ሳምሶን፣ ፍልስጥኤማውያን መጡብህ” አለችው። ነገር ግን የተልባ እግር ፈትል እሳት በነካው ጊዜ እንደሚበጣጠስ ጠፍሩን በጣጠሰው። እነርሱም የብርታቱ ምስጢር ምን እንደሆነ አላወቁም። **10** ከዚያም ደሊላ ሳምሶንን እንዲህ አለችው፣ “አንተ እኔን እንዴት እንዳታለልኸኝ ግልጽ ሆኗል፣ ሐሰትንም ነገርኸኝ። እባክህ፣ እንዴት እንደምትታሰር ንገረኝ።” **11** እርሱም እንዲህ አላት፣ “ለሥራ ጥቅም ላይ ፈጽሞ ባልዋሉ በአዲስ ገመዶች ቢያስሩኝ፣ እደክማለሁ፣ እንደ ማንኛውም ሰው እሆናለሁ።” **12** ስለዚህ ደሊላ አዲስ ገመዶች ወሰደችና በእነርሱ አሰረችው፣ እንዲህም አለችው፣ “ሳምሶን፣ ፍልስጥኤማውያን መጡብህ።” ተደብቀው ሲጠብቁ የነበሩት ሰዎች በጓዳዋ ነበሩ። ነገር ግን ሳምሶን ገመዶቹን እንደ ፈትል ክር ከክንዶቹ በጣጠሰው። **13** ደሊላም ሳምሶንን እንዲህ አለችው፣ “እስከ አሁን ድረስ አታልለኸኛልና የነገርኸኝም ውሸት ነው። አንተን ማሰር የሚቻለው እንዴት እንደሆነ ንገረኝ።” ሳምሶንም እንዲህ አላት፣ “የራሴን ጠጕር ሰባቱን ጕንጕን ከድር ጋር ጎንጉነሽ በችካል ብትቸክዪው፣ እንደ ሌላ ሰው እሆናለሁ።” **14** እርሱም በተኛ ጊዜ፣ ደሊላ የራሱን ጠጕር ሰባቱን ጕንጕን ከድሩ ጋር ጐነጐነችው፣ በችካልም ቸከለችውና፣ እንዲህ አለችው፣ “ሳምሶን፣ ፍልስጥኤማውያን መጡብህ!” እርሱም ከእንቅልፉ ነቃና ችካሉን ከነቆንዳላውና ከነድሩ ነቀለው። **15** እርስዋም እንዲህ አለችው፣ “ምስጢርህን ለእኔ ሳትነግረኝ ‘እወድሻለሁ’ ልትለኝ እንዴት ትችላለህ? ሦስት ጊዜ ቀለድህብኝ፣ እንዲህ ዓይነቱን ታላቅ ኃይል እንዴት ሊኖርህ እንደቻለ አልነገርኸኝም።” **16** ሞት እስኪመኝ ድረስ ዕለት ዕለት በቃሎችዋ እጅግ በጣም ጨቀጨቀችው፣ ከመጠን በላይም ጫና አደረገችበት። **17** ስለዚህ ሳምሶን ሁሉንም ነገር ነገራትና እንዲህ አላት፣ “ከእናቴ ማኅፀን ጀምሬ ለእግዚአብሔር ናዝራዊ ሆኜ ስለተለየሁ በራሴ ላይ ምላጭ ደርሶና ጸጉሬን ተላጭቼ አላውቅም። የራሴን ጸጕር ብላጭ ኃይሌ ከእኔ ይሄዳል፣ እደክማለሁም እንደ ማንኛውም ሰው እሆናለሁ።” **18** ደሊላም ስለ ሁሉ ነገር እውነቱን እንደነገራት ባየች ጊዜ፣ ሰዎች ላከችና የፍልስጥኤማውያንን አለቆች ጠራች፣ እንዲህም አለቻቸው፣ “ሁሉንም ነገር ነግሮኛልና እንደገና ኑ።” የዚያን ጊዜ የፍልስጥኤማውያን አለቆች ብሩን በእጃቸው ይዘው ወደ እርስዋ ሄዱ። **19** እርስዋም በጭኗ ላይ እንዲተኛ አደረገችው። ሰባቱን የራሱን ጕንጕን እንዲላጨው አንድ ሰው ጠራች፣ ኃይሉ ስለተለየው እርስዋ በቁጥጥሯ ስር ልታደርገው ጀመረች። **20** እርስዋም፣ “ሳምሶን፣ ፍልስጥኤማውያን መጡብህ!” አለችው። እርሱም ከእንቅልፉ ነቅቶ እንዲህ አለ፣ “እንደ ሌላው ጊዜ እወጣለሁ፣ ራሴንም ነጻ አወጣለሁ።” ነገር ግን እግዚአብሔር እንደ ተወው አላወቀም። **21** ፍልስጥኤማውያንም ያዙትና ዓይኖቹን አወጡት። ወደ ጋዛም ወሰዱትና በናስ ሰንሰለት አሰሩት። በእስር ቤትም ውስጥ ሆኖ እህል ይፈጭ ነበር። **22** ነገር ግን ከተላጨ በኋላ የራሱ ጠጕር እንደገና ያድግ ጀመር። **23** የፍልስጥኤማውያንም አለቆች ለአምላካቸው ለዳጎን ታላቅ መሥዋዕት ያቀርቡ ዘንድ፣ ደስም ይላቸው ዘንድ በአንድ ላይ ተሰበሰቡ። እነርሱ “አምላካችን ጠላታችንን ሳምሶንን አሸንፏል፣ በእጃችን አሳልፎ ሰጥቶናል” ብለዋልና። **24** ሕዝቡም እርሱን ባዩት ጊዜ አምላካቸውን አመሰገኑ፣ እንዲህ ብለዋልና፣ “አገራችንን ያጠፋውን፣ ከእኛም ብዙ ሰው የገደለውን ጠላታችንን አምላካችን አሸነፈው፣ በእጃችንም አሳልፎ ሰጠው።” **25** እጅግ ደስ ባላቸው ጊዜ፣ እንዲህ አሉ፣ “እንዲያስቀን ሳምሶንን ጥሩት።” ሳምሶንን ከእስር ቤት ጠሩትና እንዲስቁ አደረጋቸው። በምሰሶና በምሰሶ መካከል እንዲቆም አደረጉት። **26** ሳምሶንም እጁን የያዘውን ልጅ፣ “እደገፍባቸው ዘንድ ሕንጻውን የደገፉትን ምሰሶዎች እንድነካቸው አስጠጋኝ” አለው። **27** በዚያን ጊዜ ቤቱ በወንዶችና በሴቶች ተሞልቶ ነበር። የፍልስጥኤም አለቆች ሁሉ በዚያ ነበሩ። ሳምሶን እነርሱን ሲያዝናናቸው ይመለከቱ የነበሩ ሦስት ሺህ የሚያህሉ ወንዶችና ሴቶች በጣራው ላይ ነበሩ። **28** ሳምሶንም ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ጮኸ፣ “ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፣ እንደገና አስበኝ! አምላኬ ሆይ፣ ሁለት ዓይኖቼን ስላወጡ ፍልስጥኤማውያንን አሁን በአንድ ምት እንድበቀል፣ እባክህ፣ ይህን አንድ ጊዜ ብቻ አበርታኝ።” **29** ሳምሶንም ሕንጻው ተደግፎባቸው የነበሩትን ሁለቱን መካከለኞች ምሰሶዎች ጠምጥሞ ያዘ፣ አንዱን ምሰሶ በቀኝ እጁ ሌላውን ደግሞ በግራ እጁ ይዞ በእነርሱ ላይ ተደገፈ። **30** ሳምሶንም እንዲህ አለ፣ “ከፍልስጥኤማውያን ጋር ልሙት!” በሙሉ ኃይሉ ገፋው፣ ሕንጻውም በውስጡ በነበሩት አለቆችና በሕዝቡም ሁሉ ላይ ወደቀ። ስለዚህ እርሱ በሞተ ጊዜ የገደላቸው ሰዎች በሕይወት ሳለ ከገደላቸው ይልቅ የበለጡ ነበሩ። **31** የዚያን ጊዜ ወንድሞቹና የአባቱ ቤተ ሰቦች በሙሉ ወረዱ፣ እርሱንም ይዘው ወሰዱት፣ መልሰው አመጡትና በጾርዓና በኤሽታኦል መካከል ባለው በአባቱ በማኑሄ መቃብር ውስጥ ቀበሩት። ሳምሶን በእስራኤል ላይ ለሀያ ዓመት ፈረደ።

Judges 16:1

ከእርሷ ጋር ወደ አልጋ ሄደ

“ወደ አልጋ ሄዱ” የሚለው ሐረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግን የሚያመለክት የጨዋ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ከእርሷ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት አደረገ” ወይም “ከእርሷ ጋር ተኛ”

ለጋዛ ሰዎች ተነግሯቸው ነበር

“የጋዛ ሰዎች” የሚለው ሐረግ ከጋዛ የሆኑትን ሰዎች ያመለክታል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የሆነ ሰው ለጋዛ ሰዎች ነግሯቸዋል” (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የጋዛ ሰዎች ቦታውን ከበቡት --- ሌሊቱን ሙሉ በከተማው በር ጠበቁት

ይህ የሚያመለክተው አንዳንድ የጋዛ ሰዎች ሳምሶን ያረፈበትን ቦታ መክበባቸውንና ሌሎቹ ደግሞ እንዳያመልጥ የከተማውን በር መጠበቃቸውን ነው።

ሌሊቱን ሙሉ ፀጥ አሉ

ትርጓሜዎች ሊሆኑ የሚችሉት 1) “ሌሊቱን ሙሉ ምንም ዓይነት ድምፅ አላሰሙም” ወይም 2) “ሌሊቱን ሙሉ እርሱን ለማጥቃት ምንም ዓይነት ሙከራ አላደረጉም”።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Judges 16:3

እስከ እኩለ ሌሊት
“እስከ ሌሊቱ አጋማሽ ድረስ”

ሁለቱን መቃኖች
እነዚህ ለከተማው በር ድጋፎች ናቸው። እነዚህ መቃኖች ምናልባትም ከዛፍ ግንድ የተሰሩና በምድር ውስጥ በጥልቀት የተቀበሩ ናቸው። የከተማው በር መዝጊያዎች ከነዚህ መቃኖች ጋር የተያያዙ ነበሩ።

ቋሚ ብረቱንና ሁሉንም
ቋሚው ብረት በሮቹን ከመቃኑ ጋር ያያዙ ከባድ የብረት ቋሚዎች ሳይሆኑ አይቀሩም። የከተማይቱ በር መዝጊያዎች ምናልባትም ከከባድ እንጨት ወይም የብረት ቋሚዎች የተሠሩ ይሆናሉ።

ትከሻዎች
ክንድንና አንገትን ከሰውነት ጋር የሚያያይዘው የሰውነት ክፍል

ኬብሮን
ይህ የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Judges 16:4

የሶሬቅ ሸለቆ
ይህ በሳምሶን ቤት አቅራብያ የሚገኝ ሸለቆ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ተንኮል
እነርሱ ሊያደርጉት የማይፈልጉትን ነገር ሌላው ሰው እንዲያደርገው ማሳሳት ወይም ማታለል

ለማየት
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን አንድን ነገር መማር ማለት ነው። አ.ት፡ “መረዳት” ወይም “መማር” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ታላቅ ብርታቱ ያለበትን
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ኃይሉ ከየት እንደሚመጣ የሚያመለክት ነው። አ.ት፡ “በጣም ጠንካራ እንዲሆን የሚያደርገው ምንድነው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በምን መንገድ ልናሸንፈው እንችላለን
“እንዴት እናሸንፈው እንደሆን”

1,100 የብር ሰቅል
“አንድ ሺህ አንድ መቶ የብር ሰቅል”። (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

Judges 16:6

በቁጥጥር ስር እንድትሆን የምትታሰረው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በቁጥጥር ስር እንድትሆን ለማሰር” ወይም “አስሮ ለመግታት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

አዲስ ጠፍሮች
አብዛኛውን ጊዜ ጠፍር የሚዘጋጀው ከእንስሳ ቆዳ፤ በተለይም ከጅማት ይሠራል። “አዲስ ጠፍር” የሚሉት ቃላት በቅርብ ከታረደ እንስሳ የመጣና ያልደረቀ መሆኑን ያመለክታል።

ያልደረቀ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እስካሁን ያልደረቁ” ወይም “ገና ያልደረቁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Judges 16:8

ያልደረቁ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እስካሁን ያልደረቁ” ወይም “ገና ያልደረቁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በእነርሱ ሳምሶንን አሰረችው
“ደሊላ ሳምሶንን በአዲሶቹ ጠፍሮች አሰረችው”

አሁን
ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው ዋናው የትረካ መስመር ለአፍታ መገታቱን ለማሳየት ነው። እዚህ ጋ ደራሲው ደሊላ ሳምሶንን እንዲማርኩ ስለምታስጠብቃቸው ፍልስጥኤማውያን ዳራዊ መረጃ ይናገራል። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ፍልስጤማውያን ባንተ ላይ ናቸው
“ባንተ ላይ” የሚለው ሐረግ ሊይዙት ተዘጋጅተዋል ማለት ነው። አ.ት፡ “ፍልስጥኤማውያኑ ሊይዙህ እዚህ ናቸው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

እሳት እንደነካው የሱፍ ክር ጠፍሮቹን በጣጠሳቸው
ደራሲው የሱፍ ክር ሲቃጠል እንደሚቀልጥ የሳምሶንን በቀላሉ ጠፍሮቹን መበጣጠስ እያነጻጸረ ያብራራል። አ.ት፡ “የሱፍ ክርን እንደሚያቃጥል ጠፍሮቹን በቀላሉ በጣጠሳቸው” ወይም “ከስስ የሱፍ ክር የተሠሩ ይመስል በቀላሉ ጠፍሮቹን በጣጠሳቸው”

Judges 16:10

እንደዚህ ነው ያታለልከኝና የዋሸኸኝ
ማታለልና መዋሸት ተመሳሳይ ሲሆኑ ደሊላ ምን ያህል እንደተናደደች አጽንዖት ለመስጠት ተነግረዋል። አ.ት፡ “እጅግ አታልለኸኛል!”

ልትሸነፍ የምትችለው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሰዎች ሊያሸንፉህ የሚችሉት”

ፍልስጤማውያን ባንተ ላይ ናቸው
“ባንተ ላይ” የሚለው ሐረግ ሊይዙት ተዘጋጅተዋል ማለት ነው። አ.ት፡ “ፍልስጥኤማውያኑ ሊይዙህ እዚህ ናቸው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ተቀምጠው ይጠባበቁት ነበር
ይህ ማለት ተደብቀው ለማጥቃት ትክክለኛውን ጊዜ እየጠበቁ ነበር ማለት ነው። አ.ት፡ “ሊያጠቁት እየጠበቁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የክር ቁራጭ እንደሆኑ ያህል
ደራሲው ሳምሶን ክርን እንደሚበጣጥስ በቀላሉ ገመዶቹን እንደበጣጠሰ በማነጻጸር ያብራራል። አ.ት፡ “የክር ቁራጭ የሆኑ ያህል በቀላሉ”

Judges 16:13

አታልለኸኛል፣ ዋሽተኸኛልም
ማታለልና መዋሸት ተመሳሳይ ሲሆኑ ደሊላ ምን ያህል እንደተናደደች አጽንዖት ለመስጠት ተነግረዋል። አ.ት፡ “እጅግ አታለኸኛል”

ልትሸነፍ የምትችለው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሰዎች ሊያሸንፉህ የሚችሉት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

መጎንጎን
የቁሳቁሶችን ቁርጥራጭ በማሰባጠር እርስ በእርስ እንዲያያዙ ማድረግ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የፀጉሬን ጉንጉን
ትናንሽ የፀጉር ስብስቦች

ፈትል
ቁሳቁሶችን በመሸመን የሚሰራ ልብስ

የሸማኔ እቃ
የተለያዩ የክር ዓይነቶችን ልብስ አድርጎ ለማያያዝ የሚጠቅም መሳርያ። (የማይታወቁትን መተርጎም የሚለውን ተመልከት)

ከሸማኔ ዕቃው ጋር ቸንክሪው
“ጨርቁን ከሸማኔው ዕቃ ጋር ቸንክሪው”

መቸንከር
የሆነን ነገር በቦታው ለመያዝ በመዶሻ ሚስማር መምታት

እንደ ማንኛውም ሰው እሆናለሁ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “እንደ ማንኛውም ሰው ደካማ እሆናለሁ”

ፍልስጤማውያን ባንተ ላይ ናቸው
“ባንተ ላይ” የሚለው ሐረግ ሊይዙት ተዘጋጅተዋል ማለት ነው። አ.ት፡ “ፍልስጥኤማውያኑ ሊይዙህ እዚህ ናቸው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ፈትሉና ችካሉን ነቀለው
ሳምሶን ፀጉሩን ከሸማኔው ዕቃ ላይ ሲጎትተው ከነፈትሉ ነቀለው። ይህ በግልጽ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ፀጉሩን ከሸማኔ ዕቃ፣ ከችካሉና ከፈትሉ ጋር ጎተተው”

ችካሉ
ፈትሉን ከሸማኔው ዕቃ ጋር የሚያያይዘው ከእንጨት የተሰራ ችንካር ወይም ችካል ነው።

Judges 16:15

ምስጢርህን ሳታክፍለኝ እንዴት “እወድሻለሁ” ትለኛለህ?
ሳምሶን በርግጥ የሚወዳት ቢሆን ኖሩ ምስጢሩን ይነግራት እንደነበር ለመናገር ደሊላ ይህንን ጥያቄ ትጠይቃለች። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊጻፍ ይችላል። አ.ት፡ “ምስጢርህን አታካፍለኝምና ‘እወድሻለሁ’ በምትልበት ጊዜ እየዋሸህ ነው” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ነዘነዘችው ጨቀጨቀችው
እዚህ ጋ ደራሲው ደሊላ ለማወቅ ምትፈልገውን ነገር ሳምሶን እንዲነግራት ለማሳመን ግፊት ያደረገችበት ይመስል ሳምሶንን ለማግባባት እንዴት እንደምትሞክር ይናገራል። አ.ት፡ “ልታግባባው በጣም ሞከረች … ለማግባባት መሞከሯን ቀጠለች” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በቃሎቿ
“እርሱን በምትናገረው ንግግር”

ሞቱን እስኪመኝ ድረስ
ደራሲው እዚህ ጋ ሳምሶን ምን ያህል ምሬት እንደተሰማው አጽንዖት ለመስጠት ግነትን ይጠቀማል። አ.ት፡ “ፈፅሞ እንደመረረው” ወይም “እጅግ እንዳዘነ” (ግነት እና ጥቅል አስተያየት የሚለውን ተመልከት)

Judges 16:17

ሁሉንም ነገር ነገራት
ስለ ብርታቱ ምንጭ ሁሉንም ነገር ነገራት። ይህ በግልጽ መነገር ይችላል። አ.ት፡ “የብርታቱን ምንጭ ነገራት” ወይም “እውነቱን ነገራት”

ምላጭ
ከሰው ቆዳ ድረስ ተጠግቶ ፀጉር ለመቁረጥ የሚያገለግል ስለታም መቁረጫ

ለእግዚአብሔር ናዝራዊ
ይህ ማለት እንደ ናዝራዊ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ነበር ማለት ነው። በመሳፍንት 13፡15 ያለውን ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ለእግዚአብሔር የተሰጠ ናዝራዊ” ወይም “እንደ ናዝራዊ ለእግዚአብሔር የተሰጠ”

ከእናቴ ማህፀን
እዚህ ጋ “ከእናቴ ማህፀን” የሚያመለክተው የተወለደበትን ጊዜ ነው። ይህ ማለት ከተወለደበት ጊዜ ጀምሮ ናዝራዊ ነበር ማለት ነው። አ.ት፡ “ሕይወቴን በሙሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ፀጉሬ ከተላጨ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አንድ ሰው ፀጉሬን ቢላጨኝ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ተላጨ
ወደ ቆዳ አስጠግቶ ፀጉርን በምላጭ መቁረጥ

ኃይሌ ከእኔ ይሄዳል
ሳምሶን ስለ ብርታቱ ትቶት ሊሄድ እንደሚችል ሰው አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “ከእንግዲህ ወዲህ ብርቱ አልሆንም” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

Judges 16:18

ደሊላ ተመለከተች
እዚህ ጋ “ተመለከተች” የሚለው ቃል የሆነን ነገር መገንዘብ የሚል የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ደሊላ ተገነዘበች” ወይም “ደሊላ ዐወቀች” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ስለ ሁሉም ነገር እውነታውን
እዚህ ጋ “ሁሉም ነገር” የሚለው ቃል ስለ ሳምሶን ጥንካሬ ሁሉንም ነገር የሚያመለክት ነው። አ.ት፡ “ብርቱ ስለሆነበት እውነታ”

እንደገና ወደ ላይ ኑ
ደሊላ ገዢዎቹን እንደገና ወደ መኖያዋ እንዲመጡ እየነገረቻቸው ነው። የእርሷ ቤት ገዢዎቹ ከሚጓዙበት ከፍ ያለ ቦታ ላይ ሳይሆን አይቀርም።

ብሩን በእጆቻቸው ይዘው
ይህ ሳምሶንን ለመያዝ ከረዳቻቸው ሊሰጧት ቃል የገቡላትን ብር ወደ እርሷ አምጥተዋል ማለት ነው። አ.ት፡ “ሊሰጧት ቃል የገቡላትን ብር በመያዝ”

አስተኛችው
“እንቅልፍ እንዲወስደው አደረገችው”

በጭኗ ላይ
ይህ ማለት ጭንቅላቱን ጭኗ ላይ አድርጎ ተኝቷል ማለት ነው። ይህ በግልጽ መነገር ይችላል። አ.ት፡ “ጭንቅላቱ በጭኗ ላይ ሆኖ”

ጭን
ጭን ሰው ሲቀመጥ ደልደል የሚለው የላይኛው እግር ክፍል ነው።

ሰባቱን የፀጉር ጉንጉኖቹን
ሳምሶን በራሱ ላይ ሰባት የፀጉር ጉንጉኖች ነበሩት። ጉንጉኖች ትናንሽ የፀጉር ክምችቶች ናቸው። እዚህ ጋር ሰባቱ የፀጉሩ ጉንጉኖች “የእርሱ” መባላቸው የጭንቅላቱ ንብረቶች እንደሆኑ ተደርገው ተገልጸዋል። አ.ት፡ “በራሱ ላይ የነበሩት ሰባቱ የፀጉር ጉንጉኖች” (ንብረት የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አሸነፉት
“በቁጥጥር ስር አዋሉት”

ብርታቱ ተለይቶት ነበር
እዚህ ጋ የሳምሶን ብርታት ትቶት ሊሄድ እንደሚችል ሰው ተደርጎ ተገልጿል። አ.ት፡ “ብርታቱ ሄዶ ነበር” ወይም “ከእንግዲህ ብርቱ አልሆነም” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

Judges 16:20

ዐይኖቹን አወጡት
ይህ ማለት ዐይኖቹን ከጭንቅላቱ አውጥተዉታል ማለት ነው። “ዐይኖቹን አጠፏቸው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ወደ ታች ወደጋዛ
“ወደ ታች” የሚለው ሐረግ እዚህ ጋ ጥቅም ላይ የዋለው ሳምሶንን ከያዙበት ከቤቱ በከፍታው ዝቅ ወዳለው ወደ ጋዛ ስለ ወሰዱት ነው።

በነሐስ የእግር ብረት አሰሩት
“ከነሐስ የእግር ብረት ጋር አሰሩት” ወይም “የነሐስ የእግር ብረት በመጠቀም አሰሩት”

የእግር ብረት
በሰንሰለት መጨረሻ ላይ ያለ የእስረኛውን እግር ወይም እጅ ወይም ሁለቱንም ለማሰር የሚጠቅም መቆለፊያ ያለው

በድንጋይ ወፍጮ ይፈጭ ነበር
“የድንጋይ ወፍጮውን በክብ ይጎትት ነበር”

የድንጋይ ወፍጮ
ይህ በጣም ትልቅ፣ ከባድና ክብ ድንጋይ ነው። ተለቅ ያለ እንስሳ የድንጋይ ወፍጮውን በክብ ዓይነት እየሳበ እህል መፍጨቱ የተለመደ ነበር። እዚህ ጋ ፍልስጥኤማውያን ሳምሶን እንዲጎትተው በማድረግ እያዋረዱት ነው።

ከተላጨ በኋላ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ፍልስጥኤማውያን ከላጩት በኋላ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Judges 16:23

ዳጎን
ከፍልስጥኤማውያን ሐሰተኛ አማልክት ዋነኛው (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ድል ስለ ሰጠን
“ስላሸነፈልን”

በእጃችን እንዲገባ ስላደረግህ
እዚህ ጋ ደራሲው በገዢዎቹ ቁጥጥር ስር ስለሆነው ሳምሶን በእጃቸው ጥብቅ ተደርጎ እንደተያዘ አንዳች ነገር አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “በቁጥጥራችን ስር አድርጎታል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የሀገራችን አጥፊ
ይህ የሚያመለክተው ሳምሶንን ነው። “አጥፊ” የሚለው ቃል “አጠፋ” በሚለው ግሥ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሀገራችንን ያጠፋው ሰው”

ከእኛ ብዙዎቹን የገደለ
እዚህ ጋ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ፍልስጥኤማውያንን ነው። ተናጋሪዎቹ ሳሞሶን ከገደላቸው ሰዎች መካከል ራሳቸውን እየቆጠሩ አይደለም። አ.ት፡ “ከእኛ ሰዎች ብዙዎቹን የገደለ”

Judges 16:25

ሳምሶንን ጥሩት ሳምሶንን ጠሩት
ሳምሶን እስረኛ ስለነበር በቀጥታ መጠራት አይችልም ነበር፤ ነገር ግን ሰዎቹ የእስር ቤቱን ኃላፊዎች ሳምሶንን ወደ እነርሱ እንዲያመጡላቸው እየጠየቁ ነበር። አ.ት፡ “ሳምሶንን እንዲያመጡላቸው ጠየቋቸው ሳምሶንን አመጡት”

ልጁ
“ታዳጊው ልጅ” ይህ ትንሽ ልጅ አልነበረም፣ ይልቁንም ወጣት ነው።

ሕንጻው ያተደገፈበትን ምሰሶ እንድነካ ፍቀድልኝ
“ሕንጻውን ደግፈው የያዙትን ቋሚዎች እንድነካ ፍቀድልኝ”

Judges 16:27

አሁን
ይህ ቃል እዚህ ጋ ጥቅም ላይ የዋለው ደራሲው ስለ ዳራዊ መረጃ ሊናገር ከዋናው ታሪክ ለአፍታ መውጣቱን ለማመልከት ነው። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ሶስት ሺህ ወንዶችና ሴቶች
“3,000 ወንዶችና ሴቶች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

እየተመለከቱ
“እያዩ”

ሳምሶን እያዝናናቸው እያለ
ሳምሶን እነርሱን ለማዝናናት ምን እንዳደረገ ግልጽ አይደለም። ፍልስጥኤማውያን እንዲቀልዱበት፣ ሊያዋርዱት የሚችሉ ነገሮችን ያስደረጉት ይመስላል።

Judges 16:28

ወደ እግዚአብሔር ተጣራ
“ወደ እግዚአብሔር ጸለየ”

አስበኝ
ይህ ማለት እርሱንና ያለበትን ሁኔታ እንዲያስታውስ ማለት ነው። አ.ት፡ “አስታውሰኝ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ይህን አንድ ጊዜ ብቻ
“አንድ ጊዜ ብቻ”

በአንድ ጊዜ ፍልስጥኤማውያን ላይ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ፣ ፍልስጥኤማዊያን ስላደረጉበት ነገር ፈጽሞ ለመበቀል በእነርሱ ላይ አንድ ጊዜ የኃይል ድርጊት ለመፈጸም ይፈልጋል ማለት ነው። አ.ት፡ “በፍልስጥኤማውያን ላይ በአንድ ምት” ወይም “በፍልስጥኤማውያን ላይ በአንድ ኃይለኛ ድርጊት” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ሕንጻው ያረፈበት
“ሕንጻውን ባቆመው”

Judges 16:30

በብርታቱ ገፋው
ሳምሶን ክንዶቹን ሲዘረጋ የሕንጻውን ምሰሶዎች ገፍቶ ጣላቸው። አ.ት፡ “ምሰሶዎቹን ለመጣል ብርታቱን ተጠቀመ” ወይም “ምሰሶዎቹን ለመግፋት ኃይሉን ተጠቀመ”

የሞቱት
ይህ የሞቱትን ሰዎች ያመለክታል። “የሞቱት ሰዎች”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይበዙ ነበር
“በቁጥር ብዙ ነበሩ”

የአባቱ ቤት ሁሉ
እዚህ ጋ “ቤት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእርሱን ቤተሰብ ነው። አ.ት፡ “የአባቱ ቤተሰቦች በሙሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ወረዱ
“ወረዱ” የሚለው ቃል እዚህ ጋ ጥቅም ላይ የዋለው የሳምሶን ቤተሰብ የተጓዘበት ቦታ ከጋዛ በከፍታ የሚበልጥ ስለነበረ ነው።

ጾርዓ ኤሽታኦል
የእነዚህን ቦታዎች ስም በመሳፍንት 13፡2 እና በመሳፍንት 13፡25 እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

በአባቱ በማኑሔ የመቃብር ስፍራ
“አባቱ ማኑሔህ በተቀበረበት ስፍራ”

ማኑሔ
የዚህን ሰውዬ ስም በመሳፍንት 13፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ሳምሶን ለሃያ ዓመታት በእስራኤል ላይ ፈርዶ ነበር
ይህ ዐረፍተ ነገር ራሱ በመሳፍንት 15፡20 ላይ አለ። እዚህ ጋ የተደገመው ለምን ያህል ጊዜ በእስራኤል ላይ እንደፈረደ አንባቢዎችን ለማስታወስ ነው። አ.ት፡ “ሳምሶን ከመሞቱ በፊት በእስራኤል ላይ ለሃያ ዓመታት ፈርዷል”

ሃያ ዓመታት
“20 አመታት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 17

1 በኮረብታማውም በኤፍሬም አገር አንድ ሰው ነበር፣ ስሙም ሚካ ይባላል። **2** ለእናቱም እንዲህ አላት፣ “ከአንቺ ዘንድ ተወስዶ የነበረው 1, 100 ብር፣ የእርግማን ንግግር የተናገርሽበትና እኔም የሰማሁት እነሆ እዚህ አለ! ብሩ በእኔ ዘንድ አለ። እኔ ሰርቄዋለሁ!” እናቱም እንዲህ አለች፣ “ልጄ ሆይ፣ እግዚአብሔር ይባርክህ!” **3** እርሱም 1, 100 ብር ለእናቱ መለሰላት፣ እናቱም እንዲህ አለችው፣ “ስለ ልጄ የተቀረጸ የእንጨት ምስልና ቀልጦ የተሠራ ምስል ለማድረግ ይህን ብር ለእግዚአብሔር ለይቼዋለሁ። ስለዚህ አሁን፣ ለአንተ መልሼዋለሁ።” **4** ለእናቱም ገንዘቡን በመለሰላት ጊዜ፣ እናቱ ሁለቱን መቶ ብር ወሰደችና የተቀረጸ የእንጨት ምስልና ቀልጦ የተሠራ ምስል አድርጎ ለሰራው ለብረት ሰራተኛ ሰጠችው። ያም በሚካ ቤት ተቀመጠ። **5** ሚካ የተባለውም ሰው የጣዖታት አምልኮ ቤት ነበረውና አንድ ኤፉድና ተራፊም ሰራ፣ ከልጆቹም አንዱ ካህን ሆኖ እንዲያገለግለው አደረገ። **6** በዚያን ዘመን በእስራኤል ዘንድ ንጉሥ አልነበረም፣ ሰውም ሁሉ በዓይኖቹ ፊት ትክክል መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር። **7** አሁን በቤተ ልሔም ይሁዳ ከይሁዳ ወገን የሆነ አንድ ሌዋዊ ወጣት ሰው ነበረ። እርሱም ተግባሩን ለመፈጸም በዚያም ይቀመጥ ነበር። **8** ይህ ሰው የሚቀመጥበትን ስፍራ ለመፈለግ ቤተ ልሔም ይሁዳን ለቅቆ ሄደ። ሲጓዝም ወደ ኮረብታማው የኤፍሬም አገር ወደ ሚካ ቤት መጣ። **9** ሚካም ለእርሱ እንዲህ አለው፣ “ከወዴት መጣህ?” እርሱም እንዲህ አለው፣ “እኔ ከቤተ ልሔም ይሁዳ የመጣሁ ሌዋዊ ነኝ፣ የምኖርበትን ስፍራ ለማግኘት እየተጓዝሁ ነው።” **10** ሚካም እንዲህ አለው፣ “ከእኔ ጋር ተቀመጥ፣ ለእኔም አማካሪና ካህን ሁነኝ። እኔም በየዓመቱ አሥር ብር፣ እንደዚሁም ልብሶችንና ምግብህን እሰጥሃለሁ።” ስለዚህ ሌዋዊው ወደ ቤቱ ገባ። **11** ሌዋዊውም ከሰውዮው ጋር ለመቀመጥ ፈቃደኛ ሆነ፣ ወጣቱም ሰው ለሚካ ከልጆቹ እንደ አንዱ ሆነለት። **12** ሚካም ሌዋዊውን ለተቀደሰ ሃላፊነት ቀደሰው፣ ወጣቱም ሰው ካህኑ ሆነለት፣ በሚካም ቤት ነበረ። **13** ከዚያም ሚካ እንዲህ አለ፣ “አሁን እግዚአብሔር ለእኔ መልካም እንደሚሰራልኝ አውቄአለሁ፣ ምክንያቱም ይህ ሌዋዊ ካህን ሆኖልኛል።”

Judges 17:1

አንድ ሰው ነበር
ይህ በታሪክ ፍሰቱ ላይ አዲስን ሰው የማስተዋወቂያ መንገድ ነው። (አዲስና ነባር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቂያ የሚለውን ተመልከት)

ሚካ
ይህ የአንድ ሰው ስም ነው። ይህ የሚክያስን መጽሐፍ የጻፈው ሰው አይደለም። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

1,100 ሰቅል
“አንድ ሺህ አንድ መቶ ሰቅል” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ከአንቺ የተወሰደው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አንድ ሰው የሰረቀብሽ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ሰርቄዋለሁ
“እኔ ነኝ የወሰድኩት”

Judges 17:3

1,100 ሰቅል
“አንድ ሺህ አንድ መቶ ሰቅል” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ለየ
ይህ ማለት አንድን ነገር ለተለየ አላማ መስጠት ማለት ነው። አ.ት፡ “ተሰጠ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የቀለጠ ብረት
የተለየ ቅርጽ ለማውጣት በቅርጽ ማውጫ ውስጥ ቀልጦ የሚጨመር ብረት

እመልስልሃለሁ
“ላንተ መልሼ እሰጥሃለሁ”

ሁለት መቶ ሰቅል ብር
“200 ሰቅል ብር” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

እነርሱ በሚካ ቤት ተቀምጠው ነበር
“እነርሱ” የሚለው ቃል የብረት ቅርጾቹን ያመለክታል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሚካ በቤቱ አስቀምጧቸው ነበር” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Judges 17:5

የጣዖታት ቤት
ይህ በግልጽ ጣዖታት የሚመለኩበትን ቤት ያመለክታል። ይህ በግልጽ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ጣዖታትን የማምለኪያ ቤት”

ሁሉም በዐይኖቹ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር
ዐይን ዕይታን ይወክላል፤ ማየትም አሳብን ወይም ውሳኔን ይወክላል። አ.ት፡ “እያንዳንዱ ሰው ልክ ነው ብሎ የወሰነውን ያደርግ ነበር” ወይም “እያንዳንዱ ሰው ልክ ነው ብሎ የፈረደውን ያደርግ ነበር” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 17:7

የቤተልሔም
“ከቤተልሔም”

ከይሁዳ ነገድ የሆነ
ይህ ማለት በይሁዳ ቤተሰቦች ይኸውም በይሁዳ ነገድ መካከል ይኖር ነበር ማለት ነው። አ.ት፡ “በይሁዳ ነገድ መካከል ይኖር የነበረ”

ኃላፊነቱን ለመወጣት በዚያ ይኖር ነበር
“በዚያ ይኖርና ይሠራ ነበር”

መኖሪያ እየፈለገ
“ሌላ የመኖርያ ቦታ ለመፈለግ”

የምኖርበትን
የሚኖርበትንና የሚሠራበትን ቦታ እየፈለገ እንደሆነ ያመለክታል። አ.ት፡ “የምኖርበትና የምሠራበትን ስፍራ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Judges 17:10

አባትና ካህን
“አባት” የሚለው ቃል እዚህ ጋ አማካሪ ለማለት ጥቅም ላይ ውሏል እንጂ እውነተኛ አባትነትን አያመለክትም። አ.ት፡ “አማካሪና ካህን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በዓመት አሥር ሰቅል ብር እሰጥሃለሁ
“በየዓመቱ አሥር ጥሬ ብር እሰጥሃለሁ”

ቅያሪ ልብስ
“የልብሶች ስብስብ”

ስለዚህ ሌዋዊው ወደ እርሱ ቤት ገባ
ሌዋዊው የሚካን አሳብ መቀበሉንና ወደ ሚካ ቤት መግባቱን ያመለክታል። አ.ት፡ “ስለዚህ ሌዋዊው ግብዣውን ተቀብሎ ወደ ቤቱ ገባ”

ወጣቱ ለሚካ ከወንዶች ልጆቹ እንደ አንዱ ሆነለት
በሌዋዊውና በሚካ መካከል ያለው ግንኙነት እንደ አባትና ልጅ የጠበቀ ሆነ። አ.ት፡ “ወጣቱ ከሚካ ጋር በጣም ከመቀራረቡ የተነሣ ከወንዶች ልጆቹ እንደ አንዱ ሆነ”

Judges 17:12

ሚካ ሌዋዊውን ለየው
እዚህ ጋ “ለየው” ማለት ሚካ “ቀደሰው” ወይም “ሾመው” ማለት ነው። አ.ት፡ “ሚካ ሌዋዊውን ቀደሰው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በሚካ ቤት ነበረ
እዚህ ጋ በሚካ ቤት መኖሩ በቤቱ “እንደሆነ” ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “በሚካ ቤት ኖረ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 18

1 በዚያን ዘመን በእስራኤል ውስጥ ንጉሥ አልነበረም። የዳን ነገድ ተወላጆች የሚቀመጡበትን ርስት ይፈልጉ ነበር፣ እስከዚያ ቀን ድረስ በእስራኤል ነገዶች
መካከል ርስት አልተቀበሉም ነበርና። 2 የዳን ሰዎች ከአጠቃላይ ወገናቸው በሙሉ ከጾርዓ ጀምሮ እስከ ኤሽታኦል ድረስ በጦርነት ልምድ ያላቸውን አምስት
ሰዎች በእግራቸው ሄደው ምድሪቱን እንዲሰልሉና እንዲያዩ ላኩ። ለእነርሱም እንዲህ አሉአቸው፣ “ሂዱና ምድሪቱን ሰልሉ።” እነርሱም ወደ ኮረብታማው ወደ
ኤፍሬም አገር ወደ ሚካ ቤት መጡና ሌሊቱን በዚያ አሳለፉ። 3 በሚካ ቤት አጠገብ በነበሩ ጊዜ፣ የአንድ ወጣት ሌዋዊ ንግግር አወቁ። ስለዚህ አስቆሙትና
እንዲህ ብለው ጠየቁት፣ “ወደዚህ ማን አመጣህ? በዚህ ስፍራ ምን ታደርጋለህ? ለምን ወደዚህ መጣህ?” 4 እርሱም እንዲህ አላቸው፣ “ሚካ ለእኔ ያደረገው
ነገር ይህ ነው፦ የእርሱ ካህን እንድሆን ቀጠረኝ።” 5 እነርሱም እንዲህ አሉት፣ “የምንሄድበት መንገድ መቃናቱን ወይም አለመቃናቱን እናውቅ ዘንድ፣ እባክህ፣
የእግዚአብሔርን ምክር ጠይቅልን።” 6 ካህኑም ለእነርሱ እንዲህ አላቸው፣ “በሰላም ሂዱ። ልትሄዱ በሚገባችሁ መንገድ እግዚአብሔር ይመራችኋል።” 7
የዚያን ጊዜ አምስቱ ሰዎች ሄዱና ወደ ላይሽ መጡ፣ ሲዶናውያን በጸጥታ ያለስጋት ይኖሩ እንደነበረ ሁሉ፣ በዚያም ተዘልለው ይኖሩ የነበሩትን ሕዝብ አዩ።
በምድሪቱም በየትኛውም መልኩ የገዛቸው፣ ወይም ያስቸገራቸው አልነበረም። ከሲዶናውያን በጣም ርቀው ይኖሩ ነበር፣ ከማንኛውም ሕዝብ ጋር ምንም ግንኙነት
አልነበራቸውም። 8 በጾርዓና በኤሽታኦል ውስጥ ወደነበሩት ወንድሞቻቸው ተመለሱ። ዘመዶቻቸውም እንዲህ ብለው ጠየቁአቸው፣ “ምን ወሬ ይዛችኋል?” 9
እነርሱም እንዲህ አሉ፣ “ኑ! እንውጋቸው! ምድሪቱን አይተናታል፣ በጣም ጥሩ ናት። እናንተ ዝም ትላላችሁን? ምድሪቱን ከመውጋትና ከመውረስ አትዘግዩ። 10
በሄዳችሁ ጊዜ፣ ያለ ስጋት እንደሚኖሩ ወደሚያስቡ ሕዝብ ትደርሳላችሁ፣ ምድሪቱም ሰፊ ናት! እግዚአብሔርም ለእናንተ ሰጥቶአችኋል፣ በምድር ካለው ነገር ሁሉ
አንዳች የማይጎድልባት ስፍራ ናት። 11 ከዳን ወገን የሆኑና የጦር መሳርያ የታጠቁ ስድስት መቶ ሰዎች ከጾርዓና ከኤሽታኦል ተነሥተው ሄዱ። 12 እነርሱም ሄዱና
በይሁዳ ባለችው በቂርያትይዓሪም ሰፈሩ። እስከ ዛሬ ድረስ የዚያ ስፍራ ስም የዳን ሰፈር ብለው የሚጠሩት ለዚህ ነው፤ እርሱም ከቂርያትይዓሪም በምዕራብ በኩል
ነው። 13 እነርሱም ከዚያ ተነስተው ወደ ኮረብታማው የኤፍሬም አገር አልፈው ሄዱ፣ ወደ ሚካም ቤት መጡ። 14 ከዚያም የላይሽን አገር ሊሰልሉ ሄደው
የነበሩት አምስቱ ሰዎች ለዘመዶቻቸው እንዲህ አሉአቸው፣ “በእነዚህ ቤቶች ውስጥ ኤፉድና ተራፊም፣ የተቀረጸ ምስልና ቀልጦ የተሠራ ምስል እንዳሉ
ታውቃላችሁን? ምን እንደምታደርጉ አሁን ወስኑ።” 15 ስለዚህ ከዚያ ዘወር አሉና ወጣቱ ሌዋዊ ይኖርበት ወደነበረው ወደ ሚካ ቤት መጡ፤ ሰላምታም
አቀረቡለት። 16 በዚያን ጊዜ የጦር መሳርያ የታጠቁት ስድስት መቶ ዳናውያን በበሩ መግቢያ ቆሙ። 17 ካህኑ የጦር መሳርያ ከታጠቁት ከስድስት መቶ ሰዎች
ጋር በበሩ አካባቢ ቆሞ በነበረበት ጊዜ፣ ምድሪቱንም ሊሰልሉ ሄደው የነበሩት አምስቱ ሰዎች ወደዚያ ሄዱና የተቀረጸውን ምስል፣ ኤፉዱን፣ ተራፊሙንና ቀልጦ
የተሠራውን ምስል ወሰዱ። 18 እነዚህ ወደ ሚካ ቤት ገብተው የተቀረጸውን ምስል፣ ኤፉዱን፣ ተራፊሙንና ቀልጦ የተሠራውን ምስል በወሰዱ ጊዜ፣ ካህኑ
ለእነርሱ እንዲህ አላቸው፣ “ምን ታደርጋላችሁ?” 19 እነርሱም እንዲህ አሉት፣ “ዝም በል! እጅህን በአፍህ ላይ ጫንና ከእኛ ጋር ና፣ ለእኛም አባትና ካህን
ሁንልን። ለአንተስ ለአንድ ሰው ቤት ካህን መሆን ወይስ በእስራኤል ውስጥ ላለው ነገድና ወገን ሁሉ ካህን መሆን ይሻልሃል?” 20 የካህኑም ልብ ደስ አለው።
ኤፉዱን፣ ተራፊሙንና የተቀረጸውንም ምስል ወሰደና ከሕዝቡ ጋር ሄደ። 21 ስለዚህ እነርሱ ዞሩና ሄዱ። ሕፃናቶችን፣ ከብቶችንና ንብረታቸውን በፊታቸው
አስቀደሙ። 22 ከሚካም ቤት ጥቂት በራቁ ጊዜ፣ በሚካ ቤት አጠገብ በነበሩት ቤቶች ውስጥ የነበሩ ሰዎች ተጠራርተው ተሰበሰቡ፣ የዳን ሰዎችንም
ተከትለው ደረሱባቸው። 23 ወደ ዳንም ሰዎች ጮኹ፣ ዘወር ብለው ለሚካም እንዲህ አሉት፣ “ተሰብስባችሁ በአንድ ላይ የመጣችሁት ለምንድን ነው?” 24
እርሱም፣ “የሠራኋቸውን አማልክቴን ሰረቃችሁ፣ ካህኔንም ይዛችሁ ሄዳችሁ። ሌላ ምን የቀረኝ ነገር አለ? ‘ያስጨነቀህ ምንድን ነው?’ ብላችሁ እንዴት
ልትጠይቁኝ ትችላላችሁ።” 25 የዳን ሰዎችም እንዲህ አሉት፣ “ምንም ዓይነት ንግግር ስትናገር እንድንሰማ አታድርገን፣ አለዚያ አንዳንድ የተቈጡ ሰዎች
ይጎዱሃል፣ አንተና ቤተሰቦችህም ትሞታላችሁ።” 26 የዚያን ጊዜ የዳን ሰዎች መንገዳቸውን ሄዱ። ሚካ ከእርሱ ይልቅ እነርሱ እጅግ በጣም የበረቱ እንደሆኑ ባየ
ጊዜ፣ ተመልሶ ወደ ቤቱ ሄደ። 27 የዳን ሰዎችም ሚካ የሠራውን ጣዖትና ካህኑን ወሰዱና ወደ ላይሽ መጡ፣ በሰላምና ያለ ስጋት ተዘልሎም ወደ ተቀመጠው
ሕዝብ መጥተው በሰይፍ ስለት ገደሉአቸው፣ ከተማይቱንም በእሳት አቃጠሉአት። 28 እነርሱን የሚያድን አንድም ሰው አልነበረም ምክንያቱም ከተማይቱ ከሲዶና
በጣም ራቅ ያለች ነበረች፣ እነርሱም ከሌሎች ሰዎች ጋር ምንም ግንኙነት አልነበራቸውም። እርስዋም በቤትሮዖብ አጠገብ ባለው ሸለቆ ውስጥ ነበረች። የዳን
ሰዎችም ከተማይቱን እንደገና ሠሩና ተቀመጡባት። 29 ከተማይቱንም ከእስራኤል ወንዶች ልጆች አንዱ በሆነው በአባታቸው በዳን ስም ዳን ብለው ጠሩአት።
ነገር ግን አስቀድሞ የከተማይቱ ስም ላይሽ ነበረ። 30 የዳን ሰዎችም ለራሳቸው የተቀረጸ ምስል አቆሙ፣ የሙሴ ልጅ የጌርሶም ልጅ ዮናታን፣ እርሱና ወንዶች
ልጆቹ ምድሪቱ እስከምትያዝበት ቀን ድረስ ለዳን ሰዎች ካህናት ነበሩ። 31 ስለዚህ የእግዚአብሔር ቤት በሴሎ በነበረበት ጊዜ ሁሉ፣ ሚካ የሰራውን የተቀረጸ
ምስል አመለኩ።

Judges 18:1

በእነዚያ ቀናት
ይህ ሐረግ በታሪኩ ፍሰት ላይ ሌላ አዲስ የሁነት ጅማሬን ያስተዋውቃል። (አዲስ ሁነትን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)

በእነዚያ ቀናት... ከእስራኤል ነገዶች መካከል
ይህ ስለ እስራኤልና ስለዳን ነገድ ሕዝቦች ዳራዊ መረጃ ነው። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ምንም ርስት አልተቀበለም
ይህ በግልጽ የሚኖሩበትን መሬት እንዳልወረሱ ያመለክታል። አ.ት፡ “የመሬት ርስት አልተቀበልንም”

ከነገዳቸው በሙሉ
“በሙሉ” የሚለው ቃል በነገዱ ያሉትን ሰዎች ሁሉ ያመለክታል። አ.ት፡ “በየነገዱ መካከል ካሉት ሰዎች ሁሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ልምድ ያላቸው ጦረኞች
“ልምድ ያላቸው ተዋጊዎች”

ጾርአ
የዚህን ከተማ ስም በመስፍንት 13:2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ኤሽታኦል
የዚህን ከተማ ስም በመሳፍንት 13:25 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምድሪቱን በእግር ተጉዘው እንዲሰልሉ
“በእግር” የሚለው ሐረግ መራመድ ማለት ነው። አ.ት፡ “በእርሱ ላይ በመራመድ መሰለል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ሚካ
የዚህን ሰው ስም በመሳፍንት 17፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

Judges 18:3

የወጣቱን ሌዋዊ ንግግር ለይተው ዐወቁ
ሰውየውን በሚናገርበት ድምፁ ለይተው ዐወቁት። እዚህ ጋ “ንግግር” የሚጠቁመው “ድምፁን” ነው። አ.ት፡ “ወጣቱ ሌዋዊ ሲናገር ሰሙትና ድምፁን ዐወቁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 18:7

ላይሽ
ይህ የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ድል ያደረገ ማንም አልነበረም
“ድል አድርገዋቸው በምድራቸው የተቀመጡ ጠላቶች አልነበሩም”

ከማንም ጋር ምንም ግንኙነት አልነበራቸውም
“በውጪ ከሚኖሩ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት አልነበራቸውም”፤ ይህ ማለት ከሌሎች ከተሞች ርቀውና ከሌሎች ሰዎች ተገልለው ይኖሩ ነበር ማለት ነው።

ጾርአ
የዚህችን ከተማ ስም በመሳፍንት 13፡2 ላይ እንደተረጎምከው አድርገህ ተርጉም።

ኤሽታኦል
የዚህችን ከተማ ስም በመሳፍንት 13፡25 ላይ እንደተረጎምከው አድርገህ ተርጉም።

Judges 18:9

ምንም እየሠራህ አይደለም?
ይህ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የተጠየቀው በአሸሙር ሲሆን ትርጉሙም ተቃራኒውን ማድረግ ነበረባቸው የሚል ነው። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊጻፍ ይችላል። አ.ት፡ “አሁን የሆነ ነገር ማድረግ አለባችሁ” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እና ድርብ አሉታ የሚለውን ተመልከት)

ለማጥቃት የዘገያችሁ አትሁኑ
እነዚህ “አትሁኑ” እና “አትዘግዩ” የሚሉት አሉታዊ ቃላቶች በአንድ ላይ በቶሎ እንዲያጠቁ አዎንታዊ አሳብ ላይ አጽንዖት የሰጣሉ። “ፍጠኑ! አጥቁ” (ድርብ አሉታ የሚለውን ተመልከት)

ምድሪቱ ሰፊ ናት
“ምድሪቱ ታላቅ ናት” ይህ የምድሩን መጠን ይገልጻል።

ምድሪቱ ምንም ነገር ያልጎደላት
ሰዎቹ ለመኖር በጣም ተመራጭ ቦታ እንደሆነ አጽንዖት ለመስጠት ግነትን ተጠቅመዋል። አ.ት፡ “በዚያ የሚያስፈልገን ነገር ሁሉ ይኖረናል” (ግነት እና ጥቅል አስተያየት የሚለውን ተመልከት)

ምንም ነገር ያልጎደለው
ሁለቱ አሉታዊ ቃላት በአንድነት አዎንታዊ አሳብ ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ። አ.ት፡ “ሁሉም ነገር ያለው” (ድርብ አሉታ የሚለውን ተመልከት)

Judges 18:11

ስድስት መቶ ሰዎች
“600 ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ቂርያትይዓሪም
ይህ የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ማኹነህ ዳን
የዚህን ስፍራ ስም በመሳፍንት 13፡25 ላይ እንደተረጎምከው አድርገህ ተርጉመው።

እስከዚህ ቀን ድረስ
ይህ ማለት የሆነ ነገር እስካሁን እንደዚያው አለ ማለት ነው። “የአሁንን ” ጊዜ ያመለክታል። አ.ት፡ “እስካሁን ስሙ እንደዚያው ነው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Judges 18:13

ላይሽ
የዚህን ከተማ ስም በመሳፍንት 18፡7 ላይ እንደተረጎምከው አድርገህ ተርጉመው።

በእነዚህ ቤቶች ውስጥ ኤፉዶች አሉ፣ ... የብረት ምስል? እናደርጋለን ወስኑ
አምስቱ ሰዎች ይህንን ጥያቄ የጠየቁት ሰዎቹ ጣዖታቱን እንዲሰርቁ አሳብ ለመስጠትና ለማደፋፈር ነው። ይህ እንደ መግለጫ ሊጻፍ ይችላል፤ አመልካች የመረጃ ሐረግም በቅንፍ ውስጥ ሊሰጥ ይቻላል። አ.ት፡ “እነዚህ ቤቶች የብረት ምስል የሆነውን ኤፉድ ይዘዋል (ሰዎቹ እንዚህን ነገሮች እንዲሰርቁ አሳብ እየሰጡ ነበር።) እናደርጋለን ... ወስኑ” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እና የሚለውን ተመልከት)

በእነዚህ ቤቶች ውስጥ አሉ
“ከእነዚህ ቤቶች በአንዱ ውስጥ አለ” ወይም “በእነዚህ ቤቶች መካከል አለ”

Judges 18:15

ወደዚያ ገቡ
“ገቡ”

ሰላምታ ሰጡት
“እርሱን” የሚለው ቃል ሌዋዊውን ያመለክታል።

ስድስት መቶ የዳን ሰዎች
“600 የዳን ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

Judges 18:17

ስድስት መቶ ሰዎች
“600 ወንዶች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

Judges 18:19

ለአንድ ሰው ቤት ካህን መሆን ይሻልሃል በእስራኤል ላለ አንድ ነገድ?
ይህንን ጥያቄ መልስ በማይሻ መልኩ የሚጠይቁት የነገሩን እውነትነት ለማመልከት ነው። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊጻፍ ይችላል። አ.ት፡ “ለአንድ ሰው ካህን ከመሆን ይልቅ በእስራኤል ላለ ነገድ እና ጎሳ ካህን መሆን ይሻልሃል” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

የካህኑ ልብ ተደሰተ
እዚህ ጋ ካህኑ በተሰማው ስሜት ላይ አጽንዖት ለመስጠት ”ልቡ” ተብሏል። አ.ት፡ “ካህኑ ተደስቶ ነበር”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Judges 18:21

ትንንሾቹን ልጆች ከፊት ለፊታቸው አደረጓቸው
በዚህ መልኩ የሚጓዙት ልጆቹን ለመጠበቅ ነው። ሚካና ሰዎቹ ቢያጠቋቸው መጀመሪያ የሚያገኙት ጦረኞቹን እንጂ ልጆቹን አይሆንም። አ.ት፡ “ትንንሾቹን ልጆች ለመጠበቅ ከፊት ለፊታቸው አደረጓቸው”

በጥሩ ርቀት
“ጥቂት ርቀት”፣ ይህ ለመለካት የሚበቃውን ርዝመት አጭር ርቀት ይለዋል። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በሚካ ቤት አቅራብያ ባሉት ቤቶች ውስጥ የነበሩ ሰዎች አንድ ላይ ተጠርተው ነበር
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በቤቱ አቅራቢያ ባሉ ቤቶች ውስጥ የነበሩትን ሰዎች አንድ ላይ ጠራቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በዳን ሰዎች ላይ ደረሱባቸው
ይህ ከኋላ ተከትለዋቸው እንደሮጡ ያመለክታል። ይህ በግልጽ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ከዳን ሰዎች ኋላ በመሮጥ ደረሱባቸው”

ወደ ኋላቸው ተመለሱ
“የዳን ሰዎች የሆኑት ወደ ኋላቸው ዞሩ”

ተጠራርታችሁ የተሰባሰባችሁት ለምንድነው?
ይህ የወቀሳ ጥያቄ ነው። እንደ መግለጫ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እኛን ለማሳደድ ሰዎችህን ጠርተህ መሰብሰብ አልነበረብህም”። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

አንድ ላይ ተጠርተው ነበር
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እነዚህን ሰዎች አንድ ላይ ጠሯቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Judges 18:24

የሰራኋቸውን አማልክቶቼን
ሚካ አማልክቶቹን አልሠራቸውም፤ የሠራቸው ባለ ሙያ የሆነ ሰው ነው። አ.ት፡ “ለራሴ ያሠራኋቸውን አማልክት” ወይም “ባለ ሙያ የሠራልኝን አማልክት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሌላ ምን ቀረኝ?
ሚካ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ለእርሱ አስፈላጊ የሆኑት ነገሮች አሁን እንደሌሉት አጽንዖት ለመስጠት ነው። አ.ት፡ “ምንም የቀረኝ ነገር የለም” ወይም “ለእኔ አስፈላጊ የሆነውን ነገር በሙሉ ወስዳችሁብኛል” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

“ምን ሆንክ?” ብላችሁ እንዴት ትጠይቁኛላችሁ
ሚካ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው የዳን ሰዎች የሆኑት በእርግጥ ምን እንዳሳሰበው እንደሚያውቁ አጽንዖት ለመስጠት ነው። አ.ት፡ “እጅግ እንዳዘንኩ ታውቃላችሁ!” ወይም “በእኔ ላይ ባደረጋችሁት ነገር ምን ያህል እንደተቸገርኩ ታውቃላችሁ!” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ምንም አይነት ነገር ስትናገር እንዳንሰማህ
“ስትናገር እንዳንሰማህ” የሚለው ሐረግ የዳን ሰዎች ሚካ ስለሆነው ነገር የሚያወራውን መስማታቸውን ያመለክታል፤ ነገር ግን ሚካ ስለተፈጠረው ነገር ማውራቱን ከሌሎች ሰዎች መስማታቸውንም ይጨምራል። አ.ት፡ “ምን እንደተናገርክ ማወቅ እንፈልጋለን” ወይም “ስለዚህ ጉዳይ የፈለግኸውን ተናገር” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ምንም አይነት ነገር ስትናገር እንዳንሰማህ
“ምንም ዓይነት ነገር” የሚለው ሐረግ የዳን ሰዎች ወደ ሚካ ቤት መጥተው ጣዖቶቹን መስረቃቸውን የሚጠቁም የትኛውንም መረጃ ያመለክታል። ይህ በግልጽ መነገር ይችላል። አ.ት፡ “ስለዚህ ጉዳይ ምንም ነገር ስትናገር እንዳንሰማህ” ወይም “ስለሆነው ነገር እንዳች ስትናገር እንዳንሰማህ”

አንተና ቤተሰቦችህ ትገደላላችሁ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አንተንና ቤተሰብህን እንገላለን” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

መንገዳቸውን ሄዱ
ይህ ጉዟቸውን ቀጠሉ ማለት ነው። አ.ት፡ “ጉዟቸውን ቀጠሉ” ወይም “መጓዛቸውን ቀጠሉ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ለእርሱ እጅግ የበረቱ ነበሩ
ይህ የሚያመለክተው ሚካና ሰዎቹ እንዳይዋጓቸው የዳን ሰዎች እጅግ ብርቱ መሆናቸውን ነው። አ.ት፡ “እርሱና ከእርሱ ያሉት ሰዎች እንዳይዋጓቸው እጅግ ብርቱዎች ነበሩ”

Judges 18:27

ሚካ ሠርቷቸው የነበሩት
ሚካ አማልክቶቹን አልሠራቸውም፤ ይልቁን የሠራለት ባለ ሙያ ነበር። ደግሞም ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ለሚካ የተሠሩለት ነገሮች” ወይም “የሚካ ነገሮች” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ላይሽ
ይህንን በመሳፍንት 18፡17 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

በሰይፍ ስለት
“በሰይፎቻቸው”። እዚህ ጋ “ሰይፉ” ወታደሮቹ በጦርነት የተጠቀሙባቸውን ሰይፍና ሌሎች የጦር መሳሪያዎች ይወክላል።

ከማንም ጋር ምንም ግንኙነት አልነበራቸውም ነበር
“በውጪ ከሚኖሩ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት አልነበራቸውም”፤ ይህ ማለት ከሌሎች ከተሞች ርቀውና ከሌሎች ሰዎች ተገልለው ይኖሩ ነበር ማለት ነው። ይህንን ሐረግ በመሳፍንት 18፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ቤትሮዓብ
ይህ የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Judges 18:30

x
ይህ ሚካን በካህንነት ያገለግለው የነበረው የወጣቱ ሌዋዊ ስም ነው። ይህ ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “የወጣት ሌዋዊው ስም የሙሴ ልጅ የጌርሳም ልጅ ዮናታን ነበር” (እና ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ምድሪቱ እስከተያዘችበት ቀን ድረስ
ይህ የዳን ሰዎች በጠላቶቻቸው የሚያዙበትን የወደፊት ጊዜ የሚያመለክት ነው። እዚህ ጋ የምድሪቱ መያዝ በጠላት እንደተማረከ እስረኛ ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ጠላቶቻቸው ምድራቸውን እስከያዙበት ቀን ድረስ” ወይም “ጠላቶቻቸው ማርከው እስከወሰዷቸው ቀን ድረስ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የሠራቸው
ሚካ አማልክቶቹን አልሠራቸውም፤ ይልቁንም ባለ ሙያ ነበር የሠራለት። አ.ት፡ “ተሠርተዉለት የነበሩት” ወይም “የእርሱ ባለ ሙያ የሠራለት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 19

1 በዚያም ዘመን፣ በእስራኤል ውስጥ ንጉሥ ባልነበረበት ጊዜ፣ በኮረብታማው የኤፍሬም አገር እጅግ በጣም ሩቅ በሆነ አካባቢ ለአጭር ጊዜ የኖረ አንድ ሌዋዊ ሰው ነበረ። እርሱም አንዲትን ሴት ቁባት አድርጎ ወሰዳት። 2 ነገር ግን ቁባቱ ለእርሱ ታማኝ አልነበረችም፤ እርሱን ተወችውና ተመልሳ ወደ አባትዋ ቤት ወደ ቤተ ልሔም ይሁዳ ሄደች። እርስዋም በዚያ አራት ወር ቆየች። 3 የዚያን ጊዜ ባልዋ ተነሣና ተመልሳ ወደ እርሱ እንድትመጣ ለማባበል ተከትሏት ሄደ። የእርሱ አገልጋይና ሁለት አህዮች ከእርሱ ጋር ነበሩ። እርስዋም ወደ አባትዋ ቤት አስገባችው።የልጅቱ አባት ባየው ጊዜ ደስ አለው። 4 የልጂቱ አባት፣ አማቱም በቤቱ ለሦስት ቀን እንዲቆይ ለመነው። እነርሱም በሉ፣ ጠጡ፣ ሌሊቱንም በዚያ አሳለፉ። 5 በአራተኛው ቀን ማልደው ተነሡ፣ እርሱም ለመሄድ ተዘጋጀ፣ ነገር ግን የልጂቱ አባት አማቹን እንዲህ አለው፣ “እንድትበረታ እንጀራ ብላ፣ ከዚያ መሄድ ትችላለህ።” 6 ስለዚህ ሁለቱም በአንድ ላይ ለመብላትና ለመጠጣት ተቀመጡ። ከዚያም የልጂቱ አባት እንዲህ አለ፣ “እባክህ ሌሊቱን ደግሞ እዚህ ለማሳለፍ ፈቃደኛ ሁን፣ መልካም ጊዜም ይሁንልህ።” 7 ሌዋዊው ለመሄድ በማለዳ በተነሳ ጊዜ፣ የወጣቷ ሴት አባት እንዲቆይ ለመነው፣ ከዚህ የተነሳ እቅዱን ለወጠና ሌሊቱን በዚያ አሳለፈ። 8 በአምስተኛው ቀን ለመሄድ ማልዶ ተነሣ፣ ነገር ግን የልጂቱ አባት እንዲህ አለ፣ “ሰውነትህን አበርታ፣ እስከ ማምሻ ድረስ ቆይ አለው። ስለዚህ ሁለቱም አብረው በሉ። 9 ሌዋዊው፣ ቁባቱና አገልጋዮቹ ለመሄድ በተነሱ ጊዜ፣ የልጂቱ አባት አማቱ እንዲህ አለው፣ “ተመልከት፣ አሁን ቀኑ እየመሸ ነው። እባክህ ሌላ ሌሊት በዚህ ቆዩ፣ መልካም ጊዜም ይሁንልህ። ነገ በማለዳ ተነስታችሁ ወደ ቤታችሁ ተመልሳችሁ መሄድ ትችላላችሁ።” 10 ነገር ግን ሌዋዊው ሌሊቱን በዚያ ለማሳለፍ ፈቃደኛ አልነበረም። ተነሳና ሄደ። ኢያሩሳሌምም ወደ ተባለችው ወደ ኢያቡስ ሄደ። ሁለት የተጫኑ አህዮች ነበሩት፣ ቁባቱም ከእርሱ ጋር ነበረች። 11 ወደ ኢያቡስም በቀረቡ ጊዜ መሸባቸው፣ አገልጋዩም ለጌታው እንዲህ አለው፣ “ና፣ ወደ ኢያቡሳውያን ከተማ እንሂድና ሌሊቱን በዚያ እናሳልፍ።” 12 ጌታውም፣ “የእስራኤል ሕዝብ ወገን ወዳልሆነ ወደ እንግዳ ሕዝብ ከተማ ውስጥ አንገባም። እኛ ወደ ጊብዓ እንሄዳለን።” 13 ሌዋዊውም ለወጣቱ ሰው እንዲህ አለው፣ “ና፣ ከእነዚህ ስፍራዎች ወደ አንዱ እንሂድ፣ ሌሊቱንም በጊብዓ ወይም በራማ እናሳልፍ።” 14 ስለዚህ መንገዳቸውን ቀጠሉ፣ የብንያም ነገድ ወደምትሆነው ወደ ጊብዓ ግዛት ሲቀርቡ ፀሐይ ገባችባቸው። 15 እነርሱም ሌሊቱን በጊብዓ ለማሳለፍ ወደዚያ አቀኑ። እርሱም ወደ ውስጥ ገባና በከተማው አደባባይ ተቀመጠ፣ ሌሊቱን በዚያ ያሳልፉ ዘንድ ወደ ቤቱ የወሰዳቸው ማንም ሰው አልነበረምና። 16 ነገር ግን በዚያን ጊዜ አንድ ሽማግሌ ሰው ከእርሻ ሥራው በምሽት እየመጣ ነበር። እርሱም ከኮረብታማው ከኤፍሬም አገር ነበረ፣ እርሱም በጊብዓ በእንግድነት ተቀምጦ ነበር። ነገር ግን በዚያ ስፍራ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ብንያማውያን ነበሩ። 17 እርሱም ዓይኑን አነሳና መንገደኛውን በከተማው አደባባይ አየው። ሽማግሌውም እንዲህ አለ፣ “ወዴት ትሄዳለህ? ከወዴትስ መጣህ?” 18 ሌዋዊውም እንዲህ አለው፣ “እኛ ከቤተ ልሔም ይሁዳ በጣም ሩቅ ወደሆነው ወደ ኮረብታማው ወደ ኤፍሬም አገር እንሄዳለን፣ እኔም የመጣሁት ከዚያ ነው። ወደ ቤተ ልሔም ይሁዳ ሄጄ ነበር፣ አሁን ወደ እግዚአብሔር ቤት እየሄድሁ ነው፣ ነገር ግን ወደ ቤቱ የሚወስደኝ ማንም ሰው የለም። 19 ለአህዮቻችን ገለባና ገፈራ አለን፣ ለእኔና እዚህ ላለችው ለሴት አገልጋይህ፣ ከአገልጋዮችህም ጋር ላለው ለዚህ ወጣት ሰው እንጀራና የወይን ጠጅ አለን። አንዳችም አላጣንም።” 20 ሽማግሌውም ሰላምታ አቀረበላቸው፣ “ሰላም ለእናንተ ይሁን! የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ እኔ እሰጣችኋለሁ። በአደባባይ ግን ሌሊቱን አትደሩ” አለው። 21 ስለዚህም ሰውየው ሌዋዊውን ወደ ቤቱ ወሰደው፣ ለአህዮቹም ገፈራ ሰጣቸው። እግራቸውን ታጠቡ፣ በሉም ጠጡም። 22 እነርሱም መልካም ጊዜ ነበራቸው፣ ክፉ የሆኑ የከተማይቱ ሰዎች ያደሩበትን ቤት ከበቡ፣ በሩንም ይደበድቡ ነበር። የቤቱ ባለቤት ለሆነው ለሽማግሌው እንዲህ አሉት፣ “ከእርሱ ጋር መተኛት እንድንችል ወደ ቤትህ የገባውን ሰው አምጣው።” 23 ሰውየውም፣ የቤቱ ባለቤት፣ ወደ እነርሱ ሄደና እንዲህ አላቸው፣ “አይሆንም፣ ወንድሞቼ ሆይ፣ ይህን ክፉ ነገር እባካችሁ አታድርጉ! ይህ ሰው ወደ ቤቴ የገባ እንግዳ ስለሆነ፣ ይህን ክፉ ነገር አትሥሩ። 24 ተመልከቱ፣ ድንግል ልጄና የእርሱም ቁባት እዚህ አሉ። አሁን ሄጄ ላምጣቸው። አስነውሩአቸው፣ የፈለጋችሁትንም አድርጉባቸው። ነገር ግን በዚህ ሰው ላይ እንደዚህ ያለ ክፉ ነገር አታድርጉበት!” 25 ነገር ግን ሰዎቹ እርሱን አልሰሙትም፣ ስለዚህ ሰውዮው ቁባቱን ያዛትና ወደ ውጭ አወጣላቸው። እነርሱም ያዟትና ከእርሷ ጋር ተኙ፣ ሌሊቱን በሙሉ አመነዘሩባት፣ ጎህም ሲቀድ ለቀቁአት። 26 ሴቲቱም በማለዳ መጣችና ጌታዋ ባለበት በሰውዮው ቤት በር ወደቀች፣ ጸሐይ እስኪወጣ ድረስ እዚያው ተዘረረች። 27 ጌታዋም በማለዳ ተነሣና የቤቱን በር ከፈተ፣ መንገዱንም ለመሄድ ወጣ። እርሱም ቁባቱ እጅዋን በመድረኩ ላይ ዘርግታ በበሩ ተዘርራ አያት። 28 ሌዋዊውም እንዲህ አላት፣ “ተነሺ። እንሂድ።” ነገር ግን ምንም መልስ አልነበረም። እርሱም በአህያው ላይ ጫናት፣ ተነሥቶም ወደ ቤቱ ሄደ። 29 ሌዋዊውም ወደ ቤቱ በመጣ ጊዜ፣ ቢላዋ ወሰደ፣ ቁባቱንም ይዞ ቆራረጣት፣ ብልት በብልት ለአሥራ ሁለት ቄራርጦ ቁራጮቹን ወደ እስራኤል አገር ሁሉ ላከው። 30 ይህንን ያየ ሁሉ እንዲህ አለ፣ “የእስራኤል ሕዝብ ከግብፅ ምድር ከወጡ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ እንዲህ ያለ ነገር ከቶ አልተደረገም ወይም አልታየም። ስለ ነገሩ አስቡበት! ምክር ስጡን! ምን ማድረግ እንዳለብን ንገሩን!”

Judges 19:1

በእነዚያ ቀናት
ይህ ሐረግ በታሪክ ፍሰቱ ላይ የሌላ ሁነትን ጅማሬ ያስተዋውቃል። (አዲስ ሁነትን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)

ሩቅ
አብዛኞቹ ሰዎች ከሚኖሩበት የራቀ

ለእርሱ ታማኝ አልነበረችም
ይህ ማለት እርሷ ለግንኙነታቸው ታማኝ አልነበረችምና ከሌሎች ወንዶች ጋር መተኛት ጀምራለች ማለት ነው። አስፈላጊ ከሆነ ይህ በግልጽ መነገር ይችላል። አ.ት፡ “ከሌሎች ወንዶች ጋር መተኛት ጀመረች”

Judges 19:3

አገልጋዩና ሁለት አህዮች ከእርሱ ጋር ነበሩ
“ከእርሱ ጋር አገልጋዩንና ሁለት አህዮችን ወሰደ”

ዐማቱ፣ የልጅቱ አባት አግባባው
“ዐማቱ፣ ይኸውም የልጅቱ አባት አግባባው” ወይም “የልጅቱ አባት አግባባው”

እንዲቆይ አግባባው
“ስለተናገረው ለመቆየት ወሰነ”

Judges 19:5

አዘጋጀ
ሌዋዊው አዘጋጀ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በቁራሽ እንጀራ ራስህን አበርታ
እዚህ ጋ “እንጀራ” “ምግብ”ን ያመለክታል። አ.ት፡ “ለመጓዝ እንድትበረታ ጥቂት ምግብ ብላ”

ምሽቱን ለማሳለፍ እባክህ ፈቃድህ ይሁን
“እባክህ ደግመህ እደር”

Judges 19:7

ራስህን እያበረታህ እስከ ከሰዓት ቆይ
አማቱ በመብላት ራሱን እንዲያበረታ አሳብ እየሰጠው ነው። ለመሄድ እስከ ከሰዓት እንዲቆይም እየጠየቀው ነው። ይህ በግልጽ መነገር ይችላል። አ.ት፡ “ለመጓዝ እንድትበረታ ጥቂት ምግብ ብላ፤ እስከ ከሰዓት ቆይና ትሄዳለህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና የሚለውን ተመልከት)

Judges 19:9

አሁን ቀኑ ወደ መምሸቱ ቀርቧል
“ቀኑ እየተገባደደ ነው” ወይም “ምሽት ሊሆን ነው”

Judges 19:10

ይህም ኢየሩሳሌም ነው
“ከጊዜ በኋላ ኢየሩሳሌም ተብላ ተጠርታለች”

የተጫኑ ጥንድ አህዮች ነበሩት
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በሁለቱ አህዮቹ ላይ ኮርቻዎችን ጫነባቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ና፣ እንሂድ
ይህ አሳብ ለመስጠት የሚጠቅም የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ብንሄድ ይሻላል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ወደ ... ጎራ እንበል
ይህ ማለት ጉዟቸውን በመግታት የሆነ ቦታ ላይ እንዲያርፉ ማለት ነው። አ.ት፡ “እዚህ ጋ እንቆይ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Judges 19:12

ወደ ... ጎራ እንበል
ይህ ማለት ጉዟቸውን በመግታት የሆነ ቦታ ላይ እንዲያርፉ ማለት ነው። ተመሳሳዩን ሐረግ በመሳፍንት 19:11 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እዚህ ጋር እንረፍ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ና፣ እንዲህ እናድርግ
ይህ አሳብ ለመስጠት ጥቅም ላይ የዋለ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “እንድ... አሳብ አቀርባለሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Judges 19:14

ጎራ አሉ
ይህ ማለት ጉዟቸውን በመግታት የሆነ ቦታ ላይ እንዲያርፉ ማለት ነው። ተመሳሳዩን ሐረግ በመሳፍንት 19:11 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ቆሙ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በከተማይቱ አደባባይ
ሰዎች ቀን ላይ የሚሰባሰቡበት የገበያ ስፍራ

ወደ ቤቱ ወሰዳቸው
የዚህ ሐረግ ትርጉም አንድ ሰው በቤቱ እንዲያደሩ ጋበዛቸው ማለት ነው። አ.ት፡ “ያንን ሌሊት በቤታቸው እንዲያሳልፉ ጋበዟቸው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Judges 19:16

ብንያማውያን
ብንያማዊ ሰው የብንያም ተወላጅ ነበር። ይህንን የሕዝብ ወገን ስም በመሳፍንት 3:15 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ዓይኖቹን አንስቶ
ሰውየው ቀና አለና በዙሪያው ያለውን ተመለከተ። አ.ት፡ “ቀና አለ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በከተማይቱ አደባባይ
ሰዎች ቀን ላይ የሚሰባሰቡበት የገበያ ስፍራ። ይህንን በመሳፍንት 19:14 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Judges 19:18

ወደ ቤቱ የሚወስደኝ ማነው
ይህ ሐረግ የሚያመለክተው ሌሊቱን በዚያ እንዲያሳልፍ ሌላውን ሰው ወደ ቤቱ የሚጋብዝን ሰው ነው። አ.ት፡ “በቤቱ እንዳድር የጋበዘኝ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የሚወስደኝ
እዚህ ጋ ሌዋዊው “እኔ” ይላል፣ ነገር ግን እርሱ እያመለከተ ያለው ራሱን፣ አገልጋዩንና ቁባቱን ጭምር ነው። አ.ት፡ “የሚወስደን”

በዚያ እንጀራና ወይን አለ
ወደ አድራጊ ድምፅ ቀይረው። አ.ት፡ “ብዙ እንጀራና ወይን አለን” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ለእኔና ለሴት አገልጋይህ፣ እንዲሁም ከአገልጋይህ ጋር ላለው ለዚህ ወጣት
ሌዋዊው አክብሮቱን ለማሳየት ራሱንና ከእርሱ ጋር ያሉትን ሌሎቹንም በሦስተኛ መደብ አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “እኔ፣ ቁባቴና አገልጋዬ” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

የጎደለን ምንም የለም
ይህ አዎንታዊ መግለጫ ሆኖ ሊጻፍ ይችላል። አ.ት፡ “የሚያስፈልገን ሁሉ አለን”

Judges 19:20

ብቻ አትደፉ
“አትደፉ”። “ብቻ” የሚለው ቃል እዚህ ጋ ጥቅም ላይ የዋለው ሌዋዊው እንዲያደርግ ስላልፈለገው ጉዳይ አጽንዖት ለመስጠት ነው።

አደባባይ
ይህ የከተማይቱን አደባባይ ያመለክታል። ይህንን በመሳፍንት 19:17 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሌዋዊውን ወደ ቤቱ አመጣው
ይህ ማለት ሌዋዊው በቤቱ እንዲያድር ጋበዘው ማለት ነው። ሌዋዊውን በመጋበዙ ቁባቱንና አገልጋዩንም ደግሞ ጋብዟቸዋል። አ.ት፡ “ሌዋዊውንና አገልጋዮቹን በቤቱ እንዲያድሩ ጋበዛቸው” (የአነጋገር ዘይቤ እና የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Judges 19:22

ልባቸውን ያስደስቱ ነበር
“ልባቸውን ያሰደስቱ” የሚለው ሐረግ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ከአንድ ሰው ጋር ጥሩ ጊዜ ማሳለፍ ማለት ነው። አ.ት፡ “በአንድ ላይ ጥሩ ጊዜ እያሳለፉ ነበር” ወይም “ራሳቸውን ያስደስቱ ነበር” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

አንዳንድ ሰዎች -- ቤቱን ከበቡት
አንዳንድ ሰዎች በቤቱ ዙሪያ ቆሙ

Judges 19:24

ተመልከቱ
ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው የሰዎቹን ትኩረት ለማግኘት ነው። አ.ት፡ “አድምጡ”

ሰዎቹ አልሰሙትም
እዚህ ጋ ደራሲው “መስማት” በማለት የሚናገረው ስለ “መስማማት” ነው። አ.ት፡ “ሰዎቹ ግብዣውን አለተቀበሉትም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሰውየው ቁባቱን ይዞ
የሰውየው ማንነት አሻሚ ነው። አ.ት፡ “ሌዋዊው ቁባቱን ይዞ”

ማለዳ ላይ
“ፀሐይ በምትወጣበት ጊዜ” ወይም “ንጋት ሲሆን” ይህ ፀሐይ መውጣት የጀመረችበትን ጊዜ ያመለክታል።

ነግቶ ነበር
ይህ ውጪው ብርሃን የሆነበትን ጠዋት ያመለክታል። አ.ት፡ “ፀሐይ ሙሉ በሙሉ ወጥታ ነበር” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Judges 19:27

ይሁን እንጂ ምንም ምላሽ አልነበረም
ሴቲቱ ሞታ ስለነበር ምላሽ አልሰጠችም። ይህ በግልጽ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ይሁን እንጂ ሞታ ስለነበር አልመለሰችለትም”

Judges 19:29

የተቆራረጠ አካል
“በክፍል በክፍል”። ደራሲው ይህንን ሥዕላዊ መግለጫ የሚጠቀመው ሌዋዊው አካሏን በተለየ አኳኋን በመቆራረጥ ስላደረገው ነገር አጽንዖት ለመስጠት ነው። “የተቆራረጠ አካል” የአንድን ሰው እጅና እግር ያመለክታል። በቋንቋህ ተመሳሳይ ሐረግ ከሌለ ይህ አገላለጽ ከትርጉምህ ውስጥ መቅረት ይኖርበት ይሆናል። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

አሥራ ሁለት ቁርጥራጭ
“12 ቁርጥራጭ” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ቁርጥራጮቹን በእስራኤል ምድር ወደ ሁሉም ስፍራ ላካቸው
ይህ ማለት የተለያዩ ቁርጥራጮቹን ወደ አሥራ ሁለት የእስራኤል አካባቢዎች ልኳል ማለት ነው። አ.ት፡ “እያንዳንዱን ቁራጭ ወደ ተለያዩ የእስራኤል ክፍሎች ልኳል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 20

1 የዚያን ጊዜ የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ እንደ አንድ ሰው ሆነው ወጡ፣ ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ድረስ፣ የገለዓድ አገር ሰዎችንም ጨምሮ፣ በእግዚአብሔር ፊት
በምጽጳ ተሰበሰቡ። 2 የሕዝቡም ሁሉ መሪዎች፣ የእስራኤል ነገዶች ሁሉ፣ እግረኞች ሆነው በሰይፍ የሚዋጉ 400, 000 ሰዎች በእግዚአብሔር ሕዝብ ጉባኤ
ውስጥ ስፍራቸውን ያዙ። 3 በዚህ ጊዜ የእስራኤል ሕዝብ እስከ ምጽጳ ድረስ እንደ ሄዱ የብንያም ሕዝብ ሰሙ። የእስራኤልም ሕዝብ እንዲህ አሉ፣ “ይህ ክፉ
ነገር እንዴት እንደ ተደረገ ንገሩን?” 4 ሌዋዊውም፣ የተገደለችው ሴት ባል፣ እንዲህ ብሎ መለሰ፣ “እኔና ቁባቴ ሌሊቱን በዚያ ለማሳለፍ የብንያም ግዛት
ወደሆነችው ወደ ጊብዓ መጣን። 5 በዚያ ሌሊት የጊብዓ ሰዎች በእኔ ላይ ተነሱ፣ ሊገድሉኝም አስበው ቤቱን ከበቡት። ቁባቴንም ያዙና ከእርስዋ ጋር ተኙ፣
እርስዋም ሞተች። 6 እኔም ቁባቴን ወሰድሁና ሰውነቷን ቆራረጌጥኋት፣ ቁርጥራጩንም በእስራኤል ርስት ወደሚገኝ ወደ እያንዳንዱ ክልል ላክሁት፣ ምክንያቱም
እንዲህ ዓይነቱን ክፋትና መአት በእስራኤል ላይ ፈጽመዋልና። 7 አሁንም፣ እናንተ እስራኤላውያን ሁላችሁም ተነጋገሩ፣ ምክራችሁንም ስጡ፣ ለዚህ ነገርም
ፍርዳችሁን ስጡ!” 8 ሕዝቡም ሁሉ እንደ አንድ ሰው ሆነው በአንድ ላይ ተነሱ፣ እንዲህም አሉ፣ “ከእኛ ዘንድ ማንም ሰው ወደ ድንኳኑ አይሄድም፣ ማንም ሰው
ወደ ቤቱ አይመለስም! 9 ነገር ግን አሁንም በጊብዓ ላይ ማድረግ ያለብን ነገር ይህ ነው፦ ዕጣው እንደሚመራን እንወጋታለን። 10 ከእስራኤል ነገዶች በሙሉ
ለሕዝቡ ስንቅ እንዲይዙ ከመቶው አስር ሰው፣ ከሺህ መቶ ሰው፣ ከአስር ሺህ አንድ ሺህ ሰው እንወስዳለን፣ ይህም ሕዝቡ ወደ ብንያም ጊብዓ በሚመጣበት ጊዜ
እነርሱ በእስራኤል ላይ ለፈጸሙት ክፋት ይቀጧቸው ዘንድ ነው።” 11 ስለዚህም የእስራኤል ወታደሮች በሙሉ በአንድ ዓላማ በመስማማት በከተማይቱ ላይ
ለመዝመት ተሰበሰቡ። 12 የእስራኤልም ነገዶች ወደ ብንያም ነገድ ሁሉ እንዲህ ብለው ሰዎችን ላኩ፣ “በእናንተ መካከል የተደረገው ይህ ክፉ ነገር ምንድር
ነው? 13 ስለዚህ እንድንገድላቸውና ይህንን ክፋት ከእስራኤል ሙሉ ለሙሉ ለማስወገድ በጊብዓ ውስጥ ያሉትን እነዚህን ክፉ ሰዎች አውጥታችሁ ስጡን።”
ነገር ግን ብንያማውያን የወንድሞቻቸውን የእስራኤልን ሕዝብ ቃል አልሰሙም። 14 የዚያን ጊዜ የብንያም ሕዝብ ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ለመዋጋት ዝግጅት
ያደርጉ ዘንድ ከየከተማው ወጥተው ወደ ጊብዓ ተሰበሰቡ። 15 የብንያም ሕዝብ ከየከተማው በአንድ ላይ ለመዋጋት መጡ፣ በዚያም ቀን በሰይፍ ስለት
ለመዋጋት የሰለጠኑ 26, 000 ወታደሮች ነበሩ፤ ከዚህ በተጨማሪ ከጊብዓ ነዋሪዎች ሰባት መቶ የተመረጡ ሰዎች ተቈጠሩ። 16 ከእነዚህ ወታደሮች መካከል
ሰባት መቶ የተመረጡ ግራኝ ሰዎች ነበሩ፤ እያንዳንዳቸውም ድንጋይ ወንጭፈው አንዲት ጠጕርስ እንኳ አይስቱም። 17 የእስራኤል ወታደሮች፣ ከብንያም ወገን
የሆኑትን ሳይጨምር፣ በሰይፍ ስለት ለመዋጋት የሰለጠኑ አራት መቶ ሺህ ሰዎች ተቆጠሩ። እነዚህ በሙሉ የጦር ሰዎች ነበሩ። 18 የእስራኤልም ሕዝብ ተነሱ፣
ወደ ቤቴል ወጡ፣ ከእግዚአብሔርም ምክር ጠየቁ። እንዲህም ብለው ጠየቁ፣ “የብንያምን ልጆች ለመውጋት ለእኛ መጀመርያ ማን ይውጣልን?”
እግዚአብሔርም እንዲህ አለ፣ “ይሁዳ በመጀመርያ ይዋጋል።” 19 የእስራኤልም ሕዝብ በማለዳ ተነሱና በጊብዓ ፊት ለወጊያ ተዘጋጁ። 20 የእስራኤልም
ወታደሮች ከብንያም ጋር ለመዋጋት ወጡ። እነርሱም በጊብዓ ከእነርሱ ጋር ለመዋጋት ቦታ ቦታቸውን ይዘው ተሰለፉ። 21 የብንያም ወታደሮች ከጊብዓ ወጥተው
መጡ፣ በዚያም ቀን ከእስራኤላውያን ሰራዊት 22, 000 ሰዎች ገደሉ። 22 ነገር ግን የእስራኤል ወታደሮች ራሳቸውን አበረቱ፣ በመጀመርያው ቀን ተሰልፈው
በነበረበት ስፍራ ላይ እንደገና ቦታ ቦታቸውን በመያዝ የውጊያውን መስመር አዘጋጁ። 23 የእስራኤልም ሕዝብ ወደ ላይ ወጡና እስከ ማታ ድረስ በእግዚአብሔር
ፊት አለቀሱ፡፡ከእግዚአብሔርም ምሪትን ፈለጉ እንዲህም ብለው ጠየቁ፣ “ከወንድሞቻችን ከብንያም ሕዝብ ጋር ለመዋጋት እንደገና ወደዚያ መቅረብ
ይገባናልን?” እግዚአብሔርም “በእነርሱ ላይ ውጡና ግጠሟቸው” አለ። 24 ስለዚህም በሁለተኛው ቀን የእስራኤል ወታደሮች የብንያምን ወታደሮች ለመዋጋት
ሄዱ። 25 በሁለተኛው ቀን የብንያም ወታደሮች ከጊብዓ እነርሱን ሊወጉ ወጡና ከእስራኤል ወታደሮች 18, 000 ሰዎች ገደሉ። እነዚህም ሰዎች ሁሉ በሰይፍ
ለመዋጋት የሰለጠኑ ነበሩ። 26 የዚያን ጊዜ የእስራኤል ወታደሮች ሁሉ፣ ሕዝቡም ሁሉ ወደ ቤቴል ወጡና አለቀሱ፣ በዚያም በእግዚአብሔር ፊት ተቀመጡ፣
እነርሱም በዚያ ቀን እስከ ምሽት ድረስ ጾሙ፣ በእግዚአብሔር ፊት የሚቃጠል መሥዋዕትና የሰላም መሥዋዕት አቀረቡ። 27 የእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔርን
ጠየቁ፣ በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት በዚያ ነበረ፣ 28 በእነዚህ ጊዜያቶች የአሮን ልጅ የአልዓዛር ልጅ ፊንሐስ በታቦቱ ፊት ያገለግል ነበር፣
“ከወንድሞቻችን ከብንያም ሕዝብ ጋር አንድ ጊዜ ለመዋጋት እንደገና እንሂድ ወይስ እንቅር?” እግዚአብሔርም እንዲህ አለ፣ “ጥቃት ፈጽሙባቸው፣ ነገ እነርሱን
እንድታሸንፉ እረዳችኋለሁና።” 29 ስለዚህ እስራኤል በጊብዓ ዙሪያ በምስጢራዊ ስፍራዎች የተደበቁ ሰዎች አኖሩ። 30 የእስራኤል ወታደሮች ከብንያም
ወታደሮች ጋር ለሦስተኛ ቀን ተዋጉ፣ ከዚህ በፊት እንዳደረጉት በጊብዓ ላይ የውጊያ መስመራቸውን ዘርግተው ተሰለፉ። 31 የብንያምም ሕዝብ ሄዱና ሕዝቡን
ተዋጉ፣ ከከተማይቱም እንዲወጡ ተደረጉ። ከሕዝቡም አንዳንዶቹን መግደል ጀመሩ። ከእስራኤልም ወገን የሞቱ ሠላሳ የሚያህሉ ሰዎች በእርሻዎቹና
በመንገዶቹ ነበሩ፣ ከመንገዶቹ አንዱ ወደ ቤቴል የሚወስድ ነው፣ ሌላኛው ደግሞ ወደ ጊብዓ የሚወስድ ነው። 32 የዚን ጊዜ የብንያምም ሕዝብ እንዲህ አሉ፣
“እንደ በፊቱ ተሸንፈዋል፣ ከእኛ እየሸሹ ነው።” ነገር ግን የእስራኤል ወታደሮች እንዲህ አሉ፣ “እንሸሽ፣ ከከተማይቱ እንዲወጡና ወደ መንገዶቹ እንዲሄዱ
እናድርጋቸው።” 33 የእስራኤልም ወታደሮች በሙሉ ከስፍራቸው ተነሱና በበኣልታማር ለውጊያ ራሳቸውን አዘጋጅተው ተሰለፉ። በምስጢራዊ ስፍራ ተደብቀው
የነበሩት የእስራኤል ወታደሮችም ከነበሩበት ስፍራ ከጊብዓ ወጥተው ሮጡ። 34 ከእስራኤልም ሁሉ 10, 000 የተመረጡ ሰዎች በጊብዓ ላይ መጡ፣
ጦርነቱም በርትቶ ነበር፣ ነገር ግን ብንያማውያን ጥፋት ወደ እነርሱ ቀርቦ እንደነበር አላወቁም። 35 እግዚአብሔርም ብንያምን በእስራኤል ፊት ድል አደረገ።
በዚያም ቀን የእስራኤል ወታደሮች 25, 100 የብንያም ሰዎችን ገደሉ። የሞቱት ሰዎች በሙሉ በሰይፍ ለመዋጋት ስልጠና የወሰዱ ነበሩ። 36 ስለዚህ
የብንያም ወታደሮች እንደ ተሸነፉ አዩ። የእስራኤልም ሰዎች ለብንያም ስፍራ ለቀቁላቸው፣ ምክንያቱም ከጊብዓ ውጭ በድብቅ ስፍራዎች ባስቀመጡአቸው ሰዎች
ላይ ተማምነው ነበርና። 37 የዚያን ጊዜ ተደብቀው የነበሩት ሰዎች ተነሱና ፈጥነው ወደ ጊብዓ ሮጡ፣ በከተማይቱም ውስጥ የሚኖረውን ሰው በሙሉ
በሰይፋቸው ገደሉ። 38 በእስራኤል ወታደሮችና በምስጢር በተደበቁት ሰዎች መካከል ከከተማው የታላቅ ጢስ ደመና በምልክትነት እንዲያስነሡ ስምምነት
ተደርጎ ነበር። 39 የእስራኤልም ወታደሮች በውጊያው ጊዜ ከጦርነቱ ርቀው እንዲያፈገፍጉ ነበር። የዚያን ጊዜ ብንያማውያን ማጥቃት ጀመሩ ሠላሳ
የእስራኤልንም ሰዎች ገደሉ፣ እነርሱም እንዲህ አሉ፣ “እንደ መጀመርያው የጦርነት ጊዜ በእኛ ፊት መሸነፋቸው እርግጠኛ ነው።” 40 ነገር ግን የጢሱ ዓምድ
ከከተማው ወደ ላይ መውጣት በጀመረ ጊዜ፣ ብንያማውያን ወደ ኋላቸው ሲመለከቱ ጢሱ ከከተማዋ በሙሉ ወደ ሰማይ ሲወጣ አዩ። 41 የዚያን ጊዜ
የእስራኤል ወታደሮች ዞረው አጠቋቸው። የብንያም ሰዎችም ደነገጡ፣ በእነርሱ ላይ ጥፋት እንደመጣባቸው አይተዋልና። 42 ስለዚህ ከእስራኤል ወታደሮች
ተመልሰው ወደ ምድረ በዳው መንገድ ሸሹ። ነገር ግን ውጊያው ተከታትሎ ደረሰባቸው። የእስራኤልም ወታደሮች ከከተማዎቹ ወጡና በቆሙበት ስፍራ
ገደሉአቸው። 43 እነርሱም ብንያማውያንን ከበቡና ተከትለዋቸው ሄዱ፤ በመኑሔም አሸነፉአቸው፣ ከጊብዓ በስተ ምሥራቅ በኩል እስካለው ስፍራ ድረስ
አሳደዱአቸው። 44 ከብንያም ነገድም 18, 000 ወታደሮች ሞቱ፣ እነዚህ ሰዎች በሙሉ በጦርነት ምርጥ ተዋጊዎች ነበሩ። 45 እነርሱም ተመልሰው በምድረ
በዳ ወዳለው ወደ ሬሞን ዓለት ሸሹ። እስራኤላውያንም ከእነርሱ ተጨማሪ አምስት ሺህ ሰዎችን በየመንገዱ ገደሉ። እነርሱም ተከታተሉአቸው፣ ወደ ጊድአምም
በቅርብ እየተከታተሉአቸው ተጨማሪ ሁለት ሺህ ሰዎችን ገደሉ። 46 በዚያ ቀን የሞቱት የቢኒያም ወታደሮች በሙሉ 25, 000 በሰይፍ ለመዋጋት ልዩ ስልጠና
የወሰዱ ሰዎች ነበሩ፤ እነዚህ በሙሉ በጦርነት ምርጥ ተዋጊዎች ነበሩ። 47 ነገር ግን ስድስት መቶ ሰዎች ተመልሰው በምድረ በዳ ወዳለው ወደ ሬሞን ዓለት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሸሹ። ለአራት ወራት ያህል በሬሞን ዓለት ተቀመጡ። **48** የእስራኤልም ወታደሮች በብንያም ሕዝብ ላይ እንደገና ተመለሱ፣ ሞላውን ከተማ፣ ከብቶችንና ያገኙትንም ሁሉ አጠቁ ደግሞም ገደሉ። በመንገዳቸው ያገኙትን ማንኛውንም ከተማ ሁሉ በእሳት አቃጠሉ።

Judges 20:1

እንደ አንድ ሰው
ይህ ንጽጽር የሚናገረው አንድ ቡድን እንደ አንድ ሰው መንቀሳቀሱን ነው። ይህ የሚያመለክተው በቡድን የሆኑ ሰዎች በተመሳሳይ መንገድ ሁሉንም ነገር በጋራ የሚያደርጉ መሆናቸውን ነው። አ.ት፡ “አንድ ሰው የሆኑ ያህል” (ንጽጽር የሚለውን ተመልከት)

ከዳን እስከ ቤርሳቤህ
ይህ በጥቅሉ ምድሪቱን ያመለክታል። አ.ት፡ “ከአሥራ አንዱ ነገዶች በሙሉ”

እግዚአብሔር -- **400,000** እግረኛ ሰዎች
“እግዚአብሔርና በተጨማሪም 400,000 መደበኛ ወታደሮች መጡ”

ለውጊያ የተዘጋጁ
“ወደ ጦርነት ለመሄድ ብቁ የሆኑ”። የሚሄዱት እርስ በእርስ ለመዋጋት አልነበረም።

Judges 20:3

አሁን
ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው ዋናው የትረካ መስመር ለአፍታ መገታቱን ለማሳየት ነው። እዚህ ጋ የመጽሐፉ ደራሲ የብንያም ሰዎች ስለሚያውቁት ነገር ዳራዊ መረጃ ይናገራል። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ወደ ምጽጳ ወጥተው ነበር
ምጽጳ የምትገኘው ከፍ ባሉት ተራራዎች ላይ ነበር።

ሌሊቱን ለማሳለፍ
“ለሌሊቱ” ወይም “አንድ ሌሊት ለማደር”

Judges 20:5

ክፋትና የጭካኔ ተግባር
“የጭካኔ ተግባር” የሚለው ቃል “ክፋት”ን ያብራራዋል። አ.ት፡ “አሰቃቂ ክፋት”

አሁን
ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው የሌዋዊውን ንግግር መደምደሚያ ለማስተዋወቅ ነው።

እዚህ ላይ አስተያየትና ምክራችሁን ስጡ
“አስተያየት” እና “ምክር” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት አንድን ነገር ሲሆን አጽንዖት ለመስጠት ተደግመዋል። ሁለቱ ሊጣመሩ ይችላሉ። አ.ት፡ “ስለዚህ ጉዳይ ምን ማድረግ እንደሚኖርብን ወስኑ”

Judges 20:8

እንደ አንድ
ይህ ንጽጽር የሚናገረው እንደ አንድ ሰው ስለሚንቀሳቀስ ቡድን ነው። ሁሉም በተመሳሳይ መንገድ በአንድ ላይ ተንቀሳቀሱ። አ.ት፡ “አንድ ሰው የሆኑ ያህል” (ንጽጽር የሚለውን ተመልከት)

ከእኛ ማንም ወደ ድንኳኑ አይሄድም ... ከእኛ ማንም ወደ ቤቱ አይመለስም
እነዚህ ሁለት አንቀጾች ስለ አንድ ነገር ሁለቴ መናገራቸው በመሠረቱ አጽንዖት ለመስጠት ነው። ሊጣመሩ ይችላሉ። “ማንም . . . አይሄድም” እና “ማንም . . . አይመለስም” የሚሉት ቃላት ሰዎቹ በዚያ መቆየታቸውን እንዴት እንደሚቀጥሉ አጽንዖት ይሰጣል። በአዎንታዊ ድምፅ ሊነገሩ ይችላሉ። አ.ት፡ “ሁላችንም እዚሁ እንቆያለን”

አሁን ግን
እነዚህ ቃላት ሰዎቹ ከመጀመሪያው ጩኸት በኋላ የተናገሩትን ዐቢይ ጉዳይ ያስተዋውቃሉ።

ዕጣው እንደ መራቸው
እግዚአብሔር የሚፈልገውን ለማወቅ ምልክት የተደረገባቸውን ጠጠሮች መወርወርን ወይም ማንከባለልን ያካትታል።

Judges 20:10

ከመቶ ሰዎች አሥሩ . . . ከሺህ አንድ መቶ . . . ከአሥር ሺ አንድ ሺ
“ከ100 ሰው 10፣ ከ1,000 ሰው 100፣ ከ10,000 ሰው 1,000” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

አቅርቦቶች
ሰዎቹ የሚያስፈልጋቸው ምግብና ሌሎች ነገሮች

በከተማይቱ ላይ ተሰበሰቡ
“ከተማይቱን ለመውጋት በአንድ ላይ ተሰበሰቡ”

Judges 20:12

ለሞት አብቋቸው
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ግደሏቸው” ወይም “አስወግዷቸው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የወንድሞቻቸው ድምፅ
እዚህ ጋ “ድምፅ” የሚያመለክተው የተናገሩትን መልዕክታቸውን ነው። አ.ት፡ “ወንድሞቻቸው የተናገሩትን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 20:15

ሃያ ስድስት ሺህ
“26,000” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ሰባት መቶ
“700” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ግራኝ
ግራኝ የሆነ ሰው ከቀኝ እጃቸው ይልቅ በግራ እጃቸው የበለጠ መሥራት ከሚችሉ ሰዎች አንዱ ነው።

ድንጋይ በማስወንጨፍ ጸጉር የማይስቱ
ይህ የሚያመለክተው በሚያስደንቅ ሁኔታ ዒላማቸውን የሚመቱ መሆናቸውን ነው። ይህ በአዎንታዊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በጸጉር ላይ እንኳን ድንጋይ ወርውረው መምታት ይችላሉ” ወይም “እንደ ጸጉር በቀጠነ ነገር ላይ ድንጋይ ወርውረው መምታት ይችላሉ”

Judges 20:17

ሳይቆጠሩ
“ሳይጨመሩ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

400,000
“አራት መቶ ሺህ ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

የእግዚአብሔርን ምሪት
“ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔርን ጠየቁ” ወይም “እንዴት መቀጠል እንዳለባቸው እግዚአብሔርን ጠየቁ”

Judges 20:19

ሠፈራቸውን ወደ ጊብዓ አዛወሩ
ስለ ዕብራይስጡ ጽሑፍ ትርጓሜ አንዳንድ ጥያቄዎች አሉ። ሠፈራቸውን በጊብዓ አቅራቢያ አደረጉ ከሚለው ትርጉም ይልቅ ሰራዊቱ ተጉዞ በጊብዓ ትይዩ ለጦርነት ተዘጋጅተው ቆሙ ማለት ይሆናል።

ሃያ ሁለት ሺህ
“22,000” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

Judges 20:22

ራሳቸውን አበረታቱ
እዚህ ጋ “አበረታቱ” የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን እርስ በእርሳቸው ተበረታቱ ማለት ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ለጦርነት ተሰለፉ
ይህ ምናልባት እስራኤላውያኑ በመሰለፍ ለቀጣዩ ቀን ጦርነት ተዘጋጅተዋል ማለት ሊሆን ይችላል። አ.ት፡ “በቀጣዩ ቀን ለመዋጋት ተዘጋጁ”

ከእግዚአብሔር ምሪት ፈለጉ
እንዴት ባለ መንገድ እንደ ፈለጉ አልተገለጸም። ምናልባት ካህኑ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ዕጣ ጥሎ ይሆናል።

Judges 20:24

አሥራ ስምንት ሺህ
“18,000” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

Judges 20:26

በእግዚአብሔር ፊት
“በእግዚአብሔር ሀልዎት” ወይም “ለእግዚአብሔር”

Judges 20:27

የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት . . . በእነዚያ ቀናት በታቦቱ ፊት ያገለግል ነበር
ይህ አንባቢው፣ ሕዝቡ እግዚአብሔር ምላሽ እንዲሰጣቸው እንዴት እንደጠየቁ መገንዘብ እንዲችል ለመርዳት ደራሲው የጨመረው ዳራዊ መረጃ ነው። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

በእነዚያ ቀናት በዚያ ነበር
“በእነዚያ ቀናት በቤቴል ነበር”

በታቦቱ ፊት ያገለግል ነበር
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “በታቦቱ ፊት በክህነት ያገለግል ነበር”

ማጥቃት
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “የብንያምን ሰራዊት አጥቁ”

Judges 20:29

እስራኤል ሰዎቹን ቦታ አስያዙ
እዚህ ጋ “እስራኤል” የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። አ.ት፡ “እስራኤላውያን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ድብቅ ቦታዎች
“በደፈጣ”

Judges 20:31

ከሰዎቹ ጋር ተዋጉ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “ከእስራኤል ሰዎች ጋር ተዋጉ”

ከከተማይቱ ተስበው ወጡ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የእስራኤል ሰዎች ከከተማይቱ ስበው አወጧቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ከሰዎቹ ጥቂቶቹን መግደል ጀመሩ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “የብንያም ሰዎች ከእስራኤል ሰዎች ጥቂቶቹን መግደል ጀመሩ”

Judges 20:32

ልክ እንደ መጀመሪያው
“ልክ እንደ ቀድሞው” ወይም “ልክ እንደ መጀመሪያዎቹ ሁለት ጊዜያት”

በኣል ታማር
ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ማሬህ ጊብዓ
ይህ የአንድ ቦታ ስም ነው። ሌሎች ትርጉሞች ምናልባት “የጊብዓ ሜዳዎች” ወይም “ከጊብዓ በስተምዕራብ” ወይም “ማሬህ ጌባ” (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Judges 20:34

አሥር ሺህ
“10,000” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

የተመረጡ ሰዎች
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን እነዚህ በተለየ ሁኔታ ጥሩ ወታደሮች ነበሩ ማለት ነው። አ.ት፡ “በሚገባ የሰለጠኑ ወታደሮች” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ጥፋታቸው እንደ ቀረበ
እዚህ ጋ የጥፋት መቅረብ አጠገባቸው እንደ ቆመ ያህል ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ወዲያውኑ ፈጽሞ ሊሸነፉ ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

25,100 ሰዎች
“ሃያ አምስት ሺህ አንድ መቶ ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Judges 20:36

የእስራኤል ሰዎች ከጊብዓ ውጪ . . . ባሉት ሰዎች ስለተማመኑ ለብንያም ሰዎች አፈገፈጉላቸው
ከዚህ ዐረፍተ ነገር እስከ ቁጥር 41 መጨረሻ ድረስ ያለው የደፈጣ ተዋጊዎቹ ብንያማውያንን እንዴት እንዳሸነፏቸው ጸሐፊው ለአንባቢያን ለማብራራት የጨመረው ዳራዊ መረጃ ነው።

ለብንያማውያን አፈገፈጉላቸው
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ሆን ብለው ወደ ኋላ ተመልሰዋል ማለት ነው። አ.ት፡ “ብንያማውያን ወደ ፊት እንዲመጡ ፈቅደውላቸው ነበር” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በሰዎቹ ተማምነው ነበር
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን በሰዎቻቸው ታምነዋል ማለት ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Judges 20:39

ከጦርነቱ የሚመለሱ
“ከጦርነቱ የሚያፈገፍጉ”

በፊታችን ተሸንፈዋል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አሸንፈናቸዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Judges 20:40

ጥፋት
ታላቅ ጉዳት፣ መከራ፣ ስቃይ

መጡባቸው
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ደረሰባቸው ማለት ነው። አ.ት፡ “ደረሰባቸው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Judges 20:42

ነገር ግን በጦርነቱ ድል ተደረጉ
ይህ አንድ ሰው ሌላውን በሚይዝበት መልኩ የተነገረው ስለ ጦርነት ነው። አ.ት፡ “ነገር ግን የእስራኤል ወታደሮች ያዟቸው” ወይም “ነገር ግን ከጦርነቱ ለማምለጥ አልቻሉም” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

Judges 20:43

ኖሃህ
ይህ የአንድ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ጨፈጨፏቸው
የብንያማውያን መደምሰስ እስራኤላውያን በሬሳዎቻቸው ላይ እንደተረማመዱ ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “ሙሉ በሙሉ ደመሰሷቸው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አሥራ ስምንት ሺህ
“18,000” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

በጦርነት የታወቁ ነበሩ
“በጦርነት ውስጥ በጀግንነት የተዋጉ ነበሩ”

Judges 20:45

ተመልሰው ሸሹ
“የቀሩት ብንያማውያን ተመልሰው ሸሹ”

አምስት ሺህ ... ሁለት ሺህ
“5,000 ... 2,000” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ጊዶም
ይህ የአንድ ቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ሃያ አምስት ሺህ
“25,000” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

Judges 20:47

ስድስት መቶ
“600” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

በብንያም ሰዎች ላይ ተመለሱባቸው
እነዚህ ወደ ሬሞን ዐለት የሸሹት የብንያም ሰዎች ወታደሮች ሳይሆኑ ገና በከተማው ውስጥ የነበሩት ናቸው።

ከተማው
እዚህ ጋ “ከተማው” የሚያመለክተው በዚያ ከተማ የሚኖሩትን ሰዎች ነው። አ.ት፡ “በከተማው የነበረው ሁሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በመንገዳቸው
ይህ የአነጋገር ዘይቤ የሚያመለክተው ወደ ከተማይቱ በሚሄዱበት ጊዜ ያገኙትን ነገር ሁሉ ነው። አ.ት፡ “ወደ ... መጡ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 21

1 በዚያን ጊዜ የእስራኤል ወታደሮች በምጽጳ “ከእኛ ማንም ሰው ሴት ልጁን በጋብቻ ለብንያማውያን መዳር የለበትም” በማለት ቃል ገብተው ነበር። **2** ከዚያም ሕዝቡ ወደ ቤቴል ሄዱና በዚያ በእግዚአብሔር ፊት እስከ ምሽቱ ድረስ ተቀመጡ፣ ድምፃቸውንም ከፍ በማድረግ አምርረው አለቀሱ። **3** እነርሱም እንዲህ ሲሉ ጮኹ፣ “የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፣ ይህ በእስራኤል ለምን ሆነ? ዛሬ ከእኛ አንዱ ነገድ መታጣቱ ለምንድን ነው?” **4** በሚቀጥለውም ቀን ሕዝቡ በጠዋት ተነሡና በዚያ መሠዊያ ሠሩ፣ የሚቃጠልና የሰላም መሥዋዕትንም አቀረቡ። **5** የእስራኤልም ሕዝብ እንዲህ አሉ፣ “ከእስራኤል ነገዶች በሙሉ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ ያልመጣ የትኛው ነው?” በምጽጳ ወደ እግዚአብሔር ፊት ስላልመጣ ማንም ሰው በጣም ወሳኝ የሆነ ቃል ኪዳን አድርገው ነበርና። እነርሱም እንዲህ አሉ፣ “እርሱ ፈጽሞ ሊገደል ይገባዋል።” **6** የእስራኤልም ሕዝብ ስለ ወንድማቸው ስለ ብንያም አዘኑ። እነርሱም እንዲህ አሉ፣ “ዛሬ ከእስራኤል ነገድ አንዱ ተቆርጧል። **7** ሴቶች ልጆቻችንን ከእነርሱ ለአንዳቸውም ቢሆን በጋብቻ ላንሰጥ ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ስለገባን ለተረፉት ሚስቶችን የሚሰጣቸው ማን ነው?” **8** እነርሱም አሉ፣ “ከእስራኤል ነገድ በምጽጳ ወደ እግዚአብሔር ያልመጣ የትኛው ነው?” ከኢያቢስ ገለዓድ ወደ ጉባኤው አንድም ሰው አለመምጣቱን አወቁ። **9** ሕዝቡም በቅደም ተከተል ተሰልፈው እንዲቆጠሩ በተደረገ ጊዜ፣ እነሆ፣ ከኢያቢስ ገለዓድ ነዋሪዎች ማንም ሰው በዚያ አልነበረም። **10** ጉባኤውም 12, 000 ኃያላን ሰዎችን ወደ ኢያቢስ ገለዓድ ልከው በዚያ ያሉትን ሰዎች ሴቶችንና ሕፃናትንም ጭምር ጥቃት እንዲያደርሱባቸውና እንዲገድሏቸው አዘዙአቸው። **11** “እንግዲህ የምታደርጉት ይህ ነው፦ ወንዱን በሙሉ እንዲሁም ከወንድ ጋር የተኛችውንም ሴት በሙሉ ግደሉ።” **12** ሰዎቹም በኢያቢስ ገለዓድ ከሚኖሩት መካከል ከወንድ ጋር ተኝተው የማያውቁ አራት መቶ ወጣት ሴቶች አገኙ፣ እነርሱንም በከነዓን ወዳለው በሴሎ ወደሚገኘው ሰፈር ወሰዷቸው። **13** ጉባኤውም በሙሉ መልክት ላኩ፣ በሬሞን ዓለት ለነበሩት ለብንያም ሕዝብ የሰላም ጥሪ እንዳቀረቡላቸውም ነገሩአቸው። **14** ሲለዚህ በዚያን ጊዜ ብንያማውያን ተመለሱ፣ የኢያቢስ ገለዓድንም ሴቶች ሰጧቸው። ነገር ግን ለሁሉም የሚበቁ ሴቶች አልነበሩም። **15** ሕዝቡም በብንያም ላይ በሆነው ገር አዘኑ፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር በእስራኤል ነገዶች መካከል ስብራት አድርጓልና። **16** የዚያን ጊዜ የጉባኤው መሪዎች እንዲህ አሉ፣ “የብንያም ሴቶች ተገድለዋልና፣ ለተረፉት ብንያማውያን ሚስቶችን እንዴት እናግኝላቸው?” **17** እንዲህም አሉ፣ “ከእስራኤል አንድ ነገድ እንዳይጠፋ ከብንያም አሁን በሕይወት ላሉት ሰዎች ርስት ሊኖራቸው ይገባል። **18** ከሴቶች ልጆቻችን ሚስቶች ልንሰጣቸው አንችልም። የእስራኤል ሕዝብ፣ ‘ለብንያም ሚስት የሚሰጥ ርጉም ይሁን’ የሚል ቃል ኪዳን ገብተው ነበርና።” **19** ስለዚህ እንዲህ አሉ፣ “በቤቴል በሰሜን በኩል፣ ከቤቴልም ወደ ሴኬም በሚወስደው መንገድ በምሥራቅ በኩል፣ በለቦና በደቡብ በኩል ባለችው በሴሎ በየዓመቱ የእግዚአብሔር በዓል እንዳለ ታውቃላችሁ።” **20** እነርሱም ለብንያም ሰዎች እንዲህ ብለው አዘዙአቸው፣ “ሂዱና በምስጢር ተሸሸጉ፣ በወይኑ ስፍራም ተደበቁ። **21** የሴሎ ልጃገረዶች ለመጨፈር የሚወጡበትን ጊዜ ተመለከቱ፣ የዚያን ጊዜ ከወይኑ ስፍራ ፈጥናችሁ ውጡና እያንዳንዳችሁ ከሴሎ ልጃገረዶች ለየራሳችሁ ሚስት ውሰዱ፣ ከዚያም ወደ ብንያም ምድር ተመለሱ። **22** አባቶቻቸው ወይም ወንድሞቻቸው ሊጣሉን በመጡ ጊዜ፣ እንዲህ እንላቸዋለን፣ ‘ምህረት አድርጉልን! ባልና ሚስት ሆነው ይጽኑ ምክንያቱም በጦርነቱ ጊዜ እኛ ለያንዳንዳቸው ሚስት አላገኘንላቸውም። እናተ ደግሞ ሴቶች ልጆቻችሁን ለእነርሱ ስላልሰጣችሁ፣ ቃል ኪዳኑን በተመለከተ በደለኞች አይደላችሁም።’” **23** የብንያምም ሕዝብ እንዲሁ አደረጉ፣ በቍጥራቸው መጠን የሚያስፈልጋቸውን ያህል ሚስቶች ይጨፍሩ ከነበሩት ልጃገረዶች ወሰዱ፣ ሚስትም ይሆኗቸው ዘንድ ይዘዋቸው ሄዱ። እነርሱም ወደ ርስታቸው ስፍራ ተመልሰው ሄዱ፤ ከተሞችንም እንደገና ሠሩ፣ በውስጣቸውም ኖሩ። **24** በዚያን ጊዜ የእስራኤል ሕዝብ ያን ስፍራ ለቀቁና ወደ ቤታቸው ሄዱ፣ እያንዳንዱም ወደ ነገዱና ወደ ወገኑ ሄደ፣ እያንዳንዱም ወደ ርስቱ ተመለሰ። **25** በዚያም ዘመን በእስራኤል ውስጥ ንጉሥ አልነበረም። እያንዳንዱ ሰው በዓይኖቹ ፊት መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር።

Judges 21:1

የእስራኤል ሰዎች ከብንያማውያን ጋር እንዳይጋቡ ቃል ኪዳን ገብተው ነበር
ይህ ዳራዊ መረጃ እስራኤላውያን ከብንያማውያን ጋር ከመዋጋታቸው በፊት ስላደረጉት ቃል ኪዳን ለአንባቢው ይናገራል። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ብንያማውያን
ይህ የብንያም ተወላጆች ስም ነው። ይህንን በመሳፍንት 3:15 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፣ ዛሬ ከነገዶቻችን አንዱን አጥተናልና ይህ ለምን በእስራኤል ላይ ሆነ?
የእስራኤል ሰዎች ይህንን ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የተጠቀሙት ጥልቅ ሐዘናቸውን ለመግለጽ ነው። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ሆይ፣ ከእስራኤል ነገዶች አንዱ ሙሉ በሙሉ በመጥፋቱ በጣም አዝነናል” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

Judges 21:4

እስራኤላውያኑ፣ “ከእስራኤል ነገዶች ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ጉባዔ ያልመጣው የትኛው ነው?” አሉ
ሰዎቹ ብንያማውያንን ከመውጋታቸው በፊት በምጽጳ እያሉ የእስራኤላውያኑ ጉባዔ የተናገሩትን ያመለክታል።

በምጽጳ ወደ እግዚአብሔር ያልመጣውን ማንንም ቢሆን የሚመለከት አስፈላጊ የሆነ መሐላ አድርገው ነበር፤ እንዲህ አሉ፣ “እርሱ በእርግጥ መሞት ይገባዋል”።
ይህ እስራኤላውያኑ ብንያማውያኑን ከመውጋታቸው በፊት በምጽጳ ስላደረጉት መሐላ ለአንባቢው ለማብራራት የቀረበ ዳራዊ መረጃ ነው። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

እርሱ በእርግጥ መሞት ይገባዋል
እዚህ ጋ “እርሱ” የሚያመለክተው ወደ ምጽጳ ያልሄደውን ማንኛውንም ሰው ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በእርግጥ ያንን ሰው እንገድለዋለን” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Judges 21:6

ወንድማቸው ብንያም
ይህ የሚናገረው ስለ ብንያም ነገድ ሲሆን ለነገዱ ያላቸውን ቅርበት ለማሳየት እንደ እስራኤል ወንድም ታይቷል። አ.ት፡ “የተረፉት ብንያማውያን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከእስራኤል አንድ ነገድ ተቆርጧል
የብንያም ነገድ መጥፋት ከእስራኤል በቢላዋ የተቆረጠ ያህል ተነግሯል። ይህ ግነት ነው፣ ምክንያቱም 600 ሰዎች ገና ቀርተው ነበር። ይሁን እንጂ ብንያማውያን ሴቶች ተገድለው ስለ ነበር የነገዱ የወደፊት ዕጣ ፈንታው በጥያቄ ውስጥ ነበር። አ.ት፡ “አንድ ነገድ ተደምስሷል” (ዘይቤአዊ አነጋገር፣ ግነት እና ጥቅል አስተያየት የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሴቶች ልጆቻችንን ላንድርላቸው በእግዚአብሔር ፊት መሐላ አድርገናልና ለተረፉት ለእነዚያ ሚስቶችን ማን ያመጣላቸዋል?
እስራኤላውያኑ ለተረፉት ጥቂት ብንያማውያን ሚስቶችን ለማቅረብ ፈልገዋል፣ ነገር ግን በምጽጳ ያደረጉት መሐላ ይህንን ከማድረግ አግዷቸዋል።

Judges 21:8

ኢያቢስ ገለዓድ
ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ሰዎች በኃላፊነት ስሜት ተሰብስበው ነበር
“በምጽጳ የተሰበሰቡት ሰዎች ተጠያቂነት ነበረባቸው”

ከኢያቢስ ገለዓድ ተወላጆች አንድም ሰው በዚያ አልነበረም
ይህ የሚያመለክተው ቀደም ሲል በምጽጳ የተደረገውን ጉባዔ ነው። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “ከኢያቢስ ገለዓድ ተወላጆች አንድም ሰው በምጽጳ አልተገኘም ነበር”

አሥራ ሁለት ሺህ
“12,000” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

የኢያቢስ ገለዓድን ተወላጆች፣ ሴቶችንና ልጆችን ጨምሮ በሰይፍ ስለት ምቷቸው
በዚህ ጥቅል መመሪያ ላይ የሚቀጥለው ቁጥር የማይመለከተው ማንን እንደሆነ ይጨምራል።

በሰይፍ ስለት ምቷቸው
“በሰይፎቻችሁ ግደሏቸው”

Judges 21:11

ኢያቢስ ገለዓድ
ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። ይህንን በመሳፍንት 21:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ከወንድ ጋር ያልተኙ
ይህ የግብረ ሥጋ ግንኙነትን ለማመልከት በጨዋነት የተነገረ አነጋገር ነው።

አራት መቶ ወጣት ሴቶች
“400 ወጣት ሴቶች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

Judges 21:13

የሰላም ጥሪ አቀረቡላቸው
የነገር ስም የሆነው “ሰላም” በግሣዊ ሐረግ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ከእነርሱ ጋር መዋጋታቸውን ለማቆም ፈለጉ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ኢያቢስ ገለዓድ
ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። ይህንን በመሳፍንት 21:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ለሁሉም የሚበቁ ሴቶች አልነበሩም
ከኢያቢስ ገለዓድ የተገኙት አራት መቶ ሴቶች ብቻ ሲሆኑ ብንያማውያኑ ስድስት መቶ ሰዎች ነበሩ።

በእስራኤል ነገዶች መካከል ልዩነትን አደረገ
“የእስራኤል ነገዶች አንድ እንዳይሆኑ አደረጋቸው”

Judges 21:16

ብንያማውያን
ይህ የሚያመለክተው የብንያምን ተወላጆች ነው። ይህንን በመሳፍንት 3:15 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ብንያማውያን ሴቶች ተገድለው ነበርና
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ብንያማውያን ሴቶችን በሙሉ ገደልናቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ከእስራኤል እንዳይጠፉ ... ርስት መኖር አለበት
እስራኤላውያኑ እያጋነኑ ነው። ቀደም ሲል ለአራት መቶ ብንያማውያን ሚስቶችን ሰጥተዋቸዋል፣ በመሆኑም፣ ነገዱ ሙሉ በሙሉ አይጠፋም። (ግነት እና ጥቅል አስተያየት የሚለውን ተመልከት)

Judges 21:18

ለብንያም ሚስትን
እዚህ ጋ ብንያም የሚያመለክተው የብንያም ተወላጅ የሆኑትን ወንዶች ነው። አ.ት፡ “ለብንያማውያን ወንዶች ሚስት”

እርሱም ከቤቴል በስተሰሜን፣ ከቤቴል ወደ ሴኬም ከሚወስደው መንገድ በስተምስራቅና ከሊባኖስ በስተደቡብ
ይህ የሴሎ ከተማ የሚገኝበትን አካባቢ ለአንባቢው ለማብራራት የተሰጠ ዳራዊ መረጃ ነው። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ለቦና
ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Judges 21:20

እያንዳንዳችሁ ሚስት የምትሆናችሁን ጥለፉ ... ተመልሳችሁ ወደ ብንያም ምድር ሂዱ
ብንያማውያኑ እነዚህን ሴቶች ይዘው ወደ ገዛ ምድራቸው ተመልሰው እንደሚሄዱ ይታወቃል። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “እያንዳንዳችሁ ከሴሎ ልጃገረዶች አንዷን መያዝና ሚስት እንድትሆናችሁ ከእናንተ ጋር ወደ ብንያም ምድር መውሰድ ይኖርባችኋል”

Judges 21:22

ምህረት አሳዩን
የነገር ስም የሆነው “ምህረት” እንደ ድርጊት ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ደግነትን አድርጉልን” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

በጦርነቱ ጊዜ ለእያንዳንዱ ወንድ ሚስት ስላላገኘንለት ነው
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “ከኢያቢስ ገለዓድ ጋር በተዋጋን ጊዜ ለእያንዳንዳቸው ሚስት ስላላገኘን”

ሴት ልጆቻችሁን ለእነርሱ ላለመስጠት ... ንጹሐን ናችሁ
ይህ የሚያመለክተው የሴሎን ሰዎች ነው። እነርሱ ሴቶች ልጆቻቸውን ለብንያማውያን በፈቃደኝነት አልሰጡም፣ በመሆኑም ይህንን ላለማድረግ የገቡትን መሐላ አላፈረሱም።

Judges 21:23

የሚያስፈልጓቸው ሚስቶች ቁጥር
ይህ የሚያመለክተው ከኢያቢስ ገለዓድ ሚስቶችን ላላገኙ ሁለት መቶ ብንያማውያን ለእያንዳንዳቸው አንዲት ሚስት ነው። (መሳፍንት 21:14ን ተመልከት)።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Judges 21:25

በእስራኤል ንጉሥ አልነበረም
“እስራኤል ገና ንጉሥ አልነበራትም”

በዐይኑ ፊት ትክክል የመሰለውን
ዐይን ማየትን፣ ማየትም አሳብን ወይም ፍርድን ይወክላል። አ.ት፡ “ልክ ነው ብሎ የሚፈርደውን” ወይም “ልክ ነው ብሎ የሚያስበውን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Ruth

Ruth

Chapter 1

1 መሳፍንት ይገዙ በነበረበት ዘመን በምድሪቱ ላይ ራብ ነበረ። አንድ ከበተልሔም ይሁዳ የሆነ ሰው ከሚስቱና ከሁለቱ ልጆቹ ጋር ወደ ሞአብ አገር ሄደ። 2 የሰውዮው ስም አቤሜሌክ ይባል ነበር፣ የሚስቱም ስም ኑኃሚን ይባላል። የሁለቱም ወንዶች ልጆቹ ስም መሐሎንና ኬሌዎን፣ የይሁዳ ቤተልሔም ኤፍራታውያን ነበሩ። እነርሱም ወደ ሞዓብም አገር ደረሱና በዚያ ተቀመጡ። 3 የኑኃሚንም ባል አቤሜሌክ ሞተ እርስዋም ከሁለቱ ወንዶች ልጆችዋ ጋር ቀረች። 4 እነዚህ ወንዶች ልጆች ከሞዓባውያን ሴቶች ሚስቶችን ወሰዱ፤ የአንዷ ስም ዖርፋ ነበር፣ የሌላኛዋ ስም ደግሞ ሩት ነበረ። በዚያም ለአሥር ዓመታት ያህል ተቀመጡ። 5 ከዚያም መሐሎንና ኬሌዎን ሁለቱም ሞቱ፣ ኑኃሚንም ያለ ባልዋና ያለ ሁለቱ ልጆችዋ ብቻዋን ተለይታ ቀረች። 6 በዚያን ጊዜ ኑኃሚን ከሁለቱ ምራቶችዋ ጋር ሞአብን ለመልቀቅና ወደ ይሁዳ ለመመለስ ወሰነች። እርስዋም በሞዓብ ምድር ሳለች እግዚአብሔር የተቸገሩትን ሕዝቡን እንደረዳቸውና መብልን እንደ ሰጣቸው ሰማች። 7 ስለዚህ እርስዋ ከሁለቱ ምራቶችዋ ጋር ከነበረችበት ስፍራ ለቀቀች፣ ከዚያም ወደ ይሁዳ ምድር ለመመለስ መንገዱን ይዘው ወደታች ሄዱ። 8 ኑኃሚን ለምራቶችዋ “ሂዱ፣ እያንዳንዳችሁ ወደ እናታችሁ ቤት ተመለሱ። ለሞቱትና ለእኔ ታማኝነት እንዳሳያችሁን ሁሉ፣ እግዚአብሔር ለእናንተ ታማኝነቱን ያሳያችሁ። 9 ጌታ እያንዳንዳችሁን በሌላ ባል ቤት ዕረፍት ይስጣችሁ” አለቻቸው። ከዚያም ሳመቻቸው፣ እነርሱም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው አለቀሱ። 10 እነርሱም “አይሆንም! ከአንቺ ጋር ወደ ሕዝብሽ እንመለሳለን” አሉአት። 11 ኑኃሚን ግን “ልጆቼ ሆይ፣ ተመለሱ! ለምን ከእኔ ጋር ትሄዳላችሁ? ባሎቻችሁ ይሆኑ ዘንድ ለእናንተ የሚሆኑ ወንዶች ልጆች በማሕጸኔ አሁን አሉን? 12 ልጆቼ ሆይ፣ ተመለሱ፣ በራሳችሁ መንገድ ሂዱ፤ ባል ለማግባት በጣም አርጅቻለሁና። ዛሬ ማታ ባል አገኛለሁ ብየ እንኳ ተስፋ ባደርግና ወንዶች ልጆችን ብወልድ፣ 13 እነርሱ እስኪያድጉ ድረስ ትጠብቃላችሁን? እየጠበቃችሁ አሁን ባል ሳታገቡ ትቀራላችሁን? አይሆንም፣ ልጆቼ ሆይ! ከእናንተ ይልቅ ሁኔታው እኔን እጅግ በጣም ያስመርረኛል፣ ምክንያቱም የእግዚአብሔር እጅ በእኔ ላይ ወጥቶአልና። 14 በዚያን ጊዜ ምራቶችዋ ድምፃቸውንም ከፍ አደረጉና እንደገና አለቀሱ። ዖርፋም አማትዋን ሳመቻትና ተሰናበተቻት፣ ሩት ግን ተጠግታ ያዘቻት። 15 ኑኃሚንም “አድምጪኝ፣ እነሆ የባልሽ ወንድም ሚስት ወደ ሕዝብዋና ወደ አማልክትዋ ተመልሳለች። ከባልሽ ወንድም ሚስት ጋር አንቺም ተመለሽ” አለቻት። 16 ነገር ግን ሩት “ከአንቺ ርቄ እንድሄድ አታድርጊኝ፣ ወደምትሄጅበት እሄዳለሁና፤ በምትቆይበትም እቆያለሁና፤ ሕዝብሽ ሕዝቤ ይሆናል፣ አምላክሽም አምላኬ ይሆናል። 17 በምትሞችበትም እሞታለሁ፣ በዚያም እቀበራለሁ። ከሞት በቀር እኛን አንድም ነገር ቢለየን እግዚአብሔር ይቅጣኝ፣ ከዚህም በላይ ያድርግብኝ” አለቻት። 18 ኑኃሚን ሩት ከእርስዋ ጋር ለመሄድ እንደ ወሰነች ባየች ጊዜ፣ ከእርስዋ ጋር መከራከር አቆመች። 19 ስለዚህ ሁለቱም ወደ ቤተ ልሔም ከተማ እስኪመጡ ድረስ ተጓዙ። ወደ ቤተ ልሔምም በደረሱ ጊዜ፣ ከተማው በሙሉ ስለ እነርሱ እጅግ በጣም ተደነቁ። ሴቶችም “ይህች ኑኃሚን ናትን?” አሉ። 20 እርስዋ ግን “ኑኃሚን ብላችሁ አትጥሩኝ። ሁሉን የሚችል አምላክ ሕይወቴን መራራ አድርጎታልና፣ ማራ በሉኝ” አለቻቸው። 21 በሙላት ሄድሁ፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ወደ ቤቴ ባዶዬን እንደገና መለሰኝ። ታዲያ እግዚአብሔር አዋርዶኝ፣ ሁሉንም የሚችል አምላክ አስጨንቆኝ እያያችሁ ለምን ኑኃሚን ትሉኛላችሁ?” አለቻቸው። 22 ስለዚህ ኑኃሚንና ምራትዋ ሞአባዊት ሩት ከሞዓብ አገር ተመለሱ። እነርሱ የገብስ መከር በተጀመረ ጊዜ ወደ ቤተልሔም መጡ።

Ruth 1:1

እንዲህም ሆነ
“እንዲህም ሆነ” ይሄ የተለመደ የታሪካዊ ተረካ አጀማመር ነው።

መሳፍንት በሚገዙበት ዘመን
“መሳፍንት ይፈርዱ በነበረ ገዜ”

በምድሪቱ
ይሄ የሚያመላክተው የእስራኤልን ምድር ነው። “በአገሩ”

አንድ ሰውም
“አንድ ሰው” ይሄ አንድን ገፀባህሪ ወደ ትረካው ማስገቢያ ማስተዋወቅያ ተልምዷዊ መንገድ ነው።

የቤተልሔም ይሁዳ የኤፍራታ ሰዎች
ከኤፍሬም ጎሳ ነገድ የሆኑ፤ በይሁዳ ክልል በሆነው በቤተልሄም የሰፈሩ ሰዎች ነበሩ።

Ruth 1:3

እርሷ እና ሁለቱ ልጆችዋ በቻ ቀሩ
“ኑኃሚንም ከሁለት ልጆቿ ጋር በቻዋን ቀረች“

ሚስት አገቡ ወሰዱ
”ሴቶች ሚስት አገቡ ወሰዱ “ ይሄ ሚስት ማግባትን ያመለክታል

ከሞዓባውያን ሴቶች
የኑኃሚን ወንድ ልጆች ከሞዓብ ጎሳ ነገድ የሆኑ ሴቶች። ሞዓባውያን ሌሎች አማልክትን ያመልኩ ነበር።

የአንዲቱ ስም . . . የሁለተኛይቱም ስም
“. . . የተባሉ የሞዓብ ሴቶች“

አስር ዓመት ያህል
አቤሜሌክ እና ኑኃሚን ወደ ሞዓብ ከመጡ ከአስር ዓመት በኋላ፤ ልጆቻቸው መሓሎን እና ኬሌዎን ሞቱ።

ተለይታ ቀረች
ኑኃሚን መበለት ሆነች።

Ruth 1:6

ርሷም በሞአብ ምድር ሳለች
“እርሷም በሞአብ ሳለች”። ዜናው የመጣው ከእስራኤል አገር እንደሆነ ያመላክታል። እግዚአብሄር እስራኤልን እንደጎበኘ በሞአብ ምድር ሳለች ሰማች።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እግዚአብሔር
በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለህዝቡ የተገለጠበት ስም ነው። (የእግዛብሔርን ስም ስለመተርጎም በቃላት አተረጓጎም መምሪያ ገፁ ላይ ተመልከቱ)

ሕዝቡን እንደጎበኘ እና እህል እንደሰጣቸው
ሕዝቡን እንደጎበኘ እንጀራም እንደሰጣቸው

ምራቶቿን
ምራቶችዋ፤ ወንድ ልጆቿን ያገቡት ሴቶች

መንገድ ይዘው ጉዟቸውን ቀጠሉ
“የሚመልሳቸውን መንገድ ይዘው።” መንገድ ይዘው የሚለው በአንድ መንገድ መሄድን የሚያመላክት አባባል ነው።

Ruth 1:8

ምራቶች
የወንድ ልጆች ሚስቶች ወይንም የወንድ ልጆቿ መበለቶች

እያንዳንዳችሁ
ኑኃሚን የምታዋራው ሁለት ሰዎችን ነበር፤ ከዚህ በመቀጠልም እናንተ ብላ ስትናገር ሁለቱን በማስመልከት ነው።

ወደ እናቶቻችሁ ቤት
“ወደ እናቶቻችሁ ቤትም”

በጎ ነገር እንዳደረጋችሁ
“ቸርነትን እንዳደረጋችሁ”

በጎነት
“ቸርነት” የ ፍቅር፣ የበጎነት፣ እና ታማኝነትን ያመላክታል።

ለሞቱት
“ለሞቱት ባሎቻችሁ” ን ኡኃሚን በዚህ የሞቱትን ልጆችዋን ማመላከት ነው የፈለገችው።

ያድርግላችሁ
“እንደዚሁ ያድርግላችሁ” ወይንም “እንዲደረግላችሁ ይፍቀድ”

ያሳሪፋችሁ
እዚህ ጋር “ያሳርፋችሁ” የሚለው በትዳርም የሚገኘውን ደህንነትን ያጠቃልላል።

በምታገቡት ባል ቤት
ከአዳዲስ ባሎቻችሁ፣ ከሌላ ሰው ባል ጋር አይደለም። ይሄ የሚያመላክተው በባልየው ቤት ውስጥ እና ከባልየው የሃፍረት ከለላ ስር ማለት ነው።

እነርሱም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው አለቀሱ
ድምፅን ከፍ ማድረግ ለጮክ በሎ ማውራትን የሚያመላክት አባባል ነው። ምራቶቷም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ወይንም አምርረው አለቀሱ።

ተመልሰን ... እንሄዳለን
“እንመለሳለን” ዓርፋ እና ሩት “እኛ” ብለው ሲናገሩ ስለራሳቸው እንጂ ስለ ሩት አንነበረም የሚናገሩት።

ከአንቺ ጋር
እዚህ ጋር “አንቺ” የሚለው የሚያመላክተው ኑኃሚንን ነው።

Ruth 1:11

ከእኔ ጋር ለምን ትሄዳላችሁ?
ይህ ምላሽ የሚሰጥለት ጥያቄ አይነት አይደለም። “ከእኔ ጋር መሄዱ ትርጉም አይሰጥም።” ወይንም “ከእኔ ጋር መሄድ የለባችሁም።”

ባል የሚሆኗችሁ ሌሎች ልጆች ከእንግዲህ የምወልድ ይመስላችኋልን?
ኑኃሚን በዚህ ጥያቄዋ ለእነርሱ የሚሆኑ ወንድ ልጆች ከዚህ ወድያ ልትወልድላቸው እንደማትችል ትናገራለች። “መቼስ ለእናንተ ባል መሆን የሚችሉ ሌሎች ወንድ ልጆች ከዚህ በኋላ መውለድ አልችልም።”

ባል እንዳላገባ እጅግ አርጅቻለሁ
ባል የማግባቱ ምክንያት በግልፅ ተጠቅሷል። “ሌሎች ወንድ ልጆች እንዳልወልድ”

ልጆች ብወልድ
“መፀነስ” ወይንም “ወንድ ልጆች መውለድ”

እስኪያድጉ ድረስ ትጠብቃላችሁን? እነርሱን በመጠበቅ እስከዚያ ሳታገቡ ትቈያላችሁን?
እነኚህ ምላሽ የሚሰጥላቸው ጥያቄዎች አይነት አይደሉም። “ታገብዋቸው ዘንድ እስኪያድጉ አትጠብቋቸውም። አሁን ማግባትን ትመርጣላችሁ”

ሁኔታው ከእናንተ ይልቅ ለእኔ እጅግ መራራ ነው
መራራነት የሃዘን እና የሰቆቃ መገለጫ ነው፤ በዚህም የሃዘንዋ መንሳኤ ምን እንደሆነ ማወቁ አያዳግትም። “የእናንተ ባል አለመኖር እኔን ያሳዝነኛል።

የእግዚአብሔር እጅ በእኔ ላይ ተነሥቶአልና
“እጅ” የሚለው የእግዚአበሔርን ኃይል ወይንም ተፃዕኖ ያሳያል። “የእግዚአብሔር እጅ በእኔ ወጥቶአልና።”

Ruth 1:14

ድምፃቸውን ከፍ አድርገው አለቀሱ
ይህ የሚያመላክተው አምርረው እንዳለቀሱ እና ጮክ ብለው እንደተጣሩ ነው።

እነሆ የባልሽ ወንድም ሚስት
“ልብ በይ፤ ምክኛቱም አሁን የምልሽ ነገር እውነትና ጠቃሚ ነው፤ ባልንጀራሽ።”

ሩት ግን ልትለያት ስላልፈለገች ተጠመጠመችባት
“ሩት ኝ ተጠጋቻት።” “ሩት ልትለያት አልወደደችም።” ወይንም “ ሩት አልለያትም አለች።”

የባልሽ ወንድም ሚስት
“ባልንጀራሽ”

አማልክትዋ
ዓርፋ እና ሩት ልጆችዋን ከማግባትዋ በፊት የሞአባውያንን አማልክት ያመልኩ ነበር። በትዳራቸዋም ውስጥ ሳሉ የኑኃሚንን አምላክ ማምለክ ጀምረው ነበር።

Ruth 1:16

ወደ ምትሄጅበት
“ወደ ምትኖሪበት”

ሕዝብሽ ሕዝቤ
ሩት በዚህ የምታመላክተው የኑኃሚንን ህዝቦች ነው፤ እስራኤላውያንን። “የአገርሽን ሕዝቦች እንደ እራሴ ሕዝቦች እቆጥራለሁ።” ወይንም “ዘመዶችሽን እንደ ዘመዶቼ እቆጥራለሁ።”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በምትሞቺበት እሞታለሁ
ይህ ሩት እስከ ዕድሜዋ ፍፃሜ ከኑኃሚን ጋር በአንድ ቦታ እና ከተማ የመሆን ፍላጎቷን ያሳያል።

ብለይሽ እግዚአብሔር ይፍረድብኝ፤ ከዚህም የከፋ ያድርግብኝ።
ይህ የሚያመላክተው ሩት አደርጋለሁ ያለችውን ባታደርግ፤ እግዚአብሔር እንዲቀጣት እየጠየቀች እንደሆነ ነው። “እግዚአብሔር አይፍቀድ እንደማለት ነው።”

ከመናገር ዝም አለች
“ኑኃሚን ሩትን መጐትጐቷን ተወች”

Ruth 1:19

እንደ ደረሱም
“እንዲህ ሆነ።” ይህ የታሪኩ አዲስ ምዕራፍ መነሻ አመላካች ነው።

ከተማው በሙሉ
“ከተማው” የሚለው በዛ የሚኖሩ ሰዎችን በሙሉ ያመላክታል። “የከተማይቱ ሰዎች ሁሉ።”

ይህች ኑኃሚን ናትን?
ኑኃሚን በቤተልሔም ከኖረች በዙ ዓመታትን አስቆጥራል በሎም ባሏ እና ወንድ ልጆቿ አብረዋ አልነበሩም፤ እናም በዛ የነበሩት ሴቶች ኑኃሚን ስለመሆኗ መጠራጠራቸውን የሚያመናክት እባባል ነው። እንደ እውነተኛ ጥያቄ ቁጠሩት።

ኑኃሚን ብላችሁ አትጥሩኝ
“ኑኃሚን” የሚለው ስም “የእኔ ደስታ” የሚል ትርጉም ነው ያለው። ኑኃሚንም ባሏን እና ልጆቿን ስላጣች፤ ስሟ ሕይወቷን እንደሚመጥን አይሰማትም።

ማራ
መራራ፤ የስሙ ትርጉም ሲሆን፤ ብዙውን ግዜ ይህ ስም ሲተረጎም እንደሚያወጣው ስም “ማራ” ተበሎ ይተረጎማል።

በሙላት ወጣሁ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ባዶዬን መለሰኝ
ኑኃሚን ከቤተልሔም ስትወጣ በልዋ እና ሁለት ወንዶች ልጆችዋ በሕይወት ነበሩ፤ ደስተኛም ነበረጭ ኑኃሚን ለባልዋ እና ሁለት ልጆችዋ ሞት ተጠያቂ የምታደርገው እግዚአብሔርን ነው። ወደ እስራኤልም ብቻዋን እንድትመለስ ያደረገው እርሱ ነው።

አስጨንቆኛል
“ፍርድን አሳልፎብኛል።”

አዋርዶኛል
መከራ አምጥቶብኛል

Ruth 1:22

ኑኃሚንም እና . . . ሩት
“ኑኃሚንም” የሚለው ቃል መደምደምያ የሆነውን መጨረሻ ላይ የሆነውን ነገር ጠቋሚ አያያዥ ቃል ያሳያል። በእናንተ ቋንቋ ይህንን ሊተካ የሚችን ቃል ተጠቀሙ።

የገብስም መኸር በደረሰ ግዜ
“የገብስ አዝመራ” የሚለውን ስንኝ ሊተካ በሚችል ቅል ሊተረጎም ይችላል። “የገብስ አዝመራ በሚሰበሰብበት ወቅት”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 የኑኃሚን ባል አቤሜሌክ፣ በጣም ባለጠጋና ኃያል ሰው የሆነ ቦዔዝ የሚባል ዘመድ ነበረው። 2 ሞዓባዊቱ ሩት ኑኃሚንን “አሁን ልሂድና ወደ እርሻዎች ገብቼ
እህል ልቃርም። በፊቱ ሞገስ የማገኘውን ሰው እከተላለሁ” አለቻት። ኑኃሚንም “ልጄ ሆይ፣ ሂጂ” አለቻት። 3 ሩት ሄደችና ከአጫጆችም በኋላ በእርሻ ውስጥ
ቃረመች። እርስዋም የአቤሜሌክ ዘመድ ወደሆነው ወደ ቦዔዝ እርሻ እንደ አጋጣሚ ሆኖ ደረሰች። 4 እነሆም፣ ቦዔዝ ከቤተ ልሔም መጣና ለአጫጆቹ
“እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን” አላቸው። እነርሱም “እግዚአብሔር ይባርክህ” ብለው መለሱለት። 5 ከዚያም ቦዔዝ በአጫጆቹ ላይ ተቆጣጣሪ የነበረውን
አገልጋዩን “ይህች ወጣት ሴት የማን ናት?” አለው። 6 አጫጆቹንም የሚቆጣጠረው አገልጋይ “ይህች ወጣት ሞዓባዊት ከሞዓብ ምድር ከኑኃሚን ጋር
የመጣች ናት” አለው። 7 እርስዋም ‘ከአጫጆቹ በኋላ እየተከተልሁ የእህል ቃርሚያ እንድቃርምና እንድለቅም እባክህ ፍቀድልኝ አለች’ አለው። ስለዚህ እርስዋም
ወደዚህ መጣች፣ በቤት ጥቂት ከማረፍዋ በስተቀር፣ ከጠዋት ጀምራ እስከ አሁን ድረስ መቃረም ቀጥላለች።” 8 የዚያን ጊዜ ቦዔዝ ሩትን “ልጄ ሆይ፣ እኔን
እያዳመጥሽኝ ነውን? ወደ ሌላ እርሻ ሄደሽ አትቃርሚ፤ ከእርሻየ አትሂጂ፣ ይልቁንም በዚህ ቆዪና ከወጠት ሴቶች ሰራተኞቼ ጋር አብረሽ ስሪ። 9 ዓይኖችሽ ሰዎቹ
ወደሚያጭዱበት ስፍራ ብቻ ይመልከቱ፣ ሌሎቹንም ሴቶች ተከተያቸው። ሰዎቹን እንዳይነኩሽ አላዘዝኋቸውምን? ሲጠማሽ ወደ ውኃ ማሰሮዎቹ ሄደሽ ወንዶቹ
ከቀዱት ውኃ መጠጣት ትችያለሽ” አላት። 10 ከዚያም በግንባርዋ መሬቱን በመንካት በቦዔዝ ፊት ሰገደች። እርስዋም “እኔ እንግዳ የሆንሁት ታስበኝ ዘንድ
በአንተ ፊት ሞገስ ያገኘሁት ለምንድን ነው?” አለችው። 11 ቦዔዝም ለእርስዋ “ባልሽ ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ የሰራሽው ስራ ሁሉ ለእኔ ተነግሮኛል። አማትሽን
ለመከተልና ወደ ማታውቂው ሕዝብ ለመምጣት አባትሽንና እናትሽን የተወለድሽባትንም ምድር ትተሻል። 12 ስለ ስራሽ እግዚአብሔር ይክፈልሽ። ከክንፉ በታች
መጠጊያ ካገኘሽበት ከእስራኤል አምላክ ከእግዚአብሔር ሙሉ ደመወዝሽን ተቀበይ” አላት። 13 እርስዋም “ጌታዬ ሆይ፣ ምንም እንኳ እኔ ከሴት አገልጋዮችህ
እንደ አንዲቱ ባልሆንም አጽናንተኸኛልና፣ እኔን በደግነት አናግረኸኛልና በፊትህ ሞገስን ላግኝ” አለቸው። 14 በምሳም ጊዜ ቦዔዝ ለሩት እንዲህ አላት፦ “ወደዚህ
ነይ፣ እንጀራም ብዪ፣ ጉርሻሽንም በሆምጣጤው ወይን አጥቅሺው።” በአጫጆቹም አጠገብ ተቀመጠች፣ እርሱም የተጠበሰ እህል ሰጣት፣ እርስዋም
እስክትጠግብ ድረስ በላች፣ የቀረውንም አተረፈች። 15 ለመቃረም ስትነሳ፣ ቦዔዝ ወጣት አገልጋዮቹን “በነዶው መካከልም እንድትቃርም ፍቀዱላት፣ ምንም
መጥፎ ነገር ለእርስዋ አትናገሩአት። 16 ደግሞም ከነዶው ዘለላዎች አስቀርታችሁ በእርግጠኝነት ልተተዉላት ይገባል፣ እንድትቃርም ለእርስዋ ተዉላት።
እርስዋንም አትውቀሱአት” ብሎ አዘዛቸው። 17 ስለዚህ በእርሻው ውስጥ እስከ ማታ ድረስ ቃረመች። ከዚያም የቃረመችውን እህል ወቃችው፣ የወቃችውም
እህል አንድ የኢፍ መስፈሪያ ያህል ገብስ ሆነ። 18 እርስዋም ተሸክማው ወደ ከተማ ሄደች። አማትዋም የቃረመችውን አየች። ሩትም በልታ ከጠገበች በኋላ
የተረፋትን የተጠበሰ እህል አውጥታ ለእርስዋ ሰጠቻት። 19 አማትዋም ለእርስዋ እንዲህ አለቻት፦“ዛሬ የቃረምሽው ወዴት ነው? ለመስራትስ ወዴት ሄድሽ?
የረዳሽ ሰው የተባረከ ይሁን።” ከዚያም ሩት ለአማትዋ የቃረመችበት እርሻ ባለቤት ስለሆነው ሰው ነገረቻት። እርስዋም “ዛሬ ቃርሚያ የቃረምሁበት እርሻ ባለቤት
ስሙ ቦዔዝ ይባላል” አለቻት። 20 ኑኃሚንም ለምራትዋ “ታማኝነቱን በሕያዋንና በሙታን ላይ ባልተወው በእግዚአብሔር የተባረከ ይሁን” አለቻት። ኑኃሚንም
ደግሞ “ይህ ሰው ለእኛ የቅርብ ዘመዳችን ነው፣ ከሚቤዡን አንዱ ነው” አለቻት። 21 ሞዓባዊቱ ሩትም “በእርግጥም፣ እንዲህ አለኝ፣ ‘መከሬን ሁሉ
እስኪጨርሱ ድረስ ከወጣት ወንዶች ሰራተኞቼ አትራቂ።’” 22 ኑኃሚንም ለምራትዋ ለሩት “ልጄ ሆይ፣ ከወጣት ሴቶች ሰራተኞቹ ጋር ብትወጪ መልካም ነው፣
በሌላ በየትኛውም እርሻ ጉዳት እንዳያገኝሽ” አለቻት። 23 ስለዚህም እርስዋ እስከ ገብሱና ስንዴው መከር መጨረሻ ድረስ ልትቃርም ወደ ቦዔዝ ሴቶች
ሰራተኞች ተጠግታ ቆየች። እርስዋም ከአማትዋ ጋር ትኖር ነበር።

Ruth 2:1

ለኑኃሚን ባል የሚዛመደው
ይህ ስንኝ ትረካው ከመቀጠሉ በፊት አዲስ መረጃን ያስተዋውቃል። በእናንተ ቋንቋ አዲስ መረጃን ወደ ምንባብ ለማስተዋወቅ የምትጠቀሙበት መንገድ ካለ እርሱን ተጠቀሙ።

ኃያል ሰው
“ባለጸጋ” ይህ የሚያሳየው ቦኤዝ ባለጸጋ እና በማህበረሰቡ በመልካም ዝና የታወቀ ሰው ነበረ።

ማዓባዊቷ ሩትም
እዚህ ጋር ትረካው ይቀጥላል። በቋንቋችሁም ታሪክ ከተቋረጠ በኋላ እንዴት እንደሚቀጥል ልብ በሉ።

ማዓባዊቷ
ሴቲቱ ከሞዓብ ስለመሆኗ መጠቆምያ ሌላኛው መንገድ ነው።

ቅርሚያ የሚያስቃርም
“ከእህሉ ዘለላ እንድቃርም” ወይንም “አጨዳ ላይ ከኋላ የተተወ የእህል ዘለላ ለማንሳት”

የእህል ዘለላ
“ዕራሱ” ወይንም “ክምችቱ” የእህሉን ዋና ፍሬ የያዘ “ዘለላ”።

በፊቱ ሞገስ የማገኘውን
“በፊቱ ሞገስ ማግኘት” የሚለው አባባል በሰው ዘንድ ተቀባይነት ማግኘትን ያመላክታል። ሩት ፈቃድ ማግኘትን በአንድ ሰው ፊት ሞገስን እንደማግኘት አድርጋ ትናገራለች። በፊቱ፤ የሚለው አገላለፅ በመታየት፣ በአስተሳሰብ እና በአወሳሰን ተቀባይነት ማግኘትን ያመላክታል።

ልጄ
ሩት ኑኃሚንን እንደ እናቷ ነበር የምትንከባከባት። ብትርጉም ቋንቋው ልጅን የሚተካ ቃል መጠቀም ከተቻለ እርሱን መጠቀም ይቻላል።

Ruth 2:3

እንደአጋጣሚም
ሩት ስትቃርምበት የነበረው እርሻ የኑኃሚን ዘመድ የሁነው ቦኤዝ እርሻ መሆኑን አታውቅም ነበር።

እነሆም፣ ቦኤዝ
“እነሆም” የሚለው ቃል የቦኤዝ መምጣት በታሪኩ ላይ የሚጫወተውን ትልቅ ሚና አመላካች ነው። የዚህ ዓይነት ሚና የሚጫወት ቃል በቋንቋችሁ ካለ እርሱን መጠቀም አስፈላጊ ነው።

ከቤተልሔም መጣ
እርሻው ከቤተልሔም ያልታወቀ ዕርቀት ላይ ይገኛል።

ይባርክህ
“መልካምን ነገር ይስጥህ” ወይንም “ደስተኛ ያርግህ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ruth 2:5

ይህች ወጣት ሴት የማን ናት?
ቦኤዝ እዚህ ጋር እየጠየቀ ያለው 1) ስለ ሩት ባል ወይንም 2) ስለሩት ወላጆች ውይንም ጠባቂዎች ነው።

አዛዥ
“ኃላፊነት ላይ ያለው” ወይንም “እየተቆጣጠረ ያለው”

በቤት
“በጎጆ” ወይንም “በመጠለያ” ይሄ በእርሻ መሃከል ከፀሃይ ጊዜያዊ መጠለያ ወይንም የመናፈሻ ጎጆ ነበር።

Ruth 2:8

ልጄ ሆይ፥ ትሰምያለሽ
የሄ እንደ ትዕዛዝ ቃል ልንመለከተው እንችላለን። “ስሚኝ ልጄ” ወይንም የምለውን ነገር ልብ በይ ልጄ።”

ልጄ
ይሄ በዕድሜ የሚያንስ ሰወን የመናገርያ መንገድ ነው። ሩት የቦኤዝ ልጅ አይደለችም። ይህ ቃል ሲተረጎም ልጅን ለማለት ተፈልጎ አለመሆኑን ልብ የበሉ።

ወደምያጭዱበት ስፍራ ተመልከቺ
መመልከት አንደን ነገር ማየትን እና አትክሁሮት መስጠትን ያመለክታል። “እርሻውን ብቻ ተመልከቺ” ወይንም “ለእርሻው ብቻ አትክሁሮት ስጪ።”

አዝዣለሁ
“አላዘዝኩምን?” የሚል ጥያቄ አዘል፤ ንግግሩ ማስረገጫ ቃል። “ጉበዛዚቱን አዝዣለሁ።”

ወንዶቹ . . . ልጃገረዶቹ
“ወጣት ወንድ ሰራተኞች . . . ወጣት ሴት ሰራተኞች።” ወንዶሽ የሚለው ቃል በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ ይውላል። ወይንም ጎበዛዚቱ ይለዋል፤ ይሄ በእርሻው ላይ በአጨዳ ላይ ያሉ ሰራተኞችን ያመላክታል።

እንዳያስቸግሩሽ
ለማለት የተፈለገው፤ 1) ወንዶቹ እንዳይጎዱሽ። 2) በዚህ እርሻ ከመቃረም እንዳይከለክሉሽ።

ጎበዛዚቱ ከቀዱት ወሃ
ከቀዱት ማለት ከውሃ ገድጓድ ካወጡት ወይንም ውሃ ከማጠራቀምያው ማድጋ ካወጡጥ

Ruth 2:10

በግንባርዋም ተደፍታ፥ በምድር ላይ ሰገደችለት
ይሄ የአክብሮት የፍርሃት ማሳያ ነው። ስላደረገላት ነገር በማመስገን ለቦኤዝ አክብሮትን እያሳየች ነው። የትህትናም ማሳያ ነው።

ባይተዋር የሆንኩት እኔ . . . በፊትህ ሞገዝ ለማግኘት የበቃሁት እንዴት ነው?
ሩት ከልብዋ ትክክለኛ ጥያቄአን እየጠየቀች ነው።

ባይተዋር
ሩት በግልዋ ለእስራኤል አምላክ ተሰጥታለች፤ ነገር ግን በውጪው የምትታወቀው እንደ “ሞዓባዊቷ” ነው።

ነግረውኛል
“ሰምቻለሁ” ይሄ በቀጥተኛ መልኩ፤ “ሰዎች ነግረውኛል” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል።

ሕዝብ እንደመጣሽ
ቦኤዝ መጠቆም የፈለገው ሩት በማታውቀው የኑኃሚን መንደር፣ አገር እና ኃይማኖት መሃከል ለመኖር መምጣቷን ነው።

ዋጋሽን ይክፈልሽ
“ይስጥሽ” ወይንም “መልሶ ይክፈልሽ”

ስላደረግሽው
“ለሰራሽ” ለታማኝነትሽ፤ ከኑኃሚን ጋር በቤተልሄም ለመኖር ስለመምረጥሽ እና የኑኃሚንን አምላክ ስላመንሽ።

በእግዚአብሔር ዘንድ ደሞዝሽ ፍጹም ይሁን
ይሄ ቅኔአዊ አገላለፅ ሲሆን፤ ከዚህ በፊት ካለው ዓረፍተ ነገር ጋር ይመሳሰላል። “የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ብድራትሽን አትረፍርፎ ይመልስልሽ”

በክንፉ ጠላ ሥር ለመጠለል የመጣሽበት
ቦኤዝ እግዚአብሔር የሚተማመኑበትን እንዴት አድርጎ እንደሚከልል ለመግለፅ የሚጠቀመው ንፅፅር፤ ወፎች ጫጩቶቺን በክንፏ ጥላ ስር የምታደርግላቸውን እንክብካቤ ነው። “

Ruth 2:13

በዓይንህ ሞገስ ላግኝ
“ሞገስ ላግኝ” የሚለው ተቀባይነት ማግኘትን ወይንም በእርስዋ ደስተኛ መሆንን ያመላክታል። “በዓይኖችህ” የሚለው ምልከታን የሚያሳይ ሲሆን፤ ምልከታም የእርሱን ግምገማ ለማሳየት የሚጠቅም ዘይቤአዊ አገላለፅ ነው።

ከባርያዎቹ እንደ አንዲቱ ሳልሆን
ይህ ቃል ሊኖረው የሚችለው ትርጉም 1) ሩት ከቦኤዝ አገልጋዮች መሃከል አንዷ አልነበረችም። 2) ሩት ከ ኑኃሚን ልጆች መሃከል አንዱን ማግባቷ በቤተልሔም ምንም ዓይነት ጥቅም እንደምያስገኝላት አላሰበችም።

Ruth 2:14

በምሳም ግዜ
ይህ የሚያሳየው በዕኩለ ቀን መሆኑን ነው።

እንጀራሽንም በሆምጣጤው አጥቅሽ
ይህ በዕርሻ የሚበላ ቀላል ምግብ ነው። ሰዎች መሬት ላይ የተነጠፈ ምንጣፍ ላይ ይቀመጣሉ፤ በመሓከልም የወይን ሆምጣጥጤ ይቀመጥና በተቆረሰ እንጀራ እያጠቀሱም ይመገባሉ።

የወርይ ሆምጣጤ
በእንጀራ እየተጠቀሰ የሚበላ። እስራኤላውያን ይህንን ወይን ይበልጥ ሆምጣጤ እንዲሆን ያፈሉት ነበር።

Ruth 2:15

ደግሞም ልትቃርም በተነሳች ግዜ፤ ቦኤዝ ጎበዛዝቱን
በዚህ ትዕዛዝ ዐውድ ውስጥ፣ ቦኤዝ ይህንን መመርያ ሲሰጥ ሩት ልጸማ በማትችልበት ዕርቀት ላይ እንደነበረ እንረዳለን።

ስትነሳም
“ስትቆምም”

በነዶው መካከል እንኳ
“እንኳ” የሚለው ቃል የሚያመላክተው “ከተለመደው በላይ እና ባሻገር” መሆኑን ነው። ቦኤዝ ሩት ከነዶው ዙርያ እንድትቃርም ይፈቅዱ ዘንድ ለሰራተኞቹ ተዕዛዝ ይሰጣል። ብዙውን ግዜ የሚቃርሙ ሰዎች ወደ ነዶው እንዲጠጉ አይፈቀድም።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከታሰረው ነዶ ላይ ጥቂት ጠቂቱን እየመዘዛቹ
“ከነዶው አስቀርታችሁ ተዉላት” ወይንም “ከነዶው ላይ የ እህሉን ዘለላ ወስዳችሁ ተዉላት”

አታስቀይሟት
“አታሳፍሯት” ወይንም “አታዋርዷት”

Ruth 2:17

ወቃችው
የሚበላውን የእህሉን ክፍል ከገለባው ለየችው።

የእህሉ ዘለላ
ይሄ የሚሰበሰበወሀል የሚበላው ፍሬ ክፍል ለው

አንድ የኢፍ መስፈሪያ
አንድ የኢፍ መስፈሪያ 22 ሊትር ያክላል። “22 ሊትር የሚያህል ገብስ”

ያንንም ይዛ ወደ ከተማው ሄደች
ሩት እህሉን ተሸክማ ወደቤቷ እንደሂአደች ያመላክታል።

አማቷ . . . አየች
“ኑኃሚን”

Ruth 2:19

ዛሬ የቃረምሽው ከየት ነው? የትስ ቦታ ስትሰሪ ዋልሽ?
ኑኃሚን የጠየቀችው ጥያቄ ተመሳሳይ ሲሆን፤ ሩት ስላሳለፈችው ቀን ለማወቅ እጅግ ጓጉታ እንደሆነ ያስታውቃል።

የተባረከ ይሁን
እግዚአብሔር ቦኤዝ ለሩት እና ለኑኃሚን ስላሳያቸው ቸርነት እንዲባርካቸው እየጠየቀች ነው።

በጎነቱን . . . ያልተወ
“ታማኝነቱን ያልተወ” ትርጉሙ ሊሆን የሚችለው 1) ቦኤዝ እንደቤተሰብ ለኑኃሚን ያለበትን ኃላፊነት አስታውሷል። 2)ኑኃሚን በቦኤዝ ውስጥ ስራን እየሰራ ያለውን እግዚአብሔር ማለቷ ነው። 3) እግዚአብሔር ለሕያዋን እና ለሙታን ታማኝነቱን መጠበቁን ላማመልከት ነው።

ለሕያዋን
“በሕይወት ላሉ ሰዎች ሁሉ።” ኑኃሚን እና ሩት “ሕያዋን” ነበሩ።

ለሙታን
የኑኃሚን ባል እና ልጆች “ሞተው” ነበር። “ሙታን” የሚለውን ቃል ሊተካ የሚችል ሌላ ተተኪ ቃል ካለ እርሱን መጠቀም ይቻላል።

ዘመዳችን ነው፤ የመቤዠት ግዴታ ካለባቸው
የሁለተኛው ስንኝ መጀመርያውን የደግመዋል ያሰፋዋልም። በዕብራውያን ይህ አትክሁሮት የመስጫ መንገድ ነው።

የመቤዠት . . . ዘመዶች
የሚቤዥ ዘመድ ማለት አንዲት መበለት የገንዘብ እና ሌላ ችግር ውስጥ እንዳትገባ አግብቶ አንድ ልጆች አብሯት ወልዶ የሚያድናት ማለት ነው።

Ruth 2:21

ደግሞም . . . ብሎኛል
“ደግሞ . . . አለኝ።” ይህ የሚያመላክተው ከዚህ በኋላ ቦኤዝ አለኝ የምትለው ነገር ጠቃሚ እንደሆነ ነው።

ከሰራተኞቼ አትለዪ
ቦኤዝ ሰራተኞቹ ሊሲጧት የሚችሉትን ጥበቃ ያመላክታል።

ብትወጪ
“መሄድ ስሻልሻል።”

ጉዳት ሊያገኝሽ
ለማለት ተፈልጎ የሚሆነው 1)ሌሎች ሰራኞች ሩትን ለጎዷት ይችላሉ እጂንም ይዘው ሊደፍሯት ይችላሉ። 2)በሌሎች እርሻ የእርሻው ባለቤተስከ መኝር መጨረሻ ድረስ እንዳትቃርም ልትከለከል ትችላለጭ

Ruth 2:23

ተጠግታ
ሩትም እስከቀኑ መጨረሻ ድረስ በቦኤዝ እርሻ ስትሰራ ዋለች፤ ደንነቷም ተጠበቀ።

ከአማቷም ጋር ኖረች
ሩት ማታ ላይ ለመተኛት ወደ ኑኃሚን ቤት ትሄድ ነበር።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 አማትዋም ኑኃሚን ለእርስዋ “ልጄ ሆይ፣ ታርፊ ዘንድ፣ ነገሮችም ለአንቺ መልካም ይሆኑልሽ ዘንድ፣ የምታርፊበትን ስፍራ አልፈግልሽምን?” አለቻት። **2** አሁንም ቦዔዝ፣ ከወጣት ሴቶች ሰራተኞቹ ጋር የነበርሽበት ሰው፣ ዘመዳችን አይደለምን? ተመልከቺ፣ እርሱ ዛሬ ማታ በአውድማው ላይ ገብሱን በመንሽ ይበትናል። **3** ስለዚህ፣ ታጠቢ፣ ሽቶሽን ተቀቢ፣ ልብስሽን ቀይሪ፣ ወደ አውድማውም ውረጂ። ነገር ግን መብላትና መጠጣት እስኪጨርስ ድረስ ለሰውዮው አትታወቂ። **4** በተኛም ጊዜ፣ ወደ እርሱ መሄድ እንድትችይ እርሱ የተኛበትን ስፍራ ማስታወስሽን እርግጠኛ ሁኚ፣ እግሩን ግለጪ፣ በዚያም ተጋደሚ። ከዚያም የምታደርጊውን እርሱ ይነግርሻል። **5** ሩትም ለኑኃሚን “የተናገርሽኝን ሁሉ አደርጋለሁ” አለቻት። **6** ስለዚህ ወደ አውድማውም ወረደች፣ እርስዋም አማትዋ የሰጠቻትን ትዕዛዝ ተከተለች። **7** ቦዔዝም በበላና በጠጣ ጊዜ፣ ልቡም ደስ ባለው ጊዜ፣ በእህሉ ክምር ጫፍ ሊተኛ ሄደ። ከዚያም ሩት በቀስታ መጣች፣ እግሩንም ገለጠች፣ ተኛችም። **8** እኩለ ሌሊት በሆነ ጊዜ ሰውዮው ደነገጠ። እርሱም ዘወር አለ፣ አንዲትም ሴት እዚያው እግርጌው ተኝታ ነበረች። **9** እርሱም “ማን ነሽ? አለ። እርስዋም “እኔ ሴት አገልጋይህ ሩት ነኝ” አለችው። አንተ የቅርብ ዘመዴ ነህና ልብስህን በሴት አገልጋይህ ላይ ዘርጋ አለችው። **10** ቦዔዝም፣ “ልጄ ሆይ፣ በእግዚአብሔር የተባረክሽ ሁኚ። ከመጀመርያው ይልቅ በመጨረሻ ብዙ ደግነት አሳይተሻል፣ ምክንያቱም ድሃም ይሁን ባለጠጋ ከወጣት ወንዶች ከአንዳቸውም ጋር አልሄድሽምና” አላት። **11** አሁንም፣ ልጄ ሆይ፣ አትፍሪ! ያልሽውን ሁሉ አደርግልሻለሁ፣ ምክንያቱም በከተማየ ያሉ ሕዝብ ሁሉ ምግባረ መልካም ሴት እንደ ሆንሽ ያውቃሉ። **12** አሁን እኔ የቅርብ ዘመድ መሆኔ እውነት ነው፤ ይሁን እንጂ ከእኔ የበለጠ የሚቀርብ ዘመድ አለ። **13** ዛሬ ሌሊት እዚህ ቆዪ፣ ነገም ጠዋት የዋርሳነትን ግዴታ እርሱ የሚፈጽም ከሆነ፣ መልካም ነው፣ የዋርሳነትን ግዴታ ይፈጽም። ነገር ግን እርሱ ለአንቺ የዋርሳነትን ግዴታ ባይፈጽም፣ ሕያው እግዚአብሔርን እኔ አደርገዋለሁ። እስከ ማለዳ ድረስ ተኚ። **14** ስለዚህ እስከ ማለዳ ድረስ በእግርጌው ተኛች። ነገር ግን አንዱ ሌላውን ማወቅ ከመቻሉ በፊት ተነሳች። ቦዔዝ “ሴት ወደ አውድማው መምጣትዋን ማንም እንዳያውቅ” ብሎ ነበርና። **15** ከዚያም ቦኤዝ “የለበስሽውን ልብስ አምጭና ያዢው” አላት። በያዘችም ጊዜ ስድስት ትልቅ መስፈሪያ ገብስ በልብሷ ላይ ሰፍሮ አሸከማት። የዚያን ጊዜ እርሱ ወደ ከተማ ሄደ። **16** ሩት ወደ አማትዋ በመጣች ጊዜ “ልጄ ሆይ፣ እንዴት ነሽ?” አለቻት። ሩትም ሰውዮው ለእርስዋ ያደረገውን ሁሉ ነገረቻት። **17** እርስዋም “እነዚህ ስድስት መስፈሪያ ገብስ እርሱ የሰጠኝ ናቸው፣ ‘ወደ አማትሽ ባዶ እጅሽን አትሂጂ’” ብሏልና። **18** ኑኃሚንም “ልጄ ሆይ፣ ይህ ጉዳይ እንዴት እንደሚሆን እስከምታውቂ ድረስ በዚህ ቆዪ፣ ሰውዮው ይህን ነገር ዛሬ እስኪጨርስ ድረስ አያርፍምና” አለች።

Ruth 3:1

አማቷ
ኑኃሚን የሩት ሟች ባል እናት ናት

ልጄ
ሩት የኑኃኒንን ልጅ በማግባት ብሎም አብራት ወደ ቤተልሔም በመመለስ የኑኃሚን ልጅ ሆናለች።

የሚመችሽን ቤት እንድፈልግልሽ አይገባኝምን?
“መልካም እንዲሆንልሽ እረፍት አልፈልግልሽም?” ኑኃሚን ይሄንን ጥያቄ በመጠየቅ ያቀደችላትን ለመናገር ትጠቀምበታለች። “እረፍት የመታረጊበትን ቦታ ልፈልግልሽ ይገባኛል” ወይንም “ የሚንከባከብሽ ባል ልፈልግልሽ ይገባኛል።”

የምታርፊበት ቦታ
ትርጉሙ ሊሆን የሚችለው፤ 1) በቀጥታ የምትኖርበትን ቤት ማግኘት ወይንም 2) በማስጠጋት ረገድ የሚንከባከባት ባል ስለመፈለግ። ኑኃሚን ሁለቱንም ማለት ፈልጋ ሊሆንም ይችላል።

ከሴቶች ሠራተኞቹ ጋር አብረሽ የነበርሽበት
የዚህ ግልፅ ትርጉም ከሴቶቹ ጋር እየሰራች እንደነበረ ሊያሳይ ይገባል። “ከገረዶቹ ጋር የለበርሽበት።”

ዘመዳችን አይደለምን?
ኑኃሚን ከዚህ በፊት ለሩት የነገረቻትን ነገር እያስታወሰቻት ነው የሚሆነው። “እርሱ ዘመዳችን ነው።”

አሁንም
“ልብ በይ።” ከዚህ በኋላ የምትላትን ነገር እንድታስተውል እያመለከቻት ነው።

ያበራል
“በመንሽ ይበትናል” ይህ በንፍስ ድጋፍ ሰብሉን ከገለባው የመለየት ሂደት ነው።

Ruth 3:3

ሽቶ ተቀቢ
ይህ መልካም ማዓዛ ያለው ጣሳጭ ሻታ ያለው ዘይት ሊሆን ይችላል። በሁን ግዜ ሽቶ የሚባለው ማለት ነው።

ወደ አውድማው ውረጂ
ይህ የሚያሳየው ከከተማው ወጥቶ ወደሚወቃበት ቦታ ምሄድን ነው።

እግሩን ገልጠሽ
ይህ የሚያመላክተው የለበሰውን መደረብያ እግሩ ጋር መግለጥ እና እግሮቹ እንዲበርዳቸው ማድረግ የሚለውን ነው።

ተኚ
“ከእግሩ ሳር ተኚ”

ከዚያም የምታደርጊውን ራሱ ይነግርሻል
እዚህ ጋር ያለው የባህል ልማድ በእርግጥ ባይታወቅም፤ በባህላሽው የሚታወቅ እና ተቀባይነት ያለው ሴት ልጅ አንድ ወንድ እንዲያገባት ፈቃደኛ እንደሆነች የምታስታውቅበት መንገድ ነው። ቦኤዝም ልማዱ ገብቶት መቀበልም መተውም ይሸላል።

ይነግረሻል
“ሲነሳም፣ እርሱ እራሱ።”

ደስም ከተሰኘ
ይህ በልቡ የሆነ ነገርን ያሳያል። ሰክሮ ነበር ማለት አይደለም። “ሰውነቱም ደስ ከተሰኘ” ወይንም “ከረካ በኋላ”

በቀስታ
“በድብቅ” “ድምጽ ሳታሰማ ማንም ሰው ሳይሰማ”

እግሩንም ገልጣ
“መደረብያውን ከእግሩ ላይ ገልጣ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ተኛች
“ከእግሩ ስር ተኛች”

Ruth 3:8

እንዲህም ሆነ
በትረካው ውስጥ የሆነን አንደ ክስተት ለማስታወቅ የሚጠቅም ስንኝ ነው። በቋንቋችሁ ይህንን የሚያደርግ ቃል ካለ እርሱን መጠቀምን አስቡ።

እኩለ ሌሊት ላይ
“መንፈቀ ሌሊትም በሆነ ግዜ”

ደነገጠ
“አንዳች ነገር አስደነገጠው”

ገልበጥ ሲልም
“ዘወርም አለ”

አንዲት ሴት እገርጌው ተኝታ አገኘ
ሲቲቱ ሩት ነበረች፤ ቦኤዝ ግን ጨልሞ ስለነበር ሊያውቃት/ሊለያት አልቻለም።

አገልጋይህ
ሩት ለቦኤዝ ምላሽ የሰጠችው በትህትና ነበር

ልብስህን ጣል አርግብኝ
ይህ ጋብቻን የሚያመላክት አባባል ነው።

ቅርብ የስጋ ዘመድ
ለዘመዶቹ ኃላፊነት ያለበት ልዩ ዘመድ

Ruth 3:10

ልጄ
ቦኤዝ ይህንን የተጠቀመው ታናሹ እንዳሆነች ሴት ለሩት ያለውን አክበሮት ነው።

ከዚህ በፊት ካደረግሽው ይልቅ ያሁኑ በጎነትሽ ይበልጣል
“ከበፊተኛው ይልቅ በመጨረሻው ግዜ ቸርነት አድርገሻል።”

በመጨረሻው ግዜ ቸርነት
ይህ ሩት ቦኤዝ እንዲያገባት ስለመጠየቁ ነው። የኑኃሚንን ዘመድ በማግባት ሩት ለኑኃሚን የሚያስፈልጋትን ነገር ማቅረብ ትችላለች በዚህም ቸርነትን ታደርጋለች።

ከዚህ በፊት
ይህ የሚያሳየው ሩት ከዚህ በፊትም ለአማቷ እየቃረመች እንደተንከባከበቻት እና አብራት በለቆየት ያደረገችውን ነው።

ፈልገሽ አልሄድሽምና
“አልተከተልሽምና” ሩት ኑኃሚንን ዘንግታ ከኑኃሚን ዘመዶች ውጪ ለማግባት ባል መፈለግ ስትችል ይህንን አላደረገችም።

Ruth 3:12

ከእኔ ይልቅ . . . ቅርብ የስጋ ዘመድ
መበለቲቷን መርዳት ቅርብ የሆነው ወንድ ዘመድ ኃላፊነት ነው።

ሊቤዥሽ ከፈለገ
ቦኤዝ እየተናገረ ያለው ቅርብ ከሆነ ከሞተው የሩት ባል የስጋ ዘመድ የሚጠበቀውን ሩትን የማግባት እና የቤተሰቡን ስም የዞ የመቀጠል ሃላፊነት ነው።

በሕያው እግዚአብሔር
“ሕያው እግዚአብሔርን” ይህ በዕብራይስጥ የተለመደ መሃላ ነው።

Ruth 3:14

እግርጌው ተኛች
ሩት ከቦኤዝ እግር ስር ተኛች። ቦኤዝ አላወቃትም፣ ምንም አላደረጉም።

ሰው ተለይቶ ሊታወቅ በማይችልበት ሰዓት
ይህን አገላለፅ ከበርሃን ጋር አያይዞ መግለፅ ይቻላል። “ገና ጨለማ ሳለ”

የደረብሽውን ልብስ
በትከሻ ላይ የመደረብ ልብስ

ስድስት መስፈርያ ገብስ
ክብደቱ በውል ባይገለፅም። ቸር የሆነ ልገሳ እንደሆነ ይገመታል፣ ነገር ግን ሩት ልትሸከመው የምትችለው ያህል።

አሸከማት
የገብሱ መጠን ሩት በራስዋ ልታነሳው የምትችለው ያክል አልነበረም።

እርሱም ወደከተማይቱ ሄደ
“ወደ ከተማ ተመለሰች” አንዳንድ ቅጂዎች “ተመለሰ” ሲሉ ሌሎች ደግሞ “ተመለሰች” ይሉታል።

Ruth 3:16

የሄድሽበት ጉዳይ እንዴት ሆነ
ኑኃሚን በዚህ ጥያቄ ማለት የፈለገችውን በሌላ ቃል ግልጽ ማድረግ ይቻላል። “ልጄ ምን ሆነ?” ወይንም “ቦኤዝ ምን ዓይነት ምላሽ ሰጠሽ?”

ሰውየው ያደረገላትን ሁሉ
“ቦኤዝ ያደረገላትን ሁሉ”

ባዶ እጅሽን አትመለሺ
“ባዶ እጅሽን አትሂጂ” ወይንም “ምንም ሳትይዢ እንዳትሄጂ” ወይንም “የሆነ ነገር የመሄድሽን እርገት፣ እኛ ሆኚ

እልባት ካላገኘ
ይህ ማን የኑኃሚንን ንብረት እንደሚገዛ እና ሩትን እንደሚያገባ የሚወሰነውን ውሳኔ ያመላክታል።

በር
“የከተማይቱ በር” ወይንም “የቤተልሔም በር” ይህ ቅጥር ወዳላት የቤተልሔም ከተማ ዋና መግቢያ በር ነው። የማህበረሰባዊ ጉዳዬች ላይ ውይይት የሚደረግበትም ክፍት ቦታ በበሩ አቅራብያ ነበር።

የቅርብ ዘመድ
በሕይወት ያላ ቅርቡ የአቤሜሌክ ዘመድ

ከከተማይቱ ሽማግሌዎች
“የከተማይቱ መሪዎች”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 ቦዔዝም ወደ ከተማይቱ በር ሄደና በዚያ ተቀመጠ። ወዲያውኑ ቦዔዝ ሲናገርለት የነበረው የቅርብ ዘመድ መጣ። ቦዔዝም ለእርሱ “ወዳጄ ሆይ፣ ና በዚህም
ተቀመጥ” አለው። ሰውየውም መጣና ተቀመጠ። 2 ቦዔዝም ከከተማይቱ ሽማግሌዎች አሥር ሰዎች ወሰደ፣ “በዚህ ተቀመጡ” አላቸው። እነርሱም
ተቀመጡ። 3 ቦዔዝም የቅርብ ዘመድ ለሆነው፣ “ከሞዓብ ምድር የተመለሰችው ኑኃሚን የወንድማችንን የአቤሜሌክን ቁራሽ መሬት ትሸጣለች። 4 እኔም ለአንተ
አስታውቅህ ዘንድ አሰብሁ እንዲህም አልሁ፦ ‘ይህንን መሬት በዚህ በተቀመጡት በሕዝቤ ሽማግሌዎች ፊት ግዛው።’ መቤዠት ብትፈልግ ተቤዠው። ነገር ግን
መቤዠት የማትፈልግ ከሆነ ግን ከአንተ በቀር ሌላ የሚቤዥ የለምና፣ እኔም ከእአንተ በኋላ ነኝና እንዳውቀው ንገረኝ” አለው። የዚያን ጊዜ ሌላኛው ሰው
“እቤዠዋለሁ” አለው። 5 ቦዔዝም “ከኑኃሚን እጅ እርሻውን በምትገዛበት ቀን፣ የሞተውን ሰው ስም በርስቱ ላይ እንድታስነሣለት የምዋቹን ሰው ሚስት
ሞዓባዊቱን ሩትን ደግሞ መውሰድ አለብህ” አለ። 6 የቅርብ ዘመድ የሆነውም “የራሴን ርስት ሳልጎዳ እርሻውን ለራሴ መቤዠት አልችልም። እኔ ልቤዠው
አልችልምና የእኔን የመቤዠት መብት ለራስህ ውሰድ” አለ። 7 በጥንት ዘመን መቤዠትና የሸቀጦች መለዋወጥ በተመለከተ በእስራኤል ዘንድ አንድ ልማድ
ነበረ። ሁሉንም ነገር ለማጽናት ሰው ጫማውን ያወልቅና ለባልንጀራው ይሰጠዋል፤ በእስራኤል ውስጥ ሕጋዊ ስምምነት የሚኖረው በዚህ ሁኔታ ነበር። 8 ስለዚህ
የቅርብ ዘመዱ ቦዔዝ፣ “አንተ ለራስህ ግዛው” አለው። እርሱም ጫማውን አወለቀ። 9 ቦዔዝም ለሽማግሌዎቹና ለሕዝቡ ሁሉ፣ “ለአቤሜሌክ የነበረውን ሁሉ
እንደዚሁም ለኬሊዎንና ለመሐሎንም የነበረውን ሁሉ ከኑኃሚን እጅ እኔ መግዛቴን እናንተ ዛሬ ምስክሮች ናችሁ። 10 ከዚህም በላይ ስለ መሐሎን ሚስት ስለ
ሞዓባዊቷ ሩት፦ የምዋቹን ሰው ስም በርስቱ ላይ እንዳስነሣ፣ ስሙ ከወንድሞቹ መካከልና ከአገሩም ደጅ እንዳይጠፋ፣ እኔ ደግሞ እርስዋ ሚስቴ እንድትሆን
ወስጃታለሁ። እናንተም ዛሬ ምስክሮች ናችሁ” አላቸው። 11 በበሩ የነበሩ ሕዝብ ሁሉና ሽማግሌዎቹም እንዲህ አሉ፦ “እኛ ምስክሮች ነን። እግዚአብሔር ወደ
ቤትህ የመጣችውን ሴት የእስራኤልን ቤት እንደ ገነቡት እንደ ሁለቱ እንደ ራሔልና ልያ ያድርጋት። አንተም በኤፍራታ ባለጠጋ ሁን፣ በቤተ ልሔምም እንደገና
የታወቅህ ሁን። 12 ቤትህ እግዚአብሔር ከዚህች ወጣት ሴት በሚሰጥህ ዘር በኩል ትዕማር ለይሁዳ እንደወለደችለት እንደ ፋሬስ ቤት ይሁን” አሉት። 13
ስለዚህ ቦዔዝ ሩትን ወሰደ፣ ሚስቱም ሆነች። እርሱም ከእርስዋ ጋር ተኛ፣ እግዚአብሔርም ልጅ እንድትፀንስ ፈቀደላት፣ እርዋም ወንድ ልጅ ወለደች። 14
ሴቶችም ለኑኃሚን፣ “ዛሬ የሚቤዥ የቅርብ ዘመድ ያላሳጣሽ እግዚአብሔር ይባረክ። ይህ ሕጻን ስሙ በእስራኤል ውስጥ የገነነ ይሁን። 15 ይህ ልጅ ለአንቺ
ሕይወትሽን የሚያድስ እርጅናሽንም የሚመግብ ይሁን፣ የምትወድሽ፣ ከሰባትም ወንዶች ልጆች ይልቅ ለአንቺ የምትሻል፣ ምራትሽ ይህን ልጅ ወልዳለችና። 16
ኑኃሚንም ሕፃኑን ወሰደችው፣ በእቅፍዋም አስቀመጠችው፣ እርሱንም ተንከባከበችው። 17 ጎረቤቶቿ የሆኑት ሴቶችም “ለኑኃሚን ወንድ ልጅ ተወለደላት” እያሉ
ስም ሰጡት።እነርሱም ስሙን ኢዮቤድ ብለው ጠሩት። እርሱም የዳዊት አባት የሆነው፣ የእሴይ አባት ሆነ። 18 አሁንም እነዚህ የፋሬስ ትውልድ ነበሩ፦ ፋሬስ
የኤስሮም አባት ሆነ፣ 19 ኤስሮምም የአራም አባት ሆነ፣ አራምም የአሚናዳብ አባት ሆነ፣ 20 አሚናዳብም የነአሶን አባት ሆነ፣ ነአሶንም የሰልሞን አባት ሆነ፣
21 ሰልሞንም የቦዔዝ አባት ሆነ፣ ቦዔዝም የኢዮቤድ አባት ሆነ፣ 22 ኢዮቤድ የእሴይ አባት ሆነ፣ እሴይም የዳዊት አባት ሆነ።

Ruth 4:3

ኑኃሚን መሬት ልትሸጥ ነው።
ለቅርብ ዘመድ፤ የቤተዘመዱን መሬት የመግዛት እና ቤተሰቡን የመንከባከብ ኃላፊነት አለበት። አሁን ደግሞ ይህ ሰው የኑኃሚንን መሬት መግዛት፤ ሩትን ማግባት እና ኑኃሚንን መንከባከብ ይኖርበታል።

ፊት
ይህ የሚደረገውን ስምምነት ህጋዊ እና ፍፁም ያደርገዋል።

መቤዠት
ይህ ማለት መሬቱን መግዛት እና በቤተሰቡ ውስጥ እንዲቆይ ማድረግ ማለት ነው።

ከአንተ ቀጥሎ . . . ስለ ሆንሁ
ቦኤዝ በቀጣይነት መሬቱን ሊቤዥ የሚችለው ዘመድ እርሲ ነበር።

Ruth 4:5

በምትገዛበት ዕለጥ. . . አለብህ
በዚህ የቦኤዝ አነጋገር ለሰውዬው መሬቱን ከመግዛት ጋር አብሮ ያለውን ኃላኢነት ይነግረዋል።

ከኑኃሚን
“ከኑኃሚን እጅ” ይህ የሚያመለክተው መሬቱ የኑኃሚን መሆኑን ነው።

ሩትን አብረህ መውሰድ
“ሩትንም ማግባት”

የሟቹን ሚስት . . . ሩት
“ሩት የአቤሜሌክ ልጅ መበለት”

የሟቹን ስም . . . ለማስጠራት
“ንብረቱን የሚወርስ ወንድ ልጅ እንዲኖራት እና የሞተውን ባሏን ስም እንዲያስቀጠል።”

የራሴን ርስት አደጋ ላይ ሊጥል
ሩት ለምትወልድለት ልጆች ደግሞ የራሱን ሃብት ማካፈል ስለሚኖርበት

የኔን የሜቤዠት ስልጣን አንተ ውሰደው
“አንተው እራስህ ተቤዠው” ወይንም “በእኔ ፈንታ አንተ ተቤዠው።”

Ruth 4:7

ልማድ ነበረ
ጸሃፊው ሩት በነበረችበት ዘመን በልውውጥ ግዜ የሚደረገውን ነገር እያብራራ ነው።

በጥንት ግዜም
“በጥንት ዘመን።” ይህ የሚያመላክተው መጸሓፉ በተጻፈበት እና ታሪኩ በተፈፀመበት ግዜ ልማዱ እንደተለወጠ ነው።

ጫማውን
“ነጠላ ጫማውን።”

ለባልንጀራውም
ይህ የሚያመላክተው ከእርሱ ጋር ስምምነት እያደረገ ያለውን ሰው ነው። በዚህ ግዜ ቅርብ የስጋ ዘመድ የተባለው ሰው ለቦኤዝ እንደማለት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ruth 4:9

ለሽማግሌዎቹ እና ለህዝቡ ሁሉ
ይህ ማለት በስብሰባቸው ላይ የነበሩት ሰዎች ሁሉ ማለት እንጂ በከተማው ያሉ ሰዎች ሁሉ ማለት አይደለም።

የአቤሜሌክን፣ የኬሌዎንን እና የመሓሎንን ንብረት በሙሉ
ይህ የሚያመላክተው የኑኃሚን ሟች ባል እና ልጆች ሃብት በሙላ ማለት ነው።

ከኑኃሚን
“ከኑኃሚን እጅ” ለንብረቱ ሁላ ኃላፊ የነበረችው እና የምትሰጠው ኑኃሚን ለመሆኗ ማሳያ ነው።

የሟቹን ስም በርስቱ ላይ ለማስጠትራት
ሩት የምትወልደው የመጀመርያ ልጅ ህጋዊ የመሓሎን ልጅ ተደርጎ ይቆጠራል። ቦኤዝም ከኑኃሚን የገዛውን መሬት ይወርሳል። “የሞተውን ሰውዬ መሬት የሚወርስ ወንድ ልጅ እንድሰጣት።”

የሟቹ ስም ከወንድሞቹ መካከል ከአገሩ ደጅ እንዳይጠፋ
መረሳት የሚታየው ቀድሞ ይኖሩ ከነበሩ ሰዎሽ ስም ዝርዝር እንደመቆረጥ ነው። “በወንደሞቹ ትውልድ ዘንድ እና በከተማው እንዳይረሳ።”

ከአገሩ ደጅ
ይህ የሚያመላክተው የከተማውን ደጅ ሲሆን፤ በዚህም ቦታ የመሬት ባለቤትነትን በተመለከተ ውሳኔ የሚሰጥበት ቦታ ነው።

Ruth 4:11

በከተማይቱ በር የነበሩ ሁሉ
“ሌሎች በበር አቅራብያ ይሰበሰቡ የነበሩ ሁሉ።”

ወደ ቤትህ የምትገባውን
ይህ ምሳሌያዊም ቀጥተኛም ትርጉም አለው። ሩት ቦኤዝን ስታገባው ወደቤቱ ትገባለጭ ቤት መግባት ማለት ደግሞ ቤተሰቡን መቀላቀልንም ያመላክታል።

እንደ ራሔል እና ልያ
እነኚህ የያዕቆብ ሁለት ሚስቶች ሲሆኑ ስማቸውም ወደ እስራኤል ተቀይሯል።

የእስራኤልን ቤት እንደሰሩ
“ብዙ ልጆችን ወልደው የእስራኤል ሐዝብ ያደረጉ።”

በኤፍራታ የበረታ
ኤፍራታ ቦኤዝ በቤተንሔም የሚነኝበት ነገድ ነው።

ቤትህ እንደ
እግዚአብሔር ይሁዳን በልጁ በፋሬስ እጅጉን ባርኮት ነበር፤ ሰዎቹም በተመሳሳይ መንገድ ቦኤዝን በሩት ልጆች እንዲባርከው እግዚአብሔርን ጠየቁጥ

ትዕማር ለይሁዳ እንደወለደችው
ተዕማር መበለት ነበረች። ይሁዳም ከእርሷ ወንድ ልጅ ወለደ፤ የቤተሰቡም ስም በዛ ቀጠለ።

እግዚአብሔር . . . በሚሰጥህ ዘር
እግዚአብሔር በሩት በኩል ልጅ እንደሚሰጠው

Ruth 4:13

ቦኤዝ ሩትን ወሰዳት
“ቦኤዝ ሩትን አገባት” ወይንም “ቦኤዝ ሩትን እንደ ሚስት ወሰዳት”

ወደ እርሷ ገባ
ቦኤዝ ሩትን እንዳወቃት የሚያሳይ ነው። “ቦኤዝ ሩትን ደረሰባት”

ቅርብ የስጋ ዘመድ ያላሳጣሽ
አዎንታዊ ትርጉም ሊሰጠው ይችላል። “ዛሬ የቅርብ ዘመድ የሰጠሽ”

ስሙ ይግነን
ይሄ የሚያመላክተው የኑኃሚንን የልጅ ልጅ ዝና እና ባህርይ ነው።

ሕይወትሽን ያድሳታል
ኑኃሚን በልጅ ልጇ ምክኛት እንዴት በድጋሚ ደስታን እና ተስፋን እንደምትለማመድ ሊያሳይ ይችላል። “ድስታን በድጋሚ ወደ አንቺ የሚያመጣ” ወይንም “በድጋሚ እንደ ወጣት የሚያበረታሽ።”

በእርጅና ዘመንሽም ይጦርሻል
“ባረጀሽ ግዜ የሚንከባከብሽ።”

ከሰባት ወንድ ልጆች የምትበልጥ
በእስራኤላውያን “ሰባት” የፍፁምነት ቁጥር ነው። የኑኃሚን ወንድ ልጆች ሳይወልዱላት ሞቱ፤ ሩት ግን ከቦኤዝ የልጅ ልጅ ወለደችላት። “ከምንም ዓይነት ልጅ የምትሻል።”

Ruth 4:16

ኑኃሚን ልጁን ተቀብላ
ሉጁን እንደያዘችው እንጂ ከሩት እንደወሰደችባት መታየት የለበትም።

ታቀፈችው
“ከደረቷ አስጠግታ ያዘችው።”የሄ የፍቅር እና መውደድ ማሳያ ነው።”

ለኑኃሚን ወንድ ልጅ ተወለደላት
“ልጁ ለኑኃሚን እንደልጇ ነው።” ኑኃሚን ልጁን ባትወልደውም የእርሷ የልጅ ልጅ እንደሆነ የታወቀ ነበር።

የዳዊት አባት
“የንጉስ ዳዊት አባት።” ንጉስ የሚለው ያልተጠቀሰው የመጀመርያዎቹ አንባብያን ዳዊት ንጉስ እንደነበረ ስለሚረዱ ነው።

Ruth 4:18

የፋሬስ ቤተሰብ ትውልድ
“ከእርሱ የወጡት ትውልዶች።” ከፋሬስ የተለሳበት ምክንያት ከዚህ በፊት ፋሬስ የይሁዳ ልጅ መሆኑ ስለተገለጠ ነው፤ ከእርሱም ቀጥሎ የቤተሰቡን ዝርዝር መናገር የቀጥላል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: 1 Samuel

1 Samuel

Chapter 1

1 በተራራማው በኤፍሬም አገር በራማ መሴፋ የሚኖር አንድ ሰው ነበር፤ ስሙ ሕልቃና ይባላል፥ እርሱም የኤፍሬማዊው የናሲብ ልጅ፥ የቶሑ ልጅ፥ የኤሊዮ ልጅ፥ የኢያርምኤል ልጅ ነበር። 2 እርሱም ሁለት ሚስቶች ነበሩት፤ ስማቸውም የአንደኛዋ ሐና፥ የሁለተኛዋም ፍናና ነበር። ፍናና ልጆች ነበሯት፣ ሐና ግን አንድም ልጅ አልነበራትም። 3 ይህም ሰው በየዓመቱ ለሠራዊት ጌታ ለእግዚአብሔር ለመስገድና መሥዋዕት ለማቅረብ ወደ ሴሎ ይሄድ ነበር። የእግዚአብሔር ካህናት የሆኑት ሁለቱ የኤሊ ወንዶች ልጆች አፍኒንና ፊንሐስ በዚያ ነበሩ። 4 በየዓመቱ ሕልቃና የሚሠዋበት ጊዜ ሲደርስ፥ ለሚስቱ ፍናና፥ ለወንዶችና ሴቶች ልጆችዋ በሙሉ ሁልጊዜ ከመሥዋዕቱ ሥጋ ድርሻቸውን ይሰጣቸው ነበር። 5 ነገር ግን ሐናን ይወዳት ስለነበር ሁልጊዜም ድርሻዋን ሁለት ዕጥፍ አድርጎ ይሰጣት ነበር፤ እግዚአብሔር ግን ማኅፀንዋን ዘግቶት ነበር። 6 እግዚአብሔር ማኅፀንዋን ዘግቶት ስለነበር ጣውንቷ እርስዋን ለማስመረር ክፉኛ ታስቆጣት ነበር። 7 ስለዚህ በየዓመቱ ወደ እግዚአብሔር ቤት ከቤተሰብዋ ጋር በምትወጣበት ጊዜ ጣውንቷ ሁልጊዜ ታበሳጫት ነበር። በዚህ ምክንያት ታለቅስ ነበር፤ ምግብም አትበላም ነበር። 8 ባሏ ሕልቃና ሁልጊዜ "ሐና ሆይ፥ ለምንድነው የምታለቅሽው? ምግብስ የማትበዪው ለምንድነው? ልብሽ የሚያዝነውስ ለምንድነው? ከዐሥር ወንዶች ልጆች ይልቅ ላንቺ እኔ አልሻልም?" ይላት ነበር። 9 ከእነዚህ ወቅቶች በአንዱ፥ በሴሎ መብላታቸውንና መጠጣታቸውን ከጨረሱ በኋላ ሐና ተነሣች። ካህኑ ዔሊ በእግዚአብሔር ቤት መግቢያ በራፍ በወንበሩ ላይ ተቀምጦ ነበር። 10 እርሷም እጅግ አዝና ነበር፤ ወደ እግዚአብሔር ጸለየች፥ አምርራም አለቀሰች። 11 እንዲህ ስትልም ስዕለት ተሳለች፣ "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፥ የአገልጋይህን ጉስቁልና ብትመለከትና ብታስበኝ፥ አገልጋይህን ባትረሳኝ፥ ነገር ግን ወንድ ልጅን ብትሰጠኝ፥ እኔም የሕይወት ዘመኑን ሁሉ ለእግዚአብሔር እሰጠዋለሁ፥ መቼም ቢሆን ጸጉሩ አይላጭም"። 12 በእግዚአሔር ፊት ጸሎቷን ቀጥላ እያለች ዔሊ አፏን ይመለከት ነበር። 13 ሐና በልቧ ትናገር ነበር። ከንፈሮችዋ ይንቀሳቀሱ ነበር፥ ድምፅዋ ግን አይሰማም ነበር። ስለዚህ ዔሊ ሰክራለች ብሎ አሰበ። 14 ዔሊም "ስካርሽ የሚቆየው እስከ መቼ ነው? ወይንሽን ከአንቺ አርቂው" አላት። 15 ሐናም፣ "ጌታዬ ሆይ፥ አይደለም፥ እኔ ልቤ በሐዘን የተጎዳብኝ ሴት ነኝ። ወይን ወይም የሚያሰክር መጠጥ አልጠጣሁም፥ ነገር ግን ነፍሴን በእግዚአብሔር ፊት እያፈሰስኩ ነው። 16 አገልጋይህን እንደ ኃፍረተ ቢስ ሴት አትቁጠረኝ፤ ይህን ያህል ጊዜ የተናገርኩት እጅግ ከበዛው ሐዘኔና ጭንቀቴ የተነሣ ነው" በማለት መለሰችለት። 17 ከዚያም ዔሊ፣ "በሰላም ሂጂ፤ የእስራኤል አምላክ የለመንሽውን ልመና ይስጥሽ" ብሎ መለሰላት። 18 እርሷም፣ "አገልጋይህ በዐይንህ ፊት ሞገስን ላግኝ" አለችው። ከዚያም መንገዷን ሄደች፥ በላችም፤ ከዚያም በኋላ ፊቷ ሐዘንተኛ አልሆነም። 19 እነርሱም ማልደው ተነሥተው በእግዚአብሔር ፊት ሰገዱ፥ ከዚያም ወደ መኖሪያቸው ወደ አርማቴም ተመለሱ። ሕልቃና ከሚስቱ ከሐና ጋር ተኛ፥ እግዚአብሔርም አሰባት። 20 ጊዜው ሲደርስም ሐና አረገዘችና ወንድ ልጅ ወለደች። "ከእግዚአብሔር ስለ እርሱ ለምኜ ነበር" ስትል ስሙን ሳሙኤል ብላ ጠራችው። 21 ሕልቃናና ቤተ ሰቡ በሙሉ ለእግዚአብሔር ዓመታዊውን መሥዋዕት ለማቅረብና ስዕለታቸውን ለመፈጸም ዳግመኛ ወደ ሴሎ ወጡ። 22 ሐና ባሏን "ልጁ ጡት መጥባት እስኪያቆም እኔ አልሄድም፤ ከዚያም በእግዚአብሔር ፊት እንዲታይና ለዘላለም በዚያ እንዲኖር አመጣዋለሁ" ብላው ስለነበረ አልሄደችም። 23 ባሏም ሕልቃና፥ "መልካም መስሎ የታየሽን አድርጊ። ጡት መጥባቱን እስኪያቆም ቆዪ፥ ብቻ እግዚአብሔር ቃሉን ያጽና" አላት። ስለዚህ ልጁ ጡት መጥባቱን እስኪያቆም ድረስ በቤት በመቆየት ተንከባከበችው። 24 ጡት መጥባቱን ባስቆመችው ጊዜ፥ እርሱን ከሦስት አመት ወይፈን፥ አንድ ኢፍ ዱቄትና አንድ ጠርሙስ ወይን ጋር በሴሎ ወደሚገኘው ወደ እግዚአብሔር ቤት ወሰደችው። ልጁ ገና ሕፃን ነበር። 25 ወይፈኑን አረዱት፤ ልጁንም ወደ ዔሊ አመጡት። 26 እርሷም፥ "ጌታዬ ሆይ፥ ሕያው እንደመሆንህ፥ እዚህ አጠገብህ ቆማ ወደ እግዚአብሔር የጸለየችው ሴት እኔ ነኝ። 27 ስለዚህ ልጅ ጸለይኩኝ፥ እግዚአብሔርም የለመንኩትን ልመና ሰጥቶኛል። 28 ለእግዚአብሔር ሰጥቼዋለሁ፤ በሕይወት በሚኖርበት ዘመን ሁሉ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ይሆናል"። እነርሱም በዚያ ለእግዚአብሔር ሰገዱ።

---

1 Samuel 1:1

አርማቴም
ይህ የአንዲት ትንሽ መንደር ስም ሲሆን ከኢየሩሳሌም በሰሜን ምዕራብ ስምንት ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ የምትገኝ ሳትሆን አትቀርም። (የስሞች አተረጓገም መንገድ፦ ተመልከት)

መሴፋ
ይህ የመሴፍ ትውልድ የሆኑ የሰዎች ስብስብ ስም ነው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ፦ ተመልከት)

ሕልቃና ... ኢያሬም ... ኢሊዩ ... መሴፍ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ፦ ተመልከት)

ፍናና
ይህ የአንዲት ሴት ስም ነው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ፦ ተመልከት)

1 Samuel 1:3

ያም ሰው
"ያም ሰው' የሚለው ሕልቃናን ያመለክታል።

ያህዌ
ይህ እርሱ በብሉይ ኪዳን ለሕዝቡ የገለጠው የእግዚአብሔር ስም ነው። ያህዌን በሚመለከት እንዴት እንዴት እንደሚተረጎም የትርጉም ቃላት ገጽን ተመልከት።

ዔሊ፣ አፍኒንና ፊንሐስ
እንዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ፦ ተመልከት)

1 Samuel 1:5

ሐና
ይህ የአንዲት ሴት ስም ነው። ይህንን በ1 ሳሙኤል 1፡2 እንዴት እንደምትተረጉም ተመልክት። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት።)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ማኅፀንዋን ዘግቶ ነበር
"መካን አድርጓት ነበር' ወይም "ወደ እርግዝና እንዳትመጣ አግዷት ነበር'

ተፎካካሪዋ በጣም ታበሳጫት ነበር
ሌላኛዋ ሚስት (ጣውንትዋ) ሐናን ብዙ ጊዜ ታሳዝናትና ታዋርዳት ነበር

1 Samuel 1:7

ተፎካካሪዋ
የሕልቃና ሌላኛዋ ሚስት ፍናና ነች። ተፎካካሪ ማለት ሌላውን ሰው በመቃወም የሚወዳዳር ሰው ማለት ነው። በዚህ ጉዳይ ሕልቃና አብልጦ እንዲወዳት ፍናና ሐናን በመቃወም ትወዳደራት ነበር።

ሐና ሆይ ለምን ታለቅሻለሽ? ለምንስ አትቀምሽም? ለምንስ ልብሽ ያዝንብሻል? እኔስ ከአሥር ልጆች አልሻልልሽምን?
አስፈላጊ ከሆነ አሳብ ገላጭ ጥያቄዎች በገላጭ አባባል ሊተረጎሙ ይችላሉ። አት፡- "ሐና ማልቀስ የለብሽም። እኔ ለአንቺ ከአሥር ልጆች ይልቅ ስለምሻልሽ ልትበይና ልብሽም ደስ ሊለው ይገባል።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄዎች ተመልከት)

ከአስር ልጆች ይልቅ
ሐና ምን ያህል ለእርሱ አስፈላጊ እንደሆነች አጽንዖት ለመስጠት ሕልቃና አጋኖ እየተናገረ ነው። አት፡- "ማንኛውም ልጅ ሊሆነው ከሚችለው በላይ' (ግነትና ማጠቃለያ ተመልከት)

1 Samuel 1:9

አጠቃላይ መረጃ
ሐና ወደ እግዚአብሔር መጸለይ ጀመረች ዔሊም ተመለከታት።

በኋላም ሐና ተነሣች
ግልጽ ያልሆነ መረጃ በዚህ ስፍራ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። ወይ የሐና ድንኳን ከመገናኛው ድንኳን ቀጥሎ ነበር ወይም ለመጸለይ ከድንኳንዋ ወደ መገናኛው ድንኳን ሄዳ ነበር። አት፡- "በኋላም ሐና ተነሣች ለመጸለይም ወደ እግዚአብሔር ቤት ሄደች።' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ይልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ካህኑም ዔሊ
"ም' የሚለው ቃል እየተተረከ የዋናው ታሪክ ፍሰት መቋረጡን ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል። በዚህ ስፍራ ጸሐፊው በታሪኩ ስለሌላ አንድ ሰው ይነግረናል። ይህም ሰው ካህኑ ዔሊ ነው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ፡- ተመልከት)

የእግዚአብሔር መቅደስ
"መቅደሱ' በእርግጥ ድንኳን ነበር ነገር ግን ሕዝቡ ያመልክበት የነበረ ስፍራ ስለ ነበር፣ በዚህ ስፍራ መቅደስ ብሎ መተረጎም ይበልጥ የተመረጠ ነው።

በልባዋ ትመረር ነበር
ምንም ልጆች ስለሌላትና የባሏ ሌላኛዋ ሚስቱ ፍናና ያለማቋረጥ ታዋርዳት ስለነበር ሐና እጅግ ትታወክና ታዝን ነበር። (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትንና ያልተገለጸ መረጃን ተመልከት)

1 Samuel 1:11

አያያዥ አሳብ
ሐና ወደ እግዚአብሔር የምታደርገው ጸሎት ቀጠለ።

የባርያህን መከራ
መከራ የሚለው የነገር ስም በማሰሪያ አንቀጽ ሐረግነት ሊተረጎም ይችላል። ይህ የሚከተሉትን ሊያመለክት ይችላል፡- 1) የሐናን ማርገዝ አለመቻል። አት፡- "ማርገዝ ካለመቻሌ የተነሣ ምን ያህል መከራ እየተቀልኩ ነው' ወይም 2) ፍናን እርሷን ሁል ጊዜ የምታዋርድበትን መንገድ። አት፡- "ያቺ ሴት ምን ያህል መከራ እያሳየችኝ አንደሆነ' (የነገር ስሞች ተመልከት)

አስበኝ
እግዚአብሔር ስለ ሐና እርምጃ እንዲወስድ የቀረበ የተለየ ልመና ነው። ሐና ላይ ምን እየሆነባት እንዳለ እግዚአብሔረ ያውቃል፣ አልረሳም።

ባርያህን አትርሳ
ይህ ሐረግ የሚለው ነገር "አስበኝ' ከሚለው ጋር ተመሣሣይ ነው ማለት ይቻላል። (አጓዳኝነት ተመልከት)

1 Samuel 1:12

ዔሊ ይመለከታት ነበር
ዔሊ ሊቀ ካህናት ነበር፣ በመሆኑም በእግዚአብሔር መገናኛ ድንኳን ነበረ በእርሷም ኃላፊነት ነበረበት። (የስሞች አተረጓገም መንገድ፡- ተመልከት)

1 Samuel 1:15

እኔስ ልባዋ ያዘነባት ሴት ነኝ
"እኔ እጅግ ያዘንኩ ሴት ነኝ።'

በእግዚአብሔር ፊት ነፍሴን አፈሰስሁ
ይህ "ጥልቅ የሆነ ስሜቴን ለእግዚአብሔር እየነገርኩ ነኝ' የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ ንግግር ነው። (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ባሪያህን እንደ ... አትቁጠር
ሐና ትህትናዋን ለማሳየት ስለ ራሷ በሁለተኛ መደብ ተውላጠ ስም ትናገራለች። በአንደኛ መደብ ተውላጠ ስም ሊተረጎም ይችላል። አት፡- "ባርያህን እንደ ... አትቁጠረኝ' ወይም "አትቁጠረኝ' (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሦሥተኛ መደብ ተመልከት)

ከጭንቀቴና ከብስጭቴ ብዛት እስከ አሁን ተናግሬአለሁ
እንደ 1:15፣ ሐዘንተኛ ልብ እንዳላት የተነገረ ሌላ የአባባል መንገድ ነው። ብዛት፣ ጭንቀት እና ብስጭት የሚሉት የነገር ስሞች በቅጽልነት እና በማሰሪያ አንቀጽነት ሊተረጎሙ ይችላሉ። አት፡- "እስካሁን የተናገርኩት በጣም ስላዘንኩና ተፎካካሪዬ እጅግ ስላበሳጨችኝ ነው።' (የነገር ስም ተመልከት)

ጭንቀትና ብስጭት
እነዚህ ሁለቱም ቃላት ተፎካካሪዋ ታበሳጫት ስለነበር ሐና ታዝንና ትናደድ ነበር የሚል ትርጉም አላቸው። (የሁለት ነገሮች ተመሳሳይነት ተመልከት)

ጭንቀት
ፍናና ታስቆጣትና ታናድዳት ነበር።

ብስጭት
ፍናና ክፉ ስለሆነችባት ሐና ይሰማት የነበረውን የሐዘንና የውርደት ስሜት እያመለከተች ነው።

1 Samuel 1:17

ዔሊም ... መለሰላት
ዔሊ በማደሪያው ድንኳን የሚኖር ሊቀ ካህናት ነበር።

ባርያህ ... ታግኝ
ለሊቀ ካህናቱ ለዔሊ ያላትን አክብሮት ለማሳየት ሐና ራስዋን በሁለተኛ መደብ ተውላጠ ስም ትተራለች። ይህ በአንደኛ መደብ ተውላጠ ስም ሊተረጎም ይችላል። (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሦሥተኛ መደብ ተመልከት)

በዓይንህ ፊት ሞገስ ላግኝ
በዚህ ስፍራ "ሞገስ ላግኝ' ማለት ተቀባይነት ማግኘት ወይም የእርሱ በእርሷ መደሰት የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ ንግግር ነው። በዚህ ስፍራ ዓይን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ማየትን የሚያመለክት ስም ሆኖ ጥቅም ላየ ውሏል፣ ማየት ደግሞ የአንድን ነገር ዋጋ መበየንን ወይም መወሰንን ይወክላል። (ምትክ ስምና ስዕላዊ ንግግርን ተመልከት)

በላችም፣ ፊትዋም
በዚህ ስፍራ ፊትዋ የሚወክለው ራሷን ሐናን ነው። አስፈላጊ ከሆነ ይህን የተለያየ ዐረፍተ ነገር ማድረግ ትችላለህ። አት፦ "በላች። እርሷ ነበረች' ወይም "በላች። እርሷ እንደ ነበረች ሰዎች ማየት ቻሉ።' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

1 Samuel 1:19

አሰባት
ሐና ይገጥማት የነበረውን ነገር እግዚአብሔር ያውቅ ነበር፣ አልዘነጋትም። በ1 ሳሙኤል 1፡11 የሚገኙትን ተመሣሣይ ቃላት እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ሐና ጸነሰች
ሐና አረገዘች

1 Samuel 1:21

ቤቱ
ቤት የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን ለማመልከት ጥቅም ላይ ይውል የነበር ስዕላዊ ስም ነው። አት፦ "ቤተሰቡ' (ምትክ ስም ተመልከት)

ጡት እስኪተው
ወተት መጠጣት ማቆምና ጠንካራ ምግብ ብቻ መመገብ መጀመር

በእግዚአብሔር ፊት ይታይ ዘንድ፣ በዚያም ለዘላለም ይሆን ዘንድ
ሳሙኤል ከዔሊ ጋር በቤተ መቅደስ እንዲኖርና እንዲያገለግል እንደምታደርግ ሐና ለእግዚአብሔር ቃል ገብታ ነበር (1ሳሙ 1፡11)።

ልጅዋን አጠባች
"ለልጅዋ ወተት ሰጠች'

1 Samuel 1:24

አፍ
አንድ አፍ 22 ሊትር ደረቀ ነገር ያህል ነው።

ጠርሙስ
ወይን የሚቀመጠው ከእንስሳት ቆዳ በተሰራ እቃ ነው (አቁማዳ)፣ በብርጭቆ ጠርሙስ አልነበረም።

1 Samuel 1:26

ጌታዬ ሆይ በሕያው ነፍስህ እምላለሁ!
በዚህ ስፍራ "በሕያው ነፍስህ' የሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ሐና ታማኝና እውነተኛ እንደሆነች ያሳያል። አት፦ "ጌታዬ ሆይ፣ የምነግርህ ፈጽሞ እውነት ነው።' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

የለመንሁትን ልመናዬን ሰጥቶኛል
"ልመና' የሚለው ስም አንድ ነገር እንዲያደርግ ለሌላ ሰው የቀረበን ይፋ ጥያቄ ያመለክታል። በማሰሪያ አንቀጽነት ሊተረጎም ይችላል። "ልመናን መስጠት' የሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ሰውዬው የጠየቀውን ማድረግ ማለት ነው። አት፦ "እንዲያደርግ አጥብቄ የጠየቅሁትን ለማድረግ ተስማማ' (የነገር ስምና ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ለእግዚአብሔር የተሰጠ ይሆናል
በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊተረጎም ይችላል። አት፦ "ለእግዚአብሔር ሰጥቼዋለሁ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

እግዚአብሔርን አመለከ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) እርሱ የሚለው ሕልቃናን ሊያመለክት ይችላል ወይም 2) እርሱ የሚለው ሁለቱንም ሕልቃናንና ቤተ ሰቡን የሚያመለክት ተለዋጭ ስም ነው። (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 ሐናም እንዲህ በማለት ጸለየች፥ “ልቤ በእግዚአሔር በደስታ ተሞላ። ቀንዴም በእግዚአብሔር ከፍ አለ። በማዳንህ ደስ ብሎኛልና አፌ በጠላቶቼ ላይ ተከፈተ።
2 አንተን የሚመስልህ የለምና፥ እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ የለም፤ እንደ አምላካችን ያለም ዐለት የለም። 3 ከእንግዲህ አትታበዩ፤ አንዳች የዕብሪት ንግግር
ከአፋችሁ አይውጣ። እግዚአብሔር ዐዋቂ አምላክ ነውና፤ ሥራዎች ሁሉ በእርሱ ይመዘናሉ። 4 የኃያላን ሰዎች ቀስት ተሰብሯል፥ የተሰናከሉት ግን ኃይልን
ታጥቀዋል። 5 ጠግበው የነበሩት እንጀራ ለማግኘት ሲሉ ለሥራ ተቀጠሩ፤ ተርበው የነበሩት ረሃብተኝነታቸው አብቅቷል። መካኒቱ እንኳን ሰባት ወልዳለች፥ ብዙ
ልጆች የነበሯት ሴት ግን ጠውልጋለች። 6 እግዚአብሔር ይገድላል፥ ያድናልም። ወደ ሲዖል ያወርዳል፥ ያነሣልም። 7 እግዚአብሔር ድሃ ያደርጋል፥ ባለጸጋም
ያደርጋል። እርሱ ያዋርዳል፥ ደግሞም ከፍ ያደርጋል። 8 እርሱ ድሃውን ከመሬት ያነሣዋል። ምስኪኖችን ከልዑላን ጋር ሊያስቀምጣቸውና የክብርን ወንበር
ሊያወርሳቸው ከአመድ ክምር ላይ ብድግ ያደርጋቸዋል። የምድር መሠረቶች የእግዚአብሔር ናቸውና ዓለምን በእነርሱ ላይ አድርጓል። 9 የታመኑ ሰዎችን እግር
ይጠብቃል፥ ማንም በኃይሉ አያሸንፍም፤ ክፉዎች ግን በጨለማ ውስጥ ወዳለው ጸጥታ ይጣላሉ። 10 እግዚአሔርን የሚቃወሙ ይደቅቃሉ፤ እርሱ ከሰማይ
ያንጎደጉድባቸዋል። እግዚአብሔር በምድር ዳርቻዎች ላይ ይፈርዳል፤ የእርሱ ለሆነው ንጉሥ ኃይልን ይሰጠዋል፥ ለቀባውም ቀንዱን ከፍ ያደርግለታል።” 11
ከዚያም ሕልቃና በራማ ወደሚገኘው ቤቱ ሄደ። ልጁም በካህኑ በዔሊ ፊት እግዚአብሔርን ያገለግል ነበር። 12 የዔሊ ወንዶች ልጆች ምንም የማይረቡ ነበሩ።
እግዚአብሔርን አያውቁም ነበር። 13 የካህናቱ ልማድ ከሕዝቡ ጋር እንደዚያ ነበርና፥ ማንኛውም ሰው መሥዋዕት ሲያቀርብ፥ ሥጋው እየተቀቀለ እያለ የካህኑ
አገልጋይ ሦስት ጣት ያለው ሜንጦ ይዞ ይመጣ ነበር። 14 እርሱም ወደ ድስቱ፥ ወይም ወደ አፍላሉ፥ ወይም ወደ ምንቸቱ ውስጥ ያጠልቀው ነበር። ሜንጦው
ያወጣውንም ሁሉ ካህኑ ለራሱ ይወስደው ነበር። ይህንን ወደዚያ ወደ ሴሎ በሚመጡት እስራኤላውያን ሁሉ ላይ ያደርጉ ነበር። 15 ይልቁንም ስቡን
ከማቃጠላቸው በፊት የካህኑ አገልጋይ ይመጣና የሚሠዋውን ሰው፥ “ጥሬውን ብቻ እንጂ የተቀቀለውን ሥጋ ከአንተ አይቀበልምና ለካህኑ እንድጠብስለት ሥጋ
ስጠኝ" ይለው ነበር። 16 ሰውየው፥ "መጀመሪያ ስቡን ማቃጠል አለባቸው፥ ከዚያም የፈለከውን ያህል መውሰድ ትችላለህ" ካለው ያ ሰው መልሶ፥ "አይደለም፥
አሁኑኑ ስጠኝ፤ እምቢ ካልክም በግድ እወስደዋለሁ" ይለው ነበር። 17 የእግዚአብሔርን መስዋዕት ንቀዋልና የእነዚህ ወጣቶች ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት
እጅግ ታላቅ ነበር። 18 ትንሹ ልጅ ሳሙኤል ግን ከተልባ እግር ጨርቅ የተሠራ ኤፉድ ለብሶ እግዚአብሔርን ያገለግል ነበር። 19 እናቱም ዓመታዊውን መሥዋዕት
ለማቅረብ ከባሏ ጋር በምትመጣበት ጊዜ በየዓመቱ አነስተኛ መደረቢያ ልብስ እየሠራች ታመጣለት ነበር። 20 ዔሊም ሕልቃናን እና ሚስቱን እንዲህ በማለት
ባረካቸው፥”ከእግዚአብሔር በለመነችው ልመና ምክንያት እግዚአብሔር ከዚህች ሴት ተጨማሪ ልጆችን ይስጥህ።“ ከዚያም ወደ ራሳቸው መኖሪያ ተመለሱ።
21 እግዚአብሔር እንደገና ሐናን ረዳት፥ እንደገናም አረገዘች። እርሷም ሦስት ወንዶችና ሁለት ሴት ልጆችን ወለደች። እንዲሁም ትንሹ ልጅ ሳሙኤል
በእግዚአብሔር ፊት አደገ። 22 ዔሊ በጣም አርጅቶ ነበር፤ ልጆቹ በእስራኤላውያን ሁሉ ላይ እያደረጉ ያሉትን በሙሉ እና በመገናኛው ድንኳን መግቢያ
ከሚያገለግሉት ሴቶች ጋር እንደ ተኙ ሰማ። 23 እርሱም እንዲህ አላቸው፥”ስለ ክፉ ሥራችሁ ከዚህ ሕዝብ ሁሉ ሰምቻለሁና እንደዚህ ያሉትን ነገሮች
የምትፈጽሙት ለምንድነው? 24 ልጆቼ ሆይ፥ የምሰማው መልካም ወሬ አይደለምና ልክ አይደላችሁም። የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዲያምጽ ታደርጉታላችሁ። 25
አንድ ሰው ሌላውን ቢበድል፥ እግዚአብሔር በእርሱ ላይ ይፈርዳል፤ አንድ ሰው ግን በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን ቢሠራ ስለ እርሱ የሚናገር ማን ነው?" እነርሱ
ግን እግዚአሔር ሊገድላቸው ፈልጓልና የአባታቸውን ቃል አልሰሙም። 26 ትንሹም ልጅ ሳሙኤል አደገ፥ በእግዚአብሔርና በሰዎችም ፊት ደግሞ በሞገስ እያደገ
ሄደ። 27 አንድ የእግዚአብሔር ሰው ወደ ዔሊ መጥቶ እንዲህ አለው፥ “እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፥ 'በግብፅ አገር፥ በፈርዖን ቤት ባሪያዎች በነበሩ ጊዜ
ለአባትህ ቤት ራሴን ገለጥኩኝ፤ 28 ከእስራኤል ነገዶች ሁሉ ካህን እንዲሆነኝ፥ ወደ መሠዊያዬ እንዲወጣ፥ ዕጣን እንዲያጥንልኝ፥ በፊቴም ኤፉድ እንዲለብስ
መረጥኩት። የእስራኤል ሕዝብ በእሳት የሚያቀርበውን መባ ሁሉ ለአባትህ ቤት ሰጠሁ። 29 ታዲያ በማደሪያዬ ያዘዝኩትን መሥዋዕትና መባ የምትንቁት
ለምንድነው? በሕዝቤ በእስራኤል ከሚቀርበው መስዋዕት ሁሉ በተመረጠው እየወፈራችሁ ልጆችህን ከእኔ በላይ ያከበርከው ለምንድነው?' 30 የእስራኤል
አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፥ 'ቤትህና የአባትህ ቤት ለዘላለም በፊቴ እንዲመላለስ ተስፋ ሰጥቼ ነበር'። አሁን ግን እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፥
'ይህንን ማድረግ ከእኔ ይራቅ፥ የሚያከብሩኝን አከብራለሁና የሚንቁኝ ግን ፈጽሞ ይናቃሉ። 31 ተመልከት፥ ከእንግዲህ በቤትህ ሽማግሌ የሚሆን አንድም ሰው
እንዳይኖር ያንተን ኃይልና የአባትህን ቤት ኃይል የምቆርጥበት ቀን ቀርቧል። 32 በማድርበት ስፍራም መከራን ታያለህ። ለእስራኤል መልካም ነገር ቢሰጥም
ከእንግዲህ በቤትህ ሽማግሌ የሚሆን አንድ ሰው አይኖርም። 33 ያንተ የሆኑትና ከመሠዊያዬ የማልቆርጣቸው ማናቸውም ዐይኖችህን እንዲያፈዝዙና
ሕይወትህን በሐዘን እንዲሞሉት አደርጋቸዋለሁ። በቤተ ሰብህ ውስጥ የተወለዱ ወንዶች ሁሉ ይሞታሉ። 34 በሁለቱ ወንዶች ልጆችህ በአፍኒን እና በፊንሐስ
የሚደርስባቸው ምልክት ይሆንሃል፤ ሁለቱም በአንድ ቀን ይሞታሉ። 35 በልቤና በነፍሴ ውስጥ ያለውን የሚፈጽም ታማኝ ካህን ለራሴ አስነሣለሁ።
የማያጠራጥር ቤት እሠራለታለሁ፤ ለዘላለምም በቀባሁት ንጉሥ ፊት ይሄዳል። 36 ከቤተ ሰብህ የተረፈ ሁሉ ጥቂት ጥሬ ብርና ቁራሽ እንጀራ እንዲሰጠው
ለመለመን በዚያ ሰው ፊት መጥቶ ይሰግዳል፥ 'ቁራሽ እንጀራ መብላት እንድችል እባክህ ከካህናቱ ኃላፊነቶች በአንዱ ስፍራ መድበኝ'" ይለዋል።

---

1 Samuel 2:1

አጠቃላይ መረጃ
ሐና ለእግዚአብሔር መዝሙር ዘመረች። (አጓዳኝነት ተመልከት)

ልቤ ፈነደቀ
"ታላቅ ደስታ አለኝ'

በእግዚአብሔር
"ከእግዚአብሔር ማንነት የተነሣ' ወይም "እግዚአብሔር እጅግ ታላቅ ከመሆኑ የተነሣ'

ቀንዴ ከፍ ከፍ አለ
ቀንድ የብርታት ምልክት ነው። አት:- "አሁን ብርቱ ነኝ' (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

1 Samuel 2:2

አያያዥ አሳብ
ሐና ለእግዚአብሔር መዘመሯን ቀጥላለች። (አጓዳኝነት ተመልከት)

እንደ አምላካችን ያለ ዓለት የለም
ይህ እግዚአብሔር ብርቱና የታመነ ነው የሚለው ሌላኛው አባባል ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ዓለት
ይህ ዓለት ከበስተኋላው ለመደበቅ ወይም በላዩ ላይ ለመቆም እና አንድ ሰው ከጠላቶቹ በላይ እጅግ ከፍ ለማለት በቂ የሆነ ዓለት ነው።

1 Samuel 2:3

አያያዥ አሳብ
ሐና ለእግዚአብሔር መዘመሯን ቀጥላለች። ሌሎች ሰዎች እየሰሟት እንዳሉ አድርጋ ትናገራለች። (አጓዳኝነት ተመልከት)

አትታበዩ
"በትዕቢት አትናገሩ'

ሥራዎች በእርሱ ይመዘናሉ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት እርሱ የሰዎችን ሥራዎች ይመዝናል ወይም ሰዎች የሚያደርጉትን ለምን እንደሚያደርጉ ያውቃል (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

የኃያላን ሰዎች ቀስት ተሰብሮአል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች። 1) ቀስቶቹ ራሳቸው ተሰብረዋል ወይም 2) ቀስት የያዙ ሰዎች ከማድረግ ተከለከሉ። አት፦ "ኃያላን ቀስተኞች ሰዎች ከማድረግ ተከለከሉ'

የኃያላን ሰዎች ቀስት ተሰብሮአል
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "እግዚአብሔር የኃያላን ሰዎችን ቀስት ይሰብራል' ወይም "እግዚአብሔር ኃያላን ሰዎችን እንኳን ደካሞች ያደርጋል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ደካሞች **(**የሚሰናከሉ**)** እንደ መታጠቂያ ኃይልን ታጥቀዋል
ይህ ዘይቤአዊ ንግግር ከእንግዲህ ወዲህ አይሰናከሉም ነገር ግን ኃይላቸው እንደ መታጠቂያ ጠብቆ አብሯቸው ይኖራል ማለት ነው። አት፦ "የሚሰናከሉትን ብርቱዎች ያደርጋቸዋል' (˜ይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

መታጠቂያ ... ታጥቀዋል
ይህ ለሥራ ለመዘጋጀት አንድን ነገር በወገብ ዙሪያ ስለማሰረ ጥቅም ላይ የሚውል አጠቃላይ ቃል ነው።

1 Samuel 2:5

አያያዥ አሳብ
ሐና ለእግዚአብሔር መዘመሯን ቀጥላለች። (አጓዳኝነት ተመልከት)

ሰባት ወልዳለች
"ሰባት ልጆች ወልዳለች'

ደክማለች
ደካማ፣ ሐዘንተኛና ብቸኛ መሆን

1 Samuel 2:6

አያያዥ አሳብ
ሐና ለእግዚአብሔር መዘመሯን ቀጥላለች። (አጓዳኝነት ተመልከት)

እግዚአብሔር ይገድላል፣ ያድናል ... ያወርዳል፣ያወጣል ... ድሀ ያደርጋል፣ ባለጠጋም ያደርጋል፣ ያዋርዳል፣ ከፍ ከፍ ያደርጋል
እግዚአብሔር ሁሉን ይቆጣጠራል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

1 Samuel 2:8

አያያዥ አሳብ
ሐና ለእግዚአብሔር መዘመሯን ቀጥላለች። (አጓዳኝነት ተመልከት)

ከመሬት ... ከጉድፍ
በማኅበረ ሰቡ ውስጥ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ጥቅም ላይ የሚውል ዘይቤአዊ ንግግር ነው። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

ችግረኞች
የሚያስፈልጓቸው ነገሮች የሌሏቸው።

1 Samuel 2:9

አያያዥ አሳብ
ሐና ለእግዚአብሔር መዘመሯን ቀጥላለች። (አጓዳኝነት ተመልከት)

የታማኞቹን ሰዎች እግር ይጠብቃል
በዚህ ስፍራ "እግር' የሚለው ስም አንድ ሰው ለሚሄድበት መንገድ ጥቅም ላይ የሚውል ስዕላዊ ንግግር ነው፣ በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ሰው ሕይወቱን ለመኖር የወሰነበትን መንገድ የሚያመለክት ዘይቤአዊ ንግግር ነው። አት፦ "የተሳሳተ ውሳኔ እንዳይወስኑ ታማኞቹን ይጠብቃል' ወይም "ታማኞቹን ሰዎች ተገቢ ውሳኔ እንዲወስኑ ያስችላቸዋል።' (ስዕላዊና ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

ኃጢአን ግን ዝም ብለው በጨለማ ይቀመጣሉ
በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን ይገድላል በሚል ሊገለጽ የሚችለው የተነገረበት የአክብሮት መንገድ ነው። አት "እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን በጨለማ ዝምታ ውስጥ ያስቀምጣል' ወይም "እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን በጨለማና በሙታን የዝምታ ዓለም ውስጥ ያስቀምጣል' (የማያስደስትን ቃል በሌላ ቃል መጠቀም ተመልከት)

ኃጢአን በዝምታ እንዲቀመጡ ይደረጋሉ
"በዝምታ እንዲቀመጡ ይደረጋሉ' የሚሉት ቃላት "ዝም እንዲሉ ይደረጋሉ' ለሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ናቸው። (ፈሊጣዊ ንግግር እና አድራጊና ተደረጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

በኃይሉ
"ኃይለኛ ከመሆኑ የተነሳ'

1 Samuel 2:10

አያያዥ አሳብ
ሐና ለእግዚአብሔር መዘመሯን ቀጥላለች። (አጓዳኝነት ተመልከት)

እግዚአብሔርን የሚቃወሙ ይደቅቃሉ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "እግዚአብሔር እርሱን የሚቃወሙትን ያደቅቃቸዋል።' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ያደቅቃቸዋል
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር "ያሸንፋቸዋል' ማለት ነው። (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

እስከ ምድር ዳርቻ
በሁሉ ስፍራ የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፦ "ምድር ሁሉ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

የመሲሑን ቀንድ ከፍ ከፍ ያደርጋል
ቀንድ የጥንካሬ ምልክት ነው። ተመሣሣይ ቃላትን በ1ሳሙኤል 2:1 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። አት፦ "የመረጠውን መሪ ከጠላቶቹ በላይ ብርቱ ያደርገዋል' (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

መሲሑ
ይህ እግዘአብሔር ሰውዬውን በዘይት እንደቀባው አድርጎ የሚናገረው እግዚብሔር ለዓላማው ስለ መረጠውና ሥልጣን ስለ ሰጠው ነው። አት፦

"የቀባው' ወይም "የመረጠው' (ዘይቤአዊ ንግግርና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽን ተመልከት)

1 Samuel 2:12

አጠቃላይ መረጃ
ሰዎች እንስሳትን በመሥዋዕትነት ሲያቀርቡ በመጀመሪያ የእንስሳውን ስብ ማቃጠል፣ ሥጋውን መቀቀልና መብላት አለባቸው።

እግዚአብሔርን አያውቁም ነበር
"እግዚአብሔርን አይሰሙም ነበር' ወይም "እግዚአብሔርን አይታዘዙም ነበር'

ልማድ
ልማድ ሰዎች በቋሚነት የሚያከናውኑት ተግባር ነው።

ወደ ድስቱ ... ወይም ምንቸቱ ... ወይም አፍላሉ ... ወይም ቶፋው
እነዚህ ምግብ የሚበስልባቸው ዕቃዎች ናቸው። ቋንቋህ ለእነዚህ ዕቃዎች የተለያዩ ቃላት ከሌለው በአጠቃላይ መልኩ ሊገለጹ ይችላላል።አት፡- "በማናቸውም ሰዎች ሥጋ በሚያበስሉባቸው ውስጥ'

ድስት
ከሸክላ የተሠራ ማብሰያ

ምንቸት
የሸክላ ድስት

አፍላላ
ተለቅ ያለ ማብሰያ ድስት

ቶፋው
አነስተኛ ማብረጃ

1 Samuel 2:15

አጠቃላይ መረጃ
ሰዎች እንስሳትን በመሥዋዕትነት ሲያቀርቡ በመጀመሪያ የእንስሳውን ስብ ማቃጠል፣ ሥጋውን መቀቀልና መብላት አለባቸው።

የባሰ፣ በፊት
"ከዚያም እንኳን የባሰ ያደርጉ ነበር። በፊት'

ያቃጥሉት
በተጨባጭ የሚያቃጥለውን ሰው ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አት፡- "መሥዋዕት ያቀርብ የነበረው ሰው መስዋዕቱን ወደ ካህናቱ ያመጣዋል፣ ካህናቱም ያቃጥሉታል።' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትንና ያልተገለጸ መረጃን ተመልከት)

እጠብስለት ዘንድ ለካህኑ ሥጋ ስጠኝ
"እንዲጠብሰው ለካህኑ እሰጠው ዘንድ ሥጋ ስጠኝ'

መጥበስ
እሳት ላይ ማብሰል

መቀቀል
በፈላ ውኃ ማብሰል

ጥሬ
ያልበሰለ

የእግዚአብሔርን ቁርባን ይንቁ ነበር
እግዚአብሔር ቁርባንን በሚመለከት የሰጠውን መመሪያ ወጣቶቹ አይወዱም ትኩረትም አይሰጡትም ነበር።

1 Samuel 2:20

ለእግዚአብሔር ካቀረበችው ልመና የተነሣ
ሐና እግዚአብሔር ልጅ እንዲሰጣት ለመነችው፣ በመቅደስም እንዲያገልገል ልጁን ለመስጠት ቃል ገባች።

በእግዚአብሔር ፊት
ይህም እግዚአብሔር እርሱን በሚያይበትና ሳሙኤል ስለ እግዚአብሔር ለማር በሚችልበት ቦታ ማለት ነው።

1 Samuel 2:22

ስለ ምን እንዲህ ያለ ነገር ታድርጋላችሁ?
ይህ አሳብ ገላጭ ጥያቄ በገላጭ አባባል ይችላል። አት፡- "እንዲህ ዓይነት ነገር ማድረጋችሁ በጣም አሳዛኝ ነው።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

1 Samuel 2:25

ስለ እርሱ የሚናገር ማን ነው?
ይህ አሳብ ገላጭ ጥያቄ በገላጭ አባባል ሊተረጎም ይችላል። አት፡- "በእርግጥ ስለ እርሱ የሚናገር ማንም የለም።'(አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ስለ እርሱ የሚናገር
"ምሕረት እንዲያደርገለት እግዚአብሔርን የሚለምንለት'

የአባታቸው ድምጽ
በዚህ ስፍራ የአባት ድምጽ አባታን ይወክላል። አት፡- "አባታቸው' ወይም "አባታቸው ያላቸውን' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

1 Samuel 2:27

የእግዚአብሔር ሰው
ብዙ ጊዜ ይህ ሃረግ የእግዚአብሔር ነቢይ ማለት ነው። አት "ከእግዚአብሔር ቃላት የሚሰማና የሚናገር ሰው'

ቤት ... ራሴን አልገለጥሁምን
ይህ አሳብ ገላጭ ጥያቄ እንደሚከተለው ሊተረጎም ይችላል። አት "ቤት ... ራሴን እንደገለጥሁ ልታውቅ ይገባሃል።'

ለአባትህ ቤት
"ቤት' የሚለው ስም በቤቱ ውስጥ ላሉ ሰዎች ምትክ ስም ነው። አት ፡- "የአባትህ ቤተሰብ' (ምትክ ስም ተመልከት)

አባትህ
አሮን

ወደ መሠዊያዬ ይወጣ ዕጣንም ያጥን ዘንድ
ይህ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ማቅረብን ያመለክታል።

ኤፉድንም በፊቴ ይለብስ ዘንድ
"ኤፉድ መልበስ' የሚሉት ቃላት ኤፉድ ለሚለብሱት ካህናት ሥራ ምትክ ስም ነው። አት፡- "ካህናት ያደርጉ ዘንድ ያዘዝኩትን ያደርግ ዘንድ።' (ምትክ ስም ተመልከት)

1 Samuel 2:29

አያያዥ አሳብ
የእግዚአብሔር ሰው ለዔል መናገሩን ቀጠለ

በማደሪያዬ ... መሥዋዕቴን ስለምን ናቃችሁ?
ይህ አሳብ ገላጭ ጥያቄ የሚገሥጽ ነው። በገላጭ አባባልነት ሊተረጎም ይችላል። አት "በማደሪያዬ ... መሥዋዕቴን ልትንቁ አይገባችሁም።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ማደሪያዬን
"ሕዝቤ ቁርባን ለእኔ የሚያቀርቡበት ቦታ'

ከእያንዳንዱ ቁርባን በተሻለው ራሳችሁን ለማወፈር
ከቁርባኑ የተሻለው ክፍል ለእግዚአብሔር ቁርባን ሆኖ መቃጠል ነበረበት፣ ካህናቱ ግን፡ ይበሉት ነበር።

የአባትህ ቤት
"ቤት' የሚለው ስም በቤቱ ውስጥ ላሉ ሰዎች ምትክ ስም ነው። ይህንን በ1ሳሙኤል 2:27 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አት ፡- "የአባትህ ቤተሰብ' (ምትክ ስም ተመልከት)

በፊቴ ልትሄድ ይገባሃል
ይህ "ለእኔ በመታዘዝ ኑር' የሚል ትርጉም ያለው ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር ተመልከት)

ይህን ማድረግ ከእኔ ይራቅ
"በእርግጥ ቤተሰብህ እኔን ለዘላለም እንዲያገለግለኝ አልፈቅድም'

የናቁኝ በጥቂቱ ይከብራሉ
"በጥቂቱ ይከበራሉ' የሚሉት ቃላት "እጅግ ይዋረዳሉ' ለሚለው የማያስደስት ቃል በምጸት የተተካ ቃል ነው። ይህ በአድራጊ አንቀጽ እንደሚከተለው ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "የሚንቁኝን በጥቂቱ አከብራለሁ' ወይም "የሚንቁኝን በእጅጉ አዋርዳለሁ' (ምጸት፣የማያስደስትን ቃል በሌላ ቃል መጠቀም እና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

1 Samuel 2:31

እይ
"የምናገረውን በጥንቃቄ አድምጥ' ወይም "የምናገረው ነገር በጣም አስፈላጊ ነው'

የአንተንና የአባትህን ቤት ብርታት እቆርጣለሁ
"... ብርታት እቆርጣለሁ' የሚለው የብርቱዎችንና የወጣቶችን ሞት በማይከብድ ቃል ለመተካት ጥቅም ላይ የዋለ ሳይሆን አይቀርም። "የአባትህ ቤት' የሚሉት ቃላት "ቤተሰብህ' ለሚለው ምትክ ናቸው። (የማያስደስትን ቃል በሌላ ቃል መጠቀም እና ምትክ ቃል ተመልከት)

ማንኛውም ሽማግሌ ቢሆን
"ማንኛውም ሽማግሌ ቢሆን' ወይም "ያረጀ ማንኛውም ሰው ቢሆን'

ዓይኖችህ እንዳይሠሩ ያደርጋል
"እይታህን እንድታጣ ያደርጋል' ወይም "ዓይነ ስውር እንድትሆን ያደርጋል'

1 Samuel 2:34

የታመነ ካህን አስነሳለሁ
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፡- "አንድ ሰው ካህን አደርጋለሁ።' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ለራሴ (ለእኔ)
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፡- "እንዲያገለግለኝ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

በልቤና በነፍሴ ያለውን
"እንዲያደርግ የምፈልገውንና እንዲያደርግ የምነግረውን'

የታመነ ቤት እሠራለታለሁ
በዚህ ስፍራ "ቤት' የሚለው "ትውልድን' የሚመለክት ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፡- "ሁሌም ሊቀ ካህን ሆኖ የሚያገለግል ትውልድ እንደሚኖረው ቃል እገባለሁ።'(ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

1 Samuel 2:36

እርሱ
እግዚአብሔር የሚያስነሳው የታመነ ካህን

ቁራሽ እንጀራ እበላ ዘንድ
በዚህ ስፍራ "ቁራሽ እንጀራ' የሚለው "ምግብን' ለማመልከት ጥቅም ላይ የዋለ ነው። አት፡- "አንዳች የምበላው ነገር እንዲኖረኝ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 ትንሹ ልጅ ሳሙኤል በዔሊ ሥር ሆኖ እግዚአብሔርን ያገለግል ነበር። 2 በእነዚያ ቀናት የእግዚአብሔር ቃል እምብዛም አይገኝም ነበር፤ ትንቢታዊ ራዕይም አይዘወተርም ነበር። በዚያን ጊዜ፥ ዔሊ ዐይኖቹ ከመፍዘዛቸው የተነሣ አጥርቶ ማየት ባቃተው ጊዜ፥ በአልጋው ላይ ተኝቶ እያለ፥ 3 የእግዚአብሔር መብራት ገና አልጠፋም ነበር፥ ሳሙኤል የእግዚአብሔር ታቦት ባለበት በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ተኝቶ ነበር። 4 እግዚአብሔር ሳሙኤልን ጠራው፥ እርሱም፥ “አቤት!” አለው። 5 ሳሙኤል ወደ ዔሊ ሮጠና፥ “ጠርተኸኛልና ይኸው መጥቻለሁ” አለው፤ ዔሊም፥ “እኔ አልጠራሁህም፤ ተመልሰህ ተኛ” አለው። ስለዚህ ሳሙኤል ሄደና ተኛ። 6 እግዚአብሔር እንደገና፥ “ሳሙኤል” ብሎ ተጣራ። ሳሙኤልም እንደገና ተነሥቶ ወደ ዔሊ ሄደና፥ “ጠርተኸኛልና ይኸው መጥቻለሁ” አለው። ዔሊም፥ "ልጄ ሆይ፥ እኔ አልጠራሁህም፤ ተመልሰህ ተኛ" ብሎ መለሰለት። 7 ሳሙኤል እግዚአብሔርን ገና አላወቀም ነበር፥ ከእግዚአብሔር ምንም ዓይነት መልዕክት ገና አልተገለጠለትም ነበር። 8 እግዚአብሔር ሳሙኤልን እንደገና ለሦስተኛ ጊዜ ጠራው። ሳሙኤልም እንደገና ተነሥቶ ወደ ዔሊ ሄደና፥ “ጠርተኸኛልና ይኸው መጥቻለሁ” አለው። ከዚያም ልጁን እግዚአብሔር እንደ ጠራው ዔሊ አስተዋለ። 9 ዔሊም ሳሙኤልን፥ "ሂድና ተመልሰህ ተኛ፤ ደግሞ ከጠራህም፥ 'እግዚአብሔር ሆይ፥ አገልጋይህ እየሰማህ ነውና ተናገር' ማለት አለብህ" አለው። ስለዚህ ሳሙኤል እንደገና ወደ ስፍራው ተመልሶ ተኛ። 10 እግዚአብሔርም መጥቶ ቆመ፤ እንደ ቀድሞው ሁሉ፥ "ሳሙኤል፥ ሳሙኤል" ብሎ ጠራው። ከዚያም ሳሙኤል፥ "አገልጋይህ እየሰማህ ነውና ተናገር" አለው። 11 እግዚአብሔርም ሳሙኤልን እንዲህ አለው፥ "ተመልከት፥ የሚሰማውን ሁሉ ጆሮውን ጭው የሚያደርግ አንድ ነገር በእስራኤል ላይ አደርጋለሁ። 12 በዚያም ቀን፥ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ስለ ቤቱ የተናገርኩትን ሁሉ በዔሊ ላይ አመጣበታለሁ። 13 ልጆቹ በራሳቸው ላይ እርግማንን ስላመጡና እርሱም ስላልከለከላቸው፥ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እርሱ ስለሚያውቀው ኃጢአት በቤቱ ላይ እንደምፈርድ ነግሬዋለሁ። 14 በዚህ ምክንያት የቤቱ ኃጢአት በመሥዋዕት ወይም በመባ ይቅር እንዳይባል ለዔሊ ቤት ምያለሁ።" 15 ሳሙኤል እስኪነጋ ተኛ፤ ከዚያም የእግዚአብሔርን ቤት በሮች ከፈተ። ሳሙኤል ግን ስለየው ራዕይ ለዔሊ ለመንገር ፈራ። 16 ከዚያም ዔሊ ሳሙኤልን ጠርቶ፥ "ልጄ ሳሙኤል ሆይ" አለው። ሳሙኤልም፥ "አቤት!" ብሎ መለሰለት። 17 እርሱም፥ "የነገረህ ቃል ምንድነው? እባክህ አትደብቀኝ። ከነገረህ ቃል ሁሉ አንዱን ብትደብቀኝ እግዚአብሔር ይህን ያድርግብህ፤ ከዚያም የባሰውን ጨምሮ ያድርግብህ" አለው። 18 ሳሙኤል ሁሉንም ነገር ነገረው፤ ከእርሱም ምንም አልደበቀም። ዔሊም፥ "እርሱ እግዚአብሔር ነው። መልካም መስሎ የታየውን ያድርግ" አለ። 19 ሳሙኤል አደገ፥ እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ነበር፥ ከትንቢታዊ ቃሉ ሳይፈጸም የቀረ አንድም አልነበረም። 20 ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ያሉት እስራኤላውያን በሙሉ ሳሙኤል የእግዚአብሔር ነቢይ እንዲሆን መመረጡን ዐወቁ። 21 እግዚአብሔር እንደገና በሴሎ ተገለጠ፥ እርሱም በቃሉ አማካይነት በሴሎ ራሱን ለሳሙኤል ገለጠለት።

---

1 Samuel 3:1

የእግዚአብሔር ቃል ብርቅ ነበር
እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ ለሕዝብ አይናገርም ነበር

የእግዚአብሔር መብራት
ይህ በመገናኛው ድንኳን ቅዱስ ስፍራ በሁሉም ቀን እና ባዶ እስኪሆን ድረስ ሌሊቱን ሁሉ የሚነደው ሰባት መቅረዝ ያለው መብራት ነው።

የእግዚአብሔር መቅደስ
"መቅደሱ' በእርግጥ ድነኳን ነበር ነገር ግን ሕዝቡ ያመልክበት የነበረ ስፍራ ስለ ነበር፣ በዚህ ስፍራ መቅደስ ብሎ መተረጎም ይበልጥ የተመረጠ ነው። ይህንን በ1ሳሙኤል 1:9 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

1 Samuel 3:5

ልጄ
ዔሊ የሳሙኤል እውነተኛ አባት አልነበረም። ዔሊ የሳሙኤል አባት እንደሆነ አድርጎ መናገሩ እንዳልተበሳጨ ነገር ግን ሳሙኤል ሊሰማው እንደሚገባ ለሳሙኤል ለማሳየት ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር ተመልከት)

1 Samuel 3:7

ምንም መልእክት ከእግዚአብሔር ዘንድ ገና አልተገለጠለትም ነበር
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "እግዚአብሔር ምንም መልእክት መቼም አልገለጠለትም ነበር' ወይም "እግዚአብሔር ምንም መልእክት ፈጽሞ አልገለጠለትም ነበር።' (አድጊራኒና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመለከት)

1 Samuel 3:9

አገልጋይህ
ሳሙኤል ለእግዚአብሔር አክበሮትን ለማሳየት ራሱን እንደ ሌላ ሰው አድርጎ ሳሙኤል ለእግዚአብሔር እንዲናገር ዔሊ ነገረው። አት፦ 'እኔ ነኝ' (ተውላጠ ስም ተመልከት)

1 Samuel 3:10

እግዚአብሔርም መጥቶ ቆመ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጎሞች፦ 1)እግዚአብሔር በተጨባጭ ተገልጦአል በሳሙኤልም ፊት ቆሞአል 2)እግዚአብሔር መገኘቱን ለሳሙኤል እንዲታወቅ አድርጓል

አገልጋይህ
ሳሙኤል ለእግዚአብሔር አክበሮትን ለማሳየት ራሱን እንደ ሌላ ሰው አድርጎ ለእግዚአብሔር ተናገረ። አት፦ 'እኔ ነኝ' (ተውላጠ ስም ተመልከት)

የሰማውን ሁሉ ጆሮች ጭው የሚያደርግ
በዚህ ስፍራ "ጆሮች ጭው የሚያደርግ' የሚለው ስለ ሰሙት ነገር እያንዳንዳቸው ይደነግጣሉ የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፦ "የሚሰማውን እያንዳንዱን ያስደነግጣል' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ጭው
በተለምዶ ከቅዝቃዜ የተነሳ ወይም ያንን የሰወነት ክፍል ሰዎች በእጃቸው ከመምታቸው የተነሳ አንድ ሰው በትንሽ የተሳለ ነገር በቀላሉ ሲወጋ የሚሰማው የመወጋት ስሜት ዓይነት ነው።

1 Samuel 3:12

ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ
ይህ ሙሉነትን የሚያሳይ ስዕላዊ ንግግር ነው። አት፦ "ፈጽሞ ሁሉን ነገር' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መርገምን በራሳቸው ላይ አመጡ
"የሚያደርጓቸውን እነዚያን ሰዎች እቀጣለሁ ብሎ እግዚአብሔር የተናገረባቸውን እነዚያን ነገሮች አደረጉ'

የዔሊ ቤት ኃጢአት በመሥዋዕትና በቁርባን ፈጽሞ አይሰረይም
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊተረጎም ይችላል። አት፡- "የቤቱን ኃጢአት ሊያስተሰርይ የሚችል ማንም ሊያቀርበው የሚችል መስዋዕት ወይም ቁርባን የለም' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

የዔሊ ቤት ኃጢአት
በቤተሰቡ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች የፈጸሙት ኃጢአት ነው

1 Samuel 3:15

የእግዚአብሔር ቤት
"ቤት' የተባለው በተጨባጭ "ድንኳን' ነበር፣ ነገር ግን በዚህ ስፍራ "ቤት' ብሎ መተርጎሙ እጅግ የተሻለ ነው።

ልጁ
ዔሊ የሳሙኤል እውነተኛ አባት አልነበረም። ዔሊ የሳሙኤል አባት እንደሆነ አድርጎ መናገሩ እንዳልተበሳጨ ነገር ግን ሳሙኤል ሊመልስለት እንደሚገባ ለሳሙኤል ለማሳየት ነው። ይህንን በ1ሳሙኤል 3፡6 እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት። (ዘይቤአዊ አነጋገር ተመልከት)

1 Samuel 3:17

የተናገረውን ቃል
"እግዚአብሔር የሰጠው መልእክት'

እግዚአብሔር እንዲህ ያድርግብህ እንዲህም ይጨምርብህ
ይህ ዔሊ ምን ያህል የምሩን እንደሆነ አጽንዖት የሚሰጥ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፡- "እግዚአብሔር እኔን እንደሚቀጣ በተናገረበት ተመሳሳይ መንገድ ይቅጣህ፣ ከዚያም በላይ እንኳን ይጨምርብህ።' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

1 Samuel 3:19

ከቃሉም አንዳች በምድር ላይ አይወድቅም ነበር
በዚህ ስፍራ ያልተፈጸሙ መልእክቶች መሬት ላይ እንደወደቁ ተገልጸዋል። ይህ አዎንታዊ በሆነ መልኩ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "የተነበያቸው ነገሮች ሁሉ ይፈጸሙ ነበር' (ዘይቤአዊ ንግግርና ሁኔታን በማንበብ ላይ የተመሠረተ ትንቢት ተመልከት)

እስራኤል ሁሉ
"በእስራኤል ያሉ ሰዎች ሁሉ'

ከዳን እስከ ቤርሳቤህ
"በምድሪቱ ክፍል ሁሉ' የሚልን አሳብ የሚያመለክት ስዕላዊ ንግግር ነው። አት፡- "ከምድሪቱ አንደኛው ጫፍ እስከ ሌላኛው ጫፍ' ወይም "ከሰሜን ጥግ ከዳን እስከ ደቡብ ጥግ እስከ ቤርሳብህ'

ሳሙኤል ተሾመ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይቻላል። አት፡- "እግዚአብሔር ሳሙኤልን ሾመ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 የሳሙኤልም ቃል ወደ እስራኤላውያን ሁሉ መጣ። በዚህ ወቅት እስራኤላውያን ከፍልስጥኤማውያን ጋር ለመዋጋት ሄዱ። የጦር ሰፈራቸውንም በአቤንኤዘር
አደረጉ፥ ፍልስጥኤማውያንም የጦር ሰፈራቸውን በአፌቅ አደረጉ። 2 ፍልስጥኤማውያንም ከእስራኤላውያን ጋር ለመዋጋት ተሰለፉ። ውጊያው በተፋፋመ ጊዜ
እስራኤላውያን አራት ሺህ ሰዎቻቸው በውጊያው ሜዳ በመገደላቸው በፍልስጥኤማውያን ተሸነፉ። 3 ሕዝቡ ወደ ጦር ሰፈሩ በመጣ ጊዜ፥ የእስራኤል
ሽማግሌዎች፥ "እግዚአብሔር ዛሬ በፍልስጥኤማውያን ፊት እንድንሸነፍ ያደርገን ለምንድነው? ከእኛ ጋር እንዲሆንና ከጠላቶቻችን ኃይል እንዲያድነን
የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦት ከሴሎ እናምጣው" አሉ። 4 ስለዚህ ሕዝቡ ወደ ሴሎ ሰዎችን ላኩ። ከዚያ በኪሩቤል ላይ የሚቀመጠውን የሠራዊቱን ጌታ
የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦት አመጡ። ሁለቱ የዔሊ ልጆች አፍኒንና ፊንሐስ ከእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት ጋር በዚያ ነበሩ። 5 የእግዚአብሔር የቃል
ኪዳን ታቦት ወደ ጦር ሰፈሩ በመጣ ጊዜ፥ የእስራኤል ሕዝብ በሙሉ በታላቅ ዕልልታ ጮኹ፥ ምድሪቱም አስተጋባች። 6 ፍልስጥኤማውያን የዕልልታውን ድምፅ
በሰሙ ጊዜ፥ “ይህ በዕብራውያኑ የጦር ሰፈር የሚሰማው የዕልልታ ድምፅ ምን ማለት ይሆን? አሉ። ከዚያም የእግዚአብሔር ታቦት ወደ ጦር ሰፈሩ እንደ መጣ
ተገነዘቡ። 7 ፍልስጥኤማውያኑ ፈሩ፤ እነርሱም፥”እግዚአብሔር ወደ ጦር ሰፈሩ መጥቷል" አሉ። 8 እነርሱም፥ "ወዮልን! እንደዚህ ያለ ነገር ከአሁን በፊት
አልሆነም! ወዮልን! ከዚህ ኃያል አምላክ ክንድ ማን ያድነናል? ይህ በምድረ በዳ ግብፃውያንን በልዩ ልዩ ዓይነት መቅሠፍት የመታቸው አምላክ ነው። 9 እናንተ
ፍልስጥኤማውያን በርቱ፥ ወንድነታችሁንም አሳዩ፥ ካልሆነ እነርሱ ባሪያዎቻችሁ እንደነበሩ ባሪያዎቻቸው ትሆናላችሁ። ወንድነታችሁ ይታይ፥ ተዋጉም" አሏቸው።
10 ፍልስጥኤማውያኑ ተዋጉ፥ እስራኤላውያንም ተሸነፉ። እያንዳንዱ ወደ ቤቱ ሸሸ፥ የተገደሉትም እጅግ ብዙ ነበሩ፤ ከእስራኤል ሠላሳ ሺህ እግረኛ ወታደር
ወደቀ። 11 የእግዚአብሔር ታቦት ተወሰደ፥ ሁለቱ የዔሊ ልጆች አፍኒንና ፊንሐስም ሞቱ። 12 በዚያው ቀን አንድ ብንያማዊ ከውጊያው መስመር ወደ ሴሎ በሩጫ
መጣ፥ በደረሰ ጊዜ ልብሱን ቀድዶና በራሱ ላይ አፈር ነስንሶ ነበር። 13 እርሱ በደረሰ ጊዜ፥ ዔሊ ስለ እግዚአብሔር ታቦት በመስጋት ልቡ ታውኮበት ስለነበረ
በመንገዱ ዳር ወንበሩ ላይ ተቀምጦ ነበር። ሰውየው ወደ ከተማ ገብቶ ወሬውን በነገራቸው ጊዜ፥ ከተማው በሙሉ አለቀሱ። 14 ዔሊ የልቅሶውን ድምፅ በሰማ
ጊዜ፥ “የዚህ ሁካታ ትርጉሙ ምንድነው?” አለ። ሰውየው ፈጥኖ መጣና ለዔሊ ነገረው። 15 በዚህ ጊዜ ዔሊ የዘጠና ስምንት ዓመት ሽማግሌ ነበር፤ ዓይኖቹ
አጥርተው አያዩም ነበር፥ ማየትም አይችልም ነበር። 16 ሰውየውም ዔሊን፥ “ከውጊያው መስመር የመጣሁት እኔ ነኝ። ዛሬ ከውጊያው ሸሽቼ መጣሁ” አለው።
ዔሊም፥ “ልጄ ሆይ፥ ነገሩ እንዴት እየሆነ ነው?” አለው። 17 ወሬውን ያመጣው ያ ሰው መልሶ፥ “እስራኤላውያን ከፍልስጥኤማውያን ፊት ሸሹ። ደግሞም
በሕዝቡ መካከል ታላቅ ዕልቂት ሆኗል። ሁለቱ ወንዶች ልጆችህ፥ አፍኒን እና ፊንሐስ ሞተዋል፥ የእግዚአብሔር ታቦትም ተወስዷል” አለው። 18 እርሱም
የእግዚአብሔርን ታቦት ጠቅሶ በተናገረ ጊዜ፥ ዔሊ በመግቢያው በር አጠገብ ከተቀመጠበት ወንበር ላይ ወደ ኋላው ወደቀ። ስላረጀና ውፍረት ስለነበረው
አንገቱ ተሰብሮ ሞተ። እርሱም በእስራኤላውያን ላይ ለአርባ ዓመታት ፈርዶ ነበር። 19 በዚህ ጊዜ ምራቱ የፊንሐስ ሚስት አርግዛ የመውለጃ ሰዓቷ ደርሶ ነበር።
የእግዚአብሔር ታቦት መማረኩን፥ ዐማቷና ባሏ መሞታቸውን በሰማች ጊዜ ተንበርክካ ወለደች፥ ነገር ግን ምጡ አስጨነቃት። 20 ለመሞት በምታጣጥርበት
ጊዜ ያዋልዷት የነበሩ ሴቶች፥ "ወንድ ልጅ ወልደሻልና አትፍሪ“ አሏት። እርሷ ግን አልመለሰችላቸውም ወይም የነገሯትን በልቧ አላኖረችውም። 21 እርሷም
የእግዚአብሔር ታቦት ስለተማረከና ስለ ዐማቷና ስለ ባልዋ "ክብር ከእስራኤል ተለየ!" ስትል ልጁን ኤካቦድ ብላ ጠራችው። 22 እርሷም፥”የእግዚአብሔር
ታቦት ስለተማረከ ክብር ከእስራኤል ተለየ!" አለች።

---

1 Samuel 4:1

አቤንኤዘር ... አፌቅ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ፡- ተመልከት)

እስራኤላውያን በፍልጥኤማውያን ተሸነፉ የተገደሉትም
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊተረጎም ይችላል። አት፡- "ፍልስጥኤማውያን እስራኤላውያንን አሸነፉ ገደሏቸውም' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ
ተመልከት)

አራት ሺህ የሚያህሉ ሰዎችን
በዚህ ስፍራ አራት ሺህ የሚለው ቁጥር የሚጠጋጋ ቁጥር ነው። ከዚያ ቁጥር በጥቂት ከፍም ዝቅም ሊል ይችላል። የሚያህሉ የሚለው ቁርጥ ያለ ቁጥር
እንዳልሆነ አመላካች ነው። አት፡- "አራት ሺህ የሚያህሉ ሰዎች' (ቀጥሮች ተመልከት)

1 Samuel 4:3

ሕዝቡ
ጦርነቱን ይዋጉ የነበሩ ወታደሮች

እግዚአብሔር በፍልስጥኤማውያን ፊት ስለ ምን መታን? ከጠላቶቻችንም ... እናምጣ
ሽማግሌዎቹ በእርግጥ እግዚአብሔር ለምን እንደመታቸው አላወቁም ነበር፣ ነገር ግን ከእነርሱ ጋር እንዲሆን የቃል ኪዳኑን ታቦታ በማምጣት እንዴት
በእርግጠኛነት ሁለተኛ እንዳይደገም እደሚያደርጉ እንደሚያውቁ በስህተት
አሰቡ።

በኪሩቤልም ላይ የሚቀመጠውን
ኪሩቤል በቃል ኪዳኑ ታቦት መክደኛ ላይ የሚገኙ እንደሆኑ ግልጽ ማድረግ ያስፈልግሃል። የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች እግዚአብሔር በላይ በሰማይ
በዙፋኑ እንደተቀመጠ ሁሉ የቃልኪዳኑ ታቦት አግዚአብሔር እግሩን የሚያኖርበት የእግሩ መረገጫ እንደሆነ በአብዘኛው ይናገራሉ። አት፡- "በቃል
ኪዳኑ ታቦት ከኪሩቤል በላይ በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ይልተደረገ መረጃ ተመልከት)

የት ነበሩ
በሴሎ ነበሩ

1 Samuel 4:5

የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት ወደ ሰፈር በገባ ጊዜ
"ሕዝቡ የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦት ወደ ሰፈር ባመጡ ጊዜ' ትርጉሙን ግልጽ ለማድረግ ለመረዳት ምቹ የሆነ መረጃን ለመጨመር ጥቂት
መግለጫዎች አስፈላጊ ናቸው። አት፡- "ሕዝቡ ከአፍኒንና ከፊንሐስ ጋር የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦት ተሸከሙ ወደ ሰፈርም አመጡት።'
(እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

የእግዚአብሔር ታቦት ወደ ሰፈር ገባ
"ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ ሰፈር አመጡት'

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Samuel 4:7

አሉ ... አሉ
"ለራሳቸው አሉ ... ለእርስ በእርሳቸው አሉ' ወይም "ለእርስ በእርሳቸው አሉ ... ለእርስ በእርሳቸው አሉ'ሁለተኛው ሐረግ ፍልስጥኤማውያን ለርስ በርሳቸው ያሉትን በግልጽ ያመለክታል። የመጀመሪያው ሐረግ ግን ወይ ያሰበቱን ወይም ለእርስ በእርሳቸው ያሉትን ሊያመለክት ይችላል። ከተቻለ ለማን እንደተነገረ አታመልክት።

እግዚአብሔር መጥቶአል
ፍልስጥኤማውያን በብዙ አማልክት ያመልካሉ፣ ስለዚህ ከእነዚያ አማልክት መካከል አንዱ ወይም የማያመልኩት አንዱ ወደ ሰፈር እንደመጣ አምነዋል። ሌላኛው ሊሆን የሚችለው ትርጉም "ያህዌ መጥቶአል' ሲሉ የእስራኤልን አምላክ መደበኛ ስም እየጠሩ ነበር የሚለው ነው። ምክንያቱም 4:8 ስለ "አማልክት' ይናገራል፣ አንዳንድ ትርጉሞች "እግዚአብሔሮች መጥተዋል' ይላሉ፣ ይኼውም፣ "አማልክት መጥተዋል' ማለት ነው። (ተውላጠ ስሞች ተመልከት)

ከእነዚህ ኃያላን አማልክት እጅ ማን ያድነናል?
ይህ አሳብ ገላጭ ጥያቄ ጥልቅ ፍርሃት መግለጫ ነው። በገላጭ አባባል ሊጻፍ ይችላል። አት፡- "ከእነዚአህ ኃያላን አማልክት እጅ ሊያድነን የሚችል ማንም የለም።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄዎች ተመልከት)

እነዚህ አማልክት ...የመቱ አማልክት
ምክንያቱም በቁጥር 7 አምላክ (ወይም እግዚአብሔር) የሚለው ቃል በነጠላ ቁጥር ነው፣ ሊሆኑ ከሚችሉ ብዙ አማልክት መካከል አንዳቸውን ወይም የእስራኤልን አምላክ መደበኛ ስም በመጠቀም "ይህ ኃያል እግዚአብሔር ... የመታ እግዚአብሔር' በሚያመለክት መልኩ በርካታ ትርጉሞች "ይህ ኃያል አምላክ ... የመታ አምላክ' ይላሉ። (ተውላጠ ስሞች ተመልከት)

ሰዎች ሁኑ
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፡- "ብርቱዎች ሁኑ ተዋጉ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

1 Samuel 4:10

እስራኤላም ተሸነፉ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። "እስራኤል' የሚለው የእስራኤልን ሠራዊት ያመለክታል። አት፡- "የእስራኤልን ሠራዊት አሸነፉ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ እና ተለዋጭ ስም ተመልከት)

የእግዚአብሔር ታቦት ተወሰደ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ፍልስጥኤማውያን የእግዚአብሔርንም ታቦት ወሰዱ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

1 Samuel 4:12

ልብሱን ቀድዶ በራሱም ላይ ትቢያ ነስንሶ
ይህ በእስራኤል ባሕል ጥልቅ ሐዘን መግለጫ መንገድ ነው።

ልቡ ተናውጦ ነበር
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ሲሆን በጣም ፈርቶ ወይም ስለ አንድ ነገር ታውኮ ነበር ማለት ነው። (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ከተማይቱ ሁሉ
ይህ በከተማይቱ ያሉ ሰዎች ሁሉ ለሚለው ምትክ ቃል ነው። (ምትክ ቃል ተመልከት)

1 Samuel 4:14

ሰውዬው
"የብንያም ሰው'

1 Samuel 4:16

ልጄ
ዔሊ የሌላኛው ሰው እውነተኛ አባት አልነበረም። ዔሊ የሰውዬው አባት እንደሆነ አድርጎ መናገሩ እንዳልተበሳጨ ነገር ግን ሊመልስለት እንደሚገባ ለሰውዬው ለማሳየት ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር ተመልከት)

እስራኤል ከፍልስጥኤማውያን ፊት ሸሹ
ይህ ስለሆነው ነገር አጠቃላይ መግለጫ ነው። የቀሩት የሰውዬው ንግግሮች ዝርዝሩን ያቀርባሉ።

ደግሞ በሕዝቡ ዘንድ ... ሁለቱም ልጆችህ ...
"አሁን አንድ የባሰ ነገር እነግርሃለሁ ... አሁን አንድ የባሰ ነገር እነግርሃለሁ' ወይም "ሕዝቡ ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን ሁለቱ ልጆችህም'

የእግዚአብሔር ታቦት ተወሰደ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ፍልስጥኤማውያን የእግዚአብሔርን ታቦት ወሰዱ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

1 Samuel 4:18

ሰውዬው በጠቀሰ ጊዜ
ብንያማዊው ሰው በጠቀሰ ጊዜ

በጠቀሰ
"በተናገረ'

አንገቱ ተሰብረ
ይህ በአድራጊ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ስለወደቀ አንገቱ ተሰበረ' ወይም "ሲወድቅ አንገቱን ሰበረ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

1 Samuel 4:19

ምራቱ
የዔሊ ምራት

የእግዚአብሔር ታቦት ተማረከ
ይህ በአድራጊ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- ፍልስጥኤማውያን የእግዚአብሔርን ታቦት ማረኩ (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ያሉአትን በልባዋ አላኖረችውም
"ላሉት ምንም ትኩረት አልሰጠችም' ወይም "የተሻለ እንዲሰማት ፈቀደች'

1 Samuel 4:21

ኤካቦድ
ስሙ ሐረግ ሲሆን ክብር የለም ማለት ነው። አንዳንድ ጊዜ የአንድ ሰው ስም ስለ ግለሰቡ፣ ስለ ቦታ ወይም ስለ ሚያመለክተው ነገር መረጃ ይሰጣል። (የስሞች አተረጓጎም መንገድ፡- ተመልከት)

የእግዚአብሔር ታቦት ስለ ተማረከ ... የእግዚአብሔር ታቦት ተማርኳልና
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ፍልስጥኤማውያን የእግዚአብሔርን ታቦት ስለማረኩ ... ፍልስጥኤማውያን የእግዚአብሔርን ታቦት ከመማረካቸው የተነሣ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 5

1 ፍልስጥኤማውያንም የእግዚአብሔርን ታቦት በመማረክ ከአቤንኤዘር ወደ አሽዶድ አመጡት። **2** እነርሱም የእግዚአብሔርን ታቦት ማርከው ወደ ዳጎን ቤት ወስደው በዳጎን አጠገብ አቆሙት። **3** የአሽዶድ ሰዎች በቀጣዩ ቀን ማልደው በተነሡ ጊዜ፥ ዳጎን በእግዚአብሔር ታቦት ፊት በምድር ላይ በግምባሩ ተደፍቶ አዩ። ስለዚህ ዳጎንን አንሥተው በስፍራው መልሰው አቆሙት። **4** ነገር ግን በማግስቱ ማልደው በተነሡ ጊዜ፥ ዳጎን በእግዚአብሔር ታቦት ፊት በምድር ላይ በግምባሩ ተደፍቶ አዩ። በደጁ መግቢያ ውስጥ የዳጎን ራሱና እጆቹ ተሰብረው ወድቀው ነበር። የቀረው የዳጎን ሌላው የአካል ክፍሉ ብቻ ነበር። **5** ለዚህ ነው እስካሁን እንኳን የዳጎን ካህናትና ሌላ ማንኛውም ሰው በአሽዶድ ወደሚገኘው ወደ ዳጎን ቤት በሚመጣበት ጊዜ የዳጎንን ደጅ መግቢያ ሳይረግጥ የሚያልፈው። **6** የእግዚአብሔር እጅ በአሽዶድ ሰዎች ላይ ከብዶ ነበር። በአሽዶድና በዙሪያው ባሉት ላይ ጥፋትን በማምጣት በእባጭ መታቸው። **7** የአሽዶድ ሰዎች የሆነባቸውን ባስተዋሉ ጊዜ፥ “እጁ በእኛና በአምላካችን በዳጎን ላይ ከብዳለችና የእስራኤል አምላክ ታቦት ከእኛ ጋር መቆየት የለበትም” አሉ። **8** ስለዚህ ወደ ፍልስጥኤማውያን ገዢዎች ልከው በአንድ ላይ ሰበሰቧቸው፤ እነርሱም፥ "በእስራኤል አምላክ ታቦት ላይ ምን እናድርግ?" አሏቸው። እነርሱም፥ “የእስራኤል አምላክ ታቦት ወደ ጌት ይምጣ” ብለው መለሱላቸው። የእስራኤልን አምላክ ታቦት ወደዚያ ወሰዱት። **9** ነገር ግን ወደዚያ ካመጡት በኋላ የእግዚአብሔር እጅ በከተማዪቱ ላይ ሆነ፥ ታላቅ መደናገርንም አደረገባቸው። ልጅና ዐዋቂውን፥ የከተማውን ሰዎች አስጨነቀ፤ ሰውነታቸውም በእባጭ ተወረረ። **10** ስለዚህ የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ አቃሮን ላኩት። ነገር ግን የእግዚአብሔር ታቦት ወደ አቃሮን እንደ መጣ፥ አቃሮናውያን፥ "እኛንና ሕዝባችንን እንዲገድል የእስራኤልን አምላክ ታቦት ወደ እኛ አምጥተዋል" በማለት ጮኹ። **11** ስለዚህ ወደ ፍልስጥኤማውያን ገዢዎች በመላክ ሁሉንም በአንድ ላይ ሰበሰቧቸው፤ እነርሱም፥ “እኛንና ሕዝባችንን እንዳይገድል የእስራኤልን አምላክ ታቦት ላኩት፥ ወደ ስፍራውም ይመለስ" አሏቸው። በዚያ የእግዚአብሔር እጅ እጅግ ስለበረታባቸው በከተማው ሁሉ የሞት ድንጋጤ ነበረ። **12** ከሞት የተረፉት ሰዎች በእባጮቹ ይሠቃዩ ስለነበር የከተማዪቱ ጩኸት ወደ ሰማያት ወጣ።

---

1 Samuel 5:1

አሁን
ቃሉ የታሪኩ አዲስ ክፍል መጀመሩን ያሳያል። ቋንቋህ ተመሳሳይ ትርጉም የሚሰጥ ቃል ወይም ሐረግ ካለ በዚህ ስፍራ ልትጠቀም ትችላለህ።

የእግዚአብሔር ታቦት
ይህንን በ1ሳሙኤል 3:3 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። ይህ በ1ሳሙኤል 4:3-4 "የእግዚአብሔር የኪዳኑ ታቦት' ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው።

የዳጎን ቤት
ይህ የፍልስጥኤማውያንን አምላክ የዳጎንን ቤተ ጣዖት የሚያመለክት ነው።

አነሆም ዳጎን
"ዳጎንን ለማየት እጅግ በአድናቆት ነበሩ'

ዳጎን በምድር ላይ በግምባሩ ወድቆ ነበር
እግዚአብሔር በሌሊት ሐውልቱ በግምባሩ እንዲወድቅ እንዳደረገ አንባቢው ማስተዋል አለበት። (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

1 Samuel 5:4

ዳጎን ወደቀ
እግዚአብሔር ዳጎንን እንዲወድቅ እንዳደረገ አንባባዊ ማስተዋል አለበት።

የዳጎን ራስ እጆቹም ተቆርጠው ወድቀው ነበር
እግዚአብሔር ጠላቱን እንዳሸነፈና የጠላቱን ራስና እጆች እንደቆረጠ ወታደር ዓይነት ነበር።

ስለዚህ፣ እስከ ዛሬ ድረስ
ጸሐፊው ከዋናው ታሪክ ወጣ ያለ ጥቂት የመነሻ ታሪክ መረጃ እየሰጠ ነው። (ታሪካዊ ዳራ መረጃ ተመልከት)

እስከ ዛሬ ድረስ
በዚህ ስፍራ "ዛሬ' የሚለው ቃል የሚያመለክትው ጸሐፊው መጽሐፉን እስከሚጽፈበት ድረስ የነበረውን ጊዜ ነው።

1 Samuel 5:6

የእግዚአብሔርም እጅ በላያቸው ከበደች
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። "እግዚአብሔር በጽኑ ፈረደባቸው' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

እጢ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጎሞች:- 1) ከቆዳ ስር የሚወጣ የሚያሰቃይ እባጭ ወይም 2) የአህያ ኪንታሮት

አዛጦንና ድንበሯን
የከተማይቱ ስም በከተማይቱ ለሚኖሩ ሰዎች ምትክ ስም ነው። "በአዛጦን የሚኖሩ ሰዎችና በአዛጦን ዙሪያ የሚኖሩ ሰዎች' (ምትክ ቃል ተመልከት)

የአዛጦን ሰዎች አወቁ
"የአዛጦን ሰዎች አስተዋሉ'

የእስራኤል አምላክ ታቦት
ይህንን በ1ሳሙኤል 3:3 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። ይህ በ1ሳሙኤል 4:3-4 "የእግዚአብሔር የኪዳኑ ታቦት' ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው።

1 Samuel 5:8

የእግዚአብሔር እጅ በእነርሱ ላይ ሆነች
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት:- "እግዚአብሔር ቀጣቸው' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

በታናሹም በታላቁም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች:- 1) እድሜን የሚያሳይ ስዕላዊ ንግግር ነው። አት:- "በሁሉ እድሜ የሚገኙ ሰዎች' ወይም 2) ማኅበራዊ መደብን የሚያሳይ ስዕላዊ ንግግር ነው። አት:- "ከድሆችና ደካሞች አንስቶ እሰከ ባለጸጎቹና ብርቱዎቹ ሰዎች' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

እጢ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጎሞች:- 1) ከቆዳ ስር የሚወጣ የሚያሰቃይ እባጭ ወይም 2) የአህያ ኪንታሮት 1ሳሙኤል 5:6ን እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Samuel 5:10

ጮኹ
ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

1 Samuel 5:11

የእስራኤል አምላክ ታቦት
ይህንን በ1ሳሙኤል 3፡3 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። ይህ በ1ሳሙኤል 4፡3-4 "የእግዚአብሔር የኪዳኑ ታቦት' ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው።

የእስራኤል አምላክ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጎሞች፡- 1) የእስራኤልን አምላክ መደበኛ ስም እየጠሩ ነበር ወይም 2) "የእስራኤል አምላክ'፣ እስራኤል ከብዙ አማልክት መካከል አንዱን ያመልኩ እንደነበር ያምኑ ነበር። 1ሳሙኤል 5፡7 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

በከተማይቱ ሁሉ የሞት ድንጋጤ ነበር
"ለሞቱ ስለሆነ የከተማይቱ ሰዎች ሁሉ ፈርተው ነበር'

የእግዚአብሔር እጅ በዚያ እጅግ ከብዳ ነበረች
እጁ የእግዚብሔር ሰዎችን ስለ መቅጣተ ምትክ ቃል ነው። "እግዚአብሔር በዚያ ሰዎችን እጅግ እየቀጣ ነበር' (ምትክ ቃል ተመልከት)

ያልሞቱትም ሰዎች
ይህ በተጨባጭ ብዙ ሰዎች እንደሞቱ ያመላክታል። (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

እጢ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጎሞች፡- 1) ከቆዳ ስር የሚወጣ የሚያሰቃይ እባጭ ወይም 2) የአህያ ኪንታሮት 1ሳሙኤል 5፡6ን እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት።

የከተማይቱ ጩኸት ወደ ሰማያት ወጣ
ከተማ የሚለው ቃል ለከተማው ሕዝብ ምትክ ቃል ነው። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) "ወደ ሰማያት ወጣ' የሚለው ቃል "ታላቅ ነበር' ለሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፡- "የከተማይቱ ሰዎች ድምፃቸውን በጣም ከፍ አድርገው ጮኹ' ወይም 2) "ሰማያት' የሚለው ቃል ለሕዝቡ አማልክት ምትክ ቃል ነው። አት፡- "የከተማይቱ ሕዝብ ወደ አማልክቶቻቸው ጮኹ' (ምትክ ቃልና ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 6

1 የእግዚአብሔር ታቦት በፍልስጥኤማውያን አገር ከተቀመጠ ሰባት ወር ሆነው። **2** ከዚያም የፍልስጥኤም ሰዎች ካህናትንና ጠንቋዮችን ጠርተው፥ “የእግዚአብሔርን ታቦት ምን እናድርገው? ወደ አገሩ እንዴት አድርገን መመለስ እንዳለብን ንገሩን” አሉአቸው። **3** ካህናቱና ጠንቋዮቹም፥ "የእስራኤልን አምላክ ታቦት መልሳችሁ የምትልኩ ከሆነ ያለስጦታ አትላኩት፤ በተቻለ መጠን የበደል መስዋዕትም ላኩለት። ከዚያም ትፈወሳላችሁ፥ እናንተም እስካሁን ድረስ እጁን ከላያችሁ ላይ ያላነሣው ለምን እንደሆነ ታውቃላችሁ"። **4** ሕዝቡም፥ “የምንመልሰው የበደል መስዋዕት ምን መሆን አለበት?”አሏቸው። እነርሱም እንዲህ በማለት መለሱላቸው፥ "አምስት የወርቅ እባጮችንና አምስት የወርቅ አይጦችን፥ በቁጥር አምስት መሆኑም የፍልስጥኤማውያንን ገዢዎች ቁጥር የሚወክል ነው። እናንተንና ገዢዎቻችሁን የመታው ተመሳሳይ መቅሰፍት ነውና። **5** ስለዚህ ምድራችንን ባጠፋው በእባጮቻችሁና በአይጦቻችሁ አምሳል ማድረግ አለባችሁ፥ ለእስራኤል አምላክም ክብርን ስጡ። ምናልባት እጁን ከእናንተ፥ ከአማልክቶቻችሁና ከምድሪቱ ላይ ያነሣ ይሆናል። **6** ግብፃውያንና ፈርዖን ልባቸውን እንዳደነደኑ ለምን ልባችሁን ታደነድናላችሁ? ያን ጊዜ ነበር የእስራኤል አምላክ ክፉን ያደረገባቸው፤ ታዲያ ግብፃውያኑ ሕዝቡን አልለቀቋቸውም እነርሱስ ከዚያ አልወጡም? **7** እንግዲህ አዲስ ሠረገላና እስካሁን ቀንበር ያልተጫነባቸውን ሁለት የሚያጠቡ ላሞች አዘጋጁ። ላሞቹን በሠረገላው ጥመዷቸው፥ እምቦሳዎቻቸውን ግን ከእነርሱ ለይታችሁ በቤት አስቀሩአቸው። **8** ከዚያም የእግዚአብሔርን ታቦት ወስዳችሁ በሠረገላው ላይ አኑሩት። የበደል መስዋዕት አድርጋችሁ የምትመልሱለትን የወርቁን አምሳያዎች በሳጥን ውስጥ አድርጋችሁ በአንደኛው ጎኑ አስቀምጡ። ከዚያም ልቀቁትና በራሱ መንገድ እንዲሄድ ተዉት። **9** ከዚያም ተመልከቱ፥ ወደ ራሱ ምድር፥ ወደ ቤት ሳሚስ በመንገዱ ከሄደ፥ ይህንን ታላቅ ጥፋት ያመጣው እግዚአብሔር ነው ማለት ነው። ካልሆነ ግን፥ ይህ በአጋጣሚ የደረሰብን እንጂ የመታን የእርሱ እጅ እንዳልሆነ እናውቃለን"። **10** ሰዎቹም እንደተነገራቸው አደረጉ፤ ሁለት የሚያጠቡ ላሞችን ወሰዱና በሠረገላው ጠመዷቸው፥ እምቦሳዎቻቸውንም ከቤት እንዳይወጡ አደረጉ። **11** የወርቁን አይጥና የእባጮቻቸው ምሳሌ የሆነውን ከያዘው ሳጥን ጋር የእግዚአብሔርን ታቦት በሠረገላው ላይ አደረጉት። **12** ላሞቹም በቤት ሳሚስ አቅጣጫ ቀጥ ብለው ሄዱ። እነርሱም በዚያው ጎዳና፥ ወደ ግራም ወደ ቀኝም ሳይሉ ቁልቁል ሄዱ። የፍልስጥኤማውያን ገዢዎችም እስከ ቤት ሳሚስ ዳርቻ ድረስ ከበስተኋላቸው ተከተሏቸው። **13** በዚህ ጊዜ የቤት ሳሚስ ሰዎች በሸለቆው ውስጥ ስንዴአቸውን በማጨድ ላይ ነበሩ። ቀና ብለው ባዩ ጊዜ ታቦቱን ተመለከቱ፥ ደስም አላቸው። **14** ሠረገላው የቤት ሳሚስ ሰው ወደሆነው ወደ ኢያሱ እርሻ መጥቶ በዚያ ቆመ። በዚያም ትልቅ ቋጥኝ ነበር፥ የሠረገላውን እንጨት በመፍለጥ ላሞቹን ለእግዚአብሔር የሚቃጠል መሥዋዕት አድርገው አቀረቡ። **15** ሌዋውያኑ የእግዚአብሔርን ታቦትና አብሮት የነበረውን፥ የወርቁ ምስሎች የነበሩበትን ሳጥን፥ ከሠረገላው አውርደው በትልቁ ቋጥኝ ላይ አስቀመጡት። በዚያው ቀን የቤት ሳሚስ ሰዎች ለእግዚአብሔር የሚቃጠል መሥዋዕት አቀርቡ፥ መሥዋዕቶችንም ሠዉ። **16** አምስቱ የፍልስጥኤማውያን ገዢዎች ይህንን ባዩ ጊዜ በዚያው ቀን ወደ አቃሮን ተመለሱ። **17** የፍልስጥኤም ሰዎች ለእግዚአብሔር የበደል መስዋዕት አድርገው የመለሷቸው የወርቅ እባጮች እነዚህ ናቸው፤ አንዱ ስለ አሽዶድ፥ አንዱ ስለ ጋዛ፥ አንዱ ስለ አስቀሎና፥ አንዱ ስለ ጌት እና አንዱ ስለ አቃሮን ነበር። **18** የወርቁ አይጥ አምስቱ ገዢዎች ከሚገዟቸው የተመሸጉ የፍልስጥኤማውያን ከተሞችና መንደሮች ቁጥር ሁሉ ጋር ቁጥሩ ተመሳሳይ ነበር። የእግዚአብሔርን ታቦት ያስቀመጡበት ያ ታላቅ ቋጥኝ በቤት ሳሚስ በኢያሱ እርሻ ውስጥ እስከ ዛሬ ድረስ ምስክር ሆኖ ይኖራል። **19** ወደ ታቦቱ ውስጥ ተመልክተዋልና እግዚአብሔር ከቤት ሳሚስ ሰዎች ጥቂቶቹን መታቸው። እርሱም ሰባ ሰዎችን ገደለ። እግዚአብሔር ሕዝቡን ክፉኛ ስለመታቸው ሕዝቡ አለቀሱ። **20** የቤት ሳሚስ ሰዎችም፥ “በዚህ ቅዱስ አምላክ በእግዚአብሔር ፊት መቆም የሚችል ማነው? ከእኛስ ወደ ማን ይሄዳል?” አሉ። **21** በቂርያትይዓሪም ወደሚኖሩት መልዕክተኞች ልከው፥ “ፍልስጥኤማውያን የእግዚአብሔርን ታቦት መልሰዋል፤ ወደዚህ ውረዱና ውሰዱት” አሏቸው።

---

1 Samuel 6:1

ካህናትና ጠንቋይችን
እነዚህ ዳጎንን የሚያመልኩ የአሕዛብ ካህናትና ጠንቋዮች ናቸው።

እንዴት እንደምንሰደው ንገሩን
ፍልስጥኤማውያን ከዚህ ወዲያ እግዚአብሔርን ሳያሰቆጡ ታቦቱን እንዴት እንደሚያስወግዱት ማወቅ ፈለጉ።

1 Samuel 6:3

የእስራኤል አምላክ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጎሞች፡- 1) የእስራኤልን አምላክ መደበኛ ስም እየጠሩ ነበር ወይም 2) "የእስራኤል አምላክ'፣ እስራኤል ከብዙ አማልክት መካከል አንዱን ያመልኩ እንደነበር ያምኑ ነበር። 1ሳሙኤል 5፡7 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

የበደል መሥዋዕት መልሱለት እንጂ ባዶውን አትስደዱት
ባዶውን አትስደዱት የሚሉት ቃላት አንድን ነገር አጠንክሮ መናገሪያ መንገድ ናቸው። አት፡- "የበደል መሥዋዕት መስደድ አለባችሁ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ትፈወሳላችሁ
"ከእንግዲህ ወዲህ አትታመሙ'

እናንተ
እናንተ የሚለው ተውላጠ ስም የብዙ ቁጥር እንደመሆኑ ፍልስጥኤማውያንን ሁሉ ያመለክታል። (አንተ/እናንተ ተመልከት)

እጁ ከእናንተ አለመራቁ ስለምን ነው
በዚህ ስፍራ "እጅ' የሚለው ቃል እግዚአብሔር መከራን ለማምጣትና ለመቅጣት ያለውን ኃይል ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለ ምትክ ቃል ነው። አት፡- "መከራችሁን ለምን አላቀለላችሁም' (ምትክ ቃል ተመልከት)

እጢ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጎሞች፡- 1) ከቆዳ ስር የሚወጣ የሚያሰቃይ እባጭ ወይም 2) የአህያ ኪንታሮት 1ሳሙኤል 5፡6ን እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት።

አይጦች
ከአንድ በላይ አይጥ

1 Samuel 6:5

ምሳሌዎች
ምሳሌ እውነተኛው ነገር የሚመስል ነገር ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እጢ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጎሞች፡- 1) ከቆዳ ስር የሚወጣ የሚያሰቃይ እባጭ ወይም 2) የአህያ ኪንታሮት 1ሳሙኤል 5፡6ን እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት።

የሚያወድሙ
"የሚያጠፉ'

የእስራኤል አምላክ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጎሞች፡- 1) የእስራኤልን አምላክ መደበኛ ስም እየጠሩ ነበር ወይም 2) "የእስራኤል አምላክ'፣ እስራኤል ከብዙ አማልክት መካከል አንዱን ያመልኩ እንደነበር ያምኑ ነበር። 1ሳሙኤል 5፡7 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

እጁን ከእናንተና ከአማልክቶቻችሁ፣ ከምድራችሁም ያነሳል
በዚህ ስፍራ "እጅ' የሚለው ቃል እግዚአብሔር መከራን ለማምጣትና ለመቅጣት ያለውን ኃይል ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለ ምትክ ቃል ነው። አት፡- "እናንተን፣ አማልክቶቻችሁንና ምድራችሁን መቅጣት ያቆማል' (ምትክ ቃል ተመልከት)

ግብጻውያንና ፈርዖንም ልባቸውን እንዳደነደኑ ልባችሁን ለምን ታደነድናላችሁ?
ካህናቱና ጠንቋዮቹ አሳብ ገላጭ ጥያቄ በመጠቀም፣ እግዚአብሔርን መታዘዝ እምቢ ካሉ ምን ሊሆን እንደሚችል ትኩረት ሰጥተው እንዲያስቡ ፍልስጥኤማውያንን አጥብቀው እያስገነዘቡ ነው። (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ልባችሁን ታደነድናላችሁ
ይህ ግትር መሆንና ለእግዚአብሔር ፈቃድ አለመታዘዝ የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ ንግግር ነው። (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ግብጻውያን ሕዝቡን አልሰደዱአቸውምን እነርሱም አልሄዱምን?
ይህ እግዚአብሔር በግብጻውያን ላይ መከራ ማምጣቱን እንዲያቆም በስተመጨረሻ ግብጻውያን እንዴት እስራኤላውያን ከግብጽ እንዲወጡ እንዳደረጉ ፍልስጥኤማውያንን ለማሳሳብ የተጠቀሙበት አሳብ ገላጭ ጥያቄ ነው። (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

1 Samuel 6:7

ሁለት የሚያጠቡ ላሞች
እስከ አሁን ወተት የሚጠጡ ጥጆች ያሉአቸው ሁለት ላሞች

ይሄድም ዘንድ ስደዱት
እንደተለመደው ሁለቱ ላሞች ወደ ጥጆቻቸው ወደ ቤት መመለስ ይኖርባቸው ነበር።

ወደ ቤትሳሚስ ከሄደ ... እግዚአብሔር ነው
ላሞቹ ጥጆቻቸው በስተኋላ በፍልስጥኤማውያን ሰፈር እያሉ ወደ ቤትሳሚስ ለመንከራተት ይመርጣሉ ብሎ ማሰብ የማይመስል ነው።

1 Samuel 6:10

ሁለት የሚያጠቡ ላሞች
እስከ አሁን ወተት የሚጠጡ ጥጆች ያሉአቸው ሁለት ላሞች። 1ሳሙኤል 6፡7ን እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

አይጦች
ይህን በ1ሳሙኤል 6፡4 እንዳለው ተርጉም።

የእባጮቻቸውን ቅርጾች
"የእባጮቻቸውን ምሳሌዎች'

እጢ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጎሞች፡- 1) ከቆዳ ስር የሚወጣ የሚያሰቃይ እባጭ ወይም 2) የአህያ ኪንታሮት 1ሳሙኤል 5፡6ን እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት።

ላሞቹ ወደ ቤትሳሚስ አቅጣጫ አቅንተው ሄዱ
በአብዛኛው የሚያጠቡ ላሞች ወደ ጥጆቻቸው ይመለሳሉ፣ ነገር ግን እነዚህ ላሞች ወደ ቤትሳሚስ ሄዱ።

እምቧ እያሉ ሄዱ
እምቧ ማለት ላሞች በድምጻቸው የሚፈጥሩት ጩኸት ነው።

ወደ ቀኝም ወደ ግራም አላሉም
"ከአውራ ጎዳናው አልወጡም።' ይህ በአዎንታ እንደሚከተለው ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "በአውራው ጎዳና ዘለቁ' ወይም "ቀጥ ብለው ወደ ፊት ይሄዱ ነበር'

1 Samuel 6:13

አሁን
ቃሉ የታሪኩ አዲስ ክፍል መጀመሩን ያሳያል። ቋንቋህ ተመሳሳይ ትርጉም የሚሰጥ ቃል ወይም ሐረግ ካለ በዚህ ስፍራ ልትጠቀም ትችላለህ።

የቤትሳሚስ ሰዎች
እስራኤላውያን ነበሩ።

ዓይናቸውን ከፍ አድርገው
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፡- "አሻቅበው አዩ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

1 Samuel 6:14

ታላቅ ድንጋይ በዚያ ነበር
ሰዎች ላሞቻቸውን ሲሰው ይህን ድንጋይ እንደ መሠዊያ ይጠቀሙበት ነበር።

ሌዋውያኑ የእግዚአብሔርን ታቦት አወረዱ
ይህ የሆነው ላሞቹን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጎ ለማቅረብ ሰረገላውን ለማንደንድ ከመፍለጣቸው በፊት ነው።

ከእርሱ ጋር የነበረውን የወርቅ ዕቃ ያለበትን
ሳጥኑ የአይጥና የእባጭ የወርቅ ምሳሌዎች ይዟል

1 Samuel 6:16

የፍልስጥኤማውያን አምስቱ አለቆች
"የፍልስጥኤማውያን አምስቱ ነገሥታት'

1 Samuel 6:17

እጢ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጎሞች፡- 1) ከቆዳ ስር የሚወጣ የሚያሰቃይ እባጭ ወይም 2) የአህያ ኪንታሮት 1ሳሙኤል 5፡6ን እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት።

አይጦች
ይህን በ1ሳሙኤል 6፡4 እንዳለው ተርጉም።

የተመሸጉ ከተሞች
በውስጥ ያለውን ሕዝብ ከጠላቶቻቸው ጥቃት ለመጠበቅ በዙሪያቸው ትላልቅ ቅጥሮች የተገነቡላቸው ከተሞች ናቸው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ታላቁም ድንጋይ እስከ ዛሬ ድረስ ምስክር ሆኖ አለ
ድንጋዩ ማየት እንደሚችል እንደ አንድ ግለሰብ ተጠቅሷል። አት፡- "ታላቁ ድንጋይ ... እስከ ዛሬ ድረስ በዚያ አለ፣ሰዎችም በላዩ ላይ የተፈጸመውን ያስታውሳሉ።' (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየትን ተመልከት)

ኢያሱ
የሰው ስም (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

ቤትሳሚሳውያን
ይህ ከቤትሳሚስ የሆነ ሰው የሚጠራበት ነው። አት፡- "ከቤትሳሚስ' (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

እስከ ዛሬ ድረስ
ጸሐፊው መጽሐፉን እስከጻፈበት ጊዜ ድረስ

1 Samuel 6:19

ወደ ታቦቱ ውስጥ ተመልክተዋል
ታቦቱ እጅግ ቅዱስ ስለ ነበር ማንም ወደ ውስጥ እንዲመለከት አልተፈቀደለትም። ታቦቱን እንኳን ለማየት የተፈቀደላቸው ካህናት ብቻ ናቸው።

50,070 ሰዎች
"አምሳ ሺህ እና ሰባ ሰዎች' (ቁጥሮች ተመልከት)

በዚህ ቅዱስ አምላክ በእግዚአብሔር ፊት መቆም ማን ይችላል?
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) ሕዝቡ ስለ እግዚብሔር ያደረበትን ፍርሃት ለመግለጽ አሳብ ገላጭ ጥያቄ ነው። አት፡- "ቅዱስ ስለሆነ እግዚአብሔርን መቋቋም የሚችል ማንም የለም!' ወይም 2) መረጃ ለማግኘት የቀረበ ጥያቄ ነው። በእግዚአብሔር ፊት መቆም የሚለው ሐረግ እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ ካህናትን የሚያመለክት ነው። ሕዝቡ እግዚአብሔር ታቦቱን እንዲይዝ የፈቀደለትን ካህን እፈለገ መሆኑን ያመላክታል። አት፡- "በመካከላችን ይህን ቅዱስ አምላክ፣ ያህዌን ማገልገልና ታቦቱን ማስተዳደር የሚችል ካህን አለን?' (አሳብ ገላጭ ጥያቄዎችንና እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ታቦቱ ከእኛ ወደ ማን ይሄዳል?
መረጃ ለማግኘት የቀረበ ጥያቄ ነው። ሁለተኛ እንዳይቀጣቸው እግዚአብሔርና ታቦቱ ወደ አንድ ቦታ እንዲሄዱ ሕዝቡ እንደፈለገ ይጠቁማል። አት፡- "እግዚአብሔር ሁለተኛ እንዳይቀጣን ይህን ታቦት ወዴት መስደድ እንችላለን?' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

1 Samuel 6:21

ቂርያትይዓሪም
ይህ የቦታ ስም ነው። (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 7

[1] የቂርያትይዓሪም ሰዎች መጥተው የእግዚአብሔርን ታቦት ወሰዱ፥ በኮረብታው ላይ ወዳለው ወደ አሚናዳብ ቤት አስገቡት። የእግዚአብሔርን ታቦት
እንዲጠብቅ ልጁን አልዓዛርን ለዚህ አገልግሎት ለዩት። [2] ታቦቱ በቂርያትይዓሪም ከተቀመጠ ብዙ ዓመት አለፈው፥ ሃያ ዓመትም ሆነው። የእስራኤል ቤት ሁሉ
አዘኑ፥ ወደ እግዚአብሔር ለመመለስም ፈለጉ። [3] ሳሙኤል የእስራኤልን ሕዝብ በሙሉ እንዲህ አላቸው፥ "በሙሉ ልባችሁ ወደ እግዚአብሔር የምትመለሱ
ከሆነ እንግዶቹን አማልክትና አስታሮትን ከመካከላችሁ አስወግዱ፥ ልባችሁን ወደ እግዚአብሔር መልሱ፥ እርሱንም ብቻ አምልኩት፥ ያን ጊዜ ከፍልስጥኤማውያን
እጅ ያድናችኋል"። [4] ከዚያም የእስራኤል ሕዝብ በኣልንና አስታሮትን አስወገዱ፥ እግዚአብሔርን ብቻም አመለኩ። [5] ከዚያም ሳሙኤል፥ "እስራኤልን በሙሉ
ምጽጳ ላይ ሰብስቡ፥ እኔም ስለ እናንተ ወደ እግዚአብሔር እጸልያለሁ“ አላቸው። [6] እነርሱም በምጽጳ ተሰበሰቡ፥ ውሃም ቀድተው በእግዚአብሔር ፊት አፈሰሱ።
በዚያም ቀን ጾሙ፥”በእግዚአብሔር ላይም ኃጢአትን አድርገናል“ አሉ። ሳሙኤል በእስራኤል ሕዝብ ላይ የፈረደውና ሕዝቡን የመራው በዚያ ነበር። [7]
የእስራኤል ሕዝብ በምጽጳ መሰብሰባቸውን ፍልስጥኤማውያን በሰሙ ጊዜ፥ የፍልስጥኤማውያን ገዢዎች እስራኤልን ለማጥቃት መጡ። የእስራኤል ሰዎች
ይህንን በሰሙ ጊዜ ፍልስጥኤማውያንን ፈሩ። [8] ከዚያም የእስራኤል ሕዝብ ሳሙኤልን፥”ከፍልስጥኤማውያን እጅ እንዲያድነን፥ ስለ እኛ ወደ አምላካችን ወደ
እግዚአብሔር መጣራትህን አታቁም“ አሉት። [9] ሳሙኤል የሚጠባ ግልገል ወስዶ ለእግዚአብሔር ሙሉውን የሚቃጠል መስዋዕት አድርጎ ሠዋው። ከዚያም
ሳሙኤል ስለ እስራኤል ወደ እግዚአብሔር ጮኸ፥ እግዚአብሔርም መለሰለት። [10] ሳሙኤል የሚቃጠለውን መስዋዕት በማቅረብ ላይ እያለ ፍልስጥኤማውያን
እስራኤልን ለማጥቃት ቀረቡ። ነገር ግን በዚያን ቀን እግዚአብሔር በፍልስጥኤማውያን ላይ በታላቅ ድምፅ አንጎደጎደባቸው፥ አሸበራቸውም፥ በእስራኤልም ፊት
ተሸንፈው ሸሹ። [11] የእስራኤል ሰዎችም ከምጽጳ ተነሥተው ፍልስጥኤማውያንን አሳደዱ፥ ከቤትካር በታች እስካለው ቦታ ድረስ ተከትለው ገደሏቸው። [12]
ከዚያም ሳሙኤል አንድ ድንጋይ አንሥቶ በምጽጳና በሼን መካከል አቆመው።”እስካሁን ድረስ እግዚአብሔር ረድቶናል“ በማለት አቤንኤዘር ብሎ ጠራው። [13]
ስለዚህ ፍልስጥኤማውያን ተሸነፉ፥ የእስራኤልን ድንበርም አልፈው አልገቡም። በሳሙኤል የሕይወት ዘመን ሁሉ የእግዚአብሔር እጅ በፍልስጥኤማውያን ላይ
ከብዳ ነበር። [14] ፍልስጥኤማውያን ከእስራኤል የወሰዷቸው ከአቃሮን እስከ ጌት ያሉ መንደሮች ለእስራኤል ተመለሱላቸው፤ እስራኤላውያን ድንበሮቻቸውን
ከፍልስጥኤማውያን አስመለሱ። በዚያን ጊዜ በእስራኤላውያንና በአሞራውያን መካከል ሰላም ነበረ። [15] ሳሙኤል በሕይወት ዘመኑ ሁሉ በእስራኤል ላይ
ፈረደ። [16] በየዓመቱ ወደ ቤቴል፥ ወደ ጌልገላና ወደ ምጽጳ ይዘዋወር ነበር። በእነዚህ ስፍራዎች ሁሉ በእስራኤላውያን መካከል ባሉ አለመግባባቶች ላይ
ይፈርድ ነበር። [17] ከዚያም መኖሪያው በዚያ ነበርና ወደ ራማ ይመለስ ነበር፤ በዚያም ደግሞ በእስራኤላውያን አለመግባባት ላይ ይፈርድ ነበር። በዚያም ደግሞ
ለእግዚአብሔር መሠዊያን ሠራ።

---

1 Samuel 7:1

ቂርያትይዓሪም
ይህ የቦታ ስም ነው። (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)

አሚናዳብ ... አልዓዛር
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)

ሀያ ዓመታት
20 ዓመታት (ቁጥሮች ተመልከት)

1 Samuel 7:3

የእስራኤል ቤት ሁሉ
"ቤት' የሚለው ቃል በቤት ውስጥ የሚኖሩትን ሰዎችና ትውልዳቸውን የሚያመለክት ምትክ ቃል ነው። አት፡- "የእስራኤል ትውልድ' ሁሉ ወይም "የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ' (ምትክ ቃል ተመልከት)

በሙሉ ልባችሁ ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ
በዚህ ስፍራ "በሙሉ ልብ' የሚለው ለአንድ ነገር ፈጽሞ መሰጠት የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፡- "እግዚአብሔርን ብቻ ለማምለክና ለመታዘዝ ፈጽማችሁ የተሰጣችሁ ሁኑ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመለክት)

1 Samuel 7:5

እስራኤል ሁሉ
"የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ' ወይም "እስራኤላውያን ሁሉ'

ውኃ ቀድተው በእግዚአብሔር ፊት አፈሰሱ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ሕዝቡ የጾም ክፍል አድርገው የራሳቸውን ወኃ አልተጠቀሙም ወይም 2) ከምንጭ ወይም ከጉድጓድ ውኃ አገኙ፣ በኃጢታቸውም ለመጸጸታቸው እንደ ውጪያዊ ምልክት በምድር ላይ አፈሰሱት። (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

1 Samuel 7:7

የፍልስጥኤማውያን አለቆች በእስራኤል ላይ ጥቃት አደረሱ
በእስራኤል ላይ ጥቃት ያደረሱት ሠራዊቶቹ እንጂ አለቆቹ ራሳቸው እንዳልሆኑ በግልጽ ማስቀመጥ ይቻላል። አት፡- "የፍልስጥኤማውየን አለቆች ሠራዊታቸውን እየመሩ በእስራኤል ላይ ጥቃት አደረሱ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ከፍልስጥኤማውያን እጅ አድነን
እጅ የሰውዬውን ኃይል የሚያሳይ ምትክ ቃል ነው። አት፡- "ከፍልስጥኤማውያን ሠረዊት አድነን' ወይም "የፍልስጥኤማውያን ሠራዊት እንዳይጎዱን አድርግ' (ምትክ ቃል ተመልከት)

1 Samuel 7:9

የሚጠባ የበግ ጠቦት
እስካሁን ድረስ የእናቱን ወተት የሚጠጣ ጠቦት

ጮኸ
"ለእርዳታ ጮኸ'

እግዚአብሔር መለሰለት
"እንዲያደርግ ሳሙኤል የጠየቀውን እግዚአብሔር አደረገ'

1 Samuel 7:10

ሳሙኤልም ... በቤትካር
ይህ ጸሐፊው "እግዚአብሔር መለሰለት' ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ ያብራራል (1ሳሙኤል 7:9)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ግራ አጋባቻው
"ግራ መጋባት' የሚለው ቃል በዚህ ስፍራ ጥቅም ላየ የዋለው ፍልስጥኤማውያን በግልጽ ማሰብ አልቻሉም ለማለት ነው። አት፡- "በግልጽ ማሰብ እንዳይችሉ አደረጋቸው' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

በእስራኤልም ፊት ድል ተመቱ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊተረጎም ይችላል። አት፡- ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እግዚአብሔር በእስራኤል ፊት ድል መታቸው ወይም 2) እስራኤል ድል መታቸው (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ድል መምታት
ሰዎችን ድል መምታት ማለት ምንም ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት ማሸነፍ ነው።

ቤትካር
ይህ የቦታ ስም ነው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

1 Samuel 7:12

ድንጋይ ወስዶ አኖረ
በዚያ ምድር እስራኤላውያንን ሌሎች ሕዝቦች አስፈላጊ ነገሮች ሲሆኑ ለእግዚአብሔር እርዳታ ማስታወሻ እንዲሆን ትልቅ ድንጋይ ያኖራሉ።

ምጽጳ ... ሼን
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

1 Samuel 7:13

ፍልስጥኤማውያን ተገዙ
ጸሐፊው እንዴት ፍልስጥኤማውያን እንዴት በቁጥጥር ስር እንደዋሉ መናገሩን ፈጸመ። ቋንቋህ ትረካን የሚደመድምበት መንገድ ካለው እዚህ ጋ መጠቀም ትችላለህ።

ፍልስጥኤማውያን ተገዙ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊተረጎም ይችላል። አት፡- "እግዚብሔርን ፍልስጥኤማውያንን አስገዛቸው' ወይም "እግዚአብሔር ፍልስጥኤማውያንን ጉዳት ከማድረስ አገዳቸው' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ወደ እስራኤል ድንበር አልመጡም
ፍልስጥኤማውያን ሊያጠቁአቸው ወደ እስራኤል ድንበር አይገቡም ነበር።

የእግዚአብሔር እጅ በፍልስጥኤማውያን ላይ ነበረች
እጅ የሚለው ቃል ለኃይል ምትክ ቃል ነው። አት፡- "እግዚአብሔር በፍልስጥኤማውያን ላይ ኃይሉን ይጠቀም ነበር' (ምትክ ቃል ተመልከት)

ከተሞች ... ከእስራኤል ለእስራኤል ተመለሱ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) በዚህ ስፍራ "እስራኤል' የሚለው ቃል የሚያመለከትው የእስራኤልን "ምድር' ነው። ከእስራኤል ... እግዚአብሔር ከተሞችን ለእስራኤል ምድር መለሰ ወይም 2) "እስራኤል' የሚለው ቃል በዚያ ለሚኖረው ሕዝብ ምትክ ቃል ነው። አት፡- "ከእስራኤል ... የእስራኤል ሕዝብ ከተሞቹን የኔ ናቸው ማለት ቻለ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽና ምትክ ቃል ተመልከት)

1 Samuel 7:15

ይዞር ነበር
በአስቸጋሪ ዙር ከቦታ ቦታ ይጓዝ ነበር

በመግቶች ላይ ይወስን ነበር
ሙግት ማለት ክርክር ወይም በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚፈጠር አለመስማማት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 8

1 ሳሙኤል በሸመገለ ጊዜ ልጆቹን በእስራኤል ላይ ፈራጆች አድርጎ ሾማቸው። 2 የመጀመሪያ ልጁ ስም ኢዮኤል፥ የሁለተኛው ስም አብያ ነበር። እነርሱም በቤርሳቤህ ፈራጆች ነበሩ። 3 ነገር ግን ልጆቹ ነውረኛ ጥቅም ፈላጊዎች ሆኑ እንጂ በእርሱ መንገድ አልሄዱም። ጉቦ እየተቀበሉ ፍትሕን አዛቡ። 4 ከዚያም የእስራኤል ሽማግሌዎች በአንድነት ተሰብስበው በራማ ወደሚኖረው ወደ ሳሙኤል መጡ። 5 እነርሱም፥ "ተመልከት፥ አንተ ሸምግለሃል፥ ልጆችህም በመንገድህ አይሄዱም። እንደ ሌሎች ሕዝቦች ሁሉ እንዲፈርድልን ንጉሥ አንግሥልን" አሉት። 6 ነገር ግን፥ “እንዲፈርድልን ንጉሥ ስጠን” ባሉት ጊዜ ነገሩ ሳሙኤልን ቅር አሰኘው። ስለዚህ ሳሙኤል ወደ እግዚአብሔር ጸለየ። 7 እግዚአብሔርም ሳሙኤልን እንዲህ አለው፥ “በላያቸው ላይ ንጉሥ እንዳልሆን የተቃወሙት እኔን እንጂ አንተን አይደለምና በሚሉህ ነገር ሁሉ የሕዝቡን ቃል ታዘዝ። 8 ከግብፅ ካወጣኋቸው ጊዜ ጀምሮ እኔን ትተው ሌሎች አማልክቶችን በማምለክ ሲያደርጉት የነበረውን ያንኑ አሁን እያደረጉ ነው፤ በአንተም ላይ የሚያደርጉት እንደዚሁ ነው። 9 አሁንም የሚሉህን ስማቸው፤ ነገር ግን በላያቸው የሚገዛው ንጉሥ የሚያደርግባቸውን እንዲያውቁ አጥብቀህ አስጠንቅቃቸው"። 10 ስለዚህ ሳሙኤል ንጉሥ ለጠየቀው ሕዝብ የእግዚአብሔርን ቃል በሙሉ ነገራቸው። 11 እርሱም እንዲህ አላቸው፥ "ንጉሡ በላያችሁ ላይ የሚገዛው እንዲህ ነው። ወንዶች ልጆቻችሁን ወስዶ ፈረሰኞች እንዲሆኑና በሠረገላዎቹ ፊት እንዲሮጡ በሠረገላዎቹ ላይ ይሾማቸዋል። 12 እርሱም ለራሱ ሻለቃዎችንና ሃምሳ አለቃዎችን ይሾማል። አንዳንዶቹ መሬቱን እንዲያርሱ፥ ሌሎቹም እህሉን እንዲያጭዱ፥ አንዳንዶቹ የጦር መሳሪያዎችንና ሌሎቹም የሠረገላ ዕቃዎችን እንዲሠሩለት ያደርጋቸዋል። 13 ሴቶች ልጆቻችሁን ደግሞ ሽቶ ቀማሚዎች፥ ወጥ ሠሪዎችና እንጀራ ጋጋሪዎች እንዲሆኑ ይወስዳቸዋል። 14 በጣም ምርጥ የሆነውን መሬታችሁን፥ የወይን ቦታችሁንና የወይራ ዛፋችሁን ወስዶ ለአገልጋዮቹ ይሰጣቸዋል። 15 ከእህላችሁና ከወይናችሁ አንድ ዐሥረኛውን ወስዶ ለሹማምንቱና ለአገልጋዮቹ ይሰጣቸዋል። 16 ወንዶችና ሴቶች አገልጋዮቻችሁን፥ ከወጣት ልጆቻችሁና ከአህዮቻችሁ የተመረጡትን ይወስዳል፤ ሁሉንም ለእርሱ እንዲሠሩ ያደርጋቸዋል። 17 ከበግና ከፍየል መንጋዎቻችሁ አንድ ዐሥረኛውን ይወስዳል፥ እናንተም አገልጋዮቹ ትሆናላችሁ። 18 በዚያም ቀን ለራሳችሁ ስለመረጣችሁት ንጉሥ ታለቅሳላችሁ፤ ነገር ግን በዚያን ቀን እግዚአብሔር አይመልስላችሁም”። 19 ሕዝቡ ግን ሳሙኤልን ለመስማት እምቢ አሉ፤ 20 ሳሙኤልንም፥ “አይሆንም፥ ንጉሣችን እንዲፈርድልን፥ በፊታችን እንዲሄድና ጦርነቶቻችንን እንዲዋጋልን፥ እንደ ሌሎች ሕዝቦች ሁሉ ለእኛም ንጉሥ ሊሆንልን ይገባል” አሉት። 21 ሳሙኤል የሕዝቡን ቃል ሁሉ በሰማ ጊዜ እርሱም በእግዚአብሔር ጆሮ ደግሞ ተናገረው። 22 እግዚአብሔርም ሳሙኤልን፥ “ቃላቸውን ታዘዝና ንጉሥ አድርግላቸው” አለው። ስለዚህ ሳሙኤል የእስራኤልን ሰዎች፥ “እያንዳንዱ ወደገዛ ከተማው ይሂድ” አላቸው።

---

1 Samuel 8:1

ነውረኛ ትርፍ ያሳድዱ ነበር
ጸሐፊው ሰው ወይም እንስሳ ከሳሙኤል ልጆች አምልጠው ይሮጡ የነበር ይመስል፣ የሳሙኤልም ልጆች ሰውና እንስሳ በተጨባጭ ያሳድዱ የነበሩ ይመስል፣ ሕዝቡ ለሳሙኤል ልጆች ስለሚሰጠው ገንዘብ ይናገራል። (ምትክ ቃል ተመልከት)

ፍርድን ያጣምሙ ነበር
ክፉ ለሚያደርጉ በማድላት ይፈርዳሉ

1 Samuel 8:4

በመንገድህ አይሄዱም
አንድ ሰው የሚኖርበት መንገድ እንደ ጎዳና ተገልጾአል። አት፦ አንተ የምታደርጋቸውን ነገሮች አያደርጉም ወይም አንተ ታደርገው እንደ ነበር ጽድቅ የሆነውን ነገር አያደርጉም ነበር። (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

እንደ ሕዝቦች ሁሉ የሚፈርድልን ንጉሥ ሹምልን
ሊሆኑ የሚችል ትርጉሞች፣ 1) "እንዲፈርድልን የሕዝቦችን ሁሉ ነገሥታት የሚመስል ንጉሥ ሹምልን' ወይም 2) "የሕዝቦች ነገሥታት በሚፈርዱላቸው መንግድ የሚፈርድልን ንጉሥ ሹምልን'

የሚፈርድልን ንጉሥ ሹምልን
አለቆቹ በስህተት ንጉሡና ከእርሱም በኋላ ልጆቹ በጽድቅ ይገዛሉ ብለው አመኑ።

1 Samuel 8:6

የሚፈርድልን ንጉሥ ሥጠን ... ነገር ግን ሳሙኤልን አስከፋው
ሕዘቡ ምግባረ ብልሹ የሆኑ ልጆቹን አስውግዶ ሌሎች የታመኑ ፈራጆችን እንዲሾምላቸው ሳይሆን ሌሎች አገራት እንዳላቸው ዓይነት በላያቸው ላይ የሚገዛ ንጉሥ በመፈለጋቸው ሳሙኤል ደስተኛ አልሆነም።

የሕዝቡን ቃል ስማ
ቢዘህ ስፍራ "ቃል' የሕዝቡን ፈቃድና ፍላጎት የሚያመልክት ምትክ ቃል ነው። (ምትክ ቃል ተመልከት)

ነገር ግን የተቃወሙት እኔ ነው
ሕዝቡ የተቃወሙት ምግባረ ብልሹ የሆኑትን ፈራጆች ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ንጉሣቸው እንዳይሆን እየተቃወሙት እንደ ነበር እግዚአብሔር ያውቅ ነበር።

1 Samuel 8:8

ከግብጽ አወጣኋቸው
ይህ ከብዙ ዓመታት በፊት እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብጽ ባርነት ነጻ ማውጣቱን ያመለክታል።

አሁን ቃላቸውን ስማ
"አሁን እንድታደርግ የሚጠይቁህን አድርግ'

በጽኑ አስጠንቅቃቸው
ስታስጠነቅቃቸው የምር አድርገው

1 Samuel 8:10

ወጉ ይህ ነው ... ይወስዳል
የንጉሥ ወግ መውሰድ ይሆናል። ይህ የሚወስዳቸውን ነገሮች ዝርዝር ይጀምራል።

በእናንተ ላይ የሚነግሠው የንጉሥ ወግ ይህ ነው
ወግ የሚለው የነገር ስም በማሰሪያ አንቀጽነት ሊተረጎም ይችላል። አት፦ "በላያችሁ የሚነግሠው ንጉሥ የሚያደርገው እንዲህ ነው' ወይም "በላያችሁ የሚነግሠው ንግሥ የሚሠራው እንዲህ ነው' (የነገር ስም ተመልከት)

ሰረገለኞቹ ያደርጋቸዋል
ወደ ጦርነት ሰረጋላ ያስነዳቸዋል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ፈረሰኞቹ ይሆናሉ
ወደ ጦርነት ፈረሶችን ይጋልባሉ

1 Samuel 8:13

አያያዥ አሳቦች
ሳሙኤል ንጉሥ የሚስዳቸውን ነገሮች መናገሩን ቀጠለ።

ሽቶ ቀማሚዎች
ሰውነቱን የሚቀባው መልካም ሽታ ያለው ዘይት መሥራት

የወይራ እርሻ
የወይራ ዛፍ ማሳ

የእህላቸሁን አንድ አሥረኛ
እህላቸውን በአሥር እኩል ቦታ መክፈልና ከእነዚያ ክፍሎች አንዱን ለንጉሥ አለቆችና አገልጋዮች መስጠት ይኖርባቸዋል። (ክፍልፋይ ተመልከት)

የወይናችሁን አንድ አሥረኛ
በወይን እርሻቸው ያመረቱትን በአሥር እኩል ቦታ መክፈልና ከእነዚያ ክፍሎች አንዱን ለንጉሥ አለቆችና አገልጋዮች መስጠት ይኖርባቸዋል። (ክፍልፋይ ተመልከት)

አለቆች
እነዚህ የንጉሡ ሠራዊት አዛዦች ናቸው።

1 Samuel 8:16

አያያዥ አሳቦች
ሳሙኤል ንጉሥ የሚስዳቸውን ነገሮች መናገሩን ቀጠለ።

የመንጋችሁን አንድ አሥረኛ
መንጋቸውን በአሥር እኩል ቦታ መክፈልና ከእነዚያ ክፍሎች አንዱን ለንጉሥ አለቆችና አገልጋዮች መስጠት ይኖርባቸዋል። አንድ አሥረኛን በ1ሳሙኤል 8፡15 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት (ክፍልፋዮች ተመልከት)

ባሮቹ ትሆናላችሁ
"ባሮቹ እንደሆናችሁ ይሰማችኋል'

ትጮኻላችሁ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡-1)ከንጉሡ እንዲያድናቸው ሕዝቡ እግዚአብሔርን ይጠይቃሉ 2)የከፋ አገዛዙን አንዲያቆም ሕዝቡ ንጉሡን ይጠይቃሉ

1 Samuel 8:21

ለእግዚአብሔር ጆሮች ደገማቸው
በዚህ ስፍራ የእግዚአብሔር ጆሮች የሚለው እግዚአብሔርን ያመለክታል። ሕዝቡ ያሉትን ሁሉ በመድገም ሳሙኤል ወደ እግዚአብሔር ጸለየ። አት፡- ለእግዚአብሔር ደገማቸው (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

ቃላቸውን ስማ
"ቃላቸውን' የሚለው ምትክ ቃል የሕዝቡን ፈቃድ ያመለክታል። አት፡- "ሕዝቡን ታዘዝ' (ምትክ ቃል ተመልከት)

አንግሥላቸው
አንድን ሰው በላያቸው ላይ አንግሥላቸው። አንድን ሰው ንጉሥ ማድረግን በሚመለከት የተለመደ ቃል በቋንቋህ ካለ ተጠቀም።

ወደ ከተማው ሄደ
"ወደ ቤት'

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 9

1 ከብንያም ወገን ጽኑ ኃያል የሆነ አንድ ሰው ነበር። ስሙ ቂስ ሲሆን እርሱም የአቢኤል ልጅ፥ የጽሮር ልጅ፥ የብኮራት ልጅ፥ የብንያማዊው የአፌቅ ልጅ ነበር። 2 እርሱም ሳኦል የሚባል መልከ መልካም ወጣት ልጅ ነበረው። ከእርሱ የሚበልጥ መልከ መልካም ሰው በእስራኤል ሕዝብ መካከል አልነበረም። ከሕዝቡ ሁሉ ይልቅ ቁመቱ ረጅም ነበር። 3 የሳኦል አባት የቂስ ሴት አህዮች ጠፍተው ነበር። ስለዚህ ቂስ ልጁን ሳኦልን፥ “ከአገልጋዮቻችን አንዱን ውሰድ፤ ተነሥናም አህዮቹን ፈልግ” አለው። 4 ስለዚህ ሳኦል በኮረብታማው በኤፍሬም አገር በኩል አልፎ ወደ ሻሊሻ ምድር ሄደ፥ ነገር ግን አላገኟቸውም። ከዚያም በሻዕሊም ምድር በኩል አለፉ፥ ነገር ግን በዚያ አልነበሩም። ከዚያም በብንያማውያን ምድር በኩል አለፉ፥ ነገር ግን አላገኟቸውም። 5 ወደ ጹፍ ምድር በመጡ ጊዜ፥ ሳኦል ከእርሱ ጋር የነበረውን አገልጋዩን፥ "ና እንመለስ፥ አለበለዚያ አባቴ ስለ አህዮቹ ማሰቡን ትቶ ስለ እኛ መጨነቅ ይጀምራል" አለው። 6 ነገር ግን አገልጋዩ እንዲህ አለው፥ “ስማኝ፥ በዚህ ከተማ ውስጥ አንድ የእግዚአብሔር ሰው አለ። እርሱም የተከበረ ሰው ነው፤ የሚናገረው ነገር ሁሉ ይፈጸማል። ወደዚያ እንሂድ፤ በየትኛው አቅጣጫ መሄድ እንዳለብን ሊነግረን ይችል ይሆናል"። 7 ከዚያም ሳኦል አገልጋዩን፥ "ታዲያ ወደ እርሱ የምንሄድ ከሆነ ለዚያ ሰው ምን ልንሰጠው እንችላለን? እንጀራው ከከረጢታችን አልቋል፥ ለእግዚአብሔር ሰው የምናቀርበው ምንም ስጦታ የለንም። ምን አለን?"አለው። 8 አገልጋዩም ለሳኦል፥ "ይኸውና፥ የሰቅል ጥሬ ብር አንድ አራተኛው አለኝ፥ በየትኛው አቅጣጫ መሄድ እንዳለብን እንዲነግረን ለእግዚአብሔር ሰው እሰጠዋለሁ" ሲል መለሰለት። 9 (ቀደም ሲል በእስራኤል ውስጥ፥ አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመጠየቅ በሚሄድበት ጊዜ፥ "ኑ፥ ወደ ባለ ራዕዩ እንሂድ" ይል ነበር። የዛሬው ነቢይ ቀደም ሲል ባለ ራዕይ ተብሎ ይጠራ 10 ነበር። ከዚያም ሳኦል አገልጋዩን፥”መልካም ብለሃል። ና፥ እንሂድ“ አለው። ስለዚህ የእግዚአብሔር ሰው ወደነበረበት ከተማ ሄዱ። 11 ኮረብታው ላይ ወዳለው ከተማ በመውጣት ላይ እያሉ ወጣት ሴቶች ውሃ ለመቅዳት ሲወጡ አገኟቸው፤ ሳኦልና አገልጋዩም፥”ባለ ራዕዩ በዚህ አለ? “ በማለት ጠየቋቸው። 12 እነርሱም እንዲህ በማለት መለሱላቸው፥ "አዎን፤ ተመልከቱ፥ እንዲያውም ከፊታችሁ እየቀደመ ነው። ዛሬ ሕዝቡ በኮረብታው ራስ ላይ ስለሚሠዉ ወደ ከተማው ይመጣልና ፍጠኑ። 13 ወደ ከተማው እንደገባችሁ ለመብላት ወደ ኮረብታው ራስ ከመውጣቱ በፊት ታገኙታላችሁ። መሥዋዕቱን የሚባርከው እርሱ ስለሆነ፥ እርሱ ከመምጣቱ በፊት ሕዝቡ አይበሉም፤ ከዚያ በኋላም የተጋበዙት ይበላሉ። ወዲያውኑ ታገኙታላችሁና አሁን ወደ ላይ ውጡ።” 14 ስለዚህ ወደ ላይ ወደ ከተማው ወጡ። ወደ ከተማይቱ በመግባት ላይ እያሉም ሳሙኤል ወደ ኮረብታው ራስ ለመውጣት በእነርሱ አቅጣጫ ሲመጣ አዩት። 15 ሳኦል ከመምጣቱ ከአንድ ቀን በፊት እግዚአብሔር ለሳሙኤል እንዲህ ሲል ገልጦለት ነበር፥ 16 “ነገ በዚህ ሰዓት ከብንያም ምድር አንድ ሰው እልክልሃለሁ፥ በሕዝቤ በእስራኤል ላይ መስፍን እንዲሆን ትቀባዋለህ። እርሱም ሕዝቤን ከፍልስጥኤማውያን እጅ ያድናቸዋል። እርዳታ በመፈለግ መጮኻቸው ወደ እኔ ደርሷልና ሕዝቤን በርኅራኄ ተመልክቻለሁ።” 17 ሳሙኤል ሳኦልን ባየው ጊዜ፥ እግዚአብሔር እንዲህ አለው፥”ስለ እርሱ የነገርኩህ ሰው ይህ ነው! ሕዝቤን የሚገዛው ሰው እርሱ ነው።“ 18 ከዚያም ሳኦል በበሩ አጠገብ ወደ ሳሙኤል ቀረብ ብሎ፥”የባለ ራዕዩ ቤት የት እንደሆነ ንገረኝ“ አለው። 19 ሳሙኤልም ለሳኦል እንዲህ በማለት መለሰለት፥”ባለ ራዕዩ እኔ ነኝ። ከእኔ በፊት ቀድማችሁ ወደ ኮረብታው ራስ ውጡ፥ ዛሬ ከእኔ ጋር ትበላላችሁና። ነገ ጠዋት በአዕምሮህ ያለውን ነገር ሁሉ እነግርህና አሰናብትሃለሁ። 20 ከሦስት ቀን በፊት ጠፍተው የነበሩት አህዮች ተገኝተዋልና ስለ እነርሱ አታስብ። የእስራኤል ሁሉ ምኞት የተቀመጠው በማን ላይ ነው? በአንተና በአባትህ ቤት ሁሉ ላይ አይደለም? “ 21 ሳኦልም፥ "ከእስራኤል ነገዶች ትንሹ የሆነው ብንያማዊ አይደለሁም? ጎሳዬስ ከብንያም ነገድ ጎሳዎች ሁሉ የመጨረሻው አይደለም? ታዲያ እንዲህ ባለ ሁኔታ ለምን ትናገረኛለህ?"ሲል መለሰለት። 22 ከዚያም ሳሙኤል ሳኦልንና አገልጋዩን ወደ አዳራሹ አስገብቶ ሠላሳ ከሚያህሉ ከተጋበዙት ሰዎች ከፍ ባለው ስፍራ ላይ አስቀመጣቸው። 23 ሳሙኤልም ወጥ ሠሪውን፥ "'ለብቻ አስቀምጠው' ብዬ የሰጠሁህን ድርሻ አምጣው" አለው። 24 ወጥ ሠሪውም በመሥዋዕቱ ጊዜ ያነሣውን ጭኑንና ከእርሱ ጋር ያለውን አምጥቶ በሳኦል ፊት አኖረው። ከዚያም ሳሙኤል፥ "የተቀመጠልህን ተመልከት! ለአንተ እስከተወሰነው ሰዓት ድረስ የቆየልህ ነውና ብላው። አሁን 'ሕዝቡን ጋብዣለሁ' ማለት ትችላለህ" አለው። ስለዚህ በዚያን ቀን ሳኦል ከሳሙኤል ጋር በላ። 25 ከኮረብታው ራስ ወደ ከተማው በወረዱ ጊዜ፥ በቤቱ የጣሪያ ወለል ላይ ሳሙኤል ከሳኦል ጋር ተነጋገረ። 26 ከዚያም በነጋ ጊዜ ሳሙኤል በጣሪያው ወለል ላይ ሳኦልን ተጣርቶ፥ "መንገድህን እንድትሄድ አሰናብትህ ዘንድ ተነሥ" አለው። ስለዚህ ሳኦል ተነሣ፥ እርሱና ሳሙኤል ሁለቱም ወደ ጎዳናው ሄዱ። 27 ወደ ከተማው ዳርቻ በመሄድ ላይ እያሉ፥ ሳሙኤል ሳኦልን፥ "አገልጋዩ ከፊታችን ቀድሞ እንዲሄድ ንገረው፥ (እርሱም ቀድሞ ሄደ) አንተ ግን የእግዚአብሔርን መልዕክት እንዳስታውቅህ እዚህ ጥቂት መቆየት አለብህ" አለው።

---

1 Samuel 9:1

አጠቃላይ መረጃ
በእነዚህ ቁጥሮች ጸሐፊው የሚሰጠው የታሪካዊ ዳራ መረጃ ለአንባቢ መናገር የሚቻልበት ሌላ መንገድ በቋንቋህ ካለ እዚህ ጋ መጠቀም ትችላለህ።
(ታሪካዊ ዳራ መረጃ ተመልከት)

ተሰሚነት ያለው ሰው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) ባላጠጋ ሰው ነበር 2) የመሣፍንት ዘር ነበር 3) ኃያልና ጎበዝ ሰው ነበር

ቂስ ... አቢኤል ... ጽሮር ... ብኮራት ... አፌቅ
እነዚህ የሳኦል የትውልድ ሐረግ ሰዎች ስም ነው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

ብንያማዊ
ብንያማዊ ከብንያም ነገድ የሆነ ሰው ነው

መልከ መልካም
ሲታይ መልካም የሆነ

ከሕዝቡም ሁሉ ይልቅ ከትከሻውና ከዚያም በላይ ቁመቱ ዘለግ ያለ ነበረ
በእስራኤል የነበሩ ሌሎች ረጃጅም ሰዎች ትከሻው ጋ አይደርሱም ነበር።

1 Samuel 9:3

አሁን
ጸሐፊው የታሪካዊ ዳራ መረጃ መስጠቱን ጨርሶ (1ሳሙኤል 9፡1-2) የታሪኩን አዲስ ዋና ክፍል ይጀምራል።

ተነሣና ሂድ
"እያደረግህ ያለውን አቁምና ሂድ'

ተራራማው የኤፍሬም አገር ... የሻሊሻ ምድር ... የሻዕሊ ምድር ... የብንያም ምድር
እነዚህ ሁሉ በእስራኤል ውስጥ ያሉ አካባቢዎች ናቸው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

አላገኙአቸውም ... አልነበሩም ... አላገኙአቸውምም
ሁሉም አህዮችን የሚያመልክቱ ናቸው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Samuel 9:5

የጹፍ ምድር
ይህ ከኢየሩሳሌም በስተሰሜን የሚገኝ በእስራኤል ውስጥ ያለ አካባቢ ነው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

የእግዚአብሔር ሰው
ይህ ሐረግ በአብዛኛው የእግዚአብሔር ነቢይ ማለት ነው። ይህንን በ1ሳሙኤል 2:27 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። አት፦ "ከእግዚአብሔር ቃል ሰምቶ የሚናገር ሰው'

በጉዟችን የትኛውን መንገድ መሄድ እንዳለብን
"አህዮቹን ለማግኘት የትኛውን መንገድ መሄድ አለብን?'

1 Samuel 9:7

ለሰውዬው ምን እናመጣለታለን
ሥጦታ መሥጠት ለእግዚአብሔር ሰው የአክብሮት ምልክት ነው።

የእግዚአብሔር ሰው
ይህ ሐረግ በአብዛኛው የእግዚአብሔር ነቢይ ማለት ነው። ይህንን በ1ሳሙኤል 2:27 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። አት፦ "ከእግዚአብሔር ቃል ሰምቶ የሚናገር ሰው'

የሰቅል ሩብ
"የሰቅል አንድ አራተኛ'። ሰቅል በብሉይ ኪዳን አገልግሎት ይሰጥ የነበረ የገንዘብ ዓይነት ነው። (የመጽሐፍ ቅዱስ ገንዘቦችና ክፍልፋዮች ተመልከት)

1 Samuel 9:9

ቀድሞ በእስራኤል ... ባለ ራእይ
ይህ በዕብራዊ ጸሐፊ የተጨመረ ባሕላዊ መረጃ ነው። ይህንን መረጃ በዚህ ስፍራ ማስቀመጥ በቋንቋህ የተለመደ ካልሆነ ወደ ቁጥር 11 መጨረሻ ሊወሰድ ይችላል። (ታሪካዊ ዳራ መረጃ ተመልከት)

ዛሬ ነቢይ የሚባለው ቀድሞ ባለ ራእይ ይባል ነበር
"ባለ ራእይ የሚለው ዛሬ ነቢይ ለሚባለው የጥንት መጠሪያ ነበር።'

1 Samuel 9:12

ሕዝቡ ዛሬ መሥዋዕት ያቀርባሉ
ይህ በመገናኛው ድንኳን መከናወን ያለበት የኃጢአት መሥዋዕት ሳይሆን፣ የበዓል ወይም የበኩራት መሥዋዕቶችን የሚመለክት ይመስላል።

1 Samuel 9:14

ወደ ኮረብታው መስገጃ መውጣት
ይህ ለእግዚአብሔር መሥዋዕትና ቁርባን ለማቅርብ ሕዝቡ ቅዱስ ቦታ ብለው የሰየሙት ስፍራ ነው። ጸሐፊው በከተማይቱ ዙሪያ ካለው ቅጥር ውጪ ይገኝ እንደ ነበር ይጽፋል።

1 Samuel 9:15

አጠቃላይ መረጃ
ጸሐፊው ታሪኩን መናገር ያቆምና አንባቢው በመቀጠል የሚሆነውን እንዲረዳ የታሪካዊ ዳራ መረጃ ይሰጣል። (ታሪካዊ ዳራ መረጃ ተመልከት)

ልዑል ይሆን ዘንድ ትቀባዋለህ
በዚህ ስፍራ ልዑል የሚለው ቃል ንጉሥ በሚለው ፈንታ ጥቅም ላይ ውሏል። የእስራኤል ንጉሥ እንዲሆን እግዚአብሔር የመረጠው ሰው ይህ ነው። (የማያስደስትን ቃል በሌላ ቃል መጠቀም ተመልከት)

የብንያም ምድር
"ከብንያም ነገድ የሆኑ ሰዎች የሚኖሩበት ምድር'

ከፍልስጥኤማውያን እጅ
በዚህ ስፍራ እጅ የሚለው ቃል ቁጥጥር ለሚለው ምትክ ቃል ነው። አት፦ "ከፍልስጥኤማውያን ቁጥጥር' ወይም "ከእንግዲህ ወዲያ ፍልስጥኤማውያን አይቆጣጠሩአቸውም'

ሕዝቤን በሐዘኔታ ተመልክቼአለሁና
"ሕዝቤ መከራ እያዩ ናቸው እኔም ልረዳቸው እፈልጋለሁ'

1 Samuel 9:17

እግዚአብሔር አለው
"እግዚአብሔር ሳሙኤልን አለው'

ባለ ራእዩ
"የእግዚአብሔር ነቢይ'

1 Samuel 9:20

የእስራኤል ምኞት ለማን ነው? ለአንተና ለአባትህ ቤት አይደለምን?
እነዚህ ጥያቄዎች ሳኦል እስራኤል የሚፈልጉት እግዚአብሔር ንጉሥ እንዲሆን የወደደው ሰው ለመሆኑ የጥልቅ መረዳት ማሳያ ናቸው። ጥያቄዎቹ በገላጭ አባባል ሊገለጹ ይችላሉ። አት፦ "የእስራኤል ምኞት ሁሉ ያረፈው በአንተ ላይ እንደሆነ ልታውቅ ይገባሃል። ዓይናቸውን በአንተና በአባትህ ቤት ላይ ጥለዋል።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄዎች ተመልከት)

እኔ ከእስራኤል ... ብንያማዊ አይደለሁምን? ከብኒያም ነገድ ... አይደለሁምን? እንዲህስ ያለውን ነገር ለምን ነገርኸኝ?
ብንያም በእስራኤል ትንሹ ነገድና ሌሎች እስራኤላውያን እንደማይጠቅም ነገድ የሚቆጥሩት ስለሆነ ሳኦል ግርምቱን እየገለጠ ነው። በተጨማሪም፣ ሳኦል አባል የሆነበትን ጎሳ ብንያማውያን እንደማይጠቅም ይቆጥሩት ነበር። እነዚህ ጥያቄዎች በገላጭ አባባል ሊተረጎሙ ይችላሉ። አት፦ እኔ ከነገዶች ሁሉ አስፈላጊነቱ የመጨረሻ ዝቅተኛ ከሆነው ከብንያም ነገድ ነኝ። ጎሳዬም በነገዳችን አስፈላጊነቱ የመጨረሻ ዝቅተኛ ጎሳ ነው። የእስራኤል ሕዝብ እኔንና ቤተሰቤን አስፈላጊ ነገር እንድናደርግ እንደሚፈለጉን ለምን እንደምትነግረኝ ልረዳ አልቻልኩም። (አሳብ ገላጭ ጥያቄዎች ተመልከት)

1 Samuel 9:22

አዳራሽ
መሥዋዕት በሚያቀርቡበት ስፍራ በአቅራቢያው ሰዎች በአንድነት የሚመገቡበት ትልቅ ሕንፃ እንደነበር አንባቢው እንደሚያውቅ ጸሐፊው ይገምታል።

ራስ ስፍራ
የክብር መቀመጫ

ሠላሣ ሰዎች
"30 ሰዎች' (ቁጥሮች ተመልከት)

1 Samuel 9:23

በእርሱ ላይ የነበረውን
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) ሳኦል ከስጋው ጋር ሊበላው የነበረ ሌላ ምግብ ወይም 2) የወይፈኑ ሌሎች ክፍሎች

ሳሙኤልም አለ
በመጀመሪያው ቋንቋ ተናጋሪው ማን እንደሆነ ግልጽ አይደለም። ወጥ ቤቱም ለሳኦል እየተናገረ ሊሆን ይችላል። አት፦ "ወጥ ቤቱም አለ'

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Samuel 9:25

በሰገነቱ ላይ
ይህ ለቤተሰብና ለእንግዶች ለመብላት፣ ለመጎብኘትና ለመተኛት የተለመደ ቦታ ነው። በምሽትና በሌሊት ከቤቱ ውስጠኛ ክፍል ይልቅ የመቀዝቀዝ ሁኔታ ይታይበታል።

ሳሙኤል ሳኦልን ከሰገነቱ ላይ ጠራና አለው
ሳኦል በሰገነቱ ላይ ያደርግ የነበረው ግልጽ ሊደረግ ይቻላል። አት፦ "ሳኦል በሰገነቱ ላይ ተኝቶ ሳለ፣ ሳሙኤል ጠራውና አለ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

1 Samuel 9:27

በፊታችን እንዲያለፍ "–ብላቴናውም አለፈ –' አንተ ቁም
እነዚህን ቃላት ሁሉ ሳሙኤል ተናግሮ ሊሆን ይችላል። አት፦ "ከፊታችን ይለፍ፣ ከፊታችንም ሲያለፍ፣ አንተ ቆይ'

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 10

1 ከዚያም ሳሙኤል የዘይቱን ጠርሙስ ወስዶ በሳኦል ራስ ላይ አፈሰሰው፤ ሳመውም። እርሱም እንዲህ አለው፥ "በርስቱ ላይ ገዢ እንድትሆን እግዚአብሔር
ቀብቶሃል፤ 2 ዛሬ ከእኔ ተለይተህ ስትሄድ፥ የብንያም ወሰን በሆነው በጼልጻህ፥ በራሔል መቃብር አጠገብ ሁለት ሰዎች ታገኛለህ። እነርሱም፥ 'ስትፈልጋቸው
የነበሩት አህዮች ተገኝተዋል። አሁን አባትህ ስለ አህዮቹ ማሰቡን ትቶ፥ "ስለ ልጄ ምን ባደርግ ይሻለኛል?" በማለት ተጨንቋል“ ይሉሃል። 3 ከዚያ አልፈህ
ትሄድና በታቦር ወደሚገኘው ወደ በሉጥ ዛፍ ትመጣለህ። ወደ ቤቴል፥ ወደ እግዚአብሔር የሚሄዱ አንደኛው ሦስት የፍየል ጠቦቶች ይዞ፥ ሌላኛው ሦስት ዳቦ
ተሸክሞ፥ ሌላኛው ደግሞ ወይን ጠጅ የተሞላ አንድ አቁማዳ ተሸክሞ ሦስት ሰዎች ይገናኙሃል። 4 ሰላምታ ከሰጡህ በኋላ ሁለት ዳቦ ይሰጡሃል፥ ከእጃቸውም
ትቀበላቸዋለህ። 5 ከዚህ በኋላ የፍልስጥኤም የጦር ሠፈር ወዳለበት ወደ እግዚአብሔር ኮረብታ ትመጣለህ። ወደ ከተማው በምትደርስበት ጊዜ፥ አንድ
የነቢያት ቡድን በፊታቸው መሰንቆ፥ ከበሮ፥ እምቢልታና በገና ይዘው ከተራራው ሲወርዱ ትገናኛቸዋለህ፤ እነርሱም ትንቢት ይናገራሉ። 6 የእግዚአብሔር መንፈስ
በኃይል ይመጣብሃል፥ አንተም ከእነርሱ ጋር ትንቢት ትናገራለህ፥ እንደ ሌላ ሰው ሆነህም ትለወጣለህ። 7 እነዚህ ምልክቶች በሚፈጸሙልህ ጊዜ፥ እግዚአብሔር
ከአንተ ጋር ነውና እጅህ ያገኘውን ሁሉ አድርግ። 8 ቀድመኸኝ ወደ ጌልገላ ውረድ። ከዚያም የሚቃጠለውን መባ ለማቅረብና የሰላሙን መባ ለመሠዋት ወደ
አንተ እወርዳለሁ። ወደ አንተ እስክመጣና ልታደርገው የሚገባህን እስከማሳይህ ድረስ ሰባት ቀን ቆይ።“ 9 ሳኦል ከሳሙኤል ተለይቶ ለመሄድ ፊቱን ባዞረ ጊዜ
እግዚአብሔር ሌላ ልብ ሰጠው። እነዚህ ምልክቶች ሁሉ በዚያው ቀን ተፈጸሙ። 10 እነርሱም ወደ ኮረብታው በመጡ ጊዜ፥ የነቢያት ቡድን ተገናኙት፥
የእግዚአብሔርም መንፈስ በኃይል መጣበት፥ ከእነርሱም ጋር ትንቢት ተናገረ። 11 ቀድሞ ያውቁት የነበሩት ሁሉ እርሱም ከነቢያት ጋር ትንቢት ሲናገር ባዩት ጊዜ፥
እርስ በእርሳቸው፥ “የቂስን ልጅ ምን ነካው? አሁን ሳኦል ከነቢያት አንዱ መሆኑ ነው?” ተባባሉ። 12 በዚያው ስፍራ የነበረ አንድ ሰው፥ “አባታቸው ማነው?”
ሲል መለሰ። በዚህ ምክንያት፥ “ሳኦልም ከነቢያት አንዱ ነው?” የሚል ምሳሌአዊ አባባል የተለመደ ሆነ። 13 ትንቢት መናገሩን በጨረሰ ጊዜ ወደ ተራራው ራስ
መጣ። 14 ከዚያም የሳኦል አጎት፥ እርሱንና አገልጋዩን፥ “የት ነበር የሄዳችሁት?” አላቸው። እርሱም፥ “አህዮቹን ለመፈለግ ነበር፤ ልናገኛቸው እንዳልቻልን ባየን
ጊዜ ወደ ሳሙኤል ሄድን” ብሎ መለሰለት። 15 የሳኦልም አጎት፥ “ሳሙኤል የነገረህን እባክህ ንገረኝ" አለው። 16 ሳኦልም አጎቱን፥ "አህዮቹ መገኘታቸውን
በግልጽ ነገረን" ብሎ መለሰለት። ሳሙኤል ነግሮት የነበረውን የንግሥና ጉዳይ ግን አልነገረውም። 17 ሳሙኤል ሕዝቡን በአንድነት በእግዚአብሔር ፊት ወደ
ምጽጳ ጠራቸው። 18 እርሱም የእስራኤልን ሕዝብ እንዲህ አላቸው፥”የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር የሚለው ይህንን ነው፥ 'እስራኤልን ከግብፅ አወጣሁት፥
ከግብፃውያን እጅና ካስጨነቋችሁ መንግሥታት ሁሉ እጅ አዳንኋችሁ'። 19 ነገር ግን ዛሬ እናንተ ከመከራና ከጭንቃችሁ ሁሉ የሚያድናችሁን አምላካችሁን
ተቃውማችኋል፤ እርሱንም፥ 'በላያችን ላይ ንጉሥ አንግሥልን' ብላችሁታል። አሁን በየነገዳችሁና በየጎሣችሁ ራሳችሁን በእግዚአብሔር ፊት አቅርቡ"። 20
ስለዚህ ሳሙኤል የእስራኤልን ነገዶች በሙሉ አቀረበ፥ የብንያም ነገድም ተመረጠ። 21 ከዚያም የብንያምን ነገድ በየጎሣቸው አቀረበ፤ የማጥሪ ጎሣም
ተመረጠ፤ የቂስ ልጅ ሳኦልም ተመረጠ። ነገር ግን በፈለጉት ጊዜ ሊያገኙት አልቻሉም። 22 ከዚያም ሕዝቡ”ገና የሚመጣ ሌላ ሰው አለ? “ በማለት
እግዚአብሔርን ተጨማሪ ጥያቄዎች ለመጠየቅ ፈለጉ። እግዚአብሔርም፥”ራሱን በዕቃዎቹ መካከል ደብቋል" በማለት መለሰላቸው። 23 ከዚያም ሮጠው ሄዱና
ሳኦልን ከዚያ አመጡት። በሕዝቡ መካከል በቆመ ጊዜ፥ ከሕዝቡ ሁሉ ይልቅ ቁመቱ ረጅም ነበር። 24 ሳሙኤልም ሕዝቡን፥ "እግዚአብሔር የመረጠውን ይህንን
ሰው ታዩታላችሁ? በሕዝቡ ሁሉ መካከል እንደ እርሱ ያለ የለም! “ አላቸው። ሕዝቡም ሁሉ፥”ንጉሥ ለዘላለም ይኑር! “ በማለት ጮኹ። 25 ከዚያም ሳሙኤል
የንግሥናን ደንብና ልማዶች ለሕዝቡ ነገራቸው፥ በመጽሐፍ ጽፎም በእግዚአብሔር ፊት አስቀመጣቸው። ከዚያም ሳሙኤል እያንዳንዱ ወደ ገዛ መኖሪያው
እንዲሄድ ሕዝቡን ሁሉ አሰናበተ። 26 ሳኦልም ደግሞ በጊብዓ ወደሚገኘው መኖሪያው ሄደ፥ እግዚአብሔር ልባቸውን የነካቸው አንዳንድ ኃያላን ሰዎችም ከእርሱ
ጋር ሄዱ። 27 አንዳንድ የማይረቡ ሰዎች ግን፥”ይህ ሰው ሊያድነን እንዴት ይችላል? “ አሉ። እነዚህ ሰዎች ሳኦልን ናቁት፥ ምንም ዓይነት ስጦታዎችንም
አላመጡለትም። ሳኦል ግን ዝም አለ።

---

1 Samuel 10:1

የዘይቱን ብርሌ ወስዶ በሳኦል ራስ ላይ አፈሰሰው
በእስራኤል ባሕል፣ አንድ ነቢይ በአንድ ሰው ራስ ላይ ዘይት ሲያፈስስ፣ ግለሰቡ ከእግዚአብሔር ዘንድ በረከት ይቀበላል።

ብርሌ
ከተጠበሰ የሸክላ አፈር የሚሠራ ትንሽ መያዣ

በርስቱ ላይ አለቃ ትሆን ዘንድ እግዚአብሔር አልቀባህምን?
ሳሙኤል ለጥያቄው የሚሰጠውን መልስ ያውቃል። በእስራኤል ላይ ንጉሥ ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር እንደመረጠው ሳኦልን እያሳሰበው ነው። አት፡- "በርስቱ ላይ አለቃ ትሆን ዘንድ እግዚአብሔር በእርግጥ ቀብቶሃል።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ጼልጻህ
ይህ የቦታ ስም ነው። (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)

የልጄን ነገር እንዴት አደርጋልሁ?
አሁን የሳኦል አባት ስለ ሳኦል መጨነቅ ጀመረ ሊያገኘውም ፈለገ።

1 Samuel 10:3

ታቦር
ይህ የቦታ ስም ነው። (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)

ከእጃቸው ተቀበል
እጆች ለግለሰቦች ተለዋጭ ስም ነው። "ከእነርሱ ውሰድ' ወይም "ተቀበል' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

1 Samuel 10:5

ከበሮ
የሚመታ የታምቡር ራስ የሚመስል ያለው እና ሲንቀጠቀጥ ድምጽ የሚሰጡ የብረት ቁራጮች በጎኑ ዙሪያ ያለው የሙዚቃ መሣሪያ ነው። (የማይታወቁትን መተርጎም ተመልከት)

የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል ይወርድብሃል
ይወርድባሃል የሚለው ቃል የእግዚአብሔር መንፈስ በሳኦል ላይ ተጽእኖ ያድርጋል ማለት ነው። በዚህ ስፍራ ሳኦልን እንዲተነብይና እንደ ሌላ ሰው እንዲከውን ያደርገዋል ማለት ነው። (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Samuel 10:7

እጅህ የምታገኘውን ሁሉ አድርግ
በዚህ ስፍራ ሳሙኤል ስለ ሳኦል እጆች ነገሮችን ለማግኘት እንደሚጥር ግለሰብ አድርጎ ይናገራል። አት፡- "ለማድረግ ትክክል እንደሆነ የምታስበውን ሁሉ አድርግ' (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየትን ተመልከት)

1 Samuel 10:9

እግዙአብሔር ሌላ ልብ ሰጠው
እግዚብአብሔር ሳኦልን ቀድሞ ያስብበት ከነበረበት መንገድ በተለየ መንገድ እንዲያስብ አስቻለው። (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል ወረደበት
ሳሙኤል የእግዚአብሔር መንፈስ ወደ ሳኦል እንደሚሮጥና እርሱንም ሙሉ ለሙሉ እንደሚቆጣጠር ግለሰብ አድርጎ ይናገራል። ይህንን በ1ሳሙኤል 10፡6 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። አት፡- "የእግዚአብሔር መንፈስ ሙሉ ለሙሉ ተቆጣጠረው' (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየትን ተመልከት)

1 Samuel 10:11

የቂስን ልጅ ያገኘው ምንድን ነው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ሕዝቡ መረጃ እየጠየቀ ነው 2) ሳኦል አስፈላጊ ሰው አይደለም የሚል ትርጉም ያለው አሳብ ገላጭ ጥያቄ ነው። አት፡- "ቂስ አስፈላጊ ሰው አይደለም፣ ልጁ ነቢይ ሆነ የሚለው እውነት ሊሆን አይችልም።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

የቂስ ልጅ
"ሳኦል የቂስ ልጅ'

አባታቸውስ ማን ነው
ይህ ሰው፣ ነቢይ መሆን የአንድ ሰው ወላጆች እነማን ከመሆናቸው ጋር የሚያያዝው ምንም ነገር እንደሌለ ሕዝቡን ለማሳሳብ አሳብ ገላጭ ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ ጥያቄ በገላጭ አባባል ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "የእነዚህ የሌሎቹ ነቢያት ወላጆች እነማን መሆናቸው አስፈላጊ ነገር አይደለም። ቁም ነገሩ፣ በሚያስገርም ሁኔታ፣ ሳኦል የእግዚአብሔርን መልእክት መናገሩ ነው።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄዎች ተመልከት)

ስለዚህም፡- "ሳኦል ደግሞ ከነቢያት ወገን ነውን?' የሚል አባባል ሆነ
ይህ በእስራኤላውያን መካከል ምሳሌ ሆነ። አንድ ሰው ከዚያ በፊት አድርጎት የማያውቀውን ነገር ሳይታሰብ አድርጉት ሲገኝ አድናቆትን ለመግለጽ ሰዎች በግልጽ ይህን ይላሉ። አት፡- "ሰዎች አንዳንድ ዘገባዎችን ማመን ባቃታቸው ጊዜ፣ ከዚያም የተነሳ፣ ለሳኦል ስለሆነው አሰቡና እንዲህ አሉ፣ ‘በውኑ ሳኦል ከነቢያት አንዱ ነውን?'' (ምሳሌዎችንና እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

1 Samuel 10:14

ከዚያም የሰኦል አጎት እንዲህ አለው
"ከዚያም የሳኦል የአባቱ ወንድም እንዲህ አለው'

የመንግሥቱን ነገር በሚመለከት አልነገረውም
"እግዚአብሔር የእስራኤል ንጉሥ እንዲሆን እንደሾመው ሳኦል ለአጎቱ አልነገረውም'

1 Samuel 10:17

እስራኤልን ከግብጽ አወጣሁ
እስራኤል የሚለው ስም ለእስራኤል ሕዝብ ምትክ ስም ነው። አት፡- "የእስራኤልን ሕዝብ ከግብጽ አወጣሁ' (ምትክ ቃል ተመልከት)

ዛሬ
ሳሙኤል ፀሐይ ለመጨረሻ ከጠለቀችበት አንስቶ ያለውን ጊዜ ብቻ ሳይሆን፣ እስራኤል እግዚአብሔርን መቃወም ከጀመሩበት አንስቶ ስላለው ጊዜ ይናገራል።

የግብጻውያን እጅ ... የመንግሥታት ሁሉ እጅ
እጅ የሚለው ቃል ለኃይል ምትክ ቃል ነው። አት፡- "የግብጻውያን ኃይል ... የመንግሥታት ሁሉ ኃይል'

ንጉሥ አንግሥልን
"የሚገዛንን ንጉሥ ስጠን'

በየነገዳችሁና በየወገናችሁ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ
"በየነገዳችሁና በየወገናችሁ በአንድ ተሰበሰቡና በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም ኑ'

1 Samuel 10:20

የብንያም ነገድ ተመረጠ ... የማጥሪን ወገን ተመረጠ ... የቂስ ልጅ ሳኦል ተመረጠ
ይህ በአድርጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊተረጎም ይችላል። እግዚአብሔር የመረጠውን ሕዝቡ ያወቀበት መንግድ ብሎ አለመተረጎም እጅግ የተሻለ ነው። አት፡- "እግዚአብሔር የብንያምን ነገደ መረጠ ... እግዚአብሔር የማጥሪንን ወገን መረጠ ... እግዚአብሔር የቂስን ልጅ ሳኦልን መረጠ' (አድርጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

1 Samuel 10:22

ከሕዝቡም ሁሉ ይልቅ ከትከሻውና ከዚያም በላይ ቁመቱ ዘለግ ያለ ነበረ
በእስራኤል የነበሩ ሌሎች ረጃጅም ሰዎች ትከሻው ጋ አይደርሱም ነበር። ይህን በ1ሳሙኤል 9፡2 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

1 Samuel 10:25

የንግሥና ወጎችና መመሪያዎች
ንግሥና የሚለው የነገር ስም በመጠሪያ ሐረግነት ሊተረጎም ይችላል። አት፡- "ንጉሥ ሊከተላቸው የሚያስፈልጉ ወጎችና መመሪያዎች' (የነገር ስም ተመልከት)

1 Samuel 10:26

እግዚአብሔር ልባቸውን የነካ
የእግዚአብሔር የሰውን ልብ መንካት የእግዚአብሔር በአእምሮአቸው ውስጥ አንድን ነገር ማስቀመጥ ወይም አንድን ነገር እንዲያደርጉ ማንቀሳቀስ የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፡- "እግዚአብሔር አስተሳሰባቸውን ስለቀየረ ከሳኦል ጋር ለመሄድ የፈለጉ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ይህ ሰው እንዴት ያድነናል?
ይህ ማሸሟጠጥን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የሚውል አሳብ ገላጭ ጥያቄ ነው። አት፡- "ይህ ሰው ሊያድነን ኃይል የለውም።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ናቁት
እጅግ አልወደዱትም ወይም ናቁት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 11

1 አሞናዊው ናዖስ ሄዶ ኢያቢስ ገለዓድን ከበባት። የኢያቢስ ሰዎች ሁሉ ናዖስን፥ "ከእኛ ጋር ቃል ኪዳን አድርግ፥ እኛም እናገለግልሃለን" አሉት። **2** አሞናዊው ናዖስም፥ "የሁላችሁንም ቀኝ ዐይኖቻችሁን በማውጣት በመላው እስራኤል ላይ ኃፍረትን አመጣለሁ፥ በዚህ ቅድመ ሁኔታ ከእናንተ ጋር ቃል ኪዳን አደርጋለሁ" ብሎ መለሰላቸው። **3** የኢያቢስ ሽማግሌዎችም፥ "ወደ እስራኤል ወገኖች ሁሉ መልዕክተኞችን እንድንልክ ለሰባት ቀናት ታገሰን። ከዚያም የሚያድነን አንድም ባይኖር ለአንተ እንገዛለን" በማለት መለሱለት። **4** መልዕክተኞቹም ሳኦል ወደሚኖርበት ወደ ጊብዓ መጥተው የሆነውን ነገር ለሕዝቡ ነገሯቸው። ሕዝቡም ሁሉ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው አለቀሱ። **5** በዚህ ጊዜ ሳኦል ከእርሻ በሬዎቹን እየነዳ መጣ። ሳኦልም፥ "ሕዝቡ ምን ሆኖ ነው የሚያለቅሰው?" አለ። እነርሱም የኢያቢስ ሰዎች ያሉትን ለሳኦል ነገሩት። **6** ሳኦል የነገሩትን በሰማ ጊዜ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል መጣበት፥ እጅግም ተቆጣ። **7** የበሬዎቹን ቀንበር ወስዶ ፈለጣቸውና ወደ እስራኤል ወሰኖች ሁሉ በመልዕክተኞች እጅ ላከው። እርሱም፥ "ሳኦልንና ሳሙኤልን ተከትሎ በማይመጣው ሁሉ በበሬዎቹ ላይ እንዲህ ይደረግበታል" አለ። ከዚያም ከእግዚአብሔር ታላቅ ፍርሃት በሕዝቡ ላይ ወደቀ፥ እንደ አንድ ሰው ሆነው ተሰብስበው መጡ። **8** ቤዜቅ በተባለ ስፍራ በሰበሰባቸው ጊዜ፥ የእስራኤል ሰዎች ሦስት መቶ ሺህ፥ የይሁዳም ሰዎች ሠላሳ ሺህ ነበሩ። **9** እነርሱም ለመጡት መልዕክተኞች፥ "ለኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች፥ 'ነገ ፀሐይ ሞቅ በሚልበት ሰዓት እንታደጋችኋለን' ብላችሁ ንገሯቸው" አሏቸው። መልዕክተኞቹ ሄደው ለኢያቢስ ሰዎች ነገሯቸው፥ እነርሱም እጅግ ደስ አላቸው። **10** ከዚያም የኢያቢስ ሰዎች ናዖስን፥"ነገ እንገዛልሃለን፥ አንተም ደስ የሚያሰኝህን ልታደርግብን ትችላለህ" አሉት። **11** በቀጣዩ ቀን ሳኦል ሕዝቡን በሦስት ቡድን ከፈላቸው። ሊነጋጋ ሲል ወደ ጦር ሠፈሩ መካከል መጡ፥ አሞናውያንንም አጠቁ፥ ቀኑ እስኪሞቅ ድረስም አሸነፏቸው። በሕይወት የተረፉትም ከእነርሱ ሁለቱ አንድ ላይ ሆነው እስከማይታዩ ድረስ ተበታተኑ። **12** በዚያን ጊዜ ሕዝቡ ሳሙኤልን፥ "'ሳኦል በእኛ ላይ እንዴት ይነግሣል?' ያለው ማን ነበር? እንድንገድላቸው ሰዎቹ ይምጡልን" አሉት። **13** ነገር ግን ሳኦል፥ "ዛሬ እግዚአብሔር እስራኤልን ታድጎታልና በዚህ ቀን ማንም መገደል የለበትም" አላቸው። **14** ሳሙኤልም ሕዝቡን፥ "ኑ፥ ወደ ጌልገላ እንሂድና በዚያ መንግሥቱን እናድስ" አላቸው። **15** ስለዚህ ሕዝቡ ሁሉ ወደ ጌልገላ ሄደው በእግዚአብሔር ፊት በጌልገላ ሳኦልን አነገሡት። በዚያም በእግዚአብሔር ፊት የሰላምን መባ ሠዉ፥ ሳኦልና የእስራኤል ሰዎችም ሁሉ እጅግ ደስ አላቸው።

---

1 Samuel 11:1

ናዖስ
ይህ ሰው የአብርሃም የወንድም ወይም የእኅት ልጅ የሎጥ ትውልድ የሆነ አሞናዊ ነው። (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)።

ኢያቢስ ገለዓድ
ይህ የቦታ ስም ነው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

አወጣለሁ
"ቆርጬ አወጣለሁ' ወይም "ጎትቼ አወጣለሁ'

ውርደት አመጣባችኋለሁ
"ውርደት አለብሳችኋለሁ' ወይም "አሳፋሪ ስም አለብሳችኋለሁ'

1 Samuel 11:3

ሰባት ቀናት
"7 ቀናት' (ቁጥሮች ተመልከት)

1 Samuel 11:4

ጊብዓ
ይህ የቦታ ስም ነው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

1 Samuel 11:6

የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል ወረደበት
ወረደበት የሚለው ቃል የእግዚአብሔር መንፈስ በሳኦል ላይ ተጽእኖ ያድርጋል ማለት ነው። በዚህ ሁኔታ እንደ ንጉሣቸው ሕዝቡ በፍርሃት እንዲያከብሩትና ሠራዊቱን እንዲቀላቀሉ እንዲያደርግ ሳኦልን አስችሎታል። 1ሳሙኤል 10:6ን እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ተከትሎ የማይወጣ
ናዖስንና አሞናውያንን ለመወጋት የእስራኤል ሰዎች ሁሉ እንዲመጡ ሳያል ጥሪ እያስተላለፈ ነበር።

ከዚያም የእግዚአብሔር ድንጋጤ በሕዝቡ ላይ ወደቀ
እንደ ንጉሣቸው ሳኦልን በፍርሃት እንዲያከብሩት እግዚአብሔር ሕዘቡን አስቻለ። በውጤቱም ሰዎቹ ከሳኦል ጋር በቤዜቅ በአንድነት ተሰበሰቡ።

ቤዜቅ
ይህ በኢያቢስ ገለዓድ አቅራቢያ የምትገኝ ከተማ ስም ነው። (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)

የእስራኤል ሰዎች ሦሥት መቶ ሺህ፣ የይሁዳም ሰዎች ሠላሣ ሺህ ነበሩ
"የእስራኤል ሰዎች 300,000፣ የይሁዳም ሰዎች 30,000 ነበሩ' (ቁጥሮች ተመልከት)

1 Samuel 11:9

መልእክተኞቹን አሉአቸው
"አሉአቸው' የሚለው ሳሙኤልንና ሳሙኤልን ያመለክታል።

ፀሐይ በሞቀች ጊዜ
"ከቀኑ እጅግ ሞቃት ከሆነው ክፍል በፊት' ወይም "ከቀትር በፊት'

ኢያቢስ ገለዓድ ... ኢያቢስ
እነዚህ የቦታዎች ስሞች ናቸው። በ1ሳሙኤል 11:1 እንዴት እንደተረጎምሃቸው ተመልከት።

ናዖስ
ይህ የንጉሥ ስም ነው። ይህንን ስም በ1ሳሙኤል 11:1 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

1 Samuel 11:11

በነጋውም
ይህ ከንጋት በፊት አብዛኛው ሕዝብ ገና በሰፈሩ ተኝቶ የነበረበት ጊዜ ነው።

1 Samuel 11:14

ሳኦልን በእግዚአብሔር ፊት አነገሡት
"እግዚአብሔር እያየ ሳኦልን አነገሡት'

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በዚያም በእግዚአብሔር ፊት የሰላም መሥዋእት አቀረቡ
ከአሮን ወይም ከሌዊ ቤት ባይሆንም እንኳን መሥዋዕት ማቅረብ የሳሙኤል
የእግዚአብሔር አገልግሎት ክፍል ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 12

1 ሳሙኤል እስራኤላውያንን በሙሉ እንዲህ አላቸው፥”የነገራችሁኝን በሙሉ ሰምቻችኋለሁ፥ ንጉሥንም በላያችሁ ላይ አንግሼላችኋለሁ። **2** አሁንም፥ በፊታችሁ የሚሄድላችሁ ንጉሥ ይኸውላችሁ፤ እኔ አርጅቻለሁ፥ ጸጉሬም ሸብቷል፤ ልጆቼም ከእናንተ ጋር ናቸው። ከልጅነቴ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በፊታችሁ ኖሬአለሁ። **3** ይኸው በፊታችሁ ነኝ፤ በእግዚአብሔርና እርሱ በቀባው ፊት መስክሩብኝ። የማንን በሬ ወስጃለሁ? የማንንስ አህያ ወስጃለሁ? ማንን አታለልሁ? በማንስ ላይ ግፍ ሠራሁ? ዓይኖቼን ለማሳወር ከማን እጅ ጉቦ ተቀበልሁ? መስክሩብኝና እመልስላችኋለሁ።“ **4** እነርሱም፥”አላታለልከንም፥ ግፍም አልሠራህብንም ወይም ከማንም እጅ ምንም ነገር አልሰረቅህም“ አሉ። **5** እርሱም፥”በእጄ ላይ ምንም እንዳላገኛችሁ ዛሬ እግዚአብሔር በእናንተ ላይ ምስክር ነው፥ እርሱ የቀባውም ምስክር ነው“ አላቸው። እነርሱም፥”እግዚአብሔር ምስክር ነው“ ብለው መለሱ። **6** ሳሙኤልም ሕዝቡን፥”ሙሴንና አሮንን የመረጣቸው፥ አባቶቻችሁንም ከግብፅ ምድር ያወጣቸው እግዚአብሔር ነው። **7** አሁን እንግዲህ፥ እግዚአብሔር ለእናንተና ለአባቶቻችሁ ስለ ሠራላችሁ የጽድቅ ሥራ ሁሉ እንድሟገታችሁ በእግዚአብሔር ፊት ራሳችሁን አቅርቡ። **8** ያዕቆብ ወደ ግብፅ በመጣ ጊዜ አባቶቻችሁ ወደ እግዚአብሔር ጮኹ። እግዚአብሔር፥ ከግብፅ ምድር እየመሩ አውጥተው በዚህ ስፍራ እንዲቀመጡ ያደረጓቸውን ሙሴንና አሮንን ላከ። **9** እነርሱ ግን አምላካቸውን እግዚአብሔርን ረሱ፤ እርሱም የሐጾር ሠራዊት አዛዥ በሆነው በሲሣራ እጅ፥ በፍልስጥኤማውያን እጅና በሞአብ ንጉሥ እጅ ሸጣቸው፤ እነዚህ ሁሉ አባቶቻችሁን ተዋጓቸው። **10** እነርሱም ወደ እግዚአብሔር በመጮህ፥ "እግዚአብሔርን ትተን በኣልንና አስታሮትን በማገልገላችን ኃጢአት አድርገናል። አሁን ግን ከጠላቶቻችን እጅ አድነን፥ እኛም እናገለግልሃለን' አሉት። **11** ስለዚህ እግዚአብሔር ይሩበኣልን፥ ባርቅን፥ ዮፍታሔንና ሳሙኤልን ልኮ በሰላም እንድትኖሩ በዙሪያችሁ ባሉ ጠላቶቻችሁ ሁሉ ላይ ድልን ሰጣችሁ። **12** እናንተም የአሞን ሕዝብ ንጉሥ ናዖስ እንደመጣባችሁ ባያችሁ ጊዜ፥ አምላካችሁ እግዚአብሔር ንጉሣችሁ ሆኖ እያለ፥ 'አይሆንም፥ ይልቁን በላያችን ላይ ንጉሥ መንገሥ አለበት' አላችሁኝ። **13** አሁንም እናንተ የመረጣችሁት፥ እንዲሆንላችሁ የጠየቃችሁትና እግዚአብሔርም በእናንተ ላይ ንጉሥ እንዲሆን የመረጠው ንጉሥ ይኸውላችሁ። **14** እናንተም እግዚአብሔርን ብትፈሩት፥ ብታገለግሉት፥ ድምፁንም ብትታዘዙና በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ላይ ባታምጹ ያን ጊዜ እናንተና በላያችሁ የሚገዛው ንጉሣችሁ የአምላካችሁ የእግዚአብሔር ተከታዮች ትሆናላችሁ። **15** የእግዚአብሔርን ድምፅ ባትታዘዙ፥ ነገር ግን በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ላይ ብታምጹ፥ ያን ጊዜ በአባቶቻችሁ ላይ እንደነበረ የእግዚአብሔር እጅ በእናንተ ላይ ይሆናል። **16** አሁንም፥ ራሳችሁን አቅርቡና እግዚአብሔር በዓይናችሁ ፊት የሚያደርገውን ይህንን ታላቅ ነገር ተመልከቱ። **17** ዛሬ የስንዴ መከር ነው አይደል? ነጎድጓድና ዝናብን እንዲልክ እግዚአብሔርን እጠራለሁ። ከዚያም ለራሳችሁ ንጉሥ በመጠየቃችሁ በእግዚአብሔር ፊት ያደረጋችሁት ክፋት ታላቅ እንደሆነ ታውቃላችሁ፥ ታያላችሁም“። **18** ስለዚህ ሳሙኤል እግዚአብሔርን ጠራ፤ በዚያው ቀን እግዚአብሔር ነጎድጓድንና ዝናብን ላከ። ሕዝቡም ሁሉ እግዚአብሔርንና ሳሙኤልን በጣም ፈሩ። **19** ከዚያም ሕዝቡ ሁሉ ሳሙኤልን፥ "እንዳንሞት፥ ስለ አገልጋዮችህ ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ጸልይ። ለራሳችን ንጉሥ በመጠየቃችን በኃጢአታችን ሁሉ ላይ ይህንን ክፋት ጨምረናልና” አሉት። **20** ሳሙኤል እንዲህ ሲል መለሰላቸው፥ “አትፍሩ። ይህንን ሁሉ ክፋት አድርጋችኋል፥ ነገር ግን እግዚአብሔርን በሙሉ ልባችሁ አገልግሉት እንጂ ከእግዚአብሔር ፊታችሁን አትመልሱ። **21** የማይጠቅሙ ናቸውና ሊረዷችሁ ወይም ሊረቧችሁ የማይችሉትን ከንቱ ነገሮች አትከተሉ። **22** እግዚአብሔር የራሱ ሕዝብ ሊያደርጋችሁ ስለ ወደደ፥ ስለ ታላቅ ስሙ ሲል ሕዝቡን አይጥላቸውም። **23** ስለ እናንተ መጸለይን በመተው በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን ማድረግ ከእኔ ይራቅ። ይልቁንም፥ መልካሙንና ትክክለኛውን መንገድ አስተምራችኋለሁ። **24** ብቻ እግዚአብሔርን ፍሩት፥ በሙሉ ልባችሁም በእውነት አገልግሉት። ያደረገላችሁን ታላላቅ ነገሮች አስቡ። **25** ክፉ በማድረግ ብትጸኑ ግን እናንተና ንጉሣችሁ ትጠፋላችሁ”።

---

1 Samuel 12:1

ንጉሡ በፊታችሁ ይሄዳል ... እኔም በፊታችሁ ሄድሁ
እነዚህ መግለጫዎች ሳሙኤልና ሳኦል የኖሩትን የሕይወት ዓይነት ሕዝቡ በተጨባጭ ማየት ችሏል ማለት ነው። አት፡- "የንጉሡ ሕይወት ታይቷል ... የእኔ ሕይወት ታይቷል' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

1 Samuel 12:3

በዚህ አለሁ፣በእግዚአብሔርና እርሱ በቀባው ፊት መስክሩብኝ
በዚህ ንግግሩ ሳሙኤል አንዳች ተገቢ ያልሆነ ነገር በማንም ላይ አድርጎ ከሆነ ሕዝቡ እንዲናገር እየሞገተ ነው። አት፡- "አሁን በፊታችሁ ቆሜያለሁ። ምንም ዓይነት ተገቢ ያልሆነ ነገር አድርጌ ከሆነ በእግዚአብሔርና በቀባው በንጉሡ ፊት እንድትናገሩ እጠይቃችኋለሁ።' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

የማንን በሬ ወሰድሁ? የማንንስ አህያ ወሰድሁ?
እንሰሳቶቻቸውን ያልሰረቀባቸውን ሰዎች ለማሳሳብ ሳሙኤል አሳብ ገላጭ ጥያቄ ይጠቀማል። አት፡- "እኔ ውድ የሆነ እንስሳ ፈጽሞ ከማንም አልሰረቅሁም' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ማንንስ ሸነገልሁ
ሁልጊዜ ታማኝ እንደ ነበር ለመናገር ሳሙኤል ሌላ አሳብ ገላጭ ጥያቄ ይጠቀማል። አት፡- "እኔ ማንንም አልታለልኩም ወይም ከማንም ጉቦ አልተቀበልሁም።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

መስክሩብኝ እኔም እመለሳለሁ
"ከእነዚህ ክፉ ነገሮች ማናቸውንም አድርጌ ከሆንሁ አሁን ተናገሩ፣ የወሰድኩትንም እመለሳለሁ። ማናኛውንም ስሕተት አስተካክላለሁ።'

1 Samuel 12:4

ከማንም እጅ ... በእጄ
እነዚህ ሃረጎች ግለሰቡ ምን ሃብት እንዳፈራ ወይም ከሌሎች ወሮታን ለማግኘት ምን እንዳደረገ የሚገልጽ ነው። አት፡- ይህ ምንም እንዳልሰረቀ፣ ወይም ጉቦ እንዳልሰጠና እንዳልተቀበለ የተናገረበት ጨዋ መንገድ ነው።

1 Samuel 12:6

የእግዚአብሔር የጽድቅ ሥራ ሁሉ
በመልካምነትና በዓላማ ለተሞላው፣ እግዚአብሔር ለእስራኤል ላደረገው ታሪክ ትኩረት እንዲሰጡ ሳሙኤል አየተጣራ ነው።

1 Samuel 12:8

ለሲሣራ ... ለፍልስጥኤማውያን ... ለሞአብ ንጉሥ እጅ
"ለሲሣራ ... ለፍልስጥኤማውያን ... ለሞአብ ንጉሥ ኃይል'

ያዕቆብ ... ሙሴ ... አሮን ... ሲሣራ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አዞር
ይህ የቦታ ስም ነው። (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)

ሸጣቸው
ይህ ባሮቻቸው እንዲሆኑ እግዚአብሔር ለጠላቶቻቸው አሳልፎ መስጠቱን የሚገልጽ ነው።

1 Samuel 12:10

ወደ እግዚአብሔር ጮኹ
(እነርሱ) የእስራኤልን ሕዝብ የሚያመለክት ነው

ይሩ ባአል
ይህ አንዳንዴ ይሩባአል በሚል ይተረጎማል። ይህ ሐሰተኛ አማልክትን ለመዋጋት የጻድቅ የክብርና የጥንካሬ ስም ነው።

እግዚአብሔር ላከ ... ድልም ሰጣችሁ
ሳሙኤል ከሕዝቡ የኃጢአት ኑዛዜና የእርዳታ ጥሪ በኋላ እግዚአብሔር ምን እንዳደረገላቸው ታሪኩን ይናገራል። (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ይሩ ባአል፣ ባርቅ፣ ዮፍታሔና ሳሙኤል
እነዚህ እግዚአብሔር ያስነሳቸው ጥቂት የመሳፍንት ስሞች ናቸው። ሳሙኤል ራሱን በዚህ ዝርዝር ውስጥ አካቷል። (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)

በአሊምንና አስታሮትን አገለገሉ
በዚህ ስፍራ ማገልገል ሐሰተኛ አማልክትን የማምለክን ተግባር ያመለክታል። አት፦ ሐሰተኛ አማልክትና ሴት አማልክትን አመለኩ (ምትክ ቃል ተመልከት)

የጠላቶቻችን እጅ
ይህ አረፍተ ነገር ኃይልን ለማመልከት "እጅ' የሚለውን ቃል ይጠቀማል። አት፦ "የጠላቶቻችን ኃይል ወይም የበላይነት' (ምትክ ቃል ተመልከት)

1 Samuel 12:12

እንዲህ አይሁን! ነገር ግን ንጉሥ ይንገሥልን
ይህ አረፍተ ነገር እግዚአብሔር ትናንትና ስላዳናቸው በእግዚአብሔር ስለመታመን በነገራቸው ጊዜ የእስራኤል ሕዝብ ሳሙኤልን በመቃወም ስላሰዩት ብርቱ ምላሽ ይናገራል።

የመረጣችሁትንና የጠየቃችሁትን
እነዚህ ሁለት ቃላት ሕዝቡ የፈለገው ንጉሥ ይህ ነው የሚል ተመሣሣይ ትርጉምና አጽንዖት አላቸው። (አጓዳኝነት ተመልከት)

1 Samuel 12:14

ብትፈሩ ... ብታገለግሉ ... ብትታዘዙ ... ባታምጹ
ይህ ምን ያህል አስፈላጊ እነደሆነ አጽንዖት ለመስጠት እነዚህ ተመሣሣይ ቃላት ጥቅም ላይ ውለዋል። (አጓዳኝነት ተመልከት)

በአባቶቻችሁ ላይ እንደሆነ፣ የእግዚአብሔር እጅ በእናንተ ላይ ትሆናለች
ይህ እጁ በእነርሱ ላይ እነደሆነች ሁሉ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚቀጣ ይናገራል። በዚህ ስፍራ "እጅ' የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ኃይልና የበላይነት ይወክላል። አት፦ "እግዚአብሔር አባቶቻችሁን እንደቀጣ ይቀጣችኋል' (ምትክ ቃል ተመልከት)

1 Samuel 12:16

በዓይኖቻችሁ ፊት
በዚህ ስፍራ "ዓይኖች' የሚለው ቃል የእስራኤልን ሕዝብ ይወክላል። አት፦ "የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ሊያይ በሚችልበት ግልጽ ስፍራ' (ተለዋጭ ቃል ተመልከት)

የስንዴ መከር ዛሬ አይደለምን?
ሳሙኤል የመከር ጊዜ እንደሆነ ያውቃል። በአብዛኛው በዚህ ጊዜ ዝናብ እንደማይዘንብ ስለዚህ የእግዚአብሔር ፍርድ በመሆኑ ዝናቡ መከራቸውን እንደሚያጠፋ ሕዝቡ እንዲያውቅ አጽንዖት ለመስጠት አሳብ ገላጭ ጥያቄ ይጠቀማል። አት፦ "የመከር ጊዜ ነው በአብዛኛውም በዚህ ጊዜ አይዘንብም' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ነጎድጓድና ዝናብ ይልካል
ሳሙኤል በመከር ጊዜ እህሉን የሚያጠፋ ከባድ ዝናብ በመላክ ንጉስ ስለመጠየቃቸው እግዚአብሔር እሥራኤልን እንዲቀጣ ይጠይቃል።

1 Samuel 12:19

እንዳንሞት
የኃጢአት የመጨረሻ ቅጣት ሞት ነው። እግዚአብሔር ይጨቁኗቸው የነበሩትን ሕዝቦች እንዳጠፋ የእስራኤል ሕዝብ አይቷል። እንደሌሎቹ ሕዝቦች "ለጥፋት እንዳይሰጡ' ተጨንቀው ነበር።

አትፍሩ
ሕዝቡ ክፉ አደረጉ እንዳያጠፋቸውም እግዚአብሔርን ፈሩ። አት፦ "ከዚህ ኃጢአት የተነሣ እግዚአብሔር ይቆጣል ያጠፋናልም ብላችሁ አትፍሩ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ከንቱ ነገርን ለመከተል ፈቀቅ አትበሉ
"ሐሰተኛ አማልክትን ማምለክ አትከታተሉ'

1 Samuel 12:22

ስለ ታላቅ ስሙ
በዚህ ስፍራ ስም የእግዚአብሔርን ክብር ያመላክታል። አት፦ "ስለዚህ ሕዝቡ እግዚአብሔርን በማክበርና በመፍራት ይኖራል።' (ምትክ ቃል ተመልከት)

ስለ እናንተ መጸለይን በመተው እግዚአብሔርን እበድል ዘንድ ይህ ከእኔ ይራቅ
ሳሙኤል በጸለየ ጊዜ እግዚአብሔር ከላከው ዝናብና ነጎድጓድ የተነሣ ሕዝቡ በፍርሃት ተሞላ። አንዳንድ ሰዎች ሳሙኤል ጸሎቱን እነርሱን ለመጉዳት ሊጠቀምበት እንደሚችል ሳያምኑ አልቀሩም። (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 13

1 ሳኦል መንገሥ በጀመረ ጊዜ ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ነበር፤ በእስራኤል ላይ አርባ ዓመት በነገሠ ጊዜ፥ **2** ከእስራኤል ሦስት ሺህ ሰዎች መረጠ። አንዱ ሺህ ከዮናታን ጋር በብንያም ጊብዓ ሲሆኑ ሁለቱ ሺህ በኮረብታማው አገር በቤቴልና በማክማስ ከእርሱ ጋር ነበሩ። የቀሩትን ወታደሮች ወደየቤታቸው፥ እያንዳንዱንም ወደ ድንኳኑ አሰናበታቸው። **3** ዮናታን በጊብዓ የነበረውን የፍልስጥኤማውያን ጦር ድል አደረገ፥ ፍልስጥኤማውያንም ይህንን ሰሙ። ከዚያም ሳኦል፥ “ዕብራውያን ይስሙ” በማለት በምድሪቱ ሁሉ ላይ መለከት አስነፋ። **4** ሳኦል የፍልስጥኤማውያንን ጦር እንዳሸነፈ፥ ደግሞም እስራኤላውያን በፍልስጥኤማውያን እንደ ግም መቆጠራቸውን እስራኤላውያን በሙሉ ሰሙ። ከዚያም ወታደሮቹ በጌልገላ ሳኦልን ለመከተል በአንድ ላይ ተሰበሰቡ። **5** ፍልስጥኤማውያንም ከእስራኤል ጋር ለመዋጋት በአንድ ላይ ተሰበሰቡ፤ ሦስት ሺህ ሠረገሎች፥ ስድስት ሺህ ሠረገላ ነጂዎችና የሠራዊቱም ቁጥር በባህር ዳርቻ እንዳለ አሸዋ ነበሩ። እነርሱም መጥተው ከቤትአዌን በስተምሥራቅ ማክማስ ላይ ሰፈሩ። **6** የእስራኤል ሰዎች ችግር ውስጥ መግባታቸውንና ሕዝቡም መጨነቁን ባዩ ጊዜ፥ ሕዝቡ በዋሻዎች፥ በየቁጥቋጦ ሥር፥ በዐለቶች፥ በገደሎችና በጉድጓዶች ውስጥ ተደበቁ። **7** አንዳንድ ዕብራውያንም የዮርዳኖስን ወንዝ በመሻገር ወደ ጋድና ገለዓድ ምድር ሄዱ። ሳኦል ግን ገና በጌልገላ ነበር፥ የተከተለው ሕዝብ በሙሉ በፍርሃት ይንቀጠቀጥ ነበር። **8** እርሱም ሳሙኤል በሰጠው ቀጠሮ መሠረት ሰባት ቀን ቆየ። ነገር ግን ሳሙኤል ወደ ጌልገላ አልመጣም ነበር፥ ሕዝቡም ከሳኦል ተለይቶ መበታተን ጀምሮ ነበር። **9** ሳኦልም፥ "የሚቃጠለውን መባና የሰላሙን መባዎች አምጡልኝ" አለ። ከዚያም የሚቃጠለውን መባ አቀረበ። **10** የሚቃጠለውን መባ ማቅረቡን እንደ ጨረሰ ሳሙኤል ወደዚያ ደረሰ። ሳኦልም ሊገናኘውና ሰላምታ ሊሰጠው ሄደ። **11** ከዚያም ሳሙኤል፥ "ያደረግከው ምንድነው?" አለው። ሳኦልም፥ "ሕዝቡ ትተውኝ እየሄዱ እንዳሉ፥ አንተም በቀጠሮው ሰዓት አለመምጣትህን፥ ፍልስጥኤማውያንም በማክማስ መሰብሰባቸውን ባየሁ ጊዜ፥ **12** 'አሁን ፍልስጥኤማውያን ወደ ጌልገላ በእኔ ላይ ሊወርዱብኝ ነው፥ እኔም የእግዚአብሔርን ሞገስ አልለመንኩም' ብዬ አሰብኩኝ። ስለዚህ የሚቃጠለውን መሥዋዕት ለማቅረብ ግድ ሆነብኝ“ ብሎ መለሰለት። **13** ሳሙኤልም ሳኦልን፥”ያደረግከው ስንፍና ነው። አምላክህ እግዚአብሔር የሰጠህን ትዕዛዝ አልጠበቅክም። በዚህ ቀን እግዚአብሔር መንግሥትህን በእስራኤል ላይ ለዘላለም ሊያጸናልህ ነበር። **14** አሁን ግን አገዛዝህ አይቀጥልም። እግዚአብሔር ያዘዘህን አልታዘዝክምና እርሱ እንደ ልቡ የሚሆንለትን ሰው ፈልጓል፥ እግዚአብሔርም በሕዝቡ ላይ መስፍን እንዲሆን መርጦታል" አለው። **15** ከዚያም ሳሙኤል ከጌልገላ ተነሥቶ ወደ ብንያም ጊብዓ ወጣ። ሳኦል ከእርሱ ጋር የነበሩትን ሰዎች ቆጠራቸው፥ ስድስት መቶ የሚያክሉ ነበሩ። **16** ሳኦል፥ ልጁ ዮናታንና ከእነርሱ ጋር የነበሩት ሰዎች በብንያም ጊብዓ ቆዩ። ፍልስጥኤማውያን ግን በማክማስ ሰፍረው ነበር። **17** ከፍልስጥኤም ጦር ሰፈር ወራሪዎች በሦስት ቡድን ተከፍለው መጡ። አንደኛው ቡድን ወደ ሦጋል ምድር ወደ ዖፍራ ታጠፈ። **18** ሌላኛው ቡድን በቤትሖሮን አቅጣጫ ታጠፈ፥ ሌላኛውም ቡድን በምድረ በዳው አቅጣጫ ወደ ስቦይም ሸለቆ ቁልቁል ወደሚያሳየው ወሰን ዞረ። **19** ፍልስጥኤማውያን፥ “ዕብራውያን ለራሳቸው ሰይፍ ወይም ጦር እንዳይሠሩ" ብለው ስለነበረ፥ በመላው እስራኤል ብረት ሠሪ አልተገኘም። **20** ነገር ግን የእስራኤል ወንዶች ሁሉ፥ እያንዳንዱ የማረሻውን ጫፍ፥ ዶማውን፥ ጠገራውንና ማጭዱን ለማሳል ወደ ፍልስጥኤማውያን ይወርድ ነበር። **21** የክፍያው ዋጋ ለማረሻው ጫፍና ለዶማው የሰቅል ሁለት ሦስተኛ፥ ጠገራ ለማሳልና መውጊያውን ለማቃናት የሰቅል አንድ ሦስተኛ ነበር። **22** ስለዚህ በጦርነቱ ቀን ሰይፍና ጦር በሳኦልና በዮናታን እጅ ብቻ እንጂ ከእነርሱ ጋር ከነበሩት ወታደሮች በአንዱም እጅ ሰይፍ ወይም ጦር አልነበረም። **23** የፍልስጥኤማውያን ሠራዊት ወደ ማክማስ መተላለፊያ ወጣ።

---

1 Samuel 13:1

አጠቃላይ መረጃ
ሳሙኤል በጌልጌላ የሳኦልን መንግሥት አደሰለት ሳሙኤልም ጌታን እንዲከተሉ ሕዝቡን አሳሰበ።

ሳኦል ሠላሣ ሁለት ዓመቱ ነበር ... በእስራኤልም ላይ
በጥንት ቅጂዎች የዚህ ጥቅስ ጽሑፍ የተጎዳ ይመስላል፣ ስለዚህ የዘመናችን እትሞች የተለያዩ ትርጉሞችን ይዘዋል። ሁሉም ሊሆን የሚችለውን የተሻለውን የመጀመሪያውን ጽሑፍ ትርጉም ለማቅረብ ጥረት አድርገዋል።

ሦሥት ሺህ ሰዎች መረጠ
"3,000 ሰዎች መረጠ' (ቁጥሮች ተመልከት)

ሁለት ሺህ ሰዎች ከእርሱ ጋር ነበሩ
"2,000 ሰዎች ከእርሱ ጋር ነበር' (ቁጥሮች ተመልከት)

ማክማስ
የከተማ ስም ነው (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)

የብንያም ጊብዓ
ጊብዓ ከተማ ነው። ይህንን በ1ሳሙኤል 10:26 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

የቀሩትን ወታደሮች ወደ ቤት ሰደዳቸው
"የቀሩትን ወታደሮች ቤት ሰደዳቸው'

1 Samuel 13:3

የፍልስጥኤማውያን ጭፍራ
"የፍልስጥኤማውያን የጦር ሰፈር'

ናሲብ
ይህ የፍልስጥኤም ጭፍራ የሰፈረበት የከተማ ስም ነው። (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)

ሳኦል እንዳሸነፈ እስራኤላውያን ሁሉ ሰሙ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) ዮናታን ለፈጸመው ጥቃት ሳኦል ኃላፊነቱን እየወሰደ ነበር ወይም 2) ዮናታን በፈጸመው ጥቃት የተገኘውን ድል ሳኦል እየወሰደ ነበር

እስራኤል ለፍልስጥኤም እንደ ብስባሽ ሽታ ሆነች
ፍልስጥኤማውያን ለእስራኤል ያላቸው ጥላቻ እስራኤላውያን ፍልስጥኤማውያንን የሚረብሽ መጥፎ ሽታ እንደሆኑ ተደርጎ ተገለጸአል። አት፦ "ፍልስጥኤማውያን እስራኤላውያንን ጠሉአቸው' (ዘይቤአዊ አነጋገር ተመልከት)

ወታደሮቹ ሳኦልን ለመከተል ወደ ጌልጌላ ተሰበሰቡ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ ሳኦል ወታደሮቹ እንዲከተሉት በጌልጌላ እንዲሰበሰቡ ጠራቸው (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Samuel 13:5

ሦሥት ሺህ ... ስድስት ሺህ
"3000 ... 6000' (ቁጥሮች ተመልከት)

ወታደሮቹ በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ ብዙ ነበሩ
ለመቁጠር እስከሚያስቸግር ድረስ የወታደሮቹ ስብስብ ታላቅ ነበር የሚል ግነት ነው። (ግነትና አጠቃላይነት ተመልከት)

ማክማስ
ይህ የቦታ ስም ነው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

ቤትአዌን
ይህ የቦታ ስም ነው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

1 Samuel 13:6

አጠቃላይ መረጃ
ፍልስጥኤማውያን እስራኤልን ለመዋጋት በአንድነት ተሰበሰቡ።

ሕዝቡ
ይህ ሐረግ የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል።

ሕዝቡ ታውኮ ነበር
"ሕዝቡ በጣም ተጨንቆ ነበር'

ተንቀጥቅጠው ተከተሉት
ሕዝቡ በጣም ፈርተው ነበር

1 Samuel 13:8

ሳሙኤል በቀጠረው ቀን
"እንደሚመጣ ሳሙኤል በነገራቸው ጊዜ መሠረት'

ሕዝቡ ከሳኦል ተለይተው ተበታተኑ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ሕዝቡ ሳኦልን ትቶ መሄድ ጀመረ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ)

ከዚያም የሚቃጠል መሥዋዕት አቀረበ
የሚቃጠል መሥዋዕትን ለእግዚአብሔር ማቅረብ የተፈቀደው ለአሮን ወገን ብቻ ነበር

1 Samuel 13:11

ያደረግኸው ምንድር ነው?
በእውነቱ ሳሙኤል እየጠየቀ ሳይሆን ሳኦልን እየገሰጸው ነበር። ትክክል ባይሆኑም እንኳን ሳኦል ለድርጊቶቹ ሊከላከል ፈለገ። (አሳብ ገላጭ ጥያቄዎች ተመልከት)

ማክማስ
ማክማስ የቦታ ስም ነው። ይህንን በ1ሳሙኤል 13:2 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

1 Samuel 13:13

የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አልጠበቅህም
ሳሙኤል እስኪመጣና ለእግዚብሔር የሚቃጠል መሥዋዕት እስኪሰዋ ድረስ ሳኦል መጠበቅ ነበረበት። እርሱ ራሱ መሠዋት አልነበረበትም።

መንግሥትህን አጽንቶልህ ነበር
"መንግሥትህን አቁሞልህ ነበር' ወይም "መንግሥትህን አውቆልህ ነበር' ወይም "መንግሥትህን መርጦ ነበር'

መንግሥትህ አይቀጥልም
ይህ በአዎንታዊ መንገድ የቀረበ ምፀት ነው። አት፡- "መንግሥትህ በቅርቡ ያከትማል' (ምፀት ተመልከት)

እንደ ልቡ የሆነ ሰው
በዚህ ስፍራ ልብ የእግዚአብሔርን ፍላጎትና ፈቃድ ይወክላል። "እንደ ልቡ የሆነ ሰው' የሚለው ሐረግ እግዚአብሔር የሚፈልገውን የሚያደርግ ሰው የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፡- "ይፈልገው የነበረ ዓይነት ሰው' ወይም "የሚታዘዘው ሰው' (ምትክ ቃልና ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

1 Samuel 13:15

ሳሙኤል ተነሣና ሄደ
"ሳሙኤል ትቶ ሄደ' ለሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ነው። (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ከጌልጌላ ተነስቶ ሄደ
ጌልጌላ ከተማ ነው። ይህንን በ1ሳሙኤል 7፡15 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

የብንያም ጊብዓ
ጊብዓ ከተማ ነው። ይህንን በ1ሳሙኤል 10፡26 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ስድስት መቶ ሰዎች
"600 ሰዎች' (ቁጥሮች ተመልከት)

የብንያም ጊብዓ
ጊብዓ ከተማ ነው። ይህንን በ1ሳሙኤል 13፡03 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ፍልስጥኤማውያን በማክማስ ሰፈሩ
ማክማስ የቦታ ስም ነው። ይህንን በ1ሳሙኤል 13፡02 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

1 Samuel 13:17

አደጋ ጣዮች መጡ
አደጋ ጣዮች በአብዛኛው ለምግባቸውና ሌሎች ቁሳ ቁሶች በጠላት መንደር ላይ ጥቃት የሚያደርሱ የጦር ሰዎች ናቸው።

ዖፍራ ... ሦጋል ምድር ... ቤትሐሮን ... ስቦይም ሸለቆ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

1 Samuel 13:22

አጠቃላይ መረጃ
ታሪኩ ይቀጥላል።

ሰይፍና ጦር አልነበረም
ይህ ለምን የሳኦል ሠራዊት እንደፈሩ በከፊል ያሳያል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 14

1 አንድ ቀን የሳኦል ልጅ ዮናታን ወጣቱን ጋሻ ጃግሬውን፥"ና፥ በፍልስጥኤማውያን ሠራዊት ላይ በሌላ አቅጣጫ እንሂድባቸው“ አለው። ለአባቱ ግን
አልነገረውም። 2 ሳኦል መጌዶን በሚባል በጊብዓ ዳርቻ በሮማኑ ዛፍ ሥር ሰፍሮ ነበር። 3 እርሱም በሴሎ የእግዚአብሔር ካህን የነበረው የዔሊ ልጅ፥ የፊንሐስ
ልጅ፥ የኢካቦድ ወንድም የአኪጦብ ልጅ የሆነው፥ ኤፉድ ይለብስ የነበረውን አኪያን ጨምሮ ስድስት መቶ ያህል ሰዎች ከእርሱ ጋር ነበሩ። ዮናታን መሄዱን ሕዝቡ
አላወቀም ነበር። 4 ዮናታን ወደ ፍልስጥኤማውያኑ ጦር ሰፈር አቋርጦ ለመሄድ ባሰበባቸው በመተላለፊያዎቹ መካከል በግራና በቀኙ በኩል ሾጣጣ ድንጋዮች
ነበሩ። የአንደኛው ሾጣጣ ድንጋይ ስም ቦጼጽ ሲሆን የሁለተኛው ስም ሴኔ ነበር። 5 አንደኛው ቀጥ ያለው ድንጋይ የቆመው በስተሰሜን በሚክማስ ፊት ለፊት
ሲሆን ሌላኛው በጊብዓ ፊት ለፊት በስተደቡብ ነበር። 6 ዮናታንም ወጣት ጋሻ ጃግሬውን፥ "ና፥ ወደእነዚህ ወዳልተገረዙት ጦር ሰፈር እንሻገር። እግዚአብሔር
በብዙ ወይም በጥቂት ሰዎች ከማዳን ሊከለክለው የሚችል ነገር የለምና፥ ምናልባት እግዚአብሔር ይሠራልን ይሆናል" አለው። 7 ጋሻ ጃግሬውም፥ "በልብህ
ያለውን ሁሉ አድርግ። ወደፊት ቀጥል፥ ተመልከት፥ የምታዝዘኝን ሁሉ ለመፈጸም ከአንተ ጋር ነኝ" ብሎ መለሰለት። 8 ከዚያም ዮናታን እንዲህ አለው፥ "ወደ
እነርሱ ተሻግረን እንታያቸዋለን። 9 እነርሱም፥ 'ወደ እናንተ እስክንመጣ እዚያው ቆዩ' ካሉን በስፍራችን እንቆያለን፥ ወደ እነርሱም አንሻገርም። 10 ነገር ግን፥ 'ወደ
እኛ ውጡ' ብለው ቢመልሱልን እግዚአብሔር በእጃችን አሳልፎ ሰጥቶናልና ወደ እነርሱ እንሻገራለን።” 11 ስለዚህ ሁለቱም ራሳቸውን ለፍልስጥኤማውያን ጦር
ገለጡ። ፍልስጥኤማውያኑም፥ “ተመልከቱ፥ ዕብራውያኑ ከተደበቁባቸው ጉድጓዶች ወጥተው እየመጡ ነው" ተባባሉ። 12 ከዚያም የጦር ሰፈሩ ሰዎች ወደ
ዮናታንና ጋሻ ጃግሬው በመጣራት፥”ወደ እኛ ውጡ፥ አንድ ነገርም እናሳያችኋለን" አሏቸው። ዮናታን ጋሻ ጃግሬውን፥ “እግዚአብሔር በእስራኤል እጅ አሳልፎ
ሰጥቷቸዋልና ተከተለኝ" አለው። 13 ዮናታን በእጁና በእግሩ ተንጠላጥሎ ወጣ፥ ጋሻ ጃግሬውም ከኋላው ተከተለው። ፍልስጥኤማውያኑ በዮናታን ተገደሉ፥ ጋሻ
ጃግሬውም ከኋላው ተከትሎ ጥቂቶቹን ገደለ። 14 ዮናታንና ጋሻ ጃግሬው በፈጸሙት በዚያ የመጀመሪያ ጥቃት አንድ ጥማድ በሬ ሊያርሰው በሚችለው የመሬት
ስፋት ላይ ሃያ ያህል ሰዎችን ገደሉ። 15 በጦር ሰፈሩ፥ በእርሻውና በሕዝቡ መካከል ሽብር ሆነ። የጦር ሰፈሩና ወራሪዎቹም እንኳን ተሸበሩ። ምድሪቱ
ተንቀጠቀጠች፥ ታላቅ ሽብርም ሆነ። 16 በብንያም ጊብዓ የነበሩ የሳኦል ጠባቂዎች፥ የፍልስጥኤም ወታደሮች ሲበተኑና ወዲያና ወዲህ ሲራወጡ ተመለከቱ።
17 ከዚያም ሳኦል ከእርሱ ጋር ለነበሩት ሰዎች፥”ቁጠሩና ከእኛ የጎደለ ማን እንደሆነ ዕወቁ“ አላቸው። በቆጠሩ ጊዜም ዮናታንና ጋሻ ጃግሬው ታጡ። 18
ሳኦልም አኪያን፥ "የእግዚአብሔርን ኤፉድ ወደዚህ አምጣው" አለው። በዚያ ቀን አኪያ ኤፉድ ለብሶ ከእስራኤል ወታደሮች ጋር ነበር። 19 ሳኦል ከካህኑ ጋር
በመነጋገር ላይ እያለ በፍልስጥኤማውያን የጦር ሰፈር የነበረው ሁከት መጨመሩን ቀጠለ። ሳኦልም ካህኑን፥ "እጅህን መልስ" አለው። 20 ሳኦልና ከእርሱ ጋር
የነበሩት ሰዎች ሁሉ በሩጫ ወደ ጦርነቱ ሄዱ። የእያንዳንዱ ፍልስጥኤማዊ ሰይፍ በራሱ ዜጋ ላይ ነበር፥ ታላቅ ግራ መጋባት ውስጥ ነበሩ። 21 ቀድሞ
ከፍልስጥኤማውያን ጋር የነበሩና አብረዋቸው ወደ ጦር ሰፈሩ የገቡት ዕብራውያን እነርሱም እንኳን አሁን ከሳኦልና ከዮናታን ጋር ከነበሩት እስራኤላውያን ጋር
ተባበሩ። 22 በኤፍሬም አቅራቢያ በኮረብታዎቹ ውስጥ የተደበቁ የእስራኤል ሰዎች ሁሉ ፍልስጥኤማውያን መሸሻቸውን በሰሙ ጊዜ እነርሱም እንኳን ለውጊያ
በኋላቸው አሳደዷቸው። 23 ስለዚህ እግዚአብሔር በዚያን ቀን እስራኤልን አዳነ፥ ውጊያውም ቤትአዌንን አልፎ ሄደ። 24 ሳኦል፥”ጠላቶቼን እስከምበቀልበት
እስከ ምሽት ድረስ የትኛውንም ዓይነት መብል የሚበላ ቢኖር የተረገመ ይሁን“ ብሎ ሕዝቡን አምሎ ስለነበረ በዚያን ቀን የእስራኤል ሰዎች ተጨነቁ። ስለዚህ
ከሠራዊቱ አንዱም ምግብ አልቀመሰም። 25 ከዚያም ሕዝቡ ሁሉ ወደ ጫካ ውስጥ ገባ፥ ማርም በምድሩ ላይ ነበር። 26 ሕዝቡ ወደ ጫካ በገባ ጊዜ ማሩ
ይፈስስ ነበር፥ ነገር ግን ሕዝቡ መሓላውን ስለፈራ በእጁ ጠቅሶ ወደ አፉ ያደረገ አንድም አልነበረም። 27 ዮናታን ግን አባቱ ሕዝቡን በመሓላ ማሰሩን አልሰማም
ነበር። በእጁ ላይ የነበረውን በትር ጫፉን በማሩ እንጀራ ውስጥ አጠቀሰው። እጁን አንሥቶ ወደ አፉ አደረገው፥ ዐይኖቹም በሩለት። 28 ከዚያም ከሰዎቹ
አንዱ፥”ሕዝቡ በረሃብ ቢደክምም እንኳን አባትህ፥ 'በዚህ ቀን ምግብ የሚበላ የተረገመ ይሁን' ብሎ ሕዝቡን ከመሓላ ጋር አጥብቆ አዝዞአል" ብሎ መለሰለት።
29 ከዚያም ዮናታን፥ "አባቴ በምድሪቱ ላይ ችግር ፈጥሯል። ከዚህ ማር ጥቂት በመቅመሴ ዐይኖቼ እንዴት እንደበሩ ተመልከቱ። 30 ሕዝቡ ከጠላቶቻቸው
ከበዘበዙት ላይ ዛሬ በነጻነት በልተው ቢሆን ኖሮ ምንኛ በተሻለ ነበር? ምክንያቱም አሁን በፍልስጥኤማውያን መካከል የተገደሉት ያን ያህል ብዙ አይደሉም“
አለ። 31 እነርሱም በዚያን ቀን ፍልስጥኤማውያንን ከሚክማስ ጀምሮ እስከ ኤሎን ድረስ መቱአቸው። ሕዝቡም እጅግ ደከሙ። 32 ሕዝቡም ተስገብግበው ወደ
ብዝበዛው ተጣደፉ፥ በጎችን፥ በሬዎችንና ጥጆችንም በመሬት ላይ አረዱ። ሕዝቡም ከነደሙ በሉ። 33 ከዚያም ለሳኦል፥ "ተመልከት፥ ሕዝቡ ከነደሙ
በመብላታቸው በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት በመሥራት ላይ ናቸው" አሉት። ሳኦልም፥ "ተላልፋችኋል፥ አሁንም ትልቅ ድንጋይ አንከባልላችሁ አምጡልኝ“ አለ።
34 በመቀጠልም፥ "ወደ ሕዝቡ ሂዱና፥ 'እያንዳንዱ ሰው በሬውንና በጉን እዚህ አምጥቶ በማረድ ይብላ። ከነደሙ በመብላት በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን
አታድርጉ' ብላችሁ ንገሯቸው" አለ። ስለዚህ በዚያ ምሽት እያንዳንዱ በሬውን እያመጣ በዚያ ዐረደው። 35 ሳኦል ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሠራ፥ ይኸውም
ለእግዚአብሔር የሠራው የመጀመሪያው መሠዊያ ነበር። 36 ከዚያም ሳኦል፥ "ሌሊቱን ፍልስጥኤማውያንን እናሳድ፥ እስኪነጋም ድረስ ሀብታቸውን እንበዝብዝ፤
ከእነርሱም አንድ በሕይወት አናስቀር“ አለ። እነርሱም፥”መልካም መስሎ የታየህን ሁሉ አድርግ“ ብለው መለሱለት። ካህኑ ግን፥”እዚሁ እግዚአብሔርን
እንጠይቅ“ አለ። 37 ሳኦልም እግዚአብሔርን እንዲህ ሲል ጠየቀ፥”ፍልስጥኤማውያንን ላሳድዳቸው? በእስራኤል እጅ አሳልፈህ ትሰጣቸዋለህ? “። ነገር ግን
በዚያን ቀን እግዚአብሔር አልመለሰለትም። 38 ከዚያም ሳኦል፥”የሕዝቡ አለቆች የሆናችሁ ሁሉ ወደዚህ ቅረቡ፤ ዛሬ ይህ ኃጢአት እንዴት እንደመጣብን
መርምሩና ዕወቁ። 39 እስራኤልን ያዳነ ሕያው እግዚአብሔርን! ልጄ ዮናታን ቢሆን እንኳን በእርግጥ እርሱ ይሞታል" አለ። ነገር ግን ከሕዝቡ ሁሉ አንዱም
እንኳን አልመለሰለትም። 40 እርሱም እስራኤልን በሙሉ፥ “እናንተ በአንድ በኩል ቁሙ፥ እኔና ልጄ ዮናታን በሌላው በኩል እንቆማለን” አላቸው። ሕዝቡም
ሳኦልን፥ “መልካም መስሎ የታየህን አድርግ” አሉት። 41 ስለዚህ ሳኦል የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔርን፥ “በቱሚም አሳየኝ” አለው። ዮናታንና ሳኦል በዕጣ
ተያዙ፥ ሕዝቡ ግን የተመረጠ ሆነና አመለጠ። 42 ከዚያም ሳኦል፥ “በእኔና በልጄ በዮናታን መክከል ዕጣ ጣሉ” አለ። ዮናታንም በዕጣ ተያዘ። 43 ሳኦልም
ዮናታንን፥ “ያደረግኸውን ንገረኝ” አለው። ዮናታንም፥ “በእጄ በነበረው በትር ጫፍ ጥቂት ማር ቀምሻለሁ። ይኸው ለመሞት ዝግጁ ነኝ” አለ። 44 ሳኦልም፥
“ዮናታን ሆይ፥ ባትሞት እግዚአብሔር በእኔ ላይ እንዲሁ ያድርግ፥ ይጨምርም” አለ። 45 ሕዝቡም ሳኦልን፥ “ለእስራኤል ይህንን ታላቅ ድል ያመጣ ዮናታን
መሞት ይገባዋል? ይህ ከእርሱ ይራቅ! እርሱ ዛሬ ከእግዚአብሔር ጋር ሠርቷልና ሕያው እግዚአብሔርን! ከራስ ጸጉሩ አንድ በምድር ላይ አይወድቅም" አሉት።
ስለዚህ ሕዝቡ ዮናታንን ከመሞት አዳነው። 46 ከዚያም ሳኦል ፍልስጥኤማውያንን ማሳደዱን አቆመ፥ ፍልስጥኤማውያንም ወደ ስፍራቸው ሄዱ። 47 ሳኦል
እስራኤልን መግዛት በጀመረ ጊዜ፥ በየአቅጣጫው ከነበሩ ጠላቶቹ ሁሉ ጋር ተዋጋ። እርሱም ከሞዓብ፥ ከአሞን ሰዎች፥ ከኤዶም፥ ከሱባ ነገሥታትና
ከፍልስጥኤማውያን ጋር ተዋጋ። በደረሰበት ሁሉ በቅጣት ያሰቃያቸው ነበር። 48 ከአማሌቃውያን ጋር በጀግንነት ተዋግቶ ድል አደረጋቸው። እስራኤላውያንንም
ከዘራፊዎቻቸው እጅ አዳናቸው። 49 የሳኦል ወንዶች ልጆች ዮናታን፥ የሱዊና ሜልኪሳ ነበሩ። የሁለቱ ሴቶች ልጆቹ ስም፥ የመጀመሪያ ልጁ ሜሮብና ታናሿ
ሜልኮል ይባሉ ነበሩ። 50 የሳኦል ሚስት ስም አኪናሆም ነበር፥ እርሷም የአኪማአስ ልጅ ነበረች። የሠራዊቱ አዛዥ ስም፥ የሳኦል አጎት የኔር ልጅ አበኔር ነበር።
51 ቂስ የሳኦል አባት ነበር፤ የአበኔር አባት ኔርም የአቢኤል ልጅ ነበር። 52 በሳኦል ዘመን ሁሉ ከፍልስጥኤማውያን ጋር ከባድ ጦርነት ይካሄድ ነበር። ሳኦል
ኃያል ወይም ብርቱ የሆነ ሰው ባየ ጊዜ ሁሉ ያንን ወደ ራሱ ይሰበስብ ነበር።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Samuel 14:1

አጠቃላይ መረጃ
ዮናታን በፍልስጥኤማውያን ሠራዊት ላይ ሁለተኛ ጥቃቱን ጀመረ።

ወጣቱ ጋሻ ጃግሬው
የጌታውን የጦር መሣሪያዎች የመሸከም ኃላፊነት ያለበት ከአሥራ ሦሥት እስከ አሥራ ዘጠኝ ዓመት ባለ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ልጅ

የፍልስጥኤማውያን የጦር ካምፕ
ይህ የፍልስጥኤማውያን ሠራዊት የሰፈረበት የጦር ሰፈር ነው።

1 Samuel 14:2

ጊብዓ
ይህ ከኢየሩሳሌም በስተሰሜን የሚገኝ የኮረብታ ስም ነው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

ከሮማኑ ዛፍ በታች
ፍሬው ወፍራም ሸፋን ያለው፣ ክብ፣ ቀይና የሚበሉ ብዙ ዘር የያዘ ዛፍ ነው

መጊዶን
መጊዶን ከኢየሩሳሌም በስተሰሜን የሚገኝ የቦታ ስም ነው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

ስድስት መቶ ሰዎች ከእርሱ ጋር ነበሩ
"600 ሰዎች ከእርሱ ጋር ነበሩ' (ቁጥሮች ተመልከት)

የአኪጦብ ልጅ **(**የኢካቦድ ወንድም**)**
"አኪጦብ' እና "ኢካቦድ' የሰዎች ስሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

የዔሊ ልጅ ፊንሐስ
ፊንሐስ ከካህናት አንዱ ነበር። ይህንን በ1ሳሙኤል 1:03 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

1 Samuel 14:4

ሌላኛውም ሾጣጣ ድንጋይ ሴኔ ይባል ነበረ
ይህ የሌላኛው ሾጣጣ ድንጋይ ስም ነበር። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

ማክማስ ... ጊብዓ
ከኢየሩሳሌም በስተሰሜን የሚገኙ ከተሞች (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

1 Samuel 14:6

ወጣቱ ጋሻ ጃግሬው
የጌታውን የጦር መሣሪያዎች የመሸከም ኃላፊነት ያለበት ከአሥራ ሦሥት እስከ አሥራ ዘጠኝ ዓመት ባለ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ልጅ። ይህንን በ1ሳሙኤል 14:1 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ወደ እነዚህ ቆላፋን **(**ያልተገረዙ**)**
ይህ አይሁድ ላልሆኑ ወንዶች ጥቅም ላይ የሚውል ክበረ ነክ ቃል ነው።

በእኛ ፈንታ ይሠራ
"እኛን ለመደገፍ ይሠራ' ወይም "ይረዳን'

ምንም ነገር እግዚአብሔርን ከማዳን አያቆመውም
ይህ ድርብ አሉታዊ አሳብ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር ማዳን ይችላል' (ድርብ አሉታዊ ተመልከት)

በብዙ ወይም በጥቂት
እነዚህ ጥጎች በመካከል ያሉትን ነገሮች ሁሉ ያካትታሉ። አት፡- "በማንኛውም የሰው ቁጥር' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በልብህ ያለውን ማንኛውንም ነገር
በዚህ ስፍራ ልብ የዮናታንን ፍልጎቶች ያመላክታል። አት፡- "ማድረግ የምትፈልገውን የትኛውንም ነገር' (ምትክ ቃል ተመልከት)

1 Samuel 14:8

ወደ እነርሱ እንወጣም
"ፍልስጥኤማውያን ወደ ሚገኙበት ወደ ሌላኛው የሸለቆ አቅጣጫ እንሄድም።'

በእጃቸን አሳልፎ ሰጥቶአቸዋል
በዚህ ስፍራ እጅ እነርሱን ለማሸነፍ የሆነውን ኃይል ያመለክታል። አት፡- እነርሱን ለማሸነፍ ያስችለናል (ምትክ ቃል ተመልከት)

ይህ ምልክት ይሆነናል
"ይህ ጌታ ከእኛ ጋር እንደሆነ ያረጋግጥልናል'

1 Samuel 14:11

ለፍልስጥኤማውያን ጭፍራ ራሳቸውን ገለጡ
"የፍልስጥኤማውያን ወታደሮች እንዲያዩአቸው ፈቀዱ'

የጦር ሠፈር
የሠራዊት ከምፕ

ከተደበቁበት ጉድጓድ ይወጣሉ
ዕብራውያን እንደ እንሰሳ በጉድጓድ ውስጥ ተደብቀው እንደ ነበር ፍልስጥኤማውያን አመልከቱ። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

አንድ ነገር እናሳያችኋለን
ይህ አንድ ትምህርት አስተምራችኋለሁ የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ ንግግር ነው። (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

በእስራኤል እጅ አሳልፎ ሰጣአቸው
በዚህ ስፍራ እጅ የሚለው የሚያመለክተው ፍልስጥኤማውያንን ለማሸነፍ የሆነውን ኃይል ነው። አትለ- እስራኤላውያን እንዲያሸንፉ አስቻላቸው። (ምትክ ቃል ተመልከት)

1 Samuel 14:13

ዮናታን በእጁና በእግሩ ወጣ
ይህን ያደረገው በጣም ከፍ ያለ ስለ ነበረ ነው። ይህ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አት፡- "በጣም ከፍ ያለ ስለ ነበረ ዮናታን እጆቹንና እግሮቹን በመጠቀም ወጣ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ፍልስጥኤማውያን በዮናታን ተገደሉ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊደረግ ይቻላል። አት፡- "ዮናታን ፍልስጥኤማውያንን ገደለ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ከእርሱ በኋላ ጋሻ ጃግሬው ጥቂቶችን ገደለ
"የዮናታን ጋሻ ጃግሬ ተከተለው የፍልስጥኤማውያንንም ወታደሮች ገደለ'

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Samuel 14:15

በሰፈሩም በእርሻውና በሕዝቡም መካከል ሽብር ሆነ
ሽብር የሚለው የነገር ስም በማሰሪያ አንቀጽነት ወይም በቅጽልነት ሊተረጎም ይችላል። አት፡- "በሰፈርና በእርሻ የነበሩ የፍልስጥኤማውያን ወታደሮችና ከእነርሱ ጋር የነበረው ሕዝብ ሁሉ ተሸበሩ' ወይም "በሰፈርና በእርሻ የነበሩ የፍልስጥኤማውያን ወታደሮችና ከእነርሱ ጋር የነበረው ሕዝብ ሁሉ በጣም ፈሩ' (የነገር ስም ተመልከት)

ዘራፊዎች **(**አደጋ ጣዮች**)**
የእስራኤልን ከተሞች የሚዘርፉ ፍልስጥኤማውያን

ምድሪቱ ተናወጠች
ምክንያቱን መግለጽ ሊረዳ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር ምድሪቱን አናወጣት' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

1 Samuel 14:16

ጊብዓ
ይህቺ ሳኦል የተወለደባት ከተማ ነበረች። "ጊብዓ'ን በ1ሳሙኤል 10፡26 እንደተረጎምኸው ተርጉም። (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)

ወዲህና ወዲያ እየተራወጡ ተበታተኑ
እነዚህ ሁለት ሃረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ይጋራሉ ወታደሮቹም በሁሉም አቅጣጫዎች ይሮጡ የነበረ በመሆኑ ላይ አጽንዖት ያደርጋሉ። (አጓዳኝነት ተመልከት)

1 Samuel 14:18

የእግዚአብሔርን ታቦት ወደዚህ አምጣ
ጥቂት ትርጉሞች በዚህ ስፍራ "የእግዚአብሔር ታቦት' በሚለው ምትክ "ኤፉድ' ይላሉ። (ልዩ ልዩ ትርጉሞች ተመልከት)

ግርግርታ
ትልቅ ድምጽና ትርምስምስ

እጅህን መልስ
ይህ "እያደረግህ ያለውን አቁም' የሚል ፈሊጣዊ ንግግር ይመስላል። እግዚአብሔርን ምሪት ለመጠየቅ አኪያ ታቦቱን እንዲጠቀም ሳኦል አልፈቀደም። አት፡- "በዚህ ጊዜ የተቀደሰውን ሰንዱቅ አታምጣ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

1 Samuel 14:20

ከእርሱ ጋር የነበሩት ሕዝብ
ከሳኦል ጋር የቀሩ የእስራኤል ሠራዊት ቅሬታ

የእያንዳንዱ ፍልስጥኤማዊ ሰይፍ በባልንጀራው ላይ ነበረ
ሰይፎችን በሚመለከት ልክ ሕያዋን ሰዎች እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "የፍልስጥኤም ወታደሮች እርስ በእርሳቸው በሰየፎቻቸው ተጠቃቁ' (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየትን ተመልከት)

1 Samuel 14:22

በኮረብታዎቹ የተሸሸጉት የእስራኤል ሰዎች
ይህ ደፈጣን እያመለከተ አይደለም። እነዚህ ወታደሮች የተሸሸጉት ፍልስጥኤማውያንን ስለፈሩ ነበር። ይህ በግልጽ ሊቀመጥ ይችላል። አት፡- የፈሩ የእስራኤል ወታደሮች በኮረብታዎች ተሸሽገው ነበር። (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ቤትአዌን
ይህ በእስራኤል የሚገኝ ቦታ ነው። ይህንን በ1ሳሙኤል 13፡05 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)

1 Samuel 14:24

ከወታደሮቹ ማንም ምግብ አልቀመሰም ነበር
ከሳኦል መሃላ የተነሣ ምንም መቅመስ እንዳልተፈቀደ ወታደሮቹ ተረድተው ነበር።

ሕዝቡ ወደ ዱር ገባ
የፍልስጥኤም ወታደሮች ወደ ጫካ ሸሽተው ነበር የእስራኤል ወታደሮችም ወደዚያ ተከትለዋቸው ነበር።

የሚፈስ ማር ነበር
በጫካ ውስጥ ምን ያህል ማር እንደነበር ለመግለጽ የተነገረ ግነት ነው። አት፡- "በሁሉ ሥፍራ በርካታ ማር ነበር' (ግነትና አጠቃላይነት ተመልከት)

ማንም እጁን ወደ አፉ አልዘረጋም
በዚህ ስፍራ የአንድ ሰው እጁን በአፉ ማድረጉ መብላትን የሚያሳይ ምትክ ቃል ነው። አት፡- "ማንም ምንም አልበላም' (ምትክ ቃል ተመልከት)

ሕዝቡ መሐላውን ፈርቶ
ሕዝቡ ይፈሩ የነበረው መሐላውን ሳይሆን መሐላውን ከመስበር ጋር የተያያዘውን ቅጣት ነበር። አት፡- "ሕዝቡ መሐላውን ከሰበሩ ሳኦል የሚያደርግባቸውን ፈሩ' (ምትክ ቃል ተመልከት)

1 Samuel 14:27

አጠቃላይ መረጃ
ዮናታን የአባቱን መሐላ አወቀ።

ሕዝቡን በመሐላ አሰራቸው
በዚህ ስፍራ መሐላን የመታዘዝ ግዴታን በሚመለከት ሕዝቡ በገመድ እንደታሰረ ዓይነት ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "ሕዝቡ መሐላውን እንዲያከብር አዘዘ' (ዘይቤአዊ አነጋገር ተመልከት)

እጁን ወደ አፉ አደረገ
በዚህ ስፍራ እጁን ወደ አፉ የሚለው ለመብላት ምትክ ቃል ነው። አት፡- "ጥቂት ማር በላ' (ምትክ ቃል ተመልከት)

ዓይኑ በራ
በረታ የሚል ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፡- "እንደገና ብርታት አገኘ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

1 Samuel 14:29

ለምድሪቱ
የእስራኤልን ሕዝብ የሚወክል ምትክ ቃል ነው። አት፡- "ለእስራኤል' (ምትክ ቃል ተመልከት)

ዓይኔ በራ
በረታ የሚል ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፡- "እንደገና ብርታት አገኘ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ሕዝቡ ካገኙት ... ምን ያህል የተሻለ
ሕዝቡ እንዲበላ ሊፈቀድለት ይገባ እንደነበር ለመግለጽ ዮናታን ይህንን በሁኔዎች ላይ የተደገፈ ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ አሳብ ገላጭ ዐረፍተ ነገር ሊሆን ይችላል። አት፡- "ሕዝቡ ከጠላቶቻቸው የማረኩትን ዛሪ በነፃነት በልተው ቢሆን ኖሮ ድላችን የተሻለ ይሆን ነበር።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄና ሊሆኑ የሚችሉ ሁኔታዎች ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምርኮ
ይህ ቃል ሕዝቡ ከጠላቶቻቸው ጋር በነበራቸው ጦርነት የወሰዷቸውን ነገሮች ያመለክታል።

ስለዚህ አሁን ግድያው ታላቅ አልሆነም
በጦርነቱ ወቅቱ ወታደሮቹ ሊበሉ ስላልቻሉ፣ ቀኑ የረዘመውን ያህል እየደከሙ ሄዱ። ከዚህ የተነሣ ብዙ ፍልስጥኤማውያንን መግደል አልቻሉም።

1 Samuel 14:31

አጠቃላይ መረጃ
የዮናታን ቃል ሠራዊቱን ከነበረባቸው ከፍተኛ ረሃብ የተነሣ እግዚአብሔርን እንዲበድሉ አደረጋቸው።

ማክማስ
ይህ የቦታ ስም ነው። ይህንን በ1ሳሙኤል 13:02 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ኤሎን
በዛብሎን እስራኤል የሚገኝ ቦታ ነው (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

ሕዝቡ
እስራኤላውያንን ያመለክታል።

ከደማቸው ጋር በሉአቸው
በጣም ተርበው ስለነበር ከመብላታቸው በፊት ደሙን አላፈሰሱም ነበር። ይህ በሙሴ በኩል ለሕዝበ እሥራኤል የተሰጠውን ሕግ መተላለፍ ነበር። ይህ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አት፦ "በሕጉ እንደታዘዘው አስቀድመው ደማቸውን ሳያፈስሱ በሏቸው' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

1 Samuel 14:33

ከደሙ ጋር በመብላታችሁ
ይህ በሙሴ በኩል ለሕዝበ እሥራኤል የተሰጠውን ሕግ መተላለፍ ነበር። ይህ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አት፦ "በሕጉ እንደታዘዘው አስቀድመው ደሙን ሳያፈስሱ ሥጋ በመብላታቸው'

በታማኝነት አላደረጋችሁም
ሁሉም ወታደር ታማኝነቱን ስላላጓደለ ሳኦል ሠራዊቱን ሁሉ በታማኝነት እንዳላደረገ መክሰሱ አጠቃላይ ፍረጃ ነው። (ግነትና አጠቃላይነት ተመልከት)

አሁን ትልቅ ድንጋይ አንከባላችሁ አቅርቡልኝ
ድንጋዩ እንሰሳቱን ከፍ አድርጎ ስለሚይዝ ደማቸውን ማፍሰስን ቀላል ያደርገዋል በዚህ እረዱና ብሉ ይህ ሳኦልን ደሙ ከእንሰሳው በተገቢ ሁኔታ ተወግዶ መሆኑን ለማየት ያስችለዋል።

1 Samuel 14:35

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቡ ለማረድና ለመብላት እንሰሳቶቻቸውን ወደ ትልቁ ደንጋይ እንዲያመጡ ሳኦል ነገራቸው።

ሳኦል ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሠራ
ሳኦል ይህን መሠዊያ የሠራው ሕዝቡ በ1ሳሙኤል 14:33 ወደ እርሱ ካመጡለት ትልቅ ድንጋይ ይሁን ግልጽ አይደለም።

1 Samuel 14:36

አጠቃላይ መረጃ
ሳኦል ከፍልስጥኤማውያን ጋር የነበረውን ጦርነት ለመቀጠል ፈልጓል።

ከመካከላቸው አንድ እንኳ በሕይወት እንዲኖር አንተው
ለግድያው አጽንዖት ለመስጠት ይህ በአሉታዊ መንገድ ተገልጾአል። በአዎንታዊ መልኩም ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "እያንዳንዳቸውን እንግደል' (ምጸት ተመልከት)

ደስ የሚያሰኝህን ሁሉ አድርግ
ጦርነቱን ለመቀጠል ሳኦል የሠራዊቱን ድጋፍ አግኝቶአል።

ወደ እግዚአብሔር እንቅረብ
በዚህ ስፍራ "ወደ እግዚአብሔር መቅረብ' እርሱን ምክር ከመጠየቅ ጋር ተያይዟል። አት፦ "ምን ማደረግ እንዳለብን እግዚአብሔርን እንጠይቅ' (ምትክ ቃል ተመልከት)

በእስራኤል እጅ አሳልፈህ ትሰጣቸዋለህን?
በዚህ ስፍራ "እጅ' እነርሱን ለማሸነፍ የሚሆንን ኃይል ያመለክታል። አት፦"እንድናሸንፋቸው አስችለን' (ምትክ ቃል ተመልከት)

በዚያን ቀን ግን እግዚአብሔር አልመለሰለትም
ይህ እግዚአብሔር ሳኦልን ለመርዳት ፈቃደኛ እንዳልሆነ ያመላክታል።

1 Samuel 14:38

ሕዝቡ
ይህ እስራኤላውያንን ያመልከታል

ዛሬ ይህ ኃጢአት በምን እንደሆነ እወቁ
"ኃጢአት የሠራውን እወቁ'

በልጄ በዮናታን ቢሆን ፈጽሞ ይሞታል
ሳኦል ዮናታን በደለኛ እንደሆነ ስላላመነ ይህንን ሊሆን እንደ ሚችል ሁኔታ አድርጎ ገለጸ። (ሊሆን የሚችል ሁኔታ ተመልከት)

ከሕዝቡም አንድ የመለሰለሰት ሰው አልነበረም
አብዛኛዎቹ ዮናታን የሳኦልን መሐላ እንደሰበረ ስለሚያውቁ ዝም አሉ። ይህ በግልጽ ሊቀመጥ ይችላል። አት፦ "ሰዎቹ በደለኛው ማን እንደነበረ ያውቁ ነበር ነገር ግን ማናቸውም ለሳኦል ምንም አላሉም።' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

1 Samuel 14:40

እስራኤልንም ሁሉ ... አለ
በዚያ የነበሩት የእስራኤል ወታደሮች ብቻ ስለሆኑ ይህ አጠቃላይነት ነው። አት፦ "በዚያ ለነበሩት የእስራኤል ወታደሮች እንዲህ አለ' (ግነትና አጠቃላይነት ተመልከት)

ቱሚም ስጠን
በዚያን ጊዜ እስራኤላውያን ከእግዚአብሔር ምሪት ለመቀበል ኡሪምና ቱሚም የተባሉ የተለዩ ድንጋዮች ይጠቀሙ ነበር። አት፦ "በቱሚም አማካይነት አስታውቀን' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ቱሚም
ይህ ከመጀመሪያ ቋንቋ በትውስት የተወሰደ ነው። (ቅጂ ወይም ትውስት ቃላት ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሳኦልና ዮናታን በዕጣው ተለዩ፣ ሕዝቡ ግን ነፃ ሆነ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይቻላል። አት፡- ዕጣዎቹ ዮናታን ወይም ሳኦል በደለኞች እንደሆኑ ነገር ግን ሠራዊቱ በደለኛ እንዳልሆነ አመለከቱ (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ከዚያም ዮናታን በዕጣው ተለየ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- ከዚያም ዕጣው ዮናታን በደለኛ እንደሆነ አመለከተ (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

1 Samuel 14:43

አጠቃላይ መረጃ
ዕጣው ዮናታን ኃጢአት እንዳደረገ አሳየ።

ያደረግኸውን ንገረኝ
"እንዴት ኃጢአት እንዳደረግህ ንገረኝ' ወይም "ያደረግኸው ስሕተት ምን እንደሆነ ንገረኝ'

እሞታለሁ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ለመሞት ፈቃደኛ ነኝ' ወይም 2) "ያንን ስላደረግሁ በሞት ልቀጣ ይገባኛል'

እግዚአብሔር እንዲህ ያድርግብኝ እንዲህም ይጨምርብኝ፤ ዮናታን ሆይ ፈጽም ትሞታለህ
ከአንድ ቀን ባነሰ ጊዜ ውስጥ ሳኦል ትርጉም የሌለው መሐላ አደረገ። አት፡- ዮናታን፣ ካልገደልኩህ እግዚአብሔር ይግደለኝ

1 Samuel 14:45

አጠቃላይ መረጃ
ሠራዊቱ ከሳኦል ለዮናታን ተከላከለ ጠበቀውም።

በውኑ ለእስራኤል ይህን ታላቅ ድል ያደረገ ዮናታን ይሞታልን? ይህ አይሁን!
ሕዝቡ ሳኦልን ገሰፀ። ይህ አሳብ ገላጭ ጥያቄ በገላጭ አባባል ሊተረጎም ይችላል። አት፡- ዮናታን ይህን ታላቅ ድል ለእስራኤል አድርጓል። በእርግጥ ዮናታን አይሞትም። (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ሕያው እግዚአብሔርን
ሕዝቡ በዮናታን ላይ አንዳች ነገር እንዲሆን አንዳማየፈቅዱ ቁርጠኛነታቸውን እየገለጹ ነበር።

ከራሱ ጠጉር አንዲት በምድር ላይ አትወድቅም
ይህ ግነት የእስራኤል ሕዝብ እንዴት ዮናታንን እንደሚጠብቁትና ደህንነቱን እንደሚከታተሉ ያሳያል። ይህ ምፀት በአዎንታዊ መልኩ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- ከየትኛውም ጉዳት እንጠብቀዋለን (ግነትና አጠቃላይነት እና ምፀት ተመልከት)

1 Samuel 14:47

አጠቃላይ መረጃ
ለአጭር ጊዜ ሳኦል በታላቅ ድፍረት የእስራኤላውያንን ጠላቶች በማሸነፍ አገልግሏል።

እስራኤል
ይህ የእስራኤልን ሕዝብ የሚወክል ምትክ ቃል ነው። አት፡- "እስራኤላውያን' (ምትክ ቃል ተመልከት)

ሞዓብ
ይህ የሞዓብ ሕዝብን ያመለክታል። አት፡- "ሞዓባውያን' (ምትክ ቃል ተመልከት)

ዔዶም
ይህ የዔዶም ሰዎችን ያመለክታል። አት፡- "ዔዶማውያን' (ምትክ ቃል ተመልከት)

በየሄደበትም ሁሉ
"ሠራዊቱን በላከበት ሥፍራ ሁሉ'

ከ ...እጅ
እጅ የሚለው ቃል ቁጥጥርን ይወክላል። አት፡- "ከ ... ቁጥጥር' (ምትክ ቃል ተመልከት)

1 Samuel 14:49

አጠቃላይ መረጃ
ይህ በሳኦል ቤተሰብ ዙሪያ ታሪካዊ ዳራ ነው።

የሱዊ ... ሜልኪሳ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

ሜሮብ ... ሜልኮል
እነዚህ የሴቶች ስሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

አኪናሆም ... አኪማአስ
እነዚህ የሴቶች ስሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

አቤኔር ... ኔር ... ቂስ ... አቢኤል
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

1 Samuel 14:52

በሳኦልም እድሜ ሁሉ
"በሳኦል የሕይወት ዘመን ሁሉ'

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 15

1 ሳሙኤልም ሳኦልን እንዲህ አለው፥”እግዚአብሔር በሕዝቡ በእስራኤል ላይ ንጉሥ ትሆን ዘንድ እንድቀባህ ላከኝ። አሁንም የእግዚአብሔርን ቃል ስማ። **2** የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የሚለው እንዲህ ነው፥ 'እስራኤል ከግብፅ በወጣ ጊዜ አማሌቅ እየተቃወመ በመንገዱ ላይ ያደረገበትን አስታውሻለሁ። **3** አሁንም ሂድና አማሌቅን ምታ፥ ያላቸውን ሁሉ ፈጽመህ ደምስስ። አትራራላቸው፥ ወንድና ሴቱን፥ ልጅና ሕፃኑን፥ በሬና በጉን፥ ግመልና አህያውን ግደል።" **4** ሳኦል ሕዝቡን በጥላኢም ከተማ ሰብስቦ ቆጠራቸው፤ እነርሱም ሁለት መቶ ሺህ እግረኞችና ዐሥር ሺህ የይሁዳ ሰዎች ነበሩ። **5** ከዚያም ሳኦል ወደ አማሌቅ ከተማ መጥቶ በሸለቆው ውስጥ አደፈጠ። **6** ከዚያም ሳኦል ቄናውያንን፥ "ከግብፅ በመጡ ጊዜ ለእስራኤል ሕዝብ በሙሉ ደግነትን አሳይታችኋልና ከእነርሱ ጋር እንዳላጠፋችሁ፥ ከአማሌቃውያን መካከል ተለይታችሁ ውጡና ሂዱ" አላቸው። ስለዚህ ቄናውያን ከአማሌቃውያን ተለይተው ሄዱ። **7** ሳኦልም አማሌቃውያንን ከኤውላጥ ጀምሮ ከግብፅ በስተምሥራቅ እስካለችው እስከ ሱር ድረስ መታቸው። **8** የአማሌቃውያኑን ንጉሥ አጋግን ከነሕይወቱ ያዘው፤ ሕዝቡን ሁሉ በሰይፍ ስለት ፈጽሞ አጠፋቸው። **9** ነገር ግን ሳኦልና ሕዝቡ አጋግን፥ እንዲሁም ምርጥ የሆኑትን በጎች፥ በሬዎች፥ የሰቡትን ጥጆችና የበግ ጠቦቶች በሕይወት ተዉአቸው። መልካም የሆነውን ሁሉ አላጠፉም። የተናቀውንና ዋጋ ቢስ የሆነውን ነገር ሁሉ ግን ፈጽመው ደመሰሱ። **10** ከዚያም የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል ወደ ሳሙኤል መጣ፥ **11** "እኔን ከመከተል ስለተመለሰና ያዘዝኩትንም ስላልፈጸመ ሳኦልን በማንገሤ ተጸጽቻለሁ"። ሳሙኤልም ተቆጣ፤ ሌሊቱን በሙሉ ወደ እግዚአብሔር ሲጮህ አደረ። **12** ሳሙኤልም ሳኦልን በጠዋት ለመገናኘት ማልዶ ተነሣ። ለሳሙኤልም፥ "ሳኦል ወደ ቀርሜሎስ መጥቶ ለራሱ ሐውልት አቆመ፥ ከዚያም ተመልሶ ወደ ጌልገላ ወረደ" ብለው ነገሩት። **13** ከዚያም ሳሙኤል ወደ ሳኦል መጣ፥ ሳኦልም፥ "አንተ በእግዚአብሔር የተባረክህ ነህ! የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ፈጽሜአለሁ" አለው። **14** ሳሙኤልም፥ "ታዲያ ይህ በጆሮዬ የምሰማው የበጎች ድምፅና የበሬዎች ግሣት ምንድነው?" አለው። **15** ሳኦልም፥ "ከአማሌቃውያኑ ያመጧቸው ናቸው። ሕዝቡ ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ለመሠዋት ምርጥ የሆኑትን በጎችና በሬዎች በሕይወት አስቀሯቸው። የቀሩትን ፈጽመን አጥፍተናል" ብሎ መለሰለት። **16** ከዚያም ሳሙኤል ሳኦልን፥ "አድምጠኝ፥ በዛሬው ሌሊት እግዚአብሔር የነገረኝን እነግርሃለሁ" አለው። ሳኦልም፥ "ተናገር!" አለው። **17** ሳሙኤልም እንዲህ አለው፥ "በራስህ ግምት ታናሽ ብትሆንም በእስራኤል ነገዶች ላይ አለቃ ተደረግህ። እግዚአብሔርም በእስራኤል ላይ ንጉሥ አድርጎ ቀባህ፤ **18** እግዚአብሔርም፥ 'ሂድና ኃጢአተኞቹን አማሌቃውያንን ፈጽመህ አጥፋቸው፥ እስኪጠፉም ድረስ ተዋጋቸው' ብሎ በመንገድህ ልኮህ ነበር። **19** ታዲያ የእግዚአብሔርን ድምፅ ያልታዘዝከው ለምንድነው? ከዚያ ይልቅ ግን ከምርኮው በመውሰድ በእግዚአብሔር ፊት ክፋትን አደረግህ።" **20** ሳኦልም ሳሙኤልን፥ "የእግዚአብሔርን ድምፅ በትክክል ታዝዣለሁ፥ እግዚአብሔር በላከኝም መንገድ ሄጃለሁ። የአማሌቅን ንጉሥ አጋግን ማርኬዋለሁ፥ አማሌቃውያንንም በሙሉ ፈጽሜ ደምስሻለሁ። **21** ሕዝቡ ግን ከምርኮው ላይ ጥቂት በጎችንና በሬዎችን፥ ሊጠፉም የነበሩ ምርጥ ነገሮችን ለአምላክህ ለእግዚአብሔር በጌልገላ ሊሠዉአቸው ወሰዱ" አለው። **22** ሳሙኤልም፥ "የእግዚአብሔርን ድምፅ ከመታዘዝ የበለጠ በሚቃጠል መባና መሥዋዕት እግዚአብሔር ደስ ይሰኛል? ከመሥዋዕት መታዘዝ ይሻላል፥ ከአውራ በግ ስብም መስማት ይሻላል። **23** እምቢተኝነት እንደ ምዋርተኝነት ኃጢአት ነው፥ እልኸኝነትም እንደ አመጸኝነትና እንደ ክፋት ነው። የእግዚአብሔርን ቃል ንቀሃልና እርሱም ደግሞ ንጉሥ እንዳትሆን ንቆሃል“ አለው። **24** ከዚያም ሳኦል ሳሙኤልን፥”ኃጢአትን ሠርቻለሁ፤ ሕዝቡን ስለፈራሁና ቃላቸውን ስለታዘዝኩ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝና የአንተን ቃል ተላልፌአለሁ። **25** አሁንም እባክህን ኃጢአቴን ይቅር በለኝ፥ ለእግዚአብሔር እንድሰግድም ከእኔ ጋር ተመለስ“ አለው። **26** ሳሙኤልም ሳኦልን፥”ከአንተ ጋር አልመለስም፤ የእግዚአብሔርን ቃል ንቀሃልና አንተም በእስራኤል ላይ ንጉሥ እንዳትሆን እግዚአብሔር ንቆሃል" አለው። **27** ሳሙኤል ለመሄድ ዘወር ባለ ጊዜ፥ ሳኦል የልብሱን ጫፍ ያዘ፥ እርሱም ተቀደደ። **28** ሳሙኤልም፥ "እግዚአብሔር ዛሬ የእስራኤልን መንግሥት ከአንተ ቀደደው፥ ከአንተ ለሚሻለው ለጎረቤትህም አሳልፎ ሰጠው። **29** ደግሞም የእስራኤል ኃይል አይዋሸም፥ አሳቡንም አይለውጥም፥ እርሱ አሳቡን መለወጥ ይችል ዘንድ ሰው አይደለምና“ አለው። **30** ከዚያም ሳኦል፥”ኃጢአትን አድርጌአለሁ። አሁን ግን እባክህ በሕዝቤ ሽማግሌዎችና በእስራኤል ፊት አክብረኝ። ለአምላክህ ለእግዚአብሔር እንድሰግድ ከእኔ ጋር ተመለስ“ አለው። **31** ስለዚህ ሳሙኤል ከሳኦል ኋላ ተመለሰ፥ ሳኦልም ለእግዚአብሔር ሰገደ። **32** ከዚያም ሳሙኤል፥”የአማሌቃውያንን ንጉሥ አጋግን አምጡልኝ“ አለ። አጋግ በሠንሠለት አንደታሠረ ወደ እርሱ መጣና፥”ለካስ ሞት እንዲህ መራራ ነው“ አለ። **33** ሳሙኤልም፥”ሰይፍህ እናቶችን ልጅ ዐልባ እንዳደረጋቸው አሁን እናትህ በሴቶች መካከል ልጅ ዐልባ ትሆናለች“ ብሎ መለሰለት። ከዚያም ሳሙኤል አጋግን በእግዚአብሔር ፊት በጌልገላ ቆራረጠው። **34** ሳሙኤል ወደ ራማ ሄደ፥ ሳኦልም ወደ ቤቱ ወደ ሳኦል ጊብዓ ሄደ። **35** ሳሙኤል እስከሞተበት ጊዜ ድረስ ሳኦልን አላየውም፥ ለሳኦልም አለቀሰለት። እግዚአብሔርም ሳኦልን በእስራኤል ላይ በማንገሡ አዘነ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 16

1 እግዚአብሔርም ሳሙኤልን፥ “በእስራኤል ንጉሥ እንዳይሆን ለናቅኩት ለሳኦል የምታለቅስለት እስከ መቼ ነው? በወንዶች ልጆቹ መካከል ለራሴ ንጉሥ
የሚሆነውን መርጫለሁና ወደ ቤተ ልሔማዊው ወደ እሴይ እልክሃለሁ። የዘይት መያዣ ቀንድህን በዘይት ሞልተህ ሂድ” አለው። 2 ሳሙኤልም፥ “እንዴት መሄድ
እችላለሁ? ሳኦል ከሰማ ይገድለኛል” አለ። እግዚአብሔርም፥ “አንዲት ጊደር ይዘህ ሂድና፥ 'ለእግዚአብሔር ልሠዋ መጥቻለሁ' በል። 3 እሴይንም ወደ
መሥዋዕቱ ጥራው፥ እኔም የምታደርገውን አሳይሃለሁ። የምነግርህንም እርሱን ትቀባልኛለህ” አለው። 4 ሳሙኤልም እግዚአብሔር እንደተናገረው አደረገ፥ ወደ
ቤተ ልሔምም ሄደ። የከተማይቱም ሽማግሌዎች እየተንቀጠቀጡ ሊገናኙት መጡና፥ “በሰላም ነው የመጣኸው?” አሉት። 5 እርሱም፥ “በሰላም ነው።
ለእግዚአብሔር ልሠዋ መጥቻለሁ። ራሳችሁን ለእግዚአብሔር ቀድሱና ከእኔ ጋር ወደ መሥዋዕቱ ኑ”አላቸው። እሴይንና ወንዶች ልጆቹንም ቀደሳቸው፥ ወደ
መሥዋዕቱም ጠራቸው። 6 እነርሱ በመጡ ጊዜም፥ ወደ ኤልያብ ተመልክቶ እግዚአብሔር የሚቀባው በእርግጥ በፊቱ ቆሟል ብሎ በልቡ አሰበ። 7 ነገር ግን
እግዚአብሔር ሳሙኤልን፥ "እኔ ንቄዋለሁና ውጫዊ ገጽታውን ወይም የቁመቱን ዘለግታ አትመልከት። እግዚአብሔር ሰው እንደሚያይ አያይምና፤ ሰው ውጫዊ
ገጽታን ያያል፥ እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል" አለው። 8 ከዚያም እሴይ አሚናዳብን ጠርቶ በሳሙኤል ፊት እንዲያልፍ አደረገው። ሳሙኤልም፥ "እግዚአብሔር
ይኸኛውንም አልመረጠውም“ አለ። 9 ከዚያም እሴይ ሳማን አሳለፈው። ሳሙኤልም፥ "እግዚአብሔር ይኸኛውንም አልመረጠውም“ አለ። 10 እሴይ ሰባቱን
ወንዶች ልጆቹን በሳሙኤል ፊት እንዲያልፉ አደረጋቸው። ሳሙኤልም እሴይን፥”እግዚአብሔር ከእነዚህ አንዳቸውንም አልመረጠም“ አለው። 11 ሳሙኤልም
እሴይን፥”ወንዶቹ ልጆችህ እነዚህ ብቻ ናቸው? “ አለው። እርሱም፥”የሁሉ ታናሽ የሆነው ገና ቀርቷል፥ እርሱ ግን በጎች እየጠበቀ ነው" ብሎ መለሰ።
ሳሙኤልም እሴይን፥ "ልከህ አስመጣው፤ እርሱ እዚህ እስኪመጣ ድረስ አንቀመጥምና" አለው። 12 እሴይም ልኮ አስመጣው። በመጣ ጊዜም ልጁ ቀይ፥
ዐይኖቹ የተዋቡና መልከ መልካም ገጽታ ነበረው። እግዚአብሔርም፥ "ያ ሰው እርሱ ነውና ተነሣ፤ ቀባውም" አለው። 13 ሳሙኤልም የዘይቱን ቀንድ አንሥቶ
በወንድሞቹ መካከል እርሱን ቀባው። ከዚያን ቀን ጀምሮ የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ላይ በኃይል መጣበት። ሳሙኤልም ተነሥቶ ወደ አርማቴም ሄደ። 14
የእግዚአብሔር መንፈስ ከሳኦል ተለየ፥ በምትኩም ከእግዚአብሔር የታዘዘ ክፉ መንፈስ አሠቃየው። 15 የሳኦል አገልጋዮችም፥ "ተመልከት፥ ክፉ መንፈስ
ከእግዚአብሔር ዘንድ እያሠቃየህ ነው። 16 ደህና አድርጎ በገና መደርደር የሚችል ሰው እንዲፈልጉ ጌታችን በፊቱ ያሉትን አገልጋዮቹን ይዘዝ። ከዚያም
ከእግዚአብሔር ዘንድ ክፉ መንፈስ በሆነብህ ጊዜ እርሱ ይጫወትልሃል፥ አንተም ደኅና ትሆናለህ" አሉት። 17 ሳኦልም አገልጋዮቹን፥ "በገና በደንብ መደርደር
የሚችል ሰው ፈልጋችሁ አምጡልኝ" አላቸው። 18 ከዚያም ከወጣቶቹ አንዱ እንዲህ ሲል መለሰ፥ "ደኅና አድርጎ በገና መደርደር የሚችለውን፥ ጽኑ፥ ኃያል፥
ተዋጊ፥ በንግግሩ ጠንቃቃና መልከ መልካም የሆነውን የቤተ ልሔማዊውን የእሴይን ልጅ አይቻለሁ፥ እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ነው።" 19 ስለዚህ ሳኦል
መልዕክተኞችን ወደ እሴይ ልኮ፥ "ከበጎች ጋር ያለውን ልጅህን ዳዊትን ላክልኝ" አለው። 20 እሴይም እንጀራና ወይን ጠጅ የተሞላ አቁማዳ የተጫነበትን አህያ፥
ከፍየል ጠቦት ጋር አስይዞ ልጁን ዳዊትን ወደ ሳኦል ላከው። 21 ከዚያም ዳዊት ወደ ሳኦል መጣና አገልግሎቱን መስጠት ጀመረ። ሳኦል እጅግ ወደደው፥
ዳዊትም ጋሻ ጃግሬው ሆነ። 22 ሳኦልም፥ "በዐይኔ ፊት ሞገስን አግኝቷልና ዳዊት በፊቴ እንዲቆም ፈቃድህ ይሁን“ ብሎ ወደ እሴይ ላከ። 23 በሳኦል ላይ
ከእግዚአብሔር ዘንድ ክፉ መንፈስ በሚሆንበት ጊዜ ሁሉ ዳዊት በገና አንሥቶ ይደረድርለት ነበር። ስለዚህ ሳኦል ይታደስና ደኅና ይሆን ነበር፥ ክፉውም መንፈስ
ከእርሱ ይርቅ ነበር።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 17

1 ፍልስጥኤማውያን ሠራዊታቸውን ለውጊያ አዘጋጁ። እነርሱም የይሁዳ በሆነችው በሰኮት ተሰበሰቡ። በሰኮትና በዓዜቃ መካከል በምትገኘው በኤፌስደሚምም
ሰፈሩ። 2 ሳኦልና የእስራኤል ሰዎችም ተሰብስበው በኤላ ሸለቆ ሰፈሩ፥ ፍልስጥኤማውያንን ለመግጠምም ስፍራቸውን ያዙ። 3 ፍልስጥኤማውያን በአንደኛው
ወገን ተራራ ላይ ቆሙ፥ በዚህኛው ወገን ባለው ተራራ ላይ እስራኤላውያኑ ቆሙ፥ በመካከላቸውም ሸለቆ ነበር። 4 የጌት ሰው ጎልያድ የሚባል አንድ ጀግና
ከፍልስጥኤማውያን የጦር ሰፈር ወጣ፥ ቁመቱም ስድስት ክንድ ከስንዝር ነበር። 5 በራሱ ላይ ከነሐስ የተሠራ የራስ ቁር ደፍቶ፥ ጥሩርም ለብሶ ነበር። ጥሩሩም
አምስት ሺህ የነሐስ ሰቅል ይመዝን ነበር። 6 በእግሮቹ ላይ የነሐስ ገምባሌዎች አድርጎ ነበር፥ በትከሻዎቹም መሓል ቀለል ያለ የነሐስ ጦር ነበር። 7 የጦሩ
ዘንግ እንደ ሸማኔ መጠቅለያ ወፍራም ነበር። የጦሩ ጫፍ ስድስት መቶ የብረት ሰቅል ይመዝን ነበር። ጋሻ ጃግሬው በፊቱ ሄደ። 8 እርሱም ተነሥቶ በእስራኤል
ሠልፈኞች ላይ እንዲህ በማለት ጮኸ፥ “ለውጊያ የተሰለፋችሁት ለምንድነው? እኔ ፍልስጥኤማዊ፥ እናንተ የሳኦል አገልጋዮች አይደላችሁም? ለራሳችሁ አንድ
ሰው ምረጡና ወደ እኔ ይውረድ። 9 እርሱ ለዋጋኝ ቢችልና ቢገድለኝ እኛ አገልጋዮቻችሁ እንሆናለን። ነገር ግን ባሸንፈውና ብገድለው እናንተ አገልጋዮቻችን
በመሆን ታገለግሉናላችሁ።” 10 ፍልስጥኤማዊው ደገመና፥ “ዛሬ የእስራኤልን ሰልፈኞች እገዳደራቸዋለሁ። እንድንዋጋ አንድ ሰው ስጡኝ" አለ። 11
ፍልስጥኤማዊው የተናገረውን ሳኦልና እስራኤላውያን ሁሉ በሰሙ ጊዜ እጅግ ፈሩ፥ ተስፋም ቆረጡ። 12 ዳዊት በይሁዳ የሚኖረው የቤተ ልሔም ኤፍራታዊው
የእሴይ ልጅ ነበር። እሴይ ስምንት ወንዶች ልጆች ነበሩት። በሳኦል ዘመን እሴይ በዕድሜው ያረጀና ከወንዶቹ ሁሉ በዕድሜ የገፋ ሰው ነበር። 13 የእሴይ ሦስቱ
ታላላቅ ልጆች ሳኦልን ተከትለው ወደ ጦርነቱ ሄደው ነበር። ወደ ጦርነት የሄዱት የሦስቱ ወንዶች ልጆች ስም፥ የመጀመሪያው ልጅ ኤልያብ፥ ተከታዩ አሚናዳብና
ሦስተኛው ሣማ ይባሉ ነበር። 14 ዳዊት የሁሉም ታናሽ ነበር። ትልልቆቹ ሦስቱ ሳኦልን ተከተሉት። 15 ዳዊት በሳኦል ሠራዊትና በቤተ ልሔም የሚገኙትን
የአባቱን በጎች በመጠበቅ ተግባር ወዲያና ወዲህ ይመላለስ ናበር። 16 ፍልስጥኤማዊው ኃያል ሰው ለአርባ ቀናት በየጠዋቱና በየምሽቱ ለጦርነት ዝግጁ
መሆኑን ለማሳየት ይቀርብ ነበር። 17 ከዚያም እሴይ ልጁን ዳዊትን እንዲህ አለው፥”ከዚህ ከተጠበሰው እሸት ዐሥር ኪሎና እነዚህን ዐሥር ዳቦዎች በጦር ሰፈሩ
ውስጥ ላሉት ወንድሞችህ ፈጥነህ ውሰድላቸው። 18 በተጨማሪም እነዚህን ዐሥር የአይብ ጥፍጥፎች ለሻለቃቸው ስጠው። ወንድሞችህ ያሉበትን ሁኔታ
ተመልከትና ደኅና ስለመሆናቸው ማረጋገጫ አምጣልኝ። 19 ወንድሞችህ ከሳኦልና ከእስራኤል ሰዎች ሁሉ ጋር ፍልስጥኤማውያንን እየተዋጉ በኤላ ሸለቆ
ናቸው።“ 20 ዳዊት ማልዶ ተነሣና በጎቹን ለእረኛ ዐደራ ሰጠ። እርሱም እሴይ እንዳዘዘው የወንድሞቹን ስንቅ ይዞ ሄደ። ሠራዊቱ ወደ ውጊያው ግምባር እየፎከረ
በመውጣት ላይ እያለ ዳዊት ወደ ጦር ሰፈሩ ደረሰ። 21 እስራኤላውያንና ፍልስጥኤማውያን፥ ሠራዊት በሠራዊት ላይ ለውጊያ ተሰለፉ። 22 ዳዊት የያዘውን ዕቃ
ለስንቅ ጠባቂው ዐደራ ሰጥቶ ወደ ሠራዊቱ በመሮጥ ለወንድሞቹ ሰላምታ አቀረበ። 23 ከእነርሱ ጋር እየተነጋገረ እያለ ጎልያድ ተብሎ የሚጠራው፥ ከጌት
የመጣው ፍልስጥኤማዊ ከሰልፈኞች መካከል ወጥቶ የቀድሞውን የሚመስል ቃል ተናገረ። ዳዊትም ሰማቸው። 24 የእስራኤል ሰዎች ሁሉ ሰውዬውን ባዩት
ጊዜ፥ ከእርሱ ሸሹ፥ እጅግም ፈርተውት ነበር። 25 የእስራኤልም ሰዎች፥ "ይህን የሚወጣውን ሰው አያችሁት? እስራኤልን ለመገዳደር ነው የመጣው። እርሱን
የሚገድለውን ሰው ንጉሡ እጅግ ያበለጽገዋል፥ ልጁን ይድርለታል፥ የአባቱንም ቤት በእስራኤል ውስጥ ከግብር ነጻ ያደርጋቸዋል" ይባባሉ ነበር። 26 ዳዊትም
በአጠገቡ የቆሙትን ሰዎች፥ "ይህንን ፍልስጥኤማዊ ለሚገድልና ከእስራኤል ኀፍረትን ለሚያስወግድ ሰው ምን ይደረግለታል? የሕያው እግዚአብሔርን ሠራዊት
ሊንቅ ይህ ያልተገረዘ ፍልስጥኤማዊ ማን ሆነና ነው?" አላቸው። 27 ከዚያም ሰዎቹ ቀደም ሲል የተናገሩትን ደግመው፥ "ስለዚህ እርሱን ለሚገድለው
የሚደረግለት ይህ ነው" አሉት። 28 ዳዊት ከሰዎቹ ጋር ሲነጋገር የሁሉ ታላቅ የሆነው ወንድምየው ኤልያብ ሰማው። ኤልያብም በዳዊት ላይ ቁጣው ነድዶ፥
"ወደዚህ የወረድከው ለምንድነው? እነዚያንስ ጥቂት በጎች በምድረ በዳ ውስጥ ለማን ተውካቸው? እኔ ትዕቢትህንና የልብህን ክፋት አውቃለሁ፤ ወደዚህ
የወረድከው ውጊያውን ለማየት ነውና" አለው። 29 ዳዊትም፥ "አሁን እኔ ምን አደረኩ? እንዲያው መጠየቄ ብቻ አልነበረም?" አለው። 30 ከእርሱ ወደ ሌላው
ዞር ብሎ በተመሳሳይ መንገድ ተናገረ። ሰዎቹም የቀድሞውን የሚመስል መልስ ሰጡት። 31 ዳዊት የተናገረው ቃል በተሰማ ጊዜ፥ ወታደሮች ቃሉን ለሳኦል
ነገሩት፥ እርሱም ዳዊትን አስጠራው። 32 ከዚያም ዳዊት ሳኦልን፥ "በዚያ ፍልስጥኤማዊ ምክንያት የማንም ልብ አይውደቅ፤ አገልጋይህ ሄዶ ከፍልስጥኤማዊው
ጋር ይዋጋል" አለው። 33 ሳኦልም ዳዊትን፥ "አንተ ከዚህ ፍልስጥኤማዊ ጋር ለመዋጋት መሄድ አትችልም፤ አንተ ገና ልጅ ነህ፥ እርሱ ደግሞ ከወጣትነቱ ጀምሮ
ተዋጊ ነው" አለው። 34 ዳዊት ግን ሳኦልን፥ "አገልጋይህ የአባቴን በጎች እጠብቅ ነበር። አንበሳ ወይም ድብ መጥቶ ከመንጋው ጠቦት በሚወስድበት ጊዜ 35
በኋላው ተከትዬ እመታውና ከአፉ አስጠለው ነበር። ሊያጠቃኝ በተነሣብኝ ጊዜም ጉሮሮውን ይዤ እመታውና እገድለው ነበር። 36 አገልጋይህ አንበሳና ድብ
ገድያለሁ። የሕያው እግዚአብሔርን ሠራዊት ስለተገዳደረ ይህም ያልተገረዘ ፍልስጥኤማዊ ከእነርሱ እንደ አንዱ ይሆናል" አለው። 37 ዳዊትም፥ "እግዚአብሔር
ከአንበሳና ከድብ መዳፍ አድኖኛል። ከዚህም ፍልስጥኤማዊ እጅ ያድነኛል" አለው። 38 ከዚያም ሳኦል ዳዊትን፥ "ሂድ፥ እግዚአብሔርም ከአንተ ጋር ይሁን"
አለው። ሳኦል የራሱን የጦር መሣሪያ ለዳዊት አስታጠቀው። በራሱ ላይ የነሐስ ቁር ደፋለት፥ ጥሩርም አለበሰው። 39 ዳዊትም ሰይፉን በጦር ልብሱ ላይ
ታጠቀው። ነገር ግን አልተለማመደውምና ለመራመድ አቃተው። ከዚያም ዳዊት ሳኦልን፥ "አልተለማመድኳቸውምና በእነዚህ መዋጋት አልችልም" አለው።
ስለዚህ ዳዊት ከላዩ ላይ አወለቃቸው። 40 በትሩን በእጁ ያዘ፥ ከጅረቱም አምስት ድቡልቡል ድንጋዮች መርጦ በእረኛ ኮሮጆው ውስጥ ጨመራቸው።
ፍልስጥኤማዊውን በሚቀርብበት ጊዜ ወንጭፉን ይዞ ነበር። 41 ፍልስጥኤማዊውም በፊት ለፊቱ ከሚሄደው ጋሻ ጃግሬው ጋር መጥቶ ወደ ዳዊት ቀረበ። 42
ፍልስጥኤማዊው ዙሪያውን ሲመለከት ዳዊትን ባየው ጊዜ ቀይ፥ መልከ መልካም ገጽታ ያለው ትንሽ ልጅ ብቻ ስለነበረ ናቀው። 43 ፍልስጥኤማዊው ዳዊትን፥
"በትር ይዘህ የምትመጣብኝ እኔ ውሻ ነኝ?" አለው። ፍልስጥኤማዊውም በአማልክቶቹ ስም ዳዊትን ረገመው። 44 ፍልስጥኤማዊውም ዳዊትን፥ "ወደ እኔ ና፥
እኔም ሥጋህን ለሰማይ ወፎችና ለምድር አራዊት እሰጣለሁ" አለው። 45 ዳዊትም ለፍልስጥኤማዊው እንዲህ ሲል መለሰለት፥ "አንተ ሰይፍ፥ ጦርና ጭሬ ይዘህ
ትመጣብኛለህ። እኔ ግን አንተ ባቃለልከው፥ የእስራኤል ሠራዊት አምላክ በሆነው፥ በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ። 46 ዛሬ እግዚአብሔር በአንተ ላይ
ድልን ይሰጠኛል፥ እገድልሃለሁ፥ ራስህንም ከሰውነትህ ላይ አነሣዋለሁ። ዛሬ የፍልስጥኤምን ሠራዊት ሬሳ ለሰማይ ወፎችና ለምድር አራዊት እሰጣለሁ፥
ይኸውም ምድር ሁሉ በእስራኤል አምላክ እንዳለ እንዲያውቅና 47 በዚህ የተሰበሰበው ሁሉ እግዚአብሔር በሰይፍ ወይም በጦር ድልን እንደማይሰጥ
እንዲያውቁ ነው። ጦርነቱ የእግዚአብሔር ነውና እናንተንም በእጃችን ላይ አሳልፎ ይሰጣችኋል።" 48 ፍልስጥኤማዊው ተነሥቶ ዳዊትን በቀረበው ጊዜ ዳዊት
ሊገናኘው ወደ ጠላት ጦር በፍጥነት ሮጠ። 49 ዳዊት እጁን ወደ ኮሮጆው አስገብቶ አንድ ድንጋይ ከዚያ ወሰደ፥ ወነጨፈውና የፍልስጥኤማዊውን ግንባር
መታው። ድንጋዩም በፍልስጥኤማዊው ግንባር ውስጥ ጠልቆ ገባ፥ እርሱም በግንባሩ በምድር ላይ ተደፋ። 50 ዳዊት ፍልስጥኤማዊውን በወንጭፍና በድንጋይ
አሸነፈው። ፍልስጥኤማዊውንም መትቶ ገደለው። በዳዊት እጅ ሰይፍ አልነበረም። 51 ከዚያም ዳዊት ሮጠና በፍልስጥኤማዊው ላይ ቆመ፥ ከእርሱም ሰይፉን
ወሰደ፥ ከሰገባው አወጣና ገደለው፥ በእርሱም ራሱን ቆርጦ አነሣው። ፍልስጥኤማውያን ጀግናቸው መሞቱን ባዩ ጊዜ ሸሹ። 52 ከዚያም የእስራኤልና የይሁዳ
ሰዎች እልል እያሉ ተነሥተው ፍልስጥኤማውያንን እስከ ሸለቆውና እስከ ኤቅሮን መግቢያ ድረስ አሳደዷቸው። የፍልስጥኤማውያኑ ሬሳ ከሸዓራይም እስከ ጌትና
ዔቅሮን ድረስ በየመንገዱ ወድቆ ነበር። 53 የእስራኤል ሰዎች ፍልስጥኤማውያንን ከማሳደድ ተመለሱና የጦር ሰፈራቸውን በዘበዙ። 54 ዳዊት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የፍልስጥኤማዊውን ራስ ወስደ፥ ወደ ኢየሩሳሌምም አመጣው፥ የጦር መሣሪያውን ግን በድንኳኑ ውስጥ አኖረው። **55** ዳዊት ፍልስጥኤማዊውን ለመጋጠም ሲሄድ ሳኦል ባየው ጊዜ፥ የሰራዊቱን አዛዥ አበኔርን፥ "አንተ አበኔር፥ ይህ ወጣት የማን ልጅ ነው?" አለው። አበኔርም፥ "ንጉሥ ሆይ፥ በሕያውነትህ እምላለሁ፥ አላውቅም" አለው። **56** ንጉሡም፥ "የማን ልጅ እንደሆነ ምናልባት ሊያውቁት የሚችሉትን ጠይቅ" አለው። **57** ዳዊት ፍልስጥኤማዊውን ገድሎ በተመለሰ ጊዜ፥ አበኔር ወሰደው፥ የፍልስጥኤማዊውን ራስ በእጁ እንደያዘ ወደ ሳኦል አመጣው። **58** ሳኦልም፥ "አንተ ወጣት፥ የማን ልጅ ነህ?" አለው። ዳዊትም፥ "እኔ የቤተ ልሔማዊው የአገልጋይህ የእሴይ ልጅ ነኝ" ብሎ መለሰለት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 18

1 ለሳኦል መናገሩን በጨረሰ ጊዜ የዮናታን ነፍስ በዳዊት ነፍስ ታሰረች፥ ዮናታንም እንደ ራሱ ነፍስ አድርጎ ወደደው። **2** በዚያ ቀን ሳኦል ዳዊትን ወደ ራሱ አገልግሎት ወሰደው፤ ወደ አባቱ ቤት እንዲመለስ አላሰናበተውም። **3** ዮናታን ዳዊትን እንደ ራሱ ነፍስ አድርጎ ስለወደደው በመካከላቸው የወዳጅነት ቃል ኪዳን አደረጉ። **4** ዮናታን የለበሰውን ካባ አውልቆ ከጦር ልብሱ ጋር፥ እንዲሁም ሰይፉን፥ ቀስቱንና መታጠቂያውን ለዳዊት ሰጠው። **5** ዳዊት ሳኦል ወደሚልከው ቦታ ሁሉ ይሄድ ነበር፥ ይከናወንለትም ነበር። ሳኦልም በተዋጊዎቹ ላይ ሾመው። ይህም በሕዝቡ ዓይን ሁሉ ደግሞም በሳኦል አገልጋዮች ፊት ደስ የሚያሰኝ ሆነ። **6** ፍልስጥኤማውያንን ድል አድርገው ወደ መኖሪያቸው በመመለስ ላይ እያሉ ከእስራኤል ከተሞች ሁሉ ንጉሥ ሳኦልን ለመገናኘት፥ ሴቶች በከበሮና በሙዚቃ መሳሪያዎች በደስታ እየዘመሩና እየጨፈሩ መጡ። **7** ሴቶቹም ሲጫወቱ እየተቀባበሉ ይዘምሩ ነበር፤ እነርሱም፥ "ሳኦል ሺዎችን ገደል፥ ዳዊትም ዐሥር ሺዎችን ገደለ" እያሉ ዘመሩ። **8** ሳኦል እጅግ ተቆጣ፥ ይህም መዝሙር አስከፋው። እርሱም፥ "ለዳዊት ዐሥር ሺዎች አሉ፥ ለእኔ ግን ሺዎችን ብቻ። ታዲያ ከመንግሥት በቀር ምን ቀረው?" አለ። **9** ሳኦል ከዚያን ቀን ጀምሮ ዳዊትን በጥርጣሬ ዐይን ተመለከተው። **10** በቀጣዩ ቀን በሳኦል ላይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ክፉ መንፈስ መጣበት። እርሱም በቤት ውስጥ እንደ ዕብድ ይለፈልፍ ነበር። ስለዚህ ዳዊት በየቀኑ ያደርግ እንደነበረው በገናውን ይደረድር ነበር። ሳኦልም በእጁ ጦር ይዞ ነበር። **11** ሳኦል፥ "ዳዊትን ከግድግዳው ጋር አጣብቀዋለሁ" ብሎ በማሰብ ጦሩን ወረወረበት። ነገር ግን ዳዊት ከሳኦል ፊት ሁለት ጊዜ እንዲህ ባለ መንገድ አመለጠ። **12** እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር እንጂ ከእርሱ ጋር ስላልነበረ ሳኦል ዳዊትን ፈራው። **13** ስለዚህ ሳኦል ከፊቱ አራቀው፥ ሻለቃም አድርጎ ሾመው። በዚህ ሁኔታ ዳዊት በሕዝቡ ፊት ይወጣና ይገባ ነበር። **14** እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለነበረ ዳዊት የሚሠራው ሁሉ ይከናወንለት ነበር። **15** እንደ ተከናወነለት ሳኦል ባየ ጊዜ እጅግ ፈራው። **16** ነገር ግን በፊታቸው ይወጣና ይገባ ስለነበረ እስራኤልና ይሁዳ ሁሉ ዳዊትን ወደዱት። **17** ከዚያም ሳኦል ዳዊትን፥ "ትልቋ ልጄ ሜሮብ ይቹት። እርሷን እድርልሃለሁ። ብቻ ጎብዝልኝ፥ የእግዚአብሔርን ጦርነቶችም ተዋጋ" አለው። ሳኦል፥ "እጄ በእርሱ ላይ አይሁን፥ ነገር ግን የፍልስጥኤማውያን እጅ በእርሱ ላይ ይሁን" ብሎ አስቦአልና። **18** ዳዊትም ሳኦልን፥ "የንጉሥ አማች ለመሆን እኔ ማነኝ? ሕይወቴ ወይም የአባቴ ቤተ ሰብ በእስራኤል ውስጥ ምንድነው?" አለው። **19** ነገር ግን የሳኦል ልጅ ሜሮብ ለዳዊት የምትዳርበት ጊዜ ሲደርስ ለመሓላታዊው ለኤድሪኤል ተዳረች። **20** ነገር ግን የሳኦል ልጅ ሜልኮል ዳዊትን ወደደችው። ለሳኦል ነገሩት፥ ይህም እርሱን ደስ አሰኘው። **21** ከዚያም ሳኦል፥ "ወጥመድ እንድትሆነውና የፍልስጥኤማውያን እጅ በእርሱ ላይ እንድትሆን እርሷን እድርለታለሁ" ብሎ አሰበ። ስለዚህ ሳኦል ዳዊትን ለሁለተኛ ጊዜ፥ "አማቼ ትሆናለህ" አለው። **22** ሳኦል አገልጋዮቹን እንዲህ ሲል አዘዛቸው፥ "ዳዊትን በምስጢር እንዲህ በሉት፥ 'አስተውል፥ ንጉሡ በአንተ ደስ ብሎታል፥ አገልጋዮቹም ሁሉ ይወዱሃል። እንግዲያው የንጉሡ አማች ሁን'" **23** ስለዚህ የሳኦል አገልጋዮች ይህንን ቃል ለዳዊት ነገሩት። ዳዊትም፥ "እኔ ድሃና ብዙም የማልታወቅ ሰው ሆኜ እያለሁ የንጉሥ አማች እንድሆን ማሰባችሁ ጉዳዩ እንዴት ቀልሎ ታያችሁ?" አላቸው። **24** የሳኦል አገልጋዮችም ዳዊት የተናገረውን ቃል ነገሩት። **25** ሳኦልም፥ "ለዳዊት እንዲህ ትሉታላችሁ፥ 'የንጉሡን ጠላቶች ለመበቀል ከአንድ መቶ የፍልስጥኤማውያን ሸለፈት ብቻ በቀር ንጉሡ ምንም ጥሎሽ አይፈልግም'"። ዳዊት በፍልስጥኤማውያን እጅ እንዲወድቅ ለማድረግ ሳኦል አሰበ። **26** አገልጋዮቹ ይህንን ቃል ለዳዊት በነገሩት ጊዜ የንጉሡ አማች መሆን ዳዊትን ደስ አሰኘው። **27** እነዚያ ቀናት ከማብቃታቸው በፊት፥ ዳዊት ከሰዎቹ ጋር ሄዶ ሁለት መቶ ፍልስጥኤማውያንን ገደለ። ዳዊት የንጉሡ አማች ይሆን ዘንድ ሸለፈቶቹን አመጣ፥ ለንጉሡም ሙሉውን ቁጥር አስረከቡ። ስለዚህ ሳኦል ልጁን ሜልኮልን ዳረለት። **28** እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር እንደነበረ ሳኦል አየ፥ ዐወቀም። የሳኦል ልጅ ሜልኮልም ወደደችው። **29** ሳኦልም ዳዊትን የበለጠ ፈራው። ሳኦል የዳዊት ጠላቱ እንደሆነ ቀጠለ። **30** ከዚያም የፍልስጥኤም ልዑላን ብዙ ጊዜ ያደርጉት እንደነበረው ለጦርነት መጡ፥ ዳዊት ከሳኦል አገልጋዮች ሁሉ በበለጠ ሁኔታ የተሳካለት ሆነ፥ በመሆኑም ስሙ እጅግ የተከበረ ሆነ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 19

1 ሳኦል ልጁን ዮናታንን እና አገልጋዮቹን በሙሉ ዳዊትን እንዲገድሉት ነገራቸው። የሳኦል ልጅ ዮናታን ግን ዳዊትን እጅግ ይወድደው ነበር። 2 ስለዚህ ዮናታን
ዳዊትን፥ "አባቴ ሳኦል ሊገድልህ ይፈልጋል። በመሆኑም ለራስህ ጥንቃቄ አድርግ፥ በነገውም ቀን በምስጢራዊ ቦታ ተደበቅ። 3 አንተ ባለህበት አካባቢ ሄጄ
በአባቴ አጠገብ እቆማለሁ፥ ስለ አንተም አነጋግረዋለሁ። አንዳች ነገር ካገኘሁኝም እነግርሃለሁ“ አለው። 4 ዮናታንም ለአባቱ ለሳኦል ስለ ዳዊት መልካምን ነገር
ተናገረ፥ እንዲህም አለው፥”ንጉሡ በአገልጋዩ በዳዊት ላይ ክፉ ነገር አያድርግ። እርሱ ክፉ አላደረገብህም፥ እርሱ የሠራው ሥራ ለአንተ መልካም ሆኖልሃልና። 5
ነፍሱን በእጁ ላይ ጥሎ ፍልስጥኤማዊውን ገደለ። እግዚአብሔርም ለእስራኤል በሙሉ ታላቅ ድልን ሰጠ። አንተም አይተህ ደስ ብሎህ ነበር። ያለምንም
ምክንያት ዳዊትን በመግደልህ በንጹህ ደም ላይ ለምን ኃጢአት ትሠራለህ?“ 6 ሳኦልም ዮናታንን ሰማው። ሳኦልም፥”ሕያው እግዚአብሔርን! ዳዊት
አይገደልም“ ብሎ ማለ። 7 ከዚያም ዮናታን ዳዊትን ጠራው፥ ዮናታንም ይህንን ነገር ሁሉ ነገረው። ዮናታንም ዳዊትን ወደ ሳኦል አመጣው፥ እርሱም
እንደቀድሞው በፊቱ ነበረ። 8 እንደገናም ጦርነት ሆነ። ዳዊት ወጥቶ ከፍልስጥኤማውያን ጋር ተዋጋ፥ በታላቅ አገዳደልም ድል አደረጋቸው። እነርሱም ከፊቱ
ሸሹ። 9 ሳኦል በእጁ ጦሩን እንደያዘ በቤቱ ተቀምጦ እያለ ክፉ መንፈስ ከእግዚአብሔር ዘንድ በሳኦል ላይ መጣበት፥ ዳዊትም በገና ይደረድር ነበር። 10 ሳኦል
በጦሩ ዳዊትን ከግድግዳው ጋር ለማጣበቅ ሞከረ፥ ዳዊት ግን ከሳኦል ፊት ዘወር አለ፥ ስለዚህ የሳኦል ጦር በግድግዳው ላይ ተሰካ። በዚያ ምሽት ዳዊት ሸሽቶ
አመለጠ። 11 ሳኦልም በማግስቱ ይገድለው ዘንድ ከብበው እንዲጠብቁት ወደ ዳዊት ቤት መልዕክተኞች ላከ። የዳዊት ሚስት ሜልኮልም፥”በዚህ ሌሊት
ሕይወትህን ካላዳንክ ነገ መገደልህ ነው“ አለችው። 12 ስለዚህ ሜልኮል ዳዊትን በመስኮት እንዲወርድ አደረገችው። እርሱም ሄደ፥ ሸሽቶም አመለጠ። 13
ሜልኮልም የቤተሰቡን የጣዖት ምስል ወስዳ በአልጋው ውስጥ አጋደመችው። በራስጌው ከፍየል ጸጉር የተሠራ ትራስ አስቀመጠች፥ በልብስም ሸፈነችው። 14
ሳኦል ዳዊትን የሚወስዱ መልዕክተኞች በላከ ጊዜ እርሷ፥ "አሞታል" አለቻቸው። 15 ከዚያም ሳኦል ዳዊትን እንዲያዩት መልዕክተኞች ላከ፥ እርሱም፥
"እንድገድለው ከነዐልጋው አምጡልኝ" አላቸው። 16 መልዕክተኞቹ ወደ ቤት በገቡ ጊዜ፥ በዐልጋው ውስጥ የቤተሰቡ የጣዖት ምስል፥ በራስጌውም ከፍየል
ጸጉር የተሠራው ትራስ ነበር። 17 ሳኦል ሜልኮልን፥ "ጠላቴ እንዲሄድና እንዲያመልጥ በማድረግ ለምን አታለልሽኝ?" አላት። ሜልኮልም ለሳኦል፥ "'ልሂድ፥
አለበለዚያ እገድልሻለሁ' ስላለኝ ነው" ብላ መለሰችለት። 18 ዳዊትም ሸሽቶ አመለጠ፥ ሳሙኤል ወዳለበት ወደ ራማም ሄደ፥ ሳኦል ያደረገበትንም ሁሉ ነገረው።
ከዚያም እርሱና ሳሙኤል ሄዱ፥ በነዋትም ተቀመጡ። 19 ለሳኦልም፥ "ዕወቀው፥ ዳዊት በራማ ነዋት ነው" ተብሎ ተነገረው። 20 ሳኦልም ዳዊትን እንዲይዙት
መልዕክተኞችን ላከ። እነርሱም ትንቢት የሚናገሩ የነቢያትን ጉባዔ፥ ሳሙኤልንም መሪያቸው ሆኖ ባዩ ጊዜ በሳኦል መልዕክተኞች ላይ የእግዚአብሔር መንፈስ
መጣባቸው፥ እነርሱም ደግሞ ትንቢት ተናገሩ። 21 ይህ ሁኔታ ለሳኦል በተነገረው ጊዜ፥ ሌሎች መልዕክተኞችን ላከ፥ እነርሱም ደግሞ ትንቢት ተናገሩ። ስለዚህ
ሳኦል እንደገና ለሦስተኛ ጊዜ ሌሎች መልዕክተኞችን ላከ፥ እነርሱም ደግሞ ትንቢት ተናገሩ። 22 ከዚያም እርሱ ደግሞ ወደ አርማቴም ሄደ፥ በሜኩ ወዳለው
ጥልቅ የውሃ ጉድጓድም መጣ። እርሱም፥”ሳሙኤልና ዳዊት የት ነው ያሉት? “ ብሎ ጠየቀ። አንደኛው ሰው፥”በራማ ነዋት ናቸው“ ብሎ መለሰለት። 23
ሳኦልም በራማ ወዳለው ነዋት ሄደ። የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱም ላይ መጣ፥ በራማም ወደሚገኘው ወደ ነዋት እስኪደርስ ድረስ በመንገድ ላይ ትንቢት
ይናገር ነበር። 24 እርሱም ደግሞ ልብሶቹን አወለቀ፥ በሳሙኤል ፊት እርሱም ደግሞ ትንቢት ተናገረ፥ ያን ቀንና ሌሊቱን ሁሉ ራቁቱን ተጋደመ። እነርሱም፥”ሳኦል
ከነቢያት አንዱ ሆነ እንዴ? “ ያሉት በዚህ ምክንያት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 20

1 ከዚያም ዳዊት በራማ ካለው ከነዋት ሸሽቶ መጣና ዮናታንን፥”ምን አድርጌአለሁ? ጥፋቴስ ምንድነው? በአባትህ ፊት ኃጢአቴ ምን ቢሆን ነው ሕይወቴን
ለማጥፋት የሚፈልገው? “ አለው። 2 ዮናታንም ዳዊትን፥”ይህ ከአንተ ይራቅ፥ አትሞትም። ነገሩ ትልቅም ይሁን ትንሽ ሳይነግረኝ አባቴ ምንም አያደርግም።
አባቴ ይህንን ነገር ለምን ይደብቀኛል? ነገሩ እንዲህ አይደለም። 3 ዳዊት ግን እንደገና ማለና፥ “በፊትህ ሞገስ ማግኘቴን አባትህ ያውቃል። እርሱም፥ 'ይህንን
ዮናታን አይወቅ፥ ካልሆነ ያዝናል' ይላል። በሕያው እግዚአብሔር ስም፥ በሕያው ነፍስህም እምላለሁ፥ በእኔና በሞት መካከል የቀረው አንድ እርምጃ ነው"
አለው። 4 ዮናታን ዳዊትን፥ "የምትጠይቀኝን ሁሉ አደርግልሃለሁ" አለው። 5 ዳዊትም ዮናታንን፥ "ነገ አዲስ ጨረቃ የምትታይበት ቀን ነው፥ ከንጉሡ ጋር
ለመብላት መቀመጥ ይኖርብኛል። እስከ ሦስተኛው ቀን ምሽት ድረስ በመስኩ ውስጥ ሄጄ እንድደበቅ ፍቀድልኝ" አለው። 6 አባትህ እኔን በማጣቱ ከጠየቀህ፥
"ዳዊት፥ መላው ቤተ ሰቡ ዓመታዊ መሥዋዕት ስለሚያቀርቡ ወደ ቤተ ልሔም ይሄድ ዘንድ እንድፈቅድለት አጥብቆ ለመነኝ' በለው። 7 እርሱም፥ 'መልካም ነው'
ካለህ ነገሩ ለአገልጋይህ ሰላም ሆኗል ማለት ነው። ነገር ግን እርሱ እጅግ ከተቆጣ ክፉ ሊያደርግብኝ እንደወሰነ በዚህ ታውቃለህ። 8 እንግዲህ አገልጋይህን
በርኅራኄ ተመልከተኝ። በእግዚአብሔር ፊት ከአገልጋይህ ጋር ቃል ኪዳን አድርገሃልና። ኃጢአት ቢገኝብኝ ግን አንተው ግደለኝ፤ ለምንስ ወደ አባትህ
ትወስደኛለህ?" አለው። 9 ዮናታንም፥ "ይህ ከአንተ ይራቅ! አባቴ ክፉ ሊያደርግብህ መወሰኑን ባውቅ አልነግርህም?" 10 ዳዊትም ዮናታንን፥ "አባትህ አንደ
አጋጣሚ በቁጣ ቢመልስልህ ማን ይነግረኛል?" አለው። 11 ዮናታንም ዳዊትን፥ "ና፥ ወደ መስኩ እንሂድ" አለው። ሁለቱም ወደ መስኩ ሄዱ። 12 ዮናታንም
ዳዊትን እንዲህ አለው፥ "የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ምስክር ይሁን። ነገ ወይም በሦስተኛው ቀን እንደዚህ ባለው ሰዓት አባቴን በምጠይቀው ጊዜ፥ ስለ
ዳዊት በጎ አሳብ ካለው ልኬብህ አላሳውቅህም? 13 አባቴ በአንተ ላይ ክፉ ማድረጉ የሚያስደስተው ከሆነ በሰላም እንድትሄድ ባላሳውቅህና ባላሰናብትህ
እግዚአብሔር በዮናታን ላይ ይህንን እና ከዚህም የከፋውን ያድርግበት። ከአባቴ ጋር እንደነበረ እግዚአብሔር ከአንተም ጋር ይሁን። 14 አንተስ በሕይወት
በምኖርበት ዘመን እንዳልሞት የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታማኝነት አታሳየኝም? 15 እግዚአብሔር የዳዊትን ጠላቶች፥ እያንዳንዳቸውን ከምድር ላይ
በሚያጠፋበት ጊዜ የቃል ኪዳን ታማኝነትህን ከቤቴ አታጥፋ"። 16 ሰለዚህ ዮናታን ከዳዊት ቤት ጋር ቃል ኪዳን አደረገና”እግዚአብሔር ከዳዊት ጠላቶች እጅ
ይጠይቀው“ አለ። 17 ዮናታን ነፍሱን እንደሚወዳት ዳዊትን ይወደው ስለነበረ፥ ለእርሱ ከነበረው ፍቅር የተነሣ ዳዊት እንደገና እንዲምልለት አደረገ። 18 ከዚያም
ዮናታን እንዲህ አለው፥”ነገ አዲስ ጨረቃ የምትታይበት የወር መጀመሪያ ቀን ነው። ወንበርህ ባዶ ስለሚሆን ላትኖር ነው። 19 ለሦስት ቀናት ከቆየህ በኋላ፥
ፈጥነህ ውረድና በዚህ ጉዳይ ካሁን በፊት ወደተደበቅህበት ስፍራ መጥተህ በኤዜል ድንጋይ አጠገብ ቆይ። 20 በዒላማ ላይ የምወረውር መስዬ ሦስት
ፍላጻዎችን ወደዚያ አቅራቢያ እወረውራለሁ። 21 ከእኔ ጋር ያለውን ታዳጊ ወጣት እልከውና፥ 'ሂድ ፍላጻዎቹን ፈልግ' እለዋለሁ። ታዳጊውን ልጅ፥ 'ተመልከት፥
ፍላጻዎቹ አጠገብህ ናቸው፤ ውሰዳቸው' ካልኩት ሕያው እግዚአብሔርን! ለአንተ ደኅንነት እንጂ ጉዳት አይሆንብህምና ትመጣለህ። 22 ነገር ግን ታዳጊውን
ወጣት፥ 'ተመልከት፥ ፍላጻዎቹ ከአንተ በላይ ናቸው' ካልኩት እግዚአብሔር አሰናብቶሃልና መንገድህን ሂድ። 23 እኔና አንተ ያደረግነውን ስምምነት በሚመለከት
እግዚአብሔር በእኔና በአንተ መካከል ለዘላለም ምስክር ነው።" 24 ስለዚህ ዳዊት በመስኩ ውስጥ ተደበቀ። አዲስ ጨረቃ በሆነ ጊዜ ንጉሡ ምግብ
ለመብላት ተቀመጠ። 25 ንጉሡ እንደተለመደው በግድግዳው አጠገብ በነበረው በመቀመጫው ላይ ተቀመጠ። ዮናታን ተነሣ፥ አበኔርም በሳኦል አጠገብ
ተቀምጦ ነበር። የዳዊት ቦታ ግን ባዶ ነበር። 26 በዚያን ቀን ሳኦል ገና ምንም አልተናገረም፥ ምክንያቱም፥ "አንድ ነገር ደርሶበት ይሆናል፥ ወይም በሕጉ መሰረት
አልነጻም ይሆናል፤ በርግጥ ባይነጻ ነው" ብሎ ሳላሰበ ነው። 27 ነገር ግን አዲስ ጨረቃ በታየችበት ማግስት፥ በሁለተኛው ቀን የዳዊት ስፍራ ባዶ ነበር። ሳኦል
ልጁን ዮናታንን፥ "የእሴይ ልጅ ዳዊት ትላንትም ይሁን ዛሬ ወደ ማዕድ ያልመጣው ለምንድነው?" አለው። 28 ዮናታንም ለሳኦል እንዲህ በማለት መለሰለት፥
"ዳዊት ወደ ቤተ ልሔም ለመሄድ እንደፈቅድለት አጥብቆ ለመነኝ። 29 እርሱም፥ 'እባክህን እንድሄድ ፍቀድልኝ። በዚያ ከተማ ቤተሰባችን የሚያቀርበው
መሥዋዕት አለ፥ እኔም በዚያ እንድገኝ ወንድሜ አዞኛል። አሁንም በፊትህ ሞገስን ካገኘሁ፥ ወንድሞቼን አያቸው ዘንድ እንድሄድ እባክህን ፍቀድልኝ' አለኝ። ወደ
ንጉሡ ማዕድ ያልመጣው በዚህ ምክንያት ነው።" 30 ከዚያም የሳኦል ቁጣ በዮናታን ላይ ነደደ፥ እርሱም እንዲህ አለው፥ "አንተ የጠማማና አመጸኛ ሴት ልጅ!
ለራስህ ኃፍረትና ለእናትህ የዕርቃንነት ኃፍረት የእሴይን ልጅ እንደ መረጥክ የማላውቅ መሰለህ? 31 የእሴይ ልጅ በምድር ላይ እስካለ ድረስ አንተም ሆንክ
መንግሥትህ አትጸኑም። አሁንም በእርግጥ መሞት የሚገባው ነውና ልከህ አስመጣልኝ።“ 32 ዮናታንም አባቱን ሳኦልን፥”የሚገደለው በምን ምክንያት ነው?
ያደረገውስ ምንድነው? “ ሲል መለሰለት። 33 በዚያን ጊዜ ሳኦል ሊገድለው ጦሩን ወረወረበት። ስለዚህ አባቱ ዳዊትን ለመግደል መወሰኑን ዮናታን ተረዳ። 34
ዮናታን እጅግ ተቆጥቶ ከማዕድ ተነሣ፥ አባቱ ስላዋረደው ስለ ዳዊት አዝኖ ነበርና በወሩ በሁለተኛው ቀን ምንም ምግብ አልበላም። 35 በማግስቱ ዮናታን
ከዳዊት ጋር ወደተቀጣጠሩበት መስክ ሄደ፥ አንድ ታዳጊ ወጣትም አብሮት ነበር። 36 እርሱም ታዳጊውን ወጣት፥”ሩጥ፥ የምወረውራቸውን ፍላጻዎች ሰብስብ“
አለው። ታዳጊው ወጣት በሚሮጥበት ጊዜ ፍላጻውን ከበላዩ ላይ ወረወረው። 37 ታዳጊው ወጣት ዮናታን የወረወረው ፍላጻ ወደ ወደቀበት ስፍራ በደረሰ ጊዜ፥
ዮናታን ታዳጊውን ተጣርቶ፥ "ፍላጻው ከአንተ በላይ ነው" አለው። 38 ዮናታንም ታዳጊውን፥ "ቶሎ በል፥ ፍጠን፥ አትዘግይ!" አለው። ስለዚህ የዮናታኑ ታዳጊ
ወጣት ፍላጻዎቹን ሰብስቦ ወደ ጌታው መጣ። 39 ታዳጊው ወጣት ግን አንዳች የሚያውቀው አልነበረም። ጉዳዩን የሚያውቁት ዮናታንና ዳዊት ብቻ ነበሩ። 40
ዮናታን የጦር መሣሪያዎቹን ለታዳጊው ወጣት ሰጥቶ፥ "ሂድ፥ ወደ ከተማ ውሰዳቸው" አለው። 41 ታዳጊው ወጣት እንደ ሄደ፥ ዳዊት ከጉብታው ኋላ ተነሣ፥ ወደ
ምድርም ተጎንብሶ ሦስት ጊዜ ሰገደ። እርስ በእርሳቸው ተሳሳሙ፥ ተላቀሱም፥ ዳዊትም አብዝቶ አለቀሰ። 42 ዮናታንም ዳዊትን፥”'እግዚአብሔር፥ በእኔና በአንተ፥
በዘሬና በዘርህ መካከል ለዘላለም ይሁን' ተባብለን በእግዚአብሔር ስም ተማምለናልና በሰላም ሂድ” አለው። ከዚያም ዳዊት ተነሥቶ ሄደ፥ ዮናታንም ወደ ከተማ
ተመለሰ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 21

1 ከዚያም ዳዊት ካህኑን አቢሜሌክን ለማግኘት ወደ ኖብ መጣ። አቢሜሌክም ዳዊትን ለመገናኘት እየተንቀጠቀጠ መጣና፥ “አንድም ሰው አብሮህ ያልሆነውና ብቻህን የሆንከው ለምንደነው?” አለው። **2** ዳዊትም ካህኑን አቢሜሌክን፥ “ንጉሡ ለአንድ ጉዳይ ልኮኛል። እርሱም፥ 'ስለምልክህ ጉዳይና ያዘዝኩህን ነገር ማንም እንዳያውቅ'ብሎኛል። ወጣቶቹንም የሆነ ቦታ ላይ እንዲጠብቁኝ ነግሬአቸዋለሁ። **3** ታዲያ አሁን እጅህ ላይ ምን አለ? አምስት እንጀራ ወይም ያለውን ነገር ስጠኝ” አለው። **4** ካህኑም ለዳዊት መልሶ፥ “ማንኛውም ሰው የሚበላው እንጀራ የለኝም፥ ነገር ግን ታዳጊ ወጣቶቹ ራሳቸውን ከሴቶች ጠብቀው ከሆነ የተቀደሰ እንጀራ አለ” አለው። **5** ዳዊትም ለካህኑ እንዲህ ሲል መለሰለት፥ “በእርግጥ በእነዚህ ሦስት ቀናት ከሴቶች ተጠብቀናል። ለተራ ተልዕኮ በሚወጡበት ጊዜ ራሳቸውን ካነጹ ለዚህ ተልዕኮማ ከእኔ ጋር ያሉት ወጣቶች ሰውነት ለእግዚአብሔር እንዴት የበለጠ የተቀደሰ አይሆንም?” **6** ስለዚህ ከተነሣ በኋላ በስፍራው ትኩስ እንጀራ ይደረግ ዘንድ፥ ከእግዚአብሔር ፊት ከተነሣው፥ ከገጸ ሕብስቱ በስተቀር ሌላ እንጀራ በዚያ አልነበረምና፥ ካህኑ ለእግዚአብሔር የተቀደሰውን እንጀራ ሰጠው። **7** በዚያም ቀን ከሳኦል አገልጋዮች አንዱ በእግዚአብሔር ፊት በእዚያ ቆይቶ ነበር፤ ስሙ ዶይቅ የሚባል ኤዶማዊ፥ የሳኦል የእረኞቹ አለቃ ነበር። **8** ዳዊት አቢሜሌክን፥ "እዚህ ጦር ወይም ሰይፍ ይኖርሃል? የንጉሡ ጉዳይ አስቸኳይ ስለነበረ ሰይፌንም ሆነ መሣሪያዬን ይዤ አልመጣሁም“ አለው። **9** ካህኑም፥”በዔላ ሸለቆ የገደልከው የፍልስጥኤማዊው የጎልያድ ሰይፍ በጨርቅ ተጠቅልሎ እዚህ ከኤፉዱ ኋላ አለ። ሌላ የጦር መሣሪያ በዚህ የለምና እርሱን ልትወስደው ብትፈልግ ውሰደው።" ዳዊትም፥ "እንደ እርሱ ያለ ሌላ ሰይፍ የለም፤ እርሱን ስጠኝ" አለው። **10** በዚያን ቀን ዳዊት ተነሥቶ ከሳኦል ፊት ሸሸ፥ ወደ ጌት ንጉሥ ወደ አንኩስም ሄደ። **11** የአንኩስ አገልጋዮችም ንጉሡን፥ "ይህ የምድሪቱ ንጉሥ የሆነው ዳዊት አይደለም? 'ሳኦል ሺዎችን ገደለ፥ ዳዊት ዐሥር ሺዎችን ገደለ' እያሉ ስለ እርሱ በዘፈን እየተቀባበሉ ዘምረውለት አልነበረም? አሉት። **12** ዳዊት ይህንን ቃል በልቡ አኖረው፥ የጌትን ንጉሥ አንኩስንም እጅግ ፈራው። **13** በፊታቸውም አዕምሮውን ለወጠ፥ በያዙት ጊዜም እንደ ዕብድ ሆነ፤ የቅጥሩን በር እየቧጨረም ለሃጩን በጺሙ ላይ አዝረከረከ። **14** አንኩስም አገልጋዮቹን፥ “ተመልከቱ፥ ሰውዬው ዕብድ እንደሆነ ታያላችሁ። **15** ወደ እኔ ለምን አመጣችሁት? ይህንን ሰው በፊቴ እንዲያብድ ወደ እኔ ያመጣችሁት ያበዱ ሰዎችን ስላጣሁኝ ነው? በእርግጥ እንዲህ ያለው ሰው ወደ ቤቴ ይገባል?” አላቸው።

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 22

1 ስለዚህ ዳዊት ያንን ትቶ ወደ ዓዶላም ዋሻ አመለጠ። ወንድሞቹና የአባቱ ቤተሰብ በሙሉ ይህንን በሰሙ ጊዜ ወደዚያ ወደ እርሱ ወረዱ። **2** የተጨነቁ፥ ዕዳ ያለባቸውና የተከፉ ሁሉ ወደ እርሱ ተሰበሰቡ። ዳዊትም አዛዣቸው ሆነ። ከእርሱም ጋር ወደ አራት መቶ የሚጠጉ ሰዎች ነበሩ። **3** ዳዊት ከዚያ በሞዓብ ወዳለችው ወደ ምጽጳ ሄደ። እርሱም የሞዓብን ንጉሥ፥ “እግዚአብሔር የሚያደርግልኝን እስካውቅ ድረስ እባክህን አባቴና እናቴ አንተጋ እንዲኖሩ ፈቃድህ ይሁን” አለው። **4** እነርሱንም በሞዓብ ንጉሥ ዘንድ ተዋቸው። ዳዊት በጠንካራው ምሽግ ውስጥ በነበረበት ጊዜ ሁሉ አባቱና እናቱ ከንጉሡ ጋር ኖሩ። **5** ከዚያም ነቢዩ ጋድ ዳዊትን፥ “በጠንካራው ምሽግ ውስጥ አትቆይ። እርሱን ትተህ ወደ ይሁዳ ምድር ሂድ” አለው። ስለዚህ ዳዊት ያንን ትቶ ወደ ሔሬት ጫካ ሄደ። **6** ዳዊት ከእርሱ ጋር ከነበሩት ሰዎች ጋር መገኘቱን ሳኦል ሰማ። ሳኦል በጊብዓ ከአጣጥ ዛፍ ስር በእጁ ጦሩን እንደያዘ ተቀምጦ ነበር፥ አገልጋዮቹም ሁሉ በዙሪያው ቆመው ነበር። **7** ሳኦል በዙሪያው የቆሙትን አገልጋዮቹን እንዲህ አላቸው፥ “እናንተ የብንያም ሰዎች ሆይ፥ አሁን ስሙ! የእሴይ ልጅ ለእያንዳንዳችሁ እርሻና የወይን ቦታ ይሰጣችኋል? ሁላችሁም በእኔ ላይ ስላደማችሁበት ምትክ ሻለቆችና መቶ አለቆችስ አድርጎ ይሾማችኋል? **8** ልጄ ከእሴይ ልጅ ጋር ቃል ኪዳን ባደረገ ጊዜ ከእናንተ አንዱም አልነገረኝም። አንዳችሁም ስለ እኔ አላዘናችሁም። ልጄ አገልጋዬን ዳዊትን በእኔ ላይ ሲያነሣሣው ከእናንተ ማንም አልነገረኝም። ዛሬ ተደብቋል፥ እኔን ለማጥቃትም ይጠባበቃል።" **9** ከዚያም በሳኦል አገልጋዮች መካከል ቆሞ የነበረው ኤዶማዊው ዶይቅ፥ "የእሴይን ልጅ ወደ ኖብ፥ ወደ አኪጦብ ልጅ ወደ አቢሜሌክ መጥቶ አይቼዋለሁ። **10** አቤሜሌክም እግዚአብሔር ዳዊትን እንዲረዳው ጸለየለት፥ እርሱም ስንቅና የፍልስጥኤማዊውን የጎልያድን ሰይፍ ሰጠው" አለው። **11** ንጉሡም የአኪጦብን ልጅ ካህኑን አቢሜሌክንና የአባቱን ቤተሰብ በሙሉ፥ እንዲሁም በኖብ ይኖሩ የነበሩትን ካህናት እንዲጠራ መልዕክተኛ ላከ። ሁሉም ወደ ንጉሡ መጡ። **12** ሳኦልም፥ "የአኪጦብ ልጅ ሆይ፥ አሁን ስማ!" አለው። እርሱም፥ "ጌታዬ ሆይ፥ ይኸው አለሁ” ብሎ መለሰለት። **13** ሳኦልም እንዲህ አለው፥ “አንተና የእሴይ ልጅ በእኔ ላይ ያሤራችሁት ለምንድነው? ዛሬ እንደሚያደርገው ሁሉ በእኔ ላይ እንዲነሣና በምስጢራዊ ቦታ እንዲደበቅ እንጀራና ሰይፍ ሰጠኸው፥ ይረዳው ዘንድ ወደ እግዚአብሔር የጸለይክለት ለምንድነው?” **14** አቢሜሌክም ለንጉሡ፥ “የንጉሡ አማችና በጠባቂዎቹ ላይ የበላይ የሆነ፥ በቤትህም የተከበረ፥ በአገልጋዮችህ ሁሉ መካከል እንደ ዳዊት የታመነ ማነው? **15** እግዚአብሔር እንዲረዳው ስጸልይለት የዛሬው የመጀመሪያዬ ነውን? ይህ ከእኔ ይራቅ! ንጉሡ ምንም ነገር በአገልጋይህ ወይም በአባቴ ቤት ሁሉ ላይ አያኑር። አገልጋይህ ከዚህ ሁሉ ነገር አንዱንም አላውቅምና" ብሎ መለሰለት። **16** ንጉሡም፥ "አቢሜሌክ ሆይ፥ አንተና የአባትህ ቤት በሙሉ በእርግጥ ትሞታላችሁ" ብሎ መለሰለት። **17** ንጉሡም በዙሪያው የቆሙትን ጠባቂዎች፥ "መሸሹን እያወቁ አላስታወቁኝምና፥ እጃቸውም ከዳዊት ጋር ነውና፥ ዙሩና የእግዚአብሔርን ካህናት ግደሏቸው” አላቸው። የንጉሡ አገልጋዮች ግን የእግዚአብሔርን ካህናት ለመግደል እጆቻቸውን አላነሡም። **18** ከዚያም ንጉሡ ዶይቅን፥ "ዙርና ካህናቱን ግደላቸው" አለው። ስለዚህ ኤዶማዊው ዶይቅ ዞረና መታቸው፤ በዚያም ቀን ከተልባ እግር የተሠራ ኤፉድ የለበሱ ሰማንያ አምስት ሰዎችን ገደለ። **19** እርሱም የካህናቱን ከተማ ኖብን፥ ወንዶችንና ሴቶችን፥ ልጆችንና ሕፃናትን፥ በሬዎችን፥ አህዮችንና በጎችን በሰይፍ ስለት መታቸው። ሁሉንም በሰይፍ ስለት ገደላቸው። **20** ነገር ግን አብያታር የተባለው የአኪጦብ ልጅ፥ የአቢሜሌክ ልጅ አመለጠ፥ ወደ ዳዊትም ሸሸ። **21** አብያታርም ሳኦል የእግዚአብሔርን ካህናት እንደ ገደለ ለዳዊት ነገረው። **22** ዳዊትም አብያታርን፥ “ኤዶማዊው ዶይቅ በዚያ በነበረ ጊዜ በእርግጥ ለሳኦል እንደሚነግረው በዚያን ቀን ዐውቄ ነበር። ለአባትህ ቤተ ሰብ ሁሉ መሞት ተጠያቂው እኔ ነኝ! ። **23** ከእኔ ጋር ተቀመጥ፥ አትፍራ። ያንተን ነፍስ የሚፈልግ የእኔንም ነፍስ የሚፈልግ ነው። ከእኔ ጋር በሰላም ትኖራለህ” አለው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 23

1 ለዳዊትም፥ "ፍልስጥኤማውያን ቅዒላን በመውጋት ላይ ናቸው፥ ዐውድማውንም እየዘረፉ ነው“ ብለው ነገሩት። **2** ስለዚህ ዳዊት እግዚአብሔር እንዲረዳው ጸለየ፥ እርሱም፥”እነዚህን ፍልስጥኤማውያን ሄጄ ልምታቸው? “ ብሎ ጠየቀ። እግዚአብሔርም ዳዊትን፥”ሂድና ፍልስጥኤማውያንን ምታ፥ ቅዒላንም አድን“ አለው። **3** የዳዊት ሰዎችም፥”ተመልከት፥ እዚሁ በይሁዳ ሆነን እየፈራን ነው። በፍልስጥኤማውያን ላይ ወደ ቅዒላ ለመውጣትማ ይልቁን እንዴት አስፈሪ አይሆንብንም? “ አሉት። **4** ከዚያም ዳዊት እግዚአብሔር እንዲረዳው እንደገና ጸለየ። እግዚአብሔርም፥”ተነሥ፥ ወደ ቅዒላ ውረድ። በፍልስጥኤማውያን ላይ ድልን እሰጥሃለሁ“ ብሎ መለሰለት። **5** ዳዊትና ሰዎቹም ሄደው ከፍልስጥኤማውያን ጋር ተዋጉ። የቀንድ ከብቶቻቸውን ወሰዱ፥ እነርሱንም በታላቅ አገዳደል መቷቸው። ስለዚህ ዳዊት የቅዒላን ነዋሪዎች አዳናቸው። **6** የአቢሜሌክ ልጅ አብያታር ወደ ቅዒላ ወደ ዳዊት በሸሸ ጊዜ ኤፉዱን ይዞ ወርዶ ነበር። **7** ዳዊት ወደ ቅዒላ መሄዱ ለሳኦል ተነገረው። ሳኦልም፥ "በሮችና መቀርቀሪያዎች ወዳሏት ከተማ በመግባቱ በራሱ ላይ ዘግቷልና እግዚአብሔር በእጄ ላይ ጥሎታል" አለ። **8** ሳኦልም ወደ ቅዒላ ወርደው ዳዊትንና ሰዎቹን እንዲከቡ ሠራዊቱን ሁሉ ለጦርነት ጠራቸው። **9** ዳዊትም ሳኦል ክፉ ሊያደርግበት እንዳቀደ ዐወቀ። እርሱም ካህኑን አብያታርን፥ "ኤፉዱን ወደዚህ አምጣው" አለው። **10** ዳዊትም፥ "የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፥ ሳኦል በእኔ ምክንያት ከተማይቱን ለማጥፋት ወደ ቅዒላ ለመምጣት እንደሚፈልግ አገልጋይህ በእርግጥ ሰምቷል። **11** አገልጋይህ እንደ ሰማው፥ ሳኦል ወደዚህ ይወርዳል? የቅዒላ ሰዎችስ በእጁ አሳልፈው ይሰጡኝ ይሆን? የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፥ እባክህን ለአገልጋይህ እንድትነግረኝ እለምንሃለሁ” አለ። እግዚአብሔርም፥ “አዎን፥ ወደዚህ ይወርዳል” አለው። **12** ዳዊትም፥ “የቅዒላ ሰዎች እኔንና ሰዎቼን በሳኦል እጅ አሳልፈው ይሰጡናልን?” ብሎ ጠየቀው። እግዚአብሔርም፥ “አሳልፈው ይሰጧችኋል" አለ። **13** ከዚያም ዳዊትና ወደ ስድስት መቶ የሚደርሱ ሰዎቹ ተነሡ፥ ከቅዒላም ወጥተው ሄዱ፥ ከቦታ ቦታም እየተዘዋወሩ ሄዱ። ዳዊት ከቅዒላ መሸሹ ለሳኦል ተነገረው፥ እርሱም ማሳደዱን አቆመ። **14** ዳዊትም በዚፍ ምድረ በዳ ውስጥ ባለው በኮረብታማው አገር፥ በምድረ በዳው ባለ ምሽግ ውስጥ ኖረ። ሳኦል በየቀኑ ይፈልገው ነበር፥ እግዚአብሔር ግን በእጁ ላይ አልጣለውም። **15** ዳዊት በዚፍ ምድረ በዳ ሖሬሽ በተባለ ቦታ ነበር፤ ሳኦልም የእርሱን ሕይወት ለማጥፋት እንደ ወጣ አየ። **16** ከዚያም የሳኦል ልጅ ዮናታን ተነሥቶ በሖሬሽ ወደሚገኘው ወደ ዳዊት ሄደ፥ በእግዚአብሔር ስም አበረታታው። **17** እንዲህም አለው፥ "የአባቴ የሳኦል እጅ አያገኝህምና አትፍራ። አንተ በእስራኤል ላይ ንጉሥ ትሆናለህ፥ እኔም ምክትልህ እሆናለሁ። አባቴ ሳኦልም ደግሞ ይህንን ያውቃል።" **18** እነርሱም በእግዚአብሔር ፊት ቃል ኪዳን አደረጉ። ዳዊት በሖሬሽ ቆየ፥ ዮናታንም ወደ ቤቱ ተመለሰ። **19** ዚፋውያንም በጊብዓ ወዳለው ወደ ሳኦል መጥተው፥ "ዳዊት ከየሴሞን በስተደቡብ በሚገኘው በኤኬላ ኮረብታ ላይ፥ በሖሬሽ ምሽጎች ውስጥ በመካከላችን ተደብቋል፤ **20** አሁንም ንጉሥ ሆይ! ወደዚህ ውረድ፥ ደስ ባለህ ጊዜ ወደዚህ ውረድ! በንጉሡ እጅ አሳልፎ የመስጠቱ ድርሻ የእኛ ይሆናል” አሉት። **21** ሳኦልም፥ “ስለ እኔ ተቆርቁራችኋልና እግዚአብሔር ይባርካችሁ። **22** ሂዱና በይበልጥ እርግጠኛ ሁኑ። የት እንደ ተደበቀና በዚያ ማን እንዳየው መርምሩና ዕወቁ። እጅግ ተንኮለኛ ስለመሆኑ ተነግሮኛል። **23** ስለዚህ ልብ በሉ፥ ራሱን የሚደብቅባቸውን ቦታዎች በሙሉ መርምሩ። የተረጋገጠ መረጃ ይዛችሁልኝ ተመለሱ፥ ከዚያ በኋላ እኔም ከእናንተ ጋር እሄዳለሁ። በምድሪቱ ላይ ካለ፥ በይሁዳ ሺዎች ሁሉ መካከል እፈልገዋለሁ” አላቸው። **24** እነርሱም ተነሡ፥ ሳኦልንም ቀድመው ወደ ዚፍ ሄዱ። ዳዊትና ሰዎቹ ከየሴሞን በስተደቡብ በዓረባ በምትገኘው በማዖን ምድረ በዳ ውስጥ ነበሩ። **25** ሳኦልና ሰዎቹም እርሱን ሊፈልጉት ሄዱ። ይህም ለዳዊት ተነገረው፥ ስለዚህ ወደ ዐለታማው ኮረብታ ወርዶ በማዖን ምድረ በዳ ውስጥ ኖረ። ሳኦል በሰማ ጊዜ ዳዊትን በማዖን ምድረ በዳ አሳደደው። **26** ሳኦል በተራራው በአንዱ ወገን ሄደ፥ ዳዊትና ሰዎቹም በተራራው በወዲያኛው ወገን ይሄዱ ነበር። ዳዊት ከሳኦል ለማምለጥ ተቻኮለ። ሳኦልና ሰዎቹ ዳዊትንና ከእርሱ ጋር የነበሩትን ሰዎች ለመያዝ እየከበቧቸው በነበሩበት ጊዜ **27** አንድ መልዕክተኛ ወደ ሳኦል መጥቶ፥ “ፍልስጥኤማውያን ምድሪቱን ወረዋታልና ፈጥነህ ና" አለው። **28** ስለዚህ ሳኦል ዳዊትን ከማሳደድ ተመልሶ ፍልስጥኤማውያንን ለመዋጋት ሄደ። በዚህ ምክንያት ያ ስፍራ የማምለጫ ዐለት ተብሎ ተጠራ። **29** ዳዊት ከዚያ ወጥቶ በዓይንጋዲ ባሉ ምሽጎች ውስጥ ኖረ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 24

1 ሳኦል ፍልስጥኤማውያንን ከማሳደድ በተመለሰ ጊዜ፥ "ዳዊት በዓይንጋዲ ምድረ በዳ ውስጥ ነው" ተብሎ ተነገረው። 2 ከዚያም ሳኦል ከእስራኤል ሁሉ
የተመረጡትን ሦስት ሺህ ሰዎች ይዞ ዳዊትንና ሰዎቹን ለመፈለግ ወደ ዓይንጋዲ ሄደ። 3 እርሱም በመንገዱ በበጎች ማደሪያ አቅራቢያ ወደነበረ ዋሻ መጣ።
ሳኦልም ለመጸዳዳት ወደዚያ ገባ። ዳዊትና ሰዎቹ በዋሻው ውስጥ ከኋላ ጥጉጋ ተቀምጠው ነበር። 4 የዳዊት ሰዎችም፥ "'ደስ ያሰኘህን እንድታደርግበት
ጠላትህን በእጅህ ላይ አሳልፌ እሰጥሃለሁ' ባለህ ጊዜ እግዚአብሔር የተናገረው ስለዚህ ቀን ነው” አሉት። ከዚያም ዳዊት ተነሥቶ በጸጥታ በደረቱ እየተሳበ
ወደ ፊት በመሄድ የሳኦልን የካባውን ጫፍ ቆረጠው። 5 ከዚህ በኋላ የሳኦልን የካባውን ጫፍ ስለ ቆረጠ ዳዊትን ኅሊናው ወቀሰው። 6 እርሱም ሰዎቹን፥
"እግዚአብሔር በቀባው በጌታዬ ላይ እጄን በማንሣት እንዲህ ያለውን ነገር ማድረግን እግዚአብሔር ከእኔ ያርቀው" አላቸው። 7 ስለዚህ ዳዊት የእርሱን ሰዎች
በዚህ ቃል ገሰጻቸው፥ በሳኦል ላይ አደጋ እንዲጥሉበት አልፈቀደላቸውም። ሳኦል ተነሥቶ ከዋሻው ወጣና መንገዱን ቀጠለ። 8 ከዚህ በኋላ ዳዊት ተነሥቶ
ከዋሻው በመውጣት ሳኦልን፥ "ጌታዬ፥ ንጉሥ ሆይ!" በማለት ተጣራ። ሳኦል ወደ ኋላው ዘወር ብሎ በተመለከተ ጊዜ፥ ዳዊት በመስገድ አክብሮትን አሳየው። 9
ዳዊትም ሳኦልን፥ “ 'ዳዊት ሊጎዳህ ይፈልጋል' የሚሉህን ሰዎች ለምን ትሰማቸዋለህ? 10 በዋሻው በነበርን ጊዜ እግዚአብሔር ዛሬ እጄ ላይ ጥሎህ እንደነበረ
ዓይኖችህ አይተዋል። አንዳንዶቹ እንድገድልህ ነግረውኝ ነበር፥ እኔ ግን ራራሁልህ። እኔም፥ 'በእግዚአብሔር የተቀባ ስለሆነ፥ በጌታዬ ላይ እጄን አላነሣም'
አልኩኝ። 11 አባቴ ሆይ ተመልከት፥ በእጄ ላይ ያለውን የካባህን ቁራጭ ተመልከት። የካባህን ጫፍ ቆረጥኩኝ እንጂ አልገደልኩህም፥ በመሆኑም በእጄ ላይ
ክፋትና ክህደት እንደሌለ ዕወቅ፤ ምንም እንኳን ሕይወቴን ለማጥፋት ብታሳድደኝም፥ እኔ አልበደልኩህም። 12 እግዚአብሔር በእኔና በአንተ መካከል ይፍረድ፥
እግዚአብሔር ይበቀልልኝ፥ እጄ ግን ባንተ ላይ አትሆንም። 13 የጥንቱ ምሳሌ፥ 'ከክፉ ሰው ክፋት ይወጣል' ይላል። እጄ ግን ባንተ ላይ አትሆንም። 14
የእስራኤል ንጉሥ የወጣው በማን ላይ ነው? የምታሳድደው ማንን ነው? የሞተን ውሻ! ቁንጫን! 15 እግዚአብሔር ፈራጅ ይሁን፥ በእኔና በአንተ መካከል
ይመልከት፥ ይፍረድም፥ ጉዳዬን ተመልክቶም ከእጅህ እንዳመልጥ ይርዳኝ።” 16 ዳዊት ይህንን ቃል ለሳኦል ተናግሮ በጨረሰ ጊዜ፥ ሳኦል፥ “ልጄ ዳዊት! ይህ
ድምፅህ ነው?” አለው። ሳኦልም ድምፁን አሰምቶ አለቀሰ። 17 እርሱም ዳዊትን እንዲህ አለው፥ "በክፋት ስመልስልህ በደግነት መልሰህልኛልና ከእኔ ይልቅ
አንተ ጻድቅ ነህ። 18 እግዚአብሔር በእጅህ ላይ በጣለኝ ጊዜ አልገደልከኝምና በጎነትን እንዳደረግህልኝ ዛሬ አሳይተሃል። 19 አንድ ሰው ጠላቱን ቢያገኘው
በሰላም ያሰናብተዋል? ዛሬ ስላደረግህልኝ ነገር እግዚአብሔር ቸርነትን ያድርግልህ። 20 አሁንም፥ በእርግጥ ንጉሥ እንደምትሆንና የእስራኤል መንግሥት
በእጅህ እንደሚጸና ዐውቃለሁ። 21 ከእኔ በኋላ ዘሮቼን እንደማታጠፋና ስሜንም ከአባቴ ቤት እንደማትደመስሰው በእግዚአብሔር ማልልኝ።" 22 ስለዚህ ዳዊት
ለሳኦል ማለለት። ከዚያም ሳኦል ወደ ቤቱ ሄደ፥ ዳዊትና ሰዎቹ ግን ወደ አምባው ወጡ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 25

1 ሳሙኤል ሞተ። እስራኤላውያን ሁሉ ተሰብስበው አለቀሱለት፥ በራማም በቤቱ ቀበሩት። ከዚያም ዳዊት ተነሥቶ ወደ ፋራን ምድረ በዳ ወረደ። 2 በማዖን አንድ
ሰው ነበር፥ ንብረቱም በቀርሜሎስ ይኖር ነበር። ሰውዬው እጅግ ባለጸጋ ነበር። እርሱም ሦስት ሺህ በጎችና አንድ ሺህ ፍየሎች ነበሩት። በቀርሜሎስም በጎቹን
ይሸልት ነበር። 3 የሰውየው ስም ናባል፥ የሚስቱም ስም አቢግያ ነበር። ሴቲቱ ብልህና መልኳም የተዋበ ነበረች። ሰውየው ግን አስቸጋሪና በምግባሩ ክፉ ነበር።
እርሱም የካሌብ ቤተ ሰብ ተወላጅ ነበር። 4 ዳዊት በምድረ በዳ ውስጥ ሳለ ናባል በጎቹን እንደሚሸልት ሰማ። 5 ስለዚህ ዳዊት ዐሥር ወጣቶችን ላከ። ዳዊትም
ወጣቶቹን እንዲህ አላቸው፥ “ወደ ቀርሜሎስ ውጡ፥ ወደ ናባልም ሂዱና በስሜ ሰላምታ አቅርቡለት። 6 እርሱንም እንዲህ በሉት፥ 'በብልጽግና ኑር፥ ሰላም ላንተ፥
ለቤትህና ያንተ ለሆነው ሁሉ ይሁን። 7 ሸላቾች እንዳሉህ ሰምቻለሁ። እረኞችህ ከእኛ ጋር ነበሩ፥ ምንም ጉዳት አላደረስንባቸውም፥ በቀርሜሎስ በነበሩበት ጊዜ
ሁሉ አንድም አላጡም። 8 ወጣቶችህን ጠይቃቸው፥ እነርሱም ይነግሩሃል። አሁንም በግብዣህ ቀን መጥተናልና ወጣቶቼ በዓይንህ ፊት ሞገስ ያግኙ። በእጅህ
ያለውን ማንኛውንም ነገር ለአገልጋዮችህና ለልጅህ ለዳዊት እባክህን ስጠው።" 9 የዳዊት ወጣቶች በደረሱ ጊዜ፥ በዳዊት ስም ይህንን ሁሉ ለናባል ነገሩትና
ምላሹን ጠበቁ። 10 ናባልም ለዳዊት አገልጋዮች፥ "ዳዊት ማነው? የእሴይስ ልጅ ማነው? በእነዚህ ቀናት ከጌቶቻቸው የሚኮበልሉ ብዙ አገልጋዮች አሉ። 11
ታዲያ እንጀራዬን፥ ውሃዬንና ለሸላቾቼ ያረድኩትን ሥጋ ወስጄ ከየት እንደ መጡ ለማላውቃቸው ሰዎች መስጠት ይኖርብኛል?" ሲል መለሰላቸው። 12 ስለዚህ
የዳዊት ወጣቶች ዞረው በመመለስ የተባለውን ሁሉ ነገሩት። 13 ዳዊትም ሰዎቹን፥ "ሁሉም ሰው ሰይፉን ይታጠቅ" አለ። ስለዚህ ሁሉም ሰይፎቻቸውን ታጠቁ።
ዳዊትም ደግሞ ሰይፉን ታጠቀ። አራት መቶ የሚያህሉ ሰዎች ዳዊትን ተከተሉት፥ ሁለት መቶዎቹም ከስንቅና ትጥቃቸው ጋር ቆዩ። 14 ነገር ግን ከወጣቶቹ
አንዱ፥ ለናባል ሚስት ለአቢግያ እንዲህ ሲል ነገራት፥”ዳዊት ከምድረ በዳ ለጌታችን ሰላምታ ለማቅረብ መልዕክተኞች ላከ፥ ጌታችን ግን ሰደባቸው። 15 ሰዎቹ
ግን ለእኛ በጣም ጥሩዎች ነበሩ። በመስኩ ላይ እያለን ከእነርሱ ጋር በሄድንበት ጊዜ ሁሉ አንድም አልጎደለብንም፥ እነርሱም አልጎዱንም። 16 በጎቹን እየጠበቅን
ከእነርሱ ጋር በቆየንበት ጊዜ ሁሉ ቀንና ሌሊት አጥር ሆነውልን ነበር። 17 በጌታችንና በቤተሰቡ ሁሉ ላይ ክፉ ታስቦአልና ይህንን ዕወቂ፥ ምን ማድረግ
እንዳለብሽም አስቢበት። እርሱ የሚረባ ሰው አይደለምና ማንም ሊያነጋግረው አይችልም“። 18 አቢግያም ፈጥና ሁለት መቶ እንጀራ፥ ሁለት ጠርሙስ የወይን
ጠጅ፥ ቀደም ብሎ የተዘጋጀ አምስት በግ፥ አምስት መስፈሪያ የተጠበሰ እሸት፥ አንድ መቶ የወይን ዘለላና ሁለት መቶ የበለስ ፍሬ ጥፍጥፍ ወስዳ በአህዮች ላይ
ጫነች። 19 ከእርሷ ጋር የነበሩትንም ወጣቶች፥ "በፊቴ ቅደሙ፥ እኔም እከተላችኋለሁ" አለቻቸው። ለባልዋ ለናባል ግን አልነገረችውም። 20 እርሷም በአህያዋ
ላይ በመቀመጥ ተራራውን ተከልላ በመውረድ ላይ እያለች ዳዊትና ሰዎቹ ወደ እርሷ ወረዱ፥ እርሷም አገኘቻቸው። 21 ዳዊትም፥”የእርሱ ከሆነው ሁሉ አንድ
እንኳን እንዳይጠፋበት፥ ይህ ሰው የነበረውን ሁሉ በምድረ በዳ መጠበቄ በእርግጥም በከንቱ ነበር፥ ስላደረግሁት በጎነት ክፋትን መልሶልኛልና። 22 ነገ ጠዋት
የእርሱ ከሆነው ሁሉ አንድ ወንድ እንኳን ባስቀርለት እግዚአብሔር በእኔ በዳዊት ላይ ይህንኑ ያድርግብኝ፥ ደግሞም ይጨምርብኝ" ብሎ ነበር። 23 አቢግያ
ዳዊትን ባየችው ጊዜ፥ ከአህያዋ ላይ ፈጥና ወረደች፥ በዳዊትም ፊት አጎንብሳ ወደ ምድር ሰገደች። 24 በእግሩ ላይ ወድቃም እንዲህ አለችው፥ "ጌታዬ ሆይ፥
በደሉ በእኔ ላይ ብቻ ይሁን። እባክህን አገልጋይህ እንድናገርህ ፍቀድልኝ፥ የአገልጋይህንም ቃል ስማ። 25 ጌታዬ ለዚህ ለማይረባው ናባል ትኩረት አይስጥ፥
እርሱ እንደ ስሙ ነው። ስሙ ናባል ነውና ጅልነትም ከእርሱ ጋር ነው። እኔ አገልጋይህ ግን የላካቸውን የጌታዬን ወጣቶች አላየሁም። 26 አሁንም ጌታዬ ሆይ፥
በሕያው እግዚአብሔር ስም፥ በሕያው ነፍስህም እምላለሁ፤ ደም ከማፍሰስና በራስህ እጅ ከመበቀል እግዚአብሔር አግዶሃልና፥ አሁንም ጠላቶችህና በጌታዬ
ላይ ክፉ ለማድረግ የሚፈልጉ እንደ ናባል ይሁኑ። 27 አሁንም አገልጋይህ ወደ ጌታዬ ያመጣሁት ይህ ስጦታ ጌታዬን ለሚከተሉ ወጣቶች ይሰጥ። 28 እባክህን
የአገልጋይህን መተላለፍ ይቅር በል፥ አንተ ጌታዬ፥ የእግዚአብሔርን ጦርነት በመዋጋት ላይ ስላለህ፥ እግዚአብሔር በርግጥ ለጌታዬ እውነተኛ የሆነን ቤት
ይሠራል፥ በሕይወት ዘመንህም ሁሉ ክፋት አይገኝብህም። 29 ሰዎች ተነሥተው ሕይወትህን ለማጥፋት ቢያሳድዱህም የጌታዬ ሕይወት በአምላክህ
በእግዚአብሔር በሕያዋን አንድነት የታሰረች ትሆናለች፤ እርሱም የጠላቶችህን ሕይወት ከወንጭፍ ኪስ እንደሚወረወር፥ በወንጭፍ ይወረውራል። 30 ይህ በሆነ
ጊዜ፥ እግዚአብሔር ተስፋ የሰጠህን መልካም ነገር ሁሉ ለጌታዬ በፈጸመ ጊዜ፥ በእስራኤልም ላይ መሪ ባደረገህ ጊዜ፥ 31 ይህ ጉዳይ ሐዘን አይሆንብህም፥
ለጌታዬም የልብ ጸጸት አይሆንም፥ ያለ ምክንያት ደም ያፈሰስክ፥ በራስህም እጅ የተበቀልክ አትሆንም። እግዚአብሔር ለጌታዬ ስኬትን ባመጣልህ ጊዜ
አገልጋይህን አስበኝ።" 32 ዳዊትም አቢግያን፥ "ዛሬ እንድታገኚኝ የላከሽ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ቡሩክ ይሁን። 33 ደም በማፍሰስ ከሚሆን በደልና
በራሴ እጅ ስለ ራሴ ከመበቀል ጠብቀሽኛልና ጥበብሽ የተባረከ ነው፥ አንቺም የተባረክሽ ነሽ። 34 በእውነት፥ አንቺን ከመጉዳት የጠበቀኝ የእስራኤል አምላክ
ሕያው እግዚአብሔርን፥ እኔን ለመገናኘት ፈጥነሽ ባትመጪ ኖሮ፥ ያለምንም ጥርጥር ነገ ጠዋት ለናባል አንድ ወንድ ሕፃን ልጅ አይቀርለትም ነበር“ አላት። 35
ስለዚህ ዳዊት ያመጣችለትን ከእጇ ተቀበላት፤ እርሱም፥ "ወደ ቤትሽ በሰላም ሂጂ፤ ይኸው ቃልሽን ሰማሁ፥ ተቀበልኩሽም" አላት። 36 አቢግያም ተመልሳ ወደ
ናባል ሄደች፤ እርሱም የንጉሥ ግብዣን የመሰለ ግብዣ በቤቱ ያደርግ ነበር፤ ናባልም በጣም ሰከሮ፥ ልቡም ደስ ብሎት ነበር። ስለዚህ እስኪነጋ ድረስ ምንም
ነገር አልነገረችውም። 37 ከነጋ በኋላ፥ የናባል ስካር በበረደ ጊዜ፥ ሚስቱ እነዚህን ነገሮች ነገረችው፤ ልቡ ቀጥ አለ፥ እርሱም እንደ ድንጋይ ሆነ። 38 ዐሥር ቀን
ካለፈ በኋላ እግዚአብሔር ናባልን ስለመታው ሞተ። 39 ናባል መሞቱን ዳዊት በሰማ ጊዜ፥”የመሰደቤን ምክንያት ከናባል እጅ የተቀበለና አገልጋዩን ከክፉ
የጠበቀ ጌታ እግዚአብሔር ቡሩክ ይሁን። እርሱም የናባልን ክፉ ሥራ በራሱ ላይ መለሰበት“ አለ። ከዚያም ዳዊት ወደ አቢግያ መልዕክተኛ ልኮ ሚስት አድርጎ
ሊወስዳት አናገራት። 40 የዳዊት አገልጋዮች ወደ ቀርሜሎስ፥ ወደ አቢግያ በመጡ ጊዜ፥ "ሚስቱ እንድትሆኚው ልንወስድሽ ዳዊት ወዳንቺ ልኮናል" አሏት። 41
እርሷም ተነሣች፥ በግምባርዋ ወደ ምድር ሰግዳ፥ "ይኸው፥ ሴት አገልጋይህ፥ የጌታዬን አገልጋዮች እግር የማጥብ አገልጋይ ነኝ" አለች። 42 አቢግያም ፈጥና
ተነሣች፥ ከተከተሏት ከአምስት ሴት አገልጋዮቿ ጋር በአህያ ተቀመጠች፥ የዳዊትን መልዕክተኞች ተከትላ ሄደች፥ ሚስትም ሆነችው። 43 በተጨማሪም ዳዊት
ኢይዝራኤላዊቱን አኪናሆምን ሚስት እንድትሆነው ወሰዳት፥ ሁለቱም ሚስቶቹ ሆኑ። 44 ሳኦል የዳዊት ሚስት የነበረችውን ልጁን ሜልኮልን፥ በጋሊም ለሚኖረው
ለሌሳ ልጅ ለፈልጢ ሰጥቶ ነበር።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 26

1 ዚፋውያን ወደ ሳኦል ወደ ጊብዓ መጥተው፥ “ዳዊት በምድረ በዳው ፊት ለፊት በኤኬላ ኮረብታ ላይ ተደብቋል?” አሉት። 2 ከዚያም ሳኦል ተነሣ፥ ከእስራኤል
የተመረጡትን ሦስት ሺህ ሰዎች ይዞ ዳዊትን ለመፈለግ ወደ ዚፍ ምድረ በዳ ወረደ። 3 ሳኦልም በምድረ በዳው ፊት ለፊት ባለው በኤኬላ ኮረብታ ላይ፥
በመንገዱ ዳር ሰፈረ። ዳዊት ግን በምድረ በዳው ቆይቶ ነበር፥ ሳኦል በምድረ በዳው ከበስተኋላው እንደመጣ አየ። 4 ስለዚህ ዳዊት ሰላዮችን ላከና በርግጥም
ሳኦል በመምጣት ላይ መሆኑን ዐወቀ። 5 ዳዊት ተነሥቶ ሳኦል ወደ ሰፈረበት ስፍራ ሄደ፤ ሳኦልና የሰራዊቱ አዛዥ የኔር ልጅ አበኔር የተኙበትን ስፍራ አየ፤ ሳኦል
በሰፈሩ ውስጥ ተኝቶ ነበር፥ ሕዝቡም በዙሪያው ሰፍሮ ነበር፥ ሁሉም እንቅልፍ ወስዷቸው ነበር። 6 ከዚያም ዳዊት ኬጢያዊውን አቢሜሌክንና የኢዮአብን ወንድም
የጽሩያን ልጅ አቢሳን፥ "ወደ ሳኦል ወደ ጦር ሰፈሩ ውስጥ ከእኔ ጋር የሚወርድ ማነው?" አላቸው። አቢሳም፥ "እኔ ከአንተ ጋር እወርዳለሁ" አለው። 7 ስለዚህ
ዳዊትና አቢሳ በሌሊት ወደ ሰራዊቱ ሄዱ። ሳኦል በሰፈሩ መካከል ተኝቶ፥ ጦሩም ከራስጌው በምድር ላይ ተተክሎ ነበር። አበኔርና ወታደሮቹ በዙሪያው ተኝተው
ነበር። 8 አቢሳም ዳዊትን፥ "እግዚአብሔር ዛሬ ጠላትህን በእጅህ ላይ ጣለው። አሁንም፥ በአንድ ምት ብቻ በጦር ከምድር ጋር እንዳጣብቀው ፍቀድልኝ፥ ሁለተኛ
መምታትም አያስፈልገኝም" አለው። 9 ዳዊትም አቢሳን እንዲህ አለው፥ "አትግደለው፤ እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጁን ዘርግቶ ከበደል መንጻት የሚችል
ማነው? 10 ሕያው እግዚአብሔርን! እግዚአብሔር ራሱ ይገድለዋል፥ ወይም ቀኑ ደርሶ ይሞታል፥ ወይም ወደ ጦርነት ሄዶ ይሞታል። 11 እርሱ በቀባው ላይ እጁን
ማንሣትን እግዚአብሔር ከእኔ ያርቀው፤ አሁን ግን፥ በራስጌው ያለውን ጦርና የውሃውን ኮዳ ይዘህ እንድንሄድ እለምንሃለሁ።" 12 ስለዚህ ዳዊት በሳኦል ራስጌ
የነበረውን ጦርና የውሃ ኮዳ ወሰደና ሄዱ። ከእግዚአብሔር ከባድ እንቅልፍ ስለወደቀባቸው ሁሉም አንቀላፍተው ነበርና አንድም የነቃ፥ ያየ ወይም ያወቀ
አልነበረም። 13 ከዚያም ዳዊት በሌላኛው ወገን ወጣ፥ በተራራው ጫፍ ላይም ርቆ ቆመ፤ በመካከላቸው ሰፊ ርቀት ነበረ። 14 ዳዊትም ወደ ኔር ልጅ ወደ
አበኔርና ወደ ሕዝቡ ጮኾ፥ "አበኔር ሆይ፥ አትመልስምን?" አለው። አበኔርም፥ "በንጉሡ ላይ የምትጮኸው አንተ ማነህ?" ብሎ መለሰለት። 15 ዳዊትም
አበኔርን፥ "አንተ ጀግና አይደለህም? በእስራኤልስ አንተን የሚመስልህ ማነው? ታዲያ ጌታህን ንጉሡን ያልጠበቅኸው ለምንድነው? አንድ ሰው ጌታህን ንጉሡን
ለመግደል መጥቶ ነበርና። 16 ይህ ያደረግኸው ነገር መልካም አይደለም። ሕያው እግዚአብሔርን! ሞት የሚገባህ ነህ፥ ምክንያቱም እግዚአብሔር የቀባውን
ጌታህን አልጠበቅኸውም። አሁንም፥ የንጉሡ ጦርና በራስጌው የነበረው የውሃ ኮዳ የት እንዳለ ተመልከት" አለው። 17 ሳኦልም የዳዊት ድምፅ መሆኑን ለየና፥
"ልጄ ዳዊት፥ ይህ ድምፅህ ነው?" አለው። ዳዊትም፥ "ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፥ ድምፄ ነው" አለው። 18 እርሱም እንዲህ አለው፥ "ጌታዬ አገልጋዩን የሚያሳድደው
ለምንድነው? ምን አድርጌአለሁ? በእጄስ ያለው ክፋት ምንድነው? 19 አሁንም ጌታዬ ንጉሡ የአገልጋይህን ቃል እንድትሰማ እለምንሃለሁ። በእኔ ላይ ያነሣሣህ
እግዚአብሔር ከሆነ መስዋዕትን ይቀበል፤ ሰዎች ከሆኑ ግን በእግዚአብሔር ፊት የተረገሙ ይሁኑ፥ 'ሄደህ ሌሎች አማልክቶችን አምልክ' ብለው የእግዚአብሔርን
ርስት አጥብቄ እንዳልይዝ ዛሬ አባረውኛልና። 20 ስለዚህ፥ አንድ ሰው በተራሮች ላይ ቆቅን እንደሚያድን፥ የእስራኤል ንጉሥ ቁንጫን ለመፈለግ መጥቷልና ደሜ
ከእግዚአብሔር ፊት ርቆ በምድር ላይ እንዲፈስ አታድርግ።“ 21 ከዚያም ሳኦል፥”ኃጢአትን አድርጌአለሁ። ልጄ ዳዊት፥ ተመለስ፤ ዛሬ ሕይወቴ በዐይንህ ፊት
ከብራለችና ከእንግዲህ ወዲህ ክፉ አላደርግብህም። ስንፍናን አድርጌአለሁ፥ እጅግም ተሳስቻለሁ“ አለው። 22 ዳዊትም እንዲህ ሲል መለሰለት፥”ንጉሥ ሆይ
ተመልከት! ጦርህ ያለው እዚህ ነው፥ ከወጣቶቹ አንዱ ይምጣና ይውሰድልህ። 23 ዛሬ እግዚአብሔር በእጄ ላይ ጥሎህ እያለ በእርሱ የተቀባውን
አልመታሁትምና እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ እንደ ጽድቁና ታማኝነቱ ይክፈለው። 24 ተመልከት፥ ዛሬ ሕይወትህ በዐይኔ ፊት እንደ ከበረች የእኔም ሕይወት
በእግዚአብሔር ዐይን አብልጣ የከበረች ትሁን፥ ከመከራዬም ሁሉ ያድነኝ።“ 25 ከዚያም ሳኦል ዳዊትን፥”ልጄ ዳዊት፥ በርግጥ ታላላቅ ነገሮችን እንድታደርግና
እንዲከናወንልህ የተባረክህ ሁን“ አለው። ስለዚህ ዳዊት መንገዱን ሄደ፥ ሳኦልም ወደ ስፍራው ተመለሰ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 27

1 ዳዊትም፥”አሁንም አንድ ቀን በሳኦል እጅ እሞታለሁ፤ ወደ ፍልስጥኤማውያን ምድር ከመሸሸ የሚሻል አማራጭ የለኝም፤ ያን ጊዜ ሳኦል በእስራኤል ወሰኖች ሁሉ ውስጥ እኔን መፈለጉን ያቆማል፤ በዚህ መንገድ ከእጁ አመልጣለሁ" ብሎ በልቡ አሰበ። **2** ዳዊትም ተነሣ፥ እርሱና ከእርሱ ጋር የነበሩት ስድስት መቶ ሰዎች ወደ ጌት ንጉሥ ወደ አሜህ ልጅ ወደ አንኩስ ተሻገሩ። **3** ዳዊትና ሰዎቹ እያንዳንዱ ከቤተሰቡ ጋር፥ እርሱም ከሁለቱ ሚስቶቹ፥ ከኢይዝራኤላዊቱ ከአኪናሆምና የናባል ሚስት ከነበረችው ከቀርሜሎሳዊቷ ከአቢግያ ጋር በጌት ከአንኩስ ጋር ኖሩ። **4** ዳዊት ወደ ጌት መሸሹን ሳኦል ሰማ፥ ስለዚህ ከዚህ በኋላ አልፈለገውም። **5** ዳዊትም አንኩስን፥ "በዐይንህ ፊት ሞገስ አግኝቼ ከሆነ፥ በዚያ እኖር ዘንድ በአገሪቱ ካሉት ከተሞች በአንዲቱ ስፍራ ይስጡኝ፤ አገልጋይህ በንጉሣዊ ከተማ ከአንተ ጋር ለምን ይኖራል?" አለው። **6** ስለዚህ በዚያን ቀን አንኩስ ጺቅላግን ሰጠው፤ እስከዛሬ ድረስ ጺቅላግ የይሁዳ ነገሥታት የሆነችው ለዚህ ነው። **7** ዳዊት በፍልስጥኤም ምድር የኖረበት ቀን ሲቆጠር አንድ ዓመት ከአራት ወር ሆነው። **8** ዳዊትና ሰዎቹ ጌሹራውያንን፥ ጌርዛውያንን እና አማሌቃውያንን በመውረር የተለያዩ ቦታዎችን አጠቁ፤ እነዚህ ሕዝቦች እስከ ሱርና እስከ ግብፅ ምድር ድረስ ባለው አካባቢ ይኖሩ የነበሩ ናቸው። እነርሱም ከጥንት ጀምሮ በዚያ ምድር ይኖሩ ነበር። **9** ዳዊትም ምድሪቱን መታ፥ ወንዱንም ሆነ ሴቱን በሕይወት አልተወም፤ በጎችን፥ በሬዎችን፥ አህዮችን፥ ግመሎችን እና ልብሶችን ወሰደ፤ ተመልሶም እንደገና ወደ አንኩስ መጣ። **10** አንኩስ፥ "ዛሬ በማን ላይ ወረራ ፈጸማችሁ?" ብሎ ይጠይቅ ነበር፥ ዳዊትም፥ "በይሁዳ ደቡብ ላይ" ወይም "በደቡብ ይረሕምኤላውያን ላይ" ወይም "በደቡብ ቄናውያን ላይ" ብሎ ይመልስለት ነበር። **11** "ስለዚህ ስለ እኛ፥ 'ዳዊት እንዲህና እንዲህ አደረገ' ለማለት እንዳይችሉ" ብሎ ነበርና ዳዊት ወደ ጌት ይዞ ለመምጣት በማሰብ ወንድ ወይም ሴት በሕይወት አያስቀርም ነበር። በፍልስጥኤም አገር በኖረበት ጊዜ ሁሉ ያደረገው እንደዚህ ነበር። **12** አንኩስም፥ "የራሱ የሆነው የእስራኤል ሕዝብ አምርሮ እንዲጠላው አድርጓል፤ ስለዚህ ለዘላለም አገልጋዬ ይሆናል” ብሎ ስላሰበ ዳዊትን አመነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 28

1 በዚያም ዘመን ፍልስጥኤማውያን ከእስራኤል ጋር ለመዋጋት ሠራዊታቸውን ሁሉ በአንድ ላይ ሰበሰቡ። አንኩስም ዳዊትን፥ “አንተና ሰዎችህ ያለ ጥርጥር ከእኔ
ጋር ወደ ጦርነቱ እንደምትወጡ ዕወቅ” አለው። 2 ዳዊትም አንኩስን፥ “ስለዚህ አገልጋይህ ምን ሊያደርግ እንደሚችል ታያለህ” አለው። አንኩስም ዳዊትን፥
“ስለዚህ እኔም በቋሚነት የግል ጠባቂዬ አደርግሃለሁ" አለው። 3 ሳሙኤል ሞቶ ነበር፤ እስራኤል ሁሉ አልቅሰውለት በከተማው በራማም ቀብረውት ነበር።
ሳኦል ከሙታንና ከመናፍስት ጋር የሚነጋገሩትን ከምድሪቱ አጥፍቶ ነበር። 4 ፍልስጥኤማውያን በአንድነት ተሰባስበው በመምጣት ሹነም ላይ ሰፈሩ፤ ሳኦልም
እስራኤልን በሙሉ በአንድነት ሰብስቦ ጊልቦዓ ላይ ሰፈረ። 5 ሳኦል የፍልስጥኤማውያንን ሰራዊት ባየ ጊዜ ፈራ፥ ልቡም እጅግ ተንቀጠቀጠ። 6 ይረዳው ዘንድ
ወደ እግዚአብሔር በጸለየ ጊዜም እግዚአብሔር በህልም፥ ወይም በኡሪም፥ ወይም በነቢያት አልመለሰለትም። 7 ከዚያም ሳኦል አገልጋዮቹን፥ "ወደ እርሷ ሄጄ
ምክሯን እንድጠይቅ ከሞተ ጋር መነጋገር እችላለሁ የምትል ሴት ካለች ፈልጉልኝ" አላቸው። አገልጋዮቹም፥ "ከሞተ ጋር መነጋገር እችላለሁ የምትል ሴት
በዓይንዶር አለች" አሉት። 8 ሳኦል ሌላ ልብስ በመልበስ ራሱን ቀይሮ ከሁለት ሰዎች ጋር ሄደ፤ እነርሱም በሌሊት ወደ ሴቲቱ ሄዱ። እርሱም፥ "የምነግርሽን ሰው
አስነሥተሽ ከሞተው ጋር በመነጋገር እንድትጠነቁይልኝ እለምንሻለሁ" አላት። 9 ሴቲቱም፥ "ሳኦል ከሙታንና ከመናፍስት ጋር የሚነጋገሩትን ከምድሪቱ
በማጥፋት ያደረገውን ታውቃለህ። ታዲያ እንድሞት ለሕይወቴ ወጥመድ የምታዘጋጀው ለምንድነው?" አለችው። 10 ሳኦልም በእግዚአብሔር ስም ምሎላት፥
"ሕያው እግዚአብሔርን! በዚህ ጉዳይ ምንም ቅጣት አይደርስብሽም” አላት። 11 ሴቲቱም፥ “ማንን ላስነሣልህ?” አለችው። ሳኦልም፥ “ ሳሙኤልን አስነሽልኝ”
አላት። 12 ሴቲቱም ሳሙኤልን ባየችው ጊዜ በታላቅ ድምፅ ጮኻ ሳኦልን፥ "አንተ ራስህ ሳኦል ሆንህ ሳለ ለምን አታለልከኝ?" አለችው። 13 ንጉሡም፥
"አትፍሪ፤ ምንድነው ያየሽው?" አላት። ሴቲቱም ሳኦልን፥ "አንድ መንፈስ ከምድር ሲወጣ አያለሁ" አለችው። 14 እርሱም፥ “ምን ይመስላል?” አላት። እርሷም፥
"አንድ ካባ የለበሰ ሽማግሌ እየመጣ ነው" አለችው። ሳኦልም ሳሙኤል እንደሆነ ዐወቀ፥ አክብሮቱን ለማሳየትም በምድር ላይ ሰገደለት። 15 ሳሙኤልም
ሳኦልን፥ "እኔን በማስነሣት የምታስቸግረኝ ለምንድነው?" አለው። ሳኦልም፥ "በጣም ተጨንቄአለሁ፥ ፍልስጥኤማውያን ጦርነት ዐውጀውብኛል፥ እግዚአብሔር
ትቶኛል፥ በሕልምም ሆነ በነቢያት አይመልስልኝም። ምን ማድረግ እንዳለብኝ እንድታስታውቀኝ ለዚህ ነው የጠራሁህ" ብሎ መለሰለት። 16 ሳሙኤልም እንዲህ
አለው፥ "ታዲያ እግዚአብሔር ከተወህና ጠላት ከሆነህ የምትጠይቀኝ ምንድነው? 17 እግዚአብሔር አደርገዋለሁ ብሎ የነገረህን እርሱን ነው ያደረገብህ።
እግዚአብሔር መንግሥትን ከእጅህ ቀዶ ለሌላ ሰው፥ ለዳዊት ሰጥቶታል። 18 የእግዚአብሔርን ድምፅ ስላልታዘዝክና ጽኑ ቁጣውን በአማሌቅ ላይ ስላልፈጸምክ
ዛሬ ይህንን አድርጎብሃል። 19 በተጨማሪም እግዚአብሔር አንተንና እስራኤልን በፍልስጥኤማውያን እጅ አሳልፎ ይሰጣል። አንተና ልጆችህ ነገ ከእኔ ጋር
ትሆናላችሁ። በተጨማሪም እግዚአብሔር የእስራኤልን ሰራዊት በፍልስጥኤማውያን እጅ አሳልፎ ይሰጣል።“ 20 ከዚያም ሳኦል በሳሙኤል ቃል ምክንያት እጅግ
ስለፈራ ወዲያውኑ በቁመቱ ሙሉ በምድር ላይ ወደቀ። በዚያ ቀንና ሌሊት ምግብ ስላልበላ ምንም አቅም አልነበረውም። 21 ሴቲቱም ወደ ሳኦል መጥታ እጅግ
መጨነቁን አየች፥ እርሷም እንዲህ አለችው፥ "እኔ አገልጋይህ ቃልህን ሰምቻለሁ፤ ሕይወቴን በእጄ ላይ ጥዬ የነገርከኝን ቃል ሰምቻለሁ። 22 አሁንም እንግዲህ
አንተም ደግሞ የእኔን የአገልጋይህን ቃል እንድትሰማና ጥቂት ምግብ እንዳቀርብልህ እለምንሃለሁ። መንገድህን ለመሄድ ዐቅም እንድታገኝ ብላ። 23 ሳኦል ግን፥
"አልበላም" በማለት እንቢ አለ። ነገር ግን አገልጋዮቹ ከሴቲቱ ጋር በመሆን ለመኑት፥ እርሱም ቃላቸውን ሰማ። ስለዚህ ከምድር ላይ ተነሥቶ ዐልጋ ላይ
ተቀመጠ። 24 ሴቲቱም በቤቷ የደለበ ጥጃ ነበራት፤ ፈጥና አረደችው፤ ዱቄትም ወስዳ ለወሰችው፤ ቂጣ አድርጋም ጋገረችው። 25 እርሷም በሳኦልና
በአገልጋዮቹ ፊት አቀረበችላቸው፥ እነርሱም በሉ። ከዚያም በዚያው ሌሊት ተነሥተው ሄዱ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 29

1 ፍልስጥኤማውያንም ሰራዊታቸውን ሁሉ አፌቅ ላይ ሰበሰቡ፤ እስራኤላውያንም በኢይዝራኤል ምንጭ አጠገብ ሰፈሩ። **2** የፍልስጥኤማውያኑ መሳፍንት በመቶዎችና በሺዎች እየሆኑ አለፉ፤ ዳዊትና ሰዎቹም ከአንኩስ ጋር በደጀንነት አለፉ። **3** ከዚያም የፍልስጥኤም መሳፍንት፥ "እነዚህ ዕብራውያን እዚህ ምን ይሠራሉ?" አሉ። አንኩስም ለሌሎቹ የፍልስጥኤም መሳፍንት፥ "ይህ በእነዚህ ቀናት ሁሉ ከእኔ ጋር የነበረው፥ የእስራኤል ንጉሥ የሳኦል አገልጋይ ዳዊት አይደለምን? ደግሞም በእነዚህ ዓመታት ሁሉ ወደ እኔ ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ምንም ስህተት አላገኘሁበትም” አላቸው። **4** ነገር ግን የፍልስጥኤም መሳፍንት በእርሱ ላይ ተቆጥተው፥ “ያንን ሰው ወደ ሰጠኸው ወደ ስፍራው እንዲመለስ አሰናብተው፥ በውጊያው ውስጥ ጠላት እንዳይሆንብን ከእኛ ጋር ወደ ጦርነት አትላከው። ይህ ሰው ከጌታው ጋር ሰላምን የሚፈጥረው በምንድነው? የሰዎቻችንን አንገት በመቁረጥ አይደለምን? **5** ይህ በዘፈን እየተቀባበሉ፥ 'ሳኦል ሺዎችን ገደለ፥ ዳዊት ዐሥር ሺዎችን ገደለ" ያሉለት ዳዊት አይደለምን?" አሉት። **6** ከዚያም አንኩስ ዳዊትን ጠርቶ፥ "ሕያው እግዚአብሔርን! አንተ ጥሩ ሰው ነህ፥ በእኔ አመለካከት በሰራዊቱ ውስጥ መውጣትህና መግባትህ መልካም ነው፤ ወደ እኔ ከመጣህበት ጊዜ ጀምሮ እስከዛሬው ቀን ድረስ ምንም ስህተት አላገኘሁብህም። ይሁን እንጂ መሳፍንቱ አልደገፉህም። **7** ስለዚህ አሁን የፍልስጥኤም መሳፍንት ቅር እንዳይሰኙ ተመለስና በሰላም ሂድ" አለው። **8** ዳዊትም አንኩስን፥ “ግን ምን አድርጌአለሁ፥ እንዳልሄድና ከጌታዬ ከንጉሡ ጠላቶች ጋር እንዳልዋጋ በእነዚህ በፊትህ በኖርኩባቸው ቀናት በአገልጋይህ ላይ ምን አግኝተህብኛል?” አለው። **9** አንኩስም ለዳዊት፥ “አንተ በእኔ ዕይታ ነቀፌታ እንደማይገኝበት እንደ እግዚአብሔር መልአክ ነህ፤ ይሁንና የፍልስጥኤም መሳፍንት፥ 'ከእኛ ጋር ወደ ጦርነት አይሄድም' ብለዋል። **10** ስለዚህ ከአንተ ጋር ከመጡት ከጌታህ አገልጋዮች ጋር ማልዳችሁ ተነሡ፤ ማልዳችሁ ተነሡና ሲነጋላችሁ ሂዱ" ብሎ መለሰለት። **11** ስለዚህ ዳዊትና ሰዎቹ በጠዋት ለመሄድ፥ ወደ ፍልስጥኤማውያንም ምድር ለመመለስ ማልደው ተነሡ። ፍልስጥኤማውያን ግን ወደ ኢይዝራኤል ወጡ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 30

1 እንዲህም ሆነ፥ ዳዊትና ሰዎቹ በሦስተኛው ቀን ወደ ጺቅላግ በመጡ ጊዜ አማሌቃውያን በኔጌብና በጺቅላግ ላይ ወረራ ፈጽመው ነበር። እነርሱም ጺቅላግን
መቱ፥ አቃጠሏትም፥ 2 ሴቶችንና በውስጧ የነበረውን ትንሽና ትልቅ ሁሉ ማረኩ። ይዘዋቸው መንገዳቸውን ሄዱ እንጂ አንዱንም አልገደሉም። 3 ዳዊትና ሰዎቹ
ወደ ከተማይቱ በመጡ ጊዜ ከተማይቱ በእሳት ተቃጥላ፥ ሚስቶቻቸው፥ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸው ተማርከው ተወስደው ነበር። 4 ከዚያም ዳዊትና ከእርሱ ጋር
የነበሩት ሰዎች ለማልቀስ ኃይል እስከማይኖራቸው ድረስ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው አለቀሱ። 5 ሁለቱ የዳዊት ሚስቶች፥ ኢይዝራኤላዊቱ አኪናሆምና
የቀርሜሎሳዊው የናባል ሚስት የነበረችው አቢግያ ተማርከው ነበር። 6 የሕዝቡም ሁሉ መንፈስ፥ እያንዳንዱም ስለ ወንዶችና ሴቶች ልጆቹ ስላዘነ በድንጋይ
ሊወግሩት ይነጋገሩ ስለነበር ዳዊት እጅግ ተጨነቀ፤ ዳዊት ግን በአምላኩ በእግዚአብሔር ራሱን አበረታ። 7 ዳዊትም የአቢሜሌክን ልጅ ካህኑን አብያታርን፥
"ኤፉዱን ወደዚህ እንድታመጣልኝ እለምንሃለሁ" አለው። አብያታር ኤፉዱን ለዳዊት አመጣለት። 8 ዳዊትም ምሪት ለማግኘት ወደ እግዚአብሔር፥ "ይህንን ወራሪ
ብከተል እደርስበታለሁ?" ብሎ ጸለየ። እግዚአብሔርም፥ "ተከተላቸው፥ ያለጥርጥር ትደርስባቸዋለህ፥ ሁሉንም ነገር ታስመልሳለህ" ብሎ መለሰለት። 9 ስለዚህ
ዳዊትና ከእርሱ ጋር የነበሩት ስድስት መቶ ሰዎች ሄዱ፤ ከእነርሱ ወደ ኋላ የቀሩት ወደሚቆዩበት ወደ ባሦር ወንዝ መጡ። 10 ነገር ግን ዳዊት ከአራት መቶ ሰዎች
ጋር መከታተሉን ቀጠለ፤ ሁለት መቶዎቹ በጣም ስለ ደከሙ የባሦርን ወንዝ መሻገር አልቻሉምና ወደ ኋላ ቀሩ። 11 እነርሱም በሜዳው ላይ አንድ ግብፃዊ
አገኙና ወደ ዳዊት አመጡት፤ ምግብ ሰጡትና በላ፥ እንዲጠጣም ውሃ ሰጡት፤ 12 ደግሞም ከበለስ ጥፍጥፍ ቁራጭና ሁለት የወይን ዘለላ ሰጡት። ለሦስት
ቀንና ሌሊት ምንም ምግብ አልበላም፥ ውሃም አልጠጣም ነበርና በበላ ጊዜ እንደገና ብርታት አገኘ። 13 ዳዊትም፥ "አንተ የማን ነህ? ከየትስ ነው የመጣኸው?"
አለው። እርሱም፥ "እኔ የአማሌቃዊ አገልጋይ፥ ግብፃዊ ወጣት ነኝ፤ ከሦስት ቀናት በፊት ታምሜ ስለነበር ጌታዬ ትቶኝ ሄደ። 14 እኛም በከሊታውያን ኔጌብ፥
የይሁዳ በሆነው ምድርና በካሌብ ኔጌብ ላይ ወረራ ፈጸምን፥ ጺቅላግንም አቃጠልናት“ አለው። 15 ዳዊትም፥”ወደዚህ ወራሪ አካል መርተህ ልታወርደኝ
ትፈቅዳለህ? “ አለው። ግብፃዊውም፥”እንዳትገድለኝ ወይም በጌታዬ እጅ ላይ አሳልፈህ እንዳትሰጠኝ በእግዚአብሔር ማልልኝ እንጂ ወደ ወራሪው አካል መርቼ
አወርድሃለሁ“ አለው። 16 ግብፃዊው ዳዊትን እየመራው ወደ ታች ባወረደው ጊዜ፥ ወራሪዎቹ ከፍልስጥኤማውያን ምድርና ከይሁዳ ምድር ከወሰዱት ምርኮ
ሁሉ የተነሣ እየበሉና እየጠጡ፥ እየጨፈሩም በምድሩ ሁሉ ተበትነው ነበር። 17 ዳዊትም ደንገዝገዝ ሲል ጀምሮ እስከ ማግስቱ ምሽት ድረስ መታቸው።
በግመሎች ተቀምጠው ከሸሹት ከአራት መቶ ወጣቶች በስተቀር አንድም ሰው አላመለጠም። 18 ዳዊት አማሌቃውያን ወስደዋቸው የነበሩትን ሁሉ አስመለሰ፤
ሁለቱን ሚስቶቹንም አዳነ። 19 ትንሽ ይሁን ትልቅ፥ ወንዶች ልጆች ይሁኑ ሴቶች ልጆች፥ ምርኮም ይሁን ወራሪዎቹ ለራሳቸው ከወሰዱት ማንኛውም ነገር አንዱም
አልጠፋም። ዳዊት ሁሉን ነገር አስመለሰ። 20 ዳዊትም ሰዎቹ ከሌሎች ከብቶች ፊት ይነዷቸው የነበሩትን የበጉን፥ የፍየሉንና የላሙን መንጋ ሁሉ ወሰደ።
እነርሱም፥ "ይህ የዳዊት ምርኮ ነው" አሉ። 21 ዳዊት ሊከተሉት እጅግ ደክሟቸው በባሦር ወንዝ አጠገብ እንዲቆዩ ወደተደረጉት ወደ ሁለት መቶዎቹ ሰዎች
መጣ። እነዚህ ሰዎች ዳዊትንና ከእርሱ ጋር የነበሩትን ሰዎች ለመገናኘት ወጡ። ዳዊት ወደ እነዚህ ሰዎች በመጣ ጊዜ ሰላምታ ሰጣቸው። 22 ከዚያም ከዳዊት
ጋር ሄደው በነበሩት ሰዎች መካከል ክፉዎችና የማይረቡት ሁሉ፥”እያንዳንዱ ሚስቱንና ልጆቹን ይዞ ከመሄድ በስተቀር እነዚህ ሰዎች ከእኛ ጋር ስላልሄዱ፥
ካስመለስነው ምርኮ ምንም አንሰጣቸውም“ አሉ። 23 ከዚያም ዳዊት፥”ወንድሞቼ ሆይ፥ እግዚአብሔር በሰጠን ነገር እንዲህ ልታደርጉ አይገባም። እርሱ
ጠበቀን፥ በእኛ ላይ የመጡትንም ወራሪዎች በእጃችን ላይ አሳልፎ ሰጠን። 24 በዚህ ጉዳይ ማን ይሰማችኋል? ወደ ጦርነት የሄደው የየትኛውም ሰው ድርሻ
ስንቅና ትጥቅ ከጠበቀ ከየትኛውም ሰው ድርሻ ጋር እኩል ይሆናል፤ ሁሉም እኩል ይካፈላሉ" አላቸው። 25 ዳዊት ለእስራኤል ደንብና ሥርዓት ስላደረገው፥
ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከዚህ ቀን ድረስ እንደዚሁ ሆነ። 26 ዳዊት ወደ ጺቅላግ በመጣ ጊዜ፥ ከምርኮው ጥቂቱን፥ "ይህ ከእግዚአብሔር ጠላቶች ካገኘነው
ምርኮ ለእናንተ የተላከ ስጦታ ነው“ብሎ ለይሁዳ ሽማግሌዎችና ለወዳጆቹ ላከላቸው። 27 የላከውም፥ በቤቴል፥ በደቡብ ራሞት፥ በየቲር፥ 28 በአሮኤር፥
በሺፍሞት፥ በኤሽትሞዓ ለነበሩ ሽማግሌዎች ነበር። 29 እንዲሁም በራካል፥ በይረሕምኤላውያንና በቄናውያን ከተሞች፥ 30 በሔርማ፥ በቦራሣን፥ በዓታክ፥ 31
በኬብሮን፥ እንዲሁም ዳዊት ራሱና ሰዎቹ አዘውትረው ይሄዱባቸው በነበሩ ስፍራዎች ሁሉ ለሚኖሩ ሽማግሌዎች ላከላቸው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 31

1 ፍልስጥኤማውያን ከእስራኤል ጋር ተዋጉ። የእስራኤል ሰዎች ከፍልስጥኤማውያን ፊት ሸሹ፥ በጊልቦዓ ተራራ ላይም ተገድለው ወደቁ። **2** ፍልስጥኤማውያንም ሳኦልንና ልጆቹን በቅርብ ርቀት ተከተሏቸው። ፍልስጥኤማውያንም ልጆቹን ዮናታንን፥ አሚናዳብንና ሜልኪሳን ገደሏቸው። **3** ውጊያው በሳኦል ላይ በረታበት፥ ቀስተኞችም አገኙት። በእነርሱም ምክንያት በጽኑ ሕመም ላይ ነበር። **4** ሳኦልም ጋሻ ጃግሬውን፥"ሰይፍህን ምዘዝና ውጋኝ። አለበለዚያ፥ እነዚህ ያልተገረዙ መጥተው ይሳለቁብኛል" አለው። **5** ጋሻ ጃግሬው ግን እጅግ ፈርቶ ስለነበረ እምቢ አለ። ስለዚህ ሳኦል የራሱን ሰይፍ ወስዶ በላዩ ላይ ወደቀበት። ጋሻ ጃግሬው ሳኦል መሞቱን ባየ ጊዜ እርሱም ደግሞ ሰይፉ ላይ ወድቆ አብሮት ሞተ። **6** ስለዚህ ሳኦል፥ ሦስቱ ወንዶች ልጆቹና ጋሻ ጃግሬው ሞቱ፤ እነዚህ ሰዎች ሁሉ በአንድ ቀን ሞቱ። **7** ከሸለቆው በወዲያኛው ወገን የነበሩትና ከዮርዳኖስ በላይ የነበሩት የእስራኤል ሰዎች፥ የእስራኤል ሰዎች መሸሻቸውን፥ ሳኦልና ልጆቹ መሞታቸውን ባዩ ጊዜ ከተሞቻቸውን ትተው ሸሹ፥ ፍልስጥኤማውያንም መጥተው ተቀመጡባቸው። **8** በማግስቱ እንዲህ ሆነ፥ ፍልስጥኤማውያን የሞቱትን ሰዎች ትጥቅ ለመግፈፍ በመጡ ጊዜ ሳኦልና ሦስቱ ልጆቹ በጊልቦዓ ተራራ ላይ ወድቀው አገኟቸው። **9** እነርሱም ራሱን ቆረጡት፥ የጦር መሣሪያውንም ገፈፉት፥ ወደ ፍልስጥኤማውያን ምድር ሁሉ ለጣዖት መቅደሶቻቸውና ለሕዝቡ ወሬውን እንዲያደርሱ መልዕክተኞችን ላኩ። **10** የጦር መሣሪያውን በአስታሮት መቅደስ ውስጥ አስቀመጡት፥ ሬሳውንም በቤትሳን ከተማ የግንብ አጥር ላይ አንጠለጠሉት። **11** የኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች ፍልስጥኤማውያን በሳኦል ላይ ያደረጉትን በሰሙ ጊዜ **12** ተዋጊ የሆኑ ሰዎች ሁሉ ተነሥተው ሌሊቱን ሁሉ ተጉዘው የሳኦልንና የልጆቹን ሬሳ ከአጥሩ ላይ ወሰዱ። ወደ ኢያቢስ ሄዱ፥ በዚያም አቃጠሏቸው። **13** ከዚያም አጥንቶቻቸውን በመውሰድ በኢያቢስ ባለው የአጣጥ ዛፍ ሥር ቀበሯቸው፥ ሰባት ቀንም ጾሙ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: 2 Samuel

2 Samuel

Chapter 1

1 ሳዖል ከሞተ በኋላ፣ ዳዊት በአማሌቃውያን ላይ ጥቃት ከማድረስ በመመለስ በጺቅላግ ሁለት ቀን ቆየ። 2 በሦስተኛው ቀን የተቀዳደደ ልብስ የለበሰ፣ በራሱም ላይ ትቢያ የነሰነሰ አንድ ሰው ከሳኦል ሰፈር መጣ። ወደ ዳዊት እንደ ደረሰም ወደ መሬት ለጥ ብሎ ሰገደለት። 3 ዳዊትም “ከወዴት መጣህ?” ሲል ጠየቀው። እርሱም፣ “ከእስራኤላውያን ሰፈር አምልጬ የመጣሁ ነኝ” ሲል መለሰ። 4 ዳዊትም፣ “እስቲ የሆነውን ሁሉ ንገረኝ” አለው። እርሱም “ሰዎቹ ከጦርነት ሸሽተዋል፤ ብዙዎቹ ወድቀዋል ደግሞም ሞተዋል፤ ሳዖልና ልጁ ዮናታንም ሞተዋል” አለ። 5 ዳዊትም ለወጣቱ፤ “ሳኦልና ልጁ ዮናታን መሞታቸውን እንዴት አወቅህ?” ሲል ጠየቀው። 6 ወጣቱም እንዲህ ሲል መለሰ፤ “ድንገት ወደ ጊልቦዓ ተራራ ወጥቼ ነበር፤ እዚያም ሳኦል ጦሩን ተደግፎ ሳለ፣ ሠረገሎችና ፈረሰኞች ተከታትለው ደረሱበት፤ 7 ወደ ኋላውም ዞር ሲል እኔን ስላየ ጠራኝ፤ እኔም ‘እነሆኝ አለሁ’ አልኩት። 8 እርሱም፣ ‘አንተ ማን ነህ?’ ሲል ጠየቀኝ። እኔም፣ ‘አማሌቃዊ ነኝ’ ብዬ መለስሁለት። 9 እርሱም አለኝ ‘እኔ በታላቅ ስቃይ ውስጥ እገኛለሁ፤ ነፍሴ ግን አልወጣችም፤ እባክህ በላዬ ቆመህ ግደለኝ’ አለኝ። 10 ስለሆነም፣ ከወደቀ በኋላ እንደማይተርፍ ስለወቅሁ፤ በላዩ ቆሜ ገደልሁት፤ በራሱ ላይ የነበረውን ዘውድና የክንዱን አንባር ወስጄ እነሆ፣ ለጌታዬ አምጥቻለሁ።” አለው። 11 ከዚያም ዳዊት ልብሱን ቀደደ፤ ከእርሱም ጋር የነበሩት ሁሉ እንደዚሁ አደረጉ። 12 የወደቁት በሰይፍ ነበርና ለሳኦል ለልጁ ለዮናታንና ለእግዚአብሔር ሕዝብ አዘኑ፤ አለቀሱ፤ እስከ ማታም ድረስ ጾሙ። 13 ዳዊትም ወጣቱን ሰውዬ፣ “የየት አገር ሰው ነህ?” ሲል ጠየቀው። እርሱም፣ “በአገሪቱ ውስጥ በመጻተኛነት የሚኖር አማሌቃዊ ልጅ ነኝ” ብሎ መለሰ። 14 ዳዊትም፣ “እግዚአብሔር የቀባውን ንጉሥ በገዛ እጅህ ስትገድል ለምን አልፈራህም?” ሲል ጠየቀው። 15 ዳዊትም ከጎልማሶቹ አንዱን ጠርቶ፣ “ግደለው” አለው፤ ጎልማሳው ሰው ሄዶ መታው፣ አማሌቃዊውም ሞተ። 16 ከዚያም ዳዊት ለሞተው አማሌቃዊ፣ “‘እግዚአብሔር የቀባውን ገድያለሁ’ ስትል አፍህ መስክሮብሃልና ደምህ በራስህ ላይ ነው” አለው። 17 ከዚያም ዳዊት ለሳዖልና ለልጁ ለዮናታን የሚከተለውን የሐዘን እንጉርጉሮ አንጎራጎረ። 18 እንዲሁም የቀስት እንጉርጉሮ የተባለውን ለይሁዳ ሕዝብ እንዲያስተምሩ አዘዘ፤ ይህም በያሸር መጽሐፍ ተጽፎአል። 19 “እስራኤል ሆይ፣ ክብርህ ሞቶአል፣ በተራሮችህ ላይ ተገድሎአል! ኃያላኑ እንዴት ወደቁ! 20 የፍልስጥኤም ሴቶች ልጆች እንዳይደሰቱ፣ ያልተገረዙት ሴት ልጆች ፌሽታ እንዳያደርጉ ይህን በጌት አትናገሩ፣ በአስቆሎናም መንገዶች አታውጁት። 21 እናንት የጊልቦዓ ተራሮች ሆይ ጠል አያረስርሳችሁ፣ ዝናብም አይውረድባችሁ፤ የቁርባን እህል የሚያበቅሉም እርሻዎች በዚያ አይኑሩ፤ በዚያ የኃያሉ ሰው ጋሻ ረክሶአልና፣ የሳዖል ጋሻ ከእንግዲህ በዘይት አይወለወልም። 22 ከሞቱት ሰዎች ደም፣ ከኃያላኑም ገላ የዮናታን ቀስት ተመልሶ አልመጣም፤ የሳዖልም ሰይፍ በከንቱ አልተመለሰም። 23 ሳዖልና ዮናታን በሕይወት እያሉ የሚዋደዱና ግርማ ያላቸው ነበሩ፤ ሲሞቱም አልተለያዩም፤ከንስርም ይልቅ ፈጣኖች ከአንበሳም ይልቅ ብርቱዎች ነበሩ። 24 እናንተ የእስራኤል ቆነጃጅት ሆይ፤ ሐምራዊ ቀሚስና ቀጭን ፈትል ላለበሳችሁ ፤ ልብሶቻችሁንም በወርቅ-ዘቦ ላስጌጠላችሁ ለሳዖል አልቅሱለት። 25 ኃያላን እንዴት እንዲህ በጦርነት መካከል ወደቁ! ዮናታን ከፍ ባሉ ስፍራዎቻችሁ ላይ ሞቶአል። 26 ወንድሜ ዮናታን ሆይ፤ እኔ ስለ አንተ አዘንሁ፤ አንተ ለእኔ እጅግ ውድ ነበርህ፤ ፍቅርህ ለእኔ ድንቅ ነበር፤ ከሴት ፍቅርም የላቀ ነበር። 27 ኃያላን እንዴት ወደቁ፤ የጦር መሣሪዎቹስ እንዴት ከንቱ ሆኑ!”

---

2 Samuel 1:1

ጺቅላግ
ይህ በይሁዳ ደቡባዊ ክፍል የሚገኝ የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በሶስተኛው ቀን
"ከሶስት ቀናት በኋላ" (ተከታታይ ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ልብሱ ተቀዶ እና በራሱ ላይ ትቢያ ነስንሶ
በዚህ ባህል፣ የራስን ልብስ መቅደድ እና በራስ ላይ አመድ መነስነስ የሃዘን መግለጫ ድርጊት ነበር። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ምድር ዝቅ ብሎ እና ራሱን ደፍቶ
ይህ አሁን የእስራኤል ንጉሥ ለሆነው ለዳዊት ራሱን ዝቅ አድርጎ ያሳየበት መንገድ ነበር። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 1:3

ብዙዎች ወደቁ ደግሞም ብዙዎች ሞቱ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ብዙዎች ቆስለው ነበር ደግሞም ብዙዎች ተገድለው ነበር" ወይም 2) "ብዙዎች ቆስለው እና ተገድለው ነበር"

2 Samuel 1:6

በአጋጣሚ በዚያ ተገኝቼ ነበር
ይህ ሃሳብ ትኩረት የሚያደርገው ሰውየው ሳኦልን ለማገኘት እቅድ እንዳነበረው ነው

ሳኦል በጦሩ ላይ ዘመም ብሎ ነበር
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ሳኦል ደክሞና ጦሩን ራሱን ለመደገፊያነት ተጠቅሞበት ነበር ወይም 2) ሳኦል በራሱ ጦር ላይ በመውደቅ ራሱን ለመግደል እየሞከረ ነበር። (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 1:8

‘ማን ነህ?' አለኝ። እኔም እንዲህ ብዬ መለስኩለት፣ ‘እኔ አማሌቃዊ ነኝ።'
ይህ ቀጥተኛ ጥቅስ በርቱዕ/ቀጥተኛ ንግግር ሊገለጽ ይችላል። "ማን እንደሆንኩ ጠየቀኝ፣ እኔም አማሌቃዊ እንደሆንኩ ነገርኩት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅሶች የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ አማሌቃዊ ነኝ
እነዚህ ህዝቦች ዳዊት በ2 ሳሙኤል 1:1 ላይ ድል ያደረጋቸው እነዚያው ሰዎች ናቸው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ታላቅ መከራ አገኘኝ
የሳኦል መከራ የተገለጸው አንዳች አስጨናቂ ነገር አንቆ እንደያዘው ተደርጎ ነው። "እጅግ ተጨነቅኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ህይወቴ ገና አላለፈችም/ነፍሴ አልወጣችም
ይህ ፈሊጥ ትረጉሙ እርሱ ገና በህይወት አለ ማለት ነው። "እስከ አሁን በህይወት አለሁ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከወደቀ በኋላ በህይወት አይቀጥልም
"መሞቱ አይቀርም"

2 Samuel 1:11

ዳዊት ልብሱን ቀደደ... ከእርሱ ጋር ያሉ ሰዎችም እንደዚያው አደረጉ
ዳዊትና የእርሱ ሰዎች በንጉሥ ሳኦል ሞት ማዘናቸውን ለመግለጽ ልብሳቸውን ቀደዱ። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ለያህዌ ህዝብ፣ እና ለእስራኤል ቤት
ሁለቱ ሃሳቦች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። "ቤት" የሚለው ቃል የእስራኤልን ትውልዶች የሚወክል ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ነገር ግን፣ "ህዝብ" እና "ቤት" የሚሉት ሁለቱም ቃላት ምናልባት የእስራኤልን ወታደሮች የሚወክሉ ስኔክቲክ/የነገሩን ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ናቸው። "ለእስራኤላውያን ወታደሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እንዲሁም ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

ያህዌ
ይህ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ራሱን ለህዝቡ የገለጸበት ስም ነው። ይህ እንዴት እንደሚተረጎም የትርጉም ስለ ያህዌ የቃል ትርጉም ገጽን ይመልከቱ)

በሰይፍ ወደቁ
እዚህ ስፍራ "ወደቁ" የሚለው መገደልን በትሁት መንገድ የሚገልጽ ነው። እንደዚሁም፣ "ሰይፍ" ውጊያን ይወክላል/ይገልጻል። ይህ በዚህ ስፍራ "ተገድለዋል" ማለት ነው። "በጦርነት ሞተዋል" ወይም "ጠላቶች በጦርነቱ ገድለዋቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

አንተ ከየት ነህ?
በ2ሳሙኤል 1:8 ውስጥ ሰውየው አስቀድሞውኑ አማሌቃዊ መሆኑን ገልጽዋል። ዳዊት ሰውየው ይህንን በግልጽ እንዲያረጋግጥለት ይጠይቀዋል፣ ምክንያቱ ዳዊት በሰውየው ላይ ጽኑ ፍርድ ሊፈርድበት ስለሆነ ነው።

2 Samuel 1:14

በእጅህ... ያህዌ የቀባውን ስትገድል ስለ ምን አልፈራህም?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ ያገለገለው ሰውየውን ለመገሰጽ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እጅህ... እርሱ የቀባውን ሲገድል ያህዌን መፍራት ነበረብህ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ የቀባው ንጉሥ
ይህ የሚያመለክተው ሳኦልን ነው።

በገዛ እጆችህ
ይህ ሀረግ የሚገልጸው ራስህ አንድ ነገር ማድረግህን ነው። "ራስህ" ወይም "በግል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

መትተህ ጣለው/ውደቅበት
የዚህ ፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉም "ግደለው" ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልቱ)

ደምህ በራስህ ላይ ነው
እዚህ ስፍራ "ደም" የሚያመለክተው "ደም ማፍሰስ" የሚለውን ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሲሆን የሚያያዘውም ከሞት ጋር ነው። እዚህ ስፍራ "ራስህ" የሚለው ሰውየውን እና ተጠያቂ መሆኑን የሚያመለክት ስኔክቲክ/የነገሩን ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ነው። "ለሞትህ ራስህ ተጠያቂ ነህ" ወይም "ለሞትህ ምክንያት የሆንከው ራስህ ነህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ስኔክቲክ/የነገሩን ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

የራስህ አፍ በራስህ ላይ መስክሯል
እዚህ ስፍራ "የራስህ አፍ" የሚለው የሚያመለክተው ሰውየውን ራሱን ነው። "በራስህ ላይ መስክረሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የነገሩን ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 1:17

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለሳኦልና ለዮናታን የሀዘን እንጉርጉሮ ተቀኘ

የቀስት እንጉርጉሮ
ይህ የእንጉርጉሮው ርእስ ነበር

በያሻር መጽሐፍ የተጻፈ ነበር
ይህ ለአንባቢው ወደፊት ምን ተደርጎ እንደነበር እንዲያውቅ በዝማሬው ላይ ተጨማሪ የመረጃ ዳራ ሆኖ የተጻፈ ነው። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ) የያሻር መጽሐፍ "ያሻር" የሚለው ቃል ትርጉሙ "ቀጥተኛ/በተጠንቀቅ" ማለት ነው። "የውጊያ ውሎ" መጽሐፍ በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ ክብር፣እስራኤል፣ ሞቷል
"የአንተ ክብር" የሚለው ሳኦልን ያመለክታል። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሃያሉ
"ሃያል" የሚለው ሀረግ ሳኦልን እና ዮናታንን ሁለቱንም ያመለክታል። ይህ ስማዊ ቅጽል የብዙ ቁጥር ነው፤ "ሃያላኑ" ተብሎ ሊገለጽም ይችላል። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ስማዊ ቅጽል የሚሉትን ይመልከቱ)

ወደቀ
"ወደቀ" የሚለው ቃል በዚህ ስፍራ "ሞተ" ማለት ነው። (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

ይህንን በጌት አትናገሩ... በአስቀሎና መንገዶችም አታውጁ
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ የተደገሙትም የግጥሙ እንጉርጉሮ ክፍል ሆነው ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጌት...አስቀሎና
ጌት እና አስቀሎና ከፍልስጥኤማውያን ታላላቅ ከተሞች ሁለቱ ናቸው። ሳኦልን እና ዮናታንን የገደሉት ፍልስጥኤማውያን ናቸው።

የፍልስጥኤም ሴት ልጆች ሃሴት እንዳያደርጉ... ያልተገረዙት ሴት ልጆች ክብረ በዓል እንዳያደርጉ
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤የተደገሙትም የግጥሙ ክፍል ሆነው ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ያልተገረዙት ሴት ልጆች
ይህ ሀረግ የሚያመለክተው እንደ ፍልስጥኤማውያን ያሉትን ያህዌን የማይከተሉ ህዝቦችን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 1:21

የጊልቦዓ ተራሮች
ዳዊት የእርሱን እንጉርጉሮ እንደሚሰሙት አድርጎ በቀጥታ ለ"ጊልቦዓ ተራሮች" ይናገራል። (አፖስተሮፊ የሚለውን ይመልከቱ)

ጠልም ሆነ ዝናብ አይገኝባችሁ
ዳዊት ንጉሥ ሳኦል በጦርነት የሞተበትን ምድር ይረግማል፣ ይህ የሚያደርገው እግዚአብሔር ለቀባው ነጉሥ ካለው ታላቅ አክብሮት/ውዳሴ የተነሳ ነው

የሃያላኑ ጋሻ ረከሰ
እዚህ ስፍራ "ሃያል" የሚለው የሚያመለክተው ሳኦልን ነው። ጋሻው የረከሰበት ምክንያት ምድር ላይ በመውደቁ እና የንጉሡ ደም በላዩ ስለፈሰሰበት ነበር። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የሳኦል ጋሻ ከእንግዲህ በዘይት አይቀባም
የሳኦል ጋሻ ከቆዳ የተሰራ ነበር። ጋሻውን ለመንከባከብ በዘይት ይወለወል ነበር። "ከእንግዲህ ለሳኦል ጋሻ ማንም ግድ አይለውም"

ከተገደሉት የፈሰሰው ደምና ከታላላቆቹ አካል የዮናታን ቀስት ወደ ኋላ አላለም፣ ደግሞም የሳኦል ሰይፍ ባዶውን አይመለሰም
ሳኦል እና ዮናታን እዚህ ስፍራ ላይ የቀረቡት ብርቱ እና እጅግ ጀግና ተዋጊዎች ሆነው ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሳኦል ሰይፍ ባዶውን አይመለሰም
የሳኦል ሰይፍ የተገለጸው በገዛ ራሱ መመለስ እንደሚችል ህይወት እንዳለው ነገር ሆኖ ነው። ባዶውን ከመመለስ ይልቅ፣ የገደላቸውን የሳኦልን ጠላቶች ደም ይዞ ይመጣ ነበር። (ሰውኛ ዘይቤ እና ምፀት የሚሉትን ይመልከቱ)

2 Samuel 1:23

በሞታቸውም አልተለያዩም ነበር
"አልተለያዩም ነበር" የሚለው ሀረግ የዋለው ሁልጊዜም አብረው ነበሩ የሚለውን ለማጉላት ነው። "በሞት እንኳን አብረው ነበሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ከንስር ፈጣኖች ነበሩ፣ ከአንበሶች ይልቅ ጠንካሮች ነበሩ
ሳኦል እና ዮናታን የተገለጹት ከንስር ፈጣኖች እንደ ነበሩ እና ከአንበሳ ይልቅ ጠንካሮች እንደነበሩ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ማን በሐምራዊ ቀሚስና አለበሳችሁ ማንስ አስጌጣችሁ፣ ማን በልብሳችሁ ላይ የወርግ ጌጥ አደረገላችሁ
"ማን ምርጥ ልብስና ጌጥ ሰጣችሁ።" እነዚህ ሁለት ሀረጋት፣ ለሴቶቹ ውድ እና የሚስቡ ልብሶች መሰጠታቸውን የሚገልጽ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 1:25

ሀያላኑ በጦርነቱ መሃል እንዴት ወደቁ
ይህ ሀረግ በቁጥር 27 ላይ የእስራኤል ምርጥ ተዋጊዎች መሞታቸውን አጉልቶ ለማሳየት ተደግሟል። "ሀያላኑ ሰዎች በጦርነቱ ሞቱ/ ሀያላኑ እንዴት ወደቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ሀያላኑ
እዚህ ስፍራ "ሀያል" የሚለው ቃል ብዙ ቁጥርን ሲያመለክት፣ ሳኦልን እና ዮናታንን ብቻ ሳይሆን መላውን የእስራኤል ወታደሮች ሊያመለክት ይችላል። "ሀያል ጦረኞች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ወደቀ
"ወደቀ" የሚለው ቃል በዚህ ስፍራ "ሞተ" ማለት ነው። (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

ዮናታን ተገደለ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ዮናታን በጦርነቱ ውስጥ ሞተ" ወይም "ጠላት ዮናታንን ገደለው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በከፍታ ስፍራችሁ
ዳዊት ይህንን የግጥሙን ክፍል ለጊልቦዓ ተራሮች በ2ሳሙኤል 1፡21 እንደተናገረው መናገሩን ይቀጥላል። (አፖስትሮፊ የሚለውን ይመልከቱ)

ወንድሜ ዮናታን
እዚህ ስፍራ "ወንድም" የሚለው ቃል የዋለው በጣም ቅርብ ወዳጅ/ጓደኛ በሚል ስሜት ነው።

የአንተ ፍቅር ለእኔ፣ ከሴት ፍቅር ይልቅ አስደናቂ ነበር
እዚህ ስፍራ "ፍቅር" የሚለው ቃል የዋለው በጓደኝነት እና ታማኝነት ስሜት ነው። ዮናታን ለዳዊት ያለው ታማኝነት አንዲት ሴት ለባሏ እና ለልጇችዋ ካላት ታማኝነት እንኳን የበለጠ ነበር።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 ከዚህ በኋላ ዳዊት፤ “ከይሁዳ ከተሞች ወደ አንዲቱ ልውጣን?” ብሎ እግዚአብሔርን ጠየቀ፣ እግዚአብሔርም፣ “ወደ ኬብሮን” ብሎ መለሰለት። 2 ስለዚህ
ዳዊት ከሁለቱ ሚስቶቹ ከኢይዝራኤላዊቷ ከአኪናሆምና የቀርሜሎሳዊው የናባል ሚስት ከነበረችው ከአቢግያ ጋር ሄደ። ጠየቀ። እግዚአብሔርም፣ “ውጣ” ብሎ
መለሰለት። ዳዊትም፣ “ወደ የትኛው ከተማ ልሂድ?” ብሎ ጠየቀ። 3 ዳዊት ቤተ ሰቦቻቸውን ይዘው የመጡትን ከእርሱ ጋር የነበሩትን ሰዎች ወደሚኖሩበት ወደ
ኬብሮን ይዟቸው መጣ። 4 ከዚያ በኋላም የይሁዳ ሰዎች ወደ ኬብሮን መጥተው ዳዊትን በይሁዳ ቤት ላይ ንጉሥ አድርገው ቀቡት። የኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች
ሳኦልን እንደቀበሩት ለዳዊት ነገሩት። 5 ስለዚህ ወደ ኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች መልእክተኞች ልኮ እንደዚህ አላቸው፣ “ጌታችሁን ሳኦልን በመቅበር ይህንን በጎነት
ስላሳያችሁ በእግዚአብሔር የተባረካችሁ ናችሁ። 6 አሁንም እግዚአብሔር ጽኑ ፍቅሩንና ታማኝነቱን ይገለጥላችሁ፤ እናንተ ይህን ስላደረጋችሁ እኔም እንደዚሁ
በጎ ነገር አደርግላችኋለሁ። 7 እንግዲህ እጆቻችሁ ይጠንክሩ፣ በርቱ፤ ጌታችሁ ሳኦል ሞቶአልና፣ የይሁዳ ቤትም እኔን ቀብተው በላያቸው አንግሠውኛል።” 8
የሳኦል ሠራዊት አዛዥ፣ የኔር ልጅ አብኔር ግን የሳፆልን ልጅ ኢያቡስቴን ወስዶ ወደ መሃናይም አሻገረው፤ 9 ኢያቡስቴንም በገለዓድ፣ በአሴር፣ በኢይዝራኤል፣
በኤፍሬምና በብንያም እንዲሁም በእስራኤል ሁሉ ላይ አነገሠው። 10 የሳኦል ልጅ ኢያቡስቴ በእስራኤል ላይ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው አርባ ዓመት ነበረ፣ ሁለት
ዓመትም ገዛ። የይሁዳ ቤት ግን ዳዊትን ተከተለ። 11 ዳዊት በኬብሮን በይሁዳ ቤት ላይ ንጉሥ የሆነበት ዘመን ሰባት ዓመት ከስድስት ወር ነበር። 12 የኔር ልጅ
አብኔርና የሳኦል ልጅ የኢያቡስቴ አገልጋዮች ከመሃናይም ተነሥተው ወደ ገባዖን ሄዱ። 13 እነርሱንም የጽሩይ ልጅ ኢዮአብና የዳዊት ሰዎች በገባዖን ኩሬ አጠገብ
ተገናኟቸው፤ በዚያም አንዱ ወገን በኩሬው ወዲህ ማዶ፣ ሌላው ወገን ደግሞ በኩሬው ወዲያ ማዶ ተቀመጠ። 14 አበኔርም ለኢዮአብ፣ “ጎልማሶች ይነሡና
እርስ በርሳቸው ይጋጠሙ” አለው። ኢዮአብም፣ “እሺ፣ ይነሡ” አለ። 15 ከዚያ በኋላም ከብንያምና ከሳኦል ልጅ ከኢያቡስቴ ወገን አሥራ ሁለት፣ የዳዊት
አገልጋዮች ከሆኑት ደግሞ አሥራ ሁለት ጎልማሶች ተነሥተው በአንድነት ተሰባሰቡ። 16 እያንደንዱም ሰው የባላጋራውን ራስ በመያዝ ሰይፉን በጎኑ እየሻጠበት
ተያይዘው ወደቁ። ስለዚህ በገባዖን ያለው ያ ስፍራ በዕብራይስጥ ‘ሐልቃት አዙሪም’ ወይም ‘የሰይፍ ምድር’ ተባለ። 17 በዚያን ዕለት ጦርነቱ እጅግ ከባድ
ነበር፣ አበኔርና የእስራኤል ሰዎች በዳዊት አገልጋዮች ድል ሆኑ። 18 ሦስቱ የጽሩይ ወንዶች ልጆች ኢዮአብ፣ አቢሳና አሣሄል እዚያው ነበሩ። አሣሄል እንደ ዱር
ሚዳቋ በሩጫ ፈጣን ነበር፤ 19 አሣሄል በየትኛውም አቅጣጫ ዞር ሳይል አበኔርን በቅርበት ተከታተለው። 20 አበኔርም ወደ ኋላው ዞር ብሎ በመመልከት፣
“አሣሄል አንተ ነህን?” አለው። እርሱም፣ “እኔ ነኝ” ሲል መለሰለት። 21 አበኔርም፣ “ወደ ቀኝህ ወይም ወደ ግራህ ዘወር በልና አንዱን ጎልማሳ ይዘህ
መሣሪያውን ንጠቀው” አለው፤ አሣሄል ግን እርሱን መከታተሉን አልተወም ነበር። 22 እንደገናም አቤኔር “እኔን መከታተል ብትተው ይሻልሃል፤ እኔስ ለምን
ከመሬት ጋር ላጣብቅህ? ከዚያስ የወንድምህን የኢዮአብን ፊት ቀና ብዬ እንዴት አያለሁ?” አለው። 23 አሣሄል ግን ዘወር ለማለት እምቢ አለ፤ ስለዚህ አብኔር
በጦሩ ጫፍ አከላቱን ወጋው፤ ጦሩም በአካሉ በሌላው ወገን ዘልቆ ወጣ፤ አሣሄልም ወደቀ፣ በዚያ ስፍራም ሞተ። ስለሆነም አሣሄል ወደ ወደቀበት ይመጣ
የነበረ እያንዳንዱ ሰው በዚያ ስፍራ ሲደርስ ይቆም ነበር። 24 ኢዮአብና አቢሳ ግን አበኔርን አሳደዱት፤ ፀሐይም በምትጠልቅበት ጊዜ ወደ ገባዖን ምድረ በዳ
በሚወስደው መንገድ ከጋይ አጠገብ ወዳለው ወደ አማ ኮረብታ ደረሱ። 25 የብንያም ሰዎችም ከአበኔር በስተኋላ ተሰብስበው በተራራው ጫፍ ላይ ቆሙ። 26
ከዚያ በኋላም አበኔር ኢዮአብን ጠርቶ፣ “ሰይፍ ለዘላለም ማጥፋት አለበትን? ውጤቱ በመጨረሻ መራራ መሆኑን አንተ አታውቅምን? ሰዎችህ ወንድሞቻቸውን
ማሳደድ እንዲያቆሙ የማትነግራቸውስ እስከ መቼ ድረስ ነው?” አለው። 27 ኢዮአብም ፣ “ሕያው እግዚአብሔርን፣ ይህን ባትናገር ኖሮ፣ ወታደሮቼ እስኪነጋ
ድረስ ወንድሞቻቸውን ባሳደዱ ነበር” ብሎ መለሰ። 28 ስለዚህ ኢዮአብ ቀንደ መለከቱን ነፋ፤ ሰዎቹም ሁሉ ቆሙ፤ ከዚያ በኋላም እስራኤልን አላሳደዱም፣
መዋጋታቸውንም አልቀጠሉም። 29 አበኔርና ሰዎቹም ሌሊቱን ሁሉ በዓረባ በኩል አለፉ፤ ዮርዳኖስን ተሻግረው በማግሥቱ ጥዋት ሲጓዙ ቆይተው ከዚያ በኋላ
ወደ መሃናይም ደረሱ። 30 ኢዮአብም አበኔር ከማሳደድ ተመለሰ። አሣሄልና ከዳዊት ወታደሮች አሥራ ዘጠኙ የጎደሉባቸውን ሰዎቹን ሁሉ ሰበሰበ። 31 የዳዊት
ሰዎች ግን ከአበኔር ጋር ከነበሩት ሦስት መቶ ሥልሳ ብንያማውያንን ገድለዋል። 32 ከዚያ በኋላም አሣሄልን ከወደቀበት አንሥተው ቤተ ልሔም በነበረው በአባቱ
መቃብር ቀበሩት። ኢዮአብና ሰዎቹ ሌሊቱን ሁሉ ገሥግሠው ኬብሮን ሲደርሱ ሌሊቱ ነጋላቸው።

---

2 Samuel 2:1

ከዚህ በኋላ
"ዳዊት ለሳኦል እና ዮናታን ሞት ካለቀሰ/ካዘነ በኋላ"

ከይሁዳ ከተሞች ወደ አንደኛዋ ለመውጣት
በዚህን ጊዜ ዳዊት በጸቅላግ ነበር። ዳዊት "መውጣት" የሚለውን ሀረግ የተጠቀመው ጸቅላግ ከይሁዳ ይልቅ ከባህር ወለል ዝቅ ብላ ስለምትገኝ ነው። "ከይሁዳ ከተሞች ወደ አንዲቱ ወጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ዳዊት ከሁለቱ ሚስቶቹ ጋር ወጣ
በዚህን ጊዜ ዳዊት በጸቅላግ ነበር። ተራኪው "መውጣት" የሚለውን ሀረግ የተጠቀመው ጸቅላግ ከኬብሮን ይልቅ ከባህር ወለል ዝቅ ብላ ስለምትገኝ ነው። ዳዊት ከሁለቱ ሚስቶቹ ጋር ወደ ኬብሮን ወጣ።

2 Samuel 2:4

ንጉሥ ዳዊት ተቀባ
በዚህ ተምሳሌታዊ ድርጊት፣ በዳዊት ራስ ላይ ዘይት ያፈሰሱት ንጉሥ ሆኖ መመረጡን ለማሳየት ነው። (ተምሳሌታዊ/ትዕምርታዊ ድርጊት)

የይሁዳ ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው የዋለው "ነገድ" በሚል ትርጉም ነው። "የይሁዳ ነገድ"

ኢያቢስ ገለዓድ
ይህ በገለዓድ ግዛት የሚገኝ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 2:6

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ከኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች ጋር ተነጋገረ።

እነዚህ ነገሮች
ሳኦልን ቀበሩት

እጆቻችሁ ይጠንክሩ
እዚህ ስፍራ "እጆች" የሚለው የሚያመለክተው የኢያቢስ ገለዓድን ሰዎች ነው። "ጠንክሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/የነገሩን ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ንጉሥ እሆን ዘንድ ቀብተውኛል
በዚህ ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት፣ በዳዊት ራስ ላይ ዘይት ያፈሰሱት ንጉሥ ሆኖ መመረጡን ለማሳየት ነው። (ምልክታዊ/ትዕምራታዊ ድርጊት)

2 Samuel 2:8

ኔር... ኢያቡስቴ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

መሃናይም... ገለዓድ... ኢይዝራኤል
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 2:10

የይሁዳ ቤት ዳዊትን ተከተለው
የዳዊትን ተዕዛዝ መቀበል የተገለጸው እርሱን "መከተል" ተደርጎ ነው። "የይሁዳ ነገድ ዳዊትን ንጉሣቸው አድርገው ታዘዙት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኝ። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳ ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው የዋለው "ነገድ" በሚል ትርጉም ነው።

2 Samuel 2:12

አቤኔር... ኔር... አቤኔር...ሳኦል... ጽሩያ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 2:16

አብረው ወደቁ
ሞቱ የሚለው በትሁት መንገድ የተገለጸበት ነው። "ሁለቱም ሞቱ" በሚለው ወስጥ እንደሚገኘው። (የፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

የሰይፍ ምድር
ይህ በዚያ ምን እንደሆነ/እንደተፈጸመ ለሰዎች ለማስታወስ የተሰጠ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚያን ቀን ውጊያው እጅግ የከፋ ነበር
ይህ የወጣቶቹን ግጥሚያ ተከትሎ የመጣ ታላቅ ጦርነት መሆኑን በሚገባ ለመግለጽ ሊረዳ ይችላል። "ከዚያ የተቀሩትም ደግሞ መዋጋት ጀመሩ። በዚያን ቀን እጅግ ጽኑ ውጊያ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 2:18

ጽሩያ... ኢዮአብ... አቢሳ... አሣሄል... አቤኔር
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አሳኤል እግሮቹ እንደ ዱር ሚዳቋ ፈጣን ነበር
እዚህ ስፍራ አሳኤል የተነጻጸረው እጅግ ፈጣን ሯጭ ከሆነው እንስሳ ከሚዳቋ ጋር ነው። "አሳኤል እጅግ ፈጥኖ መሮጥ ይችላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የዱር ሚዳቋ
ይህ ትንሽ፣ አራት እግር ያለው እና በራሱ ላይ ሁለት ትልልቅ ቀንዶች ያሉት በፍጥነት የሚሮጥ እንስሳ ነው።

ወደ የትኛውም አቅጣጫ ዘወር ሳይል እርሱን ተከተለው
እዚህ ስፍራ "ዘወር ሳይል" የሚለው የተገለጸው የአቤኔርን ፍለጋ እንዴት በቅርበት እንደተከተለው በአሉታዊ መልኩ ትኩረት ለመስጠት ነው። "በሄደበት ሁሉ ተከተለው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

2 Samuel 2:20

አሣሄል
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ዞር በል...ወደ ቀኝህ ወይም ወደ ግራህ ፈቀቅ በል
"እኔን ማሳደድህን አቁም... አቤኔርን ማሳደድህን አቁም"

ከወጣቶቹ ወንዶች መሃል አንዱን ጎበዝ ያዝና ትጥቁን ቀማው
አቤኔር አሳሄልን የአቤነርን ያህል አደገኛ ሊሆን የማይችልን ሌላ ወጣት ወታደርን እንዲገድል እና እንዲዘርፍ ይጠይቀው ነበር። እርሱ አሳሄልን ለገድለው አልፈለገም። "ከሌላ ወታደር ጋር ተዋግተህ መሳሪያውን ምርኮ አድርገህ ውሰድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 2:22

ለምን ከምድር ጋር ላጣብቅህ?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ አሳሄልን ስላጋጠመው አደጋ ለማስጠንቀቅ ውሏል። "ወደ ምድር ማጣበቅ" የሚለው ትሁት በሆነ አገላለጽ "መግደል" ማለት ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና የፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚሉትን ይመልከቱ)

ወንድምህን ኢዮአብን እንዴት ፊቴን አቅንቼ ማየት እችላለሁ?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ አቤኔር መዋጋት እና አሳኤልን መግደል እንደማይፈልግ አጉልቶ ይገልጻል፣ ለዚህም ምክንያቱ ጉዳዩ አቤኔር ከኢዮአብ ጋር ያለውን ግንኙነት ሊያጠፋ የሚችል መሆኑ ነው። እዚህ ላይ "ፊቴን ወደ ኢዮአብ አቀናለሁ" የሚለው ኢዮአብን ለማየት እጅግ አፍራለሁ የሚል ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ወንድምህን ኢዮአብን ለማየት እጅግ አፍራለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና የፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚሉትን ይመልከቱ)

ወደ ጎን ዘወር በል
ይህ ማለት "ቁም" ወይም "ማሳደድህን አቁም" ማለት ነው።

የጦሩ ዱልዱም ጫፍ
ይህ የሚያመለክተው ስል ያልሆነውን ወይም ምንም ነገር ለመውጋት ያልተበጀ የጦሩ መያዣ ስፍራ ነው። አቤኔር ይሞክር የነበረው አሳኤል እንዳይከተለው ማድረግ ብቻ እንጂ ሊገድለው አላሰበም የሚል አንድምታ አለው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 2:24

አቢሳ
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የአማ ኮረብታ...ገባኦን
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 2:26

አቤኔር ተጣራ
"አቤኔር ጮኸ"

ሰይፍ ለዘለዓለም ያጠፋልን?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ አጉልቶ የሚያሳየው ጦርነቱ እጅግ ለረጅም ጊዜ መቆየቱን ነው። እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚያመለክተው ጦርነቱን ነው። በጦርነቱ ውስጥ የተካሄደው ግድያ የተገለጸው ወታደሮቹን የዱር አውሬ እንደበላቸው ተደርጎ ነው። "ሰይፎቻችንን እርስ በእርስ ለመዋጋት እና ለመገዳደል መጠቀማችንን መቀጠል የለብንም" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት እንዲሁም ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

በመጨረሻ ይህ መራራ እንደሚሆን አታውቅምን?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተራዘመ ጦርነት ለበለጠ መከራ እንደሚዳርግ ኢዮአብ እውቅና እንዲሰጥ ለማስገደድ ውሏል። እዚህ ስፍራ "መራራ" የሚለው ቃል እጅግ አሰቃቂ የሆነን መከራ ለመግለጽ የዋለዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት/ ነው። " ይህ ከቀጠለ እጅግ የከፋ ችግር እንደመሆን በሚገባ ታውቃለህ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚሉትን ይመልከቱ)

የአንተ ሰዎች ወንድሞቻቸውን ከማሳደድ ይመለሱ ዘንድ የማትናገረው እስከ መቼ ድረስ ነው?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ ኢዮአብ እስራኤላውያን ወገኖቻቸውን መውጋት እንዲያቆም ለማሳመን የታቀደ ነው። እዚህ ስፍራ "ወንድም" የሚለው ቃል የዋለው የእስራኤል አገር ሰዎችን ለመወከል ነው። "እስራኤላውያን እርስ በእርሳቸው እንዳይገዳደሉ አሁን ይህንን አቁም!" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

ሕያው እግዚአብሔርን!
ይህ በጣም ጠንካራ መሃላ ነው። "እግዚአብሔር ምስክሬ ነው" ወይም "እግዚአብሔር ያልኩት እውነት መሆኑን ያጸናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ያንን ካልተናገርክ ... እስከ ማለዳ ወንድሞቻቸውን ያሳዱ
አቤኔር ለኢዮአብ በጥበብ ካልመለሰለት፣ ይህ መላምታዊ ሃሳብ ሊሆን የሚችለውን ነገር ያስረዳል። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 2:28

መለከት ንፉ
መለከቶች ሩቅ ስፍራ ለሚገኙ ወታደሮች ትዕዛዝ ለማስተላለፍ ያገለግሉ ነበር። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እስራኤልን አላሳደደም
እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚለው ቃል የሚያመለክተው እስራኤላውያን ወታደሮችን ነው። "እስራኤላውያን ወታደርችን ማሳደድ አልቀጠሉም" (ስኔክቲክ/የነገሩን ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ዓረባ... መሃናይም
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 2:30

አሣሄል
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ከአቤኔር ጋር **360** የብንያም ሰዎች
"ከብንያም 360 ሰዎች አቤኔርን የተከተሉ" አቤኔር አልሞተም

360 ሰዎች
"ሶስት መቶ ስልሳ ወንዶች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ከብንያም
ይህ ሀረግ "ከብንያም ነገድ" ማለት ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አሣሄልን አሉት
"የአሣሄልን በድን ይዘው ሄዱ"

በኬብሮን ቀኑ መሸቶ ነጋባቸው
"በማግስቱ ንጋት ላይ ኬብሮን ደረሱ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 በሳዖል ቤትና በዳዊት ቤት መካከል ለረጅም ጊዜ የቆየ ጦርነት ነበረ። ዳዊት እየበረታ ሲሄድ የሳዖል ቤት ግን እየደከመ ሄደ። 2 በኬብሮን ለዳዊት ወንዶች
ልጆች ተወለዱለት። የበኩር ልጁ፣ ከኢይዝራኤላዊቷ ከአኪናሆም የተወለደው አምኖን ነበር። 3 ሁለተኛው፣ የቀርሜሎሳዊው የናባል ሚስት ከነበረችው ከአቢግያ
የተወለደው ኪልአብ ነበር። ሦስተኛ የነበረው፣ አቤሴሎም የጌሹር ንጉሥ ከነበረው ከተልማይ ልጅ ከመዓካ የተወለደው ነበር። 4 አራተኛው፣ ልጁ ከአጊት
የተወለደው አዶንያስ፣ አምስተኛው፣ ከአቢጣል የተወለደው ሰፋጥያ፣ 5 ስድስተኛው፣ ከዳዊት ሚስት ከዔግላ የተወለደው ይትርኃም ነበር፤ እነዚህ ወንዶች ልጆች
ለዳዊት በኬብሮን የተወለዱለት ነበሩ። 6 የሳኦል ቤትና የዳዊት ቤት በጦርነት ላይ በነበሩበት ጊዜ አበኔር በሳዖል ቤት ራሱን ጠንካራ አድርጎ ነበር። 7 ሳኦል
የኢዮሄል ልጅ ሪጽፋ የተባለች ቁባት ነበረችው፤ ኢያቡስቴም አበኔርን፣ “ለምንድን ነው ከአባቴ ቁባት ጋር የተኛኸው?” አለው። 8 አብኔርም በዚያን ጊዜ
በኢያቡስቴ ንግግር እጅግ ስለተቆጣ እንዲህ አለ፣ “እኔ ለይሁዳ የተሰጠሁ የውሻ ራስ ነኝን? አንተን ለዳዊት አሳልፌ ባለመስጠቴ እኔ ዛሬ ለአባትህ ለሳኦል ቤት
ለወንድሞቹና ለወዳጆቹ ታማኝነቴን አሳይቻለሁ፤ ይህም ሆኖ ሳለ አንተ ከዚህች ሴት ጋር በፈጸምሁት ነገር ትከሰኛለህን? 9 እግዚአብሔር ለዳዊት መንግሥትን
ከሳዖል ቤት አውጥቶ 10 ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ባለው በእስራኤልና በይሁዳ ዙፋኑን እንደሚያጸና በመሐላ የገባለት ተስፋ እንዲፈጸም ባለደርግ እግዚአብሔር
በእኔ በአበኔር ላይ ክፉ ያድርግብኝ ከዚያ የባሰም ያምጣብኝ።” 11 ኢያቡስቴም አበኔርን ፈርቶት ስለነበረ አንዲት ቃል ስንኳ ሊመልስለት አልቻለም። 12
ከዚያም አበኔር ለዳዊት፣ “ይህች ምድር የማን ናት? ከእኔ ጋር ቃል ኪዳን አድርግ፣ እነሆ፣ እስራኤል ሁሉ ወደ አንተ እንዲመለሱ ለማድረግ እጄ ከአንተ ጋር
እንደሆነ ትመለከታለህ” ብለው እንዲነግሩለት መልእክተኞችን ላከ። 13 ዳዊትም፣ “መልካም ከአንተ ጋር ቃል ኪዳን እገባለሁ፤ ነገር ግን ከአንተ የምሻው አንድ
ነገር፤ ወደ እኔ በምትመጣበት ጊዜ የሳዖልን ሴት ልጅ ሜልኮልን ይዘህልኝ ካልመጣህ ፊቴን ማየት እንደማትችል እንድታውቅ ነው።” አለው። 14 ከዚያም
ዳዊት፣ “የመቶ ፍልስጥኤማውያን ሸለፈት ማጫ የከፈልሁባትን ሚስቴን ሜልኮልን ስጠኝ” ብሎ ወደ ሳኦል ልጅ ወደ ኢያቡስቴ መልእክተኞች ላከበት። 15
ስለዚህም ኢያቡስቴ መልእክተኛ ልኮ፣ ሜልኮልን ከባሏ ከሌሳ ልጅ ከፍልጢኤል ወሰዳት። 16 ባሏም እስከ ብራቂም ከተማ ድረስ እያለቀሰ ተከትሎአት ሄደ፤
ከዚያም አበኔር፣ “አሁን፣ ወደ ቤትህ ተመለስ” አለው። ስለዚህም ተመለሰ። 17 አበኔር ከእስራኤል ሽማግሌዎች ጋር እንደዚህ በማለት ተመካከረ፤ “ባለፈው
ጊዜ ዳዊትን በላያችሁ ለማንገሥ ሞክራችሁ ነበር፤ 18 እግዚአብሔር ለዳዊት፣ ‘በባሪያዬ በዳዊት ሕዝቤን እስራኤልን ከፍልስጥኤማውያን እጅና ከጠላቶቻቸው
ሁሉ እጅ እታደጋቸዋለሁ’ ብሎ ስለተናገረው፣ ይህን አሁኑኑ አድርጉት።” 19 አበኔርም ራሱ ሄዶ ለብንያማውያን ይህንን ነገራቸው፤ ከዚያም በኋላ አበኔር
እስራኤልና መላው የብንያም ቤት ለማድረግ የፈለገውን ሁሉ በመግለጽ ለዳዊት ለመንገር ወደ ኬብሮን ሄደ። 20 ከሃያ ሰዎች ጋር አበኔር በዳዊት ፊት ለመቅረብ
ወደ ኬብሮን በመጡ ጊዜ ዳዊት ግብዣ አደረገላቸው። 21 አበኔርም ለዳዊት፣ “ከአንተ ጋር ቃል ኪዳን እንዲያደርጉና በፈለግኸውም ሁሉ ላይ እንድትገዛ
ተነሥቼ እስራኤልን ሁሉ ወደ አንተ እሰበስባለሁ” በማለት ገለጸለት። ዳዊትም አሰናበተው፤ አበኔርም በሰላም ሄደ። 22 ከዚያ በኋላ የዳዊትና የኢዮአብ
ወታደሮች ከዘመቻ ሲመለሱ ብዙ ምርኮ ይዘው መጡ። ዳዊት አሰናብቶት ስለነበረና እርሱም በሰላም ስለሄደ አበኔር በኬብሮን ከዳዊት ጋር አልነበረም። 23
ኢዮአብና አብሮት የነበረው ሠራዊት ሁሉ እዚያ እንደ ደረሱ፣ “የኔር ልጅ አበኔር ወደ ንጉሡ መጣ ንጉሡም አሰናበተው እርሱም በሰላም ሄደ” ብለው ለኢዮአብ
ነገሩት። 24 ስለዚህ ኢዮአብ ወደ ንጉሡ ገብቶ እንዲህ አለ፣ “ምን ማድረግህ ነው? እነሆ አበኔር መጥቶልህ ለምን ይሄድ ዘንድ አሰናበትኸው? 25 የኔር ልጅ
አበኔር የመጣው አንተን ሊያታልልህ፣ ዕቅድህን ለማወቅና የምታደርገውን ማንኛውንም ነገር ለማጥናት እንደሆነ አታውቅምን?” 26 ኢዮአብ ከዳዊት ዘንድ
በወጣ ጊዜ አበኔር ዘንድ መልእክተኞችን ላከ እነርሱም ከሴይር የውሃ ጉድጓድ አጠገብ መለሱት። ዳዊት ግን ይህን አላወቀም ነበር። 27 አበኔር ወደ ኬብሮን
በተመለሰ ጊዜ ኢዮአብ በቆይታ ለማነጋገር ወደ ቅጥሩ ዞር አደረገው በዚያም ሆዱን ወግቶ ገደለው፤ በዚህም ዓይነት መንገድ የወንድሙን የአሣሄልን ደም
ተበቀለ። 28 ዳዊት ይህንን በሰማ ጊዜ እንዲህ አለ፣ “እኔም ሆንሁ መንግሥቴ ከኔር ልጅ ከአብኔር ደም በእግዚአብሔር ፊት ለዘላለም ንጹሕ ነን፤ 29 ደሙ
በኢዮአብ ራስና በአባቱ ቤት ሁሉ ላይ ይሁን፤ ፈሳሽ ነገር የሚወጣው ወይም አሠቃቂ የቆዳ በሽታ ያለበት፣ በምርኩዝ የሚሄድ አንካሳ፣ ወይም በሰይፍ የሚገደል
ወይም ምግብ አጥቶ የሚራብ ሰው ከኢዮአብ ቤት አይታጣ።” 30 ስለዚህ ወንድማቸውን አሣሄልን በገባዖን በተደረገው ጦርነት ገድሎባቸው ነበርና፣ ኢዮአብና
ወንድሙ አቢሳ አበኔርን ገደሉት። 31 ዳዊት ለኢዮአብና አብሮት ለነበረው ሕዝብ ሁሉ፣ “ልብሳችሁን ቀዳችሁ፣ ማቅ ለብሳችሁ በአበኔር አስከሬን ፊት አልቅሱ”
አላቸው፤ ንጉሥ ዳዊትም አስከሬኑን ከሚያጅበው ሕዝብ ጋር አብሮ ይሄድ ነበር። 32 አበኔርንም በኬብሮን ቀበሩት፤ ንጉሡም በአበኔር መቃብር ላይ ጮኾ
አለቀሰ፤ ሕዝቡም ሁሉ እንደዚሁ አለቀሱ። 33 ንጉሡም በሐዘን እንጉርጉሮ ለአበኔር አለቀሰ፣ “አበኔር እንደ ተራ ሰው ሊሞት ይገባው ነበር? 34 እጆችህ
አልታሰሩም፤ እግሮችህ በእግር ብረት አልገቡም፤ ሰዎች በግፈኞች ፊት እንደሚወድቁ አንተም እንደዚህ ወደቅህ።” ሕዝቡም ሁሉ እንደገና አለቀሱለት። 35 ገና
ቀን ሳለ ምግብ እንዲበላ ለማድረግ ሕዝቡ ሁሉ ወደ ዳዊት መጡ፤ ዳዊት ግን፣ “ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት እንጀራ ወይም ማንኛውንም ነገር ብቀምስ
እግዚአብሔር ክፉ ያድርግብኝ ከዚያም የባሰ ያምጣብኝ” ብሎ ማለ። 36 ሕዝቡም ሁሉ የዳዊትን ሐዘን ተመለከቱ፤ ንጉሡ የሚያደርገው ሁሉ በእርግጥ ደስ
ያሰኛቸው ስለነበረ፣ በዚህም ደስ አላቸው። 37 ስለዚህ የኔር ልጅ አበኔር ይገደል ዘንድ የንጉሡ ፍላጎት እንዳልነበረ ሕዝቡ ሁሉና እስራኤል በሙሉ በዚያን ዕለት
ዐወቁ። 38 ንጉሡ ለአገልጋዮቹ እንደዚህ አላቸው፣ “በዛሬይቱ ዕለት በእስራኤል መስፍንና ታላቅ ሰው መውደቁን አላወቃችሁምን? 39 ምንም እንኳን የተቀባሁ
ንጉሥ ብሆንም እኔ ደካማ ነኝ፤ እነዚህ የጽሩይ ልጆች እጅግ ጨካኞች ሆነውብኛል። እንደ ክፋቱ በመቅጣት እግዚአብሔር ለክፉ አድራጊው እንደ እጁ ሥራ
መጠን ይክፈለው።”

---

2 Samuel 3:1

አሁን
እዚህ ስፍራ የዋለው በታሪኩ ፍሰት ላይ መቆሚያ ለማድረግ ነው። በዚህ ስፍራ ሳሙኤል በዳዊት እና በሳኦል ደጋፊዎች መካከል ስለ ተደረገው ጦርነት መረጃ ይሰጣል። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው ቃል የዋለው "ደጋፊዎች" ለማለት ነው። እየበረታ እና ይበልጥ እየበረታ ሄደ ይህ ዘይቤያዊ አነጋገር ዳዊትን የሚደግፉት ሰዎች ጨመረ ማለት ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እየደከመ እና ይበልጥ እየደከመ ሄደ
ይህ ዘይቤያዊ አነጋገር የሳኦልን ቤተሰብ የሚደግፉት ሰዎች ቀነሰ ማለት ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Samuel 3:2

ለዳዊት ወንድ ልጆች ተወለዱለት
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል:: "የዳዊት ሚስቶች ስድሰት ወንድ ልጆችን ወለዱ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አንደኛ ልጅ... ሁለተኛ ልጅ... ሶስተኛ
ይህ የዳዊት ልጆች የቁጥር ቅደም ተከተል ነው:: (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

አኪናሆም...አቢግያ... መዓካ
እነዚህ የሴቶች ስሞች ናቸው:: እነዚህ የዳዊት ሚስቶች ናቸው:: (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ኪልአብ...ናባል... ተልማይ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው:: (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 3:4

አራተኛ ልጅ... አምስተኛ ልጅ... ስድስተኛው
ይህ የዳዊት ልጆች የቁጥር ቅደም ተከተል ነው:: (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

አዶንያስ... ሰፋጥያስ...ይትረኃም
እነዚህ የዳዊት ወንድ ልጆች ስሞች ናቸው:: (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አቢት...አቢጣል...ዔግላ
እነዚህ የዳዊት ሚስቶች ስሞች ናቸው:: (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 3:6

እንዲህም ሆነ
ይህ በዳዊት ደጋፊዎች እና በሳኦል ቤት ትግል ታሪክ አካሄድ አዲስ ትዕይንትን ያስተዋውቃል:: (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

የሳኦል ቤት
ይህ ከሳኦል ቤት እና ደጋፊዎች መሃል ከሳኦል ሞት በኋላ ማን ርስቱን መቆጣጠር ይገባኛል እንደሚል የሚያመለክት ነው

የዳዊት ቤት
ይህ የዳዊትን ደጋፊዎች የሚያመለክት ነው::

ከሳኦል ቤት አቤኔር ራሱን አበረታ
የአቤኔር በሳኦል ቤት ላይ ሃይሉን እየጨመረ መሄድ የተገለጸው፣ ልክ በአካል ጠንካራ እየሆነ እንደመጣ ተደርጎ ነው:: "አቤኔር በሳኦል ቤት እና ደጋፊዎች ላይ የበለጠ ሃይል አገኘ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሪጽፋ...አኪ
እነዚህ የሴቶች ስሞች ናቸው:: (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ኢያቡስቴ
ይህ የወንድ ስም ነው፤ የሳኦል ልጅ ነው:: (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ከአባቴ ቁባት ጋር ለምን ተኛህ?
ኢያቡስቴ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው እንደ ንጉሥ ራሱን የቆጠረውን አቤኔርን ለመገሰጽ ነበር:: "ከአባቴ ቁባት ጋር ለመተኛት መብት የለህም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

አብረህ ተኛህ
ይህ ለወሲባዊ ግንኙነት ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት/ ነው::

2 Samuel 3:8

እኔ ለይሁዳ የምወግን፣ የውሻ ራስ ነኝን?
አቤኔር ስለ ራሱ፣ እስራኤላውያን ለመገበው ታማኝ ነው ብለው እንደሚቆጥሩት ውሻ ሁሉ እርሱ የውሻ ራስ ተደርጎ እንደተቆጠረ ይናገራል:: እዚህ ስፍራ "ለይሁዳ መሆን" የሚለው የሚያመለክተው አቤኔር ዳዊት ለሚገኝበት ለይሁዳ እንጂ ለሳኦል ቤት አለመቆጠሩን ነው:: "እኔ ክጄ ለይሁዳ ሆንኩን?" ወይም "እኔ ለዳዊት የምሰራ ከሃዲ አይደለሁም!" (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

በዳዊት እጅ ላይ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው የሚወክለው ለማሸነፍ ያለን አቅም ነው:: "በዳዊት መሸነፍ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን አንተ አሁን ይህችን ሴት በሚመለከት ጥፋተኛ አድርገህ ትከሰኛለህ?
አቤኔር ይህንን ጥያቄ የሚያነሳው ኢያቡስቴን ለመገሰጽ ነው:: አቤኔር በእርግጥ ከሪጽፋ ጋር ስለ መተኛቱ ወይም በሃሰት ስለመወንጀሉ ግልጽ የሆነ ነገር የለም:: ሊሰጡ የሚችሉ ትርጓሜዎች እነዚህ ናቸው: 1) አቤኔር ጥፋተኛ የሚሆነው: "ከዚህች ሴት ጋር በመተኛቴ ልትበሳጭ አይገባህም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው ወይም 2) አቤኔር ጥፋተኛ የማይሆነው: "ከዚህች ሴት ጋር ተኝተሃል ብለህ ልታስብ አይገባህም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 3:9

እኔ ይህን ካላደረገኩ፣ እግዚአብሔር ይህንን በእኔ ላይ ያድርግ...ከዚህም በላይ ይጨምርብኝ
በዚያን ዘመን የዚህ አይነት መሃላ ነበር:: አቤኔር መሃላውን ካልጠበቀ እግዚአብሔር እጅግ አድርጎ እንዲፈርድበት ይጠይቃል:: የእናንተ ቋንቋ መሃላን የሚገልጽበት መንገድ ሊኖረው ይችላል:: "እኔ ይህ ካላደረግኩ እግዚአብሔር እንዲህ ይቅጣኝ " በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው::

የሳኦል ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው የሚያመለክተው የሳኦልን ቤት እና ከሳኦል ሞት በኋላ በህይወት የተረፉትን ነው:: "የሳኦል ቤትና ደጋፊዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው::

የዳዊት ዙፋን
ይህ ሀረግ የዳዊትን የንጉሥነት ስልጣን ያመለክታል

2 Samuel 3:12

ለዳዊት
አንዳንድ ቅጂዎች "በኬብሮን በነበረበት ጊዜ" የሚል ይጨምራሉ፣ ሌሎቹ ግን ይህን አይጨምሩም:: በእናንተ ብሔራዊ ቅጂ ውስጥ ካለ ይህንን መጨመር ሊኖርባችሁ ይችላል:: (የቅጂ ልዩነቶች የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የማን ምድር ነው?
የዚህ ጥያቄ የመጀመሪያው ጽሁፍ ግልጽ አይደለም:: ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) አቤኔር ምድሪቱን ለዳዊት ለመስጠት ሃይል አለው:: "ይህ ምድር የእኔ ነው!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: ወይም 2) ዳዊት ምድሪቱን

ለመግዛት በእግዚአብሔር የተመረጠ ነው፡ "ምድሪቱ በትክክል የአንተ ናት!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እጄ ከአንተ ጋር ነው
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው የሚወክለው አበኔር ለዳዊት ያቀረበለትን እርዳታ ነው፡፡ "እኔ እረዳሃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በመጀመሪያ ሚልኮልን ካላመጣሃት በስተቀር ፊቴን ማየት አትችልም
ዳዊት አቤኔርን የሚገኛኝበትን ሁኔታ ገልጽዋል፡፡ እዚህ ስፍራ "ፊት" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ራሱን ዳዊትን ነው፡፡ "በመጀመሪያ ሚልኮልን ወደ እኔ ካላመጣሃት በስተቀር ልታየኝ አትችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ሚልኮል
ይህ የሳኦል ሴት ልጅ ስም ነው፡፡የዳዊት የመጀመሪያ ሚስቱ ነበረች፡፡ (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 3:14

አንድ መቶ የፍልስጥኤማውያን ሸለፈቶች
ይህ ሚልኮልን ለማግባት ሳኦል ይፈቅድለት ዘንድ ዳዊት የገደላቸውን ሰዎች ቁጥር ይወክላል፡፡ እነዚህ ሰዎች እዚህ ስፍራ የተቆጠሩት በ"ሸለፈቶቻቸው" ነው፡፡ "ሸለፈት" የወንድን መራቢያ ብልት የሚሸፍን የቆዳ እጥፋት ነው፡፡ (ቁጥሮች እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከባሏ ወሰዳት
ፈልጢኤል የሚልኮል ሁለተኛ ባሏ ነበር፡፡ (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ብራቂም
ይህ የአንድ መንደር ስም ነው፡፡ (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 3:17

አሁን አድርጉት
"ስለዚህ አሁን ዳዊትን ንጉሣችሁ አድርጉት"

በባሪያዬ በዳዊት እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው የሚያመለክተው ዳዊት ፍልስጥኤማውያንን ለማሸነፍ ያለውን ሃይል ነው፡፡ "እኔ ባርያዬን ዳዊትን አበረታዋለሁ ደግሞም" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የፍልስጥኤማውያን እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው የሚያመለክተው ፍልስጥኤማውያን በእስራኤላውያን ላይ ያላቸውን ሃይል ነው፡፡ "የፍልስጥኤማውያን ሃይል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የጠላቶቻቸው እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው የሚያመለክተው በእስራኤላውያን ላይ ያለን ሃይል ነው፡፡ "የጠላቶቻቸው ሁሉ ሃይል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 3:19

የብንያም ህዝብ...መላው የብንያም ቤት
እነዚህ ሁለት ሃሳቦች፣ የእስራኤል አንድ ነገድ የነበሩትን የብንያምን ትውልድ ያመለክታሉ፡፡ (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሃያዎቹ የእርሱ ሰዎች
ከአቤኔር ጋር የመጡ ወንዶች ቁጥር፡፡ (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 3:21

መላው እስራኤል
ይህ ሀረግ "መላው የእስራኤል አገር" ማለት ነው፡፡ (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህም ዳዊት አበኔርን አሰናበተው
በወዳጅነት ተለያዩ፡፡ ዳዊት በአበኔር አልተበሳጨም፡፡

2 Samuel 3:22

ምርኮ
እነዚህ ከጠላት የተወሰዱ ነገሮች ናቸው

አበኔር በኬብሮን ከዳዊት ጋር አልነበረም
አበኔርወደ ቤት ለመመለስ ተነስቶ ነበር

ለኢዮአብ ነገሩት
"የሆነ ሰው ለኢዮአብ ነገረው"

ኔር
ይህ የወንድ ስም ነው፡፡ የሳኦል ቅድም አያት ነው፡፡ (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 3:24

ያደረግከው ምንድን ነው?
ኢዮአብ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው አበኔርን በሰላም በማሰናበቱ ዳዊትን ለመገሰጽ ነው፡፡ "ይህን ማድረግ አልነበረብህም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ለምን አሰናበትከው፣ እና እርሱ ሄደ?
ኢዮአብ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው ዳዊት አበኔር እንዲያመልጥ በመተዉ ለመገሰጽ ነው፡፡ ይህ በአረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል፡፡ "አበኔር እዚህ ነበር አንተ አሰናበትከው!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የምታደርገውን ነገር ሁሉ...አታውቅምን?
ኢዮአብ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው አበኔር በዳዊት ላይ እያሴረ እንደሆነ ሊያሳምነው ነው፡፡ "አንተ በእርግጥ አታውቅምን... የምታደርገውን ነገር ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የሴይር ጉድጓድ
"ሴይር" የውሃ ጉድጓዱ የሚገንበት ስፍራ ነው፡፡ (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Samuel 3:27

የበሩ መግቢያ መሃል
ይህ የሚያመለክተው በኬብሮን በከተማይቱ ቅጥር ካሉት በሮች አንዱን ነው። በዩዲቢ ትርጉም ውስጥ እንደተመለከተው የከተማ በሮች የተገነቡት በከተማይቱ ቅጥር እንደሚገኙ ግንቦች ክፍል ሆነው ነው። በመተላለፊያ መንገዶቹ አጠገብ ወደ እንግዶች መቀበያ እና ንግድ እንዲሁም የፍትህ ስርአቶች ወደ ሚካሄዱባቸው ክፍሎች የሚወስዱ በሮች ይገኛሉ። ኢዮአብ አበኔርን የገደለው ምናልባት ከእነዚህ ክፍሎች በአንደኛው ነው።

የአሣኤል ደም
እዚህ ስፍራ "ደም" የሚለው ቃል የተያያዘው ከአሣኤል ሞት ጋር ነው። "የአሣኤል ሞት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አሣኤል
ይህ ወንድ የሆነ ሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 3:28

ኔር... አቢሳ...አሣኤል
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የአበኔር ደም
እዚህ ስፍራ "ደም" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የአበኔርን ሞት ነው። ተመሳሳዩን ሀረግ በ2ሳሙኤል3:27 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። "የአበኔር ሞት" ወይም "የአበኔር መገደል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በኢዮአብ ራስ እና በአባቱ ቤት ሁሉ ላይ ይውደቅ
የዚህ ሀረግ ትርጉም የጥፋቱ ውጤት በኢዮአብ እና በቤቱ ላይ አንዳች ከባድ ነገር እንደሚናድባቸው ያህል ይድረስ ማለት ነው። "ሁልጊዜ ለኢዮአብ እና ለአባቱ ቤት የመከራ ምክንያት ይሁንባቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በአባቱ ቤት ላይ ሁሉ
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ትውልዶች የሚለውን ነው። "የኢዮአብ አባት ትውልዶች ሁሉ) በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የሚወድቅ አይታጣ
ይህ ድርብ አሉታ የሚያጎላው ሁሌም የተዘረዘሩት ችግሮች የሚገጥመው ሰው የማይታጣ መሆኑን ነው። "ሁሌም በዚያ ይህ ይሁን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በሰይፍ ይገደል
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው በሃይል የሆነ ሞትን ነው። "በሃይል ይሞታሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ምግብ ይጡ
"ይራቡ"

2 Samuel 3:31

ልብሳችሁን ቅደዱ፣ ማቅ ልበሱ
እነዚህ ሀዘናቸውን እና ትካዜያቸውን ለመግለጽ ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊቶች ነበሩ። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊቶች)

ንጉሡ አነባ ጮኾም አለቀሰ
"አለቀሰ" እና "ጮኾ አለቀሰ" የሚሉት ቃላት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ደግሞም ዳዊት ምን ያህል ለአበኔር እንዳዘነ ትኩረት ይሰጣሉ። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 3:33

አበኔር ሰነፍ እንደሚሞት መሞት አለበትን
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የዋለው ሞቱ አግባብ የሌለው መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። "አበኔር በውርደት መሞት አልነበረበትም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እጆችህ አልታሰሩም። እግሮችህም በሰንሰለት አልተያዙም
እነዚህ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ሃሳብን ይገልጻሉ። በአንድ ዐረፍተ ነገር ውስጥ ሊቀርቡ ይችላሉ። "በማናቸውም መንገድ በእስርቤት ያለህ ወንጀለኛ አልነበርክም" ወይም "ሙሉ ለሙሉ ከስህተት ንጹህ ነበርክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እጆችህ አልታሰሩም ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ማንም እጆችህን አላሰረም ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እግሮችህ አልታሰሩም ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ማንም እግሮችህን በሰንሰለት አላሰረም ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የፍትህ አልባነት ልጆች
ይህ የሚያመለክተው ፍትህ አልባ የሆኑ ሰዎችን ወይም ክፉዎችን ነው። "ክፉ ሰዎች"በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 3:35

ህዝቡ ሁሉ መጡ
ይህ ይሁን ተብሎ የተደረገ ማጋነን የዋለው የእስራኤል ህዝብ ዳዊትን በሀዘኑ ሊያጽናኑት መፈለጋቸውን ለማሳየት ነው። "ብዙ ህዝብ መጣ" በሚለው ውሰጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያያት የሚሉትን ይመልከቱ)

እንዲህ ባላደርግ፣ እግዚአብሔር እንዲህ ያድርግብኝ፣ እንዲህም ይጨምርብም
ይህ በዚያ ዘመን የነበረ የመሃላ አይነት ነው። ዳዊት እግዚአብሔርን ፀሐይ ከመጥለቋ አስቀድሞ አንዳች ነገር ቢቀምስ በጽኑ እንዲቀጣው ይጠይቃል። የእናንተ ቋንቋ መሃላን የሚያደርግበት መንገድ ሊኖረው ይችላል። "እንዲህ ባደርግ እግዚአብሔር እንዲቀጣኝ እጠይቃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

2 Samuel 3:37

በዛሬው ቀን በኢየሩሳሌም አንድ ልዑል እና ታላቅ ሰው እንደ ወደቀ አታውቁምን?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የዋለው ዳዊት ምን ያህል አበኔርን እንደሚያከብረው ለማሳየት ነው። እዚህ ስፍራ "ወደቀ" የሚለው ቃል "ሞተ" ሚለውን የሚገልጽ ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት/ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ዛሬ አንድ ታላቅ ልዑል በኢየሩሳሌም

መሞቱ በእርግጥ እውነት ነው!" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚሉትን ይመልከቱ)

ልዑል እና ታላቅ ሰው
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ሁለቱም የሚያመለክቱት አበኔርን ነው። "ታላቅ ልዑል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሄንዲየዲስ/ ሁለት በ ‘እና' የሚገናኙ ቃላት አንድን ጥልቅ ሃሳብ የሚገልጹበት ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኔር...ጽሩያ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ጨካኝ
እንደ- እንስሳ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 አበኔር በኬብሮን መሞቱን የሳኦል ልጅ ኢያቡስቴ በሰማ ጊዜ እጆቹ ዛሉ፣ መላው እስራኤልም ተጨነቀ። 2 በዚህ ጊዜ የሳኦል ልጅ የወታደር ጭፍራ መሪዎች
የነበሩ ሁለት ሰዎች ነበሩት፤ የአንደኛው ስም በዓና ሲሆን የሌላኛው ስም ደግሞ ሬካብ ይባሉ ነበር። እነርሱም ከብንያም ነገድ የብኤሮት ተወላጅ የሆነው የሬሞን
ልጆች ነበሩ (ብኤሮት ከብንያም ክፍል እንደ አንዱ ትቆጠር ነበር፤ 3 የብኤሮት ሕዝብ ወደ ጌቴም በመሸሸ እስከ ዛሬ በዚያ ይኖራሉ) ። 4 የሳኦል ልጅ ዮናታን
ሁለት እግሮቹ ሽባ የሆኑ አንድ ልጅ ነበረው። እርሱም የሳዖልና የዮናታን ወሬ ከኢይዝራኤል በመጣ ጊዜ የአምስት ዓመት ልጅ ነበር። በዚህን ጊዜ ሞግዚቱ ይዛው
ለመሸሸ አነሣችው፣ ነገር ግን ይዛው በምትሮጥበት ጊዜ የዮናታን ልጅ ወደቀና ሽባ ሆነ። ስሙም ሜምፊቦስቴ ይባል ነበር። 5 በዚህ ጊዜ የብኤሮታዊው የሬሞን
ልጆች ሬካብና በዓና ሞቃት በነበረበት በቀትሩ ሰዓት እርሱ ዕረፍት እያደረገ ሳለ ወደ ኢያቡስቴ ቤት ሄዱ። 6 ትጠብቅ የነበረችው ሴት ስንዴ በምታበጥርበት
ጊዜ እንቅልፍ ወስዷት ነበርና ሬካብና በዓና በቀስታ አልፈዋት ገቡ። 7 ስለዚህ ወደ ቤት ከገቡ በኋላ በክፍሉ ተኝቶ ሳለ አጠቁት ገደሉትም። ከዚያ በኋላ ራሱን
ቆርጠው በመውሰድ ሌሊቱን ሁሉ በዓረባ መንገድ ተጓዙ። 8 የኢያቤስቴንም ራስ ወደ ኬብሮን ወደ ዳዊት ዘንድ አምጥተው፣ “አንተን ሊገድል ይፈልግ የነበረው
የጠላትህ የሳያል ልጅ የኢያቡስቴ ራስ ይኸውልህ፤ እነሆ እግዚአብሔር በዛሬው ቀን ስለ ጌታዬ ስለ ንጉሡ ሳያልንና ዘሩን ተበቅሎአል።” አሉት። 9 ዳዊትም
ለብኤሮታዊው ለሬሞን ልጆች ለሬካብና ለወንድሙ ለበዓና ምላሽ በመስጠት እንዲህ አላቸው፣ “ከመከራ ሁሉ ያዳነኝ ሕያው እግዚአብሔርን፣ 10 የምሥራች
ያመጣልኝ መስሎት ‘እነሆ ሳኦል ሞተ’ ብሎ የነገረኝን ሰው ይዤ ጺቅላግ ላይ ገደልሁት፤ እንግዲህ ወሬውን ላመጣው ለዚያ ሰው የሸለምሁት ይህንን ነበር። 11
ታዲያ በገዛ ዐልጋው ላይ ዐርፎ የተኛውን ንጹሕ ሰው ክፉ ሰዎች የገደሉት ከሆነ እንዴት ይልቅ ደሙን ከእጆችሁ አልፈልግ፣ ከዚህ ምድርስ አልደመስሳችሁ?”
12 ስለዚህም ዳዊት ጎልማሶቹን አዘዘ፤ እነርሱም ገደሏቸው፤ እጅና እግራቸውንም ቆርጠው በኬብሮን ካለው ኩሬ አጠገብ ሰቀሏቸው። ነገር ግን የኢያቡስቴን
ራስ ወስደው ኬብሮን በሚገኘው በአብኔር መቃብር ውስጥ ቀበሩት።

---

2 Samuel 4:1

ኢያቡስቴ... በዓና...ሬካብ...ሬሞን
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እጆቹ ደከሙ
በዚህ ሀረግ "እጆቹ" የሚለው የሚወከወለው ኢያቡስቴን ነው። "ኢያቡስቴ ደካማ ሆነ" ወይም "ኢያቡስቴ አቅሙን በሙሉ አጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚህን ጊዜ...የሳኦል ልጅ ሁለት ሰዎች ነበሩት
ይህ በዓና እና ሬካብ የተባሉ ሰዎችን ወደ ታሪኩ ያስተዋውቃል። (አዲስ እና ነባር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

ብኤሮት ጭምር የብንያም ክፍል ተደርጎ ስለተወሰደ፣ እና ብኤሮታውያን ወደ ጌቴም ስለሸሹ እስከ ዛሬ ድረስ በዚያ ይኖራሉ
እዚህ ስፍራ ላይ ጸሐፊው ስለ ብኤሮት ለአንባቢ የመረጃ ዳራ ይሰጣል። የብኤሮት ግዛት የብንያም ነገድ ምድር ክፍል ነበር። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

ብኤሮት ጌቴም
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 4:4

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ ሀረግ ዋናውን ታሪክ ቆም አድርጎ በኢያቡስቴ በኩል ሳይሆን በዮናታን በኩል የሳኦል ትውልድ ስለሆነው ስለ ሜምፊቦስቴ የመረጃ ዳራ ይሰጣል። ሜምፊቦስቴ ቆየት ብሎ በመጽሐፉ ውስጥ ትልቅ ገጸ ባህሪ ይሆናል። (የመረጃ ዳራ እና አዲስ እና ነባር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚሉትን ይመልከቱ)

እግሩ ሽባ የሆነ
ይህ ሀረግ "መራመድ የማይችል" ማለት ነው።

ዕድሜው አምስት አመት
ይህ አባቱ በሞተ ጊዜ የዮናታን ልጅ ዕድሜ ነበር። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ ሳኦል እና ዮናታን የተነገሩ ወሬዎች
ይህ የሚያመለክተው ስለ ሞታቸው የተነገረውን ወሬ ነው

ሞግዚት/ነርስ
ትንሽ ልጅን ለመንከባከብ የምትቀጠር ሴት ወይም ልጃገረድ

ሽባ ሆነ
ይህ ሜምፊቦስቴ እንዴት እንደተጎዳ እና መራመድ የማይችል እንደሆነ ይገልጻል።

ሜምፊቦስቴ
ይህ የሳኦል የልጅ ልጅ፣ የዮናታን ወጣት ወንድ ልጅ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 4:5

አጠቃላይ መረጃ
ታሪኩ በ2፡ሳሙኤል4፡2 ላይ ወደሚገኘው የበዓን እና ሬካብ ድርጊቶች ይመለሳል።

የቀኑ ሙቀት
የቀኑ እኩሌታ፣ ቀኑ ሞቃት በሚሆንበት ክፍለ ጊዜ

ስንዴ ማበጠር
"ገለባውን ከስንዴው መለየት"

2 Samuel 4:8

ህይወትህን ይፈልግ ነበር
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር "ሊገድልህ ይፈልግ ነበር" ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ህያው እግዚአብሔርን
ይህ ዳዊት ሊያደርግ ከሚችላቸው ጠንካራ መሃላዎች አንዱ ነው፣ያህዌ ምስክሬ ነው እንደሚለው። "በያህዌ እምላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ህይወቴን ያዳነው
እዚህ ስፍራ "ህይወት" የሚለው የሚያመለክተው ራሱን ዳዊትን ነው።ይህ ማለት ያህዌ ዳዊትን በህይወት ጠብቆታል ማለት ነው። "እኔን ያዳነኝ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

(ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 4:11

ምን ያህል ይበልጥ... አሁን የእርሱን ደም ከእናንተ እጅ ልፈልግና ከዚህ ምድር ላስወግዳችሁ አይገባኝምን?
ይህ ጥያቄ የዋለው ሰዎቹ በቸልታ የማይታለፍ ከባድ ወንጀል መፈጸማቸውን ለማሳየት ነው። በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እናንተ ይበልጥ ጥፋተኞች ናችሁ! ከእጃችሁ ደሙን መፈለግ እና እናንተን ከዚህ ምድር ማስወገድ የእኔ ሃላፊነት ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእጃችሁ ደሙን መፈለግ
"ደሙን" የሚለው ሀረግ የኢያቡስቴን ህይወት ይወክላል። እዚህ ስፍራ "ከእጃችሁ" የሚለው የሚወክለው በ 2 ሳሙኤል 4፡5 የገቡትን ከብኤሮት የሆነው የሬሞን ልጆች ሬካብን እና በዓናን ነው። "በኢያቡስቴ ሞት ተጠያቂ አደርጌ እይዛችኋለሁ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እጆቻቸውን እና እግሮቻቸውን ቆረጡ ደግሞም ሰቀሏቸው
ይህ ኢያቡስቴን ለማክበር የተደረገ ምልክታዊ ድርጊት ነበር። ይህ ተብራርቶ ሊገለጽ ይችላል። "ጭንቅላቱን በመቃብር በመቅበር ኢያቡስቴን አከበሩት" (ምልክታዊ ድርጊት እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 5

1 የእስራኤል ነገዶች በሙሉ ወደ ኬብሮን ወደ ዳዊት መጥተው እንዲህ አሉ፣ “እነሆ እኛ የዐጥንትህ ፍላጭ የሥጋህ ቁራጭ ነን፤ 2 ሳኦል በእኛ ላይ ነግሦ
በነበረበት ባለፈው ጊዜ የእስራኤልን ሠራዊት የምትመራ አንተ ነበርህ፤ እግዚአብሔርም፣ ‘ሕዝቤን እስራኤልን ትጠብቃለህ፣ በእስራኤልም ላይ ገዥ ትሆናለህ’
ብሎህ ነበር።” 3 ስለዚህም የእስራኤል ሽማግሌዎች በሙሉ ወደ ንጉሡ ወደ ኬብሮን መጡ፤ ንጉሥ ዳዊትም ኬብሮን ላይ በእግዚአብሔር ፊት ከእነርሱ ጋር
ቃል ኪዳን አደረገ፤ እነርሱም ዳዊትን ቀብተው በእስራኤል ላይ አነገሡት። 4 ዳዊት በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ነበረr፤ አርባ ዓመትም ገዛ። 5
በኬብሮን በይሁዳ ላይ ለሰባት ዓመት ከስድስት ወር፣ ኢየሩሳሌም ሆኖም በመላው እስራኤልና በይሁዳ ላይ ሠላሳ ሦስት ዓመት ነገሠ። 6 ንጉሡና ሰዎቹ
የምድሪቱ ነዋሪዎች በሆኑት በኢያቡሳውያን ላይ ለመዝመት ወደ ኢየሩሳሌም ሄዱ። እነርሱም ለዳዊት፣ “በዕውሮችና በአንካሶች ልትመለስ ካልሆነ በስተቀር አንተ
ወደዚህ አትገባም፤ ዳዊት እዚህ መምጣት አይችልም” አሉት። 7 ይሁን እንጂ ዳዊት የጽዮንን አምባ ያዘ፤ ይህችም አሁን የዳዊት ከተማ የሆነችው ነች። 8
በዚያን ጊዜ ዳዊት እንደዚህ አለ፣ “ኢያቡሳውያንን የሚያጠቃ በውሃ መተላለፊያው ሸቅብ መውጣት አለበት፤ በዚያም ዳዊትን የሚጠሉትን ዕውሮችንና
አንካሶችን ያገኛል።” እንግዲህ ሰዎች፣ “አንካሶችና ዕውሮች ወደ ቤተ መንግሥት መግባት አይችሉም” ያሉት ከዚህ የተነሣ ነው። 9 በመሆኑም ዳዊት
በአምባይቱ ኖረ፤ የዳዊት ከተማም ብሎ ጠራት። ከሸንተረሩ አንሥቶ ወደ ውስጥ ዙሪያዋን ምሽግ ገነባባት። 10 የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር
ስለነበረ፣ ዳዊት እጅግ እየበረታ ሄደ። 11 በዚህ ጊዜ የጢሮስ ንጉሥ ኪራም መልእክተኞችን፣ የዝግባ እንጨት፣ አናጢዎችንና ድንጋይ ጠራቢዎችን ወደ ዳዊት
ላከ፤ እነርሱም ለዳዊት ቤት ሠሩለት። 12 እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ንጉሥ አድርጎ እንዳጸናውና ስለ ሕዝቡም ስለ እስራኤል ሲል መንግሥቱን ከፍ
እንዳደረገለት ዳዊት አወቀ። 13 ኬብሮንን ትቶ ወደ ኢየሩሳሌም ከመጣ በኋላ ዳዊት በኢየሩሳሌም ተጨማሪ ቁባቶችን አስቀመጠ ሚስቶችንም አገባ፤ ተጨማሪ
ወንዶችና ሴቶች ልጆችም በኢየሩሳሌም ተወለዱለት። 14 በኢየሩሳሌም የተወለዱለትም ልጆች ስም፣ ሳሙስ፣ ሶባብ፣ ናታን፣ ሰሎሞን፣ 15 ኢያቤሐር፣
ኤሊሱዔ፣ ናፌቅ፣ ናፍያ፣ 16 ኤሊሳማ፣ ኤሊዳሄ፣ ኤሊፋላት ይባሉ ነበር። 17 ዳዊት በእስራኤል ላይ ንጉሥ ሆኖ መቀባቱን ፍልስጥኤማውያን በሰሙ ጊዜ፣
እርሱን ለመፈለግ በሙሉ ኃይላቸው ወጡ፤ ዳዊት ግን ይህን ሰምቶ ወደ ምሽጉ ወረደ። 18 በዚህ ጊዜ ፍልስጥኤማውያን መጥተው በራፋይም ሸለቆ
ተበታትነው ሰፈሩ። 19 ዳዊትም ከእግዚአብሔር ዘንድ እንዲህ ሲል ዕርዳታ ጠየቀ፣ “ፍልስጥኤማውያንን ወጥቼ ልውጋቸውን? በእነርሱስ ላይ ድል
ትሰጠኛለህ?” እግዚአብሔርም ለዳዊት፣ “በፍልስጥኤማውያን ላይ በእርግጥ ድል እሰጥሃለሁና ውጋቸው” አለው። 20 ስለዚህ ዳዊት በበአልፐራሲም ወጋቸው
በዚያም ድል አደረጋቸው። እርሱም፣ “የጎርፍ ውሃ ጥሶ በመውጣት እንደሚያፈራርስ እግዚአብሔርም ጠላቶቼን በፊቴ አፈራረሳቸው” በማለት ስሜቱን ገለጸ።
ከዚህ የተነሣም የዚያ ቦታ ስም በአልፐራሲም ተባለ። 21 ፍልስጥኤማውያን ጣዖቶቻቸውን እዚያ ትተው ስለነበር ዳዊትንና ሰዎቹን ወሰዷቸው። 22
ፍልስጥኤማውያን እንደ ገና መጥተው በራፋይም ሸለቆ በድጋሚ ተበታትነው ሰፈሩ። 23 ስለዚህ ዳዊት እንደገና ከእግዚአብሔር ዕርዳታ ጠየቀ፤
እግዚአብሔርም፣ “በፊት ለፊት በኩል አትውጋቸው፤ ይልቁኑ በስተኋላቸው በኩል በመክበብ በበለሳኑ ዛፎች ፊት ለፊት ግጠማቸው። 24 በበለሳኑ ዛፎች ጫፍ
ላይ የሰልፍ ጉዞ ድምፅ ስትሰማ የፍልስጥኤማውያንን ሠራዊት ለመምታት እግዚአብሔር ቀድሞ ወጥቶአልና በዚያን ጊዜ በኃይል አጥቃ” አለው። 25
ስለዚህም ዳዊት እግዚአብሔር እንዳዘዘው ፍልስጥኤማውያንን ከገባዖን እስከ ጌዘር ድረስ ገደላቸው።

---

2 Samuel 5:1

እኛ የአንተ ስጋ እና አጥንት ነን
ይህ ሀረግ "ዘመድ" ማለት ነው። "እኛ ከአንተ ጋር የተዛመድን ነን" ወይም "እኛ ከአንድ ቤተሰብ ነን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ብዙም ሩቅ በማይባል ዘመን
ይህ ታሪካዊ መረጃ ነው። ሳኦል ከዳዊት አስቀድሞ ንጉሣቸው ነበር። (ታሪካዊ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

ህዝቤን እስራኤልን ትጠብቃለህ፣ ደግሞም እነርሱን ትመራለህ
እነዚህ ሁለት ሀረጋት/አንቀጾች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ደግሞም ያህዌ ዳዊትን ለንጉሥነት እንደመረጠው አጉልተው ይገልጻሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ህዝቤን እስራኤልን ትጠብቃለህ፣
እዚህ ስፍራ በህዝብ ላይ መግዛት የሚለው የተገለጸው ለእነርሱ እረኛ መሆን በሚል ነው። "ለህዝብ ለእስራኤል ጥበቃ ታደርጋለህ" ወይም "ህዝቤን እስራኤልን ትመራለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 5:3

ዳዊትን በእስራኤል ላይ ንጉሥ አድርገው ቀቡት
"መቀባት" እግዚአብሔር ዳዊትን ንጉሥ አድርጎ እንደመረጠው እውቅና መስጠታቸውን የሚገልጽ ምልክታዊ ድርጊት ነው። (ምልክታዊ/ትዕምርታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 5:6

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት እና የእስራኤል ሰራዊት ኢያቡሳሌምን አጠቁ

በዕውራን እና ሽባዎች ልትባረሩ ካልፈለጋችሁ በስተቀር ወደዚህ አትመጡም
ይህ በአዎንታዊ ዐረፍተ ነገር መገለጽ ይችላል። "ወደዚህ ብትመጡ፣ እናንተን ዕውራን እና ሽባዎች እንኳን ሊመልሷችሁ ይችላሉ"

ዕውራን እና ሽባዎች
እዚህ ስፍራ "ዕውራን" እና "ሽባዎች" የሚሉት ስማዊ ቅጽሎች ናቸው። "ማየት የማይችሉ ሰዎች እና መራመድ የማይችሉ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 5:8

ዳዊት፣ "ኢያቡሳውያንን የሚመታ" አለ
ዳዊት የሚነጋገረው ከወታደሮቹ ጋር ነበር። "ዳዊት ለወታደሮቹ እንዲህ አለ፣ ‘የኢያቡስን ሰዎች ማስወጣት የሚፈልግ"

‘ዕውራን እና ሽባዎች'
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1)ይህ የሚያመለክተው በእርግጥ ሽባ እና ዐይነ ስውር የሆኑትን ወይም 2)በኢየሩሳሌም ከተማ የሚኖሩ ኢያቡሳውያን ሁሉም ደካማ እና ስንኩላን የሆኑ ያህል የሚቆጥር ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ዘይቤ ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Samuel 5:11

ኪራም
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አናጢዎች
በእንጨት የሚሰሩ

ግንበኞች
በድንጋይ ወይም በጡብ የሚሰሩ

2 Samuel 5:13

ሳሙስ...ሶባብ...ናታን...ሰሎሞን...ኢያቤሐር...ኤሊሱዓ...ናፌቅ...ያፍያ...ኤሊሳማ...ኤሊዳሄ...ኤሊፋላት
እነዚህ የዳዊት ወንዶች ልጆች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእርሱ ብዙ ወንዶች እና ሴቶች ልጆች ተወለዱለት
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ብዙ ወንዶች እና ሴቶች ልጆች ነበሩት" ወይም "ብዙ ወንዶች እና ሴቶች ልጆችን ወለዱለት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእርሱ የተወለዱለት
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሚስቶቹ ለእርሱ የወለዱለት" ወይም "እርሱ ነበረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 5:17

ዳዊት በእስራኤል ላይ ንጉሥ ሆኖ ተቀብቶ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እስራኤል ዳዊትን ንጉሥ አድርጎ ቀብቶት ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉም ሊፈልጉት ወጡ
እዚህ ስፍራ "ሁሉም" የሚለው የፍልስጥኤም ሰራዊትን በአጠቃላይ ለማለት ነው። "የፍልስጥኤም ሰራዊት እርሱን ለመፈለግ ወጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

ራፋይም ሸለቆ
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 5:19

በኣልፐራሲም
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሞልቶ እንደሚፈነዳ የጎርፍ ውሃ ያህዌ ጠላቶቼን በፊቴ አፈራረሳቸው
በዚህ ስፍራ ዳዊት ያህዌ የሰጠውን ድል የሚገልጸው፣ የጎርፍ ውሃ በዙሪያው የሚገኘውን ስፍራ እንደሚያጥለቀልቅ እና ምድሩን እንደሚሸፍን ደግሞም ጥፋት እንደሚያደርስ አይነት አድርጎ ነው። "ጎርፍ ምድርን እንደሚያጥለቀልቅ ያህዌ ጠላቶቼን አፈራረሳቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 5:22

ፍልስጥኤማውያን ዳግም ተመለሱ
እነርሱ "ተመለሱ" የተባለበት ምክንያት ፍልስጥኤማውያን የሚኖሩት ከዳዊት ጠንካራ ይዞታ ዝቅ ባለ ስፍራ ስለሆነ ነው።

የራፋይም ሸለቆ
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የበለሳም እንጨቶች/ደን
"በለሳም" አዛፍ አይነት ነው፣ "እንጨቶች" የሚለው በአንድነት የበቀሉ የበለሳም ዛፎችን ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 5:24

ስትሰሙ... የፍልስጥኤም ሰራዊትን ለመጥቃት ያህዌ በፊታችሁ ይሄዳል
ይህ በ 2ሳሙኤል 5:23 ላይ ያህዌ ለዳዊት መስጠት የጀመረው ትዕዛዝ ቀጣይ ክፈል ነው። በዚህ ስፍራ ያህዌ ስለ ራሱ በሶስተኛ መደብ ይናገራል። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚሉትን ይመልከቱ)

በበለሳም እንጨቶች አናት ላይ በሚነፍሰው ንፋስ የሰልፍ ድምጽ ስትሰሙ
ይህ የሚናገረው ነፋስ በቅጠሎች መሃል ሲያልፍ እንደሚያሰማው አይነት የሰልፈኛ ድምጽ ስለ መስማት ነው። "ነፋስ በበለሳም ዛፎች አናት ላይ ሰልፈኞች እንደሚያሰሙት ድምጽ ሲነፍስ" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይምልከቱ)

ገባዖን... ጌዝር
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 6

1 ዳዊት እንደ ገና ከእስራኤል የተመረጡትን ሠላሳ ሺህ ሰዎች ሰበሰበ። **2** ዳዊትና አብረውት ያሉት ሰዎች ሁሉ በኪሩቤል ላይ በዙፋኑ በተቀመጠው በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ስም የተጠራውን የእግዚአብሔርን ታቦት ለማምጣት በይሁዳ ወዳለው ወደ በአል ሄዱ። **3** የእግዚአብሔርን ታቦት በአዲስ ሠረገላ ላይ አኑረው በኮረብታ ላይ ካለው ከአሚናዳብ ቤት አውጥተው አመጡ። ልጆቹ ዖዛና አሒዩ አዲሱን ሠረገላ ይመሩ ነበር። **4** የእግዚአብሔርን ታቦት በላዩ ላይ አኑረው ሠረገላውን በኮረብታ ላይ ካለው ከአሚናዳብ ቤት አውጥተው አመጡ፤ አሒዩ ከታቦቱ ፊት ለፊት ይሄድ ነበር። **5** ዳዊትና የእስራኤል ቤት በሙሉ በጥድ እንጨት በተሠሩ የሙዚቃ መሣሪያዎች ማለትም በበገና፣ በመሰንቆ፣ በከበሮ፣ በጸናጽልና በቃጭል መጫወትና ደስታቸውን መግለጽ ጀመሩ። **6** ወደ ናኮን ዐውድማ ሲደርሱም በሬዎቹ ስለተደናቀፉ፤ ዖዛ የእግዚአብሔርን ታቦት ለመያዝ እጁን ዘረጋ በእጁም ያዘው። **7** ከዚያ በኋላ የእግዚአብሔር ቁጣ በዖዛ ላይ ነደደ፤ በዚያም ስፈራ እግዚአብሔር ስለ ኃጢአቱ መታው። ዖዛም በዚያ በእግዚአብሔር ታቦት አጠገብ ሞተ። **8** እግዚአብሔር ዖዛን ስለመታው ዳዊት ተቆጣ፤ የዚያን ቦታም ስም ፔሬዝ ዖዛ ብሎ ጠራው። ያም ቦታ እስከ ዛሬ ድረስ ፔሬዝ ዖዛ ተብሎ ይጠራል። **9** ዳዊት በዚያን ቀን እግዚአብሔርን ስለ ፈራ፣ “የእግዚአብሔር ታቦት ወደ እኔ እንዴት ሊመጣ ይችላል?” ብሎ ጠየቀ። **10** ስለዚህ ዳዊት የእግዚአብሔርን ታቦት ከእርሱ ጋር ወደ ዳዊት ከተማ ይዞት ለመሄድ አልፈቀደም፤ በዚህ ፋንታ አቅጣጫ ለውጦ የጌት ሰው ወደ ሆነው ወደ አቢዳራ ቤት ወሰደው። **11** የእግዚአብሔርም ታቦት የጌት ሰው በሆነው በአቢዳራ ቤት ሦስት ወር ተቀመጠ፤ እርሱንና ቤተሰቡንም ሁሉ እግዚአብሔር ባረካቸው። **12** በዚህ ጊዜ፣ “በእግዚአብሔር ታቦት ምክንያት የአቢዳራን ቤተሰብና ያለውን ሁሉ እግዚአብሔር ባረከለት” ብለው ለዳዊት ነገሩት። ስለዚህ ዳዊት ወደዚያ ሄዶ የእግዚአብሔርን ታቦት ከኦቤድ ኤዶም ቤት ወደ ዳዊት ከተማ በደስታ አመጣው። **13** የእግዚአብሔርን ታቦት ተሸክመው የነበሩት ሰዎች ስድስት እርምጃ በሄዱ ቁጥር አንድ በሬና አንድ የሰባ ጥጃ ይሠዋ ነበር። **14** ዳዊትም የበፍታ ኤፉድ ብቻ በወገቡ ታጥቆ በሙሉ ኃይሉ በእግዚአብሔር ፊት ይጨፍር ነበር። **15** ስለዚህ ዳዊትና መላው የእስራኤል ቤት እልል እያሉና ቀንደ መለከት እየነፉ የእግዚአብሔርን ታቦት ይዘውት መጡ። **16** የእግዚአብሔር ታቦት ወደ ዳዊት ከተማ እየገባ ሳለ የሳዖል ልጅ ሜልኮል በመስኮት ሆና ተመለከተች፤ ንጉሥ ዳዊትም በእግዚአብሔር ፊት ሲዘልና ሲጨፍር አየችው፤ ከዚያ በኋላም በልቧ ናቀችው። **17** ከዚያም የእግዚአብሔርን ታቦት አምጥተው ዳዊት በተከለለት ድንኳን በተዘጋጀለት በማዕከላዊ ስፍራ አኖሩት። ከዚያ በኋላም ዳዊት የሚቃጠል መሥዋዕትና የኅብረት መሥዋዕት በእግዚአብሔር ፊት አቀረበ። **18** ዳዊት የሚቃጠል መሥዋዕትና የኅብረት መሥዋዕት ማቅረብ በፈጸመ ጊዜ ሕዝቡን በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ስም ባረከ። **19** ከዚያ በኋላ ለመላው እስራኤል፣ ለሕዝቡ ሁሉ ለወንዱም ለሴቱም ለእያንዳንዱ ሰው አንዳንድ እንጀራ፣ አንዳንድ ሙዳ ሥጋና አንዳንድ የዘቢብ ጥፍጥፍ አከፋፈለ። ከዚያ በኋላ ሕዝቡ ሁሉ እያንዳንዱ ወደየቤቱ ሄደ። **20** ከዚያ በኋላ ቤተሰቡን ለመባረክ ተመለሰ። የሳዖል ልጅ ሜልኮልም ዳዊትን ልትቀበለው መጣችና እንደዚህ አለች፣ “ራሳቸውን ከሚያራቁቱ ባለጌዎች እንደ አንዱ ዛሬ የእስራኤል ንጉሥ በአገልጋዮቹ መካከል በነበሩት ገረዶች ፊት ራሱን በማራቆቱ ምን ያህል የተከበረ ነበር!” **21** ዳዊትም ለሜልኮል እንዲህ ሲል መለሰላት፣ “እኔን ከአባትሽና ከቤተሰቡ ሁሉ በላይ በመረጠኝና በእግዚአብሔር ሕዝብ በእስራኤል ላይ መሪ አድርጎ በሾመኝ በእግዚአብሔር ፊት ያንን አድርጌአለሁ። በእግዚአብሔር ፊት ሐሴት አደርጋለሁ! **22** እንዲያውም ከዚህም የበለጠ ራሴን ዝቅ አደርጋለሁ፣ ከዚህም የባሰ የተናቅሁ እሆናለሁ፤ ነገር ግን በጠቀስሻቸው ገረዶች ፊት እከብራለሁ።” **23** ስለዚህም የሳኦል ልጅ ሜልኮል እስከምትሞተችበት ጊዜ ድረስ ልጅ አልወለደችም ነበር።

---

2 Samuel 6:1

አሁን
ይህ ቃል የታሪኩን አዲስ ክፍል ያመለክታል

የተመረጡ የእስራኤል ወንዶች በሙሉ
ይህ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/የእስራኤልን ሰራዊት ይወክላል። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሰላሳ ሺህ
"30,000" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ከይሁዳ በአል የእግዚአብሔርን ታቦት ለማምጣት
ታቦቱን ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚወስዱ ተጠቁሟል። "ይሁዳ ውስጥ ከምትገኘው በኣላ የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ ኢየሩሳሌም ለመውሰድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያ የእግዚአብሔርን ታቦት ለማምጣት
ኢየሩሳሌም ከሞላ ጎደል ከሁሉም ሌሎች የእስራኤል ስፍራዎች ከፍ ያለች ናት፣ ስለዚህ ለእስራኤላውያን ወደ ኢየሩሳሌም እንውጣ ወይም ከእርሷ እንውረድ ማለት የተለመደ ነበር።

ወደ ላይ ማምጣት
"ማምጣት" የሚለው ቃል "መውሰድ" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። (መሄድ እና መምጣት የሚሉትን ይመልከቱ)

በአል
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰራዊት ጌታ በያህዌ ስም የተጠራ
የያህዌ ስም በታቦቱ ላይ ተጽፎ ነበር

ከኪሩቤል በላይ በዙፋኑ የተቀመጠው
ኪሩብ በቃል ኪዳኑ ታቦት መክደኛ ላይ የሚገኙ መሆናቸውን ግልጽ ማድረግ ሊያስፈልግ ይችላል። የመጸሐፍ ቅዱስ ጸሐፍት ብዙውን ጊዜ የቃል ኪዳኑ ታቦት፣ በላይ በሰማይ በዙፋኑ የተቀመጠው የያህዌ እግሮች ማረፊያ እንደሆነ አድርገው ይናገራሉ። "በቃል ኪዳኑ ታቦት ከኪሩብ በላይ በዙፋኑ የተቀመጠው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው/የነገሰው
በዙፋን ላይ መቀመጥ

2 Samuel 6:3

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት እና የእስራኤል ህዝብ ሰራዊት የቃል ኪዳኑን ታቦት አመጡ/አንቀሳቀሱ

አሚናዳብ...ዖዛ...አሒዮ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መላው የእስራኤል ቤት
ይህ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሚወክለው የእስራኤልን ህዝብ ነው። "ከእርሱ ጋር የነበሩ ሌሎች እስራኤላውያን ሁሉ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ታምቡሪኒ/ከበሮ መሰል የሙዚቃ መሳሪያ
ታምቡሪኒ ከአናቱ ከበሮ የሚመስል በዙሪያው ቁርጥራጭ ብረታ ብረት ያሉት ሲመታ ወይም ሲያርገፈግፉት ሙዚቃዊ ድምጽ የሚሰጥ መሳሪያ ነው። (ያልታወቁትን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

ራትል/ የቅል ቅርጽ ያለው የሚንሸዋሸዋ /ጽናጽል መሰል የሙዚቃ መሳሪያ
በሸፋን ውስጥ የሚገኝና ጠጣር የሆኑ ነገሮች በውስጡ የያዘ ሲርገፈገፍ ዜማዊ ድምጽ የሚሰጥ የሙዚቃ መሳሪያ። (ያልታወቁትን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

ሲምባል/ ሙዚቃ ማጀቢያ ሳህን መሰል የሙዚቃ መሳሪያ
ሁለት ስስ፣ ክብ የብረት ሳህን መሰል የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን ሲጋጭ ከፍ ያለ ሙዚቃዊ ድምጽ ይሰጣል

2 Samuel 6:6

ናኮን
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌ ቁጣ ነደደ
እዚህ ስፍራ "የያህዌ ቁጣ" የተገለጸው እሳት እንደሆነ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኃጢአት ሆነበት
ያህዌ ማንም ታቦቱን እንዳይነካ አዝዞ ስለነበር ዖዛ ታቦቱን መንካቱ ኃጢአት ሆኖበት ነበር። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 6:8

የዖዛ ስብራት
ይህ የቦታ ስም ነው። ተርጓሚ " ‘የዖዛ ስብራት' የሚለው ስም ‘የዖዛ ቅጣት' ማለት ነው" የሚል የግርጌ ማስታወሻ ሊጨምርበት ይችላል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እስከ ዛሬ ድረስ
ይህ ማለት ይህ እስከተጻፈበት ጊዜ ድረስ ማለት እንጂ እሰከ አሁን እስከ ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ማለት አይደለም።

የያህዌ ታቦት እንዴት ወደ እኔ ሊመጣ ይችላል?
ዳዊት ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት ታቦቱን ወደ ኢየሩሳሌም ለማምጣት መፍራቱን ለማጉላት ነው። "የያህዌን ታቦት ከእኔ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ይዜ ለመምጣት እጅግ ፈርቻለሁ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 6:10

የጌቱ ኦቤድ ኤዶም/አቢዳራ
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱን ባረከው
እዚህ ስፍራ "እርሱ" የሚለው የሚያመለክተው የጌቱን አቢዳራን ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 6:12

አሁን/በዚህ ጊዜ
ይህ ቃል የታሪኩን አዲስ ክፍል ይጀምራል

ለንጉሥ ዳዊት ተነገረው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች ለንጉሥ ዳዊት ነገሩት" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አቢዳራ ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው የሚወክለው ቤተሰብን ነው። "አቢዳራ እና ቤተሰቡ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔርን ታቦት አመጣ
ኢየሩሳሌም በእስራኤል ከሚገኙ ከሞላጎደል ከሌሎቹ ሁሉም ስፍራዎች ይልቅ ከፍ ያለች ነበረች፣ ስለዚህም ለእስራኤላውያን ወደ ኢየሩሳሌም መውጣት እና ከእርሷ መውረድ ብሎ መናገር የተለመደ ነገር ነበር። "የእግዚአብሔርን ታቦት አመጣ" ወይም "የእግዚአብሔርን ታቦት ወሰደ"

አመጣ
"አመጣ" የሚለው ቃል "ወሰደ" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። (መሄድ እና መምጣት የሚሉትን ይመልከቱ)

2 Samuel 6:14

ዳዊት በያህዌ ፊት በሙሉ አቅሙ ይጨፍር ነበር
እዚህ ስፍራ መጨፈር በደስታ ያህዌን የማምለክ ሁኔታ ነበር

በፍታ/ሊኖ
ከቃጫ ተክል ከሚገኝ ላይነን የተሰራ ልብስ

የእስራኤል ቤት በሙሉ
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው የሚወከወለው የእስራኤልን ሰዎች ነው። "ከእርሱ ጋር የነበሩ ሌሎች እስራኤላውያን ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 6:16

አሁን... በእርሷ ልብ
"አሁን" የሚለው ቃል በታሪኩ ፍሰት ምልክት ያደርጋል። እዚህ ስፍራ ተራኪው ስለ ሜልኮል መረጃ ይሰጣል

ሜልኮል
ሜልኮል የንጉሥ ሳኦል ልጅ እና የዳዊት የመጀመሪያ ሚስቱ ነበረች። በ2ሳሙኤል 3:13 ይህ ስም እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።

በልቧ ናቀችው
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚለው የሚወክለው አስተሳሰብን ወይም ስሜትን ነው። "በማንቋሸሽ አየችው" ወይም "አፌዘችበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በያህዌ ፊት
"ለ ያህዌ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Samuel 6:18

በሰራዊት ጌታ በያህዌ ስም ህዝቡን ባረከ
በ "ሰራዊት ጌታ በያህዌ ስም" መባረክ ማለት በያህዌ ሃይል እና ስልጣን ወይም የእርሱ ተወካይ ሆኖ መባረክ ማለት ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የዘቢብ ቂጣ/ኬክ
ጣፋጭ ከደረቅ ወይን የተሰራ ዳቦ

2 Samuel 6:20

ወደ ውጭ መውጣት
እዚህ ስፍራ "መምጣት" የሚለው "መሄድ" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። (መሄድ እና መምጣት የሚሉትን ይመልከቱ)

ዛሬ የእስራኤል ነጉሥ እንዴት ከበረ
ይህ ምፀታዊ አነጋገር ነው። ሚልኮል ተቃራኒውን ማለቷ ነበር፣ ዳዊት ያደረገው የሚያስከብረውን ነገር ነው ብላ አላመነችም። ሜልኮል ንጉሥ ዳዊት ሲጨፍር የታየበትን አለባበስ እና ባህሪይ የተናገረችው በማቃለል ነበር። (ምፀት ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በባሪያ ልጃገረዶች ዐይኖች ፊት
እዚህ ስፍራ "የባሪያ ልጃገረዶች ዐይኖች" የሚወክለው ባሪያ ልጃገረዶችን ነው። "በባሪያ ልጃገረዶች ፊት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ባለጌ ተራሰው
ሜልኮል ዳዊትን ያነጻጸረችው ከባለጌ እና ሞኝ ሰዎች ጋር ነው

2 Samuel 6:21

ከአንቺ አባት በላይ እንድሆን የመረጠኝ ማን ነው
እዚህ ስፍራ "የአንቺ" የሚለው የሚያመለክተው ሜልኮልን ነው። (አንተ የሚለውን ቃል መልኮች ይመልከቱ)

በያህዌ ህዝብ ላይ፣ በእስራኤል ላይ
እዚህ ስፍራ "የያህዌ ህዝብ" እና "እስራኤል" የሚሉት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚህም ይልቅ ክብሬን እጥላለሁ
ዳዊት ምጸታዊ እየሆነ ነው፤ በቃላት ከተናገረው ተቃራኒውን እየገለጸ ነው። በእርግጥ ያደረገው ነገር የሚያወርድ ነገር ነው ብሎ አይምንም ወይም ወደፊትም ወራዳ ተግባር አደርጋለሁ እያለ አይደለም። (ምፀት ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በራሴ ዐይኖች ፊት ራሴን አዋርዳለሁ
እዚህ ስፍራ "በራሴ ዐይኖች ፊት" የሚለው የሚወክለው አንድ ሰው ስለ አንድ ነገር ስፍራ የሚሰጠውን ወይም የሚያስበውን ነው። "ራሴን ዝቅ አደርጋለሁ" ወይም "ራሴን ሞኝ እንደሆነ ሰው እቆጥራለሁ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን አንቺ ባልሻቸው በእነዚህ ባሪያ ልጃገረዶች ዘንድ እከበራለሁ
ይህ አድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንቺ ያልሻቸው ባሪያ ልጃገረዶች ያከብሩኛል" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እሰከ ዕለተ ሞቷ ድረስ ልጅ አልነበራትም
"አንድም ልጅ ለመውለድ አልቻለችም ነበር"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 7

1 ንጉሡ በቤቱ ተደላድሎ ከተቀመጠና እግዚአብሔርም በዙሪያው ካሉት ጠላቶቹ ሁሉ ካሳረፈው በኋላ፣ 2 ለነቢዩ ለናታን ንጉሡ እንደዚህ አለው፣ “እነሆ፤ እኔ
ከዝግባ በተሠራ ቤተ መንግሥት ውስጥ እኖራለሁ፤ የእግዚአብሔር ታቦት ግን በድንኳን ውስጥ ይኖራል” አለው። 3 ከዚያ በኋላ ናታን ለንጉሡ፣ “እግዚአብሔር
ካንተ ጋር ስለሆነ ያሰብኸውን ሁሉ አድርግ” አለው። 4 ነገር ግን በዚያች ሌሊት እንደዚህ የሚል የእግዚአብሔር ቃል ወደ ናታን መጣ፣ 5 “ሂድና ለባሪያዬ
ለዳዊት እንደዚህ በለው፣ ‘እግዚአብሔር የሚልህ እንደዚህ ነው፣ የምኖርበትን ቤት አንተ ትሠራልኛለህን? 6 የእስራኤልን ሕዝብ ከግብፅ ካወጣሁበት ጊዜ
አንሥቶ እስከ ዛሬ ድረስ በድንኳን ማደሪያ ውስጥ ሆኜ እንቀሳቀስ ነበር እንጂ በቤት ውስጥ ኖሬ አላውቅምና፤ 7 በመላው የእስራኤል ሕዝብ መካከል
በተመላለስሁባቸው በሁሉም ስፈራዎች ሕዝቤን እስራኤልን እንዲጠብቁ ከሾምኋቸው መሪዎች ለአንዱ ስንኳ፣ ‘ከዝግባ እንጨት ለምን ቤት አልሠራህልኝም?’
ብያለሁን? 8 እንግዲህ አሁን ለባሪያዬ ለዳዊት እንደዚህ በለው፣ ‘የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የሚለው ይህንን ነው፣ በሕዝቤ በእስራኤል ላይ ገዥ ትሆን ዘንድ
ከመስክ በጎችን ትከተል ከነበርህበት ስፍራ ወሰድሁህ፤ 9 በሄድህበት ሁሉ እኔ ከአንተ ጋር ነበርሁ፤ ጠላቶችህንም ሁሉ ከፊትህ አጠፋሁልህ’፤ በምድር ላይ
ስማቸው ታላቅ እንደሆነው እንደ አንዱ ለአንተ ታላቅ ስም አደርግልሃለሁ። 10 ከእንግዲህ ወዲያ በራሳቸው መኖሪያ እንዲኖሩ እንጂ እንዳይናወጡ ለሕዝቤ
ለእስራኤል ቦታ እሰጣቸዋለሁ፣ በዚያም እተክላቸዋለሁ። ከዚህ በፊት እንደሆነውም ከእንግዲህ ወዲህ ክፉ ሕዝብ አይጨቁናቸውም፤ 11 መሳፍንትን በሕዝቤ
በእስራኤል ላይ ባዘዝሁበት ጊዜ እንዳደረጉባቸው ከእንግዲህ ወዲህ አያደርጉባቸውም፤ ከጠላቶችህም ሁሉ አሳርፍሃለሁ። ከዚህም ባሻገር፣ እኔ እግዚአብሔር
ቤት እንደምሠራልህ እነግርሃለሁ። 12 ዕድሜህ በሚጠናቀቅበት ጊዜና ከአባቶችህ ጋር በምታርፍበት ጊዜ ከአብራክህ የሚወጣ ዝርያ አስነሳልሃለሁ፣
መንግሥቱንም አጸናለሁ። 13 እርሱ ለእኔ ቤት ይሠራልኛል፤ እኔም የመንግሥቱን ዙፋን ለዘላለም አጸናለሁ። 14 እኔ አባት እሆነዋለሁ፣ እርሱም ልጄ ይሆናል።
ኃጢአት በሚያደርግበት ጊዜ በሰዎች በትር እቀጣዋለሁ፣ የሰው ልጆች በሚገረፉበትም ግርፋት እገርፈዋለሁ፤ 15 ከፊትህ ካስወገድሁት ከሳኦል ላይ
እንደወሰድሁ ኪዳናዊ ታማኝነቴ ከእርሱ አይርቅም። 16 ቤትህና መንግሥትህ በፊትህ ለዘላለም የጸና ይሆናል፤ ዙፋንህም ለዘላለም የጸና ይሆናል።” 17 ናታን
ለዳዊት እንደዚህ ተናገረ፣ ይህንንም ሁሉ ነገር ነገረው፤ ጠቅላላውንም ራእይ ገለጸለት። 18 ከዚያም ንጉሥ ዳዊት ገባና በእግዚአብሔር ፊት ተቀመጠና እንደዚህ
አለ፣ “እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፣ እኔ ማን ነኝ? እስከዚህ ደረጃስ ታደርሰኝ ዘንድ ቤተሰቤስ ምንድን ነው? 19 ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፣ ይህ በፊትህ ታናሽ
ነገር ነው። ስለ ባሪያህ ቤተሰብ እንኳን ለረጅም ጊዜ የሚሆነውን ተናገርህ፣ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ ከዚህ በኋላ የሚኖረውንም ትውልዴን አሳየኸኝ! 20 እኔ
ዳዊት ከዚህ በላይ ለአንተ ምን እላለሁ? ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ ባሪያህን አክብረኸዋል። 21 ስለ ቃልህ ብለህ፣ ዓላማህንም ትፈጽም ዘንድ ይህን ታላቅ
ነገር አድርገሃል፤ ለባሪያህም ገልጸህለታል። 22 ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ ታላቅ ነህና እንደ አንተ ያለም የለም፤ በገዛ ጆሮቻችንም እንደ ሰማን ከአንተም
በቀር አምላክ የለም። 23 አንተ እግዚአብሔር መጥተህ ለራስህ እንዳዳንከው በምድር ላይ እንዳለው እንደ ሕዝብህ ያለ በምድር ላይ ምን ሕዝብ አለ? ይህንን
ያደረግኸው ለራስህ ሕዝብን ታስነሳ ዘንድ፣ ለራስህም ስምህን ታስጠራ ዘንድና ታላቅና አስፈሪ ነገር በምድርህ ታደርግ ዘንድ ነው። ከግብፅ ከዋጀኸው
ከሕዝብህ ፊት አሕዛብንና ጣዖቶቻቸውን አባረርህ። 24 እስራኤልን ሕዝብህ አድርገህ ለዘላለም አጸናህ፣ አንተም፣ እግዚአብሔር ሆይ አምላክ ሆንህላቸው። 25
አሁንም ባሪያህንና ቤተሰቡን በሚመለከት የሰጠኸውን ተስፋ ለዘላለም አጽናለት፤ እንደተናገርኸውም አድርግለት። 26 የእኔ፣ የባሪያህ የዳዊት ቤት በፊትህ
በሚጸናበት ጊዜ ሕዝቦች፣ ‘የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የእስራኤል አምላክ ነው’ ይሉ ዘንድ ስምህ ለዘላለም ታላቅ ይሁን። 27 አንተ የሠራዊት ጌታ
እግዚአብሔር፣ የእስራኤል አምላክ ለባሪያህ ቤት እንደምትሠራለት ገልጸህለታልና፤ ለዚህ ነው እኔ ባሪያህ ወደ አንተ ለመጸለይ ድፍረት ያገኘሁት። 28 አሁን፣ ጌታ
እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ አምላክ ነህ፣ ቃሎችህም የታመኑ ናቸው፤ ይህንን መልካም የተስፋ ቃል ለባሪያህ ገብተህለታል። 29 በፊትህ ለዘላለም የሚቀጥል
ይሆን ዘንድ፣ እንግዲህ አሁን የባሪያህን ቤት መባረክ አንተን ደስ ያሰኝህ። አንተ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፣ እነዚህን ነገሮች ተናግረሃልና በበረከትህ የባሪያህ ቤት
ለዘላለም የተባረከ ይሆናል።”

---

2 Samuel 7:1

እንዲህ ሆነ
እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ የዋለው የታሪኩን አዲስ ጅማሬ ለማመልከት ነው። የእናንተ ቋንቋ ይህን ለማድረግ መንገድ ካለው፣ እዚህ ስፍራ ያንን ማድረግ ትችላላችሁ። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

በዙሪያው ከነበሩ ጠላቶቹ ሁሉ አሳረፈው
"ከከበቡት ጠላቶቹ ሁሉ አሳረፈው" እዚህ ስፍራ "እረፍት" የሚለው ረቂቅ ስም ነው። "የጠላት ወገን እስራኤልን ማትቃቱን እንዲያቆም አደረገ!" (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ከዝግባ በተሰራ ቤት ውስጥ እኖራለሁ
ዝግባ በጥንካሬው የሚታወቅ የዛፍ አይነት ነው። በባህላችሁ እኩል የሆነ አይነት ዛፍ ካለ፣ ያንን ስም መጠቀም ትችላላችሁ፣ ካልሆነ ይህንን ለውጣችሁ መጠቀም ትችላላችሁ። "እኔ በጠንካራ፣ ቋሚነት ያለው ቤት ውስጥ እኖራለሁ" (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ታቦት በድንኳን ውስጥ ይኖራል
ድንኳኖች ጊዜያዊ መኖሪያ ናቸው። በባህላችሁ ድንኳን ከሌለ፣ ይህንን የተለየ ቃል ልተሰጡት ትችላላችሁ። "የእግዚአብሔር ታቦት በጊዜያዊ ስፍራ ይኖራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 7:3

በልብህ ያለውን አድርግ
እዚህ ስፍራ "ልብ"የሚለው የሚወክለው አዕምሮን ነው። "ማድረግ ያለብህን አድርግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ ከአንተ ጋር ስለሆነ
እዚህ ስፍራ "ከአንተ ጋር" የሚለው እግዚአብሔር ዳዊትን እየረዳው እና እየባረከው ነው ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌ ቃል ወደ ናታን እንዲህ ሲል መጣ፣ "ሂድ"
"የያህዌ ቃል ወደ.. መጣ" የሚለው ፈሊጥ የዋለው ከእግዚአብሔር ዘንድ ልዩ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። "ያህዌ ለናታን መልዕክት ሰጠው። እንዲህም አለው፣ ‘ሂድ' ወይም "ያህዌ ለናታን ይህንን መልዕክት ተናገረው፡ ‘ሂድ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

"ሂድ እና ባሪየዬን ዳዊትን እንዲህ በለው፣ ‘ያህዌ እንዲህ ይላል፡ የምናርበትን ቤት አንተ ተሰራልኛለህን? በለው
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ ይዟል። ቀጥተኛ ባልሆነ ጥቅስ መተገረጎሙ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። "እንዲህ በለው፣ ‘ሂድና ዳዊትን እኔ የምናርበትን ቤት

እሰራለሁ ብሎ ያስብ እንደሆነ ጠይቀው።" (በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ እና ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅሶች የሚሉትን ይመልከቱ)

የምኖርበትን ቤት አንተ ትሰራልኛለህን?
ያህዌ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት ዳዊት የያህዌን ቤት የሚገነባው እርሱ አለመሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ምልክ ሊተረጎም ይችላል። "አንተ ለእኔ ቤት አትሰራልኝም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የመለውን ይመልከቱ)

ቤት ስራልኝ
እዚህ ስፍራ "ቤት" ማለት ቤተመቅደስ ማለት ነው። በ2 ሳሙኤል 7:11 ላይ ያህዌ እንዲህ እርሱ ለዳዊት ቤት እገነባለታለሁ ይላል። በዚያ ስፍራ "ቤት" የሚለው ቤተሰብን ነው። የእናንተ ቋንቋ ሁለትንም ቃላት መግለጽ የሚችል ቃል ካለው በዚህ ስፍራ እና በ2 ሳሙኤል 7:11 ላይ ተጠቀሙበት።

2 Samuel 7:6

ለየትኛው ህዝቤን እንዲመራልኝ ለቀባሁት የእስራኤል መሪ ‘ለምን ቤት አልሰራችሁልኝም?' በማለት ተናግሬያለሁን?"
ይህ በጥያቄ ውስጥ ጥያቄ ይዟል። ቀጥተኛው ጥቅስ ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅስ ተደርጎ መጻፍ ይችላል። "እስራኤልን እንዲመራ ከቀባሁት መሪ ውስጥ የትኛውን መሪ ለምን የዝግባ ቤት አልሰራህልኝም ስል የጠየቅኩት አለን?" (በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ እና ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅሶች የሚሉትን ይመልከቱ)

ለየትኛው የእስራኤል መሪ ምን ነገር ተናግሬ አውቃለሁ
ያህዌ በፍጹም የትኛውንም የእስራኤል መሪ ቤት እንዲሰራለት እንዳልጠየቀ ትኩረት ለመስጠት ይህንን ጥያቄ ተጠቅሟል። "ለየትኛውም የእስራኤል መሪ በፍጹም ምንም ነገር አላልኩም" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ህዝቤን እስራኤልን እንዲጠብቅ ለቀባሁት
የእስራኤል ህዝብ መሪዎች የተገለጹት እረኞች እንደሆኑ እና ህዝቡ ደግሞ የተገለጸው በግ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለምን የጥድ ቤት አልሰራችሁልኝም?
ያህዌ መሪዎቹን ይህንን ጥያቄ ጠይቋቸው ቢሆን ኖሮ፣ የጥድ ቤት ስላልሰሩለት የሚገስጽ ጥያቄ ይጠቀም ነበር። ነገር ግን፣ ያህዌ አስቀድሞ ይህንን ጥያቄ እንዳልጠየቃቸው ተናግሯል። "የጥድ ቤት ልትሰሩልኝ ይገባል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 7:8

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ቃል ኪዳኑን ለንጉሥ ዳዊት በነብዩ ናታን በኩል ይገልጥለታል።

አሁን
ይህ "በዚህን ጊዜ" ማለት አይደለም፣ ነገር ግን ለቀጣዩ ጠቃሚ ነጥብ ትኩረት ለመስጠት ውሏል።

ለባሪያዬ ለዳዊት፣ "የሰራዊት ጌታ ያህዌ የሚለው ይህንን ነው፡ ‘እኔ አነሳሁህ... ስምህን ከፍ አደርገዋለሁ፣ በምድር ላይ ስማቸው ታላቅ እንደሆኑት ታላቅ አደርግሃለሁ' በለው።
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ ይዟል። ቀጥተኛ የሆነውን ጥቅስ በዩዲቢ ውስጥ እንደሚገኘው ቀጥተኛ ባልሆነ ጥቅስ መተገረጎሙ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። "ለባሪያዩ ለዳዊት እኔ እንዳነሳሁት... ስሙን ከፍ ታላቅ እንዳደረግኩት፣ በምድር ላይ ስማቸው ታላቅ እንደሆኑት ታላላቆች እንዳደረኩት ንገረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ እና ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅሶች የሚሉትን ይመልከቱ)

ለባሪያዬ ለዳዊት እንዲህ በለው
ያህዌ ለነብዩ ናታን አሁንም ለዳዊት መናገር ያለበትን እየነገረው ነው

ለግጦሽ ከምታሰማራበት ስፍራ አነሳሁህ
የዳዊት የእረኝነት ስራ የተገለጸው በጎቹን በሚጠብቅበት ስፍራ ነው። "እረኛ ከነበርክበት ስፍራ አነሳሁህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ከአንተ ጋር ነበርኩ
እዚህ ስፍራ "ከአንተ ጋር" የሚለው ያህዌ ዳዊትን ረድቶታል ደግሞም ባርኮታል ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጠላቶችህን ሁሉ እቆርጣለሁ
የያህዌ የዳዊትን ጠላቶች መደምሰስ የተገለጸው፣ አንድ ሰው የልብስ ቁራጭን እንደሚቆርጥ ወይም ከዛፍ ላይ ቅርንጫፉን እንደሚቆርጥ ያህዌ የዳዊትን ጠላቶች እንደቆረጣቸው ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ስምህን ታላቅ አደርገዋለሁ
እዚህ ስፍራ "ስም" የሚለው የሚወክለው ክብርን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ታላላቆች
"ታላላቆች" የሚለው ሀረግ ዝነኛ ሰዎች ማለት ነው።

2 Samuel 7:10

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ በነቢዩ ናታን በኩል ለንጉሥ ዳዊት ቃል ኪዳኑን መግለጹን ቀጠለ

እኔ ቦታ እሰጣለሁ
"እኔ ቦታ እመርጣለሁ"

በዚያ እተክላቸዋለሁ
ያህዌ ህዝቡን በምድሪቱ በቋሚነት ማኖሩ እና ጥበቃው የተገለጸው በምድሪቱ እንደሚተክላቸው ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህ አትጨነቁም/አትቸገሩም
ይህ በአድርጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ማንም ከእንግዲህ አያስጨንቃቸውም" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ከቀናቱ አንስቶ
"ከጊዜው አንስቶ"

ዳኞችን አዛለሁ
የእስራኤል ህዝብ ወደ ከነዓን ምድር ከገባ በኋላ እና የሚገዛቸው ንጉሥ ከማግኘታቸው በፊት፣ እግዚአብሔር "ዳኞች/ፈራጆች" ተብለው የሚጠሩ መሪዎችን በችግራቸው ጊዜ እንዲመሯቸው ይሾምላቸው ነበር።

በህዝቤ በእስራኤል ላይ እንዲሆኑ
በስልጣን መሆን የተገለጸው በአንድ ሰው ላይ የበላይ መሆን ተብሎ ነው። "ህዝቤን እስራኤልን እንዲመሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አሁን ከጠላቶቻችሁ ሁሉ አሳርፋችኋለሁ... ቤት እንደምሰራላችሁ በእርግጥ እነግራችኋለሁ።
በ 2ሳሙኤል 7:8-9 ቀጥተኛውን ጥቅስ፣ ቀጥተኛ ባልሆነ ጥቅስ ተርጉማችሁ ከሆነ፤ እዚህ ስፍራ "አንተ" የሚለውን "እርሱ" ወይም "የእርሱ" ብላችሁ መተርጎም ሊያስፈልግ ይችላል። "አሁን ከጠላቶቹ ሁሉ አሳርፈዋለሁ... ቤት እንደምሰራለት በእርግጥ እነግረዋለሁ" (በጥቅስ ውስጥ የሚገኝ ጥቅስ እና ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ጥቅሶች)

ከጠላቶቻችሁ ሁሉ አሳርፋችኋለሁ
"ከጠላቶቻችሁ ሁሉ እጠብቃችኋለሁ" እዚህ ስፍራ "እረፍት" የሚለው ረቂቅ ስም ነው። "ጠላቶቻችሁ ሁሉ እንንተን ማጥቃት እንዲያቆሙ አደርጋለሁ" (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ቤት እሰራልሃለሁ
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሚያመለክተው የዳዊት ትውልዶች የእስራኤል መሪ ሆነው እንደሚቀጥሉ ነው። በ 2ሳሙኤል 7:4 ያህዌ ዳዊትን እርሱ የያህዌ ቤትን የሚሰራ መሆኑን ይጠይቀዋል። በዚያ ስፍራ "ቤት" የሚለው ቃል የሚወከወለው ቤተመቅደስን ነው። ቋንቋችሁ ሁለቱንም ሃሳቦች የሚገለጽ ቃል ካለው በዚህ ስፍራ እና በ 2ሳሙኤል 7:4 ላይ ተጠቀሙበት። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 7:12

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ በነቢዩ ናታን በኩል ለንጉሥ ዳዊት ቃል ኪዳኑን መግለጹን ቀጠለ

ቀናቶቻችሁ ሲያበቁ እና ከአባቶቻችሁ ጋር ስታሸልቡ
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው የተጣመሩት ትኩረት ለመስጠት ነው። ሁለቱም አገላለጾች ሞትን በተሻሉ ቃላት የሚገልጹ ናቸው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

ከአንተ በኋላ ትውልድ አስነሳለሁ
ያህዌ የዳዊትን ትውልድ መሾሙ የተገለጸው ያህዌ እርሱን እንደሚያነሳቀው ወይም ከፍ እንደሚያደርገው ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከአብራክህ የሚወጣው
ይፍ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ሰውየው የዳዊት ትውልድ ነው ማለት ነው። (ፈሊጣው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መንግስቱን አጸናለሁ
እዚህ ስፍራ "መንግስቱ" የሚለው የሚወክለው የመግዛት ሀይሉን ነው። "በጣም ሃያል ንጉሥ እንዲሆን አደርገዋለሁ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ለእኔ ስም ቤት
እዚህ ስፍራ "ስም" የሚያመለክተው ያህዌን ነው። "ለእኔ የዘለዓለም/ቋሚ መኖሪያ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የመንግሥቱን ዙፋን ለዘለዓለም እንነባለሁ
እዚህ ስፍራ "ዙፋን" የሚወክለው የሰውየውን እንደ ንጉሥ የመግዛት ሃይል ነው። "ግዛቱ በእስራኤል ለዘለዓለም እንዲጸና አደርጋለሁ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ለእርሱ አባት እሆናለሁ፣ እርሱም ልጄ ይሆናል
በ 2ሳሙኤል7:12-14 የቀረበው ትንቢት የዳዊትን ልጅ ሰለሞንን ይመለከታል። ነገር ግን የትንቢቱ ገጽታዎች የሚሟሉት በኢየሱስ ነው። ስለዚህ፣ እዚህ ስፍራ "አባት" እና "ልጅ" የሚሉትን ቃላት በቋንቋችሁ በሚገኘው የስጋ አባትእና ልጅ የተለመደው ቃል መተረጎሙ ይመረጣል።

2 Samuel 7:15

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ በነቢዩ ናታን በኩል ለንጉሥ ዳዊት ቃል ኪዳኑን መግለጹን አጠናቀቀ

የቃል ኪዳኔ ታማኝነት ከሳኦል እንደራቀ፣ ከእርሱ ግን አልወስድበትም
"ታማኝነት" የሚለው ቃል "በታማኝነት ወዳጅ" እንደሚለው ረቂቅ ስም ነው። "ሳኦልን መውደዴን እንዳቋረጥኩት፣ እርሱን በታማኝነት መውደዴን በፍጹም አላቋርጥም"በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ከአንተ በፊት። የአንተ ቤት... ከአንተ በፊት ። የአንተ ዙፋን
በ 2ሳሙኤል7:8-9 ቀጥተኛ ጥቅስን ቀጥተኛ ባልሆነ ጥቅስ ተርጉማችሁ ከሆነ፣ አሁን እዚህ ላይ "አንተ" የሚለውን "ዳዊት" ወይም "እርሱ" ወይም "የእርሱ" ብላችሁ በዩዲቢ እንደሚገኘው መተረጎም ሊያስፈልጋችሁ ይችላል። "ከዳዊት በፊት። የዳዊት ቤት... ከእርሱ በፊት። የእርሱ ዙፋን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅሶች የሚለውን ይመልከቱ)

ቤትህ እና መንግስትህ በፊትህ ለዘለዓለም የጸና ይሆናል። ዙፋንህ ለዘለዓለም ይመሰረታል።
እነዚህ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ ደግሞም የዳዊት ስርወ መንግስት ለዘለዓለም እንደሚጸና ያጎላሉ።(ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቤትህ እና መንግስትህ በፊትህ ለዘለዓለም የጸና ይሆናል።
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው ቃል፣ ንጉስ ሆኖ የሚገዛውን የዳዊትን ትውልድ ይወክላል። እዚህ "መንግስት" ማለት "ቤት" የማለት ያህል ተመሳሳይ ነገር ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ጭምር ሊጻፍ ይችላል። "ቤተሰብህን ሳጸና እና እነርሱ በእስራኤል ላይ ለዘለዓለም ሲገዙ ትመለከታለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ዙፋንህ ለዘለዓለም ይመሰረታል።
እዚህ "ዙፋን" የሚወክለው ንጉስ ሆኖ የመግዛት ሃይልን ነው። "ትውልድህ በእስራኤል ላይ ለዘለዓለም እንዲገዛ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ ቃላት ሁሉ
"እነዚህ ነገሮች ሁሉ።" ይህ ያህዌ የተናገረውን ያመለክታል።

ስለ ጠቅላላው ራዕይ ነገረው
"ያህዌ ለእርሱ ስለ ገለጠለት ነገር ሁሉ ነገረው

2 Samuel 7:18

ያህዌ አምላክ፤ እስከዚህ ደረጃ ያደረስከኝ፣ እኔ ማን ነኝ፣ ቤቴስ ምንድን ነው?
ዳዊት ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው የያህዌን አዋጅ ሲሰማ የተሰማውን ጥልቅ ስሜት ለመግለጽ ነው። ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። " ያህዌ አምላክ ሆይ፣ እኔ እና ቤተሰቤ ለዚህ ክብር የተገባን አይደለንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በአንተ ዐይኖች ፊት/በፊትህ
እዚህ ስፍራ እይታ የሚወክለው ፍርድን ወይም ሚዛንን ነው። "በአንተ ፍርድ/ሚዛን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ ባሮች ቤተሰብ
እዚህ ስፍራ ዳዊት ራሱን "የአንተ ባሪያ" በማለት ይገልጻል። ይህ በመጀመሪያ መደብ ሊገለጽ ይችላል። "የእኔ ቤተሰብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

በሚመጣው ታላቅ ጊዜ
ይህ የሚናገረው ስለ ጊዜ ነው፤ ጊዜ እየተጓዘ እንደሚመጣ እና አንድ ስፍራ እንደሚደርስ ነገር ተደርጎ ተገልጽዋል። "እና ወደፊት በእነርሱ ላይ ምን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ ባርያ
እዚህ ስፍራ ዳዊት ራሱን "የአንተ ባሪያ" በማለት ይገልጻል። ይህ በመጀመሪያ መደብ ሊገለጽ ይችላል። "የእኔ ቤተሰብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 7:21

ስለ ቃልህ ስትል
"ልታደርግ ቃል በገባኸው ምክንያት"

የራስህን አላማ ልትፈጽም
"ልታደርግ ያቀድከውን ለመፈጸም"

ለባሪያህ
ዳዊት ራሱን "የአንተ ባሪያ።" በማለት ይገልጻል። ይህ በመጀመሪያ መደብ ሊጻፍ ይችላል። "ለ እኔ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ በገዛ ጆሮቻችን እንደ ሰማነው
"በገዛ ጆሮቻችን" የሚለው ሀረግ የዋለው ትኩረት ለመስጠት ነው። "እኛ ራሳችን እንደ ሰማነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ እንደ ሰማነው
እዚህ ስፍራ "እኛ" የሚለው የሚያመለክተው ዳዊትን እና የእስራኤልን ህዝብ ነው። (የሚያካትት እና የማያካትት "እኛ" የሚለውን ይመልከቱ)

እስራኤል እንዳንተ ያለ ህዝብ ማን ነው፣ አምላኩ እግዚአብሔር ሄዶ ያዳነው በምድር ላይ ብቸኛ ህዝብ እንዳንተ ማን ነው?
ዳዊት ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው፣ እንደ እስራል ያለ ሌላ ህዝብ እንደሌለ ትኩረት ለመስጠት ነው። "እስራኤል እንዳንተ ያለ ሌላ ህዝብ የለም፣ እግዚአብሔር ለራሱ ሄዶ በምድር ላይ ያዳነው አንድ ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ለራስህ ስም የለየኸው
እዚህ ስፍራ "ስም" የሚወክለው የያህዌን ክብር ነው። "ሁሉም ህዝብ አንተ ማን እንደሆንክ እንዲያውቅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ለምድርህ
እዚህ ስፍራ "ምድር" የሚወክለው ህዝብን ነው። "ለአንተ ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ወገን ህዝብ አባረርህ
እዚህ ስፍራ "ህዝብ" የሚለው የሚወክለው በከነዓን ይኖሩ የነበሩ ሰዎችን ወገን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 7:24

አጠቃላይ መረጃ
ዳዊት ከያህዌ ጋር መነጋገሩን ቀጠለ።

ስለዚህ አሁን
እዚህ ስፍራ "አሁን" የሚለው "በዚህን ጊዜ" ማለት አይደለም። ነገር ግን ወደ ተከታዩ ጠቃሚ ነጥብ ትኩረትን ለመሳብ ውሏል።

ለባሪያህ እና ለቤቱ የገባኸው ቃል ኪዳን ለዘለዓለም የጸና ይሁን
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ለእኔ እና ለቤቴ የገባኸውን ቃል ኪዳን ፈጽመው፣ ቃል ኪዳንህም ለዘላለም የጸና ይሁን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ባሪያህ እና ቤተሰቡ/ቤቱ
ዳዊት ስለ ራሱ በሶስተኛ መደብ እየተናገረ ነው። ይህ በአንደኛ መደብ ሊጻፍ ይችላል። "እኔ እና የእኔ ቤት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ስምህ ለዘለዓለም ታላቅ ይሁን
እዚህ ስፍራ "ስም" የሚወክለው የያህዌን ክብር ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የእኔ የባሪያህ፣ የዳዊት ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው የሚወክለው ቤተሰብን ነው። "የእኔ ቤተሰብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በፊትህ የጸና ነው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ከአንተ የተነሳ የተጠበቀ ነው" ወይም "ከአንተ የተነሳ ይቀጥላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 7:27

ለባሪያህ ቤት ትሰራለታለህ
ዳዊት ራሱን "የአንተ ባሪያ" እያለ ይጠቅሳል/ያመለክታል። "ለእኔ ቤት ትሰራልኛለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእርሱ ቤት ትሰራለታለህ
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሚያመለክተው የዳዊት ትውልድ የእስራኤል መሪ ሆኖ እንደሚቀጥል ነው። በ 2ሳሙኤል 7:4 ያህዌ ዳዊትን እርሱ የያህዌን ቤት የሚሰራ መሆኑን ይጠይቀዋል። በዚያ ስፍራ "ቤት" የሚለው ቃል የሚወክለው ቤተመቅደስን ነው። በቋንቋችሁ ሁለቱንም ሃሳቦች የሚገልጽ ቃል ካለ በዚህ ስፍራ እና በ 2ሳሙኤል 7:4 ላይ ያንን ቃል ተጠቀሙ። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አሁን
ይህ "በዚህን ጊዜ" ማለት አይደለም፣ ነገር ግን ለቀጣዩ ጠቃሚ ነጥብ ትኩረት ለመስጠት ውሏል።

ቃሎችህ የታመኑ ናቸው
"እኔ አንተ የምትናገረውን አምናለሁ"

በአንተ በረከት የባሪያህ ቤት ለዘለዓለም የተባረከ ይሆናል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንተ ቤቴን ለዘለዓለም መባረክህን ትቀጥላለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የባሪያህ ቤት
እዚህ ስፍራ ዳዊት ራሱን "የአንተ ባሪያ" በማለት ይገልጻል።" "የእኔ ቤት" ወይም "የእኔ ቤተሰብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው ቃል የሚወክለው የዳዊትን ቤተሰብ ነው።
(ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን
ይመልከቱ)

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 8

1 ከዚህ በኋላ ዳዊት ፍልስጥኤማውያንን ወጋቸው ድልም አደረጋቸው። ስለዚህ ዳዊት ጋትና መንደሮችዋን ከፍልስጥኤማውያን ቁጥጥር ነጻ አወጣት። **2** ከዚያ በኋላም ዳዊት ሞዓባውያንን ድል አደረገ፤ በመሬት ላይ አጋድሞ በገመድ ለካቸው፤ በገመድ ከተለኩትም ሁለት እጅ ሲገድል፣ አንድ እጅ ግን በሕይወት ይተው ነበር። ስለዚህ ሞዓባውያን የዳዊት አገልጋዮች ሆኑ፣ ግብርም ገበሩለት። **3** ከዚህ በኋላ ደዊት በኤፍራጥስ ወንዝ አጠገብ ያለውን ግዛቱን ለማስመለስ ይጓዝ በነበረበት ጊዜ የሱባን ንጉሥ የረአብን ልጅ አድርአዛርን ድል አደረገው። **4** ዳዊትም ከእርሱ ላይ 1700 ሠረገሎችና 20, 000 እግረኞች ማረከ። ለመቶ ሠረገሎች የሚሆኑትን አስቀርቶ ዳዊት የሠረገሎቹን ፈረሶች ሁሉ ቋንጃዎች ቆረጠ። **5** ከደማስቆ አራማውያን የሱባን ንጉሥ አድርአዛርን ለመርዳት በመጡ ጊዜ ሃያ ሁለት ሺህ አራማውያን ሰዎችን ገደለ። **6** ከዚያም የደማስቆ ክፍል በሆነው በአራም የጦር ሰፈሮችን አቋቋመ፤ አራማውያንም ለእርሱ አገልጋዮች ሆነው ተገዙለት፣ ግብርም ገበሩለት። ዳዊት በሄደበት ሁሉ እግዚአብሔር ድልን ሰጠው። **7** የአድርአዛር አገልጋዮች ይዘዋቸው የነበሩትን የወርቅ ጋሻዎች ዳዊት ወሰዳቸው ወደ ኢየሩሳሌምም አመጣቸው። **8** ቤጣህና ቤሮታይ ከተባሉ ከአድርአዛር ከተሞችም ዳዊት እጅግ ብዙ ናስ ወሰደ። **9** የሐማት ንጉሥ ቶዑ ዳዊት መላውን የአድርአዛርን ሠራዊት ድል ማድረጉን በሰማ ጊዜ፣ **10** ዳዊት ከአድርአዛር ጋር ስለ ተዋጋና ድል ስላደረገው ደግሞም አድርአዛር ከቶዑ ጋር ተዋግቶ ስለ ነበረ፣ ቶዑ ልጁን የራምን ሰላምታ ይሰጠው ዘንድና ይባርከው ዘንድ ወደ ዳዊት ላከው። የራምም ከእርሱ ጋር የብር፣ የወርቅና የናስ ዕቃዎች ይዞ መጣ። **11** ንጉሥ ዳዊትም ድል ካደረጋቸው መንግሥታት ሁሉ ማለትም **12** ከአራም፣ ከሞዓብ፣ የአሞን ሕዝብ፣ ከፍልስጥኤማውያን ከአማሌቅ እንዲሁም ከሱባ ንጉሥ ከረአብ ልጅ ከአድርአዛር ከበዘበዛቸው ዕቃዎችና ካገኛቸው ብርና ወርቅ ጋር እነዚህን ለእግዚአብሔር ቀደሰ። **13** ዳዊት የጨው ሸለቆ በተባለው ስፍራ ከአሥራ ስምንት ሺህ ሰዎቻቸው ጋር የነበሩትን አራማውያንን ድል አድርጎ ከተመለሰ በኋላ ስሙ ገነነ። **14** በመላው ኤዶም የጦር ሰፈሮችን አቋቋመ፤ ኤዶማውያን ሁሉ የዳዊት አገልጋዮች ሆኑ፤ እግዚአብሔርም ዳዊት በሄደበት ስፈራ ሁሉ ድልን ሰጠው። **15** ዳዊት በመላው እስራኤል ላይ ነገሠ፤ ሕዝቡንም ሁሉ በፍትሐዊነትና በጽድቅ አስተዳደረ። **16** የጽሩያ ልጅ ኢዮአብ የሠራዊቱ አለቃ ሲሆን፣ የአሒሉድ ልጅ ኢዮሣፍጥም ታሪክ ጸሐፊ ነበረ። **17** የአኪጦብ ልጅ ሳዶቅና የአብያታር ልጅ አቢሜሌክ ካህናት ሲሆኑ፣ ሠራያ ጸሐፊ ነበር። **18** የዮዳሔ ልጅ በናያስ የከሊታውያንና የፈሊታውያን አለቃ ሲሆን፣ የዳዊት ወንዶች ልጆች ደግሞ የንጉሡ ተቀዳሚ አማካሪዎች ነበሩ።

---

2 Samuel 8:1

ዳዊት አጠቃቸው
እዚህ ስፍራ ዳዊት የሚወክለው ወታደሮቹን/ሰራዊቱን ነው። "ዳዊት እና ሰራዊቱ/ወታደሮቹ አጠቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 8:2

ከዚያም እርሱ አሸነፈ
እዚህ ስፍራ "እርሱ" የሚለው የሚያመለክተው ወታደሮቹን የሚወክለውን ዳዊትን ነው። "ከዚያ እነርሱ አሸነፉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ወንዶቻቸውን በመስመር/ገመድ ይለካል ... የሚገድላቸውን በሁለት መስመር ሲለካ፣ በአንድ መስመር የሚቀሩት በህይወት ይተርፋሉ
እዚህ ስፍራ "መስመሩ" "ገመድ" ነው። ዳዊት ወታደሮቹን ለመለካት መሬት ላይ አጋድሞ በሶስት ቡድን ይለያቸዋል። በሁለቱ ቡድኖች የሚገኙ ወንዶች ሲገደሉ፣ ሶስተኛው ቡድን በህይወት ይተርፋል።

2 Samuel 8:3

ከዚያም ዳዊት አድርአዛርን አሸነፈ
እዚህ "ዳዊት" እና "አድርአዛር" ሁለቱም ሰራዊታቸውን ይወክላሉ። "ከዚይም ዳዊት እና ሰራዊቱ የአድርአዛርን ሰራዊት አሸነፉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

አድርአዛር...ረአብ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሱባ
ይህ በአራማ ውስጥ የሚገኝ የአካባቢ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ግዛቱን ለመመለስ
"በአካባቢው ላይ ያለውን የበላይነት መልሶ ለማግኘት" ወይም "አካባቢውን መልሶ ለመያዝ"

1,700 ሰረገሎች
"አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሰረገሎች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሃያ ሺህ እግረኞች
"20,000 እግረኞች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ዳዊት የፈረሶችን ቋንጃ ቆረጠ
ይህ ፈረሶች መሮጥ እንዳይችሉ በኋላ እግራቸው የሚገኝን ጅማት የመቁረጥ ልምምድ ነው

በቂ የሆነ አስቀረ
"በቂ የሆነ ነገር አቆየ" ወይም "በቂ ቆጠበ"

አንድ መቶ ሰረገሎች
"100 ሰረገሎች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 8:5

ዳዊት ገደለ
ዳዊት ወታደሮቹን ይወክላል። "ዳዊት እና ወታደሮቹ ገደሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ሃያ ሁለት ሺህ ሶርያውያን ወንዶች
"22,000 የሶርያ ወንዶች/ወታደሮች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በሶርያውያን ግዛት የጦር ሰፈሮችን አቋቋመ
" ብዙ የእርሱ ወታደሮች ቡድኖች በሶርያ እንዲቆዩ አዘዘ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Samuel 8:7

ዳዊት ወሰደ... ንጉስ ዳዊት ወሰደ
እዚህ ስፍራ ዳዊት የሚወክለው ወታደሮቹን ነው። "የዳዊት ወታደሮች ወሰዱ... የንጉስ ዳዊት ወታደሮች ወሰዱ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ቤጣህ እና ቤሮታይ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 8:9

ቶዑ...አዶራም
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሐማት
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ዳዊት አሸነፈ
እዚህ ስፍራ ዳዊት የሚወክለው ሰራዊቱን ነው። "የዳዊት ሰራዊት አሸነፈ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 8:11

አማሌቅም
"እናም አማሌቃውያን"

የተዘረፉት ንብረቶች
እነዚህ ወታደሮች ከማረኩት ህዝብ የሚወስዷቸው ዋጋ ያላቸው ነገሮች ናቸው።

የሱባ ንጉስ የረአብም ልጅ አድርአዛር
በ 2ሳሙኤል 8፡3 ላይ እነዚህ ስሞች እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ

2 Samuel 8:13

የዳዊት ስም በሚገባ የታወቀ ነበር
እዚህ ስፍራ "ስም" የሚለው የሚወክለው የዳዊትን ክብር ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ዳዊት እጅግ ዝነኛ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

የጨው ሸለቆ
ይህ የቦታ ስም ነው። ትክክለኛ ስፍራው አይታወቅም። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አስራ ስምንት ሺህ ወንዶች
"18,000 ወንዶች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በመላው ኤዶም የጦር ሰፈሮች አቋቋመ
"በኤዶም ዙሪያ በሙሉ የወታደር ቡድኖቹን እንዲቆዩ አዘዘ"

2 Samuel 8:15

የጽሩያ ልጅ ኢዮአብ
በ 2ሳሙኤል 2፡13 ላይ እነዚህ ስሞች እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

አሒሉድ... አሒቱብ...አቢሜሌክ... ሰራያ... ዮዳሔ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አሒሉድ ጸሐፊ ነበር
ጸሐፊ ከህዝቡ ጋር የሚነጋገር የንጉሡን ትዕዛዝም የሚነግራቸው ሰው ነበር። "አሒሉድ አዋጅ ተናጋሪ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከሊታውያን... ፈሊታውያን
እነዚህ የህዝብ ወገን ስሞች ናቸው። እነዚህ ሰዎች የዳዊት ጠባቂዎች ነበሩ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 9

1 ዳዊትም፣ “ስለ ዮናታን ስል ቸርነት አደርግለት ዘንድ ከሳዖል ቤት የቀረ ሰው ይኖር ይሆን?” በማለት ጠየቀ። **2** በሳኦል ቤተሰብ ውስጥ ሲባ የሚባል አንድ አገልጋይ ነበረ፤ እነርሱም ወደ ዳዊት እንዲሄድ ነገሩት። ንጉሡም፣ “አንተ ሲባ ነህን?” ብሎ ጠየቀው። ሲባም፣ “አዎን፣ እኔ አገልጋይህ ነኝ” ብሎ መለሰ። **3** ንጉሡም፣ “የእግዚአብሔርን ቸርነት እንዳደርግለት ከሳኦል ቤት የቀረ ሰው የለምን?” በማለት ጠየቀው። ሲባም ለንጉሡ፣ “ዮናታን እግሩ ሽባ የሆነ አንድ ልጅ አለው” ብሎ መለሰ። **4** ንጉሡም፣ “ወዴት ነው ያለው?” አለው። ሲባም ለንጉሡ፣ “ሎዶባር በተባለ ስፍራ በዓሚኤል ልጅ በማኪር ቤት ይገኛል” ብሎ መለሰለት። **5** በዚህን ጊዜ ንጉሥ ዳዊት ሎደባር ወደሚገኘው ወደ ዓሚኤል ልኮ ከማኪር ቤት ሜምፊቦስቴን አስመጣው። **6** የሳኦል ልጅ፣ የዮናታን ልጅ ሜምፊቦስቴ ወደ ዳዊት መጥቶ ለጥ ብሎ እጅ በመንሣት ለዳዊት አክብሮቱን ገለጠ። ዳዊትም፣ “ሜምፊቦስቴ” ብሎ ጠራው። እርሱም፣ “እነሆ፣ አገልጋይህ” አለ። **7** ዳዊትም፣ “አትፍራ፤ ስለ አባትህ ስለ ዮናታን ስል በእርግጥ ቸርነት አደርግልሃለሁና። የአያትህንም የሳኦልን ምድር በሙሉ እመልስልሃለሁ፤ ዘወትርም ከገበታዬ ትበላለህ።” አለው። **8** ሜምፊቦስቴም ለጥ ብሎ እጅ ነሣና፣ “እንደ ሞተ ውሻ የሆንኩትን እኔ አገልጋይህን በሞገስ ትመለከተኝ ዘንድ እኔ ማን ነኝ?” **9** ከዚያም ንጉሡ የሳኦልን አገልጋይ ሲባን ጠርቶ እንዲህ አለው፤ “የሳኦልና የቤተሰቡ የሆነውን ሁሉ ለጌታህ ልጅ ሰጥቼዋለሁ። **10** አንተ፤ ልጆችህና አገልጋዮችህ የጌታችሁ የልጅ ልጅ የሚበላውን እንዲያገኝ መሬቱን እረሱለት፣ ምርቱንም አግቡለት። የጌታህ የልጅ ልጅ ሜምፊቦስቴ ግን ምን ጊዜም ከገበታዬ ይበላል።” በዚያን ጊዜ ሲባ ዐሥራ አምስት ልጆችና ሃያ አገልጋዮች ነበሩት። **11** ከዚያም ሲባ ንጉሡን፣ “ጌታዬ ንጉሥ፣ አገልጋዩን ያዘዘውን ሁሉ፣ አገልጋይህ ይፈጽመዋል” አለው። ንጉሡም በተጨማሪ፣ “ሜምፊቦስቴ በበኩሉ ከንጉሡ ልጆች እንደ አንዱ ከገበታዬ የሚበላ ይሆናል” አለ። **12** ሜምፊቦስቴ ሚካ የተባለ አንድ ትንሽ ልጅ ነበረው፤ የሲባ ቤተሰቦች በሙሉ የሜምፊቦስቴ አገልጋዮች ነበሩ። **13** ስለዚህ ሜምፊቦስቴ ይኖር የነበረው በኢየሩሳሌም ነበር፣ ሁለት እግሮቹም ሽባ ቢሆኑም ሁልጊዜ ከንጉሡ ገበታ ይበላ ነበር።

---

2 Samuel 9:1

ስለ ዮናታን ስል
"ለዮናታን ባለኝ ፍቅር ምክንየት"

ስለ ዮናታን ስል
ዮናታን የሳኦል ልጅ እና የዳዊት የልብ ወዳጅ ነበር

ሲባ
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ የአንተ ባሪያ ነኝ
ሲባ ራሱን "የአንተ ባሪያ" በማለት ለዳዊት ያለውን ታላቅ አክብሮት ያሳያል

2 Samuel 9:3

የእግዚአብሔርን መልካምነት አደርግለት ዘንድ
"ደግነት/መልካምነት" የሚለው ረቂቅ ስም "ደግ/መልካም" ተብሎ ሊጻፍ ይችላል። "ለእግዚአብሔር ቃል እንደገባሁ መልካም እሆንለታለሁ"

እግሩ ሽባ የሆነው ማን ነው
"የተጎዳው የማን እግር ነው።" እዚህ ስፍራ "እግር" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የመራመድን ችሎታ ነው። "መራመድ የማይችለው ማን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ማኪር... ዓሚኤል
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሎዶባር
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 9:5

ንጉስ ዳዊት ላከ
ዳዊት መልዕክተኞችን መላኩ ግልጽ ነው። (ኢሊፕሲስ/የተተወ ወይም የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

ሜምፊቦስቴ
ይህንን በ 2ሳሙኤል4፡4 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ወደ ዳዊት መጣ
"መምጣት" የሚለው ቃል "መሄድ" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። (ሄደ እና መጣ የሚሉትን ይመልከቱ)

እኔ የአንተ ባሪያ
ሜምፊቦስቴ ራሱን "የአንተ ባሪያ" በማት የሚገልጸው ለዳዊት ያለውን ክብር ለማሳየት ነው።

2 Samuel 9:7

ዮናታን፣ ለአባትህ ስል
"ዮናታን፣ አባትህን ስለምወደው"

ሁልጊዜም ከገበታዬ ትበላለህ
እዚህ ስፍራ "ገበታዬ" የሚለው የሚወክለው ከዳዊት ጋር አብሮ መሆንን ወይም የእርሱን መገኘት/አብሮነት ነው። ከንጉሱ ጋር በገበታው ቀርቦ መብላት ታላቅ ክብር ነበር። "ሁሌም ከእኔ ጋር አብረህ ትቀርባለህ/ትበላለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ሞተ ውሻ የሆንኩትን ባሪያህን በሞገስ ትመለከተኝ ዘንድ ባሪያህ ምንድን ነው?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ ሜምፊቦስቴ ንጉሱ እርሱን ይንከባከበው ዘንድ የሚያበቃው ነገር እንደሌለው መረዳቱን ያሳያል። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እኔ እንደ ሞተ ውሻ ነኝ። ደግነትን ልታሳየኝ የተገባሁ አይደለሁም። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የሞተ ውሻ የምመስል
እዚህ ስፍራ ሜምፊቦስቴ የሳኦልን ትውልድ ይወክላል፣ ደግሞም ራሱን "ከሞተ ውሻ" ጋር ያነጻጽራል። ውሾች እንደ ቤት እንስሳ የማይቆጠሩ፣ እንክብካቤ የማይደረግላቸው እና ጥቅማቸው ይህ ነው የማይባሉ እንስሳት ነበሩ። የሞተ ውሻ ከዚህ ይልቅ የማይረባ ተደርጎ ይወሰዳል። "እንደ እኔ ያለው እንደ ሞተ ውሻ እርባና የሌለው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Samuel 9:9

ሁሌም ከገበታዬ ትመገባለህ
እዚህ ስፍራ "ገበታ" የሚለው የሚወክለው ከዳዊት ጋር አብሮ መሆንን ወይም የእርሱን መገኘት/አብሮነት ነው። ከንጉሱ ጋር በገበታው ቀርቦ መብላት ታላቅ ክብር ነበር። "ሁሌም ከእኔ ጋር አብረህ ትቀርባለህ/ትበላለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አሁን ሲባ... ባሮች
እዚህ ስፍራ "አሁን" የሚለው በዋናው የታሪክ አካሄድ ላይ የገባ ነው። ተራኪው ስለ ሲባ የመረጃ ዳራ ይሰጣል። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

አስራ አምስት ወንድ ልጆች እና ሃያ ባሪያዎች
"15 ወንድ ልጆች 20 ባሪያዎች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 9:11

የአንተ ባሮች ጌታዬ ንጉሡ ባሮቹን ያዘዘውን ሁሉ ያደርጋሉ
ሲባ ራሱን "የአንተ ባሪያ" በማለት ሲገልጽ ዳዊትን ደግሞ " የእኔ ጌታ" በማለት ይናገራል። "እኔ፣ የአንተ ባሪያ አንተ ንጉሴ አደርገው ዘንድ ያዘዝከኝን ሁሉ አደርጋለሁ" (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ሚካ
ይህ የሜምፊቦስቴ ልጅ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በሲባ ቤት የሚኖሩ ሁሉ
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው የሚወክለው የሲባን ቤተሰብ ነው። "መላው የሲባ ቤተሰብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ሁሌም ከንጉሱ ገበታ ይበላ ነበር
እዚህ ስፍራ "ገበታ" የሚለው የሚወክለው ሁሌም ከዳዊት ጋር አብሮ መሆንን ወይም ከእርሱ ጋር መገኘትን ነው። ከንጉሱ ጋር ሆኖ ከገባታው መብላት ታላቅ ክብር ነበር። "ሁሌም ከንጉሱ ጋር ሆኖ ከገበታው ይበላ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ምንም እንኳን ሁለቱም እግሮቹ ሽባ ቢሆኑም
"ምንም እንኳን ሁለቱም እግሮቹ የተጎዱ ቢሆኑም።" እዚህ ስፍራ "እግር" የሚለው የሚወክለው መራመድ መቻልን ነው። "መራመድ የማይችል ቢሆንም" በሚለው ውስጥ አንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 10

1 ከዚህ በኋላ የአሞናውያን ንጉሥ ሞተ፣ ልጁ ሐኖንም በእርሱ ምትክ ንጉሥ ሆነ። **2** ዳዊትም፣ “አባቱ ቸርነትን እንዳደረገልኝ ሁሉ እኔን ለናዖስ ልጅ ለሐኖን ቸርነትን አደርግለታለሁ።” አለ። ስለዚህ በአባቱ ምክንያት ከደረሰበት ኃዘን ያጽናኑት ዘንድ ዳዊት አገልጋዮቹን ላከ። አገልጋዮቹም ወደ አሞን ምድር ገቡ። **3** የአሞን ሕዝብ መሪዎች ግን ለጌታቸው ለሐኖን እንደዚህ አሉት፣ “አንተን እንዲያጽናኑ ሰዎቹን በመላኩ ዳዊት በእርግጥ አባትህን በማክበር ነው ብለህ ታስባለህን? ዳዊት ሰዎቹን የላከው ከተማይቱን እንዲመለከቱና ያጠፏትም ዘንድ እንዲሰልሏት አይደለምን?” **4** ስለዚህ ሐኖን የዳዊትን ሰዎች ይዞ፤ የእያንዳንዳቸውን ጢም በከፊል ላጨ፣ ልብሳቸውንም እስከ ቂጣቸው ድረስ አሳጥሮ በመቁረጥ መልሶ ሰደዳቸው። **5** ይህንን ለዳዊት በገለጹለት ጊዜ፣ ሰዎቹ እጅግ አፍረው ነበርና መልእክተኞችን ወደ እነርሱ ላከ። ንጉሡም፣ “ጢማችሁ እስኪያድግ በኢያሪኮ ቆዩና ከዚያ በኋላ ተመለሱ” አላቸው። **6** የአሞን ሰዎች ለዳዊት መጥፎ ጠረን እንዳላቸው ሰዎች እንደሆኑበት ባወቁ ጊዜ የአሞን ሰዎች መልእክተኞችን ልከው ከቤትሮዖብና ከሱባ ሃያ ሺህ አራማውያን እግረኛ ወታደሮችን፣ ከንጉሥ መዓካ አንድ ሺህ ሰዎችን ደግሞም ከጦብ ዐሥራ ሁለት ሺህ ሰዎችን ቀጠሩ። **7** ዳዊት ይህን በሰማ ጊዜ ኢዮአብን ከመላው ተዋጊ ሠራዊት ጋር ላከው። **8** አሞናውያን ወጥተው በከተማቸው መግቢያ በር ላይ ሲሰለፉ፤ የሱባና የረአብ አራማውያን ሰዎች ለብቻቸው ሜዳው ላይ ቆሙ። **9** ኢዮአብም ከፊትና ከኋላው ጦር እንደ ከበበው ባየ ጊዜ፣ በእስራኤል በጀግንነታቸው ከታወቁት ጥቂቶቹን መርጦ በአራማውያን ግንባር አሰለፋቸው። **10** የቀሩትን ሰዎች ደግሞ በወንድሙ በአቢሳ ሥር መድቦ በአሞናውያን ሠራዊት ግንባር አሰለፋቸው። **11** ኢዮአብም እንዲህ አለ፤ “አራማውያን የሚያይሉብኝ ከሆነ አንተ መጥተህ ትረዳኛለህ፤ አሞናውያን የሚያይሉብህ ከሆነ እኔ መጥቼ እረዳሃለሁ። **12** እንግዲህ በርታ ለሕዝባችንና ለአምላካችን ከተሞች ጠንካሮች መሆናችንን እናስመስክር፤ እግዚአብሔርም ለዓላማው መልካም መስሎ የታየውን ያደርጋል።” **13** ከዚያም ኢዮአብና አብሮት የነበረው ሠራዊት ከእስራኤል ሠራዊት ፊት እንዲሸሹ ወደ ተገደዱት ወደ አራማውያን በመገሥገሥ ወደ ጦርነቱ ሄዱ። **14** አራማውያን መሸሻቸውን አሞናውያን ባዩ ጊዜ፣ እነርሱም ከአቢሳ ፊት ሸሽተው ወደ ከተማይቱ ውስጥ ገቡ። ከዚህ በኋላ ኢዮአብ ከአሞናውያን ሕዝብ ተመልሶ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ። **15** አራማውያን በእስራኤላውያን እየተሸነፉ እንደሆኑ ባዩ ጊዜ እንደ ገና ተሰባሰቡ። **16** አድርአዛር ከኤፍራጥስ ወንዝ ማዶ ወደነበሩት ወደ አራማውያን ሠራዊት መልእክተኞችን ላከ፤ እነርሱም በአድርአዛር ሠራዊት አዛዥ በሶባክ መሪነት ወደ ዔላም መጡ። **17** ይሄ ነገር ለዳዊት በተነገረው ጊዜ መላውን እስራኤልን ሰበሰበ፤ ከዚያም ዮርዳኖስን ተሻግሮ ወደ ዔላም ሄደ። አራማውያን ለጦርነት ተሰልፈው ዳዊትን ገጠሙት ተዋጉትም። **18** አራማውያን ከእስራኤል ፊት ሸሹ፤ ዳዊትም ሰባት መቶ ሠረገለኞችንና አርባ ሺህ ፈረሰኞችን ገደለ። የሠራዊቱ አዛዥ ሶባክም ቆስሎ በዚያ ሞተ። **19** የአድርአዛር አገልጋዮች የነበሩት ነገሥታት ሁሉ በእስራኤል መሸነፋቸውን ባዩ ጊዜ ከእስራኤላውያን ጋር ሰላም መሠረቱ ተገዙላቸውም። ስለዚህም ሶርያውያን ከዚያ በኋላ አሞናውያንን መርዳት ፈሩ።

---

2 Samuel 10:1

አሞን... ሐኖን
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ... በእርግጥ እንዲህ ታሰባለህ
መሪዎች ጥያቄውን የተጠቀሙበት የአሞን ንጉስ ዳዊትን አንዳያምነው ለመጠቆም ነው። "አንተ...እንዲህ ማሰብህ ስህተት ነው!" በሚለው ውስጥ አንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ለመሰለል
ስለ ሌላ ሰው በድብቅ መረጃ ለማግኘት/ለማወቅ

ዳዊት ... እርሷን ያጠፋት አይደለምን?
መሪዎች ጥያቄውን የተጠቀሙበት የአሞን ንጉስ ዳዊትን አንዳያምነው ለመጠቆም ነው። "ዳዊት... እርሷን የጣለ እንደሆነ ልታውቅ ይገባሃል" በሚለው ውስጥ አንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሷን ይጥል/ያጠፋ ዘንድ
እዚህ ስፍራ "እርሷን" የሚለው በዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ከተማን የሚወክል ነው። "እኛን ይወር ዘንድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከተማይቱ
እዚህ ስፍራ "ከተማይቱ" የሚለው የሚያመለክተው የአሞናውያንን ዋና ከተማ ረባትን ነው።

2 Samuel 10:4

ግማሽ ጺማቸውን ላጨ
ይህ ድርጊት ሰዎቹን ለማዋረድ መሳደብ ማለት ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በጥልቅ አፍረው
እዚህ ስፍራ "በጥልቅ" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ "በጣም" ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያ ተመለሱ
ወደ ኢየሩሳሌም መመለሳቸው ግልጽ ነው። (ኢሊፕስስ/የተተወ ወይም የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 10:6

ለዳዊት የተጠሉ/መጥፎ ሽታ ሆኑ
"የተጠሉ/መጥፎ ሽታ ሆኑ" የሚለው ሀረግ "አጥቂዎች/ጠላቶች ሆኑ" ለሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "እንደ መጥፎ ሽታ ለዳዊት ጠላቶች/አጥቂ ሆኑበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ቤትሮዖብ...ሱባ...መዓካ...ጦብ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሃያ ሺህ... አንድ ሺህ... አስራ ሁለት ሺህ
"20,000... 1,000...12,000" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ከተማቸው መግቢያ በር
እዚህ ስፍራ "ከተማይቱ" የሚለው የሚያመለክተው የአሞናውያንን ዋና ከተማ ረአብን ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Samuel 10:9

አጠቃላይ መረጃ:
ከሶርያውያን እና ከአሞን ጋር ውጊያው ቀጠለ።

የተቀረውን ህዝቡን በወንድሙ በአቢሳ እጅ አደረጋቸው
"ወንድሙን አቢሳን ለተቀረው ሰራዊት ሃላፊ አደረገ"

2 Samuel 10:11

አጠቃላይ መረጃ:
ኢዮአብ ሰራዊቱን ለውጊያ ዝግጁ አደረገ

አንተ ለእኔ፣ እኔ ለአንተ፣ አቢሳ አንተ እኔን ልትረዳ ይገባሃል
እዚህ ስፍራ "እኔ" የሚለው የሚያመለክተው ኢዮአብን ነው። ኢዮአብ እና አቢሳ እራሳቸውን እና ሰራዊታቸውን ይወክላሉ። "አንተ ለእኛ፣ እኛ ለአንተ ነን፤ ኢቢሳ የአንተ ሰራዊት እኛን መታደግ አለበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 10:13

ከአቢሳ
እዚህ ስፍራ ኢቢሳ የሚወክለው ራሱን እና ወታደሮቹን ነው። "ከኢቢሳ እና ወታደሮቹ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ከተማይቱ
እዚህ ስፍራ "ከተማይቱ" የሚለው የሚያመለክተው የአሞናውያንን ዋና ከተማ ረአብን ነው።

ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው ሄዱ
"ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ"

2 Samuel 10:15

ሶርያውያን በእስራኤል ፊት እንደተሸነፉ ባዩ ጊዜ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሶርያውያን እስራኤላውያን እያሸነፏቸው እንደሆነ ባወቁ ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አድርአዛር... ሶባክ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ከኤፍራጥስ ወንዝ ባሻገር
ይህ ማለት በኤፍራጥስ ወንዝ ምስራቅ

ወደ ኤላም መጡ
እዚህ ስፍራ "ወደ ...መጡ" የሚለው "ወደ... ሄዱ" ወይም "በ... ተሰበሰቡ" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል።

ኤላም
የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 10:17

ዳዊት ይህ ሲነገረው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ዳዊት ስለዚህ ሲሰማ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን የመልከቱ)

መላውን እስራኤል ሰበሰበ
እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚለው የሚወክለው የእስራኤልን ሰራዊት ነው። "መላውን የእስራኤል ሰራዊት በአንድነት ሰበሰበ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ኤላም
ይህ የወንድ ስም በ 2 ሳሙኤል10:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ

በዳዊት ላይ ደግሞም እርሱን ወጉት
እዚህ ስፍራ ዳዊት የሚወክለው ራሱን እና የእርሱን ወታደሮች ነው። "በዳዊት እና ወታደሮቹ ላይ ደግሞም እነርሱን ተዋጉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ዳዊት ገደለ
እዚህ ስፍራ ዳዊት የሚወክለው ራሱን እና የእርሱን ወታደሮች ነው። "በዳዊት እና ወታደሮቹ ገደሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባት መቶ... አርባ ሺህ
"700... 40,000" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

የሰራዊታቸው አለቃ ሶባክ ቆስሎ ነበር ደግሞም በዚያ ሞተ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እስራኤላውያን የሶርያን ጦር አለቃ ሶባክን አቆሰሉት፣ እርሱም በዚያ ሞተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ሶባክ...አድርአዛር
እነዚህ የወንድ ስሞች በ 2 ሳሙኤል10:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ

በእስራኤል እንዴት እንደ ተሸነፉ አዩ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እስራኤላውያን እንዳሸነፏቸው አወቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 11

1 ነገሥታት ወደ ጦርነት መውጣታቸው የተለመደ በነበረበት በፀደይ ወራት ዳዊት ኢዮአብን፣ አገልጋዮቹንና መላውን የእስራኤል ሠራዊት ወደ ዘመቻ ላካቸው፤
እነርሱም አሞናውያንን አጠፉ፤ ረባትንም ከበቡአት። ዳዊት ግን በኢየሩሳሌም ቀረ። 2 ከዚህም የተነሣ በአንድ የምሽት ወቅት ዳዊት ከዐልጋው ተነስቶ በቤተ
መንግሥቱ ሰገነት ወዲያና ወዲህ ይመላለስ ነበር፤ በዚያም ስፍራ ሆኖ አንዲት ሴት ገላዋን ስትታጠብ አየ፤ ሴቲቱም እጅግ በጣም ውብ ነበረች። 3 ዳዊትም
ሰው ልኮ ስለ ሴቲቱ የሚያውቁ ሰዎችን አጠያየቀ። አንድ ሰውም፣ “ይህች የኤልያብ ልጅ፣ የኬጢያዊው የኦርዮን ሚስት አይደለችምን?” 4 ከዚያም ዳዊት
መልእክተኞች ልኮ አስመጣት፤ ወደ እርሱም ገባች፣ (ከወር አበባ ጊዜዋ የነጻችበት ወቅት ነበርና) አብሮአት ተኛ። ከዚያም ተመልሳ ወደ ቤቷ ሄደች። 5 ሴቲቱ
ፀነሰች፣ “አርግዣለሁ” ብላም ወደ ዳዊት መልእክት ላከችበት። 6 ከዚያ በኋላም ዳዊት ለኢዮአብ፣ “ኬጢያዊውን ኦርዮንን ወደ እኔ ላክልኝ” ብሎ መልእክት
ላከበት። ስለዚህም ኢዮአብ ኦርዮንን ወደ ዳዊት ላከው። 7 ኦርዮን በደረሰ ጊዜ ኢዮአብና ሠራዊቱ በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ እንዲሁም ጦርነቱ እንዴት እየተካሄደ
እንዳለ ጠየቀው። 8 ዳዊትም ለኦርዮን፣ “ወደ ቤትህ ሄደህ እግርህን ተታጠብ” አለው። ኦርዮንም ከቤተ መንግሥቱ ወጣ፣ ንጉሡም ኦርዮን ከወጣ በኋላ ስጦታ
አስከትሎ ላከለት። 9 ኦርዮን ግን ከጌታው አገልጋዮች ጋር በቤተ መንግሥቱ ቅጥር በር ተኛ እንጂ ወደ ቤቱ አልወረደም ነበር። 10 ለዳዊት “ኦርዮ ወደ ቤቱ
አልሄደም” ብለው በነገሩት ጊዜ፣ ዳዊት ኦርዮንን፣ “ከመንገድ መግባትህ አይደለምን? ለምን ወደ ቤትህ ያልሄድኸው ለምንድን ነው?” ሲል ጠየቀው። 11
ኦርዮም ዳዊትን፣ “ታቦቱ፣ እስራኤልና ይሁዳ በድንኳን ሆነው፣ ጌታዬ ኢዮአብና የጌታዬም አገልጋዮች ገላጣ ሜዳ ላይ ሰፍረው፤ ለመብላትና ለመጠጣት
እንዲሁም ከሚስቴ ጋር ለመተኛት እንዴት ወደ ቤቴ እሄዳለሁ? እንዲህ ያለውን ነገር እንደማላደርገው በነፍስህ እምላለሁ።” አለው። 12 ከዚህም የተነሣ ዳዊት
ለኦርዮ፣ “ዛሬ ደግሞ በዚህ እደርና ነገ አሰናብትሃለሁ” አለው። ስለዚህ ኦርዮ በዚያ ዕለትና በማግሥቱ እዚያው ኢየሩሳሌም ቆየ። 13 ዳዊትም ባስጠራው ጊዜ
በእርሱ ፊት በላ ደግሞም ጠጣ፣ ዳዊትም እንዲሰክር አደረገው፤ ሲመሸም ኦርዮን በአልጋው ላይ ለመተኛት የጌታው አገልጋዮች ወዳሉበት ሄደ፣ ወደ ቤቱ ግን
አልሄደም። 14 ስለዚህ በማግስቱ ሲነጋ ዳዊት ለኢዮአብ ደብዳቤ ጽፎ በኦርዮን እጅ ላከለት። 15 በደብዳቤውም ውስጥ ዳዊት፣ “ኦርዮንን ውጊያው
በተፋፋመበት ግንባር መድበው፤ ከዚያም እንዲመታና እንዲሞት ከኋላው አፈግፍጉ” ብሎ ጻፈ። 16 ስለዚህ ኢዮአብ የከተማይቱን መከበብ እየተመለከተ ሳለ
ጠንካሮቹ የጠላት ሠራዊት እየተዋጉ እንዳሉ በሚያውቅበት ግንባር ኦርዮንን መደበው። 17 የከተማይቱ ሰዎች ወጥተው ከኢዮአብ ጋር ጦርነት በገጠሙበት
ጊዜ ከዳዊት ወታደሮች ጥቂቶቹ ሞቱ፣ እንዲሁም ኬጢያዊው ኦርዮንም በዚያ ሞተ። 18 ኢዮአብም በጦርነቱ የሆነውን ሁሉ ለዳዊት በላከበት ጊዜ፣ 19
መልእክተኛውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፣ “ጦርነቱን በሚመለከት ሁሉንም ነገር ለንጉሡ ከጨረስክ በኋላ፣ 20 ምናልባት ንጉሡ ይቆጣና፣ ‘ለመዋጋት ስትሉ ወደ
ከተማይቱ ይህን ያህል የተጠጋችሁት ስለምንድን ነው? በግንቡ ቅጥር ላይ ሆነው ፍላፃ እንደሚወርውሩባችሁ አታውቁም ኖሮአል? 21 የይሩቤሼትን ልጅ
አቤሜሌክን የገደለው ማነው? በቴቤስ እንዲሞት ያደረገችው አንዲት ሴት ከግንቡ ላይ የወፍጮ መጅ ስለለቀቀችበት አይደለምን? ወደ ግንቡ ቅጥር ይህን
ያህል የተጠጋችሁት ለምንድን ነው?’ይልህ ይሆናል። በዚያን ጊዜ፣ ‘አገልጋይህ ኬጢያዊው ኦርዮም ሞቶአል’ ብለህ ንገረው።” 22 ስለዚህ መልእክተኛው
ተነሥቶ ወደ ዳዊት ዘንድ ሄደ፣ ኢዮአብ እንዲናገር የላከውን ማንኛውንም ነገር ነገረው። 23 መልእክተኛውም ለዳዊት እንዲህ አለው፣ “እኛ በመጀመሪያ ከነበረው
ይልቅ ጠላት በርትቶ ነበር ወደ ሜዳው ወደ እኛ ዘንድ መጡ፤ እኛም እስከ ቅጥሩ መግቢያ በር ድረስ አሳድደን መለስናቸው። 24 የእነርሱም ባለ ፍላጻዎች
ከግንቡ ላይ ሆነው በወታደሮችህ ላይ ቀስት ወረወሩ፣ ከንጉሡ አገልጋዮችም ጥቂቶችን ገደሉ፤ አገልጋይህ ኬጢያዊው ኦርዮም ሞተ።” 25 ከዚያ በኋላ ዳዊት
ለመልእክተኛው፣ “ለኢዮአብ፣ ‘መቼም ሰይፍ አንድ ጊዜ ይህን፣ ሌላ ጊዜም ሌላውን ይበላልና ይህ አያሳዝንህ። በከተማይቱ ላይ ውጊያህን አጠናክረህ
አፍርሳት።’ በለው፣ ኢዮአብን አበረታታው።” 26 ስለዚህ የኦርዮ ሚስት ባሏ መሞቱን በሰማች ጊዜ አምርራ አለቀሰችለት። 27 የሐዘኗም ጊዜ ካበቃ በኋላ ዳዊት
ልኮ ቤርሳቤህን ወደ ቤቱ ወሰዳት፣ ሚስቱም ሆነች፣ ወንድ ልጅም ወለደችለት፤ ነገር ግን ዳዊት ያደረገው ነገር እግዚአብሔርን አሳዘነው።

---

2 Samuel 11:1

በፀደይ ወቅት እንዲህ አጋጠመ
"በፀደይ ወቅት ይህ ሆነ።" ይህ በታሪኩ ፍሰት አዲስ ትዕይንትን ያስተዋውቃል። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

በጊዜው
"በአመቱ ወቅት"

ዳዊት ኢዮአብን፣ አገልጋዮቹን እና መላውን የእስራኤል ሰራዊት ላከ
ዳዊት እነርሱን ወደ ጦርነት ላከ። ይህ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። እንደዚሁም "የእርሱ" የሚለው ቃል ዳዊትን ያመለክታል። "ዳዊት ኢዮአብን፣ አገልጋዮቹን፣ እና መላውን የእስራኤል ሰራዊት ወደ ጦርነት ላከ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የአሞን ሰራዊት
"የአሞናውያን ሰራዊት"

ረባት
ይህ የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 11:2

ስለዚህም እንዲህ ሆነ
"እናም እንዲህ ሆነ" ወይም "ስለዚህ እንዲህ ሆነ" ጸሐፊው ይህንን ሀረግ የተጠቀመው ቀጣዩን ትዕይንት በታሪኩ ፍሰት ውስጥ ለማስገባት ነው። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ)

ሰውነቷን ትታጠብ የነበረች ሴት
ሴትየዋ በሰገነት/ጣራ ላይ አልነበረችም፣ በቤቷ አጥር ግቢ ውጭ ሆና ገላዋን እየታጠበች ሳትሆን አትቀርም። "በቤቷ አጥር ግቢ ውስጥ ትታጠብ የነበረች አንዲት ሴት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እናም ዳዊት ላከ
እዚህ ስፍራ "ላከ" የሚለው ቃል ዳዊት መልዕክተኛ ላከ ማለት ነው። "እናም ዳዊት መልዕክተኛ ላከ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመለከቱ) ስለ ሴትየዋ የሚያውቀዉ ሰዎችን ጠየቀ ዳዊት ሴትየዋ ማን እንደሆነች ለማወቅ እየሞከረ ነበር። "እርሱ" የሚለው ቃል ዳዊትን ሲያመለክት፣ ደግሞም ዳዊት ለላከው መልዕክተኛ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። መልዕክተኛው ስለ እርሷ ሰዎችን መረጃ ይጠይቅ ነበር። "መልዕክተኛው እርሷ የሚያውቁ ሰዎችን ስለማንነቷ መረጃ ይጠይቅ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ይህች ቤርሳቤህ አይደለችምን... እርሷስ የኬጢያዊው የኦርዮ ሚስት አይደለችምን?
ይህ ጥያቄ መረጃ ይሰጣል፣ ደግሞም በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ይህች ቤርሳቤህ ናት... እርሷም የኬጢያዊው የኦርዮ ሚስት ናት " በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 11:4

ወሰዳት
"እናም እርሱ ወሰዳት።" እዚህ ዳዊት ሴቲቱን ወሰዳት ይላል፣ ነገር ግን በእርግጥ የሆነው፣ የወሰዷትና ወደ እርሱ ያመጧት እርሱ የላካቸው መልዕክተኞች ናቸው። "እነርሱ ወደ እርሱ አመጧት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እርሷ ወደ እርሱ መጣች፣ ደግሞም እርሱ ከእርሷ ጋር ተኛ
" እርሷ ወደ እርሱ መጣች" የሚለው ሀረግ ዳዊት ከሴቲቱ ጋር ተኛ ለሚለው ጉልህ ገለጻ ነው። እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ እናም አብረው መተኛታቸውን ለማጉላት በአንድነት ቀርበዋል። "ከእርሷ ጋር ተኛ" ወይም "ከእርሷ ጋር ግንኙነት አደረገ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የወር አበባ
የሴት ወርሃዊ የመንጻት ጊዜ

"እኔ አርግዣለሁ።" ስትል ወደ ዳዊት ልካ ነገረችው
እዚህ ስፍራ "ልካ" ማለት መልዕክተኛ ላከች ማለት ነው። ማርገዟን ወደ ዳዊት መልዕክተኛ ላከች። "እንዳረገዘች እንዲነግሩት ወደ ዳዊት መልዕክተኛ ላከችበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 11:6

ከዚያም ዳዊት ላከ
እዚህ ስፍራ "ላከ" የሚለው ዳዊት መልዕክተኛ ላከ ማለት ነው። "ከዚያም ዳዊት መልዕክተኛ ላከ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኢዮአብ እንዴት እንደሆነ፣ ሰራዊቱ ምን እያደረገ እንደሆነ፣ እና ጦርነቱ እንዴት እየተካሄደ እንደ ነበር
ዳዊት ኢዮአብ እና ሰራዊቱ ደህና ስለ መሆናቸው እና ስለ ጦርነቱ አካሄድ ይጠይቅ ነበር። "ኢዮአብ ደህና ከሆነ፣ ሌሎች ወታደሮችም ደህና ከሆኑ፣ ደግሞም ጦርነቱ እንዴት እየተካሄደ እንደሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ቤትህ ውረድ
"ወደ ታች ውረድ" ለሚለው ሀረግ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የኦርዮ ቤት ከንጉሱ ቤተ መንግስት ዝቅ ባለ ስፍራ ላይ ይገኝ ነበር ወይም 2) የኦርዮ ቤት ከንጉሱ ቤተ መንግስት ይልቅ ያነሰ ጠቃሚነት ነበረው። "ወደ ቤትህ ሂድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እግርህን ታጠብ
ይህ ሀረግ ከእለት ስራ በኋላ ምሽቱን ለማረፍ ወደ ቤት መመለስ ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ምሽቱን እረፍ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሱ ለኦርዮ ስጦታ ላከለት
ዳዊት ለኦርዮ ስጦታውን እንዲያመጣለት አንድ ሰው ላከ። ይህ በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "ንጉሱ ለኦርዮ ስጦታ እንዲወሰድለት አንድ ሰው ላከ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 11:9

የእርሱ ጌታ
"የእርሱ" የሚለው ቃል ኦርዮን ያመለክታል፤ "ጌታ" የሚለው ደግሞ ዳዊትን ያመለክታል።

የመጣኸው ከመንገድ አይደለምን? ስለምን ወደ ቤትህ አትወርድም/አትሄድም?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የዋለው ኦርዮን ሚስቱ ለማየት መሄድን መቃወሙን ለማጉላት ነው፤ ሃሳቡ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ከእንዲህ አይነት ረጅም መንገድ ከመጣህ በኋላ፣ አሁን ወደ ቤትህ መውረድ አለብህ " በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እስራል እና ይሁዳ
ይህ ሰራዊታቸውን ያመለክታል። "የእስራኤል እና የይሁዳ ሰራዊቶች" (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ከሚስቴ ጋር .... እንዴት ወደ ቤቴ መሄድ ይሆንልኛል?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የዋለው ኦርዮ ሚስቱን ለማየት መሄዱን መቃወሙን ለማጉላት ነው፤ ይህ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "በሰራዊቴ ውስጥ የሚገኙት ሌሎች ወታደሮች በአደጋ ላይ ሆነው ከሚስቴ ጋር ለመሆን...ወደ ቤቴ መሄድ በደል መፈጸም ይሆንብኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

በህያው ነፍስህ እምላለሁ፣ ይህንን በፍጹም አላደርገውም
ኦርዮ ሌሎች ወታደሮች በጦርነት ላይ እያሉ ወደ ቤቱ ሚስቱ ዘንድ እንደማይሄድ ጠንካራ የቃል ኪዳን መሃላ ያደርጋል። ይህን ቃል ኪዳን የሚያደርገው የቃል ኪዳኑን እውነተኛነት ከንጉሱ ህያውነት እርግጠኝነት ጋር በማነጻጸር ነው። " ይህንን እንደማላደርገው በጽኑ ቃል እገባለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 11:12

በፊቱ በላ ጠጣም
"ኦርዮ ከዳዊት ጋር በላ ጠጣም"

ወደ እርሱ ቤት መውረድ
"ወረደ" ለሚለው ቃል ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የኦርዮ ቤት ከንጉሱ ቤተ መንግስት ዝቅ ባለ ስፍራ ላይ ይገኝ ነበር ወይም 2) የኦርዮ ቤት ከንጉሱ ቤተ መንግስት ይልቅ ያነሰ ጠቃሚነት ነበረው። በ 2 ሳሙሴል 11:8 ላይ የሚገኘው "ወደ ቤትህ ውረድ" የሚለው ይህ ተመሳሳይ ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ወደ ቤትህ ውረድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 11:14

በኦርዮ እጅ ላከው
"የኦርዮ እጅ" የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው ኦርዮን ራሱን ነው። " ይህን ለእርሱ እንዲያደርስ ኦርዮን ራሱን ላከው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

እጅግ በተፋፋመው ጦርነት በጣም ከፊት
"በጦርነቱ ግንባር ውጊያው በከፋበት በጣም ከፊት"

ከእርሱ ይሸሹ
"ወታደሮቹን ከእርሱ ወደ ኋላ እንዲርቁ እዘዛቸው"

ተመትቶ ሊገደል ይችላል
"ሊቆስል እና ሊገደል ይችላል"

2 Samuel 11:16

ከተማይቱ ስትከበብ
"ከበባ" የሚለው ቃል "ከበበ" እና "አጠቃ" በሚሉ ግሶች ሊገለጽ ይችላል። "የእርሱ ሰራዊት ከተማዋን ከብቦ አጠቃ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ጥቂት የዳዊት ወታደሮች ወደቁ
"ወደቁ" የሚለው ቃል የወታደሮቹ መገደል በተሻለ መንገድ የተገለጸበት ነው። "የዳዊት ወታደሮች ተገደሉ" ወይም "ከዳዊት ወታደሮች ጥቂቶችን ገደሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ) እናም ኬጢያዊው ኦርዮም በዚያ ተገደለ ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ኬጢያዊውን ኦርዮን ጨምሮ" ወይም "የከተማይቱ ሰዎች ኬጢያዊውን ኦርዮንም ገደሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 11:18

ኢዮአብ ለዳዊት ቃል/ መልዕክት ላከ
"ቃል ላከ" የሚለው ሀረግ የሆነውን ለማድረስ መልዕክት ላከ ማለት ነው። "ኢዮአብ የሆነውን ለዳዊት ለማድረስ መልዕክት ላከ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ለምን ወደ ግንቡ ... ይህን ያህል ተጠጋችሁ?
ኢዮአብ ዳዊት እነዚህን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች በመጠየቅ ይገስጸኛል ብሎ ነበር። እነዚህ ጥያቄዎች በዐረፍተ ነገር ሊጻፉ ይችላሉ። "ለመዋጋት ይህንን ያህል ወደ ከተማይቱ መቅረብ አልነበረባችሁም። በግንቡ ላይ ሆነው እንደሚመቷችሁ ማወቅ ነበረባችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ከግንቡ ሆነው እንደሚወረውሩ
ይህ የሚያመለክተው የከተማዋ ሰዎች በከተማዋ ግንብ አናት ላይ ሆነው ወደ ጠላቶቻቸው ቁልቁል ቀስታቸውን እንደሚወረውሩ ነው። "ከከተማዋ ግንብ አናት ላይ ሆነው ቀስቶቻቸውን በእናንተ ላይ እንደሚወረውሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 11:21

የሩቤ-ሼትን ልጅ አቤሜሌክን የገደለው ማን ነው?
ኢዮአብ ዳዊት እነዚህን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች በመጠየቅ ይገስጸኛል ብሎ ነበር። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። " የሩቤ-ሼት ልጅ አቤሜሌክ እንዴት እንደተገደለ አስታውስ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የሩቤ-ሼት ልጅ አቤሜሌክ
ይህ የወንድ ስም ነው። አባቱ ጌድዮን በሚባልም ስም ይታወቅ ነበር። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አንዲት ሴት በቴቤስ ከግንቡ የወፍጮ መጅ በጣለችበት ወቅት ሰውየው አልሞተምን?
ኢዮአብ ዳዊት እነዚህን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች በመጠየቅ ይገስጸኛል ብሎ ነበር። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በቴቤስ ከግንቡ አናት ላይ ሆና የወፍጮ መጅ ስትጥልበት ሰውየው እንደሞተ አስታውሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የወፍጮ መጅ
ከባድ ድንጋይ፣ እህል ለመፍጨት የሚያገለግል

ከግንቡ
"ከከተማዋ ግንብ አናት"

ቴቤስ
ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ለምን ወደ ግንቡ ይህን ያህል እጅግ ተጠጋችሁ?
ኢዮአብ ዳዊት እነዚህን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች በመጠየቅ ይገስጸኛል ብሎ ነበር። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ወደ ግንቡ ይህን ያህል እጅግ መጠጋት አልነበረባችሁም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 11:22

በሩ/መግቢያው
"የከተማው መግቢያ"

2 Samuel 11:24

አጭሩ ውርወራቸው
"አጭር የሚባለው የቀስት ውርወራቸው"

ጥቂት የንጉሱ ወታደሮች ተገደሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ጥቂቶቹን የንጉሱን አገልጋዮች ገደሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የንጉሱ አገልጋዮች
እዚህ ስፍራ "አገልጋዮች" የሚለው የሚያመለክተው ወታደሮችን አንጂ ባሮችን አይደለም፣ ምክንያቱም ወታደሮች የንጉሱ አገልጋዮች ነበሩ።

አገልጋይህ ኬጢያዊው ኦርዮን ተገድሏል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አገልጋይህን ኬጢያዊውን ኦርዮንን ገድለውታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰይፍ ይህንን ያንንም ይበላል
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚለው የሚያመለክተው በሰይፍ አንድን ሰው የሚገድልን ሰው ነው። እንደዚሁም ደግሞ፣ አንድን ሰው በሰይፍ መግደል የተገለጸው ሰይፍ ሰዎችን "እንደሚበላ" ተደርጎ ነው። "አንደኛው ሰው በሰይፍ እንደሚገደል ሌላኛውም ሊገደል ይችላል" ወይም "በጦርነት ውስጥ ማንኛውም ሰው ሊሞት ይችላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ውጊያህን ይበልጥ አጠንክረው
"ይበልጥ ጠንክረህ ተዋጋ"

2 Samuel 11:26

እጅግ አዘነች
እዚህ ስፍራ ጸሐፊው ሃዘኗ እጅግ ውስጧ እንደገባ አድርጎ ገልጽዋል። "እጅግ አዘነች" ወይም "በታላቅ ሁኔታ አዘነች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሀዘን
ከመከራ፣ ተስፋ ከመቁረጥ ወይም ከክፉ አጋጣሚ የሚመጣ የመከፋት ጥልቅ ስሜት

ዳዊት ልኮ ወደ ቤት አስመጣት
እዚህ ስፍራ "ልኮ" የሚለው ቃል እርሷን ለማግኘት እና ወደ እርሱ እንዲያመጧት መልዕክተኛ ላከ ማለት ነው። "ዳዊት ቤት እንዲያመጧት መልዕክተኛ ወደ እርሷ ላከ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

ያህዌን ደስ አላሰኘም
"ያህዌን አሳዘነ" ወይም "ያህዌን አስከፋ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 12

1 እግዚአብሔር ናታንን ወደ ዳዊት ላከው፤ እርሱም ወደ ዳዊት መጥቶ እንዲህ አለው፣ “በአንድ ከተማ ሁለት ሰዎች ነበሩ፤ ከእነርሱም አንዱ ባለጠጋ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ድኻ ነበረ። 2 ባለጠጋው እጅግ ብዙ መንጋዎችና የቀንድ ከብቶች ነበሩት፤ 3 ድኻው ግን ከገዛትን ካሳደጋት ከአንዲት መሲና በግ በስተቀር ሌላ አልነበረውም። ይህች በግ ከእርሱ ጋር ኖረች ከልጆቹም ጋር አደገች። በጊቱ እንዲያውም ከእርሱ ጋር ትበላ፣ ከጽዋውም ትጠጣ ነበር፤ በእቅፉም ትተኛ ነበር፣ ለእርሱም እንደ ሴት ልጁ ነበረች። 4 አንድ ቀን አንድ እንግዳ ወደ ባለጠጋው ቤት መጣ፤ ባለጠጋው ግን ለእንግዳው ምግብ ለማቅረብ ከራሱ መንጋ ወይም ከቀንድ ከብቶቹ አንድ እንሰሳ ለመውሰድ ፈቃደኛ አልነበረም። ከዚያ ይልቅ የድኻውን መሲና ጠቦት ወስዶ ለእንግዳው ምግብ አድርጎ አዘጋጀለት።” 5 ዳዊትም በባለጠጋው ላይ ቁጣው ነደደ፣ በንዴትም ለናታን፣ “ሕያው እግዚአብሔርን ይህን ያደረገው ሰው ሞት ይገባዋል! 6 እንዲህ ያለውን ነገር በማድረጉና ለደኻውም ባለመራራቱ ስለ በጊቱ አራት ዕጥፍ መክፈል አለበት።” 7 ከዚያ በኋላም ናታን ለዳዊት፣ “ያ ሰው አንተ ነህ፤ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንደዚህ ይላል፣ ‘በእስራኤል ላይ ንጉሥ ትሆን ዘንድ ቀባሁህ ከሳኦልም እጅ ታደግሁህ፤ 8 የጌታህን ቤት ሰጠሁህ፣ የጌታህንም ሚስቶች በብትህ አስታቀፍሁህ፤ የእስራኤልና የይሁዳን ቤት ሰጠሁህ፤ ይህም ሁሉ አንሶህ ቢሆን ብዙ ሌሎች ነገሮችንም ጨምሬ በሰጠሁህ ነበር። 9 ስለዚህ በእርሱ ፊት ክፉ የሆነውን ታደርግ ዘንድ የእግዚአብሔርን ሕግ ለምን አቃለልህ? ኬጢያዊውን ኦርዮንን በሰይፍ ገደለህ፣ ሚስቱንም ወስደህ የራስህ ሚስት አደረግኸት። ኦርዮንን በአሞናውያን ሠራዊት ሰይፍ ገደልኸው። 10 እኔን አቃለኸኛልና የኬጢያዊውንም የኦርዮንን ሚስት ሚስትህ አድርገህ ወስደሃልና ሰይፍ ከቤትህ በፍጹም አይርቅም።’ 11 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ ‘ከራስህ ቤት ጥፋት አስነሳብሃለሁ፤ ዓይንህ እያየም ሚስቶችህን ወስጄ ለጎረቤትህ እሰጠዋለሁ፣ እርሱም በቀን ብርሃን ከሚስቶችህ ጋር ይተኛል። 12 አንተ ኃጢአትህን በስውር እኔ ግን ይህንን ነገር በቀን ብርሃን በእስራኤል ሁሉ ፊት እገልጠዋለሁ።’” 13 ከዚያም ዳዊት ለናታን፣ “እግዚአብሔርን በድያለሁ” አለው። ናታንም ለዳዊት መለሰለት፣ “እግዚአብሔር ኃጢአትህን አስወግዶልሃል። አንተ አትሞትም፤ 14 ይሁን እንጂ በዚህ ድርጊትህ እግዚአብሔርን ስላቃለልህ የተወለደልህ ልጅ በእርግጥ ይሞታል።” 15 ከዚያ በኋላ ናታን ወጥቶ ወደ ቤቱ ሄደ። እግዚአብሔርም የኦርዮን ሚስት ለዳዊት የወለደችለትን ልጅ እግዚአብሔር አስጨነቀው እጅግም ታመመ። 16 ዳዊት ስለ ልጁ እግዚአብሔርን ለመነ፤ ጾመም ከዚያም ወደ ክፍሉ ገብቶ ሌሊቱን ወለሉ ላይ ተኝቶ አደረ። 17 የቤተሰቡ ሽማግሌዎችም ከወለሉ ላይ ያነሱት ዘንድ በአጠገቡ ቆሙ፣ እርሱ ግን አልተነሳም፣ ከእነርሱም ጋር አልበላም። 18 በሰባተኛውም ቀን ልጁ ሞተ። “እነሆ፣ ልጁ ገና በሕይወት ሳለ ስናነጋግረው ድምፃችንን አልሰማንም፣ ታዲያ፣ ልጁ ሞቶአል ብንለው በራሱ ላይ ምን ያደርግ ይሆን?!” ብለው ስለነበረ፣ የዳዊት አገልጋዮች ልጁ እንደ ሞተ ለመንገር ፈርተው ነበር። 19 ነገር ግን እርስ በርሳቸው ሲንሾካሾኩ ዳዊት በተመለከተ ጊዜ፣ ልጁ እንደ ሞተ ዳዊት ተገነዘበ፤ ለአገልጋዮቹም፣ “ልጁ ሞተ?” ብሎ ጠየቃቸው። እነርሱም፣ “ሞቶአል” ብለው መለሱለት። 20 ከዚያም ዳዊት ከወለሉ ላይ ተነስቶ ታጠበ፣ ቅባት ተቀባ ደግሞም ልብሱን ለወጠ፤ ወደ እግዚአብሔር ቤትም ሄዶ አምልኮ አቀረበ፣ ከዚያ በኋላም ወደ ራሱ ቤተ መንግሥት ተመለሰ። ምግብ እንዲያቀርቡለት በጠየቀ ጊዜ አቀረቡለት፣ እርሱም በላ። 21 ከዚያ በኋላ አገልጋዮቹ፣ “እንደዚህ ያደረግኸው ለምንድን ነው? ልጁ በሕይወት እያለ ጾምህ አለቀስህም፤ ልጁ ከሞተ በኋላ ግን ተነሥተህ በላህ” አሉት። 22 ዳዊትም፣ “ልጁ ገና በሕይወት ሳለ ጾምሁ አለቀስሁም፤ ‘ልጁ በሕይወት ይኖር ዘንድ እግዚአብሔር ቸርነት ያደርግልኝ እንደሆነ ማን ያውቃል’ ብዬ ነበር። 23 አሁን ግን፣ እርሱ ሞቶአልና ለምን እጾማለሁ? መልሼ ላመጣው እችላለሁን? እኔ ወደ እርሱ እሄዳለሁ እንጂ እርሱ ወደ እኔ አይመለስም።” 24 ከዚያም ዳዊት ሚስቱን ቤርሳቤህን አጽናናት፤ ወደ እርሷም ገብቶ አብሮአት ተኛ። ከዚህም የተነሣ ወንድ ልጅ ወለደች፣ ልጁም ሰሎሞን የሚል ስም ተሰጠው፤ እግዚአብሔርም ወደደው። 25 ስለሆነም እግዚአብሔር ስለወደደው ይዲድያ ተብሎ እንዲጠራ በነቢዩ በናታን በኩል ቃል ላከ። 26 በዚያን ጊዜም ኢዮአብ የአሞናውያን የንጉሥ ከተማ የነበረችውን ረባትን ወግቶ ምሽጉን ያዘ። 27 ስለሆነም ኢዮአብ ወደ ዳዊት መልእክተኞችን በመላክ እንዲህ አለው፣ “ረባትን ወግቼ የከተማይቱን የውሃ ማከፋፈያ ይዤአለሁ። 28 እንግዲህ አሁን፣ የቀረውን ሠራዊት አሰባስበህ በከተማይቱ ዙሪያ ሠፍረህ ያዛት፤ ምክንያቱም እኔ ከተማይቱን ከያዝኳት በስሜ መጠራቷ ነው።” 29 ስለዚህ ዳዊት መላውን ሠራዊት አሰባስቦ ወደ ረባት ሄዶ ከተማይቱን ወግቶ ያዛት። 30 ዳዊት ከሞሎክ ራስ ላይ ዘውዱን ወሰደ፤ የዘውዱም ክብደት አንድ መክሊት ወርቅ ሲሆን የከበረ ዕንቁም በላዩ ላይ ነበረበት። ዘውዱም በዳዊት ራስ ላይ ተጫነ። ከዚያም እጅግ ብዙ የከተማይቱን ምርኮ አመጣ። 31 በከተማይቱ የነበሩትንም ሰዎች አውጥቶ በመጋዝ፣ በብረት መቆፈሪያና በመጥረቢያ እንዲሠሩ አስገደዳቸው፤ የሸክላ ጡብም እንዲሠሩ አደረጋቸው። ዳዊት የአሞን ሕዝብ ከተሞች ሁሉ ይህንኑ ተግባር እንዲፈጽሙ አደረጋቸው። ከዚያም ዳዊትና ሠራዊቱ በሙሉ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ።

---

2 Samuel 12:1

ሴት የበግ ጠቦት
ሴት ጠቦት በግ

ለእርሱ እንደ ሴት ልጁ ነበረች
ይህ የዚህን ሰው እና የግልገሉን ቅርበት ያመለክታል። "ከሴት ልጆቹ አንዲቱን የሆነች ያህል ጠቦቷን ይወዳት ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 12:4

ሴት የበግ ጠቦት
ግልገል፣ ሴት በግ

ለእንግዳው
ለእንግዳው ይበላ ዘንድ ሊያቀርብለት። "ለእንገዳው እንዲመገብ ሊያቀርብለት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ዳዊት በቁጣ ነድዶ ተነሳ
እዚህ ስፍራ ጸሐፊው ዳዊት እንዴት በጣም እንደተቆጣ የሚገልጸው ከቁጣው የተነሳ አካሉ እንደ ጋለ አድርጎ ነው። "ዳዊት በቁጣ ነደደ" ወይም "ዳዊት በጣም ተናደደ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በናታን ተቆጣ
ይህ ማለት ዳዊት ናታንን በቁጣ ተናገረው

በያህዌ ህያውነት እምላለሁ
ይህ የሚገልጸው መሃላ መማሉን ወይም በጽኑ ቃል መግባቱን ነው። "በያህዌ ህያውነት እናገራለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ሰው ይሙት
ይህ ማለት ይገደል ማለት ነው። እንደዚሁም፣ ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሊገደል" ወይም "ሊሞት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ) የሚለውን ይመልከቱ)

የወሰደዳትን ግልገል አራት እጥፍ አድርጎ መመለስ ይገባዋል
ሃብታሙ ሰው ለድሃው እንዲመልስ የሚጠበቅበት መጠን ትንሽዋ ጠቦት ከምታወጣው አራት እጥፍ እንዲሆን ነበር። "ለድሃው የጠቦቷን ዋጋ አራት እጥፍ ሊመልስለት ይገባል" (ቁጥሮች እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ማዘን
ለተጎዳ ወይም ላልተወደደ ሰው አዘኔታና ፍቅር ማሳየት።

2 Samuel 12:7

ከሳኦል እጅ ያዳነኝ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚያመለክተው መቆጣጠርን ነው። "ከሳኦል ቁጥጥር" ወይም "ከሳኦል ሀይል" በሚለው ወስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የጌታህን ሚስቶች በክንዶችህ
እዚህ ስፍራ ያህዌ ዳዊት የጌታውን ሚስቶች እንደ ራሱ ሚስቶች ማግኘቱን የገለጸው፣ "በእርሱ ክንዶች ውስጥ" መሆናቸውን በመናገር ነው። "የጌታህን ሚስቶች እንደ ራስህ ሚስቶች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤልን እና የይሁዳ ቤትን ጭምር ሰጥቼሃለሁ
እዚህ ስፍራ የያህዌ ዳዊትን እንዴት በእስራኤል እና ይሁዳ ላይ ንጉስ አድርጎ የእርሱን ስልጣን እንደሰጠው የተናገረው የእስራኤልን እና የይሁዳን ቤት እንደ ስጦታ አድርጎ እንደሰጠው በመግለጽ ነው። "የ...ቤት" የሚለው ሀረግ "የ... ሰዎች" ማለት ነው። "በእስራኤል እና ይሁዳ ሰዎች ላይ ንጉስ አድርጌ ስልጣን ሰጥቼሃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ በጣም ትንሽ ቢሆን እንኳን
"በቂ ሰጥቼህ ባይሆን እንኳን"

2 Samuel 12:9

በእርሱ ዐይኖች ፊት ክፉ የሆነውን ለማድረግ... ለምን የያህዌን ነገር አቃለልህ?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የዋለው ዳዊትን ለመገሰጽ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የያህዌን ነገር ማቃለል አልነበረብህም... በእርሱ ዐይኖች ፊት ክፉ የሆነውን ማድረግ አልነበረብህም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ ዐይኖች ፊት ክፉ የሆነውን
እዚህ ስፍራ "እይታ/በዐይኖቹ ፊት" የሚለው የሚያመለክተው የያህዌን ፈቃድ ነው። "እርሱ ክፉ የሚለው" ወይም "በያህዌ ዐይኖች ክፉ የሆነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኬጢያዊውን ኦርዮን በሰይፍ መታኸው
ዳዊት ራሱ ኦርዮን አልገደለም፣ ይልቁንም በጦርነት ውስጥ እንዲሞት ሁኔታዎችን አበጀ። "በሰይፍ" የሚለው ሀረግ የሚገልጸው ኦርዮ በጦርነቱ ወቅት እንዴት እንደ ሞተ ነው። "ኬጢያዊው ኦርዮ በጦርነቱ ውስጥ እንዲሞት ሁኔታውን አበጀህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በአሞን ሰራዊት ሰይፍ ገደልከው
ዳዊት ራሱ ኦርዮን አልገደለም፤ ይልቁንም፣ እስራኤል ከአሞን ጋር ሲዋጋ በጦርነት ውስጥ ኦርዮ እንዲሞት ሁኔታዎችን አበጀ። "በሰይፍ" የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው በጦርነቱ ወስጥ እንዴት እንደ ሞተ ነው። "ከአሞን ሰራዊት ጋር ሲዋጋ በጦርነቱ ውስጥ እርሱ እንዲሞት አደራጀህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሰይፍ ከቤትህ አይጠፋም
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው በጦርነት የሚሞቱ ሰዎችን ነው። እንደዚሁም የዳዊት "ቤት" የሚለው የሚያመለክተው የእርሱን ትውልዶች ነው። "ከትውልድህ ጥቂቶቹ ሁሌም በጦርነት ይሞታሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 12:11

ከራስህ ቤት ውስጥ
እዚህ ስፍራ የዳዊት "ቤት" የሚለው የሚያመለክተው ቤተሰቡን ነው። "ከራስህ ቤተሰብ መካከል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በገዛ ዐይኖችህ ፊት
እዚህ ስፍራ ዳዊት የተጠቀሰው በዐይኖቹ በሚለው ሲሆን ይህም የሚሆነውን እርሱ እንደሚያይ አጉልቶ ለማሳየት ነው። "አንተ እያየህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በቀን ብርሃን
"በእኩለ ቀን ብርሃን።" አንድን ነገር "በግልጽ" የማድረግ ሃሳብ ወይም ሰዎች የሚደረገውን ነገር በግልጽ እያወቁ ማድረግ ብዙውን ጊዜ "በቀን ብርሃን" ማድረግ በሚል ይነገራል። "በገሃድ" ወይም "የሚሆነውን ሁሉም ይመለከታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኃጢአት ፈጸምክ
"በደልክ"

በእስራኤል ሁሉ ፊት
ይህ ሀረግ የሚናገረው የእስራኤል ሰዎች በሚስቶቹ ላይ የሆነውን እያወቁ በእርግጥ ሲሆን እንዳዩ አድርገው እንደመሰከሩ ተደርጎ ነው። "በመላው የእስራኤል ሰዎች ፊት" ወይም "መላው የእስራኤል ሰዎች ስለዚህ ነገር ያውቃሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ትቶልሃል/ምሮሃል
ያህዌ የዳዊትን ኃጢአት ይቅር ብሏል። ይህ እዚህ ስፍራ የተነገረው ያህዌ ኃጢአቱን ይቅር ያለው ተራምዶት እንዳለፈው አንድ ነገር እና እንደተወለት ተደርጎ ነው። "ይቅር የተባለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ አትሞትም/አትገደልም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። አንዳንዴ ሰዎች በኃጢአታቸው ምክንያት ይሞታሉ፣ ነገር ግን እርሱ ከሴትየዋ ጋር በፈጸመው ኃጢአት አይሞትም። ይህ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "አትሞትም" ወይም "በዚህ ኃጢአት ምክንያት አትሞትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Samuel 12:14

ንቆሃል
እጅግ አንድን ሰው ወይም አንድን ነገር አለመውድ ወይም መጥላት

ለአንተ የሚወለደው ልጅ
"ለአንተ የሚወለደው" የሚለው ሀረግ የዳዊት ህጻን ልጅ ማለት ነው። "የሚወለደው የአንተ ልጅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ ያንን ልጅ ቀጣው... እናም ታመመ
እዚህ ስፍራ ጸሐፊው ያህዌ ህጻኑ እንዲታመመ ማድረጉን ያህዌ ህጻኑን እንደ ቀጣው ይናገራል። "ያህዌ ህጻኑን ቀጣው... እናም ህጻኑ በጣም ታመመ" ወይም "ያህዌ ህጻኑ ... በጣም እንዲታመመ አደረገ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የኦርዮ ሚስት ለዳዊት የወለደችው ልጅ
ይህ ማለት እርሷ ለዳዊት ስለ ወለደችለት ዳዊት የህጻኑ አባት ነበር። "የኦርዮ ሚስት የወለደችለት፣ የዳዊት ልጅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 12:16

ተማጸነ/ለመነ
መለመን ወይም በታከላቅ መሻት መጸለይ

ውስጥ ገባ
ዳዊት ብቻውን ወደ ክፍሉ ገባ። "ወደ ክፍሉ ውስጥ ገባ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱን ከመሬት ለማንሳት
"ከመሬት እንዲነሳ ለመኑት"

እንዲህም ሆነ
"እንዲህ ሆነ"

የእኛን ድምጽ/ንግግር አልሰማም
ይናገሩ እንደነበር ትኩረት ለመስጠት፣ አገልጋዮች እዚህ የተጠቀሱት በድምጻቸው ነው። "እርሱ እኛን አልሰማንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰነክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰባተኛው ቀን
"7ተኛው ቀን።" ይህ የሚያመለክተው ህጻኑ ከተወለደ ከሰባት ቀናት በኋላ ነው። "ከተወለደ ከሰባተኛ ቀን በኋላ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ተመልከት
ይህ የሚያገለግለው የሰዎችን ትኩረት ለመሳብ ነው። "ስማ/አድምጥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ልጁ መሞቱን ብንነግረው በራሱ ላይ ምን ያደርግ ይሆን?
አገልጋዮቹ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የጠየቁት ፍራቻቸውን ለመግለጽ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ልጁ መሞቱን ብንነግረው ራሱን ይጎዳል ብለን ፈርተናል!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 12:19

እርስ በእርሳቸው ያንሾካሽኩ ነበር
"በጣም በጸጥታ እርስ በእርሳቸው ይነጋገሩ ነበር"

ዳዊት ተረዳ/አወቀ
"ዳዊት ገባው"

ዳዊት ተነሳ
"ዳዊት ብድግ አለ"

2 Samuel 12:21

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ ሀረግ፣ ዳዊት ያህዌ ይህ እንዲሆን መፍቀዱን መገንዘቡን አጉልቶ የሚያሳይ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የያዘ ነው።

ህጻኑ በህይወት እንዲኖር ያህዌ ደግነቱን ያሳየኝ ይፈቅድ እንደሆነ ማን ያውቃል?
ዳዊት ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የጠየቀው ያህዌ ህጻኑ በህይወት እንዲኖር ይፈቅድ እንደሆነ ማንም አለማወቁን ለማጉላት ነው። ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ያህዌ ምህረት አድርጎልኝ ህጻኑ በህይወት እንዲኖር ይፍቀድ አይፍቀድ ማንም አያውቅም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን አሁን እርሱ ሞቷል፣ ስለዚህ ስለምን እጾማለሁ?
ዳዊት ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የጠየቀው ከዚህ በኋላ የሚጾምበት ምክንያት እንደሌለ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አሁን እርሱ ሞቷል ከእንግዲህ መጾም ምንም ጥቅም የለውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ገና ልመልሰው እችላለሁን?
ዳዊት ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የጠየቀው ልጁ ዳግም ወደ ህይወት ሊመለስ አለመቻሉን ትኩረት ለመስጠት ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ወደ ህያውነት ልመልሰው አልችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እርሱ እሄዳለሁ
ዳዊት ሲሞት ልጁ ወዳለበት እንደሚሄድ ይጠቁማል። "ስሞት እርሱ ወዳለበት እሄዳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 12:24

ወደ እርሷ ሄደ፣ እናም ከእርሷ ጋር ተኛ
"ወደ እርሷ ሄደ" የሚለው ሀረግ ዳዊት ከእርሱ ሚስት ጋር ግንኙነት ማድረጉን በግልጽ የሚያሳይ ነው። እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው አብረው መተኛታቸውን ለማጉላት አገልግለዋል። "ከእርሷ ጋር ተኛ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በነቢዩ ናታን በኩል ቃል ላከ
እዚህ ስፍራ "ቃል" የሚለው የሚያመለክተው ያህዌ ናታን ለዳዊት እንዲነግረው የነገረውን/የላከውን መልዕክት ነው። "እንዲነግረው ናታንን ላከው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ይዲድያ
ይህ የዳዊት ልጅ የሰሎሞን ሌላው ስም ነው። ይህም ያህዌ ለእርሱ የመረጠለት ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Samuel 12:26

ኢዮአብ ተዋጋ.. እርሱ ያዘ
እዚህ ስፍራ ጸሐፊው "ኢዮአብ" ይላል፤ ነገር ግን እርሱ የሚያመለክተው ኢዮአብን እና አብረውት የሚዋጉትን ወታደሮቹን ነው። "ኢዮአብ እና የእርሱ ወታደሮች ተዋጉ...እነርሱ ያዙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ረባት
ከዚህች ከተማ ጋር መዋጋት በቀጥታ/ቃል በቃል ከረባት ሰዎች ጋር መዋጋት ማለት ነው። በ2 ሳሙኤል 11:1 ውስጥ በተተረጎመው ተመሳሳይ መልክ ይህ ስም በተመሳሳይ ይተርጎም። "የረባት ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህም ኢዮአብ ወደ ዳዊት መልዕክተኞችን ልኮ እንዲህ አለ
"ስለዚህ ኢዮአብ ወደ ዳዊት እንዲህ ለማለት መልዕክተኞችን ላከ"

የከተማይቱን የውሃ ጣብያ/ማቀረቢያ ስፍራ ያዝ
አንድን ቦታ "መውሰድ" ወይም ምልክት ማድረግ ማለት ቦታውን መቆጠጣጠር ማለት ነው። "የከተማይቱን ውሃ ማቅረቢያ ስፍራ በቁጥጥር ስር ማድረግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ተዋጋሁ... እኔ ወሰድኩ... እኔ ብወስድ
እዚህ ስፍራ ኢዮአብ በእርግጥ ስለ ራሱ እና ስለ ወታደሮቹ ሲያመለክት ስለ ራሱ ይናገራል። "እኔ እና ወታደሮቼ ተዋጋን... ወታደሮቼ እና እኔ ያዝን...እኔ እና ወታደሮቼ ብንይዝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በተቃራኒ መስፈር
ይህ ማለት መክበብ እና ማጥቃት ማለት ነው። "በጦር ሀይል መክበብ" ወይም "ከብቦ መያዝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ውሰዳት...ከተማይቱን ውሰድ
አንድን ቦታ "መውሰድ" ወይም ምልክት ማድረግ ማለት ቦታውን መቆጠጣጠር ማለት ነው። "እርሷን ተቆጣጠራት...ከተማይቱን ተቆጣጠራት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ስም ይሰጣታል/ትሰየማለች
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች ይሰይሟታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 12:29

ተዋጋ
እዚህ ስፍራ ጸሐፊው በእርግጥ ስለ ዳዊት እና ወታደሮቹ እየተናገረ ሳለ ስለ ዳዊት ይናገራል። "ዳዊት እና ወታደሮቹ ተዋጉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ታላንት
ይህ በዘመናዊ የክብደት መለኪያ ሊጻፍ ይችላል። "ወደ 33 ኪ.ግ የሚጠጋ" በሚለው ውስጥ። (መጽሐፍ ቅዱሳዊ የክብደት መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

የከበረ ድንጋይ
እንደ እንቁ፣ ሩቢ፣ ሰንፔር፣ መረገድ፣ ወይም ኦፔል የመሰሉ በጥቂቱ የሚገኙ የከበሩ ድንጋዮች

ዘውዱ በዳዊት ራስ ላይ ተጫነ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ዘውዱን በዳዊት ራስ ላይ ጫኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ አባረራቸው/አስወጣቸው
እዚህ ስፍራ ጸሐፊው በእርግጥ የዳዊትን ወታደሮች እያመለከተ ሳለ ስለ ዳዊት ይናገራል። "እነርሱ አባረሯቸው/አስወጧቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ዝርፊያ
ከተሸነፈ ጠላት ውድ ነገሮችን መውሰድ

በብዙ ቁጥር
"በብዙ መጠን"

2 Samuel 12:31

ህዝቡን አስወጣ
ዳዊት ህዝቡን ራሱ አላስወጣም: እንዲያስወጧቸው ወታደሮቹን አዝዟል። "ዳዊት ህዝቡን እንዲያስወጡ ወታደሮቹን አዘዘ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

መጋዞች፣ የብረት መቆፈሪያ/ዶማ፣ እና መጥረቢያዎች
እነዚህ እንጨት መቁረጫ ወይም መሬት መቆፈሪያ መሳሪያዎች ናቸው

የጡብ ማቃጠያ
ጡቦች የሚደርቁበት እን የሚጠነክሩበት/የሚቃጠሉበት ምድጃ

የአሞን ሰዎች ሁሉም ከተሞች
ይህ የሚያመለክተው በከተሞቹ ውስጥ የሚኖሩትን ሰዎች ነው። "የአሞን ከተሞች ነዋሪዎች በሙሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 13

1 ከዚህ በኋላ የዳዊት ልጅ አምኖን የዳዊት ሌላ ልጅ የአቤሴሎም ሙሉ እኅት በነበረችው በውቧ ግማሽ እህቱ በትዕማር እጅግ ተማረከ። 2 በእኅቱ በትዕማር
ምክንያት እስኪታመም ድረስ አምኖን እጅግ ተጨነቀ። ድንግል ስለነበረች በእርሷ ላይ ምንም ነገር ማድረግ ለአምኖን የማይቻል መሰለው። 3 አምኖን ግን
የዳዊት ወንድም የሳምዕ ልጅ ኢዮናዳብ የተባለ ወዳጅ ነበረው። ኢዮናዳብ እጅግ ተንኮለኛ ሰው ነበር። 4 ኢዮናዳብም ለአምኖን፣ “የንጉሥ ልጅ ሆይ፣ በየጥዋቱ
ጭንቀት የሚሰማህ ለምንድን ነው? አትነግረኝምን?” ብሎ ጠየቀው። አምኖንም፣ “የወንድሜን የአቤሴሎምን እህት ትዕማርን አፍቅሬ ነው” ብሎ መለሰለት።
5 በዚህን ጊዜ ኢዮናዳብ፣ “የታመምህ መስለህ አልጋህ ላይ ተኛ፣ አባትህ ሊጠይቅህ ሲመጣም፣ ‘እህቴ ትዕማር የምበላውን ምግብ ታቀርብልኝ ዘንድ እባክህ
ላክልኝ፤ ምግቡንም ዓይኔ እያየ ከእጇ እንድጎርስ እዚሁ መጥታ ታዘጋጅልኝ’ ብለህ ጠይቀው።” 6 ስለዚህ አምኖን የታመመ ሰው መስሎ ተኛ፤ ንጉሡም
ሊጠይቀው በመጣ ጊዜ አምኖን ለንጉሡ፣ “ለሕመሜ የሚሆን ጥቂት ምግብ በፊቴ እንድታዘጋጅልኝና ከእጇም እንድበላ እባክህ እህቴን ትዕማርን ላክልኝ”
ብሎ ጠየቀው። 7 ከዚያም ዳዊት፣ “አሁን ሂጂና ለወንድምሽ ለአምኖን ምግብ አዘጋጂለት” በማለት በቤተ መንግሥቱ ወደ ነበረችው ትዕማር መልእክት
ላከባት። 8 ስለዚህም ትዕማር ወንድሟ አምኖን ወደተኛበት ቤት ሄደች፤ ጥቂት ሊጥ ወስዳ ካቦካችው በኋላ ቂጣ አደረገችው፣ ጋገረችውም። 9 ከዚያም
መጋገሪያውን አውጥታ ቂጣውን አቀረበችለት፣ እርሱ ግን መብላት አልፈለገም። ስለዚህ አምኖን በዘያ ለነበሩት ለሌሎቹ፣ “ማንኛውንም ሰው ከዚህ ከእኔ ዘንድ
አስወጡልኝ” አላቸው፤ ስለዚህ ሰው ሁሉ ከእርሱ ዘንድ ወጣ። 10 ከዚያም አምኖን ትዕማርን፣ “ምግቡን ከእጅሽ እበላ ዘንድ ወደዚህ ወደ ክፍሌ አምጭልኝ”
አላት። 11 ምግቡን ባመጣችለት ጊዜ አምኖን እጇን ያዛትና፣ “እህቴ ሆይ፣ ነይ ከእኔ ጋር ተኚ” አላት። 12 እርሷም፣ “አይሆንም፣ ወንድሜ ሆይ፣ አታስገድደኝ፤
ይህን የመሰለ ነገር በእስራኤል ሊደረግ አይገባውምና። ይህን አሳፋሪ ነገር አታድርግ። 13 ይሄ ነገር ከሚያስከትልብኝ ዕፍረት ለማምለጥስ ወዴት መሄድ
እችላለሁ? ይህም ድርጊት አንተን በመላው እስራኤል ኀፍረተ-ቢስ ጅል አድርጎ ያስቆጥርሃል። እባክህ፣ ለንጉሡ እንድትነግረው እጠይቅህሃለሁ፤ እንድታገባኝ
ይፈቅድልሃል።” 14 ይሁን እንጂ አምኖን አልሰማትም። ከትዕማር ይልቅ ብርቱ ስለ ነበረ ይዟት ከእርሷ ጋር ተኛ። 15 ከዚያም አምኖን ትዕማርን ከመጠን በላይ
ጠላት፤ አፍቅሯት ከነበረውም ይልቅ ጠላት። አምኖንም፣ “ተነሺ፣ ውጭልኝ” አላት። 16 እርሷ ግን፣ “አይሆንም፣ ምክንያቱም እኔን በማስወጣት የምታደርገው
ይህ ክፉ ነገር ቀድመህ ካደረግኸው ይልቅ የከፋ ነው።” አምኖን ግን እርሷን አልሰማትም። 17 ከዚያ ይልቅ የግል አገልጋዩን ጠርቶ፣ “ይህችን ሴት ከእኔ ዘንድ
አስወጥተህ፣ በሩን ቀርቅረው” አለው። 18 ከዚህ በኋላ አገልጋዩ አስወጣትና በሩን ከበስተኋላዋ ቀረቀረባት። ድንግል የሆኑት የንጉሡ ሴት ልጆች እንደዚያ
ይለብሱ ነበርና፣ ትዕማር በጣም ያጌጠ ቀሚስ ለብሳ ነበር። 19 ትዕማር በራሷ ላይ ማቅ ነሰነሰች፣ ቀሚሷንም ቀደደች። እጇንም በራሷ ላይ አድርጋ ሄደች፣
በምትሄድበትም ወቅት ድምፅዋን ከፍ አድርጋ አለቀሰች። 20 ወንድሟ አቤሴሎምም፣ “ወንድምሽ አምኖን ካንቺ ጋር ነበርን? ሆኖም፣ እህቴ ሆይ፣ አሁን ዝም
በይ። ወንድምሽ ስለሆነ ነገሩን በልብሽ አትያዢው።” ስለሆነም ትዕማር በወንድሟ በአቤሴሎም ቤት ብቸኛ ሆና ኖረች። 21 ነገር ግን ንጉሥ ዳዊት ይህንን ሁሉ
በሰማ ጊዜ እጅግ ተቆጣ፤ 22 አቤሴሎም ለአምኖን ምንም አልተናገረውም፤ ስላደረገባት ነገር እህቱንም ትዕማርን ስላስነወራት ጠልቶት ነበርና። 23 ከሁለት
ሙሉ ዓመት በኋላ አቤሴሎም በጎቹን በኤፍሬም አጠገብ በነበረው በቤላሶር ከተማ በጎችን የሚሸልቱ ሰዎች አስመጥቶ ነበር፤ አቤሴሎምም የንጉሡን ልጆች
ወደዚያ ስፍራ ጋበዛቸው። 24 አቤሴሎም ወደ ንጉሡ ሄዶ፣ “እነሆ፣ ባሪያህ በጎችን የሚሸልቱ አስመጥቷል፣ንጉሡና አገልጋዮቹ እባክህን ከባሪያህ ጋር ይምጡ”
አለው። 25 ንጉሡም ለአቤሴሎም፣ “ልጄ ሆይ፣ ሁላችንም መሄድ የለብንም፤ ሸክም እንሆንብሃለን” ብሎ መለሰለት። አቤሴሎም ንጉሡን አደፋፈረው፣ እርሱ
ግን መሄድ ባይፈልግም አቤሴሎምን ባረከው። 26 ከዚህ በኋላ አቤሴሎም፣ “ይሄ ካልሆነ፣ እባክህ ወንድሜ አምኖን ከእኛ ጋር ይሂድ” አለው። ስለዚህ ንጉሡ
አቤሴሎምን፣ “አምኖን አብሮአችሁ የሚሄደው ለምንድን ነው?” ብሎ ጠየቀው። 27 አቤሴሎም አጥብቆ ስለለመነው፣ አምኖንና የንጉሡ ልጆች አብረውት
እንዲሄዱ ፈቀደ። 28 አቤሴሎም አገልጋዮቹን፣ “ልብ ብላችሁ አድምጡ፣ አምኖን ወይን ጠጅ ጠጥቶ መስከር ሲጀምርና እኔ ‘አምኖንን ምቱት’ ስላችሁ፣ በዚያን
ጊዜ ግደሉት፤ አትፍሩ። ያዘዝኋችሁ እኔ ነኝና በርቱ፣ ጠንክሩ።” ብሎ አዘዛቸው። 29 ስለዚህ የአቤሴሎም አገልጋዮች እንዳዘዛቸው በአምኖን ላይ አደረጉበት።
ከዚያ በኋላም የንጉሡ ልጆች በየበቅሎአቸው ላይ ተቀምጠው ሸሹ። 30 እነርሱም እየሄዱ በመንገድ ላይ ሳሉ፣ “አቤሴሎም የንጉሡን ልጆች ሁሉ ገደለ፣
አንድም የተረፈ የለም” የሚል ዜና ለዳዊት ደረሰው። 31 ከዚያ በኋላ ንጉሡ ተነሥቶ ልብሱን ቀደደ፣ በወለሉም ላይ ተጋደመ፣ አገልጋዮቹም ልብሳቸውን ቀደው
በአጠገቡ ቆሙ። 32 የዳዊት ወንድም የሳምዓ ልጅ ኢዮናዳብ ግን፣ “የሞተው አምኖን ብቻ ነውና የንጉሡ ልጆች የሆኑትን ጎልማሶች ሁሉ ገድለዋቸዋል ብሎ
ጌታዬ አይመን። አምኖን እህቱን ትዕማርን ከደፈራት ቀን አንስቶ አቤሴሎም ይህንን ሲያቅድ ነበር፤ 33 ስለሆነም የሞተው አምኖን ብቻ ነውና፣ የንጉሡ ልጆች
ሁሉ ሞተዋል ብሎ እስከሚያምን ድረስ ጌታዬ ንጉሡ የሚለውን ዜና ወደ ልቡ አያስገባው።” 34 አቤሴሎም ሸሸ። ለጥበቃ የቆመውም አገልጋይ ቀና ብሎ
ሲመለከት ከእርሱ በስተምዕራብ ካለው ኮረብታ ጥግ ባለው መንገድ ብዙ ሰዎች ሲመጡ አየ። 35 በዚያን ጊዜ ኢዮናዳብ ለንጉሡ፣ “እነሆ፣ የንጉሡ ልጆች
እየመጡ ነው፤ ልክ ባሪያህ እንዳለው ነው።” 36 ስለሆነም ተናግሮ እንደጨረሰ፣ የንጉሡ ልጆች ደረሱ፣ ድምፃቸውንም ከፍ አድርገው አለቀሱ። ንጉሡና
አገልጋዮቹም ሁሉ አምርረው አለቀሱ። 37 አቤሴሎም ኮብልሎ የጌሹር ንጉሥ ወደ ሆነው ወደ ዓሚሁድ ልጅ ወደ ተልማይ ሄደ። ዳዊትም ስለ ሞተው ልጁ
ዘወትር ያለቅስ ነበር። 38 አቤሴሎም ለሶስት ዓመታት ወደ ቆየበት ወደ ጌሹር ሸሽቶ ሄደ። 39 በልጁ በአምኖን ሞት ከደረሰበት ሐዘን ተጽናንቶ ስለነበረ ንጉሥ
ዳዊት በሃሳቡ ወደ አቤሴሎም የመሄድ ናፍቆት አደረበት።

---

2 Samuel 13:1

ከዚህም በኋላ እንዲህ ሆነ
"ከዚህ በኋላ እንዲህ ሆነ።" ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ፍሰት አዲስ ትዕይንትን ለማስተዋወቅ ነው። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

ግማሽ እህት/በአባት ወይም በእናት ብቻ የሚገኙ
አምኖን እና ትዕማር አባታቸው አንድ ሲሆን በእናት ይለያያሉ

ሙሉ እህት/በአባትና በእናት የሚገናኙ
አቤሴሎም እና ትዕማር በአባትም በእናትም ይገናኛሉ

አምኖን በእህቱ በትዕማር ምክንያት እስኪታመም ድረስ እጅግ ተረብሾ ነበር
አምኖን የተረበሸው ከእህቱ ከትዕማር ጋር ለመተኛት ፍላጎት ስለነበረው ነው። "አምኖን ለእህቱ ትዕማር በነበረው ፍላጎት ህመም እስኪሰማው ድረስ እጅግ ተረብሾ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Samuel 13:3

የሳምዓ ልጅ ኢዮናዳብ፣ የዳዊት ወንድም
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። ሳምዓ ልጅ የዳዊት ወንድም ነበር (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ብልጥ/ነገረኛ
አታላይ ወይም አስመሳይ

ድባቴ/መጫጫን
ደስታ የማጣት ከፍተኛ ስሜት

አትነግረኝምን?
ስለ ድባቴው እየጠየቀው መሆኑ ግልጽ ነው፤ ይህ በገልጽ ሊጻፍ ይችላል። አንደዚሁም፣ ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ አምኖን ለምን እንደ ተደበተ ከኢዮናዳብ የቀረበለት ጥያቄ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ለምን እንደ ተደበትክ አትነግረኝምን?" ወይም "እባክህ፣ ለምን እንደ ተደበትክ ንገረኝ" በሚል ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

2 Samuel 13:5

ኢዮናዳብ
በ2 ሳሙኤል 13:3 ላይ ይህ ስም እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ከእርሷ እጅ በላ... ከእርሷ እጅ እበላ/እጎርስ ዘንድ
ይህ እርሷ በግል ምግብ እንድታዘጋጅለት የቀረበ ጥያቄ ነው። "ራስዋ ይህን እኔን ታገልግለኝ... መብላት እንድችል እርሷ ታቅርብልኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የታመመ መሰለ
ይህ ማለት የታመመ ለመምሰል ሀሰተኛ ገጽታ አሳየ

ለህመሜ ከእኔ ፊቴ ለፊት
ታሟልና ጉዳዩ ከምግቡ አይደለም፣ ነገር ግን ይልቁንም ያስፈለገው እንክብካቤው ነው። "ከእኔ ፊቴ ለፊት" የሚለው ሀረግ በእርሱ ፊት ምግቡን እንድታዘጋጅለት ለትዕማር የቀረበ ጥያቄ ነው። "ታምሜያለሁና ከእኔ ፊት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 13:7

ዳዊት ቃለ ላከ
ይህ ማለት ከትዕማር ጋር ለመነጋገር መልዕክተኛ ላከ። "ዳዊት መልዕክተኛ ላከ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሊጥ
ለመጋጋር የሚውል የዱቄት እና ፈሳሽ ድብለቅ

አቦካች
ሊጡን ለማደባለቅ እጇችዋን ተጠቀመች

እርሱ እያየ
ይህ ማለት ትዕማር ዳቦውን በፊቱ አዘጋጀች። "በእርሱ ፊት" ወይም "እርሱ ባለበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህም ሁሉም እርሱ ካለበት ወደ ውጭ ወጡ
"አንድ ሰው ከሚገኝበት መውጣት" ማለት እነርሱን ለብቻቸው መተው ማለት ነው። "ስለዚህ ሁሉም እርሱን ትቶ ወጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 13:10

ከእጅሽ እበላ/እጎርስ ዘንድ
ይህ ለእርሱ ምግቡን ታቀርብለት ዘንድ ለትዕማር የቀረበ ጥያቄ ነው። "ለእኔም ምግቡን እንድታቀርቢልኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አታስገድደኝ
ከእርሱ ጋር ስለ መተኛት ያለውን ሁኔታ እየተናገረች ነው። "ከአንተ ጋር እንድተኛ አታስገድደኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

አስፈሪ
በጣም አሳፋሪ

2 Samuel 13:13

አጠቃላይ መረጃ:
ትዕማር ከአምኖን ጋር መነጋገሯን ቀጠለች

እኔስ እፍረቴን እንዴት ማስወገድ እችላለሁ?
ትዕማር ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የምትጠይቀው ከወንድሟ ጋር ብትተኛ ምን ያህል እንደሚያሳፍራት ትኩረት ለመስጠት ነው። ትዕማር እፍረቷን ማስወገድን የምትገልጸው ልታመልጠው የምትፈልገው ጠላት ወይም ስቃይ አድራሽ እንደሆነ አድርጋ ነው። "ይህን ብታደርግ፣ በሄድኩበት ሁሉ ነውር ተሸካሚ እሆናለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 13:15

እኔን በማስውጣት የምታደርገው ታላቅ ክፋት የከፋ ይሆናል
"ይህ ታላቅ ክፋት" የሚለው ረቂቅ ስም፣ ግስ ሆኖ ሊጻፍ ይችላል። "እኔን ማስወጣትህ በጣም ክፉ ይሆናል! ይህ እንዲያውም የከፋ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ከኋላዋ በሩን ቀረቀረባት
ይህ ማለት ተመልሳ እንዳትገባ በሩን በላይዋ መዝጋት ማለት ነው። "ተመልሳ እንዳትገባ በሩን ዘጋባት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 13:18

ከኋላዋ በሩን ቀረቀረባት
ይህ ማለት ተመልሳ እንዳትገባ በሩን በላይዋ መዝጋት ማለት ነው። "ተመልሳ እንዳትገባ በሩን ዘጋባት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በራሷ ላይ አመድ ነሰነሰች ቀሚሷንም ደግሞ ቀደደች። እጆቿን በራሷ ላይ ጫነች
እነዚህ በእስራኤል ባህል የለቅሶ እና የሀዘን ድርጊቶች ናቸው። "በጣም ማዘኗን ለማሳየት በራሷ ላይ አመድ ነሰነሰች ቀሚሷንም ደግሞ ቀደደች። ከዚያም ሀዘኗን ለመግለጽ፣ እጆቿን ጭንቅላቷ ላይ ጫነች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊቶች)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Samuel 13:20

ወንድምሽ አምኖን ከአንቺ ጋር ነበርን?
ይህ በጨዋ/ትሁት መልክ አምኖን ከአንቺ ጋር ግንኙነት አድርጎ ነበርን ማለት ነው። "ወንድምሽ አምኖን ከአንቺ ጋር ተኝቶ ነበርን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

ጸጥ በይ/ዝም በይ
ይህ ማለት ስለ አንድ ነገር ለማንም አለመናገር ማለት ነው። "ስለዚህ ጉዳይ ለማንም አትናገሪ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህንን ነገር በልብሽ አትያዥው
"አንድን ነገር በልብ መያዝ" የሚለው ሀረግ "ስለዚያ ነገር መጨነቅ" ማለት ነው። "ስለሆነው ነገር አትጨነቂ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህም ትዕማር ለብቻዋ ቀረች
ይህ ማለት አላገባችም ማለት ነው።

ምንም አልተናገረም
"አልተናገረም"

2 Samuel 13:23

ከሁለት ድፍን አመታት በኋላ እንዲህ ሆነ
ይህ የሚያስረዳው ሁለት ሙሉ አመታት እንዳለፉ እና በታሪኩ ፍሰት ቀጣዩ ትእይንት እንደጀመረ ነው። "ሙሉ አመታት" የሚለው ይህ ሀረግ ትርጉሙ ሙሉ አመታት ነበሩ ማለት ነው። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

ሸላቾች
እነዚህ የበጎችን ፀጉር/ሱፍ የሚሸልቱ ሰዎች ናቸው

ቤላሶር
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አሁን ተመልከት
ይህ አንድ ሰው ቀጥሎ የሚነገረውን ነገር እንዲሰማ ትኩረቱን ለመሳብ የዋለ ሀረግ ነው። "ስማ/አድምጥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

የአንተ አገልጋይ/አገልጋይህ
አቤሴሎም አክብሮቱን ለመግለጸ ራሱን "የአንተ አገልጋይ/አገልጋይህ" በማለት ይጠራል።

በግ ሸላቾች አሉት
የእስራኤል ሰዎች በጎቻቸውን ከሸለቱ በኋላ መደገሳቸው የተለመደ መበር

ንጉሡ
የሚነጋገረው ከአባቱ ጋር ቢሆንም አክብሮቱን ለመግለጽ "ንጉሡ" ብሎ ይጠራዋል እንጂ "አንተ" እያለ አያነጋግረውም።

2 Samuel 13:25

እባክህ ወንድሜ አምኖን ከእኛ ጋር ይሂድ
በእስራኤል ባህል ብዙውን ጊዜ ታላቅ ወንድም አባቱን ሊወክል ይችላል። አምኖን የዳዊት ታላቅ ልጅ ነበር።

አምኖን ለምን ከእናንተ ጋር ይሄዳል?
ዳዊት አምኖን የአቤሴሎም ወዳጅ እንዳልሆነ ያውቃል።

2 Samuel 13:27

አቤሴሎም ዳዊትን ተጫነው/አጥብቆ ጠየቀው
እዚህ ስፍራ ጸሐፊው አቤሴሎም አብሯቸው እንዲሄድ ዳዊት ይፈቅድ ዘንድ አምኖን የጠየቀበትን ሁኔታ በእርሱ ላይ አካላዊ ጫና እንዳሳረፈ አድርጎ ያቀርበዋል። "አቤሴሎም አምኖን ይመጣ ዘንድ ዳዊትን ለመነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አትፍሩ
ይህ የሚያመለክተው አምኖንን በመግዳላቸው ሊከተል የሚችለው ውጤት ሊያስፈራቸው እንደማይገባ ነው። ይህ በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "የንጉሱን ልጅ በመግደላችሁ እንወነጀላለን ብላችሁ አትፍሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ያዘዝኳችሁ እኔ አይደለሁምን?
አቤሴሎም ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠይቀው ለአምኖን መገደል እርሱ ተጠያቂ እንደሚሆን ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው፤ ምክንያቱም ያዘዛቸው እርሱ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ይህን አንድታደርጉ ያዘዝኳችሁ እኔ ነኝ" ወይም "ለእርሱ መግደል ተጠያቂ የምሆነው እኔ ነኝ ምክንያቱም ይህን እንድታደርጉ እኔ አዝዣችኋለሁ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

እናንተን አላዘዝኳችሁም
አቤሴሎም ያደርጉት ዘንድ እነርሱን ያዘዘው ነገር በጥያቄው ውስጥ ሊገለጽ ይችላል። "እርሱን እንድትገድሉት አላዘዝኳችሁም" (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

የንጉሱ ወንዶች ልጆች ሁሉ
ይህ የሞቱትን አቤሴሎምን እና አምኖንን አይጨምርም። ይህ የሚያካትተው ወደ ድግሱ እንዲሄዱ ንጉሱ የፈቀደላቸውን የተቀሩትን ወንድ ልጆች ነው። "የተቀሩት የንጉሱ ወንድ ልጆች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

እያንዳንዱ ሰው
ይህ የሚያመለክተው ድግሱን ትተው የወጡትን የንጉሱን ወንዶች ልጆች ነው።

2 Samuel 13:30

ስለዚህም እንዲህ ሆነ
"እንዲህም ሆነ።" እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ፍሰት ቀጣዩን ትዕይንት ለማስተዋወቅ ነው። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

በመንገድ ላይ
"በመንገድ በመጓዝ ላይ"

እንዲህ የሚል ወሬ ወደ ዳዊት ደረሰ
እዚህ ላይ አንድ ሰው በእርግጥ ደርሷ ለዳዊት ወሬውን ሲነግረው ወሬው ደረሰ ይላል። "አንድ ሰው መጥቶ ወሬውን ለዳዊት እንዲህ ሲል ነገረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያም ንጉሡ ተነሳ
"ከዚያ ንጉሡ ተነስቶ ቆመ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ልብሱን ቀደደ፣ በምድርም ላይ ወደቀ
እነዚህን ነገሮች ያደረገው እጅግ ማዘኑን ለመግለጽ ነው። "ልብሱን ቀደደ፣ አምርሮ በማዘን ምድር ላይ ወደቀ" (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ልብሶቻቸውን ቀደዱ
እነርሱ ይህንን ያደረጉት ሀዘናቸውን ለመግለጽ እና ከንጉሱ ጋር ለማዘን ነው። "ልብሶቻቸውንም ቀደዱ፣ ከንጉሱ ጋር አዘኑ" (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 13:32

ኢዮናዳብ...ሳምዓ
እነዚህን የወንድ ስሞች በ2 ሳሙኤል 13:3 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ

ጌታዬ ይህንን አይመን/አይቀበል
"ጌታዬ፣ ይህንን አይመን"

ጌታዬ
ኢዮአብ አክብሮቱን ለመግለጽ ዳዊትን "ጌታዬ" ይለዋል

አምኖን እህቱን አስገደዳት
ይህ አምኖን እህቱን ደፈራት የሚለውን በጨዋ/ትሁት ቋንቋ ለመግለጽ ነው። (የፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

ጌታዬ ንጉሱ አይቀበል/አያስብ
"ንጉሱ የእኔ ጌታ፣ አይቀበል/አያስብ"

ይህንን ወሬ በልቡ አያኑር
"አንድን ነገር ወደ ልብ መውሰድ/በልብ ማኖር" የሚለው ሀረግ "ስለዚያ ነገር መጨነቅ" ማለት ነው። "ስለዚህ ወሬ አትጨነቅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 13:34

መጠበቁን ቀጠለ/ነቅቶ ጠበቀ
ይህ ማለት አገልጋዩ በከተማይቱ ግንብ ሲጠብቅ ሳለ ጠላትን በንቃት ይከታተል ነበር። "ይጠብቅ የነበረው" ወይም "በከተማይቱ ግንብ ይጠብቅ የነበረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ዐይኖቹን አቅንቶ
እዚህ ስፍራ አገልጋዩ ያደርግ የነበረው ጥበቃ የተገለጸው ዐይኖቹን ወደ ላይ እንዳነሳ ተደርጎ ነው። "አቅንቶ ተመለከተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህም ሆነ
ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ፍሰት ቀጣዩን ትዕይንተ ለማስተዋወቅ ነው። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

ድምጻቸውን አነሱ
እዚህ ስፍራ የወንዶች ልጆቹ ጩኸት የተነገረው ድምጻቸው ወደ ሰማይ እንዳነሱት አንድ ነገር ተደርጎ ነው። "ጮኹ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 13:37

ተልማይ... ዓሚሁድ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእርሱ ወንድ ልጅ
" ለወንድ ልጁ ለአሞን"

ለሶስት አመታት በነበረበት
"ለሶስት አመታት በቆየበት"

ንጉስ ዳዊት ናፈቀ
እዚህ ስፍራ የዳዊትን ናፍቆት ለማጉላት ያሳሰበው ሁኔታ ተገልጽዋል።

በአምኖን ሞት ከደከረሰበት ሀዘን ተጽናና
"ከዚህ በኋላ በአምኖን ሞት ማዘኑ አልቀጠለም።" ይህ የሚያመለክተው አቤሴሎም ወደ ጌሹር ከሸሸ በኋላ ያለውን ሶስት አመት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 14

1 የጽሩያ ልጅ ኢዮአብ የንጉሡ ልብ አቤሴሎምን እንደ ናፈቀ ተረዳ። 2 ስለዚህም ኢዮአብ ወደ ቴቁሔ ልኮ አንዲት ብልኅ የሆነች ሴት አስመጥቶ፣ “ሐዘንተኛ
በመምሰል የሐዘን ልብስ ልበሺ፣ እባክሽን ዘይት አትቀቢ ነገር ግን ለብዙ ጊዜ እንዳዘነች መስለሽ ታዪ። 3 ከዚያም ወደ ንጉሡ ሄደሽ እኔ የምገልጽልሽን
ንገሪው።” ስለዚህ ኢዮአብ ለንጉሡ የምትናገረውን ነገር ነገራት። 4 ከቴቁሔ የመጣችውም ሴት ለንጉሡ ለመንገር በገባችበት ጊዜ በንጉሡ ፊት ለጥ ብላ እጅ
በመንሣት፣ “ንጉሥ ሆይ፣ እርዳኝ” አለች። 5 ንጉሡም፣ “ችግርሽ ምንድን ነው?” አላት። ሴቲቱም፣ “እኔ በእውነቱ ባሏ የሞተባት ባልቴት ነኝ። 6 እኔ ባሪያህ
ሁለት ልጆች ነበሩኝ፣ እነርሱም ሜዳ ላይ እርስ በርሳቸው ተጣሉ፣ የሚገላግላቸውም ሰው አልነበረም። አንደኛውም ሌላኛውን መታውና ገደለው። 7 መላው
ቤተሰብም አሁን በባሪያህ ላይ ተነሥቶ፣’ስለገደለው ስለ ወንድሙ ዋጋ እንዲከፍልና እኛም እንድንገድለው ወንድሙን የገደለውን ሰው አውጥተሽ ስጪን’ አሉኝ፤
ወራሽ የሆነውንም ያጠፉ ዘንድ ይፈልጋሉ። በዚህም ዓይነት የቀረኝን አንድ የጋለ ፍም አጥፍተው፣ ባሌን በምድር ላይ ያለ ስምና ያለ ዘር ሊያስቀሩት ነው።” 8
ስለዚህ ንጉሡ ለሴቲቱ፣ “አንቺ ወደ ቤትሽ ሂጂ፣ አንድ ነገር እንዲደረግልሽ እኔ ትዕዛዝ እሰጣለሁ” አላት። 9 የቴቁሔዪቱም ሴት ለንጉሡ፣ “ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፣
በደሉ በእኔና በአባቴ ቤተሰብ ላይ ይሁን፤ ንጉሡና ዙፋኑ ከበደል የነጹ ይሁኑ” አለች። 10 ንጉሡም፣ “ማንም ሰው ቢናገርሽ ወደ እኔ ዘንድ አምጪው ከዚያ
በኋላም አያስቸግርሽም” በማለት መለሰላት። 11 ከዚያ በኋላ ሴቲቱ፣ “ደም ተበቃዩ ሌላ ሰው እንዳያጠፋና ልጄንም እንዳያጠፉት፣ እባክህን ንጉሥ
እግዚአብሔር አምላክህን አሳስብልኝ” አለችው። ንጉሡም፣ “ሕያው እግዚአብሔርን ከልጅሽ ራስ አንዲት ፀጉር እንኳ አትወድቅም” ብሎ መለሰላት። 12 ከዚያ
በኋላም ሴቲቱ፣ “ባሪያህ ለጌታዬ ለንጉሡ ተጨማሪ ቃል እንድናገር እባክህ ፍቀድልኝ” አለችው። ንጉሡም፣ “ተናገሪ” አላት። 13 ስለዚህ ሴቲቱ፣ “ታዲያ፣
እንዲህ ያለውን ነገር በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ያሰብኸው ለምንድን ነው? ምክንያቱም ይህንን በመናገሩ ንጉሡ ራሱን በደለኛ እንደሚያደርግ ሰው ነው፣
የኮበለለውን ልጁን ንጉሡ ወደ ቤቱ አልመለሰውምና። 14 ሁላችንም እንሞት ዘንድ ይገባናልና፣ እንደገናም ሊሰበሰብ እንደማይችል እንደ ፈሰሰ ውሃ ነንና።
እግዚአብሔር ግን የሰውን ሕይወት አይወስድም ይልቁንም ከፊቱ ራሱን ያስኮበለለውን ሰው ወደ ራሱ የሚመልስበት መንገድ ይፈልጋል እንጂ። 15 እንግዲህ
አሁን ለጌታዬ ለንጉሡ ይህንን ልናገር የመጣሁት ሕዝቡ እንድፈራ ስላደረጉኝ ነው። ከዚህም የተነሣ ባሪያህ ለራሷ፣ ‘አሁን ለንጉሡ እናገራለሁ፣ ምናልባትም
ንጉሡ የባሪያውን ጥያቄ ይቀበል ያደርግላት ይሆናል። 16 እኔንና ልጄን ከእግዚአብሔር ርስት ሊያጠፋን ካለው ሰው እጅ ያድን ዘንድ ባሪያውን ያወጣ ዘንድ
ንጉሡ ይሰማኛልና፣’ አለች። 17 ከዚያ በኋላም ባሪያህ፣ ‘እግዚአብሔር ሆይ፣ የጌታዬ የንጉሡ ቃል እፎይታን የሚሰጠኝ ይሁን፣ ምክንያቱም መልካሙን ከክፉው
በመለየት ጌታዬ ንጉሡ እንደ እግዚአብሔር መልአክ ነውና’ እግዚአብሔር አምላክህ ከአንተ ጋር ይሁን።” 18 ከዚያ በኋላም ንጉሡ ለሴቲቱ፣ “እኔ ለምጠይቅሽ
ጥያቄ እባክሽ ምንም ነገር አትደብቂኝ” አላት። 19 ንጉሡም፣ “በዚህ ሁሉ የኢዮአብ እጅ ከአንቺ ጋር የለም?” ሴቲቱም፣ “ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፣ በሕያው ነፍስህ
እምላለሁ፤ ጌታዬ ንጉሡ ከተናገረው አንዳችም ነገር ማንም ሰው ወደ ቀኝም ወደ ግራም ማምለጥ አይችልም። ያዘዘኝና ባሪያህም የተናገረችውን እነዚህን ነገሮች
እንድናገር የነገረኝ ባሪያህ ኢዮአብ ነው። 20 ባሪያህ ኢዮአብ ይህንን ያደረገው ነገሮች እየሄዱበት ያለውን አቅጣጫ ለመለወጥ ነው። እንደ እግዚአብሔር
መልአክ ጥበብ ጌታዬ ጠቢብ ነው፤ በምድሪቱም የሚሆነውን ማንኛውንም ነገር ያውቃል።” 21 ስለዚህ ንጉሡ ለኢዮአብ፣ “እነሆ፣ እኔ አሁን ይህንን አደርጋለሁ።
እንግዲህ ሂድና ወጣቱን አቤሴሎምን አምጣው” አለው። 22 ስለዚህ ኢዮአብ ለንጉሡ አክብሮቱንና ምስጋናውን ለመግለጽ ጎንበስ ብሎ እጅ ነሳ። ኢዮአብም፣
“ዛሬ ባሪያህ በጌታዬ በንጉሡ ፊት ሞገስ እንዳገኘ አወቅሁ፣ ንጉሡ የባሪያውን ጥያቄ ፈጽሞለታልና” 23 ስለዚህ ኢዮአብ ተነሥቶ ወደ ጌሹር ሄደ፣
አቤሴሎምንም ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ። 24 ንጉሡም፣ “ወደ ራሱ ቤት መመለስ ይችላል፣ ነገር ግን ፊቴን አያይም” ስለዚህ አቤሴሎም ወደ ቤቱ
ተመለሰ፣ የንጉሡን ፊት ግን አላየም። 25 በመላው እስራኤል ከአቤሴሎም ይልቅ በመልከ መልካምነቱ የተመሰገነ ማንም አልነበረም። ከእግር ተረከዙ ጀምሮ
እስከ አናቱ ድረስ ምንም እንከን አልነበረበትም። 26 ይከብደው ስለ ነበረ የራሱን ፀጉር በሚቆረጥበት ጊዜ ፀጉሩን ይመዝነው ነበር፣ በንጉሡም የመመዘኛ ልክ
ሁለት መቶ ሰቅል ይመዝን ነበር። 27 አቤሴሎምም ሦስት ወንዶች ልጆችና ትዕማር የምትባል አንድ ሴት ልጅ ነበሩት። ሴት ልጁም ውብ ነበረች። 28
አቤሴሎምም የንጉሡን ፊት ሳያይ ሁለት ሙሉ ዓመት በኢየሩሳሌም ኖረ። 29 ከዚህ በኋላ ወደ ንጉሡ ይወስደው ዘንድ አቤሴሎም ወደ ኢዮአብ መልእክት ላከ፣
ኢዮአብ ግን ሊመጣ አልፈለገም። ስለዚህ አቤሴሎም ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ኢዮአብ መልእክት ላከ፣ ኢዮአብ ግን አሁንም አልመጣም። 30 ስለዚህ አቤሴሎም
ለአገልጋዮቹ፣ “ኢዮአብ በእኔ እርሻ አጠገብ እርሻ አለው፣ በዚያም ገብስ አለው፤ ሂዱና በገብሱ ላይ እሳት ልቀቁበት” አላቸው። ስለዚህ የአቤሴሎም አገልጋዮች
በእርሻው ላይ እሳት ለቀቁበት። 31 ከዚያም ኢዮአብ ተነስቶ ወደ አቤሴሎም ቤት መጣና፣ “አገልጋዮችህ በእርሻዬ ላይ እሳት የለቀቁበት ለምንድን ነው?”
አለው። 32 አቤሴሎምም ለኢዮአብ፣ “እነሆ፣ ወደ አንተ ዘንድ፣ ‘ወደ ንጉሡ እልክህ ዘንድ ወደ እኔ ዘንድ መጥተህ ለንጉሡ፣ ከጌሹር ለምን መጣሁ? እዚያው
ብቆይ ይሻለኝ ነበር’ ብለህ እንድትነግርልኝ መልእክት ልኬብህ ነበር። ስለዚህ አሁን የንጉሡን ፊት ልይ፣ በደለኛ ከሆንኩም ይግደለኝ” አለው። 33 ስለዚህ
ኢዮአብ ወደ ንጉሡ ዘንድ ሄዶ ነገረው። ንጉሡም አቤሴሎምን ባስጠራው ጊዜ አቤሴሎም በንጉሡ ፊት ለጥ ብሎ እጅ ነሣ፣ ንጉሡም አቤሴሎምን ሳመው።

---

2 Samuel 14:1

አሁን
ይህ ቃል እዚህ ስፍራ ላይ የዋለው በዋናው ታሪክ ፍሰት ላይ ማቆሚያ ምልክት ለማድረግ ነው። እዚህ ጸሐፊው በታሪኩ ውስጥ ስለ አዲስ ሰው ይናገራል።

ጽሩያም
ይህ የወንድ ስም በ2 ሳሙኤል 2፡13 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ተረዳ
ይህ ማለት ኢዮአብ ዳዊት ያስብ የነበረውን ለይቶ አውቋል ወይም ተረድቷል ማለት ነው።

ወደ ቴቁሔ ቃል ላከ ደግሞም ብልህ ሴት አስመጣ
ይህ ማለት ኢዮአብ አንድ ሰው መልዕክት አስይዞ ወደ ቴቁሔ ላከ ደግሞም አንዲት ሴት ወደ እርሱ እንዲያመጡ አደረገ። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "መልዕክት አስይዞ አንድ ሰው ወደ ቴቁሄ ላከ ደግሞም አንዲት ብልህ ሴት ወደ እርሱ ይዘው መጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ቴቁሔ
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የሞተው
ይህ በአጠቃላይ ስለ ሞቱ ሰዎች ሳይሆን፣ ስለ አንድ የሞተ ሰው ያመለክታል። "አንድ የሞተ ሰው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Samuel 14:4

በመሬት ላይ በፊቷ ተደፋች
ይህን ያደረገችው ለንጉሱ ያላትን ክብር እና መታዘዝ ለማሳየት ነው። "በምድር ላይ በፊቷ በመደፋት ለንጉሱ ያላትን ክብር አሳየች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

አንዱ ሌላውን መታው
"ከወንድ ልጆቼ አንዱ ሌላውን በአንድ ነገር መታው"

2 Samuel 14:7

መላው ጎሳ
"መላው ቤተሰቤ"

የአንተ አገልጋይ
ሴትየዋ ለንጉሡ ያላትን ክብር ለማሳየት ራስዋን "የአንተ አገልጋይ" ብላ ትጠራለች።

ወደ ሞት ጣሉት
ይህ መግደል ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ወራሹንም ደግሞ ያጠፉታል
ጥፋተኛውን ወንድሙን ከገደሉት የቤተሰቡን ሀብት የሚወርስ ልጅ አይተርፍም። የዚህ ሃሳብ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ይህንን ካደረጉ፣ የቤተሰባችንን ወራሽ ያጠፋሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህ ከሆነ የቀረኝን የሚነደውን ከሰሌን ያጠፉታል
እዚህ ስፍራ ሴትየዋ በህወት የቀረውን ብቸኛ ልጇን የምትገልጸው እንደሚነድ የከሰል ቁራጭ አድርጋው ነው። ልጇን የሚገድሉትን ሰዎች የምትገልጸው የሚነደውን ከሰል እንደሚያጠፉ አድርጋ ነው። "በዚህ መንገድ የቀረኝን ብቸኛ ልጅ ይገድሉታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለባሌ ስም ሆነ ዘር አያስቀሩለትም
ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊገለጽ ይችላል። "ለባሌ ስምም ሆነ ዘር አያስቀሩለትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ/ድርብ አሉታ የሚለውን ይመልከቱ)

ስምም ሆነ ዘር/ትውልድ
ይህ የሚያመለክተው ወንድ ልጅ የቤተሰቡን ስም ወደ ተከታዩ ትውልድ የሚያሸጋግር መሆኑን ነው። "የቤተሰባችንን ስም የሚጠብቅ ወንድ ልጅ አይኖርም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

በምድር ገጽ
"በምድር።" ይህ ገላጭ ሀረግ የሚያጎላው ባል ከሞተ በኋላ የቤተሰቡ መስመር/ሀረግ በምድር ላይ ሊቀጥል አለመቻሉን ነው። "የምድር ገጽ" የሚለው የሚያመለክተው ሰዎች የሚራመዱበትን ምድር ነው።

2 Samuel 14:8

አንዳች ነገር ለአንቺ እንዲደረግ አዛለሁ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እኔ ስለዚህ ጉዳይሽ አዛለሁ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ቴቁሔ
ይህን የቦታ ስም በ2 ሳሙኤል 14፡12 ላይ እንደ ተረጎሙት ይተርጉሙት።

ጥፋቱ/ኃጢአቱ በእኔ እና በአባቴ ቤተሰብ ላይ ይሁን
ይህ ማለት ህዝቡ፣ ንጉሱ የሴትየዋን ቤተሰብ በመርዳቱ ተሳስቷል ቢል ንጉሱ ጥፋተኛ አይሁን። የዚህ ሃሳብ ሙሉ ትርጉም ሊብራራ ይችላል። "የእኛን ቤተሰብ በመርዳቱ ማንም ንጉሱን ጥፋተኛ ቢያደርግ፣ በዚያ ምትክ የእኔ ቤተሰብ ጥፋተኛ ይደረግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሡ እና ዙፋኑ
እዚህ ስፍራ "ዙፋን" የሚለው ቃል የሚያመለክተው በዳዊት ስፍራ ንጉስ የሚሆነውን ሰው ነው። "ንጉሡ እና የእርሱ ትውልድ" ወይም "ንጉሱ እና ቤተሰቡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ጥፋተኛ አይሆኑም
"ንጹሃን ናቸው።" ይህ የሚያመለክተው ወደፊት ማንም ንጉሱን ጥፋተኛ አድርጎ ቢቆጥር፣ እርሱ በዚህ ጉዳይ ንጹህ ይሆናል። "ይህን ጉዳይ በሚመለከት ንጹህ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 14:10

የሚናገርሽን ማናቸውንም ነገር
እዚህ ስፍራ ማስፈራራት የተገለጸው በአጠቃላይ እንደ መናገር ነው። "የሚያስፈራሽ" ወይም "በማስፈራራት የሚናገርሽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህ አይነካሽም
እዚህ ስፍራ ዳዊት ሰውየው እርሷን አይነካትም በሚል፣ አንድ ሰው እርሷን አያስፈራራትም ወይም አይጎዳትም በሚል ይናገራል። ዳዊት ሴትየዋን የሚያስፈራራት ሰው ዳግም እንዲያስቸግራት እንደማይፈቅድ በውስጠ ታዋቂ ተጠቁሟል። የዚህ ሃሳብ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ዳግም እንደማያስፈራራሽ አረጋግጥልሻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

2 Samuel 14:12

የአንተ አገልጋይ
ሴትየዋ ለንጉሡ ያላትን አክብሮት ለማሳየት ራሷን "የአንተ አገልጋይ" በማለት ትገልጻለች።

ሌላ ቃል ልናገር
"ስለ ሌላ ነገር መናገር።" ሴትየዋ ንጉሡን ስለ ሌላ ርዕስ እንድትናገር እየተየቀች ነው።

ተናገሪ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ንጉሡ ንግግሯን እንድትቀጥል ፈቃድ እየሰጣት ነበር። "ለእኔ መናገር ትችያለሽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ህዝብ ላይ ለምን እንዲህ ያለ ነገር አሰብህ?
ሴትየዋ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የጠየቀችው ዳዊት በአቤሴሎም ላይ ስላደረሰው ነገር ለመገሰጽ ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አሁን የተናገርከው ራሱ ስህተት መስራትህን ያረጋግጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ንጉሡ ጥፋት እንዳለበት ሰው/በደለኛ ነው።
ሴትየዋ ፊት ለፊት ባትናገርም ንጉሡ በደለኛ መሆኑን ለመጠቆም፣ በደለኛ ከሆነ አንድ ሰው ጋር ንጉሡን ታነጻጽራለች። "ንጉሡ ራሱን ጥፋተኛ አድርጓል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

የተሳደደው ልጁ
"እርሱ ያሳደደው ልጁ"

ሁላችንም ሟች ነን፣ ሁላችንም በምድር ላይ እንደ ፈሰሰ... ዳግም እንደ ማይታፈስ ውሃ ነን
እዚህ ስፍራ ሴትየዋ ስለ ሞተ አንድ ሰው በመሬት ላይ እንደ ፈሰሰ ውሃ አድርጋ ትናገራለች። "ሁላችንም ሟች ነን፣ ከሞትን በኋላ ዳግም ወደ ህይወት መመለስ አንችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር... የተጣሉት ይጠገኑ ዘንድ መንገድ አለው
ሴትየዋ ዳዊት ልጁን መልሶ መቀበል እንዳለበት እያመላከተች ነው። ይህ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር ከፊቱ ያስወገደውን እየመለሰ ነው፣ አንተም ለልጅህ እንደዚያው ማድረግ ይገባሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 14:15

ሰዎች አስፈራርተውኛልና
የታወቀው መረጃ ሊቀርብ ይችላል። "ሰዎች እንድፈራ ስላደረጉኝ መጥቻለሁ" (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ አገልጋይ
ሴትየዋ ለንጉሡ ያላትን ክብር ለማሳየት ራስዋን "የአንተ አገልጋይ" ብላ ትጠራለች።

ከሰው እጅ
ይህ ሀረግ ፈሊጥ ነው። እንደዚሁም፣ "እጅ" የሚለው የሰውን የቁጥጥር አቅም የሚያመለክት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ከሰውየው ቁጥጥር ውጭ" በሚለው ውሰጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የጌታዬ የንጉሡ ቃል
"የጌታዬ የንጉሡ መልዕክት"

ጌታዬ ክፉው ከመልካሙ ለመለየት.... ልክ እንደ እግዚአብሔር መልአክ ነው
እዚህ ስፍራንጉሡ ዳዊት ከ "እግኢአብሔር መልአክ" ጋር ተነጻጽሯል። "ንጉሡ እንደ እግዚአብሔር መልአክ ነው፣ ምክንያቱም ሁለቱም ክፉውን ከመልካሙ ለይቶ መናገር ይችላሉ" (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 14:18

እባክሽ የምጠይቅሽን ሁሉ ከእኔ አትደብቂ
እዚህ ስፍራ አሉታዊ ዐረፍተ ነገሩ የዋለው ትኩረት ለመስጠት ነው፤ ሆኖም በአዎንታዊ መልክ ሊገለጽ ይችላል። "እባክሽ ስለምጠይቅሽ ነገር ሁሉ እውነቱን ንገሪኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምፀት/ላይዶልስ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚህ ሁሉ የኢዮአብ እጅ ከአንቺ ጋር አይደለምን
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የኢዮአብን ተጽዕኖ ነው። "ኢዮአብ በዚህ ሁሉ ተጽዕኖ አላሳደረብሽምን" ወይም "እነዚህ ነገሮች እንድትናገሪ የላከሽ ኢዮአብ ነውን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በህያው ነፍስህ
"የአንተ ህያውነት እርግጥ የሆነውን ያህል።" እዚህ ስፍራ ሴትየዋ ዳዊት የተናገረውን ነገር እርግጠኝነት እርሱ በህይወት መኖሩ እርግጥ ከመሆኑ ጋር የምታነጻጽረው የእርሱ ሃሳብ ምን ያህል እውነት እንደሆነ ለማጉላት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሡ ከተናገረው ሁሉ ማንም ወደ ቀኝም ወደ ግራም .... ሊል አይችልም
እዚህ ስፍራ ሴትየዋ ከንጉሡ ጋር መነጋገር እና እውነቱን ከእርሱ መሸሸግ ያለው ያለውን አስቸጋሪነት የምትገልጸው ወደ የትኛውም አቅጣጫ ማምለጥ ካቃተው ሰው ጋር በማነጻጸር ነው። "ማንም እውነቱን ከማወቅ ሊያግድህ አይችልም" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ቀኝ ወይም ወደ ግራ
አገላለጹ ሁለት ጽንፎችን ያሳያል ትርጉሙም "ወዴትም" ማለት ነው። "በፍጹም የትም" ወይም "የትም ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜሪዝም/ጽንፍ የሚለውን ይመልከቱ)

ጌታዬ ጠቢብ ነው
"ንጉሡ ጌታዬ ጠቢብ ነው"

እንደ እግዚአብሔር መልአክ ጥበብ፣ ጠቢብ ነው
ሴትየዋ የዳዊትን ጥበብ ከመልአክ ጥበብ ጋር ያነጻጸረችው ዳዊት ምን ያህል ጥበበኛ እንደሆነ ለማጉላት ነው። "እንደ እግዚአብሔር መልአክ፣ አንተ በጣም ጠቢብ ነህ" (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 14:21

ስለዚህ ንጉሡ ኢዮአብን እንዲህ አለው
በውስጠ ታዋቂነት ንጉሡ ኢዮአብን ያናግረው ዘንድ እርሱን/አቤሶሎምን እንዲያመጣው ተናግሯል። የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ከዚያም ንጉሡ ኢዮአብን ጠርቶ እንዲህ አለው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አሁን ተመልከት/እነሆ
ይህ ሀረግ የዋለው የአንድን ሰው ትኩረት ቀጥሎ ወደ ሚነገረው ነገር ለመሳብ ነው። "ስማ/አድምጥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ይህ ነገር
ይህ የሚያመለክተው ኢዮአብ ንጉሡ እንዲያደርግ የሚፈልገውን ነው። የዚህ ሃሳብ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "እኔ አደርገው ዘንድ አንተ የምትፈልገው ነገር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ኢዮአብ ፊቱን ወደ ምድር ደፍቶ እጅ ነሣ
ኢዮአብ ይህንን ያደረገው ንጉሡን ለማክበር እና የንጉሡን ታላቅነት ለማሳየት ነው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት)

የአንተ አገልጋይ
ኢዮአብ ለንጉሡ ያለውን ክብር ለማሳየት ራሱን "የአንተ አገልጋይ" ሲል ይጠራል/ያመለክታል።

በዐይኖችህ ሞገስ አግኝቻለሁ
"ሞገስ አግኝቻለሁ" የሚለው ሀረግ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ በአንድ ሰው ፊት ተቀባይነት ማግኘት ማለት ነው። እንደዚሁም "ዐይኖች" የሚለው ለማየት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሲሆን ደግሞም ማየት ፍርድን ወይም ምዘናን ይወክላል። "አንተ በእኔ ደስ ተሰኝተሃል" ወይም "አንተ እኔን ተቀብለሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እንዲሁም ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በዚያ ውስጥ ንጉሡ
"ምክንያቱም ንጉሡ"

ንጉሡ የአገልጋዩን ጥያቄ መለሰ
"እንድታደርግልኝ የጠየቅኩህን አደረግህ"

2 Samuel 14:23

አሁን
ይህ ቃል በዋናው ታሪክ ፍሰት መቆሚያ ያበጃል። ይህ አዲስ ክፍል ተከትሎ ለሚመጣው የታሪክ ክፍል የመረጃ ዳራ ይሰጣል። (የመረጃ ዳራ የመለውን ይመልከቱ)

እንደ አቤሴሎም በውበቱ የተደነቀ ሰው ማንም አልነበረም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች ማንንም ካደነቁት ይልቅ አቤሴሎምን በውበቱ አደነቁ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ውበት/ቁንጅና
መልካም እና ለዕይታ ደስ የሚያሰኝ፣ በተለይ ለፊት/ገጽታ ውበት

ከእግሩ ጫማ አስከ አናቱ ጫፍ በእርሱ ላይ ነቀፌታ አልነበረም
ይህ ማለት መላ ሰውነቱ ያለ ነቀፊታ ነበር። "ከአካሉ በአንዱም ላይ ነቀፊታ አልነበረም" በሚለው ውሰጥ እንደሚገኘው። (ሚሪዝም/ጽንፍ የሚለውን ይመልከቱ)

ሁለት መቶ ሰቅል
ይህ በዘመናዊ መለኪያ ሊጻፍ ይችላል። "ሁለት ተኩል ኪሎ ግራም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መጽሐፍ ቅዱሳዊ የክብደት መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

የንጉሡ የክብደት መለኪያ
ንጉሡ የሰቅልን መደበኛ ክብደት እና ሌሎች ክብደቶችን እና መለኪያዎችን የሚወስንበት መለኪያ አለው

ለአቤሴሎም ሶስት ወንዶች እና አንድ ሴት ልጅ ተወልደውለት ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አቤሴሎም ሶስት ወንድ ልጆች እና አንድ ሴት ልጅ ነበረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

2 Samuel 14:25

አሁን
ይህ ቃል በዋናው ታሪክ ፍሰት መቆሚያ ያበጃል። ይህ አዲስ ክፍል ተከትሎ ለሚመጣው የታሪክ ክፍል የመረጃ ዳራ ይሰጣል። (የመረጃ ዳራ የመለውን ይመልከቱ)

እንደ አቤሴሎም በውበቱ የተደነቀ ሰው ማንም አልነበረም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች ማንንም ካደነቁት ይልቅ አቤሴሎምን በውበቱ አደነቁ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ውበት/ቁንጅና
መልካም እና ለዕይታ ደስ የሚያሰኝ፣ በተለይ ለፊት/ገጽታ ውበት

ከእግሩ ጫማ አስከ አናቱ ጫፍ በእርሱ ላይ ነቀፌታ አልነበረም
ይህ ማለት መላ ሰውነቱ ያለ ነቀፊታ ነበር። "ከአካሉ በአንዱም ላይ ነቀፊታ አልነበረም" በሚለው ውሰጥ እንደሚገኘው። (ሚሪዝም/ጽንፍ የሚለውን ይመልከቱ)

ሁለት መቶ ሰቅል
ይህ በዘመናዊ መለኪያ ሊጻፍ ይችላል። "ሁለት ተኩል ኪሎ ግራም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መጽሐፍ ቅዱሳዊ የክብደት መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

የንጉሡ የክብደት መለኪያ
ንጉሡ የሰቅልን መደበኛ ክብደት እና ሌሎች ክብደቶችን እና መለኪያዎችን የሚወስንበት መለኪያ አለው

ለአቤሴሎም ሶስት ወንዶች እና አንድ ሴት ልጅ ተወልደውለት ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አቤሴሎም ሶስት ወንድ ልጆች እና አንድ ሴት ልጅ ነበረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

2 Samuel 14:28

የንጉሡ ፊት
እዚህ "የንጉሡ ፊት" የሚለው የሚያመለክተው ንጉሡን ራሱን ነው። "ንጉሡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

አቤሴሎም ወደ ኢዮአብ ቃል ላከ
እዚህ ስፍራ "ቃል" የሚለው "መልዕክት" ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ይህም ማለት አቤሴሎም ጥያቄ አስይዞ ወደ ኢዮአብ መልዕክተኛ ላከ። "አቤሴሎም እርሱን ይልከው ዘንድ እየጠየቀ ወደ ኢዮአብ መልዕክተኛ ላከ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ንጉሡ ይልከው ዘንድ
አቤሴሎም ኢዮአብ ወደ እርሱ እንዲመጣ የፈለገው እርሱን እንዲያየው እና ንጉሡን ማየት እንዲችል እንዲያስታርቀው መሆኑ በስውር ተጠቅሷል። የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "ወደ እርሱ እንዲመጣ እና ንጉሡን ይመለከት ዘንድ እንዲያስታርቀው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህ አቤሴሎም ለሁለተኛ ጊዜ ቃል ላከ
እዚህ ስፍራ "ቃል" የሚለው "መልዕክት" ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ይህ ማለት በተመሳሳይ ጥያቄ ወደ ኢዮአብ መልዕክተኛ ላከ። የዚህ ሙሉ ትርጉሙ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ስለዚህም አቤሴሎም በተመሳሳይ ጥያቄ ዳግም ወደ ኢዮአብ መልዕክተኛ ላከ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

2 Samuel 14:30

እዩ
እዚህ ስፍራ ይህ ቃል የዋለው ሰዎችን አንድ ነገር ለማስታወስ ነው። "እንደምታውቁት"

2 Samuel 14:32

ተመልከት/ትኩረት ስጥ
"ትኩረት ሰጥ፣ ምክንያቱም የምናገረው እውነትም ጠቃሚም ነው"

ቃል ላክሁ
እዚህ ስፍራ "ቃል" የሚለው "መልዕክት" ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ይህ ማለት መልዕክተኛ ላከ ማለት ነው። "መልዕክተኛ ላክሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ለንጉሡ ለመንገር
እዚህ ስፍራ ለንጉሡ መልዕክት የተጻፈው ተናጋሪው አቤሴሎም እንደሆነ ተደርጎ ነው። አቤሴሎም ኢዮአብን በእርሱ ምትክ ሆኖ መልዕክቱን እንዲናገር ይጠይቀዋል። የዚህ ሃሳብ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "በእኔ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምትክ ሆነህ ለንጉሡ እንድትናገር" ወይም "ንጉሡን ስለ እኔ እንድትጠይቅ" (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የንጉሡ ፊት
እዚህ ስፍራ "የንጉሡ ፊት" የሚለው የሚያመለክተው ንጉሡን ራሱን ነው። "ንጉሡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በንጉሡ ፊት ወደ ምድር ዝቅ ብሎ ሰገደ
አቤሴሎም ለንጉሡ ክብር እያሳየ ነው። "ንጉሡን ለማክበር ወደ ምድር ዝቅ ብሎ ሰገደ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሡ አቤሴሎምን ሳመው
ይህ የሚያመለክተው ንጉሡ አቤሴሎምን ይቅር ማለቱንና መልሶ መቀበሉን ነው። የዚህ ሙሉ ትርጉሙ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ እንዲሁም ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 15

1 ከዚህ በኋላ አቤሴሎም ሠረገላና ፈረሶች እንዲሁም ፊት ፊቱ የሚሮጡ ሃምሳ ሰዎች ለራሱ አዘጋጀ። 2 አቤሴሎም በማለዳ ተነሥቶ ወደ ከተማይቱ መግቢያ በር በሚወስደው መንገድ ዳር ይቆማል። ሙግት ያለበት ማንኛውም ሰው ዳኝነት ለማግኘት ወደ ንጉሡ ሲመጣ፣ በዚያን ጊዜ አቤሴሎም ወደ እርሱ ይጠራውና፣ “ከየትኛው ከተማ ነው የመጣኸው?” ይለው ነበር። ሰውዬውም፣ “አገልጋይህ ከእስራኤል ነገዶች ከአንዱ ነው?” ይለው ነበር። 3 ከዚህም የተነሣ አቤሴሎም፣ “ተመልከት፣ ጕዳይህማ ትክክልና ተገቢም ነው፤ ነገር ግን ጕዳይህን ለመመልከት ከንጉሡ ሥልጣን የተሰጠው ማንም ሰው የለም።” ይለው ነበር። 4 ከዚህ ጋር በማያያዝ አቤሴሎም፣ “ሙግት ወይም ጕዳይ ያለው ማንኛውም ሰው ወደ እኔ እንዲመጣና እኔም ፍትሕ እንድሰጠው በምድሪቱ ዳኛ ሆኜ መሾም እመኛለሁ” ይል ነበር። 5 ስለዚህ ክብርን ሊሰጠው ማንኛውም ሰው ወደ አቤሴሎም በሚመጣበት ጊዜ አቤሴሎም እጁን ዘርግቶ ይይዘውና ይስመው ነበር። 6 ከንጉሡ ፍትሕ ለማግኘት በሚመጡ እስራኤላውያን ሁሉ አቤሴሎም እንደዚህ ያደርግ ነበር። በዚህም ሁኔታ አቤሴሎም የእስራኤላውያንን ልብ ሰረቀ። 7 በአራተኛው ዓመት ፍጻሜ አቤሴሎም ለንጉሡ፣ “ለእግዚአብሔር የተሳልሁትን ስእለት ለማድረስ ወደ ኬብሮን እንድሄድ እባክህን ፍቀድልኝ። 8 ባሪያህ በአራም በጌሹር በነበርኩበት ጊዜ፣ ‘እግዚአብሔር በእርግጥ ወደ ኢየሩሳሌም ዳግመኛ የመለሰኝ እንደሆነ በኬብሮን እሰግዳለሁ’ ብዬ ተስዬ ነበር።” 9 ንጉሡም፣ “በሰላም ሂድ” አለው፤ ስለዚህ አቤሴሎም ወደ ኬብሮን ሄደ። 10 አቤሴሎም ግን ወደ መላው የእስራኤል ነገዶች፣ “የመለከትን ድምፅ በሰማችሁ ጊዜ ‘አቤሴሎም በኬብሮን ነገሠ’ ማለት ይገባችኋል” የሚሉ ሰላዮችን ላከ። 11 ከአቤሴሎምም ጋር ሁለት መቶ የተጋበዙ ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም ሄዱ። አቤሴሎም ምን እንዳቀደ ምንም ነገር ሳያውቁ በየዋህነት ነበረ የሄዱት። 12 አቤሴሎም መሥዋዕት በሚያቀርብበት ጊዜ የዳዊት አማካሪ ለሆነው ለአኪጦፌል ወደሚኖርበት ወደ ጊሎ መልእክት ላከበት። አቤሴሎምን ይከተለው የነበረው ሕዝብ እየጨመረ ስለነበረ የአቤሴሎም ሤራ ጠንካራ ነበር። 13 “የእስራኤል ሰዎች ልብ አቤሴሎምን እየተከተለ ነው።” የሚል መልእክተኛ ወደ ዳዊት መጣ። 14 ስለዚህ ዳዊት በኢየሩሳሌም ለነበሩት አገልጋዮቹ ሁሉ፣ “ተነሡ እንሸሽ፤ ያለበለዚያ አንዳችንም ከአቤሴሎም እጅ ማምለጥ አንችልም፤ አሁኑኑ ለመውጣት ተዘጋጁ አለዚያ እርሱ መጥቶ ይይዘናል በእኛም ላይ ጥፋት ያደርስብናል፣ ከተማይቱንም በሰይፍ ይመታታል።” አላቸው። 15 የንጉሡም አገልጋዮች፣ “እነሆ፣ ጌታችን የወሰነውን ማንኛውንም ለማድረግ አገልጋዮችህ ዝግጁ ነን” በማለት ለንጉሡ ነገሩት። 16 ንጉሡ ከእርሱም ጋር መላው ቤተሰቡ ሄዱ፣ ነገር ግን ቤተ መንግሥቱን ይጠብቁ ዘንድ ቁባቶች የነበሩ አሥር ሴቶችን እንዲቀሩ አደረገ። 17 ንጉሡና እርሱን ተከትሎ መላው ሕዝብ ከሄደ በኋላ ከመጨረሻው ቤተ ሲደርሱ ቆሙ። 18 ሠራዊቱ ሁሉ ከእርሱ ጋር ተጓዙ፣ ከሊታውያን፣ ፈሊታውያን እንዲሁም ከጌት አብረውት የመጡት ስድስት መቶ ጌታውያን በንጉሡ ፊት አለፉ። 19 ከዚያም ንጉሡ ጌታዊውን ኢታይን፣ “አንተ ደግሞ ከእኛ ጋር የመጣኸው ለምንድን ነው? እንግዳና ስደተኛ ነህና ተመልሰህ ሄደህ ከአቤሴሎም ጋር ቆይ፤ ወደ ራስህ አገር ሂድ። 20 የወጣኸው ገና ትላንት ስለሆነ፣ ከእኔ ጋር በየቦታው ለምን እንድትንከራተት ላድርግህ? ወዴት እንደምሄድ እንኳን አላውቅም። ስለዚህ ተመለስ የአገርህንም ሰዎች መልሳቸው፤ በጎነትና ታማኝነት ከአንተ ጋር ይሁን።” አለው። 21 ኢታይ ግን ለንጉሡ፣ “ሕያው እግዚአብሔርን እንዲሁም በጌታዬ በንጉሡ እምላለሁ፤ ሕይወትም ይሁን ሞት ንጉሡ ወደሚሄድበት ወደየትኛውም ቦታ አገልጋይህም ይሄዳል።” ብሎ መለሰለት። 22 ስለዚህ ዳዊት ለኢታይ፣ “እንግዲያውስ፣ ከእኛ ጋር መሄድህን ቀጥል” አለው። ከእርሱ ጋር ከነበሩት ሰዎች ሁሉና አብረውት ከነበሩት ቤተሰቦቹ ሁሉ ጋር ጌታዊው ኢታይ ከንጉሡ ጋር ተጓዘ። 23 ሕዝቡ ሁሉ ንጉሡም ራሱ የቄድሮንን ወንዝ ሲሻገሩ የአገሩ ሕዝብ ድምፁን ከፍ አድርጎ አለቀሰ። ሕዝቡ ሁሉ ወደ ምድረ-በዳ በሚወስደው መንገድ ተጓዘ። 24 ሳዶቅም እንኳን የእግዚአብሔርን የኪዳን ታቦት ከተሸከሙት ሌዋውያን ጋር በዚያ ነበር። የእግዚአብሔርን ታቦት አስቀመጡትና አብያታር ከእነርሱ ጋር ሆነ፤ እነርሱም ሕዝቡ ሁሉ ከከተማይቱ እስኪወጡ ድረስ ጠበቁ። 25 ንጉሡም ሳዶቅን፣ “ታቦቱን ወደ ከተማይቱ ይዘህ ተመለስ፣ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ ካገኘሁ ወደዚህ መልሶ ያመጣኛል፣ ታቦቱንና እርሱም የሚኖርበትን ስፍራ እንደገና ያሳየኛል። 26 ነገር ግን እርሱ፣ ‘በአንተ አልተደሰትሁም’ ካለኝ፣ እነሆ፣ በፊቱ አለሁ፣ መልካም መስሎ የታየውን ያድርግብኝ።” 27 ንጉሡ ለካህኑ ለሳዶቅ፣ “አንተ ነቢይ አይደለህምን? አንተ ከሁለቱ ልጆችህ፣ ከልጅህ አኪማአስና ከአብያታር ልጅ ከዮናታን ጋር ሆናችሁ በሰላም ወደ ከተማይቱ ተመለሱ። 28 ከአንተ ዘንድ መልእክት እስካገኝ ድረስ፣ እነሆ፣ እኔ በአረባ በሚገኘው በወንዙ መሻገሪያ እቆያለሁ።” 29 ስለዚህ ሳዶቅና አብያታር የእግዚአብሔርን ታቦት ይዘው ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው እዚያው ቆዩ። 30 ዳዊት ግን እያለቀሰ በባዶ እግሩ የደብረ ዘይትን ተራራ ሸቅብ ወጣ፣ ራሱንም ተከናንቦ ነበር። ከእርሱ ጋር የነበረውም እያንዳንዱ ሰው ራሱን ተከናንቦ ነበር፤ እየሄዱም ሳሉ ያለቅሱ ነበር። 31 አንድ ሰውም ለዳዊት፣ “በሤራው ውስጥ ከአቤሴሎም ጋር ካሉት አንደኛው አኪጦፌል ነው” ብሎ ነገረው። ስለዚህ ዳዊት፣ “እባክህ፣ እግዚአብሔር ሆይ፣ የአኪጦፌልን ምክር ወደ ሞኝነት ለውጠው” ብሎ ጸለየ። 32 ዳዊት እግዚአብሔር ወደሚመለክበት ወደ መንገዱ ጫፍ በደረሰ ጊዜ፣ አርካዊው ኩሲ መጎናጸፊያውን ቀድዶ ትቢያ በራሱ ላይ ነስንሶ ሊገናኘው መጣ። 33 ዳዊትም ለእርሱ፣ “አብረኸኝ ብትሄድ ሸክም ትህንብኛለህ፤ 34 ነገር ግን ወደ ከተማይቱ ተመልሰህ አቤሴሎምን ‘ንጉሥ ሆይ፣ አገልጋይህ እሆናለሁ፣ ቀድሞ የአባትህ አገልጋይ እንደ ነበርሁ ሁሉ አሁን ደግሞ የአንተ አገልጋይ እሆናለሁ’ ብትለው የአኪጦፌልን ምክር በማደናገር ትረዳኛለህ። 35 ካህናቱ ሳዶቅና አብያታር እዚያው ከአንተ ጋር አሉልህ አይደለምን? በንጉሡ ቤተ መንግሥት የምትሰማውን ማንኛውንም ነገር ለካህናቱ ለሳዶቅና ለአብያታር መንገር አለብህ። 36 የሳዶቅ ልጅ አኪማአስና የአብያታር ልጅ ዮናታን ሁለቱ ወንዶች ልጆች በዚያ አብረዋቸው መሆናቸውን አረጋግጥ። የምትሰማውን ማንኛውንም ነገር በእነርሱ በኩል ላክልኝ።” 37 ስለዚህ የዳዊት ወዳጅ ኩሲ አቤሴሎም ኢየሩሳሌም በገባበት በዚያው ወቅት ወደ ከተማይቱ መጣ።

---

2 Samuel 15:1

እንዲህም ሆነ
ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ፍሰት ቀጣዩን ትዕይንት ለማስተዋወቅ ነው። (አዲስ ትዕይንት ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

በፊቱ ከሚሮጡ ሀምሳ ሰዎች ጋር
እነዚህ ሰዎች አቤሴሎምን ለማክበር ከሰረገላው ፊት ይሮጣሉ። "እርሱን ለማክበር በፊቱ ከሚሮጡ ሀምሳ ሰዎች ጋር" (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ አገልጋይ
አንድ ሰው ለአቤሴሎም ጥያቄ ምላሽ በሚሰጥበት ወቅት ለእርሱ ክብር ለመስጠት "የአንተ አገልጋይ" በማለት ራሱን ይጠራ ነበር።

2 Samuel 15:3

አቤሴሎምም ያንን ሰው እንዲህ ይለው ነበር
ሰውየው ለአቤሴሎም ጉዳዩን እንደሚናገር በውስጠ ታዋቂነት ተጠቅሷል። ይህ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "አቤሴሎም ሰውየውን ችግሩ ምን እንደሆነ ይጠይቀዋል፣ ከዚያም ሰውየው ፍትህ እንደሚፈልግ ለአቤሴሎም አብራርቶ ይናገራል። ከዚያም አቤሴለም ለሰውየው እንዲህ ይላል" በሚለው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መልካም እና ትክክል
እነዚህ ቃላት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው በአንድነት የዋሉት የእርሱ ጉዳይ መልካም እንደሆነ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ጉዳይህን ለመስማት
ጉዳይን "መስማት" ማለት ነገሩን መስማት እና በዚያ ላይ የውሳኔ ፍርድ መስጠት ማለት ነው። "ጉዳይህን ለመበየን/በጉዳይህ ላይ ፍርድ ለመስጠት" ወይም "የአንተን ጉዳይ ከላይ ሆኖ ለማየት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 15:5

እጁን ዘርግቶ ያቅፍና ይስም ነበር
ይህ ድርጊት የወዳጅነት ሰላምታ ነው። "በማቀፍና በመሳም እንደ ወዳጅ ሰላምታ ይሰጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ፍርድ ለማግኘት
ይህ ማለት ለክርክራቸው ብይን ለማግኘት ወደ ንጉሡ ይመጣሉ። "ለክርክራቸው ብይን ለማግኘት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚህ አይነት አቤሴሎም የእስራኤልን ሰዎች ልብ ሰረቀ
የዚህ ዐረፍተ ነገር ትርጉም አቤሴሎም ሰዎች ከዳዊት ይልቅ ለእርሱ ታማኝ እንዲሆኑ ያሳምናቸው ነበር ማለት ነው። እዚህ ስፍራ ጸሐፊው እርሱ ልባቸውን ሰረቀ በማለት ሰዎች እንዴት ለአቤሴሎም ታማኝ እንደሆኑ ይናገራል። "አቤሴሎም በዚህ መንገድ የእስረኤል ሰዎች ለእርሱ ታማኝ እንዲሆኑ አሳመናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 15:7

እንዲህም ሆነ
ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ፍሰት ቀጣዩን ትዕይንት ለማስተዋወቅ ነው። (አዲስ ትዕይንት ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

አቤሴሎም ከ ... አራት አመት በኋላ
ይህ የሚያመለክተው እርሱ ከኢየሩሳሌም ከተመለሰ ከአራት አመት በኋላ ነው። "አቤሴሎም ወደ ኢየሩሳሌም ከተመለሰ ከአራት አመት በኋላ፣ እርሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እናም በኬብሮን ለያህዌ የተሳልኩትን ለመስጠት
"በኬብሮን ለያህዌ የገባሁትን ስለት ለመፈጸም"

ለአገልጋይህ
እዚህ ስፍራ አቤሴሎም ራሱን በዚህ መንገድ የሚገልጸው ንጉሡን ለማክበር ነው።

2 Samuel 15:9

ስለዚህም አቤሴሎም ተነሳ
"ስለዚህም አቤሴሎም ሄደ"

በመላው እስራኤል ነገዶች
እዚህ ስፍራ የእስራኤል ነገዶች የሚኖሩበት ስፍራ የተጠቀሰው ራሳቸውን ነገዶቹን ተደርጎ ነው። "በእስራኤል ነገዶች ምድር በሙሉ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የመለከት ደምጽ
"መለከት ሲነፋ"

2 Samuel 15:11

የተጋበዙት
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እርሱ የጋበዛቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በየዋህነታቸው ሄዱ
"በየዋህነት ሄዱ"

ወደ አኪጦፌል ላከ
ይህ ማለት አኪጦፌልን እንዲያገኙትና ወደ እርሱ እንዲያመጡት መልዕክተኛ ላከ። "... የነበረውን አኪጦፌልን አግኝተው እንዲያመጡት መልዕክተኛ ላከ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አኪጦፌል
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ጊሎ
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 15:13

የእስራኤል ሰዎች ልብ ከ... በኋላ ሄደ
እዚህ ስፍራ ሰዎች "በልባቸው" የተጠቀሱት ለአቤሴሎም ያላቸውን ታማኝነት ለማጉላት ነው። "የእስራኤል ሰዎች ለ...ታማኞች ናቸው" ወይም "የእስራኤል ሰዎች... እየተከተሉ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ከአቤሴሎም እናምልጥ... ፈጥኖ ...እናም እርሱ...ያመጣብናል
እዚህ ስፍራ ዳዊት ስለ አቤሴሎም እና ከእርሱ ጋር ስላሉት ሰዎች በአንድነት ስለ "አቤሴሎም" እንደሚናገር አድርጎ ይናገራል፤ ምክንያቱ ሰዎቹ የአቤሴሎምን ስልጣን ስለተቀበሉ/ስለተከተሉት ነው። "ከአቤሴሎም እና ከሰዎቹ እናምልጥ... እርሱ እና ሰዎቹ በፍጥነት... እናም... ያመጡብናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ከተማይቱን በሰይፍ ስለት ያጠቃታል
"ከተማይቱ" የሚለው በከተማዋ የሚኖሩ ሰዎችን የሚያመለክት ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "የሰይፍ ስለት" የሚለው የእስራኤላውያንን ሰይፎች የሚያመለክት እና በጦርነት ሰዎቹን መግደላቸውን የሚያጎላ ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ነው። "የከተማችንን ሰዎች ያጠቃሉ ደግሞም በሰይፎቻቸው ይገድሏቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

ጥፋት ያወርዱብናል
ይህ ጥፋት እንዲደርስ ምክንያት መሆን ማለት ነው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Samuel 15:16

ቤቱን እንዲጠብቁ
እዚህ ስፍራ "መጠበቅ" የሚለው ቃል ጥንቃቄ ማድረግ ማለት ነው። "ቤቱን እንዲጠብቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በመጨረሻው ቤት
ይህ የሚያመለክተው ከተማይቱን ለቀው ሲወጡ የሚመጡበትን የመጨረሻ ቤት ነው። "ከተማይቱን ለቀው ሲወጡ የመጨረሻው ቤት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከሊታውያን... ፈሊታውያን
የእነዚህን የህዝብ ወገኖች ስም በ2 ሳሙኤል 8፡18 ላይ እንደ ተረጎሙት በተመሳሳይ ይተርጉሙ።

ጌትያውያን
ይህን የህዝብ ወገን ስም በ2 ሳሙኤል 6፡10 ላይ እንደ ተረጎሙት በተመሳሳይ ይተርጉሙ።

ስድስት መቶ ወንዶች
"600 ወንዶች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 15:19

ኢታይ
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ጌትያዊ
ይህን የህዝብ ወገን ስም በ2 ሳሙኤል 6፡10 ላይ እንደ ተረጎሙት በተመሳሳይ ይተርጉሙ።

ለምን ከእኛ ጋር ትመጣለህ?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚያመለክተው ንጉሡ እነርሱ ከእርሱ ጋር መሄድ አለባቸው ብሎ አንደማያስብ ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንተ ከእኛ ጋር መሄድ አያስፈልግህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ለምን አንተ ከእኛ ጋር እንድትንከራተት አደርጋለሁ?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ ዳዊት ኢታይ እንዲመጣ አለመፈለጉን ያጎላል። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ከእኛ ጋር እንድትዞር ላደርግ አልፈልግም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የመጣኸው ገና ትናንትን ነው
እዚህ ስፍራ "ትናንት" የሚለው በቅርብ ጊዜ የሚለውን ለማጋነን ነው። የጌት ሰው ኢታይ በዚያ ብዙ አመት ኖሯል። "በዚህ ስፍራ የኖርከው ለአጭር ጊዜ ብቻ እንደመሆኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

ታማኝነት እና እውነተኝነት ከአንተ ጋር ይሁኑ
ይህ ዳዊት ለእርሱ የሰጠው በረከት/ምርቃት ነው። "ያህዌ ሁሌም ለአንተ ታማኝነቱን እና እውነቱን ያድርግልህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 15:21

ህያው እግዚአብሔርን! በጌታዬ በንጉሡ ህይወት እምላለሁ
እዚህ ስፍራ ተናጋሪው ብርቱ ቃል ኪዳን ይገባል። ቃል ኪዳኑን የመጠበቁን እርግጠኝነት ከያህዌ እና ከንጉሡ ህያውነት ጋር ያነጻጽራልለ። "በያህዌ እና በንጉሡ ህይወት በጽኑ ቃል እገባለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አገልጋይህ
እዚህ ስፍራ ኢታይ ራሱን በዚህ መንገድ የሚገልጸው ንጉሡን ለማክበር ነው።

በሞትም ሆነ በህይወት
"አንተን እየደገፍኩ ብገደል እንኳን"

መላው አገር በጮኸት አለቀሰ
ብዙዎቹ የእስራኤል ሰዎች ንጉሡ ለቆ ሲወጣ በጮኸት አለቀሱ። እዚህ ይህ ማጠቃለያ የቀረበው መላው አገር አለቀሰ በሚል ነው። "በመንገድ የነበረው ህዝብ ሁሉ አለቀሰ" ወይም "ብዙ ህዝብ አለቀሰ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

ከፍ ባለ ድምጽ
እዚህ የሚያለቅሰው ህዝብ የተነገረው ሁሉም አንድ ከፍ ያለ ድምጽ እንደተጋሩ ተደርጎ ነው። "ጮኸው/ከፍ ባለ ድምጽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ቄድሮን ሸለቆ
ይህ ኢየሩሳሌም አጠገብ የሚገኝ ቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 15:24

በያህዌ ዐይኖች ሞገስ አግኝቻለሁ
እዚህ "የያህዌ ዐይኖች" የሚለው የሚያመለክተው የያህዌን ፈቃድና ሃሳብ ነው። በሰዎች ዘንድ "ሞገስ ካገኘህ" በአንተ ተደስተዋል ማለት ነው። "ያህዌ በእኔ ደስ ተሰኝቷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

እርሱ በሚኖርበት
"የእርሱ መገኘት ባለበት።" የቃል ኪዳኑ ታቦት የሚወክለው የያህዌን መገኘት ነው። ይህ የሚያመለክተው ታቦቱ የሚገኝበትን ስፍራ ነው። "የተቀመጠበት ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 15:27

አኪማስ
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አብያታር
ይህን የወንድ ስም በ2 ሳሙኤል 8፡17 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

አንተ ነቢይ አይደለህምን?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ ሳዶቅን ለመገሰጽ ሲውል በዐረፍተ ነገር ሊተረጎምም ይችላል። "ሊሆን ያለውን ማወቅ ትችላለህ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እይ/እነሆ
ይህ ቃል አድማጩ ቀጥሎ ለሚነገረው ትኩረት እንዲሰጥ የሚያደርግ ነው። "ስማ/አድምጥ" በሚለው ወስጥ እንደሚገኘው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከአንተ ቃል እስኪመጣ ድረስ
ይህ ለንጉሡ መልዕክተኛ መላክን የሚያመለክት ነው። "ለእኔ መረጃ ለመስጠት ወደ እኔ መልዕክተኛ እስክትልክ ድረስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

መረጃ እንድትሰጠኝ
እዚህ ስፍራ ንጉሡ በኢየሩሳሌም እየሆነ ስላለው መረጃ እንደሚደርሰው ይጠቁማል። "በኢየሩሳሌም እየሆነ ያለውን እንድትነግረኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 15:30

ባዶ እግር
ጫማ ወይም ነጠላ ጫማ/ሰንደል ሳይደረግ

ራሱ ተከናንቦ
ይህ የሀዘን እና ሀፍረት ምልክት ነው። "ራሱን በሀዘን ተከናንቦ " በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

አኪጦፌል
ይህን የወንድ ስም በ2 ሳሙኤል 15፡11 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

ሴረኞች/አድመኞች
በአንድ ሌላ ሰው ላይ በተቃውሞ አብረው የሆኑ ሰዎች

እባክህ የአኪጦፌልን ምክር ከንቱ አድርግ
ዳዊት ያህዌን የአኪጦፌልን ምክር ሞኝነት እና ጥቅም የሌለው እንዲያደርግ ይለምናል። "እባክህ አኪጦፌል የሚመክረውን ምክር ሁሉ ሞኝነት እና እርባና ቢስ አድርገው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 15:32

እንዲህም ሆነ
ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ፍሰት ቀጣዩን ትዕይንት ለማስተዋወቅ ነው። (አዲስ ትዕይንት ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

በመንገዱ ጫፍ
እዚህ ስፍራ"ጫፍ" ሚለው ቃል የዋለው ዳዊት ከታች ወደ ላይ ስለወጣ እና ወደ ኮረብታው ጫፍ ስለሄደ ነው። "ከኮረብታው ጫፍ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ይመለክበት በነበረበት ስፍራ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች በአንድ ወቅት እግዚአብሔርን ያመልኩ በነበረበት ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ኩሲ
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አርካዊ
ይህ የአንድ ወገን ህዝብ የሆኑ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ልብሱን ቀዶ እና ራሱ ላይ አፈር ነስንሶ
ይህ ሀፍረትን እና መጸጸትን የሚገልጽ ድርጊት ነው። እዚህ ስፍራ "አፈር" የሚለው "ትቢያ" ነው። "እጅግ ማዘኑን ለማሳየት ልብሱን ቀደደ፣ በራሱም ላይ ትቢያ ነሰነሰ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

የአኪጦፌልን ምክር ከንቱ ታደርግልኛለህ
ዳዊት ለኩሲ የአኪጦፌልን ምክር ሁሉ ከንቱ እንዲያደርግ ሀሳብ ያቀርብለታል። "የአኪጦፌልን ምክር በማፍረስ/በመቃወም ልታገለግለኝ ትችላለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 15:35

ካህናቱ ሳዶቅ እና አብያታር ከአንተ ጋር አይደሉምን?
ዳዊት ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠይቀው ኩሲ ብቻውን እንደማይሆን ሊነግረው ፈልጎ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ካህናቱ ሳዶቅ እና አብያታር አንተን ለመርዳት በዚያ ይገኛሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የምትሰማውን ሁሉ
ይህ አጠቃላይ አስተያየት ነው። ይህ ማለት ማናቸውንም ጠቃሚ እና መረጃ ሊሆኑ የሚችሉ የሚሰማቸውን ነገሮች ማለት እንጂ እያንዳንዷን ቃል ማለት አይደለም። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

አኪማአስ...ዮናታን
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በእጃቸው
"እጃቸው" የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው ወጣት ወንዶችን ሲሆን እነርሱም መልዕክተኛ ሆነው ያገለግላሉ ማለት ነው። "ልጆቻቸው ለእኔ እንዲነግሩኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 16

1 ዳዊት ከተራራው ጫፍ ባሻገር ጥቂት እልፍ ብሎ እንደሄደ ሲባ የተባለው የሜምፊቦስቴ አገልጋይ፣ ሁለት መቶ እንጀራ አንድ ሙሉ ጥፍጥፍ ዘቢብ አንድ መቶ
ጥፍጥፍ በለስና አንድ አቁማዳ የወይን ጠጅ የተጫኑ ሁለት አህዮች ይዞ ተገናኘው። 2 ንጉሡም ሲባን፣ “ይህን ሁሉ ያመጣኸው ለምንድን ነው?” ሲል
ጠየቀው። ሲባም፣ “አህዮቹን የንጉሡ ቤተ ሰቦች እንዲቀመጡባቸው፣ እንጀራውንና በለሱን ከአንተ ጋር ያሉት ሰዎች እንዲበሉት፣ የወይን ጠጁ ደግሞ በምድረ-
በዳ የደከመ ማንኛውም ሰው እንዲጠጣው ነው” አለው። 3 ንጉሡም፣ “የጌታህ የልጅ ልጅ የት ነው?” አለው። ሲባም ለንጉሡ፣ “’ዛሬ የእስራኤል ቤት
የአባቴን መንግሥት ለእኔ ይመልስልኛል’ እያለ ስለነበረ፣ እነሆ፣ በኢየሩሳሌም ተቀምጦአል” ብሎ መለሰለት። 4 ከዚያም ንጉሡ ሲባን፣ “የሜምፊቦስቴ የነበረው
ሁሉ ከእንግዲህ፣ እነሆ፣ የአንተ ሆኖአል” አለው። ሲባም፣ “ጌታዬ ንጉሥ ሆይ በትሕትና በፊትህ እጅ እነሣለሁ፣ በፊትህ ሞገስ ላግኝ” አለው። 5 ንጉሥ ዳዊት
ወደ ብራቂም ሲደርስ ከሳዖል ቤተሰብ ነገድ የሆነ የጌራ ልጅ ሳሚ ብቅ አለ፡ እርሱም እየመጣ ሳለ ይራገም ነበር። 6 የንጉሡ ወታደሮችና የክብር ዘቦቹ ሁሉ
በዳዊትና ግራና ቀኝ ቢኖሩም እንኳን፣ በዳዊትና በሹማምንቱ ላይ ድንጋይ ይወረውርባቸው ነበር። 7 ሳሚም እንደዚህ ብሎ ተራገመ፣ “ውጣ፣ ከዚህ ውጣ፣ አንተ
ወሮበላ፣ አንተ የደም ሰው፤ 8 በእርሱ ምትክ የነገሥህበትን የሳዖልን ቤተሰብ ደም ብድራት ሁሉ እግዚአብሔር እየከፈለህ ነው። እግዚአብሔር መንግሥቱን
በልጅህ በአቤሴሎም እጅ አሳልፎ ሰጥቷል። አሁንም አንተ የደም ሰው ስለሆንክ ጥፋት ደርሶብሃል።” 9 ከዚህ በኋላ የጽሩይ ልጅ አቢሳ፣ “ይህ የሞተ ውሻ
ንጉሡ ጌታዬን ለምን ይራገማል? እባክህ፣ ተሻግሬ ልሂድና ራሱን ልቁረጠው” አለ። 10 ንጉሡ ግን፣ “እናንተ የጽሩያ ልጆች፣ እኔ ከእናንተ ጋር ምን አለኝ? እርሱ
የሚረግመኝ ምናልባት እግዚአብሔር፣ ‘ዳዊትን ርገመው’ ብሎት ይሆናል። ታዲያ እርሱን፣ ‘ንጉሡን ለምን ትረግማለህ?’ ሊለው የሚችለው ማን ነው?” 11
ስለዚህ ዳዊት ለአቢሳና ለአገልጋዮቹ ሁሉ፣ “ከአብራኬ የወጣው ልጄ ነፍሴን ሊያጠፋት ከፈለገ፣ ይህ ብንያማዊ ምን ያህል ጥፋቴን አይፈልግ? እግዚአብሔር
እንዲራገም አዞት ይሆናልና፣ ተዉት፣ ይራገም። 12 ምናልባት የተሰነዘረብኝን ውርደት እግዚአብሔር ተመልክቶ ስለ ዛሬው እርግማኑ በጎ ያደርግልኝ ይሆናል።”
13 ስለዚህም ዳዊትና ሰዎቹ በመንገዱ ጉዟቸውን ቀጠሉ፣ ሳሚም በኮረብታው ጥግ ጥግ እየሄደ ድንጋይ ይወረውር አቧራም ይበትንበት ነበር። 14 ከዚህ በኋላ
ንጉሡና ከእርሱ ጋር የነበሩት የእስራኤል ሰዎች ደከሙ፣ እነርሱም ለምሽቱ በሚቆሙበት ጊዜ እርሱ ዕረፍቱ አደረገ። 15 አቤሴሎምና ከእነርሱ ጋር የነበሩት
የእስራኤል ሰዎች ሁሉ በበኩላቸው ወደ ኢየሩሳሌም መጡ፣ አኪጦፌልም ከእርሱ ጋር ነበረ። 16 የዳዊት ወዳጅ፣ አርካዊው ኩሲም ወደ አቤሴሎም በመጣ
ጊዜ፣ “ንጉሥ ሆይ፣ ለዘላለም ንገሥ! ንጉሥ ሆይ፣ ለዘላለም ንገሥ!” አለው። 17 አቤሴሎምም ኩሲን፣ “ለወዳጅህ ያለህ ታማኝነት ይሄ ነው? ለምን ከእርሱ
ጋር አልሄድህም?” አለው። 18 ኩሲም አቤሴሎምን፣ “አይሆንም፣ ይልቁኑ እግዚአብሔርና ይህ ሕዝብ እንዲሁም የእስራኤል ሰዎች ሁሉ ከመረጡት ከእርሱ
ጋር ነው እኔ የምሆነው፣ ከእርሱም ጋር እቆያለሁ። 19 ላገለግለው የሚገባኝ ሰው ማን ነው? በልጁስ ፊት ላገለግል አይገባኝምን? በአባትህ ፊት እንዳገለገልሁ
በአንተም ፊት አገለግላለሁ።” 20 ከዚያ በኋላ አቤሴሎም ለአኪጦፌል፣ “ምን ማድረግ እንደሚገባን ምክርህን ስጠን” አለው። 21 አኪጦፌልም
ለአቤሴሎም፣ “ቤተ መንግሥቱን እንዲጠብቁ አባትህ ከተዋቸው ቁባቶቹ ጋር ግባና ተኛ፣ ከዚያም አንተ ለአባትህ መጥፎ ጠረን እንዳለው ሰው እንደሆንክበት
እስራኤል ሁሉ ይሰማል፤ ከዚያም ከአንተ ጋር ያሉት ሰዎች ሁሉ እጅ ይበረታል።” 22 ስለዚህ በቤተ መንግሥቱ ሰገነት ላይ ለአቤሴሎም ድንኳን ተከሉለት፤
አቤሴሎምም መላው እስራኤል እያየው ከአባቱ ቁባቶች ጋር ተኛ። 23 በዚያን ጊዜ አኪጦፌል ይሰጠው የነበረው ምክር ከእግዚአብሔር ከራሱ አፍ እንደ
መስማት ያለ ነበር። ዳዊትም ሆነ አቤሴሎም ለአኪጦፌል ምክር የነበራቸው ግምት እንደዚህ ነበር።

---

2 Samuel 16:1

ሲባ
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሜምፊቦስቴ
ይህን የወንድ ስም በ2 ሳሙኤል 4፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

ሁለት መቶ የተቦካ...አንድ መቶ ጥፍጥፍ... አንድ መቶ ዘለላ
"200 የተጋገረ...100 ጥፍጥፍ... አንድ መቶ ዘለላ" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

የተጋገር እንጀራ
"እንጀራ"

የዘቢብ ዘላላ... የበለስ ጥፍጥፍ
እነዚህ ሀረጎች የሚያመለክቱት በአንድነት የተጨመቁ ዘቢብ እና በለስን ነው

ዘቢብ
የደረቀ ወይን

አቁማዳ ወይን
"አቁማዳ ሙሉ ወይን"

መድከም
አቅም ማጣት እና ድካም መሰማት

2 Samuel 16:3

የጌታህ የልጅ ልጅ
" የጌታህ የልጅ ልጅ፣ ሜምፊቦስቴ"

የልጅ ልጅ
የአንድ ሰው የወንድ ወይም የሴት ልጁ ልጅ

እይ/እነሆ
ይህ ቃል አድማጩ ቀጥሎ ለሚነገረው ትኩረት እንዲሰጥ የሚያደርግ ነው። "ስማ/አድምጥ" በሚለው ወስጥ እንደሚገኘው።

የእስራኤል ቤት
ይህ የስስራኤልን ህዝብ ያመለክታል። "የእስራኤል ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የአባቴን መንግሥት ለእኔ ይመልሳል
እንዲገዛ የሚፈቀዶለት የሳኦል ትውልድ ስለመገኘቱ የተገለጸው መንግስቱ ለቤተሰባቸው እንደሚመለስ ተደርጎ ነው። "አያቴ ይገዛው የነበረውን መንግስት እንድገዛ ትፈቅድልኛለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሜምፊቦስቴ
ይህን የወንድ ስም በ2 ሳሙኤል 4፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለአንተ በትህትና/ዝቅ ብዬ እሰግዳለሁ
ሲባ እዚህ ስፍራ ይህን ሲናገር በንጉሡ ፊት ወደቆ አልሰገደም። ይህ ማለት በንጉሡ ፊት ቢሰግድ በሚያሳየው በዚያው አይነቱ ትህትና ንጉሡን ያገለግላል ማለት ነው። "በታላቅ ትህትና አገለግልሃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በዐይኖች ፊት ሞገስ ላግኝ
"ሞገስ ማግኘት" የሚለው ሀረግ በአንድ ሰው ዘንድ ተቀባይነትን ማግኘት የሚል ትርጉም አለው። እንደዚሁም "ዐይኖች" መታየት ለሚለው ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሲሆን፣ መታየት ፍትህን ወይም ሚዛንን ይወክላል። "አንተ በእኔ ደስ እንድትሰኝ እፈልጋለሁ" ወይም "አንተ በእኔ ደስ እንዲልህ እመኛለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

2 Samuel 16:5

ብራቂም
የዚህችን ከተማ ስም በ 2 ሳሙኤል 3፡16 ላይ በተተረጎመው መሰረት ይተርጉሙ

ሳሚ...ጌራ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው።

ቢኖሩም አንኳን
"ምንም እንኳን በዚያ ቢኖሩም"

ጠባቂች/የክብር ዘቦች
እነዚህ ክብር ያለውን ሰው የሚጠብቁ ሰዎች ናቸው

2 Samuel 16:7

ክፉ/ተንኮለኛ
ክፉ፣ ወንጀለኛ ወይም ህግ የማያከብር ሰው

የደም ሰው
እዚህ ስፍራ "ደም" የሚለው የሚያመለክተው እርሱ ተጠያቂ ለሆነባቸው በጦርነት ለተገደሉ ሰዎች ሁሉ ነው። "ነብሰ ገዳይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ የስራህን እየከፈለህ ነው
ያህዌ እነርሱን በመቅጣት እየከፈላቸው ነው። ይህ በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "ያህዌ ቀጥቶሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በሳኦል ቤት ውስጥ ላፈሰስከው ደም
እዚህ ስፍራ "ደም" የሚለው የሚያመለክተው ከሳኦል ቤት የተገደሉ ሰዎችን ነው። ንጉሡ ለእነርሱ መሞት ተጠያቂ ነው። "ብዙዎቹን የሳኦል ቤተሰቦች በመግደል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በማን ስፍራ/የማንን ስፍራ ይዘህ ስትገዛ ኖርክ
ዳዊት ንጉሥ ሆኖ የገዛው ሳኦል አስቀድሞ ይገዛቸው የነበሩትን እነዚያኑ ህዝቦች ነው። "ንጉሥ ሆነህ የገዛኸው በማን ስፍራ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በአቤሴሎም እጅ ውስጥ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው የሚያመለክተው በቁጥጥር ስር ማድረግን ነው። "በአቤሴሎም ቁጥጥር ስር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 16:9

አቢሳ
ይህ የወንድ ስም በ 2 ሳሙኤል 2፡18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ጽሩያ
ይህ የወንድ ስም በ 2 ሳሙኤል 2፡13 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ለምን ይህ የሞተ ውሻ ጌታዬን ንጉሡን ይራገማል?
አቢሳ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው በሰውየው ላይ ቁጣውን ለመግለጽ ነው።ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ይህ የሞተ ውሻ ንጉሡን በዚህ መንገድ መናገር የለበትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ምናልባት እርሱ እኔን የሚረግምበት ምክንያት
"እኔን የሚረግምበት ምክንያት"

እርሱን ማን ‘ለምን ንጉሡን ትራገማለህ' ሊለው ይችላል?
ይህ እንደ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተነገረው መልሱ "ማንም" የሚለው መሆኑን ለማጉላት ነው።ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። ማንም ቢሆን ‘ለምን ንጉሡን ትራገማለህ?' ብሎ ሊጠይቀው አይችልም። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 16:11

ከአብራኬ የተወለደ የእኔው ልጅ
ዳዊት ልጁን በዚህ መንገድ የገለጸው በልጁ እና በአባቱ መሃል ያለውን ጥብቅ ትስስር ለማጉላት ነው። "የራሴ ልጅ" ወይም "ውድ ልጄ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ህይወቴን መውሰድ/ለመንጠቅ ይፈልጋል
ይህ አንድን ሰው መግደልን ሻል ባለ ቃል መግለጽ ነው። "ሊገድለኝ ይፈልጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

ይልቁንስ ይህ ብንያማዊ ምን ያህል ይበልጥ የእኔን ጥፋት ይፈልጋል?
ዳዊት ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ሰውየው ሊገድለው በመፈለጉ የማይደነቅ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በእርግጥ ይህ ብንያማዊ የእኔን ጥፋት ይፈልጋል!" ወይም "ይህ ብንያማዊ የእኔን ጥፋት መፈለጉ አያስደንቀኝም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥፋቴን ይፈልጋል
እዚህ ስፍራ ዳዊት ሰውየው እርሱን ለመግደል ያለውን ፍላጎት የሚገልጸው ሰውየው ሊያጠፋው የሚፈልገው ነገር ዳዊትን እንደሆነ አድርጎ ነው። "እኔ እንድገደል ይፈልጋል" ወይም "ሊገድለኝ ይፈልጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ተዉት ግድ የለም ይራገም
እዚህ ስፍራ "ተዉት ግድ የለም" የሚለው ሀረግ እያደረገ የሚገኘውን አለማስቆም ማለት ነው። "እኔን መራገሙን አታስቁሙት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይመለከት ይሆናል
እዚህ ስፍራ "መመልከት" የሚለው "ስፍራ ሰጥቶት/ተመልክቶ" ማለት ነው። "ዋጋ ይሰጠው ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በላዬ የተለቀቀው/የወደቀ መከራ
እዚህ ስፍራ ዳዊት መከራን የሚገልጸው ብንያማዊያን በላዩ ፈትተው እንደለቀቁት አደገኛ እንስሳ አድርጎ ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 16:13

ሳሚ ከእርሱ አጠገብ በተራራው አናት ጥግ ጥጉን ይሄድ ነበር
ምንም እንኳን ከታራው አናት ላይ ቢሆነም፣ ሳሚ ከዳዊት እና ከወታደሮቹ ትይዩ ይሄድ ነበር

2 Samuel 16:15

አኪጦፌል
ይህ የወንድ ስም በ 2 ሳሙኤል 15:12 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ኩሲ
ይህ የወንድ ስም በ 2 ሳሙኤል 15:32 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህም ሆነ
"እንዲህ ሆነ።" ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ፍሰት ቀጣዩን ትዕይንት ለማስተዋወቅ ነው። (አዲስ ትዕይንት ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

አርካዊ
ይህ የህዝብ ወገን በ 2 ሳሙኤል 15:32 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 16:17

ታማኝነት
ብርቱ የድጋፍ እና ፍቅር ስሜት

ለወዳጅህ ያለህ ታማኝነት ይህ ነውን? ለምን ከእርሱ ጋር አልሄድክም?
እነዚህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች የተጠየቁት ኩሲን ለመተቸት ነው። እነዚህ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎሙ ይችላሉ። "ለዳዊት ታማኝ ወዳጅ ነበርክ፡ ከእርሱ ጋር መሄድ ነበረብህ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የህዌ እርሱን
ኩሲ እየገለጸ ያለው አቤሴሎምን ነው

እርሱን... ያ ሰው ነው... ከእርሱ ጋር
እዚህ ስፍራ ኩሲ ትኩረቱን ከእርሱ ላይ አንስቶ በያህዌ እና እርሱ በመረጠው ህዝብ ላይ ለማድረግ አቤሴሎምን በሶስተኛ መደብ እየገለጸ/እያመለከተ ነው። ይህ በሁለተኛ መደብ ሊጻፍ ይችላል። "አንተ ነህ... ያ ሰው አንተ ነህ... ከአንተ ጋር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 16:19

ማገልገል ያለብኝ ማንን ነው? ልጁን በስሩ ሆኜ ማገልገል የለብኝምን?
ኩሲ እነዚህን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች የጠየቀው አቤሴሎምን ለማገልገል መፈለጉን ለማጉላት ነው። በዐረፍተ ነገር ሊጻፉ ይችላሉ። "ማገልገል የሚገባኝ የዳዊትን ልጅ ብቻ ነው፣ ስለዚህም እርሱን በስሩ ሆኜ አገለግላለሁ።" ወይም "አንተ የዳዊት ልጅ በመሆንህ አንተን ማገልገል ይገባኛል።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 16:20

አኪጦፌል
ይህ የወንድ ስም በ 2 ሳሙኤል 15:12 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ቤተ መንግሥቱን እንዲጠብቁ
"ለመጠበቅ" የሚለው ሀረግ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ/እንዲንከባከቡ ማለት ነው። "ቤተ ምንግሥቱን መጠበቅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለአባትህ ክፉ ሽታ በመሆን
አኪጦፌል አቤሴሎም ለአባቱ ክፉ ሽታ የሆነ ያህል እንዲያስቆጣው ይመክረዋል። "አባትህን አስቆጣው/ስሜቱን ጉዳው" ወይም "አባታህን በታለቅ ሁኔታ ንቀፍ/ስደብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከአንተ ጋር ያሉ ሁሉ ክንድ ይጠነክራል/ይበረታል
እዚህ ስፍራ አቤሴሎምን የተከተሉ ሰዎች የተገለጹት በእጆቻቸው ነው። ወሬው ሰዎቹ ለአቤሴሎም ያላቸውን ታማኝነት ሲያጠነክር ህዝቡንም ያበረታታል። ይህ በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "የዚህ ወሬ አንተን የሚከተሉትን ሁሉ ታማኝነት ያጠነክራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

2 Samuel 16:22

ዘረጉ
"አበጁ"

እስራኤል ሁሉ እየተመለከተ
ይህ ማለት ህዝቡ ደንኳኑን እና አቤሴሎም ከሴቶቹ ጋር ወደ ደንኳኑ ውስጥ ሲገባ እና ሲወጣ ይመለከት ነበር ማለት ነው። "መላው እስራኤል" የሚለው ሀረግ በቤተ መንግሥቱ አቅራቢያ የሚገኙ ሰዎች ብቻ ይህን ሊመለከቱ እንደሚችሉ የሚገልጽ አጠቃላይ አስተያየት ነው። "ወደ ድንኳን ሲገባ እስራኤላውያን ሊመለከቱ የሚችሉበት ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚለውን ይመልከቱ)

የአኪጦፌል ምክር... አንድ ሰው ...እንደ መስማት ማለት ነበር
እዚህ ስፍራ ጸሐፊው ሰዎች ምን ያህል የአኪጦፌልን ምክር በቀጥታ ከእግዚአብሔር መስማትን ያህል እንሚያምኑበት ያነጻጽራል። "በነዚያ ወቅት ሰዎች የአኪጦፌልን ምክር ከ... እንደ ተጠየቀ/እንደ መጣ አድርገው ያምኑበት ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በቀጥታ እንደ ሰማ
እዚህ ስፍራ የእግዚአብሔር አፍ የሚለው የሚወክለው ራሱን እግዚአብሔርን እና የእርሱን ቃል ነው። "እግዚአብሔር በራሱ አፍ የተናገረውን ያህል" ወይም "አንድ ሰው በራሱ በእግዚአብሔር ሲነገር የሰማውን ያህል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ተጠቃሽ ተውላጠ ስም የሚሉትን ይመልከቱ)

የአኪጦፌል ምክር በሙሉ በዳዊት እና በአቤሴሎም በሁለቱም... ይታይ/ይቆጠር ነበረው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ዳዊት እና አቤሴሎም ሁለቱም የአኤጦፌልን ምክር... ይመለከቱ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይታይ/ይቆጠር ነበር
"ይታሰብ ነበር"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 17

1 ከዚህ በኋላ አኪጦፌል ለአቤሴሎም፣ “አሥራ ሁለት ሺህ ሰው መርጬ በዛሬይቱ ሌሊት አባትህን አሳድደዋለሁ፤ 2 በደከመውና ዐቅም ባነሰው ጊዜ ድንገት
ደርሼ በማስፈራት አስደንቀዋለሁ፤ አብሮት ያለው ሕዝብም ይሸሻል፣ በንጉሡ ላይ ብቻ ጥቃት አደርስበታለሁ። 3 ሙሽራ ወደ ባሏ እንደምትመጣ ሕዝቡን ሁሉ
ወደ አንተ እመልሳለሁ፤ ሕዝቡም ሁሉ በአንተ ሥር በሰላም ይሆናል።” 4 አኪጦፌል የተናገረውም አቤሴሎምንና የእስራኤልን ሽማግሌዎች ሁሉ ደስ
አሰኛቸው። 5 ከዚያ በኋላ አቤሴሎም፣ “አርካዊውን ኩሲን አሁን ጥሩትና እስቲ፣ እርሱ ደግሞ የሚለውን እንስማ” አለ። 6 ኩሲ ወደ አቤሴሎም በመጣ ጊዜ፣
አኪጦፌል ያለውን ከገለጸለት በኋላ፣ ኩሲን፣ “አኪጦፌል ያለውን እናድርግ? ካልሆነም የምትመክረንን አንተ ንገረን።” 7 ስለዚህ ኩሱ ለአቤሴሎም፣
“አኪጠፌል በዚህን ጊዜ የሰጠው ምክር መልካም አይደለም።” ካለ በኋላ፣ 8 ኩሲ በመቀጠል፣ “አባትህና ሰዎቹ ብርቱ ተዋጊዎችና ግልገሎቿ በሜዳ
እንደተነጠቁባት ድብ መራሮች እንደሆኑ አንተ ታውቃለህ። አባትህ የጦር ሰው ነው፣ በዛሬው ሌሊት ከሠራዊቱ ጋር አይተኛም። 9 እነሆ፣ አሁን እንኳ በአንዱ ዋሻ
ወይም በሌላ ቦታ ተደብቆ ይሆናል። በውጊያው መጀመሪያ ላይ ከአንተ ሰዎች ጥቂቶቹ ቢሞቱ፣ ያንን የሰማ ማንኛውም ሰው፣ ‘አቤሴሎምን ይከተሉ በነበሩት ላይ
እልቂት ተፈጽሟል’ ይላል። 10 ከዚያ በኋላ አባትህ ኃያል ሰው ስለሆነና ከእርሱም ጋር ያሉት በጣም ብርቱዎች መሆናቸውን መላው እስራኤል ስለሚያውቅ
ልባቸው እንደ አንበሳ ልብ የሆነው እጅግ ጀግና የሆኑት እንኳን ይፈራሉ። 11 ስለዚህ እኔ የምመክርህ በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ ብዙ የሆነው ከዳን እስከ
ቤርሳቤህ ያለው መላው የእስራኤል ሕዝብ ወደ አንተ ይሰብሰብ፣ አንተም በግልህ ወደ ጦርነቱ ግባ። 12 ከዚያ በኋላ እርሱ በየትኛውም ቦታ ቢሆን
እንመጣበታለን፣ ጤዛም ምድርን እንደሚሸፍን በላዩ ላይ እንወድቅበታለን። ከእርሱ ማንኛውንም ሰው ወይም እርሱን ራሱንም እንኳን ቢሆን በሕይወት አንተውም።
13 ወደ አንዲት ከተማ የሚያፈገፍግ እንኳ ቢሆን፣ እስራኤል ሁሉ ገመድ አምጥቶ አንድ እንኳ እስከማይቀር ድረስ ከተማይቱን ወደ ወንዝ ውስጥ ስበን
እንከታታለን።” 14 ከዚያም አቤሴሎምና የእስራኤል ሽማግሌዎች ሁሉ፣ “የአርካዊው ኩሲ ምክር ከአኪጦፌል ምክር ይልቅ የተሻለች ነች” አሉ። በአቤሴሎም
ላይ ጥፋት ይመጣ ዘንድ እግዚአብሔር የአኪጦፌል መልካም ምክር ተቀባይነት እንዳያገኝ አደረገ። 15 ከዚያም ኩሲ ለካህናቱ ለሳዶቅና ለአብያታር፣
“አኪጦፌል አቤሴሎምንና የእስራኤልን ሽማግሌዎች ምን ምን ማድረግ እንዳለባቸው መክሮአቸው ነበር፣ እኔ ግን የተለየ ምክር ሰጠኋቸው። 16 እንግዲህ
እናንተ ፈጥናችሁ ወደ ዳዊት ዘንድ ሂዱና ፣ ‘በአረባ ባለው የወንዙ መሻገሪያ እንዳታድር፣ ነገር ግን እንደ ምንም ብለህ ተሻገር፤ አለበለዚያ ንጉሡና አብሮት
ያለው ሕዝብ በሙሉ ትዋጣላችሁ’ በሉት።” 17 በዚህ ጊዜ፣ ዮናታንና አኪማአስ በዓይንሮጌል ባለችው ምንጭ ይጠብቁ ነበር፣ ወደ ከተማ ሲገቡ እንዳይታዩ
አንዲት ሴት አገልጋይ ወደ እነርሱ እየሄደች መልእክቶችን ታቀብላቸው ነበር፤ እነርሱም በዚያን ጊዜ ለዳዊት ሄደው ይነግሩት ነበር። 18 በዚህን ጊዜ ግን አንድ
ወጣት አያቸውና ለአቤሴሎም ሄዶ ነገረ። ስለዚህ ዮናታንና አኪማአስ ፈጥነው በግቢው ውስጥ የውሃ ጉድጓድ ወደነበረው በብራቂም ወደ ነበረ ሰው ቤት
መጡ። 19 የሰውዬው ሚስት የውሃ ጉድጓዱን መሸፈኛ ወስዳ በጉድጓዱ አፍ ላይ ዘረጋችው ከዚያ በኋላም ዮናታንና አኪማአስ በውሃ ጉድጓድ ዘንድ እንዳሉ
ማንም እንዳያውቅ በላዩ ላይ እህል አሰጣችበት። 20 የአቤሴሎም ሰዎች በቤት ወደነበረችው ሴትዮ መጡና፣ “አኪማአስና ዮናታን ወዴት አሉ?” አሏት፤
እርሷም፣ “ወንዙን ተሻግረው ሄደዋል” አለቻቸው። ስለዚህ ፈልገው ሊያገኟቸው ስላልቻሉ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ። 21 እነርሱ ከሄዱ በኋላ አኪማአስና ዮናታን
ከጉድጓዱ ወጡ፤ ወደ ዳዊትም ዘንድ ሄደው፣ “ተነሣና ፈጥነህ ወንዙን ተሻገር፣ ምክንያቱም አኪጦፌል አንተን በሚመለከት እንደዚህና እንደዚያ ብሎ ምክር
ሰጥቶአል።” 22 ከዚያ በኋላ ዳዊትና ከእርሱ ጋር የነበረው ሕዝብ ተነሡ፣ የዮርዳኖስንም ወንዝ ተሻግረው ሄዱ፤ ሲነጋም ዮርዳኖስን መሻገር አቅቶት የቀረ
አንድም ሰው አልነበረም። 23 አኪጦፌልም ምክሩን እንዳልተቀበሉት ባየ ጊዜ አህያውን ጭኖ ቤቱ ወዳለበት ወደ መኖሪያ ከተማው ሄደ፣ ጉዳዩንም መልክ
ካስያዘ በኋላ በገዛ እጁ ታንቆ ሞተ። በዚህ አኳኋን ሞተና በአባቱ መቃብር ተቀበረ። 24 ከዚያ በኋላ ዳዊት ወደ መሃናይም መጣ፤ አቤሴሎምም ከእርሱ ጋር
ከነበሩት ከመላው የእስራኤል ሰዎች ጋር ዮርዳኖስን ተሻገረ። 25 ከዚህ በኋላም አቤሴሎም በኢዮአብ ምትክ አሜሳይን በሠራዊቱ ላይ ሾመ፤ አሜሳይ
የእስራኤላዊው የዮቴር ልጅ ነበር። ዮቴር ከኢዮአብ እናት ከጽሩያ እህት ከናዖስ ልጅ ከአቢግያ ጋር ተኝቶ የነበረ ነው። 26 ከዚህ በኋላ እስራኤላውያንና አቤሴሎም
ከበገለዓድ ምድር ሰፈሩ። 27 ዳዊት ወደ መሃናይም በመጣ ጊዜ ከአሞናውያን ከተማ ከራባ የመጣው፣ የናዖስ ልጅ ሾቢ፣ ከሎዶባር የመጣው የዓሚኤል ልጅ
ማኪርና ከሮግሊም የመጣው ገለዓዳዊው ቤርዜሊ፣ 28 መተኛ ምንጣፎችና ብርድ ልብሶች፣ ጎድጓዳ ሳህኖችና ድስቶች እንዲሁም ዳዊትና ከእርሱ ጋር የነበሩት
ሰዎች ይበሉ ዘንድ ስንዴ፣ የገብስ ዱቄት፣ የተጠበሰ እሸት፣ ባቄላ፣ ምስር፣ 29 ማር፣ ቅቤ፣ በግና እርጎ አመጡ። እነዚህ ሰዎች፣ “ሕዝቡ በምድረ-በዳ ተርቦአል፣
ደክሞአል ደግሞም ተጠምቶአል” ብለው ነበር።

---

2 Samuel 17:1

አኪጦፌል
ይህ የወንድ ስም በ 2 ሳሙኤል 15፡12 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አስራ ሁለት ሺህ ወንዶች
"12፣000 ወንዶች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

መነሳት እና
"መጀምር"

መምጣት
"መድረስ"

የዛለ እና ደካማ
እነዚህ ቃላት በመሰረቱ አንድ አይነት ትርጉም ሲኖራቸው በአንድ ላይ የቀረቡት ዳዊት ምን ያህል ደካማ እንደነበር ለማጉላት ነው። "ደካማ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

በፍርሃት አስጨንቀዋለሁ
እዚህ ስፍራ "ፍርሀት" የሚለው ቃል "መፍራት" ከሚለው ቅጽል ጋር ሊገለጽ ይችላል። "እርሱን አስጨንቀዋለሁ፣ ደግሞም እንዲፈራ አድረገዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሡን ብቻ እመታለሁ
ንጉሡን ለመግደል ማቀዱ ተመላክቷል። ይህ በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "ንጉሡን ብቻ እገድለዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ህዝቡን ሁሉ እመልሳለሁ
ይህ የሚያመለክተው ከዳዊት ጋር የነበሩ ሰዎችን ሁሉ ነው። "ከእርሱ ጋር የነበሩ ሰዎችን ሁሉ እመልሳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ባሏ እንደምትመጣ ሙሽራ
እዚህ ስፍራ አኪጦፌል የህዝቡን ደስታ የሚገልጸው ከሙሽሪት ደስታ ጋር በማነጻጸር ነው። "እናም ሙሽሪት ወደ ባሏ ስትመጣ ደሰ እንደሚላት በደስታ ይመጣሉ" ወይም "እናም በደስታ ይመጣሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሰላም ይሆናሉ
ይህ ማለት ሰላም ማግኘት ወይም በሰላም መኖር ማለት ነው። "በሰላም ይኖራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በስርህ
ይህ የሚያመለክተው ከንጉሡ ስልጣን በታች መሆንን ነው።"ከስልጣንህ በታች" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 17:5

አርካዊው ኩሲ
ይህ የወንድ ስም በ 2 ሳሙኤል 15፡32 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አኪጦፌል
ይህ የወንድ ስም በ 2 ሳሙኤል 15፡12 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 17:8

እነርሱ ልጇ እንደተነጠቁባት ድብ ናቸው
እዚህ ስፍራ የወታደሮቹ ቁጣ የተነጻጸረው ግልገሎቿ ከእርሷ ከተወሰዱባት አንዲት እናት ድብ ጋር ነው። "ግልገሎቿ እንደ ተወሰዱባት እናት ድብ ተቆጥተዋል።" ወይም "እነርሱ በጣም ተቆጥተዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ድብ
በአራት እግሩ የሚራመድ ስል መንጋጋ እና ጥርሶች ያለው ግዙፍ ፀጉራም እንስሳ

የጦር ሰው ነው
ይህ ማለት በብዙ ጦርሜዳ የተዋጋ እና የጦርነት መንገዶችን በሚገባ የሚያውቅ። "በብዙ ጦርሜዳ የተዋጋ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እይ/እነሆ
ይህ ቃል አድማጩ ቀጥሎ ለሚነገረው ትኩረት እንዲሰጥ የሚያደርግ ነው። "ስማ/አድምጥ" በሚለው ወስጥ እንደሚገኘው።

ጉድጓድ
የተቆፈረ ጥልቅ መሬት

ወይም በሌላ አንድ ስፍራ
ይህ እርሱ ሊደበቅበት የሚችልበት ሌላ ስፍራ ነው። "ወይም በሌላ ስፍራ ተደብቋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

ከአንተ ሰዎች ጥቂቶች በተገደሉ ጊዜ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የእርሱ ወታደሮች ከአንተ ሰዎች ጥቂቶችን በገደሉ ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አቤሴሎምን በተከተሉ ወታደሮች መሃል እርድ/እልቂት ተፈጸመ
"ማረድ/ማለቀ" የሚለው ስም ብዙ ሰዎች በጭካኔ የተገደሉበት ትዕይንት ማለት ነው። ይህ እንደ ግስ ሊገለጽ ይችላል። "አቤሴሎምን ከተከተሉት ወታደሮች ብዙዎቹ ታረደዋል" ወይም "የጠላት ወታደሮች አቤሴሎምን ከተከተሉት ወታደሮች ብዙዎችን ገድለዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ልቦቻቸው እንደ አንበሳ ልብ የሆነ
እዚህ ስፍራ ወታደሮች የተገለጹት የእነርሱ "ልቦች" በሚለው ነው። እንደዚሁም፣ ጠንካራ ጀግንነታቸው ከአንበሳ ብርታት ጋር ነው። "እንደ አንበሶች ጀግና የሆኑ" ወይም "በጣም ጀግና የሆኑ" (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

2 Samuel 17:11

መላው እስራኤል በአንድነት ወደ አንተ ይሰበሰብ ዘንድ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። እንደዚሁም፣ እዚህ ስፍራ "መላው እስራኤል" የሚለው የእስራኤል ወታደሮችን ብቻ ይወክላል። "እናንተ የእስራኤል ወታደሮች በአንድነት መሰብሰብ ይኖርባችኋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከዳን እስከ ቤርሳቤህ
ይህ ሀረግ ከሰሜናዊ የእስራኤል ድንበር አንስቶ እስከ ደቡብ ድንበር ድረስ ማለት ነው። "ከጠቅላላው የእስራኤል ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጽንፍ የሚለውን ይመልከቱ)

በባህር ዳርቻ እንደሚገኝ አሸዋ የበዛ
ይህ የእስራኤል ወታደር ብዛት በባህር ዳርቻ እንደሚገኝ የአሸዋ ቅንጣት ብዛቱ ተጋኖ በንጽጽር የተገለጸበት ነው። "ሊቆጠር እስከማይቻል ድረስ እጅግ ብዙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና ጥቅል አስተያየት እንደዚሁም ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

በየግል ወደ ጦርነት ትሄዳላችሁ
"በየግል" የሚለው ሀረግ ሌላውን ሰው መላክ ሳይሆን ይልቁንም እራስህ መሄድ ማለት ነው። "እንግዲያው አንተው ራስህ ወደ ጦርነት ምራቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ ላይ ውደቅበት
ይህ ማለት ይሁን ብሎ እርሱ ወዳለበት በመሄድ ጥቃት ማድረስ ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጤዛ በምድር ላይ እንደሚወርድ እኛ እንወርድበታለን
የአቤሴሎም ሰራዊት የተገለጸው ጤዛ በማለዳ ምድርን እንደሚሸፍን በዳዊት ሰራዊት ላይ እንደሚወርድበት ተደርጎ ነው። "እኛ የዳዊትን ሰራዊት እናጠቃለን ደግሞም ሙሉ ለሙሉ እናሸንፋለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጤዛ
በምሽት ወደ ምድር ሊወድቅ የሚችል ፣ ምድርን የሚሸፍን እና በማለዳ እርጥበቱ የሚታይ ጭጋግ ወይም እርጥበት ያለው ቀዝቃዛ ውሃ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከእርሱ ወንዶች አንድ እንኳን... በህይወት አናስተርፍም/አናስቀርም
ይህ አሉታዊ ዐረፍተ ነገር ያገለገለው ትኩረት ለመስጠት ነው፤ ይህ በአዎንታ ሊጻፍ ይችላል፡፡ "የእርሱን ወንዶች በሙሉ እንገድላለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ እራሱ
እነዚህ ሁለቱም ቃላት ዳዊትን ያመለክታሉ፡፡ "ዳዊት ራሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ተጠቃሽ ተውላጠ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 17:13

ከዚያም መላው እስራኤል
ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን ወታደሮች እንጂ መላውን እስራኤላዊ አይደለም፡፡ "ከዚያም መላው ወታደራችን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደዚያች ከተማ ገመድ እናመጣለን ደግሞም ወደ ባህር ውስጥ እናሰጥማታለን
ይህ ማለት ወታደሮች የከተማይቱ ቅጥር ያፈርሳሉ፤ ፍርስራሹንም ጎትተው ወደ ባህር ይጥላሉ፡፡ "ከተማይቱን እንደመስሳለን ደግሞም ድንጋዬቹን በገመድ ስበን ወደ ባህር እንጨምራለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ትናንሽ ድንጋይ እንኳን በዚያ እስከማይገኝ ድረስ
ይህ ከተማይቱን ምን ያህል ሙሉ ለሙሉ እንደሚያጠፏት ለመግለጽ የቀረበ ግነት ነው፡፡ ከከተማይቱ እያንዳንዲቱን ድንጋይ ጠርገው አያስወግዱም፡፡ "ከተማይቱ ሙሉ ለሙሉ እስክትጠፋ ድረስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ኩሸት እና ጥቅል አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

አርካዊው ኩሲ
ይህ የወንድ ስም በ 2 ሳሙኤል 15፡32 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡፡ አርካዊ የህዝብ/ሰዎች የቡድን ስም ነው፡፡

አኪጦፌል
ይህ የወንድ ስም በ 2 ሳሙኤል 15፡12 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡፡

የአኪጦፌልን መልካም ምክር መቃወም/መጣል
"አለመቀበል/መጣል" የሚለቀው ቃል "ተቃወመ/ጣለ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል፡፡ "የእስራኤል ወንዶች የአኪጦፌልን መልካም ምክር ላለመቀበል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመለከቱ)

በአቤሴሎም ላይ ጥፋት ለማምጣት
በአንድ ነገር ላይ አንደን ነገር ለ "ማምጣት" ማለት በእነርሱ ላይ እንዲሆን ማለት ነው፡፡ "ጥፋት በአቤሴሎም ላይ እንዲመጣ ምክንያት መሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 17:15

ሳዶቅ... አብያታር
እነዚህን የወንድ ስሞች በ 2 ሳሙኤል 15፡24-25 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡፡ (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚህና ይህን በመሰለ መንገድ
ይህ ሀረግ፣ ማለትም "እንደዚህ አይነት" የሚለው የሚያመለክተው አኬጦፌል ቀደም ሲል በ2 ሳሙኤል 17፡1-3 ላይ አቤሴሎምን የመከረውን ምክር ነው፡፡ (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የመሻገሪያ ዳርቻ
መሻገሪያ ሰዎች በእግራቸው ሊያቋርጡት የሚችሉት የወንዙ ጥልቀት የሌለው የውሃ ክፍል ነው፡፡ ዳርቻ ከዮርዳኖስ ወንዝ ሁለትም ጎኖች የሚገኝ መሬት ነው

በማናቸውም ብልሃት/መንገድ
ይህ ማለት አንድ ነገር ስለ ማድረግ እርግጠኛ መሆን ነው፡፡ "ለማድረግ እርግጠኛ መሆን" ወይም "ለማድረግህ እርግጠኛ ሁን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሡ ይዋጣል
እዚህ ንጉሡ እና ህዝቡ መገደላቸው የተገለጸው በጠላቶቻቸው "እንደሚዋጡ" ተደርጎ ነው፡፡ "ንጉሡ ይገደላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 17:17

ዮናታን...አኪማአስ
እነዚህን የወንድ ስሞች በ 2 ሳሙኤል 15፡27 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡፡ (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

መልዕክቱ ሲደርስ
እዚህ ስፍራ "መልዕክት" የሚለው የተገለጸው ወደ እነርሱ እንደሚመጣ ነገር ነው፤ እውነቱ ግን መልዕክቱን የምታደርሰው ወደዚያ የምትመጣው ሴት ናት፡፡ "መልዕክቱን ስታደርስላቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በዚህ ጊዜ
"አንድ ጊዜ"

ስለዚህም ዮናታን እና አኪማአስ ሄዱ
ወጣቱ ሰው ለአቤሴሎም ስለ እነርሱ በዚያ መኖር መናገሩን እንዳወቁ ተጠቅሷል፡፡ ይህ በግልጽ ሊጻፍ ይችላል፡፡ "ዮናታን እና አኪማአስ ወጣቱ ያደረገውን ነገር ስለ ደረሱበት/ስላወቁ ተነስተው ሄዱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የሮጌል ምንጭ...ብራቂም
እነዚህ እየሩሳሌም አጠገብ የሚገኙ የቦታ ስሞች ናቸው፡፡ ብራቂም ትንሽ ከተማ ናት፡፡ (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ወረዱ
"ወደ ታች ገብተው/ወርደው ተደበቁ"

2 Samuel 17:19

የቤቱ ሴት
"የሰውየው ሚስት

አኪማአስ...ዮናታን
እነዚህን የወንድ ስሞች በ 2 ሳሙኤል 15፡27 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡፡ (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 17:21

እንዲህም ሆነ
"እንዲህ ሆነ፡፡"ይህ ሀረግ በታሪኩ ፍሰት ቀጣዩን ትዕይንት ያመለክታል፡፡ (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በፍጥነት ውሃውን ተሻገሩ
እዚህ ስፍራ "ውሃው" የሚለው የሚያመለክተው የዮርዳኖስን ወንዝ ነው። "ባህሩን በፍጥነት ተሻገሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ይህንን እና ያንን ምክር ሰጠ
"ይህንን እና ያንን" የሚለው ፈሊጥ በአንባቢው ቀደም ሲል በሚታወቅ መረጃ ስፍራ የዋለ ነው። እዚህ ቦታ ይህ የሚያመለክተው አኪጦፌል አቤሴሎምን በ 2 ሳሙኤል 17:1-3 የመከረውን ነው። ይህ መረጃ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "አሁን አንተን ለማጥቃት አቤሴሎም እርሱን ከሰራዊት ጋር እንዲልክ መክሮታል" (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

እስከ ጠዋት የዮርዳኖስን ወንዝ ያልተሻገረ ማንም አልነበረም
ይህ አሉታዊ ዐረፍተ ነገር የዋለው ሁሉም ወንዙን ማቋረጣቸውን ለማጉላት ነው። በአዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በማለዳ እያንዳንዳቸው ዮርዳኖስን አቋረጡ" (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 17:23

አኪጦፌል ተመለከተ
"አኪጦፌል አወቀ" ወይም "አኪጦፌል ተረዳ/ተገነዘበ"

የእርሱን ምክር አልተከተሉም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አቤሴሎም የእርሱን ምክር አልተከተለም" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አህያውን ጫነ
በላዩ ላይ ይቀመጥበት ዘንድ በአህያው ጀርባ ንጣፍ ወይም ቁረበት አደረገ።

ነገሮቹን በስርአት አደራጀ/ተሰነዳዳ
ለቤተሰቦቹ ከሞቱ በኋላ ምን ሊያደርጉ እንደሚገባ በመናገር ለህልፈቱ ተሰናዳ። "ለ ህልፈቱ/ሞቱ ተዘጋጀ/ተሰነዳዳ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 17:24

መሃናይም...ገለዓድ
የእነዚህ ቦታዎችን ስም በ2 ሳሙኤል 2:8-9 ላይ በተተረጎመው አይነት ይተርጉሙ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አሜሳይ... ኢዮአብ... ዬቴር...ናዖስ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። ኢዮአብ እና ጽሩያ (የኢዮአብ እናት) በ 2 ሳሙኤል 2:13 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እስማኤላዊ
የዚህ ቃል ትርጉም ሰውየው የእስማኤል ዘር ነው ማለት ነው። አንዳንድ ትርጉሞች እዚህ ስፍራ "እስራኤላዊ" ይላሉ። የግርጌ ማስታወሻ ይምለከቱ። በአካባቢያችሁ መጽሐፍ ቀዱስ ከተተረጎመበት በብዙዎቹ ቋንቋዎች ውስጥ የሚገኘውን ቃል መጠቀም ይችላሉ።

አቢግያ...ጽሩያ
እነዚህ የሴቶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 17:27

እንዲህም ሆነ
ይህ ሀረግ በታሪኩ ፍሰት ቀጣዩን ትዕይንት ያመለክታል። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

መሃናይም...ረባት... ሎዶባር...ሮግሊም
እነዚህ የከተሞች ወይም የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሾቢ...ናዖስ...ማኪር...ዓሚኤል...ቤርዜሊ
እነዚህ የሰዎች ቡድኖች/ወገን ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አሞናውያን... ገለዓዳውያን
እነዚህ የሰዎች ቡድኖች/ወገን ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

መተኛ ምንጣፎች እና ብርድ ልብሶች
ምንጣፍ ለስላሳ የሆነ ለመኝታ የሚነጠፍ ነገር ነው፣ ብርድ ልብስ ደግሞ ለሙቀት የሚለበስ ልብስ ነው

ዱቄት
እንጀራ ወይም ዳቦ ለማዘጋጀት ወደ ደቃቅነት/ልምነት የተፈጨ የእህል

የተጠበሰ
በእሳት የተዘጋጀ

ባቄላ
በስሎ የሚበላ ጥራጥሬ

ምስር
በስሎ የሚበላ የጥራጥሬ አይነት

እርጎ
የረጋ ወተት

ጥማት
ውሃ ወይም የሚጠጣ ነገር መፈለግ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 18

1 ዳዊት አብሮት የነበሩትን ወታደሮች ቆጠረ፤ በእነርሱም ላይ የሻለቆችንና የመቶ አለቆችን ሾመላቸው። 2 ከዚህ በኋላ ዳዊት ሠራዊቱን ሲሦውን በኢዮአብ፣ ሲሦውን በኢዮአብ ወንድም በጽሩይ ልጅ በአቢሳ፣ ሲሦውን ደግሞ በጌታዊው በኢታይ አዛዥነት ሥር ላካቸው። ንጉሡም ለሠራዊቱ፣ “እኔ ራሴም አብሬአችሁ በእርግጥ እወጣለሁ” አላቸው። 3 ሰዎቹ ግን፣ “አንተ መውጣት የለብህም፤ እንድንሸሽ ብንገደድ፣ ሰዎቹ ስለ እኛ ግድ አይኖራቸውም ወይም ከእኛ ግማሻችን እንኳን ብንሞት ደንታም የላቸውም። አንተ ግን ከእኛ አሥር ሺሁ ያህል ነህ፤ ስለዚህ በከተማ ሆነህ ልትረዳን ዝግጁ ብትሆን የተሻለ ነው።” አሉት። 4 ስለዚህ ንጉሡ፣ “መልካም መስሎ የታያችሁን ሁሉ አደርጋለሁ” አላቸው። ስለዚህ ሠራዊቱ ሁሉ በመቶና በሺህ እየሆነ ተሰልፎ ሲወጣ ንጉሡ በከተማይቱ ቅጥር በር ቆሞ ነበር። 5 ንጉሡ ኢዮአብን፣ አቢሳንና ኢታይን፣ “ለእኔ ስትሉ ለወጣቱ ለአቤሴሎም ራሩለት” ብሎ አዘዛቸው። ሕዝቡ ሁሉ አቤሴሎምን በሚመለከት ንጉሡ ይህንን ትዕዛዝ ለአዛዦቹ ሲሰጣቸው ሰሙ። 6 ስለዚህ እስራኤልን ይወጋ ዘንድ ሠራዊቱ ከከተማ ወጣ፤ ውጊያውም እስከ ኤፍሬም ደን ተስፋፋ። 7 በዚያ የእስራኤል ሠራዊት በዳዊት ወታደሮች ድል ሆነ፤ በዚያ ሃያ ሺህ ሰው የሞተበት ታላቅ እልቂት በዚያ ቀን ነበረ። 8 ውጊያው በገጠሩ ሁሉ ተስፋፋ፣ በሰይፍ ካለቀውም ይልቅ ጫካ ውጦ ያስቀረበው ሰው በለጠ። 9 አቤሴሎም ከዳዊት ሰዎች ከጥቂቶቹ ጋር ተገናኘ። አቤሴሎምም በበቅሎው እየጋለበ ነበር፤ በቅሎውም ጥቅጥቅ ያሉ ቅርንጫፎች በነበሩት የወርካ ዛፍ ሥር ያልፍ ነበርና ራሱ በዛፉ ቅርንጫፎች ተያዘ። የተቀመጠበት በቅሎ ከሥሩ አልፎ ሲሄድ እርሱ በሰማይና በምድር ተንጠልጥሎ ቀረ። 10 አንድ ሰው ይህንን ተመልክቶ፣ “እነሆ፣ አቤሴሎም በወርካ ዛፍ ላይ ተንጥልጥሎ አየሁት” ብሎ ለኢዮአብ ነገረው። 11 ኢዮአብም ስለ አቤሴሎም ለነገረው ሰው፣ “እነሆ፣ አንተ አየኸው፣ ታዲያ መትተህ ለምን ወደ መሬት አልጣልከውም? እኔ አሥር የብር ሰቅልና ቀበቶ በሸለምኩህ ነበር።” 12 ሰውዬውም ለኢዮአብ፣ “አሥር ሺህ ሰቅል የምቀበል ብሆንም እንኳን እጄን ዘርግቼ የንጉሡን ልጅ ባልነካሁም ነበር፤ ምክንያቱም አንተን፣ አቢሳንና ኢታይን ንጉሡ፣ ‘አንድም ሰው ወጣቱን አቤሴሎምን እንዳይነካው’ ብሎ ሲያዛችሁ ሁላችንም ሰምተናል። 13 ውሸት በመናገር ሕይወቴን አደጋ ላይ ብጥል እንኳን (ከንጉሡ የሚደበቅ ምንም ነገር አይኖርምና) አንተ ታጋልጠኝ ነበር።” አለው። 14 ከዚህ በኋላ ኢዮአብ፣ “እኔ አንተን አልጠብቅም” አለ። ስለዚህ ኢዮአብ ሦስት ጦር ወስዶ ገና በሕይወት እያለና በወርካው ዛፍ ላይ ተንጠልጥሎ ሳለ በአቤሴሎም ልብ ላይ ተከላቸው። 15 ከዚያ በኋላም ከኢዮአብ ጋሻ ጃግሬዎች አሥሩ አቤሴሎምን በመክበብ ወግተው ገደሉት። 16 ከዚያም ኢዮአብ ቀንደ-መለከቱን ነፋ፣ ኢዮአብም ከልክሏቸው ስለነበረ ሠራዊቱ እስራኤልን ከማሳደድ ተመለሰ። 17 አቤሴሎምን ወስደው በጫካ ውስጥ ወደነበረ አንድ ትልቅ ጉድጓድ ውስጥ ጣሉት፤ እስራኤልም ሁሉ እያንዳንዱ ሰው ወደ ቤቱ በሚሸሽበት ጊዜ በአስከሬኑ ላይ ታላቅ የድንጋይ ክምር ከመሩበት። 18 አቤሴሎም፣ “የስሜን መታሰቢያ የሚያስጠራ ልጅ የለኝምና” በማለት ገና በሕይወቱ ሳለ ለራሱ አንድ ትልቅ የድንጋይ ሐውልት በንጉሡ ሸለቆ አቁሞ ነበር። ሐውልቱንም በስሙ ጠርቶት ስለነበረ፣ እስከዚህ ቀን ድረስ ‘የአቤሴሎም ሐውልት’ ተብሎ ይጠራል። 19 በዚህ ጊዜ የሳዶቅ ልጅ አኪማአስ እግዚአብሔር ከጠላቶቹ እንዳዳነው ሄጄ ለንጉሡ የምሥራች ልንገረው አለ። 20 ኢዮአብም፣ “ዛሬ የምሥራቹን የምታደርስለት አንተ አይደለህም፣ ሌላ ጊዜ ታደርስለታለህ፤ የንጉሡ ልጅ ስለሞተ ምንም የምሥራች አታደርስም።” 21 ከዚያም ኢዮአብ ለአንድ ኩሻዊ፣ “ሂድና ለንጉሡ ያየኸውን ተናገር” አለው። ኩሻዊውም ኢዮአብን እጅ ነሥቶ እየሮጠ ሄደ። 22 የሳዶቅ ልጅ አኪማአስም እንደገና ለኢዮአብ፣ “ምንም ዓይነት ነገር ይሁን፣ እባክህ፣ ኩሻዊውን ተከትዬው ልሩጥ” አለው። ኢዮአብም፣ “ለየምሥራቹ ምንም ብድራት እንደማታገኝ እያወቅህ፣ ልጄ ሆይ፣ ለምን ትሮጣለህ?” ብሎ መለሰለት። 23 “የሆነው ይሁን፣ እሮጣለሁ” አለ፣ አኪማአስ። ስለዚህ ኢዮአብ ፣ “እንግዲያውስ፣ ሩጥ” ብሎ መለሰለት። ከዚያም አኪማአስ በሜዳው መንገድ በኩል ሮጠ፣ ኩሻዊውንም ቀደመው። 24 ዳዊት በውስጠኛውና በውጭኛው በሮች መካከል ተቀምጦ ነበር። ጠባቂው ቅጥሩ ላይ ወዳለው ወደ በሩ ሰገነት ጣራ ወጥቶ ወደ ውጭ ዓይኑን አንስቶ ሲመለከት አንድ ብቻውን የሚሮጥ ሰው እየተቃረበ ነበር። 25 ጠባቂው ተጣራና ለንጉሡ ነገረው፤ ከዚያም ንጉሡ፣ “ብቻውን ከሆነ መልካም ዜና በአንደበቱ አለ” አለ። ሯጩ እየተጠጋ መጥቶ ወደ ከተማይቱ ቀረበ። 26 ከዚያም ጠባቂው ሌላ የሚሮጥ ሰው አስተዋለ፤ ጠባቂውም ዘበኛውን ጠራና፣ “እነሆ፣ ብቻውን የሚሮጥ ሌላ ሰው አለ” አለው። ንጉሡም፣ “እርሱም መልካም ዜና አለው” አለ። 27 ስለዚህ ጠባቂው፣ “ከፊት እየሮጠ ያለው ሰው አሯሯጥ የሳዶቅን ልጅ የአኪማአስን ሩጫ ይመስለኛል” አለ። ንጉሡም፣ “እርሱ ጥሩ ሰው ነው፣ እርሱም የሚመጣው የምሥራች ይዞ ነው” አለ። 28 ከዚያ በኋላ አኪማአስ ተጣርቶ ለንጉሡ፣ “ሁሉም ደኅና ነው” አለና በንጉሡ ፊት ለጥ ብሎ እጅ ነሥቶ፣ ወደ መሬት እያቀረቀረ፣ “በጌታዬ በንጉሡ ላይ እጃቸውን ያነሡትን ሰዎች አሳልፎ የሰጠህ እግዚአብሔር አምላክህ የተባረከ ይሁን” አለው። 29 ንጉሡም፣ “ወጣቱ አቤሴሎም ደህና ነውን? ሲል ጠየቀ። አኪማአስም፣ “ኢዮአብ እኔን የንጉሡን አገልጋይ በላከኝ ጊዜ ትልቅ ሁካታ ነበር፣ ምን እንደሆነ ግን እኔ አላወቅሁም” አለው። 30 ከዚያ በኋላ ንጉሡ፣ “እልፍ በልና ቁም” አለው። ስለዚህ አኪማአስ እልፍ ብሎ ዝም ብሎ ቆመ። 31 ከዚያ በኋላ ወዲያውኑ ኩሻዊው ደረሰና፣ “ለጌታዬ ለንጉሡ የምሥራች አለኝ፣ እግዚአብሔር በንጉሡ ላይ የተነሡብህን ሁሉ ዛሬ ተበቅሎልሃልና” አለው። 32 ንጉሡም ኩሻዊውን፣ “ወጣቱ አቤሴሎም ደህና ነውን?” አለው። ኩሻዊውም፣ “የጌታዬ የንጉሡ ጠላቶች እንዲሁም በእርሱ ላይ ጉዳት ለማድረስ በአንተ ላይ የሚነሡብህ ሁሉ እንደዚያ ወጣት ይሁኑ” ብሎ መለሰለት። 33 በዚያን ጊዜ ንጉሡ ጥልቅ የሆነ ሐዘን አዘነ፤ በቅጥሩ በር ዐናት ላይ ወዳለችው ቤት ገብቶም አለቀሰ። እየሄደም ሳለ፣ “ልጄ አቤሴሎም ሆይ! ልጄ አቤሴሎም! በአንተ ፈንታ ምነው እኔ በሞትሁ ኖሮ! አቤሴሎም ልጄ፣ ልጄ!” እያለ ያለቅስ ነበር።

---

2 Samuel 18:1

ዳዊት ከእርሱ ጋር የነበሩትን ወታደሮች ቀጠረ፣ ደግሞም ሾማቸው።
ዳዊት ራሱ ህዝቡን ሁሉ አልቆጠረም፣ ህዝቡን የቆጠሩት ሌሎች ሰዎች ናቸው። ዳዊት ከእርሱ ጋር የነበሩትን የሚቆጠሩትን እና የሚሾማቸውን ወታደሮች አስተዳደረ/ለየ" ወይም "ዳዊት ከእርሱ ጋር የነበሩትን እና የሚሾማቸውን ወታደሮች አደራጀ። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሻለቆች እና የመቶ አለቆች
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እነዚህ ቁጥሮች መሪዎቹ የሚመሯቸውን ወታደሮች ትክክለኛ ቁጥር ይወክላሉ። "የ1,000 ወታደሮች እና የ100 ወታደሮች መሪዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው ወይም 2) "ሺህ" ወይም "መቶ" በሚል የተተረጎሙት ቃላት ቁርጥ ያለ ቁጥርን አይመክሉም፣ ነገር ግን ብዙ ወይም ትንሽ ቁጥር ያለውን የወታደር ክፍል ለመሰየም የዋለ ነው። "የትልቅ/ብዙ ወታደራዊ ክፍል አዛዥ እና አነስተኛ ቁጥር ያለው የወታደር ክፍል አዛዥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

አለቃ/አዛዥ
አለቃ በተወሰኑ የወታደር ስብስቦች/ቡድን ላይ ስልጣን ያለው ሰው

አንድ ሶስተኛ... ሌላ ሲሶ/ሶስተኛ
የሰራዊቱ አንድ ሶስተኛ... የሰራዊት ሌላ ሲሶ/ሶስተኛ። "ሲሶ/አንድ ሶስተኛ" እኩል የሆኑ ሶስት ክፍሎች አንድ ክፍል/አንድ እጅ። (ክፍልፋይ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አቢሳ... ጽሩያ
እነዚህ የወንድ ስሞች በ2 ሳሙኤል 2፡18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ኢታይ
ይህ የወንድ ስም በ2 ሳሙኤል 15፡19 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ጌታዊ
ይህ ከፍልስጤም ከተማ ከጌት የሆነን ሰው ያመለክታል።(ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔም ራሴ በእርግጥ ከእናንተ ጋር እወጣለሁ
ይህ ማለት ከእነርሱ ጋር ለጦርነት አብሯቸው ይመጣል ማለት ነው። ይህ ይበልጥ በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "እኔ ራሴ ከእናንተ ጋር አብሬ ለጦርነት እወጣለሁ" ወይም "እኔ በግል ወደ ጦርነት አብሬያችሁ እሄዳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 18:3

ከእኛ ግማሹ
"ግማሽ" የሚለው ቃል እኩል ከሆኑ ሁለት ክፍሎች አንዱን ያመለክታል። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ አንተ አስር ሺህ ከምንሆነው ይልቅ ይበልጥ አስፈላጊ ነህ
ይህ ማለት የጠላት ሰራዊት ንጉሥ ዳዊትን መግደል 10,000 ወንዶችን ከመግደል ይልቅ ይበልጥ ጠቃሚ አድርጎ ይቆጥራል ማለት ነው። እዚህ ስፍራ 10,000 የሚለው ቁጥር የዋለው በጣም ብዙ ቁጥር ያለው ሰው የሚለውን ለማጉላት ነው። "ከእኛ 10,000 ሰው ከመግደል ይልቅ አንተን ይገድላሉ" ወይም "ለእነርሱ ከእኛ ብዙ ሰው ከመግደል ይልቅ አንተን መግደል ይበልጥ ይጠቅማቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ እና ኩሸት እንደዚሁም ጥቅል አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

አስር ሺህ
"10,000" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ከከተማ ሆንህ እኛን ለመርዳት ዝግጁ ሁን
ዳዊት ከከተማ ሆኖ በምክር እና ሰዎችን በመላክ ሊረዳቸው ይችላል። ይህ ይበልጥ በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "አንተ እዚህ በከተማ ቆይተህ ለእኛ እርዳታ ላክልን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 18:5

አቢሳ
ይህ የወንድ ስም በ2 ሳሙኤል 2፡18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ኢታይ
ይህ የወንድ ስም በ2 ሳሙኤል 15፡19 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ እኔ ስትሉ ከወጣቱ ሰው ከአቤሴሎም ጋር የምታደርጉትን በእርጋታ/ርህራሄ አድርጉ
"ስለ እኔ ስትሉ፣ ወጣቱን አቤሴሎምን አትጉዱት/ራሩለት።" "በእርጋታ አድርጉ/ራሩለት" የሚለው ሀረግ ለአንድ ሰው መልካም መሆንና ያንን ሰው አለመጉዳት ነው።

ስለ እኔ
"የእኔ ደህንነት" ወይም "የእኔ ጉዳይ"

2 Samuel 18:6

በእስራኤል ላይ ተነስቶ ወደ ገጠር/ ሜዳ መውጣት
ይህ ማለት ወጥተው በጦርነት ገጠሟቸው ማለት ነው። "ወደ ሜዳ/ገጠር ወጥተው ከእስራኤል ጋር ተዋጉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በእስራኤል ላይ
እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚለው የሚያመለክተው ወታደሮቻቸውን እንጂ መላውን እስራኤላዊ አይደለም። "በእስራኤላውያን ወታደሮች ላይ"በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/የነገሩን ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚያ ከዳዊት ወታደሮች አስቀድሞ የእስራኤል ሰራዊት ተሸነፈ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በዚያ የዳዊት ሰራዊት የእስራኤልን ሰራዊት አሸነፉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ታላቅ እልቂት/መተራረድ
ብዙ ሰዎች በጭካኔ የሚገደሉበት ትዕይንት ሃያ ሺህ ወንዶች "20,000 ወንዶች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በሰይፍ ከሞቱት ይልቅ በጫካው የተፈጁት/የተበሉት ወንዶች በለጡ
እዚህ ስፍራ "ጫካ/ዱር" የተገለጸው ህይወት እንዳለውና እርምጃ መውሰድ እንደሚችል ተደርጎ ነው። "ሰይፍ" የሚያመለክተው በሰይፍ የሚዋጉትን የዳዊት ወታደሮች ነው። "የዳዊት ወታደሮች በሰይፍ ከገደሏቸው ይልቅ በጫካ ውስጥ አደገኛ ነገሮች የገደሏቸው ሰዎች በዙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

2 Samuel 18:9

አቤሴሎም ከዳዊት ጥቂት ወታደሮች ጋር በድንገት ተገናኘ
ይህ በጦርነቱ ወቅት ያጋጠመ ተዕይነት ነው። ይህ ይበልጥ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "በጦርነቱ ወቅት አቤሴሎም ከጥቂት የዳዊት ወታደሮች ጋር ተገጣጠመ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ጭንቅላቱ በግንድ ቅርንጫፎች መሃል ተይዞ ነበር
አቤሴሎም በዛፍ ቅርንጫፎች ሊያዝ የሚችል ረጅም ፀጉር ነበረው። "ፀጉሩ በዛፍ ቅርንጫፎች ተይዞ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

መወዛወዝ
መሰቀል ወይም በቀስታ መወዛወዝ

እነሆ/ተመልከት
እዚህ ስፍራ ይህ ቃል ያገለገለው ቀጥሎ ለሚነገረው የአንባቢውን ትኩረት ለመሳብ ነው። "ስማ/አድምጥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ለምን መትተህ ወደ ምድር አታወርደውም ነበር?
የዚህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ ትርጉም ሊገድለው ይገባ ነበር ማለት ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "መትቶ ማውረድ" የሚለው ሀረግ መግደል ማለት ነው። "መትተህ ወደ ምድር ልታወርደው ይገባ ነበር!" ወይም "ወዲያውኑ ልትገድለው ይገባ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚሉትን ይመልከቱ))

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አስር የብር ሰቅል
ይህ በዘመናዊ መለኪያ ሊጻፍ ይችላል። "አስር የብር ሳንቲም" ወይም "110 ግራም ብር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መጽሐፍ ቅዱሳዊ የገንዘብ መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀበቶ
ይህ ለየት ያለ ቀበቶ ሲሆን ሰውየው ታላቅ ወታደር እና ሊከበር የሚገባው መሆኑን ለሰዎች የሚያሳይ ነው።

2 Samuel 18:12

አንድ ሺህ የብር ሰቅል
"1,000 የብር ሰቅል።" ይህ በዘመናዊ መለኪያ ሊጻፍ ይችላል። "1,000 የብር ሳንቲም" ወይም "11 ኪሎ ግራም ብር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መጽሐፍ ቅዱሳዊ የገንዘብ መለኪያ እና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

እጄን በንጉሡ ልጅ ላይ አላሳርፍም ነበር
"እጄን አላሳርፍም" የሚለው ቃል አልመታም ማለት ነው። "የንጉሡን ልጅ አልመታም ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ማንም ሊነካው አይገባም
እዚህ ስፍራ "መንካት" የሚለው የሚያመለክተው "መጉዳትን" ነው። "ማንም ሊጎዳ አይገባም" ወይም "አትጉዱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሀሰተኝነት
"ሀሰተኝነት" የሚለው ቃል በግሳዊ ሀረግ ሊገለጽ ይችላል። እንደዚሁም፣ ይህ የንጉሡን ትዕዛዝ አለመጠበቅን ያመለክታል። ይህ ይበልጥ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "ስህተት የሆነ ነገር መፈጸም" ወይም "ንጉሡን አለመታዘዝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከንጉሡ ተደብቆ የሚቀር ምንም ነገር የለም
እዚህ ሰውየው የሚናገረው ንጉሡ እንዴት ከሞላ ጎደል ስለ ሁሉም ነገር እንደሚያውቅ ሲሆን ማናቸውም ነገር የሚለውም አካላዊ ቁስ ሆኖ ንጉሡ የዚይን ስፍራ እንደሚያውቅ አድርጎ ነው። "ንጉሡ የማያውቀው አንዳች ነገር የለም" ወይም "ንጉሡ ስለሚሆነው እያንዳንዱ ነገር ይሰማል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 18:14

እኔ አንተን መጠበቅ አልችልም
ኢዮአብ ከሰውየው ጋር መነጋገሬን መቀጠል አይኖርብኝም ማለቱ ነው። "ከአንተ ጋር በመነጋጋር ምንም ተጨማሪ ጊዜ አላባክንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የአቤሴሎም ልብ
እዚህ ስፍራ የአቤሴሎም ልብ የሚለው የሚያመለክተው ደረቱን ወይም የላይኛውን የሰውነት ክፍሉን ነው። "ደረት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

የጦር ትጥቅ/ልብስ
ይህ የሚያመለክተው ራሱን ለመጠበቅ ስለሚለብሰው የጦር ልብስ እና መሳሪያውን ጭምር ነው። "የጦር ልብስና ትጥቅ/መሳሪያ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

2 Samuel 18:16

ኢዮአብ ሰራዊቱን ከልክሎ ነበርና መለከት ነፋ፣ እናም ሰራዊቱ እስራኤልን ከማሳደድ ተመለሰ
ይህ ኢዮአብ መለከት በመንፋት ምን እንዳዘዘ ይገልጻል። "ከዚያም ኢዮአብ ሰራዊቱን ወደ ኋላ ለመመለስ መለከት ነፋ፣ እናም ሰራዊቱ እስራኤልን ከማሳደድ ተመለሰ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እስራኤልን ከማሳደድ ተመለሰ
እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚያመለክተው የእስራኤላውያንን ሰራዊት ነው። "የእስራኤላውያንን ሰራዊት ከማሳደድ ተመለሰ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

አቤሴሎምን ወስደው ወረወሩት
"የአቤሴሎምን አካል/በድን ወስደው ወረወሩት"

በድኑን ከትልቅ የድንጋይ ክምር ስር ቀበሩ
በድኑን ጉድጓድ ውስጥ ከጨመሩ በኋላ በደንጋይ ክምር ሸፈኑት። ይህ ይበልጥ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "በድኑን በብዙ የድንጋይ ክምር ሸፈኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መላው እስራኤል በሚሸሸበት ጊዜ
እዚህ ስፍራ "መላው እስራኤል" የሚለው የሚያመለክተው የእስራኤልን ወታደሮች ነው። "መሸሸ" የሚለው ቃል "ማምለጥ" ማለት ነው። "መላው የእስራኤል ወታደሮች በሚያመልጡበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

2 Samuel 18:18

የንጉሥ ሸለቆ
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የስሜን መታሰቢያ የሚሸከመውን/ስሜን የሚያስቀጥለውን
አቤሴሎም "ስሜ/የእኔ ስም" የሚለውን ሀረግ የተጠቀመው ራሱን እና ቤተሰቡን ሀረግ ለማመልከቱ ነው። "ሰዎች እኔን የሚያስታውሱበትን፣ የቤተሰቤን ስም ለመሸከም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህም እስከ ዛሬ ድረስ የአቤሴሎም መታሰቢያ ተብሎ ይጠራል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ስለዚህም ሰዎች ከዚያን ጊዜ ቀን አንስቶ የአቤሴሎም መታሰቢያ ብለው ይጠሩታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እስከ ዛሬ ቀን ድረስ
እዚህ ስፍራ ዛሬ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የተጻፈበትን ጊዜ ነው።

2 Samuel 18:19

አኪማአስ
ይህ የወንድ ስም በ2 ሳሙኤል 15፡27 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

መልካሙን ወሬ ይዞ ወደ ንጉሡ ሮጠ
እዚህ ስፍራ አኪማአስ ስለ መሮጥ የሚናገረው ወደ ንጉሡ ሄዶ መለካሙን ወሬ/የምስራቹን እርሱ እንደተሸከመው አንድ ነገር ወይም አካል አድርጎ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

"መልካሙን ወሬ ለንጉሡ ለመናገር ሮጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የጠላቶቹ እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው መቆጣጠርን/መያዝነን ነው። "ጠላቶቹን መቆጣጠር/መያዝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ወሬውን ያመጣው/ወሬ ነጋሪው
"ወሬን የሚያደርሰው/የሚናገረው ሰው"

ምንም ወሬ አታደርስም
ይህ የሚያመለክተው ለንጉሡ ወሬ አለማምጣትን ነው። "ወሬውን ለንጉሡ አትናገርም/አታደርስም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 18:21

ያየኸውን ለንጉሡ ተናገር
ኢዮአብ እርሱ ሄዶ ለንጉሡ ስለ ጦርነቱ ወሬውን እንዲናገር እየነገረው ነው

2 Samuel 18:24

አሁን
ይህ ቃል እዚህ ስፍራ የዋለው በዋናው ታሪክ ፍሰት ላይ መቆሚያ እና በታሪኩ አዲስ ክፍል ጅማሬ ለማበጀት ነው።

ዐይኖቹን አቀና/አነሳ
እዚህ ስፍራ ጠባቂው/ዘበኛው አንድ ነገር መመልከቱ የተገለጸው ልክ ዐይኖቹን ወደ ላይ ከፍ እንዳደረገ ተደርጎ ነው። "ወደ ከተማው አሻግሮ ተመለከተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በአፉ የምስራች አለ
እዚህ ስፍራ ንጉሡ ሰውየው መልዕክት ያለው መሆኑን የገለጸው ወሬው በአፉ ላይ የሚገኝ ነገር ወይም አካል እንደሆነ አድርጎ ነው። "የሚነግረን ወሬ አለው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 18:26

ከፊት የሚሮጠው ሰው አሯሯጥ የሳዶቅን ልጅ የአኪማአስን ሩጫ ይመስላል
ዘበኛው የሰውየውን አሯሯጥ ከአኪማአስ ሩጫ ጋር ያነጻጸረው አኪማአስ ይሆናል የሚል ግምት ለመስጠት ነው። "ከፊት የሚሮጠው የሳዶቅ ልጅ አኪማአስ ይመስለኛል፣ ምክንያቱም አሯሯጡ እንደ አኪማአስ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 18:28

በንጉሡ ፊት ወደ ምድር ዝቅ ብሎ ሰገደ
ይህን ያደረገው ንጉሡን ለማክበር ነው። "ንጉሡን ለማክበር ወደ ምድር ዝቅ ብሎ በንጉሡ ፊት ሰገደ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ የተባረከ ይሁን
"ያህዌ ይመስገን።" እዚህ ስፍራ "መባረክ" ማለት ማወደስ ማለት ነው።

በጌታዬ በንጉሡ ላይ እጃቸውን ያነሱ ሰዎች
እዚህ ስፍራ አኪማአስ ንጉሡን የተቃወሙ ሰዎችን የገለጸው እጃቸውን በእርሱ ፊት ወደ ላይ እንዳነሱ አድርጎ ነው። "ጌታዬን ንጉሡን የተቃወሙ እና የወጉ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ታላቅ ረብሻ
ይህ ማለት ሰዎች የሚያደርጉት ነገሮች ትክክል ባልሆኑበት ሁኔታ እንደሚደረገው ያለ ነገር ነበር

ዞር በልና እዚህ ቁም
"ከመንገድ ዞር በል" ወይም "ዞር ብለህ ቁም"

2 Samuel 18:31

በተቃውሞ መነሳት
ይህ ማለት መቃወም ማለት ነው። "በተቃውሞ ተነሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የጌታዬ የንጉሡ ጠላቶች ... ያ ወጣት ሰው እንደሆነው ይሁኑ
ኩሻዊው ንጽጽሩን የተጠቀመበት ትሁት በሆነ መንገድ የአቤሴሎምን ሞት ለንጉሡ ለመናገር ነው። ይህ ይበልጥ ቀጥተኛ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "ጠላቶችህ ሁሉ ያ ወጣት በሞተበት መንገድ ቢሞቱ እወዳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተጻጻሪ ዘይቤ እና ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

ራሱን መቆጣጣር እጅግ ተስኖት ነበር
"እጅግ አዝኖ ነበር" ወይም "በሀዘን ተውጦ ነበር"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 19

1 “እነሆ፣ ንጉሡ ለልጁ ለአቤሴሎም እያለቀሰ ነው” ተብሎ ለኢዮአብ ተነገረው። 2 “ንጉሡ ለልጁ እያለቀሰ ነው” የሚለውን ሠራዊቱ በዚያን ቀን ሰምቶ
ስለነበረ፣ የዚያን ቀኑ ድል ለሠራዊቱ ወደ ኃዘን ቀንነት ተለወጠ። 3 ከጦርነት ሸሽተው የሚመጡ በኀፍረት ሹልክ ብለው እንደሚገቡ በዚያን ቀን ወታደሮቹ ሹልክ
ብለው ወደ ከተማ ይገቡ ነበር። 4 ንጉሡ ፊቱን ሸፍኖና ድምፁን ከፍ አድርጎ፣ “ልጄ አቤሴሎም ሆይ፣ አቤሴሎም፣ ልጄ፣ ልጄ!” እያለ አለቀሰ። 5 ከዚያም
ኢዮአብ ወደ ቤት ወደ ንጉሡ ዘንድ ገብቶ፣ “የሚወዱህን ትጠላለህና የሚጠሉህንም ትወዳለህና ዛሬ ሕይወትህን፣ የወንዶችና የሴቶች ልጆችህን ሕይወት፣
የሚስቶችህን ሕይወት እንዲሁም የቁባቶችህን ሕይወት ያዳኑትን የወታደሮችህን ሁሉ ፊት አሳፍረሃል። 6 የሚጠሉህን ትወዳለህ የሚወዱህን ትጠላለህ፤ የጦር
አዛዦችና ወታደሮች ለአንተ ምንም እንዳይደሉ ዛሬ አሳይተሃልና። ዛሬ አቤሴሎም በሕይወት በኖረና እኛ ሁላችንም ብንሞት፣ ያ ደስ ያሰኝህ እንደነበረ አምናለሁ።
7 ስለዚህ አሁንም ተነሥተህ ውጣና ለወታደሮችህ በትሕትና ተናገራቸው፣ ባትሄድ ግን፣ በእግዚአብሔር ስም እምላለሁ፣ በዛሬው ሌሊት አንድም ሰው ከአንተ ጋር
አይቀርም። ይሄ ደግሞ ከልጅነትህ ጀምሮ እስካሁን ከደረሰብህ መከራ ሁሉ የከፋ ይሆንብሃል።” 8 ስለዚህ ንጉሡ ተነሥቶ በከተማይቱ በር አጠገብ ተቀመጠ፣
ለሰዎችም ሁሉ፣ “እነሆ፣ ንጉሡ በበሩ ተቀምጦአል” ተብሎ ተነገራቸው። ከዚያ በኋላም ሰዎች ሁሉ በንጉሡ ፊት መጡ። በዚህን ጊዜ በእስራኤል ሰው ሁሉ
ወደየቤቱ ሸሽቶ ነበር። 9 በመላው እስራኤል በየነገዱ ያሉ ሰዎች ሁሉ እርስ በርሳቸው፣ “ንጉሡ ከጠላቶቻችን እጅ አስጥሎናል፤ ከፍልስጥኤማውያንም እጅ
አድኖናል፤ አሁን ደግሞ ከአቤሴሎም ሸሽቶ ከአገር ወጥቷል። 10 በላያችን ላይ የቀባነውም አቤሴሎም በጦርነቱ ተገድሏል። ስለዚህ ንጉሡን መልሰን
ስለማምጣት ለምን አንነጋገርም?” እያሉ ይነጋገሩ ነበር። 11 ንጉሥ ዳዊት ወደ ካህናቱ ወደ ሳዶቅና ወደ አብያታር ልኮ፣ “ለይሁዳ ሽማግሌዎች፣ ‘ወደ ቤተ
መንግሥቱ ይመልሰው ዘንድ የመላው የእስራኤል ልብ ለንጉሡ ድጋፍ የሚሰጥ ነውና፣ ንጉሡን ወደ ቤተ መንግሥቱ ለመመለስ እናንተ የመጨረሻዎቹ
የምትሆኑት ለምንድን ነው? 12 እናንተ የሥጋዬ ቁራጭ የአጥንቴ ፍላጭ ናችሁ። ታዲያ፣ ንጉሡን ለመመለስ እናንተ የመጨረሻዎቹ የሆናችሁት ለምንድን ነው?’
13 ለአሜስያም፣ ‘አንተስ የሥጋዬ ቁራጭ የአጥንቴ ፍላጭ አይደለህምን? ከአሁን ጀምሮ በኢዮአብ ምትክ የሠራዊቴ አዛዥ ባለደርግህ እግዚአብሔር ይህንን
ያድርግብኝ፣ ከዚህም የባሰ ይጨምርብኝ’” በሉ ብሎ መልእክት ላከ። 14 “አንተና ሰዎችህ ሁሉ ተመለሱ” ብለው ወደ ንጉሡ መልእክት እስኪልኩ ድረስ
የአንድ ሰው ልብ እንደነበራቸው ያህል የይሁዳን ሁሉ ልብ ማረከ። 15 ስለዚህ ንጉሡ ተመልሶ ወደ ዮርዳኖስ መጣ። የይሁዳም ሰዎች ዮርዳኖስን ሲሻገር
ለማጀብ፣ ንጉሡን ለመገናኘት ወደ ጌልጌላ መጡ።” 16 ከብራቂም የሆነው የጌራ ልጅ ሳሚ ንጉሥ ዳዊትን ለመቀበል ከይሁዳ ሰዎች ጋር ፈጥኖ ወረደ። 17
ከእርሱ ጋር ከብንያም አንድ ሺህ ሰዎች ነበሩ፤ ደግሞም ከሲባ ከሳዖል አገልጋይ ጋር አሥራ አምስት ልጆቹና ሃያ አገልጋዮቹ ነበሩ። በንጉሡ ፊት ዮርዳኖስን
አቋረጠው ተሻገሩ። 18 የተሻገሩት የንጉሡን ቤተሰብ ለማምጣትና እርሱ መልካም ነው ያለውን ለማድረግ ነበር። 19 ሳሚ ለንጉሡ፣ “ጌታዬ እኔን በደለኛ
አድርጎ አይቁጠረኝ ወይም ጌታዬ ንጉሡ ከኢየሩሳሌም በወጣበት ቀን ባሪያህ በግትረኛነት ያደረገውን ትኩረት አይስጠው። ንጉሥ ሆይ፣ እባክህ ይህንን በልብህ
አታኑረው። 20 ባሪያህ ኃጢአት ማድረጌን አውቃለሁ። ከመላው የዮሴፍ ቤት ጌታዬ ንጉሡን ለመቀበል የመጀመሪያ ሆኜ ዛሬ የመጣሁት እነሆ፣ ለዚህ ነው።”
አለ። 21 ነገር ግን የጽሩይ ልጅ አቢሳ፣ “እግዚአብሔር የቀባውን ተረግሟልና ስለዚህ ጉዳይ ሳሚ ሊገደል አይገባውምን?” 22 ከዚያ በኋላ ዳዊት፣ “ዛሬ ለእኔ
ጠላቶች ትሆኑኝ ዘንድ እናንተ የጽሩያ ልጆች ከእናንተ ጋር ምን አለኝ? ዛሬ በእስራኤል አንድ ሰው ሊገደል ይገባዋል? በእስራኤል ላይ ንጉሥ መሆኔን ያወቅሁት
በዛሬው ቀን አይደለምን?” 23 ስለዚህ ንጉሡ ለሳሚ፣ “አትሞትም” አለው። ስለዚህ ንጉሡ በመሐላ ቃል ገባለት። 24 ከዚያ በኋላ የሳዖል ልጅ ሜምፊቦስቴ
ንጉሡን ለመቀበል መጣ። ንጉሡ ከሄደበት ቀን ጀምሮ በሰላም ወደ ቤቱ እስከተመለሰበት ቀን ድረስ በእግሩ ሱሪ አላስገባም፣ ጢሙን አልተላጨም ወይም
ልብሱን አላጠበም። 25 ስለዚህም ንጉሡን ለመቀበል ወደ ኢየሩሳሌም በመጣ ጊዜ፣ ንጉሡ፣ “ሜምፊቦስቴ ከእኔ ጋር ለምን አልሄድክም?” አለው። 26
እርሱም፣ “ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፣ አገልጋዬ አታለለኝ፣ ምክንያቱም፣ ‘እኔ ባሪያህ ሽባ ስለሆንኩኝ እንድቀመጥበትና ከንጉሡ ጋር እንድሄድ አህያዬን እጭናለሁ’ ብዬ
ነበርና። 27 አገልጋዬ ሲባ እኔን ባሪያህን ለጌታዬ ለንጉሡ አማ፤ ጌታዬ ንጉሡ ግን እንደ እግዚአብሔር መልአክ ነው። ስለዚህ በዓይንህ ፊት መልካም መስሎ
የታየህን አድርግብኝ። 28 የአባቴ ቤት ሰዎች ሁሉ በጌታዬ በንጉሡ ዘንድ የሞት ሰዎች ነበሩና፤ ነገር ግን ባሪያህን በገበታህ ከሚበሉት አንዱ አድርገህ
አስቀመጥኸኝ። ስለዚህ አሁንም በንጉሡ ፊት ልቅሶዬን ለመቀጠል እኔ ምን መብት አለኝ?” 29 ከዚያ በኋላም ንጉሡ፣ “ከዚህ በላይ መግለጫ መስጠት ምን
ያስፈልጋል? እርሻውን አንተና ሲባ እንድትካፈሉት ወስኛለሁ።” 30 ስለዚህ ሜምፊቦስቴ ለንጉሡ፣ “ጌታዬ ንጉሡ ወደ ራሱ ቤት በሰላም ስለመጣ፣ ግድ የለም፣
እርሱ ሁሉንም ይውሰደው” አለው። 31 ከዚያም ገለዓዳዊው ቤርዜሊ ከንጉሡ ጋር ዮርዳኖስን ለመሻገር ከሮግሊም መጣ፣ ንጉሡም ዮርዳኖስን ሲሻገር
አጀበው። 32 ቤርዜሊ ሰማንያ ዓመት የሆነው ሽማግሌ ሰው ነበር። እጅግ ባለጠጋ ሰው ስለነበረ፣ ንጉሡ በመሃናይም በቆየበት ጊዜ ስንቅ አምጥቶለት ነበር።
33 ንጉሡም ለቤርዜሊ፣ “ከእኔ ጋር ና፣ እኔ በኢየሩሳሌም የምትመገበውን አቀርብልሃለሁ” አለው። 34 ቤርዜሊም ለንጉሡ፣ “ከንጉሡ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም
እሄድ ዘንድ ከሕይወት ዘመኔ ምን ያህል ቢቀር ነው? 35 እኔ ሰማንያ ዓመቴ ነው፤ መልካሙንና ክፉውን መለየት እችላለሁን? ባሪያህ የሚበላውንስ ሆነ
የሚጠጣውን ጣዕም መለየት ይችላልን? የሚዘፍኑ ወንዶችንና የሚዘፍኑ ሴቶችን ከእንግዲህ መስማት እችላለሁን? ስለዚህ ባሪያህ በጌታዬ በንጉሡ ላይ ለምን
ሸክም ይሆናል? 36 ባሪያህ የሚፈልገው ከንጉሡ ጋር ዮርዳኖስን መሻገር ብቻ ነው። ንጉሡ ለባሪያው ይህንን ያህል ብድራት ለምን ይከፍለኛል? 37 በአገሬ
እሞት ዘንድ፣ በአባቴና በእናቴ መቃብር አጠገብ እቀበር ዘንድ፣ እባክህ ወደ አገሬ እንድመለስ ፍቀድልኝ። ነገር ግን አገልጋይህ ከመዓም ከዚህ አለ፣ እርሱ ከአንተ
ጋር ይሻገር፣ የመሰለህን መልካም ነገር አድርግለት።” 38 ንጉሡም፣ “ከመዓም ከእኔ ጋር ይሻገራል፣ ለአንተም መልካም መስሎ የታየህን አደርግለታለሁ፤
ከእኔም የምትፈልገውን ማንኛውንም ነገር እኔ አደርግልሃለሁ።” 39 ከዚያም ሰዎቹ ሁሉ ዮርዳኖስን ተሻገሩ፤ ከዚያም ንጉሡ ተሻገረ፣ ንጉሡም ቤርዜሊን ሳመው
ባረከውም። ከዚህ በኋላ ቤርዜሊ ወደ ራሱ አገር ተመለሰ። 40 ስለዚህ ንጉሡ ወደ ጌልጌላ ተሻገረ፣ ከመዓምም ከእርሱ ጋር ተሻገረ። የይሁዳ ሠራዊት
ንጉሡንና የእስራኤልን ግማሽ ሠራዊት ይዞ ተመለሰ። 41 ወዲያውም የእስራኤል ሰዎች ሁሉ ወደ ንጉሡ መጥተው ለንጉሡ፣ “ወንድሞቻችን የይሁዳ ሰዎች
አንተን ዳዊትንና ቤተሰቡን እንዲሁም የዳዊትን ሰዎች ሰርቀው ዮርዳኖስን አሻግረው ለምን አመጧቸው?” 42 ስለዚህ የይሁዳ ሰዎች ለእስራኤል ሰዎች፣
“ይህንን ያደረግነው ንጉሡ የቅርብ ዘመዳችን ስለሆነ ነው። ታዲያ እናንተ በዚህ ለምን ትቆጣላችሁ? እኛ የበላነውና ንጉሡ መክፈል ያለበት አንዳች ነገር አለ?
ለእኛስ አንዳች ስጦታ ሰጥቶናል?” 43 የእስራኤል ሰዎች ለይሁዳ ሰዎች፣ “እኛ ከዳዊት ጋር የሚዛመዱ አሥር ነገዶች አሉን፣ ስለዚህ እኛ ከእናንተ ይልቅ
በዳዊት ዘንድ መብት አለን። ታዲያ እናንተ እኛን ለምን ትንቁናላችሁ? ንጉሡን ለማምጣት ያቀረብነው ሃሳብ በመጀመሪያ ሊሰማ የሚገባው አልነበረምን? ነገር
ግን የይሁዳ ሰዎች የሰጡት መልስ የእስራኤል ሰዎች ከሰጡት መልስ ይልቅ እጅግ የከረረ ነበር።”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Samuel 19:1

ኢዮአብ ተነገረው/ሰማ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንድ ሰው ለኢዮአብ ነገረው" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ፣ ንጉሡ አለቀሰ
እዚህ ስፍራ "እነሆ" የሚለው ቃል የዋለው የአንባቢውን ትኩረት ቀጥሎ ወደሚነገረው ነገር ለመሳብ ነው። "እነሆ፣ ንጉሡ አለቀሰ"

በመሆኑም የዚያን ቀን በሰራዊቱ ዘንድ ድሉ ወደ ለቅሶ ተለወጠ
ይህ ማለት መላው ሰራዊት ድሉን ከማክበር ይልቅ አለቀሰ። "በዚያን ቀን ድሉን ከማክበር ይልቅ መላው ሰራዊት አለቀሰ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 19:3

ከጦርነት ሸሽቶ በሀፍረት እንደተመለሰ ህዝብ
ጸሐፊው ወታደሮቹ ወደ ከተማ የተመለሱበትን መንገድ ያነጻጸረው ወታደሮች ከጦርነት በሸንፈት ከሚሸሹበት ሁኔታ ጋር ነው። ይህ እንዲያፍሩ መደረጋቸውን ያጎላል። "ስላፈሩ ከጦርነት የሚሸሹ ሰዎች ወደ ኋላ እንደሚሉ ህዝቡ በተመሳሳይ መንገድ ህዝቡ ተሰርቆ/በምስጥር ገባ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በምስጥር/በስውር
በሌሎች ሳይታዩ መንቀሳቀስ/መጓዝ

ንጉሡ ፊቱን ሸፈነ
ይህ ሀዘንን እና ለቅሶን ፈግለጫ መንገድ ነው። "ንጉሡ ፊቱን በመሸፈን ሀዘኑን ገለጸ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 19:5

ዛሬ የወታደሮችህን ፊት ሁሉ አሳፈርክ
እዚህ ስፍራ ከሀፍረታቸው የተነሳ ወታደሮች ፊታቸውን እንዴት መደበቅ እንዳለባቸው ለማጉላት የተገለጹት በፊታቸው ነው። "ዛሬ ወታደሮችህን በሙሉ በሀፍረት ፊታቸውን እንዲሸፍኑ አድርገሃል" ወይም "ዛሬ ወታደሮችህ በሙሉ እንዲያፍሩ አድርገሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

ይህ ለአንተ ምንም ማለት አይደለም
ይህ ሀረግ ማጋነን ነው፣ ሆኖም ዳዊት ለሰራዊቱ ያሳየው በጣም ዝቅ ያለ ዋጋ ይገልጻል። "ለአንተ ዋጋቸው በጣም ያነሰ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

እኛ ሁላችንም ሞተን አቤሴሎም በህይወት ተርፎ ቢሆን ያ አንተን ባስደሰተህ ነበር
ተናጋሪው መላ ምታዊ ሁኔታን እየሰጠ ነው። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 19:7

በያህዌ እምላለሁ
ኢዮአብ በጣም ጠንካራ መሃላ እያደረገ ነው። "በ ያህዌ እምላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ የማትሄድ ከሆነ፣ ከአንተ ጋር እንድም ሰው አይቀርም
ይህ ማለት የዳዊት ወታደሮች ከእርሱ ጋር የሚቀሩት እርሱ ከሄደ ብቻ ነው። "አንተ ከሄድክ ብቻ ከአንተ ጋር የሚቀር ወታደር ይኖራል" (ድርብ አሉታ የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ሰው እንኳን ከአንተ ጋር አይቀርም
ይህ ለእርሱ ታማኝ ሆነው የሚቀሩትን ያመለክታል። "ለአንተ አንድ ሰው እንኳን ታማኝ ሆኖ አይቀርም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ህዝቡ ሁሉ ሰምቶ ነበር
ይህ የተጠቃለለ አስተያየት ነው። ብዙዎቹ ሰዎች ለማለት ነው። በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እዚያ የነበሩት ብዙዎቹ ሰዎች ሌሎች ሲናገሩ ሰምተዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት እንዲሁም አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

እነሆ፣ ንጉሡ ተቀምጧል
እዚህ ስፍራ "እነሆ" የሚለው ቃል የዋለው የአንባቢውን ትኩረት ቀጥሎ ወደሚነገረው ለመሳብ ነው። "እነሆ፣ ንጉሡ ተቀምጧል"

ህዝቡ ሁሉ
እዚህ ስፍራ "ህዝቡ" የሚለው የሚያመለክተው ዳዊትን የተከተለውን ህዝብ ነው። እዚህ "ሁሉ" የሚለው የተጠቃለለ አስተያየት ነው። ብዙ ቁጥር ያላቸው መጥተው በእርሱ ዙሪያ ተሰባሰቡ ማለት ነው። "ብዙ ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

ስለዚህም እስራኤል ሸሸ፣ እያንዳንዱ ሰው ወደየ ቤቱ ሸሸ
እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚለው አቤሴሎምን የተከተለውን የእስራኤል ወታደር ያመለክታል። "እናም እያንዳዱ የእስራኤል ወታደር ወደየ ቤቱ ሸሸ" ወይም "መላው የእስራኤል ወታደር ወደየ ቤታቸው ሸሹ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

2 Samuel 19:9

ከጠላቶቻችን እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" ማለት መቆጣጠር ማለት ነው። "ከጠላቶቻችን ቁጥጥር ስር" ወይም "ከጠላቶቻችን ቁጥጥር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከፍልስጥኤማውያን እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" ማለት መቆጣጠር ማለት ነው። "ከፍልስጥኤማውያን ቁጥጥር ስር" ወይም "ከፍልስጥኤማውያን ቁጥጥር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከአቤሴሎም የተነሳ ከምድሪቱ ውጭ
ይህ ማለት ከአቤሴሎም በመሸሸ አገር ለቆ ወጥቷል ማለት ነው። ይህ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "ከአቤሴሎም በመሸሸ ከአገር ወጥቷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሡን ስለ መመለስ ለምን አንድ ነገር አትናገሩም?
ይህ ማለት አሁን አቤሴሎም ስለ ሞተ ዳዊትን ስለ መመለስ ጉዳይ ማሰብ አለባቸው ማለት ነው። ጥያቄው በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ንጉሡን ዳግም ስለ መመለስ መነጋጋር አለብን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ንጉሡ
ይህ ዳዊትን ያመለክታል

2 Samuel 19:11

ወደ ሳዶቅ እና አብያታር ላከ
ይህ ማለት ዳዊት ወደ ሳዶቅ እና አብያታር መልዕክተኛ ላከ ማለት ነው። "ወደ ሳዶቅ እና አብያታር መልዕክተኛ ላከ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሡን ዳግም ለመመለስ...እርሱን ወደ ቤተመንግሥቱ ለመመለስ ለምን እናንተ የመጨረሻዎቹ ትሆናላችሁ?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠየቀው በይሁዳ የሚገኙ ሽማግሌዎችን ለመገሰጽ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ንጉሡን ለመቀበል እና ወደ ቤተ መንግስቱ ለመመለስ፣ የእስራኤል መንግሥት ሰዎች ሳይሆኑ እናንተ የመጀመሪያዎቹ መሆን ነበረባችሁ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ንግግር ንጉሡን ለማምጣት እስከ ተቀበለ ድረስ፣
"ንግግር" የሚለው ስም "ተናገረ" ወይም "አለ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "መላው እስራኤል ስለ ንጉሡ ደግፎ እስከተናገረ እና ሊመልሰው እስከ ፈለገ ድረስ" ወይም "የእስራኤል ሰዎች የሚናገሩት ንጉሡ እንዲመለስ እስከ ደገፈ ድረስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሡን ወደ ቤተ መንግሥቱ ለመመለስ
እዚህ ስፍራ ንጉሡ እንዲመራ ስልጣኑን መመለስ የተገለጸው እርሱን ወደ ቤተ መንግሥቱ እንደ መመለስ ተደርጎ ነው። "የንጉሡን ስልጣን እንደ ንጉሥነቱ ለማደስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ ወንድሞቼ፤ የስጋየዬ ቁራጭ የአጥንቴ ፍላጭ ናችሁ
ንጉሡ እነዚህን ሀረጎች የተጠቀመው በቅርበት የተዛመዱ መሆናቸውን ለመግለጽ ነው። አንድ ስጋ ነን ወይም አንድ ስጋ አለን ማለት ቤተሰብ መሆንን ወይም ከአንድ ነገድ መሆንን የሚገለጽ ዘይቤ ነው። "እናንተ ወንድሞቼ ናችሁ እኛ አንድ ስጋ እና አጥንት አለን" ወይም "እናንተ ወንድሞቼ ናችሁ፣ የቅርብ ዘመዶቼ ናችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሡን ዳግም ለመመለስ እናንተ ለምን የመጨረሻዎቹ ትሆናላችሁ?
እዚህ ስፍራ ይህ ሁለተኛው ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ ሲሆን የይሁዳን ሽማግሌዎችንም ጭምር ይገስጻል። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "እናንተ ንጉሡን ዳግም ለመመለስ፣ የመጨረሻ ሰይሆን የመጀመሪያዎቹ መሆን ይገባችሁ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 19:13

አሜሳይ
ይህንን የወንድ ስም በ2 ሳሙኤል 17:25 ላይ እንዴት እንደ ተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ ስጋዬ እና አጥንቴ አይደላችሁምን?
እዚህ ስፍራ ዳዊት ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ዘመድ መሆናቸውን ለማጉላት ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "እናንተ ስጋ እና አጥንቶቼ ናችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ስጋዬ እና አጥንቴ ናችሁ
እዚህ ስፍራ ዳዊት ስለ እነርሱ መዛመድ የሚናገረው አንድ አይነት ስጋ እና አጥነት አለን በማለት ነው። በ 2 ሳሙኤል 19:12 ላይ ተመሳሳዩ ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ዘመዶቼ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር እንዲህና እንዲያ ያድርግብኝ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ እግዚአብሔር ይግደለኝ/ያንሳኝ ማለት ነው።"እግዚአብሔር ያንሳኝ/ይግደለኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ልቦቻቸውን ማረከ
እዚህ የወንዶቹ ታማኝነት የተገለጸው እንደ ልቦቻቸው ተደርጎ ነው። "ታማኝነታቸውን አገኘ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ አንድ ሰው
ይህ የሚገልጸው ወንዶቹ ለንጉሡ በታማኝነታቸው እንደ አንድ ሰው በአንድ ሃሳብ መተባበራቸውን ነው። "እናም በአንድነት ተባብረው ነበር" ወይም "ለንጉሡ በታማኝነታቸው ተባብረው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለንጉሡ ላኩ
ይህ ማለት ለንጉሡ መልዕክት ላኩ ማለት ነው። "እነርሱ ለንጉሡ መልዕክት ላኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 19:16

ጌራ...ሲባ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። "ሲባ" የሚለውን ስም በ 2 ሳሙኤል 9:2 ላይ እንደ ተረጎሙት በተመሳሳይ ይተርጉሙት። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ብራቂም
የዚህን ቦታ ስም በ 2 ሳሙኤል 3:16 ላይ እንደ ተረጎሙት በተመሳሳይ ይተርጉሙት። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ሺህ ወንዶች ... አስራ አምስት ወንዶች ልጆች... ሃያ አገልጋዬች
"1,000 ወንዶች... 15 ወንዶች ልጆች ... 20 አገልጋዬች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሡ በተገኘበት
ይህ ማለት ንጉሡ በዚያ ነበር ደግሞም የሚደረገውን ያውቅ ነበር። "ንጉሡ በነበረበት ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 19:19

በልብህ አኑረው
ይህ "ማታወስ" ማለት ነው። "አስታውስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ አገልጋይ
እዚህ ስፍራ ሳሚ ራሱን በዚህ መንገድ የሚገልጸው በንጉሡ ፊት ራሱን ዝቅ ለማድረግ እና ንጉሡን ለማክበር ነው።

ወደ ልብህ አታስገባው
"አንድን ነገር ወደ ልብ ማስገባት" ማለት ስለ አንድ ነገር በጥንቃቄ ማሰብ ወይም በዚያ ነገር መጨነቅ ማለት ነው። "በዚህ አትጨነቅበት" ወይም "እጅግ ግድ አይበልህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Samuel 19:21

አቢሳ
ይህ የወንድ ስም በ2 ሳሙኤል 2፡18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ጽሩያ
ይህ የወንድ ስም በ2 ሳሙኤል 2፡13 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ የቀባውን ሰድቧልና ሳሚ ለዚህ ስራው ሞት አይገባውምን?
አቢሳ በሳሚ ላይ እጅግ የተቆጣው ዳዊትን በመራገሙ ሲሆን ሞት እንደሚገባውም ተናግሯል። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ያህዌ የቀባውን ስለሰደበ ሳሚ መገደል ይገባዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ የቀባው
ይህ ዳዊትን ያመለክታል። ይህ ማለት ያህዌ ንጉሥ አድርጎ የቀባው ሰው እርሱ ነው። "ያህዌ ንጉሥ አድርጎ የቀባው ሰው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ዛሬ እንዲህ ታማክሩኝ ዘንድ ...እኔ ከእናንተ ጋር ምን አለኝ?
ዳዊት ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው አቢሳን ለመገሰጽ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። " እናንተ የጽሩያ ልጆች፣ እኛ ከእናንተ ጋር የጋራ የሆነ ምንም ነገር የለንም! ዛሬ ታማክሩኝ ዘንድ አንዳች ጥሩ ምክንያት የላችሁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ዛሬ በእስራኤል ውስጥ አንዳች ሰው ይገደላልን? ዛሬ በእስራኤል ላይ ንጉሥ መሆኔን አላወቅኩምን?
ዳዊት ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው አቢሳን መውቀሱን ለመቀጠል ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ዛሬ በእስራኤል አንዳች ሰው አይገደልም፣ ምክንያቱም ዛሬ እኔ በመላው እስራኤል ላይ ነግሻለሁ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ሰው ይገደላልን
"ይገደላልን" የሚለው ሀረግ መገደል ወይም መረሸን ማለት ነው። "አንድ ሰው ይገደላልን" ወይም "አንድ ሰው እንዲገደል ትዕዛዝ እሰጣለሁን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ዛሬ በእስራኤል ሁሉ ላይ መንገሤን አላወቅኩምን?
የዚህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት አማራጮች፡ 1)"አሁንም የእስራኤል ንጉሥ መሆኔን አውቃለሁ" ወይም "ዛሬ በእስራኤል ሁሉ ላይ ንጉሥ የሆንኩት እኔ ነኝ!" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 19:24

ሜምፊቦስቴ
ይህ የወንድ ስም በ2 ሳሙኤል 4፡4 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእግሩ መጫሚያ አላደረግም/ጫማ አላደረገም
"ለእግሩ እንክብካቤ አላደረገም።" የሜምፊቦስቴ እግሮች ሸባ ነበሩ። የዚህ ሀረግ ትርጉም ለእግሩ ተገቢ አንክብካቤ አላደረገም ማለት ነው።

ሜምፊቦስቴ፣ ለምን ከእኔ ጋር ሳትሄድ ቀረህ?
ዳዊት ሜምፊቦስቴን ዳዊት እና እርሱን የሚከተሉ ሰዎች ሁሉ እየሩሳሌምን ለቀው ሲሄዱ እርሱ ለምን እንዳልተከተለው ይጠይቀዋል። "ሜምፊቦስቴ፣ እኔ እየሩሳሌምን ለቅቄ ስወጣ አንተ ለምን አልተከተልከኝም?" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 19:26

ሲባ
ይህ የወንድ ስም በ2 ሳሙኤል 9:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሡ ጌታዬ እንደ እግዚአብሔር መልአክ ነው
እዚህ ስፍራ የዳዊት ጥበብ የተነጻጸረው ከመልአክ ጥበብ ጋር ነው። "ንጉሡ ጌታዬ እንደ እግዚአብሔር መልአክ ብልህ ነው" (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በዐይኖችህ ፊት መልካም መስሎ የታየህን አድርግ
ይህ ማለት ትክክል መስሎ የታየህን አድርግ ማለት ነው። "ለማድረግ ትክክል ነው ብለህ ያመንክበትን አድርግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በንጉሡ በጌታዬ ፊት የአባቴ ቤት ሁሉ እንደ ሞቱ ሰዎች ናቸው
ሜምፊቦስቴ የእርሱ ቤተሰቦች ሞት እንደሚገባቸው የገለጸው ቀድሞውኑ እንደ ተገደሉ እና የሞቱ እንደሆኑ አድርጎ ነው። "የአባቴ ቤቱ ሁሉ ንጉሡ ጌታዬ እንዲገደሉ ትዕዛዝ ሊያወጣባቸው የተገባቸው ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የአባቴ ቤት
ይህ የአባቱን ዘመዶች ያመለክታል። "የአባቴ ቤተ ዘመዶች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህ አሁንም ወደ ንጉሡ ከዚህ በላይ እጮህ/እናገር ዘንድ ምን መብት አለኝ?
ሜምፊቦስቴ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ከንጉሡ አንዳች ነገር ለመጠየቅ ምንም መብት እንደሌለው አጉልቶ ለመናገር ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ስለዚህ፣ ንጉሡ ለእኔ ሌላ ተጨማሪ ነገር አንዲያደርግ ለመጠየቅ ምንም መብት የለኝም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 19:29

ለምን ሌላ ማብራሪያ ትጨምራለህ?
ዳዊት ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ከሲባ ጋር እርሱ ስላለው ግጭት መናገሩን መቀጠል እንደማያስፈልገው ሊነግረው ስለ ፈለገ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ይህንን ከዚህ በላይ ማብራራት አያስፈልግህም።" ወይም "በእርግጥ ከዚህ በላይ መናገር አያስፈልግህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 19:31

ቤርዜሊ
ይህ የወንድ ስም በ2 ሳሙኤል 17:27 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ገለዓዳዊ
ይህ የሰዎች ቡድን/የወገን ስም በ2 ሳሙኤል 17:27 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሮግሊም...መሃናይም
እነዚህ የቦታ ስሞች በ2 ሳሙኤል 17:27 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የዮርዳኖስ
የዮርዳኖስ ወንዝ

የሰማንያ አመት አድሜ
"የ80 አመት እድሜ" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ለንጉሡ የሚያስፈልገውን አዘጋጀ
"ንጉሡ የሚያስፈልገውን አቀረበ"

2 Samuel 19:34

ከንጉሡ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም እሄድ ዘንድ ከእድሜዬ የምኖርበት ምን ያህል ቀናት ቀረኝና ነው?
እዚህ ቤርዜሊ ማለት ዳዊትን ለማጀብ አንዳች ምክንያት የሌለው ሽማግሌ ሰው ነው። ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "በእርግጥ የምኖርበት ዘመን እያበቃ ያለ ሰው ነኝ። ከንጉሡ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ በቂ ምክንያት የለኝም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰማንያ አመት አድሜ
"የ80 አመት እድሜ" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በመልካሙ እና በክፉው መካከል መለየት እችላለሁን?
ቤርዜሊ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ለምን ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ እንዳልፈለገ ለማጉላት ነው። እዚህ "መልካም" እና "ክፉ" የሚሉት ቃላት የዋሉት አስፈላጊ የሆነ እና ያልሆነውን ለማመልከት ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "አስፈላጊ በሆነው እና ባልሆነው መሃል መለየት አልችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

አገልጋይህ የምበላውን ወይም የምጠጣውን ጣዕሙን መለየት እችላለሁን?
ቤርዜሊ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ለምን ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ እንዳልፈለገ ለማጉላት ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "የምበላውን እና የምጠጣውን ጣዕሙን ላጣጥም አልችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህ የሚዘምሩ ወንዶችና እና የሚዘምሩ ሴቶችን ድምጽ መስማት/መለየት እችላለሁን?
ቤርዜሊ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ለምን ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ እንዳልፈለገ ለማጉላት ነው።ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "የሚዘምሩ ወንዶችን እናየሚዘምሩ ሴቶችን ድምጽ በትክክል መስማት አልችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

አገልጋይህ ለምን ለጌታዬ ለንጉሡ ሸክም ይሆናል?
ቤርዜሊ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው በንጉሡ ላይ ሸክም መሆን አለመፈለጉን ለማጉላት ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "አገልጋይህ ከአንተ ጋር በመሄድ ለአንተ ሸክም መሆን የለበትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሡ ለምን ለእኔ እዲህ ባለ ወረታ ይመልስልኛል?
ቤርዜሊ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ንጉሡ ለምን በእንዲህ ያለ መንገድ ወረታ እንደሚያደርግለት አለማወቁን ለማጉላት ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ንጉሡ ለምን እንዲህ አይነት ታላቅ ወረታ እንደሚያደርግልኝ አላውቅም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 19:37

አጠቃላይ መረጃ:
ቤርዜሊ የእርሱን ቦታ ከዳዊት ከመዓም እንዲወስድ ይፈቀድለት ዘንድ ጠየቀ

ከመዓም
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በአባቴ እና በእናቴ መቃብር
ይህ ማለት ከመቃብራቸው አጠገብ መሞት ይፈልጋል ማለት አይደለም፣ ነገር ግን ይልቁንም፣ እነርሱ በተቀበሩበት ከተማ መቀበር ይፈልጋል ማለት ነው። ይህ ይበልጥ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "የአባቴ እና የእናቴ መቃብር ባለበት" ወይም "አባቴ እና እናቴ በተቀበሩበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ይሻገር
ይህ የሚያመለክተው የዮርዳኖን ወንዝ መሻገርን ነው። "እርሱ ዮርዳኖስን ይሻገር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 19:38

ከመዓም ከእኔ ጋር ወንዙን ይሻገራል
ይህ የሚያመለክተው የዮርዳኖስን ወንዝ መሻገርን ነው። ይህ ይበልጥ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "ከመዓም ከእኔ ጋር ወንዙን ይሻገራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 19:40

ወደ ጌልገላ መሻገር
የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻገሩ። "ወደ ጌልገላ ወንዙን ተሻገሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

ከመዓም
ይህ ስም በ2ሳሙኤል19:37 እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

መላው የይሁዳ ሰራዊት ንጉሡን እና የእስራኤልን ሰራዊት እኩሌታ አሻገረ
"የይሁዳ ሰራዊት እና የእስራኤል ሰራዊት እኩሌታ ንጉሡን አሻገረ"

ንጉሡን አሻገሩት
የዮርዳኖስን ወንዝ ከንጉሡ ጋር ተሻገሩ። "ንጉሡ ወንዙን ሲያቋርጥ አጀቡት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

ወንድሞቻችን የይሁዳ ሰዎች ... እና መላው የዳዊት ሰዎች ለምን ከእርሱ ጋር ሆኑ?
የእስራኤል ሰዎች ይህንን ጥያቄ ያዋሉት በይሁዳ ሰዎች የተካዱ ሆኖ ስለተሰማቸው ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "አንተን እንደ ንጉሥ ያልደገፉህ ወንድሞቻችን የይሁዳ ሰዎች አንተን እና ቤተሰብህን ዮርዳኖስን የማሻገር እድል ማግኘታቸው አግባብ አይደለም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተን ሰረቁ
የእስራኤል ሰዎች የይሁዳ ሰዎችን ንጉሡ የእነርሱ እንዳልሆነ እና የሰረቁት ነገር ይመስል ዮርዳኖስን ሲሻገር በማጀባቸው ተናገሩ። "አንተን ከእኛ ወሰዱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የዮርዳኖስ
የዮርዳኖስ ወንዝ

2 Samuel 19:42

ታዲያ ለምን ስለዚህ ነገር ተቆጣችሁ?
የይሁዳ ሰዎች ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የጠየቁት የእስራኤልን ሰዎች ለመገሰጽ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ነገር ግን እናንተ

በዚህ ነገር ለመበሳጨት የሚያበቃ ምንም ምክንያት የላችሁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሡ ወጪ የሚያደርግበትን አንዳች ነገር በልተናልን? ለእኛ አንዳች ስጦታ ሰጥቶናልን?
የይሁዳ ሰዎች ጥያቄውን የጠየቁት ከንጉሡ አንዳችም ነገር አለመውሰዳቸውን ለመግለጽ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ንጉሡ ለቀለባችን ከፍሎ አያውቅም፣ ደግሞም አንዳች ስጦታም ሰጥቶን አያውቅም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእናንተ ይልቅ እኛ በዳዊት ላይ የበለጠ መብት አለን
"እኛ ከእናንተ ይልቅ ከዳዊት ላይ ልንጠይቅ የምንችለው አለን።" "የበለጠ መብት" የሚለው ምን ማለት እንደሆነ ይበልጥ ግልጽ ማድረጉ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። " እኛ ከእናንተ ይልቅ ንጉሡን ለማገልገል እና ከንጉሡ ጋር ለመሆን የበለጠ መብት አለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህ ከሆነ እናንተ እኛን ስለምን ትንቁናላችሁ?
የእስራኤል ሰዎች ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠይቁት ቁጣቸውን ለመግለጽ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "እኛን ልትንቁን አይገባችሁም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሣችንን ለመመለስ ያቀረብነው ሃሳብ ቅድሚያ አግኝቶ መደመጥ አልነበረበትምን?
የእስራኤል ሰዎች ይህንን ጥያቄ የጠየቁት የይሁዳን ሰዎች ስለ ነገሩ ለማስታወስ እና ለመገሰጽ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ንጉሡን እንመልሰዋለን! የሚለውን ሀሳብ ለማቅረብ እኛ የመጀመሪያዎቹ ነበርን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳ ሰዎች ቃል ከእስራኤል ሰዎች ቃል ይልቅ ጠንካራ ነበር
"የይሁዳ ሰዎች የእስራኤል ሰዎች ከተናገሩት ይልቅ ጠንካራ ንግግር ተናገሩ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 20

1 በዚህ ጊዜ በዚሁ ስፍራ የቢክሪ ልጅ ስሙ ሳቤዔ የተባለ አንድ ችግር ፈጣሪ ብንያማዊ ነበር። እርሱም መለከት ነፍቶ፣ “እኛ ከዳዊት ጋር ድርሻ የለንም፣
ከእሴይ ልጅም ጋር ርስት የለንም፤ እስራኤል ሆይ፣ እያንዳንዱ ሰው ወደ ቤቱ ይመለስ” አለ። 2 ስለዚህ የእስራኤል ሰዎች ሁሉ ዳዊትን ከድተው የቢክሪን ልጅ
ሳቤዔን ተከተሉ። የይሁዳ ሰዎች ግን ከዮርዳኖስ አንስተው እስከ ኢየሩሳሌም ድረስ ንጉሣቸውን አጥብቀው ተከተሉ። 3 ዳዊት በኢየሩሳሌም ወዳለው ቤተ
መንግሥቱ በመጣ ጊዜ ቤተ መንግሥቱን እንዲጠብቁ ትቶአቸው የነበሩትን ዐሥሩን ቁባቶች በአንድ ቤት ውስጥ አስገብቷቸው በአንድ ዘበኛ እንዲጠበቁ
አደረገ። የሚያስፈልጋቸውን አቀረበላቸው፣ ነገር ግን ከዚያ በኋላ ከእነርሱ ጋር አልተኛም። 4 እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ ተዘግቶባቸው እንደ መበለት ይኖሩ ነበር።
ከዚያ በኋላ ንጉሡ ለአሜሳይ፣ “በሦስት ቀን ውስጥ የይሁዳ ሰዎች ሁሉ እንዲሰባሰቡ ጥራቸው፣ አንተም እዚህ መገኘት አለብህ” አለው። 5 ስለዚህ አሜሳይ
የይሁዳ ሰዎች እንዲሰባሰቡ ለመጥራት ሄደ፣ ነገር ግን ንጉሡ ካዘዘው ቀነ-ገደብ በላይ ቆየ። 6 ስለዚህ ዳዊት ለአቢሳ፣ “አሁን የቤክሪ ልጅ ሳቤዔ አቤሴሎም
ካደረሰው ይልቅ የባሰ ጉዳት ያደርስብናል። የጌታህን አገልጋዮች ወታደሮቼን ያዝና አሳደው፣ አለበለዚያ የተመሸጉ ከተሞችን ያገኝና ከዓይናችን ይሰወራል።”
አለው። 7 በዚያን ጊዜ የኢዮአብ ሰዎች ከከሊታውያን ከፈሊታውያን እንዲሁም ከሌሎች ኃያላን ጦረኞች ጋር ተከትለውት ወጡ። የቤክሪን ልጅ ሳቤዔን ያሳድዱ
ዘንድ ከኢየሩሳሌም ወጡ። 8 ገባዖን ከሚገኘው ታላቅ ዐለት በደረሱ ጊዜ አሜሳይ ሊገናኛቸው መጣ፣ ኢዮአብ በሰገባው ውስጥ የገባ ሰይፍ በወገቡ
የታጠቀበትን ቀበቶ የሚያካትት የጦር ሜዳ ልብሱን ለብሶ ነበር። ወደፊት እየተራመደ ሳለም ሰይፉ ወደቀ። 9 ኢዮአብም አሜሳይን፣ “ወንድሜ ሆይ፣ ደህና
ነህን?” አለው። ኢዮአብም አሜሳይን እንደሚያፈቅረው አድርጎ ለመሳም ጢሙን ይዞ ሳበው። 10 አሜሳይ ኢዮአብ በግራ እጁ ይዞት የነበረውን ጩቤ
አላስተዋለም። ኢዮአብ አሜሳይን ሆዱን ወጋው፣ ሆድ-ዕቃውም በምድር ላይ ተዘረገፈ። ኢዮአብ እንደገና አልወጋውም፣ አሜሳይም ሞተ። ስለዚህ ኢዮአብና
ወንድሙ አቢሳ የቤክሪን ልጅ ሳቤዔን አሳደዱ። 11 ከዚያ በኋላ ከኢዮአብ ሰዎች አንዱ በአሜሳይ አጠገብ ቆመና፣ “ኢዮአብን የሚደግፍና የዳዊት የሆነ
ኢዮአብን ይከተል” አለ። 12 በዚህን ጊዜ አሜሳይ በደም ተጨማልቆ በመንገዱ መካከል ወድቆ ነበር። ሰዎች ሁሉ ቆመው እንደቀሩ ሰውዬው ተመልክቶ
የአሜሳይን ሬሳ ከመንገድ ጎትቶ ወደ እርሻ ውስጥ አስገባው። ወደ አጠገቡ የደረሰ ማንኛውም ሰው ቆሞ ይቀር እንደነበረ ተመልክቶ ልብስ በላዩ ጣል
አደረገበት። 13 አሜሳይ ከመንገድ ዞር ከተደረገ በኋላ የቤክሪ ልጅ ሳቤዔን ለማሳደድ ሰዎች ሁሉ ኢዮአብን ተከተሉ። 14 ሳቤዔአም በእስራኤል ነገዶች ሁሉ
መካከል አልፎ ወደ አቤል ቤትማዓካና ተሰባስበው ሳቤዔን ያሳድዱ ወደነበሩት ወደ መላው የቤክሪያውያን ግዛት መጣ። 15 ደረሱበትና አቤል ቤትመዓካ ላይ
ከበቡት። በከተማይቱም ላይ ግድግዳውን አስጠግተው የአፈር ድልድል ሠሩበት። ከኢዮአብ ጋር የነበረውም ሠራዊት ግንቡን ለመናድ ደበደበው። 16 ከዚያ
በኋላ አንድ ብልህ ሴት ከከተማ ውስጥ ተጣራችና፣ “ስማኝ፣ እባክህን ስማኝ ኢዮአብ፤ እንዳነጋግርህ ወደዚህ ጠጋ በል” አለችው። 17 ስለዚህ ኢዮአብ ጠጋ
አለ፣ ሴቲቱም፣ “አንተ ኢዮአብ ነህን?” አለችው። እርሱም፣ “አዎን፣ ነኝ” አለ። እርሷም ከዚያ በኋላ ለእርሱ፣ “የባሪያህን ቃል ስማ” አለችው። እርሱም፣
“እየሰማሁ ነው” ብሎ መለሰላት። 18 ከዚያ በኋላም እርሷ፣ “በቀደሙት ጊዜያት ‘በእርግጥ ምክርን ከአቤል ጠይቅ ምክሩም ችግሮችን ይፈታል’ ይሉ ነበር።
19 እኛ በእስራኤል ውስጥ እጅግ ሰላማዊና ታማኝ ከሆኑት ከተሞች አንዱ ነን። በእስራኤል ውስጥ እናት የሆነችውን ከተማ ለማጥፋት እየሞከርክ ነው።
የእግዚአብሔርን ርስት ለምን ለመዋጥ ትፈልጋለህ?” 20 ስለዚህ ኢዮአብ፣ “መዋጥ ወይም ማጥፋት ከእኔ የራቀ ይሁን፣ 21 ያ እውነት አይደለም። ነገር ግን
ከኮረብታማው ከኤፍሬም አገር የሆነ ሳቤዔ የተባለ የቤክሪ ልጅ እጁን በንጉሡ ላይ ፣ በዳዊት ላይ አንስቷል፤ እርሱን ብቻ አሳልፋችሁ ስጡኝ፣ ከተማውን ለቅቄ
እወጣለሁ” ብሎ መለሰላት። ሴቲቱም ለኢዮአብ፣ “ራሱ በቅጥሩ ላይ ይወረወርልሃል” አለችው። 22 ከዚያም ሴቲቱ በጥበብዋ ወደ ሕዝቡ ሁሉ ሄደች።
የቤክሪን ልጅ የሳቤዔን ራስ ቆርጠው በቅጥሩ ላይ ለኢዮአብ ወረወሩለት። እርሱም ቀንደ-መለከቱን ነፋ፣ የኢዮአብም ሰዎች ከተማይቱን ለቀው እያንዳንዱ ሰው
ወደየቤቱ ሄደ። 23 በዚህን ጊዜ ኢዮአብ በሠራዊቱ ሁሉ ላይ የበላይ ነበር፣ የዮዳሄ ልጅ በናያስ ደግሞ በከሊታውያንና በፈሊያታውያን ላይ አለቃ ሆነ። 24
አዶኒራም በግዳጅ ሥራ ላይ ለተሰማሩት አለቃ ሆነ፣ የአሒሉድ ልጅ ኢዮሣፍጥ ደግሞ ታሪክ ጸሐፊ ሆነ፤ 25 ሱሳ ጸሐፊ፣ ሳዶቅና አብያታር ካህናት ነበሩ፤ 26
እንዲሁም የኢያዕር ሰው ዒራስ የዳዊት ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆነ።

---

2 Samuel 20:1

በተመሳሳይ ስፍራ ለመሆን
ይህ የጌልገላን ከተማ ያመለክታል።

ሳቤዔ... ቢክሪ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ ከዳዊት ምንም ድርሻ የለንም፣ ከእሴይም ልጅ ምንም ርስት የለንም
ሁለቱም ሀሳቦች አንድን ነገር ይገልጻሉ። ሳቤዔ እርሱ እና የእስራኤል ነገድ ከዳዊት ጋር ምንም ዝምድና እንደሌላቸው ትኩረት ይሰጣል። "የዳዊት ትውልድ እና የአባቱ ቤት የእኛ ወገን አይደሉም" ወይም "እኛ የዳዊት ወይም የአባቱ ቤት ወገን አይደለንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

2 Samuel 20:3

ቤቱን ለመጠበቅ
እዚህ ስፍራ "ለመጠበቅ" የሚለው ሀረግ እንክብካቤ ለማድረግ የሚልትርጉም አለው። "ቤቱን ለመንከባከብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋጋር የሚለውን ይመልከቱ)

በጠባቂ ስር በሚገኝ ቤት
x

2 Samuel 20:4

አሜሳይ
ይህ ሰው የዳዊት ሰራዊት የጦር አዛዥ ነው። የዚህ ሰው ስም በ2 ሳሙኤል 17:25 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Samuel 20:6

አቢሳ
ይህ ሌላኛው የዳዊት ሰራዊት የጦር አዛዥ ነው። የዚህ ሰው ስም በ2 ሳሙኤል 2፡18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ብዙ ጉዳት ያደርስብናል
"የበለጠ ይጎዳናል"

የጌታችሁ አገልጋዮች፣ የእኔ ወታደሮች
"የእኔ ወታደሮች" የሚለው ሀረግ የትኞቹ "አገልጋዮች" እንደሆኑ ግልጽ ያደርጋል። ዳዊት ራሱን "የእናንተ ጌታ" በማለት ዝቅ ያለ ስልጣን ካለው ሰው ጋር ንግግር በሚደረግበት መደበኛ የአነጋጋር መንገድ ይገልጻል።

ተከትለህ አባረው
"ከኋላ አሳደው"

የተመሸገ ከተማ ያገኛል
ይህ ማለት ሳቤዔ እና የእርሱ ወታደሮች ከዳዊት ሰራዊት ለመደበቅ ወደ እነዚህ ከተሞች ይገባሉ ማለት ነው። "እርሱ" የሚለው ቃል የሚወከወለው ሳቤዔን ሲሆን ነገር ግን እርሱን እና የእርሱን ወታደሮች ጭምር ያመለክታል። "እርሱ እና የእርሱ ሰዎች በተመሸገ ከተማ ራቸውን ይደብቃሉ" ወይም "እርሱ እና የእርሱ ሰዎች በተመሸጉ ከተሞች ይሸሸጋሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከእይታችን ውጭ
እዚህ ስፍራ ዳዊት ሳቤዔ እና የእርሱ ሰዎች ሊደበቁ እንደሚችሉ እና የዳዊት ሰራዊት ሊይዛቸው እንደሚቸገር ትኩረት ለመስጠት ሰራዊቱን የሚገልጸው በእይታቸው ነው። "ከእኛ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከሊታውያን ... ፈሊታውያን
እነዚህ ንጉሥ ዳዊትን ለመጠበቅ የረዱ የሰዎች ቡድን/ የወገን ስሞች ናቸው። እነዚህ የወንድ ስሞች በ2 ሳሙኤል 8፡18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 20:8

እነርሱ በደረሱ ጊዜ
"ኢዮአብ እና የይሁዳ ሰዎች በደረሱ ጊዜ "

ቀበቶ
ልብስን ለመታጠቅ ወይም መሳሪያን ለማንገት የሚያገለግል የቆዳ ወይም የሌላ ነገር ቀራጭ

ሰገባ ያለው ሰይፍ
ይህ ማለት ሰይፉ በሰገባው ውስጥ ነበር።

ሰይፉ ወደቀ
ኢዮአብ አሜሳይን ለማታለል ሰይፉን በመጣል እንዳልታጠቀ አድርጎ እንዲያስብ በማድረግ አሜሳይ ወደ እርሱ እንዲቀርብ አደረገ። "ኢዮአብ ሰይፉ ወደ መሬት እንዲወቅድ የተወው አሜሳይ እርሱ እንዳልታጠቀ አድርጎ እንዲያስብ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 20:9

የአክስቴ ልጅ
አሜሳይ የኢዮአብ እናት እህት ልጅ ነበር

አሜሳይን ሊስመው በቀኝ እጁ ጺሙን ይዞ ወደ እርሱ አስጠጋው
ይህ ወንዶች እርስ በእርሳቸው ሰላምታ የሚሰጣጡበት የተለመደ መንገድ ነበር

ጩቤ
ለመደበቅ ቀላል የሆነ አጭር ሰይፍ ሲሆን ብዙውን ጊዜ ለጨበጣ ውጊያ እና ለግድያ የሚያገለግል ነው

ሆድ ዕቃው ተዘረገፈ
"አንጀቱ ተዘረገፈ"

2 Samuel 20:11

ለዳዊት የሆነ
"ለአንድ ሰው" መሆን ማለት ያንን ሰው መደገፍ ማለት ነው። "ዳዊትን የሚደግፍ" ወይም "ለዳዊት ታማኝ የሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አሜሳይ በደም ተነክሮ ወድቆ ነበር
"አሜሳይ በደሙ ተነክሮ ይንከባለል ነበር።" አሜሳይ ገና ነፍሱ ስላልወጣች በደሙ ተነክሮ ሲንከባለል ቢቆይም በዚህን ጊዜ ግን ሳይሞት አልቀረም። ይህ በዚህ መንገድ የተገለጸው አካሉ ምን ያህል በአሰቃቂ ሁኔታ ውስጥ እንደሚገኝ ለመግለጽ ነው። "አሜሳይ ሞቶ በደም ተነክሮ ተጋድሞ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እርሱ ሲደርሱ...ህዝቡ ሁሉ ቀጥ ብሎ ይቆም ነበር
ይህ ማለት መሄዳቸውን ያቆሙ እና የአሜሳይን በድን አትኩረው ይመለከቱ ነበር። "ሁሉም ሰዎች ቀጥ ብለው እየቆሙ የአሜሳይን በድን ይመለከቱ ነበር... ወደ እርሱ ሲደርሱ እየቆሙ በድኑን አትኩረው ይመለከቱ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አሜሳይን ተሸከመው
"የአሜሳይን በድን ተሸከመ"

አሜሳይ ከመንገድ ዘወር ከተደረገ በኋላ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰውየው አሜሳይን ከመንገድ ዞር ካደረገ በኋላ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ማሳደዱ ሲያበቃ
ይህ ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊገለጽ ይችላል። "አሳደደ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 20:14

ሳቤዔአለፈ
እዚህ ስፍራ "ሳቤዔ" የሚለው የሚያመለክተው እርሱን እና ሰራዊቱን ነው። "ሳቤዔ እና የእርሱ ሰራዊት" ወይም "ሳቤዔ እና የእርሱሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የቤት መዓካው አቤል
"አቤል ቤትመዓካ።" ሁለቱም ስሞች አንድን ቦታ ያመለክታሉ ምናልባትም ሊጣመሩ ይችላሉ። ይህ ከተማ በዳን ነገድ አቅራቢያ የሚገኝ ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ቢክሪያውያን
ይህ የሰዎች ቡድን/ የወገን ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ደግሞም ሳቤዔን አሳደዱ
"ደግሞም ሳቤዔን ተከተሉት"

እነርሱ ደረሱበት
"ኢዮአብ እና ወታደሮቹ እርሱ ላይ ደረሱበት"

2 Samuel 20:17

የባሪያህን ቃል አድምጥ
ሴትየዋ ራስዋን "የአንተ አገልጋይ" በማለት ትገልጻለች። ይህ በስልጣን ከፍ ካለ ሰው ጋር በትህትና መነጋገሪያ መንገድ ነው።

ያ ምክር ለነገሩ ፍጻሜ ይሰጣል
"ያ ምክር ችግሩን ይፈታል"

በእስራኤል ውስጥ እጅግ ሰላማዊ እና ትክክለኛ
ይህ ከተሞቹን ይገልጻል። "በእስራኤል እጅግ ሰላማዊ እና ትክክለኝ ከተሞች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

በእስራኤል እናት የሆነች ከተማ
ይህ በእስራኤል አገር የዚህን ከተማ ጠቀሜታ እንደ ተከበረች እናት አድርጎ ይገልጻል። "በእስራኤል የሚኖር ሁሉ እናቱን እንደሚያከብር የሚያከብራት ከተማ" ወይም "በጣም ጠቃሚ እና እስራኤል ሁሉ የሚያከብራት ከተማ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለምን የያህዌን ርስት ለመዋጥ ትፈልጋለህ?
እዚህ ስፍራ ሴትየዋ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመችው ለኢዮአብ ማድረግ የማይገባቸውን እንዳያደርጉ ለመጠቆም ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ያህዌ ርስቱ ያደረጋትን ከተማ መደምሰስ የለባችሁም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

መዋጥ
እዚህ ስፍራ ሴትየዋ ከተማይቱ የሚዋጥ ምግብ የሆነች ያህል ሰራዊቱ እንደሚደመስሳት ትገልጻለች። "መደምሰስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌ ርስት
እዚህ ስፍራ ከተማይቱ እንደ ያህዌ ርስት የተገለጸችው የያህዌ መሆኗን ለመጉላት ነው። "የያህዌ የሆነች ከተማ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 20:20

ይህ ከእኔ ይራቅ፣ ከእኔ ይራቅ
ይህንን ሀረግ የደጋገመው ነገሩን በፍጹም የማያደርገው መሆኑን ለማጉላት ነው። "በእውነት፣ በእውነት በፍጹም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ልውጣት ወይም ልደመስሳት
ይህ የሚያመለክተው ከተማይቱን ስለ መደምሰስ ነው። ይህ ይበልጥ ግልጽ ተደርጎ ሊገለጽ ይችላል። "ከተማችሁን ልውጣት ወይም ልደመስሳት ይገባል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

መዋጥ ወይም መደምሰስ
እነዚህ ሁለቱም ሀረጋት መደምሰስ ማለት ናቸው። በመጀመሪያው ሀረግ "መደምሰስ" የተገለጸው እንደ "መዋጥ" ተደርጎ ነው። እነዚህ በአንድነት ሊቀርቡ ይችላሉ። "ከተማይቱን ማፍረስ ወይም መደምሰስ" ወይም "መደምሰስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትረጉም እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እጁን አነሳ
ይህ ማለት አንድን ሰው መቃወም እና መዋጋት ማለት ነው። "ተቃወመ" ወይም "በአመጸ መቃወም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱን ብቻ አሳልፈው እንዲሰጡ
ኢዮአብ የከተማይቱን ሰዎች ለእርሱ ሳቤዔን አሳልፈው እንዲሰጡት ጠየቅ። "ይህን ሰው ለእኛ አሳልፋችሁ ስጡን" ወይም "ይህንን ሰው ለእኛ ስጡን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከከተማይቱ እወጣለሁ
እዚህ ስፍራ "እኔ" የሚለው የሚያመለክተው ኢዮአብን እና ወታደሮቹን ጭምር ነው። "እኛ ከከተማይቱ እንወጣለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ጭንቅላቱ ተቆርጦ ይወረወራል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ጭንቅላቱን እንወረውራለን/ ይጣልላችኋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያም ሴቲቱ ወደ ህዝቡ ሁሉ በጥበብ ሄደች
ይህ ማለት ሴትየዋ በጥበብ አደረገች ደግሞም ለህዝቧ ማድረግ ያለባቸውን ተናገረች። "ከዚያም ጥበበኛዋ ሴት ለህዝቡ በሙሉ ተናገረች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እያንዳንዱ ሰው ወደ የቤቱ
"እያንዳንዱ ሰው ወደ የራሱ ቤት ሄደ"

2 Samuel 20:23

አሁን
"አሁን" በዋናው ታሪክ ፍሰት ላይ አዲስ መስመር ያበጃል። ይህ አዲስ ክፍል ንጉሥ ዳዊትን ስለሚያገለግሉ ሰዎች የመረጃ ዳራ ይሰጣል። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

ኢዮአብ በ... ላይ ነበረ... የዮዳሄ ልጅ በናስያ በ...ላይ ነበረ... አዶኒራም በ... ላይ ነበረ
"በ...ላይ ነበረ" የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው በአንድ ወገን ላይ ስልጣን ያለው መሆንን ነው። "ኢዮአብ በ... ላይ ስልጣን ነበረው፤ የዮዳሄ ልጅ በናስያ በ... ላይ ስልጣን ነበረው፤ አዶኒራም በ...ላይ ስልጣን ነበረው" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የዳሄ... ኢዮሣፍጥ... አሒሉድ
የእነዚህን ወንዶች ስሞች በ 2 ሳሙሴል 18፡16-18 ላይ በተረጎሙት መሰረት ይተርጉሙት። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ከሊታውያን...ፈሊታውያን
እነዚህን የሰዎች/ቡድን ወገኖች ስሞች በ 2 ሳሙሴል 18፡16-18 ላይ በተረጎሙት መሰረት ይተርጉሙት። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የጉልበት ስራ እንዲሰሩ የተገደዱ ወንዶች
"ባሪያ ሰራተኞች"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አዶኒራም... ሱሳ...ዒራስ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ኢያዕራውያን
ይህ የሰዎች/ቡድን ወገን ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 21

1 በዳዊት ዘመን ለሶስት ተከታታይ ዓመታት ራብ ሆነ፣ ዳዊትም የእግዚአብሔርን ፊት ፈለገ።ስለዚህ እግዚአብሔር፣ “ሳዖልና ገዳይ ቤተሰቡ ገባዖናውያንን
እንዲሞቱ ስላደረገ ይህ ረሃብ በአንተ ላይ ነው” አለ። 2 እንግዲህ ገባዖናውያን ከአሞራውያን የተረፉ እንጂ የእስራኤል ሕዝብ ወገን አልነበሩም። የእስራኤል
ሕዝብ እንደማይገድሏቸው ምለውላቸው ነበር፣ ሳዖል ግን ለእስራኤልና ለይሁዳ ሕዝብ ከነበረው ቅናት የተነሣ እንዲሁ ሁሉንም የመግደል ሙከራ አድርጎ ነበር።
3 ስለዚህ ዳዊት ገባዖናውያንን በአንድነት ጠራቸውና፣ “ምን ላደርግላችሁ? የእርሱን በጎነትና ተስፋ ቃሉን የሚወርሱትን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ትባርኩ ዘንድ
ስርየትን እንዴት ማድረግ እችላለሁ?” አላቸው። 4 ገባዖናውያንም፣ “በእኛና በሳዖል ወይም በቤተሰቡ መካከል ያለው የብርና የወርቅ ጉዳይ አይደለም።
በእስራኤልም ውስጥ ማንም ሰው እንየዲገደል የምናደርግ እኛ አይደለንም።” ብለው መለሱለት። ዳዊትም፣ “የምትጠይቁትን ማንኛውንም ነገር ቢሆን እኔ ያንን
አደርግላችኋለሁ” አላቸው። 5 እነርሱም ለንጉሡ፣ “እንድንጠፋና በእስራኤል ክልል ውስጥ ምንም ስፍራ እንዳይኖረን ሁላችንንም ለመግደል ሙከራ
ካደረገውና በእኛ ላይ ሤራ ካውጠነጠነው 6 ከእርሱ ዝርያዎች ሰባት ሰዎች ለእኛ ተላልፈው ይሰጡን እኛም በእግዚአብሔር በተመረጠው በሳዖል አገር በጊብዓ
በእግዚአብሔር ፊት እንሰቅላቸዋለን” አሉት። ስለዚህ ንጉሡ፣ “እነርሱን እሰጣችኋለሁ” አላቸው። 7 ንጉሡ ግን በእርሱና በሳዖል ልጅ በዮናታን ስለነበረው
የእግዚአብሔር መሐላ የሳዖልን ልጅ የዮናታንን ልጅ ሜምፊቦስቴን አዳነው። 8 ነገር ግን ንጉሡ የኢያህሄል ልጅ ሪጽፋ ለሳዖል የወለደቻቸውን ሁለቱን ወንዶች ልጆች
ሄርሞንንና ሜምፊቦስቴን ወሰዳቸው፣ በተጨማሪም ዳዊት የሳዖል ልጅ ሜልኮል ለመሓላታዊው ለቤርዜሊ ልጅ ለኤስድሪኤል የወለደቻቸውን አምስት ወንዶች
ልጆች ወሰዳቸው፣ 9 በገባዖናውያንም እጅ አሳልፎ ሰጣቸው። እነርሱም በተራራው ላይ በእግዚአብሔር ፊት ሰቀሏቸው፣ ሰባቱም አንድ ላይ ሞቱ። የተገደሉት
በመከራ ወቅት፣ የገብስ መከር በሚሰበሰብባቸው የመጀመሪያዎቹ አምስት ቀናት ነበረ። 10 ከዚያ በኋላ የኢያህሄል ልጅ ሪጽፋ ከመከር መሰብሰብ ጊዜ ጀምሮ
ዝናብ በእነርሱ ላይ እስኪወርድባቸው ድረስ በአስከሬኖቹ አጠገብ ባለው ተራራ ለራሷ ማቅ ወስዳ ዘረጋች። የሰማይ ወፎች በቀን፣ የዱር አራዊት በማታ
እንዲነኳቸው አልፈቀደችም። 11 የሳዖል ቁባት የኢያህሄል ልጅ ሪጽፋ ያደረገችው ለዳዊት ተነገረው። 12 ስለዚህ የሳዖልንና የልጁን የዮናታንን አጥንት ሳዖልን
በጊልቦዓ ከገደሉት በኋላ ሰቅለውት ከነበረበት ከቤትሻን አደባባይ ከሰረቁት ከኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች ዘንድ ዳዊት ሄዶ አመጣ። 13 ዳዊት ከዚያ ስፍራ
የሳዖልንና የልጁን የዮናታንን አጥንት እንዲሁም በዚያ የተሰቀሉትን የሰባት ሰዎች አጥንትም ሰብስቦ ወሰደ። 14 የሳዖልንና የልጁን የዮናታንን አጥንት በብንያም
አገር በጼላ በአባቱ በቂስ መቃብር ቀበሩአቸው። ንጉሡም ያዘዘውን ነገር ሁሉ አከናወኑ። ከዚያ በኋላ ለምድሪቱ የተደረገውን ጸሎት እግዚአብሔር መለሰ። 15
ከዚያ በኋላ ፍልስጥኤማውያን ከእስራኤል ጋር እንደገና ውጊያ ገጠሙ። ስለዚህ ዳዊት ከሠራዊቱ ጋር ወርዶ ከፍልስጥኤማውያን ጋር ተዋጋ። ዳዊት በጦርነቱ
የሰውነት መዛል አጋጠመው። 16 የኃላኑ ዝርያ የነበረውና የናስ ጦሩ ሦስት መቶ ሰቅል የሚመዝነው እንዲሁም አዲስ ሰይፍ የታጠቀው ይሽቢብኖብ ዳዊትን
ለመግደል አቀደ። 17 ነገር ግን የጽሩይ ልጅ አቢሳ ፍልስጥኤማዊውን ወግቶ በመግደል ዳዊትንም ታደገው። ከዚያ በኋላም የዳዊት ሰዎች፣ “የእስራኤል
መብራት እንዳታጠፋ ከእንግዲህ አንተ ከእኛ ጋር መውጣት የለብህም” ብለው ማሉለት። 18 ከዚህ በኋላ ጎብ በተባለ ስፍራ የራፋይም ዝርያ የነበረው
ኩስታዊው ሴቦካይ ሳፋንን የገደለበት ጦርነት ከፍልስጥኤማውያን ጋር እንደገና ተደረገ። 19 ጎብ ላይ ከፍልስጥኤማውያን ጋር በተደረገ ጦርነት የቤተልሔሙ
የየዓሬዓርጊም ልጅ ኤልያናን የጦሩ ዘንግ እንደ ሸማኔ መጠቅለያ የሆነውን የጌት ሰው ጎልያድን ገደለ። 20 ጋዛ ላይ በተደረገ ሌላ ጦርነት በእጆቹ ላይ ስድስት
ስድስት ጣቶች በእግሮቹም ላይ ስድስት ጣቶች ባጠቃላይ ሃያ አራት ጣቶች የነበሩት ታላቅ ቁመት የነበረው ሰው ነበር። እርሱም የራፋይም ዝርያ ነበር። 21
እርሱም በእስራኤል ላይ ባፌዘ ጊዜ የዳዊት ወንድም የሣማ ልጅ ዮናታን ገደለው። 22 እነዚህ የጋዛዋ ራፋይም ዝርያዎች ነበሩ፣ እነርሱም በዳዊት እጅና
በወታደሮቹ እጅ ተገደሉ።

---

2 Samuel 21:1

የያህዌን ፊት አየ
እዚህ ስፍራ "ፊት" ለያህዌ መገኘት ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ነው። የዚህ ትርጉም ዳዊት ስለ ድርቁ ምላሽ ለማግኘት ወደ ያህዌ ጸለየ ማለት ነው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በሳኦል እና በእርሱ ነብሰ ገዳይ ቤተሰብ ምክንያት
ሳኦል ብዙ ገባዖናውያንን ገድሎ ነበር፣ በመሆኑም የሳኦል ትውልድ በዚህ ኃጢአት ምክንያት ጥፋተኞች ነበሩ።

2 Samuel 21:2

አሁን
"አሁን" በዋናው ታሪክ ፍሰት ላይ አዲስ መስመር ያበጃል። ይህ አዲስ ክፍል ስለ ገባዖናውያን የመረጃ ዳራ ይሰጣል። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእናንተ ምን ላደርግላችሁ ይገባል? እንዴት ማስተሰረያ ቃል ኪዳን... ላደርግ እችላለሁ?
እነዚህ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። "መልካምነቱን እና ቃል ኪዳኑን የሚወርሰውን የያህዌን ህዝብ ትባርኩ ዘንድ ይህንን ኃጢአት ለማስወገድ ምን ማድረግ እችላለሁ?" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 21:4

ይህ የብር እና የወርቅ ጉዳይ አይደለም
"ችግሩን ገንዘብ አይፈታውም"

2 Samuel 21:5

"በእኛ ላይ ያሴረ"
"በእኛ ላይ ክፉ ካቀደ"

ከእርሱ ትውልድ ሰባት ወንዶች ለእኛ አሳልፋችሁ ስጡን
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የአንተ ሰዎች ከእርሱ ትውልዶች ሰባት ሰዎች እንዲሰጡን አድርግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ እንሰቅላቸዋለን
"እኛ እነርሱን ሰቅለን እንገድላቸዋለን"

በሳኦል ጊብዓ
ሳኦል ከጊብዓ ከተማ ነበር።

በያህዌ የተመረጠ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ያህዌ የመረጠው እርሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Samuel 21:7

ሜምፊቦስቴ
ሜምፊቦስቴ የዮናታን ልጅ ነበረ። በ 2 ሳሙኤል 4:4 ላይ ይህ ስም እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ሪጽፋ... ኢዮሄል
ሪጽፋ ሴት ናት አባቷ ኢዮሄል ነበር። በ2 ሳሙኤል 3:7 ላይ እነዚህ ስሞች እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

ሄርሞን እና ሜምፊቦስቴ... ኤስድሪኤል... ቤርዜሊ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። ይህ ሜምፊቦስቴ የዮናታን ልጅ የሆነው ሜምፊቦስቴ አይደለም። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሜሮብ
ይህ የሴት ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

መሐላታዊያን
ይህ የሰዎች ቡድን/ የወገን ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ለገባዖናውያን አሳልፎ ሰጣቸው
እዚህ ስፍራ "የገባዖናውያን እጆች" የሚለው የሚወክለው የገባዖን ሰዎችን ቁጥጥር/የበላይነት ነው። "ለገባዖናውያን አሳልፎ ሰጣቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱም ተገደሉ
ይህ በአድርጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ገባዖናውያን እነርሱን ገደሏቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድርጊ ወይም ተደርጊ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 21:10

ሪጽፋ... ኢዮሄል
ሪጽፋ ሴት ናት አባቷ ኢዮሄል ነበር። በ2 ሳሙኤል 3:7 ላይ እነዚህ ስሞች እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

ይህ ለዳዊት ተነገረው
ይህ በአድርጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "አንድ ሰው ለዳዊት ነገረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድርጊ ወይም ተደርጊ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 21:12

ኢያቢስ ገለዓድ
ኢያቢስ በገለዓድ አካባቢ ሚገኝ ከተማ ነው። ይህ በ2 ሳሙኤል 2:4 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

የህዝብ አደባባይ
ይህ በከተማ መግቢያ በር አጠገብ የሚገኝ ሰዎች የተለያዩ የንግድ ተግባራትን የሚያከናውኑበት ስፍራ ነው።

ቤት ሳን
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ጊልቦዓ
ይህ የቦታ ስም በ 2 ሳሙኤል 1:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

የተሰቀሉት
ይህ በአድርጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ገባዖናውያን በስቅላት የገደሏቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድርጊ ወይም ተደርጊ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 21:14

ጹላ
ይህ በብንያም የሚገኝ የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ቂስ
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ አባት
"የሳኦል አባት"

2 Samuel 21:15

ይሸቢ-ብኖብ
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሶስት መቶ ሰቅል
"300 ሰቅል።" ይህ ወደ 3.4 ኪሎ ግራም የሚጠጋ ነው። (የመጽሐፍ ቅዱስ ክብደት መለኪያ እና ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

የጽሩያ ልጅ አቢሳ
አቢሳ እና ጽሩያ የወንድ ስሞች ናቸው። እነዚህ ስሞች በ 2 ሳሙኤል 2:18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

የእስራኤልን መብራት ማጥፋት የለብህም
"የእስራኤል መብራት" የሚለው የዳዊትን መሪነት የሚወክል እና ዳዊት ከሞተ የእስራኤል ህዝብ ግልጽ ምሪት እንደሚያጣ የሚያሳይ ዘይቤ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 21:18

ከዚህ በኋላ እንዲህ ሆነ
ይህ ሀረግ የታሪኩን አዲስ ክፈል ይጀምራል። ቋንቋችሁ ይህን ለማድረግ መንገድ ካለው፣ እዚህ ስፍራ ይህንን ለመጠቀም ትችላላችሁ።

ጎብ
ይህ የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሴቦካይ... ሳፍ... የዓሬዓርጊም ልጅ ኤልያናን... ጎልያድ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው :: (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ኩሳታዊ...ራፋማዊ... ቤተልሔማዊ... ጌታዊ
እነዚህ የሰዎች ቡድኖች/የወገኖች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ራፋይም
ይህ የህዝብ ወገን በግዙፋን ተዋጊዎቹ ይታወቅ ነበር። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ጦሮቻቸው እንደ ሸማኔ መጠቅለያ ነበር
አንድ ሰው ሲሸምን የ"ሸማኔ መጠቅለያ" ተብሎ ከሚጠራ ትልቅ እንጨት ጋር በተያያዙ መቆንጠጫዎች መሃል ክሮቹን ያሳልፋል። ይህ ማለት የጎልያድ ጦር ከመደበኛው ጦር ትልቅ ነበር ማለት ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Samuel 21:20

በቁጥር ሃያ አራት
"በአጠቃላይ 24 የእጅ እና የእግር ጣቶች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ራፋይም
ይህ የህዝብ ወገን በግዙፋን ተዋጊዎቹ ይታወቅ ነበር። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የሣማ ልጅ ዮናታን
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። ሣማ የዳዊት ወንድም ነበር። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ የተገደሉት በዳዊት እና በወታደሮቹ እጅ ነበር
እዚህ ስፍራ "በ...እጅ" ማለት "አማካይነት" ወይም "በ..." ማለት ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ዳዊት እና ወታደሮቹ እነርሱን ገደሏቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 22

1 እግዚአብሔር ከጠላቶቹ ሁሉና ከሳዖል እጅ በታደገው ጊዜ፣ ዳዊት በዚህ መዝሙር ያሉትን የቅኔ ቃላት ለእግዚአብሔር ዘመረ። 2 እንዲህም እያለ ጸለየ፣
“እግዚአብሔር ዐለቴ፣ አምባዬና ታዳጊዬ ነው። 3 እግዚአብሔር የምጠጋበት ዐለቴ፣ ጋሻዬና የድነቴ ቀንድ ነው። እርሱም ጠንካራ ምሽጌ፣ መጠጊያዬና ከግፍ
የሚያድነኝ ነው። 4 ሊመሰገን የሚገባውን እግዚአብሔርን እጠራለሁ፤ ከጠላቶቼም እድናለሁ። 5 የሞት ማዕበል ከበበኝ፤ የከንቱነት ጎርፍም አጥለቀለቀኝ። 6
የሲዖል ገመድ ተጠመጠመብኝ፣ የሞትም ወጥመድ አጥምዶ ያዘኝ። 7 በጨነቀኝ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ተጣራሁ፣ አምላኬን ጠራሁት፣ ከመቅደሱ ድምፄን
ሰማኝ፤ ለረድኤት ያደረግሁት ጥሪም ወደ ጆሮው ደረሰ። 8 በዚያን ጊዜ ምድር ተንቀጠቀጠች እግዚአብሔር ተቆጥቶ ነበረና የሰማይ መሠረቶች ተናወጡ
ተንቀጠቀጡም። 9 ከአፍንጫው ጢስ፣ ከአፉም ፍሙን የሚያግል የሚንበለበል እሳት። 10 ሰማይን ከፍቶ ወረደ፣ ድቅድቅ ጨለማም ከእግሩ በታች ነበር። 11
በኪሩቤል ላይ ተቀምጦ በረረ፣ በንፋስም ክንፍ ተቀምጦ ሲበር ታየ። 12 በሰማይ ላይ ያሉ ከባድ የዝናብ ደመናዎችን በማሰባሰብ ጨለማን እንደ ድንኳን
እንዲከበው አደረገ። 13 በፊቱ ካለው ነጎድጓድ የእሳት ፍም ወረደ። 14 እግዚአብሔር ከሰማይ አንጎደጎደ፣ የልዑልም ድምፅ አስተጋባ። 15 ፍላፃውን ወረወረ
ጠላቶቹንም በተነ - መብረቁ እንዲበርቅ አደረገ፣ በታተናቸውም። 16 በዚያን ጊዜ የውሃ መውረጃዎች ታዩ፣ እግዚአብሔር ባስተጋባው የክተት ድምፅ፣
ከአፍንጫው በሚወጣ የእስትንፋስ ግፊት የምድር መሠረቶች ተጋለጡ። 17 ከላይ እጁን ዘርግቶ ያዘኝ፣ እየተንዶለዶለ ካለውም ውሃ አወጣኝ። 18 ብርቱ
ከሆነው ጠላቴ፣ ከሚጠሉኝም ታደገኝ፣ በእኔ ላይ እጅግ በርትተውብኝ ነበርና። 19 በጭንቀቴ ጊዜ መጡብኝ፣ እግዚአብሔር ግን ድጋፍ ሆነኝ። 20 እርሱም ሰፋ
ወዳለ ስፍራ አወጣኝ። በእኔ ደስ ተሰኝቶ ነበርና አዳነኝ። 21 እግዚአብሔር እንደ ጽድቄ መጠን ብድራትን ከፍሎኛል፣ እንደ እጄም ንጽሕና መጠን ወደ ስፍራዬ
መልሶኛል። 22 የእግዚአብሔርን መንገድ ጠብቄአለሁና፣ ከአምላኬም ዞር በማለት ክፋትን አላደረግሁም። 23 የጽድቅ ሥርዓቱ በፊቴ ናቸውና፣ ከድንጋጌም
ፈቀቅ አላልሁም። 24 ቅንነቴን በፊቱ ጠብቄ ነበርና፣ ራሴንም ከኃጢአት አርቄ ነበር። 25 ስለዚህ እግዚአብሔር ወደ ጽድቅ ደረጃዬ፣ በፊቱ ካለኝ የንፅሕና አቋሜ
መልሶኛል። 26 ታማኝ ለሆነው ታማኝነትህን ታሳያለህ፣ ነቀፋ ለሌለበትም ሰው ነቀፋ የሌለብህ መሆንህን ታሳያለህ። 27 ከንጹሑች ጋር ንጹሕ መሆንህን ስታሳይ
ለተጣመሙት ግን ጠማማ ነህ። 28 የተጎሳቆሉትን ታድናለህ፣ ዐይኖችህ ግን በትዕቢተኞች ላይ ነው፣ ታዋርዳቸውማለህ። 29 እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ
መብራቴ ነህና፣ እግዚአብሔር ጨለማዬን ያበራል። 30 በአንተ መሰናክሉን ጥሼ አልፋለሁ፣ በአምላኬ ቅጥሩን እዘላለሁ። 31 የእግዚአብሔር መንገድማ ፍጹም
ነው፣ የእግዚአብሔር ቃል ንፁሕ ነው። ወደ እርሱ ለሚጠጋ ለማንኛውም ሰው ጋሻ ነው። 32 ከእግዚአብሔር በቀር አምላክ ማን ነው? ከአምላካችንስ በቀር
አምባ ማን ነው? 33 እግዚአብሔር መጠጊያዬ ነው፣ ነቀፋ የሌለበትንም ሰው በመንገዱ ይመራዋል። 34 እንደ ዋላ እግሮች እግሮቼን ፈጣን ያደርጋቸዋል፣
በተራራም ላይ ያቆመኛል። 35 እጆቼን ለውጊያ፣ ክንዴንም የናስ ቀስት ለመለጠጥ ያሠለጥናቸዋል። 36 የድነትን ጋሻ ሰጥተኸኛል፣ ሞገስህም ታላቅ
አድርጎኛል። 37 በእግሮቼ ሥር ያለውን ስፍራ ሰፊ አድርገህልኛል፣ ስለዚህ እግሮቼ አልተንሸራተቱም። 38 ጠላቶቼን አሳደድኋቸው፣ አጠፋኋቸውም።
እስካጠፋቸውም ድረስ አልተመለስሁም። 39 ፈጽሜ አጠፋኋቸው፣ አደቀቅኋቸውም፣ ተመልሰው መነሣት አይችሉም። በእግሬ ሥር ወድቀዋል። 40 እንደ ጦር
መታጠቂያ ኃይልን በእኔ ላይ አደረግህ፣ በላዬ ላይ የተነሡትንም ከእኔ በታች አደረግኸቸው። 41 የጠላቶቼን ማጅራት ሰጠኸኝ፣ የሚጠሉኝንም
አፈራረስኳቸው። 42 ዕርዳታ ለማግኘት ተጣሩ ነገር ግን ማንም አላዳነቸውም፣ ወደ እግዚአብሔር ተጣሩ እርሱ ግን አልመለሰላቸውም። 43 እንደ አቧራ መሬት
ላይ ፈጨኋቸው፣ በመንገድ ላይ እንዳለ ጭቃም ረገጥኋቸው። 44 ከራሴ ሕዝብ ክርክር አድነኸኛል፣ የሕዝቦችም ራስ አድርገህ አጽንተኸኛል፣ የማላውቀው
ሕዝብ ያገለግለኛል። 45 ባዕድ ሕዝቦች ለእኔ ለመስገድ ተገደዱ፣ ስለ እኔ እንደሰሙ ወዲያውኑ ታዘዙኝ። 46 ባዕዳን ከምሽጋቸው እየተንቀጠቀጡ ወጡ። 47
እግዚአብሔር ሕያው ነው! ዐለቴ የተመሰገነ ይሁን፣ የድነቴ ዐለት እግዚአብሔር ከፍ ይበል። 48 በቀልን የሚበቀልልኝ፣ ሕዝብንም ከእኔ ሥር የሚያደርግልኝ
አምላክ ይሄ ነው። 49 ከጠላቶቼ ነፃ ያወጣኛል። እንዲያውም በእኔ ላይ ከተነሡት በላይ አውጥተኸኛል። ከግፍኞች ታድገኸኛል። 50 ስለዚህ እግዚብሔር
ሆይ፣ በሕዝቦች መካከል ለአንተ ምስጋና አቀርባለሁ፣ ለስምህም ምስጋና መዝሙር እዘምራለሁ። 51 እግዚአብሔር ለንጉሡ ታላቅ ድልን ይሰጠዋል፣ ኪዳናዊ
ታማኝነቱን እርሱ ለቀባው፣ ለዳዊትና ለዘሮቹ ለዘላለም ያሳየዋል።”

---

2 Samuel 22:1

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበው መዝሙር ይጀምራል። የሚናገረውን ለማጉላት ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን ይጠቀማል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከጠላቶቹ ሁሉ እጅ፣ ደግሞም ከሳኦል እጅ
ይህ በአጠቃላይ ከሁሉም ጠላቶች ወደ አንድ የዳዊት ጠላት፣ ወደ ንጉሥ ሳኦል የሚሄድ ነው።

ከ...እጅ መዳን
ይህ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ "ከ... ሃይል መዳን" ማለት ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ የእኔ አለት ነው፣ የእኔ ምሽግ
ይህ ዘይቤ የሚያሳየው ከአንድ ክፍል ከ "አለት" አጠቃላይ ወደ ሆነ ነገር ማለትም ወደ "ምሽግ" የሚደረግ ሽግግርን ነው። ምሽግ ከብዙ ትልልቅ አለቶች የሚገነባ ነው። ይህ ማለት ያህዌ የእርሱን ህዝብ ከጉዳት ለመጠበቅ ጥንካሬ አለው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 22:3

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበው መዝሙር ይቀጥላል። የሚናገረውን ለማጉላት ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን ይጠቀማል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር አለቴ ነው... እርሱ ጋሻዬ ነው፣ የደህንነቴ ቀንድ፣ የእኔ መሸሸጊያ
እነዚህ ዘይቤዎች በሙሉ የእግዚአብሔር ጥንካሬ እና ሃይልና ምልክቶች ናቸው። የእግዚአብሔርን ህዝቡን የመጠበቅ እና የማዳን ችሎታ ያጎላሉ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሊወደስ የሚገባው ማን ነው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ውዳሴ ሊቀበል የሚገባው ማን ነው" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ከጠላቶቼ እድናለሁ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እርሱ ከጠላቶቼ ያድነኛል" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Samuel 22:5

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበው መዝሙር ይቀጥላል:: የሚናገረውን ለማጉላት ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን ይጠቀማል:: (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሞት ማዕበል ከበበኝ፣ የጥፋት ጎርፍ ውሃ ዋጠኝ
ዳዊት ሊገድሉት የሚፈልጉትን ከፉ ሰዎች ሊውጠው ከደረሰ የጎርፍ ውሃ ጋር ያነጻጽራቸዋል:: እነዚህ ዐረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ የዋሉትም ትኩረት ለመስጠት ነው:: (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

የጥፋት ውሃ ጎርፍ
ይህ በመንገዱ ላይ ሚያገኘውን ሁሉ እየጠራረገ ሚያጠፋ በፍጥነት የሚወርድ የጎርፍ ውሃ ምስል ነው::

የሲኦል ገመድ ተጠመጠበብኝ፤የሞት ወጥመድ ያዘኝ
ዳዊት ስለ ሞት እና ሲኦል የሚናገረው፣ አዳኝ እንስሳን እንደሚያጠምድ ሞት እና ሲኦል እርሱን ሊያጠምዱት የሚሞክሩ ሰዎች እንደሆኑ አድርጎ ነው:: እነዚህ ሀረጋት ተመሳሳይ ትረጉም አላቸው ያገለገሉትም ትኩረት ለመስጠት ነው:: (ሰውኛ ዘይቤ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

2 Samuel 22:7

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበው መዝሙር ይቀጥላል:: የሚናገረውን ለማጉላት ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን ይጠቀማል:: (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በጭንቀቴ
"በታላቅ መከራዬ"

ከመቅደሱ ድምጼን ሰማ
ዳዊት የሚያመለክተው ያህዌ የሚኖርበትን ሰማያዊ መቅደስ ነው:: ምድራዊው መቅድ ገና አልተገነባም ነበር::

የእርዳታ ጥሪዬ ወደ ጆሮዎቹ ገባ
እዚህ ስፍራ "የእርሱ ጆሮዎች" የሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሚያመለክተው ያህዌን እና ለእርዳታ የዳዊትን ጥሪ ማድመጡን ነው:: "እርሱ ሊረዳኝ ልመናዬን ሰማ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ ጆሮዎች
ዳዊት ስለ ያህዌ ጆሮዎች እንዳሉት አድርጎ ይናገራል:: (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 22:8

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበው መዝሙር ይቀጥላል:: የሚናገረውን ለማጉላት ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን ይጠቀማል:: (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያም ምድር ተናወጠች... በቁጣው እሳት ነደደ
ዳዊት ከጠላቶቹ ለመዳን ለእርዳታ ላሰማው ጩኸት የያህዌ ምላሽ ይህ ነው:: ዳዊት የምድርን መንቀጥቀጥ እና ከያህዌ እሳት የመምጣትን ምናብ የተጠቀመው የያሀድዌን አሰጨናቂ ቁጣ ለማጉላት ነው:: (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ምድር ተናወጠች...ሰማያትም ተንቀጠቀጡ
ዳዊት ሁለቱን ጽንፎች የገለጸው በፍጥረት ውስጥ የሚገኘውን ሁሉ ለማካተት ነው:: (ጽንፍ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ተቆጥቷል እና ተንቀጠቀጡ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል:: "የእግዚአብሔር ቁጣ አናወጣቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ከአፍንጫው...ከአፉ
ዳዊት ያህዌ እነዚህ የሰው አካሎች እንዳሉት አድርጎ ይናገራል:: (ሰውኛ የሚለውን ይመልከቱ)

በቁጣው ፍም ተቀጣጠለ
እዚህ ስፍራ የያህዌ ቁጣ ከሰል እንዲቀጣጠል እና እንዲነድ የሚያደርግ ከእሳት ጋር ተወዳድሯል:: "ከአፉ የሚወጣው ነበልባል እሳት ያነዳል" ወይም "እንዲሁም እርሱ የሚነድ እሳት ከአፉ ይልካል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 22:10

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበው መዝሙር ይቀጥላል:: የሚናገረውን ለማጉላት ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን ይጠቀማል:: (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ሰማያትን ከፈተ... በሰማያት ጥቅጥቀው ያለ የዝናብ ደመና ነበረ
ዳዊት ያህዌ እርሱን ያዳነበትን መንገድ የገለጸው በአንድ ስፍራ እንደ ተከማቸ ሀይለኛ የዝናብ ደመና ከበዙ ጠላቶች አዳነኝ በማለት ነው:: ይህ የእግዚአብሔርን ሃይል እና ቁጣውንም ያጎላል:: (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከእግሮቹ ስር
ዳዊት እግአብሔር እንደ ሰው እግር እንዳለው አድርጎ ይናገራል:: (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በነፋስ ክንፎች ላይ ታየ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል:: "እርሱ በነፋስ ክንፎች ላይ ታየ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የነፋስ ክንፎች
ይህ አገላለጽ ነፋስ ወፍ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል:: (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጨለማን በዙሪያው ድንኳን አደረገ
እዚህ ስፍራ ያህዌ የፈጠረው ጨለማ የተነጻጸረው እርሱን ሙሉ ለሙሉ ከሸፈነ ድንኳን ጋር ነው:: "እርሱ ራሱን በጨለማ ውስጥ ሰወረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 22:13

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበው መዝሙር ይቀጥላል:: የሚናገረውን ለማጉላት ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን ይጠቀማል:: (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከፊቱ ከወጣው መብረቅ ... መብረቅ ወጣ አጠፋቸውም
ዳዊት ከጠላቶቹ ሊያድነው የመጣውን፣ ከአውሎ ነፋስ ጋር የሚያነጻጽረውን ያህዌን መግለጹን ቀጥሏል:: ይህ በዳዊት ጠላቶች ላይ የእግዚአብሔርን ሀይል እና ቁጣ ያጎላል:: (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከፊቱ ከወጣው መብረቅ የእሳት ነበልባል ወደቀ
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ከደማቅ ብርሃኑ የሚነድ እሳት ላከ" ወይም 2) "ከእርሱ ድምቀት መብረቅ ላከ"

እጅግ ከፍ ያለው ከፍ ባለ ድምጽ ተናገረ። ቀስቶችን ወረወረ
ዳዊት አንድ ሰው እነዚህን ነገሮች እንደሚያደርግ ያህዌ ማድረጉን ይገልጻል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀስቶችን መረወረ... መብረቅ ወጣ
ዳዊት ከያህዌ አውሎ ነፋስ የሚወጣውን መብረቅ ወታደር ከሚጠቀምበት ቀስት ጋር ያነጻጽራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 22:16

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል። የሚናገረውን ለማጉላት ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን ይጠቀማል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያም የባህር መንገዶች ታዩ... የአፍንጫው እስትንፋስ
ያህዌ በዳዊት ጠላቶች ላይ ሊቀጣ መነሳቱ የተነጻጸረው በውቅያኖስ ጥልቅ ክፍል እና በመሬት ላይ ነውጥ ከሚፈጥረው ሀይሉ ጋር ነው። ይህ የእርሱን ታላቅ ሀይል እና ብርቱ ቁጣ ያሳይል። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

የባህር መንገዶች ተገለጡ/ታዩ
ይህ ማለት የባህር ውሃ ስፍራቸውን ለቀው የውቅያኖስ ወለል ተገለጠ ማለት ነው።

መሰረቶች... ተራቆቱ
ዳዊት የያህዌን ቁጣ ከከምድር መናወጥ ጋር ያነጻጽራል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የያህዌ ዘለፋ የምድርን መሰረቶች ገለጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 22:17

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል። የሚናገረውን ለማጉላት ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን ይጠቀማል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከብዙ ውሃ አወጣኝ
ዳዊት ጠላቶቹን ሊያሰጥመው ከሚያስፈራራው የውሃ ሙላት ጋር ያነጻጽራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ከብርቱ ጠላቶቼ አዳነኝ
የዳዊት ጠላቶች ከፍ ያለ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ነበሩ። ከጠላቶቹ ሁሉ ስላዳነው እግዚአብሔርን ያመሰግናል።

2 Samuel 22:19

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል። የሚናገረውን ለማጉላት ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን ይጠቀማል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በመከራዬ/ጭንቀቴ ቀን ሊቃወመኝ በእኔ ላይ ተነሱ
"ጠላቶቼ በትልቅ ችግር በሆንኩበት ጊዜ በተቃውሞ ተነሱብኝ"

በመከራዬ ቀን
"በመከራዬ ጊዜ"

ነገር ግን ያህዌ ደጋፊዬ ነበር
"ነገር ግን ያህዌ ደገፈኝ" ወይም "ነገር ግን ያህዌ እኔን እረዳኝ"

ሰፊ ስፍራ
ይህ የሚያመለክተው አደጋ የሌለበትን እና ጠላቶቹ እርሱን ሊያጠምዱ የማይችሉበተን ስፍራ ነው።

በእጆቼ ንጽህና መጠን
እዚህ ስፍራ "የእጆቼ ንጽህና" ማለት "ጽድቅ" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው። "ትዕዛዛቱን ጠብቄአለሁና" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋጋር እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

2 Samuel 22:22

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል።

የያህዌን መንገዶች ጠብቄአለሁ
እዚህ ስፍራ "የያህዌ መንገዶች" የሚለው የሚያመለክተው ያህዌ እርሱ የሆነ ህዝብ ማድረግ የሚፈልገውን ነገር ነው። ይህ ማለት ዳዊት ያደረገው ያህዌ ያዘዘውን ነገር ነው።

በፊቴ ነበር
ይህ ማለት ዳዊት በቀጣይነት ስለ እግዚአብሔር ትዕዛዛት/ድንጋጌዎች ያነብና ያስብ ነበር ነው።

2 Samuel 22:24

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል።

ራሴን ከኃጢአት ጠብቄአለሁ
ይህ ያህዌን መበደልን አለመምረጥን ያሳያል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ ዐይኖች ፊት ባለኝ ንጽህና መጠን
እዚህ ስፍራ "የእኔ ንጽህና" የሚለው ትርጉሙ "የእኔ ጽድቅ" ማለት ነው። "ምክንያቱም እርሱ ያዘዘውን ማድረጌን እርሱ ያውቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋጋር እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

2 Samuel 22:26

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል።

አንተ ለጠማሞች ዘወርዋራ ነህ
እዚህ ስፍራ "ጠማማ" የሚለው የማያስደስት መሆን ወይም ተንኮለኛ ማለት ሲሆን፤ "ዘወርዋራ" ማለት መልካም እና ትክክል ከሆነው የሚርቅ ማለት ነው። ይህ ማለት እግዚአብሔር ክፉ ሰዎችን ምን እንደሚያደርግ ያውቃል።

2 Samuel 22:28

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል።

የአንተ ዐይኖች ትዕቢተኞችን ይቃወማል
እዚህ ስፍራ "የአንተ ዐይኖች" የሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሚያመለክተው ያህዌ የሚመለከተውን ነገር ነው።

ይህ ማለት ያህዌ ትዕቢተኞች የሚያደርጉትን ይመለከታል ማለት ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዝቅ ታደርጋቸዋለህ
"ኩራታቸውን ታዋርዳለህ"

ያህዌ፣ አንተ ብርሃኔ ነህ። ያህዌ አንተ ጨለማዬን ታበራለህ
ይህ ዘይቤ ያህዌን ከመብራት ጋር ያነጻጽራል፤ ይህም ማለት ነገሮች ተስፋ ቢስ የሆኑ በመሰሉ ጊዜ ያህዌ ለዳዊት ብርሃን ይሰጠዋል ደግሞም እንዲመለከት ይረዳዋል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 22:30

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል።

በቅጥሩ ላይ መሮጥ እችላለሁ
እዚህ ስፍራ "ቅጥር" የሚለው የድንጋይ ቅጥርን ወይም አንድን የተወሰነ ወታደራዊ ቡድን/ጭፍራን ሊያመለክት ይችላል። ይህ ማለት በየትኛውም መንገድ ቢሆን እግዚአብሔር ዳዊት ጠላቶቹን እንዲያሸንፍ ረድቶታል ማለት ነው።

ቅጥርን እዘላለሁ
ዳዊት የያህዌን እርዳታ አጉልቶ እየተናገረ ነው። "ከተማቸውን የከበበውን ቅጥር መውጣት እችላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

የያህዌ ቃል ንጹህ ነው
"ያህዌ የሚናገረው ሁሉ እውነት ነው"

እርሱ ጋሻ ነው
"ጋሻ" የሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር የእግዚአብሔርን ህዝቡን የመጠበቅ ሀይል ያጎላል። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 22:32

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል።

ከያህዌ በቀር አምላክ ማን ነው፣ ደግሞስ ከአምላካችን በቀር አለት ማን ነው?
ዳዊት ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው ከያህዌ በስተቀር አምላክ እንደሌለ አጉልቶ ለመናገር ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ያህዌ ብቻውን አምላክ ነው። የእኛ አምላክ ብቻ አለት ነው።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

አለት ማን ነው
ዳዊት የያህዌን ጥንካሬ እና ህዝቡን ለመጠበቅ ያለውን ችሎታ ለማጉለት ከአለት ጋር ያነጻጽረዋል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ነውር የሌለበተን ሰው በመንገዱ ይመራዋል
ያህዌ ነውር የሌለበትን ሰው በደህንነት ይጠብቀዋል ደግሞም እርሱን ሊጎዳ የሚችለውን ማናቸውንም ነገር ከመንገዱ ያስወግድለታል።

2 Samuel 22:34

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል።

እግሮቼን እንደ አጋዘን ፈጣን አድረጓቸዋል፤ ደግሞም እኔን በኮረብቶች ከፍታ ላይ አቁሞኛል
እዚህ ስፍራ የዳዊት እግሮች ግነትን በመጠቀም ከአጋዘን ጋር ተነጻጽረዋል። ያህዌ ለዳዊት በፍጥነት የመንቀሳቀስ ጥንካሬን፤ ደግሞም ለጥበቃ እና እረፍት አስተማማኝ ስፍራን ሰጥቶታል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ኩሸት እንዲሁም አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

የእኔ እጆች...እና የእኔ እግሮች
እነዚህ ሁለቱም ዳዊትን የሚመለከቱ ናቸው። (ስኔክቲክ/የነገሩን ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የነሐስ ቀስትን ለማጠፍ
ከብረት የተሰራ ቀስትን መጠቀም የሚችለው በጣም ጠንካራ ሰው ብቻ ነው።

2 Samuel 22:36

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል።

የደህንነትህ ጋሻ
ዳዊት የያህዌ እርሱን የሚጠብቅበትን ሀይል አንድን ወታደር ከጠላቶቹ ከሚጠብቀው ጋሻ ጋር ያነጻጽራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ ሞገስ
እግዚአብሔር የዳዊትን ጸሎት መልሷል፣ ደግሞም በረከትንና በጠላቶቹ ላይ ስኬትን ሰጥቶታል።

ለእግሮቼ ሰፊ ስፍራ አዘጋጅተህልኛል
ያህዌ ዳዊትን ጠላቶቹ ሊያጠምዱት በማይችሉበት አስተማማኝ ስፍራ አኑሮታል። እዚህ ስፍራ ተጠብቆ የመቆም ችሎታውን ለማጉላት ራሱን የገለጸው በእርሱ "እግሮች" ነው። (ስኔክቲክ/የነገሩን ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 22:38

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል።

ጠላቶቼን አሳድዳቸዋለሁ
"ጠላቶቼን አባርራቸዋለሁ"

እርሱን አጠፋኋቸው/በላኋቸው ደግሞም አዋረድኳቸው
እዚህ ስፍራ ዳዊት ራሱን ከዱር እንስሳ ጋር ያነጻጽራል። "የዱር እንስሳ ያደነውን እንደሚበላ ሙሉ ለሙሉ አጠፋኋቸው" በሚለው ውሰጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከእግሮቼ በታች
እዚህ ሰፍራ "እግር" የሚለው የሚያመለክተው በጠላቶቹ ላይ ያለውን የድል ሀይል እና የበላይነት ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 22:40

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል።

ለጦርነት እንደሚታጠቁት ቀበቶ በላዬ ጥንካሬን አደረግህ
እዚህ ሰፍራ ያህዌ የሰጠው ጥንካሬ የተነጻጸረው ዳዊት ታላላቅ ነገሮችን እንዲያደርግ ከሚረዳው የጦር ሜዳ ቀበቶ ጋር ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በላዬ የሚነሱብኝን ከበታቼ ጣልካቸው
"ተቃውመው የሚዋጉኝን እንዳሸንፋቸው ረዳኸኝ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የጠላቶቼን ጀርባ ሰጠኸኝ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ዳዊት ጠላቶቹ ሲሸሹ ጀርባቸውን ይመለከት ነበር ወይም 2) ዳዊት ጠላቶቹን ካሸነፈ በኋላ እግሮቹን በጠላቶቹ አንገት ላይ ያደርግ ነበር

ድምጥማጣቸውን አጠፋኋቸው
"ሙሉ ለሙሉ አጠፋኋቸው"

2 Samuel 22:42

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል።

እነርሱ ጮኹ
"ጠላቶቼ ጮኹ"

ወደ ያህዌ ጮኹ፣ እርሱ ግን አልመለሰላቸውም
ያህዌ ፍርድ የሚሰጥበት ጊዜ ደረሰባቸው።

እንደ ምድር ትቢያ... እንደ መንገድ ጭቃ
ይህ ዳዊት ጠላቶቹን ሙሉ ለሙሉ አጠፋቸው ማለት ነው። "እንደ ምድር ትቢያ" እና "እንደ መንገድ ጭቃ" የሚሉት እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው የማሉትም ትኩረት ለመስጠት/ሃሳቡን ለማጉላት ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ትይዩ ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

2 Samuel 22:44

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል።

ከራሴ ህዝብ ከተነሳብኝ ክርክር
ይህ የሚያመለክተው ከእስራኤላውያን መሃል በንጉሥ ዳዊት ላይ ያመጹበትን ነው።

አንተ የህዝብ መሪ አደረግኸኝ
"አንተ በህዝብ ላይ መሪ አድርገኽ ሾምከኝ።" እዚህ ስፍራ "ህዝቦች" የሚለው የሚያመለክተው ከእስራኤል ህዝብ በተጨማሪ ሌላውን ህዝብ ነው።

የማላውቀው ሌላ ህዝብ
"ባዕዳን/የውጭ ሰዎች"

ባዕዳን ሊሰግዱልኝ ተገደዱ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በዕዳን ወድቀው ሰገዱልኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 22:47

አለቴ የተመሰገነ ይሁን። አምላኬ ከፍ ይበል
እነዚህ ዐረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው የዋሉትም ትኩረት ለመስጠት/ለማጉላት ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሁሉም ሰው አለቴን ያወድሰው/ያመስግነው። እያንዳንዱ ሰው እግዚአብሔርን ከፍ ከፍ ያድርግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ተነጻጻሪ ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

የእኔ አለት...አለቱ
ዳዊት ያህዌን ከአለት ጋር የሚያነጻጽረው ህዝቡን ለመጠበቅ ያለውን ሀይል ለማጉላት ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ህዝብን ከስሬ የሚያስገዛልኝ
"ባዕድ ህዝብን ከበታቼ የሚያስገዛልኝ"

ከተነሱብኝ በላይ ከፍ ከፍ አደረግከኝ
"ከጠላቶቼ አዳንከኝ ክብርንም ሰጠኸኝ"

ከአመጸኞች ሰዎች
"ሊጎዱኝ ከሚፈልጉ"

2 Samuel 22:50

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል።

ለስምህ
እዚህ ስፍራ "ስም" የሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሚያመለክተው የያህዌን ታላቅነት/ክብር ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ለቀባው የቃል ኪዳኑን ታማኝነት አሳየ
እዚህ ስፍራ ዳዊት የሚያመለክተው ያህዌ በ2 ሳሙኤል 7:8 ላይ የገባውን ቃል ኪዳን ሊሆን ይችላል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 23

1 እነዚህ ተወዳጁ የእስራኤል ዘማሪ፣ በያዕቆብ አምላክ የተቀባው፣ እጅግ የተከበረው፣ የእሴይ ልጅ የዳዊት የመጨረሻ ቃሎች ናቸው። **2** የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ተናገረ፣ ቃሉም በምላሴ ላይ ነበረ። **3** የእስራኤል አምላክ ተናገረ፣ የእስራኤልም ዐለት እንደዚህ አለኝ፣ “ሰዎችን በጽድቅ የሚገዛ፣ በፈሪሀ-እግዚአብሔር የሚያስተዳድር፣ **4** እርሱ ከዝናብ በኋላ ብሩሕ በሆነው የፀሐይ ብርሃን ከምድር እንደሚበቅል ለምለም ሣር፣ ደመና የሌለባት ፀሐይ ጥዋት ስትወጣ እንደሚፈነጠቅ የማለዳ ብርሃን ነው። **5** በእርግጥ የእኔ ቤተሰብ በእግዚአብሔር ፊት እንደዚህ አይደለምን? ከእኔስ ጋር ሥርዓት ያለውና በሁሉም መንገድ እርግጠኛ የሆነ የዘላለም ቃል ኪዳን አልገባምን? ድነቴን ከፍ ከፍ አድርጎ፣ ማንኛውንም ፍላጎቴን አይፈጽምልኝምን? **6** ነገር ግን በእጅ ሊሰበሰቡ ስለማይችሉ ሁላቸውም እንደሚጣሉ እሾሆች ከንቱዎች ናቸው። **7** እነርሱን የሚነካ የብረት መሣሪያ መጠቀም ወይም የጦር ዘንግ መያዝ ስላለበት ባሉበት መቃጠል ይገባቸዋል።” **8** የዳዊት ምርጥ ወታደሮች ስም የሚከተለው ነው፦ የታህክሞን ሰው ዮሴብ የሦስቱ አለቆች አለቃና በአንድ ውጊያ ላይ ስምንት መቶ ሰዎችን የገደለ ነው። **9** ከእርሱ ቀጥሎ የአሆሃዊው የዱዲ ልጅ ኤልዓዘር ነበረ፣ እርሱም ከሶስቱ ኃያላን ሰዎች አንዱ ነበር። እርሱም ጦርነት ለመግጠም የተሰባሰቡ ፍልስጥኤማውያን በተገዳደሩ ጊዜና የእስራኤልም ሰዎች በፈገፈጉ ጊዜ በዚያ ነበር። **10** ኤልኤዘር እስኪዝልና እጁ ከሰይፉ ጋር ተጣብቆ እስኪቀር ድረስ ከፍልስጥኤማውያን ጋር ቆሞ ተዋጋ። የዚያን ቀን እግዚአብሔር ታላቅ ድል አስገኘ። ከኤልኤዘር በኋላ ሠራዊቱ የተመለሰው አስከሬኖቹን ለመግፈፍ ብቻ ነበር። **11** ከእርሱም በኋላ የአሮዳዊው የአጌ ልጅ ሣማ ነበር። ፍልስጥኤማውያኑ የምስር እርሻ በነበረበት ተሰብስበው ሳሉ ሠራዊቱ ከ እነርሱ ሸሸ። **12** ሣማ ግን በእርሻው መካከል ቆሞ ተቋቋማቸው ፍልስጥኤማዊውንም ገደለው እግዚአብሔርም ታላቅ ድል ሰጣቸው። **13** ከሰላሳዎቹ ወታደሮች ሶስቱ በመከር ጊዜ ወደ አዶላም ዋሻ ወደ ዳዊት ዘንድ ሄዱ። የፍልስጥኤም ሠራዊት በራፋይም ሸለቆ ሰፍረው ነበር። **14** በዚያን ጊዜ ዳዊት በአንድ ዋሻ በምሽጉ ውስጥ ሲሆን ፍልስጥኤማውያን ግን በቤተልሔም ተደራጅተው ነበር። **15** ዳዊትም ውሃ ተጠምቶ፣ “በበሩ አጠገብ ካለችው ጉድጓድ የምጠጣውን ውሃ ምነው አንድ ሰው በሰጠኝ!” አለ። **16** ስለዚህ እነዚህ ሶስቱ ኃያላን ፍልስጥኤማውያንን ጥሰው አልፈው በበሩ አጠገብ ካለችው ከቤተልሔም ጉድጓድ ውሃ ቀዱ። ውሃውንም ይዘው ለዳዊት አመጡለት፣ እርሱ ግን ሊጠጣው ስላልፈቀደ በእግዚአብሔር ፊት አፈሰሰው። **17** ከዚያ በኋላም፣ “እግዚአብሔር ሆይ፣ ይህንን እጠጣው ዘንድ ከእኔ ይራቅ፤ ሕይወታቸውን አደጋ ላይ የጣሉ ሰዎችን ደም ልጠጣ ይገባኛልን?” ከዚህም የተነሣ ሊጠጣው አልፈቀደም። ሶስቱ ኃያላን ያደረጓቸው ነገሮች እነዚህ ናቸው። **18** የኢዮአብ ወንድምና የጽሩያ ልጅ አቢሳ የሶስቱ አለቃ ነበር። በአንድ ወቅት ከሶስት መቶዎቹ ጋር በጦሩ ተዋግቶ ገደላቸው። ከሶስቱ ወታደሮች ጋር በተያያዘ ብዙውን ጊዜ ስሙ ይጠቀሳል። **19** እርሱ ከእነርሱም ይልቅ ዝነኛ አልነበረምን? እርሱ የሶስቱ አለቃ ሆኖ ተሾመ። ይሁን እንጂ የእርሱም ዝና ከሶስቱ እጅግ ዝነኛ ከነበሩት ወታደሮች ጋር የሚስተካከል አልነበረም። **20** የቀብጽኤል አገር ሰው የሆነው የዮዳሄ ልጅ በናያስ ታላቅ ጀብዱ የሠራ ጠንካራ ሰው ነበረ። እርሱም ሁለቱን የአርኤል ልጆች ገደለ። በረዶ በጣለበትም ወቅት በጉድጓድ ውስጥ ገብቶ አንበሳ ገድሎአል። **21** ደግሞም አንድ ግዙፍ ግብፃዊም ገድሎአል። ግብፃዊው በእጁ ጦር የያዘ ቢሆንም በናያስ በትር ብቻ ይዞ ገጠመው። ጦሩን ከግብፃዊው እጅ ቀምቶ በራሱ ጦር ገደለው። **22** በናያስ እነዚህን ጀብዱዎች ፈጸመ ከሶስቱም ኃያላን ጋርም ስሙ የተጠራ ሆነ። **23** በአጠቃላይ ከነበሩት ሰላሳ ወታደሮች ይልቅ ከፍ ያለ ግምት የተሰጠው ነበረ፣ ሆኖም የሶስቱ እጅግ ምርጥ ወታደሮችን ያህል ታላቅ ግምት የተሰጠው አልነበረም። ሆኖም ዳዊት የክቡር ዘበኞቹ አለቃ አደረገው። **24** ሰላሳዎቹ የሚከተሉትን ያካተተ ነበር፣ የኢዮአብ ወንድም አሣሄል፣ የቤተልሔሙ ሰው የዱዲ ልጅ ኤልያናን፣ **25** አሮዳዊው ሣማ፣ አሮዳዊው ኤሊቃ፣ **26** ፈሊጣዊው ሴሌስ፣ የቴቁሐዊው የዒስካ ልጅ ዒራስ፣ **27** ዓኖቶታዊው አቢዔዜር፣ ኩስታዊው ምቡናይ ፣ **28** አሆሃዊው ጸልሞን፣ ነጦፋዊው ማህራይ፣ **29** የነጦፋዊው የበዓና ልጅ ሔሌብ፣ ከብንያም ወገን የጊብዓ ሰው የሆነው የሪባይ ልጅ ኢታይ፣ **30** ጲርዓቶናዊው በናያስ፣ የገዓስ ሸለቆ ሰው ሂዳይ፣ **31** ዓረባዊው አቢዔልቦን፣ በርሑማዊው ዓዝሞት፣ **32** ሸዓልቦናዊው ኤሊያሕባ፣ የአሳን ልጆች፤ ዮናታን የተባለው፣ **33** የአሮዳዊው የሣማ ልጅ፣ የአሮዳዊው የሻራር ልጅ አሒአም፣ **34** የማዕካታዊው የአሐሰባይ ልጅ ኤልፋላት፣ የጊሎናዊው የአኪጦፌል ልጅ ኤሊአም፣ **35** ቀርሜሎሳዊው ሐጽሮ፣ አርባዊው ፈዓራይ፣ **36** የሱባ ሰው የሆነው የናታን ልጅ ይግዓል፣ **37** አሞናዊው ጻሌቅ፣ የጽሩያ ልጅ የኢዮአብ ጦር መሣሪያ ያዥ የነበረው ብኤሮታዊው ነሃራይ፣ **38** ይትራዊው ዔራስ ፣ ይትራዊው ጋሬብ፣ **39** እንዲሁም ኬጢያዊው ኦርዮ፤ በጠቅላላው ሠላሳ ሰባት ነበሩ።

---

2 Samuel 23:1

አሁን
ይህ የመጽሐፉን አዲስ ክፍል ጅማሬ ያሳያል።

እነዚህ የመጨረሻ ቃላት ናቸው
ይህ የሚያመለክተው ዳዊት በ2 ሳሙኤል 23:2-7 የሚናገረውን ነው።

እጅግ የተከበረው ሰው፣ በያቆብ አምላክ የተቀባው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የያዕቆብ አምላክ እጅግ ያከበረው እና የቀባው ሰው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በያዕቆብ አምላክ የተቀባው
መቀባት የሚካሄደው በሰውየው ራስ ላይ ዘይት በማፍሰስ ነበር። ይህ ይደረግ የነበረው እንደ ንጉሥ ወይም ካህን ሆኖ እግዚአብሔርን የሚያገለግልን ሰው ለመምረጥ ነበር። (ተምሳሌታዊ/ምልክታዊ ድርጊታዊ የሚለውን ይመልከቱ)

መዝሙረኛው
ይህ መዝሙረ ዳዊትን ወይም መዝሙሮችን የጻፈው ሰው ነው።

በእኔ
በዳዊት

የእርሱ ቃል አንደበቴ ላይ ነበር
እዚህ ስፍራ "በአንደበቴ ላይ" የሚለው ለዳዊት ንግግር ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "እርሱ የምናገረውን መልዕክት ሰጠኝ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 23:3

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ ቀጣይ የዳዊት ማጠቃለያ ቃል ነው።

የእስራኤል አምላክ፣ የእስራኤል አለት፣ ይናገራል... እኔ
እዚህ ስፍራ "የእስራኤል አምላክ" የሚለው "የእስራኤል አለት" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው። ሁለቱ ሀረጋት በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ነገርን ይገልጻሉ። ዳዊት እግዚአብሔርን ከአለት ጋር የሚያነጻጽረው እርሱ ህዝቡን ለመጠበቅ ያለውን ሀይል ለማጉላት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እግዚአብሔርን በመፍራት የሚመራ፣ በሰዎች ላይ በጽድቅ የሚገዛ
እነዚህ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች ንጉሡ እግዚአብሔርን እንደሚያከብር እና እግዚአብሔር እርሱ እንዲያደርግ የሚፈልገውን እንደሚያደርግ ይገልጻሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ፍርሃት /እግዚአብሔርን በመፍራት
"እግዚአብሔርን መፍራት/ማክበር"

እርሱ እንደ ማለዳ ብርሃን ይሆናል... ከዝናብ በኋላ እንደሚወጣ ፀሐይ
እዚህ ስፍራ እግዚአብሔር ንጉሡን ከማለዳ ብርሃን እና ከዝናብ በኋላ ከሚወጣ ዝናብ ጋር ያነጻጽረዋል። እነዚህ ይህ ንጉሥ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ እና ለህዝቡ መባረክ ምክንያት መሆኑን የሚገልጹ መንገዶች ናቸው። "እርሱ ለሁሉም ደስታ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤያዊ የሚሉትን ይመልከቱ)

2 Samuel 23:5

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ ቀጣይ የዳዊት ማጠቃለያ ቃል ነው።

በውኑ የእኔ ቤት በያህዌ ፊት እንደዚህ አይደለምን?
እዚህ ስፍራ ላይ ዳዊት ከእግዚአብሔር ጋር መስማማቱን ይናገራል። ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "የእኔ ቤት በውኑ በእግዚአብሔር ፊት እንዲሁ አይደለምን!" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ... መንገድ አላበጀምን?
ዳዊት እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ቃል ኪዳን እንዳደረገ እውቅና ይሰጣል። ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እርሱ በእርግጥ... መንገድ ያበጃል።" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ስርአት ያለው እና እርግጠኛ
ይህ ማለት የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን በዳዊት ቤት የታመነ፣ በሚገባ የተቀናጀ እና የማይለወጥ ነው።

እርሱ ደህንነቴን፣ መሻቴን... ፍጹም አላደረገምን?
ዳዊት ሁልጊዜም እግዚአብሔር እንደሚረዳው እና እንደሚያበለጽገው ያምናል። ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እርሱ ደህንነቴን ፍጹም ያደርጋል ደግሞም መሻቴን ሁሉ ይሰጠኛል።" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 23:6

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ ቀጣይ የዳዊት ማጠቃለያ ቃል ነው።

ረብ የለሾች አንዳች እንደማይጠቅም እንደሚጣል እሾክ ይሆናሉ
እዚህ ስፍራ ክፉ ሰው ጥቅም ከሌለው እሾህ ጋር ተነጻጽሯል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ክፉ ሰው እንደምንጥለው እሾህ እርባና ቢስ እና አደገኛ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ምክንያቱም እነዚህ በሰው እጅ ሊሰበሰቡ አይችሉም
"ምክንያቱም ማንም ሰው ሳይጎዳው እሾህን በእጁ መልቀም አይችልም"

ባሉበት ሊቃሉ ይገባል
"እሾህ በተገኘበት በዚያው ስፍራ ሊቃጠል ይገባዋል።" ይህ እግዚአብሔር ክፉ ሰዎችን ያጠፋቸዋል ማለት ነው።

2 Samuel 23:8

ዮሴብ
ይህ የወንድ ስም ነው። ሌሎች ቅጂዎች ዮሴብ በሴትቤት፣ ያሾብዓም፣ ኢሽባል፣ ወይም ኢያቡስቴ ይላሉ፤ ምክንያቱም የተለያዩ ጥንታዊ ቅጂዎች እነዚህ ልዩነቶች አሏቸው። ተርጓሚዎች በትርጉም ስራዎቻቸው በግርጌ ማስታወሻዎች ይህንን ማለት ሊመርጡ ይችላሉ (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሃቻሞንቲ
ይህ የህዝብ ወገን/ ቡድን ስም ነው። "የሃቻሞን ልጅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ስምንት መቶ
"800" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 23:9

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ የዳዊትን ታላላቅ ወታደሮች ዝርዝር ማቅረቡን ይቀጥላል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰራዊቱ ከኤልዔዘር በኋላ ተመለሰ
ይህ ማለት ሰራዊቱ አልአዛር ከጦርነት ከተመለሰ በኋላ ተመለሰ። "የእስራኤል ሰራዊት አልዔዘር ጦርነቱን ካሸነፈ በኋላ ወደ ጦር ሜዳው ተመለሰ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከሞቱት ለመግፈፍ ብቻ
"ከጠላቶቻቸው በድን ላይ የሚፈልጉትን ለመግፈፍ ብቻ"

2 Samuel 23:11

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ የዳዊትን ታላላቅ ወታደሮች ዝርዝር ማቅረቡን ይቀጥላል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የምስር እርሻ
" ምስር የተዘራበት እርሻ"

ምስር
እንደ አተር ያለ ለምግብ የሚሆን ጠፍየፍ ያለ ፍሬ (የማይታወቀውን መተረጎም የሚለውን ይመልከቱ)

ሰራዊቱ ሸሸ
"የእስራኤል ሰራዊት ሸሸ"

2 Samuel 23:13

ከሰላሳዎቹ ውስጥ ሶስቱ
እነዚህ በ 2ሳሙኤል 23:8-12 ውስጥ የተጠቀሱት እንዚያው ሶስቱ ወታደሮች አይደሉም

ሰላሳዎቹ
"30ዎቹ" ወይም "ሰላሳዎቹ የእስራኤል ጀግና ወታደሮች።" የዚህ ሀሳብ ሙሉ ትርጉም ይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። (ቁጥሮች እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የዓዶላም ዋሻ
"ዓዶላም ከተማ አቅራቢያ የሚገኝ ዋሻ::" ዓዶላም የሚገኘው ቤተልሔም አጠገብ ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የራፋይም ሸለቆ
ይህ የቦታ ስም ነው። ይህ በ2 ሳሙኤል 5:18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

በጠንካራ ይዞታው/በምሽጉ
"በተጠበቀ ቦታው"

ፍልስጥኤማውያን በቤተልሔም ይገኙ ነበር
"ጥቂት ፍልስጥኤማውያን ወታደሮች የቤተልሔምን መንደር ተቆጣጥረው ነበር"

2 Samuel 23:15

ሰራዊቱን ሰብረው
"በጠላት ሰራዊት በኩል እየተዋጉ"

ህይወታቸውን ለአደጋ አሳልፈው የሰጡትን ወታደሮች ደም እጠጣለሁን?
ዳዊት ውሃውን ከደም ጋር ያነጻጸረበት ምክንያት ወታደሮቹ ውሃውን ለእርሱ ለማምጣት ህይወታቸውን ለአደጋ አጋልጠው ስለ ነበረ ነው። ጥያቄውን የተጠቀመበት ይህን ለማጉላት ነው። ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ይህንን ውሃ መጠጣት ውሃወን ለአኔ ለማምጣት ህይወታቸውን በአደጋ ላይ የጣሉትን ወታደሮች ደም እንደ መጠጣት ነው" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

2 Samuel 23:18

አቢሳ... ጽሩያም
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። በ2 ሳሙኤል 2:18 ላይ በተተረጎመው መሰረት ይተርጎሙ።

በሶስቱ ላይ አለቃ
ይህ ማለት ሄደው ለዳዊት ውሃ ካመጡት ውስጥ አቢሳ የሶስቱ መሪ ነበር።

ሶስት መቶ ወንዶች
"300 ወንዶች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልቱ)

እርሱ ብዙ ጊዜ ከሶስቱ ወታደሮች ጋር ይጠቀስ ነበር
ይህ በአድርጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች ብዙውን ጊዜ ስለ ሶስቱ የጀግኖች ጀግና ሲናገሩ እርሱን ይጠቅሱታል" (አድርጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ከሶቱ እንኳን ይበልጥ ታዋቂ አልነበረምን?
ይህ ጥያቄ የዋለው እርሱ ምን ያህል ታዋቂ እንደነበረ ለማጉላት ነው። ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እርሱ ከሶቱ አንኳን ይበልጥ ታዋቂ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ይበልጥ የታወቁ ሶስት ወታደሮች
ይህ የሚያመለክተው ዮሴብ በሴትቤትን፣ ኤልዔዘርን፣ እና ሻማህን ነው። አቢሳ እንደነዚህ ሶስት ወታደሮች ዝነኛ አልነበረም።

2 Samuel 23:20

ቀብጽኤል
ይህ የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ዮዳሄ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህ በ2 ሳሙኤል 8:18 እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

አሬል
ይህ የወንድ ስም ነው።

2 Samuel 23:22

ይህን ጀብዱ ፈጽም
"ይህን ታላቅ ስራ አከናውን"

ከሶስቱ ታላላቅ ሰዎች ጋር ስሙ የተጠራ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች ሶስቱን ታላላቅ ሰዎች እንደሚያመሰግኑ እርሱንም ያመሰግኑታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በአጠቃላይ ሰላሳዎቹ ወታደሮች ከሚታዩት ይልቅ እርሱ ይበልጥ የከበረ ነበር፤ ሆኖም ግን የሶስቱን ታላላቅ ሰዎች ያህል ከፍ ብሎ አይታይም ነበር።
"ከሶስቱ እጅግ ምርጥ ወታደሮች በስተቀር፤ ከሌሎቹ 30 ወታደሮች ይበልጥ ዝነኛ ነበር። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሶስቱ ታላላቅ ወታደሮች
ይህ የሚያመለክተው ዮሴብ በሴትቤት፣ ኤልዔዘርን እን ሻማህን ነው።

የእርሱ ጠባቂ / የክብር ዘብ
ዳዊትን የሚጠብቁ ወታደሮች ቡድን

2 Samuel 23:24

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ የዳዊት ታላላቅ ወታደሮች ዝርዝር ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰላሳዎቹ
"በጣም ዝነኞቹ 30 ወታደሮች" (ቁጥሮች እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

2 Samuel 23:29

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ የዳዊት ታላላቅ ወታደሮች ዝርዝር ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 23:33

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ የዳዊት ታላላቅ ወታደሮች ዝርዝር ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 23:37

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ የዳዊትን ታላላቅ ወታደሮች ዝርዝር ያጠቃልላል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በጠቅላላው ሰላሳ ሰባት ነበሩ
"በጠቅላላው 37 ነበሩ" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 24

1 እንደገናም እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ እጅግ ተቆጣ፤ ዳዊትንም በእነርሱ ላይ በማስነሳት፣ “ሂድ እስራኤልንና ይሁዳን ቁጠር” አለው። 2 ንጉሡ አብሮት
ለነበረው ለኢዮአብ፣ “ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ወደ እስራኤል ነገዶች ሁሉ ሂዱ፣ ለጦርነት ብቁ የሆኑትንም ጠቅላላ ብዛት ማወቅ እችል ዘንድ ሕዝቡን ሁሉ
ቁጠሩ።” አለው። 3 ኢዮአብም ለንጉሡ፣ “እግዚአብሔር አምላክህ የሕዝቡ ቁጥር መቶ እጥፍ ያብዛ፣ የጌታዬ የንጉሡ ዓይንም ይህንን ለማየት ያብቃው። ነገር
ግን ጌታዬ ይህንን ለማድረግ ለምን ፈለገ?” 4 ይሁን እንጂ የንጉሡ ቃል የኢዮአብንና የሠራዊት አለቆችን ቃል የሚሸር የመጨረሻ ቃል ነበር። ስለዚህ
የእስራኤልን ሕዝብ ይቆጥሩ ዘንድ ኢዮአብና የሠራዊቱ አለቆች ከንጉሡ ፊት ወጡ። 5 ዮርዳኖስን ተሻገሩና ከከተማው በስተደቡብ በሸለቆው ዘንድ ባለው
በአሮዔር አጠገብ ሠፈሩ። ከዚያም በጋድ በኩል አድርገው ወደ ኢያዜር ተጓዙ። 6 ወደ ገለዓድና ወደ ተባሶን አደሰይ፣ ቀጥሎም ወደ ዳንየዓን ከዚያም ዞረው
ወደ ሲዶና ሄዱ። 7 ወደ ጢሮስ ምሽግና ወደ ኤዊያውያንና ወደ ከነዓናውያን ከተሞች ደረሱ። ከዚያም በይሁዳ ቤርሳቤህ ወዳለችው ወደ ኔጌቭ ወጡ። 8
በመላው ምድሪቱ ከተዘዋወሩ በኋላ ከዘጠኝ ወር ከሃያ ቀናት በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ። 9 ከዚያም ኢዮአብ ለንጉሡ የተዋጊ ወንዶችን ጠቅላላ ቁጥር
ዘገባ አቀረበ። በእስራኤል ሰይፍን መምዘዝ የሚችሉ ስምንት መቶ ሺህ ጀግኖች ሲኖሩ በይሁዳ ደግሞ አምስት መቶ ሺህ ሰዎች ነበሩ። 10 ሰዎቹን ከቆጠረ
በኋላ ዳዊት በልቡ ተጨነቀ። ስለዚህ ለእግዚአብሔር፣ “ይህንን በማድረጌ ታላቅ ኃጢአት ሠርቻለሁ። የሠራሁት እጅግ የስንፍና ሥራ ነውና፣ እግዚአብሔር ሆይ፣
የባሪያህ በደል አስወግድ።” 11 ዳዊት ጠዋት ከመኝታው ሲነሣ፣ የእግዚአብሔር ቃል ወደ ዳዊት ባለ ራእይ ወደ ነቢዩ ጋድ እንዲህ ሲል መጣ፣ 12 “ሂድና
ለዳዊት፣ ‘እግዚአብሔር የሚለው ይህንን ነው፣ ሶስት ምርጫ እሰጥሃለሁ፣ አንዱን ምረጥ’” 13 ስለዚህ ጋድ ወደ ዳዊት ሄደና፣ “የሦስት ዓመት ረሃብ ወደ
ምድርህ ይምጣን? ወይስ እነርሱ እያሳደዱህ ከጠላቶችህ ለሶስት ወራት ብትሸሽ ይሻልሃል? ወይስ በአገርህ የሶስት ቀን ቸነፈር ይምጣብህ? ለላከኝ ምን
መልስ እንደምሰጥ አሁን ወስን” አለው። 14 ዳዊትም ጋድን፣ “እጅግ ተጨንቄአለሁ፤ ምሕረታዊ አደራረጉ እጅግ ታላቅ ስለሆነ በእግዚአብሔር እጅ እንውደቅ
እንጂ በሰው እጅ አንውደቅ” አለው። 15 ስለዚህ እግዚአብሔር ህከጥዋት እስከ ተወሰነ ጊዜ ቸነፈሩን በእስራኤል ላይ ላከ፣ ከዳን እስከ ቤርሳቤህም ሰባ ሺህ
ሰዎች ሞቱ። 16 መልአኩ ኢየሩሳሌምን ለማጥፋት እጁን በዘረጋ ጊዜ፣ እግዚአብሔር ስለደረሰው ጉዳት ተፀፀቶ ሕዝቡን እያጠፋ የነበረውን መልአክ፣
“ይበቃል፣ እጅህን ሰብስብ” አለው። በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ በኢያቡሳዊው በኦርና ዐውድማ አጠገብ ቆሞ ነበር። 17 ሕዝቡን እየቀሠፈ የነበረውን
መልአክ ባየ ጊዜ ዳዊት ለእግዚአብሔር፣ “ኃጢአት ሠርቻለሁ፣ የማይገባም ነገር አድርጌአለሁ። ነገር ግን እነዚህ በጎች ምን ያደረጉት ነገር አለ? እባክህን የአንተ
እጅ እኔንና የአባቴን ቤተሰብ ይቅጣ።” ብሎ ለእግዚአብሔር ተናገረ። 18 ከዚያ በኋላ ጋድ በዚያን ቀን ወደ ዳዊት መጣና፣ “ውጣና በኢያቡሳዊው በኦርና
አውድማ ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሥራ” አለው። 19 ስለዚህ ዳዊት ጋድ እንደ ነገረውና እግዚአብሔር እንዳዘዘው ወጣ። 20 ኦርና ሲመለከት ንጉሡና
አገልጋዮቹ ሲደርሱ አየ። ስለዚህ ኦርና ወጣ ብሎ በንጉሡ ፊት ለጥ ብሎ እጅ ነሣ። 21 ከዚያ በኋላም ኦርና፣ “ጌታዬ ንጉሡ ወደ ባሪያው ዘንድ ለምን መጣ?”
ዳዊትም መለሰ፣ “ቸነፈሩ ከሕዝቡ ይወገድ ዘንድ ለእግዚአብሔር መሠዊያ የምሠራበትን የአንተን ዐውድማ እገዛ ዘንድ ነው።” 22 ኦርናም ለዳዊት፣ “ጌታዬ
ንጉሡ የራስህ አድርገህ ውሰደው። በፊትህ ደስ ያሰኘህንም አድርግበት። እነሆ፣ ለሚቃጠል መሥዋዕት በሬዎች፣ ለማገዶም የሚሆን የመውቂያ ዕቃና ቀንበር
በዚህ አለ። 23 ይህንን ሁሉ ንጉሤ ሆይ፣ እኔ ኦርና ለአንተ እሰጣለሁ” አለና ከዚያ በኋላ፣ “እግዚአብሔር አምላክህ ይቀበልህ” አለው። 24 ንጉሡም ለኦርና፣
“አይሆንም፣ ይህንን በዋጋ መግዛት ይኖርብኛል። ምንም ነገር ያላወጣሁበትን አንድም ነገር ለእግዚአብሔር የሚቃጠል መሥዋዕት አድርጌ አላቀርብም” አለው።
ስለዚህ ዳዊት ዐውድማውንና በሬዎቹን በሃምሳ የብር ሰቅል ገዛ። 25 ዳዊት በዚያ ላይ ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሠራና የሚቃጠል መሥዋዕትና የኅብረት
መሥዋዕት አቀረበ። ስለዚህ እግዚአብሔር ስለ ምድሪቱ ተለመነው፣ በእስራኤል የነበረውም ቸነፈር ቆመ።

---

2 Samuel 24:1

የያህዌ ቁጣ በእስራኤል ላይ ነድዶ ነበር
"ነደደ" የሚለው ቃል እሳት ጀመረ ማለት ነው። እዚህ ስፍራ የያህዌ ቁጣ የተነጻጸረው ከእሳት ጋር ነው። "የያህዌ ቁጣ እንደ እሳት መንደድ ጀመረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ዳዊትን በእነርሱ ላይ አንቀሳቀሰ
"ዳዊት እነርሱን እንዲቃወም አደረገ"

ሂዱ፣ እስራኤልን እና ይሁዳን ቁጠሩ
በሙሴ ህግ፣ እግዚአብሔር የእስራኤል ነገሥታትን ተዋጊዎችን/ወታደሮችን እንዳይቆጥሩ ከልክሏል። የዚህ ሀሳብ ሙሉ ትርጉም ይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዳን እስከ ቤርሳቤህ
ይህ ሀረግ የሁለት ቦታዎችን ስም ይዟል፤ ዳን በሩቅ ሰሜን፣ እና ቤርሳቤህ በሩቅ ደቡብ አጠቃላዩን አገሪቱን ለመወከል ተጠቅሰዋል። (ጽንፎች የሚለውን ይመልከቱ)

ለጦርነት የበቃውን/የሚሆን...ሁሉንም ህዝብ ቁጠሩ
ይህ በጣም ወጣት፣ ወይም በጣም ሸማግሌ፣ ወይም ለመዋጋት አካላቸው ብቁ ካልሆኑት በስተቀር ሌሎችን ወንዶች መቁጠር ማለት ነው።

2 Samuel 24:3

መቶ ጊዜ...ይብዛ
ይህ ማለት "አሁን ያለው እያንዳንዱ ሰው 100 እጥፍ ቢሆን።" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

የንጉሡ ቃል ኢዮአብን አሸነፈ
x

2 Samuel 24:5

እነርሱ ተሸገሩ
"ኢዮአብ እና የሰራዊቱ አዛዦች ተሻገሩ"

አሮኤር
ከአርኖር ወንዝ ዳርቻ በስተ ሰሜን የሚገኝ ከተማ ነበር። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ኢያዜር
ይህ በጋድ ውስጥ የሚገኝ ከተማ ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ተባሶን አዳሰይ
ይህ በሔቲ ህዝቦች ምድር የቃዴስ ከተማን ሊያመለክት ይቸላል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Samuel 24:8

እነርሱ ሄዱ
"ኢዮአብ እና የጦር አዛዦቹ ሄዱ

ዘጠኝ ወር ከ ሃያ ቀን
"9 ወር ከ 20 ቀን" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያም ኢዮአብ የተቆጠሩትን የተዋጊ ወታደሮች አጠቃላይ ቁጥር ለንጉሡ አሳወቀ
"ከዚያ ኢዮአብ ለጦርነት ዝግጁ የሆኑ ወንዶችን ቁጥር ለንጉሡ ተናገረ"

በእስራኤል
ይህ የሚያመለክተው የሰሜን እስራኤል ነገድን ነው

800,000 500,000
"ስምንት መቶ ሺህ... አምስት መቶ ሺህ" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰይፍ መምዘዝ የሚችሉ
ይህ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሚያመለክተው በሰራዊቱ ለውጊያ ብቁ የሆኑ ወንዶችን ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከይሁዳ
ይህ የሚያመለክተው የይሁዳን ደቡባዊ ነገድ ነው።

2 Samuel 24:10

ዳዊት ልቡ አዘነ
እዚህ ስፍራ "ልብ" የዳዊትን ስሜት እና ህሊና ሁኔታ ለመግለጽ የዋለ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ዳዊት ተጸጸተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እንግዲህ፣ ያህዌ የአገልጋዮን በደል ይቅር ይበል
ዳዊት "የአገልጋዩን" ሲል የሚገልጸው ራሱን ነው። ይህ ስልጣን ያለውን ለማክበር የትህትና አገላለጽ ነው።

2 Samuel 24:11

የያህዌ ቃል ለዳዊት መልዕክት ወደሚያመጣለት ወደ ነቢዩ ጋድ መጣ፣ " ሂድ
"የያህዌ ቃል ወደ...መጣ" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር የዋለው ከእግዚአብሔር ልዩ መልእክትን ለማምጣት ነው። ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር በ2 ሳሙኤል 7:4 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ለዳዊት መልዕክት ለሚያመጣለት ለነቢዩ ጋድ መልእክት ሰጠው። እንዲህም አለው፣ ‘ሂድ' ወይም "ያህዌ ለዳዊት መልዕክት ለሚያመጣለት ለነብዩ ጋድ ‘ሂድ' የሚል መልዕክት ተናገረው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የዳዊት መልዕክት አምጪ/ባለ ራዕይ
ይህ ማለት ጋድ በንጉሣዊ ቤተ መንግስት በግልጽ የሚታወቅ ነቢይ ነበር።

2 Samuel 24:13

በትልቅ ችግር ውስጥ ነኝ
"እጅግ አስጨናቂ በሆነ ችግር ውስጥ ነኝ"

በሰው እጅ ከመውደቅ በያህዌ እጅ ላይ እንውደቅ
እዚህ ስፍራ "እጆች" የሚለው የሚያመለክተው ሀይልን ወይም የማድረግ አቅምን ነው። "ያህዌ እንጂ ሰው አይቅጣን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 24:15

የተወሰነ ጊዜ
ይህ እግዚአብሔር መቅሰፍቱን ለማቆም የወሰነበት ጊዜ ነው።

ሰባ ሺህ
"70,000" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ከዳን እስከ ቤርሳቤህ
እዚህ ስፍራ በሰሜን ጫፍ የሚገኘው ዳን እና በደቡብ ጫፍ የሚገኘውን በርሳቤ መጠቀሱ መላው የእስራኤል አገር መጠቀሱ ነው። (ጽንፎች የሚለውን ይመልከቱ)

መልአኩ አያሩሳሌምን ሊያጠፋት እጆቹን ዘርግቶ ደረሰ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የመልአኩን ሀይል ለመግለጽ የዋለ ነው። "መልአኩ በኢያሩሳሌ የሚኖሩ ሰዎችን ሊያጠፋ ተቃርቦ ነበር" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ ከደረሰው ጥፋት የተነሳ ምህረት አደረገ
ይህ ማለት ያህዌ መልአኩ ሊያደርስ ያለውን ክፉ ነገር አስቆመ። "ያህዌ ስለ ደረሰው ጥፋት አዘነ"

እጅህን መልስ
"እጅ" የሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሚገልጸው የመልአኩን ሀይል ነው። "ከዚህ በላይ ጉዳት አታድርስባቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ኦርና
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ዐውድማ
ዐውድማ ፍሬውን ከገለባ ለመለየት የተዘጋጀ ለጥ ያለ ወለል

2 Samuel 24:17

በድያለሁ፣ ማድረግ ከሚገባኝ የተገላቢጦሹን አድርጊያለሁ
እነዚህ ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው ተያይዘው የቀረቡት ለሀሳቡ ትኩረት ለመስጠት ነው። "እጅግ በድያለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ በጎች ግን ምን አደረጉ?
ዳዊት ይህን ጥያቄ የተጠቀመው እና ህዝቡን ከበጎች ጋር ያነጻጸረው እነርሱ ምንም እንዳላጠፉ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እነዚህ ተራ ዜጎች ምንም ጥፋት አልፈጸሙም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

እባክህ የአንተ እጅ ይቅጣኝ/በአንተ እጅ ልውደቅ
x

2 Samuel 24:18

ፊቱን ወደ ምድር ዝቅ አድርጎ ለንጉሡ ሰገደ
ለንጉሡ ጥልቅ አክብሮት እና ክብር እያሳየ ነበር። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Samuel 24:21

መቅሰፍቱ ከህዝቡ ይወገድ ዘንድ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ያህዌ ይህንን መቅሰፍት ከህዝቡ ያስወግድ ዘንድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በአንተ ዐይን/በአንተ እይታ መልካም የሆነውን
እዚህ ስፍራ ማየት የሚለው የሚገልጸው ፍርድን ወይም ሚዛን ነው። "አንተ መልካም ነው የምትለውን" ወይም "በአንተ ሚዛን መልካም የሆነውን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የመውቂያ ዕቃ
ፍሬ ከገለባ የሚለይበት

2 Samuel 24:24

ዋጋ ያልከፈልኩበትን... አላቀርብም
ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊጻፍ ይችላል። "የምሰዋው ... ዋጋ ያወጣሁበትን ነገር ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ድርብ አሉታ የሚለውን ይመልከቱ)

ሃምሳ ሰቅል
"50 ሰቅል" (ቁጥሮች እና መጽሐፍ ቅዱሳ ገንዘብ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ ምድሪቱ
"ምድር" የሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሚወክለው የእስራኤልን ሰዎች ነው። "በእስራኤል ህዝብ ስም/ የእስራኤልን ህዝብ ወክሎ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከእስራኤል ላይ መቅሰፍቱ ተከለከለ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ይወርድ የነበረውን መቅሰፍት ከለከለ" ወይም "እግዚአብሔር ከእስራኤል መቅሰፍቱን አራቀ/ከለከለ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: 1 Kings

1 Kings

Chapter 1

1 ንጉስ ዳዊትም ሸምግሎ እና እድሜውም ገፍቶ ነበር። ምንም እንካ ልብስ ቢድርቡለትም፣ ሊያሞቀው አልቻለም። 2 ስለዚህ አገልጋዮቹ፣ "ለንጉስ አንዲት ወጣት ልጃገረድ እንፈልግለት እና ታገልግለው ትንከባከበውም። ንጉሱም እንዲሞቀው ክንዱ ውስጥ ትተኛ፣' አሉት። 3 ስለዚህም አንዲት ቆንጆ ልጃገረድ ለማግኘት በመላው እስራኤል ፈለጉ። ሱነማዊቱን አቢሳን አገኙ፤ ወደ ንጉሡም አመጡአት። 4 እርስዋም እጅግ ውብ ነበረች፤ እርስዋም ንጉሡን አገለገለችው፣ ተንከባከበችውም፤ ነገር ግን ንጉሡ ከእርስዋ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት አላደረገም። 5 በዚያን ጊዜ የአኒት ልጅ አዶንያስ “ንጉሥ እሆናለሁ” በማለት ራሱን ከፍ አደረገ። ስለዚህ በፊቱ የሚሮጡ ሃምሳ ፈረሰኞችንና ሠረገሎችን ለራሱ አዘጋጀ። 6 አባቱም ይህን ወይም ያንን ለምን ታደርጋለህ ብሎ ገስጾት አያውቅም ነበር። አዶንያስም ከአቤሴሎም በኋላ የተወለደ፣ እጅግ መልከ መልካም ነበር። 7 እርሱም ከጽሩያ ልጅ ከኢዮአብና ከካህኑ ከአብያታር ጋር አሤረ፤ እነርሱም አዶንያስን ተከትለው ረዱት። 8 ነገር ግን ካህኑ ሳዶቅ፣ የዮዳሄ ልጅ በናያስ፣ ነቢዩ ናታን፣ ሳሚ፣ ሬሲምና ዳዊትን የሚደግፉ ኃያላን አዶንያስን አልተከተሉትም። 9 አዶንያስም ዓይንሮጌል አቅራቢያ ባለው በዞሔሌት ድንጋይ ላይ በጎችን፣ በሬዎችንና የሰቡ ወይፈኖችን ሠዋ። እርሱም፣ የንጉሡን ልጆች ወንድሞቹን ሁሉ፣ የይሁዳን ሰዎች ሁሉና የንጉሡን አገልጋዮች ጋበዛቸው። 10 ነገር ግን ነቢዩ ናታንን፣ በናያስን፣ ኃያላን ሰዎችን፣ ወይም ወንድሙን ሰሎሞንን አልጋበዛቸውም። 11 ከዚያም ናታን፣ ለሰሎሞን እናት ለቤርሳቤህ እንዲህ ሲል ነገራት፦ “ጌታችን ዳዊት ሳያውቅ የአኒት ልጅ አዶንያስ መንገሡን አልሰማሽምን? 12 ስለዚህ የራስሽንና የልጅሽን የሰሎሞንን ሕይወት ለማትረፍ እንድትችዪ ልምከርሽ። 13 ወደ ንጉሥ ዳዊት ሂጂ፤ እንዲህም በዪው፣ “ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፣’ልጅሽ ሰሎሞን ከእኔ በኋላ ይነግሣል፣ በዙፋኔም ይቀመጣል’ ብለህ ለአገልጋይህ ምለህልኝ አልነበረምን? ታዲያ አዶንያስ የሚነግሠው ለምንድን ነው?”። 14 በዚያም ከንጉሡ ጋር በመነጋገር ላይ እያለሽ እኔም ካንቺ በኋላ እገባና የተናገርሽው ሁሉ እውነት መሆኑን አረጋግጣለሁ” አላት። 15 ስለዚህ ቤርሳቤህ ወደ ንጉሡ ክፍል ሄደች። ንጉሡ እጅግ ስለ ሸመገለ ሱነማይቱ አቢሳ ታገለግለው ነበር። 16 ቤርሳቤህም ራስዋን ዝቅ አድርጋ ለንጉሡ እጅ ነሣች፤ ንጉሡም፣ “ምን ትፈልጊያለሽ?” አላት። 17 እርሷም እንዲህ አለችው፤ “ጌታዬ ሆይ፣ ለአገልጋይህ፣ ‘በእርግጥ ልጅሽ ሰሎሞን ከእኔ በኋላ ይነግሣል፣ በዙፋኔም ይቀመጣል’ ብለህ በአምላክህ በጌታ እግዚአብሔር ስም ምለህ ነበር። 18 ይኸው አሁን አዶንያስ ነግሦአል፤ አንተም ጌታዬ ንጉሡ ይህንን አታውቅም። 19 ስለዚህ በሬዎችን፣ የሰቡ ኮርማዎችንና ብዙ በጎች ሠውቷል። ደግሞም የንገሡን ልጆች፣ ካህኑን አብያታርንና የሠራዊቱን አዛዥ ኢዮአብን ጋብዟቸዋል፤ አገልጋይህን ሰሎሞንን ግን አልጋበዘውም። 20 ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፣ የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ከአንተ ከጌታዬ በኋላ በዙፋንህ የሚቀመጠው ማን መሆኑን አንድታስታውቀው በመጠባበቅ ላይ ነው። 21 አለበለዚያ ግን ጌታዬ ንጉሡ ከአባቶቹ ጋር በሚያንቀላፋበት ጊዜ እኔና ልጄ ሰሎሞን እንደ ወንጀለኛ እንቆጠራለን። 22 እርስዋ ለንጉሡ በመናገር ላይ እያለች ነቢዩ ናታን ገባ። 23 አገልጋዮቹም ለንጉሡ፣ “ነቢዩ ናታን እዚህ ነው” ብለው ነገሩት። እርሱም ወደ ንጉሡ ፊት በቀረበ ጊዜ በግምባሩ ምድር ላይ በመደፋት ለንጉሡ ሰላምታ አቀረበ። 24 ናታንም፣ “ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፣ ‘አዶንያስ ከእኔ በኋላ ይነግሣል፣ በዙፋኔም ይቀመጣል’ ብለሃልን? 25 እርሱ ዛሬ ወርዶ ብዙ በሬዎችን፣ የሰቡ ጥጆችንና በጎችን ሠውቷል፤ ደግሞም የንጉሡን ልጆች ሁሉ፣ የሠራዊቱን አዛዥ ኢዮአብንና ካህኑን አብያታርን ጋብዟል። ንጉሥ አዶንያስ ለዘላለም ይኑር! በማለት በፊቱ በመብላትና በመጠጣት ላይ ናቸው። 26 ነገር ግን እኔን አገልጋይህን፣ ካህኑን ሳዶቅን፣ የዮዳሄን ልጅ በናያስንና አገልጋይህን ሰሎሞንን ወደ ግብዣው አልጠራንም። 27 ከአንተ በኋላ በዙፋንህ ላይ የሚቀመጠው ማን እንደሆነ ለእኛ ለአገልጋዮችህ ሳትነግረን ይህንን ያደረግኸው ጌታዬ ንጉሡ ነህን?” 28 ከዚያም ንጉሡ ዳዊት፣ “ቤርሳቤህን ጥሩልኝ” አለ። እርስዋም ንጉሡ ወዳለበት መጥታ በፊቱ ቆመች። 29 ንጉሡም ማለና፣ “ከደረሰብኝ መከራ ሁሉ የታደገኝ ጌታ እግዚአብሔር ሕያው የመሆኑን ያህል፤ 30 ‘ልጅሽ ሰሎሞን ከእኔ በኋላ ይነግሣል፣ በዙፋኔም ላይ በእኔ ቦታ ይቀመጣል’ ብዬ በእስራኤል አምላክ በጌታ እግዚአብሔር ስም የማልኩትን መሓላ ዛሬ እፈጽመዋለሁ” አላት። 31 ቤርሳቤህም ወደ መሬት በግንባሯ በመደፋት ለንጉሡ አክብሮቷን ካሳየች በኋላ፣ “ጌታዬ ንጉሡ ዳዊት ለዘለዓለም ይኑር!” አለች። 32 ንጉሥ ዳዊትም፣ “ካህኑን ሳዶቅን፣ ነቢዩን ናታንን እና የዮዳሄን ልጅ በናያስን ጥሩልኝ” አለ። እነርሱም በንጉሡ ፊት ቀረቡ። 33 ንጉሡም እንዲህ አላቸው፦ የጌታችሁን አገልጋዮች ከእናንተ ጋር ውሰዱ፤ ልጄን ሰሎምንንም እኔ በምቀመጥባት በቅሎ አስቀምጡትና ወደ ግዮን አውርዱት። 34 ካህኑ ሳዶቅና ነቡዩ ናታን ቀብተው በእስራኤል ላይ ያንግሡትና መለከት በመንፋት “ንጉሥ ሰለሞን ለዘላለም ይኑር!” በሉ። 35 ከዚያም ተከትላችሁት ትመጣላችሁ፣ እርሱም መጥቶ በዙፋኔ ላይ ይቀመጣል፤ በእኔ ምትክ ይነግሣልና። በእስራኤልና በይሁዳ ላይ እንዲገዛ ሾሜዋለሁ”። 36 የዮዳሄ ልጅ በናያስም ለንጉሡ እንዲህ ሲል መለሰ፦ “ይሁን! ይህንንም የጌታዬ የንጉሡ አምላክ ጌታ እግዚአብሔር ያጽናው። 37 ጌታ እግዚአብሔር ከጌታዬ ከንጉሡ ጋር እንደ ሆነ እንዲሁ ከሰሎሞን ጋር ይሁን፤ ዙፋኑንም ከጌታዬ ከንጉሥ ዳዊት ዙፋን የበለጠ ያድርገው” አለው። 38 ስለዚህ ካህኑ ሳዶቅ፣ ነቢዩ ናታን፣ የዮዳሄ ልጅ በናያስ፣ ከሊታውያንና ፈሊታውያን ወረዱ፤ ሰሎሞንን በንጉሥ ዳዊት በቅሎ ላይ በማስቀመጥ ወደ ግዮን አመጡት። 39 ካህኑ ሳዶቅ ዘይት ያለበትን ቀንድ ከድንኳን ወስዶ ሰሎሞንን ቀባው። በዚያን ጊዜ መለከት ነፉ፣ ሕዝቡም፣ “ንጉሥ ሰሎሞን ለዘላለም ይኑር!” አሉ። 40 ሕዝቡም ሁሉ ተከትሎት ወጣ፣ ሕዝቡም እምቢልታ እየነፉ በታላቅ ደስታ ደስ አላቸው፣ ከድምፃቸው የተነሣ ምድር ተንቀጠቀጠች። 41 አዶንያስና ከእርሱ ጋር የነበሩት እንግዶች ሁሉ ምግባቸውን እንደጨረሱ ይህንን ድምፅ ሰሙ። ኢዮአብ የእምቢልታውን ድምፅ በሰማ ጊዜ፣ “ይህ በከተማ ውስጥ የሚሰማው ሁካታ ምንድን ነው?” አለ። 42 እርሱ ገና በመናገር ላይ እያለ የካህኑ የአብያታር ልጅ ዮናታን መጣ። አዶንያስም፣ “ና ግባ፤ አንተ ጥሩ ሰው ስለሆንክ መልካም ዜና ይዘህ ሳትመጣ አትቀርም” አለው። 43 ዮናታንም ለአዶንያስ እንዲህ ሲል መለሰለት፦ “ጌታችን ንጉሥ ዳዊት ሰሎሞንን እንግሦታል፤ 44 ንጉሡም ከእርሱ ጋር ካህኑን ሳዶቅን፣ ነቢዩን ናታንን፣ የዮዳሄን ልጅ በናያስን፣ ከሊታውያንን እና ፈሊታውያንን ልኳል። እነርሱም ሰለሞንን በንጉሡ በቅሎ ላይ አስቀመጡት። 45 ካህኑ ሳዶቅና ነቢዩ ናታንም በግዮን ቀብተው አነገሡት፤ ደስ እያላቸውም ከዚያ ወጡ፣ በከተማው ሁካታ የሆነው ለዚህ ነው። የሰማችሁት ድምፅም ይኸው ነው። 46 ደግሞም ሰሎሞን በመንግሦቱ ዙፋን ላይ ተቀምጧል። 47 ከዚህም በላይ ከፍተኛ ሥልጣን ያላቸው ባለሟሎች ሁሉ ወደ ንጉሡ ዳዊት ቀርበው አምላክህ እግዚአብሔር ሰሎሞንን ከአንተ ይበልጥ ዝናውን ያግንነው፣ መንግሥቱንም ይበልጥ ታላቅ ያድርገው ሲሉ አክብሮታቸውን ገልጠዋል፤ ከዚህ በኋላ ንጉሥ ዳዊት በአልጋው ላይ ሳለ ለእግዚአብሔር ሰገደ። 48 ዛሬ ከእኔ ዘሮች መካከል አንዱ በእኔ እግር ተተክቶ እንዲነግሥ ያደረገና ይህን ለማየት ያበቃኝ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይክበር ሲል እግዚአብሔርን አመሰገነ። 49 አዶንያስ የጠራቸው ተጋባዦች ሁሉ ይህን በሰሙ ጊዜ እጅግ ፈሩ፤ ሁሉም ተነሡ፤ እያንዳንዱም በየፊናው ተበተነ፤ 50 አዶንያስም ሰሎሞንን ስለፈራ ወደ ተቀደሰው ድንኳን ሄዶ የመሠዊያውን ቀንዶች በመያዝ ተማጠነ። 51 ሰዎቹም ሰሎሞንን፣ አዶንያስ አንተን ከመፍራቱ የተነሣ የመሠዊያውን ቀንዶች ይዞ ከሁሉ በፊት ንጉሥ ሰሎሞን የማይገድለኝ መሆኑን በማረጋገጥ በመሐላ ቃል ይግባልኝ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በማለት እየተማጠነ ነው ሲሉ ነገሩት። **52** ንጉሥ ሰሎሞንም መልካም ሰው ከሆነ ከራስ ጠጉሩ አንዲት እንኳን አትነካበትም፤ ክፉ ሆኖ ከተገኘ ግን ይሞታል ሲል መለሰ። **53** ከዚህ በኋላ ንጉሥ ሰሎሞን አዶንያስን ከመሠዊያው አውርደው ያመጡት ዘንድ መልእክተኞችን ላከ፤ አዶንያስ ወደ ንጉሡ ፊት በመቅረብ ወደ መሬት ራሱን ዝቅ አድርጎ እጅ ነሣ፤ ንጉሡም ወደ ቤትህ ሂድ አለው።

---

1 Kings 1:1

ልብስም ደረቡለት
እንዲሞቀውም ለንጉስ ዳዊት ብዙ ልብስ ደረቡለት

ሸመገለ እድሜው በዛ
“በጣም ያረጀ” ሁለቱ ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው የተጣመሩትም አፅንኦት ለመስጠት ነው።

1 Kings 1:3

ፈለጉ
“የንጉሡም አገልጋዮች ፈለጉ”

በእስራኤልም አገር ሁሉ
ይህ በጥቅሉ ነው። ተርጓሚ “በእስራኤል ምድር ሁሉ”

አቢሳ
ይህ የሴት ስም ነው

ሱናማይት
ከ ሱናም ከተማ የሆነ ግለሰብ

ንጉሡ
“ንጉሥ ዳዊት”

1 Kings 1:5

የአጊትም ልጅ አዶንያስ
አጊት የዳዊት ሚስት ነበረች

እሆናለሁ ብሎ ተነሳ
“መኩራራት ጀመረ”

ፈረሰኞች
እነዚህ በፈረስ የሚጎተት ሰረገላ የሚነዱ(የሚጋልቡ) ናቸው።

በፊቱም የሚሮጡ ሃምሳ ሰዎች
እነዚህ ሰዎች መንገድ ለመጥረግና (ለማቅናትና) ለጥበቃ ከሰረገሎች ፊት የሚሄዱ ናቸው።

----------ብሎ አልተቆጣውም
“አልተቆጣውም”። “ጠይቆትም አያውቅም” ወይም “ሊያናድደውም አልፈለገምና አልጠየቀውምም”

እንዲህ ለምን ታደርጋለህ?
ይህ አባት ልጁን ለመገሠፅ የሚሆን የግነት ጥያቄ ነው። ተርጓሚ “የሠራኸው ሥህተት እንደሆነ ማወቅ አለብህ።” (የግነት ጥያቄ ተመልከት)

ከአቤሴሎም በኋላ ተወልዶ ነበር
ዳዊት የሁለቱም የአቤሴሎምና የአደንያስ አባት ሲሆን ነገር ግን በእናት ይለያያሉ። አቤሴሎም ተወለደ ከዚያም አዶኒያስ

1 Kings 1:7

ሴራውም.....ከኢዮአብ ጋር ነበር
“አዶኒያስ እቅዱን ከኢዮአብ ጋር ተማከረ”

እዮአብ.....ፅሩያ.....አብያታ.....አዶንያስ.....ሳደቅ.....በናያስ....የዳሄ.....ናታን ....ሳሚ....ሬሰ
እነዚህ የሰዎች (ወንዶች) ሥም ናቸው

አዶንያስን ተከትለው ይረዱት ነበር
“አዶንስን ደገፉትም ረዱትም” ወይም “ለመርዳት ቃል ገቡና አዳንያስን ረዱት”

1 Kings 1:9

ፍሪዳዎች
“እንዲሠቡ ብዙ ቀለብ የተሠጣቸው ወይፈኖች” ወይም “ለመሥዋትነት የተዘጋጁ የተለዩ ጥጆዎች”

በዞሔሌት ድንጋይ
ይህ በእየሩሳሌም አቅራቢያ የሚገኝ አለታማ ሥፍራ ነው።

ዓይንሮጌል
ይህ ሰዎች ውሃ የሚያገኙበት የምንጭ ሥም ነው።

ወንድሞቹን ሁሉ .....ሰዎች ሁሉ
ይህ ጥቅል (በአንድ ላይ) ነው።

ወንድሞቹ ሁሉ...የንጉሥንም ልጆች
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሣሣይ ሠዎችን ይገልፃሉ።

የንጉሥንም በሪያዎች የይሁዳ ሰዎች
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሣሣይ ሠዎችን ይገልፃሉ።

1 Kings 1:11

አልሰማሽም?
የዚህ ጥያቄ አላማ ናታን ለቤርሳቤህ ሊነግራት የፈለገውን መረጃ መግቢያ ነው። ተርጓሚ “የሰማሽ አትመስይም” ወይም “ሰምተሻል?” (የግነት ጥያቄ ተመልከት)

የአጊት ልጅ አዶንያስ እንደነገሠ
“የአጊት ልጅ አዶንያስ ንጉሥ ለመሆን እየሞከረ መሆኑን”

አጊት
የአዶንያስ እናት የዳዊት ሚስት

1 Kings 1:13

አጠቃላይ መረጃ
ነብዩ ናታን ለቤርሳቤህ መናገሩን ቀጥሎአል

ለባሪያህ .....በዙፋኔም .....አልማልህልኝምን?
የዚህ ጥያቄ አላማ ዳዊት ለቤርሳቤህ ቃል የገባውን ለማስታወስ ነው። ተርጓሚ “ለባሪያህ በዙፋኔ ምለሀል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለባሪያህ
ለዳዊት ያላትን ከበሬታ ለማሣየት ቤርሣቤህ ልክ እንደሌላ ሠው ሆና ዳዊትን ታናግራዋለች ተርጓሚ “ለእኔ ለባሪያህ”

በዙፋኔም ይቀመጣል
በዙፋን ላይ መቀመጥ ንጉሥ ለመሆን ዘይቤአዊ ንግግር ነው። (ዘይቤአዊ ተመልከት)

ስለ ምንስ አዶንያስ ይነግሣል?
ዳዊት አትኩሮት እንዲሠጥ ቤርሣቤህ ጥያቄ መጠቀሟ ነው። ተርጓሚ “ስለዚህ አዶንያስ መንገስ የለበትም”

ቃልሽንም አፀናለሁ
“የተናገርሽው እውነት መሆኑን ንገሪው”

1 Kings 1:15

ወደ ንጉሡ ወደ እልፍኝ
“ንጉሡ ወደ ተኛበት ክፍል

ሱናማይቱም አቢሳ
ይህቺ እንድትንከባከበው ያሳደጋት ወጣት ልጃ-ገረድ የንጉሥ ዳዊት አገልጋይ ነች። የ1 ነገሥት 1:3 ትርጉም ተመልከት

አጎንብሳ ለንጉሡ እጅ ነሣች
በንጉሡ ፊት ዝቅ ብላ ወደ መሬት አጎነበሰች

ምን ትፈልጊያለሽ?
“ምን ላደርግልሽ እችላለሁ?

ምለህለኛል
“አንተ ራስህ ምለህልኛል”

ለባሪያህ
ለዳዊት ያላትን ከበሬታ ለማሣየት ቤርሣቤህ ልክ እንደሌላ ሰው ሆና ዳዊትን ታናግረዋለች ተርጓሚ “እኔ ባሪያህ”

እግዚአብሔር (ያህዌ)
ይህ በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር ለህዝቡ የተገለጠበት ስም ነው።

በዙፋኔም ይቀመጣል
በዙፋን ላይ መቀመጥ ንጉሥ የመሆን ዘይቤአዊ ንግግር ነው። የ1 ነገሥት 1:3 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ “ልክ እኔ እንደነበርኩ ንጉሥ ይሆናል”።

1 Kings 1:18

አጠቃላይ መረጃ
ቤርሣቤህ ለንጉሥ ዳዊት መናገርዋን ቀጥላለች

እነሆ
“ተመልከት” ወይም “አድምጥ” ወይም “ለምነግርህ ነገር ትኩረት ስጥ”

ብዙ በሬዎች፤ ፍሪዳዎች ፤ በጎችንም
“ብዙ በሬዎች፤ፍሪዳዎችና በጎች”

1 Kings 1:20

አጠቃላይ መረጃ
ቤርሣቤህ ለንጉሥ ዳዊት መናገርዋን ቀጥላለች

የእስራኤል አይን ሁሉ ይመለከትሃል
እዚህ ጋር “አይን” ህዝቡን ይገልፃል። እዚህ ጋር “አይን ሁሉ ይመለከትሃል” ፈሊጣዊ ሲሆን ህዝብ በጉጉት ይጠብቁሃል ለማለት ነው። ተርጓሚ “የእስራኤል ህዝብ ሁሉ በጉጉት ይጠብቁሃል”

ዙፋን ላይ የሚቀመጠውን
ዙፋን ላይ መቀመጥ ንጉሥ የመሆን ዘይቤአዊ ንግግር ነው። የ1 ነገሥት 1፡3 ትርጉም ተመልከት ተርጓሚ “ንጉሥ ይሆናል”

ጌታዬ ከአባቶችህ ጋር ባንቀላፋህ ጊዜ
ለዳዊት ያላትን ከበሬታ ለማሣየት ቤርሣቤህ ልክ እንደሌላ ሠው ሆና ዳዊትን ታናግረዋለች። ተርጓሚ “ከአባቶችህ ጋር ስታንቀላፋ”

ከአባቶችህ ጋር ባንቀላፋህ
ይህ “ሞት” በትህትና ሲገለፅ ነው።

እኔና ልጄ ሰለሞን እንደ ኃጥአተኞች እንቆጠራለን
ይህ በገቢር መልኩ ሊገለፅ ይችላል። ተርጓሚ አዲሱ ንጉሥ ልጄ ሰለሞንና እኔን እንደ ኃጢአተኛ ይቆጥረናል።

1 Kings 1:22

አጠቃላይ መረጃ
ነብዩ ናታን ለንጉሥ ዳዊት ተናገረ

በግምባሩ..... ተደፍቶ
“በጣም አጎንብሶ”

1 Kings 1:24

አጠቃላይ መረጃ
ነብዩ ናታን ለንጉሥ ዳዊት መናገሩን ቀጥሏል።

ከእኔ በኋላ አዶኒያስ ይነግሣል በዙፋኔም ላይ ይቀመጣል ብለሃልን?
ይህ በተዘዋዋሪ (ቀጥተኛ ባልሆነ) ጥቅስ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ ከአንተ በኋላ አዶኒያስ እንደሚነግሥ በዙፋንህም ላይም እንደሚቀመጥ ተናግረሃልን?

በዙፋኔም ላይ ይቀመጣል
ዙፋን ላይ መቀመጥ ንጉሥ የመሆን ዘይቤአዊ ንግግር ነው። የመክብበ 1 1፡13 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ “እርሱም እንደኔ ንጉስ ይሆናል።

በፊቱ እየበሉና እየጠጡ
ምናልባት አዶኒያስ በጋበዛቸው ሰዎች ጠረጴዛ ላይ ተቀምጦ ሲመገቡና ሲጠጡ ይመለከታቸው ነበር። ዋናው ሃሳብ ዮናታን የጠቀሳቸው ሰዎች ከአዶኒያስ ጋር ሆነው በዓል ሲያደርጉ ነበር። ተርጓሚ “ከእርሱ ጋር መብላትና መጠጣት” ወይም “እርሱ በሚያያቸው ቦታ ላይ ሆነው መብላትና መጠጣት”

1 Kings 1:26

አጠቃላይ መረጃ
ነብዩ ናታን ለንጉሥ ዳዊት መናገሩን ቀጥሏል

በውኑ ይህ ነገር ከጌታዬ ከንጉሥ የተደረገ ነውን? ለባሪያህም ከአንተ በኋላ በጌታዬ በንጉሱ ዙፋን ላይ የሚቀመጠውን አልነገርህምን?
ናታን ዳዊትን በሦስተኛ ወገን ይወክላል ይህ ለንጉሡ ያለውን ከበሬታ ማሣያ መንገድ ነው። በሁለተኛ ወገን ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “አንተ በጌታዬ በንጉሡ ዙፋን ላይ የሚቀመጠው ማን እንደሆነ ለባሪያህ አልነገርህምን?”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Kings 1:28

አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ዳዊት ለቤርሣቤህ ቃል ማሃላ አደረገ (ማለ)

ወደ ንጉሡም ገባች በንጉሡ ፊት ቆመች
“በንጉሥ ፊት ቆመች” ወይም “ወደ ንጉሡ ተመለሠች”

እንደ ማልሁልሽ
ቃል ገባ

በእኔም ፋንታ በዙፋኔ ላይ ይቀመጣል
በዙፋን ላይ መቀመጥ ንጉሥ የመሆን ዘይቤአዊ ንግግር ነው። የ1 ነገሥት 1:13 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ “በእኔም ቦታ ይሆናል እንደ እኔም ንጉሥ ይሆናል።”

ጌታዬ ንጉሥ ዳዊት ለዘላለም በሕይወት ይኑር
ቤርሣቤህ ዳዊት ለዘላለም እንደማይኖር ታውቃለች። ይህ መልካም ንጉሥ መሆኑን ማሳያ ነው።

1 Kings 1:32

የጌታችሁን ባሪያዎች
ናታን፤ ዮዳሄና በናያስ አሁንም ዳዊት ንጉሥ እንደሆነ እንዲያስታውሱ ዳዊት ስለሌላ ሠው የሚናገር በማስመሠል ስለ ራሱ ይናገራል። ተርጓሚ “ባሪያዎቼ”

ግዮን
ይህ የውሃ ምንጭ ሥም ነው።

1 Kings 1:35

አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ዳዊት በሠለሞን ቦታ ሆኖ ንጉሥ ስለ ሚሆነው መናገሩን ቀጥሏል።

እርሱም መጥቶ በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ
“በዙፋን ላይ ይቀመጥ” የሚሉት ቃላት ንጉስ የመሆን ዘይቤ ናቸው። ነ1 ነገሥት 1:13 1:17 እና 1:30 እዚህ ጋር ዳዊት በቀጥታ ሰለሞን በእርሱ ዙፋን ላይ እንደሚቀመጥ ይናገራል።

ይሆን ዘንድ
ተስማምተውም ንጉሥ ዳዊት ያለውን ያደርጋሉ።

የጌታዬም የንጉሥ አምላክ ይህን ይናገር
በናያስ ለዳዊት ያለውን አክብሮት ለማሣየት ለሌላ ሠው የሚናገር በማስመሰል ለዳዊት ይናገራል። ተርጓሚ “ጌታዬ ንጉሡ…….. ከአንተጋ እንደነበር”

ዙፋኑንም ከጌታዬ ከንጉሥ ዳዊት ዙፋን የበለጠ ያድርግ
“ዙፋን” የሚለው ቃል 1) ዙፋን ላይ የሚቀመጠው ሰው ተርጓሚ ዙፋኑ ላይ የሚቀመጠውን ሰው ከጌታዬ ከንጉሡ ዳዊት የበለጠ ያደርጋል ወይም 2) በዙፋኑ ላይ ከሚቀመጠው መንግስት የበለጠ ተርጓሚ “መንግሥቱን ከጌታዬ ከንጉሥ ዳዊት መንግስት የበለጠ ገናና ያደርጋል።”

1 Kings 1:38

አጠቃላይ መረጃ
የእስራኤል ህዝብ ሠለሞንን ንጉሥ አድርገው በእስራኤል ላይ ሾሙት

ከሊታውያንና ፈሊታውያን
እነዚህ የሰዎች ስብስብ ሥሞች ናቸው

ግዮን
ይህ ንፁህ ውሃ ከምድር የሚፈልቅበት የምንጭ ስም ነው።

ከድንኳኑ የቅብዓቱን ቀንድ ወሰደ
ይህ በተለየ የእንስሳ ቀንድ የተቀመጠን የወይራ ዘይት ከተቀመጠበት ከእግዚአብሔር ድንኳን ካህኑ ሲወስድ ማለት ነው።

የቅብዓቱን ቀንድ ወስዶ
አማራጭ ትርጉሞች 1) በወይራ ዘይት የተሞላ የእንስሳ ቀንድ 2) እውነተኛውን ቀንድ የሚተካ ነገር ግን ሠዎች አሁንም ቀንድ ብለው የሚጠሩት። ተርጓሚ “የዘይት ማስቀመጫውን ወስዶ”

ሕዝቡም ሁሉ
ይህ በጥቅል ነው

1 Kings 1:41

አጠቃላይ መረጃ
አዶንያስ ታላቅ ጩኸት ሰማ ወሬውን (ዜናውን) እየጠበቀ ነው።

1 Kings 1:43

አጠቃላይ መረጃ
አዶኒያስ ሰለሞን ንጉስ እንደሆነ አወቀ

1 Kings 1:46

አጠቃላይ መረጃ
ዮናታን ሥለ ሰለሞን ለአዶንያስ መናገሩን ቀጥሏል።

በመንግስቱ ዙፋን ላይ ተቀምጦአል
አማራጭ ትርጉሞች 1) እነዚህ ቃላት ንጉስ የመሆን ዘይቤአዊ ንግግሮች መሆናቸውን የ1 ነገስት 1:35 ተመሣሣይ ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ: አሁን ንጉስ ነው። ወይም 2) ሰለሞን በአካል በዙፋን ላይ ተቀምጦ ነበር።

ዛሬ በዙፋኔ ላይ የሚቀመጠውን
አማራጭ ትርጉሞች 1) እነዚህ ቃላት ንጉሥ የመሆን ዘይቤአዊ ንግግሮች መሆናቸውን። የ 1ነገስት 1:35 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ “ዛሬ እንደ እኔ ንጉሥ ሊሆን ያለ” ወይም 2) ሰለሞን በአካል በዙፋን ላይ ተቀምጦ ነበር።

1 Kings 1:49

አጠቃላይ መረጃ
አዶንያስ ንጉሥ ሰለሞንን ፈራ

ተነሥተውም
ሌላ አማራጭ ትርጉም “ፈጥነው እርምጃ መውሰድ ጀመሩ” ነው።

አዶንያስም---- የመሠዊያውን ቀንድ ይዞአል
የመሠዊያው ቀንድ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ኃይልና ጥበቃ ነው። ነገር ግን አዶንያስ በትክክል ድንኳኑ ወዳለበት ቦታ ሄደ ትክክለኛውን ቀንድ ለማንሳት ስለሄደ በዚሁ መልኩ መተርጎም አለብህ/ሽ።

አዶንያስም------ተነስቶ ሄደ
ሌላ አማራጭ ትርጉም “አዶንያስ-----ፈጥኖ ሄደ” ነው።

ሰለሞንን ፈራ
ባሪያው ለንጉስ ሰለሞን ያለውን ከበሬታ ለማሳየት እንደ ሌላ ሰው አድርጎ ንጉሥ ሰለሞንን ያናግረዋል። ተርጓሚ “ፈርቶሃል፤ንጉሥ ሰለሞን”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ባሪያውን-----እንዳይገለጥ
አዶንያስ ለንጉሥ ሰለሞን ያለውን ከበሬታ ሌሎች እንዲያውቁ ንጉስ ሰለሞንን እንደሌላ ሠው ያናግረዋል። ተርጓሚ “እርሱ አይገድለኝም”

1 Kings 1:52

አጠቃላይ መረጃ
ሰለሞን የአዶንያስን ነፍስ አዳነ

ከእርሱ አንዲት ጠጉር እንኳ በምድር ላይ አትወድቅም
ይህ ሰለሞን አዶንያስን እንደሚያድነው የግነት ንግግር ነው። ተርጓሚ “በራሱ ጠጉር አንዳችም አትወድቅም ” ወይም “እኔ አድነዋለው”

እርሱ--- ክፋት የተገኘበት
“ክፋት” የሚለው ስውር ስም እንደ ግስ ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። በማስቀመጫ ውስጥ እንደተቀመጠ ዕቃ ሆኖ ተመስሎአል። ይህ በገቢር መልክ ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ “ክፉ የሆነ ነገርን አደረገ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 ዳዊት የሚሞትበት ቀን በተቃረበ ጊዜ ልጁን ሰሎሞንን ጠርቶ እንዲህ ሲል አዘዘው፤ 2 እነሆ እኔ ሰው ሁሉ እንደሚሞት የምሞትበት ጊዜ ተቃርቦአል፤
እንግዲህ በርታ ቆራጥ ሰው ሁን። 3 አምላክህ እግዚአብሔር እንድታደርግ የሚያዝህን ሁሉ አድርግ፣ በምትሄድበት ስፍራ ሁሉ የምታደርገው ማናቸውም ነገር
እንዲከናወንልህ በሙሴ አማካይነት በተሰጠው ሕግ የተጻፉትን የእግዚአብሔርን ሕግ ትእዛዝ፣ ሥርዓትና ፈቃድ ሁሉ ጠብቅ። 4 በዚህ ሁሉ ታዛዥ ሆነው ቢኖሩ
በፍጹም ልባቸውና በፍጹም ነፍሳቸው በፊቴ በቅንነት ቢመላለሱ በእስራኤል ዙፋን ላይ ነግሦ የሚገዛ ዘር አላሳጣህም ብሎ የነገረኝን የተስፋ ቃል ይፈጽማል።
5 የጽሩያ ልጅ ኢዮአብ በእኔና የእስራኤል ሕዝብ የጦር መሪዎች በነበሩት በሁለቱ፣ በኔር ልጅ በአበኔርና በዬቴር ልጅ በአሜሳይ ላይ ያደረገውን ታውቃለህ፤ ሁለቱ
በጦርነት ጊዜ ላፈሰሱት ደም ተበቅሎ በሰላም ጊዜ እነርሱን በመግደል የወገቡን ቀበቶና የእግሩን ጫማ በደም በከለ። 6 እንግዲህ ባለህ ጥበብ በኢዮአብ ላይ
ልትፈጸምበት የሚገባውን አድርግ፤ ዕድሜ ጠግቦ በሰላም እንዲሞት አትፍቀድለት። 7 ይሁን እንጂ የገለዓዳዊው የቤርዜሊ ልጆች ከወንድምህ ከአቤሴሎም
ፊት በሸሸሁ ጊዜ ወደ እኔ መጥተው የቸርነት ሥራ ስላደረጉልኝ፣ መልካም አድርግላቸው፤ በማዕድህም ከሚመገቡ መካከል ይሁኑ። 8 ከዚህም ጋር መረሳት
የሌለበት የብንያም ክፍል በሆነችው በባሑሪም ከተማ ውስት የሚኖረው የጌራ ልጅ ሳሚ ወደ መሃናይም በሄድኩበት ቀን በእኔ ላይ የስደብ ውርጅብኝ
አውርዶብኛል፤ ይሁን እንጂ በዮርዳኖስ ወንዝ አጠገብ ባገኘኝ ጊዜ እንደማላስገድለው በእግዚአብሔር ስም ምየለታለሁ። 9 ስለዚህ አንተ እርሱንም ከቅጣት ነጻ
አታድርገው። አንተ ጥበበኛ ሰው ስለሆንህ ምን መደረግ እንዳለበት ታውቃለህ። በሽመገለም ጊዜ በሞት ትቀጣዋለህ። 10 ከዚያም ዳዊት ከአባቶቹ ጋር
አንቀላፋ፤ በዳዊትም ከተማ ተቀበረ። 11 ዳዊት በኬብሮን ሰባት ዓመት፣ በኢየሩሳሌም ሠላሳ ሦስት ዓመት፣ በድምሩ አርባ ዓመት በእስራኤል ላይ ነገሠ። 12
ሰሎሞንም በአባቱ ዙፋን ተተክቶ ነገሠ፤ የመንግሥቱም ሥልጣን እጅግ የጸና ሆነ። 13 የአኒት ልጅ አዶንያስ ወደ ሰሎሞን እናት ወደ ቤርሳቤህ መጣ።
ቤርሳቤህም ወደ እኔ የመጣኸው በሰላም ነውን? ስትል ጠየቀችው፤ እርሱም አዎን በሰላም ነው ሲል መለሰላት። 14 ቀጠል አድርጎም እኔ የምጠይቅሽ ጉዳይ
አለኝ አላት። እርስዋም ጉዳይህን ተናገር አለችው። 15 አዶንያስም እንዲህ አላት፣ ንጉሥ መሆን የሚገባኝ እኔ እንደ ነበርኩና ይህንንም የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ
በተስፋ ይጠባበቅ እንደ ነበር አንቺ ታውቂያለሽ። ነገር ግን ጉዳዩ ከእግዚአብሔር ስለ ተወሰነ ነገሩ ተለውጦ መንግሥቱ ለወንድሜ ተሰጥቶአል። 16 አሁንም
የምጠይቅሽ አንድ ጉዳይ ስላለኝ እምቢ በማለት አታሳፍሪኝ። ቤርሳቤህም ጉዳይህን ተናገር አለችው። 17 እርሱም እንዲህ አላት፦ ንጉሥ ሰሎሞን አንቺን እምቢ
እንደማይልሽ አውቃለሁ፤ ስለዚህ አቢሳ ተብላ የምትጠራውን ሱነማይት ልጃገረድ ሚስት ትሆነኝ ዘንድ እንዲሰጠኝ እባክሽ አማልጅኝ አላት። 18 እርስዋም
መልካም ነው፤ ይህን ለንጉሡ እነግርልሃለሁ አለችው። 19 ስለዚህ ቤርሳቤህ የአዶንያስን ጉዳይ ልትነግረው ወደ ንጉሡ ገባች። ንጉሡም ከተቀመጠበት
ተነሥቶ እናቱን እጅ በመንሣት ተቀበላት። እርሱም በዙፋኑ ላይ ከተቀመጠ በኋላ ሌላ ዙፋን አስመጥቶ በቀኙ አስቀመጣት። 20 እርስዋም እንድትፈጽምልኝ
የምጠይቅህ አንድ ትንሽ ጉዳይ አለኝ፣ እባክህ እምቢ በማለት አታሳፍረኝ አለችው። ንጉሡም እናቴ ሆይ አላሳፍርሽምና ጠይቂኝ አላት። 21 እርስዋም ወንድምህ
አዶንያስ አቢሳን እንዲያገባት ፍቀድለት አለችው። 22 ንጉሡም አቢሳን ለሚስትነት እንድሰጠው ብቻ ለምን ትጠይቂኛሽ? መንግሥቴንም ጭምር እንድለቅለት
ለምን አልጠየቅሽኝም? እርሱ ታላቅ ወንድሜ ነው፤ ለምንስ ለካህኑ አብያታርና ለኢዮአብም ልዩ አስተያየት እንዳደርግላቸው አትጠይቂላቸውም? አላት። 23
ከዚህ በኋላ ሰሎሞን፣ በእግዚአብሔር ስም እንዲህ ሲል ማለ፦ አዶንያስ ይህን በመናገሩ በሕይወቱ እንዲከፍል ባላደርግ እግዚአብሔር ይፍረድብኝ፤
በበለጠም ይቅጣኝ አለ። 24 እግዚአብሔር በአባቴ በዳዊት ዙፋን ላይ አስቀምጦኝ መንግሥቴን የጸና አድጎልኛል፤ ይህን መንግሥት ለእኔና ለዘሮቼ በመስጠት
ቃሉን ጠብቆአል፤ እንግዲህ አዶንያስ በዚህ በዛሬው ቀን በሞት እንደሚቀጣ በሕያው እግዚአብሔር ስም እምላለሁ። 25 ስለዚህ አዶንያስን እንዲገድለው ንጉሥ
ሰሎሞን ለዮዳሄ ልጅ ለበናያስ ትእዛዝ አስተላለፈ፤ በናያስም ሄዶ አዶንያስን ገደለው። 26 ከዚህ በኋላ ንጉሥ ሰሎሞን ካህኑን አብያታርን እንዲህ አለው፦
በአናቶት ወዳለው እርሻህ ሂድ፤ አንተ በሞት ልትቀጣ ይገባህ ነበር፣ ነገር ግን የልዑል እግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦት በአባቴ በዳዊት ፊት ስለተሸከምህ፣
ከእርሱም ጋር የመከራው ሁሉ ተካፋይ ስለ ነበርክ እኔ አሁን አልገድልህም። 27 ከዚህ በኋላ ሰሎሞን አብያታርን የእግዚአብሔር ካህን ሆኖ ከሚያገለግልበት
የክህነት ሥልጣን ሸሮ አባረረው፤ በዚህም ዓይነት እግዚአብሔር በሴሎ ስለ ካህኑ ዓሊ፣ ስለ ትውልዱ የተናገረው ቃል ተፈጸመ። 28 የአቤሴሎም ደጋፊ
ባይሆንም የአዶንያስ ደጋፊ የነበረው ኢዮአብ፣ ይህን የተፈጸመውን ነገር ሁሉ ሰማ፤ ስለዚህም ሸሽቶ ወደ ጌታ እግዚአብሔር ድንኳን ሄደ፤ በዚያም የመሠዊያውን
ቀንዶች ይዞ ተማጠነ። 29 ኢዮአብ ወደ ጌታ እግዚአብሔር ድንኳን ሸሽቶ መሄዱንና በመሠዊያው አጠገብ መገኘቱን ሰሎሞን በሰማ ጊዜ ኢዮአብን
እንዲገድለው ለበናያስ ትእዛዝ አስተላለፈ። 30 እርሱም ወደ ጌታ እግዚአብሔር ድንኳን ሄዶ ኢዮአብን ከዚህ ድንኳን እንድትወጣ ንጉሡ አዞሃል አለው። ኢዮአብ
ግን፣ አልወጣም እዚሁ እሞታለሁ አለ። በናያስም ተመልሶ ኢዮአብ ያለውን ለንጉሡ ነገረው። 31 ሰሎሞን በናያስን እንዲህ አለው፦ ኢዮአብ እንዳለህ ግደለውና
ቅበረው፤ በዚህ ሁኔታ ኢዮአብ ካፈሰሰው ንጹሕ ደም የእኔንና የአባቴን ቤት የነጻን ታደርገናለህ። 32 አባቴ ዳዊት ሳያውቅ ኢዮአብ ስለ ገደላቸው ስለ እነዚያ ሁለት
ሰዎች ደም እግዚአብሔር ኢዮአብን ይቀጣዋል፤ ኢዮአብ ከእርሱ የተሻሉትን ሁለት ንጹሓን ሰዎች ገድሎአል፤ እነርሱም የአስራኤል ጦር አዛዥ አበኔርና የይሁዳ
ጦር አዛዥ አሜሳይ ነበሩ። 33 ኢዮአብ እነዚህን ሰዎች በመግደሉ ደማቸው በእርሱና በዘሮቹ ለዘለዓለም ይመለስባቸው። ነገር ግን ለዳዊትና ለዘሮቹ፣ ለቤቱና
በዙፋኑ ለሚቀመጡት የእግዚአብሔር ሰላም ለዘለዓለም ጸንቶ ይኑር። 34 ስዚህ በናያስ በታዘዘው መሠረት ኢዮአብን ገደለው፤ በቤቱም አጠገብ በሚገኘው
በረሓ ተቀበረ። 35 ንጉሥ ሰሎሞን በኢዮአብ ፈንታ በናያስን የሠራዊት አዛዥ፣ በአብያታርም ፈንታ ሳዶቅን ካህን አድርጎ ሾማቸው። 36 ከዚህ በኋላ ንጉሥ
ሰሎሞን ሳሚን አስጠርቶ እንዲህ ሲል አዘዘው፦ በዚህ በኢየሩሳሌም የራስህን መኖሪያ ቤት ሠርተህ ተቀመጥ፤ ከዚያ የትም እንዳትሄድ፤ 37 ከከተማይቱ
ወጥተህ የቄድሮንን ወንዝ ተሻግረህ ብትገኝ በእርግጥ ትሞታለህ፤ ለደምህም ተጠያቂው ራስህ ነህ። 38 ሳሚም ንጉሥ ሆይ፣ ውሳኔህ መልካም ነው።
አገልጋይህ አንተ ጌታዬ እንዳልከው አደርጋለሁ ሲል መለሰ። ስለዚህ በኢየሩሳሌም ብዙ ጊዜ ተቀመጠ። 39 ከሦስት ዓመት በኋላ ግን ሁለቱ የሳሚ አገልጋዮች
የመዓካ ልጅ ወደ ሆነው አንኩስ ተብሎ ወደሚጠራው ወደ ጌት ንጉሥ ኮብልለው ሄዱ፤ ሳሚም ባሪያዎቹ በጌት መኖራቸው ተነገረው። 40 ሳሚም አህያውን
ጭኖ እነርሱን ለመፈለግ በጌት ወደሚኖረው ወደ ንጉሥ አንኩስ ሄደ፤ እነርሱንም በዚያ ስላገኛቸው ወደ ቤት መልሶ አመጣቸው። 41 ንጉሥ ሰሎሞን ሳሚ
ከኢየሩሳም ወደ ጌት ሄዶ መመለሱን ሰማ። 42 ንጉሡም ሳሚን አስጠርቶ ከኢየሩሳሌም እንዳትወጣ በእግዚአብሔር ስም አስምዬህ አልነበረምን? ወጥተህ
ብትገኝ ግን በእርግጥ እንደምትሞት አስታውቄህ አልነበረምን? በዚህስ ተስማምተህ ትእዛዜን እንደምትፈጽም ቃል ገብተህልኝ አልነበረምን? አለው። 43
ታዲያ በእግዚአብሔር ስም ከማልህ በኋላ ትእዛዜንስ ስለምን አላከበርክም? 44 በአባቴ በንጉሥ ዳዊት ላይ የፈጸምከውን በደል ሁሉ በሚገባ ታውቃለህ፤ አንተ
ስላደረግኸው ክፉ ነገር እግዚአብሔር ራሱ ይቀጣሃል። 45 እኔን ግን እግዚአብሔር ይባርከኛል፤ የዳዊት መንግሥትም ለዘለዓለም ጸንቶ ይኖራል። 46 ከዚህም
በኋላ ለዮዳሄ ልጅ ለበናያስ ሳሚን እንዲገድል ትእዛዝ አስተላለፈ፤ በናያስም ሄዶ ሳሚን ገደለው፤ በዚህም ዓይነት መንግሥቱ በሰሎሞን እጅ የጸና ሆነ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Kings 2:1

እኔ የምድሩን ሁሉ መንገድ እሄዳለሁ
ይህ “እኔ እሞታለሁ” ብሎ የመናገር የትህትና ንግግር ነው።

ሰውም ሁን
የጎደለው ሊሞላ ይችላል። ተርጓሚው “ሰው መሆንህን ለሁሉም አሣይ” ወይም “መልካም ሰው መሆንህን ሁሉም ያስተውል ዘንድ ኑር”

በመንገዱም ትሄድ ዘንድ
በመንገድ መሄድ የሰው የሕይወት አኗኗሩ ዘይቤአዊ ንግግር ነው። ተርጓሚ “ እርሱ እንዳዘዘ ኑሩ”

በመንገዱም ትሄድ ዘንድ
“ይከናወንልህ ዘንድ” ወይም “መልካም ይሆንልህ ዘንድ”

የተናገውን ቃል ያፀና ዘንድ ነው
“ሊያደርግ ቃል የገባውን ያደርጋልና”

ልጆችህ---አይቆረጥብህም
እግዚአብሄር ለዳዊት ሲናገር “አንተ” እና “የአንተ” በማለት ነው።

በፊቴ በእውነት ----ቢሄዱ
እግዚአብሄር ለዳዊት ይናገራል ስለዚህ “በፊቴ” የሚለው ቃል እግዚአብሄርን ይወክላል።

በፍፁም ልባቸውና በፍፁም ነፍሳቸው
በፍፁም ልባቸው የሚለው ፈሊጣዊ ንግግር “ፈፅሞ” ማለት ሲሆን በፍፁም ነፍሳቸው የሚለው ደግሞ “በሙሉ ማንነት” ማለት ነው። እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው። ተርጓሚ “በሁለንተናቸው” ወይም “በሙሉ ኃይላቸው”

ከእስራኤል ዙፋን ሰው አይቆረጥብህም
“ዙፋን” የሚለው ቃል በዙፋን ላይ ለሚቀመጠው ንጉሥ ዘይቤ ነው። ምፀቱ “አይቋረጥብህም” በቀና መልኩ በዚህ መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ “ዘርህ የእስራኤል ንጉሥ ከመሆን አይቋረጥም” ወይም “ከዘር ሐረግህ አንዱ ሁልጊዜ የእስራኤል ንጉሥ ይሆናል”

1 Kings 2:5

አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ዳዊት ለሰለሞን እንዴት እስራኤልን መምራት እንዳለበት መናገሩን ቀጥሎአል።

ኢዮአብ---በእኔ ላይ ያደረገውና ያደረገው
ተርጓሚ “ኢዮአብ----በእኔ ላይ ያደረገው- ያ ያደረገው ነው”።

የሰልፉንም ደም በሰላም አፈሰሰ
አማራጭ ትርጉሞች 1) “ልክ በጦርነት ያለ ያክል እነዚያን ሠዎች በሰላም ጊዜ ገደለ” 2) “በጦርነት ጊዜ ሰዎችን ስለገደሉ፣ በሰላሙ ጊዜ ተበቀላቸው።”

በወገቡም ባለው ድግና በእግሩ ባለው ጫማ ንፁህ ደም አኖረ
አማራጭ ትርጉሞች 1) ኢዮአብ የገደላቸውን በጣም ከመቅረቡ የተነሳ ደማቸው በድጉና በጫማው ላይ ፈሰሰ 2) ደም የሚለው ቃል ለግድያው ተጠያቂ የዘይቤ ንግግር ሲሆን ድግና ጫማ ደግሞ የኢያአብ የአዘዥነት ሥልጣን ማሣያ ዘይቤአዊ ንግግር ነው። ስለዚህ ዳዊት እያለ ያለው ኢዮአብ በግድያ የተከሰሰ ስለሆነ የሠራዊቱ አዛዥ መሆን የለበትም። ወይም ደግሞ ይህንን እንዳለ መተርጎም የተሻለ ነው።

ሸበቱንም በሰላም ወደ መቃብር አታውርደው
እዚህ ጋር ሸበት የእርጅና ምልክት መሆኑን ያሳያል። ይሄውም “ሸበቱን” የሚለው ነው። ተርጓሚ “ኢዮአብ ሳያረጅ የአመፃ ሞት መሞቱን አረጋግጥ”

1 Kings 2:7

አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ዳዊት ለሰለሞን እንዴት እስራኤልን መምራት እንዳለበት መናገሩን ቀጥሏል

ቤርዜሊ
የሰው (ወንድ) ስም ነው።

በማዕድህም ከሚበሉት መካከል ይሁኑ
ማዕድ የሚለው ቃል በቤት ውስጥ የመመገቢያ ጠረጴዛ ማሳያ ዘይቤአዊ ንግግር ነው። ተርጓሚ “በቤትህ እንዲመገቡ ተቀበላቸው”

1 Kings 2:8

አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ዳዊት ለሰለሞን እንዴት እስራኤልን መምራት እንዳለበት መናገሩን ቀጥሏል።

ጌራ------ሳሚ
የሰዎች ስም(ወንዶች)

ብንያማዊው
የብንያም ነገድ

መሃናይም---ብራቂም
የቦታ ሥሞች

ያለቅጣት አትተወው
ይህ በበጎ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። ተርጓሚ “ እርሱን ለመቅጣት እርግጠኛ ሁን”

ሸበቱንም ከደም ጋር ወደ መቃብር አውርድ
ደም በአመፅ የመሞት ዘይቤ ሲሆን ሸበት ደግሞ የሙሉ ሰውነት ምሳሌአዊ ንግግር ነው። ተርጓሚ - “የአመፃ ሞት መሞቱን እርግጠኛ ሁን”

1 Kings 2:10

አጠቃላይ መረጃ
ዳዊትም ሞተ ሰለሞንም እርሱን ተክቶ የእስራኤል ንጉስ ሆነ

ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ
የዳዊት ሞት በእንቅልፍ እንደወደቀ ተደርጎ ተነግሮአል። ተርጓሚ “ሞተ”

ዳዊትም---ተቀበረ
ይህ በገቢር መልኩ ሊተረጎም ይችላል።” ተርጓሚ “ዳዊትን ----ቀበሩት”

ዳዊትም በእስራኤል ላይ የነገሠው ዘመን
“ዳዊት በእስራኤል ላይ የነገሰው ጊዜ(ዘመን) ወይም “ዳዊት በእስራኤል ላይ የነገሠበት”

በአባቱ ዙፋን ላይ ተቀመጠ
ዙፋን የንጉስን ሥልጣን ያመለክታል። ተርጓሚ “አባቱ ንጉሥ እንደነበረ፤ ዳዊት ንጉሥ ሆነ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መንግስቱም እጅግ ፀና
ይህ በገቢር መልኩ ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ “እግዚአብሔር የሰለሞንን መንግስት እጅግ አፀና” ወይም “እግዚአብሔር ሰለሞንን መንግስቱን ፈፅሞ እንዲቆጣጠር አደረገው”

1 Kings 2:13

አጠቃላይ መረጃ
አዶንያስ ቤርሳቤህን ሊናገር መጣ

በሰላም
ክፉ ማድረግ ሳይፈልግ

እስራኤልም ሁሉ
ይህ በጥቅሉ ነው።

መንግስቱ---ለወንድሜ ሆኖአል
ይህ በገቢር መልኩ ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ “እግዚአብሔር መንግስቱን ለወንድሜ ሰጥቷል” ወይም “ወንድሜ ንጉስ ሆኖአል”

1 Kings 2:16

አጠቃላይ መረጃ
አዶንያስ ልመናውን ለቤርሳቤህ አቀረበ

አታሳፍሪኝ----አያሣፍርሽምና
ማፈር የሚለው ቃል አንድን ሰው ለመመልከት የአለመፈለግ ዘይቤአዊ ንግግር ነው። በሌላ መልኩ ደግሞ አንድ ሰው የጠየቀውን የአለማድረግ ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “የጠየኩሽን እምቢ አትበይኝ”----የጠየቅሽውን እምቢ አይልምና።

ሱናማይቱን አቢሳን
1 ነገስት 1:3 ተመልከት

1 Kings 2:19

አጠቃላይ መረጃ
ቤርሳቤህ የአዶንያስን ልመና(ጥያቄ) ይዛ ወደ ንጉስ ሰለሞን ሄደች

ንጉሡም ------ተነሳ
“ንጉሱም ከተቀመጠበት ከዙፋኑ ተነስቶ ቆመ”

ወንበር አስመጣላት
ይህ በገቢር መልኩ ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ - ወንበር እንዲያመጡ ለአንድ ሠው ነገረ

የንጉሡም እናት
ቤርሳቤህ

አታሳፍሪኝ---አላሳፈርሽኝም
ማፈር አንድን ሰው ለማየት (ለመመልከት) የአለመፈለግ ዘይቤአዊ ንግግር ነው። በሌላ መልኩ ደግሞ አንድ ሰው የጠየቀውን (የለመነውን) ነገር ያለመፈለግ ዘይቤ ነው። የ1ነገስት 2:16-17 ትርጉም ተመልከት።ተርጓሚ “እኔ የምጠይቅሽን እምቢ አትይኝም-----የምትጠይቂኝን እምቢ አልልሽም”

ሱናማይቱ አቢሳ---ለአዶንያስ ትዳርለት
ይህ በገቢር መልኩ ሊተረጎም ይችላል። “ሱናማይቱ አቢሳ እንዲያገባት ለአዶንያስ ፍቀድለት” ወይም “ሱናማይቱ አቢሳን ለአዶንያስ ሚስት አድርገህ ስጠው”

1 Kings 2:22

አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ሰለሞን ለቤርሳቤህ ጥያቄ ምላሽ ሰጠ

ለአዶንያስ ለምን ትለምኝለታለሽ------መንግስትን ደግሞ ለምኚለት---ፅሩያ
ንጉሥ ሰለሞን በእናቱ ጥያቄ ተቆጥቷል። ተርጓሚ “ለአዶንያስ በመጠየቅሽ ስህተት ሰርተሻል”። ይህ እርሱ መንግስትን ከመጠየቅ ጋር አንድ ነው---ፅሩያ

አዶንያስ ይህን ቃል በሕይወቱ ላይ አለመናገሩ እንደ ሆነ እግዚአብሔር ይህን ያድርግብኝ ይህንም ይጨምርልኝ
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አዶንያስ ይህን ጥያቄ በማቅረቡ እኔ ካልቀጣሁት እግዚአብሔር እኔን ለመቅጣት ሙሉ መብት ይኖረዋል። ብሎም ሊጨምርብኝ

1 Kings 2:24

አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ሰለሞን አዶንያስን ቀጣ

ዙፋን ላይ ያስቀመጠኝ
ዙፋን የሚለው ቃል እግዚአብሔር ሰለሞን እንዲገዛ የሰጠውን ስልጣን ይገልፃል።

ቤትን የሰራልኝ
እዚህ ጋር ቤት የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔር ሰለሞን የሰጠው የዘር ሐረግ ከእርሱ በኋላ ስለመንገሳቸው ነው።

1 Kings 2:26

አጠቃላይ መረጃ
ሰለሞን አብያታርን ከክህነት አወጣው

አባቴም የተቀበለውን መከራ ሁሉ-----ተቀበልሁ
ዳዊት ወደ ንግስና ከመምጣቱ በፊት አብያታር ከዳዊት ጋር መከራን ተቀበለ

የእግዚአብሄር ቃል
“እግዚአብሄር ስለተናገራቸው ነገሮች”

ቃል ይፈፀም ዘንድ
ይህ ስለ ንጉስ ሰለሞን ነው።

1 Kings 2:28

አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ሰለሞን ኢዮአብን እንዲገድል በናያስን አዘዘ

ለኢዮአብም ወሬ ደረሰለት
“ኢዮአብም ሰለሞን ንጉሥ ከሆነ በኋላ ያደረገውን ሰማ”

የመሠዊያውን ቀንድ
የመሠዊያው ቀንድ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ኃይልና ጥበቃ ነው።

ሰለሞን ኢዮአብ----ሸሸቶ-----ሰማ
ይህ በገቢር ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ “የሆነ ሰው ኢዮአብ እንደሸሸ ለሠለሞን ነግሮአል”

1 Kings 2:30

አጠቃላይ መረጃ
በናያስም ኢዮአብን ሊገድለው ሄደ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ኢየአብም በከንቱ ያፈሰሰውን ደም ከእኔና ከአባቴ ቤት ታርቅ ዘንድ ገድለህ ቅበረው።
እዚህ ጋር “ቤት” ሥለ ዳዊት የዘር ሐረግ ሲሆን “ደም” ወንጀልን ይገልፃል። ተርጓሚ ኢዮአብ በከንቱ ያፈሰሰው ደም ከእኔና ከቤተሰቤ ይርቅ ዘንድ ወስደህ ቅበረው። ወይም “ኢዮአብ የሰዎች ደም በከንቱ በማፍሰሱ ምክኒያት እግዚአብሔር በእኔና በአባቴ ቤት ላይ ወንጀል አድርጎ እንዳይቆጥር ቅበረው።”

1 Kings 2:32

አጠቃላይ መረጃ
ለምን ኢዮአብ መሞት እንዳለበት ሰለሞን ያብራራል።

እግዚአብሔር ደሙን በራሱ ላይ ይመልሰው
“በራሱ” ላይ የሚለው ቃል ኢዮአብን ይገልፃል “ደም” ደግሞ የመግደል ዘይቤአዊ ንግግር ነው። “ደሙን በራሱ ላይ” የሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ደግሞ ግለሰቡ በግድያ ምክኒያት እንደወንጀለኛ መቆጠሩ ማለት ነው። ተርጓሚ “ኢዮአብ ሰዎችን በመግደሉ ምክኒያት (ሰበብ) ላደረገው ድርጊት እግዚአብሔር እንደ በዳይ እንዲያየው እፈልጋለው፡”።

የሚሻሉትን----ፃድቃን
እነዚህ ሁለት ቃላት ቢመሰረቱ አንድ አይነት ትርጉም ሲኖራቸው አበኔርና አሜሳይ ከኢዮአብ የተሻሉ መሆናቸውን አፅንኦት ለመስጠት ነው።

ደማቸውም በኢዮአብ ራስና በዘሩ ራስ ላይ ይመልስ
“ደም” የሚለው ቃል የግድያ ዘይቤ ነው። “ደማቸው---ራስ ላይ” የሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ደግሞ ግለሰቡ በግድያው ምክኒያት እንደ ወንጀለኛ መወሰድ አለበት ማለት ነው። ተርጓሚ እኔ እግዚአብሔር ኢዮአብንና ዘሩን ተጠያቂ እንዲያደርግ እፈልጋለሁ።

ለቤቱ ለዙፋኑም
“ቤት” ና “ዙፋን” የሚሉት ቃላት ለቤተሰብና ለመንግስት የዘይቤ ንግግር ናቸው። ተርጓሚ “ለዳዊት ዘርና ለዳዊት መንግስት”

1 Kings 2:34

አጠቃላይ መረጃ
በነያስ ኢዮአብን ገደለው ከዚያም የንጉሥ ሰለሞን ጦር አዛዥ ሆነ

በቤቱ ተቀበረ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ኢዮአብን በራሱ ቤት ውስጥ ቀበሩት”

በቤቱ
ቤት የሚያመለክተው ቤቱ ያለበት መሬት ነው። እስራኤላውያን ሰዎችን (ሙታንን) ከቤት ውጭ በመቃብር ቦታ ይቀብራሉ “ቤተሰቡ በሚኖሩበት ቦታ”

1 Kings 2:36

አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ሰለሞን ለሳሚ በእየሩሳሌም እንዲቆይ አለበለዚያ ግን እንደሚሞት ነገረው።

ደምህ በራስህ ላይ ይሆናል።
እዚህ ጋር “ደም” የጥፋት ዘይቤ ሲሆን “ራስ” ደግሞ ግለሰብን ማሣያ ዘይቤ ነው። ተርጓሚ ለሞትህ አንተ ራስህ ተጠያቂ ትሆናለህ

1 Kings 2:39

አጠቃላይ መረጃ
ሳሚ እየሩሳሌምን ለቀቀ

ጌት-----መዓካ----አንኩስ
የሰዎች ስም

ጌት
የፍልስጤም ከተማ

ሳሚም ተነሳ
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። “ሳሚም ፈጠነ”

1 Kings 2:41

አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ሰለሞን ሳሚ እየሩሳሌምን በመልቀቁ ፈረደበት

ሰለሞንም----ሰማ
ይህ በገቢር መልኩ ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ “የሆነ ሰው ለሰለሞን ነገረው”።

እንዳትሞት እውቅ ብዬ------አላስማልሁህምን?
ሳሚ ቃል የገባውን (የማለውን) ማሃላ ሰለሞን ሲያስታውሰው። ተርጓሚ “እንዳትሞት እውቅ ብዬ----እንዳስማልሁህ በደንብ ታውቃለህ”

1 Kings 2:43

አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ሰለሞን ሳሚ እየሩሳሌም በመልቀቁ ፈረደበት

መሓላ ስለ ምን አልጠበቅህም?
አማራጭ ትርጉሞች- 1) ሰለሞን መልስ እየጠየቀው ነው? ወይም 2) “ማሃላን በማፍረስህ ስህተት ሠርተሃል”

ክፋትህን በራስህ ላይ ይመልሳል
እዚህ ጋር ራስ ግለሰቡን ይወክላል። ክፋትን ደግሞ በግለሰቡ ራስ ላይ እንደሚቀመጥ ዕቃ ወይም ፈሳሽ ነገር አድርጎ ይናገራል። ተርጓሚ “ለክፋትህ ሁሉ ተጠያቂ ያደርግሃል”

1 Kings 2:45

አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ሰለሞን ሳሚ እንዲሞት ትዕዛዝ ሰጠ

የዳዊትም ዙፋን በእግዚአብሄር ፊት ለዘላለም ይፀናል።
እዚህ ጋር የዳዊት ዙፋን የዳዊትንና የእርሱን ዘር ሐረግ ስልጣንና ግዛት ይወክላል።

በሰለሞን እጅ
“እጅ” የሰለሞንን ስልጣንና ጉልበት ይገልፃል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 ሰሎሞን የግብፅን ንጉሥ የፈርዖንን ሴት ልጅ በማግባት ከንጉሡ ጋር ወዳጅነት መሠረተ። የፈርዖንንም ልጅ አምጥቶ ቤተ መንግሥቱን፣ ቤተ መቅደሱንና
የኢየሩሳሌምን ከተማ ቅጥር ዙሪያውን ሠርቶ እስኪጨርስ ድረስ በዳዊት ከተማ አኖራት። **2** በዚያን ጊዜ በእግዚአብሔር ስም ቤተ መቅደሱ ገና አልተሠራም
ነበር፤ ከዚህም የተነሣ በየኮረብታው መሥዋዕት ያቀርቡ ነበር። **3** ሰሎሞን እግዚአብሔርን ይወድ ነበር፤ የአባቱንም የዳዊትን መመሪያ ይጠብቅ ነበር፤ ይሁን
እንጂ እንስሶችን እያረደ በተለያዩ ኮረብቶች ላይ መሥዋዕት ያቀርብና ዕጣንም ያጥን ነበር። **4** ታላቅ መሠዊያ የሚገኘው በገባዖን ስለነበር አንድ ቀን ንጉሥ
ሰሎሞን መሥዋዕት ለማቅረብ ወደዚያ ሄደ። በዚያም መሠዊያ ላይ አንድ ሺህ የሚቃጠል መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ። **5** እግዚአብሔርም በዚያች ሌሊት
በገባዖን ለሰሎሞን በሕልም ተገለጠለትና ምን እንድሰጥህ ትፈልጋህ? ጠይቅ አለው። **6** ሰሎሞንም እንዲህ ሲል መለሰ፦ አገልጋይህ የነበረው አባቴ ዳዊት፣
ታማኝና ቅን ሰው በመሆኑ ጽኑ ፍቅርህን አሳይተኸዋል። ዛሬም በእርሱ ፈንታ በዙፋኑ የሚቀመጥ ልጅ በመስጠት ታላቅና ጽኑ የሆነውን የማያቋርጥ ፍቅርህን
ገልጠህለታል። **7** እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ እነሆ እኔ በዕድሜዬ ልጅ ብሆንም በአባቴ ቦታ ተተክቼ እንድነግሥ ፈቃድህ ሆኖአል። እኔም መግባትንና
መውጣትን የማልችል ነኝ። **8** እነሆ፣ የአንተ እንዲሆን በመረጥከውና ከብዛቱ የተነሣ ሊቆጠር በማይችል ሕዝብ መካከል አለሁ። **9** ስለዚህ ክፉውንና በጎውን
በመለየት ሕዝብህን በማስተዋል በትክክል ፍርድ ለመምራት የሚያስችለኝን ጥበብ ስጠኝ። ይህ ካልሆን ይህን ታላቅ ሕዝብህን ሊመራ ማን ይችላል? **10** ይህ
የሰሎሞን ጥያቄ እንግዚአብሔርን ደስ አሰኘው፤ **11** ስለዚህም እግዚአብሔር እንዲህ አለው፦ ለራስህ ረጅም ዕድሜ ወይም ሀብት ለማግኘት ወይም ጠላቶችህ
እንዲጠፉልህ መመኘት ሳይሆን በትክክለኛ ፍርድ ማስተዳደር የምትችልበትን ጥበብ ጠይቀሃል። **12** እነሆ የጠየቅኸውን አደርጋለሁ፤ እንዲያውም ማንም ሰው
ከዚህ በፊት ካገኘውና ወደ ፊት ሊያገኘው ከሚችለው የሚበልጥ ጥበብንና አስተዋይነትን እሰጥሃለሁ። **13** ከዚህም በላይ አንተ ያልጠየቅከውንም ሁሉ ጨምሬ
ሰጥቼሃለሁ፤ ይኸውም በዘመንህ ማናቸውም ንገሥታት ያላገኙትን ብጽግናና ክብር አሰጥሃለሁ። **14** አባትህ ዳዊት እንዳደረገው በመንገዴ ብትሄድ ለእኔም
ብትታዘዝ ሕጌንና ትእዛዞቼንም ብትፈጽም ረጅም ዕድሜ እሰጥሃሁ። **15** ሰሎሞን ከእንቅልፉ በነቃ ጊዜ እግዚአብሔር በሕልም ተገልጦ ያነጋገረው መሆኑን
ተገነዘበ፤ ከዚህ በኋላ ሰሎሞን ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶ ሄደ፤ በእግዚአብሔርም የቃል ኪዳን ታቦት ፊት ቆሞ የሚቃጠል መሥዋዕትና የኅብረት መሥዋዕት
ለእግዚአብሔር አቀረበ፤ ከዚህም በኋላ ለአገልጋዮቹ ሁሉ ግብዣ አደረገ። **16** አንድ ቀን ሁለት ሴተኛ አዳሪዎች መጥተው በሰሎሞን ፊት ቀረቡ። **17** ከእነርሱም
አንደኛይቱ እንዲህ አለች ንጉሥ ሆይ ይህች ሴትና እኔ በአንድ ቤት አብረን ስንኖር፣ በዚያውም በምንኖርበት ቤት ወንድ ልጅ ወለድኩ። **18** እኔ በወለድኩ
በሦስተኛው ቀን እርስዋም ወንድ ልጅ ወለደች። በዚያ ቤት ውስጥ ከሁለታችን በቀር ሌላ ማንም አልነበረም። **19** ከዕለታት አንድ ቀን ሌሊት በላዩ ላይ ተኝታበት
ስለ ታፈነ ልጁ ሞተ። **20** እኔ ተኝቼ ሳለሁ ሌሊት ተነሥታ ታቅፌው የተኛሁትን ልጄን ወስዳ በእርስዋ አልጋ ላይ ካስተኛች በኋላ የሞተውን ልጅዋን አምጥታ በእኔ
አልጋ ላይ በጎኔ አስተኛችው። **21** በማግስቱ ማለዳ ተነሥቼ ልጄን ለማጥባት ስዘጋጅ ሞቶ አገኘሁት፤ ትኩር ብዬ ስመለከተው እኔ የወለድኩት ልጅ አለመሆኑን
ተገነዘብኩ። **22** ሁለተኛይቱ ሴት ግን አይደለም፣፣ በሕይወት ያለው ልጅ የእኔ ነው፣ የሞተው ግን የአንቺ ነው አለች። የመጀመሪያይቱ ሴት አይደለም የሞተው
የአንቺ ነው፤ በሕይወት ያለው ግን የእኔ ልጅ ነው አለች። በዚህ ዓይነት በንጉሡ ፊት ተከራከሩ። **23** ከዚህ በኋላ ንጉሥ ሰሎሞን አንደኛዋ በሕይወት ያለው ልጅ
የእኔ ነው፣ የሞተው ግን የአንቺ ነው ትላለች፤ ሌላይቱም ደግሞ አይደለም የአንቺ ልጅ ሞቶአል፤ የእኔ ልጅ በሕይወት ያለው ነው ትላታለች አለ። **24** ንጉሡም
ሰይፍ እንዲያመጡለት አዘዘ፤ ሰይፍም አመጡለት። **25** በሉ እንግዲህ በሕይወት ያለውን ልጅ ለሁለት ቁረጡና ለእያንዳንዱ ሴት ግማሽ አካሉን ስጡ ሲል
አዘዘ። **26** እውነተኛይቱ ግን ለልጅዋ በመራራት አዝና ንጉሥ ሆይ፣ እባክህ ልጁን አትግደለው፤ ለእርስዋ ይሰጣት አለች። ሌላይቱ ሴት ግን፣ ለእኔም ለእርስዋም
አይሁን፤ ለሁለት ይቆረጥ አለች። **27** ከዚህ በኋላ ሰሎሞን ሕፃኑን አትግደሉት፤ እውነተኛይቱ እናት እርስዋ ስለሆነች ለመጀመሪያይቱ ሴት ስጡአት ሲል አዘዘ።
28 እስራኤላውያን ይህን የፍርድ ውሳኔ በሰሙ ጊዜ ሰሎሞን የሕዝብ ጉዳዮችን በትክክለኛ ፍርድ የሚወስንበትን ጥበብ እግዚአብሔር የሰጠው መሆኑን ስለ
ተገነዘቡ ታላቅ አክብሮት ሰጡት።

---

1 Kings 3:1

አጠቃላይ መረጃ
ሰለሞን ግብፃዊቷን አገባ

ሰለሞን ለግብፅ ንጉሥ ለፈርዖን አማች ሆነ የፈርኦንን ልጅ አገባ
ሁለቱ ነገስታት አብረው ይሠሩና ጠላቶቻቸውን በጋራ ይወጉ ዘንድ፣ ሰለሞን
የግብፅ ንጉሥ ለፈርዖን አማች ሆነ

ቅጥር ሠርቶ እስኪፈፅም ድረስ
ቅጥሩን ሠርቶ ከጨረሰ በኋላም በዳዊት ከተማ ውስጥ ነበረች

የእግዚአብሄርንም ቤት
“ቤተ- መቅደሱ”

እስከዚያም ቀን ድረስ...መቅደስ አልተሰራም
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “እስከዚያ ቀን ድረስ ማንም
መቅደስ አልሰራም”

ለእግዚአብሄር ስም
“ስም” የሚለው ቃል ለአንድ ሰው ዘይቤና “ስም” የሚለው ቃል በዚህ ሐረግ
ውስጥ የሚመለክ ስም መሆኑን ነው። ተርጓሚ “ሰዎች እግዚአብሄርን
የሚያመልኩበትን”

በአባቱም በዳዊት ሥርዓት ይሄድ ነበር
የሰው የአኗኗር ዘይቤና መንገድ እንደሚሄድ ሰው ተደርጎ ተነግሯል። ተርጓሚ
“አባቱ ዳዊት የታዘዘውን ሕግጋት መታዘዝ (ታዘዘ)”

1 Kings 3:4

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሄር ለሰለሞን ምን ማድረግ እንደሚፈልግ ጠየቀው

ዋና የኮረብታ መስገጃ
“መስዋዕት ለማቅረብ በጣም የተመረጠ ሥፍራ” ወይም “በጣም አስፈላጊ
መሰዊያ”

ምን እንደምሰጥህ ጠይቅ
“የምትፈልገውን ነገር ጠይቀኝ እኔም እሰጥሃለሁ” ወይም “ምን ትፈልጋለህ?
ጠይቅ እኔም እሰጥሃለሁ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Kings 3:6

አጠቃላይ መረጃ
ሰለሞን ለእግዚአብሄር ጥያቄ ምላሽ ሰጠ

1 Kings 3:10

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለሰለሞን ጥበብን አብዝቶ ሠጠው

የጠላቶችህንም ነፍስ
“ነፍስ” የመግደል ሃይል ዜይቤ ነው። ተርጓሚ “ ጠላቶችህን የመግደል አቅም (ሃይል)”

ለመንህ .....እኔ እንደቃልህ አድርጌልሃለው
“ከእኔ ጋር ስለተነጋገርህ የጠየቅከው ሁሉ አደርግልሃለው”

ጥበበኛና አስተዋይ ልቦና ሰጥቼሃለሁ
ልብ ሰው ስለሚያስበውና ስለሚመኘው ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “ጥበበኛና ብዙ ነገሮችን የምትረዳ አደርግልሃለሁ”

1 Kings 3:13

ትጠብቅ ዘንድ በመንገዴ
ሕይወትን መኖር መንገድ እንደመሄድ ሆኖ ተገልፆአል። “እኔ እንደምፈልገው ኑር ታዘዝም”

እድሜህን አረዝመዋለሁ
“ረጅም እድሜ እንድትኖር አደርጋለሁ”

1 Kings 3:15

እነሆም
“እነሆም” የሚለው ቃል ሰለሞን ደስ የሚል ነገር ማየቱን ያሣያል።

1 Kings 3:16

አጠቃላይ መረጃ
ሁለት ጋለሞቶች ሰለሞን ውሳኔ እንዲሰጥ ጠየቁት

1 Kings 3:18

አጠቃላይ መረጃ
ሁለቱም ጋለሞታዎች ታሪካቸውን ለሰለሞን ነገሩት

ተኛችበት
ሕፃኑን እንዲሞት አደረገው ብሎ ማስቀመጥ የተሻለ ነው። ተርጓሚ “በድንገት በልጇ ላይ በመንከባለሏ አፈነችው (ታፈነ)

ባርያህ
ሴትዬዋ ለሠለሞን ያላትን አክብሮት ለማሳየት እራሷን እንደሌላ ሠው አድርጋ ታናግረዋለች። ተርጓሚ “እኔ”

1 Kings 3:21

አጠቃላይ መረጃ
ሁለቱ ጋለሞታዎች ታሪካቸውን ለሠለሞን መንገር ቀጥለዋል።

ልጄንም አጠባ ዘንድ
ይህ ማለት ከጡቷ ወተት መስጠት ማለት ነው።

በንጉሱ ፊት
x

1 Kings 3:23

አጠቃላይ መረጃ
ሰለሞን ለሁለቱ ሴቶች ውሳኔ ሰጠ

1 Kings 3:26

አጠቃላይ መረጃ
እውነተኛይቱ የልጅ እናት ንጉሡ የልጁን ሕይወት እንዲድን

አንጀትዋ ስለ ልጅዋ ናፍቆአልና
ይህ ሴትዬዋ ስለ ልጅዋ ብዙ ናፍቆት እንዳላት የሚያሳይ ነው። ተርጓሚ “ልጅዋን በታላቅ ፍቅር ወዳዋለች”

እስራኤል ሁሉ
ይህ ጥቅል ንግግር ነው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 ንጉሡ ሰሎሞን በመላው አስራኤል ላይ ነግሦ ነበር። 2 ንጉሡም የሾማቸው ባለሥልጣኖች እነዚህ ናቸው። እነርሱም፦ ዓዛርያስ የተባለው የሳዶቅ ልጅ፦ ካህን ነበር። 3 ኤልያፍና አኪያ የተባሉ የሴባ ልጆች የቤተ መንግሥት ጸሐፊዎች ነበሩ። ኢዮሣፍጥ የተባለው የአሒሉድ ልጅ ታሪክ ጸሐፊና የመዛግብት ኃላፊ ነበር። 4 በናያስ የተባለው የዮዳሄ ልጅ የጦር ሠራዊት አዘዥ ነበር። ሳዶቅና አብያታር ካህናት ነበሩ። 5 ዓዛርያስ የተባለው የናታን ልጅ፦ የክፍለተ አገራት ገዢዎች የበላይ ኃላፊ ነበር። የናታን ልጅ ዛቡድ፦ ካህንና የንጉሡ አማካሪ ነበር። 6 አሒሳር የተባለው፦ የቤተ መንግሥት አገልጋዮች ኃላፊ፤ አዶኒራም የተባለው የዓብዳ ልጅ፦ የግዳጅ ሥራ ተቆጣጣሪና ኃላፊ ነበር። 7 ንጉሡ ሰሎሞንም በመላው እስራኤል ለንጉሡና ለንጉሡ ቤተ ሰብ ቀለብ የሚያዘጋጁ ዐሥራ ሁለት ባለሥልጣኖች ነበሩት። እያንዳንዳቸውም በዓመት ውስጥ ለአንድ ወር ቀለብ የማቅረብ ግዴታ ነበረባቸው። 8 የእነዚህም ዐሥራ ሁለት ገዢዎችና የሚያስተዳድሩአቸው ግዛቶች ስም ዝርዝር ከዚህ የሚከተለው ነው፦ ቤንሑር፦ ኮረብታማ የሆነችው የኤፍሬም አገር ገዢ፤ 9 ቤንዴር፦ የማቃጽ የሻዓልቢም፤ የቤትሻሜሽ፦ የኤሎንና የቤት ሐናን ከተሞች ገዢ፤ 10 ቤንሔሴድ፦ የአሩቦትና የሶኮ ከተሞችና የመላው የሐፌር ግዛት አስተዳዳሪ፤ 11 ጣፋት የተባለችውን የሰሎሞንን ሴት ልጅ አግብቶ የነበረው ቤን አሚናዳብ የመላው የዶር ግዛት አስተዳዳሪ፤ 12 በዓና የተባለው የአሒሉድ ልጅ፦የታዕናክና የመጊዶ ከተሞች፤ እንዲሁም በቤትሳን አጠገብ ያለው ግዛት በሙሉ በጸርታን ከተማ አጠገብ ያለው ግዛትና በኢይዝራኤል ከተማ በስተደቡብ ያለው ግዛት፤ እንዲሁም አቤልመሖላና ዮቅምዓም ተብለው እስከሚጠሩት ከተሞች ድረስ ያለው ግዛት ሁሉ አስተዳዳሪ፤ 13 በገለዓድ ራሞት ቤን ጌቤር ተብላ የምትጠራው ከተማ በገለዓድ የምናሴ ዘር የሆነው የኢያዕር ጎሣ ይዞታዎች የሆኑት መንደሮች፤ በባሳን አርጎብ ተብላ የምትጠራው ግዛት እንዲሁም በሮቻቸው የነሐስ መወርወሪያ ባሉአቸው የቅጥር ግንቦች የተመሸጉ በድምሩ የስልሳ ታላላቅ መንደሮች አስተዳዳሪ፤ 14 አሒናዳብ የተባለው የዔዶ ልጅ፦ የመሃናይም ክፍለ አገር ገዢ፤ 15 መካከል ባስማት ተብላ የምትጠራውን የሰሎሞንን ሴት ልጅ አግብቶ የነበረው አኪማአስ፦ የንፍታሌም ግዛት አስተዳዳሪ፤ 16 በዓና የተባለው የሑሻይ ልጅ፦ የአሴር ግዛትና የበዓሎት ከተማ ገዢ፤ 17 ኢዮሣፍጥ የተባለው የፋሩሕ ልጅ፦ የይሳኮር ግዛት አስተዳዳሪ፤ 18 ሳሚ የተባለው የኤላ ልጅ፦ የብንያም ግዛት አስተዳዳሪ፤ 19 ጊቤር የተባለው የኡሪ ልጅ፦ በአሞራውያን ንጉሥ በሴዎንና በባሳን ንጉሥ በዐግ ትገዛ የነበረችው የገለዓድ ግዛት አስተዳዳሪ፤ እነዚህን ዐሥራ ሁለቱን አስተዳዳሪዎች የሚቆጣጠር በመላ አገራቱ ሌላ አንድ የበላይ ኃላፊ ነበር። 20 የይሁዳና የእስራኤል ሕዝብ ብዛት እንደ ባሕር ዳር አሸዋ ነበር፤ እነዚህ ሁሉ እየበሉና እየጠጡ ዘወትር ደስ እየተሰኙ ነበር። 21 የሰሎሞንም ግዛት ከኤፍራጥስ ወንዝ ጀምሮ እስከ ፍልስጥኤም ግዛት፣ ከዚያም አልፎ እስከ ግብፅ ወሰን ያለውን አገር ሁሉ ያጠቃልል ነበር፤ የእነዚህም አገሮች ሕዝቦች በጠቅላላ ሰሎሞን በነበረበት ዘመን ሁሉ ለእርሱ ተገዢዎች ሆነው ይገብሩለት ነበር። 22 ሰሎሞንም በየቀኑ ለቀለብ የሚሆን አምስት ሺህ ኪሎ ግራም ያህል ምርጥ ዱቄት፤ ዐሥር ሺህ ኪሎ ግራም ያህል ነበር። 23 በበረት ውስጥ እየተመገቡ የደለቡ ዐሥር ሰንጋዎችና በግጦሽ መስክ ተሰማርተው የተመገቡ ሃያ ፍሪዳዎች፣ አንድ መቶ በጎች፤ ከዚህም ሌላ አጋዘኖች፣ የሜዳ ፍየሎች፤ ሚዳቆዎችና ምርጥ ወፎች ያስፈልጉት ነበር። 24 ሰሎሞን ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተ ምዕራብ ያለው ምድር ሁሉ ከቲፍሳ ከተማ ጀምሮ እስከ ጋዛ ከተማ ድረስ ይገዛ ነበር፤ ይህም ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተምዕራብ የሚገኙትን ነገሥታት ሁሉ ያጠቃልላል፤ ጎረቤቱ ከሆኑት አገሮችም ሁሉ ጋር በሰላም ይኖር ነበር። 25 በኖረበትም ዘመን ሁሉ ከዳር እስከ ቤርሳቤህ ድረስ መላው የይሁዳና የእስራኤል ሕዝብ ያለ ስጋት በሰላም ይኖር ነበር፤ እያንዳንዱ ቤተ ሰብ ለራሱ የሆነ የወይን ተክልና የበለስ ዛፍ ስለ ነበረው በእነዚህ ተክሎች ጥላ ሥር ያርፍ ነበር። 26 ሰሎሞን ሠረገላ የሚስቡ አርባ ሺህ ፈረሶች፣ ለጦርነት የሚያገለግሉ ዐሥራ ሁለት ሺህ ፈረሶች ነበሩት። 27 ለሰሎሞንና በቤተ መንግሥቱ ለሚቀለቡት ሁሉ የሚያስፈልገውን ምግብ የሚያቀርቡ ዐሥራ ሁለቱ ገዢዎች እያንዳንዳቸው በተመደበላቸው ወር ምንም ነገር ሳያጓድሉ በወቅቱ ያመጡ ነበር። 28 ከዚህም በቀር እያንዳንዱ ገዢ እንደሚችለው ሌላም አገልግሎት ለሚያበረክቱ የጋማ ከብቶች ገብስና ገለባ ያቀርብ ነበር። 29 እግዚአብሔር ለሰሎሞን አጅግ አስደናቂ የሆነ ጥበብንና አስተተዋይነትን እንዲሁም እንደ ባሕር ዳር አሸዋ ወሰን የማይገኝለትን ዕውቀት ሰጠው። 30 የሰሎሞንም ጥበብ ከምሥራቅ አገርና ከግብፅም ጥበበኞች እጅግ የላቀ ነበረ። 31 እርሱ ከሰዎች ሁሉ የሚበልጥ ታላቅ ጥበበኛ ነበረ፤ ከኢይዝራኤላዊው ኤታን፣ የማሖል ልጆች ከሆኑት ከሮማን ከካልኮልና ከዳርዓዕ የሚበልጥ ጥበበኛ ነበረ፤ ዝናውም ከፍ ብሎ በጎረቤት ሕዘቦች ሁሉ ዘንድ አስተጋባ። 32 ሦስት ሺህ ምሳሌዎችንና አንድ ሺህ አምስት የመዝሙር ድርሰቶች ነበሩት። 33 ሰሎሞን ከሊባኖስ ዛፍ ጀምሮ በቤት ግንብ ላይ እስከሚበቅለው ሂሶጵ ድረስ ስለ ዛፎችና ስለ ተክሎች ምሳሌዎችን ተናግሮአል፤ እንዲሁም ስለ ልዩ ልዩ እንስሶች፣ ወፎች፣ በሆዳቸው እየተሳቡ ስለሚሄዱ ፍጥረቶችና ስለዓሣዎች አስተምሮአል። 34 በመላው ዓለም የሚገኙ ነገሥታት ስለ ሰሎሞን ጥበብ ለመስማት ይመጡ ነበር። ስለ ጥበቡም የሰሙት ከምድር ነገሥታት ሁሉ ወደ እርሱ መጥተዋል።

---

1 Kings 4:1

አጠቃላይ መረጃ
ይህ የሰለሞን ባለሥልጣናት ዝርዝር ነው።

ዓዛሪያ...ሳድቅ...ኤልያፍ...አኪያ...አሒልድ...ሴባ...አጹሳፍጥ...በናያስ...አብያታር...ዮዳሄ
የሰዎቸሀ (ወንዶች) ስም

1 Kings 4:5

አጠቃላይ መረጃ
የሰለሞን ባላስልጣናት ሥም ዝርዝር ቀጥሏል

ዓዛሪያ...ናታን...ዛቡድ...አሒሳር...አዶኒራም...ዓብዳ
የሰዎች(ወንዶች) ሥም

አስገባሪ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ሰለሞን እንዲሰሩለት ያስገደዳቸው ሰዎች”

1 Kings 4:7

አጠቃላይ መረጃ
የሰለሞን ባለሥልጣናት ዝርዝር ቀጥሏል

ሑር...ዴቀር...ሔሴድ
እነኝህ የሰዎች ስም ዝርዝር ናቸው

በተራራማው ሀገር...በማቃፅ....በአሩቦት
“የተራራማው ሀገር ሹም ማን ነበረ...የማቃፅ ሹም ማን ነበረ...የአሩቦት ሹም ማን ነበረ”

ኤፍሬም...ማቃፅ...ሸዓልቢም...ቤትሳሚስ...ኤሎን ቤትሓንን...አሩቦት...ሶኮት...ኦፌር
እነኝህ የቦታ ሥሞች ናቸው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Kings 4:11

አጠቃላይ መረጃ
የሰለሞን ሹሞች ሥምና ማስተዳደር የጀመሩበት የቦታዎች ስም ዝርዝር ናቸው።

አሚናዳብ...ጌበር...አያዕር...ምናሴ..አሒናዳብ...ኢዶ
የሰዎች ስም ዝርዝር

በዶር...በታዕናክ...በሬማት ዘገለዓድ...በመሃናይም
የዶር ሹም አስተዳደር ማን ነበረ...የታዕናክ ሹም አስተዳደር ማን ነበር... የሬማት ዘገለዓድ ሹም አስተዳደር ማን ነበረ...የመሃናይም ሹም አስተዳደር ማን ነበር!

ጣፋት
የሴት ስም

ዶር...ቤትሳን...ፀርታን...ኢይዝራኤል...በቤትሳምና አቤልማሖላን...ዮቅምዓም በሬማት ዘገለዓድ በአርጎብ በበሳን...በመሃናይም
የቦታ ስሞች

1 Kings 4:15

አጠቃላይ መረጃ
የሰለሞን ሹሞችና የአስተዳደራቸው የቦታ ሥሞች

አኪማአስ...በዓና...ኩሲ...አዮሳፍጥ..ፋሩዋ
የሰዎች ስም(የወንድ)

በንፍታሌም...በአሴር...በይሳኮር
የንፍታሌም ሹም አስተዳደር ማን ነበር፣ የአሴር ሹም አስተዳደር ማን ነበር፣ የይሳኮር ሹም አስተዳደር ማን ነበር

ባስማት
የሴት ስም

ንፍታሌም...አሴር...ይሳኮር
በእስራኤል ልጆች ነገድ የተሰየሙ የቦታ ስሞች

በአሎት
የቁራሽ መሬት ስም

1 Kings 4:18

አጠቃላይ መረጃ
የሰለሞን የሹም ስሞችና የሚያስተዳድሯቸው የቦታ ስሞች ዝርዝር ቀጥሏል

ሳሚ...ኤላ...ጌበር..ኡሪ...ሴዎን..ዐግ
የሰዎች ስም(የወንድ)

ቢንያም
የእስራኤል ልጅ የነገድ ስም

ገለዓድ...ባሳን
የቁራሽ መሬት ስሞች

የሴዎን...ምድር
“ቀድሞ የሴዎን ምድር የነበረ”

አሞራውያን
የአንድ ወገን ሰዎች ስም

በምድር
እዚህ ጋር ምድር የይሁዳን ምድር ይገልፃል። የመጀመሪያዎች ሹሞች በተለያዩ የእስራኤል ቦታዎች ያስተዳድሩ ነበር።

1 Kings 4:20

ይሁዳና እስራኤልም እንደ ባህር አሸዋ ብዛት ብዙ ነበሩ
ተናጋሪው ከብዛታቸው የተነሳ ለቁጥር እንደሚያታክቱ ለመግለፅ የግነት ንግግር የተጠቀመበት ነው። ይሁዳና እስራኤል በይሁዳና በእስራኤል በሚኖሩ ሰዎች ዘይቤአዊ ንግግር ናቸው። ተርጓሚ “ልክ እንደ ባህር አሸዋ በይሁዳና በእስራኤል ምድር ብዙ ሰዎች ነበሩ” ወይም “አንድ ሰው ሊቆጥር ከሚችለው በላይ በይሁዳና በእስራኤል ብዙ ሰዎች ነበሩ”

ከወንዙ
የኤፍራታ ወንዝ

ሰላሳ ኮር
ኮር የደረቅ ነገር መለኪያ ነው

ዋላ...ሚዳቋ...የበረሀ ፍየል
በጣም ፈጣን የሆኑ ባለ አራት እግር እንስሳዎች ናቸው።

ዋላ
ከተጠቀሱት እንስሳት ከአንድ በላይ የሆነ ዝርያ

የሰቡ ወፎች
ይሰቡ ዘንድ ሰዎች የቀለቡዋቸው አእዋፍ ናቸው

1 Kings 4:24

ቲፍሳ
የቁራሽ መሬት ስም

ይሁዳና እስራኤል
ይሁዳና እስራኤል በይሁዳና በእስራኤል ምድር ለሚኖሩ ሰዎች ዘይቤ ናቸው።

እያንዳንዱ ከወይኑና ከበለሱ በታች ተዘልሎ ይቀመጥ ነበር
እያንዳንዱ ቤት (ቤተሰብ) የወይንና የበለስ ቦታ ነበረው። ይህ የሚያመለክተው ጦርነት ላይ ስላልሆነ የሚያርሱበት ጊዜ ስለነበራቸው እያንዳንዱ በሰላምና በፀጥታ ይኖሩ ነበር።

ከዳን ጀምሮ እስከ ቤርሳቤህ
x

1 Kings 4:26

የፈረስ ጋጥ
ጋጥ እንደ ፈረስ ያሉ እንስሳት የሚጠበቁበትና እንክብካቤ የሚደረግበት ቦታ ነው።

ወደ ንጉስ ሰለሞን ማዕድ የሚቀርቡትን
“ከንጉስ ሰለሞን ጋር የሚመገቡትን” ወይም “አብረውት ይመገቡ ዘንድ ንጉሥ ሰለሞን የጋበዛቸው”

እያንዳንዱ በየወሩ
በየወሩ ምግብ ያመጡለት ዘንድ 1ነገስት 4፡7-9 ሰለሞን አስራ ሁለቱን ሹሞች እያንዳንዳቸውን ወክሏል

ምንም አያጎድሉም ነበር
ይህ በሌላ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። ተርጓሚ “ሰለሞን የሚፈልገውን ነገር ሁሉ ያቀርቡለት ነበር”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Kings 4:29

እግዚአብሔር ለሰለሞን እጅግ ብዙ ጥበብና ማስተዋል...ሰጠው
ጥበብና ማስተዋል የሚባሉት ስውር ቃላት እንደ ግስ ሊተረጎሙ ይችላል። እግዚአብሔር ሰጠው ማለት እግዚአብሔር እነዚህን ብቃቶች እንዲኖረው አደረገ።ተርጓሚ እግዚአብሔር ሰለሞን ጥበበኛና ብዙ ነገሮች የሚረዳ ሰው አደረገው።

በባህርም ዳር እንዳለ አሸዋ የልብ ስፋት
ሰለሞን ስለብዙ ነገሮች መረዳት የቻለ ነበር “ስፋት” የሚለው ስውር ቃል እንደ ቅፅል ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ “ሰለሞን ብዙ ነገሮችን መረዳት የቻለ ነበር”

የሰለሞንም ጥበብ ከሰዎች ሁሉ ጥበብ..በለጠ
ሰለሞን ከጥበበኞች ሁሉ በላይ ጥበበኛ ነበረ

1 Kings 4:32

ዝግባ...ሂሶጵ
እነዚህ ቃላት ሁሉንም ተክሎች የሚያጠቃልል ስሞች ናቸው። ተርጓሚ የዝግባ ዛፍ...“የሂሶጵተክል” ወይም “ከዛፍ ሁሉ ትልቁ...አነስተኛ ጥቅም ያለው ተክል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 5

1 የጢሮስ ንጉሥ ኪራም ከዳዊት ጋር ወዳጅነቱን አጽንቶ ቆይቶ ነበር፤ እርሱም ሰሎሞን በአባቱ በዳዊት ፈንታ መንገሡን በሰማ ጊዜ ወደ እርሱ መልእክተኞቹን
ላከ። 2 ሰሎሞንም ወደ ኪራም እንዲህ የሚል መልእክት ላከ። 3 አባቴ ዳዊት በዙሪያው ከነበሩት ከብዙ ጦርነቶች የተነሣ ለእግዚአብሔር አምላክ በስሙ
ቤተ መቅደስ ለመሥራት አለመቻሉን ታውቃለህ፤ እግዚአብሔርም በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ጠላቶቹን ከእግሩ በታች አንበረከካቸው። 4 አሁን ግን አምላኬ
እግዚአብሔር በሁሉም ድንበር እረፍት ሰጥቶኛል። ምንም ዓይነት ጠላት ወይም አደጋ የሚጥል የለብኝም። 5 ስለዚህ እግዚአብሔር ለአባቴ ለዳዊት፦ ከአንተ
በኋላ የማነግሠው ልጅህ ለእኔ በስሜ ቤተ መቅደስ ይሠራልኛል ሲል ተናግሮት ስለነበር፤ ለአምላኬ ለእግዚአብሔር በስሙ ቤተ መቅደስ ለመሥራት አሁን
አቅጃለሁ። 6 ስለዚህም የሊባኖስ ዛፍ እንጨት የሚቆርጡ ሰዎች ወደ ሊባኖስ ላክልኝ። የእኔም ሰዎች ከእነርሱ ጋር አብረው እንዲሠሩ አደረጋለሁ፤ ለአንተም
ሰዎች የምትወስነውን ደመወዝ እከፍላለሁ፤ አንተም እንደምታውቀው፣ የእኔ ሰዎች ስለ ዛፍ አቆራረጥ የአንተን ሰዎች ያህል ዕውቀት የላቸውም። 7 ኪራም
የሰሎሞን መልእክት ሲደርሰው እጅግ ተደሰቶ፣ በእርሱ ፈንታ ተተክቶ በዚህ በታላቅ ሕዝብ ላይ እንዲነግሥ ይህን የመሰለ ጥበበኛ ልጅ ለዳዊት የሰጠው
እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን አለ። 8 ከዚህ በኋላ ኪራም ከዚህ የሚከተለውን መልእክት ለሰሎሞን ላከ፤ የላክልኝን መልእክት ሰምቻለሁ፤ የምትፈልገውን ሁሉ፣
የሊባኖሱን ዛፍና የዝግባውን ግንድ አዘጋጅልሃለሁ። 9 የእኔ ሰዎችም ግንዶችን ከሊባኖስ ወደ ባሕር ያወርዳሉ፤ አስረውም አንተ ወደምትፈልገው ጠረፍ በውኃ
ላይ ተንሳፍፈው እንዲደርሱ ያደርጋሉ፤ በዚያም የእኔ ሰዎች ማሰሪያውን ፈተው ለአንተ ሰዎች ያስረክቡአቸዋል፤ አንተም በበኩልህ ለቤተ ሰቤ ምግብ በመስጠት
ፍላጎቴን ትመልስልኛለህ። 10 በዚህ ዓይነት ኪራም ለሰሎሞን የሚያስፈልገውን የሊባኖሱን ዛፍና የዝግባ ግንድ ሁሉ ሰጠው። 11 ሰሎሞንም በበኩሉ ለኪራም
ቤተ ሰቦች ቀለብ የሚሆን ሃያ ሺህ መስፈሪያ ስንዴና ሃያ መስፈሪያ ንጹሕ ዘይት ሰጠ። ይህንንም በየዓመቱ ይሰጥ ነበር። 12 እግዚአብሔር አስቀድሞ የሰጠውን
የተስፋ ቃል በመጠበቅ ለሰሎሞን ጥበብ ሰጠው፤ በሰሎሞንና በኪራም መካከል ሰላም ነበር፤ ሁለቱም የጋራ ስምምነት አደረጉ። 13 ንጉሥ ሰሎሞን
ከመላው እስራኤል ሠራተኞችን መለመለ፤ የግዳጅ ሠራተኞችም ሠላሳ ሺህ ነበሩ። 14 ዐሥር ሺህ የሚያህሉትን ለአንድ ወር ወደ ሊባኖስ በፈረቃ ላካቸው።
ለአንድ ወር በሊባኖስ ሁለት ወር በቤታቸው ነበሩ። አዶኒራም የተባለው ሰው በግዳጅ ሠራተኞች ላይ ኃላፊ ነበር። 15 ንጉሥ ሰሎሞን በኮረብታማው አገር
ድንጋይ የሚፈልጡ ሰማኒያ ሺህ፣ የተፈለጠውን ድንጋይ ተሸክመው የሚያመጡ ሰባ ሺህ ሰዎች ነበሩት። 16 የእነዚህ ሠራተኞች የበላይ ሆነው ሥራውን
የሚቆጣጠሩ ሦስት ሺህ ሦስት መቶ ሰዎች ነበሩ። 17 በዚህ ዓይነት ሠራተኞቹ በንጉሥ ሰሎሞን ትእዛዝ ለቤተ መቅደሱ መሠረት የሚሆን ታላላቅ ድንጋዮችን
ፈለጡ። 18 የሰሎሞንና የኪራም አናጢዎችና ግንበኞች የጌባላውያንም ሰዎች ቤተ መቅደሱን ለመሥራት የሚያስችላቸውን ድንጋይና እንጨት ሁሉ አዘጋጁ።

---

1 Kings 5:1

አጠቃላይ መረጃ
ሰለሞን ስለቤተመቅደስ ስራው ከንጉሥ ኪራም ጋር አወራ

ኪራም ለዳዊት በዘመኑ ሁሉ ወዳጁ ነበረ
ኪራም ለዳዊት ሁልጊዜ የቅርብ ወዳጁ ነበረ

እግዚአብሔር ከእግሩ በታች እስኪጥልለት ድረስ
ጠላትን ከእግር ስር መጣል ማለት ማሸነፍ ወይም መማረክ ማለት ነው። ተርጓሚ “እግዚአብሔር ዳዊት ጠላቶቹን እንዲያሸንፍ ይረዳው ነበር።” ወይም
“ እግዚአብሔር ዳዊትን ጠላቶቹን እንዲያሸንፍ ይረዳው ስለነበር ዳዊት ጊዜ አልነበረውም።”

በዙሪው ስለነበረ ሰልፍ
ሌላ አማራጭ ትርጉም፦ “በጠላቶቹ ሰፍም ስለተከበበ ወይም “ በሁሉም አቅጣጫ ከጠላቶቹ ጋር ፍልሚያ ላይ ስለነበር”

እግዚአብሔር ከእግሩ በታች እስኪጥልለት ድረስ
ይህ እግዚአብሔር ለዳዊት በጠላቶቹ ላይ ፍፁም በላይነትን ከእግሩ በታች ስለመጣሉ ይናገራል።

1 Kings 5:4

አጠቃላይ መረጃ
ሰለሞን ከንጉሥ ኪራም ጋር ስለ ቤተ-መቅደስ ግንባታው ማውራቱን ቀጥሏል

በዙሪያዬ...ዕረፍት ሰጥቶኛል
ሰለሞን ንጉሥ ከመሆኑ በፊት ንጉሥ ዳዊትና የእስራኤል ሕዝብ በጦርነት ላይ ነበሩ ነገር ግን አሁን ንጉሥ ሰለሞንና የእስራኤል ሕዝብ በእረፍትና በሰላም
ጊዜ ላይ ነበሩ

ጠላትም ክፉም ነገር የለብኝም
ክፋትን የሚያደርግ ሰውም ጉዳት የሚያደርስ የተፈጥሮ ክስተትም። ይህ በዚህ መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ከጠላቶቻችንና ከተፈጥሮ አደጋዎች ተጠብቀናል”

ክፉ ነገር
ጠላት

ጥፋት
በሰዎችና በንብረታቸው ላይ ጉዳት የሚያደርስ ክስተት

ስለዚህ
ይህ ቀጥሎ ካሉት ቃላት አፅንኦት ለመስጠት ነው። “አድምጥ(ጡ) ይህ እኔ የማደርገው ነው።” “ወይም” እግዚአብሔር ለእኔ ስላደረገው ይህ እኔ የማደርገው ነው።

ለስሜ...ለአምላኬ ለእግዚአብሔር ስም
“ስም” የሚለው ቃል ለግለሰብ (ለአንድ ሰው) ዘይቤ ነው። ተርጓሚ አምላኬ እግዚአብሔር የሚኖርበት ቦታ...እኔ የምኖርበት።

በዙፋንህ ላይ የማስቀምጠው
እዚህ ጋር ዙፋን እንደ ንጉሥ መግዛትን ይገልፃል። ተርጓሚ “ከአንተ በኋላ ንጉስ ለማደረግ (ለመሆን ማድረግ)”

1 Kings 5:6

አጠቃላይ መረጃ
ሰለሞን ከንጉሥ ኪራም ጋር ስለ ቤተ- መቅደስ ግንባታው ማውራቱን ቀጥሏል

ከወገኔ እንደ ሲዶናውያን እንጨት መቁረጥ የሚያውቅ እንደሌለ
ያንተ ሠራተኞች ከእኔ ሰዎች የተሻለ እንጨት መቁረጥ ይችላሉ

ሲዶናውያን
የሲዶን ከተማ ሕዝብ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Kings 5:7

አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ኪራም ለሰለሞን መለሰ

የሰለሞንን ቃል
“ሰለሞን ያለው”

እግዚአብሔር ዛሬ ይመስገን
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ዛሬ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ”

ዝግባ
ዝግባ ቤተ-መቅደስ ለመሥራት የሚያገለግል ዋጋ ያለው እንጨት ነው

1 Kings 5:9

አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ኪራም ለሰለሞን መልስ መስጠቱን ቀጥሏል

በታንኳ አድርጌ
እንዲንሳፈፉ አንድ ላይ ማሰር

በዚያም እፈታዋለሁ
ይህ በገቢር መልኩ ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ ሰራተኞቼ ግንዶቹን ይፈታሉ

አንተም ፈቃዴን ታደርጋለህ
“የምፈልገውን ማድረግ ትችላለህ” ወይም “ልትከፍለኝ ትችላለህ”

1 Kings 5:10

አጠቃላይ መረጃ
ጥድ የሚለው ቃል ብዙ አይነት ዛፎችን ሊገልጽ ይችላል። ዝግባንም ጨምሮ

መስፈሪያ ስንዴ **(ቆሮስ)**
ይህ የደረቅ ነገር መስፈሪያ ሲሆን ኮርም ደግሞ የፈሳሽ ነገር መስፈሪያ ነው። የትኛው መስፈሪያ እንደታሰበ ግልፅ አይደለም።

በየአመቱ
ከአመት ወደ አመት(በየአመቱ)

1 Kings 5:13

አጠቃላይ መረጃ
ሰለሞን ቤተ መቅደሱ እንዲገነባ ሰዎችን አስገደደ

ከእስራኤል ሁሉ ገባሮቹን መርጦ
እንዲሠሩ ገባሮቹን ከእስራኤል ሁሉ

በየወሩ
ያ ማለት አንድ ወር በሊባኖስ ሁለት ወር ደግሞ በቤት የሚቆዩ ሦስት ወገኖች ነበሩ

አንድ ወርም በሊባኖስ ሁለት ወርም በቤታቸው
እያንዳንዱ ወገን (ግሩፕ) አንድ ወር በሊባኖስ በሥራ ላይ ከዚያ ደግሞ ሁለት ወር በእስራኤል በቤታቸው የሚቆዩ ነበሩ።

ገባሮቹን ...ሰዎች
ይህ በገቢር መልኩ ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ “እንዲሠሩለት ሰለሞን የመረጣቸው (ያስገደዳቸው) ሰዎች።”

1 Kings 5:15

አጠቃላይ መረጃ
ሰለሞን ቤተ-መቅደሱ እንዲሠራ ሠዎችን ማስገደዱን ቀጥሏል።

ሰባ ሺህ
70,000

ሰማንያ ሺህ
80,000

ጠራቢዎች
ድንጋይ ከመሬት ቆፍረው በሚፈለገው ቅርፅ የሚጠርቡ ሰዎች

3,300 ሹሞች
“ሶስት ሺህ ሶስት መቶ ሹሞች”

1 Kings 5:17

አጠቃላይ መረጃ
ሰለሞን ቤተ-መቅደሱ እንዲሠራ ሠዎችን ማስገደዱን ቀጥሏል።

ታላላቅ ምርጥ ምርጥ ድንጋዮችን ይቆፋፍሩና ይጠርቡ ዘንድ
“ከተራራው ወስጥ ጥሩና ትልልቅ ድንጋዮችን ቆፈሩና በሚፈለገው ቅርፅ ጠረቡ”

ጌባላውያን
ከጌባል ከተማ ሕዝብ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 6

1 ስለዚህ ሰሎሞን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ መሥራት ጀመረ። ይህም የእስራኤል ሕዝብ ከግብጽ ምድር ከወጡ ከአራት መቶ ሰማኒያ ዓመት በኋላ፣ ሰሎሞን በእስራኤል ላይ በነገሠ በአራተኛው ዓመት ዚፍ ተብሎ በሚጠራው በሁለተኛው ወር ነበር። 2 ቤተ መቅደሱም በውስጥ በኩል ርዝመቱ ሃያ ሰባት ሜትር፣ ወርዱ ዘጠኝ ሜትር፣ ቁመቱ ዐሥራ ሦስት ሜትር ተኩል ነበር። 3 በመግቢያው በር የሚገኘው በረንዳ ቁመቱ አራት ሜትር ተኩል፣ ወርዱ ልክ እንደ ቤተ መቅደሱ ዘጠኝ ሜትር ነበር። 4 የቤተ መቅደሱም ሕንፃ ከውስጥ ሰፋ፣ ከውጪ ጠበብ ያሉ መስኮቶች ነበሩት። 5 በቤተ መቅደሱን ሕንፃ ፊት ለፊት ግድግዳ ዙሪያ ክፍሎችን ሠራ፤ በዋናው መግቢያ በር በውጪና በውስጥ ክፍሎች ሠራ፤ በዙሪያውም ክፍሎችን አደረገ። 6 የታችኛው ፎቅ ክፍል ወርዱ አምስት ክንድ፣ የመካከለኛ ፎቅ ክፍል ስድስት ክንድ፣ የሦስተኛው ፎቅ ክፍል ወርድ ሰባት ክንድ ነበር፤ የእንያዳንዱ ወለል ግንብ ከታች በኩል ካለው የወለል ግንብ የሳሳ ነበር፤ ሠረገሎቹ ወደ ቤተ መቅደሱ ግድግዳ እንዳይገቡ ለማድረግ ከቤተ መቅደሱ ግድግዳ ውጪ ዐረፍቶችን አደረገ። 7 ቤተ መቅደሱ የታነጸባቸው ድንጋዮች ተጠርበው የተዘጋጁት በዚያው በተፈለጡበት ቦታ ነበር፤ ቤተ መቅደሱ በሚሠራበት ጊዜ የመዶሻ፣ የመጥረቢያ ወይም የሌላ ብረት ነክ መሣሪያ ድምፅ አይሰማም ነበር። 8 ከቤተ መቅደሱ በስተደቡብ በኩል በምድር ደረጃው ላይ መግቢያ በር ነበር። ከዚያ በደረጃዎቹ መካከለኛ ደረጃ ወደ ላይ ያስኬዳል። እንዲሁም ከመካከለኛው ደረጃ ወደ ሦስተኛ ደረጃ ይወስዳል። 9 በዚህ ሁኔታ ሰሎሞን የቤተ መቅደሱን ሕንፃ ሥራ ፈጸመ፤ ጣራውንም ከውስጥ በኩል ከሊባኖስ ዛፍ እንጨት በተሠራ አግዳሚ ሠረገላና ጠርብ ቤቱን ሸፈነው። 10 የእያንዳንዱ ፎቅ ቁመት አምስት ክንድ ከፍታ ሆኖ ከውጪ በኩል ወደ ቤተ መቅደሱ ተጠግቶ የተሠራው ባለ ሦስት ፎቅ ተጨማሪ ሕንፃ ከዋናው ሕንፃዎች ከሊባኖስ ዛፍ በተሠሩት አግዳሚ ወራጆች የተያያዘ ነበር። 11 የእግዚአብሔር ቃል ወደ ሰሎሞን እንዲህ ሲል መጣ፦ 12 እየተሠራ ያለውን ቤተ መቅሰደስ በተመለከተ፣ በትእዛዜ መንገድ ብትሄድና ቅን ፍርድ ብታደርግ ለአባትህ ለዳዊት እንዳደረግሁ የሰጠሁትን ተስፋ አጸናልሃለሁ። 13 በሕዝቤ በእስራኤል መካከል እኖራለሁ፣ ከቶም አልተዋቸውም። 14 ስለዚህ ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን ሠርቶ ጨረሰ። 15 ከዚያ የቤተ መቅደሱን የውስጥ ግድግዳዎች በሊባኖስ ዝግባ ሠራ፤ ከወለሉ እስከ ጣራው ድረስ ከሊባኖስ ዛፍ እንጨት ተጠርቦው በተሠሩ ሳንቃዎች ለበደ፤ የወለሉም ጣውላ ከሊባኖስ ዛፍ እንጨት የተሠራ ነበር። 16 ውስጣዊ ክፍል ከቤተ መቅደሱ በስተ ኋላ ገባ ብሎ ተሠራ፣ የእርሱም ርዝመት ዘጠኝ ሜትር ሲሆን ከወለሉ እስከ ጣራው ድረስ ከሊባኖስ ዛፍ እንጨት ተጠርቦ በተሠራ ሳንቃ የተከፈለ ነበር፤ ይህንን ክፍል ቅድሰተ ቅዱሳን ውስጠኛ ክፍል እንዲሆን ነው። 17 ከቅድስተ ቅዱሳኑ ፊት ለፊት የሚገኘውም የተቀደሰ ክፍል ርዝመት አርባ ክንድ ነበር። 18 የሊባኖስ ዛፍ እንጨት ሳንቃዎች በአበባ እንቡጦችና በፈኩ አበባዎች ቅርጽ አኒጠው ነበር፤ ውስጡም ሁሉ ከሊባኖስ ዛፍ እንጨት ተጠርቦ በተሠራ ሳንቃ ስለ ተለበጠ የግንቡ ድንጋዮች አይታዩም ነበር። 19 ሰሎሞንም ከቤተ መቅደሱ ውስጥ በስተኋላ በኩል የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት የሚቀመጥበት ውስጣዊ ክፍል አዘጋጀ። 20 ይህም ውስጣዊ ክፍል ርዝመቱ ዘጠኝ ሜትር፣ ወርዱ ዘጠኝ ሜትር፣ ቁመቱ ዘጠኝ ሜትር ሲሆን፣ በሙሉ በንጹሕ ወርቅ የተለበጠ ነበር፤ መሠዊያውም ከሊባኖስ ዛፍ እንጨት ተጠርቦ በተሠራ ሳንቃ የተለበጠ ነበር። 21 ሰሎሞንም ቤተ መቅደሱን በውስጥ በኩል በንጹሕ ወርቅ ለበጠው፤ እርሱም ክፈፉን በተሸጋገሩ የወርቅ ሰንሰለቶች አስጌጠው። 22 የቅድስት ቅዱሳኑ ውስጠኛ በወርቅ ለበጠው። 23 ሰሎሞንም እያንዳንዱ ዐሥር ክንድ የሆነ ከወይራ እንጨት በሁለት ኪሩቤል አምሳል የተቀረጹ ሥዕሎች በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ ሠራ። 24 የኪሩቡ አንደኛው ክንፍ አምስት ክንድ፤ የኪሩቡም ሁለተኛው ክንፍ አምስት ክንድ ነበረ፤ ከአንደኛው ክንፍ ጫፍ ጀምሮ እስከ ሁለተኛው ክንፍ ጫፍ ድረስ ዐሥር ክንድ ነበረ። 25 ሁለተኛውም ኪሩብ ዐሥር ክንድ ነበረ፤ የሁለቱም ኪሩቤል ቅርጽና መጠን ተመሳሳይ ነበር። 26 የአንዱ ኪሩብ ቁመት ዐሥር ክንድ ነበረ፤ የሁለተኛውም ኪሩብ እንዲሁ ነበረ። 27 ኪሩቤልንም በቅድስት ቅዱሳኑ ውስጥ እንዲቆሙ አደረገ፤ ስለዚህም የተዘረጉ ሁለቱ ክንፎቻቸው በክፍሉ መካከለኛ ቦታ ላይ ተገናኝተው ሌሎቹ ሁለቱ ክንፎቻቸው ደግሞ በተዘረጉበት አቅጣጫ ግንቦቹን ይነኩ ነበር። 28 ሰሎሞንም ሁለቱን ኪሩቤል በወርቅ ለበጣቸው። 29 የዋናውን ክፍልና የውስጠኛውን ክፍል ግንቦች በሙሉ በኪሩቤል፣ በዘንባባ ዛፎችና በፈኩ የአበባ ቅርጾች አስጌጣቸው። 30 እርሱም ከውስጥና ከውጪ በኩል ያሉትን ክፍሎች ወለል በወርቅ ለበጣቸው። 31 ከወይራ እንጨት የተሠራ ሁለት ተካፋች በር በቅድስተ ቅዱሳኑ መግቢያ እንዲቆም አደረገ፤ በሩም አምስት ማእዘን ያለው ሆኖ አናቱ ላይ ቀጥ ብሎ የተሠራ ቅስት ነበር። 32 ሁለቱን በሮች በኪሩቤል፤ በዘንባባ ዛፎችና በፈኩ የአበባ ቅርጾች አስጌጣቸው፤ እርሱም በሮቹን፣ ኪሩቤልን፣ የዘንባባ ዛፎቹንና ቅርጾቹን በወርቅ ለበጣቸው። 33 በዚህ ዓይነት ሰሎሞን ደግሞ ወደ ዋናው ክፍል ለሚያደርሰው መግቢያ በር ከወይራ እንጨት የተሠራ ባለ አራት ማእዘን ክፈፍ አበጀለት። 34 ሁሉቱንም በሮች ከዝግባ እንጨት ሠራ፤ አንዱ በር በማጠፊያ ከተያያዘ ከሁለት ሳንቃ ተደረገ፤ ሁለተኛውም በር በማጠፊያ ከተያያዘ ከሁለት ሳንቃ ተደረገ። 35 እነርሱን ሙሉ በሙሉ በወርቅ በተለበጡ በኪሩቤል፣ በዘንባባ ዛፎችና በፈኩ የአበባ ቅርጾች አስጌጣቸው። 36 በቤተ መቅደሱ ፊት ለፊት አንድ የውስጥ አደባባይ ሠራ፤ በዚህም አደባባይ ዙሪያ በየሦስቱ ዙር የድንጋይ ረድፍ አንድ የሊባኖስ ዛፍ ሠረገላ ሳንቃ የተጋደመበት ግንብ አደረገ። 37 የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ መሠረቱ የተጣለው ሰሎሞን በነገሠ በአራተኛው ዓመት ዚፍ ተብሎ በሚጠራው በሁለተኛው ወር ነበር። 38 ሰሎሞን በነገሠ በዐሥራ አንደኛ ዓመቱ ቡል ተብሎ በሚጠራው በስምንተኛው ወር ላይ የቤተ መቅደሱ ሁሉም ክፍሎችና ሁሉም ንድፍ ተጠናቀቀ። ሰሎሞንም ቤተ መቅደሱን ለመሥራት ሰባት ዓመት ወሰደበት።

---

1 Kings 6:1

አጠቃላይ መረጃ
ተራኪው የቤተ-መቅደሱን ልኬት (ወርድና ስፋት) ዝርዝር

ሰለሞን .....መሥራት ጀመረ
ሰለሞን ሠራተኞቹን ሕንፃውን እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ “ግንባታውን እንዲጀምሩ ሠለሞን ሠራተኞቹን አዘዘ”

480ኛ .....አራተኛ
ይህ የ480 እና 4 ተራ አቀማመጥ ነው።

ዚፍ በሚባለው በሁለተኛው ወር
“ዚፍ” በእብራዊያን በቀን መቁጠሪያ የሁለተኛው ወር ስም ነው። ይህ የሚያዚያ ወር መጨረሻ ወይም የግንቦት ወር መጀመሪያ ገደማ ነው (በአውሮፓ አቆጣጠር)

ስድሳ **(**ስልሳ**)** ክንድ ወርድ፣ ሃያ ክንድ ስፋት ና ሠላሳ ክንድ ርዝመት
60 ክንድ ወርድ፣ 20 ክንድ ስፋትና ቁመቱም ሠላሳ ክንድ። አንድ ክንድ 46 ሴ.ሜ ነው። ይህ በዘመናዊ መስፈሪያ እንደገና ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ 27.6 ሜትር ወርድ፣ 9.2 ሜትር ስፋትና 13.8 ሜትር ከፍታ (ርዝመት)

1 Kings 6:3

አጠቃላይ መረጃ
ተራኪው የቤተ- መቅደሱን ልኬት መዘርዘሩን ቀጥሏል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወለል
በኮለን የተሰራ የአንድ ሕንፃ ክፍል ሆኖ ጣሪያው ወደ ሕንፃው መግቢያ በር ይመራል። ይህ ወለል ምናልባት ከፍተኛው የሕንፃ ግድግዳ ጋር የሚገኝና ቤተ መቅደሱን የከበበ ነው።

ሃያ ክንድ...አስር ክንድ
አንድ ክንድ= 46ሳ.ሜ ነው።ተርጓሚ “9.2ሜ...4.6ሜ”

መስኮቶች አደረገ
ሰለሞን ሠራተኞቹን ሕንፃውን እንዲሰሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ “መስኮቶችን አደረጉ”

1 Kings 6:5

አጠቃላይ መረጃ
ተራኪው የቤተ-መቅደሱን ልኬት መዘርዘሩን ቀጥሏል

ሠራ....አደረገ
ሰለሞን ሠራተኞቹን ሕንፃውን እንዲሰሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ “ሰሩ.... አደረጉ”

በዙሪያውም ጓዳዎችን አደረገ
“በውጭ በኩል ካለው ግድግዳ ዙሪያ ጓዳዎችን አደረገ”

የታችኛውም ደርብ...የመካከለኛውም ደርብ...የሦስተኛውም
ይህ በእያንዳንዱ ወለል ያሉትን ጓዳዎች ይወክላል

አምስት ክንድ...ስድስት ክንድ...ሰባት ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሴ.ሜ ነው። ተርጓሚ “2.3 ሜ ገደማ...2.8 ሜ ገደማ... 3.2ሜ ገደማ”

ከቤቱ ግንብ ውጭ ዓረፍቶች አደረገ
“የትንንሽ ጓዳዎቹን አግዳሚ እንዲረዳ (እንዲደግፍ) በዋናው ግንብ ዙሪያ ሁሉ ድጋፍ አደረጉ”

አግዳሚ
አግዳሚ ሕንፃ (ቤት) የሚደግፍ ረጅምና ከባድ እንጨት ነው።

1 Kings 6:7

ቤቱም
እዚህ ጋር “ቤት” የእግዚአብሔርን ቤት (ቤተ-መቅደስን) ይገልፃል።

ፈፅመው በተወቀሩ ድንጋየች
ውቅር (ካባ) ሠዎች በመሳሪያ ከተራራ ሥፍራ ድንጋይ ጠርበው ቅርፅ የሚሰጡበት ቦታ ነው። በካባው ቦታ ካዘጋጁ በኋላ ወደ ቤተ-መቅደሱ ያመጡታል።

የታችኛው ደርብ...መካከለኛው ደርብ...ሦስተኛው ድርብ
በአጠቃላይ ሦስት ወለሎች ነበሩ። አንዳንድ ቋንቋዎች ይህ የታችኛው ወለል፣ አንደኛ ወለል (ፎቅ) እና በሁለተኛ ወለል (ፎቅ) ይሉታል።

1 Kings 6:9

ሰለሞን ሠርቶ...ከደነው...አጋጠማቸው
ሠለሞን ሠራተኞቹን ሕንፃውን እንዲሰሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ የሰለሞን ሠራተኞች ሠሩ...ከደኑ...አጋጠሙ።

በዝግባ...ደርብ (አግዳሚ)
ደርብ (አግዳሚ) ...ህንፃን (ቤትን) የሚደግፍ ረጅምና ከባድ እንጨት ነው። የ 1ነገስት 6፡6 ትርጉምን ተመልከት

በዝግባው...ሳንቃዎች
ሳንቃ ጠፍጣፋና ልሙጥ እንጨት ሲሆን ለወለልና ለግድግዳ የሚያገለግል ነው።

ቤቱን ሠርቶ
በ1ነገስት 6፡5 የተጠቀሱትን አይነት ጓዳዎች ጋር ይመሳሰላል።

በቤቱም ሁሉ ዙሪያ
ይህ ሐረግ ለተሸፈኑት ግድግዳዎች ዘይቤአዊ ንግግር ነው። ተርጓሚ የውስጠኛውን ክፍል የሸፈነ የውጭ ግድግዳ

አምስት ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሴ.ሜ ነው። ተርጓሚ “2.3ሜ”

በዝግባ እንጨት
እንጨት የሚለው ቃል ለግንባታ ለሚያገለግሉ እንጨቶች የወለል ስም ነው። ለምሳሌ አግዳሚና ሳንቃ

1 Kings 6:11

የእግዚአብሔር ቃል ወደ ሰለሞን መጣ እንዲህ ሲል - ስለዚህ
የእግዚአብሔር ቃል...መጣ የሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ከእግዚአብሔር የተለየ መልዕክት እንዳለ ለማመልከት ነው። ተርጓሚ “እግዚአብሔር ለሰለሞን መልዕክት ሰጠ።” እንዲህ ሲል “ስለዚህ” ወይም እግዚአብሔር ለሰለሞን ይህን መልዕክት ተናገረ- ስለዚህ

ስለምትሰራው ቤት
ሰለሞን ሠራተኞቹ ሕንፃውን እንዲሰሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ “ሠራተኞችህ ስለሚሰሩት ቤት”

በሥርዓቴ ብትሄድ
“ብትሄድ” የሚለው ቃል “ብትኖር” ለሚለው ቃል ዘይቤ ነው። ወይም “ብትታዘዝ” ተርጓሚ “በየጊዜው ሥርዓቴን ሁሉ ታዘዝ (ጠብቅ)”

ፍርዴንም ብታደርግ
አማራጭ ትርጉሞች 1) “ሕጌን ሁሉ አድርግ (ጠብቅ)” ወይም 2) “የምትመራውን ህዝብ በቅንነት ምራ”

ትመላለስባትም ዘንድ ትዕዛዜን ሁሉ ብትጠብቅ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሰረቱ አንድ አይነትሲሆኑ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የመጠበቅን አስፈላጊነት አፅንዖት ለመስጠት ነው። ተርጓሚ “እንድታደርግ የነገርኩህን ሁሉ በጥንቃቄ ታዘዝ”

ለአባትህ ለዳዊት የነገርሁትን ቃል ከአንተ ጋር አፀናለሁ
“ለአንተ አደርጋለሁ ብዬ ለዳዊት ቃል የገባሁትን ሁሉ አደርጋለሁ”

1 Kings 6:14

ሰለሞንም ቤቱን ሰራው ፈፀመው...መሠረቱን ...ለበጠው
ሰለሞን ሠራተኞች ሕንፃውን እንዲሰሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ “የሰለሞን ሠራተኞች ቤቱን ሰሩት፤ፈፀሙት...መሰረቱን ለበጡት”

የቤቱንም...ውስጡን
“በየጓዳዎቹ (ክፍሎቹ) መካከል ያሉትን ግድግዳዎች”

1 Kings 6:16

ሃያ ክንድ...ጋረደ...የቤቱንም ውስጥ ...ለበጠው
ሰለሞን ሰራተኞቹ ሕንፃውን እንዲሰሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ “ሃያ ክንድ እንዲጋርዱ...የቤቱንም ውስጥ እንዲለብጡ አዘዛቸው”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሃያውን ክንድ ጋረደ
“ሃያ ክንድ የሚረዝም ክፍል ሠራ”

ሃያ ክንድ...አርባ ክንድ
አንድ ክንድ 46ሴ.ሜ ነው። ተርጓሚ “9.2 ሜ...18.4ሜ”

ቅድስተ- ቅዱሳት
“ዋናው ክፍል (ጓዳ)”

በፈነዳ አበባ
“የፈነዳ አበባ”

1 Kings 6:19

አበጀ ..... ለበጠው
ሰለሞን ሠራተኞቹ ሕንፃውን እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ “አበጁ....ለበጡት

ሀያ ክንድ
“9.2 ሜ”

ቅድስተ-ቅዱሳኑን በዝግባ እንጨት ሸፈነው
“ይህ ቅድስተ-ቅዱሳን እጣን ለማጨስ ያገለግል ነበር”

1 Kings 6:23

ሠራ
“ሰለሞን እነሱ (ሠራተኞች) እንዲሠሩት አዘዘ”

የወይራ እንጨት
ከወይራ ዛፍ የሆነ እንጨት

አስር ክንድ ....አምስት ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሴ.ሜ ነው። ተርጓሚ “4.6.ሜ....2.3 ሜ”

ክንፉ ድረስ
ከአንደኛው ክንፍ ጫፍ እስከ ሌላኛ ክንፋ ጫፍ ድረስ ያለ ርቀት

አንድ መልክ
ተመሣሣይ መጠን

1 Kings 6:27

አኖራቸው ..... ለበጣቸው
ይህን ሥራ ሠለሞን ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ “አኖሯቸው .....ለበጧቸው”

በውስጠኛው ቤት
በጣም ለተቀደሠ ሥፍራ የተለየ ሥም ነው

ደሠ ሥፍራ የተለየ ሥም ነው ለበጣቸው
“ሸፈነ” የ1 ነገስት 6:21 ትርጉምን ተመልከት

1 Kings 6:29

ቀረፀ..... ለበጠ
ሰለሞን ሰራተኞቹ ሥራውን እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ “ እንዲቀርፁ አዘዛቸው ..... እንዲለብጡ አደረጋቸው”

ለበጠ
ሸፈነ

1 Kings 6:31

ሰለሞን አደረገ...እርሱ ሰራ ...ለበጠ
ይህን ሥራ ሰለሞን ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል ተርጓሚ “እነርሱ አደረጉ.... እነርሱ ሰሩ..... እነርሱ ለበጡ”

መቃን
በላይኛው የበር ክፍል ያለ ማዕዘን (መቃን) ማዕዘን በአምስቱም በኩል የሚገኝ የቤተ መቅደስ ሥፍራ

1 Kings 6:33

አደረገ ...ቀረፀ ....ለበጠ
ይህን ሥራ ሰለሞን ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ “እነርሱ አደረጉ ....ቀረፁ .....ለበጡ”

እንዲሁም ለመቅደሱ መግቢያ ከወይራ እንጨት አራት ማዕዘን መቃን አደረገ። ሁለቱምን ደጆች ከጥድ እንጨት ሠራ
“ሰለሞን እንዲሁ ለመቅደሱ መግቢያ አራት ማዕዘን መቃን ከወይራ እንጨት አደረገ። ሁለት የጥድ እንጨት በር ደግሞ በተመሣሣይ መልኩ አደረገ”

ማዕዘን -
በአምስት የቤተ መቅደስ ክፍል ገፅ የሚገኝ

ሁለተኛው ደጅ
“ይህ ማለት እያንዳንዱ በር ሁለት ክፍል ሲኖረው በማጠፊያ የተገናኙና በአንድ ላይ እንዲታጠፍ ተደርገዋል።”

1 Kings 6:36

ሁለተኛውንም አደባባይ... ሠራው
ይህን ሥራ ሰለሞን ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ “ሁለተኛውንም አደባባይ ....ሠሩት”

በዝግባ ሳንቃ (በሌላ ቦታ አግዳሚ ተብሎ ተተርጉሟል)
ሳንቃ ሕንፃውን የሚደግፍ ረጅም ከባድ እንጨት ነው። የ1 ነገስት 6፡6 ትርጉምን ተመልከት።

1 Kings 6:37

በአራተኛው አመት ... በአሥራ አንደኛውም አመት
“አራተኛ” ና “አሥራ አንደኛ” የሚሉት ቃላት የ “አራት” ና “የአሥራ አንድ” ተራ ማሣያ ናቸው ፀሐፊው ከሚቆጥረው ተነስተህ ድርጊቱን ግልፅ ልታደርገው ትችል ይሆናል። ተርጓሚ “ሰለሞን ከነገሰበት ጊዜ ጀምሮ አራተኛው አመት....አስራ አንደኛው አመት ሠለሞን ንጉሥ ከሆነ በኋላ።”

የእግዚአብሔር ቤት
“ቤተ መቅደሱ”

ዚፉ በሚባል ወር
“ዚፉ” በእብራዊያን ቀን አቆጣጠር ሁለተኛው ወር ነው። ይህም የሚያዝያ ማገባደጃ ሳምንትና የግንቦት የመጀመሪያቹ ሳምንታት (በአውሮፓዊያኑ የቀን አቆጣጠር) ማለት ነው። የ1 ነገሥት 6፡1 ትርጉምን ተመልከት

ቡል በሚባል በስምንተኛው ወር
“ቡል” በእብራዊያን ቀን አቆጣጠር ስምንተኛው ወር ነው። ይህም የጥቅምት ወር ማገባደጃ ሳምንትና የሕዳር ወር የመጀመርያው ሳምንት (በአውሮፓዊያኑ አቆጣጠር) ማለት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ቤቱ እንደ ክፍሎቹና እንደ ሥርዓቱ ሁሉ ተጨረሰ
ይህ በገቢር መልኩ ሊተረጎም ይችላል።ተርጓሚ “የቤቱን ክፍሎች ሁሉ ሠርተው ጨረሱ። ሰለሞን ሥሩ ባላቸው መሠረት ሠርተው ጨረሱ”

...ውስጥ ሠራው
ይህን ሥራ ሰለሞን ለሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። የሰለሞን ሠራተኞች...ውስጥ ሠሩ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 7

1 ሰሎሞንም ለራሱ የሚሆን ቤተ መንግሥት ሠራ፤ ቤተ መንግሥቱንም ለመሥራት ዐሥራ ሦስት ዓመት ፈጀበት። **2** እርሱም የሊባለኖስ ጫካ ተብሎ የተጠራውን ቤተ መንግሥት ሠራ። ርዝመቱም ወርዱ አንድ መቶ ክንድ፣ ስፋቱም አምሳ ክንድ፤ ቁመቱም ሠላሳ ክንድ ነበር። ቤተ መንግሥቱ አራት ረድፍ ሆኖ ከዝግባ እንጨት ምሰሶዎች የተሠሩ ሲሆን፣ በምስሶዎቹ ላይ አግዳሚ ሠረገላዎች ተጋድመው ነበር። **3** የእነዚህ ዕቃ ቤቶች ጣራ ከሊባኖስ ዛፍ እንጨት የተሠራ ነበር። በምስሶዎቹም ላይ በነበሩ አግዳሚዎች ቤቱ በዝግባ ሳንቃ ተሸፍኖ ነበር። ምስሶዎቹም በአንዱ ረድፍ ዐሥራ አምስት፣ በአንዱ ረድፍም አምስት እየሆኑ አርባ አምስት ነበሩ። **4** ትይዩ የሆኑት የሕንፃው ሁለት ግንቦች እያንዳንዳቸው በመደዳ ሦስት፣ ሦስት መስኮቶች ነበሩአቸው። **5** በሮቹና መስኮቶቹ ሁሉ ባለአራት ማእዘን መቃኖች ነበሩአቸው፤ ለእያንዳንዱ ግንብ በረድፍ የተሠሩ ሦስት ሦስት መስኮቶች ነበሩት፤ የእያንዳንዱ ግንብ መስኮቶች ከሌላው ግንብ መስኮቶች ጋር ትይዩ ነበሩ። **6** ምሰሶዎች ያሉበትን ቤት ሠራ፤ ርዝመቱም አምሳ ክንድ፣ ስፋቱም ሠላሳ ክንድ ነበረ፤ በእርሱም ፊት ደግሞ ምሶሶና መድረክ ያለበት ወለል ነበረ። **7** ሰሎሞን ችሎት ተቀምጦ የፍርድ ውሳኔ የሚሰጥበትም የዙፋን አዳራሽ ሠራ። ከወለሉ እስከ ጣራው ድረስ ከሊባኖስ ዛፍ እንጨት በተሠራ ሳንቃ የተሸፈነ ነበር። **8** ከችሎቱም አዳራሽ በስተ ኋላ በሚገኘው ሌላ አደባባይ ሰሎሞን የሚኖርበትን ሕንጻ እንደ ሌሎቹ ሕንጻዎች አድርጎ አሠራ፤ የግብጽ ንጉሥ የፈረዖን ልጅ ለነበረቸው ሚስቱም ተመሳሳይ መኖሪያ ቤት አሠራለት። **9** እነዚህ ሁሉ ሕንፃዎችና ታላቁ አደባባይ ጭምር ከመሠረታቸው እስከ ድምድማታቸው በጥሩ ታላላቅ ድንጋዮች አኒጠው የተሠሩ ነበሩ፣ ድንጋዮቹም በዚያ በድንጋይ መፍለጫ ስፍራ በፊትም በኋላም በልክ ተፈልፍለውና ተጠርበው የመጡ ነበር። **10** የቤቱ መሠረት የተሠራው በጣም ታላላቅና ውድ በሆኑ ስምንትና ዐሥር ክንድ ርዝመት ባላቸው ድንጋዮች የተሠሩ ነበር። **11** እነዚህም ውድና በልክ ከተፈለፈሉ ድንጋዮችና ከሊባኖስ ዛፍ እንጨት የተሠሩ አግዳሚ ሠረገሎች ነበሩ። **12** የቤተ መንግሥቱ አደባባይ ወደ ቤተ መቅደሱ የሚያስገባው በር በእያንዳንዱ ባለ ሦስት ረድፍ የጥርብ ድንጋይ ሕንፃ ላይ አንዳንድ ረድፍ የሊባኖስ ዛፍ እንጨት ሠረገላ የተጋደመባቸው ግንቦች ነበሩ። **13** ንጉሡ ሰሎሞንም ሔራም የተባለውን ሰው ከጢሮስ ከተማ አመጣ። **14** ሔራም እናቱ ባል የሞተባት የንፍታሌም ነገድ ተወላጅ ነበረች፣ አባቱም የጢሮስ ተወላጅ ሲሆን እርሱም ነሐስ አቅልጦ በመሥራት ጥበብ የሠለጠነ ባለሙያ ነበር። ሔራም በእጅ ጥበብ ብዙ ልምድ ያለው ብልህ ሰው ነበር፤ እርሱም የነሐስ ጥበብ ሥራ ለንጉሡ ለመሥራት ወደ ንጉሥ ሰሎሞን መጣ። **15** ሔራም የእያንዳንዳቸው ቁመት ዐሥራ ስምንት ክንድ፣ የዙሪያ ስፋታቸው ዐሥራ አምስት ክንድ ሁለት የነሐስ ምሶሶዎችን ሠራ። **16** እንዲሁም በምሶሶዎቹ ላይ የሚቆሙ የእያንዳንዳቸው ቁመት አምሰት ክንድ የሆነ ሁለት የነሐስ ጉልላቶችን ሠራ። **17** በምሶሶዎቹም ራስ ላይ የነበሩትን ጉልላቶች ያስጌጡ ዘንድ በሰባት ረድፍ የተሠሩ መረቦችን ሠራ። አንዱን መረብ ለአንድ ጉልላት ሁለተኛውን መረብ ለሁለተኛው ጉልላት አደረገ። **18** ስለዚህም ሔራም ምሶሶዎቹ ጫፍ ላይ ያሉትን ጉልላቶች ለማስጌጥ ሮማኖችን በሁለት ረድፍ ሠራ። ለየእያንዳንዱም ጉልላት እንዲሁ አደረገ። **19** በወለሉ ምሶሶዎች አናት ላይ ያሉት ጉልላቶች ቁመታቸው አራት ክንድ ሲሆን የሱፍ አበባን በሚመስል ሥራ ተጊጠው ነበር። **20** እነርሱም ከመረቡ በላይ ባለው ክብ ስፍራ እንዲቆሙ ተደረገ፤ በእያንዳንዱም ጉልላት ዙሪያ በሁለት ረድፍ የተደረደሩ ሁለት መቶ የሮማን ቅርጾች ነበሩ። **21** ሔራም ከነሐስ የተሠሩትን ሁለት ምስሶዎች በቤተ መቅደሱ መግቢያ በር ፊት ለፊት አቆማቸው። ከቤተ መቅደሱም መግቢያ በር በስተደቡብ በኩል የቆመው ምሶሶ «ያኪን» ተብሎ ተጠራ፤ በስተ ሰሜን በኩል የቆመው ምሶሶ ደግሞ «ቦዔዝ» ተባለ። **22** በምሶሶዎቹ ጫፍ ላይ የሱፍ አበባ የሚመስሉ ከነሐስ የተሠሩ ጉልላቶች ነበሩ። የምስሶዎቹም ሥራ በዚህ ዓይነት ተፈጸመ። **23** ሔራም ዐሥር ክንድ ጥልቀት፣ የክብ ማእከል ርዝመት አምስት ክንድ ዙሪያ ያለው አንድ ክብ ገንዳ ከነሐስ ሠራ። ባሕሩም ዙሪያው ሠላሳ ክንድ ነበር። **24** የገንዳው አፍ ውጪኣዊ ክፈፍ ሁሉ ከገንዳው ጋር አንድ ወጥ ሆነው በቅል አምሳል ከነሐስ የተሠሩና በሁለት ረድፍ የተደረደሩ ቅርጾች ነበሩት። **25** ገንዳውም ከነሐስ በተሠሩ ዐሥራ ሁለት የበሬ ምስሎች ጀርባ ላይ ተቀመጠ። ኮርማዎቹም በየአቅጣጫው ፊታቸውን ወደ ውጪ መልሰው ሦስቱ ወደ ሰሜን፤ ሦስቱ ወደ ደቡብ፣ ሦስቱ ወደ ምሥራቅ፣ ሦስቱ ወደ ምዕራብ የሚመለከቱ ይመስሉ ነበር። **26** የገንዳውም ጎኖች ውፍረት አንድ መዳፍ ነበር፤ የጽዋ ቅርጽ ያለው አበባ የሚመስል የአፉ ክፈፍ የሱፍ አበባ ቅርጽ ነበረው፤ ይህም ገንዳ አርባ ሺህ ሊትር ያህል ውሃ የሚይዝ ነበር። **27** ሔራም ዐሥር መቀመጫዎችን ከነሐስ ሠራ። የእያንዳንዱ ርዝመት አራት ክንድ፣ ቁመቱ አራት ክንድ፣ ሦስት ክንድ ስፋት ነበር። **28** የመቀመጫዎቹ ሥራም እንዲህ ነበር። የዕቃ መቀመጫዎቹም የተሠሩት በክንፎቹ መካከል ልሙጥ በሆነ ነገር ነበር። **29** ልሙጥ በሆነውም ነገር ላይ በአንበሶች፣ በበሬዎችና በኪሩቤል አምሳል የተቀረፁ ምስሎች ነበሩ። ከአንበሶቹ፣ ከበሬዎቹና ከኪሩቤሉ ቅርፆች ራስጌና ግርጌ የአበባ ጉንጉን የሚመስሉ ቅርፆች ነበሩ። **30** እያንዳንዱ የዕቃ ማስቀመጫ ከነሐስ የተሠሩ አራት መንኮራኩሮች ነበሩባቸው። መንኮራኩሮቹም የሚሽከረከሩበት የነሐስ ወስከምቶች ነበራቸው፤ እንዲሁም በአራቱ ማእዘኖች የመታጠቢያ ገንዳ መደገፊያዎች ነበሩ፤ መደገፊያዎቹም የአበባ ጉንጉን በሚመስሉ ቅርፆች አኒጠው ነበር። **31** የመታጠቢያ ገንዳውም አንገት አንድ ክንድ ነበር፤ እርሱም ክብ ነበር፤ ቁመቱም አንድ ክንድ ነበር፤ በአንገቱም ላይ ማስጌጫ ቅርፅ ነበረበት፤ የገንዳው ተሸካሚ ግን አራት ማእዘን ነበር እንጂ ክብ አልነበረም። **32** የመንኮራኩሮቹም ቁመት አንድ ተኩል ክንድ ነበር፤ መንኮራኩሮችም በዕቃ ማስቀመጫው ጠፍጣፋ ነሐስ ሥር ነበሩ፤ የመንኮራኩሮቹም ወስከምቶች ከዕቃ ማስቀመጫዎቹ ጋር አንድ ወጥ ሆነው የተሠሩ ነበሩ። **33** መንኮራኩሮቹም የሠረገላ መንኮራኩሮችን ይመስሉ ነበር። ወስከምቶቻቸው፣ ቅርጾቻቸውና አቃፊዎቻቸው ሁሉም ከብረት ቀልጠው የተሠሩ ነበሩ። **34** እያንዳንዱ የዕቃ ማስቀመጫ አራት ማእዘን በየግርጌአቸው ከእነርሱ ጋር አንድ ወጥ ሆነው ከነሐስ የተሠሩ አራት ደጋፊዎች ነበሩአቸው። **35** በእያንዳንዱ የዕቃ ማስቀመጫ ጫፍ ዙሪያ ክፈፍ ላይ ተኩል ክንድ ርዝመት ያለው አንድ ክብ ቅርፅ ነበር፤ መደገፊያዎቹና ጠፍጣፋ ነሐሶቹ ከዕቃ ማስቀመጫው ጋር አንድ ወጥ ሆነው የተሠሩ ነበሩ። **36** በእነዚህ መደገፊያዎችና ጠፍጣፋ ነሐሶች መካከል ባለው ክፍት ቦታ ሁሉ በኪሩቤል፣ በአንበሶችና በዘንባባ ዛፎች አምሳል ሔራም ሠራቸው። እንዲሁም ዙሪያቸው የአበባ ጉንጉን በሚመስሉ ቅርፆች አኒጠው ነበር። **37** እንግዲህ ዐሥሩን ባለመንኩራኩር የዕቃ ማስቀመጫዎች የሠራቸው በዚህ ዓይነት ነበር። መጠናቸውና ቅርፃቸው እኩል ስለተቀረጹ ሁሉም ተመሣሣይ ነበሩ። **38** ሔራም ለእያንዳንዱ የዕቃ ማስቀመጫ ዐሥር የነሐስ መታጠቢያ ገንዳዎች ሠራ። የእያንዳንዱ ገንዳ ዙሪያ አጋማሽ ስፋት አራት ክንድ ያህል ሲሆን፣ አርባ ሊትር ያህል ውሃ ይይዝ ነበር። **39** ሔራም አምስቱን የዕቃ ማስቀመጫዎች ከቤተ መቅደሱ በስተደቡብ፣ የቀሩትንም አምስቱን ከቤተ መቅደሱ በስተሰሜን በኩል አቆመ። ገንዳውን ደግሞ በቤተ መቅደሱ ደቡባዊ ምሥራቅ ማእዘን ላይ አቆመው። **40** ሔራምም ድስቶችን፣ መጫሪያዎችንና ጎድጓዳ ሳህኖችን ሠራ።

በዚህ ዓይነትም ለንጉሥ ሰለሞን ሊሠራለት የጀመረውን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ሥራ ፈጸመ። **41** ሁለቱ ምሰሶዎች፣ በምሶሶዎቹም ላይ የነበሩትን ጉልላቶች የሚመስሉ ሳህኖችን፣ በምሶሶውም ላይ የነበሩትን ሁለቱን ጉልላቶች የሚሸፍኑትን ሁለቱን መረቦች ሠራ። **42** በእያንዳንዱ ጉልላት ላይ በመረብ አምሳል የተሠሩት ሰንሰለቶች፣ በእያንዳንዱ ጉልላት ቅርፅ ላይ በሁለት ዘርፍ አንዳንድ መቶ ዙር የሆኑ ከነሐስ የተሠሩ አራት መቶ የሮማን ቅርፆችን ሠራ። **43** ዐሥሩ ባለመንኮራኩር የዕቃ ማስቀመጫዎች፣ ዐሥሩ የመታጠቢያ ገንዳዎች ነበሩ። **44** ውሃ ማጠራቀሚያ ገንዳ፣ ገንዳውን ደግፈው የሚይዙ የዐሥራ ሁለቱን በሬዎች ቅርፅ ሠራ። **45** ድስቶቹን፣ መጫሪያዎቹንና ጎድጓዳ ሳህኖቹን ሠራ። ሌሎችንም ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አገልግሎት ይውሉ ዘንድ ሔራም እነዚህን ሁሉ ዕቃዎች ለሰለሞን የሠራለት ከተወለወለ ንፁህ ነሐስ ነበር። **46** ንጉሥ ሰለሞን እነዚህን ሁሉ ያሠራው በዮርዳኖስ ሸለቆ በሱኮትና ጻርታን መካከል በሚገኘው በሸክላ ስፍራ ነበር። **47** ከነሐስ የተሠራው ይህ ሁሉ ዕቃ እጅግ ብዙ ስለ ነበር፣ ሰለሞን በሚዛን እንዲለካ አላደረገውም፣ ስለዚህ ክብደቱ ምን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ያህል እንደሆነ ተወስኖ አልታወቀም። **48** ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አገልግሎት ይውሉ ዘንድ ሰለሞን ያሠራቸው ዕቃዎች ሁሉ በንጹሕ ወርቅ ያጌጡ ነበሩ። እነርሱም የወርቁ መሠዊያ፣ ለእግዚአብሔር የሚቀርበው ኅብስት ማኖሪያ የወርቅ ጠረጴዛ ናቸው። **49** በቅድስተ ቅዱሳኑ ፊት ለፊት አምስቱ በስተደቡብ፣ አምስቱ ደግሞ በስተ ሰሜን የሚቀመጡት ዐሥሩ የወርቅ መቅረዞች፣ አበባዎች፣ የመብራት ቀንዲሎች፣ የእሳት መቆስቆሻዎች ሁሉ ከወርቅ የተሠሩ ነበሩ። **50** ሰሎሞንም ጽዋዎችን፣ የአመድ ማጠራቀሚያዎችን፣ ጎድጓዳ ሳህኖችን፣ የዕጣን ማቅረቢያ ሳህኖችን፣ ማንደጃዎችን፣ ለቅድስተ ቅዱሳን በሮችንና ለቤተ መቅደሱ ውጪኣዊ በሮች የሚያገለግሉ ማጠፊያዎችን ከንጹሕ ወርቅ አሠራ። **51** በዚህ ዓይነት ንጉሥ ሰለሞን የቤተ መቅደሱን ሥራ ሁሉ ከፈጸመ በኋላ አባቱ ዳዊት ለእግዚአብሔር ቤት አገልግሎት እንዲውል የለየውን ብሩን፣ ወርቁንና ሌላውንም ዕቃ በሙሉ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ግምጃ ቤት ውስጥ አኖረው።

---

1 Kings 7:1

አጠቃላይ መረጃ
ፀሐፊው ስለ ሰለሞን ቤተ-መንግስት (ቤት) እየፃፈ ነው

ሰለሞን.....በ...ሠራ
ይህን ስራ ሰለሞን ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ “የሰለሞን ሠራተኞች በ..... ሠሩ”

የራሱን ቤት
“ቤተ-መንግሥት”

የሊባኖስ ዱር ቤት
“የሊባኖስ ዱር ቤት የሚባል ቤት”

አንድ መቶ ክንድ .....ሃምሳ ክንድ ...ሠላሳ ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሴ.ሜ ነው። ተርጓሚ “46ሜ .....23ሜ 13.8ሜ”

አግዳሚ
አግዳሚ ረጅምና ጠንካራ እንጨት ሆኖ ግድግድና ጣሪያ ለመደገፍ የሚያገለግል ነው።

1 Kings 7:3

አጠቃላይ መረጃ
ሥለ ሊባኖስ ዱር ቤት አወቃቀር አንዳንድ ገለፃዎች በጥልቀት ተሰጥተዋል።

ቤቱ በዝግባ ሳንቃ ተሸፍኖ ነበር
ይህ በገቢር መልኩ ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ “አናጢዎቹ ከዝግባ ሳንቃ ጣሪያ ከሠሩ በኋላ ከአግዳሚዎቹ ጋር አያያዟቸው”

አግዳሚ
አግዳሚ ረጅምና ጠንካራ እንጨት ሆኖ ግድግድና ጣሪያ ለመደገፍ የሚያገለግል ነው።

ሁለት አራት ማዕዘን
“አራት ማዕዘን” ቅርፅ ያለው ሥፉራ

1 Kings 7:6

አጠቃላይ መረጃ
ፀሐፊው ሥለ አዳራሹ ምሰሶዎች ይፅፋል።

አዕማድ
በውስን ርቀት የተደረደሩ አምዶች

ሃምሳ ክንድ ...ሠላሳ ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሳ.ሜ. ነው። ተርጓሚ “23 ሜ... 13.8 ሜ”

መድረክ ያሉበት ወለል (ኮሪደር)
የአንድ ሕንፃ ቋሚና ጣሪያ ያለው ክፍል ሲሆን ወደ ሕንፃው መግቢያ የሚወስድና የሚያገናኝ ነው። የ 1 ነገሥት 6፡ 3 ትርጉም ተመልከት።

1 Kings 7:7

አጠቃላይ መረጃ
ፀሐፊው ሥለ ዙፋኑ አዳራሽ ይፅፋል።

ሰለሞን .....አደረገ
ይህን ሥራ ሰለሞን ሠራተኞቹን እንዲሠሩ አዞ ይሆናል። ተርጓሚ “ሠለሞን ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አደረገ”

ዙፋን ያለበት የፍርድ ቤት
አማራጭ ትርጉሞች 1) “ዙፋኑን የሚያኖርበት ቤት” 2) “የንጉሡ መቀመጫ ቤት ተብሎ የተሰየመ ቤት”

በዝግባ እንጨት ተሸፍኖ ነበር
ይህ በገቢር መልኩ ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ “ሠራተኞቹ ወለሉን በዝግባ እንጨት ሸፈኑት”

1 Kings 7:8

አጠቃላይ መረጃ
ፀሐፊው ስለ ቤተ-መንግሥት ዙሪያ መፃፉን ቀጥሏል።

በሌላውም አደባባይ ወስጥ የነበረውን መኖርያ ቤት እንዲሁ ሠራ
ይህ በገቢር መልኩ ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ “ሰለሞን በዚሁ መልኩ በሌላ አደባባይ የሚሠራለት ሠው ነበረው”

እንዲሁ ሠራ
ይህን ሥራ ሰለሞን ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ “እንዲሁ እንዲሠሩ አዟቸው ነበር”

1 Kings 7:9

አጠቃላይ መረጃ
ፀሐፊ ለሕንፃው ሥራ ስለተጠቀሙት ድንጋይ ይፅፋል።

እነዚህም .....በጥሩ በተጠረበና ....በልክ በተከረከመ ድንጋይ ተሠርተው ነበር
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ሠራተኞቹ በጥሩ በተጠረበና...በልክ በተከረከመ ድንጋይ አስጊጠው ነበር።”

በልክ በተከረከመ ድንጋይ.... በታላቅ ድንጋይ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ሠራተኞች በልክ በከረከሙት በታላቅ ድንጋይ።”

በ.....ድንጋይ ተሠርተው ነበር
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል ተርጓሚ “ሠራተኞቹ በ.....ድንጋይ ሠርተው ነበር።”

ከመሠረቱ ጀምሮ እስከ ጉልላቱ ድረስ .....በውስጥና በውጭ
ፀሐፊው ሠራተኞቹ ለመሠረቱና በጠቅላላው ህንፃ ሥራ ውድ ድንጋዮችን መጠቀማቸውን አፅንኦት እየሠጠ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መሠረቱም ....ተሠርቶ ነበር
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ሠራተኞቹ መሠረቱን ..... ሠርተው ነበር።”

አስር ወይም ስምንት ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሳ.ሜ.ነው። ተርጓሚ “4.6 ሜ ገደማ 3.7 ሜ”

1 Kings 7:11

የዝግባ ሳንቃ
ሳንቃ (በሌላ ቦታ አግዳሚ) ረጅም እንጨት ሆኖ ለድጋፍ የሚያገለግል ነው

ሦስቱ ተራ በተጠረበ ድንጋይ አንዱም ተራ በዝግባ ሳንቃ
የ1ኛ ነገሥት 6፡ 36 ትርጉም ተመልከት።

1 Kings 7:13

ከጢሮስ አስመጣ
ኪራም የንጉሥ ሰለሞንን ግብዣ ተቀብሎ ወደ እዬሩሳሌም ሊመጣ

የባል አልባ ሴት ልጅ.....አባቱም የጠሮስ ሰው
ባል አልባ ማለት ባሉዋ የሞተባት ሴት መሆኗን እናውቃለን

ኪራም.....በጥበብና በማስተዋል በብልሃትም ተሞልቶ ነበር
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ጥበብና ማስተዋል የሚሉት ቃላት በመሠረቱ አንድ አይነት ነገር ሲሆኑ አፅንኦት ለመስጠት በጋራ ይሆናሉ። ጥበብ ልክ እንደሚፈስ ፈሳሽ እግዚአብሔር ወደ እቃ እንደሚያፈስ አይነት ነገር ሆኖ ተነግሮአል። እናም ኪራም ልክ እንደዚያ ዕቃ እንደነበር ሆኖ ተገልጿል። ተርጓሚ “እግዚአብሔር ለኪራም ጥበብ ማስተዋልና ብልሃትን ሠጠው።”

1 Kings 7:15

አስራ ስምንት ክንድ ....አስራ ሁለት ክንድ ...አምስት ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሳ.ሜ. ነው። 8.3 ሜ ገደማ 5.5 ሜ.....2.3 ሜ.

የዙርያውም
ዙርያ የአንድ ክብ የሆነ ነገር ርዝመት ወይም ልኬት ነው።

ሁለቱን ጉልላት
በሁለቱም ምሰሶዎች እያንዳንዳቸው የተዋቡ

ከፈሰሰ ናስ
የፀሐይ ብርሃን አንዲያንፀባርቅ ነሐስ አፈሰሱ (ወለወሉ) “የሚያንፀባርቅ ነሐስ”

1 Kings 7:18

ሠራ
ይህን ሥራ ኪራም ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ “ኪራም ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዘዘ”

ሮማኖችንም .....ሁለት ተራ
ሮማን የፍራፍሬ አይነት ሲሆን ጠንካራና ቀይ ሽፋንና በውስጡ የሚጨመቁ ፍሬዎችን ይዟል። ኪራም እውነተኛውን የሮማን ፍሬ ለማስዋብያነት አልተጠቀመም የተጠቀመው ከነሃስ የተሠሩ የሮማን ፍሬዎች ናቸው።

ጉልላቶች ላይ የሱፍ አበባ የሚመስል ሥራ አራት ክንድ አድርጎ ቀረፀ
የሱፍ አበባ አበባቸው በአንድ ጥግ ሠፋ ብሎ በአንድ ጥግ ደግሞ ጠባብ ነው። እነዚህ ቃላት በገቢር መልኩ ሊቀመጡ ይችላሉ። ተርጓሚ “ ኪራም ጉልላቶቹን ከነሃስ በተሰሩ የሱፍ አበባዎች አራት ክንድ ከፍ አድርጎ አስዋበ”

በወለሉም አዕማድ
የ1 ነገስት 7:6 ትርጉምን ተመልከት

አራት ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሳ.ሜ. ነው ተርጓሚ “1.8 ሜ. ገደማ።”

1 Kings 7:20

ሁለት መቶ ሮማኖች
“200 ሮማኖች” የነገስት 7፡18 ትርጉም ተመልከት

አቁሞ
ይህን ሥራ ኪራም ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ ”አቆሙ”

የቀኙንም ዓምድ አቁሞ ያቁም ብሎ ጠራው
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “በቀኝ በኩል ያለው አምድ ያቁም ይባላል።”

የግራውንም ዓምድ በለዝ ብሎ ጠራው።
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “በግራ በኩል ያለው አምድ በለዝ ይባላል።”

የአዕማዱ ሥራ ተጨርሶ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ኪራም አምዶቹን ጨርሰ” ወይም “የኪራም ሰዎች አምዶቹን ጨረሱ”

1 Kings 7:23

ሠራ
ይህን ሥራ ኪራም ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ “እንዲሠራ አዘዛቸው”

ክብ ኩሬ
ይህ ከነሃስ የተሠራ የውሃ ማቆሪያ ወይም ውሃ የሚያቁር ሥፋራን ይገልፃል።

በቀለጠ.....
ኪራም ነሃስ አቅልጦ ቅርፅ አበጀ

አስር ክንድ... አምስት ክንድ... ሰላሳ ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሳ.ሜ. ነው። ተርጓሚ 4.6ሜ....2.3 ሜ...13.8ሜ

ከዳር እስከ ዳር
ከአንድ ጠርዝ እስከ ሌላኛው

ዙሪያ
ዙርያ የአንድ ክብ የሆነ ነገር ርዝመት ወይም ልኬት ነው።

ኩሬ በጉብጉቦች አዞረ
ጉብጉብ (ቅል) ጠንካራ ክብ እንደሀረግ በመሬት ላይ የሚያድግ ተክል ነው።

ክብ ሠራ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ኪራም በተሠራ ክብ”

1 Kings 7:25

ኩሬውም
ይህ ለመስዋዕትነት የተዘጋጀ የውሃ ማቋሪያ ነሃስን ወይም ጉድጓድን ይገላፃል ።

ላይ ተቀምጦ ነበር
“ከላይ ነበር”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ኩሬውም በላያቸው ነበር
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “የኪራም ሠራተኞች ኩሬውን በነሃስ በተቀረፁ በሬዎች ላይ አስቀምጠው ነበር”

ከንፈሩም እንደ ፅዋ ከንፈር ተሠርቶ ነበር እንደ ሱፍ አበባዎች ሆኖ ተከርክሞ ነበር።
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ ኪራም ከንፈሩን የፅዋ ከንፈር እንዲመስል አድርጎ ሠራው ወደ ወጭም እንደ ሱፍ አበባ ሆኖ ተከረከመ።

ሁለት ሺህም የባዶስ
ባዶስ የፈሳሽ መስፈሪያ ሲሆን ከ22 ሊትር ጋር ይስተካከላል። ተርጓሚ “2,000 ባዶስ” ወይም “44,000 ሊትር”

1 Kings 7:27

ሠራ
ይህን ሥራ ኪራም ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ ኪራምም እንዲሠሩ አዘዛቸው ወይም “እነርሱም ሠሩ”

አራት ክንድ... ሦስት ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሳ.ሜ. ነው። ተርጓሚ “1.8 ሜ ገደማ ...1.4ሜ”

የመቀመጫውም ሥራ እንዲህ ነበር
ይህ ማለት ፀሐፊው መቀመጫውን በሚከተለው መልኩ ይገልፃል።

በክፈፎቹም መካከል በነበሩ ሰንበሮች ላይ አንበሳዎችና በሬዎች ኪሩቤል ነበሩ
በአንበሳዎች፤በበሬዎችና በኪሩቤል ቅርፆች ተውበው በመቀመጫዎቹ ጎኖች ተያይዛዋል። ሰን እዚህ ጋር ሰን (የመታጠቢያ) ሞላላ ቅርፅ ያለው ነሐስን ይገልፃል።

1 Kings 7:30

አራት የናስ መንኩራኩሮች .....ወሰከምት
ለእያንዳንዱ ጥንድ መንኩራኩር አንድ ወሰከምት ነበር። ተርጓሚ “አራት የናስ መንኩራኩሮች እና ሁለት መሰከምቶች”

በአራቱ ማዕዘን
“የእያንዳንዱ መቀመጫ አራት ጎኖች

የመታጠቢያ ሰን.....እግሮች
እያንዳንዱ እግር ከመታጠቢያ ሰን ጋር በአንድ ላይ ነበር። ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ኪራም እግሮቹን (ድጋፎቹን) ሞላላ ቅርፅ ካላቸው ጋር አያያዘ።”

አንድ ክንድና ተኩል .....አንድ ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሳ.ሜ. ነው። ተርጓሚ “70 ሳ.ሜ. ገደማ ....50 ሳ.ሜ.”

ክፈፉ ግን አራት ማዕዘን ነበር
የመቀመጫዎች ክፈፎች አራት ማዕዘን ነበሩ። ይህ ሐረግ ወደ 1ነገስት 7፡ 28- 29 ማብራርያ ይመልሰናል።

1 Kings 7:32

ሰንበሮቹ
ሰንበሮቹ ወሰከምትን ይወክላሉ ሰንበር ወሰከምቶቹ የሚገቡበትን ቧንቧ ይወክላል።

አንድ ክንድ ተኩል
አንድ ክንድ 46 ሳ.ሜ. ነው። ተርጓሚ “70 ሳ.ሜ. ገደማ

የመንኩራኩሮቹም ሥራ እንደ ሠረገላ መንኩራኩር ነበር
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ያችላል። ተርጓሚ “ኪራም መንኩራኩሮቹን እንደ አነስተኛ ሠረገላ መንኩራኩር ሠራ”

ወሰከምቶቹ.....ክፈፉ.....ቅትርቶቹም
“ቹም” የሚለው ቅጥያ.....መንኩራኩሩን ይወክላል።

1 Kings 7:34

በእያንዳንዱ መቀመጫ በአራቱም ማዕዘን በኩል አራት ደጋፊዎች ነበሩ
“በእያንዳንዱ መቀመጫ በአራቱም ማዕዘን መደገፊያ ነበር”

ስንዝር...ነገር ነበር
“ስንዝር” የአንድ ክንድ ግማሽ ሲሆን 1 ክንድ 46 ሳ.ሜ ነው። ተርጓሚ “23 ሳ.ሜ ስፋት”

በመቀመጫውም ላይ የነበሩ መያዣዎችና ሰንበሮች ከእርሱ ጋር ይጋጠሙ ነበር
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ኪራም በእያንዳንዱ መቀመጫ ላይ መያዣዎችና ሰንበሮችን አያይዟል።”

1 Kings 7:36

ቀረፀ...አደረገ
ይህን ሥራ ኪራም ሠራተኞቹ እንዲሰሩ አዘ ይሆናል። ተርጓሚ “እነርሱ ቀረፁ... እንዲሰሩ አዘዛቸው”

በዙሪያውም...አደረገ
“ውም” የሚለው ቅጥያ ...ኪሩቤልን፣ አንበሶችንና የወይራ ዛፍን ይወክላል።

በዙሪያውም ሻኩራ አደረገ
“ሻኩራ” የሚለው ቃል ድቡልቡል ቅርፅ ያለው ናስን ይገልፃል። ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “በሁሉም ዙሪያ ሻኩራ ነበር”

ሁሉም በምስልና በመጠን በንድፍም ትክክሎች ነበሩ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ ኪራም ሁሉንም መቀመጫዎች በአንድ ንድፍ ሠራቸው ወይም “ሁሉንም መቀመጫዎች በአንድ አይነት ንድፍ ሠሩዋቸው”

ሁሉም በምስልና በመጠን....ትክክሎች ነበሩ
ሁሉም መቀመጫ ተመሣሣይ መጠንና ምስል ነበራቸው።

1 Kings 7:38

አሥሩንም...ሠራ..አምስቱንም ....አኖራቸው...አኖረው
ይህን ሥራ ኪራም ሠራተኞቹ እንዲሰሩ አዘ ይሆናል። ተርጓሚ “ኪራም አስር እንዲሰሩ አደረገ....ኪራም አምስት እንዲያኖሩ አደረገ...እንዲያኖሩት አዘዛቸው”

አርባ የባዶስ መስፈርያ
ባዶስ የመጠን መለኪያ ሲሆን ከ22 ሊትር ጋር ይስተካከላል። ተርጓሚ “88 ሊትር ገደማ” ወይም “90 ሊትር ገደማ”

አራት ክንድ
አንድ ክንድ 46ሣ.ሜ ነው ተርጓሚ “ 1.8ሜ ገደማ”

በቤቱ ቀኝ .....በ....ግራ
በቀኝ በኩል..... በግራ በኩል

በቤቱ ቀኝ በአዜብ በኩል
በሁለቱ አቅጣጫዎች መካከል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Kings 7:40

ኪራምም .....ሠራ ጨረሰ
ይህን ሥራ ኪራም ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ “ኪራም እንዲሠሩ አደረገ.....ጨረሱ”

ኩብ የሚመስሉትን ጉልላቶች
ጉልላቶች በኩብ ቅርፅ ተቀርፀዋል።

መርበቦች
እርስ በርስ የተጠላለፈ የብረት ዘንጎች

1 Kings 7:42

አደረገ
ይህን ስራ ኪራም ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ “ሰሩ”

አራት መቶ ሮማኖች
400 ሮማኖች ሮማን የፍራፍሬ አይነት ሲሆን ጠንካራና በቀይ ሽፋን ተሸፋኖ በውስጡ የሚጨመቁ ፍሬዎች አሉት። የ1ነገስት 7:18 ትርጉምን ተመልከት።

1 Kings 7:44

አደረገ.....
ይህን ሥራ ኪራም ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ “አደረጉ”

ይህ ዕቃ ሁሉ
“ይህ መሣሪያ (መገልገያ)ሁሉ”

የጋለ ናስ
“ፀሐይ እንዲያንፀባርቅ ሆኖ የጋለ (የተዘጋጀ) ናስ”

1 Kings 7:46

ሰለሞን.....ሳያመዛዝን አኖረ
ይህ ስራ እንዲሠራ ሠለሞን ሠራተኞቹን አዞ ይሆናል። ተርጓሚ “ሰለሞንም .....ሳያመዛዝን ሰራተኞቹ እንዲያኖሩ አድርጓል”

በዮርዳኖስ ሜዳ
“ሜዳማ (ጠፍጣፋ) በዮርዳኖስ ወንዝ ዳር የሚገኝ ሜዳማ መሬት”

በሱኮትና በፀርታን
“የከተሞች ስም”

የናሱም ሚዛን.....አይቆጠርም
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “የናሱን ሚዛን ማንም ሊቆጥር አልቻለም”

1 Kings 7:48

ሰለሞንም.....አሠራ
ይህ ሥራ እንዲሠራ ሰለሞን ሠራተኞቹን አዞ ይሆናል። ተርጓሚ “የሰለሞን ሰራተኞች ሠሩ(አሠሩ)”

የገፀም ጎብስት የነበረበትን.....ገበታ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ካህናቱ የገፀን ጎብስት የሚያኖሩበት ገበታ”

የአበባዎችና ቀንደሎች
“አበባዎችና” “ቀንዲሎች” የፋኖሱ አንድ አካል

1 Kings 7:50

ከጥሩ ወርቅ የተሠረሰሩትን ፅዋዎች.....አሠራ
ይህ ሥራ እንዲሠራ ሰለሞን ሠራተኞቹን አዞ ይሆናል። ተርጓሚ “ሠራተኞቹ ከጥሩ ወርቅ ፅዋዎች እንዲሰሩ አደረገ”

ለደጆች የሚሆኑትን የወርቅ ማጠፍያዎች አሠራ
እዚህ ጋር ማጠፊያ 1) በሩ የሚያያዝበት ብረት ወይም 2)በሩ የሚንጠለጠልበት ብረት ሊሆን ይች

1 Kings 7:51

ንጉሥ ሰለሞን በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ያሠራው ስራ ሁሉ ተፈፀመ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ሠራተኞቹ ንጉስ ሰለሞን እንዲሠሩ ያዘዛቸውን የእግዚአብሔርን ቤት ሠርተው ፈፀሙ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 8

1 ከዚህ በኋላ ሰሎሞን የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦት የዳዊት ከተማ ከሆነችው ከጽዮን ለማምጣትና ወደ ቤተ መቅደሱ ለማስገባት የእስራኤል የነገድ
መሪዎችና የጎሣ አለቆች ሁሉ እርሱ ወደሚገኝበት ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሰበሰቡ ጠራ። 2 የእስራኤልም ወንዶች ሁሉ በዓሉ በሚከበርበት ኤታኒም ተብሎ
በሚጠራው በሰባተኛው ወር ወደ ንጉሥ ሰሎሞን ተሰበሰቡ። 3 መሪዎቹ ሁሉ በተሰበሰቡ ጊዜም ካህናቱ የቃል ኪዳኑን ታቦት አንሥተው ተሸከሙ። 4 ካህናቱም
የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦት፣ የመገናኛ ድኳንና በድንኳኑም ውስጥ የነበሩትን ንዋያተ ቅዱሳት ሁሉ አምጥተው ወደ ቤተ መቅደስ አገቡ። 5 ንጉሥ
ሰሎሞንና መላው የእስራኤል ሕዝብ በቃል ኪዳኑ ታቦት ፊት ተሰበሰቡ፤ ከብዛቱም የተነሣ ሊቆጠር የማይችል ብዙ በጎችና የቀንድ ከብት መሥዋዕት አድርገው
አቀረቡ። 6 ከዚህም በኋላ ካህናቱ የቃል ኪዳኑን ታቦት ተሸክመው ወደ ቤተ መቅደሱ ውስጠኛ ክፍል፣ በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ወደ ቦታው አምጥተው
በኪሩቤል ክንፎች ሥር አኖሩት። 7 የተዘረጉ የኪሩቤል ክንፎችም የታቦቱን መሸከሚያ መሎጊያዎች ሸፍነው ነበር። 8 መሎጊያዎቹ ረጃጅሞች ስለ ሆኑ
ጫፎቻቸው በቤተ መቅደሱ ውስጥ በቅድስተ ቅዱሳኑ ፊት ለፊት ለሚቆም ሰው ሁሉ በግልጽ ይታዩ ነበር፤ በሌላ አቅጣጫ የሚቆም ግን አያያቸውም። እስከ
ዛሬም እዚያው ይገኛል። 9 የእስራኤል ሕዝብ ከግብጽ ምድር እንደወጡ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ቃል ኪዳ በገባ ጊዜ ሙሴ በሲና ተራራ በቃል ኪዳን ታቦት
ውስጥ ካኖራቸው ከሁለቱ የድንጋይ ጽላቶች በቀር በቃል ኪዳን ታቦት ውስጥ ሌላ ምንም ነገር አልነበረም። 10 ካህናቱ ከቅድስተ ቅዱሳን እንደ ወጡ
የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ድንገት በደመና ተሞልቶ ነበር። 11 በደመናውም ውስጥ የነበረው የእግዚአብሔር ክብር ቤቱን ስለ ሞላ ካህናቱ ቆመው
አገልግሎታቸውን ለማከናወን አልቻሉም ነበር። 12 በዚህ ጊዜ ሰሎሞን እንዲህ ሲል ጸለየ፦- እግዚአብሔር አምላክ ሆይ! አንተ በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ
እኖራለሁ ብለሃል፤ 13 እነሆ አሁን ግርማ ሞገስ ያለው ቤተ መቅደስ ለአንተ ሠርቻለሁ፤ እርሱም አንተ ለዘለዓለም የምትኖርበት ቦታ ይሆናል። 14 የእስራል ጉባኤ
ሁሉ ቆመው ሳሉ፤ ንጉሥ ሰሎሞን ፊቱን ወደ እነርሱ መልሶ የእግዚአብሔር በረከት በእርሱ ላይ እንዲወርድ እንዲህ ሲል ጸለየ፤ 15 የእስራኤል አምላክ
እግዚአብሔር ይመስገን! ለአባቴ ለዳዊት የገባውን ቃል ኪዳን አጽንቶ ጠብቆአል፤ እርሱም እንዲህ የሚል ነው፦- 16 ሕዝቤን ከግብጽ ካወጣሁበት ጊዜ ጀምሮ
ስሜ የሚጠራበት ቤተ መቅደስ የሚሠራበት በመላው እስራኤል ምንም ዓይነት ከተማ አልመረጥኩም ነበር፤ አሁን ግን በሕዝቤም በእስራኤል ላይ ይነግሥ
ዘንድ ዳዊትን መረጥኩ። 17 ቀጥሎም ሰሎሞን እንዲህ አለ፤ አባቴ ዳዊት ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስን ለመሥራት አቅዶ ነበር፤ 18
እግዚአብሔርም አባቴን ዳዊትን ስሜ የሚጠራበትን ቤተ መቅደስ ትሠራ ዘንድ በልብህ ማሰብህ መልካም ነው። 19 ነገር ግን እርሱን የሚሠራልኝ ልጅህ ነው
እንጂ አንተ አይደለህም፤ ከአንተ የሚወለደው ልጅ ቤተ መቅደሴን ይሠራል አለው። 20 እነሆ እግዚአብሔር የሰጠውን የተስፋ ቃል ጠብቆአል፤ ስለዚህ እኔ
በአባቴ ፈንታ ተተክቼ የእስራኤል ንጉሥ ሆኜአለሁ፤ ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስን ሠርቼአለሁ። 21 እግዚአብሔር ከግብጽ ምድር
ባወጣቸው ጊዜ ከቀድሞ አባቶቻችን ጋር ቃል ኪዳን የገባበት የድንጋይ ጽላት ለሚገኝበት ታቦት ማኖሪያ የሚሆን ቦታ በቤተ መቅደሱ ውስጥ አዘጋጅቼአለሁ።
22 ከዚህ በኋላ ሰሎሞን በሕዝቡ ፊት ተነሥቶ በእግዚአብሔር መሠዊያው ፊት ቆመ፤ እጆቹንም ወደ ሰማይ ዘረጋ። 23 እንዲህም አለ፦- የእስራኤል አምላክ
እግዚአብሔር ሆይ! ለአገልጋዮቹ ቃል ኪዳኑን የሚጠብቅና ከልባቸው ታማኞች እስከ ሆኑ ድረስ ፍቅሩን የሚያጸና በላይ በሰማይ በታችም በምድ እንደ አንተ ያለ
አምላክ የለም! 24 ለአባቴ ለዳዊት የሰጠኸውንም የተስፋ ቃል አጽንተሃል፤ በአፍህ የተናገርከውም ቃል ሁሉ እነሆ ዛሬ በእጅህ ተፈጽሞአል። 25 አሁን
የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ሆይ! ለአባቴ ለዳዊት አንተ ታደርገው በነበረው ዓይነት ልጆችህ ታዛዦች ቢሆኑና በፊቴም በቅንነት ቢመላለሱ ሁልጊዜ ከዘርህ
በእስራኤል ዙፋን ላይ በፊቴ የሚነግሥ ልጅ አላሳጣህም ስትል የተናገርከውን የተስፋ ቃል ፈጽም። 26 አሁንም የእስራኤል አምላክ ሆይ! አገልጋይህ ለነበረው
ለአባቴ ለዳዊት የሰጠኸው የተስፋ ቃል ሁሉ እንዲፈጸም አድርግ። 27 በውኑ እግዚአብሔር በምድር ላይ ይኖራልን? እነሆ ሰማያት፤ ከሰማያትም በላይ ያለው
ሰማይ ሊይዝህ አይችልም፤ እኔ የሠራሁት ይህ ቤተ መቅደስ ምንኛ ያንስ። 28 ይሁን እንጂ እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ! ወደ አገልጋይህ ጸሎትና ልመና
ተመልከት፤ ዛሬም አገልጋይህ በፊትህ የሚጸልየውን ጸሎትና ጩኸት ስማ። 29 ስሜ ይጠራበታል ወዳልከው ወደዚህ ቤተ መቅደስ ቀንና ሌሊት ተመልከት፤
እኔም አገልጋይህ ወደዚህ ቤተ መቅደስ የምጸልየውን ጸሎት ስማ። 30 ፊታችንን ወደዚህ ቤተ መቅደስ መልሰን በምንጸልይበት ጊዜ የእኔንና የእስራኤልን ሕዝብ
ጸሎት ስማ፤ ከመኖሪያህ ከሰማይ ሆነህ ስማን፤ ይቅርም በለን። 31 አንድ ሰው ባልንጀራውን መበደሉን የሚገልጥ ክስ ቀርቦበት በዚህ ቤተ መቅደስ ውስጥ
ወደሚገኘው መሠዊያ አምጥተውት ከበደል ንጹሕ መሆኑን በመሐላ በሚያረጋግጥበት ጊዜ፣ በሰማይ ሆነህ ስማ፤ 32 ለአገልጋዮችህም ፍርድን ስጥ፤
ይኸውም በደል የሠራው ሰው በጥፋቱ መጠን እንዲቀጣ፣ ንጹሕ የሆነውም ነጻ እንዲወጣ አድርግ። 33 ሕዝብህ እስራኤል በደል ሠርተው አንተን
በማሳዘናቸው ምክንያት በጠላቶቻቸው ድል ሲሆኑ ተጸጽተው ወደ አንተ በመመለስ ወደዚህ ቤተ መቅደስ ቢመጡና የአንትን ይቅርታ ለማግኘት ራሳቸውን ዝቅ
አድርገው በትሕትና ቢለምኑህ፤ 34 አንተ በሰማይ ሆነህ ጸሎታቸውን ስማ፤ በምርኮ የሚገኙትንም ሕዝብህን ኃጢአት ይቅር በማለት ለቀድሞ አባቶቻቸው ወደ
ሰጠሃቸው ምድር መልሰህ አግባቸው። 35 የእስራኤል ሕዝብ በደል ሠርተው አንተን በማሳዘናቸው ምክንያት ዝናብ እንዳይዘንብላቸው አድርገህ በምትቀጣቸው
ጊዜ በፈጸሙት በደል በመጸጸት ፊታቸውን ወደዚህ ቤተ መቅደስ መልሰው በትሕትና ቢለምኑህ፤ 36 አንተ በሰማያት ሆነህ ጸሎታቸውን ስማ፤ የአገልጋዮችህን
የእስራኤልን ኀጢአት ይቅር በል፣ በልብ ቅን የሆነውንም ነገር ማድረግ ይችሉ ዘንድ አስተምራቸው፤ ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር ሆይ፣ ለዘለዓለም ርስት
አድርገህ ለሕዝብህ በሰጠሃቸው በዚህች ምድር ዝናብ እንዲዘንብ አድርግ። 37 በምድሪቱ ላይ ረሐብ ወይም ቸነፈር በሚመጣበት ጊዜ፣ እንዲሁም አህላቸው
በውርጭ በዋግና በአንበጣ ወይም በኩብኩባ መንጋ በሚወድምበት ጊዜ ወይም ጠላቶቻቸው በሕዝብህ ላይ አደጋ በሚጥሉበት ጊዜ ወይም በሕዝብህ ላይ
ልዩ በሽታና ደዌ በሚደርስባቸው ጊዜ፣ 38 በሕዝብህ በእስራኤል መካከል ልብ የሚያሸብር መራር ሐዘን ደርሶባቸው እጆቻቸውን ወደዚህ ቤተ መቅደስ
በመዘርጋት በሚጸልዩበት ጊዜ፣ ጸሎታቸውን ስማ። 39 በምትኖርበት በሰማይ ሆነህ ጸሎታቸውን በመስማት ይቅር በላቸው፤ እርዳቸውም፣ በሰው ልብና አእምሮ
ያለውን አሳብ ሁሉ መርምረህ የምታውቅ አንተ ብቻ ነህ፤ ስለዚህ ለእያንዳንዱ ሰው እንደ ሥራው መጠን የሚገባውን ዋጋ ስጠው። 40 በዚህም ዓይነት ሕዝብህ
ለቀድሞ አባቶቻችን ርስት አድርገህ በሰጠሃቸው ምድር በሚኖሩበት ዘመን ሁሉ ለአንተ ታዛዦች እንዲሆኑና እንዲያከብሩህ አድርግ። 41 በተጨማሪም የሕዝብህ
የእስራኤል ወገን ያልሆነ፣ የውጪ አገር ሰው ከስምህ የተነሣ ከሩቅ ቢመጣ፤ 42 ስለስምህ ገናናነት፣ ስለታላቁ እጅህና ከፍ ስላለው ክንድህ ሰምተው፣ በዚህ
ቤተ መቅደስ ቢመጡና ቢጸልዩ፣ 43 ከምትኖርበት ከሰማይ ሆነህ የዚያን ሰው ጸሎት ስማ፤ እንድታደርግለት የሚለምንህንም ሁሉ ፈጽምለት፤ ሕዝብህ
እስራኤላውያን እንደሚያደርጉት በመላው ዓለም የሚኖሩ ሕዝቦች አንተን በማወቅ እንዲታዘዙህና እንዲያከብሩህ አድርግ፣ ይህም በሚሆንበት ጊዜ ይህ እኔ
የሠራሁት ቤተ መቅደስ የአንተ ስም የሚጠራበት መሆኑን ያውቃሉ። 44 ጠላቶቻቸውን ለመዋጋት እንዲዘምቱ ሕዝብህን በምታዝበት ጊዜ በየትኛውም ስፍራ
ሆነው ወደዚህች ወደ መረጥኻት ከተማና እኔ ለአንተ ወደ ሠራሁት ወደዚህ ቤተ መቅደስ ፊታቸውን መልሰው በሚጸልዩበት ጊዜ፣ 45 በሰማያት ሆነህ
ጸሎታቸውንና ልመናቸውን ስማ፤ በችግራቸውም እርዳቸው። 46 ሕዝብህ ኃጢአት በመሥራት አንተን ሲያሳዝኑህ አንተም ተቆጥተህ ጠላቶቻቸው ድል
እንዲነሡአቸውና ወደ ሌላ አገር ማርከው እንዲወስዱአቸው በምታደርግበት ጊዜ፣ ሩቅ ወይም ቅርብ ቢሆን፣ 47 ምርኮኞች ሆነው በሚኖሩባት በዚያች አገር ሳሉ
ኀጢአት ሠርተናል፤ በድለናና፤ ዐመፀናል ብለው በመናዘዝ ተጸጽተው ንስሓ ቢገቡ፣ 48 ማርከው በወሰዱአቸው በጠላቶቻቸው አገር ሳሉ በፍጹም ልባቸው
በእውነትና በቅን መንፈስ ተጸጽተው ንስሓ በመግባት አንተ ለቀድሞ አባቶቻችን ወደ ሰጠሃቸው ወደዚህች ምድር፣ አንተም ወደ መረጥኻት ወደዚህች ከተማ፣ እኔ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለአንተ ወደ ሠራሁት ወደዚህ ቤተ መቅደስ ፊታቸውን መልሰው ቢጸልዩ፣ **49** ከዚያ በመኖሪያህ በሰማይ ሆነህ ጸሎታቸውንና እርዳታ ፈልገው ሲለምኑህ በመስማት ፍረድላቸው፤ **50** ኃጢአታቸውንና አንተን ያሳዘኑበትን በደል ሁሉ ይቅር በል፤ ጠላቶቻቸውም እንዲራሩላቸው አድርግ፤ **51** እነርሱ እንደ እቶን እሳት ከሚያቃጥል ከግብጽ ምድር ያወጣሃቸውና የመረጥካቸው ሕዝብህ ናቸው። **52** በጠሩህ ጊዜ ሁሉ ትሰማቸው ዘንድ ለአገልጋይህና ለሕዝብህ ልመና ዓኖችህ የተገለጡ ይሁኑ። **53** እግዚአብሔር አምላክ ሆይ! የቀድሞ አባቶቻችንን ከግብጽ ምድር ባወጣህ ጊዜ ከዓለም ሕዝብ ሁሉ መካከል እስራኤልን የራስህ ሕዝብ እንዲሆን የመረጥከው መሆኑን በአገልጋይህ በሙሴ አማካይነት ተናግረሃል። **54** ሰሎሞንም እጆቹን እንደ ዘረጋ ተንበርክኮ በመሠዊያው ፊት ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ ቆይቶ ጸሎቱን ከፈጸመ በኋላ ተነሥቶ ቆመ። **55** ድምፁንም ከፍ አድርጎ በዚያ ተሰብስቦ የነበረውን ሕዝብ ሁሉ እንዲህ ሲል ባረከ፦ **56** በገባው የተስፋ ቃል. መሠረት ለሕዝቡ ለእስራኤል ሰላምን የሰጠ እግዚአብሔር ይመስገን። በአገልጋዩ በሙሴ አማካይነት ከሰጠው መልካም ተስፋ አንድም የቀረ ቃል የለም። **57** አምላካችን እግዚአብሔር ከቀድሞ አባቶቻችን ጋር እንደነበረ ሁሉ ከእኛ ጋርም ይኑር። ምን ጊዜም አይተወን፤ አይጣለንም። **58** ለቀድሞ አባቶቻችን የሰጠውን ትዕዛዞች፣ ደንቦችና ሥርዓቶች በመጠበቅ ወደ እርሱ ልባችንን በማዘንበል ለእርሱ ታዛዦች እንድንሆን ያድርገን። **59** የእኔ የአገልጋዩና የሕዝቡ የእስራኤል የየዕለት ፍላጎት ይሟላ ዘንድ ለእግዚአብሔር ያቀረብኳቸው ልመናዎች ቀንና ሌሊት ወደ እግዚአብሔር አምላክ ይቅረቡ። **60** የዓለም ሕዝቦች ሁሉ እግዚአብሔር ብቻ አምላክ መሆኑንና ከእርሱም ሌላ አምላክ አለመኖሩን ያውቃሉ። **61** ስለዚህም በዛሬው ቀን በድንጋጌው ለመመላለስና ትእዛዞቹንም ታከብሩ ዘንድ ለአምላካችሁ ለእግዚአብሔር ለአምላካችን በልባችሁ ታማኞች ሁኑ። **62** ስለዚህ ንጉሥ ሰሎሞንና እስራኤላውያን ሁሉ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቀረቡ። **63** ሰሎሞንም ሃያ ሁለት ሺህ የቀንድ ከብቶችንና አንድ መቶ ሃያ በጎችን የኅብረት መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር አቀረበ። በዚህም ዓይነት ንጉሥ ሰሎሞንና እስራኤላውያን ሁሉ ቤተ መቅደሱን ለእግዚአብሔር የተለየ አድርገው ቀደሱት። **64** አሁንም በዚያኑ ቀን ከቤተ መቅደሱ ፊት ለፊት ያለውን አደባባይ መካከለኛ ክፍል ለእግዚአብሔር የተለየ አድርጎ ቀደሰው፤ ቀጥሎም በሙሉ የሚቃጠለውን መሥዋዕት፣ የእህል ቁርባንና የኅብረት መሥዋዕት፣ የእንስሶች ስብ ሁሉ ለእግዚአብሔር አቀረበ፤ ይህንንም ያደረገበት ምክንያት ከነሐስ የተሠራው መሠዊያ ይህን ሁሉ መሥዋዕት መያዝ ስለማይችል ነው። **65** በዚያ ቤተ መቅደስ ሰሎሞንና የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ሰባት ቀን ሙሉ ባጠቃላይ ዐሥራ አራት ቀኖች የዳስ በዓል አክብረው ሰነበቱ፤ በስተ ሰሜን ከሐማት መተላለፊያ አንሥቶ በስተ ደቡብ እስከ ግብጽ ድንበር ድረስ ካለው ምድር ሁሉ የመጣው ሕዝበ እጅግ ብዙ ነበር። **66** በሚቀጥለው ቀን ሰሎሞን ሕዝቡን ሁሉ አሰናበተ፤ ሁሉም ሰሎሞንን መረቁ እግዚአብሔር ለአገልጋዩ ለዳዊትና ለሕዝቡ፣ ለእስራኤል ስለ አደረገው በጎ ነገር ሁሉ ደስ ብሎአቸው ወደየቤታቸው ሄዱ።

---

1 Kings 8:1

የእስራኤልን ሽማግሌዎች..... ሰበሰበ
“የእስራኤልን ሽማግሌዎች አንድ ላይ ጠራ”

የእስራኤል ሰዎች
ይህ አንድም 1) በ8:1 ላይ የተዘረዘሩትን ሰለሞን ወደ እየሩሳሌም የጠራቸው ወይም 2) “በአጠቃለይ ለድግሱ ወደ እየሩሳሌም የተጓዙትን ሁሉ” ሊገልፅ ይችላል።

በበዓሉ
ይህ የሱኮትን ድግስ (በዓል) በተለምዶ የቤተ-አምልኮ ድግስ በመባልም ይታወቃል።

ኤታኒም በሚባል በሰባተኛው ወር
ኤታኒም በዕብራዊያን የቀን አቆጣጠር ሰባተኛው ወር ሲሆን በምዕራባዊያኑ ቀን አቆጣጠር የመስከረም ወር መገባደጃ ሳምንት ወይም የጥቅምት ወር የመጀመርያዎቹ ሳምንት ነው።

1 Kings 8:3

የእስራኤል ማህበር ሁሉ
ይህ በጥቅል ነው

የማይቆጠሩትን .....በጎችና በሬዎች
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ማንም ሊቆጥራቸው የማይችል የበዙ በጎችና በሬዎች”

1 Kings 8:6

በቤቱ በቅድስተ-ቅዱሳን ውስጥ .....በታች
“ወደ ውስጠኛው የቤቱ ክፍል ያም በጣም ወደ ተቀደሰው ስፍራ .....በታች”

መሎጊያዎቹም.....ነበሩ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። “ካህናቱ ይሸከሙበት የነበሩ መሎጊያዎች”

1 Kings 8:12

እግዚአብሔር በጨለማው.....ብሎአል
ሰለሞን ለእግዚአብሔር ያለውን ክብር ለማሳየት ከሆነ ሰው ጋር እያወራ ያለ በማስመሰል ይናገራል።

ማደርያ ቤት
በጣም የተከበረ ሰው የሚኖርበት መኖርያ ቤት

1 Kings 8:14

የእስራኤል ጉባዔ ሁሉ
“በዚያ የተሰበሰበው የእስራኤል ህዝብ ሁሉ”

የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይመስገን
ይህ እንዳለ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ

በእጁም
“እጅ” በእጁ ውስጥ ላለው ጉልበት የዘይቤ ንግግር ነው። ተርጓሚ “በጉልበቱም”

ስሜ በዚያ ይሆን ዘንድ
“ስሜ” ለአንድ ሰው የዘይቤ ንግግርና የሚመለክ ሰው ስም ነው። የነገስት 3፡2 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ “ሰዎች ያመልኩኝ ዘንድ”

1 Kings 8:17

አባቴ ዳዊት .....በልቡ አሰበ .... በልብህ አስበሃልና.....በልብህ ማሰብህ
ዳዊት የተመኘውን በመያዣ ውስጥ እንዳለ ዕቃ አድርጎ ሲናገር ልብን ደግሞ እንደ ዕቃ መያዣ አድርጎ ይናገራል። ተርጓሚ “አባቴ ዳዊት ተመኘ .....ለማድረግ መመኘት.....ተመኘህ”

ለእግዚአብሔር ስም..... ለስሜ
“ስም” ለአንድ ሰው የዘይቤ ንግግርና የሚመለክ ሰው ስም ነው። የነገስት 3፡2 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ “ሰዎች እግዚአብሔርን የሚያመልኩበት ቤት .....“ሰዎች እኔን የሚያመልኩበት ቤት”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Kings 8:20

የተናገረውን ቃል አፀና
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። ተርጓሚ “ልክ እንደተናገረው አደረገ”

በአባቴ በዳዊት ፋንታ ተነሣሁ
ከፍታ የጉልበተኛነት ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “አባቴ ዳዊት የነበረውን ጉልበት አገኘው”

በእስራኤል ዙፋን ላይ ተቀመጥሁ
“ዙፋን” በዙፋን ላይ ተቀምጠው ስለሚሠራ ሥራ ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “በእስራኤል ላይ እገዛለሁ”

ለእግዚአብሔር ስም
“ስም” ለአንድ ሰው የዘይቤ ንግግር ነውና የሚመለክ ሰው ስም ነው። 1ነገስት 3:2 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ “ሰዎች እግዚአብሔርን የሚያመልኩበት”

የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ባለበት..... በዚያ
እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን የፃፈበት ድንጋይ እራሱ ቃል ኪዳን እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። ተርጓሚ “እግዚአብሔር ቃልኪዳኑን የፃፈበት ድንጋይ ናቸው (በዚያ)”

1 Kings 8:22

የእስራኤል ጉባኤ ሁሉ
“የተሰበሰቡ የእስራኤል ህዝብ ሁሉ”

ለባሪያዎችህ ቃል ኪዳንና ምህረትን የምትጠብቅ
ተርጓሚ በታማኝነት ቃልኪዳንህን የምትወድ ወይም “ለቃል ኪዳንህ ታማኝ የሆንክ”

በፍፁም ልባቸው በፊትህ ለሚሄዱ
የሰው የአኗኗር ዘይቤ ልክ ሰው በመንገዱ እንደሚሄድ ተደርጎ ተነግሯል። ተርጓሚ “አንተ እንዲኖሩ የምትፈልገውን ኑሮ በሙሉ ልባቸው መኖር”

በእጅህ ፈፀምኸው
“እጅ” በእጅ ውስጥ ላለው ጉልበት ዘይቤ ነው “ በጉልበትህ ያልከውን ፈፀምኽ”

1 Kings 8:25

በእስራኤል ዙፋን የሚቀመጥ
“ዙፋን” በዙፋን ላይ ተቀምጠው ለሚሰሩት ሥራ ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “በእስራኤል ላይ ለመግዛት

በፊቴ እንደ ሄድህ ..... መንገዳቸውን ቢጠብቁ
የሰው የኑሮ ዘይቤ አንድ በመንገድ እንደሚሄድ ተደርጎ ተነግሮአል። ተርጓሚ “እንደምፈልገው ኖረሃል.....እኔ እንደምፈልገው ቢኖሩ”

1 Kings 8:27

በውኑ እግዚአብሔር.....በምድር ላይ ይኖራልን?
አማራጭ ትርጉሞች 1)ሰለሞን ጥያቄ ጠይቆ ትክክለኛውን መልስ እየጠበቀ ነው። 2) ጥያቄው የግነት ሲሆን ሰለሞን እግዚአብሔር በመሬት ላይ ለመኖር ትልቅና ገናና ሆነ አፅንኦት ለመስጠት ነው። ተርጓሚ “በእርግጥ እግዚአብሔር በምድር ላይ ለመኖር አይቻለውም!”

በውኑ እግዚአብሔር
እዝህ ጋር ሰለሞን ስለ እግዚአብሔር እንደ ሦስተኛ ወገን አድርጎ ይናገራል። እንደ ሁለተኛ ወገን ሊቀመጥ ይችላል። “በውኑ አንተ”

ተመልከት
“እኔ ልናገር ያለው ጠቃሚ ነው” ወይም “እውነታው ያ ነው”

ይልቁንስ እኔ የሠራሁት ቤት እንዴት ያንስ
“ስለዚህ ይህ እኔ የሠራሁት ቤት በእርግጥ አንተን ሊይዝ አይችልም”

ወደ ባሪያህ ፀሎትና ልመና ተመልከት
“ፀሎት” ና “ልመና” የሚሉት ቃል በመሰረቱ በትርጉም ተመሣሣይ ሲሆኑ ጥያቄውን ሲያቀርብ ትሁት እንደነበር አፅንኦት ለመስጠት ነው። ሰለሞን እራሱን “ባሪያህ” ብሎ ይገልፃል።ይህም ለእግዚአብሔር ያለውን አክብሮት ለማሳየት ነው። ይህ እንደ አንደኛ ወገን ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “እንድትረዳኝ ዛሬ ስጠራህ እኔ ባሪያህን አድምጠኝ”

1 Kings 8:29

ወደዚህ .....ዓይኖችህ .....ይሁኑ
ዓይን የአንድ ሰው ሁለንተና ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “ወደዚህ ተመልከት”

ሌሊትና ቀን
ተርጓሚ “ሁልጊዜ” ወይም “(ሳታቋርጥ)”

በዚያ ስሜ.....ስፍራ
እነዚህ ሁለት ቃላት እግዚአብሔር በመቅደስ እንደሚኖር አፅንኦት ለመስጠት ነው።

ባሪያህ .....የሚፀልየውን
ሰለሞን ስለራሱ “ባሪያህ” እያለ ይናገራል። ይህም ለእግዚአብሔር ያለውን አክብሮት ለማሣየት ነው። ይህ እንደ አንደኛ ወገን ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “እኔ ባሪያህ... የምፀልየውን”

የባሪያህና ሕዝብህ እስራኤል .....ልመና ሰማ
ሰለሞን ስለራሱ “ባሪያህ” እያለ ይናገራል። ይህም ለእግዚአብሔር ያለውን አክብሮት ለማሳየት ነው። ይህ እንደ አንደኛ ወገን ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “የእኔ የባሪያህንና የሕዝብህ እስራኤልን ልመና ሰማ”

1 Kings 8:31

መሐላ ቢጫን
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “የሆነ ሰው እንዲምል ጠየቀው”

በላዩም
እዚህ ጋር በላዩም የሚለው ቃል ሙሉ ሰውነትን (ሰውን) ይወክላል። ተርጓሚ “በላዩ”

እንደ ፅድቁም ክፈለው
“ፃድቅ ስለሆነ የሚገባውን መክፈል”

1 Kings 8:33

ሕዝብህ እስራኤል ..... በጠላቶቻቸው ፊት ድል በተመቱ ጊዜ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ጠላት ሕዝብህ እስራኤልን ድል በመታ ጊዜ”

ቢመለሱ ስምህን ሊያከብሩ
አማራጭ ትርጉሞች 1) “አንተን እንደበደሉ ቢናዘዙ ወይም 2) ቢያመሰግኑህ” ወይም 3) “ከዚህ በኋላ እንታዘዝሃለን ቢሉ”

ቢለምኑህ
ተርጓሚ “ይቅር እንድትላቸው ቢጠይቁህ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Kings 8:35

ሰማይ በተዘጋ ጊዜ ዝናብም ባልዘነበ ጊዜ
“ሰማይ” ልክ እግዚአብሔር ዝናብ እንደሚያጠራቅምበት ውሃ መያዣ ተደርጎ ተነግሮአል። ተርጓሚ “ዝናብ እንዲወርድ (እንዲዘንብ) አትፈቅድም”

ስምህንም ቢያከብሩ
የ1ነገስት 8:33 ትርጉምን ተመልከት አማራጭ ተርጉሞች 1) “አንተን እንደበደሉ ቢናዘዙ ወይም 2) ቢያመሰግኑህ” ወይም 3) “ከዚህ በኋላ እንታዘዝሃለን ቢሉ”

የሚሄዱበትንም
የሰው የኑሮ ዘይቤ በመንገድ እንደሚጓዝ ሰው ተመስሏል። ተርጓሚ “የሚኖሩበትንም”

1 Kings 8:37

ዋግ ወይም አረማም
እነዚህ የግብርና ቃላት ሲሆኑ በዝናብ እጥረት ወይም ብዛት የምርት መሞትን ይገልፃል።

አንበጣ ወይም ኩብኩባ
አንበጣ እህልን በመብላት የሚያጠፋ ነው። ኩብኩባ ደግሞ በማደግ ላይ ያለ አንበጣ ነው።

የሕዝብህም.....ማናቸውም ሰው.....ፀሎትና ልመና ቢፀልይ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ማንም ሰው ወይም ሕዝብህ ሁሉ ቢፀልዩ”

ፀሎትና ልመና
ፀሎትና ልመና በመሠረቱ ተመሣሣይ ትርጉም ሲኖራቸው አንድ ሰው ልመናን ሲያቀርብ አፅንኦት ለመስጠት ነው። የ1ነገስት 8:28 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ “ልመናዎች”

የልቡን ሕመም አውቆ
አማራጭ ትርጉሞች 1)የሠውየው ኃጢአት እንደሕመም ተነግሮአል። ተርጓሚ “በልቡ ያለውን ኃጢአት አውቆ” ወይም 2) “ሕመም በኃጢአት ምክንያት ለሚሆን ጥቃት ዘይቤ ነው። ተርጓሚ ሕመሙ የራሱ ኃጠአት ውጤት መሆኑን አውቆ”

1 Kings 8:41

ብርቱይቱንም እጅህን የተዘረጋወንም ክንድህን
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሰረቱ አንድ ሲሆኑ የእግዚአብሔርን ኃይል ይገልፃሉ

በዚህ በሠራሁት ቤት ስምህ እንደተጠራ
“ስምህ እንደተጠራ” የሚለው ሐረግ እግዚአብሔር የቤቱ ባለቤት መሆኑን ይገልፃል።ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ እኔ የሰራሁት ቤት ባለቤትነቱ የአንተ ነው።”

1 Kings 8:44

ሕዝብህም .....ቢወጡ.....ቢፀልዩ
ሰለሞን ሲናገር ይህ መላ-ምታዊ ሁኔታ አልተከሰተም ነገር ግን ወደፊት እንደሚከሰት ሰለሞን አውቋል።

ለስምህ
“ስም” የሚለው ቃል ለአንድ ሰው ዘይቤ ሲሆን ለ “ስም” የሚገልፀው የሚመለክ ስም መሆኑን ነው የ1ነገስት 3:2 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ “ሰዎች አንተን የሚያመልኩበት”

ፀሎታቸውንና ልመናቸውን
ፀሎትና ልመና በመሰረቱ ተመሣሣይ ትርጉም ሲኖራቸው ሠዎች ልመናን ለማድረግ ትሁት መሆናቸውን ለማሣየት አፅንኦት ለመስጠት ነው። የ1ነገስት 8:28 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ “ልመናቸው”

1 Kings 8:46

ቢበድሉ.....በ....ሆነው.....ንሰሐ ቢገቡ
ሰለሞን ሲናገር ይህ መላ-ምታዊ ሁኔታ አልተከሰተም ነገር ግን ወደፊት እንደሚከሰት ሰለሞን አውቋል።

በተማረኩበትም አገር
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “እንደ ስደተኞች ጠላቶቻቸው ወደ ወሰዷቸው ቦታ”

ማራኪዎች
ሌሎችን እንደ እስረኛ የሚጠብቁ ሰዎች

ኃጠአት ሠርተናል በድለንማል ክፉንም አድርገናል
ሁለቱ አንድ አይነት ናቸው። ሁለቱ አንድ ላይ ምን ያህል የሰዎች ድርጊት መጥፎ እንደሆነ አፅንኦት ለመስጠት ነው።

ኃጢአት ሠርተናል በድለንማል
ሁለት አንድ አይነት ነገር ሲሆኑ ምን ያህል ሰዎች እንደበደሉ አፅንኦት ለመስጠት ነው።

1 Kings 8:48

በፍፁም ልባቸውና በፍፁም ነፍሳቸው
በፍፁም ልባቸው የሚለው ፈሊጣዊ “ፈፅሞ” ማለት ሲሆን በፍፁም ነፍሳቸው የሚለው ደግሞ በሁለንተናቸው ማለት ነው። እነዚህ ሁለቱ ሀረጎች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው የ1ነገስት 2:4 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ “በሁለንተናቸው” ወይም “በሙሉ ኃይላቸው” በ...አገር “በምድራቸው ሲኖሩ ሳለ” ወደ ምድራቸው “ወደ እነርሱ ወደ ሆነው ምድር” ይህ የእስራኤል ህዝብን ይገልፃል።

ለስምህ
“ስም” የሚለው ቃል ለአንድ ሰው ዘይቤ ሲሆን ለ “ስም” የሚገልፀው የሚመለክ ስም መሆኑን ነው። የ1ነገስት 3:2 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ “ሰዎች አንተን የሚያመልኩበት”

1 Kings 8:49

ፀሎታቸውንና ልመናቸውን
x

1 Kings 8:51

ከብረት እቶን
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ሰዎች ብረት ከሚያቀልጡበት ከእቶን”

ዓይኖችህ የተገለጡ ይሁኑ
ዓይን ለሙሉ ሰው ዘይቤ ነው ተርጓሚ “እባክህ ትኩረት ስጥ”

1 Kings 8:54

ፀሎትና ልመና
ፀሎትና ልመና በመሠረቱ ተመሣሣይ ትርጉም ሲኖራቸው አንድ ሰው ልመናን ሲያቀርብ አፅንኦት ለመስጠት ነው። የ1ነገስት 8:28 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ “ልመናዎች”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እግዚአብሔር ይመስገን
ይህ በሌላ መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ይመስገን እግዚአብሔር”

ከመልካም ተስፋ ሁሉ አንድ ቃል አልወደቀም
ይህ በሌላ መልኩ ሊቀመጥ ይችላል ተርጓሚ “እግዚአብሔር መልካም ተስፋ ቃሉን ሁሉ ፈፀመ (አደረገ)”

1 Kings 8:57

አይተወን አይጣለንም
እነዚህ ሁለት ቃላት በመሰረቱ በትርጉም አንድ ሲሆኑ እግዚአብሔር ከህዝቡ ጋር እንዲሆን ለሰለሞን ምኞት አፅንኦት ለመስጠት ነው።

ልባችንን ወደ እርሱ ያዘነብል ዘንድ
እዚህ ጋር ልብ የሰዎችን ምኞትና ስሜት ይወክላል። አንድን ሰው ለማስደሰት መመኘት ወደ እዚያኛው ሰው ልብ እንደሚያዘነብል ተደርጎ ተነግሮአል። ተርጓሚ እርሱን ለማስደሰት እንድንመኝ አድርግ

በመንገዱም ሁሉ እንሄድ ዘንድ
እዚህ ጋር “በመንገዱም” እርሱ ሰዎች እንዲሄዱበት ለሚፈልገው መንገድ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። ተርጓሚ “እርሱ እንዲሚፈልግብን መኖር”

1 Kings 8:59

በቀንና በሌሊት
“ሁል ጊዜ” ወይም “ሳይቋረጥ”

ልባችሁ ንፁህ ይሁን
“ሙሉ በሙሉ የተሰጣችሁ ሁኑ”

በሥርዓቱ ትሄዱ ዘንድ
የሰው የኑሮ ዘይቤው መንገድን እንደሚጓዝ ሰው ሆኖ ተነግሮአል። ተርጓሚ “ሁል ጊዜ በሥርዓቱ ሂዱ”

1 Kings 8:62

ሀያ ሁለት ሺህ በሬዎች
22,000 በሬዎች

መቶ ሃያ ሺህ በጎች
x

1 Kings 8:65

ከእርሱም ጋር እስራኤል ሁሉ.....የእስራኤል ልጆች ሁሉ
እነዚህ ጥቅል ሐረጎች አንድም 1)1ነገስት 8፡1 ላይ የተዘረዘሩትን ሰለሞን ወደ እዬሩሳሌም የጠራቸው ወይም 2) ለግብዣው ወደ እዬሩሳሌም የተጓዙትን ነው በእስራኤል የሚኖር ሁሉ ላይሆን ይችላል።

ስምንተኛው ቀን
ስምተኛው የሚለው ቃል ለ“8” ተራ ነው

ተደስተው ሐሤትም
ሁለቱም በመሠረቱ አንድ አይነት ትርጉም ሲኖራቸው የተቀናጁትም አፅንኦት ለመስጠት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 9

1 ንጉሥ ሰሎሞንም ቤተ መቅደሱንና ቤተ መንግሥቱን እንዲሁም ሊሠራው የፈለገውን ሌላውንም ሁሉ ከፈጸመ በኋላ፣ 2 እግዚአብሔር ከዚህ በፊት በገባዖን
እንደ ተገጠለት አሁንም እንደገና ተገለጠለት። 3 ከዚያም እግዚአብሔር እንዲህ አለው፦ በፊቴ ያቀረብከውን ጸሎትና ልመና ሰምቻለሁ፤ እርሱም ለዘለዓለም
ለስሜ መጠሪያ እንዲሆን የሠራኸውን ቤተ መቅደስ ቀድሼዋለሁ፤ ዘወትርም ዓይኔና ልቤ በዚያ ይሆናል። 4 አንተ ግን አባትህ ዳዊት እንዳደረገው በቅንነትና
በታማኝነት በፊቴ ብትመላለስ፣ ሕጌንና ሥርዓቴን ብትጠብቅ፣ ያዘዝኩህንም ሁሉ ብትፈጽም፣ 5 ለአባትህ ለዳዊት ከዘሮችህ በእስራኤል ዙፋን ላይ የሚነግሥ
ልጅ አታጣም በማለት የሰጠሁትን የተስፋ ቃል በመጠበቅ ዙፋንህ በእስራኤል ላይ ለዘለዓለም ጸንቶ እንዲኖር አደርጋለሁ። 6 ነገር ግን አንተ ወይም ዘሮችህ
እኔን መከተል ትታችሁ የሰጠኋችሁን ሕጎችና ትእዛዞች ባትፈጽሙና ባዕዳን አማልክትን ብታመልኩና ብትሰግዱላቸው፤ 7 እስራኤላውያንን ከሰጠኋቸው ምድር
ተነቃቅለው እንዲባረሩ አደርጋለሁ፤ ስሜ እንዲጠራበት የቀደስኩትንም ይህንን ቤተ መቅደስ እተወዋለሁ፤ በየአገሩ የሚኖሩ ሕዝቦች ሁሉ እስራኤልን መሳለቂያና
መዘባበቻ ያደርጓታል። 8 ይህ ከፍ ከፍ ብሎ የሚታየው ቤተ መቅደስ ፈርሶ የፍርስራሽ ክምር ይሆናል፤ በዚያ በኩል የሚያልፉ ሰዎች ሁሉ ይህንን አይተው
በመደንገጥ እግዚአብሔር ይህንን አገርና ይህንን ቤተ መቅደስ ለምን እንዲህ አደረገ በማለት ይሳለቁበታል። 9 ራሳቸው በሚሰጡት መልስ፣ የእስራኤል ሕዝብ
የቀድሞ አባቶቻቸው ከግብጽ ምድር ያወጣቸውን አምላካቸውን እግዚአብሔርን በመተዋቸው ምክንያት ነው፤ ከዚህም በቀር ለእግዚአብሔር የነበራቸውን
ታማኝነት ትተው ሌሎች አማልክት አመለኩ፤ ሰገዱላቸውም፤ እግዚአብሔር ይህን ሁሉ የጥፋት መቅሠፍት ያመጣባቸውም ስለዚህ ነው የሚል ይሆናል። 10
ሰሎሞንም ቤተ መቅደሱንና ቤተ መንግሥቱን ለመሥራት የፈጀበት ጊዜ ሃያ ዓመት ነበር። 11 የጢሮስ ንጉሥ ኪራም ለዚህ ሁሉ ሥራ ለሰሎሞን
የሚያስፈልገውን የሊባኖስ ዝግባ ከብዙ ወርቅ ጋር ሰጥቶት ነበር፤ ሥራውም ሁሉ ከተፈጸመ በኋላ ሰሎሞን በገሊላ ምድር የሚገኙትን ሃያ ታናናሽ ከተሞችን
ለኪራም ሰጠው። 12 ኪራምም ሄዶ ከተሞቹን አየ፤ ነገር ግን ደስ አላሰኙትም፤ 13 ኪራምም ወንድሜ ሆይ! የሰጠኸኝ ከተሞች እነዚህ ምንድን ናቸውን?
አለው። በዚህ ምክንያት እስከ ዛሬ ድረስ አካባቢው በሙሉ «ካቡል» እየተባለ ይጠራል። 14 ኪራም ለንጉሥ ሰሎሞን የላከለት ወርቅ አንድ መቶ ሺህ መክሊት
ነበር። 15 ሰሎሞን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስና ቤተ መንግሥቱን፣ የኢየሩሳሌምንም ቅጥር የሠሩለትና ከከተማይቱም በስተ ምሥራቅ በኩል ያለውን ሚሎ
ተብሎ የሚጠራውን ጎድጓዳ ስፍራ መጥተው ያስተካከሉለት የጉልበት ሥራ ዋጋ ነበር፤ እንዲሁም ሐጸር፤ መጊዶናጊዜር ተብለው የሚጠሩ ከተሞችም
እንዲሠሩለት አደረገ። 16 ቀደም ሲል የግብጽ ንጉሥ ፈረዖን በጌዜር ላይ አደጋ ጥሎ፣ ነዋሪዎችዋን ከነዓናውያንን ገድሎ ከተማይቱንም አቃጥሎ በቁጥጥሩ
ሥር አድርጓት ነበር፤ ከዚያም በኋላ ለሴት ልጁ ለሰሎሞን ሚስት እንደ ስጦታ ሰጣት። 17 ሰሎሞንም ጊዜርንና የታችኛው ቤት ሖሮን እንደገና አሠራ። 18
ባዕላት በይሁዳ በረሓማ አገር የምትገኝ ታማር ተብለው የሚጠሩትን ከተሞች እንደገና ሠራ። 19 እነዚህም የስንቅ ማከማቻዎች፣ ፈረሶችና ሠረገሎች
የሚጠበቁባቸው ከተሞችን ሠራ። ሰሎሞንም በኢየሩሳሌም፤ በሊባኖስና በግዛቱ ሁሉ የሚፈልገውን ገነባ። 20 እነዚህም ትውልዶች የእስራኤል ወገን ያልሆኑና
የሚያገለግሉ አሞራውያን፣ ሒታውያን፣ ፈሪዛውያን፣ ኤዊያውያንና ኢያቡሳውያን ተብለው የሚጠሩ ናቸው። 21 ለሰሎሞን የጉልበት ሥራ ይሠሩለት የነበሩት
የግዳጅ ሥራ ሠራተኞች እስራኤላውያን ምድራቸውን ርስት አድርገው በወረሱ ጊዜ የገደሏቸው የከነዓን ሕዝብ ተውልዶች ነበሩ። 22 ሰሎሞን ከእስራኤላውያን
ወገን ማንንም ባሪያ አድርጎ አላሠራም፤ በዚህ ፈንታ እነርሱ ባለሥልጣኖች፣ ወታደሮች፣ የጦር መኮንኖች፣ የጦር አዛዦች፣ ሠረገላ ለሚነዱ ሁሉ ኃላፊዎችና
ፈረሰኞች ሆነው ያገለግሉ ነበር። 23 ሰሎሞን ለሚያከናውነው የሕንጻ ሥራ የጉልበት ሥራ ይሠሩ ዘንድ ለተመደቡት ሰዎች አምስት መቶ ኃምሳ ኃላፊዎች
ነበሩአቸው። 24 የግብጽ ንጉሥ የፈረዖን ልጅ የነበረችው ሚስቱ ከዳዊት ከተማ ራሱ ወዳሠራላት ቤተ መንግሥት ከተዘዋወረች በኋላ ሰሎሞን የሚሎን ከተማ
ገነባ። 25 ሰሎሞን ለእግዚአብሔር ባሠራው መሠዊያ ላይ የሚቃጠለውን መሥዋዕትና የኅብረት መሥዋዕት በዓመት ሦስት ጊዜ ያቀርብ ነበር፤ ከዚህም ሁሉ
ጋር ለእግዚአብሔር የሚቃጠለውን ዕጣን ያሳርግ ነበር፤ በዚህም ዓይነት የቤተ መቅደሱ ሥራ ተፈጸመ። 26 እንዲሁም ንጉሥ ሰሎሞን በኤዶም ምድር በቀይ
በሕር ዳርቻ በምትገኘው በኤላት አጠገብ ባለችው በዔጽዮን ጋብር መርከቦችን ሠራ። 27 ንጉሥ ኪራምም ከሰሎሞን ሰዎች ጋር የሚያገለግሉ የሠለጠኑ
መርከበኞችን ላከለት። 28 እነርሱም በመርከብ ተጉዘው ወደ ኦፊር ምድር ከሄዱ በኋላ ወደ ንጉሡ ወደ ሰሎሞን ሲመለሱ አራት መቶ ሃያ መክሊት ወርቅ
ይዘውለት መጡ።

---

1 Kings 9:3

ፀሎትህንና ልመናህን
ፀሎትና ልመና በመሠረቱ አንድ አይነት ትርጉም ሲኖራቸው የሰለሞን ጥያቄ ከቅንነት እንደሆነ እግዚአብሔር እውቅና እንደሠጠው አፅንኦት ለመስጠት ነው የ1ነገስት 8:28 ትርጉምን ተመልከት።

ለዘላለምም ስሜ በዚያ ያድር ዘንድ
“ስም” ለአንድ ግለሰብ ዘይቤአዊ ነው። ተርጓሚ “ለዘላለም በዚያ ለመኖርና ባለቤትነት ማሳያ”

ዓይኖቼና ልቤም .....በዚያ ይሆናሉ
“ዓይንና ልብም” የሰውን ሙሉ ሁለንተና ዘይቤ ናቸው። ተርጓሚ “ጥበቃና ጥንቃቄ አደርግለታለው”

1 Kings 9:4

ዳዊትም አባትህ ..... እንደ ሄደ አንተ ደግሞ በፊቴ ብትሄድ
የሰው የኑሮ ዘይቤው መንገድን እንደሚጓዝ ሰው ሆኖ ተነግሮአል። ተርጓሚ “ዳዊትም አባትህ....እንደ ኖረ አንተ ደግሞ ካንተ እንደምጠብቀው ብትኖር”

በየዋህ ልብና በቅንነት
እነዚህ ሁለት ቃላት በመሰረቱ ተመሣሣይ ሲሆኑ ዳዊት ምን ያህል ፃድቅ እንደነበር አፅንኦት ለመስጠት ነው።

1 Kings 9:6

ትእዛዜንና ሥርዓቴን
እዚህ ጋር ትእዛዝና ሥርዓት በመሰረቱ አንድ አይነት ነገር ሲሆኑ እግዚአብሔር እንዳዘዘ አፅንኦት ለመስጠት ነው።

ሌሎችን አማልክት ብታመልኩ ብትሰግዱላቸውም
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች በመሠረቱ አንድ አይነት ሲሆኑ የተጣመሩትም አፅንኦት ለመስጠት ነው።

ለስሜም.....እጥለዋለሁ
እዚህጋር “ስም” የሚለው ቃል የሆነ ነገር ላለው ሰው ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “ለራሴም .....እጥለዋለሁ”

ከፊቴም እጥለዋለሁ
“ከፊቴ” የሚለው ስውር ቃል “እይታ” ከሚለው ግስ ጋር ሊገለፅ ይችላል ወደ አንድ ነገር መመልከት ለሚደረግለት ጥበቃ ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “ከዚህ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወዲህ ወደማላየው ቦታ አስቀምጠዋለሁ” ወይም “ከዚህ በኋላ ጥበቃ ስለማደርግለት አስወግደዋለው”

1 Kings 9:8

ይህ ቤት ባድማ ይሆናል
“ይህ ቤት” (ቤተ-መቅደስ) ይፈርስና ቅሪቱም ቁልል አፈር (ድንጋይም)ይሆናል።

“እያፏዋጨ ..... ይደነቃል”
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “አድናቆትና የሚያዋርድ ድምፅ ያሰማል”

ሰገዱላቸውም..... አመለኩዋቸውም
ሁለቱ ቃላት በመሠረቱ አንድ አይነት ናቸው። “ሰገዱላቸውም” የሚለው ቃል ሰዎች ለአምልኮ የሚጠቀሙትን የሰውነት አቋም ይገልፃል።

1 Kings 9:10

ሀያ ዓመት በተፈፀመ ጊዜ
“ከ20 ዓመት በኃላ”

ሰለሞንም .....ቤት የሠራበት
ቤቱን ለመስራት ሰለሞንን ሌሎች ሰዎች እንደረዱት አንባቢው በሚረዳበት መንገድ መተርጎም የተሻለ ነው።

1 Kings 9:12

ወንድሜ ሆይ የሰጠኸኝ እነዚህ ከተሞች ምንድር ናቸው?
ኪራም ሰለሞንን እየገሠፀው ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ-ነገር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “እነዚህ የሰጠኸኝ ከተሞች ለምንም የሚጠቅሙ አይደሉም”

እስከ ዛሬም ድረስ .....ተጠሩ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “እስከ ዛሬም ድረስ ሰዎች ይጠሩዋቸዋል”

1 Kings 9:15

ሰለሞን.....ነገሮችን መልምሎ ነበር
“ሰለሞን.....የሚሠሩለትን ስዎች የፈለገበት”

ሚሎን
አማራጭ ትርጉሞች 1) “የእርከን ዘዴ” ወይም “ለባስ አፈር”

የግብፅም ንጉሥ ፈርኦን ወጥቶ ነበር
ግለሰብ የሚያዘው ሰራዊት ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “የግብፅ ንጉስ ፈርኦን ሠራዊት ወጥቶ....ነበር”

1 Kings 9:17

ሰለሞን ጌዝርን .....ሠራ
ይህንን ለመሥራት ሰለሞንን ሌሎት ሰዎች እንደረዱት አንባቢው በሚረዳበት መንገድ መተርጎም የተሻለ ነው።

1 Kings 9:22

ሰለሞን ከእስራኤል ልጆች ማንንም ባሪያ አላደረገም
ሰለሞን የእስራኤል ልጆች እንዲሠሩ አላስገደደም

1 Kings 9:23

550 ነበሩ
“አምስት መቶ ሃምሳ” ነበሩ

1 Kings 9:24

ሚሎን ሠራ
አማራጭ ትርጉሞች 1)እርከን ዘዴ ሠራ 2) ለባስ አፈር ሠራ የ1ነገስት 9፡15 ትርጉምን ተመልከት (ሚሎን የሚለውን)

1 Kings 9:25

መሰዊያ .....በእግዚአብሔር ፊት
የ1ነገስት 8፡64 ትርጉምን ተመልከት

1 Kings 9:26

ንጉስ ሰለሞን.....ሠራ
ይህን ለመስራት ሰለሞንን ሌሎች ሰዎች እንደረዱት አንባቢው በሚረዳበት መንገድ መተርጎም የተሻለ ነው።

መርከቦችን
“በርካታ ቁጥር ያላቸው መርከቦች”

420 መክሊት ወርቅ
“አራት መቶ ሀያ” መክሊት ወርቅ መክሊት የወርቅ መለኪያ ሲሆን ከ33 ኪ.ግ ጋር ይስተካከላል። ተርጓሚ ወደ 14,000 ኪ.ግ ገደማ ወርቅ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 10

1 ንግሥተ ሳባ እግዚአብሔር ለሰሎሞን ስለ ሰጠው አስደናቂ ጥበብ የሚነገረውንም ሁሉ ሰማች፤ ስለዚህ አስቸጋሪ በሆኑ ከባድ ጥያቄዎች ልትፈትነው ወደ
ኢየሩሳሌም መጣች። 2 ብዙ የክብር አጃቢዎችን በማስከተል በግመሎች የተጫነ ሽቶ፣ የከበረ ዕንቁና ብዙ ወርቅ ይዛ መጣች፤ ከሰሎሞንም ጋር በተገናኙ ጊዜ
በአሳብዋ ያለውን ጥያቄ ሁሉ አቀረበችለት፤ 3 እርሱም ላቀረበችለት ጥያቄ ሁሉ መልስ ሰጣት፤ ከጠየቀችው ሳይመልስለት የቀረ ምንም ዓይነት እንቆቅልሽ
አልነበረም። 4 ንግሥተ ሳባ ጥበብ የተሞላበትን የሰሎሞንን አነጋገር አዳመጠች፤ የሠራውንም ቤተ መንግሥት አየች። 5 በሰሎሞን ገበታ ላይ የሚቀርበውን
የምግብ ዓይነት፣ የመኳንንቱን መኖሪያ አካባቢዎች፣ የቤተ መንግሥቱን አሠራርና አደረጃጀት፣ የደንብ ልብሳቸውን ዓይነት፣ በግብዣ ጊዜ የሚያገለግሉትን
አሳላፊዎችና በቤተ መቅደስም ያቀረባቸውን መሥዋዕቶችን ሁሉ ተመለከተች፤ በዚህም ሁሉ የተሰማት አድናቆት ከጠበቀቸው በላይ ሆነባት፤ 6 ስለሥራህ
ውጤትና የጥበብህ ታላቅነት በአገሬ ሳለሁ የሰማሁት ሁሉ እውነት ነው አለች። 7 ነገር ግን እዚህ ድረስ መጥቼ በዐይኔ እስካይ ድረስ የተነገረኝን ሁሉ
አላመንኩም ነበር፤ በጆሮዬ የሰማሁት በዐይኔ ያየሁትን እኩሌታ እንኳ አይሆንም፤ በእርግጥም ጥበብህና ሀብትህ በአገሬ ሳለሁ ከተነገረኝ በጣም ይበልጣል።
8 ሁልጊዜ በፊትህ በመገኘት ጥበብ የሞላበት ንግግርህን የሚሰሙ ሚስቶችህና አገልጋዮችህ እንዴት የታደሉ ናቸው! 9 አምላክህ እግዚአብሔር ይመስገን፤
እርሱ አንተን መርጦ የእስራኤል ንጉሥ በማድረግ በአንተ መደሰቱን ገልጦልሃል፤ ለእስራኤል ያለውም ፍቅር ለዓላማው ስለ ሆነ ጽድቅና ፍትሕ ጸንቶ እንዲኖር
ታደርግ ዘንድ የእስራኤል ንጉሥ አድርጎሃል። 10 ንግሥተ ሳባ ያመጣችለትን ስጦታ ሁሉ ለንጉሥ ሰሎሞን አበረከተችለት፤ ይኸውም ከአራት ሺህ ኪሎ
የሚበልጥ ወርቅ፣ እጅግ ብዙ ሽቶና የከበረ ዕንቁ ነበር፤ እርስዋ ለሰሎሞን ያበረከተችው የሽቶ ብዛት ከዚያ በኋላ ከቀረበለት የሽቶ ገጸ በረከት ሁሉ እጅግ
የሚበልጥ ነበር። 11 ከኦፊር ወርቅ ብዙ ያመጡለት የኪራም መርከቦች ከዚያው ከኦፊር ብዙ የሰንደል እንጨትና የከበረ ዕንቁ አምጥተውለት ነበር። 12
ሰሎሞን ከዚሁ ከሰንደል እንጨት የቤተ መቅደሱንና የቤተ መንግሥቱን መከታዎች፤ መዘምራን የሚያገለግሉባቸውን በገናዎችና መሰንቆዎች አሠራ፤ ይህም
የሰንደል እንጨት ወደ እስራኤል አገር ከመጣው የሰንደል እንጨት ሁሉ የሚበልጥ ነበር፤ ከዚያ በኋላ ይህን የመሰለ የሰንደል እንጨት ከቶ ታይቶ አይታወቅም።
13 ንጉሥ ሰሎሞን ከተለመደው የልግሥና ስጦታ ጋር የሳባ ንግሥት የጠየቀቸውን ሁሉ ሰጣት። ከዚህ በኋላ ንጉሥተ ሳባ ከክብር አጃቢዎችዋ ጋር ወደ አገርዋ
ተመልሳ ሄደች። 14 ንጉሥ ሰሎሞን በየዓመቱ ሃያ ሦስት ሺህ ኪሎ ያህል የሚመዝን ወርቅ ያገኝ ነበር፤ 15 ይህም ሁሉ ነጋዶዎች ከሚከፍሉት ቀረጥ፤ ከንግድ
ከሚገኘው ትርፍ እንዲሁም ከዐረብ ነገሥታትና ከእስራኤል ክፍላተ አገር አስተዳዳሪዎች ከሚገባለት ግብር ጋር ተጨማሪ ነበር። 16 ንጉሥ ሰሎሞን ሁለት መቶ
ታላላቅ ጋሻዎች አሠርቶ እያንዳንዱን ጋሻ በሰባት ኪሎ ያህል ወርቅ አስለበጠው። 17 እንዲሁም ሦስት መቶ ታናናሽ ጋሻዎችን አሠርቶ እያንዳንዱን በሁለት ኪሎ
ያህል ወርቅ አስለበጠው፤ እነዚህንም ሁሉ ሊባኖስ ጫካ ተብሎ በሚጠራው አዳራሽ ውስጥ አኖራቸው። 18 እንዲሁም ንጉሥ ሰሎሞን ከዝሆን ጥርስ አንድ
ትልቅ ዙፋን አሠርቶ በንጹሕ ወርቅ አስለበጠው። 19 ወደ ዙፋኑ መወጣጫ ስድስት ደረጃዎች ነበሩ፤ የዙፋኑ ጀርባ ራስጌው ክብ ነበር፤ በዙፋኑ ግራና ቀኝ
የክንድ ማሳረፊያዎች ነበሩት፤ በክንድ ማሳረፊያዎቹ ጎን አንዳንድ የአንበሳ ምስሎች ቆመው ነበር። 20 በእያንዳንዱ ደረጃ በሁለት በኩል አንዳንድ የአንበሳ
ምስል በድምሩ ዐሥራ ሁለት የአንበሳ ምስሎች ቆመዋል። ይህን የመሰለ ዙፋን በሌላ በየትኛውም አገር ተሠርቶ አያውቅም ነበር። 21 በሰሎሞን ዘመን ብር
ምንም ዋጋ ስላልነበረው ሰሎሞን የሚጠጣባቸው ዋንጫዎች ሁሉና የሊባኖስ ጫካ ተብሎ በሚጠራው አዳራሽ ውስጥ የሚገኙት ዕቃዎች በሙሉ ከንጹሕ
ወርቅ እንጂ ከብር አልተሠሩም፤ 22 ሰሎሞን ከኪራም መርከቦች ጋር በውቅያኖስ ላይ የሚጓዙ ሌሎች የተርሴስ መርከቦችም ነበሩት፤ እነርሱ በየሦስት ዓመት
ወርቅ፣ ብር፣ የዝሆን ጥርስ፣ ጦጣዎችንና ዝንጀሮዎችን ያመጡለት ነበር። 23 ንጉሥ ሰሎሞን ከምድር ነገሥታት ሁሉ የሚበልጥ ሀበታምና ጥበበኛ ነበር፤ 24
በመላው ዓለም የሚገኙ ሰዎችም ሁሉ እግዚአብሔር የሰጠውን ጥበብ የሞላበትን ንግግር ይሰሙ ዘንድ ወደ እርሱ መምጣት ይፈልጉ ነበር። 25 ወደ እርሱም
የሚመጡት ሁሉ የብርና የወርቅ፣ የልብስ፣ የጦር መሣሪያዎች፣ የሽቶ፣ የፈረሶች የበቅሎዎች ስጦታዎች ያመጡለት ነበር፤ ይህም በየዓመቱ የሚደረግ ነበር። 26
ሰሎሞንም ሠረገሎችና ፈረሶች ሰበሰበ፤ እርሱም አንድ ሺህ አራት መቶ ሠረገሎችና ዐሥራ ሁለት ሺህ ፈረሶኞች ነበሩት፤ ከእነርሱም ከፊሎቹን ከእርሱ ጋር
በኢየሩሳሌም፣ ሌሎቹ ደግሞ በልዩ ልዩ ከተሞች ተመድበው እንዲኖሩ አደረገ። 27 በግዛቱም ዘመን ሁሉ በኢየሩሳሌም ብር እንደ ድንጋይ፣ ብዛቱም እንደ
ሊባኖስ ዛፍ፣ በይሁዳ ኮረብቶች ግርጌ በየትኛውም ስፍራ እንደሚበቅለው ሾላም ይቆጠር ነበር። 28 ሰሎሞን ፈረሶችን ከግብጽና ከቀዌ ያስመጣ ነበር፤
የንጉሡም ነጋዴዎች ፈረሶችን በገንዘብ ገዝተው ከቀዌ ያመጡለት ነበር። 29 እያንዳንዱ ፈረስ በስድስት መቶ ጥሬ ብር፣ እያንዳንዱም ሠረገላ በአንድ መቶ
ሃምሳ ጥሬ ብር ከግብጽ አገር ተገዛ። ከዚያም ለሒታውያንና ለሶርያውያን ነገሥታት ተሸጡ።

---

1 Kings 10:1

በእግዚአብሔር ስም የወጣለትን የሰለሞን ዝና
እዚህ ጋር እግዚአብሔር “በስሙ” ተወክሏል።አማራጭ ትርጉሞች 1) ተርጓሚ “የእግዚአብሔርን ስም የሚያከብር የሰለሞንን ዝና” ወይም 2) ተርጓሚ “እግዚአብሔር የሰጠው የሰለሞን ዝና”

በልብዋ ያለውን ሁሉ
ይህ ጥቅል ነው። ተርጓሚ “ማወቅ የምትፈልገውን ነገር ሁሉ”

1 Kings 10:3

የሎሌዎቹንም አሠራር
አማራጭ ትርጉሞች 1) “ሎሌዎቹ በማዕድ ዙሪያ እንዴት እንደተቀመጡ” ወይም 2)“ሎሌዎቹ የሚኖሩበት ሥፍራ”

ነፍስ አልቀረላትም
ይህ ፈሊጣዊ ነው። ተርጓሚ “በጣም ተገርማ ነበር”

1 Kings 10:6

በአገሬ ሳለው የሰማሁት.....ነው
“በአገሬ ሳለው ሰምቼ ነበር”

ጥበብህና ስራህ
እዚህ ጋር ጥበብ የሚለው ቃል ስራህ የሚለውን ቃል ሊገልፅ ይችላል። ተርጓሚ “በጥበብ የተሞላው አባባልህ”

በዓይኔ እስካይ ድረስ
በዓይኔ የሚለው ቃል እርሷ ራሷ እንዳየችው አፅንኦት ይሠጣል። ተርጓሚ “እኔ ለራሴ አይቼ ነበር”

ስለነገርህና ስለጥበብህ..... እኩሌታውን አልነገሩኝም
ይህ ያለ ጉልት አፃፃፍ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ከነገርህና ከጥበብህ.....እኩሌታውን እንኳ አልነገሩኝም” ወይም “ከነገሩኝ በላይ እጅግ በጣም ባለጠጋና ጥበበኛ ነህ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Kings 10:8

በፊትህ ሁልጊዜ የሚቆሙ
ይህ ፈሊጣዊ ነው። ተርጓሚ “ሊያገለግሉህ ሁልጊዜ በፊትህ የሚጠባበቁ”

አምላክህ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ሰዎች እግዚአብሔር አምላክህን ያመስግኑ”

በእስራኤል ዙፋን ያስቀመጠህ
“ዙፋን” በዙፋን ላይ ስለተቀመጠው ንጉስ ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “የእስራኤል ንጉስ ያደረገህ”

1 Kings 10:10

120 መክሊት መርቅ
“አንድ መቶ ሀያ መክሊት ወርቅ” “መክሊት” የወርቅ መለኪያ ሲሆን ከ33 ኪ.ግ ጋር ይስተካከላል። ተርጓሚ “ወደ 4,000 ኪ.ግ ገደማ ወርቅ”

እንደሰጠችው ያለ የሸቱ ብዛት ከዚያ ወዲያ አልመጣም
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ንግስተ ሳባ የሰጠችውን ሸቱ ያክል ማንም ለንጉስ ሰለሞን ሰጥቶት አያውቅም”

1 Kings 10:11

ንጉሡም.....አደረገ
ይህንን ለመሥራት ሰለሞንን ሌሎች ሰዎች እንደረዱት አንባቢው በሚረዳበት መንገድ መተርጎም የተሻለ ነው። ተርጓሚ “ንጉሡ ለሠራተኞቹ እንዲሠሩ አደረገ”

የሰንደል እንጨት
ምናልባት ደስ የሚያሰኝ ሽታ (መዓዛ) ያለው የእንጨት አይነት ነው።

አልመጣም አልታየም
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “እንዲህ ያለ ብዛት ማንም ዳግም አይቶ አያውቅም”

ዛሬም ድረስ
x

1 Kings 10:13

የወደደችውን ሁሉ.....የለመነችውን ሁሉ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ አንድ አይነት ነገር ሲሆን አፅንኦት ለመስጠት ተጣምረዋል።

በገዛ እጁ
“ምክንያቱም እንደ ንጉሥ እጅግ ብዙ ነበረው።”

1 Kings 10:14

በየዓመቱ
ይህ የሰለሞን የየአመቱ የንግስና ዘመን የሚገልፅ እንጂ የአንድ አመት ብቻ አይደለም

666 መክሊት ወርቅ
“ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት” መክሊት የወርቅ መለኪያ ሲሆን የ33 ኪ.ግ ልኬት ነው። ተርጓሚ “ወደ 22,000 ኪ.ግ የሚጠጋ ወርቅ”

1 Kings 10:16

ንጉሡም ሰለሞን .....አሠራ
ለአንባቢው ሌሎች ሰዎች ይህን ለመስራት ሰለሞንን እንደረዱት ተደርጎ ቢተረጎም የተሻለ ነው። ተርጓሚ “የንጉሥ ሰለሞን ሠራተኞች ሠሩት”

ሁለት መቶ አላበሸ አግሬ ጋሻ
“200 አላበሸ አግሬ ጋሻ”

1 Kings 10:18

ንጉሡም አሠራ
ለአንባቢው ሌሎች ሰዎች ይህን ለመስራት ሰለሞንን እንደረዱት ተደርጎ ቢተረጎም የተሻለ ነው። ተርጓሚ “የንጉሡ ሠራተኞች ሠሩት”

ከዝሆን ጥርስ.....ዙፋን
የዝሆን ጥርስ ጠንካራ ሆኖ ከትላልቅ እንስሳት ጥርስ የተሠራ ነጭ ቀለም ያለው ነገር ነው

ዝንጀሮ
ይህ በአፍሪካ የሚገኝ የድር እንስሳ ነው። ወደ እጅና እግር አከባቢ ከሰው ጋር የመመሣሠል ነገር ያለው ሲሆን ረጅም ጭራ አለው። አንዳንድ ሰዎች ዝንጀሮን የጦጣ ዝርያ አድርገው ያስባሉ።

1 Kings 10:23

ምድርም ሁሉ
ይህ ጥቅል ነው። ተርጓሚ “ከሁሉም ሥፍራ የመጡ ሰዎች” ወይም “ከተለያየ ቦታ የሆኑ ሰዎች”

የሰለሞንን ፊት ይመኝ ነበር
“ፊት” አንድን ሰው የማውራትና የማዳመጥ ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “ሰለሞንን ማዳመጥ ይመኝ ነበር” ወይም “ሰለሞንን መጎብኘት ተመኘ (ፈለገ)”

1 Kings 10:26

1400 ሰረገሎች አስራ ሁለት ሺህ ፈረሰኞች
“አንድ ሺህ አራት መቶ ሰረገሎች 12,000 ፈረሰኞች”

ንጉሡም ብሩን በኢየሩሳሌም እንደ ድንጋይ እንዲበዛ አደረገው
ፀሐፊው በኢየሩሳሌም የነበረውን ብር አጋንኖ ያሳያል። ተርጓሚ “ንጉሡ እጅግ በጣም ብዙ ብር ነበረው በመሬት ላይ ድንጋይ የሚበዛውን ያክል የሚበዛ ብር ነበረ።”

1 Kings 10:28

ከግብፅ.....አስመጣ
ይህ በገቢር መልኩ ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ “እነዚህ ነጋዴዎች በግብፅ ምድር ከነበሩ ሰዎች አመጡ”

ቀዌ
ይህ የአንድ ግዛት ስም ነው። ተርጓሚ “አንዳንድ ሰዎች ቀዌ በትንሿ እሲያ ከምትኝ ከስልቢያ ጋር ይመሣሠልባቸዋል።”

ሰረገላ.....ይወጣ ነበር
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ነጋዴዎቹ ሰረገላ ገዙ”

ስድስት መቶ.....ብር .....መቶ ሃምሳ ብር
ስድስት መቶ ሰቅል ብር.... መቶ ሃምሳ ሰቅል ብር 600ብር... 150 ብር ወይም 1ሰቅል ከ11 ግራም ጋር ስለሚስተካከል 6.6ኪ.ግ ብር..... 1.7ኪ.ግ ብር ሊሆን ይችላል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ስድስት መቶ (ሰቅል)ብር
600 (ሰቅል) ብር

150 (ሰቅል**)** ብር
አንድ መቶ ሃምሳ (ሰቅል)ብር

ያወጡላቸው ነበር
ይህ በገቢር መልኩ ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ “የእርሱ ነገጋዴዎች አብዛኛዎቹን ሸጡአቸው”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 11

1 ሰሎሞን ብዙ የባዕዳን አገሮችን ሴቶች አፈቀረ፤ እነዚህም፦ የግብጽ ንጉሥ የፈረዖን ልጅ፣ የሒታውያን፣ የሞአባውያን፣ የአሞራውያን፣ የኤዶማውያንና
የሲዶናውያን ሴቶች ልጆችን አፈቀረ። 2 እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን፣ አሕዛብ ሴቶችን ያገባችሁ እንደ ሆነ በእርግጥ ወደ አማልክቶቻቸው ስለሚስቡአችሁ
እነርሱን አታግቡ ብሎ አስጠንቅቆአቸው ነበር። እነዚህ ሰሎሞን የወደዳቸው ሴቶች እግዚአብሔር እንዳያጋቡ ከከለከላቸው ሕዝቦች መካከል ናቸው። ይህ
ትእዛዝ ቢኖርም ሰሎሞን ግን በእነርሱ ፍቅር ተነደፈ። 3 ሰሎሞን የነገሥታት ልጆች የሆኑ ሰባት መቶ ሚስቶችና ሦስት መቶ ቁባቶች ነበሩት። ሚስቶቹም
ሰሎሞንን ከእግዚአብሔር እንዲርቅ አደረጉት። 4 በተለይም በዕድሜ እየሸመገለ በሄደ መጠን ለባዕዳን አማልእክት እንዲሰግድ አደረጉት። ሰሎሞንም እንደ
አባቱ እንደ ዳዊት ሙሉ ልቡን ለእግዘአብሔር አላስገዛም። 5 የሲዶናውያን ሴት አምላክ የነበረችውን ለአስታሮትንና ሞሎክ ተብሎ የሚጠራውን ተለይቶ
የሚታወቀውን የአሞናውያንን አምላክ ተከተለ። 6 ሰሎሞንም በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነውን ነገር በማድረጉ አባቱ ዳዊት እንዳደረገው እግዚአብሔርን
በቅንነት አልተከተለም። 7 ከኢየሩሳሌም በስተ ምሥራቅ በሚገኘው ተራራ ላይ ከሞሽ ተብሎ ለሚጠራው ለሞአባውያን አምላክና ሞሎክ ተብሎ ለሚጠራው
ለአሞናውያን አምላክ የመስገጃ ስፍራዎችን ሠራ። 8 እንዲሁም የባዕዳን አገር ሚስቶቹ ሁሉ ለየአማልክቶቻቸው ዕጣን የሚያጥኑባቸውንና መሥዋዕት
የሚያቀርቡባቸውን ስፍራዎች ሠራ። 9 የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ሁለት ጊዜ የተገለጠለት ቢሆንም፣ ከእርሱ እየራቀ በመምጣቱ እግዚአብሔር
ሰሎሞንን ተቆጣው። 10 ባዕዳን አማልክትን እንዳያመልክ አዘዘው። ነገር ግን ሰሎሞን ለእግዚአብሔር አልታዘዘም። 11 ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲህ አለው፦
ከእኔ ጋር የገባኸውን ቃል ኪዳን ስላፈረሰክና ሕጌንም ስላልፈጸምክ መንግሥትህን ከአንተ ወስጄ ከአገልጋዮችህ ለአንዱ እሰጣለሁ። 12 ይሁን እንጂ ለአባትህ
ለዳዊት ስል ይህን የማደርገው አንተ ባለህበት ዘመን ሳይሆን በልጅህ መንግሥት ጊዜ ይሆናል። 13 ሆኖም ሁሉንም መንግሥት አልወስድም፤ ለአገልጋዬ
ለዳዊትና ለመረጥኩት ከተማ ለኢየሩሳሌም ስል ለልጅህ አንዱን ነገድ እሰጠዋለሁ። 14 ስለዚህም እግዚአብሔር የኤዶማውያኑን ነገሥታት ዘር ሀዳድን
በሰሎሞን ላይ ጠላት አድርጎ አስነሣበት። እርሱም ከኤዶም ንጉሣዊ ቤተ ሰብ ነበር። 15 ዳዊት ከኤዶማውያን ጋር ይዋጋ በነበረ ጊዜ፣ የጦር አዛዡ ኢዮአብ
ለመቅበር ወጥቶ በነበረበት ጊዜ፣ በኤዶም ወንዶች ሁሉ ተገድለው ነበር። 16 ኢዮአብና የእስራኤል ሠራዊት የኤዶምን ወንዶች ልጆች ገድለው እስኪጨርሱ
ድረስ ስድስት ወራት በዚያ ቆይተዋል። 17 ነገር ግን ከሞት የተረፉትና ሀዳድ በአባቱ አገልጋዮች ወደ ግብጽ ተወሰዱ። በዚያን ጊዜ ሀዳድ ገና ሕፃን ነበር። 18
እነርሱም ከምድያም ተነሥተው ሰዎችን ወደ ግብፅ ወደወሰዱበት ወደ ፋራን ሄዱ፤ በዚያም የግብፅ ንጉሥ ፈርዖን ለሀዳድ ቤት፣ መሬትና ምግብ ሰጠው። 19
ሀዳድም በንጉሡ ፈርዖን ፊት ታላቅ ሞገስ አገኘ። ስለዚህ ንጉሡም የሚስቱን የጣፍኔስን እኅት ለሀዳድ ሚስት እንድትሆነው ሰጠው። 20 የጣፍኔስንም እኅት
ጌንባት ተብሎ የሚጠራውን ወንድ ልጅ ለሀዳድ ወለደችለት፤ እርሱንም ንግሥቲቱ ወስዳ በቤተ መንግሥት አሳደገችው፤ ከፈረዖንም ወንዶች ልጆች ጋር ኖረ። 21
ሀዳድ በግብጽ ሳለ የንጉሥ ዳዊትንና የሠራዊቱን አዛዥ የኢዮአብን መሞት በሰማ ጊዜ፣ ወደ አገሬ ተመልሼ እንድሄድ አሰናብተኝ ሲል ፈረዖንን ጠየቀ። 22
ከዚያም ፈረዖን ስለምን ትሄዳለህ? ወደ አገርህ ለመሄድ የፈለግከው ከቶ ምን ተጓድሎብህ ነው? አለው። ሀዳድም ምንም የተጓደለብኝ ነገር የለም፤ ብቻ ወደ
ትውልድ አገሬ እንድመለስ ፍቀድልኝ ሲል ለንጉሡ መለሰ። 23 እንደገናም እግዚአብሔር ረዞን ተብሎ የሚጠራውን የኤሊዓዳ ልጅ በሰሎሞን ላይ ሌላ ጠላት
አድርጎ አስነሣበት። ረዞን የጾባ ንጉሥ ከነበረው ከጌታው ከዞአብ ንጉሥ ከሀዲድዔዚር ኮብልሎ ነበር። 24 ዳዊት ሀዲድዔዚርን ድል ባደረገበት ጊዜ፣ ረዞን
ለራሱ ጦር ሰብስቦ የጥቂት ኃይል አለቃ ሆኖ ነበር። የረዞን ጦር ወደ ደማስቆ ሄደው እዚያ መኖር ጀመሩ፤ በኋላም ደማስቆን ተቆጣጠረ። 25 በሰሎሞን
ዘመነ መንግሥት ሁሉ ሀዳድ ካደረሰበት ችግር በተጨማሪ ረዞን የእስራኤል ጠላት ነበር። ስለዚህ ረዞን በሶርያ ላይ ገዢ ሆኖ በእስራኤል ላይ ጠላትነቱን
ቀጠለ። 26 የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም፣ ኤፍሬማዊው የሰሎሞን ባለሥልጣናት አንዱ የሆነው፣ ጸሬዳ ተብሎ የምትጠራው ክፍል ተወላጅ የሆነ፣ የእናቱም ስም
ጽሩዓ፣ ባልዋ የሞተባት ሴት ነበረች፤ እርሱም በሰሎሞን ላይ እጁን አነሣ። 27 ኢዮርብዓም በሰሎሞን ላይ እጁን ያነሣበት ምክንያት፤ በዚያን ጊዜ ሰሎሞን
ከኢየሩሳሌም በስተ ምሥራቅ ሚሎ ተብሎ የሚጠራውን ጎድጓዳ ስፍራ በመሙላት እየደለደለና የአባቱን የዳዊትን ከተማ ቅጥሮች እየጠገነ ነበር። 28
ኢዮርብዓም ጽኑዕ ኃያል ሰው ነበር። ሰሎሞንም ይህን ተመልክቶ ወጣቱ ትጉህና ብርቱ ሠራተኛ በመሆኑ በዮሴፍ ነገድ ግዛት ላይ ሁሉ ኃላፊ አድርጎ ሾመው።
29 በዚያን ጊዜ ኢዮርብዓም ከኢየሩሳሌም ወጥቶ በጉዞ ላይ ሳለ፣ ሴሎናዊው ነቢዩ አኪያ በመንገድ ላይ አገኘው። አኪያም አዲስ መጎናጸፊያ ለብሶ ሁለት
ሰዎች ለብቻ በሜዳ ላይ ነበሩ። 30 አኪያም የለበሰውን አዲስ መጎናጸፊያ አውልቆ ከዐሥራ ሁለት ቆራረጠው። 31 ኢዮርብዓምንም እንዲህ አለው፤ የእስራኤል
አምላክ እግዚያብሔር እንዲህ ይላል፦ «ዐሥሩን ቁራጭ ለራስህ ውሰድ፤ ‹መንግሥትን ከሰለሞን ወስጄ ዐሥሩን ነገድ ለአንተ እሰጥሃለሁ፣ 32 ለአገልጋዬ
ለዳዊትና ከሁሉም የእስራኤል ነገዶች ለመረጥኳት ለኢየሩሳሌም ከተማ ስል ለሰለሞን አንድ ነገድ አስቀርቼለታለሁ። 33 ይህንንም የማደርገው ሰሎሞን እኔን
ትቶ ባዕዳን አማልክትን፦ አስታሮት ተብላ የምትጠራውን የሲዶና አምላክ፣ ካሞሽ ተብሎ የሚጠራውን የሞአብ አምላክና ሞሎክ ተብሎ የሚጠራውን
የአሞናውያን አምላክ ስላመለከ ነው። አባቱ ዳዊት እንዳደረገ በፊቴ ትክክል የሆነውን፣ ሕጎቼንና ትእዛዞቼንም አልጠበቀም። 34 ይሁን እንጂ ከሰለሞን እጅ
መንግሥትን በሙሉ አልወስድበትም፤ በዚህ ፈንታ በሕይወት እስካለም ድረስ በሥልጣን ላይ እንዲቆይ አደርገዋለሁ፤ ይህንንም የማደርገው ለመረጥኩትና
ሕጎቼንና ትእዛዞቼን ለፈፀመው ለአገልጋዬ ለዳዊት ስል ነው። 35 ነገር ግን መንግሥትን ከሰለሞን ልጅ ወስጄ ለአንተ ዐሥሩን ነገዶች እሰጥሃለው። 36 ስሜ
እንዲጠራባት በመረጥኳት በኢየሩሳሌም አገልጋዬ ዳዊት በፊቴ አንድ ዘር ይኖረው ዘንድ ለልጁ አንድ ነገድ እሰጠዋለው። 37 ኢዮርብዓም ሆይ! እኔ አንተን
የእስራኤል ንጉሥ አድርጌሃለሁ፤ አንተ በወደድከው ግዛት ሁሉ ላይ መሪ ትሆናለህ። 38 አገልጋዬ ዳዊት እንዳደረገው በፍፁም ልብህ ብትታዘዘኝ፣ በሕጎቼና
በትእዛዞቼ ጸንተህ ብትኖር፣ በእኔ ፊት ሞገስ ብታገኝ፣ እኔ ዘወትር ከአንተ ጋር እሆናለሁ፤ በእስራኤል ላይ እንድትነግሥም አደርግሃለሁ፤ ለዳዊት ባደረግሁት
ዓይነት ዘሮችህ ከአንተ በኋላ እንደሚነግሡ አረጋግጥልሃለሁ። 39 በሰለሞን ኃጢአት ምክንያት የዳዊትን ትውልዶች እቀጣለሁ፤ ነገር ግን የምቀጣቸው
ለዘላለም አይደለም። 40 ከዚህም የተነሣ ሰለሞን ኢዮርብዓምን ለመግደል ሞከረ። ነገር ግን ኢዮርብዓም ወደ ግብፅ ንጉሥ ሺሻቅ በመኮበለል አመለጠ፤
ሰለሞን እስከ ሞተበት ጊዜ ድረስ እዚያው ቆየ። 41 ሰለሞን ያደረገው ሌላው ነገር፣ ያከናወነው ተግባርና ጥበቡ ሁሉ በሰለሞን የታሪክ መጽሐፍ የተመዘገበ
አይደለምን? 42 ሰለሞንም በኢየሩሳሌም በመላው እስራኤል ላይ የነገሠበት ዘመን አርባ ዓመት ነበር። 43 ከዚህ በኋላ ሰለሞን ሞተ፣ በአባቱ በዳዊት
ከተማም ተቀበረ፤ ልጁም ሮብዓም በአባቱ በሰለሞን ተተክቶ ነገሠ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Kings 11:1

ንጉሱም ሰለሞን
“ንጉሡም” የሚለው ቃል በዋናው ታሪክ ውስጥ ሌላ የታሪኩን ክፍል ለማሳየት ተራኪው የተጠቀመበት ነው።

ሞዓባውያን....አሞናውያን.... ኤዶማውያን..... ሲዶናውያን..... ኬጢያውያን
“እነዚህ የሰዎች የጎሳ ስም ናቸው”

አምላኮቻቸውን ትከተሉ ዘንድ.....ልባችሁን ያዘነብላሉና
የአንድ ሰው ልብ ማዘንበል ማለት የልቡን ሃሳብ እንዲለውጥ ማሳመን ማለት ነው።“የእነርሱን አምላክ እንድታመልኩ አሳመኑአችሁ”

1 Kings 11:3

ወይዛዝር የሆኑ ሰባት መቶ ሚስቶች ሦስት መቶ ቁባቶች
ወይዛዝር የሆኑ 700 ሚስቶችና 300 ቁባቶች

ልቡን አዘነበሉት
የአንድን ሰው ልብ ማዘንበል ማለት የልቡን ሃሳብ (ፍቅር) እንዲለውጥ ማድረግ ማለት ነው። የ1ነገስት 11:01 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ “ልቡን ከእግዚአብሔር መለሰ” ወይም “የእነርሱን አምላክ እንዲያመልክ አሳመኑት”

የአባቱ ዳዊት ልብ .....ፍፁም እንደነበረ.....ልቡ እንዲሁ አልነበረም
ልብን ፍፁም ማድረግ ሙሉ በሙሉ መስጠትን ወይም መውደድን ይገልፃል። ተርጓሚ “እንደ ዳዊት ሙሉ በሙሉ የተሰጠ አልነበረም”

1 Kings 11:5

አስታሮትን.....ሚልኮምን
እነዚህ የሐሰተኛ አማልክት ስሞች ናቸው።

ሲዶናውያን
ይህ የአንድ ጎሳ ህዝብ ስም ነው።

ሚልኮምን ተከተለ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገርን
“ፊት” የሚለው ቃል የአንድ ሰው አመለካከትን ይገልፃል። ተርጓሚ “እግዚአብሔር እንደ ክፉ ያየውን”

1 Kings 11:7

ካሞሽ.....ሞሎክ
እነዚህ የሐሰተኛ አማልክት ሥሞች ናቸው

ለአማልክቶቻቸው.....መሥዋዕትም .....አደረገ
ይህ ሰለሞን በሰራው መስገጃ ሥፍራ መሆኑን ለማሳየት ነው።

1 Kings 11:9

ልቡን አርቆአልና
“ልብን” የሚለው ቃል ሐሳቡን ፍቅሩን መቀየሩን ያሳያል። የ1ነገስት 11:01 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ “ሰለሞን እግዚአብሔርን ማምለክ አቆመ”

ሁለት ጊዜም ተገለጠለት
“እግዚአብሔር ለሰለሞን ሁለት ጊዜ ተገለጠለት”

1 Kings 11:11

መንግስትህ ከአንተ ቀዳድጄ
x

1 Kings 11:14

ሃዳድ
ይህ የሰው (የወንድ)ስም ነው።

ዳዊት በኤዶምያስ በነበረ ጊዜ .....ሃዳድ ገና ብላቴና ሳለ
ይህ ከረጅም ጊዜ በፊት የተከሰተ ነው።

1 Kings 11:18

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ክፍል በ1ነገስት 11:15 ለጅመረው መረጃ ተከታይ ነው።

ከምድያምም ....መጡ
“መጡ” የሚለው ቃል በ1ነገስት 11:17 እንደተጠቀሰው ሃዳድና ሌሎች ኤዶማውያንን ይወክላል።

ምድያም....ፋራን ...ግብፅ
እነዚህ የቦታ ሥሞች ናቸው።

ቴቄምናስ
ይህ የሴት ስም ነው።

ጌንባት.....ሃዳድ
ይህ የሰዎች (የወንድ) ስም ነው።

ዳዊት ከአባቶቹ ጋር እንዳንቀላፋ
ይህ በትህትና መልኩ የዳዊትን ሞት ይገልፃል። ተርጓሚ “ዳዊት አረፈ” ወይም “ዳዊት ሞተ”

1 Kings 11:23

ሬዘን ....ኤልያዳ ....አድርአዘር
እነዚህ የሰዎች (የወንዶች) ስሞች ናቸው።

ሱባ.....ደማስቆስ..
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው።

ዳዊትም .....በገደለ ጊዜ
እዚህ ጋር “ዳዊት” ዳዊትንና የዳዊትን ሠራዊት ይገልፃል። ተርጓሚ “የዳዊት ሠራዊት ድል ባደረገ ጊዜ”

በሰለሞን ዘመን ሁሉ
“ሰለሞን በሕይወት በነበረበት ጊዜ” ወይም “የሰለሞን የሕይወት ዘመን”

ሬዘን .....የእስራኤል ጠላት ነበር
“ሬዘን እስራኤልን አብዝቶ ይጠላ ነበር”

1 Kings 11:26

ናባጥ .....ኢዮርብዓም
እነዚህ የሳዎች (የወንዶች) ስም ናቸው።

ሳራራ.....ሚሎን
እነዚህ የቦታ ሥሞች ናቸው።

ፅሩዓ
ይህ የሴት ስም ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በንጉሡም ያመፀበት
“ያመፀበት” የሚለው ቃል ስልጣንን፣ ጉልበትና ቁጥጥርን በመጠቀም አንድን ሰው መቃወምን ይገልፃል። ተርጓሚ “በንጉሡም ላይ አመፀበት”

ሰለሞን ሚሎን ሠራ
ሚሎን በ1ነገስት 9፡15 ላይ ባለው መሠረት ይተርጎም።

1 Kings 11:28

ፅኑ ኃይል ሰው
አማራጭ ትርጉም 1) ታላቅ ጦረኛ ወይም 2) “በጣም ብቁ ሰው” 3) “ባለጠጋና ተፅዕኖ ፈጣሪ ሰው”

ሾመው
“አዛዥ አደረገው”

ሥራ ሁሉ
ሥራ የሚለው ቃል ሰለሞን ለመንግስቱ እንዲሠሩ ያዘዛቸውን ሥራ ሁሉ ይገልፃል። ይህ ዘይቤአዊ ንግግር ነው።

በዮሴፍ ነገድ
ይህ ከኤፍሬምና ከምናሴ ወገን የሆኑና የዮሴፍ ነገድን ይገልፃል።

አኪያ
ይህ የሰው (ወንድ) ሥም ነው

ሴሎናዊው
ሴሎናዊው የሆነ ወገን ህዝብ ነው።

1 Kings 11:31

አለው
አለው የሚለው ቃል አኪያን (አኪያ መናገሩን) ይገልፃል።

መንግስቱን እቀድዳለሁ
እዚህ ጋር እቀድዳለሁ የሚለው ቃል በግድ ለመቀማት ዘይቤ ነው። ይህ ልክ ሰው ልብስን እንደሚቀድ ነው። የ1ነገስት 11፡11 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ “መንግስቱን በግድ (በጉልበት) ቀማው”

ከሰለሞን እጅ
እዚህ ጋር እጅ የአንድን ሰው ሥልጣን፣ቁጥጥርና ጉልበት ዘይቤአዊ ንግግር ነው። ተርጓሚ “የሰለሞን ቁጥጥር”

ሰለሞን .....ይቀርለታል
ይህ ለሰለሞን ነገድ የተነገረ ሲሆን ተርጓሚ “ለሰለሞን ልጅ ይቀርለታል።” ወይም “ለሰለሞን ነገድ ይቀርለታል

1 Kings 11:34

አጠቃላይ መረጃ
አኪያ እግዚአብሔር ለእዮርባአም ያለውን መናገሩን ቀጥሏል።

አልወስድም
አልወስድም የሚለው ቃል እግዚአብሔር መናገሩን ያሳያል

ከእጁ
እዚህ ጋር “እጅ” የአንድ ሰው ስልጣን፣ ቁጥጥርና ጉልበት ያሳያል ተርጓሚ “ከቁጥጥሩ”

እሰጥሃለው
ይህ ቃል ለእዮርባአም መሆኑን ያሳያል

በፊቴ ሁል ጊዜ መብራት ይሆንለት ዘንድ
“መብራት” የሚለው ቃል የአንድ ሰው ተፅዕኖና ምሪት ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “ኪዳኔን በመታዘዙ አንድ ተፅዕኖና ምሪት ሁልጊዜ የሚገዛ ነገድ (Hei)ለዳዊት ቤት ይሆናል”

1 Kings 11:37

አጠቃላይ መረጃ
አኪያ እግዚአብሔር ያለውን ለእዮርባአም መናገሩን ቀጥሏል።

እወስድሃለው
ይህ ቃል እግዚአብሔር ለእዮርባአም መናገሩን ያሳያል።

በፊቴ የቀናውን
“ፊት” የአንድ ሰው አመለካከት ወይም ሃሳብ ዘይቤ ነው። ይህ በተለምዶ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። የ1ነገሰት 11:33 ትርጉምን ተመልከት

ፅኑ ቤት እሠራልሃለሁ
“ቤት እሰራልሃለሁ” የሚለው ሐረግ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሥርወ-መንግስትን የመመስረት ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “ረጅም ዘመን ያለው መንግስትን መመስረት”

1 Kings 11:40

ሺሻቅ
ይህ የሰው(የወንድ) ስም ነው።

1 Kings 11:41

በሰለሞን ታሪክ መፅሐፍ ተፅፎአል
ይህ በሌላ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። ተርጓሚ “በሰለሞን ታሪክ መፅሐፍ ልታገኘው ትችላለህ”

በሰለሞን ታሪክ መፅሐፍ
ይህ መፅሐፍ በአሁኑ ወቅት አይገኝም/የለም

ሰለሞን ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ.....ተቀበረ
x

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 12

1 ሮብዓምም ወደ ሴኬም ሄደ፤ ምክንያቱም እስራኤል ሁሉ እርሱን ለማንገሥ ወደ ሴኬም መጥተው ነበር። 2 ከንጉሡ ሰሎሞን በመሸሸ ወደ ግብጽ ኮብልሎ
በዚያው በግብጽ ይኖር የነበረው የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም ይህን ወሬ በሰማ ጊዜ ተመልሶ መጣ። 3 ስለዚህ የእስራኤል ጉባኤ ሁሉ ወደ እርሱ ልከው ጠሩት፤
ወደ ሮብዓም ቀርበው እንዲህ አሉት፦ 4 አባትህ ሰሎሞን በእኛ ላይ ከባድ የአገዛዝ ቀንበር አክብዶብን ነበር። አሁን አባትህ የጫነብንን ከባድ የሥራ ሸክም
አቃልልን፣ ለአንተም እንገዛልሃለን አሉት። 5 ሮብዓምም ከሦስት ቀን በኋላ ተመልሳችሁ ኑ አላቸው፤ ስለዚህ ሕዝቡ ሄዱ። 6 ከዚህ በኋላ ንጉሥ ሮብዓም የአባቱን
የሰሎሞን ዘመን አማካሪዎች የነበሩትን ሽማግሌዎች በአንድነት ሰብስቦ እንግዲህ ለዚህ ሕዝብ መልስ መስጠት እንድችል ምን ትመክሩኛላችሁ? ሲል
ጠየቃቸው። 7 ሽማግሌዎቹም ዛሬ ለእነዚህ ሰዎች ታዛዥ ሆነህ ብታገለግላቸው ለጥያቄአቸውም ተስማሚ የሆነ መልስ ብተሰጣቸው እነርሱም ዘወትር
በታማኝነት ያገለግሉሃል ሲሉ መለሱለት። 8 ነገር ግን ሮብዓም የሽማግሌዎቹን ምክር ቸል በማለት አብሮ አደጎቹ ወደነበሩት አሁን ደግሞ አማካሪዎቹ ወደሆኑት
ወጣቶች ሄደ። 9 የአገዛዝ ቀንበር እንዳቀልላቸው ለጠየቁኝ ምን መልስ እንደምሰጣቸው ምን ትመክሩኛላችሁ? ሲል ጠየቃቸው። 10 እነርሱም እንዲህ ሲሉ
መለሱለት፤ አንተ የምተሰጣቸው መልስ ይህ ነው፤ የእኔ ታናሽ ጣት ከአባቴ ወገብ ይበልጥ ትወፍራለች! 11 አባቴ በእናንተ ላይ ከባድ የአገዛዝ ቀንበር
ጭኖባችሁ ነበር፣ እኔ ደግሞ የአገዛዝ ቀንበር ይበልጥ እንዲከብድባችሁ አደርጋለሁ፣ አባቴ በአለንጋ ይገርፋችሁ ነበር፤ እኔ ግን በሚናደፍ ጊንጥ እገርፋችኋለሁ!
12 ከሦስት ቀን በኋላ ኢዮርብዓምና ሕዝቡ ሁሉ ንጉሡ በሰጣቸው ቀጠሮ መሠረት ተመልሰው ወደ ሮብዓም መጡ። 13 ንጉሥ ሮብዓምም ሽማግሌዎቹ
የሰጡትን ምክር ትቶ ሕዝቡን በማመናጨቅ መልስ ሰጣቸው። 14 ወጣቶቹ በሰጡት ምክር መሠረት አባቴ በእናንተ ላይ ከባድ የአገዛዝ ቀንበር ጭኖባችሁ
ነበር፤ እኔ ደግሞ የአገዛዝ ቀንበር ይበልጥ እንዲከብድባችሁ አደርጋለሁ፤ አባቴ በአለንጋ ይገርፋችሁ ነበር፤ እኔ ግን በጊንጥ እገርፋችኋለሁ! ሲል መለሰላቸው።
15 ይህም ከሴሎ በመጣው በነቢዩ አኪያ አማካይነት ስለ ናባጥ ልጅ ስለ ኢዮርብዓም እግዚአብሔር የተናገረው ቃል እንዲፈጸም ነው። ነጉሥ ሮብዓምም
የሕዝቡን አሳብ ችላ በማለት ሳይቀበል የቀረበትም ምክንያት እግዚአብሔር ይህን ለውጥ ለማድረግ ስለ ወሰነ ነው። 16 ሕዝቡ ንጉሥ ሮብዓም ጥያቄውን
እንዳልተቀበለው በተገነዘበ ጊዜ ከዳዊት ጋር ምን ድርሻ አለን? የእስራኤል ሕዝብ ሆይ! ወደየቤትህ ሂድ! ዳዊት ሆይ፣ የራስህን ቤት ጠብቅ ብለው መለሱለት።
ስለዚህ የእስራኤል ሕዝብ ወደየቤቱ ሄደ። 17 ሮብዓምም በይሁዳ ግዛት በሚኖሩት ሕዝብ ላይ ብቻ ነገሠ። 18 ከዚህ በኋላ ንጉሥ ሮብዓም የግዳጅ ሥራ ኃላፊ
የነበረውን አዶኒራምን ወደ እስራኤላውያን እንዲሄድ ላከው፤ እነርሱ ግን በድንጋይ ወግረው ገደሉት፤ በዚህ ጊዜ ሮብዓም በፍጥነት ወደ ሠረገላው ገብቶ ወደ
ኢየሩሳሌም በመሄድ አመለጠ። 19 ከዚያን ጊዜም ጀምሮ ሰሜናዊው ክፍል እስራኤል በሚል በዳዊት ሥርወ መንግሥት ላይ ዐመፀ። 20 እስራኤልም ሁሉ
ኢዮርብዓም ከግብጽ ተመልሶ መምጣቱን በመገንዘብ ወደ ጉባዔያቸው ጠርተው በእስራኤል ላይ አነገሡት፤ ለዳዊት ትውልዶች ታማኝ ሆኖ የቀረው የይሁዳ
ነገድ ብቻ ነበር። 21 ሮብዓም ወደ ኢየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ ከይሁዳና ከብንያም ነገዶች ተውጣጥተው የተመለሱ አንድ መቶ ሰማኒያ ምርጥ ወታደሮች ጠርቶ
በአንድነት ሰበሰበ፤ ይህም የእስራኤልን ነገዶች ለመዋጋትና እንደገና መንግሥትን ወደ ሰሎሞን ልጅ ሮብዓም ለመመለስ ነበር። 22 ነገር ግን የእግዚአብሔር
ቃል ወደ እግዚአብሔር ሰው ወደ ሳማያ እንዲህ ሲል መጣ። 23 ለሮብዓምና ለመላው የይሁዳና የብንያም ነገዶች ለቀሩትም ሕዝብ ሁሉ እንዲህ በል፦ 24
ከወንድሞቻችሁ ከእስራኤላውያን ጋር በመዋጋት አደጋ አትጣሉ፤ ሁላችሁም ወደየቤታችሁ ሂዱ፤ ይህ የሆነው በእኔ ፈቃድ ነው ብሎ አዘዘው። እነርሱም
ለእግዚብሔር ቃል በመታዘዝ ወደየቤታቸው ተመልሰው ሄዱ። 25 ኢዮርብዓምም በኮረብታማው በኤፍሬም አገር የምትገኘውን ሴኬምን ከተማ አድርጎ ሠርቶ
ኖረባት። ከዚያም ተነሥቶ የጵንኤልን ከተማ ሠራ። 26 ኢዮርብዓምም አሁን መንግሥቱ ወደ ዳዊት ቤት ይመለሳል ብሎ በልቡ አሰበ። 27 ይህ የእስራኤል
ሕዝብ ወደ ኢየሩሳሌም እየሄደ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ መስዋዕት የሚያቀርብ ከሆነ፣ የሕዝቡ ልብ ወደ ይሁዳ ንጉሥ ወደ ጌታቸው ወደ ሮብዓም
ይመለሳል። ከዚያ እኔን ይገሉኛል፤ ወደ ይሁዳ ንጉሥ ወደ ሮብዓምም ይመለሳሉ። 28 ስለዚህ ሮብዓም በጉዳዩ ከመከረበት በኋላ የሁለት ጥጆች ምስል ከወርቅ
አሠርቶ ለሕዝቡ ከዚህ በፊት እንደምታደርጉት ለመስገድ እስከ ኢየሩሳሌም መሄድ አድካሚ ነው። የእስራኤል ሕዝብ ሆይ፦ ከግብጽ ምድር ያወጣችሁ
አማልክትህ እነሆ እነዚህ ናቸው! አለ። 29 ከዚህ በኋላ ከወርቅ የተሠሩት ሁለት የኮርማ ምስሎች አንዱን በቤቴል ሁለተኛውንም በዳን አቆመ። 30 ስለዚህ ይህ
ድርጊት ኃጢአት ሆነ። ሰዎቹም እስከ ዳን ድረስ በጣዖቱ ፊት ተሰልፈው ሄዱ። 31 ኢዮርብዓምም በኮረብታዎች ላይ የማምለኪያ ስፍራዎችን አዘጋጅቶ የሌዊ
ነገድ ካልሆኑ ቤተ ሰቦች መካከል ማንኛውንም ሰው ካህን አድርጎ ሾመ። 32 ኢዮርብዓም በይሁዳ በሚደረገው በዓል ዓይነት ስምንተኛ ወር በገባ በዐሥራ
አምስተኛው ቀን የባዕድ አምልኮ በዓል እንዲደረግ ወሰነ፤ ከወርቅ ላሠራውም ምስሎች በቤቴል በሚገኘው መሠዊያ ላይ ለጥጃ ምሰሉ መሥዋዕት አቀረበ፤
በዚህም በቤተል ለማምለኪያ ባሠራቸው ስፍራዎች የሚያገለግሉ ካህናትን መደበ። 33 ኢዮርብዓምም በዓል እንዲሆን እርሱ ራሱ በወሰነው ስምንተኛ ወር በገባ
በዐሥራ አምስተኛው ቀን ወደ ቤቴል ሄደ። በዚያ የእስራኤል ሕዝብ በዓል እንዲያከብር መስዋዕት አዘጋጅቶ ዕጣን ለማጠን ወደ መሠዊያው ሄደ።

---

1 Kings 12:1

እስራኤል ሁሉ መጥተው ነበርና
እስራኤል የሚለው ቃል መዋጋት የሚችሉትን የእስራኤል ወንዶችን ሁሉ ይገልፃል። እስራኤል ሁሉ የሚለው ሀረግ ደግሞ ሁሉንም የእስራኤል ሰዎች (ወንዶችን) ይገልፃል። ተርጓሚ “ሁሉም የእስራኤል ሰዎች (ወንዶች) መጥተው ነበርና”

እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ ድርጊቱ መጀመሩን ማሳያ ነው።

እዮርብአም.....ናባጥ
እነዚህ የሰዎች (ወንዶች) ስም ናቸው።

1 Kings 12:3

ጠርተውት ነበር
“ጠርተውት” የሚለው ቃል እዮርብአምን መሆኑን ያሳያል።

የከበደውን ቀንበር
“ከባድ ቀንበር” የከባድ ሥራ ወይም በጣም የሚጠበቅብን ነገር ማሳያ ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “ክፉኛ አንገላቱአቸው” ወይም “በጣም እንድንሠራ አስገደዱን”

1 Kings 12:6

በፊቱ ይቆሙት ከነበሩት ሽማግሌዎች
“በፊቱ መቆም” የሚለው ሐረግ ንጉሡን ማገልገላቸውን ማሳያ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። ተርጓሚ “ያማክሩቱ የነበሩት ሽማግሌዎች” ወይም “ሰለሞንን ይታዘዙት የነበሩት ሽማግሌዎች”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Kings 12:8

አባትህ የጫነብንን ቀንበር አቃልልልን
ቀንበር ማቃለል ሸክም የማንሣትን ማሳያ ዘይቤ ነው። “አባትህ እንደጨከነብን አንተ አትጨክንብን” ወይም “አባትህ በጣም እንዳሠራን እንድንሠራ አታስገድደን”

1 Kings 12:10

ታናሺቱ ጣቴ ከአባቴ ወገብ ትወፍራለች
ይህ ዘይቤ የሚያሳየው ሮብአም ከአባቱ በላይ ጨካኝና አስቸጋሪ መሆኑን ያሳያል ተርጓሚ “ሸክማችሁን ለማክበድ የማደርገው ነገር አባቴ ከጫነባችሁ እጅግ በጣም የከበደ ነው።”

አባቴ በአለንጋ ገርፎአችኋል እኔ ግን በጊንጥ እገርፋችኋለሁ
ይህ ዘይቤ የሚያሳየው ሮብአም ያቀደው ቅጣት ከአባቱ ቅጣት የከፋ መሆኑን ነው። ተርጓሚ “አባቴ ሊያስገድዳችሁ አለንጋ ተጠቀመ እኔ ግን የከፋ ቅጣትን እጠቀማለሁ።”

በጊንጥ እገርፋችኋለሁ
ጊንጥ የሚለው ቃል ምናልባት 1) ጫፍ ላይ ሹል ያለው መግረፍያ (አለንጋ) ወይም 2) ሸረሪት መሳይ የሚናደፉ መርዛማ ፍጡር ሊሆን ይችላል።

1 Kings 12:12

እኔ ግን በቀንበራችሁ ላይ እጨምራለሁ
ከባድ ቀንበር፤የከባድ ስራ ወይም በጣም የሚጠበቅብን ነገር ማሳያ ዘይቤ ነው ተርጓሚ “ክፉኛ አንገላቱአችሁ” ወይም “በጣም እንድትሠሩ አስገደዱአችሁ” የ1ነገስት 12፡4 ትርጉምን ተመልከት።

አባቴ በአለንጋ ገርፎአችኋል እኔ ግን በጊንጥ እገርፋችኋለሁ
ይህ ዘይቤ የሚያሳየው ሮብአም ያቀደው ቅጣት ከአባቱ ቅጣት የከፋ መሆኑን ነው። ተርጓሚ “አባቴ ሊያስገድዳችሁ አለንጋ ተጠቀመ እኔ ግን የከፋ ቅጣትን እጠቀማለሁ።”

1 Kings 12:15

ከእግዚአብሔር ዘንድ ተመድቦ ነበርና
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ሲሆን በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ነገሮች እንዲህ እንዲሆኑ እግዚአብሔር አደረገ”

በአኪያ አድርጎ.....ለአዮርብዓም የተናገረውን
የተናገረውን የሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ለሌላ ሰው የሚነገር መልዕክትን መስጠት ይገልፃል።

አኪያ.....እዮርብዓም.....ናባጥ
እነዚህ የሰዎች (ወንዶች) ስሞች ናቸው።

ሴሎናዊ
ይህ ከሴሎን ከተማ የሆኑ ሰዎችን ይገልፃል።

1 Kings 12:16

እስራኤልም ሁሉ
እዚህ ጋር “እስራኤል” የሚለው ቃል መዋጋት የሚችሉትን የእስራኤል ወንዶችን ሁሉ ይገልፃል። እስራኤል ሁሉ የሚለው ሐረግ ገግሞ ጥቅል ሲሆን ሁሉንም የእስራኤል ወንዶች ማለት ነው። ተርጓሚ “የእስራኤል ወንዶች ሁሉ”

በዳዊት ዘንድ ምን ክፍል አለን?
“ክፍል” የሚለው ቃል ዘይቤ ሲሆን ትርጉሙም ድርሻ፣ ጣልቃ ገብነት ወይም ፍላጎት ማለት ነው። ይህ ጥያቄ በቀላል አረፍተ-ነገር ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ “በዳዊት ቤት ወስጥ ምንም ድርሻ አይኖረንም”

በእሴይም ልጅ ዘንድ ርስት የለንም
“የእሴይ ልጅ” ለእሴይ ልጅ ለዳዊት ዘይቤ ነው። ርስት ደግሞ ከዳዊት ስኬት ለእነዚህ ሰዎች የቀረው ድርሻ ነው። ተርጓሚ “ከእሴይ ነገድ ጋር ምንም ነገር የለንም”

እስራኤል ሆይ ወደ ድንኳኖቻችሁ ተመለሱ
እዚህ ጋር ድንኳን የአንድን ሰው የመኖሪያ ስፍራ መግለጫ ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “እስራኤል ሆይ ወደ ቤቶቻችሁ ሂዱ (ተመለሱ)”

ዳዊት ሆይ አሁን ቤትህን ተመልከት
እዚህ ጋር ቤት ለዳዊት የዘር ሀረግ ጉልበትና ክብር ማሳያ ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “የዳዊት ነገድ ሆይ አሁን መንግስትህን ተንከባከብ (ጠብቅ)”

1 Kings 12:18

አዶኒራም
ይህ የሰው (ወንድ) ስም ነው።

እስራኤል ሁሉ
እዚህ ጋር “እስራኤል” የሚለው ቃል ለእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ዘይቤ ነው። እስራኤል ሁሉ የሚለው ሀረግ ደግሞ ጥቅል ሲሆን ሁሉም የእስራኤል ሕዝብ ማለት ነው። ተርጓሚ “በዚያ የነበሩ የእስራኤል ህዝብ ሁሉ”

ከዳዊት ቤት
እዚህ ጋር ቤት የሚለው ቃል ቤተሰብ ወይም የዘር ሐረግን ይወክላል። ተርጓሚ “ነገሥታት ከዳዊት ዘር ሐረግ ናቸው”

1 Kings 12:20

እስራኤልም ሁሉ .....በሰሙ ጊዜ
“እስራኤልም ሁሉ” የሚለው ሐረግ ሁሉንም የእስራኤል ሊወክል ለሚችለው ብቁ ማህበረሰብ ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “ሁሉም የእስራኤል መሪዎች በሰሙ ጊዜ”

በእስራኤል ሁሉ ላይ አነገሡት
“እስራኤል” የሚለው ቃል በግልፅ በሮብዓም ላይ ያመፁትን የሰሜኑ አስር ነገዶች ይገልፃል። ተርጓሚ “በአስሩ የእስራኤል ነገድ ላይ አነገሡት”

የዳዊትን ቤት
“የዳዊት የዘር ሐረግ”

1 Kings 12:21

ከይሁዳ ቤት ሁሉና ከብንያም ነገድ
እዚህ ጋር “ቤት” ነገድ ወይም የዘር ሀረግን የሚገልፅ ዘይቤ ነው። ነገድ የሚለው ቃል ደግሞ በተለየ መልኩ ከዚያ ነገድ ስለሆኑት ወታደሮች ነው። ተርጓሚ “ከይሁዳና ከብንያም ነገድ የሆኑት ወታደሮች ሁሉ”

180,000 ሰልፈኞች
አንድ መቶ ሰማንያ ሺህ ሰልፈኞች

የእስራኤል ቤት
እዚህ ጋር ቤት ከአሥሩ የእስራኤል ነገዶች የተመሠረተ መንግስትን ይወክላል። ተርጓሚ “የእስራኤል መንግስት” ወይም “የአስሩ የእስራኤል ነገድ ህዝቦች”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Kings 12:22

የእግዚአብሔር ቃል .....እንዲህ ይላል።
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ሲሆን እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለህዝቡ የተናገረውን ለማስተዋወቅ ያገለግላል። ተርጓሚ “እግዚአብሔር ይህን መልዕክት ተናገረ …እንዲህም አለ” ወይም “እግዚአብሔር እነዚህ ቃላት ተናገረ ..እንዲህም አለ”

ሳመያ
ይህ የሰው(ወንድ) ስም ነው።

የእግዚአብሔር ሰው
የእግዚአብሔር ሰው የሚለው ሐረግ ለእግዚአብሔር ነብይ የአክብሮት መጥሪያ ስም ነው። ተርጓሚ “የእግዚአብሔር የሆነ ሰው። ወይም “የእግዚአብሔር ነብይ”

ለይሁዳና ለብንያም ቤት ሁሉ
እነዚህ “ቤት” ነገድን ወይም የዘር ሐረግን የመግለጫ ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “ከይሁዳና ከብንያም ነገድ የሆኑ ህዝቦች ሁሉ

የእስራኤልንም ልጆች ወንድሞቻችሁን
“ወንድሞቻችሁን” ና የእስራኤል ልጆች የሚሉት ቃላት የተጣበቁና የሰሜኑ አስር ነገዶች የሚገልፅ ሲሆን በእነርሱ፤ በይሁዳና በብንያም መካከል ያለውን ቤተሰባዊ ግንኙነት አፅንኦት ለመስጠት ነው።

ይህ ነገር ከእኔ ዘንድ ነውና
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ምክንያቱም እነዚህ ነገሮች እንዲሆኑ አደረኩ”

1 Kings 12:25

በልቡ.....አለ
እዚህ ጋር ልብ ለሰው የውስጥ ህሊናውን፤ሃሳቡን፤መነሣሣት ወይም ስሜት ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “ለራሱ….አሰበ”

ወደ ዳዊት ቤት
እዚህ ጋር “ቤት” ነገድን ወይም የዘር ሐረግን መግለጫ ዘይቤ ነው።ተርጓሚ “ከዳዊት ዘር ሀረግ የሆኑት ነገስታት”

ይህ ሕዝብ .....ቢወጣ
“ሕዝብ” የሚለው ቃል የሰሜኑን አስር የእስራኤል ነገዶች ይገልፃል።

የዚህ ህዝብ ልብ
እዚህ ጋር ልብ የሕዝብ ማዘንበል ወይም ፍቅርን መግለጫ ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “የዚህ ህዝብ ማዘንበል” ተርጓሚ የዚህ ልብ ማዘንበል

ወደ ጌታቸው ወደ ይሁዳ ንጉሥ ወደ ሮብዓም ይመለሳል።
እነዚህ ሐረጎች በመሠረቱ አንድ አይነት ሲሆኑ አዮርባዓም ሕዝቡ ወደ ሮብአም ጥያቄ ይመለሣል ብሎ መፍራቱን አፅንኦት ለመስጠት ነው።

1 Kings 12:28

ያወጡህን
ይህ ቃል ለሕዝቡ የዘር ሐረግ የሚያመለክት ዘይቤ ነው ተርጓሚ “የዘር ሐረግ ህን ያወጡትን”

1 Kings 12:31

በኮረብታቹም ላይ መስገጃዎችን ሠራ
ይህንን ሥራ በእዮርባአም ትዕዛዝ የሠሩት ሠራተኞች በራሱ በአዮርባአም ስም ተወክላዋል። ተርጓሚ “የአዮርባዓም ሠራተኞች በኮረብቶቹም ላይ መስገጃዎችን ሠሩ”

በኮረብቶቹም ላይ መስገጃዎችን
ይህ የመስገጃ (የማምለኪያ) ቤቶችን ያመለክታል። የዚህ አረፍተ-ነገር ሙሉ ትርጉሙ ግልፅ ሊደረግ ይችላል። ተርጓሚ “በኮረብቶቹም ላይ የማምለኪያ ቤቶችን”

ክህናትን አደረገ
ወንዶችን ካህናት አድርጎ ሾማቸው

በስምንተኛው ወር በአስራ አምስተኛውም ቀን
ይህ በእብራውያን ቀን አቆጣጠር ስምንተኛው ወር ነው። ለሥራ አምስተኛው ቀን በምዕራባዊያን ቀን አቆጣጠር የታህሳስ ወር መጀመሪያ አከባቢ ነው። ተርጓሚ “የስምንተኛው ወር አሥራ አምስተኛው ቀን”

መሠዊያው ላይ ሠዋ
“ላይ” የሚለው ቃል መሠዊያዎች በከፍታ ቦታ ላይ ስለሚገኙ ወደ ተቀደሰ ስፍራ የመሄድ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። ተርጓሚ “በመሠዊያ ላይ መሥዋዕት አቀረበ (ሠዋ)”

በልቡ ባሰበው ቀን
“እርሱ ባሰበው ወር ውስጥ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 13

1 የእግዚአብሔርን ቃል ይዞ አንድ ነብይ ከይሁዳ ወደ ቤቴል ደረሰ፤ ኢዮርብዓም ዕጣን ለማጠን በመሠዊያው አጠገብ ቆሞ ነበር። 2 ነቢዩም እንዲህ ሲል በጩኸት የትንቢት ቃል ተናገረበት፦ «መሠዊያ! መሠዊያ ሆይ! እግዚአብሔር ስለ አንተ የሚለው ቃል ይህ ነው፦ ‹እነሆ ከዳዊት ቤተ ሰብ ኢዮአስ ተብሎ የሚጠራ ልጅ ይወለዳል፤ እርሱም በኮረብታ ላይ ለተሠራው ለአህዛብ መሠዊያ አገልጋዮች ሆነው መሥዋዕት የሚያቀርቡትን ካህናት በአንተው ላይ ያርዳቸዋል፤ የሰዎችንም አጥንት በአንተ ላይ ያቃጥላል።› 3 በዚያው ቀን ነቢዩ ምልክት ሰጠ፤ ይህ መሠዊያ ተሰባብሮ ይወድቃል፤ በእርሱም ላይ ያለው አመድ ይበተናል፤ ይህንንም የትንቢት ቃል በእኔ አማካኝነት የተናገረው ራሱ እግዚአብሔር ለመሆኑ ምልክት ይሆናል›» አለው። 4 ንጉሥ ኢዮርብዓምም ይህን በሰማ ጊዜ እጁን አንሥቶ ወደ ነቢዩ በማመልከት ያዙት የሚል ትእዛዝ ሰጠ፤ የንጉሡም ክንድ ወዲውኑ ድርቅ ብሎ ቀረ፤ የዘረጋውን እጁን መመለስ አልቻለም። 5 የእግዚአብሔርም ነቢይ በእግዚአብሔር ስም በተናገረው የትንቢት ቃል መሠረት የተሰጠው ምልክት ተፈጸመ፤ መሠዊያው ወዲያውኑ ተሰባብሮ ወደቀ፤ አመዱም መሬት ላይ ፈሰሰ። 6 ንጉሡ ኢዮርብዓምም፣ እባክህ እጄ እንዲመለስልኝ ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ጸልይልኝ ሲል የእግዚአብሔርን ነቢይ ለመነው። የእግዚአብሔርም ነቢይ ወደ እግዚአብሔር ጸልዮለት የንጉሡ እጅ ዳነች። እንደ ቀድሞም ሆነች። 7 ከዚህ በኋላ ንጉሡ ነቢዩን ና ከእኔ ጋር አብረህ ወደ ቤቴ ግባ፤ እህልም ቅመስ፤ ስጦታ እሰጥሃለሁ አለው። 8 የእግዚአብሔር ነቢይ ግን የሀብትህን እኩሌታ ብትሰጠኝ እንኳ ወደ ቤትህ ከአንተ ጋር አልሄድም፤ እህል ውሃም እዚህ ቦታ አልቀምስም አለ። 9 ምንም ዓይነት እህል ውሃ እንዳልቀምስና ወደ ቤቴ ስመለስም በመጣሁበት መንገድ እንኳ እንልሄድ እግዚአብሔር አዞኛል ሲል መለሰለት። 10 ስለዚህ ወደ ቤቴል የመጣበትን መንገድ በመተው በሌላ መንገድ ተመልሶ ሄደ። 11 በዚያን ጊዜ በቤቴል የሚኖር አንድ ሽማግሌ ነቢይ ነበር። ወንዶች ልጆቹ ወደ እርሱ ቀርበው፣ ከይሁዳ የመጣው ነቢይ በቤቴል ስላደረገውና በንጉሥ ኢዮርብዓምም ላይ ስለ ተናገረው ቃል ሁሉ አወሩለት። 12 አባታቸውም ታዲያ ያ የእግዚአብሔር ነቢይ ከዚያ ተነሥቶ በየትኛው መንገድ ሄደ? ሲል ጠየቃቸው፤ እነርሱም የሄደበትን መንገድ በማመልከት አሳዩት፤ 13 ከዚህም በኋላ እርሱ አህያዬን ጫኑልኝ አላቸው፤ ልጆቹም አህያውን ጭነውለት፣ ሽማግሌው ነቢይ በአህያው ላይ ተቀምጦ፣ 14 ከይሁዳ የመጣው የእግዚአብሔር ነቢይ የሄደበትን መንገድ አቅጣጫ ይዞ ተከተለው፤ በአንድ የወርካ ዛፍ ሥር ተቀምጦም አገኘው። ሽማግሌውም ከይሁዳ የመጣኸው የእግዚአብሔር ነቢይ አንተ ነህን? ሲል ጠየቀው። እርሱም አዎን እኔ ነኝ ሲል መለሰለት። 15 ሽማግሌውም ወደ ቤቴ ገብተህ ከእኔ ጋር እህል ብላ አለው። 16 ከይሁዳ የመጣው የእግዚአብሔር ነቢይ ግን ከአንተ ጋር አብሬ ወደ ቤትህ መሄድም ሆነ በዚህ ቦታ ከአንተ ጋር ምንም ዓይነት እህል ውሃ መቅመስ አልችልም ሲል መለሰለት። 17 በዚህ ቦታ ምንም ዓይነት እህል ውሃ እንዳልቀምስ፣ በመጣሁበት መንገድ እንኳ ተመልሼ እንዳልሄድ እግዚአብሔር አዞኛል አለው። 18 ከዚህ በኋላ ከቤቴል የመጣው ሽማግሌው ነቢይ፣ እኔም እንዳንተው ነቢይ ነኝ፤ ከእኔ ጋር ወደ ቤቴ ወስጄ እንዳስተናግድህ ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክ ነግሮኛል አለው። ነገር ግን ሽማግሌው ነቢይ የተናገረው በውሸት ነበር። 19 ስለዚህ ከይሁዳ የመጣው የእግዚአብሔር ነቢይ ከሽማግሌው ነቢይ ጋር አብሮት ወደ ቤቱ ሄደ፤ ከእርሱም ጋር ተመገበ። 20 በገበታም ቀርበው ሳሉ የእግዚአብሔር ቃል ወደ ሽማግሌው ነቢይ መጣ። 21 ከይሁዳ ለመጣው የእግዚአብሔር ሰው እንዲህ አለው፤ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ አምላክህ እግዚአብሔር ያዘዘህን ትእዛዝ ባለመታዘዝ የእግዚአብሔርን ቃል አልታዘዝክም። 22 ይህን በማድረግ ፈንታ እኔ በዚያ ምንም ዓይነት እህል ውሃ እንዳትቀምስ ወዳዘዝኩህ ወዳዚያ ቦታ ተመልሰህ በላህ፤ ይህንንም በማድረግህ ምክንያት ትገደላለህ፤ ሬሳህም በቤተ ሰብህ መቃብር አይቀበርም። 23 ከተመገቡም በኋላ ሽማግሌው ነቢይ ከይሁዳ መልሶ ላመጣው የእግዚአብሔር ነቢይ አህያውን ጫነለት፤ 24 እርሱም በአህያው ላይ ተቀምጦ ሄደ፤ በመንገድም አንበሳ አገኘውና ገደለው፤ ሬሳውም በመንገድ ላይ ተጋደመ፤ አህያውና አንበሳውም በሬሳው አጠገብ ቆመው ነበር። 25 ሰዎች በዚያ በኩል ሲያልፉ አጠገቡ ከቆመው አንበሳ ጋር ሬሳው በመንገድ ላይ ተጋድሞ አዩ፣ ሽማግሌው ነቢይ ወደሚኖርበት ወደ ቤቴል ከተማ መጥተውም አወሩለት። 26 ሽማግሌው ነቢይ ይህን በሰማ ጊዜ፣ ያ ሰው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ያልጠበቀው ነቢይ ነው፤ ስለዚህም እግዚአብሔር እንደ ተናገረው አንበሳ ቦጫጭቆ እንዲገለው አሳልፎ ሰጥቶታል ማለት ነው አለ። 27 ከዚህም በኋላ ልጆቹን አህያዬን ጫኑልኝ አላቸው፤ እነርሱም ጫኑለት። 28 በአህያው ላይ ተቀምጦ ሄደ፤ በነቢዩ ሬሳ አጠገብ አህያውና አንበሳው እስካሁን እንደ ቆሙ በመንገድ ላይ ተጋድሞ አገኘው። አንበሳውም የነቢዩን ሬሳ አልበላም፤ በአህያውም ላይ አደጋ አላደረሰበትም ነበር። 29 ሽማግሌው ነቢይ ሬሳውን አንሥቶ በአህያው ላይ ጫነው፤ እንዲለቀስለትና እንዲቀበር ወደ ቤቴል መልሶ ወሰደው። 30 ሽማግሌውም ነቢይ በገዛ ራሱ ቤተ ሰብ መቃብር ቀበረው፤ እነርሱም ወንድሜ ሆይ ወንድሜ ሆይ እያሉ አለቀሱለት። 31 ከቀብሩም ሥነ ሥርዓት በኋላ ሽማግሌው ነቢይ ለልጆቹ እንዲህ አላቸው፤ እኔ ስሞት በዚህ መቃብር ቅበሩኝ፤ ሬሳዬንም ከእርሱ ሬሳ አጠገብ አጋድሙት። 32 በቤቴል በሚገኘው መሠዊያ ላይና በሰማርያ ታናናሽ ከተሞች በየኮረብታው ባሉት የማምለኪያ ስፍራዎች ላይ ከእግዚአብሔር በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት ይህ የእግዚአብሔር ነቢይ የተናገረው የትንቢት ቃል በእርግጥ ይፈጸማል። 33 ይህም ሁሉ ሆኖ የእስራኤል ንጉሥ ኢዮርብዓም ከሚያደርገው ክፉ ነገር ሁሉ አልተመለሰም፤ ይልቁንም እርሱ በሠራቸው መሠዊያዎች የሚያገለግለውን ማንኛውንም ሰው ካህን አድርጎ ይሾመው ነበር። 34 ይህም ኃጢአቱ ለቤተ ሰቡ መጥፋትና ከምድር ገጽ ለመደምሰሱ ምክንያት ሆነ።

---

1 Kings 13:1

እነሆም አንድ የእግዚአብሔር ሰው በእግዚአብሔር ቃል ከይሁዳ ቤቴል መጣ።
መረጃው የሚያሳየው እግዚአብሔር የእግዚአብሔርን ሰው ወደ ቤቴል መላኩን ነው። ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “እግዚአብሔር የእግዚአብሔርን ሰው ከይሁዳ ወደ ቤቴል ላከ”

የእግዚአብሔር ሰው
ይህ ለነብይ ሌላ የመጠሪያ ስም ነው። ተርጓሚ “ነብይ”

ከይሁዳ .....መጣ
“ከይሁዳ.....መጣ”

የእግዚአብሔር ቃል
“የእግዚአብሔር መልዕክት” ወይም “መልዕክተ እግዚአብሔር”

በመሠዊያውም ላይ.....ጮኸ
እዚህ ጋር ጮኸ የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ሰው መሆኑን ያመለክታል።

በመሠዊያውም ላይ .....ጮኸ
ይህ ማለት እርሱ (ነብዩ) ከፍ ባለና ወቀሳ በተሞላበት ድምፅ ትንቢት ተናገረ። ማለት ነው። ተርጓሚ “ከፍ ባለ ድምፅ በመሠዊያ ላይ ትንቢት ተናገረ።”

መሠዊያ ሆይ መሠዊያ ሆይ
ነብዩ መሠዊያው ሰው የሆነ ያክል የሚሠማው ይመስል ይናገር ነበር ይህንንም አፅንኦት ለመስጠት ሁለት ጊዜ ተናገረ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ስሙ አዮስያስ የሚባል ልጅ ለዳዊት ቤት ይወለዳል
x

1 Kings 13:4

በእርሱም ላይ የዘረጋት እጅ ደረቀች
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “እግዚአብሔር የነካው ሰው እጅ ደረቀች”

ደረቀች
“ጠወለገች” ወይም “ሰለለች”

መሠዊያው ተሰነጠቀ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “እግዚአብሔር መሠዊያውን ሰነጠቀ”

የእግዚአብሔር ሰው በእግዚአብሔር ቃል እንደ ሰጠው ምልክት
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “የእግዚአብሔር ሰው እንዳለው እንደ ምልክታም በእግዚአብሔር ቃል።”

የእግዚአብሔር ቃል
“የእግዚአብሔር መልዕክት” ወይም “መልዕክተ-እግዚአብሔር”

1 Kings 13:6

የአምላክህን የእግዚአብሔርን ፊት ለምን
ተርጓሚ “የአምላክህን የእግዚአብሔርን ፊት ለምንልኝ”

እጄም ወደ እኔ ትመለስ ዘንድ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “እግዚአብሔር እጄን ይመልስ ዘንድ”

የንጉሡም እጅ ወደ እርሱ ተመለሰች እንደቀድሞም ሆነች
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። “እግዚአብሔር የንጉሡን እጅ መለሠ እንደ ቀድሞም ሆነች”

ወደ ቤት ና እንጀራም ብላ
ተርጓሚ “ከእኔ ጋር ወደ ቤት ና ምግብም ብላ”

1 Kings 13:8

የቤትህን እኩሌታ
“የቤትህን ግማሽ”

እንጀራ አትብላ፤ውኃም አትጠጣ በመጣህበትም መንገድ አትመለስ
“እንጀራም አትብላ፤ ውኃም አትጠጣ ወይም በመጣህበት መንገድ እንዳትመለስ”

በሌላ መንገድ ሄደ
“በሌላ መንገድ ሆደ”

1 Kings 13:11

ልጆቹም .....የሄደበትን መንገድ አመለከቱት
ይህ መረጃ የሚያሳየው የእግዚአብሔር ሰው በየት በኩል እንደሄደ ልጆቹ ለአባታቸው ማሳየታቸውን ነው።

ጫኑልኝ
ይህ ማለት ሰው እንዲቀመጥበት (እንዲጋልብ) ኮርቻን በእንስሳ ጀርባ ማስቀመጥን ይገልፃል።

1 Kings 13:14

ሸማግሌ ነብይ
ይህ በቤቴል ይኖር የነበረውን ነብይ ይገልፃል።

አለው
ሸማግሌው ነብይ ለእግዚአብሔር ሰው አለው።

አለ
የእግዚአብሔር ሰው መልስ ሰጠው የሚለውን ይገልፃል

ከእኔ ጋር ወደ ቤቴ ና
ወደ ቤትህ ውስጥ ገባ

እዚህም ስፍራ
“በቤቴል”

በእግዚአብሔር ቃል ተብሎልኛልና
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “እግዚአብሔር በቃሉ አዘዘኝ”

የእግዚአብሔር ቃል
x

1 Kings 13:18

መለአክም.....በእግዚአብሔር ቃል ተናገረኝ
“መልአክ፤ ከእግዚአብሔር ዘንድ መልዕክት አስተላለፈልኝ”

በእግዚአብሔር ቃል
“የእግዚአብሔር መልዕክት” ወይም “መልዕክተ-እግዚአብሔር”

1 Kings 13:20

በማእድም ተቀመጠው ሳሉ
ይህ መረጃ እስካሁን ምግብ በመመገብ ላይ መሆናቸውን ያመለክታል። ተርጓሚ “በመዕድ ሆነው በመመገብና በመጠጣት ላይ እያሉ”

የእግዚአብሔርም ቃል ወደ መለሰው ነብይ መጣ.....ከይሁዳ ወደ መጣው ወደ እግዚአብሔር ሰው እግዚአብሔር እንዲህ ይላል።
የእግዚአብሔር ቃል.....መጣ የሚለው ፈሊጣዊ ንግግር የተለየ መልዕክት ከእግዚአብሔር እንዳለ ለማስተዋወቅ ነው። የነገስት 6:11 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ “እግዚአብሔር ከይሁዳ ለመጣው ለነብዩ መልዕክት ሰጠው እግዚአብሔር እንዲህ ይላል” ወይም “እግዚአብሔር ከይሁዳ ለመጣው ነብይ መልዕክት ተናገረ። እግዚአብሔር”

የእግዚአብሔር ቃል .....መጣ
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር እግዚአብሔር የተለየ መልዕክት እንደለው ለማስተዋወቅ ነው። ተርጓሚ “እግዚአብሔር መልዕክት ሰጠ” ወይም “እግዚአብሔር ተናገረ”

መለሰው
ይህ ቃል ስለ እግዚአብሔር ሰው መሆኑን ይገልፃል።

ጮኸ
ይህ ድምፁን ከፍ አድርጎ ለእግዚአብሔር ሰው መናገሩን ይገልፃል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Kings 13:23

አህያውን ጫነለት
ይህ ማለት የእግዚአብሔር ሰው እንዲቀመጥበት ኮርቻ በአህያ ጀርባ ላይ አስቀመጠለት የ1ነገስት 13:13 ትርጉምን ተመልከት

ሬሳው በመንገድ ወድቆ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። “ሬሳውን በመንድ ተወ (ጣለ)”

ሬሳውን
የሞተው ሰውነቱን

መጥተውም .....አወሩ
ይህ የሚመለክተው በመንገድ ያዩትን መሆኑን ነው። ተርጓሚ “መጥተው ያዩትን አወሩ”

1 Kings 13:26

ሬሳው
የሞተ የእግዚአብሔር ሰው ሰውነት

በመንገድ ወድቆ
“በመንገድ ተንጋሎ”

1 Kings 13:29

አነሣ
ከፍ ማድረግ

ሬሳ
የሞተ ሰውነት

አለቀሱለት
ይህ ቃል ስለ ነብዩና ልጆቹ መሆኑን ያመለክታል።

ዋይ ወንድሜ ሆይ
እዚህ ጋር “ዋይ” የመራራ ሀዘን መግለጫ ቃል ነው።

1 Kings 13:31

ቀበረውም
ይህ ቃል ቀባሪው ስማባሌው ነብይ መሆኑን የተቀበረው ደግሞ የእግዚአብሔር ሰው መሆኑን ያሳያል።

አጥንቶቼንም በአጥንቶቹ አጠገብ አኑሩ
እዚህ ጋር “አጥንቶቼ” የሚለው ቃል ሙሉ ሰውነቱን ይወክላል። ተርጓሚ “ሬሳዬን ከእርሱ አጥንት አጠገብ አኑሩ”

ለኮረብታዎቹ መስገጃ
ይህ መረጃ መስገጃዎቹ የማምለኪያ ቦታ መሆናቸውን ያሳያል። ተርጓሚ “በኮረብታዎቹ ላይ የማምለኪያ ሥፍራ”

1 Kings 13:33

ይህ ነገር ለኢዮርብዓም ቤት ኃጢአት ሆነ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ይህ ነገር በማድረጉ የኢዮርብዓም ቤት ኃጢአትን አደረገ”

ይህ ነገር
ይህ ሐረግ ኢዮርብዓም ቤተ-መቅደስ ሰርቶ ካህናትን ማስቀመጡን ያሳያል።

እስኪፈርስም ከምድርም እስኪጠፋ ድረስ .....ለኢዮርብዓም ቤት
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር የኢዮርብዓምን ቤት አፈረሰም አጠፋም”

እስኪፈርስም.....እስኪጠፋም
ይህ ከላይ ካለው ጋር ተቀራራቢ ትርጉም አለው። ተርጓሚ “ፈፅሞ መፍረስ (መጥፋት)”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 14

1 በዚያን ጊዜ የንጉሥ ኢዮርብዓም ወንድ ልጅ አቢያ በጠና ታሞ ነበር። **2** ስለዚህ ኢዮርብዓም ሚስቱን እንዲህ አላት፦ የእኔ ሚስት መሆንሽን ማንም እንዳያውቅ ልብስሽን ለውጠሽ ሌላ ሴት በመምሰል እኔ የእስራኤል ንጉሥ እንደምሆን የትንቢት ቃል የተናገረው ነቢይ አኪያ ወደሚኖርባት ወደ ሴሎ ሂጂ። **3** ዐሥር እንጀራ፣ ጥቂት ሙልሙል ዳቦና አንድ ገንቦ ማር ውሰጂለት፤ ስለ ልጁ ሁኔታ እርሱ ይነግርሻል። **4** ስለዚህ የኢዮርብዓም ሚስት ይህን ሁሉ አዘጋጅታ በሴሎ ወደሚገኘው ወደ አኪያ ቤት ሄደች። ነቢዩ አኪያም በዕድሜው ከመሸምገሉ የተነሣ ዓይኖቹ ፈዘው ስለነበር ለማየት አልቻለም። **5** እግዘዚአብሔር ለአኪያ እንዲህ አለው፦ የኢዮርብዓም ሚስት ስለታመመው ልጅዋ ልትጠይቅህ እየመጣች ነው። የኢዮርብዓም ሚስት እዚያ በደረሰች ጊዜ ሌላ ሴት ለመምሰል ስለምትሞክር ይህንኑ ተናገራት። **6** ነገር ግን ነቢዩ አኪያ ወደ በሩ ስትቀርብ የኮቴን ድምፅ ሰምቶ እንዲህ አላት፤ ግቢ፣ የኢዮርብዓም ሚስት መሆንሽን አውቃለሁ፤ ሌላ ሴት ለመምሰል ስለምን ሞከርሽ? ለአንቺ እነግርሽ ዘንድ የታዘዝኩት አሳዛኝ ዜና አለ። **7** ወደ ኢዮርብዓም ሂጂ፤ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር የሚለውን ንገሪው፤ ቃሉም ይህ ነው፤ ‹ከሕዝብ መካከል መርጬ የሕዝቤ የእስራኤል መሪ አደረግሁህ። **8** መንግሥትንም ከዳዊት ትውልድ ወስጄ ለአንተ ሰጠሁህ፤ ነገር ግን አንተ ታማኝ ሆኖ ትእዛዜን እንደጠበቀውና እኔ ደስ የምሰኝበትን እንዳደረገ እንደ አገልጋዬ እንደ ዳዊት ሆነህ አልተገኘህም። **9** ይልቁንም ከአንተ በፊት መሪዎች ከነበሩ ሰዎች የከፋ ኃጢአት ሠራህ፤ እኔንም ትተህ ጣዖቶችንና ከብረት የተሠሩ ምስሎችን ለማምለክ በመነሣትህ ቁጣዬን አነሣሥተሃል። **10** በዚህ ምክንያት እነሆ፣ በኢዮርብዓም ቤት ላይ ክፉ ነገርን አመጣለሁ፤ ከቤቱም ነፃም ሆነ ባርያ ወንድ ልጅን ሁሉ ከእስራኤል አጠፋለሁ፤ ፋንድያን አቃጥለው እንደሚጨርሱት የኢዮርብዓምን ቤት አወድማለሁ። **11** በከተማ የሚሞተውን ማንኛውንም የቤተ ሰብህን አባል ውሾች ይበሉታል፤ በሜዳ ላይ የሚሞቱንም የሰማይ አሞራ ይበላቸዋል፤ ይህን የተናገርኩት እኔ እግዚአብሔር ነኝ።” **12** አኪያም የሚናገረውን የትንቢት ቃል በመቀጠል ለኢዮርብዓም ሚስት እንዲህ አላት፣ እንግዲህ አሁን ወደ ቤትሽ ተመልሰሽ ሂጂ፤ ወደ ከተማም እግሮችሽ እንደረገጡ ወዲያውኑ ልጁ ይሞታል። **13** እስራኤላውያንም ሁሉ አዝነውና አልቅሰው ይቀብሩታል። የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር የተደሰተበት ልጅ እርሱ ብቻ ስለሆነ ከኢዮርብዓም ቤተ ሰብ ሥርዓተ ቀብር በሚገባ የሚፈፀምለት እርሱ ብቻ ይሆናል። **14** እግዚአብሔርም በዚያን ቀን የኢዮርብዓምን ቤት የሚያጠፋ ንጉሥ ያስነሣል። ይኸውም አሁን ነው። **15** እግዚአብሔር እስራኤልን ይቀጣል፤ እርሱም በውሃ ውስጥ እንደሚወዛወዝ ሸንበቆ ይወዛወዛል። አሼራ ተብላ የምትጠራውን ሴት አምላክ ጣዖት በመሥራት እግዚአብሔርን ስላስቆጡት፣ የእስራኤልን ሕዝብ ቀድሞ ለአባቶቻቸው ከሰጣቸው መልካም ምድር ይነቅላል፤ ከኤፍራጥስ ወንዝ ማዶ እንዲበታተኑም ያደርጋል። **16** ኢዮርብዓም ኃጢአት ከመሥራቱ የተነሣና የእስራኤልንም ሕዝብ ወደ ኃጢአት ስለመራ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ይተዋል።» **17** ስለዚህ የኢዮርብዓም ሚስት ተነሥታ ወደ ቲርሳ ተመልሳ ሄደች። ወደ ቤትዋ ደጃፍ አንደ ደረሰች ወዲያውኑ ልጁ ሞተ። **18** እግዚአብሔር በአገልጋዩ በነቢዩ አኪያ በኩል በነገረው መሠረት እስራኤላውያን በሐዘን አልቅሰው ቀበሩት። **19** ንጉሥ ኢዮርብዓም ያደረጋቸው ሌሎች ነገሮች ሁሉ፣ የተዋጋቸው ጦርነቶችና አገዛዙም እንዴት እንደ ነበር ሁሉም ነገር በእስራኤል ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኛል። **20** ኢዮርብዓም ለሃያ ሁለት ዓመት ነገሠ፤ ከአባቶቹም ጋር አንቀላፋ፤ ልጁም ናዳብ በእርሱ ፈንታ ተተክቶ የእስራኤል ንጉሥ ሆነ። **21** የሰለሞን ልጅ ሮብዓም በይሁዳ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው አርባ አንድ ዓመቱ ነበር። እርሱም እግዚአብሔር ከመላው የእስራኤል ነገዶች ለስሙ መጠሪያ እንድትሆን በመረጣት ከተማ በኢየሩሳሌም መኖሪያውን አድርጎ ዐሥራ ሰባት ዓመት ገዛ። የሮብዓምም እናት አሞናዊት ስትሆን፣ ስምዋም ናዕማ ነበር። **22** የይሁዳ ሕዝብ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ አደረገ፤ የቀድሞ አባቶቻቸው ሲያደርጉት ከነበረው ይበልጥ ክፉ ነገር በማድረጋቸው የእግዚአብሔርን ቁጣ አነሣሡት። **23** ለባዕዳን አማልክትም የማምለኪያ ስፍራዎችን ሠሩ፤ በኮረብታዎች ላይና በዛፍ ጥላ ሥር የሚያመልኩአቸውን የድንጋይ ቅርፆችና የኤሼራን ምስሎች አቆሙ። **24** ከእነዚህም ሁሉ የከፋ በእነዚያ ሕዝቦች የማምለኪያ ስፍራዎች የቤተ ጣዖት አመንዝራዎች ነበሩ። አሕዛብ ይፈፅሙት የነበረውን እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ፊት ነቃቅሎ ያባረራቸውን አሳፋሪ ነገር ሁሉ ይፈፅሙ ነበር። **25** ሮብዓም በነገሠ በአምስተኛው ዓመት የግብፅ ንጉሥ ሺሻቅ በኢየሩሳሌም ላይ አደጋ ጣለ። **26** በቤተ መቅደስና በቤተ መንግሥት ተከማችቶ የነበረውንም ሀብት ሁሉ፣ ሰለሞን ከወርቅ ያሠራቸውን ጋሻዎች ጭምር ዘርፎ ወሰደ። **27** እነርሱንም ለመተካት ንጉሥ ሮብዓም ጋሻዎችን ከነሐስ አሠርቶ የቤተ መንግሥቱን ቅጥር በር በሚጠብቁ አለቆች እንዲጠበቁ አደረገ። **28** ንጉሡ ወደ ቤተ መቅደሱ በመጣ ቁጥር፣ የቤተ መቅደሱ ዘበኞች ጋሻዎችን አንግበው ይቀበሉታል፤ ከሄደም በኋላ ጋሻዎቹን መልሰው ዘበኞች በሚጠበቁበት ማከማቻ ያኖሩ ነበር። **29** ንጉሥ ሮብዓም ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ በይሁዳ ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኝ የለምን? **30** በዚህም ዘመን ሁሉ ሮብዓምና ኢዮርብዓም እርስ በርሳቸው በማያቋርጥ ጦርነት ላይ ነበሩ። **31** ሮብዓም ሞተ፤ በዳዊት ከተማ በሚገኘው በነገሥታቱ መካነ መቃብር ተቀበረ። ልጁም አቢያ በእርሱም ፈንታ ተተክቶ ነገሠ።

---

1 Kings 14:1

ለውጪና
“እራስሽን ለሌሎች ቀይርና (ለወጪና)”

እንዳትታወቂ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ማንም አያውቅሽም”

1 Kings 14:4

እነሆ .....የእዮርብዓም ምስት
“እነሆ” የሚለው ቃል ትኩረት እንዲሠጥ መፈለጉን ያሳያል።

ትጠይቅህ ዘንድ .....ትመጣለች
ተርጓሚ “ምክር ልትጠይቅህ ወደ አንተ ትመጣለች”

አንዲህና እንዲህ በላት
x

1 Kings 14:6

ስለ ምንስ ሌላ ቤት መሰልሽ?
ይህ ጥያቄ የሚያሳየው አኪያ እራሷን እንደለወጠች ማወቁን ነው።ተርጓሚ “ሌላ ሰው መምሰልሽን ተይ (አቁሚ) እኔ ማን እንደሆንሽ አውቄሻለሁ”

እኔም ብርቱ ወሬ ይዤ ተልኬልሻለሁ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። “ብርቱ ወሬ እንድሠጥሽ (እንድነግርሽ) እግዚአብሔር ልኮኛል”

ከፍ አድርጌህ ነበር
“አሞገስኩህ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መንግስቱን ቀድጄ .....ነበር
ልብስ እንደሚቀድ ሰው እግዚአብሔር አብዛኛውን መንግስት መጉልበት አስወግዶአል።

ተከተለኝ
“ታዘዘኝ”

1 Kings 14:9

ወደ ኋላም ጣልከኝ
ሰው የሚይፈልገውን ዕቃ ወርውሮ አንደጣለው ኢዮርብዓምም እግዚአብሔርን አላከበረውም ተርጓሚ “ፈፅሞ ተውከኝ”

እነሆ
“አትኩሮት ስጥ” ይህ ቃል የተጨመረው ቀጥሎ የሚመጣው ነገር ወሳኝ ነገር መሆኑን ለማመልከት።

እቆርጣለሁ .....ፈፅሜ እጠርጋለሁ
እነዚህ ሁለት ቃልት በትርጉም በጣም ተመሣሣይ ሲሆኑ አፅንኦት ለመስጠት አንድ ላይ ሆነዋል።

ከእዮርብዓም .....በእስራኤል ወንድ ሁሉ እቆርጣለሁ
ቀርንጫፍን ከዛፍ እንደሚቆርጥ የእዮርብዓምን ቤት እንደሚቆርጥና ምንም የዘር ሐረግ እንዳይኖረው እግዚአብሔር ይናገራል። ተርጓሚ “በእስራኤል ያሉ ወንዶች ልጆችህን አጠፋለሁ” ሰውም ፋንድያን እስኪጠፋ ድረስ እንደሚጠርግ እኔ የእዮርብዓምን ቤት ፈፅሜ እጠርጋለሁ ይህ ምሳሌያዊ ንግግር የእዮርብዓምን የዘር ሐረግ መወገድ ፋንድያ ከሣርና ደረቅ ነገር ጋር ተደባልቆ ፈፅሞ እንደሚቃጠል ጋር ያነፃፅራል።

1 Kings 14:11

ከእዮርብዓምም ወገን በከተማይቱ ውስጥ የሞተውን ውሾች ይበሉታል
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ውሾች ከእዮርብዓም ወገን የሆኑትንና በከተማ ውስጥ የሞተውን ይበሉታል።

በሜዳውም የሞተውን የሰማይ ወፎች ይበሉታል
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። የሰማይ ወፎች በሜዳ የሞተውን ማንንም ይበላሉ።

እግርሽም ወደ ከተማ በገባ ጊዜ
እዚህ ጋር እግር የሚለው ቃል ሙሉ ሰውነትን የሚወክል ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “የእስራኤል ህዝብ”

ይቀብሩትማል
“በመቃብር መቅበር”

በእዮርብዓም ቤት
እዚህ ጋር “ቤት” የሚለው ቃል ለቤተሰብ ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “በእዮርብዓም ቤተሰብ ሁሉ”

በእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ዘንድ.....መልካም ነገር ተገኝቶበታልና
“ዘንድ” የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ፍርድ መይም ምዘና ይወክላል።ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ያገኘው (የፈረደው) ነገር ሁሉ መልካም ሆነ አገኘ”

1 Kings 14:14

የእዮርብዓምን ቤት ያጠፋል
ፀሐፊው፣አድሱ የእስራኤል ንጉስ ሰው የዛፍን ቅርንጫፍ እንደሚቆርጥ ሁሉ የእዮርብዓምን ቤት የዘር ሐረግ እንዳይኖረው እንደሚያጠፋው ይናገራል። ተርጓሚ “የእዮርብዓምን የዘር ሀረግ (ትውልድ) ያጠፋል።”

ሸምበቆ በውኃ ውስጥ እንደሚንቀሳቀስ እግዚአብሔር እንዲሁ እስራኤልን ይመታል
እዚህ ጋር ፀሐፊው ንፅፅርን በመጠቀም እንዴት እግዚአብሔር ፍርድን ወደ እስራኤል እንደሚያመጣ ይገልፃል። ተርጓሚ “ሸንበቆ በውኃ ውስጥ እንደሚንቀሳስ እግዚአብሔር እንዲሁ እስራኤልን ይቀጣል”

ሸንበቆ በውኃ ውስት እንደሚንቀሳቀስ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “የወንዝ ውኃ ሸምበቆ እንደሚያንቀሳቅስ ሁሉ”

ከዚች ከመልካሚቱ ምድር እስራኤልን ይነቅላል።
እግዚአብሔር እስራኤልን ከተክል ጋር በማወዳደር ከመሬት ውስጥ ፈንቅሎ ሥሩን ያወጣል። ተርጓሚ “ከዚች መልካም ምድር እስራኤልን ፈፅሞ ያጠፋል”

ይበትናቸዋል
“ይበትናቸዋል” ወይም “ይለያቸዋል”

1 Kings 14:17

ቴርሳ
ይህ ንጉሥ እዮርብዓም ይኖርበት የነበረ የከተማ ስም ነው።

እስራኤል ሁሉ ቀበሩት አለቀሱለትም
ይህ ጥቅል ሀሳብ ሲሆን የእስራኤል ህዝብ ቀብረው አለቀሱለት ማለት ነው። ተርጓሚ “ሰዎች ሊቀብሩት ብዙ ቁጥር ያለው የእስራኤል ሕዝብ በቀብሩ ላይ ተገኝተው አለቀሱለት”

እንደ ተነገረው እንደ እግዚአብሔር ቃል
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “እግዚአብሔር አንደተናራቸው”

በ.....እግዚአብሔር ቃል
“በእግዚአብሔር መልዕክት” ወይም “በመልዕክተ-እግዚአብሔር”

1 Kings 14:19

እነሆ
“ተመልከት” ወይም “ለራስህ ተመልከት”

በ.....ተፅፎአል
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። “በ.....ተፅፎ ታገኛቸዋለህ” ወይም “የሆነ ሰው.....በ.....ፅፎአቸዋል”

በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ መፅሐፍ
ይህ በአሁኑ ጊዜ የማይገኝ መፅሐፍን ይገልፃል።

ሀያ ሁለት ዓመት
“22 ዓመት”

ከአባቶቹም ጋር
ከአባቶቹም ጋር አንቀላፋ የሮብዓም ሞት እንቅልፉን እንደተኛ ሰው ተደርጎ ተነግሮአል የ1ነገስት 2:10 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ “ሞተ” ወይም “አረፈ”

1 Kings 14:21

አርባ አንድ አመት .....አሥራ ሰባት አመት
“41 ዓመት .....17 አመት”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ስሙን ያኖርበት ዘንድ
እዚህ ጋር ስሙን ያኖርበት ዘንድ የሚለው ሐረግ ለ “መኖር” ዘይቤ ሲሆን እግዚአብሔር የሚመለክባትን ቤተ-መቅደስ ይገልፃል። ተርጓሚ “የሚኖርበት” ወይም “የሚመለክበት”

የእናቱም ስም
ይህ ሐረግ የሚገልፀው ሮብዓምን ነው።

ናዕማ
ይህ የሴት ስም ነው።

ይሁዳም .....ሠራ
እዚህ ጋር ይሁዳ የይሁዳን ህዝብ ይወክላል። ተርጓሚ “የይሁዳ ህዝብ ሠሩ”

በእግዚአብሔር ፊት ክፉ
እዚህ ጋር የእግዚአብሔር ፊት የሚለው ሐረግ የእግዚአብሔር ፍርድን ወይም ምዘናን ይወክላል። የ1ነገስት 11፡6 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ “በእግዚአብሔር ፍርድ ክፉ” ወይም “እግዚአብሔር ክፉ ነው ያለውን”

በ.....ኃጢአት አስቆጡት
አስቆጡት የሚለው ቃል በቅፅል መልኩ ይገለፃል። ተርጓሚ “ቁጡ አደረጉት ”

አባቶቻቸው
“የዘር ሐገጋቸው” ወይም “የዘር ግንዳቸው”

1 Kings 14:23

እነርሱም .....ሰሩ
እነርሱም የሚለው ቃል የይሁዳን ህዝብ ይገልፃል።

ለራሳቸው ሠሩ
ለራሳቸው የሚለው ቃል በኮረብታ ቦታዎች ለሚሰሩት ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “ለራሳቸው ጥቅም ሠሩ”

ከፍ ባለው ኮረብታ ሁሉ ላይ ቅጠሉ ከለመለመ ሁሉ በታች
ይህ ምናልባት ለሐሰት አምልኮ በዚያ ሀገር ብዙ ቦታዎች መኖራቸውን ማሳያ የግነት ንግግር ነው። ተርጓሚ “ከፋ ባለ ኮረብታና በለመለመ ዛፍ ሁሉ ሥር”

ሰዶማውያን
“አምልሞታዊ መልክ ያለው” ወይም “ወንድ ጋለሞታዎችን” ይህ ምናልባት ከባዕድ አምልኮ ጋር የተያያዙ የወንድ ጋለሞታዎችን ይገልፃል።

1 Kings 14:25

ሮብዓምም በነገሠ በአምስተኛው ዓመት
ይህ የሮብዓምን አምስተኛ አመት የንግስና ዘመንን (አመትን) ይገልፃል። ተርጓሚ “ሮብዓም ንጉስ በነበረበት በአምስተኛው አመት”

በአምስተኛው አመት
“በ5 ዓመት”

ሺሻቅ በእየሩሳሌም ላይ መጣ
የግብፅ ንጉስ “ሺሻቅ” እርሱንና ከእርሱ ጋር የነበሩትን የግብፅ ሠራዊት ይገልፃል። ተርጓሚ “ሺሻቅ ከእርሱ ጋር የነበሩት የግብፅ ሠራዊት በእየሩሳሌም ላይ መጡ”

ሺሻቅ
ይህ የሰው (ወንድ) ስም ነው የ1ነገስት 11፡40 ትርጉምን ተመልከት

ላይ መጣ
ይህ ፊሊጣዊ ሲሆን ትርጉሙም ለማጥቃት መዝመት ማለት ነው።

ሁሉንም ወሰደ
ይህ ጥቅል ነው። የተገገውን የትኛውንም ዋጋ ያለው ነገር መውሰዱን ያመለክታል።

ወሰደ
ይህ ቃል ሺሻቅንና ከእርሱ ጋር የነበሩትን ወታደሮች ይወክላል። ተርጓሚ ሺሻቅና ወታደሮቹ ወሰዱ

ሰለሞን የሰራውን
x

1 Kings 14:27

ንጉስ ሮብዓም....ጋሶችን ሰራ
እዚህ ጋር “ንጉስ ሮብኣም” ለእረሱ ጋሻ የሚሰራለትን ሰው ይወክላል። ተርጓሚ የንጉስ ሮብዓም ሰራተኞች ጋሾችን ሰሩ

በዘበኞች ቤት
ይህ ቤት የወርቅ ጋሾቹ የሚቀመጡበት ቤት ነበር

በዘበኞች አለቆች እጅ አኖራቸው
እዚህ ጋር “እጅ” ጥንቃቄ ወይም ሀላፊነትን ይወክላል። ተርጓሚ “የአለቆቹ ኃላፊነት አደረጋቸው”

የንጉሡም ቤት ደጅ በሚጠብቁ
እዚህ ጋር “ደጅ” መግቢያን ይወክላል። ተርጓሚ “የንጉሱንም ቤት መግቢያ በሚጠብቁ”

በዘበኞች ይሸከሙአቸው ነበር
“የነሃስ ጋሾችን የሚሸከሙ ዘበኞች”

1 Kings 14:29

በይሁዳ ነገስታት ታሪክ መፅሃፍ የተፃፈ አይደለምን
ይህ በገቢር መልኩ ሊገለፅ የሚችል መልሱም አዎንታዊ እንደሚሆን ይገመታል። ጥያቄው የግነት የግነት የሆነው አፅንኦት ለመስጠትም ነው። ተርጓሚ “በይሁዳ ነገስታት ታሪክ ተፅፈዋል” ወይም “ከይሁዳ ነገስታት ታሪክ መፅሐፍ ማንበብ ትችላላችሁ”

በይሁዳ ነገስታት ታሪክ መፅሐፍ
ይህ በአሁኑ ጊዜ የሌለን መፅሐፍ ይገልፃል።

በዘመኑ ሁሉ...ሰልፍ ነበረ
“የማቋርጥ ሰልፍ (ጦርነት) ነበረ ” ወይም “የማያቋርጥ ፍልሚያ ነበረ”

በርብዓምና በኢዮርብዓም መካከል ሰልፍ ነበር
የነገስታቱ ስም እነርሱንና ሰራዊታቸውን ይወክላል። ተርጓሚ “የሮብዓምና የኢዮርብዓም ሰራዊቶች ደጋግመው ደጋግመው በፍልሚያ ታ ተዋጉ” ወይም “የሮብዓምና ህዝቡና የኢዮርብዓም ህዝብ በተከታታይ በጦር ኔዳ ተጋጠሙ (ጦርነት ገጠሙ)”

ከአባቶቻቹ ጋር አንቀላፉ
የኢዮርብዓም ሞት እንቅልፍን እንደተኛ ሰው ሆኖ ተነግሮአል።የ1ነገስት 2፡10 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ “ሞተ” ወይም “አረፈ”

ከ....ጋር ተቀበረ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ህዝቡ ቀበረው”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 15

1 ኢዮርብዓም በእስራኤል ላይ በነገሠ በዐሥራ ስምንተኛው ዓመት አቢያ የይሁዳ ንጉሥ ሆነ። 2 እርሱም በኢየሩሳሌም ሦስት ዓመት ነገሠ። የእናቱ ስም ማዕካ
ሲሆን፣ እርስዋም የአቤሴሎም ልጅ ነበረች። 3 አቢያም እንደ ቀደሙት አባቶቹና እንደ ዳዊት በእግዚአብሔር አምላክ ዘንድ ፍፁም ታማኝ ሆኖ አልተገኘም።
አባቱ ሮብዓም ይፈፅመው የነበረውን ኃጢአት ሁሉ መሥራት ቀጠለ። 4 የሆነ ሆኖ ከእርሱ በኋላ በኢየሩሳሌም እንዲነግሥና ኢየሩሳሌምንም እንዲያጠናክር
አምላኩ እግዚአብሔር ስለ ዳዊት ሲል ለአቢያ አንድ ወንድ ልጅ ሰጠው። 5 እግዚአብሔር ይህንን ያደረገበት ምክንያት ዳዊት በሂታዊው ኦርዮን ላይ ከፈጸመው
ኃጢአት በቀር በእግዚአብሔር ፊት በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ትክክለኛ ነገር አድርጎአል፤ ከትእዛዙም ፈቀቅ አላለም። 6 በሮብዓምና ኢዮርብዓም ዘመን ተጀምሮ
የነበረው ጦርነት፣ በአቢያ ዘመነ መንግሥትም ነበር። 7 አቢያ ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ በይሁዳ ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኝ የለምን? 8
አቢያም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ በዳዊትም ከተማ ተቀበረ። በእርሱም ፈንታ ልጁ አሳ ተተክቶ ነገሠ። 9 ኢዮርብዓም በእስራኤል ላይ በነገሠ በሃያኛው ዓመት
አሳ የይሁዳ ንጉሥ ሆነ። 10 እርሱም በኢየሩሳሌም አርባ አንድ ዓመት ገዛ። አያቱም ማዕካ ተብላ የምትጠራ የአቤሴሎም ልጅ ነበረች። 11 አሳም አያቱ ዳዊት
እንዳደረገው ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ደስ የሚያሰኝ ነገር ሠራ። 12 ንጉሥ አሳ የቤተ ጣዖት አመንዝራዎችን ሁሉ ከአገሩ አስወገደ፤ ከእርሱም በፊት የነበሩ
ነገሥታት የሠሩአቸውን ጣዖታት ሁሉ ነቃቅሎ ጣለ። 13 አያቱ ማዕካ አሼራ ተብላ የምትጠራውን የሴት አምላክ አስጸያፊ ጣዖት ስለ ሠራች ከእቴጌነት ሽሮ ከቤተ
መንግሥት አስወጣት፤ የሠራችውንም ጣዖት ሰባብሮ በቄድሮን ሸለቆ ውስጥ በእሳት አቃጠለው። 14 አሳ በኮረብቶች ላይ የሚገኙ የአሕዛብ የማምለኪያ
ቦታዎችን በሙሉ አላስወገደም፤ ይሁን እንጂ በዘመኑ ሁሉ የአሳ ልብ ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር ፍጹም ነበር። 15 አባቱ ለእግዚአብሔር ቤት የተለየ እንዲሆኑ
ያደረጋቸውንና እርሱም ራሱ የለያቸውን ወርቅና ብር አሠርቶ ንዋያተ ቅዱሳትን ሁሉ በቤተ መቅደስ አኖረ። 16 የይሁዳ ንጉሥ አሳና የእስራኤል ንጉሥ ባኦስ
በሥልጣን በነበሩበት ዘመን ሁሉ የእርስ በርስ ጦርነት ነበር። 17 የእስራኤል ንጉሥ ባኦስ ማንም ሰው አሳ በሚገዛበት በይሁዳ ምድር እንዳይወጣና እንዳይገባ
ለመከላከል ራማን ምሽግ አድርጎ መሥራት ጀመረ። 18 ከዚያም ንጉሥ አሳ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስና በቤተ መንግሥቱ የተረፈውን ወርቅና ብር ሁሉ
ወሰደ። እርሱም በአገልጋዮቹ እጅ በደማስቆ ከተማ ለነበረው የአዚን ልጅ የጣብሪሞን ልጅ ለሆነው ለሶርያ ንጉሥ ቤን ሀዳድ ስጦታ አድርጎ ላከለት። እርሱም
እንዲህ አለ፦ 19 የእኔ አባትና የአንተ አባት ያደርጉት በነበረው ዓይነት በመካከላችን ቃል ኪዳን ይኑር። እነሆ ብርና ወርቅ ስጦታ እንዲሆንህ ልኬልሃለሁ።
የእሰራኤል ንጉሥ ባኦስ እኔን እንዲለቀኝ ቀደም ሲል ከእርሱ ጋር ያደረግኸውን ቃል ኪዳን አሁን እንድታቋርጥ ይሁን። 20 ንጉሥ ቤን ሀዳድም አሳ ባቀረበው
አሳብ ተስማምቶ የጦር አዛዦቹንና ሠራዊቱን በመላከ በእስራኤል ከተሞች ላይ አደጋ እንዲጥሉ አደረገ። እነርሱም ዒዮን፣ ዳን፣ አቤልቤተማሪካና የገሊላ ባሕር
ተብለው የሚጠሩ ከተሞች በገሊላ ባሕር አጠገብ የሚገኘው አገርና የንፍታሌም ግዛት ሁሉ ናቸው። 21 ንጉሥ ባኦስ የሆነውን ነገር ሁሉ በሰማ ጊዜ የራማን
ምሽግ መሠራት እንዲቆም አድርጎ ወደ ቲርጻ ሄደ። 22 ከዚህም በኋላ ንጉሥ አሳ ባኦስ ራማን ለመመሸግ አከማችቶት የነበረውን ድንጋይና እንጨት ከዚያ
ለማንሣት እንዲረዳው ሕዝቡ አንድም ሳይቀር እንዲመጣ ወደ ይሁዳ ግዛቶች ሁሉ ትእዛዝ አስተላለፈ፤ ንጉሥ አሳ ከዚያ የተገኘውን ድንጋይና እንጨት ሁሉ
ወስዶ በምጽጳና በብንያም ግዛት ውስጥ የምትገኘውን የጌባዕን ከተማ ምሽግ አድርጎ ሠራበት። 23 ንጉሥ አሳ ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ የጀግንነት ሥራውና
የሠራቸውም ከተሞች በይሁዳ ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኝ የለምን? ንጉሥ አሳ በዕድሜ በሸመገለ ጊዜ ከእግሩ ሕመም የተነሣ ሽባ ሆኖ ነበር።
24 ንጉሥ አሳም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ በዳዊትም ከተማ በሚገኘው በነገሥታት መቃብር ተቀበረ። በእርሱም ፈንታ ተተክቶ ልጁ ኢዮሣፍጥ ነገሠ። 25 አሳ
በይሁዳ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት የአዮርብዓም ልጅ ናዳብ የእስረኤል ንጉሥ ሆነ። እርሱም ሁለት ዓመት ገዛ። 26 ከእርሱም በፊት እንደ ነበረው እንደ አባቱ
በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት በመሥራት የእስራኤልን ሕዝብ ወደ ኃጢአት መራ። 27 የይሳኮር ነገድ የሆነው የአኪያ ልጅ ባኦስ ናዳብን ድል አድርጎ ገደለው፤
በዚያም ጊዜ ናዳብና ሠራዊቱ በፍልስጥኤም ግዛት የምትገኘውን የገባቶንን ከተማ በመክበብ ላይ ነበሩ። 28 ይህም የሆነው የይሁዳ ንጉሥ አሳ በነገሠ
በሦስተኛው ዓመት ነው፤ በዚህ ዓይነት ባኦስ በናዳብ ፈንታ ተተክቶ የእስራኤል ንጉሥ ሆነ። 29 ንጉሥ ባኦስ እንደነገሠ ወዲያውኑ የኢዮርብዓምን ቤተ ሰብ
በሙሉ ገደለ። እግዚአብሔር በአገልጋዩ በሴሎኣዊው በነቢዩ አኪያ አማካይነት በተናገረው ቃል መሠረት የኢዮርብዓም ወገን በሙሉ ተገደሉ። በሕይወት የተረፈ
አንድም አልነበረም፤ 30 ይህም የሆነበት ምክንያት ኢዮርብዓም ራሱ በሠራው ኃጢአትና የእስራኤልን አምላክ የእግዚአብሔርን ቁጣ ስላነሣሣ ነው። 31 ናዳብ
ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ በእስራኤል ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኝ የለምን? 32 የይሁዳ ንጉሥ አሳ እና የእስራኤል ንጉሥ ባኦስ በሥልጣን
ዘመናቸው ሁሉ የእርስ በርስ ጦርነት ላይ ነበሩ። 33 አሳ በይሁዳ በነገሠ በሦስተኛው ዓመት የአኪያ ልጅ ባኦስ በመላው እስራኤል ላይ ነገሠ። እርሱም በቲርጻ
ሃያ አራት ዓመት ገዛ። 34 ከእርሱም በፊት እንደ ነበረው እንደ ንጉሥ ኢዮርብዓም ባኦስ ኃጢአት በመሥራትና የእስራኤልንም ሕዝብ ወደ ኃጢአት በመምራት
በእግዚአብሔር ፊት ክፉ አደረገ።

---

1 Kings 15:1

በናባጥ ልጅ በንጉሥ ኢዮርብዓም አስራ ስምንተኛ አመት
ይህ የሚያመለክተው የኢዮርብዓምን ንግሥና አስራ ስምንተኛ አመት ነው። "ኢዮርብዓም ለ አስራ ስምንት አመታተት ያህል የእስራኤል ንጉሥ ከሆነ በኋላ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በአስራ ስምንተኛው አመት
"በ18ተኛው አመት" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉንም አይነት ኃጢአቶች አደረገ/ በኃጢአት መንገድ ተራመደ
ማድረግ/መራመድ የሚወክለው በኃጢአት መኖርን ነው፣ እናም በኃጢአት መራመድ የሚለው እነዚያን ኃጢአቶች መፈጸምን ነው። "አብያ እነዚይን ኃጢአቶች ማድረጉን ቀጠለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከእርሱ ዘመን በፊት አባቱ ያደርግ የነበረውን
እነዚህ ቁጥሮች በርካታ ነገሥታትን የሚያመለክቱ እንደመሆናቸው፣ የአብያን አባት ስም ማካተቱ ሊጠቅም ይችላል። ይህ መረጃ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "አባቱ ሮብዓም፣ ከአብያ ዘመን አስቀድሞ እንዳደረገው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ ዘመን
ይህ ሀረግ የሚወክለው እርሱ ንጉሥ የነበረበትን ጊዜ ነው። የዚህ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "አብያ ንጉሥ ከነበረበት ጊዜ አስቀድሞ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ልቡ እንደ ዳዊት ልብ...አልተሰጠም ነበር
ልብ የሚወክለው መላ ስብዕናን ነው። "እንደ ዳዊት... አብያ ልቡን የሰጠ ሰው አልነበረም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 15:4

ለእርሱ በእየሩሳሌም መብራት ሰጠው
እዚህ ስፍራ "መብራት" የሚለው ቃል የሚወክለው ዳዊት ንጉሥ እንደነበረ በእርሱ ስፍራ የሚነግሥን የእርሱን ትውልድ ነው። "ለዳዊት በእየሩሳሌም የሚነግሥ ትውልድ ሰጠው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከእርሱ በኋላ የእርሱን ወንድ ልጅ በማስነሳት
"ከእርሱ በኋላ የአብያን ወንድ ልጅ በማስነሳት" ወይም "ለአብያ ወንድ ልጅ በመስጠት"

በዐይኖቹ ፊት ትክክል ሆኖ የታየውን
እዚህ ስፍራ ዐይኖች የሚለው የሚወክለው ማየትን፣ ሲሆን ማየት ደግሞ ሀሳብን ወይም ፍርድን ይወክላል። "ያህዌ ትክክል ነው የሚለው" ወይም "ያህዌ ትክክል ነው ብሎ የሚቆጥረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ የህይወት ዘመን ሁሉ
"ዳዊት በኖረበት ዘመን በሙሉ" ወይም "በዳዊት የህይወት ዘመን ሁሉ"

1 Kings 15:7

የይሁዳ ነገሥታት ስራዎች በተጻፈበት መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ አይደለምን?
ይህ ጥያቄ የዋለው አንባቢያን ስለ አብያ ያለው መረጃ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንደሚገኝ ለማሳወቅ ወይም ለማስታወስ ነው። ይህ በ1ነገሥት 14:29 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። ቃለ ምልልሳዊው ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "እነዚህ ታሪኮች የይሁዳ ነገሥታት የፈጸሟቸው ድርጊቶች በተጻፉባቸው መጽሐፍት ውስጥ ተጽፈዋል።" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳ ነገሥታት ስራዎች በተጻፈበት መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ አይደለምን?
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንድ ሰው ይህንን የይሁዳ ነገሥታት ድርጊቶች በተጻፈበት መጽሐፍ ጽፎታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በአብያ እና በኢዮርብዓም መሃል
"አብያ" እና "ኢዮርብዓም" የሚሉት ስሞች የሚወክሉት ንጉሦቹን እና ሰራዊቶቻቸውን ነው። "በአብያ እና በኢዮርብዓም ሰራዊቶች መሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 15:9

በእስራኤል ንጉሥ በኢዮርብዓም ሃያኛ አመት
ይህ የሚያመለክተው የኢዮርብዓምን ሃያኛ አመት ንግሥና/ዘመነ መንግሥት ነው። "ኢዮርብዓም በእስራኤል ከነገሰ ከሃያ አመታት ያህል በኋላ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በሃያኛው አመት
በ20ኛው አመት" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

አርባ አንድ አመታት
"41 አመታት" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በያህዌ ዐይኖች ትክክል የሆነውን
እዚህ ስፍራ ዐይኖች የሚለው የሚወክለው ማየትን ሲሆን፣ ማየት ደግሞ ፍርድን ይወክላል። ያህዌ የዓሳን ድርጊቶች ተመልክቶ አጽድቋል። "ያህዌ ተመልክቶ ትክክል ነው የሚለው" ወይም "ያህዌ ትክክል ነው የሚለው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 15:12

የቤተ ጣኦት ወንደቃዎች
ይህ የሚያመለክተው ምናልባትም ከጣኦት አምልኮ ጋር የተያያዘ የወንዶች ምንዝር አዳሪነትን ሊሆን ይችላል። "ሃይማኖታዊ አመንዝሮች" ወይም "ለጣኦት አገልግሎት የሚሰጡ አመንዝሮች" ወይም "ወንድ የሆኑ በአመንዝራነት የሚሰሩ"

አሳ አስጸያፊ ምስሎችን አፈረሰ
አሳ ንጉሥ ስለ ነበረ፣ መኳንንቱን ምስሎችን እንዲርጡ ነግሯቸው ሊሆን ይችላል። "አሳ አስጸያፊዎቹ ምስሎች እንዲፈርሱ አደረገ" ወይም "አሳ እነርሱ አስጸያፊዎቹን ምስሎች እንዲያፈርሱ አደረገ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 15:14

ነገር ግን ከፍ ያሉት ስፍራዎች አልተወሰዱም ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አሳ ግን ሰዎቹ ከፍ ያሉ ስፍራዎችን እንዲወስዱ አላዘዘም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የአሳ ልብ ሙሉ ለሙሉ የተሰጠ ነበር
ልብ ሰውየውን ይወክላል። "አሳ ሙሉ ለሙሉ የተሰጠ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በዘመኑ በሙሉ
"በኖረበት ዘመን ሁሉ" ወይም "በህይወት ዘመኑ በሙሉ"

1 Kings 15:16

በዘመናቸው ሁሉ
ይህ የሚያመለክተው እንደ ነገሥታት ሲገዙ የኖሩበትን ዘመን ነው። "በይሁዳ እና በእየሩሳሌም ሲገዙ በኖሩባቸው ዘመናት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በይሁዳ ላይ በቁጣ ተነሳ
"ይሁዳን ወጋ"

ራማን ሰራት
የባኦስ ሰራዊት በመጀመሪያ ራማን እንደወረራት ተጠቁሟል። የዚህ ሀሳብ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ራማን ወረራት ደግሞም ምሽግ አድርጎ ሰራት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 15:18

በአገልጋዮቹ እጅ ላይ አስቀመጣት
ነገሮችን በእጆቻቸው ላይ ማስቀመት የሚወክለው እነዚያን ነገሮች ለእነርሱ መስጠትን ነው። እነርሱ እንዲያደርጉ የሚፈልገውን በእርሷ እንደሚያደርጉ ተጠቁሟል። የዚህ ሀሳብ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ይህን ለአገላጋዮቹ አደራ ሰጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንዲህ አለ
ይህ ማለት በአገላጋዮቹ አማካይነት ተናገረ ማለት ነው። አሳ ለአገልጋዮቹ ለቤን ሀዳድ ምን እንደሚናገሩ እና እንደሚያደርጉ ነገራቸው። የዚህ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "አሳ ለአገልጋዮቹ ለቤን ሀዳድ እንዲነግሩት ነገራቸው" ወይም "አሳ በአገልጋዮቹ በኩል ለቤን ሀዳድ እንዲህ ሲል መልዕክት ላከ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

በእኔ እና በአንተ መሃል ቃል ኪዳን ይኑር
በሁለት ሰዎች መካከል ቃል ኪዳን መኖር የሚያመለክተው ሁለቱ ሰዎች በመሃላቸው ቃል ኪዳን እንዳለ ነው። "እርስ በእርሳችን ቃል ኪዳን ይኑረን" ወይም "የሰላም ስምምነት እናድርግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ፣ እኔ
"እኔ፣ ከአንተ ጋር ለመተማመኛ ስምምነት እፈልጋለሁ"

ከእስራኤል ንጉሥ ከባኦስ ጋር ያለህን ቃል ኪዳን አፍርስ
ቃል ኪዳንን ማፍረስ የሚወክለው አንድ ሰው ሊያደርግ ቃል የገባውን መሰረዝን እና አለማድረግን ነው። "ከእስራኤል ንጉሥ ከባኦስ ጋር የገባኸውን ኪዳን አፍርስ" ወይም "ለእስራኤል ንጉሥ ለባኦስ ከእርሱ ጋር ኪዳን ባደረግከው መሰረት ታማኝ አትሁንለት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከእስራኤል ንጉሥ ከባኦስ ጋር ያለህን ቃል ኪዳን አፍርስ
x

1 Kings 15:20

እንዲህም ሆነ
እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ውስጥ ትልቅ ክንዋኔን ለማመልከት ነው። የእናንተ ቋንቋ ይህንን ለመግለጽ መንገድ ካለው እዚህ ስፍራ ያንን መጠቀም ትችላላችሁ።

ራማን መገንባት አቆመ
ንጉሥ ባኦስ ለሰራተኞቹ በመንገር ይህንን አደረገ። "ሰራተኞቹ ራማን መገንባት እንዲያቆሙ አደረገ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ቴርሳ
ይህ የከተማ ስም ነው። ይህ በ1 ነገሥት 14፡17 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።

ማንም ከዚህ ነጻ አልነበረም
ይህ በአዎንታም ሊተረጎም ይችላል። "እያንዳንዱ ሰው የንጉሥ አሳን አዋጅ መታዘዝ አለበት"

1 Kings 15:23

የይሁዳ ነገሥታት ስራዎች በተጻፈበት መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ አይደለምን?
ይህ ጥያቄ የዋለው አንባቢያን ስለ አብያ ያለው መረጃ በዚህ ሌሎች መጽሐፍት ውስጥ እንደሚገኝ ለማሳወቅ ወይም ለማስታወስ ነው። ይህ በ1ነገሥት 14:29 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። ቃለ ምልልሳዊው ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "እነዚህ ታሪኮች የይሁዳ ነገሥታት የፈጸሟቸው ድርጊቶች በተጻፉባቸው መጽሐፍት ውስጥ ተጽፈዋል።" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳ ነገሥታት ስራዎች በተጻፈበት መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ አይደለምን?
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንድ ሰው ይህንን የይሁዳ ነገሥታት ድርጊቶች በተጻፈበት መጽሐፍ ጽፎታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አሳ ከአባቶቹ ጋር ተኛ
እዚህ ስፍራ መተኛት ሞትን የሚወክል ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት/ ነው። "አብያ እንደ አባቶቹ ሁሉ ሞተ" ወይም "እንደ አባቶቹ ሁሉ አብያ ሞተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚሉትን ይመልከቱ)

ከእነርሱ ጋር ተቀበረ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ከአባቶቹ ጋር ቀበሩት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አባቱ ዳዊት
እዚህ ስፍራ "አባት" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የጥንት አባቶችን ነው።

1 Kings 15:25

አያያዥ ሀሳብ፡
ቀሪው ምዕራፍ 15 እና 16 ስለ እስራኤል ነገሥታት ነው። እነዚህ ድርጊቶች የይሁዳ ንጉሥ አሳ በህይወት በነበረበት ወቅት የተፈጸሙ ናቸው።

የይሁዳ ንጉሥ አሳ ሁለተኛ አመት
ይህ የሚያመለክተው የአሳን ዘመነመንግሥት ሁለተኛ አመት ነው። የዚህ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል፡፤ "አሳ የይሁዳ ንጉሥ በነበረባቸው ለሁለት አመት ለተጠጉ ጊዜያት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ለሁለት አመታት በእስራኤል ላይ ነገሠ
"ናዳብ በእስራኤል ላይ ለሁለት አመታት ነገሠ"

በያህዌ እይታ ክፉ የሆነውን
የያህዌ እይታ የሚለው የሚወክለው የያህዌን ፍርድ ነው። "በያህዌ ፍርድ/ ሚዛን ክፉ የሆነውን" ወይም "ያህዌ ክፉ ብሎ የሚቆጥረውን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በአባቱ መንገድ ሄደ
እዚህ ስፍራ መሄድ የሚወክለው ድርጊትን ነው። "አባቱ ያደረገውን ተመሳሳይ ነገር አደረገ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በገዛ ራሱ ኃጢአት
በራሱ ኃጢአት መራመድ የሚለው የሚገልጸው አባቱ ካደረገው በተለየ መንገድ ኃጢአት መስራቱን ነው። "በራሱ መንገድ ኃጢአት አደረገ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በዚህም እስራኤልን ወደ ኃጢአት መራ
ሰዎች አንድ ነገር እንዲያደርጉ መምራት የሚገልጸው ያንን ነገር እንዲያደርጉ ሰዎች ላይ ተጽዕኖ ማሳደርን ነው። "ኃጢአት በመስራት እስራኤልም እንዲበድል ተጽዕኖ አሳደረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 15:27

በናዳብ ላይ አሴረ
"ንጉሥ ናዳብን ለመግደል በምስጢር አሴረ/ተንኮል ጠነሰሰ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ገባቶን
ይህ የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ናዳብ እና መላው እስራኤል
"መላው እስራኤል" የሚለው ሀረግ ከእስራኤል ወታደሮች አመዛኙን የሚወክል ነው። "ናዳብ እና በርካታው እስራኤል ወታደር" ወይም "ናዳብ እና የእስራኤል ሰራዊት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እናኩሸት እንደዚሁም አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

ገባቶንን ከበው ነበር
"ስለዚህም የገባቶን ሰዎች ለእነርሱ እጃቸውን እንዲሰጡ፣ ከተማይቱን ከበው ነበር"

በእርሱ ስፍራ ነገሠ
"በእርሱ ስፍራ" የሚለው ሀረግ ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ "በእርሱ ምትክ" ማለት ነው።" "በናዳብ ምትክ ንጉሥ ሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 15:29

ባኦስ የኢዮርብዓምን ቤተሰብ በሙሉ ገደለ። አንድም የኢዮርብዓምን ትውልድ እስትንፋስ አላስቀረም።
እነዚህ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ የተጣመሩት ትውልዶቹ መገደላቸውን ትኩረት ለመስጠት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መላው የኢዮርብዓም ቤተሰብ
ኢዮርብዓም የንጉሥ ናዳብ አባት ነበር።

ከኢዮርብዓም ቤተሰብ አንድም በእስትንፋስ አላስቀረም
እስትንፋስ የሚወክለው በህይወት መትረፍን ነው። "ከኢዮርብዓም ቤተሰብ አንዱንም በህይወት አላስቀረም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ የንግሥና መስር
"የኢዮርብዓም የንግሥና መስመር/ዘር ሀረግ"

ያህዌ ልክ በአገልጋዩ በሴሎናዊው በአኪያ እንደተናገረው
በ1 ነገሥት 14፡10-11 ላይ ያህዌ በነቢዩ አኪያ በኩል ቤተሰቡን እንደሚያጠፋ ለኢዮርብዓም ተናግሮታል።

ሴሎናዊው አኪያ
"ከሴሎና የሆነው፣ አኪያ"

ኢዮርብዓም ለፈጸማቸው ኃጢአቶች እና እስራኤልን ወደ ኃጢአት ለመምራቱ
"ኃጢአት" የሚለው ረቂቅ ስም በግሥ መልኩ ሊገለጽ ይችላል። "ኢዮርብዓም ኃጢአት በመፈጸሙ ምክንያት እና በተመሳሳይ መንገድ እስራኤልን ወደ ኃጢአት በመምራቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እስራኤልን ወደ ኃጢአት በመምራቱ
ሰዎችን አንድ ነገር እንዲያደርጉ መምራት የሚገልጸው አንድ ነገር እንዲፈጸሙ ተጽዕኖ ማሳደርን ነው። "እስራኤል ኃጢአት እንዲያደርግ ተጽዕኖ በማሳደሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 15:31

የይሁዳ ነገሥታት ስራዎች በተጻፈበት መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ አይደለምን?
ይህ ጥያቄ የዋለው አንባቢያን ስለ ናዳብ ያለው መረጃ በዚህ ሌሎች መጽሐፍት ውስጥ እንደሚገኝ ለማሳወቅ ወይም ለማስታወስ ነው። ይህ በ1ነገሥት 14:29 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። ቃለ ምልልሳዊው ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "እነዚህ ታሪኮች የይሁዳ ነገሥታት የፈጸሟቸው ድርጊቶች በተጻፉባቸው መጽሐፍት ውስጥ ተጽፈዋል።" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳ ነገሥታት ስራዎች በተጻፈበት መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ አይደለምን?
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንድ ሰው ይህንን የእስራኤል ነገሥታት ድርጊቶች በተጻፈበት መጽሐፍ ጽፎታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በዘመናቸው ሁሉ
ይህ የሚያመለክተው ንጉሥ ሆነው የገዙበትን ዘመን በሙሉ ነው። ይህ በ1 ነገሥት 15:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "በእስራኤል እና በይሁዳ በገዙባቸው ዘመናት ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

1 Kings 15:33

አያያዥ ሀሳብ፡
ይህ ምዕራፍ በ1 ነገሥት 15:27-28 ባለው ክፍል ባኦስ እንዴት እንደነገሠ ይናገራል። እነዚህ ቁጥሮች ባኦስ እንዴት የእስራኤል ንጉሥ መሆን እንደጀመረ መናገር ይጀምራሉ።

ቴርሳ
ይህ የከተማ ስም ነው። ይህ በ1 ነገሥት 14፡17 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።

በያህዌ እይታ ክፉ የሆነውን
የያህዌ እይታ የሚለው የሚወክለው የያህዌን ፍርድ ነው። "በያህዌ ፍርድ/ ሚዛን ክፉ የሆነውን" ወይም "ያህዌ ክፉ ብሎ የሚቆጥረውን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በኢዮርብዓም መንገድ ሄደ
እዚህ ስፍራ መሄድ የሚወክለው ድርጊትን ነው። "ኢዮርብዓም ያደረገውን ተመሳሳይ ነገር አደረገ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ ኃጢአት እስራኤልን ወደ በደል በመራበት
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች "የእርሱ" እና "እርሱ" የሚያመለክቱት 1)በኦስን ወይም 2)ኢዮርብዓምን ነው።

እስራኤልን ወደ ኃጢአት በመምራቱ
ሰዎችን አንድ ነገር እንዲያደርጉ መምራት የሚገልጸው አንድ ነገር እንዲፈጸሙ ተጽዕኖ ማሳደርን ነው። "እስራኤል ኃጢአት እንዲያደርግ ተጽዕኖ በማሳደሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 16

1 በሐናኒ ልጅ በነቢዩ ኢዩ አማካይነት እግዚአብሔር ስለ ባኦስ የተናገረው ቃል እንዲህ ሲል መጣ፦ 2 እኔ ግን ከትቢያ አንሥቼ የሕዝቤ የእስራኤል መሪ
እንድትሆን ከፍ ከፍ አደረግሁህ፤ ታዲያ አንተ እንደ ኢዮርብዓም ኃጢአት ሠራህ፤ ሕዝቤንም ወደ ኃጢአት መራህ፤ የኃጢአታቸውም ብዛት የእኔን ቁጣ
አነሣሥቶአል። 3 ስለዚህ ኢዮርብዓምን እንዳሰወገድኩ አንተንና ቤተ ሰብህንም አስወግዳለሁ። 4 በከተማይቱ ውስጥ የሚሞተውን ማንኛውንም የባኦስ ቤተ ሰብ
ውሾች ይበሉታል፤ በሜዳ ላይ የሚሞተውንም የሰማይ አሞራዎች ይበሉታል። 5 ባኦስ ያደረገው ሌላው ነገርና የጀግንነት ሥራዎቹም ሁሉ በእስራኤል ነገሥታት
የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኝ የለምን? 6 ባኦስም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ በቲርጻም ተቀበረ። በእርሱም ፈንታ ተተክቶ ልጁ ኤላ ነገሠ። 7 እግዚአብሔር
በነቢዩ ኢዩ አማካይነት በባኦስና በቤተ ሰቡ ላይ የትንቢት ቃል የተናገረው፣ ባኦስ በፈጸመው ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት ክፉ በማድረጉ ነበር። ባኦስ
እግዚአብሔርን ያስቆጣውም ከእርሱ ፊት የነበረው ንጉሥ ባደረገው ዓይነት ስለ ሠራው ክፉ ነገር ብቻ ሳይሆን የኢዮርብዓምንም ቤተ ሰብ ሁሉ በመግደሉ
ጭምር ነበር። 8 አሳ በይሁዳ በነገሠ በሃያ ስድስተኛው ዓመት የባኦስ ልጅ ኤላ በእስራኤል መንገሥ ጀመረ። በቲርጻም ሁለት ዓመት ገዛ። 9 የሠረገላዎቹ
እኩሌታ ኃላፊ የሆነ ዚምሪ ከጦር መኮንኖቹ አንዱ በንጉሡ ላይ ዐደመ። ኤላም በቲርጻ ከተማ የቤተ መንግሥቱ ኃላፊ በሆነው አርጻ ተብሎ በሚጠራው ባለሟሉ
ቤት ብዙ መጠጥ ጠጥቶ ሰክሮ ነበር። 10 በዚህ ጊዜ ዚምሪ ወደዚያ ቤት ገብቶ ኤላን ገደለው፤ እርሱም በኤላ ፈንታ የይሁዳ ንጉሥ አሳ በነገሠ በሃያ
ሰባተኛው ዓመት ተተክቶ ነገሠ። 11 ዘምሪም በዙፋን ላይ እንደተቀመጠ ወዲያውኑ የባኦስ ቤተ ሰብ አባላት የሆኑትን በሙሉ ገደለ፤ የባኦስ ዘመድና ወዳጅ
የሆነውን ወንድ አንድ እንኳ ሳይቀር ሁሉንም በሞት ቀጣ። 12 እግዚአብሔር ነቢዩ በኢዩ አማካይነት በባኦስ ላይ በተናገረው ትንቢት መሠረት ዚምሪ የባኦስን ቤተ
ሰብ በሙሉ ፈጀ። 13 ይህም የሆነበት ምክንያት ባኦስና ልጁ ኤላ ጣዖት በማምለካቸውና የእስራኤልን ሕዝብ ወደ ኃጢአት በመምራታቸው፣ የእስራኤልንም
አምላክ የእግዚአብሔርን ቁጣ በማነሣሣታቸው ነው። 14 ኤላ ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ በእስራኤል ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኝ የለምን? 15
አሳ በይሁዳ በነገሠ በሃያ ሰባተኛው ዓመት ዚምሪ በቲርጻ ለሰባት ቀኖች ብቻ በእስራኤል ላይ ነገሠ። በዚያን ጊዜ የአስራኤል ወታደሮች በፍልስጥኤም
የምትገኘውን የገባቶንን ከተማ ከበው ነበር። 16 ዘምሪ ዐምፆ ንጉሡን መግደሉን በሰሙ ጊዜ በዚያው እንዳሉ ወዲያውኑ የጦር አዛዥ የነበረውን ዖምሪን አነገሡ።
17 ዖምሪና ወታደሮቹ የገባቶንን ከበባ አቆሙ፤ ከዚያም ገሥግሠው ሄደው ቲርጻን ከበቡ። 18 ዘምሪ ከተማይቱ እንደተያዘች ባየ ጊዜ በቤተ መንግሥቱ ውስጠኛ
ክፍል ወዳለው ምሽግ ውስጥ ገብቶ በቤተ መንግሥቱ ላይ እሳት ለቀቀበት፤ እርሱም በእሳት ነበልባል ተቃጥሎ ሞተ። 19 ይህ የሆነው እርሱ በሠራው
ኃጢአትና እስራኤልንም ወደ ኃጢአት በመምራቱ ምክንያት ከእርሱ በፊት እንደ ነበረው እንደ ኢዮርብዓም እግዚአብሔርን ስላስቆጣው ነው። 20 ዘምሪ የሠራው
ሌላው ነገር ሁሉና ያደረገውም ሤራ ጭምር በእስራኤል ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ የሚገኝ አይደለምን? 21 በዚያን ጊዜ የእስራኤል ሕዝብ ከሁለት
ተከፍለው ነበር። ከዚህም የተነሣ አንደኛው ክፍል ታምኒን ተብሎ የሚጠራውን የጎናትን ልጅ ለማንገሥ ሲፈልግ ሌላው ክፍል ደግም ዖምሪን ለመደገፍ ይፈልግ
ነበር። 22 ነገር ግን የዖምሪ ተከታዮች ከጎናት ልጅ ታምኒን ይልቅ ጠንካራ ነበሩ። ስለዚህም ታምኒን ተገደለ፤ ዖምሪም ንጉሥ ሆነ። 23 በዚህ ዓይነት አሳ በይህዳ
በነገሠ በሠላሳ አንደኛው ዓመት ዖምሪ በእስራኤል ላይ ነግሦ ዐሥራ ሁለት ዓመት ገዛ። የመጀመሪያዎቹን ስድስት ዓመቶች የገዛውም መቀመጫውን በቲርጻ
አድርጎ ነበር። 24 ከዚያም በኋላ ሳምር ተብሎ ከሚጠራው ሰው የሰማርያ ኮረብታን በስድስት ሺህ ጥሬ ብር ገዛው። ዖምሪ በኮረብታው ላይ ከተማ ቆረቆረ፤
ከተማይቱንም ቀድሞ የኮረብታው ባለንብረት በሆነው በሳምር ስም ሰማርያ ብሎ ሰየማት። 25 ዖምሪ ከእርሱ በፊት ከነበሩት ነገሥታት ይበልጥ የከፋ ኅጢአት
በመሥራቱ እግዚአብሔርን አሳዘነ። 26 እርሱ በሠራው ኃጢአትና አስራኤልን ወደ ኃጢአት በመምራት ዋጋ ወደሌላው ጣዖት አምልኮ መምራቱ ከእርሱ በፊት
እንደ ነበረው እንደ ኢዮርብዓም የእስራኤልን አምላክ የእግዚአብሔርን ቁጣ አነሣሣ። 27 ዖምሪ ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉና ያከናወነውም ሁሉ በእስራኤል
ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኝ የለምን? 28 ዖምሪም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ በሰማርያም ተቀበረ፤ በእርሱም ፈንታ ተተክቶ ልጁ አክዓብ ነገሠ። 29
የይሁዳ ንጉሥ አሳ በነገሠ በሠላሳ ስምንተኛው ዓመት የዖምሪ ልጅ አክዓብ በእስራኤል ነገሠ። የዖምሪ ልጅ አክዓብ በሰማርያ ሃያ ሁለት ዓመት ነገሠ፤ 30
የዖምሪ ልጅ አክዓብ ከእርሱ በፊት ከነበሩት ሁሉ የባሰ ክፉ ነገር በያህዌ ፊት አደረገ። 31 አክዓብ ንጉሥ ኢዮርብዓም የሠራውን ኅጢአት እንደ ቀላል ነገር አድርጎ
በመቁጠር እርሱም ራሱ ያንኑ ኃጢአት ሠራ፤ ከዚህም ሁሉ አልፎ የሲዶና ንጉሥ የኤትበዓል ልጅ የሆነችውን አረማዊቷን ኤልዛቤልን አገባ፤ ባዓል ተብሎ
የሚጠራውንም ጣዖት አመለከ፤ ሰገደለትም። 32 በሰማርያ ለባዓል ቤተ መቅደስ አሠርቶ መሠዊያ ሠራለት። 33 አሼራ ተብላ የምትጠራውንም የሴት አምላክ
ምስል አቆመ፤ ከእርሱ በፊት ከነበሩትም የእስራኤል ነገሥታት ሁሉ ይበልጥ የእስራኤልን አምላክ የእግዚአብሔርን ቁጣ የሚያነሣሣ ኃጢአት ሠራ። 34
በአክዓብ ዘመነ መንግሥት አኪኤል ተብሎ የሚጠራ የቤቴል ተወላጅ ኢያሪኮን መልሶ ሠራ፤ እግዚአብሔር በነዌ ልጅ በኢያሱ አማካይነት አስቀድሞ በተናገረው
ቃል መሠረት አኪኤል የኢያሪኮን የመሠረት ድንጋይ በሚያኖርበት ጊዜ በነዌም ልጅ በኢያሱ እንደ ተነገረው እንደ እግዚብሔር ቃል፣ የበኩር ልጁ አቢሮን
ሞተበት፤ የቅጥርዋንም በሮች በሚሠራበት ጊዜ ታናሹ ልጁ ሠጉብ ሞተ።

---

1 Kings 16:1

የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል መጣ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር እግዚአብሔር ተናገረ ማለት ነው። ይህ በ1 ነገሥት 6፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ እንዲህ ሲል መልዕክቱን ሰጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ምንም እንኳን እኔ አንተን ከፍ ባደርግህም
ይህ እግዚአብሔር ለባኦስ ይነግረው ዘንድ ለኢዩ የሰጠው መልዕክት ነው። "አንተ" የሚለው ቃል ባኦስን ያመለክታል።

ከአፈር ላይ ከፍ አደረግሁህ
"ከአፈር ላይ አነሳሁህ።" መሬት አፈር ላይ መቀመጥ የሚገልጸው ጥቅም የሌለው መሆንን ነው። አንድን ሰው ከፍ ከፍ ማድረግ የሚገልጸው ሰውየውን ጠቃሚ ማድረግን ነው። "ጥቅም ከማይሰጥ ስፍራ አነሳሁህ" ወይም "ምንም ሀይል ወይም በሰዎች ላይ ተጽዕኖ ማሳደር በማትችልበት ጊዜ አንስቼ ጠቃሚ አደረግሁህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በኢዮርብዓም መንገድ ሄድክ
መሄድ የሚወክለው ማድረግን ነው። ኢዮርብዓም እና ባኦስ ሁለቱም ኃጢአት ሰርተዋል። የዚህ ሀሳብ ሙሉ ትርጉም ይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ኢዮርብዓም ያደረገውን ተመሳሳይ ነገር አንተም አደረግህ" ወይም "ኢዮርብዓም እንደበደለ/ኃጢአት እንደ ሰራ አንተም በደልክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Kings 16:3

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለባኦስ በእርሱ ላይ የሚያደርሰውን መንገሩን ቀጥሏል።

እነሆ፣ ባኦስን እና ቤተሰቡን እኔ ሙሉ ለሙሉ ጠራርጌ አጠፋለሁ
ያህዌ ለባኦስ እየተናገረ ነው፤ "የእርሱ ቤተሰብ" የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው የባኦስን ቤተሰብ ነው። ይህ "አንተ" እና "የአንተ" የሚሉትን ቃላት በመጠቀም ሊተረጎም ይችላል። "ባኦስ ሆይ፣ አድምጥ። እኔ ሙሉ ለሙሉ አንተን እና የአንተን ቤተሰብ ጠርጌ አጠፋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ሙሉ ለሙሉ ጠርጌ አጠፋለሁ
ጠራርጎ ማጥፋት የሚገልጸው መደምሰስን ነው። "እኔ ሙሉ ለሙሉ አጠፋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 16:5

የእስራኤል ነገሥታት ስራዎች በተጻፈበት መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ አይደለምን?
ይህ ጥያቄ የዋለው አንባቢያን ስለ ባኦስ ያለው መረጃ በዚህ ሌሎች መጽሐፍት ውስጥ እንደሚገኝ ለማሳወቅ ወይም ለማስታወስ ነው። ይህ በ1ነገሥት 15:31 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። ቃለ ምልልሳዊው ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "እነዚህ ታሪኮች የእስራኤል ነገሥታት የፈጸሟቸው ድርጊቶች በተጻፉባቸው መጽሐፍት ውስጥ ተጽፈዋል።" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ

የእስራኤል ነገሥታት ስራዎች በተጻፈበት መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ አይደለም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንድ ሰው ይህንን የእስራኤል ነገሥታት ድርጊቶች በተጻፈበት መጽሐፍ ጽፎታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ባኦስ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ/ተኛ
እዚህ ስፍራ መተኛት ሞትን የሚወክል ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት/ ነው። "ባኦስ እንደ አባቶቹ ሁሉ ሞተ" ወይም "እንደ አባቶቹ ሁሉ ባኦስ ሞተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚሉትን ይመልከቱ)

ተቀበረ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች እርሱን ቀበሩት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ቴርሳ
ይህ የከተማ ስም ነው። ይህ በ1 ነገሥት 14:17 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።

በእርሱ ስፍራ ነገሠ
"በእርሱ ስፍራ" የሚለው ሀረግ ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ "በእርሱ ምትክ" ማለት ነው።" "በባኦስ ምትክ ንጉሥ ሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 16:7

የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል መጣ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለህዝቡ አዲስ ነገርን ለማስተዋወቅ የሚውል ነው። ይህ በ1 ነገሥት 6:11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህን መልዕክት ተናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በያህዌ እይታ ሲታይ እርሱ ያደረገውን ክፉ የሆነውን ሁሉ
የያህዌ እይታ የሚለው የሚወክለው የያህዌን ፍርድ ነው። "ባኦስ ያደረገው በያህዌ ፍርድ/ሚዛን ክፉ የሆነውን" ወይም "ባኦስ ያደረገውን ያህዌ ክፉ ብሎ የሚቆጥረውን ነገር ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ እንዲቆጣ ለማነሳሳት
"ቁጣ" የሚለው ረቂቅ ስም "መቆጣት" በሚለው ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። "ያህዌ በጣም እንዲቆጣ የሚያደርግ" ወይም "እግዚአብሔርን በጣም የሚያስቆጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በእጆቹ ስራ
እዚህ ስፍራ ባኦስ የተወከለው በ"እጆቹ" ነው። ይህ የሚናገረው ድርጊቶቹን ሁሉ እንደ እርሱ "ስራ" አድርጎ ነው። "ባኦስ ባደረጋቸው ነገሮች" (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 16:8

ቴርሳ
ይህ የከተማ ስም ነው። ይህ በ1 ነገሥት 14:17 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።

የእርሱ አገላጋይ ዘምሪ
"የኤላ አገልጋይ ዘምሪ"

የገሙሱ የእርሱ ሰረገሎች አዛዥ
እዚህ ስፍራ "ሰረገላ" የሚለው ቃል የሚወክለው ሰረገሎቹን የሚነዱትን ወታደሮች ነው። "የእርሱ ገሚሶቹ ሰረገሎች ነጂዎች አዛዦች" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ራሱ መጠጥ ጠጥቶ ነበር
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ብዙ ወይን መጠጣት እንዲሰክር አድርጎት ነበር" ወይም "ሰክሮ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በቤቱ ላይ የበላይ የነበረው
በቤቱ ላይ የበላይ መሆን በንጉሥ ኤላ ቤት ሃላፊ መሆንን ያመለክታል። "በኤላ ቤት ባሉ ነገሮች ላይ ሃላፊ የነበረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አጥቅቶ ገደለው
"ኤላን አጥቅቶ ገደለው"

በእርሱ ስፍራ ንጉሥ ሆነ
"በእርሱ ስፍራ" የሚለው ሀረግ ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ "በእርሱ ምትክ" ማለት ነው። "በኤላ ምትክ ነገሠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 16:11

አንድም ወንድ በህይወት አልተወም
ይህ ማለት ሁሉንም አዋቂ ወንዶች እና ወንድ ልጆች ገድሏል ማለት ነው። "አንድ እንኳን ወንድ በህይወት አልተወም"

የያህዌ ቃል
"ከያህዌ ዘንድ የመጣ መልዕክት" ወይም "የያህዌ መልዕክት"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በነቢዩ በኢዩ በኩል በባኦስ ላይ እርሱ የተናገረው
"በ" ነቢይ መናገር የሚወክለው ለአንድ ነቢይ መንገር እና ነቢዩ ሲናገር ማለት ነው። "በባኦስ ላይ እንዲናገር ያህዌ ለነቢዩ ለኢዩ የነገረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ እስራኤልን ወደ ኃጢአት መሩ
ሰዎችን አንድ ነገር እንዲያደርጉ መምራት የሚገልጸው አንድ ነገር እንዲፈጸሙ ተጽዕኖ ማሳደርን ነው። "እስራኤል ኃጢአት እንዲያደርግ ተጽዕኖ አሳደሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ እስራኤልን ወደ ኃጢአት መሩ
"እስራኤል" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ለአስሩ ሰሜናዊ የእስራኤል ነገዶች ነው። ባኦስ እና ኤላ የእነርሱ ንጉሦች ነበሩ።

የእስራኤልን አምላክ፣ ያህዌን በጣኦቶቻቸው አስቆጡት
እግዚአብሔር ህዝቡን የተቆጣው ጣኦቶችን ስላመለኩ ነው። የዚህ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ጣኦቶችን በማምለካቸው ምክንያት የእስራኤልን አምላክ ያህዌን አስቆጡት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል አምላክ
እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የያዕቆብ ትውልድ የሆኑትን አስራ ሁለቱንም ነገዶች በአጠቃላይ ነው።

1 Kings 16:14

የእስራኤል ንጉሦች...እነርሱ አልተጻፉምን?
ይህ ጥያቄ የዋለው በዚህ ሌላ መጽሐፍ ስለ ኤላ መረጃ እንዳለ ለአንባቢው መረጃ ለመስጠት ወይም ለማስታወስ ነው። ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል፤ ይህ በ1 ነገሥት 15:31 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "የእስራኤል ነገሥታት በፈጸሟቸው ድርጊቶች መጽሐፍ ውስጥ እነዚህ ተጽፈዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በእስራኤል... አልተጻፉምን?
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንድ ሰው ስለ እነርሱ በእስራኤል ነገስታት ድርጊቶች መጽሐፍ ጽፏል።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 16:15

ቴርሳ
ይህ የከተማ ስም ነው። ይህ በ1 ነገሥት 14፡17 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ

ሰራዊቱ በገባቶን ሰፍሮ ነበር
"ሰራዊት" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእስራኤልን መንግስት ሰራዊት ነው።

ገባቶን
ይህ የከተማ ስም ነው።ይህ በ1 ነገሥት 15:27 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመለከቱ።

በዚያ የሰፈረው ሰራዊት እንዲህ ሲሉ ሰማ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በዚያ የሰፈሩት ወታደሮች እንዲህ ሲናገሩ ሰሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

መላው እስራኤል
በሁለቱም ጊዜያት ይህ ሀረግ አገልግሏል፣ ይህም የሚወክለው የእስራኤልን ሰራዊት ነው። "ሁሉም" የሚለው ቃል ትርጉም "ብዙዎቹ" የሚል ማጠቃለያ ነው። "መላው የእስራኤል ሰራዊት" ወይም "በእስራኤል ሰራዊት ውስጥ አብዛኛው ወታደር" ወይም "የእስራኤል ሰራዊት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ኩሸት እንሰዚሁም አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

1 Kings 16:18

ከተማይቱ ተወስዳ/ተይዛ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ይኸውም ዖምሪ እና ሰራዊቱ ከተማይቱን ያዟት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በያህዌ ፊት ክፉ የነበረውን
የያህዌ እይታ የሚለው የሚወክለው የያህዌን ፍርድ ነው። "በያህዌ ፍርድ/ ሚዛን ክፉ የሆነውን" ወይም "ያህዌ ክፉ ብሎ የሚቆጥረውን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በኢዮርብዓም መንገድ መሄድ
መሄድ የሚወክለው ማድረግን ነው። "ኢዮርብዓም ያደረገውን ተመሳሳይ ነገር አንተም አደረግህ" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እስራኤልን ወደ ኃጢአት መምራት
ሰዎች አንድ ነገር እንዲያደርጉ መምራት የሚገልጸው አንድ ነገር እንዲፈጸሙ ተጽዕኖ ማሳደርን ነው። "እስራኤል ኃጢአት እንዲያደርግ ተጽዕኖ ማሳደር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ የፈጸመው ክህደት
ክህደቱ የሚያመለክተው ዘምሪ የእስራኤልን ንጉሥ ኤላን ለመግደል ያደረገውን ሴራ ነው። የዚህ ሀሳብ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "በንጉሥ ኤላ እንዴት ሴራ ፈጸመ" ወይም "የእስራኤልን ንጉሥ እንዴት እንደ ገደለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ነገሥታት ስራዎች በተጻፈበት መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ አይደለምን?
ይህ ጥያቄ የዋለው አንባቢያን ስለ ዘምሪ ያለው መረጃ በዚህ ሌሎች መጽሐፍት ውስጥ እንደሚገኝ ለማሳወቅ ወይም ለማስታወስ ነው። ይህ በ1ነገሥት 14:29 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። ቃለ ምልልሳዊው ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "እነዚህ ታሪኮች የእስራኤል ነገሥታት የፈጸሟቸው ድርጊቶች በተጻፉባቸው መጽሐፍት ውስጥ ተጽፈዋል።" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በእስራኤል ነገሥታት ...የተጻፈ አይደለምን?
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንድ ሰው ይህንን የእስራኤል ነገሥታት ድርጊቶች በተጻፈበት መጽሐፍ ጽፎታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 16:21

ታምኒንን ተከትሎ...ዖምሪን ተከትሎ
እዚህ ስፍራ "መከተል" የሚወክለው እርሱን መደገፍ ወይም ንጉሥ ለማድረግ መፈለግን ነው። "እርሱን ለማንገስ፣ የጎናትን ልጅ ታምኒን መደገፍ፣ እንደዚሁም እኩል ድጋፍ ለዖምሪ ማድረግ" ወይም "የጎናትን ልጅ ታምኒን ለማንገሥ መፈለግ፣ እና ገሚሱ ዖምሪን ለማንገሥ መፈለጉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ታምኒን ከሚከተሉ ሰዎች ይልቅ ጠንካሮች ነበሩ
"ታምኒን የተከተሉትን ሰዎች አሸነፈ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Kings 16:23

ቴርሳ
ይህ የከተማ ስም ነው። ይህ በ1 ነገሥት 14፡17 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ፡

ሳምር
ይህ የሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሁለት መክሊት/ታላንት ብር
ይህንን ወደ ዘመናዊ መለኪያ መለወጥ ይችላሉ። "ወደ 66 ኪሎ ግራም የሚጠጋ ብር" (መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት ወቅት የክብደት መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ከተማ ሰራ/ገነባ
"እርሱ" የሚለው ቃል ዖምሪን ያመለክታል። ሰዎቹ ከተማ እንደሚመሰርቱ አዘዘ። "ዖምሪ ህዝቡ ከተማ እንዲገነባ አደረገ" ወይም "በዖምሪ ትዕዛዝ ህዝቡ ከተማ ገነባ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ

በሳምር ስም
ይህ ፈሊጥ ሲሆን "ሳምርን ለማክበር" ወይም "ህዝቡ ሳምርን ያስታውሰው ዘንድ" የሚል ትርጉም አለው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 16:25

በያህዌ ፊት ክፉ የነበረውን
የያህዌ እይታ የሚለው የሚወክለው የያህዌን ፍርድ ነው። "በያህዌ ፍርድ/ሚዛን ክፉ የሆነውን" ወይም "ያህዌ ክፉ ብሎ የሚቆጥረውን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም በሄደበት መንገድ ሁሉ ሄደ
መሄድ የሚወክለው ማድረግን ነው። "የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም ያደረገውን ተመሳሳይ ነገር አደረገ" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እስራኤልን ወደ ኃጢአት በመራበት በእርሱ ኃጢአት
"የእርሱ" ወይም "እርሱ" የሚለው ለሚያመለክተው ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1)ባኦስ ወይም 2)ኢዮርብዓም

በእርሱ በደሎች
በኃጢአት መመላለስ ለሚለው ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1)ኢዮርብዓም እንደ በደለ መበደል። "እርሱ ኢዮርብዓም እንደ በደለ በድሏል" ወይም 2) ኃጢአትን ልምድ አድርጎ መያዝ/መፈጸም። "እርሱ ዘወትር ይበድላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እስራኤልን ወደ ኃጢአት በመራበት
ሰዎች ኃጢአት እንዲሰሩ መምራት የሚገልጸው ኃጢአት እንዲፈጸሙ ተጽዕኖ ማሳደርን ነው። "እስራኤል ኃጢአት እንዲያደርግ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ የእርሱ በደሎች" ወይም "እንዲህ ባለ ሁኔታ ኃጢአት በመፈጸም ሰዎች ኃጢአት እንዲሰሩ ተጽዕኖ አሳድሯል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እርባና ቢስ በሆኑ ጣኦቶቻቸው... ያህዌን ለቁጣ ማነሳሳት
እግዚአብሔር ህዝቡን የተቆጣው ጣኦቶችን ስላመለኩ ነው። ተመሳሳይ የሆነው ሀረግ በ1 ነገሥት 16:13 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እርባና ቢስ የሆኑ ጣኦቶችን በማምለክ ምክንያት የእስራኤልን አምላክ ያህዌን ማስቆጣት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እርባና ቢስ የሆኑ ጣኦቶቻቸው
እዚህ ስፍራ "እርባና ቢስ/ጥቅም የለሽ" የሚለው ቃል ጣኦቶች አንዳች ነገር ማድረግ እንደማይችሉ ሰዎችን ያሳስባል/ያስታውሳል። "እርባና ቢስ የሆኑ፣ ጣኦቶቻቸው" ወይም "ምንም ጥቅም የሌላቸው ጣኦቶቻቸው" (መለየትን ከመረጃ መስጠት ወይም ማስታወስ ጋር ማስተያየት የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል አምላክ
እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የያዕቆብ ትውልዶች የሆኑትን አስራ ሁለቱን ነገዶች በሙሉ ነው።

1 Kings 16:27

የእስራኤል ነገሥታት ስራዎች በተጻፈበት መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ አይደለምን?
ይህ ጥያቄ የዋለው አንባቢያን ስለ ዖምሪ ያለው መረጃ በዚህ ሌሎች መጽሐፍት ውስጥ እንደሚገኝ ለማሳወቅ ወይም ለማስታወስ ነው። ይህ ቃለ ምልልሳዊው ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። ይህ በ1 ነገሥት 15:31 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እነዚህ ታሪኮች የእስራኤል ነገሥታት የፈጸሟቸው ድርጊቶች በተጻፉባቸው መጽሐፍት ውስጥ ተጽፈዋል።" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በእስራኤል ነገሥታት ...የተጻፈ አይደለምን?
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንድ ሰው ይህንን የእስራኤል ነገሥታት ድርጊቶች በተጻፈበት መጽሐፍ ጽፎታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ዖምሪ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ/ተኛ
እዚህ ስፍራ መተኛት ሞትን የሚወክል ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት/ ነው። "ዖምሪ እንደ አባቶቹ ሁሉ ሞተ" ወይም "እንደ አባቶቹ ሁሉ ዖምሪ ሞተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚሉትን ይመልከቱ)

በእርሱ ስፍራ ነገሠ
"በእርሱ ስፍራ" የሚለው ሀረግ ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ "በእርሱ ምትክ" ማለት ነው።" "በዖምሪ ምትክ ንጉሥ ሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 16:29

በያህዌ ፊት ክፉ የነበረውን
የያህዌ እይታ የሚለው የሚወክለው የያህዌን ፍርድ ነው። "በያህዌ ፍርድ/ሚዛን ክፉ የሆነውን" ወይም "ያህዌ ክፉ ብሎ የሚቆጥረውን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 16:31

በናባጥ ልጅ በኢዮርብዓም መንገድ መሄድን እና ኃጢአት መስራትን አክአብ እንደ ቀላል ነገር ቆጥሮት ነበር
ይህ አክአብ የከፋ ኃጢአት መስራትን ፈልጎ እንደነበር ያሳያል። የዚህ ሀሳብ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "አክአብ በናባጥ ልጅ በኢዮርብዓም ኃጢአት መሄድን እንደ ቀላል ነገር ቆጥሮት ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለአክአብ ይህ ጥቂት/ እዚህ ግባ የማይባል ነገር ነበር
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ለአክአብ" የሚለው ሀረግ አክአብ አንድ ነገር አስቦ ቀይም ተመልክቶ ነበር ማለት ነው። "አክአብ ይህ ተራ ነገር አድርጎ ተመልክቶት ነበር" ወይም "አክአብ ይህ ኃጢአት ትንሽ እንደሆነ አስቦ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር ሚለውን ይመልከቱ)

የማይረባ ነገር
"ጥቂት እንደሆነ ነገር" ወይም "በቂ እንዳልሆነ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በናባጥ ልጅ በኢዮርብዓም ኃጢአት መሄድ
በኢዮርብዓም ኃጢአት መሄድ የሚወክለው ኢዮርብዓም እንደ ሰራው ኃጢአት መስራትን ነው። "የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም እንደ በደለ መበደል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በዓልን ማምለክ እና ለእርሱ መስገድ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። "ለእርሱ መስገድ" የሚለው ሀረግ የሚገልጸው ሰዎች በአምልኮ ጊዜ የሚኖራቸውን የአቋም ሁኔታ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል አምላክ
እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚለው ቃል የሚያመለክተው አስራ ሁለቱን የእስራኤል ነዶች በሙሉ ነው።

የእስራኤል ነገሥታት
እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚለው ቃል የሚያመለክተው አስሩን ነገዶች የሚይዘውን የእስራኤልን መንግስት ነው።

1 Kings 16:34

በበኩር ልጁ በኢብሮን የህይወት ዋጋ
ከተማይቱን መገንባት የሚያስከትለው ነገር የተገለጸው አኪኤል እንደሚከፍለው ዋጋ ተደርጎ ነው። "ኃጢአቱ ሚያስከትለው የበኩር ልጁ የኢብሮንን መሞት ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የመጨረሻ ልጁ ሠጉብ ህይወቱን ያጣል
ሞት የተገለጸው ህይወቱን በማጣት ነው። "የመጨረሻ ልጁ ሠጉብ፣ ሞተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የከተማይቱን መግቢያ በሮች ሲገነባ
"አኪኤል የከተማይቱን መግቢያ በር በሚገነባበት ጊዜ"

የያህዌን ቃል ይጠበቅ ዘንድ
"በያህዌ ቃል መሰረት"

የያህዌ ቃል
"ከያህዌ ዘንድ የመጣው መልዕክት" ወይም የያህዌ መልዕክት"

በነዌ ልጅ በኢያሱ የተናገረው
"በ" አንድ ሰው መናገር የሚወክለው እንዲናገር ለአንድ ሰው መንገርን እና ያንን የሚያደርገውን ሁለቱንም ሰዎች ነው። "ያህዌ እንዲናገር ያደረገው የነዌ ልጅ ኢያሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 17

1 በገለዓድ የምትገኘው ቴስቢያዊው ነቢዩ ኤልያስ ነጉሥ አክዓብን በእኔ ቃል ካልሆነ በቀር በሚቀጥሉት ዓመቶች በምድር ላይ ጠል ወይም ዝናብ እንደማይኖር እኔ በማገለግለው በእስራኤል አምላክ በሕያው እግዚአብሔር ስም እነግርሃለሁ አለው። **2** የእግዚአብሔር ቃል ወደ ኤልያስ እንዲህ ሲል መጣ፤ **3** ከዚህ ተነሥተህ ወደ ምሥራቅ ሂድ፤ እዚያም ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ በሚገኘው ኮራት ተብሎ በሚጠራው ሸለቆ ተሸሸግ። **4** የምትጠጣውንም ውሃ ከዚያው ወንዝ ታገኛለህ፤ ቁራዎችም ምግብ እንዲያመጡልህ አዝዣለሁ። **5** ኤልያስም እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት ሄዶ በኮራት ሸለቆ ተቀመጠ። **6** ከወንዙም ውሃ ጠጣ፤ ቁራዎችም ዘወትር ጧትና ማታ እንጀራና ሥጋ ያመጡለት ነበር። **7** ነገር ግን ዝናብ ጠፍቶ ድርቅ ከመሆኑ የተነሣ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ያ ወንዝ ደረቀ። **8** የእግዚአብሔርም ኤልያስን እንዲህ አለው፦ **9** እንግዲህ አሁን ከዚህ ተነሥተህ ሂድ፤ በሲዶና በምትገኘው በስራፕታ ከተማ ተቀመጥ፤ እነሆ በዚያ የምትኖር አንዲት መበለት እንድተመግብህ እዝዣለሁ አለው። **10** ስለዚህ ኤልያስ ወደ ሰራፕታ ሄደ፤ ወደ ከተማይቱም ቅጥር በር በደረሰ ጊዜ አንዲት ባልዋ የሞተባት ሴት እንጨት ስተለቅም አይቶ እባክሽ የምጠጣው ውሃ አምጪልኝ አላት። **11** ውሃም ልታመጣለት በመሄድ ላይ ሳለች ወዲያውኑ ጠርቶ እባክሽ በተጨማሪ ትንሽ እንጀራ አምጪልኝ አላት። **12** እርስዋም እንዲህ ስትል መለሰችለት፦ ምንም እንጀራ እንደሌለኝ በአምላክህ በሕያው እግዚአብሔር ስም እምላለሁ፤ በዱቄት ዕቃዬ ውስጥ ካለችው ከአንድ እፍኝ ዱቄትና በማሰሮዬ ውስጥ ካለችው ከጥቂት የወይራ ዘይት በቀር ምንም የለኝም፤ ወደዚህ የመጣሁት ትንሽ እንጨት ለቃቅሜ ቤቴ በመመለስ ይህችኑ ትንሽ ዱቄት ለእኔና ለልጄ ለመጋገር ነው፤ ይህችም የመጨረሻ ምግባችን ናት፤ ከዚያ በኋላ ይህችኑ በልተን እንሞታለን። **13** ኤልያስም እንዲህ አላት፣ አይዞሽ አትጨነቂ፤ ሄደሽ ምግብሽን አዘጋጂ፤ አስቀድመሽ ግን ከዚች ካለችሽ ዱቄት ለእኔ ትንሽ እንጎቻ ጋግረሽ አምጪልኝ፤ የቀረውንም ለራስሽና ለልጅሽ ጋግሪው። **14** የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እኔ እግዚአብሔር ዝናብን እስከማወርድ ድረስ ዱቄቱ ከማስቀመጫው ዕቃ፣ ዘይቱም ከማሰሮው ከቶ አያልቅም ሲል ተናግሮአል። **15** አርስዋም ሄዳ ኤልያስ እንደ ነገራት አደረገች፤ እርስዋ፣ ቤተ ሰብዋና ኤልያስ ለብዙ ቀን የሚሆን በቂ ምግብ አገኙ። **16** እግዚአብሔር በኤልያስ አማካይነት በሰጠው ተስፋ መሠረት ዱቄቱ ከማኖሪያው ዕቃ፣ ዘይቱም ከማሰሮው አላለቀም። **17** ከጥቂት ጊዜም በኋላ የዚያች ባልዋ የሞተባት ሴት ልጅ ታመመ፤ ሕመሙም እየባሰበት ስለ ሄደ በመጨረሻ ሞተ። **18** እርስዋም ኤልያስን የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፣ ስለምን ይህን አደረግህብኝ? ወደዚህ የመጣኸው ኃጢአቴን አስታውሰህ ልጄ እንዲሞትብኝ ለማድረግ ነውን? ስትል ጠየቀችው። **19** ኤልያስም ልጅሽን ወደ እኔ አምጪው አላት። ልጁንም ከዕቅፍዋ ወስዶ እርሱ ወደሚኖርበት ሰገነት አውጥቶ በአልጋው ላይ አጋደመው። **20** ከዚህ በኋላ ኤልያስ ድምፁን ከፍ በማድረግ እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ ስለምን በዚህች ባልዋ በሞተባት ሴት ላይ ይህን የመሰለ አሠቃቂ ነገር አደረግህ? እርስዋ እኔን በማስተናገድ ታላቅ ቸርነት አድርጋልኛለች፤ ታዲያ አንተ ስለምን ልጅዋ እንዲሞት አደረግህ ሲል ጸለየ። **21** ከዚህ በኋላ ኤልያስ በልጁ ላይ ሦስት ጊዜ ተዘርሮ እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፣ እባክህ ይህን ልጅ ከሞት አስነሣው ሲል ጸለየ። **22** እግዚአብሔርም የኤልያስን ጸሎት ሰማ፤ የልጁም እስትንፋስ እንደገና ተመልሶለት ዳነ። **23** ኤልያስም ልጁን ከሰገነት ወደ ምድር ቤት አውርዶ ለእናቱ ሰጣትና እነሆ ልጅሽ ከሞት ወደ ሕይወት ተመልሶአል! አላት። **24** እርስዋም እነሆ አንተ የእግዚአብሔር ሰው መሆንህንና እግዚአብሔርም በአንተ አማካይነት የተናገረው እውነት መሆኑን አሁን ዐወቅሁ! ስትል መለሰችለት።

---

1 Kings 17:1

ቴስብያዊ
ይህ ከቴስብያ የሆኑ ሰዎች የወል ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ቴስብ
ይህ በገለዓድ ግዛት የምተገኝ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል አምላክ ህያው እግዚአብሔርን
ይህ ሀረግ እርሱ የሚናገረው እውነት መሆኑን ትኩረት የሚሰጥ መሀላ ነው።

በፊቱ የቆምኩት
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን "ማገልገል" የሚል ትርጉም አለው። "እኔ የማገለግለው እርሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጤዛ
በምሽት ጊዜ በተክሎች ላይ የሚፈጠር የውሃ ጠብታዎች

1 Kings 17:2

የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል መጣ
የዚህ ፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉም እግዚአብሔር ይናገራል ማለት ነው። ይህ በ1 ነገሥት 6:11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ የእርሱን መልዕክት ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኮራት
ይህ በጣም ትንሽ የሆነ ወራጅ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህ ይሆናል
ይህ ሀረግ የዋለው ያህዌ በድርቅ ወቅት እንዴት ለኤልያስ እንክብካቤ እንደሚያደርግለት ለማስተዋወቅ ነው። "በዚያ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ቁራዎች
ትልቅ፣ ጥቁር ወፎች (የማይታወቁትን ነገሮች መተረጎም የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 17:5

የያህዌ ቃል እንደሚያዘው
እዚህ ስፍራ "ቃሉ" የሚለው የሚወክለው ያህዌን ራሱን ነው። "ያህዌ እንዳዘዘው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የኮራት ጅረት
ይህ በጣም ትንሽ የሆነ ወንዝ ስም ነው። ይህ በ1 ነገሥት 17:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በምድሪቱ
"በዚያ አካባቢ" ወይም "በዚያች አገር"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Kings 17:8

የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል መጣ
የዚህ ፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉም እግዚአብሔር ይናገራል ማለት ነው። ይህ በ1 ነገሥት 6፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ የእርሱን መልዕክት ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እርሱ መጣ
እዚህ ስፍራ "እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኤልያስን ነው።

ሰራፕታ
ይህ ከተማ ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ፣ እኔ
"ትኩረት ስጡ፣ ምክንያቱም እኔ፡ ቀጥሎ የምናገረው እውነተኛ እና ጠቃሚም ነገር ነው"

1 Kings 17:11

በህያው አምላክህ ስም
ይህ ሀረግ እርሷ የምትናገረው እውነት መሆኑን የሚያጎላ መሃላ ነው

አንድ እፍኝ ምግብ/አንዴ የሚበላ
"ትንሽ ምግብ"

ምግብ
"ዱቄት።" ይህ ዳቦ ለመጋገር/ለማዘጋጀት የሚያገለግል ነው።

እነሆ፣ እኔ
"እኔ፣ ምን እንደማደርግ ልንገርሽ"

ሁለት እንጨት
ይህ ሁለት እንጨቶች ወይም ጥቂት ጭራሮዎችን ሊያመለክት ይችላል። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ያለቺንን በልተን፣ ከዚያ እንሞታለን
ከዚያ ወዲያ ምንም የሚበሉት ምግብ ስለሌለ እንደሚሞቱ ተጠቁሟል። "ያቺን በልተን፣ ከዚያ በኋላ በረሃብ እንሞታለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያ በኋላ ለአንቺ እና ለልጅሽ አዘጋጂ
በውስጠ ታዋቂነት ተጨማሪ ዳቦ ለማዘጋጀት ዱቄት እና ዘይት እንደሚኖር ተነግሯል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 17:14

ያህዌ ዝናብ ላከ/ሰጠ
ይህ ፈሊጥ ሲሆን ያህዌ ዝናብ አዘነበ ማለት ነው። "ያህዌ ዝናብ አዘነበ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሷ እና ኤልያስ፣ ከባሏ ጋር፣ ለብዙ ቀን ተመገቡ
በመጀመሪያው በተጻፈበት ቋንቋ እንዲህ ይላል፣ "እናም እርሷ፣ እርሱ እና የእርሷ ባል ለብዙ ቀናት ተመገቡ።" "እርሱ" የተባለው ማን እንደሆነ ግልጽ አይደለም። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ኤልያስ፣ መበለቲቱ፣ እና የእርሷ ወንድ ልጅ ለብዙ ቀናት ተመገቡ ወይም 2) መበለቲቱ፣ እና በእርሷ ቤት የሚኖሩ ሁሉ ለብዙ ቀናት ተመገቡ።

ከቤተሰቧ ጋር
"ቤተሰብ" ለሚለው ሊሰጥ የሚችለው ትርጉም 1) ይህ የመበለቲቱን ወንድ ልጅ ብቻ ያመለክታል ወይም 2) ይህ በእርሷ ቤት የሚኖሩ ሌሎች ሰዎችን ሲያመለክት ነገር ግን እነማን እነደሆኑ በታሪኩ ውስጥ አልተጠቀሰም ወይም 3) ይህ የእርሷን ወንድ ልጅ እና በእርሷ ቤት የሚኖሩ ሌሎችን ያመለክታል

ልክ የያህዌ ቃል እንደተናገረው
እዚህ ስፍራ "ቃል" የሚወክለው ያህዌን ራሱን ነው። "ልክ ያህዌ እንደ ተናገረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 17:17

የቤቱ ባለቤት፣ የሴትየዋ ወንድ ልጅ
"የቤቱ ባለቤት የሆነችው ሴት ወንድ ልጅ"

በውስጡ የቀረ የህይወት እስትንፋስ አልነበረም
ይህ የልጁ መሞት ሻል ባለ ቋንቋ የተገለጸበት መንገድ ነው። "መተንፈስ አቁሞ ነበር" ወይም "ሞቶ ነበር" (ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ሰው
"የእግዚአብሔር ሰው" የሚለው ሀረግ የነቢይ ሌላው መጠሪያ ነው።

የቱ ኃጢአቴ
ይህ ማለት በአጠቃላይ የተሰራን ኃጢአት እንደጂ አንድ የተለየ ኃጢአትን አያመለክትም። "የትኖቹ ኃጢአቶቼ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ክፍለ ስማዊ ሀረጎች የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 17:19

እርሱ በነበረበት ስፍራ
እዚህ ቦታ "እርሱ" የሚለው የሚያመለክተው ኤልያስን ነው።

በገዛ ራሱ አልጋ ላይ
እዚህ ቦታ "የእርሱ" የሚለው የሚያመለክተው ኤልያስን ነው።

አንተም ደግሞ ተቀብላ የምታስተናግደኝ መበለት ላይ ልጇን በመግደል ጥፋትን ታመጣባታለህን?
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ኤልያስ በእውነት ጥያቄ እየጠየቀ ነው። "ተቀብላ የምታስተናግደኝን መበለት፣ ልጇን በመግደል ለምን ብዙ እንድትሰቃይ ታደርጋለህ" ወይም 2) ኤልያስ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት ምን ያህል እንዳዘነ ለመግለጽ ነው። "በእርግጥ፣ ተቀብላ የምታስተናግደኝን መበለት ልጇን በመግደል ይበልጥ እንድተሰቃይ አታደርግም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተም በመበለቲቱ ላይ ጥፋት ታመጣለህ
መበለቲቱ መሰቃየቷ የተገለጸው "ጥፋት" እንደ ዕቃ በእርሷ ላይ የተቀመጠ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ደግሞ ጥፋት ታመጣባታለህ
እዚህ ስፍራ "ደግሞ/በተጨማሪ" የሚለው ትርጉም ድርቅ ካደረሰባት ጥፋት በተጨማሪ ማለት ነው።

ራሱን በትንሹ ልጅ ላይ ዘረጋ
ይህ ፈሊጥ ነው። "በትንሹ ልጅ ላይ ተጋደመ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Kings 17:22

ያህዌ የኤልያስን ድምጽ ሰማ
እዚህ ስፍራ "ድምጽ" የሚወክለው ኤልያስ የጸሌውን ነው። "ያህዌ ለኤልያስ ጸሎት ምላሽ ሰጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የትንሹ ልጅ ህይወት ወደ እርሱ ተመለሰች፣ እናም ነቃ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። "ትንሹ ልጅ ዳግም ወደ ህይወት ተመለሰ" ወይም "ትንሹ ልጅ እንደገና ህያው ሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ ክፍል
እዚህ ስፍራ "የእርሱ" የሚለው የሚያመለክተው ኤልያስን ነው።

እነሆ፣ ልጅሽ በህይወት አለ
እዚህ ስፍራ "እነሆ" የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚሆነው አስደናቂ መረጃ ያነቃናል።

የያህዌ ቃል በአፍህ እውነት ነው
"በአፍህ ያለው የያህዌ መልዕክት እውነት ነው።" "አፍ" የሚለው ቃል የሚወክለው ኤልያስ የተናገረውን ነው። "ከያህዌ ዘንድ የተናገርከው መልዕክት እውነት ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 18

1 ከብዙ ጊዜ በኋላ በሦስተኛው ዓመት የእግዚአብሔር ቃል ወደ ኤልያስ እንዲህ ሲል መጣ፦ ሄደህ ራስህን ለንጉሥ አከዓብ ግለጥለት እኔም በምድር ላይ
ዝናብን አዘንባለሁ አለው። 2 ኤልያስም በታዘዘው መሠረት ወደ አከዓብ ሄደ፤ በዚህ ጊዜ በሰማርያ ረሃብ እጅግ ጸንቶ ነበር። 3 ስለዚህ ንጉሥ አክዓብ የቤተ
መንግሥቱ ኃላፊ የሆነውን አብድዩን ጠራው፤ አብድዩ እግዚአብሔርን የሚፈራ መንፈሳዊ ሰው ነበር። 4 ኤልዛቤል የእግዚአብሔርን ነቢያት ታስገድል በነበረበት
ጊዜ አብድዩ አንድ መቶ የሚሆኑትን የእግዚአብሔርን ነቢያት ከሁለት ከፍሎ ጎምሳ ጎምሳውን በዋሻዎች ከሸሸጋቸው በኋላ እህልና ውሃ በማቅረብ መግቦአቸው
ነበር። 5 አከዓብ አብድዩን ፈረሶችንና በቅሎዎችን ከሞት የምናድንበት በቂ ሣር እናገኝ እንደሆን በምድሪቱ ወደሚገኘው ምንጭና ወንዝ እስቲ ሂድና እይ።
ምናልባት እንስሳትን ከሞት ማዳን እንችል ይሆናል አለው። 6 እያንዳንዳቸው በአገሪቱ ወደየትኛው ክፍል ሄደው መፈለግ እንዳባቸው ከተስማሙ በኋላ አከዓብና
አብድዩ ለየብቻቸው በሁለት አቅጣጫ ተሰማሩ። 7 አብድዩ በሚሄድበት መንገድ ላይ ሳለ በድንገት ኤልያስን አገኘው፤ ኤልያስ መሆኑንም ስላወቀ በግንባሩ ወደ
መሬት ለጥ ብሎ እጅ ከነሣው በኋላ ጌታዬ ኤልያስ በእውነት አንተ ነህን? ሲል ጠየቀው። 8 ኤልያስም አዎን እኔ ነኝ፤ እዚህ መሆኔን ሄደህ ለጌታህ ንገረው ሲል
መለሰለት። 9 አብድዩም እንዲህ አለው፤ ንጉሥ አክዓብ እኔን ባሪያህን ይገድለኝ ዘንድ በእጁ አሳልፈህ የምትሰጠኝ ምን በደል ሠርቼ ነው? 10 ንጉሡ አንተን
ለማግኘት ፈልጎ በዓለም ላይ መልእክተኛ ያልላከበት አገር እንደሌለ በአምላክህ በሕያው እግዚአብሔር ስም እምላለሁ፤ የአንድ አገር መሪ አንተ በአገሩ ውስጥ
አለመኖርህን ለንጉሥ አክዓብ በመሐላ እያረጋገጠለት ቆይቶአል። 11 አሁን አንተ ግን ኤልያስ ተገኝቶአል ብለህ ለጌታህ ንገር ትለኛለህ። 12 እኔ ከዚህ እንደ
ሄድኩ ወዲያውኑ የእግዚአብሔር መንፈስ አንተን ወዳልታወቀ ቦታ ቢወስድህ እኔ ምን ይበጀኛል? አንተ በዚህ ቦታ መኖርህን ለአከዓብ ነግሬው ሳያገኝህ ቢቀር
እኔን በሞት ይቀጣኛል፤ ከልጅነቴ ጀምሬ እግዚአብሔርን የምፈራ ሰው መሆኔን አስታውስ። 13 ደግሞስ ኤልዛቤል የእግዚአብሔርን ነቢያት ስታስገድል
በነበረችበት ጊዜ አንድ መቶ የሚሆኑትን ነቢያት ከሁለት በመክፈል ጎምሳ ጎምሳውን በዋሻ ውስጥ ሸሽጌ እህልና ውሃ በማቅረብ ስመግባቸው መኖሬን
አልሰማህምን? 14 ታዲያ፣ አሁን አንተ እዚህ መሆንህን ሄደህ ለንጉሥ አክአብ ንገር ትለኛለህን? ይህን ባደርግ ንጉሡ ይገድለኛል!» 15 ኤልያስም «ዛሬ
ለንጉሡ እንደምገለጥለት በማገለግለውና ሁሉን ቻይ በሆነው በእግዞአብሔር ስም ቃል እገባልሃለሁ!» ሲል መለሰለት። 16 ከዚህ በኋላ አብድዩ ሄዶ ለንጉሥ
አክዓብ ነገረው፤ አክዓብም ተነሥቶ ኤልያስን ለመገናኘት ሄደ፤ 17 አክዓብ ኤልያስን ባየው ጊዜም «በእስራኤል ላይ ይህን ችግር ያመጣህ አንተ እዚህ ነህን?»
አለው። 18 ኤልያስም እንዲህ ሲል መለሰ፦ «የእግዚአብሔርን ትእዛዛት በመጣስ ባዓል ተብሎ ለሚጠራው የባዕድ አምላክ ምስሎች በመስገድ ችግር
የምታመጡ አንተና የአባትህ ቤተ ሰብ ናችሁ እንጂ እኔ በእስራኤል ላይ ችግር የማመጣ አይደለሁም! 19 ይልቅስ እስራኤላውያንን ሁሉ እንዳገኛቸው አራት
መቶ ሃምሳ የበዓል ነቢያትንና በንግሥት ኤልዛቤል ማእድ የሚቀለቡትን አራት መቶ የኤሼራ ነቢያትን በቀርሜሎስ ተራራ ሰብስብልኝ።» 20 ስለዚህም አክዓብ
ለእስራኤላውያን ሁሉና ለነቢያት በሙሉ ጥሪ አድርጎ በቀርሜሎስ ተራራ እንዲሰበሰቡ አስደረገ። 21 ኤልያስም ወጥቶ ለሰዎቹ፦ «እስከ መቼ ድረስ በሁለት
ልብ ስታወላውሉ ትኖራላችሁ? እንግዲህ እግዚአብሔር እውነተኛ አምላክ ከሆነ እርሱን አምልኩ! ወይም ባዓል እውነተኛ አምላክ ከሆነ እርሱኑ አምልኩ!»
አላቸው። ሕዝቡ ግን አንዲት ቃል እንኳ አልመለሱም። 22 ከዚህ በኋላ ኤልያስ እንዲህ አለ፦ «ከእግዚአብሔር ነቢያት የቀረሁት እኔ ብቻ ነኝ። አራት መቶ ጎምሳ
የባዓል ነቢያት ግን እነሆ በዚህ አሉ። 23 እንግዲህ ሁለት ኮርማዎችን አምጡና የባዓል ነቢያት አንዱን ወስደው ይረዱት፤ ሥጋውንም ቆራርጠው እንጨት
በመረብረብ በዚያ ላይ ያኑሩት፤ ነገር ግን እሳት አያድርጉበት። እኔም ሁለተኛውን ኮርማ ወስጄ እንደዚሁ አደርጋለሁ። 24 ከዚህ በኋላ የባዓል ነቢያት ወደ
አምላካቸው ይጸልዩ፤ እኔም ወደ እግዚአብሔር እጸልያለሁ፤ እሳትን ወደ መሥዋዕቱ በመላክ መልስ የሚሰጥ እርሱ እውነተኛ አምላክ ይሁን። ሕዝቡም ድምፁን
ከፍ አድርጎ ይህ መልካም ነው በማለት መልስ ሰጡ። 25 ከዚህ በኋላ ኤልያስ የባዓልን ነቢያት እናንተ ብዙ ስለ ሆናችሁ በመጀመሪያ አንዱን ኮርማ መርጣቸሁ
በማረድ ወደ አምላካችሁ ጸልዩ፤ ነገር ግን እንጨቱ ላይ እሳት አታደርጉበት አላቸው። 26 እነርሱም የመጣላቸውን ኮርማ ወስደው በመሥዋዕት አዘጋጅተው እስከ
እኩለ ቀን ድረስ ወደ ባዓል ጸለዩ። ባዓል ሆይ እባክህ ስማን! እያሉ ጮኹ። በሠሩትም መሠዊያ ዙሪያ እየዘፈኑ ዞሩ፤ ነገር ግን ምንም መልስ አላገኙም። 27
እኩለ ቀን ሲሆን ኤልያስ ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ ጸልዩ! እርሱ አምላክ አይደለም እንዴ? እርሱ በአሳብ ተውጦ ይሆናል! ወይም ራሱን ያዝናና ይሆናል!
ወይም ወደ ሩቅ አገር ሄዶ ይሆናል! ወይም ተኝቶ ያንቀላፋ ይሆናልና እንዲነቃ ቀስቅሱት! እያለ ያፌዝባቸው ጀመር። 28 ስለዚህም ነቢያቱ ድምፃቸውን ከፍ
አድርገው እየጸለዩ በሥርዓታቸው መሠረት ደማቸው እስኪፈስ ድረስ በቢላዋና በጩቤ ሰውነታቸውን ያቆስሉ ነበር። 29 እኩለ ቀን ካለፈም በኋላ የሠርክ
መሥዋዕት እስከሚቀርብበት ጊዜ ድረስ እየተራወጡ ይቀባጥሩ ነበር፤ ይሁን እንጂ ምንም መልስ አላገኙም፤ ድምፅም አልተሰማም። 30 ከዚህ በኋላ ኤልያስ
ሰዎቹን ወደ እኔ ቅረቡ አላቸው፤ ሁሉም በዙሪያው ተሰበሰቡ፤ እርሱም ፈርሶ የነበረውን የእግዚአብሔር መሠዊያ በማደስ ሠራው። 31 እግዚአብሔር ከዚያ በፊት
እስራኤል ብሎ ከሰየመው ከያዕቆብ ልጆች በዐሥራ ሁለቱ ነገዶች ስም ዐሥራ ሁለት ድንጋዮችን ወሰደ። 32 እነዚህንም ድንጋዮች ረብርቦ በእግዚአብሔር ስም
መሠዊያ ሠራ። በዙሪያውም ዐሥራ አራት ሊትር ውሃ የሚይዝ ጉድጓድ ማሰ። 33 እንጨቱንም በመሠዊያው ላይ በመረብረብ ኮርማውን በብልት በብልቱ ቆራርጦ
በእንጨቱ ላይ አኖረ። 34 በአራት ጋን ውሃ ሞልታችሁ በመሥዋዕቱና በእንጨቱ ላይ አፍስሱት! አላቸው። እነርሱም እንዲሁ አደረጉ፤ አሁንም ጨምሩበት
አላቸው፤ እነርሱም እንዲሁ አደረጉ። 35 ውሃውም በመሠዊያው ዙሪያ ፈሰሰ፤ ጉድጓዱንም ሞላው። 36 ከቀትር በኋላ የሠርክ መሥዋዕት በሚቀርብበት ሰዓት
ነቢዩ ኤልያስ ወደ መሠዊያው ቀርቦ እንዲህ ሲል ጸለየ፤ የአብርሃም፣ የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ የእስራኤል አምላክ መሆንህን፣
እኔም እግዚአብሔር ሆይ፣ የአንተ አገልጋይ መሆኔን፣ እኔም ይህንን ሁሉ ያደረግኹት በቃልህ መሠረት መሆኑን አንተ ራስህ ግለጥ። 37 አምላኬ ሆይ፣ ይህ
ሕዝብ አንተ እውነተኛ አምላክ መሆንህንና ወደ አንተም ያቀረብከው አንተ ራስህ መሆንህን እንዲያውቅ እባክህ መልስ ስጠኝ፤ አምላክ ሆይ ስማኝ! 38 ከዚህ
በኋላ እግዚአብሔር እሳትን ላከ፤ ያ እሳት መሥዋዕቱን፣ እንጨቱንና ድንጋዩን በላ፤ ምድሩንም ለበለበ፤ በጉድጓዱ የነበረውንም ውሃ አደረቀ። 39 ሰዎቹም ይህን
ባዩ ጊዜ በግንባራቸው መሬት ላይ ተደፍተው በመደነቅ እግዚአብሔር አምላክ ነው! እውነተኛ አምላክ እርሱ ብቻ ነው! አሉ። 40 ኤልያስም የባዓል ነቢያትን
ያዙ፤ አንድም ሰው እንዳያመልጥ ሲል አዘዘ። ሕዝቡም በሙሉ ያዛቸው፤ ኤልያስም ወደ ቂሶን ወንዝ እየመራ ወስዶ በዚያ ሁሉንም ገደላቸው። 41 ከዚህ በኋላ
ኤልያስ ንጉሥ አክዓብን እንግዲህ ሄደህ እህልና ውሃ ቅመስ፤ እኔ አሁን የከባድ ዝናም ነጎድጓድ ድምፅ መቃረቡን እየሰማሁ ነው አለው። 42 አክዓብ እህልና ውሃ
ለመቅመስ ሲሄድም ኤልያስ ወደ ቀርሜሎስ ተራራ ወጣ፤ እዚያም በሁለቱ ጉልበቶቹ መካከል ራሱን ወደ መሬት ደፋ። 43 አገልጋዩን፣ ሂድና ወደ ባሕሩ
አቅጣጫ ተመልከት አለው። አገልጋዩም ሄዶ ሲመለስ ምንም ነገር አይታየኝም አለው፤ አገልጋዩ እየተመላለሰ ያይ ዘንድ ኤልያስ ሰባት ጊዜ አዘዘው፤ 44
በሰባተኛውም ጊዜ አገልጋዩ ተመልሶ ከአንድ ሰው መዳፍ የማትበልጥ ትንሽ ደመና ከባሕር ስትወጣ አየሁ አለው። ኤልያስም ወደ ንጉሥ አክዓብ ሂድና ዝናቡ
ሳያቆምህ በፍጥነት ወደ ሠረገላህ ገብተህ ወደ ቤትህ ተመልሰህ ሂድ ብለህ ንገረው ሲል አዘዘው። 45 ከጥቂት ጊዜም በኋላ ሰማዩ በጥቁር ደመና ተሸፈነ፤
ነፋሱም ነፈሰ፤ ብርቱ ዝናብም ይዘንብ ጀመረ። ነጉሥ አክዓብም በሠረገላው ተቀምጦ ወደ ኢይዝራኤል ሄደ፤ 46 የእግዚአብሔርም ኃይል በኤልያስ ላይ ወረደ፤
ኤልያስም ልብሱን በወገቡ ዙሪያ ጠበቅ አድርጎ በመታጠቅ እስከ ኢይዝራኤል መግቢያ በር ድረስ በአክዓብ ፊት ቀድሞ ይሮጥ ነበር።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Kings 18:1

የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል መጣ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር የዋለው ከእግዚአብሔር ዘንድ ልዩ መልዕክት ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በ1 ነገሥት 6፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ የእርሱን መልዕክት ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በምድሪቱ ላይ ዝናብ ላከ
"በምድሪቱ ላይ እንዲዘንብ አደረገ"

አሁን ችጋሩ/ረሃቡ ታላቅ ነበር
"አሁን" የሚለው ቃል እዚህ ስፍራ የዋለው በዋናው የታሪክ አካሄድ ላይ ማረፊያ ለማበጀት ነው። እዚህ ላይ ጸሐፊው ድርቁ/ችጋሩ ምን ያህል ሰማርያን እንደጎዳት የመረጃ ዳራ ይሰጠናል። (የመረጃ ዳራ/መነሻ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 18:3

አሁን አብድዩ ያህዌን አከበረ
"አሁን" የሚለው ቃል እዚህ ስፍራ የዋለው በዋናው የታሪክ አካሄድ ላይ ማረፊያ ለማበጀት ነው። እዚህ ላይ ጸሐፊው በታሪኩ ውስጥ ስለ አዲስ ሰው ይነግረናል።

አንድ መቶ ነቢያት በሃምሳ ከፍሎ ደበቃቸው
"100 ነቢያትን በቡድን 50 እያደረገ ደበቃቸው" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 18:5

ፈረሶችን እና በቅሎዎችን በህይወት ጠበቀ...ሁሉንም እንስሳት አዳነ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው ትኩረት ለመስጠት ተጣምረዋል። "ፈረሶችን እና በቅሎዎችን ከሞት አዳናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አክአብ በራሱ በአንድ መንገድ ሄደ ደግሞም አብድዩ በሌላ መንገድ ሄደ
"በራሱ" የሚለው የሚለው ሀረግ አክአብ እና አብድዩ በተለያየ አቅጣጫ መሄዳቸውን ያጎላል፣ ይህ ማለት ከአክአብ ጋር ማንም አልነበረም ማለት አይደለም። "አክአብ ቡድኑን በአንድ አቅጣጫ ሲመራ አብድዩም ቡድኑን በሌላ አቅጣጫ መርቷል። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 18:7

ጌታዬ ኤልያስ
እዚህ ስፍራ "ጌታ" የሚለው ቃል የዋለው ክብርን መግለጫ ተደርጎ ነው።

ሄደህ ለጌታህ ፣ 'እነሆ፣ ኤልያስ እዚህ አለ ብለህ ንገረው።'
እዚህ ስፍራ "ጌታ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው አክዓብን ነው።

እነሆ፣ ኤልያስ
"ኤልያስ ሆይ፣ ትኩረት ስጠኝ፣ ምክንያቱም ቀጥሎ የምናገረው እውነትም ጠቃሚም ነው"

1 Kings 18:9

እርሱ ይገድለኝ ዘንድ ... እኔ ምን በድያለሁ?
አብድዩ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ንጉሥ አክአብ በኤልያስ ላይ ባለው ቁጣ ምክንያት እርሱ የሚደርስበትን አደጋ ትኩረት ለመስጠት ነው። "እርሱ ይገድለኝ ዘንድ...እኔ በአንተ ላይ ስሀተት አልፈጸምኩም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

አገልጋይህን ለአክዓብ እጅ አሳልፈህ ትሰጥ ዘንድ
"እጅ" ለሃይል እና ቁጥጥር ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "አገልጋይህን ለአክዓብ አሳልፈህ ለመስጠት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ አገልጋይ
አብድዩ ኤልያስን ለማክበር ራሱን የኤልያስ አገልጋይ ሲል ይናገራል።

በህያው አምላክህ እምላለሁ
ይህ መሃላ የሚያገለግለው እርሱ እየተናገረ ያለው ነገር እውነት መሆኑን ለማጉላት ነው።

ጌታዬ ሰዎችን ያላከበት አገር ወይም ግዛት የለም
እዚህ ስፍራ "አገር ወይም ግዛት የለም" የሚለው ሰዎች ኤልያስን ፍለጋ በጣም ሩቅ ስፍራ ድረስ መሄዳቸውን በማጋነን የዋለ አገላለጽነው። ይህ በአዎንታ ሊገለጽ ይችላል። "ጌታዬ ሰዎችን ወደ እርብ እና ሩቅ አገራት እና ግዛቶች ልኳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት እንደዚሁም ጥንድ አሉታዎች የሚሉትን ይመልከቱ)

አሁን ግን
ይህ ሀረግ የዋለው ኤልያስ፣ አብድዩ ያደርገው ዘንድ የነገረው ነገር አደገኛ መሆኑን ለማጉላት ነው።

1 Kings 18:12

ዳቦ እና ውሃ.....አንተ አልሰማህምን?
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኔ ያደረግሁትን አንተ በእርግጥ ሰምተሃል...ዳቦ እና ውሃ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ጌታዬ
እዚህ ስፍራ "ጌታ" የሚለው ቃል ኤልያስን የሚያመለክት የአክብሮት አገላለጽ ነው።

አንድ መቶ የያህዌን ነቢያት በየሀምሳው
"100 የያህዌ ነቢያትን በየቡድን 50" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 18:14

ሄደህ ኤልያስ እዚህ እንደሚገኝ
እነዚህ ቃላት በ1 ነገሥት 18፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመለከቱ።

ጌታዬ
እዚህ ስፍራ "ጌታ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው አክአብን ነው።

በህያው ያህዌ ህይወት እምላለሁ
እርሱ የሚናገረው እውነት መሆኑን የሚያጎላ መሃላ ነው።

በፊቱ የቆምኩት እርሱ
"በፊቱ መቆም" አንድ ሰው ባለበት ስፍራ ለመቆም እና እርሱን ለማገልገል ዝግጁ መሆንን የሚገልጽ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "እኔ የማገለግለው እርሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 18:16

ኤልያስ ያለውን ለእርሱ ነገረው
"አብድዩ ለአክዓብ ኤልያስ እንዲነግረው የነገረውን መልዕክት አደረሰ/ተናገረ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አንተ ነህን? በእስራኤል ላይ ችግር የምታደርሰወቅ አንተ ነህ!
አክዓብ ይህን ጥያቄ ያነሳው ስለ ኤልያስ ማንነት ትኩረት ሰጥቶ እርግጠኛ ለመሆን ነው። "ስለዚህም አንተ በዚህ አለህ። አንተ በእስራኤል ላይ ችግር የምታደርስ ነህ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 18:18

መላው እስራኤል
ይህ የሰሜኑን አስር የእስራኤል ግዛቶች መሪዎች እና ህዝብ የሚገልጽ ማጠቃላያ ነው። (ኩሸት እና አጠቃላ አስተያየት እንደዚሁም ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

450 ነቢያት
"አራት መቶ ሃምሳ ነቢያት" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

አራት መቶ ነቢያት
400 ነቢያት (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 18:20

ወደ...ቃል ላክ ደግሞም ሰብስባቸው
"ቃል" የሚለው የሚወክለው የአክዓብን መልዕክት ሲሆን መልዕክቱን ለሚያደርሰው መልዕክተኛም ሜቶኖሚ/ ነው። ይህ ለታወቀ መልዕክት የዋለ የተለመደ ሃሳብ ነው። "ወደ... መልዕክት ላክ ከዚም ሰብስባቸው" ወይም "ስብሰባ ለመሰብሰብ... መልዕክተኛ ላክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እንደዚሁም ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

እስከ መቼ በሃሳባችሁ እያወላወላችሁ ትቆያላችሁ?
ኤልያስ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ህዝቡ እንዲቆርጥ ለመገፋፋት ነው።፤ ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ለረጅም ጊዜ መወሰን አልቻላችሁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመለከቱ)

ለእርሱ አንድም ቃል አልመለሱም
"ምንም አልተናገሩም" ወይም "ዝም አሉ"

1 Kings 18:22

እኔ ብቻ፣ ብቻዬን ቀረሁ
"እኔ" የሚለው ቃል የተደጋገመው ትኩረት ለመስጠት ነው።

450 ወንዶች
"አራት መቶ ሀምሳ ወንዶች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

የአምላካችሁን ስም ጥሩ...የያህዌን ስም እጠራለሁ
"ስም" ለአንድ ሰው እውቅና እና ክብር ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ሲሆን፣ እርሱን "መጥራት" ወደ እርሱ ማመልከትን ይገልጻል። "ወደ አምላካችሁ ተጣሩ... ወደ ያህዌ እጣራለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉም ህዝብ እንዲህ ሲል መለሰ፣ "ይህ መልካም ነው።"
"ህዝቡ ሁሉ እንዲህ አሉ፣ ‘ይህ መደረግ ያለበት መልካም ነገር ነው።’"

1 Kings 18:25

ይህ አዘጋጁ
"መስዋዕት ለማቅረብ ዝግጁ አድርጉ"

እናንተ ብዙ ሰዎች ናችሁ
እዚህ ስፍራ "እናንተ" የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ነው። (አንተ/አንቺ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)

ወይፈኑን ወሰዱ
"የበዓል ነቢያት ወይፈኑን ወሰዱ"

ለእነርሱ የተሰጣቸውን ወይፈን
ይህ በዐድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ለእነርሱ የተሰጣቸውን ወይፈን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን ድምጽ አልነበረም፣ አሊያም መልስ የሚሰጥ ማንም አልነበረም
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው፣ የሃሰተኛ ነቢያቱን ጸሎት የሚመልስ ማንም አልነበረም። "ድምጽ" የሚለው ቃል የሚናገርን ክፍል ይወክላል። "ነገር ግን በዓል አንዳች አልመለሰም ወይም አንዳች አላደረገም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

1 Kings 18:27

ምናልባት በሀሳብ ላይ ይሆናል
"ምናልባት እያሰበ ይሆናል" ወይም "በሃሳብ ላይ ሆኖ ሊሆን ይችላል"

ራሱን ከህመም እያስታገሰ
ይህ ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት/ ከባድ የሆነውን ሀሳብ ሻል ባለ መንገድ መግለጫ ነው። ኤልያስ በበዓል ላይ ያለውን ንቀት በፌዝ ይገልጻል። "በመታጠቢያ ቤት ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚሉትን ይመልከቱ)

ሊቀሰቀስ ያስፈልገዋል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ልትቀሰቅሱት ያስፈልጋችኋል" ወይም "ከተኛበት ልታነቁት ይገባችኋል" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ አሁንም ይረበሹ ነበር
"እንስሳዊ ባህሪያቸውን ማሳየታቸውን ቀጥለዋል።" ነቢያቱ ብዙውን ጊዜ ያልተለመደ መንገድ ወይም ጤናማ ያልሆነ ድርጊት ይፈጽሙ ነበር። በዚህ ሁኔታ ሲጨፍሩ በዓልን ጮኸው ይጣሩ፣ እና ራሳቸውን በስለት ይቆርጡ ነበር።

የምሽት መስዋዕት ሲያቀርቡ
"የምሽት መስዋዕት ማቅረብ"

ነገር ግን ድምጽ አልነበረም ወይም ማንም የሚመልስ አልነበረም፤ ለልመናቸው አንዳች ትኩረት የሚሰጥ አልነበረም
እነዚህ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ደግሞም ለሀሰተኛ ነቢያት ጸሎት ምላሽ የሚሰጥ አለመኖሩን ትኩረት ይሰጣሉ። "ነገር ግን በዓል አንዳች ነገር አልተናገረም ወይም አላደረገም ወይም ትኩረት እንኳን ሊሰጣቸው አልቻለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

ድምጽ አልነበረም ወይም መልስ የሚሰጥ ማንም አልነበረም
ይህ በ1 ነገሥት 18:26 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

1 Kings 18:30

አስራ ሁለት ድንጋዮች
"12 ድንጋዮች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በያህዌ ስም
እዚህ ስፍራ "ስም"ለክብር እና እውቅና ሜቶኖሚ/ ነው። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ያህዌን ለማክበር" ወይም 2) "በያህዌ ስልጣን።" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ቦይ
ትንሽ የተቆፈረ የውሃ መሄጃ

ሁለት ሴየ/ቁና እህል። አንደ ሴየ/ቁና የእፍ አንድ ሶስተኛ ነው
ሴየ ወደ 7.7 ሊትር መጠን አለው። "ወደ 15 ኪሎ እህል የሚይዝ" (መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት ወቅት የመጠን መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 18:33

እንጨቱን ለማንደድ ረበረበ
በዚህ ዐረፍተ ነገር "በመሰዊያው ላይ" የሚለው እንጨቱን ያስቀመጠበትን ስፍራ ያሳያል። "እንጨቱን ለማንደድ በመሰዊያው ላይ ረበረበው/አደረገው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው (ኢሊፕሲስ/የተተወ ወይም የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

አራት ገንቦ
"4 ገንቦ" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ቦይ
ይህ በ 1 ነገሥት 18፡30 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመለከቱ።

1 Kings 18:36

እንዲህ ሆነ
እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ውስጥ አስፈላጊ እና ጥቅም የሚሰጥ ጊዜን ለማመልከት ነው። የእናንተ ቋንቋ ይህን የሚገልጽበት መንገድ ካለው እዚህ ስፍራ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ።

የአብርሃም፣ የይስሀቅ እና የእስራኤል አምላክ ያህዌ
እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚለው የሚያመለክተው ያዕቆብን ነው። እግዚአብሔር የያዕቆብን ስም (በዘፍጥረት 32፡28) ወደ እስራኤል ቀይሮ የያዕቆብን ትውልዶች "እስራኤል" ሲል ጠርቷል።

ይህ ዛሬ ይታወቅ
ይህ በዐድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ይህ ህዝብ ዛሬ እንዲታወቅ አድርግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ ስማኝ... እነሆ ስማኝ
ይህ ሀረግ የተደገመው ኤልያስ ወደ ያህዌ የሚያሰማውን ልመና ለማጉላት ነው።

ልባቸውን ዳግም ወደ ራስህ መልስ
የሰዎች "ልብ" ለህዝቡ ታማኝነት እና ወዳጅነት ሜቶኖሚ/ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ዳግም ለአንተ ታማኝ እንዲሆኑ አድርግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 18:38

የያህዌ እሳት ወደቀ
"የያህዌ እሳት ከላይ ወረደ"

ላሰችው
አሳቱ የተነጻጸረው የተጠማ ሰው ውሃ ከመጠጣቱ ጋር ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ እርሱ አምላክ ነው! ያህዌ እርሱ አምላክ ነው!
ሀረጉ የተደጋገመው ትኩረት ለመስጠት ነው።

1 Kings 18:41

የብዙ ዝናብ ድምጽ ነበር
"የሀይለኛ ዝናብ እንደሚመጣ ድምጽ ተሰማ"

ወደ ምድር አጎንብሶ ፊቱን በጉልበቶቹ መሃል አደረገ
ይህ ለጸሎት የሆነ አቀማመጥን ይገልጻል።

1 Kings 18:43

ሰባት ጊዜ
"ሰባት" የሚለው ቃል በቁጥር "7" ሊጻፍ ይችላል። "7 ጊዜያት" እንደሚለው። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

የሰውን እጅ የሚያክል ያህል ትንሽ
ከርቀት፣ የሰው እጅ የሚያህል ደመና ላይታይ ይችላል።

1 Kings 18:45

እንዲህ ሆነ
እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ውስጥ አዲስ ደረጃ የሚያሳይ ድርጊት መጀመሩን ለማመልከት ነው። የእናንተ ቋንቋ ይህን የሚገልጽበት መንገድ ካለው እዚህ ስፍራ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ።

የያህዌ እጅ በኤልያስ ላይ ነበር
እዚህ ስፍራ "እጅ" ለጥንካሬ ሜቶኖሚ/ ነው። "ያህዌ ለኤልያስ ሀይሉን ሰጠው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ልብሱን በቀበቶው አጥብቆ ካሰረ በኋላ
ኤልያስ ረጅሙን ልብሱን በወገቡ ዙሪያ ጠበቅ አድርጎ በማሰር እንደ ልቡ እንዲሮጥ እገሮቹን ነጻ አደረገ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 19

1 ኤልያስ ያደረገውን ሁሉና የባዓልንም ነቢያት በሙሉ እንዴት እንደ ገደላቸው ንጉሥ አክዓብ ለሚስቱ ለኤልዛቤል ነገራት። 2 ስለዚህ እርስዋ በእነዚያ ነቢያት ላይ ያደረግኸውን እኔም ነገ ልክ በአሁኑ ሰዓት በአንተ ላይ ሳላደርግብህ ብቀር አማልክት በሞት ይቀሥፉኝ ስትል ወደ ኤልያስ የዛቻ መልእክት ላከች። 3 ኤልያስም ስለ ፈራ ሕይወቱን ለማትረፍ ከአገልጋዩ ጋር በይሁዳ ወደምተገኘው ወደ ቤርሳቤህ ከተማ ሄደ። አገልጋዩንም በዚያ ተወው፤ 4 ኤልያስ ራሱ አንድ ቀን ሙሉ በበረሓ ተጓዘ። ከዚህ በኋላ፣ በአንድ የክትክታ ዛፍ ጥላ ሥር ተቀመጠ፣ ሞቱንም በመመኘት እግዚአብሔር ሆይ፣ አሁንስ ይብቃኝ፤ ከቀድሞ አባቶቼ አልበልጥምና ነፍሴን ውሰድ! ሲል ጸለየ። 5 ከዚህ በኋላ በዛፉ ሥር ጋደም እንዳለ እንቅልፍ ወሰደው፤ በድንገትም አንድ መልአክ መጥቶ በመዳሰሰ ቀሰቀሰውና ተነሥተህ ብላ! አለው። 6 ኤልያስ ተነሥቶ ዞሮ በተመለከተ ጊዜ በድንጋይ ሙቀት የበሰለ የዳቦ ሙልሙልና አንድ ገንቦ ውሃ በራስጌው ተቀምጦ አየ፤ ከበላና ከጠጣም በኋላ ተመልሶ እንደገና ተኛ። 7 የእግዚአብሔርም መልአክ ተመልሶ መጥቶ የምትሄድበት መንገድ ሩቅ ስለ ሆነ ተነሥተህ ብላ! ሲል ዳግመኛ ኤልያስን ቀሰቀሰው። 8 ኤልያስም ተነሥቶ ምግቡን በላ፤ ውሃውንም ጠጣ። ከዚያም ምግብ ባገኘው ኃይል እስከ ተቀደሰው የሲና ተራራ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ሙሉ ተጓዘ። 9 እዚያም እንደ ደረሰ ወደ አንድ ዋሻ ገብቶ እዚያ ዐደረ። በድንገትም እግዚአብሔር፣ ኤልያስ ሆይ! እዚህ ምን ታደርጋለህ? ሲል ጠየቀው። 10 ኤልያስም ሁሉን የምትችል አምላኬ ሆይ! እኔ ለአምላክነትህ በመቅናት ዘወትር አንተን ብቻ አገለግላለሁ፤ የእስራኤል ሕዝብ ግን ከአንተ ጋር የገቡትን ቃል ኪዳን አፍርሰዋል፤ መሠዊያዎችህንም ሰባብረዋል፤ ነቢያትህንም ሁሉ ገድለዋል፤ እነሆ እኔ ብቻዬን ቀርቻለሁ፤ እነርሱ ግን እኔንም እንኳ ሊገድሉኝ ይፈልጋሉ! ሲል መለሰ። 11 እግዚአብሔርም ኤልያስን ካለህበት ወጥተህ በተራራው ጫፍ ላይ በፊቴ ቁም አለው፤ ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር በአጠገቡ አለፈ፤ ብርቱ ነፋስም በፊቱ በመላክ ኮረብቶችን ሰነጣጠቀ፤ ዐለቶችንም ሰባበረ፤ እግዚአብሔር ግን በነፋሱ ውስጥ አልነበረም። ነፋሱም ከቆመ በኋላ ምድሪቱ ተናወጠች፤ እግዚአብሔር ግን በምድር መናወጥ ውስጥ አልነበረም። 12 ከምድሪቱም ነውጥ በኋላ እሳት መጣ፤ እግዚአብሔር ግን በእሳቱ ውስጥ አልነበረም፤ ከእሳቱም በኋላ የሹክሹክታ ድምፅ ተሰማ። 13 ኤልያስ የሹክሹክታውን ድምፅ በሰማ ጊዜ ፊቱን በመጎናጸፊያ ሸፈነ፤ ወጥቶም በዋሻው መግቢያ በር አጠገብ ቆመ፤ አንድ ድምፅም ኤልያስ ሆይ፣ እዚህ ምን ታደርጋለህ? ሲል ጠየቀው። 14 ኤልያስም ሁሉን የምትችል አምላኬ ሆይ፣ እኔ ለአምላኬ በመቅናት ዘወትር አንተን ብቻ አገለግላለሁ፤ የእስራኤል ሕዝብ ግን ከአንተ ጋር የገቡትን ቃል ኪዳን አፍርሰዋል፤ መሠዊያዎችህንም ሰባብረዋል፤ ነቢያትህንም ሁሉ ገድለዋል፤ እነሆ እኔ ብቻዬን ቀርቻለሁ፤ እነርሱ ግን እኔን እንኳ ሊገድሉኝ ይፈልጋሉ ሲል መለሰ። 15 እግዚአብሔርም እንዲህ አለው፤ በደማስቆ ከተማ አጠገብ ወደሚገኘው በረሓ ተመልሰህ ሂድ፤ እዚያም በደረስህ ጊዜ አዛሄልን ቀብተህ በሶርያ ላይ አንግሠው፤ 16 የናሜሲን ልጅ ኢዩንም ቀብተህ በእስራኤል ላይ አንግሠው፤ የአቤል ምሖላ ተወላጅ የሆነውን የሣፋጥን ልጅ ኤልሳዕንም ቀብተህ በአንተ ፈንታ ነቢይ እንዲሆን አድርገው። 17 ከአዛሄል እጅ ከመገደል ተርፎ የሚያመልጠውን ማንኛውንም ሰው ኢዩ ይገድለዋል፤ ከኢዩ እጅ የሚያመልጠውንም ኤልሳዕ ይገድለዋል። 18 ይሁን እንጂ ለእኔ ታማኞች የሆኑ ለባዓል ያልሰገዱና ለምስሉም ያልሰገዱ ሰባት ሺህ ሰዎችን በእስራኤል ምድር በሕይወት እንዲተርፉ አደርጋለሁ። 19 ኤልያስም ከዚያ ከሄደ በኋላ የሣፋጥን ልጅ ኤልሳዕን ሁለት በሬዎች ጠምዶ ሲያርስ አገኘው፤ ከእርሱም ጋር በፊቱ በአሥራ አንድ ጥማድ በሬዎች የሚያርሱ ደቦኞች ነበሩ፤ ኤልሳዕም በመጨረሻ አሥራ ሁለተኛውን ጥማድ ያርስ ነበር፤ ኤልያስም መጎናጸፊያውን አውልቆ በኤልሳዕ ላይ ደረበለት። 20 በዚህ ጊዜ ኤልሳዕ በሬዎቹን ተቶ ወደ ኤልያስ በመሮጥ አባቴና እናቴን ስሜ እንድሰናበት ፍቀድልኝ፤ ከዚያም በኋላ እከተልሃለሁ አለው። ኤልያስም፣ እሺ ተመልሰህ ሂድ፤ እኔ አልከለክልህም! ሲል መለሰለት። 21 ከዚህ በኋላ ኤልሳዕ ወደ ጥማድ በሬዎቹ ተመልሶ አረዳቸው። የተጠመዱበትንም ቀንበር በማንደድ ሥጋቸውን ቀቅሎ ለሰዎቹ አቀረበላቸው፤ እነርሱም በሉ፤ ከዚህ በኋላ ኤልያስን ተከትሎ በመሄድ ረዳቱ ሆነ።

---

1 Kings 19:1

አማልዕክት እንዲህ ያድርጉብኝ፣ እንዲህም ይጨምሩብኝ
ይህ እንደ ጥብቅ መሃላ የሚያገለግል ንጽጽር ነው። "አማልዕክት አኔን ይግደሉኝ ከዚያም የከፋ ክፉ ነገሮችን ያድርሱብኝ"

የአንተን ህይወት ከሞቱት ነቢያት እንደ አንዱ ህይወት ካላደረግሁ
"አንተ እነዚያን ነቢያት እንደ ገደልክ እኔም አንተን ካልገደልኩ"

እርሱ ተነሳ
"እርሱ ተነስቶ ቆመ"

1 Kings 19:4

እርሱ ራሱ የአንድ ቀን ጉዞ ተጓዘ
"ራሱ" የሚለው ቃል የዋለው እርሱ ብቻውን እንደሆነ ትኩረት ለመስጠት ነው። "ለብቻው ብዙ ቀናት ተጓዘ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ደጋጋሚ ተውላጠ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የመጥረጊያ ዛፍ
"የመጥረጊያ ዛፍ" በበረሃ የሚበቅል ተክል ነው። (የማይታወቀውን መተረጎም የሚለውን ይመልከቱ)

መሞት ተመኘ/ ይሞት ዘንድ ራሱ ጥያቄ አቀረበ
"ይሞት ዘንድ ጸለየ"

ያህዌ ሆይ፣ አሁንስ ይህ ይበቃኛል
"ያህዌ ሆይ፣ እነዚህ ችግሮች እጅግ በዙብኝ"

በከሰል/ፍም ላይ የተጋገረ ዳቦ
ይህ በዐድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በጋለ ድንጋይ/ፍም ላይ አንድ ሰው የጋገረው ዳቦ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የገንቦ ውሃ
"በመያዣ/ማጠራቀሚያ ውስጥ የሚገኝ ውሃ"

1 Kings 19:7

ለአንተ እጅግ ብዙ ይሆናል
"ለአንተ እጅግ አስቸጋሪ ይሆናል።"

በዚያ ምግብ ሃይል አርባ ቀን እና አርባ ምሽት ተጓዘ
"ያ ምግብ 40 ቀን እና 40 ምሽት ለመጓዝ ሀይል ሰጠው" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Kings 19:9

በዚያ በሚገኝ ዋሻ
እዚህ ስፍራ "እዚያ" የሚለው ቃል የኬብሮንን ተራራ ያመለክታል። ዋሻ በተራራ አጠገብ የሚገኝ ወደ ተፈጥሮ ክፍሎች ወይም ከመሬት በታች ወደሚገኝ ክፍል የሚመራ ክፍት ስፍራ ነው።

የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል ወደ እርሱ መጣ፣ "ምን
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር የዋለው ከእግዚአብሔር ዘንድ ልዩ መልዕክት ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በ1 ነገሥት 6፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ለእርሱ መልዕክት ሰጠው" እንዲህም አለው፣ 'ምን" ወይም "ያህዌ ለእርሱ ይህ መልዕክት ሰጠው፡ 'ምን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኤልያስ ሆይ፣ እዚህ ምን ታደርጋለህ?
ያህዌ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ኤልያስን ለመገሰጽ እና ግዴታውን ሊያስታውሰው ነው። "ኤልያስ ሆይ፣ መገኘት ያለብህ እዚህ ስፍራ አይደለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ብቻ፣ ብቻዬን ቀረሁ
"እኔ" የሚለው ቃል የተደጋገመው ትኩረት ለመስጠት ነው።

1 Kings 19:11

ከእኔ በፊት በተራራው ላይ
እዚህ ስፍራ "ከእኔ በፊት" የሚለው ከአንድ ሰው ፊት ለመቆም ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "እኔ ባለሁበት በተራራው ላይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 19:13

በመጎናጸፊያው ፊቱን ጠረገ
"ፊቱን በመጎናጸፊያው ሸፈነ።" መጎናጸፊያ ትልቅ ካባ፣ መላ ሰውነትን የሚሸፍን ጨርቅ ነው።

ከዚያም ወደ እርሱ ድምጽ መጣ
"ከዚያም ድምጽ ሰማ"

እዚህ ምን እየሰራህ ነው... ደግሞም እነርሱ ህይወቴን ከእኔ ለመውሰድ እየሞከሩ ነው
ይህ ክፍል በ1 ነገሥት 19:9-10 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

እኔ ብቻ፣ ብቻዬን ቀረሁ
"እኔ" የሚለው ቃል የተደጋገመው ትኩረት ለመስጠት ነው።

1 Kings 19:15

ነቢያት በአንተ ስፍራ
"በአንተ ምትክ ነቢያት

1 Kings 19:17

እንዲህ ይሆናል
ይህ ሀረግ የዋለው ኤልያስ ያህዌ ያደርግ ዘንድ ያዘዘውን ሲያደርግ የሚሆነውን ነገር ለማስተዋወቅ ነው። "የሚሆነው

ከአዛሄል ሰይፍ ያመለጠውን ሁሉ
"ሰይፍ" በጦርነት ለሚገደሉ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። "አዛኤል በሰይፍ ያልገደላቸውን ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ለራሴ አስቀራለሁ
እዚህ ስፍራ "እኔ" እና "እኔ ራሴ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ያህዌን ነው። "ከሞት አድናለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ደጋጋሚ ተውላጠ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባት ሺህ ሰዎች
"7,000 ሰዎች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ለበዓል ጉልበቶቻቸው ያልተነበረከኩ፣ እና አፋቸው እርሱን ያልሳመ
"ወደ ታች ማጎንበስ/መንበርከክ" እና "መሳም" ሰዎች ጣኦቶችን ለማምለክ ለሚያደርጓቸው ድርጊቶች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ናቸው። ድርጊቶቹ የተጣመሩት ትኩረት ለመስጠት ነው። "ለበዓል ያልሰገዱ እና በዓልን ያልሳሙ" ወይም "በዓልን ያላመለኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

1 Kings 19:19

ሳፋጥ
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አስራ ሁለት ጥማድ በሬዎች
"12 ጥማድ በሬዎች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ራሱ በአስራ ሁለቱ ጥማዶች ያርስ ነበር
"እርሱ ራሱ" የሚለው ቃል ኤልሳ በመጨረሻው ጥማድ ያርስ እንደነበር ያመለክታል፤ የተቀሩት ሰዎች በሌሎች አስራ አንዱ ጥማዶች ያርሱ ነበር። (ደጋጋሚ ተውላጠ ስም እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

እርሱ፣ እባክህ አለው
"እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኤልሳን ነው።

1 Kings 19:21

እርሱ ይህን ለሰዎች ሰጠ
ኤልሳ የበሰለውን ስጋ ለከተማው ሰዎች ሰጣቸው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 20

1 የሶርያ ንጉሥ ቤን ሀዳድ መላ ሠራዊቱን በአንድነት ሰበሰበ። ብዙ ፈረሶችና ሠረገሎች ያሉአቸው ሠላሳ ሁለት ነገሥታት ከእርሱ ጋር ነበሩ። የእስራኤል ዋና ከተማ የሆነችውን ሰማርያ ጦርነት ገጠመ። 2 እርሱም ሀዳድ በከተማይቱ ወደሚገኘው ወደ እስራኤል ነጉሥ ወደ አክዓብ፣ ቤን ሀዳድ እንዲህ ይላል ብሎ መልእክተኞችን ላከ፦ 3 ብርህና ወርቅህ ውብ የሆኑት ሚስቶችህና ልጆችህ ምርጥ የሆኑ ሁሉ የእኔ ናቸው። 4 የእስራል ንጉሥም ጌታዬ ንጉሥ አንተ እንዳልከው ይሁን ብሎ መለሰ። እኔ የእኔ የሆነ ሁሉ የአንተ ናቸው አለ። 5 ከጥቂት ጊዜም በኋላ እነዚያው መልእክተኞች ከንጉሥ ቤን ሀዳድ ሌላ ትእዘዝ ይዘው እንደገና ወደ አክዓብ መጡ፤ ትዕዛዙ እንዲህ የሚል ነበር፤ ብርህን፣ ሚስቶችህንና ልጆችህን ማስረክብ እንዳለብህ መልእክት ልኬብህ ነበር። 6 አሁን ደግሞ ቤትህንና የአገልጋዮችህን ቤት ሁሉ ይበረብራሉ። በርብረውም በዓይናቸው ደስ ያላቸውን ንብረት ሁሉ ይዘው እንዲመጡ የጦር መኮንኖቼን ነገ በዚህ ጊዜ እልካለሁ። እነርሱም ነገ ጧት በዚሁ ሰዓት እዚያ ይደርሳሉ። 7 የእስራኤልም ንጉሥ አክዓብ የአገሪቱን ሽማግሌዎች ሁሉ ጠርቶ ይህ ሰው ምን ዓይነት ጠብ እንደሚፈልግ ተመልከቱ አለ። ከዚህ በፊት ሚስቶቼንና ልጆቼን፣ ብሬንና ወረቄን እንዳስረክበው ጠይቆኝ ተስማምቼ ነበር አላቸው። 8 ሽማግሌዎቹና ሕዝቡም ሁሉ እርሱ ለሚልህ ነገር ሁሉ ግምት አትስጠው፤ ከፍላጎቱ ጋር አትስማማው አሉት። 9 ስለዚህም አክዓብ ለቤን ሀዳድ መልእክተኞች ለጌታዬ ለንጉሡ ከዚህ በፊት ባቀረብክልኝ ጥያቄ ተስማምቼ ነበር፤ አሁን ባቀረብክልኝ በሁለተኛው ጥያቄ ግን ልስማማበት አልችልም ብሎአል ብላችሁ ንገሩት አላቸው። መልእክተኞቹም ተመልሰው በመሄድ መልሱን ነገሩት፤ 10 ቤን ሀዳድም በሰማርያ ለእያንዳንዱ ወታደር አንዳንድ ጭብጥ ዐፈር ሊዳረስ እስከማይችል ድረስ ብዙ ወታደሮችን ባላሰልፍ አማልክት ይቅሠፉኝ ብሎ የዛቻ መልእክቱን መልሶ ላከበት። 11 የእስራኤል ንጉሥ መልእክተኞቹን፣ በወታደር መኩራራት የሚገባው ከጦርነት ድል በኋላ እንጂ ከጦርነት በፊት አይደለም፣ ብላችሁ ለንጉሥ ቤን ሀዳድ ንገሩት ሲል መለሰላቸው። 12 ቤን ሀዳድና የእርሱ የጦር ቃል ኪዳን ጓደኞቹ የሆኑ ሌሎችም ነገሥታት በድንኳኖቻቸው ውስጥ ሆነው ሲጠጡ ሳሉ የአክዓበ መልእክት ደረሳቸው፤ በዚህን ጊዜ ቤን ሀዳድ ለጦርነት እንዲዘጋጁ ትእዛዝ ሰጠ። ስለዚህም ፈጥነው በመንቀሳቀስ ከተማውን ለማጥቃት ቦታ ቦታቸውን ያዙ። 13 በዚያን ጊዜ አንድ ነቢይ ወደ እስራኤል ንጉሥ አክዓብ ቀርቦ፣ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ይህንን ታላቅ ጦር አየህን? እነሆ እግዚአብሔር ዛሬ የቤን ሀዳድን ሠራዊት በእጅህ አሳልፌ እሰጥሃለሁ። አንተም ደግሞ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ታውቃለህ ይልሃል አለው። 14 አክዓብም ግንባር ቀደም ሆኖ የሚዘምተው ማን ይሁን? ሲል ጠየቀ። ነቢዩም እግዚአብሔር በአውራጃ አስተዳዳሪዎች የሚታዘዙ ወጣት ወታደሮች ግንባር ቀደም ሆነው ይዝመቱ ይላል አለው። ንጉሡም ጦርነቱን ማን ይጀምር? ሲል ጠየቀ። ነቢዩም አንተ ራስህ ጀምር አለው። 15 ስለዚህ ንጉሡ ብዛታቸው ሁለት መቶ ሠላሳ ሁለት ብቻ የሆነ በአውራጃ አስተዳዳሪዎች ትእዛዝ ሥር የሆኑትን ወጣት ወታደሮችን ጠራ። ቀጥሎም ጠቅላላ ብዛቱ ሰባት ሺህ የሆነ የእስራኤልን ሠራዊት ጠራ። 16 እነርሱም እኩለ ቀን ላይ ሄዱ። ቤን ሀዳድና የእርሱ የጦር ቃል ኪዳን ጓደኞች የሆኑ ሠላሳ ሁለቱ ነገሥታት በድንኳኖቻቸው ውስጥ በመጠጥ ሰክረው ነበሩ። 17 ወጣቶቹም ወታደሮች ግንባር ቀደም ሆነው ወደ ፊት አመሩ። ቤን ሀዳድ ልኮአቸው የነበሩትም ቃፊሮች አንድ የወታደር ቡድን ከሰማርያ ወጥቶ ወደዚህ እየመጣ መሆኑን ነገሩት። 18 ቤን ሀዳድም ቃፊሮቹን፣ አመጣጣቸው ለጦርነትም ይሁን ለሰላም ይዛቸሁ አምጡልኝ ሲል አዘዘ። 19 ስለዚህ በእስራኤል ሠራዊት ደጀንነት በአውራጃ አስተዳደሪዎች የሚታዘዙ ወጣቶቹ ወታደሮች ግንባር ቀደም ሆነው ወጡ። 20 እያንዳንዱም ውጊያ የገጠመውን ጠላቱን ገደለ። ሶርያውያንም ሸሹ፤ እስራኤላውያንም ያሳድዱአቸው ጀመር። ቤን ሀዳድ ግን በፈረሱ ላይ ተቀምጦ ከጥቂት ፈረሰኞች ጋር ሸሽቶ አመለጠ። 21 ንጉሥ አክዓብም ወደ ጦሩ ሜዳ ገብቶ የጠላትን ፈረሶችና ሠረገሎችን ማረከ። በሶርያውያን ላይ ታላቅ ጥፋት በማድረስ ድል አደረጋቸው። 22 ስለዚህ ነቢዩ ወደ ንጉሥ አክዓብ ቀርቦ፦ የሶርያ ንጉሥ በሚመጣው የጸደይ ወራት እንደገና አደጋ ስለሚጥልብህ ተመልሰህ ሂድና ሠራዊትህን በማጠናከር አደራጅ፤ ጥንቃቄ የሞላበትንም የጦርነት ስልት አዘጋጅ አለው። 23 አገልጋዮቹም ንጉሥ ቤን ሀዳድን እንዲህ አሉት፦ የእስራኤል አማልክት የተራራ አማልክት ናቸው። እስራኤላውያን እኛን ማሸነፍ የቻሉት ስለዚህ ነው። በሜዳማ ስፍራዎች ጦርነት ብንገጥማቸው ግን እናሸንፋለን። 24 ስለዚህ አሁን ሠላሳ ሁለቱን ነገሥታት ከጦር አዛዥነታቸው ሽረህ በእነርሱ ቦታ ሌሎችን የጦር አዛዦች ሹም። 25 ከዚህ በፊት የተደመሰሰውን የሚያህል ብዙ ሠራዊትና በቀድሞዎቹ ልክ ፈረሶችንና ሠረገሎችን አደራጅ፤ ከዚያ በኋላ እስራኤላውያንን በሜዳ ተዋግተን ድል እንነሣቸዋለን። ስለዚህ ቤን ሀዳድም በእነርሱ ምክር ተስማምቶ ለመፈጸም ወሰነ። 26 ከዚያም በተከታዩ የጸደይ ወቅት ሠራዊቱን በአንድነት ጠርቶ እስራኤልን ለመዋጋት ወደ አፌቅ ከተማ ገሠገሠ። 27 እስራኤላውያን ተጠርተው ከሚያስፈልጋቸው ስንቅና ትጥቅ ጋር ለጦርነት ተዘጋጁ፤ እነርሱም ወደ ጦርነቱ በመዝመት በሁለት ቡድን ተከፍለው ከሶርያውያን ፊት ለፊት ባለው ቦታ ሰፈሩ። የእስራኤል ወታደሮች ቁጥር አገሩን ካጥለቀለቀው ከሶርያውያን ሠራዊት ብዛት ጋር ሲነጻጸር ከሁለት የተከፈለሉ የጥቂት ፍየሎች መንጋዎች ይመስሉ ነበር። 28 አንድ የእግዚአብሔር ነቢይ ወደ ንጉሥ አክዓብ ቀርቦ እግዚአብሔር የተናገረው ቃል ይህ ነው፤ ሶርያውያን፦ እግዚአብሔር የኮረብቶች አምላክ እንጂ የሜዳዎች አምላክ አይደለም ብለዋል፤ ከዚህም የተነሣ እኔ እጅግ ብዙ የሆነውን ሠaርዊታቸውን በእጅህ አሳልፌ እሰጣለሁ። አንተና ሕዝብህም እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ታውቃላችሁ አለው። 29 ስለዚህ ሶርያውያንና እስራኤላውያን ፊት ለፊት ተፋጠው በየጦር ሰፈራቸው እስከ ሰባት ቀን ቆዩ፤ በሰባተኛውም ቀን ጦርነት ጀምረው በዚያኑ ቀን እስራኤላውያን አንድ መቶ ሺህ የሶርያውያንን እግረኛ ጦር ወታደሮችን ገደሉ። 30 ከሞት የተረፉትም ሶርያውያን ሸሽተው ወደ አፌቅ ከተማ ገቡ፤ በዚያም ቁጥራቸው ሃያ ሰባት ሺህ በሚሆኑት ወታደሮች ላይ የከተማው ቅጥር ተንዶባቸው አለቁ። ቤን ሀዳድም አምልጦ ወደ ከተማይቱ ገብቶ ከአንድ ቤት በስተ ኋላ በኩል ባለው ክፍል ውስጥ ተደበቀ። 31 የቤን ሀዳድ አገልጋዮች ወደ እርሱ ቀርበው፣ የእስራኤል ነገሥታት ምሕረት አድርጊዎች መሆናቸውን ሰምተናል፤ ስለዚህ በወገባችን ማቅ ታጥቀን፣ በራሳችንም ገመድ ጠምጥመን ወደ እስራኤል ንጉሥ ሄደን ምሕረት እንድንጠይቀው ፍቀድልን፤ ምናልባትም ሕይወትህን ያተርፍ ይሆናል አሉት። 32 ከዚህም በኋላ እነርሱ በወገባቸው ማቅ ታጥቀው በራሳቸውም ገመድ ጠምጥመው ወደ ንጉሥ አክዓብ በመሄድ አገልጋይህ ቤን ሀዳድ ምሕረት አድርገህ ሕይወቱን እንድታተርፍለት ይማጠንሃል አሉት። አክዓብም እርሱ እስከ አሁን በሕይወት አለ ማለት ነውን? ከሆነስ መልካም ነው፤ እንግዲህ እርሱ ለእኔ እንደ ወንድም ነው ሲል መለሰላቸው። 33 የቤን ሀዳድ አገልጋዮችም የምሕረት መልእክት ይጠባበቁ ስለ ነበር አክዓብ ወንድሜ ሲል በሰሙ ጊዜ ወዲያውኑ ቀበል አድገርው አንተ እንዳልከው ቤን ሀዳድ በእርግጥ ወንድምህ ነው አሉት። አክዓብም ወደ እኔ አምጡት! አላቸው። ቤን ሀዳድም በመጣ ጊዜ አክዓብ ወደ ሠረገላው ገብቶ እንዲቀመጥ ቤን ሀዳድን ጋበዘው። 34 ቤን ሀዳድም አክዓብን አባቴ ከአባትህ የወሰዳቸውን ከተሞች እመልስልሃለሁ፤ አባቴ በሰማርያ እንዳደረገው ሁሉ አንተም በደማስቆ ለራስህ የንግድ ማእከል ልታቋቁም ትችላለህ አለው። አክዓብም እንግዲያውስ በዚህ ስምምነት መሠረት እኔም በነጻ እለቅሃለሁ ሲል መለሰለት። አክዓብም በዚህ ዓይነት ከእርሱ ጋር የውል ስምምነት አድርጎ በነጻ እንዲሄድ ፈቀደለት። 35 የነቢያት ወገን የሆነ አንድ ነቢይ በእግዚአብሔር ታዞ የእርሱ ጓደኛ የሆነውን ሌላ ነቢይ ምታኝ አለው። ነቢዩ ግን እርሱን ለመምታት እምቢ አለ። 36 ስለዚህም ያ ነቢይ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መፈጸም እምቢ ስላልክ ከእኔ ተለይተህ እንደ ሄድክ ወዲያውኑ አንበሳ ይገድልሃል አለው፤ ከእርሱ ተለይቶ እንደ ሄደ አንበሳ በድንገት ወደ እርሱ መጥቶ ገደለው። 37 ከዚህም በኋላ ነቢዩ ወደ ሌላ ሰው ሄዶ ምታኝ አለው፣ ያም ሰው መትቶ አቆሰለው፤ 38 ነቢዩ ማንነቱ እንዳይታወቅ ፊቱን በጨርቅ ሸፈነ፤ ሄዶም በዚያ በኩል የሚያልፈውን የእስራኤል ንጉሥ ለመጠበቅ በመንገድ ዳር ቆመ። 39 ንጉሡም በአጠገቡ ሲያልፍ ነቢዩ ተጣርቶ እንዲህ ሲል ጮኸ፦ ንጉሥ ሆይ እኔ በጦርነት ውስጥ በወጊያ ላይ ነበርኩ፤ በዚያን ጊዜም ከወታደሮቹ አንዱ ከጠላት ወገን አንድን ሰው ማርኮ በማምጣት ይህን ሰው ጠብቅ፣ ቢያመልጥ ግን በእርሱ ፈንታ አንተ ትገደላለህ ወይም ሠላሳ አንድ መክሊት የሚመዝን ብር መቀጫ ትከፍላለህ አለኝ። 40 ነገር ግን እኔ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሥራ በዝቶብኝ ወዲያ ወዲህ ስል ሰውየው አምልጦ ሄደ። ንጉሡም በራስህ ላይ ስለ ፈረድህ መቀጣት ይገባሃል አለው። **41** ነቢዩ ፊቱ የተሸፈነበትን ጨርቅ ፈጥኖ አወለቀ፤ ንጉሡም ይህ ሰው ከነቢያት ወገን አንዱ መሆኑን ወዲያውኑ አወቀ። **42** ነቢዩም ንጉሡን እንዲህ አለው፦ እግዚአብሔር የተናገረው ቃል ይህ ነው፤ እኔ ይገደል ብዬ የፈረድኩበት ሰው እንዲያመልጥ ስለ ፈቀድህ በእርሱ ፈንታ አንተ በሞት ትቀጣለህ፤ የዚያ ሰው ሠራዊት አምልጦ እንዲሄድ ስላደረገ ሠራዊትህም ይደመሰሳል። **43** ስለዚህ ንጉሡ እያዘነና እየተበሳጨ ወደ ቤቱ ወደ ሰማርያ ተመልሶ ሄደ።

---

1 Kings 20:1

ቤን ሀዳድ
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰላሳ ሁለት አነስተኛ ንጉሦች
"32 አነስተኛ ንጉሦች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

አነስተኛ ንጉሦች
"አነስተኛ የህዝብ ቁጥር የሚገዙ ንጉሦች"

1 Kings 20:4

አንተ እንዳልከው ይሁን
ይህ ስምምነትን የሚገልጽ ፈሊጥ ነው። "ከአንተ ጋር እስማማለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ነገ በዚህን ጊዜ
"ነገ ልክ በዛሬው ሰዓት"

እነርሱን በዐይናቸው ፊት ደስ እንዳሰኛቸው
እዚህ ስፍራ "ዐይኖች" የሚለው የሚወክለው ትኩረት ሰትተው አንዳች ነገር የሚመለከቱ እና ያንን የሚገልጹ ሰዎችን ያመለክታል። "እነርሱን ደስ የሚያሰኘውን ነገር በሙሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 20:7

የአገሪቱን
"የአገሪቱ" የሚለው የሚወክለው በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ሁሉ ነው። "የእስራኤል ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ልብ ብላችሁ ተመለከቱ
"ልብ በሉ" የሚለው በጥንቃቄ ምልከታ ለማድረግ ፈሊጥ ነው። "የቅርብ ትኩረት ስጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈለጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ቀድሞ ያለውን አልተቃወምኩትም
ይህ በአዎንታ ሊተረጎም ይችላል። "ለጠየቀው ስምምነቴን ገልጫለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ አሉታ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 20:9

አማልዕክት ይህን ያድርጉብኝ ይህንንም ይጨምሩብኝ
ይህ በትልቅ ትኩረት የተሰጠ መሃላ ነው። ይህ በ 1 ነገሥት 19:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

የሰማርያ አመድ እኔን ለሚከተል ለእያንዳንዱ ሰው አንድ እፍኝ የሚደርስ ቢሆን እንኳን
ቤን ሀዳድ የእርሱ ሰራዊት በሰማርያ የሚገኘውን ነገር ሁሉ እንደሚያጠፋ እያስፈራራ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 20:11

ለቤን ሀዳድ እንዲህ በሉት፣ ‘የጦር ልብሱን የለበሰ ማንም ሰው... እርሱ ያንን እንዳወለቀው
ይህ ምክር ለመስጠት የሚውል ገለጻ ነው። "የጦርነት ልብስ መታጠቅ" ለጦርነት ዝግጁ ለመሆን ሜቶኖሚ/ ነው። "ቤን ሀዳድን እንዲህ በሉት፣ ‘ገና ያልተዋጋኸውን ጦርነት በድል እንደተወጣ ሰው አትኩራራ።’" (ምሳሌያዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

1 Kings 20:13

ከዚያ እነሆ
"እነሆ" የሚለው በታሪኩ ውስጥ አዲስ ሰው በድንገት ብቅ እንደሚል ያነቃናል። የእናንተ ቋንቋ ይህን የሚገልጽበት መንገድ ሊኖረው ይችላል።

ይህን ታላቅ ሰራዊት አያችሁን?
ያህዌ ይህን ጥያቄ የሚጠይቀው የቤን ሀዳድን ሰራዊት መጠን እና ጥንካሬ አጉልቶ ለመግለጽ ነው። "ይህንን ታላቅ ሰራዊት ተመልከቱ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ፣ ዛሬ በእጃችሁ ላይ እጥለዋለሁ/አደርገዋለሁ
"እነሆ" የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚሆነው አስደናቂ መረጃ ትኩረት እንደንሰጥ ያነቃናል።

በእጃችሁ ላይ አደርገዋለሁ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል ሀይልን ያመለክታል። "በዚያ ሰራዊት ላይ ድል እሰጣችኋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በማን?
አክዓብ ‘ይህን ታደርጋለህን' የሚለውን ቃል ትቶታል። "ይህን በማን ታደርጋለህ?" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኢሊፕሲስ/የተተወ ወይም የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

አክዓብ ወጣት መኮንኖችን ጠራ
"አክዓብ ወጣት መኮንኖችን ሰበሰበ"

ሁሉም ወታደሮች፣ መላው የእስራኤል ሰራዊት
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው ተጣምረው የቀረቡት ትኩረት ለመስጠት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባት ሺህ
"7,000" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 20:16

እነርሱ ወጥተው ሄዱ
እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው የሚያመለክተው የእስራኤል ወታደሮችን ነው።

ሰላሳ ሁለት አነስተኛ ንጉሦች
ይህ በ1 ነገሥት 20፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ቤን ሀዳድ በወጣት ቃፊሮች መውጣት እንዳለበት ተነግሮት ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ቤን ሀዳድ የላካቸው ቃፊሮች መረጃ ሰጡት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ወጣት ቃፊሮች/ስካውቶች
"ስካውት/ቃፊር" ስለ ጠላት ሰራዊት መረጃ የሚሰበስብ ወታደር ነው።

1 Kings 20:18

ቤን ሀዳድ እንዲህ አለ
ቤን ሀዳድ ለወታደሮቹ እንሚናገር ግልጽ ነው። "ቤን ሀዳድ ለወታደሮቹ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኢሊፕሲስ/የተተወ ወይም የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ... ወደ ወሰዷቸው ስፍራ
እዚህ ስፍራ "እነርሱ" እና "የእነርሱ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት የስስራኤልን ሰራዊት ነው

ስለዚህ ሰራዊቱ....ወጣቶቹን መኮንኖች ተከተለ
"የእስራኤል ሰራዊት...ወጣቶቹን እስራኤላውያን መኮንኖች ተከተለ"

1 Kings 20:20

እስራኤል እነርሱን ተከተለ
"እስራኤል" ለመላው የእስራኤል አገር ወታደሮች ሴኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ነው። "የእስራኤል ሰራዊት ወንዶች ሁሉ እነርሱን ተከተለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ንጉሥ ወጥቶ ጥቃት አደረሰ
"ንጉሡ" እርሱን ለሚያገለግሉ ወታደሮች እና ለንጉሡ ሴኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ነው። "የእስራኤል ንጉሥ እና የእርሱ ወታደሮች ወጥተው ጥቃት አደረሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 20:22

ራስህን አጠናክር
"ራስህን" የሚለው የሚወክለው በሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የንጉሡን ሰራዊት ነው። "ሀይልህን አጠናክር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

መረዳት እና ማቀድ
እነዚህ ሁለት ቃላት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው የተጣመሩት ትኩረት ለመስጠት ነው። "መወሰን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

በሚመጣው አመት
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "በቀጣዩ አመነት ፀደይ ወቅት" ወይም 2) "በሚመጣው አመት በዚህን ጊዜ።"

እኛ በአንድነት እንዋጋ... እኛ ብርቱዎች ነን
"እኛ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው አገልጋዮችን፣ ንጉሡን፣ እና ጠቅላላውን ሰራዊቱን በአንድ ላይ ነው። (ሁሉንም አካታች የሆነ "እኛ" የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 20:24

ሁሉንም ንጉሦች ከስልጣናቸው ስፍራ አስወግዳቸው
"ወታደሮችህን የሚመሩትን ሰላሳ ሁለቱን ንጉሦች በሙሉ ማስወገድ አለብህ"

1 Kings 20:26

አፌቅ
ይህ የከተማ ስም ነው። (ስሞች አንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በእስራኤል ላይ መነሳት/እስራኤልን መውጋት
"እስራኤል" የሚለው የሚወክለው የእስራኤልን ሰራዊት ነው። "ከእስራኤል ሰራዊት ጋር መዋጋት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ሰዎች ተሰባስበው እና አቅርቦት አግኝተው ነበር
ይህ በዐድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የእስራኤል ሰራዊትም ደግሞ በአንድነት ተሰበሰበ፣ አዛዦችም ለጦርነት የሚያስፈልጋቸውን ትጥቅ ሰጧቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ትንንሽ ሁለት የፍየል መንጎች
ይህ ተነጻጻሪ ዘይቤ የእስራኤልን ሰራዊት ከሁለት ትንንሽ የፍየሎች መንጋ ጋር ያነጻጽራል። "የእስራኤላውያን ሰራዊት እንደ ሁለት የፍየሎች መንጋ ትንሽ እና ደካማ መስሎ ታየ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 20:28

የእግዚአብሔር ሰው
ይህ የነቢይ ሌላው መጠሪያ ነው። "ነቢይ" እንደሚለው

ይህን ታላቅ ሰራዊት በእጅህ አሳልፌ እሰጥሃለሁ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው የሚያመለክተው ሀይልን ነው። "በዚህ ታላቅ ሰራዊት ላይ ለአንተ ድል እሰጥሃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 20:29

ሰባት ቀናት
"7 ቀናት" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

100,000
"አንድ መቶ ሺህ" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

እግረኞች
"እግረኛ" በእግሩ የሚጓዝ ወታደር ነው።

አፌቅ
ይህ የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሃያ ሰባት ሺህ
"27,000" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 20:31

እነሆ ተመልከት/አድምጥ
ይህ እነርሱ የሚናገሩነትን ያጎላል። "አድምጠን" ወይም "የምንነግርህን ትኩረት ሰጥተህ ስማ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በወገባችን ዙሪያ ማቅ እናደርጋለን፣ በራሳችን ላይ ገመድ እንጠመጥማለን
ይህ መማረክ ምልክት ነው

እስከ አሁን በህይወት አለን?
አክአብ ይህን ጥያቄ ያነሳው መደነቁን ለመግለጽ ነው። "እርሱ እሰከ አሁን በህይወት በመኖሩ ተደንቄያለሁ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ወንድሜ ነው
እዚህ ስፍራ "ወንድሜ/የእኔ ወንድም" መልካም ወዳጅ ለሆነ ሰው ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። "እርሱ ለእኔ ልክ እንደ ወንድም ነው" ወይም "እርሱ ልክ እንደ ቤተሰብ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 20:33

አሁን ሰዎቹ
"አሁን" የሚለው ቃል "በዚህ ጊዜ" ማለት አይደለም፤ ነገር ግን ቀጥሎ ለሚሆነው ጠቃሚ ነጥብ ትኩረትን ለመሳብ የዋለ ነው።

ከአክዓብ ዘንድ ለሆነ ማናቸውም ምልክት
"ምልክት" ትርጉም ለሚሰጥ ድርጊት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ/ ነው። "ከአክዓብ ዘንድ ለሆነ፣ አክዓብ ምህረት ለመስጠት መፈለጉን ለሚያሳይ ማናቸውም ድርጊት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 20:35

ከነቢያት ወንዶች ልጆች አንዱ
"ከነቢያት ወገን መሃል አንዱ"

የያህዌ ቃል
"ከያህዌ ዘንድ የሆነ መልዕክት" ወይም "የያህዌ መልዕክት"

1 Kings 20:39

አገልጋይህ ወጥቶ ይሄዳል
ነቢዩ ራሱን በሶስተኛ መደብ መግለጹ ለንጉሡ ላለው ክብር ምልክት ነው።

ወደ ጦርነቱ ግለት
እዚህ ስፍራ "የጦርነቱ ግለት" እጅግ ከባድ እና ከባድ የሆነውን ውጊያ የሚገልጽ ፈሊጥ ነው። "ጦርነቱ በጣም በበረታበት ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ ህይወት በእርሱ ህይወት ምትክ ይሰጣል
"አንተ በእረሱ ስፍራ ትሞታለህ"

አንድ ታላንት/መክሊት ብር
ታላንት/መክሊት ወደ 33 ኪሎግራም የሚጠጋ የክብደት መለኪያ ነው። "33 ኪሎግራም ብር" (መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት ወቅት የክብደት መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

እዚህና እዚያ ማለት
በጣም መሯሯጥን እና በስራ መያዝን የሚወክል ፈሊጥ ነው። "ሌሎች ነገሮችን ማድረግ" ወይም "ይህንን እና ያንን ማድረግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 20:41

ከእጅህ ለቀኸዋል
እዚህ ስፍራ "እጅ" ለሀይል ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "መልቀቅ" ወይም "ህይወትን ማዳን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ ህይወት በእርሱ ህይወት ስፍራ ይሆናል፣ ደግሞም
የአንተ ህዝብ በእርሱ ህዝብ ቦታ ይሆናል "አንተ በእርሱ ምትክ ትሞታለህ፣ ደግሞም ህዝብህ በእርሱ ህዝብ ምትክ ይሞታል"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 21

1 ከጥቂት ጊዜ በኋላ ናቡቴ ተብሎ የሚጠራ ሰው በኢይዝራኤል በሚገኘው በንጉሥ አክዓብ ቤተ መንግሥት አጠገብ የራሱ ርስት የሆነ አንድ የወይን ተክል
ቦታ ነበረው። 2 አንድ ቀን አክዓብ ናቡቴን የወይን ተክል ቦታህን ስጠኝ፤ በቤተ መንግሥቴ አጠገብ ስለ ሆነ የአትክልት ቦታ ላደርገው እፈልጋለሁ፤ በምትኩ
ከእርሱ የተሻለ የወይን ተክል ቦታ እሰጥሃለሁ፤ ልትሸጠው ብትፈልግም የተሻለ ዋጋ እከፍልሃለሁ አለው። 3 ናቡቴም ይህንን የወይን ተክል ቦታ የወረስኩት
ከቅድም አያቶቼ ነው፤ ለአንተ ከመስጠትስ እግዚአብሔር ይጠብቀኝ! ሲል መለሰለት። 4 አክዓብ ኢይዝራኤላዊው ናቡቴ ከአባቶቼ የወረስኩትን ለአንተ
አልሰጥህም ስላለው በንዴት እየተበሳጨ ወደ ቤቱ ገባ፤ ፊቱንም ወደ ግድግዳ አዙሮ በአልጋው ላይ ተጋደመ፤ ምግብ መብላትም አልፈቀደም። 5 ሚስቱም
ኤልዛቤል ወደ እርሱ ቀርባ እንደዚህ ያበሳጨህ ነገር ምንድን ነው? ስለምንስ ምግብ አትበላም? ስትል ጠየቀችው። 6 እርሱም እኔን ያበሳጨኝ ከናቡቴ ያገኘሁት
መልስ ነው፤ ይኸውም የእርሱን የወይን ተክል ቦታ እንድገዛ ወይም ከፈለገ ልዋጩን እንድሰጠው ብጠይቀው የወይን ተክል ቦታውን አልሰጥህ ብሎ አናደደኝ
ሲል መለሰላት። 7 ኤልዛቤልም እንግዲህ አንተ የእስራኤል ንጉሥ ሆነህ ሳለህ እንደዚህ መሆን ይገባሃልን? ይልቅስ ተነሥ ተደሰት፤ እህል ውሃም ቅመስ። እኔ
የናቡቴን የወይን ተክል ቦታ እንድታገኝ አደርጋለሁ አለችው። 8 ስለዚህ እርስዋ ደብዳቤ ጽፋና በአክዓብ ስም ፈርማ የእርሱን ማኅተም አተመችበት፤
ደብዳቤውንም ናቡቴ ወደሚኖርባት ወደ ኢይዝራኤል ባለሥልጣኖችና ሽማግሌዎች ላከች። 9 ደብዳቤውም እንዲህ የሚል ነበር፦ የአንድ ቀን ጾም አውጁ፤
ሕዝቡንም በአንድነት ሰብስቡ፤ ለናቡቴም የክብር ቦታ ስጡት፤ 10 እግዚአብሔርንና ንጉሡን ሰድቦአል ብለው የሚናገሩ ሁለት የሐሰት ምስክሮችንም አቅርቡ፤
ከዚያ በኋላ ናቡቴን ከከተማው ውጪ አወጥታችሁ በድንጋይ ተወግሮ ይሙት። 11 ስለዚህ የኢይዝራኤል ባለሥልጣኖችና ሽማግሌዎችም በደብዳቤው
እንደተገለጸው ኤልዛቤል ያዘዘቻቸውን አደረጉ። 12 የአንድ ቀን ጾም አወጁ፤ ሕዝቡንም በአንድነት ሰበሰቡ፤ ለናቡቴም የክብር ቦታ ሰጡት። 13 ሁለቱም የሐሰት
ምስክሮች ተነሥተው ናቡቴ እግዚአብሔርንና ንጉሡን ሰድቦአል ብለው በሕዝቡ ፊት በሐሰት መሰከሩበት፤ ስለዚህም ከከተማይቱ ውጪ በመውሰድ በድንጋይ
ወግረው ገደሉት። 14 ናቡቴ ተወግሮ ተገድሎአል የሚል መልእክትም ወደ ኤልዛቤል ላኩ። 15 ኤልዛቤልም መልእክቱን እንደ ተቀበለች ወዲያውኑ አክዓብን
ናቡቴ ሞቶአል፤ አሁን ተነሥተህ ሂድና ለአንተ ለመሸጥ እምቢ ያለውን የወይን ቦታ ርስት አድርገህ ውሰድ አለችው። 16 አክዓብም የናቡቴን የወይን ተክል ቦታ
ለመውረስ ወዲያውኑ ተነሥቶ ሄደ። 17 ከዚያም የእግዚአብሔር ቃል ወደ ቴስቢያዊው ወደ ኤልያስ እንዲህ ሲል መጣ። 18 ተነሥተህ ሂድና የእስራኤልን ንጉሥ
አክዓብን በሰማርያ አግኘው፤ እርሱ የናቡቴን የወይን ተክል ቦታ ለመውረስ ሄዶአል፣ በዚያው ታገኘዋለህ፤ 19 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ብለህ መናገር አለብህ፣
ናቡቴን ገድለህ ሀብቱንም ወሰድክበትን? ከዚያም እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ የናቡቴን ደም ውሾች በላሱበት ስፍራ የአንተንም ደም እንደዚሁ ይልሱታል። 20
አክዓብ ኤልያስን ባየው ጊዜ ጠላቴ ሆይ አገኘኸኝን? አለው። እርሱም እንዲህ አለ፣ አዎን አግኝቼሃለሁ፤ በእግዚአብሔር ላይ ክፉ ለማድረግ ራስህን ሸጠከውን?
አለው። 21 ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲህ ይልሃል፣ እነሆ በአንተ ላይ መቅሠፍትን አመጣብሃለሁ፤ አንተን ከፊቴ አስወግዳለሁ፤ ከቤተ ሰብህም ውስጥ ወንድ
የሆነውን ሁሉ ባሪያ ሆነ ነጻ ሰው አጠፋለሁ። 22 እስራኤልን ወደ ኃጢአት በመምራታችሁ ቁጣዬን ስለ አነሣሣህ ቤተ ሰብህን እንደ ናባጥ ልጅ እንደ ንጉሥ
ኢዮርብዓም ቤተ ሰብና እንደ አኪያ ልጅ እንደ ንጉሥ ባኦስ ቤተ ሰብ ለጥፋት የተጋለጠ ይሆናል። 23 ስለ ኤልዛቤልም እግዚአብሔር የሚለው ይህ ነው፦
በኢይዝራኤል ከተማ ውስጥ ሬሳዋን ውሾች ይበሉታል። 24 ከአክዓብም የሆነውን ሁሉ በከተማው ውስጥ የሚሞተውን ማንኛውንም ሰው ውሾች ይበሉታል፤
በገጠርም በየሜዳው የሚሞተውን ሁሉ የሰማይ አሞራዎች ይበሉታል። 25 በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገር በማድረግ ለኤልዛቤል ኃጢአት ራሱን አሳልፎ የሸጠ
አክዓብን የሚመሰል ማንም አልነበረም። ይህን ሁሉ ያደረገው ሚስቱ ኤልዛቤል ወደ ክፋት ስለ መራችው ነው። 26 አክዓብ ከፈጸመው አሳፋሪ በደል ሁሉ
ዋናው እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ፊት ነቃቅሎ ያጠፋቸውን የአሞራውያንን ጣዖት ማምለኩ ነበር። 27 አከዓብም ይህንን በሰማ ጊዜ፦ ልብሱን ቀዶ ማቅ
ለበሰ፤ ማቁን እንደ ለበሰ ይተኛ ነበር፤ ሲሄድም ከጭንቀቱ ብዛት የተነሣ አዘኖ ነበር። 28 የእግዚአብሔርም ቃል ወደ ቴስቢያዊው ወደ ኤልያስ እንዲህ ሲል
መጣ፦ 29 አክዓብ በእኔ ፊት ራሱን እንዴት እንዳዋረደ ተመልክተሃልን? እግዚአብሔርም በፊቴ ራሱን ስላዋረደ በሕይወቱ ዘመን መቅሠፍትን በአክዓብ ቤተ ሰብ
ላይ አላመጣበትም፤ የማመጣውም በልጁ ዘመን ይሆናል።

---

1 Kings 21:1

ከጥቂት ጊዜ በኋላ
ይህ ሀረግ የታሪኩን አዲስ ክፍል ጅማሬ ያመለክታል፣ ደግሞም እነዚህ ትዕይንቶች ቆይቶ እንደሚፈጸሙ ያመለክታል፤ ናቡቴ የወይን እርሻውን ቆይቶ እንደሚወስድ አስተውሉ። የእናንተ ቋንቋ የታሪኩን አዲስ ክፍል ጅማሬ የሚያመለክትበት መንገድ ካለው እዚህ ስፍራ ያንን መጠቀም ትችላላችሁ። "ከጥቂት ጊዜ በኋላ የሆነው ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

ኢይዝራኤላዊው ናቡቴ
ይህ ከኢዝራኤል የሆነው ሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰማርያ ንጉሥ
"ሰማርያ" የእስራኤል መንግሥት ዋና ከተማ የነበረች ስትሆን እዚህ ስፍራ መላውን አገር ትወክላለች። "የእስራኤል ንጉሥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 21:3

እኔ አሳልፌ መስጠቴን ያህዌ ይከልክል
ይህ ሀረግ ቀጣዩ ነገር እንደማይሆን ትኩረት የሚሰጥ መሃላ ነው። "ያህዌ ይህንን ባለመፍቀዱ ምክንያት፣ እኔ በፍጹም ይህን አልሰጥህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የአባቶቼን ውርሰ ርስት ለአንተ እሰጥ ዘንድ
አባቶቹ ቋሚ ሀብት አድርገው የወረሱት ምድር የተገለጸው ውርሰ ርስት ተደርጎ ነው። "አባቶቼ ርስት አድርገው የተቀበሉትን መሬት ለአንተ መስጠት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 21:5

ለምን ልብህ እጅግ አዘነ
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚያመለክተው የሰውን ጠቅላላ ማንነት እና ስሜት ነው። "ለምን እንዲህ እጅግ አዘንክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እስከ አሁንስ ድረስ እስራኤልን እየገዛህ አይደለምን?
ኤልዛቤል ይህንን አሉታዊ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመችው አክዓብን ለመገሰጽ ነው። ይህ በአዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንተ እስካሁን እስራኤልን እየገዛህ ነው!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ልብህ ደስተኛ ይሁን
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚያመለክተው የሰውን ጠቅላላ ማንነት እና ስሜት ነው። "ደስተኛ ሁን" ወይም "ተበረታታ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 21:8

በአክዓብ ስም ደብዳቤ ጻፈች
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) በደብዳቤው ላይ የአክዓብን ስም ጻፈች። "ደብዳቤ ጽፋ በአክዓብ ስም ፈረመችበት" ወይም 2) "ስም" የሚለው ቃል ለስልጣን ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "በአክአብ ስም ደብዳቤ ጻፈች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከእነርሱ ጋር የተቀመጡ/የሚኖሩ ባለጸጎች
"ባለጸጋ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ባለጸጋ ሰዎችን ነው። "ከናቡቴ ጋር የሚኖሩ ባለጸጋ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ናቡቴን ከህዝቡ በላይ አስቀምጡ
ናቡቴን በክብር ስፍራ ማስቀመጥ የሚለው የተገለጸው፤ በዚያ ከነበሩ ሰዎች በላይ ከፍ ብሎ እንደ ተቀመጠ ተደርጎ ነው። "ናቡቴን በህዝቡ መሃል ከፍ ባለ ስፍራ አስቀምጡት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ ላይ ይመስክሩበት
"እርሱን ወንጅሉት/በሀሰት ክሰሱት"

1 Kings 21:11

በናቡቴ ከተማ የሚኖር ባለጸጋ
"ባለጸጋ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሃብታም ሰዎችን ነው። "በናቡቴ ከተማ የሚኖሩ ባለጸጋ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

በደብዳቤዎቹ ውስጥ ተጽፎ እንደነበረው
ይህ በአድርጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በደብዳቤዎቹ ውስጥ እንደጻፈችው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ናቡቴን ከህዝቡ በላይ አስቀመጡት
ናቡቴን በክብር ስፍራ ማስቀመጥ የሚለው የተገለጸው፤ በዚያ ከነበሩ ሰዎች በላይ ከፍ ብሎ እንደ ተቀመጠ ተደርጎ ነው። ይህ ሀሳብ በ1 ነገሥት 21:9 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ናቡቴን በሰዎች መሃል በክብር ስፍራ አስቀምጡት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከናቡቴ ፊት ተቀመጡ
"ከናቡቴ ፊት ለፊት ተቀመጡ"

እነርሱ ተሸክመው አወጡት
እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የከተማዋን ሰዎች ነው።

ናቡቴ በድንጋይ ተወግሮ ተገደለ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኛ ናቡቴን በድንጋይ ወገርነው፣ እርሱም ሞተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 21:15

ናቡቴ በድንጋይ ተወግሮ ተገደለ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች ናቡቴን በድንጋይ ወገሩት፣ እርሱም ሞተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ናቡቴ በህይወት የለም፣ ሞቷል
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው የኤልዛቤልን ሀሳብ መፈጸም ያጎላሉ። "ናቡቴ ሞቷል!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 21:17

የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል መጣ
የዚህ ፈሊጥ ትርጉም ያህዌ ተናገረ ወይም መልዕክት ላከ ማለት ነው። ይህ በ1 ነገሥት 6:11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ተናገረ" ወይም "ያህዌ ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 21:19

ገድላችሁት ደግሞም ርስቱን ወሰዳችሁን?
ያህዌ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው አክዓብን ለመገሰጽ ነው። "ናቡቴን ገደላችሁት ደግሞም የወይን እርሻውን ሰረቃችሁት!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተን ደም፣ የአንተን ደም
ይህ የተደገመው ትኩረት ለመስጠት ነው

ጠላቴ ሆይ፣ አገኘኸኝን?
አክዓብ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው በኤልያስ ላይ ያለውን ቁጣ ለመግለጽ ነው። ይህም ኤልያስ አክዓብን "ማግኘቱ" ሊያመለክት የሚችለው ኤልያስ የአክዓብን ድርጊቶች ማወቁን እንጂ በአካል እርሱን ማግኘቱን አይደለም። "ጠላቴ ሆይ፣ አንተ እኔን አገኘኸኝ!" ወይም "ጠላቴ ሆይ፣ እኔ ያደረግኸውን ደረስክበት!" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ክፉ የሆነውን ለማድረግ ራስህን አሳልፈህ ሸጥክ
ክፉ የሆነን ነገር ለማድረግ ራሱን አሳልፎ የሰጠ ሰው፣ ራሱን ለክፉ አሳልፎ እንደሸጠ ተደርጎ ይገለጻል። "ክፉ የሆነውን ነገር ለማድረግ ራስህን አሳልፈህ ሰጥተሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 21:21

እነሆ
"ተመልከት" ወይም "አድምጥ" ወይም "ቀጥሎ ለምነግርህ ትኩረት ስጥ"

በእስራኤል ከአንተ ዘንድ ሙሉ ለሙሉ እያንዳንዱን ወንድ ልጅ እና ባሪያ እንዲሁም ነጻ ሰው ጨርሼ እቆርጣለሁ፣ አጠፋለሁ
ያህዌ የአክዓብን ቤተሰብ እንደሚያጠፋ እና ትውልድ እንዳይኖረው እንደሚያደርግ የገለጸው እሳት እንጨትን እንደሚበላ እንደዚሁም አንድ ሰው የዛፍን ቅርንጫፍ በሙሉ እንደሚቆርጥ አድርጎ ነው። "በእስራኤል የአንተን ወንድ ልጆች ሁሉ ባሪያም ሆነ ነጻ ሰው ሳላስቀር አጠፋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ቤተሰብህን እንደ ኢዮርብዓም ቤተሰብ አደርጋለሁ...
እንደዚሁም እንደ ባኦስ ቤተሰብ አደርግሃለሁ ያህዌ የአክዓብን ቤተሰብ፣ የኢዮርብዓምን እና የባኦስን ቤተሰብ እንዳጠፋቸው ያጠፋል።

1 Kings 21:23

የአክዓብ የሆነ ሁሉ
"የአክዓብ ቤተሰብ የሆነ ሁሉ"

1 Kings 21:25

ክፉ የሆነውን ለማድረግ ራሱን የሸጠውን
ክፉ የሆነን ነገር ለማድረግ ራሱን አሳልፎ የሰጠ ሰው፣ ራሱን ለክፉ አሳልፎ እንደሸጠ ተደርጎ ይገለጻል። ይህ ሀሳብ በ1 ነገሥት 21፡20 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ክፉ የሆነን ነገር ለማድረግ ራሱን አሳልፎ የሰጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በያህዌ ዕይታ ክፉ የሆነውን
"በ...እይታ" የሚለው ሀረግ የሚያመለክው አስተያየት ነው። ይህ በ1 ነገሥት 11፡6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ክፉ ብሎ የሚቆጥረውን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከእስራኤል ህዝብ ፊት ያስወገዳቸው
እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚያመለክተው መላውን የእስራኤል አስራ ሁለት ነገዶች እነጂ ሰሜናዊውን ግዛት ብቻ አይደለም። "ከእስራኤል ህዝብ መገኘት ያስወገዳቸው" ወይም "ከእስራኤል ህዝብ ምድር ፊት ያስወጣቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 21:27

የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል መጣ
የዚህ ፈሊጥ ትርጉም ያህዌ ተናገረ ወይም መልዕክት ላከ ማለት ነው። ይህ በ1 ነገሥት 6፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ተናገረ" ወይም "ያህዌ ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አክዓብ እንዴት ራሱን በእኔ ፊት ትሁት እንዳደረገ አየህን?
እግዚአብሔር ይህንን ጥያቄ ያዋለው የአክዓብ መጸጸት እውነተኛ እንደሆነ ለኤልያስ ለማሳየት ነው። "አክዓብ ራሱን እንዴት በእኔ ፊት ትሁት እንዳደረገ ተመልክቻለሁ።" ወይም "አክዓብ እንዴት በእኔ ፊት ትሁት እንዳደረገ ተመልከት።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ ዘመን...በልጁ ዘመን
"በእርሱ የህይወት ዘመን... በልጁ የህይወት ዘመን"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 22

1 በእስራኤልና በሶሪያ መካከል ያለ ጦርነት ሦስት ዓመት አለፈ። 2 ይሁን እንጂ በሦስተኛው ዓመት የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ የእስራኤልን ንጉሥ አክዓብን
ለመጎብኘት ሄደ። 3 የእስራኤል ንጉሥ ለአገልጋዮቹ እንዲህ አለ፦ በገለዓድ የምትገኘውን ራሞት ከሶርያ ንጉሥ ለማስመለስ ምንም ዓይነት እርምጃ ያልወሰድነው
ስለምንድን ነው? ራሞት እኮ የእኛ ይዞታ ናት አላቸው። 4 ስለዚህ እርሱም ኢዮሣፍጥን ለጦርነት ወደ ራሞት ከእኔ ጋር ትሄዳለህን? ሲል ጠየቀው።
ኢዮሣፍጥም እኔ እንደ አንተ ነኝ፤ ሕዝቤም እንደ አንተ ሕዝብ ነው፤ ፈረሶቼም እንደ አንተ ፈረሶች ናቸው አለው። 5 ኢዮሳፍጥም፣ ነገር ግን መጀመሪያ
የእግዚአብሔርን ፈቃድ ጠይቅ ሲል መለሰለት። 6 ከዚያም አክዓብ አራት መቶ የሚሆኑትን ነቢያቱን ጠርቶ ወደ ራሞት ለጦርነት ልውጣ ወይስ ልቅር? ሲል
ጠየቃቸው። እነርሱም ሄደህ ተዋጋ፤ እግዚአብሔርም በንጉሡ እጅ አሳልፎ ይሰጣል ሲሉ መለሱለት። 7 ኢዮሣፍጥ ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምንጠይቅበት
ሌላ የእግዚአብሔር ነቢይ የለምን? ሲል ጠየቀ። 8 አክዓብም የይምላ ልጅ የሆነ ሚክያስ የተባለ ሌላ ነቢይ አለ፤ ነገር ግን እኔ እርሱን አልወደውም፤ እርሱ ምን
ጊዜም ስለ እኔ ክፉ እንጂ መልካም የትንቢት ቃል አይናገርም ሲል መለሰለት። ኢዮሣፍጥም ይህን ማለት አይገባህም፤ አለው። 9 ከዚያም አክዓብ ከቤተ
መንግሥቱ አገልጋዮች አንዱን ጠርቶ የይምላ ልጅ ሚክያስን ፈልገህ በማግኘት በፍጥነት እንዲመጣ አድርግ ሲል አዘዘው። 10 የእስራኤል ንጉሥ አክዓብና
የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ ሁለቱ ነገሥታት ልብሰ መንግሥታቸውን ለብሰው በሰማርያ የቅጥር በር አጠገብ በሚገኘው ሜዳ በየዙፋናቸው ላይ ተቀምጠው
ነበር። ነቢያቱም ሁሉ በነገሥታቱ ፊት ቀርበው ትንቢት ይናገሩ ነበር። 11 ከእነርሱም አንዱ ሴዴቅያስ ተብሎ የሚ. ጠራው የክንዓና ልጅ ከብረት የተሠሩ ቀንዶች
ይዞ አክዓብን እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ ከብረት በተሠሩ በእነዚህ ቀንዶች ሶርያውያንን ወግተህ ፍጹም የሆነ ድልን ትቀዳጃለህ አለው። 12 ሌሎቹም ነቢያት
ይህንኑ ቃል በመደገፍ በራሞት ላይ ዝመት፣ ታሸንፋለህ፤ እግዚአብሔርም ድልን ይሰጥሃል አሉት። 13 ሚክያስን ለመጥራት ሄዶ የነበረው መልእክተኛ በዚሁ
ጊዜ ሚክያስን ሌሎቹ ነቢያት በሙሉ ንጉሥ አክዓብ ድል የሚያደርግ መሆኑን የሚያረጋግጥ የትንቢት ቃል ተናግረዋል፤ ስለዚህ አንተም እንደእነርሱ ብታደርግ
ይሻልሃል አለው። 14 ሚክያስ ግን እግዚአብሔር የሚገልጥልኝን ቃል ብቻ እንደምናገር በሕያው እግዚአብሔር ስም እምላለሁ! ሲል መለሰለት። 15 ሚክያስም
ወደ ንጉሥ አክዓብ ፊት በቀረበ ጊዜ ንጉሡ፣ ሚክያስ ሆይ፣ ንጉሥ ኢዮሣፍጥና እኔ ወደ ራሞት ሄደን ጦርነት እንክፈት ወይስ እንተው? ሲል ጠየቀው።
ሚክያስም ዘምተህ አደጋ ጣልባት ታሸንፋለህ፤ እግዚአብሔርም በእጅህ አሳልፎ ይሰጥሃል፤ ሲል መለሰለት። 16 ከዚያም አክዓብ፣ አንተ ግን በእግዚአብሔር
ስም የትንቢትን ቃል ስትነግረኝ እውነቱን መግለጥ እንደሚገባህ ስንት ጊዜ እነግርሃለሁ አለው። 17 ሚክያስም መላው የእስራኤል ሠራዊት ጠባቂ እንደሌላቸው
በጎች በኮረብታዎች ላይ ተበታትነው አያለሁ፤ እግዚአብሔርም፣ እነዚህ ሰዎች መሪ የላቸውም፤ ስለዚህ ወደየቤታቸው በሰላም ይመለሱ ብሎአል ሲል መለሰለት።
18 አክዓብም ኢዮሣፍጥን እርሱ ሁልጊዜ ስለ እኔ ክፉ እንጂ መልካም የትንቢት ቃል አይናገርም ብዬህ አልነበረምን? አለው። 19 ሚክያስም ንግግሩን
በመቀጠል እንዲህ አለ፤ እንግዲህ እግዚአብሔር የሚለውን ስማ፤ እግዚአብሔር በሰማይ ባለው ዙፋኑ ላይ ተቀምጦ መላእክቱም ሁሉ በቀኝና በግራው ቆመው
አየሁ። 20 እግዚአብሔርም አክዓብን ወደ ራሞት ሄዶ በዚያ እንዲገደል ሊያሳስተው የሚችል ማን ነው? አለ፤ ከመላእክቱም መካከል አንዱ ሌላ ነገር ሌላውም
ሌላ ነገር አለ። 21 በመጨረሻ ግን አንድ መንፈስ ወደ እግዚአብሔር ፊት ቀርቦ እኔ ላሳስተው እችላለሁ አለ። 22 እግዚአብሔርም እንዴት አድርገህ ልታሳስተው
ትችላለህ? አለው። መንፈሱም፣ ሄጄ የአክዓብ ነቢያት ሁሉ ሐሰት እንዲናገሩ አደርጋለሁ ሲል መለሰለት፤ እግዚአብሔርም እንግዲያውስ ሄደህ አሳስተው፤
ይከናወንልሃል አለው። 23 ሚክያስም እነሆ እግዚአብሔር እነዚህን የአንተን ነቢያት የሐሰት ቃለ እንዲነግሩህ ያደረገው እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ በአንተ ላይ
ጥፋት ሊያመጣብህ እግዚአብሔር ራሱ ወስኖአል! ሲል ንግግሩን ደመደመ። 24 ከዚያም የክንዓና ልጅ ሴዴቅያስ ወደ ሚክያስ ቀርቦ በጥፊ መታውና ከመቼ
ወዲህ ነው የእግዚአብሔር መንፈስ ከእኔ አልፎ አንተን ያነጋገረህ? አለው። 25 ሚክያስም በውስጥ ወዳለው ክፍል ሄደህ በምትሸሸግበት ጊዜ ታውቀዋለህ
ሲል መለሰለት። 26 በዚህን ጊዜ ንጉሥ አክዓብ ከጦር መኮንኖቹ አንዱን ሚክያስን ያዘው፤ ወደ ከተማይቱ ገዢ ወደ አሞንና ወደ ልዑል ኢዮአስ ውሰደው፤ 27
እኔም በደህና እስክመለስ ድረስ እስር ቤት አስገብተው ደረቅ እንጀራና ውሃ ብቻ እየሰጡት እንዲቆይ ያድርጉ ሲል አዘዘው። 28 ሚክያስም አንተ በደህና
ከተመለስክማ እግዚአብሔር በእኔ አማካይነት አልተናገረም ማለት ነው! አለው፤ ቀጥሎም ድምፁን ከፍ በማድረግ በዚህ የምትገኙ ሕዝቦች ሁሉ እኔ
የተናገርኩትን ሁሉ ልብ ብላችሁ አድምጡ አለ። 29 ስለዚህ የእስራኤል ንጉሥ አክዓብና የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ ወደ ገለዓድ ምድር ወደምትገኘው ራሞት
ከተማ ለመዋጋት ሄዱ። 30 አክዓብም ኢዮሣፍጥን ወደ ጦርነት ለመሄድ ስንነሣ እኔ ሌላ ሰው መስዬ ለመታየት ተራ ልብስ እለብሳለሁ፣ አንተ ግን ልብሰ
መንግሥትህን ልበስ አለው። ስለዚህ የእስራኤል ንጉሥ አክዓብ ሌላ ልብስ ለብሶ ማንነቱን በመሰወር ዘመተ። 31 የሶርያ ንጉሥም በንጉሡ ላይ እንጂ በሌላ
በማንም ላይ አደጋ አትጣሉ ብሎ ለሠላሳ ሁለቱ የሠረገላ ጦር አዛዦች ትእዛዝ አስተላለፈ። 32 ስለዚህ ንጉሥ ኢዮሣፍጥን ባዩ ጊዜ በርግጥ እርሱ የእስራኤል
ንጉሥ ነው ብለው በእርሱ ላይ አደጋ ሊጥሉበት ከበቡት፤ ኢዮሣፍጥም በጮኸ ጊዜ፣ 33 እርሱ የእስራኤል ንጉሥ አለመሆኑን በማረጋገጥ በእርሱ ላይ አደጋ
ከመጣል ተመለሱ። 34 ነገር ግን በአጋጣሚ አንድ የሶርያ ወታደር ፍላጻ በማስፈንጠር ንጉሥ አክዓብን በጦር ልብሱ መገናኛ ላይ ወጋው፤ ንጉሥ አክዓብም
የሠረገላ ነጂውን ክፉኛ ቆስያለሁ፤ ስለዚህ ሠረገላውን መልሰህ ከጦር ሜዳው ውጣ! ሲል አዘዘው። 35 ጦርነቱም በተፋፋመ ጊዜ ንጉሥ አክዓብ በሶርያውያን
ፊት ለፊት በሠረገላው ላይ ተደግፎ ነበር፤ በዚያውም ቀን ምሸት ሞተ። 36 ፀሐይ በመጥለቅ ላይ እያለች፣ እያንዳንዱ ሰው ወደየአገሩና ወደየከተማው ይመለስ
የሚል ትእዛዝ ከእስራኤል ጦር አዛዦች ተነገረ። 37 ስለዚህ ንጉሥ አክዓብ ሞተ፤ ሬሳውም ወደ ሰማርያ ተወስዶ ተቀበረ። 38 ሠረገላውም በሰማርያ ኩሬ
ታጠበ፤ እግዚአብሔርም አስቀድሞ በተናገረው መሠረት ደሙን ውሾች ላሱት፤ በዚያም ኩሬ ሴተኛ አዳሪዎች ታጠቡበት። 39 ንጉሥ አክዓብ ያደረጋቸው ነገሮች
ሁሉ ምን እንደ ሠራና የሠራቸውም ከተሞች ሁኔታ ጭምር በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተመዝግቦ ይገኝ የለምን? 40 ንጉሥ አክዓብም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤
በእርሱም ፈንታ ልጁ አካዝያስ ተተክቶ ነገሠ። 41 የእስራኤል ንጉሥ አክዓብ በነገሠ በአራተኛው ዓመት የአሳ ልጅ ኢዮሣፍጥ የይሁዳ ንጉሥ ሆነ። 42
ኢዮሣፍጥም በሠላሳ አምስት ዓመት ዕድሜው ነግሦ ሃያ አምስት ዓመት በኢየሩሳሌም ገዛ። እናቱም ዐዙባ ተብላ የምትጠራ የሺልሒ ልጅ ነበረች። 43
ኢዮሣፍጥ ከእርሱ በፊት እንደ ነበረው እንደ አባቱ አሳ በእግዚአብሔር ፊት መልካም የሆነውን ነገር ሁሉ አደረገ። ሆኖም ግን የአሕዛብ ማምለኪያ ስፍራዎችን
አልደመሰሰም ነበር፤ ስለዚህም ሕዝቡ በእነዚያ ቦታዎች መሥዋዕት ማቅረብና ዕጣን የማጠን ተግባሩን አልተወም ነበር። 44 ኢዮሣፍጥም ከእስራኤል ንጉሥ
ጋር ሰላም መሠረተ። 45 ኢዮሣፍጥ ያደረጋቸው ነገሮች፣ በጦርነት ላይ ያሳየው ጀግንነትም ሁሉ በይሁዳ ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ውስጥ ተመዝግቦ ይገኝ
የለምን? 46 ከአባቱ ከአሳ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ የተረፉትንና በአሕዛብ የማምለኪያ ቦታዎች የጣዖት አመንዝራዎችን ሁሉ አስወገደ። 47 በዚያን ዘመን
የኤዶም ምድር የራስዋ ንጉሥ አልነበራትም፤ ከዚህም የተነሣ በይሁዳ ንጉሥ በሚሾመው እንደራሴ ትገዛ ነበር። 48 ንጉሥ ኢዮሣፍጥ ውቅያኖስን አቋርጠው
ከኦፊር ወርቅ የሚያመጡለትን የተርሴስ ዓይነት መርከቦች አሠርቶ ነበር፤ ነገር ግን መርከቦቹ በኤጽዮንጋብር ወደብ ላይ ስለ ተሰበሩ መጓዝ አልቻሉም። 49
ከዚያ በኋላ የእስራኤል ንጉሥ አካዝያስ መርከበኞቹ ከኢዮሣፍጥ መርከበኞች ጋር በኅብረት እንዲሠሩ የውል ድርድር አቅርቦ ነበር፤ ኢዮሣፍጥ ግን አሳቡን
አልተቀበለም። 50 ንጉሥ ኢዮሣፍጥ ሞተ፤ በዳዊት ከተማ በሚገኘውም በነገሥታት መካነ መቃብር ተቀበረ፤ በእርሱም ፈንታ ተተክቶ ልጁ አዮራም ነገሠ። 51
የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ በነገሠ በዐሥራ ሰባተኛው ዓመት የአክዓብ ልጅ አካዝያስ በሰማርያ የእስራኤል ንጉሥ ሆነ። 52 እርሱም የአባቱን የአክዓብን፣ የእናቱን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የኤልዛቤልንና የእስራኤልን ሕዝብ ወደ ኃጢአት የመራውን የንጉሥ ኢዮርብዓምን መጥፎ አርአያነት በመከተል በእግዚአብሔር ፊት በደል ሠራ። **53** ከእርሱም በፊት እንደ ነበረው እንደ አባቱ ባዓል ተብሎ ለሚጠራው ባዕድ አምላክ በመስገድና በማገልገል የእስራኤልን አምላክ የእግዚአብሔርን ቁጣ አነሣሣ።

---

1 Kings 22:1

ሶስት አመታት
"3 አመታት" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህም ሆነ
እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ውስጥ አዲስ ደረጃ የሚያሳይ ድርጊት መጀመሩን ለማመልከት ነው። የእናንተ ቋንቋ ይህን የሚገልጽበት መንገድ ካለው እዚህ ስፍራ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ።

1 Kings 22:3

ሬማት ገለዓድ የእኛ እንደሆነች ታውቃላችሁን፣ ነገር ግን እኛ ከአራም እጅ እርሷን ለመውሰድ ምንም እያደረግን አይደለም?
አክዓብ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው እስከ አሁን ሬማት ገለዓድን መልሰው መያዝ እንደመበረባቸው ትኩረት ለመስጠት ነው። "ሬማት ገለዓድ የእኛ ናት፣ ነገር ግን እኛ ከአራም ንጉሥ መልሰን ልንወስዳት ምንም ነገር አላደረግንም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ከአራም ንጉሥ መልሰን ልንወስዳት
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል ሀይልን ያመለክታል። "ከአራም ንጉሥ ቁጥጥር ስር ነጻ ልናወጣት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ያው እንደ አንተው ነኝ፣ የእኔ ህዝብ እንዳንተ ህዝብ ነው፣ ደግሞም የእኔ ፈረሶች የአንተ ፈረሶች ናቸው
ኢዮሳፍጥ ለአክዓብ፣ የእርሱ ሰዎች እና የእርሱ ፈረሶች የአክዓብም መሆናቸውን ይነግረዋል፤ ይህም ማለት አክዓብ ደስ እንዳሰኘው ሊያዝባቸው ይቻላል ማለት ነው። "እኔ፣ የእኔ ወታደሮች፣ እንደዚሁም ፈረሶቼ አንተ በወደድከው መንገድ ልትተቀምባቸው የምትችላቸው የአንተም ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 22:5

አራት መቶ ወንዶች
"400 ወንዶች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ጌታ እርሷን ለንጉሡ እጆች አሳልፎ ይሰጥ እንደሆነ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል ሀይልን ያመለክታል። "ጌታ ንጉሡ ሬማት ገለዓድን እንዲማርካት ይፈቅድ እንደሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 22:7

ንጉሡ ይህንን አይበል
ኢዮሳፍጥ አክዓብን በሶስተኛ መደብ የሚጠቅሰው ለእርሱ ክብርን ለማሳየት ነው። "ያንን ማለት የለብህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 22:10

ለራሱ የብረት ቀንዶች አሰርቶ
"ለራሱ የብረት ቀንዶች አሰራ"

እስኪጠፉ ድረስ እነዚህን አረማውያን ታባርራቸዋለህ/ታስወጣቸዋለህ
የነቢያቱ ድርጊቶች አክዓብ አረማውያንን የሚያሸንፍበትን መንገድ የሚገልጽ ትምዕርታዊ/ ምልክታዊ ድርጊቶች ናቸው። የአክዓብ ሰራዊት በሬ ሌላውን እንስሳ እንደሚያጠቃው በታላቅ ጥንካሬ አሸናፊ ይሆናል። (ትምዕርታው/ ምልክታዊ ድርጊት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ እሰኪጠፉ/እስኪፈጁ ድረስ
የጠላትን ሰራዊት መደምሰስ የተገለጸው እነርሱን እንደመፍጀት ተደርጎ ነው። ይህ በዐድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል፤ "አንተ እስክትፈጃቸው ድረስ" ወይም "አንተ እስክትደመስሳቸው ድረስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

እርሷን ለንጉሡ እጅ አሳላፎ ይሰጣታል
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል ሀይልን ያመለክታል። "ንጉሡ እንዲማርካት/ እንዲይዛት ፈቅዷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 22:13

እነሆ ተመልከት
"አድምጥ" ወይም "ቀጥሎ ለምነግርህ ትኩረት ስጥ"

የነቢያቱ ቃል በአንድ አፍ ለንጉሡ መልካም ነገርን አወጀ
ነቢያቱ በሙሉ አንድ አይነት ነገር መናገራቸው የተገለጸው በአንድ ሰው አፍ እንደተናገሩ ተደርጎ ነው። "ሁሉም ነቢያት ተመሳሳይ የሆነ መልካም ነገሮችን ለንጉሡ አወጁ/ተናገሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተም ቃል ከእነርሱ እንደ አንዱ ይሁን
እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው የሚያመለክተው "የነቢያቱን ቃል ነው።" "አንተም የምትናገረው እነርሱ ከተናገሩት ጋር የተስማማ ይሁን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መሄድ/መውጠት ይኖርብናል
"እኛ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው አክዓብን፣ ኢዮሳፍጥን፣ እና የእነርሱን ሰራዊት ሲሆን ሚክያስን አይጨምርም። (አካታች እና የማያካትት "እኛ" የሚለውን ይመልከቱ)

ለንጉሡ እጅ አሳልፎ ይሰጣታል
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል ሀይልን ያመለክታል። "ንጉሡ እንዲማርካት/ እንዲይዛት ፈቅዷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 22:16

በያህዌ ስም...ስንት ጊዜ መጠየቅ ይኖርብኛል?
አክዓብ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው ከጭንቀት የተነሳ ሚክያስን ለመገሰጽ ነው። "በያህዌ ስም... ብዙ ጊዜ ጠየቅሁ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በያህዌ ስም
እዚህ ስፍራ "ስም" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ስልጣንን ነው። "እንደ ያህዌ ተወካይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እስራኤልን በሙሉ ተመለከትኩ
እዚህ ስፍራ "መላው እስራኤል" የሚለው የእስራኤልን ሰራዊት ያመለክታል። "መላውን የእስራኤል ሰራዊት እመለከታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

እረኛ እንደሌላቸው በጎች
የህዝቡ ሰራዊት የተነጻጸሩት የሚመራቸው ማንም ከሌላቸው በጎች ጋር ነው፣ ምክንያቱም እረኛቸው፣ ንጉሡ ሞቷል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ እረኛ የላቸውም
ያህዌ ንጉሡን የሚገልጸው እረኛ እንደሆነ አድርጎ ነው። እረኛ በጎቹን ለመጠበቅ እና ለመንከባከብ ሃላፊነት እንዳለበት ሁሉ፣ ንጉሡም ህዝቡን የመምራት እና የመጠበቅ ሀላፊነት አለበት።"እነዚህ ሰዎች ከእንግዲህ መሪ አይኖራቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 22:18

አልነገርኩህምን ... እርሱ ጥፋት ብቻ?
አክዓብ ይህንን ጥያቄ ያነሳው ስለ ሚክያስ የተናገረው ነገር እውነት መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። "ጥፋትን ብቻ እንደሚናገር...አልነገርኩህም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በሬማት ገለዓድ ይወድቃል
የአክዓብ በጦርነት ውስጥ መሞት የተገለጸው እንደሚወድቅ ተደርጎ ነው። "በሬማት ገለዓድ ይሞታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚሉትን ይመልከቱ)

ከእነርሱ አንዱ እንዲህ አለ...ደግሞም ሌላው እንዲህ አለ
"አንዱ...ደግሞም ሌላው" የሚለው የሚያመለክተው በቀደመው ቁጥር ለቀረበው ለያህዌ ጥያቄ ከሰማያት ጭፍሮች ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ መላዕክት የሚሰጡትን ምላሽ ነው።

1 Kings 22:21

በእርሱ ነቢያት ሁሉ አፍ የሀሰት መንፈስን በማስቀመጥ
እዚህ ስፍራ "መንፈስ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የነቢያትን ዝንባሌ ሲሆን "አፋቸው" የሚለው የሚወክለው እነርሱ የሚናገሩትን ነው። "የእርሱ ነቢያት ሁሉ ሀሰት እንዲናገሩ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ
"አድምጥ" ወይም "ቀጥሎ ለምነግርህ ትኩረት ስጥ"

አንተ ታያለህ
"ለጥያቄህ መልሱን ታውቃለህ።" የሴዴቅያስ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ቢተረጎም፣ ይህ ሀረግ በስውር ያለውን መረጃ ለማቅረብ ይተረጎማል። "የያህዌ መንፈስ ለእኔ እንደተናገረ ታውቃለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 22:24

የያህዌ መንፈስ አንተን የተናገረው፣ እኔን በየት መንገድ አልፎ ነው?
ሰዴቅያስ ይህንን ምጸታዊ ጥያቄ የጠየቀው ሚክያስን ለመስደብ እና ለመገሰጽ ነው። "የያህዌ መንፈስ እኔን አልፎ አንተን የሚናገርህ አይምሰልህ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ
"አድምጥ" ወይም "ቀጥሎ ለምነግርህ ትኩረት ስጥ"

አንተ ታያለህ
"ለጥያቄህ መልሱን ታውቃለህ።" የሴዴቅያስ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ቢተረጎም፣ ይህ ሀረግ በስውር ያለውን መረጃ ለማቅረብ ይተረጎማል። "የያህዌ መንፈስ ለእኔ እንደተናገረ ታውቃለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 22:29

አክዓብ፣ የእስራኤል ንጉሥ፣ እንዲሁም ኢዮሣፍጥ፣ የይሁዳ ንጉሥ ወጡ
እዚህ ስፍራ ንጉሦቹ በሰራዊታቸው ታጅበው ራሳቸውን ይወክላሉ። "አክአብ፣ የእስራኤል ንጉሥ፣ እና ኢዮሣፍት፣ የይሁዳ ንጉሥ ሰራዊታቸውን መሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ራሱን ሰውሮ
ይህ ማለት የተለመደ ገጽታን ለውጦ ላለመታወቅ መሞከር ነው።

1 Kings 22:31

ሰላሳ ሁለት አዛዦች
"32 አዛዦች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ብርቱ ያልሆኑትንም ሆነ ብርቱዎቹን ወታደሮች አታጥቁ
"ብርቱ ያልሆኑ" እና "ብርቱ ወታደሮች" የሚለውን ሁለቱንም መጥቀሱ ንጉሡ መላውን ወታደር ማለቱ ነው። "የትኞቹንም ወታደሮች አታጥቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜሪዝም/ደካር እስከ ዳር/ከጽንፍ ጽንፍ የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህም ሆነ
እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ውስጥ አዲስ ደረጃ የሚያሳይ ድርጊት መጀመሩን ለማመልከት ነው። የእናንተ ቋንቋ ይህን የሚገልጽበት መንገድ ካለው እዚህ ስፍራ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ።

1 Kings 22:34

ቀስቱን ሳያነጣጥር አስፈነጠረ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) አክዓብ መሆኑን ሳያውቅ ወደ አንድ ወታደር ዒላማ አድርጎ አነጣጠረ ወይም 2) ቀስቱን ያነጣጠረው በአይምሮው ልዩ ዒላማ ሳይኖር ነው።

1 Kings 22:35

ንጉሡ በሰረገላው ላይ ተደግፎ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንድ ሰው ንጉሡን በሰረገላው ላይ ደግፎት ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ጩኸቱ ቀጠለ
እዚህ ስፍራ "ጩኸት" የሚወክለው ይጮሁ የነበሩ ወታደሮችን ነው። "ወታደሮቹ መጮህ ጀመሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እያንዳንዱ ሰው ወደ ከተማው መመለስ ይኖርበታል፤ ደግሞም እያንዳንዱ ሰው ወደ አካባቢው መመለስ ይኖርበታል
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትረጉም አላቸው፣ የተጣመሩት ትኩረት ለመስጠት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Kings 22:37

ወደ ሰማርያ አመጡት
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ወታደሮቹ በድኑን ወደ ሰማርያ አመጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ቀበሩት
"ሰዎች ቀበሩት"

የያህዌ ቃል እንደተናገረው
እዚህ ስፍራ "የያህዌ ቃል" የሚወክለው ራሱን ያህዌን ነው። "ያህዌ እንደተናገረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 22:39

በእስራኤል ነገሥታት ስራዎች መጽሐፍ ውስጥ ተጽፈው የሚገኙ አይደለምን?
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል፤ ደግሞም መልሱ አዎንታዊ እንደሆነ መገመት ይቻላል። ጥያቄው ቃለ ምልልሳዊ ሲሆን ያገለገለውም ትኩረት ለመስጠት ነው። ይህ በ1 ነገሥት 15:31 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እነዚህ ታሪኮች የእስራኤል ነገሥታት የፈጸሟቸው ድርጊቶች በተጻፉባቸው መጽሐፍት ውስጥ ተጽፈዋል።" ወይም "በእስራኤል ንጉሦች ተግባራት መጽሐፍት ውስጥ ልታነቧቸው ትችላላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ/ተኛ
የአክዓብ መሞት የተገለጸው እንደተኛ ተደርጎ ነው። እዚህ ስፍራ መተኛት ሞትን የሚወክል ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት/ ነው። ይህ በ1 ነገሥት 2:10 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚሉትን ይመልከቱ)

1 Kings 22:41

የሰላሳ አምስት አመት ሰው
"የ35 አመት ሰው" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሃያ አምስት አመታት
"25 አመታት" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 22:43

በአባቱ፣ በአሳ መንገድ ሄደ
የአንድ ሰው ባሕሪይ የሚገለጸው ያ ሰው በመንገድ ላይ እየሄደ እንደሆነ ተደርጎ ነው። "አባቱ አሳ፣ ያደረገውን ተመሳሳይ ነገር አደረገ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በያህዌ ዐይኖች ፊት ትክክል የሆነውን
እዚህ ስፍራ "ዐይኖች" የሚወክለው ማየትን ሲሆን የያህዌ ሃሳብ የተነገረው እርሱ ማየት እንደሚችል ተደርጎ ነው። "ያህዌ ትክክል ነው ብሎ የሚቀበለው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከፍ ያሉትን ስፍራዎች አላጠፋም ነበር
ይህ በዐድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እርሱ ከፍ ያሉትን ስፍራዎች አላጠፋቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

1 Kings 22:45

በይሁዳ ነገሥታት ስራዎች መጽሐፍ ውስጥ ተጽፈው የሚገኙ አይደለምን?
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል፤ ደግሞም መልሱ አዎንታዊ እንደሆነ መገመት ይቻላል። ጥያቄው ቃለ ምልልሳዊ ሲሆን ያገለገለውም ትኩረት ለመስጠት ነው። ይህ በ1 ነገሥት 14:29 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እነዚህ ታሪኮች የይሁዳ ነገሥታት የፈጸሟቸው ድርጊቶች በተጻፉባቸው መጽሐፍት ውስጥ ተጽፈዋል።" ወይም "በይሁዳ ንጉሦች ተግባራት መጽሐፍት ውስጥ ልታነቧቸው ትችላላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

1 Kings 22:48

መርከቦቹ ተሰብረው ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "መርከቦቹ ተሰብረው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ/ተኛ
የኢዮሣፍት መሞት የተገለጸው እንደተኛ ተደርጎ ነው። ይህ በ1 ነገሥት 2:10 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሞተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚሉትን ይመልከቱ)

ከእነርሱ ጋር ተቀበረ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች እርሱን ቀበሩት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 22:51

ለሁለት አመታት ነገሠ
"ለ2 አመታተት ገዛ" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በያህዌ እይታ ክፉ የሆነውን
የያህዌ እይታ የሚነገረው ያህዌ ያንን ነገር እንዳየው ተደርጎ ነው። "ያህዌ ክፉ ብሎ የሚቆጥረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በአባቱ መንገድ ሄደ፣ በእናቱ መንገድ ሄደ፣ በናባጥ ልጅ በኢዮርብዓም መንገድ ሄደ
የአንድ ሰው ባሕሪይ የሚገለጸው ያ ሰው በመንገድ ላይ እየሄደ እንደሆነ ተደርጎ ነው። "አባቱ፣ እናቱ፣ እና የናባጥ ልጅ በኢዮርብዓም ያደረጉትን ተመሳሳይ ነገር አደረገ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እስራኤልን ወደ ኃጢአት መራ
እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእስራኤልን መንግሥት የመረቱትን አስሩን ሰሜናዊ ነገዶች ነው።

እርሱ በዓልን አገለገለ፣ ደግሞም አመለከው
"አገለገለ" እና "አመለከ" የሚሉት ቃላት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል አምላክ
እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚለው ቃል የሚያመለክተው መላውን አስራ ሁለቱን የያዕቆብ ትውልድ ነገዶች ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: 2 Kings

2 Kings

Chapter 1

1 አክዓብ ከሞተ በኋላ ሞአብ በአስራኤል ላይ ዐመፀ። 2 በዚያን ጊዜ የአስራኤል ንጉሥ አካዝያስ በሰማርያ ቤተ መንግሥቱ ሳለ ከሰገነቱ ላይ ወድቆ ክፉኛ
ቆስሎ ነበር፤ እርሱም እኔ ከዚህ ሕመም እድን እንደሆነ በፍልስጥኤም የአቃሮን ከተማ አምላክ የሆነውን ብዔልዜቡል ጠይቁልኝ ብሎ መልእክተኞቹን ላከ። 3
ነገር ግን የእግዚአብሔር መልአክ ቴስቢያዊውን ኤልያስን እንዲህ ሲል አዘዘው፤ ተነሥተህ የሰማርያ ንጉሥ አካዝያስ የላካቸውን መልእክተኞች ለመገናኘት
ውጣ፤ እንዲህም ብለህ ንገራቸው፤ የአቃሮንን አምላክ ብዔልዜቡልን ለመጠየቅ የምትሄዱት በእስራኤል ዘንድ አምላክ የለም ብላችሁ ነውን? 4 ስለዚህ
እግዚአብሔር እነሆ አንተ ትሞታለህ እንጂ አትፈወስም፤ ከተኛህበት አልጋም አትነሣም፤ ብሎሃል በሉት። ከዚያም ኤልያስ ትቶ ሄደ። 5 መልእተኞቹም ወደ ንጉሡ
ተመልሰው ሄዱ፤ ንጉሡም ስለምን ተመልሳችሁ መጣችሁ? ሲል ጠየቃቸው። 6 እነርሱም እንዲህ ሲሉ መለሱለት፤ አንድ ሰው በመንገድ አግኝቶን ወደ አንተ
ተመልሰን እንድንመጣና እግዚአብሔር ስለ አንተ የተናገረውን እንድናስረዳህ አዘዘን፤ እርሱም እንዲህ የሚል ነው፤ የአቃሮንን አምላክ ብዔልዜቡልን ለመጠየቅ
መልእክተኞች የላክህበት ምክንያት ምንድን ነው? ስለዚህ ትሞታለህ እንጂ ከዚህ ሕመም አትፈወስም፤ ከተኛህበትም አልጋ አትነሣም! 7 ንጉሡም በመንገድ
ያገኛችሁት ይህንን ቃል የነገራችሁ ያ ሰው እንዴት ያለ ነው? ሲል ጠየቃቸው። 8 እነርሱም ጠጉራም ልብስ ለብሶ በወገቡ ዙሪያ የጠፍር ቀበቶ የታጠቀ ነው ሲሉ
መለሱለት። ንጉሡም እርሱማ ኤልያስ ነው! አለ። 9 ከዚህም በኋላ ንጉሡ አንዱን የጦር መኮንን ከኀምሳ ሰዎች ጋር ሄዶ ኤልያስን ይዞ ያመጣለት ዘንድ
አዘዘው። መኮንኑም ኤልያስን በአንድ ኮረብታ ላይ ተቀምጦ አገኘውና የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ወርደህ ወደ እርሱ እንድትመጣ ንጉሡ አዞሃል አለው። 10
ኤልያስም እኔስ የእግዚአብሔር ሰው ከሆንኩ እሳት ከሰማይ ወርዶ አንተንና ኀምሳውን ሰዎችህን ይብላ አለው፤ ወዲያውኑ እሳት ከሰማይ ወርዶ መኮንኑንና
ኀምሳዎቹን ሰዎች በላ። 11 ንጉሡም እንደገና ሌላውን መኮንን ከኀምሳ ሰዎች ጋር ላከ፤ እርሱም ወደ ኤልያስ ወጥቶ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፣ አሁኑኑ ወርደህ
ወደ እርሱ እንድትመጣ ንጉሡ አዞሃል አለው። 12 ኤልያስም እኔስ የእግዚአብሔር ሰው ከሆንኩ እሳት ከሰማይ ወርዶ አንተንና ኀምሳውን ሰዎችህን ይብላ
አለው፤ ወዲያውኑ የእግዚአብሔር እሳት መኮንኑንና ኀምሳዎቹን ሰዎች በላ። 13 ንጉሡም ለሦስተኛ ጊዜ ከኀምሳ ሰዎች ጋር ሌላ መኮንን ላከ፤ ይህኛው መኮንን
ግን ወደ ኮረብታው በመውጣት በኤልያስ ፊት በጉልበቱ ተንበርክኮ እንዲህ ሲል ለመነ፤ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፣ ለእኔና ከእኔ ጋር ላሉት ሰዎች ምሕረት
አድርግልን፤ ሕይወትችንንም ከሞት አድን፣ 14 ሌሎቹን ሁለት መኮንኖችና ተከታዮቻቸውን ሁሉ ከሰማይ የወረደ እሳት በልቶአቸዋል፤ ለእኔ ግን እባክህ ምሕረት
አድርግልኝ። 15 የእግዚአብሔርም መልአክ ኤልያስን ከእርሱ ጋር አብረህ ውረድ፤ ከቶም አትፍራ አለው። ስለዚህም ኤልያስ ከመኮንኑ ጋር ወደ ንጉሡ ወረደ።
16 እግዚአብሔር የሚለው ይህ ነው፤ የአቃሮንን አምላክ ብዔልዜቡልን እንዲጠይቁ መልእክተኞችን የላክህ በእስራኤል አምላክ እንደሌለ በመቁጠርህ ነውን?
ስለዚህ ከተኛህበት አልጋ ሳትወርድ ትሞታለህ እንጂ አትድንም አለው። 17 ስለዚህ እግዚአብሔር በኤልያስ አማካይነት በተናገረው ቃል መሠረት አካዝያስ
ሞተ። አካዝያስ ወንዶች ልጆች ስላልነበሩት በእርሱ ፈንታ ተተክቶ ወንድሙ ኢዮራም ነገሠ። ይህም የሆነው የኢዮሣፍጥ ልጅ ኢዮራም በይሁዳ በነገሠ
በሁለተኛው ዓመት ነበር። 18 ንጉሥ አካዝያስ ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ በእስራኤል ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኝ የለምን?

---

2 Kings 1:1

ሞዓብ ዐመፀ
‹‹በሞዓብ የሚኖር ሕዝብ ዐመፀ››

ሰገነቱ ላይ ሳለ ከዐይነ ርግቡ
ሰገነቱ ቤተ መንግሥቱ ጣራ ላይ የተሠራ ክፍል ነው። ዐይነ ርግቡ መድረክ ወይም የመስኮት ሸፋን እንዲሆን ጌጥ ባለው ሁኔታ አንዱ በሌላው ላይ እንዲሻገር ተደርጐ ከቀጫጭን እንጨት ጣውላዎች ተሠራ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቤተ መንግሥቱ ጣራ ላይ ባለው ክፍል ዙሪያ የተሠሩ ቀጫጭን የእንጨት ጣውላዎች››

ብዔል ዜቡል
(ስሞችን እንዴት እንደምትተረጉም ተመልከት)

2 Kings 1:3

ያህዌ
ይህ ብሉይ ኪዳን ውስጥ ለሕዝቡ የተገለጠ የእግዚአብሔር ስም ነው። ይህን እንዴት እንደምትተረጉመው ስለ ያህዌ ከትርጉም ቃል ገጽ ተመልከት።

ቴስብያዊ
ይህ የሚያመለክተው በቴስቢ ከተማ የሚኖር ሰውን ነው።

የአቃሮንን አምላክ ብዔል ዜቡልን ለመጠየቅ የምትሄዱ በእስራኤል አምላክ ስለሌለ ነውን?
ይህ ብዔል ዜቡልን በመጠየቃቸው እንደ ተግሣጽ የቀረበ ጥያቄ ነው። ይህን በዐረፍተ ነገር መጻፍ ይቻላል። የእስራኤልን አምላክ በሚገባ ያውቁ ስለ ነበር እንዲህ መሆኑ ስላቅ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እናንት ሞኞች! እስራኤል ውስጥ አምላክ መኖሩን በሚገባ ታውቃላችሁ፤ ይሁን እንጂ፣ ያንን እንደማያውቅ ሰው የአቃሮንን አምላክ ብዔል ዜቡልን ለመጠየቅ ሰዎች ልካችኃል!››

ቡዔል ዜቡልን ለመጠየቅ
‹‹ለመጠየቅ›› የሚለው ቃል አንድን ጉዳይ አስመልክቶ የሌላውን ሰው ሐሳብ ወይም አስተያየት መጠየቅ ማለት ነው።

ስለዚህ ያህዌ እንዲህ ይላል
ይህ ያህዌ ለንጉሥ አካዝያስ የላከው መልእክት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ለንጉሥ አካዝያስ እንዲህ ይላል››

2 Kings 1:5

መልእክተኞቹ ወደ ንጉሡ አካዝያስ ሲመለሱ
ከኤልያስ ጋር ከተገናኙ በኋላ መልእክተኞቹ ወደ አቃሮን ሳይሄዱ ወደ ንጉሡ ተመልሰዋል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የአቃሮንን አምላክ ብዔል ዜቡልን ለመጠየቅ ሰዎች የምትልከው በእስራኤል አምላክ ስለሌለ ነውን?
ጥያቄው የቀረበው ብዔል ዜቡልን ለመጠየቅ በማሰቡ እንደ ተግሣጽ ነው። ይህን ዐረፍተ ነገር ማድረግ ይቻላል። የእስራኤልን አምላክ በሚገባ ያውቁ ስለ ነበር እንዲህ ማድረጋቸው ስላቅ ነው። 2 ነገሥት 3፥3 ላይ ያለውን ጥያቄ እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አንተ ሞኝ በእስራኤል አምላክ መኖሩን በሚገባ ታውቃለህ፤ የአቃሮንን አምላክ ብዔል ዜቡልን ለመጠየቅ ሰዎች የላክኸው ግን ይህን እንደማያውቅ ሰው ነው!››

ከተኛህበት ዐልጋ አትነሣም
ንጉሥ አካዝያስ በተጐዳ ጊዜ ዐልጋ ላይ ተኝቶ ነበር። ከእንግዲህ እንደማይድንና ከተኛበት ዐልጋ እንደማይነሣ ያህዌ ተናገረ 2 ነገሥት 3፥4 ላይ ያለውን ዐረፍተ ነገር እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእንግዲህ አትድንም፤ ከተኛህበትም ዐልጋ አትነሣም››

2 Kings 1:7

ጠጉራም ልብስ የለበሰ
የዚህ ትርጒም፣ 1) ጠጉሩ ልበስ የሆነለት እስኪመስል ድረስ ጠጉራም ነበር ማለት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በጣም ጠጉራም ነበር።›› ወይም 2) ‹‹ልብሶቹ ከጠጉር የተሠሩ ነበሩ››

2 Kings 1:9

ከዚያም ንጉሡ አንድ የአምሳ አለቃ ከአምሳ ወታደሮች ጋር ወደ ኤልያስ ላከ
ኤልያስን ወደ እርሱ እንዲያመጣ ንጉሡ የአምሳ ወታደሮች መሪ ላከ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከዚያም ንጉሡ ኤልያስን እንዲይዙት የአምሳ አለቃውን ከአምሳ ወታደሮች ጋር ላከ››

አምሳ ወታደሮች
‹‹50 ወታደሮች ተመልከት››

እኔ የእግዚአብሔር ሰው ከሆንሁ እሳት ትውረድ...
አምሳ አለቃው ኤልያስን የእግዚአብሔር ሰው ብሎታል፤ ይሁን እንጂ፣ አምሳ አለቃውና ንጉሡ ለኤልያስ ተገቢውን ክብር አልሰጡትም ኤልያስ እንዲህ ያለው እሳት ከሰማይ እንድትወርድ ኤልያስ በእርግጥ የእግዚአብሔር ሰው እንደ ሆነና ክብርም እንደሚገባው ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እኔ የእግዚአብሔር ሰው ስለሆንሁ እሳት ከሰማይ ትውረድ...›› ወይም፣ ‹‹አንተ እንዳልኸው እኔ የእግዚአብሔር ሰው ከሆንሁ እሳት ከሰማይ ትውረድ...››

ከሰማይ
‹‹ከላይ ከሰማይ››

2 Kings 1:11

አምሳ ወታደሮች
‹‹50 ወታደሮች ተመልከት››

እኔ የእግዚአብሔር ሰው ከሆንሁ እሳት ከሰማይ ትውረድ
አምሳ አለቃው ኤልያስን የእግዚአብሔር ሰው ብሎታል፤ ይሁን እንጂ፣ አምሳ አለቃውና ንጉሡ ለኤልያስ ተገቢውን ክብር አልሰጡትም። ኤልያስ እንዲህ ያለው እሳት ከሰማይ እንድትወርድና በእርግጥ የእግዚአብሔር ሰው እንደ ሆነና ክብርም እንደሚገባው ለማሳየት ነው። 2 ነገሥት 1፥10 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እኔ የእግዚአብሔር ሰው ስለሆንሁ እሳት ከሰማይ ትውረድ...›› ወይም፣ ‹‹አንተ እንዳልኸው እኔ የእግዚአብሔር ሰው ከሆንሁ እሳት ከሰማይ ትውረድ...››

የእግዚአብሔር እሳት
እንዲህ ማለት ከእግዚአብሔር ዘንድ እሳት መጣች ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከእግዚአብሔር ዘንድ እሳት››

2 Kings 1:13

አምሳ ጦረኞች
‹‹50 ጦረኞች›› ወይም፣ ‹‹50 ወታደሮች›› ‹‹ተመልከት››

ለመነው
‹‹ተማፀነው››

እነዚህ የአምሳዎቹ አገልጋዮችህ
አምሳ አለቃው ለእርሱ ክብር ለማሳየት የእርሱ አገልጋዮች የኤልያስ አገልጋዮች መሆናቸውን ተናገረ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የእኔ አምሳ ወታደሮች››

የእኔና የእነዚህ... ነፍስ በፊትህ የከበረች ትሁን
እዚህ ላይ የኤልያስ፣ ‹‹ፊት›› የሚወክለው ፍርድን ወይም መመርመርን ነው። በሕይወት እንዲኖሩ አምሳ አለቃው ኤልያስን እየለመነ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እባክህን የእኔና የእነዚህ... ነፍስ በአንተ ዘንድ የከበረች ትሁን›› ወይም ‹‹የእኔና የእነዚህ ነፍስ በፊትህ ዋጋ ታግኝ፤ እኛንም አትግደለን››

ነፍሴ በፊትህ የከበረች ትሁን
እዚህ ላይ የኤልያስ ‹‹ፊት›› የሚወክለው ፍርድን ወይም መመርመርን ነው። ለእርሱ ቸርነት እንዲያደርግና እንዳይገድለው አምሳ አለቃው እንደ ገና አልያስን እየለመነ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እባክህን ቸርነት አድርግልኝ›› ወይም፣ ‹‹እባክህን አትግደለኝ››

2 Kings 1:15

ለመሆኑ የአቃሮንን አምላክ ብዔል ዜቡልን ስለ ራስህ ለመጠየቅ መልእክተኞች የላክኸው በእስራኤል አምላክ ስለሌለ ነውን?
ጥያቄው ያቀረበው ብዔል ዜቡልን ለመጠየቅ በማሰቡ እንደ ተግሣጽ ነው። ይህን በዐረፍተ ነገር መጻፍ ይቻላል። ንጉሡ በእስራኤል አምላክ መኖሩን በሚገባ ያውቅ ስለ ነበር እንዲሁ ማድረጉ ስለቅ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አንተ የምትጠይቀው አምላክ በእስራኤል እንደሌለ እያሰብህ ነው!›› ወይም፣ ‹‹አንተ ሞኝ! የምትጠይቀው አምላክ በእስራኤል እንዳለ በሚገባ ታውቃለህ፤ ግን እያደረግህ ያለኸው ያንን እንደማያውቅ ነው።››

ከተኛህበት ዐልጋ ፈጽሞ አትነሣም
ንጉሥ አካዝያስ በተጐዳ ጊዜ ዐልጋ ላይ ተኝቶ ነበር። ከእንግዲህ እንደማይድንና ከዐልጋ እንደማይነሣ ያህዌ ተናገረ። 2 ነገሥት 3፥4 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከእንግዲህ አትድንም፤ ከተኛህበትም ዐልጋ አትነሣም››

2 Kings 1:17

ኤልያስ እንደ ተናገረው እንደ ያህዌ ቃል
‹‹ያህዌ ለኤልያስ እንደ ነገረውና ኤልያስ እንደ ተናገረው››

የኢዮሣፍጥ ልጅ ኢዮራም በይሁዳ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት
ኢዮራም በኢየሩሳሌም የነገሠው ምን ያህል ጊዜ እንደ ነበር በማሳየት ኢዮራም በእስራኤል መንገሥ የጀመረበትን ጊዜ ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የኢዮሳፍጥ ልጅ ኢዮራም የይሁዳ ንጉሥ በሆነ በሁለተኛው ዓመት››

በእስራኤል... የተጻፈ አይደለምን?
ይህን በዐረፍተ ነገር ማስቀመጥ ይቻላል፤ እንደ ተሸጋሪ ግሥ ማቅረብም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በእስራኤል... ተጽፈዋል›› ወይም፣ ‹‹ስለ እነዚህ ነገሮች አንድ ሰው በእስራኤል... ጽፎአል››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 እግዚአብሔር ኤልያስን በዐውሎ ነፋስ ወደ ሰማይ የሚወስድበት ጊዜ ደረሰ፤ ኤልያስና ኤልሳዕ ከጌልጌላ ተነሥተው ጉዞ ጀመሩ። **2** በመንገድም ሳሉ ኤልያስ ኤልሳዕን እነሆ አንተ በዚህ ቆይ እኔ ወደ ቤቴል እንድሄድ እግዚአብሔር አዞኛል አለው። ኤልሳዕ ግን እኔ በሕያው እግዚአብሔር ስም እምላለሁ፣ ከቶ ከአንተ አልለይም ሲል መለሰለት፤ ስለዚህም አብረው ወደ ቤቴል ሄዱ። **3** በዚያ የሚኖሩ የነቢያት ጉባኤ ወደ ኤልሳዕ ሄደው፣ እግዚአብሔር ዛሬ ጌታህን ከአንተ ለይቶ እንደሚወስደው ታውቃለህን? ሲሉ ጠየቁት። ኤልሳዕም አዎን ዐውቃለሁ፣ ነገር ግን ዝም በሉ ሲል መለሰላቸው። **4** ከዚህም በኋላ ኤልያስ ኤልሳዕን እነሆ አንተ በዚህ ቆይ እኔ ወደ ኢያሪኮ እንድሄድ እግዚአብሔር አዞኛል አለው። ኤልሳዕ ግን እኔ በሕያው እግዚአብሔር ስም እምላለሁ ከቶ ከአንተ አልለይም፣ ሲል መለሰለት። ስለዚህም አብረው ወደ ኢያሪኮ ሄዱ። **5** በዚህም የሚኖሩ የነቢያት ጉባኤ ወደ ኤልሳዕ ሄደው እግዚአብሔር ዛሬ ጌታህን ከአንተ ለይቶ እንደሚወስደው ታውቃለህን? ሲሉ ጠየቁት። ኤልሳዕም አዎን አውቃለሁ፤ ነገር ግን ዝም በሉ ሲል መለሰላቸው። **6** ከዚህም በኋላ ኤልያስ ኤልሳዕን እነሆ አንተ በዚህ ቆይ፤ እኔ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ እንድሄድ እግዚአብሔር አዞኛል አለው። ኤልሳዕ ግን እኔ በሕያው እግዚአብሔር ስም እምላለሁ ከቶ ከአንተ አልለይም፤ ሲል መለሰለት። እነዚህም አብረው ጉዞአቸውን ቀጠሉ። **7** ከነቢያቱም ኀምሳው ተከትለዋቸው ወደ ዮርዳኖስ ሄዱ፤ ኤልያስና ኤልሳዕም በዮርዳኖስ ወንዝ አጠገብ ቆሙ፤ ኀምሳውም ነቢያት ደግሞ ጥቂት ራቅ ብለው ቆመው ነበር፤ **8** ከዚህ በኋላ ኤልያስ ካባውን አውልቆ በመጠቅለል ውሃውን መታው፤ ውሃው ወደ ቀኝና ወደ ግራ ተከፍሎላቸው ኤልያስና ኤልሳዕ በደረቅ ምድር ተሸገሩ። **9** በዚህም ኤልያስ ኤልሳዕን እኔ ከአንተ ከመወሰዴ በፊት ምን እንዳደርግልህ እንደምትፈልግ ንገረኝ አለው። ኤልሳዕም ያንተ ተተኪ እንድሆን የሚያስችለኝ መንፈስ በእጥፍ ይሰጠኝ ሲል መለሰለት። **10** ኤልያስም «ያቀረብከው ጥያቄ ከባድ ነው፤ ነገር ግን እኔ ከአንተ ተለይቼ ስወሰድ ብታየኝ ይህን የጠየከውን ስጦታ መቀበል ትችላልህ፤ ባታየኝ ግን ልታገኘው አትችልም» ብሎ መለሰለት። **11** እየተነጋገሩ እርምጃቸውን ቀጠሉ፤ ከዚያም በኋላ ፈረሰኞች የሚስቡአቸው የእሳት ሠረገሎች ድንገት ገብተው ሁለቱን ለዩአቸው፤ ኤልያስም በዐውሎ ነፋስ ወደ ሰማይ ተወሰደ። **12** ኤልሳዕም ይህን ሁሉ እያየ «የእስራኤል ሠረገሎችና ፈረሰኞች የሆንከው አባቴ ሆይ! አባቴ ሆይ!» እያለ ወደ ኤልያስ ጮኸ፤ ከዚያም በኋላ ኤልያስን ዳግመኛ አላየውም። ኤልሳዕም ከሐዘን ብዛት የተነሣ ልብሱን ከሁለት ቀደደ፤ **13** ከኤልያስም የወደቀውን ካባ ከመሬት አነሣ፤ ከዚያም ሄዶ በዮርዳኖስ ወንዝ ደርቻ ቆመ። **14** ውሃውንም በኤልያስ ካባ መትቶ፣ «የኤልያስ አምላክ እግዚአብሔር ወዴት ነው?» አለ፤ ከዚያም በኋላ እንደገና በመታው ጊዜ ውሃው ወደ ቀኝና ግራ ተከፍሎለት ወደ ማዶ ተሻገረ። **15** ከኢያሪኮ የመጡት ነቢያት እርሱን ባዩት ጊዜ፣ «በኤልያስ ላይ ዐድሮ የነበረው የመንፈስ ኀይል በኤልሳዕ ላይ አርፏል!» አሉ፤ ወደ እርሱም በመቅረብ ጎንበስ ብለው እጅ ነሡት **16** «እነሆ! በዚህ ጠንካራ የሆንን ኀምሳ ሰዎች አለን፤ እንሂድና ጌታህን እንፈልገው፤ ምናልባት የእግዚአብሔር መንፈስ አንሥቶ ወስዶ በአንድ ተራራ ወይም ሸለቆ ውስጥ አሳርፎት ይሆናል።» ኤልሳዕም “አትሂዱ” ሲል መለሰ። **17** እነርሱ ግን እምቢ በማለት እስኪያፍር ድረስ አጥብቀው ስለ ለመኑት በጉዳዩ ተስማማና ኀምሳ ሰዎች ሄደው ሦስት ቀን ሙሉ ኤልያስን ፈለጉት፤ ነገር ግን ሊያገኙት አልቻሉም። **18** ከዚያም በኋላ በኢያሪኮ ሆኖ ወደሚጠብቃቸው ወደ ኤልሳዕ ተመለሱ፤ ኤልሳዕም «እኔ ቀድሞውንስ አትሂዱ ብያችሁ አልነበረምን?» አላቸው። **19** ጥቂት ሰዎች ከኢያሪኮ ወደ ኤልሳዕ መጥተው «ጌታችን አንተ እንደምታውቀው ይህች ምድር መልካም ናት፤ ውሃው ግን መጥፎ በመሆኑ ምድሪቱ ምርት አትሰጥም፤ ስለሁኔታው እንለምንሃለን» አሉት። **20** ኤልሳዕም «በአዲስ ሳህን ውስጥ ጨው ጨምራችሁ አምጡልኝ» ብሎ አዘዘ። እነርሱም እንዳዘዛቸው አድርገው አመጡለት። **21** እርሱም ወደ ምንጩ ሄዶ በውሃ ውስጥ ጨው በመጨመር «እግዚአብሔር የሚለው ይህ ነው ‹እኔ ይህን ውሃ በመፈወስ ንፁህ እንዲሆን አደርጋለሁ፤ ከዚህም በኋላ ዳግመኛ የሞትና የምርት መጨንገፍ ምክንያት አይሆንም›» ሲል ተናገረ። **22** ከዚያም ጊዜ ጀምሮ ኤልሳዕ በተናገረው መሠረት ውሃው እስከ ዛሬ ድረስ ንጹሕ ሆነ። **23** ኤልሳዕም ወደ ቤቴል ለመሄድ ከኢያሪኮ ተነሣ። በመንገድ ሳለ ከከተማይቱ በርከት ያሉ ልጆች ወጥተው ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ አንተ ራሰ መላጣ! ራሰ መላጣ! ከዚህ ውጣ እያሉ ጮኹበት። **24** ኤልሳዕም መለስ ብሎ ዙሪያውን በመቃኘት አትኩሮ ተመለከታቸውና በእግዚአብሔር ስም ረገማቸው፤ በዚህም ጊዜ ሁለት እንስት ድቦች ከጫካ ወጥተው ከእነዚያ ልጆች መካከል አርባ ሁለቱን ሰባብረው ጣሉአቸው። **25** ኤልሳዕም ወደ ቀርሜሎስ ተራራ ወጣ፤ ዘግየት ብሎ ግን ወደ ሰማርያ ተመለሰ።

---

2 Kings 2:1

እንዲህም ሆነ
‹‹እንዲህ ተደረገ›› ይህ ሐረግ ታሪኩ ውስጥ ቀጥሎ የተደረገውን ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል።

በዐውሎ ነፋስ
ዙሪያውን የሚሽከረከር ከባድ ነፋስ

ሕያው ያህዌ በሕያው ነፍስህም
‹‹ያህዌ ሕያው የመሆኑንና አንተም ሕያው የመሆንህን ያህል። እዚህ ላይ ኤልሳዕ የያህዌንና የኤልያስን ሕያውነት እርሱ ከሚናገረው ነገር እርግጠኝነት ጋር ይነጻጸራል። ይህ ጠንከር ያለ ተስፋ የሚሰጠበት ቃል ነው። ‹‹ያንን በመሐላ አረጋግጥልሃለሁ››

2 Kings 2:3

የነቢያት ልጆች
እነዚህ በቀጥታ የነቢያት ልጆች ሳይሆኑ፣ የነቢያት ስብስብ ናቸው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የነቢያት ስብስብ››

ሕያው ያህዌን በሕያው ነፍስህም እምላለሁ ከአንተ አልለይም
‹‹ያህዌ ሕያው እንደ መሆኑ፣ አንተም ሕያው እንደ መሆንህ ከአንተ አልለይም።›› እዚህ ላይ ኤልሳዕ የያህዌንና የኤልያስን ሕያውነት ከሚናገረው ነገር እርግጠኝነት ጋር ያነጻጽራል። ይህ ቃል ኪዳን የሚደረግበት መንገድ ነው። 2 ነገሥት 2፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከአንተ እንደማልለይ እምላለሁ››

2 Kings 2:5

በኢያሪኮ የነበሩትም የነቢያት ልጆች ወደ ኤልሳዕ መጥተው እንዲህ አሉት።
‹‹ኤልያስና ኤልሳዕ ወደ ኢያሪኮ ሲመጡ እዚያ የነበሩ የነቢያት ልጆች ኤልሳዕን እንዲህ አሉት››

የነቢያት ልጆች
እነዚህ በቀጥታ የነቢያት ልጆች ሳይሆኑ የነቢያት ስብስብ ናቸው። 2 ነገሥት 2፥3 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የነቢያት ስብስብ››

ሕያው ያህዌን በሕያው ነፍስህም እምላለሁ
‹‹ያህዌ ሕያው እንደ መሆኑ፣ አንተም ሕያው እንደ መሆንህ ከአንተ አልለይም›› እዚህ ላይ ኤልሳዕ የያህዌንና የኤልያስን ሕያውነት ከሚናገረው ነገር እርግጠኝነት ጋር ያነጻጽራል። ይህ ቃል ኪዳን የሚደረግበት መንገድ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ነው። 2 ነገሥት 2፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተገኘምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከአንተ እንደማልለይ እምላለሁ››

2 Kings 2:7

ከልጆቹ አምሳው
‹‹ከልጆቹ 50››

የነቢያት ልጆች
እነዚህ በቀጥታ የነቢያት ልጆች ሳይሆኑ፣ የነቢያት ስብስብ ናቸው። 2 ነገሥት 2፥3 እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የነቢያት ስብስብ››

ከእነርሱ ትይዩ ቆመ
ይህ ማለት ፊታቸውን ወደ እነርሱ አድረገው ቆሙ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ፊታቸውን ወደ እነርሱ አድርገው ቆመ›› ወይም፣ ‹‹እነርሱን እያዩ ቆሙ››

መጐናጸፊያ
ከላይ የሚለበስ ልብስ

ውሃው ግራና ቀኝ ተከፈለ፤ ሁለቱም በደረቅ ምድር ተሻገሩ
‹‹ኤልያስና ኤልሳዕ በደረቅ ምድር ወደ ማዶ እንዲሻገሩ የዮርዳኖስ ወንዝ ውሃ ለሁለት ተከፈለ››

በሁለቱም በኩል
‹‹ግራና ቀኝ›› ይህ የሚያመለክተው፣ ኤልያስ ውሃውን ከመታበት ግራና ቀኝ ያለውን ነው።

2 Kings 2:9

እንዲህም ሆነ
‹‹እንዲህ ተደረገ››

ተሻገሩ
ይህ የሚያመለክተው ዮርዳኖስን ወንዝ መሻገርን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በዮርዳኖስ ወንዝ ተሻገሩ››

ከአንተ ከመውሰዴ በፊት
ይህን እንደ ተሻጋሪ ግሥ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ እኔን ከአንተ ከመውሰዱ በፊት››

መንፈስህ በዕጥፍ እንዲያድርብኝ
እዚህ ላይ የኤልያስ መንፈስ መንፈሳዊ ኃይሉን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአንተን መንፈሳዊ ኃይል ሁለት እጅ››

2 Kings 2:11

እነሆ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እነሆ›› የሚለው ቃል ቀጥሎ ያለውን አስደናቂ ነገር በንቃት መጠበቅ እንዳለብን ያመለክታል።

የእሳት ሠረገላና የእሳት ፈረሶች
‹‹የእሳት›› የሚለው በእሳት መከበባቸውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በእሳ የተከበበ ሠረገላና በእሳት የተከበቡ ፈረሶች››

በዐውሎ ነፋስ ወደ ሰማይ ዐረገ
‹‹በዐውሎ ነፋስ ወደ ሰማይ ተወሰደ።›› ‹‹ዐውሎ ነፋስ›› የሚለውን ቃል 2 ነገሥት 2፥1 ስትተረጉም በተጠቀምህበት ቃል ተርጉመው።

አባቴ! አባቴ!
ኤልሳዕ የሚያከብረውን መሪ እየተጣራ ነው።

ከሁለት ቦታ ቀደደ
ብዙውን ጊዜ ሰዎች ልብሳቸውን የሚቀዱት በጣም ለማዘናቸውና ለመተከዛቸው ምልክት እንዲሆን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምን ያህል ማዘኑን ለማሳየት ሁለት ቦታ ቀደደው››

2 Kings 2:13

መጐናጸፊያ
መጐናጸፊያ ነቢዩ ከላይ የሚደርበው ልብስ ነው። የአገልግሎቱ ምልከት ነበር። ኤልሳዕ የኤልያስን መጐናጸፊያ ሲወስድ፣ እንደ ነቢይ የኤልያስን ቦታ መውሰዱን ማመልከቱ ነበር።

የኤልያስ አምላክ ያህዌ ወዴት ነው?
ያህዌ ከኤልያስ ጋር እንደ ነበረ ሁሉ፣ ከእርሱም ጋር መኖሩን ኤልሳዕ እየጠየቀ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የኤልያስ አምላክ ያህዌ፣ ከእኔ ጋር ነህን?››

በግራና በቀኝ ተከፍሎለት ተሻገረ
ውሃው ለሁለት ተከፈለ፤ ኤልሳዕም ቀደም ሲል ከኤልያስ ጋር በነበረ ጊዜ እንደ ሆነው በደረቅ መሬት ወደ ማዶ ተሻገረ።

በሁለቱም በኩል
‹‹ግራና ቀኝ›› ይህ የሚያመለክተው ኤልያስ ውሃውን የመታበትን ግራና ቀኝ ነው።

2 Kings 2:15

የነቢያት ልጆች
እነዚህ በቀጥታ የነቢያት ልጆች ሳይሆኑ፣ የነቢያት ስብስብ ናቸው። 2 ነገሥት 2፥3 ላይ ይህን እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የነቢያት ስብስብ››

በፊቱ ወደ መሬት ዝቅ ብለው እጅ ነሡ
ጥልቅ አክብሮታቸውንና እርሱን እንደ መሪ መቀበላቸውን እያሳዩ ነበር።

የኤልያስ መንፈስ በኤልሳዕ ላይ ዐርፎአል
እዚህ ላይ የኤልያስ፣ ‹‹መንፈስ›› የሚያመለክተው የእርሱን መንፈሳዊ ኀይል ነው። ይህ ክፍል ኤልያስ የነበረው መንፈስ እንደ አንዳች ግዙፍ ነገር ኤልሳዕ ላይ ማረፉን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኤልሳዕ ኤልያስ የነበረው ዐይነት መንፈሳዊ ኀይል ነበረው ወይም፣ ‹‹ኤልያስ የነበረው መንፈሳዊ ኀይል አሁን ኤልሳዕ ላይ ሆነ››

እነሆ፣ እኛ አገልጋዮችህ እዚህ አምሳ ጠንካራ ሰዎች አሉን
‹‹አምሳ ጠንካራ ሰዎች›› ሲሉ እነዚህ ሰዎች ስለ ራሳቸው እየተናገሩ ነበር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነሆ፣ እዚህ አምሳ ሰዎች አለን፤ እኛ አገልጋዮችህ ነን፤ ስለዚህ አሁን እንሂድ››

አምሳ ጠንካራ ሰዎች
‹‹50 ጠንካራ ሰዎች››

2 Kings 2:17

ዕፍረት እስኪሰማው ድረስ ግድ አሉት
የነቢያት ልጆች፣ ‹‹አይሆንም›› ማለት እስኪቸገር ድረስ አጥበቀው ኤልሳዕን ጠየቁት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጥያቄያቸውን አልቀበልም ማለት እስኪቸገር ድረስ የነቢያት ልጆች ደጋግመው ኤልሳዕን ጠየቁት››

ቀድሞንስ ቢሆን አትሂዱ ብያችሁ አልነበረምን?
ኤልሳዕ ይህን ያለው ምን እንደሚሆን ቀድሞውኑ ነግሮአቸው ለነበረው አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህን በዐረፍተ ነገር ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱን ስለማታገኙ መጀመሪውኑ አትሂዱ ብያችሁ ነበር!

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Kings 2:19

የከተማዪቱም ሰዎች
‹‹የከተማዋ መሪዎች››

ይህች ከተማ ለኑሮ የተመቸች ናት
ይህ ማለት ከተማዋ ያለችው ጥሩ ቦታ ላይ ነው ማለት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከተማዋ ምቹ ቦታ ላይ ናት›› ወይም፣ ‹‹ከተማዋ ጥሩ ቦታ ላይ ናት››

ጌታችን እንደምታያት
እዚህ ላይ ኤልሳዕ፣ ‹‹ጌታችን›› የተባለው እርሱን ለማክበር ነው።

ፍሬያማ
ጥሩ ፍሬ የምትሰጥ

2 Kings 2:21

ይህን ውሃ ፈውሼዋለሁ
ይህ የሚያመለክተው የመፈወስ ያህል ያህዌ ውሃውን ጥሩ ማድረጉን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ውሃውን ንጹሕ አድርጌአለሁ››

ከእንግዲህ ሞት ወይም ፍሬ ቢስ መሆን አይኖርም።
ይህ የሚያመለክተው መጥፎ ውሃ የሚያደርገውን ነገር ነው። ይህንንም አዎንታዊ በሆነ መልኩ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእንግዲህ ይህ ውሃ የሚያደርገው ሞት ወይም ፍሬ ቢስነት አይኖርም›› ወይም፣ ‹‹ከአሁን ጀምሮ ይህ ውሃ ሕይወት ያመጣል፤ ምድሪቱ ፍሬያማ እንድትሆንም ያደርጋል››

ውሃው ተፈወሰ
ይህንን፣ ‹‹ውሃው እንደ ተፈወሰ ነው›› ማለት ይቻላል።

እንደ ተናገረ... እስከ ዛሬ ድረስ
ይህ የሚያመለክተው እስከ አሁን ድረስ ያለ ነገርን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኤልሳዕ በተናገረው ቃል መሠረት እስከ ዛሬ ድረስ ንጹሕ እንደ ሆነ አለ››

2 Kings 2:23

ከዚያ ተነሥቶ ወደ ቤቴል ወጣ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ወጣ›› የተባለው ከኢያሪኮ ይልቅ ቤቴል ከፍታ ቦታ ላይ ስለ ነበረች ነው።

ውጣ
ልጆቹ ኤልሳዕ ከዚያ እንዲሄድ ፈልገዋል፤ ይህንንም የገለጹት፣ ‹‹ውጣ›› በማለት ነበር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከዚህ ውጣ››

መላጣ
ራሱ ላይ ጠጉር የሌለው ሰው ማለት ነው። መላጣ በመሆኑ ልጆቹ ኤልሳዕ ላይ እያፌዙ ነበር።

ከልጆቹ አርባ ሁለቱን
‹‹42 ልጆች››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ በነገሠ በአሥራ ስምንተኛው ዓመት የአክዓብ ልጅ ኢዮራም በእስራኤል ላይ በሰማርያ ነገሠ፤ እርሱም ዐሥራ ሁለት ዓመት ገዛ። **2** እርሱም በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራ ሠራ። ነገር ግን እንደ አባቱና እናቱ አልነበረም፤ ምክንያቱም በዓል ተብሎ የሚጠራውን አባቱ አሠርቶት የነበረውን በዕድ አምላክ ምስል አስወገደ። **3** ይህም ሆኖ ከእርሱ በፊት እስራኤል ወደ ኃጢአት የመራው የናባጥ ልጅ የንጉሥ ኢዮርብዓምን አምልኮ ተከተለ እንጂ አላስወገደውም። **4** የሞአብ ንጉሥ ሞሳ በግ አርቢ ነበር፤ በየዓመቱም አንድ መቶ ሺህ ጠቦት የአንድ መቶ ሺህ በጎች ጠጕር ለእስራኤል ንጉሥ ይገብር ነበር፤ **5** ነገር ግን የእስራኤል ንጉሥ አካዓብ በሞተ ጊዜ የሞአብ ንጉሥ ሞሳ በእስራኤል ላይ ዐመፀ። **6** በዚያን ጊዜ ንጉሥ ኢዮራም ወዲያውኑ ከሰማርያ ወጥቶ ወታደርቹን ሁሉ በአንድነት ሰበሰበ፤ **7** ወደ ይሁዳ ንጉሥ ወደ ኢዮሣፍጥም የሞአብ ንጉሥ በእኔ ላይ አምፆብኛል፤ በእርሱ ላይ በማደርገው ጦርነት ከእኔ ጋር ትተባበራለህን? የሚል መልእክት ላከ። ንጉሥ ኢሣፍጥም አዎን እተባበርሃለሁ፤ እኔን እንደ ራስህ፣ ሠራዊቴን እንደ ሠራዊትህ፣፣ ፈረሶቼንም እንደ ፈረሶችህ መቁጠር ትችላለህ ሲል መለሰለት። **8** እርሱም ልናጠቃ የምንችለው በየትኛው መንገድ ነው? ሲል ጠየቀው። ንጉሥ ኢዮራምም በኤዶም በረሓ የሚገኘውን ዙሪያ መንገድ ይዘን እንጓዛለን ሲል መለሰለት። **9** ስለዚህም ንጉሥ ኢዮራም፣ እንዲሁም የይሁዳና የኤዶም ነገሥታት ለዘመቻ ወጡ፤ ከሰባት ቀን ጉዞም በኋላ ውሃ አለቀባቸው፤ ለሠራዊቱም ሆነ ለጭነት እንስሶቻቸው ምንም ውሃ አልነበረም። **10** የእስራኤል ንጉሥ ይህ ምንድን ነው? እግዚአብሔር ሦስታችንንም ነገሥታት ለሞአብ ንጉሥ አሳልፎ ሊሰጠን ነውን? ወየልን ሲል ጮኸ። **11** ንጉሥ ኢዮሣፍጥም በእርሱ አማካይነት እግዚአብሔርን መጠየቅ እንድንችል በዚህ አንድ ነቢይ የለም? ሲል ጠየቀ። ከንጉሥ ኢዮራም ሠራዊት አዛዦች አንዱ፣ ቀድሞ የኤልያስ ረዳት የነበረው የሣፋጥ ልጅ ኤልሳዕ እዚህ አለ ሲል መልስ ሰጠ። **12** ንጉሥ ኢዮሣፍጥም የእግዚአብሔር ቃል በእርሱ ዘንድ ይገኛል አለ፤ ከዚያም በኋላ ሦስቱም ነገሥታት ወደ ኤልሳዕ ሄዱ። **13** ኤልሳዕም የእስራኤልን ንጉሥ ኢዮራምን እኔ ለአንተ ማድረግ የሚገባኝ ምንድን ነው? ወደ አባትህና እናትህ ነቢያት ሂድ። ንጉሥ ኢዮራምም መልሶ አይደለም፣ ሦስታችንንም ነገሥታት ለሞአብ ንጉሥ አሳልፎ ለመስጠት የጠራን እግዚአብሔር ነው አለ። **14** ኤልሳዕም እኔ በማገልግለው በሕያው እግዚአብሔር ስም እምላለሁ፣ አንተን ለመርዳት ለመጣው ለይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ ክብር ስል ነው እንጂ ለአንተስ ምንም ነገር ላደርግልህ ባልተገባ ነበር። **15** ነገር ግን በገና የሚደረድር ሰው አምጡልኝ አለ። ባለ በገናውም በሚደረድርበት ጊዜ የእግዚአብሔር ኃይል በኤልሳዕ ላይ ወርዶ እንዲህ አለ። **16** እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በዚህ የደረቀ ሸለቆ ሁሉ የውሃ ጕድጓድ ቆፍሩ። **17** ምንም ዝናብና ነፋስ ባታዩም ይህ ሸለቆ በውሃ የተሞላ ይሆናል። እናንተ፣ የቀንድ ከብቶቻችሁና የጭነት እንስሶቻችሁ ሁሉ የምትጠጡት በቂ ውሃ ታገኛላችሁ። **18** ነገር ግን ይህን ማድረግ በእግዚአብሔር ዘንድ ቀላል ነገር ነው። ከዚህ በላይ እርሱ በሞአባውያን ላይ ድልን ያጎናጽፋችኋል። **19** የተመሸጉና ምርጥ የሆኑ ከተሞቻቸውን ሁሉ ድል አድርጋችሁ ትይዛላችሁ፤ የፍራፍሬ ዛፎቻቸውን ሁሉ ትቆርጣላችሁ፤ ምንጮቻቸውን ትደፍናላችሁ፤ ለም የሆኑ የእርሻ ቦታዎቻቸውን በማበላሸት ድንጋይ ትከምሩባቸዋላችሁ። **20** በማግስቱም ጠዋት መሥዋዕት የሚቀርብበት ሰዓት ሲደርስ ከኤዶም በኩል የውሃ ምንጭ ፈልቆ ምድሩን ሸፈነው። **21** ሞአባውያንም ሦስቱ ነገሥታት አደጋ ሊጥሉባቸው መምጣታቸውን በሰሙ ጊዜ፣ ከሸማግሌ እስከ ወጣት መሣሪያ መያዝ የሚችሉ ሰዎች ሁሉ ተጠርተው ወጥተው ለጦርነት መጡ። **22** በማግስቱም ጠዋት ከእንቅልፋቸው ነቅተው ሲመለከቱ በውሃው ላይ የሚያበራው የፀሐይ ነጸብራቅ እንደ ደም ቀይ መስሎ ታያቸው። **23** ስለዚህም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በመጮኽ፣ ይህ ነገር ደም ነው፤ የሦስቱ ጠላቶቻችን ሠራዊቶች እርስ በርሳቸው በመተራረድ ተላልቀዋል፤ እንግዲህ ሄደን ሰፈራቸውን እንዝረፍ ተባባሉ። **24** እነርሱ ወደ ሰፈር በደረሱ ጊዜ እስራኤላውያን ተነሥተው አደጋ በመጣል ወደ ኋላ መለሱአቸው፤ እስራኤላውያን አገሪቱን ወርረው ሞአባውያንን ጨፈጨፉአቸው። **25** ከተሞቻቸውን ደመሰሱ፤ ለም በሆነው እርሻ ውስጥ በሚያልፉበትም ጊዜ እያንዳንዱ እስራኤላዊ አንዳንድ ድንጋይ ይወረውርበት ስለ ነበር በመጨረሻ እርሻዎቹ ሁሉ በድንጋይ ተሸፈኑ፤ ምንጮቻቸውን ደፈኑ፤ የፍራፍሬ ዛፎቻቸውንም ሁሉ ቆረጡ፤ በመጨረሻም የአገሪቱ ዋና ከተማ የነበረችው ቂርሔሬስ ብቻ ቀረች፤ እርስዋንም ድንጋይ የሚወነጭፉ ጦረኞች ከበው አደጋ ጣሉባት። **26** የሞአብ ንጉሥ ድል እንደ ተመታ ባረጋገጠ ጊዜ ሰይፍ የታጠቁ ሰባት መቶ ሰዎችን እስከትሎ የጠላት ጦር የተሰለፈበትን መስመር ጥሶ ለማምለጥና ወደ ሶሪያ ንጉሥ ለመሄድ ቢሞክርም ከቶ አልተሳካለትም። **27** ስለዚህ በእርሱ ምትክ መንገሥ የሚገባውን የመጀመሪያ ልጁን በከተማይቱ ግንብ ላይ ለሞአብ አምላክ መሥዋዕት አደርጎ አቀረበ። ስለዚህ በእስራኤል ዘንድ ከፍ ያለ ቁጣ ነበር። እስራኤላውያንም ለሞአብ ንጉሥ ከተማይቱን ለቀው ወደ አገራቸው ተመለሱ።

---

2 Kings 3:1

የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሳፍጥ በነገሠ በዐሥራ ስምንተኛው ዓመት
ይህ የሚያመለክተው አሁን ያለው የይሁዳ ንጉሥ ምን ያህል ዓመት እንደ ገዛ በማሳየት ኢዮራም መንገሥ የጀመረበትን ጊዜ ነው። የዚህን ዐረፍተ ነገር ትርጕም በጣም ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ኢዮሳፍጥ የይሁዳ ንጉሥ በሆነ በዐሥራ ስምንተኛው ዓመት››

ዐሥራ ስምንተኛው ዓመት
‹‹18 ዓመት››

የአክአብ ልጅ ኢዮራም
አንዳንዴ ይህ ሰው ኢዮሮብዓም ተብሎ ተጠርቷል። ይህ 2 ነገሥት 1፥17 ላይ ካለው ‹‹ኢዮራም›› የተለየ ነው።

በያህዌ ፊት ክፉ የሆነውን
እዚህ ላይ፣ ‹‹ፊት›› የያህዌን ሐሳብ ወይም አስተያየት ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ ክፉ ብሎ የሚያስበውን›› ወይም፣ ‹‹በያህዌ ፍርድ ክፉ የሆነውን››

አባትና እናቱ እንደ ፈጸሙት ዐይነት አልነበረም
ይህ የሚያመለክተው ወላጆቹን ያህል ባይሆንም፣ እርሱም ብዙ ኀጢአት ማድረጉን ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አባቱና እናቱ ያደረጉትን ያህል ክፉ ነገር አላደረገም።››

የበአል ሐውልት
ምንም እንኳ ሐውልቱ ምን ዐይነት እንደ ነበር ባይታወቅም፣ በአልን ለማምለክ ጥቅም ላይ የሚውል ነበር። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በአል የሚመለክበት ሐውልት››

በኀጢአት ተያዘ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ‹‹በኀጢአት ተያዘ›› ያንን ማድረግ ቀጠለ ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ኀጢአት ማድረጉን ቀጠለ››

ናባጥ
ይህ የሰው ስም ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከዚያ ዘወር አላለም
ከአንድ ነገር፣ ‹‹ዘወር›› ማለት ያንን ማድረግ መተው ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያንን ኀጢአት ማድረጉን አልተወም›› ወይም፣ ‹‹ያንን ኀጢአት ማድረግ ቀጠለ››

2 Kings 3:4

100,000 ጠቦትና **100,000** አውራ በግ ጠጉር ለእስራኤል ንጉሥ ይገብር ነበር
ሞሳ እንዲህ ያደርግ የነበረው መንግሥቱ በእስራኤል ንጉሥ ቁጥጥር ሥር ስለ ነበር ነው። የዚህን ዐረፍተ ነገር የተሟላ ትርጉም ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መንግሥቱ በእስራኤል ንጉሥ ቁጥጥር ሥር ስለ ነበር በየዓመቱ 100,000 ጠቦትና የ100,000 አውራ በግ ጠጉር ለእስራኤል ንጉሥ የመስጠት ግዴታ ነበረበት››

100,000 ጠቦት… **100,000** አውራ በግ
‹‹አንድ መቶ ሺህ ጠቦት… አንድ መቶ ሺህ አውራ በግ››

እስራኤልን ሁሉ ለጦርነት አንቀሳቀሰ
‹‹የእስራኤልን ሕዝብ ሁሉ ለጦርነት ማዘጋጀት›› እዚህ ላይ፣ ‹‹እስራኤል ሁሉ›› አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤል ወታሮችን ሁሉ ይመለከታል። የእስራኤል ወታደሮችን ሁሉ ለጦርነት አንቀሳቀሰ››

2 Kings 3:7

አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ኢዮራም ለንጉሥ ኢዮሳፍጥ እየተናገረ ነው።

ሞዓብ ላይ አብረኸኝ ትዘምታህን?
የሚናገረው ለኢዮሳፍጥ ቢሆንም፣ እርሱንና ሰራዊቱንም ይመለከታል። እዚህ ላይ ‹‹ሞዓብ›› — ‹‹የሞዓብን ሠራዊት›› ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተና ሰራዊትህ ሞዓብ ላይ ለመዝመት ከእኔ ጋር ትሄዳላችሁን?››

አዎን አብሬህ እዘምታለሁ
እርሱና ሰራዊቱ ንጉሥ ኢዮራም ጋር አብረው ሞዓብ ላይ እንደሚዘምቱ ኢዮሳፍጥ እየተናገረ ነው። ‹‹አዎን፣ አብረንህ እንሄዳለን››

እኔ እንደ አንተው ነኝ፤ ሕዝቤ እንደ ሕዝብህ ፈረሶቼም እንደ ፈረሶችህ ናቸው
ኢዮራም በእርሱና በሕዝቡ በፈረሶቹም ለዓላማው እንዲጠቀም ኢዮሳፍጥ ራሱን እየሰጠ ነው። እርሱ የኢዮራም መሆኑን እየተናገረ ነው። የዚህን ዐረፍተ ነገር ትርጉም ይበልጥ የተሟላ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንድናደርግ ምትፈልገውን ለማድረግ ዝግጁ ነን። ሰራዊቴም ሆነ ፈረሶቼ አንተን ለመርዳት ዝግጁ ናቸው።

በኤዶም ምድረ በዳ
‹‹በኤዶም ምድረ በዳ ውስጥ››

2 Kings 3:9

የእስራኤል ንጉሥ ከይሁዳ ንጉሥና ከኤዶም ንጉሥ ጋር ለመዝመት ተነሣ
ይህ የሚያመለክተው በሰራዊቶቻቸው የታጀቡ ንጉሦችን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤል ንጉሥና ሰራዊቱ ከይሁዳ ንጉሥና ከሰራዊቱ እንዲሁም ከኤዶም ንጉሥና ከሰራዊቱ ጋር ዘመተ››

ሰባት ቀን ዞሩ
ይህም ማለት 1) ንጉሦቹ ወዴት እንደሚሄዱ እርግጠኞች አልነበሩም፤ ስለዚህ መንገዳቸውን ይለዋወጡ ነበር ማለት ነው፤ ወይም 2) ንጉሦቹ የሚሄዱበትን ያውቁ ነበር፤ በሞዓብ ዙሪያ ዞሩ። (2 ነገሥት 3፥8)

ወዮ! ያህዌ እኛን ሦስት ነገሥታት የጠራን ለሞዓብ አሳልፎ ሊሰጠን ነውን?
የነበሩበት ሁኔታ ምን ያህል አስጨናቂና ግራ የሚያጋባ መሆኑን ለማሳየት ንጉሡ ይህን ጠይቋል። ይህን እንደ ዐረፍተ ነገር ማቅረብ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኛን ሦስት ነገሥታት ያህዌ በሞዓብ እንድንያዝ የፈለገ ይመስላል!››

ለሞዓብ እጅ አሳልፎ ሊሰጠን
እዚህ ላይ፣ ‹‹ሞዓብ›› ሰራዊቱን ያመለክታል። ‹‹ለሞዓብ እጅ›› በሞዓብ ሰራዊት ‹‹ቁጥጥር›› ሥር መሆኑን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለሞዓብ ቁጥጥር አሳልፎ ሊሰጠን›› ወይም፣ ‹‹የሞዓብ ሰራዊት ድል እንዲያደርገን››

2 Kings 3:11

በእርሱ አማካይነት ያህዌን ለመጠየቅ እንድንችል የያህዌ ነቢይ እዚህ የለምን?
ኢዮሳፍጥ እንዲህ በማለት የጠየቀው፣ እዚያ ነቢይ መኖሩንና እርሱን ፈልገው ማግኘት እንዳለባቸው ለማመልከት ነው። ይህን እንደ ዐረፍተ ነገር ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በዚህ ቦታ የያህዌ ነቢይ እንደሚኖር እርግጠኛ ነኝ፤ በእርሱ አማካይነት ያህዌን እንድጠይቅ የት እንደማገኘው ንገሩኝ››

ሣፋጥ
ይህ የሰው ስም ነው።

የኤልያስን እጅ ያስታጥብ የነበረው
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር የኤልያስ ረዳት ማለት ነው። ‹‹እጅ ማስታጠብ›› ኤልያስን ያገለግል የነበረበትን መንገድ የሚገልጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የኤልያስ ረዳት የነበረው››

የያህዌ ቃል ከእርሱ ዘንድ ይገኛል
ይህ ማለት ነቢይ ነበር፤ መናገር ያለበትን ያህዌ ይነግረው ነበር ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ የነገረውን ይናገር ነበር››

ወደ እርሱ ወረዱ
ኤልሳዕን ለማየትና ምን ማድረግ እንዳለባቸው ከእርሱ ለመጠየቅ ሄዱ። ይህን ዐረፍተ ነገር የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኤልሳዕን ለማየትና ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለመጠየቅ ወደ እርሱ ሄዱ።››

2 Kings 3:13

ከአንተ ጋር ምን የሚያገናኘኝ ነገር አለ?
ኤልሳዕ ይህን ጥያቄ ያቀረበው ንጉሡና እርሱ ምንም የጋራ የሆነ ነገር እንደሌላቸው አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህን እንደ ዐረፍተ ነገር ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከአንተ ጋር ምንም ጉዳይ የለኝም›› ወይም፣ ‹‹ከአንተ ጋር ምንም የምጋራው ነገር የለኝም››

በሞዓብ እጅ አሳልፎ ሊሰጣቸው
እዚህ ላይ፣ ‹‹የሞዓብ እጅ›› የሞዓብን፣ ‹‹ቁጥጥር›› ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለሞዓባውያን ቁጥጥር አሳልፎ ሊሰጣቸው›› ወይም፣ ‹‹በሞዓብ ሰራዊት እንዲያዙ ለማድረግ››

በፊቱ የቆምሁት የሰራዊት ጌታ ሕያው ያህዌን
‹‹በፊቱ የቆምሁት የሰራዊት ጌታ ያህዌ በእርግጥ ሕያው እንደ ሆነ። እዚህ ላይ ኤልሳዕ የያህዌን ሕያው መሆን እርግጠኝነት፣ ለኢዮሳፍጥ ሲል እንጂ ኢዮራምን እንደ ቁም ነገር እንደማይቆጥረው ከነበረው እርግጠኝነት ጋር ያነጻጽራል። ይህ የመሐላ ያህል ነበር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በፊቱ የቆምሁት የሰራዊት ጌታ ያህዌ ሕያው የመሆኑን ያህል ይህንንም በእርግጠኝነት ነው የምነግርህ››

በፊቱ የቆምሁት
እዚህ ላይ ያህዌን ማገልገል በፊቱ መቆም እንደ ሆነ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የማገለግለው ያህዌ››

የይሁዳን ንጉሥ ኢዮፍጥን ባላከብር ኖሮ፣ አንተን አላይም ወይም ጉዳዬ አልልህም ነበር
ይህን በአዎንታዊ መልኩ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተን የማናግርህ የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሳፍጥን ስለማከብር ነው››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የኢዮሳፍጥን ፊት አከብራለሁ
እዚህ ላይ የኢዮሳፍጥ ፊት የእርሱን መገኘት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኢዮሳፍጥን አከብራለሁ››

አንተን አላይም ወይም ጉዳዬ አልልህም ነበር
የእነዚህ ሁለት ሐረጎች ትርጉም ተመሳሳይ ሲሆን፣ ለኢየራም ይህን ያህል ግምት እንደሌለው አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከአንተ ጋር ምንም ዐይነት ጉዳይ የለኝም››

2 Kings 3:15

ከዚያም እንዲህ ሆነ
‹‹እንዲህ ተደረገ››

በገና ደርዳሪ
በገና የማጫወት ሰው

የያህዌ እጅ በኤልሳዕ ላይ መጣ
እዚህ ላይ፣ ‹‹የያህዌ እጅ›› የያህዌን፣ ‹‹ኀይል›› ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የያህዌ ኀይል በኤልሳዕ ላይ መጣ››

ሸለቆ
እዚህ ላይ ሸለቆ ውሃ እንዲጠራቀምበት ሠራተኞች የቆፈሩት ረጅም የውሃ መውረጃ ነው።

ሸለቆው ውሃ ይሞላል
ይህን ተሻጋሪ ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህን የወንዝ ሸለቆ ውሃ እሞላዋሁ››

እናንተ ትጠጣላችሁ
እዚህ ላይ ያህዌ የሚሰጠውን ውሃ መጠጣትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እናንተም ውሃውን ትጠጣላችሁ››

2 Kings 3:18

ይህ በያህዌ ፊት ቀላል ነው
የያህዌ ፊት የያህዌን ፍርድና መርማሪነት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ይህን እንደ ቀላል ነገር ነው የሚያየው›› ወይም፣ ‹‹ይህን ማድረግ ለያህዌ ቀላል ነገር ነው››

የተመሸገ ከተማ
የተመሸገ ከተማ ጠላት እንዳያጠቃው ዙሪያውን ረጃጅም ግንብ ያለው ከተማ ነው።

መልካሙን ዕርሻ በድንጋይ ታበላሹታላችሁ
ይህ ማለት መልካሙ እርሻ ጥቅም ላይ እንዳይውል በድንጋይ ትሞሉታላችሁ ማለት ነው። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መልካሙን እርሻ ድንጋይ በመሙላት ጥቅም እንዳይሰጥ ታደርጉታላችሁ››

2 Kings 3:20

ውሃ እየጐረፈ መጣ
‹‹ውሃ መፍሰስ ጀመረ›› ምድሪቱም ውሃ በውሃ ሆነች

‹‹ወዲያውኑ ምድሪቱ በውሃ ተሞላች›› ምድሪቱ
አገር፣ ቦታ

2 Kings 3:21

በዚህ ጊዜ
ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው ዋናውን ታሪክ ገታ ለማድረግ ነው። የሞዓብ ሰራዊት ሦስቱን ነገሥታት ጦርነት ለመግጠም እያደረጉ ለነበረው ዝግጅት ጸሐፊው ዳራ የሚሆን መረጃ ያቀርባል።

መሣሪያ መያዝ የቻለ ሁሉ
እዚህ ላይ፣ ‹‹መሣሪያ›› መዋጋት መቻል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መዋጋት የሚችል ሰው ሁሉ››

ነገሥታቱ... መጡ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ነገሥታት›› ሰራዊቶቻቸውንና ነገሥታቱ ራሳቸውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ነገሥታቱ ከሰራዊቶቻቸው ጋር መጡ›› ወይም፣ ‹‹ነገሥታቱና ሰራዊቶቻቸው መጡ››

እንደ ደም ቀልቶ ታያቸው
እዚህ ላይ ውሃው ቀይ ሆኖ መታየቱን ከደም ቀለም ጋር ያነጻጽራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ደም ቀይ ሆነ››

እንግዲህ ሞዓብ
ወታደሮቹ ራሳቸውን፣ ‹‹ሞዓብ›› በማለት ነው የሚገልጹት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሞዓብ ወታደሮች››

ወደ ምርኮህ ዙር
‹‹ንብረታቸውን መዝረፍ›› ወታደሮች ጠላቶቻቸውን ካሸነፉ በኃላ ማንኛውንም ዋጋ ያለው ነገር ከከተሞቻቸው ይዘርፉ ነበር።

2 Kings 3:24

የእስራኤል ሰፈር
እዚህ ላይ ‹‹እስራኤል›› የሚያመለክተው የእስራኤልን ወታደሮች እንጂ፣ ጠቅላላውን የእስራኤል ሕዝብ አይደለም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እስራኤላውያን ድንኳኖቻቸውን ተክለው የነበረበት ቦታ››

እስራኤላውያን ወጓቸው
‹‹እስራኤላውያን›› የሚያመለክተው የእስራኤል ወታደሮችን እንጂ፣ ጠቅላላውን የእስራኤል ሕዝብ አይደለም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤል ወታደሮች ወጓቸው››

ከፊታቸው ሸሹ
‹‹ከፊታቸው ሮጠው አመለጡ››

ቂር ሐራሴት
ይህ የሞዓብ ዋና ከተማ ነው።

ከነድንጋይዋ ቀርታ ነበር
የከተማዋ ግንቦችና ሕንጻዎች ከድንጋይ የተሠሩ ነበሩ። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የድንጋይ ግንቦቿና ሕንፃዎቹ እንዳሉ ነበሩ።››

ባለ ወንጭፉ
‹‹ወንጭፍ›› ከእንስሳት ቆዳ የተሠራ ረጅም ገመድ ሲሆን፣ ጫፍ ላይ ድንጋይ ወይም ሌላ ጠጣር ነገር ተደርጐለት ከሩቅ ይወነጨፍ ነበር።

2 Kings 3:26

ንጉሥ ሞሳ
የዚህን ንጉሥ ስም 2 ነገሥት 3፥4 ላይ በተረጐምህበት መንገድ ተርጉመው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በጦርነቱ መሸነፉን እንዳወቀ
‹‹ሰራዊቱ መሸነፉን...››

ሰይፍ የታጠቁ ሰባት መቶ ሰዎች
‹‹700 ሰይፍ የታጠቁ...››

ሰይፍ የታጠቁ
በሰይፍ የሚዋጉ ወታደሮች

ጥሶ ለመግባት
‹‹በጎይል አሸንፎ...›› ጦር ሜዳ ላይ የተሰለፉ ወታደሮች በጣም ብዙ ስለ ነበሩ አልፎ ለመሄድ አስቸጋሪ ነበር።

የሚቃጠል መሥዋዕት አድርጐ አቀረበው
ንጉሥ ሞሳ እስኪሞት ድረስ ልጁን በእሳት አቃጠለው። ይህን ያደረገው ለሐሰተኛው አምላክ ለካሞስ መሥዋዕት እንዲሆን ነበር። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል።

በእስራኤልም ላይ ታላቅ ቁጣ ሆነ
እዚህ ላይ ‹‹ቁጣ›› የሚለውን ቃል ግሥ ማድረግ ይቻላል። የተቆጣው ማን እንደ ነበር ሁለት ትርጉሞች ሊኖሩ ይችላሉ። 1) ሞዓባውያን ወታደሮች። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሞዓባውያን ወታደሮች እስራኤልን በጣም ተቆጡ›› ወይም 2) እግዚአብሔር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔር እስራኤልን በጣም ተቆጣ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 የነቢያት ጉባኤ አባል የነበረ፣ ባልዋ የሞተባት አንዲት ሴት ወደ ኤልሳዕ መጥታ፣ ጌታዬ ሆይ፣ ባሌ ሞቶብኛል፤ እርሱም አንተ እንደምታውቀው እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ነበር። ነገር ግን እነሆ ለባሌ ገንዘብ አበድሮት የነበረ አንድ ሰው በባሌ ዕዳ ፈንታ ሁለት ወንዶች ልጆቼን ወስዶ ባሪያ አደርጎ ሊገዛቸው ፈልጎአል አለችው። 2 ኤልሳዕም ታዲያ ምን እንዳደርግልሽ ትፈልጊያለሽ? በቤትሽ ምን እንዳለሽ ንገሪኝ? ሲል ጠየቃት። እርስዋም በትንሽ ማሰሮ ከሚገኝ የወይራ ዘይት በቀር ሌላ ምንም የለኝም ስትል መለሰችለት። 3 ኤልሳዕም እንዲህ አላት፦ ወደ ጎረቤቶችሽ ሄደሽ ማግኘት የምትችዪውን ያህል ባዶ ማድጋ ለምኚ፤ 4 ከዚህም በኋላ አንቺና ልጆችሽ ቤት ገብታችሁ በሩን ዝጉ። የማሰሮውንም ዘይት ወደ ማድጋዎቹ ማንቆርቆር ጀምሪ፤ እያንዳንዱ ማድጋ በሚሞላበት ጊዜ ለብቻው በማግለል አኑሩት። 5 ስለዚህም ሴትዮዋ ወደ ቤትዋ ሄዳ ከልጆችዋ ጋር በሩን ዘጋች፤ ዘይት የነበረበትን ትንሽ ማሰሮ አንሥታም ልጆችዋ እያቀረቡላት በማንቆርቆር በየማድጋዎቹ ሞላች። 6 ማድጋዎቹንም ሁሉ ከሞሉ በኋላ ሌላ ትርፍ የለም ወይ ስትል ጠየቀች፤ ከልጆችዋም አንዱ ሌላ ማድጋ የለም ሲል መለሰላት። ከዚያ በኋላ ዘይቱ መውረዱን አቆመ። 7 እርስዋም ተመልሳ ወደ ነቢዩ ኤልሳዕ ሄደች፤ እርሱም እንግዲህ ዘይቱን ሸጠሽ ዕዳሽን ክፈይ፤ ለአንቺና ለልጆችሽ መተዳደሪያ የሚሆንም ብዙ ገንዘብ ይተርፍሻል አላት። 8 አንድ ቀን ኤልሳዕ አንዲት ሀብታም ሴት ወደምትኖርበት ወደ ሱነም ሄደ፤ እርስዋም ምግብ እንዲበላ ጋበዘችው፤ ከዚያን ዕለት ጀምሮ ወደ ሱነም በሚመጣበት ጊዜ ሁሉ በቤትዋ ይመገብ ነበር። 9 እርስዋም ባልዋን እንዲህ አለችው፤ ብዙ ጊዜ ወደ ቤታችን የሚመጣው ይህ ሰው የተቀደሰ የእግዚአብሔር ሰው ስለ መሆኑ እርግጠኛ ነኝ። 10 ስለዚህም በሰገነቱ ላይ አንድ ትንሽ ክፍል ሠርተን በዚያች ውስጥ አል፣ ጠረጴዛ፣ ወንበርና የፋኖስ መብራት እናኑርለት፤ እርሱም ወደ እኛ በሚመጣበት ጊዜ እዚያ ያርፋል። 11 አንድ ቀን ኤልሳዕ ወደዚያ እንደገና ሄደ፤ ወደ ተሠራለት ክፍል ገብቶ እረፍት አደረገ። 12 ኤልሳዕም ለአገልጋዩ ግያዝ እንዲህ አለ፦ «ይህችን ሱናማዊት ጥራት» በጠራትም ጊዜ መጥታ በፊቱ ቆመች። 13 ኤልሳዕም ግያዝን እንዲነግራት እንዲህ አለው፦ «እኛን ለመንከባከብ ይህን ሁሉ ተቸገረሽ፤ እኛ ደግሞ ለአንቺ ምን እናድርግልሽ? ለንጉሥ ወይም ለጦር አዛዥ ስለ አንቺ ልንነግርልሽ እንችላለን? በላት አለው። እርስዋም «በዘመዶቼ መካከል ስለምኖር በዚህ ስፍራ ምንም የሚቸግረኝ ነገር የለም» ስትል መለሰችለት። 14 ኤልሳዕም ግያዝን «ታዲያ ምን ልናደርግላት እችላለን?» ሲል ጠየቀው። ግያዝም "እነሆ ልጅ የላትም፣ ባሏም ሸምግሎአል" አለ። 15 ኤልሳዕም ጥራት አለው። ሲጠራትም መጥታ በበሩ አጠገብ ቆመች። 16 ኤልሳዕም አላት፦ በመጪው ዓመት በዚህ ጊዜ ወንድ ልጅ ትታቀፊያለሽ አላት። እርስዋም ጌታዬ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ! እባክህ አገልጋይህን አትዋሻት አለችው። 17 ሴቲቱም ፀነሰች፤ ልክ ኤልሳዕ የተናገረው ጊዜ ሲደርስ በዓመቱ ወንድ ልጅ ወለደች። 18 ሕፃኑም በአደገ ጊዜ አንድ ቀን አባቱ ከአጫጆች ጋር ወዳለበት ሄደ። 19 እርሱም በድንገት "ራሴን! ራሴን!" ብሎ ወደ አባቱ ጮኸ። አባትየውም አንዱን አገልጋይ ጠርቶ፦ "ልጁን ወደ እናቱ ውሰድ" ሲል አዘዘው። 20 አገልጋዩም ልጁን ተሸክሞ ወደ እናቱ ባመጣው ጊዜ እርስዋም ተቀብላው በጉልበትዋ እንደታቀፈችው ቆይቶ እኩለ ቀን ላይ ሞተ። 21 ሴቲቱም ተነሥታ ልጁን በእግዚአብሔር ሰው አልጋ ላይ አስተኝታ በሩን ዘግታበት ተመልሳ ሄደች። 22 ባልዋንም ጠርታ "አንድ አገልጋይና አንድ አህያ ላክልኝ፤ ወደ እግዚአብሔር ሰው ዘንድ ሄጄ እመለሳለሁ አለችው። 23 ባልዋ "ለምን መሄድ ትፈልጊያለሽ? ዛሬ ሰንበት ወይም የጨረቃ በዓል የሚከበርበት ቀን አይደለም" አላት። እርስዋም "ግድ የለም፤ እንዳልኩህ አድርግ" አለችው። 24 እርስዋም አህያው እንዲጫንላት ካደረገች በኋላ አገልጋዩን "በተቻለ መጠን አህያው እንዲፈጥን አድርግ፤ እኔም ካልነገርኩህ በቀር ቀስ ብሎ እንዲሄድ ዕድል አትስጠው" ስትል አዘዘችው። 25 እርስዋም ከዚያ ተነሥታ ኤልሳዕ ወደነበረበት ወደ ቀርሜሎስ ተራራ ወጣች። የእግዚአብሔርም ሰው ገና በሩቅ ሳለች ወደ እርሱ ስትመጣ አይቶ አገልጋዩን ግያዝን «ተመልከት! ያቺ ሱነማዊት ወደዚህ እየመጣች ነው! አለው። 26 ፈጠን ብለህ ሂድና የእርስዋን፤ የባልዋንና የልጅዋን ደኅንነት ጠይቃት» አለው። እርስዋም ግያዝን «ሁላችንም ደኅና ነን» ስትል ነገረችው። 27 ወደ ኤልሳዕ ወደ ተራራው በመጣች ጊዜ እግሮቹን ያዘች፤ በዚህ ጊዜ ግያዝ ሊያርቃት ፈለገ፤ ኤልሳዕ ግን «ተዋት፤ እርስዋ ተጨንቃለች፣ እግዚአብሔርም ከእኔ ሰውሮታልና ምንም የነገረኝ ነገር የለም» አለው። 28 ሴቲቱም «ጌታዬ፣ ልጅ እንድትሰጠኝ ጠይቄህ ነበርን? ‹አታሳስተኝ› ብዬ ነግሬህ አልነበረምን?» አለችው። 29 ኤልሳዕም ግያዝን አለው፦ «ለጉዞ በፍጥነት ተነሣና ምርኩዜን በእጅህ ያዝ። ወደ ቤትዋ ሂድ። በመንገድ ማንንም ብታገኝ ሰላምታ አትስጥ፤ ማንም ሰላምታ ቢሰጥህ መልስ አትስጥ። ምርኩዜን በልጁ ፊት ላይ አኑር!» አለው። 30 የልጁ እናት ግን ኤልሳዕን «በምትተማመንበት በሕያው እግዚአብሔር ስምና በነፍስህ እምላለሁ፤ ከቶ አንተን ትቼ አልሄድም!» አለችው፤ ስለዚህ እርስዋን ተከትሎ ለመሄድ ተነሣ፤ 31 ግያዝም ወደ ፊት ቀድሞአቸው የኤልሳዕን ምርኩዝ በልጁ ፊት ላይ አኖረ፤ ነገር ግን ልጁ ግን አልተናገረም፣ አልሰማም። ስለዚህም ተመልሶ ሄዶ ኤልሳዕን «ልጁ አልተነሣም» አለው። 32 ኤልሳዕም ወደ ቤቱ በደረሰ ጊዜ ልጁ ሞቶ አልጋ ላይ ነበር። 33 ስለዚህ ኤልሳዕ ገባና በሩን በልጁና በራሱ ላይ ዘግቶ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ። 34 ሄዶም በልጁ ላይ ተጋደመ፤ አፉን በአፉ ላይ፣ ዐይኖቹን በአይኖቹ ላይ፣ እጆቹን በእጆቹ ላይ አደረገ፤ ራሱን በልጁ ላይ ዘርግቶ ተጋደመ፤ የልጁም ሰውነት መሞቅ ጀመረ። 35 ከዚያም፣ ኤልሳዕ ተነሥቶ በክፍሉ ውስጥ ወዲያና ወዲህ ይመላለስ ጀመር፤ እንደገናም ተመለሰና በመዘርጋት በልጁ ላይ ተጋደመ። ልጁም ሰባት ጊዜ ካስነጠሰው በኋላ ዐይኖቹን ከፈተ። 36 ስለዚህ ኤልሳዕ ግያዝን ጠርቶ እንዲህ አለ፣ ሱነማይቱን ጥራት አለው። እርሱም ጠራት፣ እርስዋም በመጣች ጊዜ ኤልሳዕ ልጅሽ ይኸውልሽ አንሽው አላት። 37 እርስዋ ወደ መሬት ለጥ ብላ በኤልሳዕ ጫማ ላይ በመውደቅ እጅ ነሣች፤ ከዚያም በኋላ ልጅዋን ይዛ ሄደች። 38 ከዚያም ኤልሳዕ ወደ ጌልጌላ መጣ። በአገሪቱ ራብ በነበረበት ጊዜ የነቢያት ልጆች በፊቱ ተቀምጠው ነበር። እርሱም አገልጋዩን እንዲህ አለው፦ ትልቅ ድስት ጥደህ ለነቢያቱ ልጆች ወጥ ሥራላቸው አለው። 39 ከነቢያቱም አንዱ ቅጠላ ቅጠል ለመልቀም ወደ ሜዳ ሄደ። እርሱም በጫካ ውስጥ የበቀለ የቅል ሐረግ አገኘ፤ መሸከም የሚችለውን ያህል በርከት ያለ ቅል ቆርጦ አመጣ። እርሱም ከተፈውና ወጡ ውስጥ ጨመረው፤ ነገር ግን ምን እንደሆነ ዐላወቁም። 40 እነርሱም ወጡን ለሰዎቹ እንዲመገቡት አወጡ። በኋላም እየበሉ ሳለ ጮኸው፣ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፣ በድስቱ ውስጥ ሞት አለ! አሉት፤ ስለዚህም ሊበሉት አልቻሉም። 41 ነገር ግን ኤልሳዕ እንዲህ አለ፦ ጥቂት ዱቄት አምጡልኝ። ያመጡትን ዱቄት በድስቱ ውስጥ ጨምሮ እንዲህ አለ፦ ለሰዎች እንዲበሉ ወጡን አውጡ። ከዚያ በወጡ ውስጥ የሚጎዳ ነገር አልተገኘም። 42 በዓል ሻሊሻ ተብሎ ከሚጠራው ስፍራ አንድ ሰው ወደ እግዚአብሔር ሰው መጥቶ በመከር ጊዜ በመጀመሪያ ከተወቃው ሃያ የገብስ የዳቦ ሙልሙሉችና አዲስ የተቆረጠ እሸት በከረጢቱ አመጣለት። እርሱም ይህን እንዲበሉ ለነቢያት ልጆች ስጡአቸው አለ። 43 አገልጋዩም እንዲህ አለ፦ በመቶ ሰዎች ፊት ይህን ምን ብዬ ማቅረብ አለብኝ? ነገር ግን ኤልሳዕ አለ፦ እንዲበሉ ለሰዎቹ ስጣቸው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ይበላሉ ያተርፉማል። 44 ስለዚህም አገልጋዩ ምግቡን አቀረበላቸው፣ እግዚአብሔርም በተናገረው መሠረት ሁሉም በልተው ከጠገቡ በኋላ የተረፈ ምግብ ነበር።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Kings 4:1

የነቢያት ልጆች
እነዚህ የነቢያት ስብስብ እንጂ፣ በቀጥታ የነቢያት ልጆች አልነበሩም። 2 ነገሥት 2፥3 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ነቢያት››

አገልጋይህ ባሌ
‹‹አገልጋይህ የነበረው ባሌ››

ባለ ዕዳ
ለሰዎች ገንዘብ የሚያበድር ሰው

አገልጋይህ ምንም ነገር የላትም
ለእርሱ ያላትን አክብሮት ለማሳየት ሴትዮዋ የኤልሳዕ አገልጋይ እንደ ሆነች ተናገረች

ከጥቂት ዘይት በቀር በቤቷ ምንም
ይህ ማጋነን ነው። ያላት ንብረት የዘይት ማድጋ ብቻ ነበር።

2 Kings 4:3

ወደ ውስጥ ግቢ
ይህ ወደ ቤታቸው መግባት ማለት ነው። የተሟላውን ዐረፍተ ነገር የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ወደ ቤትሽ ግቢ››

2 Kings 4:5

ዕቃዎች
‹‹ማድጋዎች››

2 Kings 4:7

የእግዚአብሔር ሰው
ይህ የሚያመለክተው ኤልሳዕን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕ››

የተረፈው የአንቺና የልጆችሽ መተዳደሪያ ይሁን
ምግብና ልብስ የመሳሰሉ አስፈላጊ ነገሮችን ለመግዛት ገንዘቡን ተጠቀመበት ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የተቀረውን ገንዘብ አንቺና ልጆችሽ ለኑሮ የሚያስፈልጋችሁን ለመግዛት ተጠቀሙበት።

2 Kings 4:8

ሹነም
ይህ የአንድ ከተማ ስም ነው።

ከእርሷ ጋር ምግብ እንዲበላ አጥብቃ ለመነችው
በዚያ በኩል ሲያልፍ ጐራ ብሎ እቤቷ ምግብ እንዲበላ ጠየቀችው ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ወደ ቤቷ መጥቶ ምግብ እንዲበላ ጠየቀችው››

በዚያም ባለፈ ቁጥር
‹‹በሹነም በኩል ሲያልፍ››

መሆኑን አውቃለሁ
‹‹ይህን በሚገባ እረዳለሁ››

አዘውትሮ በደጃችን የሚያልፍ
‹‹ሁልጊዜ በደጃችን በኩል የሚያልፍ››

2 Kings 4:10

አጠቃላይ መረጃ
ያቺ ሀብታም ሴት ስለ ኤልሳዕ ለባልዋ እየተናገረች ነው።

እናስገባለን
ይህ የሚያመለክተው ያቺን ሀብታም ሴትና ባልዋን ነው።

2 Kings 4:12

ግያዝ
ይህ የሰው ስም ነው።

ሱነማዪቱን ጥራት
‹‹ሰነማዪቱን ሴት ጥራት›› ይህ የሚያመለክተው ኤልሳዕ እቤቷ ይኖር የነበረውን ከሹነም የሆነችውን ሴት ነው።

ለእኛ ስትይ በጣም ተቸግረሻል
‹‹በጣም ተቸግረሻል›› የሚለው አንዳች ነገር ለማድረግ ከፍ ያለ ጥረት አድርገሻል ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለእኛ ይህን ለማድረግ ትልቅ ጥረት አድርገሻል›› ወይም፣ ‹‹ለእኛ ይህን ለማድረግ ከባድ ዋጋ ከፍለሻል››

ምን እንዲደረግልሽ ትፈልጊያለሽ?
ይህን፣ ‹‹ምን እናድርግልሽ?›› በማለት መተርጐም ይቻላል።

የምንነግርልሽ ጉዳይ አለን?
ለንጉሡ ወይም ለሰራዊቱ አዛዥ እንዲነግርላት የምትፈልገው ነገር ካለ ኤልሳዕ ሴትዮዋን እየጠየቀ ነው። ይህን ጥያቄ ግልጽ በሆነ ሁኔታ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ስለ አንቺ ጥያቄ እናቅርብ?››

እኔ እኮ የምኖረው በገዛ ወገኖቼ መካከል ነው
ቤተ ሰቧ የሚያስፈልጋትን ሁሉ ስለሚያደርግላት ሴትዮዋ ምንም እንደማያስፈልጋት እየተናገረች ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በቤተ ሰቤ ተከብቤ ነው ያለሁት፤ እነርሱ ስላሉ ምንም የሚጐድለኝ የለም››

2 Kings 4:14

ጥራት
‹‹እንድትመጣ ንገራት››

በጠራትም ጊዜ
‹‹እንድትመጣ ግያዝ ሲነግራት››

እበራፉ ላይ
መተላለፊያው ላይ ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹መውጫ መግቢያው ላይ››

ልጅ
‹‹ወንድ ልጅ››

ጌታዬ የእግዚአብሔር ሰው
ሴትዮዋ በእነዚህ ሁለት መጠሪያዎች የተጠቀመችው ኤልሳዕን ለማመልከት ነው።

አገልጋይህ
ለእርሱ ያለትን አክብሮት ለማሳየት ሴትዮዋ ራሷን አገልጋይህ አለች።

2 Kings 4:17

የዛሬ ዓመት በዚሁ ጊዜ
‹‹በሚቀጥለው ዓመት በዚሁ ጊዜ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ራሴን! ራሴን!
ሕመም ስለ ነበረው ልጁ ይህን ተናገረ። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ራሴን አሞኛል! ራሴን አሞኛል!››

እስከ እኩለ ቀን ድረስ በእናቱ ጉልበት ላይ ተቀመጠ፤ ከዚያም ሞተ
እዚህ ላይ ጉልበት ያለው የሴትዮዋን ጭን ነው። እስኪሞት ድረስ ልጁ ጭኗ ላይ ነበር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኩለ ቀን እስኪሆንና እስኪሞት ድረስ ጭኗ ላይ አደረገችው››

2 Kings 4:21

የእግዚአብሔር ሰው
‹‹የእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕ››

ወደ እግዚአብሔር ሰው በፍጥነት ደርሼ እንድመለስ
ሴትዮዋ ኤልሳዕን ለማግኘት እንደምትሄድ እንጂ፣ የምትሄደው ልጇቸው ስለ ሞተ መሆኑን አልተናገረችም። ይህንን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቶሎ ወደ እግዚአብሔር ሰው ሄጄ፣ ቶሎ እንድመጣ› ልጃቸው መሞቱን ግን ለባልዋ አልተናገረችም››

2 Kings 4:23

ደህና ነው
ሴትዮዋ ይህን ያለችው ባልዋ እንደ ነገረችው ካደረገ እንደዚያ እንደሚሆን ስላወቀች ነው። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ የምጠይቅህን ካደረግህ ደህና ይሆናል››

አህያውን ጭና
አህያውን የጫነው አገልጋዩ እንጂ፣ ሴትዮዋ ራሷ አይደለችም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አገልጋዩ አህያውን ጫነላት››

2 Kings 4:25

ተነሥታ የእግዚአብሔር ሰው ወዳለበት ቀርሜሎስ ተራራ ሄደች
‹‹የእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕ ወደ ነበረበት የቀርሜሎስ ተራራ ሄደች››

የእግዚአብሔር ሰው በሩቅ ሲያያት
‹‹ገና ሩቅ እያለች ኤልሳዕ ስትመጣ አያት››

ደህና ነው
‹‹መልካም ነው›› ወይም፣ ‹‹አዎን፣ ሁሉም ደህና ነው››

2 Kings 4:27

ተራራው
‹‹የቀርሜሎስ ተራራ››

እግሩ ላይ ተጠመጠመች
ይህም ማለት ተንበረከከች ወይም እፊቱ መሬት ላይ ተጋድማ እግሩን አጥብቃ ያዘች ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እፊቱ መሬት ላይ ወድቃ በእጆቿ እግሩን ያዘች››

ያህዌ ይህን ለምን ከእኔ እንደ ሰወረውና እንዳልነገረኝ አልገባኝም
ኤልሳዕ ሴትዮዋ ምን ያህል እንዳዘነች ማየት ችሏል፤ ያህዌ ግን የችግሯን ምክንያት አልገለጸለትም።

2 Kings 4:28

ጌታዬ፤ ለመሆኑ እኔ ልጅ እንድትሰጠኝ ጠይቄህ ነበርን? አኩል ተስፋ እንዳትሰጠኝ አላልሁህምን?››
ሴትዮዋ ይህን የጠየቀችው በሆነው ነገር ምን ያህል እንደ ታወከች ለማሳየት ነበር። ወንድ ልጅ እንደምትወልድ በነገራት ጊዜ ከኤልሳዕ ጋር የተነጋገረችውን እየተናገረች ነው። ይህን ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንዳትዋሸኝ ነገርሁህ እንጂ፣ ልጅ እንድትሰጠኝ አልጠየቅሁህም!››

እንግዲህ ወገብህን ታጠቅ
‹ለጉዞ ተዘጋጅ››

ሰው ብታገኝ ሰላም አትበል፤ ማንም ሰው ሰላም ቢልህ መልስ አትስጥ
ኤልሳዕ ግያዝ በተቻለ መጠን ቶሎ እንዲሄድ፣ ከሰው ጋር ለመነጋገር መንገድ ላይ እንዳይቆም ፈልጓል።

2 Kings 4:30

ሕያው ያህዌን በሕያው ነፍስህም
‹‹ሕያው ያህዌን፣ በሕያው ነፍስህም›› የሚለው እናትየው እየማለች እንደ ሆነ ያመለክታል። እናትየው የያህዌንና የኤልሳዕን ሕያውነት ከምትናገረው ነገር እርግጠኝነት ጋር አነጻጽራለች። ይህ መሐላ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ እምላለሁ››

ልጁ ግን አይናገርም ወይም አይሰማም ነበር
ይህ ማለት ሕይወት አልነበረውም ማለት ነው። ይህንን ይበልጥ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ልጁ ግን ምንም የሕይወት ምልክት አላሳየም››

ልጁ አልነቃም
እዚህ ላይ እንቅልፍ ከሞት ጋር ተመሳስሎአል። አማራጭ ትርጉም ‹‹እንደ ሞተ ነው››

2 Kings 4:32

ኤልሳዕ ወደ ውስጥ ገባ፤ ከዚያም በሩን በራሱና በልጁ ላይ ዘጋ
‹‹ኤልሳዕ ልጁ ተኝቶ ወደ ነበረበት ክፍል ገብቶ በሩን ዘጋ››

2 Kings 4:35

በልጁ ላይ ተጋደመ
‹‹ልጁ ላይ ተዘረጋ››

ሱነማዪቱ
‹‹ሱነማዪቱ ሴት››

በእግሩ ላይ ወደቀች፤ በምድርም ላይ ተደፋች
የታላቅ አድናቆትና አክብሮት ምልክት በሆነ ሁኔታ ሴትዮዋ ኤልሳዕ ፊት አጐነበሰች። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምስጋናዋን ለመግለጽ ፊትዋን ወደ መሬት አድርጋ ኤልሳዕ ፊት አጐነበሰች››

2 Kings 4:38

የነቢያት ልጆች
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። እነዚህ ልጆች የነቢያት ስብስብ እንጂ፣ በቀጥታ የነቢያት ልጆች አይደለም። 2 ነገሥት 2፥3 ላይ ይህን እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። ‹‹የነቢያት ስብስብ››

ወጥ
ብዙውን ጊዜ ይህ ማሰሮ ውስጥ የሚቀቀል የሥጋና የአትክልት ምግብ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ዱር በቀል ሐረግ
ይህ አትክልት ዱር የሚበቅል ማለት ማንም ያልተከለው ነበር።

በልብሱ ሙሉ ይዞ
በእጁ መያዝ ከሚችለው በላይ ብዙ የዱር ሐረግ መያዝ የሚችልበት ቦታ ለማግኘት ሲል የቀሚሱን ጠርዝ እስከ ወገቡ ድረስ አጠፈ።

ምን እንደ ሆነ ግን ማንም አላወቀም
ምን ዐይነት የዱር ሐረግ እንደ ሆነ ባለማወቃቸው ለመብል መልካም መሆን አለመሆኑን አላወቁም። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ነገር ግን ለመብል መልካም መሆን አለመሆኑን አላወቁም።

2 Kings 4:40

ወጡ ወጣ
‹‹ወጡን ሳህን ላይ አውጡት››

ምንቸቱ ውስጥ ሞት አለ
ይህ ማለት ምንቸቱ ውስጥ የሚገድል ነገር አለ ማለት እንጂ፣ አንዳች የሞተ ነገር ምንቸቱ ውስጥ አለ ማለት አይደለም። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ምንቸቱ ውስጥ እኛን የሚገድል ነገር አለ››

በምንቸቱ ውስጥ ጨመረው
‹‹ምንቸቱ ውስጥ ወዳለው ወጥ ጨመረው››

ለሰዎቹ አቀረበላቸው
‹‹ሰዎቹ እንዲበሉት አቀረበላቸው››

2 Kings 4:42

በአልሻሊሻ
ይህ የከተማ ስም ነው።

ሃያ ሙልሙል
‹‹20 ሙልሙል››

ከበኩራቱ ፍሬ
‹‹መጀመሪያ ከተገኘው ፍሬ የተጋገረ››

የእሸት ዛላ
‹‹ትኩስ እሸት›› ይህ ከአዲሱ መከር የተገኘ እህል ማለት ነው።

ይህን እንዴት አድርጌ ለመቶ ሰው አቀርባለሁ?
ሰውየው ይህን የጠየቀው ለመቶ ሰው የሚበቃ እንጀራ አለመኖሩን ለማመልከት ነው። ይህን በዐረፍተ ነገር ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹መቶ ሰው ለመመገብ አይበቃም››

መቶ ሰው
‹‹100 ሰው››

የያህዌ ቃል
እዚህ ላይ ያህዌ ከተናገረው ጋር ተያይዞአል። ይህ ሐረግ ያህዌ ራሱን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 5

1 የሶርያ ጦር አዛዥ የነበረው ንዕማን በሶርያ ንጉሥ ዘንድ ታላቅና የተከበረ ነበር፤ ምክንያቱም በእርሱ አማካይነት እግዚአብሔር ለሶርያ ሠራዊት ድልን አጎናጽፎ ነበር። እርሱም ደግሞ ጠንከራና ብርቱ ሰው ነበር፤ ነገር ግን ለምጻም ነበር። **2** ሶርያውያን በእስራኤላውያን ላይ ወረራ በፈጸሙበት ጊዜ አንዲት ትንሽ እስራኤላዊት ልጃገረድ ማርከው ወስደው ነበር፤ እርስዋም ለንዕማን ሚስት ሠራተኛ ሆና ታገለግል ነበር። **3** ልጃገረዲቱም እመቤትዋን እንዲህ አለቻት፦ «ጌታዬ በሰማርያ ወደሚገኘው ነቢይ ቢሄድ እወዳለሁ! እርሱም ጌታዬን ከዚህ ለምጽ ሊያነፃው ይችላል!» አለቻት። **4** ንዕማንም ይህን በሰማ ጊዜ ወደ ንጉሡ ቀርቦ ልጃገረዲቱ ያለችውን ሁሉ ነገረው። **5** ስለዚህ የሶርያ ንጉሥ እንዲህ አለ፣ «ለእስራኤል ንጉሥ ደብዳቤ እልካለሁ፤ አሁን አንተ ሂድ» ብሎ ፈቀደለት። ንዕማንም ዐሥር መክሊት ብር፣ ስድስት ሺህ መሐለቅ ወርቅና ዐሥር መለወጫ ልብስ አስጭኖ፣ ጉዞውን ቀጠለ። **6** እርሱም ለእስራኤል ንጉሥ የተጻፈለትን ደብዳቤ ወሰደ፣ ደብዳቤውም እንዲህ ይላል፦ «ይህ ደብዳቤ የኔ አገልጋይ ስለሆነው ስለ ንዕማን ጉዳይ የሚገልጥ ነው፤ ከለምጹም እንድትፈውሰው ወደ አንተ ልኬዋለሁ» የሚል ነበር። **7** የእስራኤልም ንጉሥ ደብዳቤውን ባነበበ ጊዜ በቁጣ ልብሱን ቀደደ፤ እንዲህም አለ፦ «የሶሪያ ንጉሥ ይህን ሰው እንድፈውስለት እንዴት ይገምታል? እኔ ሰውን ከለምጽ እፈውስ ዘንድ የማዳንና የመግደል ሥልጣን ያለኝ እግዚአብሔር መሰልኩትን? ይህ አባባል ከእኔ ጋር ጠብ ለመጀመር የፈለገ ይመስላል!» አለ። **8** ስለዚህ የእግዚአብሔር ሰው ነቢዩ ኤልሳዕ የእስራኤል ንጉሥ ልብሱን መቅደዱን በሰማ ጊዜ ወደ ንጉሡ እንዲህ ሲል መልእክት ላከ፦ «ስለምን ልብስህን ቀደድክ? ሰውየውን ወደ እኔ ላከው፤ እርሱም በእስራኤል ነቢይ መኖሩን ያውቃል!» አለው። **9** ስለዚህም ንዕማን ከፈረሶችና ከሠረገላዎቹ ጋር ወደ ኤልሳዕ ቤት መጥቶ በር ላይ ቆመ። **10** ኤልሳዕም አንዱን አገልጋይ ልኮ «ሄደህ በዮርዳኖስ ወንዝ ሰባት ጊዜ ራስህን በማጥለቅ ታጠብ፤ ሰውነትህም ይመለሳል፤ ንጹሕም ትሆናለህ› ብለህ ለዚህ ሰው ንገረው» ሲል ተናገረው። **11** ንዕማን ግን ተቆጥቶ ለመመለስ ተነሣ፤ እንዲህም አለ፦ “እኔ ነቢዩ መጥቶ የአምላኩን የእግዚአብሔርን ስም ጠርቶ በሽታዬ ያለበትን ቦታ በእጆቹ በመዳሰስ ከለምጽ በሽታዬ ይፈውሰኛል ብዬ ነበር። **12** በእስራኤል ከሚገኙት ወንዞች ይልቅ በአገሬ በደማስቆ የሚገኙት አባናና ፋርፋ አይሻሉምን? በእነርሱ ታጥቤ ንጹሕ መሆን አልችልምን?” ስለዚህ ተነሥቶ ሄደ።› **13** የንዕማንም አገልጋዮች ወደ እርሱ ቀርበው፦ «ጌታችን ሆይ፣ ነቢዩ ሌላ ከባድ ነገር እንድታደርግ ቢያዝህ ኖሮ ትፈፅመው ነበር፤ ታዲያ ነቢዩ ባዘዘህ መሠረት ታጥበህ ከበሽታህ መንጻት ምን ይከብድሃል?» አሉት። **14** ከዚያም ንዕማን የእግዚአብሔር ሰው ባዘዘው መሠረት ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ወርዶ ሰባት ጊዜ በመነከር ታጠበ፤ ከበሽታውም ፈጽሞ ነጻ። ሰውነቱም እንደ ሕፃን ልጅ ገላ በመታደስ ፍፁም ጤናማ ሆነ። **15** ንዕማንና አጃቢዎቹ ወደ እግዚአብሔር ሰው ተመልሰው መጥተው በፊቱ ቆሙ። ንዕማንም እንዲህ አለ፦ «ከእስራኤል አምላክ በቀር በምድር ላይ ሌላ አምላክ እንደሌለ እነሆ አሁን ዐወቅሁ። ስለዚህም ከአገልጋይ ይህን ስጦታ እባክህ ተቀበለኝ» አለው። **16** ኤልሳዕ ግን «በፊቱ ቆሜ በማገለግለው በሕያው እግዚአብሔር ስም እምላለሁ፤ ምንም ስጦታ አልቀበልህም» ሲል መለሰለት። ንዕማንም ስጦታውን እንዲቀበል አጥብቆ ቢለምነውም ኤልሳዕ ሊቀበለው አልፈቀደም። **17** ስለዚህም ንዕማን እንዲህ አለ፦ «ስጦታዬን የማትቀበለኝ ከሆነ ለሌሎች ባዕዳን አማልክት የሚቃጠልም ሆነ ሌላ አይነት መሥዋዕት የማቀርበውን ከአሁን ጀምሮ ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር ብቻ ለማቅረብ ስለወሰንሁ የሁለት በቅሎ ጭነት አፈር ይዤ እንድሄድ ፍቀድልኝ።» **18** ስለዚህም የአገሬን ንጉሥ በማጀብ ሬሞን የተባለ ባዕድ አምላክ ወደሚመለክበት መቅደስ ብገባና ብሰግድም እንኳ እግዚአብሔር በዚህ ጉዳይ ይቅር እንደሚለኝ ተስፋ አደርጋለሁ፤ በእርግጥም በዚህ ጉዳይ ይቅር ይለኛል።» **19** ኤልሳዕም «በሰላም ሂድ!» አለው፤ ንዕማንም ተሰናብቶ ሄደ። **20** እርሱም ጥቂት ራቅ ብሎ እንደ ሄደ፣ የኤልሳዕ አገልጋይ ግያዝ ለራሱ እንዲህ አለ፦ «ጌታዬ ሶሪያዊው ንዕማን ካመጣው ስጦታ ሳይቀበል አሰናብቶታል። በሕያው እግዚአብሔር ስም እምላለሁ፣ ተከትዬው ሄጄ ከእርሱ አንድ ነገር ማግኘት አለብኝ» ሲል በልቡ አሰበ። **21** ስለዚህም ግያዝ ንዕማንን ከኋላው ተከተለው። ንዕማንም መለስ ብሎ አንድ ሰው እየሮጠ ሲከተለው ባየ ጊዜ እርሱን ለመገናኘት ከሠረገላው ወርዶ እንዲህ አለ፦ «ሁሉ ነገር ሰላም ነው?» **22** ግያዝም፦ «ሁሉ ነገር መልካም ነው። ጌታዬ በኮረብታማው በኤፍሬም አገር የሚኖሩ ሁለት ወጣት የነቢያት ልጆች ድንገት መጡብኝ፤ አንድ መክሊት ብርና ሁለት መቀየሪያ ልብሶች ላክልኝ ብሎ ልኮኛል» ሲል መለሰለት። **23** ንዕማንም፦ «እባክህ ሁለት መክሊት ብር ለመስጠት በጣም ደስተኛ ነኝ» ሲል መለሰለት። ብሩን በሁለት ከረጢት ሞልቶ ከሁለት መለወጫ ልብሶች ጋር በሁለት አገልጋዮች አስይዞ ከግያዝ ፊት እንዲሄዱ አደረገ። **24** ግያዝም ወደ ኮረብታው በደረሰ ጊዜ፣ ግያዝ ሁለቱን ከረጢት ብር ከእጃቸው ወስዶ ወደ ቤት አስገባ። እነርሱንም አሰናብቶአቸው ሄዱ። **25** ወደ ቤት ተመልሶ ገብቶ በጌታው በኤልሳዕ ፊት በቆመ ጊዜ ኤልሳዕ እንዲህ አለው፦ «ግያዝ ከወዴት መጣህ?» እርሱም፦ «ጌታዬ፣ አገልጋይህ የትም አልሄድኩም» ሲል መለሰ። **26** ኤልሳዕም ለግያዝ፦ «ሰውየው አንተን ለመገናኘት ከሠረገላው ሲወርድ እኔ በመንፈስ ከአንተ ጋር አልነበርኩምን? እነሆ አሁን ገንዘብና ልብስ፣ የወይራና የወይን ተክል ቦታ፣ በግና የቀንድ ከብት ወይም አገልጋዮችን ለመቀበል ጊዜው ነውን? **27** ስለዚህ እነሆ የንዕማን ለምጽ ወደ አንተና ዘሮችህ ለዘላለም ይተላለፋል» አለው። ግያዝም ከፊቱ ወጥቶ ሄደ፣ ለምጹም እንደ በረዶ ነጭ ሆነ።

---

2 Kings 5:1

በጌታው ዘንድ
‹‹ዐይን›› ንጉሡ ስለ አንዳች ነገር የሚያስበውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በንጉሡ አስተሳሰብ››

ያህዌ በዚህ ሰው አማካይነት ለሶርያ ድል ስለ ሰጠ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ሶርያ›› የሶርያ ሰራዊትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በንዕማን በኩል ያህዌ ለሶርያ ሰራዊት ድል ሰጥቶ ነበር››

ሶርያውያን ወጥተው ሄዱ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ሶርያውያን›› የሶርያን ሰራዊት ያመለክታል።

በቡድን ዘረፉ
‹‹የጥቂት ሰዎች ጥቃት›› እንዲህ ማት በቁጥር ጥቂት ሆነው ጠላትን ለማጥቃት ሄዱ ማለት ነው።

2 Kings 5:3

ልጃገረዲቱ ለእመቤትዋ እንዲህ አለች
በሶርያውያን ሰራዊት ከእስራኤል ተማርካ የነበረችው ልጃገረድ ለንዕማን ሚስት እንዲህ አለች።

ጌታዬ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ጌታዬ›› ንዕማንን ያመለክታል።

2 Kings 5:5

ደብዳቤ እጽፋለሁ
ንጉሡ ለንዕን ለእስራኤል ንጉሥ የሚወስደው ደብዳቤ ሊሰጠው ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በአንተ በኩል ደብዳቤ እልካለሁ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ዐሥር መክለት ብር፤ ስድስት ሺህ ሰቅል ወርቅ
‹‹10 መክለት ብር፤ 6,000 ሰቅል ወርቅ›› ይህን በዘመኑ ልኬት መዳፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹330 ኪሎ ግራም ወርቅ፤ 6,000 ሰቅል ወርቅ››

ዐሥር ሙሉ ልብስ ይዞ ሄደ
ይህ ከሶርያ ንጉሥ ለእስራኤል ንጉሥ የተላከ ስጦታ ነበር። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለእስራኤል ንጉሥ ስጦታ ዐሥር ሙሉ ልብስ ይዞ ሄደ››

2 Kings 5:7

ልብሱን ቀደደ
ሰዎች ታላቅ ሐዘን ውስጥ ሲሆኑ፣ ብዙ ጊዜ ልብሳቸውን ይቀደዱ ነበር። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ማዘኑን ለማሳየት ልብሱን ቀደደ››

ከለምጹ እንድፈውሰው ይህን ሰው ወደ እኔ መላኩ እኔ ገድዬ ማዳን የምችል አምላክ ሆኜ ነውን?
ንጉሡ ይህን የጠየቀው የሶርያ ንጉሥ ጥያቄ በጣም የሚያናድድና እርሱ ማድረግ የማይችለው መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህን በዐረፍተ ነገር መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሶርያ ንጉሥ እኔ በሞትና በሕይወት ላይ ሥልጣን ያለኝ አምላክ እንደ ሆንሁ ሳያስብ አልቀረም፤ ይህን ሰው ከለምጹ እንደፈውሰው ይፈልጋል፤ እኔ ግን ያን ማድረግ አልችልም››

እንግዲህ ጠብ ሲፈልገኝ እዩ
የእስራኤል ንጉሥ የደብዳቤው እውነተኛ ምክንያት ንዕማን እንዲፈወስ መጠየቅ መሆኑን አላመነም፤ ዋናው ምክንያት ጠብ ፍለጋ መሆኑን ነው ያሰበው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከእኔ ጋር ጠብ ለመፍጠር ሰበብ እየፈለገ ይመስላል››

2 Kings 5:8

አጠቃላይ መረጃ
ኤልሳዕ ንዕማንን በተመለከተ ከእስራኤል ንጉሥ ጋር እየተነጋገረ ነው።

ልብስህን ለምን ቀደድህ?
ኤልሳዕ ይህን የጠየቀው ይህን ያህል መናደድና ልብሱንም መቅደድ እንዳልነበረበት አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ይህን ያህል መናደድና ልብስህንም መቅደድ አልነበረብህም››

ሥጋህ ይፈወሳል
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። ‹‹ሥጋህ ደህና ይሆናል››

አንተም ትነጻለህ
ይህም ማለት ከእንግዲህ ርኩስ አይሆንም ማለት ነው። በእግዚአብሔር ፊት በመንፈሳዊ ደረጃ ንጹሕ ያልሆነ ወይም ተቀባይነት የሌለው ሰው በአካላዊ ደረጃም ንጹሕ እንዳይደለ ይታሰብ ነበር። ለምጽ ያለበትን ሰው እግዚአብሔር እንደ ርኩስ ወይም ንጹሕ እንዳልሆነ ነበር የሚያየው።

2 Kings 5:11

እነሆ
ይህ ቀጥሎ ለሚነገረው ነገር የሰውን ትኩረት ለመሳብ የሚነገር ቃል ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አድምጥ››

የያህዌን ስም
እዚህ ላይ ያህዌ በስሙ ተጠርቷል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ››

ቦታው ላይ
‹‹ቆዳዬ ላይ በሽታው ያለበት ቦታ›› ወይም፣ ‹‹ለምጹ ያለበት ላይ››

አባናና ፋርፋር ከየትኞቹም የእስራኤል ውሆች አይሻሉምን?
ንዕማን ይህን የጠየቀው አባናና ፋርፋር ከዮርዳኖስ ወንዝ የተሻሉ መሆናቸውን አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህን ዐረፍተ ነገር ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በአገሬ በሶርያ ያሉት የአባናና የፋርፋር ወንዞች በእስራኤል ካሉት የትኞቹም ወንዞች በጣም የተሻሉ ናቸው››

አባናና ፋርፋር
እነዚህ የወንዝ ስሞች ናቸው።

በእነርሱ ታጥቤ መንጻት አልችልምን?
ንዕማን ይህን የጠየቀው በቀላሉ በሌሎች ወንዞች መታጠብ እንደሚችል አጽንዖት ለመስጠት ነው። በእነዚህ ወንዞች መታጠብ በዮርዳኖስ እንደ መታጠብ ሊፈውሰው እንደሚችል ያምናል። ይህን ዐረፍተ ነገር ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በእነዚህ ወንዞች ታጥቤ መፈወስ አለብኝ›› ወይም፣ ‹‹በእነዚህ ወንዞች ታጥቤ በቀላሉ መፈወስ እችላለሁ!››

በቁጣ ተመልሶ ሄደ››
‹‹በጣም ተቆጥቶ ሄደ››

2 Kings 5:13

አባቴ
‹‹አባቴ›› ወይም፣ ‹‹ጌታው›› ብለው በመጥራት አገልጋዮቹ ያላቸውን ክብር እያሳዩ ነው።

አታደርገውም ነበርን?
አገልጋዮቹ ይህን የተናገሩት በጥንቃቄ ንዕማንን ለመገሠጽ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያንን በሚገባ ማድረግ ነበረብህ!››

ቢልህ ምን አስቸገረህ?
ከባዱን ትእዛዝ ለመፈጸም ፈቃደኛ የመሆኑን ያህል ቀላሉን ለመፈጸም የበለጠ ፈቃደኛ መሆን ይገባው እንደ ነበር አጽንዖት ለመስጠት አገልጋዩ በንጽጽር አቅርቧል። ‹‹ያንን ለመፈጸም ምንኛ መታዘዝ ይገባህ ነበር›› ወይም፣ ‹‹ከዚያ የበለጠስ ቢሆን መታዘዝ አልነበረብህም?››

ታዲያ፣ ‹‹ታጠብና ንጻ›› ቢልህ ምኑ አስቸገረህ?
አገልጋዩ ይህን የጠየቀው ኤልሳዕ ያዘዘውን ማድረግ እንዳለበት አጽንዖት ሰጥቶ ለንዕማን ለመናገር ነው። ይህን ዐረፍተ ነገር ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እርሱ ‹‹ታጠብና ንጻ›› ሲልህ ከዚያ የበለጠ እንኳ መታዘዝ ነበረብህ››

የእግዚአብሔር ሰው
‹‹የእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕ››

ሥጋውም እንደ ትንሽ ልጅ ሥጋ ሆነ፤ ነጻም
ይህ የሚናገረው ከተፈወሰ በኋላ ቆዳውን ከሕፃን ልጅ ጋር በማነጻጸር የንዕማን ቆዳ ምን ያህል ለስላሳ እንደ ሆነ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሥጋው ተፈወሰ፤ እንደ አንድ ሕፃን ልጅ ቆዳው ለሰለሰ›› ወይም፣ ‹‹ቆዳው ደህና ሆነ፣ እንደ ሕፃን ልጅ ቆዳ ለስላሳ ሆነ››

ሥጋው
‹‹ቆዳው›› ተፈወሰ ይህን በሌላ መንገድ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለምጹ ጠፋ››

2 Kings 5:15

እነሆ
ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው ቀጥሎ ለሚነገረው ትኩረትን ለመሳብ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አድምጥ››

በእስራኤል እንጂ በዓለም ሁሉ ሌላ አምላክ አለመኖሩን ተረድቻለሁ
‹‹በምድር ሁሉ ብቸኛው አምላክ ያለው እስራኤል ውስጥ ነው።››

በፊቱ የቆየሁት ሕያው ያህዌን
‹‹በፊቱ የቆምሁት ያህዌ ሕያው መሆኑን የማውቀውን ያህል›› እዚህ ላይ ኤልሳዕ ያህዌ ሕያው የመሆኑን እርግጠኝነት ከንዕማን ስጦታ ለመቀበልም የዚያን ያህል ፈቃደኛ ካለ መሆኑ ጋር ያነጻጽራል። ይህ መሐላ የመፈጸም መንገድ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ሕያው የመሆኑን ያህል፣ እኔም ከአንተ ምንም አልቀበልም››

በፊቱ የቆምሁት
እዚህ ላይ ያህዌን ማገልገል፣ በፊቱ መቆም ማለት እንደ ሆነ ተነግሮአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የማገለግለው››

ምንም ነገር አልቀበልም
ይህ ስጦታ አልቀበልም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምንም ስጦታ አልቀበልም››

2 Kings 5:17

ከሆነ
በውስጠ ታዋቂነት የሚታወቀውን መረጃ ማቅረብ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያመጣሁልህን ስጦታ የማትቀበል ከሆነ››

ለባርያህ ይሰጠው
ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስጠኝ››

ሁለት የበቅሎ ጭነት ዐፈር
ንዕማን ወደ አገሩ የሚወሰድ ሁለት ጭነት ዐፈር ጠይቋል። ከዚያ በኋላ ዐፈሩ ላይ መሠዊያ ይሠራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለያህዌ መሠውያ እንድሠራበት ሁለት የበቅሎ ጭነት የሚያህል ዐፈር ከእስራኤል ይሰጠኝ››

አገልጋይህ
እርሱን ለማክበር ንዕማን ራሱን የኤልሳዕ አገልጋይ በማለት ይጠራል።

ለያህዌ እንጂ ለሌላ አምላክ የሚቃጠል ወይም ሌላ መሥዋዕት ስለማላቀርብ
ይህን በአዎንታዊ መልኩ ማስቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእንግዲህ ለያህዌ እንጂ ለሌላ አምላክ የሚቃጠል ወይም ሌላ መሥዋዕት አላቀርበም›› ወይም ‹‹የሚቃጠል ወይም ሌላ መሥዋዕት የማቀርበው ለያህዌ ብቻ ነው።››

ጌታዬ
ይህ የሚያመለክተው ንዕማን የሚያገለግለውን የሶርያንን ንጉሥ ነው

ክንዴን ሲደገፍ
‹‹ክንዴ ላይ ደገፍ ሲል›› ይህ ማለት ያረጀ ወይም ታማሚ ሰው ስለ ነበር ለሬሞን በሚሰግድበት ጊዜ ንዕማን ንጉሡን ይረዳው ነበር ማለት ነው።

በሰላም ሂድ
‹‹ወደ ቤትህ ሂድ፤ አትጨነቅ›› ወይም፣ ‹‹ምንም ሳትፈራ ሂድ››

2 Kings 5:20

እንደ ሄደ
‹‹ንዕማን ሄደ››

ግያዝ
2 ነገሥት 4፥12 ላይ የዚህን ሰው ስም እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

እነሆ
ይህ ቃል ጥቅም ላይ የሚውለው ቀጥሎ ለሚነገረው ነገር ትኩረት ለመሳብ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አድምጥ››

ሶርያዊው ንዕማን ያመጣውን አለመቀበሉ ደግሞ አይደል
‹‹ሶርያዊው ንዕማንን በነጻ አሰናብቶታል››

አለመቀበል
‹‹ምንም ሳይቀበል››

ከእጁ
እዚህ ላይ ንዕማንን ከእጁ በሚል ቃል የገለጸው ስጦታን በሚያመላክት መልኩ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእርሱ››

ሕያው ያህዌን
‹‹ያህዌ ሕያው እንደ ሆነ›› እዚህ ላይ ግያዝ ያህዌ ሕያው የመሆኑን እርግጠኝነት፣ እርሱም ያሰበውን በእርግጠኝነት ከማድረጉ ጋር አነጻጽሮታል። ይህ መሐላ ማድረግ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ሕያው እንደ ሆነ እኔም ቃሌን እሰጣለሁ››

ከነቢያት ልጆች
ይህ ማለት የነቢያት ስብስብ እንጂ፣ በቀጥታ የነቢያት ልጆች ናቸው ማለት አይደለም። 2 ነገሥት 2፥3 ላይ ይህን ሐረግ እንዴ እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከነቢያት መካከል››

እባክህ አንድ መክሊት ብርና ሁለት ሙሉ ልብስ ስጣቸው
ለነቢያት ወስዶ እንዲሰጣቸው እነዚህን ነገሮች ለእርሱ እንዲሰጠው ግያዝ ንዕማንን እየጠየቀው ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለእነርሱ እንድሰጥ እባክህን አንድ መክሊት ብርና ሁለት ሙሉ ልብስ ስጠኝ››

እነሆ
ይህ ቃል ጥቅም ላይ የሚውለው ቀጥሎ ለሚነገረው ነገር ትኩረትን ለመሳብ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አድምጥ››

አንድ መክሊት ብር
ይህን በዘመኑ መለኪያ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹33 ኪሎ ግራም ብር››

2 Kings 5:23

ሁለት መክሊት
ይህን በዘመኑ መለኪያ መጻፍ ይቻላል። ይህ መክሊት ከብር የተሠራ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሁለት የብር መክሊት›› ወይም፣ ‹‹66 ኪሎ ግራም ብር››

በሁለት አደረገ
‹‹ሰጣቸው››

ንዕማን ግያዝን አስጨንቆ ለመነው
ስጠታዎቹን እንዲወስድ ንዕማን አጥብቆ ጠየቀው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስጦታዎቹን እንዲወስድ ንዕማን ግያዝን አጥብቆ ለመነው››

አገልጋይህ
እዚህ ላይ ግያዝ የንዕማን አገልጋይ መሆኑን እየተናገረ ነው።

2 Kings 5:26

ያ ሰው ሊገናኝህ ከሰረገላው ሲወርድ መንፈሴ ከአንተ ጋር አልሄደምን?
ኤልሳዕ ይህን የጠየቀው ግያዝ ያደረገውን እንዲያይ ያህዌ እንዳስቻለው አጽንኦት ለመስጠት ነው። ይህን በዐረፍተ ነገር ማስቀመጥ ይቻላል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ንዕማን ሰረገላውን አቁሞ ከአንተ ጋር ሲነጋገር መንፈሴ እንዳየህ መገንዘብ ነበረብህ››

ጊዜው ገንዘብና... ሴት አገልጋይ የሚቀበሉበት ነውን?
ኤልሳዕ ይህን የጠየቀው፣ ይህ ስጦታ የሚቀበሉበት ጊዜ አለመሆኑን አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህን እንደ ዐረፍተ ነገር መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህ ገንዘብና... የሴት አገልጋይ የሚቀበሉበት ጊዜ አይደለም››

የንዕማን ለምጽ በአንተና በዘርህ ላይ ይጣበቃል
ይህ የንዕማን ለምጽ ከእርሱ ተወስዶ ለግያዝ የተሰጠው በሚመስል መልኩ ግያዝና ዘሩ የንዕማንን ለምጽ እንደሚወስዱ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ንዕማን ለምጽ እንደ ነበረው አንተና ዘርህም ለምጻም ትሆናላችሁ››

ከዚያም ግያዝ ከፊቱ ወጣ
‹‹ከፊቱ›› የሚለው ሐረግ ኤልሳዕ እርሱን ማየት ከሚችልበት አካባቢ ማለት ነው። ኤልሳዕ ከነበረበት ክፍል ወጥቶ ሄደ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ግያዝ ክፍሉን ለቅቆ ሲወጣ...››

እንደ በረዶ ነጭ ሆነ
ለምጽ ቆዳን ነጭ ያደርጋል። እዚህ ላይ የግያዝ ለምጽ ከበረዶ ጋር ተመሳስሎአል። አማራጭ ትርጉም፣ ቆዳው እንደ በረዶ ነጭ ሆነ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 6

1 የነቢያት ልጆችም ኤልሳዕን፦ «ከአንተ ጋር የምንኖርበት ስፍራ ከሁላችንም ጠባብ ነው አሉት። 2 ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ሄደን ዛፍ ቆርጠን የምንኖርበትን ቤት በዚያ እንድንሠራ ፍቀድልን!» አሉት። ኤልሳዕም «መልካም ነው ቀጥሉ!» በማለት መለሰላቸው። 3 ከእነርሱም አንዱ ኤልሳዕን አብሮአቸው እንዲሄድ ጠየቀው፤ ኤልሳዕም እሄዳለሁ አላቸው። 4 እርሱም አብሮአቸው ሄደ፤ ወደ ዮርዳኖስም በደረሱ ጊዜ ዛፍ የመቁረጥ ተግባራቸውን ጀመሩ። 5 ነገር ግን አንዱ ዛፍ በመቁረጥ ላይ ሳለ መጥረቢያው ወድቆ ውሃው ውስጥ ጠለቀ፤ እርሱም ድምፁን ከፍ አድርጎ፦ - «ጌታዬ ሆይ! መጥረቢያው የተዋስኩት ነው፣ ምን አደርጋለሁ?» ሲል ጮኸ። 6 የእግዚአብሔርም ሰው፦ «በየት በኩል ነው የወደቀው?» ሲል ጠየቀው። ሰውየውም መጥረቢያው የወደቀበትን ስፍራ አሳየው። እርሱም አንድ እንጨት ቆርጦ ወደ ውሃው በጣለ ጊዜ መጥረቢያው ተንሳፈፈ። 7 ኤልሳዕም፦ «ውሰደው» አለው። ሰውየውም ጎንበስ ብሎ አነሣው። 8 እነሆ፣ የሶርያ ንጉሥ ከእስራኤል ጋር ጦርነት ከፍቶ ነበር። እርሱም ከጦር አዛዦቹ ጋር ተማክሮ የሚሰፍሩበትን ቦታ መረጠ። 9 የእግዚአብሔርም ሰው፦ - «ሶርያውያን ደፈጣ አድርገው ስለሚጠብቁህ ከዚህ ወደዚያ ስፍራ አትቅረብ» ብሎ ወደ እስራኤል ንጉሥ ላከ። 10 የእስራኤልም ንጉሥ ወታደሮቹ ወደሚኖሩበት፣ የእግዚአብሔር ሰው ወደተናገረበትና ወዳስጠነቀቀበት ስፍራ ላከ። ይህም ድርጊት ከአንድ ጊዜ ወይም ከሁለት ጊዜ በላይ ንጉሡ እዚያ ሲሄድ ከጥበቃ ጋር ነበር። 11 የሶርያ ንጉሥም፦ «ከእኛ መካከል ከእስራኤል ንጉሥ ጋር ግንኙነት ያለው ማን እንደሆነ አትነግሩኝምን?» ሲል ጠየቃቸው። 12 ከእነርሱም አንዱ «ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፣ ከእኛ መካከል ይህን የሚያደርግ ማንም የለም፤ በመኝታ ክፍልህ እንኳ ሆነህ የምትናገረውን ሁሉ ሳይቀር ለእስራኤል ንጉሥ ምሥጢሩን የሚገልጥለት ኤልሳዕ የተባለው ነቢይ ነው» ሲል መለሰለት። 13 የሶርያው ንጉሥ፦ «እርሱ የሚገኝበትን ስፍራ ፈልጉ፤ እኔም ልኬ እማርከዋለሁ» አላቸው። በዚህም ጊዜ ኤልሳዕ በዶታይን እንደሚኖር ተነገረው። 14 ስለዚህ ንጉሡ በፈረሶችና በሠረገሎች የተጠናከረ ብዙ ሠራዊት ወደ ዶታይን ላከ። እነርሱም በሌሊት ደርሰው ከተማዪቱን ከበቡ። 15 በማግስቱም ማለዳ የኤልሳዕ አገልጋይ ከመኝታው ተነሥቶ ከቤት ሲወጣ፣ በፈረሶችና በሠረገሎች የታጀቡ የሶርያ ወታደሮች ከተማዪቱን መክበባቸውን አየ። ወደ ኤልሳዕም ተመልሶ፦ - «ጌታዬ ወዮ! ምን ማድረግ ይሻለናል?» ሲል ጠየቀው። 16 ኤልሳዕም «አይዞህ አትፍራ፤ ከእነርሱ ጋር ከተሰለፈው ይልቅ ከእኛ ጋር የተሰለፈው ሠራዊት ይበልጣል» አለው። 17 ኤልሳዕም «እግዚአብሔር ሆይ! ማየት እንዲችል ዐይኖቹን ክፈትለት!» ሲል ጸለየ፤ እግዚአብሔርም የኤልሳዕን አገልጋይ ዐይኖች ከፈተለት፤ በኮረብታው ብዙ የእሳት ፈረሶችና ሠረገሎች በኤልሳዕ ዙሪያ እንዳሉ ተመለከተ። 18 ሶርያውያንም ወደ እርሱ በወረዱ ጊዜ ኤልሳዕ እንዲህ ሲል ጸለየ፦ «እግዚአብሔር ሆይ! እነዚህ ሰዎች እንዲታወሩ አድርግ!» እግዚአብሔርም ኤልሳዕ እንደ ጸለየው፣ ዐይኖቻቸው እንዲታወሩ አደረገ። 19 ከዚህም በኋላ ኤልሳዕ ሶርያውያንን፦ «መንገድ ተሳስታችኋል፤ የምትፈልጓት ከተማ ይህች አይደለችም፤ ይልቅስ ወደምትፈልጉት ሰው እኔ ልምራችሁ፣ ተከተሉኝ» ብሎ ወደ ሰማርያ መራቸው። 20 ወደ ሰማርያም በደረሱ ጊዜ ኤልሳዕ፦ «እግዚአብሔር ሆይ! እነዚህ ሰዎች ማየት እንዲችሉ ዐይኖቻቸውን ክፈት!» ሲል ጸለየ። እግዚአብሔርም ዐይኖቻቸውን በከፈተላቸው ጊዜ በሰማርያ መካከል መሆናቸውን ተረዱ። 21 የእስራኤልም ንጉሥ ሶርያውያንን ባያቸው ጊዜ «ጌታዬ! ልግደላቸውን? ልግደላቸውን?» ሲል ኤልሳዕን ጠየቀው። 22 ኤልሳዕም «አይሆንም! እንኳን እነዚህን በሰይፍህና በቀስትህ የማረካቸውን ወታደሮች መግደል አይገባህም፤ ይልቅስ የሚበሉትንና የሚጠጡትን ምግብ አቅርብላቸውና ወደ ንጉሣቸው ተመልሰው እንዲሄዱ አድርግ» አለው። 23 ስለዚህም የእስራኤል ንጉሥ ለእነርሱ ታላቅ ግብዣ አደረገላቸው፤ ከበሉና ከጠጡም በኋላ ወደ ሶርያ ንጉሥ መልሶ ላካቸው፤ ከዚያም ጊዜ ጀምሮ ሶርያውያን በእስራኤል ምድር ላይ ወረራ ማድረጋቸውን አቆሙ። 24 ከዚህ በኋላ የሶርያ ንጉሥ ቤን ሀዳድ መላ ሠራዊቱን ሰብስቦ በእስራኤል ላይ በማዝመት ጉዳት አደረሰ፤ የሰማርያን ከተማም ከበበ። 25 ስለዚህ በሰማርያ ጽኑ ራብ ነበር። ከዚህም የተነሣ የአንድ አህያ ራስ ሰማኒያ መክሊት ብር፣ ሁለት መቶ ግራም የሚያህል የርግብ ኩስ ዋጋ እስከ አምስት መክሊት ብር ይሸጥ ነበር። 26 አንድ ቀን የእስራኤል ንጉሥ በከታማዪቱ የቅጥር ግንብ ላይ በሚመላለስበት ጊዜ አንዲት ሴት፦ - «ንጉሥ ሆይ እባክህ እርዳኝ!» ስትል ጮኸች። 27 ንጉሡም «እግዚአብሔር ካልረዳሽ እኔ እንዴት ልረዳሽ እችላለሁ? ከአውድማው ወይንስ ከወይን መጭመቂያው ይመጣልን? 28 ለመሆኑ ችግርሽ ምንድን ነው?» ሲል ጠየቃት። እርስዋም እንዲህ ስትል መለሰችለት፦ «ባለፈው ቀን ይህች ሴት ‹ዛሬ ያንቺን ልጅ እንብላ፤ በማግስቱ ደግሞ የእኔን ልጅ እንበላለን› ስትል አሳብ አቀረበች። 29 ስለዚህም የእኔን ልጅ ቀቅለን በላን፤ በማግስቱም ‹ልጅሽን አምጪና እንብላ› ብዬ ጠየቅኋት፤ እርስዋ ግን ደበቀችው።» 30 ንጉሡም ይህንን የሴትዮዋን ቃል በሰማ ጊዜ በሐዘን ልብሱን ቀደደ፤ በግንቡ ላይ በመሆኑ በአቅራቢያው የነበረው ሕዝብ ንጉሡ በውስጡ ማቅ ለብሶ እንደ ነበር አዩ። 31 ንጉሡም ድምፁን ከፍ በማድረግ «የዛሬይቱ ጀምበር ከመጥለቅዋ በፊት የሳፋጥ ልጅ የኤልሳዕ ራስ ሳይቆረጥ ቢያድር እግዚአብሔር እኔን በሞት ይቅጣኝ!» ሲል ተናገረ። 32 በዚህ ጊዜ ኤልሳዕ ከሽማግሌዎች ጋር በቤቱ ተቀምጦ ነበር። ንጉሡም ኤልሳዕን ይዞ የሚመጣ መልእክተኛ ላከ። የንጉሡ መልእክተኛ ከመድረሱም በፊት ኤልሳዕ ሽማግሌዎቹን፦ «ይህ ነፍሰ ገዳይ እኔን ለማስገደል አንድ ሰው ልኮአል! እነሆ እርሱ እዚህ በሚደርስበት ጊዜ በሩን ዝጉ፤ ወደ ውስጥም እንዲገባ አትፍቀዱለት፤ ንጉሡም እርሱን ተከትሎ መጥቶ በኋላው ይገኛል» አላቸው። 33 ገና ይህን ተናግሮ ሳይጨርስ ንጉሡ ድንገት ከተፍ ብሎ «ይህን መከራ ያመጣው እግዚአብሔር ነው፤ ታዲያ ከዚህ በላይ እግዚአብሔርን የምጠብቀው ለምንድን ነው?» አለ።

---

2 Kings 6:1

የነቢያት ልጆች
እነዚህ የነቢያት ስብስብ እንጂ፣ የነቢያት ልጆች ናቸው ማለት አይደለም። 2 ነገሥት 2፥3 ላይ ይህን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ አጠገብ እንሂድ››

አገልጋዮችህ
እዚህ ላይ የነቢያት ልጆች የተባሉት ነቢያት ለእርሱ ክብር ለማሳየት የኤልሳዕ አገልጋዮች መሆናቸውን ተናግረዋል።

2 Kings 6:4

አጠቃላይ መረጃ
ኤልሳዕ ዛፎች ለመቁረጥ ከነቢያት ጋር ሄደ።

የመጥረቢያው ራስ ውሃ ውስጥ ገባ
የመጥረቢያ ራስ የሚያመለክተው ብረቱን ነው። ይህም ማለት የመጥረቢያው ብረት ከእጀታው ተለይቶ ውሃ ውስጥ ወድቋል ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የመጥረቢያው ብረት ከእጀታው ተለይቶ ውሃ ውስጥ ወደቀ››

አዬ ጉድ፤ አዬ ጉድ
ይህ ሰው እንዲህ ያለው ምን ያል መደንገጡን ለማሳየት ነው። በአንተ ቋንቋ ይህን የምትገልጽበት ቃል ካለህ ተጠቀምበት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የተውሶ ነበር
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የተዋስሁት ነበር››

2 Kings 6:6

የእግዚአብሔርም ሰው አለ
‹‹የእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕ ጠየቀ››

እንጨት ቆርጦ ወደ ውሃው ውስጥ በመጣል የመጥረቢያው ብረት እንዲንሳፈፍ አደረገ
ተአምር ለማድረግ እግዚአብሔር በኤልሳዕ ተጠቀመ። የመጥረቢያው ብረት ውሃው ላይ ተንሳፈፈ፤ ነቢዩ እስኪወስደው እዚያው ቆየ።

ብረቱ እንዲንሳፈፍ አደረገ
‹‹ብረቱ ተንሳፈፈ››

ብረቱ
‹‹የመጥረቢያው ራስ›› የመጥረቢያው ራስ ከብረት የተሠራ ነበር።

2 Kings 6:8

በዚህ ጊዜ የሶርያ ንጉሥ ከእስራኤል ጋር ይዋጋ ነበር
‹‹የሶርያ ንጉሥ ከእስራኤል ጋር ይዋጋ በነበረ ጊዜ››

አሁን
ይህ ቃል እዚህ ቦታ ጥቅም ላይ የዋለው የዋናውን ታሪክ ፍሰት ገታ ለማድረግ ነው። እዚህ ላይ ጸሐፊው ስለ አዲስ የታሪኩ ክፍል መናገር ይጀምራል።

‹‹በዚህ በዚህ ቦታ እሰፍራለሁ›› አለ
የሶርያ ንጉሥ የት እንደሚሰፍር ለአማካሪዎቹ እየተናገረ ነበር። ‹‹በዚህ በዚህ›› የሚሉት ሐረጎች ቦታውን በጽሑፍ ባለ ማስፈር ስለ አካባቢው መረጃ የሚሰጡ ናቸው። ይህን ሐረግ በቋንቋህ በትክክል መተርጎም የማይቻል ከሆነ ቀጥተኛ ባልሆነ አነጋገር መተርጎም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሚሰፍርበት ቦታ የት እንደ ሆነ ነገራቸው››

የእግዚአብሔር ሰው
‹‹የእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕ››

ሶርያውያን በዚያ ታች ወርደዋልና በዚያ በኩል እንዳታልፍ ተጠንቀቅ
ሶርያውያን የሰፈሩበትን ትክክለኛ ቦታ ኤልሳዕ አወቀ፤ ራሳቸውን ለአደጋ እንዳያጋልጡ የእስራኤልን ንጉሥና ወታደሮቹን አስጠነቀቀ።

2 Kings 6:10

የእግዚአብሔር ሰው የነገረውን ቦታ አስቃኘ
ይህ የሚያመለክተው 2 ነገሥት 6፥9 ላይ ወደዚያ እንዳይሄድ ኤልሳዕ ንጉሡን ያስጠነቀቀውን ቦታ ነው።

እንደዚህ ካሉት ቦታዎች ራሱን እንዲጠብቅ ከአንድ ሁለት ጊዜ በላይ አስጠነቀቀው
አደጋው ከመምጣቱ በፊት ሕዝቡን እንዲያስጠነቅቅ፣ የሶርያ ሰራዊት የሚያጠቃበትን ቦታ ኤልሳዕ ለንጉሡ ይነግረው ነበር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኤልሳዕ የእስራኤልን ንጉሥ ብዙ ጊዜ በዚህ መልኩ አስጠነቀቀው፤ እስራኤላውያንም ከአደጋ ተጠበቁ››

ከእስራኤል ንጉሥ ጋር የተወዳጀ እንዳለ ለምን አትነግሩኝም?
የሶርያ ንጉሥ ለእስራኤል ንጉሥ መረጃ የሚሰጥ ሰው ወታደሮቹ መካከል ሊኖር እንደሚችል አሰበ። ያ ከሐዲ ማን እንደ ሆነ ለማወቅ ይህን ጠየቀ። ይህን በዐረፍተ ነገር ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለእስራኤል ንጉሥ እየሠራ ያለው ማን እንደ ሆነ ንገሩኝ!›› ወይም፣ ‹‹ዕቅዶቻችንን ለእስራኤል ንጉሥ የሚናገረው ማንኛችሁ እንደ ሆናችሁ ንገሩኝ?››

ከእስራኤል ንጉሥ ጋር
ይህም ማለት ወዳጅ የሆነ ሰው ማለት ነው። እዚህ ላይ ግን ለእስራኤል ንጉሥ መረጃ የሚሰጥ ሰው ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤልን ንጉሥ የሚረዳ›› ወይም፣ ‹‹ለእስራኤል ንጉሥ ታማኝ የሆነ››

2 Kings 6:12

አላደረግንም
አገልጋዮቹ ከንጉሡ ወታደሮች አንዱ እንኳ ለእስራኤል ንጉሥ መረጃ እንዳልሰጡ ተናገሩ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኛ እንዲህ አላደረግንም››

ንጉሥ ጌታዬ
ይህ የሚያመለክተው የሦርያን ንጉሥ ነው።

አንተ በእልፍኝህ ሆነህ እንኳ የምትናገረውን
‹‹በግል መኝታ ቤትህ ውስጥ እንኳ ሆነህ የምትናገረውን››

ሰዎች ልኬ እንዳስይዘው
ንጉሡ ኤልሳዕን የሚይዙ ሰዎች መላክ ዐቅዶአል። እርሱ ራሱ ሊይዘው አላቀደም አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሚይዙትን ሰዎች እልካለሁ››

እነሆ
እዚህ ላይ ቀጥሎ ለሚነገረው ነገር የንጉሡን ትኩረት ለመሳብ ይህ ቃል ተነግሮአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስማ››

በዶታይን ይገኛል
‹‹ኤልሳዕ በዶታይን ነው››

ዶታይን
ይህ የከተማ ስም ነው።

2 Kings 6:14

ስለዚህ ንጉሡ
ይህ የሚናገረው ስለ ሶርያ ንጉሥ ነው።

የእግዚአብሔር ሰው
‹‹ኤልሳዕ›› ወይም፣ ‹‹የእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕ››

እነሆ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እነሆ›› የሚለው ቃል ባየው ነገር አገልጋዩ መደነቁን ያመለክታል። ‹‹ጠዋት በማለዳ ተነሥቶ ወደ ውጭ ሲወጣ… አየ።

አገልጋዩ እንዲህ አለ
አገልጋዩ ያየውን ለንጉሡ ለመንገር ተመልሶ ገባ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አገልጋዩም ወደ ውስጥ ተመልሶ ኤልሳዕን…››

ከእኛ ጋር ያሉት ከእነርሱ ጋር ካሉት ይበልጣሉ
በጦርነት ጊዜ ከሰዎች ጋር መሆን፣ ከእነርሱ ጋር ሆኖ መዋጋት ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጦርነት ከእኛ ጋር ያሉት ከእነርሱ ጋር ካሉት ይበልጣሉ››

2 Kings 6:17

ያይ ዘንድ እባክህ ዐይኖቹን ክፈትለት
አገልጋዩ ሌሎች ሰዎች ማየት ያልቻሉትን ማለት በዙሪያቸው ያሉትን የእሳት ፈረሶችና ሰረገሎች ማየት እንዲችል ኤልሳዕ እየጠየቀ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንዲያይ አድርገው››

እነሆም አየ
‹‹ማየት ቻለ፤ ያየውም››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እነሆ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እነሆ›› የሚለው ባየው ነገር አገልጋዩ መደነቁን ያመለክታል። የእሳት ፈረሶችና ሰረገሎች… ተራራውን ሞልተውት ነበር። ‹‹ተራራው በፈረሶች ተሸፍኖ ነበር››

በኤልሳዕ ዙሪያ
ይህ ኤልሳዕ የነበረበትን ከተማ ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ኤልሳዕ በነበረበት ከተማ ዙሪያ››

ይህን ሕዝብ
ይህ የሚናገረው ስለ ሶርያ ወታደሮች ነው።

በዕውርነት ምታው
‹‹እነዚህን ሰዎች ዕውር አድርጋቸው›› ይህ የሚያመለክተው ያህዌ እንዳያዩ እንዳደረጋቸው ነው።

መንገዱ በዚህ አይደለም፤ ከተማዪቱም ይህች አይደለችም
የሚፈልጉት ከተማ ውስጥ አለመሆናቸውን በመናገር ኤልሳዕ የሶርያን ወታደሮች ግራ እያጋባቸው ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹መንገዱ ይህ አይደለም፤ የምትፈልጉትም ከተማ ይህ አይደለም››

2 Kings 6:20

በዚያን ጊዜ
‹‹እንዲህም ሆነ›› ወይም፣ ‹‹ያኔ›› እንዲያዩ የእነዚህን ሰዎች ዐይን ክፈት

ኤልሳዕ ሰዎቹ እንደ ገና እንዲያዩ ያህዌን ጠየቀ።
አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እነዚህ ሰዎች እንዲያዩ አድርግ››

ያህዌም ዐይኖቻቸውን ከፈተ… አዩ
ያህዌ ሰዎቹ እንደ ገና እንዲያዩ ፈቀደ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ ዕውርነታቸውን አነሣ›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ አጥርተው እንዲያዩ ፈቀደ››

እነሆ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እነሆ›› የሚለው ባዩት ነገር ሶርያውያን መደነቃቸውን ያመለክታል።

ባያቸው ጊዜ
‹‹የሶርያ ወታደሮችን ባያቸው ጊዜ››

አባቴ ሆይ
ንጉሡ ነቢዩ ኤልሳዕን እያናገረ ነው፤ አክብሮቱን ለማሳየት፣ ‹‹አባቴ›› አለው።

ልገደላቸውን? ልፍጃቸውን?
እዚህ ላይ የእስራኤል ንጉሥ ስለ ወታደሮቹ ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እነዚህን የጠላት ወታደሮች እንዲገድሉ ወታደሮቼን ልዘዛቸውን?››

2 Kings 6:22

ኤልሳዕም መለሰ
ኤልሳዕ ለእስራኤል ንጉሥ ጥያቄ መልስ እየሰጠ ነው።

ለመሆኑ በሰይፍህና በቀስትህ የማረክሃቸውን ትገድላቸው ዘንድ ይገባሃልን?
ኤልሳዕ ይህን የጠየቀው ንጉሡ እነዚህን ሰዎች እንዳይገድላቸው ለመናገር ነው። ‹‹ሰይፍ›› እና፣ ‹‹ቀስት›› በጦርነት ጊዜ ወታደሮች የሚጠቀሙባቸው መሣሪያዎች ናቸው። ይህን ዐረፍተ ነገር ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በጦርነት የያዝሃቸውን ሰዎች እንደማትገድል ሁሉ እነዚህንም ሰዎች መግደል የለብህም››

እንዲበሉና እንዲጠጡ እንጀራና ውሃ አቅርብላቸው
እዚህ ላይ፣ ‹‹እንጀራ›› በአጠቃላይ ምግብን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሚበሉትን እንጀራ፣ የሚጠጡትን ውሃ ስጣቸው››

ወደ ጌታቸውም ይሂዱ
ይህ የሚያመለክተው የሶርያን ንጉሥ ነው።

ስለዚህ ንጉሡ ብዙ ምግብ አቀረበላቸው
ምግብ እንዲያቀርቡ ንጉሡ አገልጋዮቹን አዘዘ። እርሱ ራሱ ምግቡን አላዘጋጀም። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ስለዚህ ንጉሡ ብዙ ምግብ እንዲያቀርቡላቸው አገልጋዮቹን አዘዘ።

አደጋ ጣዮች
‹‹እነዚያ ሰዎች››

የእስራኤልን ምድር ለመውረር ከዚያ በኋላ አልተመለሱም
ይህ ማለት ለረጅም ጊዜ እስራኤልን አላጠቁም ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የእስራኤልን ምድር ማጥቃታቸውን ለረጅም ጊዜ አቆሙ››

2 Kings 6:24

ቤንሐዳድ
የሶርያ ንጉሥ ስም። ስሙ፣ ‹‹የሐዳድ ልጅ›› ማለት ነው።

ሰማርያን አጠቃ
ንጉሡና ሰራዊቱ ሰማርያን አጠቁ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰማርያን አጠቁ››

እነሆ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እነሆ›› የሚለው ቃል ቀጥሎ ለምናገኘው መረጃ ያነቃናል።

የአንድ አህያ ጭንቅላት… ተሸጠ
ይህን በሌላ መልክ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የአንድ አህያ ጭንቅላት በ… ተሸጠ››

በሰማንያ ሰቅል ብር
‹‹በ80 ሰቅል ብር››

ሩብ
እኩል መጠን ካላቸው አራት ክፍሎች አንዱ ክፍል አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አንድ አራተኛ›› ወይም፣ ‹‹ሩብ›› ወይም ¼

የርግብ ኩስ
‹‹ተሸጠ›› የሚለውን ቃል ካለፈው ሐረግ መረዳት ይቻላል። ያንን እዚህ መድገም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የርግብ ኩስ… ተሸጠ›› ወይም፣ ‹‹የርግብ ኩስ… አወጣ››

በቅጥሩ ላይ በሚመላለስበት ጊዜ
‹‹በከተማው ግንብ ላይ ሲመላለስ››

ጌታዬ
ሴትዮዋ ንጉሡን እንዲህ በማለት የጠራቸው አክብሮትን ለማሳየት ነው።

2 Kings 6:30

ሴቲቱ ያለችውን ቃል ሲሰማ
‹‹እርሷና ሌላዋ ሴት ያደረጉትን ስትናገር ስማ››

ልብሱን ቀደደ
ንጉሡ ምን ያል እንዳዘነ ለማሳየት ከላይ የሚደርበውን መጐናጸፊያ ቀደደ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በሐዘን ልብሱን ቀደደ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በቅጥሩ ላይ በሚመላለስበትም ጊዜ
2 ነገሥት 6፥24 ላይ ሴትየዋ ስትጠራው ንጉሡ በከተማው ግንብ ላይ እየተመላለሰ ነበር፤ አሁንም እንደዚያው እያደረገ ነው።

በውስጥ ማቅ ለብሶ ነበር
ከልብሱ ውስጥ ማቅ መልበሱ ንጉሡ ምን ያህል እንዳዘነና እንደ ታወከ ያሳያል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከውጭ ከለበሰው ሥር ንጉሡ ማቅ ለብሶ ነበር›› ወይም፣ ‹‹በጣም አዝኖ ስለ ነበር ከካባው ሥር ማቅ ለብሶ ነበር››

እግዚአብሔር ይህን ያድርግብኝ ከዚህም የባሰ ያምጣብኝ
በሰማርያ ከተማ ከሆነው የተነሣ ነቢዩ ኤልሳዕን ሳይቀጣው እንዲያውም ሳይገድለው ከቀረ እግዚአብሔር እንደሚቀጣው ንጉሡ ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እግዚአብሔር ይቅጣኝ ይግደለኝ››

የሳፋጥ ልጅ የኤልሳዕ ራስ ዛሬ በዐንገቱ ላይ ካደረ
ይህ የሚያመለክተው ኤልሳዕ አንገቱ ተቆርጦ እንደሚገደል ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ዛሬ የሳፋጥ ልጅ የኤልሳዕ አንገት ሳይቆረጥ ቢቀር›› ወይም፣ ‹‹ዛሬ ወታደሮቼ የሳፍጥ ልጅ የኤልሳዕን አንገት ሳይቆርጡ ካደሩ››

2 Kings 6:32

ንጉሡም መልእክተኛ ቀድሞት እንዲሄድ አደረገ
‹‹ከንጉሡ ፊት›› ማለት ከአገልጋዮቹ አንዱ መሆን ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የእስራኤል ንጉሥ ከአገልጋዮቹ አንዱን እንደ መልእክተኛ ላከ››

የተላከውም ሰው ከመድረሱ በፊት ኤልሳዕ ለሽማግሌዎቹ
እዚህ ላይ ኤልሳዕ የንጉሡ መልእክተኞች ከመምጣታቸው በፊት ለሽማግሌዎቹ ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹መልእክተኛው ከመድረሱ በፊት ኤልሳዕ ለሽማግሌዎች እንዲህ አለ››

ይህ ነፍሰ ገዳይ ራሴን ለመቁረጥ ሰው መላኩን ታያላችሁ?
እዚህ ላይ ኤልሳዕ ይህን የጠየቀው ወደ ንጉሡ መልእክተኛ ትኩረት ለመሳብና ንጉሡን ለመዝለፍ ነው። ይህን በዐረፍተ ነገር መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ይህ የነፍሰ ገዳይ ልጅ ራሴን የሚቆርጥ ሰው መላኩን ተመልከቱ››

የነፍሰ ገዳይ ልጅ
ይህም ማለት የእስራኤል ንጉሥ የነፍስ ገዳይ ባሕርይ ነበረው ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ይህ ነፍሰ ገዳይ›› ወይም፣ ‹‹ያ ነፍሰ ገዳይ››

መላኩን
አንድ ሰው መላኩ ግልጽ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለ… ሰው ልኳል››

ራሴን ለመቁረጥ
ይህ መሰየፍ ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ራሴን ቆርጦ ለመጣል›› ወይም፣ ‹‹ራሴን ለመሰየፍ››

እነሆ አሁንም
እዚህ ላይ ኤልሳዕ በዚህ ቃል የተጠቀመው ቀጥሎ ለሚናገረው የሽማግሌዎቹን ትኩረት ለመሳብ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እንድታደርጉ የምፈልገውን ስሙ››

በሩን ዘግታችሁ እንዳይገባ አድርጉ
በተዘጋ በር ማንም መግባት አይችልም። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ወደ ውስጥ እንዳይገባ በሩን ዝጉ››

የጌታው እግር ኮቴ ከኃላው ይሰማ የለምን?
ኤልሳዕ ይህን ለሽማግሌዎቹ የተናገረው ንጉሡ ከኃላው እየመጣ መሆኑን በእርግጠኝነት ለመናገር ነው። ይህን በዐረፍተ ነገር መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የጌታው እግር ኮቴ ድምፅ ከኃላው ነው›› ወይም፣ ‹‹እርሱ ከደረሰ በኃላ ንጉሡም ወዲያው ይመጣል››

እነሆ መልእክተኛው
‹‹የምነግራችሁ ነገር እውነትና አስፈላጊ ስለሆነ ልብ በሉ››

ይህ ጥፋት
‹‹በእርግጥ ይህ ጥፋት›› እዚህ ላይ፣ ‹‹እነሆ›› ለሚከተለው አጽንዖት ይሰጣል። ‹‹ይህ ጥፋት›› የሚለው ሐረግ በሰማርያ የሚመጣውን ራብና የሚያስከትለውን ችግር ያመለክታል።

ታዲያ፣ እኔ ከእግዚአብሔር ምን እጠብቃለሁ?
ንጉሡ ይህን የጠየቀው ያህዌ ይረዳናል ብሎ እንደማያምን አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህን በዐረፍተ ነገር መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ እንደሚረዳን በማመን የምጸናው ለምንድነው?›› ወይም፣ ‹‹ከእንግዲህ የያህዌን ረድኤት አልጠብቅም››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 7

1 ኤልሳዕም፦ «እግዚአብሔር የሚለውን ቃል ስማ! ነገ በዚህ ጊዜ ሦስት ኪሎ ምርጥ ስንዴ ወይም ስድስት ኪሎ ገብስ በአንድ ጥሬ ብር በሰማርያ በር ይሸመታል» አለ። 2 በዚህ ጊዜ የንጉሡ ባለሥልጣን ለእግዚአብሔር ሰው እንዲህ ሲል መለሰለት፦ እግዚአብሔር የሰማይ መስኮቶችን እንኳ ቢከፍት ይህ ሊሆን ይችላልን? ኤልሳዕም እንዲህ ሲል መለሰለት፦ ይህ ሲፈጸም በዐኖችህ ብቻ ትመለከታለህ፤፤ አንተ ግን ከዚህ ምንም አትበላም። 3 አራት ለምጻሞች ከሰማርያ ከተማ በር ቆመው ነበር። እርስ በርሳቸውም እንዲህ ተባባሉ፦ እስክንሞት ለምን እዚህ እንቀመጣለን? 4 ወደ ከተማ እንግባ ካልን በከተማው ራብ ስላለ እንሞታለን። ነገር ግን እዚህ ከተቀመጠንም መሞታችን ነው፤ ወደ ሶርያውያን ጦር ሰፈር እንሂድ፤ በሕይወት ካቆዩንም በሕይወት እንኖራለን፤ ከገደሉንም መሞት ብቻ ነው። 5 ስለዚህም ቀኑ ሊመሽ ሲል ወደ ሶርያውያን ጦር ሰፈር ሊሄዱ ተነሡ፤ ወደ ሰፈሩም በደረሱ ጊዜ እዚያ ማንም አልነበረም። 6 ይህም የሆነበት ምክንያት እግዚአብሔር የሶርያ ጦር የፈረሶች፣ የሠረገሎችና ሌሎችንም ከፍተኛ የሠራዊት ድምፅ እንዲሰሙ አድርጎ ስለነበረ ነው፤ እርስ በርሳቸውም እንዲህ አሉ፦ የእስራኤል ንጉሥ የሒታውያንና የግብፃውያንን ሠራዊት ቀጥሮ እኛን እያጠቃ ነው። 7 ስለዚህ ሠራዊቱ በሌሊት ተነሥቶ ሸሽቷል፤ ድንኳኖቻቸውን፣ ፈረሶቻቸውንና በሰፈሩ ያለውን ሁሉ ትተው ሕይወታቸውን ለማትረፍ ሸሹ። 8 ለምጻሞቹም ወደ ሶርያውያን ሰፈር ዳርቻ በደረሱ ጊዜ ወደ አንዱ ድንኳን በገቡ ጊዜ በሉ፣ ጠጡ፤ ብር፣ ወርቅና ልብስም ወስደው ደበቁ። እንደገና ተመልሰው ወደ ሌላ ድንኳን ገብተው ያለውን ወስደው እንደበፊቱ አደረጉ። 9 ከዚያም እርስ በርሳቸው እንዲህ ተባባሉ፦ መልካም አላደረግንም። ዛሬ የምሥራች የሚሆን ታላቅ ነገር አግኝተናል፤ ነገር ግን ዝም ብለናል። እስኪነጋም ዝም ብንል ቅጣት ይደርስብናል። አሁን ተነሥተን እንሂድና ለንጉሡ ቤተ ሰብ እንንገር። 10 ስለዚህ ሄደው የከተማውን በር ጠባቂዎች ተጣሩ፤ እንዲህ ብለውም ነገሩአቸው፦ ወደ ሶርያውያን ሰፈር ሄደን ነበር፤ ነገር ግን ማንም አልነበረም፤ አንዲት ድምፅ እንኳን የለም፤ ነገር ግን ፈረሶችና አህዮች እንደታሰሩ አሉ፣ እንዲሁም ድንኳኖቹም እንዳሉ ናቸው። 11 ከዚያም የበር ጠባቂዎቹ ወሬውን ተናገሩ፤ ከዚያም እስከ ንጉሡ ቤተ ሰብ ድረስ ተሰማ። 12 ንጉሡም በሌሊት ተነሥቶ ለአገልጋዮቹ እንዲህ አለ፦ ሶርያውያን የደረጉብንን እነግራችኋለሁ፤ እንደተራብን ስለሚያውቁ ራሳቸውን ለመሰወር ሰፈሩን ለቀው ወደ ገጠር ሄደዋል፤ እንዲህም ይላሉ፦ ምግብ ፍለጋ ከከተማ ሲወጡ በሕይወት እንይዛቸዋለን፤ ወደ ከተማም እንወስዳቸዋለን። 13 ከንጉሡም ባለሥልጣናት አንዱ መልሶ እንዲህ አለ፦ ጥቂት ሰዎች ከሞት ከተረፉት አምስት ፈረሶች እንድንወስድ እለምንሃለሁ። በዚህ ከተማ የተረፈው ሕዝብ ከዚህ በፊት እንደሞቱ ሰዎች ሁሉ ከሞት የሚያመልጥ አይደለም። ስለዚህ የሆነውን ነገር ለማወቅ እንድንችል እነርሱን እንላክ። 14 ንጉሡም ሁለት ሠረገላዎችን ከፈረሶች ጋር ከሶርያውያን ሠራዊት በኋላ እንዲህ ሲል ላካቸው፦ ሂዱና ተመልከቱ። 15 እነርሱም ከሶርያውያን ኋላ ወደ ዮርዳኖስ ሄዱ፤ በየመንገዱም ሁሉ ሶርያውያን ሲሸሹ ጥለው የሄዱትን ብዙ ልብስና መሣሪያ ሁሉ አገኙ። መልእክተኞቹም ተመልሰው ለንጉሡ ነገሩት። 16 ሕዝቡ ሄደው የሶርያውያንን ሰፈር ዘረፉ። ስለዚህም እግዚአብሔር ከዚህ በፊት እንደተናገረው ሦስት ኪሎ ምርጥ ስንዴ ወይም አምስት ኪሎ የገብስ ዱቄት በአንድ ብር ተሸመተ። 17 ንጉሡም የከተማዪቱ ቅጥር በር በባለሥልጣኑ ኃላፊነት እንዲጠበቅ አድርጎ ነበር፤ ነገር ግን ያንን አገልጋይ ሕዝቡ ረጋጦት በዚያው ሞተ። 18 ይህም የሆነው ንጉሡ የእግዚአብሔርን ሰው ለማነጋገር በሄደ ጊዜ የተናገረው ይፈጸም ዘንድ ነበር። 19 ስለዚህም የእግዚአብሔር ሰው ለንጉሡ፣ በዚህ ጊዜ በሰማርያ ከተማ በር ሦስት ምርጥ ስንዴ ወይም ስድስት ኪሎ ገብስ በአንድ ብር ይሸመታል ብሎት ነበር። 20 በዚያም ባለሥልጣኑ ለእግዚአብሔር ሰው እንዲህ ሲል መልሶ ነበር፦ እግዚአብሔር የሰማይ መስኮቶችን እንኳ ቢከፍት ይህ እንዴት ይሆናል? ኤልሳዕም፦ ይህ ሲሆን በዐይንህ ብቻ ትመለከታለህ፤ ነገር ግን ከዚህ ምንም አትበላም ብሎት ነበር። 20 እንግዲህ ያ የንጉሡ ባለሥልጣን በሰማርያ ከተማ ቅጥር በር ላይ ሕዝብ ረጋግጦት ለመሞት የበቃው ይህ ትንቢት ስለ ተፈጸመበት ነው።

---

2 Kings 7:1

አንድ መስፈሪያ ማለፊያ ዱቄት በአንድ ሰቅል፣ ሁለት መስፈሪያ ገብስም በአንድ ሰቅል ይሸጣል
እስራኤላውያን ከዚያ በፊት ከነበረው ጊዜ ይልቅ ለእነዚህ ሸቀጦች አነሥተኛ ገንዘብ እንደሚከፍሉ ነው የሚጠቁመው። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰዎች አንዱን መስፈሪያ ማለፊያ ዱቄት በአንድ ሰቅል፣ ሁለቱን መስፈሪያ ገብስም በአንድ ሰቅል ይሸጣሉ››

አንድ መስፈሪያ ማለፊያ ዱቄት... ሁለት መስፈሪያ ገብስ
እዚህ ላይ፣ ‹‹መስፈሪያ›› የሚለው ቃል፣ ‹‹ሴህ›› ሲሆን፣ 7 ሊትር የሚሆን የደቃቅ ነገሮች መለኪያ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹7 ሊትር ማለፊያ ዱቄት... 14 ሊትር ገብስ››

ሰቅል
ሰቅል ከ11 ግራም ጋር የሚመጣጠን መለኪያ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹11 ግራም ብር›› ወይም ‹‹አንድ የብር ሳንቲም››

ንጉሡ በክንዱ ላይ የተደገፈው የጦር አዛዥ
የንጉሡ የግል ረዳት የሆነው ከፍተኛ ሹም፣ ንጉሡ በክንዱ የሚደገፍበት ሰው መሆኑ ተመልክቷል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለንጉሡ ቅርብ የሆነው የጦር አዛዥ›› ወይም፣ ‹‹የንጉሡ የግል ረዳት የሆነው የጦር አዛዥ››

ያህዌ የሰማያትን መስኮት ቢከፍት እንኳ
እህሎች እንዲያድጉ ያህዌ ብዙ ዝናብ ማዝነቡ ከሰማይ መስኮቶች ብዙ ውሃ እንዲወርድ ከማድረግ ጋር ተመሳስሎአል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ ብዙ ዝናብ ከሰማይ ቢያዘንብ እንኳ››

ይህ ሊሆን ይችላልን?
የጦር አዛዡ ይህን የተናገረው አለማመኑን ለመግለጽ ነው። ይህን ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ይህ በፍጹም ሊሆን አይችልም››

አንተው ራስህ በዐይንህ ታየዋለህ
‹‹አንተው ራስህ በዐይንህ›› የሚለው ሐረግ ኤልሳዕ የተናገረው ትንቢት ሲፈጸም በእርግጥ እንደሚያይ አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ይህ ሲሆን፣ አንተው ራስህ ትመለከታለህ››

ይሁን እንጂ ከዚያ አንዳች አትቀምስም
‹‹ከገብሱ ዱቄት ምንም አትበላም››

2 Kings 7:3

እነሆ
ይህ ቃል እዚህ ጥቅም ላይ የዋለው ዋናውን የታሪክ ፍሰት ገታ ለማድረግ ነው። እዚህ ላይ ጸሐፊው የታሪኩን አዲስ ክፍል ያቀረባል።

እስክንሞት ድረስ በዚህ የምንቆየው ለምንድነው?
ሰዎቹ አራት ቢሆኑም ይህን የጠየቀው አንዱ ነው። ጥያቄው ይህን ማድረግ እንዳለባቸው አጽንዖት ይሰጣል። ይህን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እስክንሞት ድረስ በፍጹም እዚህ መቀመጥ የለብንም››ዝም ካሉን ሕይወታችን ትተርፋለች፤ ከገደሉንም ያው ሞቶ መገላገል ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Kings 7:5

መሸትሸት ሲል
ይህ የሚያመለክተው ፀሐይ ከጠለቀች በኃላ ከመጨለሙ በፊት የለውን ምሸት ነው።

ከሰፈሩ ውጪ
‹‹ዳርቻ››

የሠረገሎችንና የፈረሶችን እንዲሁም የብዙ ሰራዊት ድምፅ ሶርያውያን...
የሶርያ ሰራዊት ወደ ጦርነቱ እየመጣ ያለ የብዘ ወታደሮች ድምፅ ሰማ። ይሁን እንጂ፣ ጌታ እንዲሰሙ አድርጓቸው ነው እንጂ፣ ምንም ወታደር አልነበረም።

እርስ በርሳቸውም
‹‹የሶርያ ወታደሮች እርስ በርሳቸው››

የኬጢያውያንና የግብፃውያንን ነገሥታት
እዚህ ላይ፣ ‹‹ነገሥታት›› የሚለው ነገሥታቱንና ሰራዊቱን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የኬጢያውያንና የግብፃውያን ሰራዊት››

አምጥቶብናል
‹‹ሊወጉን›› ወይም፣ ‹‹ሊወርሩን››

2 Kings 7:7

አጠቃላይ መረጃ
ሶርያውያን ብዙ የጠላት ሰራዊት ወደ ሰፈራቸው እየመጣ ነው ብለው እንዲያስቡ ጌታ ካደረገ በኃላ የሆነው እንዲህ ነበር።

መሸትሸት ሲል
ይህ ፀሐይ ከጠለቀች በኃላ ጨለማ ከመሆኑ በፊት ያለው ጊዜ ነው።

ዘረፉ
ይህ አሸናፊው ሰራዊት ከተሸናፊው የሚወስደውን ነገር ያመለክታል። እዚህ ላይ፣ ‹‹ብርና ወርቅ፣ ልብሶች›› ናቸው የተጠቀሱት።

2 Kings 7:9

እስኪነጋ ድረስ
‹‹ጠዋት እስኪሆን››

ቅጣት ይደርስብናል
አራቱን ሰዎች የሚቀጣው ሰው ራሱ ቅጣት እንደ ሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ይቀጡናል›› ወይም፣ ‹‹አንድ ሰው ይቀጣናል››

ወደ ቤተ መንግሥት በፍጥነት ሄደን እንንገር
እዚህ ላይ፣ ‹‹ቤተ መንግሥት›› ንጉሡ ቤት ውስጥ የሚኖሩትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለንጉሡና ለሰዎቹ እንንገር››

ስለዚህ ሄደው
ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወታደሮቹ እዚያው እያሉ ሄደው››

ዜናውም በቤተ መንግሥት ተሰማ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። ‹‹ከዚያም ሰዎቹ ቤተ መንግሥት ውስጥ ተናገሩ!›› ወይም፣ ‹‹ከዚያም ሰዎቹ ለንጉሡና ቤተ መንግሥቱ ውስጥ ላሉት ተናገሩ››

2 Kings 7:12

ያደረጉብንን
‹‹ሊያደርጉብን ያሰቡትን›› ወይም፣ ‹‹እኛን ለማታለል ያደረጉትን››

ከነሕይወታቸው እንማርካቸዋለን
ይህ ማለት ከነሕይወታቸው ይይዙዋቸዋል እንጂ አይገድሏቸውም ማለት ነው።

በከተማዪቱ ውስጥ ከተረፉት ፈረሶች
አብዛኞቹ የእስራኤላውያን ፈረሶች በራብ ምክንያት ሞተዋል። ይህን ዐረፍተ ነገር የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በከተማዪቱ ውስጥ በሕይወት ካሉት ፈረሶች››

ዕጣ ፈንታቸውም በዚህ ከቀሩት እስራኤላውያን ሁሉ ዕድል ጋር አንድ ነው።
ወደ ሶርያውያን ሰራዊት ሰፈር የሚሄዱት ድርሻ ከተማ ውስጥ ከቀሩት እስራኤላውያን ድርሻ ጋር እኩል ነው። በራብ ይሞታሉ ወይም በሶርያ ወታደሮች ሊያዙ ይችላሉ።

እንይ
ማየት የፈለጉትን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነዚህ ለምጻሞች የነገሩን እውነት መሆኑን እንይ››

2 Kings 7:14

ሂዱና እዩ
ንጉሡ ሄደው እንዲያዩ የፈለገውን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነዚህ ለምጻሞች የተናገሩት እውነት መሆኑን ሂዱና እዩ››

እስከ ዮርዳኖስ ድረስ ተከተሏቸው
‹‹ሶርያውያን ወታደሮች የሄዱበትን መንገድ እስከ ዮርዳኖስ ወንዝ ድረስ ተከተሉ››

ልብስና ዕቃ በየመንገዱ ላይ ተበታትኖ ነበር
ይህ ግነት ሲሆን፣ ሰዎቹ በሄዱበት መንገድ እነዚህ ነገሮች ተበታትነው አዩ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በየመንገዱ ልብሶችና ዕቃዎች ነበሩ››

2 Kings 7:16

ሰፈሩን በዘበዙ
ይህ ከተሸነፈው ሰራዊት ንብረት መውሰድ ማለት ነው።

ስለዚህ አንድ መስፈሪ ማለፊያ ዱቄት በአንድ ሰቅል፣ ሁለት መስፈሪያ ገብስም በአንድ ሰቅል ተሸጠ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለዚህም ሰዎቹ አንዱን መስፈሪያ ማለፊያ ዱቄት በአንድ ሰቅል፣ ሁለቱን መስፈሪያ ገብስም በአንድ ሰቅል ሸጡ››

አንድ መስፈሪያ ማለፊያ ዱቄት... ሁለት መስፈሪያ ገብስ
እዚህ ላይ፣ ‹‹መስፈሪያ›› ተብሎ የተተረጐመው፣ ‹‹ሴህ›› የሚለው ቃል ሲሆን፣ ደረቅ ነገሮች በሚለኩበት መለኪያ ከ7 ሊትር ጋር እኩል ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹7 ሊትር ማለፊያ ዱቄት... 14 ሊትር ገብስ››

ሰቅል
ሰቅል ከ11 ግራም ጋር የሚተካከል መለኪያ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹11 ግራም የሚያህል ብር›› ወይም፣ ‹‹አንድ የብር ሳንቲም››

የያህዌ ቃል እንደ ተናገረው
እዚህ ላይ፣ ‹‹ቃል›› ያህዌን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ እንደ ተናገረው››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ንጉሡ እጁን ይደገፈው የነበረው የጦር አለቃ
የንጉሡ የቅርብ ረዳት የነበረው ከፍተኛ ባለ ሥልጣን ንጉሡ እጁን ይደግፈው የነበረ ሰው እንደ ሆነ ተነግሮአል 2 ነገሥት 7፥2 ላይ ያለውን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለንጉሡ ቅርብ የነበረው የጦር አዛዥ›› ወይም፣ ‹‹የንጉሡ የቅርብ ረዳት የነበረው የጦር አዛዥ

ሕዝቡ ሲጋፋ ረጋገጠው
ሕዝቡ ምግብ ለማግኘት እየተጣደፉ ስለ ነበር፣ ሰውየው ጋር ተጋጩ፤ ረጋግጠውም ገደሉት።

2 Kings 7:18

አጠቃላይ መረጃ
በእነዚህ ጥቅሶች ጸሐፊው 2 ነገሥት 7፥1-2 ላይ ያለውን በድጋሚ በማቅረብ የሆነውን ነገር ያሳጥራል።

በዚህ ጊዜ
‹‹ነገ በዚህ ጊዜ››

ሁለት መስፈሪያ ገብስ... አንድ መስፈሪያ ማለፊያ ዱቄት
እዚህ ላይ፣ ‹‹መስፈሪያ›› ተብሎ የተተረጐመው፣ ‹‹ሴህ›› የተሰኘው ቃል ሲሆን፣ በደረቅ ነገር መለኪያ ከ7 ሊትር ጋር እኩል ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹14 ሊትር ገብስ... 7 ሊትር ማለፊያ ዱቄት››

ሰቅል
ሰቅል ከ11 ግራም ጋር እኩል የሆነ መስፈሪያ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹11 ግራም የሚያህል ብር›› ወይም፣ ‹‹አንድ የብር ሳንቲም››

እይ
‹‹ተመልከት›› ወይም፣ ‹‹ስማ›› ወይም፣ ‹‹የምነግርህን ልብ በል››

ያህዌ የሰማይን መስኮቶች ቢከፍት እንኳ
እህል እንዲበቅል ያህዌ ዝናብ ማዝነቡ የሰማይ መስኮቶች ጋር ተመሳስሎአል። 2 ነገሥት 7፥2 ላይ ያለውን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ከሰማይ ብዙ ቢያዘንብ እንኳ››

ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?
የጦር አዛዡ እንዲህ ያለው አለማመኑን ለማሳየት ነው። ጥያቄውን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። 2 ነገሥት 7፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህ በፍጹም አይሆንም››

አንተው ራስህ በዐይንህ ታያለህ
‹‹በዐይንህ ታያለህ›› የሚለው ሐረግ ኤልሳዕ ትንቢት የተነገረውን የጦር አዛዡ በእርግጥ እንደሚያይ አጽንዖት ይሰጣል። 2 ነገሥት 7፥2 እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህ ሲሆን አንተው ራስህ ታያለህ››

ግን አንዳች ነገር አትቀምስም
‹‹ከዚያ ገብስ ምንም አትበላም››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 8

1 ኤልሳዕም ልጅዋን ከሞት ያስነሣላትን፣ በሱነም የነበረችውን ሴት አስቀድሞ እንዲህ ሲል ነግሮአት ነበር፡- እግዚአብሔር እስከ ሰባት ዓመት የሚቆይ ራብ
በዚህች ምድር ላይ ልኮአል፤ ከቤተ ሰብሽ ጋር በሕይወት ለመትረፍ ከዚህ ተነሥተሽ ወደ ሌላ ስፍራ ሂጂ። **2** ስለዚህም የኤልሳዕን ምክር ሰምታ ከነቤተ ሰብዋ
ወደ ፍልስጥኤም አገር በመሰደድ እስከ ሰባት ዓመት ቆየች። **3** ሴቲቱም ከሰባቱ የራብ ዓመቶች ፍፃሜ በኋላ ከፍልስጥኤም አገር ተመልሳ መጣች፤ ስለ
መኖሪያ ቤትዋና ስለ እርሻ መሬትዋ ለመጠየቅ ወደ ንጉሡ ሄደች። **4** ንጉሡም ከእግዚአብሔር ሰው አገልጋይ ከግያዝ ጋር፡- «ኤልሳዕ ስላደረጋቸው ታላላቅ
ነገሮች ንገረኝ» እያለ ይነጋገር ነበር። **5** ግያዝም ኤልሳዕ እንዴት የሞተውን ሕፃን እንዳስነሣው ለንጉሡ እየነገረ እያለ ኤልሳዕ ሕፃኑን ከሞተ ያስነሣላት ሴት
ንጉሡን ስለ መኖሪያ ቤትዋና ስለ እርሻ መሬቷ ለመጠየቅ መጣች። ግያዝም እንዲህ አለ፡- «ጌታዬ ንጉሥ ሆይ! ሴቲዮዋ እነሆ ይህች ናት፤ ኤልሳዕ ከሞት
ያስነሣው ልጅዋም ይሄ ነው!» **6** ንጉሡም ሴቲቱን ስለ ሕፃኑ በጠየቃት ጊዜ በሚገባ አስረዳችው። ስለዚህ ንጉሡ አንዱን ባለሥልጣን ስለ እርስዋ እንዲህ ሲል
አዘዘ፡- የእርስዋ የሆነውን ማናቸውንም ነገርና የእርሻ መሬትዋን ከሰባት ዓመት ጀምሮ አገሩን ከለቀቀችበት እስካሁን ያለውን ሰብል ጭምር እንዲመልስላት
አዘዘው። **7** የሶርያ ንጉሥ ቤን ሀዳድ በታመመ ጊዜ ኤልሳዕ ወደ ደማስቆ ሄደ። ንጉሡም የእግዚአብሔር ሰው መምጣቱን ሰማ። **8** ንጉሡም አዛሄልን፡-
«በእጅህ አንድ ስጦታ ይዘህ ወደ እግዚአብሔር ሰው ሂድና ከዚህ ሕመም እድናለሁን? ብለህ ጠይቅ አለው። **9** ስለዚህ አዛሄል በደማስቆ ከሚገኘው ምርጥ
የምድር በረከት ሁሉ በአርባ ግመሎች ጭኖ ወደ ኤልሳዕ ሄደ። አዛሄልም መጥቶ በኤልሳዕ ፊት ቆመና፡- «ልጅህ ንጉሥ ቤን ሀዳድ ከሕመሙ ይድን እንደሆነ
እንድትነግረው እጠይቅህ ዘንድ ልኮኛል» አለው። **10** ኤልሳዕም፡- «ቤን ሀዳድን አንተ በርግጥ ትድናለህ ብለህ ንገረው፣ ነገር ግን እንደሚሞት እግዚአብሔር
ገልጦልኛል፤» አለው። **11** ከዚያም ኤልሳዕ ፊቱን በማጥቆር ትኩር ብሎ እስኪያፍር ድረስ አዛሄልን ተመለከተው፤ የእግዚአብሔርም ሰው እንባውን ማፍሰስ
ጀመረ። **12** አዛሄልም፡- «ጌታዬ ስለምን ታለቅሳለህ?» ሲል ጠየቀው። ኤልሳዕም፡- «በእስራኤል ሕዝብ ላይ የምትፈፅመውን አሰቃቂ ነገር ስለማውቅ ነው።
ምሽጎቻቸውን በእሳት ታቃጥላለህ፤ ወጣቶቻቸውን በሰይፍ ትገድላለህ፤ ሕፃናቶቻቸውን በድንጋይ ትከሰክሳለህ፤ የእርጉዞች ሴቶችንም ሆድ ትሰነጥቃለህ» ሲል
መለሰለት። **13** አዛሄልም፡- «ይህን ታላቅ ነገር የሚያደርግ አገልጋይህ ማን ሆኖ ነው? ይህ ሰው ውሻ ብቻ ነው ሲል ጠየቀው። ኤልሳዕም፡- «አንተ የሶርያ ንጉሥ
እንደምትሆን እግዚአብሔር ገልጦልኛል» ሲል መለሰለት። **14** ከዚያም አዛሄል ተመልሶ ወደ ጌታው ወደ ንጉሡ መጣ። «ኤልሳዕ ምን አለህ?» ሲል ቤን
ሀዳድ ጠየቀው። አዛሄልም፡- «አንተ በእርግጥ እንደምትድን ነግሮኛል» ሲል መለሰለት። **15** ነገር ግን በማግስቱ አዛሄል ብርድ ልብስ ወስዶ ውሃ ውስጥ
ነከረ፤ ከዚያም በቤን ሀዳድ ፊት ወረወረውና ታፍኖ ሞተ። አዛሄልም በቤን ሀዳድ ፈንታ ተተክቶ የሶርያ ንጉሥ ሆነ። **16** የእስራኤል ንጉሥ የአክአብ ልጅ ኢዮራም
በነገሠ በአምስተኛው ዓመት ኢዮራም በይሁዳ መንገሥ ጀመረ። እርሱም የይሁዳ ንጉሥ የኢዮሳፍጥ ልጅ ነበር። **17** እርሱም በነገሠ ጊዜ ሠላሳ ሁለት ዓመቱ
ነበር። መቀመጫውንም በኢየሩሳሌም አድርጎ ስምንት ዓመት ነገሠ። **18** ሚስቱም የአክዓብ ልጅ ስለነበረች የእስራኤል ነገሥታት ይፈፅሙት የነበረውን እንደ
አክዓብ ቤተ ሰብ የክፋት መንገድ ተከተለ። በእግዚአብሔርም ፊት ክፉ ሥራ ሠራ። **19** ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ከዘሩ መንግሥታትን እንደማያጠፋ ለአገልጋዩ
ለዳዊት ተስፋ ሰጥቶት ስለ ነበር ይሁዳን ማጥፋት አልፈለገም። **20** በኢዮራም ዘመነ መንግሥት ኤዶም በይሁዳ ላይ ዐመፀ፤ ለራሳቸውም ንጉሥ አነገሡ። **21**
ስለዚህም ኢዮራም ሠረገሎቹን በመላ አሰልፎ ወደ ጸዒር ዘመተ። የኤዶም ሠራዊትም ኢዮራምን በከበቡ ጊዜ፤ በሌሊት ተነሥተው የሠረገሎቹን አዛዦች
አጠቁአቸው፤ ነገር ግን የኢዮራም ሠራዊት ሮጠው ወደየቤታቸው ተበታተኑ። **22** ስለዚህ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኤዶም በይሁዳ አገዛዝ ላይ አመፀ። በተመሳሳይ
ጊዜም የልብና ከተማ አመፀች። **23** ኢዮራም ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ በይሁዳ የነገሥታት ታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኝ የለምን? **24** ኢዮራም ሞተ፤
በዳዊት ከተማም በሚገኘው በአባቶቹ መካነ መቃብር ተቀበረ። ከዚያም አካዝያስ በእርሱ ፈንታ ተተክቶ ነገሠ። **25** የእስራኤል ንጉሥ የአክዓብ ልጅ ኢዮራም
በነገሠ በዐሥራ ሁለተኛው ዓመት የኢዮራም ልጅ አካዝያስ የይሁዳ ንጉሥ ሆነ። **26** አካዝያስ በነገሠ ጊዜ የሃያ ሁለት ዓመት ወጣት ነበረ። እርሱም በኢየሩሳሌም
አንድ ዓመት ገዛ። እናቱ ጎቶልያ ተብላ የምትጥራው የእስራኤል ንጉሥ የዘንበሪ ልጅ ነበረች። **27** አካዝያስ የንጉሥ አክዓብን መንገድ ተከተለ፤
በእግዚአብሔርም ፊት ክፉ አደረገ። ምክንያቱም አካዝያስ የንጉሥ አከዓብን ልጅ ስለሚያገባ ነበር። **28** አካዝያስም ከንጉሥ አከዓብ ልጅ ከኢዮራም ጋር ሆኖ
ከሶርያ ንጉሥ ከአዛሄል ጋር ለመዋጋት ወደ ራሞት ገለዓድ ዘመተ። ሶርያውያንም ኢዮራምን አቆሰሉት። **29** ኢዮራምም ከሶሪያ ንጉሥ አዛሄል ጋር በሬማት
በተደረገው ጦርነት የደረሰበትን ቁስሉን ለመታከም ወደ ኢይዝራኤል ከተማ ተመለሰ። ስለዚህ የኢዮራም ልጅ አካዝያስ የይሁዳ ንጉሥ የአከዓብ ልጅ ኢዮራም
ስለደረሰበት ጉዳት ለመጠየቅ ወደ ኢይዝራኤል ከተማ ሄደ።

---

2 Kings 8:1

በዚህ ጊዜ
ይህ ቃል እዚህ ጥቅም ላይ የዋለው የዋናውን ታሪክ ፍሰት ገታ ለማድረግ ነው። ጸሐፊው የታሪኩን አዲስ ክፍል መናገር ይጀምራል።

ልጇን ከሞት ያስነሣላትን ሴት
የዚህች ሴትና የልጇ ታሪክ 2 ነገሥት 4፥8 ላይ ይገኛል።

ከሞት ያስነሣላት
‹‹ወደ ሕይወት የመለሰላት››

ተነሺና... ተነሥታ የእግዚአብሔር ሰው እንደ ነገራት አደረገች
እዚህ ላይ መነሣት አንድ ሰው ሲያደርግ የነበረውን በማቆም የተነገረውን ማድረግ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የምነግርሽን አድርጊ... እርሷም የእግዚአብሔር ሰው የነገራትን አደረገች››

የእግዚአብሔር ሰው
‹‹የእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕ››

2 Kings 8:3

ለንጉሡ
ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን ንጉሥ ነው።

ስለ ቤቷና ስለ መሬቷ
ሴትዮዋ ስትሄድ ቤቷና ንብረቷ ተወስዶ ነበር። እንዲመለስላት እየለመነች ነው። የዚህን ትርጉም የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቤቷና ንብረቷ እንዲመለስላት››

ስለ ልጇ
ይሄ የሚያመለክተው ስለ ልጇ መሞትና ኤልሳዕ እንዴት እንዳስነሣላት ነው። ይህን ዐረፍተ ነገር የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ልጇ ላይ ስለሆነው ጉዳይ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የእርሻዋን ሰብል በሙሉ
ይህ የሚያመለክተው እርሷ ከሄደች ጀምሮ እርሻዋ ማስገኘት የሚችለውን ገንዘብ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእርሻዋ ማግኘት የነበረባትን ጥቅም ሁሉ››

2 Kings 8:7

ቤንሓዳድ
ይህ የሶርያ ንጉሥ ስም ነው። ስሙ፣ ‹‹የሐዳድ ልጅ›› ማለት ነው። 6፥24 ላይ የዚህን ሰው ስም እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

አዛሄል
ይህ የሰው ስም ነው።

ገጸ በረከት ይዞ
አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን አዛሄል ብዙ ገጸ በረከት ይወስዳል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ብዙ ገጸ በረከት ወስዶ››

በእጅህ
ይህ ሐረግ፣ ስጦታዎቹን ይዞ እንዲሄድ ማለት ነው። ‹‹ይዘህ ሂድ››

የእግዚአብሔር ሰው
‹‹የእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕ››

በእርሱ በኩል ያህዌን ጠይቅ
‹‹እግዚአብሔርን እንዲጠይቅ ለኤልሳዕ ንገረው››

የአርባ ግመል ጭነት
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በአርባ ግመል አስጭኖ››

አርባ ግመሎች
‹‹40 ግመሎች››

የሶርያ ንጉሥ ልጅህ ቤንሐዳድ
ቤንሐዳድ በቀጥታ የኤልሳዕ ልጅ አልነበረም፤ አዛሄል እንዲህ ያለው በመካከላቸው የነበረውን ጥብቅ ግንኙነት ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ልጅህ የሆነው የሶርያ ንጉሥ ቤንሐዳድ››

2 Kings 8:10

እስኪያፍር ድረስ
‹‹አዛሄል ምቾት እስኪያጣ ድረስ››

ጌታዬ
አዛሄል ኤልሳዕን እንዲህ ያለው እርሱን ለማክበር ነው።

ስለማውቅ ነው
እግዚአብሔር ለኤልሳዕ ወደ ፊት የሚሆነውን አሳይቶታል።

አንተ የምታደርገውን
አንተ የሚለው የሚወክለው አዛሄልን ቢሆንም፣ እዚህ ላይ ግን ወደ ፊት ንጉሥ ሲሆን በእርሱ ሥር የሚሆኑትን ወታደሮች ነው።

ታቃጥላለህ… ትገድላለህ
‹‹አንተ›› የሚለው የሚወክለው አዛሄልን ቢሆንም፣ እዚህ ላይ የሚያመለክተው አዛሄልን ሳይሆን ወታደሮቹን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወታደሮችህ ያቃጥላሉ… ወታደሮችህ ይገድላሉ››

ሕፃናታቸውንም በምድር ላይ ትፈጠፍጣለህ
‹‹ትንንሽ ልጆቻቸውን ትጨፈልቃለህ›› — ይህ ልጆቹን የሚገድሉ ወታደሮችን ጭካኔ ያመለክታል።

ጐልማሶቻቸውን በሰይፍ ትገድላለህ
ይህ ማለት ሰዎቹ በጦርነት ይገደላሉ ማለት ነው። ሰይፍ በጦርነት ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውል ዋና መሣሪያ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጦርነት ሰዎቻቸውን በሰይፍ ትገድላለህ››

ያረገዙ ሴቶቻቸውን ሆድ ትቀድዳለህ
ይህ ለይቶ የሚያመክተው የማሕፀን መቀደድን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያረገዙ ሴቶቻቸውን ማሕፀን በሰይፍ ትቀድዳለህ››

2 Kings 8:13

አገልጋይህ ይህን ጀብዱ መፈጸም እንዴት ይችላል?
አዛሄል ራሱን የኤልሳዕ አገልጋይ በማለት ይጠራል። አዛሄል እንዲህ ያለው ኤልሳዕ የተናገረውን አሰቃቂ ነገር መፈጸም እችላለሁ ብሎ አለማመኑን አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህን በዐረፍተ ነገር መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንዲህ ያለውን ጀብዱ ማድረግ አልችልም›› ወይም፣ ‹‹እንዲህ ያለውን ጀብዱ ለማድረግ ለመሆኑ እኔ ማን ነኝ››

ይህን ጀብዱ
‹‹ይህን አሰቃቂ ነገር›› እዚህ ላይ፣ ‹‹ጀብዱ›› ሰፊ ውጤት ያለውን አሰቃቂ ነገር ለማመልከት ነው።

እንደ ውሻ የሚቆጠር
አዛሄል ስለ ራሱ እየተናገረ ነው። ራሱን ከውሻ ጋር በማነጻጸር ዝቅተኛነቱንና ተፅዕኖ ማድረግ የማይችል መሆኑን እየተናገረ ነው። እዚህ ላይ ውሻ ዝቅተኛ እንስሳን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ እንደ ውሻ ዐቅመ ቢስ ነኝ›› ወይም፣ ‹‹እኔ እንደ ዝቅተኛው እንስሳ ዐቅመ ቢስ ነኝ››

ወደ ጌታው ተመለሰ
‹‹ጌታው›› የሚለው የሚያመለክተው ቤንሐዳድን ነው።

እንዲሞት ፊቱን ሸፈነው
ይህ ማለት ቤንሐዳድ በውሃ በራሰ ወፍራም ልብስ ታፈነ ማለት ነው። ይህን ዐረፍተ ነገር ይበልጥ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቤንሐዳድ መተንፈስ ስላልቻለ ሞተ››

2 Kings 8:16

አጠቃላይ መረጃ
ኢዮራም የይሁዳ ንጉሥ ሆነ የአክዓብ ልጅ ኢዮሆራም በእስራኤል በነገሠ በአምስተኛው ዓመት ይህ የሚገልጸው የአሁኑ የእስራኤል ንጉሥ ኢዮሆራም ምን ያህል ዓመት እንደ ገዛ በመግለጽ ኢዩራም በይሁዳ ላይ መንገሥ የጀመረበትን ጊዜ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአክዓብ ልጅ ኢዮሆራም የእስራኤል ንጉሥ በሆነ አምስተኛው ዓመት›› ወይም፣ ‹‹የአክዓብ ልጅ ኢዮሆራም በእስራኤል በነገሠ አምስት ዓመት ሲሆነው››

አምስተኛ ዓመት
‹‹5 ዓመት››

ኢዮራም መግዛት ጀመረ
የኢዮሣፍጥ ልጅ ኢዮራም የይሁዳ ንጉሥ ሆነ

ሰላሣ ሁለት ዓመት
‹‹32 ዓመት››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Kings 8:18

ኢዮራም የእስራኤልን ነገሥታት መንገድ ተከተለ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ተከተለ›› የሚለው እንደ ንጉሥ እንዴት እንደ ኖረና እንደ ገዛ የሚያመለክት ነው። በታሪክ ውስጥ በዚህ ጊዜ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የነበሩት የእስራኤል ነገሥታት ክፉዎች ነበሩ። ይህን ዐረፍተ ነገር የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከእርሱ በፊት እንደ ነገሡት የእስራኤል ነገሥታት ሁሉ ኢዮራም ክፉ ንጉሥ ነበር››

የአክዓብ ቤት እንዳደረገው
እዚህ ላይ የአክዓብ፣ ‹‹ቤት›› የአክዓብን ቤተ ሰብና የቅርብ ዘመዶቹን ያመለክታል። አክዓብ የኢዮራም ሚስት አባት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የተቀሩት የአክዓብ ቤተ ሰቦች እንዳደረጉት››

የአክዓብን ልጅ አግብቶ ነበር
ኢዮራም ያገባው የአክዓብን ልጅ ነበር

በያህዌ ፊት ክፉ ድርጊት ፈጸመ
የያህዌ፣ ‹‹ፊት›› የያህዌን ፍርድ ወይም መለኪያ ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በእግዚአብሔር ፍርድ ክፉ ድርጊት›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ክፉ የሚለውን››

ይሁዳን ሊያጠፋ
እዚህ ላይ ‹‹ይሁዳ›› እዚያ የሚኖረው ሕዝብ ስም ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የይሁዳን ሕዝብ ሊያጠፋ››

ምንጊዜም ዘር እንደሚያሳጣው ነግሮት ነበር
‹‹ምንጊዜም ቢሆን ዘር እንደሚሰጠው ያህዌ ለዳዊት ቃል ገብቶለት ስለ ነበር›› ይህ ልጆቹ ሁሌም ይሁዳን እንደሚገዙ ያህዌ ለዳዊት የሰጠውን ተስፋ ቃል ያመለክታል። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ልጆቹ ሁሌም ይሁዳን እንደሚገዙ ያህዌ ለዳዊት ነግሮት ስለ ነበር››

2 Kings 8:20

ኤዶም ዐምፆ
‹‹ኤዶም በ… ላይ ዐመፀ››

የይሁዳ እጅ
እዚህ ላይ ‹‹እጅ›› የይሁዳን ተቆጣጣሪነት፣ ‹‹ይሁዳ›› ደግሞ በተለይ የይሁዳን ንጉሥ ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከይሁዳ ንጉሥ ቁጥጥር››

የራሱን ንጉሥ አነገሠ
‹‹ለራሳቸው ንጉሥ ሾሙ››

ከዚያም ኢዮራም ተሻገረ
‹‹ተሻገረ›› የሚለውን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ኢዮራም የጠላትን ድንበር ተሻገረ››

2 Kings 8:22

አጠቃላይ መረጃ
የይሁዳ ንጉሥ ኢዮራም ሞተ፤ ልጁ አካዝያስ ነገሠ

ኤዶም እስከ ዛሬ ድረስ በይሁዳ ላይ እንደ ዐመፀ ነው
ከዚያ በኋላ ኤዶም በይሁዳ ቁጥጥር ሥር አልሆነም፤ እስከ ዛሬም እንደዚያው ነው››

በይሁዳ ላይ
‹‹ይሁዳ›› የይሁዳን ንጉሥ ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በይሁዳ ንጉሥ ላይ›› ወይም፣ ‹‹በይሁዳ ንጉሥ ሥልጣን ላይ››

እስከ ዛሬ ድረስ
ይህ እስከ ተጻፈ ድረስ

ልብናም በዚሁ ጊዜ ዐምፆ ነበር
እንደ ኤዶም ሁሉ ልብና በይሁዳ ንጉሥ ላይ ዐመፀ። ‹‹ልብና›› እዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የልብና ሕዝብ››

በኢዮራም ዘመነ መንግሥት የተከናወነው ሌላው ነገር
‹‹ስለ ኢዮራም ታሪክና ያደረገውን ለማንበብ››

በይሁዳ… ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?
ጥያቄው የቀረበው ኢዮራምን የሚመለከት መረጃ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንደሚገኝ ለአንባቢ ለመንገር ወይም ለማሳሰብ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እነዚህ ነገሮች በይሁዳ… ተጽፈዋል›› ወይም፣ ‹‹ስለዚያ ሁሉ በይሁዳ… ተጽፎአል››

ኢዮራም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ ከእነርሱም ጋር ተቀበረ
‹‹አንቀላፋ›› ማለት ‹‹ሞተ›› የሚለው ሌላ ቃል ነው። ከሞተ በኋላ አባቶቹ በተቀበሩበት መቃብር ተቀበረ። ‹‹ተቀበረ›› የሚለውን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ኢዮራም እንደ አባቶቹ አንቀላፋ፤ ከአባቶቹም ጋር ቀበሩት››

ልጁ አካዝያስም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ
‹‹ከዚያም የኢዮራም ልጅ አካዝያስ ነገሠ››

2 Kings 8:25

አጠቃላይ መረጃ
አካዝያስ የይሁዳ ንጉሥ ሆነ

የአክዓብ ልጅ ኢዮራም በነገሠ በዐሥራ ሁለተኛው ዓመት
የአሁኑ ንጉሥ ኢዮራም ምን ያህል ዘመን በእስራኤል እንደ ነገሠ በመግለጽ አካዝያስ በይሁዳ መንገሥ የጀመረበትን ዘመን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የአክዓብ ልጅ ኢዮራም የእስራኤል ንጉሥ በሆነ በዐሥራ ሁለተኛው ዓመት››

ዐሥራ ሁለተኛ ዓመት
‹‹12ኛ ዓመት››

ሃያ ሁለት ዓመት
‹‹22 ዓመት››

ጐቶልያ… ዖምሪ
ጐቶልያ የአንድ ሴት ስም ነው። ዖምሪ የአንድ ሰው ስም ነው።

አካዝያስ በ… መንገድ ሄደ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ሄደ›› የሰውን ጸባይ ወይም አኗኗር ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አካዝያስ እንደ ሌሎቹ ኖረ››

የአክዓብ ቤት
እዚህ ላይ፣ የአክዓብ፣ ‹‹ቤት›› ቤተ ሰቡን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የአክዓብ ቤተ ሰብ››

በያህዌ ፊት ክፉ የሆነውን
የያህዌ ፊት የያህዌን ፍርድና መለኪያ ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በያህዌ ፍርድ ክፉ የሆነውን›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ እንደ ክፉ የሚያስበውን››

የአክዓብን ልጅ አገባ
ይህ የሚያመለክተው አካዝያስ ከአክዓብ ጋር ያለውን ቀረቤታ ነው። የአካዝያስ አባት የአክዓብን ልጅ አግብቶ ነበር። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የአክዓብን ልጅ ያገባ ሰው ልጅ›› ወይም፣ ‹‹የንጉሥ አክዓብ የአማች ልጅ››

2 Kings 8:28

አካዝያስ ከአክዓብ ልጅ ከኢዮራም ጋር ሆኖ የሶርያ ንጉሥ አዛሄል ላይ ዘመተ

እዚህ ላይ የተጠቀሰው የሦስት ነገሥታት ስም አብረዋቸው ያሉ ሰራዊቶችንም ይመለከታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የአካዝያስ ሰራዊት፣ የሶርያ ንጉሥ አዛሄልን ለመውጋት ከእስራኤል ንጉሥ ኢዮራም ሰራዊት ጋር ተባበረ››

ለማገገም

ይህን፣ ‹‹እንዲፈወስ›› ወይም፣ ‹‹እንዲሻለው›› በማለት መተርጐም ይቻላል።

የሶርያ ንጉሥ አዛሄል ላይ

‹‹አዛሄል›› የሚለው ራሱንና ሰራዊቱን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሶርያ ንጉሥ አዛሄል ሰራዊት››

ኢዮራም ቆስሎ ነበር

ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሶርያውያን ኢዮራምን አቁስለውት ነበር››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 9

1 ነቢዩ ኤልሳዕም ከነቢያት ልጆች አንዱን ጠርቶ እንዲህ አለ፦ «በገለዓድ ወደምትገኘው ወደ ሬማት ለመሄድ ተዘጋጅ፤ ይህንንም የዘይት ማሰሮ ያዝ። 2 እዚያም
በደረስህ ጊዜ የኢዮሳፍጥ ልጅ የናሜሲ ልጅ የሆነውን ኢዩን ፈልግ፤ እርሱንም ከጓደኞቹ በመለየት ወደ ውስጥ አስገባው። 3 ይህን የወይራ ዘይት በራሱ ላይ
አፍስስበትና እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ‹አንተ በእስራኤል ላይ ንጉሥ እንድትሆን ቀብቼሃለሁ› ብለህ ንገረው አለው። ከዚያም በሩን ከፍተህ ከዚያ ስፍራ
ተነሥተህ ሸሽ፤ አትዘገይም።» 4 ስለዚህም ወጣቱ ነቢይ ወደ ሬማት ሄደ። 5 እዚያም በደረሰ ጊዜ የጦር አዛዦች ተቀምጠው ነበር። ወጣቱም ነቢይ እንዲህ
አለ፦ «ጌታዬ የምነግርህ መልእክት አለኝ» አለው። ኢዩም፦ «ለማናችን ነው የምትነግረው?» ሲል ጠየቀው። ወጣቱም ነቢይ፦ «የምናገረው ለአንተ ነው
ጌታዬ» ሲል መለሰለት። 6 ስለዚህ ኢዩ ተነሥቶ ወደ ቤት ገባ፤ ወጣቱ ነቢይም ዘይቱን በኢዩ ራስ ላይ አፈሰሰበትና እንዲህ አለው፦ «የእስራኤል አምላክ
እግዚአብሔር የሚናገረው ይህ ነው፦ ‹በእግዚአብሔር ሕዝብ በእስራኤል ላይ ንጉሥ እንድትሆን ቀብቼሃለሁ። 7 አንተም የአክዓብን የጌታህን ቤተ ሰብ መግደል
አለብህ፤ በዚህም በኤልዛቤል የተገደሉትን፣ የአገልጋዮቼን የነቢያቴንና የእግዚአብሔር አገልጋዮችን ደም በሙሉ እበቀላለሁ። 8 መላው የአክዓብ ቤተ ሰብና
ትውልዱ ሁሉ ይጠፋሉ፤ ከእርሱ ቤተ ሰብ ወንድ የሆነውን ማንኛውንም ባሪያም ሆነ ነጻ ሰው አጠፋለሁ። 9 የእስራኤል ነገሥታት በነበሩት በናባጥ ልጅ
በኢዮርብአምና በአኪያ ልጅ በባኦስ ቤተሰቦች ላይ ያደርግኹትን ሁሉ በአክዓብ ቤተ ሰብ ላይ እፈፅማለሁ። 10 ኤልዛቤል የመቀበር ዕድል እንኳ አታገኝም፤
የኤልዛቤልን ሬሳ በኢይዝራኤል ከተማ ውሾች ይበሉታል፤ ማንም አይቀብራትም።» ከዚያም ወጣቱ ነቢይ በሩን ከፍቶ ከዚያ ክፍል ወጥቶ ሸሸ። 11 ከዚያም
ኢዩ ወደ ንጉሡ አገልጋዮች በመጣ ጊዜ አንዱ፦ «ሁሉ ነገር ሰላም ነውን? ለመሆኑ ይህ እብድ ወደ አንተ ለምን መጣ?» ሲሉ ጠየቁት። ኢዩም «ሰውየውንም
ሆነ እርሱ የሚናገረውን እናንተ ታውቁታላችሁ» አላቸው። 12 እነርሱም «ይህ ሐሰት ነው። አንተ ንገረን» ሲሉ መለሱለት። ኢዩም፦ «በእስራኤል ላይ ንጉሥ
እንድትሆን እግዚአብሔር ቀብቼሃለሁ›› አለኝ ሲል አስረዳቸው። 13 ከዚያም እነርሱ ወዲያውኑ ልብሳቸውን እያወለቁ ኢዩ በሚራመድበት ደረጃ ላይ አነጠፉ።
በዚያም ላይ እንዲቆም አድርገው እምቢልታ ነፉ፤ ድምፃቸውንም ከፍ አድርገው «ኢዩ ንጉሥ ነው!» ሲሉ ጮኹ። 14 በዚህ ሁኔታ የኢዮሳፍጥ ልጅ የናሜሲ ልጅ
ኢዩ በንጉሥ ኢዮራም ላይ ሤራ ማካሄድ ጀመረ። ኢዮራም ከሶርያ ንጉሥ አዛሄል ጋር በሬማት ገለዓድና እስራኤል በሙሉ ሲከላከሉ፤ ነገር ግን በዚያን ጊዜ
በኢይዝራኤል ውስጥ በማገገም ላይ ነበር። 15 ስለዚህም ኢዩ የጦር መኮንኖች «እናንተ በእርግጥ ከእኔ ጋር ከሆናችሁ በኢይዝራኤል የሚኖረውን ሕዝብ
ለማስጠንቀቅ አንድ ወሬ ከሬማት ወጥቶ እንዳያመልጥ አድርጉ» አላቸው። 16 ከዚህም በኋላ ኢዩ በሠረገላው ላይ ተቀምጦ ወደ ኢይዝራኤል ገሠገሠ፤ በዚህ
ጊዜ ኢዮራም ገና ከቁስሉ አልዳነም ነበር፤ የይሁዳ ንጉሥ አካዝያስም ሊጠይቀው መጥቶ በዚያ ነበር። 17 በኢይዝራኤል ከተማ መጠበቂያ ግንብ ላይ
የነበረው ጠባቂ ኢዩና ተከታዩ ጭፍራ ሲመጡ ከሩቅ አይቶ «ሰዎች እየጋለቡ በቡድን ሲመጡ አያለሁ!» አለ። ኢዮራምም «አንድ ፈረሰኛ ልከህ የሚመጡትን
ሰዎች ሰላም ነውን? ብሎ እንዲጠይቅ አድርግ» አለው። 18 መልእክተኛውም ጋልቦ ሄዶ ኢዩን፦ «ንጉሡ አመጣጥህ በሰላም ነውን?» ይልሃል ሲል
ጠየቀው። ኢዩም፣ «አንተ ከሰላም ጋር ምን ግንኙነት አለህ? ይልቅስ ወደ ኋላ አልፈህ ተከተለኝ!» ሲል መለሰለት። ከዚያም ጠባቂው፦ «መልእክተኛው
በመምጣት ላይ ወዳለው ጭፍራ ደርሶአል፤ ነገር ግን ተመልሶ አልመጣም» ሲል ለንጉሡ ነገረው። 19 ሌላም መልእክተኛ ተልኮ ያንኑ ተመሳሳይ ጥያቄ ለኢዩ
አቀረበለት። ኢዩም፦ «አንተ ከሰላም ጋር ምን ግንኙነት አለህ? ይልቅስ ወደ ኋላ አልፈህ ተከተለኝ!» ሲል መለሰለት። 20 ጠባቂውም እንደገና፦ «እርሱ
ተገናኝቶአል ነገር ግን ተመልሶ አልመጣም» አለ። ‹ምክንያቱም የሠረገላ አነዳዱ እንደ እብድ ሰው እንደ ናሜሲ ልጅ እንደ ኢዩ ነው! ልክ ኢዩን ይመስላል!»
ሲል ተናገረ። 21 ስለዚህ ንጉሥ ኢዮራም፦ «ሠረገላ አዘጋጁልኝ» አለ። ሠረገላውም ተዘጋጅቶለት ኢዮራም የእስራኤል ንጉሥና የይሁዳ ንጉሥ አካዝያስ በየግል
ሠረገላችው እየጋለቡ ኢዩን ሊገናኙት ወጡ። እነርሱም ኢዩን የናቡቴ ርስት በነበረው እርሻ ላይ አገኙት። 22 ኢዮራምም፦ «ኢዩ ሆይ አመጣጥህ በሰላም ነውን?»
ሲል ጠየቀ። ኢዩም፦ «የእናትህ የኤልዛቤል የአመንዝራይቱ ጣዖትና ጥንቆላ ሥራ በዝቶ እያለ ምን ሰላም አለ?» ሲል መለሰለት። 23 በመሆኑም ኢዮራም፦
«አካዝያስ ሆይ! ይህ ክሕደት ነው!» እያለ ሠረገላውን መልሶ ሸሸ። 24 ኢዩ ቀስቱን ስቦ ባለው ኀይል ሁሉ ፍላጻውን ባስፈነጠረ ጊዜ ኢዮራምን ወግቶ
በትከሻዎቹ መካከል ወደ ልቡ ዘለቀ፤ ኢዮራምም ሞቶ በሠረገላው ውስጥ ወደቀ። 25 ኢዩም ቢድቃር ተብሎ የሚጠራውን የጦር አዛዥ «ሬሳውን አንሥተህ
በኢይዝራኤላዊው በናቡቴ ርስት በነበረው እርሻ ላይ ወርውረህ ጣለው አለው። እኔና አንተ የንጉሥ ኢዮራም አባት ከነበረው ከአክዓብ በስተኋላ እየጋለብን ስንሄድ
እግዚአብሔር በአክዓብ ላይ የተናገረውን ቃል አስታውስ። 26 ‹ትናንትና የናቡቴንና የልጆቹን መገደል አየሁ፤ በዚሁ እርሻ ላይ እንደምቀጣህ እምላለሁ› የሚል
ነበር።» ስለዚህ ኢዩ «እግዚአብሔር የተናገረው ቃል ይፈፀም ዘንድ የኢዮራምን ሬሳ አንሥተህ የናቡቴ ርስት በነበረው እርሻ ላይ በመወርወር ጣለው» ሲል
የጦር አዛዡን አዘዘው። 27 የይሁዳ ንጉሥ አካዝያስ ይህን ባየ ጊዜ በሠረገላው ላይ ተቀምጦ ወደ ቤት ሀጋን ከተማ ሸሸ። ኢዩ ተከታትሎ እያሳደደው «እርሱንም
ደግሞ በሠረገላው ውስጥ ግደሉት» አለ። እነርሱም ተከታትለው በኢዮርብዓም ከተማ አጠገብ በጉር በሠረገላው ሳለ ወጉት፤ አካዝያስም ወደ መጊዶ ከተማ
ሸሸ፤ በዚያም ሞተ። 28 አገልጋዮቹም ሬሳውን በሠረገላ ወደ ኢየሩሳሌም ወስደው በዳዊት ከተማ በሚገኘው በአባቶቹ መካነ መቃብር ቀበሩት። 29 አካዝያስ
የይሁዳ ንጉሥ የሆነው የእስራኤል ንጉሥ የአክዓብ ልጅ ኢዮራም በነገሠ በዐሥራ አንደኛው ዓመት ነበር። 30 ኢዩም ወደ ኢይዝራኤል በደረሰ ጊዜ፣ ኤልዛቤል
ይህን ሰምታ ዐይንዋን ተኳለች፤ ጠጉርዋንም ተሠርታ በመስኮት ትመለከት ነበር። 31 ኢዩም የቅጥሩን በር አልፎ ሲገባ «አንተ ዘምሪ! አንተ የጌታህ ገዳይ፣
እዚህ ደግሞ የመጣሃው በሰላም ነውን?» አለችው። 32 ኢዩ ቀና ብሎ ወደ ላይ በመመልከት፦ «ከእኔ ጋር የሚተባበር ማን ነው?» አለ። ቁጥራቸው ሁለት
ወይም ሦስት የቤተ መንግሥት ባለ ሥልጣኖች በመስኮት ወደ እርሱ ተመለከቱ። 33 ኢዩም «ኤልዛቤልን ወደ ታች ወርውሯት!» አላቸው። እነርሱም አንሥተው
በወረወሯት ጊዜ ደምዋ በግንቡና በፈረሶች ላይ ተረጨ ኢዩም ሬሳዋን በፈረስና ሠረገላው ረጋገጠ። 34 ኢዩም ወደ ቤተ መንግሥቱ ገብቶ ተመገበ፤ ጠጣም።
ከዚያም «የንጉሥ ልጅ ነችና ያችን የተረገመች ሴት ቅበሩአት» አለ። 35 ሊቀብሩዋት የሄዱ ሰዎች ግን ከራስ ቅልዋ፣ ከእግሮችዋና ከእጆችዋ መዳፍ በቀር
ምንም አላገኙም። 36 ይህንንም ለኢዩ በነገሩት ጊዜ ኢዩ እንዲህ አለ፤ «ይህ ሁሉ የተፈፀመው እግዚአብሔር በአገልጋዩ በቴስቢያዊው በኤልያስ አማካይነት
አስቀድሞ በተናገረው መሠረት ነው፤ ይኸውም ‹የኤልዛቤልን ሬሳ በኢይዝራኤል ውሾች ይበሉታል። 37 ከሬሳውም የሚተርፈው እንደ ፍግ በዚያ ይበተናል፤
ስለዚህም ማንም እርሷነቷን ለየቶ በማወቅ፦ ይህች ኤልዛቤል ናት ሊል አይችልም።»

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Kings 9:1

የነቢያት ልጆች
ይህ የነቢያት ስብስብ ማለት እንጂ፣ የነቢያት ልጆች ነበሩ ማለት አይደለም 2 ነገሥት 2፥3 ላይ ያለውን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የነቢያት ስብስብ››

በእጅህ
‹‹በእጅህ›› የሚለው ሐረግ ማሰሮውን ይዞ የሚሄደው እርሱ መሆኑን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ይዘህ››

ሬማት ዘገለዓድ
ይህን የከተማ ስም፣ 2 ነገሥት 8፥28 ላይ ያለውን በተረጐምህበት መንገድ ተርጕመው።

የናምሲ የልጅ ልጅ የኢዮሣፍጥ ልጅ ኢዩ
ይህ ማለት ኢዮሣፍጥ የኢዩ አባት ነበረ፤ ናምሲ የኢዮሣፍጥ አባት ነበረ ማለት ነው።

ከጓደኞቹ
ይህ ከኢዩ ጋር የተቀመጡ ሰዎችን ያመለክታል።

አስገባው
‹‹ከእርሱ ጋር ሂድ›› ወይም፣ ‹‹ውሰደው››

ወደ እልፍኝ
‹‹ወደ ጓዳ››

2 Kings 9:4

እነሆ
ጸሐፊው፣ ‹‹እነሆ›› በተሰኘው ቃል የተጠቀመው ቀጥሎ ላለው ትኩረት ለመሳብ ነው። ይህን ለማለት በቋንቋህ ሌላ መንገድ ካለ ተጠቀምበት።

የሰራዊቱ ጦር መኰንኖች በአንድነት ተቀምጠው ነበር
ኢዩ ከጦር መኰንኖቹ ጋር ተቀምጦ ነበር። በቋንቋህ እንደዚያ ማድረግ አስፈላጊ ከሆነ የታሪኩ ፍሰት ውስጥ ኢዩን ማስተዋወቅ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ኢዩና ሌሎች የጦር መኰንኖች አብረው ተቀምጠው ነበር››

2 Kings 9:7

አጠቃላይ መረጃ
ወጣቱ ነቢይ የእስራኤል ንጉሥ እንዲሆን ከቀባው ኢዩ ጋር እየተነጋገረ ነው።

የአገልጋዮቼን የነቢያትን ደም እንዲሁም የያህዌን አገልጋዮች ደም እበቀል ዘንድ
እዚህ ላይ፣ የነቢያትና የአገልጋዮች፣ ‹‹ደም›› ሞታቸውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የአገልጋዮቼ የነቢያትንና የያህዌን አገልጋዮች መገደል ለመበቀል›› ወይም፣ ‹‹ስለ አገልጋዮቼ ነቢያትና ስለ ያህዌ አገልጋዮች ሞት እንድቀጣቸው››

ደም
ውስጠ ታዋቂ የሆነውን ግሥ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ደማቸውን እንድበቀል››

በኤልዛቤል እጅ የተገደሉትን
ይህን በሌላ መልክ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ኤልዛቤል አገልጋዮቿን በማዘዝ ያስገደለቻቸውን›› ወይም፣ ‹‹በኤልዛቤል ትእዛዝ የተገደሉትን››

በኤልዛቤል እጅ
ይህ ማለት በኤልዛቤል ትእዛዝ የተገደሉ ሰዎች ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በኤዛቤል ትእዛዝ›› ወይም፣ ‹‹ኤልዛቤል ስላዘዘች››

የአክዓብ ቤት በሙሉ ይጠፋል፤ ማንኛውንም የአክዓብ ወንድ ልጅ እቆርጣለሁ።
‹‹እቆርጣለሁ›› አገድላለሁ ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የአክዓብ ቤት ሁሉ ይጠፋል፤ በቤተ ሰቡ ያለ ማንኛውም ወንድ ልጅ እንዲገደል አደርጋለሁ›› ወይም፣ ‹‹ማንኛውንም ወንድ ልጅ ጨምሮ የአክዓብ ቤተ ሰብ ሁሉ ይጠፋል››

ማንኛውም ወንድ ልጅ
ሐረጉ ጥቅም ላይ የዋለው ማንኛውንም ወንድ ለማመልከት ነው፤ ‹‹ልጅ›› የሚለው ግን ልጆችንም እንደሚጨምር ግልጽ አድርጐታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ማንኛውም ወንድ››

2 Kings 9:9

አጠቃላይ መረጃ
ወጣቱ ነቢይ የእስራኤል ንጉሥ እንዲሆን ለቀባው ለኢዩ የያህዌን ቃል መናገሩን ቀጥሏል።

የአክዓብን ቤት እንደ... አደርጋለሁ
ይህ ማለት ኢዮሮብዓምን ባኦስንና ቤተ ሰቡን እንዳጠፉ ሁሉ ያህዌ አክዓብንና ቤተ ሰቡን ያጠፋል ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹... እንዳስወገድሁ የአክዓብንም ቤት አስወግዳለሁ››

ቤት
ይህ ቃል ሦስት ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል። በእያንዳንዱ ጊዜ፣ ‹‹ቤት የሚለው ስሙ የተጠቀሰው ሰው፣ ‹‹ቤተሰብ›› ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የ... ቤተ ሰብ››

ናባጥ... አኪያም
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው። ናባጥ የሚለውን ስም 2 ነገሥት 3፥3 ላይ ያለውን እንደ ተረጐምህ ተርጕመው።

ኤልዛቤልን... ውሾች ይበሏታል።
ይህ ማለት የሞተ አካሏን ውሾች ይበሉታል ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የኤልዛቤልን ሬሳ ውሾች ይበሉታል››

2 Kings 9:11

የጌታው አገልጋዮች
ይህ ንጉሥ አክዓብን የሚያገለግሉ ሌሎች ባለ ሥልጣኖች ያመለክታል።

ይህ እብድ
‹‹ወፈፌ ሰው››

ሰውየውንም ሆነ የሚናገረውን ታውቃላችሁ
ኢዩ እርሱ ወጣት ነቢይ እንደ ሆነና ወጣት ነቢያት ደግሞ በአጠቃላይ ስለሚናገሩት ነገር ሁሉም እንደሚያውቁ ይናገራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንደ እርሱ ያሉ ወጣት ነቢያት የሚናገሩትን ታውቃላችሁ››

ንገረን
‹‹እርሱ ያለውን ንገረን››

እንዲህና እንዲህ አለኝ
‹‹ስለ ተለያዩ ነገሮች ነገረኝ››

ልብሳቸውን እያወለቁ በሚራመድበት ደረጃ ላይ አነጠፉ
በዚህ ባሕል መሠረት እግሮቹ ቆሻሻውን መሬት እንዳይረግጡ ልብሶችን አውልቆ እግር ሥር ማንጠፍ ለንጉሡ ያላቸውን ክብር መግለጫ መንገድ ነበር።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከላይ ያለውን ልብሳቸውን እያወለቁ እንዲራመድበት ኢዩ ፊት አኖሩ››

መለከትም ነፍተው እንዲህ አሉ
ሁሉም ሰው መለከት አይነፋም። መለከት የሚነፋው አንድ ሰው ብቻ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከእነርሱ አንዱ መለከት ነፍቶ እንዲህ አለ››

2 Kings 9:14

ናሜሲ
የዚህን ሰው ስም 2 ነገሥት 9፥2 እንደ ተረጐምህ ተርጒመው።

አሁን ኢዮራም
ይህ ቃል እዚህ ጥቅም ላይ የዋለው የዋናውን ታሪክ ፍሰት ገታ ለማድረግ ነው። ኢዮራም እንዴት እንደ ቆሰለና ለማገገም ወደ ኢይዝራኤል እንደ ሄደ ጸሐፊው የታሪኩን ዳራ መረጃ ያቀርባል።

እስራኤል ሁሉ
ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን ሰራዊት ብቻ እንጂ፣ በእስራኤል የሚኖረውን ሁሉ አይደለም። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እርሱና ሰራዊቱ›› ወይም፣ ‹‹እርሱና የእስራኤል ሰራዊት››

ለማገገም
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ቁስሉ እንዲሻለው››

ሶርያውያን ካደረሱበት ቁስል
ይህ ማለት የቆሰለው ከሶርያውያን ጋር ሲዋጋ ነበር ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከሶርያ ሰራዊት ጋር ሲዋጋ ኢዮራም ከደረሰበት ቁስል››

በሶርያ ንጉሥ አዛሄል ላይ
ይህ የሚያመለክተው አዛሄልና ሰራዊቱን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በሶርያ ንጉሥ በአዛሄልና በሰራዊቱ››

አዛሄል
የዚህን ሰው ስም 2 ነገሥት 8፥8 ላይ እንደ ተረጐምኸው ተርጒመው።

ኢዩ ለኢዮራም አገልጋዮች እንዲህ ከሆነ
ይህ የሚናገረው ከኢዮራም ጋር በሬማት ዘገለዓድ ስለ ነበሩት ባለ ሥልጣኖች ነው።

እንግዲህ ሐሳባችሁ እንዲህ ሆነ
‹‹ከእኔ ጋር የምትስማሙ ከሆነ›› ኢዩ ይህን ያለው ንጉሥ ለመሆንና ያለውን ሐሳብ ሕዝቡ ይደግፉ እንደ ሆነ ለማመልከት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በእውነት ንጉሣችሁ እንድሆን የምትፈልጉ ከሆነ››

ይህን ነገር ወደ ኢይዝራኤል ሄዶ እንዳይናገር
ይህ የሚያመለክተው የኢዩን ዕቅድ ለኢዮራምና ለሰራዊት መናገርን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በኢይዝራኤል ያለውን ንጉሥ ኢዮራምና ሰራዊቱን ለማስጠንቀቅ››

አሁን አካዝያስ
እዚህ ላይ፣ ‹‹አሁን›› የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው የዋናውን ታሪክ ፍሰት ገታ ለማድረግ ነው። እዚህ ላይ ጸሐፊው አካዝያስ ኢዮራምን ስለ ጐበኘበት ምክንያት ዳራ የሚሆን መረጃ ይሰጣል።

2 Kings 9:17

ማማ ላይ ያቆመው ጠባቂ
ዘበኛ

የኢዩ ወታደሮች መቅረባቸውን ከሩቅ አይቶ
‹‹ኢዮና ወታደሮቹ ገና ሩቅ እያሉ››

ከሰላም ጋር ምን ጉዳይ አለህ?
ኢዩ ይህን ጥያቄ ያቀረበው ለሰላም ቢሆን ወይም ባይሆን፣ የእርሱ ጉዳይ እንዳይደለ ለመልእክተኛው ለመናገር ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለሰላም መምጣት አለመምጣቴ የአንተ ጉዳይ አይደለም›› ወይም፣ ‹‹ለሰላም መምጣት አለመምጣቴን ማወቅ የአንተ ጉዳይ አይደለም››

መልእክተኛው ከእነርሱ ዘንድ ደርሶአል፤ ነገር ግን ተመልሶ አልመጣም
ንጉሡ ላቀረበው ጥያቄ መልስ ይዞ መልእክተኛው ተመልሶ አለመምጣቱን ለንጉሥ ኢዮራም ተናገረ።

2 Kings 9:19

ስለዚህ ንጉሡ ሌላ ፈረሰኛ ላከ
‹‹ስለዚህ ንጉሥ ኢዮራም ከኢዩና ከሰራዊቱ ጋር እንዲገናኝ ሁለተኛ ፈረሰኛ ላከ።››

ሁለተኛ ሰው
ቀደም ሲል ኢዮራም አንድ ሰው ልኮ ነበር። ይኸኛው ቀጣዩ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሌላ ሰው››

ከሰላም ጋር ምን ጉዳይ አለህ?
ኢዩ ይህን ጥያቄ ያቀረበው የመጣው ለሰላም ቢሆን ወይም ባይሆን፣ ያ የእርሱ ጉዳይ አለመሆኑን ለመልእክተኛው ለመንገር ነው። ይህን በዐረፍተ ነገር መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለሰላም መምጣት አለመምጣቴ የአንተ ጉዳይ አይደለም››

ሠረገላ አነዳዱ ልክ እንደ ናሜሲ ልጅ እንደ ኢዩ አነዳድ ነው
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሠረገላው ነጂ አነዳድ የኖሜሲ ልጅ የኢዩን አነዳድ ይመስላል››

2 Kings 9:21

እያንዳንዱ በሠረገላው
‹‹እያንዳንዱ በገዛ ራሱ ሠረገላ››

... አገኙት
‹‹ኢዩ የነበረበት ቦታ ሲደርሱ››

ናቡቴ
ይህ የሰው ስም ነው።

ኢይዝራኤላዊው
ይህ ከኢይዝራኤል የሆነ ሰው ማለት ነው።

የእናትህ የኤልዛቤል የጣዖት አምልኮና መተት እንዲህ በዝቶ እያለ ምን ሰላም አለ?
ኢዩን ይህን የጠየቀው የመጣው ለሰላም እንዳይደለ ለማመልከት ነው። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እናትህ ኤልዛቤል መተትና ግል ሙትናዋ እንዲሁም ጣዖት አምልኮ በዝቶ እያለ ሰላም ሊኖር አይችልም››

2 Kings 9:23

ሰረገላውን አዙሮ ሸሸ
‹‹ሰረገላውን ወደ ኃላ አዙሮ ሸሸ››

ክዳት
ማታለል ወይም ማሳሳት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በሙሉ ኀይሉ
‹‹በኀይሉ ሁሉ›› ወይም፣ ‹‹በብርታቱ ሁሉ››

ሠረገላው ውስጥ ዘፍ ብሎ ወደቀ
ኢዮራም በቀስት ተወግቶ ሞተ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ኢዮራም ሠረገላው ውስጥ ሞቶ ወደቀ››

2 Kings 9:25

ቢድቃር
ይህ የሰው ስም ነው።

አንሣውና ጣለው
‹‹ሬሳውን አንሥተህ ጣል›› ወይም፣ ‹‹በድኑን አንሣና ጣል››

አስታውስ
‹‹አትርሳ››

አባቱን አክዓብን
ይህ ማለት የጋለቡት ከአክዓብ ሰረገላ ተከትለው ነበር ማለት ነው።

የናቡቴንና የልጆቹን ደም
እዚህ ላይ፣ ‹‹ደም›› የሚያመለክተው ግድያን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የናቡቴንና የልጆቹን መገደል››

እንድትከፍል አደርግሃለሁ
ይህ ማለት ለፈጸመው ክፉ ነገር ለአክዓብ ተገቢ ቅጣት ይሰጣል ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ላደረግኸው ክፉ ነገር የሚገባህን እሰጥሃለሁ››

አንሣውና በዚሁ እርሻ ውስጥ ጣለው
‹‹ሬሳውን አንሥተህ ናቡቴ እርሻ ውስጥ ጣለው››

በያህዌ ቃል መሠረት
‹‹የተነገረን ትንቢት እንዲፈጸም››

2 Kings 9:27

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ኢዩ ኢዮራምን ከገደለ በኃላ የይሁዳ ንገሥ አካዝያስ ላይ የሆነ ነው።

ይህን ሲያይ
‹‹ኢዮራም ላይ የሆነውን ሲያይ››

ቤት ሀጋን... ጉር... ይብለዓም... መጊዶ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው።

በጉር ዐቀበት
‹‹ዐቀበት›› ወደ ጉር ሲሄዱ የሚወጡት ኮረብታ ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ወደ ጉር በሚወስደው መንገድ››

ከአባቶቹ
‹‹ከጥንት ወላጆቹ››

2 Kings 9:29

የአክዓብ ልጅ ኢዮራም በነገሠ በዐሥራ አንደኛው ዓመት
የአሁኑ የእስራኤል ንጉሥ ስንት ዓመት እንደ ገዛ በማመልከት አካዝያስ መግዛት የጀመረበትን ጊዜ ያሳያል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የአክዓብ ልጅ ኢዮራም የእስራኤል ንጉሥ በሆነ በዐሥራ አንደኛው ዓመት››

ዐሥራ አንደኛ ዓመት
‹‹ከጥንት ወላጆቹ››

2 Kings 9:30

ዐይኗን ተኳኩላ፤ ጠጉራንም አሰማምራ
‹‹ዐይኗን ተኳኩላ፣ ጠጉርዋን ተሠርታ››

ጌታህን የገደልህ አንተ ዘምሪ የመጣኸው በሰላም ነውን?
ኤልዛቤል ይህን የጠየቀችው ኢዩ የመጣው በሰላም እንዳልሆነ ለማመልከት ነው። ይህን በዐረፍተ ነገር መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አንተ ጌታህን የገደልህ ዘምሪ፣ የመጣኸው ለሰላም አይደለም››

ጌታህን የገደልህ አንተ ዘምሪ
እዚህ ላይ ኤልዛቤል፣ ‹‹ዘምሪ›› ያለችው ነፍሰ ገዳይ መሆኑን ለማመልከት ነው። ዘምሪ ንጉሥ መሆን ስለ ፈለገ፣ የእስራኤልን ንጉሥ የገደለ የጦር አዛዥ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ዘምሪ ጌታውን እንደ ገደለ አንተም ጌታህን የገደልህ››

ዘምሪ
ይህ የሰው ስም ነው።

አብሮኝ ያለ ማነው?
‹‹አብሮ መሆን›› ታማኝና ተባባሪ መሆን ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለእኔ ታማኝ የሆነ››

2 Kings 9:33

ወደ ታች ወርውሩአት
ኢዩ ኤልዛቤልን በመስኮት እንዲወረውሩአት ለጃንደረቦቹ እየነገረ ነው።

ኢዩ ረገጣት
ይህ ማለት ፈረሶቹ ረጋገጡአት ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰረገላውን ይስቡ የነበሩ የኢዩ ፈረሶች በኮቴአቸው ረጋገጡአት››

አሁን ተመልከቱ
‹‹አሁን ተመልከቱ›› ማለት ቦታው ተለይቶ ሚነገረው ልብ በሉ ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አሁን ሂዱ››

ምንም ቢሆን የንጉሥ ልጅ ናትና
x

2 Kings 9:35

ሌላ ያገኙት አልነበረም
‹‹ከአካቧ የቀረ አልነበረም›› ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያገኙት ከአካቧ የተረፈ››

ከእጇ መዳፍ በቀር
መዳፍ የእጅ ውስጥ ክፍል ነው።

ቴስቢያዊው
ይህ ከቴስቢ የሆነ ሰው ማለት ነው። 2 ነገሥት 1፥3 ላይ ይህን እንዴት እንደተረጐምኸው ተመልከት።

የኤልዛቤል ሥጋ እርሻ ውስጥ እንደ ፍግ ስለሚሆን ማንም ይህች ኤልዛቤል ናት አይልም
ይህ ፍግ እርሻ ውስጥ እንደሚበታተን የኤልዛቤልም ሥጋ ቁርጥራጭ እርሻ ውስጥ መበታተኑን ይናገራል። ሥጋዋ በጣም ስለሚበጣጠስ ማንም ሰብሰቦ መቅበር አይችልም። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የኤልዛቤል ሥጋ እንደ ፍግ እርሻ ውስጥ ይበታተናል... ስለዚህ እርሷ መሆንዋን ማንም ማወቅ አይችልም››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ፍግ ለማዳበሪያ የሚውል ነገር	ማንም፣ ‹‹ይህች ኤልዛቤል ናት›› ሊል አይችልም ‹‹ማንም እርሷ መሆንዋን አያውቅም›› ወይም፣ ‹‹ማንም ኤልዛቤል ናት ብሎ መናገር አይችልም››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 10

1 በዚህ ጊዜ የአክዓብ ሰባ ትውልድ በሰማርያ ይገኝ ነበር። ኢዩ ደብዳቤ ጽፎ አንዳንድ ቅጂ ለከተማዪቱ ገዢዎች፣ የአገር ሽማግሌዎችና የአክዓብ ትውልድ
ጠባቂዎች ሁሉ ላከ። ደብዳቤውም እንዲህ ይላል፦ 2 «እናንተ ለንጉሡ ትውልድ፣ ፈረሶችና ሠረገሎች የጦር መሣሪያዎችና የተመሸጉ ከተሞች በእናንተ
በእጃችሁ ለሚገኙ ሁሉ ኃላፊዎች ናችሁ። እንግዲህ ይህ ደብዳቤ እንደ ደረሳችሁ ወዲያውኑ፦ 3 ከንጉሡ ትውልድ የተሻለውን አንዱን መርጣችሁ በአባቱ ዙፋን
አንግሡት፤ ለእርሱም ለሥርወ መንግሥቱ ተዋጉለት!» የሚል ነበር። 4 ነገር ግን እነርሱም በፍርሃት ተሸብረው «ንጉሥ ኢዮራምና ንጉሥ አካዝያስ ሊቋቋሙት
ያልቻሉትን እኛ እንዴት ኢዩን ልንቋቋመው እንችላለን?» አሉ። 5 ስለዚህም የቤተ መንግሥቱ ጎላፊና የከተማዪቱ ገዢ ከታወቁ የአገር ሽማግሌዎችና ከአሳዳጊ
ሞግዚቶች ጋር በመተባበር ለኢዩ «እኛ አገልጋዮችህ ነን፤ አንተ የምታዘንን ሁሉ ለመፈጸም ዝግጁዎች ነን፤ እኛ ማንንም አናነግሥም፤ አንተ መልካም መስሎ
የታየህን አድርግ» ሲሉ መልእክት ላኩ። 6 ኢዩም፦ «እናንተ ከእኔ ጋር ከተባበራችሁና ትእዛዜንም ለመፈፀም ዝግጁዎች ከሆናችሁ ነገ በዚህ ጊዜ የንጉሥ
አክዓብን ዘሮች ሁሉ ራሶቻቸውን ቆርጣችሁ ወደ ኢይዝራኤል ይዛችሁልኝ እንድትመ›ጡ› ሲል ሌላ ደብዳቤ ጻፈላቸው። ሰባውም የንጉሥ አክዓብ ትውልድ
በታወቁ የአገር ሽማግሌዎች ጥበቃ ሥር ነበሩ። 7 የኢዩ ደብዳቤ እንደ ደረሳቸው የሰማርያ መሪዎች ሰባውንም የአክዓብ ተወላጆች በሙሉ ገደሉ፤ ራሶቻቸውንም
በመቁረጥ በቅርጫት ሞልተው በኢይዝራኤል ወደ ነበረው ወደ ኢዩ ላኩለት። 8 ኢዩም የአክዓብ ትውልድ ራሶች ተቆርጠው መምጣታቸውን በሰማ ጊዜ
በከተማይቱ ቅጥር በር በሁለት ረድፍ ተከምረው እስከ ተከታዩ ቀን ጠዋት ድረስ እንዲቆዩ ትእዛዝ ሰጠ። 9 በማግስቱ ማለዳ ላይ ኢዩ ወደ ከተማይቱ ቅጥር በር
ሄዶ በዚያ ለተሰበሰቡት ሕዝብ እንዲህ ሲል ተናገረ፤ «በንጉሥ ኢዮራም ላይ በማሤር የገደልኩት እኔ ነበርኩ፤ ስለዚህም እናንተ በዚያ ጉዳይ አትጠየቁበትም፤
ነገር ግን እነዚህን ሁሉ የገደለ ማነው? 10 ይህም ሁሉ እግዚአብሔር ስለ አክዓብ ትውልድ የተናገረው ቃል እውነት መሆኑን ያስረዳል፤ እግዚአብሔር በአገልጋዩ
በነቢዩ ኤልያስ አማካይነት የተናገረውን ቃል ፈፅሞታል።» 11 ከዚህም በኋላ ኢዩ በኢይዝራኤል የሚኖሩትን ሌሎቹን የአክዓብን ዘመዶችና ባለሥልጣናት
የነበሩትን እንዲሁም የቅርብ ወዳጆቹንና ካህናቱን አንድም ሳይቀር ሁሉንም ገደለ። 12 ኢዩ ከኢይዝራኤል ተነሥቶ ወደ ሰማርያ ሄደ፤ በመንገድ ሳለም «የእረኞች
ሰፈር» ተብሎ በሚጠራው ቦታ ሲደርስ፦ 13 ከሚቹ የይሁዳ ንጉሥ አካዝያስ ዘመዶች መካከል ጥቂቶቹን አግኝቶ «እናንተ እነማን ናችሁ?» ሲል ጠየቀ።
እነርሱም ‹እኛ የአካዝያስ ዘመዶች ነን፤ አሁንም የንግሥት ኤልዛቤልን ልጆችና የቀሩትንም ንጉሣውያን ቤተ ሰብ እጅ ለመንሣት ወደ ኢይዝራኤል መሄዳችን
ነው» ሲሉ መለሱለት። 14 ኢዩም «እነዚህን ሰዎች ከነሕይወታቸው ያዙአቸው!» ሲል ለጭፍሮቹ ትእዛዝ ሰጠ፤ ጭፍሮቹም ያዙአቸው፤ ኢዩም በዚያው በቤት
ኤክድ አጠገብ ገደላቸው። ብዛታቸውም በሙሉ አርባ ሁለት ሲሆን ከእነርሱ አንድ እንኳ በሕይወት አልተረፈም። 15 ኢዩ ተነሥቶ እንደገና ጉዞ ቀጠለ፤ በመንገድ
ሳለም የሬካብን ልጅ ኢዮናዳብን አገኘ፤ ኢዩም ሰላምታ ከሰጠው በኋላ «የእኔ ልብ ከአንተ ጋር እንደ ሆነ የአንተ ልብ ከእኔ ጋር ነውን?» ሲል ጠየቀው።
ኢዮናዳብም «አዎን ከአንተ ጋር ነው» ሲል መለሰለት። ኢዩም «እንግዲያውስ ጨብጠኝ» ሲል መለሰለት፤ እጅ ለእጅ ተያይዘው ኢዩ ደግፎት በሠረገላው ላይ
አስቀመጠው። 16 «ከእኔ ጋር ሆነህ እኔ ለእግዚአብሔር ምን ያህል ታማኝ እንደ ሆንኩ ራስህ ተመልከት» አለው፤ አብረውም እየጋለቡ ወደ ሰማርያ ሄዱ። 17
ወደ ሰማርያ በደረሱ ጊዜ ኢዩ አንድም ሳያስቀር በሰማርያ ያሉትን የአክዓብን ዘመዶች በሙሉ ፈጀ፤ ይህም ሁሉ የሆነው እግዚአብሔር በነቢዩ ኤልያስ አማካይነት
በተናገረው ቃል መሠረት ነበር። 18 ከዚያም ኢዩ የሰማርያን ሕዝብ በአንድነት ጠርቶ እንዲህ አላቸው፤ «ንጉሥ አክዓብ ባዓልን ያገለገለው በመጠኑ ነበር፤ እኔ
ግን ከእርሱ ይበልጥ ላገለግለው እፈልጋለሁ፤ 19 ስለዚህም የባዓልን ነቢያት በሙሉ ባዓልን የሚያመልኩትንና ካህናቱን ጭምር በአንድነት ጠርታችሁ
ሰብስቡልኝ፤ በምንም ምክንያት የሚቀር አይኑር፤ እኔ ለባዓል ታላቅ መሥዋዕት ስለማቀርብ በዚያ የማይገኝ ማንም ሰው ቢኖር በሕይወት አይኖርም።» ይህም
ሁሉ ባዓልን የሚያመልኩትን ሁሉ ለመግደል ኢዩ ያቀደው የተንኮል ዘዴ ነበር። 20 ከዚህም በኋላ ኢዩ «ባዓል ተብሎ ለሚጠራው ጣዖት ክብረ በዓል ይደረግ!»
ሲል ትእዛዝ ሰጠ፤ ይህም በዐዋጅ ተነገረ። 21 ኢዩም በእስራኤል ምድርና ባዓልን ለሚያመልኩ ሁሉ መልእክት ላከ። ማንም ከጫፍ እስከ ጫፍ ሳይመጣ የቀረ
አልነበረም፤ ሁሉም ወደ ባዓል ቤተ መቅደስ ገብተው ዳር እስከ ዳር ሞሉት። 22 ከዚያ ኢዩ የተቀደሱ አልባሳት ጎላፊ የሆነው ካህን አልባሳትን ሁሉ አውጥቶ
ለባዓል አምላኪዎች እንዲያመጣላቸው አዘዘ። እንደታዘዘውም አልባሳቱን አመጣላቸው። 23 ስለዚህም ኢዩ ራሱ ከሬካብ ልጅ ከኢዮናዳብ ጋር አብሮ ወደ ባዓል
ቤተ መቅደሱ ገባ፤ በዚያም ለሕዝቡ በዚህ የሚገኙት የባዓል አምላኪዎች ብቻ መሆናቸውንና እግዚአብሔርን የሚያመልክ አንድም አለመኖሩን በሚገባ
አረጋግጡ ሲል ተናገረ። 24 ከዚያም እርሱና ኢዮናዳብ ለባዓል ልዩ ልዩ መሥዋዕትንና የሚቃጠል መሥዋዕትን ለማቅረብ ሄዱ። ኢዩም በባዓል ቤተ መቅደሱ
ዙሪያ ሰማኒያ ወታደሮች በማሰለፍ እነዚህን ሁሉ ሰዎች እንድትገድሉ፣ ከእነርሱ አንድ እንኳ የሚያመልጥ ሰው ቢኖር በዚያ ሰው ምትክ እርሱ ራሱ ይገደላል ሲል
መመሪያ ሰጥቶአቸው ነበር። 25 ኢዩ መሥዋዕቱን አቅርቦ እንዳበቃ ወዲያውኑ ለጠባቂዎችና ለአዛዡ፦ ሂዱና ማንም ሰው እንዳያመልጥ ግደሉአቸው አለ።
እነርሱም በሰይፍ ስለት ሁሉንም ገደሉአቸው፤ ሬሳቸውንም ሁሉ እየጎተቱ ወደ ውጪ ጣሉ፤ ጠባቂና የጦር አዛዦቹ ወደ ባዓል ቤተ መቅደሱ ውስጠኛ ክፍል ገቡ።
26 ከዚያም በባዓል ቤተ መቅደስ የነበረውን የድንጋይ ዐምዶች ወደ ውጪ አውጥተው በእሳት አቃጠሉት። 27 ከዚያም የባዓል አምላኪዎቹን አጸድ አፍርሰው
የባዓልን ቤተ መቅደስ አጠፉ፤ እስከዛሬ ድረስ ቤተ መቅደሱንም መጸዳጃ እንዲሆን አደረጉት። 28 ኢዩ በእስራኤል የነበረውን የባዓልን አምልኮ ያስወገደው
በዚህ ዓይነት ነበር። 29 ነገር ግን ኢዩ እስራኤልን ወደ ኃጢአት የመራውን የናባጥ ልጅ የንጉሥ ኢዮርብዓምን፣ በቤተልና በዳን፣ የወርቅ ጥጃ የጣዖት ማምለኪያ
ምስል ያቆመበትን የኃጢአት መንገድ አልተከተልም። 30 ስለዚህም እግዚአብሔር ኢዩን፦ በአክዓብ ትውልድ ሁሉ ላይ ልታደርግ የሚገባህን በዐይኖቼ ፊት
ትክክል የሆነውን ፈጽመሃል፤ ከዚህም የተነሣ የአንተ ትውልድ እስከ አራት ትውልድ ድረስ በእስራኤል ላይ እንደሚነግሡ የተስፋ ቃል እስጥሃለሁ አለው። 31
ኢዩ ግን ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር ሕግ በፍጹም ልቡ ታዛዥ ሆኖ አልተገኘም፤ እርሱም እስራኤልን ወደ ኃጢአት ከመራበት ከኢዮርብዓም ኃጢአት
አልተመለሰም። 32 በዚያም ዘመን እግዚብሔር የእስራኤልን ግዛት እንዲቀነስ አደረገ፤ የሶርያ ንጉሥ አዛሄል እስራኤልን ድል ነሥቶ የእስራኤልን ግዛት ድንበሮች
ያዘ። 33 እርሱም የያዘው ግዛት ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምሥራቅ በስተ ደቡብ በኩል ከአርኖን ወንዝ በላይ እስከምትገኘው እስከ አሮዔር ከተማ የሚደርስ ሲሆን
ይህም የጋድ የቶቤልና በምሥራቅ የሚገኘው የምናሴ ነገድ እኩሌታ ይኖሩባቸው የነበሩትን ሸለቆ የገለዓድንና የባሳንን ግዛቶች ያጠቃልላል። 34 ኢዩ ያደረገው
ሌላው ነገርና የጀግንነት ሥራውም ሁሉ በእስራኤል ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኝ የለምን? 35 ከዚህም በኋላ ኢዩ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤
በሰማርያም ተቀበረ። በእርሱም ፈንታ ተተክቶ ልጁ ኢዮአካዝ ነገሠ። 36 ኢዩም በሰማርያ እስራኤልን ለሃያ ስምንት ዓመት ገዛ።

---

2 Kings 10:1

ሰባ ወንዶች ልጆች
‹‹70 ወንዶች ልጆች››

ኢዩ ደብዳቤ ጽፎ... ወደ ሰማርያ ላከ
ይህ ማለት ኢዩ ደብዳቤ የሚያደርስ መላእክተኛ ላከ ማለት ነው። አማራጭ
ትርጕም፣ ‹‹ኢዩ ደብዳቤ ጻፈ፤ ወደ ሰማርያ እንዲያደርሰውም መልእክተኛ
ላከ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንዲህ የሚል ነበር... ‹‹የጌታችሁ››
‹‹ደብዳቤው፣ ‹‹የጌታችሁ›› የሚል ነበር

በአባቱ ዙፋን አስቀምጡት
ዙፋን ላይ መቀመጥ ንጉሥ መሆን ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በአባቱ ቦታ ንጉሥ አድርጉት››

ስለ ጌታችሁ ቤት
‹‹ስለ ጌታችሁ ዘሮች›› - ንጉሥ እንዲሆን የመረጡት ሰው የአክዓብ ወራሽ ተብሏል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለጌታችሁ ዘር ተዋጉ›› ወይም፣ ‹‹ተዋጉለት››

2 Kings 10:4

እነርሱ ግን እጅግ ፈርተው ነበር
‹‹በጣም ፈሩ››

ሁለት ነገሥታት
‹‹ሁለት ነገሥታት፣ ኢዮራምና አካዝያስ››

ኢዩ ፊት መቆም አልቻሉም
እዚህ ላይ፣ ‹‹መቆም›› ችግሩን መቋቋም ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ኢዩን መቋቋም አይችሉም›› ወይም፣ ‹‹ኢዩን መዋጋት አይችሉም››

እኛ እንዴት ልንቋቋመው እንችላለን?
ሰዎቹ ይህን ያሉት ኢዩን እንደማይችሉት ለመናገር ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እኛም ብንሆን እርሱን መቋቋም አንችልም›› ወይም፣ ‹‹እኛም አንችለውም››

የከተማዪቱ ገዥ
‹‹የከተማዪቱ ከንቲባ›› እዚህ ላይ፣ ‹‹ገዥ›› ሥልጣንና ኀላፊነት ያለው ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በከተማዋ ላይ ኀላፊ የነበረው ሰው››

የልጆቹ ሞግዚቶች
ይህ ማለት የንጉሡን ልጆች ያሳደጉ ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የንጉሡን ልጆች ያሳደጉ››

በዐይንህ ፊት ደስ የሚያሰኝህን አድርግ
እዚህ ላይ፣ የኢዩ፣ ‹‹ዐይን›› የእርሱን፣ ‹‹ፊት›› ያመለክታል፤ የእርሱ ፊት እርሱ የሚያስበውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ትክክል የመሰለህን አድርግ›› ወይም፣ ‹‹መልካም መስሎ የታየህን አድርግ››

2 Kings 10:6

ደግሞ ጻፈላቸው
ኢዩራም አንድ ደብዳቤ ጽፎ ነበር፤ ይህ ሁለተኛው ነው አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እንደ ገና ደብዳቤ ጻፈላቸው›› ወይም፣ ‹‹ሌላ ደብዳቤ ጻፈላቸው››

የእኔ ወገን ከሆናችሁ
‹‹የአንድ ሰው ወገን መሆን›› ለእርሱ ታማኝ መሆንና ደጋፊው መሆን ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለእኔ ታማኝ ከሆናችሁ››

ስሙ
ሰምታቸሁ ታዘዙ

ለቃሌ
የኢዩ፣ ‹‹ቃል›› እርሱ የተናገረውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የምነግራችሁን››

ራሳቸውን ቆርጣችሁ... ወደ እኔ ኑ
የአክዓብን ልጆች ራሶች ቆርጠው ለኢዩ እንዲያመጡ ነው የተነገረው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ራሳቸውን ቆርጣችሁ አምጡልኝ››

የጌታችሁን ልጆች ራስ ቆርጣችሁ
ይህ የሚያመለክተው እነርሱን ገድሎ ራሳቸውን መቁረጥ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የጌታችሁን ልጆች ግደሉ፤ ራሳቸውንም ቁረጡ››

በቁጥር ሰባ... ሰባ ሰዎች
‹‹በቁጥር 70... 70 ሰዎች››

አሳዳጊዎቻቸው
ሲንከባከቧቸውና ሲያስተምሯቸው የነበሩ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሲያሳድጓቸው የነበሩ›› ወይም፣ ‹‹ሲንከባከቧቸው የነበሩ››

ወደ ኢዩ ላኳቸው
ይህ ማለት ቅርጫቶቹን ለኢዩ የሚያደርሱ ሰዎች ላኩ ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ወደ ኢዩ የሚያደርሱ ሰዎች ላኩ››

2 Kings 10:8

ከንጉሡ ልጆች
‹‹የአክዓብ ልጆች››

ኢዩ ወጥቶ ቆመ
‹‹ኢዩ ወደ ከተማው በር ወጥቶ ሰዎቹ ፊት ቆመ››

እናንተ ንጹሐን ናችሁ
ንጹህ የሆኑት ከምን እንደ ነበር መግለጽ ይቻላል። ምናልባትም 1)‹‹ኢዮራም ላይ በሆነው ንጹሐን ናችሁ›› ማለት ሊሆን ይችላል። ወይም 2) በኢዮራምና በቤተ ሰቡ ሞት ኃላፊነት የለባችሁም።›› ‹‹ኢዮራምና ቤተ ሰቡ ላይ ከደረሰው እናንተ ንጹሐን ናችሁ›› ማለት ሊሆን ይችላል።

እነሆ
ኢዩ ይህን ቃል የተጠቀመው ቀጥሎ ወደሚናገረው የሰዎቹን ትኩረት ለመሳብ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አድምጡ›› ወይም፣ ‹‹ቃሌን ስሙ››

እነዚህን ሁሉ ግን የፈጃቸው ማን ነው?
ኢዩ ይህን የጠየቀው ስለ ሁኔታው ሕዝቡ በጥልቀት እንዲያስቡ ለማድረግ ነው። ይህን በዐረፍተ ነገር መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጒሞቹም 1) ‹‹ለ70ዎቹ የአክዓብ ልጆች ሞት ተጠያቂዎቹ የሰማርያ ሰዎች ናቸው›› 2) ‹‹እነዚህ ሰዎች እንዲሞቱ የያህዌ ፈቃድ ነበር››

2 Kings 10:10

በእርግጥ ዕወቁ
‹‹ተረዱ›› ወይም፣ ‹‹ይህን ሐቅ ልብ በሉ››

ከያህዌ ቃል አንዲቱ እንኳ ወድቃ እንደማትቀር
ይህ የሚናገረው ያህዌ ይሆናል ያለው ሁሉ እንደሚሆን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከያህዌ ቃል አንዲቱም አትወድቅም›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ የተናገረው ሁሉ ይሆናል››

ያህዌ የተናገረውን ፈጽሞአል
ይህ የሚናገረው እርሱ ራሱ የገደላቸው ይመስል፤ ያህዌ የአክዓብ ልጆች እንዲሞቱ ማድረጉን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ እንደዚያ እንዲሆን አደረገ››

ኢዩ ሁሉንም ገደለ... ካህናቱን
ኢዩ እንዲገደሉ አዘዘ እንጂ፣ እርሱ በግሉ እነዚህን ሰዎች ሁሉ አልገደለም። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ኢዩ ሁሉም እንዲገደሉ አዘዘ›› ወይም፣ ‹‹ኢዩ ሁሉ እንዲገደሉ አዘዘ››

የተረፉትን ሁሉ
‹‹በሕይወት ያሉትን ሁሉ›› ወይም፣ ‹‹የቀሩትን ሁሉ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አንድ እንኳ እስከማይተርፍ ድረስ
ይህ ሁሉም ተገደሉ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሁሉም እስኪሞቱ ድረስ›› ወይም፣ ‹‹ሁሉም እስኪያልቁ ድረስ››

2 Kings 10:12

ቤት ኤከድ ወደ ተባለው የበግ ጠባቂዎች ቤት
ይህ በጐች የሚሸለቱበት ቦታ ስም ነው።

ለሰላምታ ወደዚህ ወርደን
‹‹ሰላም ለማለት መጥተናል››

የንጉሡ ልጆች
‹‹የንጉሥ ኢየራም ልጆች››

ከነሕይወታቸው ያዛቸው
ይህ ሳይገድሉ መያዝ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያዛቸው›› ወይም፣ ‹‹አሰራቸው››

ከነሕይወታቸው ወስደው
‹‹ያዛቸው››

አርባ ሁለቱን ሰዎች
‹‹42 ሰዎች››

አንድ እንኳ አላስቀረም
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሁሉንም ገደላቸው››

2 Kings 10:15

የሬካብ ልጅ ኢዮናዳብ
ይህ የሰው ስም ነው።

ልቤ ከአንተ ጋር እንደ ሆነ ልብህ ከእኔ ጋር ነውን?
እዚህ ላይ የሰው፣ ‹‹ልብ›› ታማኝነቱን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ ለአንተ ታማኝ እንደ ሆንሁ ታማኝ ትሆንልኛለህን?››

እንግዲያውስ እጅህን ስጠኝ
‹‹እንደዚያ ከሆነ እጅህን እጄ ላይ አስቀምጥ›› ወይም፣ ‹‹እንደዚያ ከሆነ፣ እንጨባበጥ›› በብዙ አገሮች ሁለት ሰዎች ከተጨባበጡ ስምምነታቸውን ያረጋግጣል።

ያለኝን ቅናት እይልኝ
‹‹ቅናት›› የሚለው ቃል ቅጽልን ሊያመለክት ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቀናተኛ መሆኔን እይልኝ››

ንጉሣዊ ዘር
‹‹ንጉሣዊ ቤተ ሰብን ሁሉ››

ለነቢዩ ለኤልያስ በተነገረው የያህዌ ቃል መሠረት
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ የሰጠው ኤልያስ የተናገረው ትንቢት እንዲፈጸም››

2 Kings 10:18

ሕዝቡን ሁሉ በአንድነት ሰበሰበ
‹‹ሕዝብ ሁሉ ወደዚያ እንዲመጡ ጠራ››

ሕዝቡ ሁሉ ተሰበሰቡ
‹‹የሰማርያ ሕዝብ ሁሉ››

በጣም አገለገሉ
‹‹ከአክዓብ የበለጠ አገለገሉ››

አንድ እንኳ እንዳይቀር
‹‹አንድ እንኳ እንዳይተርፍ››

የማይመጣ ቢኖር ግን በሕይወት አይኖርም
ይህ ማለት ካልመጡ ይገደላሉ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የማይመጣ ካለ እንገድለዋለን››

ጉባኤ ጥሩ
ይህ ማለት አንድ ነገር ለማድረግ ጊዜ መወሰን ማለት ነው። እዚህ ላይ ግን ለበአል ጉባኤ ለማድረግ እየተዘጋጁ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ተዘጋጁ››

2 Kings 10:21

ከዚያም ኢዩ መልእክት ላከ
ይህን መልእክቱ ወደ አገሩ ሁሉ የሚያደርሱ መልእክተኞች ላከ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከዚያም ኢዩ መልእክተኞ ላከ›› ወይም፣ ‹‹ከዚያ ኢዩ መልእክት ላከ››

ስለዚህ ሳይመጣ የቀረ አልነበረም
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በአልን የሚያመልኩ ሁሉ እዚያ ነበሩ›› ወይም፣ ‹‹ሁሉም መጡ››

ዳር እስከ ዳር ሞላ
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቤቱን ሞሉት››

የልብስ ቤቱ ጎላፊ
እዚህ ላይ፤ ‹‹ጎላፊ›› የሚጠብቅ፣ የሚቆጣጠር ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የካህናቱ ልብስ ጎላፊ›› ወይም፣ ‹‹የካህናቱን ልብስ የሚጠብቅ››

2 Kings 10:23

ለበአል አገልጋዮች እንዲህ አለ
‹‹ኢዩ በአልን ለማምለክ በቤተ ጣዖቱ ለነበሩ ሰዎች እንዲህ አለ››

የበአል አገልጋዮች ብቻ
‹‹እዚህ መገኘት ያለባቸው የበአል አገልጋዮች ብቻ ናቸው››

በእጃችሁ ከሰጠኃችሁ ሰዎች አንድ እንኳ እንዲያመልጥ ያደረገ
እዚህ ላይ የሰዎቹ፣ ‹‹እጅ›› በእነርሱ ‹‹ቁጥጥር›› ያለ ማለት ነው። በቤተ ጣዖቱ ዙሪያ በመሆናቸው፣ ሁኔታው በቁጥጥራቸው ሥር ነበር፤ ሰዎች ቢያመልጡ ኀላፊነቱ የእነርሱ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እጃችሁ ላይ ካሉት ሰዎች አንዱ እንኳ ቢያመልጥ›› ወይም፣ ‹‹ውስጥ ካሉት ሰዎች አንድ እንኳ ሲያመልጥ››

አንድ እንኳ እንዲያመልጥ ያደረገ በገመዱ ይገባባታል
‹‹እንዲያመልጥ ያደረገ ይገደላል››

በገመዱ ይገባበታል
ይህ በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። ይህ መገደል በጨዋ ቃል ሲገለጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕይወቱን እናጠፋለን›› ወይም፣ ‹‹እንገድለዋለን››

በጠፋው ሰው ቦታ
‹‹በጠፋው ሰው ሕይወት ለውጥ›› እንደማይሞት አጽንዖት ለመስጠት እዚህ ላይ ሰውየው፣ ‹‹ሕይወት›› ተብሏል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለ ሰውየው››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Kings 10:25

ለጠባቂዎቹና ለጦር አለቆቹ እንዲህ አለ
ምናልባት ኢዩ ለጠባቂዎቹ ከመናገሩ በፊት ከቤተ ጣዖቱ መውጣቱን መግለጽ ያስፈልገህ ይሆናል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከበአል ቤተ ጣዖት ወጥቶ ለጠባቂዎቹና ለጦር አለቆቹ እንዲህ አላቸው››

በሰይፍ
ሰዎቹ የበአልን አገልጋዮች የገደሉት በሰይፍ ነበር። ይህ ሐረግ የራሳቸውን ሰይፍ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሰይፋቸው››

ወደ ውጭ አውጥታችሁ ጣሏቸው
ይህ ማለት የሞቱትን ሰዎች ከቤተ ጣዖቱ አውጥቶ መጣል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሬሳቸውን ከቤተ ጣዖቱ አውጥታችሁ ጣሉ››

የኩስ መጣያ አደረገው
‹‹የሕዝብ ሽንት ቤት አደረገው››

እስከ ዛሬ ድረስ
ይህ ማለት ያ ነገር እስከ አሁን ድረስ አለ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከዚያ ወዲህ ሁሌም እንዲሁ ነው››

2 Kings 10:29

የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓምን ኀጢአት አልተወም
ይህ ማለት ኢዩ ኢዮርብዓም ያደርግ የነበረውን ኀጢአት እያደረገ ነበር ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም ያደረገውን ኀጢአት ማድረጉን አልተወም››

ናባጥ
ከ2 ነገሥት 3፥3 የዚህን ሰው ስም እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

የእስራኤል ኀጢአት
‹‹እስራኤል›› እዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤል ሕዝብ ኀጢአት››

ስላደረግህ
‹‹ስለ ፈጸምህ›› ወይም፣ ‹‹በማድረግህ››

በዐይኔ ፊት መልካም
ዐይን ማየትን፣ ማየት ደግሞ ሐሳብንና ፍርድን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መልካም ነው ያልሁትን›› ወይም፣ ‹‹መልካም እንደ ሆነ ያሰብሁትን››

የአክዓብ ቤት
የአክዓብ፣ ‹‹ቤት›› የእርሱ፣ ‹‹ቤተ ሰብ›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአክዓብ ቤተ ሰብ››

በልቤ ያለውን ሁሉ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ልቤ›› - ‹‹ምኞትን›› ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንድታደርግ የምመኘው ሁሉ›› ወይም፣ ‹‹እንድታደርግ የምፈልገውን ሁሉ››

ዙፋን ላይ ይቀመጣል
ዙፋን ላይ መቀመጥ ንጉሥ መሆን ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይነግሣል››

እስከ አራት ትውልድ
ይህ ልጁን፣ የልጅ ልጁን፣ አያቱንና ቅድመ አያቱን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹4ኛ ትውልድ›› ወይም፣ ‹‹አራተኛ ትውልድ››

ኢዩ የያህዌን ሕግ ለመጠበቅ ጥንቃቄ አላደረገም
እዚህ ላይ፣ ‹‹መጠበቅ›› የሚያመለክተው፣ ‹‹መኖርን›› ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኢዩ በያህዌ ሕግ መሠረት ለመኖር አልተጠነቀቀም››

በፍጹም ልቡ
እዚህ ላይ ‹‹ልብ›› የሰውን ፈቃድና ምኞት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሚያደርገው ሁሉ›› ወይም፣ ‹‹በሙሉ ፈቃደኝነት››

ከኢዮርብዓም ኀጢአት አልራቀም
ከአንድ ነገር ‹‹መራቅ›› ያንን ማድረግ ማቆም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኢዮርብዓም ባደረገበት መንገድ ኀጢአት ማድረጉን አልተወም››

2 Kings 10:32

የእስራኤልን ምድር መቀናነስ ጀመረ
‹‹በእስራኤል ቁጥጥር ሥር የነበረው መሬት እያነሰ እንዲሄድ አደረገ››

ክልል
አንድ አካባቢ

አዛሄል ድል መታ
‹‹አዛሄል›› የሚያመለክተው ሰውየውንና ሰራዊቱን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አዛሄልና ሰራዊቱ›› ወይም፣ ‹‹የንጉሥ አዛሄል ሶርያዊ ሰራዊት››

አዛሄል
2 ነገሥት 8፥8 ይህን ስም እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ
‹‹ከዮርዳኖስ ምሥራቅ ካለ ምድር››

አሮዔር... ባሳን
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው።

አርኖን
‹‹የአርኖን ወንዝ›› ይህ የወንዝ ስም ነው።

2 Kings 10:34

በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?
ይህን ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ማስቀመጥ ይቻላል። 2 ነገሥት 1፥18 ይህን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ መጽሐፍ ተጽፎአል››

ኢዩ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ በሰማርያም ቀበሩት
ይህ ኢዩ ሞተ ማለት ነው። ከእነርሱ ጋር የተኛ ይመስል አባቶቹ በተቀበሩበት በታ መቀበሩን ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኢዩ ሞተ፤ አባቶቹም በተቀበሩበት ቦታ በሰማርያ ተቀበረ››

ኢዮአካዝ
ይህ የሰው ስም ነው።

ኢዩ በሰማርያ ተቀምጦ በእስራኤል ላይ የነገሠው ሃያ ስምንት ዓመት ነበር
‹‹ኢዩ ሰማርያ ሆኖ በእስራኤል ሃያ ስምንት ዓመት ነገሠ››

ሃያ ስምንት ዓመት
‹‹28 ዓመት››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 11

1 የንጉሥ አካዝያስ እናት ጎቶልያ የልጅዋን መገደል እንደ ሰማች ተነሥታ የንጉሣውኑን ቤተ ሰብ አባላት በሙሉ ገደለች። **2** ከእርስዋም እጅ ማምለጥ የቻለ
የአካዝያስ ልጅ ኢዮአስ ብቻ ነበር፤ ነገር ግን አክስቱ የነበረችው በአባትዋ በኩል የንጉሥ አካዝያስ እኅት የንጉሥ ኢዮራም ልጅ ዮሳቤት ከሞቱት ከንጉሥ ልጆች
መካከል ወስዳ በመደበቅ ከሞት አዳነችው፤ እርሰዋም ሞግዚቱን ወስዳ በቤትዋ መኝታ ክፍል ውስጥ ስለደበቀችው በጎቶልያ እጅ ሳይገደል ቀረ። **3** ጎቶልያ
በነገሠችበት ስድስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ዮሳቤት ሕፃኑን ኢዮአስን በመደበቅ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በመንከባከብ አሳደገችው። **4** ነገር ግን በሰባተኛው
ዓመት ካህኑ ዮዳሄ ለንጉሡ ክብር ዘቦችና ለቤተ መንግሥቱ ጠባቂዎች ሁሉ ኃላፊ ወደሆኑት የጦር አዛዦች ሁሉ ልኮ ወደ ቤተ መቅደስ እንዲመጡ
አስጠራቸው፤ በዚያም ሊያደርገው ያቀደውን ይስማሙበት ዘንድ በመሐላ እንዲያረጋግጡለት አደረገ፤ ከዚያም በኋላ የአካዝያስን ልጅ ኢዮአስን አሳያቸው። **5**
የሚከተለውንም ትእዛዝ ሰጣቸው፤ በሰንበት ቀን ለጥበቃ በምትሰማሩበት ጊዜ ከእናንተ ከሦስት አንዱ እጅ ቤተ መንግሥቱን ይጠብቅ፤ **6** ሌላው አንድ ሦስተኛ
እጅ የሱርን የቅጥር በር ይጠብቅ፤ የቀረው አንድ ሦስተኛ እጅ ደግሞ ከሌሎቹ ጥበቃዎች በስተኋላ ያለውን ቅጥር በር ይጠብቅ። **7** በሰንበት ቀን ከጥበቃ ነጻ
የሆኑት ሁለቱ ቡድኖች ንጉሡን ለመከላከል ቤተ መቅደሱን ይጠብቁ፤ **8** ንጉሥ ኢዮአስን በዙሪያው በምትጠብቁበትም ጊዜ ሰይፋችሁን መዛችሁ ወደሚሄድበት
ስፍራ ሁሉ አብራችሁ ሂዱ፤ ወደ እናንተ ለመቅረብ የሚደፍር ማንም ቢኖር ይገደል። ንጉሡ ሲወጣና ሲገባ ከእርሱ አትለዩ። **9** የጦር አዛዦቹም ካህኑ ዮዳሄ
የሰጠውን መመሪያ በመቀበል በሰንበት ቀን ለጥበቃ የሚሰማሩትንና ከጥበቃም የሚወጡትን ጭፍሮቻቸውን ጭምር አሰልፈው ወደ ካህኑ ዮዳሄ አመጡ። **10**
ዮዳሄም በእግዚአብሔር ቤት የነበሩትን የንጉሥ ዳዊት ጦሮችና ጋሻዎች አውጥቶ ለጦር አለቆቹ ሰጣቸው። **11** ጭፍሮቹም ሰይፋቸውን እንደ መዘዙ ንጉሡን
ከበው በቤተ መቅደሱ በቀኝና በግራ በመሠዊያው አጠገብ እንዲቆሙ አደረጋቸው። **12** ከዚያም ዮዳሄ ኢዮአስን አቅርቦ በራሱ ላይ ዘውድ ጫነለት፤
ለመንግሥቱ መመሪያ የሆነውንም ሕግ አንድ ቅጂ አስረከበው፤ በዚህ ዓይነት ኢዮአስ ተቀብቶ ነገሠ። ሕዝቡም በእጆቸው እያጨበጨቡ፣ ረጅም ዕድሜ ለንጉሡ
አሉ። **13** ንግሥት ጎቶልያ የክብር ዘቦቹንና የሕዝቡን ጩኸት ድምፅ በሰማች ጊዜ ሕዝቡ ወደተሰበሰበበት ወደ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ መጣች። **14** እዚያ
እንደ ደረሰች አዲሱ ንጉሥ በተለመደው ባሕል መሠረት በቤተ መቅደሱ መግቢያ በሚገኘው ዐምድ አጠገብ ቆሞ አየቸው፤ እርሱም በጦር አዛዦችና
በእምቢልታ ነፊዎች ታጅቦ ነበር፤ ሕዝቡም ሁሉ በደስታ ተሞልተው እልል እያሉ እምቢልታ ይነፉ ነበር፤ ጎቶልያ በድንጋጤ ልብስዋን ቀዳ ይህ በክሕደት የተፈጸመ
ሤራ ነው ስትል ጮኸች። **15** ዮዳሄም የጦር አለቆችን ግራና ቀኝ በተሰለፉት ዘቦች መካከል ጎቶልያን አውጥታችሁ ውሰዱአት፤ እርስዋን ለመከተል የሚሞክር
ቢኖር ይገደል ሲል አዘዛቸው። **16** እነርሱም እርስዋን አፈፍ አድርገው በመያዝ ወደ ቤተ መንግሥት ወሰዱአት፤ እዚያ የፈረስ መግቢያ ቅጥር በር ተብሎ
በሚጠራው ስፍራ ገደሉአት። **17** ዮዳሄ፣ ንጉሡና ሕዝቡ የእግዚአብሔር ሕዝብ ይሆኑ ዘንድ ከእግዘአብሔር ጋር ቃል ኪዳን እንዲገቡ አደረገ፤ እንዲሁም
በንጉሡና በሕዝቡ መካከል ቃል ኪዳን እንዲኖር አደረገ። **18** ከዚህም በኋላ ሕዝቡ ወደ ባዓል ቤተ መቅደስ ሄዶ አፈራረሰው፤ መሠዊያዎቹንና ምስሎቹን ሁሉ
ሰባበረ፤ ማታን ተብሎ የሚጠራውንም የባዓል ካህን በመሠዊያዎቹ ፊት ለፊት ገደሉት። ዮዳሄም ቤተ መቅደሱን በየተራ የሚጠብቁ ዘበኞችን መደበ፤ **19**
ከዚህም በኋላ እርሱ፣ የጦር አለቆች፣ የንጉሡ የክብር ዘብና የቤተ መንግሥቱ ጠባቂዎች ንጉሡን ከቤተ መቅደስ እስከ ቤተ መንግሥት አጅበው እንዲሄዱና
ሕዝቡም ሁሉ ከኋላ እንዲከተል አደረገ፤ ኢዮአስም በዘብ ጠባቂዎች ቅጥር በር በኩል ገብቶ በዙፋኑ ላይ ተቀመጠ። **20** ጎቶልያ በቤተ መንግሥት በሰይፍ ስለ
ተገደለች ሰው ሁሉ ተደሰተ፤ ከተማይቱም ጸጥ አለች። **21** ኢዮአስም በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ሰባት ዓመት ነበር።

---

2 Kings 11:1

ጐቶልያ... ዮሳቤት... ኢዮአስ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው

ልጇ መሞቱን በሰማች ጊዜ
‹‹ልጇ መሞቱን ባወቀች ጊዜ››

ተነሥታ የንጉሣዊ ቤተ ሰብ ልጆች ገደለች
ጐቶልያ ራሷ ልጆቹን አልገደለችም። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጐቶልያ ንጉሥ
የሚሆኑ የአካዝያስ ቤተ ሰብ አባሎች እንዲገደሉ አገልጋዮቿን አዘዘች››

የአካዝያስን ልጅ ኢዮአስን ለገድሉ ከነበሩት ልዑላን መካከል ሰርቃ ወሰደችው።
እንዳይገድሉትም ከጐቶልያ በመደበቅ እርሱንና ሞግዚቱን በአንድ እልፍኝ ሸሸገቻቸው
‹‹የአካዝያስ ትንሹን ልጅ ኢዮአስን ወስዳ እርሱንና ሞግዚቱን ቤተ መቅደስ
ባለው መኝታ ቤት ደበቀቻቸው ስለዚህ ሳይገደሉ ቀሩ››

ጐቶልያ አገሩ በምትገዛበት ጊዜም በያህዌ ቤት ተሸሸገ
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ኢዮአስና
ዮሳቤት ጐቶልያ አገሩን በምትገዛበት ዘመን ስድስት ዓመት በያህዌ ቤት
ተደበቁ››

ምድር
ይህ በምድር የሚኖሩ ሰዎች ተለዋጭ ስም ነው። አማራጭ ትርጕም፣
‹‹የይሁዳ ሕዝብ››

2 Kings 11:4

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
የንጉሥ አካዝያስ ልጆች ከተገደሉ በኋላ የንጉሥ አካዝያስ ልጅ ኢዮአስ ቤተ
መቅደሱ ውስጥ ከተደበቀ በኋላ የተፈጸመውን ታሪክ ይቀጥላል።

በሰባተኛውም ዓመት
‹‹በጐቶልያ አገዛዝ ሰባተኛው ዓመት›› ወይም፣ ‹‹ጐቶልያ ትገዛ በነበረበት
7ኛው ዓመት››

ዮዳሄ
ሊቀ ካህኑ

የመቶ አለቆች
ይህ የባለ ሥልጣኖች መጠሪያ ነው። አማራጭ ትርጕሙ፣ 1) ‹‹መቶ››
የሚለው እነዚህ ባለ ሥልጣኖች ምን ያህል ወታደር ከእነርሱ ሥር እንደ ነበር
በትክክል ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የ100 ወታደሮች አዛዦች››
ወይም 2) ‹‹መቶ›› የሚለው ቃል በትክክል ቁጥርን የሚገልጽ ሳይሆን፣
የሚያመለክተው ሰራዊቱ ውስጥ ያለውን ምድብ ነው። አማራጭ ትርጕም፣
‹‹የወታደራዊ ምድብ አዛዦች››

ካራውያን
እነዚህ የተወሰኑ የቤተ መንግሥት ጠባቂዎች ቡድን ናቸው።

ወደ ራሱ አመጣቸው
‹‹መጥተው እርሱን እንዲያገኙ አደረገ›› - እነዚህ ወታደሮች የሆነውን ነገር
ቤተ መቅደስ ውስጥ ለሊቀ ካህኑ ለዮዳሄ ነገሩት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የንጉሡን ልጅ አሳያቸው
የንጉሥ አካዝያስ ልጅ ኢዮአስ በሕይወት መኖሩን ዮዳሄ ነገራቸው።

2 Kings 11:7

አጠቃላይ መረጃ
ዮዳሄ ንጉሥ ኢዮአስን ለሚጠብቁ ወታደሮች መመሪያ እየሰጠ ነው።

ንጉሡን
ነቅተው ከማንኛውም አደጋ ንጉሡን መጠበቅ ነበረባቸው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ንጉሥ ኢዮአስን ለመጠበቅ››

እናንተን የሚቀርባችሁ ቢኖር
‹‹ንጉሡ ኢዮአስን እየጠበቃችሁ እያለ እናንተን የሚቀርባችሁ ቢኖር ይገደል›› ረድፍ ማለት መደዳውን ያሉ ወታደሮች ማለት ነው።

ይገደል
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ግደሉት››

ንጉሡ በሚወጣበትም ሆነ በሚገባበት ጊዜ ሁሉ አትለዩት
እነዚህ የሚቃረኑ የሚመስሉ ሁለት ነገሮች ንጉሡ የሚያደርገውን ማንኛውንም ነገር ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሁልጊዜ ከአጠገቡ አትለዩ››

2 Kings 11:9

የመቶ አለቆች
‹‹የመቶ አለቆች›› የሚለው ሐረግ ምናልባት ወታደራዊ ሥልጣን ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉሞቹ፤ 1) ‹‹መቶ›› የሚለው ቃል እነዚህ አዛዦች ሥር ያሉ ሰዎችን ቁጥር የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የ100 ወታደሮች አዛዥ›› ወይም 2) መቶ ተብሎ የተተረጐመው የወታደራዊ ምድብ ስም እንጂ፣ በትክክል ቁጥርን የሚያመለክት አይደለም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የወታደራዊ ምድብ አዛዥ›› 2 ነገሥት 11፥4 ላይ ያለውን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

እያንዳንዱ
‹‹እያንዳንዱ አዛዥ››

ያህዌ ቤት ውስጥ ነበሩ
‹‹ቤተ መቅደስ ውስጥ ተቀምጠው ነበር››

2 Kings 11:11

ከቤተ መቅደሱ ግራና ቀኝ፤ መሠዊያውና ቤተ መቅደስ አጠገብ።
አንዳንድ ትርጉሞች ‹‹ቤተ መቅደስ›› የሚለውን፣ ‹‹ቤተ መንግሥት›› በማለት ተርጉመዋል። እነዚህ ትርጉሞች፣ ‹‹ከቤተ መንግሥቱ ግራና ቀኝ፤ መሠዊያውና ቤተ መቅደሱ አጠገብ›› ይላሉ።

የንጉሡን ልጅ ኢዮአስን አውጥቶ
x

2 Kings 11:13

የጠባቂዎቹ ጩኸት
ይህ የሚያመለክተው የሁሉንም ወታደሮች ድምፅ ነው።

ሕዝቡ ወዳለበት ወደ ቤተ መቅደሱ ሄደች
‹‹ሕዝቡ ተሰብስቦ ወደ ነበረበት ወደ ቤተ መቅደሱ ሄደች››

ስትመለከት እነሆ ንጉሡ እዚያ ቆሞ ነበር
‹‹እዚያ ስትደርስ ንጉሥ ኢዮአስ ቆሞ ስታይ ተገረመች››

በዐምዱ አጠገብ
‹‹ቤተ መቅደስ ውስጥ ከነበሩ ዐምዶች በአንዱ››

በወጉ መሠረት
‹‹ሁሌም ንጉሡ ይቆምበት የነበረው ቦታ››

መለከት ነፊዎች
‹‹መለከት የሚነፉ ሰዎች››

ጐቶልያም ልብሷን ቀዳ
በጣም መቆጣቷንና መናደዷን ለማሳየት ልብሷን ቀደደች።

ክዳት ነው! ክዳት ነው!
‹‹ከሐዲዎች ነችሁ! አታለላችሁኝ!››

2 Kings 11:15

የመቶ አለቆች
‹‹የመቶ አለቆች›› የሚለው ሐረግ ምናልባት ወታደራዊ ሹመት ሊያመለክት ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ 1) ‹‹መቶ›› የሚለው ቃል በእነዚህ አዛዦች ሥር ያሉ ወታደሮችን ብዛት ሊያመለክት ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የ100 ወታደሮች አዛዥ›› ወይም 2) መቶ ተብሎ የተተረጐመው ቃል የሚያመለክተው የወታደራዊ ምድብ ስም እንጂ፣ ቁጥርን አይደለም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የወታደራዊ ምድብ አዛዥ›› 2 ነገሥት 11፥4 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

በረድፍ በተሰለፉ ጭፍሮች መካከል አውጧት
‹‹ተርታውን ከተሰለፉ ጠባቂች መካከል አውጧት›› ወይም፣ ‹‹ግራና ቀኙን ከተሰለፉ ወታደሮች ውሰዷት›› ረድፍ መደዳውን የተሰለፉ ወታደሮች ሰልፍ ነው።

2 Kings 11:17

በንጉሡና በሕዝቡም መካከል
‹‹በንጉሡና በሕዝቡ መካከል ኪዳን ተደረገ››

የአገሩም ሕዝብ ሁሉ
ይህ በጣም ብዙ ሕዝብ የበአልን ቤተ ጣዖት ማፍረሱን የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከአገሩ ሕዝብ አብዛኛው››

የበአል ቤት
‹‹የበአል ቤተ ጣዖት››

ማታን
ይህ የወንድ ካህን ስም ነው።

2 Kings 11:19

አጠቃላይ መረጃ
አዲሱን ንጉሥ ኢዮአስን ከቤተ መቅደስ ወደ ቤተ መንግሥት ወሰዱት

የመቶ አለቆች
‹‹መቶ አለቆች›› የሚለው ሀረግ ምናልባት ወታደራዊ ሹመት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉሞች፣ 1) ‹‹መቶ›› የሚለው ቃል በእነዚህ ሹሞች ሥር ያለውን ወታደር ብዛት ሊያመለክት ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የ100 ወታደሮች አዛዥ›› ወይም 2) ‹‹መቶ›› ተባሎ የተተረጐመው ቃል ወታደራዊ ምድብን እንጂ፣ ትክክለኛ ቁጥር የሚያመለክት አይደለም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወታደራዊ ምድብ አዛዥ›› 2 ነገሥት 11፥4 ላይ ያለውን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ካራውያን
ይህ የቤተ መንግሥቱ ጠባቂዎች አንድ የተለየ ምድብ ነው።

ንጉሡን ከያህዌ ቤተ መቅደስ አውጥተው ወደ ቤተ መንግሥት ሄዱ
‹‹ንጉሡን ከቤተ መቅደስ ወደ ቤተ መንግሥት አመጡት››

የአገሩም ሕዝብ ሁሉ ደስ አለው
ይህ አብዛኛው ለማለት ነው፣ ደስ ያላላቸው ሰዎችም እንደሚኖሩ ግልጽ ነው።
አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በአገሩ ያሉ ብዙ ሰዎች››

ከተማዪቱ ጸጥ አለች
‹‹ከተማዪቱ ተረጋጋች›› ወይም፣ ‹‹ከተማዪቱ ሰላማዊ ሆነች››

2 Kings 11:21

ኢዮአስ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ሰባት ዓመት ነበር
ኢዮአስ 7 ዓመቱ ነበር

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 12

1 ኢዩ በእስራኤል በነገሠ በሰባተኛው ዓመት ኢዮአስ የይሁዳ ንጉሥ ሆነ። እርሱም በኢየሩሳሌም አርባ ዓመት ገዛ። እናቱም ሳብያ ተብላ የምትጠራ የቤርሳቤህ
ከተማ ተወላጅ ነበረች። 2 ካህኑም ዮዳሄ ይመክረውና ያስተምረው ስለ ነበር፣ ኢዮአስ በዕድሜው ዘመን ሁሉ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሥራ ሠራ። 3 ነገር
ግን በየኮረብታዎቹ ላይ የሚገኙት የአሕዛብ ማምለኪያዎች ስላልተደመሰሱ ሕዝቡ በዚያ ዕጣን እያጠኑ መሥዋዕት ማቅረባቸውን እንደ ቀጠሉ ነበር። 4
ኢዮአስም ካህናትን ጠርቶ በቤተ መቅደስ ከሚቀርበው መሥዋዕት ጋር ግንኙነት ባለው ሁኔታ መባ ሆኖ የሚገባውን ገንዘብ ሁሉ በጥንቃቄ እንዲጠብቁ አዘዘ፤
ይኸውም ቋሚ ከሆነው ከዘወትር መሥዋዕት ጋር መባ ሆኖ የሚቀርበውንና በበጎ ፈቃድ ሕዝቡ የሚያመጣውን ስጦታ ሁሉ የሚያጠቃልል ነበር። 5 እያንዳንዱ
ካህን ከሚያገለግላቸው ሰዎች የሚገኘውን የገንዘብ መባ ሁሉ በጥንቃቄ የመጠበቅ ኃላፊነት ተሰጠው። ገንዘቡንም እንዳስፈላጊነቱ ለቤተ መቅደሱ ጥገና
አገልግሎት እንዲያውሉት ነገራቸው። 6 ነገር ግን ኢዮአስ እስከ ነገሠበት እስከ ሃያ ሦስተኛው ዓመት ድረስ ካህናቱ በቤተ መቅደሱ ላይ ምንም ዓይነት እድሳት
አላደረጉም። 7 ስለዚህም ኢዮአስ ዮዳሄንና ሌሎቹንም ካህናት ወደ እርሱ ጠርቶ ቤተ መቅደሱን ያላደሳችሁበት ምክንያት ምንድን ነው? ከዛሬ ጀምሮ
የምትቀበሉትን ገንዘብ መያዝ የለባችሁም፤ ለቤተ መቅደሱ እድሳት ይውል ዘንድ ገንዘቡን አስረክቡ አላቸው። 8 ካናቱም በዚህ ተስማምተው ቤተ መቅደሱን
በራሳቸው ለማደስ የነበራቸውን ተግባር አቆሙ። 9 በዚህ ፈንታ ዮዳሄ አንድ ሣጥን ወስዶ በመክደኛው ላይ ቀዳዳ አበጀ፤ ሣጥኑንም ወስዶ ወደ ቤተ መቅደስ
ሲገቡ በስተ ቀኝ በሚገኘው መሠዊያ አጠገብ አኖረው፤ የየዕለቱ ተረኞች የነበሩትም ካህናት ለአምልኮ የሚመጡት ሰዎች የሚሰጡትን የገንዘብ መባ እየተቀበሉ
በሣጥኑ ውስጥ ያስገቡት ነበር። 10 ሣጥኑም በሚሞላበት ጊዜ የቤተ መንግሥቱ ጸሐፊና ሊቀ ካህናቱ እየመጡ ገንዘቡን በመቁጠር በከረጢት እያሰሩ ያኖሩት
ነበር። 11 ትክክለኛውን ሒሳብ አጣርተው ከመዘገቡ በኋላ ለቤተ መቅደሱ እድሳት ሥራ ኃላፊዎች ያስረክቡ ነበር፤ እነርሱም ገንዘቡን ተረክበው ለአናጢዎችና
ለግንበኞች ይሰጡ ነበር። 12 ለድንጋይ ጠራቢዎች፣ ለማደሻ አገልግሎት የሚውል እንጨትና ድንጋይ ለሚገዙና እንዲሁም ለልዩ ልዩ አስፈላጊ ነገሮች ለሚውል
ተግባር ሁሉ ይከፍሉ ነበር። 13 ነገር ግን ከብር ለሚሠሩ ጎድጓዳ ሳሕኖች የዐመድ ማጠራቀሚያ ጎድጓዳ ወጭት፣፣ እምቢልታ ወይም ደግሞ ከብርና ከወርቅ
ለሚሠሩ ንዋያተ ቅዱሳት ከዚያ ገንዘብ ላይ ተነሥቶ የሚከፈል ሒሳብ አልነበረም። 14 ያ ገንዘብ በሙሉ በቤተ መቅደሱ እድሳት ተግባር ላይ ለተሰማሩት
ሠራተኞች ብቻ የሚውል ነበር። 15 ለሥራው ኃላፊነት የተመረጡትም ሰዎች ፍጹም ታማኞች ስለ ነበሩ ገንዘቡን የሰጡአቸው ሰዎች አይቆጣጠሩአቸውም
ነበር። 16 ስለ በደልና ስለ ኃጢአት መሥዋዕት የሚከፈለው ገንዘብ ግን ለካህናቱ ጥቅም የሚውል እንጂ ወደ ቤተ መቅደሱ ውስጥ አይገባም ነበር። 17 በዚያ
ጊዜ የሶርያ ንጉሥ አዛሄል በጌት ከተማ ላይ አደጋ ጥሎ ያዛት፤ ቀጥሎም በኢየሩሳሌም ላይ አደጋ ለመጣል ተመለሰ። 18 የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአስም ከእርሱ
በፊት የነበሩትን ነገሥታት ማለትም ኢዮሳፍ፣ ኢዮራምና አካዝያስ ለእግዚአብሔር ለይተው ያኖሩትን መባና የራሱን መባ ጨምሮ በቤተ መቅደስና በቤተ መንግሥት
ግምጃ ቤቶች የነበረውን ወርቅ ሁሉ በመሰብሰብ ገጸ በረከት አድርጎ ለንጉሥ አዛሄል ላከለት። ሐዛሄልም ይህን ተቀብሎ ሠራዊቱን ከኢየሩሳሌም መለሰ። 19
ንጉሥ ኢዮአስ ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ መጽሐፍ ውስጥ ተመዝግቦ ይገኝ የለምን? 20 ከዚህ በኋላ የንጉሥ ኢዮአስ ባለሥልጣኖች
አንድ ላይ ተነሥተው አድመውበት ወደ ሲላ ሲሄድ በሚሎ ጥቃት አደረሱበት። 21 የሰምዓት ልጅ ዮዛካርና የሾሜር ልጅ ዮዛባት ኢዮአስን ገደሉት። በዳዊት
ከተማ በሚገኘው የነገሥታት መካነ መቃብር ተቀበረ፤ በእርሱም ፈንታ ተተክቶ ልጁ አሜስያስ ነገሠ።

---

2 Kings 12:1

ኢዩ በነገሠ በሰባተኛው ዓመት
‹‹ኢዩ በእስራኤል ላይ በነገሠ 7 ዓመት ሲሆነው››

ኢዮአስ መንገሥ ጀመረ
‹‹ኢዮአስ በይሁዳ ነገሠ››

ሳቢያ
‹‹ሳቢያ የተባለች የቤርሳቤህ ከተማ ተወላጅ››

በያህዌ ፊት መልካም ነገር አደረገ
ዐይን ማየትን፣ ማየት ደግሞ ሐሳብንና ፍርድን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ መልካም ነው የሚለውን›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ መልካም ነው ብሎ
የሚያስበውን››

ያስተምረው ነበር
‹‹ይመራው ነበር››

ከፍታ ቦታዎቹ ግን አልተወገዱም
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል፤ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሕዝቡ ግን ከፍታ ቦታዎቹን አላፈረሰም››

ሕዝቡ በከፍታዎቹ መሥዋዕት ያቀርብና ዕጣን ያጥን ነበር
በእነዚህ ቦታዎች እንዳያመልኩ ያህዌ ሕዝቡን ከልክሎ ነበር። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹መሥዋዕት ለማቅረብና ዕጣን
ለማጠን ሕዝቡ ያህዌ ወደማይፈልጋቸው ቦታዎች እየሄደ ነበር››

2 Kings 12:4

በስእለት ወደ ያህዌ ቤት የገባው ገንዘብ
ይህ ቤተ መቅደሱን ለመርዳት ሕዝቡ የሰጠውን ገንዘብ ያመለክታል። በተቀረው የዐረፍተ ነገር ክፍል ግልጽ እንዲሆነው ይህ ገንዘብ በሦስት መልኩ
ነበር የሚመጣው።

ያህዌ ልባቸውን ስለነሣሣው የሚሰጥ ገንዘብ
ይህ ሕዝቡ በነጻነት ለያህዌ የሚሰጡትን ገንዘብ ያመለክታል።

2 Kings 12:6

በሃያ ሦስተኛው የኢዮአስ ዘመነ መንግሥት
‹‹ኢዮአስ በነገሠ በሃያ ሦስተኛው ዓመት››

በቤተ መቅደሱ ውስጥ የፈረሰውን ያላደሳችሁት ለምንድነው?
ኢዮአስ ይህን ያለው ካህናቱን ለመገሠጽ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ቤተ መቅደሱን ማደስ ነበረባችሁ››

የፈረሰውን ለማደስ ይዋል
‹‹የፈረሰውን ለሚያድሱ ሠራተኞች ክፈሉት››

2 Kings 12:9

ይልቁን ዮዳሄ
‹‹ካህናቱ ገንዘብ ከመሰብሰብ ይልቅ ዮዳሄ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወደ ያህዌ ቤት በሚያስገባው በስተ ቀኝ በኩል
‹‹ወደ ቤተ መቅደስ በሚገባበት በቀኝ በኩል››

ያስገቡ ነበር
‹‹ሳጥኑ ውስጥ ያስገቡ ነበር›› ወይም፣ ‹‹ገንዘብ መያዣው ውስጥ ያስገቡ ነበር››

የመጣው ገንዘብ
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሕዝቡ ያመጣው ገንዘብ››

ገንዘቡን በየከረጢቱ ውስጥ በማስገባት ቆጠሩ
ብዙ ትርጒሞች ይህን የበለጠ ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ተረጉመውታል፤ ‹‹ገንዘቡን ቆጥረው በየከረጢቱ ውስጥ አኖሩት››

ገንዘቡን በየከረጢቱ ማኖር
ለዚህ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ገንዘቡን በከረጢት ማኖር›› ወይም፣ ‹‹ገንዘቡን በከረጢት መቋጠር››

የተገኘው ገንዘብ
‹‹ሳጥን ውስጥ የተገኘው ገንዘብ››

2 Kings 12:11

ተመዝኖ
‹‹ተቆጥሮ››

በሰዎቹ እጅ
‹‹እጅ›› የሚወክለው ሰዎችን ነው፤ ‹‹ለሰዎቹ››

የቤተ መቅደሱን ሥራ በጎላፊነት
‹‹ቤተ መቅደሱን ለሚያደሱት››

ለድንጋይ ጠራቢዎች
ድንጋይ ትክክለኛ ቅርጽ እንዳይዝ የሚጠርቡ ሰዎች

ዕንጨትና ጥርብ ድንጋይ መግዣ
‹‹ዕንጨት ለመግዛት፣ ድንጋይ ለማስጠረብ››

ለማደስ መከፈል ላለበት ሁሉ
‹‹አስፈለጊ ለሆነው ዕድሳት ሁሉ የሚከፈል››

2 Kings 12:13

ለዚያ ግን ምንም አልተከፈለም
‹‹ለቤተ መቅደሱ ሥራ ለመክፈል አልዋለም››

የብር ጽዋዎች መኰስተሪያዎች፣ ድስቶች፣ መለከቶች ወይም ለሌላው የወርቅም ሆነ የብር ሥራ
እነዚህ መሥዋዕት ማቅረብን ወይም በዓላት ማክበርትን ለመሳሰሉ የተለያዩ የቤተ መቅደስ ሥራዎች ካህናቱ የሚጠቀሙባቸው ዕቃዎች ናቸው።

2 Kings 12:15

ለሠራተኞቹ እንዲከፍሉ ገንዘቡ የተሰጣቸው ላይ ተቆጣጣሪ ማድረግ አላስፈለጋቸውም
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ገንዘቡን ተቀብለው ለዕድሳቱ ሠራተኞች የሚከፍሉ ሰዎች ላይ ተቆጣጣሪ ማድረግ አላስፈለገም››

ተጠያቂ መሆን
ምን ያህል ገንዘብ እንደ ተሰጠና እንደ ተከፈለ መዝገብ መያዝ

ስለ በደል መሥዋዕት ስለ ኀጢአት መሥዋዕት የሚቀርበው ገንዘብ ወደ ያህዌ ቤተ መቅደስ አይገባም ነበር
ገንዘቡ ለጥገናው ሥራ አይውልም ነበር። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከበደል መሥዋዕትና ከኀጢአት መሥዋዕት የሚገኘው ገንዘብ ለያህዌ ቤተ መቅደስ ዕድሳት ሥራ ለሚደረግ ክፍያ አይውልም ነበር››

2 Kings 12:17

የሶርያ ንጉሥ አዛሄል አጠቃ... አዛሄል ፊቱን አዞረ
ይህ አዛሄልና የሶርያን ሰራዊት ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ንጉሥ አዛሄልና ሰራዊቱ አጠቁ... ለማጥቃት ፊታቸውን አዞሩ››

አዛሄል
ይህ የሶርያ አገር ንጉሥ ስም ነው።

ያዛት
‹‹አሸንፎ ተቆጣጠራት››

ኢዮሳፍጥና ኢዮሆራም አካዝያስ፣ አባቱ
እነዚህ ቀድሞ የነበሩ የይሁዳ ነገሥታት ናቸው።

ቀደሱ
‹‹ለዩ››

በዕቃ ቤቶቹ የተገኘው ወርቅ
‹‹ግምጃ ቤት ውስጥ ተቀምጦ የነበረ ወርቅ››

አዛሄልም ከኢየሩሳሌም ተመለሰ
ኢዮአስ ለአዛሄል የሰጠው ስጦታ ኢየሩሳሌምን እንዳያጠቃ አደረገው። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ስለዚህ አዛሄል ኢየሩሳሌምን ማጥቃቱን ትቶ ተመለሰ››

2 Kings 12:19

ይህ ሁሉ በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለም?
ጥያቄው የቀረበው እነዚህ ነገሮች በጽሑፍ የሰፈሩ መሆናቸውን ለአንባቢው ለማስገንዘብ ነው። 2 ነገሥት 8፥23 ላይ ይህን ሐረግ እንዴት ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እነዚህ ሁሉ በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ መጽሐፍ ተጽፈዋል››

ሲላ
ይህ ቦታ የት እንደ ሆነ አይታወቅም

ሰምዓት... የዛካር... ዮዛባት... ሸሜር... አሜስያስ
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው

ከአባቶቹ ጋር
‹‹አባቶቹ በተቀበሩበት ቦታ››

በእግሩ ተተክቶ ነገሠ
‹‹ቀጣዩ የይሁዳ ንጉሥ ሆነ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 13

1 የአካዝያስ ልጅ ኢዮአስ በይሁዳ በነገሠ በሃያ ሦስተኛው ዓመት የኢዩ ልጅ ኢዮአካዝ በሰማርያ ለዐሥራ ሰባት ዓመት ለመግዛት የእስራኤል ንጉሥ ሆነ። **2** እርሱም ከእርሱ በፊት እንደ ነበረው እንደ ናባጥ ልጅ ንጉሥ ኢዮርብዓም ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራ ሠራ። ከክፉ ሥራውም ከቶ አልራቀም። **3** ስለዚህም እግዚአብሔር በእስራኤል ሕዝብ ላይ ተቆጥቶ ለሶርያ ንጉሥ አዛሄል፣ እንዲሁም ለልጁ ለቤን ሀዳድ በተደጋጋሚ አሳልፎ ሰጥቶአቸዋል። **4** ከዚህ በኋላ ኢዮአካዝ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤ እግዚአብሔርም የሶርያ ንጉሥ በእስራኤላውያን ላይ የፈጸመባቸው ግፍ እጅግ ከባድ መሆኑን ተመልክቶ የኢዮአካዝን ጸሎት ሰማ። **5** ስለዚህም እግዚአብሔር እስራኤልን ከሶርያውያን እጅ ነጻ የሚያወጣቸውን መሪ ላከላቸው፤ እነርሱም ከዚያ በፊት በነበረው ዓይነት በሰላም ኖሩ። **6** ይህም ሁሉ ሆኖ ንጉሥ ኢዮርብዓም እስራኤልን ወደ ኃጢአት ከመራበት ከክፉ ሥራቸው አልተመለሱም፤ እስካሁንም አሼራ ተብላ የምትጠራውን የሴት አምላክ ምስል በሰማርያ ማምለክ ቀጠሉ። **7** ንጉሥ ኢዮአካዝ ከኀምሳ ፈረሰኞች፣ ከዐሥር ሰረገሎችና ከዐሥር ሺህ ወታደሮች በቀር ሌላ የተደራጀ የጦር ኃይል አልነበረውም፤ ይህም የሆነበት ምክንያት ሠራዊቱን የሶርያ ንጉሥ በአውድማ እንዳለ እብቅ አድርጎ ስለ ደመሰሰበት ነው። **8** ንጉሥ ኢዮአካዝ የፈጸመው ሌላው ተግባርና የጀግንነት ሥራው ሁሉ በእስራኤል ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኛል። **9** ኢዮአካዝም ሞተ፤ በሰማርያም ተቀበረ፤ በእርሱም ፈንታ ተተክቶ ልጁ ዳግማዊ ኢዮርብዓም ነገሠ። **10** የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአስ በነገሠ በሠላሳ ሰባተኛው ዓመት የኢዮአካዝ ልጅ ዮአስ በሰማርያ የእስራኤል ንጉሥ ሆነ፤ በዚያም ዐሥራ ስድስት ዓመት ገዛ። **11** እርሱም እስራኤልን ወደ ኃጢአት የመራ የንጉሥ ኢዮርብዓምን መጥፎ ምሳሌነት በመከተል ኃጢአት በመሥራቱ እግዚአብሔርን አሳዘነ። **12** ዮአስ የፈጸመው ሌላው ነገር ሁሉ እንዲሁም በይሁዳ ንጉሥ አሜስያስ ላይ ባደረገው ጦርነት የፈጸመው ጀግንነት ጭምር በእስራኤል ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኛል። **13** ከዚህ በኋላ ዮአስ ሞተ፤ በሰማርያም በሚገኘው መካነ መቃብር ተቀበረ፤ በእርሱም ፈንታ ተተክቶ ልጁ ዳግማዊ ኢዮርብዓም ነገሠ። **14** ነቢዩ ኤልሳዕ በብርቱ ደዌ ታሞ ነበር፤ ተኝቶም ለሞት በሚያጣጥርበት ጊዜ የእስራኤል ንጉሥ ዮአስ ሊጠይቀው ሄዶ፣ ድምፁን ከፍ በማድረግ «አባቴ ሆይ! አባቴ ሆይ! አንተ እኮ የእስራኤል ሕዝብ ጎይላቸውና ጋሻ መከታቸው ነህ!» እያለ አለቀሰለት። **15** ኤልሳዕም ንጉሡን «አንድ ቀስትና ፍላጻዎች ውሰድ» ሲል አዘዘው፤ ዮአስም እንደታዘዘው አደረገ ኤልሳዕም **16** ለማስፈንጠር ተዘጋጅ» አለው፤ ንጉሡም እንደታዘዘው አደረገ፤ ኤልሳዕም እጆቹን በንጉሡ እጆች ላይ አኖረ። **17** ኤልሳዕ «የምሥራቁን መስኮት ክፈት» አለ፤ ንጉሡም ከፈተው፤ ኤልሳዕም «ፍላጻውን አስፈንጥር!» አለው፤ ንጉሡም ፍላጻውን እንዳስፈነጠረ ወዲያውኑ ኤልሳዕ፣ «ፍላጻ ነህ፤ በአንተም አማካይነት እግዚአብሔር ሶርያውያንን ድል ያደርጋል፤ ሶርያውያንን ድል እስክትነሣቸው ድረስ በአፌቅ ከተማ ትወጋቸዋለህ።» **18** ከዚህም በኋላ ኤልሳዕ ንጉሡን «ሌሎቹንም ፍላጻዎች አንሥተህ በእነርሱ ምድርን ምታ!» አለው። ንጉሡም ምድርን ሦስት ጊዜ መትቶ አቆመ። **19** ይህም ኤልሳዕን አስቆጣው፤ ስለዚህም ንጉሡን «አምስት ወይም ስድስት ጊዜ መተህ ቢሆን ኖሮ በሶርያውያን ላይ ፍጹም ድልን ትቀዳጅ ነበር፤ አሁን ግን ሦስት ጊዜ ብቻ ድል ትነሣቸዋለህ» አለው። **20** ኤልሳዕም ሞተ፤ ተቀበረም። ከሞአብ የመጡ አደጋ ጣዮች በየዓመቱ የእስራኤልን ምድር ይወጉ ነበር። **21** አንድ ጊዜ የአንድ ሰው ሥርዓተ ቀብር በሚፈጸምበት ሰዓት በእነዚያ አደጋ ጣዮች መካከል አንድ ቡድን ሲመጣ ስለታየ የሚቀበረውን ሬሳ ወደ ኤልሳዕ መቃብር ውስጥ በችኮላ በመወርወር ጥለውት ሸሹ፤ ያም ሬሳ ከኤልሳዕ አስክሬን ጋር በተገናኘበት ቅጽበት ወዲያውኑ ከሞት ተነሥቶ ቆመ። **22** ኢዮአካዝ በነገሠበት ዘመን ሁሉ የሶርያ ንጉሥ አዛሄል እስራኤላውያንን በመውረር ያስጨንቃቸው ነበር፤ **23** እግዚአብሔር ግን በቸርነቱ ምሕረትን በማድረግ ረዳቸው እንጂ እንዲደመሰሱ አልፈቀደም፤ ይህንን ያደረገበት ምክንያት ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ የሰጠውን ቃል ኪዳን በማሰብ ሕዝቡን ስላልረሳው ነው። **24** የሶርያ ንጉሥ አዛሄል በሞተ ጊዜ፣ በእርሱ ፈንታ ተተክቶ ልጁ ቤን ሀዳድ ነገሠ። **25** ከዚህም በኋላ የእስራኤል ንጉሥ ዮአስ ቤን ሀዳድን ሦስት ጊዜ ድል ነሥቶ በኢዮአካዝ ዘመነ መንግሥት ቤን ሀዳድ ይዞአቸው የነበሩትን ከተሞች አስመለሰ።

---

2 Kings 13:1

የይሁዳ ንጉሥ የአካዝያስ ልጅ ኢዮአስ በነገሠ በሃያ ሦስተኛው ዓመት
‹‹ኢዮአስ ይሁዳን ለ23 ዓመት ያህል ከገዛ በኋላ

በሰማርያ ከተማ በእስራኤል ላይ ነገሠ
‹‹በሰማርያ በሚገኘው የእስራኤል መንግሥት ገዛ››

ዐሥራ ሰባት ዓመት ገዛ
‹‹ኢዮአካዝ ለ17 ዓመት ንጉሥ ነበረ››

በያህዌ ፊት ክፉ ሥራ ሠራ
የያህዌ ፊት የያህዌን ፍርድና ሚዛን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በያህዌ ፍርድ ክፉ የሆነ›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ክፉ የሚለውን››

የኢዮርብዓምን ኀጢአት ተከተለ
‹‹ኢዮርብዓም የሚያደርገውን ኀጢአት አደረገ››

ኢዮአካዝ ከዚሁ ድርጊት አልተመለሰም
ኀጢአትን ማድረግ መተው ከእነርሱ መመለስ እንደ ሆነ ተነግሯል። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ኢዮአካዝ የኢዮርብዓምን ኀጢአት ማድረጉን አልተወም›› ወይም፣ ‹‹ኢዮአካዝ የኢዮርብዓምን ኀጢአት ማድረጉን ቀጠለ››

2 Kings 13:3

የያህዌ ቁጣ በእስራኤል ላይ ነደደ
ያህዌ እስራኤልን መቆጣቱ ቁጣው የሚነድ እሳት እንደ ሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ በእስራኤል ላይ በጣም ተቆጣ››

የሶርያው ንጉሥ አዛሄልና ልጁ ቤንሐዳድ በነበሩበት ዘመን ሁሉ አሳልፎ በእጃቸው ሰጣቸው
እዚህ ላይ፣ ‹‹እነርሱ›› የሚለው የሚያመለክተው እስራኤልን ነው፤ ‹‹እጅ›› የሚለው እነርሱን የተቆጣጠረውን ኀይል ሥልጣን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሶርያ ንጉሥ አዛሄልና ልጁ ቤንሐዳድ በተደጋጋሚ እስራኤላውያንን በጦርነት ድል አደረጉ››

ያህዌን ለመነ
‹‹ወደ ያህዌ ጸለየ››

የሶርያ ንጉሥ እስራኤልን እንዴት አድርጎ እንዳስጨነቀ አይቶአል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚናገሩት ስለ አንድ ጉዳይ ሲሆን፣ የተደጋገሙት አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሶርያ ንጉሥ እስራኤልን በጣም ማስጨነቁን አዬ››

የሚታደጋቸው ሰው
‹‹የሚያድናቸው ሰው››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከሶርያውያን ጭቁና (እጅ) ተላቀቁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› እነርሱን የተቆጣጠረ ኀይልና ሥልጣን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከሶርያውያን ነጻ አወጣቸው››

2 Kings 13:6

ከኢዮርብዓም ቤት ኀጢአት አልተመለሱም
ኀጢአትን ማቆም ከኀጢአት መመለስ እንደ ሆነ ተናግሯል። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል፤ አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እስራኤል ኢዮርብዓም ሲያደርግ የነበረውን ኀጢአት ማድረግ አልተወም›› ወይም፣ ‹‹እስራኤል ኢዮርብዓም ሲፈጽም የነበረውን ኀጢአት መፈጸም ቀጠለ››

የኢዮርብዓም ቤት
‹‹የኢዮርብዓም ቤተ ሰብ››

አጠፋቸው
‹‹የኢዮአካዝን ሰራዊት ድል አደረገ››

እንደ ዐውድማ ብናኝ አደረገው
የሶርያ ሰራዊት የእስራኤልን ሰራዊት ክፉኛ ድል አደረገ፤ የቀረውም በመከር ጊዜ ዐውድማ ላይ እንደሚረገጥ ብናኝ ጥቅም የለሽ ሆነ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በመከር ጊዜ ሠራተኞች በእግራቸው እንደሚያደቁት ገለባ ረገጣቸው››

2 Kings 13:8

በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?
ጥያቄው የቀረበው የኢዮአካዝ ሥራ በሌላ መጽሐፍ ተጽፎ የሚገኝ መሆኑን ለአንባቢው ለማሳሰብ ነው። 2 ነገሥት 1፥18 ላይ ይህ እንዴት እንደ ተተረጐመ ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የእስራኤል ነገሥታት ታሪክ በተጻፈበት መጽሐፍ ተጽፎአል።››

ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ
ይህ ማለት ሞተ ማለት ነው።

2 Kings 13:10

በይሁዳ ንጉሥ በኢዮአስ ሰላሣ ሰባተኛው ዓመት
‹‹ዮአስ ይሁዳን ለ37 ዓመት ከገዛ በኋላ››

የኢዮአካዝ ልጅ ዮአስ በሰማርያ ከተማ እስራኤል ላይ መንገሥ ጀመረ
‹‹የኢዮአካዝ ልጅ ዮአስ በሰማርያ ሆኖ እስራኤልን መግዛት ጀመረ››

ዮአስ
ይህ የኢዮአካስ ልጅ የእስራኤል ንጉሥ ስም ነው።

በያህዌ ፊት ክፉ ሥራ ሠራ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ፊት›› የእግዚአብሔርን ሐሳብና ፍርድ ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ ክፉ ነው የሚለውን አደረገ››

የኢዮርብዓምን ኀጢአት ማድረግ አልተወም
ኀጢአትን ማቆም ኀጢአትን መተው እንደ ሆነ ተነግሯል። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ዮአስ ኢዮርብዓም ሲያደርገው የነበረውን ኀጢአት ማድረጉን አልተወም›› ወይም፣ ‹‹ዮአስ የኢዮርብዓምን ኀጢአት ማድረጉን ቀጠለ››

እስራኤልን ካሳተበት ኀጢአት
‹‹ኢዮርብዓም እስራኤል እንዲበደል ካደረገበት››

በዚያው ገፋበት
ኀጢአት በኀጢአት መንገድ መሄድ እንደ ሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ዮአስ ይህንኑ ኀጢአት ማድረጉን ቀጠለ››

2 Kings 13:12

በይሁዳ ንጉሥ በአሜስያስ ላይ ያካሄደው ጦርነት
እዚህ ላይ፣ የዮአስ፣ ብርታት የእርሱ ጉልበት እንደ ሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከይሁዳ ንጉሥ አሜስያስ ሰራዊት ጋር ሲዋጋ የእርሱ ሠራዊት ያሳየው ኀይል››

በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?
ጥያቄው የቀረበው ኢዮአስ ያደረገው ሁሉ በሌላ የታሪክ መጽሐፍ ተጽፎ የሚገኝ መሆኑን ለአንባቢው ማሳሰቢያ ለመስጠት ነው። 2 ነገሥት 1፥18 ይህ እንዴት እንደ ተተረጐመ ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የእስራኤል ነገሥታት ታሪክ በሚጻፍበት መጽሐፍ ተጽፎአል።››

ዮአስ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ
ይህ ሞተ ማለት ነው።

ኢዮርብዓም በዙፋኑ ተቀመጠ
እዚህ ላይ፣ ‹‹በዙፋን፣ መቀመጥ›› መንገሥ ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከእርሱ በኋላ ኢዮርብዓም ነገሠ›› ወይም፣ ‹‹ቀጥሎ ኢዮርብዓም ነገሠ››

2 Kings 13:14

አለቀሰለት
‹‹ኤልሳዕ ታሞ ስለ ነበር አለቀሰ››

አባቴ! አባቴ!
ኤልሳዕ በሥጋ የንጉሡ አባት አልነበረም። ንጉሥ ዮአስ እንዲህ ያለው ለአክብሮት ነው።

የእስራኤል ሠረገሎችና ፈረሰኞች ሊወስዱህ ነው
ይህ 2 ነገሥት 2፥11-12 ላይ ያለውን የኤልያስን ወደ ሰማይ መወሰድ ያመለክታል። ዮአስ ይህን ያለው ኤልሳዕ እንደሚሞት ለመናገር ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የእስራኤል ሠረገሎችና ፈረሰኞች ወደ ሰማይ ሊወስዱህ ነው››

ፈረሰኞች
እነዚህ ሠረገሎችን የሚነዱ ሰዎች ናቸው። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የሠረገሎች ነጂ››

2 Kings 13:17

አጠቃላይ መረጃ
ኤልሳዕ ለእስራኤል ንጉሥ ለዮአስ እየተናገረ ነው።

የምሥራቁን መስኮት ክፈት
‹‹በስተ ምሥራቅ በኩል ያለውን መስኮት ክፈት›› ወይም ‹‹ወደ ምሥራቅ ያለውን መስኮት ክፈት››

ከፈተውም
ይህ የሆነው ዮአስ ቀስቱንና ፍላጻዎቹን ከወሰደ በኋላ ስለ ነበር፤ መስኮቱን የከፈተው አገልጋዩ ሳይሆን አይቀርም። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አገልጋዩም ከፈተው››

አስፈነጠረ
‹‹ዮአስ ፍላጻውን አስፈነጠረ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይህ የያህዌ የድል ቀስት! ሶርያ ድል የምትሆንበት ቀስት ነው!
በፍላጻውና በድል መካከል ያለውን ግንኙነት በጣም ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሶርያውያን ላይ ድል እንደሚሰጥህ ይህ ቀስት ከያህዌ የሆነ ምልክት ነው›› ወይም ‹‹ይህ ቀስት ያህዌ በሶርያውያን ላይ የሚሰጥህን ድል ያመለክታል››

አፌቅ
ይህ በእስራኤል ያለ ከተማ ነው።

የእግዚአብሔር ሰው ተቆጣው
‹‹ኤልሳዕ በንጉሥ ዮአስ በጣም ተቆጣ››

እስክታጠፋቸው ድረስ
‹‹ጨርሶ እስክታወድማቸው ድረስ›› ወይም፣ ‹‹እስክትደመስሳቸው ድረስ››

2 Kings 13:20

እነሆ
ይህ የዋናውን ታሪክ ፍሰት ገታ ለማድረግ ጥቅም ላይ የዋለ ቃል ነው። ይህ ክፍል ቀጥሎ ላለው ታሪክ ዳራ የሚሆን መረጃ ይሰጣል።

በየዓመቱ መጀመሪያ
‹‹በመፀው ወቅት በየዓመቱ››

አንድ ሰው ሲቀብሩ
‹‹አንዳንድ እስራኤላውያን ሰው ሲቀብሩ››

የሞዓባውያንን ቡድን አዩ
ሞዓባውያንን መፍራታቸውን ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሞዓባውያን አደጋ ጣዮች ወደ እነርሱ ሲመጡ አይተው ፈሩ።

የኤልሳዕ መቃብር
‹‹ኤልሳዕ የተቀበረበት ቦታ››

ሰውየው የኤልሳዕን ዐፅም እንደ ነካ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ሰውየው›› የሚያመለክተው የሰውየውን ሬሳ ነው። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሰውየው ሬሳ የኤልሳዕን ዐፅም እንደ ነካ››

ድኖ በእግሩ ቆመ
‹‹የሞተው ሕይወት አገኘ፤ ተነሥቶም ቆመ››

2 Kings 13:22

ያህዌ ግን ራራላቸው፤ አዘነላቸው
ይህን ታሪክ በትንንሹ መከፋፈል ይጠቅማል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ ስላዘነ ረዳቸው››

ስለዚህም ያህዌ አላጠፋቸውም
ያህዌ እስራኤልን ያላጠፋው ከኪዳኑ የተነሣ ነው። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ያላጠፋቸው በዚህ ምክንያት ነው›› ወይም፣ ‹‹ከኪዳኑ የተነሣ ያህዌ አላጠፋቸውም››

ከፊቱም አላስወገዳቸውም
የያህዌ ችላ ማለት እርሱ ካለበት ቦታ እስራኤልን በግልጽ ከመተው ጋር ተመሳስሎአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አልተዋቸውም››

አዛሄል... ቤንሐዳድ... ዮአስ... ኢዮአካዝ
እነዚህ የነገሥታት ስሞች ናቸው

ዮአስ ሦስት ጊዜ ድል አደረገው
እዚህ ላይ ስለ ‹‹ዮአስ›› እና፣ ‹‹እርሱ የሚለው የሚያመለክተው ስለ ነገሥታቱና ስለ ሰራዊቱ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዮአስ ሰራዊት የቤንሐዳድን ሰራዊት ሦስት ጊዜ ድል አደረገ››

የእስራኤልንም ከተሞች መልሶ ያዘ
‹‹ዮአስ ቤንሐዳድ ይዞአቸው የነበሩትን የእስራኤል ከተሞች ተቆጣጠረ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 14

1 የኢዮአካዝ ልጅ ዮአስ በእስራኤል ላይ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት የኢዮአስ ልጅ አሜስያስ የይሁዳ ንጉሥ ሆነ። 2 እርሱም በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ሃያ አምስት
ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ሃያ ዘጠኝ ዓመት ገዛ፤ እናቱም ከኢየሩሳሌም ዮዓዳን ተብላ የምትጠራ ነበረች። 3 አሜስያስ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሥራ
ሠርቶአል፤ ይሁን እንጂ እንደ ቀድሞ አያቱ እንደ ንጉሥ ዳዊት አልነበረም፤ እንደ ዳዊት በመሆን ፈንታ የአባቱን የኢዮአስን ፈለግ ተከተለ። 4 ይኸውም
በየኮረብታዎቹ ላይ የተሠሩትን የአሕዛብ ማምለኪያዎችን አላፈረሰም፤ ከዚህም የተነሣ ሕዝቡ በየኮረብታዎቹ መሥዋዕት ማቅረቡንና ዕጣን ማጠኑን እንደቀጠለ
ነበር። 5 አሜስያስ መንግሥቱን አደላድሎ እንደ ያዘ ወዲያውኑ፣ ቀደም ሲል ነግሦ የነበረውን አባቱን የገደሉትን ባለሥልጣኖች በሞት ቀጣ፤ 6 ይሁን እንጂ
ልጆቻቸውን አልገደለም፤ ይልቁንም በኦሪት ሕግ እግዚአብሔር «ልጆቻቸው በፈጸሙት ኃጢአት ወላጆች በሞት አይቀጡበትም፤ ወላጆችም በፈጸሙት ኃጢአት
ልጆች በሞት አይቀጡበትም፤ እያንዳንዱ ሰው ራሱ በፈጸመው ወንጀል ብቻ በሞት ይቀጣል» ሲል የሰጠውን ትእዛዝ ፈጽሞአል። 7 አሜስያስ «የጨው ሸለቆ»
እየተባለ በሚጠራው ስፍራ ዐሥር ሺህ የሚሆኑ የኤዶም ወታደሮችን ፈጀ፤ ሴላ ተብላ የምትጠራውንም ከተማ ይዞ «ዮቅትኤል» ብሎ ጠራት፤ እስከ አሁንም
በዚሁ ስም ትጠራለች። 8 ከዚህ በኋላ አሜስያስ ወደ እስራኤል ንጉሥ ወደ ኢዩ ልጅ ወደ ዮአስ መልእክተኞችን በመላክ «እንግዲህ ና ፊት ለፊት ጦርነት
እንግጠም!» ሲል ለጦርነት አነሣሣው። 9 ንጉሥ ዮአስ ግን እንዲህ ሲል መለሰለት «አንድ ጊዜ በሊባኖስ ተራራ ላይ የምትገኝ ኩርንችት የሊባኖስ ዛፍ ‹ለወንድ
ልጄ ሚስት ትሆነው ዘንድ ሴት ልጅህን ስጠኝ› ስትል መልእክት ላከችበት፤ ነገር ግን አንድ የሊባኖስ አውሬ እግረ መንገዱን በዚያ ሲያልፍ ስለ ረገጣት ያቺ
ኩርንችት ሞተች። 10 አሜስያስ ሆይ! እነሆ አንተ ኤዶማውያንን ድል ስላደረግህ ልብህ በትዕቢት ተሞልቶአል፤ ባገኘኸውም ድል በመደሰት ዐርፈህ በቤትህ
ብትቀመጥ ይሻልሃል፤ በአንተና በሕዝብህ ላይ መከራና ውድቀት ስለ ምን ታስከትላለህ?» 11 አሜስያስ ግን የዮአስን መልስ ከምንም አልቆጠረውም፤
ስለዚህም ንጉሥ ዮአስ ሠራዊቱን አስከትሎ በአሜስያስ ላይ በመዝመት በይሁዳ ምድር በምትገኘው በቤት ሳሚስ ጦርነት ገጠመው። 12 ይሁዳም ድል
ተመታ፤ ወታደሮቹም ሁሉ ተበታትነው ወደየቤታቸው ተመለሱ። 13 ዮአስም የአካዝያስን ልጅ፣ የኢዮአስን ልጅ አሜስያስን ከነሕይወቱ ማረከው፤ ወደ
ኢየሩሳሌምም ለመድረስ ገሠገሠ፤ እዚያም እንደ ደረሰ ከኤፍሬም ቅጥር በር «የማዕዘን ቅጥር በር» ተብሎ እስከሚጠራው በር ድረስ ጠቅላላ ርዝመቱ ሁለት
መቶ ሜትር የሆነውን የቅጥር ግንብ አፈረሰ። 14 በዚያም ያገኘውን ወርቅና ብር ሁሉ፣ የቤተ መቅደሱን ንዋያተ ቅዱሳትና የቤተ መንግሥቱን ሀብት ሁሉ ጭኖ
ወደ ሰማርያ ተመለሰ፤ በመያዣ ስም የተማረኩ ሰዎችንም ይዞ ሄደ። 15 ንጉሥ ዮአስ ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ እንዲሁም በይሁዳ ንጉሥ በአሜስያስ ላይ
ባደረገው ጦርነት የፈጸመው የጀግንነት ሥራ ጭምር በእስራኤል ነገሥታት መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኛል። 16 ዮአስ ሞተ፤ በሰማርያ በሚገኘውም የነገሥታት
መካነ መቃብር ተቀበረ፤ በእርሱም ፈንታ ተተክቶ ዳግማዊ ኢዮርብዓም ነገሠ። 17 የእስራኤል ንጉሥ የኢዮአካዝ ልጅ ዮአስ ከሞተ በኋላ፣ የይሁዳ ንጉሥ የዮአስ
ልጅ አሜስያስ ዐሥራ አምስት ዓመት ቆየ። 18 አሜስያስ ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ በይሁዳ ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኛል። 19 አሜስያስን
ለመግደል በኢየሩሳሌም ሤራ ተጠንስሶ ነበር፤ ስለዚህ አሜስያስ ሸሽቶ ወደ ለኪሶ ከተማ ሄደ፤ ነገር ግን ጠላቶቹ ወደ ለኪሶ ሰዎችን ልከው እዚያ አስገደሉት።
20 ሬሳውም በፈረስ ተጭኖ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ፤ በዳዊት ከተማ በሚገኘውም የነገሥታት መካነ መቃብር ተቀበረ። 21 የይሁዳም ሕዝብ የዐሥራ ስድስት
ዓመት ልጁ የነበረውን ዓዛርያስን አነገሡት፤ 22 ዓዛርያስም ቀድሞ ተይዞ የነበረችውን ኤላትን ከአባቱ ሞት በኋላ በጦር ኃይል ድል ነሥቶ አስመልሶ እንደገና
ሠራት። 23 የኢዮአስ ልጅ አሜስያስ በይሁዳ በነገሠ በዐሥራ አምስተኛው ዓመት የዮአስ ልጅ ኢዮርብዓም በእስራኤል ነገሠ፤ እርሱም በሰማርያ አርባ አንድ
ዓመት ገዛ። 24 ዳግማዊ ኢዮርብዓምም እስራኤልን ወደ ኃጢአት የመራ ከእርሱ በፊት የነበረውን የናባጥ ልጅ የኢዮርብዓምን መጥፎ አርአያነት በመከተል
ኃጢአት በመሥራቱ እግዚአብሔርን አሳዘነ። 25 ቀድሞ የእስራኤል ይዞታ የነበረውን በስተሰሜን ከሐማት መተላለፊያ ጀምሮ በስተ ደቡብ እስከ ሙት ባሕር
የሚገኘውን ግዛት ሁሉ ድል ነሥቶ እንደገና አስመለሰ፤ ይህም ሁሉ የተፈጸመው በጋትሔፌር ተወላጅ አገልጋይ በሆነው በአሚታይ ልጅ በነቢዩ ዮናስ አማካይነት
የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር በሰጠው የተስፋ ቃል መሠረት ነበር። 26 እግዚአብሔር የእስራኤላውያንን አሠቃቂ መከራ ተመለከተ፤ በእስራኤል ውስጥ
ባርያዎችም ሆኑ ነጻ ሰዎች ረዳት አልነበራቸውም። 27 ይሁን እንጂ እነርሱ ለዘለዓለም ፈጽሞ እንዲደመሰሱ የእግዚአብሔር ፈቃድ አልነበረም፤ ስዚህ በዳግማዊ
ኢዮርብዓም አማካይት አዳናቸው። 28 ዳግማዊ ኢዮርብዓም ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ፣ በጦርነት ላይ ያሳየው ጀግንነት፣ እንዲሁም የይሁዳ ግዛት የነበሩት
ደማስቆና ሐማት ለእስራኤል እንዲመለሱ ያደረገበት ታሪካዊ ነገር ሁሉ በእስራኤል ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኛል። 29 ከዚህ በኋላ ዳግማዊ
ኢዮርብዓም ሞተ፤ በነገሥታት መካነ መቃብርም ተቀበረ፤ በእርሱም ፈንታ ተተክቶ ልጁ ዘካርያስ ነገሠ።

---

2 Kings 14:1

የእስራኤል ንጉሥ የኢዮአካዝ ልጅ ዮአስ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት
‹‹የኢዮአካዝ ልጅ ዮአስ የእስራኤል ንጉሥ በሆነ በሁለተኛው ዓመት››

የኢዮአስ ልጅ አሜስያስ በይሁዳ መንገሥ ጀመረ
‹‹የኢዮአስ ልጅ አሜስያስ የይሁዳ ንጉሥ ሆነ››

መንገሥ ሲጀምር ሃያ አምስት ዓመቱ ነበር።
‹‹ንጉሥ ሲሆን 25 ዓመት ሆኖት ነበር››

በኢየሩሳሌም ተቀምጦ ሃያ ዘጠኝ ዓመት ገዛ
‹‹ለ29 ዓመት በኢየሩሌም ነግሦ ነበር››

ዮዓዳን
(ስሞች እንዴት እንደሚረጐሙ ተመልከት)

በያህዌ ፊት መልካም ነገር አደረገ፤ ግን እንደ አባቱ እንደ ዳዊት አልነበረም።
‹‹የያህዌ ፊት›› የእርሱን ዐይን፣ የእርሱ ዐይን ደግሞ ፍርዱን ያመለክታል።
አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ኤሜስያስ በያህዌ ፊት ብዙ መልካም ነገሮች አደረገ፤
ሆኖም አባቱ ዳዊት ያደረገውን ያህል መልካም ነገሮች አላደረገም››

የአባቱን የዮአስን ፈለግ ተከተለ
ዮአስ ለያህዌ ታዘዙ መልካም ነገርንም አደረገ፤ ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ
ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አባቱ ዮአስ ያደረገውን መልካም ነገር
አደረገ››

2 Kings 14:4

አጠቃላይ መረጃ
አሜስያስ የይሁዳ ንጉሥ ሆኖ የመግዛቱ ታሪክ ቀጥሏል።

ከፍታ ቦታዎቹን ግን አላስወገደም
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። ከፍታ ቦታዎች ለአረማውያን
አምልኮ የሚውሉ ነበሩ። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ
ትርጕም፣ ‹‹ከፍታ ቦታዎቹን አላስወገደም››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መሥዋዕት ማቅረቡንና ዕጣን ማጨሱን
ከፍታ ቦታዎቹ ለአረማውያን አምልኮ የሚውሉ ናቸው። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በከፍታ ቦታዎቹ ለአረማውያን አማልክት መሥዋዕት አቀረበ፤ ዕጣን አጠነ››

በዚሁ ጊዜ
ይህ ጥቅም ላይ የዋለው አዲስ ሁኔታ ለማስተዋወቅ ነው።

መንግሥቱ እንደ ጸናለት
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አሜስያስ ሲደላደልና መንግሥታዊ ሥልጣኑና አገዛዙ ሲረጋጋ››

አገልጋዮቹን ገደለ
አሜስያስ ባለ ሥልጣኖቹን እንዲገድሉ ያደረገውሌሎች ሹማምንት በማዘዝ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አገልጋዮቹ ባለ ሥልጣኖቹን እንዲገደሉ አዘዘ››

2 Kings 14:6

አጠቃላይ መረጃ
አባቱ ንጉሥ ዮአስ ከሞተ በኃላ ንጉሥ አሜስያስ ምን እንዳደረገ ተራከው ይናገራል››

የነፍስ ገዳዩን ልጆች አልገደላቸውም
ንጉሥ አሜስያስ አባቱን የገደሉ ሰዎችን ልጆች እንዲገድሉ አገልጋዮቹን አለዘዘም። እንዲገደሉ ቢፈልግ ኖሮ፣ አገልጋዮቹን ያዝዝ ነበር እንጂ፣ ያንን እርሱ ራሱ ማድረግ የለበትም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አገልጋዮቹ የእነዚያን ባለሥልጣን ልጆች እንዲገደሉ አላዘዘም››

አባቶች በልጆቻቸው፣ ልጆችም በአባቶቻቸው ኀጢአት መገደል የለባቸውም
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች አባቶችን ለልጆቻቸው ኀጢአት፣ ልጆችንም በአባቶቻቸው ኀጢአት መግደል የለባቸውም››

እያንዳንዱ በራሱ ኀጢአት ይገደል
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እያንዳንዱ ሰው በኀጢአቱ መሞት አለበት››

እርሱ ገደለ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እርሱ›› የሚያመለክተው ሰራዊቱን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአሜስያስ ሰራዊት ገደለ›› ወይም፣ ‹‹የአሜ ስያስ ወታደሮች ገደሉ››

ዐሥር ሺህ ወታደሮች
‹‹10,000 ወታደሮች››

የጨው ሸለቆ
ይህ ከሙት ባሕር በስተ ደቡብ የሚገኝ ቦታ ስም ነው።

ሴላን በጦርነት የያዘና
የሚናገረው ስለ ንጉሥ አሜስያስ ሲሆን፣ እርሱንና ሰራዊቱን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የንጉሥ አሜስያስ ሰራዊት የሴላን ከተማ ያዘ››

ሴላ... ዮቅትኤል
ለሴላ ከተማ ሌላ ስም አወጡላት። አዲሱ ስሟ ዮቅትኤል ነበር።

2 Kings 14:8

አሜስያስ የኢዩ ልጅ፣ የኢዮአካዝ ልጅ ወደ ሆነው ወደ እስራኤል ንጉሥ ወደ ኢዮአስ፣ ‹‹ናና ፊት ለፊት ይዋጣልን›› ብሎ መልእክተኞች ላከበት
እዚህ ላይ፣ ‹‹ይዋጣልን›› የሚለው ሰራዊቱንም ይጨምራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከዚያም አሜስያስ፣ ‹‹መጥተህ ሰራዊቶቻችን ጦርነት ይግጠሙ›› በማለት ወደ ንጉሥ ኢዮአስ መልእክተኞች ላኩ››

የሊባኖስ ኩርንችት... ኩርንችቱን በእግሩ ረገጠው
ይህ የቃላት ስዕልና ዕንቆቅልሽ ነው። የሊባኖስ ዝግባ ትልቅ ሲሆን፣ ኩርንችት ደግሞ ትንሽና የማይረባ ነው። ኢዮአስ ራሱን ከሊባኖስ ዝግባ፣ አሜስያስን ከኩርንችት ጋር በማመሳሰል ጥቃት እንዳይሰነዝር አሜስያስን እያስጠነቀቀ ነው። በቋንቋህ ተመሳሳይ ንጽጽር ካለህ ልትጠቀምበት ትችላለህ።

ኩርንቺት
እሾኻማ ቁጥቋጦ

ሴት ልጅህን ለልጄ በሚስትነት ስጠው
ይህን ቀጥተኛ ጥቅስ ቀጥተኛ ወዳልሆነ ጥቅስ መለወጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዝግባው ሴት ልጁን ለኩርንቺቱ ወንድ ልጅ እንዲድርለት ጠየቀው››

በእርግጥ ኤዶምን ድል አድርገሃል
ይህ ኢዮአስ ለአሜስያስ የሰጠው ማስጠንቀቂያ ክፍል ነው። ‹‹አሜስያስ አንተ በእርግጥ ኤዶምን ድል አድርገሃል››

ልብህ አለመጠን አይኩራራ
ይህ ትዕቢትን የሚያመለክት የፈሊጥ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ባደረግኸው ነገር በጣም ታብየሃል››

ድል በማድረግህ አትንጠራራ
‹‹ባገኘኸው ድል አትርካ››

የራስህን ውድቀት ለምን ትሻለህ?
ኢዮአስ ይህን የጠየቀው እርሱን እንዳያጠቃ አሜስያስን ለማስጠንቀቅ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ራስህ ላይ ሽንፈት የሚያመጣብህን ጠብ መጫር የለብህም››

2 Kings 14:11

አሜስያስ ግን አልሰማም
እዚህ ላይ፣ ‹‹አልሰማም›› ማለት ማስጠንቀቂያውን አልተቀበለም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይሁን እንጂ፣ አሜስያስ የኢዮአስን ማስጠንቀቂያ አልተቀበለም››

ስለዚህ የእስራኤል ንጉሥ ኢዮአስ አጠቃ... ከይሁዳ ንጉሥ አሜስያስ ጋር ገጠሙ››
የእነዚህ ነገሥታት ሰራዊት አብረው ወደ ጦርነት ሄዱ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኢዮአስና ሰራዊቱ አሜስያስና ሰራዊቱን ለመግጠም ወደ ውጊያ ሄዱ››

ቤትሳሚስ
ይህ እስራኤል ድንበር አጠገብ ያለ የይሁዳ ከተማ ነው።

ይሁዳ በእስኤል ድል ሆነ
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እስራኤል ይሁዳን አሸነፈ››

እያንዳንዱም ሸሸ
‹‹ይሁዳ ሰራዊት ውስጥ የነበረ ሰው ሁሉ ወደ ቤቱ ሸሸ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Kings 14:13

አጠቃላይ መረጃ
የእስራኤል ሰራዊት በቤትሳሚስ የይሁዳን ሰራዊት ድል ካደረገ በኃላ የሆነ ነው።

እርሱ መጣ... እርሱ ወሰደ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እርሱ›› የተባለው የኢዮአስ ሰራዊት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኢዮአስና ሰራዊቱ መጡ... የኢዮአስ ሰራዊት ወሰዶ››

የኤፍሬም ቅጥር በር... የማእዘን ቅጥር በር
እነዚህ በኢየሩሳሌም ቅጥር ላይ የነበሩ በሮች ናቸው።

አራት መቶ ክንድ
‹‹180 ሜትር ያህል››

ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሴንቲሜትር ያህል ነው።

ምርኮኞችን ይዞ ወደ ሰማርያ ተመለሰ
ይህ የሚያመለክተው አሜስያስ እንደ ገና እንዳያጠቃ ለመከላከል ኢዮአስ እነዚህን ምርኮኞች መውሰድ መፈለጉን ነው። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእንግዲህ አሜስያስ ችግር እንዳይፈጥርባቸው ለማድረግ እስረኞችን ወደ ሰማርያ ወሰዱ››

2 Kings 14:15

ይህ ሁሉ በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?
ይህ ጥያቄ የቀረበው የኢዮአካዝ ሥራ በሌላ መጽሐፍ ተጽፎ የሚገኝ መሆኑን አንባቢውን ለማሳሰብ ነው። 2 ነገሥት 1፥18 ላይ ይህ ሐረግ እንዴት እንደ ተተረጐመ ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤል ነገሥታት ታሪክ በተጻፈበት መጽሐፍ ተጽፎአል››

ከዚያም ኢዮአስ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ
ይህ ሞተ የማለት ሌላ ቃል ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከዚያም ኢዮአስ ሞተ››

በእግሩ ተተክቶ ነገሠ
‹‹ከእርሱ በኃላ ነገሠ››

2 Kings 14:17

በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?
ይህ ጥያቄ የቀረበው እነዚህ ሁሉ ተጽፈው ያሉ መሆኑን አንባቢውን ለማሳሰብ ነው። 2 ነገሥት 8፥23 ላይ ይህ ሐረግ እንዴት እንደ ተተረጐመ ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የይሁዳ ነገሥታት ታሪክ በተጻፈበት መጽሐፍ ተጽፈዋል››

አሜስያስ ላይ በኢየሩሳሌም አሤሩበት
ሤራ አንድ ሰው ወይም አንድ ነገር ላይ ጉዳት ለማድረስ በሚስጢር ማቀድ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በኢየሩሳሌም አንዳንድ ሰዎች አሜስያስ ላይ ተማከሩበት››

ለኪሶ
ይህ በደቡብ ምዕራብ ይሁዳ ያለ ከተማ ነው።

እነርሱ ግን የሚከታተሉት ሰዎች ወደ ለኪሶ ላኩ
‹‹ሤራውን የጠነሰሱ ዎች አሜስያስን እንዲከታተሉ ሌሎች ሰዎች ወደ ለኪሶ ላኩ››

2 Kings 14:20

አጠቃላይ መረጃ
ይህ የሆነው አሜስያስ ከሞተ በኃላ ነው።

በፈረስ ተጭኖ አመጡት
‹‹የአሜስያስን ሬሳ በፈረስ ጭነው አመጡት››

የይሁዳ ሕዝብ በሙሉ ዕድሜው ዐሥራ ስድስት ዓመት የሆነውን ዓዛርያስን በአባቱ በአሜስያስ ፈንታ አነገሡት
ይህ አጠቃላይ አነጋገር ነው። አንዳንድ ንጉሥ መሆኑን የማይወዱ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የይሁዳ ሕዝብ ዐሥራ ስድስት ዓመት የሆነውን ዓዛርያስን በአባቱ በአሜስያስ ቦታ አነገሡት››

ኤላትን እንደ ገና የሠራ ዓዛርያስ ነበር
ዓዛርያስ ይህን ያደረገው ብቻውን አይደለም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኤላት እንድትሠራ ያዘዘ ዓዛርያስ ነበር›› ወይም፣ የኤላትን እንደ ገና መሠራት ሲቆጣጠር የነበሩ ዓዛርያስ ነበር››

ዓዛርያስ
በዚህ ዘመን ይህ ንጉሥ ይበልጥ የሚታወቀው፣ ‹‹ዖዝያን›› በተሰኘ ስሙ ነው።

ኤላት
የይሁዳ ከተማ

ወደ ይሁዳ መለሳት
‹‹እንደ ገና ወደ ይሁዳ አመጣት››

ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ
ይህ ሞተ ለማለት ነው።

2 Kings 14:23

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ንጉሥ ከሆነ በኃላ ንጉሥ ዖዝያን ያደረገውን ይናገራል።

አሜስያስ በነገሠ በዐሥራ አምስተኛው ዓመት
‹‹አሜስያስ ንጉሥ በሆነ 15ኛው ዓመት››

አርባ አንድ ዓመት
‹‹41 ዓመት››

በያህዌ ፊት ክፉ
‹‹ፊት›› የፍርድ ወይም የግንዛቤ ምሳሌ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በያህዌ ሐሳብ ክፉ የሆነ›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ክፉ የሚለውን››

ከኢዮርብዓም ኀጢአት አልተመለሰም
ኀጢአትን መተው መንገድን መተው እንደሆነ ተነግሯል። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኢዮርብዓም ሲያደርግ የነበረውን ኀጢአት ማድረጉን አልተወም›› ወይም፣ ‹‹ኢዮርብዓም ሲያደርግ የነበረውን ኀጢአት ማድጉን ቀጠለ››

ድንበር አስመለሰ
ይህ ሰራዊቱ ድንበሩን ወደ ምድሩ መለሰ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰራዊቱ ከዚያ በፊት የእስራኤል የነበሩ ግዛቶችን እንደ ገና ድል አደረገ››

ሌቦሐማት
ይህ ሐማት ተብሎም ይጠራል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የአረባ ባሕር
‹‹ሙት ባሕር››

2 Kings 14:26

በጣም መራራ ነበር
በጣም ከባድ የሆነ ስቃይ፣ መራራ ጣዕም እንዳለው ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጣም ከባድ ነበር››

እስራኤልን የሚታደግ አልነበሩም
‹‹እስራኤልን ማዳን የሚችል አልነበረም››

ጠረገ
እስራኤልን ጨርሶ ማጥፋት ያህዌ ጠረጋቸው ማለት መሆኑ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሙሉ በሙሉ አጠፋቸው››

የእስራኤል ስም
‹‹የእስራኤል ስም›› እስራኤልንና ነዋሪዎቹን ሁሉ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤል ሕዝብ››

ከሰማይ በታች
‹‹በምድር››

በኢዮአስ ልጅ በኢዮርብዓም እጅ ታደጋቸው
‹‹እጅ›› የጎይል ሌላ ስም ነው። ‹‹ኢዮአስ›› ኢዮአስንና ሰራዊቱን ሁሉ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ድል እንዲያደርግ ንጉሥ ኢዮርብዓምንና ሰራዊቱን ረዳ››

2 Kings 14:28

በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?
ጥያቄው የቀረበው የኢዮአካዝ ተግባር በሌላ የታሪክ መጽሐፍ ተጽፎ እንደሚገኝ ለአንባቢ ለማሳሰብ ነው። 2 ነገሥት 1፥18 ላይ ይህ ሐረግ እንዴት እንደ ተተረጐመ ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤል ነገሥታት ታሪክ በተጻፈበት መጽሐፍ ተጽፎአል››

ኢዮርብዓም ከአባቶቹ ከእስራኤል ነገሥታት ጋር አንቀላፋ
x

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 15

1 ዳግማዊ ኢዮርብዓም በእስራኤል በነገሠ በሃያ ሰባተኛው ዓመት የአሜስያስ ልጅ ዓዛርያስ በይሁዳ ንጉሥ ሆነ። 2 እርሱም በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ዐሥራ
ስድስት ዓመት ነበረ፤ እርሱም በኢየሩሳሌም ሃምሳ ሁለት ዓመት ገዛ፤ እናቱም ይኮልያ ተብላ የምትጠራ የኢየሩሳሌም ተወላጅ ነበረች። 3 እርሱም የአባቱን
መልካም አርአያነት በመከተል እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሥራ ሠራ። 4 ነገር ግን በየኮረብቶቹ ላይ የነበሩትን የአሕዛብን የማምለኪያ ቦታዎች አላጠፋቸውም
ነበር፤ ስለዚህም ሕዝቡ በየኮረብቶቹ ላይ መሥዋዕት ማቅረባቸውንና ዕጣን ማጠናቸውን እንደ ቀጠሉ ነበር፤ 5 በኋላም እግዚአብሔር ዓዛርያስን በቆዳ በሽታ
መታው፤ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ ይህ በሽታ ስላልለቀቀው ከሥራው ሁሉ ተገልሎ በተለየ ቤት ውስጥ ለብቻው ይኖር ነበር፤ በዚህም ጊዜ መንግሥቱን ሲመራ
የቆየው ልጁ ኢዮአታም ነበር። 6 ንጉሥ ዓዛርያስ ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ በይሁዳ ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ውስጥ ተመዝግቦ ይገኛል። 7 ዓዛርያስም ሞተ፤
በዳዊት ከተማ በሚገኘው በቀድሞ አባቶቹ መካነ መቃብር ተቀበረ፤ በእርሱም ፈንታ ተተክቶ ልጁ ኢዮአታም ነገሠ። 8 ዓዛርያስ በይሁዳ በነገሠ በሠላሳ
ስምንተኛው ዓመት የዳግማዊ ኢዮርብዓም ልጅ ዘካርያስ በእስራኤል ነገሠ፤ እርሱም በሰማርያ ስድስት ወር ገዛ። 9 እርሱም ከእርሱ በፊት እንደ ነበሩት ነገሥታት
ሁሉ ኃጢአት በመሥራት እግዚአብሔርን አሳዘነ፤ እዲሁም እስራኤልን ወደ ኃጢአት መራ፤ የናባጥ ልጅ የንጉሥ ኢዮርብዓምን መጥፎ አርአያነት ተከተለ። 10
ሰሎም ተብሎ የሚጠራው የኢያቤስ ልጅ ሤራ በማድረግ ይብልዓም ተብላ በምትጠራው ስፍራ ንጉሥ ዘካርያስን ገድሎ በእርሱ ፈንታ ነገሠ። 11 ንጉሥ
ዘካርያስ ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ በእስራኤል ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኛል። 12 በዚህም ዓይነት እግዚአብሔር ለንጉሥ ኢዩ ልጆችህ እስከ
አራት ትውልድ በእስራኤል ይነግሣሉ ሲል የተናገው የተስፋ ቃል ተፈጸመ። 13 ዓዛርያስ በይሁዳ በነገሠ በሠላሳ ዘጠነኛው ዓመት የኢያቤስ ልጅ ሰሎም
የእስራኤል ንጉሥ ሆነ። እርሱም በሰማርያ አንድ ወር ብቻ ገዛ። 14 ምናሔ ተብሎ የሚጠራው የጋዲ ልጅ ከቲርጻ ተነሥቶ ወደ ሰማርያ ሄደ፤ የኢያቤስን ልጅ
ሰሎምን ገድሎም በእርሱ ፈንታ ነገሠ። 15 ሰሎም ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ እንዲሁም እርሱ የጠነሰሰው ሤራ ሁሉ በእስራኤል ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ
ተመዝግቦ ይገኛል። 16 ምናሔም ከቲርጻ ተነሥቶ በሚያልፍበት ጊዜ የቲፍሳን ከተማ ነዋሪዎችና በዙሪያዋ የነበረውን ግዛት ሁሉ ደመሰሰ። ይህንንም ያደረገበት
ምክንያት የከተማይቱ ነዋሪዎች ለእርሱ እጃቸውን ለመስጠት ባለመፍቀዳቸው ነበር፤ ከዚህም የተነሣ ነፍሰ ጡሮችን እንኳ ሳይምር ሆዳቸውን ቀደደ። 17
ዓዛርያስ በይሁዳ በነገሠ በሠላሳ ዘጠነኛው ዓመት የጋዲ ልጅ ምናሔም በእስራኤል ነገሠ። እርሱም በሰማርያ ዐሥር ዓመት ገዛ። 18 እስከ ዕድሜው ፍጻሜ
ድረስ እስራኤልን ወደ ኃጢአት የመራ የናባጥ ልጅ የኢርብዓምን መጥፎ አርአያነት በመከተል ኃጢአት በመሥራቱም እግዚአብሔርን አሳዘነ። 19 የአሦር ንጉሠ
ነገሥት ፎሐ እስራኤልን ወረረ፤ ምናሔም በአገሩ መንግሥት ላይ ሥልጣኑን እንዲያጸናለትና እንዲደግፈው ለመማጠን ሠላሳ አራት ሺህ ኪሎ የሚመዝን ብር
እጅ መንሻ አድርጎ ለፎሐሰጠው። 20 ምናሔም ገንዘቡን የሰበሰበው የእስራኤል ከበርቴዎች እየንዳንዳቸው ኀምሳ ጥሬ ብር አዋጥተው እንዲሰጡ በማስገደድ
ነበር። በዚህም ዓይነት ፎሐ በሰላም ወደ አገሩ ተመልሶ ሄደ። 21 ምናሔም ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ በእስራኤል ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ
ይገኛል። 22 ምናሔም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ በእርሱም ፈንታ ተተክቶ ልጁ ፋቂስያስ ነገሠ። 23 ዓዛርያስ በይሁዳ በነገሠ በኀምሳኛው ዓመት የምናሔም ልጅ
ፋቂስያስ በእስራኤል ነገሠ፤ እርሱም በሰማርያ ሁለት ዓመት ገዛ። 24 እስራኤልን ወደ ኃጢአት የመራ የናባጥ ልጅ የንጉሥ ኢዮርብዓምን መጥፎ አርአያነት
በመከተል ኃጢአት ስለ ሠራ እግዚአብሔርን አሳዘነ። 25 በፋቂስያስ ሠራዊት መካከል ፋቁሔ ተብሎ የሚጠራው የሮሜልዩ ልጅ የሆነ አንድ የጦር አዛዥ
ከኀምሳ የገለዓድ ሰዎች ጋር ሆኖ ሤራ ጠነሰሰ፤ በሰማርያ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ በሚገኘው ምሽግ ውስጥ ዘልቆ በመግባትም ፋቂስያስን ከአርጎብና ከአርዬ
ጋር ገድሎ በፋቂስያስ ፈንታ ተተክቶ ነገሠ። 26 ፋቂስያስ ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ በእስራኤል ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኛል። 27 ዓዛርያስ
በይሁዳ በነገሠ በኀምሳ ሁለተኛው ዓመት የሮሜልዩ ልጅ ፋቁሔ በእስራኤል ነገሠ፤ እርሱም በሰማርያ ሃያ ዓመት ገዛ። 28 እስራኤልን ወደ ኃጢአት የመራውን
የናባጥ ልጅ የንጉሥ ኢዮርብዓምን መጥፎ አርአያነት በመከተል ኃጢአት ስለ ሠራ እግዚአብሔርን አሳዘነ። 29 የአሦር ንጉሠ ነገሥት ቴልጌልቴልፌልሶር ዒዮን፣
አቤልቤትመዓካ፣ ያኖዋ፣ ቃዴስና ሐጾር ተብለው የሚጠሩትን ከተሞች እንዲሁም የገለዓድን፣ የገሊላንና የንፍታሌምን ግዛቶች በመውረር ሕዝቡን ወደ አሦር
ማርኮ የወሰደው ይኸው ፋቁሔ በነገሠበት ዘመን ነበር። 30 የዖዝያንም ልጅ ኢዮአታም በይሁዳ በነገሠ በሃያኛው ዓመት የኤላ ልጅ ሆሴዕ በንጉሥ ፋቁሔ ላይ
ሤራ ጠነሰሰ፤ እርሱንም ገድሎ በእስራኤል ላይ ነገሠ። 31 ፋቁሔ ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ በእስራኤል ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኛል። 32
የሮሜልዩ ልጅ ፋቁሔ በእስራኤል በነገሠ በሁለተኛው ዓመት የዖዝያን ልጅ ኢዮአታም የይሁዳ ንጉሥ ሆነ። 33 በነገሠም ጊዜ ዕድሜው ሃያ አምስት ዓመት
ነበር፤ በኢየሩሳሌም ዐሥራ ስድሰት ዓመት ገዛ። እናቱም ኢየሩሳ ተብላ የምትጠራ የሳዶቅ ልጅ ነበረች። 34 የአባቱንም የዖዝያንን መልካም አርአያነት በመከተል
እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሥራ ሠራ። 35 ነገር ግን በየኮረብቶቹ ላይ የነበሩትን የአሕዛብን መሠዊያዎች አላስወገደም፤ ሕዝቡም መሥዋዕት ማቅረባቸውንና
ዕጣን ማጠናቸውን እንደ ቀጠሉ ነበር፤ የቤተ መቅደሱን ሰሜናዊ ቅጥር በር ያሠራው ይኸው ኢዮአታም ነበር። 36 ኢዮአታም ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ በይሁዳ
ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኛል። 37 እግዚአብሔር በመጀመሪያ የሶርያ ንጉሥ ረአሶንና የእስራኤል ንጉሥ ፋቁሔ በይሁዳ ላይ አደጋ እንዲጥሉባት
የላካቸው ይኸው ኢዮአታም በይሁዳ በነገሠበት ዘመን ነበር። 38 ኢዮአታምም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ በዳዊት ከተማ በሚገኘው የነገሥታት መካነ መቃብርም
ተቀበረ፤ በእርሱም ፈንታ ተተክቶ ልጁ አካዝ ነገሠ።

---

2 Kings 15:1

ኢዮርብዓም በነገሠ በሃያ ሰባተኛው ዓመት
ይህ የአዝዛዝ ዘመኑ ሃያ ሰባተኛ ዓመት መሆኑን በግልጽ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኢዮርብዓም በነገሠ በ27 ዓመት››

ዓዛርያስ
በዚህ ዘመን ይህ ንጉሥ ይበልጥ የሚወቀው፣ ‹‹ዖዝያን በተሰኘው ስም ነው።

ይካልያ
ይህ የዓዛርያስ እናት ስም ነው

መልካም ነገር አደረገ
‹‹ዓዛርያስ መልካም ነገር አደረገ››

በያህዌ ዐይን ፊት መልካም ነገር
ዐይን ማየትን ይወክላል፤ ማየት ደግሞ ሐሳብና ፍርድን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በያህዌ ፍርድ መልካም ነገር›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ መልካም የሚለውን››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Kings 15:4

በየኮረብታው ላይ ያሉት የማምለኪያ ስፍራዎች አልተወገዱም
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ኮረብቶቹን ማንም አላስወገደም›› ወይም፣ ‹‹ዓዛርያስ ኮረብቶቹ እንዲወገዱ አላደረገም››

አልተወገደም
መወገድ ጨርሶ መደምሰስ ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አልተደመሰሱም ነበር››

እስከሚሞትባት ቀን ድረስ
አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ››

ቤተ ሰቡን የሚያስተዳድረው የንጉሡ ልጅ ኢዮአታም ነበር
‹‹ቤተ ሰቡን›› የሚለውን በቤተ መንግሥቱ የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታል። ዓዛርያስ ለምጻም ስለ ነበር በተለየ ቤት መኖር ነበረበት። ልጁ ኢዮአታም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

በቤቱ ሁሉ ኀላፊ ሆነ
በቤቱ ሁሉ ኀላፊ መሆን በቤቱ ላይ ባለ ሥልጣን መሆን ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በቤቱ ሁሉ ባለ ሥልጣን ሆነ›› ወይም፣ ‹‹በዓዛርያስ ቤተ መንግሥት ባለ ሥልጣን ሆነ››

2 Kings 15:6

በይሁዳ... የተጻፈ አይደለምን?
ይህ ጥያቄ የቀረበው ዓዛርያስን የሚመለከት መረጃ በዚህ ሌላ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ መሆኑን ለአንባቢው ለማሳሰብ ነው። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። 2 ነገሥት 8፥23 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐመኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በይሁዳ... ተጽፎአል›› ወይም፣ ‹‹በይሁዳ... ማንበብ ትችላላችሁ››

ዓዛርያስ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ
እንቅልፍ ሞትን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ዓዛርያስ እንደ አባቶቹ ሞተ›› ወይም፣ ‹‹እንደ አባቶቹ ዓዛርያስም ሞተ››

ከአባቶቹ ጋር ቀበሩት
‹‹ቤተ ሰቡ አባቶቹ በተቀበሩበት ቀበሩት››

በእግሩ ተተክቶ ነገሠ
‹‹በእግሩ ተተክቶ›› የሚለው ሐረግ፣ ‹‹በእርሱ ቦታ›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በዓዛርያስ ቦታ ንጉሥ ሆነ››

2 Kings 15:8

ዓዛርያስ በነገሠ በሠላሳ ስምንተኛው ዓመት
ይህ የአገዛዙ ሠላሳ ስምንተኛው ዓመት መሆኑን ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የይሁዳ ንጉሥ ዓዛርያስ በነገሠ 38ኛው ዓመት››

የኢዮርብዓም ልጅ ዘካርያስ
ይህ ኢዮርብዓም በዚህ ስም የሚጠራ ሁለተኛው የእስራኤል ንጉሥ ነው። የንጉሥ ዮአስ ልጅ ነው።

በሰማርያ ከተማ በእስራኤል ላይ ስድስት ወር ነገሠ
ሰማርያ የእስራኤል ንጉሥ በሆነ ጊዜ ንጉሥ ዘካርያስ የሚኖርባት ከተማ ነበረች። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በሰማርያ ሆኖ፣ በእስራኤል ላይ ስድስት ወር ነገሠ››

ክፉ አደረገ
‹‹ዘካርያስ ክፉ አደረገ››

በያህዌ ዐይን ፊት ክፉ አደረገ
የያህዌ ዐይን የሚወክለው የያህዌን ፍርድ ነው። 2 ነገሥት 3፥2 ላይ ይህን እንዴ እንደ ተረጐመኸው ተመለከት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በያህዌ ፍርድ ክፉ የሆነውን›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ክፉ የሚለውን››

ከናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም ኀጢአት አልተመለሰም
ከኀጢአት መመለስ ያንን አለማድረግን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ዘካርያስ የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓምን ኀጢአት ማድረግን እንቢ አላለም›› ወይም፣ ‹‹የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም ያደረገውን ኀጢአት አደረገ››

የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም
ይህ ኢዮርብዓም የእስራኤልን መንግሥት ከመሠረቱ ዐሥሩ ሰሜናዊ ነገዶች የመጀመሪያው ንጉሥ ነበር።

እስራኤልን ካሳተበት ኀጢአት
እዚህ ላይ ‹‹እስራኤል›› በእስራኤል መንግሥት ያለውን ሕዝብ ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የእስራኤልን ሕዝብ ካሳተበት ኀጢአት››

2 Kings 15:10

ሰሎም... ያቤስ
እነዚህ የሁለት ሰዎች ስም ናቸው።

በዘካርያስ ላይ
‹‹በንጉሥ ዘካርያስ ላይ››

ኢብልዓም
ይህ የከተማ ስም ነው።

በእግሩም ተተክቶ ነገሠ
ሰሎም በዘካርያስ ቦታ ንጉሥ ሆነ

በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተመዝግቦአል
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተመዝግቦ ካለበት መጽሐፍ ማንበብ ትችላላችሁ።›››

ይህ የያህዌ ቃል ነበር
ቁጥር 10 ላይ የተነገሩት ሁኔዎታዎች የያህዌ ቃል ፍጻሜዎች ነበሩ ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ዘካርያስ ላይ የደረሰው በያህዌ ቃል መሠረት ነበር›› ወይም፣ ‹‹ዘካርያስ ላይ በደረሰው የያህዌ ቃል ተፈጸመ››

ልጆችህ እስከ አራት ትውልድ ድረስ በእስራኤል ዙፋን ላይ ይቀመጣሉ።
ዙፋን ላይ መቀመጥ ንጉሥ መሆን ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ልጆችህ እስከ አራት ትውልድ ድረስ የእስራኤል ነገሥታት ይሆናሉ››

2 Kings 15:13

የይሁዳ ንጉሥ ዓዛርያስ በነገሠ በሠላሳ ዘጠነኛው ዓመት
ይህ የእርሱ አገዛዝ ሠላሳ ዘጠነኛው ዓመት እንደ ነበር በግልጽ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ዓዛርያስ የይሁዳ ንጉሥ በሆነ 39 ዓመቱ››

ሰሎም... ኢያቤስ
እነዚህ የሁለት ሰዎች ስም ናቸው። 2 ነገሥት 15፥10 ላይ እንዴት እንደ ተረጐመኸው ተመልከት።

ምናሔም... ጋዲ
እነዚህ የሁለት ሰዎች ስሞች ናቸው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በሰማርያ ተቀምጦ አንድ ወር ብቻ ገዛ
የእስራኤል ንጉሥ በሆነ ጊዜ የሚቀመጠው በሰማርያ ከተማ ነበር። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰሎም በሰማርያ ተቀመጠ፤ በእስራኤል ላይ አንድ ወር ብቻ ነገሠ››

በእግሩ ተተክቶ ነገሠ
‹‹በእግሩ ተተክቶ›› ማለት፣ ‹‹በእርሱ ቦታ›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በሰሎም ፈንታ ነገሠ››

2 Kings 15:15

የጠነሰሰውም ሤራ
‹‹ሤራ›› የተሰኘውን ቃል፣ ‹‹ዕቅድ›› ብሎ መተርጐም ይቻላል። ይህ ሤራ ምን እንደ ነበር በግልጽ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ንጉሥ ዘካርያስን ለመግደል ያወጣው ዕቅድ›› ወይም፣ ‹‹ንጉሥ ዘካርያስን መግደሉ››

በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎአል
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ከተጻፈበት መጽሐፍ ማንበብ ትችላላችሁ።››

ቲፍሳ
ይህ የከተማ ስም ነው። አንዳንድ ቅጂዎች፣ ‹‹ታፑ›› ይላሉ። ይህ የሌላ ከተማ ስም ነው።

2 Kings 15:17

የይሁዳ ንጉሥ ዓዛርያስ በነገሠ በሠላሳ ዘጠነኛው ዓመት
ይህ የአገዛዙ ሠላሳ ዘጠነኛው ዓመት እንደ ሆነ በግልጽ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ዓዛርያስ የይሁዳ ንጉሥ በሆነ በ39 ዓመት››

በያህዌ ዐይን ፊት ክፉ ነገር
የያህዌ፣ ዐይን የያህዌን ፍርድ ይወክላል። 2 ነገሥት 3፥2 ላይ ይህን እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በያህዌ ፍርድ ክፉ ነገር›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ክፉ የሚለውን››

ዘመኑንም ሁሉ
‹‹ዘመን›› የሚለው፣ ‹‹በኖረበት›› ተብሎ ሊተረጐም ይችላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በሕይወት በኖረበት ጊዜ ሁሉ››

ከናባጥ ልጅ ከኢዮርብዓም ኀጢአት አልተመለሰም
ከኀጢአት መራቅ ያንን ኀጢአት አለማድረግ ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ዘካርያስ የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም ኀጢአት ማድረግን እንቢ አላለም›› ወይም፣ ‹‹የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም ያደረገውን ኀጢአት አደረገ››

እስራኤልን ካሳተበት ኀጢአት
እዚህ ላይ ‹‹እስራኤል›› የሚለው ቃል፣ የእስራኤልን መንግሥት ሕዝብ ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የእስራኤል ሕዝብ ኀጢአት እንዲሠሩ ካደረገው››

2 Kings 15:19

የአሦር ንጉሥ ቴልጌልቴልፌልሶር ምድሪቱን ወረረ
‹‹የአሦር ንጉሥ ቴልጌልቴልፌልሶር›› የሚለው ቴልጌልቴልፌልሶርንና ሰራዊቱን ይወክላል

በምድሪቱ መጣ
‹‹በምድሪቱ መጣ›› የሚለው ምድሪቱን ለመውረር ለማለት ነው። ‹‹ምድሪቱ›› የእስራኤልን ምድር ሲሆን እዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የእስራኤልን ሕዝብ ለመውረር ከሰራዊቱ ጋር መጣ››

አንድ ሺህ መክሊት ብር
‹‹1000 መክሊት ብር›› ይህን ወደ ዘመኑ ምንዛሬ መለወጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሠላሳ ሦስት ኪሎ ግራም ብር›› ወይም፣ ‹‹ሠላሳ ሦስት ሜትሪክ ቶን ብር››

የቴልጌልቴልፌልሶር ርዳታ ለማግኘት
‹‹ርዳታ›› የሚለውን፣ ‹‹ድጋፍ›› በማለት መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ቴልጌልቴልፌልሶር እንዲደግፈው››

የእስራኤልን መንግሥት በእጁ ለማጽናት
የእስኤልን መንግሥት በእጁ ማጽናት መንግሥቱን መግዛት ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በእስራኤል መንግሥት ላይ አገዛዙን ለማጠናከር››

ይህን ገንዘብ ከእስራኤል ሰበሰበ
‹‹ይህን ገንዘብ ከእስራኤል ወሰደ››

አምሳ ሰቅል ብር
ይህን ወደ ዘመኑ ምንዛሬ መለወጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ስድስት መቶ ግራም ብር›› ወይም፣ ‹‹የኪሎ ግራም ሦስት አምስተኛ ብር››

በዚያች ምድር አልቆየም
‹‹በእስራኤል ምድር አልቆየም››

2 Kings 15:21

በእስራኤል... ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን
ይህ ጥያቄ የቀረበው ምናሴን የተመለከተ መረጃ በሌላው መጽሐፍ የሚገኝ መሆኑን አንባቢን ለማሳሰብ ነው። 2 ነገሥት 1፥18 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የእስራኤል ነገሥታት ታሪክ በተጻፈበት መጽሐፍ ተጽፎአል››

ምናሔም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ
አንቀላፋ ሞተ ማለት ነው። 2 ነገሥት 10፥35 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ምናሔም እንደ አባቶቹ ሞተ›› ወይም፣ ‹‹እንደ አባቶቹ ምናሔም ሞተ››

ፋቂስያስ
ይህ የሰው ስም ነው።

በእግሩ ተተክቶ ነገሠ
‹‹በእግሩ ተተክቶ›› የሚለው ሐረግ፣ ‹‹በቦታው›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በምናሔም ቦታ ነገሠ››

2 Kings 15:23

የይሁዳ ንጉሥ ዓዛርያስ በነገሠ በአምሳኛው ዓመት
ይህ የአገዛዙ አምሳኛው ዓመት መሆኑን በግልጽ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በይሁዳ ንጉሥ ዓዛርያስ 50ኛ ዓመት››

ፋቂስያስ
ይህ የሰው ስም ነው።

በያህዌ ዐይን ፊት ክፉ ነገር
የያህዌ ዐይን የያህዌን ፍርድ ይወክላል። 2 ነገሥት 3፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በያህዌ ፍርድ ክፉ የሆነ ነገር›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ክፉ የሚለውን ነገር››

ከናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም ኀጢአት አልተመለሰም ኀጢአትን መተው ያንን አለማድረግ ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ፋቂስያስ የናባጥ ልጅ የኢዮርብዓምን ኀጢአት ማድረግን እንቢ አላለም›› ወይም፣ ‹‹የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም ያደረገውን ኀጢአት አደረገ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እስራኤልን ካሳተበት ኀጢአት
እዚህ ላይ፣ ‹‹እስራኤል›› በእስራኤል መንግሥት ያለውን ሕዝብ ይወክላል።

2 Kings 15:25

ፋቁሔ... ሮሜልዩ
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው

አሤረበት
‹‹ሊገድለው በስውር መከረ››

አምሳ ሰዎች
‹‹50 ሰዎች››

አርኄብ... አርያ
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው

የቤተ መንግሥት ምሽግ
‹‹የተመሸገ የቤተ መንግሥቱ አካል›› ወይም፣ ‹‹የቤተ መንግሥቱ መከለያ ቦታ››

በእግሩ ተተክቶ ነገሠ
‹‹በእግሩ ተተክቶ›› የሚለው፣ ‹‹በእርሱ ቦታ›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በፋቁሔ ቦታ ነገሠ››

በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎአል
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ይህን በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ መጽሐፍ ማንበብ ይቻላል››

2 Kings 15:27

የይሁዳ ንጉሥ ዓዛርያስ በነገሠ በአምሳኛው ሁለተኛው ዓመት
ይህ በእርሱ አገዛዝ አምሳ ሁለተኛው ዓመት መሆኑን በግልጽ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በይሁዳ ንጉሥ ዓዛርያስ 52ኛ ዓመት››

በያህዌ ዐይን ፊት ክፉ ነገር አደረገ
የያህዌ ዐይን የያህዌን ፍርድ ይወክላል። 2 ነገሥት 3፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በያህዌ ፍርድ ክፉ ነገር›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ክፉ ነው የሚለውን››

ከናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም ኀጢአት አልተመለሰም
ከኀጢአት መመለስ ያንን አለማድረግ ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ዘካርያስ የናባጥ ልጅ የኢዮርብዓምን ኀጢአት ለማድረግ እንቢ አላለም›› ወይም፣ ‹‹የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓምን ኀጢአት አደረገ››

2 Kings 15:29

በእስራኤል ንጉሥ በፋቁሔ ዘመን
ይህ የሚያመለክተው የፋቁሔን የግዛት ዘመን መሆኑን በግልጽ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ንጉሥ ፋቁሔ የእስራኤል ንጉሥ በነበረበት ዘመን›› ወይም፣ ‹‹በእስራኤል ንጉሥ በፋቁሔ ዘመን››

ቴልጌል-ቴልፌልሶር
2 ነገሥት 15፥19 ላይ ይህ ሰው፣ ‹‹ፑል›› ተብሎአል።

ዒዮን... አቤልቤትመዓካን... ያኖን... ቃዴስ... ሐጾር... ገለዓድ... ገሊላ...
እነዚህ የከተሞች ወይም የክልሎች ስሞች ናቸው።

ሕዝቡን ወደ አሦር ወሰደው
እዚህ ላይ፣ ‹‹እርሱ›› የሚያመለክተው ቴልጌል-ቴልፌልሶርን ሲሆን፣ እርሱንና ሰራዊቱን ይወክላል። ሕዝቡን ወደ አሦር መውሰድ ወደ አሦር እንዲሄዱ ማስገደድን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እርሱና ሰራዊቱ ወደ አሦር እንዲሄድ ሕዝቡን አስገደዱ››

ሕዝቡ
የትኛው ሕዝብ እንደ ሆነ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በእነዚህ ቦታዎች የነበረ ሕዝብ›› ወይም፣ ‹‹የእስራኤል ሕዝብ››

ሆሴዕ... ኤላ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው።

አሤረበት
ሤራ ሰው ወይም አንዳች ነገር ላይ ጉዳት ለማድረስ ድብቅ ዕቅድ ማለት ነው።

አደጋ ጥሎ ገደለው
‹‹ሆሴዕ ፋቁሔ ላይ አደጋ ጥሎ ገደለው››

በእግሩ ተተክቶ ነገሠ
‹‹በእግሩ ተተክቶ›› የሚለው ሐረግ፣ ‹‹በእርሱ ቦታ›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በፋቁሔ ቦታ ነገሠ››

የዖዝያን ልጅ ኢዮአታም በነገሠ በሃያኛው ዓመት
ይህ የአገዛዙ ሃያኛው ዓመት መሆኑን ይበልጥ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የዖዝያን ልጅ ኢዮአታም በነገሠ በ20ኛው ዓመት››

በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ መጽሐፍ ተጽፎ ይገኛል
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ይህን በተመለከተ በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ መጽሐፍ ማንበብ ትችላላችሁ››

2 Kings 15:32

የእስራኤል ንጉሥ የሮሜልዩ ልጅ ፋቁሔ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት።
ይህ የአገዛዙ ሁለተኛ ዓመት መሆኑን ይበልጥ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የሮሜልሑ ልጅ ፋቁሔ የእስራኤል ንጉሥ በሆነ በ2ኛው ዓመት››

የዓዛርያስ ልጅ ኢዮአታም በይሁዳ መንገሥ ጀመረ
‹‹የዓዛርያስ ልጅ ኢዮአታም የይሁዳ ንጉሥ ሆነ››

ዕድሜ ሃያ አምስት ዓመት ነበር... ዐሥራ ስድስት ዓመት
‹‹ዕድሜው 25 ዓመት ነበር... 16 ዓመት››

ኢየሩሳ
ይህ የሴት ስም ነው።

2 Kings 15:34

በያህዌ ዐይን ፊት መልካም ነገር
ዐይን ዕይታን ይወክላል፤ ዕይታ ደግሞ ሐሳብን ወይም ፍርድን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በያህዌ ፍርድ መልካም ነገር›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ መልካም የሚለውን ነገር››

ኮረብቶች ላይ ያሉ ማምለኪያዎችን አላስወገደም
ይህን በሌላ መል ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ማንም የኮረብቶቹን ማምለኪያዎች አላስወገደም›› ወይም፣ ‹‹ኢዮአታም የኮረብቶቹን ማምለኪያዎች ማንም እንዲያስወግድ አላደረገም››

አልተወገዱም
መወገድ መደምሰስን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አልተደመሰሱም››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ኢዮአታም የላይኛውን በር መልሶ ሠራ
‹‹ኢዮአታም ሠራ›› የሚለው የኢዮአታም ሠራተኞች መሥራታቸውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ኢዮአታም ሠራተኞቹ የላይኛውን በር እንዲሠሩ አደረገ››

በይሁዳ... ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?
ጥያቄው የቀረበው ኢዮአታምን በተመለከተ መረጃ በዚህ ሌላ መጽሐፍ ውስጥ እንደሚገኝ ለአንባቢው ለማሳሰብ ነው። 2 ነገሥት 8፥23 ላይ ያለውን እንዴት እንደ ተረጐመኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ መጽሐፍ ተጽፎአል››

በዚያ ዘመን
ይህ አንድ ወቅትን ያመለክታል። ይህ ወቅት የትኛው እንደ ነበር የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በዚያ ጊዜ›› ወይም፣ ‹‹ኢዮአታም የይሁዳ ንጉሥ በነበረ ጊዜ››

ረአሶን
ይህ የሰው ስም ነው።

ፋቁሔ... ሮሜልዩ
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው። ፋቁሔ የእስራኤል ንጉሥ ነበር። 2 ነገሥት 15፥37 ላይ ይህን እንዴት እንደተረጐመኸው ተመልከት።

ኢዮአታም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ
አንቀላፋ ሞተ ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ኢዮአታም እንደ አባቶቹ ሞተ›› ወይም፣ ‹‹አባቶቹ እንደ ሞቱ ኢዮአታምም ሞተ››

በእግሩ ተተክቶ ነገሠ
‹‹በእግሩ ተተክቶ›› የሚለው ሐረግ፣ ‹‹በእርሱ ቦታ›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በኢዮአታም ቦታ ነገሠ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 16

1 የሮሜልዩ ልጅ ፋቁሔ በእስራኤል በነገሠ በዐሥራ ሰባተኛው ዓመት የኢዮአታም ልጅ አካዝ የይሁዳ ንጉሥ ሆነ። 2 አካዝም በሚነግሠበት ጊዜ ዕድሜው ሃያ ዓመት ነበር። እርሱም በኢየሩሳሌም ዐሥራ ስድስት ዓመት ገዛ። እርሱም የቀድሞ አባቱን የንጉሥ ዳዊትን መልካም አርአያነት አልተከተለም። በአምላኩም በእግዚአብሔር ፊት ደስ የማያሰኝ ሥራ ሠራ። 3 ይልቁንም የእስራኤልን ነገሥታት መጥፎ አርአያነት ተከተለ። የራሱን ልጅ እንኳ ሳይቀር ለጣዖታት የሚቃጠል መስዋዕት አድርጎ አቀረበ፤ ይህንንም ድርጊት የእስራኤል ሕዝብ ወደ ተስፋይቱ ምድር ከመግባቱ በፊት እግዚአብሔር ከእስራኤል ምድር ያስወገዳቸውን አሕዛብ ይሠሩት የነበረውን አስጸያፊ ድርጊት በመከተል ነበር። 4 አካዝ በየኮረብቶቹ ላይ በተሠሩት የአሕዛብ ማምለኪያ ስፍራዎችና በእያንዳንዱም ዛፍ ሥር መሥዋዕት በማቅረብ ዕጣን አጠነ። 5 የሶርያ ንጉሥ ረአሶንና የእስራኤል ንጉሥ ፋቁሔ በኢየሩሳሌም ላይ አደጋ ለመጣል መጡ፤ ከበቧትም። ነገር ግን አካዝን ድል ሊያደርጉት አልቻሉም። 6 በዚያን ጊዜ የሶርያ ንጉሥ ረአሶን የኤላትን ከተማ አስመልሶ በቁጥጥሩ ሥር በማድረግ በዚያ የነበሩትን አይሁድ አስወጣ። ከዚያም በኤላት የሰፈሩት ኤዶማውያን እስከ አሁንም በዚያ ይኖራሉ። 7 ስለዚህም ንጉሥ አካዝ ወደ አሦር ንጉሠ ነገሥት ወደ ቴልጌልቴልፌልሶር «እኔ ለአንተ ታማኝ አገልጋይህ ነኝ፤ አደጋ ከጣሉብኝ ከሶርያና ከእስራኤል ነገሥታት እጅ መጥተህ እኔን አድነኝ» በማለት መልእክተኞችን ላከ። 8 አካዝም በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስና በቤተ መንግሥቱ ዕቃ ግምጃ ቤት የተገኘውን ብርና ወርቅ ሰብስቦ ለዚሁ ለአሦር ንጉሥ ገጸ በረከት በማድረግ ላከለት። 9 ከዚያም የአሦር ንጉሥ ቴልጌልቴልፌልሶር የአካዝን ጥያቄ በመቀበል ዘምቶ ደማስቆን በቁጥጥሩ ሥር አደረገ። ንጉሥ ረአሶንንም ገደለ፤ ሕዝቡንም ማርኮ ቂር ተብላ ወደምትጠራው ስፍራ ወሰደው። 10 ንጉሥ አካዝም ከንጉሠ ነገሥት ቴልጌልቴልፌልሶር ጋር ለመገናኘት ወደ ደማስቆ ሄደ። በደማስቆም አንድ መሠዊያ አየ። ያንንም መሠዊያ በተመሳሳይ ሁኔታ መሥራት የሚያስችለውን ቅርጽ አዘጋጅቶ ለካህኑ ለኦሪያ ላከለት። 11 ስለዚህ ኦሪያ ንጉሥ አካዝ ከደማስቆ በላከለት ንድፍ መሠረት መሠዊያ ሠራ። 12 ንጉሡም ከደማስቆ በተመለሰ ጊዜ መሠዊያውን ተመለከተ፤ ወደ መሠዊያው ቀርቦም መሥዋዕት አቀረበ። 13 በመሠዊያውም ላይ የሚቃጠል የእንስሶች መሥዋዕትና የእህል መባ አቀረበ። የመባውን ወይን ጠጅና የኅብረት መሥዋዕት ደም አፈሰሰበት። 14 ከነሐስ ተሠርቶ ለእግዚአብሔር የተለየውም መሠዊያ በዚያ አዲስ መሠዊያ፣ በቤተ መቅደሱ መካከል ነበር፤ ያንንም መሠዊያ አስነሥቶ እርሱ ባሠራው በአዲሱ መሠዊያ በስተሰሜን በኩል አኖረው። 15 ከዚያም ካህኑን ኦሪያን እንዲህ ሲል አዘዘው፤ ይህንን የእኔን ታላቅ መሠዊያ ማለዳ ለሚቀርበው የሚቃጠል መሥዋዕት በምሽት ለሚቀርበውም የእህል መባ ስለ ንጉሡና ስለ ሕዝቡ የሚቀርበው የሚቃጠል መሥዋዕትና የእህል መባ የሚቀርብበትና የሕዝቡ የወይን ጠጅ መባ የሚፈስበት እንዲሆን አድርግ፤ የሚሠዉትንም የእንስሳት ደም ሁሉ በእርሱ ላይ አፍስስ፤ ከነሐስ የተሠራው መሠዊያ ግን እኔ ራሴ የምፈልገውን ነገር የምጠይቅበት እንዲሆን አድርግ። 16 ካህኑም ኦሪያን ንጉሡ አካዝ እንዳዘዘው አደረገ። 17 ንጉሥ አካዝም በቤተ መቅደስ ውስጥ መገልገያ የነበሩትን ከነሐስ የተሠሩ መንኩራኩሮች ቆርጦ ልሙጥ የሆነውን ነገር ከጎናቸው ወስደ። በእነርሱ ላይ የነበሩትንም የመታጠቢያ ሳሕኖች ወሰደ፤ ከነሐስ የተሠራውን የውሃ ማጠራቀሚያ ገንዳ ከታች በኩል ተሸክመውት ከነበሩት ከነሐስ ከተሠሩት ከዐሥራ ሁለት የበሬ ቅርጾች ጀርባ ላይ አንሥቶ ከድንጋይ በተሠራ መሠረት ላይ አኖረው። 18 አካዝ ከአሦር ንጉሠ ነገሥት የተነሣ በቤተ መቅደሱ የሠሩትን የሰንበት መግቢያ መንገድ ንጉሡ ከእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በውጪው በኩል ከሚገባበት መግቢያ ጋር አስወገደው። 19 ንጉሥ አካዝ ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ በይሁዳ ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኛል። 20 አካዝም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ በዳዊት ከተማ በሚገኘው በአባቶቹ መካነ መቃበር ተቀበረ። በእርሱም ፈንታ ተተክቶ ልጁ ሕዝቅያስ ነገሠ።

---

2 Kings 16:1

የሮሜልዩ ልጅ ፋቁሔ በነገሠ በዐሥራ ሰባተኛው ዓመት

ይህ የአገዛዙ ዐሥራ ሰባተኛ ዓመት መሆኑን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሮሜልዩ ልጅ ፋቁሔ ንጉሥ በሆነ 17ኛ ዓመት››

ፋቁሔ... ሮሜልዩ

ይህ የሰዎች ስም ነው። ፋቁሔል የእስራኤል ንጉሥ ነበር። 2 ነገሥት 15፥25 ላይ ይህን እንዴ እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

በያህዌ ዐይን ፊት መልካም ነገር

የያህዌ ዐይን ዕይታን ይወክላል፤ ዕይታ ደግሞ ሐሳብ ወይም ፍርድን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በያህዌ ፍርድ መልካም የሆነውን ነገር›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ መልካም ነው የሚለውን ነገር››

አባቱ ዳዊት ያደረገውን

ዳዊት መልካም ነገር አድርጐ ነበር

2 Kings 16:3

እርሱም የእስራኤልን ነገሥታት መንገድ ተከተለ

መመላለስ ፀባይንና ድርጊትን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ንጉሥ አካዝ የእስራኤል ነገሥታት ያደረጉትን አደረገ›› ወይም፣ ‹‹እርሱ የእስራኤል ነገሥታት ያደረጉትን አደረገ››

የአሕዛብን ርኩሰት ተከትሎ

‹‹መከተል›› ሌሎች ያደረጉትን ማድረግ ማለት ነው። እዚህ ላይ የሚናገረው በዚያ ምድር የሚኖሩ ሰዎችን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሌላ አገር ሕዝብ›› ያህዌ ያሳደዳቸውን

‹‹ማሳደድ›› — ‹‹ማስገደድ›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከዚያ እንዲሄዱ ያህዌ ያስገደዳቸውን››

ከእስራኤል ሕዝብ ፊት

የእስራኤል ሕዝብ ወደ ምድሪቱ ሲመጡ፣ የእነዚያ መንግሥታት ሕዝቦች ሸሹ። ይህ ምን ማለት መሆኑን ይበልጥ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ወደ ምድሪቱ በመጡ የእስራኤል ሕዝብ ፊት›› ወይም፣ ‹‹የእስራኤል ሕዝብ ወደ ምድሪቱ ሲመጡ››

ኮረብታ ላይ ባሉ ማምለኪያ ስፍራዎች ቅጠሉ በተንሰራፋው ዛፍ ሥር

ሌሎች ሕዝቦች አማልክቶቻቸውን የሚያመልኩት በእንዲህ ያሉ ቦታዎች ነበር

ቅጠሉ በተንሰራፋው ዛፍ ሥር ሁሉ

እግዚአብሔር የፈለገው ሕዝቡ በኢየሩሳሌም መሥዋዕት እንዲያቀርቡለት ነው። እዚህ ላይ፣ ‹‹ሁሉ›› የሚለው ቃል! ንጉሥ አካዝ በሌሎች ብዙ ቦታዎች መሥዋዕት በማቅረብ ምን ያህል ለእግዚአብሔር ባለ መታዘዝ የጸና ሰው መሆኑን የሚያመለክት ግነት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ቅጠሉ በተንሰራፋ ብዙ ዛፍ ሥር ሁሉ›› ወይም፣ ‹‹በአገሩ ባለ ቅጠሉ በተንሰራፋው ዛፍ ሥር ሁሉ››

2 Kings 16:5

ረአሶን... ፋቁሔ... ሮሜልዩ

እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው። 2 ነገሥት 15፥37 ላይ እንዴት እንደ ተረጐምሃቸው ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አካዝን ለመክበብ
አካዝ በኢየሩሳሌም ነበር። እዚህ ላይ፣ ‹‹አካዝ›› እርሱንና ከእርሱ ጋር በኢየሩሳሌም የነበሩ ሰዎች ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አካዝ የነበረበትን ከተማ ለመክበብ›› ወይም፣ ‹‹አካዝንና በከተማው የነበሩ ሌሎችንም ለመክበብ››

ኤላትን ወደ ሶርያ መለሰ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ሶርያ›› እዚያ የሚኖሩ ሰዎች ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የኤላት ከተማን ለሶርያ ሕዝብ መለሰ››

ኤላት
ይህ የከተማ ስም ነው። 2 ነገሥት 14፥22 እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

የይሁዳን ሰዎች ከኤላት አሳደደ
‹‹ኤላትን ለቀው እንዲወጡ የይሁዳን ሰዎች አስገደደ››

እስከ ዛሬ
ይህ ማለት ይህ መጽሐፍ እስከ ተጻፈ ድረስ ማለት ነው።

2 Kings 16:7

ቴልጌል-ቴልፌልሶር
2 ነገሥት 15፥19 ላይ ይህ ሰው፣ ‹‹ፑል›› ተብሎ ተጠርቷል። 2 ነገሥት 15፥29 ስሙን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

እኔ አገልጋይህም ልጅህም ነኝ
አገልጋይና ልጅ መሆን ለሥልጣን መገዛትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ አገልጋይህና እንደ ልጅህ እታዘዝሃለሁ››

ከሶርያ ንጉሥ እጅና ከእስራኤል ንጉሥ እጅ
‹‹እጅ›› - ‹‹ጎይልን›› ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከሶርያ ንጉሥ ጎይልና ከእስራኤል ንጉሥ ጎይል››

ከሚወጉኝ
አካዝን የሚወጉ ነገሥታት፣ አካዝንና ሕዝቡን የሚወጉ ነገሥታት ሰራዊት ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሠራዊታቸው ከሚወጉኝ›› ወይም፣ ‹‹ሰራዊታቸው እኔን ከሚወጋኝ››

የአሦር ንጉሥ ደማስቆን አጠቃ
‹‹ንጉሥ›› የሚለው ቃል ንጉሠንና ሰራዊቱን ይወክላል። ደማስቆ እዚያ የሚኖረውን ሕዝብ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአሦር ንጉሥና ሰራዊቱ የደማስቆን ሕዝብ አጠቁ››

ሕዝቧን ማርኮ ወደ ቂር አፈለሳቸው
ሕዝብን ‹‹ማፍለስ›› ወደ አንድ ቦታ እንዲሄዱ ማስገደድ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕዝቡን እስረኛ አድርጐ ወደ ቂር እንዲሄድ አስገደደ››

ቂር
አማራጭ ትርጉሞች 1) የከተማ ስም ነው፤ ወይም 2) ቃሉ፣ ‹‹ከተማ›› ማለት ሲሆን የአሦርን ዋና ከተማ ያመለክታል።

2 Kings 16:10

ከዝርዝር ጥናቱ ጋር
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል፤ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለግንባታው ሥራ ሠራተኞቹ የሚያስፈልጋቸውን መመሪያ ሁሉ››

2 Kings 16:13

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ከደማስቆ ከተመለሰና ካህኑ አርያ የሠራለትን መሠዊያ ከጐበኘ በኃላ ንጉሥ አካዝ ያደረገው ነው።

የሚቃጠል መሥዋዕት አቀረበ
‹‹ንጉሥ አካዝ የሚቃጠል መሥዋዕት አቀረበ››

መሠዊያው ላይ
ይህ አርያ እንዲሠራለት ንጉሥ አካዝ የነገረው መሠዊያ ነው።

ያህዌ ፊት የነበረው የናስ መሠዊያ
ይህ መሠዊያ በእግዚአብሔር መመሪያ መሠረት የእስራኤል ሕዝብ ከብዙ ጊዜ በፊት ሠርተውት የነበረ ነው።

ያህዌ ፊት የነበረው የናስ መሠዊያ
‹‹ያህዌ ፊት›› የሚለው ሐረግ ባለፈው ጊዜ ያህዌ ክብሩን ያሳየበትን ቦታ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቤተ መቅደሱ ፊት የነበረው የናስ መሠዊያ››

ቤተ መቅደሱ ፊት... በመሠዊያውና በያህዌ ቤተ መቅደስ መካከል
እነዚህ ሐረጐች የናሱ መሠዊያ የነበረበትን ቦታ ይናገራሉ። ሁለቱም ስለ አንድ ቦታ ይናገራሉ።

2 Kings 16:15

ትልቁ መሠዊያ
ይህ እንዲሠራለት አካዝ ለአርያ የነገረው አዲሱን መሠዊያ ያመለክታል።

የንጉሡ የሚቃጠል መሥዋዕትና የእህል ቁርባን
አካዝ፣ ‹‹ንጉሡ›› እና፣ ‹‹የእርሱ›› ሲል ስለ ራሱ መናገሩ ነው። ንጉሡ መሥዋዕቱን በጥንቃቄ ነበር የሚመለከተው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሚቃጠል መሥዋዕቴና የእህል መሥዋዕቴ›› ወይም፣ ‹‹ንጉሣዊ የሚቃጠል መሥዋዕትና የእህል መሥዋዕት››

2 Kings 16:17

ተንቀሳቃሹ መቆሚያ
‹‹ተንቀሳቃሽ መቆሚያ›› ወይም፣ ‹‹ሰረገላ›› እነዚህ መቆሚያዎች ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ እንዲችሉ ተሸከርካሪዎች ነበሩት።

የመታጠቢያ ሳሕኖች አስወገደ
‹‹ጐድጓዳውን ሳሕን አስወገደ›› ይህ ከናስ የተሠራ ገንዳ ወይም የውሃ መያዣ ነው።

በአሦር ንጉሥ ምክንያት
ለምን ይህን እንዳደረጉ የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአሦርን ንጉሥ ደስ ለማሰኘት››

2 Kings 16:19

በይሁዳ... ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?
ጥያቄው የቀረበው አካዝን የሚመለከት መረጃ በዚህ ሌላ መጽሐፍ ውስጥ እንደሚገኝ አንባቢውን ለማሳሰብ ነው። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። 2 ነገሥት 8፥23 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ መጽሐፍ ተጽፎአል›› ወይም፣ ‹‹አንድ ሰው በይሁዳ... መጽሐፍ ጽፎታል››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አካዝም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ
አንቀላፋ ሞተ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አካዝ እንደ አባቶቹ ሞተ›› ወይም፣ ‹‹እንደ አባቶቹ አካዝም ሞተ››

ከአባቶቹ ጋር ተቀበረ
ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ከአባቶቹ ጋር ቀበሩት››

በእግሩ ተተክቶ ነገሠ
‹‹በእግሩ ተተክቶ›› የሚለው ሐረግ፣ ‹‹በቦታው›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በአካዝ ቦታ ነገሠ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 17

1 አካዝ በይሁዳ በነገሠ በዐሥራ ሁለተኛው ዓመት የኤላ ልጅ ሆሴዕ በእስራኤል ንጉሥ ሆነ። እርሱም በሰማርያ ዘጠኝ ዓመት እስራኤልን ገዛ። 2 እርሱም
በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገር አደረገ። ሆኖም እርሱ ያደረገው ኃጢአት ከእርሱ በፊት የነበሩ የእስራኤል ነገሥታት የፈጸሙት አልነበረም። 3 የአሦር ንጉሥ
ስልምናሶር ጦርነት በገጠመው ጊዜ ተሸንፎ ሆሴዕ እጁን በመስጠት በየዓመቱ ይገብርለት ጀመር። 4 ነገር ግን ከጥቂት ዓመቶች በኋላ ንጉሥ ሆሴዕ ሴጎር
ተብሎ ወደሚጠራው ወደ ግብጽ ንጉሥ መልእክተኞች በመላክ ይረዳው ዘንድ ጠየቀው፤ በየዓመቱ ለአሦር ንጉሥ ይሰጠው የነበረውንም ግብር አቆመ።
ስልምናሶር ይህን በሰማ ጊዜ ሆሴዕን አስይዞ ወህኒ ቤት አስገባው። 5 ከዚህ በኋላ ስልምናሶር አገሪቱን ወርሮ ሰማርያን ለሦስት ዓመት ከበባት። 6 ከዚያም
ሆሴዕ በነገሠ በዘጠነኛው ዓመት ስልምናሶር ድል አድርጎ ሰማርያን ያዘ፤ እስራኤላውያንንም ማርኮ ወደ አሦር ወሰዳቸው፤ ከእነርሱም ጥቂቶቹን በአላሔ
ከተማ፣ ጥቂቶቹን በጎዛን አውራጃ ውስጥ በሚገኘው በአቦር ወንዝ አጠገብ፣ እንዲሁም ሌሎቹን በሜዶን ከተሞች እንዲሰፍሩ አደረገ። 7 ይህም ምርኮ
የሆነው እስራኤላውያን በሠሩት ኃጢአት ከግብጽ ንጉሥ ከፈርዖን እጅ በመታደግ አውጥቶ ወደ ተስፋይቱ ምድር የመራቸውን አምላካቸውን እግዚአብሔርን
ኃጢአት በመሥራት በማሳዘናቸው ነበር። ሕዝቡም ባዕዳን አማልክትን አመለኩ። 8 ሕዝቡም ከፊታቸው ያጠፋላቸውን የአሕዛብን መጥፎ ልማድ ተከተሉ፤
እንዲሁም የእስራኤል ነገሥታት ያሠራጩትን መጥፎ ልማድ ተቀባዮች ሆኑ። 9 እስራኤላውያንም አምላካቸው እግዚአብሔር የሚጠላውን ነገር ሁሉ አደረጉ።
ከዘብ ጠባቂዎች ማማ አንሥቶ እስከ ትልቅ ከተማ ድረስ በገጠር ከተሞቻቸው ሁሉ በየኮረብታዎቹ የአሕዛብ ማምለኪያ ስፍራዎችን ሠሩ። 10 በኮረብቶች ሁሉ
ላይና በየዛፉ ጥላ ሥር የድንጋይ አምዶችንና አሼራ ተብላ የምትጠራውን ሴት አምላክ ምስሎች አቆሙ። 11 እግዚአብሔርም ከፊታቸው ያስወጣቸውን
የአረማውያን ሕዝብ ልማድ በመከተል በአሕዛብ መሠዊያዎች ሁሉ ላይ ዕጣን አጠኑ፤ በዚህም ክፉ ሥራቸው ሁሉ የእግዚአብሔርን ቁጣ አነሣሡ፤ 12
እግዚአብሔርም እንዳያደርጉ የተናገራቸውን ጣዖታትን አመለኩ። 13 እግዚአብሔርም እስራኤልንና ይሁዳን የሚያስጠነቅቁ መልእክተኞችንና ነቢያትን በመላክ፣
ከክፉ መንገዳችሁ ሁሉ ተመለሱ፤ አገልጋዮቼ በሆኑት ነቢያትና ባለ ራዕዮች አማካይነት ለቀድሞ አባቶቻችሁና ለእናንተም በሰጠሁት ሕጎችና ትእዛዞች የተጻፈውን
ሥርዓቴን ጠብቁ ብሎ ነግሮአቸው ነበር። 14 እነርሱ ግን መታዘዝ አልፈለጉም፤ በአምላካቸው በእግዚአብሔር እንዳልታመኑ እንደ ቀድሞ አባቶቻቸው እልከኞች
ሆኑ። 15 የሰጣቸውንም ድንጋጌ አልተቀበሉም፤ ከቀድሞ አባቶቻቸው ጋር የገባውንም ቃል ኪዳን አልጠበቁም፤ የሰጣቸውንም ማስጠንቀቂያዎች ሁሉ ቸል አሉ፤
ለከንቱ ጣዖቶች በመስገድ ራሳቸውም ከንቱዎች ሆኑ፤ የእነርሱን መጥፎ ምሰሌነት እንዳይወርሱ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ትእዛዝ ባለመስማት በዙሪያቸው
የሚኖሩትን የአሕዛብ ልማድ ሁሉ ተከተሉ። 16 የአምላካቸውን የእግዚአብሔርን ትእዛዞች ሁሉ ቸል አሉ። የሚሰግዱላቸውን ከብረት የተሠሩ ሁለት ጥጆችን
አቆሙ። እንዲሁም አሼራ ተብላ የምትጠራውን ሴት አምላክ ምስል ሠሩ፣ ለከዋክብትም ሰገዱ፣ ባዓል ተብሎ ለሚጠራውም ባዕድ አምላክ አገልጋዮች ሆኑ።
17 ለእነዚያም አሕዛብ አማልክት ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን የሚቃጠል መሥዋዕት አድርገው አቀረቡ፤ ከሙታን ጠሪዎችና ከጠንቋዮችም ምክር ጠየቁ፤
እግዚአብሔር ለሚጠላው ክፉ ነገር ሁሉ ራሳቸውን አሳልፈው በመስጠት የእግዚአብሔርን ቁጣ አነሣሡ። 18 ስለዚህም እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ
ተቆጥቶ የይሁዳን መንግሥት ብቻ በማስቀረት እስራኤላውያንን ከፊቱ አስወገደ። 19 የይሁዳ ሰዎችም ቢሆኑ አምላካቸው እግዚአብሔር የሰጣቸውን ትእዛዞች
አልጠበቁም ነበር። እነርሱም የእስራኤል ሕዝብ የተቀበሉትን ልማድ ተከታዮች ነበሩ። 20 ስለዚህም እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ሁሉ ተዋቸው፤ ከፊቱም
እስኪወገዱ ድረስ ለጠላቶቻቸው አሳልፎ በመስጠት ቀጣቸው። 21 እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከይሁዳ ከለየ በኋላ እስራኤላውያን የናባጥ ልጅ
ኢዮርብዓምን መርጠው አነገሡ፤ ኢዮርብዓምም እግዚአብሔርን እንዲተዉ በማድረግ አሠቃቂ ወደ ሆነ ኃጢአት መራቸው። 22 በአገልጋዮቹ ነቢያት ሁሉ
አማካይነት እግዚአብሔር እስራኤልን ከፊቱ እስኪያስወግድ ድረስ እስራኤላውያን የኢዮርብዓምን ኃጢአት ሲሠሩ ኖሩ እንጂ ከዚያ አልራቁም። 23 ስለዚህ
እስራኤላውያን ከአገራቸው ተማርከው በመወሰድ እስከ ዛሬ ድስ በአሦር ይኖራሉ። 24 የአሦር ንጉሠ ነገሥት በባቢሎን ኩታ፣ ዓዋና፣ ሐማትና ሴፈርዋይ ተብለው
በሚጠሩት ከተሞች ይኖሩ የነበሩትን አሕዛብ አምጥቶ ተሰደው በሄዱት በእስራኤላውያን እግር በመተካት በሰማርያ ከተሞች እንዲሰፍሩ አደረገ፤ እነርሱም
እነዚህን ከተሞች ወርሰው በዚያ መኖር ጀመሩ። 25 እነርሱም በዚያ ሰፍረው መኖር እንደ ጀመሩ እግዚአብሔርን አላመለኩትም ነበር። ስለዚህም እግዚአብሔር
አንበሶችን በመላክ ከእነርሱ ጥቂቶቹን ሰባብረው እንዲገድሉ አደረገ። 26 ለአሦርም ንጉሠ ነገሥት በሰማርያ ከተሞች ሰፍረው እንዲኖሩ ያደረግሃቸው ሕዝቦች
የዚያችን አገር አምላክ ሕግ የሚያውቁ ሆነው አልተገኙም፤ ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔር ሰባብረው የሚገድሉ አንበሶችን ላከባቸው የሚል ወሬ ደረሰው። 27
ስለዚህ ንጉሠ ነገሥቱ ማርኮ ካመጣቸው ካህናት አንዱን ወደዚያ ላኩ፤ ወደዚያ ተመልሶ በመሄድ የዚያች አገር አምላክ ያዘዘውን ሕግ ለሕዝቡ
እንዲያስተምራቸው አድርጉ ሲል አዘዘ። 28 ስለዚህም ከሰማርያ ተማርኮ የተወሰደ አንድ እስራኤላዊ ካህን ተመልሶ በመሄድ በቤተል ተቀመጠ፤ በዚያ ሕዝቡ
እግዚአብሔርን እንዴት ማምለክ እንደሚገባቸው አስተማራቸው። 29 በሰማርያ የሰፈሩት ሕዝቦች ግን የየራሳቸውን ጣዖት መሥራት ቀጥለው እስራኤላውያን
ባሠሩአቸው በከፍተኛ ማምለኪያ ቦታዎች አኖሩአቸው፤ እያንዳንዱ ቡድን በሚኖርበት ከተማ ሁሉ የየራሱን ጣዖት አቆመ። 30 በዚህም ዓይነት የባቢሎን ሰዎች
ሱኮትበኖት በተባለው አምላክ ስም ጣዖት ሠሩ፤ እንዲሁም የኩታ ሰዎች ኤርጌል ተብሎ በሚጠራው ባዕድ አምላክ ስም ጣዖት ሠሩ፤ የሐማት ሕዝብ አሲማት
ተብሎ በሚጠራው ባዕድ አምላክ ስም ጣዖት ሠሩ፤ 31 የዓዋ ሕዝብ ኤልባዝርና ተርታቅ ተብለው በሚጠሩ አማልክቶቻቸው ስም ጣዖቶቻቸውን ሠሩ፤
የሴፈርዋይምም ሕዝብ አድራሜሌክና ዓናሜሌክ ተብለው ለሚጠሩ አማልክቶቻቸው ልጆቻቸውን የሚቃጠል መሥዋዕት አድርገው አቀረቡ። 32 እነዚሁ ሰዎች
በተጨማሪ ለእውነተኛው አምላክ ለእግዚአብሔር ይሰግዱ ነበር። ከእያንዳንዳቸውም ቡድን በአረማውያን የማምለኪያ ስፍራዎች የሚያገለግሉና መሥዋዕት
የሚያቀርቡላቸውን ካህናት መረጡ። 33 በዚህ ዓይነት እግዚአብሔርን ማክበርና ማምለክ ጀመሩ። በሌላ በኩል ግን ቀድሞ ይኖሩባቸው በነበሩት ሕዝቦች
ይፈጽሙት በነበረው ልማድ መሠረት ለባዕዳን አማልክት ይሰግዱ ነበር። 34 ይህንኑ አሮጌ ልማዳቸውን እስከ አሁን ድረስ በመፈጸም ላይ ናቸው። እነርሱም
እግዚአብሔርን አያመልኩም ወይም ስሙ እስራኤል ተብሎ ለተጠራው ለያዕቆብ ልጆች እግዚአብሔር በሰጣቸው ደንቦች፣ ሥርዓቶች፣ ሕጎችና ትእዛዞች ጸንተው
አልኖሩም። 35 እግዚአብሔርም ከእነርሱ ጋር ቃል ኪዳን በመግባት እስራኤላውያንን እንዲህ ሲል አዞአቸው ነበር፦ ባዕዳን አማልክትን አታምልኩ፣ ለእነርሱም
አገልጋዮች በመሆን አትስገዱላቸው፣ መሥዋዕትንም አታቅርቡላቸው። 36 በታላቅ ኃይልና በሥልጣን ከግብጽ ምድር ላወጣኋችሁ ለእኔ ለእግዚአብሔር ታዛዦች
ሁኑ፤ መስገድና መሥዋዕት ማቅረብ የሚገባችሁ ለእኔ ብቻ ነው። 37 ጽፌ የሰጠኋችሁንም ድንጋጌና ሥርዓቱን ሕጎችና ትእዛዞቹን ሁልጊዜ ጠብቁ፣ ባዕዳን
አማልክትንም አትከተሉ። 38 እኔ ከእናንተ ጋር የገባሁትንም ቃል ኪዳን አትርሱ፤ ባዕዳን አማልክትንም አታምልኩ። 39 እኔን አምላካችሁን እግዚአብሔርን ፍሩ፤
እኔም ከኃይለኛው ጠላቶቻችሁ እጅ አድናችኋለሁ። 40 ነገር ግን እነዚያ ሕዝቦች ይህን መስማት ትተው አሮጌ ልማዳቸውን ተከተሉ። 41 እነዚያ ሕዝቦች በዚሁ
ዓይነት እግዚአብሔርን ማምለክ ጀመሩ፤ በሌላ በኩል ግን ለጣዖቶቻቸው ይሰግዱ ነበር፤ ዘሮቻቸውም እስከ ዛሬ ድረስ ይህንኑ ዓይነት አምልኮ እንደ ቀጠሉ
ናቸው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Kings 17:1

የኤላ ልጅ ሆሴዕ
ሆሴዕ የሰሜናዊው የእስራኤል መንግሥት ንጉሥ ሆነ።

ኤላ
ይህ የሰው ስም ነው።

በሰማርያ ከተማ ነገሠ
ሰማርያ የእስራኤል ዋና ከተማ ነበረች።

በያህዌ ፊት ክፉ
ለሙሴ ለተሰጠው የያህዌ ሕግ አልታዘዘም። ‹‹ፊት›› ፍርድንና ሐሳብን ያመለክታል። ‹‹ለያህዌ ክፉ ነገር››

ሰልምናሶር
ይህ የሰው ስም ነው።

ሆሴዕ ተገዛለት፤ ገበረለትም
ሆሴዕ የአሦር ንጉሥ ያዘዘውን አደረገ፤ ንጉሡ እስራኤልን እንዳያጠፋ ገንዘብ ይሰጠው ነበር።

2 Kings 17:4

ሲጐር
ይህ የሰው ስም ነው።

በየዓመቱ
‹‹በዓመት በዓመቱ››

ይህ ወህኒ ቤት አስገባው
‹‹አሰረው››

ከበባት
እጅ እንድትሰጥ ለማስገደድ በከተማው ዙሪያ ወታደሮች አሰፈረ

እስራኤልን በምርኮ ወደ አሦር አፈለሰ
‹‹እስራኤል›› እዚያ የሚኖር ሕዝብ ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የእስራኤልን ሕዝብ ወደ አሦር ወሰደ››

አላሔ... አቦር ወንዝ... ጐዛን
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው

ሜዶን
ይህ የሕዝብ ስም ነው

2 Kings 17:7

አጠቃላይ መረጃ
በእስራኤል ላይ የያህዌን ፍርድ አሳጥሮ ለማቅረብ ታሪኩ ቆም ብሏል።

ይህ ምርኮ
ይህ የሚያመለክተው የእስራኤላውንን በአሦራውያን መወረር ነው።

እጅ
‹‹እጅ›› የመቆጣጠር፣ የሥልጣን ወይም የጎይል ሌላ መጠሪያ ነው።

ልማድ ስለ ተከተሉ
‹‹ተከተሉ›› የሚለው የሰዎች አኗኗር ሁኔታ ወይም መንገድ ማለት ነው።

2 Kings 17:9

አጠቃላይ መረጃ
ታሪኩ የያህዌን እስራኤል ላይ ፍርድ በአጭሩ ማቅረብ ቀጥሏል።

በእያንዳንዱ ኮረብታ ላይና በእያንዳንዱም የተንሰራፋ ዛፍ
ይህ በብዛት ሐሰተኛ አማልክት ይመለኩ እንደ ነበር ለማሳየት የቀረበ ግነት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በኮረብታውና በተንሰራፋው ዛፍ››

2 Kings 17:11

አጠቃላይ መረጃ
ታሪኩ የያህዌን እስራኤል ላይ ፍርድ በአጭሩ ማቅረብ ቀጥሏል።

ያህዌን የሚያስቆጣ ክፉ ነገር አደረጉ
ይህን የማቅረብ አማራጭ ትርጕሞች 1)‹‹ያህዌን የሚያስቆጣ ብዙ ክፉ ነገሮች አደረጉ›› ወይም፣ ‹‹ያህዌን የሚያስቆጣ ብዙ ጎጢአት አደረጉ››

ይህን ማድረግ አይገባችሁም ቢለቸውም
‹‹ያህዌ ቢያስጠነቅቃቸውም››

2 Kings 17:13

አጠቃላይ መረጃ
ታሪኩ የያህዌን እስራኤል ላይ ፍርድ በአጭሩ ማቅረብ ቀጥሏል።

ያህዌ በነቢያት በኩል መሰከረባቸው
ያህዌ በነቢያት በኩል ተናገረ

ከክፉ መንገዶች ተመለሱ
‹‹የምታደርጉን ክፉ ነገር አቁሙ››

አገልጋዮቼ ነቢያትን ወደ እናንተ ላክሁ
የእግዚአብሔር ሕግ እንዲያሳስቡና እንዲታዘዙ ሕዝቡን ለማሳሰብ ያህዌ ነቢያትን ልኮ ነበር።

2 Kings 17:14

አጠቃላይ መረጃ
የያህዌን እስራኤል ላይ ፍርድ በአጭሩ ይቀጥላል

ዐንገታቸውን አደነደኑ
የእግዚአብሔርን ሕግ ለመከተልና በአምላካቸው በያህዌ ለመታመን ፈቃደኛ አልሆኑም

ሥርዐቱን ናቁ
ለእግዚአብሔር ሕግ መታዘዝ እንቢ አሉ

ከንቱ ነገር ተከተሉ
በዙሪያቸው ያሉ ሰዎችን ልማድ ተከተሉ

አትምሰሏቸው
‹‹እንደ እነርሱ አትሁኑ››

2 Kings 17:16

አጠቃላይ መረጃ
የያህዌ እስራኤል ላይ ፍርድ በአጭሩ ቀጥሏል።

ምስል ሠሩ
ይህ ብረት አቅልጠው ቅርጽ ማስያዣ ላይ አፈሰሱ ማለት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጥንቆላና መተት አደረጉ
ወደ ፊት የሚሆነውን ለመናገር አስማት አደረጉ

ክፉ ነገር ለማድረግ ራሳቸውን ሸጡ
‹‹ራስን መሸጥ›› ክፉ የሆነውን ለማድረግ ሙሉ በሙሉ ራስን መስጠት ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ክፉ ነው ያለውን ለማድረግ ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን ሰጡ››

ከፊቱ አስወገዳቸው
‹‹ፊት›› ከእንግዲህ ያህዌ ስለ እነርሱ እንዳያስብ ትኩረት መንፈግ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ትኩረቱን ከእነርሱ አነሣ››

2 Kings 17:19

አጠቃላይ መረጃ
የያህዌ እስራኤል ላይ ፍርድ ይሁዳም ወደ ጣዖት አምልኮ መውደቁን ያመለክታል።

ይሁዳ
ይሁዳ የሚለው ቦታ እዚያ የሚኖርን ሕዝብ ያመለክታል። ‹‹የይሁዳ ሕዝብ››

አስጨነቃቸው
‹‹ያህዌ እስራኤላውያንን ቀጣ››

በማራኪዎቻቸው እጅ አሳልፎ ሰጣቸው
‹‹እጅ›› የመቆጣጠር፣ የጎይል ወይም የሥልጣን ሌላ መጠሪያ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ንብረታቸውን ለሚዘርፉ አሳልፎ ሰጣቸው››

ከፊቱ እስኪያስወግዳቸው ድረስ
‹‹ፊቱ›› የእርሱን ትኩረትና ለእነርሱ ማሰብን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጨርሶ እስኪተዋቸው ድረስ›› ወይም፣ ‹‹ከእንግዲህ በፊቱ እስከማይሆኑ ድረስ››

2 Kings 17:21

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ እስራኤል ላይ የፈረደበት ምክንያት ከጀርባው ያለውን ታሪክ በማቅረብ ቀጥሏል።

እስራኤልን ቀደደ
‹‹ቀደደ›› በከባድ ሁኔታ መለየት ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ የእስራኤልን ሕዝብ አስወገደ››

ከዳዊት ንጉሣዊ ዘር
‹‹ከዳዊት ዘር መንግሥት››

እስራኤላውያንን ያህዌን ከመከተል አራቀ
‹‹እስራኤላውያንን ያህዌን ከመከተል መለሰ››

ከእነርሱ አልራቁም
እስራኤላውያን እነዚያን ኀጢአት ማድረግ አልተዉም›› ወይም፣ ‹‹ከእነዚያ ኀጢአቶች አልራቁም››

ስለዚህ ያህዌ ከፊቱ አስወገዳቸው
እዚህ ላይ፣ ‹‹ፊት›› ትኩረትንና ለእነርሱ ማሰብን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለዚህም ያህዌ የእርሱን ትኩረት ከማግኘት አራቃቸው››

2 Kings 17:24

አጠቃላይ መረጃ
አረማዊ ሃይማኖታቸውን ይለማመዱ በነበሩ አዲሶቹ የአሦር ሰፋሪዎች የያህዌ ፍርድ መምጣቱን ቀጥሏል።

ኩታ... አዋና... ሐማት... ሴፈርዋይ
እነዚህ የአሦር መንግሥት ከተሞች ናቸው።

በዚያ መኖር እንደ ጀመሩም
‹‹እነዚህ ሰዎች መጀመሪያ እዚያ ሲኖሩ››

ወስዳችሁ በሰማርያ ከተሞች ያኖራችኃቸው ሕዝቦች
‹‹ከሌሎች አገሮች አንሥታችሁ በሰማርያ ከተሞች እንዲኖሩ የላካችኃቸው ሕዝቦች››

የዚያ አገር አምላክ ምን እንደሚፈልግ አላወቁም
‹‹እስራኤላውያን በዚያ ምድር የሚያመልኳቸውን አማልክት አላወቁም››

2 Kings 17:27

ከሰማርያ ማርካችሁ ካመጣችኃቸው ካህናት አንዱን ውሰዱ›› ያስተምር
‹‹ሳምራዊው ካህን አሁን እዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ያስተምር››

2 Kings 17:29

ሱኮትበኖት... ኔርጋል... አሰማት... አልባዝር... ተርታቅ... አድራሜሌክ... አናሜሌክ
እነዚህ ወንዶችና ሴቶች አማልክት ስሞች ናቸው።

ኩታ... ሐማት
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው።

ኣዋውያን... ሴፈርዋም
እነዚህ የሕዝብ ስሞች ናቸው።

ልጆቻቸውን የሚቃጠል መሥዋዕት አድርገው አቀረቡ
‹‹የገዛ ልጆቻቸውን ሠው›› ወይም፣ ‹‹መሥዋዕት እንዲሆኑ ልጆቻቸውን በእሳት አቃጠሉ

2 Kings 17:32

እነርሱ
የአሦር ንጉሥ በሰማርያ ከተሞች እንዲኖሩ ያመጣቸውን አረማውያን ሕዝብ ይመለከታል።

2 Kings 17:34

የመጡበትን ሕዝብ ልማድ ተከተሉ
‹‹የቀድሞ ልማዳቸውን ማድረግ ቀጠሉ››

ያህዌንም በአግባቡ አያመልኩም
እነዚህ ሰዎች የሚፈልጉት የያህዌን ቁጣ ለማብረድ ነበር። ያህዌ የሚፈልገውን ለማወቅ ወይም ከእርሱ ጋር ግንኙነት ለማድረግ አይፈልጉም።

2 Kings 17:36

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ክፍል ያህዌን ለማምለክ በቀረበ ጥሪ ወደ መጠናቀቅ ተቃርቧል።

በታላቅ ኀይልና በተዘረጋች ክንድ
x

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Kings 17:39

አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ላይ መልእክቱ የሚጠናቀቀው ያህዌን ብቻ እንዲያመልኩ ጥሪ በማቅረብ ነው።

አልሰሙም
‹‹መስማት›› ልብ ማለትና የሰሙትን መፈጸም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አልታዘዙም››

እነዚህ ሕዝቦች ያህዌን ፈሩ
እነዚህ ሰዎች ያህዌን የሚፈሩት አማልክቶቻቸውን ላለማስቆጣት እንደሚያደርጉት እርሱንም ላለማስቆጣት ብቻ ነበር።

ዛሬም እንደ ቀጠሉበት ነው
‹‹እስከ ዛሬ ድረስ ያንኑ እያደረጉ ነው›› - ‹‹ዛሬም›› የሚለው ሐረግ ጸሐፊው የነበረበትን ዘመን ያመለክታል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 18

1 የኤላ ልጅ ሆሴዕ በእስራኤል በነገሠ በሦስተኛው ዓመት የአካዝ ልጅ ሕዝቅያስ የይሁዳ ንጉሥ ሆነ። 2 ሕዝቅያስም ሲነግሥ ዕድሜው ሃያ አምስት ዓመት
ነበር። እርሱም በኢያሩሳሌም ሃያ ዘጠኝ ዓመት ገዛ። እናቱም አቢያ የምትባል የዘካርያስ ልጅ ነበረች። 3 ሕዝቅያስም የአባቱን የንጉሥ ዳዊትን መልካም
አርአያነት በመከተል እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሥራ ሠራ። 4 የአሕዛብን የማምለክያ ስፍራዎች አስወገደ፤ የድንጋይ ዐምዶችንም ሰባብሮ አጠፋ፤ ኣሼራ
ተብላ በምትጠራው ሴት አምላክ ስም የተቀረጹትን ምስሎች ሁሉ አፈረሰ። ሙሴ ከነሐስ ሠርቶት የነበረውን ኔሑሽታን ተብሎ የሚጠራውን የእባብ ምስል
ሰባብሮ አደቀቀ፤ ምክንያቱም እስከዚያን ጊዜ ድረስ እስራኤላውያን ለእርሱ ዕጣን ያጥኑለት ነበር። 5 ሕዝቅያስ በእስራኤል አምላክ በእግዚአብሔር ተማመነ፤
ከእርሱ በፊትም ሆነ ከእርሱ ወዲህ እርሱን የመሰለ ሌላ ንጉሥ በይሁዳ አልተነሣም። 6 ሕዝቅያስም ለእግዚአብሔር ታማኝ ስለ ሆነ ከእግዚአብሔር መንገድ
የራቀበት ጊዜ የለም፤ ለሙሴ የሰጣቸውን ትእዛዞች ሁሉ በጥንቃቄ ይፈጽም ነበር። 7 ስለዚህም እግዚአብሔር ከሕዝቅያስ ጋር ስለነበረ የሚሠራው ሁሉ
ይከናወንለት ነበር። ሕዝቅያስም በአሦር ንጉሠ ነገሥት ላይ ዐምፆ ለእርሱ መገዛትን አሻፈረኝ አለ። 8 ፍልስጥኤማውያንንም ድል ነሥቶ ከትንሽ እስከ ታላቅ
የተመሸጉ ከተማ ጋዛንና በዙሪያው የሚገኘውን ግዛት፣ የሚኖሩበትን ስፍራ ሁሉ አጠቃ። 9 ሕዝቅያስ በነገሠ በአራተኛው ዓመት ማለትም የኤላ ልጅ ሆሴዕ
በእስራኤል በነገሠ በሰባተኛው ዓመት የአሦር ንጉሥ ስልምናሶር በእስራኤል ላይ አደጋ በመጣል ሰማርያን ከበበ። 10 በሦስተኛውም ዓመት መጨረሻ ሰማርያ
በሙሉ ተያዘች፤ ይህም የሆነው ሕዝቅያስ በነገሠ በስድስተኛው ዓመት ሆሴዕም በነገሠ በዘጠነኛው ዓመት ነበር። 11 የአሦር ንጉሠ ነገሥት እስራኤላውያንን
ማርኮ ወደ አሦር በመውሰድ ከእነርሱ ጥቂቶቹን በአላሔ ከተማ፣ ጥቂቶቹን በጋዛ አውረጃ በሚገኘው በአቦር ወንዝ አጠገብ፣ ሌሎቹን ደግሞ በሜዶን ከተሞች
እንዲሰፍሩ አደረገ። 12 ይህም የሆነበት ምክንያት እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር ባለመታዘዛቸው ነበር፤ ይኸውም እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር የገባውን ቃል
ኪዳን አፈረሱ፣ በእግዚአብሔር አገልጋይ በሙሴ አማካይነት ለተሰጠ ሕግ ሁሉ ታዛዦች ሆነው አልተገኙም፤ ለመስማትም ሆነ ሕጉን ለመጠበቅ አሻፈረን አሉ።
13 ከዚያም ሕዝቅያስ በነገሠ በዐሥራ አራተኛው ዓመት የአሦር ንጉሠ ነገሥት ሰናክሬም አደጋ በመጣል የተመሸጉትን የይሁዳ ከተሞች ያዘ። 14 ስለዚህም
የይሁዳ ንጉሥ ሕዝቅያስ በለኪሶ ሰፍሮ ለነበረው ለሰናክሬም፣ እኔ በድያለሁ፤ እባክህን እኔን ተወኝ፤ የምትጠይቀኝን ሁሉ እልክልሃለሁ ሲል መልእክት ላከ።
ንጉሠ ነገሥቱም ለይሁዳ ንጉሥ ሕዝቅያስ እኔ የምፈልገው ሦስት መቶ መክሊት ብርና ሠላሳ መክሊት ወርቅ እንድትልክልኝ ነው ሲል መለሰለት። 15 ስለዚህም
ሕዝቅያስ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስና በቤተ መንግሥተ ዕቃ ግምጃ ቤት የነበረውን ብር ሁሉ ሰብስቦ ላከለት። 16 እንዲሁም በእግዚዚብሔር ቤተ መቅደስ
መግቢያ በሮች ላይ ተለብጦ የነበረውን ወርቅና እርሱም ራሱ በቤተ መቅደሱ የበር ዐምዶች ላይ ለብጦት የነበረውን ወርቅ ጭምር ወደ ሰናክሬም ላከ። 17 ነገር
ግን የአሦር ንጉሠ ነገሥት እንደገና የተጠናከረ ታላቅ ሠራዊት ከለኪሶ ተንቀሳቅሶ ወደ ኢየሩሳሌም በመዝመት በሕዝቅያስ ላይ አደጋ እንዲጥልበት አዘዘ፤
ሠራዊቱም ከፍተኛ ሥልጣን ባላቸው ሦስት የጦር አዛዦቹ የሚመራ ነበር። እነርሱም ወደ ኢየሩሳሌም እንደ ደረሱ ከላይኛው ኩሬ ውሃ በሚተላለፍበት ቦይ
አጠገብ ወደ ልብስ አጣቢዎች መስክ የሚወስደውን መንገድ ያዙ። 18 ከዚያ ወደ ሕዝቅያስ መልእክት ላኩበት፤ ሕዝቅያስም አገልጋዮቹ የሆኑ ሦስት
ባለሥልጣኖች ሄደው እንዲገናኙአቸው አዘዘ። እነርሱም የቤተ መንግሥቱ ኃላፊ የሆነው የኬልቂያስ ልጅ ኤልያቄም፣ የቤተ መንግሥት ጸሐፊ የሆነው ሳምናስና
የቤተ መዛግብት ኃላፊ የሆነው የአሳፍ ልጅ ዮአስ ነበሩ። 19 ስለዚህም የአሦር ዋና የጦር አዛዥ እንዲህ አላቸው፦ ለሕዝቅያስ እንዲህ በሉት፣ ‘ታላቁ የአሦር
ንጉሥ እንዲህ ይላል፦ እንደዚህ የተማመንክበት ነገር ምንድን ነው? 20 በጦርነት የሚረዳ ኃይል እንዳለህ የተናገርከው ከንቱ ቃላት ናቸው፤ በእኔ ላይ ለማመጽ
የቻልከው በምን ተማምነህ ነው? 21 የግብጽ ንጉሥ ይረዳኛል ብለህ አስበህ ከሆነ የተቀጠቀጠ ሸምበቆ እንደሚመረኮዝ ሰው መሆንህ ነው፤ እርሱ ተሰብሮ
ስንጣሪው እጅህን ያቆስልሃል፤ እንግዲህ የግብጽ ንጉሥ ፈርዖን ለሚተማመኑበት ሁሉ እንዲህ ነው’ ሲል ተናገረ። 22 የአሦር የጦር አዛዥ ንግግሩን በመቀጠል
እንደገና እንዲህ አለ፦ አምላክህ እግዚአብሔር እንደሚረዳህ ታስብ እንደሆነ፣ ይህ እንዳይሆን አንተ የእግዚአብሔርን የተቀደሱ ስፍራዎችንና መሠዊያዎችን
ደምስሰህ የይሁዳና የኢየሩሳሌም ሕዝብ ማምለክ የሚገባቸው ኢየሩሳሌም ውስጥ በሚገኘው በአንድ መሠዊያ ብቻ ነው ብለህ ወስነሃል። 23 አሁንም በንጉሠ
ነገሥቱ ስም ለፍልሚያ እጠይቅሃለሁ፤ መጋለብ የሚችሉ በቂ ሰዎች ታገኝ አንደ ሆነ እስቲ ሁለት ሺህ ፈረሶች ልስጥህ። 24 አንተ እጅግ በጣም ዝቅተኛ
ከሆነው ከአሦር ተራ የጦር መኮንን ጋር እንኳ መወዳደር አትችልም፤ ግብጻውያን ሠረገሎችንና ፈረሶችን ይልኩልኛል ብለህ የምትጠባበቀውም በዚሁ ምክንያት
ነው። 25 እኔ በአንተ አገር ላይ አደጋ የጣልኩባትና የደመሰስኳት ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ይመስልሃልን? እግዚአብሔር ራሱ በዚህች አገር ላይ አደጋ
እንድጥልባትና እንድደመስሳት አዞኛል። 26 ኤልያቄም፣ ሳምናስና ዮአስ ይህን የጦር አዛዥ ትርጉሙን ስለምናውቅ በሶርያ ቋንቋ እንድትነግረን እንለምንሃለን፤
በቅጥር ላይ ያሉት ሕዝብ ሁሉ በሚሰሙት በዕብራይስጥ ቋንቋ አትናገረን አሉት። 27 የጦር አዛዡም፣ የአሦር ንጉሠ ነገሥት ይህን ሁሉ ለእናንተና ለንጉሣቸሁ
ብቻ እንድናገር የላከኝ መሰላችሁን? እንደ እናንተ ኩሳቸውን ለመብላትና ሽንታቸውን ለመጠጣት ለሚገደዱ ሰዎችም ጭምር ስለ ሆነ እኔ የምናገረውን በቅጥር
ላይ ያሉት ሰዎች ሁሉ እንዲሰሙት እንድናገር አልላከኝምን? ሲል መለሰላቸው። 28 ከዚያም የአሦር የጦር አዛዥ ከተቀመጠበት ተነሥቶ ቆመ፤ ድምፁንም ከፍ
አድርጎ በዕብራይስጥ ቋንቋ እንዲህ እያለ ጮኸ፦ የአሦር ንጉሠ ነገሥት የሚነግራችሁን ስሙ፤ 29 በሕዝቅያስ አትታለሉ፤ እርሱ ሊያድናችሁ ከቶ አይችልም። 30
ሕዝቅያስ፣ በእግዚአብሔር ታመኑ፤ እርሱ ያድናችኋል፤ ከተማችንም በአሦርያውያን ሠራዊት እጅ እንዳትገባ ይከላከልልናል እያለ የሚሰብካችሁን አትስሙት። 31
ሕዝቅያስ የሚላችሁን አታዳምጡ፤ የአሦር ንጉሠ ነገሥት ከከተማችሁ ወጥታችሁ እጃችሁን እንድትሰጡ አዞአችኋል፤ ይህን ብታደርጉ ሁላችሁም እያንዳንዳችሁ
የወይን ተክሎቻችሁን ዘለላና የበለስ ዛፎቻችሁን ፍሬ ትበላላችሁ፤ ከጉድጓዶቻችሁም ውሃ ትጠጣላችሁ። 32 ይህም ሁሉ የሚሆነው ንጉሠ ነገሥቱ የእናንተን
አገር ወደምትመስል ምድር ወስዶ እስከሚያሰፍራችሁ ድረስ ነው፤ በዚያችም ምድር ወይን ጠጅ የሚገኝባቸው የወይን ተክል ቦታዎችና በቂ የእንጀራ እህል
የሚመረትባቸው እርሻዎች አሉ፤ ምድሪቱም የወይራ ፍሬና የወይራ ዘይት እንዲሁም ማር የሞላባት ናት። ንጉሠ ነገሥቱ የሚያዛችሁን ብትፈጽሙ በሕይወት
ትኖራላችሁ እንጂ አትሞቱም። ስለዚህ ሕዝቅያስ፣ “እግዚአብሔር ይታደጋችኋል” እያለ በመስበክ አያሙኛችሁ። 33 ለመሆኑ ከሌሎች ሕዝቦች አማልክት አንዱ
እንኳ ከአሦር ንጉሠ ነገሥት እጅ አገሩን ያዳነ ይገኛልን? 34 ታዲያ ይህ ከሆነ የሐማትና የአርፋድ አማልክት የት አሉ? የሴፈርዋይ፣ የሄናና የዒዋ አማልክትስ የት
ደረሱ? ከእነርሱ አንዱ እንኳ ሰማርያን ከእጄ ማዳን ችሎአልን? 35 የእነዚህ ሁሉ አገሮች አማልክት ንጉሠ ነገሥቶቻቸውን ለማዳን የቻሉበት ጊዜ አለን? ታዲያ
እንግዲህ እናንተ እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ያድናታል ብላችሁ የምታስቡት እንዴት ነው? 36 ሕዝቡም ቀደም ሲል ንጉሥ ሕዝቅያስ ባዘዛቸው መሠረት አንዲት
ቃል ሳይናገሩ ዝም አሉ። 37 ከዚያም ኤልያቄም፣ ሳምናስና ዮአስ በሐዘን ልብሳቸውን ቀደዱ፤ ወደ ንጉሥ ሕዝቅያስ ቀርበው የአሦራውያን የጦር አዛዥ
የተናገረውን አስረዱት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Kings 18:1

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቅያስ በአባቱ በአካዝ ቦታ በይሁዳ ነገሠ

ሆሴዕ... ኤላ... ዘካርያስ
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው።

አብያ
ይህ የሴት ስም ነው።

በያህዌ ዐይን ፊት መልካም ነገር አደረገ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ዐይን›› የያህዌን ትኩረትና ሐሳብ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ንጉሥ ሕዝቅያስ ለያህዌ መልካም ነገር አደረገ›› ወይም፣ ‹‹ሕዝቅያስ ያህዌ መልካም የሚለውን አደረገ››

2 Kings 18:4

አጠቃላይ መረጃ
የንጉሥ ሕዝቅያስ ታሪክ ቀጥሏል።

በየኮረብታው ላይ ያሉትን ማምለኪያዎች አስወገደ፤ አዕማደ ጣዖታትን ሰባበረ
‹‹ሕዝቅያስ ከፍታው ቦ የነበረውን ማምለኪያ አስወገደ፤ የመታሰቢያ ድንጋዮችን ሰባበረ፤ የአሼራን እንጨት አዕማዶች ቆረጠ››

ነሑሽታን
ስሙ፣ ‹‹የናስ እባብ ጣዖት›› ተብሎ ሊተረጐም ይችላል።

2 Kings 18:6

አጠቃላይ መረጃ
የንጉሥ ሕዝቅያስ ታሪክ ቀጥሏል።

ከያህዌ ጋር ተጣበቀ
‹‹ተጣበቀ›› ከእርሱ ታማኝ በመሆን ጸና ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕዝቅያስ ለያህዌ ታማኝ ሆነ›› ወይም፣ ‹‹ሕዝቅያስ ለያህዌ ታማኝ በመሆን ጸና››

በሚሄድበት ሁሉ ተከናወነለት
‹‹ሕዝቅያስ በሄደበት ሁሉ ስኬታማ ነበር››

የተመሸገች ከተማ
ዙሪያውን በግንብ የተከበበች ከተማ

2 Kings 18:9

ሆሴዕ... ኤላ... ስልምናሶር
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው

2 Kings 18:11

አላሔ... አቦር ወንዝ... ጐዛን
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው

ሜዶን
ይህ የሕዝብ ስም ነው

የአሦር ንጉሥ እስራኤልን ማርኮ ወደ አሦር አፈለሳቸው
‹‹የአሦር ንጉሥ እስራኤላውያንን ከአገራቸው ወስደው በአሦር እንዲያኖሩዋቸው ሰራዊቱን አዘዘ››

የያህዌ ድምፅ
‹‹ድምፅ›› የያህዌ ትእዛዝ መልእክት ማለት ነው አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የያህዌ ትእዛዝ››

2 Kings 18:13

ሰናክሬም
ይህ የሰው ስም ነው።

ለኪሶ
ይህ የከተማ ስም ነው

የተመሸጉ ከተሞች
ለጥበቃ እንዲሆን ዙሪያውን በግንብ የተከበቡ ከተሞች። 2 ነገሥት 18፥8 ላይ፣ ‹‹የተመሸጉ ከተሞች›› እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

ከእኔ ተመለሰ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ከእኔ›› የሚለው የሕዝቅያስን መንግሥት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰራዊትህን ከግዛቴ መልስልኝ››

የምትጠይቀኝን ሁሉ እከፍላለሁ
‹‹ክፈል የምትለኝን ሁሉ እሰጣለሁ››

መክሊት
ይህ ገንዘብ ለመመዘን ጥቅም ላይ የሚውል ነገር ስም ነው። አንድ መክሊት 33 ኪሎ ግራም ይመዝናል።

ግምጃ ቤቶች
ይህ ገንዘብና የከበሩ ነገሮች የሚቀመጡበት ቤተ መንግሥት ውስጥ ያለ ቦታ ነው።

2 Kings 18:16

የአሦር ንጉሥ ታላቅ ሰራዊትን በማንቀሳቀስ ታርታንና ዋናውን አዛዥ ራብሳሪሰን ላከ።
ሰናክሬም ንጉሥ ሕዝቅያስ ጋር እንዲገናኙ ከሰራዊቱ ውስጥ ታርታንና ራብሳሪስን የሚባሉ አዛዦች ጨምሮ ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም ላከ።

ታራታን... ሰብሳሪስ
አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች እነዚህን እንደ ተፅውዖ ስም ያስቀምጣሉ። ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች እንደ ሹመት ያስቀምጣሉ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ታርታሮች... ሰብሰሪሶች›› ወይም፣ ‹‹የወታደሮች መሪ... የቤተ መንግሥት ሹም››

ለኪሶ
ይህ የከተማ ስም ነው።

የላይኛው ኩሬ መስኖ
‹‹ላይኛው ኩሬ›› ውሃ የሚጠራቀምበትና ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ የሚፈሰው ቦይ

መጥተው ቆሙ
‹‹ንጉሥ ሕዝቅያስ መጥቶ እንዲያገኛቸው እዚያ ጠበቁት››

ኤልያቄም... ኬልቅያስ... ሰምናስ... ዮአስ... አሳፍ
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው።

2 Kings 18:19

አጠቃላይ መረጃ
ራፋስቂስ የአሦርን ንጉሥ መልእክት ለንጉሥ ሕዝቅያስ ሰዎች እየተናገረ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የትምክህትህ ምክንያት ምንድነው? ...በእኔ ላይ እንዲህ ያመፅኸውስ በማን ተማምነህ ነው?
የአሦር ንጉሥ (በመልእክተኛው በራፋስቂስ በኩል) እነዚህን ጥያቄዎች ያቀረበው ንጉሥ ሕዝቅያስ ራሱንና የግብፅን ርዳታ እንዲጠራጠር እንጂ፣ መልስ በመፈለግ አይደለም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በማንም አትተማመን። በእኔ ላይ በማመፅህ ጅል ሆነሃል››

በዚህ በተቀጠቀጠ ሸምበቆ
የአሦር ንጉሥ ደካማ ሸንበቆ ነው፤ አንተን የሚደግፍህ ይመስልሃል፤ ስትደገፍበት ግን ተሰብሮ ይወጋሃል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የግብፅ ደካማ ርዳታ››

ሰው ቢደገፍበት... ወግቶ የሚያቆስል
ሸንበቆን ምርኩዝ የሚያደርግ ሰው ምን እንደሚሆን በመግለጽ ተናጋሪው በተለዋጭ ዘይቤ ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰው በዚህ ቢደገፍ ጉዳት ይደርስበታል››

2 Kings 18:22

አጠቃላይ መረጃ
ራፋስቂስ የአሦርን ንጉሥ መልእክት ለንጉሥ ሕዝቅያስ ሰዎች እየተናገረ ነው።

እርሱ ከፍታ ቦታ በኢየሩሳሌም አይደለምን?
ጠያቂው አድማጮቹ መልሱን እንደሚያውቁ ይገነዘባል፤ የሚጠይቀው አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእርሱ ከፍታ ቦታ ያለው በኢየሩሳሌም መሆኑን ማስታወስ አለባችሁ!››

2 Kings 18:24

አጠቃላይ መረጃ
ራፋስቂስ የአሦርን ንጉሥ መልእክት ለንጉሥ ሕዝቅያስ ሰዎች እየነገረ ነው።

ከጌታዬ የበታች ሹማምንት እንኳ አንዱን እንዴት መመለስ ትችላለህ?
ይህን ጥያቄ የሚያቀርበው የሕዝቅያስ ጦር የመዋጋት ዐቅም እንደሌለው አጽንዖት ለመስጠት ነው። የሕዝቅያስ ሰራዊት ላይ ለማፌዝ ግነት ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፣ 1) ‹‹ከንጉሡ ወታደሮች ታናሽ የሆነውን እንኳ ማሸነፍ አትችልም›› ወይም 2) ‹‹የበታች ሹሙ የሚያዝዛቸውን ወታደሮች እንኳ ማሸነፍ አትችልም››

አደጋ ጥዬ ይህችን ስፍራ ለማጥፋት የመጣሁት ያለ ያህዌ ፈቃድ ይመስልሃልን?
ይህን ጥያቄ ያቀረበው እስራኤልን እንዲያጠፋ ስኬት የሰጠው ያህዌ መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወደዚህ መጥተን ምድሪቱን እንድናጠፋ የነገረን ያህዌ ራሱ ነው!››

2 Kings 18:26

ኤልያቂም... ኬልቅያስ... ሰምናስ... ዮአስ
የእነዚህን ሰዎች ስም 2 ነገሥት 18፥18 ላይ እንደ ተረጐምህ ተርጉመው።

ቅጥሩ ላይ ባሉ ሰዎች ጆሮ
‹‹ጆሮ›› የመስማት ችሎታን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በቅጥሩ ላይ ያሉ ሰዎች ሰምተው እንዳይፈሩ››

ጌታዬ ይህን እንድናገር የላከኝ ለጌታችሁና ለእናንተ ብቻ ነውን? እነርሱም እንደ እናንተው ገና ኩሳቸውን ይበሉ ዘንድ፣ ሽንታቸውንም ይጠጡ ዘንድ በቅጥሩ ላይ ለተቀመጡት ጭምር አይደለምን?
ይህን የጠየቀው አድማጮቹ መልሱን እንዲሚያውቁ በማሰብ ሲሆን፣ ፍላጐቱ የኢየሩሌምን ሕዝብና መሪዎች ማዋረድና ድል ማድረግ መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጌታዬ የላከኝ ወደ እናንተና ወደ ጌታችሁ ብቻ ሳይሆን፣ በሕይወት ለመኖር የገዛ ኩሳቸውን ለሚበሉና የገዛ ሽንታቸውን ለሚጠጡት ለዚህ ከተማ ሰዎች ጭምር ነው››

2 Kings 18:28

ከጎይሌ
‹‹ጎይሌ›› የንጉሠን ችሎታ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእኔ›› ወይም፣ ‹‹የሰራዊቴ ጎይል››

ይህች ከተማ ለአሦር ንጉሥ አልፋ አትሰጥም
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአሦር ንጉሥ ሰራዊት ይህችን ከተማ እንዲይዝ ያህዌ በፍጹም አይፈቅድም››

እጅ
‹‹እጅ›› መቆጣጠርን፣ ሥልጣንና ጎይልን ያመለክታል።

2 Kings 18:31

ከእኔ ጋር ሰላም መሥርቱ፤ እጃችሁን ስጡ
‹‹ከከተማው ወጥታችሁ እጃችሁን ስጡኝ›› ወይም፣ ‹‹እጃችሁን ለመስጠት ከእኔ ጋር ተስማሙ፤ ከከተማ ወጥታችሁ ወደ እኔ ኑ››

ከገዛ ወይኑ.. ከገዛ በለሱ... ከገዛ ጉድጓዱም ውሃ
እነዚህ የምግብና ውሃ መገኛዎች ሰላምንና መተረፍረፍን ይወክላሉ። ይህ ይህን ሐሳብ ለመግለጽ የተለመደ አባባል ነው።

እህልና አዲስ የወይን ጠጅ... እንጀራና የወይን እርሻ... የወይራ ፍሬና ማር
ይህ የመልካምና በየዕለቱ ሕይወት የበዛ ነገር የማግኘት ምሳሌ ነው።

2 Kings 18:33

አጠቃላይ መረጃ
ራፋስቂስ የአሦርን ንጉሥ መልእክት ለንጉሥ ሕዝቅያስ ሰዎች እየተናገረ ነው።

ከአሕዛብ አማልክት... ከአሦር?
ይህን የጠየቀው መልሱን ስለሚያውቁ አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከአሕዛብ አማልክት አንዱ እንኳ ከአሦር አላዳኑዋቸውም››

የአርፋድ አማልክት የት ደረሱ?
ይህን የጠየቀው መልሱን ስለሚያውቁ አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአርፋድን አማልክት አጥፍቻለሁ››

ሐማት... አርፋድ... ሴፈርዋይም... ሄና... ዒዋም... ሰማርያ
እነዚህ እዚያ የሚኖሩ ሰዎችን የሚወክሉ የቦታ ስሞች ናቸው።

ከእጁ
‹‹እጅ›› መቆጣጠርን፣ ጎይልንና ሥልጣንን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእኔ ቁጥጥር››

አገሩን ከእኔ ለማዳን የቻለ አምላክ አለን?
ይህን የጠየቀው መልሱን ስለሚያውቁ አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ማንኛውም አምላክ ምድሩን ከእኔ ጎይል አላዳነም››

ከጎይሌ
‹‹ጎይሌ›› ያ ጎይል ያለውን ሰው ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእኔ››

ያህዌ ኢየሩሳሌምን እንዴት ከእጁ ማዳን ይችላል?
ይህን የጠየቀው መልሱን ስለሚያውቁ አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ኢየሩሳሌምን ከእኔ ማዳን የሚችልበት አንድም መንገድ የለም››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Kings 18:36

ኤልያቄም... ሰምናስ... ዮአስ... አሳፍ...
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው።

የቤተ መንግሥቱ አዛዥ
‹‹ቤተ መንግሥቱን የሚያስተዳድር››

ጸሐፊው
‹‹ታሪክ መዝጋቢ››

ዋና አዛዥ
x

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 19

1 ንጉሥ ሕዝቅያስ ይህን ሁሉ በሰማ ጊዜ በሐዘን ልብሱን ቀደደ፤ ማቅ ለብሶም ወደ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ሄደ። 2 ወዲያውም የቤተ መንግሥቱ ኃላፊ የሆነውን ኤልያቄምን፣ የቤተ መንግሥቱን ጸሐፊ ሳምናስንና ሽማግሌዎች ካህናትን ወደ አሞጽ ልጅ ወደ ነቢዩ ኢሳይያስ ላከ፤ እነርሱም ራሳቸው ማቅ ለብሰው ነበር። 3 ለኢሳይያስም እንዲነግሩት የላከው መልእክት ከዚህ የሚከተለው ነው፦ ዛሬ የታላቅ መከራ ቀን ነው፤ የሚያሳፍር ቅጣትና ውርደት እየደረሰብን ነው፤ የምትወልድበት ጊዜ ደርሶ ለማማጥ አቅም እንዳነሣት ሴት ሆነናል። 4 የአሦር ንጉሠ ነገሥት ሕያው እግዚአብሔርን እንዲሰድብለት ከፍተኛ ባሥልጣኑን ልኮአል፤ አምላክህ እግዚአብሔር ይህን ስድብ ሰምቶ ተሳዳቢው ይቀጣ ይሆናል። ስለዚህ ከሕዝባችን መካከል በሕይወት ለተረፉት ሰዎች እባክህ ወደ እግዚአብሔር ጸልይ። 5 የንጉሥ ሕዝቅያስ መልእክተኞች ወደ ኢሳይያስ በመጡ ጊዜ፣ 6 ኢሳይያስ፣ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ብላችሁ ለንጉሣችሁ ንገሩት አላቸው፣ የአሦር ንጉሥ አገልጋዮች ሲሰድቡኝ ስለ ሰማችሁት ቃል አትፍሩአቸው። 7 እነሆ እኔ የሽብር ወሬ የሚያሰማ መንፈስ እልክበታለሁ፤ ስለዚህ ወደ አገሩ ተመልሶ እንዲሄድ፣ እዚያ በገዛ ምድሩ በሰይፍ ተመትቶ እንዲሞት አደርጋለሁ። 8 ከዚያ የአሦር የጦር አዛዥ፣ የአሦር ንጉሥ ከሰፈሩ ከለኪሶ ተነሥቶ ልብናን ሊያጠቃ እንደ ሄደ በመስማቱ እርሱም ወደ ለኪሶ ሄደ። 9 ኢትዮጵያ ንጉሥ በቲርሃቅ የሚመራ የግብጽ ሠራዊት እነርሱን ለመውጋት በመገሥገሥ ላይ መሆኑን ሰናክሬም ሰማ፤ ወዲያውኑ የአሦር ንጉሠ ነገሥት ወደ ሕዝቅያስ እንዲህ የሚል ደብዳቤ በመልእክተኞች እጅ ላከ፦ 10 «የይሁዳ ንጉሥ ሕዝቅያስ ሆይ፣ የምትታመንበት አምላክ ኢየሩሳሌም በአሦር ንጉሠ ነገሥት እጅ አትወድቅም ብሎ አያታልልህ፤ 11 የአሦር ነገሥታት አገሮችን ሁሉ እንዴት ፈጽመው እንደ ደመሰሱ ሰምተሃል፤ አንተስ የምታመልጥ ይመስልሃልን? 12 የቀድሞ አባቶቼ የጎዛንን፣ የካራንና የሬጼፍን ከተሞች አጥፍተዋል፤ በተላሳር የሚኖሩትን የዓዴንን ሕዝብ ገድለዋል፤ ይህ ሁሉ ሲሆን፣ ከአማልክቶቻቸው አንድ እንኳ ሊያድናቸው ችሎአልን? 13 ለመሆኑ የሐማት፣ የአርፋድ፣ የሴፈርዋይም፣ የሄናዕና የዒዋ ከተሞች ነገሥታት የት አሉ?» 14 ንጉሥ ሕዝቅያስ ደብዳቤውን ከመልእክተኞች ተቀብሎ አነበበው፤ ወደ ቤተ መቅደስም ወስዶ ደብዳቤውን በእግዚአብሔር ፊት ዘረጋው። 15 እንዲህ ሲልም ጸለየ፦ «የሠራዊት አምላክ፣ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፤ በኪሩቤል ላይ የተቀመጥህ፣ አንተ ብቻ አምላክ ነህ፤ የዓለምንም መንግሥታት የምትመራ አንተ ነህ፤ ሰማይንና ምድርን የፈጠርህ አንተ ነህ። 16 አሁንም እግዚአብሔር ሆይ፤ የደረሰብንን ነገር ሁሉ ተመልከት፣ አንተን ሕያው የሆነከውን አምላክ በመስደብ ሰናክሬም የተናገረውን የዛቻ ቃል ሁሉ አድምጥ፤ 17 እግዚአብሔር ሆይ፣ የአሦር ነገሥታት ብዙ ሕዝቦችንና ምድራቸውን መደምሰሳቸው እርግጥ ነው። 18 ከእንጨትና ከድንጋይ ተጠርበው የተሠሩ የሰው እጅ ሥራ እንጂ አማልክት ስላልነበሩ በእሳት ላይ ጥለው አጠፉአቸው። 19 እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፣ አንተ ብቻ አምላክ መሆንህን የዓለም መንግሥታት ሁሉ ያውቁ ዘንድ አሁን ከአሦር ንጉሥ አድነን።» 20 ከዚያም የአሞጽ ልጅ ኢሳይያስ ወደ ንጉሥ ሕዝቅያስ እንዲህ የሚል መልእክት ላከ፦ «የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ ‹ስለ አሦር ንጉሠ ነገሥት ስለ ሰናክሬም ዛቻ ወደ እኔ የጸለይከውን ጸሎት ሰምቻለሁ። 21 ስለ እርሱ እግዚአብሔር የተናገረው ቃል ይህ ነው፦ የጽዮን ድንግል ትንቅሃለች፤ ታፌዝብሃለች፤ አንተ እየሸሸህ ሳለህ፣ የኢየሩሳሌም ልጃገረዶች ከኋላህ ሆነው ራሳቸውን ይነቀንቁብሃል። 22 የሰደብከውና የተዳፈርከው ማንን ነው? ድምፅህንስ ከፍ ያደረግኸው በማን ላይ ነው? በትዕቢትስ ዐይንህን ያነሳኸው በማን ላይ ነው? በእስራኤል ቅዱስ በእግዚአብሔር ላይ ነው። 23 በመልእክተኞችህ አማካይነት፣ በእግዚአብሔር ላይ ስድብን አብዝተሃል፤ ‹በሠረገሎቼ ከፍተኛ ወደ ሆኑት ተራራዎች፣ ወደ ሊባኖስ ጫፍ ወጥቻለሁ፤ ረጃጅሞቹን የሊባኖስ ዛፎችዋንና ምርጦቹን ዝግባ ቆርጬአለሁ፤ ወደ ዳርቻዋና ውብ ወደሆነው ጫካዋ ደርሼአለሁ፤› ብለሃል። 24 ‹በባዕድ አገር ጉድጓድ ቆፍሬ ውሃ ጠጣሁ፤ በእግሬ ኮቴዎች የግብጽን ወንዞች አድርቄአለሁ› ብለህ ታብየሃል። 25 ሰናክሬም ሆይ! አስተውል፤ ጥንቱኑ እኔ እንደ ወሰንኩት፣ በቀድሞው ዘመን እንዳቀድኩትና አሁን በሥራ ላይ ባዋልኩት መሠረት የተጠናከሩ ከተሞችን ወደ ፍርስራሽ ክምርነት እንድትለውጥ ያደረግኹህ እኔ መሆኔን አልሰማህምን? 26 የእነዚያ አገር ነዋሪዎች ኃይላቸው ተዳክሞ፣ ተስፋ በመቁረጥ እንዲያፍሩ ተደርገው በምሥራቅ ነፋስ እንደተመቱ የመስክ አትክልቶች፣ እንደ ቀጨጩ አረንጓዴ ቡቃያዎች፣ በጣራ ላይ እንደበቀሉ ሣር ናቸው። 27 እኔ ግን መነሣትህንና መቀመጥህን፣ መውጣትህንና መግባትህን፣ እንዲሁም እኔን መቃወምህን ዐውቃለሁ። 28 በእኔ ላይ ያለው ተቃውሞህና ትዕቢትህ ወደ ጆሮዬ ደርሶአል፤ በአፍንጫህ ትናጋ፣ በአፍህም ልጓም አድርጌ፣ በመጣህበት መንገድ እመልስሃለሁ።» 29 ከዚያም ኢሳይያስ ንጉሥ ሕዝቅያስን አንዲህ አለው፤ «ይህ ሁሉ እንደሚፈጸም ምልክቱ ይህ ነው፣ በአሁኑና በሚቀጥለው ዓመት ሳይዘሩት የሚበቅለውንና የገቦውን እህል ትበላላችሁ፤ በሦስተኛው ዓመት ግን የራሳችሁን እህል ዘርታችሁ ታመርታላችሁ፤ ወይንም ተክላችሁ ፍሬውን ትበላላችሁ፤ 30 በይሁዳ ከጥፋት የተረፉት ሁሉ ወደ መሬት ሥር ሰድደ እንደሚያድግና እንደሚያፈራ ተክል ይሆናሉ፤ 31 ከኢየሩሳሌምና ከጽዮን ተራራ የተረፉት ወገኖች ይወጣሉ፤ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ይህን ይፈጽማል።» 32 ስለዚህ እግዚአብሔር ስለ አሦራውያን ንጉሠ ነገሥት የተናገረውም ቃል ይህ ነው፦ «ሰናክሬም ወደዚህች ከተማ ፈጽሞ አይገባባትም፤ አንድ ፍላጻ እንኳ አይወረውርባትም፤ ጋሻ ያነገበ ወታደርም ወደ እርስዋ አይቀርብም፤ በአፈር ቁልልም አትከበብም። 33 እርሱ ወደዚህች ከተማ ሳይገባ በመጣበት መንገድ ተመልሶ ይሄዳል፤ ይህን የተናገርኩ እኔ እግዚአብሔር ነኝ። 34 ስለ ራሴ ክብርና ለአገልጋዬ ለዳዊት ስለ ሰጠሁት የተስፋ ቃል ይህችን ከተማ እኔ ራሴ ተከላክዬ አድናታለሁ።» 35 በዚያው ሌሊት የእግዚአብሔር መልአክ ወደ አሦራውያን ሰፈር አልፎ አንድ መቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ ወታደሮችን ገደለ፤ በማግስቱ በማለዳ ሰዎች በሚነቁበት ጊዜ ሁሉም ሞተው ተገኙ። 36 ስለዚህ የአሦራውያን ንጉሠ ነገሥት ሰናክሬም ወደ ኋላው በማፈግፈግ ወደ ነነዌ ተመለሰ። 37 ከዕለታት በአንዱ ቀን ናሳራክ በሚል ስም በሚጠራው ባዕድ አምላኩ ቤተ መቅደስ ውስጥ በስግደት ላይ እንዳለ፣ ከልጆቹ ሁለቱ በተለይ አደራሜሌክና ሳራሳር ተብለው የሚጠሩት በሰይፍ ገደሉት፤ እነርሱም ወደ አራራት አምልጠው ሄዱ፤ በእርሱም ፈንታ ተተክቶ ከልጆቹ አንዱ አስራዶን የተባለው ነገሠ።

---

2 Kings 19:1

የያህዌ ቤት
ይህ፣ ‹‹የያህዌ ቤተ መቅደስ›› ሌላ መጠሪያ ነው።

ኤልያቄም... ስምናስ... ኢሳይያስ... አሞጽ
እነዚህ ሁሉ የሰው ስሞች ናቸው።

ኤልያቄምን ላከ
‹‹ሕዝቅያስ ኤልያቄምን ላከ››

ሁሉም ማቅ ለብሰው ነበር
‹‹የሐዘን ልብስ ለብሰው ነበር››

2 Kings 19:3

ይህች ዕለት የጭንቀት ቀን ናት
‹‹ይህች የጭንቀት ጊዜ ናት››

ልጆች ሊወለዱ ምጥ እንዳፋፋመች፣ ነገር ግን ለመገላገል ዐቅም እንደ ታጠባት ሰዓት ናት።
ይህ ጠላትን ለመዋጋት ሕዝቡና መሪዎቹ ዐቅም ያጡበትን ሁኔታ የሚያመለክት ምሳሌ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የአዛዡ ቃል ሁሉ
‹‹ዋናው አዛዥ የተናገረው ሁሉ››

ጸሎት አቅርብ
ጸሎት ማቅረብ ከእኛ በላይ ላለው ለያህዌ አጥብቆ መጸለይን የሚያመለክት ምሳሌያዊ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አጥብቀህ ጸልይ››

2 Kings 19:5

አንድ ዐይነት መንፈስ አሳድርበታለሁ፤ የሆነ ወሬም ሲሰማ ወደ አገሩ ይመለሳል
የአሦርን ንጉሥ ዝንባሌ እቆጣጠራለሁ፤ ስለዚህም አንድ ወሬ ሲደርሰው ወደ አገሩ ይመለሳል።

አንድ ዐይነት መንፈስ አሳድርበታለሁ
‹‹ሐሳቡን እቆጣጠራለሁ›› ወይም፣ ‹‹የተለየ ሐሳብ እንዲያስብ አደርገዋለሁ›› እዚህ ላይ፣ ‹‹መንፈስ›› መንፈሳዊ ማንነትን ሳይሆን፣ የሚያመለክተው ዝንባሌና ሐሳብን ነው።

በሰይፍ እንዲወድቅ አደርገዋለሁ
‹‹በሰይፍ መውደቅ›› መገደል ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በሰይፍ እንዲሞት አደርገዋለሁ›› ወይም፣ ‹‹ሰዎች በሰይፍ እንዲገድሉት አደርጋለሁ››

2 Kings 19:8

የጦር አዛዡ
‹‹በንጉሡ ሥር ያለ የአሦር ባለ ሥልጣን››

ልብና… ለኪሶ
እነዚህ ይሁዳ መንግሥት ውስጥ ያሉ ከተሞች ናቸው።

ሰናክሬም… ቲርሐቅ
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው።

ሊወጋው በመገሥገሥ ላይ መሆኑን
‹‹አሦርን ለመውጋት ሰራዊቱን አዘጋጀ››

ስለዚህ ላከ
‹‹ስለዚህ ሰናክሬም ላከ››

መልእክት
መልእክቱ በጽሑፍ ነበር።

2 Kings 19:10

አጠቃላይ መረጃ
ይህ የአሦር ንጉሥ ሰናክሬም ለንጉሥ ሕዝቅያስ የላከው መልእክት ነው።

በምትመካበት አምላክ እንዳያታልልህ
‹‹የምታምኑትን አምላክ አትተማመኑ፤ እርሱ እየዋሻችሁ ነው››

የአሦር ንጉሥ እጅ
‹‹እጅ›› መቆጣጠርን፣ ሥልጣንና ኀይልን ያመለክታል።

እነሆ ምን እንዳደረጉ ሰምተሃል
‹‹መስማትህን ልብ በል›› ወይም፣ ‹‹በእርግጥ ሰምተሃል›› እዚህ ላይ፣ ‹‹እነሆ›› ቀጥሎ ለሚነገረው ትኩረት ለመሳብ ጥቅም ላይ ውሏል።

ታዲያ፣ አንተስ ከዚህ የምታመልጥ ይመስልሃልን?
ሰናክሬም እንዲህ ያለው እግዚአብሔር እንደማያድናቸው አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አምላክህ አያድንህም›› ወይም፣ ‹‹አንተም ብትሆን ማምለጥ አትችሉም››

2 Kings 19:12

አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ሰናክሬም ለንጉሥ ሕዝቅያስ እየተናገረ ነው።

የአሕዛብ አማልክት አድነዋቸዋልን… አርፋድ?
ጥያቄው ሕዝቅያስ መልሱን እንደሚያውቅ ያስባል፤ አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የአሕዛብ አማልክት በእርግጥ ሕዝቡን ማዳን አልቻሉም… አርፋድ››

አባቶቼ
‹‹የቀድሞ የአሦር ነገሥታት›› ወይም፣ ‹‹የቀድሞ የአሦር ነገሥታት ሰራዊት››

ጐዛን… ካራን… ራፊስ… ኤደን… ተላሰር… ሐማት… አርፋድ… ሴፈርዋይን… ሄና… ዒዋ
እነዚህ ሁሉ የቦታ ስሞች ናቸው።

2 Kings 19:14

ደብዳቤው
ይህ ደብዳቤ የአሦር ንጉሥ ሰናክሬም ለሕዝቅያስ የላከው ነው።

በኪሩቤል ላይ የተቀመጥህ
ኪሩቤል በቃል ኪዳኑ ታቦት መክደኛ ላይ ያሉ መሆኑን በመግለጽ ይህን ማብራራት ያስፈልግህ ይሆናል። የቃል ኪዳኑ ታቦት በላይ በሰማይ ዙፋኑ የሚቀመጥ የያህዌ እግር ማረፊያ መሆኑን የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ብዙ ጊዜ ይናገራሉ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የቃል ኪዳኑ ታቦት ባለበት ከኪሩቤል በላይ በዙፋንህ የምትቀመጥ››

2 Kings 19:16

አጠቃላይ መረጃ
ከአሦር ንጉሥ ከሰናክሬም ደብዳቤውን ካገኘ በኋላ ንጉሥ ሕዝቅያስ ወደ ያህዌ እየጸለየ ነው።

ጆሮህን አዘንብልና ስማ፤ ያህዌ ሆይ፣ ዐይንህን ክፈትና እይ
ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች ሰናክሬም የሚለውን ልብ እንዲል ለያህዌ የቀረቡ ልመናዎች ናቸው።

ጆሮህን አዘንብልና ስማ
‹‹አዘንብል›› እና፣ ‹‹ስማ›› የተሰኙ ቃሎች አንድ ዐይነት ትርጒም ያላቸው ሲሆኑ፣ ለልመናው አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ ሆይ፣ እባክህ እርሱ የሚለውን ስማ››

ያህዌ ሆይ፣ ዐይንህን ክፈትና እይ
‹‹ዐይንህን ክፈት›› እና፣ ‹‹እይ›› የተሰኙት ቃላት አንድ ዐይነት ትርጒም ያላቸው ሲሆኑ፣ ለልመናው አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ ሆይ፣ እባክህ እየሆነ ያለውን ልብ በል››

አማልክቶቻቸውን በእሳት አቃጥለዋል
‹‹የአሦር ነገሥታት የአሕዛብን አማልክት በእሳት አቃጥለዋል››

አሦራውያን በእርግጥ አጥፍተዋቸዋል
‹‹አሦራውያን ሕዝቡንና አማልክቶቻቸውን አጥፍተዋል››

2 Kings 19:19

አጠቃላይ መረጃ
ከአሦር ንጉሥ ከሰናክሬም ደብዳቤን ከተቀበለ በኋላ ንጉሥ ሕዝቅያስ እየጸለየ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እማጸንሃለሁ
‹‹እለምንሃለሁ››

ከነይሉ
‹‹ከአሦር ንጉሥ ጎይል›› ወይም፣ ‹‹ከአሦር ንጉሥ ሰራዊት››

2 Kings 19:20

ድንግሊቱ የጽዮን ልጅ
‹‹ድንግል ልጅ›› የተባሉት ወጣትነትን፣ ንቃትንና ውበትን በሚያመለክት መልኩ የኢየሩሳሌም ሰዎች ናቸው። ‹‹ልጅ›› የሚለውን አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች የከተሞችን ግላዊ ባሕርይ ለመግለጽ ተቅመውበታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የምታምሩ የኢየሩሳሌም ሕዝቦች››

ድንግሊቱ የጽዮን ልጅ ትንቅሃለች፤ ታቃልልሃለችም፤ የኢየሩሳሌም ልጅ ራስዋን ትነቀንቅብሃለች
ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች አንድ ዐይነት ነገር ነው የሚናገሩት

የኢየሩሳሌም ልጅ
‹‹ልጅ›› የኢየሩሌም ሕዝብ ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የኢየሩሌም ከተማ ሕዝብ››

ራሷን ትነቀንቅብሃለች
ይህ ድርጊት በአሦራውያን ትዕቢት ማፌዝን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ታፌዝብሃለች››

የሰደብኸውና ያቃለልኸው ማንን ነው? ድምፅህንስ ከፍ ያደርግኸው? ዐይንህንስ በኩራት ያነሣኸው በማን ላይ ነው? በእስራኤል ቅዱስ ላይ ነው እንዴ?
ሰናክሬምን ለመገሠጽ ያህዌ እነዚህን ጥያቄዎች አቅርቧል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እኔን ሰድበኸኛል፤ አዋርደኸኛል! በእኔ በእስራኤል ቅዱስ ላይ ለመታበይ ድምፅህን ከፍ አድርገሃል ዐይንህን አንሥተሃል!››

ዐይንህን በኩራት አንሥተሃል
‹‹ዐይንህ ማንሣት›› ፊት ላይ የሚታይ ትዕቢትና እብሪት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በጣም በትዕቢት ተመለከትህ››

የእስራኤል ቅዱስ
የእስራኤል አምላክ ያህዌ ማለት ነው።

2 Kings 19:23

አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ሰናክሬምን በተመለከተ ለነቢዩ ኢሳይያስና ለንጉሥ ሕዝቅያስ ያህዌ የሰጠው መልእክት እንደ ቀጠለ ነው። ተጓዳኝ አቀራረብ ይጠቀማል።

ጌታን አቃልለሃል
‹‹ማቃለል›› በግልጽ መቃወም ወይም ማፌዝ ነው።

ወጥቻለሁ... ቆርጫለሁ... ገብቻለሁ
ይህ የሰናክሬም ፉከራ የሚፈጸመው በሰራዊቱ ነው። ‹‹እኔ›› የሚለው ተውላጠ ስም እርሱንና ሰራዊቱን ይወክላል።

በእግሬ ጫማዎችም የግብፅን ምንጮች ሁሉ ረግጬ አድርቄአለሁ
ይህ ፉከራ ሰናክሬም በጣም ብዙ ወታደሮች ስለ ነበሩት ወንዙን በሚሻገሩበት ጊዜ ውሃውን እንደሚያደርቁ ያመለክታል። ይህ የወታደሮቹን ብዛት የሚያሳይ ግነት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በግብፅ ምንጮች ውስጥ በማለፍ አደረቅነው!››

2 Kings 19:25

አጠቃላይ መረጃ
የአሦር ንጉሥ ሰናክሬምን በተመለከተ ለነቢዩ ኢሳይያስና ለንጉሥ ሕዝቅያስ ያህዌ የሰጠው መልእክት እንደ ቀጠለ ነው። ተጓዳኝ አቀራረብ ይጠቀማል።

ከብዙ ጊዜ በፊት... ያደረግሁትን አልሰማህምን
መናገር የፈለገውን አጽንዖት በመስጠት ሰሚው መልሱን እንደሚያውቅ ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በእርግጥ ከብዙ ጊዜ በፊት... ያደረግሁትን ታውቃለህ››

የተመሸጉትን ከተሞች
‹‹መያዝ የማይቻሉ ከተሞች›› ወይም፣ ‹‹በረጅሙ ግንብ የተከበቡ ከተሞች››

ሜዳ ላይ እንደ በቀለ ተክል... እንደ ጠወለገ ሣር
የአሦራውያንን ግሥጋሤ ሜዳ ላይ ካለና ከጠወለገ ሣር ጋር ያነጻጽሩዋል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሜዳ ላይ እንዳለ ተክልና ሣር›› ወይም፣ ‹‹እንደሚገባ ያልተተከለ ደካማ ተክል››

በቤት ጣራ ላይ በቅሎ፣ ገና ሳያድግ እንደ ጠወለገ ሣርም ሆነዋል
የአሦራውያንን ግሥጋሤ እንደሚገባ ለማደግ ከማይችሉ ደካማ ተክሎች ጋር ያነጻጽራል። አማራጭ ትርጒም፣ ከማደጉ በፊት እንደ ሣር›› ወይም፣ ‹‹ከመርዛሙ በፊት እንደ ነበረ ሣር››

2 Kings 19:27

አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ሰናክሬምን በተመለከተ ለነቢዩ ኢሳይያስና ለንጉሥ ሕዝቅያስ ያህዌ የሰጠው መልእክት እንደ ቀጠለ ነው። ተጓዳኝ አቀራረብ ይጠቀማል።

በእኔ መቆጣትህ
‹‹እኔ ላይ በቁጣ መጮኽህ››

እብሪትህ ወደ ጆሮዬ ደርሶአል
‹‹ጆሮ›› መስማትና ማድመጥን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የትዕቢት ንግግርህን ሰምቻለሁ››

ስናጋዬን በአፍንጫህ አደርጋለሁ፤ ልጓሜን በአፍህ አገባለሁ
‹‹ስናጋ›› እና፣ ‹‹ልጓም›› (ፈረሶች መቆጣጠሪያ) ያህዌ ሰናክሬምን እንደሚቆጣጠር ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እንደ እንስሳ እመራሃለሁ››

በመጣህበትም መንገድ እንድትመለስ አደርጋለሁ
ኢየሩሳሌምን ከመውረሩ በፊት ሰናክሬም ወደ አገሩ መመለሱን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ኢየሩሳሌምን ከመውረርህ በፊት በመጣህበት መንገድ ወደ አገርህ እንድትመለስ አደርጋለሁ››

2 Kings 19:29

አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ላይ ኢሳይያስ ለንጉሥ ሕዝቅያስ እየተናገረ ነው። ተጓዳኝ አቀራረብ ይጠቀማል።

የገቦ እህል
‹‹ሳይዘራ የበቀለ እህል››

በሕይወት የተረፈው የይሁዳ ቤት ሥሩን ሰዶ ፍሬ ያፈራል።
የትሩፋኑን መመለስ ሳይዘራ ከበቀለና ፍሬ ከሚሰጥ ተክል ጋር ያነጻጸረዋል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በሕይወት የተረፈው የይሁዳ ሕዝብ ወደ ሕይወትና ወደ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ብልጽግና ይመለሳል›› ወይም፣ ‹‹በይሁዳ የሚቀሩት ያበለጽጋሉ፤ ብዙ ልጆችም ይወልዳሉ››

የያህዌ ቅናት ይህን ታደርጋለች
‹‹ያህዌ የሚወስደው ከባድ ርምጃ ይህን ያደርጋል››

2 Kings 19:32

አጠቃላይ መረጃ
ነቢዩ ኢሳይያስ ለንጉሥ ሕዝቅያስ የተናገረው የያህዌ መልእክት እዚህ ላይ ያበቃል። ተጓዳኝ አቀራረብ ይጠቀማል።

አንዲት ፍላጻ አይወረውርባትም
‹‹ፍላጻ›› ማንኛውንም የውጊያና የጥፋት መሣሪያዎች ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እዚህ ውጊያ አያደርግም››

በዐፈር ቁልል አይከባትም
‹‹ከተማዋን ለመያዝ እንዲያመቻቸው ዙሪያዋን የዐፈር ቁልል አያደርጉም››

ይላል ያህዌ
እርሱ የተናገረው እውነት መሆኑን ለማሳየት ያህዌ ስሙን ጠርቶ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ እንዲህ ይላል›› ወይም፣ ‹‹እኔ ያህዌ ይህን ብያለሁ››

ስለ ራሴና ስለ ባርያዬም ስለ ዳዊት
‹‹ስለ ራሴ ክብርና በሚገባ እኔን ላገለገለው ንጉሥ ዳዊት ስለ ገባሁት ቃል››

2 Kings 19:35

እንዲህ ሆነ
‹‹ተደረገ››

185,000 ወታደሮች
‹‹አንድ መቶ ሰማንያ አምስት ሺህ ወታደሮች››

ሰዎቹ ሲነቁ
‹‹በሕይወት የተረፉ ሲነሡ››

አድራሜሌክ... ሰርሳር... አስራዶን
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 20

1 በዚያን ዘመን ንጉሥ ሕዝቅያስ በጠና ታሞ ለሞት ተቃርቦ ነበር። የአሞጽ ልጅ ነቢዩ ኢሳይያስ ሊጎበኘው ሄዶ፦ «እግዚአብሔር ‹ከሕመምህ አትድንም፤ መሞትህም ስለማይቀር ሁሉን ነገር አስተካክል› ብሎሃል» ሲል ነገረው። **2** ሕዝቅያስም ፊቱን ወደ ግድግዳው መልሶ፣ ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ጸለየ፦ **3** «እግዚአብሔር ሆይ! በታማኝነትና በቅንነት እንዳገለገልኩህ፣ አንተ የምትደሰትበትንም ነገር ለማድረግ ዘወትር እጥር እንደነበር ታስብ ዘንድ እለምንሃለሁ!» እያለ በመጸለይ ምርር ብሎ አለቀሰ። **4** ኢሳይያስ ከንጉሡ ፊት ወጥቶ የቤተ መንግሥቱን መካከለኛ አደባባይ አልፎ ከመሄዱ በፊት፣ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል መጣለት፦ **5** «ሕዝቤን ወደሚመራው ወደ ንጉሥ ሕዝቅያስ ተመልሰህ በመግባት እንዲህ በለው፦ ‹እኔ የቀድሞ አባትህ የዳዊት አምላክ እግዚአብሔር ጸሎትህን ሰምቻለሁ፤ እንባህንም ተመልክቻለሁ፤ እኔ እፈውስሃለሁ፤ ከሦስት ቀንም በኋላ ወደ ቤተ መቅደስ ትወጣለህ። **6** በዕድሜህም ላይ ዐሥራ አምስት ዓመት እጨምርልሃለሁ፤ አንተንና ይህችን የኢየሩሳሌምን ከተማ ከአሦር ንጉሥ እጅ በመታደግ አድናለሁ። ስለ ክብሬና ለአገልጋዬ ለዳዊት ስለ ሰጠሁት የተስፋ ቃል ከተማይቱን በመከላከል እጠብቃታለሁ።’” **7** ስለዚህ ኢሳይያስ የንጉሡን አገልጋዮች «የበለስ ፍሬ ጥፍጥፍ አምጡልኝ» ብሎ አመጡለት፤ በቁስሉ ላይ ባደረጉለት ጊዜ የሕዝቅያስ ቁስል ተፈወሰ። **8** ንጉሥ ሕዝቅያስም ኢሳይያስን «እግዚአብሔር እንደሚፈውሰኝና ከሦስት ቀን በኋላ ወደ ቤተ መቅደስ መሄድ እንደምችል በምን ምልክት ዐውቃለሁ?» ሲል ጠየቀው። **9** ኢሳይያስም «እግዚአብሔር የሰጠውን የተስፋ ቃል የሚፈጽም ስለ መሆኑ ራሱ ምልክት ይሰጥሃል፤ እንግዲህ አሁን የምትመርጠው ጥላው ዐሥር ደረጃ ወደ ፊት እንዲሄድ ነው? ወይስ ዐሥር ደረጃ ወደ ኋላ እንዲመለስ?» ሲል ጠየቀው። **10** ሕዝቅያስም «ጥላው ዐሥር ደረጃ ወደ ፊት እንዲሄድ ማድረግ ይቀላል፤ ስለዚህ ዐሥር ደረጃ ወደ ኋላ እንዲመለስ አድርግልኝ» አለው። **11** ኢሳይያስም ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤ እግዚአብሔርም ንጉሥ አካዝ ባሠራው ደረጃ ላይ ያረፈው ጥላ ዐሥር ደረጃ ላይ ያረፈው ጥላ ዐሥር ደረጃ ወደ ኋላ እንዲመለስ አደረገ። **12** በዚያኑ ጊዜ የባቢሎን ንጉሥ የባላዳን ልጅ መሮዳክ ባላዳን፣ ንጉሥ ሕዝቅያስ መታመሙን ሰምቶ ከገጸ በረከት ጋር ደብዳቤ ላከለት። **13** ሕዝቅያስ መልእክተኞቹን በደስታ ተቀበላቸው፤ በቤተ መንግሥቱም የዕቃ ግምጃ ቤት ያለውን ሀብት በሙሉ፣ ብሩንና ወርቁን፣ ቅመማ ቅመሙንና ሽቶውን፣ የጦር መሣሪያውንም ሁሉ አሳያቸው፤ በቤተ መንግሥቱ ግምጃ ቤትም ሆነ በመንግሥቱ በማንኛውም ስፍራ ካለው ሀብት ሁሉ ያላሳያቸው አንድም አልነበረም። **14** በዚያን ጊዜ ነቢዩ ኢሳይያስ ወደ ንጉሥ ሕዝቅያስ ሄዶ፣ «እነዚህ ሰዎች ከወዴት መጡ? ምንስ ነገሩህ?» ብሎ ጠየቀው። ሕዝቅያስም «እነርሱ የመጡት ባቢሎን ከሚባል ከሩቅ አገር ነው» ሲል መለሰለት። **15** ኢሳይያስም «በቤተ መንግሥቱ ምን አዩ» ሲል ጠየቀው። ሕዝቅያስም «ሁሉን ነገር አይተዋል፤ በግምጃ ቤቱ ካለው ሀብት ሁሉ ለእነርሱ ያላሳየኋቸው አንድም ነገር የለም» አለ። **16** ኢሳይያስም ንጉሡን እንዲህ አለው፦ «ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ **17** ‹የቀድሞ አባቶችህ እስከዚህች ቀን ድረስ ያከማቹት፣ በቤተ መንግሥትህ ያለው ሀብት ሁሉ ተጠራርጎ ወደ ባቢሎን የሚወሰድበት ጊዜ ይመጣል፤ ምንም ነገር አይቀርም። **18** ከዘሮችህም አንዳንዶቹ ወደ ባቢሎን ተማርከው በመሄድ በባቢሎን ቤተ መንግሥት ጃንደረቦች ሆነው እንዲያገለግሉ ይደረጋል።›» **19** ንጉሥ ሕዝቅያስም በተለይ በእርሱ ዘመን በሰላም የመኖር ዋስትና እንዳለው ስለ ተረዳ «ከእግዚአብሔር ተልከህ የተናገርከኝ ቃል መልካም ነው» ሲል መለሰ። **20** ንጉሥ ሕዝቅያስ ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ የጀግንነት ሥራው ጭምር፣ እንዲሁም የውሃ ማጠራቀሚያ ገንዳ እንዴት እንደ ሠራና ወደ ከተማይቱ ውሃ ለማምጣት ያስቆፈረው የመሬት ውስጥ ቦይ አሠራር ሁሉ በይሁዳ ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኛል። **21** ሕዝቅያስም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ በእርሱም ፈንታ ተተክቶ ልጁ ምናሴ ነገሠ።

---

2 Kings 20:1

ቤትህን አስተካክል
‹‹ቤት›› በንጉሥ ሕዝቅያስ ሥር ያለውን ነገር ሁሉ ይመለከታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ለቤተ ሰብህና ለመንግሥትህ የመጨረሻ መመሪያ ስጥ››

አስብ
ይህ ያህዌን አስታውስ ለማለት የተለመደ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አስታውስ››

ሄድሁ
ይህ፣ ‹‹ሕይወቴን እንደ ኖርህ›› ለማለት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው።

በዐይንህ ፊት መልካም የሆነውን
እዚህ ላይ ዐይን ፍርድንና ግንዛቤን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በፍርድህ መሠረት››

2 Kings 20:4

የያህዌ ቃል መጣ
‹‹ቃል›› ያህዌ ለኢሳይያስ የገለጠውን መልእክት ይወክላል። ይህ የተለመደ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ ቃል ተናገረ››

ጸሎትህን ሰምቻለሁ፤ እንባህንም አይቻለሁ
ተጓዳኝ አስተሳሰብን በመጠቀም አንድ መልእክት ለማቅረብ ሁለተኛው የመጀመሪያውን ያጠናክራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጸሎትህን ሰማሁ፤ እንባህንም አየሁ››

በሦስተኛው ቀን
‹‹ከአሁን ጀምሮ ሁለት ቀን›› ኢሳይያስ ይህን የተናገረበት ቀን የመጀመሪያ ቀን ነው፤ ስለዚህም፣ ‹‹ሦስተኛው ቀን›› - ‹‹ከአሁን ጀምሮ ሁለት ቀን›› እንደ ማለት ነው።

2 Kings 20:6

አጠቃላይ መረጃ
በነቢዩ ኢሳይያስ በኩል ለንጉሥ ሕዝቅያስ መልእክት ከያህዌ እየመጣ ነው።

ዐሥራ አምስት ዓመት
15 ዓመት

ከአሦር ንጉሥ እጅ
‹‹እጅ›› ኀይል፣ ሥልጣንና መቆጣጠር ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከአሦር ንጉሥ ቁጥጥር››

ትኩስ የበለስ ጥፍጥፍ
‹‹የሞቀ ወይን ጥፍጥፍ መለጠፍ››

እነርሱም አዘጋጅተው ዕባጩ ላይ አደረጉለት
‹‹የሕዝቅያስ አገልጋዮች ይህን አደረጉ፤ ሕዝቅያስ ቁስል ላይ አኖሩ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Kings 20:8

ዐሥር ደረጃ ወደ ፊት ይቅደም ወይስ ዐሥር ደረጃ ወደ ኋላ ይመለስ?
‹‹ጥላው›› የተገኘው እንዴት እንደ ነበር ይበልጥ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ የፀሐይ ብርሃን ደረጃው ላይ የሚፈጥረውን ብርሃን ያህዌ ዐሥር ርምጃ ወይም ዐሥር ርምጃ ወደ ኋላ እንዲያደርገው ትፈልጋለህን?››

ዐሥር ደረጃ
ይህ አገላለጽ የሚያመለክተው 2 ነገሥት 20፥11 ላይ የተጠቀሰውን፣ ‹‹የአካዝን ደረጃዎች›› ነው። ምናልባትም ይህ ደረጃ የፀሐይ ጨረር ወደ ፊት ሲሄድ ቀኑ ምን ያህል እንደ ሆነ እንዲቆጥርበት ለንጉሥ አካዝ የተሠራ የተለየ ደረጃ ሊሆን ይችላል። በዚህ ሁኔታ ቀን ሲሆን ጊዜውን ለማወቅ ያገለግላል።

2 Kings 20:10

ጥላው ዐሥር ደረጃ ወደ ፊት መሄዱ ቀላል ነው
ለምን ቀላል እንደ ሆነ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። ‹‹ይህ ተፈጥሮአዊ ሂደት ስለ ሆነ ጥላው ዐሥር ደረጃ ወደ ፊት እንዲሄድ ማድረግ ቀላል ነው››

የአካዝ ደረጃ
ይህ የቀኑን ጊዜ እንዲያውቅበት ለንጉሥ አካዝ የተሠራ የተለየ ደረጃ ሊሆን ይችላል። ደረጃዎቹ ጊዜ የሚቆጥሩት በቀኑ ጊዜ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለንጉሥ አካዝ የተሠራ ደረጃ››

2 Kings 20:12

መርዱክ — ባልዳን... ባልዳን
እነዚህ የባቢሎን ንጉሥና ወንድ ልጆቹ ስሞች ናቸው።

ደብዳቤውን ሰማ
‹‹ደብዳቤዎቹን በጥንቃቄ አሰበባቸው›› ወይም 2) ‹‹የባቢሎንን ንጉሥ ደብዳቤ ሰማ››

በቤቱ መንግሥቱም ሆነ በመላው ግዛቱ ሕዝቅያስ ሳያሳያቸው የቀረ ምንም ነገር አልነበረም
‹‹ያላሳያቸው... ምንም አልቀረም›› አጽንዖት ለመስጠት ጥቅም ላይ የዋለ ግነት ነው። ሕዝቅያስ ማንኛውንም ጠቃሚ ነገር አሳያቸው ማለት ነው። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕዝቅያስ በቤቱም ሆነ በመንግሥቱ ያለውን ማንኛውንም ጠቃሚ ነገር አሳየው››

2 Kings 20:14

እነዚህ ሰዎች
ይህ የሚያመለክተው ከመርዱክ — ባልዳን መልእክትና ስጦታ ያመጡትን ሰዎች ነው።

በቤቴ ያለውን ሁሉ ዐይተዋል፤ ጠቃሚ ከሆኑት ነገሮቼ ያላሳየኃቸው ምንም የለም
ይህን ነጥብ አጽንዖት ለመስጠት ሕዝቅያስ አንዱን ሐሳብ ሁለት ጊዜ ደጋግሞአል።

ጠቃሚ ከሆኑት ነገሮቼ ያላሳየኃቸው ምንም የለም
‹‹ምንም›› እና ‹‹የለም›› ሐሳቡን አዎንታዊ ለማድረግ አንደኛው ሌላውን ይሸረዋል። ግነቱ ጥቅም ላይ የዋለው ለአጽንዖት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጠቃሚ ነገሮቼን ሁሉ አሳየኃቸው››

2 Kings 20:16

ከዚያም ኢሳይያስ ሕዝቅያስን እንዲህ አለው
ኢሳይያስ ለምን እንደ ተናገረ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለሰዎቹ ማንኛውንም ጠቃሚ ነገሮቹን በማሳየት ሕዝቅያስ ሞኝነት ማድረጉን አሳይያስ ስላወቀ እንዲህ አለው››

የያህዌ ቃል
‹‹የያህዌ መልእክት››

እነሆ... ጊዜ በእርግጥ ይመጣል
‹‹ስማ፣ አንድ ቀን ጊዜ ይመጣል››፤ ‹‹እነሆ›› ጥቅም ላይ የዋለው ኢሳይያስ ለሕዝቅያስ ለሚናገረው ትኩረት ለመሳብ ነው።

ጊዜ
‹‹ጊዜ›› ያልተወሰነ ጊዜን ያመለክታል።

2 Kings 20:19

አስቦአልና
‹‹ሕዝቅያስ ስላሰበ››

እኔ እስካለሁ ድረስ ሰላምና ጸጥታ ከተገኘ የሆነው ቢሆን ምን ቸገረኝ?
መልሱን ቢያውቅ እንኳ ሕዝቅያስ ይህን የጠየቀው ለአጽንዖት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በዘመኔ ሰላምና ጸጥታ እንደሚኖር እርግጠኛ መሆን እችላለሁ››

ኩሬ
ውሃ የተጠራቀመበት ትንሽ ቦታ

ቦይ
ውሃ የሚተላለፍበት መስመር

በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?
ጥያቄው የቀረበው እነዚህ ነገሮች ተጽፈው እንደሚገኙ ለአንባቢው ለማሳሳብ ነው። 2 ነገሥት 8፥23 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ መጽሐፍ ተጽፎአል››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 21

1 ምናሴ በይሁዳ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ዐሥራ ሁለት ዓመት ነበር፤ እርሱም በኢየሩሳሌም ኀምሳ አምስት ዓመት ገዛ። እናቱም ሐፍሴባ ተብላ ትጠራ ነበረ። 2 እስራኤላውያን ወደ ተስፋይቱ አገር በሚገቡበት ጊዜ እግዚአብሔር ከፊታቸው ነቃቅሎ ያጠፋቸውን የአሕዛብን አሳፋሪ ልማድ በመከተል ምናሴ የሠራው ኃጢአት እግዚአብሔርን አሳዘነ። 3 ምናሴ አባቱ ሕዝቅያስ አጥፍቶአቸው የነበሩትን የአሕዛብ መስገጃ ስፍራዎች እንደገና እንዲሠሩ አደረገ። የእስራኤል ንጉሥ አክዓብ ባደረገውም ዐይነት ባዓል ተብሎ ለሚጠራው ባዕድ አምላክ መሠዊያዎችን፣ አሼራ ተብላ የምትጠራውን ሴት አምላክ ምስልን ሠራ፤ የሰማይ ከዋክብትንም አመለከ። 4 እግዚአብሔር እንዲመለክበት ባዘዘው ስፍራ ማለትም በቤተ መቅደስ ውስጥ አረማዊ መሠዊያዎችን አቆመ። 5 በሁለቱም የቤተ መቅደሱ አደባባዮች የሰማይ ከዋክብት የሚመለኩባቸውን መሠዊያዎች ሠራ። 6 የገዛ ልጁንም መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ፤ እርሱም ራሱ ሟርተኛና አስማተኛ ሆኖ ከጠንቋዮችና ከሙታን ጠሪዎች ምክርን ይጠይቅ ነበር፤ በዚህም ሁሉ አድራጎቱ ታላቅ ኃጢአት በመሥራቱ የእግዚአብሔርን ቁጣ አነሣሣ። 7 በቤተ መቅደሱም ውስጥ የአሼራን ምስል አኖረ፤ ይህም ቤተ መቅደስ እግዚአብሔር ለዳዊትና ለልጁ ለሰሎሞን «ይህ በኢየሩሳሌም የሚገኘው ቤተ መቅደስ እኔ ለዘለዓለም እንድመለክበት ከዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች ግዛት ሁሉ የመረጥኩት ስፍራ ነው። 8 የእስራኤል ሕዝብ ትእዛዞቼን ቢጠብቁና ለአገልጋዬ ለሙሴ የሰጠሁትንም ሕግ ቢፈጽሙ፣ ለቀድሞ አባቶቻቸው ከሰጠኋቸው ከዚህች ምድር ተነቃቅለው እንዲጠፉ አላደርግም» ሲል ነግሮአቸው የነበረው ነው። 9 የይሁዳ ሰዎች ግን ለእግዚአብሔር ቃል ታዛዦች ሆነው አልተገኙም፤ ይልቁንም ምናሴ እስራኤላውያን ወደፊት እየገፉ ሲመጡ እግዚአብሔር ከፊታቸው ነቃቅሎ ያጠፋላቸው ሕዝቦች ይፈጽሙት ከነበረው ይበልጥ ወደ ክፉ ኃጢአት መራቸው። 10 ስለዚህ እግዚአብሔር በአገልጋዮቹ በነቢያት አማካይነት እንዲህ ሲል ተናገረ፦ 11 «የይሁዳ ንጉሥ ምናሴ ይህን ሁሉ አሳፋሪ ነገር አደረገ፤ ይኸውም ቀድሞ ከነዓናውያን ይፈጽሙት ከነበረው ሁሉ የከፋ ነው፤ በሠራቸውም ጣዖቶች የይሁዳን ሕዝብ ወደ ኃጢአት መራ። 12 ስለዚህ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ላይ የመጣው በጣም ከባድ መቅሰፍት ይህ ነው፤ ስለ እርሱም የሚሰማ ሰው ሁሉ በድንጋጤ ጆሮው ጭው ይላል። 13 ሰማርያንና የእስራኤልን ንጉሥ አክዓብን ከነዘሮቹ እንደ ቀጣሁ ኢየሩሳሌምንም እቀጣለሁ፤ ሳሕን ከተወለወለ በኋላ ተደፍቶ እንደሚቀመጥ፣ እኔም ኢየሩሳሌምን ከኃጢአት አጸዳታለሁ። 14 ከጥፋት የተረፈውን ሕዝቤን ለጠላቶቹ ተላልፎ እንዲሰጥ እተወዋለሁ፤ እርሱም ይማረካል፤ ንብረቱም ይዘረፋል። 15 በእነርሱም ላይ ይህን ሁሉ የማደርግበት ምክንያት የቀድሞ አባቶቻቸው ከግብጽ ከወጡበት ጊዜ አንሥቶ እስከ አሁን ድረስ ኃጢአት ሠርተው እኔን በማሳዘናቸውና ቁጣዬን በማነሣሣታቸው ነው።» 16 ከዚህም በተጨማሪ ምናሴ የይሁዳን ሕዝብ ወደ ጣዖት አምልኮና እግዚአብሔርን ወደሚያሳዝን ኃጢአት ከመምራት አልፎ፣ ንጹሓን የሆኑትን ብዙ ሰዎችን በመፍጀት የኢየሩሳሌምን መንገዶች በደም እንዲጥለቀለቁ አድርጎአል። 17 ምናሴ ያደረገው ሌላው ነገርና የፈጸመው ኃጢአት ሁሉ በይሁዳ ነገሥታት የታሪክ መጽሓፍ ተመዝቦ ይገኛል። 18 ምናሴም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ በቤተ መንግሥቱ ግቢ «የዖዛ አትክልት ስፍራ» ተብሎ በሚጠራው ቦታ ተቀበረ። በእርሱም ፈንታ ተተክቶ ልጁ አሞን ነገሠ። 19 አሞን በይሁዳ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ሃያ ሁለት ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ሁለት ዓመት ገዛ። እናቱም ሜሶላም ተብላ የምትጠራ የዮጥባ ከተማ ተወላጅ የሐሩስ ልጅ ነበረች። 20 አሞን እንደ አባቱ እንደ ምናሴ ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሠራ። 21 የአባቱንም መጥፎ አርአያነት ሁሉ ተከተለ፤ አባቱ ይሰግድላቸውና ያመልካቸው የነበሩትንም ጣዖቶች ሁሉ አመለከ። 22 የቀድሞ አባቶቹን አምላክ እግዚአብሔርንም ተወ፤ እግዚአብሔርንም አልተከተለም። 23 አገልጋዮቹ ባለሥልጣኖችም በአሞን ላይ አድመው በራሱ ቤት ውስጥ ገደሉት። 24 የይሁዳም ሕዝብ የአሞንን ገዳዮች ደምስሰው ልጁን ኢዮስያስን አነገሡ። 25 አሞን ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ በይሁዳ ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኛል። 26 አሞን «የዖዛ አትክልት ስፍራ» ተብሎ በሚጠራው መካነ መቃብር ተቀበረ። በእርሱም ፈንታ ተተክቶ ልጁ ኢዮስያስ ነገሠ።

---

2 Kings 21:1

ሐፍሴባ
የንጉሥ ምናሴ እናት።

የያህዌ ዐይን ፊት ክፉ ነገር
የያህዌ ዐይን የያህዌን ፍርድና ግንዛቤ ይወክላል። 2 ነገሥት 3፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በያህዌ ፍርድ ክፉ የሆነ ነገር›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ክፉ የሚለውን ነገር››

አስጸያፊ ልማድ
የኮረብታውን ማምለኪያ ስፍራ ሠራ... ለበአል መሠዊያዎችን አቆመ፤ የአሼራንም ምስል ዐምድ ሠራ

የኮረብታውን ማምለኪያ ስፍራ ሠራ... ለበአል መሠዊያዎችን አቆመ፤ የአሼራንም ምስል ዐምድ ሠራ
ይህን እንዲሠሩለት ምናሴ አገልጋዮቹን ማዘዝ ይችላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የኮረብታው ማምለኪያ እንዲሠራ አደረገ.. የበአልን መሠዊያዎች አስገነባ፤ የአሼራን ዐምድ አሠራ›› ወይም፣ ‹‹ሠራተኞቹ የኮረብታውን ማምለኪያ እንዲሠሩለት አደረገ፤ ...የበአልንም መሠዊያዎች አሠራቸው፤ የአሼራን ዐምድ አሠራ››

2 Kings 21:4

አጠቃላይ መረጃ
የንጉሥ ምናሴ አገዛዝ ታሪክ ቀጥሏል።

ስሜን በኢየሩሳሌም ለዘላለም አኖራለሁ
ስም የሰው መጠሪያ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ኢየሩሳሌም የእኔ ማንነት ለዘላለም በሚታወቅበት ቦታ ትሆናለች››

በሁለቱም በያህዌ ቤት አደባባዮች ለሰማይ ከዋክብት ሰራዊት ሁሉ መሠዊያዎች ሠራ
እነዚህን መሠዊያዎች ያሠራው ሕዝቡ መሥዋዕት እንዲያቀርቡባቸውና እንዲያመልኩባቸው መሆኑ ግልጽ ነው። እነዚህን መሠዊያዎች ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዘዘ እንጂ፣ እርሱ ራሱ አልሠራቸውም። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሕዝቡ ከዋክብትን እንዲያመልክና መሥዋዕት እንዲያቀርብላቸው በሁለቱ የያህዌ ቤት አደባባዮች መሠዊያዎች ሠራ››

ልጁን በእሳት ውስጥ አሳለፈ
ልጁን ለምን በእሳት ውስጥ እንዳሳለፈና ከዚያ በኋላ ምን እንደ ሆነ ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለአማልክት መሥዋዕት እንዲሆን እስኪሞት ድረስ ልጁን በእሳት አቃጠለ››

ምክር ጠየቀ
‹‹መረጃ ጠየቀ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በያህዌ ዐይን ፊት ብዙ ክፉ ነገር አደረገ
የያህዌ ዐይን የያህዌን ፍርድና ግንዛቤ ይወክላል። 2 ነገሥት 3፥2 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በያህዌ ፍርድ ብዙ ክፉ ነገሮች›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ክፉ የሚላቸውን ብዙ ነገሮች››

2 Kings 21:7

አጠቃላይ መረጃ
የንጉሥ ምናሴ አገዛዝ ታሪክ ቀጥሏል።

እርሱ ያደረገው
ምናሴ ራሱ ያንን አላደረገም። ያንን ያደረጉ አገልጋዮቹ ናቸው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ምናሴ አገልጋዮቹ ያንን እንዲያደርጉ አዘዘ

ስሜን ለዘላለም አኖራለሁ
ያህዌ ስሙን ቤተ መቅደሱ ላይ ማኖሩ፣ የአምልኮ ቦታ መሆኑን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሰዎች ለዘላለም እንዲያመልኩኝ የምፈልገው ቦታ››

የእስራኤል እግሮች
እግሮች ሰውየውን ይወክላሉ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የእስራኤል ሕዝብ›› ወይም፣ ‹‹እስራኤላውያን››

ያህዌ በእስራኤላውያን ፊት ካጠፋቸው አሕዛብ ይልቅ
እዚህ ላይ፣ ‹‹አሕዛብ›› እስራኤላውያን ከመምጣታቸው በፊት በከነዓን ምድር ይኖሩ የነበሩትን ሕዝቦች ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እስራኤላውያን ወደ ምድሪቱ እየገሠገሡ እያለ ያህዌ ካጠፋቸው ሕዝቦች ይልቅ››

2 Kings 21:10

በጣዖታቱ፣ ስለዚህ የእስራኤል አምላክ ያህዌ እንዲህ አለ፤ እነሆ
ይህ ማለት 1) ያህዌ በሦስተኛ ሰው ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በመጀመሪያ ሰው ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በጣዖታቱ፣ ስለዚህ የእስራኤል አምላክ እኔ ያህዌ ይህን እላለሁ፤ እነሆ›› ወይም 2) ነቢዩ ያህዌ የተናገረውን እያቀረበ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በጣዖታቱ፤ ስለዚህ የእስራኤል አምላክ ያህዌ ይህን ይላል፤ እነሆ››

ለሚሰማ ሁሉ ጆሮዎቹ ጭው እንዲሉ ለሚያደርግ
አካላዊ ስሜቱ ምክንያት የሆነውን ስሜታዊ ሁኔታ ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ የሚያደርገውን የሚሰሙ ይደነግጣሉ››

2 Kings 21:13

በሰማርያ ላይ ያዘጋጀሁትን መለኪያ ገመድ፣ የአክዓብንም ቤት የለካሁበትን ቱንቢ፣ በኢየሩሳሌም ላይ እዘረጋለሁ
‹‹መለኪያ ገመድ›› እና፣ ‹‹ቱንቢ›› ሕዝብ ላይ ለመፍረድ ያህዌ የሚጠቀምበት መስፈርት ተለዋጭ ዘይቤ ናቸው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ኢየሩሳሌም ላይ የምፈርደው ሰማርያና የአክዓብ ቤት ላይ በተጠቀምሁበት መስፈርት መሠረት ነው››

ሰማርያ ላይ
ሰማርያ ዋና ከተማ ስትሆን፣ የእስራኤልን መንግሥት ሕዝብ ሁሉ ትወክላለች። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በእስራኤል ሕዝብ ላይ››

ቱንቢ
ግንቡ ትክክል መሆን አለመሆኑን የሚያሳይ በቀጭን ሲባጐ የተያዘ ክብደት ያለው ነገር።

የአክዓብ ቤት
‹‹ቤት›› ቤተ ሰብን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የአክዓብ ቤተ ሰብ››

እጥላለሁ
‹‹እተዋለሁ›› ወይም፣ ‹‹እንቃለሁ››

ለጠላቶቻቸው እጅ እሰጣቸዋለሁ
እዚህ ላይ የጠላቶች፣ ‹‹እጅ›› በእነርሱ ቁጥጥር ሥር መሆንን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጠላቶቻቸው ድል እንዲያደርጓቸው፣ ምድራቸውን እንዲወስዱ››

2 Kings 21:16

በተጨማሪም ምናሴ
‹‹እንዲሁም ምናሴ›› ወይም፣ ‹‹ከዚህም ሌላ ምናሴ››

ምናሴ ብዙ ንጹሕ ደም አፈሰሰ
‹‹ብዙ ንጹሕ ደም›› በግፍ ሰዎችን መግደል ማለት ነው። አንባቢው ይህን መረዳት እንዲችል ምናሴ ይህን እንዲያደርግ የረዱት ሌሎች ሰዎች መሆናቸውን መተርጐም የተሻለ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ምናሴ ወታደሮቹን ብዙ ንጹሐን ሰዎች እንዲገድሉ አዘዘ።››

ኢየሩሳሌምን ከዳር እስከ ዳር በሞት ሞላ
ግነቱ የሚያመለክተው በመላው ኢየሩሳሌም ምናሴ የገደላቸውን ሰዎች ብዛት ነው። ‹‹ሞት›› የሚለው ‹‹በሞቱ ሰዎች›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በኢየሩሳሌም ብዙ ሰዎች ሞተው ነበር››

በያህዌ ዐይን ፊት ክፉ የሆነ ነገር
የያህዌ ዐይን የያህዌን ፍርድና ግንዛቤ ይወክላል። 2 ነገሥት 3፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በያህዌ ፍርድ ክፉ የሆነ ነገር›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ክፉ የሚለውን ነገር››

በይሁዳ... ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?
የጥያቄው መልስ አዎንታዊ መሆኑን መረዳት ይቻላል፤ ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። ጥያቄው የቀረበው አጽንዖት ለመስጠት ነው። 2 ነገሥት 8፥23 ላይ ይህን ሐረግ እንዴ እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በይሁዳ... ተጽፎአል›› ወይም፣ ‹‹በይሁዳ... ይገኛል››

ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ
በሌላ መልኩ ይህ፣ ‹‹እንደ አባቶቹ ሞተ›› ማለት ነው።

የዖዛ አትክልት ቦታ
ይህም ማለት 1) ‹‹በአንድ ወቅት ዖዛ የሚባል ሰው የነበረ አትክልት ቦታ›› ወይም፣ 2) ‹‹ዖዛ አትክልት››

አሞን
ይህ የሰው ስም ነው።

2 Kings 21:19

አሞን... ሐሩስ
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው።

ሜሱላም
ይህ የሴት ስም ነው።

ዮጥባ
ይህ የከተማ ስም ነው

በያህዌ ዐይን ፊት ክፉ ነገር
የያህዌ ዐይን የያህዌን ፍርድና ግንዛቤ ይወክላል። 3፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በያህዌ ፍርድ ክፉ የሆነ ነገር›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ክፉ የሚለውን ነገር››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Kings 21:21

አባቱ የሄደበትን መንገድ ሁሉ ተከተለ
‹‹አባቱ በተመላለሰበት መንገድ ተመላለሰ›› አንድ ሰው የሚኖርበት መንገድ የሚመላለስበት መንገድ እንደ ሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አባቱ በኖረበት ፈጽሞ ኖረ››

ያህዌን ተወ
‹‹ከያህዌ ራቀ›› ወይም፣ ‹‹ለያህዌ ደንታ አልነበረውም››

በእርሱ ላይ አሤሩ
‹‹እርሱ ላይ ጉዳት ለማድረስ ተማክረው ሠሩ››

2 Kings 21:24

የአገሩ ሕዝብ
ይህ አጠቃላይ ንግግር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በይሁዳ ያሉ አንዳንድ ሰዎች››

አሤሩበት
‹‹እርሱን ለመጉዳት ዐቀዱ፤ እንደዚያም አደረጉ›› 2 ነገሥት 21፥23 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

በይሁዳ... ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?
መልሱ አዎንታዊ እንደሚሆን ግምት ውስጥ በማስገባት፣ ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። ጥያቄው የቀረበው አጽንዖት ለመስጠት ነው። 2 ነገሥት 8፥23 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በይሁዳ... ተጽፈዋል›› ወይም፣ ‹‹በይሁዳ... ማግኘት ይቻላል››

ዖዛ አትክልት ቦታ
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹በአንድ ወቅት ዖዛ የሚባል ሰው የነበረ አትክልት ቦታ›› ወይም 2) ‹‹የዖዛ አትክልት ቦታ›› 2 ነገሥት 21፥18 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 22

1 ኢዮስያስ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ገና ስምንት ዓመት ነበር። በኢየሩሳሌም ሠላሳ አንድ ዓመት ገዛ። እናቱም ይዲዳ ተብላ የምትጠራ የባሱሮት ከተማ ተወላጅ
የሆነው የአዳያ ልጅ ነበረች። 2 ኢዮስያስ የቀድሞ አባቱን የዳዊትን መልካም ምሳሌነት በመከተል በእግዚአብሔር ፊት መልካም ነገር አደረገ። ወደ ግራም ቀኝም
አላለም። 3 ኢዮስያስ በነገሠ በዐሥራ ስምንተኛው ዓመት የሜሶላም የልጅ ልጅ፣ የኤዜልያስ ልጅ የሆነውን የቤተ መንግሥቱን ጸሓፊ ሳፋንን እግዚአብሔር
እንዲህ ይላል በማለት መልእክት ወደ ቤተ መቅደስ ላከው። 4 «ኬልቂያስ ተብሎ ወደሚጠራው ወደ ሊቀ ካህናቱ ሄደህ፣ ወደ ቤተ መቅደስ በሚያስገባው በር
አጠገብ በየተራ ከሕዝቡ ገንዘብ የመሰብሰብ ኃላፊነት የተሰጣቸው ካህናት እስከ አሁን ምን ያህል ገንዘብ ከሕዝቡ እንደሰበሰቡ የሚገልጥ የሒሳብ ማስረጃ
ይዘህ እንድትመጣ አለው። 5 የመቅደሱን እድሳት ለመቆጣጠር ለተሾሙት ሰዎች ያስረክቡ፤ እነርሱም የተረከቡትን ገንዘብ ቤተ መቅደሱን ለሚጠግኑ፣
ለአናጢዎች፣ ለግንበኞችና ለድንጋይ ጠራቢዎች ይክፈሉ። 6 እንዲሁም ለቤተ መቅደሱ እድሳት ሳንቃዎችንና የተጠረቡ ድንጋዮችን ይግዙ። 7 ነገር ግን የሥራው
ኃላፊዎች ፍጹም ታማኞች ስለ ሆኑ እነርሱን ስለ ገንዘቡ አወጣጥ መቆጣጠር አያስፈልግም።» 8 ጸሐፊው ሳፋን ከንጉሡ የተላከውን ትእዛዝ ለኬልቂያስ
ሰጠው፤ ኬልቂያስም «የሕጉን መጽሐፍ በቤተ መቅደሱ ውስጥ አገኘሁ» ብሎ ለሳፋን ሰጠው፤ ሳፋንም ተቀብሎ አነበበው። 9 ጸሐፊውም ሄደና «አገልጋዮችህ
በቤተ መቅደሱ ውስጥ የነበረውን ገንዘብ ተቀብለው ለእድሳቱ ሥራ ኃላፊዎች ለሆኑት ሰዎች አስረክበዋል» ሲል አስረዳ። 10 ከዚያም ጸሐፊው ሳፋን ለንጉሡ
«ካህኑ ኬልቂያስ አግኝቶ የሰጠኝ መጽሐፍ» ነው አለው። 11 ንጉሡም፣ የሕጉ መጽሐፍ ሲነበብ በሰማ ጊዜ በሐዘን ልብሱን ቀደደ። 12 እርሱም ለካህኑ
ለኬልቂያስ፣ የሳፋን ልጅ ለሆነው ለአኪቃም፣ የሚክያስ ልጅ ለሆነው ለዓክቦር፣ የቤተ መንግሥቱ ጸሐፊ ለሆነው ለሳፋንና የንጉሡ የቅርብ አገልጋይ ለሆነው
ለዓሳያ የሚከተለውን ትእዛዝ ሰጠ። 13 «እንግዲህ ሂዱና እኔና የይሁዳ ነዋሪ ሕዝብ በዚህ በተገኘው መጽሐፍ ስላለው ትምህርት ማወቅ እንችል ዘንድ
እግዚአብሔርን ጠይቁ፤ የቀድሞ አባቶቻችን በዚህ መጽሐፍ የተጻፈውን መመሪያ ስላልተከተሉ እግዚአብሔር በእኛ ላይ በጣም ተቆጥቶአል።» 14 ካህኑ
ኬልቂያስ፣ አኪቃም፣ ዓክቦር፣ ሳፋንና ዓሳያ በኢየሩሳሌም አዲስ በተሠራው ሰፈር የምትኖረውን ሕልዳና ተብላ የምትጠራውን ነቢይቱን የሴሌም ሚስት
ለመጠየቅ ሄዱ። የሐርሐስ የልጅ ልጅ የቲቅዋ ልጅ የሆነው የቤተ መቅደስ አልባሳት ኃላፊ ነበር፤ እነርሱም የሆነውን ሁሉ ለነቢይቱ አስረዱአት። 15 እርስዋም
እንዲህ አለቻቸው፣ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር የሚለው ይህ ነው፦ ወደ እኔ ለላካችሁ ሰው እንዲህ ብላችሁ ንገሩት፦ 16 «እግዚአብሔር የሚለው ይህ
ነው፤ የይሁዳ ንጉሥ ባነበበው መጽሐፍ ውስጥ በተጻፈው መሠረት በዚህች ቦታና በሕዝብዋ ላይ ክፉ ነገርን አመጣለሁ። 17 እነርሱ እኔን ትተው ለባዕዳን
አማልክት መሥዋዕት አቅርበዋል፤ በእጃቸው በሠሩአቸው ጣዖታት ሁሉ እኔን አስቆጥተውኛል፤ ቁጣዬም አይበርድም። 18 እግዚአብሔርን ለመጠየቅ ለላካችሁ
ለይሁዳ ንጉሥ እንዲህ በሉት፤ እኔ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር የምለው ይህ ነው፤ ‹አንተ በዚያ መጽሐፍ የተነገረውን ቃል ሰምተህ፦ 19 ይህችን ቦታና
ሕዝብዋን የተረገሙና ባድማ እንደማደርግ የተናገርኩትን ቃል በሰማህ ጊዜ ልብህ ተነክቶ ራስህን በማዋረድህ፣ ልብስህን በመቅደድና በፊቴም በማልቀስህ
ጸሎትህን ሰምቼአለሁ። 20 ከዚህም የተነሣ በኢየሩሳሌም ላይ የማመጣውን ቅጣት በዐይንህ ሳታየው እስከምትሞትበት ጊዜ ድረስ ተፈጸሚ አይሆንም፤
ስለዚህም አንተ በሰላም እንድትሞት አደርጋለሁ።» ሰዎቹም ይህን መልእክት ይዘው ወደ ንጉሥ ኢዮስያስ ተመለሱ።

---

2 Kings 22:1

ሠላሳ አንድ ዓመት
‹‹31 ዓመት››

ይዲዳ
ይህ የሴት ስም ነው።

አዳያ
ይህ የሰው ስም ነው።

ባሱሮት
ይህ ይሁዳ ውስጥ ያሉ ከተማ ስም ነው

በያህዌ ዐይን ፊት መልካም ነገር አደረገ
‹‹ዐይን›› የያህዌን ሐሳብ ወይም ስለ ነገሮች ያለውን ግንዛቤ ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ መልካም ነው የሚለውን አደረገ›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ እንደሚያስበው መልካም ነገር አደረገ››

አባቱ ዳዊት በሄደበት መንገድ ሁሉ ሄደ
‹‹አባቱ ዳዊት በሄደበት መንገድ ሁሉ ሄደ›› ኢዮስያስ ዳዊት እንዳደረገው ማድረጉ ዳዊት በሄደበት መንገድ መሄዱ እንደሆነ ተነግሮአል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አባቱ ዳዊት በኖረበት መንገድ ኖረ›› ወይም፣ ‹‹አባቱ የዳዊትን ምሳሌ ተከተለ››

ወደ ቀኝም ወደ ግራም አላለም
ሙሉ በሙሉ ለያህዌ መታዘዝ ለአንድ ሰው በትክክለኛው መንገድ መሄድና ከዚያም ወደ ኃላ አለማለት እንደ ሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ምንም ያህዌን ደስ የማያሰኝ ነገር አላደረገም›› ወይም፣ ‹‹ለያህዌ ሕግ ሙሉ በሙሉ ታዘዘ››

2 Kings 22:3

እንዲህም ሆነ
ቋንቋህ የታሪኩን አዲስ ክፍል ለመጀመር የሚጠቀምበት መንገድ ካለው እዚህ ላይ ተጠቀምበት።

በዐሥራ ስምንተኛውም ዓመት
ዐሥራ ስምንት በተለምዶ 18 ማለት ነው።

ሳፋን... አዜልያስ... ሜሶላም... ኬልቅያስ
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው

የያህዌ ቤት... ቤተ መቅደስ ውስጥ
‹‹የያህዌ ቤት›› እና፣ ‹‹ቤተ መቅደስ›› አንድ ናቸው።

ወደ ኬልቅያስ ውጣ
‹‹ውጣ›› የሚል ቃል የተጠቀመው የያህዌ ቤተ መቅደስ የንጉሡ ኢዮስያስ ቤት ከነበረበት ከፍ ያለ ቦታ ላይ ስለነበር ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ወደ ኬልቅያስ ሂድ››

የበር ጠባቂዎች ከሕዝቡ ሰብስበው ወደ ያህዌ ቤት ያመጡትን
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የቤተ መቅደሱ ጠባቂዎች ከሕዝቡ ሰብስበው ወደ ያህዌ ቤተ መቅደስ ያመጡት ገንዘብ››

በሠራተኞቹ እጅ ይሰጥ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› ጠቅላላ ሠራተኞቹን ይመለከታል። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ገንዘቡን ለሠራተኞቹ እንዲሰጥ ለኬልቅያስ ንገረው››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Kings 22:6

አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ኢዮስያስ ለሊቀ ካህናቱ ኬልቅስ የላከው መልእክት ይቀጥላል

ገንዘብ ይስጥ... ተሰጣቸው... ስለ ተሰጣቸው
እዚህ ላይ፣ ‹‹እነርሱ›› እና፣ ‹‹የእነርሱ›› የሚለው 2 ነገሥት 22፥5 ላይ የያህዌ ቤት ሥራ ላይ ኀላፊነት የተሰጣቸውን ሠራተኞች ያመለክታል።

አናጢዎች
በእንጨት የሚሠሩ ሰዎች

ግንበኞች
በድንጋይ የሚሠሩ ሰዎች

የተሰጣቸውን ገንዘብ መቆጣጠር አያስፈልግም
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሠራተኞቹ የቤተ መቅደሱ ሠራተኞች ስለ ሰጧቸው ገንዘብ ዝርዝር ጉዳይ ማቅረብ አያስፈልጋቸውም››

በታማኝነት ተጠቅመውበት ስለ ነበር
‹‹በአግባቡ ስለ ተጠቀሙበት››

2 Kings 22:8

ኬልቅያስ
ይህ ሰው ስም ነው። 2 ነገሥት 18፥18 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐሙት ተመልከት።

የሕጉ መጽሐፍ
ሕግ የተጻፈው በጥቅልል መጽሐፍ ሊሆን ይችላል። ጥቅልል መጽሐፍ በአንድ ረጅም ፓፒረስ ወይም ቆዳ ተጽፎ የተጠቀለለ ነው።

በሠራተኞቹ እጅ ተሰጠ
‹‹እጅ›› ጠቅላላ ሠራተኞቹን ይመለከታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ለሠራተኞቹ ተሰጣቸው››

2 Kings 22:11

እንዲህም ሆነ
በቋንቋህ የታሪኩን መጀመሪያ ክፍል ለማመልከት የምትጠቀምበት ቃል ካለ እዚህ ተጠቀምበት።

የሕጉን መጽሐፍ ቃል ሰማ
‹‹ቃል›› የሕጉን መልእክት ያመለክታል፤ አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በመጽሐፉ ተጽፎ የነበረውን ሕግ ሰማ›› ወይም፣ ‹‹በጥቅልል መጽሐፍ የተጻፈውን ሕግ ሰማ››

ልብሱን ቀደደ
ይህ በጣም ማዘንን ወይም መተከዝን የሚያመለክት ድርጊት ነው።

አኪቃም... ሰፋን... ዓክቦር... ሚክያ... ዓሳያ
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው።

ሂዱና ያህዌን ጠይቁ
የያህዌን ፈቃድ ለማወቅ ሰዎች ወደ ያህዌ ነቢዪት ሄደው እንዲጠይቁ ንጉሡ ማዘዙ እንደ ነበር 22፥14 ላይ ግልጽ ሆኗል።

ጠይቁ
ወደ ሰው ሄዶ ምክር መጠየቅ

የዚህ የተገኘው መጽሐፍ ቃል
‹‹ቃል›› — ሕግን ይወክላል። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ኬልቅያስ ባገኘው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያለ ሕግ››

በእኛ ላይ የሚነደው የያህዌ ቁጣ ታላቅ ነውና
የያህዌ ቁጣ የሚነድ እሳት እንደ ሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ በጣም ተቆጥቶናል››

እኛን በተመለከተ የተጻፈው
ይህ የሚያመለክተው ለእስራኤል የተሰጠውን ሕግ ነው። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንድናደርገው ሙሴ በሕጉ የጻፈው ሁሉ›› ወይም፣ ‹‹በሙሴ በኩል ያህዌ ለእስራኤል የሰጠው ሕግ ሁሉ››

2 Kings 22:14

ሕልዳና
ይህ የሴት ስም ነው

ሰሎም... ቲቁዌ... ሐርሐስ
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው

የአልባሳት ጠባቂው
ይህም ማለት 1) ካህናቱ ቤተ መቅደሱ ውስጥ የሚለብሷቸውን ልብሶች የሚጠብቅ፣ ወይም 2) የንጉሡን ልብሶች በአግባቡ የሚይዝ ማለት ሊሆን ይችላል።

በሁለተኛው ሰፈር በኢየሩሳሌም ኖረች
እዚህ ላይ፣ ‹‹ሁለተኛው ሰፈር›› ከኢየሩሳሌም በስተ ሰሜን የተሠራውን አዲሱ የከተማው ክፍል ማለት ነው። ‹‹ሁለተኛ›› በተለምዶ 2 ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በኢየሩሳሌም በአዲሱ ሰፈር ኖረች››

ወደ እኔ ለላካችሁ ሰው
እዚህ ላይ፣ ‹‹ሰው›› ንጉሥ ኢዮስያስን ማለት ነው።

በዚህ ቦታና በሕዝቡ ላይ ታላቅ ጥፋት አመጣለሁ
ያህዌ አስቸጋሪ ነገሮችን ማድረጉ፣ ሕዝቡ ላይ ጥፋት ማምጣት እንደ ሆነ ተነግሮአል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በዚህ ቦታና እዚህ በሚኖሩ ላይ ከባድ ችግር አመጣለሁ››

በዚህ ቦታ
‹‹በኢየሩሳሌም›› ይህ መላውን የይሁዳን ምድር የሚወክለውን የኢየሩሳሌምን ከተማ ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ይሁዳ ላይ››

2 Kings 22:17

አጠቃላይ መረጃ
በነቢዪቱ ሕልዳና በኩል ያህዌ ለንጉሥ ኢዮስያስ የላከው መልእክት ቀጥሏል።

ቁጣዬ በዚህ ቦታ ላይ ይነዳል፤ አይጠፋምም
የያህዌ ቁጣ የሚነድ እሳት እንደ ሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በዚህ ቦታ የሚመጣው ቁጣዬ እንደማይጠፋ እሳት ይሆናል››

በዚህ ቦታ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ቦታ›› በኢየሩሳሌምና በይሁዳ የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በዚህ ሕዝብ››

ስለ ሰማኸው ቃል
እዚህ ላይ፣ ‹‹ቃል›› ሕልዳና የተናገረችው መልእክት ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ስለ ሰማኸው መልእክት››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ልብህ ስለ ተነካ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ልብ›› የሰውን ውስጣዊ ሁኔታ ይወክላል። በጎጢአት ማዘን የልብ መነካት እንደ ሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጣም ስላዘንህ›› ወይም፣ ‹‹ንስሐ ስላደረግህ››

ለርግማንና ለጥፋት የተዳረጉ
‹‹ጥፋት›› እና ‹‹ርግማን›› የተሰኙትን ቃሎች በተለየ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምድሪቱን ለማጥፋት እነርሱንም ለመርገም››

ልብስህንም ቀደድህ
ይህ በጣም ማዘንና መተከዝን የሚያመለክት ድርጊት ነው።

ያህዌ እንዲህ ይላል
የሚናገረውን ነገር እርግጠኝነት ለማመልከት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። 2 ነገሥት 19፥33 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ የሚለው ይህን ነው›› ወይም፣ ‹‹ይህ እኔ ያህዌ የተናገርሁት ነው››

2 Kings 22:20

አጠቃላይ መረጃ
ይህ በነቢዩት ሕልዳና በኩል ያህዌ ለንጉሥ ኢዮስያስ የላከው መልእክት ፍጻሜ ነው።

ስለዚህ ወደ አባቶችህ እሰበስብሃለሁ፤ ወደ መቃብርህ በሰላም እሰበስብሃለሁ
ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው። ሁለቱም ትሞታለህ ማለት ናቸው አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለዚህ እንድትሞትና በሰላም እንድትቀበር አደርጋለሁ››

ዐይኖችህ አያዩም
እዚህ ላይ፣ ‹‹ዐይኖች አለማየታቸው›› መከራ አይደርስብህም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አይደርስብህም››

ዐይኖችህ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ዐይኖች›› መላውን የሰው ሁለንተና ያመለክታል።

በዚህ ቦታም የሚመጣውን መከራ
ያህዌ መከራ እንዲሆን ማድረጉ፣ ጥፋት ያህዌ ወደዚያ ቦታ የሚያመጣው ነገር እንደ ሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በዚህ ቦታ የሚመጣው ከባድ ነገር››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 23

1 ስለዚህ ንጉሥ ኢዮስያስ የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን የታወቁ ሽማግሌዎችን ሁሉ ጠርቶ ሰበሰባቸው። 2 እነርሱም ካህናት፣ ነቢያት፣ ሌሎችም ሰዎች ከታናሾች ጀምሮ እስከ ታላቆች ድረስ ወደ ቤተ መቅደስ መጡ፤ ንጉሡም በዚያ ጠፍቶ በነበረውና በቤተ መቅደስ በተገኘው መጽሐፍ የሰፈረውን ቃል በሙሉ ለሕዝቡ አነበበ። 3 ንጉሡም በዐምዱ አጠገብ ቆሞ በሙሉ ልቡና አሳቡ እግዚአብሔርን ለመከተልና ትእዛዞቹን፣ ደንቦቹንና ድንጋጌዎቹን ለመጠበቅ በእርሱ ፊት ቃል ኪዳን አደረገ። ስለዚህም በዚህ የተጻፈውን ቃል ኪዳን አረጋገጠ፤ ሕዝቡም ሁሉ በቃል ኪዳኑ ለመቆም ተስማሙ። 4 ንጉሡም ኢዮስያስ ሊቀ ካህናቱን ኬልቅያስን፣ ረዳቶቹ የሆኑትን ካህናትና የቤተ መቅደስ በር ዘብ የሚጠብቁ ተረኞችን ጠርቶ ለባዓልና አሼራ ተብላ ለምትጠራው ሴት አምላክ፣ እንዲሁም ለከዋክብት ማምለኪያ ያገለግሉ የነበሩትን ዕቃዎች ሁሉ ከቤተ መቅደስ ያወጡ ዘንድ አዘዛቸው። ንጉሡም እነዚህን ዕቃዎች ሁሉ ከኢየሩሳሌም ውጪ ባለው በቄድሮን ሸለቆ በእሳት አቃጥሎ ዐመዱን ወደ ቤቴል ወሰደው። 5 በይሁዳ ከተማዎችና በኢየሩሳሌም አቅራቢያ ባሉት ስፍራዎች ሁሉ በየኮረብታው ላይ በነበሩት መሠዊያዎች መሥዋዕት ያቀርቡ ዘንድ የይሁዳ ነገሥታት ሾመዋቸው የነበሩትን ካህናት ሁሉ ከሥራ አሰናበተ፤ ባዓል ተብሎ ለሚጠራው ባዕድ አምላክ፣ ለፕላኔቶች፤ ለፀሐይ፣ ለጨረቃ፣ ለፀሐይና ለሰማይ ከዋክብት ሁሉ መሥዋዕት በማቅረብ የሚያገለግሉ ካህናትን ሁሉ አስወገደ። 6 አሼራ ተብላ የምትጠራውን ሴት አምላክ ምስል ከቤተ መቅደስ ነቅሎ ከከተማይቱ በማውጣት ወደ ቄድሮን ሸለቆ ወስዶ በእሳት አቃጠለው፤ ትቢያ እስኪሆንም አድቅቆ፣ በሕዝብ መቃብር ላይ በተነው። 7 ግብረ ሰዶም የሚፈጽሙ፣ በቤተ መቅደሱ ውስጥ የሚያገለግሉ ሴቶች አሼራ ተብላ ለምትጠራው ሴት አምላክ መጋረጃ የሚፈትሉበትን ክፍል ሁሉ አጸዳ። 8 በይሁዳ ከተሞችና በመላ አገሪቱ ከጌባ እስከ ቤርሳቤህ የነበሩትን ካህናት ሁሉ ወደ ኢየሩሳሌም አመጣ። መሥዋዕት ያቀርቡባቸው የነበሩትን መሠዊያዎች ሁሉ ርኩስ መሆናቸውን አወጀ፤ እንዲሁም የከተማይቱ ገዢ ኢያሱ ወደ ከተማይቱ ሲገቡ ከዋናው ቅጥር በር በስተግራ በኩል ባሠራው ቅጥር በር አጠገብ የሚገኙትን መስገጃዎች አፈራረሰ። 9 የከፍታ ቦታ ካህናት በቤተ መቅደስ በኢየሩሳሌም ለማገልገል ያልተፈቀደላቸው ቢሆንም በወንድሞቻቸው ዘንድ የነበረውን እርሾ ያልነካውን ሕብስት በሉ። 10 ንጉሥ ኢዮስያስ በሔኖም ሸለቆ የነበረውን «ቶፌት» ተብሎ የሚጠራውን የአሕዛብ ማምለኪያ ቦታ የረከሰ መሆኑን አስገነዘበ፤ ከዚህም የተነሣ «ሞሌክ» ተብሎ ለሚጠራው አምላክ ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን መሥዋዕት አድርጎ የሚያቀርብ ማንም እንዳይኖር ተከለከለ። 11 የይሁዳ ነገሥታት ለፀሐይ አምልኮ መድበዋቸው የነበሩትን ፈረሶች ሁሉ አስወገደ። ለዚሁ አምልኮ ያገለግሉ የነበሩትን ሠረገሎች አቃጠለ። እነዚህ ሁሉ ቀደም ሲል ታላቁ ባለሥልጣን ናታን ሜሌክ በሚኖርባቸው ክፍሎች አጠገብና በቤተ መቅደሱ አደባባይ ቅጥር በር አጠገብ ይገኙ ነበር። 12 ንጉሥ አካዝ ባሠራቸው መኖሪያ ክፍሎች ጣራ ላይ በሚገኘው ቤተ መንግሥት የይሁዳ ነገሥታት አሠርተዋቸው የነበሩትን መሠዊያዎችና በቤተ መቅደሱ ሁለት አደባባዮች ንጉሥ ምናሴ አሠርቶአቸው የነበሩትን መስገጃዎች ሁሉ ኢዮስያስ ደመሰሳቸው፤ መሠዊያዎቹን ሰባብሮ ወደ ቄድሮን ሸለቆ ወስዶ ጣላቸው። 13 ንጉሡም ከኢየሩሳሌም በስተ ምሥራቅ ከርኩሰት ተራራ በስተ ደቡብ አስታሮት ተብሎ ለሚጠራው ለአሞን አምላክ ንጉሥ ሰሎሞን አሠርቶአቸው የነበሩትን አስጸያፊ ምስሎች፣ የሲዶናውያንና የሞዓባውያን አስጸያፊ የሆኑ ጣዖታትን ሁሉ ደመሰሰ። 14 ንጉሥ ኢዮስያስ የድንጋይ አምዶችን ሁሉ ሰባበረ፤ አሼራ ተብላ የምትጠራውንም የሴት አምላክ ምስሎች ሰባብሮ ጣለ። እነርሱም ቆመውበት የነበረውን የድንጋይ ዐምዶች ሰባብሮ ስፍራውንም የሙታን አጥንት ሞላበት። 15 እስራኤልን ወደ ኃጢአት የመራ የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም በቤቴል አሠርቶት የነበረውን የማምለኪያ ቦታ ኢዮስያስ አፈራርሶ ጣለው፤ መሠዊያውን ነቅሎ የተመሠረተበትን ድንጋይ ሁሉ ሰባብሮ በማድቀቅ እንደ ትቢያ አደረገው፤ የአሼራንም ምስል በእሳት አቃጠለ። 16 ከዚያም ኢዮስያስ ዙሪያውን ሲመለከት፣ በኮረብቶች ላይ የተሠሩ መቃብሮች አየ፤ በእነዚያም መቃብሮች ውስጥ የነበረውን አፅም ሁሉ አስወጥቶ በመሠዊያው ላይ በእሳት አቃጠለው። በዚህም ዓይነት መሠዊያው የረከሰ መሆኑን አስገነዘበ፤ ኢዮስያስ ይህንን ሁሉ በማድረጉ ከብዙ ጊዜ በፊት በተደረገ የአምልኮ በዓል ላይ ንጉሥ ኢዮርብዓም በመሠዊያው አጠገብ ቆሞ ሳለ ነቢዩ የተናገረው የትንቢት ቃል ተፈጸመ። ንጉሥ ኢዮስያስ ዙሪያውን ሲመለከት ይህንን የእግዚአብሔር ቃል ተናግሮ የነበረው ነቢይ የተቀበረበትን መካነ መቃብር የማን ነው ሲል ጠየቀ። 17 የቤቴል ሕዝብ ከይሁዳ መጥቶ በዚህ መሠዊያ ላይ ይህንን አንተ ያደረግኸውን ነገር ሁሉ እንደሚፈጸምበት ተናግሮ የነበረው የነቢዩ መቃብር ነው ሲሉ መለሱለት። 18 ኢዮስያስም እንዳለ ይኑር፣ የእርሱ አፅም ከዚህ መንቀሳቀስ የለበትም ሲል መለሰ። ስለዚህም የእርሱም ሆነ የሰማርያው ነቢይ አፅሞች ከዚያ እንዲነሡ አልተደረገም። 19 ከዚያም ንጉሥ ኢዮስያስ በማንኛይቱም የእስራኤል ከተማ የእስራኤል ነገሥታት አሠርተዋቸው የነበሩትን የእግዚአብሔርን ቁጣ ለማነሣሣት ምክንያት የሆኑ የአሕዛብ ማምለኪያ ስፍራዎችን ሁሉ አፈራረሰ። በቤቴል ያደረገውን ሁሉ በእነዚያ መሠዊያዎች ላይ ፈጸመ። 20 በእነዚያ መሠዊያዎች ላይ ያገለግሉ የነበሩትንም የአሕዛብ ካህናት ሁሉ አረዳቸው። በመሠዊያዎቹም ላይ አጥንቶቻቸውን አቃጠለ። ከዚያም ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ። 21 ከዚያም ንጉሥ ኢዮስያስ በቃል ኪዳን መጽሐፍ በተጻፈው መሠረት ለአምላካቸው ለእግዚአብሔር የፋሲካ በዓል ያከብሩ ዘንድ ሕዝቡን አዘዘ። 22 መሳፍንት የሕዝቡ ገዢዎች ከነበሩበት ጊዜ አንሥቶ እስከ አሁን በማናቸውም የእስራኤል ወይም የይሁዳ ነገሥታት አማካይነት ይህንን የመሰለ የፋሲካ በዓል ተከብሮ አያውቅም። 23 ነገር ግን ኢዮስያስ በነገሠ በዐሥራ ስምንተኛው ዓመት የእግዘአብሔር ፋሲካ በዓል በኢየሩሳሌም ተከበረ። 24 ሊቀ ካህናቱ ኬልቂያስ በቤተ መቅደስ ባገኘው መጽሐፍ ውስጥ የተጻፈው ሕግ ሁሉ ተፈጻሚነት እንዲኖረው በማሰብ፣ ንጉሥ ኡዮስያስ ከኢየሩሳሌምና ከሌላውም የይሁዳ ከተማ ሁሉ መናፍስት ጠሪዎችንና ጠንቋዮችን ሁሉ የቤተ ሰብ አማልክት ጣዖቶችንና ሌሎችም አረማዊ የአምልኮ መፈጸሚያ ዕቃዎችን ሁሉ አስወገደ። 25 ለኦሪት ሕግ በመታዘዝ በፍጹም ልቡ፣ በፍጹም ነፍሱና በፍጹም ኃይሉ እግዚአብሔርን ያገለገለ እንደ ንጉሥ ኢዮስያስ ያለ ከእርሱም በፊት ሆነ ከእርሱ በኋላ ከቶ አልነበረም። 26 ይሁን እንጂ ይህም ሁሉ ሆኖ ንጉሥ ምናሴ ባደረገው ክፉ ነገር ምክንያት በይሁዳ ላይ የነደደው የእግዚአብሔር ቁጣ እስከ አሁን ድረስ ገና አልበረደም ነበር። 27 ስለዚህ እግዚብሔር እንዲህ አለ፦ በእስራኤል ላይ ያደረግኹትን ነገር ሁሉ በይሁዳ ላይ አደርጋለሁ፤ ይኸውም የይሁዳን ሕዝብ ከፊቴ አስወግዳለሁ፤ የመረጥኳትን ከተማ ኢየሩሳሌምንና ስሜ በዚያ ይጠራል ብዬ የነበረውንም ቤተ መቅደስ እተዋለሁ። 28 ንጉሥ ኢዮስያስ ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ በይሁዳ ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኛል። 29 በኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት ኒካዑ የተባለው የግብጽ ንጉሥ የአሦርን ንጉሠ ነገሥት ለመርዳት ሠራዊቱን እየመራ ወደ ኤፍራጥስ ወንዝ ተጓዘ። ንጉሥ ኢዮስያስም መጊዶ ላይ የግብጽን ሠራዊት ለማገድ ጦርነት ገጥሞ በዚያ ውጊያ ላይ ተገደለ። 30 አገልጋዮቹም ባለሥልጣኖች ሬሳውን በሠረገላ ወደ ኢየሩሳሌም አምጥተው እዚያ በነገሥታት መካነ መቃብር ተቀበረ። የይሁዳም ሰዎች የኢዮስያስን ልጅ ኢዮአክስን መረጡ፣ በአባቱም ፈንታ አነገሡት። 31 ኢዮአክስ በይሁዳ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ሃያ ሦስት ዓመት ነበር። በኢየሩሳሌም ሦስት ወር ገዛ፤ እናቱም አሚጣል ተብላ የምትጠራ የልብና ከተማ ተወላጅ የሆነው የኤርምያስ ልጅ ነበረች። 32 ኢዮአክስ የቀድሞ አባቶቹ እንዳደረጉት በእግዚብሔር ፊት ክፉ አደረገ። 33 እርሱንም ኒካዑ ተብሎ የሚጠራው የግብጽ ንጉሥ ኢዮአክስ በኢየሩሳሌም እንዳይነግሥ በሐማት ምድር በምትገኘው በሪብላ አስሮ ይሁዳ ሦስት ሺህ አራት መቶ ኪሎ ብር ሠላሳ አራት ኪሎ ወርቅ ግብር እንዲከፍል ባደረገው ጊዜ የኢዮአክስ ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ ሆነ። 34 ንጉሥ ኒካዑ የኢዮአክስ ልጅ ኤልያቄም በአባቱ በኢዮስያስ ፈንታ ተተክቶ በይሁዳ እንዲነግሥ አደረገ። ስሙንም በመለወጥ ኢዮአቄም ብሎ ጠራው። ኢዮአክስ በንጉሥ ኒካዑ ተማርኮ ወደ ግብጽ ተወሰደ፤ በዚያም ሞተ። 35 ኢዮአቄም ለግብጽ ንጉሥ ለኒዑዑ የጠየቀውን ብርና ወርቅ ከፈለ። ይህንንም ለማድረግ እንደየችሎታቸው በሕዝቡ ላይ ግብር ጣለ። 36 ኢዮአቄም በይሁዳ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ሃያ አምስት ዓመት ነበር። በኢየሩሳሌም ዐሥራ አንድ ዓመት ገዛ፤ እናቱም ዘቢዳ ተብላ የምትጠራ የሩማ ከተማ ተወላጅ የሆነው የፈዳያ ልጅ ነበረች። 37 ኢዮአቄም የቀድሞ አባቶቹ እንዳደረጉት በእግዚብሔር ፊት ክፉ አደረገ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Kings 23:1

የይሁዳና የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ሁሉ
ይህ አጠቃላይ ንግግር ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ብዙ ሌሎች ሰዎች››

ከታናሹ እስከ ታላቁ
ይህ አነጋገር በመሓል ያሉትን ሁሉ ይመለከታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በጣም ታላቅ ከሆነው እስከ በጣም ታናሽ የሆነው››

እንዲሰሙት በሙሉ አነበበላቸው
‹‹ከዚያም መስማት እንዲችሉ ንጉሡ ድምፁን ከፍ አድርጎ አነበበላቸው››

የተገኘውን
2 ነገሥት 22፥8 ላይ ኬልቅያስ መጽሐፉን እንዳገኘ ተገልጿል። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። ‹‹ኬልቅያስ ያገኘው›› ወይም፣ ‹‹ተገኝቶ የነበረው››

2 Kings 23:3

ያህዌን እንደሚከተል
የሰው አኗኗር መንገድ ላይ መሄድ እንደ ሆነ ተነግሯል፤ አንድን ሰው ‹‹መከተል›› ያ ሰው የሚያደርገውን ማድረግና ሌሎችም እንዲያደርጉ መፈለግ ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለያህዌ በመታዘዝ መኖር››

ትእዛዞቹን፣ ደንቦቹን፣ ሥርዐቶቹን
እነዚህ ቃሎች ተመሳሳይ ነገር ይጋራሉ። ሁሉም በአንድነት ያህዌ በሕጉ ላዘዘው ሁሉ አጽንዖት ይሰጣሉ።

በፍጹም ልቡ በፍጹም ነፍሱ
‹‹በፍጹም ልቡ›› ማለት፣ ‹‹ሙሉ በሙሉ›› ማለት ነው፤ ‹‹በፍጹም ነፍሱ›› ማለት፣ ‹‹በሙሉ ሁለንተናው›› ማለት ነው። እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጒም አላቸው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በሙሉ ሁለንተናው›› ወይም፣ ‹‹በፍጹም ኀይሉ››

በመጽሐፍ የተጻፈውን
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በዚህ መጽሐፍ የተካተተውን››

በኪዳኑ መቆም
‹‹ለኪዳኑ ውል መታዘዝ›› ማለት ነው።

2 Kings 23:4

ከእርሱ በታች ያሉትን ካህናት
‹‹እርሱን የሚያገለግሉ ሌሎች ካህናት››

በር ጠባቂዎች
የቤተ መቅደሱን በሮች የሚጠብቁ ሰዎች

ለበአል... ለከዋክብት ሁሉ
‹‹በአልን ለማምለክ ሰዎች የሚጠቀሙባቸው... ከዋክብትን እንዲያመልኩ ሰዎች የሚጠቀሙባቸው››

አቃጠላቸው... ወሰደ... አስወገደ
‹‹እርሱ›› የሚለው የሚያመለክተው ኢዮስያስን ነው። እነዚህን ነገሮች እንዲያደርጉ ወራተኞቹን አዘዘ። ኬልቅያስና ሲረዱት የነበሩ ካህናትም እነዚህን ነገሮች አድርገዋል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አቃጠላቸው... ወሰዳቸው... አስወገዳቸው››

የቄድሮን ሸለቆ... ቤቴል
የቦታ ስሞች

ለፀሐይና ለጨረቃ፣ ለስብስብ ከዋክብትና ለመላው የሰማይ ከዋክብት
‹‹በአልን፣ ፀሐይና ጨረቃን፣ ስብስብ ከዋክበትንና ሌሎች ከዋክብትን ሁሉ ለማምለክ››

2 Kings 23:6

አጠቃላይ መረጃ
ለያህዌ መልእክት በሰጠው ምላሽ መሠረት ንጉሥ ኢዮስያስ ያደረገውን ማቅረብ ቀጥሏል።

አመጣ... አቃጠለ... ሰባበረ... ወረወረ... አጸዳ
‹‹እርሱ›› የሚለው ኢዮያስን ነው። እነዚህን ነገሮች እንዲያደርጉ ሠራተኞቹን አዘዘ። ኬልቅያስና እርሱን የሚረዱ ካህናትም እነዚህን ነገሮች አድርገዋል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አመጣቸው... አቃጠላቸው... ሰባበራቸው... ወረወራቸው... አጸዳ››

ልብሶች መፍተል
‹‹ልብሶች መሥራት››

2 Kings 23:8

ኢዮስያስ አመጣ... አረከሰ... አጠፋ
እነዚህን ነገሮች እንዲያደርጉ ኢዮስያስ ሠራተኞቹን አዘዘ። ኬልቅያስና እርሱን የሚረዱ ካህናት እነዚህን ነገሮች አድርገዋል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እንዲያመጡ... እንዲያረክሱና... እንዲያቃጥሉ አዘዘ››

ጌባ... ቤርሳቤህ
የቦታ ስሞች

ኢያሱ (አገረ ገዢው)
‹‹ኢያሱ የተባለው አገረ ገዥ›› ወይም፣ ‹‹ኢያሱ የተባለው የከተማ መሪ›› ይኸኛው ከብሉይ ኪዳኑ መጽሐፈ ኢያሱ የተለየ ኢያሱ ነው።

ወንድሞቻቸው
እዚህ ላይ፣ ‹‹ወንድሞች›› ቤተ መቅደሱ ውስጥ የሚያገለግሉ ካህናት ጓደኞቻቸውን ያመለክታል።

2 Kings 23:10

ቶፌት... የሄኖም ሸለቆ
የቦታ ስሞች

ወንድ ወይም ሴት ልጁን ለሞሎክ በእሳት የሚቃጠል መሥዋዕት እንዲያቀርብበት
‹‹ለሞሎክ መሥዋዕት እንዲሆኑ ወንድ ወይም ሴት ልጁን በእሳት ማቃጠል››

አስወገደ
ኢዮስያስ ይህን እንዲያደርግ የረዱ ሌሎች ሰዎች ምናልባትም፣ ኬልቅያስና፣ ‹‹ከእርሱ ሥር ያሉ ካህናት›› (2 ነገሥት 23፥4) ሳይረዱት እንዳልቀረ አንባቢው መረዳት በሚችልበት ሁኔታ መተርጐም የተሻለ ነው።

ፈረሶቹ
ይህም ማለት 1) የእውነት ፈረሶች ወይም 2) የፈረሶች ምስል ሊሆን ይችላል።

ለፀሐይ አምልኮ የሰጡአቸውን
‹‹መስጠት›› ለአምልኮ መለየትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ፀሐይን ለማምለክ ማዋል››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ናታን ሜሌክ
x

2 Kings 23:12

ንጉሥ ኢዮስያስ አስወገደ... ኢዮያስ አደቀቀ... ንጉሡ አወደመ... ሰባበረ... አረከሰ
ይህን እንዲያደርጉ ኢዮስያስ ሠራተኞቹን አዘዘ። ምናልባትም ኬልቅያስና እሱን የሚረዱ ካህናት ይህን ለማድረግ ሳይረዱት አልቀረም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ንጉሡ ኢዮስያስ እንዲያስወግዱ... እንዲያደቅቁ... እንዲያወድሙ... እንዲሰባብሩ... እንዲያረክሱ አዘዘ።››

ቄድሮን ሸለቆ
የቦታ ስም። 2 ነገሥት 23፥4 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

ስፍራውንም በሙታን ዐጥንት ሞላው
‹‹ከእንግዲህ ለማምለኪያ እንዳያውሉት ያንን ቦታ በሰዎች አጥንት ሞላው››

2 Kings 23:15

ኢዮስያስ ፈጽሞ አፈረሰ... አቃጠለ... አደቀቀ... አቃጠለ
ይህን ለማድረግ ሌሎች ሰዎች ምናልባትም ኬልቅያስና፣ ‹‹ከእርሱ በታች ያሉ ካህናት›› (2 ነገሥት 23፥4) ኢዮስያስን ሳይረዱት እንዳልቀረ አንባቢው መረዳት በሚችልባት ሁኔታ መተርጐሙ የተሻለ ነው።

አስቀድሞ እንደ ተናገረው
‹‹እንዲህ እንደሚሆን እንደ ተናገረው››

2 Kings 23:17

ሐውልት
ለሰው ክብር የሚቆም ምስል። መቃብር አንድ ዐይነት ሐውልት ነው።

ዐፅሙን እንዳለ ተዉት፤ የእርሱን... ዐፅም
‹‹ስለዚህ ዐፅሙን ወይም ዐፅሞቹን አልነኳቸውም››

2 Kings 23:19

ኢዮስያስ አስወገደ... አደረገ... ዐረደ... አቃጠለ
ይህን ለማድረግ ሌሎች ምናልባትም፣ ኬልቅያስና፣ ‹‹ከእርሱ በታች ያሉ ካህናት›› (2 ነገሥት 23፥4) ኢዮስያስን ሳይረዱት እንዳልቀሩ አንባቢው መረዳት በሚችልበት ሁኔታ መተርጐሙ የተሻለ ነው።

የተደረገውን
‹‹ያደረገውን››

የሰው ዐጥንት አቃጠለባቸው
ዐጥንቶቹን ያቃጠለበትን ምክንያት ግልጽ ማድረግ ያስፈልገህ ይሆናል። ‹‹ከእንግዲህ ማንም እንዳይጠቀምባቸው በላያቸው የሰው ዐፅም አቃጠለባቸው››

2 Kings 23:21

ፋሲካን አክብሩ
‹‹ፋሲካን ማክበር አለባችሁ››

እንደዚህ ያለ ፋሲካ መቼም ተከብሮ አያውቅም
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤል ልጆች በ... ዘመን እንደ ሆነው ታላቅ ፋሲካ አክብረው አያውቁም››

እስራኤልን ገዛ
‹‹እስራኤል›› የሚለው ስም፣ ‹‹ዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ልጆች›› ማለት ነው።

በእስራኤልና በይሁዳ ነገሥታት ዘመን
‹‹እስራኤል የራሳቸው ነገሥታት በነበሩዋቸው ዘመን፤ ይሁዳም የራሳቸው ነገሥታት በነበሩዋቸው ዘመን››

የያህዌ ፋሲካ ተከበረ
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የይሁዳ ሕዝብ ይህን የያህዌ ፋሲካ አከበሩ››

2 Kings 23:24

አስወገደ... መናፍስት
‹‹እነዚያን መናፍስት አባረረ›› ወይም፣ ‹‹እነዚያ መናፍስት እንዲወገዱ ሕግ አወጣ››

ከሙታን ወይም ከመናፍስት የሚነጋገሩ
2 ነገሥት 21፥6 ላይ፣ ‹‹ከሙታን የሚነጋገሩ... ከመናፍስት የሚነጋገሩ›› የሚለውን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

መተት
ሰዎች የተለየ ኀይል እንዳላቸው የሚያስቡዋቸው ነገሮች

ወደ ያህዌ የተመለሰ
‹‹ሙሉ በሙሉ ራሱን ለያህዌ የሰጠ››

ከእርሱም በኋላ እንደ ኢዮስያስ ያለ ንጉሥ አልተነሣም
‹‹ከዚያ ጊዜ ወዲህ ኢዮስያስን የመሰለ ንጉሥ አልነበረም››

2 Kings 23:26

ይሁን እንጂ
ጸሐፊው በዚህ ቃል የተጠቀመው ኢዮስያስ ያደረጋቸው እነዚህ ነገሮች ሁሉ መልካም ቢሆኑም፣ ያህዌ አሁንም በይሁዳ እንደ ተቆጣ መሆኑን ለማሳየት ነው።

ያህዌ በይሁዳ ላይ ከነደደው አስፈሪ ቁጣው ገና አልበረደም ነበር
እሳት የቁጣ ምሳሌ ነው፤ እሳት ማንደድ መቆጣት ማለት ነው። ‹‹ቁጣ›› የሚለውን ቃል ለየት ባለ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በ... ተቆጥቶ ስለ ነበር ያህዌ ከቁጣው ገና አልበረደም ነበር››

ለቁጣ እንዲነሣሣ
‹‹እርሱን ለማስቆጣት››

ከፊቴ
‹‹እኔ ካለሁበት›› ወይም፣ ‹‹ከአጠገቤ››

ስሜ በዚያ ይሆናል
ስም ሰዎች ለሰው የሚሰጡትን ክብር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች እኔን እዚያ ያከብሩኛል››

2 Kings 23:28

በይሁዳ... ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?
መልሱ አዎንታዊ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። ጥያቄው የቀረበው አጽንዖት ለመስጠት ነው። 2 ነገሥት 8፥23 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በይሁዳ... ማግኘት ትችላላችሁ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በዘመኑ የግብፅ ንጉሥ ፈርዖን ኒካዑ
‹‹በኢዮስያስ ዘመን የግብፅ ንጉሥ ፈርዖን ኒካዑ››

ኒካዑ... መጊዶ
ኒካዑ የሰው ስም ነው፤ መጊዶ የቦታ ስም ነው።

2 Kings 23:31

ሃያ ሦስት ዓመት
‹‹23 ዓመት››

አሚጣል
ይህ የሴት ስም ነው

ልብና... ሪብላ... ሐማት
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው

በያህዌ ዐይን ፊት ክፉ ነገር
የያህዌ ዐይን የያህዌን ፍርድና ግንዛቤ ይወክላል። 2 ነገሥት 3፥2 ላይ ይህንን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በያህዌ ፍርድ ክፉ ነገር›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ክፉ የሚለውን ነገር››

በሰንሰለት አስረው
‹‹በሰንሰለት›› መታሰር፣ መያዝና በቁጥጥር ሥር መሆንን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እስር ቤት አስገባው››

ይሁዳን አስከፈለ
‹‹የይሁዳ ሕዝብ እንዲሰጡት አስገደደ››

መቶ መክሊት ብር... አንድ መክሊት
መክሊት 33 ኪሎ ግራም ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹3,300 ኪሎ ግራም... 33 ኪሎ ግራም››

2 Kings 23:34

ኢዮአቄም የአገሩ ሰዎች እንዲከፍሉ አደረገ
‹‹ኢዮአቄም ከአገሩ ሰዎች ግብር ሰበሰበ››

የአገሩ ሕዝብ
‹‹የይሁዳ አገር ሕዝብ›› ሌሎች ትርጉሞች፣ 1) ‹‹በይሁዳ ምድር የሚኖር ሕዝብ›› ወይም፣ 2) ‹‹በዚያ ምድር የሚኖሩ ሀብታሞና ታዋቂ ሰዎች›› እንደ ማለት ነው።

2 Kings 23:36

ዘቢዳ
የሴት ስም

ፈዳያ
የሰው ስም

ሩሚያ
የቦታ ስም

በያህዌ ዐይን ፊት ክፉ ነገር አደረገ
የያህዌ ዐይን የያህዌን ፍርድና ግንዛቤ ይወክላል። 2 ነገሥት 3፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በያህዌ ፍርድ ክፉ ነገር›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ክፉ የሚለውን ነገር››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 24

1 በኢዮአቄም ዘመነ መንግሥት የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ይሁዳን ወረረ፤ ኢዮአቄምም ሦስት ዓመት ከገበረለት በኋላ እንደገና አመፀ። **2** እግዚብሔር በአገልጋዮቹ በነቢያት አማካይነት ይሁዳን ስለ ማጥፋት የተናገረው ትንቢት እንዲፈጸም ወራሪ ቡድኖች ባቢሎናውያንን፣ ሶርያውያንን፣ ሞአባውያንንና አሞናውያንን በኢዮአቄም ላይ አስነሣበት። **3** ይህም ሁሉ የሆነው ንጉሥ ምናሴ በፈጸመው ኃጢአት ምክንያት የይሁዳን ሕዝብ ከፊቱ ለማስወገድ እግዚብሔር ባዘዘው መሠረት ነው። **4** በተለይ ምናሴ የንጹሓንን ሰዎች ደም በማፍሰሱና ኢየሩሳሌምንም በንጹሓ ደም በመሙላቱ ምክንያት ይህ ሁሉ ሊፈጸም ችሎአል። ከዚህም የተነሣ እግዚብሔር ለምናሴ ምሕረት ሊያደርግለት አልፈቀደም። **5** ኢዮአቄም ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ በይሁዳ ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኛል። **6** ኢዮአቄምም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ በእርሱም ፈንታ ልጁ ዮአኪን ነገሠ። **7** የባቢሎን ንጉሥ ከኤፍራጥስ ወንዝ እስከ ግብጽ ሰሜናዊ ጠረፍ ድረስ የግብጽ ይዞታ የነበረውን ሁሉ በቁጥጥሩ ሥር አድርጎ ስለ ነበረ፣ የግብጽ ንጉሥና ሠራዊቱ ከዚያ በኋላ ከግብጽ ውጪ ዘመቻ አላደረጉም። **8** ዮአኪን በይሁዳ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ዐሥራ ስምንት ዓመት ነበረ፤ በኢየሩሳሌም ሦስት ወር ገዛ። እናቱም ኔስታ ተብላ የምትጠራው የኢየሩሳሌም ተወላጅ የሆነው የኤልናታን ልጅ ነበረች። **9** አባቱ እንዳደረገው ሁሉ በእግዚብሔር ፊት ክፉ አደረገ። **10** በዚያን ጊዜ የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ኢየሩሳሌምን አጠቃ፤ ከተማይቱንም ከበባት። **11** ሠራዊቱ ከብቦ በነበረበት ጊዜ የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ወደ ኢየሩሳሌም መጣ። **12** የይሁዳ ንጉሥ ዮአኪን ከእናቱ፣ ከልዑላን መሳፍንቱ፣ ከጦር አዛዦቹና ከባለሥልጣናቱ ጋር ወደ ባቢሎን ንጉሥ ተወሰዱ። የባቢሎን ንጉሥም በነገሠ በስምንተኛው ዓመት ዮአኪንን ማረከው። **13** ናቡከደነፆርም በቤተ መቅደስና በቤተ መንግሥት የነበረውን ሀብት ሁሉ ጠራርጎ ወደ ባቢሎን ወሰደ። ቀደም ሲል እግዚብሔር በተናገውም ቃል መሠረት ንጉሥ ሰሎሞን ለእግዚብሔር ቤተ መቅደስ አሠርቶት የነበረውን የወርቅ ዕቃ ሁሉ ሰባበረ። **14** ናቡከደነፆር የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ልዑላን፣ መሳፍንቱን ሁሉና ሌሎችንም ታላላቅ ሰዎች ጭምር በድምሩ ዐሥር ሺህ ሰዎች ማርኮ ወሰደ። ከእርሱም ጋር የዕደ ጥበብ ዐዋቂዎችንና የብረት አንጣሪዎችን ሁሉ ወሰደ፤ በይሁዳ እንዲቀሩ ያደረገው የመጨረሻዎቹን ድኾች ብቻ ነበር። **15** ናቡከደነፆር ዮአኪንን አስሮ ከእናቱ፣ ከሚስቶቹ፣ ከአገልጋዮቹ፣ ከባለሥልጣኖቹና ከይሁዳ ታላላቅ ሰዎች ጋር በአንድነት ሰብስቦ ወደ ባቢሎን ወሰዳቸው። **16** የባቢሎን ንጉሥ ሰባት ሺህ ለውጊያ ብቃት ያላቸው ወንዶችን እንዲሁም አንድ ሺህ ብረት ቀጥቃጮችንና ዕደ ጥበበኞችን ወደ ባቢሎን ወሰደ። **17** ናቡከደነፆርም በዮአኪን ምትክ ማታንያ ተብሎ የሚጠራውን የዮአኪንን አጎት በይሁዳ አነገሠው፤ ስሙንም በመለወጥ ሴዴቅያስ ብሎ ጠራው። **18** ሴዴቅያስ በይሁዳ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ሃያ አንድ ዓመት ነበር። በኢየሩሳሌም ዐሥራ አንድ ዓመት ገዛ። እናቱም አሚጣል ተብላ የምትጠራ የልብና ከተማ ተወላጅ የነበረው የኤርምያስ ልጅ ነበረች። **19** እርሱም አባቱ ኢዮአቄም ባደረገው ዓይነት በእግዚአብሔር ክፉ አደረገ። **20** እግዚብሔር ከፊቱ እስኪያስወግዳቸው ድረስ በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ሕዝብ ተቆጥቶ ነበር። ሴዴቅያስም በባቢሎን ንጉሥ ላይ ዐመፀ።

---

2 Kings 24:1

በአዮአቄም ዘመን
‹‹ኢዮአቄም የይሁዳ ንጉሥ በነበረ ዘመን››

ይሁዳን አጠቃ
ናቡከደነፆር ይሁዳን ካጠቃ በኋላ የሆነውን ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ይሁዳን አጥቅቶ ድል አደረገ››

ይህም በአገልጋዮቹ በነቢያት አማካይነት በተነገረው የያህዌ ቃል መሠረት ነው
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንዲህ የሆነው በባርያዎቹ በነቢያት በኩል ያህዌ በተናገረው ቃል መሠረት ነው›› ወይም፣ ‹‹ይህ በትክክል እንዲህ እንደሚሆን ያህዌ ለባርያዎቹ ለነቢያት እንደ ተናገረው ነው››

2 Kings 24:3

በያህዌ አፍ
እዚህ ላይ፣ ‹‹አፍ›› የያህዌን ትእዛዝ ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ እንዳዘዘው››

ከፊቱ አስወገደ
‹‹አባረረ›› ወይም፣ ‹‹አጠፋ››

2 Kings 24:5

በይሁዳ... ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?
ይህ በተጻፈበት ዘመን ሰዎች ይህን መረጃ ያውቁ ስለ ነበር ጥያቄው ምላሽ የሚያስፈልገው አልነበረም። ይህን በዐረፍተ ነገር መጻፍ ይቻላል። በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። 2 ነገሥት 8፥23 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐመኸው ተመልከት። ‹‹በእርግጥ በይሁዳ... ተጽፈዋል›› ወይም፣ ‹‹በይሁዳ... ማግኘት ትችላላችሁ››

ከአባቶቹ ጋር አንቀላፉ
አንቀላፋ ሞተ ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሞተ፤ ከአባቶቹም ጋር ተቀበረ››

2 Kings 24:8

ኔስታ... ኤልናታን
ኔስታ የሴት ስም ነው። ኤልናታን የወንድ ስም ነው።

በያህዌ ዐይን ፊት ክፉ ነገር
የያህዌ ዐይን የያህዌን ፍርድና ግንዛቤ ይወክላል። 2 ነገሥት 3፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐመኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በያህዌ ፍርድ ክፉ ነገር›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ክፉ የሚለውን››

አባቱ ያደረገውን ሁሉ አደረገ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ሁሉ›› አጠቃላይ ንግግር ነው። አባቱ ያደረገውን የመሰለ ኀጢአት ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አባቱ ሲያደርግ የነበረውን ዐይነት ኀጢአት አደረገ››

2 Kings 24:10

የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአቄም ወደ ባቢሎን ንጉሥ ሄደ፤ እርሱ እናቱ፣ አገልጋዮቹ ልዕልቶቹ ባለ ሥልጣኖቹ
ኢዮአቄም ናቡከደነፆርን ለማግኘት የሄደበትን ምክንያት ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአቄም፣ ከእናቱ፣ ከአገልጋዮቹ፣ ከልዕልቶቹና ከባለ ሥልጣኖቹ ጋር እጁን ለመስጠት የባቢሎን ንጉሥ ወዳለበት ሄደ››

የባቢሎን ንጉሥ በነገሠ በስምንተኛው ዓመት ማርኮ ወሰደው
‹‹የባቢሎን ንጉሥ ከነገሠ ሰባት ዓመት በኋላ ዮአኪንን ማርኮ ወሰደው››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Kings 24:13

የእስራኤል ንጉሥ ሰሎሞን ያሠራቸውን
ሰሎሞን ይህን ያደረገው በሌሎች ሰዎች ርዳታ መሆኑን አንባቢው መረዳት እንዲችል አድርገህ መተርጐም ይኖርብህ ይሆናል።

ኢየሩሳሌምን ሁሉ ወደ ምርኮ ወሰደ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ኢየሩሳሌም›› እዚያ የሚኖር ሕዝብ ማለት ነው። ‹‹ሁሉ›› አጠቃላይ አነጋገር ነው። በጣም አስፈላጊ የሆኑ ሰዎችን ሁሉ ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ናቡከደነፆር በጣም አስፈላጊ የሆኑ ሰዎችን ሁሉ ከኢየሩሳሌም ወሰደ››

የእጅ ባለሙያዎችንና ቀጥቃጮችን
‹‹ከብረታ ብረት ነገሮችን መሥራትና መጠገን የሚያውቁ ሰዎች››

በዚያ የቀሩ የመጨረሻዎቹ ያገሪቱ ድኾች ብቻ ነበሩ
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በምድሪቱ የቀሩ በጣም ድኾች የሆኑ ሰዎች ብቻ ነበሩ››

2 Kings 24:15

ሰባት ሺህ... አንድ ሺህ
‹‹7,000... 1,000››

ማታንያ
ይህ የሰው ስም ነው።

2 Kings 24:18

ሃያ አንድ... ዐሥራ አንድ
‹‹21... 11››

አሚጣል
ይህ የሴት ስም ነው

ኤርምያስ
ይህ የሰው ስም ነው

ልብና
ይህ የቦታ ስም ነው

በያህዌ ዐይን ፊት ክፉ ነገር
የያህዌ ዐይን የያህዌን ፍርድና ግንዛቤ ይወክላል። 2 ነገሥት 3፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በያህዌ ፍርድ ክፉ ነገር›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ክፉ የሚለውን ነገር››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 25

1 ናቡከደነፆር መላው ሠራዊቱን አስከትቶ ሴዴቅያስ በነገሠ በዘጠነኛው ዓመት፣ ዐሥረኛው ወር በገባ በዐሥረኛው ቀን ከባቢሎን መጥቶ በኢየሩሳሌም ላይ
ዘመተ፤ ወታደሮቹ ከከተማይቱ ውጪ ሰፍረው ዙሪያውን የሚከብብ አጥር ሠሩ። 2 ከበባው እስከ ሴዴቅያስ ዐሥራ አንደኛ ዓመት ዘመነ መንግሥት ድረስ ቆየ። 3
ስለዚህም አራተኛው ወር በገባ በዘጠነኛው ቀን ራቡ በጣም ስለ ጸና ሕዝቡ የሚመገበው እንዳችም ምግብ አልነበረም። 4 ከዚያም የከተማይቱ ቅጥር ተጣሰ፤
የባቢሎን ወታደሮች ከተማይቱን ዙሪያውን ከበው በመያዝ ቢጠብቁም እንኳ የይሁዳ ንጉሥ ወታደሮች በሌሊት አምልጠው ወጡ፤ ወደ ንጉሡ የአትክልት ቦታ
ከሚያስገባው መንገድ ተነሥተው ሁለቱን ቅጥሮች በሚያያይዘው የቅጥር በር በኩል በማለፍ ወደ ዮርዳኖስ ሸለቆ አቅጣጫ ሸሹ። 5 ነገር ግን የከላደውያን
ሠራዊት ንጉሥ ሴዴቅያስን በኢያሪኮ አጠገብ በሚገኝ ሜዳ ላይ አሳደደው። ወታደሮቹም ጥለውት ሸሹ። 6 ሴዴቅያስ ተይዞ በሪብላ ከተማ ወደሚገኘው ወደ
ባቢሎን ንጉሥ ተወሰደ። በዚያም ፍርድ አስተላለፉበት። 7 ሴዴቅያስም ዐይኑ እያየ ልጆቹ በፊቱ ታረዱ። ከዚህም በኋላ ናቡከደነፆር የሴዴቅያስን ዐይኖች
አውጥቶ አሳወረው፤ እጆቹንም በነሐስ ሰንሰለት አስሮ ወደ ባቢሎን ወሰደው። 8 ናቡከደነፆር በባቢሎን በነገሠ በዐሥራ ዘጠነኛው ዓመት፣ አምስተኛው ወር
በገባ በሰባተኛው ቀን ናቡዘረዳን ተብሎ የሚጠራው የናቡከደነፆር የክብር ዘበኞቹ አዛዥ ኢየሩሳሌም ገባ። 9 እርሱም ቤተ መቅደሱን፣ ቤተ መንግሥቱን፣
በከተማው የሚኖሩትን የታላላቅ ሰዎች ቤት፣ በከተማው ውስጥ የሚገኙትንም ሌሎች ቤቶች ሁሉ በእሳት አቃጠለ። 10 በክብር ዘቡ አዛዥ ሥር የነበሩት
የባቢሎናውያን ወታደሮች በሙሉ የኢየሩሳሌምን ዙሪያ አጥር ደመሰሱ። 11 ከዚህ በኋላ ናቡዘረዳን በከተማይቱ ቀርተው የነበሩትንና ሌሎችን ሰዎች እንዲሁም
ከድተው ወደ ባቢሎናውያን የተጠጉትን ሁሉ ምርኮ አድርጎ ወደ ባቢሎን ወሰዳቸው። 12 ነገር ግን ምንም ሀብት የሌላቸውን የመጨረሻ ድኾች አትክልት
ኮትኳቾችና መሬት አራሾች እንዲሆኑ በይሁዳ ምድር ትቶአቸው ሄደ። 13 ባቢሎናውያን በቤተ መቅደሱ ውስጥ የነበሩትን የነሐስ አምዶች፣ ባለ መንኮራኩር
የዕቃ ማስቀመጫዎችንና ከነሐስ የተሠራውን ታላቅ የውሃ ማጠራቀሚያ ገንዳ ሰባበሩ፤ ነሐሱንም ሁሉ ወደ ባቢሎን ወሰዱት። 14 እነርሱም ምንቸቶችን፣
መጫሪያዎችን፣ መኮስተሪያዎችን፣ የዕጣን ማስቀመጫዎችንና ከነሐስ የተሠሩ የቤተ መቅደስ መገልገያ ዕቃዎችን ሁሉ ወሰዱ። 15 ጽናዎችንና ዱካዎችን
ከብርና ከወርቅ የተሠሩ በመሆናቸው ወሰዱአቸው። 16 ንጉሥ ሰሎሞን ለቤተ መቅደስ ያሠራቸውን ሁለቱን አምዶች፣ ባለመንኮራኩር የዕቃ ማስቀመጫዎችንና
ታላቁን የውሃ ማጠራቀሚያ ገንዳዎቸ፣ በክብደታቸው ምክንያት ሊመዝኑአቸው አልቻሉም። 17 አንዱ አምድ ስምንት ሜትር ነበረው፤ ጉልላቱ ከነሐስ የተሠራ
ነበር፤ የጉልላቱም ቁመት አንድ ሜትር ከሠላሳ ሳንቲ ሜትር ነበር፤ በዙሪያውም ከነሐስ በተሠራ መረብ ላይ የሮማን ፍሬ ቅርጽ የመሰለ ባለፈርጥ ጌጥ
ተሠርቶበት ነበር። 18 የሠራዊቱ አዛዥ ናቡዘረዳን ሊቀ ካህናቱን ሠራያን በማዕርግ የእርሱ ምክትል የሆነውን ካህኑን ሶፎንያስንና ሦስቱን የቤተ መቅደስ ዘበኞች
እስረኛ አደርጎ ወሰዳቸው። 19 ከከተማይቱም የወታደሮች አዛዥ የሆነው አንድ ባለሥልጣን እስከዚያ ጊዜ ድረስ በከተማይቱ የነበሩትን አምስቱን የንጉሥ
አማካሪዎች፣ የአገሩን ሕዝብ ለወታደርነት ይመለምል የነበረው መኮንንና ሌሎችንም ስልሳ ሰዎችን ወሰደ። 20 ከዚያም ናቡዘረዳን እነዚህን ሁሉ ይዞ በሐማት
ግዛት በምትገኘው በሪብላ ከተማ ወደነበረው ወደ ባቢሎን ንጉሥ ወሰዳቸው። 21 የባቢሎንም ንጉሥ በዚያ እነርሱን አስደብድቦ በማሠቃየት በሞት ቀጣቸው።
በዚህም ዐይነት የይሁዳ ሕዝብ ከአገራቸው ተማርከው ተወሰዱ። 22 የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር የሳፋን የልጅ ልጅ የአኪቃምን ልጅ ጎዶልያስን ወደ ባቢሎን
ተማርከው ሳይወሰዱ ለቀሩት ሰዎች ሁሉ ኃላፊ ይሆን ዘንድ የይሁዳ ገዢ አድርጎ ሾመው። 23 እጃቸውን ያልሰጡ የይሁዳ የጦር መኮንኖችና ወታደሮች
የባቢሎን ንጉሥ ጎዶልያስን ገዢ አድርጎ እንደ ሾመው በሰሙ ጊዜ ወደ ምጽጳ መጥተው ከእርሱ ጋር ተገናኙ፤ እነዚህም የጦር መኮንኖች የናታንያ ልጅ
እስማኤል፣ የቃሬያ ልጅ የሐናን፣ የነጦፋ ከተማ ተወላጅ የሆነው የተንሑሜት ልጅ ሠራያና የማዕካ ተወላጅ የሆነው ያእዛንያ ነበሩ። 24 ጎዶልያስ እነርሱንና
ወታደሮቻቸውን እንዲህ አላቸው፤ ከባቢሎናውያን ባለሥልጣኖች የተነሣ ምንም ዐይነት ፍርሃት ሊያድርባችሁ እንደማይገባ ቃል እገባላችኋለሁ፤ በዚህች ምድር
ኑሮአችሁን መሥርቱ፤ ለባቢሎን ንጉሥ ገብሩ፤ ይህን ብታደርጉ ሁሉ ነገር ይቃናላችኋል። 25 ነገር ግን በዚያው ዓመት በሰባተኛው ወር ከንጉሣዊ ቤተ ሰብ
የነበረውና የኤሊሳማ የልጅ ልጅ የሆነው የናታንያ ልጅ እስማኤል ከዐሥር ሰዎች ጋር ሆኖ ወደ ምጽጳ ሄደ፤ በዚያም አደጋ ጥሎበት ጎዶልያስን ገደለው፤
እንዲሁም ከእርሱ ጋር የተገኙትን አይሁዳውያንንና ባቢሎናውያንን ሁሉ ገደለ። 26 ከዚህም የተነሣ ባቢሎናውያንን ስለፈሩ እስራኤላውያን ሀብታሞችና ድኾች
ከጦር ሠራዊት መኮንኖች ጋር በአንድነት ተነሥተው ወደ ግብጽ ሸሹ። 27 ዮርማሮዴቅ በነገሠበት ዓመት የይሁዳን ንጉሥ ዮአኪንን ከእስራት በመፍታት ምሕረት
አደረገለት፤ ይህም የሆነው ዮአኪን ተማርኮ በሄደ በሠላሳ ሰባት ዓመቱ፣ በዐሥራ ሁለተኛው ወር በሃያ ሰባተኛው ቀን ነበር። 28 ዮርማሮዴቅ ለዮአኪን መልካም
ነገር አደረገለት፤ እንደ እርሱ ተማርከው በባቢሎን በስደት ከሚኖሩ ነገሥታት ሁሉ የላቀ የክብር ማዕረግ ሰጠው። 29 ስለዚህም ዮአኪን በእስር ቤት የነበረውን
ልብስ ለውጦ እስከ ዕድሜው ፍጻሜ ድረስ ከንጉሡ ማዕድ እንዲመገብ ተፈቀደለት። 30 እርሱም በኖረበት ዘመን ሁሉ በየቀኑ ለማናቸውም ለሚያስፈልገው
ነገር ያውለው ዘንድ የዘወትር ቀለብ ይሰጠው ነበር።

---

2 Kings 25:1

በዘጠነኛው ዓመት
(የቁጥር አጻጻፍ ይመልከቱ)

በዐሥረኛው ወር፣ ከወሩም በዐሥረኛው ቀን
ይህ ዐሥረኛ ወር በዕብራውያን ቀን አቆጣጠር ነው። በምዕራባውያን ቀን መቁጠሪያ ዐሥረኛው ቀን ታህሣሥ መጨረሻ ላይ ነው። ዝናብና በረዶ
የሚኖርበት ቀዝቃዛ ወቅት ነው።

ሰራዊቱን ሁሉ ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም መጣ
‹‹ኢየሩሳሌም›› እዚያ የሚኖሩ ሰዎች ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ለመውጋት ሰራዊቱን ይዞ መጣ›› ወይም፣
‹‹ኢየሩሳሌምን ድል ለማድረግ ሰራዊቱን ይዞ መጣ››

በአራተኛ ወር በዘጠነኛው ቀን
ይህ አራተኛ ወር በዕብራውያን ቀን አቆጣጠር ነው። በምዕራባውያን ቀን መቁጠሪያ ዘጠነኛው ቀን ሰኔ መጨረሻ ላይ ነው። ይህ ጥቂት ወይም ምንም
ዝናብ የማይኖርበት ደረቅ ወቅት ነው።

የምድሪቱ ሕዝብ
እነዚህ ጦርነቱ ሲጀመር ከአጐራባች ሰፈሮች ወደ ኢየሩሳሌም የሸሹ ስደተኞችን ጨምሮ የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ናቸው።

2 Kings 25:4

የከተማዪቱ ቅጥር ተጣሰ
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የባቢሎን ሰራዊት ቅጥሩን ጥሶ ወደ ከተማ ገባ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሲዋጉ የነበሩ ሰዎች ሁሉ
‹‹ተዋጊዎች ሁሉ››

በበሩ በኩል
‹‹በሩን አልፎ››

ከለዳውያን
አንዳንድ ትርጉሞች፣ ‹‹ከለዳውያን›› ሌሎች ደግሞ፣ ‹‹ባቢሎናውያን›› ይላሉ። ሁለቱም አንድ ሕዝብ ነው የሚመለክቱት።

ንጉሡ... በኩል ሸሸ
‹‹ንጉሥ ሴዲቅያስም ሸሸ፤ ወደ... ሄደ››

ወታደሮቹ ሁሉ ተለይተውት ተበታተኑ
ይህን በሌላ መልኩ መተርጎም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወታደሮቹ ሁሉ ከእርሱ ሸሹ›› ወይም፣ ‹‹ከለዳውያን ወታደሮቹን ሁሉ አባረሩ››

2 Kings 25:6

ሪብላ
ይህ የቦታ ስም ነው።

ቅጣት ተፈረደበት
‹‹እርሱን ለመቅጣት ምን እንደሚያደርጉ ወሰኑ››

በዐይኑ ፊት አረዱበት
‹‹ዐይን›› የሰውን ሁለንተና ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወንዶች ልጆቹ ሲገደሉ እንዲመለከት ንጉሥ ሴዲቅያስን አስገደዱት››

ዐይኖቹን አወጣ
‹‹ናቡከደነፆር የሴዴቅያስን ዐይኖች አወጣ›› ናቡከደነፆር ይህን እንዲያደርግ ሌሎች ሰዎች ሳይረዱት እንዳልቀረ አንባቢው እንዲገነዘብ በተሻለ መልኩ መተርጎም ይቻላል።

2 Kings 25:8

በአምስተኛው ወር፤ ከወሩም በሰባተኛው ቀን
አምስተኛው ወር በዕብራውያን ቀን አቆጣጠር ነው። በምዕራባውያን ቀን መቁጠሪያ ሰባተኛው ቀን ሐምሌ መጨረሻ ላይ ነው።

በዐሥራ ዘጠነኛው ዓመት
‹‹19ኛው ዓመት››

ናቡዘረዳን
ይህ የሰው ስም ነው።

በኢየሩሳሌም ዙሪያ ያሉ ቅጥሮችን ሁሉ፣ ሁሉ
‹‹በኢየሩሳሌም ዙሪያ ባሉ ቅጥሮች የሆነው ይህ ነበር››

ከእርሱ በታች
‹‹የእርሱን ትእዛዝ የሚከተሉ››

2 Kings 25:11

ቀርቶ የነበረው ሕዝብ... ከተማ፣ እነዚያ
‹‹በከተማው የቀረ ሕዝብ ሁሉ... ከተማ፣ እነዚያ››

በከተማው የቀረ ሕዝብ
‹‹በከተማው ቀርቶ የነበረ ሕዝብ››

ወደ ንጉሡ ሄዱ
‹‹ከተማውን ትተው ወደ ንጉሡ ሄዱ››

2 Kings 25:13

የናስ ዐምዶቹ... ያህዌ፣ ከለዳውያን
‹‹የናስ ዐምዶቹ ላይ የሆነው እንዲህ ነው፤ ያህዌ ከለዳውያን››

መቆሚያ
ይህ ትልቁን ተንቀሳቃሽ የናስ መቆሚያ ያመለክታል፤ መቆሚያው መንኮራኩሮች ነበሩት። ‹‹ተንቀሳቃሹ የናስ መቆሚያ›› ወይም፣ ‹‹መንኮራኩሮች ያሉት የናስ መቆሚያ››

የናስ ሰሐን
‹‹ትልቁ የናስ መታጠቢያ››

አድቅቆ ሰባበራቸው
‹‹አደቀቃቸው›› ወይም፣ ‹‹ሰባበራቸው››

መኮስተሪያዎች
መኮስተሪያዎች መሠዊያውን ለማጽዳት የሚያገለግሉ ነገሮች ናቸው፤ ብዙውን ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውሉት ከባድ ያሉ ቆሻሻዎችን፣ አሸዋን ወይም ዐመድን ለመጥረግ ነው።

ካህናቱ የሚያገለግሉባቸው ነገሮች
‹‹ካህናቱ ቤተ መቅደሱ ውስጥ ሲያገለግሉ የሚጠቀሙባቸው››

ዐመድ ማስወገጃ ድስቶች
የሚናገረው ስለ የትኛው ዐመድ እንደ ሆነ ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከመሠዊያው ላይ ዐመድ ለማስወገድ የሚያገለግሉ ድስቶች

2 Kings 25:16

ባሕሩ
‹‹ትልቅ የናስ መታጠቢያ›› 2 ነገሥት 25፥13 ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

መቆሚያዎች
2 ነገሥት 25፥13 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

ስምንት ክንድ... ሦስት ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሳንቲሜትር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹8.3 ሜትር ያህል... 1.4 ሜትር ያህል››

ቅርጽ ያለባቸው ናሶች
‹‹የእጅ ሥራ ያለባቸው›› ወይም፣ ‹‹ቅርጻ ቅርጽ ያለበት የናስ ክፍል››

ባለ መርበብ ሥራዎች
እነዚህ የመረብ ቅርጽ ያላቸው ጥልፍልፍ ገመዶች ናቸው

ከናስ የተሠሩ
‹‹ሙሉ በሙሉ ከናስ የተሠሩ››

2 Kings 25:18

የክብር ዘቡ አዛዥ
2 ነገሥት 25፥8 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

ሠራያ
ይህ የሰው ስም ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሁለተኛው ካህን
ይህ የሚያመለክተው ሶፎንያስን ነው። ሌላው አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከሠራያ በታች ያለው ካህን››

በር ጠባቂዎች
2 ነገሥት 7፥10 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት

እስረኛ አድርጐ ወሰዳቸው
‹‹እንዳያመልጡ ያዛቸው››

የተዋጊዎቹ አለቃ
አንዳንድ ትርጉሞች፣ ‹‹የወታደሮቹ ጎላፊ የሆኑ ጃንደረቦች›› ይላሉ። ጃንደረባ ብልቱ የተቆረጠ ሰው ማለት ነው።

ለውትድርና የሚመለምል ዋና የጦር አለቃ
ይህም ማለት፣ 1) ሰዎች ወታደር እንዲሆኑ የሚያስገድድ አለቃ፤ ወይም 2) ወታደሮች መሆን ያለባቸውን ሰዎች ስም የሚጽፍ አለቃ

2 Kings 25:20

ናቡዘረዳን
ይህ የሰው ስም ነው። 2 ነገሥት 25፥8 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

ሪብላ
ይህ የቦታ ስም ነው። 2 ነገሥት 25፥6 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

አስገደላቸው
በሌላ መልኩ ይህ፣ ‹‹ገደላቸው›› ማለት ነው። ንጉሡ ይህን እንዲያደርግ ሌሎች ሰዎች ሳይረዱት እንዳልቀሩ አንባቢው መገንዘብ እንዲችል የበለጠ ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል።

በዚህ መንገድ ይሁዳ ከአገሩ በምርኮ ተወሰደ
‹‹ይሁዳ ከገዛ ምድሩ በምርኮ ተወሰደ››

ይሁዳ ከምድሩ ተወስዶ
ይሁዳ የሕዝብ ስም ሲሆን፣ የሕዝቡ የራሳቸው መጠሪያ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የይሁዳ ሕዝብ ከምድራቸው ተወሰደ››

2 Kings 25:22

ጐዶልያስ… አኪቃም… ሳፋን… እስማኤል… ናታን… ዮሐን… ቃሬያ… ሠራያ… …ተንሑሜት …ያዛንያ

ነጦፋዊ
ይህ የሚያመለክተው ነጦፋ የሚባል ሰው ዘር ነው።

ማዕካታዊ
ይህ የሚያመለክተው ማዕካታ ከሚባል ቦታ የመጣ ሰው ነው።

2 Kings 25:25

ሰባተኛ ወር
ይህ ሰባተኛ ወር በዕብራውያን ቀን አቆጣጠር ነው። በምዕራባውያን ቀን አቆጣጠር የመስከረም ማብቂያና የጥቅምት መጀመሪያ ነው።

ኤሊሰማ
ይህ የሰው ስም ነው።

ሕዝቡ ሁሉ
ይህ አጠቃላይ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ብዙ ሰዎች››

ከታናሹ እስከ ታላቁ
ይህ አጠቃላይ በሆነ ደረጃ፣ ‹‹ሁሉም›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጣም አስፈላጊ ከሆነው ዝቅተኛ አስፈላጊነት እስካለው ድረስ›› ወይም፣ ‹‹ሁሉም››

2 Kings 25:27

በሠላሳ ሰባተኛው ዓመት
(የቁጥር አጻጻፍ ይመለከቷል)

ዐሥራ ሁለተኛው ወር ከወሩም በሃያ ሰባተኛው ቀን
ዐሥራ ሁለተኛው ወር በዕብራውያን ቀን አቆጣጠር ነው። በምዕራባውያን ቀን አቆጣጠር ሃያ ሰባተኛው ቀን ሚያዝያ መጀመሪያ ላይ ነው።

ዮሮሜሮዴቅ
ይህ የሰው ስም ነው

2 Kings 25:28

ከሌሎች ነገሥታት የበለጠ ክብር ያለው መቀመጫ
ገበታ ላይ ጥሩ ቦታ እንዲይዝ ማድረግ እርሱን ማክበር መሆኑ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከሌሎች ነገሥታት የበለጠ ክብር››

የእስር ልብሱን ጣለ
የዮአቂምን የእስር ልብሱን መጣሉ፣ ነጻ ሰው ሆነ ማለት እንደ ሆነ ተነግሯል።

ከንጉሡ ማዕድ
‹‹ከንጉሡና ከባለ ሥልጣኖቹ ጋር››

የዕለት ቀለቡ ይሰጠው ጀመር
ይህን በሚከተለው መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የዕለት ምግቡን እንዲያገኝ ንጉሡ አዘዘ››

የዕለት ቀለብ
‹‹ምግብ የመግዣ ገንዘብ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: 1 Chronicles

1 Chronicles

Chapter 1

1 አዳም፣ ሴት፣ ሄኖስ፣ **2** ቃይናን፣ መላልኤል፣ ያሬድ፣ **3** ሄኖክ፣ ማቱሳላ፣ ላሜሕ፣ኖኅ። **4** የኖኅ ወንዶች ልጆች፤ ሴም፣ካምናያፌት። **5** የያፌት ወንዶች ልጆች፤ ጋሜር፣ማጎግ፣ማዴ፣ያዋን፣ቶቤል፣ሞሳሕ፣ቴራስ። **6** የጋሜር ወንዶች ልጆች፤ አስከናዝ፣ሪፋት፣ቴርጋማ። **7** የያዋን ወንዶች ልጆች፤ ኤሊሳ፣ተርሴስ፣ኪቲም፣ሪድኢ። **8** የካም ወንዶች ልጆች፤ ኪሽ፣ ምፅራይም፣ ፋጥናኪነዓን። **9** የኩሽ ወንዶች ልጆች፤ ሳባ፣ ኤውላጥ፣ ሰብታ፣ ራዕማናሰብቃታ። ያራዕማ ወንዶች ልጆች፤ ሳባናድዳን ነበሩ። **10** ኩሽ ናምሩድን ወለደ፤ እርሱም በምድር ላይ የመጀመሪያው ኀያል ጦረኛ ሆነ። **11** ምፅራይም የሉዲማውያን፣ የዐናማውያን፣ የላህባማውያን፣ የነፍተሂማውያን፣ **12** የፈትሩሲማውያን፣ የፍልስጥኤማውያን ቅድመ አባቶች የሆኑት የከስሉሂማውያንና የከፍቶሪማውያን ነገዶች አባት ነው። **13** ከነዓን የበኩር ልጁ የሆነው የሶዶን እንዲሁም የከጢያውያን፣ **14** የኢያቡሳውያን፣ **15** የኤዊውያን፣ የዐርካውያን፣ **16** የሲኒውያን፣ የአራዴዎውያን፣ የሰማርያውያን፣ የአማቲያውያን አባት ነው። **17** የሴም ወንዶች ልጆች፤ ኤላም፣ አሦር፣ አርፋክስድ፣ ሉድ፣ አራም። የአራም ወንዶች ልጆች፤ ዑፅ፣ ሁል፣ ጌቴር፣ ሞሳሕ። **18** አርፋክስድ ሳላን ወለደ። **19** ዔርቦ ወንዶች ልጆች ወለደ፤ በዘመኑ ምድር ስለተከፈለች፣ የአንደኛው ስም ፋሌቅ ተብሎ ተጠራ፣ **20** ዮቅጣንም፡ አልሞዳድን፣ ሣሌፍን፣ ሐስረሞትን፣ ያራሕን፣ **21** ሀዶራምን፣አውዛልን፣ደቅላን፣ **22** ዖባልን፣ አቢማኤልን፣ ሳባን፣ **23** ኦፋርን፣ ኤውላጥን፣ ዮባብን ወለደ፤ እነዚህ ሁሉ የዮቅጣን ወንዶች ልጆች ናቸው። **24** ሴም፣ አርፋክስድ፣ ሳለ፣ **25** ዔቦር፣ ፋሌቅ፣ ራግው፣ **26** ሴሮህ፣ ናኮር፣ ታራ፣ **27** እንዲሁም በኋላ አብርሃም የተባለ አብራም። **28** የአብርሃም ወንዶች ልጆች፤ይስሐቅና እስማኤልሲሆኑ። **29** የእነዚህ ዘሮች የሚከተሉት ናቸው፤ የእስማኤል በኩር ልጅ ነባዮት፣ ቄዳር፣ ነብ፣ ዳኤል፣ መብሳም፣ **30** ማስማዕ፣ ዱማ፣ ማሣ፣ ኩዳን፣ ቴማን፣ **31** ኢጡር፣ ናፌስ፣ ቄድማ፣ እነዚህ የእስማኤል ወንዶች ልጆች ናቸው። **32** የአብርሃም ቁባት ኬጡራ የወለደቻቸው ወንዶች ልጆች ዘምራን፣ ዮቅሳን፣ ሜዳን፣ ምድያም፣ የስቦቅና፣ ስዌሕ ናቸው። የዮቅሳን ወንዶች ልጆች፤ ሳባ፣ ድዳን፣ **33** የምድያም ወንዶች ልጆች፤ ጌፈር፣ ዔፌር፣ ሄኖኅ፣ አቢዳዕ፣ ኤልዳዓ፣ እነዚህ ሁሉ የኬጡራ ዘሮች ናቸው። **34** አብርሃም ይስሐቅን ወለደ። የይስሐቅ ወንዶች ልጆች፤ ዔሳው፣ እስራኤል። **35** የዔሳው ወንዶች ልጆች፤ ኤልፋዝ፣ ራጉኤል፣ የዑስ፣ የዕላም፣ ቆሬ። **36** የኤልፋዝ ወንዶች ልጆች ቴማር፣ ኦማር፣ ሰፎ፣ ጎቶም፣ ቄኔዝ፣ ቲምናዕ፣ አማሌቅ። **37** የራጉኤል ወንዶች ልጆች፤ ናሑት፣ ዛራ፣ ሣማ፣ ሚዛህ። **38** የሴይር ወንዶች ልጆች፤ ሎጣን፣ ሦባል፣ ጽብዖን፣ ዓና፣ ዲሶን፣ ኤጽር፣ ዲሳን። **39** የሎጣን ወንዶች ልጆች፤ ሖሪ፣ ሄማም፣ ቲሞናዕ፣ የሎጣን፣ እኅት ነበረች። **40** የሦባል ወንዶች ልጆች፤ ዓልዋን፣ ማኔሐት፣ ዔናል፣ ስፎ፣ አውናም። የጽብዖን ወንዶች ልጆች፤ አያ፣ ዓና። **41** የዓና ወንድ ልጅ፤ ዲሶን። የዲሶን ወንዶች ልጆች፤ ሔምዳን፣ ኤስባን፣ ይትራን፣ ክራን። **42** የኤጽር ወንዶች ልጆች፤ ቢልሐን፣ ዛዕዋን፣ ዓቃን። የዲሳን ወንዶች ልጆች፤ ዑፅ፣ አራን። **43** በእስራኤል አንድም ንጉሥ ገና ሳይነግሥ በኤዶም ምድር የነገሡ ነገሥታት እነዚህ ናቸው። የቢዖር ልጅ ባላቅ፤ ከተማይቱም ዲንሃባ ትባል ነበር። **44** ባላቅ ሲሞትም የባሳራ ሰው የሆነው የዛራ ልጅ ኢዮባብ በእግሩ ተተክቶ ነገሠ። **45** ኢዮባብ ሲሞት የቴማን አገር ሰው የሆነው ሑሳም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ። **46** ሑሳም ሲሞት በሞዓብ ምድር ምድያ ምን ድል ያደረገው የባዳድ ልጅ በእግሩ ተተክቶ ነገሠ። የከተማይቱም ስም ዓዊት ተባለ። **47** ሃዳድም ሲሞት የመሥሬቃ ሰው የሆነው ሠምላ በእግሩ ተተክቶ ነገሠ። **48** ሠምላም ሲሞት በወንዙ አጠገብ ያለችው የረኆቦት ሰው የሆነው ሳኡል በእግሩ ተተክቶ ነገሠ። **49** ሳኡልም ሲሞት የዓክቦል ልጅ የሆነው በኣልሐናንም ሲሞት በእግሩ ተተክቶ ነገሠ። **50** በኣልሐናን ሲሞት ሀዳድ በእግሩ ተተክቶ ነገሠ። ከተማው ፋዑ ትባል ነበር፤ ሚስቱ መሄጣብኤል ትባልላለች፤ እርሷም የሜዛሃብ ልጅ የመጥሬድ ልጅ ነበረች። **51** ሀዳድም ሞተ። ዋና ዋናዎቹ የኤዶም ሕዝብ አለቆች እነዚህ ነበሩ፤ ቲምናዕ፣ ዓልዋ፣ የቴት፣ **52** አህሊባማ፣ ኤላ፣ ፊኖን፣ ቄኔዝ፣ ቴማን፣ ሚብሳር፣ **53** ቄኔዝ፣ ቴማን፣ ሚብሳር፣ **54** መግዲኤል፣ ዒራም። እነዚህ የኤዶም አለቆች ነበሩ።

---

1 Chronicles 1:1

ሄኖክ... ቃየን... መላልኤል... ያሬድ... ሄኖክ... ማቱሳላ... ላሜሕ።
እነዚህ ሁሉ የሰዎች ስሞች ናቸው :: በዝርዝር ውስጥ እያንዳንዱ ሰው የቀጣዩ ሰው አባት ወይም ቅድመ አያት ነበር :: ቋንቋዎ ይህን መግለፅ የሚያስችልበት ሁኔታ ካለ እዚህ ጋር መጠቀም ይቻላል። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

ላሜሕ። የኖህ ልጆች ::
አንባቢዎችዎ ኖህ የላሜህ ልጅ እንደነበረ ማየት ከፈለጉ እና ቋንቋዎ ምልክት ሊያደርግበት የሚችልበት መንገድ ካለው እዚህ መጠቀም አለብዎት ::

1 Chronicles 1:5

የያፌት ልጆች፤ ጋሜር፥ ማጎግ፥ ማዴ፥ ያዋን፥ ቶቤል፥ ሞሳሕ፥ ቴራስ
እነዚህ ሁሉ የሰዎች ስሞች ናቸው :: (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ : ይመልከቱ)

ኪቲም፥ ሮድኢ
እነዚህ የሰዎች ቡድኖች ስሞች ናቸው :: (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ : ይመልከቱ)

ሮድኢ
ይህ ስም አንዳንድ ጊዜ “ዶዶናውያን” የሚል ነው። (የቅጂ ልዩነቶች፡ ይመልከቱ)

1 Chronicles 1:8

አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ያሉት ሁሉም ስሞች የሰዎች ስሞች ናቸው :: (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Chronicles 1:11

ሉዲምን፥ ዐናሚምን፥ ላህቢምን፥ ነፍተሂምን፥ ፈትሩሲምን፥ ፍልስጥኤማውያን የወጡበትን ከስሉሂምን፥ ከፍቶሪምን
የሰዎች ቡድን ስሞች። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)
ፍልስጥኤማውያንም ከእርሱ የመጡ ናቸው። “የፍልስጥኤማውያን አባቶች”

1 Chronicles 1:13

ሲዶን
ይህ የሰው የወንድ ነው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)

ኬጢያውያን... ኢያቡሳውያን... አሞራውያን ... ጌርጌሳዊውን ... ኤዊያዊውን ... ዐርካዊውን ... ሲኒያዊውን፥ አራዴዎንን፥ ሰማሪዎንን፥ አማቲን
የሰዎች ቡድን ስሞች። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)

1 Chronicles 1:17

አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ያሉት ሁሉም ስሞች የሰዎች ስሞች ናቸው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)

1 Chronicles 1:20

አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ያሉት ሁሉም ስሞች የሰዎች ስሞች ናቸው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)

1 Chronicles 1:24

አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ያሉት ሁሉም ስሞች የሰዎች ስሞች ናቸው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)

1 Chronicles 1:28

አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ያሉት ሁሉም ስሞች የሰዎች ስሞች ናቸው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)

1 Chronicles 1:32

አጠቃላይ መረጃ
ከኬቱራ በስተቀር ሁሉም እዚህ ያሉት ስሞች የወንዶች ስሞች ናቸው ። ኬቱራ የሴት ስም ነው። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)

1 Chronicles 1:34

አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ያሉት ሁሉም ስሞች የሰዎች ስሞች ናቸው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)

1 Chronicles 1:38

ከቲምና በስተቀር እዚህ ያሉት ሁሉም ስሞች የወንዶች ስሞች ናቸው ።
ቲምና የሴት ስም ነው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)

1 Chronicles 1:41

አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ያሉት ሁሉም ስሞች የወንዶች ስሞች ናቸው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)

1 Chronicles 1:43

ባላቅ ... ቢዖር ... ኢዮባብ ... ባሶራ ... ሑሳም
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)

ሳኡልዲንሃባ ... ባሶራ
እነዚህ የቦታዎች ስሞች ናቸው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ : ይመልከቱ)

በእርሱም ፋንታ የቴማን አገር ሰው ሑሳም ነገሠ የቴማን ዘሮች ከሚኖሩበት አገር ሑምሳ ከእሱ በኋላ ነገሠ
ይህ የሰዎች ቡድን ስም ነው። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)

1 Chronicles 1:46

ሑምሳ ... ሃዳድ ... ባዳድ ... ሠምላ ... ሳኡል
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)

ዓዊት ... መሥሬቃ ... ረሆቦት
እነዚህ የቦታዎች ስሞች ናቸው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ : ይመልከቱ)

1 Chronicles 1:49

እነዚህ የቦታዎች ስሞች ናቸው ። **(**ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ**)**
ሳኡል ... በኣልሐናን ... ዓክቦር ... ሃዳድ ... መጥሬድ ... ሜዛሃብ

ፋዑ
ይህ የቦታ ስም ነው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)

መሄጣብኤል
ይህ የሴት ስም ነው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 የእስራኤል ወንዶች ልጆች እነዚህ ነበሩ፤ ሮቤል፣ ስምዖን፣ ሌዊ፣ ይሁዳ፣ ይሳኮር፣ ዛብሎን፣ 2 ዳን፣ ዮሴፍ፣ ብንያም፣ ንፍታሌም፣ ጋድ፣ እሴር። 3 የይሁዳ
ወንዶች ልጆች፤ ዔር፣ አውናን፣ ሴሎም፣ እነዚህን ጆስቱን ከከነዓን ሚስቱ ከሴዋ ወለደ። የበኩር ልጁ ዔር በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሰው ሆነ፤ እግዚአብሔር
ቀፈፈው። 4 የልጁም ሚስት የነበረችው ትዕማር ፋሬስንና ዛራን ወለደችለት፤ ይሁዳም ባጠቃላይ አምስት ወንዶች ልጆች ነበሩት። 5 የፋሬስ ወንዶች ልጆች፤
ኤስሮም፣ ሐሙል። 6 የዛራ ወንዶች ልጆች፤ ዘምሪ፣ ኤታን፣ ሄማን፣ ከልኮል፣ ዳራ፣ ባጠቃላይ አምስት ናቸው። 7 የከሚር ወንድ ልጅ አካን፤ እርሱም ፈፅሞ
መደምሰስ የነበረበት ነገር ሰርቆ በእስራኤል ላይ ጥፋት እንዲመጣ ያደረገ ነው። 8 የኤታን ወንድ ልጅ፤ አዛርያ። 9 የኤስሮን ወንዶች ልጆች፤
ይረሕምል፣አራም፣ካሌብ። 10 አራም አሚናዳብን ወለደ፤አሚናዳብም የይሁዳ ሕዝብ መሪ የሆነውን ነአሶንን ወለደ፤ 11 ነአሶን ሰልሞንን ወለደ፤ሰልሞን ቦዔንን
ወለደ። 12 ቦዔዝ ኢዮቤድን ወለደ፤ኢዮብይድ እሴይን ወለደ። 13 የእሴይ ወንዶች ልጆች፤ የብኩር ልጁ ኤልያብ፣ ሁለተኛ ልጁ አሚናዳብ፣ ሦስተኛ ልጁ ሣማ፣
14 አራተኛው ልጁ ናትናኤል፣ አምስተኛ ልጁ ራዳይ፣ 15 ስድስተኛ ልጁ አሳም፣ ሰባተኛ ልጁ ዳዊት። 16 እኅቶቻቸውም ጽሩያና አቢግያ ነበሩ። የጹሩያ ሦስት
ወንዶች ልጆች አቢሳ፣ ኢዮአብና አሣኤል ነበሩ። 17 አቢግያ አሜሳይን ወለደች፣ አባቱም ዬቴር የተባለ እስማኤላዊ ነበረ። 18 የኤስሮም ልጅ ካሌብ ከሚስቱ
ከዓዙባና እንዲሁም ከይሪዖት ወንዶች ልጆች ወለደ፥ ከዓዜባ የተወለዱት ወንዶች ልጆች እነዚህ ናቸው። ያሳብ፣ ሶባብ፣ አርዶን፣ 19 ዓዙባ ስትሞት፣ ካሌብ
ኤፍራታን አገባ፤ እርሷም ሆርን ወለደችለት። 20 ሆርኡሪን ወለደ፤ ኡሪም ባስልኤልን ወለደ። 21 ከዚህም በኋላ ኤስሮም ሥልሳ ዓመት ሲሆነው የገለዓድን አባት
የማኪርን ልጅ አገባ፤ እርሷም ሠጉብን ወለደችለት። 22 ሠጉብም ኢያዕርን ወለደደ፤ እርሱም በገለዓድ ምድር ሃያ ሦስት አተሞች ያስተዳድር ነበር። 23 ይሁን
እንጂ ጌሹና አራም፣ ቄናትንና በዙሪያዋ የሚገኙትን ሥልሳ መነደሮች ጨምሮ የኢያዕርን ከተሞች ነጠቁት። እነዚህ ሁሉ የገለዓድ አባትየማኪር ዘሮች ነበሩ። 24
ኤስሮም በካሌብ ኤፍራታ ከሞተ በኋላ፣ ሚስቱ አቢያ የቴቁሔን አባት አሸሑርን ወለደችለት። 25 የኤስሮም የበኩር ልጅ የይረሕምኤል ወንዶች ልጆች፤ የበኩር
ልጁ ራም፣ ቡናህ፣ ኦሬን፣ ኦጼን፣ አኪያ። 26 ይረሕምኤል ዓጣራ የተባለች ሌላ ሚስት ነበረችው፤ እርሷም የኦናምን እናት ነበረች። 27 የይረሕምኤል የበኩር
ልጁ የራም ወንዶች፤ መዓስ፣ ያሚን፣ ዔቄር። 28 የኦናም ወንዶች ልጆች፤ ሸማይና ያዳ። የሸማይ ወንዶች ልጆች፤ ናዳብና አቢሱር። 29 የአቢሱር ሚስት አቢካኢል
ትባላለች፤ እርሷም አሕባንንና ሞሊድ የተባሉ ልጆች ወለደችለት። 30 የናባድ ወንዶች ልጆች፤ ሴሌድ፣አፋይም፣ሴሌድ፣ወንድ ልጅ ሳይወልድ ሞተ። 31 የአፋይም
ወንድ ልጅ፤ይሺዒ።ይሺዒም ሶሳን ወለደ።ሶሳን አሕልይን ወለደ። 32 የሸማይ ወንድም የያዳ ወንዶች ልጆች፤ዬቴር፣ዮናታን፣ዬቴርም ልጅ ሳይወልድ ሞተ። 33
የዮናታን ወንዶች ልጆች፤ፌሌት፣ዛዛ። እነዚህ የይረሕምኤል ዘሮች ነበሩ። 34 ሶሳን ሴቶች እንጂ ወንዶች ልጆች አልነበሩትም። እርሱም ኢዮሄል የተባለ ግብፃዊ
አገልጋይ ነበርረው። 35 ሶሳን ልጁን ለአገልጋዩ ለኢዮሄል ሚስት ትሆነው ዘንድ ሰጠው፤ እርሷም ዓይታ የተባለ ወንድ ልጅ ወለደችለት። 36 ዓታይ ናታንን
ወለደ፣ናታንም ዛባድን ወለደ፣ 37 ዛባድ ኤፍላን ወለደ፤ ኤፍላል ዖቤድን ወለደ፤ 38 ዖቤድ ኢዩን ወለደ፤ ኢዩ ዓዛርያስን ወለደ፤ 39 ዓዛርያስ ኬሌስን ወለደ፤
ኬሌስ ኤልዓሣ ወለደ፤ 40 ኤልዓሣ ሲስማይን ወለደ፤ ሲስማይ ሰሎምን ወለደ፤ 41 ሰሎም የቃምያን ወለደ፤ የቃምያም ኤሊሳማን ወለደ። 42 የይረሕምኤል
ወንድም የካሌብ ወንዶች ልጆች፤ የበኩር ልጁ ሞሳ ሲሆን፤ እርሱም ዚፍን ወለደ፤ ዚፍም መሪሳን ወለደ፤ መሪ ሳም ኬብሮንን ወለደ። 43 የኬብሮን ወንዶች
ልጆች፤ ቆሬ፣ ተፋዋ፣ ሬቄም፣ ሸማዕ። 44 ሸማዕ ርችሐምን ወለደ፤ ረሐምም ዮርቅዓምን ወለደ። ሬቄም ሸማይን ወለደ፤ 45 ሸማይም ማዖንን ወለደ፤ ማዖንም
ቤት ጹርን ወለደ። 46 የካሌብ ቁባት ዔፋ ሐራንን፣ ሞዳን፣ ጋዜዝን ወለደች። ሐራንም ጋዜዝን ወለደ። 47 የያህዳይ ወንዶች ልጆች፤ ሬጌም፣ ኢዮታም፣ ጌሻን፣
ፋሌጥ፣ ዔፋ፣ ሸዓፍ። 48 የካሌብ ቁባት ማዕካ ሼቤርን፣ ቲርሐናን ወለደለችለት። 49 እንዲሁም የመድማናን አባት ሸዓፍን፣ የመክቢናንና የጊብዓን አባት ሱሳን
ወለደች። ካሌብ ዓክሳ የተባለች ልጅ ነበረችው። 50 የኤፍራታ የበኩር ልጅ የሑር ወንዶች ልጆች ሦባል የቂርያት ይዓሪም አባት፤ 51 ሰልሞን የቤተልሔም አባት፤
ሐሬፍ የቤት ጋዴር አባት። 52 የቂርያትይዓሪም አባት የሦባል ዘሮች፤ የመናሕታውያን ነዋሪዎች እኩሌታ፣ ሀሮኤ፤ 53 እንዲሁም የቂርያትይዓሪም ጎሣዎች፤
ይትራውያን፤ ፉታውያን፣ ሹማታውያን፣ ሚሸራውያን፤ ጾርዓውያንና ኤሽታኦውያን ከእነዚህ የመጡ ጎሣዎች ነበሩ። 54 የሰልሞን ዘሮች፤ ቤተልሔም፣ ነጦፋውያን፣
ዓጣሮት ቤት ዮአብ፣ የመናሕታውያን እኩሌታ፣ ጾርዓውያን። 55 በያቤጽ የሚኖሩ የጸሐፍት ጎሣዎች ቲርዓውያን፣ ሺምዓታውያን፣ ሡካታውያን። እነዚህ ከሬካብ ቤት
አባት ከሐማት የመጡ ቄናውያን ናቸው።

---

1 Chronicles 2:1

አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ያሉት ሁሉም ስሞች የሰዎች ስሞች ናቸው :: (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)

1 Chronicles 2:3

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ዝርዝር የወንድም የሴቶች ስሞችንም ያካትታል :: (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)

ዔር ... አውናን እና ሴሎም ... ሴዋ ... ፋሬስን ... ዛራን
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው :: (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ : ይመልከቱ)

ከሴዋ ልጅ ተወለዱለት
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። አት: “ሹዋ የወለደቻቸው ወንዶች ልጆች” (ገባሪ ወይም ተገባሪ፡ ይመለከቱ)

ያህዌ
በብሉይ ኪዳን ለህዝቡ የገለጠው የእግዚአብሔር ስም ይህ ነው :: ይህንን እንዴት እንደሚተረጉሙ በተመለከተ ስለ ያህዌ የትርጉም ገጽ ይመልከቱ።

ፋሬስንና ዛራን ወለደችለት
“ወንዶች ልጆቹን ፋሬስንና ዛራን ወለደ”

በያህዌ ፊት
ያህዌ እይታ ፍርዱን ወይም ግምገማውን ይወክላል :: አት: - “ያህዌ እንደ ፈረደ” (ዜይቤ፡ ይመልከቱ)

ያህዌ ገደለው
አንባቢው ያህዌ ምናልባት ዔርን የሚገደለለት ሰው እንደነበረው መገንዘብ አለበት :: (የባሕሪ ስም፡ ይመልከቱ)

ትዕማር
ይህ የሴት ስም ነው :: (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)

ምራቱም
ይህ ለልጁ ሚስት ማጣቀሻ ነው ::

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አምስት ወንዶች ልጆች
“5 ልጆች” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

1 Chronicles 2:5

አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ያሉት ሁሉም ስሞች የወንዶች ስሞች ናቸው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ይመልከቱ)

ለእግዚአብሔር ተለይቶ የነበረው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር ህዝቡን እንዲያጠፋ ይፈልጋል ።

1 Chronicles 2:9

አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ያሉት ሁሉም ስሞች የወንዶች ስሞች ናቸው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ይመልከቱ)

1 Chronicles 2:13

አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ያሉት ሁሉም ስሞች የወንዶች ስሞች ናቸው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ይመልከቱ)

ሁለተኛው… ሦስተኛው… አራተኛው… fiኛው… ስድስተኛው… ሰባተኛው።
“ልጅ” የሚለው ቃል ታውቋል ። ደግሞም ፣ ቁጥሮቹ በመደበኛ መልክ ናቸው ። አት: “ሁለተኛው ልጅ… ሦስተኛው ልጅ .. አራተኛው ልጅ… አምስተኛው ልጅ… ስድስተኛው ልጁ… ሰባተኛው ልጁ” (ግድፈተ ቃላት እና ሕገኛ ቁጥሮች : ይመልከቱ)

1 Chronicles 2:16

አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ጽሩያ እና አቢግያ በስተቀር እዚህ ያሉት ሁሉም ስሞች የወንዶች ስሞች ናቸው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ይመልከቱ) ጽሩያ እና አቢግያ የሴቶች ስሞች ናቸው ።

እስማኤላዊው ዬቴር
ዬቴር የእስማኤል ዘር

1 Chronicles 2:18

ካሌብ … ሄዝሮን … ያሳር … ሶባብ … አርዶን ሆር… ኡሪ… ባስልኤል።
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ ይመልከቱ)

ዓዙባ … ይሪዖትም … ኤፍራታ
እነዚህ የሴቶች ስሞች ናቸው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ይመልከቱ)

1 Chronicles 2:21

አጠቃላይ መረጃ
በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያሉት ሁሉም ስሞች የወንዶች ስሞች ናቸው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ይመልከቱ)

ወለደችለት
መውለድ

በገለዓድ ምድር
ለቦታው በሰው ስም ስያሜ የሰጡት ሰዎች ናቸው።

1 Chronicles 2:23

ጌሹር … አራም
እነዚህ በአባቶቻቸው ስም የተሰየሙ የሕዝቦች ስሞች ናቸው። አራምን በ1 ዜና 1፡17 እንደተረጎሙት ይተርጉሙ።

ኢያዕርን ከቄናትና
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ይመልከቱ)

ማኪር … ገለዓድ … ኤስሮም … ካሌብ … አሸሑር … ቴቁሔ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ ይመልከቱ)

ኤፍራታ
ይህ የሴት ስም ነው።

ወለደ
ልጁን ወለደ

1 Chronicles 2:25

አጠቃላይ መረጃ
ከዓጣራ በስተቀር በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያሉት ስሞች ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው። ዓጣራ የሴት ስም ነው። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ ይመልከቱ)

1 Chronicles 2:29

አጠቃላይ መረጃ
ከአቢካኢል በስተቀር በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያሉት ስሞች ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው። አቢካኢል የሴት ስም ነው። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ ይመልከቱ)

1 Chronicles 2:34

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ስሞች በሙሉ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ይመልከቱ)

ወለደ
‹‹ልጅ ወለደ››

1 Chronicles 2:36

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ስሞች በሙሉ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ይመልከቱ)

1 Chronicles 2:39

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ስሞች በሙሉ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ይመልከቱ)

1 Chronicles 2:42

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ስሞች በሙሉ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የኬብሮንም አባት ... የራም አባት ... የዮርቅዓምን አባት ... የቤት ጹር አባት
አንዳንድ ቅጂዎች “የኬብሮን ነገድ መስራች... የራሀም ነገድ መስራች ፣ የዮራም ነገድ መስራች... የሻማም ነገድ መስራች በማለት ይላሉ።

1 Chronicles 2:45

አጠቃላይ መረጃ
ከዔፋ በስተቀር ሁሉም ስሞች የወንዶች ስሞች ናቸው ። ዔፋ የሴት ስም ነው። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ይመልከቱ)

1 Chronicles 2:48

አጠቃላይ መረጃ
ከማዕካ እና ዓክሳ በስተቀር ሁሉም ስሞች የወንዶች ስሞች ናቸው። ማዕካ እና ዓክሳ የሴት ስም ነው። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ይመልከቱ)

ደግሞም ወለደች
ደግሞም ወለደች

ሆር ... ሦባል ... ሦባል... ሐሬፍ
እነዚህ ስሞች በሙሉ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ይመልከቱ)

ኤፍራታ
ይህ ስም የሴት ስም ነው። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ይመልከቱ)

የቂርያትይዓሪም አባት ... የቤተ ልሔም አባት ... የቤት ጋዴር አባት
እነዚህ ሁሉ የከተሞች ስሞች ናቸው ። ከተሞቹ በከተሞቹ ለሚኖሩት ሰዎች መገለጫዎቻቸው ናቸው ። አት: የቂርያትይዓሪም መስራች ... የቤተ ልሔም መስራች ... የቤት ጋዴር መስራች (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ ይመልከቱ)

1 Chronicles 2:52

አጠቃላይ መረጃ
(ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ይመልከቱ)

ለቂርያትይዓሪም አባት ሦባል
ሦባል የሰውየው ስም ነው፣ ቂርያትይዓሪም የከተማው ስም ነው። ይህን በ1 ዜና 2:50 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ይመልከቱ)

መናሕታውያ ... ይትራው፣ ሹማታ .. ፉታውያን, ሹማታውያን... ሚሸራውያን... ጾርዓውያንና ... ኤሽታኦላውያን
እነዚህ የጎሳዎች ስሞች ናቸው።

1 Chronicles 2:54

ሰልሞን ... ሐማት
የሰዎች ስሞች (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ይመልከቱ)

ቤተ ልሔም ... ዓጣሮትቤትዮአብ ... ያቤጽ
የከተሞ ስሞች (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ይመልከቱ)

ነጦፋውያን, **Atroth Beth Joab** ... መናሕታውያን... ጾርዓውያን... ቲርዓውያን፥, ሺምዓታውያን፥, እና ሡካታውያን... ቄናውያን... ሬካብ
እነዚህ የነገዶች ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 ዳዊት በኬብሮን ሳለ የወለዳቸው ወንዶች ልጆች እነዚህ ነበሩ፤ ከኢይዝራኤላዊቷ ከአኪናሆም የተወለደው የብኩር ልጁ አምኖን፣ሁለተኛው ከቀርሜሎሳዊቷ
ከአቢግያ የተወለደው ዳንኤል፣ 2 ሦስተኛው ከጌሹር ንጉሥ ከተማይ ልጅ ከመዓካ የተወለደው አቤሴሎም፣አራተኛው የአጊት ልጅ አዶንያስ፣ 3 አምስተኛው
ከሚስቱ ከዔግላ የተወለደው ይትረኃም። 4 እነዚህ ስድስቱ የተወለዱት ዳዊት በኬብሮን ሆኖ ሰባት ዓመት ተኩል በገዛበት ጊዜ ነበር። ዳዊት በኢየሩሳሌም ሠላሳ
ሦስት ዓመት ነገሠ፤ 5 በዚያም የወለዳቸው ልጆች እነዚህ ነበሩ፤ ሳሙስ፣ ሶባብ፣ ናታን፣ ሰለሞን፣ እነዚህ አራት ወንዶች ልጆች ከዓሚኤል ልጅ ከቤርሳቤህ
የተወለዱ ናቸው። 6 እንዲሁም ሌሎች ወንዶች ልጆች ነበሩት፤ ስማቸውም ኢያቤሐር፣ ኤሊሱዔ፣ ኤሊፋላት፣ 7 ኖጋ፣ ናፌቅ፣ ያፍያ፣ 8 ኤሊሳማ፣ ኤሊዳሄ፣
ኤሊፋላት ይባላል፤ ባጠቃላይ ዘጠነኛ ነበሩ። 9 ከቁባቶቹ ከወለዳቸው ወንዶች ልጆች ሌላ እነዚህ ሁሉ ልጆቹ ነበሩ፤ እነዚህም ትዕማር የምትባል እኅት
ነበረቻቸው። 10 የሰሎሞን ልጅ ሮብዓም ነበረ፤ የሮብዓም ልጅ አቢያ፣ የአቢያ ልጅ አሳ፣ የአሳ ልጅ ኢዮሣፍጥ፣ 11 የኢዮሣፍጥ ልጅ ኢዮራም፣ የኢዮራም ልጅ
አካዝያስ፣ የአካዝያስ ልጅ ኢዮአስ፣ 12 የኢዮአስ ልጅ አሜስያስ፣ የአሜስያስ ልጅ ዓዛርያስ፣ የዓዛርያስ ልጅ ኢዮአታም፣ 13 የኢዮአታም ልጅ አካዝ፣ የአካዝ ልጅ
ሕዝቅያስ፣ የሕዝቅያስ ልጅ ማናሴ፣ 14 የምናሴ ልጅ አሞጽ፣ የአሞጽ ልጅ ኢዮስያስ፣ 15 የኢዮስያስ ወንዶች ልጆች፣ በኩሩ ዮሐናን በኩሩ ዮሐናን፣ ሁለተኛ
ልጁ ኢዮአቄም፣ ሦስተኛ ልጁ ሴዴቅያስ፣ አራተኛ ልጁ ሰሎም። 16 የኢዮአቄም ዘሮች፤ ልጁ ኢኮንያ፣ ልጁ ሴዴቅያስ። 17 የምርኮኛው የኢኮንያን ዘሮች፣ ልጁ
ሰላትያል፣ 18 መልኪራም፣ ፈዳያ፣ ሼናጻር፣ ይቃምያ፣ ሆሻማ፣ ነዳብያ። 19 የፈዳያ ወንዶች ልጆች፤ ዘሩባቤል ወንዶች ልጆች፥ ሜሱላም፣ ሐናንያ፣ እኅታቸው
ሰሎሚት ትባላለች። 20 ሌሎችም አምስት ልጆች ነበሩ፤ እነርሱም ሐሹባ፣ ኦሄል፣ በራክያ፣ ሐሳድያ፣ ዮሻብሐሴድ። 21 የሐናንያ ዘሮች፤ ፈላጥን፣ የአብድዩና
የሴኬንያ ወንዶች። 22 የሴኬንያ ዘሮች፤ ሸማያና ወንዶች ልጆቹ፤ ሐሙስ፣ ይግአል፣ ባሪያሕ፣ ነዓርያ፣ ሻፋጥ፣ ባጠቃላይ ስድስት ነበሩ። 23 የነዓርያ ወንዶች
ልጆች፤ ኤልዩዔናይም 24 ወንዶች ልጆች፤ ሆዳይዋ፣ ኤልያሴብ፣ ፌልያ፣ ዓቁብ፣ ዮሐናን፣ ደላያ፣ ዓናኒ፤ ባጠቃላይ ሰባት ናቸው።

---

1 Chronicles 3:1

ዳዊት
ዳዊት የእሰይ ልጅ ሲሆን ከይሁዳ ነገድ ነበር። (1 ዜና 2፡15ን፡ ይመልከቱ)

ኢኖም ... አቢግያ፥... መዓካ፥... ሀጊት ... አቢጣል፥... ዔግላ
እነዚህ በሙሉ የሴቶች ስሞች ሲሆኑ የዳዊት ሚስቶች ነበሩ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ይመልከቱ)

ከተልማይ... ሰፋትያ ... ይትረኃም
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ይመልከቱ)

ዳንኤል
ይህ ሰው ከእስራኤላዊው ነብይ ጋር አንድአይነት ስም አለው ነገር ግን ሌላ ሰው ነው።

1 Chronicles 3:4

ለሰባት አመት ከስድስት ወር የነገሰበት ቦታ
ይህ ብቻው እንደ ተናጠል አረፍተ ነገር መተርጎም ይችላል። አት: “ዳዊት በዚይ ሰባት አመት ከስድስት ወር ነገሰ።“

ሰላሳ ሶስት አመት
“33 አመታት” (ቁጥሮች፡ ይመልከቱ)

ዓሚኤል... ሳሙስ፥... ሶባብ፥... ናታን፥
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ይመልከቱ)

1 Chronicles 3:6

አጠቃላይ መረጃ
ከትዕማር በስተቀር በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያሉት ስሞች ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው። ትዕማር የሴት ስም ነው። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ ይመልከቱ)

1 Chronicles 3:10

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ነገስታት የሆኑ የዳዊት የዘር ሀረግ ዝርዝር መጀመሪያ ነው። በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያሉት ስሞች ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው።የሰሎሞንም ልጅ ሮብዓም ነበረ. የሮብአም ልጁ አቢያ ሰሎሞን ከአንድ በላይ ልጅ ነበረው። ይህ እውነት በዝርዝሩ ውስጥ ያሉትን ሌሎች ወንዶችም ይመለከታል። አት: “ሰሎሞን የሮብዓምን አባት ነበረ። ሮብዓም የአብያ አባት ነበረ”

ዓዛርያስ፥
ይህ ለዖዝያን ሌላ ስም ሲሆን፣ ይበልጥ የታወቀው ስም ነው። ተርጎሚዎች ለዚህ ንጉስ ሁሉጊዜ “ዖዚያን” ለመጠቀም መወሰን ይችላሉ።

1 Chronicles 3:13

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ነገስታት የሆኑ የዳዊት ዘሮችን ዝርዝር ይቀጥላል። በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያሉት ስሞች ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው። እነዚህን አረፍት ነገሮች በ1 ዜና 3:10 ይስሯቸው።

1 Chronicles 3:15

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ነገስታት የሆኑ የዳዊት ዘሮችን ዝርዝር ይቀጥላል። በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያሉት ስሞች ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው። እነዚህን አረፍት ነገሮች በ1 ዜና 3:10 ይስሯቸው።

1 Chronicles 3:17

አጠቃላይ መረጃ
በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያሉት ስሞች ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው። (የስሞችን አተረጓጎም ፡ይመልከቱ)

ኢኮንያን
አንዳንድ ቅጂዎች “ኢኮንያን,” ይላሉ ይህም የ “ኢኮንያን” ተለዋጭ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የምርኮኛውም
በግዞት ስለ ተወሰደ ይህ ለዮአኪን የተሰጠ ርዕስ ሊሆን ይችላል። ሆኖም አንዳንድ ቅጂዎች ቃሉን እንደ “አሲር ፣” እንደ የአንዱ ልጅ ስም ይመለከቱታል።

1 Chronicles 3:19

አጠቃላይ መረጃ
ከሰሞሚት በስተቀር በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያሉ ስሞች በሙሉ የወንዶች ስሞች ናቸው። ሰሞሚት የሴት ስም ነው። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

አብድዩ
ይህ ሰው ከነቢዩ አብድዩ ስም ጋር ተመሳሳይ ነው ነገር ግን ሌላ ሰው ነው። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

ተጨማሪ ዘሮቻቸው አርናን, አብድዩ, እና ሴኬንያ
ዕብራይስጡ በጣም ግልፅ ስላልሆነ የተለያዩ ቅጂዎች እነዚህ ሕዝቦች በመካከላቸው የተለያየ ግንኙነት ይሰጧቸዋል።

1 Chronicles 3:22

አጠቃላይ መረጃ
በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያሉት ስሞች ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 የይሁዳ ዘሮች፤ ፋሬስ፣ ኤስሮም፣ ከርሚ፣ ሆር፣ ሦባል። 2 የሦባል ልጅ ራያ ኢኤትን ወለደ፤ ኢኤትደግሞ አሑማይንና ላሃድን ወለደ፤ እነዝዝዚህ የጾርዓውያን
ጎሣዎች ናቸው። 3 የኤጣም ወንዶች ልጆች እነዚህ ናቸው፤ ኢይዝራኤል፣ ይሽማ፣ ይደባሽ። እኅታቸው ሃጽሌልፎኒ ትባላለች። 4 ፋኑኤል ጌዶርን ወለደ፤ ኤጽር
ደግሞ ሑሻ ምን ወለደ። እነዚህ የኤፍራታ የበኩር ልጅና የቤተልሔም አባት የሆነው የሆር ዘሮች ናቸው። 5 የቴቁሔ አባት አሸሑር፣ ሔላና ነዕራ የተባሉ ሁለቱ
ሚስቶች ነበሩት። 6 ነዕራም አሑዛምን፣ ኦፌርን፣ ቴምኒን፣ አሐሽታሪን ወለደችለት፤ የነዕራ ዘሮች እነዚህ ነበሩ። 7 የሔላ ወንዶች ልጆች፤ ዼሬት፣ ይጽሐር፣ ኤትናን
ናቸው። 8 የቆጽ ወንዶች ልጆች ደግሞም ዓኑብ፣ ጾቤባና፣ የሃሩም ናቸው። 9 ያቤጽ ከወንድሞቹ ይልቅ የተከበረ ሰው ነበረ፤ እናቱም "በጣር የወለድድኩት"
ስትል ስሙን ያቤጽ አለችው። 10 ያቤጽም፣ "አቤቱ፤ እንድትባርከኝ፣ ግዛቴንም እንድታሰፋልኝ እለምንሃለሁ፣ እጅህ ከእኔ ጋር ትሁን፣ ከሥቃይና ከጉዳትም
ጠብቀኝ" በማለት ወደ እስራኤል አምላክ ጮኸ።እግዚአብሔርም የለመነውን ሰጠው። 11 የሹሐ ወንድም ክሉብ ምሒርን ወለደ፤ ምሒርን ወለደ፤ ምሒርም
ኤሽቶን ወለደ፤ 12 ኤሽቶን ቤትራፋንና ፋሴሐን ወለደ፤ የዒርናሐሽን ከተሞች የቁረቁረ እርሱ ነው። እነዚህ የሬካ ሰዎች ናቸው። 13 የቄኔዝ ወንዶች ልጆች፤
ሐታት፣ መዖኖታይ። 14 መዖታይ ደግሞ ዖፍራን ወለደ። ሠራያ የኢዮአብ አባት ሲሆን፣ ኢዮአብ ጌሐራሺምን ወለደ፤ የእደ ጥበብ ባለ ሙያዎች ስለ ነበሩ ይህ
ስም ተሰጣቸው። 15 የዮፎኔ ልጅ የካሌብ ወንዶች ልጆች፤ ዒሩ፣ ኤላ፣ ነዓም። የኤላ ልጅ ቄኔዝ። 16 የይሃልኤል ወንዶች ልጆች፤ ዚፍ፣ ዚፋ፣ ቲርያ፣አሣርኤል።
17 የዕዝራ ሜሬድ፣ዔፌር፣ያሎን። ከሜሬድ ሚስቶች እንዲቱ ማርያምን፣ ሽማይንና የኤሽትሞዓን አባት ፅሽባን ወለደች። 18 አይሁዳዊት ሚስቱም የጌዶርን አባት
የሬድን፣ የጆኮን አባት ሔቤርን፣ የዛኖዋን አባት ይቁቲኤልን ወለደች፤ እነዚህም ሜሬድ ያገባት የፈርዖን ልጅ የቢትያ ልጆች ናቸው። 19 የሆዲያ ሚስት የነሐም
እኅት ወንዶች ልጆች፤ የገርሚው የቅዒላ አባት፣ ማዕካታዊው ኤሽትሞዓ። 20 የሺሞን ወንዶች ልጆች፤ አምኖን፣ ሪና፣ ቤንሐናን፣ ቲሎን። የይሺዒ ዘሮች፤ ዞሔትና
ቤንዞሔት። 21 የይሁዳ ልጅ የሴሎም ወንዶች ልጆች፤ የሌካ አባት ዔር፣ የመሪሳና በቤት አሸቤዓ የበፍታ ጨርቅ ሠሪ የሆኑት ጎሣዎች አባት ለዓዳ፣ 22 ዮቂም፣
የኮዜባ ሰዎች፣ ኢዮአስ፣ ሞዓብን የገዛ ሣራፍና ያሹቢሌሔም። ታሪካቸውም ጥንታዊነት ያለው ነው። 23 ሰዎቹ ነበጣዒምና በጋዴራ የሚቀመጡ ሸክላ ሠሪዎች
ነበሩ፤ በዚያም በመቀመጥ ለንጉሡ ሸክላ ይሠሩ ነበር። 24 የስምዖን ዘሮች፤ ነሙኤል፣ ያሚን፣ ያሪን፣ ዛራ፣ ሳኡል፣ 25 ሰሎም የሳኡል ልጅ ነው፤ መብሳም
የሰሎም ልጅ ነው፤ ማስማዕ ደግሞ የመብሳም ልጅ ነው። 26 የማስማዕ ዘሮች ልጁ ሃሙኤል፣ ልጁ ዘኩር፣ ልጁ ሰሜኢ። 27 ሰሚኤ ዐሥራ ስድስት ወንዶችና
ስድስት ሴቶች ልጆች ነበሩት፤ ወንድሞቹ ግን ብዙ ልጆች አልነበሯቸው፤ ስለዚህ ጎሣቸው በሙሉ እንደ ይሁዳ ሕዝብ ብዙ አልነበረም። 28 የኖረባችውም
ቦታዎች እነዚህ ናቸው። ቤርሳቤህ፣ ሞላዳ፣ ሐጻርሹዓል፣ 29 ቢልሃ፣ ዔጼም፣ ቶላድ፣ 30 ቤቱኤል፣ ሔርማ፣ ፊቅላግ፣ 31 ቤትማርካቦት፣ ሐጸርሲሲም፣ ቤትቢሪ፣
ሸዓራይም፣ እስከ ዳዊት ዘመነ መንግስት ድረስ የኖሩት በእነዚህ ከተሞች ነው። 32 በአካባቢያቸው የሚገኙት ወንደሮች ደግሞ ኤጣም፣ ዓይን፣ ሬሞን፣ ቶኬን፣
ዓሻን የተባሉ አምስት ከተሞች ናቸው፤ 33 በእነዚህ ከተሞች ዙሪያ በአል የሚዝችልቁ መንደሮች ነበሩ፤ መኖሪያቸው በዚሁ ሲሆን፤ የትውልድ መዝገብም
አላቸው። 34 ሞሾብብ፣ የምሌክ፣ የአሜስያስ ልጅ ኢዮስያስ፣ 35 ኢዮኤል፣ የዮሺብያ ልጅ፣ የሠራያ የዓጂኤል ልጅ ኢዩ 36 እንዲሁም ኤልዩዔናይ፣ ያዕቆብ፣
ፅሾሐያ፣ ዓሣያ፣ ዓሲዔል፣ ዩሲምኤል፣ በናያስ፣ 37 የሺፊ ልጅ ዚዛ፣ የአሎን ልጅ፣ የይዳያ ልጅ፣ የሺምሪ ልጅ፤ የሸማያ ልጅ፤ 38 እነዚህ ስማቸው ከላይ
የተዘረዘረው ሰዎች የየጎሣቸው መሪዎች ነበሩ፤ የቤተሰባቸው ብዛት እጅግ በጣም እየጨመረ ሄደ፤ 39 እነርሱም ለከብቶቻቸው ግጦሽ ፍለጋ ከሸለቆው
በስተምስራቅ እስካለው እስከ ጌደር መግቢያ ድረስ ዘልቀው ሄዱ። 40 በዚያም ለምለምና ያማረ የግጦሽ ቦታ አገኙ፤ ምድሪቱም ሰፊ፤ ሰላምና ጸጥታ የሰፈነበት
ነበረች። በቀድሞ ቀመን በዚህ ምድር ይኖሩ የነበሩት አንዳንድ የካም ዘሮቼ ናቸው። 41 እነዚህ ስማቸው ከላይ የተዘረዘሩው ወደዚሁ ቦታ የመቱት በይሁዳ ንጉሥ
በሕዝቅያስ ዘመን ነበረ፤ እነርሱም በድንኳኖቻቸው ውስጥ በነበሩበት በካም ወገኖችና በምዑናውያን ላይ አደጋ በመጣል ፈፅመው አላጠፋአቸው፤ ይህም እስከ
ዛሬ ድረስ በግልጽ ይታያል። ለመንጎቻቸው በቂ ግጦሽ ቦታ ስላላገኙ፣ በዚያ መኖር ጀመሩ። 42 ከእነዚሁ አምስት መቶ የሚሆኑ የስምዖን ወገኖች በይሽዒ ልጆች
በፈላጥያ፣ በነዓርያ፣ በረፋያና በዑዝኤል ተመርተው የሴይርን ኩረብታማ አገር ወረሩ። 43 አምልጠው የቀሩትን አማሌቅውያን ፈጅተው እስከ ዛሬ በዚያው
ይኖራሉ።

---

1 Chronicles 4:1

አጠቃላይ መረጃ
ከዚራውያን በስተቀር በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያሉት ሁሉም ስሞች የወንዶች ስሞች ናቸው። ጾርዓውያን ስማቸው ከሚኖሩበት ከጾራ ከተማ የወሰዱ የሰዎች ቡድን ስም ነው። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

1 Chronicles 4:3

ኤጣም ... ጌዶርም... ሑሻም
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

ኢይዝራኤል፥... ይሽማ፥... ይድባሽ፥... ፋኑኤል፥... ኤጽር... ሆር... ኤፍራታ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።(የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

ሃጽሌልፎ
እነዚህ የሴቶቸ ስሞች ናቸው። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

እነዚህ የሆር ልጆች ናቸው
“ጵንኤል እና ኤዘር የሆር ትውልድ ናቸው።” ይህ ወደ ሚቀጥለው ዝርዝር ይጠቁማል።

ኤፍራታ
ይህ የሴት ስም ነው። ይህን በ1 ዜና 2:50 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

1 Chronicles 4:5

አሸሑር... ቴቁሔም
የእነዚህን ወንዶች ስሞች በ1 ዜና 2:24 እንዴት እንደተረጎም ይመልከቱ።

አሑዛም፥... ኦፌር፥... ዼሬት፥ ይጽሐር፥... ኤትናን... ቆጽ... ዓኑብ፥... ጾቤባ፥... አሐርሔል... ሃሩም
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

ቴምኒ፥... አሐሽታሪ
እነዚህ ስሞች እንደ ወንዶች ስሞች ተወስደዋል። ቢሆንም ግን አንዳንድ ቅጂዎች በአሹር ልጆች የተጀመሩ ነገዶች አድርገው ይረዷቸዋል።

ሔላ... ነዕራ
እነዚህ የሴቶቸ ስሞች ናቸው። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወለደ
“ወንዶች ልጆቹን ወለደ”

የሃሩምንም ልጅ የአሐርሔልን ወገኖች ወለደ
አዲስ ዓረፍተ ነገር እዚህ ሊጀመር ይችላል። “ኩዝም የሀሩም ተከታይ ዘር ሆኗል እንዲሁም ከሀሩም ልጅ አሸርኤል የመጡት ነገዶች።

1 Chronicles 4:9

ያቤጽ
ይህ የወንድ ስም ነው። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

አገሬንም አስፋው
“የበለጠ መሬት ስጠኝ”

እጅህም ከእኔ ጋር ትሁን
ሊሆኑ የሚችሉ ፍችዎች የእግዚአብሔር እጅ 1) ለምሪቱ፣ ለኃይሉ ወይም ለጥበቃው ትክክለኛ መግለጫ ነው። አት: “ትመራኛለህ” ወይም “ታበለጽገኛለህ” ወይም “ትጠብቀኛለህ” ወይም 2) ለራሱ የባሕሪ ስም። አት: ከእኔ ጋር ትሆናለህ” (የባህሪ ስም እና Synecdoche: ይመልከቱ)

እግዚአብሔርም የለመነውን ሰጠው
“ጸሎቱ” የሚሉት ቃላት ያቤጽ በጸሎቱ ውስጥ ለጠየቀው ምሳሌያዊ ትርጉም ነው ። አት: - “ያቤጽ የጠየቀውን አደረገለት”

1 Chronicles 4:11

ክሉብ... ሹሐ... ምሒር... ኤሽቶን... ቤትራ ፋንና... ፋሴሐ... ተሒና
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

ተሒና, ዒርናሐሽን አባት
ኢር ናሃሽ ከተማ ሊሆን ይችላል። አት: - “የናሃሽ ከተማ መሥራች የሆነው ታህናን”

ናሃሽ ... ሬካ
እነዚህ የቦታዎች ስሞች ናቸው።

1 Chronicles 4:13

አጠቃላይ መረጃ
ኬን የየፎኒ እና የካሌብ ዘሮች እንደመሆናቸው የቁጥር ድልድይ መፍጠር እና ቁጥር 15ን ከቁጥር 13 ጋር ማዋሃድ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። (ቁጥር ድልድዮች: ይመልከቱ)

ቄኔዝ... ጎቶንያልና ... ሠራያ ... ሐታት ... መዖኖታይ ... ዖፍራን ... ኢዮአብ ... ዮፎኒም ... ዒራ... ኤላ ... ነዓም ... የይሃሌልኤል ... ዚፍ... ዚፋ... ቲርያ... አሣርኤል
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

የጌሃራሽምን ... እነርሱም ጠራቢዎች ነበሩ
ጌሃራሽምን “የሸለቆ ጠራቢዎች” ማለት ነው። ይህ ከማብራሪያ ጋር ግልፅ ሊደረግ ይችላል። አት: “ጌሃራሽምን፣ ‘የጠራቢዎች ሸለቆ’ ማለት ነው። እንዲህ ተብሎ የተጠራው ሕዝቦቹ ጠራቢዎች ስለነበሩ ነው።

ጠራቢዎች
ነገሮችን በመፍጠር ወይም በመገንባቱ የተካኑ ሰዎች

1 Chronicles 4:19

ሆዲያ ... ነሐም ... ቅዒላ ... ኤሽትሞዓ ... ሸሞንም ... አምኖን... ሪና... ቤንሐናን... ቲሎን ... ይሽዒም ... ዞሔትና ... ቢንዞሔት
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

ገርሚው
ከጋር ሰዎች ቡድን የሆነ ሰው

ማዕካታዊው
ማካ እንዲሁም ማካት ተብሎ ከሚጠራ ቦታ የሆነ ሰው (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

1 Chronicles 4:21

ሴሎም ... ዔር... ለዓዳ... ዮቂም... ኢዮአስ... ሣራፍ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

በፍታ የሚሠሩ
ከተቀጠቀጠ ሸንበቆ ልብስ የሚሰሩ ሰዎች (የማይታወቁትን ይተርጉሙ: ይመልከቱ)

ሸክላ ሠራተኞች
ዕቃዎችን ከሸክላ የሚሠሩ ሰዎች

ሌካ ... መሪሳ ... ቤትአበሳ ... ኮዜባ ... ያሹቢሌሔም ... በነጣዒም ... ጋዴራ
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው።

1 Chronicles 4:24

ነሙኤል... ያሚን... ያሪን... ዛራ... ሳኡል... ሰሎም... መብሳም... ማስማዕ... ሃሙኤል... ዘኩር ... ሰሚያ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

ዛኩር የልጅ ልጁ
የሚስማ የልጅ ልጅ

የልጅ ልጅ
የሚስማ የልጅ ልጅ ልጅ

1 Chronicles 4:27

አስራስድስት ወንድ ልጆችና ስድስት ሴቶች ልጆች
“16 ወንዶች ልጆች እና 6 ሴት ልጆች”

ሞላዳ... አዛርሰኦል
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው።

1 Chronicles 4:29

አጠቃላይ መረጃ
የስምኦን ልጆች የኖሩባቸው ከተሞች ዝርዝር ይቀጥላል ።

ቢልሃ... ዔጼም... ቶላድ... ቤቱኤል... ሔርማ... ጸቅላግ... ቤትማርካቦት... ሐጸርሱሲም... ቤትቢሪ... ሸዓራይም
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው።

1 Chronicles 4:32

አጠቃላይ መረጃ
የስምኦን ልጆች የኖሩባቸው ከተሞች ዝርዝር ይቀጥላል ።

ኤጣም... ዓይን... ሬሞን... ቶኬን... ዓሻን
እነዚህ የመንደሮች ስሞች ናቸው።

የነበሩ መንደሮቻቸውም
በዋና ከተማው አቅራቢያ ነገር ግግ ከውጭ የነበሩ መንደሮች

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በኣልም
ይህ የከተማ ስም ነው።

1 Chronicles 4:34

ምሾባብ፥... የምሌክ፥... ኢዮስያ፥... አሜስያስ... ኢዮኤል... ኢዩ... ዮሺብያ... ሠራያ ... ዓሢኤል... ኤልዮዔናይ... ያዕቆባ... የሾሐያ... ዓሣያ... ዓዲዔል... ዩሲምኤል... በናያስ... ዚዛ... ሺፊ... አሎን... ይዳያ... ሺምሪ... ሸማያ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

እነዚህ በስም የተጠቀሱት መሪዎች ነበሩ።
‹‹እነዚህ ወንዶች መሪዎች ነበሩ።››

ነገዶቻቸው በከፍተኛ ሁኔታ ጨምረዋል
ጎሳው በጎሳው ውስጥ ላሉት ሰዎች ትክክለኛ መግለጫ ነው። አት: “በየወገናቸው ያለው የሕዝብ ብዛት እጅግ ጨምሯል”

1 Chronicles 4:39

ጌዶር
ይህ የከተማ ስም ነው።

ለእንስሶቻቸው መሰማሪያ ቦታ
መንጎቻቸውን ሣር መመገብ የሚችሉበት መሬት ነው

የተትረፈረፈ እና ጥሩ የግጦሽ መስክ
“ለእንስሶቻቸው ብዙ ጥሩ ምግብ ያላቸው የግጦሽ መሬቶች”

ከካም
የካም ዘሮች የሆኑ የሕዝቦች ስብስብ

ምዑናውያንን
የሕዝቦች ስብስብ አት: “የማአን ዘሮች”

1 Chronicles 4:42

አምስት መቶ ወንዶች
“500 ወንዶች”

ፈላጥያ... ነዓርያ... ረፋያ... ዑዝኤል ... ይሸዒ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

ያመለጡትንም የአማሌቃውያንን ቅሬታ
“የቀሩት አማሌቃውያን መመጸኛዎች” መመጸኛዎች ከአገራቸው እንዲወጡ የተገደዱ ሰዎች

እስከ ዛሬ ድረስ
ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ።” ይህ የሚያመለክተው ደራሲው ይህንን ዘገባ የጻፈበትን ቀን ነው ::

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 5

1 የእስራኤሌ በኩር ልጅ የሮቤል ልጆች፤ ሮቤል የበኩር ልጅ ቢሆንም፤ የአባቱን መኝታ ስላረከሰ፤ የበኩርናው መብቱ ለእስራኤል ልጅ ለዮሴፍ ልጆች
ተሰጥቶአል። ከዚህም የተነሣ ትውልዱ የበኩርነቱን ተራ ይዞ ሊቁጥል አልቻለም። 2 ይሁዳ ከወንድሞቹ ይልቅ ብርቱ ነበረ፤ ገዥ የወጣው ከእርሱ ቢሆንም፣
የበኩርነት መብቱ የተላለፈው ለዮሴፍ ነበረ። 3 የእስራኤል የበኩር ልጅ የሮቤል ወንዶች ልጆች፤ ሄኖኅ፣ ፋሉሶ፣ አስሮን፣ ከርሚ ነበሩ። 4 የኢዮኤል ዘሮች ልጁ
ሸማያ፣ ልጁ ጎግ፣ ልጁ ስሜኢ፣ 5 ልጁ ሚካ፣ ልጁ ራያ፣ ልጁ ቢኤል፣ 6 የአጆር ንጉስ ቴልጌል ቴልፌልሶር ማኮር የወሰደው ልጅ ብኤራ ነበሩ። 7 የቤተሰቡ
የዘር ትውልድ በየጎሣ በየጎሣው ሲቁጠር እንደሚከተለው ነው፤ የጎሣ አለቃ የሆነው ኢዮኤል፣ ዘካርያስ፣ 8 የኢዮኤል ልጅ፣ እነዚህ ከአሮዔር እስከ ናባውና እስከ
በኣልሜዎን ድረስ በሚገኘው ምድር ላይ ሰፈሩ። 9 ከብቶቻቸው በገለዓድ ምድር በዝተው ስለነበር በምስራቅ በኩል ወደ ኤፍራጥስ ወንዝ እስከ ምድረ በዳው
ዳርቻ ድረስ የሚገኘውን ምድር ያዙ። 10 በሳኦልም ዘመነ መንግሥት በእጃቸው ተመትተው ድል ከተደረጉት አጋራውያን ጋር ተዋጉ፤ በመላው የገለዓድ ምሥራቃዊ
ክፍል የሚገኙትን መኖሪያዎቻቸውን ያዙ። 11 የጋድ ነገድ ደግሞ ከእነርሱ ቀጥሎ እስከ ሰልካ ድረስ በሚገኘው በባሳን ምድር ኖሩ፤ 12 አለቃው ኢዮኤል፣
ሁለተኛው ሳፋም ከዚህም ያናይና ሰፋጥ ሆነው በባሳን ተቀመጡ። 13 ቤተ ዘመዶቻቸውም በየቤተሰቡ እነዚህ ነበሩ፤ ሚካኤል፣ ሜሱላም፣ ሳባ፣ የራይ፣ ያካን፣
ዙኤ፣ ኦቤድ፣ ባጠቃላይ ስባት ነበሩ። 14 እነዚህ ደግሞ የቢዝ ልጅ፣ የዬዳይ ልጆች፣ ኦቤድ፣ የኢዬሳይ ልጅ፣ የሚካኤል ልጅ፣ የገለዓድ ልጅ፣ የኢዳይ ልጅ፣
የዑሪ ልጅ፣ የሑሪ ልጅ፣ የአቢካኢል ልጆች ናቸው። 15 የቤተሰባቸው አለቃ የኑጊ ልጅ፣ የአብዲኤል ልጅ አሒ ነበረ። 16 እነዚህም በገለኣድ፣ በባሳንና እስከ
ዳርቻዋ በሚገኙት መንደሮች እንዲሁም በሳሮን በሚገኙ የግጦሽ ስፍራዎች ሁሉና ከዚያም ወዲያ አልፈው ተቀመጡ። 17 እነዚህ ሁሉ ትውልድ በመዝገብ
የሰፈሩት በይሁዳ ንጉሥ በኢዮአታምና በእስራኤል ንጉሥ በኢዮርብዓም ዘመነ መንግሥት ነው። 18 የሮቤል፣ የጋድና፣ የምናሴ ነገድ እኩሌታ አርባ አራት ሺህ
ብቁ የጦር ሰዎች ነበሩአቸው። እነርሱም ጋሻ መያዝ፣ ሰልፍ መምዘዝና ቀስት መሳብ የሚችሉ ጠንካራና በውጊያ የሠለጠኑ ናቸው። 19 እነዚህም በአጋራውያን፣
በኢጡር፣ በናፌስ፣ በናዳብ ላይ ዘመቱ። 20 በጦርነቱም ላይ ወደ እግዚአብሔር ጮኸው ስለ ነበር፣ በውጊያው ረዳቸው፣ አጋራው ያንንና የጦር አጋሮቻቸውን
ሁሉ አሳልፎ ሰጣቸው፤ ስለ ታመኑበትም ፀሎታቸውን ሰማ። 21 የአጋራውያንንም እንስሶች ማረኩ፤ እነዚህም አምሳ ሺህ ግመሎች፣ 250 000 በጎችና ሁለት
ሺህ አህዮች ነበሩ። እንዲሁም 100 000 ሰው ማረኩ። 22 ውጊያው የእግዚአብሔር ስለነበር ሌሎችም ብዙ ሰዎች ተገደሉ። እስከ ምርኮ ጊዜ ምድሪቱ
በእጃቸው ነበረች። 23 የምናሴ ነገድ እኩሌታ ህዝብ ቁጥር ብዙ ነበረ፣ እነርሱም ከባሳን ጀምሮ እስከ በኣልአርሞንዔም ድረስ ባለው ምድር ሰፈሩ፤ ይህም እስከ
ሳኔር አርሞንዔም ተራራ ድረስ ማለት ነው። 24 የየቤተሰቡ አለቆች እነዚህ ነበሩ፤ ዔፌር፤ ይሽዒ፣ ኤሊኤል፣ ዓዝርኤል፣ ኤርምያ፣ ሆዳይዋ፣ ኢያድኤ፤ እነዚህ ጀግና
ተዋጊዎች የታወቁ ሰዎችና የየቤተሰባቸው አለቆች ነበሩ። 25 ይሁን እንጂ ለአባቶቻቸው አምላክ ታማኞች አልሆኑም፤ እግዚአብሔር ከፊታቸው ያጠፋቸው
የምድሪቱን ከሕዝብ አማልክት በማምለክ አመነዘሩ 26 ስለዚህ የእስራኤል አምላክ የአሦርን ንጉሥ የፎሐት መንፈስ ይኸውም የቴልጌል ቴፌልሶርን መንፈስ
አነሣሥቶ የሮቤልን፣ የጋድንና፣ የምናሴን ነገድ እኩሌታ ማርኮ እንዲወሰድ አደረገ። እነዚህንም ወደ ጎዛን ወንዝ ዳርቻ አፈለሳቸው፤ እነርሱም እስከ ዛሬ ድረስ
በዚያ ይገኛሉ።

---

1 Chronicles 5:1

የሮቤል
“እንዲሁም” የሚለው ቃል ከትውልዶች ዝርዝር ወደ ወደ ሮቤል ታሪካዊ ዳራ መረጃ ለመሸጋገር እንዲያገለግል የገባ ነው።

ነገር ግን ... ብኩርናው ለእስራኤል ልጅ ለዮሴፍ ልጆች ተሰጠ
ይህ በገባሪ ቅርጽ ሊቀመጥ ይችላል። አት: “ነገር ግን እስራኤል የሮቤልን የብኩርና መብት ለሌላው የእስራኤል ልጅ ለዮሴፍ ልጆች ሰጡ”

የአባቱን ምንጣፍ ስላረከሰ
ይህ ስለ ሮቤል ከአባቱ ሁለተኛ ሚስት ጋር ስለ መተኛት ለመናገር ለስላሳ መንገድ ነው። መደብ አንድ ወንድና ሚስቱ አብረው የሚኙበት ቦታ ነው።

ትውልዱ ግን ከብኩርና ጋር አልተቈጠረም
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊገለጽ ይችላል። አት: “ስለዚህ የቤተሰብ ታሪክ ዝርዝሩ ሮቤልን የበኩር ልጅ አያደርገውም” (ገባሪ እና ተገባሪ: ይመልከቱ)

ሄኖኅ... ፈሉሶ... አስሮን... ከርሚ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

1 Chronicles 5:4

ኢዮኤል... ሸማያ... ጎግ... ሰሜኢ... ሚካ... ራያ... ቢኤል... ብኤራ... ቴልጌልቴልፌልሶር
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

1 Chronicles 5:7

በየወገናቸው በተቈጠረ ጊዜ
ይህ አዲስ ዓረፍተ ነገር ሊጀምር ይችላል- “በትውልድ ሐረጉ መዝገቦቻቸው እንደ... ይመዘግባቸዋል

የትውልዶቻቸው መዝገብ
በቤተሰብ ውስጥ ያሉ ሰዎች እርስ በእርስ እንዴት እንደሚዛመዱ የሚያሳዩ መዛግብቶች

ኢዮኤል... ዘካርያስ... ቤላ... ዖዛዝ... ሸማዕ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። አሮዔር... ናባው ... በኣልሜዎን እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው።

1 Chronicles 5:10

አጋራውያን
ይህ የሰዎች ቡድን ስም ነው።

በአጋራውያን ድንኳን አደሩ በገለዓድ ምሥራቅ በኩል ባለው አገር ሁሉ በድንኳኖቻቸው ተቀመጡ
ድንኳኑ ለሚኖሩበት ሕዝብ ሲንዶቼ ነው። አት: - “የሐጋራውያንን ምድር ሁሉ እና ሕንፃዎችን ሁሉ ወሰዱ” ወይም “በሐጋራውያን ግዛት ሁሉ ይኖሩ ነበር”

1 Chronicles 5:11

ሰልካ
ይህ የከተማ ስም ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ኢዮኤል... ሳፋም... ያናይ... ሳፋጥ ... ሚካኤል... ሜሱላም... ሳባ... የራይ... ያካን... ዙኤ... ኦቤድ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

1 Chronicles 5:14

አቢካኢል... ዑሪ... ዩራ ... ገለዓድም... ሚካኤል ... ኢዬሳይ... ዬዳይ... ቡዝ... ኢህ ... አብዲኤል... ጉኒ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

1 Chronicles 5:16

ኖሩ
“የጋድ ነገድ ይኖር ነበር”

መሰምርያዎች
እንስሳት ሣር የሚመግቡባቸው አካባቢዎች

እነዚህ ሁሉ በትውልድ ሐረግ መዝገብ ተዘርዝረዋል
ይህ በገባሪ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። አት: “የዘር ሐረግ መዝገቦች ሁሉንም ዘርዝረዋል” ወይም “የቤተሰባቸው የትውልድ ሐረግ መዝገቦች ሁሉንም ዘርዝረዋል”

እነዚህ ሁሉ
ይህ ከቀደሙት ሰዎች መካከል ምን ያህል እንደሚጠቅስ ግልፅ አይደለም።

1 Chronicles 5:18

ሮቤል
ይህ ከሮቤል ለሆነው ነገድ መጠሪያ ነው።

ጋድ
ይህ ከጋድ ለሆነው ነገድ መጠሪያ ነው።

44,760 ወታደሮች
“አርባ አራት ሺህ ሰባት መቶ ስድሳ ወታደሮች”

ጋሻና ሰይፍ የሚይዙ፥ ቀስተኞችም
ወታደሮቹ በተሸከሙት መሣሪያ በጦርነት ረገድ የተካኑ ናቸው። አት: - “ሁሉም በጦር ሜዳ በጥሩ እንዲዋጉ የሰለጠኑ”

አጋራውያን... ኢጡር... ናፌስ... ናዳብ
እነዚህ የሕዝቦች ስሞች ናቸው።

1 Chronicles 5:20

ወደ እግዚአብሔር ጮኸዋልና
“እስራኤላውያን እግዚአብሄር እንዲረዳቸው ፀለዩ”

እንስሶቻቸውን ያዙ
“እስራኤላውያን አጋራውያን እንስሶች ያዙ”

አምሳ ሺህ ግመሎች
“50,000 ግመሎች”

250,000 በጎች
ሁለት መቶ አምሳ ሺህም በጎች

ሁለት ሺህም አህዮች
“2,000 አህዮች”

100,000 ወንዶች
“ከሰዎችም መቶ ሺህ”

ጦርነቱ ከእግዚአብሄር ነበረ
በጦርነት ውስጥ የእግዚአብሔር እገዛ ጦርነቱን ያመጣው እሱ እንደሆነ አዘጋገቡ ያሳያል።AT: “እግዚአብሔር ስለረዳቸው”

1 Chronicles 5:23

በኣልአርሞንዔም... ሳኔር
እነዚህ የተራሮች ስሞች ናቸው።

ዔፌር፥... ይሽዒ፥... ኤሊኤል፥... ዓዝርኤል፥... ኤርምያ፥... ሆዳይዋ፥... ኢያድኤል
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

የአባቶች ቤቶች
በተለያዩ ቤቶች የሚኖሩ ዝምድና ርቀት ያለው ዝምድና ያላቸው ቤተሰቦች፣ ይህን ‹ጎሳ› ይላቸዋል UDB

1 Chronicles 5:25

ፑል ... ቴልጌልቴልፌልሶር
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

ሮቤል ... ጋድ
x

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 6

1 የሌዊ ወንዶች ልጆች፤ ጌድሶን፣ቀዓት፣ሜራሪ፣ 2 የቀዓት ወንዶች ልጆች፤እንበረም፣ ይሰዓር፣ኬብሮን፣ዑዝኤል። 3 የእምበረም ልጆች፤ አሮን፣ሙሴ፣ማርያም። የአሮን ወንዶች ልጆች፤ናዳብ፣አብዮድ፣አልዓዛር፣ኢታምር። 4 አልዓዘር ፊንሐስን ወለደ፤ ፊንሐስ አቡሲን ወለደ፤ 5 አቢሲ ኦዚን ወለደ፤ 6 ኦዚ ዘራእያን ወለደ፤ዘራእያ መራዮትን ወለደ፤ 7 መራዮት አማርያን ወለደ፤አማርያ አኪጦብን ወለደ፤ 8 አኪጦብ ሳዶቅን ወለደ፤ 9 ሳዶቅ አኪማአስን ወለደ፤አኪማአስ ዓዛርያስን ወለደ፤ዓዛርያስ ዮሐናን ወለደ፤ 10 ዮሐናን ዓዛርያስ ወለደ፤እርሱም ሰለሞን በኢየሩሳሌም ባሠራው ቤተ መቅደስ በክህነት ያገለግል ነበር፤ 11 ዓዛርያስ አማርን ወለደ፤አማርያም አኪጦብን ወለደ፤ 12 አኪጦብ ስሳዶቅን ወለደ፤ሳዶቅ ሰሎምን ወለደ፤ 13 ሰሎም ኬሌቅያስን ወለደ፤ኬሌቅያስ ዓዛርያስ ሠራያን ወለደ፤ 14 ዓዛርያስ ሠራያን ወለደ፤ሠራያ ኢዮሴዴቅን ወለደ፤ 15 እግዚአብሔር የይሁዳና የእየሩሳሌም ሕዝብ በናቡከደነፆር እጅ ተማርከው እንዲወሰዱ ባደረገ ጊዜ ኢዮሴዴቅም አብሮ ተማርኮ ሄደ። 16 የሌዊ ወንዶች ልጆች፤ ጌድሶን፣ቀዓት፣ሜራሪ። 17 የጌድሶን ወንዶች ልጆች፤ሎቢኒ፣ሰሜኢ። 18 የቀሃት ወንዶች ልጆች፤እምበረም፣ይስዓር፣ኬቤሮን፣ዑዝኤል። 19 የሜራሪ ወንዶች ልጆች፤ሞሖሊ፣ሙሲ። በየአባቶቻቸው ቤተሰብ የተቁጠሩ የሌዊ ጎሣዎች የሚከተሉት ናቸው፤ 20 ከጌርሶን፤ ልጁ ሎቢኒ፣ልጅ ኢኤት፣ልጁ ዛማት፣ 21 ልጁ ዮአክ፣ልጁ አዶ፣ልጁ ዛራ፣ልጁ ያትራይ። 22 የቀዓት ዘሮች፤ ልጁ አሚናዳብ፣ልጁ ቆሬ፣ልጁ አሴር፣ 23 ልጁ ህልቃና፣ልጁ አቢሳፍ፣ልጁ አሴር፣ 24 ልጁ ኢኢት፣ልጁ ኡርኤል፣ልጁ ዖዝያ፣ልጁ ሳውል። 25 የሕልቃና ዘሮች፤ አማሢ፣አኪሞት። 26 ልጁ ሕልቃና፣ልጁ ሱፊ፣ልጁ ናሐት፣ 27 ልጁ ኤልያብ፣ልጁ ይሮሐም፣ልጁ ሕልቃና፣ልጁ ሳሙኤል። 28 የሳሙኤል ወንዶች ልጆች፤የበኩር ልጁ ኢዮኤል፣ሁለተኛው ልጁ አብያ። 29 የሜራሪ ዘሮች፤ ሞሖሊ፣ልጁ ሎቤኒ፣ልጁ ሰሜኢ፣ልጁ ዖዛ፣ 30 ልጁ ሳምን፣ልጁ ሐግያ፣ልጁ ዓሣያ። 31 ታቦቱ ከገባ በኋላ፣ዳዊት የመዘምራን አለቃ አድርጎ በእግዚአብሄር ቤት የሾማቸው ሰዎች እነዚህ ናቸው፤ 32 እርሱም ሰሎሞን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በኢየሩሳሌም እስኪሠራ ድረስ፣በማደሪያው ይኸውም በመገናኛ ድንኳን ፊት ሆነው እየዘመሩ ያገለግሉ ነበር፣አገልግሎታቸውንም የሚያከናውኑት በወጣላቸው ደንብ መሠረት ነው። 33 ከወንዶች ልጆቻቸው ጋር ሆነው ያገለገሉ ሰዎች እነዚህ ናቸው፤ከቀዓታዊያን ልጆች፤ሙዚቃ ተጫዋቹ ኤማን፣የኢዮኤል ልጅ፣የሳሙኤል ልጅ፤ 34 ሳሙኤል የሕልቃና ልጅ ነበረ፤ ሕልቃና ፣የይሮሐም ልጅ፣ይብኤሊኤል ልጅ፣የቶዋ ልጅ፣ 35 የሱፍ ልጅ፣የሥልቃና ልጅ፣የመሐት ልጅ፣የአማሢ ልጅ፣ 36 የሕልቃና ልጅ፣የኢዮኤል ልጅ፣የዓዛርይስስ ልጅ፣የሶፎንያስ ልጅ፣ 37 የታሐት ልጅ፣የአሴር ልጅ፣የአብያሳፍ ልጅ፣የቆሬ ልጅ፣ 38 የይስዓር ልጅ፣የቃዓት ልጅ፣የሌዊ ልጅ፣የእስራኤል ልጅ። 39 እንዲሁም የሔማን ወንድም አሳፍ በስተቀኙ ሆኖ ያገለግል ነበር፤ አሳፍ የበራክያ ልጅ፤የሳምዓ ልጅ፤ 40 የሚካኤል ልጅ፣ 41 የኤትኒ ልጅ፣የዛራ ልጅ፣የዓዳያ ልጅ፣ 42 የኤታን ልጅ፣የዛማት ልጅ፣የሰሜኢ ልጅ፣ 43 የኢኤት ልጅ፣የጌድሶን ልጅ፣የሌዊ ልጅ፣ 44 በስተግራቸው በኩል አብረዋቸው ያሉት የሜራሪ ልጆች፣የቂሳ ልጅ ኤታን፣የአብዲ ልጅ፣የማሎክ ልጅ፣ 45 የሐሸብያ ልጅ፣የአሰያስ ልጅ፣የኬልቅያስ ልጅ፣ 46 የአማሲ ልጅ፣የባኒ ልጅ፣የሰሜር ልጅ፣ 47 የሞሖሊ ልጅ፣የሙሲ ልጅ፣የሜራሪ ልጅ፣የሌዊ ልጅ፣ 48 ሌዋውያን ወንድሞቻቸው ግን የእግዚአብሔር ቤት የማደሪያ ድንኳን ተግባር እንዲያከናውኑ ተመድበው ነበር። 49 አሮንና ልጆቹ የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ ባዘዝው ምሠረት ስለእስራኤል ማስተሰሪያ በቅድስት ቅዱሳኑ ውስጥ የሚያከናውነውን ተግባር ሁሉ፣በመሠዊያ ላይ የሚቃጠል መሥቃዕትና በዕጣኑ መሠዊያ ላይ የሚቀርበውም መሥዋዕት የሚቀርቡት ግን አሮንና ዘሮቹ ብቻ ነበሩ። 50 የአሮን ዝርያዎች እነዚህ ነበሩ፤ ልጁ አልዓዛር፣ልጅ ፊንሐስ፣ልጁ አቢሹ፣ 51 ልጁ ቡቂ፣ልጁኦዚ፣ልጁ ዘራአያ፣ 52 ልጁ መራዮት፣ልጁ አማርያ፣ልጁ አኪጦብ፣ 53 ልጁ ሳዶቅ፣ልጁ አኪማአስ። 54 መኖሪያዎቻቸው እንዲሆኑ የተመደቡላቸው ቦታቸው እነዚህ ናቸው፤የመጀመሪያ ዕጣ የእነርሱ ስለ ሆነ፣ከቀዓት ጎሣ ለሆኑት ለአሮን ዘሮች የተመደቡላቸው መኖሪያቸው እነዚህ ነበሩ። 55 ለእነርሱም በይሁዳ ምድር የሚገኘው ኬብሮንና በዙሪያዋ ያለው የግጦሽ ቦታ ተሰጠ፣ 56 በኬብሮን ዙሪያ የሚገኙት የዕርሻ ቦታዎችና መንደሮች ግን ለዮፎኒ ልጅ ለካሌብ ተሰጡ። 57 ለአሮን ዘሮች የመማፀኛ ከተሞች የሆኑትን ኬብሮንን፣ልብናን፣የቲርን፣ኤሽትሞዓን፣ 58 ሖሎንን፣ዳቤርን፣ከነመሰማሪዎቻቸው። 59 ዓሳንን፣ዮታን፣ቤትሳኒስን ከነመሰማሪዎቻቸው ሰጡ። 60 ከብንያም ነገድ ድርሻ ላይ ገባዖንን፣ጌባን፣ጋሌማን፣ዓናቶትን ከነመሰማሪያዎቻቸው ሰጡ። ለቀዓት ዘሮች የተከፋፈሉ እነዚህ ከተሞች ባጠቃላይ ዐሥራ ሦስት ናቸው። 61 ለቀሩት የቀዓት ዘሮች ደግሞ ከምናሴ ነገድ እኩሌታ ድርሻ በዕጣ ዐሥር ከተሞች ተሰጧቸው። 62 ለጌድሶን ነገድ በየጎሣቸው ከይሳኮር፣ከአሴር፣ከንፍታሌምና በባሳን ከሚገኘው ከምናሴ ነገድ ድርሻ ላይ ዐሥራ ሦስት ከተሞች ተመደቡላቸው። 63 ለሜራሪ ዘሮች በየጎሣቸው ከሮቤል፣ከጋድና ከዛብሎን ድርሻ ላይ ዐሥራ ሁለት ከተሞች በዕጣ ተመደቡላቸው። 64 እስራኤላዊያን ከተሞቹን በዚሁ ሁኔታ መድበው ከነመሰማሪያዎቻቸው ለሌዋውያኑ ሰጧቸው። 65 ቀደም ብለው የተጠቀሱትንም ከተሞች ከይሁዳ ከስምዖንና ከብንያም ነገድ ላይ ወስደው በዕጣ መደቡላቸው። 66 ለአንዳንድ የቀዓት ጎሣዎችም ከኤፍሬም ነገድ ድርሻ ላይ ከተሞች ተሰጣቸው። 67 በኮረብታማው በኤፍሬም ምድር የሚገኙትን ሴኬምን(የማማፀኛ ከተማ) ፣ጌዝርን፣ 68 ዮቅምዓምን፣ቤትሖሮን፣ 69 ኤሎንንና ጋትሪሞን ከነመሰማሪዎቻቸው ሰጧቸው። 70 እንዲሁም እስራኤላውያን ከምናሴ ነገድ እኩሌታ ድርሻ ላይ ዓኔርና ቢልዓም የተባሉትን ከተሞች ከነመሰማሪያዎቻቸው ወስደው ለሩት የቀዓት ጎሣዎች ሰጧቸው። 71 ለጌድሶናውያን ከምናሴ ነገድ እኩሌታ፣ በባሳን የሚገኘውን ጎላንና አስታሮትን ከነመሰማሪያዎቻቸው ተሰጠ፤ 72 ከይሳኮር ነገድ፤ ቃዴስን፣ዳብራትን 73 ራሞትንና ዓኔምናን ከነመሰማሪያዎቻቸው ወሰዱ፤ 74 ከአሴር ነገድ መዓሳልን፣ዓብዶን፣ 75 ሑቆቅንና፣ረአብን ከነመሰማሪያዎቻቸው ወሰዱ፤ 76 ከንፍታሌም ነገድ በገሊላ የሚገኘውን ቃዴስን፣ሐሞንንና፣ቂርያታይምን ከነመሰማሪያዎቻቸው ወሰዱ። 77 ከሌዋውያን የቀሩት የሜራሪ ጎሣዎች ደግሞ ከዚህ የሚከተለው ወሰዱ፤ከዛቢሎን ነገድ ዮቅኒዓምን፣ቀርታህን፣ሬሞንና፣ታቦርን፣ከነመሰማሪዮቻቸው ወሰዱ። 78 ከዮርዳኖስ ወንዝ ማዶ ኪኢያሪኮ በስተምስራቅ ከሚገኘውን ቦሶርን፣ያሳን፣ 79 ቅዴሞትንና ሜፍዓትን ከነመሰማሮያዎቻችው ወሰዱ፤ 80 ከጋድ ነገድ በገለዓድ የምትገኘውን ሬማትን፣መሃናይምን፣ 81 ሐሴቦንና ኢያዜርን ከነመሰማሪያዎቻቸው ወሰዱ።

---

1 Chronicles 6:1

ጌድሶን፣... ቀዓት፣... ሜራሪ... እንበረም... ይስዓር... ኬብሮን... ዑዝኤል።... ናዳብ፣... አብዮድ፣... አልዓዛር፣... ... ኢታምር።
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

1 Chronicles 6:4

አልዓዛር፣... አቢሱ... ቡቂ... ኦዚ... ዘራእያ... መራዮት
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Chronicles 6:7

መራዮት... አማርያ... አኪጦብ... ሳዶቅ... አኪማአስ... ዮሐናን
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

1 Chronicles 6:10

አማርያ... አኪጦብ... ሳዶቅ... ሰሎምን
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

ሰሎሞን ገነባ
አንባቢው ሰለሞን ምናልባት ሥራውን እንዲሠሩ ሰራተኞችን እንደቀጠረ መገንዘብ አለበት ።

1 Chronicles 6:13

ኬልቅያስ... ሠራያ... ኢዮሴዴቅ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን በናቡከደነፆር እጅ ባስማረከ
ናቡከደነጾር በሠራዊቱ በኩል ያለው ኃይል ሠራዊቱን ለመምራት እንደሚጠቀምባቸው የእሱ (“እጅ”) አካል እንደሆነ ተገልጻል። አት: “የናቡከደነጾር ሠራዊት የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን ሠራዊት ድል እንዲያደርግና ሕዝቡን በምርኮ እንዲወስድ ፈቀደ” (Synecdoche: ይመልከቱ)

1 Chronicles 6:16

ጌድሶ... ቀዓት፥... ሜራሪ
የእነዚህ ወንዶች ስም እንደ 1 ዜና 6:1 ይተርጉሙ።

ሎቤኒ... ሰሜኢ እንበረም፥... ይስዓር፥... ኬብሮን፥... ዑዝኤል
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

1 Chronicles 6:19

ሜራሪ... ሞሖሊ፥... ሙሲ... ሎቤኒ፥... ኢኤት፥... ዛማት፥... ዮአክ... አዶ፥... ዛራ፥... ያትራይ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

1 Chronicles 6:22

አሚናዳብ፥... ቆሬ፥... አሴር፥... ሕልቃና፥... አቢሳፍ... ታሐት... ኡሩኤል... ዖዝያ፥... ሳውል
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

1 Chronicles 6:25

ሕልቃና... አማሢ፥... አኪሞት... ሱፊ፥... ናሐት፥... ኤልያብ፥... ይሮሐም፥
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

1 Chronicles 6:28

ኢዮኤል፥... ሜራሪ... ሞሖሊ፥... ሎቤኒ፥... ሰሜኢ፥... ዖዛ፥... ሰሜኢ... ሐግያ፥... ዓሣያ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

ሁለተኛውም
ሁሉተኛው ልጅ

1 Chronicles 6:31

በእግዚአብሔር ቤት
“ሰዎች ከያህዌ ጋር የሚገናኙበት” ይህ በዳዊት ጊዜ ድንኳን ነበረ።

ታቦቱ እዚያ አረፈ
“የእስራኤል ሕዝብ ታቦቱን በዚያ አኖሩ”

በመገናኛ ድንኳን ማደሪያ
አማራጭ ትርጉሞች የሚሆኑት 1) “የመገናኛው ድንኳን” እና “ማደሪያው” ሁለቱም ለተመሳሳይ ነገር የሚያገለግሉ ናቸው ወይም 2) ማደሪያው የመገናኛው ድንኳን ክፍል ነው፣ “የመገናኛው ድንኳን ውስጠኛ ክፍል”

በየተራቸውም ያገለግሉ ነበር
“ሥራቸውን ሠሩ” ወይም “የተለያዩ ስራዎቻቸውን ሠሩ”

በተሰጣቸው መመሪያ መሠረት
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊቀርብ ይችላል። አት: “ዳዊት በሰጣቸው መመሪያ መሠረት” ወይም “በተሰጣቸው መመሪያ መሠረት”

1 Chronicles 6:33

እነዚህ ናቸው
“እነዚህ ሙዚቀኞች ነበሩ”

ከቀዓት ልጆች
ይህ የሕዝቦች ስም የቀዓት ወገን ነው (1 ዜና 6:1).

ወደኋላ ማየት
ይህ ማለት ዝርዝሩ ከቅርብ ጊዜ ወደቆየው በቅደም ተከተል እየሄደ ነው ማለት ነው።

ኤማን... ይሮሐም... የኤሊኤል... የቶዋ... የሱፍ... መሐት
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

ሕልቃና... አማሢ
የእነዚህን ወንዶች ስሞች በ1 ዜና 6:25 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

1 Chronicles 6:36

ታሐት... አሴር... አሴር... ይስዓር... ቀዓት
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

1 Chronicles 6:39

የሀማን ወንድሞች
“ከሄማን የሥራ ባልደረባው”

በቀኙም የቆመ
የአንድ ሰው ስልጣን በሚቆምበት ቦታ ተገለጸል። የአንድ ሰው የቀኝ ጎን ትልቅ ስልጣን ያለው ሰው የሚቆምበት ቦታ ነው ።

በራክያ... ሳምዓ... ሚካኤል... በዓሢያ... መልክያ... ኤትኒ ... ዛራ... ዓዳያ... ኤታን... ዛማት... ሰሜኢ... ኢኤት... ጌድሶን
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

1 Chronicles 6:44

በሄማን በግራቸውም በኩል
”በሄማን ግራ ጎን ላይ መቆም ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወንድሞቻቸው
“የሥራ ባልደረቦቹ”

ኤማን ... ኤታን
የእነዚህን ወንዶች ስሞች በ1 ዜና 2:6 እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ።

ቂሳ... አብዲ ... ማሎክ ... ሐሸብያ ... አሜስያስ ... ኬልቅያስ ... አማሲ ... ባኒ ... ሴሜር
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

ሞሖሊ ... ሙሲ
ሜራሪ

1 Chronicles 6:48

ወንድሞቻቸውም ሌዋውያን ... ተሰጡ
ይህ በገባሪ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። አት: “እግዚአብሄር ስራውን እንዲሰሩ ረዳቶቻቸውን ሌዋውያንን ሾሞላቸው ነበር”

1 Chronicles 6:49

እነዚህ መስዋቶች ለእስራኤል ያስተሰርዩ ነበር
“ለእስራኤል ሕዝብ ኃጢአት ማስተሰረያ እነዚህን ሁሉ አቅርበዋል”

1 Chronicles 6:50

አጠቃላይ መረጃ
በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያሉት ስሞች ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው።

የአሮንም ልጆች እነዚህ ናቸው
“እነዚህ የአሮን ዘሮች ናቸው”

1 Chronicles 6:54

የአሮን ልጆች እንዲቀመጡበት የተሰጠ ቦታ
ይህ በገባሪ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። አት: “እነዚህ የአሮን ዘሮች እንዲኖሩበት የሰጣቸው ቦታ ነው”

ለአሮን ልጆች ለቀዓት
“የአሮን ዘሮች ቆሬያውያን የሚኖሩበት”

ለቀዓት ወገኖች (አንደኛው ዕጣ ነበረ)
ሕዝቦች የት እንደሚኖሩ ለመወሰን እስራኤላውያን ዕጣ ለመጣል ወሰኑ። አት: “ቆሬያውያን። መጀመሪያ የወጣው ዕጣ የእነርሱ ነበር”

ለቀዓት
ይህ ከቆሬ ዘሮች የሆነ የሕዝቦች ቡድን ስም ነው (1 ዜና 6:1)። ይህን በ1 ዜና 6:33 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

ለእነርሱ ... ኬብሮንን ...ሰጡ
“ኬብሮን ለቀዓት ሰዎች ሰጡ”

በእርስዋም ዙሪያ የነበረውን መሰምርያ
ለእንስሳ የሚበላው ሣር ያለባት ምድር። ይህን See በ1 ዜና 5:16 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

1 Chronicles 6:57

ኬብሮን ... ልብና... የቲር... ኤሽትሞዓ... ሖሎን... ዳቤር
እነዚህ የቦታዎች ስሞች ናቸው።

መሰምርያዋን
ለእንስሳ የሚበላው ሣር ያለባት ምድር። ይህን በ1 ዜና 5:16 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

1 Chronicles 6:59

ዓሳን... ቤትሳሚስ... ጌባ... ጋሌማት... ዓናቶት
እነዚህ ዝርዝሮች ሁሉ የከተሞች ስሞች ናቸው።

መሰምርያዋን
ለእንስሳ የሚበላው ሣር ያለባት ምድር። ይህን በ1 ዜና 5:16 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

ከተሞቻተው ሁሉ ... አሥራ ሦስት ነበሩ
“በአጠቃላይ 13 ከተሞች ነበሯቸው”

1 Chronicles 6:61

ለጌድሶንም ልጆች በየወገናቸው ... አሥራ ሦስት ከተሞች ተሰጡ
“የጌድሶን ዘሮች ነገዶች 13 ከተሞችን አገኙ”

ቀአት ... ጌድሶን
የእነዚህን ወንዶች ስሞች በ1 ዜና 6:1 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

1 Chronicles 6:63

ሜራሪ
የዚህን ወንድ ስም በ1 ዜና 6:1 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

ከመሰምርያዎቻቸው
ለእንስሳ የሚበላው ሣር ያለባት ምድር። ይህን በ1 ዜና 5:16 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

አስቀድመው የተጠቀሱት ከተሞች
በ1 ዜና 6:55 እና 1 ዜና 6:60 የተጠቀሱ ከተሞች።

1 Chronicles 6:66

ቀዓት
ይህ የሕዝቦች ስም የቀዓት ወገን ነው (1 ዜና 6:1). ይህን የቤተሰብ ስም በ1 ዜና 6:33 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

ሴኬም... ጌዝር... ዮቅምዓምን... ቤትሖሮንን... ኤሎን... ጋትሪሞን
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው።

መሰማሪያዋ
ለእንስሳ የሚበላው ሣር ያለባት ምድር። ይህን 1 ዜና 5:16 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

1 Chronicles 6:70

ዓኔርን... ቢልዓምን
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው።

መሰምርያዋን
ለእንስሳ የሚበላው ሣር ያለባት ምድር። ይህን በ1 ዜና 5:16 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Chronicles 6:71

ጌድሶን
የዚህን ወንድ ስም በ1 ዜና 6:1 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

ጎላን... አስታሮት... ቃዴስ... ዳብራት... ራሞት... ዓኔም
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው።

መሰምርያዋ
ለእንስሳ የሚበላው ሣር ያለባት ምድር። ይህን በ1 ዜና 5:16 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

1 Chronicles 6:74

መዓሳል... ዓብዶን... ሑቆቅ... ረአብ... ቃዴስ... ... ሐሞን... ቂርያታይም
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው።

መሰምርያዋ
ለእንስሳ የሚበላው ሣር ያለባት ምድር። ይህን በ1 ዜና 5:16 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

1 Chronicles 6:77

የተቀሩት ልጆች ከዛብሎን ነገድ ተቀበሉ
ይህ በገባሪ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። አት: “የዛብሎን ነገድ እረግትን ሰጠ..... ዘሮች”

ለሜራሪ
“ሜራሪን” በ1 ዜና 6:1 እንዳለው ይተርጉሙ።

ሬሞን... እና ታቦርና... ቦሶርና... ያሳና... ቅዴሞትና... ሜፍዓትና
እነዚህ ሁሉ የከተሞች ስሞች ናቸው።

መሰምርያዋ
ለእንስሳ የሚበላው ሣር ያለባት ምድር። ይህን 1 ዜና 5:16 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

እናም ከሮቤል ነገድ
በ1 ዜና 6:78-79 ያለው መረጃ ይበልጥ ግልፅ ሆኖ መረዳት እንዲቻል አቀማመጡ ተቀይሯል።

ከሮቤል ነገድ
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። አት: “የሮቡል ነገድ ይህን ሰጠ” ወይም “ከሮቤል ነገድም ይህንም ወሰዱ”

1 Chronicles 6:80

ሬማትና... መሃናይምና... ሐሴቦንና... ኢያዜርና
እነዚህ ሁሉ የከተሞች ስሞች ናቸው።

መሰምርያዋ
ለእንስሳ የሚበላው ሣር ያለባት ምድር። ይህን በ1 ዜና 5:16 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 7

1 የይሳኮር ወንዶች ልጆች፤ ቶላ፣ፋዋ፣ያሱብ፣ሺምሮን፣ባጠቃላይ አራት ናቸው። **2** የቶላ ወንዶች ልጆች፤ኦዚ፣ርረፋያ፣ይሪኤል፣የሕማይ፣ይብሣም፣ሽሚኤል፣እነዚህ የየቤተሰባቸው አለቆች ናቸው።በዳዊት ዘመነመንግሥት ከቶላ ዘሮች በየትውልድ ሀረጋቸው የተቁጠሩ የቶላ ዘሮች ብርቱ ተዋጊዎች ነበሩ፤ቁጥራቸው ሃያ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ነበረ። **3** የኦዚ ወንድ ልጅ፤ይዝረሕያ። የይዝረሕያ ወንዶች ልጆች፤ሚካኤል፣አብድዩ፣ይሺያ፣አምስቱም አለቆች ነበሩ። **4** ብዙ ሚስቶችና ልጆች ስለ ነበሩአቸው፣ከነቤተሰባቸው የትውልድ ሐረግ ለውጊያ ብቁ የሆኑ 36000 ሰዎች ነበሩአቸው። **5** ከይስኮር ጎሣዎች ሁሉ የተመዘገቡት ተዋጊዎች የቤተሰቦቹ ትውልድ ቁጥር ባጠቃላይ 87000 ነበሩ። **6** ሦስቱ የብንያም ወንዶች ልጆች፤ ቤላ፣ቤኬብ፣ይዲኤል። **7** የቤላ ወንዶች ልጆች፤ ኤሴቦንም፣ኦዚ፣ዑዝኤል፣ኢያሪሙት፣ዒሪ፣ባጠቃላይ አምስት ሲሆኑ፣ የቤተ ሰብ አለቆች ናቸው፤በትውልድ ሐረግ መዝገባቸው 22034 ተዋጊ ሰዎች ተመዝገበዋል። **8** የቤኬር ወንዶች ልጆች፤ዝሚራ፣ኢዮአስ፣አልዓዛር፣ኤልዮዔናይ፣ዖምሪ፣ ኢያሪሙት፣አብያ፣ዓናቶት፣ዔሌሜት፣እነዚህ ሁሉ የቤኬር ልጆች ነበሩ። **9** በትውልድ ሐረግ መዝገባቸውም ውስጥ የየቤተ ሰባቸው አለቆችና ሃያ ሺህ ሁለት መቶ ተዋጊዎች ተመዝግበዋል። **10** የይዲኤል ልጅ፤ ቢልሐን።የቢልሐን ወንዶች ልጆች፤ የዑስ፣አሲሳኦር፣ **11** እነዚህ ሁሉ የይዲኤል ልጆች የየቤተሰቡ አለቆች ነበሩ፤እነርሱም ለውጊያ ብቁ የሆኑ 17200 ተዋጊዎች ነበሯቸው። **12** (ሳፈንና ሁፊም የዒር ዘሮች ሲሆኑ ሑሺም ደግሞ የአሐር ዘር ነው።) **13** የንፍታሌም ወንዶች ልጆች፤ ያህጽሔል፣ጉኒ፣ዬጽር፣ሺሌም፤እነዚህ የባላ የልጅ ልጆች ናቸው። **14** የምናሴ ዘሮች፤ ሶርያዊት ቁባቱ የወለደችለት ልጁ አሥርኤል ነው።እርሷም የገለዓድን አባት ማኪርያ የወለደች ናት፤ **15** ማኪርም ከሑፊምና ከሳፊም ወገኖች ሚስት አገባ።እኅቱም መዓካ ትባል ነበር።ሌላው ዘሩ ሰለጰዓድ ሲሆን፣እርሱም ሴቶች ልጆች ብቻ ነበሩት። **16** የሚከር ሚስት መዓካ ወንድ ልጅ ወለደች፣ስሙንም ፋሬስ አለችው።የወንድሙም ስም ሱሮስ ይባላል፤ወንዶች ልጆቹም ኡላምና ራቄም ነበሩ። **17** የኡላም ወንድ ልጅ፤ባዳን፣እነዚህ የምናሴ ልጅ፣የማኪር ልጅ፣የገለዓድ ወንዶች ልጆች ናቸው፤፤ **18** እኅቱ መለኬት ኢሱድን፣አቢዔዝርንና መሐላን ወለድች። **19** የሸሚዳ ወንዶች ልጆች ደግሞ እነዚህ ነበሩ፤ አሒያንምምሴኬም፣ሊቅሒ፣አኒዓም። **20** የኤፍሬም ዘሮች፤ ሹቱላ፣ልጁ ባሬድምምልጁ ታሐት፣ልጁ ኤልዓዳ፣ልጁ ታሐት፣ **21** ልጁ ዛባድ፣ልጁ ሹቱላ።ኤድርና ኤልዓድ ከብቶች ለመስረቅ በወረዱ ጊዜ፣የአገሩ ተወለጆች በሆኑት በጌት ሰዎች ተገደሉ። **22** አባታቸውም ኤፍሬም ብዙ ቀን አለቀሰላቸው፤ዘመዶቹም መጥተው አፅናኑት። **23** ከዚያም ወደ ሚስቱ ገብቶ ተኛ፤እርሷም ፀነሰች፤ወንድ ልጅም ወለደች፤በቤተሰቡ ላይ ከደረሰው መከራ የተነሣ ስሙን በሪያ አለው። **24** ሴት ልጁ ስሟ ሲኢራ ይባላል፤እርሷም የታችኛውና የላይኛውን ቤት ሖሮንንና ኡዜን ሼራን የተባሉትን ከተሞች የቁረቁረች ናት። **25** ልጁ ፋፌ፣ልጁ ሬሴፍ፣ልጁ ቴላ፣ልጁ ታሐን፣ **26** ልጁ ለአዳን፣ልጁ ዓሚሁድ ልጁ ኤሊሳማ፣ **27** ልጁ ነዌ፣ልጁ ኢያሱ። **28** በምድራቸውና መኖሪያቸው ቤቴልንና በዙሪያዋ የሚገኙት ከተሞች በስተምሥራቅ ነዓራን፣በስተ ምዕራብ ጌዝርንና መንደሮቿን በሙሉ ታጠቃልል ነበር። **29** በምናሴ ወሰን ላይ ቤትሳን፣ታዕናክ፣መጊዶና ዶና ከነመንደሮቻቸው ነበሩ።በእነዚህም መንደሮች የእስራኤል ልጅ የዮሴፍ ዘሮች ነበር። **30** የአሴር ወንዶች ልጆች፤ዩምና፣የሱዋ፣የሱዊ፣በሪዓ፣እኅታቸውም ሤራሕ ትባል ነበር። **31** የበሪዓ ወንዶች ልጆች፤ሐቤርም የቢርዛዊት አባት መልኪኤል። **32** ሔቤርም ያፍሌጥን፣ሳሜርን፣ኮታምንና እኅታቸውን ሶላን ወለደ። **33** የያፍሌጥ ወንዶች ልጆች፤ ፋሴክ፣ቢምሃል፣ዓሲት፣የያፍሌጥ ወንዶች ልጆች እነዚህ ነበሩ ። **34** የስሜር ወንዶች ልጆች፤ አ፣ሮአጋ፣ይሑባ፣አራም። **35** የወንድሙ የኤላም ወንዶች ልጆች፤ጾፋ ይምና፣ሰሌስ፣ዓማል። **36** የጾፋ ወንዶች ልጆች፤ ሱዋ፣ሐርኔፍር፣ሦጋል፣ቤሪ፣ይምራ፣ **37** ቤጼር፣ሆድ፣ሳማ፣ ሰሊሳ፣ይትራን፣ብኤራ። **38** የዬቴር ወንዶች ልጆች፤ዮሮኒ፣ፊስጳ፣አራ። **39** የዑላ ወንዶች ልጆች፤ኤራ፣ሐኒኤል፣ሪጽያ። **40** እነዚህ ሁሉ የአሴር ዜሮች ናቸው።እነርሱም የቤተ ሰብ አለቆች፣ምርጥ ሰዎች፣ብርቱ ተዋጊዎችና ድንቅ መሪዎች ነበሩ።ለውጊያ ብቁ የሆኑት ወንዶች ቁጥር 26000 ነበር። 39የዑላ ወንዶች ልጆች፤ኤራ፣ሐኒኤል፣ሪጽያ። 40እነዚህ ሁሉ የአሴር ዜሮች ናቸው።እነርሱም የቤተ ሰብ አለቆች፣ምርጥ ሰዎች፣ብርቱ ተዋጊዎችና ድንቅ መሪዎች ነበሩ።ለውጊያ ብቁ የሆኑት ወንዶች ቁጥር 26000 ነበር።

---

1 Chronicles 7:1

አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ያሉት ስሞች ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው።

heads of their fathers' houses
“የአባቶች ቤቶች” የሚሉት ቃላት UDB “ጎሳዎች” ብሎ የሚጠራውን በተለምዶ በተለያዩ ቤቶች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን የሚመለከቱ የተራራቁ ቤተሰቦችን፣ ሰዎችን ይመለከታል።

ቁጥራቸው **22,600**
“ቁጥራቸው ሀያ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ሆነ” ወይም “22,600 ወንዶች ነበሩ” (ቁጥሮች፡ ይመልከቱ)

በዳዊት ጊዜ
“በዳዊት የሕይወት ዘመን” ወይም “ዳዊት በሕይወት እያለ”

1 Chronicles 7:4

ከእነሱ ጋር ነበሩ
ሌላ አማራጭ ትርጉም “ከመካከላቸው ነበሩ” የሚል ነው ።

ሠላሳ ስድስት ሺህ ጦር ለጦርነት
“ለጦርነት ዝግጁ የሆኑ 36,000 ወታደሮች”

ሰማንያ ሰባት ሺህ ተዋጊ ወንዶች
“87,000 ተዋጊ ወንዶች”

1 Chronicles 7:6

አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ያሉት ስሞች ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው።

22,034 ተዋጊ ወንዶች
“ሀያ ሁለት ሺህ ሠላሳ አራት”

የአባቶች ቤቶች
“የአባቶች ቤቶች” የሚሉት ቃላት UDB “ጎሳዎች” ብሎ የሚጠራውን በተለምዶ በተለያዩ ቤቶች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን የሚመለከቱ የተራራቁ ቤተሰቦችን፣ ሰዎችን ይመለከታል።

1 Chronicles 7:8

አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ያሉት ስሞች ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው።

20,200 የአባቶቻቸው ቤቶች አለቆች
“ሀያ ሺህ ሁለት መቶ የቤተሰብ መሪዎች”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Chronicles 7:11

የይዲኤል... የሚር... ሑሺም
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

በነገዳቸው የተቆጠሩ **17,200** በነበሩ
“የነገድ ዝርዝሩ ብዛት 17,200 ነው”

17,200 ቤቶች አለቆች
“አስራ ሰባት ሺህ ሁለት መቶ የቤት ራሶች” (ቁጥሮች፡ ይመልከቱ)

ሳፊን፥... ሑሺም... ሑፊም
እነዚህ የነገዶች ስሞች ናቸው።

1 Chronicles 7:13

ያሕጽኤል፥, ጉኒ፥, ዬጽር፥, እና ሺሉም፥
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

የባላ የልጅ ሎጆች
“የቢልሀል የልጅ ልጆች” ቢልሀል የሴት ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጉሙ፡ ይመልከቱ)

1 Chronicles 7:14

እሥርኤልና, ... ሰለጰአድ... ፋሬስ... ሱሮስ... ኡላም፥... ራቄም
እነዚህ ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው።

የማኪር, የገለአድ አባት
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

ሶርያይቱ ቁባቱ የወለደችለት
“እቁባቲቱ አራሚን ወለደች”

ሑሺም... ሑፊም መዓካ
ይህ የሴት ስም ነው።

1 Chronicles 7:17

አጠቃላይ መረጃ
ከሀሞሌኬት በስተቀር እዚህ ያሉት ስሞች በሙሉ የወንዶች ስሞች ናቸው። ሀሞሌኬት የሴት ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጉሙ፡ ይመልከቱ)

1 Chronicles 7:20

አጠቃላይ መረጃ
ከጋት በስተቀር እነዚህ ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው። ጋት የቦታ ስም ነው።

የጌት ሰዎች ከብቶቻቸውን ሊወስዱ ወርደው ነበርና የገደሉአቸው ልጆቹ ኤድርና ኤልዓድ ነበሩ
ይህ በተገባር ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። አት: “የጌት ሰዎች፣ የአገሩ ሰዎች, ኢዝርን እና ዲሊድን ገደሉ” (ገባሪና ተገባሪ: ይመልከቱ)

ከብቶቻቸውን ሊወስዱ ወርደው ነበርና
“ወንድሞች ከጌት ሰዎች ከብቶችን ለመስረቅ ሄዱ”

1 Chronicles 7:23

አረገዘችም፥ ወንድ ልጅም ወለደች
“ፀነሰች ወንድ ልጅም ወለደች”

ጠራው
“ስም ሰጠው”

በሪዓ
ይህ የወንድ ስም ነው።

ሲአራ
ይህ የሴት ስም ነው።

ላይኛውን ቤትሖሮንንና ኡዜንሼራን የሠራች ሲአራ
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው።

1 Chronicles 7:25

አጠቃላይ መረጃ
በዚህ ያሉት ስሞች ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው።

1 Chronicles 7:28

ግዛታቸውና ማደሪያቸው ቤቴልና መንደሮችዋ
ረኪክ የሆኑት “ይዞታ” እና “መኖሪያ” ስሞች እነደ ግሳዊ ሀረጎች መተርጎም ይችላሉ። አት: - “በቤቴል ተይዘው ይኖራሉ... መንደሮች” ወይም “በቤቴል ውስጥ ተይዘው ይኖራሉ ::

ቤቴልና... ዶርና
በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያሉት ስሞች ሁሉ የከተሞች ስሞች ናቸው።

በእነዚህ የእስራኤል ልጅ የዮሴፍ ልጆች ተቀመጡ
“የእስራኤል ልጅ የዮሴፍ ዘሮች በእነዚህ ከተሞች ይኖሩ ነበር”

1 Chronicles 7:30

አጠቃላይ መረጃ
ከሴራ እና ሹዋ በስተቀር እዚህ ያሉት ሁሉም ስሞች የወንዶች ስሞች ናቸው :: ሴራ እና ሹዋ የሴቶች ስሞች ናቸው።

1 Chronicles 7:33

አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ያሉት ስሞች ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው።

1 Chronicles 7:36

አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ያሉት ስሞች ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው።

1 Chronicles 7:39

አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ያሉት ስሞች ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው።

የተመረጡ ... ሰዎች
“ጠቃሚ ሰዎች”

የአባቶቻቸው ቤቶች
“የአባቶች ቤቶች” የሚሉት ቃላት UDB “ጎሳዎች” ብሎ የሚጠራውን በተለምዶ በተለያዩ ቤቶች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን የሚመለከቱ የተራራቁ ቤተሰቦችን፣ ሰዎችን ይመለከታል።

በትውልዳቸውም በሰልፍ ለመዋጋት የተቈጠሩ ሀያ ስድስት ሺህ ሰዎች ነበሩ
“በጎሳ ዝርዝሩ መሠረት ለጦርነት ብቁ የሆኑ 26,000 ወንዶች ነበሩ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 8

1 የብንያም አምስት ወንድ ልጆች የነበሩት የብኩር ልጅን ቤላን ፤ አስቤልን፣ አሐራን፣ 2 ኖሐን፣ ራፋን ወለደ። 3 የቤላ ወንዶች ልጆች እነዚህ ነበሩ፤አዳር
ጌራ፣አቢሁድ፣አቡሁድ፣ 4 አቢሱ፣ናዕማን፣ኦሖዋ፣ 5 ጌራ፣ሰፋፋ፣ሒራም። 6 በጌባ ይኑሩ የነበሩትና በኋላም በምርኮ ወደ መናሐት የተወሰዱት የኤሁድ ዘሮች
እነዚህ ናቸው። 7 ናዕማን፣አኪያ፣ጌራ፣በምርኮ ጊዜ እየመራ የወሰዳቸው የዖዛና የኢሒሑድ አባት ጌራ ነበረ። 8 ሽሐራይም ሚስቶቹን ሑሺምንና በዕራን ከፍታ
በኋላ በሞዓብ ምድር ወንዶች ልጆች ወለደ። 9 ከሚስቱ ከሖዴሽ ዮባብን፣ዲብያን፣ማሴን፣ማልካምን፣ 10 ይዑጽን፣ሻክያንና ሚርማን ወለደ፤እነዚህም የቤተ ሰብ
አለቆች የነበሩ ልጆቹ ናቸው። 11 ሑሺም ከተባለች ሚስቱ አቢጡብና ኤልፍዓል የተባሉ ወንዶች ልጆች። 12 የኤልፍዓል ወንዶች ልጆች፤
ዔቤር፣ሚሻም፣እንዲሁም ኦኖንና ሎድ የተባሉ ከተሞች ከነመንደሮቻቸው የቁረቁረ ሻሜድ፣ 13 በኤሌን ይኖሩ ለነበሩ ቤተሰቦች አለቆችና የጋት ነዋሪዎችን
አስወጥተው ያሳደዱ በሪዓና ሸማዕ። 14 አሒዮ፣ሻሻቅ፣ይሬምት፣ 15 ዝባድያ፣ዓራያ፣ዔድር፣ 16 ሚካኤል፣ይሽጳናዮሐ የበሪያ ወንዶች ልጆች ነበሩ። 17
ዝባድያ፣ሜሱላም፣ህዝቂ፣ሔቤር፣ 18 ይሽምራይ፣ ይዝሊያና፣ዮባብ፣የኤልፍዓል ወንዶች ልጆች ነበሩ። 19-21 ሺሜኢ እነዚህ ወንዶች ልጆች
ያቃም፣ዝክሪ፣ዘብዲ፣ኤሊዔናይ፣ጲልታይ፣ኤሊኤል ፣ዓዳያ፣ብራያና፣ሺምራት ነበሩት። 22 ይሽጳን፣ዔቤር፣ኤሊኤል፣ 23 ዓብዶን፣ዝክሪ፣ሐናን፣ 24
ሐናንያ፣ኤላም፣ዓንቶትንያ 25 ይፍዴያና ፋኑኤል የሶሴቅ ወንዶች ልጆች ነበሩ። 26 ሸምሸራይ፣ሸሃሪያ፣ጎቶልያ፣ 27 ያሬሽያ፣ኤልያስና፣ዝክሪ የይሮሐም ወንዶች
ልጆች ነበሩ። 28 እነዚህ ሁሉ በየትውልድ ሐርረጋቸው የተቁጠሩ አለቆችና የቤተ ሰብ መሪዎች ሲሆኑ፣የሚኖሩትም በኢየሩሳሌም ነበረ። 29 የገባዖን አባት
ይዒኤል በገባዖን ኖረ፣ሚስቱ መዓካ ትባል ነበር። 30 የበኩር ልጁም አብዶን ይባል ነበር፣የእርሱም ተከታታዮች ዱር፣ቂስ፣በኣል፣ኔር፣ናዳብ፣ 31
ጌዶር፣አሂዮ፣ዛኩርና፣ 32 የሺምዓ አባት ሚቅሎት ነበሩ።እነዚህም ከሥጋ ዘመዶቻቸው ጋር በኢየሩሳሌም ከተማ አቅራቢያ ይኖሩ ነበር። 33 ኔር ቂስን ወለደ፣ቂስ
ሳኦልንወለደ፣ሳኦልም ዮናታንን፣ሜልኪሳን፣አሚናዳብን፣አስበኣልን ወለደ። 34 የዮናትን ወንድ ልጅ መሪበኣልን፣እርሱም ሚካን ወለደ። 35 የሚካ ወንዶች ልጆች
ፒቶን፣ ሜሌክ፣ ታሬዓ፣ አካዝ ነበሩ። 36 አካዝ ይሆዓዳን ወለደ፤ ይሆዓዳም ዔሌሜትን፣ ዓዝሞትን፣ ዘምሪን ወለደ፤ ዘምሪም ሞዳን ወለደ። 37 ሞጻ ቢንዓን ወለደ፤
ቢንዓ ረፋያን ወለደ፤ ረፋያ ኤልዓሣን ወለደ። ኤልዓሣም ኤሴልን ወለደ። 38 ኤሴል ስድስት ወንዶች ልጆች ነበሩት፤ እነርሱም ዓዝሪቃም፣ ቦክሩ፣ እስማኤል፣
ሸዓርያ፣ አብድዩ፣ ሐናን ናቸው። እነዚህ ሁሉ የኤሴል ልጆች ነበሩ። 39 የእርሱ ወንድም የኤሴቅ ወንዶች ልጆች የበኩር ልጁ ኡላም፣ ሁለተኛው ልጁ ኢያስ፣
ሦስተኛው ልጁ ኤላፋላት ናቸው። 40 የኡላም ልጆች ጦረኞችና ቀስተኞች ነበሩ። ብዙ ልጆችና የልጅ ልጆች ነበሩዋቸው፤ ጠቅላላ ቁጥራቸው አንድ መቶ ሃምሳ
ነበር። እነዚህ ሁሉ የብንያም ዘሮች ናቸው።

---

1 Chronicles 8:1

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው።

1 Chronicles 8:6

አጠቃላይ መረጃ
ከጊባና ከማናሀት በስተቀር እነዚህ ሁሉ ስሞች የወንዶች ስሞች ናቸው። ጊባና ማናሀት የሴቶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

የአባቶቻቸው ቤቶች
“የአባቶች ቤቶች” የሚሉት ቃላት UDB “ጎሳዎች” ብሎ የሚጠራውን በተለምዶ በተለያዩ ቤቶች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን የሚመለከቱ የተራራቁ ቤተሰቦችን፣ ሰዎችን ይመለከታል።

ተማረኩ
“መልቀቅ አስፈለጋቸው” ወይም “መልቀቅ ነበረባቸው”

1 Chronicles 8:8

ሸሐራይምም... ዮባብን፥... ዲብያን፥... ማሴን፥... ማልካምን፥... ይዑጽን፥... ሻክያን፥... ሚርማን... አቢጡብንና... ኤልፍዓልን
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

ሑሺምንና... በዕራን... ከሖዴሽ
እነዚህ የሰተቶች ስሞች ናቸው።

ሸሐራይምም ሚስቶቹን ሑሺምንና ... ልጆች ወለደ
“ሸሐራይም እና ሚስቱ ሑሺም የሚከተሉት ልጆች ነበሯቸው።”

የአባቶቻቸው ቤቶች
“የአባቶች ቤቶች” የሚሉት ቃላት UDB “ጎሳዎች” ብሎ የሚጠራውን በተለምዶ በተለያዩ ቤቶች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን የሚመለከቱ የተራራቁ ቤተሰቦችን፣ ሰዎችን ይመለከታል።

1 Chronicles 8:12

የኤልፍዓልም... ዔቤር፥... ሚሻም፥... ሻሚድ፤... በሪዓ፥... ሸማዕ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

ኦኖንና... ሎድን... አይሎን
እነዚህ የቦታዎች ስሞች ናቸው።

የአባቶቻቸው ቤቶች
“የአባቶች ቤቶች” የሚሉት ቃላት UDB “ጎሳዎች” ብሎ የሚጠራውን በተለምዶ በተለያዩ ቤቶች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን የሚመለከቱ የተራራቁ ቤተሰቦችን፣ ሰዎችን ይመለከታል።

1 Chronicles 8:14

አጠቃላይ መረጃ
በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያሉት ስሞች ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው።

አፍላ ... እና አየአብ
በ1ኛ ዜና 8:17-18 ያለው መረጃ ትርጉሙ በቀላሉ እንዲገባ ተደርጓል። (ድልድይ ቁጥሮች: ይመልከቱ)

1 Chronicles 8:19

አጠቃላይ መረጃ
በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያሉት ስሞች ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አጠቃላይ መረጃ
በ1ኛ ዜና 8:19-21 ያለው መረጃ ትርጉሙ በቀላሉ እንዲገባ ተደርጓል።
(ቁጥር ድልድይ እና ስሞች እንዴት እንደሚተረጎም: ይመልከቱ)

1 Chronicles 8:22

አጠቃላይ መረጃ
በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያሉት ስሞች ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው።

አጠቃላይ መረጃ
በ1ኛ ዜና 8:22-25 ያለው መረጃ ትርጉሙ በቀላሉ እንዲገባ ተደርጓል።
(ቁጥር ድልድይ እና ስሞች እንዴት እንደሚተረጎም: ይመልከቱ)

1 Chronicles 8:26

አጠቃላይ መረጃ
በቁጥር 26 እና 27 ውስጥ ያሉት ስሞች ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው።
(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎም: ይመልከቱ)

የአባቶች ቤቶች
“የአባቶች ቤቶች” የሚሉት ቃላት UDB “ጎሳዎች” ብሎ የሚጠራውን በተለምዶ በተለያዩ ቤቶች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን የሚመለከቱ የተራራቁ ቤተሰቦችን፣ ሰዎችን ይመለከታል።

1 Chronicles 8:29

አጠቃላይ መረጃ
ከመካ እና ከገባኦን በስተቀር እዚህ ያሉት ሁሉም ስሞች የወንዶች ስሞች ናቸው ። ማዕዳ የሴት ስም ሲሆን ገባኦን የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎም: ይመልከቱ)

የሚስቱ ስም መዓካ የነበረው የገባዖን አባት ይዒኤል ... በገባዖን ተቀመጡ
እዚህ “አባት” እዚህ በገባኦን ከተማ መሪ እንደ ሆነ ያየኤልን ሁኔታ ያመለክታል። አት: - “የገባኦን መሪ የነበረው ኢዩኤል በገባኦን ይኖር ነበር። የሚስቱም ስም መዓካ ነበር ” (ፈሊጥ: ይመልከቱ)

የበኩር ልጅ
“የኢያኤል የመጀመሪያ ልጅ”

1 Chronicles 8:32

አጠቃላይ መረጃ
ከኢየሩሳሌም በስተቀር በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያሉት ስሞች ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው።

1 Chronicles 8:35

አጠቃላይ መረጃ
በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያሉት ስሞች ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው።

1 Chronicles 8:38

አጠቃላይ መረጃ
በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያሉት ስሞች ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው።

ሁለተኛው የዑስ እና ሦስተኛው ኤሊፋላት
“ከዑላም በኋላ የተወለደው ኤሽ ፣ እና ከዩኡስ በኋላ የተወለደችው ኤሊፌላት” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

ብዙ ልጆች እና የልጅ ልጆች ፣ በአጠቃላይ **150**
“በአጠቃላይ አንድ መቶ አምሳ ወንዶች ልጆች እና የልጅ ልጆች”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 9

1 እስራኤል ሁሉ በየትውልድ ሐረጋቸው ተቁጥረው ስማቸው በእስራኤል ነገሥታት መዝገብ ላይ ሰፈረ።የይሁዳ ሕዝብ ከፈፀሙት በደል የተነሣ ተማርከው ወደ ባቢሎን ተወሰዱ። **2** በመጀመሪያ በየርስታቸውና በየከተሞቻቸው ተመልሰው የሰፈሩት ጥቂት እስራኤላውያን፣ካህናት፣ሌዋውያንና ቤተመቅደሱ ውስጥ የጉልበት ሥራ የሚሠሩ አገልጋዮች ነበሩ። **3** በእየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩ የይሁዳ፣የብንያም፣የኤፍሬምና ምናሴ ነገዶች የሚከተሉት ናቸው፤ **4** ከሰፋሪዎችም መካከል ይሁዳ ልጅ፣ከፋሬስ ዘሮች፣የባኒ ልጅ፣የአምሪ ልጅ፣የዖምሪ ልጅ፣የዓሚሁድ ልጅ ዑታይ። **5** ከሴሎናውያን፦የበኩር ልጁ ዓሣያና ወንዶች ልጆቹ። **6** ከዛራውያን ዝርያዎች መካከል ይዑኤል፤ የሕዝቡ ቁጥር 690 ነበረ። **7** ከብንያማዊን፦የሐስኑኤ ልጅ፣የሆዳይዋ ልጅ፣የሜሱላ ልጅ ስሉ። **8** የይሮሐም ልጅ ብኔያ፣የሚክሪ ልጅ፣የኦዚ ልጅ ኤላ፣የይብንያ ልጅ፣የራጉኤል ልጅ፣የሰፋ ጥያ ልጅ ሜሱላም። **9** በትውልድ ሐረግ መዝገቡ ላይ በተጻፈው መሠረት ከብንያም ነገድ የሕዝቡ ቁጥር ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ስድስት ነበረ፤እነዚህ ሁሉ ወንዶች የቤተሰብ አለቆች ነበሩ። **10** ከካህናቱ፦ ዮዳኤ፣ዮአሪብ፣ያኪን፣ **11** የእግዚአብሔር ቤት አለቃ የሆነው የአኪጦብ ልጅ፣የጻድኮር ልጅ፣የይሮሐም ልጅ፣የሜሱላም ልጅ፣የኬልቅያስ ልጅ ዓዛርያስ። **12** የመልክያ ልጅ፣የጳስኮር ልጅ፣የሳዶቅ ልጅ፣ዓዳያ፣የኢሜር ልጅ፣የምሺላሚት ልጅ፣የሜሴላም ልጅ፣የየሕዜራ ልጅ፣የዓዲኤል ልጅ መዕሣይ። **13** የቤተሰብ አለቃ የነበሩ ካህናት ቁጥር አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሥልሳ ነበረ፤እነዚህም በእግዚአብሔር ብት ለሚከናወነው አገልግሎት ብቁ ሰዎች ነበሩ። **14** ከሌዋውያን ወገን፦ ከሜራሪ ዘሮች የአሳብያ ልጅ፣የዓዝሪቃም ልጅ፣የአሱብ ልጅ፣ሸማያ፣ **15** በቅበቃር፣ኤሬስ፣ጋላልና የአሳፍ ልጅ የዝክሪ፣የሚካ ልጅ፣መታንያ። **16** የኤዶም ልጅ፣የጋላል ልጅ፣ይችሰሙስ ልጅ፣አብድያ።እንዲሁም በነጦፋውያን ከተሞች የኖረው የሕልቅና ልጅ፣የአሳ ልጅ በራክያ። **17** የቤተ መቅደስ በር ጠባቂዎች፦ሰሎም፣ዓቁብ፣ጡልሞን፣አሂማንና ወንድሞቻቸው፣አለቃቸው ሰሎም ነበረ፤ **18** እነርሱም በስተ ምስራቅ በሚገኘው በንጉስ በር እካሁን ድረስ ተመድቦአል።እነዚህ የሌዋያኑ ሰፈር በር ጠባቂዎች ነበሩ። **19** የቆሬ የአብያሳፍ ልጅ፣የቆሬ ልጅ ሰሎምና ክእነሱም ቤተሰብ የሆኑት ቆሬያውያን ወደ እግዚአብሔር ማደሪያ የሚያስገባውን በር ይጠብቁ እንደ ነበር ሁሉ፣እነዚህም ወደ ቤተ መቅደሱ የሚያስገባውን በር ይጠብቁ ነበር። **20** በቀድሞ ጊዜ የበር ጠባቂዎቹ አለቃ የአላዓዛር ልጅ ፊንሐስ ነበረ፥እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበረ። **21** ወደ መገኛው ድንኳን የምያስገባው በር የሚጠብቀው ደግሞ የሜሱላም ልጅ ዘካሪያስ ነበረ። **22** መግቢያ በሮቹን እንዲጠብቁ የተመረጡ ባጠቃላይ ሁለት መቶ ዐሥራ ሁለት ነበሩ።እነርሱም በትውልድ ሐረጋቸው መሠረት በሚኖሩባቸው መንደሮች ተቁጥረው ተመዘገቡ፤በር ጠባቂዎቹን በዚያ ቦታ ላይ የመደቡላቸው ዳዊትና ባለ ራእዩ ሳሙኤል ነበሩ። **23** የማደሪያውን ድንኳን ምማለትም የእግዚአብሔርን ቤት የሚጠብቁትንም እነርሱና ዘሮቻቸው ነበሩ። **24** በር ጠባቂዎቹም በምሥራቅ፣በምዕራብ፣በሰሜንና፣በደቡብ በሚገኙት በአራቱም ማዕዘኖች ላይ ነበሩ። **25** ወንድሞቻቸውም በየመንደሮቻቸው ሆነው በየጊዜው እየወጡ የጥበቃውን ሥራ ሰባት ሰባት ቀን ያግዙአቸው ነበር። **26** ሌዋውያን የነበሩት አራቱ የበር ጠባቂ አለቆች ግን በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የሚገኙትን ክፍሎችና ግምጃ ቤቶች በኃላፊነት ይጠብቁ ነበር። **27** የጥበቃውን ሥራ የሚያከናውኑት እነርሱ በመሆናቸው የሚያድሩትም በዚያው በእግዚአብሔር ቤት አካባቢ ነበረ፤ጠዋት ጠዋትም ደጆቹን የሚከፋፍቱት እነርሱ ነበሩ። **28** ከእነርሱም አንዳንዶቹ ለብቤተመቅደሱ አገልግሎት የሚውሉ ዕቃዎችን በኃላፊነት ይጠብቁ ነበር፤ዕቃዎቹም በሚገቡበትና በሚወቱበት ጊዜ ሁሉ ይቁትሩ ነበር፤ **29** ሌሎቹ ሌዋውያን ደግሞ ዕቃዎቹንና የቤተ መውደሱን ንዋያት ቅድሳት፣ዱቄቱን፣የወይን ጠጁን፣የወይራ ዘይቱን፣ዕጣኑን የሸቱውን ቅመማ ቅመም እንዲጠብቁ ተምመድበው ነበር። **30** ከካህናቱም አንዳንዶቹ የሸቱውን ቅመማ ቅመም ይለውሱ ያዘጋጁ ነበር። **31** የቆሬያዊው የሰሎም በኩር ልጅ ሌዋዊው ማቲትያ የቁርባኑን እንጀራ የመጋገር ኅላፊነት ተሰጥቶት ነበር። **32** በየሰንበቱ የተሰጠው ከቀዓታውያን ወንድሞቻቸው መካከል ለአንዳንዶቹ ነበር። **33** የሌዋውያን ቤተ ሰብ አለቆች የነበሩት መዘምራኑ ደግሞ በብይተ መቅደሱ ክፍሎች ውስጥ እንዲኖሩና ከሌላው ሥራ ሁሉ ነፃ ሌሊት የሚሠሩት ሥራ ነበራቸው። **34** እነዚሁ ሁሉ የሌዋውያን ቤተ ሰብ አለቆች ሲሆኑ፣በትውልድ ሐረጋቸ መሠረት ተመዘገቡ፤የሚኖሩትም በኢየሩሳሌም ነበረ። **35** የገባዖን አባት ይዒኤል የሚኖረው በገባዖን ነበረ፤የሚስቱም ስም መዓካ ይባላል። **36** የበኩር ልጁ ዓብዶን ሲሆን፣የእርሱም ተከታዮች ዱር፣ቂስ፣በኣል፣ኔር፣ናዳብ፣ **37** ጌዶር፣አሒዮ፣ዛኩር፣ሚቅሎት ነበሩ። **38** ሚቅሎት ሳምአን ወለደ፣እርሱም ከዘመዶቻቸው ጋር በኢየሩሳሌም አቅራቢያ ይኖሩ ነበር። **39** ኔር ቂስን ወለደ፤ቂስ ሳኦልን ወለደ፤ሳኦል ዮናታን፣ሜልኪሳን፣አሚናዳብን፣አስበኣልን ወለደ። **40** የዮናታ ወንድ ልጅ፤ መሪበኣል ነው፤መሪበኣል ሚካን ወለደ **41** የሚካ ወንዶች ልጆች፤ፒቶን፣ሜሌክ፣ታሬዓ፣አካዝ። **42** አካዝ የዕራን ወለደ፤ዘምንሪን ሞፃን ወለደ። **43** ሞፃም ቢንዓን ወለደ፤ልጁ ረፋያ ነበረ፤ልጁ ኤልዓሣ፣ልጁ ኤሴል። **44** ኤሴል ስድስት ወንዶች ልጆች ነበሩ፤ስማቸውም፦ዓዝሪቃም፣ቦክሩ፣እስማኤል፣ሸዓርያ፣አብድዩ ሐናን እነዚህ የኤሴል ወንዶች ልጆች ናቸው።

---

1 Chronicles 9:1

እስራኤልም ሁሉ በየትውልዳቸው ተቈጠሩ
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። የትውልድ ሐረጉን የፃፉ ሰዎች ቀደም ሲል የሞቱ ሰዎችን ስም እንዳካተቱ አንባቢው መገንዘብ አለበት። አት: - “እስራኤላውያን ሁሉ እራሳቸውን በትውልድ ሐረግ መዘነቡ”

በየትውልዳቸው
አባቶችንና ተከታይ ዘሮች የሚገልፅ የቤተሰብ መዝገብ

መጽሐፍ ተጽፈዋል በእስራኤል
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። አት: - “ስሞቹን በመጽሐፉ ጻፉ… እስራኤል” ”

በእስራኤል ነገሥታት መጽሐፍ
ይህ የጠፋ መጽሐፍን ይወክላል።

ተማረኩ
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። አት: - “ባቢሎናውያን በምርኮ ወሰዷቸው”

1 Chronicles 9:4

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው።

ከሴሎናዊያንም
ከሴላህ የመጣው ሕዝብ ቡድን ስም ይህ ነው።

numbered 690
“ቁጥራቸው ስድስት መቶ ዘጠና ነበር” (ቁጥሮች እና ግድፈተ ቃላት: ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Chronicles 9:7

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው።

ቁጥራቸው **956**
“ዘጠኝ መቶ ሰማንያ ስድስት ሰዎች ተቆጠሩ”

የአባቶቻቸው ቤቶች አለቆች ነበሩ
“የዘመዶቻቸው መሪዎች” የረዘሙ ቤተሰቦች ብዙውን ጊዜ በተለያዩ ቤቶች ውስጥ የሚኖሩ ፣ UDB “ጎሳዎች” ብሎ የሚጠራቸው እርስ በእርሱ የሚዛመዱ ሰዎች ናቸው።

1 Chronicles 9:10

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው።

የእግዚአብሔርም ቤት
ከባቢሎን ከተመለሱ በኋላ ህዝቡ የገነባው ሁለተኛው ቤተ መቅደስ

1 Chronicles 9:12

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው።

ማገልገል ሥራ እጅግ ብልሃተኞች ሰዎች ነበሩ
“እነዚህ ችሎታ ያላቸው ሰዎች ሠሩ”

የእግዚአብሔርም ቤት
ከባቢሎን ከተመለሱ በኋላ ህዝቡ የገነባው ሁለተኛው ቤተ መቅደስ

የአባቶቻቸውም ቤቶች
ረዘም ያለ ቤተሰብ ፣ እርስ በእርስ የተዛመዱ ሰዎች ብዙውን ጊዜ በተለያዩ ቤቶች ፣ ጎሳዎች ውስጥ ይኖሩ ነበር

ተቆጠሩ **1,760**
“አንድ ሺህ ስድሳ ካህናት ተቆጠሩ” ወይም “አሥራ ሰባት መቶ ስድሳ ካህናትተቆጠሩ”

1 Chronicles 9:14

አጠቃላይ መረጃ
ከ “ነጦፋታውያን” በስተቀር እዚህ ያሉት ሁሉም ስሞች የወንዶች ስሞች ናቸው። ነጦፋውያን ቡድኖች ነበሩ።

ከልጆቹ መካከል
“ከዘሮቹ አንዱ”

1 Chronicles 9:17

በረኞችም
“ዘበኞች ነበሩ” ወይም “በረኞች ነበሩ”

ሰሎም፥... ዓቁብ፥... ተልሞን ... አሒማን፥... የቆሬም... የአብያሳፍ
እነዚህ ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው።

ለሌዊ ልጆች ሰፈር በረኞች ነበሩ
“የሌዊ ዘሮች ከሰፈሩ በስተ ምሥራቅ በኩል የንጉሱን በር ይጠብቁ ነበር”

ቆሬያውያን
የቆሬ ዘሮች

የመግቢያ መድረክ ... መግቢያ
እነዚህ ሐረጎች ሁለቱም የመገናኛ ድንኳኑን መግቢያ ወይም የመገናኛውን ድንኳን ያመለክታሉ ።

መግቢያ
ይህ ከባቢሎን ከተመለሱ በኋላ ህዝቡ ለገነቡት ለሁለተኛው ቤተመቅደስ መግለጫ ነው ።

1 Chronicles 9:20

አጠቃላይ መረጃ
ከያህዌ በስተቀር እነዚህ ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው።

አለቃቸው
“የቆሬ ልጆች አለቃ” (1 ዜና 9:19: ይመልከቱ)

1 Chronicles 9:22

አጠቃላይ መረጃ የመድረኩ በረኞች ይሆኑ ዘንድ የተመረጡ
እነዚህን ሰዎች የመረጠው ግልፅ አይደለም፣ ስለሆነም በገባሪ ቅርፅ መተርጎም ካለብዎ የርስዎን ቋንቋ አጠቃላይ መንገድ ይጠቀሙ። አት: - “በር ጠባቂ አንዲሆኑ የመረጡት”

ቁጥራቸው **212**
“ቁጥራቸው ሁለት መቶ አሥራ ሁለት”

ስማቸውም በመንደሮቻቸው ውስጥ በሰዎች መዝገቦች ውስጥ ተመዝግቧል
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። አት: - “በሰዎች መንደሮች ውስጥ ያሉት መዛግብቶች የእነዚህን ሰዎች ስም አካትተዋል” (ገባሪና ተገባሪ: ይመልከቱ)

ልጆቻቸውም
“ዘሮቻቸው”

1 Chronicles 9:25

ወንድሞቻቸውም
“የዘበኞች ወንድሞች”

በየሰባትም ቀን ከእነርሱ ጋር ሊሆኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ ይገቡ ነበር
“ለመርዳት ተራዎችን በመውሰድ ለ7 ቀናት ይመጡ ነበር”

አራቱ የበረኞች አለቆች ዘወትር በሥራቸው ይቀመጡ ነበር
እነዚህን ሰዎች ማን እንደሾመ ግልፅ አይደለም፣ ስለሆነም በገባሪ ቅርፅ መተርጎም ካለብዎ የርስዎን ቋንቋ አጠቃላይ መንገድ ይጠቀሙ። አት: - “አራቱን መሪዎች... ክፍሎቹን እንዲጠብቁ ሾሙ”

በእግዚአብሔርም ቤት
ከባቢሎን ከተመለሱ በኋላ ህዝቡ የሰሩት ሁለተኛው ቤተ መቅደስ

1 Chronicles 9:28

አንዳንዶች
“አንዳንዶቹ ዘበኞች”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ዕቃውም በቊጥር ይገባና ይወጣ ነበርና ከእነዚህ አንዳንዱ በማገልገያው ዕቃ ላይ ሹሞች ነበሩ
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። አት: - “ሰዎች ሊጠቀሙባቸው ያሰቧቸውን እቃዎች ይቆጥሩ ነበር ፣ እናም ሰዎች ሲያመልሷቸው እቃዎቹን ይቆጥሩ ነበር”

ከእነርሱም አንዳንዶቹ ሹሞች ነበሩ
እነዚህን ሰዎች ማን እንደሾመ ግልፅ አይደለም፣ ስለሆነም በገባሪ ቅርፅ መተርጎም ካለብዎ የርስዎን ቋንቋ አጠቃላይ መንገድ ይጠቀሙ። አት: - “መሪዎቹ አንዳንዶቹን እንዲንከባከቧቸው ተመደቡ” ወይም “የተወሰኑት ደግሞ ተንከባክበው ነበር”

1 Chronicles 9:30

ማቲትያ... የሰሎም
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

የቆሬያዊውም... ከቀዓታውያን
እነዚህ የቡድኖች ስሞች ናቸው።

በገጹ ኅብስት
ስለ “በገጹ ኅብስት” ልዩ ብያኔ “ዳቦ” የሚለውን የትርጉም ገጽ ይመልከቱ።

1 Chronicles 9:33

የአባቶቻቸው ቤቶች
“የአባቶች ቤቶች” የሚሉት ቃላት UDB “ጎሳዎች” ብሎ የሚጠራውን በተለምዶ በተለያዩ ቤቶች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን የሚመለከቱ የተራራቁ ቤተሰቦችን፣ ሰዎችን ይመለከታል።

ያለሌላ ሥራ በየጓዳቸው ይቀመጡ ነበር
“ሌላ ሥራ አይሰሩም ነበር”

የተሰጣቸውን ሥራ ማከናወን
“ማድረግ የሚያስፈልጓቸውን ሥራዎች ማጠናቀቅ”

ሌሊትና ቀን
ይህ ማለት “በማንኛውም ጊዜ” ሲሆን ከቋንቋዎ ወይም ከባህልዎ ተመሳሳይ ትርጉም የሚሰጥ ሐረግ ወይም ቃል በመጠቀም ሊተረጎም ይችላል። (ሜሪዝም: ይመልከቱ)

እነዚህ ከሌዋውያን የአባቶቻቸው ቤቶች አለቆች በየትውልዳቸው አለቆች ነበሩ
“የቤተሰብ ታሪክ ዝርዝሮች የእነዚህ የሌዋውያን የቤተሰብ መሪዎችን ስሞች ያካትታል”

1 Chronicles 9:35

አጠቃላይ መረጃ
ከሚካህ በስተቀር እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። ከሚካህ የሴት ስም ነው።

የገባዖን... የገባዖን
“የገባኦን ሰው ... የገባኦን ከተማ”

1 Chronicles 9:38

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው።

1 Chronicles 9:41

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 10

1 ከዚህ በኋላ ፍልስጥኤማውያን ራኤላውያንም ከፊታቸ ሸሹ፤ብዙዎች በጊቦልቦን ተራራ ላይ ሞቱ። 2 ፍልስጥኤማውያን ሳኦልንና ልጆቹን ይበልጥ
አሳደዱአቸው የሳኦልም ልጆች ዮናታን፣አሚናዳብንና ሜልካሳን ገደሉ፤ 3 ሳኦል በተሰለፈበት ግንባር ውጊያው በረታ፤ቀስተኞችም አግኝተው አቁሰሉት። 4 ሳኦል
ጋሻ ጃግሬውን፣"እነዚህ ሸለፈታምኘች መሳለቂያ እንዳያደርጉኝ ሰልፍህን መዝዘህ ውጋኝ"አለው።ጋሻ ጃግሬው ግን እጅግ ፈርቶ ሰለ ነበር አልደፍርም፤ስለዚህ
ሳኦል በገዛ ሰይፉ ላይ ወድቆ ሞተ። 5 ጋሻ ጃግሬውም ሳኦል መሞቱን ሲያይ፤እርሱም በሰይፉ ላይ ወድቆ ሞተ። 6 ስለዚህ ሳዖልና ሦስት ልጆቹ ሞቱ፤ቤተ
ሰዎቹም ሁሉ አብረው ሞቱ። 7 በሸለቆው ውስጥ የነበሩት እስራኤላዊያን ሁሉ ሰራዊቱ እንደ ሸሸ፣ሳኢልና ልጆቹም እንደ ሞቱ ባዩ ጊዜ ከተሞቻቸውን ለቀው
ሸሹ፤ፍልስጥኤማውያንመጥተው ከተሞቹን ያዙ። 8 በማግሥቱ ፍልስጥኤማውያን የሞቱትን ለመግፈፍ ሲመጡ፣ሳኦልና ልጆቹ በጊልቦዓ ተራራ ላይ ወድቀው
አገኙአቸው። 9 ሳኦልን ከገፈፉ፣ረሱን ከቁረጡና መሣሪያውንም ከወሰዱ በኋላ፣ለአማልክቶቻቸውና ለሕዝቡ የምሥራቹን እንዲነግሩ ወደ መላው የፍልስጥኤም
ምድር መልክዕተኞች ላኩ። 10 ከዚህም መሣሪያውን በአማልክቶቻቸው ቤተ ጣዖት አኖሩ፤ራሱንም በዳጎን ቤተ ጣዖት ውስጥ አንጠለጠሉት። 11 የኢያቢስ
ገለዓድ ነዋሪዎች ሁሉ ፍልስጥኤማውያን በሳኦል ላይ ያደረጉትን በሰሙ ጊዜ፤ 12 ብርቱ የሆኑ ሰዎች ሄደው የሳኦልንና የልጆቹን ሬሳ አንሥተው ወደ ኢያቢስ
አመጡ፤ዐጽማቸውንም ኢያቢስ ውስጥ በሚገኘው ትልቁ ዛፍ ሥር ቀበሩ፤ከዚህያም ሰባት ቀን ጾሙ። 13 ሳኦል እግዚአብሔር ስላታዘዘ ሞተ፤የእግዚአብሔር
ቃል አልጠበቀም፤ይልቁንም ከሙታን ጠሪ ምክርን ጠየቀ፤ 14 ይህን ከእግዚአብሔር አልጠየቀም፤ስስለዚህ እግዚአብሔር ገደለው፤መንግሥቱንም ወደ እሴይ
ልጅ ወደ ዳዊት እንዲተላለፍ አደረገ።

---

1 Chronicles 10:1

የእስራኤልም ሰዎች ከፍልስጥኤማውያን ፊት ሸሹ፥ ተወግተውም በጊልቦአ ተራራ ላይ ወደቁ
እነዚህ ሰዎች የእስራኤል ወታደሮች መሆናቸውን ያመለክታል። አት: - “የእስራኤልም ሠራዊት ሁሉ ከፍልስጥኤማውያን ፊት ሸሹ”

የእስራኤልም ሰዎች ... ወደቁ
ይህ ምናልባት ጠቅላይ መግለጫ ነው። ሁሉም ወታደሮች የሸሹ ቢሆንም ሁሉም የሞቱ አይስልም። አት: - “እያንዳንዱ የእስራኤል ሰው... አብዛኞቹ ሞቱ”

አሚናዳብን ... ሜልኪሳንም
እነዚህን ስሞች በ1 ዜና 8:33 እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት እንደሞተረጎሙ: ይመልከቱ)

1 Chronicles 10:4

ሰይፍህን መዝዘህ ውጋኝ አለው
መውጋት ሞትን ለሚያስከትል ድርጊት የባህሪ ስም ነው። አት: - “በሱ ግደለኝ”

እነዚህ ቈላፋን መጥተው
“ያልተገረዘ” የሚል ስያሜ የተሰጠው መግለጫ እንደ ቅፅል ተደርጎ ሊገለጽ ይችላል። አት: - “እነዚህ ያልተገረዙ ሰዎች ይመጣሉ” ወይም “እነዚህ ያልተገረዙ ሰዎች ይመጣሉ”

እነዚህ ቈላፋን
እዚህ “ያልተገረዘ” የ“ያህዌ” ያልሆኑ ሰዎችን ይወክላል። አት: “እነዚህ የእግዚአብሔር ያልሆኑ ሰዎች” ወይም “እነዚህ አረማውያን ፍልስጤማውያን”

እነዚህ ቈላፋን መጥተው
ምናልባትም ሠይፉ በሰውነቱ ውስጥ እንዲገባ እጀታውን መሬት ላይ በማጣበቅ ሲወድቅ ይወጋዋል። ድርጊቱ ውጤቱ ሞት የሆነውን ነገር ገላጭ ነው። ይህን በ1 ዜና 10:4 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። አት: - “ራሱን በሰይፉ ገደለ”

1 Chronicles 10:5

በሰይፉ ላይ ወድቆ
ምናልባትም ሠይፉ በሰውነቱ ውስጥ እንዲገባ እጀታውን መሬት ላይ በማጣበቅ ሲወድቅ ይወጋዋል። ድርጊቱ ውጤቱ ሞት የሆነውን ነገር ገላጭ ነው። ይህን 1 ዜና 10:4 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። አት: - “ራሱን በሰይፉ ገደለ”

ሦስቱ ልጆቹ
“ሞተ” የሚለው ቃል በቀዳሚው ሐረግ መረዳት ይቻላል። ሊደገም ይችላል። አት. “ሦስት ልጆቹም ሞቱ”

1 Chronicles 10:7

የእስራኤል ሰዎች ሁሉ
ይህ ምናልባት ጠቅላይ መግለጫ ነው። አት: - “የእስራኤል ሰዎች”

ሸሹ
“የእስራኤል ወታደሮች ሸሹ”

ፍልስጥኤማውያንም መጥተው ተቀመጡባቸው
“ፍልስጥኤማውያን መጥተው እስራኤላውያን ጥለዋቸው በሄዱት ከተሞች ይኖሩ ነበር።” ይህ ምናልባት የተከሰተው በቁጥር 8-12 ውስጥ ከተከናወኑት ክስተቶች በኋላ ሊሆን ይችላል።

እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ በታሪኩ ውስጥ አንድን አስፈላጊ ክስተት ለማመልከት እዚህ ጥቅም ላይ ውሏል። ቋንቋዎ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

የሞቱትን ለመግፈፍ
“ዋጋ ያለው ነገር ሁሉ ከሰውነቱ ማስወግድ”

1 Chronicles 10:9

ገፈፉትም፥
ፍልስጤማውያን ሁሉንም ከሳኦል አካል አስወገዱ”

ለጣኦቶቻቸውና ለሕዝቡ የምሥራች ይወስዱ ዘንድ
የሆነውን ነገር ለሕዝቡ ነገሩ ፤ ጣኦቶቻቸውንም በጸሎት አወደሱ።

የምሥራች ይወስዱ ዘንድ
አንድ ሰው ስለተፈጠረው ነገር ለሌሎች የሚናገር ሰው ግለሰቡ ጠንከር ያለ ነገር ተሸክሞ ለሌሎች ሰዎች እንደሰጠ ተደርጎ ይገለጻል ። አት: - “የሆነውን ነገር መንገር”

መሣሪያውንም አንሥተው
“ፍልስጥኤማውያን የሳኦልን ጋሻ አደረጉ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በዳጎን
ይህ የሐሰት አምላክ ስም ነው።

1 Chronicles 10:11

የኢያቢስ ገለዓድም ሰዎች ሁሉ ፍልስጥኤማውያን ... በሰሙ ጊዜ
ሁለቱም “ሁሉም” የሚሉት ቃላት አጠቃላይ መግለጫዎች ናቸው። የከተማዋ ስም በከተማው ውስጥ ለሚኖሩት ሰዎች ትክክለኛ ስም ነው ፣ እናም የሰዎች ቡድን ስም የዚያ ህዝብ ቡድን ወታደሮች ስያሜ ነው። AT: “የኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች የፍልስጥኤማውያን ጭፍራ ወታደሮች በሰሙ ጊዜ”

የኢያቢስ ገለዓድም
ይህ በጊልያድ ውስጥ የሚገኝ ከተማ ስም ነው ::

አጥንቶቻቸውን
አጥንቶች የሞተን ሰውነት ይወክላሉ። አት: - “ሰውነታቸውን”

ሰባት ቀንም
“7 ቀናት”

1 Chronicles 10:13

አያያዥ መግለጫ
እነዚህ ቁጥሮች ሳውል ለምን እንደሞተ ጠቅለል ያደርጉናል። ቋንቋዎ ይህ የታሪኩ መስመር አካል አለመሆኑን ለማሳየት መንገድ ካለው፣ እዚህ ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

እግዚአብሔርንም ስላልጠየቀ
“እግዚአብሔር እንዲመራው አልጠየቅም”

መንግሥቱንም ወደ እሴይ ልጅ ወደ ዳዊት አሳለፈው
እዚህ “መንግሥትን ሠጠው” ማለት ለአንድ ሰው በመንግሥቱ ላይ ስልጣንን መስጠትን የሚያሳይ ፈሊጥ ነው። አት.: - “የእሴይ ልጅ ፣ ዳዊትን ማንገስ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 11

1 እስራኤል ሁሉ በኬብሮን ወደ እነሆ፤እኛ የገዛ ሥጋህና ደምህ ነን፤ 2-3 በቀደመው ዘመን ሳኦል ንጉሥ ሆኖ ሳለ እስራኤልን ወደ ጦርነት የምትመራ አንተ
ነበርህ፤እግዚአብሔር አምላክም፣ሕዝቤን እስራኤልን የምትጠብቅ አንተ ነህ፤ንጉሥ ዳዊት ወዳለበት ወደ ኬብሮን መጡ፤ዳዊትም በኬብሮን በእግዚአብሔር ፊት
ከእነሱ ጋር ቃል ኪዳን ገባ።እግዚአብሔር በሳሙኤል አማካይነት በሰጠው ተስፋ መሠረት ዳዊትን ቀብተው በእስራኤል ላይ አነገሡት። 4 ዳዊትና እስራኤላዊያን
ሁሉ ኢያቡስ ወደምትባለው ወደ ኢየሩሳሌም ሄዱ።በዚያም የሚኖሩ ኢያቡሳዊያን፤ 5 ዳዊትን "ወደዚያ ፈፅሞ አትገባም"አሉት፤ዳዊትግን የጽዮንን ምሽግ
ያዘ፤እርሷም የዳዊት ከተማ ናት። 6 ዳዊትና "ኢያቡሳዊያንን ቀድሞ የሚወጋ ሰው የሰራዊቱ አዛዥ ይሆናል"አለ፤ስለዚህ የጽሩያ ልጅ ኢዮአብ በመጀመሪያ
ወጣ፤እርሱም አዛዥ ለመሆን በቃ። 7 ከዚያም ዳዊት መኖሪያውን በዐባምዩቱ ውስጥ አደረገ፤ከዚያም የተነሣ የዳዊት ከተማ ተባለች። 8 ዳዊትም ከሚሎ ጀምሮ
የከተማይቱን ዙሪያ ቅጥር ሠራ፤ኢዮአብ ደግሞ የቀረውን የከተማይቱን ክፍል መልሶ ሠራ። 9 እግዚአብሔር ጸባኦት ከእርሱ ጋር ሰለ ነበር ዳዊት በየጊዜው
እየበረታ ሄደ። 10 የዳዊት ጎያላን ሰዎች አለቆች እነዚህ ናቸው፤እነርሱም እግዚአብሔር በሰጠው ተስፋ መሠረት መንግሥቱን በምድሪቱ ሁሉ ትስፋ ዘንድ ከሌሎች
እስራኤላዊያን ጋር ሆነው ለመንግሥቱ ብርቱ ድጋፍ ሰጡ። 11 ዳዊት ጎያላን ሰዎች ስም ዜርዜር ይህ ነው፤ ሐክሞናዊው ያሶብዓም የጦር መኮንኖች አለቃ
ነበረ፤እነርሱም ጦሩን አንድቶ በአንድ ጊዜ ሦስት መቶ ሰው ገደለ። 12 ከእርሱም ቀጥሎ ከሦስቱ ጎያላን አንዱ የሆነው የአሆሃዊው የዱዲ ልጅ አልዓዘር ነው፤
13 እርሱም ፍልስጥኤማዊያን ለጦርነት በተሰበሰቡ ጊዜ በፈስደሚም ከዳዊት ጋር አብሮ ነበረ፤ገብስ በሞላበት የእርሻ ቦታ ወታደሮቹ ከፍልስትኤማውያን ፊት
ሸሹ፤ 14 ይሁን እንጂ በእርሻው መካከል ቦታ ይዘው ስለ ነበረ ፍልስጥኤማውያንን ገደሉ፤እግዚአብሔር ታላቅ ድል ሰጣቸው። 15 ከፍልስጥኤማውያን ሰራዊት
ጥቂቱ በራፋይም ሸለቆ ሰፍሮ ሳለ፣ከሠላሳዎቹ አለቆች ጆስቱ ዳዊትን ለመገናኘት በዓዶላም ዋሻ አጠገብ ወደሚገኘው ወደ ዐለቱ ወረዱ። 16 በዚያን ጊዜ
ዳዊት በምሽጉ ውስጥ ነበረ፤የፍልስጥኤማዊያን ሰራዊት ደግሞ በቤተልሔም ነበረ። 17 ዳዊትም ውሃ ፈልጎ ነበርና፣"ከቤተ ልሔም በር አቅራቢያ ከሚገኘው
ጉድጓድ የምጠጣው ውሃ ማን ባመጣልኝ!" አለ። 18 በዚህ ጊዜ ጆስቱ የፍልስጥኤማውያንን ሰራዊት ጥሰው በማለፍ በቤተ ልሔም በር አጠገብ ከሚገኘው
ጉድጓድ ውሃ ቀድተው ለዳዊት አመጡለት፤እርሱ ግን ሊጠጣው ስላልፈለገ በእግዚአብሔር ፊት አፈሰሰው፤ 19 ከዚያም "ይህን ከማድረግ እግዚአብሔር
የጠብቀኝ፤ይህ በሕይወታችን ቁርጠው የሄዱትን የእነዚህን ሰዎች ደም እንደ መጠጣት አይደለምን?"አለ።ይህን ለማምጣት በሕይወታቸው ቁርጠው ስለ
ነበር፣ዳዊት ሊጠጣው አልፈለገም። 20 የኢዮአብ ወንድም አቢሳ የጆስቱ አለቃ ነበረ። እርሱም ጦሩን አንሥቶ ሦስት መቶ ሰዎች ገደለ፤ከዚህም የተነሣ እንደ
ሦስቱ ሁሉ ዝነኛ ሆነ፤ 21 ከጆስቱ አንዱ ሆኖ ባይቁጠርም እንኳን፣እጥፍ ክብር አገኘ፤አዛዣቸውም ሆነ። 22 ከቀብስኤል የወጣውና ታላቅ ጀብዱ የሠውው
የዮዳሄ ልጅ በናያስ ብርቱ ተዋጊ ነበረ።እርሱም እጅግ ያታወቁ ሁለት የሞአብ ሰዎች ገደለ።እንዲያውም አንድ ጊዜ በረዶ ምድርን በሰፈነበት ቀን ወደ አንድ
ጉድጓድ ወርዶ አንበሳ ወደለ። 23 ደግሞም ቁመቱ አምስት ክንድ የሆነ አንድ ግብፃዊው የሸማኔ መጥቅለያ የመሰለ ቶር በእጁ ይዞ ገጠመው፤ክችግብፃዊው
ጋር እጅ ጦሩ ነጥቆ በገዛ ጦሩ ገደለው። 24 የዮሄዳ ልጅ በናያስ የፈፀመው ጀብዱ ይህ ነበር፤እርሱም እንደ ሦስቱ ጎያላን ዝነኛ ሆነ። 25 ከሠላሳዎቹም ይልቅ
የበለጠ አንዱ አልነበረመ፤ዳዊትም የክብር ዘቡ አዛዥ አደረገው። 26 ጎያላኑ ወንድም አሣሄል፤የቤተ ልሔም የዱዲ ልጅ ኤልያናን፤ 27 ሃሮራዊው
ሳሞት፣ፊሎናዊው ሴሌዴ፣ 28 የቴቁሔ ሰው የሆነው የዓስካ ልጅ፣ዒራስ፣የዓናቶቱ ሰው፣አቢዔዜር፣ 29 ኩሳዊው ሴቤካይ፣ኦሆሃዊው ዔላይ፣ 30 ነቶፋዊው
ማህራይ፣የነቶፋዊው የበዓና ልጅ ሔሌድ፣ 31 ከብንያም ወገን የጊብዓ ሰው የሆነው የሪባይ ልጅ ኤታል፣ጲርዓቶናዊው በናያስ፣ 32 የገዓስ ሸለቆዎች ሰው የሆነው
ኡሪ፣ዓረባዊው አቢኤል፣ 33 ባሕሩማዊው ዓዝሞት፣ሰዓልቦዊው ኤልያሕባ፣ 34 የጊዞናዊው የአሳን ልጆች፣የሃራራዊው የሻጌ ልጅ ዮናታን፣ 35 የሃራራዊው የሳኮር
ልጅ አሒአም፣የኡር ልጅ ኤሊፋል፣ 36 ምኬራታዊው ኦፌር፣ፍሎናዊው አኪያ፣ 37 ቀርሜሎሳዊው ሐጽሮ፣የኤዝባይ ልጅ ነዕራይ፤ 38 የናታን ወንድም
ኢዮኤል፣የሃግሪ ልጅ ሚብሐር፣ 39 አሞናዊ ጼሌቅ፣የጽሩያ ልጅ የኢዮአብ ጋሻ ጃግሬ ቤሮ ታዊው ነሃራይ፣ 40 ይትራዊው ዒራስ፣ይትራዊው ጋሬብ፣ 41
ኬጤያዊው ኦርዮ፣የአህላይ ልጅ ዛባድ፣ 42 የሮቤላዊው የሺዛ ልጅ ዓዲና፣እርሱም የሮቤላዊያንና አብረውት ለነበሩት የሠላሳ ሰዎች አለቃ ነበረ። 43 የማዕካ ልጅ
ሐናን፣ሚትናዊው ኢዮሣፍጥ፣ 44 አስታሮዊው ዖዝያ፣የአሮዔራዊው የኮታም ልጆች ሻማና ይዒኤል፣ 45 የሺምሪ ልጅ ይዲኤል፣ወንድሙም ቴዳዊው ዮሐ፣ 46
መሐዋዊው ኤሊኤል፣የኤልነዓም ልጆች ይባሪይና ዮሻውያ፣ሞዓባዊው ይትማ፣ 47 ኤሊኤል፣ዖቤድና ምጾባዊው የዕሢኤል።

---

1 Chronicles 11:1

እስራኤልም ሁሉ ወደ ዳዊት ተሰብስበው
ይህ ጠቅላይ መግለጫ በእስራኤል ውስጥ ካሉ ነገዶች ሁሉ ወደ ዳዊት እንደመጡ እንጂ፣ እያንዳንዱ ግለሰብ ማለት አይደለም። አት: “ከመላው እስራኤል ሰዎች ወደ ዳዊት መጡ” ወይም “ከእስራኤል ነገዶች ሁሉ ሰዎች ወደ ዳዊት መጡ”

እኛ የአጥንትህ ፍላጭ የሥጋህ ቍራጭ ነን
ይህ ፈሊጥ ዘመድ ናቸው ማለት ነው። አት: - “እኛ የአንተ ዘመድ ነን” ወይም “እኛ አንድ ዘር አለን”

አስቀድሞ
ይህ ታሪካዊ መረጃ ነው። ሳኦል ከዳዊት በፊት ንጉሣቸው ነበር።

ሕዝቤን እስራኤልን አንተ ትጠብቃለህ፤ በሕዝቤም በእስራኤል ላይ አለቃ ትሆናለህ ብሎህ ነበር አሉት
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሰረታዊ ነገሩ አንድ ናቸው የሚያመለክቱት ያህዌህ ዳዊትን ንጉሥ እንዲሆን የመረጠው መሆኑን ነው ። (ትይዩአዊ: ይመልከቱ)

ሕዝቤን እስራኤልን አንተ ትጠብቃለህ
እዚህ ላይ በሕዝቦች ላይ መግዛቱ እንደ እረኛ ሆኖ ተገልጻል። አት: - “ሕዝቤን እስራኤልን ትጠብቃለህ” ወይም “ሕዝቤን እስራኤልን ትመራለህ”

በእስራኤል ላይ ንጉሥ ይሆን ዘንድ ዳዊትን ቀቡት
“መቀባት” እግዚአብሄር ዳዊትን እንደ ንጉሥ አድርጎ የመረጠው መሆኑን ለማሳየት ምሳሌያዊ ድርጊት ነው።

በሳሙኤልም እጅ እንደ ተናገረው እንደ እግዚአብሔር ቃል
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። አት: - “ሳሙኤል የተናገረው የእግዚአብሔር ቃል”

1 Chronicles 11:4

ዳዊትም እስራኤልም ሁሉ
እዚህ ላይ “እስራኤል ሁሉ” የሚለው ሐረግ መላውን የእስራኤል ሠራዊት ይወክላል። አት: “ዳዊትና የእስራኤልም ሠራዊት ሁሉ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ዳዊትም እስራኤልም ሁሉ
“አሁን” የሚለው ቃል በዋናው የታሪክ መስመር ውስጥ ዕረፍትን ለማመልከት ያገለግላል። እዚህ ተራኪው ስለ ኢየሩሳሌም ዳራ መረጃን ይናገራል።

ዳዊት ግን አምባይቱን ጽዮንን ያዘ
እዚህ ላይ “ያዘ” የሚለው ቃል “የተያዘው” ወይም “ድል የተደረገ” ማለት ነው። ዳዊት ሠራዊቱን ስለመራ ፣ ስሙ በከተማዋ ላይ ለተጠቁት ሠራዊት ሁሉ ታላቅ ስም ነው። አት: - “ዳዊት የጽዮንን ምሽግ ተቆጣጠረ” ወይም “ዳዊትና የእስራኤል ሠራዊት የጽዮንን ምሽግ ያዙ”

አምባይቱን ጽዮንን ... የዳዊት ከተማ
እነዚህ ሁለቱም ስሞች የሚያመለክቱት ኢየሩሳሌምን ነው ።

አለቃም ሆነ
x

1 Chronicles 11:7

በዙሪያው ከተማ ሠራ... ኢዮአብም የቀረውን ከተማ አበጀ
“እሱ” የሚለው ቃል ዳዊትን ያመለክታል። አንባቢው ዳዊት እና ኢዮአብ ምናልባት በሌሎች ሰዎች ላይ የሠለጠኑ ሳይሆኑ እንደማይቀሩ መገንዘብ አለበት።

ከሚሎም
ይህ ምናልባት ግድግዳዎቹን ከበስተጀርባ አቧራ በማስያዝ የተገነባውን የመሬት ገጽታ መዋቅር የሚያመለክት ሊሆን ይችላል ።

1 Chronicles 11:10

ለዳዊትም የነበሩት የኃያላን አለቆች እነዚህ ናቸው
“እነዚህ የዳዊት ኃያላን መሪዎች ነበሩ”

ስለ እስራኤል እንደ ተናገረው የእግዚአብሔር ቃል ያነግሡት ዘንድ ከእስራኤል ሁሉ ጋር በመንግሥቱ ላይ አጸኑት
ይህ ሐረግ ሁለቱም የዳዊት ሠራዊት መሪዎች እና መላው ሠራዊት ዳዊት ራሱን በእስራኤል ላይ ንጉሥ እንዲያደርግ አግዞታል ማለት ነው ። አት: - “እርሱን ንጉሥ ያደርገው ዘንድ የዳዊትን መንግሥት አጥብቆ የደገፈው”

ያሾብአም
ይህ የወንድ ስም ነው።

የአክሞናዊው
ይህ ከሃክሞን ጎሳ የመጣውን ሰው ያመለክታል ።

በአንድ ጊዜ
“በአንድ ወቂያ”

1 Chronicles 11:12

ከእርሱም በኋላ
“ከያሶብዓም በኋላ”

አልዓዛር... የዱዲ
x

1 Chronicles 11:15

ከሠላሳውም አለቆች ሦስቱ
“ከ 30 ዎቹ 3”

ዓዶላም ዋሻ
በአዱላም ከተማ አቅራቢያ የሚገኘውን ዋሻ። ”ዓዱላም በቤተልሔም አቅራቢያ ይገኛል።

በራፋይም ሸለቆ
ይህ የቦታ ስም ነው ።

በዚያም ጊዜ ዳዊት በምሽጉ ውስጥ ነበረ፥
“አስተማማኝ በሆነው ዋሻው ውስጥ”

በዚያም ጊዜ ዳዊት በምሽጉ ውስጥ ነበረ፥
“ፍልስጤማውያን በቤተልሔም ወታደሮችን አሰፈሩ”

በበሩ አጠገብ ካለችው ከቤተ ልሔም ምንጭ ውሃ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚያመለክቱት ተመሳሳይውን የውሃ ምንጭ ነው ። ሁለተኛው በቤተልሔም ውስጥ የትኛው የውሃ ምንጭ እንደሆነ ያሳያል ።

1 Chronicles 11:18

ሦስቱ ኃያላን
“3 ኃያላን ሰዎች”

የፍልስጥኤማውያንን ሠራዊት ቀድደው ሄዱ
'በፍልስጥኤማውያን ሠራዊት መካከል በመዋጋት አለፉጉ'

በበሩም አጠገብ ካለችው ከቤተ ልሔም ምንጭ ውሃ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚያመለክቱት ተመሳሳይውን የውሃ ምንጭ ነው ። ሁለተኛው በቤተልሔም ውስጥ የትኛው የውሃ ምንጭ እንደሆነ ያሳያል ።

ለእግዚአብሔር አፍስሶ
ይህ ማለት ውሃውን ለያህዌ መባ አድርጎ አፈሰሰ ማለት ነው።

ይህን አደርግ ዘንድ ... ይከልክለኝ
“እንደዚህ ያለ ነገር በጭራሽ አላደርግም!” ወይም “ይህን ፈጽሞ ማድረግ የለብኝም!”

በነፍሳቸው የደፈሩትም እነዚህ ሰዎች ደም እጠጣለሁን?
ሰዎቹ ውሃውን ወደ እርሱ ለማምጣት ሕይወታቸውን አደጋ ላይ ጥለው ስለነበር ዳዊት ውሃውን እንደ ደም አድርጎ ተናገረው። ይህንን ለማጉላት ጥያቄን ይጠቀማል ። ይህ አጻጻፍ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አት: - “ሕይወታቸውን አደጋ ላይ የጣሉ የእነዚህን ሰዎች ደም እንደ ሚጠጡ ይህ ውሃ መጠጣት የለብኝም።”

1 Chronicles 11:20

የኢዮአብም
የዚህን ወንድ ስም በ1 ዜና 2:16 እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ።

የሦስቱ አለቃ
ይህም ማለት አቢሳ ለዳዊት ውኃ ያመጣ የሦስቱ መሪ ነበር።

በሦስት መቶ
“300 ሰዎች” ወይም “300 ተዋጊዎች”

በሦስቱም መካከል ስሙ የተጠራ ነበረ
ይህ በገባሪ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። አት: “ሰዎች ስለ ሦስቱ ሲናገሩ ብዙ ጊዜ እሱን ይጠቅሱ ነበር” (ጋባሪ እና ተገባሪ: ይመልከቱ)

በሦስቱ መካከል የከበረ ነበረ አለቃቸውም ሆነ
ይህ በገባሪ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሦስቱ የተወበሉትን ክብር እጥፍ በእጥፍ የተቀበለ ነው። አት: “ሰዎች ለሦስቱ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከሰጡት እጥፍ እጥፍ ክብር ሰጡት እናም እርሱ ሆነ” ወይም 2) ሦስቱ ሌሎችን ከሚያከብሩት በላይ አክብረውታል። አት: “ሦስቱ ሌሎችን ከሚያከብሩት በላይ አክብረውታል ፤ እንዲሁም ሆኗል”

1 Chronicles 11:22

በናያስ ... የዮዳሄ... የአሪኤል
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

አምስት ክንድ
“ክንድ” ከ 46 ሴንቲሜትር ጋር እኩል የሆነ የመለኪያ አሃድ ነው። አት: - “2.3 ሜትር”

የሸማኔ መጠቅለያ የመሰለ ጦር
ይህ የጦሩን መጠን ከሸማኔው ሞገድ መጠን ጋር ያነፃፅራል። አት: - “የሸመናው ሞገድ መጠን ያለው ጦር”

ወደ እርሱ ወረደ
“በናያስ ወደ ግብፃው ወረደ ።” ይህ ፈሊጥ በጦርነት ውስጥ እሱን አገኘ ማለት ነው ። አት: - “ወረደበት"

1 Chronicles 11:24

ወደ እርሱ ወረደ
“እነዚህን ታላላቅ ሥራዎች አደረጉ”

ወደ እርሱ ወረደ
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። አት: “ሦስቱን ኃያላን ሰዎች እንዳመሰገኑት ሰዎች ያወድሱት ነበር”

ከሠላሳው ይልቅ የከበረ ነበረ፥ ነገር ግን ወደ ፊተኞቹ ወደ ሦስቱ አልደረሰም
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። አት: ከ 30ዎቹ ወታደሮች የበለጠ ህዝቡ ያከብረው ነበር ፣ ግን እንደ ሶስቱ ታዋቂ ወታደሮች አይደለም

በዘበኞቹ
ዳዊትን ከጥቃት የመጠበቅ ሃላፊነት ያለው የሰዎች ቡድን ነው

1 Chronicles 11:26

አጠቃላይ መረጃ
ይህ የዳዊት ሠላሳ በጣም ወሳኝ ተዋጊዎችን ዝርዝር ይጀምራል። ዝርዝሩ የእነዚያን የነበሩትን የወንዶችና የጎሳዎችን ስም ይቀጥላል። ዝርዝሩ እስከሚቀጥለው ድረስ ይቀጥላል 1 ዜና 11:47።

1 Chronicles 11:30

አያያዥ መግለጫ
ይህ የዳዊት ሠላሳ በጣም ወሳኝ ተዋጊዎችን ዝርዝር ይቀጥላል።

1 Chronicles 11:34

አያያዥ መግለጫ
ይህ የዳዊት ሠላሳ በጣም ወሳኝ ተዋጊዎችን ዝርዝር ይቀጥላል።

1 Chronicles 11:38

አያያዥ መግለጫ
ይህ የዳዊት ሠላሳ በጣም ወሳኝ ተዋጊዎችን ዝርዝር ይቀጥላል።

1 Chronicles 11:42

አያያዥ መግለጫ
ይህ የዳዊት ሠላሳ በጣም ወሳኝ ተዋጊዎችን ዝርዝር ይቀጥላል።

ከእርሱም ጋር ሠላሳ
x

1 Chronicles 11:45

አያያዥ መግለጫ
ይህ የዳዊትን ሠላሳ በጣም ወሳኝ ተዋጊዎችን ዝርዝር ያጠናቅቃል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 12

1 ዳዊት ከቂስ ልጅ ከሳኦል ፊት ሸሽቶ በጺቅላግ ሳለ ወደ እርሱ የመጡት ሰዎች እነዚህ ናቸው፤እነርሱም በጦርነቱ ላይ ከረዱት ተዋጊዎች መካከል ነበሩ። 2 ሰዎቹ ቀስተኞች ሲሆኑ፣በቀኝም ሆነ በግራ እጃቸው ፍላጻ መወርወርና ድንጋይ መወንጨፍ የሚችሉ ነበሩ፤እነርሱም ከብንያም ነገድ የሆነው የሳኦል ሥጋ ዘመዶች ነበሩ፤ 3 አለቃቸው አሒዔዝር ነበረ፥ከእርሱም በኋላ ኢዮአስ ነበረ፤ሁለቱም የጊብዓዊው የሸማዓ ልጆች ነበሩ፤የዓዝሞት ልጆች ይዝኤልና ፋሌጥ፣በራኪያ፣ዓናቶታዊው ኢዩ፣ 4 ገባናዊው ሰማያስ ከሠላሳዎቹም መሪ ነበረ፤ርርሚያስ፣የሕዚኤል የሐንስ፣ገድሮታዊው ዮዛባት፣ 5 ኤሊዛይ፣ኢያሪሙት፣በዓልያ፣ሰማራያ፤ሐሩፋዊው ሰፋትያስ፣ 6 ቆሬያውያኑ ሕልቃና፣ይሺያ፣ዓዛኤል፣ዮዛር፣ያሻብዓም፣ 7 የጌዶር ሰው ከሆነው ደግሞ የይሮሐም ልጆች ዮዔላና ዝባድያ። 8 ዳዊት በምድረ በዳ በሚገኘው ምሽጉ ውስጥ ሳለ፣ከጋድ ነገድ የሆኑ ሰዎች መጥተውው የእርሱን ሰራዊት ተቀላቀሉ፤ከእነሱም ለውጊያ የተዘጋጁ ጋሻና ጦር ለመያዝ የሚችሉ ብርቱ ተዋጊዎች ነበሩ፤ፊታቸው እንደ አንበሳ እንደሚይዝ ሚዳቋ ፈጣኖች ነበሩ ። 9 የእነዚህም አለቃ ዔፌር ነበረ፤ሁለተኛ አዛዥ አብድዩ፣ሦስተኛው ኤልያብ፣ 10 አራተኛ መስመና፣አምስተኛው ኤርሚያስ፤ 11 ስድስተኛው ዓታይ፣ሰባተኛው ኢሊኤል፣ 12 ስምንተኛው የሐናን፣ዘጠነኛው ኤልዛባድ፣ 13 ዐሥረኛው ኤርሚያስ፣ዐሥራ አንድኛው መክበናይ። 14 እነዚህ ጋዳውያን የጦር አዛዦች ነበሩ፣ከእነሱም ታናሽ የሆነው እንደ መቶ፣ታላቅ የሆነው ደግሞ እንደ ሺህ አለቃ ይቁጠር ነበር። 15 በመጀመሪያው ወር የዮርዳኖስ ወንዝ ከአፍ እስከ ሞልቶ ሳለ፣ወንዙን ተሻግረው በስተ ምሥራቅና በስተ ምዕራብ ሸለቆዎች ይኖሩ የነበሩትን ሁሉ ከዚያ ያባረሩት እነዚህ ሰዎች ነበሩ። 16 ሌሎች ከብንያምና ከይሁዳም ወገን የሆኑ ሰዎች ዳዊት ወደሚገኝበት ምሽግ መጡ። 17 ዳዊትም እነዚህን ሰዎች ሊቀበል ወጥቶ እንዲህ አላቸው፤የመጣችሁት ልትረዱኝና በሰላም ከሆነ፤ከእኔ ጋር እንድትሰለፉ ልቀበላችሁ ዝግጁ ነኝ፤ነገር ግን እጄ ከበደል ንጹሕ ሆኖ ሳለ፤ለጠላቶቼ አሳልፋችሁ ልትሰጡኝ ከሆነ፤የአባቶቻችን አምላክ ይመልከተው፤ይፍረድውም። 18 ከዚያም እግዚአብሔር መንፈስ በሠላሳዎቹ አለቃ በዓማሣይ ላይ ወረደ፤እርሱም እንዲህ አለ፤"ዳዊት፤እኛ ክችአንተ ጋር ነን፤ሰላም ፍፁም ሰላም ለአንተ ይሁን፤አንተን ለሚረዱም ሁሉ ሰላም ይሁን፤አምላክህ ይረዳሃል"።ስለዚህ ዳዊት ተቀበላቸው፤የሰራዊቱም አለቃ አደረረጋቸው። 19 ዳዊት ከፍልስጥኤማዊያን ጋር ተባብሮ ሳኦልን ለመውጋት በሄደ ጊዜ፤ከምናሴ ነገድ የሆኑ ጥቂት ሰዎች ከድተው ከዳዊት ሰራዊት ጋር ተቀላቀሉ።እርሱ ግን ርዳታ አላደረገላቸውም፤ምክንዩም የፍልስትኤማዊያን ገዦች ምክር ካደረጉ በኋላ እንዲህ ሲሉ ልከውት ነበር፤"ከድቶ ወደ ጌታው ውደ ሳኦል ቢሄድ እኛን ያስጨርሰናል። 20 ዳዊት ወደ ጺውላግ በሄደ ጊዝዜ ከድተው ወደ እርሱ የተቀላቀሉ የምናሴ ነገድ ሰዎች እነዚህ ነበሩ፤ዓድና፣ዮዛባት፣ይዲኤል፣ሚካኤል፣ዮዛባት፣ኤሊሁ፣ ጺልታይ፤እነዚህ በምናሴ ግዛት ሳሉ የሸለቆች ነበሩ። 21 ሁሉ ብርቱ ተዋጊዎችና በዳዊትም ሰራዊት ውስጥ አዛዦች ሰለ ነበሩ፣አደጋ ጣዮችን በመውጋት ረዱት። 22 ሰራዊቱም እንደ እግዚአብሔር ሰራዊት እስኪሆን ድረስ፤፣ዳዊትን ለመርዳት በየዕለቱ ብዙ ሰዎች ይጎርፉ ነበር። 23 እግዚአብሔር ለዳዊት በገባለት ቃል ኪዳን መሠረት የሳኦል መንግሥት አንሥተው ለእርሱ ለመስጠት ዳዊት ወደ ሚገኝበት ወደ ኬቤሮን የመጡት ሰዎች ቁጥር ይህ ነው፤ 24 ጋሻና ጦር አንግበው ለጦርነት የተዘጋጁት የይሁዳ ሰዎች ስድስት ሺህ ስምንት መቶ። 25 ከስምዖን ነገድ ለጦርነት ዝግጁ የሆኑ ሰባት ሺህ አንድ መቶ። 26 ከሌዊ ነገድ አራት ሺህ ስድስት መቶ፤ 27 የአሮን ቤተ ሰብ መሪ የሆነውን ዮዳሄን ጨምሮ ሦስት ሺህ ሰባት መቶ ሰዎች፤ 28 ወጣቱ ብርቱ ተዋጊ ጸዶቅና ከቤተ ሰቡ ሃያ ሁለት የጦር አለቆች፤ 29 የሳኦል ሥጋ ዘመድ የሆኑ የብንያም ሰዎች ሦስት ሺህ፤ከነዚህም አብዛኞቹ እስከዛያች ጊዜ ድረስ ለሳኦል ቤት ታማኝ ነበሩ፤ 30 ከኤፍሬም ሰዎች በጎሣዎቻቸው ዘንድ ታዋቂ የሆኑ ብርቱ ተዋጊዎች ሃያ ሺህ ስምንት መቶ፤ 31 ከምናሴ ነገድ እኩሌታ ዐሥራ ስምንት ሺህ ሰዎች፤እነርሱም ዳዊትን ለማንገሥ በየስማቸው ተጽፈው የመጡ ነበሩ። 32 ዘመኑን የተረዱና እስራኤላዊያንም ምን ማድረግ እንደሚገባቸው የተገነዘቡ የይሳኮር ሰዎች ሁለት መቶ አለቆች፤በእነሱም ሥር ሆነው የሚታዘዙ ዘመዶቻቸው። 33 ልምድ ያላቸው፤በሁለቱም ዐይነት መሣሪያ ለመዋጋት የተዘጋጁትና ዳዊትን ለመርዳት የመጡት መንታ ልብ የሌላቸው የዛቢሎን ሰዎች ሃምሳ ሺህ፤ 34 ከንፍታሌም ሰዎች አንድ ሺህ የጦር አለቆች፤ከእነርሱም ጋር ጋሻና ጦር የያዙ ሠላሳ ሰባት ሺህ ሰዎች፤ 35 ከዳን ሰዎች ለጦርነት የተዘጋጁ ሀያ ስምንት ሺህ ስድስት መቶ፤ 36 ከአሴር ሰዎች ልምድ ያላቸውና ከጦርነት የተዘጋጁ ወታደሮች አርባ ሺህ፤ 37 ከምስራቅ የርዳኖስ ከሮቤል፣ከጋድና ከምናሴ ነገድ እኩሌታ ልዩ ልዩ ዐይነት መሣሪያ የታጠቁ አንድ መቶ ሃያ ሺህ ሰዎች። 38 እነዚህ ሁሉ በሰራዊቱ ውስጥ ለማገልገል ፈቃደኞች የሆኑ ተዋጊዎች ናቸው፤ወደ ኬብሮን የመጡትንም ዳዊትም በእስራኤል ሁሉ ላይ ለማንገሥ ወስነው ስለ ነበር ነው።የቀሩትም እስራኤላዊያን ሁሉ ዳዊትን ለማንገሥ በአንድ ሐሳብ ጸኑ። 39 የሚያስፈልጋቸውን ቤተ ሰቦቻቸው አዘጋጅተውላቸው ሰለ ነበር፣ሰዎቹ እየበሉና እየጠቱ ከዳዊት ጋር ሦስት ቀን ቁዩ። 40 እንዲሁም ሩቅ ከሆነው ከይሳኮር፣ከዛቢሎንና ከንፍታሌም አገር ሳይቀር ጎረቤቶቻቸው በአህያ፣በግመል፣በበቅሎና በበሬ ጭነው ምግብ አመጡላቸው፤በእስራኤል ታላቅ ደስታ ሰለ ሆነ ዱቄት፣የበለስና የዘቢብ ጥፍጥፍ፣የወይን ጠጅ፣የወይራ ዘይት፣የቀንድ ከብትና በጎች በገፍ ቀርበው ነበር።

---

1 Chronicles 12:1

በተሸሸገ ጊዜ
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። አት: “በፊቱ መገኘት በማይችልበት ዘመን” (ገበሪና ተገባሪ: ይመልከቱ)

በቀኝና በግራም እጃቸው ድንጋይ ሊወነጭፉ ፍላጻም ሊወረውሩ ይችሉ ነበር
“በቀኝ እጆቻቸው ወይም በግራ እጆቻቸው በድንጋይ ለመወንጨፍና ፍላጻ ለመወርወር ይችሉ ነበር”

ድንጋይ ሊወነጭፉ
ወንጭፍ አንድ ሰው ረጅም ርቀት ድንጋይ ለመወርወር የሚጠቀምበት የቆዳ መደረቢያ ነው።

1 Chronicles 12:3

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ዚቅላቅ ዳዊትን የተቀላቀሉትን የብንያም ነገድ ሰዎች ዝርዝር የሚጀምር ነው።

በሠላሳው
“30ዎቹ ወታደሮች”

1 Chronicles 12:5

አያያዥ መግለጫ
ይህ ዚቅላቅ ዳዊትን የተቀላቀሉትን የብንያም ነገድ ሰዎች ዝርዝር የሚቀጥል ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Chronicles 12:8

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ከዳዊን ጋር የተቀላቀሉትን የጋድ ነገድ የሆኑ ሰዎች ዝርዝር ይጀምራል።

ፊታቸውም እንደ አንበሳ ፊት ነበረ
እዚህ “ፊት” የሚለው ቃል ወንዶቹንና አንበሶቹን ይወክላል።ፊቶቻቸው በውጊያ ሀይለኞች መሆናቸውን ይገልጻል። አት: “አንበሶች በአደን ሀይለኞች እንደሆኑ እነርሱም በውጊያ ነበሩ”

በተራራም ላይ እንደሚዘልል ሚዳቋ ፈጣኖች ነበሩ
ይህ ቃል አጋኖ አጋዘኖች በኮረብታማ ተራራ ላይ በፍጥነት እንደሚጡት እንዲሁ እነዚህ ሰዎች በንፅፅር ተገልጸዋል።

ሚዳቋ
በኮረብቶች እና በከባድ መሬት ላይ በፍጥነት የሚሮጡ እንደ አጋዘን ያሉ እንስሳት

1 Chronicles 12:9

አያያዥ መግለጫ
ይህ ከዳዊን ጋር የተቀላቀሉትን የጋድ ነገድ ሰዎች ዝርዝር ይቀጥላል።

አለቃው ዔጼር፥ ሁለተኛው አብድዩ፥ ሦስተኛው ኤልያብ፥ አራተኛው፥... አምስተኛው... ስድስተኛው ... ሰባተኛው ... ስምንተኛው ... ዘጠነኛው ... አሥረኛው ... አሥራ አንደኛው
ይህ የሰራዊቱ መሪዎች አንደ አስፈላጊነታቸው በቅደም ተከተል ነው።

1 Chronicles 12:14

ታናሹ ከመቶ፥ .. ይመዛዘኑ ነበር
ይህ ማለት አንድ መሪ የሚመራው አነስተኛ የሰራዊቱ ቡድን 100 ሰዎች ነበሩ ማለት ነው።

ታላቁ ከሺህ ይመዛዘኑ ነበር
ይህ ማለት አንድ መሪ የሚመራው ከፍተኛው የሰራዊት ቡድን 1,000 ወንዶች ነበር ማለት ነው።

በመጀመሪያው ወር
ይህ በዕብራውያን የቀን አቆጣጠር የመጀመሪያ ወር ነው። ጊዜው በምዕራባዊ የቀን መቁጠሪያዎች የመጋቢት የመጨረሻ ክፍል እና በኤፕሪል የመጀመሪያ ክፍል ላይ ነው። የመጨረሻው ዝናብ ሲመጣ በፀደይ ወቅት መጀመሪያ ላይ ነው። (ዕብራውያን ወራት እና ሕግኛ ቁጥሮች: ይመልከቱ)

ዮርዳኖስ ከዳር እስከ ዳር ሞልቶ በነበረ ጊዜ
“ዮርዳኖሱ ዳርቻው ባለፈ ጊዜ”

በሸለቆውም ውስጥ ... የተቀመጡትን ሁሉ አባረሩ
“በሸለቆዎች ውስጥ ያሉትን ሁሉ አሳደዱ”

1 Chronicles 12:16

ከብንያምና ከይሁዳ ወገን ሰዎች
“ከብንያምና ከይሁዳ ነገድ የሆኑ ሰዎች”

የአባቶቻችን አምላክ ይመልከተው
እግዚአብሔር የሚያየው በትርጉም ሊቀርብ ይችላል። አት: - “ማድረግ የምትፈልጉትን የአባቶቻችን አምላክ ይመለከት” (ታሳቢ የሆነ እውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ: ይመልከቱ)

1 Chronicles 12:18

መንፈስም ... በአማሳይ ላይ መጣ
መንፈስም አማሳይን መጣበት ሲል መንፈስ ሀይል እንደሰጠው ተደርጎ ተገልጸል። አት: “መንፈስ አማሳይን ሀይል ሰጠው” (ዜይቤ: ይመልከቱ)

አማሳይ
ይህ የወንድ ስም ነው።

1 Chronicles 12:19

ከዱ
“ለመቀላቀል መሪዎቻቸውን ተዉ”

ወደ ጌታው ወደ ሳኦል ይመለሳል ሲሉ
“ከእና ጋር መዋጋቱን ትቶ ለጌታው ለሳኦል ይዋጋል”

ዓድና, ዮዛባት, ይዲኤል, ሚካኤል, ዮዛባት, ኤሊሁ, እና ጺልታይ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

የምናሴ ሻለቆች
ይህ እንዳንዳቸው እነዚህ ወንዶች ሺህ ወታደሮች ያሉት ቡድን ከምናሴ ነገድ ይመሩ ነበር ማለት ነው። አት “እያንዳንዱ 1,000 ወንዶችን በምሴ ነገድ ውስጥ ይመራሉ” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

1 Chronicles 12:21

አደጋ ጣዮቹ
“የዘራፊዎች ቡድን።” ይህ በአገራቱ ጫፍ የሚንቀሳቀሱትን ሰዎች የሚዘርፉ የሰዎች ቡድኖችን ይወክላል።

ዕለት ዕለት
“ሁሉንም ቀን”

እንደ እግዚአብሔርም ሠራዊት ታላቅ ሠራዊት
አማራጭ ትርጉሞች 1) ሀረጉ “እንደ እግዚአብሄር ሠራዊት” ማለት “እግዚአብሄር እንደ ሰበሰበው ሠራዊት” ወይም 2) ቃሉ “እግዚአብሄር” የሠራዊቱን ትልቅነት ለማሳየት እንደ ፈሊጥ ያገለግላል። አት: “በጣም ትቅል ሠራዊት”

1 Chronicles 12:23

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ከእያንዳንዱ ነገድ ዳዊትን የተቀላቀሉትን ወንዶች የቁጥር ዝርዝር ይጀምራል።

የሳኦልን መንግሥት ወደ እርሱ ይመልሱ ዘንድ
በሳኦል ፈንታ ዳዊትን ንጉስ ያደረጉት ሰዎች ልክ የሳኦልን መንግስት ይዞታ ለዳዊት እንደመስጠት ይገላፃል። አት: “ዳዊትን በሳኦል ቦታ ማንገስ”

እንደ እግዚአብሔርም ቃል
“የያህዌን ቃል እውነት አደረጉ” ወይም “የያህዌን ቃል ፈጸሙ”

6,800, ለጦርነት የታጠቁ
“ለጦችነት የታጠቁ ስድስት ሺህ ስምንት መቶ”

የስምዖን ልጆች
“ከስምዖን” ወይም “ከስምዖን ነገድ”

7,100 ተዋጊ ወንዶች
“ሰባት ሺህ አንድ መቶ ተዋጊ ወንዶች”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Chronicles 12:26

አያያዥ መግለጫ
ይህ ከእያንዳንዱ ነገድ ዳዊትን የተቀላቀሉ ወንዶች ቁጥር ዝርዝር ይጀምራል።

4,600 ተዋጊ ወንዶች
“አራት ሺህ ስድስት መቶ ተዋጊ ወንዶች”

ዮዳሄ
ይህ የወንድ ስም ነው።

ከእርሱ ጋር **3,700** ነበሩ
“ከእርሱ ጋር ሦስት ሺህ ሰባት መቶ ነበሩ”

1 Chronicles 12:32

አያያዥ መግለጫ
ይህ ከእያንዳንዱ ነገድ ዳዊትን የተቀላቀሉ ወንዶች ቁጥር ዝርዝር ይቀጥላል። (ቁጥሮች፡ ይመልከቱ)

ሁለት መቶ ... ሀምሳ ሺህ
“200 ... 50,000”

ዘመኑን የሚያውቁ
አማራጭ ትርጉሞች 1) እነዚህ ወንዶች እርምጃ ለመውሰድ ትክክለኛውን ጊዜ ያውቃሉ ወይም 2) እነዚህ ወንዶች በእስራኤል ውስጥ ያለውን ወቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታ በጥሩ የሚረዱ።

የማያመነቱ
ለዳዊት ታማኝ እንደሚሆኑ በውስጥ ታዋቂ ነው። አት: “ያልተከፋፈለ ታማኝነት ለዳዊት ለመስጠት የተዘጋጁ”

1 Chronicles 12:34

አያያዥ መግለጫ
ይህ ከእያንዳንዱ ነገድ ዳዊትን የተቀላቀሉ ወንዶች ቁጥር ዝርዝር ይቀጥላል።

እንድ ሺህ ... ሠላስ ሰባት ሺህ
“1,000 ... 37,000” (ቁጥሮች፡ ይመልከቱ)

ከዳን
“ከዳን” ወይም “ከዳን ነገድ”

28,600 ወንዶች
“ሀያ ስምንት ሺህ ስድስት መቶ ወንዶች”

1 Chronicles 12:36

አያያዥ መግለጫ
ይህ ከእያንዳንዱ ነገድ ዳዊትን የተቀላቀሉ ወንዶች ቁጥር ዝርዝር ይቀጥላል። (ቁጥሮች፡ ይመልከቱ)

1 Chronicles 12:38

ዳዊትን በእስራኤል ሁሉ ላይ ያነግሡት ዘንድ ... በፍጹም ልባቸው
“ዳዊትን ንጉስ ለማድረግ ቆረጡ”

በዚያ ከዳዊት ጋር ... ተቀመጡ
“እነዚህ ወታደሮች በዚይ ከዳዊት ጋር ነበሩ”

ሦስት ቀን
“3 ቀናት” (ቁጥሮች፡ ይመልከቱ)

በእስራኤል ዘንድ ደስታ ሆኖአል
The word “እስራኤል” የሚለው ቃል አገሪቱን የመሠረቱትን ሕዝቦች ይወክላል። አት: “የእስራኤል ሕዝብ እያከበሩ ነበር” (Synecdoche: ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 13

1 ዳዊትም ሻለቆችና መቶ አለቆች ከሆኑት የጦር ሹማምቱ ሁሉ ጋር ተማከረ። **2** ከዚያም ለመላምው የእስራኤል ማኅበር እንዲህ አለ፤"እንግዲህ ነገሩ መልካም መስሎ ከታያችሁ የአምላካችን የእግዚአብሔር ፍቃድ ከሆነ፤በእስራኤል ግዛት ሁሉ ለሚኖሩ በሩቅም ሆነ በቅርብ ላሉት ለቀሩትም ሆነ በቅርብ ላሉት ለቀሩት ወንድሞቻችን እንዲሁም በየራሳቸው ከተሞና መሰማሪያዎች የሚኖሩ ካህናትና ሌዋውያን መጥተው ከእኛ ጋር እንዲሰባሰቡ እንላክላቸው። **3** በሳኦል ዘመን መንግሥት ሳንፈልገው የነበረውን የአምላካችንን ታቦት መልሰን ወደ እኛ እናምጣ። **4** በገሩም በሕዝቡ ሁሉ ዘንድ ተቀባይነት ስላገኘ መላው ማኅበር ይህንኑ ለማድረግ ተስማማ። **5** ስለዚህ ዳዊ የእግዚአብሔር ታቦት ከቂርያትይዓሪም ለማምጣት ከግብፅ ወንዝ ከሺሖር ጀምሮ እስከ ሐማት መተላለፊያ ድረስ የሰፈሩትን እስራኤላውያን ሁሉ ሰበሰበ። **6** ዳዊትና እስራኤላዊያን ሁሉ በኩሩብና በኪሩብ መካከል የተቀመጠውን፣የእግዚአብሔር በይሁዳ ወዳለችው ቂርያትይዓሪም ወደ ተባለችው ወደ በኣላ ሄዱ። **7** የእግዚአብሔርም ታቦት ከአሚናዳብ ቤት በእዲስ ሠረገላ ላይ እድርገው አመጡ፤ሠረገላውን ይነዱየነበሩትም ዖዛና አሒዮ ነበሩ። **8** ዳዊትና እስራኤላዊያን ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ሆነው በቅኔና በበገና፣በመሰንቆ በከበሮ፣በጽናጽልና በመለከት በሙሉ ኅይላቸው በዓሉን በደስታ ያከብሩ ነበር። **9** ወደ ኪዶን ዐውድማ በደረሱ ጊዜ በሬዎቹ አደናቅፏቸው ሰለ ነበር፣ዖዛ ታቦቱን ለመደገፍ እጁን ዘረጋ። **10** ታቦቱን በእጁ ሰለ ነካ፣የእግዚአብሔር ቁጣ ዖዛን ላይ ነደደ፤ስለዚህም በዚያው በእግዚአብሔር ፊት ሞተ። **11** የእግዚአብሔር ቁጣ ዖዛን በድንገት ስለ ቀሠፈው ዳዊት አዘነ፤ያም ቦታ እስከ ዛሬ ድረስ የዖዛ ስብራት ተብሎ ይጠራል። **12** ዳዊት በዚያን ዕለት የእግዚአብሔር ታቦት ወደ እኔ እንዴት ማምጣት እንችላለሁ?"አለ። **13-14** ስለዚህ ታቦቱን ወደ ዳዊት ከተማ በመውሰድ ፈንታ የጋት ሰው ወደ ሆነው ወደ አቢዳራ ቤት ከቤተ ሰቡ ጋር ሦስት ወር ተቀመጠ፤እግዚአብሔርም ቤተ ሰቡንና ያለውንም ሁሉ ባረከ።

---

1 Chronicles 13:1

ከሻለቆችና ከመቶ አለቆች
አማራጭ ትርጉሞች 1) እነዚህ ቁጥሮች እነዚህ መሪዎች የመሯቸውን ወታደሮች ትክክለኛ ብዛት ያሳያል። አት: “1,000 ወታደሮች መሪዎች እና 100 ወታደሮች መሪዎች” ወይም 2) “ሺዎች” እና “መቶዎች” ተብለው የተተረጎሙት ቃላት ትክክለኛ ቁጥሮችን አያሳዩም፤ ነገር ግን የትልቅ እና የአነስተኛ የሰራዊት አከፋፈሎች ስም ናቸው። አት: “የትልቅ የሰራዊት ክፍሎች መሪዎች እና የትንሽ ሰራዊት ክፍሎች መሪዎች” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

የእስራኤልን ጉባኤ ሁሉ
ይህ በዚህ ቦታ የተሰበሰቡትን ሁሉንም እስራኤላውያን ይመለከታል። አት: - “እዚያ የተሰበሰቡት እስራኤላውያን ሁሉ” (ይመልከቱ:- ታሳቢ የሆነ ዕውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ)

ከአምላካችን ከእግዚአብሔርም ወጥቶ እንደ ሆነ
ይህ ፈሊጥ ይህ እርምጃ ያህዌ የሚቀበለው ድርጊት ነው ማለት ነው። አት: - “አምላካችን እግዚአብሔር የሚቀበለው ይህ ከሆነ” (ፈሊጥ: ይመልከቱ)

ወደ እኛ ይሰበሰቡ ዘንድ እንላክ
ይህ በቀጥተኛ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “መልእክተኞች እንዲቀላቀሉን ይንገሯቸው” ወይም “እነሱ ከእኛ ጋር ይሳተፉ” (ገባሪ ወይም ተገባሪ: ይመልከቱ)

በሕዝቡ ሁሉ ዓይን ዘንድ ቅን ነበረና
እዚህ “ዐይን” የሚለው ቃል ማየትን ይወክላል ፣ ማየትም ሀሳቦችን ወይም ፍርድን ይወክላል። አት: - “ሕዝቡ ሁሉ እነዚህ ነገሮች ትክክል እንደሆኑ አድርገው ይመለከቱ ነበር” (ዘይቤ: ተመልከት)

1 Chronicles 13:5

ዳዊት እስራኤልን ሁሉ ሰበሰበ
እዚህ ላይ “ሁሉም” የሚለው ቃል አጠቃላይ ነው። ሐረጉ ዳዊት ከመላው እስራኤል ሰዎችን ሰብስቧል ማለት እንጂ፣ በእስራኤል እያንዳንዱን ሰብስቧል ማለት አይደለም። አት: - “ዳዊት ከእስራኤል ሁሉ ሰዎችን ሰበሰበ” (ቃል አጋኖ እና ማጠቃለል: ይመልከቱ)

ሌቦ ሐማት... ቂርያትይዓሪም... በኣላ
እነዚህ የቦታዎች ስሞች ናቸው። “በኣላ” ለቂርያትይዓሪም ሌላ ስም ነው። (የስሞችን አተረጓጎም : ይመልከቱ) እነዚህ የቦታዎች ስሞች ናቸው ። ‹በኣላ› ለቂርያትይዓሪም ሌላ ስም ነው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጎሙ ይመልከቱ)

በይሁዳ ወዳለችው
በይሁዳ ያለው

የእግዚአብሔርንም ታቦት ያመጡ ዘንድ
ታቦቱን ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚወስዱት ያመለክታል። AT: “የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ ኢየሩሳሌም ለመውሰድ” (ታሳቢ የተደረገ እውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ: ይመልከቱ)

ያመጡ ዘንድ
ኢየሩሳሌምን በእስራኤል ከሚገኙ ከማንኛውም ስፍራ ከፍ ያለ ነው ፣ ስለሆነም እስራኤላውያን ወደ ኢየሩሳሌም ማወጣት እና ከእርሷ መውረድ በማለት መናገራቸው የተለመደ ነገር ነበር ።

በያህዌ ስም የሚጠራ
ይህ በቀጥተኛ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “በስም የተጠሩ” የሚለው ፈሊጥ የሚያመለክተው የነገሩ ባለቤት የሆነውን ነው። አት: - “የእግዚአብሔር የሆነው” ወይም 2) ታቦቱ የእግዚአብሔር ስም በላዩ ላይ አለ። አት: - “የያህዌን ስም የተሸከመ” (ፈሊጥን: ተመልከት)

በኪሩቤል ላይ የተቀመጠውን
ኪሩቤል ማለት በቃል ኪዳኑ ታቦት መክደኛ ላይ ያሉት መሆናቸውን ግልፅ ማደረግ ያስፈልጋል። የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች የቃል ኪዳኑን ታቦት እንደ የእግዚአብሔር መቀመጫ ከላይ ሆኖ በሰማይ በዙፋኑ ላይ እንደተቀመጠበት እግረኛ ይመስሉት ነበር። አት: “በቃል ኪዳኑ ታቦት ላይ ከኪሩቤል በላይ በዙፋኑ ላይ የሚቀመጠው” (ታሳቢ የተደረገ እውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ: ይመልከቱ)

1 Chronicles 13:7

አሚናዳብ... ዖዛና አሒዮም
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

ዳዊትና እስራኤል ሁሉ
እዚህ ላይ “ሁሉም” የሚለው ቃል አጠቃላይ ነው። አት: “ዳዊትና በዚያ የነበሩት እስራኤል ሁሉ” (ቃል አጋኖ እና ማጠቃለል: ይመልከቱ)

አውታር ባለው መሣሪያ መጫወት
“ባለ አውታር መሣሪያዎች እየተጫወቱ መዘመር”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከበሮ
መሳሪያው ሲወዘወዝ ድምፅ የሚሰጥ በዙሪያው ብረት ያለው የእጅ ከበሮ (የማይታወቁትን መተርጎም: ይመልከቱ)

ፀናፅል
ከፍተኛ ድምጽ ለመፍጠር አንድ ላይ የሚመቱ ሁለት ቀጭን እና ክብ የብረት ሳህኖች (የማይታወቁትን ይተርጉሙይመልከቱ)

1 Chronicles 13:9

ኪዶን፣ ዖዛ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

የእግዚአብሔርም ቍጣ በዖዛ ላይ ነደደ
የእግዚአብሔር ቁጣ እግዚአብሔር የተቆጣበትን ሰው እንደሚያቃጥለው ተደርጎ ተገልፆል። አት: “ያህዌ በዖዛ በጣም ተቆጥቶ ነበር” (ዘይቤ: ይመልከቱ)

በእግዚአብሄር ፊት
“በእግዚአብሔር ፊት”

በዚያም
ይህ ገባሪ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “ሰዎች ያን ስፍራ ይጠሩታል” (ገባሪ ወይም ተገባሪ፡ ይመልከቱ)

የዖዛ ስብራት
ይህ የቦታ ስም ነው። ተርጎሚዎች እንዲህ ሲሉ የግርጌ ማስታወቻ መጨመር ይችላሉ፣ “‘የዖዛ ስብራት’ ማለት ‘የዖዛ ቅጥት.’ ” (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጎሙ፡ ይመልከቱ)

እስከ ዛሬም
በ 1 ዜና 4:43 ውስጥ ይህንን ሐረግ እንዴት እንደሚተረጉሙ ይመልከቱ።

1 Chronicles 13:12

የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ እኔ እንዴት አመጣለሁ?
ዳዊት ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው ታቦቱን ወደ ኢየሩሳሌም ለማምጣት እንደሚፈራ ለማጉላት ነው። ይህ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አት: - “የእግዚአብሔርን ታቦት ከእኔ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ለማምጣት በጣም ፈራለሁ።” (መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ: ይመልከቱ)

ጌት ሰው ወደ አቢዳራይህ
የወንድ ስም ነው። “የጌት ሰው” ከጌት ከተማ የሆነ ግለሰብ ነው። (የስሞችን አተረጓጎም ፡ ይመልከቱ)

ወደ ጌት ሰው ወደ አቢዳራ ቤት አሳለፈው
“ከዖብአዴን ቤተሰብ ቤት ውስጥ”

ሦስት ወራት
“3 ወራት”

ይህዌ ቤቱን ባረከ
እዚህ “ቤት” የሚለው ቃል ለቤተሰቡ የባህሪ ስም ነው። አት: “እግዚአብሔርም ቤተሰቡን ባርኮታል” (የባህሪ ስም: ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 14

1 በዚህ ጊዜ የጢሮስ ንጉሥ ኪራም ለዳዊት ቤተ መንግሥት እንዲሠሩ መልክተኞችን፣ድንጋይ ጠራቦዎችንና አናጢዎችም ከዝግባ ዕንጨት ጋር ላከ። 2 ዳዊትም እግዚአብሄር በእስራኤል ላይ አንግሦ እንዳጽናውና ስለ ሕዝቡም ስለ እስራኤል ሲል መንግጅቱን ከፍ ከፍ እንዳደረገለት አስተዋለ። 3 ዳዊትም በኢየሩሳሌም ብዙ ሚስቶች አገባ፤ከእነሱም ወንዶችንና ሴቶች ልጆችን ወለደ። 4 በዚያ ሳለ የወለዳቸው የልጆች ስም ይህ ነው፤ሳሙስ፣ሶባብ፣ናታን፣ሰለሞን፣ 5 ኢያቤሐር፣ኤሊሱዔ፣ ኤሊፋላት፣ 6 ኖጋ፣ናፌቅ፣ያፍያ፣ 7 ኤሊሳማ፣ኤሊዳሄ፣ኤሊፋላት። 8 ዳዊት በእስራኤል ሁሉ ላይ ተቀብቶ መንገሡን ፍልስጥኤማውያን በሰሙ ጊዜ፣እርሱን ፍለጋ በሙሉ ኅይላቸው ወቱ፤ዳዊት ይህን ሰምቶ ሰለ ነበር ሊገጥማቸው ወጣ። 9 በዚህ ጊዜ ፍልስጥኤማውያን ውጥተው የራፋይምን ሸለቆ ወረሩ። 10 ስለዚህ ዳዊት፣"ወጥቼ በፍልስጥኤማዊያን ላይ አደጋ ልጣልን? አንተስ በእጄ አሳልፈህ ትሰጣቸዋለህን? ሲል እግዚአብሔር ጠየቀ።እግዚአብሔር "አዎን ውጣ! በእጅህ አሳልፌ እሰጣቸዋለሁ"ብሎ መለሰለት። 11 ስለዚህ ዳዊትና ሰዎቹ ወደ በኣልፐራሲም ወጡ፤በዚያም ድል አደረጋቸው።ዳዊትም "ውሃ ነድሎ እንደሚውጣ ሁሉ እግዚአብሄርም ጠላቶችይን በእጄ አፈርሳቸው"አለ፤ከዚህ የተነሳ ያን ቦታ "በኣልፐራሲም"ብለው ሰየሙት። 12 ፍልስጥኤማውያን አማልዕክቶቻቸውን በዚያው ጥለዋቸው ስለ ነበር፣ዳዊትት በእሳት እንዲያቃጥሏቸው አዘዘ። 13 ፍልስጥኤማውያን ሸለቆውን እንደ ገና ወረሩ፣ 14 ዳዊትም እንደገና እግዚአብሔር ጠየቀ።እግዚአብሔር እንዲህ ሲል መለሰለት "ዙሪያውን ከበህ በሾላው ዛፍ ፊት ለፊት አደጋ ጣልባቸው እንጂ በቀጥታ ወደ ላይ አትውጣ፤ 15 በሾላው ዐናት ላይ የሰልፍ ድምፅ ስትሰማ ወዲያኑ ለጦርነት ውጣ፤ይህም የፍልስጥኤማውያንን ስራዊት ለመምታት እግዚአብሔር በፊትህ ወጥቶአል ማለት ነውና። 16 ዝዝዚህ ዳዊት እግዚአብሔር እንዳለው አደረገ፤ከገባዖን ጀምሮ እስከ ጌዝር ድረስ ፍልስጥኤማውያንን መቷቸው። 17 ከዚህም የተነሳ የዳዊት ዝና በየአገሩ ሁሉ ተሰማ፤እግዚአብሔርም መንግሥታት ሁሉ እንዲፈሩት አደረገ።

---

1 Chronicles 14:1

ኪራም
ይህ የወንድ ስም ነው።

አናጢዎችንም
ከእንጨት ነገሮችን የሚሰሩ ሰዎቸ

ጠራቢዎችንም
ከድንጋይ ወይም ከሸክላ ሰዎች ነገሮችን ይሰራሉ

ቤት ይሠሩለት ዘንድ
አናጢዎችና ግንበኞቹ ለዳዊት ቤት ሠሩ ”

እንዳጸናው
“ሰሩለት”

መንግሥቱ ከፍ ብሎአልና
“ከፍ ከፍ” የሚለው ፈሊጥ ያህዌ ለዳዊት መንግሥት ታላቅ ክብርን ሰጠው ማለት ነው። ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “እግዚአብሔር የዳዊትን መንግሥት ከፍ ከፍ አደረገው” ወይም “እግዚአብሔር ለዳዊት መንግሥት ታላቅ ክብር ሰጠው” (ፈሊጥ እና ገባሪ ወይም ተገባሪ: ይመልከቱ)

ስለ ሕዝቡም ስለ እስራኤል
እዚህ “የእሱ” የሚለው ቃል ያህዌን ያመለክታል።

1 Chronicles 14:3

የወለዳቸው የልጆቹ
“ሚስቶቹ ለእርሱ የወለዱአቸው ልጆች”

ሳሙስ፣ ሶባብ፣ ናታን፣
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። በ 1 ዜና 3:5 ውስጥ እነዚህን እንዴት እንደተረጉሟቸው ይመልከቱ። (የስሞችን አተረጓጎም : ይመልከቱ)

ኢያቤሐር፣ ኤሊሱዔ፣ ኤሊፋላት፣ ኖጋ፣ ናፌቅ፣ ያፍያ፣ ኤሊሳማ፣ ኤሊዳሄ፣ ኤሊፋላት
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። እነዚህ ስሞች በ1 ዜና 3:6-8 ይገኛሉ፣ በዚያ “ኤልፋላት” የተጻፈው “ኤልፊሌት” እና ቢሊያዳ ደግሞ is spelled “ኢሊያዳ ቢሆንም እንኳን።” (የስሞችን አተረጓጎም : ይመልከቱ)

1 Chronicles 14:8

አሁን
ጸሐፊው ይህን ቃል በ1 ዜና 14:3-7 ያለውን የዳራ መረጃ መስጠት መጨረሱንና አዲሱን የታሪኩን ክፍል መጀመሩን ያሳያል። ቋንቋዎ ይህንን የሚያከናውንበት የተለየ መንገድ ሊኖረው ይችላል ።

ዳዊት ንጉሥ ሆኖ እንደተቀባ
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “የእስራኤል ሽማግሌዎች ዳዊትን ንጉሥ አድርገው ቀቡት” (ገባሪ ወይም ተገባሪ: ይመልከቱ)

ሊጋጠማቸው ወጣ
ዳዊት ጦሩን እንዲዋጓቸው እንላከ ታሳቢ ያደርጋል። አት: “ጦሩን እንዲዋጓቸው ላካቸው” (ታሳቢ የሆነ እውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ: ይመልከቱ)

በራፋይም ሸለቆ
ይህ የቦታ ስም ነው።

1 Chronicles 14:10

በእጅህ አሳልፌ እሰጣቸዋለሁና
ይህ ፈሊጥ ያህዌ ዳዊት በእነሱ ላይ ድል እንዲቀዳጅ ያስችለዋል ማለት ነው። አት: - “በእነሱ ላይ ድል ይስጥህ” (ፈሊጥ ተመልከት)

በአልፐራሲም
ይህ የቦታ ስም ነው። እንዲህ የሚል የግርጌ ማስታዎቻ መጨመር ይችላሉ፣ “‘በአልፐራሲም’ የሚለው ቃል ‘የመጠርመስ ጌታ’ ማለት ነው” (የስሞችን አተረጓጎም : ይመልከቱ)

ውኃ እንዲያፈርስ እግዚአብሔር ጠላቶቼን በእጄ አፈረሳቸው
ጎርፍ የሚያልፍበትን ሁሉ እንደሚያረነዳ እንዲሁ ዳዊት እግዚአብሄር የዳዊትን ጠላቶች በቀላሉ ማሸነሩን ይናገራል። አት: “ጎርፍ በሁሉ ነገር በቀላሉ እንደሚፈነዳ … እግዚአብሄር ጠላቶቼን በቀላሉ አሸነፈ” (ተመሳሳይነት: ይመልከቱ)

በእጄ
ይህ የዳዊትን ምንጮች ያሳያል። አት: - “ሠራዊቴን በመጠቀም” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በእሳትም አቃጠሏቸው
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “የሐሰት አማልክቶቻቸውን ለማቃጠል” (ገባሪ ወይም ተገባሪ: ይመልከቱ)

1 Chronicles 14:13

በሸለቆው
“የራፋይም ሸለቆ”

አደጋ ጣሉ
“ከፊት ጥቃት”

ከእነርሱ ዞረህ በሾላው ዛፍ ፊት ለፊት ግጠማቸው
“በሾላው ዛፎች ባለው ጫካ አልፈህ ከበስተኃላ አጥቃቸው”

በሾላው ዛፍ
እዚህ ላይ “ሾላ” የዛፍ አይነት ሲሆን ጫካዎች በአንድነት የሚያድጉ ብዙ የሾላ ዛፎችን ይገልጻል። (የስሞችን አተረጓጎም ፡ ይመልከቱ)

1 Chronicles 14:15

አያያዥ መግለጫ:
እግዚአብሔር ለዳዊት ጥያቄ መልስ መስጠቱን የቀጥላል።

በሾላውም ዛፍ እራስ ውስጥ የሽውሽውታ ድምፅ ስትሰማ
ይህ የሚያወራው በንፋሱ ቅጠሎቹ ሲወዛወዙ ስለሚያሰሙት የተራማጅ ሰራዊት ስለመስለው ድምፅ ነው። አት: “ንፋስ በሾላ ዛፎች ጫፍ ሲነፍስ የሚራመዱ ሰዎች እንደሚመስለው ድምፅ” (ዜይቤ: ይመልከቱ)

ጌዝር
ይህ የከተማ ስም ነው።

የዳዊትም ዝና በየአገሩ ሁሉ ወጣ
የዳዊትን ዝና በየአገሩ ሁሉ የሰሙ ሰዎች የዳዊት ዝና ወደነዚያ አገሮች እንደ ተጓዘ ይነገራል። አት: - “በሩቅ ያሉ ሰዎች ስለ ዳዊት ዝና ሰሙ” (ሰብአዊ: ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 15

1 ዳዊት በስሙ በተጠራችው ከተማ ለራሱ ብይቶችን ሠራ፤በእግዚአብሔር ታቦት ቦታ አዘጋጅቶ ድንኳን ተከለ። 2 ከዚያም ዳዊት፣"የእግዚአብሔርን ታቦት እንዲሸከሙና ለዘላለም በፊቱ እንዲያገለግሉ እግዚአብሔር ከመረጣቸው ከሌዋውያን በቀር፣የእግዚአብሔርን ታቦት ማንም አይሸከምም ሲል አዘዘ። 3 ዳዊት የእግዚያብሔር ታቦት ወዳዘጋጀለት ስፍራ እንዲያወጡ እስራኤላዊያን ሁሉ በኢየሩሳሌም ሰበሰበ። 4 የአሮንን ዘሮችና ሌዋዊያውያንኑም በአንድነት ሰበሰበ፤ 5 ከቀዓት ዘሮች፣አለቃውን ኡርኤልንና አንድ መቶ ሃያ የሥጋ ዘመዶቹን፤ 6 ከሜራሪ ዘሮች፤አለቃው ዓሣያንና ሁለት መቶ ሃያ የሥጋ ዘመዶቹን፤ 7 ከጌድሶን ዘሮች፤ አልቃው ኤሊኤልንና አንድ መቶ ሠላሳ የሥጋ ዘመዶቹን፤ 8 ከኤሊጻፍን ዘሮች፤አለቃውን ሸማያንና ሁለት መቶ የሥጋ ዘመዶቹን፤ 9 ከኬብሮን ዘሮች፤ አለቃው ኤሊኤልንና ሰማንያ የሥጋ ዘመዶቹ፤ 10 ከዑዝኤል ዘሮች፤አለቃውን አሚናሳብንና አንድ መቶ ዐሥራ ሁለት የሥጋ ዘመዶቹን። 11 ከዚያም ዳዊት ከህናቱን ሳዶቅንና አብያታርን፣ሌዋውያኑን ኡርኤልን፣ዓሣያን፣ኢዩኤልን፣ሸማያን፣ኤሊኤልንና አሚናዳብን ጠርቶ፣ 12 እንዲህ አልቸው፤"እንግዲህ እናንተ የሌዋውያን ቤተ ሰብ አለቆች ሰለ ሆናችሁ፣እናንተና ወንድሞቻችሁ ሌዋውያን ራሳችሁን ቀድሱ፤ከዚያም የእስራኤል አምላክ የእግዚአብሔርን ታቦት ወደአዘጋጀሁለት ቦታ አምጡ። 13 የአምላካችን የእግዚአብሔር ቁጣ በላያችን ላይ እንዲህ የነደደው እናንተ ሌዋውያኑ ቀድሞም ስላላመጣችሁት ነው፤እኛም ብንሆን ምን ማድረግ እንዳለብን በታዘዘው መሠረት አልጠየቅነውም። 14 ስለዚህ ካህናቱና ሌዋውያኑ የእስራኤልን አምላክ የእግዚአብሔር ታቦት ለማምጣት ራሳቸውን ቀደሱ። 15 ሙሴ በእግዚአብሔር ቃል እንዳዘዘው፣ሌዋውያኑ የእግዚአብሔር ታቦት በትከሻቸው ላይ በሙሉጊያዎች አድርግገው ተሸከሙ። 16 ዳዊትም በዜማ መሣሪያ ማለትም በመሰንቆ፣በበገና፣በፅናፅል እየታጀቡ የደስታ ዜማዎችን እያዜሙ መዘመራንን ከወንድሞቻቸው መካከል እንዲሾሙ ሌዋውያኑ መሪዎች ነገራቸው። 17 ስለዚህ ሌዋውያኑ የኢዮኤልን ልጅ ኤማንን ሾሙ፤ከወንድሞቹም የበራክያን ልጅ አሳፍን፣ከወንድሞቻቸው ከሜራራ ዘሮች የቂሳን ልጅ ኤታንን ሾሙ፤ 18 ከእነሱም ጋር ወንድሞቻቸውን በደረጃ ተሾሙ፤እነሱም ዘካሪያስ፣ያዝኤል፣ሰሚራ ሞት፣ይሒኤል፣ዑኒን፣ኤልያብ፣በናያስ፣መዕሤያን፣መቲትያ፣ ኤሊፍሌሁ፣ሚቅኔያ፣ደግሞም በር ጠባቂዎቹ ዖቤድ ኤዶምና ይዒኤል ነበሩ። 19 መዘመራኑ ኤማን፣አሳፍ ኤታን በናስ ጸናጽል ድምፁን ከፍ እድርገው እንዲያሰሙ ተሾሙ፤ 20 ዘካሪያስ፣ዓዝኤል፣መዕሤያና በናያስ ደግሞ በአላሞት ቅኝት መሰንቆ ይገርፉ ነበር። 21 እንዲሁም መቲትያ፣ኤሊፍሌሁ፣ሚቅኔያ፣ዖብድኤዶም፣ይዒረድኤ፣ ዓዛዝያ፣በሺሚኒት ቅኝት በገና ይደረድሩ ነበር። 22 የዝማሬው ኅላፊ ሌዋዊው አለቃ ክንያን ነበረ፤ይህን ኅላፊነት የወሰደው በዝማሬ የተካነ ስለ ነበር ነው። 23 በራክያና ሕልቃና ያታቦቱ በር ጠባቂዎች ነበሩ፤ 24 ካህናቱ ሰበኒያ፤ኢዮሣፍጥ፣ናትናኤል፣ዓማሣይ፣ዘካሪያስ፣በናያስና አልዓዛር በእግዚአብሔር ታቦት ፊት መለከት ይነፋ ነበር።ዖቤድኤዶምና ይሒያ ደግሞ ያታቦቱ በር ጠባቂዎች ነበሩ። 25 ስለዚህ ዳዊት የእስራኤል ሽማግሌዎችና የሻለቃው አዛዦች የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳኑን ታቦት ከዖቤድኤዶም ቤት በደስታ ለማምጣት ሄዱ። 26 የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት የተሸከሙትን ሌዋውያን እግዚአብሔር ረድቶአቸው ስለ ነበር፣ሰባት ኮርማዎችና ሰባት አውራ በጎች ሠው። 27 ታቦቱን የተሸከሙት ሌዋውያን ሁሉ፣መዘመራኑና የመዘመራኑ አለቃ ክናንያ የለበሱትና ዐይነት ከቀጭን በፍታ የተሠራ ልብስ ዳዊትም ለብሶ ነበር፤እንዲሁም በከፍታ የተሠራ ኤፋድ ለብሶ ነበር። 28 በዚህ ሁኔታ መላው የእስራኤል ህዝብ በሆታ ቀንደ መለከትና እምቢልታ እየነፉ፣ጽናጽል እየጸነጸሉ፣መሰንቆና በገና እየደረደሩ የእግዚአብሔር የኪዳኑን ታቦት አመጡ። 29 የእግዚአብሔር የኪዳኑ ታቦት ወደ ዳዊት ከተማ ሲገባ የሳኦል ልጅ ሚልኮል በመስኮት ሆና ተመለከተች ፤ንጉሥ ዳዊት ደስ ብሎት ሲያሸበሽብ አይታ በልቧ ናቀችው።

---

1 Chronicles 15:1

ዳዊትም በከተማው ላይ ለራሱ ቤቶችን ሠራ
ይህን ዳዊት ይህን የሚሰሩለት ሌሎች ሰዎች እንደነበሩተረ አንባቢው መረዳት እንዲችል ተደርጎ ሊተረጎም ይችላል። አት: “ዳዊት ቤት የሚሰሩለት ሰራተኞች ነበሩተ ... እንዲያዘጋጁ አደረጋቸው” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ከመረጣቸው
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “እግዚአብሔር መረጣቸው” (ገባሪ ወይም ተገባሪ: ይመልከቱ)

ዳቂት .... እስራኤልን ሁሉ ወደ ኢየሩሳሌም ሰበሰበ
እዚህ ላይ “ሁሉም” የሚለው ቃል አጠቃላይ ነው። “እስራኤል ሁሉ” የሚለው ሐረግ ዳዊት ከመላው እስራኤል ሰውዎችን መሰብሰቡን እንጂ እስራኤልን እያንዳንዱን ግለሰብ ሰብስቦ አይደለም። አት. “ዳዊት ከመላው እስራኤል በኢየሩሳሌም ሰዎችን ሰበሰበ” (ቃል አጋኖ እና ማጠቃለል: ይመልከቱ)

1 Chronicles 15:4

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ዳዊት ከእያንዳንዱ ከሌዋውያን ጎሳ ያሰባሰባቸውን ሰዎች ዝርዝር ይጀምራል። (የስሞችን እና ቁጥሮችን አተረጓጎም : ይመልከቱ)

120 ወንዶች
“አንድ መቶ ሀያ ሰዎች” (ቁጥሮችን: ይመልከቱ)

220 ወንዶች
“ሁለት መቶ ሀያ ሰዎች” (ቁጥሮችን: ይመልከቱ)

1 Chronicles 15:7

አያያዥ መግለጫ:
ይህ ዳዊት ከእያንዳንዱ ከሌዋውያን ጎሳ ያሰባሰባቸውን ሰዎች ዝርዝር ይቀጥላል። (የስሞችን እና ቁጥሮችን አተረጓጎም : ይመልከቱ)

1 Chronicles 15:11

ኡርኤልን፥ ዓሣያን፥ ኢዮኤልን፥ ሸማያን፥ ኤሊኤልን፥ አሚናዳብንም
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው :: በ 1ኛ ዜና 5-6 እና በ1 ዜና 7-10 እንዴት እንደተረጉሟቸው ይመልከቱ:: (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

1 Chronicles 15:13

አልተሸከማችሁምና
“መርከቡን አልተሸከምክም”

በመካከላችን ስብራት አደረገ
“ለመዋጋት” የሚለው ፈሊጥ በአንድ ሰው ላይ የኃይል እርምጃ መውሰድ ማለት ነው። አት: - “ጥቃት ተሰነዘረብን” ወይም “ጥቃት ሰነዘረብን” (ፈሊጥ: ተመልከት)

አልፈለግነውምና
እዚህ እግዚአብሔርን መፈለግ ማለት ምክሩን መፈለግ ማለት ነው። አት: - “መመሪያ እንዲሰጠን አልጠየቅነውም” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንዳዘዘው እንደ እግዚአብሔር ቃል
“ቃል” የሚለው ቃል በግስ ሊተረጎም ይችላል። ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “የያህዌ ቃል የሰጣቸው ሕጎች” ወይም “ያህዌ የተናገራቸው ሕጎች” (ገባሪ ወይም ተገባሪ እና ረኪክ ስሞች፡ ይመልከቱ)

1 Chronicles 15:16

አያያዥ መግለጫ፡
ይህ ሕዝቡ ታቦቱን ወደ ኢየሱሳሌም ሲያመጡ ሌዋውያኑ እንዲዘምሩና ሙዚቃ እንዲጫወቱ የሾሟቸው ሰዎች ዝርዝር ይጀምራል። (የስሞችን አተረጓጎም ፡ ይመልከቱ)

በጸናጽልም
ከፍተኛ ድምጽ ለመፍጠር አንድ ላይ የሚመቱ ሁለት ቀጭን እና ክብ የብረት ሳህኖች። ይህን 1 ዜና 13:8 እንዴት እንደተረጎሙት ይዩ (የማይታወቁ ይተርጉሙ፡ ይመልከቱ)

ድምፃቸውንም ... ከፍ እንዲያደርጉ
ይህ ፈሊጥ ማለት ጮክ ብሎ መዘመር ማለት ነው ። አት: - “በታላቅ ድምፅ መዘመር” (ፈሊጥን፡ ይመልከቱ)

ከእነርሱም ጋር በሁለተኛው ተራ የሆኑትን ወንድሞቻቸውን
ይህ ምናልባት እነዚህ ሰዎች በዝቅተኛ ቦታዎች ያገለገሉ በነር እነርሱም ለኤማን ፣ ለአሳፍ እና ለኢታን ረዳቶች ነበሩ ማለት ሊሆን ይችላል። አት: - “በዝቅተኛ ቦታ ላይ ያሉ ዘመዶቻቸው ከእነርሱ ጋር ነበሩ” ወይም “የሚከተሏቸው ዘመዶች ይረዷቸው ነበር” (ተራ ቁጥር ቁጥሮች፡ ይመልከቱ)

ሚቅንያን, በረኞችንም ዖቤድኤዶምንና ይዒኤልን
“በር ጠባቂዎች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በሮች ወይም መግቢያዎችን የሚጠብቁ ሰዎችን ነው ። እዚህ ላይ የቃል ኪዳኑን ታቦት የመጠበቅን መብት የሚያመለክት ሲሆን ለኦቤድኤዶም እና ለያ .ል ይመለከታል ። አት: - “ሚካናህ፣ እና በረኞች፣ ኦቤድ ኤዶም እና ያይል” (የተገመተ ዕውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ፡ ይመልከቱ)

1 Chronicles 15:19

አያያዥ መግለጫ፡
ሕዝቡ ታቦቱን ወደ ኢየሩሳሌም ሲያመጡ ሌዋውያኑ እንዲዘምሩና ሙዚቃ እንዲጫወቱ የሾሟቸውን ወንዶች ዝርዝር ይቀጥላል። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ይመልከቱ፡)

መዘምራንም ኤማንና አሳፍ ኤታንም ... ነበር
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “ሌዋውያን ኤማን፣ አሳፍ እና ኢታን ሙዚቀኞችን ሾሙ” (ገባሪ ወይም ተገባሪ፡ ይመልከቱ)

ጸናጽል
ከፍተኛ ድምጽ ለመፍጠር አንድ ላይ የሚመቱ ሁለት ቀጭን እና ክብ የብረት ሳህኖች። ይህንን በ1ኛ ዜና 13:8 ውስጥ እንዴት እንደተረጉሙ ይመልከቱ ። (የማይታወቁትን ይተርጉሙ፡ ይመልከቱ)

አላሞት ... ሸሚኒት
የእነዚህ ቃላት ትርጉም ግልፅ አይደለም ግን የሙዚቃ ዘይቤን ሊያመለክት ይችላል ። (የማይታወቁትን ይተርጉሙይመልከቱ)

መንገዱን መሩ
“ሌሎቹን ሙዚቀኞች መራ” ወይም “ሰልፈኛውን መራ”

1 Chronicles 15:22

አያያዥ መግለጫ፡
ይህ ሕዝቡ ታቦቱን ወደ ኢየሩሳሌም ሲያመጡ ሌዋውያኑ እንዲዘምሩና ሙዚቃ እንዲጫወቱ የሾሟቸውን ወንዶች ዝርዝር ይቀጥላል። (የስሞችን አተረጓጎም፡ ይመልከቱ)

1 Chronicles 15:25

የሻለቆችም
አማራጭ ትርጉሞች 1) the word “ሺዎች” የሚለው ቃል እያንዳንዱ መሪ የመራቸውን ወታደሮች ሊገላ ይገልጻል። አት: - “የ 1,000 ወታደሮች አዛዥ” ወይም 2) “በሺዎች” ተብሎ የተተረጎመው ቃል ትክክለኛ ቁጥሮችን አይወክልም ፣ ነገር ግን ትልቅ የጦር ሰራዊት ስም ነው። አት: - “ትልቅ የጦር ሰራዊት ክፍል አዛዥ” (ቁጥሮችን፡ ይመልከቱ)

ዖቤድኤዶም
ይህ የወንድ ስም ነው።

1 Chronicles 15:27

ዳዊትም፥ ታቦቱንም የተሸከሙ ሌዋውያን ሁሉ፥ መዘምራኑም፥ የመዘምራኑም አለቃ ከናንያ የጥሩ በፍታ ቀሚስ ለብሰው ነበር
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “ዳዊት፣ ታቦቱን የተሸከሙት ሌዋውያን ፣ ዘማሪዎቹ እና ከዘማሪዎቹ ጋር የዘማሪዎቹ አለቃ ሁሉ ጥሩ የበፍታ ቀሚስ ለብሰዋል” (ገባሪ ወይም ተገባሪ ተመልከት)

የበፍታ
ከፍላክስ አትክልት የተሰራ ልብስ

ከናንያ
ይህ የወንድ ስም ነው።

እስራኤል ሁሉ ... የቃል ኪዳን ታቦት አመጡ
እዚህ ላይ “ሁሉም” የሚለው ቃል አጠቃላይ ነው። አት: “ስለዚህ እጅግ ብዙ ሰዎች ታቦቱን አመጡ” (ቃል አጋኖ እና መጠቅለል: ይመልከቱ)

ጸናጽልና
ከፍተኛ ድምጽ ለመፍጠር አንድ ላይ የሚመቱ ሁለት ቀጭን እና ክብ የብረት ሳህኖች። ይህንን በ1ኛ ዜና 13:8 ውስጥ እንዴት እንደተረጉሙ ይመልከቱ። (የማይታወቁትን ይተርጉሙ፡ ይመልከቱ)

1 Chronicles 15:29

የእግዚአብሔርም ቃል ኪዳን ታቦት ወደ ዳዊት ከተማ በደረሰ
“ሕዝቡ የያህዌን የቃል ኪዳኑን ታቦት ወደ ዳዊት ከተማ ሲያመጡ”

ሜልኮል
ይህ የዳዊት ሚስት ስም ነው። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

በልቧ ናቀችው
እዚህ “ልብ” ሀሳቦችን ወይም ስሜቶችን ይወክላል። አት: - “ናቀችው” ወይም “ጠላችው”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 16

1 ከዚያም የእግዚአብሔር ታቦት አምጥተው ዳዊት በተከለለት ድንኳን ውስጥ አኖሩት፤የሚዋጠል መሥዕዋትና የኅብረት መሥዕዋትም በእግዚአብሔር ፊት
አቀረቡ። 2 ዳዊት የሚቃጠለውን መሥዕዋትና የኅብረቱ መሥዕዋት ከሠዋ በኋላ፣ህዝቡን በእግዚአብሔር ስም ባረከ። 3 ከዚያም ለእስራኤል ሁሉ ለወንዱም
ልችሴቱም አንዳንድ ሙልሙል ዳቦ፣አንዳንድ ጥፍጥፍ ዘቢብ ሰጠ። 4 በእግዚአብሔር ታቦት ፊት እንዲያገለግሉና ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር
ልመና፣ምስጋናና ውዳሴ እንዲቀርቡ ከሌዋውያን ሰዎች ሾሙ፤ 5 አለቃው አሳፍ ነበረ፤ከእርሱ ቀጥሎ ዘካሪያስ ሁለተኛ ሆኖ ተሾመ፤ከዚያም
ይዒኤል፣ሰሚራሞት፣ይሒኤል፣መቲትያ፣ኤልያብ፣በናያስ፣ ዖቤድኤዶም፣ይዒኤል ተሾሙ፤እነሱም በመሰንቆና በበገና ይዘምሩ ነበር፤አሳፍ ደግሞ ጽናጽል
የሚጸነጽል ሆኖ ተመደበ። 6 እንዲሁም ካህናቱ በናያስና የሕዚኤል ዘውትር በእግዚአብሔር የኪዳኑ ታቦቱ ፊት መለከት እንዲነፉ ተመደቡ። 7 በዚያም ቀን ዳዊት
በመጀመሪያ ለአሳፍና ለሥራ ጓደኞቹ ይህን የእግዚአብሔር ምስጋና መዝሙር ሰጠ፤ 8 ለእግዚአብሔር ምስጋና አቅርቡ፤ስሙንም ጥሩ፤ለአሕዛብ ያደረገውን ሁሉ
ንገሩ፤ 9 ዘምሩለት፤ውዳሴም አቅርቡለት፤ድንቅ ሥራውን ሁሉ ንገሩ፤ 10 በቅዱስ ስሙ ተጓደዱ፤እግዚአብሔር የሚፈልግ ሁሉ፤ልባቸው ሐሤት ያድርግ፤ 11 ወደ
እግዚአብሔር ወደ ኀይሉ ተምልከቱ፤ዘውትር ፊቱን ፈልጉ፤ 12 ይደረጋቸውን ድንቅ ሥራዎች፣ታምራቱንና የሰጠውንም ፍርድ አስታውሱ፤ 13 እናንተ የባሪያው
የእስራኤል ዘሮች፣እናንተ የተመረጣችሁ የያዕቆብ ልጆች። 14 እርሱ እግዚአብሔር አምልካችን ነው፤ፍርዱም በምድር ሁሉ ላዬ ነው፤ 15 ኪዳኑን እስከ
ዘላለም፣ይያዘዘውንም ቃል እስከ ሺህ ትውልድ ያስባል፤ 16 ከአብርሃም ጋር የገባውን ቃል ኪዳን፣ለይስሐቅ የማለውን መሐላ። 17 ይህንንም ለያዕቆብ ሥርዐት
አድርጎ አጸና፤ለእስራኤልም የዘላለም ኪዳን አደረገ፤ 18 እንዲህ ሱል "የምትወርሰው ርስት እንዲሆን፣የከነዓንን ምድር ለአንተ እሰታለሁ።" 19 ቁጥራቸው ገና
ጥቂት ሳለ፤በርግጥ ጥቂትና መጻተኞች ሳሉ፤ 20 ከአንዱ ሕዝብ ወደ ሌላው ሕዝብ ከአንዱም መንግሥት ወደ ሌላው መንግሥት ተንከራተቱ። 21 ማንም
እንዲጨቁናቸው አልፈቅድም፤ስለ እነርሱም ነገሥታትን ገሠጸ፤ 22 እንዲህ ሲል፤"የቀባኋቸውን አትንኩ፤በነብያቴ ላይ ክፉ አታድርጉ።" 23 ምድር ሁሉ
ለእግዚአብሔር ዘምሩ፤ማዳኑንም ዕለት ዕለት ዐውጁ። 24 ክብሩን ለአሕዛብ ተናገሩ፤ድንቅ ሥራዎቹን ለሕዝቦች ሁሉ ንገሩ። 25 እግዚአብሔር ታላቅ
ነው፤ምስጋናውም ብዙ ነው፤ከአማልዕክትም ሁሉ በላይ ሊፈራ የሚገባው ነው። 26 የአሕዛብ ሁሉ አማልክት ጣዖታት ናቸው፤እግዚአብሔር ግን ሰማያትን ሠራ።
27 በፊቱ ክብርና ሞገስ አለ፤ ብርታትና ደስታም በማድሪያው ስፍራ። 28 የአሕዛብ ወገኖች ለእግዚአብሔር ስጡ፤ክብርና ኀይልን ለእግዚአብሔር አምጡ። 29
ለስሙ የሚገባውን ክብር ለእግዚአብሔር ሰጡ፤መባ ይዛችሁ በፊቱ ቅረቡ፤በቅድስናውም ክብር ለእግዚአብሔር ሰገዱ። 30 ምድር ሁሉ በፊቱ
ትንቀጥቀጥ፤ዓለም በጽኑ ተመሥርታለች፤አትናወጥምም። 31 ሰማያት ደስ ይባላቸው፤ምድር ሐሤት ታድርግ፤በአሕዛብ መካከል፣"እግዚአብሔር
ነገሠ!"ይበሉ። 32 ባሕርና በውስጧ ያለው ሁሉ ይናውጥ፤ሜዳዎችና በእርሷ ላይ ያሉ ሁሉ ሐሤት ያድርጉ። 33 ያን ጊዜ የዱር ዛፎች በእግዚአብሔር ፊት ደስ
ይበላቸው፤በደስታ ይዘምራሉ፤በምድር ላይ ሊፈርዱ ይመጣልና። 34 ቸር ነውና እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ፍቅሩንም ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል። 35 «አዳኛችን
እግዚአብሔር ሆይ፤ታደገን፤ለቅዱስ ስምህ ምስጋና እንድናቀርብ፣በምስጋናም እንድንከብር ስብሰበን"ብላችሁ ጩኹ። 36 ከዘላለም እስከ ዘላለም፣ለእስራኤል
አምላክ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን።ከዚያም ሕዝቡ ሁሉ፣"አሜን፤እግዚአብሔር ይመስገን"አለ። 37 ዳዊትም ለእያንዳንዱ ቀን በተመደበው መሠረት ዘውትር
እንዲያገለግሉ አሳፍና የሥራ ባልደረቦቹን በዚያው በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ታቦት ፊት ተዋቸው። 38 እንዲሁም ዖቡድኤዶምና ሥልሳ ስምንቱ የሥራ
ባልደረቦቹ አብረዋቸው እንዲያገለግሉ በዚያው ተዋቸው።የኤዶታም ልጅ ዖቤድኤዶምና ሖላ የቅጥሩ በር ጠባቂዎች ሆኑ። 39 ዳዊት ካህኑን ሳዶቅንና የሥራ
ባልደረቦቹን ካህናት በገባዖን ከፍተኛ ቦታ ላይ በሚገኘው በእግዚአብሔር ድንኳን ፊት ተዋቸው፤ 40 የተዋቸውም ለእስራኤል በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት
በእግዚአብሔር ሕግ እንደ ተጻፈው ሁሉ በመሠዊያው ላይ የሚቀርበውን የሚቃጠል መሥዕዋት ላይ የሚቀርበውን የሚቃጠል መሥዋዕት ጧትና ማታ በየጊዜው
እንዲያቀርቡ ነው። 41 ደግሞም፤"ፍቅሩ ለዘላለም ነውና"እያሉ ምስጋና እንዲያቀርቡ ኤማንና ኤዶታም እንዲሁም ተመርጠውና ስማቸው ተመዝግቦ የተመደቡ
ሌሎችም አብረዋቸው ነበሩ። 42 ድምፅ መለከቱንና ጽናጽሉን ለማሰማት፤ደግሞም መንፈሳዊ መዝሙር ሲዘመር ሊጠቀሙባቸው ሌሎች መሣሪያዎች
ኅላፊዎች ኤማንና ኤዶታም ነበሩ፤የኤዶታምም ልጆች በሩን እንዲጠብቁ ተመድበው ነበር። 43 ከዚያም ህዝቡ ተነሣ፤እያንዳንዱም ወደየቤቱ ሄደ።ዳዊትም ቤተ
ሰቡን ለመባረክ ወደ ቤቱ ተመለሰ።

---

1 Chronicles 16:1

አጠቃላይ መረጃ:
በእነዚህ ቁጥሮች ላይ “እነሱ” የሚለው ቃል ካህናትንና ሌዋውያንን ያመለክታል።

በእግዚአብሔር ፊት
“ወደ እግዚአብሔር”

ዳዊትም የሚቃጠለውን መሥዋዕትና የደኅንነቱን መሥዋዕት ማቅረብ በፈጸመ ጊዜ
ይህ መስዋዕት የማቅረብ ዋነኛውን ስራ ሲሰሩ ካህናቱን ሲመራቸው ለዳዊት የባህሪ ስም ነው። (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

ዳዊትም የሚቃጠለውን መሥዋዕትና የደኅንነቱን መሥዋዕት ማቅረብ በፈጸመ ጊዜ
“በያህዌ ስም” መባረክ ማለት በያህዌ ኃይል እና ስልጣን ወይም እንደ ተወካይ መባረክ ማለት ነው። (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

ለእስራኤልም ሁሉ አካፈለ
ይህ የተከናወነው በዳዊት ስልጣን እና አመራር ነበር። (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

የዘቢብ ጥፍጥፍ
ከደረቀ ወይን ጋር የተጋገረ ጣፋጭ እንጀራ

1 Chronicles 16:4

ዘካርያስ፣ ይዒኤል፣ ሰሚራሞት፥ ይሒኤል፥ መቲትያ፥ ኤልያብ፥ በናያስ፥ ዖቤድኤዶምና፥ ይዒኤል... በናያስና የሕዚኤል
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

ከእርሱም በኋላ
ይህ ማለት በሥልጣን እና በቦታ ከእሱ ቀጥሎ ማለት ነው። (ሕገኛ ቁጥሮች: ይመልከቱ)

በጸናጽል
እነዚህ ድምፅ ለመፍጠር አንድ ላይ የሚመቱ ሁለት ቀጭንና ክብ የብረት ሰሌዳዎች ናቸው። ይህንን በ 1ኛ ዜና13፡ 8 ውስጥ እንዴት እንደተረጉሙ ይመልከቱ ። (የማይታወቁትን ይተርጉሙ፡ ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Chronicles 16:7

በዚያ ቀን
እዚህ “ያ ቀን” እዚህ ላይ የሚያመለክተው የቃል ኪዳኑ ታቦት ከኦቤድኤዶም ቤት ወደ ኢየሩሳሌም የተላለፈበትን ቀን ነው።

የምስጋና መዝሙር
“የምስጋና መዝሙር”

ስሙን ጥሩ
እዚህ “ስሙ” ያህዌን ይወክላል። አት: - “ያህዌን ይጥሩ” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

ለአሕዛብ
ይህ በአገራቱ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ያመለክታል። አት: - “የአገራቱ ሕዝቦች” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

1 Chronicles 16:10

በቅዱስ ስሙ ተጓደዱ
እዚህ “ቅዱስ ስሙ” ያህዌን ይወክላል። አት: - “በያህዌ ማንነት መመካት” ወይም “በያህዌ መመካት” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን የሚፈልግ ልብ ደስ ይበለው
እዚህ “ልብ” ያህዌን የሚፈልግን ሰው ይወክላል። አት: “ያዌን የሚሹ ሰዎች ደስ ይበላቸው” (Synecdoche: ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን ፈልጉት፥ ትጸናላችሁም
“የይሕዌን ብርታት መፈለግ” እርሱ እንዲያጠነክርህ መጠየቅ ማለት ነው። አት: “እግዚአብሔርን ፈልጉ እና ኃይሉንም እንዲሰጥ ጠይቁት” (ፈሊጥ: ይመልከቱ)

ሁልጊዜ ፊቱን ፈልጉ
“ሁልጊዜ ወደ እሱ ለመቅረብ ፈልጉ”

1 Chronicles 16:12

የሠራትን ድንቅ አስቡ “አስደናቂዎቹን ነገሮች አስታውሱ” ተአምራቱንም
የተረዱትን ግስ ማስገባት ይችላል። አት: - “ተዓምራቱን አስታውሱ” (ግድፈተ ቃላት: ይመልከቱ)

የአፉንም ፍርድ
እዚህ “አፍ” ያህዌ የተናገረውን ያመለክታል። አት: - “እሱ የተናገረው ድንጋጌዎች” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

ባሪያዎቹ የእስራኤል ዘር፥ ለእርሱም የተመረጣችሁ የያዕቆብ ልጆች ሆይ
እነዚህ ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉሞችን የሚያጋሩ ሲሆን ለማጉላት ጥቅም ላይ ይውላሉ። (ትይዩአዊ: ይመልከቱ)

ፍርዱ በምድር ሁሉ ነው
እዚህ ላይ “ምድር ሁሉ” የሚያመለክተው የምድር ሰዎችን ሁሉ ነው። አት: - “ሕጎቹ ለምድር ሕዝቦች ሁሉ” ናቸው (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

1 Chronicles 16:15

ቃል ኪዳኑን ለዘላለም፥ እስከ ሺህ ትውልድ ... አሰበ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉሞችን የሚያጋሩ ሲሆን ለማጉላት በጋራ ያገለግላሉ። እዚህ “ቃል” ቃል ኪዳኑን ያመለክታል። እዚህ “ቃል” ቃል ኪዳኑን ያመለክታል። (ትይዩአዊ እና የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

ቃል ኪዳኑን ... አሰበ
ይህ ማለት ስለ ኪዳኑ ማስታወስ እና ማሰብ ማለት ነው። አት: “ቃል ኪዳኑን አስቡ” (ፈሊጥ: ይመልከቱ)

ሺህ ትውልድ
“1,000 ትውልዶች” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

አሰበ
“ወደ አእምሮ መጥራት” የሚለው ሐረግ አንድን ነገር ማስታወስ ማለት ነው። አት: - “ያስታውሳል” (ፈሊጥ: ይመልከቱ)

ለአብርሃም ያደረገውን፥ ለይስሐቅም የማለውን
ሁለቱም “ቃል ኪዳኑ” እና “መሐላ” የሚያመለክቱት ያህዌ ለሕዝቡ የገባውን ተመሳሳይ ተስፋ ነው ። (ትይዩአዊ: ይመልከቱ)

ለይስሐቅም የማለውን
ይህ ቀደም ሲል ለይስሐቅ የገባውን መሐላ ያመለክታል። AT: “ለይስሐቅ በገባው መሐላ” (ግድፈተ ቃላት: ይመልከቱ)

የርስታችሁን
“እንደ ራስህ አካል

1 Chronicles 16:19

አያያዥ መግለጫ
በእነዚህ ቁጥሮች ላይ “እርስዎ ፣” “እነሱ ፣” “እነሱ ፣” እና “የእነሱ” የሚሉት ቃላት እስራኤልን ያመለክታሉ።

ስደተኞች
“ምድሪቱ” የሚለው ከነዓንን እንደሚያመለክት ታሳቢ ሆኗል። አት: - “በከነዓን ምድር እንግዶች” (ታሳቢ የሆነ እውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ: ይመልከቱ)

ሕዝብ ወደ ሕዝብ፥ ከመንግሥትም ወደ ሌላ ሕዝብ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው እና ለማጉላት በጋራ ጥቅም ላይ ይውላሉ። (ትይዩአዊ: ይመልከቱ)

ስለ እነርሱም
“ለእራሳቸው ደህንነት”

ቀባኋቸውን አትዳስሱ
እዚህ “መንካት” ማለት መጉዳት ማለት ነው። ይህ ህዝቡን ላለመጉዳት ያህዌ ማስጠንቀቂያን ያጠናከረበት የተጋነነ አገላለፅ ነው። አት: - “የቀባኋቸውን ሰዎች አትጎዱ” (ቃል አጋኖ እና መጠቅለል: ይመልከቱ)

1 Chronicles 16:23

አጠቃላይ መረጃ:
ትይዩነት በዕብራይስጥ ቅኔ ውስጥ የተለመደ ነው ። (ቅኔ እና ትይዩአዊ: ይመልከቱ)

ምድር ሁሉ
ይህ የምድሪቱን ሰዎች ያመለክታል። አት: “በምድሪቱ ላይ የምትኖሩ ሁሉ”

ዳኑን አውሩ
“መዳን” የሚለው ስም “መዳን” በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። አት: - “እርሱ ማዳኑን አውጁ” ወይም “የሚያድነው እርሱ መሆኑን ለሰዎች ንገሩ” (ረኪክ ስሞች: ይመልከቱ)

ዕለት ዕለት
"በየቀኑ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ክብሩን ለአሕዛብ ... ንገሩ
“በሁሉም አገር ለሕዝብ ሁሉ ስለ ታላቅ ክብሩ ተናገሩ ”

1 Chronicles 16:25

እግዚአብሔር ታላቅ፥ ምስጋናውም ብዙ ነውና
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። አት: - “ይህዌ ታላቅ ነው። እጅግ በጣም አወድሱት ”ወይም“ ያህዌ ታላቅ ነው፤ ሰዎችም እጅግ ሊያወድሱት ይገባል” (ገባሪ ወይም ተገባሪ: ይመልከቱ)

አማልክትም ሁሉ ላይ የተፈራ ነው
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። አት: - “ከሌሎች አማልክት ሁሉ በላይ እሱን ፍሩ” (ገባሪ ወይም ተገባሪ: ይመልከቱ)

ክብርና ግርማ በፊቱ ... ናቸው
ደራሲው ግርማ እና ታላቅነት በንጉሥ ፊት ሊቆም የሚችሉ ሰዎች ናቸው ብሎ ይናገራል። (ሰብአዊ: ይመልከቱ)

በፊቱ
“ዙሪያውን” ወይም “እሱ ያለበትን ቦታ”

ኃይልና ደስታ በስፍራው ውስጥ ናቸው
ደራሲው ሀይል እና ደስታ በያህዌ መቅደስ ውስጥ ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎች እንደሆኑ ይናገራል። (ሰብአዊ: ይመልከቱ)

በስፍራው
“በቤተ መቅደሱ” ወይም “በቤተ መቅደሱ ውስጥ”

1 Chronicles 16:28

ለእግዚአብሔር አምጡ
“ለያህዌ ውዳሴ ስጡት” ወይም “ያህዌን አወድሱ”

ክብርንና ኃይልን ለእግዚአብሔር አምጡ
ረኪክ የሆኑት “ክብር” እና “ሐይል” የተባሉት ስሞች እንደ ቅፅል ሊገለጹ ይችላሉ። አት.: - “ክቡርና ሀያል ስለሆነ እግዚአብሔርን አመስግኑ” (ረኪክ ስሞች: ይመልከቱ)

ለስሙ የሚገባ ክብርን ለእግዚአብሔር አምጡ
ረኪክ የሆነው “ክብር” የሚለው ስም እንደ ግስ ወይም እንደ ቅፅል ሊገለፅ ይችላል። አት: “ለስሙ እንደሚገባ ያህዌን አክብሩት” ወይም “ያህዌ ልክ እንደስሙ የከበረ መሆኑን አውጁ” (አት: - “በቤቴል ተይዘው ይኖራሉ... መንደሮች” ወይም “በቤቴል ውስጥ ተይዘው ይኖራሉ ።: ይመልከቱ)

ለስሙ የሚገባ ... አምጡ
እዚህ ላይ “ስሙ” የእግዚአብሔርን ማንነት ያመለክታል። አት: “በእርሱ ምክንያት” ወይም “እሱ ይገባዋል” ወይም “ሊቀበለው የሚገባው ነው” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

ለእግዚአብሔር ስገዱ
በተዘዋዋሪ የቀረበው መረጃ ህዝቡ ለአምልኮ መስገድ እንዳለበት ነው። አት: - “ያህዌን ለማምለክ ስገድ” (ታሳቢ የሆነ እውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ እና ምሳሌያዊ ድርጊት: ይመልከቱ)

በቅድስናው ስፍራ
ግልጽ ያልሆኑት ስሞች “ግርማ” እና “ቅድስና” እንደ ቅፅል ሊተረጎሙ ይችላሉ። አት: - “እርሱ እጅግ ውብና ቅዱስ ስለሆነ” (ረኪክ ስሞች: ይመልከቱ)

1 Chronicles 16:30

ትነዋወጥ
በፍርሃት ተንቀጠቀጡ

ምድር ሁሉ
ይህ በምድር ላይ ለሚኖሩት ሰዎች ሁሉ ዘይቤ ነው። አት: “የምድር ሕዝብ ሁሉ” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

ሰማያት ደስ ይበላቸው፥ ምድርም ሐሴትን ታድርግ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሰማያትና ምድር የሰዎች ስሜት እንዳላቸው ተደርገው ተገልጠዋል። አት: “ሰማያት ደስ እንዳላቸው ምድርም ሀሴት እንዳደረገች ይሁን” ወይም 2) “ሰማያት” እና “ምድር” በእነዚህ ቦታዎች ለሚኖሩ የባህሪ ስም ነው። አት: “በሰማያት የሚኖሩ ደስ ይበላቸው እናም በምድር የሚኖሩ ሀሴትን ያድርጉ” (ሰብአዊ እና የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

1 Chronicles 16:32

ባሕርና ሞላዋ
የተዘገበው መረጃ ይህ በባህሩ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ፍጥረታት የሚያመለክት ነው። ሰዎች እንደሚያደርጉት በደስታ እንሲጮኹ ይናገሩ ነበር። አት: - “የባሕር ፍጥረታት በደስታ እልል ይላሉ” (ታሳቢ የሆነ እውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ እና ሰብአዊ: ይመልከቱ)

በእርሷም ያሉ ሁሉ ሐሤትን ያድርጉ
“ሜዳዎቹና በውስጣቸው ያሉቱ ሁሉ ደስ ይበላቸው” ፀሀፊው ሜዳዎቹና የሚኖሩባቸው እንስሳቱ ልክ እነደ ሰዎች ስሜት እንዳላቸው አድርጎ ይናገራል። አት: “ሜዳዎቹ ራሰቸው እና የሚኖሩባቸው እንስሳቱ ደስ እንዳለቸው ተደርጎ ይቆጠር” (ሰብአዊ: ይመልከቱ)

የዱር ዛፎች በዚያን ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ደስ ይላቸዋል
ይህ የሚናገረው በደስታ እንደ ሰዎች ስለሚጮሁ ዛፎች ነው። (ሰብአዊ: ይመልከቱ)

1 Chronicles 16:34

ምህረቱም ለዘላለም ነው
ረኪክ ይሆነው “ታማኝነት የሚለው ስም” “በታናኝነት” ወይም “ታማኝ” ተብሎ መገለፅ ይችላል። አት: “እርሱ በታማኝነት ለዘላለም ይወደናልና” ወይም “ለዘላለም ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ነው” (ረኪክ ስም: ይመልከቱ)

ከአሕዛብ
እዚህ ጋር “ሌሎቹ ሕዝቦች” በእዚሁ አገራት ውስጥ ያሉትን ሕዝቦች ይወክላል። አት: - “ከሌሎች ሕዝቦች ሰዎች” ወይም “ከሌሎች ሕዝቦች ሠራዊት” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

ስምህን እናመሰግን ዘንድ
እዚህ ያህዌ “በቅዱስ ስሙ” ተጠቅሷል። አት: - “አመሰግናለሁ” ወይም “ያህዌን አመስግን” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)1 ዜና መዋዕል 16:36 የትርጉም ማስታዎሻዎች

1 Chronicles 16:36

ከዘላለም እስከ ዘላለም
ይህ ሁለት ጽንፎችን እና መንገዶችን ለሁሉም ጊዜ የሚያመለክት ነው። አት: - “ለዘለዓለም” (ሜሪዝም: ይመልከቱ)

ሕዝቡም ሁሉ
ይህ ያህዌን ለማምለክ የተሰበሰቡትን ሰዎች ስብስብ የሚያመለክት አጠቃላይ መግለጫ ነው። “ሕዝቡ” ወይም “እዚያ የነበረው ሰው ሁሉ” (ቃል አጋኖ እና መጠቅለል: ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Chronicles 16:37

ወንድሞቹን
“ዘመዶቹ”

በየቀኑ እንደሚገባቸው
ታሳቢ የተደረገው መረጃ በያህዌ ሕግ ውስጥ የተሰጠውን ዕለታዊ ሥራ ማከናወን እንደነበረባቸው ያሳያል። አት: - “በየዕለቱ በሕጉ እንደሚፈለግ” (ታሳቢ እውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ: ይመልከቱ)

የኤዶታምም፣ ያቤድኤዶምና ሖሳ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ነበሩ።

ስድሳ ስምንቱንም ወንድሞቻቸውን
“68 ዘመዶች” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

ቃል ኪዳን ታቦት ፊት ተዋቸው
“በመገናኛው ድንኳን ለማገልገል”

1 Chronicles 16:40

አጠቃላይ መረጃ:
በእነዚህ ቁጥሮች ላይ “እነሱ” እና “እነሱ” የሚሉት ቃላት ካህናትን ያመለክታሉ።

ሁል ጊዜ ጥዋትና ማታ
“በየቀኑ ጠዋት”

ኤማንንና ኤዶታምን
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

1 Chronicles 16:42

ጸናጽል
እነዚህ ድምፅ ለመፍጠር አንድ ላይ የሚመቱ ሁለት ቀጭንና ክብ የብረት ሰሌዳዎች ናቸው። ይህንን በ 1ኛ ዜና 13፡8 ውስጥ እንዴት እንደተረጉሙ ይመልከቱ ። (የማይታወቁትን መተርጎም: ይመልከቱ)

በረኞች ነበሩ
ታሳቢ የሆነው መረጃ የመገናኛውን ድንኳን ደጃፍ መጠበቅ እንደነበረባቸው የሚያሳይ ነው። አት: - “የማደሪያ ድንኳኑን በር ጠበቁ” (ታሳቢ እውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ: ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 17

1 ዳዊት በቤተ መንግሥቱ ተደላድሎ በተቀመጠበት ጊዜ፤ነቢዩ ናታንን"እነሆ እኔ ከዝግባ በተሠራ ቤት ውስጥ እኖራለሁ፤የእግዚአብሔር የኮዳኑ ታቦት ግን በድንኳን ውስጥ ይኖራል"አለው። 2 ናታንም ለዳዊት፣"እግግዚአብሔር ከአንተ ጋር ስለሆነ፣ያሰብከውን ሁሉ እድርግ"ሲል መለሰለት። 3 በዚያም ሌሊት የእግዚአብሔር ቃል ወደ ናታን መጥቶ እንዲህ አለው፤ 4 "ሂድና ለባርያዬ ለዳዊት እንዲህ ብለህ ንገረው፤እግዚአብሔር የሚለውን ይህን ነው፤እኔ የምኖርበትን ቤት የምትሠራልኝ አንንተ አይደለህም። 5 እስራኤልን ከግብፅ ካወጣሁበት ቀን ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ፤ከአንዱ ድንኳን ወደ ሌላው ማደሪያ እሄድ ነበር እንጂ፣በቤት ውስጥ አልኖርሁም። 6 ከእስራኤላዊያን ጋር በሄድኩባቸው ቦታዎች ሁሉ፣ሕዝቤን እንዲጠብቁ ላዘዝኋቸው መሮዎቻቸው ከቶ፣"ለምን ከዝግባ ዕንጨት ቤት አልሰራችሁልኝምያልሁበት ጊዜ አለን?፤ 7 "ከእንግዲህ አሁንም ለባሪያዬ ለዳዊት እንዲህ ብለህ ንገረው፤የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር የሚለው ይህን ነው፤የሕዝቤ ይእስራኤል ገዥ እንድትሆን በጎችን ከመጠበቅና ከመከትተል አንሥቶ ወሰድሁህ። 8 በሄድህበት ሁሉ ከአንተ አልተለየሁህም፤ጠላቶችህም ስምህን እንደ ምድር ታላላቅ ሰዎች ስም ገናና አደርገዋለሁ። 9 ለሕዝቤ ለእስራኤል መኖሪያ ስፍራ እሰጥተዋለሁ፤የራሳቸውም መኖሪያ ስፍራ እንዲኖራቸው ከእንግዲህም በኋላ እንዳይናወጡ አደርጋቸዋለሁ።ክፉ ሰዎች በመጀመሪያ እንዳደረጉት ሁሉ፤ከእንግዲህ አይጨቁናቸውም፤ 10 ከዚህ ቀደም በሕዝቤ በእስራኤል ላይ መሪዎች በሾምሁ ጊዜ ጨቋኞቹ ያደረጉትን ዛሬ አያደርጉትም፤ጠላቶቻችሁም ሁሉ አዋርዳቸዋለሁ።"እግዚአብሄር ቤት እንደሚሠራልህ በግልፅ እነግርሃለሁ፤ 11 ዘመንህን ጨርሰህ ወደ አባቶችህ በምትሄድበት ጊዜ፤ከአብራክህ ከተከፈሉት ልጆችህ አንዱ በእግርህ እንዲተካ አደረጋለሁ፤መንግሥቱንም አፅናለሁ፤ 12 ቤት የሚሠራልኝ እርሱ ነው፤እኔም ዙፋኑን ለዘላለም አፀናለሁ። 13 አባት እሆነዋለሁ፤እርሱም ልጅ ይሆነኛል፤ፅኑ ፍቅሬን ከአንተ በፊት ከነበረው ላይ እንደወሰድሁ፣ከእርሱ ላይ ከቶ አልወስድም። 14 በቤቴና በመንግሥቴ ላይ ለዘላለም እኖረዋለሁ፤ዙፋኑም ለዘላለም ይፀናል።" 15 ናታንም የዚህን ሁሉ ራእይ ቃል ለዳዊት ነገረው። 16 ከዚያም ንጉሥ ዳዊት ገባ፤በእግዚአብሔር ፊት ተቀምጦ እንዲህ አለ፤ "እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፤ለመሆኑ እስከዚህ ያደረሰኸኝ እኔ ማን ነኝ? ቤተ ሰብይስ ምንድን ነው? 17 አምላክ ሆይ፤ይህ በፊትህ በቂ እንዳልሆነ ቁጥረህ ስለ ወደፊቱ የባሪያህ ቤት ተናገረ።እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፤እኔንም ከሰዎች ሁሉ እጅግ የከበርረ ሰው አድርገህ ተመለከትኸኝ። 18 ባሪያህን ስላከበትኸው፣ዳዊት ከዚህ በላይ ምን ማለት ይችላል? ባሪያህ እኮ ታውቀዎልህ፤ 19 እግዚአብሔር ሆይ፤ስለ ባሪያህ ብለህና እንደ ፈቃድህም መሠረት ይህን ታላቅ ነገር አድርግሃል፤እነዚህም ታላላቅ ተስፋዎች ሁሉ እንዲታወቁ አደረግህ። 20 አቤቱ፤እንደ አንተ ያለ የለም፤በጆሮአቸን አንደ ሰማነው ሁሉ ከአንተ በቀር አምላክ የለም 21 ከግብፅ ተቤዝተህ እንዳወጣኸው እንደ ሕዝብህ እንደ እስራኤል ያለ ማን አለ? እነርሱ እግዚአብሔር ለራሱ ሊቤዣቸው ናቸው፤በሕዝብህም ፊት ታላቅና አስፈሪ ነገሮችን በማድረግ መንግሥታትን በፊታቸው አሳደድህ። 22 ሕዝብህንም እስራኤልን ለዘላለም የራስህ ሕዝብ አደረግኸው፤እግዚአብሔር ሆይ፤አንተም አምላክ ሆንህለት። 23 እግዚአብሔር ሆይ፤አሁንም ስለባሪያህ ስለ ቤቱ የሰጠኸው ተስፋ ለዘላለም የጸና ይሁን፤የሰጠኸውንም ትተስፋ ፈፅም፤ 24 ይህም ስምህ ጸንቶ እንዲኖርና ለዘላለም ታላቅ እንዲሆን ነው።ከዚያም ሰዎች "የእስራኤል አምላክ ጌታ እግዚአብሔር በእውነት የእስራኤል አምላክ ነው!"ይላሉ፤የባሪያህ የዳዊትም ቤት በፊትህ የጸና ይሆናል። 25 አምላክ ሆይ፤ቤት እንደምትሠራለት ለባሪያህ ገልጸህለታል፤ስለዚህ ባሪያህ ወደ አንተ ለመጸለይ ድፍረት አገኘ። 26 እግዚአብሄር ሆይ፤በእውነት አንተ አምላክ ነህ፤ይህንንም መልካም ተስፋ ለባሪያህ ስጥተሃል። 27 በፊትህ ለዘላለም እንዲኖር አሁንም የባሪያህን ቤት ልትባርክ ወደሃል፤እግዚአብሔር ሆዩ፤የባረክኸውን አንተ ስለ ሆንህ፣ለዘላለም የተባረከ ይሆናል።

---

1 Chronicles 17:1

እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ የታሪኩን አዲስ ክፍል ጅምር ለመጠቆም እዚህ የሚያገለገል ነው። ቋንቋዎ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። (የአዲስ ክስተት መግቢያ፡ ይመልከቱ)

በተቀመጠ ጊዜ
የመንቀሳቀስ ወይም የመቀየር ፍላጎት ሳይኖር ምቾት እና ደስተኛ

እኔ ከዝግባ በተሠራ ቤት ተቀምጫለሁ
ዝግባ በጥንካሬው የሚታወቅ ዓይነት ዛፍ ነው። በባህልዎ ውስጥ ተመጣጣኝ የሆነ የዛፍ አይነት ካለዎት ያንን ስም መጠቀም ይችላሉ፣ ካልሆነ ግን ይህን ስም እንደገና መጠቀም ይችላሉ። አት: - “እኔ ጠንካራ እና በቋሚ ቤት ውስጥ እኖራለሁ” (ታሳቢ እወቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ ይመልከቱ)

የእግዚአብሔርም ቃል ኪዳን ታቦት በመጋረጃዎች ውስጥ ተቀምጦአል
ድንኳኖች ጊዜያዊ መኖሪያ ናቸው። በባህልዎ ውስጥ ድንኳን ከሌለዎት ይህንን በተለየ ቃል መጥራት ይችላሉ። አት: - “የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታቦት ጊዜያዊ ቦታ ውስጥ ይቆያል” (ታሳቢ እወቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ ይመልከቱ)

በልብህ ያለውን ሁሉ አድርግ
እዚህ “ልብ” አእምሮን ይወክላል። አት: - “ማድረግ ያለብህን አድርግ” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነው
እዚህ “ካንተ ጋር” ማለት እግዚአብሔር ዳዊትን እየረዳ እና እየባረከው ነው ማለት ነው። (ፈሊጥ:ይመልከቱ)

1 Chronicles 17:3

የእግዚአብሔር ቃል ወደ ናታን መጣ እንዲህም አለው
“የእግዚአብሄር ቃል መጣለት” የሚለው ፈሊጥ ከእግዚአብሄር ልዩ መልዕክት መምጣቱን ለማሳየት የሚረዳ ነው። አት: “እግዚአብሄር ለናታን መልዕክት ሰጠው። ’ሂድ” ወይም “እግዚአብሄር ይህን መልዕክት ለናታን ተናገረው: ’ሂድ” አለ (ፈሊጥ :ይመልከቱ)

ሂድ፣ ለባሪያዬ ለዳዊት ንገረው። እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡ ... የምኖርበትን ቤት አትሠራልኝም
ይህ ከጥቅሶቹ ውስጥ ጥቅሶች አሉት :: እነሱን በተዘዋዋሪ ጥቅሶች ለመተርጎም አስፈላጊ ሊሆን ይችላል :: አት: - “ሂድ ፣ እኔ የምኖርበትን ቤት የሚገነባው እርሱ እንደማይሆን ለአገልጋይዬ ለዳዊት ንገረው” (በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ እና ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪ ጥቅስ: ይመልከቱ)

ቤት መስራት
እዚህ “ቤት” ማለት መቅደስ ማለት ነው :: በ 1 ዜና 17፡10 ላይ ያህዌ ለዳዊት ቤት ይሠራል ይላል። እዚያ “ቤት” ማለት ቤተሰብ ማለት ነው። ቋንቋዎ ሁለቱንም ሀሳቦች መግለፅ የሚችል ቃል ካለው እዚህ እና በ 17፡10 ውስጥ ይጠቀሙበት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እስራኤልን ካወጣሁበት
ታሳቢ የሆነው መረጃ የሚያመለክተው እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ ምድር እንዳወጣ ነው። አት: - “እስራኤልን ወደ ተስፋይቱ ምድር ከግብፅ ምድር አመጣሁ” (ታሳቢ የተደረገ እውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃን ይመልከቱ)

ድንኳን, ማደሪያ
“ድንኳን” እና “ማደሪያው ድንኳን” የሚሉት ቃላት አንድ ነገር የሚያመለክቱ ሲሆን ዘላቂ የሆነ ሕንፃ ባልነበረበት ስፍራ እንደኖረ ያጎላሉ። (ድግግሞሽ: ይመልከቱ)

ስለ ምን ቤትን ከዝግባ እንጨት አልሠራችሁልኝም? ብዬ ሕዝቤን ይጠብቅ ዘንድ ከእስራኤል ፈራጆች ላዘዝሁት ለአንዱ በውኑ ተናግሬአለሁን?
ይህ በጥቅሱ ውስጥ ጥቅስ አለው። ቀጥተኛው ጥቅስ እንደተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል። አት: “የዝግባ ቤት ለምን አልሰራችሁልኝም ብዬ ለሕዝቤ እረኛ እንዲሆኑ ከሾምኳችው የእስራኤል መሪዎችን ጠይቄያለሁን?” (በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ እና ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪ ጥቅስ: ይመልከቱ)

ከእስራኤል ፈራጆች ላዘዝሁት ለአንዱ በውኑ ተናግሬአለሁን?
ያህዌ ማንንም የእስራኤል መሪዎች ቤት እንዲሠሩለት በጭራሽ እንዳልጠየቃቸው ለማጉላት ጥያቄ ይጠቀማል። አት: - “ማንንም የእስራኤል መሪዎች አንዳች ነገር በጭራሽ አላልኩም” (መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ: ይመልከቱ)

ሕዝቤን ይጠብቅ ዘንድ
የእስራኤል ሕዝብ መሪዎች እንደ እረኞች ፣ ህዝቡም በግ እንደሆኑ ተደርጎ ተገልፃል። (ዘይቤ: ይመልከቱ)

ስለ ምን ቤትን ከዝግባ እንጨት አልሠራችሁልኝም?
ይህዌ ይህን ጥያቄ መሪዎችን ጠይቆ ቢሆን፣ ጥያቄው የዝግባ ቤት ስላልሰሩለት መተንኮሻ ነበር። ነገር ግን ፣ ያህዌ ከዚህ ቀደም ይህን ጥያቄ እንዳልጠየቃቸው ተናግሯል። አት: - “የዝግባ ቤት ልትሠሩልኝ ይገባ ነበር።” (መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ: ይመልከቱ)

1 Chronicles 17:7

አጠቃላይ መረጃ
ይህዌ ለንጉሥ ዳዊት የገባውን ቃል በነቢዩ ናታን በኩል ይገልፃል።

አሁንም
ይህ “በአሁኑ ጊዜ” ማለት አይደለም ፣ ነገር ግን ወደሚቀጥለው አስፈላጊ ነጥብ ሃሳብን ለመሳብ ይጠቅማል።

ባሪያዬን ዳዊትን እንዲህ በለው
እግዚአብሔር ለዳዊት ምን እንደሚናገር ለነቢዩ ናታን አሁንም ይነግረዋል።

አንተ መንጋውን ስትከተል ... ከበግ ጥበቃ ወሰድሁህ።
እንደ እረኛ የተገለፀው የዳዊት ስራ በጎቹም ይጠብቅ ከነበረበት ቦታ አንጻር ተገልጾል። አት: “ከእረኝነት ስራህ ወሰድሁህ” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

መንጋውን
እንስሳት ሣር የሚግጡበት መሬት። በ1 ዜና 4:39 እና 4:40 ይህንን ቃል እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

ከአንተ ጋር ነበርሁ
እዚህ “ካንተ ጋር” ማለት እግዚአብሔር ዳዊትን ረድቶታል እንዲሁም ባርኮታል ማለት ነው ። (ፈሊጥ: ይመልከቱ)

ጠላቶችህንም ሁሉ ከፊትህ አጠፋሁ
ይህዌ የዳዊትን ጠላቶች ማትፋቱ ልክ ያህዌ ከጨርቅ ላይ ብጣቂ እንደሚቆርጥ ወይም ከዛፍ ቅርንጫፍ እንደሚቆርጥ ተደርጎ ተገልጻል። (ዘይቤ: ይመልከቱ)

ለአንተ ስም አደርጋለሁ
እዚህ “ስም” የአንድን ሰው ዝና ያመለክታል። አት: - “ስምህ ታላቅና የታወቀ እንዲሆን አደርጋለሁ” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

እንደታላላቆች
“ታላላቆች” የሚለው ሐረግ ታዋቂ ሰዎች ማለት ነው።

1 Chronicles 17:9

አያያዥ መግለጫ
እግዚአብሄር ለንጉሥ ዳዊት የገባውን ቃል በነቢዩ ናታን በኩል መግለጹን ቀጠለ።

አጠቃላይ መረጃ:
በእነዚህ ቁጥሮች ላይ “የአንተ” እና “አንተ” የሚሉት ቃላት ዳዊትን ያመለክታሉ ።

ስፍራ አደርግለታለሁ
“ቦታ እመርጣለሁ”

እተክለውማለሁ
እግዚአብሔር ህዝቡን በምድሪቱ ላይ በቋሚነት ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እንዲኖሩ በማድረግ በምድሪቱ ላይ እንደሚተክላቸው ያህል ተገልጻል። አት: - “እዚያ አስቀምጣቸዋለሁ” (ሜታፈር: ይመልከቱ)

ከዚያም በኋላ አይናወጥም
ይህ ገባሪ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “ማንም በጭራሽ አያስጨንቃቸውም” (ገባሪ ወይም ተገባሪ: ይመልከቱ)

እንደቀድሞው ዘመንና
እዚህ “ቀናት” ረዘም ያለ ጊዜን ይወክላል። አት: - “ከጊዜው”(የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

ፈራጆች እንዳስነሣሁበት
የእስራኤል ሰዎች ወደ ከነዓን ምድር ከገቡ እና በኋላ ሚመሯቸው ነገሥታት ከመኖራቸው በፊት ፣ እግዚአብሔር በችግር ጊዜ እንዲመሯቸው “ፈራጆች” የተባሉ መሪዎችን ሾመ።

በሕዝቤ በእስራኤል ላይ እንዲሆን
በሥልጣን መሆን ማለት በአንድ ሰው ላይ የበላይ መሆን ተብሎ ይጠራል። አት: - “ሕዝቤን እስራኤልን ይገዛል” (ፈሊጥ ይመልከቱ)

አያስጨንቁትም
አንድን ሰው ወይም እንስሳ ማጥቃት የማይችል ማድረግ

ቤት እንዲሠራልህ
እዚህ ላይ “ቤት” የሚለው አገላለጽ የሚያመለክተው የዳዊት ዘሮች እንደ እስራኤል ገዢዎች ሆነው መቀጠላቸውን ነው። በ 1ኛ ዜና 17:4 ውስጥ እግዚአብሔር ለዳዊት ለያህዌ ቤት የሚሠራው እርሱ እንዳልሆነ ነገረው። እዚያም “ቤት” ቤተ መቅደስን ይወክላል። ቋንቋዎ ሁለቱንም ሀሳቦች መግለፅ የሚችል ቃል ካለው እዚህ እና በ17:4 ውስጥ ይጠቀሙበት። (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Chronicles 17:13

አያያዥ መግለጫ
ያህዌ ለንጉሥ ዳዊት የገባውን ቃል በነቢዩ ናታን በኩል መግለጹን ቀጠለ።

እኔም አባት እሆነዋለሁ፥ እርሱም ልጅ ይሆነኛል
በ 17 11-14 ውስጥ ያለው ትንቢት የሚያመለክተው የዳዊትን ልጅ ሰለሞንን ነው ። ነገር ግን የትንቢቱ አንዳንድ ገጽታዎች በኢየሱስ ይፈፀማሉ። ስለዚህ እዚህ “አባት” እና “ልጅ” የሚሉትን ቃላት ለመደበኛ አባት እና ልጅ በሚያገለግሉ ቃላት ይተርጎም።

ከሳኦል እንደወሰድኩት የቃል ኪዳን ታማኝነቴን ከእርሱ አላርቅም
የቃላት ስሙ “ታማኝነት” የሚለው ቃል “በታማኝነት” ሊተረጎም ይችላል። አት: - “ሳኦልን መውደዴን እንዳቆምኩ፣ እርሱን እስከ መጨረሻው እሱን መውደድ አላቆምም” (ረኪክ ስሞች: ይመልከቱ)

በቤቴና በመንግሥቴም ለዘላለም አቆመዋለሁ፤ ዙፋኑም ለዘላለም ይጸናል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን የዳዊት ሥርወ መንግሥት ለዘላለም እንደሚቆይ አፅንኦት ይሰጣሉ። (ትይዩአዊ: ይመልከቱ)

ዙፋኑም ለዘላለም ይጸናል
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “ዙፋኑን ለዘላለም አጸናለሁ” (ገባሪ ወይም ተገባሪ :ይመልከቱ)

ዙፋኑም
የንጉሥ የመግዛት መብት የሚጠቀሰው አንድ ንጉሥ በሚቀመጥበት ቦታ ነው። አት: - “የመግዛት መብቱ” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

ነገረው
“ነገረው”

እንደዚህ ነገር ሁሉ
እዚህ “ቃላት” ያህዌህ ያለውን ይወክላል። (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

1 Chronicles 17:16

አለ
“ዳዊት አለ”

አቤቱ አምላክ ሆይ፥ እስከዚህ ያደረስኸኝ እኔ ማን ነኝ? ቤቴስ ምንድር ነው?
ዳዊት ይህን ጥያቄ የጠየቀው ያህዌን አዋጅ ሲሰማ የተሰማውን ጥልቅ ስሜት ለመግለጽ ነው። ይህ መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አት: - “ያህዌ አምላክ ሆይ፣ እኔና ቤተሰቤ ፣ ለዚህ ክብር ብቁ አይደለንም። (መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ: ይመልከቱ)

ይህ ... ጥቂት ነበረ
አስፈላጊ ያልሆነ ነገር ትንሽ እንደሆነ ተገልጻል። (ፈሊጥ: ይመልከቱ)

በፊትህ
እዚህ ማየት ፍርድን ወይም ግምገማን ይወክላል። አት: - “በፍርድህ” (ዘይቤ: ይመልከቱ)

ስለ ባሪያህ ቤት
እዚህ ላይ ዳዊት ራሱን “አገልጋይህ” ሲል ጠርቶታል ። ይህ በመጀመሪያ መደብ መጠሪያ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “ቤተሰቤ”(ይመልከቱ የመጀመሪያ ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ)

ለሩቅ ዘመን
ይህ የሚናገረው ስለ ጊዜ ሲሆን፣ አንድ ነገር የሚጓዝ እና የሆነ ቦታ እንደሚደርስ ሆኖ ቀርቧአል። አት: - “እናም ወደፊት ምን ይሆናል” (ዘይቤ: ይመልከቱ)

ዳዊት ጨምሮ የሚለው ምንድር ነው?
ዳዊት ይህንን ጥያቄ ለያህዌህ የሚለው አንዳች እንደሌለው ለማጉላት ተጠቅሞበታል። አት: - “ከዚህ በላይ የምናገርህ ነገር የለም።” (መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ: ይመልከቱ)

ባሪያህ
እዚህ ላይ ዳዊት ራሱን “አገልጋይህ” ሲል ጠርቶታል። ይህ በመጀመሪያ መደብ መጠሪያ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “እኔ” (የመጀመሪያ ፣ ሁለተኛ ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ መጠሪያ ይመልከቱ)

አንተ ባሪያህን ታውቀዋለህና ለባሪያህ ስለ ተደረገ ክብር
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው እና ለማጉላት የተደጋገሙ ናቸው። (ይመልከቱ: ትይዩአዊ)

ለባሪያህ ስለ ተደረገ ክብር
“እውቅና” የሚለው ስም “ዕውቅና” በሚለው ቃል መተርጎም ይችላል። አት: - “አገልጋይህን በልዩ ሁኔታ አውቀኸዋል” (ረኪክ ስሞች: ይመልከቱ)

1 Chronicles 17:19

አያያዥ መግለጫ
ዳዊት ያህዌን መናገሩን ቀጠለ።

ስለ ባሪያህ
እዚህ ላይ ዳዊት ራሱን “አገልጋይህ” ሲል ጠርቶታል። ይህ በመጀመሪያ መደብ መጠሪያ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “ለእኔ ጥቅም” ወይም “ለእኔ ጥቅሜ” (የመጀመሪያ ፣ ሁለተኛ ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ ይመልከቱ)

እንደ ልብህም አድርገሃል
“ያሰብከውን ለማሳካት”

እንዳንተ ያለ የለም፥ ከአንተ በቀር አምላክ የለም
እነዚህ ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው እና ለማጉላት የተደጋገሙ ናቸው። (ትይዩአዊ: ይመልከቱ)

በጆሮአችንም እንደሰማን ሁሉ
እዚህ “እኛ” የሚለው ቃል ዳዊትን እና የእስራኤልን ህዝብ ያመለክታል። (አግላይ እና አካታች “እኛ”: ይመልከቱ)

ለአንተም ሕዝብ ... እንዳንተ ሕዝብ እንደ እስራኤል ያለ በምድር ላይ ሌላ ሕዝብ አለን?
ይህ ጥያቄ እንደ እስራኤል ያለ ሌላ ሕዝብ እንደሌለ የሚያስተውል አሉታዊ መልስ ይጠብቃል። እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አት: - “በምድር ላይ እንደዚህ ሕዝብ የለም ... በታላቅ እና በሚያስደንቅ ሥራዎች” (መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ: ይመልከቱ)

ግብጽ ካወጣኸው
ታሳቢ የሆነው መረጃ እነሱ ከባርነት እንደዳኑ ነው። አት: - “ከግብፅ ባርነት አዳናችሁ” (ታሳቢ የሆነ ዕውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ: ይመልከቱ)

ለአንተ ስም ታደርግ ዘንድ
እዚህ “ስም” የያህዌን ስም ይወክላል። አት: - “ለሰዎች ሁሉ ማን እንደሆንክ ለማሳወቅ” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

አሕዛብን በማሳደድ
እዚህ “ሕዝቦች” በከነዓን ይኖሩ የነበሩትን ህዝቦችን ይወክላል ። (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

1 Chronicles 17:22

አያያዥ መግለጫ
ዳዊት ያህዌን ማናገሩን ቀጠለ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አሁንም
እዚህ “አሁን” ማለት “በአሁኑ ጊዜ” አይደለም ፣ ነገር ግን ወደሚቀጥለው አስፈላጊ ነጥብ ትኩረትን ለማዞር ይጠቅማል።

ስለ ባሪያህና ስለ ቤቱ የተናገርኸው ለዘላለም የጸና ይሁን
: አት: - “ለእኔ እና ለቤቴ ቃል የገባኋውን አድርግ፣ እናም ቃል በጭራሽ አይለወጥ” (ገባሪ ወይም ተገባሪ፡ ይመልከቱ)

ስለ ባሪያህና ስለ ቤቱ
ዳዊት ስለ ራሱ በሦስተኛው መደብ መጠሪያ እየተናገረ ነው። ይህ በመጀመሪያ መደብ መጠሪያ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “እኔ እና ቤተሰቤ” (የመጀመሪያ ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ ይመልከቱ)

ዘንድ ስምህ
እዚህ “ስም” የያህዌን ዝና ይወክላል። (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

የባሪያህም የዳዊት ቤት
እዚህ “ቤት” ቤተሰብን ይወክላል። አት: - “ቤተሰቤ” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

በፊትህ ጸንቶአል
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “በአንተ ምክንያት የተጠበቀ” ወይም “ከአንተ የተነሳ ይቀጥላል” (ገባሪ ወይም ተገባሪ፡ ይመልከቱ)

1 Chronicles 17:25

አያያዥ መግለጫ
ዳዊት ያህዌን ማናገር ይቀጥላል።

ባሪያህ
ዳዊት ራሱን “አገልጋይህ” ብሎ ይጠራል። ይህ በመጀመሪያ መደብ መጠሪያ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “እኔ” (የመጀመሪያ ፣ ሁለተኛ ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ፡ ይመልከቱ)

ቤት እንድሠራለት
እዚህ ላይ “ቤት” የሚለው አገላለጽ የሚያመለክተው የዳዊት ዘር እንደ እስራኤል ገዥዎች ሆነው እንደሚቀጥሉ ነው። በ1ኛ ዜና 17፡4 እግዚአብሔር ለዳዊት ቤት የሚሠራለት እርሱ እንዳልሆነ ይነገረዋል። እዚያም “ቤት” ቤተ መቅደስን ይወክላል። ቋንቋዎ ሁለቱንም ሀሳቦች መግለፅ የሚችል ቃል ካለው እዚህ እና በ17፡4 ይጠቀሙበ ። (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

እኔ ባሪያህ ...በልቡ ደፈረ
እዚህ ላይ የተጠቀሰው “ድፍረት” የሚለው ስም “መበረታታት” በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- “እኔ አገልጋይህ ተበረታቻለሁ”

አሁንም
ይህ “በአሁኑ ጊዜ” ማለት አይደለም፣ ነገር ግን ወደሚቀጥለው አስፈላጊ ነጥብ ለመሳብ ይጠቅማል።

የባሪያህን ቤት
ዳዊት በሦስተኛው መደብ መጠሪያ ስለ ራሱ ይናገራል። ይህ በመጀመሪያ መደብ መጠሪያ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “ቤቴ” ወይም “ቤተሰቤ” (የመጀመሪያ ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ ይመልከቱ)

አቤቱ፥ ባርከኸዋል፥ ለዘላለምም ቡሩክ ይሆናል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ስላላቸው ለማጉላት እዚህ ተደግመዋል። (ትይዩአዊ፡ ይመልከቱ)

ለዘላለምም ቡሩክ ይሆናል
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “ለዘላለም በመባረክ ትቀጥላለህ” (ገበሪ ወይም ተገባሪ፡ ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 18

1 ከዚህ በኋላ ዳዊት ፍልስጥኤማዊያንን ድል መትቶ ተገዢ አደረጋቸው፤ጌትንና በዙሪያዋም የሚገኙትን መንደሮች ከፍልስጥኤማዊያን እጅ ወሰደ። 2 እንዲሁም ዳዊት ሞዓባዊያንድል አደረጋቸው፤እነሱም ገባሮቹ ሆኑ፤ግብርም አመጡለት። 3 ከዚያም በላይ ዳዊት በኤፍራጥስ ወንዝ አጠገብ የነበረው ግዛት ለመቁጣጠር በሄደ ጊዜ፣የሱባን ንጉሥ አድርአዛርን እስከ ሐማት ድረስ ዘልቆ ወጋው። 4 ዳዊትም አንድ ሺህ ሠረገላ. ሰባት ሺህ ፈረሰኛና ሃያ ሺህ እግረኛ ወታደር ማረከ፤አንድ መቶ የሠረገላ ፈረሳች ብቻ አስቀርቶ የቀሩትን ቋንጃቸውን ቁረጠ። 5 ሶርያውያንም የሱባን ንጉሥ እድርአዛርን ለመርዳት ከደማስቆ በመጡ ጊዜ፣ከእነሱ ሃያ ሁለት ሺህ ሰው ገደለ። 6 ከዚያም በሶርያ ግዛት ውስጥ ባለችው ወደማስቆ የጦር ሰፈር ፤አቋቋመ፤ሶርያውያን ገባሮቹ ሆኑ፤ግብርም አመጡለት።እግዚአብሔርም ዳዊትን በሄደበት ሁሉ ድል አጎናፀፈው። 7 ዳዊትም የአድርአዘር ጦር አለቆች ያነገቡትን የወርቅ ጋሻ ወሰደ፤ወደ ኢየሩሳሌም አመጣው። 8 ዳዊት ከአድርአዛር ከተሞች ከጢብሐትና ከኩን እጅግ ብዙ ናስ ወሰደ፤ሰለሞን የናሱን ባሕር፤ዐምዶቹንና ልዩ ልዩ የናስ ዕቃዎቹን የሠራው በዚሁ ነበር። 9 የሐማት ንጉሥ ቶዑ ዳዊት የሱባን ንጉሥ የአድርአዛርን ሰራዊት ሁሉ ድል እንደመታ ሲሰማ፣ 10 እጅ እንዲነሳውና ደስታውንም እንዲገልጥለት ልጁን አዳራምን ወደ ንጉሥ ዳዊት ላከው፤ቶዑ ከአድርአዛር ጋር ብዙ ጊዜ ጦርነት ገጥሞ ነበር።አዶራምም ከወርቅ፣ከብርና ከነስ የተጀሩ ልዩ ልዩ ዕቃዎች አመጣለት። 11 ንጉሥ ዳዊት ከሞዓብ፣ከአሞናዊያን፣ከፍልስጥኤማውያንና ከአማሌቃውያን ከእነዚህ ሁሉ መንግሥትታት የማረከውን ወርቅና ብር ከዚህ ቀደም እንዳደረገው ሁሉ፤እነዚህንም ዕቃዎች ለእግዚአብሔር ቀደሰ። 12 የጹሩያ ልጅ አቢሳ በጨው ሸለቆ ዐሥራ ስምንት ሺህ ኤዶማውያን ገደለ። 13 እርሱም በኤዶም የጦር ሰፈሮች አቋቋም፤ኤዶማውያንም ሁሉ ለንጉሥ ዳዊት ገባሮች ሆኑ።እግዚአብሔር ዳዊትን በሄደበት ሁሉ ድል አጎናጸፈው። 14 ዳዊት በመላው እስራኤል ላይ ነገሠ፤ለሕዝቡም ሁሉ ፍትሕና ጽድቅን አሰፈናላቸው። 15 የጽሩያ ልጅ ኢዮአብ የሰራዊት አዛዥ ነበረ፤የአሒሉድ ልጅ ኢዮሣፍጥ ደግሞ የቤተ መዛግብቱ ኃላፊ ነበረ። 16 የአኪጦብ ልጅ ሳዶቅና የአቤምሜሌክ ልጅ አብያታር ካህናት ነበሩ፤ሱሳ ደግሞ ጸሓፊ ነበረ። 17 የዮሄድ ልጅ በናያስ የከሊታውያንና የፊልታውያን አዛዥ ነበረ።የዳዊት ወንዶች ልጆች ከንጉሥ ቀጥሎ የበላይ ሹማምት ነበሩ።

---

1 Chronicles 18:1

ከዚህም በኋላ
“እግዚአብሔር ዳዊትን እንደሚባርክ ከገባለት ቃል አኳያ”

አንዲህ ሆነ
ይህ ሀረግ እዚህ የሚያገለግለው አዲሱን የታሪኩን ክፍል ለመጀመር ነው። ቋንቋዎ ይህ ማድረግ የሚችልበት መንገድ ካለው እዚህ ሊጠቀሙት ይቻላሉ። .

1 Chronicles 18:3

ዳዊትም ... አድርአዛርን ... መታ
እዚህ ዳዊት እና አድርአዛር ብቻቸውን እንደሆኑ ተደርጎ የተነገረ ሲሆን፣ ነገር ግን እነዚህ ነገስታት አብረዋቸው የነበሩተን ሰራዊት እንደሚወክሉ አንባቢው ሊረዳው ማድረግ ያስፈልጋል። አት: “ዳዊት እና ሰራዊቱ የአድርአዛርን ሰራዊት ድል ነሱ” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

አድርአዛርን
ይህ የወንድ ስም ነው። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

የሱባን
ይህ የአገር ስም ነው።

በኤፍራጥስ ወንዝ አጠገብ የነበረውን ግዛት ለመያዝ በሄደ ጊዜ
“ሕዝቦች በዚያ ለመያዝ ወደ ኤፍራታ ወንዝ እየሄደ ነበር”

አንድ ሺህ ሰረገሎች
“1,000 ሰረገሎች” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

ሰባት ሺህም ፈረሰኞች
እነዚህ ፈረስ ይጋልቡ የነበሩ ወራደሮች ናቸው። “7,000 ፈለሰኞች” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

ሀያ ሺህም እግረኞች
እነዚህ ይራመዱ የነበሩ ወራደሮች ናቸው። “20,000 እግረኞች” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

የሰረገሎቹን ፈረሶች ቋንጃ ቆረጠ
ከዛም በኋላ መሮጥ እንዳችሉ ዳዊት እና ወታደሮቹ ከፈረሶቹ ጀርባ ያለውን ቋንጃ ቀረጡ።

አስቀርቶ
ለልዩ አገልግሎት ማስቀረት

ለመቶ ሰረገሎች
“100 ሰረገሎች” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

1 Chronicles 18:5

ሀያ ሁለት ሺህ ሰዎችን ገደለ
“22,000 ገደለ” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

ጭፍሮች
ለተለየ አካባቢ የተመደቡ ወታደሮች

እግዚአብሔርም ዳዊት በሄደበት ሁሉ ድል ይሰጠው ነበር
“ያህዌ ለዳዊት ድልን ሰጠው”

1 Chronicles 18:7

ለአድርአዛር
ይህ የዞባ ንጉስ ነበር። ስሙን በ1 ዜና 18:3 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

ለአድርአዛር ባሪያዎች የነበሩትን
“የአድርአዛር ባሮች የሚሸከሙት”

ከጢብሐትና ... ከኩን
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

ብዙ ናስ
“ከፍተኛ መጠን ያለው ናሀስ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከዚህም ሰሎሞን የናሱን ኩሬና ዓምዶች የናሱንም ዕቃ ሠራ
ጸሀፊው ይህ ነህስ በቀጣይ ጊዜ ምን እንደሆነ ለማሳየት የዳራ መረጀ ይጭምራል። (የዳራ መረጃ :ይመልከቱ)

የናሱን ኩሬና የተባለውን
ይህ 5 ሜትር ርዝማመት ያለው ትልቅ የነህስ ሳህን ሲሆን በቤተ መቅደሱ ለስርአቶች መታጠቢያነት ይቀመጥ ነበር።

1 Chronicles 18:9

ቶዑ ... አዶራምን
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

ይዋጋ ነበርና
“በጦርነት ውስጥ መሆን”

እነዚህን ደግሞ ለእግዚአብሔር ቀደሰ
“እንዚህ እቃዎች ያህዌን ለማምለክ ብቻ እንዲያገለግሉ ወሰነ”ከአሕዛብ ሁሉ ... ወሰደ

1 Chronicles 18:12

አቢሳ ... ጽሩያ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

ከኤዶማውያን ... አሥራ ስምንት ሺህ
“18,000 ኤዲማውያን” (ቁጥሮች፡ ይመልከቱ)

በጨው ሸለቆ
ይህ በኤዶምና ይሁዳ መካከል ለጦርነት ያገለግል የነበረ ሸለቆ ስያሜ ነው።

1 Chronicles 18:14

በእስራኤል ሁሉ
“በእስራኤላውያን ሁሉ ላይ”

ለሕዝቡም ሁሉ ፍርድንና ጽድቅም አደረገላቸው
ረኪክ የሆኑት “ፍትህ” እና “ጽድቅ” የሆኑት ስሞች እንደቅጽል መጸርጎም ይችላሉ። አት: “ለሕዝቡ ሁሉ ፍትህ እና ትክክል የሆነውን አደረገ” (ረኪክ ስሞች: ይመልከቱ)

ጽሩያ ... አሒሉድም ... አኪጦብም ... አብያታር ... ሱሳ ... በናያስ ... ዮዳሄ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

ጸሐፊ
የወሳኝ ኩነቶችን ዝርዝር የሚፅፍ ሰው

አቤሜሌክም
ይህ የፊደል አንዳንድ ቅጂዎች የሚከተሉትን ‹አቢሜሌክ› መታረሙን ይወክላል። የታረመው ፊደል ይህን ቁጥር 2 ሳሙኤል 8:17 እንዲስማማ ያደርገዋል።

የአኪጦብም ልጅ ሳዶቅ፥ የአቤሜሌክም ልጅ አብያታር ካህናት ነበሩ
አንዳንድ ቅጂዎች ይህን አኪጦብ እና አቤሜሌክ ሊቀ ካህናት ነበሩ በማለት ያስተካክሉታል።

ከሊታውያንና ... ፈሊታውያን
እነዚህ የሌላ የሕዝቦች ስም ሲሆን የዳዊት ጠባቂዎች ሆነዋል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 19

1 ከዚህ በኋላ የአሞናውያን ንጉሥ ናያስ ሞተ. ልጁም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ። 2 ዳዊትም "አባቱ ለእኔ በጎ ነገር እንዳደረገልኝ እስቲ እኔም ለናያስ ልጅ ለሐኖን በጎ ነገር ላድርግለት"ብሎ አሰብ።ስለዚህ ዳዊት ስለ አባቱ ሞት ሐዘኑን ለመግለጽ ወደ ሐኖን መልክተኞችን ላከ።የዳዊት ሰዎች ሐናቸውን ለመግለጽ ሐኖን ወደሞኖርበት ወደ አሞናውያን ምድር በመጡ ጊዜ፣ 3 የአሞናውያን መኳንንት ለሐኖን "ዳዊት ሀዘኑን ለመግለጽ ሰዎችን ወደ አንተ የላከው አባትህን አክብሮ ይመስልሃን? ሰዎች ወደ አንተ የመቱት አገሩቱን ለመመርመር፣ለመሰለልና ለመያዝ አይደለምን? አሉት። 4 ስለዚህ ሐኖን የዳዊትን ሰዎች ይዞ ላጫቸውል ልብሳቸውንም እስከ መቀመጫቸው ድረስ መኻል ለመኻል ቀዶ ሰደዳቸው። 5 በሰዎቹ ላይ የደረሰባቸውን ዳዊት በሰማ ጊዜ እጅግ ዐፍረው ስለ ነበር፣ወደ እነርሱ መልክተኞችን ላከ፤ንጉሥም፣"ጢማችሁ እስኪያድግ ድረስ በኢያኮር ቁዩና ከዚያ በኋላ ትመጣላችሁ"አለ። 6 አሞናውያን በዳዊት ዘንድ እንደ ተጠሉባወቁ ጊዜ፣ሐኖንና አሞናውያን ከመሰጴጦምያ፣ከአራምመዓካና ከሱባ ሠረገሎችንና ፈረሶችን ለመከራየት አንድ ሺህ መክለት ብር ላኩ፤ 7 ከዚያም ሠላሳ ሁለት ሺህ ሠረገሎችንና ፈረሶኞችን እንዲሁም የመካዓን ንጉሥና ወታደሮች በገንዘብ ቀጠሩ፤እነርሱም መጥተው በሜድባ አጠገብ ሲሰፍሩ፣አሞናውያን ደግሞ ከየከተሞቻቸው ተሰብስበው ለጦርነት ወጡ። 8 ዳዊት ይህን ሲሰማ ኢዮአብንና መላውን ተዋጊ ሰራዊት ላከ። 9 አሞናውያንም መጥተው ወደ ከተማቸው በሚያስገባው በር ላይ ለጦርነት ተሰለፉ፤የመጡት ነገሥታት ደግሞ ብቻቸውን በሜዳው ላይ ነበሩ። 10 ኢዮአብም ከፊቱና ከኋላው ጦር መኖሩንና አየ፤ስለዚህ በእስራኤል የታወቁትን ጀግኖች መርጦ ሶርያውያንን እንዲገጥሙ አሰለፋቸው። 11 የቀሩትም ሰዎች በወንድሙ በአቢሳ ሥጋ ሆነው አሞናውያንን እንዲገጥሙ አስለፋቸው። 12 ኢዮአብም እንዲህ አለ፤"ሶርያውያን ከበረቱብኝ አንተ ትረዳኛለህ"አሞናውያን ከበረቱብህ ደግሞ እኔ እረዳሃለሁ። 13 እንግዲህ በርቱ፤ስለ ሕዝባችንና ስለ አምላካችን ከተሞች ብለን በጀግንነት እንዋጋ፤እግዚአብሔር ደስ ያሰኘውን ያድርግ።" 14 ከዚያም ኢዮአብና አብረውት ያሉት ወታደሮች ሶርያውያን ለመዋጋት ወደ ፊት ገሠገሠ፤ሶርያውያንም ከፊታቸው ሸሹ። 15 አሞናውያንም ሶርያውያን መሸሻቸውን ሲያዩ፣እርሱም ከውንድሙ ከአቢሳ ፊት ሸሽተው ወደ ከተማይቱ ገቡ፤ስለዚህ ኢዮአብ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ። 16 ሶርያውያን በእስራኤል መሸነፋቸውን ሲያዩ፣መልክተኞችን ልከው ከኤፍራጥስ ወንዝ ማዶ ያሉትን ሶርያዊያን አስመጡ፤እነዚህንም የሚመራቸው የአድርአዛር ስራዊት አዛዥ ሾፋክ ነበረ። 17 ዳዊት ይህን ሲሰማ፣እስራኤልን ሁሉ ሰብስቦ ዮርዳኖስን ተሻገረ፤ወደፊት በመገሥገሥም ከፊት ለፊታቸው የውጊያ መሥመሩን ያዘ።ዳዊትም ሶርያውያንን ጦርነት ለመግጠም ወታደሮቹን አሰለፈ፤እነርሱም ተዋጉት። 18 ይሁን እንጂ ከእስራኤል ፊት ሸሹ።ዳዊትም ሰባት ሺህ ሠረገለኞችና አርባ ሺህ እግረኛ ወታደሮች ገደለ።የሠራዊታቸው አዛዥ ሾፋክም በጦርነት ላይ ሞተ። 19 የአድርአዛርም ሹማምት በእስራኤል መሸነፋቸውን ሲያዩ፣ከዳዊት ጋር ታረቁ፤ገባሮቹም ሆኑ።ስለዚህ ሶርያውያን ከዚህ ጊዜ ጀምሮ አሞናውያንን ለመርዳት ፍቃደኞች አልሆኑም።

---

1 Chronicles 19:1

ሆነ
ይህ ሐረግ የታሪኩ አዲስ ክፍል መጀመሩን ለመጠቆም ያገለግላል ። ቋንቋዎ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ መጠቀም ይችላሉ ።

ናያስ... ለሐኖን
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው ። (የስሞችን አተረጓጎም ፡ይመልከቱ)

ደግነት አሳያለሁ... ደግነትን አሳይቷል
ደግነት የሚለው የረቂቅ ስም እንደ ድርጊት ሊገለጽ ይችላል ። ኣት: - “እኔ ደግ እሆናለሁ... ደግ ነበርኩ” (የረቂቅ ስሞችን ፡ይመልከቱ)

ማጽናናት
የሚያጽናኑህ ሰዎች ስለላከ ዳዊት አባትህን የሚያከብር ይመስልሃል? ልዑላኑ ይህንን ጥያቄ የጠየቁት ንጉሡን ከዳዊት ጋር ለማጋጨት ፈልገው ነው። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: “ዳዊት የሚያጽናኑህ ሰዎች ስለላከ አባትህን የሚያከብር አይምሰልህ።” (አወያይ መጠይቅን ፡ ይመልከቱ) አገልጋዮቹ ወደ አንተ የመጡጥ ምድሪቱን ሊሰልሏት እና ሊያጠፏት አይደለምን? ልዑላኑ ይህንን ጥያቄ የጠየቁት ንጉሡን ከዳዊት ጋር ለማጋጨት ፈልገው ነው። እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: - “በእርግጥ አገልጋዮቹ ምድሪቱን ያጠፉአት ዘንድ ለመመርመር ወደ አንተ ይመጣሉ።” (አወያይ ጥያቄን ፡ተመልከት)

1 Chronicles 19:4

ስለዚህ ሐኖን ያዛቸው
ሃኖን በግሉ ይህንን አላደረገም ፣ ነገር ግን ሐኖን የእርሱ ሰዎች እንዲያደርጉት አዘዘ ። ኣት: - “ስለሆነም የሐኖን ሰዎች ያዙአቸው” (የባህሪ ስምን ፡ ይመልከቱ)

ልብሳቸውን
ልብሳቸውን”

ከእነርሱ ጋር ለመገናኘት ልኮ ነበር “ዳዊት እነርሱን ለማበረታታት ጥቂት መልእክተኞችን ላከ”

ሃፍረታቸው ጥልቅ ነበረ
በዚህ ዘይቤ ውስጥ ሃፍረት በከፍተኛ ሁኔታ እንደጎዳቸው ለማሳየት እፍረታቸው ጥልቅ ነበር ተብሎ ተገልጾአል ። ኣት: - “በጣም አፈሩ” (ፈሊጥን፡ ይመልከቱ)

ንጉሡ
ይህ ዳዊትን ያመለክታል ።

ከዚያ ተመለሱ
“ከዚያም ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ”

1 Chronicles 19:6

በዳዊት ዘንድ እንደተጠሉ ተመለከተ
“ተጠሉ” የሚለው ቃል መጥፎ ሽታን ያመለክታል። ይህ አሞናውያን የተጠሉ እና የማይፈለጉ እንደሆኑ ይገልፃል ። ኣት: - “ለዳዊት አመጸኞች እንደ ሆኑ ተገነዘቡ” ወይም “ዳዊትን እንዳስቆጣው ተገነዘቡ” (ዘይቤ፡ ይመልከቱ)

አንድ ሺህ መክለት ... ሠላሳ ሁለት ሺህ ሰረገሎች
“1,000 መክለት... 32,000 መክለት” (ቁጥሮችን ፡ ይመልከቱ)

መክለቶች
በግምት 33 ኪሎግራም (የመጽሐፍ ቅዱስ ገንዘብን ፡ይመልከቱ)

አራም... ማዓካ... ሱባ... ሜድባ
የከተሞች ስሞች እነዚህ ናቸው። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ፡ ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሠላሳ ሁለት ሺህ ሰረገሎች
አሞናውያን አንድ ሺህ መክሊቱን በሙሉ ለማዓካ ንጉሥ ይክፈሉ ወይም የተወሰነውን ብቻ ከፍለው ቀሪዎቹን ሰረገሎችና ፈረሰኞች ለሚልኩ ሌሎች ከተሞች የሰጡት ግልፅ አይደለም ።

1 Chronicles 19:8

ስለሱ ሰማ
አሞናውያን ለጦርነት እየወጡ እንደነበሩ ሰማ ”

እነርሱን ለመገናኘት
“ከእነርሱ ጋር ሊዋጉ”

በከተማው በር ላይ
ይህ የአሞናውያንን ዋና ከተማ በር ያመለክታል።

የመጡት ነገሥታት
ይህ አሞናውያን እስራኤልን ለመውጋት እንዲረዱአቸው የቀጠሯቸውን የሶርያን ነገሥታት ይመለከታል።

በሜዳ ውስጥ በራሳቸው
ከከተማይቱ ውጭ ከዐሞን ልጆች የተለየ

1 Chronicles 19:10

የጦርነት መስመሮችን ... በጦር ግንባር ውስጥ አኖራቸው
“የጠላት ወታደሮች ለውጊያ ተሰለፉ... ወታደሮቹን ለጦርነት በሰልፍ አደራጁ”

አቢሳ
ይህ የኢዮአብ ወንድም ስም ነው። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)

1 Chronicles 19:12

በርታ... ጠንካራ መሆናችንን እናሳይ
“ደፋር ሁን... ደፋር ሁን”

ለሕዝባችንና ለአምላካችን ከተሞች
“ለሕዝባችንና ለአምላካችን ከተሞች” ወይም “ሕዝባችንን እና የአምላካችንን ከተሞች ለመጠበቅ”

በፊቱ መልካም የሆነውን
እዚህ ማየት ፍርድን ወይም ምዘናን ይወክላል ። ኣት: - “እርሱ ጥሩ እንደሆነ የሚቆጥረው” (ዘይቤያዊን ፡ ይመልከቱ)

1 Chronicles 19:14

ወደ ውጊያው ገቡ
“ወደ ጦር ግንባር ገቡ” ወይም “በጦርነቱ ወደ ጠላት ወታደሮች ቀረቡ”

ኢዮአብም ተመልሶ .. ... ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ
ኢዮአብና ወታደሮቹ በከተሞቻቸው ላይ አሞናውያንን ማጥቃታቸውን አላቋረጡም ። አሞናውያን ወደ ከተማቸው ሲገቡ ውጊያው ተጠናቀቀ እስራኤላዊያንም ወደ አገራቸው ተመለሱ ።

1 Chronicles 19:16

አጠቃላይ መረጃ
በ 1ኛ ዜና 19 ፡15 ላይ ከኢዮአብ ሸሽተው የመጡ ሶርያውያን በሌሎች ሶርያውያን ተጠናክረው እስራኤልን እንደገና እንደወጉ ቁጥር 16-19 ይናገራል ።

ሶርያውያንም አይተዋል
ሶርያውያኑ የተገነዘቡት እንዳየት ይነገራል። ኣት: - “ሶርያውያን ተረድተው ነበር” (የባህሪ ስምን ፡ ይመልከቱ)

ለማጠናከሪያነት ተልኳል
“ተጨማሪ ወታደሮችን ጠይቀዋል”

ሾፋክ...አድርአዛር
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ ይመልከቱ)

ዳዊትም ይህ ሲነገረው
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: የዳዊት መልእክተኞች ብዙ የሶርያ ሠራዊት እየመጣ መሆኑን በነገሩት ጊዜ (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ ይመልከቱ)

እርሱ ሰብስቦ ... አስተካከለ
ዳዊት እነዚህን ነገሮች ብቻውን አላደረገም። የእርሱም ሆነ የአገሬው ሰዎች ረድተውታል። ኣት: “ዳዊትና አገልጋዮቹ ተሰበሰቡ... ዳዊትና አገልጋዮቹም አደራጁ” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን፡ ይመልከቱ)

እስራኤል ሁሉ
ይህ አጠቃላይ ነው ። የእስራኤል ህዝብ በሙሉ ወደ ውጊያው አልመጡም ። ኣት: - “እጅግ ብዙ ቁጥር ያላቸው እስራኤላውያን” (ግነትን እና አጠቃላይን ፡ ይመልከቱ)

ዝግጅት አደረገ
“አደራጀ”

ተዋጉ
እዚህ “እርሱ” የሚለው ቃል ከዳዊት በተጨማሪ የዳዊትን ወታደሮች ያመለክታል ። ኣት: - “ሶርያውያን ዳዊትንና ወታደሮቹን ተዋጉ” (ሁሉን በአንዱ መወከልን ፡ ይመልከቱ)

1 Chronicles 19:18

ሰባት ሺህ ... አርባ ሺህ ገደለ
”7,000... 40,000” ተገደሉ (ቁጥሮች ፡ይመልከቱ)

እነርሱ በእስራኤል ድል ተመቱ
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “እስራኤል ድል አደረጓቸው” (ገቢራዊን ወይም ተቢሮአዊን ፡ ይመልከቱ)

ከዳዊት ጋር ታረቁ አገለገሏቸውም
ከዳዊት ጋር የሰላም ስምምነትን በማድረጉ እስራኤልን ያገለግሉ ነበር ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 20

1 ነገሥታት ለጦርነት በሚሄዱበት በፈደይ ወራት፣ኢዮአብ የጦር ሰራዊቱን እየመራ ሄዶ የአሞናውያንን አገር አጠፋ፤ወደ ራባትም ሄዶ የአሞናውያንን አገር
አጠፋ፤ወደ ራባትም ሄዶ ከበባት፤ዳዊት ግን ኢየሩሳሌም ቀርቶ ነበር።ኢዮአብም ራባትን ወግቶ አፈራረሳት፤ 2 ዳዊት የንጉሣቸውን ዘውድ ከራሱ ላይ
ወሰደ፤ክብደቱም አንድ መክሊት ወርቅ ነበረ፤ይህንንም በዳዊት ራስ ላይ ጫኑለት፤እንዲሁም ከከተማይቱ እጅግ ብዙ ምርኮ ወሰደ። 3 በዚያ የነበረውን ሕዝብ
አውጥቶ መጋዝ፣ዶማና መጥረቢያ ይዘው እንዲሠሩ አደረጋቸው።ዳዊት በሌሎቹም የአሞን ከተሞች ሁሉ ይህንኑ አደረጉ።ከዚያም ዳዊትና መላው ሰራዊቱ ወደ
ኢየሩሳሌም ተመለሱ። 4 ከዚያም በኋላ ከፍልስጥኤማዊያን ጋር በጌዝር ጦርነት ተደረገ፤በዚያ ጊዜ ኩሳታዊው ሴቦካይ የራፋይም ዘር የሆነውን ሲፋይን
ገደለ፤ፍልስጥኤማውያንም ድል ተመቱ። 5 ከፍልስጥኤማውያን ጋር ሌላ ጦርነት ተደረገ፤የያዒር ልጅ ኤልያናን የጦሩ የቦውፍረቱ እንደ ሸማኔ መጠቅለያ
የሚያህለውን የጌት ተወላጅ የሆነውን የጎልያድን ወንድም ላሕሚን ገደለ። 6 ደግሞም ጌት ላይ በተደረገ ሌላ ጦርነት፣በእጆቹና በእግሮቹ ላይ ስድስት ስድስት
ጣት በድምሩ ሃያ አራት ጣት የነበሩት አንድ ግዙፍ ሰው ነበረ፤ይህም እንደዚሁከራፋይም ዘር ነበረ። 7 እርሱም እስራኤልን በተገዳደረ ጊዜ የዳዊት ወንድም
የሳምዓ ልጅ ዮናታን ገደለው። 8 በጌት የነበሩ የራፋይም ዘሮች እነዚህ ናቸው፤እነሱም በዳዊትና ሰዎቹ እጅ ወደቁ።

---

1 Chronicles 20:1

ሆነ
ይህ ሐረግ የታሪኩ አዲስ ክፍል መጀመር ለመጠቆም እዚህ ያገለግላል ። ቋንቋዎ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ መጠቀም ይችላሉ ። ነገሥታት በተለምዶ ወደ ጦርነት የሚሄዱበት ጊዜ ነው። ይህ ከደራሲው የተሰጠ የመነሻ መረጃ ነው ። በቀዝቃዛው ክረምት ጦርነቶችን መድረግ ከባድ ነበረ ፣ ስለሆነም ነገሥታት በተለምዶ ጠላቶቻቸውን ለማጥቃት የፀደይ ወቅትን ይጠብቁ ነበር ። (ዳራዊ መረጃን :ይመልከቱ)

ነገሥታት በተለምዶ ወደ ጦርነት ይሄዳሉ... ኢዮአብም ሠራዊቱን ወደ ጦር ግንባሩ ይመራ ነበር እዚህ “ነገሥታት” ማለት ነገሥታቶቻ ሰራዊታቸውን ወደ ጦርነት ላኩ ማለት ነው ። ኢዮአብ የዳዊት ሠራዊት አለቃ ነበር። ኣት: “ነገሥታት በመደበኛነት ሠራዊታቸውን ወደ ጦርነት ይልካሉ... ኢዮአብ የዳዊትን ሰራዊት ወደ ጦርነት ይመራ ነበር” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

ምድሪቱን አወደመች
“ምድሪቱን አጥፍተዋታል።” ይህ የሚያመለክተው ጠላቶቻቸው ምግብ የሚያበቅሉበትን ምድር የሚያጠፋበት ወቅት ነው ።

እርሱም ሄዶ ረባትን ከበባት
“እርሱ” ወታደሮችንና ኢዮአብንም ያመለክታል ። ኣት: “ኢዮዓብና ወታደሮቹ በራባት ዙሪያ ሆኑ” (የባህሪ ስምን : ይመልከቱ)

1 Chronicles 20:2

ችሎታ
33 ኪሎግራም ገደማ (ስለመጽሐፍ ቅዱስን ገንዘብ :ይመልከቱ)

ዘውዱ በዳዊት ራስ ላይ ተደረገ
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ዳዊት ዘውዱን በራሱ ላይ አደረገ ወይም 2) የዳዊት ሰዎች ዘውዱን በራሱ ላይ አደረጉ ። (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

አውጥቷል... አውጥቷል
እነዚህ “እርሱ” ሁለት አጋጣሚዎች ዳዊትን ያመለክታሉ ፣ ደግሞም ዳዊት እነዚህን ነገሮች እንዲያደርግ የረዱትን የዳዊትን ወታደሮች ያመለክታሉ ። (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን : ይመልከቱ) ዘረፋ በጦርነት ውስጥ የተወሰዱ ውድ ዕቃዎች

በሾላዎች እና በብረት መጫዎቻዎች እና መጥረቢያዎች እንዲሠሩ አስገደዳቸው
እነዚህ ውሎች የተሸነፉ ሰዎች እንዲሠሩ የተገደዱትን የጉልበት ሥራን ይገልፃሉ ።

ዳዊት የሕዝቡን ከተሞች ሁሉ ይፈልጋል
ሰዎቹ የሚናገሩት በከተማቸው ነው ። ኣት: “ዳዊት የከተሞቹን ሕዝብ ሁሉ ይፈልጋል” (አንቶኒን ይመልከቱ)

1 Chronicles 20:4

ሆነ
ይህ ሐረግ የታሪኩን አዲስ ክፍል ጅምር ለመጠቆም እዚህ ያገለገለ ነው ። ቋንቋዎ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ ለመጠቀም ሊጠቀሙበት ይችላሉ ።

በጌዜር ላይ ከፍልስጥኤማውያን ጋር ሰልፍ ነበር
“እስራኤላውያን ፍልስጥኤማውያንን በጌዜር ተዋጉ”

ጌዝር... ጎባ
የከተሞች ስሞች እነዚህ ናቸው። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ፡ ይመልከቱ)

ሲቤቤኪ... ሲፓፓ... ኤሊያናን... ያኢር... ላሚ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ፡ ይመልከቱ)

ሑሻዊው ... ረፋይም... ቤተልሔም... ጋቲታዊ
እነዚህ የሰዎች ቡድኖች ስሞች ናቸው ።

ፍልስጥኤማውያንም ተዋረዱ
ይህ በንቃት ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ፍልስጥኤማውያንን አዋረዱ” (ገባሪ ወይም ተገባሪ፡ ተመልከት)

ፍልስጥኤማውያንም ተዋረዱ
ይህ በንቃት ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። አት: - “እስራኤላውያን ፍልስጥኤማውያንን ድል ማድረግ ችለዋል” ወይም “ፍልስጥኤማውያን በእስራኤላውያን ቁጥጥር ሥር ወድቀዋል”

ሠራተኞች
ረዥም እና ቀጭን ምሰሶ።

የጦራቸውም እንደ የሸመና ሞገድ ነው
የሹራብ ክር በዙሪያቸው ስለሚተሳሰሩ የሸመና ሞገድ ገመድ የሚዘረጋበት በጣም ትልቅ እንጨት ነበር። ይህ ማለት የሌህሚ ጦር ጦር በጣም ትልቅ ነበር ማለት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Chronicles 20:6

ሆነ
ይህ ሐረግ የታሪኩ አዲስ ክፍል መጀመሩን ለመጠቆም እዚህ ያገለግላል ። ቋንቋዎ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ ሊጠቀሙበት ይችላሉ ።

ራፋይም
ይህ ስም በጣም ረዥም እና ጠንካራ ለሆኑ ሰዎች የተሰጠ ስም ነው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ ይመልከቱ)

ዮናታን... ሳምዓ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው ።

እነዚህ የጌት የራፋይም ልጆች ነበሩ
እዚህ “እነዚህ” በ 1 ኛ ዜና 20 ፡4 ውስጥ ሲፋይን ፣ በ 1ኛ ዜና ምዕራፍ 20 ፡ 5 ውስጥ ለሕሚን እና በቁጥር 6 ውስጥ ግዙፍ የሆነውን ያመለክታሉ ።

በዳዊት እጅ በሠራዊቱም እጅ ተገደሉ
ዳዊትና ወታደሮቹ ሰይፍ በሚይዙበት የሰውነት ክፍሎቻቸው ተጠቅሰዋል ። ይህ በንቃት ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: “ዳዊትና ወታደሮቹ የራፋይም ዘሮችን ገደሉ” (አንዱን በሁሉ ወይም ሁሉን በአንዱ መወከልን እና ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 21

1 ሰይጣን በእስራኤል ላይ ተነሥቶ ዳዊት የእስራኤልን ሕዝብ እንዲቁጥር አነሣሣው። 2 ዳዊትም ኢዮአብንና የሰራዊቱን አዛዦች፤"ሄዳችሁ ከቤርሳቤህ እስከ ዳን ያሉትን እስራኤላዊያን ቁጠሩ፤ከዚያም ምን ያህል እንደ ሆኑ ዐውቅ ዘንድ ንገሩኝ አላቸው። 3 ኢዮአብ ግን፣እግዚአብሔር የእስራኤል ሰራዊት አሁን ካለው በላይ በመቶ ዕጥፍ ያብዛው፤ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፤ሁልስ ቢሆኑ የጌታዬ ተገዢዎች አይደሉምን? ታዲያ ጌታዬ ይህን ማድረግ ለምን አስፈለገው? ለምንስ በእስራኤል ላይ በደል ያመጣል?"አለ። 4 ይሁን እንጂ የንጉሥ ቃል ኢዮአብን አሸነፈው፤ስለዚህ ኢዮአብ ወጣ፤በመላው እስራኤል ከተዘዋወረ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ። 5 ኢዮአብም የተዋጊዎቹን ሰዎች ቁጥር ለዳዊት አቀረበ፤እነዚህም በመላው እስራኤል አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሺህ፣በይሁዳ ደግሞ አራት መቶ ሰባ ሺህ ሲሆኑ፣ሁሉም ሰይፍ መምዘዝ የሚችሉ ነበሩ። 6 ነገር ግን የንጉሡ ትእዛዝ በእርሱ ዘንድ አስጸያፊ ነበረና፣ኢዮአብ የሌዊንና የብንያም ነገድ ጨምሮ አልቁጠረም። 7 ይህ ትእዛዝ በእግዚአብሄር ዘንድ የተጠላ ነበር፤ስለዚህ እግዙአብሔርን ቀጣ። 8 ከዚያም ዳዊት እግዚአብሔርን፣"ይህን በማድረጌ እጅግ በድያለሁ፤የፈጸምኩትም የስንፍና ሥራ ስለሆነ፣የባሪያህን በደል እንድታስወግድ እለምንሃለሁ"አለ። 9 እግዚአብሔር የዳዊት ባለ ራእይ የሆነውን ጋድን እንዲህ አለው፤ 10 ሂድና ለዳዊት እንዲህ ብለህ ንገረው፤እግዚአብሔር የሚለው ይህ ነው፤እነሆ፣ሦስት ምርጫ ሰጥሃለሁ፤በአንተ ላይ እንዳደርስብህ እንዱን ምረጥ።" 11 ስለዚህ ጋድ ዳዊት ሄዶ እንዲህ አለው፤"እግዚአብሔር የሚለው ይህን ነው፤አንዱን ምረጥ፤ 12 የሦስት ዓመት ራብ ወይስ የጠላቶችህን ሰይፍ ለሦስት ወር አይሎብህ ተሰዶ መጥፋት ወይስ ሦስት ቀን የእግዚአብሔር ስይፍ መቅሠፍት በምድሪቱ ላይ ወርዶ የእግዚአብሔር መልአክ እስራኤልን ሁሉ ያጥፋ? እንዲህ ላልከኝ ምን እንደምመልስ ቁርጡን ነገረኝ። 13 ዳዊትም ጋድን፣"ችጅግ ተጨንቅይአለሁ፤ምሕረቱ ታላቅ ስለሆነ በእግዚአብሔር እጅ መውደቅ ይሻለኛል፤በሰው እጅስ አልወድቅ"አለ። 14 እለዚህ እግዚአብሔር በእስራኤል ሰባ ሺህ ሰው ዐለቀ። 15 እንዲሁም እግዚአብሔር እየሩሳሌምን እንዲያጠፋ መልአክ ላከ፤መልአኩም ሊያጠፋት ሲል እግዚአብሔር አይቶ ስለሚያደርሰው ጥፋት ዐዘን፤ህዝቡን የሚያጠፋውንም መልአክ፣"እጅህን መልስ"አለው።የእግዚአብሔር መልአክ በኢያቡሳዊያ በኦርና ዐውድማ አጠገብ ቆሞ ነበር። 16 ዳዊት ቀና ብሎ ሲመለከት፣የእግዚአብሔር መልአክ በሰማይና በምድር መካከል ቆሞ አየ፤መልአኩም በኢየሩሳሌም ላይ የተመዘዘ ሰይፍ በእጁ ይዞ ነበር፤ከዚያም ዳዊትና ሽማግሌዎች ማቅ እንደሚለብሱ በግንባራቸው ተደፉ። 17 ዳዊት እግዚአብሔር "ተዋጊዎቹ እንዲቁጠሩ ያዘዝሁ እኔ እይደለሁም? ኅጢአት የሠራሁበትም ሆነ የበደልሁት እኔ ነኝ፤እነዚህ እኮ በጎች ናቸው፤ታዲያ እነርሱ ምን አደረጉ? እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፤እጅህ በእኔና በአባቴ ቤት ላይ ትሁን እንጂ፣መቅሠፍት በሕዝብህ ላይ አይውረድ"አለ። 18 ከዚያም እግዚአብሔር መልአክ ዳዊት ወጥቶ በአቡሳዊያን በኦርና ዐውድማ ላይ ልችእግዚአብሔር መሠዊያ ይሠራ ዘንድ እንዲነግረው ጋድን አዘዘው። 19 ዳዊትም ጋድ በእግዚአብሔር ስም በነገረው ቃል መሠረት ለመፈፀም ውጣ። 20 ኦርና ስንዴ በመውቃት ላይ ሳለዘወር ሲል መለአኩን አየ፤አብረውት የነበሩት አራት ወንዶች ልጆችም ተሸሸጉ። 21 ዳዊት ወደ እርሱ እየቀረበ መጣ፤ኦርናቀና ብሎ ሲመለከት፣ዳዊትን አየው፤ከዐውድማውም ወጥቶ መሬት ላይ በግንባሩ ተደፋ ዳዊትን እጅ ነሣ። 22 ዳዊትም፣"በሕዝቡ ላይ የወረደው መቅሠፍት እንዲወገድ ለእግዚአብሔር መሠዊያ እሠራ ዘንድ ዐውድማህን ልውሰደው፤ሙሉውን ዋጋ እከፍልሃለሁ"አለው። 23 ኦርናም ዳዊትም፣"እንዲሁ ወስደው፤ጌታዬ ንጉጅ ደስ ያለውን ያድርግ፤እነሆ ለሚቃጠል መሥዋዕት በሬዎቹን፣መውቂያ በትሮቹን ለማቀጣጠያ ዕንጨት፣ስንዴው ደግሞ ለእህል ቁርባን እንዲሆን እሰጣለሁ፤ሁሉንም እኔ እሰጣለሁ።አለ። 24 ንጉሥ ዳዊት ግን ለኦርና "አይደረግም፤ሙሉውን ዋጋ እኔ እከፍላለሁ፤የአንተ የሆነውን ለእግዚአብሔር ለማውረብ አልፈልግም፤ዋጋ ያልከፈልኩበትም የሚቃጠል መሥዋዕት እድርጌ አላቀርብም" ሲል መለሰለት። 25 ስለዚህ ዳዊት ለኦርና የቦታውን ዋጋ ስድስት መቶ ስቅል ወርቅ ከፈለ። 26 ዳዊትም በዚያ ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሠርቶ የሚቃጠል መሥዕዋትና የኅብረት መሥዋዕት አቀረበ።እግዚአብሔርም ጠራ፤እግዚአብሔርም የሚቃጠል መሥዕዋት በሚቀርብበት መሠዊያ ላይ ከሰማይ በእሳት መለሰለት። 27 ከዚያም እግዚአብሔር ለመልአኩ ተናገረ፤መልአኩም ሰይፉን ወደ አፎቱ መለሰ። 28 በዚያን ጊዜ ዳዊት፤እግዚያብሔር በኢያቡሳዊው በኦርና ዐውድማ ላይ እንደ መለሰለት ሲያይ፤በዚያው ቦታ መሥዕዋት ማቅረብ ጀመረ። 29 ሙሴ በምድረ በዳ የሠራው የእግዚአብሔር ማደሪያ ድንኳንና የሚቃጠል መሥዕዋት የሚቀርብበት መሠዊያ በዚያ ጊዜ በገባዖን ኮረብታ ላይ ነበረ። 30 ዳዊት የእግዚአብሔር መልአክ ሰይፍ ሰለፈራ ወዲያ ሄዶ እግዚአብሔር ለመጠየቅ አልቻለም።

---

1 Chronicles 21:1

በእስራኤል ላይ አንድ ጠላት ተነሳ
“ባላጋራ” ለሚለው ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞችን 1) ይህ የሚያመለክተው ለእስራኤል ችግር ለማምጣት የወሰነውን ሰይጣንን ነው ወይም 2) ይህ እስራኤልን ማስፈራራት የጀመረው የጠላት ጦር ነው ::

ዳዊት እስራኤልን እንዲቆጥር አነሳሳው
ዳዊትን አሳተው፣ ቋንቋዎ አንድን ሰው በማስቆጣት ስህተት እንደሆነ የሚያውቀውን ነገር እንዲያደርግ በማድረግ ማሳሳትን የሚገልጽ ነገር ካለ ፣ እዚህ ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

ቁጥራቸውንም እንዳውቅ የእስራኤልን ሕዝብ ቁጠሩ
ከ 1ኛ ዜና 21፡ 5 በግልጽ ማየት እንደሚቻለው ዳዊት ውጊያ የሚችሉትን ሰዎች ለመቁጠር ፈልጎ ነበር ::

ከቤርሳቤህ እስከ ዳን ድረስ
እስራኤላውያን እነዚህን ሁለት ከተሞች እንደ ብዙ ደቡባዊ እና ሰሜናዊ ከተሞች አድርገው ይመለከቱ ነበር። ዳዊት እነዚህን ከተሞች እስራኤልን በሙሉ ለማመልከት ይጠቀምባቸዋል :: (ሜሪዝምን : ይመልከቱ)

መቶ እጥፍ ይበልጣል
ኢዮአብ ሠራዊቱ መቶ እጥፍ እንዲሆንለት እናየበለጠ ኃያል እንዲሆኑ እንደሚመኝ በመናገር ገለጸ። (ግነት እና ማጠቃለል ፡ ይመልከቱ)

ግን ጌታዬ ንጉሡ ፣ ሁሉም ጌታዬን አያገለግሉምን? ጌታዬ ይህን ለምን ይፈልጋል? በእስራኤል ላይ ለምን ጥፋትን ያመጣል?
ኢዮብ የሕዝብ ቆጠራው ሃሳብ መልካም እንዳልሆነ ለዳዊት ለመግለጽ እነዚህን ሦስት አወያይ ጥያቄዎችን ተጠቅሟል :: ዳዊት እግዚአብሔርን ከመታመን ይልቅ በሠራዊቱ መጠን የሚታመን ይመስላል እናም እስራኤልን ኃጢአተኛ ያደረገ ይመስላል :: እነዚህ አወያይ ጥያቄዎች እንደ መግለጫዎች ሊተረጎሙ ይችላሉ። ኣት: ግን ጌታዬ ፣ ቀድሞ ሁሉም ያገልግሉሃል :: ጌታዬ ይህን መጠየቅ የለበትም :: ወታደራዊ ኃይልዎን ብቻ በመተማመን በእስራኤል ሕዝብ ላይ ጥፋት ያመጣሉ ::” (አወያይ መጠይቅን :ይመልከቱ)

ጌታዬ ይህን ለምን ይፈልጋል?
“ይህ” የሚለው ቃል የዳዊትን የእስራኤልን ወንዶችን ለመቁጠር ያቀደውን ዕቅድ ያመለክታል ::

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Chronicles 21:4

የንጉሡ ቃል በኢዮአብ ላይ ተፈፀመ
“የኢዮአብ ተቃውሞ ቢኖርም የንጉሡ ትእዛዝ አሸነፈ”

ኢዮአብም ወጥቶ ወደ እስራኤል ሁሉ ሄደ
በ 1 ኛ ዜና ምዕራፍ 21 ፡2 ውስጥ ኢዮአብ የእስራኤልን ህዝብ ለመቁጠር እንደሄደ ከዳዊት ትእዛዝ ተረድቷል ። ይህ በግልጽ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: “ኢዮአብም ሕዝቡን ለመቁጠር ወደ እስራኤል ሁሉ ሄደ” (የሚጠበቅ ዕውቀት እና ያልተገለጸ መረጃን፡ ይመልከቱ)

1,100,000 ወንዶች
“አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሺህ ወንዶች” (ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)

ሰይፍ የሚመዝዙ ሰዎች ነበሩ
የእስራኤል ወታደሮች ሰይፉን በመምዘዝ ተግባር ተገልጸአል ። ኣት: - “ወታደር ሆነው ያገለግሉ የነበሩ ወንዶች” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

470,000 ወታደሮች
“አራት መቶ ሰባ ሺህ ወታደሮች” (ቁጥሮችን፡ይመልከቱ)

1 Chronicles 21:6

ከእነርሱ መካከል ሌዊና ቢንያም አልተጠሩም
ሌዋውያኑ አምልኮ መምራት ነበረባቸው እንጂ መዋጋት አይደለም ። ኢዮአብ ቢንያምን ለምን እንዳልቆጠረው ግልፅ አይደለም ። ይህ በገቢራዊ ቅርጽ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: “ነገር ግን ኢዮአብ የሌዊና የቢንያም ነገድ ሰዎችን አልቆጠረም” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ ይመልከቱ)

የንጉሡ ትእዛዝ ኢዮአብን ጠላው
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ኢዮአብ ዳዊት ባዘዘው ነገር ተበሳጭቶ ነበር” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ ይመልከቱ)

በዚህ እርምጃ
እዚህ “ይህ እርምጃ” የሚለው ኃረግ ውግያ የሚችሉትን የእስራኤል ወንዶች ሁሉ ለመቁጠር ያለመውን የዳዊትን ዕቅድ ያመለክታል ።

በእስራኤልም ላይ ጥቃት ሰነዘረ
የዚህ ጥቃት ባህሪ ግልፅ አይደለም ። ዳዊትን ሕዝቡን በመቁጠር እግዚአብሔር በእርሱ ላይ እንደተቆጣ ማሳወቁ በቂ ነበር ።

የአገልጋይህን በደል አስወግዱ
ይህ ፈሊጥ ነው ። ይቅርታ እዚህ ላይ የተጠቀሰው ጥፋተኝነትን ማስወገድ ተብሎ ነው ። ኣት: - “ይቅር በሉኝ” (ፈሊጥን፡ ይመልከቱ)

የአገልጋይህ በደል
ዳዊት ራሱን የእግዚአብሔር አገልጋይ ሲል ገልጾአል ። ኣት: - “በደሌ” (አንደኛ ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ ሰብዓዊን ፡ይመልከቱ)

1 Chronicles 21:11

በሰይፋቸው መያዝ
እዚህ “ጎራዴዎቻቸው” በጦርነት ውስጥ ሞትን ያመለክታሉ ። ኣት: - “በጦርነት በእነርሱ መገደላቸው” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ሰይፍ በምድሪቱ ላይ መቅሰፍት ነው
እዚህ ላይ መቅሰፍቱ “ሰይፍ” ተብሎ ተገልጾአል ምክንያቱም “ሰይፉ” የሞት መግለጫ ስለሆነ ነው። (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

በምድሪቱ ሁሉ ላይ በጥፋት
“በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች የሚኖሩትን ሰዎች መግደል”

ወደ ላከኝ መውሰድ አለብኝ
የላከው ጌታ እግዚአብሔር ነው ። ይህ በግልጽ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: “ወደ ላከኝ ወደ ጌታዬ እወስዳለሁ” (የተገመተ ዕውቀት እና ጥልቅ መረጃን ፡ ይመልከቱ)

1 Chronicles 21:13

ከሰው እጅ ይልቅ በእግዚአብሔር እጅ ልውደቅ
እዚህ “እጅ” የሚለው እስራኤልን የሚጎዳ ወይም የሚቀጣ ኃይልን ይወክላል ። ኣት: - “በሰዎች ከመቀጣት ይልቅ እግዚአብሔር ይቅጣኝ” (የባህሪ ስምን ፡ ይመልከቱ)

ልውደቅ
በመቅሰፍቱ የሚሞቱት የእስራኤል ሕዝብ ናቸው ፣ ነገር ግን ዳዊት እርሱ ራሱ እንደሚገደልና ፍርዱን እንደሚቀበል ገልጾአል።

የሰው እጅ
እዚህ “ሰው” የሚለው ቃል “ሰዎች” የሚለውን አጠቃላይ ስም ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሏል።

ምሕረቱም እጅግ ታላቅ ነው
“እግዚአብሔር እጅግ መሐሪ ነው”

በእስራኤል ላይ
እዚህ እስራኤል የሚለው የባህሪ ስም ሲሆን የእስራኤል ሕዝብን ይወክላል። (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

ሰባ ሺህ ሰዎች ሞተዋል
“70,000 ሰዎች ሞቱ” (ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)

ስለጉዳቱ አእምሮውን ለወጠ
እዚህ “አእምሮ” የሚለው ቃል የእርሱን ውሳኔ ይወክላል ። ኣት: - “ኢየሩሳሌምን ላለማጥፋት ወስኗል” (የባህሪ ስምን ፡ ይመልከቱ)

ይበቃል!
ይህ ቃል አጋኖ “በቂ ሰዎችን ገድሏል!” ማለት ነው (ታአምራዊን ፡ ይመልከቱ)

እጅህን ወደኋላ መልስ
ይህ አንድ ነገር መሥራትን ማቆም ማለት ፈሊጥ ነው ። ኣት: - “የኢየሩሳሌምን ሰዎች አትግደል” (ፈሊጥን ፡ይመልከቱ)

ኦርናን
ይህ የሰው ስም ነው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ ይመልከቱ)

1 Chronicles 21:16

በምድርና በሰማይ መካከል ቆሞ
ይህ መላዕኩ በምድር ላይ ባሉት ሰዎች ላይ ለመፍረድ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላከ መሆኑን የሚያመለክት ምሳሌያዊ ቋንቋ ነው ። (የምልክት ቋንቋን ፡ይመልከቱ)

የተመዘዘ ሰይፍ በእጁ ይዞ ወደ ላይ ወጣ
በእጁ ሰይፍ የያዘው መልአክ ኢየሩሳሌምን ለማጥቃት ዝግጁ መሆኑን የሚያሳይ ምሳሌያዊ ተግባር ነው ። ፍርዱ ህመም ስለነበረ ይህ ምሳሌያዊ ነው ። ኣት: - “ኢየሩሳሌምን ለማጥቃት ሰይፍ በእጁ ይዞ እንደተዘጋጀ ተገልጾአል ” (ምሳሌያዊ ድርጊትን ፡ይመልከቱ)

ማቅ ለብሰው መሬት ላይ ተደፉ
እነዚህ ድርጊቶች የንስሐ ምልክት ነበሩ ። (ምሳሌያዊ ድርጊትን ፡ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሠራዊቱ እንዲቆጠር ያዘዝኩት እኔ አይደለሁምን?
ዳዊት ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ሕዝቡን በመቁጠር ጥፋት የፈጸመው እርሱ እንደሆነ ለማጉላት ነው ። ኣት: - “ሠራዊቱ እንዲቆጠር ያዘዝኩት እኔ ነኝ።” (አወያይ መጠይቅን :ይመልከቱ)

ግን እነዚህ በጎች
ዳዊት የእስራኤልን ህዝብ በመሪዎቻቸው ላይ እምነት በመጣል እና በመከተል በሚታወቁት በበጎች መስሏቸዋል። (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

ምን አደረጉ?
ዳዊት ይህንን ጥያቄ እግዚአብሔር ሰዎችን እንዳይቀጣ እግዚአብሔርን ይጠይቃል ። ይህ የአጻጻፍ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: - “እነሱ በትክክል ቅጣት የሚገባውን ነገር አላደረጉም ።” (አወያይ መጠይቅን :ይመልከቱ)

እጅህ እኔን እና ቤተሰቤን ይምታ
እዚህ “እጅ” የሚለው የእግዚአብሔርን ቅጣት ይወክላል ። ኣት: - “እኔን እና ቤተሰቤን ቅጣ” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

1 Chronicles 21:18

ዳዊት መውጣት አለበት... ወደላይ ወጣ
ይህ የከፍታ ማመሳከሪያ ነው። ለወደፊት የቤተመቅደሱ ስፍራ የሆነው ይህ አውድማ በኢየሩሳሌም ውስጥ ከፍ ያለ ቦታ ነበር ።

ኦርና
በ 1 ኛ ዜና ምዕራፍ 21:15 ውስጥ የዚህን ሰው ስም እንዴት እንደተረጉሙት ይመልከቱ ።

ጋድም በእግዚአብሔር ስም እንዲያደርግ እንዳዘዘው
“በእግዚአብሔር ስም” መናገር ማለት ከኃይሉና ከስልጣኑ ወይም እንደ ተወካይ መናገር ማለት ነው ። ኣት: - “ጋድ በእግዚአብሔር ፈንታ እንደሚናገር ዳዊትም እንዲናገር አዘዘው” (የባህሪ ስምን : ይመልከቱ)

እራሳቸውን ደብቀዋል
እነርሱ መልአኩን ፈሩ ። ይህ የበለጠ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። ኣት: “መላእክትን ስለ ፈሩ ተደበቁ” (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን : ይመልከቱ)

1 Chronicles 21:21

በመሬት ላይ ተደፋ
ይህ ሐረግ ኦርናን በዳዊት ፊት እንደሰገደ ይገልጻል ። በአንድ ሰው ፊት መስገድ ትሕትናን እና አክብሮትን መግለጫ መንገድ ነው። በጣም ዝቅ ማለጥ የበለጠ ትህትናን እና አክብሮትን ያሳያል። ኣት: - “መሬት ላይ እጅግ ዝቅ አለ” (ምሳሌያዊ ድርጊትን : ይመልከቱ)

ሙሉ ዋጋ
“ይህ አውድማ የሚያወጣውን ሙሉ ዋጋ እከፍላለሁ”

1 Chronicles 21:23

እንደ ራስህ አርገህ ውሰደው
ይህ የሚያመለክተው ዳዊት ለመሬቱ ምንም ክፍያ ሳይፈጽም መሬቱን መውሰድ እንደሚችል ነው ። ኣት: - “እንደ ስጦታ ውሰዱት” (የሚጠበቅ ዕውቀት እና ያልተገለጸን መረጃ :ይመልከቱ)

በፊትህ መልካም የሆነውን
የዳዊት ግንዛቤ እንደ እይታ ተገልጾአል ። ኣት: - “ለማድረግ የፈለግከውን ሁሉ” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ) ተመልከት

አውድማ
እነዚህ ከእንጨት የተሠሩ ዓለቶች ወይም ከእንጨት የተሠሩ የብረት መከለያዎች ሲሆኑ እህልን ከገለበው ለመለየት በእህል አውድማው ላይ በበሬዎች የሚጎተቱ መውቂያዎች ናቸው። (የማይታወቁትን መተርጎምን : ይመልከቱ)

ሙሉ ዋጋ
ይህንን በ 1 ኛ ዜና መዋዕል 21 ፡ 22 ውስጥ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ ።

1 Chronicles 21:25

ስድስት መቶ ሰቅል ወርቅ
“600 ሰቅል ወርቅ” (ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

ሰቅል
ከ 11 ግራም ጋር እኩል የሆነ የክብደት መለኪያ (የመጽሐፍ ቅዱስን ገንዘብ : ይመልከቱ)

ለቦታው
“አውድማውን ለመግዛት”

ወደ እግዚአብሔር ጮኸ
“ እግዚአብሔር እንዲረዳው ጸለየ”

በሚቃጠል መሥዋዕቱ መሠዊያ ላይ ከሰማይ በእሳት መልስ ሰጠው
ዳዊት የሚቃጠለውን መሥዋዕት በሚያቀርብበት ቦታ ከሰማይ ወደ እርሱ እሳት በመላክ መልስ የሰጠው ”

መልአኩም ሰይፉን ወደ ሰገባው ውስጥ አስገባ
ሰይፉን ወደ ሰገባው ውስጥ ያስገባው መልአክ ሰዎችን መግደል እንደማይቀጥል የሚያሳይ ምሳሌያዊ ተግባር ነው ። ኣት: - መልአኩ ሕዝቡን መግደል እንደሚያቆም ለማሳየት ሰይፉን በሰገባው ውስጥ አደረገው ”(ምሳሌያዊ ድርጊትን :ይመልከቱ)

ሰገባ
ለጎራዴ ወይም ቢለ መሸፈኛ

1 Chronicles 21:28

ኦርናን
በ 1 ኛ ዜና ምዕራፍ 21 ቁጥር 15 እንደ ሆነ ስሙን ተርጉም ።

በዚያን ጊዜ ... የእግዚአብሔር መልአክ
ከቁጥር 29 - 30 ያሉት በመገናኛው ድንኳን ውስጥ በመሠዊያው ላይ ዳዊት ይህን መሥዋዕት ያቀረበው ለምን እንደሆነ የሚያስረዳ ዳራዊ መረጃ ነው ። (ዳራዊ መረጃን :ይመልከቱ)

የእግዚአብሔርን መመሪያ ለመጠየቅ
“ምን ማድረግ እንዳለበት እንዲነግረው እግዚአብሔርን መጠየቅ”

የእግዚአብሔር መልአክ ሰይፍ ፍራ
እዚህ “ሰይፍ” በእግዚአብሔርን መልአክ መገደልን ያመለክታል ። ኣት: - “በእግዚአብሔር መልአክ እንዳይገደል ፈሩ” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 22

1 ከዚያም ዳዊት፣"ከእንግዲህ የእግዚአብሔር አምላክ ቤት በዚህ ይሆናል፤እንዲሁም ስለ እስራኤል የሚቃጠል መሥዕዋት የሚቀርብበት መሠዊያ በዚሁ
ይቆማል"አለ። 2 ስለዚህ ዳዊት በእስራኤል የሞኖሩ መጻተኞች እንዲሰበሰቡ አዘዘ፤ከመካከላቸም እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የሚሠራበትን ጥጋብ ድንጋይ
እንዲያዘጋጁ ጠራቢዎች መደቡ። 3 ለቅጥር በሮች ምስማርና ማጠፊያ የሚሆን ብዙ ብረትና ከብዛቱ የተነሣ ሊመዘን የማይችል ናስ አዘጋጀ። 4 እንዲሁም
ሲዶናውያንና ጢሮሳውያን በብዛት አውጥተውለት ስለ ነበር፣ስፍር ቁጥር የሌለው የዝግባ ዕንጨት አሰናዳ። 5 ዳዊትም፣"ልጅ ሰሎሞን ወጣት ነው፤ልምዱም
የለውም፤ለእግዚአብሔር የሚሠራው ቤተ መቅደስ ደግሞ እጅግ የሚያምር፣በአሕዛብም ሁሉ ዘንድ አለበት፤ስለዚህ ሁሉንም እኔ አዘጋጃለሁ"እንዳለው ዳዊት
ከመሞቱ በፊት በብዛት አዘጋጀ። 6 ከዚያም ልጁን ሰሎሞንን ጠርቶ ለእስራኤል አምላክ ለእግዚያብሔር ቤት እንዲሥራ አዘዘው። 7 ዳዊትም ሰሎሞን እንዲህ
አለ፤"ልጄ ሆይ ለአምላክህ እግዚአብሔር ስም ቤት ለመሥራት በልቤ አሰብ ነበር፤ 8 ነገር ግን ከእግዚአብሔር እንዲህ የሚል ቃል መጣልኝ፤"አንተ ብዙ ደም
አፍስሰሃል፤በፊቴ በምድር ላይ ብዙ ደም ያፈሰስህ ስለሆነ አንተ ለስሜ ቤት አትሠራልኝም፤ 9 ነገር ግን የሰላምና የዕረፍት ሰው የሆነ ልጅ ትወልዳለህ፤
በየአቅጣጫው ካሉ ጠላቶቹ ዐሳርፈዋለሁ፤ ስሙም ሰሎሞን ይባላል። በዘመኑም ለእስራኤል ሰላምና ጸጥታን እሰጣለሁ። 10 ለስሜ ቤት የሚሰራልኝ እርሱ
ነው። እርሱ ልጅ ይሆነኛል 'እኔም አባት እሆነዋለሁ። ዙፋንም በእስራኤል ላይ ለዘላለም አጸናለሁ። 11 አሁንም ልጅ ሆይ፤ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ይሁን፤
እንድትፈጽሙ በተናገረውም መሠረት፣ ተሳክቶልህ የአምላክን የእግዚአብሔር ቤት ለመሥራት ያብቃህ። 12 በእስራኤል ላይ አለቃ ባደረገህ ጊዜ የአምላክህ
እግዚአብሔርን ትእዛዝ ትፈጽም ዘንድ እግዚአብሔር ጥበብንና ማስተዋል ይስጥህ። 13 ችግዚአብሔር በሙሴ አማካኝነት ለእስራኤል የሰጠውን ሕጉንና
ሥርዐቱን ተጠንቅቀን ብትጠብቅ ይሳካልሃል፤ አይዞህ ጠንክር፤ በርትስ፤ ተስፋም አትቁረጥ። 14 "ለእግዚአብሔር ቤት እንዲሆንም አንድ ሺህ መክሊት ወርቅ፣
አንድ ሚሊዮን መክሊት፣ ብር፣ ከብዛቱ የተነሣ ሊመዘን የማይቻል ናስና ብረት ለማዘጋጅ በተቻለኝ ሁሉ ጥሬአለሁ። ደግሞም እንጨትና ድንጋዮች አዘጋጀሁ፤
በተረፈ አንተ ጨምርበት። 15 ድንጋይ ጠራቢዎች፣ግን በኞች አናጢዎች የሆኑ ልዩ ሙያ የተጠበቡ ሰዎች አሉህ፤ 16 አነዚህ ቁጥራቸው እጅግ የበዛ
የውርቅ፣የብር፣የናስና የብረት ሠራተኞች ናቸው።በል ሥራህን ጀምር፤እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ይሁን።" 17 ከዚያም ዳዊት የእስራኤል መሪዎች ሁሉ ልጁን
ሰሎሞንን እንዲረዱት አዘዘ፤ 18 እንዲህም አለ፤"እግዚአብሔር አምላካችን እስካሁን ከእናንተ ጋር አይደለምን? በየአቅጣጫውስ ዕረፍትን ስጥቷችሁ የለምን?
የምድሪቱንም ነዋሪዎች በእጄ አሳልፎ ሰጥቶኛል፤ምድሪቱም ለእግዚአብሔር ለሕዝቡ ተገዝታለች። 19 አሁንም እግዚአብሔር የኪዳኑን ታቦትና ንዋያት ቅዱሳቱን
ለእግዚአብሔር ስም ወደሚሠራው ቤተ መቅደስ አምጥታችሁ የአምላክ የእግዚአብሔር መቅድደስ ሥሩ።

---

1 Chronicles 22:1

እዚህ ነው
“ቦታው ይህ አውድማ ነው ”

ድንጋይ ጠራቢዎች
ግንበኞች የግንብ ግድግዳዎችን እና ሕንጻዎችን ለመሥራት እንዲጠቀሙባቸው ትላልቅ ድንጋዮችን ሰብስበው በትክክለኛው መጠን በመጥረብ የሚያዘጋጁ ሰዎች ናቸው።

1 Chronicles 22:3

መጠረቂያ
ሁለት ነገሮችን የሚያገናኙ ዕቃዎች ። “ክላች” ወይም “ማጠፊያዎች”

መመዘን ከሚችለው በላይ ናስ
ይህ እጅግ ብዙ ነሐስ እንደነበር የሚያሳይ ግነት ነው ። ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ማንም ሰው ሊመዝነው የማይችል እጅግ ብዙ ናስ” (ገቢራዊን ወይም ተቢሮአዊን እና ግነትን እና አጠቃላይን ፡ ይመልከቱ)

ሊቆጠር ከሚችለው በላይ የሊባኖስ ዝግባዎች
ብዛት ያላቸው የሊባኖስ ዝግባዎች መኖራቸውን የሚያሳይ ግነት ነው። ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ማንም ሊቆጥራቸው የማይችሉት በርካታ የዝግባ ዛፎች” (ገቢራዊን ወይም ተቢሮአዊን እና ግነትን እና አጠቃላይን ፡ ይመልከቱ)

ሲዶናውያን እና የጢሮስ ሰዎች ለመቁጠር የሚታክተውን እጅግ ብዙ የዝግባ እንጨት አመጡ
ይህ ብዙ እንጨት ማን እንደሰጠ ለማብራራት የሚረዳ ዳራዊ መረጃ ነው ። (ዳራዊ መረጃን ፡ይመልከቱ)

ለእግዚአብሔር የሚሠራው ቤት
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “እርሱ ለእግዚአብሔር የሚሠራው ቤት” (ገቢራዊን ወይም ተቢሮአዊን ፡ ይመልከቱ)

በሌሎች አገሮች ሁሉ ዝነኛ እና የከበረ ይሆናል
እዚህ “አገሮች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በዚያ ይኖሩ የነበሩትን ሰዎች ነው ። ኣት: - “ስለዚህ በየትኛውም ሌላ አገር ያሉ ሰዎች ስለዚህ ጉዳይ እንዲያውቁና የከበረ እንደሆነ እንዲገነዘቡ” (የባህሪ ስምን፡ ይመልከቱ)

ለህንፃው መዘጋጀት
“ለመገንባት ተዘጋጁ”

1 Chronicles 22:6

ጠራ
“ዳዊት ጠራ”

እንዲገነባ አዘዘው...ቤት እሠራ ዘንድ አስቤ ነበር
አንባቢዎች ዳዊት ሥራውን ሠራተኞቹ እንዲሠራ አስቦ መሆኑን ሊገነዘቡት ይገባል ። ኣት: - “ለእግዚአብሔር ቤት እንዲያሠራ አዘዘው... እኔ ራሴ የቤቱን ግንባታ በበላይነት የመቆጣጠር እቅዴ” (የባህሪ ስምን፡ ይመልከቱ)

የእኔ ፍላጎት ነበር
“ዓላማዬ”

እኔ ራሴ ቤት ለመሥራት
“ራሴ” የሚለው አጸፋዊ የሚያመለክተው ዳዊት በመጀመሪያ ቤተመቅደሱን ለመገንባት አቅዶ እንደነበረበ ነው ። ኣት: - “ቤተ መቅደሱን የምሠራው እኔ እሆን ነበር” (አጸፋዊ ተውላጠ ስምን ፡ ይመልከቱ)

የአምላኬን የእግዚአብሔር ስም
እዚህ “ስም”የሚለው የእግዚአብሔርን ክብር ይወክላል ። ኣት: “አምላኬ እግዚአብሔርን ያከብሩ ዘንድ” (የባህሪ ስምን፡ ይመልከቱ)

ብዙ ደም አፍስሷል
እዚህ ላይ የሰዎች ግድያ ደማቸውን ማፍሰስ እንደሆነ ተገልጾአል ፣ህይወታቸውን የሚወክለው “ደማቸው”ነው ። ኣት: “ብዙ ሰዎችን ገድሏል” (የባህሪ ስምን፡ ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለስሜ
እዚህ “ስም” የሚለው የእግዚአብሔርን ክብር ይወክላል ። ኣት: - “እኔን ለማክበር” (የባህሪ ስምን፡ ይመልከቱ)

በፊቴ . . . . ደም አፈሰስክ
እዚህ ላይ “ዐይን” የሚያመለክተው እግዚአብሔር ያየውን ነው ። ኣት: - “በምድር ላይ ብዙ ደም እንዳፈሰስክ አየሁ” (የባህሪ ስምን፡ ይመልከቱ)

1 Chronicles 22:9

አያያዥ መግለጫ
ዳዊት ጌታ እግዚአብሔር የነገረውን ለሰሎሞን መንገር ቀጠለ።

ሰላማዊ ሰው ሁን
“ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ”

ከጠላቶቹ ሁሉ አሳርፈው
“በእርሱና በጠላቶቹ ሁሉ መካከል ሰላም ይኑር”

በሁሉም አቅጣጫ
ይህ ማለት በእስራኤል ዙሪያ በሚገኙ ሁሉም ስፍራዎች ማለት ነው ።

ስሙ ሰሎሞን ይባላል
“ሰሎሞን” የሚለው ስም “ሰላም” የሚለውን የዕብራይስጥ ቃል ይመስላል ። ይህ የበለጠ ግልፅ ሊደረግ ይችላል ። ኣት: - “ስሙ ሰሎሞን ይሆናል ፣ ይህም ሰላም የሚለውን ቃል ይመስላል” (የሚጠበቅ ዕውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን ፡ ይመልከቱ)

በእርሱ ዘመን
“እሱ በሚገዛበት ጊዜ”

ለስሜ የሚሆን ቤት
እዚህ “ስም” ክብርን ያመለክታል ። ኣት: - “ለክብሬ የሚሆን ቤተ መቅደስ” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

እርሱ ልጄ ይሆናል እኔም አባት እሆነዋለሁ
እግዚአብሔር ሰሎሞንን እንደ ልጁ አድርጎ ይመለከተዋል ። (ዘይቤያዊን ፡ ይመልከቱ)

የመንግሥቱን ዙፋን በእስራኤል ላይ ለዘላለም አቆማለሁ
እዚህ “ዙፋን” የሚለው ቃል ንጉሥ ሆኖ የመግዛትን ስልጣን ያመለክታል ። ኣት: - “ዘሩ በእስራኤል ላይ ለዘልዓለም እንዲገዛ አደርጋለሁ” (የባህሪ ስምን ፡ ይመልከቱ)

1 Chronicles 22:11

አያያዥ መግለጫ
ዳዊት ሰሎሞንን መናገሩን ቀጠለ።

አሁን
ዳዊት ሊናገር ያሰበውን አንድ ጠቃሚ ነገር ለማስተዋወቅ ይህንን ቃል ይጠቀማል ።

ይገንቡ
ሰሎሞን ህንፃውን በግሉ አይሠራውም ፣ ግን ሌሎች እንዲሠሩ ይመራል ። ኣት: - “አንተ ሰዎች እንዲገነቡ እዘዝ” (የባህሪ ስምን ፡ ይመልከቱ)

በእስራኤል ላይ ሹም ባደረገህ ጊዜ
“የእስራኤል ንጉሥ በሚያደርግህ ጊዜ”

በርቱ እና ደፋር ሁን... አትፍሩ ወይም ተስፋ አትቁረጡ
ሰሎሞን መፍራት እንደሌለበት ለማጉላት እነዚህ ሁለት ተመሳሳይ መልእክት የሚያስተላልፉ ዓረፍተ ነገሮች ተጽፈዋል ፣ (ትይዩአዊን ፡ይመልከቱ)

1 Chronicles 22:14

አያያዥ መግለጫ
ዳዊት ለሰሎሞን መናገሩን ቀጠለ።

አሁን ፣ ተመልከት በጣም ጥሩ
“አሁን ፣ ተመልከት” የሚሉት ቃላት ዳዊት አንድ አስፈላጊ ነገር ሊናገር እንደሆነ የሚጠቁም ነው ። ኣት: - “አዳምጡ! በጥሩ ሁኔታ ”

እኔ በከፍተኛ ጥረት አዘጋጃለሁ
“ለማዘጋጀት ጠንክሬ ሠርቻለሁ”

100,000 ታላንት
“አንድ መቶ ሺህ መክሊት” (ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)

መክሊቶች
ወደ 33 ኪሎግራም (መጽሐፍ ቅዱሳዊ ገንዘብን ፡ይመልከቱ)

አንድ ሚሊዮን
“1,000,000” (ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)

ለዚህ ሁሉ ተጨማሪ ማከል አለብህ
“ይህን መጠን መጨመር ይኖርብሃል”

1 Chronicles 22:15

መግለጫ በማገናኘት ላይ-
ዳዊት ለሰሎሞን መናገሩን ቀጠለ።

የድንጋይ ጠራቢዎች
እነዚህ በድንጋይ እና በህንፃዎች ውስጥ ለሚገነቡ ግንበኞች ድንጋይ የሚቆርጡ እና የሚያዘጋጁ ሰራተኞች ናቸው ።

አናጢዎች
የእንጨት ሥራ የሚሰሩ ሰዎች

ችሎታ ያላቸው የእጅ ጥበብ ባለሙያ
እዚህ “ቁጥር ሥፍር የሌላቸው” የሚለው ቁጥራቸው እጅግ ብዙ እንደነበሩ ለማጉላት ተጋኖ የተጻፈ ነው ። ኣት: - “እጅግ ብዙ ጥሩ ችሎታ ያላቸው የእጅ ጥበብ ባለሙያ እጅግ በጣም ብዙ” (ግነትን እና አጠቃላይን ፡ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ይሁን
ይህ አገላለጽ እግዚአብሔር ሰሎሞንን በፕሮጀክቱ ውስጥ ስኬታማ እንዲሆን እንደሚያግዘው የሚገልጽ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው ። (ፈሊጥን ፡ይመልከቱ)

1 Chronicles 22:17

አምላካችሁ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ነው
ይህ አገላለጽ እስራኤል እንድትበለጽግ እግዚአብሔር እንደሚረዳት የሚያሳይ አገላለፅ ነው ። (ፈሊጥን ፡ይመልከቱ)

የአንተ... አንተ
በ 1ኛ ዜና 22፡ 18-19 ውስጥ እነዚህ ስሞች በብዙ ቁጥር ተገልጸዋል ። (የእርሶን ቅርጽ ፡ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በሁሉም ስፍራ ሰላማችሁን ሰጥታችኋል
“በእስራኤል ዙሪያ የሚኖሩ አገራት ሁሉ ከአንተ ጋር በሰላም እንዲኖሩ አድርገሃቸዋል”

የክልሉን ነዋሪዎችን በእጄ አሳልፎ ሰጥቶኛል
እዚህ “እጅ” ጠላቶቹን የሚያሸንፍበትን ኃይል ያመለክታል ። ኣት: - “በአካባቢያችን በሚኖሩ ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጠኝ” (የባህሪ ስምን ፡ ይመልከቱ)

ክልሉ በጌታ እና በሕዝቡ ፊት ተገዝቷል
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። “ሌሎች ሕዝቦች ከእንግዲህ በእግዚአብሔር እና በሕዝቡ ላይ ጥቃት አያደርሱም” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ይመልከቱ)

አሁን
ይህ ቃል ዳዊት ቀጥሎ ሊናገር ያለውን አስፈላጊ ነገር ያስተዋውቃል ።

አምላከክህን እግዚአብሔርን ፈልግ
እግዚአብሔርን መፈለግ ሁለቱንም ይወክላል 1) የእግዚአብሔርን እርዳታ መጠየቅ ወይም 2) ስለ እግዚአብሔር ማሰብ እና እርሱን መታዘዝ ። (ዘይቤያዊን ፡ይመልከቱ)

በፍጹም ልብህና በፍጹም ነፍስህ
“ልብ” እና “ነፍስ” መላውን ሰው ያመለክታሉ ። ኣት: - “በሙሉ ሰውነትህ ” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን ፡ይመልከቱ)

ተነስና ቅዱሱን ስፍራ ገንባ
ሰሎሞን ሥራውን በግሉ እንደማይሠራው የታወቀ ነው። ግን ሌሎች እንዲሠሩት ያዛቸዋል ። ኣት: - “ ተነሳና እየመራህ ሠራተኞቹ ቅዱሱን ስፍራ እንዲገነቡ አድርግ ” (ዘይቤዊን ፡ይመልከቱ)

ለእግዚአብሔር ስም የተገነባው ቤት
“ስም” ክብርን ያመለክታል ። ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: “እግዚአብሔርን ለማክበር ቤተ መቅደስ ትሠራለህ” (የባህሪ ስምን እና ገቢራዊ ወይም ተብሮአዊን ፡ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 23

1 ዳዊት በሸመገለና ዕድሜው በገፋ ጊዜ፤ልጁን ሰሎሞንን በእራኤል ላይ አነገጀው። 2 እንዲሁም መላውን የእስራኤል መሪዎች፣ካህናቱ ሌዋውያኑን ሁሉ
በአንድነት ሰበሰበ። 3 ዕድሜውቸው ሥላሳና ከዚያ በላይ የሆኑ ወንዶች ሁሉ ተቁጠሩ፤ቁጥራቸውም በጠቅላላው ሠላሳ ስምንት ሺህ ነበረ 4 ዳዊትም እንዲህ
አለ፤ "ከእነዚህ መካከል ሃያ አራቱ ሺህ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ሥራ ይቁጣጠሩ፤ ስድስቱ ሺህ ደግሞ ሹሞችና ዳኞች ይሁኑ፤ 5 አራቱ ሺህ የቅጥሩ በር
ጠባቂዎች ይሁኑ፤ አራት ሺህ ደግሞ ለዚሁ ብዬ ባዘጋጀሁት የዜማ መሣሪያ እግዚአብሔር ያመስግኑ"። 6 ዳዊትም ሌዋውያኑን በሌዊ ልጆች በጌድሶን፣ በቀነዓና
በሜራሪ በየጎሣቸው መደባቸው። 7 ከጌድሳናውያን ወገን፤ ለአዳን፣ሰሜኢ። 8 የለእአዳን ወንዶች ልጆች፤ የመጀመሪያው ይሒኤል፣ ዜቶም፣ ኢዮኤል፣ባጠቃላይ
ሦስት ናቸው። 9 የስማኢ ወንዶች ልጆች፤ ሰሎሚት፣ ሀዝዝኤል፣ ሐራን፣ ባጠቃላይ ሦስት ናቸው። እነዚህ የለአዳን ቤተሰብ አለቆች ናቸው። 10 የስማኢ ወንዶች
ልጆች፤ ኢኢት፣ ዚዛ፣ የዑስ፣ በሪዓ፣ እነዚህ አራቱ የስሚኤ ልጆች ናቸው። 11 የመጀመሪያው ኢኢት፣ ሁለተኛው ደግሞ ዚዛ፣ ነበረ የዑስና በሪዓ ግን ብዙ ወንዶች
ልጆች አልነበሯቸውም፤ ስለዚህ የተቁጥዐሩት በሥራ መደብ እንደ ቤተሰብ ሆነው ነው። 12 የቀነዓት ወንዶች ልጆች፤ እንበረም፣ ይስዓር፣ ኬብሮን፣ ዑዝኤል፣
ባጠቃላይ አራት ናቸው። 13 የእንበረት ወንዶች ልጆች፤ አሮን፣ ሙሴ። አሮን የተቀደሰ እንዲሆን ተለየ፤ እርሱና ዘሮቹ ለዘላለም ቅዱስ የሆኑትን ነገሮች
እንዲቀደሱ፣ እግዚአብሔር ፊት መሥዕዋት እንዲያቀርቡ፤ በፊቱ እንዲያገለግሉና በስሙም ለዘላለም እንዲባረኩ ተለዩ። 14 እግዚአብሔር ሰው የሙሴ ወንዶች
ልጆችም እንደ ሌዊ ነገድ ሆነው ተቁጠሩ። 15 የሙሴ ወንዶች ልጆች፤ ጌርሳም፣ አልዓዛር። 16 የጌሳም ዘሮች፤ ሱባኤል። 17 የአልዓዛር ዘሮች፤ የመጀመሪያው
ረዓብያ ነበረ።አልዓዛር ሌሎች ወንዶች ልጆች ግን እጅግ ብዙ ነበሩ። 18 የይስዓር ዶዶችች ልጆች፤ የመጀመሪያው ሰሎሚት። 19 የኬብሮን ወንዶች ልጆች፤
የመጀመሪያው ዬሪያ፣ ሁለተኛው አማርያ፣ ሦስተኛው የሕዚኤል፣ አራተኛ ይቅምዓም ነበሩ። 20 የዑዝኤል ወንዶች ልጆች፤ የመጀመሪያው ሚካ፣ ሁለተኛው ይሺያ
ነበሩ። 21 የሜራሪ ወንዶች ልጆች፤ ሚሖሊ፣ ሙሲ፣ የሞሐሊ ወንዶች ልጆች አልዓዛር ቂስ ነበሩ። 22 አልዓዛር ወንድ ልጅ ሳይወልድ ሞተ፤ ልጆቹ ሴቶች ብቻ
ነበሩ፤ እርሱንም የአጎታቸው የቂስ ልጆች አገቡአቸው። 23 የሙሲ ወንዶች ልጆች፤ ሞሖሊ፣ ዔደር፣ ኢያሪሙት ባጠቃላይ ሦስት ናቸው። 24 እንግዲህ እነዚህ
የቤተሰብ አለቆች ሆነው እያንዳንዳቸው በየስማቸው ተመዝግበው የተቁጠሩት የሌዊ ዘሮች ናቸው፤ ዕድሜአቸው ሃያና ከዚያ በላይ የሆናቸው በእግዚአብሔር
ቤተ መቅደስ ውስት የሚያገለግሉ ነበሩ። 25 ዳዊት እንዲህ ብሎ ነበርና፣ "የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ዕረፍት ሰጥቷል፤ በእየሩሳሌምም
ለዘላለም ለመኖር መጥቷል፤ 26 ሌዋውያን ከእንግዲህ ወዲህ ድንኳኑን ወይም የመገልገያ ዕቃውን ሁሉ መሸከም የለባቸውም።" 27 ዳዊት በሰጠው
የመጨረሻ መመሪያ መሠረት የተቁጠሩት ሌዋውያን ዕድሜያቸው ሃያና ከዚያ በላይ ነበረ። 28 የሌዋውያኑ ተግባር በእግዚአብሔር ቤተ መቅደሱን ቅጥር ግቢና
ክፍሎች መንከባከብ፣ የተቀደሱ ዕቃዎች ሁሉ ማጻትና በእግዚአብሔር ቤት ያሉትን ሌሎች ተግባሮች ማከናውን ነበር። 29 እንዲሁም መባ ሆኖ የሚቀረውን
ኅብስት ገፅ፣ የእህል ቁርባኑን ዱቄት፣ ያለ እርሾ የሚጋገረውን ቂጣ የሚጋግሩ፣ የሚያቦኩና የሚሰፍረውንም ሆነ የሚለካውን ሁሉ በኅላፊነት የሚቁጣጠሩ እኔሩ
ነበር። 30 በየለዕቱ እግዚአብሔርን ለማመስገንና ለመወደስ ጠዋት ጠዋት ይቆኑ ነበር፤ይህንንም ማታ ማታ፣ 31 እንዲሁም በየሰንበቱ፣ በወር መባቻ በዓልና
በተደነገጉት በዓላት ሁሉ፣ የሚቃጠል መሥዕዋት ለእግዚአብሔር በሚቀርብበት ጊዜ ሁሉ ይፈፅሙ ነበር። በተወሰነላቸው ቁጥርና በተሰጠው መመሪያ መሠረት
ዘውትር በእግዚአብሔር ፊት ያገለግሉ ነበር። 32 ስለዚህ ሌዋውያኑ ለመገናኘት ድንኳንና ለመቅደሱ እንዲሁም በወንድሞቻቸው በአሮን ዘሮች ሥር ሆነው
ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ያለባቸውን ኅላፊነት ያከናውኑ ነበር።

---

1 Chronicles 23:1

አጠቃላይ መረጃ
ዳዊት ሰሎሞን እንደ ተተኪ ሌዋውያንን እና ካህናትን እና የቤተመቅደስ አገልጋዮችን እንዲያደራጅ ሾመው።

ሠላሳ ዓመትና ከዚያም በላይ የሆናቸው ሌዋውያን ተጠሩ
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ አንዳንድ የዳዊት ሰዎች 30 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆናቸውን ሌዋውያንን ይቆጥሩ ነበር” (ገቢራዊ ወይም ተብሮአዊን ፡ይመልከቱ)

እነዚህ ሁሉ ሠላሳ ስምንት ሺህ ነበሩ
“ከእነርሱ 38,000 ነበሩ” (ቁጥሮችን ፡ተመልከት)

1 Chronicles 23:4

ከእነዚህ ውስጥ ሀያ አራት ሺህ
ከእነዚህ ሌዋውያን ውስጥ 24,000” (ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)

ስድስት ሺህ
“6,000 ሌዋውያን” (ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)

መኮንኖችና ዳኞች
እነዚህ ሌዋውያን የሕግ ክርክሮዎችን ያዳምጡ እንዲሁም በሙሴ ሕግ መሠረት ፍትሕን ያሰፍኑ ነበር።

አራት ሺህ
“4,000 ሌዋውያን” (ቁጥሮችን ፡ ይመልከቱ)

የበር ጠባቂዎች
እነዚህ ሌዋውያን በቤተመቅደሱ መግቢያ ላይ ጥበቃ ያደርጉ ነበር ስለሆነም የረከሰ የሆነ ማንኛውም ሰው አይገባም ።

በየሰሞናቸው
“እንደየዘሮቻቸው ፣ተመሥርቶ”

ጌድሶናዊያን ፣ ቀዓት እና ሜራሪ
እነዚህ የሌዊ ልጆች ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ ይመልከቱ)

1 Chronicles 23:7

አጠቃላይ መረጃ
በየወገናቸው የሌዋውያን ዝርዝር ይህ ነው። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ይመልከቱ)

1 Chronicles 23:10

አጠቃላይ መረጃ
የሌዋውያን በየወገናቸው የሌዋውያን ዝርዝሮችን ይቀጥላል። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ፡ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ስለዚህ እንደ አንድ ጎሳ ተደርገው ተቆጠሩ
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ስለሆነም ዳዊት እንደ አንድ ጎሳ አድርጎ ይቆጥራቸዋል” (ገቢራዊን እና ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

1 Chronicles 23:12

አጠቃላይ መረጃ
የሌዋውያን ዝርዝሮችን በየወገናቸው ይቀጥላል። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)

የቀአት ልጆች አራት ነበሩ
“ቀአት 4 ወንዶች ልጆች ነበሩት”

አሮን እጅግ ቅዱስ የሆነውን ነገር ለመለየት ተመርጧል
ይህ በገቢራ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “እግዚአብሔር እጅግ የተቀደሱ ነገሮችን እንዲቀድስ አሮን መረጠ” (ገቢራዊን እና ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

ለዘላለምም በስሙ በረከትን መስጠት
እዚህ “በስሙ” የሚለው እንደ እርሱ ተወካይ የመናገርን ስልጣን ያመለክታል ። ኣት: - “እንደ እግዚአብሔር ወኪል በመሆን ሰዎችን ለዘላለም ይባርክ” (የባህሪ ስምን ፡ ይመልከቱ)

ወንዶች ልጆቹ ሌዋውያን እንደ ሆኑ ተቆጠሩ
የአሮን ወንዶች ልጆች እጅግ አስፈላጊ የሆኑ የሌዋውያን ነገድ ነበሩ ፣ ነገር ግን የሙሴ ልጆችም እንደ ሌዋውያን ተቆጥረዋል ። ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ሕዝቡ የሙሴን ልጆች የሌዊ ነገድ ክፍል እንደሆኑ አድርገው ይመለከቱ ነበር” (ገቢራዊን እና ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

1 Chronicles 23:15

አጠቃላይ መረጃ
የሌዋውያን ዝርዝሮችን በየወገናቸው ይቀጥላል። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)

1 Chronicles 23:19

አጠቃላይ መረጃ
የሌዋውያን ዝርዝሮችን በየወገናቸው ይቀጥላል። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)

ታላቁ... ሁለተኛው... ሦስተኛው... አራተኛው
ሁሉም ወንዶች ልጆች እንደነበሩ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: “የበኩር ልጅ... ሁለተኛው ልጅ... ሦስተኛው ልጁ... አራተኛው ልጁ” (ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

1 Chronicles 23:21

አጠቃላይ መረጃ
የሌዋውያን ዝርዝሮችን በየወገናቸው ይቀጥላል። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)

1 Chronicles 23:24

እነዚህ በየወገናቸው የሌዊ ዘሮች ነበሩ። የነገድ መሪዎች የተቆጠሩና የተዘረዘሩ መሪዎች ነበሩ
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ።
ኣት: “የዳዊት ሰዎች የቆጠሯቸውና የዘረዘሯቸው እነዚህ የሌዊ ዘሮች እና የአባቶቻቸው ስሞች እነዚህ ነበሩ። ”(ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ ይመልከቱ)

ከሃያ ዓመት ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለው
“ከ 20 ዓመት እና ከዛ በላይ” (ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

እረፍት ሰጥቷል
“ዕረፍትን” የሚለው የሚያመለክተው በአጎራባች አገራት መካከል ያለውን ሰላም ነው ። በ 1ኛ ዜና 22 ፡9 ውስጥ ያለው ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጉሙት ይመልከቱ ።

በኢየሩሳሌም ለዘላለም መኖሪያውን ያደርጋል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም ለዘላለም ይኖራል ወይም 2) የእግዚአብሔር መቅደስ በኢየሩሳሌም ውስጥ ለዘላለም ይኖራል ።

በአገልግሎቱ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ መሣሪያዎች ሁሉ
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “በአገልግሎቱ ላይ የተጠቀሙባቸውን መሣሪያ ሁሉ”

1 Chronicles 23:27

በዳዊት የመጨረሻ ቃላት ሌዋውያኑ ተቆጠሩ
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ለዳዊት የመጨረሻ ትእዛዝ ሰዎቹ ሌዋውያንን እንዲቆጥሩ ነበር” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ ይመልከቱ)

ከሃያ ዓመት ጀምሮ ከዚያም በላይ
በ 1ኛ ዜና 23 ፡24 ውስጥ ይህንን ሐረግ እንዴት እንደተረጉሙት ይመልከቱ ። (ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

ገጸ ኅብስት
ስለ “ገጸ ኅብስት” የትርጉም ገጹን ይመልከቱ ። በ 1 ኛ ዜና መዋዕል 9:32 ይህንን እንዴት እንደተረጉሙ ይመልከቱ።

ዱቄት
የተፈጨ የእህል ዱቄት

1 Chronicles 23:30

እነርሱ ቆሙ
“ሌዋውያኑም እንዲሁ በቤተ መቅደሱ ቆመው ነበር”

የሚቃጠሉ መባዎች ሁሉ ለእግዚአብሔር በሚቀርቡበት ጊዜ
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ካህናቱ ለእግዚአብሔር የሚቃጠሉ መባዎችን በሚያቀርቡበት ጊዜ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ ይመልከቱ)

በመባቻ በዓላት
እነዚህ በዓላት እያንዳንዱን የአዲስ ወር መጀመሪያ ያመለክታሉ።

በትእዛዝ የተሰጠው የተመደበው ቁጥር ሁልጊዜ በእግዚአብሔር ፊት መቅረብ ነበረበት
“የተወሰነ ቁጥር ያላቸው ሌዋውያኑ ለእግዚአብሔር መስዋዕት ያቀርቡ ዘንድ በቤተ መቅደስ ውስጥ እንዲገኙ ይመደባሉ”

1 Chronicles 23:32

እነርሱ ኃላፊ ነበሩ
“ሌዋውያኑ በኃላፊነት ቦታ ላይ ይሠሩ ነበር”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 24

1 የአሮን ልጆች አመዳደብ እንደ ሚከተለው ነበረ፤ የኦ ልጆች ናዳብ፣ አብድዩ፣ አልዓዛር፣ ኢታምር፣ ነበሩ። 2 ናዳብና አብድዩ ግን ዘር ሳይተኩ ከአባታቸው በፊት
ሞቱ፤ ስለዚህ አልዓዛርና ኢታምር ካህናት ሆነው ያገለግሉ ነበር። 3 ዳዊትም የአላዓዛር ዘር የሆነው ሳዶቅና የኢታምር ዘር ሆነው አቢሜሌክ እየረዱ
እንደየአገልግሎታቸው ሥርዓት እየለየ መደባቸው። 4 ከኢታምር ይልቅ በአልዓዛር ዘሮች መካከል ብዙ መሪዎች ተገኙ፤ አከፋፈላቸውም እንደሚከተለው ነበር፤
ከአልዓዛር ዘሮች ዐሥራ ስድስት የቤተሰብ አለቆች። 5 ከአልዓዛርና ከኢታምር ዘሮች መካከል የመቅደሱ ሹማምትና የእግዚአብሔር ሹማምት ስለ ነበሩ፣ ያለ
አድልዎ በዕጣ ለዩአቸው። 6 የሌዋውያ የናትናኤል ልጅ ጸሓፊው ሸማያ በንጉሥና በሹማምቱ፣ በካህኑ በሳዶቅ፣ በአብያታር ልጅ በአሜሌክ እንዲሁም በካህናቱና
በሌዋውያኑ ቤተሰብ አለቆች ፊት ስማቸውን ጻፊ፤ የጻፈውም አንዱን ቤተሰብ ከአልዓዛር ሌላውን ደግሞ ከኢታምር በመወሰድ ነው፤ 7 የመጀመሪያው ዕጣ
ለዮአሩብ፣ ሁለተኛውም ዕጣ ለዮዳሄ ወጣ። 8 ሦስተኛው ለካሪም፣ አራተኛው ለሥዖሪም፣ 9 አምስተኛው ለመልክያ፣ ስድስተኛው፤ 10 ሰባተኛው ለአቆስ፣
ስምንተኛው ለአብያ፣ 11 ዘጠናኝው ለኢያሱ፣ ዐሥረኛ ለሴኬንያ፣ 12 ዐሥራ አንደኛው ልች ኤሊያሴብምም ዐሥራ ሁለተኛው ለያቂም፣ 13 ዐሥራ ሦስተኛው
ለኦፓ፣ዐሣር አራተኛው ለየሼብአብ፣ 14 ዐሥራ ሰባተኛው ለቢልጋ፣ ዐሥራ ስድስተኛው ለኢሜር፤ 15 ዐሥራ ሰባተኛው ለኤዚር፣ ዐሥራ ስምንተኛው ለሃፊጼጽ፣ 16
ዐሥራ ዘጠነኛው ለፈታያ፣ ሃያኛው ለኤዜቄል፣ 17 ሃያ አንደኛው ለያኪያ፣ ሃያ ሁለተኛው ለጋሙል፣ 18 ሃያ ሦስተኛው ለድላያ፣ ሃያ አራተኛ ለመዓዝያ ውጣ። 19
የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ባዘዘውና ከቀድሞ አባታቸው ከአሮን በተሰጣቸው መመሪያ መጠረት ወደ እግዘአብሔር ቤተ መቅደስ በሚገቡበት ጊዜ፣
የተወሰነላቸው ሥርዐት ይህ ነበር። 20 የቀሩት የሌዊ ዘሮች አግሚ፦ከእንበረም ወንዶች ልጆች፤ ሱባኤል፤ ከሱባኤል ወንዶች ልጆች፤ ዬሕድያ። 21 ከረዓብያ
ወንዶች ልጆች፤ አለቃው ይሺው። 22 ከይስዓራውያን ወገን፤ ሰሎሚት ከሰሎሚት ወንዶች ልጆች፤ ያሐት። 23 የኬብሮን ወንዶች ልጆች፤ የመጀመሪያው ይሪያ፣
ሁለተኛው አማርያ፣ ሦስተኛው የሕዚኤል፣ አራተኛው ይቀምዓም። 24 የዑዝኤል ልጅ፤ ሚካ። የሚካ ወንዶች ልጆች ሻሚር። 25 የሚካ ወንድም ይሺያ፤ ከይሺያ
ወንዶች ልጆች ዘካርያስ። 26 የሜራሪ ወንዶች ልጆች፤ሞሖሊምም ሙሲ።የያዝያ ወንድ ልጅ በኖ፤ 27 የሜራሪ ወንዶች ልጆች፤ ከያዝያ በኖ፣ ሾሃም፣ ዘኩር፣
ዔብሪ። 28 ከሞሒሊ፤ አልዓዛር፤ ይህ ሰው ወንዶች ልጆች አልነበሩትም። 29 ከቂስ፣ የቂስ ወንድ ልጅ፤ ይረሕምኤል። 30 የሙሲ ወንዶች ልጆች፤ ሞሖሊ፣
ዔዳር፣ ኢያሪሙት። እነዚህ እንግዲህ እንደቤተሰባቸው የተቁጠሩ ሌዋውያን ነበሩ። 31 ወንድሞቻቸው የአሮን እንዳደረጉት ሁሉ፣ እነዚህም በንጉሥ ዳዊት፣
በሳዶቅ፣ በአቢሜሌክ እንዲሁም የካህናቱ የሌዋውያኑ ቤተሰብ አለቆች ባሉበት ዕጣ ተጣጣሉ፤ የበኩሩም ቤተሰቦች እንደ ትንሹ ወንድም ቤተሰብ እኩል ዕጣ
ተጣለላቸው።

---

1 Chronicles 24:1

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ምዕራፍ በቀደሙት ምእራፍ ውስጥ ሌዋውያኑ ወደ ተለያዩ የሥራ መደቦች እንዴት እንደ ተሠማሩ ያብራራል ::

ናዳብ ፣ አብድዮ ፣ አልዓዛር እና ኢታምርም
በ 1ኛ ዜና መዋዕል 6፡ 3 ውስጥ እንዳለው የእነዚህን ሰዎች ስሞች ይተርጉሙ ::

አቢሜሌክ
ይህ የሰው ስም ነው :: (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)

በቡድን ከፈለቸው
“የአልዓዛር እና የኢታምር ዘሮች በቡድን በቡድን ለካ”

1 Chronicles 24:4

ተከፋፈሉ
“ዳዊት ፣ ሳዶቅ እና አቢሜሌክ ተከፋፈሉ”

አሥራ ስድስት ቡድኖች
“16 ቡድኖች” (ቁጥሮችን : ይመልከቱ)

የነገድ ራሶች
“ራሶች” የሚለው በጣም አስፈላጊ ለሆኑ ሰዎች የተሰጠ ስም ነው — የነገዶች መሪዎች ነው :: አት: - “የየነገዶቹ መሪዎች” (ዘይቤያዊን : ይመልከቱ)

እነዚህ ምድቦች በየወገናቸው ስምንት ነበሩ
“ከኢታምርም ልጆች እንደ አባቶቻቸው ቤቶች 8 ክፍፍሎች ነበሩ”

ያለአንዳች ልዩነት በእጣ ተመደቡ
ክፍፍሎች ፍትሃዊ እንዲን በዕጣ ተመደቡ ”

1 Chronicles 24:6

ሸማያ
ይህ የሰው ስም ነው :: (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)

ናትናኤል
በ 1ኛ ዜና መዋዕል 15፡ 24 ውስጥ የዚህን ሰው ስም እንዴት እንደተረጉሙ ይመልከቱ ::

አቢሜሌክ
በ 1 ኛ ዜና ምዕራፍ 18፡16 ውስጥ የዚህን ሰው ስም እንዴት እንደተረጉሙ ይመልከቱ ::

አንዱንም የአባት ቤት ለአልዓዛር ፣ አንዱንም ለኢታምር ጻፈ
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ለገለፅ ይችላል :: ኣት: - “ከአልዓዛር ዘሮች አንድ በዕጣ መረጡ ፣ ከዚያ በዕጣ ከኢታምር ዘሮች ይመርጣሉ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

1 Chronicles 24:7

አጠቃላይ መረጃ
ለአልዓዛርና ለኢታምር ዘሮች ይህ አገልግሎት ነው። (ስሞችን ተራ ቁጥሮችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)

1 Chronicles 24:11

አጠቃላይ መረጃ
ለአልዓዛርና ለኢታምር ዘሮች ይህ አገልግሎት ነው። (ስሞችን ተራ ቁጥሮችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Chronicles 24:15

አጠቃላይ መረጃ
ለአልዓዛርና ለኢታምር ዘሮች ይህ አገልግሎት ነው። (ስሞችን ተራ ቁጥሮችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)

1 Chronicles 24:19

የአባቶቻቸው የአሮን ልጅ ያዘዘውን ሥርዓት በመከተል ነው
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “አባታቸው አሮን የሰጣቸውን ሕግጋት እየተከተሉ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

1 Chronicles 24:20

አጠቃላይ መረጃ
ሌሎቹ የሌዊ ልጆች ስሞች ዝርዝር ይጀምራል። ይህ ዝርዝር በ 1ኛ ዜና መዋዕል 24 :30 ውስጥ ያበቃል ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ : ይመልከቱ)

አምራም
በ 1ኛ ዜና መዋዕል 6 :3 ውስጥ የዚህን ሰው ስም እንዴት እንደተረጉሙ ይመልከቱ ።

ሹባኤል
በ 1 ኛ ዜና ምዕራፍ 23 :16 ውስጥ የዚህን ሰው ስም እንዴት እንደተረጉሙ ተመልከት ።

1 Chronicles 24:23

ኬብሮን... ይሪያ... አማሪያ... የሕዚኤል... ይቀምዓም
በ 1 ኛ ዜና 23 :19 ውስጥ እንዳለው የእነዚህን ሰዎች ስሞች ይተርጉሙ ።

ሁለተኛው... ሦስተኛው... አራተኛው
“ሁለተኛው ልጅ... ሦስተኛው ልጅ ፣ አራተኛው ልጁ” (ሕገኛ ቁጥሮችን : ይመልከቱ)

ዑዝኤል... ሚካ... ይሺያ
በ 1 ኛ ዜና 23 :20 እንዳለው የእነዚህን ሰዎች ስሞች ይተርጉሙ ።

ሻሚር... ዘካርያስ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ : ይመልከቱ)

1 Chronicles 24:26

ሜራሪ... ሞሖሊ.... ሙሲ... አልዓዛር
በ 1 ኛ ዜና 23 :21 ውስጥ እንዳለው የእነዚህን ሰዎች ስሞች ይተርጉሙ ።

ከያዝያ... ሾሃም... ዘኩር... ኤብሪ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ : ይመልከቱ)

ከያዝያ ልጅ: በኖ ... ከያዝያ: በኖ ሾሃም
ያዝያ ሌላኛው የሜራሪ ልጅ ይመስላል። ቤኖም የያዝያ ልጅ ነው። በቤተሰቦቹ መሪ ስለሆነ ቤኖ ሁለት ጊዜ ተጠቅሷል ። ሆኖም አንዳንድ መጽሐፍ ቅዱሶች እንደ ትክክለኛ ስሙ ሳይሆን “ቤኖን” “ልጁ” ብለው ተርጉመዋል። እነዚያ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚከተለው ይነበባሉ: - ከወንዶቹም ከያእያ ከልጁ ከያዝያ ከልጁ ከሾሃም።

1 Chronicles 24:29

ከቂስ - የቂስ ልጅ
ይህ በጽሑፍ ውስጥ እንደ አርዕስት ሆኖ የተጻፈ ነው ፣ ግን በበለጠ በተሟላ መልኩ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ከቂስ የተወለዱት ልጆች እነዚህ ናቸው”

ቂስ... ሙሲ
በ 1 ኛ ዜና 23 :21 ውስጥ እንዳለው የእነዚህን ሰዎች ስሞች ተርጉም ።

ይረሕምኤል... ሞሓሊ.... ዔዳር... ኢያሪሙት
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)

አቢሜሌክ
በ 1 ኛ ዜና 18 :16 እንደምናየው የዚህን ሰው ስም ይተርጉሙ ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 25

1 ዳዊት ከሰራዊቱ አለቆች ጋር ሆኖ በመሰንቆ፣ በበገና በጽናጽል ድምፅ እየታጀቡ ትንቢት የሚናገሩትን ከአሳፍ፣ ከኤማንና ከኤዶም ቤተሰብ መካከል መርጦ መደብ፤ ይህን አገልግሎት የሚያከናውኑትም ሰዎች ዝርዝር እንደ ሚከተለው ነው፤ 2 ከአሳፍ ወንዶ ልጆች፤ ዘኩር፣ ዮሴፍ፣ ነታንያ፣ አሼርኤላ። እአሳፍ ልጆች በአሳፍ አመራር ሥር ነበሩ፤ አሳፍም በንጉሥ አመራር ሥር ነበረ። 3 ከኤዶምወንዶች ልጆች፤ ዶልያስ፣ ጽሪ፣ የሻያ፣ ሰሜኢ፣ ሐሸብያ፣ መቲትያ። እነዚህ ስድስቱ በመሰንቆ እግዚአብሔርን እያመሰገነና እየወደሰ ትንቢት በተናገረው አባታቸው በኤዶታም አመራር ሥር ነበሩ። 4 ከኤማን ወንዶች ልጆች፤ ቡቅያ፣ መንታያ፣ ዓዛርዔል፣ ሱባኤል፣ ኢያሪሙት፣ ሐናንያ፣ ናኒ፣ ኤልያታ፣ ጊዶልቲ፣ ሮማንቲዔዘር፣ ዮሽብቃሻ፣ መሎቲ፣ ሆቲር፣ መሐዝዮት። 5 እነዚህም ሁሉ የንጉሡ ባለራእይ የኤማን ልጆች ነበሩ። እርሱን ከፍ ከፍ እንዲያደርጉትም እግዚአብሔር በገባለት ቃል መሠረት ተሰጡት፤ እግዚአብሔር ለኤማን ዐሥራ አራት ወንድሞችና ሦስት ሴቶች ልጆች ሰጠው። 6 እነዚህ ሁሉ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በጽናጽል፣ በመሰንቆ በበገና አገልግሎት በአባቶቻቸው አመራር ሥር ነበሩ። አሳፍ፣ ኤዶታምና ኤማን ደግሞ በንጉሥ የበላይ አመራር ሥር ነበሩ። 7 እነዚህም ከቤተዘመዶቻቸው ጋር በመሆን ሁሉም ወደ እግዚአብሔር በሚቀርበው ዜማ የሠለጠኑ የተካኑ ነበሩ፤ ቁጥራቸውም ሁለት መቶ ሰማንያ ስምንት ነበረ። 8 የሥራ ድርሻቸውንም ለመወሰን ወጣት፣ ሽማግሌ፣ መምህርም ሆነ ደቀ መዝሙር ሳይባል እኩል ዕጣ ተጣጣሉ። 9 የመጀመሪያው ዕጣ ከአሳፍ ወገን ለሆነው ዮሴፍ ወንዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤ ቁጥራቸው12 ሁለተኛው ለጎዶልያስ ወጣ፤ እነሱን ጨምሮ ለቤተ ዘመዶቹና ለወንዶች ልጆቹ፤ ቁጥራቸውም12 10 ሦስተኛው ለዛኩር፣ ወንዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤ ቁጥራቸውም12 11 አራተኛው ላይጽሪ፣ ለወንዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤ ቁጥራቸውም 12 12 አምስተኛው ለነታንያ ለወንዶቹ ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ ቁጥራቸውም 12 13 ስድስተኛው ለቡቃያ፣ ለወንዶች ልጆቹና ለዘመዶቹ ወጣ፤ ቁጥራቸውም 12 14 ሰባተኛው ለይሽርኤል፣ ለወንዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤ ቁጥራቸውም 12 15 ስምንተኛው ለየሻያ፤ ለወንዶች ልጆቹ ወጣ፤ ቁጥራቸውም 12 16 ዘጠነኛው ለመታንያ፣ ወንዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ቁጥራቸውም 12 17 ዐሥረኛው ለሰሜኢ፣ ወጣ ወንዶች ልጆችና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ ቁጥራቸውም 12 18 ዐሥራ አንደኛው ለዓዛርኤል፣ ወንዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤ ቁጥራቸውም 12 19 ዐሥራ ሁለተኛው ለሐሻብያ ለወንዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤ ቁጥራቸውም 12 20 ዐሥራ ሦስተኛው ለሱባኤል፣ ለወንዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ ቁጥራቸውም 12 21 ዐሥራ አራተኛው ለመቲትያ፣ ለወንዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤ ቁጥራቸውም 12 22 ዐሥራ አምስተኛው ለኢያሪሙት፣ ለወንዶች ልጆቹና ዘመዶቹ ወጣ፤ ቁጥራቸውም 12 23 ዐሥራ ስድስተኛው ለሐናንያ፣ ለወንዶች ልጆቹና ዘመዶቹ ወጣ፤ ቁጥራቸውም 12 24 ዐሥራ ሰባተኛ ለዮሽብቃሻ፣ ለወንዶች ልጆቹና ዘመዶቹ ወጣ፤ ቁጥራቸውም 12 25 ዐሥራ ስምንተኛው ለሐናኒ፣ ለወንዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤ ቁጥራቸውም 12 26 ዐሥራ ዘጠነኛ ለመሎቲ፣ ለወንዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤ ቁትራቸውም 12 27 ሃያኛው ለኤልያታ፣ ለወንዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤ ቁጥራቸውም 12 28 ሃያ አንድኛው ለሆቲር፣ ለወንዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤ ቁጥራቸው 12 29 ሃያ ሁለተኛው ለጊዶልቲ፣ ወንዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤ ቁጥራቸውም 12 30 ሃያ ሦስተኛው ለመሐዝዮት፣ ለወንዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤ ቁጥራቸውም 12 31 ሃያ አራተኛውም ለሮማንቲዔዘር፣ ለወንዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤ ቁጥራቸውም 12

---

1 Chronicles 25:1

በአገልግሎታቸውም
“በማደሪያ ድንኳን የተሰራ ስራ”

በጸናጽልም
ይህ ከፍተኛ ድምጽ ለማሰማት በአንድ ላይ የሚመቱ ሁለት ቀጭኑ ክብ የብረት ሰሌዳዎችን ይመለከታል። ይህን በ1 ዜና 13:8 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (የማይታወቁትን መተርጎም: ይመልከቱ)

የአሳፍ ልጆች በንጉሡ ትእዛዝ ትንቢት ከተናገረው ከአሳፍ እጅ በታች ነበሩ
“እነዚህ ይመራቸው የነበሩ የአሳፍ ልጆች ናቸው። አሳፍ በንጉሱ ቁጥጥር ሥር ትንቢት ተናግሯል ”

ኤማን ... ኤዶታም
የእነዚህን ወንዶች ስሞች እንዴት እንደተረጎሙ በ1 ዜና 16:41 ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ዘኩር፣ ዮሴፍ፣ ነታንያ፣ እና አሸርኤላ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ጎዶልያስ፣ ጽሪ፣ የሻያ፣ ሰሜኢ፣ ሐሸብያ፣ መቲትያ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

እጅ በታች
“በእይታ ስር”

1 Chronicles 25:4

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ በ1 ዜና 25:2 ተጀምሮ የነበረውን የማደሪያ ድንኳን የሚመሩትን ዝርዝር ይቀጥላል።

ቡቅያ... መሐዝዮት
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ኤማን
የዚህን ሰው ስም በ1 ዜና 16:41 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

አሥራ አራት ወንዶች ልጆችንና ሦስት ሴቶች ልጆችን
“14 ወንዶች ልጆች እና 3 ሴቶች ልጆች” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

ቀንደ መለከቱን ከፍ ያደርጉ ዘንድ
የእንስሳ ቀንድ የጥንካሬ ወይም የሥልጣን ምልክት ነው። የአንድን ሰው ቀንድ ከፍ ማድረግ እሱን ለማክበር ዘይቤ ነው። አት: - “ኤማንን ለማክበር” (ዘይቤ: ይመልከቱ)

1 Chronicles 25:6

ከአባታቸው እጅ በታች ነበሩ
“በአባቶቻቸው እይታ ሥር ነበሩ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በጸናጽልና
ይህ ከፍተኛ ድምጽ ለማሰማት በአንድ ላይ የሚመቱ ሁለት ቀጭኑ ክብ የብረት ሰሌዳዎችን ይመለከታ። ይህን በ1 ዜና 13:8 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (የማይታወቁትን መተርጎም: ይመልከቱ)

ኤዶታም... ኤማን
የእነዚህን ሰዎች ስም በ1 ዜና 16:41 እንደተረጎሙት ይተርጉሙ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

288 ተቆጠሩ
“ሁለት መቶ ሰማንያ ስምንት ሰዎች ነበሩ” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

ሁሉም ተካክለው፥ ታናሹ እንደ ታላቁ፥ አስተማሪውም እንደ ተማሪው
ይህ ጽንፎችን በመግለጽ ሁሉንም ወንዶች ይመለከታል ። አት: “ወጣቶችን ፣ ሽማግሌዎችን ፣ አስተማሪዎችን እና ተማሪዎችን ጨምሮ ሁሉም” (ሜሬዝም: ይመልከቱ)

1 Chronicles 25:9

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ ቤተሰቦች የሚያገለግሉበትን ቅደም ተከተል ለመምረጥ የተጣሉትን 24 ዕጣዎች ዝርዝር ይጀምራል። ይህ ዝርዝር በ1 ዜና 25:31 ያበቃል።

የፊተኛው ዕጣ... ሁለተኛው... ሦስተኛው... አራተኛው... አምስተኛው
“ዕጣ... ቁጥር 1... ዕጣ ቁጥር 2... ዕጣ ቁጥር 3... ዕጣ ቁጥር 4... ዕጣ ቁጥር 5.” ይህ ቤተሰቡ በዕጣ የተመረጠበትን ቅደም ተከተል ያሳያል። ይህ በቋንቋዎ ተፈጥሮአዊ ካልሆነ “የመጀመሪያው” ለ “የመጀመሪያው” እና “ቀጣዩ” ለሚቀጥሉት ሁሉ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። (ሕገኛ ቁጥሮች: ይመልከቱ)

የፊተኛው ዕጣ ... ለዮሴፍ ወጣ
በዝርዝሩ ውስጥ ላሉት ሰዎች ሁሉ ፣ ጽሑፉ “ቁጥሩ አሥራ ሁለት ሰዎች” እንደነበሩ ልዩ ያሳያል። ይህ ለዮሴፍ ቤተሰቦች እውነት ስለሆነ በግልጽ መግለፅ ይፈልጉ ይሆናል። አት: - “የመጀመሪያው ዕጣ በዮሴፍ ቤተሰብ ላይ ወደቀ ቁጥራቸው አሥራ ሁለት ሰዎች ናቸው” (ታሳቢ የሆነ እውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ: ይመልከቱ)

ዮሴፍ... ዘኩር... ነታንያ
የእነዚህን ሰዎች ስሞች በ1 ዜና 25:2 እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ሁለተኛው ወጣ
ይህ ሁለተኛውን ዕጣ ይመለከታል። እዚህ ጋር እና ሀረጎቹ ዕጣዎችን በተመለከተ ሲጠቀሱ “ዕጣ” የሚለው ቃል በግልፅ ሊገለፅ ይችላል። አት: “ሁለተኛው ዕጣ ለእከሌ ወደቀ” (ግድፈተ ቃላት: ይመልከቱ)

ጎዶልያስ
የዚህን ሰው ስም በ1 ዜና 25:3 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

አሥራ ሁለት ነበሩ
“12 ሰዎች” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

ይጽሪ
ይህ ስም በ1 ዜና 25:3 ጽሪ ተብሏል። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

1 Chronicles 25:13

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ በ1 ዜና 25:9 የተጀመረውን ዝርዝር ይቀጥላል።

ስድስተኛው... ዘጠኝኛው
“ዕጣ ቁጥር 6 ... ዕጣ ቁጥር 7 ... ዕጣ ቁጥር 8 ... ዕጣ ቁጥር 9።” ይህ ቤተሰቦቹ የተመረጡበትን ቅደም ተከተል ያሳያል። (ሕገኛ ቁጥሮች: ይመልከቱ)

ስድስተኛው ... ወጣ
ይህ ስድስተኛውን ዕጣ ይወክላል። እዚህና ሀረጎቹ ስለ ዕጣዎች ሲያወሩ “ዕጣ” የሚለው ቃል ሊተካ ይችላል። አት: “ስድስተኛው ለእከሌ ወደቀ” (ግድፈተ ቃላት: ይመልከቱ)

ቡቅያ... መታንያ
የእነዚህ ሰዎች ስም በ1 ዜና 25:4 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

አሥራ ሁለት ነበሩ
“12 ሰዎች” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

የሻያ
የዚህን ሰው ስም በ1 ዜና 25:3 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

1 Chronicles 25:17

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ በ1 ዜና 25:9 የተጀመረውን ዝርዝር ይቀጥላል።

አሥረኛው... አሥራ ሦስተኛው
“ዕጣ ቁጥር 10 ... ዕጣ ቁጥር 11 ... ዕጣ ቁጥር 12 ... ዕጣ ቁጥር 13።” ይህ ቤተሰቦቹ የተመረጡበትን ቅደም ተከተል ያሳያል። (ሕገኛ ቁጥሮች እና ቁጥሮች: ይመልከቱ)

ሰሜኢ... ሐሸብያ
የእነዚህን ሰዎች ስም በ1 ዜና 25:3 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

አሥራ ሁለቱ
“12 ሰዎች” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

ሱባኤል
የዚህን ሰው ስም በ1 ዜና 25:4 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

1 Chronicles 25:25

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ በ1 ዜና 25:9 የተጀመረውን ዝርዝር ይቀጥላል።

አሥራ ስምንተኛው... ሀያ አንደኛው
“ዕጣ ቁጥር 18 ... ዕጣ ቁጥር 19 ... ዕጣ ቁጥር 20 ... ዕጣ ቁጥር 21።” ይህ ቤተሰቦቹ የተመረጡበትን ቅደም ተከተል ያሳያል። (ሕገኛ ቁጥሮች እና ቁጥሮች: ይመልከቱ)

ሐናኒ... መሎቲ... ኤልያታ... ሆቲር
የእነዚህ ሰዎች ስሞች በ1 ዜና 25:4 እንደተረጎሙት ይተርጉሙ።

አሥራ ሁለቱ
“12 ሰዎች” (ቁጥሮች: ይመልከቱ))

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Chronicles 25:29

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ በ1 ዜና 25:9. የተጀመረውን ዝርዝር ይደመድማል።

ሀያ ሁለተኛው ... ሀያ ሦስተኛው
“ዕጣ ቁጥር 22 ... ዕጣ ቁጥር 23 ... ዕጣ ቁጥር 24።” ይህ ቤተሰቦቹ የተመረጡበትን ቅደም ተከተል ያሳያል። (ሕገኛ ቁጥሮች እና ቁጥሮች: ይመልከቱ)

ጊዶልቲ ... መሐዚዮት ... ሮማንቲዔዘር
የእነዚህን ሰዎች ስሞች በ1 ዜና 25:4 እንደተረጎሙት ይተርጉሙ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

አሥራ ሁለቱ
“12 ሰዎች” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 26

1 6 የቤተ መውደሱ በር ተባቂዎች አመዳደብ፤ ከቆሬያውያን ወገን፤ ከአሳፍ ወንዶች ልጆች አንዱ የሆነው የቆሬ ወንድ ልጅ ሜሱላም። 2 ሜሱላም ወንዶች
ልጆች ነበሩት፤ የመጀመሪያው ዘካሪያስ ሁለተኛው ይዲኤል፣ ሦስተኛው ዮዛባት፣ አራተኛው የትኒኤል፣ 3 አምስተኛው ኤላም፣ ስድስተኛው ይሆሐናን፣ ሰባተኛው
ኤሊሆዔናይ። 4 ዖቤድኤዶምም እንደዚሁም ወንዶች ልጆች ነበሩት፤ የመጀመሪያው ሸማያ፣ ሁለተኛው ዮዛባት፣ ሦስተኛው ኢዮአስ፣ አራተኛው ሣካር፣ አምስተኛው
ናትናኤል፣ 5 ስድስተኛው ዓሚኤል፣ ሰባተኛው ይሳኮር፣ ስምንተኛው ፒላቲ፤ እግዚአብሔር ዖቤድኤዶምን ባርኮታልና። 6 እንዲሁም ልጁ ሸማያ ወንዶች ልጆች
ነበሩት፤ እነሱም በቂ ችሎታ ስለነበራቸው የአባታቸው ቤት መሪዎችች ሆኔ ነበር። 7 የሸማያ ወንዶች ልጆች፤ ዖትኒ፣ ራፋኤል፣ ዖቤድ፣ ኤልዛባድ፣ ዘመዶቹ
ኤሊሁና ስማክያም እንደዚሁ በቂ ችሎታ ነበራቸው። 8 እነዚሁ ሁሉ የዖቤድኤዶም ዘሮች ሲሆኑ፣ እነሱም ሆኑ ወንዶች ልጆቻቸውና ቤተ ዘመዶቻቸው ሥራውን
ለመጅርት በቂ ችሎታ ነበራቸው። የዖቤድኤዶም ዘሮች ባጠቃላይ ሥልሳ ሁለት ነበሩ። 9 ሜሱላም በቂ ችሎታ ያላቸው ወንዶች ልጆችና ቤተ ዘመዶች ነበሩ፤
ቁጥራቸውም ባጠቃላይ ዐሥራ ሁለት ነበሩ። 10 ከሜራሪ ወገን የሆነው ሖሳ ወንዶች ልጆች ነበሩት፤ የመጀመሪያው ሸምሪ ነበረ፤ የበኩር ልጅ ባይሆንም እንኳን
አባቱ ቀዳሚ አድርጎ ነበር። 11 ሁለተኛው ኬልቅያስ፣ ሦስተኛው ጥበልያ፣ አራተኛው ዘካሪያስ፤ የሖሳ ወንዶች ልጆች ቤተ ዘመዶቹ ባጠቃላይ ዐሥራ ሦስት
ነበሩ። 12 የቤተ መቅደሱም ጠባቂዎች በአለቆቻቸው ሥር ተመድበው ልክ እንደ በተ ዘመዶቻቸው ሁሉ እግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ሥራ ለማከናውን ምድብ
ተራ ነበራቸው። 13 ለእያንዳንዱም በር ወጣት ሽማግሌ ሳይባል ለሁሉም እኩል ዕጣ ተጣለ። 14 የምስራቁ በር ዕጣ ለሴሌምያ ወጣ።ከዚያም ምክር ዕዋቂ
ለሆነው ለልጁ ለዘካሪያስ ዕጣ ጣሉ፤እርሱም የሰሜኑ በር ደረሰው። 15 የደቡብ በር ዕጣ ለዖቤኤዶም ሲወጣ፤ የግምጃ ቤቱ ዕጣ ደግሞ ለልጆቹ ወጣ። 16
የምዕራቡ በርና በላይኛው መንገድ ላይ የሚገኘው የሸሌኬት በር ዕጣዎችች ለሰፊንና ለሖሳ ወጣ። 17 በአንዱ ዘብ ጥበቃ ትይዩ ሌላ ዘብ ትበቃ ነበረ፣
በየቀኑም በምሥራቅ በኩል ስድስት፤ በሰሜን በኩል አራት፣ በደቡብ በኩል አራት፣፣ በዕቃ ቤቱ በኩል በአንድ ሂዜ ሁለት ሌዋውያን ይጠብቁ ነበር። 18
በምዕራቡ በኩል የሚገኘው አደባባዩ ደግሞ ሁለት ሆነው ይጠብቁ ነበር። 19 እንዲህ የቆየና የሜራሪ ዘሮች የሆኑት በር ጠባቂዎች ድልድይ ይህ ነበር። 20
ከሌዋውያን መካከል አኪያ የእግዚአብሔር ቤት ግምጃ ቤትና የተቀደሱት ዕቃዎች የሚቀመጡበት ግምጃ ቤት ኀላፊ ነበረ። 21 የለአዳን ዘሮች፣ በለአዳን በኩል
ጌድሶናውያን የሆኑትና ለጌድሶዊው ለለአዳን ቤተሰቦች አለቆች የሆኑት ለለአዳን ዘሮች እነዚህ ነበሩ፤ ይሒኤሊ፣ 22 የይሒኤሊ ወንዶች ልጆች፣ ዜቶምና
ወንድሙ ኢዩኤል። እነዚህም እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ግምጃ ቤት ኀላፊዎች ነበሩ። 23 ከእንበረማውያን፣ ከይስዓራውያን፣ ከኬብሮናውያን፣ ለዑዝኤላውያን፤
24 የሙሴ ልጅ የገርሳም ዘር የሆነው ሱባኤል የግምጃ ቤቱ የበላይ ኀላፊ ነበረ። 25 በአልዓዛር በኩል የሚዛመዱት፤ ልጁ ረዓብያ፣ ልጁ የሻያ፣ ልጁ ኢዮራም
ልጁ ዝክሪ፣ ልጁ ሰሎሚት። 26 ሰሎሚትና የሥጋ ዘመዶቹ ንጉሥ ዳዊት፣ የቤተሰቡ ኀላፊዎች፣ የሻለቆችና የመቶ አለቆች እንዲሁም ሌሎች የሰራዊቱ አዣች
ቀድሰው ላቀረቧቸው ንዋያት ቅድሳት ኀላፊዎች ነበሩ። 27 በጦርነቱ ከተገኘውም ምርኮ ከፊሉን ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ማደሻ እንዲሆን ቀደሱት። 28 ባለ
ራእይ ሳሙኤል፣ የቂስ ልጅ ሳኦል፣ የኔር ልጅ አቤኔር፣ ቅድሳት ሰሎሚናትና ቤተ ዘመዶቹ ይጠብቁ ነበር። 29 ከይስዓራውያን፤ ከናንያና ወንዶች ልጆቹ ከቤተ
መቅደሱ ውጭ ባለው ሥራ በእስራኤል ላይ ሹማምትና ዳኞች ሆነው ተመደቡ። 30 ከኬብሮናውያን፤ ሐሸብያ፣ ጠንካራና ጎበዝ የሆኑ ሺህ ሰባት መቶ ሰዎች
ከዮርዳኖስ በሰተ ምዕራብ በሚገኘው የእስራኤል ምድር ላለው የእግዚአብሔር ሥራና ለንጉሡም አገልግሎት ኀላዎች ሆነው ተመደቡ። 31 በኬብሮናውያን በኩል
በቤተሰቦቻቸው የትውልድ መዝገብ መሠረት ይሪያ አለቃቸው ነበረ። በዳዊት ዘመነ መንግሥት በአርባኛው ዓመት መዛግብቱ ተመርምረው ስለ ነበር፣ በገለዓድ
ውስጥ ኢያዜ በተባለ ቦታ ከኬብሮናውያን መካከል ጠንካራ ሰዎች ለጋኙ ችለዋል። 32 ይሪያም ጠንካሮችና የቤተሰባቸው አለቆች የሆኑ ሁለ ሺህ ሰባት መቶ
ሥጋ ዘመዶች ነበሩት። ንጉሥ ዳዊትም እነዚህን የእግዚአብሔር ለሆነውና የንጉሡም በሆነው ጎዳይ ላይ ሮቤልን፣ ጋድንና የምናሴ ነገድ እኩሌታ ኀላፊ አድርጎ
ሾማቸው።

---

1 Chronicles 26:1

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ የበረኞቹን ዝርዝር ይጀምራል።

ተመደቡ
ቡድኖች

ከቆሬያውያን
የዚህን የሕዝቦች ቡድን ስም በ1 ዜና 19:19 እንዴተ እንደተረጎሙ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ሜሱላም ... ዘካርያስ
የእነዚህን ሰዎች ስሞች በ1 ዜና 9:21 እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ቆሬ
የዚህን ሰው ስም በ1 ዜና 9:19 እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

አሳፍ
ይህ በ1 ዜና 9:19 ላለው ለ“ኢቢያሰፍ” አማራጭ አፃፃፍ ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ይዲኤል ... ዮዛባት ... የትኒኤል ... ኤላም ... ይሆሐናን ... ኤሊሆዔናይ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ሁለተኛው ... ሦስተኛው ... አራተኛው ... ሰባተኛው
ይህ ወንዶቹ ልጆች የተወለዱበትን ቅደም ተከተል ያሳያል። ለቋንቋዎ ምቹ ከሆነ ለእያንዳዱ ወንድ ልጅ ቀጣዩ” ማለት ይችላሉ። (ሕገኛ ቁጥሮች: ይመልከቱ)

1 Chronicles 26:4

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ በ1 ዜና 26:1 የተጀመረውን የበረኞች ዝርዝር ይቀጥላል።

ዖቤድኤዶም
የዚህን ሰው ስም በ1 ዜና 16:38 እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ሸማያ ... ዮዛባት ... ኢዮአስ ... ሣካር ... ናትናኤል ... ዓሚኤል ... ይሳኮር ... ፒላቲ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ሁለተኛው ... ሦስተኛው ... አራተኛው ... ስምንተኛው
ይህ ወንዶቹ ልጆች የተወለዱበትን ቅደም ተከተል ያሳያል። ለቋንቋዎ ምቹ ከሆነ ለእያንዳዱ ወንድ ልጅ ቀጣዩ” ማለት ይችላሉ። (ሕገኛ ቁጥሮች: ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በአባታቸው ቤት ሠለጠኑ
“በአባቶቻቸው ቤቶች መሪዎች የነበሩ።” ይህም በነገዶቻቸው መካከል መሪዎች ነበሩ ማለት ነው።

1 Chronicles 26:7

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ በ1 ዜና 26:1 የተጀመረውን የበረኞች ዝርዝር ይቀጥላል።

ሸማያ ... ዖቤድኤዶም
የእነዚህን ሰዎች ስሞች በ1 ዜና 26:4-6 እንደተረጎሙ ይተርጉሙ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ዖትኒ ... ራፋኤል ... ዖቤድ ... ኤልዛባድ ... ኤልሁ ... ሰማክያ ... ሜሱላም
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ወንድሞች
“የሲሚያ ዘመዶች” ወይም “የሲሚያ የቤተሰብ አባላት”

ስድሳ ሁለት ነበሩ
“62 ወንዶች” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

አሥራ ስምንት ... ነበሩት
“18 በአጠቃላይ” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

1 Chronicles 26:10

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ በ1 ዜና 26:1 የተጀመረውን የበረኞች ዝርዝር ይቀጥላል።

ሖሳ... ሜራሪ... ሽምሪ ... ኬልቅያስ... ጥበልያ... ዘካርያስ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ሁለተኛውም... ሦስተኛው ... አራተኛው
ይህ ወንዶቹ ልጆች የተወለዱበትን ቅደም ተከተል ያሳያል። ለቋንቋዎ ምቹ ከሆነ ለእያንዳዱ ወንድ ልጅ ቀጣዩ” ማለት ይችላሉ። (ሕገኛ ቁጥሮች: ይመልከቱ)

የሖሳ ልጆችና ወንድሞች ሁሉ አሥራ ሦስት ነበሩ
“የሖሳ ወንዶች ልጆች እና ዋርሳዎች 13 ነበሩ።” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

1 Chronicles 26:12

ሰሞነኞች
ቡድኖች

ዕጣ ተጣጣሉ
“ዕጣ ጣሉ”

ታናሹና ታላቁ
ይህ ሁሉንም ወንዶች ፅንፉን በመያዝ የሚገልፅ ነው። ተመሳሳይ ሀረግ በ1 ዜና 25:8 እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ። አት: “ወጣት ወንዶችን እና ሽማግሌ ወንዶችን ሁሉንም ጨምሮ” ወይም “በሁሉም እድሜ ያሉ ወንዶች” (ሜሬዝም: ይመልከቱ)

ዕጣ ሲጣጣሉ
ይህ በገባሪ ቅርፅ መተርጎም ይችላል። አት: “ዕጣ በጣሉ ጊዜ” ((ገባሪ ወይም ተገባሪ: ይመልከቱ))

ዘካርያስ
የዚህን ሰው ስም በ1 ዜና 26:2 እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ብልህ መካር
ይህ ጥሩ ፍርድ በመስጠት ውሳኔ የሚያደርግ ሰው ነው።

1 Chronicles 26:15

ለዖቤድኤዶም በደቡብ በኩል፥ ለልጆቹም ለዕቃ ቤቱ ዕጣ ወጣ
ይህ በገባሪ ቅርፅ ለገለፅ ይችላል። አት: “ዖቤድኤዶም የደቡቡን በር የመጠበቅ ሀላፊነት ሲኖረው ልጆቹ ደግሞ ግምጃ ቤቱ ይጠብቁ ነበር” (ገባሪ ወይም ተገባሪ: ይመልከቱ)

ዖቤድኤዶም
የዚህን ሰው ስም በ1 ዜና 26:4 እንዴት እንደተረጎም ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ለሰፊንና ለሖሳ ... ዕጣ ወጣ
ይህ በገባሪ ቅርፅ ለገለፅ ይችላል። አት: “ሰፊን እና ሖሳ የጥበቃ ሀላፊነት ነበራቸው” (ገባሪ ወይም ተገባሪ: ይመልከቱ)

ሰፊን
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ሖሳ
የዚህን ሰው ስም በ1 ዜና 26:10 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ሸሌኬት
ይህ የበር ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ጥበቃ ከጥበቃ ላይ ዕጣ
ይህ በገባሪ ቅርፅ ለገለፅ ይችላል። አት: “እያንዳንዱ ቤተሰብ ጠጥበቃ ሀላፊነት ነበረው” ወይም “እያንዳንዱ ቤተሰብ የጥበቃ ሀላፊነት የሚወጣበት የተወሰነ ጊዜ ነበረው” (ገባሪ ወይም ተገባሪ: ይመልከቱ)

1 Chronicles 26:17

ስድስት ሌዋውያን
“6 ሌዋውያን” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

በምሥራቅ... በሰሜን... በደቡብ
ይህ ሀረግ በሮቹን ይወክላል። አት: “የምስራቁ በር ... የሰሜኑ በር ... የደቡቡ በር” (ግድፈተ ቃላት: ይመልከቱ)

ለየዕለቱ አራት፥
ይህ በጥበቃ ተራ ላይ ያሉትን የወንዶች ቁጥር ይወክላል። አት: “በየለቱ አራት ወንዶች” ወይም “በየለቱ አራት ሌዋውያን” (ግድፈተ ቃላት: ይመልከቱ)

ሁለት ሁለት ነበሩ
“2 ጥንድ ወንዶች” ወይም “2 የሆኑ 2 እያንዳንቸው ወንዶች”

በደቡብ በኩል ለየዕለቱ አራት
ይህ በገባሪ ቅርፅ ለገለፅ ይችላል። አት: “አራት ወንዶች በስተምዕራብ ያለውን አምድ ይጠብቁ ነበር” (ገባሪ ወይም ተገባሪ: ይመልከቱ)

መንገድ ላይ አራት፥ በፈርባርም አጠገብ ሁለት ነበሩ
ቁጥሮቹ “አራት” እና “ሁለት” ጠባቂዎቹን ይወክላሉ። አት: “መንገዱን አራት ወንዶች ሲጠብቁ፣ አደባባዩን ሁለት ወንዶች ይጠብቁ ነበር” (ግድፈተ ቃላት: ይመልከቱ)

ተሞልተው ነበር
ይህ በገባሪ ቅርፅ ለገለፅ ይችላል። አት: “ነበረ” (ገባሪ ወይም ተገባሪ: ይመልከቱ)

ሜራሪ
የዚህን ሰው ስም በ1 ዜና 26:10 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

1 Chronicles 26:20

ለለአዳን የሆኑ የጌድሶናውያን ልጆ... ይሒኤሊ፣ ይሒኤሊ ልጆች, ዜቶም, እና ወንድሙ አዩኤል። ቤተ መዛግብት ላይ የነበሩ
“ይህኤልና ልጆቹ የላዳን ልጆች ነበሩ፣ እርሱም ከጌርሶን ሲሆን ከላደን ወገን ነበር። ይህኤል እና ልጆቹ የጌርጌሶናዊው የላዳን ቤተሰብ መሪዎች ነበሩ። ይህኤል እና ልጆቹ፣ የታም እና ኢዮኤል ወንድሙ በግምጃ ቤቱ ላይ ሀላፊዎች ነበሩ”

ለአዳን... ጌድሶናዊ
የእነዚህን ወንዶች ስሞች ልክ በ1 ዜና 23:7 እንደተረጎሙት ይተርጉሙ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ጌድሶናውያን
የግርሶን ልጆች። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ይሒኤሊ... ዜቶም... ኢዩኤል
የእነዚህ ወንዶች ስሞች ልክ በ1 ዜና 23:8 እንደተረጎሙት ይተርጉሙ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

1 Chronicles 26:23

ከእንበረማውያን... ከይስዓራውያን... ከኬብሮናውያን... ከዑዝኤላውያን
የእነዚህ ወንዶች ስሞች ልክ በ1 ዜና 23:12 እንደተረጎሙት ይተርጉሙ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ሱባኤል ... የጌርሳም ... ከአልዓዛር ... ረዓብያ
የእነዚህ ወንዶች ስሞች ልክ በ1 ዜና 23:15-17 እንደተረጎሙት ይተርጉሙ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ከአልዓዛር ልጁ
እነዚህ ይህን ስራ አብረውት ይሰሩ የነበሩ ዘመዶቹ ናቸው። አት: “ከአልዓሳር ነገድ ስራውን አብረውት ይሰሩ የነበሩ ዘመዶቹ” (ታሳቢ የሆነ እውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ: ይመልከቱ)

የሻያ... ኢዮራም ... ዝክሪ ... ሰሎሚት
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

1 Chronicles 26:26

ተሾመው ነበር
ይህ ፈሊጥ ነው። አት: “ሀላፊነት ነበራቸው” (ፈሊጥ: ይመልከቱ)

ሻለቆችና የመቶ አለቆች
አማራጭ ትርጉሞች 1) እነዚህ ቁጥሮች አዛዦቹ ይመሯቸው የነበሩትን ወታደሮች ትክክለኛ ቁጥር ያሳያል። አት: “በ1,000 ወታደሮች ላይ አለቆች እና በ100 ወታደሮች ላይ አለቆች” ወይም 2) “ሺዎች” እና “መቶዎች” የሚሉት ቃላት ትክክለኛ ቁጥሮችን የሚያሳዩ ሳይሆን ነገር ግን የትልቅ እና የትንሽ የሰራዊት ክፍሎች ስሞች ናቸው። አት: “በትልቅ የሰራዊት ክፍል ላይ አዛዦች እና በትንሽ የሰራዊት ክፍሎች ላይ አዛዦች” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

ምርኮ
ሰራዊት ከድል በኃላ ከጠላቶቹ የሚወስደው

ባለ ራእዩም ሳሙኤል፣ ... የጽሩያም ልጅ ኢዮአብ የቀደሱት
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አት: “ነብዩ ሳሙኤል ... የጹሩያ ልጅ ኢዩአብ ለያህዌ እንደለዩት” (ገባሪ ወይም ተገባሪ: ይመልከቱ)

ቂስ ... ኔር ... ጽሩያ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

የቀደሱት ... ሁሉ
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊገለጽ ይችላል። አት: “መሪዎቹ የለዩት ሁሉ” (ገባሪ ወይም ተገባሪ: ይመልከቱ)

1 Chronicles 26:29

ከይስዓራውያን ... ከኬብሮናውያን
የእነዚህን ወንዶች ስሞች በ1 ዜና 23:12 እንደተረጎሙት ይተርጉሙ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

በውጭው ሥራ በእስራኤል
“የእስራኤል ሕዝብ እለታዊ ስራ።” ይህ ከሰራዊቱ ወይም ከቤተ መቅደሱ ጋር ያልተያያዘው የእስራኤል ሕዝብ መደበኛ ስራን ይወክላል።

ከናንያና ... ሐሸብያና
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

1,700 ጽኑዓን የነበሩት
“አንድ ሺህ ሰባት መቶ ጽኑአን ሀያላን ወንዶች” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

ለእግዚአብሔር ሥራ ሁሉ ለንጉሡም አገልግሎት
“ለያሕዌ እና ለንጉሱ የሚሰራ ስራ።”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 27

1 የእስራኤል የቤተሰብ አለቆች፣ የሻልለቆች፣ መቶ አለቆች እንዲሁም ዓመቱን ሙሉ በየወሩ አለቆች እንዲሁም ዓመቱን ሙሉ በየወሩ የሚመደቡትና ዋና ዋና
ክፍሎች በተመለከተ ንጉሡን ያገለገሉ አለቆቻቸው ዜርዜር ይህ ነው። እያንዳንዱ ዋና ክፍል ሃያ አራት ሺህ ሰው ነበረው። 2 በመጀመሪያው ወር የመጀመሪያው
ዋና ክፍል የበላይ የዘብድኤል ልጅ ያሾብዓም ሲሆን፣ በሥሩ የሚታዘዙ ሃያ አራት ሺህ ሰዎች ነበሩ። 3 እርሱም የፋሬስ ዘር ሲሆን፣ በመጀመሪያው ወር የሰራዊቱ
ሹማምት ሁሉ የበላይ ነበር። 4 በሁለተኛው ወር የክፍለ ጦሩ የበላይ አዛዥ ኢሆሃዊው ዱዲ ሲሆን፣ የዚሁ ክፍል መሪ ደግሞ ሚቅሎት ነው፤ በጅሩም ሃያ አራት
ሺህ ሰው ነበረ። 5 በሦስተኛውም ወር የሦስተኛው ክፍለ ጦር የበላይ አዛዥ የካህኑ የዮዳሄ ልጅ በናያስ ነበረ፤ ዋናው እርሱ ሲሆን፤ በሥሩ ሃያ አራት ሺህ ሰው
ነበረ። 6 ይህም ከሠላሳዎቹ ይልቅ ጎያል ሲሆን፤ የሠላሳዎቹ የበላይ ነበረ፤ ልጁ ዒሚዛባድም የክፍሉ ሰራዊ አዛዥ ነበረ። 7 በአራተኛው ወር አራተኛው የበላይ
አዛዥ የኢዮአብ ወንድም አሣሣል ሲሆን፤ በእግሩ የተተካውም ልጁ ዝባድያ ነው፤ በሥሩም ሃያ አራት ሺህ ሰው ነበረ። 8 በአብምስተኛው ወር አምስተኛው የበላይ
አዛዥ ይዝራዊው ሸምሁት ሲሆን፤ በሥሩም ሃያ አራት ሺህ ሰው ነበረ። 9 በስድስተኛው ወር ስድስተኛው የበላይ አዛዥ የቴቁሐዊው የዒስካ ልጅ ዒራስ ሲሆን፣
በሥሩም ሃያ አራት ሺህ ሰው ነበረ። 10 በሰባተኛው ወር ሰባተኛው የበላይ አዛ የኤፍሬም ወገን የሆነው ፍሎናዊው ሴሌስ ሲሆን፣ በሥሩም ሃያ አራት ሺህ ሰው
ነበረ። 11 በስምንተኛው ወር ስምንተኛው የበላይ አዛዥ ከካዛራውያን ወገን የሆነው ኩሳታዊ ሲቦካይ ሲሆን፣ በሥሩም ሃያ አራት ሺህ ሰው ነበረ። 12
በዘጠነኛው ወር ዘጠነኛው የበላይ አዛዥ ከብንያም ወገን የሆነው ዓናቶታዊው አቢዔዘር ሲሆን፣በሥሩም ሃያ አራት ሺህ ሰው ነበረ። 13 በዐሥረኛው ወር
ዐሥረኛው የበላይ አዛዥ ከከዛራውያን ወገን የሆነው ነጦፋዊው ኖኤሬ ሲሆን፣ በሥሩም ሃያ አራት ሺህ ሰው ነበረ። 14 በዐሥራ አንደኛው ወር እስራ አንደኛው
የበላይ አዛዥ ከኤፌሬም ነገድ የሆነው ጲርዓቶናዊው በናያስ ሲሆን፣ በሥሩም ሃያ አራት ሺህ ሰው ነበረ። 15 በዐሥራ ሁለተኛው ወር ዐሥራ ሁለተኛ የበላይ አዛዥ
ከጎቶንያል ቤተሰብ የሆነው ነጦፋዊው ሔልዳይ ነበረ፤ በጅሩም ሃያ አራት ሰው ነበረ። 16 የየነገዱ የእስራኤል የጦር ሹማምት፤ በሮቤል ነገድ ላይ የተሾመው፣
የዝክሪ ልጅ አልዓዛር፤ በስምዖን ነገድ ላይ የተሰመው፣ የመዓካ ልጅ ሰፍጢያስ። 17 በሌዊ የተሾመው የቀሙኤል ልክ ሐሸቡያ፤ በእሮን ነገድ ላይ የተሾመው፣
ሳዶቅ። 18 በይሁዳ ነገድ ላይ የተሾመው፣ የዳዊት ወንድም ኤሊሁ፤ በይሳኮር ነገድ ላይ የተሾመው፣ የሚካኤል ልጅ ዖምሪ። 19 በዛቢሎን ነገድ ላይ
የተሾመው፣ የአብዱዩ ልጅ ይሽማያ፤ በንፍታሌም ነገድ ላይ የተሾመው፣ የዓዝሪኤል ልጅ ኢያሪሙት። 20 በኤፍሬም ነገድ ላይ የተሾመው፣ የዓዝያ ልጅ ሆሴዕ፤
በምናሴ ነገድ እኩሌታ ላይ የተሾው፣ የፈዳያ ልጅ ኢዩኤል። 21 በገለዓድ ባለው የምናሴ ነገድ እኩሌታ ላይ የተሾመው፣ የዛካርያስ ልጅ አዶ፣ በብንያም ነገድ ላይ
የተሾመው፣ የአቤኔር ልጅ የዕሢኤል። 22 በዳን ነገር ላይ የተሰመው፣ የይህሮም ልጅ ዓዛርኤል፤ እንግዲህ የእዝራኤል ነገድ እነዚሁ ነበሩ። 23 እግዚአብሔር
እስራኤልን እንደ ሰማይ ክዋክብት እንደሚያዛቸው ሃያና ከዚያ በታች ይየሆነው አልቁጠረም ነበር። 24 የጽሩያ ልጅ ኢዮአብ መቁጠር ጀመረ፤ ሆኖም
አልፈፀመውም፤ መቁጠራቸው በእስራኤል ላይ ቁጣ ስላመጣ፣ የተቁጠረውም በንጉሥ ዳዊት መዝገብ አልገባም። 25 የዓዲኤል ልጅ ዓዝሞት የቤተ
መንግሥቱ ዕቃ ጎላፊ ነበረ፤ 26 የክሉብ ልጅ ዔዝሪ ምድሪቱም ለሚያርሱት ገበሬዎች ጎላፊ ነበረ። 27 ራማታዊው ስሜኢ የውይን ተክል ቦታዎች ጎላፊ ነበረ፤
ሸፋማዊው ዘብዲ የወይን ጠጅ ዕቃ ጎላፊ ነበረ። 28 ጌድራዊው በአሐናን በምራባዊው ኩረብታዎች ግርጌ ለሚገኙት የወይንና የወርካ ዛፎች ጥበቃ ጎላፊ ነበረ፤
ኢዮአስ የዘይት ቤቱ ጎላፊ ነበረ። 29 ሳሮናዊው ሰጥራይ በሳሮን ለሚሰሩት የከብት መንጋዎች ጎላፊ ነበረ። የዓድላይ ልጅ ሻፋጥ በሸለቆው ውስጥ ላሉት
የከብት መንጋዎች ጎላፊ ነበረ። 30 እስማኤላዊው ኡቢያስ የግመሎች ጎላፊ ነበረ። ሜሮታዊው ዬሕድያ የአህዮች ጎላፊ ነበረ። 31 አረጋዊው ያዚዝ የበግና
የፍየል መንጋዎች ጎላፊ ነበረ። 32 አስተዋይ የሆነው አጎት ዮናታን አማካሪና ጸሐፊ ነበረ፤ የሐክሞኒም ልጅ ይሒኤል ደግሞ የንጉሥ ልጆች ሞግዚት ነበረ። 33
አኪጦፌል የንጉሥ አማካሪ ሲሆን፣ አርካዊው ኩሲ ደግሞ የንጉሥ ልጆች ሞግዚት ነበረ። አኪጦፌል የንጉሥ አማካሪ ሲሆን፣ አርካዊው ኩሲ ደግሞ የንጉሥ
ወዳጅ ነበረ። 34 የበናያስ ልጅ ዮዳሄና አብያታር በአኪጦፌል እግር ተተኩ። ኢዮአብም የንጉሥ የክብር ዘብ አዛዥ ሆነ።

---

1 Chronicles 27:1

እነዚህ ነበሩ
“ስሞቹ እነዚህ ናቸው”

የሺህ አለቆች የመቶ አለቆችም
አማራጭ ትርጉሞች 1) እነዚህ ቁጥሮች አዛዦቹ ይመሯቸው የነበሩትን ወታደሮች ትክክለኛ ቁጥር ያሳያል። አት: “በ1,000 ወታደሮች ላይ አለቆች እና በ100 ወታደሮች ላይ አለቆች” ወይም 2) “ሺዎች” እና “መቶዎች” የሚሉት ቃላት ትክክለኛ ቁጥሮችን የሚያሳዩ ሳይሆን ነገር ግን የትልቅ እና የትንሽ የሰራዊት ክፍሎች ስሞች ናቸው። አት: “በትልቅ የሰራዊት ክፍል ላይ አዛዦች እና በትንሽ የሰራዊት ክፍሎች ላይ አዛዦች” ይህን በ1 ዜና 13:1 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

በክፍሎች
“በተለያዩ መንገዶች” ወይም “በብዙ መንገዶች”

እያንዳንዳቸው ሀያ አራት ሺህ ሆነው በዓመት ወራት ሁሉ በየወሩ ይገቡና ይወጡ ነበር
ይህ እያንዳንዱ ክፍል ለአንድ ወር በየተራ ያገለግል ነበር ማለት ነው።

ክፍሎች እያንዳንዳቸው
“እያንዳንዱ ቡድን”

ሀያ አራት ሺህ ሆነው
“24,000 ወንዶች” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

በዓመት .. ሁሉ
“አመቱን ሁሉ”

በእርሱም ክፍል
ይህ ፈሊጥ ነው። አት: “የክፍሉ ሀላፊ” (ፈሊጥ: ይመልከቱ)

ለመጀመሪያው ወር
ይህ ዕብራውያን ጊዜ መቁጠሪያ የመጀመሪያው ወር ነው። በምዕራባውያን የጊዜ መቁጠሪያ መሠረት የማርች የመጨረሻ ክፍል እና የኤፕሬል የመጀመሪያ ክፍል ነው። (የእብራውያን ወራት እና ሕገኛ ቁጥሮች፡ ይመልከቱ)

ያሾብዓም ... የዘብድኤል ... ከፋሬስ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

1 Chronicles 27:4

በእርሱም ክፍል
“የክፍሉ ሀላፊ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በሁለተኛውም ወር
ይህ ዕብራውያን ጊዜ መቁጠሪያ ሦስተኛው ወር ነው። በምዕራባውያን የጊዜ መቁጠሪያ መሠረት የኤፕሬል የመጨረሻ ክፍል እና የሜይ የመጀመሪያ ክፍል ነው። (የእብራውያን ወራት እና ሕገኛ ቁጥሮች: ይመልከቱ)

ዱዲ ... ሚልሎት ... ዓሚዛባድ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

አሆሃዊው
የዚህን ሰው ስም በ1 ዜና 8:4 እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

በእርሱም ክፍል
“በእርሱ የወታደሮች ቡድን ውስጥ”

ሀያ አራት ሺህ ጭፍራ
“24,000 ወንዶች” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

ለሦስተኛው ወር
ይህ ዕብራውያን ጊዜ መቁጠሪያ የመጀመሪያው ወር ነው። በምዕራባውያን የጊዜ መቁጠሪያ መሠረት የሜይ የመጨረሻ ክፍል እና የጁን የመጀመሪያ ክፍል ነው። (የእብራውያን ወራት እና ሕገኛ ቁጥሮች: ይመልከቱ)

ዮዳሄ
የእነዚህ ሰዎች ስሞች በ1 ዜና 11:22 እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

በሠላሳው
“30ዎቹ።” ይህ “የዳዊትን 30 ሀያላኝ ወታደሮች” ይወክላል። (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

በሠላሳው ላይ
ይህ ፈሊጥ ነው። አት: “በ30 ሰዎች ላይ ሀላፊ” (ፈሊጥ: ይመልከቱ)

1 Chronicles 27:7

ለአራተኛው ወር አራተኛው አለቃ የኢዮአብ ወንድም አሣሄል ነበረ
“የኢዩአብ ወንድም አሣሄል የአራተኛው ወር መሪ ነበር”

ለአራተኛው ወር
“ወር 4 ።” ይህ ዕብራውያን ጊዜ መቁጠሪያ አራተኛው ወር ነው። በምዕራባውያን የጊዜ መቁጠሪያ መሠረት የጁን የመጨረሻ ክፍል እና የጁላይ የመጀመሪያ ክፍል ነው። (የእብራውያን ወራት እና ሕገኛ ቁጥሮች: ይመልከቱ)

አሣሄል ... ዝባድያ ... ሸምሁት ... ይዝራዊው
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

በእርሱም ክፍል
“የእርሱ የሰራዊት ቡድን”

ሀያ አራት ሺህ ጭፍራ
“24,000 ወንዶች” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

ለአምስተኛው ወር
“ወር 5 ።” ይህ ዕብራውያን ጊዜ መቁጠሪያ አምስተኛው ወር ነው። በምዕራባውያን የጊዜ መቁጠሪያ መሠረት የጁላይ የመጨረሻ ክፍል እና የኦገስት የመጀመሪያ ክፍል ነው። (የእብራውያን ወራት እና ሕገኛ ቁጥሮች: ይመልከቱ)

ለስድስተኛው ወር
“ወር 6” ይህ ዕብራውያን ጊዜ መቁጠሪያ ስድስተኛው ወር ነው። በምዕራባውያን የጊዜ መቁጠሪያ መሠረት የኦገስት የመጨረሻ ክፍል እና የሴፕተምበር የመጀመሪያ ክፍል ነው። (የእብራውያን ወራት እና ሕገኛ ቁጥሮች: ይመልከቱ)

ዒራስ... ዒስካ
የእነዚህ ወንዶች ስሞች በ1 ዜና 11:28 እንደተረጎሙት ይተርጉሙ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

የቴቁሐዊው
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

1 Chronicles 27:10

ለሰባተኛው ወር ሰባተኛው አለቃ ከኤፍሬም ልጆች የሆነ ፍሎናዊው ሴሌስ ነበረ
“ከኤፍሬም ወገን የሆነው ፎሎናዊው ሴሌስ የሰባተኛው ወር መሪ ነበር።”

ለሰባተኛው ወር
“ወር 7 ።” ይህ ዕብራውያን ጊዜ መቁጠሪያ ሰባተኛው ወር ነው። በምዕራባውያን የጊዜ መቁጠሪያ መሠረት የሴፕተምበር የመጨረሻ ክፍል እና የኦክቶበር የመጀመሪያ ክፍል ነው። (የእብራውያን ወራት እና ሕገኛ ቁጥሮች: ይመልከቱ)

ሴሌስ ... ሲቦካይ ... አቢዔዜር
የእነዚህን ሰዎች ስሞች በ1 ዜና 11:27-29 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ፍሎናዊው ... ኩሳታዊው ... ዓናቶታዊው
የእነዚህ ነገዶች ስሞች በ1 ዜና 11:27-29 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ሀያ አራት ሺህ ጭፍራ
“24,000 ወንዶች” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

ለስምንተኛው ወር
“ወር 8.” ይህ ዕብራውያን ጊዜ መቁጠሪያ ስምንተኛው ወር ነው። በምዕራባውያን የጊዜ መቁጠሪያ መሠረት የኦክቶበር የመጨረሻ ክፍል እና የኖቬንበር የመጀመሪያ ክፍል ነው። (የእብራውያን ወራት እና ሕገኛ ቁጥሮች: ይመልከቱ)

ከዛራውያን
የዚህን ሰው ስም በ1 ዜና 2:4 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ለዘጠኝኛው ወር
“ወር 9።” ይህ ዕብራውያን ጊዜ መቁጠሪያ ዘጠነኛው ወር ነው። በምዕራባውያን የጊዜ መቁጠሪያ መሠረት የኖጩንበር የመጨረሻ ክፍል እና የዲሴምበር የመጀመሪያ ክፍል ነው። (የእብራውያን ወራት እና ሕገኛ ቁጥሮች: ይመልከቱ)

1 Chronicles 27:13

ለአሥረኛው ወር
“ወር 10።” ይህ ዕብራውያን ጊዜ መቁጠሪያ አስረኛው ወር ነው። በምዕራባውያን የጊዜ መቁጠሪያ መሠረት የዲሴምበር የመጨረሻ ክፍል እና የጃንዋሪ የመጀመሪያ ክፍል ነው። (የእብራውያን ወራት እና ሕገኛ ቁጥሮች: ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ኖኤሬ
የዚህን ሰው ስም በ1 ዜና 11:30 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ነጦፋዊው ... ጲርዓቶናዊው
እነዚህ የቦታዎች ስሞች ናቸው።

ከዛራውያን
የዚህን ሰው ስም በ1 ዜና 2:4 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ሀያ አራት ሺህ ጭፍራ
“24,000 ወንዶች” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

ለአሥራ አንደኛው ወር
“ወር 11።” ይህ ዕብራውያን ጊዜ መቁጠሪያ አሥራ አንደኛው ወር ነው። በምዕራባውያን የጊዜ መቁጠሪያ መሠረት የጃንዋሪ የመጨረሻ ክፍል እና የፌብሯሪ የመጀመሪያ ክፍል ነው። (የእብራውያን ወራት እና ሕገኛ ቁጥሮች: ይመልከቱ)

ለአሥራ ሁለተኛው ወር
“ወር 12።” ይህ ዕብራውያን ጊዜ መቁጠሪያ አሥራ ሁለተኛው ወር ነው። በምዕራባውያን የጊዜ መቁጠሪያ መሠረት የፌብሯሪ የመጨረሻ ክፍል እና የማርች የመጀመሪያ ክፍል ነው። (የእብራውያን ወራት እና ሕገኛ ቁጥሮች: ይመልከቱ)

ሔልዳይ ... ኦትንኤል
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

1 Chronicles 27:16

አልዓዛር ... የዝክሪ ... ሰፋጥያስ... የመዓካ ... ሐሸቢያ... የቀሙኤል ... ዖምሪ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ሳዶቅ
የዚህን ሰው ስም በ1 ዜና 6:8 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ኤሊሁ
የዚህን ሰው ስም በ1 ዜና 12:20 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

የሚካኤል
የዚህን ሰው ስም በ1 ዜና 7:3 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

1 Chronicles 27:19

ይሸማያ... የአብድዩ ... ኢያሪሙት... የዓዝሪኤል ... ሆሲያ ... የዓዛዝያ ... ኢየኤል... የፈዳያ ... አዶ... የዘካርያስ ... የዕሢኤል... የአበኔር ... ዓዛርኤል... የይሮሐም
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

1 Chronicles 27:23

ከሀያ ዓመት በታች የነበሩትን
“ከ20 አመት የሆናቸው ወይም የሚያንሱ ሰዎች” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

እስራኤልን እንደ ሰማይ ከዋክብት ያበዛ ዘንድ
ይህ የእስራኤል ሕዝቦች ቁጥር እየጨመረ እንደ ከዋክብት ብዛት እንደሚሆን ይናገራል። አት: “በእስራኤል ያሉት ሕዝብ ቁጥር የሰማይ ከዋክብትን እሰኪያክል ለማብዛት” (ተመሳሳይ: ይመልከቱ)

እስራኤልን ... ያበዛ ዘንድ
እዚህ “እስራኤል” በዚያ የሚኖሩትን ሕዝብ ያሳያል። አት: “የእስራኤል የሕዝብ ብዛት ማብዛት” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

የጽሩያ
የዚህችን ሴት ስም በ1 ዜና 2:16 እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

በእስራኤል ላይ ቍጣ ሆነ
ይህ እግዚአብሄር ሕዝቡን ሲቀጣቸው የእርሱ “ቁጣ” በላያቸው እንደወደቀ አድርጎ ያወራል። አት: “እግዚአብሄር የእስራኤል ሕዝብ ቀጣ” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

ቍጥራቸውም ... አልተጻፈም።
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አት: “ይህን ቁርጥ ማንም አልጻፈም” (ገባሪ ወይም ተገባሪ: ይመልከቱ)

1 Chronicles 27:25

ዓዝሞት ... የዓዲኤል ... ዮናታን ... የዖዝያ ... ዔዝሪ ... የክሉብ ... ዘብዲ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ሹም
“ለመጠበቅ ሀላፊነት ያለበት”

ሹም ነበረ
ይህ ፈሊጥ ነው። አት: “ሀላፊ ነበር”

በግንቦችም
“ጠንካራ ግንቦች”

እርሻውን በሚያርሱት
ይህ ከመትከል በፊት ወደ ውስጥ መቆፈር ወይም ቆሻሻውን ማስወገድ ማለት ነው።

ራማታዊው
ይህ ከራማ ከተማ የሆነ ሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ሸፋማዊው
ይህ ከሸፋማ ከተማ የሆነ ሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ለወይንም ጠጅ
እነዚህ ከመሬት በታች ያሉና ወይም ለማስቀመጥ የሚያገለግሉ የሕንፃው ክፍሎች ናቸው።

1 Chronicles 27:28

ሹም ነበረ
ይህ ፈሊጥ ነው። አት: “ለዕለቱ ሀላፊ” (ፈሊጥ: ይመልከቱ)

ወይራ
x

1 Chronicles 27:30

ሹም ነበረ
ይህ ፈሊጥ ነው። አት: “የዕለቱ ሃለፊ” (ፈሊጥ: ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ኡቢያስ ... ይሕድያ ... ያዚዝ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

እስማኤላዊው
የዚህን ነገድ ስም በ1 ዜና 2:17 እንደተረጎሙት ይተርጉሙ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

አጋራዊው
የዚህን የሕዝብ ቡድን ስም በ1 ዜና 5:10 እንደተረጎሙት ይተርጉሙ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

ሜሮኖታዊው
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

እነዚህ ሁሉ ... ላይ ሹሞች
“እነዚህ ወንዶች ሁሉ”

1 Chronicles 27:32

ዮናታን ... ይሒኤል ... የሐክሞኒም ... አኪጦፌልም ... ኩሲ ... ዮዳሄ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

አርካዊውም
ይህ የነገድ ወይም የጎሳ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 28

1 ዳዊት በኢየሩሳሌም እንዲሰበሰቡ የነገዱን የጦር አለቆች፣ ንጉሡን የሚያገለግሉትን የክፍለ ጦር አዛዦች፣ የሻለቆቹን፣ የመቶ አለቆቹን፣ የንጉሥና የልጆቹ
ንብረትና ከብት ሁሉ ጎላፊ የሆኑትን፣ እንዲሁም የቤተ መንግሥቱን ሹማምት፣ ጎያላንና ጀግና ተዋጊዎቹን፣ በአጠቃላይ የእስራኤልን ሹማምት ሁሉ ጠራ። 2
ከዚያም ንጉሥ ዳዊት በእግሩ ቆሞ እንዲህ አላቸው፤ "ወንድሞቼንና ወገኖቼ ሆይ፤ እስቲ አድምጡኝ፤ እግዚአብሔር ለቃል ኪዳኑ ታቦት ማደሪያና ለአምላካችን
እግር ማረፊያ የሚሆን ኔት ለመሥራት ዐስቤ ዕቅድ አውጥቼ ነበር። 3 እግዚአብሔር ግን እንዲህ አለኝ፤ ጦረኛ ለስሜ ቤት አትሠራም። 4 ነገር ግን የእስራኤል
አምላክ እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ለዘላለም እንድነግሥ ከቤተሰቤ ሁሉ እኔን አረጠ፤ መሪ እንድሆንም ይሁዳን መረጠ፤ ከአባቴ ልጆች መካከል ደግሞ
በመላው እስራኤል ላይ እንድነግሥ ፈዋዱ ሆነ። 5 እግዚአብሔር ብዙ ልጆች ሰጥቶኛል፤ ከወንዶቹ ልጆቼ ሁሉ በእግዚአብሔር መንግሥት ዙፋን ላይ ተቀምጦ
በእስራኤል ሁሉ ላይ እንዲነግሥ ደግሞ ልጄን ሰሎሞንን መርጦታል። 6 እንዲህም አለኝ፤ ቤቴንና አደባባዮቼን የሚሠራልኝ ልጅህ ሰሎሞን ነው፤ ምክንያቱም
ልጄ እንዲሆን መርጬዋለሁ፤ እኔም አባት እሆነዋለሁ። 7 አሁን እንደሚያድርገው ሁሉ፤ ትህዛዛቶቼንና ሕጎቼን ምንጊዜም ሳያውላውል የሚፈጽም ከሆነ
መንግሥቱም ለዘላለም አጸናታለሁ። 8 እንግዲህ አሁንም ይህቺን መልካሚቱን ምድር እንድትወርሱና ለልጆቻችሁም የዘላለም ርስት አድርጋችሁ
እንድታወርስይአቸው፣ የእግዚአብሔርም ትእዛዝ ሁሉ ፊት፣ በእግዚአብሔር ጉባኤና እግዚአብሔር እየሰማ አዛችኋለሁ። 9 "አንተም ልጄ ሰሎሞን ሆይ!
እግዚአብሔር ልብን ሁሉ ስለሚመረምርና ሐሳብን ሁሉ ስለሚያውቅ፣ የአባትህን አምላክ ዕወቅ፤ በፍጹም ልብና በበጎ ፍቃድ አገግለው። 10 ለመቅደስ የሚሆን
ቤት እንድትሠራ እግዚአብሔር የመረጠህ መሆኑን አሁንም ዕስብ፤ በትርተህም ሥራ። 11 ከዚያም ዳዊት የቤተ መቅደሱን መመላለሻ፣ የሕንጻውን፣ የዕቃ
ቤቶቹን፣ 12 የፎቁንና የውስጥ ክፍሎቹን እንዲሁም የማስተሰሪያውን ቦታ ንድፍ ለልጁ መንፈስ ቅዱስ በልቡ ያሳደረውን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ
አደባባይ፤ በዙሪያው ውያሉትን ክፍሎች ሁሉ፣ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ዕቃ ቤቶችና የንዋይ ቅድሳቱን ግምጃ ቤቶች ንድፍ ሁሉ ሰጠው፤ 13 እንዲሁም
የካህናቱንና የሌዋውያኑን አመዳደብ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አገልግሎት ሥራና ለአገልግሎቱ ስለሚጠቀምባቸው ዕቃዎች ሁሉ መመሪያ ሰጠው። 14 ልዩ
ልዩ አገልግሎት የሚውሉትን የወርቅ ዕቃዎች ሁሉ መጠን፤ ልዩ ልዩ አገልግሎት የሚውሉትን የብር ዕቃዎች ሁሉ መጠን አሳወቀው፤ 15 እንደሚቀዘችና
ለቀንዲሎቻቸው የሞሆነው የእያንዳንዳቸውን የውርቅ መጠን፤ ለብሩ መቅረዞችና ለቀንዲሎቻቸው የሚያድፈልገውን የእያንዳንዳቸውን የብር መጠን፤ 16
ለያንዳንዱ ጎብስት ገጽ ጠረጴዛ የሚያስፈልገውን የወርቅ መጠን፣ ለእያንዳንዱ የብር መጠን፣ 17 ለሹካዎቹ፣ ለጎዳጓዳ ሳሕኖቹ፣ ለማንቆርቆሪያዎች
የሚያስፈልገውን ንጹሕ የውርቅ መጠን፤ ለእያንዳንዱ የብር መጠን፣ 18 ለዕጣኑ መሠዊያ የሞሆነውን የጠራ ውርቅ መጠን እንዲሁም ክንፎቻቸውን ዘርግተው
የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑን ታቦት የሚሸፍኑት ከወርቅ የተሠሩትን የኪሩቤል ጀረገላዎች ንድፍ ሰጠው። 19 ዳዊትም "ይህ ሁሉ፣በእኔ ላይ ባለው
በእግዚአብሔር እጅ በጽሑፍ ተገለተልኝ፤ የንድፋንም ዝርዝር እንድረዳ ማስተዋልን ስጠን"አለ። 20 ደግሞም ዳዊት ልጁን ሰሎሞንን እንዲህ አለው፤ "እንግዲህ
በል በርታ፤ ጠንክር፤ ሥራውንም ጀመር። አትርፍ፤ ተስፋም አትቁረጥ፤ እግዚአብሔር አምላኬ ከአንተ ጋር ነውና፤ እርሱም የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ
አገልግሎት ሥራ እስኪፈጸም ድረስ አይተውህም፤ አይጥልህም። 21 ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ሥራ ሁሉ የሚያስፈልጉትን ካህናትና ሌዋዋን ምድብም
ዝግጁ ነው።በሁሉም የእጅ በሥራው ሁሉ ይረዱሃል። ሹማምቱና ሕዝቡ ሁሉ ትእዛዝህን ይፍፈጽማሉ።

---

1 Chronicles 28:1

ሰበሰበ
በአንድነት ተጠሩ

በክፍል የሚያገለግሉትን
ተደጋግሞ ሊሰራ የሚገባው ስራ፣ ለምሳሌ በየቁ ወይም በየወሩ።

ሻለቆቹንም፥ የመቶ አለቆችንም
አማራጭ ትርጉሞች 1) እነዚህ ቁጥሮች አዛዦቹ ይመሯቸው የነበሩትን ወታደሮች ትክክለኛ ቁጥር ያሳያል። አት: “በ1,000 ወታደሮች ላይ አለቆች እና በ100 ወታደሮች ላይ አለቆች” ወይም 2) “ሺዎች” እና “መቶዎች” የሚሉት ቃላት ትክክለኛ ቁጥሮችን የሚያሳዩ ሳይሆን ነገር ግን የትልቅ እና የትንሽ የሰራዊት ክፍሎች ስሞች ናቸው። አት: “በትልቅ የሰራዊት ክፍል ላይ አዛዦች እና በትንሽ የሰራዊት ክፍሎች ላይ አዛዦች” ይህን በ1 ዜና 13:1 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

አለቆች
“ከላይ” የሚለው ቃል እዚህ እንደ ፈሊጥ አገልግሏል። አት: “ሃላፊነት የላቸው አለቆች” (ፈሊጥ: ይመልከቱ)

ሀብትና ግዛት
እነዚህ ሀለት ቃላት ንጉሱ ያለውን እቃዎች እና መሬት የሚወክሉ ሲሆን ተመሳሳይ ትርጉም ይጋራሉ። (ድርብ: ይመልከቱ)

1 Chronicles 28:2

በእግሩ ቆሞ
ይህ ፈሊጥ ነው። አት: “ቆመ” (ፈሊጥ: ይመልከቱ)

ወንድሞቼና ሕዝቤ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ዳዊትና ሕዝቡ ቤተሰብ እንደሆኑ አፅንኦት የሚሰጡ ሲሆን ተመሳሳይ ትርጉም ይጋራሉ። (ድርብ: ይመልከቱ)

ለእግዚአብሔር ለቃል ኪዳኑ ታቦትና ለአምላካችን እግር ማረፊያ
ሁሉተኛው ሀረግ የመጀመሪያውን ይፈታል። “የኪዳኑ ታቦት” ያህዌን በዙፋኑ እንዳለ የእግሩን መርገጫ፣ ይህም እግሩ በእግሩ መርገጫ ማረፉን ባሳየት ሁሉም ለእርሱ እንደሚገዛ የሚገልፅ ነው። (ትይዩአዊ እና ዘይቤ: ይመልከቱ)

ለስሜ ቤት
እዚህ እግዚአብሄር እራሱን “በስሙ” ይጠራል። አት: “ለእኔ መቅደስ” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

የሰልፍ ሰው ነህና፣ ደምም አፍስሰሃልና
“ጦርነት የለመደ እና ደም ያፈሰሰ ሰው።” ሁለቱም ገለጻዎች አንድ አይነት ነገር አጽንኦት ይሰጣሉ፣ ማለትም ዳዊት ሰዎችን እንደገደለ።. (ትይዩአዊ: ይመልከቱ)

ደምም አፍስሰሃልና
ይህ ሰዎችን መግደልን ይወክላል። አት: “ሰዎችን ገድለሀል” (የተዘዋዋሪ ንግግር: ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Chronicles 28:4

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት እስራኤላውያንን መጋገሩን ይቀጥላል።

በእስራኤል ላይ የዘላለም ንጉሥ እሆን ዘንድ ... መርጦኛል
አንድ አማራጭ ትርጉም ዳዊት ከዳዊትና ከእርሱ በኃላ እስራኤል ለዘለአዘም የሚመሩትን ልጆቹን የሚገልፅ የባሕሪ ስም ነው። አት: "በእስራኤል ላይ ለዘለአለም ንጉስ እንሆነ ዘንድ .... እኔ እና ልጆቼን መረጠ" ሌላው ዳዊት ከሙታን በትንሳኤ ከተነሳ በኃላ በእስራኤል ላይ ንጉስ በመሆን ይቀጥላል። (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

በእስራኤል ሁሉ
"የእስራኤል ምድር ሁሉ" ወይም "እስራኤላውያን በሙሉ"

ዙፋን ላይ ተቀምጦ
እዚህ "በዙፋኑ ላይ መቀመጥ" እንደ ንጉስ መምራት ማለት ነው። አት: "መምራት" ወይም "ንጉስ መሆን" (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር መንግሥት ... በእስራኤል
"የያህዌ መንግስት የሆነችው እስራኤል"

1 Chronicles 28:6

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት እስራኤላውያንን መናገሩን ይቀጥላል።

አለኝ
"እግዚአብሄር አለኝ"

ቤቴንና
"ቤት" የሚለው ቃል የያህዌን መቅደስ ይወክላል።

ልጅ ይሆነኝ ዘንድ መርጬዋለሁና፥ እኔም አባት እሆነዋለሁና
ይህ ሰሎሞን የእግዚአብሄር ትክክለኛ ልጅ ይሆናል ማለት ሳይሆን፣ ነገር ግን እርሱ እና እግዚአብሄር የሚኖራቸውን ግላዊ ግንኙነት ይገልጻል። አት: "እንደ ልጅ ላይው መርጫለው፣ እንደ አባትም እሆነዋለሁ" (ዘይቤ: ይመልከቱ)

ትእዛዜንና ፈርዴንም
እነዚህ ሁለት ቃላት በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ሲሆኑ ያህዌ ያዘዘውን ሁሉ ይወክላሉ፡ (ድርብ: ይመልከቱ)

እንደ ዛሬው
እዚህ "አንተ" የሚለው ቃል ዳዊትን ይወክላል። እንዲሁም፣ "መሰጠት" የሚለው ቃል ሊተካ ይችላል። አት: "ልክ በዛሬ እለት እንደተሰጠኃው" (ግድፈተ ቃላት: ይመልከቱ)

1 Chronicles 28:8

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ሕዝቡን መናገሩን ይቀጥላል።

አሁንም ... እስራኤል ሁሉ እያዩ... ሁላችሁም
እዚህ ዳዊት ለእስራኤል ሕዝብ ትዕዕዛዝ እየሰጠ ነው። አት: "እንግዲህ አሁን፣ በእስራአረል ሁሉ ፊት፣ በያህዌ ጉባኤ፣ በአምላካችን በእግዚአብሄር ፊት፣ ሁላችሁንም አዛችኃለው" (ታሳቢ የሆነ እውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ: ይመልከቱ)

አሁንም
ይህ ዳዊት በንግግሩ አዲስ ምዕራፍ መጀመሩን ያጠቁመማል።

እስራኤል ሁሉ, የእግዚአብሔር ጉባኤ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች አንድ አይነት ትርጉም ሲኖራቸው ሁለተኛው የመጀመሪያውን ያብራራል። ሁሉም የእስራኤል ሕዝብ ባይኖሩም ያሉቱ ሁሉን እስራኤል ይወክላሉ። አት: "ለያህዌ በዚህ ጉባኤ፣ ሁላችሁ የእስራኤል ሕዝብ" (ትይዩአዊ እና Synecdoche: ይመልከቱ)

እያዩ
"ፊት" የሚለው ሀረግ ሁሉም እንዳሉና እየሰሙ ነው ማለት ነው። አት: "እየሰሙ" (ፈሊጥ: ይመልከቱ)

ጠብቁ፥ ፈልጉም
"መጠበቀ" የሚለው ሀረግ ከ"መያዝ" ጋር ተመሳሳይ ነው። በአንድነት ቃላቱ እግዚአብሄር ያዘዘውን የማድግን አስፈላጊነት አጽንኦት ይሰጣሉ። አት: "በጥንቃቄ ታዘዙ" (ድርብ: ይመልከቱ)

ለልጆቻችሁም ለዘላለም
ይህ መሬቱ ለልጆቻቸውና ለመጪው ትውልድ ይሆናል ማለት ነው። "ከእናንተ በኃላ" የሚለው ሀረግ ፈሊጥ ነው። አት: "ልጆቻችሁ እና እናንተ ከሞታችሁ በኃላ የሚተኳችሁ ዘሮቻችሁ" (Synecdoche እና ፈሊጥ: ይመልከቱ)

1 Chronicles 28:9

የአባትህን አምላክ
ዳዊት እራሱን "አባታችሁ" በማለት ይጠራል ምክንያቱም ይህ መደበኛ ኩነት ነውና። አት: "አምላኬ" (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ: ይመልከቱ)

በፍጹም ልብና
እዚህ "ልብ" የሰውን ሁለንተና ይወክላል። አንድን ነገር "በፍጽም ልብ" ማድረግ ፈሊጥ ነው። አት: "በሙሉ መሰጠት" ወይም "ሙሉ ለሙሉ" (Synecdoche እና ፈሊጥ: ይመልከቱ)

ፈቃድም
እዚህ "መንፈስ" የሰውን ሁለንተና ሲወክል የሰውየውን ፈቃድ አጽንኦት ይሰጣል። አት: "በፈቃደኝነት" (Synecdoche: ይመልከቱ)

ልብን ሁሉ ይመረምራልና፥ የነፍስንም አሳብ ሁሉ ያውቃልና
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ሲሆኑ ያህዌ የሁሉንም ሰው ሀሳብ እና መነሻ ሃሳብ እንደሚያውቅ አጽንኦት ይሰጣል። (ትይዩአዊ: ይመልከቱ)

ልብን ሁሉ
እዚህ የሕዝቡ "ልብ" ስመተታቸውን እና መሻቸውን ይወክላል። አት: "የሁሉንም ስሜት እና መሻት ይመረምራል" (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

ብትፈልገው ታገኘዋለህ
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊጻፍ ይችላል። እንዲሁም፣ ያህዌን ስለመከተል እና እርሱን በመፈለግ እና እርሱን ባግኘት እርሱ ስለመስማቱ ያወራል። አት: "ብትፈልጉት ታገኙታላችሁ" ወይም "ያህዌ እንዲያስባችሁ ከጣራችሁ ያደርገዋል" (ገባሪ ወይም ተገባሪ እና ዘይቤ: ይመልከቱ)

አስተውል
"አስተውሉ" ወይም "ማስታሰዋችሁን እርግጠኛ ሁኑ"

ጠንክረህ ፈጽመው
The word "ጠንካራ" የሚለው ቃል ራስን መግዛትን እና ጠንካራ ባህሪን ይወክላል።

1 Chronicles 28:11

ለመቅደሱ ወለል
"የመቅደሱ ወለል" ወይም "የመቅደሱ መግቢያ።" ይህ በመቅደሱ መግቢያ ጣሪያውን የሚደግፉትን አምዶች ይወክላል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መዛግብቱም
ለከበሩ እቃዎች ግምጃ ቤት

1 Chronicles 28:13

ሚዛን
እነዚህ ካህናቱ እና ሌዋውያኑ በመቅደሱ እንዴት እንደሚሰሩ ወሳኝ መመሪያዎች ናቸው።

የካህናቱንና የሌዋውያኑንም ክፍላቸውን
“የካሕናቱ እና የሌዋውያኑ ቡድን።” ይህ ካህናቱ እና ሌሎች የመቅደሱ ሰራተኞች ግዴታቸውን ለመወጣት የሚዋቀሩበትን ቡድን የሞወክል ነው።

መቅረዙ
“እያንዳንዱ መቅረዝ በመቅደሱ አገልግሎት በምን ጥቅም ላይ እንደሚውል ወሰኑ።” የተለያየ ክብደት ያላቸው ለተለያየ አላማ የሚሆኑ የብር መቅረዞች ይኖራሉ።

1 Chronicles 28:16

ለገበታዎቹ ሁሉ
የተረዱትን ሀሳብ ማስገባት ይቻላል። አት: “ለሌሎቹ ጠረጴዛዎች የወርቁ ክብደት” (ግድፈተ ቃላት: ይመልከቱ)

1 Chronicles 28:18

ጥሩውን ወርቅ
“የተጣራ ወርቅ” ወይም “ተጨማሪ ዋጋ ያለው ወርቅ”

ለወርቁም ጽዋዎች
ይህ የወርቁን ክብደት ይወክለላል። አት: “ለንድፉ የሚሆን የወርቁ ክብደት” (ግድፈተ ቃላት: ይመልከቱ)

ይህ ሁሉ ...ተጽፎ መጣልኝ
ይህ ፈሊጥ ነው። አት: “ይህን ሁሉ ጻፍሁ” (ፈሊጥ: ይመልከቱ)

የሥራውን ሁሉ ምሳሌ አውቅ ዘንድ
ይህ የመቅደሱን ንድፍ ጥልቅ ማብራሪያ ይወክላል። አት: “ለመቅደሱ ጥልቁን ትንታኔ መረዳት እንዲችል ረዳኝ” (ታሳቢ የሆነ እውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ: ይመልከቱ)

1 Chronicles 28:20

ጠንክር፥ አይዞህ
እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሳሳይ ሲሆኑ ሰለሞን ደፋር መሆን እንዳለበት አጽንኦት ይሰጣሉ። (ድረብ: ይመልከቱ)

አትፍራ፥ አትደንግጥም
“አትፍራ” እና “አትደንግጥ” የሚሊት ቃላት ተማሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው ሰሎሞን በጭራሽ እጅ እንዳይሰጥ አጽንኦት ይሰጣሉ። እንዲሁም፣ ይህ በአውንታዊ ቅርፅ መጻፍ ይችላል። አት: “ደፋር ሁን” ወይም “ተማመን”(ድረብ: ይመልከቱ)

ከአንተ ጋር ነውና
ይህ ፈሊጥ ነው። አት: “እረዳሀለው” (ፈሊጥ: ይመልከቱ)

አይተውህም፥ አይጥልህምም
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ሲሆኑ ያህዌ ሁሌም ከሰሎሞን ጋር እንደሚሆን አጽንኦት ይሰጣል። እንዲሁም፣ ይህ በአውንታዊ ቅርጽ ልገለጽ ይችላል። አት: “እርሱ ሁል ጊዜ ከአንተ ጋር ይሆናል” (ትይዩአዊ: ይመልከቱ)

እነሆም፥ ክፍሎች በዚህ አሉ
“እዚህ ጋ ክፍሎቹ አሉ።” እዚህ ዳዊት “እይ” የሚለውን ቃል የሌዋውይኑን እና በመቅደሱ ያላቸውን ግዴታ የሚያሳየውን የክፍሎች ዝርዝር ለመወከል ይጠቀመዋል።

የካህናትና የሌዋውያን ክፍሎች
ይህን በ1 ዜና 28:13 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 29

1 ከዚያም ንጉሥ ዳዊት ለመላው ጉባኤ እንዲህ አለ፤ "እግዚአብሔር የመረጠው ልጄ ሰሎሞን ገና ወጣትና ልምድም የሌለው ነውው። ይህ ታላቅ ሕንጻ
የሚሠራውን ለሰው ሳይሆን ለእግዚአብሔ አምላክ በምሆን፣ ጅራው ከባድ ነው። 2 እኔም ያለኝን ሀብት ለአምላኬ ቤተ መቅደስ ለወርቁ ሥራ ወርቁን ለብሩ ሥራ
ብሩን፣ ለናስ ሥራ ናሱን፣ ለብረቱ ሥራ ብረቱን፣ ለዕንጨቱ ጅራ ዕንጨቱን እንዲሁም ለፈርጥ የሞሆነው መረግድ፣ ኬልቄዶን፣ ልዩ ልዩ ኅብር ያላቸውን ዐይነት
የሚያምር ድንጋይና ዕብነበረድ፣ ይህን ሁሉ በብዛት አዘጋጅቻለሁ። 3 ከዚህም በቀር ለአምላኬ ቤት ካለን ፍቅር የተነሣ ለዚህ ለተቀደሰ ቤት ከዚህ በፊት
ከሰጠሁት በተጨማሪ ለዚሁ ለእግዚአብሔር ቤተ ምቅደስ የግል ሀብቴ የሆነውን ወርቅና ብር እሰጣለሁ፤ 4 ይህም ሦስት ሺህ መክሊት ንጹሕ ብር ለቤተ
መቅደሱ የግድግዳ ግንብ ማስጌጫ 5 እንዲሁም ለወርቁ ሥራ፣ ለብሩ ሥራ፣ በባለሞያዎች ለሚሠራው ሥራ ሁሉ የሚሆን ነው። ታዲያ ዛሬ ራሱን
ለእግዚአብሔር ለመቀደስ ፍቃደኛ የሚሆን ማን ነው?። 6 ከዚያም የቤተሰቡ አሪዎች፣ የነገዱ የእስራኤል ሹማምት፣ የሻለቆችና የመቶ አለቆች እንዲሁም
በንጉሥ ሥራ ላይ የተመደቡ ሹማምት፣ በፍቃዳቸው ሰጡ፤ 7 ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ሥራ የሰጡትም አምስት ሺህ መክሊት ወርቅ፣ ዐሥር ሺህ ዳሪክ
ወርቅ፣ ዐሥር ሺህ መክሊት ናስ አንድ መቶ ሺህ መክሊት ብረት ነው። 8 የከበሩ ድንጋዮች ያለውም ሁሉ፣ በጌድሶናዊው በይሒኤል አማካኝነት ወደ እግዚአብሔር
ቤተ መቅደስ ግምጃ ቤት አስገባ። 9 ስጦታው በገዛ ፈቃደና በፍጹም ልብ የቀረበ በመሆኑ፣ አለቆች ስላደረጉት የብበጎ ፈቃድ ስጦታ ሕዝቡ ደስ አለው፤ ንጉሥ
ዳዊትም እንደዚሁ እጅግ ደስ አለው። 10 ዳዊትም በመላው ጉባኤ ፊት እግዚአብሔር እንዲህ ሲል አመሰገነ፤ "የአባታችን የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር
ሆይ፤ ከዘላለም እስከ ዘላለም ለአንተ ምስጋና ትሁን። 11 እግዚአብሔር ሆይ፤ በሰማይና በምድር ያለው ሁሉ ለአንተ ነውና፤ ታላቅነት፣ ኅይል ክብርና ግርማ የአንተ
ነው። እግዚአብሄር ሆይ፤ መንግሥትህም የአንተ ነው፤ አንተም እንደ ራስ ከሁሉ በላይ ከፍ ከፍ ያልህ ነህ። 12 ባለጠግነት ክብር የሚገኘው ከአንተ ነው፤ አንተም
የሁሉ ገዢ ነህ፤ ከፍ ከፍ ለማድረግ፣ ለሁሉም በርታትን ለመስጠት፣ ብርታትና ኅይል በእጅህ ነው። 13 አምላካችሁ ሆይ፤ አሁንም እናመሰግንሃለን፤ ለከበረው
ስምህም ውዳሴ እናቀርባለን። 14 "ሁሉ የተገኘው ከአንተ ነው፤ ለአንተም የሰጠንህ ከእጅህ የተቀበልነው ብቻ ነው። ታዲያ እንዲህ ያለ ቸርነት እናድርግ ዘንድ
እኔ ማነኝ? ሕዝቤስ ማንኝ? 15 እኛም እንደ ቀድሞ አባቶቻችን በፊትህ መጻተኞችና እንግዶች ነን፤ ዘመናችንም በምድር ላይ እንደ ጥላ ነው፤ ተስፋ ሲስም
ነው። 16 እግዚአብሔር አምላካችን ሆይ፤ ለተቀደሰው ስምህ ቤተ መቅደስ እንሠራለን ዘንድ ይህ በብዛት ያዘጋጀውን ሁሉ፤ ከእጅህ የተገኘውና ሁሉም ለአንተ
ነው። 17 አምልኬ ሆይ፤ ልብን እንደምትመረምርና ቅንነትን እንደምትወድ ዐውቃለሁ፤ እኔም ይህን ሁሉ የሰጠሁት በበጎ ፈቃደና በቀና መንፈስ ነው። አሁንም
በዚህ ያለው ሕዝብህ በበጎ ፈቃዱ እንዴት እንደ ሰጠ አይቻለሁ። 18 የአባታቸው የአብርሃም፣ የይስሐቅ፣ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፤ ይህን ዐሳብ
ለዘላለም በሕዝብህ ልብ ጠብቀው፤ ልባቸውንም ለአንተ ታማኝ አድርገው። 19 ትእዛዞችህን፣ እኔ ባዘጋጀሁለት ነገሮች ታላቅ ህንጻ ለመጅራት እንዲችል፣ ለልጄ
ለሰሎሞ ፍጹም ፈቃደኛነት ሰጠው። 20 ከዚያም ዳዊት ለመላው ጉባኤ፣ "አምላካችሁን እግዚአብሔር ወሰዱት" አላቸው። ስለዚህ የአባታቻችን አምላክ
እግዚአብሔር ወደሱ፤ በእግዚአብሔር በንጉሡም ፊት ተደፍተው ሰገዱ። 21 በማግስቱም ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ሠው፤ የሚቃጠል መስሥዕዋትም
አቀረቡ፤ ይህም አንንድ ሺህ ወይፈን፣ አንድ ሺህ አውራ በግ፣ አንድ ሺህ የበግ ጠቦት ሲሆን፤ ከመጠጥ ቁርባኖቻቸውና ከሌሎች መሥዕዋቶች ጋር ስለ
እስራኤል ሁሉ በብዛት አቀረቡ። 22 በዚህችም ዕለት በእግዚአብሔር ፊት በታላቅ ደስታ በሉ፤ ጠጡም። ከዚያም የዳዊት ልጅ ሰሎሞን ንጉሥ መሆኑን ሁለተኛ
ጊዜ በይፋ ዐወቁ፤ ገዥ እንዲሆንም በእግዚአብሔር ፊት ቀቡት፤ 23 ሰለሞንም ነግሦ በአባቱ በዳዊት ምትክ በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ ተቀመጠ፤
ተከናወነለት፤ እስራኤልም ሁሉ ታዘዙለት። 24 የጦር አለቆችና ኅያላኑ ሁሉ እንዲሁም የንጉሥ የዳዊት ወንዶች ልጆች በሙሉ ታማኝነታቸውን ለንጉሥ ሰሎሞን
አረጋ ገጡለት። 25 እግዚአብሔር ሰሎሞንን በእስራኤል ሕዝብ ዘንድ ሁሉ እጅግ ከፍ ከፍ አደረገው፤ ከእነሱ በፊት ለነበሩት የእስራኤል ነገሥታት
ያላጎናጸፋቸውን ንጉሣዊ ክብር ሁሉ ሰጠው። 26 የእሴይ ልጅ ዳዊት በእስራኤል ሁሉ ላይ ነግሦ ነበር። 27 እርሱም በኬብሮን ሰባት ዓመት፤ በእየሩሳሌም
ሠላሳ ሦስት ዓመት፣ በአጠቃላይ አርባ ዓመት ነገሠ። 28 ብዙ ዘመን ባለጠግነትና ክብር ሳይጎድልበት ዕድሜ ጠግቦ ሞተ፤ ጅጁ ልምሞን በእግሩ ተተክቶ
ነገሠ። 29 በንጉሥ ዳዊት ዘመነ መንግሥት ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻ የተከናወነው ድርጊት በባለ ራእዩ በሳሙኤል የታሪክ መጽሐፍ፣ በነብዩ በናታን
የታሪክ መጽሐፍ ተጽፎአል። 30 የተጻፈውም በሥልጣን ላይ በነበረበት ጊዜ ከፈጸማቸው ዝርዝር ጉዳዮችና በዙሪያው ከከበቡት፤ ከእስራኤልና ከሌሎች አገር
መንግሥታት ታሪክ ጋር ነው።

---

1 Chronicles 29:1

እግዚአብር ብቻውን የመረጠው
“እግዚአብሔር የመረጠው”

ለወርቁ ዕቃ ወርቁን... ለእንጨቱም ዕቃ
ይህ በገባሪ ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አት: “ሠራተኞች የወርቅ እቃዎችን እንዲሰሩ ወርቅ፣ የብር እቃዎችን እንዲሰሩ ብር፣ የነሀስ እቃዎችን እንዲሰሩ ነሀስ፣ የብረት እቃዎችን እንዲሰሩ ብረት፣ እናም የእንጨት እቃዎችን እንዲሰሩ እንጨት” (ገባሪ ወይም ተገባሪ: ይመልከቱ)

በፈርጥ የሚገባ ድንጋይን... የሚለጠፍ ድንጋይን... ... ልዩ ልዩ መልክ ያለውንም ድንጋይ
እነዚህ እያንዳንዱ ሀረጎች ለተለያየ አላማ የሚውሉ የተለያዩ የድንጋይ አይነቶችን ይወክላሉ።

ልዩ መልክ ያለው ድንጋይ
እነዚህ ወርቅ ለመስራት የሚያገለግሉ ጥቁር እና ነጭ መስመር ያላቸው ድንጋዩች ናቸው።

የሚለጠፍ ድንጋይን...
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊገለጽ ይችላል። አት: “ባለሞያዎቹ እንዲሰሯችው የተቀመጡ ድንጋዩች” ወይም “የመወጣጫ ድንጋዩች”

ልዩ ልዩ መልክ ያለውንም
ይህ በድንጋዩቹ የተሰራውን ውብ እና የተጌጠ ስራ ይወክላል።

1 Chronicles 29:3

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ስለ መቅደሱ ግንባታ ያበረከተውን መግቦት ለሕዝቡ መናገሩን ይቀጥላል።

ሦስት ሺህ መክሊት
“3,000 መክሊት” ይህ በዘመናዊ መለኪያዎች ሊገለጽ ይችላል። አት: “ወደ 100,000 ኪሎግራም ገደማ” ወይም “ወደ 100 ሜትሪክ ቶን ገደማ” (መፅሐፍ ቅዱሳዊ እና ቁጥሮች: ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከኦፊር ወርቅ
ይህ ምርጥ ጥራት እና ዋጋ ያለው ወርቅ ነው።

ሰባት ሺህም መክሊት
“7,000 መክሊት።” ይህ በዘመናዊ መለኪያዎች ሊገለጽ ይችላል። አት: “ወደ 230,000 ኪሎግራም ገደማ” ወይም “230 ሜትሪክ ቶን ገደማ” (መፅሐፍ ቅዱሳዊ እና ቁጥሮች: ይመልከቱ)

ለወርቁ ዕቃ ወርቁን... በሠራተኞች እጅ ለሚሠራው
ይህ በገባሪ ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አት: “ለባለሞያዎቹ የወርቅ እቃዎች አንዲሰሩ ወርቅ፣ የብር እቃዎች እንዲሰሩ ብርመ እናም ሁሉም አይነት ነገሮች ለሌሎቹ ስራዎቻቸው” (ገባሪ ወይም ተገባሪ: ይመልከቱ)ሥራ

ለእግዚአብሔር የሚቀድስ
“እረሱን ለእግዚአብሄር ሰጠ”

1 Chronicles 29:6

አጠቃላይ መረጃ:
(ቁጥሮች: ይመልከቱ)

የአባቶችም ቤቶች አለቆች፥ ... በንጉሡም ሥራ ላይ የተሾሙት በፈቃዳቸው አቀረቡ
ይህ በገባሪ ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አት: “ከዛም መሪዎቹ ... እናም በንጉሱ ስራ ላይ በለስልጣናቱ በፈቃደኝነት መስዋዕት አወቀረቡ” (ገባሪ ወይም ተገባሪ: ይመልከቱ)

ሻለቆችም፥ የመቶ አለቆችም
አማራጭ ትርጉሞች 1) እነዚህ ቁጥሮች አዛዦቹ ይመሯቸው የነበሩትን ወታደሮች ትክክለኛ ቁጥር ያሳያል። አት: “በ1,000 ወታደሮች ላይ አለቆች እና በ100 ወታደሮች ላይ አለቆች” ወይም 2) “ሺዎች” እና “መቶዎች” የሚሉት ቃላት ትክክለኛ ቁጥሮችን የሚያሳዩ ሳይሆን ነገር ግን የትልቅ እና የትንሽ የሰራዊት ክፍሎች ስሞች ናቸው። አት: “በትልቅ የሰራዊት ክፍል ላይ አዛዦች እና በትንሽ የሰራዊት ክፍሎች ላይ አዛዦች” ይህን በ1 ዜና 13:1 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

በንጉሡም ሥራ ላይ የተሾሙት
እዚህ “በላይ” የሚለው ቃል እንደ ፈሊጥ አገልግሏል። አት: “በንጉሱ ስራ ሀላፊ የሆኑት ባለስልጣናት” (ፈሊጥ: ይመልከቱ)

አምስት ሺህ መክሊት... መቶ ሺህም መክሊት ብረት
“5,000 መክሊት እና 10,000 ዳሬክ ወርቅ፣ 10,000 መክሊት ብር, 18,000 መክሊት ነሀስ፣ እና 100,000 መክሊት ብረት።” እነዚህ በዘመናይ መስፈሪያ ሊጻፉ ይችላሉ። አት: “165 ሜትሪክ ቶን እና 84 ኪሎግራም ወርቅ፣ 330 ሜትሪክ ቶን ብር፣ 600 ሜትሪክ ቶን ነሀስ እና 3,300 ሜትሪክ ቶን ብረት” (መፅሐፍ ቅዱሳዊ ገንዘብ: ይመልከቱ)

1 Chronicles 29:8

መዛግብት
ይህ ገንዘብ እና ዋጋ ያላቸው ቁሶች የሚቀመጡበት ቦታ ነው።

በይሒኤል
የእነዚህን ሰዎች ስሞች በ1 ዜና 23:8 እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

በጌድሶናዊው
ይህ የሌዊ የበኩር ልጅ ነው። የእነዚህን ሰዎች ስሞች በ1 ዜና 23:7 እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ: ይመልከቱ)

በፍጹም ልባቸውም
ያለምንም ጥርጥር ወይም ማመንታት በፈቃደኝነት

1 Chronicles 29:10

ተባረክ
ይህ በገባሪ ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አት: “ሕዝቦች ያክብሩህ” (ገባሪ እና ተገባሪ: ይመልከቱ)

የአባታችን የእስራኤል
እዚህ “እስራኤል” ግለሰቡን ያዕቆብን ይወክላል። አት: “ያዕቆብ አባታችን” (ታሳቢ የሆነ እውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ: ይመልከቱ)

1 Chronicles 29:12

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበው የምስጋና ጸሎት ይቀጥላል።

ኃይልና ብርታት በእጅህ ነው
ይህ የሚናገረው ሰዎች ሀያል ሆኑም አልሆኑ ያህዌ “ሀይልን እና ግርማን” በእጁ እንደሚቆጣጠር ነው። አት: “አንተ ሀይል እና ብርታት ያለውን ትወስናለህ” (ዘይቤ: ይመልከቱ)

ኃይልና ብርታት
“ሀይል” እና “ብርታት” የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ሲሆኑ የያህዌን ሀይል ታላቅነት አጽንኦት ይሰጣሉ። (ድርብ: ይመልከቱ)

ለክቡር ስምህም
እዚህ ያህዌ በስሙ ተገልጸል። አት: “ክቡር የሆንከው አንተ” ወይም “አንተ ምክንያቱም ክቡር ነህና” (የባህሪ ስም: ይመልከቱ)

1 Chronicles 29:14

አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበው የምስጋና ጸሎት ይቀጥላል።

ይህን ያህል ችለን ልናቀርብልህ እኔ ማን ነኝ? ሕዝቤስ ማን ነው?
ዳዊት ይህን መልሱ የታወቀ ጥያቄ እርሱ እና ሕዝቡ ለእግዚአብሄር ምንም ቢሰጡ ምንም ምስጋና እንደማይገባቸው ለመግለጽ ይጠቀመዋል። አት: “ሕዝቤ እና እኔ እነዚህ ነገሮች ለአንተ በፈቃደኝነት መስጠት ይገባናል!” (መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ: ይመልከቱ)

በፊትህ ስደተኞችና መጻተኞች ነን
ይህ የሰዎች ሕይወት አጭር እንደሆነ እናም በአለም ላይ የአጭር ጊዜ ጉዞ እንዳላቸው ይናገራል። አት: “ሕይወታችን አጭር ነውና በአንተ ፊት የምናልፍ መጻተኞች እና ተጎዦች ነው” (ዘይቤ: ይመልከቱ)

ዘመናችንም በምድር ላይ እንደ ጥላ ናት
ይህ የሰዎች ሕይወት አጭር እንደሆነ እናም ለአጭር ጊዜ ብቻ እንደሚታይ ጣላ መሆናቸውን ይናገራል። የሰው የሕይወት ዘመን በቀናቱ” ይገለጻል። አት: “የእኛ ጊዜ በምድር ላይ ፈጥኖ እንደሚጠፋ ጥላ ነው” (ተመሳሳይ እና Synecdoche: ይመልከቱ)

1 Chronicles 29:16

ለቅዱስ ስምህ
እዚህ ያህዌ በስሙ ተጠርቷል። AT: “አንተ” (የባህሪ ስም: ይመልከቱ)

ልብን እንድትመረምር
እዚህ “ልብ” የሰውን ሀሳብ እና ስሜት ይገልጻል። አት: “አንተ የሰውን ሀሳብ ትፈትናለህ” (የባህሪ ስም: ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በልቤ ቅንነትና
እዚህ “ልብ” የሰውን ሀሳብ እና ስሜት ይገልጻል። አት: “ለአንተ በማደርገው ሁሉ ታማኝ እና የከበረ መሆን ስለምሻ” (የባህሪ ስም: ይመልከቱ)

በደስታ አይቻለሁ
“እንደማየው ደስተኛ ነኝ”

1 Chronicles 29:18

የእስራኤልም
እዚህ “እስራኤል” “ያዕቆብ” የተባለው ግለሰቡን ይወክላል።

ይህን አሳብ በሕዝብህ ልብ ለዘላለም ጠብቅ
“ይህን በሕዝብህ ሀሳብ አን አዕምር ውስጥ ለዘላለም አኑረው”

ልባቸውንም ወደ አንተ አቅና
እዚህ የሕዝቡ “ልብ” ሀሳባቸውን እና መሻታቸውን ይገልጻል። አት: “ለአንተ ታማኝ እንዲሆኑ ምራቸው” ወይም “ለአንተ ታማኝ አድርጋቸው” (የባህሪ ስም: ይመልከቱ)

ለልጄ ለሰሎሞን ፍጹም ልብ ስጠው
“መሻት” የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊገለጽ ይችላል። አት: “ልጄን ሰሎሞን ሙሉ ለሙሉ እንዲሻ አድርገው” (ረኪክ ስሞች: ይመልከቱ)

1 Chronicles 29:20

አምላካችሁን እግዚአብሔርን ባርኩ አላቸው
“አሁን ያህዌን አመስግኑ”

ራሳቸውንም አዘንብለው ... ለንጉሡ ሰገዱ
ይህ ታላቅ ከበሬታን ለማሳየት በአንድ ሰው ፊት መሬት ላይ መተኛትን ይወክላል። አት: “ለይህዌ እና ለንጉሱ ክብር ለማሳየት ራሳቸውን መሬት ላይ ጣሉ” (ምሳሌያዊ ድርጊት: ይመልከቱ)

ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ሠዉ፥ የሚቃጠለውንም መሥዋዕት ለእግዚአብሔር አቀረቡ
ሕዝቡ በካሕናቱ ለያህዌ እንዲሰዉ እንስሳዎችን አቀረቡ። ከሕዝቡ አብዛኞቹ እንስሳዎቹን በቀጥታ እራሳቸው አልገደሉም መስዋዕትም አላቀረቡም። (የባህሪ ስም: ይመልከቱ)

አንድ ሺህ ወይፈን፥ አንድ ሺህም አውራ በጎች፥ አንድ ሺህም የበግ ጠቦቶች
“1,000 በሬዎች, 1,000 ኮርማዎች, እና 1,000 በጎች” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

1 Chronicles 29:22

በእግዚአብሔር ፊት
ይህ ፈሊጥ ነው። አት: “ለያህዌ ክብር” (ፈሊጥ: ይመልከቱ)

ሁለተኛ ጊዜ
ይህ እርሱን እንደቀቡት እና ንጉስ መሆኑን አወጁ ማለት ነው። የመጀመሪያው ጊዜ በ1 ዜና 23:1 ተገልጸል።

እርሱንም አለቃ ይሆን ዘንድ ለእግዚአብሔር ቀቡት
“በያህዌ ስልጣን” አንዳች ማድረግ በእርሱ ምትክ እና በእርሱ እውቅና ማድረግ ማለት ነው። አት: “በያህዌ ምትክ እስራኤልን እንዲመራ ቀቡት” (ተሳቢ የሆነ እውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ: ይመልከቱ)

ሰሎሞንም በአባቱ በዳዊት ዙፋን ላይ ተቀመጠ
እዚህ የእስራኤል ዙፋን እንደ “ያህዌ ዙፋን” የተገለጸው የእስራኤል ሕዝብ የያህዌ ሕዝብ መሆናቸውን አጽንኦት ለመስጠት ነው። ዙፋኑ ላይ መቀመጥ እንደ ንጉስ መምራትን ይገላጻል። አት: “ስለዚህ በበአባቱ በዳዊት ፈንታ፣ በያህዌ ሕዝብ ላይ እንደ ንጉስ፣ ሰሎሞን በዙፋኑ ተቀመጠ” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

1 Chronicles 29:24

ለሰሎሞን እጅ ሰጡት
“ለንጉስ ሰሎሞን ታማኝ እንደሚሆኑለት ነገሩት”

እግዚአብሔርም ሰሎሞንን በእስራኤል ሁሉ ፊት እጅግ አገነነው፤ ከእርሱ በፊትም ለነበሩት ለእስራኤል ነገሥታት ያልሆነውን የመንግሥት ክብር ሰጠው
እነዚህ ሁለት ሀረጎች የእስራኤል ታላቁ እና እጅግ ሀይለኛው ንጉስ ያደረገውን ሞገስ ሰሎሞን ከያህዌ መቀበሉን አጽንኦት ይሰጣሉ። (ትይዩአዊ: ይመልከቱ)

1 Chronicles 29:26

አርባ ዓመት... ሠላሳ ሦስትም ዓመት
“40 አመት ... 33 አመት” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)

ዕድሜም፥ ባለጠግነትም
“እንደ ሸማግሌ ሰው”

1 Chronicles 29:29

በባለ ራእዩ በሳሙኤል ታሪክ፥ ... በባለ ራእዩም በጋድ ታሪክ ተጽፎአል
እነዚህ የጠፉ የጽሁፍ መዛግብት ናቸው።

ያለፉት ... ተጽፈዋል
ይህ በገባሪ ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አት: “እዚያ ሰዎች ስራዎቹን ጻፉ” (ገባሪ ወይም ተገባሪ: ይመልከቱ)

የመንግሥቱ ነገርና
“ዳዊት ንጉስ በነበረ ጊዜ የሆኑ ነገሮችን”

በእርሱም በእስራኤልም በአገሮችም መንግሥታት ሁሉ ላይ ያለፉት
“እስራኤልን በመራበት ጊዜ በእርሱ እና በሕዝቡ እና በሌሎች መንግስታት የሆኑትን ነገርች ሁሉ” (ተሳቢ የሆነ እውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ: ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: 2 Chronicles

2 Chronicles

Chapter 1

1 የዳዊት ልጅ ሰለሞንም በመንግሥቱ በረታ፤ አምላኩም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበር፤ እጅግም ብርቱ ንጉሥ አደረገው። **2** ሰለሞንም ለእስራኤል ሁሉ፥ ለሻለቆች፥ ለመቶ አለቆችም፥ ለዳኞችም፥ በመላው እስራኤልም ሁሉ ለነበሩ መሳፍንት ሁሉ፥ ለአባቶች ቤቶች አለቆች ተናገረ፤ **3** የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ በምድረ በዳ የሠራው የእግዚአብሔር መገናኛ ድንኳን በገባኦን ስለነበር ሰለሞንና ጉባኤው ሁሉ እዚያ ወደነበረው የአምልኮ ሥፍራ ሄዱ። **4** ዳዊት ግን ለእግዚአብሔር ታቦት በኢየሩሳሌም ድንኳን ተክሎለት ስለነበር ከቂርያት ይዓሪም ወዳዘጋጀለት ሥፍራ አምጥቶት ነበር። **5** በተጨማሪም በሆር ልጅ በኡሪ ልጅ በባስልኤል የተሠራው የናስ መሠዊያ በዚያ በእግዚአብሔር ማደሪያ ድንኳን ፊት ነበረ፤ ሰለሞንና ጉባኤውም ወደ እርሱ ሄዱ። **6** ሰለሞንም በእግዚአብሔር ፊት በመገናኛው ድንኳን ዘንድ ወደነበረው ወደ ናሱ መሰዊያ ወጣ። በዚያም አንድ ሺህ የሚቃጠል መሥዋዕት አቀረበ። **7** በዚያም ሌሊት እግዚአብሔር ለሰለሞን ተገልጦ ፦ እንድሰጥህ የምትፈልገውን ማንኛውንም ነገር ለምነኝ አለው። **8** ሰለሞንም እግዚአብሔርን፦ ለአባቴ ለዳዊት ታላቅ የቃል ኪዳን ታማኝነት አሳይተሃል፤ እኔንም በእርሱ ምትክ ንጉሥ አድርገኸኛል፤ **9** አሁንም እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፦ ቁጥራቸው እንደ ምድር ትቢያ በሆነው ሕዝብ ላይ አንግሠኸኛልና ለአባቴ ለዳዊት የሰጠኸው የተስፋ ቃል ይፈጸም። **10** አሁንም እንደዚህ ቁጥራቸው በበዛ ሕዝብህ ላይ ሊፈርድ የሚችል ማንም ስለሌለ ይህንን ሕዝብ እመራ ዘንድ ጥበብና እውቀት ስጠኝ አለው። **11** እግዚአብሔርም ሰለሞንን፦ በልብህ የነበረው ይህ ስለነበር ባለጠግነትን፥ ሀብትን፥ ወይም ክብርን ወይም የሚጠሉህን ሰዎች ነፍስ ወይም ለራስህ ረጅም እድሜ ስላልጠየቅህ ነገር ግን ባነገሥሁህ በህዝቤ ላይ ለመፍረድ ትችል ዘንድ ለራስህ ጥበብንና እውቀትን ስለጠየቅህ **12** አሁን ጥበብና እውቀት ተሰጥተውሃል፤ ከአንተ በፊት የነበሩት ከነበራቸው እና ከአንተም በኋላ የሚመጡት ከሚኖራቸው ከየትኛውም ነገሥታት ይበልጥ ባለጠግነት፥ ሀብት፥ ክብርም እሰጥሃለሁ አለው። **13** ስለሆነም በገባኦን ከመገናኛው ድንኳን ፊት ከነበረው ከኮረብታው መስገጃ ወደ ኢየሩሳሌም መጣ። እዚያም በእስራኤል ላይ ነገሠ። **14** ሰለሞን ሰረገሎችን እና ፈረሰኞችን ሰበሰበ። በሰረገሎች ከተማዎችና ከራሱ ከንጉሡ ጋር በኢየሩሳሌም ያኖራቸው አንድ ሺህ አራት መቶ ሰረገሎች እና አሥራ ሁለት ሺህም ፈረሰኞች ነበሩት። **15** ንጉሡም ብርና ወርቅ በኢየሩሳሌም እንደ ድንጋይ እንዲበዛ አደረገው፤ የዝግባም እንጨት በቆላ እንዳሉት የሾላ ዛፎች እንዲበዛ አደረገው። **16** ከግብጽና ከቀዌ ለሰለሞን ፈረሶችን ስለ ማስመጣት የእርሱ ነጋዴዎች በገንዘብ እየገዙ ያመጡአቸው ነበር። **17** ከግብጽ አንዱን ሰረገላ በስድስት መቶ ሰቅል ብር፥ አንዱን ፈረስ በመቶ ሃምሳ ሰቅል ብር ዋጋ ያስመጡ ነበር። ለኬጢያውያንና ለሶርያ ነገሥታትም ልከው ይሸጡአቸው ነበር።

---

2 Chronicles 1:1

በእርሱ መንግስት ዘመን ተጠናክሯል /በመንግሥቱ በረታ
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “መንግሥቱን ሙሉ በሙሉ ተቆቁጣጠረ” ወይም “መንግሥቱን በሙሉ ስልጣን ገዛ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

እግዚአብሔር
ይህ በብሉይ ኪዳን ለህዝቡ የገለጠው የእግዚአብሔር ስም ነው ። ያህዌህ አተረጓጎም በተመለከ (የቃል ትርጉም ገጹን) መዝገበ ቃላቱን ይመልከቱ።

እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበር
እዚህ “ከእርሱ ጋር ነበረ” የሚለው አባባል ነው ። ኣት: - “እግዚአብሔር እርሱን ደግፎታል” ወይም “እግዚአብሔር እርሱን ረዳው”

2 Chronicles 1:2

አጠቃላይ መረጃ:
እንደ ዩ.ዲ.ቢ. በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የተከናወኑትን ክስተቶች ቅደም ተከተል እንደገና ማስተካከል ጠቃሚ ሊሆን ይችላል ። (የክስተቶች ቅደም ተከተልን : ይመልከቱ)

ለእስራኤል ሁሉ ፣ ለአለቆች . . .ለአባቶች ቤቶቸ መሪዎቸ ተናገረ።
እዚህ “እስራኤል ሁሉ” ማለት ቀጥሎ የተጠቀሱትን ሰዎች ማለት ነው ። እነሱ እስራኤልን ሁሉ ይወክላሉ ። ኣት: - “ለአለቆች . . . ለአባቶች ቤት አለቆች ተናገረ”

ሻለቆች እና መቶ አለቆች
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እነዚህ ቁጥሮች እነዚህ አለቆች የሚመሩትን ወታደሮች ብዛት ያመለክታሉ ። ኣት: - “የ 1000 ወታደሮች አዛዦች እና የ100 ወታደሮች አዛዦች” ወይም 2) “ሺህ” እና “መቶ” ተብለው የተተረጎሙት ቃላት ትክክለኛ ቁጥሮችን አይወክሉም ፣ ግን ትላልቅና ትናንሽ ወታደራዊ ምድቦች ስሞች ናቸው። ኣት: - “የትላልቅ የጦር ምድቦች አዛዦች እና የትናንሽ የጦር ምድቦች አዛዦች (ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

በእስራኤል ላሉ አለቆች(ልኡል) ሁሉ፣ የአባቶቹ ቤቶች መሪዎች
እዚህ ላይ “የአባቶች ቤቶች መሪዎች” የሚለው መሳፍንቱን የበለጠ ይገልፃሉ ። ኣት: - “በእስራኤል ሁሉ ላይ ለሚገኙ መሳፍንት ሁሉ ማለትም የአባቶች ቤቶች መሪዎች”

ለሁሉም መስፍን
እዚህ “መስፍን” ማለት በአጠቃላይ መሪዎች ማለት ነው ። የግድ የንጉሡ ልጆች ላይሆኑ ይቺላሉ። ኣት: - “ለመሪ ሁሉ”

የአባቶቹ ቤቶች መሪዎች
እዚህ “ራሶች” በጣም አስፈላጊ የሆነ አካል ምሳሌ ነው ። “ቤቶች” ቤተሰቦችን ይወክላሉ ። ኣት: - “በእስራኤል የእስራኤል ነገዶች መሪዎች ናቸው” (ዘይቤያዊ እና የባህሪ ስምን : ይመልከቱ)

ከቂርያትይዓሪም
ከኢየሩሳሌም በስተ ምዕራብ 9 ማይል ያህል ርቀት ላይ የምትገኝ ትንሽ (የስሞች አተረጓጎም: ይመልከቱ)

ድንኳን ተከለ
“ድንኳን አዘጋጁ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በሆርም ልጅ በኡሪ ልጅ በባስልኤል የተሠራው የናስ መሠዊያ
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “የሆርም የኡሪ ልጅ ባስልኤል የሠራው የነሐስ መሠዊያ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን: ይመልከቱ)

የሆርም ልጅ የኡሪ ልጅ ባስልኤል
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው ። (የስሞችን አተረጓጎም: ይመልከቱ)

2 Chronicles 1:6

ወደዚያ ወጣ
“በገባዖን ኮረብታ ላይ ወጣ”

አንድ ሺህ
“1000” (ቁጥሮችን: ይመልከቱ) ጠይቅ! ምን ልሰጥህ? ይህ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: - “ከእኔ የምትፈልገውን ሁሉ ጠይቅ።”

2 Chronicles 1:8

ለዳዊት ታላቅ ቃል ኪዳናዊ ታማኝነትን አሳይተሃል
“ታማኝነት” የሚለው የረቂቅ ስም “ታማኝነት” ወይም “በታማኝነት” ተብሎ ሊገለፅ ይችላል። ኣት: “ለዳዊት እጅግ ታላቅ ፍቅርን አሳይተኃል” ወይም “ለዳዊት በጣም ታማኝ ነበርኽ” (የረቂቅ ስሞችን: ይመልከቱ)

አሁን
እዚህ “አሁን” የሚለው ቃል ወደሚቀጥለው አስፈላጊ ነጥብ ትኩረትን ለመሳብ ይጠቅማል ።

ለአባቴ ለዳዊት የገባኸው ቃል ይፈጸም
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ታደርገው ዘንድ ለአባቴ ለዳዊት ቃል የገባውን እባክህን አድርግ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን: ይመልከቱ)

እንደ ምድር ትቢያ በሆነው በብዙ ህዝብ ላይ
ይህ ምሳሌ የእስራኤላዊያንን ብዛት ያጎላል ። ኣት: - “ስፍር ቁጥር የሌላቸው ህዝብ” ወይም “እጅግ በጣም ብዙ ህዝብ” (ዘይቤያዊን: ይመልከቱ)

ጥበብንና እውቀትን ስጠኝ
እነዚህን ያልተለመዱ ረቂቅ ስሞች ለማስወገድ “ጥበብ” እና “ዕውቀት”ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ኣት ““ ጥበበኛ እንድሆን እና ብዙ ነገሮችን እንዳውቅ አድርገኝ ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን: ይመልከቱ)

በዚህ በታላቅ ሕዝብ ላይ ሊፈርድ የሚችል ማነው?
እዚህ “ፈራጅ” ማለት ገዥ ማለት ወይም መግዛት ማለት ነው ። ሰሎሞን ያለ እግዚአብሔር እርዳታ ብዙ ሰዎችን መግዛት የማይቻል መሆኑን ለመግለጽ ጥያቄን ይጠቀማል ። ኣት: - “ያለአንተ እርዳታ ስፍር ቁጥር የሌላቸውን ህዝብ ሁሉ ማንም ሊፈርድ ይችላል።” (አወያይ መጠይቅን: ይመልከቱ)

ምክንያቱም ይህ በልብህ ውስጥ ነበር
እዚህ “ልብ” ምኞትን ያመለክታል ። ኣት: - “ይህ የአንተ ፍላጎት ነበር” ወይም “አንተ የፈለከው ይህንን ነውና” (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

የሚጠሉህን ሰዎች ሕይወት አይደለም
ወይም “የሚጠሉህን ለማሸነፍ ” ወይም “ጠላቶችህን ለመግደል”

2 Chronicles 1:12

አሁን ጥበብ እና ዕውቀት እሰጥሃለሁ
እነዚህን የሚሉትን ረቂቅ ስሞች ለማስወገድ “ጥበብ” እና “ዕውቀት”ተብሎ ሊተረጎም ይችላል ። “አሁን ጥበበኛ እና ብዙ ነገሮችን እንድታውቅ አደርግሃለሁ” (የረቂቅ ስሞችን: ይመልከቱ)

ሰሎሞንም ወደ ኢየሩሳሌም መጣ
እዚህ “ሰሎሞን” የሚለው ከእርሱ ጋር ያሉትን ሁሉንም ሰዎች ይወክላል ። ደግሞም “መጣ” የሚለው “ሄ ደ” ሊባል ይችላል። ኣት “ሰሎሞንና አብረውት ያሉት ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም ሄዱ” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን እና ሂዱ እና ኑ: ይመልከቱ)

ከመገናኛው ድንኳን ፊት
“ከመገናኛ ድንኳን”

2 Chronicles 1:14

1,400 ሠረገሎች
“አንድ ሺህ አራት መቶ ሰረገሎች” (ቁጥሮችን: ይመልከቱ)

አሥራ ሁለት ሺህ ፈረሰኞች
“12,000 ፈረሰኞች” (ቁጥሮችን: ይመልከቱ)

በሰረገሎች ከተሞች ውስጥ
ይህ ሰረገሎቹን ያከማቹትን ከተሞች የሚያሳይ ነው ።

ንጉሡም ብሩንና ወርቁን በኢየሩሳሌም እንደ ድንጋይ እንዲበዛ አደረገው
ተራኪው በኢየሩሳሌም ውስጥ የነበረውን ከፍተኛ ብር ለማጉላት የተጋነነ ትረካ ይጠቀማል ። ኣት: - “ንጉሡ በኢየሩሳሌም እጅግ ብዙ ብር ነበረው ፣ ብሩ በምድር ላይ እንዳለ ድንጋይ ብዙ ነበር” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከል እና አጠቃላይን: ይመልከቱ)

የሾላ ዛፎች
ይህ በለስ የሚመስል ፍሬ የሚያፈራ ዛፍ ነው። (የማይታወቁትን ይተርጉሙ)

ለሰሎሞን ፈረሶችን ከግብጽና ከቀዌ ስለማስመጣትን
“ማስመጣት” አንድን ነገር ከሌላ ሀገር ወደ አንድ ነገር የማምጣት ተግባር ነው። ይህ እንደ ግስ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ሰሎሞን ፈረሶቹን ከግብጽና ከቀዌ ያስመጣ ነበር” (የረቂቅ ስሞችን: ይመልከቱ)

ቀዌ
ይህ የክልል ስም ነው ። አንዳንዶች ቀዌን በትንሹ እስያ ውስጥ ከሚገኘው ከኪልቅያ ጋር አንድ ነው ብለው ያስባሉ ። (የስሞችን አተረጓጎም: ይመልከቱ)

በዋጋ
“በተቆረጠለት ዋጋ” ወይም “በገንዘብ”

ስድስት መቶ ሰቅል ብር... **150** ሰቅል
አንድ ሰቅል ከ 11 ግራም ጋር እኩል የሆነ የክብደት መለኪያ ነው። ኣት: - “6.6 ኪሎ ግራም ገደማ ብር... ወደ 1.7 ኪሎ ግራም” (መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክብደትን: ይመልከቱ)

ስድስት መቶ
“600” (ቁጥሮችን: ይመልከቱ)

ተልኳል
አንድን ነገር ከአንዱ አገር ወደ ሌላ ሀገር መላክ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 በዚህ ጊዜ ሰለሞን ለእግዚአብሔር ስም ቤት እንዲገነባ እና ለመንግሥቱ ቤተ መንግሥት እንዲገነባ አዘዘ። **2** ጭነት የሚሸከሙ ሰባ ሺህ ሰዎች እና ከተራሮች እንጨት የሚቆርጡትን ሰማንያ ሺህ ሰዎች እነርሱንም የሚቆጣጠሩ ሦስት ሺህ ስድስት መቶ ሰዎች መደበ። **3** ሰለሞንም ወደ ጢሮስ ንጉሥ ወደ ኪራም ፦የሚኖርበትን ቤት እንዲሠራ የዝግባ እንጨት በመላክ ከአባቴ ከዳዊት ጋር እንዳደረግህ ለእኔም እንደዚሁ አድርግልኝ። **4** እነሆ በእግዚአብሔር ፊት የጣፋጩን ቅመም ሽታ ለማጠን፥ የመገኘቱን ኅብስት ዘወትር ለማኖር፥ በጠዋትና በማታ፥ በሰንበታቱም ፥ በመባቻዎቹና ለአምላካችን ለእግዚአብሔር በተመደቡት ልዩ በዓላት የሚቃጠለውን መሥዋዕት ለማቅረብ ለአምላኬ ለእግዚአብሔር ስም ቤት ልገነባና ልቀድሰው ነው። ይህ ለእስራኤል ለሁልጊዜ ሕግ ነው። **5** አምላካችን ከአማልክት ሁሉ በላይ ታላቅ ስለሆነ የምሠራው ቤት እጅግ ታላቅ ይሆናል። **6** ነገር ግን መላው አጽናፈ ዓለምና ሰማይ ራሱ ሳይቀር ሊይዘው ለማይችለው ለእርሱ ለእግዚአብሔር ቤት ይሠራ ዘንድ የሚችል ማን ነው? በፊቱ መሥዋዕት ከማቅረብ በስተቀር ለእርሱ ቤት እሰራ ዘንድ እኔ ማን ነኝ? **7** በመሆኑም በወርቅ፥ በብር፥ በናስ፥ በብረት፥ እንዲሁም ሐምራዊውን፥ ቀዩን፥ ሰማያዊውን ግምጃ በመሥራት የተካነ ሰው፥ የእንጨት ቅርጻ ቅርጽ ዓይነቶችን ሁሉ መሥራት የሚያውቅ ሰው ላክልኝ። እርሱም አባቴ ዳዊት ካዘጋጃቸው በእኔ ዘንድ በይሁዳና በኢየሩሳሌም ካሉት የተካኑ ሰዎች ጋር ይሆናል። **8** አገልጋዮችህ እንጨት ከሊባኖስ መቁረጥ እንደሚያውቁ ስለማውቅ ከሊባኖስ የዝግባ እንጨቶች፥ የጥድ እንጨቶች፥ የሰንደልም እንጨቶች ላክልኝ። እነሆ ባሪያዎችህ ከባሪያዎቼ ጋር ይሆናሉ። **9** ልሠራ ያሰብኩት ቤት ታላቅና ድንቅ ይሆናልና የተትረፈረፈ ሳንቃ እንጨት እንዲያዘጋጁልኝ ነው። **10** እነሆ እንጨቱን ለሚቆርጡ ሰዎች ሀያ ሺህ የቆሮስ መስፈሪያ የተፈጨ ስንዴ፥ ሀያ ሺህ የቆሮስ መስፈሪያ ገብስ፥ ሀያ ሺህ የባዶስ መስፈሪያ የወይን ጠጅ፥ ሀያ ሺህ የባዶስ መስፈሪያ ዘይት ለባሪያዎችህ እሰጣለሁ። **11** ንጉሥ ኪራም፦ እግዚአብሔር ሕዝቡን ስለሚወዳቸው በላያቸው አንግሦሃል ብሎ መልሶ ወደ ሰለሞን መልእክት ላከ። **12** በተጨማሪም ኪራም፦ ሰማይንን ምድርን የፈጠረ፥ ለእግዚአብሔር ቤት እና ለመንግሥቱ ቤት የሚሠራ ጥበበኛና ብልሃተኛ አስተዋይም ልጅ ለንጉሡ ለዳዊት የሰጠ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን አለ። **13** አሁንም ማስተዋል የተሰጠውን የተካነውን ባለሙያዬን ሁራምን ልኬልሃለሁ። **14** ከዳን ሴት ልጆች የአንዲቱ ልጅ ነው። አባቱ የጢሮስ ሰው ነበር። ወርቁን፥ ብሩን፥ ናሱን፥ ብረቱን፥ ድንጋዩን እንዲሁም እንጨቱን፥ ሐምራዊውን፥ ሰማያዊንና ቀዩን ግምጃ ጥሩ በፍታውንም በመሥራት የተካነ ነው። የትኛውንም ዓይነት ቅርጽ በመሥራት እና የትኛውንም ዓይነት ንድፍ በማውጣትም የተካነ ነው። በተካኑት ሠራተኞችህ መካከል እና ከጌታዬ ከአባትህ ከዳዊት ብልሃተኞች ጋር ይሆን ዘንድ ስፍራ ይዘጋጅለት። **15** አሁንም ጌታዬ የተናገረውን ስንዴውንና ገብሱን ዘይቱንና የወይን ጠጁን እነዚህን ነገሮች ወደ አገልጋዮቹ ይላክ። **16** እኛም የሚያስፈልግህን ያህል እንጨት ከሊባኖስ እንጨት እንቆርጣለን። እንደ ታንኳ በባሕር ላይ ወደ ኢዮጴ እንወስድልሃለን፤ አንተም እስከ ኢየሩሳሌም ድረስ ታጓጉዘዋለህ። **17** ሰለሞንም ኣባቱ ዳዊት በእስራኤል ምድር የነበሩትን የውጪ አገር ዜጎች ሁሉ እንደቆጠረ እርሱ ያደረገበትን ዘዴ ተከትሎ ቆጠራቸው። እነርሱም አንድ መቶ ሃምሳ ሦስት ሺህ ስድስት መቶ ሆነው ተገኙ። **18** ሰባ ሺህው ጭነት እንዲሸከሙ ሰማንያ ሺህው በተራሮችም ላይ እንጨት እንዲቆርጡ እና ሦስት ሺህ ስድስት መቶው ደግሞ ሕዝቡን ለሥራ የሚያሰማሩ ተቆጣጣሪዎች እንዲሆኑ መደባቸው።

---

2 Chronicles 2:1

አሁን
ይህ የታሪኩን አዲስ ክፍል ያመለክታል።

ለእግዚአብሔር ስም ቤት እንዲሠራ አዘዘ
“ስም” የሚለው ቃል የግለሰቡ ስም ነው። አት: - “ያህዌ የሚኖርበትን ቤት እንዲሠሩ ህዝቡን አዘዘ” ወይም “ህዝቡ እግዚአብሔርን የሚያመልኩበትን ቤት እንዲሠሩ አዘዘ” (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

ለመንግሥቱ ቤተ መንግሥት
“ለመንግሥቱ የንጉሣዊው ቤተ መንግሥት” ወይም “ለራሱ ቤተ መንግሥት”

ሰባ ሺህ ሰዎች ... ሰማንያ ሺህ ወንዶች
“70,000 ወንዶች... 80,000 ወንዶች” (ቁጥሮችን: ይመልከቱ)

ሸክሞችን ለመሸከም
እነዚህ የያህዌን ቤት ለመገንባት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ብዛት ያላቸው እንደሆኑ ይታወቃል ። አት: - “ብዙ ቁሳቁሶችን ለመሸከም” (የቃላት ግድፈትን: ይመልከቱ)

3,600
“ሦስት ሺህ ስድስት መቶ” (ቁጥሮችን: ይመልከቱ)

ኪራም
ይህ የሰው ስም ነው ። (የስሞችን አተረጓጎም: ይመልከቱ)

2 Chronicles 2:4

እኔ ለአምላኬ ለእግዚአብሔር ስም ቤት እሠራለሁ
እዚህ “ስም” ግለሰቡን ይወክላል። በ 2 ኛ ዜና 2 :1 ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጉሙ ይመልከቱ ። AT: - “አምላኬ እግዚአብሔር የሚኖርበት ቤት እሠራለሁ” ወይም “ሰዎች አምላኬ እግዚአብሔርን የሚያመልኩበትን ቤት እሠራለሁ” (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

እኔ ልሰራ ነው
ሰሎሞን ህዝቡን ቤቱን እንዲሠሩ ያዛል ። ኣት: - “ሕዝቤ እንዲሠሩ ላዝ ነው” (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

የገጸንም ኀብስት
ይህ በመሠዊያው ፊት ለፊት ስለተቀመጡት 12 ዳቦዎች የሚያሳይ ነው ።

በመባቻዎቹም
ይህ ጊዜ ከጨረቃ እንቅስቃሴ ጋር የሚጣጣም የበዓል ጊዜ ነበር ።

ይህ ለእስራኤል የዘላለም ሥርዓት ነው
እዚህ “ይህ” የሚያመለክተው ህዝቡ ያህዌህን በቤተ መቅደሱ የሚያመለኩበትን መንገዶች ሁሉ ነው ። ኣት: - “እነዚህ እግዚአብሔር እስራኤልን ለዘላለም እንዲያደርግ ያዘዘው ነገሮች ናቸው”

እግዚአብሔር ይበልጣል
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ከሌሎች አማልክት ትልቅ መሆኑን ሳይሆን ከሌሎች አማልክት የበለጠ አስፈላጊ እና ኃያል መሆኑን ነው ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Chronicles 2:6

አጽናፈ ሰማይም ሆነ ሰማይ እርሱን ሊይዘው አይችልምና ለእግዚአብሔር ቤት ሊሠራለት ማን ይችላል? በፊቱ ቅዱስ ቁርባንን ከማቃጠል በቀር እኔ ቤት እሠራለት ዘንድ ኤኔ ማን ነኝ?
ሰሎሞን ማንም ሰው ለእግዚአብሔር ቤት ለመሥራት ብቁ አለመሆኑን ለማጉላት አወያይ መጠይቅን ተጠሟል ። አት: - “አጽናፈ ሰማይም ሆነ ሰማይ እንኳ እሱን ለመያዝ የሚያስችል አቅም ስለሌለው ማንም ሰው ቤት ሊሠራለጽ አይችልም። መስዋዕት የሚቀርብበት ቦታ ካልሆነ በስተቀር ለእርሱ ቤት ለመሥራት ብቁ አይደለሁም ። (አወያይ መጠይቅን: ይመልከቱ)

2 Chronicles 2:8

አገናኝ መግለጫ :
ይህ የሰሎሞንን መልእክት ለጢሮስ ንጉሥ ለኪራም ይቀጥላል ።

የዝግባና የጥድ የሰንደልም ዛፎች
እነዚህ የተለያዩ የዛፍ ዓይነቶች ናቸው ። (የማይታወቁትን ይተርጉሙ: ይመልከቱ)

ሃያ ሺህ ቆሮስ
አንድ ቆሮስ 220 ሊትር ነው። ሃያ ሺህ ቆሮስ 4,400 ኪ.ሊትር ጋር እኩል ነው. (መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይዘትን: ይመልከቱ)

ሃያ ሺ
“20,000” (ቁጥሮችን: ይመልከቱ)

የመሬት ስንዴ
“ስንዴ” የእኛ

ሀያ ሺህ መታጠቢያ ገንዳ
የመታጠቢያ ገንዳ 22 ሊትር ነው ። ሃያ ሺህ የባዶስ መታጠቢያዎች ከ 440 ኪሎሊትር ጋር እኩል ናቸው። (መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይዘትን: ይመልከቱ)

2 Chronicles 2:11

ጥበበኛና ብልሃተኛ አስተዋይም
ይህ የነገሮች ስሞችን “ብልህነት” እና “ማስተዋልን” ለማስቀረት እንደገና ሊገለፅ ይችላል ። “AT” “በጣም ብልህ እና ብዙ ነገሮችን የሚረዳ” (የረቂቅ ስሞችን: ይመልከቱ)

2 Chronicles 2:13

የማስተዋል ተሰጥኦ ያለው
የነገሮች ስም የሆነው “ማስተዋል” የሚለው ቃል “ተረድቷል” ወይም “ጠቢብ” ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። AT: “ብዙ ነገሮችን የሚረዱ” ወይም “በጣም ጥበበኛ”(የረቂቅ ስሞችን: ይመልከቱ)

ኪራምአቢ
ይህ የሰው ስም ነው ። (የስሞችን አተረጓጎም: ይመልከቱ)

እርሱ በወርቅ ሥራ የተካነ ነው ... በደማቅ ሱፍ
በ 2 ኛ ዜና ምዕራፍ 2 ቁጥር 7 እንደተረጎሙት ከነዚህ ብዙዎቹን ቃላቶች ይተርጉሙ ።

ጥሩ በፍታ
“ከፍተኛ ጥራት ያለው ጨርቅ” ወይም “ምርጥ ጨርቅ”

እርሱ የዳን ሴት ልጆች ልጅ ነው
“እናቱ ከዳን ነገድ ናት” ወይም “እናቱ ከዳን ወገን ናት”

2 Chronicles 2:15

አገናኝ መግለጫ :
ይህ ከጢሮስ ንጉሥ ከኪራም ለሰሎሞን የሚናገረውን መልእክት ይቀጥላል ።

ጌታዬ የተናገረውን እነዚህን ነገሮች ወደ ባሪያዎቹ ይላከው
ኪራም ሰለሞንን “ጌታዬ” ፣ ራሱንና ፣ የራሱን ሕዝብ “አገልጋዮቹ” ሲል ጠርቶታል። ይህ አክብሮት ማሳያ መንገድ ነው። ኣት: - “ጌታዬ አንተ የተናገርከውን እባክህን እነዚህን ነገሮች ለባሪያዎችህ ላክ” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሦስተኛ መደብ ሰብኣዊን: ይመልከቱ)

ወደ ኢየሩሳሌም ትወስደዋለህ
እዚህ “አንተ” የሚለው ሰሎሞንን ያመለክታል። ሰሎሞን ምናልባት ሌሎች ሰዎች ዋናውን ሥራ እንዲሠሩ እንዳዘዘ አንባቢዎቹ ሊገነዘቡ ይገባል ። ኣት: - “አንተ ሰዎችህን እንጨቱን ወደ ኢየሩሳሌም እንዲወስዱ ታዛቸዋለህ” (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

ሰለሞን ቆጠረ
ሰሎሞን ምናልባት ሌሎች ሰዎች ሥራውን እንዲሰሩ እንዳዘዘ አንባቢዎቹ ሊገነዘቡት ይገባል ። ኣት: - “ሰሎሞን አገልጋዮቹ እንዲቆጠሩ አድርጎአቸው ነበር” (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

እነሱ **153,600** ሆነው ተገኙ
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “153,600 መጻተኞች ነበሩ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን እና ቁጥሮችን: ይመልከቱ)

153,600
“መቶ አምሳ ሦስት ሺህ ስድስት መቶ” (ቁጥሮችን: ይመልከቱ)

ሰባ ሺህ ... ሰማንያ ሺህ
“70,000 ወንዶች... 80,000 ወንዶች” (ቁጥሮችን: ይመልከቱ)

ሸክሞችን ለመሸከም
እነዚህ የያህዌን ቤት ለመገንባት የሚያስፈልጉ በርካታ ቁሳቁሶች እንደሆኑ ይታወቃል ። አት: - “በርካታ ቁሳቁሶችን ለመሸከም” (ግድፈተ ቃልን: ይመልከቱ)

3,600
“ሦስት ሺህ ስድስት መቶ” (ቁጥሮችን: ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 ከዚህ በኋላ ሰለሞን እግዚአብሔር ለአባቱ ለዳዊት በተገለጠለት በሞሪያ ተራራ ላይ በኢየሩሳሌም የእግዚአብሔር ቤት መሥራት ጀመረ። ዳዊት እንዳቀደለት በኢያቡሳዊው በኦርና አውድማ ሥፍራውን አዘጋጀ። **2** በነገሠ በአራተኛው ዓመት በሁለተኛው ወር በሁለተኛው ቀን መሥራት ጀመረ። **3** ሰለሞንም ለእግዚአብሔር ቤት የጣለው መሠረት ስፍሮች እነዚህ ናቸው። ርዝመቱ በድሮው መለኪያ ስልሳ ክንድ ወርዱም ሃያ ክንድ ነበር። **4** በቤቱም ፊት የነበረው በረንዳ ርዝመቱ ከቤቱ ወርድ ተመሳሳይ ሆኖ ሃያ ክንድ ነበር። ቁመቱም ሃያ ክንድ ነበረ። ሰለሞንም ውስጡን በንጹህ ወርቅ ለበጠው። **5** የዋናውን ቤት ጣሪያ በጥድ እንጨት ሠራው። በንጹህ ወርቅም ለበጠው። የዘንባባ ዛፎችንና የሰንሰለቶችን አምሳል ቀረጸበት። **6** ቤቱንም በከበሩ ድንጋዮች አስጌጠው፤ ወርቁም የምሥራቅ ፈርዋይም ወርቅ ነበር። **7** አውታሮቹን፥ ሰረገሎቹን፥ ግድግዳዎቹንና በሮቹንም በወርቅ ለበጣቸው። በግድግዳዎቹም ላይ ኪሩቤልን ቀረፀ። **8** ቅድስተ ቅዱሳኑንም ሠራ፤ ርዝመቱም ከቤቱ ወርድ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ሃያ ክንድ ነበር፤ ወርዱም ሃያ ክንድ ነበር። ስድስት መቶ መክሊት በሚያህል በጥሩ ወርቅም ለበጠው። **9** የሚስማሮቹም ክብደት ሃምሳ ሰቅል ወርቅ ነበር። ከፍ ያሉ ገጽታዎቹን/ሰሌዳዎቹን በወርቅ ለበጣቸው። **10** ለቅድስተ ቅዱሳን ሁለት የኪሩቤል አምሳያዎችን ሠራ፤ ባለሙያዎችም በወርቅ ለበጡዋቸው። **11** ክንፎቹ በአጠቃላይ ከዳር እስከ ዳር ሃያ ክንድ ይረዝሙ ነበር። የአንዱ ኪሩብ ክንፍ ክፍሉ ግድግዳ ድረስ የሚደርስ አምስት ክንድ ይረዝም ነበር፤ ሌላኛው ክንፍ እንደዚሁ እስከ ሌላኛው ኪሩብ ክንፍ ድረስ የሚደርስ አምስት ክንድ ነበር። **12** የሌላኛው ኪሩብ ክንፍም ክፍሉ ግድግዳ ድረስ የሚደርስ አምስት ክንድ ይረዝም ነበር፤ ሌላኛው ክንፉም እንደዚሁ የመጀመሪያውን ኪሩብ ክንፍ የሚነካ አምስት ክንድ ነበር። **13** የእነዚህም ኪሩቤሎች ክንፎች በአጠቃላይ ሃያ ክንድ ያህል ተዘርግተው ነበር። ኪሩቤልም ፊቶቻቸው ወደ ዋናው ቤት እየተመለከቱ በእግሮቻቸው ቆመው ነበር። **14** ከሰማያዊም፥ ከሐምራዊም፥ ከቀዩም፥ ሐር እና ከጥሩ በፍታ መጋረጃውን ሠራ፤ የኪሩቤሎችንም ቅርፅ ሠራባቸው። **15** ሰለሞንም ለቤቱ ፊት ለፊት እያንዳንዳቸው ሠላሳ አምስት ክንድ ከፍታ ያላቸውን ሁለት ምሰሶዎች ሠራ። በእያንዳንዳቸውም ጫፍ ላይ የነበሩት ርዕሰ አእማድ አምስት ክንድ ከፍታ ያላቸው ነበሩ። **16** ለምሰሶዎቹም ሰንሰለቶችን አድርጎ በጫፋቸው ላይ አኖራቸው። መቶም ሮማኖች ሠርቶ ከሰንሰለቶቹ ጋር አገናኛቸው። **17** ምሰሶዎቹንም በቤት መቅደሱ ፊት ለፊት አንደኛውን በቀኝ ሌላኛውንም በግራ አቆማቸው፤ በስተቀኝ የነበረውን ምሰሶ የሚያቆም/ያኪን፥ የበስተግራውንም ምሰሶ የሚያበረታ/ቦኤዝ ብሎ ሰየመው።

---

2 Chronicles 3:1

ሰሎሞንም መሥራት ጀመረ . . . አዘጋጀ . . . ጀመረ . . ..ሰሎሞን ጣለ **(**መሠረት**)**
ሰሎሞን ሌሎች ሰዎች ሥራውን እንዲሰሩ እንዳሰማራ አንባቢዎቹ ሊገነዘቡት ይገባል። አት: - “የሰሎሞን ሠራተኞች መሥራት ጀመሩ... አዘጋጁ ፣...ጀመሩ . . . የሰሎሞን ሠራተኞች (መሠረት) ጣሉ“ (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

የሞሪያ ተራራ
ይህ የተራራ ስም ነው ። (የስሞችን አተረጓጎም: ይመልከቱ)

ኢያቡሳዊው ኦርና
“ኦርና” የሰው ስም ነው። “ኢያቡሳዊ” የቡድን ስም ነው ። (የስሞችን አተረጓጎም: ይመልከቱ)

በሁለተኛው ወር በሁለተኛ ቀን
“የ2ተኛ ወር 2ተኛ ቀን” ይህ በዕብራዊያን የቀን መቁጠሪያ ሁለተኛ ወር ነው። ሁለተኛው ቀን እንደ አውሮጳዊያን የቀን መቁጠሪያ ከሚያዝያ አጋማሽ ጋር ተቀራራቢ ነው። (የዕብራዊያን ወራት እና ሕገኛ ቁጥርን: ይመልከቱ)

በአራተኛው ዓመት
“በ 4ተኛው ዓመት” (ሕገኛ ቁጥርን: ይመልከቱ)

አሁን
በዋናው የታሪክ መስመር ውስጥ መቋረጥን ለማመልከት ይህ ቃል እዚህ ጥቅም ላይ ውሏል ። እዚህ ላይ ተራኪው ስለ መቅደሱ መጠን እና ዲዛይን ማስረዳት ይጀምራል ።

ስድሳ ክንድ ... ሀያ ክንድ
“60 ክንድ... 20 ክንድ።” አንድ ክንድ 46 ሴንቲሜትር ነው ። አት: - “27.6 ሜትር ርዝመት... 9.2 ሜትር” (ቁጥሮችን እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ርቀትን: ይመልከቱ)

2 Chronicles 3:4

ወለል
ከህንፃው የመግቢያ በር ጋር የሚያገናኝ እና የሚያገናኝ ጣሪያ እና አምድ ያለው የሕንፃ ክፍል ነው። ይህ ወለል ቤተ መቅደሱን ከከበበው ግድግዳ የፊት ክፍል ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል።

ሀያ ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሴንቲሜትር ነው ። አት: - “9.2 ሜትር” (መጽሐፍ ቅዱሳዊ ርቀትን: ይመልከቱ)

ሰሎሞን ለበጠው ... ቀረጸው ... አስጌጠው
ሰሎሞን ሥራውን የሚሰሩ ሰዎች አሰማርቶ እንደነበረ አንባቢዎች ሊገነዘቡ ይገባል ። አት: - “የሰለሞን ሠራተኞች ለበጡት የቀረጹትንም...አስጌጡት"

ዋናው አዳራሽ
ይህ የሚያመለክተው አዳራሻ ሳይሆን ሰፋ ያለ ክፍል ነው ።

2 Chronicles 3:6

አስጌጠ ... እርሱ ለበጠ... ቀረጸ
ሰሎሞን ሥራውን የሚሰሩ ሰዎች አሰማርቶ እንደነበረ አንባቢዎች ሊገነዘቡ ይገባል ። አት: - “የሰለሞን ሠራተኞች ለበጡት የቀረጹትንም...አስጌጡት" (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

የከበሩ ድንጋዮች
ውብ የሆኑ ፣ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው፣ እና ለጌጣጌጥ የሚያገለግሉ ድንጋዮች።

የፈርዋይም
ይህ ምናልባት የክልል ስም ሳይሆን አይቀርም። (የስሞችን አተረጓጎም: ይመልከቱ)

ሰረገሎች
ሰረገላ አንድን ሕንፃ ለመገንባት የሚያገለግል ረዥም ከባድ እንጨት ነው ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Chronicles 3:8

የገነባው... ለበጠው
ሰሎሞን ሥራውን የሚሰሩ ሰዎች አሰማርቶ እንደነበረ አንባቢዎች ሊገነዘቡ ይገባል ። አት: - “የሰለሞን ሠራተኞች ገነቡ....ለበጡትም

ሀያ ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሴንቲሜትር ነው ። አት: - “9.2 ሜትር” (መጽሐፍ ቅዱሳዊ ርቀትን: ይመልከቱ)

ስድስት መቶ መክሊት
“600 መክሊት” አንድ መክሊት 33 ኪሎግራም ነው። አት: - “ወደ 20 ሜትሪክ ቶን” (ቁጥሮችን እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ገንዘብን: ይመልከቱ)

አምሳ ሰቅል
“50 ሰቅል።” አንድ ሰቅል 11 ግራም ነው። አት: - “55 ኪሎግራም” ወይም “ግማሽ ኪሎግራም ያህላል” (ቁጥሮችን እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ገንዘብን: ይመልከቱ)

2 Chronicles 3:10

ሠራ
ሰሎሞን ሥራውን የሚሰሩ ሰዎች አሰማርቶ እንደነበረ አንባቢዎች ሊገነዘቡ ይገባል ። አት: - “የሰሎሞን ሠራተኞች ሠሩ” (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

ሀያ ክንድ... አምስት ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሴንቲሜትር ነው ። አት: - “9.2 ሜትር... 2.3 ሜትር” (መጽሐፍ ቅዱሳዊ ርቀትን: ይመልከቱ)

2 Chronicles 3:13

ሀያ ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሴንቲሜትር ነው ። አት: - “9.2 ሜትር” (መጽሐፍ ቅዱሳዊ እርቀትን:ይመልከቱ)

እሱ ሠራ... አስጌጠው
ሰሎሞን ሥራውን የሚሰሩ ሰዎች አሰማርቶ እንደነበረ አንባቢዎች ሊገነዘቡ ይገባል። አት: - “የሰለሞን ሠራተኞች ሠሩ.....አስጌጡት (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

ሰማያዊ ፣ ሐምራዊና ደማቅ ቀይ ሐር
እነዚህን ቃላት በ 2 ኛ ዜና ምዕራፍ 2 ቁጥር 7 እንደተቶረገመው ይተርጉሙ ።

ጥሩ በፍታ
“ከፍተኛ ጥራት ያለው ጨርቅ” ወይም “ምርጥ ጨርቅ”

ሰለሞንም እንዲሁ ሠራ ... ሠራ ... እርሱ እንዲሁ ሠራው ... አከናወነ
ሰሎሞን ሥራውን የሚሰሩ ሰዎች አሰማርቶ እንደነበረ አንባቢዎች ሊገነዘቡ ይገባል። አት: - “የሰሎሞን ሠራተኞች እንዲሁ ሠሩ... ሠሩም... እንዲሁ ሠሩ... አከናወኑ”

ሠላሳ ስምንት ክንድ... አምስት ክንድ
“35 ክንድ... 5 ክንድ።” አንድ ክንድ 46 ሴንቲሜትር ነው ። አት: - “16.1 ሜትር... 2.3 ሜትር” (ቁጥሮችን እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ እርቀትን: ይመልከቱ)

ጉልላቶች
በአዕማዶቹ አናት ላይ ያሉ ማስጌጫዎች

አንድ መቶ ሮማኖች
“100 ሮማኖች” (ቁጥሮችን: ይመልከቱ)

በቀኝ እጅ በኩል... በግራ እጅ በኩል
“በቀኝ በኩል... በግራ በኩል” ወይም “በደቡብ በኩል... በሰሜን በኩል”

ብሎ ጠራቸው
“ሰሎሞን ሰየማቸው”

ያቁም
እግዚአብሔርን “አጽኚ” እንደሆነ የሚገልጽ ስም ነው ። (የስሞችን አተረጓጎም: ይመልከቱ) በለዝ ይህ ስም “በብርቱ” ማለት ሲሆን እዚህ ላይ እግዚአብሔርን ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሏል። ምክንያቱም “በእርሱ ውስጥ ብርታት አለ” ማለት ነው ። (የስሞችን አተረጓጎም: ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 በተጨማሪም የናሱን መሠዊያ ሠራ፤ ርዝመቱ ሃያ ክንድ ነበር፤ ወርዱም ሃያ ክንድ ነበር፤ ቁመቱም አሥር ክንድ ነበር። 2 ክፈፉ ከጫፍ እስከ ጫፉ አሥር ክንድ የሆነ ከቀለጠ ብረት ትልቅ ክብ ውሃ መያዣ ኩሬም ሠራ። ቁመቱም አምስት ክንድ ነበር፤ ዙሪያውም ሰላሳ ክንድ ነበር። 3 ውሃ መያዣው ቀልጦ ሲሰራ ከአርሱ ጋር አብረው የተሠሩ ከውሃ መያዣው ዙሪያ ከክፈፉ በታች በእያንዳንዱ ክንድ ርቀት አሥር ኮርማዎች ነበሩበት። 4 ውሃ መያዣው ሦስቱ ወደ ሰሜን በሚመለከቱ፥ ሦስቱ ወደ ምዕራብ በሚመለከቱ፥ ሦስቱ ወደ ደቡብ በሚመለከቱ፥ ሦስቱ ወደ ምሥራቅ በሚመለከቱ በአሥራ ሁለት በሬዎች ላይ ተቀምጦ ነበር። ውሃ መያዣው በላያቸው ላይ ሆኖ የጀርባ የሠውነት ክፍላቸው በስተ ውስጥ ነበር። 5 ውፍረቱም አንድ ጋት ያህል ነበር። የአፉ ክፈፍም እንደ ጽዋ ከንፈር እንደ ፈነዳ የሱፍ አበባ ሆኖ ተሠርቶ ነበር። ሦስት ሺህም የባዶስ መስፈሪያ ውሃ ይይዝ ነበር። 6 ደግሞም የተለያዩ ነገሮችን ማጠቢያ አሥር ጎድጓዳ ሳህኖች ሠራ፤ አምስቱን በስተግራ አምስቱንም በስተቀኝ አኖራቸው፤ የሚቃጠለውም መሥዋዕት ለማቅረብ ጥቅም የሚሰጡ ነገሮች በውስጣቸው ይታጠቡባቸው ነበር። የውሃ መያዣው ኩሬ ግን ለካህናቱ መታጠቢያ ነበር። 7 ለንድፋቸው በተሰጠው መመሪያ መሠረት አሥሩን የወርቅ መቅረዞች ሠራ፤ በቤተ መቅደሱ ውስጥ አምስቱን በስተግራ አምስቱን በስተቀኝ አኖራቸው። 8 አሥሩንም ገበታዎች ሠርቶ በቤተ መቅደሱ ውስጥ አምስቱን በስተግራ አምስቱን በስተቀኝ አኖራቸው። አንድ መቶ የወርቅ ጎድጓዳ ሳህኖች ሠራ። 9 በተጨማሪም የካህናቱን አደባባይ እና ታላቁንም አደባባይ የአደባባዮቹንም በሮች ሠራ፤ በሮቻቸውንም በናስ ለበጠ። 10 የውሃ መያዣውንም ኩሬ በቤቱ በስተቀኝ በስተምስራቅ ፊቱን ወደ ደቡብ አዙሮ አኖረው። 11 ኪራምም ምንቸቶቹን፥ መጫሪያዎቹንና መሠዊያውን መርጨያ ጎድጓዳ ሳህኖች ሠራ። ኪራምም እንደዚህ ለንጉሥ ሰለሞን በእግዚአብሔር ቤት የሠራውን ሥራ ሁሉ - 12 ሁለቱን አዕማድ፥ በሁለቱ አዕማድ ጫፍ ላይ የነበሩትን ጉልላቶች፥ በሁለቱ አዕማድ ጫፍ ላይ የነበሩትን ጉልላቶች የሚሸፍኑትን ሁለቱን ጌጠኛ ቅርፃ ቅርፆች ጨረሰ። 13 በአዕማዱ ጫፍ ላይ የነበሩትን ጉልላቶች ለሚሸፍኑት ሁለቱ ጌጠኛ ቅርፃ ቅርፆች ለእያንዳንዳቸው ሁለት ተርታ ሮማኖች አድርጎ ለሁለቱ ጌጠኛ ቅርፃ ቅርፆች አራት መቶ ሮማኖች ሠራ። 14 ማቆሚያዎቹንና በማቆሚያዎቹ ላይ የሚቀመጡትን የመታጠቢያ ሰሃኖችንም ሠራ፤ 15 አንድ የውሃ መያዣ ኩሬ እና ከስሩ የሚሆኑትን አስራ ሁለት ኮርማዎች፥ 16 እንዲሁም ምንቸቶቹን፥ መጫሪያዎቹን፥ ሜንጦዎቹን እና ሌሎች አገልግሎት ሰጪ ቁሳቁሶችን ሁሉ ሠራ፤ ኪራም ለንጉሥ ሰለሞን ለእግዚአብሔር ቤት ከአንፀባራቂ ናስ ሠራቸው። 17 ንጉሡም በዮርዳኖስ ሜዳ በሱኮትና ዛሬታን መካከል በሸክላው መሬት ውስጥ ብረታ ብረቱ እንዲቀልጥ አስደረገ። 18 ሰለሞንም እነዚህን እቃዎች ሁሉ በብዛት እንዲሰሩ አስደረገ፤ በእርግጥም የናሱ ክብደት ሊታወቅ አይችልም ነበር። 19 ሰለሞን በእግዚአብሔር ቤት የነበሩትን የቤት ዕቃዎች፥ የወርቁን መሠዊያ፥ የመገኘቱ ሕብስት የሚቀመጥባቸውን ገበታዎች፥ 20 በቅድስተ ቅዱሳን ፊት ያበሩ ዘንድ የታቀዱትን መቅረዞችን ከቀንዲሎቹ ጋር ሠራ።እነዚህ ከንጹሕ ወርቅ የተሰሩ ነበሩ። 21 አበባዎቹም፥ ቀንዲሎቹና መኮስተሪያዎቹም የጥሩ ወርቅ ነበሩ። 22 ጉጠቶቹም፥ ጎድጓዳ ሳህኖቹም፥ ማንኪያዎቹም ፥ እጣን ማጨሻዎቹም ሁሉ ከንጹህ ወርቅ የተሰሩ ነበሩ። ወደ ቤቱ ውስጥ መግቢያዎቹን በተመለከተ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የሚያስገቡት የውስጥ በሮች እና የቤቱ ማለትም የቤተ መቅደሱ በሮች ከወርቅ የተሠሩ ነበሩ።

---

2 Chronicles 4:1

ሠራ
እዚህ “እሱ” የሚያመለክተው ሰለሞንን ነው ። ሰሎሞን ሥራውን የሚሠሩ ሰዎች አሰማርቶ እንደነበረ አንባቢዎች ሊገነዘቡ ይገባል። ኣት: - “የሰሎሞን ሠራተኞች ሠሩ” (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

ሀያ ክንድ... አሥር ክንድ..... አምስት ክንድ... ሠላሳ ክንድ... እያንዳንዱ ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሴንቲሜትር ነው ። ኣት: - “9.2 ሜትር... 4.6 ሜትር... 2.3 ሜትር... 13.8 ሜትር... በየ 46 ሴንቲ ሜትር” (መጽሐፍ ቅዱሳዊ እርቀትን: ይመልከቱ)

ክብ ኩሬ ሠራ
ይህ የሚያመለክተው ውሃ የሚይዝ ማጠራቀሚያን ወይም ገንዳን ነው ።

ከዳር እስከ ዳር
ከአንዱ ጫፍ እስከ ሌላኛው ጫፍ

ከጫፍ እስከ ጫፍ
“ከአንዱ ጠርዝ ወደ ሌላው”

በዙሪያው
ዙሪያ በክብ ነገር ወይም ሥፍራ ዙሪያ ያለው ርቀት ወይም ልኬት ነው ።

ለእያንዳንዱ ክንድ አስር
“ለአንድ ክንድ አሥር”

ኩሬውም በቀለጠ ጊዜ
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ሰራተኞቹ ኩሬውም ሲያቀልጡ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን: ይመልከቱ)

2 Chronicles 4:4

ኩሬው
ይህ ለመስዋእት ውሃ የሚይዙ ገንዳ ወይም የውሃ ገንዳ ያመለክታል ።

አሥራ ሁለት በሬዎች ላይ ተቀምጦ ነበር
“በአሥራ ሁለት በሬዎች አናት ላይ ነበሩ”

አሥራ ሁለት በሬዎች
እነዚህ ከነሐስ የተሠሩ የበሬዎች ምስሎች ናቸው። ኣት: - “አሥራ ሁለት ትላልቅ የበሬዎች ምስሎች” ወይም “አሥራ ሁለት የነሐስ በሬዎች” (ታሳቢ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን: ይመልከቱ)

በላያቸው ላይ “ኩሬው” ተቀምጦ ነበር
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “የሰለሞን ሠራተኞች 'ኩሬውን' በበሬዎች አናት ላይ አኖሩት ' (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን: ይመልከቱ)

ጀርባቸው
አራት እግር ያለው እንስሳ የኋላ ሰውነት ክፍል ነው።

ውፍረቱ አንድ ጋት የሚያህል
ይህ ወደ 8 ሴንቲሜትር ያህል ነው ። (መጽሐፍ ቅዱሳዊ እርቀትን: ይመልከቱ)

ከንፈሩም እንደ ጽዋ ከንፈር፥ እንደ ሱፍ አበባ ሆኖ ተሠርቶ ነበር
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “የሰለሞን ሠራተኞች ከንፈሩን የጽዋ ከንፈር እንዲመስል ፣ ውጪውን የሱፍ አበባ አስመስለው ቀርጸውት ነበር” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን: ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሦስት ሺህ ባዶስ
“3,000 ባዶስ።” ባዶስ ከ 22 ሊትር ጋር እኩል የሆነ የይዘት አሃድ ነው። ኣት: - “66 ኪሎሊትሮች” (ቁጥሮችን እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ እርቀትን: ይመልከቱ)

እርሱ ሠራ... እርሱ አኖረ
እዚህ ላይ “እርሱ” ሰለሞንን ያመለክታል ። ሰሎሞን ሌሎች ሰዎችን ሥራውን እንዲሠሩ እንዳሰማራ አንባቢዎች ሊገነዘቡ ይገባል ። ኣት: - “የሰለሞን ሠራተኞች ሠሩ... አኖሩ” (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

የሚቃጠለውን መባ ለመፈፀም የሚያገለግሉ ዕቃዎች በእነሱ ውስጥ መታጠብ አለባቸው
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ሰዎች በእነሱ ውስጥ የሚቃጠለውን መባ ለመፈፀም ያገለገሉ እቃዎችን ያጥቡ ነበር” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን: ይመልከቱ)

2 Chronicles 4:7

ሠራ... አኖረ... ሠራ... ሠራ
እዚህ “እሱ” ሰለሞንን ያመለክታል ። ሰለሞን ሌሎች ሰዎች ሥራውን እንዲሠሩ አሰማርቶ እንደነበረ አንባቢዎች ሊረዱ ይገባል። ኣት: - “የሰሎሞን ሠራተኞች ሠሩ... አኖሩ... ሠሩ... ሠሩ” (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

እንደ ሥርዓታቸው ተሠሩ
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “በዲዛይናቸው መሠረት” ወይም “ሰሎሞን ሠራተኞቹን እንዲቀርጿቸው ባዘዘው መሠረት”(ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን: ይመልከቱ)

በቀኝ እጅ ... በግራ
“በቀኝ በኩል... በግራ በኩል” ወይም “በደቡብ በኩል... በሰሜን በኩል”

አንድ መቶ ድስቶች
“100 ድስቶች” (ቁጥሮችን: ይመልከቱ)

ድስቶች
ለመታጠብ የሚያገለግሉ ጥልቀት ያላቸው ሳህኖች

2 Chronicles 4:9

አደባባዩን ሠራ... ደግሞም ለበጠው...አኖረ
እዚህ “እሱ” ሰለሞንን ያመለክታል ። ሰሎሞን ሌሎች ሰዎች ሥራውን እንዲሰሩ እንዳሰማራ አንባቢዎች ሊገነዘቡት ይገባል ። ኣት: - “የሰለሞን ሠራተኞች ሠሩ... ለበጡ... አኖሩ”(የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

ታላቁንም አደባባይ
“ትልቁ አደባባይ”

በቤተ መቅደሱ በስተ ምሥራቅ በኩል፣ ለበስተ ደቡብ በኩል ትይዩ ይሆናል
“ከቤተ መቅደሱ ከደቡብ ምስራቅ ጎን ቀጥሎ”

2 Chronicles 4:11

ኪራም
በ 2 ኛ ዜና ምዕራፍ 2 ቁጥር 13 ውስጥ ይህንን ስም እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ።

መርጫ ጎድጓዳ ሳህኖችን
መሠዊያውን ለመርጨት በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ደም መያዣ ሳህኖች

ኪራም የሠራውን ሥራ ጨረሰ ...
እዚህ ኪራም ቤተመቅደሱን የሰሩትን ሁሉ ይወክላል። ኣት: - “ኪራም እና ሌሎቹ ሠራተኞች የሠሩትን ሥራ ጨረሱ...።” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከል: ይመልከቱ)

ጎድጓዳ ሳህኖች ይመስላሉ ጉልላቶች
የአንድ አምድ የላይኛው ክፍል ኩልላት ይባላል ። በ 2 ኛ ዜና ምዕራፍ 3 ቁጥር 3 ላይ “ጉልላት” እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። ኣት: - “ጎድጓዳ ሳህን ቅርጽ ያላቸው አናቶች” ወይም “ሳህን ቅርጽ ያላቸው የላይኛው ክፍሎች”

ጌጣጌጥ መርበቦች
ይህ በአዕማዶቹ የላይኛው ክፍል ላይ ያለውን የጌጣጌጥ ቅርፃ ቅርጾችን ወይም ምልክቶችን ያመለክታል ። ኣት: - “ሰንሰለቶችን የሚመስሉ ቅርፃ ቅርጾች”

አራቱ መቶ ሮማኖች
“ሮማኖችን” በ 2 ዜና መዋዕል 3: 3 እንደተረጎምከው ተርጉም። (ቁጥሮችን: ይመልከቱ)

2 Chronicles 4:14

እርሱ እንዲሁም ሠራ....ኪራም-አቢ ሠራ
እዚህ ኪራም አቢ ተብሎ የተጠራው ኪራም ፣ ከእርሱ ጋር አብረው የሚሠሩትን ሁሉ ይወክላል። ኣት: “ደግሞም ኪራም-አቢ እና የእርሱ የእጅ ጥበብ ባለሙያዎቹ ሠሩ” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከል: ይመልከቱ)

ገንዳዎቹ
“ሳህኖቹን”

አንድ ኩሮና እና አሥራ ሁለት በሬዎች
ይህ ትልቅ እና ያጌጠ መታጠቢያ ነው ። በ 2 ኛ ዜና ምዕራፍ 4 ቁጥር 2 -3 እንደተረጎምከው “ኩሬ” እና “በሬዎችን” ተርጉም ።

ሌሎች ዕቃዎችን
“ሌሎች መሣሪያዎች” ወይም “ለመሠዊያው የሚያገለግሉ ሌሎች ዕቃዎች”

ከለሰለሰ ናስ
መንጸባረቅ እንዲችል ሠራተኞቹ ያለሰለሱት ናስ ።

2 Chronicles 4:17

ንጉሡ ሰሎሞን አስፈሰሰው ... ሰሎሞን ሠራ
ሰሎሞን ሌሎች ሰዎችን ሥራውን እንዲሠሩ እንዳሰማራ አንባቢዎች ሊገነዘቡ ይገባል። ኣት: - “ንጉሡ ሠራተኞቹን እንዲጥሉት አዘዘ ... የሰሎሞንም ሠራተኞች ሠቱ” (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

በጽሬዳ
ይህ የከተማ ስም ነው ። (የስሞችን አተረጓጎም: ይመልከቱ)

የናሱ ክብደት ሊታወቅ አልቻለም
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ተገቢ ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እጅግ ብዙ ናስ ስለነበረ ማንም ሊመዝነው አልሞከረም ። ኣት: - “ማንም ሰው ናሱን ሊመዝን እንኳ አልሞከረም” ወይም 2) ይህ ከፍተኛውን የነሐስ መጠን አጋኖ በመግለጽ አፅኖት የሚሰጥ ነው ። ኣት: - “ናሱ በጠቅላላ ምን ያህል እንደሚመዝን እንኳ ሊገልጽ የሚችል ማንም አልነበረም” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን እና ግነትን እና አጠቃላይን: ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Chronicles 4:19

ሰሎሞን ሠራው
ሰሎሞን በእርግጥ ሌሎች ሰዎችን ሥራውን እንዲሰሩ እንዳሰማራ አንባቢዎች ሊገነዘቡት ይገባል ። ኣት: - “የሰሎሞን ሠራተኞች ሠሩ” (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

የቤት እቃዎች ሁሉ
ይህ የሚያመለክተው በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የሚያገለግሉትን ጎድጓዳ ሳህኖች እና መሳሪያዎች ሁሉ ነው።

የገጹ ጎብስት የነበረባቸውን ገበታዎች
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: “ካህናቱ የመገናኛውን እንጀራ የሚያቀርቡባቸው ገበታዎች” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን: ይመልከቱ)

የገጹ ጎብስት
ይህ በመሠዊያው ፊት ለፊት ስለተቀመጡት 12 ዳቦዎች የሚያሳይ ነው ። በ 2 ኛ ዜና ምዕራፍ 2 ቁጥር 4 ውስጥ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ።

ውስጠኛው ቤት ፊት ለፊት እንዲቃጠሉ የተቀየሱ ነበሩ
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “በውስጠኛው ክፍል ፊት እንዲቃጠል” ወይም “ካህናቱ በውስጠኛው ክፍል ፊት ለፊት እንዲቃጠሉ ዘይት ያኖሩበታል” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን: ይመልከቱ)

ውስጠኛው ቤት
ይህ “የቅድስተ ቅዱሳኑ” ወይም “የቅዱሱ ስፍራ” ሌላው ሥም ነው ።

አበባዎቹና፣ ቀንዲሎቹ
“አበባዎቹና” እና “ቀንዲሎቹ” የመቅረዞቹ አንድ ክፍል ናቸው ።

መኮስተሪያዎች
ይህ ነገሮችን ለማንሳት የሚያገለግል በአንደኛው ጫፍ ከተገናኙ ከሁለት የእንጨት ወይም የብረት ዘንግጎች የተሠራ መሣሪያ ነው ።

ደግሞም የመብራት ማጥፊያዎች ... ሁሉ ከንጹሕ ወርቅ ተሠሩ
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ሠራተኞቹ የመብራቶቹን ማጥፊያዎች ... ከጥሩ ወርቅ...

የመብራት ማጥፊያዎች
እነዚህ የመብራት የዘይት መስመሮችን በማቋረጥ መብራቶቹን ለማጥፋት ያገለግሉ ነበር።

የውስጠኛው በሮች ... ከወርቅ የተሠሩ ነበሩ
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “ሠራተኞቹ የውስጠኛውን በሮች ... ከወርቅ ሠሩ (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን: ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 5

1 ሰለሞንም እንደዚህ ለእግዚአብሔር ቤት የሠራው ሥራ ሁሉ ተጠናቀቀ። ሰለሞንም አባቱ ዳዊት የቀደሳቸውን እቃዎች ብሩን፥ ወርቁንና የቤት እቃዎችን ሁሉ ጨምሮ አምጥቶ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ በነበሩት ግምጃ ቤቶች ውስጥ አስቀመጣቸው። **2** ከዚያም ሰለሞን የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ታቦት ከዳዊት ከተማ ማለትም ከጽዮን እንዲያመጡ የእስራኤልን ሽማግሌዎች ፥ የነገድ አለቆችን ሁሉ እና የእስራኤልን ሕዝብ ቤተሰብ መሪዎች ሰበሰበ። **3** የእስራኤልም ሰዎች ሁሉ በሰባተኛው ወር በበዓሉ ወቅት በንጉሡ ፊት ተሰበሰቡ። **4** የእስራኤልም ሽማግሌዎች ሁሉ መጡ፤ ሌዋውያንም ታቦቱን አነሱ። **5** ታቦቱንም፥ የመገናኛውንም ድንኳን፥ በድንኳኑም ውስጥ የነበሩትን ቅዱሳት ዕቃዎች በሙሉ አመጡ። ከሌዊ ነገድ የነበሩት ካህናት እነዚህን ነገሮች ሁሉ አመጡ። **6** ንጉሥ ሰለሞንና የእስራኤል ማህበር ሁሉ ሊቆጠሩ የማይችሉትን በጎችና በሬዎች እየሰዉ በታቦቱ ፊት ተሰበሰቡ። **7** ካህናቱም የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ታቦት ወደ ቤቱ ውስጠኛ ክፍል ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ከኪሩቤል ክንፍ በታች ወደ ቦታው አመጡት። **8** ኪሩቤልም በታቦቱ ስፍራ ላይ ክንፎቻቸውን ዘርግተው ነበር፤ ኪሩቤልም ታቦቱንና መሸከሚያዎቹን ምሶሶዎችም ይሸፍኑ ነበር። **9** መሸከሚያዎቹ ምሶሶዎችም እጅግ ረጅም ከመሆናቸው የተነሳ ጫፎቻቸው ከውስጠኛው ክፍል ፊት ለፊት ከቅዱሱ ሥፍራ ይታዩ ነበር፤ ነገር ግን ክውጪ መታየት አይችሉም ነበር። እስከዚህች ቀንም ድረስ በዚያ ይገኛሉ። **10** በታቦቱም ውስጥ የእስራኤል ሰዎች ከግብጽ ምድር በወጡ ጊዜ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ቃል ኪዳን ባደረገ ጊዜ ሙሴ በኮሬብ ካስቀመጣቸው ከሁለቱ ጽላቶች በስተቀር ምንም ነገር አልነበረባቸውም። **11** ካህናቱም ከቤተ መቅደሱ ቅዱስ ስፍራ ወጡ። በዚያ የነበሩትም ካህናት በተመደቡበት ክፍል ላይ ሳያተኩሩ ሁሉም ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ቀድሰው ነበር። **12** መዘምራን የነበሩትም ሌዋውያንም አሳፍን፥ ኤማንን፥ ኤዶታምን ልጆቻቸውንና ወንድሞቻቸውን ጨምሮ ሁሉም ጥሩ በፍታ ለብሰው ጸናጽል፥ በገና እና መሰንቆ/ክራር እየመቱ በመሠዊያው አጠገብ በስተምሥራቅ ቆመው ነበር። ከእነርሱም ጋር መቶ ሃያ መለከት የሚነፉ ካህናት ነበሩ። **13** መለከቱን የሚነፉትና መዘምራኑም ከመቅደሱ ሲወጡ በአንድነት ሆነው እግዚአብሔርን እያመሰገኑና እያወደሱ በአንድ ቃል ድምጻቸውን ያሰሙ ነበር። ከመለከቶቹና ከጸናጽሎቹ ከሌሎቹም መሳሪያዎች ጋር ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር።" ቸር ነውና የቃል ኪዳን ታማኝነቱ ለዘላለም የሚጸና ነውና" ብለው ዘመሩ። በዚያን ጊዜ ቤቱ የእግዚአብሔር ቤት በደመና ተሞላ። **14** የእግዚአብሔር ክብር ቤቱን ሞልቶት ስለነበር ከደመናው የተነሳ ካህናቱ ለማገልገል መቆም አልቻሉም ነበር።

---

2 Chronicles 5:1

ሰሎሞን ለእግዚአብሔር ቤት ያከናወነው ሥራ ሁሉ ተፈጸመ ሲል ሰሎሞን አኖረው
ሰሎሞን ሌሎች ሰዎች ሥራውን እንዲሰሩ እንዳሰማራ አንባቢዎች ሊገነዘቡት ይገባል ። ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “የሰሎሞን ሠራተኞች ሁሉንም ለየእግዚአብሔር ቤት ሥራ ካጠናቀቁ በኋላ ፣አመጡ” (የባህሪ ስምን እና ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን: ይመልከቱ)

ግምጃ ቤቶች
መጋዘኖች ፣ ነገሮች የሚቀመጡባቸው ወይም የተቀመጡባቸው ክፍሎች

2 Chronicles 5:2

የነገድ ራሶችን ሁሉ
እዚህ “ራሶች” ለአንድ ነገር በጣም አስፈላጊ ለሆነ አካል ምሳሌ ነው ። አት: - “የየነገዶቹ መሪዎች ሁሉ” (ዘይቤያዊን: ይመልከቱ)

የእስራኤል ሰዎች ሁሉ
ይህ ምናልባት 1) ሰሎሞን ወደ ኢየሩሳሌም የጠራውን እና በ 5: 2 ውስጥ የተዘረዘሩትን) ወይም 2) በአጠቃላይ ለበዓሉ ወደ ኢየሩሳሌም የተጓዙትን ፣ እንጂ የግድ እስራኤል ውስጥ ለሚኖሩ ወንድ ሁሉ አይደለም ። (ግነትን እና አጠቃላይን: ይመልከቱ)

በሰባተኛው ወር በበዓሉ ላይ
ይህ በዕብራይስጥ የቀን አቆጣጠር በሰባተኛው ወር በአሥራ አምስተኛው ቀን የሚከበር የዳስ በዓል ነው። ይህ በምዕራባዊያን የቀን መቁጠሪያ በጥቅምት ወር መጀመሪያ ላይ ነው። (ተመልከት/ች: የዕብራዊያንን ወራት እና ሕገኛ ቁጥርን እና ታሳቢ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን: ይመልከቱ)

2 Chronicles 5:4

የቤት ዕቃዎች
ይህ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ያገለገሉትን ጎድጓዳ ሳህኖችን እና መሳሪያዎችን ያመለክታል። በ 2 ኛ ዜና ምዕራፍ 4 ቁጥር 19 ውስጥ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የእስራኤልን ማኅበር ሁሉ
እዚህ “ሁሉ” አጠቃላይ ነው ማለትም ብዙ እስራኤላውያን ማለት ነው ። (ግነትን እና አጠቃላይን: ይመልከቱ)

ሊቆጠሩ የማይችሉ በጎች እና በሬዎች
ይህ የተሠዉትን እጅግ በጣም ብዙ እንስሳት የሚያጎላ ማጋነን ነው ። ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “ማንም ሊቆጥረው ከሚችለው በላይ የበጎች እና በሬዎች መሠዋት ” ወይም “እጅግ በጣም ብዙ በጎች እና በሬዎች መሠዋት ” (ግነት እና አጠቃላይ እና ገቢራዊ ወይም ተብሮአዊ: ይመልከቱ)

2 Chronicles 5:7

ወደ ውስጠኛው ክፍል ፣ ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ ፣ በታች
“ወደ ውስጠኛው ቤት ይኸውም ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ ሥፍራ፣ ሥር”

የተሸከመባቸው መሎጊያዎች
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “ካህናቱ የተሸከሙባቸው መሎጊያዎች” (ገቢራዊ ወይም ተብሮአዊ : ይመልከቱ)

2 Chronicles 5:9

መጨረሻዎቻቸው ታዩ ... ሊታዩ አልቻሉም
ይህ ገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “ሰዎች መጨረሻቸውን ማየት ይችላሉ... ሰዎች አያዩአቸውም”

እስከዛሬ
ይህ ማለት ጸሐፊው የጻፈበትን ቀን የሚያመለክት ነው ።

2 Chronicles 5:11

እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ በታሪኩ ውስጥ አንድን አስፈላጊ ክስተት ለማመልከት እዚህ ጥቅም ላይ ውሏል ። ቋንቋህ ይህንን የሚያከናውንበት መንገድ ካለው እዚህ መጠቀም ትችላለህ ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አሳፍ ፣ ኤማን ፣ ኤዶታም
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው ። (የስሞችን አተረጓጎም: ይመልከቱ))

ወንዶችና ወንድሞች
“ወንዶችና ሌሎች ዘመዶች”

ጽናጽል
ሁለት ቀጭን ፣ ክብ የብረት ሳህኖች ከፍተኛ ድምጽ ለመፍጠር አንድ ላይ የሚመቱ (የማይታወቀውን ይተርጉሙ: ይመልከቱ))

120 ካህናት
“አንድ መቶ ሀያ ካህናት” (ቁጥሮችን: ይመልከቱ))

በአንድነት ሆነው እግዚአብሔርን እያመሰገኑና እያከበሩ
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ እና ሲከብሩ አንድ ድምጽ ማሰማት” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን: ይመልከቱ)

ድምፃቸውን ከፍ አደረጉ
ይህ ፈሊጥ ነው ። ኣት: - “በከፍተኛ ድምፅ ዘመሩ” (ፈሊጥን: ይመልከቱ))

የቃል ኪዳኑ ታማኝነት ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል
“ቃል ኪዳናዊ ታማኝነት” የሚለው የረቂቅ ስም “ታማኝነት” ተብሎ ሊገለፅ ይችላል። ኣት: “ለዘላለም ታማኝ ነውና” (የረቂቅ ስም ፡ ይመልከቱ)

ቤቱም የእግዚአብሔርም ቤት በደመና ተሞላ
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ከዚያም ደመና የእግዚአብሔርን ቤት ሞላው” (ተመልከት/ች: ገቢራዊ ወይም ተብሮኣዊ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 6

1 ሰለሞንም፦"እግዚአብሔር በድቅድቅ ጨለማ እንደሚኖር ተናግሯል፤ 2 እኔ ግን ለዘላለም እንድትኖርበት የላቀ መኖሪያ ቤት ሠራሁልህ" አለ። 3 ከዚያም የእስራኤል ጉባኤ ቆመው በነበሩበት ንጉሡ ፊቱን ዘወር አድርጎ የእስራኤልን ጉባኤ ሁሉ ባረከ። 4 እርሱም ፦ "ለአባቴ ለዳዊት የተናገረ እና በገዛ እጆቹ የፈጸመ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ፤ 5 "ሕዝቤን እስራኤልን ከግብጽ ካወጣሁበት ቀን ጀምሮ ስሜ በዚያ የሚሆንበት ቤት በዚያ ይሠራልኝ ብዬ ከእስራኤል ነገዶች ሁሉ ማንኛውንም ከተማ አልመረጥኩም፤ በሕዝቤም በእስራኤል ላይ አለቃ ይሆን ዘንድ አንድም ሰው አልመረጥኩም፤ 6 ነገር ግን ስሜ በዚያ እንዲሆንባት ኢየሩሳሌምን መርጫለሁ፤ በሕዝቤም በእስራኤል ላይ እንዲሆን ዳዊትን መርጫለሁ" ብሎአል። 7 አሁንም ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር ቤት መስራት በአባቴ በዳዊት ልብ ነበር። 8 ነገር ግን እግዚአብሔር ለአባቴ ለዳዊት፦ "ለስሜ ቤት ትሠራ ዘንድ በልብህ ነበረ፤ ያ በልብህ የነበረ መሆኑ መልካም አደረግህ። 9 ነገር ግን ቤቱን አንተ ልትገነባው አይገባም፤ ይልቁንም ከወገብህ የሚወጣው ልጅህ እርሱ ለስሜ ቤትን ይሠራልኛል" አለው። 10 እግዚአብሔር ተስፋ እንደ ሰጠ በአባቴ በዳዊት ፈንታ ስለተነሳሁ በእስራኤልም ዙፋን ላይ ስለተቀመጥሁ እግዚአብሔር የተናገረውን ቃል ፈጽሞአል። ለእስራኤል አምላክም ለእግዚአብሔር ስም ቤት ሠራሁ። 11 ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ያደረገው የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ያለበትን ታቦቱን በዚያ ውስጥ አኖርሁ። 12 ሰለሞን የእስራኤል ጉባኤ ሁሉ ባሉበት በእግዚአብሔር መሠዊያ ፊት እጆቹን ዘርግቶ ቆመ። 13 ርዝመቱ አምስት ክንድ፥ ወርዱ አምስት ክንድ፥ ቁመቱም ሦስት ክንድ የሆነ የናስ መድረክ ሰርቶ ነበር። በአደባባዩም መሃል ላይ አድርጎት ነበር። በእርሱም ላይ በመቆም በመላው የእስራኤል ጉባኤ ፊት ተንበርክኮ እጆቹን ወደ ሰማይ ዘረጋ። 14 እንዲህም አለ፦ "የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ሆይ በፍጹም ልባቸው በፊትህ ከሚሄዱ ባሪያዎችህ ጋር ኪዳንንና የቃል ኪዳን ታማኝነትን የምትጠብቅ በሰማይም ሆነ በምድር እንዳንተ ያለ አምላክ የለም፤ ለባሪያህ 15 ለአባቴ ለዳዊት የሰጠኸውን ተስፋ የጠበቅህ አንተ፥ አዎ በአፍህ የተናገርኸውን ዛሬም እንደሆነው በእጅህ ፈጽመኸዋል። 16 አሁንም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ሆይ ለባሪያህ ለአባቴ ለዳዊት፦ "'አንተ በፊቴ እንደተመላለስህ ልጆችህ በሕጌ ይሄዱ ዘንድ ቢጠነቀቁ በእስራኤል ዙፋን የሚቀመጥ ሰው በፊቴ አታጣም' በማለት የሰጠኸውን ተስፋ ፈጽምለት። 17 እንግዲህ የእስራኤል አምላክ ሆይ ለባሪያህ ለዳዊት የሰጠኸው የተስፋ ቃል ይፈጸም። 18 በውኑ እግዚአብሔር ከሰው ጋር በምድር ላይ ይኖራልን? እነሆ መላው አጽናፈ ዓለም እና ሰማየ ሰማያት ራሱ ሊይዝህ አይችልም - ይልቁንም እኔ የሠራሁት ቤት ምንኛ ያነሰ ይችላል! 19 ነገር ግን እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ የባሪያህን ይህንን ጸሎትና ልመናውን እባክህን ተቀበል፤ ባሪያህ በፊትህ የሚጸልየውን ጩኸትና ጸሎት ስማ። 20 ባሪያህ ወደዚህ ስፍራ የሚጸልየውን ጸሎት ትሰማ ዘንድ ስምህን እንደምታደርበት ወደተናገርከው ወደዚህ ስፍራ ዓይኖችህ ወደዚህ ቤተ መቅደስ በቀንና በሌሊት የተገለጡ ይሁኑ። 21 ባሪያህና ሕዝብህ እስራኤል ወደዚህ ስፍራ በሚጸልዩበት ጊዜ ልመናዎቻቸውን ስማ፤ ከማደሪያህ ስፍራ ከሰማያት ስማ፤ ሰምተህም ይቅር በል። 22 አንድ ሰው ባልንጀራውን ቢበድልና እንዲምል ቢጠየቅ እርሱም መጥቶ በዚህ ቤት ውስጥ በመሠዊያህ ፊት ቢምል 23 ከሰማያት ሆነህ ስማ፤ አድርግም፤ በደሉን በራሱ ላይ በማድረግ በደለኛውን መልሰህ በመክፈል በባሪያዎችህ መካከል ፍረድ። ለጽድቁ ብድራትን ለመስጠት ጻድቁ ንጹህ መሆኑንም አስታውቅለት። 24 ሕዝብህ እስራኤል አንተን ከመበደላቸው የተነሳ በጠላት ድል ሲነሱ ወደ አንተ ቢመለሱ፥ በዚህም ቤተ መቅደስ ውስጥ በፊትህ ስምህን ቢጠሩ፥ ቢጸልዩና ምህረትን ቢለምኑ 25 እባክህን ከሰማያት ስማና የሕዝብህን የእስራኤልን ኃጢአት ይቅር በል፤ ለእነርሱና ለአባቶቻቸውም ወደ ሰጠሃቸው ምድር መልሳቸው። 26 አንተን ከመበደላቸው የተነሳ ሰማያት ቢዘጉና ምንም ዝናብ በማይኖርበት ጊዜ ወደዚህ ስፍራ ቢጸልዩ፥ ስምህን ቢጠሩና ስታስጨንቃቸው ከኃጢአታቸው ቢመለሱ 27 ከሰማይ ስማ፤ ሊመላለሱበት ወደሚገባቸው መልካሙ መንገድ ስትመራቸው የባሪያዎችህንና የሕዝብህን የእስራኤልን ኃጢአት ይቅር በል። ለሕዝብህ ርስት አድርገህ በሰጠሃት በምድርህ ላይ ዝናብን ላክ። 28 በምድሪቱ ላይ ርሃብ ቢኖር ወይም ቸነፈር ወይም ዋግ ወይም አረማሞ ወይም አንበጣ ወይም ኩብኩባ ቢኖር ወይም ጠላቶች በምድራቸው ውስጥ የከተማ በሮችን ቢያጠቁ ወይም ማናቸውም መቅሰፍት ወይም ደዌ ቢኖር 29 አንድም ሰው ወይም ሕዝብህ እስራኤል ሁሉ እያንዳንዱ መቅሰፍቱንና ሐዘኑን በልቡ አውቆ ወደዚህ ቤተ መቅደስ እጆቹን ዘርግቶ ጸሎትና ልመና ቢያቀርብ 30 በሰማይ በምትኖርበት ሆነህ ስማ፤ ይቅርም በል፤ የሰውን ሁሉ ልብ የምታውቅ አንተ ብቻ ስለሆንክ ልቡን ታውቃለህ፤ ለእያንዳንዱ እንደ መንገዱ ሁሉ ብድራትን ስጠው። 31 ለአባቶቻችን በሰጠሃቸው ምድር ላይ በሚኖሩበት ጊዜ ሁሉ አንተን እንዲፈሩህ በመንገድህም ይሄዱ ዘንድ ይህንን አድርግ። 32 ከሕዝብህ ከእስራኤል ወገን ያልሆነ ባእድ ሰው ደግሞ ከታላቁ ስምህ ፥ ከኃያሉ እጅህና ከተዘረጋችው ክንድህ የተነሳ ከሩቅ አገር ሲመጣ፥ ወደዚህ ቤተ መቅደስ መጥተው በሚጸልዩበት ጊዜ 33 በሰማይ በምትኖርበት ስፍራ ሆነህ ስማ፤ በምድር ላይ ያሉ ሕዝቦች ሁሉ ስምህን እንዲያውቁ፥ እንደ ሕዝብህ እንደ እስራኤል እንዲፈሩህ እና ይህ የሠራሁት ቤት በስምህ የሚጠራ መሆኑን እንዲያውቁ ባእዱ ሰው የሚለምንህን ሁሉ አድርግ። 34 ሕዝብህ አንተ በምትልካቸው በምንም መንገድ ከጠላቶቻቸው ጋር ለመዋጋት ቢወጡ ፥ አንተ ወደመረጥካት ወደዚች ከተማና ለስምህ ወደሠራሁት ወደዚህ ቤት ቢጸልዩ 35 ከሰማያት ጸሎታቸውንና ልመናቸውን ስማና በጉዳያቸው አግዛቸው። 36 ኃጢአት የማይሰራ ማንም የለምና አንተን በበደሉህ ጊዜ ተቆጥተሃቸውም ለጠላት አሳልፈህ ብትሰጣቸው ጠላት ወደ ቅርብም ሆነ ሩቅ አገር ቢያግዛቸውና እንደ ምርኮኛ ወደ ምድራቸው ቢወስዳቸው 37 በግዞት አገር ውስጥ መሆናቸውን ቢገነዘቡ፥ ንስሃ ቢገቡና በተማረኩበት ምድር ሞገስን ካንተ ቢፈልጉ፥ 'ጠማማን ነገር አድርገናል፤ በድለናል፤ እኩይ ምግባር ፈጽመናል፤' ቢሉ 38 ምርኮኛ ተደርገው በተወሰዱባት በተማረኩባት ምድር በሙሉ ልባቸውና በሙሉ ነፍሳቸው ወዳንተ ቢመለሱና ለአባቶቻቸው ወደሰጠሃቸው ምድር፥ ወደ መረጥካት ከተማና ለስምህ ወደሠራሁት ቤት ቢጸልዩ 39 በሰማያት በምትኖርበት ስፍራ ጸሎታቸውንና ልመናቸውን ስማና በጉዳያቸው አግዛቸው። የበደሉህን የሕዝብህን ኃጢአት ይቅር በል። 40 አሁንም አምላኬ ሆይ በዚህ ስፍራ ወደሚደረገው ጸሎት ዓይኖችህ የተገለጡና ጆሮዎችህ የሚያተኩሩ እንዲሆኑ እለምንሃለሁ። 41 አሁንም እግዚአብሔር አምላክ ሆይ አንተና የኃይልህ ታቦት ወደ ማረፊያህ ስፍራ ተነስ፤ እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ካህናትህ ደህንነትን ይልበሱ፤ ቅዱሳንህም በመልካምነትህ ደስ ይበላቸው። 42 እግዚአብሔር አምላክ ሆይ የቀባኸውን ሰው ፊት ካንተ አትመልሰው። ለባሪያህም ለዳዊት ያደረግህለትን የቃል ኪዳን ታማኝነት አስብ።

---

2 Chronicles 6:1

እግዚአብሔር ብሎአል
ሰሎሞን ስእግዚአብሔር ሲናገር ለሌላ ሰው የሚናገር ይመስላል ይህም ለእግዚአብሔር ያለውን አክብሮት ለማሳየት ነው። ኣት: - “እግዚአብሔር ሆይ ፣ አንተ አልህ” (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሦስተኛ መደብ ሰብዓዊን: ይመልከቱ)

በወፍራም ጨለማ ውስጥ
እዚህ “ወፍራም” የሚለው ቃል ጨለማው እጅግ በጣም ከባድ መሆኑን ያሳያል ። እግዚአብሔር ኃጢአተኛ ሰዎች እንዲመለከቱት እንደማይፈቅድ ሲናገር በጨለማ ውስጥ እንደሚኖር አስመስሎ ተናግሯል። ኣት: - “በታላቅ ጨለማ ውስጥ” (ዘይቤያዊን: ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እጅግ ከፍ ያለ መኖሪያ ቤት ሠራሁልህ
ሰሎሞን ፣ ሕዝቡ ቤተ መቅደሱን እንዲሠሩ ማዘዙን እና እንዴት መሥራት እንዳለባቸው መናገሩን እርሱ ራሱ እንደገነባው አስመስሎ ይናገራል ። ኣት: - “እኔና ሕዝብህ እጅግ ከፍ ያለ መኖሪያ ሠርተንላችኋል” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ ስለመወከል : ይመልከቱ)

ከፍ ያለ መኖሪያ ሠራሁልህ
በጣም አስፈላጊ ለሆነ ሰው የሚመጥን የሚያምር ቤተ

የእስራኤል ማኅበር ሁሉ ቆመው ነበር
“ማኅበሩ ሁሉ” የሚለው ሐረግ አጠቃላይ ነው ። ይህ ማለት እያንዳንዱ እስራኤልላዊ ቆሞ ነበር ማለት ሳየሆን ፣ እዚያ ተሰብስበው የነበሩ ሰዎች ሁሉ ቆመው ነበር ማለት ነው ። ኣት: - “የእስራኤል ሕዝብ በዚያ ቆመው ነበር” (ግነትን እና አጠቃላይን : ይመልከቱ)

2 Chronicles 6:4

የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይመስገን
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን አወድሱ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን : ይመልከቱ)

አባቴ ዳዊት
ንጉሥ ሰሎሞን በእውነቱ ከንጉሥ ዳዊት ልጆች አንዱ ነበር ።

ተፈጽሟል
“ይሄኛው እንዲከሰት አድርጓል ።” “ይሔኛው” የሚለው ቃል እግዚአብሔር ቃል የገባውን ያመለክታል። ኣት: - “የገባውን ቃል መፈጸሙን አረጋግጧል” (የሚጠበቅ እውቀጥ እና የለተገለጸ መረጃ : ይመልከቱ)

በገዛ እጆቹ
እጅ በዘይቤአዊ አነጋገር ኃይል ማለተ ነው ። ኣት: - “በኃይሉ”(የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

ስሜ በዚያ እንዲኖር
እዚህ “ስሜ” የሚለው ስያሜ የእግዚአብሔርን ሥም ይወክላል ፣ እና ስሙ በዚያ ስፍራ መኖሩ ሰዎች የእርሱን ታላቅነት በመገነዘብ እና በዚያ እንደሚያመልኩ የመለክታል ። ኣት: - “ሰዎች እዚያ እንዲያመልኩኝ ነው” (የባህሪ ስም: ይመልከቱ)

በሕዝቤ በእስራኤል ላይ አለቃ ትሆን ዘንድ
“በሰዎች ላይ አለቃ” መሆን እነርሱን መግዛትን ያመለክታል። ኣት: - “ሕዝቤን እስራኤልን ይገዛል” (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

ስሜ በዚያ ይኖር ዘንድ ነው
እዚህ “ስሜ” የሚለው ስያሜ የእግዚአብሔርን ሥም ይወክላል ፣ እና ስሙ በዚያ ስፍራ መኖሩ ሰዎች የእርሱን ታላቅነት መገንዘባቸውንና በዚያ እርሱን ማምለካቸውን የመለክታል ። ኣት: - “ሰዎች እዚያ እንዲያመልኩኝ ነው” (የባህሪ ስም : ይመልከቱ)

በሕዝቤ በእስራኤል ላይ እንዲሆን
በሰዎች ላይ “የበላይ” መሆን እነሱን መግዛትን ይወክላል ። ኣት: - “ሕዝቤን እስራኤልን እንዲገዛ” (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

2 Chronicles 6:7

አገናኘ መግለጫ
ንጉሥ ሰለሞን በቤተ መቅደሱ ውስጥ ለሕዝቡ መናገሩን ቀጠለ።

ይህ በአባቴ በዳዊት ልብ ውስጥ ነበር... በልብህ ውስጥ ነበር... በልብህ ውስጥ እንዲሆን
እዚህ ላይ የዳዊት ልብ እንደ ኮንቴይነር ተደርጎ ተገልጾአል ፣ እናም እርሱ የፈለገው ነገር በእቃ መያዥያው ውስጥ ያለ እቃ እንደሆነ በማስመሰል ተገልጾአል ። ኣት: “አባቴ ዳዊት ተመኝቶ ነበር... አንተም ተመኘህ ....ለሥራት መመኘት (የባህሪ ስም : ይመልከቱ)

ለእግዚአብሔር ሥም...ለእኔ ሥም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ያህዌህ ስም ራሱን ይወክላል ። ኣት: - “ለያህዌ... ለእኔ” ወይም 2) የያህዌ ስም ማንነቱን ይወክላል ። ኣት: - “ለያህዌ ዝና... ስለ ስሜ ሲባል” (የባህሪ ስምን : ይመልከቱ)

በልብህ ውስጥ ነበር
“በልብህ ስለሆነ” ወይም “ስለ ፈለግህ”

ከወገብህ የሚመጣው
'የአንተ ዘር የሚሆነው' ወይም “አንተ አባት የምትሆነው”

2 Chronicles 6:10

እርሱ የተናገረውን ቃል ፈጽሟል
ይህ ፈሊጥ ነው ። ኣት: - “እሱ ያደርጋል ያለውን ያለውን በትክክል ፈጽሟል” (አይዲዮን ይመልከቱ)

በአባቴ በዳዊት ምትክ ተነሳሁ
ከፍታ ኃይልን ይወክላል። ኣት: - “አባቴ ዳዊት የነበረውን ኃይል ተጎናጸፍኩ” (ዘይቤያዊን: ይመልከቱ)

በእስራኤል ዙፋን ላይ እቀመጣለሁ
ዙፋኑ በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው ሰው ተግባር የሚያመለክት ነው ። ኣት: - “በእስራኤል ላይ እገዛለሁ” (ዘይቤያዊን: ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ስም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ያእግዚአብሔር ስም ራሱን ይወክላል ። ኣት: - “ለእግዚአብሔር” ወይም 2) የእግዚአብሔር ስም ይወክላል። ኣት: - “ስለ እግዚአብሔር ስም” (ዘይቤያዊ: ይመልከቱ)

ቃል ኪዳን ያለበትን
እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑን ውል የጻፈባቸው የድንጋይ ጽላቶች ራሳቸው ቃል ኪዳን እንደሆኑ በማስመሰል ተገልጾአል። ኣት: “እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑን ውል የጻፈባቸው ጽላቶች በእነዚያ ውስጥ ናቸው” (ዘይቤያዊን: ይመልከቱ)

2 Chronicles 6:12

በእስራኤል ማኅበር ሁሉ ፊት
“በዚያ በተሰበሰበው የእስራኤል ሕዝብ ፊት”

እጆቹን ዘረጋ
“እጆቹን ወደ ላይ ዘረጋ።” የሚለው እየጸለየ መሆኑን ለማሳየት ነበር ። (ምሳሌያዊ ድርጊትን: ይመልከቱ)

ርዝመቱ አምስት ክንድ ፣ ወርዱ አምስት ክንድ ፣ ቁመቱም ሦስት ክንድ
እነዚህን ወደ ዘመናዊ መለኪያዎች መለወጥ ትችላለህ ። ኣት: - “እርዝመቱ ሁለት ሜትር ከሰላሳ አራት ሴንቲ ሜትር ፣ ወርዱ ሁለት ሜትር ከሰላሳ አራት ሴንቲ ሜትር ፣ ከፍታው አንድ ሜትር ከ ሀምሳ ሳንቲሜትር” (መጽሐፍ ቅዱሳዊ ርቀትን: ይመልከቱ)

እጆቹን ወደ ሰማይ ዘረጋ
ሰሎሞን እጆቹን ወደ ላይ ዘርግቶ ለመጸለይ በመድረክ ላይ ተንበረከከ ። እጆቹን ወደ ሰማይ መዘርጋቱ ወደ እግዚአብሔር መጸለዩን የሚያሳይበት አንድ መንገድ ነው። (ምሳሌያዊ ድርጊትን: ይመልከቱ)

2 Chronicles 6:14

በምድር ለአገልጋዮችህ ጋር ቃል ኪዳንህን ታማኝ ፍቅርን የምትጠብቅ
ይህ እንደ አዲስ ዓረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል ። ኣት.: - “በምድር ላይ። በምድር ባሪያዎችህን ለመውደድ የገባኸውን ቃል ትጠብቃለህ ።”ወይም“ ባሪያዎችህን በታማኝነት ትወዳለህ ”

በፍጹም ልባቸው በፊትህ ለሚሄዱ
ስለ አንድ ሰው አኗኗር በመንገድ ላይ እንደሚሄድ ተብሎ ተገልጾአል ። ኣት: - “ አንተ እንደምትፈልጋቸው በሙሉ ልብ ሲኖሩ”(ዘይቤያዊን: ይመልከቱ)

ለባሪያህ ለአባቴ ለዳዊት የሰጠኸውን ተስፋ የጠበቀህ ለባሪያህ ለአባቴ ለዳዊት የገባኸውን ቃል የጠበቅኸው አንተ
ቃልን መጠበቅ አንድ ሰው ቃል የገባውን ማድረግ ማለት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኣት: - “ለባሪያህ ለአባቴ ለዳዊት ቃል የገባኸውን ቃል የገባኸው አንተ ነህ” (ስለፈሊጥ: ይመልከቱ)

በአፍህ ተናገርክ
“በአፍህ” የሚለው ሐረግ እግዚአብሔር ራሱ የተናገረውን አፅን mayት ሊሰጥ ይችላል ። ቃሉን የገባው ሌላ ሰው አልነበረም ። ኣት: - “አንተ ራስህ ተናገርክ”

በእጅህ ፈጸምኸው
እጅ የሚለው የእጅ ኃይል የሚወክል ነው ። ኣት: “እናም በኃይልህ የተናገርከውን ፈጽመሃል” ወይም “የተናገርከውን በኃይልህ ፈጽመሃል” (ስለባህሪ ስም: ይመልከቱ)

ዛሬም እንደ ሆነው
ይህ ሰሎሞን ይህንን ጸሎት ያደረገበትን ቀን ይመለከታል ።

2 Chronicles 6:16

አያያዥ መግለጫ
ንጉሥ ሰሎሞን ጸሎቱን ቀጠለ ።

ቃል የገባኸውን ጠብቅ
ይህ ጥያቄ ነው ። አንድ ሰው የተናገረውን ጠበቀ ማለት ፈሊጣዊ አገላለጽ ሲሆን አንድ ሰው ቃል የገባውን ፈፀመ የሚል ትርጉም አለው ። ኣት: - “እባክህን የገባኸውን ቃል አድርግ” (ስለፈሊጥ: ይመልከቱ)

ሰው አታጣም
እግዚአብሔር ዳዊት ሰው እንደሚያገኝ ሲናገር ዳዊትን የሚወርሰው ከዳዊት ዘር እንደሚሆን ይጠቁማል ። ይህ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለጽ ይችላል ። ኣት: - “አንተ ሁል ጊዜ ከዘርህ የሚተካህ ይኖርሃል” (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸን እና እጥፍ አሉታዊን : ይመልከቱ)

በእስራኤል ዙፋን ላይ የሚቀመጥ ሰው በፊቴ
እዚህ “በፊቴ” የሚለው ቃል/ሐረግ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ሰውየውን እንደሚመርጥ እና ሰውየውም እግዚአብሔርን መታዘዝ እንደሚፈልግ ያሳያል ። (የሚጠበቅ እውቀትን እና የልተገለጸን መረጃ: ይመልከቱ)

በእስራኤል ዙፋን ላይ ለመቀመጥ
ዙፋኑ የሚያመለክት በዙፋኑ ላይ የሚቀመጠውን ሰው ተግባር ነው ። ኣት: - “በእስራኤል ላይ ይገዛል” (የባህሪ ስም : ይመልከቱ)

አንተ በፊቴ እንደ ሄድኸው በሕጌ ይሄዱ ዘንድ
አንድ ሰው የሚያሳየው በህሪይ ግለሰቡ በመንገድ ላይ እንደተጓዘ ተደርጎ ተገል። ኣት: - “እንደ ታዘዝከኝ ሕጌን እንዲታዘዙ” ወይም “ለእኔ ታማኝ እንደሆንኸ ለሕጌ ታማኝ ይሁኑ” (ዘይቤያዊን : ይመልከቱ)

ለአገልጋይህ ለዳዊት የተናገርኸው ቃል ይጽና
“ለባሪያህ ለዳዊት የነገርኸውን ቃል እንድትፈጽመው እፈልጋለሁ”

ቃልህ ይጽና
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። ኣት: - “ቃልህን አጽና” ወይም “ቃልህን ፈጽም” (ጥራዝ 2: ትርጉም: ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን: ይመልከቱ)

ቃልህ
“ቃል የገባኸው ነገር”

2 Chronicles 6:18

አያያዥ መግለጫ
ንጉሥ ሰሎሞን ጸሎቱን ቀጠለ ።

በውኑ እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ጋር በምድር ላይ ይኖራልን?
ለዚህ ጥያቄ ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሰለሞን እንዲመለስለት የሚፈልገውን ጥያቄ እየጠየቀ ነው 2) ጥያቄው አወያይ መጠይቅ ነው ፣እና ሰሎሞን እግዚአብሔር በምድር ላይ ይኖር ዘንድ በጣም ትልቅ እና ታላቅ መሆኑን አፅንኦት እየሰጠ ነው ። ኣት: - “በእርግጥ እግዚአብሔር በምድር ላይ ይኖራል ማለት አይቻልም!” (ስለአወያይ መጠይቅ: ይመልከቱ)

በውኑ እግዚአብሔር
እዚህ ሰለሞን ለእግዚአብሔር ያለውን ታላቅ አክብሮት ለማሳየት ሦስተኛ ሰብአዊ መደብ በመጠቀም ስለ እግዚአብሔር ይናገራል ። በሁለተኛው ሰብአዊ መደብ ውስጥ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ግን ታደርጋለህ” (አንደኛ ፣ ሁለተኛ ፣ ወይም ሦስተኛ መደብ ሰብአዊን : ይመልከቱ)

እነሆ
እዚህ “እነሆ” እርሱ አንድ አስፈላጊ ነገር ሊናገር መሆኑን ያሳያል ።

አጽናፈ ሰማይ እና ሰማይ ራሱ አንተን ሊይዙህ አይችሉም
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ከአጽናፈ ሰማይ እና ሰማይ ሁሉ እጅግ የሚበልጥ መሆኑን ነው ። በ 2 ዜና 2 6 ውስጥ ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸን መረጃ)

እኔ የሠራሁት ይህ ቤተ መቅደስ ምንኛ ያነሰ ነው!
“ ስለዚህ እኔ የገነባሁት ይህ ቤተ መቅደስ በእርግጠኝነት ሊይዝህ አይችልም”

እኔ የሠራሁት ይህ ቤተ መቅደስ
ሰሎሞን ፣ ሕዝቡ ቤተ መቅደሱን እንዲገነቡ ስለማዘዙ እና እንዴት አድርገው መሥራት እንዳለባቸው ስለመናገረ ሲናገር ቤቱን እርሱ ራሱ እንደገነባው አስመስሎ ተናግሯል ። AT: - “ሕዝብህ በእኔ መሪነት የሠራው ይህ ቤተ መቅደስ” ወይም “እኔና ሕዝብህ የገነባነው ይህ ቤት” (ብዙሃኑን በአንድ ወይም አንዱን በብዙሃኑ መወከል: ይመልከቱ)

ይህን የአገልጋይህን ጸሎትና ልመና አክብር
“ጸሎት” እና “ልመና” የሚሉት ቃላት በመሠረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ያሚሰጡ ሲሆን እርሱ ልመናውን በሚያቀርብበት ወቅት ከልቡ እንደሆነ ያሳያሉ ። ሰለሞን ያህዌን እንደሚከብር ለማሳየት እራሱን “አገልጋይህ” ሲል ጠርቶታል ። ይህ በመጀመሪያ መደብ ሰብዓዊ ውስጥ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “እኔ ይህንን ልመና ሳቀርብ እኔን አገልጋይህን አክብረኝ” (ስለ እጥፍ እና ስለ አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሦስተኛ መደብ ሰብዓዊ: ይመልከቱ)

አገልጋይህ በፊትህ የሚጸልየውን ጩኸትና ጸሎት አድምጥ
“ጸሎት” እና “ልመና” የሚሉት ቃላት በመሠረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ያሚሰጡ ሲሆን እርሱ ልመናውን በሚያቀርብበት ወቅት ከልቡ እንደሆነ ያሳያሉ ። ሰለሞን ያህዌን እንደሚከብር ለማሳየት እራሱን “አገልጋይህ” ሲል

ጠርቶታል ። ይህ በመጀመሪያ መደብ ሰብዓዊ ውስጥ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “እኔ ይህንን ልመና ሳቀርብ እኔን አገልጋይህን አክብረኝ” (ስለ እጥፍ እና ስለ አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሦስተኛ መደብ ሰብዓዊ: ይመልከቱ)

ዓይኖችህ ወደዚህ ቤተ መቅደስ ይክፈቱ
ክፍት የሆኑ ዓይኖች የሚለው ዘይቤ ሲሆን መየትን የሚወክል ነው ፣ እዚህ ማየት የሚለው ቃል ጥበቃን ያመለክታል ። “እባክህን ይህንን ቤተ-መቅደስ ጠብቅ” ወይም “እባክህን ይህንን ቤተ-መቅደስ ከልል” (ዘይቤያዊን: ይመልከቱ)

ቀን እና ማታ
ይህ ሜሪዝም ነው ። ኣት: - “ሁል ጊዜ” ወይም “በቋሚነት”(ስለ ሜሪዝም: ይመልከቱ)

በዚያ ስሜ ይሆናል ወዳልኸው ሥፍራ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የያህዌህ ሥም ራሱን ይወክላል ። አት: - “እንደምትገኝ ቃል የገባህበት ቦታ” ወይም 2) የእግዚአብሔር ስም ስሙን ይወክላል ። ኣት: - “ሰዎች አንተን የሚያውቁበት ቦታ እንዲሆን ቃል ቃል የገባህበት” (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

ባሪያህ ወደዚህ ስፍራ የሚጸልየውን ጸሎት
ሰለሞን ያህዌን እንደሚከብር ለማሳየት እራሱን “አገልጋይህ” ሲል ጠርቶታል ። ይህ በመጀመሪያ መደብ ሰብዓዊ ውስጥ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “እኔ አገልጋይህ ወደዚህ ቦታ የምጸልየውን ጸሎት” (ስለአንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሦስተኛ መደብ ሰብዓዊ: ይመልከቱ)

2 Chronicles 6:21

አያያዥ መግለጫ
ንጉሥ ሰሎሞን ጸሎቱን ቀጠለ ።

ስለዚህ የአገልጋይህንና የሕዝብሕን እስራኤል ልመናዎች አድምጥ
ሰሎሞን ያህዌን እንደሚያከብር ለማሳየት ስለራሱ “አገልጋይህ” ሲል ይናገራል ። ይህ በመጀመሪያ መደብ ሰብዓዊ ውስጥ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “ስለዚህ ጥያቄዎቼንና የሕዝብህን እስራኤል ልመናዎች ስማ ” (ስለ አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ ሰብዓዊ: ይመልከቱ)

ስትሰማ ይቅር በል
“ጸሎታችንን ስትሰማ እባክኽን ኃጢአታችንን ይቅር በል”

2 Chronicles 6:22

አያያዥ መግጫዎች
ንጉሥ ሰሎሞን ጸሎቱን ቀጠለ ።

መሓላ መማል ግዴታ ነው
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “አንድ ሰው እንዲምልለት ይጠይቃል” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን : ይመልከቱ)

ይህ ቤት።
ይህ ቤተመቅደሱን ያመለክታል ።

ያደረከውንም በራሱ ላይ አምጣበት
የአንድን ሰው ምግባር በራሱ ላይ ማምጣት በመጥፎ ድርጊቱ መቀጣትን ያመለክታል። አት: - “ የሚገባውን ቅጣት መስጠት” (ስለ ዘይቤያዊ: ይመልከቱ)

በራሱ ላይ
እዚህ ላይ “ራስ” ሙሉውን ሰው ያመለክታል ። አት: - “በእርሱ ላይ” (አንዱ ሁሉን ወይም ሁሉ አንዱን የሚወክልበትን አገላለጽ : ይመልከቱ)

እንደ ጽድቁም ክፈለው
“ንፁህ ስለሆነ የሚገባውን ስጠው”

2 Chronicles 6:24

ሕዝብህ እስራኤል በጠላቶች በተሸነፈ ጊዜ
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ጠላት ሕዝብህን እስራኤል ድል ሲያደርግ” (ገቢራዊ ወይም ተቢሮአዊ: ይመልከቱ)

አንተን ስለ በደሉ
“ሕዝብህ እስራኤል አንተን በድለዋልና”

ወደ እናንተ ቢመለሱ
እዚህ “ወደ አንተ ተመለሱ” እንደገና ለእግዚአብሔር መገዛትን ያመለክታል ። አት: - “እንደገና ለአንተ ከተገዙ” (ዘይቤያዊን: ይመልከቱ)

ስምህን ቢያከብሩ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “አንተን መበደላቸውን አምነው” ወይም 2) “ቢያወድሱህ” ወይም 3) “ከአሁን ጀምሮ እንደሚታዘዙህ ቢናገሩ” ።

በፊትህ ይቅርታን ቢጠይቁ
“ይቅር ባይነት” የሚለው የነገሮች ስም እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አት: - “ይቅር እንድትላቸው ቢጠይቁህ” (የረቂቅ ስሞችን: ይመልከቱ)

እባክህን ከሰማይ ስማ
“ማዳመጥ” ፈሊጥ ሲሆን ለጸሎት መልስ መስጠት ማለት ነው አት: - “እባክህን ጸሎታቸውን አክብር” ወይም “እባክህን ጸሎታቸውን መልስ” (ስለፈሊጥ : ይመልከቱ)

ለእነርሱና ለአባቶቻቸው ወደ ሰጠሃቸው ምድር መልሳቸው
ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ህዝብ ጠላቶቻቸው በሚሠያሸንፏቸው ጊዜ በሌሎች ሀገሮች ውስጥ እንደሚኖሩ ነው ። ኣት: - “ወደ ገዛ ምድራቸው መልሳቸው” (የሚጠበቅ እውቀት እና የልተገለጸ መረጃ: ይመልከቱ)

2 Chronicles 6:26

ሰማያት ሲዘጉ ዝናብም ባልዘነበ ጊዜ
ሰማዩ እግዚአብሔር ዝናብ የሚያከማችበት ቤት ነው ተብሎ ይነገራል ፣ እና እግዚአብሔር ዝናብ እንዲዘንብ በማይፈልግበት ጊዜ የቤቱን በር ይዘጋል። ኣት: - “ከሰማያት ዝናብ እንዲዘንብ ካልፈቀድክ” (ዘይቤያዊ: ይመልከቱ)

ስምህን ቢያከብሩ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “በአንተ ላይ ኃጢአት መፈጸማቸውን አምነው” ወይም 2) “ቢያወድሱህ” ወይም 3) “ከአሁን ጀምሮ እንደሚታዘዙህ ቢናገሩ” ።

ከኃጢአታቸው ቢመለሱ
እዚህ “ቢመለሱ” የሚለው ድርጊቱን ማቆምን የሚያመለክት አነጋገር ነው ። ኣት: - “ኃጢአታቸውን መሥራታቸውን ማቆም ” ወይም “በኃጢአት መፈጸማችሁን ማቆም” (ዘይቤያዊን : ይመልከቱ)

ሊሄዱበት የሚገባው መልካም መንገድ
የአንድ ሰው አኗኗር ግለሰቡ በመንገድ ላይ እየተጓዘ እንደሆነ ተደርጎ ተገልጻል ። ኣት: - “ሊኖሩበት የሚገባ መልካም መንገድ” (ዘይቤያዊን : ይመልከቱ)

ለሕዝብህ ርስት አድርገህ የሰጠሃትን ምድርህን
ምድሪቱ እንደ ርስት ሆና ተገለጸአል ምክንያቱም እግዚአብሔር ለዘላለም እንዲወርሱ ስለ ፈለገ ነው ። ኣት: - “ለህዝብህ ለዘላለም የሰጠሃቸው ምድርህ” (ዘይቤያዊን : ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Chronicles 6:28

ቸነፈር ወይም ዋግ
እነዚህ ግብርና ቋንቋዎች ሲሆኑ በሰብሎች ላይ በዝናብ እጥረት ወይም መብዛት የሚከሰቱ በጣም አዝጋሚ የሆነ የሰብሎችን ሞት የሚያመለክቱ ናቸው ።

አንበጣ ወይም ኩብኩባ
“አንበጣ” ሰብሎችን በመመገብ ጥፋት የሚያስከትል የአንበጣ ዓይነት ነው። “አባ ጨጓሬ” የሚለው ቃል የአንበጣውን የመጀመሪያ የእድገት ደረጃ ያመለክታል ።

ማንም ሰው ወይም ህዝብህ እስራኤል ሁሉ ጸሎትና እና ልመና ቢያደርግ
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “አንድ ሰው ወይም ሕዝብህ እስራኤል ሁሉ ቢፀልይ እና ቢለምን ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን: ይመልከቱ)

ጸሎት እና ልመና
“ጸሎት” እና “ልመና” የሚሉት ቃላት በመሠረቱ አንድ ዓይነት ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ ግለሰቡ ልመናውን ሲያቀርብ ከልቡ እንደነበረ ያመለክታሉ ። (ድግግሞሽ: ይመልከቱ)

በልቡ መቅሰፍቱንና ኀዘኑን አውቆ
እዚህ “መቅሰፍት” የሚለው ዘይቤያዊ አገላለጽ ሲሆን ኃጢያት ማለት ነው ፣ እና ኃጢያትና ሀዘንም በሕዝቡ ልብ ውስጥ እንደሆኑ ተገልጻል ። ኣት: - “በገዛ ልቡ ውስጥ ያለውን ኃጢአትና ኀዘን ማወቅ” (ዘይቤያዊን: ይመልከቱ)

እጆቹን ወደዚህ ቤተ መቅደስ ቢዘረጋ
ይህ ወደ ቤተ መቅደሱ አምላክ እየጸለየ መሆናቸውን የሚያሳዩበት መንገድ ነበር። በ 2 ኛ ዜና ምዕራፍ 6 ቁጥር 12 ላይ “እጆቹን ዘርግቶ” እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። (ምሳሌያዊ ድርጊትን: ይመልከቱ)

እንደ መንገዱ ሁሉ
እዚህ “መንገዶቹ” የሚለው የግለሰቡን ባህሪ ያመለክታሉ። ኣት: - “ስላደረገው ነገር” (ዘይቤያዊን: ይመልከቱ)

በመንገዶችህም ይሄዱ ዘንድ
እዚህ “በመንገድህ ይሄዱ ዘንድ” እግዚአብሔር እንደሚፈልገው መኖርና መመላለስ ያመለክታል ። ኣት: - “እንደፈለግኸው እንዲኖሩ” (ዘይቤያዊን: ይመልከቱ)

2 Chronicles 6:32

አያያዥ መግለጫ
ንጉሥ ሰሎሞን ጸሎቱን ቀጠለ ።

ማን-ስለታላቁ ስምህ ብርቱውም እጅህ፣ እና በተዘረጋ ክንድህ - መጣ
እንግዶች የሚመጡት ስለ እግዚአብሔር ታላቅነት ስለሰሙ ነው ። ኣት: - “ ስለ ታላቅ ስምህ ፣ ስለ ኃያል እጅህና ስለ ተዘረጋ ክንድህ የሚሰማ- ከመጣ” (የሚጠበቅ እውቀት ወይም ያልተገለጸ መረጃ : ይመልከቱ)

ታላቅ ስምህ
እዚህ የእግዚአብሔር ስም ማንነቱን ያሳያል ። ኣት: - “ታላቅ ስምህ” ወይም “ታላቅነትህ”((ተመልከት/ች: ዘይቤያዊ)) ኃያል እጅህንና የተዘረጋ ክንድህ እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ ተመሣሳይ ትርጉም ያላቸውና የእግዚአብሔርን ኃይል የሚያመለክቱ ናቸው ። ((ተመልከት/ች: ድግግሞሽ እና የባህሪ ስም))

ወደዚህ ቤት ጸለየ
አንድ ሰው ወደ ቤተ መቅደስ ሲጸልይ ወደ እግዚአብሔር እየጸለየ እንዳለ ያሳያል። ((ተመልከት/ች: ምሳሌያዊ ድርጊት))

ስምህን እንዲያውቁ
እዚህ የእግዚአብሔር ስም ማንነቱን ይወክላል ። ኣት: - “ስምህን እንዲያውቅ” ወይም “ታላቅነትህን እንዲያውቅ” (የባህሪ ስምን : ይመልከቱ)

እንደ ሕዝብህ እንደ እስራኤል /እንዲፈሩህ
“ያንተ ሕዝብህ እስራኤል ስምህን እንደሚያውቅ እና እንዲፈሩህ”

እኔ የሠራሁት ይህ ቤት በስምህ ተጠርቷል
“በስምህ ተጠርቷል” የሚለው ሐረግ የሚያሳየው እግዚአብሔር ቤቱን እንደያዘውና የቤቱ ባለቤት እንደሆነ ነው ። ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “እኔ የሠራሁት ይህንን ቤት የራስህ አድርገው” (ገቢራዊ ወይም ተብሮአዊ : ይመልከቱ)

ይህ የሠራሁት ቤት
ሰሎሞን ፣ ሕዝቡ ቤተ መቅደሱን እንዲሠሩ ስለማዘዙ እና እንዴት መሥራት እንዳለባቸው ስለመናገሩ ሲገልጽ እሱ ራሱ እንደሠራው አስመስሎ ተናግሯል ። በ 2 ዜና 6 18 ውስጥ ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደቶሮጎምከው ተመልከት ። ኣት: - “ሕዝብህ በእኔ መሪነት የሠራው ይህ ቤት” ወይም “እኔና ሕዝብህ የሠራነው ይህ ቤት” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መተካት: ይመልከቱ)

2 Chronicles 6:34

አያያዥ መግለጫ
ንጉሥ ሰሎሞን ጸሎቱን ቀጠለ ።

ሕዝብህ ቢወጡ ... ቢጸልዩ
እነዚህ ግምታዊ ሁኔታዎች ሲሆኑ ሰሎሞን በሚናገርበት ጊዜ አልተከሰቱም ፣ ነገር ግን ሰለሞን ወደፊት እንደሚከሰቱ ያውቅ ነበር ። ያልተከናወኑ ግን ወደፊት ሊከሰቱ ስለሚችሉ ነገሮች በአንተ ቋንቋ የለውን አገላለጽ ተጠቅመህ ግለጽ ። (መላምታዊ ሁኔታዎች: ይመልከቱ)

እነሱ ወደዚች ከተማና ቤት ቢጸልዩ
ወደ ኢየሩሳሌምና ወደ መቅደሱ መጸለይ ወደ እግዚአብሔር እንደሚጸልዩ ነው ። (ምሳሌያዊ ድርጊትን: ይመልከቱ)

እኔ የሠራሁት ቤት
ሰሎሞን ፣ ሕዝቡ ቤተ መቅደሱን እንዲሠሩ ስለማዘዙ እና እንዴት መሥራት እንዳለባቸው ስለመናገሩ ሲገልጽ እሱ ራሱ እንደሠራው አስመስሎ ተናግሯል ። ኣት: - “ሕዝብህ በእኔ መሪነት የሠራው ይህ ቤት” ወይም “እኔና ሕዝብህ የሠራነው ይህ ቤት” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከል : ይመልከቱ)

ለስምህ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የያህዌህ ስም ራሱን ይወክላል ። ኣት: - “ለአንተ” ወይም 2) የያህዌህ ስም ማንነቱን ይወክላል። ኣት: - “ስለስምህ” (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

ወደ ጸሎታቸው ፣ ልመናቸው
“ጸሎት” እና “ልመና” የሚሉት የነገሮች ስሞች እንደ ግሶች ሊገለጹ ይችላሉ። ኣት: - “ወደ አንተ ሲጸልዩ ወደ ልመናቸው” (ድግግሞሽን: ይመልከቱ)

የለመኑህንም አድርግላቸው
ይህ ከጠላቶቻቸው ጋር ሲዎጉ መርዳት ያመለክታል ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Chronicles 6:36

አያያዥ መግለጫ
ንጉሥ ሰሎሞን ጸሎቱን ቀጠለ ።

ቢበድሉ ... አንተ ብትቆጣ...እነርሱም ቢገነዘቡ ... ንስሐ ቢገቡ... ቢሉ ...ቢመለሱ... ቢለምኑህ
ሰለሞን በሚናገርበት ጊዜ እነዚህ ግምታዊ ሁኔታዎች አልተከሰቱም ፣ ነገር ግን ሰለሞን ወደፊት እንደሚከሰቱ ያውቅ ነበር ። ያልተከናወኑ ግን ወደፊት ሊከሰቱ ስለሚችሉ ክስተቶችን የሚገልጹ አገላለጾችን በቋንቋህ ካሉ ተጠቀም። (መላምታዊ ሁኔታዎችን : ይመልከቱ)

ለጠላት አሳልፈህ ስጣቸው
እዚህ ላይ “ለጠላት አሳልፈው ስጣቸው” ጠላት እነሱን እንዲይዛቸው መፍቀድን ያመለክታል ። (ዘይቤያዊን : ይመልከቱ)

ጠላት ማርኮ ቢወስዳቸው
እዚህ “ይማርኳቸዋል” አገራቸውን ለቀው እንዲሄድ ማስገደድን ያመለክታል ። አት: - “ጠላቶቻቸው እንዲሄዱ ያስገድዷቸዋል” (ዘይቤያዊን : ይመልከቱ)

በተማረኩበትም አገር ሆነው
ይህ ገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ጠላቶቻቸው በምርኮ የወሰዷቸው አገር” (ገቢራዊ ወይም ተብሮአዊ : ይመልከቱ

በፊትህ ሞገስን ለማግኘት ቢፈልጉ
“ምሕረት እንድታደርግላቸው ቢለምኑህ”

በድለናል ኃጢአትም ሠርተናል ። ክፉም አድርገናል
እነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች አንድ ዓይነት ሲሆኑ የሰዎቹ አካሄድ ምን ያህል መጥፎ እንደነበረ አጉልተው ያሳያሉ። (ተመሳሳይነቶችን : ይመልከቱ)

በድለናል ኃጢአትም ሠርተናል
ቃላቶቹ በመሠረቱ አንድ ዓይነት ትርጉም ያላቸው ሲሆን ሕዝቡ ምን ያህል ኃጢአት እንደሠሩ አጉልቶ ያሳያል ። (ድግግሞሽን: ይመልከቱ)

እነርሱ ወደእናንተ ቢመለሱ
እዚህ “ወደአንተ ቢመለሱ” ለያህዌህ እንደገና መገዛትን ያመለክታል ። አት: - “እንደገና ይገዙለታል” (ዘይቤያዊን: ይመልከቱ)

በፍጹም ልባቸው እና በፍጹም ነፍሳቸው
“በሙሉ ልባቸው” እና “በሙሉ ነፍሳቸው” የሚሉት ሐረጎች ፈሊጣዊ አገላለጽ ሲሆኑ “ሙሉ በሙሉ” እና “በሁለንተናቸው” የሚል ትርጉም አላቸው ። እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው ። አት: “ሙሉ በሙሉ” (ፈሊጥን እና ድግግሞሽን: ይመልከቱ)

ምርኮኛ አድርገው በወሰዷቸው አገር
“ጠላቶቻቸው ምርኮኛ አድርገው በወሰዷቸው አገር”

ወደ አገራቸው ብጸለዩ
ይህ እስራኤልን ያመለክታል ። ወደ እስራኤል መጸለያቸው ወደእስራኤል አምላክ ወደ እግዚአብሔር እንደጸለዩ ያሳያል ። አት: - “ወደ አገራቸው አቅጣጫ እየተመለከቱ መጸለይ” (ምሳሌያዊ ድርጊትን: ይመልከቱ)

ወደመረጥኸው ከተማ
ይህ ኢየሩሳሌምን የሚያመለክት ነው።

እኔ የሠራሁት ቤት ነው
ሰሎሞን ፣ ሕዝቡ ቤተ መቅደሱን እንዲሠሩ ስለማዘዙ እና እንዴት መሥራት እንዳለባቸው ስለመናገሩ ሲገልጽ እሱ ራሱ እንደሠራው አስመስሎ ተናግሯል ። አት: - “ሕዝብህ በእኔ መሪነት የሠራው ይህ ቤት” ወይም “እኔና ሕዝብህ የሠራነው ይህ ቤት” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን: ይመልከቱ)

ለስምህ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የያህዌህ ስም ራሱን ይወክላል ። አት: - “ለአንተ” ወይም 2) የያህዌህ ስም ማንነቱን ይወክላል። አት: - “ስለስምህ”(የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

ወደ ጸሎታቸው እና ልመናቸው
“ጸሎት” እና “ልመና” የሚሉት የነገሮች ስሞች እንደ ግሶች ሊገለጹ ይችላሉ። አት: - “ወደ አንተ ሲጸልዩ ወደ ልመናቸው” (ድግግሞሽን : ይመልከቱ)

አሁን
እዚህ “አሁን” የሚለው ቃል ወደሚቀጥለው አስፈላጊ ነጥብ ትኩረትን ለመሳብ ይጠቅማል ።

ዓይኖችህ ይከፈቱ
የተከፈቱ አይኖች ልማዳዊ አነጋገር ሲሆን ማየት ማለት ነው ። እዚህ በትኩረት መመልከትን ያመለክታል። ኣት: - “እባክህን ወደኛ አትኩር ” ወይም “እባክህን እኛን ተመልከት” (የባህሪ ስምን : ይመልከቱ)

ጆሮችህ ጸሎትን የሚያደምጡ ይሁኑ
የሚያዳምጡ ጆሮዎች በትኩረት ማዳመጥን የሚወክል ነው።።። ኣት: - “እባክህ ጸሎትን አድምጥ” (የባህሪ ስምን : ይመልከቱ)

በዚህ ሥፍራ ወደሚሆነው ጸሎት
ይህ በገቢራዊ ቅርጽ ሊገለፅ ይችላል። ኣት: - “በዚህ ቦታ ለምናቀርበው ጸሎት” ወይም “በዚህ ቦታ ጸሎት ስናቀርብ ወደኛ ተመልከት” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን : ይመልከቱ)

አቤቱ አምላክ ሆይ ፣ ወደ ማረፊያ ቦታህ ተነሣ
ይህ እግዚአብሔርን በዙፋኑ ላይ የተቀመጠ ይመስል ከዙፋኑ እንዲነሳና ወደዚህ ቦታ እንዲመጣ ይጠይቃል ። አት: - “አቤቱ አምላክ ሆይ ፣ ተነስና ወደ ማረፊያህ ስፍራ ተመለስ” (ዘይቤአዊን : ይመልከቱ)

የኃይልህ ታቦት
“የኃይልህ ተምሳሌት የሆነች ታቦት”

ካህናቶችህ... መዳንን ይልበሱ ፤
“መዳን” የሚለው የነገሮች ስም “ማዳን” በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል ። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1 ኛ) መዳንን መልበስ ማለት ምሳሌያዊ አነጋገር ሲሆን መዳንን ማግኘት ማለት ነው ። ኣት: “ካህናቶችህ... እንዳዳንካቸው ... ያውቁ” ወይም 2) መዳንን መልበስ ማለት ምሳሌያዊ አነጋገር ሲሆን መዳንን ማሳየት ማለት ነው ። አት: - “ካህናቶችህ... ሰዎችን እንዴት እንደምታድኑ ያሳዩ” (ተመልከት/ች: ዘይቤያዊን እና የረቂቅ ስሞችን : ይመልከቱ)

የቀባኸውን ሰው ፊት ከአንተ አትመልስ
የአንድን ሰው ፊት ማዞር እርሱን አለመቀበልን ያሳያል ። አት: - “የቀባህውን አትጣል” (ተመልከት/ች: ዘይቤያዊ) የቀባኸው የተቀባህ ሰው ”ቅቡዕነት በእግዚአብሔር የመመረጥ መግለጫ ነው። ንጉሥ ሰሎሞን ምናልባት ስለ ራሱ እየተናገረ ሊሆን ይችላል ። ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “የቀባኸው” ወይም “ንጉሥ እሆን ዘንድ የመረጥኸኝ እኔ” (የባህሪ ስም እና ገቢራዊ ወይም ተብሮአዊ: ይመልከቱ)

ለአገልጋይህ ለዳዊት ያደረከውን የቃል ኪዳን ታማኝነትህን አስብ
“ሥራህ” የሚለው ሐረግ “ያደረግከው” በሚል ሐረግ ሊገለጽ ይችላል ። “ኣት” “ለባሪያህ ለዳዊት ስለ ቃል ኪዳንህ ታማኝነት ስትል ያደረከውን አስታውስ ”

በልብህ ጠብቅ/አስብ
“አስታውስ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 7

1 ሰለሞን ጸሎቱን በፈጸመ ጊዜ እሳት ከሰማይ ወርዶ የሚቃጠለውን መሥዋዕትና መሥዋዕቶችን በላ፤ የእግዚአብሔርም ክብር ቤቱን ሞላ። **2** የእርሱ ክብር ቤቱን ሞልቶት ስለነበር ካህናቱ ወደ እግዚአብሔር ቤት መግባት አልቻሉም። **3** የእስራኤልም ሕዝብ ሁሉ እሳቱ ሲወርድና የእግዚአብሔር ክብር በቤቱ ላይ እንደነበር ያዩ ነበር። በድንጋዩ ወለል ንጣፍ ላይ በግንባራቸው ተደፍተው ሰገዱ፤ ለእግዚአብሔርም ምስጋና አቀረቡ። "መልካም ነውና የቃል ኪዳን ታማኝነቱም ለዘላለም ጸንቶ ይኖራልና" አሉ። **4** ንጉሡና ሕዝቡ ሁሉ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቀረቡ። **5** ንጉሥ ሰለሞንም ሃያ ሁለት ሺህ በሬዎችና መቶ ሃያ ሺህ በጎች በጎችና ፍየሎች ሰዋ። እንደዚህ ንጉሡና ሕዝቡ ሁሉ የእግዚአብሔርን ቤት ቀደሱ። **6** ካህናቱም እያንዳንዳቸው በሚያገለግሉበት ቦታ ቆመው ሌዋውያኑም "የቃል ኪዳን ታማኝነቱ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራልና" በሚለው መዝሙር እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ ንጉሥ ዳዊት ያዘጋጀውን የእግዚአብሔር የዜማ መሳሪያዎች ይዘው ቆመው ነበር። ካህናቱ ሁሉ በፊታቸው መለከቶቻቸውን ሲነፉ እስራኤላውያን ሁሉ ቆሙ። **7** ሰለሞን በእግዚአብሔር ቤት ፊት ለፊት የነበረውን የአደባባዩን መካከል ቀደሰ። በዚያም የሠራው የናስ መሠዊያ የሚቃጠለውን መሥዋዕት፥ የእህሉን ቁርባንና ስቡን መያዝ ስላልቻለ የሚቃጠለውን መሥዋዕትና የሕብረት መሥዋዕቱን ስብ በዚያ አቀረበ። **8** በዚያን ጊዜ ሰለሞን ከእርሱም ጋር እስራኤል ሁሉ ከሐማት መግቢያ እስከ ግብጽ ወንዝ ድረስ የመጡ እጅግ ታላቅ ጉባኤ ለሰባት ቀናት ለሰባት ቀናት በዓል አደረጉ። **9** መሠዊያውን ለሰባት ቀናት ቀድሰው እና በዓሉን ለሰባት ቀናት ጠብቀው ስለነበር በስምንተኛው ቀን የተቀደሰ ጉባኤ አደረጉ። **10** ሰለሞንም በሰባተኛው ወር በሃያ ሦስተኛው ቀን እግዚአብሔር ለዳዊት፥ ለሰለሞንና ለሕዝቡ ለእስራኤል ካሳየው በጎነት የተነሳ በደስታና በሐሴት ልብ ወደ የቤታቸው እንዲሄዱ ሕዝቡን አሰናበተ። **11** በመሆኑም ሰለሞን የእግዚአብሔርን ቤትና የገዛ ራሱን ቤት ጨረሰ። ለእግዚአብሔር ቤትና ለገዛ ራሱ ቤት ሰለሞን በልቡ ያሰበውን ማናቸውንም ነገር በስኬት አከናወነ። **12** እግዚአብሔርም በሌሊት ለሰለሞን ተገልጦ፦" ጸሎትህን ሰምቻለሁ፤ ይህንንም ስፍራ ለራሴ የመስዋዕት ቤት እንዲሆን መርጫለሁ" አለው። **13** ዝናብ እንዳይኖር ሰማያትን ብዘጋ ወይም ምድሪቱን እንዲበላ አንበጣን ባዝዘው ወይም በሕዝቡ መካከል ቸነፈርን ብሰድድ **14** በስሜ የተጠሩት ህዝቤ ራሳቸውን ቢያዋርዱ፥ ቢጸልዩ፥ ፊቴን ቢፈልጉና ከክፉ መንገዳቸው ቢመለሱ ከሰማይ ሆኜ እሰማለሁ፤ ኃጢአታቸውን ይቅር እላለሁ፤ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ። **15** አሁንም በዚህ ስፍራ ለሚደረግ ጸሎት ዓይኖቼ ክፍት ይሆናሉ፤ ጆሮዎቼም ያደምጣሉ። **16** አሁንም ስሜ ለዘላለም በዚያ ይኖር ዘንድ ይህንን ቤት መርጫለሁ፤ ቀድሻለሁም፤ ዓይኖቼና ልቤም ዘወትር በዚያ ይሆናሉ። **17** አንተ ደግሞ ያዘዝሁህን ሁሉ በመፈጸም እና ሥርዓቶቼንና ሕግጋቴን በመጠበቅ አባትህ ዳዊት እንደሄደ በፊቴ ብትሄድ፥ **18** ከአባትህ ከዳዊት ጋር በገባሁት በቃል ኪዳን "ከዘርህ በእስራኤል ላይ አለቃ የሚሆን አይታጣም" እንዳልኩት የመንግሥትህን ዙፋን አጸናለሁ። **19** ነገር ግን እኔን ከመከተል ብትመለሱና በፊታችሁ ያኖርኳቸውን ሥርዓቶቼንና ትዕዛዛቶቼን ብትተዉ፥ ሄዳችሁ ሌሎችንም አማልክት ብታመልኩ ብትሰግዱላቸውም፥ **20** ያን ጊዜ ከሰጠኋችሁ ምድሬ እነቅላቸዋለሁ፤ ለስሜ የቀደስኩትን ይህንን ቤት ከፊቴ እጥለዋለሁ። በሕዝቦችም ሁሉ መካከል ምሳሌና መቀለጃ አደርገዋለሁ። **21** ምንም እንኳን ይህ ቤተ መቅደስ እጅግ የላቀ ቢሆንም በአጠገቡ የሚያልፉ ሰዎች ይደነግጣሉ፤ በጥላቻ ይነጋገራሉ። "እግዚአብሔር በዚህ ምድርና በዚህ ቤት ላይ ይህንን እንዲህ ያደረገው ለምንድን ነው?" ብለው ይጠይቃሉ። **22** ሌሎችም፦ "ከግብጽ ምድር ያወጣቸውን አምላካቸውን እግዚአብሔርን ትተው ሌሎችን አማልክትን የሙጥኝ ከማለታቸው የተነሳ ፥ ስለሰገዱላቸው ስላመለኳቸው ነው። ለዚህ ነው እግዚአብሔር ይህንን ሁሉ አደጋ ያመጣባቸው" ብለው ይመልሳሉ።

---

2 Chronicles 7:1

ቤቱ
“የእግዚአብሔር ቤት” ወይም “ቤተ መቅደስ”

በግንባሩም መሬት ላይ ተደፍተው በድንጋይ ንጣፍ ላይ ሰገዱ
ይህ የትሕትና እና የአምልኮ አኳሃን ነው። አት: “ፊታቸው የድንጋይ ንጣፉኑ እየነካ መሬት ላይ ተንበረከኩ ” (ምሳሌያዊ ድርጊትን: ይመልከቱ)

የቃል ኪዳኑ ታማኝነት ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል
“ቃል ኪዳናዊ ታማኝነት” የሚለው የነገሮች ስም “ታማኝነት” ገላጭ ቃል እና “ቃል መግባት” በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል ። “AT” “እግዚአብሔር በቃል ኪዳኑ ምክንያት ሁልጊዜ ለእኛ ታማኝ ይሆናል” ወይም “እግዚአብሔር ለእኛ ቃል የገባውን ሁል ጊዜ በታማኝነት ያደርገናል ። (የረቂቅ ስምን: ይመልከቱ)

2 Chronicles 7:4

ህዝቡ ሁሉ
ይህ አጠቃላይ መግለጫ የሚያመለክተው 1) ሰሎሞን ወደ ኢየሩሳሌም የጠራቸውና እና በ 2 ኛ ዜና መዋዕል 5፡ 2 የተዘረዘሩትን ወይም 2) ለበዓሉ ወደ ኢየሩሳሌም ለተጓዙት ነው እንጂ በእስራኤል ለሚኖር ሁሉ አይደለም ። (ግነትን እና አጠቃላይን : ይመልከቱ)

ሀያ ሁለት ሺህ በሬዎች
“22,000 በሬዎች” (ቁጥሮችን : ይመልከቱ)

120,000 በጎችና ፍየሎች
“አንድ መቶ ሀያ ሺህ በጎችና ፍየሎች” (ቁጥሮችን: ይመልከቱ)

እያንዳንዱ በሚያገለግልበት ስፍራ ቆሟል
'እያንዳንዱ በተመደበለት ቦታ ቆሟል'

ሌዋውያንም ደግሞ የእግዚአብሔርን የሙዚቃ መሣሪያ ይዘው ነበር
ከቀዳማዩ ሐረግ "ቆሞ" የሚለው ቃል ተወስዷል ። ኣት: - ሌዋውያኑም እንዲሁ የእግዚአብሔርን የሙዚቃ እቃ ይዘው ቆመው ነበር ” (የቃላትን ግድፈት : ይመልከቱ)

የቃል ኪዳኑ ታማኝነት ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል
“ታማኝነት” የሚለው የረቂቅ ስም “በታማኝነት” ወይም “ታማኝ” በሚሉት ቃላት ሊገለጽ ይችላል ። በ 2 ኛ ዜና መዋዕል 7፡ 3 ላይ “የቃል ኪዳን ታማኝነትን” እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። ኣት: - “እግዚአብሔርከእኛ ጋር ለገባው ቃል ኪዳኑ ሁልጊዜ ታማኝ ነው” ወይም “እግዚአብሔር በታማኝ ፍቅር ሁልጊዜ ይወዳናል” (የረቂቅ ስሞች: ይመልከቱ)

እስራኤል ሁሉ
ይህ አጠቃላይ ቃል የሚያመለክተው በኢየሩሳሌም በዓል ላይ የነበሩትን ነውጂ በእስራኤል ለሚኖሩ ሁሉ አይደለም ። (ግነት እና አጠቃላይ : ይመልከቱ)

2 Chronicles 7:7

እርሱ የሠራውን የነሐስ መሠዊያ
ደራሲው ሰለሞን ለአንድ ሰው የነሐስ መሠዊያ እንዲሠራ ያዘዘውንና እንዴት እንደ ሚሠራው የነገረውን ራሱ እንደሰራው አድርጎ ጽፏል ። ኣት: - “ እርሱ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በትዕዛዝ ያሰራው የነሐስ መሠዊያ” ወይም “ በሰው ያሠራው የነሐስ መሠዊያ” (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

የሚቃጠለውን መሥዋዕት ፣ የእህሉን ቁርባን ስቡን መያዝ አልቻለም
ይህ የሆነበት ምክንያት ብዙ መባዎች ስለነበሩ ነው። አት: - “ከብዛቱ የተነሳ የሚቃጠል መሥዋዕት ፣ የእህሉን ቁርባን እና ስቡን መያዝ አልቻለም” (የሚጠበቅ እውቀትን እና ግልጽ ያልሆነ መረጃን : ይመልከቱ)

2 Chronicles 7:8

ከእርሱ ጋር እስራኤልን ሁሉ
ይህ አጠቃላይ ቃል የሚያመለክተው በኢየሩሳሌም በዓል ላይ የነበሩትን ነው ነውንጂ በእስራኤል ለሚኖሩ ሁሉ አይደለም ። (ተመልከት/ች: ግነት እና አጠቃላይ)

ከሌባ ሐማት እስከ ግብጽ ወንዝ ድረስ
ሌባ ሃማት ከእስራኤል በስተ ሰሜን ሲሆን፥ የግብፅም ወንዝ ከእስራኤል በስተ ደቡብ ነበር። እነዚህ ከሁሉም የእስራኤል ክፍሎች ሰዎች በበዓሉ ላይ እንደነበሩ ለማሳየት ያገለግላሉ ። አት: - “ከሰሜን ከሐማት ጀምሮ እስከ ደቡብ እስከ ግብጽ ወንዝ ድረስ” (የሚጠበቅ እውቀት እና የልተገለጸ መረጃን እና ሜሪዝምን እና የስሞችን አተረጓጎም: ይመልከቱ)

ስምንተኛው ቀን
“ስምንተኛው” የሚለው ቃል “8” የሚል መደበኛ ቁጥርን ያመለክታል ። (ሕገኛ ቁጥርን: ይመልከቱ)

እጅግ ታላቅ ጉባኤ
ይህ ልዩ ኃይማኖታዊ ስብሰባ ነበር ።

መሠዊያውን ቀደሱ
እዚህ “መቀደሱን ጠበቁ” የሚለው አገላለጽ “መቀደሱን ማክበር” ማለት ነው ።(ፈሊጥን: ይመልከቱ)

በሰባተኛው ወር በሀያ ሦስተኛው ቀን
ይህ በዕብራይስጥ የቀን አቆጣጠር ሰባተኛ ወር ነው። ሀያ ሦስተኛው ቀን በምዕራባዊው የቀን አቆጣጠር የጥቅምት ወር አጋማሽ ላይ ነው። (የዕብራዊያንን ወራትን እና ሕገኛ ቁጥርን : ይመልከቱ)

በደስታ እና በሐሴት በተሞሉ ልቦች
“ደስታ” እና “ሐሴት” የሚሉት ቃላት በመሠረቱ አንድ ዓይነት ትርጉም አላቸው ። በአድነት የደስታውን ትልቅነት ያጎላሉ ። አት: - “በጣም በተደሰቱ ልቦች” ወይም “እጅግም ደስ አላቸው” (ድግግሞሽን: ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ስላሳያቸው ቸርነት
“እግዚአብሔር ድንቅ ቸርነቱን ስላሳየ” ወይም “ እግዚአብሔር በጣም መልካም ስለ ሆነ”

ህዝቡ እስራኤል
“የእግዚአብሔር ህዝብ እስራኤል።” “የእርሱ ህዝብ” የሚለው ሐረግ እግዚአብሔር ለእስራኤል ታማኝ መሆኑን ያጎላል። (መለየትን ከማስታወቅ እና ከማስታዎስ ጋር : ይመልከቱ)

2 Chronicles 7:11

ሰለሞን የእግዚአብሔርን ቤትና የራሱን ቤት ጨረሰ
ሰሎሞን ምናልባት ሌሎች ሰዎች ሥራውን እንዲሰሩ እንዳዘዘ አንባቢዎች ሊገነዘቡ ይገባል ። ኣት: - “ሰሎሞን ያዘዛቸው ሠራተኞች የእግዚአብሔርን ቤትና የሰሎሞንን ቤት ሠርተው ጨረሱ” (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

ሰሎሞን ይሰራው ዘንድ በልብ ያሰበውን
ልብ የተነገረው እንደ በመያዣ ተመስሎ ነው ፣ ምኞቶችም ወደ ልብ እንደመጡ ይናገራል ። ኣት: - “ሰሎሞን ሊሠራው የወደደውን ሁሉ” (ዘይቤያዊን: ይመልከቱ)

በተሳካ ሁኔታ አከናወነ
ይህ ፈሊጥ ነው ። አት: - “በተሳካ ሁኔታ ጨረሰ” ወይም “በተሳካ ሁኔታ እንዲከናወን አድርጎታል” (ፈሊጥን: ይመልከቱ)

በሌሊት
“በማታ” ወይም “አንድ ማታ”

ለመሥዋዕት ቤት
“ሰዎች መስዋዕት የሚያቀርቡልኝ ቤት”

2 Chronicles 7:13

ዝናብ እንዳይዘንብ ሰማያትን ብዘጋ
እዚህ “ሰማያት” ሰማይን የሚያመለክት ሲሆን እግዚአብሔር ዝናብን የሚያከማችበት ጋን ተደርጎ ተገልጾአል ። በ 2 ዜና 6፡ 26 ላይ የሚገኘውን ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። አት: - “ዝናብ ከሰማያት እንዲዘንብ ካልፈቀድኩኝ” (ዘይቤያዊን: ይመልከቱ)

ምድሪቱን ቢበላ
“ምድር ” የሚለው ቃል በምድር ላይ ያሉትን እፀዋትን እና ሰብሎችን ይወክላል ። (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

በሕዝቤ ላይ በሽታን ብልክ
“በሽታ መላክ” የሚለው በሽታ እንዲከሰት ማድረግን ያመለክታል ። አት: - “ሕዝቤን በበሽታ እንዲይዙ ባደርግ” (ዘይቤያዊን: ይመልከቱ)

በስሜ የተጠሩ ህዝቤት
እዚህ በእግዚአብሔር ስም መጠራት የሚለው ፈሊጥ ሲሆን የእግዚአብሔር ንብረት መሆን ማለት ነው ። ኣት: - “የእኔ የሆነ” (ፈሊጥን : ይመልከቱ)

ፊቴን ፈልጉ
እዚህ የእግዚአብሄር ፊት እነርሱን መቀበሉን ያሳያል ። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች “ፊቴን ፈልጉ” የሚለው የሚያመለክተው 1) ወዲውኑ እርሱን ይቅርታ መጠየቅ። አት: - “እነርሱን ይቅር እንድል ለምኑኝ” ወይም 2) እርሱን ለማስደሰት አጥብቆ መፈለግ ። አት: - “እኔን ለማስደሰት ሞረጥ” (ዘይቤያዊን: ይመልከቱ)

ከክፉ መንገዳቸው ቢመለሱ
እዚህ “ቢመለሱ”የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ሲሆን አንድን ነገር ከመሥራት መቆጠብ ማለት ነው ፣ “መንገዶች” የሚለው ደግሞ ባህሪን ያመለክታሉ ። አት: - “ክፉ ባሕርያቸውን አቆሙ” ወይም “መጥፎ ነገሮችን ማድረጋችሁን አቁሙ” (ዘይቤያዊን: ይመልከቱ)

ምድራቸውን ይፈውሳል
ብዙ የማይበቅለው መሬት የታመመ ነው ይባላል። አት: - “ምድራቸውን መልሶ መልካም ያድርገዋል” ወይም “ምድራቸው ጥሩ ሰብል እንዲያበቅል ያደርጋል” (ተስብኦትን: ይመልከቱ)

ዓይኖቼ ይከፈታሉ
የተከፈቱ አይኖች ዘይቤ ሲሆን ማየትን ማለት ነው ። እዚህ በትኩረት መመልከትን ይወክላል። አት: - “ወደ እናንተ በትኩረት አመለከታለሁ” ወይም “እመለከታችኋለሁ”(የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

ለጸሎት ጆሮቼ ያደምጣሉ
ጆሮቼ ያደምጣሉ የሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን በትኩረት ማዳመጥ ማለት ነው ። ኣት: - “ጸሎቶችን እሰማለሁ” (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በዚህ ቦታ ለሚጸለይ ጸሎት
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል። ኣት: - “በዚህ ቦታ ለምትጸልዩት ጸሎት” ወይም “ለእናንተ በዚህ ቦታ ወደ እኔ ስትጸልዩ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን: ይመልከቱ)

2 Chronicles 7:16

ስሜ ለዘላለም በዚያ ይኖር ዘንድ ነው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የእግዚአብሔር ስም ራሱን ይወክላል ። ኣት: - “ለዘላለም በዚያ እሆን ዘንድ” ወይም 2) የእግዚአብሔር ስም የእርሱን ማንነት ይወክላል ፣ እና ስሙ በዚያ መኖሩ ሰዎች እርሱን በዚያ እያመለኩ አንዳለ ያመለክታል ። ኣት: - “ሰዎች ለዘላለም በዚያ ያመልኩኝ ዘንድ ” (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

ዘወትር ዓይኖቼና ልቤ በዚያ ይኖራሉ
እዚህ “ዐይኖቼ” የሚለው የእግዚአብሔርን ጥንቃቄ ያመለክታል ፣ “ልቤ” የሚለው ደግሞ ፍቅሩን ያመለክታል ። እነዚህ በቤተ መቅደሱ መገኘታቸው እርሱ ቤተ መቅደሱን እንደሚጠብቀው ያመለክታሉ ። አት: - “ለዘላለም እንከባከበዋለሁ ደግሞም እጠብቀዋለሁ” (የባህሪ ስምን እና የሚጠበቅ እውቀትን እና የልተገለጸ መረጃን: ይመልከቱ)

ለአንተም
እዚህ “አንተ” የሚለው ቃል ንጉስ ሰሎሞንን ያመለክታል።

አንተም አባትህ ዳዊት እንደ ሄደ በፊቴ ብትሄድ
እዚህ መሄድ ዘይቤአዊ አነጋገር ሲሆን መኖር የሚል ትርጉም አለው። በእግዚአብሔር ፊት መሄድ እሱን በመታዘዝ መኖርን ይወክላል ። አት: - “እንደ አባትህ እንደ ዳዊት ብትታዘዘኝ ”(ተመልከት/ች: ዘይቤያዊ)

አባትህ ዳዊት
ሰሎሞን ከዳዊት ልጆች አንዱ ነበር ።

ሥርዓቴንና ፍርዴንም ብትጠብቁ
“ደንቦቼንና ድንጋጌዎቼን መታዘዝ”

የመንግሥትህን ዙፋን አጸናለሁ
እዚህ ዙፋኑ መግዛትን ያመለክታል ። የሰሎሞንን መንግሥት ዙፋን ማጽናት ማለት ሰሎሞን በእስራኤል የሚገዘ ዘር እንዲኖረው ማድረግ ማለት ነው ። ኣት: - “የአንተ ዘሮች በመንግሥትህ ላይ እንዲገዙ አደርጋለሁ” (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

ዘሮችህ በእስራኤል ውስጥ ገዥ መሆናቸው መቼም ቢሆን አይወድቅም
ይህ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለጽ ይችላል ። አት: - “ከዘርህ መካከል አንዱ ሁል ጊዜ በእስራኤል ገዢ ይሆናል” ወይም “ዘርህ በእስራኤል ውስጥ ሁል ጊዜ ይገዛሉ”

2 Chronicles 7:19

ብትመለሰስ
እዚህ ከእግዚአብሄር “መራቅ” ምሳሌያዊ አነጋገር ሲሆን እርሱን ማምለክ ማቆም ማለት ነው ። አት: - “ግን እኔን ማምለክን ብታቆሙ” (ዘይቤያዊን: ይመልከቱ)

እናንተ ብትመለሱ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች “እናንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው 1) ለሁሉም የእስራኤል ሕዝብ ፣ ወይም 2) ለሰሎሞን እና ለዘሩ ነው ።

ሥርዓቴንና ትእዛዜን
እዚህ ላይ “ትዕዛዛት” እና “ሥርዓቶች” የሚሉት ቃላት በመሠረቱ በትርጉማቸው አንድ ዓይነት ሲሆኑ እግዚአብሔር ያዘዘውን ሁሉ አፅንኦት ይሰጣሉ ። (ድግግሞሽን: ይመልከቱ)

ከሰጠኋቸው ምድር እነቅላቸዋለሁ
“እነሱ” የሚለው ቃል የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል ። እግዚአብሔር ህዝቡን ከምድሩ ለቀው እንዲወጡ ስለማድረግ ሲናገር ልክ እፅዋት ከነሥራቸው ከምድር እንደሚነቀሉ ህዝቡን እንደሚነቅላቸው ተናግሯል። AT: - “የሰጠኋቸውን ምድር ለቀው እንዲወጡ አደርጋለሁ” (ዘይቤያዊን: ይመልከቱ)

ይህ ቤት
ይህ ቤተመቅደሱን ያመለክታል ።

ለስሜ ቀድሼዋለሁ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የያህዌህ ስም ራሱን እግዚአብሔርን ይወክላል ። አት: - “ለራሴ የለየሁትን” ወይም 2) የያህዌ ስም የእርሱን ማንነት ይወክላል። አት: - “እኔ ለክብሬ የለየሁትን” (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

ከፊቴ እጥላለሁ
እግዚአብሔር ቤተ መቅደሱን ስላለመቀበል ሲናገር ከእርሱ በጣም አርቆ እንደሚጥለው በሚመሸል መልኩ ይናገራል ። አት: - “እጥለዋለሁ” ወይም “ችላ እለዋለሁ” (ዘይቤያዊን: ይመልከቱ)

በሕዝቦች ሁሉ መካከል ምሳሌ እና ቀልድ አደርገዋለሁ
“ሰዎች ሁሉ ዘንድ መተረቻ ፣ መቀለጃ እንዲሆን አደርጋለሁ” ወይም “በእሱ ላይ ከማደርገው የተነሳ አሕዛብ ሁሉ ያፌዙበትና ይሳለቁበታል ”

ይደነግጣል
“ይደነቃሉ”

ይጮኻሉ
በቤተ መቅደሱ ላይ በደረሰው ነገር እንደደነገጡ የሚያሳዩት የድንጋጤ ድምጽ ነው (ምሳሌያዊ ድርጊትን: ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን ተዉ
“ለእግዚአብሔር ታማኝ አልነበሩም” ወይም “እግዚአብሔርን አልታዘዙም”

አባቶቻቸውን ከግብጽ ምድር ያወጣቸውን
ይህ ሐረግ እግዚአብሔርን ማምለክ የነበረባቸው ለምን እንደሆነ ይገልጻል ። (መለየት ከማስታወቅና ከማስታወስ ጋር : ይመልከቱ)

ሌሎች አማልክትን ያዙ
እዚህ “ያዙ” የሚለው ቃል ለእነሱ ታማኝ ለመሆን መምረጥን ያሳያል ። አት: - “ለሌሎች አማልክት ታማኝ ለመሆን መርጠዋል” (ዘይቤያዊን: ይመልከቱ)

ሰገዱላቸው አመለኩአቸውም
እነዚህ ሁለት ሐረጎች አንድ ዓይነት ትርጉም አላቸው ። “ሰገዱላቸው” የሚለው ሐረግ ሰዎች በአምልኮ ውስጥ ይጠቀሙ የነበረውን አኳሃን ያሳያል ። (ተመሳሳይነትን: ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 8

1 ሰለሞን የእግዚአብሔርን ቤትና የራሱን ቤት የሠራበትን ሃያው ዓመት መጠናቀቂያ ላይ **2** ሰለሞን ኪራም የሰጠውን ከተሞች እንደገና ሠርቶ የእስራኤል ሰዎች እንዲኖሩባቸው አደረገ። **3** ሰለሞን ሐማትሱባን አጥቅቶ አሸነፋት። **4** በምድረ በዳም የነበረችውን ታድሞርን እና በሐማትም የሠራቸውን የዕቃ ቤቱን ከተሞች ሁሉ ሠራ። **5** በቅጥሮች፥ በበሮችና በመዝጊያዎች የተመሸጉትን የላይኛውን ቤትሆሮንን እና የታችኛዋን ቤትሆሮንን ከተሞች ሠራ። **6** የባዕላትንም ከተማ፥ ሰለሞንም የነበሩትን የዕቃ ቤት ከተሞች ሁሉ፥ የሰረገላዎቹንም ከተሞች፥ የፈረሰኞቹንም ከተሞች እንዲሁም በኢየሩሳሌም፥ በሊባኖስ እና በግዛቱ ሥር በነበሩት ስፍራዎች ሊሠራ የተደሰተባቸውን ነገሮች ሁሉ ሠራ። **7** ከኬጢያውያን፥ ከአሞራውያን፥ ከፌርዜያውያን፥ ከኤዊያውያን እና ከኢያቡሳውያን የቀሩትን የእስራኤል ወገን ያልሆኑትን ሕዝብ ሁሉ፥ **8** የእስራኤል ሕዝብ ያላጠፉአቸውን በምድሪቱ ላይ ከእነርሱ በኋላ የቀሩትን ዝርያዎቻቸውን ሰለሞን እስከ ዛሬ ድረስ የግዳጅ የጉልበት ሠራተኞች አደረጋቸው። **9** ነገር ግን ሰለሞን የእስራኤል ሰዎችን አንድም የግዳጅ የጉልበት ሠራተኞች አላደረጋቸውም፤ ይልቁንም ወታደሮቹ፥ አዛዦቹ፥ ሹማምንቶቹ እና የሠረገሎቹና የፈረሰኞቹ አዛዦች አደረጋቸው። **10** እነዚህ ሁለት መቶ ሃምሳው፥ ሥራውን የሚሰሩትን ሰዎች የሚቆጣጠሩ የንጉሥ ሰለሞን ዋና ተቆጣጣሪዎችን የሚያስተዳድሩ ዋና ሹማምንቶችም ነበሩ። **11** ሰለሞንም፦ "የእግዚአብሔር ታቦት የደረሰበት ቦታ ሁሉ ቅዱስ ስለሚሆን ሚስቴ በእስራኤል ንጉሥ በዳዊት ቤት መኖር አይገባትም" በማለቱ ምክንያት የፈርኦንን ልጅ ከዳዊት ከተማ ውጪ ለእርሷ ወደ ሰራላት ቤት አመጣት። **12** ከዚያም ሰለሞን በመተላለፊያው ፊት ለፊት በሠራው በእግዚአብሔር መሠዊያ ላይ የሚቃጠል መሥዋዕት አቀረበ። **13** ዕለታዊው መርሀ ግብር በሚጠይቀው መሰረት መሥዋዕቶች አቀረበ፤ በሙሴ ትዕዛዝ የሚገኙትን መመሪያዎች በመከተል በሰንበታቱ ቀናት፥ በየመባቻዎቹ እና በተደነገጉት በዓላት በየዓመቱ ሦስት ጊዜ በየቂጣው በዓል፥ በየሰባቱ ሱባኤ በዓል እና በየዳሱም በዓል አቀረባቸው። **14** ሰለሞን የአባቱን የዳዊትን ትዕዛዝ በመከተል ካህናቱን በየክፍላቸው፥ ሌዋውያንንም ዕለታዊው መርሀ ግብር እንደሚጠብቅባቸው እግዚአብሔርን ለማወደስና በካህናቱ ፊት ለማገልገል በየሥራቸው መደባቸው። የእግዚአብሔር ሰው ዳዊት ይህንንም አዘዘ ስለነበር ደጅ ጠባቂዎችን ደግሞ በእያንዳንዱ በር በየክፍላቸው መደባቸው። **15** እነዚህ ሰዎች ንጉሡ ለካህናቱና ለሌዋውያኑ ማናቸውንም ጉዳይ ወይም መጋዘኖቹን በተመለከተ ከሰጠው ትዕዛዛቱ አላፈነገጡም። **16** እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ቤት መሠረት ከተጣለበት ቀን አንስቶ እስከ ማጠናቀቂያው ድረስ የሰለሞን ሥራ ተከናወነ። በዚህ ሁኔታ የእግዚአብሔር ቤት ተጠናቅቆ ጥቅም ላይ ዋለ ። **17** ከዚህ በኋላ ሰለሞን በኤዶምያስ ምድር የባሕር ዳርቻ ወዳሉት ወደ ዔጽዮንጋብር እና ኤላት ሄደ። **18** ኪራምም የባህርን ነገር በሚገነዘቡ መርከቦቹ የሚታዘዙ መርከቦችን ላከለት።እነርሱም ከሰለሞን አገልጋዮች ጋር ወደ ኦፊር ሄዱ። ከዚያም አራት መቶ ሃምሳ መክሊት ወርቅ ለንጉሥ ሰለሞን አመጡ።

---

2 Chronicles 8:1

ይህ ተከሰተ
እዚህ ይህ ሐረግ የታሪኩን አዲስ ክፍል መጀመሪያ ለመጠቆም የሚያገለግል ነው። ቋንቋህ ይህንን የሚያሳይበት መንገድ ካለ እዚህ ቦታ ላይ መጠቀም ትችላለህ ።

ሃያ ዓመት በተጸፈጸመ ጊዜ
“ከ 20 ዓመት በኋላ” (ቁጥሮችን: ይመልከቱ)

ሰሎሞንም የእግዚአብሔርን ቤትና የራሱን ቤት ሠራ
ስለ ሰሎሞን ቤተመቅደሱ እና ቤተ መንግሥቱ እንዲሠሩ ለህዝቡ ትእዛዝ ማስተላለፍ እና እንዴተ መሠራት እንዳለበት መግለጽ ደራሲው ሲጽፍ ሰሎሞን ራሱ እንደሠራው አስመስሎ ጽፏል ። AT(አማራጭ ትርጉም): - “ሰለሞን የእግዚአብሔርን ቤትና የራሱን ቤት አሠራ” ወይም “በሰሎሞን መሪነት ቤተ መቅደሱና ቤተመንግስቱ ተሠራ” (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

ኪራም
ኪራም የጢሮስ ንጉሥ ነበር። በ 2 ኛ ዜና ምዕራፍ 2 ቁጥር 11 ውስጥ ስሙን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። አት: - “የጢሮስ ንጉሥ ኪራም” ወይም “ንጉሥ ኪራም” (የስሞችን አተረጓጎም: ይመልከቱ)

ሰሎሞም ኪራም የሰጠውን ከተሞች ሠራ
ሰለሞን ሌሎች ሰዎች እንደገና እንዲገነቡ ስለማዘዙ ደራሲው ሲጽፍ እሱ ራሱ እንደገነባው በማስመሰል ጽፏል ። AT: -“ሰለሞን ኪራም ለእርሱ የሰጡት ከተሞች እንዲገነቡ አደረገ” ወይም “ሰሎሞን አዘዘ ህዝቡም ኪራም የሰጣቸውን ከተሞች ገነቡ” (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

2 Chronicles 8:3

ሰሎሞን ሃማትሱባን ወጋ
ሰሎሞን መላውን ሠራዊት ይወክላል ። ኣት: - “የሰለሞን ሰራዊት በሃማትሱባ ከተማ ላይ ጥቃት ሰነዘረ” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከል እና የስሞችን አተረጓጎም

በምድረ በዳ ታድሞርን ሠራ
ታድሞር በዘመናዊቷ ሶሪያ የነበረች የእስራኤል ከተማ ናት። ሰለሞን ህዝቡን አዞ ከተማዋን ስለማሠራቱ ደራሲው ሲጽፍ ሰሎሞን ራሱ እንደሠራው በሚመስል መልኩ ጽፏል። አት: - “ሰለሞን በምድረ በዳ የታድሞር ከተማ እንዲሠራ አደረገ” ወይም “ሰሎሞን አዘዘ ፣ ሕዝቡም በምድረ በዳ ታድሞር የተባለችውን ከተማ ሠሩ” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን: ይመልከቱ)

ታድሞር
ታድሞር በዘመናዊቷ ሶሪያ የነበረች የእስራኤል ከተማ ነበረች። (የስሞችን አተረጓጎም : ይመልከቱ)

የእቃ ቤት ከተሞች
“የማጠራቀሚያ ከተሞች” ወይም “የአቅርቦት ከተሞች ።” እነዚህ መንግስት ምግብ ወይም አቅርቦትን ያከማቸባቸው ከተሞች ናቸው ።

ሐማት
ሐማት ከእስራኤል በስተ ሰሜን የሚገኝ ሲሆን፣ በአሁኗ ሶሪያ ውስጥ ነበር። (የስሞችን አተረጓጎም : ይመልከቱ)

2 Chronicles 8:5

ላይኛውበን ቤትሖሮን እና ታችኛውንም ቤትሖሮን
እነዚህ በይሁዳ የነበሩ ሁለት ከተሞች ናቸው። የላይኛው ከተማ በኮረብታ አናት ላይ ሲሆን ታችኛው ከተማ በሸለቆው ውስጥ ነበር ። አት: - “ከፍ ብሎ ያለውን ቤትሮን እና ታችኛውን ቤትሖሮን” ወይም “በኮረብታው ላይ የሚገኘውን ቤትሖሮን እና በሸለቆው የሚገኛውን ቤትሖሮን” (የስሞችን አተረጓጎም: ይመልከቱ)

ባዕላትን
ይህ በእስራኤል ውስጥ የነበረ ከተማ ነው። (የስሞች አተረጓጎም: ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በመንግስቱም ምድር ሁሉ
'የነገሠባቸውን አገሮች ሁሉ'

2 Chronicles 8:7

ከኋላቸው በምድር ላይ ዘራቸው የቀረውን
“እነዚያ ሰዎች ከሞቱ በኋላ በምድሪቱ የቀሩት ዘሮቻቸው”

ገባሮች
“ባሪያዎች”

እስከ ዛሬ ድረስ
ይህ ሐረግ ሰሎሞን ገባሮች አድርጎ ስላስቀመጣቸው ዘሮች ተጨማሪ መረጃ የሚሰጥ ነው ። አት: - “እናም ዘሮቻቸው አሁንም ገባሮች ናቸው” (ስለመለየት ከማስታወቅ እና ከማስታወስ ጋር: ይመልከቱ)

እስከዛሬ
ይህ የ 2ኛ ዜና መዋዕል መጽሐፍ የተጻፈበትን ጊዜ ያመለክታል። በ 2 ኛ ዜና ምዕራፍ 5 ቁጥር 9 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ።

2 Chronicles 8:9

ሰሎሞንም ከእስራኤል ልጆች ማንንም ባሪያ አላደረገም
“ሰሎሞን ከእስራኤል ሕዝብ ማንንም ባሪያ አላደረገም”

2 Chronicles 8:11

የፈርዖን ልጅ
“ሚስቱን የፈርዖንን ልጅ”

ወደ ሠራላት ቤት
ሰሎሞን በሠራተኞቹ አማካኝነት ለሚስቱ ቤት እንዲሠራ ስለማድረጉ ደራሲው ሲጽፍ ሰለሞን ራሱ እንደሠራው አስመስሎ ጽፏል ። ኣት: “ሠራተኞቹ እንዲሠሩላት የደረገው ቤት” ወይም “ሠራተኞቹን በማዘዝ ወዳሠራለት ቤት” (የባህሪ ስምን : ይመልከቱ)

የእስራኤል ንጉሥ ዳዊት
ዳዊት የሰሎሞን አባት ሲሆን ከሰለሞን በፊት ንጉሥ ነበር ።

የእግዚአብሔር ታቦት የገባበት ቦታ ሁሉ ቅዱስ ነውና
ታቦቱን ወደ ንጉሥ ዳዊት ቤት አመጡት ተብሎ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “የእግዚአብሔር ታቦት ወደዚያ ቤት እንዲመጣ ስለተደረገ፣ የእግዚአብሔር ታቦት የገባበት ቦታ ሁሉ ቅዱስ ነው” (የሚጠበቅ እውቀትን እና የልተገለጸ መረጃን: ይመልከቱ)

2 Chronicles 8:12

እርሱ በሠራው መሠዊያው
ሰሎሞን በሠራተኞቹ መሠዊያው እንዲሠራ ስለማድረጉ ደራሲው ሲጽፍ መሠዊያውን ሰሎሞን ራሱ እንደ ሠራው ጽፏል ። ኣት: - “ሰሎሞን በሠራተኞቹ በሠራው በእግዚአብሔር መሠዊያ ላይ” ወይም “ሠራተኞቹን አዘዘ በሠራው የእግዚአብሔር መሠዊያ” (የባህሪ ስም : ይመልከቱ)

የእርሱ መሠዊያ
“የእግዚአብሔር መሠዊያ”

ወለሉ
“የቤተ መቅደሱ በረንዳ” ወይም “ወደ ቤተ መቅደሱ መግቢያ።” ይህ ከመቅደሱ ፊት ለፊት በተያያዙት ዓምዶች የተደገፈ በረንዳ ነበር።

ዕለታዊ የጊዜ ሰሌዳ ያስፈልጋል
“በየቀኑ እንደ አስፈላጊነቱ”

መመሪያዎቹን መከተል
እዚህ “መመሪያዎችን መከተል” መመሪያዎቹን መታዘዝን ያመለክታል። አት: - “መመሪያዎቹን መታዘዝ” (ዘይቤያዊን: ይመልከቱ)

በሙሴ ትእዛዝ ውስጥ የሚገኙት መመሪያዎች
“ሙሴ ያዘዛቸውን”

በየዓመቱ ሦስት ጊዜ ይዘጋጃል
“በየዓመቱ የሚያከብሯቸው ሦስቱ በዓላት”

የዳስ በዓል
“የዳስ በዓል” ይህ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያደረገውን ዝግጅት ለማሰብ ነው ። የእስራኤል ሕዝብ በምድረ በዳ በተቅበዘበዙ ጊዜ ጊዜያዊ መጠለያዎች ውስጥ ይኖሩ ነበር ። ሰብሎቻቸውን በሚሰበስቡበት እያንዳንዱ ዓመት በአትክልት ስፍራዎቻቸው ውስጥ በጊዜያዊ መጠለያዎች ውስጥ ይቆዩ ነበር ። በሁለቱም ሁኔታዎች ውስጥ እግዚአብሔር በምጋቦቱ እረድቷቸዋል ።

2 Chronicles 8:14

የአባቱን የዳዊትን ድንጋጌዎች በመጠበቅ
“በአባቱ በዳዊት ትእዛዝ መሠረት” ወይም “አባቱ ዳዊት እንዳዘዘው”

እንዲሁም የበር ጠባቂዎችን በየክፍላቸው በየቦታቸው ሾማቸው
“ለእያንዳንዱ በር ዘበኛዎችን ሾመ”

የበር ጠባቂዎች
እነዚህ በሮቹን የሚጠብቁ እና ወደ ውስጥ ለመግባት ፈቃድ ያላቸውን ብቻ የሚያስገቡ ሌዋውያን ነበሩ ።

እነዚህ ሰዎች ከትእዛዛቱ አልራቁም
እዚህ “ከትእዛዛቱ ፈቀቅ ማለት” ከተሰጠው ትእዛዝ የተለየ ነገርን ማድረግን ይወክላል። በአዎንታዊ አረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል ። አት: - “እነዚህ ሰዎች ትእዛዛቱን በጥንቃቄ ይታዘዙ ነበር” (ዘይቤያዊን : ይመልከቱ)

2 Chronicles 8:16

በሰሎሞን ያታዘዘው ሥራ ሁሉ ተጠናቀቀ
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ሰለሞን ያዘዘውን ሥራ ሁሉ አጠናቀቁ” (ገቢራዊ ወይም ተብሮአዊ)

የእግዚአብሔር ቤት መሠረት ከተጣለበት ቀን ጀምሮ
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ እነርሱ የእግዚአብሔርን ቤት ከመሠረቱበት ቀን ጀምሮ” ወይም “እነርሱ የእግዚአብሔርን ቤት መሠረት ከሠሩበት ቀን ጀምሮ” (ገቢራዊ ወይም ተብሮአዊን : ይመልከቱ)

እስከ ተጨረሰ ድረስ
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “እነርሱ ቤተ መቅደሱን ሠርተው እስከሚጨርሱ ድረስ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን : ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ቤት ተጠናቀቀ
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “የእግዚአብሔር ቤት ተጠናቀቀ” ወይም “እነርሱ የያህዌን ቤት ሠርተው አጠናቅቀዋል” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን : ይመልከቱ)

ከዚያ በባህር ዳርቻው ወደሚገኘት ዔጽዮን ጋብር እና ወደ ኤሎት
እነዚህ በቀይ ባህር ዳርቻ ያሉ ከተሞች ናቸው ። መርከቦች ያሏቸው ሰዎች መቆም የሚችሉባቸው ወደቦች ነበሯቸው። አት: - የዔጽዮን ጋብር እና የኤሎት

ከተሞች ፣ በቀይ ባህር ዳርቻ ” (የስሞች አተረጓጎምን እና የሚጠበቅ እውቀትን እና የልተገለጸን መረጃ: ይመልከቱ)

ኦፊር
ይህ የቦታ ስም ነው ። የሚገኝበት ቦታ አይታወቅም ። (ተመልከት/ች: የስሞች አተረጓጎም)

450 መክሊት ወርቅ
“አራት መቶ እና አምሳ አምስት መክሊት ወርቅ።” ይህንን ወደ ዘመናዊ ልኬት መቀየር ትችላለህ ። ኣት: - “ከስድስት-አሥራ ሺህ ኪሎግራም የሚያህል ወርቅ” ወይም “አሥራ አምስት ቶን የሚያህል ወርቅ” (ቁጥሮችን እና መጽሐፍ ቅዱሳዊን ክብደት : ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 9

1 የሳባም ንግሥት የሰለሞንን ዝና በሰማች ጊዜ በከባባድ ጥያቄዎች ልትፈትነው ወደ ኢየሩሳሌም መጣች። ቅመማ ቅመሞች፥ ብዙ ወርቆች እና በርካታ
የከበሩ ማዕድናት ከተጫኑ ግመሎች ጋር ከብዙ ጓዝ ጋር መጣች። ወደ ሰለሞን በመጣች ጊዜ በልብዋ የነበረውን ሁሉ አጫወተችው። 2 ሰለሞንም
ጥያቄዎችዋን ሁሉ መለሰላት፤ ለሰለሞንም የከበደው ምንም ነገር አልነበረም። ያልመለሰውም ምንም ጥያቄ አልነበረም። 3 የሳባም ንግሥት የሰለሞንን
ጥበብ፥ ሠርቶትም የነበረውን ቤተ መንግሥት፥ 4 በጠረጴዛው ላይ የነበረውን ምግብ፥ የአገልጋዮቹን አቀማመጥ፥ የሎሌዎቹንም ሥራ እና አለባበሳቸውን፥
አስተናጋጆቹንና አለባበሳቸውንም፥ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥም መስዋዕት የሚያቀርብበትን ሁኔታ ባየች ጊዜ አንዳች መንፈስ አልቀረላትም። 5 ንጉሡንም ፦
"ስለምትናገረው ነገርና ስለ ጥበብህ በገዛ አገሬ የሰማሁት ዘገባ እውነት ነው፤ 6 እዚህ እስክመጣ ድረስ ግን የሰማሁትን አላመንኩም ነበር፤ አሁን ዓይኖቼ
አይተውታል። ስለ ጥበብህና ሃብትህ ግማሹ እንኳን አልተነገረኝም ነበር! ከሰማሁት ዝና ትበልጣለህ።" አለችው። 7 "ጥበብህን ስለሚሰሙ ህዝብህ ምንኛ
የተባረኩ፥ ዘወትር በፊትህ የሚቆሙ አገልጋዮችህም ምንኛ የተባረኩ ናቸው። 8 ለአምላክህ እግዚአብሔር ንጉሥ ትሆን ዘንድ ባንተ ደስ የተሰኘ እና በዙፋን ላይ
ያስቀመጠህ አምላክህ እግዚአብሔር ብሩክ ይሁን። አምላክህ እስራኤልን ለዘላለም ያፀናቸው ዘንድ ስለወደደ ፍትህንና ጽድቅን እንድታደርግላቸው በላያቸው
ላይ አነገሠህ" አለችው። 9 ለንጉሡም መቶ ሃያ መክሊት ወርቅ እና ከፍተኛ መጠን ያላቸው ቅመሞችንና የከበሩ ድንጋዮችን ሰጠችው። የሳባም ንግሥት
ለንጉሡ ለሰለሞን ከሰጠችው ከእደነዚህ የሚበልጥ መጠን ያላቸው ቅመሞች እንደገና ተሰጥቶት አያውቅም። 10 ከኦፊር ወርቅ ያመጡት የኪራም
አገልጋዮችና የሰለሞን አገልጋዮች የሰንደል እንጨትና የከበሩ ድንጋዮችን አመጡ። 11 ንጉሡም ከሰንደሉ እንጨት ለእግዚአብሔር ቤትና ለራሱ ቤት ደረጃዎችን
እንዲሁም ለሙዚቀኞቹ በገናዎችንና መሰንቆዎችን/ክራሮችን አስደረገ። እንደዚህ ያለ እንጨት ከዚያ በፊት በይሁዳ ምድር ታይቶ አይታወቅም ነበር። 12 የሳባም
ንግሥት ወደ ንጉሡ ካመጣችው የበለጠ ንጉሥ ሰለሞን የተመኘችውን ሁሉ፥ የለመነችውንም ሁሉ ሰጣት። እርስዋም ተመልሳ ከአገልጋዮችዋ ጋር ወደ ራሷ
ምድር ሄደች። 13 በአንድ ዓመት ለሰለሞን የመጣለት ወርቅ ክብደት ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት መክሊት ወርቅ ነበር። 14 ይህም ነጋድራሶችና ነጋዴዎች
ካመጡት ወርቅ በተጨማሪ ነው። የዓረብም ነገሥታት ሁሉ እና የአገሪቱ ሹማምንት ለሰለሞን ወርቅና ብር ያመጡ ነበር። 15 ንጉሡም ሰለሞን በጥፍጥፍ ወርቅ
ሁለት መቶ ትልልቅ ጋሻዎችን ሠራ። በእያንዳንዳቸውም ውስጥ ስድስት መቶ ሰቅል ጥፍጥፍ ወርቅ ገብቶባቸው ነበር። 16 ከጥፍጥፍ ወርቅም ሦስት መቶ
ጋሻዎችን ሠራ። በእያንዳንዱም ጋሻ ውስጥ ሦስት ምናን ወርቅ ገብቶበት ነበር። ንጉሡም በሊባኖስ ዱር ቤተ መንግሥት ውስጥ አስቀመጣቸው። 17 ከዚያም
ንጉሡ ከዝሆን ጥርስ ታላቅ ዙፋን አሠርቶ ከሁሉ በበለጠ ወርቅ አስለበጠው። 18 ወደ ዙፋኑ የሚያደርሱ ስድስት ደረጃዎች ነበሩት፤ የዙፋኑም የላይኛው ክፍል
ከጀርባው ክብ ነበር። በመቀመጫው በእያንዳንዱ ጎን በኩል የክንድ መደገፊያዎች እና ከመደገፊያዎቹም አጠገብ ሁለት አንበሶች ቆመው ነበር። 19
በስድስቱም ደረጃዎች በእያንዳንዱ ላይ በእያንዳንዱ ጎን በኩል አንድ አንበሳ አስራ ሁለት አንበሶች ቆመው ነበር። በሌላ በየትኛውም መንግሥት እንደ እርሱ ያለ
ዙፋን አልነበረም። 20 ንጉሥ ሰለሞን የሚጠጣባቸው ዕቃዎች በሙሉ የወርቅ ነበሩ፤ በሊባኖስ ዱር ቤተ መንግሥት ውስጥ የነበሩትም የሚጠጣባቸው
ዕቃዎች በሙሉ ከንፁህ ወርቅ የተሠሩ ነበሩ። በሰለሞን ዘመን ብር ዋጋ እንዳለው የማይቆጠር ስለነበር አንዳቸውም ብር አልነበሩም። 21 ከኪራም መርከቦች
ጋር በመሆን በባሕር ላይ የሚሄዱ ብዙ መርከቦች ነበሩት። በየሦስት ዓመቱም አንድ ጊዜ መርከቦቹ ወርቅ፥ ብር እና የዝሆን ጥርስ እንዲሁም ጦጣዎችና
ዝንጀሮዎች ይዘው ይመጡ ነበር። 22 በመሆኑም ንጉሥ ሰለሞን ከዓለም ነገሥታት ሁሉ በባለጠግነትና በጥበብ በለጠ። 23 ምድር ሁሉ እግዚአብሔር በልቡ
ያኖረውን ጥበቡን ይሰሙ ዘንድ የሰለሞንን መገኘት ይፈልጉ ነበር። 24 ከዓመት ዓመት የሚጎበኙትም ግብር፥ የብርና የወርቅ ዕቃዎች፥ አልባሳት፥ የጦር
መሣሪያዎች እና ቅመማ ቅመሞች እንዲሁም ፈረሶችና በቅሎዎችን ያመጡ ነበር። 25 ሰለሞንም በሰረገሎች ከተሞችና ከራሱ ጋር በኢየሩሳሌም
በተመደበላቸው ሥፍራ ለሚያኖራቸው ለፈረሶችና ለሰረገላዎች አራት ሺህ ጋጣዎች አስራ ሁለት ሺህም ፈረሰኞች ነበሩት። 26 ከኤፍራጥስ ወንዝ ጀምሮ እስከ
ፍልስጤም ምድርና እስከ ግብፅ ዳርቻ ድረስ ባሉ ነገሥታት ሁሉ ላይ ይገዛ ነበር። 27 ንጉሡም በምድር ላይ እንዳለ ድንጋይ ያህል የበዛ ብር በኢየሩሳሌም
ነበረው። የዝግባውንም እንጨት በቆላ እንዳሉት የሾላ ዛፎች የተትረፈረፈ እንዲሆን አደረገው። 28 ለሰለሞንም ከግብፅና ከየአገሩ ሁሉ ፈረሶችን ያመጡለት
ነበር። 29 ሰለሞንን የሚመለከቱ ሌሎች ነገሮች የመጀመሪያውና የመጨረሻው በነቢዩ በናታን ታሪክ፥ በሴሎናዊውም በአሒያ ትንቢት፥ ስለ ናባጥም ልጅ ስለ
ኢዮርብዓም ባየው በባለ ራዕዩ በአዶ የተፃፉ አይደለምን? 30 ሰለሞንም በኢየሩሳሌም በእስራኤል ሁሉ ላይ አርባ ዓመት ነገሠ። 31 ከአባቶቹም ጋር አንቀላፋ፤
ሕዝቡም በአባቱ በዳዊት ከተማ ቀበሩት፤ ልጁም ሮብዓም በእርሱ ቦታ ነገሠ።

---

2 Chronicles 9:1

ከታላቅ ጓዝ ጋር መጣች
“እጅግ በጣም ብዙ የአገልጋዮች ቡድን” ወይም “እጅግ በጣም ረዥም የአገልጋዮች መስመር”

በልቧ ውስጥ ያለው ሁሉ
ይህ ጠቅለል ያለ ገለጻ ነው ። አት: - “ማወቅ የፈለገችውን ሁሉ” (ግነትን እና አጠቃላይን: ይመልከቱ)

እርሱ ያልመለሰው ጥያቄ አልነበረም
ይህ በአዎንታዊ አረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል ። አት: - “እርሱ ሁሉንም ጥያቄዎች መለሰለት” (ድርብ አሉታዊን: ይመልከቱ)

2 Chronicles 9:3

የሳባ ንግሥት የሰሎሞንን ጥበብና የሠራውን ቤተ መንግሥት ባየች ጊዜ
እዚህ ላይ “የሰሎሞንን ጥበብ አየች” የሚለው ሰሎሞን በጣም ጥበበኛ መሆኑን መገንዘቧን ያሳያል ። አት: - “የሳባ ንግሥት ሰሎሞን ጥበበኛ እንደ ሆነ ባየች ጊዜ እና እርሱ የሠራውን ቤተ መቅደስ ባየች ጊዜ (ዘይቤያዊን : ይመልከቱ)

እርሱ የሠራውን ቤተ መንግሥት
ሰሎሞን ሠራተኞቹ ቤተ መንግሥቱን እንዲሠሩለት ስለማድረጉ ደራሲው ሰሎሞን ራሱ እንደሠራው አድርጎ ጽፏል። አት: - “ሰሎሞን ሠራተኞቹ እንዲሠሩለት ያደረገው ቤተ መንግሥት” ወይም “ሠራተኞቹ አዞ ያሠራው ቤተ መንግሥት” (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

የአገልጋዮቹ መቀመጫ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) አገልጋዮቹ የሚኖሩበት ወይም 2) አገልጋዮቹ በጠረጴዛ ዙሪያ እንዴት እንደሚቀመጡ ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የወይን ጠጅ አሳላፊዎቹ
“የወይን ጠጅ አገልጋዮቹ።” እነዚህ በውስጡ ምንም መርዝ እንዳይኖር ለማረጋገጥ ንጉሡ የሚጠጣውን ወይን ጠጅ በመቅመስ የሚያገለግሉ አገልጋዮች ነበሩ ። ወይኑን ለመጠጣት ደህና ከሆነ ለንጉሡ ይሰጡታል ።

በእሷ ውስጥ ትንፋሽ አልቀረላትም
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው ። አት: - “በጣም ተደነቀች” (ፈሊጥ: ይመልከቱ)

2 Chronicles 9:5

በገዛ አገሬ የሰማሁት
“በገዛ አገሬ ሳለሁ የሰማሁት”

ቃልህና ጥበብህ
እዚህ “ጥበብ” የሚለው ቃል “ቃላት” የሚለውን ቃል ሊገልጽ ይችላል ። ኣት ““ የጥበብ ቃላትህ (ሂንዲኢያስን: ይመልከቱ)

አሁን አይኖቼ አዩት
“ዓይኖቼ” የሚለው ሐረግ እሷ ራሷን እንዳየችው የሚያጎላ ነው ። ኣት: - “አሁን እኔ ራሴ አይቻለሁ” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ ስለመወከል: ይመልከቱ)

ስለ ጥበብህና ሀብትህ ግማሹ እንኳ አልተነገረኝም
ይህ በገቢራዊ ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አት: - “ግማሽ ያህል እንኳ ስለ ጥበብህና ሀብትህ አልተነገረኝም” ወይም “ከነገሩኝ ይልቅ ብልህና ባለጸጋ ነህ” (ገቢራዊ ወይም ተብሮአዊ: ይመልከቱ)

2 Chronicles 9:7

ሕዝብህ ምንኛ የተባረኩ ናቸው!
ይህ የተደነቀች መሆኗን የሚያሳይ መግለጫ ነው ። አት: - “ሕዝብህ እጅግ የተባረከ ነው” (ግነትን: ይመልከቱ)

በፊትህ የሚቆሙ ባሪያዎችህ ምንኛ ደስተኞች ናቸው!
ይህ እስከምትደነግጥ ድረስ መደነቋን የሚያሳይ መግለጫ ነው ። AT: “በፊትህ የሚቆሙ ባሪያዎችህ እጅግ የተባረኩ ናቸው” (ትእምርተ አንክሮን : ይመልከቱ)

እነሱ ጥበብህን ይሰማሉ
እዚህ “ጥበብ” እሱ የሚናገራቸውን ጥበባዊ ነገሮች ይወክላል። አት: - “አንተ የምትናገረውን ጥበብን ያዘሉ ነገሮችን ይሰማሉ” (የባህሪ ስምን : ይመልከቱ)

ንጉሥ እንድትሆን በዙፋኑ ላይ የስቀምጥህ ዘንድ የወደደህ
እነዚህ ሐረጎች ሰዎች ያህዌን ለምን ማመስገን እንዳለባቸው ይናገራሉ ። ኣት: - “በአንተ ተደስቷል ፣ በዙፋኑም ላይ አስቀምጦሃል” (መለየትን ከማስታወቅ እና ከማስታወስ ጋር : ይመልከቱ)

በአንተ ደስ ያለው
“በአንተ ደስ የተሰኘ”

በአምላካችሁ በእግዚአብሔር ፊት ንጉሥ ትሆን ዘንድ በዙፋኑ ላይ ያስቀመጠህ
በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ የመሆን ሀሳብ እንደ ያህዌህ የመግዛትን ስልጣን ያመለክታል ። ንጉሥ መሆን “ለያህዌህ” ያህዌን እንደ ንጉሥ መወከል ማለት ነው ። ኣት: - “እንደ እርሱ እንድትገዛ ሥልጣን የሰጠ ፣ አምላክህንም እግዚአብሔር እንደ ንጉሥ እንድትወክል (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

ለዘላለም እንዲያጸናቸው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “መመስረት” በአጠቃላይ እነሱን መርዳትን ይወክላል። ኣት: - “ለዘላለም እንዲረዳቸው” ወይም 2) “መመስረት” የሚለው ቃል እንደ አንድ ህዝብ ጠንካራ ያደርጋቸዋል ። ኣት: - “ለዘላለም ሕዝብ እንዲሆኑ ለማድረግ” (ዘይቤያዊን: ይመልከቱ)

ፍርድን እና ጽድቅን እንድታደርግ ነው
“ፍትህ” እና “ፅድቅ” የሚሉት የነገሮች ስሞች “ፍትሐዊ” እና “በጽድቅ” በሚሉት ቃላት ሊገለጹ ይችላሉ ። ኣት ““ በፍትህ እና በጽድቅ እንድትገዛ ”ወይም“ ትክክል እና ጽድቅ የሆነውን እንድታደርግ ” (የረቂቅ ስምን: ይመልከቱ)

2 Chronicles 9:9

120 መክሊት
“አንድ መቶ ሀያ መክሊት።” አንድ መክሊት ከ 33 ኪሎ ግራም ጋር እኩል የሆነ የክብደት መለኪያ ነው። ይህንን ወደ ዘመናዊ ልኬት መለወጥ ትችላለህ። ኣት: - “አራት ሺህ ኪሎ ግራም ገደማ ወርቅ” ወይም “አራት ሜትሪክ ቶን የሚያህል ወርቅ” (ቁጥሮችን እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክብደትን : ይመልከቱ)

እጅግ ብዙ ቅመማ ቅመም ... ሊሰጠው የማይችለውን
“የተሰጠው ሁል የሚበልጥ ” ግስ በገቢራዊ ቀርጽ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ከሳባ ንግሥት የበለጠ ለንጉሥ ሰሎሞን ቅመማ ቅመም የሰጠው የለም (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን : ይመልከቱ)

2 Chronicles 9:10

ኪራም
ኪራም የጢሮስ ንጉሥ ነበር። በ 2 ኛ ዜና ምዕራፍ 2 ቁጥር 11 ውስጥ ስሙን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። ኣት: - “የጢሮስ ንጉሥ ኪራም” ወይም “ንጉሥ ኪራም” (የስሞችን አተረጓጎም: ይመልከቱ)

ኦፊር
ይህ የቦታ ስም ነው ። የሚገኝበት ቦታ አይታወቅም ። በ 2 ኛ ዜና ምዕራፍ 8፡ 18 ውስጥ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። (የስሞችን አተረጓጎም : ይመልከቱ)

የሰንደል እንጨት
የሰንደል እንጨት በሊባኖስ ውስጥ የሚያድግ የዛፍ አይነት ነው። ንጉሥ ኪራም እንዲህ ዓይነቱን እንጨት ለሰሎሞን ላከ። በ 2 ኛ ዜና 2 8 ውስጥ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ።

ንጉሡም ደርብ ሠራ . . . በገናንና መሰንቆዎችን ሠራ
ንጉሱ ሰራተኞቹን እነዚህን እቃዎች እንዲሠሩ ማድረጉን ደራሲው ሲጽፍ ንጉሡ እራሱ እንደሠራው አድርጎ ጽፏል። አት: - “ንጉሡ ሠራተኞቹን ደረጃዎችን .... በገናዎችን ፣ መሰንቆዎችን እንዲሠሩ አደረገ ፣” ወይም የንጉሡ ሠራተኞች ደረጃዎችን ... ደግሞም በገናዎችን እና መሰንቆዎችን ሠሩ። (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

ከዚህ በፊት በይሁዳ ምድር እንደዚህ ያለ እንጨት ታይቶ አይታወቅም ነበር
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ከዚህ በፊት በይሁዳ ምድር እንደዚህ ያለ እንጨት ማንም አይቶ አያውቅም” (ገቢራዊን እና ተብሮአዊን: ይመልከቱ)

2 Chronicles 9:13

በአንድ ዓመት ውስጥ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ የሚያመለክተው እያንዳንዱን ዓመት ወይም 2) ይህ የሚያመለክተው አንድን የተወሰነ ዓመት ነው።

666 መክሊት ወርቅ
ታለንት ከ 33 ኪሎ ግራም ጋር እኩል የሆነ የክብደት መለኪያ ነው። ይህንን ወደ ዘመናዊ ልኬት መለወጥ ትችላለህ ። ኣት: - “ሀያ ሁለት ሺህ ኪሎግራም

ወርቅ” ወይም “ወደ ሃያ ሁለት ሜትሪክ ቶን ወርቅ” (መጽሕፍ ቅዱሳዊ ክብደት እና ቁጥሮች: ይመልከቱ)

2 Chronicles 9:15

ንጉሥ ሰሎሞን ሠራ
ሰለሞን በሠራተኞቹ ስላሠራቸው ጋሻዎች ደራሲው እራሱ እንዳሠራቸው በማስመሰል ጽፏል። ኣት: - “ንጉስ ሰሎሞን ሰሎሞን ሠራተኞቹን ሠራላቸው” ወይም “የንጉሥ ሰለሞን ሠራተኞቹ እንዲሠሩት አደረገ” (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

ሁለት መቶ ትላልቅ ጋሻዎች
“200 ትላልቅ ጋሻዎች” (ቁጥሮችን: ይመልከቱ)

ጥፍጥፍ ወርቅ
“ሰዎች ቀጥቅጠው ቀጭን የሚያደርጉት ወርቅ”

እያንዳንዳቸው ስድስት ስድስት ሰቅል ወርቅ ገባ
እዚህ “የገባው” የሚለው ሐረግ አብሮ መደረግን ይወክላል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ጋሻዎቹ በወርቅ የተሸፈኑ ነበሩ። ኣት: “እያንዳንዱ ጋሻ በስድስት መቶ ሰቅል ወርቅ” ወይም 2) ጋሻዎቹ ከወርቅ የተሠሩ ነበሩ። አት: “እያንዳንዳቸውን ጋሻ ከስድስት መቶ ሰቅል ወርቅ ሠራ”

ስድስት መቶ ሰቅል ወርቅ
አንድ ሰቅል ከ 11 ግራም ጋር እኩል የሆነ የክብደት መለኪያ ነው። ይህንን ወደ ዘመናዊ ልኬት ሊለውጡት ይችላሉ። አት: - “ስድስት ተኩል ተኩል ኪሎግራም ወርቅ” (መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክብደትን : ይመልከቱ)

ስድስት መቶ ሰቅል
“ሰቅል” የሚለው ቃል በዕብራይስጡ ጽሑፍ አይታይም። አንዳንድ የቅርብ ጊዜ ትርጉሞች ከግማሽ ሰቅል ጋር ተመጣጣኝ የሆነውን ባቃ ተብሎ የሚጠራው መለኪያ ነው ብለው ያስባሉ ። ይህን ግምትን የሚያደርግ ማንኛውም ትርጉም ከሶስት ኪሎግራም ጋር እኩል የሆነ ልኬትን ያመለክታል ።

ይህንንም ሠራ
ደራሲው ሰሎሞን በሠራተኞቹ ስላሠራቸው ጋሻዎች ሲጽፍ ሰሎሞን እራሱ እንዳሠራቸው በማስመሰል ጽፏል። ኣት: - “እንደገናም ንጉሥ ሰሎሞን ሠራተኞቹን አሠራ” ወይም “ ደግመው ሠራተኞቹ ሠሩ” (የባህሪ ስምን : ይመልከቱ)

ሦስት መቶ ጋሻዎች
“300 ጋሻዎች” (ቁጥሮችን: ይመልከቱ)

በእያንዳንዱ ጋሻ ውስጥ ሦስት መቶ ሰቅል ወርቅ ነበር
እዚህ “የገባበት ሐረግ” የሚለው ሐረግ ተጨመሪ ግብአት መሆኑን ያመለክታል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ጋሻዎቹ በወርቅ የተሸፈኑ ነበሩ። ኣት: “እያንዳንዱን ጋሻ በሦስት ሚናስ ወርቅ ሸፍኗቸዋል” ወይም 2) ጋሻዎቹ ከወርቅ የተሠሩ ነበሩ። አትቲ: - “እያንዳንዱ ጋሻ በከሦስት መቶ ሰቅል ወርቅ ሠሩ”

ሦስት ሰቅል ወርቅ
ሰቅል 600 ግራም ያህል ነው ። ይህንን ወደ ዘመናዊ ልኬት መለወጥ ትችላለህ። አት: - “አንድ ሙሉ ሦስት አራተኛ ኪሎ ግራም ወርቅ” (መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክብደትን : ይመልከቱ)

ንጉሡም አስቀመጣቸው
ሰሎሞን በሠራተኞቹ ጋሻዎችን በቦታቸው እንዲያስቀምጧቸው ስለማድረጉ ደራሲው ሲጽፍ እራሱ ራሱ እንዳስቀመጣቸው በማስመሰል ጽፏል። ኣት: - “ንጉሥ ሰሎሞን ሰራተኞቹ እንዲያስቀምጧቸው አደረገ” ወይም “የንጉሥ ሰሎሞን ሠራተኞች አስቀመጧቸው” (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

የሊባኖስ ዱር ቤት
የሰለሞን ቤተ መንግሥት ከሊባኖስ ከሚገኙ ዛፎች ተሠርቷል ። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ የአንድ ትልቅ ክፍል ስም ነበር ። ኣት: - “የሊባኖስ ዱር አዳራሽ” ወይም 2) ይህ የጠቅላላው ቤተ መንግስት ስም ነበር። (የስሞችን አተረጓጎም: ይመልከቱ)

2 Chronicles 9:17

ንጉሡም ታላቅ ዙፋን ሠራ
ሰሎሞን ስላሠራቸው ዙፋን ደራሲው ሰሎሞን እራሱ እንዳሠራቸው በማስመሰል ጽፏል። ኣት: - “ንጉሡ ሠራተኞቹን ታላቁን ዙፋን እንዲሠሩ ያደርግ ነበር” ወይም “የንጉሡ ሠራተኞች ሠሩት” (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

ታላቅ የዝሆን ጥርስ ዙፋን
“በዝሆን ጥርስ ያጌጠ ታላቅ ዙፋን”

የዝሆን ጥርስ
የዝሆን ጥርስ ጠንካራ ሲሆን፣ እንደ ዝሆን ፣ ዋልሮ ፣ ወይም ጉማሬ ካሉ ትላልቅ እንስሳት ጥርሶች የሚገኝ ነጭ ንጥረ ነገር ነው ።(የማይታወቁትን ይተርጉሙ)

ሁለት አንበሶች
እነዚህ ሐውልቶች ናቸው። ኣት: - “ሁለት የአንበሶች ሐውልቶች” (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን: ይመልከቱ)

2 Chronicles 9:19

የሊባኖስ ዱር ቤት
የሰለሞን ቤተ መንግሥት ከሊባኖስ ከሚገኙ ዛፎች ተገንብቷል ። ይህንን በ 2 ኛ ዜና መዋዕል 9፡ 16 ውስጥ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ የአንድ ትልቅ ክፍል ስም ነበር ። ኣት: - “የሊባኖስ ዱር አዳራሽ” ወይም 2) ይህ የጠቅላላው የቤተ መንግስቱ ስም ነበር። አት: - “የሊባኖስ ዱር ቤተ መንግስት” (የስሞች አተረጓጎምን: ይመልከቱ)

በሰለሞን ዘመን ብር እንደ ዋጋ አይቆጠርም
በሰለሞን ዘመን ብር በጣም የተለመደ ከመሆኑ የተነሳ አንድ ንጉስ ሀብቱን ማሳየት ከፈለገ ከብር ብር አያደርገውም ። ይልቁንም ያን ያህል ያልተለመደ እና የበለጠ ዋጋ ያለው ወርቅ ይጠቀማል ። ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “ሰዎች ብርን በጣም ከፍ አድርገው አይመለከቱትም ነበር” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን : ይመልከቱ)

በሰሎሞን ዘመን
እዚህ “የሰለሞን ዘመን” የሚለው ኃረግ የሚያመለክተው ሰሎሞን የነገሠበትን ጊዜ ነው ። ኣት: - “ሰሎሞን በገዛበት ጊዜ” (የሚጠበቁ እውቀቶችንና ያልተገለጹ መረጃዎችን: ይመልከቱ)

በውቅያኖስ ላይ የሚጓዙ መርከቦችን አመጣጥ
“በውቅያኖሱ ላይ የሚጓዙ መርከቦች ስብስብ”

ከኪራም መርከቦች ጋር በመሆን
“ከኪራም መርከቦች ጋር ”

ዝንጀሮዎች እና ኤፕስ የሚባሉ እንሰሳቶችን
እዚህ “ኤፕስ” ተብሎ የተተረጎመው ቃል ከዝንጀሮዎችና ከባቡኖች የቱን እንደሚያመለክት ግልጽ አይደለም ። እዚህ “ኤፕስ” ተብሎ የተተረጎመው ቃል ዝንጀሮዎችን ይሁን ፒኮኮችን ግልጽ አይደለም ። በአጠቃላይ “ከሩቅ የመጡ እንስሳት” ወይም “ከአፍሪካ የመጡ እንስሳትን” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል ።

2 Chronicles 9:22

የምድር ነገሥታት ሁሉ
እዚህ “ሁሉ” የሚለው ቃል ጠቅለል ያለ ንግግር ነው ። አት: - “ከዓለም ዙሪያ የመጡ ነገሥታት” (ተመልከት/ች: ግነት እና አጠቃላይ)

የሰሎሞንን መገኘት ፈለገ
የአንድ ሰው መገኘት ሲባል ግለሰቡን ለማናገር እና ለማዳመጥ መቻልን ያመለክታል ። አት: - “ሰለሞንን ለመጎብኘት ፈለገ” ወይም “ሰለሞንን ለመጎብኘት መጣ” (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

እግዚአብሔር በልቡ ያኖረውን ጥበብ ይሰሙ ዘንድ
ልብ ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን የአንድን ሰው አስተሳሰብ የሚያመለክት ነው። በዚህ ሥፍራ ደግሞ የአንድ ነገር መያዣ እንደሆነ በሚመስል ሁኔታ ተነግሯል ። የነገሮች ሥም የሆነው “ጥበብ” የሚለው ቃል ጥበብ የተሞላበትን አስተሳሰብና አነጋገር የሚገልጽ ነው። ኣት: - “እግዚአብሔር ምን ያህል ጥበበኛ እንዳደረገው ለመስማት” ወይም “እግዚአብሔር እንዲናገር ያስቻለውን ጥበብ ሰሎሞን ሲናገር ለመስማት” (የባህሪ ስምን : ይመልከቱ)

እግዚአብሔር በልቡ ያኖረውን
እግዚአብሔር ጥበብን በሰሎሞን ልብ ውስጥ ማስቀመጡ ሰሎሞንን ጥበበኛ ማድረጉን ያመለክታል ። በዚህ: - “እግዚአብሔር የሰጠው” ወይም “እግዚአብሔር ከጠቢብ ስላደረገው” (የባህሪ ስምን : ይመልከቱ)

አመት አልፎ አመት
ይህ ፈሊጥ ነው ። ኣት: - “በየዓመቱ” (ፈሊጥን: ይመልከቱ)

2 Chronicles 9:25

አራት ሺህ ጋሻ ... አሥራ ሁለት ሺህ ፈረሰኞች
“4,000 ድንኳን... 12,000 ፈረሰኞች” (ቁጥሮችን: ይመልከቱ)

መሸጫዎች
ይህ ፈረሶች የተቀመጡበት አነስተኛ ሜዳ ነው ።

2 Chronicles 9:27

መሬት ላይ ያሉት ድንጋዮች
ይህ ግነት ሲሆን እጅግ ብዙ ብር እንደነበረ በማጉላት የሚያሳይ ነው። (ግነትን እና አጠቃላይን : ይመልከቱ)

እነርሱ ለሰሎሞን ፈረሶችን ከግብጽና ከየአገሩ ሁሉ ያመጡለት ነበር
“እነርሱ” የሚለው ቃል የሰሎሞን ነጋዴዎች ያመለክከታል ። ሆኖም ይህ ዓረፍተ-ነገር የነጋዴዎቹን ሥራ የሚናገር ሳይሆን የሰሎሞን ፈረሶች ከየት እንደመጡ የሚገልጽ ነው። ኣት: - “ፈረሶች ከግብፅና ከምድር ሁሉ ወደ ሰሎሞን ተወሰዱ” ወይም “የሰለሞን ፈረሶች ከግብጽና ከምድር ሁሉ የመጡ ነበሩ”

ከሁሉም አገሮች
“ሁሉም” የሚለው ጠቅለል ያለ መግለጫ ነው። አት: - “ከብዙ ሌሎች ቦታዎች” ወይም “ከብዙ ሌሎች አገሮች” (ግነትን እና አጠቃላይን : ይመልከቱ)

የመጀመሪያው እና የመጨረሻው
“የመጀመሪያው እና የመጨረሻው” የሚለው ሐረግ የሰለሞንን የግዛት ዘመን በሙሉ ይወክላል። አት: “ከመጀመሪያው እስከ ግዛቱ መጨረሻ” (ሜሪዝምን: ይመልከቱ)

የተጻፈ አይደለምን? (ይህም ስለ ናባጥ ልጅ ስለ ኢዮርብዓም መረጃ ያለው ነው)
ደራሲው ጥያቄውን ሌሎች ሰዎች ስለ ሰሎሞን እንደጸፉ ለአንባቢዎች ለማስታወስ ተጠቅሞአል ። ይሄ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል ፣ ‹ተጽፈዋል... (ይህም ስለ ናባጥ ልጅ ስለ ኢዮርብዓም መረጃ ያለው ነው)” ወይም “ሰዎች ሰለእነርሱ ጽፈዋል ... (ደግሞም ስለ ናባጥ ልጅ ስለ ኢዮርብዓም መረጃ የነበረው ነው”) ።: (አወያይ መጠይቅን: ይመልከቱ)

የነቢዩ የናታን ታሪክ... በሴሎናዊዉውም በኦሒያ ትንቢት ... በባለ ራእዩ በአዶ ራእይ
እነዚህ 2ኛ ዜና መዋዕል በተጻፉበት ጊዜ የነበሩ የአንዳንድ ጽሑፎች ስሞች ናቸው ፣ አሁን ግን የሉም።

ሴሎናዊው ኦሒያ
ይህ የእስራኤል ህዝብ በሁለት መንግስታት እንደሚከፈል የተናገረው ከሴሎና የመጣ ነቢይ ነው ።

ሴሎናዊው
ይህ ከሴሎና ከተማ የሆኑ ሰዎች ስያሜ ነው ። (የስሞች አተረጓጎም: ይመልከቱ)

ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ
ይህ ሞቱን በተመለከተ ሥርዓት ያለው አገላለጽ ነው ። አት: - “ሞተ”(ዘወርዋራን : ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 10

1 እስራኤልም ሁሉ ሊያነግሡት ወደ ሴኬም እየመጡ ስለነበር ሮብዓም ወደ ሴኬም ሄደ። 2 የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም ይህንን ሰማ (ከንጉሡ ከሰለሞን ፊት
ሸሽቶ በግብፅ ይኖር ነበር፤ ነገር ግን ኢዮርብዓም ከግብፅ ተመለሰ) 3 ልከውም አስጠሩት፤ ኢዮርብዓም እና እስራኤልም ሁሉ መጡ፤ ሮብዓምንም ተናገሩት፤ 4
"አባትህ ቀንበራችንን ከባድ አድርጎት ነበር፤ ስለዚህ አሁን አንተ ጽኑውን የአባትህን ሥራ ቀሊል፥ በእኛ ላይ ያደረገውንም ከባድ ቀንበር የማያስቸግር አድርግልን፤
እኛም እንገዛልሃለን" አሉት። 5 ሮብዓምም ፦ "ከሦስት ቀናት በኋላ ወደ እኔ ተመልሳችሁ ኑ" አላቸው፤ ሕዝቡም ሄዱ። 6 ንጉሥ ሮብዓም፦ "ለእነዚህ ሰዎች
መልስ እንድሰጣቸው እንዴት ትመክሩኛላችሁ?" ብሎ አባቱ ሰለሞን በሕይወት እያለ በፊቱ ይቆሙ የነበሩትን ሽማግሌዎች አማከራቸው። 7 እነርሱም ፦ "ለዚህ
ሕዝብ መልካም ብታደርግላቸውና ብታስደስታቸው፥ በመልካም ቃል ብታናግራቸው ሁልጊዜ አገልጋዮችህ ይሆኑልሃል፤" ብለው ተናገሩት። 8 ሮብዓም ግን
ሽማግሌዎቹ የመከሩትን ምክር ችላ ብሎ ከእርሱ ጋር ያደጉትን በፊቱም የሚቆሙትን ወጣቶች አማከራቸው። 9 "'አባትህ በእኛ ላይ ያደረገውን ቀንበር
አቅልልልን' ላሉኝ ሰዎች መልስ እንድሰጣቸው ምን ምክር ትሰጡኛላችሁ?" አላቸው። 10 ከሮብዓም ጋር ያደጉት ወጣቶች ተናገሩት፦ "'አባትህ ሰለሞን
ቀንበራችንን አከበደብን፤ አንተ ግን ልታቀልልን ይገባል' ብለው ለነገሩህ ሰዎች፦ 'ትንሿ ጣቴ ክአባቴ ወገብ ትወፍራለች' ልትላቸው ይገባል። 11 "በመሆኑም
አሁን ምንም እንኳን አባቴ ቀንበር አክብዶባችሁ የነበረ ቢሆንም እኔ ቀንበራችሁ ላይ እጨምራለሁ፤ አባቴ በአለንጋ ገርፏችሁ ነበር፤ ነገር ግን እኔ በጊንጥ
እገርፋችኋለሁ" አላቸው። 12 በመሆኑም ንጉሡ፦ "በሦስተኛው ቀን ወደ እኔ ተመልሳችሁ ኑ" ባላቸው መሠረት ኢዮርብዓምና ሕዝቡ ሁሉ በሦስተኛው ቀን ወደ
ሮብዓም መጡ። 13 ንጉሡም በጽኑ ምላሽ መለሰላቸው፤ ንጉሡም ሮብዓም የሸማግሌዎችን ምክር ቸል አለ። 14 የወጣቶቹን ምክር ተከትሎ ተናገራቸው፤
"ቀንበራችሁን ይበልጥ አከብድባችኋለሁ፤ እጨምርባችኋለሁ። አባቴ በአለንጋ ገርፏችሁ ነበር፤ ነገር ግን እኔ በጊንጥ እገርፋችኋለሁ" አላቸው። 15 በመሆኑም
ንጉሡ ሕዝቡን አልሰማም፤ እግዚአብሔር በሴሎናዊው በአሒያ ለናባጥ ልጅ ለኢዮርብአም የተናገረውን ቃሉን ይፈጽም ዘንድ በእግዚአብሔር የተደረገ ክስተት
ነበር። 16 እስራኤል ሁሉ ንጉሡ እንዳልሰማቸው ሲያዩ ሕዝቡ ፦ "ከዳዊት ምን ድርሻ አለን? ከእሴይም ልጅ ምንም ርስት የለንም! እስራኤል ሆይ
እያንዳንዳችሁ ወደየድንኳኖቻችሁ ተመለሱ። ዳዊት ሆይ የገዛ ራስህን ቤት ተመልከት" ብለው መለሱለት። በመሆኑም እስራኤል ሁሉ ወደየድንኳኖቻቸው
ተመለሱ። 17 በይሁዳ ከተሞች በሚኖሩት በእስራኤል ሕዝብ ላይ ግን ሮብዓም ነገሠባቸው። 18 ከዚያም ንጉሡ ሮብዓም አስገባሪውን አዶኒራምን ላከው፤
ነገር ግን የእስራኤል ሕዝብ በድንጋይ ወግረው ገደሉት። ንጉሥ ሮብዓም ፈጥኖ በሰረገላው ወደ ኢየሩሳሌም ሸሸ። 19 በመሆኑም እስራኤል እስከ ዛሬ ድረስ
በዳዊት ቤት ላይ አመጸ።

---

2 Chronicles 10:1

እስራኤል ሁሉ ይመጣ ነበር
እዚህ “እስራኤል” የሚለው ለእስራኤል ሰዎች የተሰጠ ስም ነው ። “ሁሉም” የሚለው ቃል ጠቅለል ያለ ገለጻ ነው ። AT: - “የእስራኤል ሰዎች እየመጡ ነበር” (የባህሪ ስምን እና ግነትን እና አጠቃላይን : ይመልከቱ)

ኢዮርብዓም ... ናባጥ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው ። በ 2ኛ ዜና 9፡ 29 እነዚህን ስሞች እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። (ተመልከት/ች: የስሞች አተረጓጎም)

1 ኢዮሣፍጥ ታላቅ ባለጠግነትና ክብር ነበረው። ከቤተሰቦቹ አንዱ ሴት ልጁን እንዲያገባ በማድረግ ከአክዓብ ጋር ራሱን አዛመደ። 2 ከተወሰኑ ዓመታት በኋላም ወደ አክዓብ ወደ ሰማርያ ወረደ። አክዓብም ለእርሱና ከእርሱ ጋር ለነበሩት ሕዝብ በርካታ በጎችንና በሬዎችን አረደላቸው። ከእርሱም ጋር ሬማት ዘገለአድን ለማጥቃት ይሄድ ዘንድም አክዓብ አሳመነው። 3 የእስራኤል ንጉሥ አክዓብ የይሁዳን ንጉሥ ኢዮሣፍጥን ፦ "ከእኔ ጋር ወደ ሬማት ዘገለአድ ትሄዳለህን?" አለው። ኢዮሣፍጥም ፦"እኔ እንደ አንተ ነኝ፤ ሕዝቤም እንደ ሕዝብህ ናቸው፤ በጦርነቱ ውስጥ ካንተ ጋር አብረን እንሆናለን" ብሎ መለሰለት። 4 ኢዮሣፍጥም የእስራኤልን ንጉሥ ፦ "እባክህን ለመልስህ በመጀመሪያ የእግዚአብሔርን ቃል ጠይቅ" አለው። 5 ከዚያም የእስራኤል ንጉሥ ነቢያቱን አራት መቶ ሰዎች በአንድነት ሰብስቦ፦ "ወደ ሬማት ዘገለአድ ለጦርነት መሄድ ይገባናል ወይስ መሄድ አይገባኝም?" አላቸው። እነርሱም ፦" እግዚአብሔር ለንጉሡ ድል ይሰጠዋልና አጥቃት!" አሉት። 6 ኢዮሣፍጥ ግን፦ "ምክር የምንጠይቀው አሁንም ሌላ የእግዚአብሔር ነቢይ የሆነ ሰው በእዚህ የለምን?" አለ። 7 የእስራኤልም ንጉሥ ኢዮሣፍጥን ፦" የእግዚአብሔርን ምክር የምንጠይቅበት አሁንም አንድ ሰው የይምላ ልጅ ሚክያስ አለ፤ ነገር ግን ችግር ብቻ እንጂ ስለእኔ ምንም ነገር መልካም ትንቢት ከቶም ተናግሮልኝ ስለማያውቅ እጠላዋለሁ" አለው።ኢዮሣፍጥ ግን ፦ "ንጉሥ እንደዚያ አይበል" አለ። 8 ከዚያም የእስራኤል ንጉሥ አንድ ሹም ጠርቶ ፦"የይምላን ልጅ ሚክያስን በፍጥነት አምጣው" ሲል አዘዘው። 9 የእስራኤል ንጉሥ አክዓብና የአስራኤል ንጉሥ ኢዮሳፍጥ መጎናጸፊያቸውን እንደለበሱ እያንዳንዳቸው በዙፋን ላይ በሰማርያ በር መግቢያ በግልጽ ሥፍራ ላይ ተቀምጠው ነቢያቱም ሁሉ በፊታቸው ትንቢት እየተናገሩ ነበር። 10 የክንዓና ልጅ ሴዴቅያስም ለራሱ የብረት ቀንዶች ሠርቶ፦ "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ 'በእነዚህ ቀንዶች አርመናውያን እስኪያልቁ ድረስ ትወጋቸዋለህ'" አለ። 11 ነቢያቱም ሁሉ፦" እግዚአብሔር በንጉሡ እጅ አሳልፎ ስለሚሰጣት ሬማት ዘገለዓድን አጥቃና አሸንፍ" እያሉ ተመሳሳይ ትንቢት ይናገሩ ነበር። 12 ሚክያስን ሊጠራ የሄደው መልዕክተኛ ፦" እነሆ የነቢያቱ ቃላት በአንድ አፍ ለንጉሡ መልካም ነገሮች ያውጃሉ። እባክህን ያንተም ቃል ከእነርሱ የአንዱን ቃል ዓይነት ይሁንና መልካም ነገሮች ተናገር" ሲል ተናገረው። 13 ሚክያስም፦"ሕያው እግዚአብሔርን የምናገረው አምላኬ እርሱ የሚለውን ነው" ብሎ መለሰ። 14 ወደ ንጉሡም በመጣ ጊዜ ንጉሡ፦" ሚክያስ ሆይ ወደ ሬማት ዘገለዓድ ለጦርነት መሄድ ይገባናል ወይስ መቅረት?"አለው። ሚክያስም፦" አጥቃና አሸንፍ! ታላቅ ድል ይሆንልሃልና!" ብሎ መለሰለት። 15 ከዚያም ንጉሡ ፦" በእግዚአብሔር ስም ከእውነቱ በቀር ሌላ ምንም ነገር እንዳትነግረኝ ስንት ጊዜ እንድትምል ላደርግህ ይገባኛል?" አለው። 16 ሚክያስም፦" እስራኤል ሁሉ እረኛ እንደሌላቸው በጎች በተራሮች ላይ ተበትነው አየኋቸው፤ እግዚአብሔርም፦ 'እነዚህ እረኛ የላቸውም። እያንዳንዱ ሰው በሰላም ወደ ቤቱ ይመለስ' አለ" ብሎ ተናገረ። 17 በመሆኑም የእስራኤል ንጉሥ ለኢዮሳፍጥ ፦" እኔን በተመለከተ ጥፋት ብቻ እንጂ መልካም ትንቢት እንደማይናገርልኝ አልነገርኩምን?" አለው። 18 ከዚያም ሚክያስ፦" እንግዲህ ሁላችሁም የእግዚአብሔርን ቃል መስማት ይገባችኋል፤ እግዚአብሔር በዙፋኑ ተቀምጦ የሰማይም ሰራዊት ሁሉ በቀኙና በግራው ቆመው እንደነበር አየሁ። 19 እግዚአብሔርም ፦" የእስራኤል ንጉሥ አክዓብ ወደ ሬማት ዘገለዓድ እንዲወጣና እንዲወድቅ የሚያታልለው ማነው?" አለ። አንዱ በእዚህ መንገድ ብሎ ሲመልስ ሌላውም በዚያ መንገድ ብሎ መለሰ። 20 ከዚያም አንድ መንፈስ መጥቶ በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ፦" እኔ አታልለዋለሁ" አለ። እግዚአብሔርም ፦"እንዴት?" አለው። 21 መንፈሱም፦" ወጥቼ በነቢያቱ ሁሉ አፍ ሐሰተኛ መንፈስ እሆናለሁ" አለ። እግዚአብሔርም፦" ታታልለዋለህ፤ ይሳካልሃልም፤ አሁንም ሂድና እንደዚሁ አድርግ" ብሎ መለሰ። 22 አሁንም እነሆ እግዚአብሔር በእነዚህ ነቢያትህ አፍ ሐሰተኛ መንፈስ አስቀምጧል፤ እግዚአብሔርም ጥፋት እንዲመጣብህ ተናግሯል። 23 የክንዓና ልጅ ሴዴቅያስም ቀረብ ብሎ ሚክያስን በጥፊ መታውና ፦"የእግዚአብሔር መንፈስ ለአንተ ሊናገር በየትኛው መንገድ ከእኔ ሄደ?" አለው። 24 ሚክያስም፦" እነሆ በዚያ ቀን ልትሸሸግ ወደ አንድ የውስጥ ክፍል ስትሸሽ ታውቀዋለህ" አለው። 25 የእስራኤል ንጉሥም ለአገልጋዮቹ ፦" እናንተ ሰዎች ሚክያስን ያዙና ወደ ከተማይቱ አስተዳዳሪ ወደ አሞንና ወደ ልጁ ወደ ኢዮአስ ውሰዱት፤" 26 ንጉሡ፦' በደህና እስከምመለስ ድረስ ይህንን ሰው እስር ቤት ውስጥ አኑሩት፤ ጥቂት ምግብ ብቻ እና ጥቂት ውሃ ብቻ መግቡት' ይላል በሉት" አላቸው። 27 ሚክያስም፦" አንተ በደህና ከተመለስህ በእኔ የተናገረው እግዚአብሔር አይደለም" አለ። ጨምሮም፦"እናንተ ሕዝብ ሁሉ ይህንን ስሙ" አለ። 28 በመሆኑም የእስራኤል ንጉሥ አክዓብና የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሳፍጥ ሬማት ዘገለዓድን ሊዋጉ ወጡ። 29 የእስራኤል ንጉሥ ኢዮሳፍጥን፦"እኔ እንዳልታወቅ አለባበሴን ለውጬ ወደ ጦርነቱ እገባለሁ፤ አንተ ግን ንጉሣዊ መጎናፊያህን ልበስ" አለው። በመሆኑም የእስራኤል ንጉሥ በአለባበሱ እንዳይታወቅ ራሱን ለውጦ ወደ ጦርነቱ ሄዱ። 30 የአራምም ንጉሥ የሰረገሎቹን አዛዦች፦ "ከፍተኛ ወይም ዝቅተኛ ወታደሮችን እንዳታጠቁ፤ ይልቁንም የእስራኤል ንጉሥን ብቻ አጥቁ" በማለት አዝዟቸው ነበር። 31 የሰረገሎቹ አለቆች ኢዮሳፍጥን ባዩ ጊዜ፦"የእስራኤል ንጉሥ ያ ነው ፤" አሉ። ሊያጠቁትም ወደ እርሱ ዞሩበት፤ ነገር ግን ኢዮሳፍጥ ሲጮህ እግዚአብሔር ረዳው። እግዚአብሔርም ከእርሱ ዞር አደረጋቸው። 32 የሰረገሎቹም አለቆች የእስራኤል ንጉሥ እንዳልነበረ ባዩ ጊዜ እርሱን ከመከታተል ተመለሱ። 33 አንድ ሰው ግን በዘፈቀደ ቀስቱን ሲስበው የእስራኤል ንጉሥን በጥሩር መገጣጠሚያዎቹ መካከል ወጋው። ያን ጊዜ አክዓብ የሰረገላውን ነጂ፦" ክፉኛ ተወግቻለሁና አቅጣጫህን ቀይርና ከጦርነቱ ውስጥ አውጣኝ። 34 በዚያን ጊዜ ጦርነቱ እጅግ የከፋ ሆነ፤ የእስራኤልም ንጉሥ አርመናውያንን እየተመለከተ እስኪመሽ ድረስ ሰረገላውን እንደተደገፈ ነበር። ፀሐይ በምታዘቀዝቅበት ጊዜ አካባቢ ሞተ።

---

2 Chronicles 18:4

የእስራኤል ንጉሥ
ይህ የሚያመለክተው ንጉሥ አክዓብን ነው ።

አራት መቶ ሰዎች
“400 ሰዎች” (ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)

አይገባኝም?
እዚህ ላይ እኔ የሚለው የሚያመለክተው ራሱን ሲሆን ከሠራዊቱ አጀብ ጋር ነው ። ኣት: - “ማድረግ የለብንም” (ሁሉን በአንድ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን ፡ይመልከቱ)

ለንጉሡ እጅ ይሰጣል
እዚህ የንጉሡ “እጅ” የእሱን ቁጥጥር ያመለክታል ። ይህ ማለት እግዚአብሔር በሬማት ዘገለዓድ ሰዎችን ለማሸነፍ ያስችላቸዋል ማለት ነው ። ኣት: - “የአንተን ሠራዊት እንዲያሸንፍ ያስችላቸዋል” (የባህሪ ስምን እና የሚጠበቅ እውቀትን ያልተገለጸ መረጃን ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 18:6

የይምላ ልጅ ሚክያስ
ይህ የወንድ ስም ነው ። (የስሞችን አተረጓጎም ፡ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Chronicles 18:9

የክንዓን
ይህ የወንድ ስም ነው ። (የስሞችን አተረጓጎም ፡ይመልከቱ)

የብረት ቀንዶች
ይህ የሚያመለክት በበሬ ቀንዶች ምስል ከብረት የተሠሩ ቀንዶችን ነው ።

ሶሪያውያንን እስኪጠፉ ድረስ ትገፋቸዋለህ
የነቢዩ ተግባር አክዓብ ሶርያውያንን እንዴት ድል እንደሚያደርግ የሚያሳይ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው ። በሬ በሌላው እንስሳ ላይ ጥቃት እንደሚሰነዝር ሁሉ የአክዓብ ሰራዊት በታላቅ ጥንካሬ ያሸነፋል ። አትቲ: - “ልክ በዚህ አይነት ቀንዶች በሬ በሌላ እንስሳ ላይ ጥቃት እንደሚያደርስ የአንተ ሠራዊት የሶሪያን ሠራዊት እስኪጠፋቸው ድረስ ያጠቃቸዋል” (ምሳሌያዊ ድርጊትን እና ዘይቤያዊን ፡ይመልከቱ)

እስኪጠፉ ድረስ
ይህ ገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “እስኪያጠፋቸው ድረስ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ይመልከቱ)

በንጉሡ እጅ አሳልፎ ሰጠችው
እዚህ “የንጉሡ እጅ” የእሱን ቁጥጥር ያመለክታል ። ይህ ማለት እግዚአብሔር በሬማት ዘገለዓድ ሰዎችን ለማሸነፍ ያስችላቸዋል ማለት ነው ። ኣት: - “ንጉሡ እንዲይዘው ፈቅዷል” ወይም “ሠራዊቶችህ እንዲይዙት ይፈቅድላቸዋል” (የባህሪ ስምን እና የሚጠበቅ እውቀትን ያልተገለጸ መረጃን ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 18:12

ሚክያስ
የዚህን ሰው ስም በ 2 ኛ ዜና መዋዕል 17 ፡7 ካለው ጋር በሚመሳሰል ሁኔታ ተርጉም ። (የስሞችን አተረጓጎም፡ይመልከቱ)

እዩ
“ስማ” ወይም “የምነግርህን ነገር በትኩረት ተከታተል”

በአንድ አፍ የነቢያት ቃል ለንጉሡ መልካም ነው
አንድ ዓይነት ቃል የሚናገሩ ነቢያት በአንድ አፍ እንደሚናገሩ ተደርጎ ተነግሯል ። “የነቢያት ቃላት” የሚለው ሐረግ ነቢያት የሚናገሩትን መልእክት ይወክላል ። ኣት: - “ነቢያቱ ሁሉ ለንጉሡ መልካም ነገሮች እንደሚሆኑ ይናገራሉ።” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

ቃሎችህ
"የምትናገረው ነገር"

ሕያው እግዚአብሔርን!
“ ልክ እንደ እግዚአብሔር ሕያው መሆኑ አስተማማኝ የሆነ ” ። ህዝቡ ቀጥሎ የሚናገሩት ነገር እውነት መሆኑን ለማሳየት ይህንን አገላለፅ ይጠቀማሉ ። ይህ ቃለ መኃላ የሚገባበት መንገድ ነው ። አት: - “በከፍተኛ መኃላ ምያለሁ” (ፈሊጥን ፡ይመልከቱ)

ወይስ እንቅር
የተረዳሀውን መረጃ ልትጨምርበት ትችላለህ ። ኣት: “ወይስ መሄድ የለብንም” (የቃላት ግድፈትን፡ይመልከቱ)

መሄድ አለብን
“እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው አክዓብን ፣ ኢዮሣፍጥን እና ሠራዊታቸውን እንጂ ሚክያስን አይደለም ። (አግላይና አካታችን ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 18:15

ስንት ጊዜ እፈልጋለሁ... በእግዚአብሔር ስም? በእግዚአብሔር ስም . . . ስንት ጊዜ አምልሃለሁ?
አክዓብ ሚክያስን ለመገሠጽ ይህን ጥያቄ በብስጭት ጠየቀው ። ኣት: - “ብዙ ጊዜ በያህዌ ስም አማልኩህ...” (አወያይ መጠይቅን፡ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ስም
እዚህ “ስም” የሚለው ቃል ስልጣንን ያመለክታል ። ኣት: - “እንደ እግዚአብሔር ወኪል” (የባህሪ ስምን፡ይመልከቱ)

እስራኤልን ሁሉ አየሁ
እዚህ “እስራኤል ሁሉ” የእስራኤልን ሠራዊት ያመለክታል ። ኣት: - “የእስራኤልን ሠራዊት ሁሉ አየሁ” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

እረኛ እንደሌላቸው በጎች
የሠራዊቱ ሰዎች እረኛቸው ንጉሡ ስለሞተ የሚመራቸው ከሌላቸው በጎች ጋር ተመሳስሏል። (ዘይቤያዊን ፡ይመልከቱ)

እነዚህ እረኛ የላቸውም
እግዚአብሔር ንጉሡ እንደ እረኛ እንደሆነ ይናገራል ። አንድ እረኛ በጎቹን የመጠበቅ እና የመንከባከብ ኃላፊነት እንዳለበት ሁሉ ፣ ንጉሡም ህዝቡን የመምራት እና የመጠበቅ ሃላፊነት አለበት ። ኣት: - “እነዚህ ሰዎች መሪ የላቸውም” (ዘይቤያዊን ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 18:17

አልነገርኩሽም... ግን ጥፋት ብቻ ነው?
አክዓብ ይህን ጥያቄ የጠየቀው ስለ ሚክያስ እውነቱን መናገሩን ለማጉላት ነው ። ኣት: - “ነግሬሃለሁ ... ግን ጥፋት ብቻ ነው! ” (አወያይ መጠይቅን ፡ ይመልከቱ)

በቀኝ እጁ እና በግራው ላይ
ይህ ማለት በግራ ጎኑ እና በቀኙ ጎን ከእርሱ አጠገብ ቆመው ነበር ማለት ነው ። አት: - “በቀኝ እና በግራ ጎኑ” (ፈሊጥን፡ይመልከቱ)

በግራ በኩል
ይህ የግራ እጁን ያሳያል ። ኣት: - “በግራ እጁ” (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 18:19

ማታለያ
ይህ ማለት አንድ የሚስብ ነገር በማቅረብ አንድን ሰው መሳብ ማለት ነው ።

በሬማት ዘገለዓድ መውደቅ
የአክዓብ በጦርነት ውስጥ መሞት መውደቅ ተብሎ ተነግሯል ። አት: - “በራሞት ዘገለዓድ መሞት” (ዘይቤያዊን እና ዘወርዋራን ፡ይመልከቱ)

አንደኛው ይህን አለ እና ሌላው ያንን አለ
ይህ ከአንድ በላይ አስተያየቶች እንደነበሩ ያመለክታል ። ከዚህ በፊት ባለው ጥቅስ ላይ “አንዱ ..እና ሌላው” የሚሉት ቃላት ለእግዚአብሔር ምላሽ የሚሰጡ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የሰማይ መላእክት እንደነበሩ ያመለክታሉ ።

2 Chronicles 18:20

በነቢያቱ ሁሉ አፍ ሐሰተኛ መንፈስ መሆን
እዚህ ላይ “መንፈስ” የሚለው ቃል የነቢያትን ዝንባሌ ያመለክታል ፣ “አፉ” የሚለው ቃል ደግሞ የሚናገሩትን ይወክላል ። ኣት: - “ነቢያቱ ሁሉ ሐሰትን እንዲናገሩ አድርጋቸው” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Chronicles 18:22

ያህዌህ ፣ አሁን ተመልከት
ያህዌህ ሆይ የምነግርህ ነገር እውነት እና አስፈላጊ ስለሆነ ተመልከት

በእነዚህ በነቢያትህ አፍ ሐሰተኛ መንፈስን አድርጓል
እዚህ ላይ “መንፈስ” የሚለው ቃል የነቢያትን ዝንባሌ ያመለክታል ፣ “አፉ” የሚለው ቃላት ደግሞ ምን እንደሚሉ ያመለክታል ። አት: - “ነቢያትህ ሐሰትን እንዲናገሩ አድርገሃቸዋል” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 18:23

ክንዓና
በ 2 ኛ ዜና ምዕራፍ 18 :10 እንዳለው የዚህ ሰው ስም ተርጉም ። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር መንፈስ ከአንተ ጋር ይናገር ዘንድ በምን መንገድ ከእኔ አለፈ?
ሴዴቅያስ ሚክያስን ለመሳደብ እና ለመገሠጽ ይህን አወያይ መጠይቅ ጠየቀ ። ኣት: - “የያህዌህ መንፈስ እኔን ትቶ ለአንተ የሚናገር አይምሰልህ!” (አወያይ መጠይቅን :ይመልከቱ)

እነሆ
“ስማ” ወይም “የምነግርህን ነገር በትኩረት ተከታተል”

ታውቃላችሁ
“የጥያቄህን መልስ ታውቀዋለህ።” የሴዴቅያስ አወያይ መጠይቅ እንደ መግለጫ ከተተረጎመ፣ ይህ ሐረግ ግልጽ መረጃን እንዲሰጥ ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። ኣት: - “የእግዚአብሔር መንፈስ እንደተናገረኝ ታውቃላችሁ” (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 18:25

የእስራኤል ንጉሥ
ይህ አክዓብን ያመለክታል ።

አሞን
ይህ የሰው ስም ነው ። (የስሞች አተረጓጎም :ይመልከቱ)

በደህና ብትመለሱ
ይህ የማይሆነውን ነገር ይገልጻል። ንጉሡ በደህና እንደማይመለስ እግዚአብሔር ለሚክያስ አስቀድሞ ነግሮታል። (መላምታዊ ሁኔታ:ይመልከቱ)

2 Chronicles 18:28

የእስራኤል ንጉሥ አክዓብና የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ ወደዚያ ወጡ
እዚህ ነገሥታቱ ራሳቸውን ከሠራዊቶቻቸው ጋር ይወክላሉ ። ኣት: - “የእስራኤል ንጉሥ አክዓብና የይሁዳ ንጉሥ ሠራዊታቸውን ወደ ሰልፍ አወጧቸው” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከል :ይመልከቱ)

ወደ ላይ ወጣ
“ተዋጉ”

ሬማት ዘገለዓድ
በ 2ኛ ዜና መዋዕል 18 :2 ውስጥ እንደተረጎምከው የዚህን ቦታ ስም ተርጉም (የስሞች አተረጓጎም :ይመልከቱ)

መልኩን ለወጠ
ይህ ማለት እንዳይለይ መደበኛውን መልክ መለወጥ ነው።

አስፈላጊዎቹንም ሆነ አስፈላጊ ያልሆኑትን ወታደሮች አታጥቁ
ንጉሡ ሁለቱንም “አስፈላጊ ያልሆኑ” እና “አስፈላጊ ወታደሮችን” በመጥቀስ ሁሉንም ወታደሮች ማለቱ ነበር ። አት: - “ማንኛውንም ወታደር አታጥቁ” (ሜሪዝምን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 18:31

የእስራኤል ንጉሥ ነው
አክዓብ የንጉሥ ልብሱን እንዲለብስ አጥብቆ በመጠየቁ ኢዮሣፍጥ በስህተት የእስራኤል ንጉሥ ነው ተባለ።

እግዚአብሔር ከእርሱ እንዲመለሱ አደረገ
“እግዚአብሔር እርሱን ማሳደዳቸውን እንዲያቆሙ አደረገ”

እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ በታሪኩ ውስጥ አንድን አስፈላጊ ክስተት ለማመልከት እዚህ ጥቅም ላይ ውሏል ። ቋንቋህ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ መጠቀም ትችላለህ ።

2 Chronicles 18:33

በድንገት ቀስቱን ገትሮ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እርሱ አክዓብ እንደ ሆነ ሳያውቅ አንድ ወታደር ለመግደል ፈልጎ ነበር ። 2) በሃሳቡ ምንም ልዩ ኢላማ ሳይኖረው ቀስቱን ገተረ

በጥሩሩ መጋጠሚያ መካከል
ይህ ሁለት የጦር ትጥቆች የሚገናኙበት ቦታ ሲሆን ለቀስት እና ለሰይፍ የተጋለጠ ነው ።

የእስራኤል ንጉሥ በሠረገላው ውስጥ ተያዘ
ይህ በገቢራዊ አረፍተነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “አንድ ሰው የእስራኤልን ንጉሥ በሠረገላው ውስጥ ይዞት ነበር” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 19

1 የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሳፍጥም ወደ ቤቱ ወደ ኢየሩሳሌም በደህና ተመለሰ። 2 ያኔ የባለ ራዕዩ የአናኒ ልጅ ኢዩ ሊገናኘው ወጣ፤ ንጉሡንም ኢዮሳፍጥን፦"ክፉውን ልትረዳ ይገባሃልን? እግዚአብሔርን የሚጠሉትን ልትወድ ይገባሃልን? ለዚህ ድርጊትህ ከእግዚአብሔር ዘንድ ቁጣ ሆኖብሃል። 3 ነገር ግን የማምለኪያ አፀዶቹን ከምድሪቱ ላይ አስወግደሃልና እግዚአብሔርን ለመፈለግ ቆርጠህ ልብህን አዘጋጅተሃልና በአንተ ዘንድ መልካምነት ተገኝቶብሃል" አለው። 4 ኢዮሳፍጥ በኢየሩሳሌም ተቀመጠ፤ ከቤርሳቤህ እስከ ተራራማው የኤፍሬም አገር ድረስ እንደገና በሕዝቡ መካከል ወጥቶ ወደ አባቶቻቸው አምላክ መለሳቸው። 5 በምድሪቱ ላይ በተመሸጉት በይሁዳ ከተሞች ሁሉ በእያንዳንዱ ከተማ ውስጥ ፈራጆችን አስቀመጠ። 6 ፈራጆቹንም፦"የምትፈርዱት ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው ስላልሆነ ምን ማድረግ እንደሚገባችሁ አጢኑ፤ በፍርድ ነገር እርሱ ከእናንተ ጋር ነው፤ 7 አሁንም የእግዚአብሔር ፍርሃት በእናንተ ላይ ይሁን። በአምላካችን በእግዚአብሔር ዘንድ ምንም በደል የለምና፤ ለሰው ፊት ማድላት ወይም መማለጃ መውሰድ የለምና በምትፈርዱበት ጊዜ ተጠንቀቁ" አላቸው። 8 በተጨማሪም ኢዮሳፍጥ በኢየሩሳሌም ከሌዋውያኑንና ከካህናቱ የተወሰኑትንና ከእስራኤል የአባቶች ቤቶች መሪዎች የተወሰኑትን የእግዚአብሔርን ፍርድ እንዲያስፈጽሙና ጠቦችን እንዲፈቱ ሾማቸው። እነርሱም በኢየሩሳሌም ተቀመጡ። 9 "እግዚአብሔርን በመፍራት፥ በታማኝነትና በፍጹም ልብ የምታደርጉት ይህ ነው፤ 10 በደም መፍሰስ ጉዳይ ቢሆን፥ በሕግና በትእዛዝ፥ በሥርዓት ወይም በድንጋጌ ጉዳዮች ቢሆን በከተሞቻቸው ከተቀመጡት ከወንድሞቻችሁ ምንም ኣይነት ጠብ ወደ እናንተ ቢመጣ እግዚአብሔርን እንዳይበድሉ፥ ቁጣ በእናንተና በወንድሞቻችሁ ላይ እንዳይወርድ ልታስጠነቅቋቸው ይገባል። እንደዚህ ብታደርጉ በኃጢአት በደለኛ አትሆኑም። 11 እነሆ ለእግዚአብሔር በሚሆኑት ነገሮች ሁሉ ላይ ሊቀ ካህናቱ አማርያ፥ በንጉሡ ጉዳዮች ሁሉ ላይ የተሾመው የይሁዳ ቤት መሪ የእስማኤል ልጅ ዝባድያ አለቆች ናቸው። ሌዋውያኑም ደግሞ የሚያገለግሏችሁ ባለሥልጣናት ይሆናሉ። በድፍረት አድርጉ፤ እግዚአብሔርም መልካም ከሆኑት ጋር ይሁን።

---

2 Chronicles 19:1

ባለ ራእዩ አናኒ
“አናኒ” የአንድ ሰው ስም ነው። በ 2 ኛ ዜና መዋዕል 16፡ 7 ውስጥ ይህንን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። (የስሞች አተረጓጎም ፡ይመልከቱ)

ሊገናኘው ወጣ
እዚህ ላይ “እሱ” የሚለው ቃል ኢዮሣፍጥን ያመለክታል ።

ክፉዎችን መርዳት አለብህን? እግዚአብሔርን የሚጠሉትን መውደድ አለብህ?
እነዚህ ጥያቄዎች ኢዮሣፍጥ አክዓብን መርዳት አልነበረበትም የሚለውን ነጥብ ለማሳየት አሉታዊ መልሶችን ይጠብቃሉ ። ኣት: - “ክፉዎችን መርዳት የለብህም! ያህዌን የሚጠሉትን መውደድ የለብህም! ” (አወያይ መጠይቅን ፡ይመልከቱ)

ክፉዎች
ይህ በአጠቃላይ ክፉ ሰዎችን ያመለክታል። ኣት: “ክፉ ሰዎች” (ስማዊ ቅጽልን ፡ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ቁጣ በላያችሁ ነው
“ቁጣ” የሚለው እረቂቅ ስም “ተቆጣ” ሊተረጎም ይችላል ። ይህ ሐረግ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “እግዚአብሔር በአንተ ላይ ተቆጥቷል” (የረቂቅ ስሞችን እና ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ይመልከቱ)

በአንተ ውስጥ አንዳንድ መልካም ነገር አለ
ረቂቅ ስም የሆነው “ጥሩ” የሚለው ቃል እንደ ቅፅል ሊተረጎም ይችላል። ይህ ሐረግ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “አንዳንድ ጥሩ ነገሮችን አድርገሃል” (የረቂቅ ስሞችን እና ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ይመልከቱ)

የማምለኪያ ዐፀዶቹን ከምድሩ አስወግደሃል
ኢዮሣፍጥ ንጉሥ ስለነበረ ፣ እነዚህን ነገሮች እንዲያደርጉ ለሠራተኞቹ ነግሮ ሊሆን ይችላል። ኣት: - “ሕዝብህ የማምለኪያ ዐፀዶችን ከምድሪቱ እንዲወስወግዱ አድርገሃቸዋል” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

የማምለኪያ ዐፀዶች
ይህንን በ 2 ኛ ዜና ምዕራፍ 14 ፡3 እንዴት እንደጸሮጎምከው ተመልከት ።

ልብህን አዘጋጅተሃል
እዚህ ልብ ፈቃዱን ይወክላል ። የኢዮሳፍጥ ፈቃድ እንደ ማይለወጥ ወይም የማይነቃነቅ ነው ተብሎ ተነግሯል ፣ ይህም ማለት እግዚአብሔርን የመሻት የማይለወጥ አቋም አለው ። ኣት: - “በጥብቅ ወስኗል” (ፈሊጥን ፡ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን ፈልግ
ኢዮሣፍጥ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን ለማድረግ መፈለጉ እርሱን እየፈለገ እንዳለ ተደርጎ ተነግሯል። ኣት: - “እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን አድርግ” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 19:4

ከቤርሳቤህ ጀምሮ እስከ ተራራማው ኤፍሬም አገር ድረስ
ይህ ማለት ኢዮሣፍጥ የነገሠበትን ምድር ሁሉ ማለትም ከደቡብ ጫፍ እስከ ሰሜን ጫፍ ያለውን ምድር ማለት ሲሆን በመካከል ያለውን መላውን መሬት ለማካተት የታሰበ ነው። ኣት: - “የይሁዳን ምድር ሁሉ” (ሜሪዝምን ፡ይመልከቱ)

ወደ እግዚአብሔር መልሶ አመጣቸው
ስለ ኢዮሣፍጥ ህዝቡን እንደቀድሞው እግዚአብሔርን እንዲያገለግል መምራቱ ደራሲው ሲናገር ቀድሞ ወደነበሩበት ቦታ እንደሚመልሳቸው በማስመሰል ተናግሯል ። ኣት: - “ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ አሳመናቸው” (ዘይቤያዊን ፡ይመልከቱ)

አባቶቻቸው
“ቅድመ አያቶቻቸው” ወይም “አባቶቻቸው”

የተመሸጉ ከተሞች
መከላከያ ለማግኘት በዙሪያቸው ግድግዳዎች ያሏቸው ከተሞች ናቸው

በእያንዳንዱ ከተማ
“ለእያንዳንዱ ከተማ”

2 Chronicles 19:6

ዳኞቹንም አለ
“ኢዮሣፍጥ ዳኞችን” አላቸው

እርሱ ከአንተ ጋር ነው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ያ እግዚአብሔር ዳኞቹ ምን እንደወሰኑ ያውቃል ወይም 2) እግዚአብሔር ዳኞቹን ስለውሳኔአቸው ተጠያቂ ያደርጋቸዋል ወይም 3) እግዚአብሔር ዳኞቹን በውሳኔዎቻቸው ውስጥ ይረዳቸዋል እንዲሁም ይመራቸዋል ። (ፈሊጥን ፡ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የእግዚአብሔር ፍርሃት በእናንተ ላይ ይሁን
ይህ በገቢራዊ አረፍተነገር ሊገለፅ ይችላል። ኣት: - “በምትፈርድበት ጊዜ እግዚአብሔርን መፍራት አለብህ”

በአምላካችን በእግዚአብሔር ላይ በደል አይኖርም ፣ አድልዎም ሆነ ጉቦ አይገኝም
“ስሕተት” ፣ “አድልዎ መደረግ” እና “ጉቦ” የሚሉት ረቂቅ ስሞች “ኃጢአት” ፣ “አድሎ” እና “ጉቦ” የሚሉትን ግሶች በመጠቀም መተረጎም ይችላሉ ። እግዚአብሔር በፍርዱ አንዱን ከሌላው አያበልጥም ወይም ጉቦ እንዲሰጥዎ አያደርግም ” (የረቂቅ ስሞችን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 19:8

የአባቶች ቤቶች አለቆች
እዚህ “ራሶች” የሚለው ዘይቤያው አነጋገር ሲሆን በጣም አስፈላጊ የሆነውን አካል የሚገልጽ ነው ፣ እና “ቤቶች” የሚለው ቤተሰቦችን ይወክላሉ ። ኣት: - “የጥንት ቤተሰቦች መሪዎች” (ዘይቤያዊን እና የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

ለእግዚአብሔር ፍርድን ይፈጽማሉ
“ፍርድ” የሚለው ረቂቅ ስም” “መፍረድ” የሚለውን ግስ በመጠቀም ሊተረጎም ይችላል ። “ኣት” “ሕዝቡን ለእግዚአብሔር ለመፍረድ” ወይም “ስለእግዚአብሄር ፈርድ ለመፍረድ” (የረቂቅ ስሞችን :ይመልከቱ)

ለክርክር ሲባል
“አለመግባባቶችን መፍታት” ወይም “አለመግባባቶችን ለመፍታት”

ለእግዚአብሔር አክብሮት ማሳየት አለብህ
የረቂቅ ስሙ “አክብሮት” የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አት: - “ያህዌን እየፈራህ ማገልገል አለብህ” ወይም “ያህዌን ስታከብር ማገልገል አለብህ” (የረቂቅ ስሞችን :ይመልከቱ)

በሙሉ ልብህ
እዚህ “ልብ” መሉውን ሰው ይወክላል ። አት: - “ከሙሉ ማንነትህ ጋር” (የባህሪ ስሞችን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 19:10

አያያዥ መግለጫ
ኢዮሣፍጥ ፈራጆች እንዲሆኑ የሾማቸውን የተወሰኑ ሌዋውያንን ፣ ካህናቱንና የእስራኤልን አባቶች የአባቶቻቸውን አለቆች ማስተማርን ቀጠለ።

አጠቃላይ መረጃ
በዚህ ጥቅስ ላይ “አንተ” እና “የአንተ” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ኢዮሣፍጥ ዳኞች እንዲሆኑ የሾማቸውን ሰዎች ነው ።

በከተሞቻቸው ከሚኖሩት ወንድሞችህ መካከል ክርክር በሚመጣበት በማንኛውም ጊዜ
ይህ በገቢራዊ አረፍተነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “በከተሞቻቸው የሚኖሩት ወንድሞችህ ክርክር ሲያመጡልህ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ ይመልከቱ)

ከወንድሞችህ
እዚህ “ወንድሞች” ለሌሎች እስራኤላዊያን አጠቃላይ ማጣቀሻ ነው።

ደም መፋሰስ
እዚህ ላይ የሰዎች ግድያ ደማቸውን ማፍሰስ እንደሆነ ተነግሯል፣ “ደም” ህይወትን ያመለክታል ። ኣት: - “የሰዎች ግድያ” ወይም “ግድያ”(የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

በአንተና በወንድሞችህ ላይ ቁጣ ይመጣል
የረቂቅ ስም የሆነው “ቁጣ” እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል “ቁጡ” ተደርጎ ሊገለፅ ይችላል ። ይህ በገቢራዊ አረፍተነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “እግዚአብሔር በአንተና በወንድሞችህ ላይ ይቆጣል” (የረቂቅ ስም እና ገቢራዊ እና ገቢራዊ ወይም ተብሮአዊ :ይመልከቱ)

2 Chronicles 19:11

አያያዥ መግለጫ
ኢዮሣፍጥ ፈራጆች እንዲሆኑ የሾማቸውን የተወሰኑ ሌዋውያንን ፣ ካህናቱንና የእስራኤልን አባቶች የአባቶቻቸውን አለቆች ማስተማርን ቀጠለ።

አጠቃላይ መረጃ
በዚህ ጥቅስ ላይ “አንተ” እና “የአንተ” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ኢዮሣፍጥ ዳኞች እንዲሆኑ የሾማቸውን ሰዎች ነው ።

አማርያን ፣ እይ
አማርያ ተመልከት የምነግርህ ነገር እውነት እና አስፈላጊ ነው ።

አማርያ... ዝባድያስ... ይስማኤል
እነዚህ ወንዶች ስሞች ናቸው ። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

በአንተ ላይ ነው
“በአንተ ላይ ተሹመዋል”

ስለ ንጉሡ ጉዳዮች ሁሉ
እዚህ ኢዮሣፍጥ ስለ ራሱ በሦስተኛ መደብ ሰብአዊ ቦታ ሆኖ ይናገራል ። ይህ በመጀመሪያ መደብ ሰብዓዊ ውስጥ ሊተረጎም ይችላል። ኣት: - “ከንጉሣዊ ጉዳዮችዎ ሁሉ” (አንደኛ ፣ ሁለተኛ፣ እና ሦስተኛ መደብ ሰብዓዊን ፡ ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 20

1 ከዚህ ጊዜ በኋላ የሞዓብና የአሞን ሕዝቦች ከእነርሱም ጋር ምዑናውያን ኢዮሳፍጥን ሊዋጉት መጡ። 2 አንዳንድ ሰዎች መጥተው፦"ከባሕሩ ማዶ ከሶሪያ
ታላቅ ሠራዊት መጥቶብሃል፤ እነሆም ዓይንጋዲ በተባለች በሐሴሶን ታማር ናቸው" ብለው ነገሩት። 3 ኢዮሳፍጥም ፈራ፤ እግዚአብሔርንም ሊፈልግ ራሱን አቀና፤
በመላው ይሁዳ ፆምን አወጀ። 4 ይሁዳም እግዚአብሔርን ይፈልግ ዘንድ በአንድነት ተሰበሰበ፤ ከመላው የይሁዳ ከተሞች ሁሉ እግዚአብሔርን ይፈልጉ ዘንድ
መጡ። 5 ኢዮሳፍጥም በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ በይሁዳና በኢየሩሳሌም ጉባዔ በአዲሱ አደባባይ ፊት ቆመ። 6 "የአባቶቻችን አምላክ እግዚአብሔር ሆይ
አንተ በሰማይ ያለህ አምላክ አይደለህምን? በሕዝቦች ነገሥታት ሁሉ ላይ ገዢ አይደለህምን? ኃይልና ብርታት በእጅህ ናቸው፤ በመሆኑም ማንም ሊቋቋምህ
የሚችል የለም። 7 አምላካችን ሆይ በዚህ ምድር ላይ የነበሩትን ነዋሪዎች ከሕዝብህ ከእስራኤል ፊት አሳድደህ ለዘላለም ለአብርሃም ዝርያዎች
አልሰጠሃትምን?" አለ። 8 እነርሱም በውስጧ ኖሩባት፤ 9 "አደጋ/መቅሰፍት ቢመጣብን - ሰይፍ፥ ፍርድ፥ ወይም በሽታ፥ ወይም ረሃብ - (ስምህ በዚህ ቤት
ስላለ) በዚህ ቤት ፊትና በፊትህ እንቆምና በመከራችን ወደ አንተ እንጮሃለን፤ አንተም ሰምተህ ታድነናለህ" በማለት ለስምህም ቅዱስ ሥፍራ በውስጥዋ ሠሩ።
10 አሁንም እነሆ እስራኤል ከግብጽ ምድር በሚወጡበት ጊዜ እንዲወሩዋቸው ያልፈቀድክላቸው ይልቁንም ዞር ብለው ያላጠፏቸው የአሞን፥ የሞዓብና የሴይር
ተራራ ሕዝቦች እዚህ ናቸው፤ 11 እነሆ ለወረታችን እንዴት እንደሚመልሱልን ተመልከት፤ እንድንወርሰው ከሰጠኸን ከምድርህ ሊያስወጡን መጥተዋል። 12
አምላካችን ሆይ አትፈርድባቸውምን? ይህንን ሊያጠቃን የመጣብንን ታላቅ ሠራዊት እንቋቋም ዘንድ ምንም ኃይል የለንም። የምናደርገውንም አናውቅም፤ ነገር
ግን ዓይኖቻችን በአንተ ላይ ናቸው" አለ። 13 ይሁዳ ሁሉ ከሕጻናቶቻቸው፥ ከሚስቶቻቸውና ከልጆቻቸው ጋር በእግዚአብሔር ፊት ቆመው ነበር። 14 በጉባዔው
መካከል የእግዚአብሔር መንፈስ ከአሳፍ ልጆች አንዱ በነበረው በሌዋዊው በማታንያ ልጅ በይዒኤል ልጅ በበናያስ ልጅ በዘካርያስ ልጅ በየሕዚኤል ላይ መጣ።
15 የሕዚኤልም፦" ይሁዳ ሁሉ የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች እና ንጉሥ ኢዮሳፍጥ ስሙ፤ እግዚአብሔር የሚላችሁ ይህ ነው፦"ከዚህ ታላቅ ሠራዊት የተነሳ አትፍሩ፤
አትደንግጡም፤ ምክንያቱም ጦርነቱ የእግዚአብሔር እንጂ የእናንተ አይደለም። 16 ነገ በእነርሱ ላይ ለጦርነት ልትወጡ ይገባል፤ እነሆ በጺጽ መተላለፊያ
መንገድ ይመጣሉ። በይሩኤል ምድረ በዳ ፊት ለፊት በሸለቆው መጨረሻ ታገኙዋቸዋላችሁ። 17 በዚህ ጦርነት እናንተ መዋጋት የሚያስፈልጋችሁ
አይደለችሁም። ይሁዳና ኢየሩሳሌም ሆይ በቦታችሁ ቁሙ፤ ዝም ብላችሁ ቁሙ፤ እግዚአብሔር ለእናንተ የሚያደርገውን ማዳን ተመልከቱ። እግዚአብሔር
ከእናንተ ጋር ስለሆነ አትፍሩ፤ አትደንግጡም፤ ነገ ለጦርነት ውጡባቸው" አለ። 18 ኢዮሳፍጥም በምድር ላይ በፊቱ ተደፋ፤ ይሁዳ ሁሉና የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች
እግዚአብሔርን በማምለክ በፊቱ ወደቁ። 19 የቀዓትና የቆሬ ዝርያዎች ሌዋውያን የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን በታላቅ ድምጽ ለማወደስ ቆመው ነበር።
20 ጥዋት በማለዳ ተነስተው ወደ ቴቁሔ ምድረ በዳ ሄዱ። እየሄዱም እያለ ኢዮሳፍጥ ቆሞ፦" ይሁዳና እናንተ የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ስሙኝ! በአምላካችሁ
በእግዚአብሔር እመኑ፤ ድጋፍ ታገኛላችሁ። በነቢያቱም እመኑ፤ ይቃናላችኋልም" አለ። 21 ከሕዝቡ ጋር ከተማከረ በኋላም ከሠራዊቱ ፊት ቀድመው እየሄዱ
"የቃል ኪዳን ታማኝነቱ ለዘላለም የሚኖር ስለሆነ ለእግዚአብሔር ምሥጋናን ስጡ" በማለት ለእግዚአብሔር የሚዘምሩትንና ለቅዱስ ክብሩ ውዳሴ የሚሰጡትን
ሾመ። 22 መዘመርና ማወደስ ሲጀምሩ ይሁዳን ለዋጉ በመጡት በአሞን፥ በሞዓብና በሴይር ተራራ ሰዎች ላይ እግዚአብሔር ድብቅ ጦር አስነስቶ በድንገት
እንዲያጠቋቸው አደረገ። እነርሱም ተሸነፉ። 23 የአሞንና የሞዓብ ሰዎች የሴይርን ተራራ ነዋሪዎች ሙሉ በሙሉ እስኪገድሉዋቸውና እስኪያጠፏቸው ድረስ
ለዋጉዋቸው ተነስተው ነበር። የሴይርን ተራራ ነዋሪዎች በጨረሷቸው ጊዜ ሁሉም እርስ በእርስ ለመጠፋፋት ተረዳዱ። 24 ይሁዳ ምድረ በዳውን
ወደሚመለከቱበት ቦታ ሲመጡ ሠራዊቱን ተመለከቱ። እነሆ ሞተው በምድሩም ላይ ወድቀው ነበር፤ አንድም ያመለጠ ሰው አልነበረም። 25 ኢዮሳፍጥና
ሕዝቡም ምርኮ ለመውሰድ በመጡ ጊዜ ሊሸከሙት ከሚችሉት በላይ የተትረፈረፈ ባለጸግነትና የከበሩ ጌጦች አገኙ፤ ለራሳቸውም በዘበዙ። እጅግ ብዙ
ስለነበርም ምርኮውን ለመውሰድ ሦስት ቀናት ፈጀባቸው። 26 በአራተኛው ቀን በበረከት ሸለቆ ውስጥ ተሰበሰቡ። በዚያም እግዚአብሔርን አወደሱ፤ ስለዚህም
የዚያ ሥፍራ ስም እስከዛሬ ድረስ "የበረከት ሸለቆ" ነው። 27 የይሁዳና የኢየሩሳሌም ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔር በጠላቶቻቸው ላይ ደስ አሰኝቷቸዋልና በደስታ
እንደገና ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ኢዮሳፍጥ እየመራቸው ተመለሱ። 28 በበገናና በመሰንቆ በመለከትም ወደ ኢየሩሳሌምና ወደ እግዚአብሔር ቤት መጡ። 29
እግዚአብሔር የእስራኤልን ጠላቶች እንደተዋጋ በሰሙ ጊዜ በሕዝቦች ነገሥታት ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ፍርሃት ሆነ። 30 በመሆኑም አምላኩ በዙሪያው ሁሉ
ሰላም ስለሰጠው የኢዮሳፍጥ መንግሥት ጸጥታ ሰፈነባት። 31 ኢዮሳፍጥ በይሁዳ ላይ ነገሠ። መንገሥ በጀመረ ጊዜ ሠላሳ አምስት ዓመቱ ነበር፤
በኢየሩሳሌምም ለሃያ አምስት ዓመታት ነገሠ። የእናቱ የሺልሒ ሴት ልጅ ስም ዓዙባ ነበር። 32 በአባቱም በዓሳ መንገዶች ሄደ፤ ከእነርሱም ፈቀቅ አላለም፤
በእግዚአብሔር ፊት ቅን የነበረውን ነገር አደረገ። 33 ነገር ግን የኮረብታው መስገጃዎች ገና አልተወገዱም ነበር። ሕዝቡም ልባቸውን ወደ አባቶቻቸው አምላክ
ገና አላቀኑም ነበር። 34 ኢዮሳፍጥን በተመለከተ ሌሎቹ ጉዳዮች የመጀመሪያውና የመጨረሻው በእስራኤል ነገሥታት መጽሐፍ እንደተመዘገበው በአናኒ ልጅ
በኢዩ ታሪክ ውስጥ ተጽፈዋል። 35 ከዚህ በኋላ የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሳፍጥ እጅግ ክፋት ከፈጸመው ከእስራኤል ንጉሥ ከአካዝያስ ጋር ራሱን አዛመደ። 36
በባህር ላይ የሚሄዱ መርከቦችን ለመገንባት ከእርሱ ጋር ተባበረ። መርከቦቹንም በዔጽዮንጋብር ገነቡ። 37 የመሪሳም ሰው የዶዳያ ልጅ አልዓዛር ፦" ከአካዝያስ
ጋር ተባብረሃልና እግዚአብሔር ሥራዎችህን አፍርሷል፤" ብሎ በኢዮሳፍጥ ላይ ትንቢት ተናገረበት። መርከቦቹም ተሰባበሩ፤ ጉዞ ለማድረግም አልቻሉም።

---

2 Chronicles 20:1

እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ በታሪኩ ውስጥ አንድን አስፈላጊ ክስተት ለማመልከት እዚህ ጥቅም ላይ ውሏል ። ቋንቋህ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ መጠቀም ትችላለህ ።

ምዑናውያን
ይህ ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምሥራቅ በኤዶም አቅራቢያ ካለው ከማይን አካባቢ የመጣ ሕዝብ ነበር። (የስሞች አተረጓጎም :ይመልከቱ)

ለመዋጋት ወደ ኢዮሣፍጥ መጣ
እዚህ ላይ “ኢዮሣፍጥ” እራሱን እና ሠራዊቱን ይወክላል ። ኣት: - “የኢዮሣፍጥን ሠራዊት ለመዋጋት መጣ” ወይም “ኢዮሣፍጥና ሠራዊቱን ለመውጋት መጣ” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከል ፡ ይመልከቱ)

እነሆ ፣ እነሱ በሓሴሶን ታማር ናቸው
እዚህ “ተመልከት” የሚለው ቃል ቀጥሎ ለተባለው ነገር አፅንዖት ለመስጠት እንደ ዘይቤያዊ አነጋገር ጥቅም ላይ ውሏል ። በሓሴሶን ታማር የነበረውን ሠራዊት ከሚናገሩበት ቦታ ሆነው ማየት አይችሉም ነበር ። ኣት: - “ቀድሞውኑ በሓሴሶን ታማር ናቸው” (ፈሊጥን :ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሓሴሶን ታማር
ይህ የቦታ ስም ነው ። የኢንጌዲ ሌላ ስም ነው ። (የስሞችን አተረጓጎም ፡ ይመልከቱ)

2 Chronicles 20:3

ለመፈለግ ራሱን አዘጋጁ
ይህ ፈሊጥ ነው ። ኣት: - “ለመሻት ወስኗል” ወይም “ለመፈልግ ራሱን ሰጠ ” (ፈሊጥን ፡ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን ለመፈለግ
የእግዚአብሔርን ምክር ስለመፈለግ ሲናገር እግዚአብሔርን መፈለግ እንደ ሆነ በማስመሰል ተናግሯል ። ኣት: - “የእግዚአብሔርን ምክር ለመፈለግ” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

ጾም አወጀ
“ጾም” የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊገለፅ ይችላል ።ኣት - “ሕዝቡም ሁሉ መጾም እንዳለባቸው አወጀ” (የረቂቅ ስሞችን ፡ይመልከቱ)

ይሁዳ ተሰብስቧል
ይህ የይሁዳን ሕዝብ ያመለክታል ። ኣት: - “የይሁዳ ሰዎች ተሰበሰቡ” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 20:5

የይሁዳና የኢየሩሳሌም
ይህ ከእነዚህ ቦታዎች የመጡ ሰዎችን ያመለክታል ። ኣት: - “የይሁዳና የኢየሩሳሌም ሕዝብ” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

በሰማይ አንተ አምላክ አይደለህምን? በብሔረ መንግሥታት ሁሉ ላይ ገዥ አይደለህምን?
ኢዮሣፍጥ እግዚአብሔር በሰማይና በሁሉም ነገር ላይ ያለውን ስልጣን ለማጉላት ኢዮሣፍጥ ይህን አወያይ መጠይቅ ይጠቀማል ። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊጻፍ ይችላል ።ኣት: - “በእውነት አንተ የሰማይ አምላክ ነህ እናም በምድር ነገሥታት ሁሉ ላይ ትገዛለህ።” (አወያይ መጠይቅን ፡ይመልከቱ)

ሥልጣን እና ብርታት በእጅህ ውስጥ ናቸው
“ኃይል” እና “ችሎታ” የሚሉት ቃላት በመሠረቱ አንድ ዓይነት ናቸው እና የእግዚአብሔር ኃይል ታላቅነት ያጎላሉ ። “እጅ” የሚለው ቃል ባለቤትነትን ያመለክታል ። ኣት: - “ታላቅ ሥልጣን አለህ” ወይም “ታላቅ ሥልጣን እና ብርታት አለህ” (ድግግሞሽን እና የሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን ፡ይመልከቱ)

አምላካችን ሆይ ፣ ለአብርሐም ዘሮች. . . የዚህችን ምድር ነዋሪዎችን አላባረርህምን ?
ኢዮሣፍጥ እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን ከምድራቸው እንዳባረረ ለማጉላት ይህንን አወያይ መጠይቅ ይጠቀማል። ለእስራኤል ሰጠ ። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊጻፍ ይችላል ። ኣት: - “በዚህ ምድር የሚኖሩትን ስለ ሕዝብህ ስለ እስራኤል ስትል ያባረርኽ እና ለአብርሐም ዘሮች በቋሚነት ስለ የሰጣቸው አንተ ነበርኽ።” (አወያይ መጠይቅን ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 20:8

ስለስምህ
እዚህ እግዚአብሔር በ “ስሙ” ተወክሏል” ኣት ““ ለአንተ ” ወይም “ አንተን ለማክበ ” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

ሰይፉ
“ሰይፉ” ጦርነትን ይወክላል። ኣት: “ጦርነት” ወይም “ውጊያ”(የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

ከዚህ ቤት በፊት
ይህ ቤተመቅደሱን ያመለክታል ።

ስምህ በዚህ ቤት ውስጥ ነው
እዚህ የእግዚአብሔር መገኘት በ “ስሙ” ተወክሏል። ኣት “ መገኘትህ በዚህ ነው በዚህ ቤት ውስጥ ” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን ፡ ይመልከቱ)

2 Chronicles 20:10

የሴይር ተራራ
ይህ ኤዶማውያን የሚኖሩበት ስፍራ ነበር ። (የስሞችን አተረጓጎም ፡ ይመልከቱ)

እነሆ ለወሮታችን ክፋት ይመልሱልና ከሰጠኸንም ርስት ያወጡን ዘንድ መጥተዋል
እዚህ ኢዮሣፍጥ እንግዳ ስለሆነ ነገር ይናገራል። ኣት: - “ለእነሱ ላሳየነው ምሕረት የሚመልሱልን እንደዚሁ ነው” እነሱ ከምድርህ ሊያስወጡን እየመጡ ነው። ” (ውስጠ ዌይራን ፡ይመልከቱ)

እንዴት እንደሆነ ተመልከት
እዚህ “ተመልከት” የሚለው ቃል ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን ቀጣይ የሚለውን ለማጉላት ጥቅም ላይ ውሏል ። (ፈሊጥን ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 20:12

አትፈርድባቸውምን?
ይህ አወያይ መጠይቅ እንደ ጥያቄ ሆኖ ያገለግላል። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊጻፍ ይችላል ። ኣት: - “እባክህን ፍረድባቸው።” (አወያይ መጠይቅን ፡ይመልከቱ)

ዓይናችን በአንተ ላይ ነው
እዚህ ላይ ህዝቡ ትኩረታቸውን ወደ እግዚአብሔር ማድረጋቸው ለማጉላት በ “ዐይኖቻቸው” ተወክለዋል ። ኣት: - “እኛ እርዳታ እንፈልጋለን” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 20:14

የእግዚአብሔርም መንፈስ መጣ
ይህ ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን የእግዚአብሔር መንፈስ ሕዚኤልን ገፋፍቶ እንዲተነቢይ አስችሎታል ለማለት ነው። ይህንን በ 2 ኛ ዜና ምዕራፍ 15 ፡1 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት (ፈሊጥን ፡ይመልከቱ)

የሕዚኤል... ዘካርያስ... በናያስ... ያይዒኤል... ማርያንያ... አሳፍ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው ። (የስሞችን አተረጓጎም ፡ይመልከቱ)

እናንተ የይሁዳ ሰዎች ሁሉ እና እናንተ የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ሁሉ ፣
እዚህ ላይ “ይሁዳ” የሚያመለክተው በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ነው ። ኣት: - “በይሁዳና በኢየሩሳሌም የምትኖሩ ሁሉ” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

ሰልፉ የእግዚአብሔር ነው እንጂ የእናንተ አይደለምና
ይህ ማለት እግዚአብሔር ጦርነቱን እና የሚሆነውን ይቆጣጠራል ማለት ነው ።

2 Chronicles 20:16

በእነርሱ ላይ ውረዱ... በእነርሱ ላይ ውጣ
ይህ አባባል ለውጊያ ከጠላት ሠራዊት ጋር መግጠም ማለት ነው ። ኣት: - “ውጣ.... በእነርሱ ላይ ውጣ” ወይም “ለመዋጋት ሂድ... ለውጊያ ሂድ” (ፈሊጥን ፡ይመልከቱ)

እነሆ
የምነግርህ ነገር እውነትም አስፈላጊም ስለሆነ ትኩረት ስጥ ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በጸጽ ማለፊያ
ይህ ከኢየሩሳሌም በስተ ደቡብ ምስራቅ ባሉት ሁለት ተራሮች መካከል ያለ ጠባብ ሸለቆ ነው። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ማዳን ከአንተ ጋር ነው
“ማዳን” የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “እግዚአብሔር ያድንህ”(የረቂቅ ስምን :ይመልከቱ)

ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን
እዚህ እነዚህ ቦታዎች ከነርሱ የመጡ ሰዎችን ይወክላሉ ። ኣት: - “የይሁዳና የኢየሩሳሌም ሰዎች” (የባህሪ ስምን:ይመልከቱ)

2 Chronicles 20:18

አጎንብሶ በግንባሩ መሬት ላይ ሰገደ ... በእግዚአብሔር ፊት ወደቀ
እነዚህ የአምልኮ ተግባራት ትህትና እና ለእግዚአብሔር መገዛት የሚገልጹ ናቸው ። (ምሳሌያዊ ድርጊትን :ይመልከቱ)

መላው ይሁዳ
እዚህ “ይሁዳ” የይሁዳን ሕዝብ ያመለክታል ። ኣት: - “የይሁዳ ሕዝብ ሁሉ” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

የቀዓት ልጆች እና የቆሬ ልጆች
እነዚህ ለቀዓትና ለቆሬ ልጆች የተሰጡ የጎሳ ስሞች ናቸው። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

በከፍተኛ ድምፅ
ይህ የሚናገረው እግዚአብሔርን አንድ ድምፅ እንዳላቸው ሰዎች በአንድነት ስለሚያመሰግኑ ሰዎች ነው። ኣት: - “በከፍተኛ ድምፅ” (ዘይቤያዊን : ይመልከቱ)

2 Chronicles 20:20

ቴቁሔ
የዚህን ከተማ ስም በ 2 ኛ ዜና 11 ፡ 6 ካለው ጋር የሚመሳሰል አድርገህ ተርጉም ። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

ትደገፋለህ
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “እርሱ ይደግፍሃል” ወይም “እሱ ይረዳሃል” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

በነቢያቱ እመኑ ፣ ይሳካላችኋል
“በእግዚአብሔር ነቢያቱ የምትታመኑ ከሆነ ይሳካላችኋል”

የቃል ኪዳኑ ታማኝነት ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል
“ታማኝነት” የሚለው የረቂቅ ስም “በታማኝነት” ወይም “ታማኝ” ተብሎ ሊገለጽ ይችላል ። በ 2 ኛ ዜና መዋዕል 7 ፡3 ውስጥ “የቃል ኪዳን ታማኝነትን” እንዴት እንደተሮጎምከው ተመልከት ። ኣት: - “እርሱ ለዘላለም ይወደናል” ወይም “ከእኛ ጋር ለገባው ቃል ኪዳኑ ታማኝ ነው” (የረቂቅ ስሞችን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 20:22

መዘመር እና ማወደስ
ለእግዚአብሔር እየዘመሩ ነበር ። ኣት: “ለመዘመር እና እግዚአብሔርን ለማወደስ” (የቃላት ግድፈትን :ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ሰዎችን ያዘጋጃል
ይህ ማለት እግዚአብሔር የተወሰኑ የጠላት ወታደሮች ሌሎች የጠላት ወታደሮችን አድፍጠው እንዲወጉ አድርጎአል ማለት ነው ። ኣት: - “እግዚአብሔር የተወሰኑ የጠላት ወታደሮችን አዘጋጀ” (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን :ይመልከቱ)

አድፍጦ ማጥቃት
ድንገተኛ ጥቃት

የሴይር ተራራ
በ 2 ኛ ዜና ምዕራፍ 20 ፡10 እንዳለው የዚህን ቦታ ስም ተመሳሳይ አድርገህ ተርጉም ። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

ተሸንፈዋል
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ድል አደረጓቸው” ወይም “አድፍጠው ያጠቋቸውን አሸነፉ” (ገቢራዊን እና ተብሮአውን : ይመልከቱ)

እነርሱን ሙሉ በሙሉ ለመግደል እና ለማጥፋት
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ አንድ ዓይነት ናቸው ። ሁለተኛው የመጀመሪያውን ያጠናክረዋል። ኣት: - “እነርሱን ፈጽሞ ለማጥፋት” (ድግግሞሽን:ይመልከቱ)

በጨረሱ ጊዜ
ይህ የሚያጠፉትን ካጠፉ በኋላ ነው ። ኣት: - “ግዲያውን በጨረሱ ጊዜ” (የሚጠበቅ እውቀጥን እና ያልተገለጸን መረጃ :ይመልከቱ)

2 Chronicles 20:24

እነሆ ፣ እነሱ ሞተዋል
አንድ አስገራሚ ክስተት ለማመልከት “እነሆ” የሚለው ቃል እዚህ ጥቅም ላይ ውሏል ።

እነርሱ ሞቱ ፣ መሬት ላይ ወደቁ
“መሬት ላይ ወደቁ” የሚለው ሐረግ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው ፣ “እነሱ ሞተዋል” ማለት ነው።(ፈሊጥን እና ድግግሞሽን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 20:25

በአራተኛው ቀን
“4ኛ ቀን” (ሕገኛ ቁጥርን :ይመልከቱ)

በበረከት ሸለቆ
ይህ የቦታ ስም ነው ። (የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)

እስከዛሬ
ይህ ማለት ጸሐፊው የጻፈበትን ቀን ነው ። ይህንን በ 2 ኛ ዜና 5 ፡9 ውስጥ እንዴት እንደተረጉሙ ይመልከቱ ።

2 Chronicles 20:27

የይሁዳና የኢየሩሳሌም ሰዎች ሁሉ
ይህ በሠራዊቱ ውስጥ ላለ እያንዳንዱን ሰው የሚያመለክት ነው ። አት: - “የይሁዳና የኢየሩሳሌም ወታደር ሁሉ” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን :ይመልከቱ)

በፊታቸው ኢዮሣፍጥ
“ኢዮሣፍጥ እየመራቸው” የሚለው ሐረግ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው ። ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለሱ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ በሠራዊቱ ሁሉ ፊት ነበረ። (ፈሊጥን : ይመልከቱ)

በጠላቶቻቸው ደስ ይበላችሁ
ጠላቶቻቸው ስለተሸነፉ ደስ አላቸው ። አት: - “በጠላቶቻቸው ሽንፈት ደስ ይበላችሁ” ወይም “ጠላቶቻቸው ስለጠፉ ደስ ይበላችሁ” (የሚጠበቅ እውቀንት እና ያልተገለጸ መረጃን :ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Chronicles 20:29

የእግዚአብሔር ፍርሃት በምድር መንግሥታት ሁሉ ላይ ነበር
“ሽብር” የሚለው ቃል “ፍርሃት” በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል ። ኣት: “የአሕዛብ መንግሥታት ሁሉ እግዚአብሔርን እጅግ ይፈሩ ነበር”

በምድር መንግሥታት
በአቅራቢያ ባሉ አገራት ውስጥ ያሉ መንግሥታት ”

የኢዮሣፍጥ መንግሥት ጸጥ አለ
ይህ መንግሥቱ ፀጥ ያለ ያህል ሰላም እንዳገኘ ይናገራል ። ኣት: - “የኢዮሣፍጥ መንግሥት ሰላም ነበር”

2 Chronicles 20:31

ሰላሳ ዓምስት ዓመት... ከሃያ አምስት ዓመት
“35 ዓመት... 25 ዓመት” (ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

የሺልሒ ልጅ አዙባ
“አዙባ” የኢዮሣፍጥ እናት ስም ነበር። ሺልሒ የአዙባ አባት ስም ነበር። (የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)

በአባቱ በአሳ መንገድ ሄደ። ከእነርሱም አልተመለሰም
ይህም ማለት አባቱ እንዳደረገው እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኘ መንገድ ኖሯል ማለት ነው ። እዚህ “መራመድ” ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን የአንድን ሰው አኗኗሩን እና ባህሪውን የሚወክል ነው ። ኣት : - “አባቱ አሳ እንዳደረገው እግዚአብሔርን ደስ አሰኘው ፤ እነዚያንም ማድረጉን አላቋረጠም።” (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን እና ፈሊጥን :ይመልከቱ)

በእግዚአብሔርም ፊት ቅን ነገር አደረገ
እዚህ ያሉት ዓይኖች ማየትን ይወክላሉ ፣ እና ማየት ፍርድን ይወክላል ። እግዚአብሔር የኢዮሳፍጥ ተግባር ተመለከተ እና ፈቀደ ። በ 2 ኛ ዜና ምዕራፍ 14 ቁጥር 2 ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጉሙ ተመልከት ። AT: - “ያህዌህ ትክክል ነው ያየውን አደረገ” ወይም “ያህዌህ ትክክል መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

የኮረብታው መስገጃዎች አልተወገዱም
ይህ በገቢራዊ አረፍተነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ከፍ ያሉትን የማምለኪያ ሥፍራዎችን አላስወገደም” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን:ይመልከቱ)

ሕዝቡ አሁንም ልባቸውን ወደ እግዚአብሔር አልመሩም ነበር
ይህ ማለት ህዝቡ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ አልፈለጉም እና ለእርሱ ያደሩ አይደሉም ። እዚህ ላይ የሰዎቹ “ልብ” ፈቃዳቸውንና እና ፍላጎታቸውን ይወክላል። አትቲ: - “አሁንም ሕዝቡ ለአምላካቸው ያደሩ አልነበሩም” ወይም “ሕዝቡ አሁንም እግዚአብሔርን ለመከተል አልተሰጡም” (የባህሪ ስምን: ይመልከቱ)

2 Chronicles 20:34

የመጀመሪያው እና የመጨረሻው
እነዚህ ሁለት ተቃራኒዎች የተሰጡት ንጉሥ ኢዮሣፍጥ በነገሠበት ዘመን ስለነበረው ነገር ሁሉ ለማመልከት ነው ። ኣት : - “ከንግስናው መጀመሪያ እስከሞተበት ጊዜ ድረስ” (ሜሪዝምን:ይመልከቱ)

እነሆ ፣ እነርሱ በታሪክ ውስጥ ተጽፈዋል... እስራኤል
እዚህ “እነሆ” የሚለው ቃል ተከታዩ አስፈላጊ መረጃ ላይ አፅንዖት ለመስጠት ጥቅም ላይ ውሏል። ኣት: - “ማንም ሰው በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ማየት ይችላል .... እና እዚያ እንደተጻፈ ማየት ይችላል”

እነርሱ የተጻፉት በ... ውስጥ የተቀረጸ ነው
ይህ በገቢራዊ አረፍተነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “እነርሱ ያሉት... በውስጣቸው ነው” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን:ይመልከቱ)

በአናኒ
በ 2 ኛ ዜና መዋዕል 16፡ 7 ውስጥ እንደተሮግምከው የዚህን ሰው ስም ተርጉሙ ። (የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)

የአናኒ ልጅ የኢዩ ታሪክ
ይህ በኢዩ የተጻፈ ታሪካዊ መዝገብ ነው ።

የእስራኤል ነገሥታት መጽሐፍ
ይህ የማይገኝ መጽሐፍ ነው። በ 2 ኛ ዜና 16፡ 11 ውስጥ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ።

2 Chronicles 20:35

መርከቦች
እነዚህ በትላልቅ የውሃ አካላት ላይ የመጓዝ አቅም ያላቸው መርከቦች ናቸው ።

ተርሴስ
ይህ የከተማ ስም ነው ። (የስሞችን አተጓጎም:ይመልከቱ)

መርከቦቹን ሠሩ
ኢዮሣፍጥ እና አካዝያስ መርከቦቹን አልሠሩም፣ ሠራተኞቻቸው ግን ሠርተዋቸዋል። አት: - “ሰራተኞቻቸው መርከቦቹን ሠሩ” (የባህሪ ስምን : ይመልከቱ)

ዔጽዮን ጋብር
በ 2 ኛ ዜና 8 :17 እንዳተሮጎምከው የዚህን ቦታ ስም ተርጉሙ ። (የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)

አልዓዛር... ዶዳያ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው ። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

መሪሳም
በ 2 ኛ ዜና 11 :8 እንደተሮጎምከው የዚህን ሰው ስም ተርጉሙ ። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

መርከቦቹ ተሰባብረዋል ስለዚህ
ይህ በገቢራዊ አረፍተነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “መርከቦቹ ተሰበሩ” ወይም “መርከቦቹ ስለተሰበሩ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

በመርከብ መጓዝ አልቻሉም
“እነሱን ሊያንቀሳቅሳቸው ማንም አልቻለም”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 21

1 ኢዮሳፍጥም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ በዳዊትም ከተማ ከእነርሱ ጋር ተቀበረ፤ ልጁም ኢዮራም በእርሱ ቦታ ነገሠ። 2 ኢዮራም የኢዮሳፍጥ ልጆች የሆኑ ወንድሞች ዓዛርያስ፥ ይሒኤል፥ ዘካርያስ፥ ዔዛርያስ፥ ሚካኤልና ሰፋጥያስ ነበሩት። እነዚህ ሁሉ የይሁዳ ንጉሥ የኢዮሳፍጥ ልጆች ነበሩ። 3 አባታቸው ብዙ የብር፥ የወርቅ እና የሌሎች የከበሩ ነገሮች እንዲሁም በይሁዳም የተመሸጉ ከተሞችን ሰጣቸው፤ ዙፋኑን ግን የመጀመሪያ ልጁ ስለነበር ለኢዮራም ሰጠው። 4 ኢዮራም በአባቱ መንግሥት ላይ በወጣና ራሱን እንደ ንጉሥ አጽንቶ በመሠረተ ጊዜ ወንድሞቹን ሁሉና የተለያዩ የእስራኤል ሌሎች መሪዎችን ጭምር በሰይፍ ገደላቸው። 5 ኢዮራምም መንገሥ በጀመረ ጊዜ ሠላሳ ሁለት ዓመቱ ነበር፤ በኢየሩሳሌምም ስምንት ዓመት ነገሠ። 6 የአክዓብን ሴት ልጅ አግብቶ ስለነበር የአክዓብ ቤት ያደርግ እንደነበር በእስራኤል ነገሥታት መንገድ ሄደ፤ በእግዚአብሔርም ፊት ክፉ የነበረውን ነገር አደረገ። 7 ነገር ግን እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር ካደረገው ቃል ኪዳን የተነሳ የዳዊትን ቤት ለማጥፋት አልፈለገም፤ ለአርሱና ለዝርያዎቹ ሁልጊዜ ሕይወት እንደሚሰጣቸው ቃል ገብቶላቸው ነበር። 8 በኢዮራም ዘመን ኤዶምያስ በይሁዳ ኃይል ላይ ዐመፀ፤ በራሳቸውም ላይ ንጉሥ ሾሙ። 9 በዚያን ጊዜ ኢዮራም ከአዛዦቹና ከሠረገላዎቹ ሁሉ ጋር ተሻገረ፤ በሌሊትም ተነስቶ እርሱንና የሠረገላዎቹን አዛዦች ከብበው የነበሩትን ኤዶማውያንን መታ። 10 በመሆኑም እስከ ዛሬዋ ቀን ድረስ ኤዶምያስ በይሁዳ ኃይል ላይ እንዳመፀ ነው። ኢዮራም የአባቶቹን አምላክ እግዚአብሔርን ስለተወ የልብና ከተማ ጭምር በዚያው ጊዜ በኃይሉ ላይ ዐመጸ። 11 በተጨማሪም ኢዮራም በይሁዳ ተራራዎች ላይ መስገጃዎችን ሠርቶ ነበር፤ የኢየሩሳሌምን ነዋሪዎችም እንደ አመንዝራ ሌሎች አማልክትን እንዲከተሉ አደረጋቸው። በዚህ መንገድ ይሁዳን ከትክክለኛው መስመር አስወጣቸው። 12 ከነቢዩም ከኤልያስ አንድ ደብዳቤ ወደ ኢዮራም መጣለት፤ የአባትህ የዳዊት አምላክ እግዚአብሔር የሚለው ይህ ነው፦" በአባትህ በኢዮሳፍጥ መንገድ ወይም በይሁዳ ንጉሥ በአሳ መንገድ ስላልሄድህ 13 ነገር ግን በእስራኤል ነገሥታት መንገድ ስለሄድህ ይሁዳንና የኢየሩሳሌምን ነዋሪዎች የአክዓብ ቤት እንዳደረገ እንደ አመንዝራ ሌሎች አማልክትን እንዲከተሉ ስላደረግሃቸው፤ በአባትህ ቤተሰብም ውስጥ ከአንተ የሚሻሉ የነበሩትን ወንድሞችህን በሰይፍ ስለገደልካቸው 14 እነሆ እግዚአብሔር ሕዝብህን፥ ልጆችህን፥ ሚስቶችህን እና ሀብትህንም ሁሉ በታላቅ መቅሰፍት ይመታል። 15 አንተም ራስህ ከበሽታው የተነሳ ከቀን ወደ ቀን አንጀትህ እስኪወጣ ድረስ በአንጀትህ ሕመም እጅግ ትታመማለህ።" 16 እግዚአብሔርም የፍልስጤማውያንን እና በኢትዮጵያውያን አጠገብ ይኖሩ የነበሩትን የዓረባውያንን መንፈስ በኢዮራም ላይ አስነሳበት። 17 እነርሱም ይሁዳን አጠቁ፤ ወረሩአትም፤ በንጉሡ ቤት ውስጥ የተገኘውን ሀብት ሁሉ ወሰዱ፤ ወንዶች ልጆቹንና ሚስቶቹንም ወሰዱ። ከታናሹ ልጁ ከአካዝያስ በስተቀር ምንም ልጅ አልቀረለትም። 18 ከዚህ ሁሉ በኋላ እግዚአብሔር ሊድን በማይችል በሽታ አንጀቱን መታው፤ 19 በተገቢው ጊዜ በሁለቱ ዓመት መጨረሻ ከሕመሙ የተነሳ አንጀቱ ወጣ፤ በብርቱ በሽታም ሞተ። ሕዝቡም ለእርሱ አባቶች እንዳደረገው ለክብሩ ምንም ችቦ አላበራም። 20 በሠላሳ ሁለት ዓመቱ ላይ መንገሥ ጀምሮ ነበር፤ በኢየሩሳሌምም ስምንት ዓመት ነገሠ፤ ማንም ሳያዝንለት ሞተ። በነገሥታቱ መቃብር ሳይሆን በዳዊት ከተማ ቀበሩት።

---

2 Chronicles 21:1

ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ
ስለኢዮሣፍጥ መሞት ሲነገር እንዳንቀላፋ ተብሎ ተነግሯል ። ኣት: “ሞተ”(ዘወርዋራን :ይመልከቱ)

የዳዊት ከተማ
ይቺ የኢየሩሳሌም ከተማ ናት። (ፈሊጥን :ይመልከቱ) አዛርያስ ፣ ይሒኤል ፣ ዘካርያስ ፣ ዔዛርያስ ፣ ሚካኤል እና ሰፋጥያስ እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው ። (የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)

የእስራኤል ንጉሥ ኢዮሣፍጥ
ደቡባዊው መንግሥት በቴክኒካዊ መንገድ “ይሁዳ” ተብሎ ተጠርቷል ፣ የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ግን የደቡባዊው መንግሥት እግዚአብሔርን በመታዘዝ ላይ ያለ በመሆኑን እውነተኛው እስራኤል እምደሆነ ለመግለጽ የፈለገ ይመስላል ።

ትልቅ ስጦታዎች
“እጅግ ብዙ ስጦታዎች”

መንግሥቱን ለኢዮራም ሰጠው
መንግሥቱ ኢዮሣፍጥ ልክ እንደ እንደ ቁስ ለኢዮራም እንደሰጠው ተደርጎ ተገጾአል ። ኣት: - “ኢዮራምን አነገሠው” (ጥራዝ 2ን :ተርጉም ዘይቤያዊን ፡ ይመልከቱ)

2 Chronicles 21:4

በአባቱ መንግሥት ላይ ተነስቷል
የሆነ ነገር ላይ “መነሳት” ማለት በፈሊጣዊ አነጋገር ነገሩን መቆጣጠር ማለት ነው ። ኣት: - “የአባቱን መንግሥት ሙሉ በሙሉ ተቆጣጠረ” (ፈሊጥን ፡ ይመልከቱ)

ወንድሞቹን ሁሉ በሰይፍ ገደላቸው
ኢዮራም ምናልባት በግሉ አላጠፋቸውም ፣ ግን ሌሎች ሰዎች ግድያውን እንዲፈጽሙለት አድርጓል ። ኣት: - “ታናናሽ ወንድሞቹን ሁሉ እንዲገደሉ አደረጋቸው” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 21:6

በመንገዱም ሄደ
ይህ ፈሊጥ ሲሆን የእነርሱን ምሳሌ ተከትሏል ማለት ነው። በ 2 ኛ ዜና 20 ፡ 32 ውስጥ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። ኣት: - “ምሳሌውን ተከተሉ” (ፈሊጥን :ይመልከቱ)

የአክዓብ ቤት እንዳደረገ
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰብ የሚገልጽ ምትክ ስም ነው ። በዚህ ሁኔታ ቤት የሚለው ቃል የአክአብን ዘሮች ያመለክታል ። ኣት: - “የአክዓብ ዘሮች ያደርጉ እንደነበሩት” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

የአክዓብንም ልጅ አገባ
“የአክዓብን ሴት ልጅ አገባ”

በእግዚአብሔር ፊት
የእግዚአብሔር እይታ ፍርዱን ወይም ግምገማውን ይወክላል ። ኣት: - “እንደ እግዚአብሔር ፍርድ” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

የዳዊት ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰብ የሚገልጽ ምትክ ስም ነው ። በዚህ ሁኔታ ቤት የሚለው የይሁዳን መንግሥት ያመለክታል ። በኤር 3 ፡18 ውስጥ ይህንን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። ኣት: - “የይሁዳ መንግሥት” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ” (የባህሪ ስምን ፡ ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለእርሱና ለዘሩ ሁል ጊዜ ሕይወት እንደሚሰጥ ቃል ገብቷል
ይሁዳን የሚገዙት ሁል ጊዜ የዳዊት ዘሮች እንደሚሆን ቃል ገብቷል ። ከዳዊት ዘር ጋር የገባው ቃል ኪዳን ይህ ነው ።

ለእርሱና ለልጆቹ ሁል ጊዜ ህይወትን ይሰጣል
“ሁልጊዜ እርሱና ዘሩ በሕይወት እንዲኖሩ ያደርጋል” ወይም “እሱንም ሆነ ዘሮቹን ፈጽሞ አታጠፏቸውም”

2 Chronicles 21:8

በኢዮራም ዘመን
“ኢዮራም በነገሠበት ዘመን”

ከይሁዳ ቁጥጥር
“በይሁዳን ቁጥጥር ላይ”

በራሳቸው ላይ ንጉሥ ሾሙ
“መሾም” የሚለው ቃል መምረጥ የሚለውን የሚገልጽ ምትክ ስም ነው ፣ እና “በራሳቸው ላይ” የሚሉት ቃላት “እነሱን የሚገዛ” የሚለውን ቃል የሚገልጽ ምትክ ስያሜ ነው ። “ኣት” “በላያቸው ላይ እንዲገዛ ንጉሥ መረጡ” (የአፀፋ ተውላጠ ስምን :ይመልከቱ)

ተሻገረ
“ድንበሩን ወደ ኤዶም መሻገር” ወይም “ወደ ኤዶም ሄደ”

ሲነሳ ሌሊት ነበር ... እርሱንና የሰረገሎቹን አዛዦች ከበቡ
ይህን ዓረፍተ ነገር እንደገና ማረም እና በተዘዋዋሪ መንገድ የተሰጠን መረጃ ማከል ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ኣት: - “ኤዶማውያን እርሱንና የሠረገላዎቹን አዛዦች ከበቡ ፤ ነገር ግን ኢዮራምና ከእርሱም ጋር የነበሩት ጭፍሮች ተዋጉ በሌሊትም አመለጡ” (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን : ይመልከቱ)

እስከ ዛሬ ድረስ
ይህ የ 2 ዜና መዋዕል መጽሐፍ የተጻፈበትን ጊዜ ያመለክታል። ይህንን በ 2 ኛ ዜና ምዕራፍ 5፡ 9 ውስጥ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ።

ልብና
ይህ በይሁዳ የሚገኝ ከተማ ነበር። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

2 Chronicles 21:11

በተጨማሪም ኢዮራም የከፍታ ቦታዎችን ሠራ
በይሁዳ ተራሮች ሁሉ እነዚህን ከፍ ያሉ ስፍራዎች እንዲሠራ ኢዮራምን ሌሎች ሰዎች ረድተውት ነበር። ኣት: - “ኢዮራምና ሕዝቡም ከፍ ያሉ መስገጃዎችን ሠሩ” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን :ይመልከቱ)

የኢየሩሳሌም ሰዎች እንደ ዝሙት አዳሪዎች እንዲኖሩ አደረጋቸው
ኢዮራምም ሕዝቡ በእርሱ ፋንታ ጣዖታትን እንዲያመልክ አደረገ። ከእነርሱ ጥቅም ለማግኘት ሌሎች አማልክትን የሚያገለግሉ ሰዎች እንደ መንፈሳዊ ዝሙት አዳሪዎች ይታያሉ ። አት. “ልክ ዝሙት አዳሪዎች ባሎቻቸው ያልሆኑትን ሰዎች እንደሚያገለግሉ የኢየሩሳሌም ሕዝብ እግዚአብሔርን ትቶ ሌሎች አማልክትን እንዲያገለግሉ አደረገ።

ይሁዳን አሳተ
እግዚአብሔርን አለመከተል ትክክለኛውን መንገድ በለመከተል ተመስሏል ። ኣት: - “ይሁዳ እግዚአብሔን እንዳይከተል አድርጓል” (ዘይቤያውን : ይመልከቱ)

2 Chronicles 21:12

ከነቢዩ ኤልያስ ደብዳቤ ወደ ኢዮራም ደረሰ
“ኢዮራምም ከነቢዩ ኤልያስ” ወይም “ነቢዩ ኤልያስ ለኢዮራም ደብዳቤ ልኮለታል”

በመንገዱም ሄደ
ይህ አባባል የእነሱን አርአያነት እንደተከተለ የሚገልጽ ነው። በ 2 ኛ ዜና 20 ፡ 32 ውስጥ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። ኣት: - “ምሳሌውን ተከተለ” (ፈሊጥን :ይመልከቱ)

እንደ ዝሙት አዳሪ ሆኑ
ኢዮራምም ሕዝቡ በእግዚአብሔር ፋንታ ጣዖታትን እንዲያመልክ አደረገ። ከእነርሱ ጥቅም ለማግኘት ሌሎች አማልክትን የሚያገለግሉ ሰዎች እንደ መንፈሳዊ ዝሙት አዳሪዎች ተቆጥረዋል ። በ 2 ኛ ዜና 21 ፡11 ውስጥ ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት ። ኣት: - “ዝሙት አዳሪዎች ባሎቻቸው ያልሆኑትን ወንዶች እንደሚያገለግል እግዚአብሔርን ትተው ሌሎች አማልክትን አገልግሉ” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

የአክዓብ ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን የሚገልጽ ምትክ ስም ነው ። በዚህ ሁኔታ እሱ የአክአብን ዘሮች ያመለክታል ። በ 2 ኛ ዜና 21፡ 6 ውስጥ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። ኣት: - “የአክዓብ ዘር” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

እይ
ይህ ኢዮራም ቀጥሎ የሚነገረውን መልእክት በትኩረት እንዲከታተል ይነግረዋል ።

በታላቅ መቅሰፍት ይመታል
“ታላቅ መቅሠፍት እንዲከሰትባቸው” አደረገ

አንተ ራስህ
“ራስህ” የሚለው ሪፍሌክሲቭ ፍርዱ በኢዮራም ላይ የሚደርስ ፍርድ መሆኑን ያጎላል ። (የአፀፋ ተውላጠ ስምን፡ ይመልከቱ)

በበሽታው ምክንያት አንጀትህ እስከሚወድቅ ድረስ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ቃል በቃል አንጀቱ ይወድቃል ወይም 2) ይህ ሞት የሚያስከትለውን የአንጀት ችግር የሚገልፅ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው ። ኣት: - “ይህ በሽታ ሞትህን እስከሚያመጣ ድረስ” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 21:16

የፍልስጥኤማውያንን እና የዓረባውያንን መንፈስ በኢዮራም ላይ እንዲነሳ አደረገ
መንፈስን ማነሳሳት ማለት አንድ ሰው እርምጃ ለመውሰድ እንዲፈልግ ማድረግን የሚገልጽ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። እዚህ “መንፈስ” ነጠላ ሲሆን ፍልስጤማውያንን እንደ አንድ ቡድን እና ዓረባውያንን እንደ አንድ ቡድን ይመለከታል ። ኣት: “ፍልስጥኤማውያንና ዓረባውያን በኢዮራም ላይ ተቆጥተው ነበር” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

በኢዮራም ላይ
እዚህ ላይ ኢዮራም የሚያመለክተው ኢዮራምን እና ይገዛው የነበረውን የይሁዳን ህዝብ ነው ። ኣት: - “በኢዮራም እና በይሁዳ ሰዎች ላይ” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን :ይመልከቱ)

በኩሾች አቅራቢያ የነበሩትን የፍልስጥኤማውያን እና የዐረባውያን መንፈስ
ፍልስጥኤማውያንና አረቦች ሁለት የተለያዩ አገራት ነበሩ ። አረባውያን በይሁዳ ደቡብምስራቅ በኩል በኩሽ አቅራቢያ ይኖሩ ነበር ፣ ፍልስጤማውያንም ከይሁዳ በስተ ምዕራብ ይኖሩ ነበር ። እነዚህ አገራት በተናጥል ተነሳሱ ። ይህ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። ኣት: - “የፍልስጤማውያን መንፈስ እና በኩሾች

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አቅራቢያ የነበሩት የአረባውያን መንፈስ” (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን ፡ይመልከቱ)

ከታናሹም ልጅ ከአካዝያስ በቀር ልጅ አልቀረለትም
“ታናሹን ልጅ ኢዮአስ በቀር ወንዶች ልጆቹን ሁሉ ወሰዱ” ወይም “ለእርሱ ያስቀሩለት ብቸኛው ወንድ ልጅ የሁሉም ታናሽ የነበረውን ኢዮአስ ነው”

ታናሽ ልጁ ኢዮአስ
ይህ ልጅ በ 2 ኛ ዜና 22፡ 26 ላይ “አካዝያስ” ተብሎ ተጠርቷል ።

2 Chronicles 21:18

እግዚአብሔርም በማይድን በሽታ አንጀቱን መታው
እዚህ “መታው” የሚለው አባባል እግዚአብሔር እንዲታመም ያደረገው ማለት ነው ። ኣት: - “እግዚአብሔርም የአንጀት ውስጥ የማይድን በሽታ እንዲሠቃይ አደረገው” (ፈሊጥን፡ይመልከቱ)

እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ በታሪኩ ውስጥ አንድን አስፈላጊ ሁኔታን ያሳያል ። ቋንቋህ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ መጠቀም ትችላለህ።

በጊዜው
ይህ ፈሊጥ ነው። የተቀጠረን ወይም የተወሰነን ጊዜ የሚያመለክት። ኣት: - “በተገቢው ጊዜ” ወይም “በትክክለኛው ጊዜ” (ፈሊጥን ፡ይመልከቱ)

ለአባቶቹ እንዳደረጉት ሁሉ ለእርሱ እሳትን በማንደድ ክብር አልሰጠም
በእስራኤል ልማድ የሞተውን ንጉሥ ለማክበር አጥንት ያነዱ ነበር ። ለእርሱ ያላቸውን ንቀት ለመግለጽ ለኢዮራም ይህን አላደረጉለትም ። ይህ በግልጽ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “በተለምዶ ነገሥታት ሲሞቱ እንደሚያከብሩ ሁሉ ሊያከብሩት ቃል አልገቡም” (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን ፡ ይመልከቱ)

ሲሄድ አንድ ሰው አላለቀሰለትም ነበር
“በመሞቱ ማንም አላዘነም”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 22

1 የኢየሩሳሌም ነዋሪዎችም የኢዮራምን ታናሽ ልጅ አካዝያስን በእርሱ ቦታ አነገሡት፤ ምክንያቱም ከአረቢያኖቹ ጋር ወደ ካምፑ የመጡባቸው የሸፍቶች ቡድን የእርሱን ታላላቆች ሁሉ ገድለዋቸው ስለነበር ነው። በመሆኑም የይሁዳ ንጉሥ የኢዮራም ልጅ አካዝያስ ነገሠ። **2** አካዝያስ መንገሥ በጀመረ ጊዜ አርባ ሁለት ዓመቱ ነበር፤ በኢየሩሳሌምም ሁለት ዓመት ነገሠ። የእናቱ ስም ጎቶልያ ነበረ፤ እሷም የዖምሪ ልጅ ነበረች። **3** እናቱ ክፉ ነገሮችን ለማድረግ መካሪው ስለነበረች እርሱም በአክዓብ ቤት መንገድ ሄደ። **4** ከአባቱ ሞት በኋላ ለገዛ ራሱ ጕዳት እስኪሆን የአክዓብ ቤት መካሪዎቹ ስለነበሩ የአክዓብ ቤት እንዳደረገ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ አደረገ። **5** ምክራቸውንም ተከተለ፤ የአራምን ንጉሥ አዛሄልን በሬማት ዘገለዓድ ሊዋጋ ከእስራኤል ንጉሥ ከአክዓብ ልጅ ከኢዮራም ጋር ሄደ። አርመናውያንም ኢዮራምን አቆሰሉት። **6** ኢዮራምም የአራምን ንጉሥ አዛሄልን በራማ በተዋጋ ጊዜ ካቆሰሉት ቁስል ይፈወስ ዘንድ ወደ ኢይዝራኤል ተመለሰ። ኢዮራም ቆስሎ ስለነበር የይሁዳ ንጉሥ የኢዮራም ልጅ አካዝያስ የአክዓብን ልጅ ኢዮራምን ሊያየው ወደ ኢይዝራኤል ወረደ። **7** አካዝያስ ኢዮራምን በመጎብኘቱ አማካይነት እንዲጠፋ እግዚአብሔር ፈቅዶ ነበር። በመጣ ጊዜ የአክዓብን ቤት እንዲያጠፋ እግዚአብሔር የመረጠውን የናሚሴን ልጅ ኢዩን ለማጥቃት ከኢዮራም ጋር ሄደ። **8** ኢዩም የእግዚአብሔርን ፍርድ በአክዓብ ቤት ላይ እየፈጸመ በነበረበት ጊዜ የይሁዳን መሪዎችና አካዝያስን የሚያገለግሉትን የአካዝያስን ወንድሞች ልጆች አገኛቸው። ኢዩም ገደላቸው። **9** ኢዩ አካዝያስን ፈለገው፤ በሰማርያም ተሸሽጎ አገኙት፤ ወደ ኢዩም አመጡት፤ እርሱም ገደለው። ከዚያም "እግዚአብሔርን በፍጹም ልቡ የፈለገው የኢዮሳፍጥ ልጅ ነው" ብለው ቀበሩት። በመሆኑም የአካዝያስ ቤት መንግሥቱን ለመምራት ምንም የቀረ ኃይል አልነበረውም። **10** የአካዝያስ እናት ጎቶልያ ልጇ መሞቱን ባየች ጊዜ ተነስታ በይሁዳ ቤት ውስጥ የነገሥታቱን ዝርያ ልጆች ሁሉ ገደለች። **11** ነገር ግን የንጉሡ ልጅ ዮሳቤት የአካዝያስ ልጅ ኢዮአስን ከተገደሉት ከንጉሡ ልጆች መካከል ሰርቃ ወሰደችው፤ እርሱንና ሞግዚቱን በመኝታ ክፍል ውስጥ አስቀመጠቻቸው። ስለዚህ የንጉሡ የኢዮራም ልጅ የካህኑ የዮዳሄ ሚስት ዮሳቤት (የአካዝያስ እኅት ስለነበረች) ጎቶልያ እንዳትገድለው ከጎቶልያ ሸሸገችው። **12** ጎቶልያ በምድሪቱ ላይ ስትገዛ ሳለ እርሱ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ለስድስት ዓመታት ተሸሽጎ ከእነርሱ ጋር ነበረ።

---

2 Chronicles 22:1

የወንዶች ቡድን ... ታላላቅ ወንዶች ልጆችን ሁሉ ገድለዋቸዋል
ይህ የ 2ኛ ዜና መዋዕል 21፡ 16-17 ለተከሰቱ ክስተቶች ዳራዊ መረጃ ነው ። ቀደም ባለው ዘገባ ላይ አካዝያስ “ኢዮአስ” ተብሎ ተጠርቷል። ንጉሥ ሲሆን ስሙን ቀይሮ ሊሆን ይችላል ። (ዳራዊ መረጃን ፡ይመልከቱ)

ታላላቅ ወንዶች ልጆቹ ሁሉ
“ሁሉም የኢየራም ታላላቅ ልጆች”

ሃያ ሁለት ዓመት
“እድሜው 22 ዓመት ነበረ” (ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)

ጎቶልያ
የአካዝያስ እናት ስም ይህ ነው። (የስሞችን አተረጓጎም ፡ይመልከቱ)

እርሱ እንዲሁ በመንገዶቹ ሄደ
እዚህ “በመንገዶቹ ሄድ” የሚለው አባባል የአክዓብን ምሳሌ ይከተላል ማለት ነው ። ይህንን በ 2 ኛ ዜና 20፡32 ውስጥ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። አት: - “እሱም ምሳሌውን ተከትሏል” (ፈሊጥን ፡ይመልከቱ)

የአክዓብ ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚገልጽ ተተኪ ስም ነው ። በዚህ ሁኔታ ቤት የሚለው የአክአብን ዘር ያመለክታል ። በ 2 ኛ ዜና ምዕራፍ 21 6 ውስጥ ይህንን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። አት: - “የአክዓብ ዘር” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 22:4

በእግዚአብሔር ፊት
የእግዚአብሔር እይታ ፍርዱን ወይም ግምገማውን ይወክላል ። አት: - “እንደ እግዚአብሔር ፍርድ” (ዘይቤያዊን ፡ይመልከቱ)

የአክዓብ ቤት ሲያደርግ እንደነበረው
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚገልጽ ተኪ ስም ነው ። በዚህ ሁኔታ እሱ የአክአብን ዘሮች ያመለክታል ። በ 2 ኛ ዜና 21፡ 6 ውስጥ ይህንን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። አት: - “የአክዓብ ዘሮች እንዳደረጉ” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

እነርሱ አማካሪዎቹ ነበሩ
“የአክዓብ ዘሮች ምክር ሰጡት”

ለጥፋቱ
“ይህም ጥፋት አመጣ”

የእነርሱን ምክርም ተከትሏል ። ሄደ
“እርሱ ደግሞ የእነርሱን ምክር ተከትሎ ፣ ሄደ” ወይም “እርሱ ደግሞ የእነርሱን ምክር ተከተለ”

በአራምን ንጉሥ በአዛሄል ላይ
አዛሄል ብቻውን እንዳልተዋጋ ፣ ነገር ግን ሠራዊቱን ከእርሱ ጋር እንደወሰደ አንባቢው መገንዘብ አለበት ። ኣት: “የአራምን ንጉሥ አዛኤልን እና ሠራዊቱን ሊወጋ ሄደ” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን ፡ይመልከቱ)

አዛኤል
ይህ የሰው ስም ነው። (የስሞችን አተረጓጎም ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 22:6

ከሰጡት ቁስል ሁሉ
“በውጊያው ከደረሰበት ቁስል”

ወደ ኢይዝራኤል ወረደ
ኢይዝራኤል ከኢየሩሳሌም ይልቅ ዝቅ ያለ ነበር ።

2 Chronicles 22:7

የአካዝያስ ጥፋት በእግዚአብሔር ዘንድ ሆነ
የ “ጥፋት” የሚለው ጽሑፍ ስም እንደ ድርጊት ሊገለጽ ይችላል። ይህ በገቢራዊ አረፍተነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “እግዚአብሔር አካዝያስን እንዲሞት አደረገው” (የረቂቅ ስሞችን እና ገቢራዊ ወይም ተብሮአዊን ፡ ይመልከቱ)

ወደ ኢየራም ሄደ... ከኢየራም ጋር ሄደ
“ኢየራም” እና “ኢየራም” ለአንድ ሰው የተሰጡ ሁለት ስሞች ናቸው ።

ናሜሲ
ይህ የሰው ስም ነው ። (የስሞችን አተረጓጎም ፡ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ በታሪኩ ውስጥ አንድን አስፈላጊ ክስተት ለማመልከት እዚህ ጥቅም ላይ ውሏል ። ቋንቋህ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ መጠቀም ትችላለህ ።

በአክዓብ ቤት ላይ የአምላክን ፍርድ ይፈጽም ነበር
ይህ የአክአብን ዘሮች መግደል ያመለክታል ። ኣት: - “እግዚአብሔር እንዳዘዘው የአክአብን ዘሮች ሁሉ መግደል”

የአክዓብ ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን የሚገልጽ ተኪ ስም ነው ። በዚህ ሁኔታ ቤት የሚለው ቃል የአክአብን ዘሮች ያመለክታል ። በ 2 ኛ ዜና21፡ 6 ውስጥ ይህንን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። ኣት: - “የአክዓብ ዘሮች” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

የአካዝያስ ወንድሞች ልጆች
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የአካዝያስ ወንድሞች ወይም 2) የአካዝያስ ዘመዶች ወንዶች ልጆች ።

2 Chronicles 22:9

ያዙት... ገደሉትም
አካዝያስን ያዙት… አካዝያስን ገደሉትም ”

“እግዚአብሔርን በፍጹም ልቡ የፈለገ የኢዮሣፍጥ ልጅ ነው” እያሉ ቀበሩት።
ጥሩ ንጉሥ የነበረው የኢዮሣፍጥ ዘር ስለሆነ አስክሬኑን በመቅበር ረገድ አክብረውታል ። ይህ የበለጠ ግልጽ ሊደረግ ይችላል ። ኣት: -እግዚአብሔርን ለማስደሰት ከፍተኛ ጥረት ያደረገው የኢዮሣፍጥ ዘር ስለሆነ ሊቀብር ይገባዋል ስላሉ አስክሬኑን ቀበሩት ።(የሚጠበቅ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ ፡ይመልከቱ)

የአካዝያስ ቤት መንግሥቱን የማስገኘት ኃይል አልነበረውም
እዚህ “የአካዝያስ ቤት” የሚለው የአካዝያስን ዘሮች የሚወክል ስም ነው ። እዚህ ላይ “የመግዛት ኃይል” የሚለው ንጉሡን የሚወክል ነው ። የአካዝያስ ትልልቆች አዋቂዎች ሁሉ ስለሞቱ ይሁዳን የሚገዛ አንድም ሰው አልነበረም። (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 22:10

ተነሥታ የንጉሡን ልጆች ሁሉ ገደለች
እዚህ ደራሲው ጎቶልያ ራሷ ልጆቹን እንደገደለች አስመስሎ ተናግሮአል ፣ ነገር ግን በአገልጋዮቿን እንዳስገደለቻቸው አንባቢው መገንዘብ ይኖርበታል ። ኣት: - “ንጉሣዊ ልጆችን ሁሉ እንዲገድሉ አገልጋዮቿን አዘዘች” (የባህሪ ስምን ፡ ይመልከቱ)

ሁሉም ንጉሣዊ ልጆች
ይህ የሚያመለክተው ወንዶቹን ብቻ ነው ፣ ምክንያቱም ንጉሥ ሊሆኑ ስለሚችሉ ነው ። ቁጥር 11 ወንዶቹ ልጆች እንደተገደሉ ያረጋግጣል ። (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን ፡ይመልከቱ)

የይሁዳ ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩት ቤተሰቦች የሚወክል ስም ነው ። በዚህ ረገድ እሱ የሚያመለክተው የይሁዳን መንግሥት ነው ። ኣት: - “ይሁዳ” ወይም “የይሁዳ መንግሥት” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

የንጉሥ ሴት ልጅ ዮሳቤት ፣ የንጉሥ ኢዮራም ልጅ ናት
እዚህ “ንጉሡ” ”የአካዝያስን አባት ኢዮራምን ያመለክታል ። (የስሞችን አተረጓጎም ፡ይመልከቱ)

ሞግዚት
ይህ የሚያመለክተው ልጅን የሚንከባከበውን ግለሰብ እንጂ ሐኪምን አይደለም ።

ወደ መኝታ ክፍል ገባ
ቁጥር 12 ይህ መኝታ ቤት በቤተመቅደስ ውስጥ እንደነበረ ግልፅ ያደርግልናል ። ዮሴባ ካህን የሆነውን ዮዳሄን አግብታ ስለነበር ወደዚያ ክፍል መግባት ትችል ነበር።

ዮዳሄ
ይህ የወንድ ስም ነው። (የስሞችን አተረጓጎም ፡ይመልከቱ)

እርሱ ከእነርሱ ጋር ነበር
“ዮአስ ከኢዮሳባ እና ዮዳሄም ጋር ነበረ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 23

1 በሰባተኛውም ዓመት ዮዳሄ ውጤት ያለው ነገር አደረገ። የመቶ አለቆቹን የይሮሐምን ልጅ ዓዛርያስን፥ የይሆሐናንን ልጅ ይስማኤልን፥ የዖቤድን ልጅ ዓዛሪያስን፥ የዓዳያንም ልጅ መዕሴያን፥ የዝክሪንም ልጅ ኤሊሳፋጥን ወስዶ ከእርሱ ጋር ቃል ኪዳን እንዲገቡ አደረገ። 2 በይሁዳ ሁሉ ዞረውም ከይሁዳ ከተሞች ሁሉ ሌዋውያንንና የእስራኤልን ቤቶች አባቶች መሪዎች ሰብስበው ወደ ኢየሩሳሌም መጡ። 3 ጉባኤውም ሁሉ ከንጉሡ ጋር በእግዚአብሔር ቤት ቃል ኪዳን አደረጉ። ዮዳሄም፦ "እነሆ እግዚአብሔር ስለ ዳዊት ዝርያዎች እንደተናገረው የንጉሡ ልጅ ይነግሣል" አላቸው። 4 "ማድረግ የሚገባችሁ ይህ ነው፤ በሰንበት ቀን ለማገልገል ከምትመጡት ከእናንተ ከካህናትና ከሌዋውያን አንድ ሦስተኛው በበሮቹ ላይ ጠባቂዎች ትሆናላችሁ። 5 አንድ ሦስተኛችሁ ደግሞ በንጉሡ ቤት ትሆናላችሁ፤ ሌላው አንድ ሦስተኛ በመሠረቱ በር ላይ ይሁኑ፤ ሕዝቡም ሁሉ በእግዚአብሔር ቤት አደባባይ ላይ ይሁኑ። 6 ከካህናቱና ከሚያገለግሉት ሌዋውያን በስተቀር ማንም ወደ እግዚአብሔር ቤት እንዲገባ አትፍቀዱ፤ እነርሱ ለዛሬው ሥራቸው ተለይተው ተመድበዋልና መግባት ይገባቸዋል። ሁሉም የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት መጠበቅ ይገባቸዋል። 7 ሁሉም ሰው የጦር መሣሪያውን በእጁ ይዞ ሌዋውያኑ ንጉሡን በሁሉም በኩል ሊከቡት ይገባቸዋል። ማንም ወደ ቤቱ ውስጥ ቢገባ ይገደል። ንጉሡም በሚገባበትና በሚወጣበት ጊዜ ሁሉ ከእርሱ ጋር ሁኑ። 8 በመሆኑም ሌዋውያኑና ይሁዳ ሁሉ በሁሉም መንገድ ካህኑ ዮዳሄ ባዘዘው መሠረት አገለገሉ። እያንዳንዱ ሰው የየራሱን በሰንበት ለማገልገል የሚገቡትንና በሰንበትም ከአገልግሎት ይወጡ የነበሩትን ሰዎች ወሰደ፤ ምክንያቱም ካህኑ ዮዳሄ የትኞቹንም የሥራ ክፍሎች አላሰናበተም ነበር። 9 ከዚያም ካህኑ ዮዳሄ በእግዚአብሔር ቤት የነበሩትን የንጉሡን የዳዊትን ጦሮች፥ ትንንሽና ትልልቅ ጋሻዎች ለአለቆቹ አመጣላቸው። 10 ዮዳሄ እያንዳንዱ ሰው የጦር መሣሪያውን እንደያዘ ከቤተ መቅደሱ ቀኝ በኩል እስከ ቤተ መቅደሱ ግራ በኩል በመሠዊያውና በቤተ መቅደሱ አጠገብ ንጉሡን እንዲከቡ ሁሉንም ወታደሮች በቦታቸው አቆማቸው። 11 ከዚያም የንጉሡን ልጅ አውጥተው፥ ዘውዱን በላዩ ላይ ደፍተው የቃል ኪዳኑ ሕግጋት የተጸፈበትን ጥቅልል ሰጡት። ከዚያም አነገሡት፤ ዮዳሄና ልጆቹም ቀቡት። ከዚያም ፦" ንጉሡ ረጅም ዘመን ይኑር!" ብለው ጮኹ። 12 ጎቶልያ የህዝቡን መሯሯጥና ንጉሡን ማወደስ ጫጫታ ስትሰማ ወደ እግዚአብሔር ቤት ወደ ሕዝቡ መጣች። 13 እነሆም ንጉሡ መግቢያው ላይ በራሱ ምሰሶ አጠገብ ቆሞ እንደነበርና አዛዦቹና መለከት ነፊዎቹ ከንጉሡ አጠገብ ቆመው እንደነበር አየች። የአገሩ ህዝብ ሁሉ ደስ እያላቸውና መለከት እየነፉ ነበር። ዘማሪዎቹም የሙዚቃ መሣሪያዎች እየተጫወቱ የውዳሴ መዝሙሮችን ይዘምሩ ነበር። ጎቶልያ ልብሷን ቀድዳ፦" አገር ከመክዳት የሚቆጠር ዓመፅ ነው! ዓመፅ ነው!" ብላ ጮኸች። 14 ካህኑ ዮዳሄ በሠራዊቱ ውስጥ መሪዎች የነበሩትን የመቶ አለቆች አውጥቶ፦ "ወደ ወታደሮቹ መካከል አውጡአት፤ የሚከተላትም በሰይፍ ይገደል" አላቸው። ካህኑ ፦"በእግዚአብሔር ቤት አትግደሉአት" ብሎ ነበር። 15 በመሆኑም ገለል ብለው ሲያሳልፏት ወደ ንጉሡ ቤት ፈረሱ በር በሚወስደው መንገድ ሄደች፤ እዚያም ገደሏት። 16 ከዚያም ዮዳሄ የእግዚአብሔር ሕዝብ ይሆኑ ዘንድ በእርሱ፥ በሕዝቡና በንጉሡ መካከል ቃል ኪዳን አደረገ። 17 ሕዝቡም ሁሉ ወደ በኣል ቤት ሄደው አፈረሱት። የበኣል መሠዊያዎቹንና ምስሎቹን አደቀቁ፤ የበኣል ካህንን ማታንን በእነዚያ መሠዊያዎች ፊት ገደሉት። 18 ዮዳሄም በሙሴ ሕግ ተጽፎ እንደነበረው በእግዚአብሔር ቤት ከደስታና ከመዝሙር ጋር የሚቃጠለውን መሥዋዕት እንዲያቀርቡ፥ ዳዊት በእግዚአብሔር ቤት ላይ የሾማቸው ሌዋውያን ዳዊት በሰጠው መመሪያ መሠረት ከካህናቱ እጅ በታች እንዲያገለግሉ ለእግዚአብሔር ቤት ኃላፊዎችን ሾመ። 19 ርኩስ የሆነ ማንም በማናቸውም መንገድ ወደ እግዚአብሔር ቤት እንዳይገባ በበሮቹ ላይ ጠባቂዎችን አኖረ። 20 ዮዳሄ ከእርሱ ጋር የመቶ አለቆቹን፥ ባላባቶቹን ፥ የሕዝቡን አስተዳዳሪዎችና የአገሩንም ሕዝብ ሁሉ ወሰደ። ንጉሡንም በኮረብታ ላይ ከነበረው ከእግዚአብሔር ቤት አወረደው። ሕዝቡም በላይኛው በር በኩል ወደ ንጉሡ ቤት መጥተው ንጉሡን በመንግሥቱ ዙፋን ላይ አስቀመጡት። 21 የአገሩም ሕዝብ ሁሉ ደስ አላቸው፤ ከተማይቱም ጸጥ አለች። ጎቶልያንም በሰይፍ ገድለዋት ነበር።

---

2 Chronicles 23:1

አጠቃላይ መረጃ
በምዕራፍ 23 ውስጥ ሁሉ ፣ ኢዮአስ “ንጉስ” ተብሎ ተጠርቷል ። አልፎ አልፎ ማንነቱን ለአንባቢዎች በትክክል ለማሳየት “ንጉሥ ዮአስ” ወይም “ንጉሱ ኢዮአስ” ተብሎ ቢጻፍ ጥሩ ሊሆን ይችላል ። (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን ፡ይመልከቱ)

ዮዳሄ
በቤተ መቅደስ ውስጥ የሚያገለግልና ለእግዚአብሔር የታመነ ሊቀ ካህን ነው። የኢዮአስ አማካሪ ነበር። (የስሞች አተረጓጎም ፡ይመልከቱ)

ጥንካሬውን አሳይቷል
የጎቶሊያን አገዛዝ ለመቃወም ጊዜው እንደሆነ ወስኖ ኢዮአስ በሕይወት መኖሩን እና ንጉሥ ለመሆን ዝግጁ መሆኑን ገለጸ ። አት: - “እርምጃ ለመውሰድ ወሰነ”

የመቶዎች አዛዦች
“የመቶዎች አዛዦች” የሚለው ሐረግ ምናልባት ወታደራዊ ማዕረግ ሊሆን ይችላል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “መቶዎች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እነዚህ አለቆች የሚመሩትን ወታደሮች ትክክለኛ መጠን ነው። አት: - “የ 100 ወታደሮች አዛዦች” ወይም 2) “መቶዎች” ተብሎ የተተረጎመው ቃል ወታደራዊ ክፍልን እንጂ ትክክለኛውን ቁጥር አይወክልም ።አት: - “የወታደራዊ ክፍል አዛዦች” (ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)

ወደ ቃል ኪዳኑ ገባ
“ስምምነት አደረገ”

አዛርያስ... ይስማኤልን... ዓዛርያስ... መዕሤያ... ኤሊሳፋጥ
እነዚህ ሰዎች በመቶዎች የሚቆጠሩ ወታደሮች አዛዦች ነበሩ። (የስሞችን አተረጓጎም ፡ይመልከቱ)

ይሮሓም... ይሆሓናን... ዖቤድ... ዓዳያ... ዝክሪ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው ። (የስሞችን አተረጓጎም ፡ይመልከቱ)

የእስራኤል አባቶች ቤቶች ራሶች
እዚህ “ራሶች” በጣም አስፈላጊ የሆነ አካል ምሳሌ ነው ። “ቤቶች” ቤተሰቦችን ይወክላሉ ። አት: - “የእስራኤል መሥራች ቤተሰቦች መሪዎች” (ዘይቤያዊን እና የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

የንጉሥ ልጅ
እዚህ “ንጉሥ” የሚለው የኢዮአስ አባትን ያመለክታል ። “የንጉሥ ልጅ ዮአስ”

2 Chronicles 23:4

አንድ ሦስተኛ... ሌላ አንድ ሦስተኛ... ሌላኛው ሦስተኛ
“አንድ ሶስተኛ... ሌላ አንድ ሶስተኛ... ሌላኛው አንድ ሦስተኛው” (ሕገኛ ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)

በበሩ ላይ ጠባቂዎች ይሆናሉ
'በቤተ መቅደስ በሮች ላይ ጠባቂዎች ይሆናሉ'

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መካከለኛው በር
ይህ በር “መካከለኛው በር” ወይም “ሱር በር” ተብሎም ተጠርቶ ሊሆን ይችላል ። እሱ በንጉሥ ቤተ መንግሥት አቅራቢያ የሚገኝ ውስጣዊ በር ነበር ።

ህዝብ ሁሉ
ይህ የተገኙትን ሁሉ የሚያመለክት አጠቃላይ መረጃ ነው ። አት: - “የተገኙት ሌሎች ሰዎች ሁሉ” (ግነትን እና አጠቃላይን ይመልከቱ)

2 Chronicles 23:6

ማንም ወደ እግዚአብሔር ቤት አይግባ
“ማንም ወደ እግዚአብሔር ቤት እንዲገባ አትፍቀድ”

ሌሎቹም ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ማክበር አለባቸው
ያንን ትእዛዝ መግለፅ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል ። ኣት: “ሌሎቹ ሁሉ እግዚአብሄር ያዘዘውን በመታዘዝ በግቢው ውስጥ መቆየት አለባቸው” (የሚጠበቁ እውቀቶችን እና ያልተገለጸ መረጃን ይመልከቱ)

ሌዋውያኑ ንጉሠን በሁሉም ጎኖች ዙሪያውን መክበብ አለባቸው
“ሌዋውያኑ ንጉሠን ለመጠበቅ በእርሱ ዙሪያ በሁሉም አቅጣጫ መክበብ አለባቸው።”

በሁሉም በኩል እያንዳንዱ ሰው የጦር መሣሪያውን በእጁ ይዞ
“ሁሉም ጎኖች ፣ እና እያንዳንዱ የቤተመቅደሱ ጠባቂ መሳሪያዎቹን መያዝ እና ለውጊያ መዘጋጀት አለበት ”

ወደ ቤት የሚገባ ሁሉ ይገደል
ይህ የቤተ መቅደሱን ጠባቂዎች እና ካህናትን አላካተተም ። ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል። አት: - “ከመቅደሱ ጠባቂዎች እና ወደ ቤተመቅደስ ከሚገቡት ካህናቱ በስተቀር ማንንም መግደል አለብህ” (የሚጠበቁ እውቀቶችን እና ያልተገለጸ መረጃን እና ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ይመልከቱ)

ሲገባ እና ሲወጣ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “በማንኛውም ጊዜ” ወይም 2) “በሄደበት ሁሉ” ናቸው ። (ፈሊጥን:ይመልከቱ)

2 Chronicles 23:8

መላው ይሁዳ
በዚያን ቀን በግቢው ውስጥ የነበሩትን የይሁዳን ሕዝብ በሙሉ የሚያመለክት ማጠቃለያ ነው ። (ግነትን እና አጠቃላይን ይመልከቱ)

ካህኑ ዮዳሄ እንዳዘዘው በሁሉም መንገድ አገልግሏል
“ካህኑ ዮዳሄ ያዘዘውን ሁሉ አደረጉ” ወይም “ካህኑ ዮዳሄ ያዘዘውን ሁሉ ታዘዙ”

እያንዳንዳቸውም ሰዎች ወሰዱ ... ማንኛቸውም ክፍሎቻቸውን ወሰዱ
ካህናቱና ዘበኞቹ በየክፍላቸው ያገለግሉ ነበር ፤ እያንዳንዱ ቡድን ለሁለት ሳምንት ይሠራል። ይህ ሁለት ምድቦች የተገኙበትን ጊዜ የሚያመለክት ነው - አገልግሎታቸውን የሚጨርሱ እና አገልግሎታቸውን የሚጀመሩ። ስለዚህ እንደተለመደው ወንዶች ሁለት እጥፍ ነበሩ።

የሰንበት አገልግሎታቸውን እየጨረሱ
በዚያኑ የሰንበት ቀን ሥራቸውን እየጨረሱ ነበር ”

2 Chronicles 23:10

አጠቃላይ መረጃ
በምዕራፍ 23 ውስጥ ሁሉ ፣ ኢዮአስ “ንጉስ” ተብሎ ተጠርቷል ። አልፎ አልፎ ማንነቱን ለአንባቢዎችዎ በትክክል ለማሳየት “ንጉሥ ኢዮአስ” ወይም “ንጉሡ ኢዮአስ” ማለት ጠቃሚ ሊሆን ይችላል ። (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልጸገለጸ መረጃን ይመልከቱ)

መሣሪያውን በእጁ ይዞ
ይህ ማለት ለውጊያ ዝግጁ ነበሩ ማለት ነው። በ 2 ዜና 23 ፡7 ውስጥ ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የንጉሥ ልጅ
እዚህ “ንጉሥ” የሚለው ቃል የኢዮአስን አባት ያመለክታል ። “የንጉሥ ልጅ ኢዮአስ”

ዘውድን በእርሱ ላይ አኖሩ
ይህ እርሱን ንጉሥ እያደረጉት እንዳለ የሚያመለክት ተግባር ነው ። (ምሳሌያዊ ድርጊትን ይመልከቱ)

የቃል ኪዳኑን ድንጋጌዎች ሰጡት
ትእዛዞቹን የያዘ ጥቅልል መስጠቱ እነርሱን መታዘዝ እንዳለበት የሚያሳይ ምሳሌያዊ ተግባር ። እነዚህ ድንጋጌዎች የሙሴ ሕግ አንድ አካል ይሁኑ ወይም ነገሥታቶች ሊታዘዙባቸው የሚገቡ የተለዩ ሕጎች ይሁኑ ግልጽ አይደለም ። ኣት: “እንዲታዘዝ የቃል ኪዳኑን ድንጋጌዎች ሰጡት” (ምሳሌያዊ ድርጊትን ፡ ይመልከቱ)

ቀባው
ይህ ንጉሥ እንዲሆን በእግዚአብሔር እንደተመረጠ የሚያመለክት ምሳሌያዊ ድርጊት ነበር ። (ተመልከት/ች: ምሳሌያዊ ድርጊት)

ንጉ **the** ለዘላለም ይኑር
“ንጉሥ ረጅም ዕድሜ ይኑር”

2 Chronicles 23:12

እነሆ
የሚከተለው መረጃ በጣም አስፈላጊ መሆኑን አንባቢውን ያነቃል ።

በመግቢያው ላይ ባለው ዓምድ ቆሞ ነበር
በንጉሡ እና በቤተመቅደሱ መግቢያ በለው ልዩ ዓምድ መካከል ያለው ግንኙነት ግልፅ አይደለም ።

የአገሬው ሕዝብ ሁሉ
ይህ በዝግጅቱ ውስጥ ብዙ ሰዎች እንደተሳተፉ ለማሳየት የቀረበ አጠቃላይ መረጃ ነው ። ኣት: - “እጅግ ብዙ የአገሩ ሕዝብ” (ግነትን እና አጠቃላይን ፡ ይመልከቱ)

ጎቶሊያ ልብሷን ቀደደች
ይህ ትልቅ ጭንቀትዋን የሚያመለክት ምሳሌያዊ ድርጊት ነበር ። (ምሳሌያዊ ድርጊትን:ይመልከቱ)

ክህደት! ክህደት!
ክህደት ማለት መንግሥት ለመገልበጥ እርምጃ መውሰድ ነው ። ጎቶሊያ በ 2 ኛ ዜና 22 ፡10-11 ውስጥ የንጉሱን ህጋዊ ወራሾች ገድላ ራስዋን ገዢ አደረገች ። ዮአስ በእሷ ፋንታ ንጉሥ በመሆኗ ተናደደች ። ግነቱ የተደጋገመው ለማጉላት ነው ። አት: - “ክህደት እየፈጸመክ ነው!”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Chronicles 23:14

ዮዳሄ
በ 2 ኛ ዜና 22 ፡11 እንዳለው የዚህን ሰው ስም ተርጉም ። (የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)

የመቶዎች አዛዦች
“የመቶዎች አዛዥ” የሚለው ሐረግ ምናልባት ወታደራዊ ማዕረግ ሊሆን ይችላል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “መቶዎች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እነዚህ አዛዦች የሚመሩትን ወታደሮች ትክክለኛ ብዛት ነው። ኣት: - “የ 100 ወታደሮች አዛዦች ” ወይም 2) “መቶዎች” ተብሎ የተተረጎመው ቃል የሚያመለክተው ትክክለኛውን ቁጥር ሳይሆን ወታደራዊ ክፍልን ነው። በ 2 ኛ ዜና 23 ፡1 ውስጥ እንዴት እንደተረጉምከው ተመልከት ። ኣት: - “የወታደር አዛዦች” (ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)

እነርሱ በሠራዊቱ ላይ ነበሩ
“በሠራዊቱ ውስጥ መሪ የነበሩት”

በደሰልፉ መካከል አውጧት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ከባችሁ ከቤተ መቅደሱ አደባባይ አውጧት” ወይም 2) “በቤተመቅደሱ ግቢ ውስጥ ካሉት ሰዎች መካከል አስወግዷት”

እርሷን የሚከተል ሁሉ በሰይፍ ይገደል
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። እርሷን የሚከተሉ ሰዎች ሊረዷት እየሞከሩ ነው ማለት ነው ። ኣት: - “እርሷን ለመርዳት የሚመጣውን ማንኛውንም ሰው ለመግደል ሰይፍህን ተጠቀም” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን እና የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን ፡ይመልከቱ)

ካህኑ እንዲህ ብሏል
“ካህኑ ዮዳሄ እንዲህ ብሏል”

ወደ ንጉሥ ቤት ወደ ፈረስ በር ገባች
አንዳንድ ትርጉሞች “ በነገሥታት ቤት መግቢያ አጠገብ ወዳለው የፈረስ በር ወሰዷት” የሚል አላቸው ።

የንጉሥ ቤት
“ንጉሣዊው ቤተ መንግሥት”

2 Chronicles 23:16

አጠቃላይ መረጃ
በምዕራፍ 23 ውስጥ ሁሉ ፣ ኢዮአስ “ንጉስ” ተብሎ ተጠርቷል ። አልፎ አልፎ ማንነቱን በትክክል ለማሳየት “ንጉሥ ዮአስ” ወይም “ንጉሡ ዮአስ” የሚለውን ብትጨምር ለአንባቢዎችህ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል ። (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን ፡ይመልከቱ)

ሕዝቡ ሁሉ ወደ በኣል ቤት ሄደ
ይህ አጠቃላይ ገለጻ ሲሆን ብዙ ሰዎች ይህንን አደረጉ ማለት ነው ። ኣት: - “እጅግ ብዙ ሰዎች ወደ በኣል ቤተ መቅደስ ሄዱ” (ግነትን እና አጠቃላይን ፡ይመልከቱ)

ማታን
ይህ የሰው ስም ነው ። (የስሞችን አተረጓጎም ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 23:18

ከካህናቱ እጅ
እዚህ “እጅ” መቆጣጠርን ይወክላል ። ኣት: - “በካህናቱ አመራር” (ተመልከት/ች: የባህሪ ስም)

ስለዚህ በማንኛውም መንገድ ርኩስ የሆነ ማንም እንዳይገባ
ለእግዚአብሔር ዓላማ ተቀባይነት የሌለው ሰው በአካል ርኩስ ተደርጎ ይገለጻል ። ኣት: - “ስለሆነም በማንኛውም መልኩ በአምላክ ዘንድ ተቀባይነት ያሌለው ማንም እንዳይገባ” (ዘይቤያዊን ፡ይመልከቱ)

ስለዚህ በየትኛውም መንገድ ርኩስ የሆነ ማንም እንዳይገባ
ይህ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: “ንፁህ ሰዎች ብቻ እንዲገቡ ማድረግ” ወይም “በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ብቻ መግባታቸውን ማረጋገጥ” (እጥፍ አሉታዊን ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 23:20

የመቶ አለቆቹ አዛዦች
“የመቶዎች አዛዦች” የሚለው ሐረግ ምናልባት ለወታደራዊ ማዕረግ ሊሆን ይችላል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “መቶዎች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እነዚህ አዛዦች የሚመሩትን ወታደሮች ትክክለኛ ቁጥር ነው። ኣት: - “የ 100 ወታደሮች አዛዦች” ወይም 2) “መቶዎች” ተብሎ የተተረጎመው ቃል ትክክለኛውን ቁጥር የሚወክል ሳይሆን ወታደራዊ ክፍልን የሚወክል ነው። AT: “የወታደራዊ ክፍል አዛዦች” በ 2 ኛ ዜና 23፡ 1 ውስጥ ይህንን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። (ቁጥሮችን ፡ ይመልከቱ)

የአገሬው ሕዝብ ሁሉ
ይህ ጠቅለል ያለ ገለጻ ነው ማለትም እርሱ ብዙ ሰዎችን ከእርሱ ጋር ወስዶ ነበር ። ኣት: - “እጅግ ብዙ የእስራኤል ሕዝብ” (ግነትን እና አጠቃላይን ፡ ይመልከቱ)

ንጉሡን ከእግዚአብሔር ቤት አመጣለት
ቤተ መቅደሱ የተገነባው በኢያሩሳሌም ከፍ ባለው ኮረብታ ላይ ነበር። አት. “ንጉ ሡን ከቤተ መቅደሱ ወደ ቤተ መንግሥቱ አወረደው”

የመንግሥት ዙፋን
“ንጉሣዊው ዙፋን”

ስለዚህ የምድሪቱ ሰዎች ሁሉ
ይህ ጠቅለል ያለ ገለጻ ነው። አብዛኛው ህዝብ ተደስቷል ለማለት ነው ። (ግነት እና አጠቃላይን:ይመልከቱ)

ከተማይቱ ፀጥ አለች
“ከተማይቱ” የከተማዋን ህዝብ ይወክላል ፣ “ዝምታ” ደግሞ ሰላምን ይወክላል። ኣት: - “ጎቶልያ ከሞተች በኋላ ኢዮአስን የሚቃወም ስላልነበረ የከተማይቱ ሕዝብ በሰላም ነበር” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 24

1 ኢዮስያስ መንገሥ በጀመረ ጊዜ ሰባት ዓመቱ ነበር፤ በኢየሩሳሌምም አርባ ዓመት ነገሠ። የቤርሳቤዋ እናቱ ስም ሳብያ ነበር። **2** ኢዮስያስ ካህኑ ዮዳሄ በነበረበት ዘመን ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ትክክል የሆነውን ነገር አደረገ። **3** ዮዳሄ ለኢዮስያስ ሁለት ሚስቶችን አጋባው፤ የወንዶችና የሴቶች ልጆች አባት ሆነ። **4** ከዚህም በኋላ ኢዮስያስ የእግዚአብሔርን ቤት ለመጠገን ወሰነ። **5** ካህናቱንና ሌዋውያኑን በአንድነት ሰብስቦ ፦"በየዓመቱ ወደ ይሁዳ ከተሞች ውጡና የአምላካችሁን ለማደስ ከእስራኤል ሁሉ ገንዘብን ሰብስቡ። በፍጥነት መጀመራችሁን እርግጠኛ ሁኑ" አላቸው። ሌዋውያኑ በመጀመሪያ ምንም አላደረጉም። **6** በመሆኑም ንጉሡ ሊቀ ካህናቱን ጠርቶ፦"ሌዋውያኑ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴ ለቃል ኪዳኑ ድንኳን ድንጋጌ የእስራኤል ጉባኤ የተጣለባቸውን ግብር ከይሁዳና ከኢየሩሳሌም እንዲያስመጡ ለምን አላደረግሃቸውም?" አለው። **7** የዚያች ክፉ ሴት የጎቶልያ ልጆች የእግዚአብሔርን ቤት አፍርሰው እና የእግዚአብሔርንም ቤት የተቀደሱ ነገሮች ሁሉ ለበኣል ሰጥተው ነበር። **8** በመሆኑም ንጉሡ ስለአዘዘ የገንዘብ ሳጥን ሰርተው በእግዚአብሔር ቤት መግቢያ በስተውጪ አስቀመጡት። **9** የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴ በምድረ በዳ በእስራኤል ላይ የጣለባቸውን ግብር ለእግዚአብሔር እንዲያመጡ በይሁዳና በኢየሩሳሌም ሁሉ አዋጅ ነገሩ። **10** መሪዎቹ ሁሉና ሕዝቡ ሁሉ ደስ ብሎአቸው ገንዘብ አመጡ፤ እስኪሞሉትም ድረስ በገንዘብ ሳጥኑ ውስጥ አስቀመጡት። **11** የገንዘብ ሳጥኑ በሌዋውያኑ እጅ ወደ ንጉሡ ሹማምንት በሚመጣበት ጊዜ ሁሉና ብዙ ገንዘብ እንዳለበት ባዩ ጊዜ ሁሉ የንጉሡ ጸሐፊና የሊቀ ካህናቱ ሹም መጥተው ከገንዘብ ሳጥኑ ገንዘቡን አውጥተው በመውሰድ ሳጥኑን ወደ ሥፍራው ይመልሱት ነበር። ከፍ ያለ መጠን ያለው ገንዘብ በመሰብሰብ ይህንንም ዕለት ዕለት ያደርጉት ነበር። **12** ንጉሡና ዮዳሄ በእግዚአብሔር ቤት የማገልገል ሥራ ለሚሠሩት ሰዎች ገንዘቡን ይሰጡ ነበር። እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቤት ለሚያድሱት ድንጋይ ጠራቢዎችና አናጢዎች እንዲሁም የብረትና የነሃስ ሥራ የሚሠሩትን ቀጥረው ያሠሩበት ነበር። **13** በመሆኑም ሠራተኞቹ አብዝተው ሠሩ፤ የጥገናውም ሥራ በእጃቸው ተከናወነ፤ የእግዚአብሔርንም ቤት በመጀመሪያ ንድፉ አቁመው አጠናከሩት። **14** በጨረሱም ጊዜ የተረፈውን ገንዘብ ወደ ንጉሡና ዮዳሄ አመጡት። ይህ ገንዘብ የእግዚአብሔርን ቤት ዕቃ ፥ ለአገልግሎትና መሥዋዕት ለማቅረብ የሚሆኑ ማንኪያዎችንና የወርቅና የብር ዕቃዎች ለማሟላት ጥቅም ላይ ዋለ። በዮዳሄ ዘመን ሁሉ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የሚቃጠል መሥዋዕት ባለማቋረጥ ያቀርቡ ነበር። **15** ዮዳሄም ሸመገለ፤ ዕድሜም ጠግቦ ሞተ። በሚሞትበት ጊዜ ዕድሜው መቶ ሠላሳ ዓመት ነበር። **16** በእስራኤልም ለእግዚአብሔርና ለእግዚአብሔር ቤት መልካም ስላደረገ በነገሥታቱ መካከል በዳዊት ከተማ ቀበሩት። **17** ዮዳሄ ከሞተ በኋላ የይሁዳ መሪዎች መጥተው ለንጉሡ ክብርን ሰጡት። ንጉሡም አዳመጣቸው። **18** የአባቶቻቸውን አምላክ የእግዚአብሔርን ቤት ትተው የማምለኪያ ዐፀዶችንና ጣዖታቱን አመለኩ።በዚህም ኃጢአታቸው ምክንያት የእግዚአብሔር ቁጣ በይሁዳና በኢየሩሳሌም ላይ መጣ። **19** ሆኖም ግን ወደ እግዚአብሔር ወደ ራሱ እንደገና እንዲያመጧቸው ነቢያትን ይልክላቸው ነበር፤ ነቢያቱም በሕዝቡ ላይ ይመሰክሩባቸው ነበር፤ እነርሱ ግን ለመስማት እምቢ አሉ። **20** የእግዚአብሔር መንፈስ በካህኑ በዮዳሄ ልጅ በዘካርያስ ላይ መጣ፤ እርሱም ከሕዝቡ በላይ ቆሞ፦"እግዚአብሔር ይህንን ይላል፤ 'የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ለምን ትተላለፋላችሁ? መልካም ነገር ሊሆንላችሁ አይችልም። እግዚአብሔርን ስለተዋችሁ እርሱም ትቶአችኋል'" አላቸው። **21** እነርሱ ግን አሴሩበት፤ በንጉሡ ትዕዛዝም በእግዚአብሔር ቤት አደባባይ ውስጥ በድንጋይ ወገሩት። **22** በዚህ ሁኔታ ንጉሡ ኢዮአስ የዘካርያስ አባት ዮዳሄ ያደረገለትን ቸርነት ችላ አለ። ይልቁንም የዮዳሄን ልጅ ገደለ። ዘካርያስም በሚሞትበት ጊዜ፦" እግዚአብሔር ይህንን ይየው፤ ይጠይቃችሁም" አለ። **23** በዓመቱ መጨረሻም የአራም ሠራዊት ሊያጠቁት በኢዮአስ ላይ መጡበት። ወደ ይሁዳና ወደ ኢየሩሳሌም መጡ፤ የሕዝቡን መሪዎች ሁሉ ገደሉ፤ ከእነርሱ የወሰዱትንም ምርኮ ሁሉ ወደ ደማስቆ ንጉሥ ላኩ። **24** የሶርያውያንም ሠራዊት የመጡት ከትንሽ ሠራዊት ጋር ነበር፤ ነገር ግን ይሁዳ የአባቶቻቸውን አምላክ ከመተዋቸው የተነሳ እግዚአብሔር እጅግ ታላቅ በነበረው ሠራዊት ላይ ድልን ሰጣቸው። በዚህ መንገድ የሶርያውያን ሠራዊት በኢዮአስ ላይ ፍርድን አመጡበት። **25** ሶርያውያን ከሄዱ በኋላ ኢዮአስ ክፉኛ ቆስሎ ነበር። ከካህኑ ከዮዳሄ ልጆች ግድያ የተነሳ የገዛ አገልጋዮቹ አሲረውበት ነበር። በአልጋው ላይ ገደሉት፤ እርሱም ሞተ፤ በነገሥታቱ መቃብር ሳይሆን በዳዊት ከተማ ቀበሩት። **26** ያሴሩበትም ሰዎች የአሞናዊቷ የሰምዓት ልጅ ዛባድ፥ የሞዓባዊቷ የሰማሪት ልጅ ዮዛባት ነበሩ። **27** የልጆቹ ነገርና ስለ እርሱ የተነገሩት ዋና ዋና ትንቢቶች እንዲሁም የእግዚአብሔርን ቤት እንደገና መገንባቱ እነሆ በነገሥታቱ መጽሐፍ ማብራሪያ ተጽፈዋል። ልጁም አሜስያስ በእርሱ ቦታ ነገሠ።

---

2 Chronicles 24:1

መግዛት ጀመረ
“የይሁዳ ንጉሥ ሆነ”

አርባ ዓመት
“40 ዓመት” (ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

ሳብያ
ይህ የሴት ስም ነው። (የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ፊት ትክክል የሆነውን ነገር
እዚህ “ዐይኖች” የሚለው ቃል ማየትን ይወክላል፣ ማየት ደግሞ ፍርድን ይወክላል ። እግዚአብሔር የኢዮአስን ተግባር አየ እና አጸናው። በ 2 ኛ ዜና 14 :1 ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት ። ኣት: - “እግዚአብሔር ትክክል እንደ ሆነ የወሰነው” ወይም “እግዚአብሔር ትክክል አድርጎ የወሰደው” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

በካህኑ በዮዳሄ ዘመን ሁሉ
ይህ አገላለጽ “ካህኑ ዮዳሄ በሕይወት እስካለ ድረስ” ማለት ነው። (ፈሊጥን፡ ይመልከቱ)

ዮዳሄ ሁለት ሚስቶችን አገባለት
“ዮዳሄ ለኢዮአስ ሁለት ሚስቶችን መረጠ”

2 Chronicles 24:4

ከዚህ በኋላ እንዲህ ሆነ
ይህ ሐረግ የታሪኩን አዲስ ክፍል መጀመሪያ ለመጠቆም እዚህ ያሚያገለግል ነው ። ቋንቋህ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ መጠቀም ትችላለህ ።

ወዲያውኑ
"ወድያው"

በመጀመሪያዎቹ ሌዋውያን ምንም ነገር አላደረጉም
ሌዋውያኑ እንዳልታዘዙ ለማሳየት “ግን” የሚለውን ማከል ጠቃሚ ሊሆን ይችላል ። ኣት: - “ሌዋውያኑ ግን ወዲያውኑ አላደረጉቱም”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Chronicles 24:6

ሌዋውያንን ለምን የቃል ኪዳኑን ሕግ አልጠየቅኸም?
ንጉሥ ዮአስ ዮዳሄ ኃላፊነቱን አልተወጣም ብሎ ለመክሰስ ይህን አወያይ መጠይቅ ጠየቀ ። እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: - “ግዴታህን ችላ ብለሃል። ሌዋውያንን የቃል ኪዳኑን ድንጋጌዎች እንድትጠይቅ ነግሬህ ነበር ... ፣ ግን አላፈፀምከውም ። ” (አወያይ መጠይቅን :ይመልከቱ)

ስለቃል ኪዳኑ ድንኳን
ምንም እንኳን ሰሎሞን የገነባው መቅደስ ቢሆንም ፣ ይህ ግብር በሙሴ ጊዜ እና ‹የመገናኛ ድንኳን› ጊዜ ጀምሮ ሲሰበሰብ የነበረ መሆኑ የሚያሳስብ ነው ።

የተቀደሱ ነገሮች
ይህ በቤተመቅደሱ ውስጥ ለአምልኮ የሚውሉትን ዕቃዎች ያመለክታል ።

ለባኣሊም
“ሰዎች ለበኣሊም ጣዖታት አምልኮ እንዲገለገሉበት”

2 Chronicles 24:8

ሳጥን
አንድ ትልቅ የእንጨት ሳጥን

አወጁ
“እነርሱ አወጁ” ወይም “እነርሱ አስታወቁ”

ሁሉም መሪዎች እና ህዝብ ሁሉ
ይህ ጠቅለል ያለ ገለጻ ነው ። ምናልባት አንዳንድ ሰዎች በዚህ መንገድ ምላሽ አልሰጡ ይሆናል ። (ግነትን እና አጠቃላይን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 24:11

እንዲሁም በየቀኑ ያደርጉ ነበር
ይህ ሐረግ አዲስ ፣ ተደጋጋሚ ድርጊትን ያስተዋውቃል ። ቋንቋህ ይህንን የሚያመለክትበት መንገድ ካለው ፣ እዚህ ልትጠቀምበት ትችላለህ ።

ውሰደው እና ወደ ስፍራው መልሰው
“ሳጥኑን ወስደህ ወደ ቦታው መልሰው”

ጠራቢዎች እና አናጢዎች
“የድንጋይ ሠራተኞች እና የእንጨት ሠራተኞች”

የብረት እና የናስ ሠራተኞች
“ከብረት እና ከናስ እቃዎችን የሚሠሩ ሰዎች”

2 Chronicles 24:13

በእጃቸው ወደፊት እየተጠገነ ሄደ
እዚህ ላይ “ወደፊት” የሚለው ቃል መሻሻልን ይወክላል ፣ “እጆች” የሚለው ቃል የእነርሱን ቁጥጥር ይወክላል ። ኣት: - “በእነሱ ቁጥጥር ስር ተሻሻለ” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

የተቀረው ገንዘብ
ይህ ሳጥኑ ውስጥ የተሰበሰበ ገንዘብ ነው ግን ለጥገናው የማይፈለግ ነው።

የቤት ዕቃዎች
ይህ ቀጥሎ ባሉት ቁጥሮች ውስጥ የተዘረዘሩትን “መገልገያዎች” እና “ማንኪያዎችን” ያመለክታል ።

በዮዳሄም ዘመን ሁሉ
ይህ ፈሊጥ የዮዳሄን ዕድሜ ያመለክታል ። ኣት: - “ዮዳሄ በሕይወት እስካለ ድረስ” ወይም “በዮዳሄ ዕድሜ ዘመን ሁሉ” (ፈሊጥን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 24:15

አርጅቶ ዕድሜም ጠግቦ ነበር
እነዚህ ሁለት ሐረጎች አንድ ዓይነት ትርጉም ያላቸው ሲሆን ለምን ያህል ጊዜ እንደኖረ አፅንዖት ይሰጣል ። ኣት: “በጣም አረጀ” (ድግግሞሽን : ይመልከቱ)

ዕድሜ ጠገበ
ይህ ፈሊጥ ረጅም ዕድሜ እንደኖረ ያሚያመለክት ነው ። (ፈሊጥን : ይመልከቱ)

ዕድሜው **130** ዓመት
“ዕድሜው አንድ መቶ ሠላሳ ዓመት” (ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

በነገሥታቱ መካከል
“በነገሥታቱ መቃብር” ወይም “በነገሥታቱ መቃብር መካከል”

ከእስራኤልም ጋር ፣ ከእግዚአብሔርና ከቤቱም ጋር ቸርነትን ሠርቶአልና
“ጥሩ” የሚለው ስያሜያዊ መግለጫ እንደ ቅፅል ሊተረጎም ይችላል። ኣት: - “ለእግዚአብሔር እና ለእግዚአብሔር ቤተ-መቅደስ በይሁዳ መልካም ነገሮችን ስላደረገ” (ስማዊ ቅጽልን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 24:17

ለንጉሡ እጅ ነሱ
“ለንጉሥ ኢዮአስ አከበሩ” ወይም “ንጉሠን አከበሩ”

የዚያን ጊዜም ንጉሡ ሰማቸው
የሚቀጥለው ጥቅስ ንጉሡ ከእግዚአብሔር ይልቅ ጣዖታትን እንዲያገለግል እንደሚፈልጉ ያሳያል ፣ እርሱም ተስማማ ። አት: - “ንጉሡም የፈለጉትን እንዲያደርግ አግባቡት” (የሚጠበቅ እውትን እና ያልተገለጸ መረጃን : ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ቁጣ በይሁዳና በኢየሩሳሌም ላይ ሆነ
የእግዚአብሔር ቁጣ በይሁዳና በኢየሩሳሌም ላይ እንደሸፈነ ነገር ተደርጎ ተገልጻል ። እዚህ ላይ “ይሁዳ” እና “ኢየሩሳሌም” የሚሉት ቃላት በዚያ ለሚኖሩት ሰዎች ተኪ መግለጫዎች ናቸው ። ኣት: - “እግዚአብሔር በይሁዳና በኢየሩሳሌም ሰዎች ላይ እጅግ ተቆጥቶ ነበር” (ዘይቤያዊን እና የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

ይህ የእነሱ ኃጢአት
“ኃጢአታቸው”

አሁንም እርሱ ሰደደ
እዚህ ላይ “አሁንም” የሚለው ቃል በእግዚአብሔር ቁጣ እና ንስሐ እንዲገቡ እድል ለመስጠት እና ፍርድን ለማስቀረት ነቢያትን መላኩ መካከል ያለውን ልዩነት ያሳያል።

ወደ ራሱ፣ እግዚአብሔር
የአፀፋው ተውላጠ ስም መመለስ ያለባቸው ወደ እግዚአብሔር እንደሆነ አጽንዖት ይሰጣል ። (የአፀፋ ተውላጠ ስም :ይመልከቱ)

እነርሱ መስማት እምቢ አሉ
“ሕዝቡ ለመታዘዝ እምቢተኛ ሆኑ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Chronicles 24:20

የእግዚአብሔር መንፈስ በዘካርያስ ላይ ወረደ
ይህ ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን የእግዚአብሔር መንፈስ በዘካርያስ ውስጥ ተገልጦ ትንቢት እንዲናገር አስችሎታል ማለት ነው ። በ 2 ኛ ዜና 15 ፡1 ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት ። (ፈሊጥን ፡ይመልከቱ)

የዮዳሄ ልጅ ዘካርያስ
ይህ የዘካርያስን መጽሐፍ የጻፈው የበራክዩ ልጅ ዘካርያስ አይደለም ።

እንዳትበለጽጉ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስለምን ትተላለፋላችሁ?
ዘካርያስ ይህንን አወያይ መጠይቅ ህዝቡን ለመገሠጽ ጠይቋል ። እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: - “ልትበለጽጉ ያልቻላችሁት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እየተላለፋች ፣ ስለሆነ ነው።” (አወያይ መጠይቅን ፡ ይመልከቱ)

የዘካርያስ አባት ዮዳሄ ያደረገለትን ደግነት ቸል አለ
የዘካርያስ አባት ዮዳሄ ለኢዮአስ ያደረገውን ቸርነት አላስተዋለም።

ከአንተ ይፈልገው
ለሠራኸው ጥፋት ይቀጣሃል ”

2 Chronicles 24:23

ይህ ሆነ
ይህ ሐረግ የታሪኩን አዲስ ክፍል መጀመሪያ ለመጠቆም እዚህ ያገለግላል ። ቋንቋህ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ መጠቀም ይችላሉ ።

ምርኮውን ሁሉ ከእነርሱ ላከ
“ምርኮውን ሁሉ ከይሁዳና ከኢየሩሳሌም ላከ”

እጅግ ታላቅ በሆነ ሰራዊት ላይ ድል ተቀዳጅቷል
'እጅግ ብዙ በሆነው በይሁዳ ሠራዊት ላይ ድል ተቀዳጅቷል'

በዚህ መንገድ ሶርያውያን በዮአስ ላይ ፍርድን አመጡበት
ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ፍርድ ነው ። ይህ እንደ ድርጊት ሊገለፅ ይችላል ። ኣት. “በዚህ መንገድ እግዚአብሔር በኢዮአስ ላይ ለመፍረድ ሶሪያዊያንን ተጠቀመባቸው” (የረቂቅ ስሞችን እና የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 24:25

ዮአስ እጅግ ቆስሎ ነበር
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ኢዮአስን እጅግ አቁስለውት ነበር” (ገቢራዊን እና ተብሮአዊን ፡ይመልከቱ)

በዮዳሄ ልጆች ሞት ምክንያት
“የዮዳሄን ልጆች ስለ ገደለ”

አልጋው ላይ ገደሉት
“አገልጋዮቹ ኢዮአስ በአልጋው ላይ ገደሉት”

ዛባድ... ዮዛባት
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው ። (የስሞችን አተረጓጎም ፡ይመልከቱ)

የአሞናዊቱ ሴት ሰምአት ... ሰማሪት ሞዓባዊት ሴት
“ሳሚት ፣ ከአሞን አገር... ሺምሪ ፣ ከሞዐብ ምድር።” የሁለት ሴቶች ስሞች ነቸው። (የስሞችን አተረጓጎም ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 24:27

ስለ ወንዶች ልጆች የሚናገረው ዘገባ
“ወንዶች ልጆቹ ስላደረጉት ነገር ተጽፎአል”

ስለ እርሱ የተነገሩ አስፈላጊ ትንቢቶች
“ነቢያት ስለ እርሱ የተናገሩት አስፈላጊ ነገር”

እነሆ እነርሱ ተጽፈዋል
እዚህ “እነሆ” ቀጥሎ ላለው መረጃ ልዩ ትኩረት እንዲሰጥ አንባቢውን ያነቃል ።

የነገሥታቱ መጽሐፍ ማብራሪያ
ይህ የማይገኝ መጽሐፍ ነው ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 25

1 አሜስያስ መንገሥ በጀመረ ጊዜ ሃያ አምስት ዓመቱ ነበር፤ በኢየሩሳሌም ሃያ ዘጠኝ ዓመት ነገሠ። የኢየሩሳሌሟ እናቱ ስም ዮዓዳን ነበር። 2 በእግዚአብሔር
ፊት ትክክለኛውን ነገር አደረገ፤ ነገር ግን በፍጹምና በተሰጠ ልብ አይደለም። 3 መንግሥቱ በሚገባ በጸናለት ጊዜ አባቱን ንጉሡን የገደሉትን አገልጋዮቹን
ገደላቸው። 4 በሙሴ ሕግ መጽሐፍ በተጻፈው መሠረት፦"አባቶች ስለ ልጆች መሞት አይገባቸውም፤ ልጆችም ስለ አባቶች መሞት አይገባቸውም። ይልቁንም
ማንኛውን ሰው ለራሱ ኃጢአት መሞት ይገባዋል" በማለት እግዚአብሔር እንዳዘዘው በማድረግ የገዳዮቹን ልጆች አልገደለም። 5 በተጨማሪም አሜስያስ
ይሁዳን በአንድነት ሰበሰበ፤ ይሁዳንና ቢንያምን ሁሉ በየአባቶቻቸው ቤቶች ከሺህ አለቆችና ከመቶ አለቆች በታች መዘገባቸው። ከሃያ ዓመትና ከዚያ በላይ
ያሉትን ቆጠረ፤ ወደ ጦርነት ሊሄዱ የሚችሉ፥ ጋሻና ጦርም ሊይዙ የሚችሉ ሦስት መቶ ሺህ የተመረጡ ሰዎች አገኘ። 6 ከእስራኤልም መቶ ሺህ ጦረኛ ሰዎች
በመቶ መክሊት ብር ቀጠረ። 7 ነገር ግን አንድ የእግዚአብሔር ሰው ወደ እርሱ መጥቶ፦"ንጉሥ ሆይ እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር፥ ከኤፍሬምም ሰዎች
ከአንዳቸውም ጋር አይደለምና የእስራኤል ሠራዊት ከአንተ ጋር አይሂዱ። 8 ነገር ግን ብትሄድ በጦርነትም ደፋርና ብርቱ ብትሆን እግዚአብሔር በጠላት ፊት
ይጥልሃል፤ ምክንያቱም የመርዳት ኃይል እና የመጣል ኃይል ያለው እግዚአብሔር ነው" አለው። 9 አሜስያስም ለእግዚአብሔር ሰው፦" ለእስራኤል ሠራዊት
ስለሰጠሁት መቶ መክሊትስ ምን እናደርጋለን?" አለው። የእግዚአብሔር ሰውም፦ "እግዚአብሔር ከዚያ እጅግ የበለጠ ሊሰጥህ ይችላል" ብሎ መለሰለት። 10
በመሆኑም አሜስያስ ከኤፍሬም ወደርሱ የመጡትን ሠራዊት ለይቶአቸው እንደገና ወደ ቤት ላካቸው። ስለዚህም በይሁዳ ላይ ቁጣቸው እጅግ ነደደ፤ ወደ
ቤትም በጋለ ቁጣ ተመለሱ። 11 አሜስያስም በርትቶ ሕዝቡን አውጥቶ ወደ ጨው ሸለቆ መራቸው፤ በዚያም አሥር ሺህ የሴይርን ሰዎች ድል ነሳቸው። 12
የይሁዳም ሠራዊት አሥር ሺህ ሰዎች ከነሕይወታቸው ማርከው ወሰዱ። ወደ ኮረብታው ጫፍ ላይ ወሰዱአቸውና ሁሉም እስኪንኮታኮቱ ድረስ ከዚያ ወደ ታች
ወረወሩአቸው። 13 ነገር ግን አሜስያስ ከእርሱ ጋር ወደ ጦርነት እንዳይሄዱ ያስመለሳቸው የሠራዊት ሰዎች ከሰማርያ እስከ ቤትሖሮን በይሁዳ ከተሞች ላይ
ጥቃት አደረሱ፤ ከሕዝቡም ሦስት ሺህ ሰዎች መትተው እጅግ ብዙ ምርኮ ወሰዱ። 14 አሜስያስ የኤዶምያስን ሰዎች ገድሎ ከተመለሰ በኋላ የሴይርን ሰዎች
ጣኦታት አምጥቶ የገዛ ራሱ አማልክት እንዲሆኑ አቆማቸው። በፊታቸውም ሰገደ፤ እጣንም አጠነላቸው። 15 ስለዚህም የእግዚአብሔር ቁጣ በአሜስያስ ላይ
ነደደ። አንድ ነቢይ ልኮ፦"የገዛ ሕዝባቸውን እንኳን ከአንተ እጅ ያላዳኑትን የአሕዛብን አማልክት ለምን ፈለግሃቸው?" አለው። 16 ነቢዩም ከእርሱ ጋር እየተነጋገረ
እያለ ንጉሡ፦"የንጉሡ አማካሪ እንድትሆን አድርገንሃል? አቁም! ለምን መገደል ይገባሃል?" አለው። ነቢዩም ንግግሩን አቁሞ፦"ይህንን ድርጊት በመፈጸምህና
ምክሬን ባለመስማትህ እግዚአብሔር ሊያጠፋህ እንደወሰነ አውቃለሁ" አለ። 17 ከዚያም የይሁዳ ንጉሥ አሜስያስ ከአማካሪዎቹ ጋር ተማክሮ፦" ና በጦርነት
ፊት ለፊት እንጋጠም" ብሎ ወደ እስራኤል ንጉሥ ወደ ኢዩ ልጅ ወደ ኢዮአካዝ ልጅ ወደ ኢዮአስ ላከ። 18 የእስራኤልም ንጉሥ ኢዮአስ መልዕክተኞችን ወደ
ይሁዳ ንጉሥ ወደ አሜስያስ መልሶ ላከና፦"በሊባኖስ የነበረ አንድ ኩርንችት፦ 'ልጅህን ለልጄ ሚስት አድርገህ ስጠው' ብሎ ወደ ሊባኖስ ዝግባ መልዕክት
ላከ፤ ነገር ግን አንድ የሊባኖስ አውሬ መንገድ ሲያልፍ ኩርንችቱን ረገጠው። 19 አንተም ፦'እነሆ ኤዶምያስን መትቻለሁ' ብለህ ልብህ ከፍ ከፍ ብሏል። በድልህ
ኩራ፤ ነገር ግን በቤትህ ተቀመጥ፤ አንተና ካንተ ጋር ይሁዳ ሁሉ ለምን በራስህ ላይ ችግር ፈጥረህ ትወድቃለህ?" አለው። 20 የይሁዳ ሰዎች ከኤዶምያስ
አማልክት ምክር ከመፈለጋቸው የተነሳ የይሁዳን ሰዎች ለጠላቶቻቸው አሳልፎ ይሰጣቸው ዘንድ ይህ ከእግዚአብሔር ታስቦ ነበርና አሜስያስ ሊሰማ
አልፈለገም። 21 ስለዚህ የእስራኤል ንጉሥ ኢዮአስ ጥቃት አደረሰ፤ እርሱና የይሁዳ ንጉሥ አሜስያስ የይሁዳ በነበረችው በቤትሳሚስ ፊት ለፊት ተጋጠሙ።
22 ይሁዳም በእስራኤል ፊት ተመታ፤ እያንዳንዱም ሰው ወደ ቤቱ ሸሸ። 23 የእስራኤል ንጉሥ ኢዮአስ የይሁዳን ንጉሥ የአካዝያስን ልጅ አሜስያስን
በቤትሳሚስ ማረከው። ወደ ኢየሩሳሌምም ይዞት መጣና ከኤፍሬም በር እስከ ማዕዘኑ በር ድረስ የኢየሩሳሌምን ቅጥር አራት መቶ ክንድ ርቀት ያህል አፈረሰው።
24 ወርቁንና ብሩን ሁሉ፥ በእግዚአብሔርም ቤት ከዖቤድኤዶም ጋር የነበሩትን ዕቃዎች በሙሉ እንዲሁም በንጉሡ ቤት የነበሩትን ዋጋ ያላቸውን ነገሮች ከታገቱት
ጋር ወስዶ ወደ ሰማርያ ተመለሰ። 25 የይሁዳ ንጉሥ የኢዮአስ ልጅ አሜስያስ፥ ከእስራኤል ንጉሥ ከኢዮአካዝ ልጅ ከኢዮአስ ሞት በኋላ አሥራ አምስት ዓመት
ኖረ። 26 አሜስያስን በተመለከተ ሌሎቹ ነገሮች የመጀመሪያውና የመጨረሻው እነሆ በይሁዳና በእስራኤል ነገሥታት መጽሐፍ የተጻፉ አይደለምን? 27
አሜስያስም እግዚአብሔርን ከመከተል ከራቀበት ጊዜ አንስቶ በኢየሩሳሌም ሴራ ያሴሩበት ጀመር። ወደ ለኪሶም ሸሸ፤ ነገር ግን ከበስተኋላው ሰዎች ላኩበት፤
እነርሱም በዚያ ገደሉት። 28 በፈረስም ጭነው መልሰው አመጡት፤ በይሁዳም ከተማ ከአባቶቹ ጋር ቀበሩት።

---

2 Chronicles 25:1

ሀያ - ዓመታት... ሃያ ዘጠኝ ዓመት
“25 ዓመት... 29 ዓመታት” (ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

ዮዓዳን
ይህ የሴት ስም ነው። (የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ፊት ትክክል የሆነውን ነገር
እዚህ “ዐይን” የሚለው ቃል ዕይታን ይወክላል ፣ እና ዕይታ ደግሞ የእግዚአብሔርን ፍርድ ወይም ግምገማ ያመለክታል ። በ 2ኛ ዜና መዋዕል 14:2 ውስጥ ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። ኣት: - “እግዚአብሔር ትክክል እንዲሆን የወሰነው” (ፈሊጥን :ይመልከቱ)

ነገር ግን በሙሉ ልብ አይደለም
እዚህ ላይ “በሙሉ ልብ” የሚለው ሐረግ “ሙሉ በሙሉ” የሚል ትርጉም አለው ። ኣት: “ነገር ግን ሙሉ በሙሉ አይደለም” (ፈሊጥን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 25:3

እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ የታሪኩ አዲስ ክፍል እንደሚጀምር ለመጠቆም ያገለግላል ። ቋንቋህ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ መጠቀም ትችላለህ ።

የሙሴ መጽሐፍ
ይህ የዘፍጥረትን ፣ የዘጸአትን ፣ የዘሌዋውያን ፣ የዘኁልቁን፣ እና የዘዳግምን መጻሕፍት የሚያመለክት ነው ።

2 Chronicles 25:5

ይሁዳን ሰበሰበ
እዚህ ላይ “ይሁዳ” የሚያመለክተው በይሁዳ የኖሩ ሰዎችን ነው ። ኣት: - “የይሁዳን ሕዝብ አንድ ላይ ሰበሰበ” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

መዘገባቸው... ቆጠራቸው
አንድ ሰው ስማቸውን በመዝገብ ላይ እንዲጽፍ አደረገ ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በአባቶቻቸው ቤቶች
እዚህ “ቤቶች” የሚለው ቃል በውስጣቸው የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚገልጽ ተኪ ስም ነው ። ኣት: - “በአባቶቻቸው ቤተሰቦች” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

ሻለቆች እና መቶ አለቆች
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እነዚህ ቁጥሮች አለቆቹ የሚመሩትን ወታደሮች ብዛት ያመለክታሉ ። ኣት: - “የ 1000 ወታደሮች አዛዦች እና የ100 ወታደሮች አዛዦች” ወይም 2) “ሺህ” እና “መቶ” ተብለው የተተረጎሙት ቃላት ትክክለኛ ቁጥሮችን አይወክሉም ፣ ግን ትላልቅና ትናንሽ ወታደራዊ ምድቦች ስሞች ናቸው። ኣት: - “የትላልቅ የጦር ምድቦች አዛዦች እና የትናንሽ የጦር ምድቦች አዛዦች ።በ 2 ኛ ዜና ምዕራፍ 1፡ 2 የሚገኘውን ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። (ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

ይሁዳንና ብንያምን ሁሉ
እዚህ “ይሁዳ” እና “ቢንያም” በሰፊው በይሁዳ መንግሥት ውስጥ የኖሩትን ሰዎች ያመለክታሉ ። ኣት: - “የይሁዳና የብንያም ሕዝብ ሁሉ” (የባህሪ ስሞችን :ይመልከቱ)

ዕድሜያቸው ሀያ ዓመት እና ከዚያ በላይ
እዚህ ከሃያዎቹ የሚበልጡ ቁጥሮች ከፍ ያሉ እንደሆኑ ይናገራል። ኣት: “ዕድሜው 20 ዓመትና ከዚያ በላይ” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

አገኛቸው
“መኖራቸውን አወቀ”

300,000... 100,000
“ሦስት መቶ ሺህ... አንድ መቶ ሺህ” (ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

የተመረጡ ወንዶች
“ብቃት ያላቸው ወታደሮች” ወይም “ችሎታ ያላቸው ጦረኞች”

አንድ መቶ መክሊት ብር
“100 መክሊት ብር።” ይህንን ወደ ዘመናዊ ልኬት መቀየር ትችላለህ። ኣት: - “ወደ ሦስት ሺ ሦስት መቶ ኪሎ ግራም ብር” ወይም “3,300 ኪሎ ግራም ብር” (ቁጥሮችን የመጽሐፍ ቅዱስ ክብደቶችን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 25:7

የእግዚአብሔር ሰው
“የእግዚአብሔር ነቢይ”

እስራኤል... የኤፍሬም ህዝብ
እነዚህ ለተመሳሳይ ቡድን የተሰጡ ሁለት ስሞች ናቸው ።

ከጠላትህ ፊት ጣልህ... ጣለህ
እዚህ ስለወታደራዊ ሽንፈት ሲናገር ንጉሡ መሬት ላይ እንደሚወረውር አድርጎ ይናገራል ። ኣት: - “ጠላትህ እንዲያሸንፍህ ያስችለዋል... ሽንፈት” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 25:9

አንድ መቶ መክሊት ያህል
“100 መክሊት ብር።” ይህንን ወደ ዘመናዊ ልኬት መቀየር ትችላለህ። ኣት: - “ወደ ሦስት ሺ ሦስት መቶ ኪሎ ግራም ብር” ወይም “3,300 ኪሎ ግራም ብር” (መጽኀፍ ቅዱሳዊ ክብደትን :ይመልከቱ)

የእስራኤል ሠራዊት ... ከኤፍሬም ወደ እርሱ የመጡ ወታደሮች ናቸው
እነዚህ አንዱን ሠራዊት የሚገልጹ ሁለት መንገዶች ናቸው ።

ስለዚህ እጅግ ተቆጡ
እዚህ የቁጣቸው መጨመር በእነርሱ ውስጥ እንደሚነድ እሳት እንደሆነ ተገልጾአል። ኣት: - “ስለዚህ ቁጣቸው በውስጣቸው እንደ እሳት ነደደ” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

ጽኑ ቁጣ
“በጣም ተቆጡ”

2 Chronicles 25:11

ደፋር ሆነ
“ደፋር ሆነ”

የጨው ሸለቆ
ይህ በሙት ባሕር አቅራቢያ የሚገኝ ቦታ ነው ።

አስር ሺህ ሰዎች... ሌላ አሥር ሺህ
“10,000 ወንዶች... ሌላ 10,000 ወታደሮች” (ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

ሁሉም ተፈጠፈጡ
ይህ ግነት ሲሆን የግድያውን ትክክለኛነት አፅንዖት የሚሰጥ ነው ። ኣት: - “ሁሉም እንዲጠፉ” (ግነትን ወይም አጠቃላይን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 25:13

አሜስያስ መልሶ የላካቸው የጦሩ ሰዎች
አሜስያስ ወደ እስራኤል የላከው የእስራኤል ሰራዊት ሰዎች ”

ቤትሖሮን
ይህ በኢየሩሳሌም አቅራቢያ በኤፍሬም የሚገኝ መንደር ነበር። (የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)

መታቸው
እዚህ “መታቸው” ማለት እነርሱን መግደል ነው ። ኣት: “ተገደለ”(ፈሊጥን : ይመልከቱ)

ሦስት ሺህ ሰዎች
“3,000 ሰዎች”

ብዙ ምርኮ ወሰደ
“እጅግ ብዙ ዋጋ ያላቸውን ነገሮች ወሰደ”

2 Chronicles 25:14

አሁን እንዲህ ሆነ
ይህ ሐረግ የታሪኩን አዲስ ክፍል ጅምር ለመጠቆም እዚህ ያገለገለ ነው ። ቋንቋህ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ መጠቀም ትችላለህ ።

የኤዶማዊያን መገደል
“ኤዶማውያንን መግደል” ወይም “ኤዶማውያንን ማሸነፍ”

የሴይር ሰዎች አማልክት
“የሴይር ሰዎች ያሚያመልኳቸው አማልክት”

ሰገደ... አጠነ
እነዚህ አምልኮን የሚያመለክቱ ተግባራት ናቸው ። (ምሳሌያዊ ድርጊትን : ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ቁጣ በአሜስያስ ላይ ነደደ
እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ በሚነድ እሳት ተመስሎ ተገልጾአል ። ኣት: - “የእግዚአብሔር ቁጣ በአሜስያስ ላይ እንደ ሚነድድ እሳት ሆነ” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

የገዛ ወገኖቻቸውን እንኳ ከእጅህ ያላዳኑትን የሌሎች ሕዝብ አማልክት ለምን ፈለግህ?
ነቢዩ አሜስያስን ድል ያደረጋቸውን ሕዝብ አቅም አልባ አማልክት ማምለኩን ለመገሠጽ ይህን አወያይ መጠይቅ ይጠቀማል ። እዚህ ላይ “እጅ” የሚለው ቃል ኃይል የሚለውን ተክቶ የገባ ቃል ነው ። ጥያቄው እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። አትቲ: - “የራሳቸውን ሕዝብ እንኳ ካንተ ኃይል የማያድኑትን ሕዝብ አማልክትን አመለካቸው።” (አወያይ መጠይቅን እና የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

የገዛ ወገኖቻቸውን እንኳ የማያድኑ አማልክት...
ይህ ጦርነቶችን የሚያሸንፈውን አማልክት እንደሚወስኑ ማሰብ በዘመኑ የተለመደ አስተሳሰብ እንደነበረ ያሳያል ።

2 Chronicles 25:16

እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ በታሪኩ ውስጥ ቀጣዩን አስፈላጊ ክስተት ለማመልከት ይጠቅማል ። ቋንቋህ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ መጠቀም ትችላለህ ።

ለንጉሡ አማካሪ አድርገንሃልን? ተው! መገደልን ለምን ትሻለህ ?
ንጉሡ እርሱን ተቃውሞ ስለተናገረ ነቢዩን ለመገሰጽ እነዚህን አወያይ መጠይቆችን ተጠቅሟል ። ጥያቄዎቹ እንደ መግለጫዎች ሊተረጎሙ ይችላሉ ። ኣት: - “ከአማካሪዎቼ መካከል አንድትሆን አልሾምኩህም። ስለዚህ ማውራት አቁም! ከእንግዲህ አንድ ነገር ብትናገር ወታደሮቼ እንዲገድሉህ እነግራቸዋለሁ! ” (አወያይ መጠይቅን :ይመልከቱ)

ይህን ሥራ አደረግህ
ይህ በ 2 ኛ ዜና 25 ፡14 ውስጥ የኤዶማውያንን አማልክት ያመለኩትን አሜስያስን ይመለከታል ።

2 Chronicles 25:17

ኢዮአስ... ኢዮአካዝ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው ። (የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)

ፊት ለፊት ተገናኙ
ይህ ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን በመልክተኛ ወይም በሌሎች ሰዎች አማካኝነት ከመግባባት ይልቅ ሁለቱም በአካል በዚያ ተገኝተዋል ማለት ነው ። ኣት: - “በአካል ተነጋገሩ” (ፈሊጥን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 25:18

በሊባኖስ የነበረው ኩርንችት... ኩርንችቱን ረገጠ
ይህ መልእክት ምሳሌያዊ መልክ ያለው ነው ። ከንቱ ኩርንችት አሜስያንን ይወክላል ፣ የሊባኖስ ዝግባው ደግሞ ኢዮስያስን ይወክላል።ኩርንችቱ በአውሬው መረገጡ መጥፎ ነገር እንደሚከሰትበት እና ይህን ለማስቆም ኃይል የሌለው መሆኑን ይገልጻል ። የምሳሌው ነጥብ አሜስያስ ኢዮአስን መገዳደር ሞኝነት መሆኑ ነው ። (ምሳሌን :ይመልከቱ)

ኩርንችት
ይህ ትንሽ ፣ ሹል እሾህ ያለው ተራ ተክል ነው።

ዝግባ
በጣም ትልቅ የዛፍ ዓይነት

ልብህ ከፍ ከፍ አደረገህ
ይህ ማለት ኩራተኛ ነው ማለት ነው ። ኣት: - “ኩራተኛ ሆነሃል” (ፈሊጥን ፡ ይመልከቱ)

አንተ ከይሁዳ ጋር ትወድቅ ዘንድ ስለምን መከራ ትሻለህ?
ኢዮስያስ አሜስያስን ከእርሱ ጋር እንዳይዋጋ ለማስጠንቀቅ ይህን አወያይ መጠይቅ ተጠቅሟል ። እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: - “አንተ ከይሁዳ ጋር ሁላችሁንም ችግር ላይ መጣል የለብህም።” (አወያይ መጠይቅን :ይመልከቱ)

መውደቅ
እዚህ “መውደቅ” “መሞት” ማለት ነው ።

ይሁዳ
እዚህ ላይ “ይሁዳ” በይሁዳ የሚኖሩትን ህዝብ የተካ ስም ነው ። አት: - “የይሁዳ ሰዎች” (ዘወርዋራን:ይመልከቱ)

2 Chronicles 25:20

ይህ ክስተት ከእግዚአብሔር ነበር
“እግዚአብሔር ይህ ነገር እንዲከሰት ፈቅዷል”

በጠላቶቻቸው እጅ ውስጥ
እዚህ “እጅ” የማሸነፍ ኃይልን ያመለክታል ። አት: - “በጠላቶቻቸው እጅ” ወይም “ጠላቶቻቸው ሊያሸንፏቸው ይችላሉ” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

ፊት ለፊት ተገናኙ
ይህ ፈሊጥ ሲሆን ሌሎች ሰዎችን ብቻ ወደ ውጊያው ከመላክ ይልቅ ሁለቱም ግለሰቦች ውጊያው ላይ ተገኝተው ነበር ማለት ነው ። በ 2 ኛ ዜና 25 ፡17 ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት ። ኣት: - “በአካል ተገናኙ።” (ፈሊጥን :ይመልከቱ)

የይሁዳ ንብረት የሆነችው ቤትሳሚስ
የቤትሳሚስ ከተማ በይሁዳ ይገኛል።

ይሁዳ በእስራኤል ፊት ተመታ
እዚህ “ይሁዳ” እና “እስራኤል” የይሁዳ እና የእስራኤልን ወታደሮች ለማለት ነው ፣ “ተመቱ” የሚለው ፈሊጥ ሲሆን “ተሸነፉ” ማለት ነው ። ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “የእስራኤል ወታደሮች የይሁዳን ወታደሮች አሸነፉ” (የባህሪ ስምን እና ፈሊጥን እና ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን:ይመልከቱ)

እያንዳንዱ ሰው
ይህ ከጦርነቱ የተረፉ የይሁዳን ወታደሮች በተመለከተ ጠቅለል ያለ መረጃ ነው ። ኣት: - “የተረፉት የይሁዳ ወታደሮች” (ግነትን እና አጠቃላይን ፡ ይመልከቱ)

2 Chronicles 25:23

ርቀቱ አራት መቶ ክንድ ነው
አንድ ክንድ 46 ሴንቲሜትር ነው ። ኣት: - “ርቀቱ 400 ክንድ” ወይም “ርዝመቱ 180 ክ.ሜ የሆነ ” (ቁጥሮችን እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ርቀትን ፡ ይመልከቱ)

ከዖቤድኤዶም ጋር
እዚህ “ዖቤድኤዶም” የሚለው የዚህን ሰው ዝርያ ያመለክታል ። አት: - “በዖቤድኤዶም ዘሮች ጥበቃ” (የባህሪ ስምን እና የስሞችን አተረጓጎም ፡ ይመልከቱ)

የንጉሥ ቤት
“ንጉሣዊው ቤተ መንግሥት”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Chronicles 25:25

የቀሩትም ጉዳዮች ... በይሁዳና በእስራኤል ነገሥታት መጽሐፍ የተጻፈ አይደለምን?
ይህንን አወያይ መጠይቅ በአሜስያስ ላይ የደረሰው ነገር በደንብ የታወቀ መሆኑን ለአንባቢው ለማስገንዘብ ይጠቅማል ። እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: - “አሜስያስን የሚመለከቱ ጉዳዮች ሁሉ እነሆ ፣ በይሁዳና በእስራኤል ነገሥታት መጽሐፍ ተጽፈዋል።” (አወያይ መጠይቅን :ይመልከቱ)

የፊተኛውና የኋለኛው የአሜስያስ ነገር
እዚህ “የፊተኛውና እና የኋለኛው” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው እነዚያን ጽንፎች እና በመካከላቸው ያሉትን ነገሮች ሁሉ ነው ። ኣት: - “አሜስያስን የሚመለከቱ ጉዳዮች ሁሉ” (ሜሪዝምን :ይመልከቱ)

እነሆ
ይህ አንባቢው ቀጥሎ ለሚነገረው እውነት ልዩ ትኩረት እንዲሰጥ ያነቃል።

የይሁዳና የእስራኤል ነገሥታት መጽሐፍ
ይህ የማይገኝ መጽሐፍ ነው።

2 Chronicles 25:27

ያህዌን ከመከተል ዞር አለ
እዚህ “ዞር አለ ” ማለት እግዚአብሔርን አልታዘዝም አለ ማለት ነው ። ኣት: - “እግዚአብሔርን መታዘዝ አቆመ” ወይም “እግዚአብሔርን መታዘዝ ጀመረ” (ፈሊጥን:ይመልከቱ)

ሴራ ማሴር ጀመሩ... ላኩ... አመጡ
ጽሑፉ “ማንን” እንደሚያመለክቱ አይገልጽም። ከተቻለ በትርጉምዎ ላይ “እነርሱ” የተባሉትን አነጋገሮች አስታውሱ።

በእሱ ላይ ሴራ ያሴሩ
የቃላት ስሙ “ሴራ” እንደ ድርጊት ሊገለጽ ይችላል ። ኣት: - “በእሱ ላይ አሴሩ” ወይም “በእሱ ላይ አሴሩ” (የረቂቅ ስሞችን :ይመልከቱ)

ለኪሶ
በይሁዳ ያለች ከተማ (የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)

መልሰው አመጡት
“አስከሬኑን አመጡ”

የይሁዳ ከተማ
ይህ የኢየሩሳሌም ሌላ ስም ነበር ፣ የዳዊት ከተማም ተብላ ትጠራ ነበር ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 26

1 የይሁዳም ሕዝብ ሁሉ አሥራ ስድስት ዓመት የነበረውን ዖዝያንን ወስደው በአባቱ በአሜስያስ ቦታ አነገሡት። **2** ኤላትን እንደገና የገነባትና ወደ ይሁዳ ወደቀድሞ ይዞታዋ የመለሳት እርሱ ነው። ከዚያ በኋላ ንጉሡ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ። **3** ዖዝያን መንገሥ በጀመረ ጊዜ አሥራ ስድስት ዓመቱ ነበር። በኢየሩሳሌምም ሃምሳ ሁለት ዓመት ነገሠ። የእናቱም ስም ይኮልያ ነበር፤ የኢየሩሳሌም ሴት ነበረች። **4** በሁሉም ነገር የአባቱን የአሜስያስ ምሳሌነት በመከተል በእግዚአብሔር ፊት ትክክለኛውን ነገር አደረገ። **5** እግዚአብሔርን መታዘዝ ባስተማረው በዘካርያስ ዘመን እግዚአብሔርን ለመፈለግ በልቡ ቆርጦ ነበር። እግዚአብሔርን በፈለገ ጊዜ እግዚአብሔር የተሳካለት አደረገው። **6** ዖዝያን ወጥቶ ከፍልስጤማውያን ጋር ተዋጋ። የጌትንና የየብናንና የአዛጦንን የከተማ ቅጥሮች አፈረሰ፤ በአዛጦን አገርና በፍልስጤማውያን መካከል ከተሞችን ገነባ። **7** እግዚአብሔርም በፍልስጤማውያን ላይ፥ በጉርበኣል በሚኖሩ ዓረባውያን ላይና በምዑናውያን ላይ ረዳው። **8** አሞናውያንም ለዖዝያን ግብር ይከፍሉ ነበር፤ እጅግ ኃይለኛ ከመሆኑ የተነሳ ዝናውም እስከ ግብጽ መግቢያ ድረስ ወደ ሌሎች አገሮች ተሰራጨ። **9** በተጨማሪም ዖዝያን በኢየሩሳሌም በማዕዘኑ በር፥ በሸለቆው በርና በቅጥሩ መዞሪያ ላይ ረጃጅም ማማዎችን ገንብቶ መሸጋቸው። **10** በቆላው እንዲሁም በደጋው እጅግ ብዙ ከብቶች ስለነበሩት በምድረ በዳው የመጠባበቂያ ማማዎችን ሠራ፤ በርካታ ጉድጓዶችንም ቆፈረ። እርሻ ይወድ ስለነበርም በኮረብታማው አገርና በፍሬያማው መስክ ውስጥ ገበሬዎችና የወይን አትክልተኞች ነበሩት። **11** በተጨማሪም ዖዝያን በጸሐፊው በይዒኤልና ከንጉሡ አለቆች በአንዱ በሐናንያ ሥልጣን ስር በነበረው በመዕሤያ በሚቆጠሩበት ቁጥር መሰረት የተደራጁ በቡድን ወደ ጦርነት ይሄዱ የነበሩ የተዋጊ ሰዎች ሠራዊት ነበሩት። **12** የአባቶቻቸውም ቤቶች አለቆች የተዋጊ ሰዎች አጠቃላይ ቁጥር ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ነበር። **13** ከበታቻቸውም ንጉሡን ከጠላቱ ለመጠበቅ የሚረዳ በብርቱ ኃይል የሚዋጋ የሦስት መቶ ሰባት ሺህ እምስት መቶ ሰዎች ሠራዊት ነበር። **14** ዖዝያንም ለሠራዊቱ ሁሉ ጋሻዎች፥ ጦሮች፥ የራስ ቁሮች፥ ጥሩሮች፥ ቀስቶችና የሚወነጭፉአቸውን ድንጋዮች አዘጋጅቶላቸው ነበር። **15** በኢየሩሳሌምም ፍላጻዎችንና ትልልቅ ድንጋዮችን ለመወርወር በግንብና በመታኮሻ ቅጥር ላይ እንዲሆኑ የተካኑ ባለሙያዎች የፈለሰፏቸውን ማንቀሳቀሻ ሞተሮች ገነባ። እጅግ እስኪበረታም ድረስ እግዚአብሔር በብዙ ረድቶታልና ዝናው እስከ ሩቅ ቦታዎች ተሰራጨ። **16** ነገር ግን ዖዝያን በበረታ ጊዜ እስኪበላሽ ድረስ ልቡ ታበየ፤ ወደ እግዚአብሔር ቤት ገብቶ በዕጣን መሠዊያው ላይ ዕጣን በማጠኑ አምላኩን እግዚአብሔርን በደለ። **17** ካህኑም ዓዛርያስ ከእርሱም ጋር ደፋር ሰዎች የነበሩ ሰማንያ የእግዚአብሔር ካህናት ተከትለውት ገቡ። **18** ንጉሡንም ዖዝያንን ተቃውመው፦"ዖዝያን ሆይ፦ ለእግዚአብሔር ዕጣን ማጠን ለእግዚአብሔር ለተቀደሱት ለካህናቱ ለአሮን ልጆች የተሰጠ እንጂ ዕጣን ማጠን ለአንተ አይደለም። ተላልፈሃልና ከቅዱሱ ቦታ ውጣ። በዚህ ነገር ከእግዚአብሔር ዘንድ ላንተ ምንም ክብር አይሆንልህም" አሉት። **19** ዖዝያንም ተቆጣ። ዕጣን የሚያጥንበትን ጥና በእጁ ይዞ ነበር። በካህናቱ ላይ በተቆጣ ጊዜ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ በዕጣኑ መሠዊያ አጠገብ በካህናቱ ፊት ግንባሩ ላይ ለምጽ ወጣበት። **20** ዋናው ካህንና ካህናቱ ሁሉ ተመለከቱት፤ እነሆ ግንባሩ ላይ ለምጻም ሆኖ ነበር። በፍጥነትም ከዚያ ቦታ አስወጡት። በእርግጥም እግዚአብሔር በለምጽ መትቶት ስለነበር እርሱም ለመውጣት ቸኮለ። **21** ንጉሡም ዖዝያን እስከሚሞትበት ቀን ድረስ ለምጻም ነበረ፤ ለምጻም በመሆኑም ከእግዚአብሔር ቤት ተገልሎ ስለነበር ከሰዎች ርቆ በተለየ ቤት ይኖር ነበር። ልጁም ኢዮአታም በንጉሡ ቤት ላይ የበላይ ሆኖ የምድሩን ሕዝብ ይገዛ ነበር። **22** ዖዝያንን በተመለከተ ሌሎቹ ነገሮች የመጀመሪያውና የመጨረሻው የአሞጽ ልጅ ነቢዩ ኢሳይያስ በጻፈው ውስጥ ይገኛሉ። **23** ዖዝያንም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ "ለምጻም ነው" ብለውም ከአባቶቹ ጋር በነገሥታቱ መቃብር ሥፍራ ቀበሩት።

---

2 Chronicles 26:1

የይሁዳ ሰዎች ሁሉ የአሥራ ስድስት ዓመት ልጅ የነበረውን ዖዝያንን ወስደው በአባቱ በአሜስያስ ፋንታ አነገሡት።
“ሁሉም” የሚለው ቃል ጠቅላል ያለ አገላለጽ ነው ። አንዳንድ ሰዎች እርሱ ንጉሥ እንዲሆን አይፈልጉ ይሆናል ። ኣት: “የይሁዳ ሕዝብ የ 16 ዓመቱን ዖዝያንን ወስዶ በአባቱ በአሜስያስ ፋንታ አነገሡት” (ግነትን እና አጠቃላይን ፡ ይመልከቱ)

አስራ ስድስት...ሃምሳ ሁለት
“16... 52” (ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)

ኤላትን የሠራው እርሱ ነበር
ዖዝያን ብቻውን አሠራውም። ኣት: - “ኤላት እንደገና እንድትሠራ ያዘዘው እርሱ ነበር” ወይም “ኤላት እንደገና የተሠራው በእርሱ ቁጥጥር ነበር” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን ፡ይመልከቱ)

ኤላት
በይሁዳ ያለች ከተማ (የስሞችን አተረጓጎም ፡ይመልከቱ)

ወደ ይሁዳ መለሳት
ወደ ይሁዳ መለሰው። ”ይህ ማለት የእርሱ ሠራዊት ከተማዋን ስለተቆጣጠረ እንደገና የይሁዳ ሆነች ።

ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ
ይህ መሞቱ የሚነገርበት መንገድ ነው ። (ዘወርዋራ አነጋገርን ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 26:4

በእግዚአብሔር ፊት ትክክል የሆነውን ነገር አደረገ
ዐይን ማየትን ይወክላል ፣ ማየት ደግሞ አመለካከትን ወይም ፍርድን ይወክላል። በ 2 ኛ ዜና 14፡ 2 ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት ። ኣት: - “እግዚአብሔር ትክክል ነው ብሎ የሚወስነው” ወይም “እግዚአብሔር ትክክል ነው የሚለው” (ዘይቤያዊን ፡ይመልከቱ)

በሁሉ የአባቱን የአሜስያስን ምሳሌ መከተል
ይህ የሚያመለክተው አባቱ በእግዚአብሔር ፊት ትክክል የሆነውን ነገር እንዳደረገ ነው ። ኣት: “አባቱ አሜስያስ እንዳደረገው” (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን ፡ይመልከቱ)

በሁሉም ነገር
ይህ ግርድፍ ነው ። ኣት: - “በተመሳሳይ መንገድ” (ግነትን እና አጠቃላይን ፡ ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን ለመፈለግ ራሱን አዘጋጀ
እዚህ“ራሱን አዘጋጅ” አንድ ነገር ለማድረግ ቁርጥ ውሳኔ መወሰንን የሚያመለክት ነው ። እግዚአብሔርን መፈለግ እርሱን ለማወቅ ፣ ለማምለክ እና ለመታዘዝን መምረጥን ያመለክታል ። ኣት: - “እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ቆርጦ ነበር” (ዘይቤያዊን ፡ይመልከቱ)

በዘካርያስ ዘመን
እዚህ ላይ “የዘካርያስ ቀናት” ዘካርያስ ካህን የነበረበትን ዘመን የሚያመለክት አገላለጽ ነው ። ኣት: - “ዘካርያስ ካህን በነበረ ጊዜ” (ዘይቤያዊን፡ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እግዚአብሔርን ይፈልግ በነበረ ጊዜ
“እግዚአብሔርን በፈለገበት ጊዜ ሁሉ”

እግዚአብሔርን ፈለገ
እግዚአብሔርን መፈለግ እርሱን ለማወቅ ፣ ለማምለክ እና ለመታዘዝ መምረጥን ያመለክታል ። ኣት: - “እግዚአብሔርን መታዘዝ መረጠ” (ዘይቤያዊን ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 26:6

ዖዝያን ወጥቶ ከፍልስጥኤማውያን ጋር ተዋጋ
እዚህ ላይ “ዖዝያን” እራሱን እና የመረጠውን ሠራዊት ይወክላል ። ኣት: - “ዖዝያን ሠራዊቱን እየመራ ከፍልስጥኤማውያን ጋር ለዋጋ ወጣ” ወይም “ዖዝያንና ሠራዊቱ ወጥተው ከፍልስጥኤማውያን ጋር ተዋጉ” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከል ፡ይመልከቱ)

አፈረሰ... ከተሞችን ሠራ... እግዚአብሔር ረዳው
እዚህ “እርሱ” እና “እርሱን” የሚሉት ተውላጠ ስሞች ዖዝያንንና ሠራዊቱን ይወክላሉ። ኣት: “ዖዝያንና ሠራዊቱ አፈረሱ... ከተሞችን ገነቡ... እግዚአብሔርም ረዳቸው” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን ፡ ይመልከቱ)

የበናን
ይህ በሰሜናዊቷ ይሁዳ የነበረ ከተማ ነው። (የስሞችን አተረጓጎም ፡ ይመልከቱ)

የአሸዶድ አገር
“በአሸዶድ ዙሪያ ያለች አገር” ወይም “በአሸዶድ አቅራቢያ”

ጉርበኣል
ይህ በአረባዊያን ምድር የሚገኝ ከተማ ነበር ። (የስሞችን አተረጓጎም ፡ ይመልከቱ)

በምዑናውያን
ይህ በሴይር አቅራቢያ ካለው ከማኦን መንግሥት ወደዚያ አካባቢ የተጓዙት ሰዎች ሳይሆኑ አይቀሩም ። (የስሞችን አተረጓጎም ፡ይመልከቱ)

እስከ ግብጽ መግቢያ ድረስ ዝናው ተዛመተ
የእርሱ ዝና መስፋፋት በተለያዩ ቦታዎች ስለ እርሱ ማወቃቸውን የሚያመለክት ነው ። ኣት: ““ እስከ ግብፅ ዳርቻ ድረስ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች እሱ ስለሚያደርገው ነገር አወቁ ”

2 Chronicles 26:9

ዖዝያን ማማዎቹን ሠሩ
እዚህ “ዖዝያን” ማማዎቹን እንዲሠሩ ያዘዛቸውን ሠራተኞች ይወክላል ። ኣት: - “ዖዝያን ሠራተኞቹ ማማዎቹን እንዲሠሩ አደረገ” ወይም “የዖዝያን ሠራተኞች ማማዎቹን ሠሩ” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

እርሱ ማማዎቹን ሠራ... ብዙ ጉድጓዶችን ቆፈረ
ዖዝያን ሠራተኞቹን አዞ ፤ እነርሱም እንዲህ አደረጉ። ኣት: - “ሠራተኞቹ ማማዎቹን እንዲገነቡ አደረገ... ብዙ ጉድጓዶችን እንዲቆፍሩ” ወይም “መጠበቂያ ማማዎችን ሠሩ... ብዙ ጉድጓዶችንም ቆፈሩ” (የባህሪ ስምን ፡ ይመልከቱ)

ብዙ ከብቶች ነበሩት... ገበሬዎች ነበሩት... እርሻን ይወድ ነበር
“እርሱ” የሚለው ቃል ዖዝያንን ያመለክታል ።

2 Chronicles 26:11

ይዒኤል... መዕሤያ ፣ አለቃው... ሐናንያ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው ። (የስሞችን አተረጓጎም ፡ይመልከቱ)

ኃያላኑን መሪዎች የነገድ አለቆች መሪዎችን
“ኃያላኑን የመሩት የቤተሰብ መሪዎች”

2,600... 307,500
“ሁለት ሺህ ስድስት መቶ... ሦስት መቶ ሰባት ሺህ አምስት መቶ”
(ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)

በእነርሱ ሥር ሠራዊት ነበር
እዚህ “እጃቸው” ሥልጣናቸውን ይወክላል። ኣት: - “በእነርሱ ሥር ሠራዊት ነበር” ወይም “ሠራዊትን ያዙ ነበር” (የባህሪ ስምን፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 26:14

ዖዝያን አዘጋጀላቸው
'ዖዝያን ምግብ ሰጣቸው'

የራስ ቁር
የራስ ቁር የራስ መከላከያ ሽፋን ነው ።

ጥሩር
ይህ ከብረት ሰንሰለቶች የተሠራ የአካል መሸፈኛ ነው ።

በብልሃተኞች እጅ የተነደፉ ማሽኖችን ሠራ
እዚህ “ማሽኖችን ሠራ” የሚለው ዖዝያን ሠራተኞቹ እንዲገነቡ ያዘዘውን ይወክላል ። ኣት: - “ሠራተኞቹ በሰለጠኑ ሰዎች የተነደፉ ማሽኖችን ሠሩ” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

ቅጥር
የከተማው ግድግዳዎች ማዕዘናት ሲሆኑ ወታደሮቹ ለውጊያ የሚመሸጉባቸው ቦታዎች ናቸው።

እርሱ በጣም ተበረታቶ
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “እግዚአብሔር እጅግ ረድቶታል” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 26:16

ልቡ ከፍ ከፍ አለ
እዚህ ልብ ከፍ ከፍ ማለት ኩራትን ያመለክታል ። ኣት: - “ኩራተኛ ሆነ”(ዘይቤያዊን ፡ይመልከቱ)

ከእርሱም ጋር ጽኑዓን የነበሩ ሰማንያ የእግዚአብሔር ካህናት
ከቀዳሚው ሐረግ "ገቡ" የሚለው ግስ ተወስዷል ። ኣት: “ከእርሱ ጋር ጽኑዓን የሆኑ ሰማንያ የእግዚአብሔር ካህናት” ወይም “ደፋር ሰዎች የነበሩት ስምንት የእግዚአብሔር ካህናት ከእርሱ ጋር አብረው ሄዱ” (የቃላት ግድፈትን ፡ ይመልከቱ)

ዖዝያን ሆይ ፥ ዕጣን ለእግዚአብሔር ታጥን ዘንድ ለአንተ አይገባም
“ዖዝያን ሆይ ዕጣን ማጨስ ለአንተ አይደለም” ወይም “ዖዝያን ሆይ ፣ ለእግዚአብሔር ዕጣን የማጠን መብት የለህም”

የአሮን ልጆች
እዚህ “ወንዶች ልጆች” ዘሮችን ይወክላሉ ። ኣት: - “የአሮን ዘሮች” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ዕጣን ለማጠን የተቀደሱ ናቸው
ይህ በንቃት ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “እግዚአብሔር ዕጣን ያጨሱ ዘንድ የቀደሰው” ወይም “እግዚአብሔር ዕጣን ያጥን ዘንድ የመረጠው”

2 Chronicles 26:19

ጥና
ይህ ዕጣን ለማቃጠል የሚያገለግል ልዩ ድስት ወይም ጎድጓዳ ሳህን ነው።

እነሆ ፥ ለምጻም ሆነ
እዚህ “እነሆ” የሚለው ቃል ካህናቱ ባዩት ነገር ተደንቀው እንደነበር ያሳያል ።

እነሱ በፍጥነት ከዚያ አባረሩት
“በፍጥነት ከዚያ እንዲወጠ አስገደዱት” ወይም “በፍጥነት አባረሩት”

እግዚአብሔር ቀሰፈው
ይህ እግዚአብሔር በሽተኛ እንዳደረገው ሲናገር ልክ እግዚአብሔር እንደመታው በማስመሰል ተናግሯል ። ኣት: “እግዚአብሔር በሽተኛ አደረገው” (ዘይቤያዊን ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 26:21

እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ
“እስከሞተበት ጊዜ ድረስ” ወይም “በቀሪው የሕይወት ዘመኑ ሁሉ”

በተለየ ቤት ውስጥ ኖረ
ይህ የሚያመለክተው ከሌሎች ቤቶችና ከሌሎች ሰዎች ርቆ መኖሩን ነው ።

ከእግዚአብሔር ቤት ተቆረጠ
እዚህ ከእግዚአብሔር ቤት “ተቆርጠ” ከቤተመቅደስ መነጠልን ይወክላል። ኣት: - “ከእግዚአብሔር ቤት ተገለለ” ወይም “ወደ ቤተመቅደስ እንዲሄድ አልተፈቀደለትም” (ዘይቤያዊን ፡ይመልከቱ)

ልጁ ኢዮዓታም በንጉሡ ቤት ላይ ተሹሞ ነበር
እዚህ ላይ ከአንድ ነገር በላይ መሆን ለእሱ ኃላፊነት ወይም ስልጣን እንዳለው ያሳያል። ኣት: - “ልጁ ኢዮአታም ለንጉ king ቤት ሀላፊ ነበር” ወይም “ልጁ ኢዮአታም በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ሹም ነበር” (ዘይቤያዊን ፡ይመልከቱ)

የንጉሡ ቤት
ይህ የንጉሡ ቤተ መንግስት የነበረውን ያመለክታል ።

2 Chronicles 26:22

ከመጀመሪያው አንስቶ እስከ መጨረሻው ዖዝያንን የሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች በአሞጽ ልጅ በነቢዩ ኢሳይያስ ተጽፈዋል።
ይህ በንቃት ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “የዖዝያንን ሌሎች ጉዳዮች ከቀድሞው እስከ መጨረሻው ድረስ ፣ የአሞጽ ልጅ ኢሳይያስ መዝግቧቸዋል” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ይመልከቱ)

ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው
(ሜሪዝምን ፡ይመልከቱ)

አሞጽ
ይህ የሰው ስም ነው ። (የስሞችን አተረጓጎም፡ይመልከቱ)

ዖዝያንም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ
ይህ መሞቱ የተነገረበት ጨዋነት ያለው መንገድ ነው ። ኣት-“እንዲሁ ዖዝያን ሞተ” (ዘወርዋራን ፡ይመልከቱ)

ከአባቶቹ ጋር ቀበሩት
“ሰዎቹ በአባቶቹ አቅራቢያ ቀበሩት” ወይም “አባቶቹ በተቀበሩበት ቀበሩት ።”

በእርሱም ፋንታ ልጁ ኢዮአታም ነገሠ
“ልጁ ኢዮአታም ከዖዝያን በኋላ ነገሠ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 27

1 ኢዮአታምም መንገሥ በጀመረ ጊዜ ሃያ አምስት ዓመቱ ነበር፤ በኢየሩሳሌምም አሥራ ስድስት ዓመት ነገሠ። የእናቱም ስም ኢየሩሳ ነበር፤ እርሷም የሳዶቅ ልጅ ነበረች። **2** በሁሉም ነገር የአባቱን የዖዝያንን ምሳሌ ተከትሎ በእግዚአብሔር ፊት ትክክለኛውን ነገር አደረገ። ወደ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ከመግባትም ተቆጠበ። ሕዝቡ ግን ገና በክፉ መንገድ ይሄዱ ነበር። **3** የእግዚአብሔርን ቤት የላይኛውን በር ሠራ፤ በዖፌልም ኮረብታ ላይ እጅግ ብዙ የግንባታ ሥራዎችን ሠራ። **4** በተጨማሪም በኮረብታማው የይሁዳ አገር ላይ ከተሞችን፥ በደኖቹ ውስጥ ደግሞ አምባዎችንና ማማዎችን ገነባ። **5** ከአሞንም ሕዝብ ንጉሥ ጋር ተዋግቶ አሸነፋቸው። በዚያው ዓመት የአሞን ልጆች አንድ መቶ መክሊት ብር፥ አሥር ሺህ መስፈሪያ ስንዴ፥ አሥር ሺህ መስፈሪያ ገብስ ሰጡት። የአሞን ሕዝብ በሁለተኛውና በሦስተኛውም ዓመት ተመሳሳዩን ያህል ሰጡት። **6** በመሆኑም ኢዮአታም በአምላኩ በእግዚአብሔር ፊት በጽናት ስለተራመደ ብርቱ ሆነ። **7** ኢዮአታምን በተመለከተ ሌሎቹ ነገሮች ጦርነቶቹ ሁሉና መንገዱ እነሆ በእስራኤልና በይሁዳ ነገሥታት መጽሐፍ ተጽፈዋል። **8** ኢዮአታም መንገሥ በጀመረ ጊዜ ሃያ አምስት ዓመቱ ነበር፤ በኢየሩሳሌም ለአሥራ ስድስት ዓመታት ነገሠ። **9** ኢዮአታምም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ በዳዊትም ከተማ ቀበሩት። ልጁም አካዝ በእርሱ ቦታ ነገሠ።

---

2 Chronicles 27:1

ዕድሜ ሃያ-አምስት ... አሥራ ስድስት ዓመት
“ዕድሜው 25 ዓመት ... የ 16 ዓመት” (ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

ኢየሩሳ
ይህ የሴት ስም ነው ። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

በእግዚአብሔርም ፊት ቅን ነገር አደረገ
እዚህ ያሉት ዓይኖች ማየትን ይወክላሉ ፣ ማየት ደግሞ ፍርድን ይወክላል ። እግዚአብሔር የኢዮአታም ድርጊቶችን አይቶ አጸደቀ። ይህንን በ 2ኛ ዜና 14 ፡ 2 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። ኣት: - “እግዚአብሔር ትክክል ነው ያለውን ነገር አደረገ” ወይም “እግዚአብሔር ትክክል እንደሆነ የቆጠረውን ያደርግ ነበር” (ዘይቤያዊን:ይመልከቱ)

በሁሉም ነገር
“እርሱ በሠራው ሁሉ”

2 Chronicles 27:3

የላይኛውን በር ሠራ... ብዙ ሠራ ፣... ከተሞችን ሠራ... ግንቦችንና ማማዎችን ሠራ
ኢዮአታም በነገሠ ጊዜ ሠራተኞቹ እነዚህን ነገሮች እንዲሠሩ አድርጎ ይሆናል። ኣት: “ሠራተኞቹ የላይኛውን በር እንዲሠሩ... ሠራተኞቹ ብዙ ነገሮችን እንዲሠሩ ፣ ሰራተኞቹ ከተማዎችን እንዲገነቡ ፣ ሰራተኞቻቸው ግንቦችንና ማማዎችን እንዲገነቡ አድርጓቸዋል” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

የዖፌል ኮረብታ
ይህ በኢየሩሳሌም የሚገኝ ኮረብታ ነው። (የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)

2 Chronicles 27:5

እንዲሁም ከአሞን ህዝብ ንጉሥ ጋር ተዋጋ
ኢዮአታም ሠራዊቱን ወደ ውጊያ እንደመራ አንባቢው እንዲረዳው አድርጎ መተርጎም ሊኖርብህ ይችላል ። ኣት: “እርሱ ሠራዊቱን ከአሞን ሕዝብ ንጉሥ ጋር እንዲዋጋ መራ” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን ፡ ይመልከቱ)

ከአሞን ህዝብ ንጉሥ ጋር
የአሞን ንጉሥ ሰራዊቱን ወደ ጌት እንደመራ አንባቢው እንዲረዳው መተርጎም የኖርብህ ይሆናል። ኣት: - “ከአሞን ንጉሥና ከሠራዊቱ ጋር” (ሁሉን በአንሱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን :ይመልከቱ)

አንድ መቶ መክሊት ብር
ይህንን ወደ ዘመናዊ ልኬት መለወጥ ትችላለህ። “መክሊት” ከ 33 ኪሎግራም ጋር እኩል ነው ። ኣት: - “100 መክሊት ብር” ወይም “3,300 ኪሎ ግራም ብር” (መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክብደትን እና ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

አሥር ሺህ መስፈሪያ ስንዴ
ይህንን ወደ ዘመናዊ ልኬት መለወጥ ትችላለህ። እዚህ “መስፈሪያ” ተብሎ የተተረጎመው ቃል “ኮር” ሲሆን እና ከ 220 ሊትር ጋር እኩል ነው ። ኣት: - “10,000 መስፈሪያ ስንዴ ” ወይም “2,200 ኪሎ ግራም ስንዴ” (የመጽሐፍ ቅዱስ ይዘትን እና ቁጥሮችን:ይመልከቱ)

አሥር ሺህ መስፈሪያ ገብስ
ይህንን ወደ ዘመናዊ ልኬት መለወጥ ትችላለህ ። እዚህ “መስፈሪያ” ተብሎ የተተረጎመው ቃል “ኮር” ሲሆን ከ 220 ሊትር ጋር እኩል ነው ። ኣት: - “10,000 መስፈሪያ ገብስ” ወይም “2,200 ኪሎ ሊትር ገብስ” (መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይዘትን እና ቁጥሮችን:ይመልከቱ)

በሁለተኛው እና በሦስተኛው ዓመት ውስጥ
“እነርሱን ባሸነፈ በሁለተኛውና በሦስተኛው ዓመት”

2 Chronicles 27:8

ዕድሜው ሃያ-አመት ... አሥራ ስድስት ዓመት
“ዕድሜው 25 ዓመት... የ 16 ዓመት” (ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

ኢዮአታም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ
የኢዮአታም ሞት እንቅልፍ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። ኣት: - “ኢዮአታም ሞተ” (ዘይቤያዊን እና ዘወርዋራን :ይመልከቱ)

ቀበሩት
“ሰዎች ቀበሩት”

በእርሱ ምትክ ነገሠ
“በእርሱ ምትክ” የሚለው ሐረግ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው ፣ “በእርሱ ፋንታ” የሚል ትርጉም አለው። ኣት: “በኢዮአታም ፋንታ ነገሠ” (ዘይቤያዊን ፡ ይመልከቱ)

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 28

1 አካዝ መንገሥ በጀመረ ጊዜ ሃያ ዓመቱ ነበረ፤ በኢየሩሳሌም አሥራ ስድስት ዓመት ነገሠ። ዝርያው ዳዊት እንዳደረገው በእግዚአብሔር ፊት ትክክለኛውን ነገር አላደረገም። **2** ይልቁንም በእስራኤል ነገሥታት መንገድ ሄደ፤ ለበኣሊምም ከብረት ቀልጠው የተሠሩ ምስሎችን ሠራ። **3** በተጨማሪም በሄኖም ልጅ ሸለቆ ውስጥ ዕጣን ዐጠነ፤ እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ፊት ያሳደዳቸውን ሕዝቦች ክፉ ልማድ ተከትሎ ልጆቹን እንደሚቃጠል መሥዋዕት በእሳት ውስጥ አሳለፋቸው። **4** በኮረብታው መስገጃዎች፥ በኮረብቶች ላይ እና በለመለመው ዛፍ ሁሉ በታች መስዋዕት ይሰዋና ዕጣን ያጥን ነበር። **5** ስለዚህ የአካዝ አምላክ እግዚአብሔር ለሶርያ ንጉሥ እጅ አሳልፎ ሰጠው። ሶርያውያንም ድል አደረጉት፤ የብዙ እስረኞችን ስብስብ ከእርሱ ወስደው ወደ ደማስቆ አመጡአቸው። አካዝ ለእስራኤልም ንጉሥ እጅ ተላልፎ ተሰጥቶ ነበር፤ እርሱም በታላቅ ግድያ አሸነፈው። **6** የአባቶቻቸውን አምላክ እግዚአብሔርን ከመተዋቸው የተነሳ የሮሜልዩ ልጅ ፋቁሔ በአንድ ቀን ከይሁዳ ሁሉም ደፋር የሆኑ አንድ መቶ ሃያ ሺህ ወታደሮችን ገደለ። **7** ኤፍሬማዊው ኃይለኛ ሰው ዝክሪ የንጉሡን ልጅ መዕሤያንና የቤተ መንግሥቱን ባለሥልጣን ዓዝሪቃምን ለንጉሡ በማዕረግ ሁለተኛ የነበረውን ሕልቃናን ገደለ። **8** የእስራኤል ሠራዊት ከዘመዶቻቸው ሁለት መቶ ሺህ ሚስቶች፥ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ምርኮ አድርገው ወሰዱ። ወደ ሰማሪያም ተሸክመው ያመጡትን እጅግ ብዙ ምርኮም ወሰዱ። **9** ነገር ግን አንድ የእግዚአብሔር ነቢይ በዚያ ነበረ፤ ስሙም ዖዴድ ነበር። ወደ ሰማርያም የሚመጣውን ሠራዊት ለመገናኘት ወጣ።" የአባቶቻችሁ አምላክ እግዚአብሔር በይሁዳ ላይ ስለተቆጣ በእጃችሁ አሳልፎ ሰጣቸው። እናንተ ግን ወደ ሰማይ በሚደርስ ቁጣ ገደላችኋቸው። **10** አሁንም የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን ወንዶችና ሴቶች እንደ ባሪያዎቻችሁ አድርጋችሁ ልትይዟቸው ታስባላችሁ። በአምላካችሁ በእግዚአብሔር ላይ በገዛ ራሳችሁ ኃጢአት በደለኞች አይደላችሁምን? **11** እንግዲያውስ አሁን ስሙኝ፤ የእግዚአብሔር የጋለ ቁጣ በእናንተ ላይ ስለሆነ ከገዛ ወንድሞቻችሁ የወሰዳችኋቸውን እስረኞች መልሳችሁ ስደዱ" አላቸው። **12** ከዚያም የተወሰኑ የኤፍሬም ሰዎች መሪዎች የዮሐናን ልጅ ዓዛርያስ፥ የምሺሌሞትም ልጅ በራክያ፥ የስሎምም ልጅ ይሒዝቅያ፥ የሐድላይም ልጅ ዓሜሳይ ከጦርነቱ ተመልሰው የመጡትን ተቃወሙአቸው። **13** "መተላለፋችን ታላቅ ስለሆነና በእስራኤል ላይ የጋለ ቁጣ ስላለባት በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት የሚሆንብንን ነገር ልታመጡብን፥ ኃጢአታችንንና መተላለፋችንን ልትጨምሩብን ስላሰባችሁ እስረኞቹን እዚህ ልታመጧቸው አይገባችሁም" አሏቸው። **14** የታጠቁት ሰዎችም እስረኞቹንንና ምርኮውን በመሪዎቹና በጉባኤው ሁሉ ፊት ተዉአቸው። **15** በስማቸው የተመደቡትም ሰዎች ተነስተው እስረኞቹን ወስደው ከመካከላቸው እርቃናቸውን የነበሩትን ሁሉ ከተማረከው ልብስ አለበሷቸው። አጎናጸፉአቸው፤ ጫማም አደረጉላቸው። የሚበሉትን ምግብና የሚጠጡትን ሰጡአቸው። ቁስላቸውን አከሙላቸው፤ የደከሙትንም በአህዮች ላይ አስቀመጧቸው። የዘንባባ ከተማ ተብላ በምትጠራዋ ኢያሪኮ ወዳሉት ቤተሰቦቻቸው መልሰው ወሰዷቸው። ከዚያም ወደ ሰማርያ ተመለሱ። **16** በዚያን ጊዜ ንጉሥ አካዝ እንዲረዱት እንዲጠይቋቸው ወደ አሦርያ ነገሥታት መልዕክተኞችን ላከ። **17** የኤዶምያስ ሰዎች አንድ ጊዜ ደግመው መጥተው ይሁዳን በማጥቃት እስረኞችን ይዘው ወስደው ነበር። **18** ፍልስጤማውያንም የቆላውን ከተሞች እና የይሁዳን ደቡባዊ ክልሎች ወርረው ነበር። ቤት ሳሚስንና ኤሎንን ፥ ግዴሮትንም፥ ሦኮን ከነመንደርዎቿ፥ ተምናን ከነመንደርዎቿ እና ጊምዞን ከነመንደርዎቿ ወስደው ነበር። በእነዚያ ቦታዎችም ውስጥ ለመኖር ሄደው ነበር። **19** በይሁዳ ክፉ ስላደረገና እግዚአብሔርንም እጅግ በጣም ስለበደለ ከእስራኤል ንጉሥ ከአካዝ የተነሳ እግዚአብሔር ይሁዳን ዝቅ ዝቅ አድርጎ ነበር። **20** የአሦርም ንጉሥ ቴልጌልፌልሶር አካዝን በማበርታት ፈንታ መጥቶ አስጨነቆት ነበር። **21** ለሦርያ ነገሥታት የከበሩትን ነገሮች ለመስጠት አካዝ የእግዚአብሔርን ቤት እና የንጉሡንና የመሪዎቹን ቤቶች ዘርፎ ነበር፤ ነገር ግን ይህ አልጠቀመውም። **22** ይኸው ንጉሥ አካዝ በመከራው ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ይበልጥ ኃጢአት ሠራ። **23** ድል ላደረጉት አማልክት ለደማስቆ አማልክት መስዋዕት አቀረበ። "የሦርያ ነገሥታት አማልክት እነርሱን ስለረዷቸው መስዋዕት ባቀርብላቸው እኔንም ይረዱኝ ይሆናል" አለ። ነገር ግን ለእርሱና ለእስራኤል ሁሉ ውድመት ሆኑ። **24** አካዝም የእግዚአብሔርን ቤት እቃዎች ሁሉ በአንድ ላይ ሰብስቦ ሰባበራቸው። የእግዚአብሔርን ቤት በሮች ዘጋ፤ ለራሱም በኢየሩሳሌም በየማዕዘኑ ሁሉ መሰዊያዎችን ሠራ። **25** በይሁዳ ከተሞች ሁሉ ለሌሎች አማልክት መሥዋዕት የሚቃጠልባቸው መስገጃዎችን ሠራ፤ በዚህ መንገድ የአባቶቹን አምላክ እግዚአብሔርን ለቁጣ ቀሰቀሰ። **26** የአካዝ የተቀሩት ድርጊቶቹና መንገዶቹ ሁሉ የመጀመሪያውና የመጨረሻው እነሆ በይሁዳና በእስራኤል ነገሥታት መጽሐፍ ተጽፎአል። **27** አካዝም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ በከተማይቱ በኢየሩሳሌምም ቀበሩት፤ ነገር ግን ወደ እስራኤል ነገሥታት መቃብር አላስገቡትም። ልጁ ሕዝቅያስ በእርሱ ቦታ ነገሠ።

---

2 Chronicles 28:1

ዕድሜ ሃያ ዓመት... አሥራ ስድስት ዓመት
“ዕድሜ 20 ዓመት... 16 ዓመት” (ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ፊት ትክክል የሆነውን ነገር አደረገ
እዚህ ዓይኖች ማየትን ይወክላሉ ፣ እና ማየት ደግሞ ፍርድን ይወክላል ። እግዚአብሔር የአካዝን ሥራ አየ ፣ አልተቀበለውምም ። ይህንን በ 2ኛ ዜና 14 :2 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። ኣት: - “እግዚአብሔር ትክክል እንደ ሆነ የወሰነው” ወይም “እግዚአብሔር ትክክል እንደሆነ የቆጠረው” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

በእስራኤል ነገሥታት መንገድ ሄደ
መሄድ ባህሪን እና ድርጊትን ይወክላል። ኣት: - “የእስራኤል ነገሥታት እንዳደረጉት ሁሉ እርሱ አደረገ ” ወይም “የእስራኤል ነገሥታት እንዳደረጉት እርሱ አደረገ” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 28:3

የቤን ሄኖም ሸለቆ
ይህ በኢየሩሳሌም ያለ ሸለቆ ነው። (የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)

በእስራኤል ልጆች ፊት
እስራኤላውያን ወደ ምድሩ ሲገቡ የተሰደዱት የነዚያ አገራት ሕዝቦች ። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልፅ ሊደረግ ይችላል ። ኣት: - “ከእስራኤል ሕዝብ ቀድመው ወደ ምድሪቱ የገቡት” ወይም “የእስራኤል ሰዎች ወደ ምድሩ ሲጓዙ” (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን :ይመልከቱ)

በኮረብቶች ላይ ባሉት መስገጃዎች ፣ በኮረብቶች ላይና በእያንዳንዱ አረንጓዴ ዛፍ ሥር
እነዚህ የሌሎች አገራት ሕዝቦች የሐሰት አማልክቶቻቸውን ያመለኩባቸው ቦታዎች ናቸው።

በእያንዳንዱ አረንጓዴ ዛፍ ሥር
እግዚአብሔር ህዝቡ በኢየሩሳሌም ቅዱስ መስዋዕትን እንዲያቀርቡ ይፈልግ ነበር ። እዚህ “እያንዳንዱ” የሚለው ቃል ግነት ሲሆን ንጉሥ አካዝ በምትኩ በሌሎች ቦታዎች መስዋዕቶችን በማቅረብ እግዚአብሔርን ላለመታዘዝ ምን ያህል ቆርጦ እንደነበረ የሚያሳይ ነው ። ኣት: - “በብዙ አረንጓዴ ዛፎች ዙሪያ ” ወይም “በአገሪቱ ባሉ ብዙ አረንጓዴ ዛፎች ሥር” (ግነትን እና አጠቃላይን : ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Chronicles 28:5

የአካዝ አምላክ እግዚአብሔር በሶሪያ ንጉሥ እጅ አሳልፎ ሰጠው
እዚህ “እጅ” የሚለው ዘይቤ ኃይልን ይወክላል። የሶርያ ንጉሥ ሠራዊት አካዝንና ሠራዊቱን እንዲያሸንፉ እግዚአብሔር አካዝን በሶርያ ንጉሥ እጅ እንዳስገባው ተደርጎ ተገልጾአል ። ኣት: - “የአካዝ አምላክ እግዚአብሔር የአራም ንጉሥ አካዝን እንዲያሸንፍ አስቻለው” (የባህሪ ስምን እና ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

ከእርሱ ወሰዱ
እዚህ ላይ “እርሱ” የአካንን ሰራዊት ይወክላል ። ኣት: - “ከአካዝ ሰራዊት ተወሰደ ” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

አካዝ እርሱን ድል ባደረገው በእስራኤል ንጉሥ እጅ ታልፎ ተሰጠ
እዚህ “እጅ” የሚለው ዘይቤ ኃይልን ይወክላል። እግዚአብሔር የእስራኤል ንጉሥ እና ሠራዊት አካዝንና ሠራዊቱን እንዲያሸንፍ ስለማስቻሉ እግዚአብሔር አካዝን በእስራኤል ንጉሥ እጅ እንዳስቀመጠው ተደርጎ ተገልጾአል ። ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: “እግዚአብሔርም የእስራኤል ንጉሥ አካዝን እንዲያሸንፍ አስችሎታል” (የባህሪ ስምን፣ ዘይቤያዊን፣ ገቢራዊን እና ተብሮኣዊን :ይመልከቱ)

የሮሜልዩ ልጅ ፋቁሔ
ይህ የእስራኤል ንጉሥ ነበር ። ሁለቱም ‹ፋቁሔ› እና ‹‹ ‹‹ ‹› ›ሮሜልዩ› የሰዎች ስሞች ናቸው ። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

120,000 ወታደሮች
“አንድ መቶ ሀያ ሺህ ወታደሮች” (ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

ዝክሪ... መዕሤያን... ዓዝሪቃም ... ሕልቃና
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው ። (የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)

ኃያል ሰው
ይህ ጀግናን የሚያመላክት ዘይቤያዊ አነጋገር ነው ። ኣት: - “ኃያል ተዋጊ” (ፈሊጥን :ይመልከቱ)

ከንጉሡ ቀጥሎ የነበረው
ይህ ዘይቤያዊ አነጋገር ይህ ሰው የንጉሡ ረዳት ነበር ማለት ሲሆን ከንጉሱ ቀጥሎ ስልጣን ያለው ሰው ነው። ኣት: - “በማዕረግ ከንጉሡ ቀጥሎ ነበር” (ፈሊጥን:ይመልከቱ)

የእስራኤል ጦር ከዘመዶቻቸው ምርኮኛ ወሰደ
“ከወገኖቻቸውም መካከል የእስራኤል ሠራዊት ምርኮኛ ወስደዋል።” “የእነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእስራኤልን ሠራዊት ነው ። ተራኪው የይሁዳ ህዝብ የእስራኤል ሰዎች ዘመዶች እንደሆኑ ይናገራል ።

200,000 ሚስቶች ፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆች
“ሁለት መቶ ሺህ ሚስቶች ወንዶችና ሴቶች ልጆች” (ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 28:9

ዖዴድ
ይህ የሰው ስም ነው ። (የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)

በእጃችሁ አሳልፎ ሰጣቸው
እዚህ “እጅ” የሚለው ቃል ኃይልን ይወክላል ። የእስራኤልን ሠራዊት የይሁዳን ሠራዊት ድል እንዲያደርግ እግዚአብሔር ስለማስቻሉ እግዚአብሔር የይሁዳን ሠራዊት በእስራኤል ሰራዊት እጅ እንዳስገኘ ተደርጎ ተገልጻል ። ኣት: - “እግዚአብሔር እንድታሸንፋቸው አስቻለህ” (የባህሪ ስምን እና ዘይቤያዊን: ይመልከቱ)

ወደ ሰማይ በሚደርስ ቁጣ ገደላችኋቸው።
የእስራኤል ሠራዊት የይሁዳን ሠራዊት የገደለበት ቁጣ እጅግ ትልቅ ከመሆኑ የተነሳ እስከ ሰማይ ድረስ ደርሷል ሲል ዖዴድ ስለ እግዚአብሔር ይናገራል ። ያደረጉትን ሁሉ እግዚአብሔር እንደሚያውቅ ያውቃል እርሱም ምላሽ ይሰጣል ማለት ነው ። ኣት: - “እግዚአብሔር ራሱ አይቶ ይበቀላችሁ ዘንድ በታላቅ ቁጣ ገደላችኋቸው” (ዘይቤያዊን እና የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን :ይመልከቱ)

ነገር ግን አምላካችሁን እግዚአብሔርን የበደላችሁት በደል በእናንተ ዘንድ የለምን?
ዖዴድ የእስራኤልን ሰራዊት ለመገሠጽ እና ጥያቄው የሚጠብቀውን አዎንታዊ መልስ ለማጉላት ይህንን አወያይ መጠይቅ ይጠይቃል ። ኣት: - “ነገር ግን እናንተ ራሳችሁ በአምላካችሁ በእግዚአብሔር ላይ በሠራችሁት ኃጢአት ጥፋተኞች ናችሁ።” (አወያይ መጠይቅን :ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ቁጣ በእናንተ ላይ ነድዶአል
ዖዴድ ስለእግዚአብሔር ከባድ ቁጣ ሲናገር ቁጣው ልክ እንደ አንድ ቁስ በላያቸው ላይ እንደ ሆነ አስመስሎ ተናግሯል። ኣት: - “በአንተ ላይ እግዚአብሔር እጅግ ተቆጥቷል” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 28:12

፤ ዮሓናን ልጅ ዓዛርያስ ፥ የምሺሌሞት ልጅ በራክያ ፤ የሰሎምም ልጅ ይሒዝቅያ እና የሓድላይ ልጅ ዓሜሳይ።
እነዚህ ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው ። (የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)

ከጦርነት በተመለሱት ላይ ተነሱባቸው
“ተነሱባቸው” የሚለው ሐረግ መቃወምን ወይም ፊት ለፊት መጋፈጥን የሚገልጽ ፈሊጥ ነው ። ኣት: - “ከጦርነት የተመለሱትን መጋፈጥ” ወይም “ከጦርነት የተመለሱትን መቃወም” (ፈሊጥን :ይመልከቱ)

ኃጢአት በእኛ ላይ የሚያመጣ ነገር ነው
መሪዎቹ እነርሱን ጭምር ጥፋተኛ እና ኃጢአተኛ የሚያደርጋቸውን ተግባር ስለመፈጸማቸው ሲናገሩ ኃጢአት እንደ አንድ ቁስ በላያቸው ላይ እንደሚመጣ ይናገራሉ ። ኣት: - “ኃጢአተኛ እና በደለኛ የሚያደርገን ነገር ” ተመልከት (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

በእስራኤል ላይ አስፈሪ ቁጣ ሆነ
ይህ ሐረግ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር አስፈሪ ቁጣ በእስራኤል ላይ መሆኑን ነው ። “አስፈሪ ቁጣ ” የሚሉት ቃላት በቃል ሐረግ ሊተረጎሙ ይችላሉ ። አት: - “እግዚአብሔር በእስራኤል ሕዝብ ላይ እጅግ ተቆጣ” (የሚጠበቅ እውቀትን እና የልተገለጸ መረጃን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 28:14

በስም የተመደቡት ወንዶች
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “መሪዎቹ በስማቸው የመደቧቸውን ሰዎች” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

ጫማ
ይህ የጫማ አይነት ነው ።

ደካማዎችን በአህዮች ላይ አስቀመጧቸው
“መራመድ የማይችሉትን በጣም ደካማ የነበሩትን በአህዮች ላይ ተቀምጠው እንዲጓዙ አደረጓቸው”

2 Chronicles 28:16

እነርሱ ቤትሳሚስንና ወሰዱ
ከተማን መውሰድ የሚለው ፈሊጥ ሲሆን ማለት ከተማዋን ማሸነፍ ወይም መያዝ ማለት ነው ። ኣት: - “ፍልስጥኤማውያን የቤትሳሚስን ያዙ” (ፈሊጥን :ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ቤትሳሚስ ፣ ኤሎንን ፣ ግዴሮትን ፣ ሦኮን... ተምናን... ጊምዞን
እነዚህ የቦታዎች ስሞች ናቸው ። (የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)

2 Chronicles 28:19

በአካዝ ምክንያት እግዚአብሔር ይሁዳን አዋረደ
“ይሁዳ” የሚለው አገላለጽ የይሁዳን ሕዝብ ይወክላል ። እግዚአብሔር ሕዝቡን ማዋረዱ በሆነ መንገድ ይሁዳን በአካል ወደ ታች ዝቅ እንዳደረገ ተደርጎ ተገልጻል ። ኣት: “እግዚአብሔር በአካዝ ምክንያት የይሁዳን ሕዝብ አዋረደ” (የባህሪ ስምን እና ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን እጅግ ሰርቶአልና
አካዝ እጅግ ኃጢአትን ስለማድረጉ ሲነገር ኃጢአት በጣም ከባድ ቁስ እንደሆነ ተደርጎ ተገልጻል ። ኣት: - “በእግዚአብሔር ላይ ብዙ ኃጢአትን አደረገ” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

ቴልጌልቴልፌልሶር
ይህ ቴልጌልቴልፌልሶር 3ኛ ሲሆን ፣ ደግሞ ፑል በመባል ይታወቃል። (ተመልከት/ች: የስሞች አተረጓጎም)

እርሱን ከማበረታታት ይልቅ አስጨነቀው
አካዝ ጠላቶቹን እንዲያሸንፍ ማገዝ አካዝን መበረታታት እንደሆነ ተደርጎ ተገልጾአል። ኣት: - “እርሱን ከመርዳት ይልቅ ችግር አመጣበት (ዘይቤያዊን: ይመልከቱ)

2 Chronicles 28:22

በመከራው ጊዜ
“መከራ ሲደርስበት”

የደማስቆ አማልክት
እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም እንደሚያድር ሁሉ፣ ሶርያውያን ደማስቆ የአማልክቶቻቸው መኖሪያ ከተማ እንደ ሆነች ያምናሉ። ኣት: - “ሶርያውያን በደማስቆ ያሚያመልኳቸው አማልክት” (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን :ይመልከቱ)

ያሸነፉጽ አማልክት
ይህ የአካዝን ሀሳብ ያሳያል ። ሶርያውያን እርሱ እና ሠራዊቱን ስላሸነፉ አካዝ ሸንፈቱን ሶርያውያን ለሚያመልኳቸው አማልክት ሰጥቷል ። ኣት: “የሶርያ ሠራዊት የሚያመልኳቸው አማልክት እርሱን እንዲያሸንፉ አስችለዋል” (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን :ይመልከቱ)

እነርሱ ለእርሱና ለእስራኤል ሁሉ ጥፋት ነበሩ
“ጥፋት” የሚለው ቃል በግስ ሊተረጎም ይችላል። ኣት: - “እነዚያ አማልክት እርሱንም ሆነ እስራኤልን ሁሉ አወደሙ” (የረቂቅ ስሞችን :ይመልከቱ)

እስራኤል ሁሉ
እዚህ ላይ “እስራኤል” ደቡባዊውን የይሁዳን መንግሥት ይወክላል ።

2 Chronicles 28:24

የእግዚአብሔር ቤት... የያህዌህ ቤት...
እዚህ “ቤት” የሚለው ቃል ቤተመቅደሱን ይወክላል ። ኣት: - “የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ... የያህዌህ ቤተ መቅደስ” (የባህሪ ስምን : ይመልከቱ)

በኢየሩሳሌም በእያንዳንዱ ማዕዘን
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ማዕዘን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የጎዳና ማዕዘኖችን ወይም ጎዳናዎች የሚገናኙባቸውን ቦታዎች ነው ። ኣት: - “በኢየሩሳሌም ጎዳናዎች ሁሉ ላይ” ወይም 2) የተለያዩ የኢየሩሳሌም አካባቢዎች የከተማዋ ማዕዘኖች እንደሆኑ ተደርገው ተገልጻል ። ኣት: - “በመላው የኢየሩሳሌም ክፍል” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

መሠዊያዎችን ለራሱ ሠራ ... መሥዋዕቶችን ያጥን ዘንድ የኮረብታ መስገጃዎችን ሠራ
አካዝ ንጉሥ ስለነበረ ሠራተኞቹ እነዚህን ከፍ ያሉ ስፍራዎች እንዲሠሩ አድርጎ ይሆናል። ኣት: - “ሠራተኞቹ መሠዊያ እንዲሠሩለት አደረገ... ሠራተኞቹ መሥዋዕቶችን ለማቃጠል ኮሮብታዎችን እንዲሠሩ አደረጋቸው” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 28:26

የፊተኛውና የኋለኛው መንገዶቹ
የአካዝ ድርጊቶች የተጓዘበት መንገድ እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሯል ። “የፊተኛውና እና የኋለኛው” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው እነዚያን ጽንፎች እና በመካከላቸው ያሉትን ነገሮች ሁሉ ነው። ኣት: - “ከንግሥናው መጀመሪያ አንስቶ እስከ ንግሥናው መጨረሻ ድረስ ያደረገውን ሁሉ” (ዘይቤያዊን እና ሜሪዝምን:ይመልከቱ)

እነሆ ፣ በመጽሐፉ ተጽፈዋል ... እስራኤል
“ማንም ሰው መጽሐፉ ላይ ማየት ይችላል... እስራኤልን እና እዚያ እንደተጻፈ ማየት ይቻላል”

እነርሱ በመጽሐፉ ተጽፈዋል
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “አንድ ሰው በመጽሐፉ ውስጥ ጻፋቸው” ወይም “በመጽሐፉ ውስጥ ስነእርሱ ማንበብ ትችላለህ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

የይሁዳና የእስራኤል ነገሥታት መጽሐፍ
ይህ ከእንግዲህ የማይገኝ መጽሐፍ ነው።

አካዝ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ
የአካዝ መሞት ማንቀላፋት እንደሆነ ተደርጎ ተገልጾአል ። ኣት: “አካዝ ሞተ” (ዘይቤያዊን እና ዘወርዋራን :ይመልከቱ)

ቀበሩት
“ሰዎች ቀበሩት”

በእርሱ ቦታ ነገሠ
“በእርሱ ቦታ” የሚለው ሐረግ ዘይቤያዊ አገላለጽ “በእርሱ ፋንታ” የሚል ትርጉም አለው ። “በአካዝ ፋንታ ነገሠ” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 29

1 ሕዝቅያስ መንገሥ በጀመረ ጊዜ ሃያ አምስት ዓመቱ ነበር፤ በኢየሩሳሌምም ሃያ ዘጠኝ ዓመት ነገሠ። የእናቱ ስም አቡ ነበር፤ የዘካርያስ ልጅ ነበረች። 2 በማንኛውም ነገር የዝርያውን የዳዊትን ምሳሌ ተከትሎ በእግዚአብሔር ፊት ትክክለኛውን ነገር አደረገ። 3 በነገሠም በመጀመሪያው ዓመት በመጀመሪያው ወር የእግዚአብሔርን ቤት በሮች ከፈተ፤ አደሳቸውም። 4 ካህናቱንና ሌዋውያኑን አምጥቶ በምሥራቅ በኩል ባለው አደባባይ ላይ በአንድነት ሰበሰባቸው። 5 "እናንተ ሌዋውያን ሆይ ስሙኝ! ራሳችሁን ለእግዚአብሔር ቀድሱ፤ የአባቶቻችሁን አምላክ የእግዚአብሔርንም ቤት ቀድሱ፤ ከተቀደሰው ሥፍራም ርኩሱን ነገር ሁሉ አስወግዱ" አላቸው። 6 አባቶቻችን ሕጉን ስለተላለፉና በአምላካችን በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገር ስላደረጉ፥ እርሱንም ትተውታል፤ ፊታቸውንም እግዚአብሔር ከሚኖርበት ሥፍራ መልሰዋል፤ ጀርባቸውንም ሰጥተውታል። 7 የበሮቹንም በረንዳዎች ዘግተዋል፤ መብራቶቹንም አጥፍተዋል። ለእስራኤል አምላክ በተቀደሰው ሥፍራ እጣን አላጠኑም ወይም የሚቃጠለውንም መስዋዕት አላቀረቡም። 8 ስለዚህ የእግዚአብሔር ቁጣ በይሁዳና በኢየሩሳሌም ላይ ወረደ፤ በገዛ ራሳችሁ ዓይኖች ማየት እንደምትችሉት ለሽብር፥ ለድንጋጤና ለመዘበቻም ማረፊያ አደረጋቸው። 9 ለዚህ ነው አባቶቻችን በሰይፍ የወደቁት፤ ለዚህም ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችን ሚስቶቻችንም በምርኮ ውስጥ አሉ። 10 አሁንም የጋለ ቁጣው ከእኛ እንዲመለስ ከእስራኤል አምላክ ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን ለማድረግ በልቤ አስቤአለሁ። 11 ልጆቼ እግዚአብሔር በፊቱ ትቆሙ፥ ታመልኩትና፥ አገልጋዮቹ ልትሆኑና ዕጣንን ልታጥኑለት ስለመረጣችሁ አሁን ታካች አትሁኑ። 12 ከዚያም ሌዋውያኑ የቀዓት ሰዎች የአሚሳ ልጅ መሐትና የዓዛርያስ ልጅ ኢዮኤል፥ የሜራሪ ሰዎች የአብዲ ልጅ ቂስና የይሃሌልኤል ልጅ ዓዛርያስ፥ የጌድሶን ሰዎች የዛማት ልጅ ዮአክና የዮአክ ልጅ ዔድን፥ 13 የኤሊጸፋንም ልጆች ሺምሪና ይዒኤል፥ የአሳፍም ልጆች ዘካርያስና መታንያ፥ 14 የኤማንም ልጆች ይሒኤልና ሰሜኢ፥ የኤዶታምም ልጆች ሸማያና ዑዝኤል ተነሡ። 15 ወንድሞቻቸውን ሰብስበው ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ቀደሱ፤ የእግዚአብሔርን ቃል በመከተል ንጉሡ እንዳዘዘው የእግዚአብሔርን ቤት ለማንጻት ወደ ውስጥ ገቡ። 16 ካህናቱም የእግዚአብሔርን ቤት ለማንጻት ወደ ውስጠኛው ክፍል ገቡ፤ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውስጥ ያገኙትን ቆሻሻ ነገር ሁሉ ወደ ቤቱ አደባባይ አወጡት። ሌዋውያንም ወደ ቄድሮን ሸለቆ ተሸክመው ሊወስዱት አወጡት። 17 ቤቱን ለእግዚአብሔር መቀደስን በመጀመሪያው ወር በመጀመሪያው ቀን ጀምረው በወሩ በስምንተኛው ቀን ወደ እግዚአብሔር በረንዳ ደረሱ። የእግዚአብሔርን ቤት በስምንት ቀናት ቀደሱ። በመጀመሪያው ወር በአሥራ ስድስተኛው ቀን ጨረሱ። 18 ከዚያም ወደ ንጉሡ ወደ ሕዝቅያስ ቤተ መንግሥት ውስጥ ገብተው፦" የእግዚአብሔርን ቤት፥ የሚቃጠል መስዋዕት የሚቀርብበትን መሠውያ ከዕቃዎቹ ሁሉ ጋር እና የመገኘቱን ሕብስት ገበታ ከዕቃዎቹ ሁሉ ጋር አንጽተናል። 19 በተጨማሪም ንጉሥ አካዝ ነግሦ በነበረበት ጊዜ በመተላለፍ የወረወራቸውን ዕቃዎች ሁሉ አዘጋጅተን ለእግዚአብሔር ቀድሰናል። እነሆ በእግዚአብሔር መሠዊያ ፊት ለፊት ይገኛሉ" አሉት። 20 ከዚያም ንጉሡ ሕዝቅያስ በማለዳ ተነስቶ የከተማዋን መሪዎች ሁሉ ሰበሰበ፤ ወደ እግዚአብሔርም ቤት ወጣ። 21 ለመንግሥቱ፥ ለቤተ መቅደሱና ለይሁዳ የኃጢአት መስዋዕት አድርገው ሰባት ወይፈኖች፥ ሰባት አውራ በጎችና ሰባት የበግ ጠቦቶችና ሰባት ወንድ ፍየሎች አመጡ። ካህናቱን የአሮንን ልጆች በእግዚአብሔር መሠዊያ ላይ እንዲያቀርቧቸው አዘዛቸው። 22 በመሆኑም ወይፈኖቹን አረዷቸውና ካህናቱ ደሙን ተቀብለው በመሠዊያው ላይ ረጩት። አውራ በጎቹንም አረዱ፤ ደሙንም በመሠዊያው ላይ ረጩት፤ የበግ ጠቦቶቹንም አረዱ፤ ደሙንም በመሠዊያው ላይ ረጩት። 23 ለኃጢአት መስዋዕት ወንድ ፍየሎቹን በንጉሡና በጉባዔው ፊት አመጧቸው፤ እጃቸውንም ጫኑባቸው። 24 ካህናቱም አረዷቸው፤ ንጉሡም ለእስራኤል ሁሉ የሚቃጠል መስዋዕትና የኃጢአት መስዋዕት ሊደረግ እንደሚገባው አዝዞ ስለነበር ለእስራኤል ሁሉ ለማስተሰረይ በመሠዊያው ላይ ደማቸውን የኃጢአት መስዋዕት አደረጉት። 25 ሕዝቅያስ ትዕዛዙ በነቢያቱ አማካይነት ከእግዚአብሔር ስለ ነበር በዳዊትና በንጉሡ ባለ ራዕይ በጋድ፥ በነቢዩ ናታንም ትዕዛዝ ሌዋውያኑን ከጽናጽል፥ ከበገናና ከመሰንቆ ጋር በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ አደራጅቶ አስቀመጣቸው። 26 ሌዋውያኑም ከዳዊት የሙዚቃ መሣሪያዎች ጋርና ካህናቱ ከመለከቶች ጋር ቆሙ። 27 ሕዝቅያስም የሚቃጠለውን መሥዋዕት በመሠዊያው ላይ እንዲያቀርቡ አዘዛቸው። የሚቃጠለውን መሥዋዕት ማቅረብ ሲጀመር የእግዚአብሔር መዝሙርም በመለከቶችና በእስራኤል ንጉሥ በዳዊት የሙዚቃ መሣሪያዎች ተጀመረ። 28 ጉባዔውም ሁሉ አመለኩ፤ መዘምራኑም ዘመሩ፤ መለከቶቹም ተነፉ፤ የሚቃጠለውን መሥዋዕት ማቅረብ እስኪፈጸም ድረስ ይህ ሁሉ ቀጠለ። 29 መስዋዕት ማቅረቡን በፈጸሙ ጊዜ ንጉሡና ከእርሱ ጋር የነበሩት ሁሉ አጎነበሱ፤ ሰገዱም። 30 በተጨማሪም ንጉሡ ሕዝቅያስና መሪዎቹ ሌዋውያኑ በዳዊትና በባለራዕዩ በአሳፍ ቃል ለእግዚአብሔር ውዳሴ እንዲዘምሩ አዘዙ። በደስታም ውዳሴዎችን ዘመሩ፤ አጎነበሱ፤ ሰገዱም። 31 ከዚያም ሕዝቅያስ፦"አሁን ራሳችሁን ለእግዚአብሔር ቀድሳችኋል። ወደዚህ መጥታችሁ ለእግዚአብሔር ቤት መሥዋዕቱንና የምስጋና መሥዋዕቱን አቅርቡ" አላቸው። ጉባዔውም መሥዋዕቱንና የምስጋና መሥዋዕቱን አቀረቡ፤ ፈቃደኛ ልብ የነበራቸውም ሁሉ የሚቃጠል መሥዋዕት አቀረቡ። 32 ጉባዔው ያቀረቡት የሚቃጠል መሥዋዕት ቁጥር ሰባ ወይፈን፥ አንድ መቶ አውራ በጎችና ሁለት መቶ ወንድ ጠቦቶች ነበሩ። እነዚህ ሁሉ ለእግዚአብሔር የሚቃጠል መሥዋዕት ነበሩ። 33 ለእግዚአብሔር የተቀደሱት እንስሳት ስድስት መቶ በሬዎችና ሦስት ሺህ በጎች ነበሩ። 34 ነገር ግን ካህናቱ የሚቃጠሉትን መሥዋዕት ሁሉ ለመግፈፍ እጅግ ጥቂት ነበሩ፤ በመሆኑም ወንድሞቻቸው ሌዋውያኑ ሥራው እስኪጠናቀቅ ድረስ፥ ሌዋውያኑም ከካህናቱ ይልቅ ራሳቸውን ለመቀደስ ይበልጥ ጥንቁቅ ስለ ነበሩ ካህናቱ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር እስኪቀድሱ ድረስ ረዷቸው። 35 በተጨማሪም እጅግ ብዙ የሚቃጠሉ መሥዋዕቶች ነበሩ፤ ከሕብረት መሥዋዕት ስብ ጋር ይከናወኑም ነበር፤ ለእያንዳንዱም የሚቃጠል መሥዋዕት የመጠጥ መሥዋዕትም ነበር። በመሆኑም የእግዚአብሔር አገልግሎት በደንብ ተደራጅቶ ነበር። 36 እግዚአብሔር ለሕዝቡ ካዘጋጀው ነገር የተነሳ ሥራው በፍጥነት በመከናወኑ ሕዝቅያስ ሕዝቡም ሁሉ ደስ አላቸው።

---

2 Chronicles 29:1

ዕድሜ ሃያ - አምስት ዓመት ... ሃያ ዘጠኝ ዓመት
“ዕድሜ 25 ዓመት... 29 ዓመት” (ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

አቡ
ይህ የሴት ስም ነው። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ፊት ትክክል የሆነውን ነገር አደረገ
እዚህ “ዐይን” የሚለው ቃል ማየትን የሚወክል ሲሆን ማየት ደግሞ ፍርድን ይወክላል :: እግዚአብሔር የሕዝቅያስን ተግባር አየ አጸደቀውም። በ 2 ኛ ዜና 14 :1 ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት :: ኣት: - “እግዚአብሔር ትክክል እንደ ሆነ የወሰነው” ወይም “እግዚአብሔር ትክክል እንደሆነ ያሰበው” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 29:3

በመጀመሪያው ወር
ይህ በዕብራይስጥ የቀን አቆጣጠር የመጀመሪያ ወር ነው። እንደ ምዕራባዊያን የቀን አቆጣጠር ወቅቱ የመጋቢት የመጨረሻ ክፍል እና የሚያዚያ የመጀመሪያ ክፍል ነው። (የዕብራዊያንን ወራት እና ሕገኛ ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የእግዚአብሔር ቤት
እዚህ “ቤት” የሚለው ቃል ቤተመቅደሱን ይወክላል ። ኣት: - “ያእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

ሕዝቅያስ በሮቹን ከፈታቸው አደሳቸውም
ሕዝቅያስ ንጉሥ ስለነበረ ሠራተኞቹ እነዚህን ነገሮች እንዲሠሩ አድርጎ ይሆናል። ኣት: “ሕዝቅያስ ሠራተኞቹን በሮቹን እንዲከፍቱ እና እንዲጠግኗቸው አዘዘ” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

በምሥራቅ በኩል
ይህ የቤተ መቅደሱን ምስራቅ ያመለክታል ። ኣት: - “በቤተ መቅደሱ በስተ ምሥራቅ” (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን :ይመልከቱ)

ርኩሰን ነገር ሁሉ ከቅዱሱ ቦታ አስወግዱ
“ርኩሰት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ህዝቡ ሌሎች አማልክትን ሲያመልኩ የጠቀሙባቸውን የነበሩትን ነገሮች ነው ። ተራኪው ስለ እነዚህ ነገሮች ሲናገር መቅደሱ ከመቆሸሹ የተነሳ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንደሌለው ይናገራል። ኣት: - “የተቀደሰውን ሥፍራ የሚያረክሱትን ነገሮችን አስወግዱ” ወይም “የተቀደሰው ስፍራ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዲያጣ የሚያደርጉትን ነገሮች አስወግዱ” (ዘይቤያዊን:ይመልከቱ)

2 Chronicles 29:6

በአምላካችን በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነውን ነገር
እዚህ “ፊት” የሚለው ቃል ፍርድን ይወክላል ። እግዚአብሔር የአባቶቻቸውን ተግባር አይቷል እናም አልተቀበለውም። ኣት: - “አምላካችን እግዚአብሔር ክፉ እንደሆነ የወሰነው” ወይም “አምላካችን እግዚአብሔር ክፉ እንደሆነ የቆጠረው” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ከሚኖርበት ስፍራ ፊታቸውን አዞሩ፣ ወደ እርሷም ጀርባቸውን አዙረዋል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው ። “ፊቶች” እና “ጀርባዎች” የሚሉት ቃላት ፊቶቻቸው ከቤተ መቅደሱ ያርቁ እና ጀርባዎቻቸውን ወደዚያ ያዞሩ የነበሩትን ሰዎች ይወክላሉ ። ኣት: - “እግዚአብሔር ከሚኖርበት ስፍራ መራቅ” (ምስስልን እና ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን : ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ከሚኖርበት ስፍራ ፊታቸውን አዞሩ፣ ወደእርሷም ጀርባቸውን አዞሩ
የሕዝቡ እግዚአብሔርን ማምለክ መተው ከቤተመቅደስ መራቅ እንደሆነ ተደርጎ ተገልጻል ። ኣት: - “የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ተዉ እርሱንም ማምለክ አቆመ” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

እግዚአብሔር የሚኖርበት ስፍራ
ይህ ቤተመቅደሱን ያመለክታል ። ኣት: - “እግዚአብሔር የሚኖርበት ቤተ መቅደስ” (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 29:8

የእግዚአብሔርም ቁጣ በይሁዳና በኢየሩሳሌም ላይ ወደቀ
እዚህ “ይሁዳ እና ኢየሩሳሌም” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት በዚያ ለሚኖሩት ሰዎች ነው ። በሕዝቅያስ እግዚአብሔር ሕዝቡን ስለመቆጣቱ ሲናገር ቁጣው በላያቸው እንደ አንድ ነገር እንደ ወረደ አድርጎ ተናግሯል። ኣት: - “እግዚአብሔር ስለተቆጣ የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ይቀጣ ነበር” (የባህሪ ስምን እና ዘይቤያዊን:ይመልከቱ)

ለድንጋጤ፣ ለማስፈራሪያ እና ለመዘበቻ
ይህ በቃል ሐረጎች ሊተረጎም ይችላል። ኣት: - “ሰዎችን የሚያሳቅቅ እና የሚያስፈራ ፣ እና ሰዎች ያሚያፌዙበት ነገር” (የረቂቅ ስሞችን :ይመልከቱ)

በገዛ ዓይንህ እንደምታይ
“በገዛ ዐይንህ” የሚለው ሐረግ ሰዎች ነጋሪ ሳያስፈልጋቸው ይህንን ለራሳቸው ማየት የሚችሉ መሆኑን ያሳያል ። ኣት: - “ለራስህ እንደምታየው”

አባቶቻችን በሰይፍ ወድቀዋል
“በሰይፍ ወድቋል” የሚለው አገላለጽ በጦርነት ውስጥ መሞት ማለት ነው። “ሠይፍ” የሚለው ቃል ሰይፍን ዋና መሣሪያቸው አድርገው ይጠቀሙባቸው የነበሩትን ወታደሮች ይወክላል ። ኣት: - “አባቶቻችን በጦርነት ሞተዋል” (ፈሊጥን እና የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 29:10

ይህ በልቤ ውስጥ ነው
እዚህ “ልብ” የሚለው ቃል ሀሳቦችን እና ዝንባሌዎችን ይወክላል ። ሕዝቅያስ ውሳኔ ስለ መወሰን ተናግሯል ያ ነገር በልቡ ውስጥ ያለ ይመስል ነበር። ኣት: - “ዓላማዬ ነው” ወይም “እኔ ወስኛለሁ” (የባህሪ ስምን እና ዘይቤያዊን : ይመልከቱ)

የቁጣ ጽናት ከእኛ ይርቃል
ሕዝቅያስም እግዚአብሔር ከእንግዲህ ወዲያ እንደማይቆጣቸው ሲናገር የእግዚአብሔር ቁጣ ከእነርሱ ዞር እንደሚመለስ ሰው አስመስሎ ተናግሯል ፣ ‹ከእንግዲህ በእኛ ላይ አይቆጣም› (ዘይቤያዊን እና ተስብኦትን :ይመልከቱ)

በፊቱ መቆም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “በመገኘቱ መቆም” ወይም 2) ይህ ፈሊጥ ሲሆን ፣ ከፍተኛ ስልጣን ያለውን ሰው ማገልገል ማለት ነው። ኣት: - “እርሱን ማገልገል” (ፈሊጥን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 29:12

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ቁጥሮች ሕዝቅያስ ያዘዘውን ሥራ መሥራት የጀመሩ የሌዋውያንን ስሞች ይዘረዝራሉ ። እነዚህ ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው። (የስሞችን አተረጓጎም፡ ይመልከቱ)

ሌዋውያኑ ተነሱ
እዚህ “ተነስቷል” የሚለው ቃል ፈሊጥ ሲሆን ሌዋውያን እርምጃ መውሰድ ጀመሩ ማለት ነው ። ኣት: - “ሌዋውያኑ መሥራት ጀመሩ” (ፈሊጥን : ይመልከቱ)

2 Chronicles 29:15

የእግዚአብሔርን ቃል በመከተል
ይህ ሐረግ ንጉሡ የእግዚአብሔርን ቃል በመታዘዝ ተዕዛዝ እንደሰጠ ያሳያል ። ኣት: - “ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ” ወይም “እግዚአብሔር ስለተናገረ”

የእግዚአብሔርን ቤት ያነጻ ዘንድ
ለእግዚአብሔር አገልግሎት ተስማሚ ስለሆን ቦታ በአካል ንፁህ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል ። (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ቤት ... የቤቱ አደባባይ
እዚህ “ቤት” የሚለው ቃል ቤተመቅደሱን ይወክላል ። ኣት: - “የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ……የቤተ መቅደሱ አደባባይ (የባህሪ ስምን : ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር መቅደስ ያገኙትን እርኩስ ነገር ሁሉ አወጡ
“ርኩስ” የሚለው ቃል ህዝቡ ሌሎች አማልክትን ለማምለክ ይጠቀሟቸው የነበሩትን እቃዎች የመለከታል ። ተራኪው ስለ እነዚህ ሲናገር ቤተመቅደሱን አንዳቆሸሹት እና ለእግዚአብሔር ተገቢ እንዳይሆን እንዳደረጉት ይናገራል ። ኣት: “በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ያገኙትን ርኩስ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ አወጡ” ወይም “ቤተ መቅደሱ ለእግዚአብሔር ተስማሚ እንዳይሆን ያደረጉትን ነገሮች ሁሉ አወጡ” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ቄድሮን ወንዝ
ከኢየሩሳሌም በስተ ምሥራቅ አቅጣጫ የሚፈስ ትንሽ የውሃ አካል ነው። አንዳንድ ጊዜ እንደ ቆሻሻ መጣያ ያገለግላል። (የስሞችን አተረጓጎም : ይመልከቱ)

በመጀመሪያው ወር በመጀመሪያው ቀን
ይህ የዕብራይስጥ የቀን አቆጣጠር የመጀመሪያ ወር ነው። የመጀመሪያው ቀን እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብፅ ያወጣበት ቀን ነው። ይህ በምዕራባዊያን የቀን መቁጠሪያ ላይ በመጋቢት አጋማሽ አካባቢ ነው። (የዕብራዊያን ወራት እና ሕገኛ ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

በዚያም ወር በስምንተኛው ቀን
ይህ በምዕራባዊያን የቀን መቁጠሪያዎች ላይ በመጋቢት መጨረሻ አካባቢ ነው። (የዕብራዊያን ወራትን እና ሕገኛ ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

ወደ እግዚአብሔር ቤት ወለል ደረሱ
“የእግዚአብሔር ቤት ወለል” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው የቤተ መቅደሱን በረንዳ ነው። “ደረሱ” ማለት ይህንን ክፍል ማጽዳት ጀመሩ ማለት ነው ። ኣት: - “የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ በረንዳ ማንጻት ጀምረው ነበር” (የባህሪ ስምን እና ፈሊጥን :ይመልከቱ)

በመጀመሪያው ወር በአሥራ ስድስተኛው ቀን
ይህ በምእራባዊያን የቀን መቁጠሪያዎች ላይ በሚያዝያ ወር መጀመሪያ አካባቢ ነው። (የዕብራዊያን ወራትን እና ሕገኛ ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 29:18

የገጹንም ጎብስት
ይህ በመሠዊያው ፊት ለፊት ስለተቀመጡት 12 ዳቦዎች የሚያሳይ ነው ። በ 2 ኛ ዜና 2 :4 ውስጥ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ።

እነሆም ፣ ሆነዋል
ተመልከታቸው። ማየት ትችላለህ እነዚሁና”

2 Chronicles 29:20

የእግዚአብሔር ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል ቤተመቅደሱን ይወክላል ። ኣት: - “የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 29:22

በሬዎቹንም አርደው ካህናቱ ደሙን ተቀበሉ
“ካህናቱ ወይፈኖችን አርደው ደሙን ወሰዱ”

እጃቸውን ጫኑባቸው
“ንጉሡና ማኅበሩ ሁሉ እጃቸውን ጫኑባቸው”

የሚቃጠል መሥዋዕት የኃጢአት መሥዋዕት ለእስራኤል ሁሉ እንዲደረግ
ይህ በገቢራዊ አረፍተነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ካህናቱ የሚቃጠለውን መሥዋዕትና የኃጢአትን መሥዋዕት ለእስራኤል ሁሉ ያድርጉ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 29:25

የእግዚአብሔር ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል ቤተመቅደሱን ይወክላል ። ኣት: - “የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

ጸናጽል
ከፍተኛ ድምጽ ለመስራት አንድ ላይ የሚመቱ ሁለት ቀጭን እና ክብ የብረት ሳህኖች። በ 2 ኛ ዜና 5 :12 ውስጥ ይህንን እንዴት እንደተረጉምከው ተመልከት ። (የማይታወቁትን :ይተርጉሙ)

በዳዊት ትእዛዝ ፣በንጉሡ ባለራእይ እንደ ጋድ፣ በነቢዩ በናታን ትእዛዝ አደራጁ
“ትዕዛዙ” የሚለው ቃል በቃላት ሐረግ ሊተረጎም ይችላል። ኣት: - “ዳዊት ፣ የንጉሡ ባለ ራእይና ፣ነብዩ ናታን እንዳዘዙት ሌዋውያንን ማደራጀት” (የረቂቅ ስሞችን :ይመልከቱ)

ትእዛዙ ከእግዚአብሔር ዘንድ በነቢያቱ አማካኝነት
“ትዕዛዙ” የሚለው ቃል በቃላት ሐረግ ሊተረጎም ይችላል።ኣት: - “እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካኝነት ይህን አእዛዝ ኣዞ ነበርና” (የረቂቅ ስሞችን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 29:27

የእግዚአብሔር መዝሙር ደግሞ ተጀመረ
“የእግዚአብሔር መዝሙ” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ለእግዚአብሔር መዝሙር የሚዘምሩ ሰዎችን ነው ። ኣት: - “ሕዝቡም ለእግዚአብሔር ያዜሙ ጀመር”

የሚቃጠለው መስዋዕት እስኪፈጸም ድረስ
ይህ በገቢራዊ አረፍተነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: “ካህናቱ የሚቃጠለውን መስዋዕት እስኪፈጽሙ ድረስ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 29:29

መባዎቹን በፈጸሙ ጊዜ
“ካህናቱ መባዎቹን ማቅረብ በጨረሱ ጊዜ”

አጎነበሱ ሰገዱም
የአምልኮ ሃሳብ በትርጉሙ ታክሎ ሊቀርብ ይችላል ። ኣት: “በስግደት እግዚአብሔርን አመለኩ” (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን : ይመልከቱ)

2 Chronicles 29:31

የምስጋናውን መሥዋዕት
እነዚህ የምስጋና መባዎች ነበሩ ።

የእግዚአብሔር ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል ቤተመቅደሱን ይወክላል ። ኣት: - “የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

ፈቃደኛ ልብ ያለው
እዚህ “ልብ” የሚለው ቃል ፈቃደኛ የሆነን ሰው ይወክላል ። ኣት: - “ፈቃደኛ የሆኑት” ወይም “የፈለጉት”(ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን : ይመልከቱ)

2 Chronicles 29:32

ሰባ ወይፈን አንድ መቶ አውራ በጎች እና ሁለት መቶ ወንድ ጠቦቶች ... ስድስት መቶ በሬዎች ሦስት ሺህ በጎች
“70 ወይፈን ፣ 100 አውራ በጎች ፣ 200 ወንድ የበግ ጠቦቶች... 600 በሬዎችና ፣3000 በጎች” (ተመልከት/ች: ቁጥሮች)

2 Chronicles 29:34

የሚቃጠለውን መባ ሁሉ ለመግፈፍ
“የሚቃጠለውን መስዋዕት ለመግፈፍ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ስራው እስኪከናወን ድረስ
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ሥራውን እስኪያጠናቅቁ ድረስ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ይመልከቱ)

ካህናቱ ራሳቸውን እስኪቀድሱ ድረስ
ቀደም ብለው የተቀደሱ ካህናት ስለነበሩ ይህ የሚያመለክተው ተጨማሪ ካህናትን ራሳቸውን እንደቀደሱ ። ኣት: - “በርካታ ካህናቱ ራሳቸውን እስኪቀድሱ ድረስ” (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን ፡ ይመልከቱ)

እራሳቸውን ለመቀደስ የበለጠ ይጠነቀቁ ነበሩ
ራሳቸውን ለመቀደስ ጠንቃቃ ስለነበሩ ይህንን ሥራ የሚሠሩ በቂ ሌዋውያን ነበሩ ። ይህ የሚያመለክተው በቂ ካህናት ያልነበሩት ካህናቱ ራሳቸውን ለመቀደስ ጥንቃቄ ስለማያደርጉ ነበር ።

2 Chronicles 29:35

ከኅብረት መስዋዕት ስብ ጋር ተሠርተው ቀረቡ
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። ኣት: - “ካህናቱ የሚቃጠለውን መሥዋዕት ከኅብረት መስዋዕት ስብ ጋር አቀረቡ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን:ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ቤት አገልግሎት ተዘጋጀ
ይህ በገቢራዊ አረፈተ ነገር ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: “ሕዝቅያስ የእግዚአብሔርን ቤት አገልግሎት አዘጋጀ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን፡ ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል ቤተመቅደሱን ይወክላል ። ኣት: - “የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ” (የባህሪ ስምን:ይመልከቱ)

በሥርዓት ተዘጋጅቷል
ይህ ፈሊጥ ሲሆን ተደራጅቶ የተዘጋጀ ነገር ማለት ነው ። እዚህ በቤተመቅደስ ውስጥ እንደገና የሚጀምረውን የክህነት አገልግሎት ያመለክታል ። ኣት: - “ተመልሷል” ወይም “እንደገና ተጀመረ” (ፈሊጥን ፡ይመልከቱ)

ሥራው በፍጥነት ተሠራ
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ሕዝቡ በፍጥነት ሥራውን አከናውነዋል” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን:ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 30

1 ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር የፋሲካን በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም ወደ እግዚአብሔር ቤት እንዲመጡ ሕዝቅያስ ወደ እስራኤልና ይሁዳ ሁሉ
መልዕክተኞችን ላከ፤ ወደ ኤፍሬምና ምናሴም ደብዳቤዎችን ጻፈ። 2 ንጉሡ፥ መሪዎቹና የኢየሩሳሌሙ ጉባዔ ሁሉ በአንድነት ከተመካከሩ በኋላ ፋሲካውን
በሁለተኛው ወር ለማክበር እየወሰኑ ነበር። 3 ካህናቱ በበቂ ቁጥር ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ስላልቀደሱና ሕዝቡም ገና ወደ ኢየሩሳሌም በአንድነት
ስላልተሰበሰበ ወዲያውኑ በዓሉን ሊያከብሩ አልቻሉም ነበር። 4 ይህ እቅድ በንጉሡና በጉባዔው ሁሉ ፊት መልካም ሆኖ ታይቶ ነበር። 5 በመሆኑም በመላው
እስራኤል ከቤርሳቤህ እስከ ዳን የእስራኤልን አምላክ የእግዚአብሔርን ፋሲካ በዓል በኢየሩሳሌም ለማክበር ሕዝቡ እንዲመጡ አዋጅ እንዲነገር ድንጋጌ
አወጡ። በእርግጥም በጽሑፍ እንደታዘዘው በብዙ ቁጥር አላከበሩትም ነበር። 6 በንጉሡ ትእዛዝ መልዕክተኞች ወደ መላው ይሁዳና እስራኤል ሁሉ የንጉሡንና
የመሪዎቹን ደብዳቤ ይዘው ሄዱ። "እናንተ የእስራኤል ሰዎች ከአሦር ነገሥታት እጅ ወዳመለጠው ቅሬታችሁ እንዲመለስ ወደ አብርሃም፥ ይስሐቅና እስራኤል
አምላክ ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ። 7 እንደምታዩት ለጥፋት አሳልፎ እስኪሰጣቸው ድረስ በአባቶቻቸው አምላክ በእግዚአብሔር ላይ እንደተላለፉት እንደ
አባቶቻችሁ ወይም ወንድሞቻችሁ አትምሰሉ። 8 አሁንም አባቶቻችሁ እንደነበሩት እናንተም አንገተ ደንዳና አትሁኑ። ይልቁንም ራሳችሁን ለእግዚአብሔር ስጡና
የጋለ ቁጣው ከእናንተ እንዲመለስ አምላካችሁን እግዚአብሔርን ለማምለክ ለዘላለም ለእግዚአብሔር ወደ ተሰጠው ቅዱስ ሥፍራው ኑ! 9 አምላካችሁ
እግዚአብሔር ቸርና መሐሪ ስለሆነ ወደ እርሱ ብትመለሱ ፊቱን ከእናንተ ስለማይመልስ ወደ እግዚአብሔር ብትመለሱ ወንድሞቻችሁና ልጆቻችሁ እንደ እስረኛ
በወሰዷቸው ሰዎች ፊት ሃዘኔታ ያገኛሉ። ወደዚህችም ምድር ይመለሳሉ። 10 በመሆኑም መልዕክተኞቹ እስከ ዛብሎን ድረስ በመላው የኤፍሬምና የምናሴ
ክልሎች ሁሉ ከከተማ ወደ ከተማ አለፉ፤ ሕዝቡ ግን ሳቁባቸው፤ አፌዙባቸውም። 11 ነገር ግን የተወሰኑ የአሴርና የምናሴ የዛብሎንም ሰዎች ራሳቸውን
አዋርደው ወደ ኢየሩሳሌም መጡ። 12 በእግዚአብሔር ቃል የንጉሡንና የመሪዎቹን ትዕዛዝ ለመፈጸም አንድ ልብ ሊሰጣቸው የእግዚአብሔር እጅ በይሁዳ ላይም
መጣ። 13 በሁለተኛው ወር የቂጣውን በዓል ለማክበር ብዙ ሰዎች፥ እጅግ ታላቅ ጉባዔ ለማክበር በኢየሩሳሌም ተሰበሰቡ። 14 ተነስተው በኢየሩሳሌም
የነበሩትን መሠዊያዎችና ለጣዖታት የሚያጥኑበትን ማጠኛዎች ሁሉ አስወገዱ፤ ወደ ቄድሮን ወንዝም ጣሉአቸው። 15 ከዚያም በሁለተኛው ወር በአሥራ
አራተኛው ቀን የፋሲካውን ጠቦቶቹን አረዱ። ካህናቱና ሌዋውያኑ አፍረው ነበርና ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ሰጡ። ወደ እግዚአብሔርም ቤት የሚቃጠል
መሥዋዕት አመጡ። 16 በእግዚአብሔር ሰው በሙሴ ሕግ የተሰጠውን መመሪያ በመከተል በየሥራ ክፍላቸው በቦታቸው ቆሙ፤ ካህናቱም ከሌዋውያኑ እጅ
የተቀበሉትን ደም ይረጩ ነበር። 17 በጉባዔው ውስጥ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ያልሰጡ እጅግ ብዙ ነበሩ፤ ስለዚህ ሌዋውያን ለእግዚአብሔር ጠቦቶቹን
ለእግዚአብሔር ለመቀደስ ነጽተው ላልነበሩት ሰዎች ሁሉ የፋሲካውን ጠቦቶች የማረዱ ኃላፊነት የእነርሱ ነበር። 18 እጅግ ብዙ ሰዎች ብዙዎቹም ከኤፍሬምና
ከምናሴ፥ ከይሳኮርና ከዛብሎን በሕጉ መሠረት ራሳቸውን አላነጹም ነበር፤ ነገር ግን እንደ ተጻፈው ትዕዛዝ ባይሆንም የፋሲካውን ምግብ በሉ፤ ሕዝቅያስም ፦"
ምንም እንኳን እንደ ቅዱሱ ሥፍራ የመንጻት መለኪያ መሠረት የነጻ ባይሆንም 19 የአባቶቹን አምላክ እግዚአብሔር አምላክን ለመፈለግ በልቡ የቆረጠውን ሰው
ሁሉ ቸሩ እግዚአብሔር ይቅር ይበለው" በማለት ፀልዮላቸው ነበር። 20 እግዚአብሔርም ሕዝቅያስን ሰማው፤ ሕዝቡንም ፈወሰ። 21 በኢየሩሳሌምም ተገኝተው
የነበሩ የእስራኤል ሰዎች በታላቅ ደስታ የቂጣውን በዓል ለሰባት ቀናት አከበሩ። ሌዋውያኑና ካህናቱም ድምጹ በጎላ የሙዚቃ መሣሪያ ለእግዚአብሔር በመዘመር
ከእለት ወደ እለት እግዚአብሔርን ያወድሱ ነበር። 22 ሕዝቅያስም ለእግዚአብሔር የሚሰጠውን አገልግሎት ያስተዋሉትን ሌዋውያን ሁሉ በማበረታታት
ተናገራቸው። በመሆኑም የሕብረት ሥጦታ መሥዋዕት እያቀረቡና ለአባቶቻቸው አምላክ ለእግዚአብሔር እየተናዘዙ በሰባቱ ቀናት በዓል ሁሉ ይመገቡ ነበር። 23
ከዚያም መላው ጉባዔ ለሌላ ሰባት ቀናት በዓሉን ለማክበር ወሰኑ፤ እንደዚህም በደስታ አደረጉ። 24 የይሁዳ ንጉሥ ሕዝቅያስ ለጉባዔው እንደ ሥጦታ ሰጥቶ
ነበር፤ መሪዎቹም ለጉባዔው አንድ ሺህ ወይፈኖችና አሥር ሺህ በጎችና ፍየሎች ሰጡ። ብዙ ቁጥር ያላቸው ካህናትም ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ሰጥተው ነበር።
25 የይሁዳ ጉባዔ ሁሉ ከካህናቱና ከሌዋውያኑ ጋር፥ ከእስራኤል በአንድነት የመጡት ሕዝብ ሁሉ፥ እንዲሁም ከእስራኤል ምድር እና በይሁዳ ይኖሩ ከነበሩት
የመጡት እንግዶች ሁሉም ደስ አላቸው። 26 በመሆኑም በኢየሩሳሌም ታላቅ ደስታ ነበር፤ ከእስራኤል ንጉሥ ከዳዊት ልጅ ከሰለሞን ጊዜ አንስቶ እንደዚህ ያለ
ነገር በኢየሩሳሌም ምንም አልነበረም። 27 ከዚያም ካህናቱ፥ ሌዋውያኑ ተነስተው ሕዝቡን ባረኩ፤ ድምጻቸውም ተሰማ፤ ፀሎታቸውም ወደ እግዚአብሔር ማደሪያ
ቅዱስ ሥፍራ ወደ ሰማይ አረገ።

---

2 Chronicles 30:1

እስራኤልና ይሁዳ ሁሉ
ይህ በአጠቃላይ የእስራኤልን ህዝብ ይወክላል ። ቀደም ሲል ህዝቡ በእነዚህ ስሞች በተጠሩ ሁለት መንግስታት ተከፍሎ ነበር ።

ኤፍሬምና ምናሴ
ኤፍሬምና ምናሴ በእስራኤል ሰሜናዊ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ሁለት ነገዶች ነበሩ። እዚህ ላይ “ኤፍሬም እና ምናሴ” የሚለው ሐረግ የሰሜናዊው እስራኤል አሥሩ ነገዶች አባላት የሆኑትን ሰዎች ሁሉ ያመለክታል ። ኣት: - “ሰሜናዊ የእስራኤል ነገዶች” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን:ይመልከቱ)

በሁለተኛው ወር ፋሲካን ለማክበር መወሰኑ
እስራኤላውያን በተለምዶ በዕብራይስጥ የቀን አቆጣጠር በመጀመሪያው ወር ፋሲካን ያከብሩ ነበር ። የመጀመሪያው ወር በምዕራባዊያን የቀን መቁጠሪያዎች ላይ የመጋቢት የመጨረሻ ክፍል እና የሚያዚያ ወር የመጀመሪያው ክፍል ነው።

ሁለተኛ ወር
ይህ በዕብራይስጥ የቀን መቁጠሪያ ሁለተኛ ወር ነው። ጊዜው በምዕራባዊያን የቀን መቁጠሪያዎች ላይ በሚያዚያ መጨረሻ እና በግንቦት መጀመሪያ መካከል ነው። (የዕብራዊያንን ወራት እና ሕገኛ ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 30:4

ይህ ሀሳብ
ይህ ፋሲካን በመጀመሪያው ወር ፋንታ በሁለተኛው ወር ለማክበር የቀረበለትን ሀሳብ ያመለክታል ።

በንጉሡና በጉባኤው ሁሉ ፊት
ዐይን ማየትን የሚወክል ሲሆን ማየት ደግሞ አመለካከትን ወይም ውሳኔን ይወክላል። ኣት: - “በንጉሡና በጉባኤው ሁሉ እይታ” ወይም “ለንጉሡና ለማኅበሩ ሁሉ” (ዘይቤያዊን:ይመልከቱ)

ከቤርሳቤህ እስከ ዳን ድረስ
እነዚህ የእስራኤል ደቡባዊ ጫፍ እና ሰሜናዊ ጫፍ ናቸው ። ጸሐፊው በዚህ መንገድ በመጥቀስ እስራኤል ሁሉ የተካተተ መሆኑን ጎላ አድርጎ አመልክቷል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

። ኣት: - “በደቡብ በኩል ከቤርሳቤህ አንስቶ እስከ ሰሜን ዳን ድረስ” (ፈሊጥ :ይመልከቱ)

እንደ ተጻፈ
“እንዲያደርጉት ተብሎ እንደተጻፈ።” ብዙ ሕዝብ ሆነው ፋሲካን ማክበር እንዳለባቸው መፃፉን ተጠቁሟል ። ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ሙሴ እንዲጠብቁት እንደጻፈው” (የሚጠበቅ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ :ይመልከቱ)

2 Chronicles 30:6

መልእክተኞች
መልዕክት የሚያደርሱ ሰዎች

እስራኤል ሁሉ እና ይሁዳ
የይሁዳ ነገድ ከእስራኤል ነገዶች ትልቁ ሲሆን በደቡባዊ የእስራኤል ክፍል ነበር። እዚህ ላይ “እስራኤል እና ይሁዳ” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው የደቡብ እስራኤል ነገዶች የነበሩትን ነው ። በ 2 ኛ ዜና 30 ፡1 ውስጥ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። ኣት: - “የእስራኤል ደቡባዊ ነገዶች” (ሂንዲዲያስን :ይመልከቱ)

ወደ እግዚአብሔር ተመለስ
እዚህ “ወደ እግዚአብሔር ተመለስ” እንደገና ለእርሱ መገዛትን ይወክላል ። ኣት: - “እንደገና ለእግዚአብሔር ተገዙ” (ዘይቤያዊን:ይመልከቱ)

ወደ ቅሬታችሁ እንዲመለስ
እዚህ “ወደ ቅሬታዎች መመለስ” ቀሪዎቹን ደግሞ መጠበቅን ያመለክታል። ኣት: “ስለዚህ ቅሬታችሁን እንደ ገና ያድናቸዋል” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

ከአሦር ነገሥታት እጅ ወዳመለጡት
“እጅ” የሚለው ቃል ብዙውን ጊዜ ኃይልን ወይም ስልጣንን ይወክላል ። እዚህ ሰዎችን ወደ ሌሎች አገሮች እንዲሄዱ የሚያስገድድበትን የንጉሡን የጭካኔ ሥልጣን ይወክላል ። ኣት: - “ከአሦር ነገሥታት ኃይል ያመለጡትን” (የባህሪ ስምን:ይመልከቱ)

2 Chronicles 30:7

አያያዥ መግለጫ
ይህ ለእስራኤል ሕዝብ የንጉሥ ሕዝቅያስ ቀጣይ መልእክት ነው ።

ወንድሞችህ
እዚህ ላይ “ወንድሞችህ” ሌሎች የእስራኤል ሰዎችን ይወክላል ። ኣት: - “ሕዝብህ”(ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

ድንጋጤ አደረጋቸው
“ድንጋጤ” የሚለው ረቂቅ ስም በ “አስፈሪ” ወይም “አሰቃቂ” በሚሉት ቃላት ሊገለፅ ይችላል ። ደራሲው እግዚአብሔር በአያቶቻቸው ላይ ስላደረገው ነገር ሲጽፍ ሌሎች ሰዎች እግዚአብሔር ምን እንዳደረገ ሲያዩ የሚሰማቸውን ስሜት በሚገልጽ ቋንቋ ጽፏል ። ኣት: - “ሰዎች ለማየት የሚፈሩት ነገር ነው ያደርጋቸው ” (የረቂቅ ስሞችን እና የባህሪ ስምን:ይመልከቱ)

ለእግዚአብሔር ራሳችሁን ስጡ
ይህ ለእግዚአብሔር መገዛትን ይወክላል ። ኣት: - “ለእግዚአብሔር ተገዙ” ወይም “ራሳችሁን ለእግዚአብሔር ስጡ” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

ወደ ቅዱስ ስፍራውም ግቡ
“የተቀደሰ ስፍራ” የሚለው በኢየሩሳሌም የሚገኘውን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ያመለክታል ። ኣት: “ ቅዱስ ነውና በኢየሩሳሌም ወዳለው ወደ ቤተ መቅደሱ ኑ”ወይም“ በኢየሩሳሌም ወደሚገኘው ቤተ መቅደሱ ኑ ” (የባህሪ ስምን:ይመልከቱ)

ጸኑ ቁጣው ከእናንተ ይመለስ ዘንድ
ደራሲው ስለ ቁጣ ሲጽፍ ፣ እንደ ሰብአዊ አካል ከሰዎች የሚርቅ አስመስሎ ነው። የእግዚአብሔር ቁጣ ከእነሱ መመለሱ ከእንግዲህ በእነርሱ ላይ ቁጣው እንዳልቀጠለ ያሳያል ። ኣት: - “ከእንግዲህ በእናንተ ላይ እንዳይቆጣ” (ተስብኦትን :ይመልከቱ)

ወደ እግዚአብሔር ብትመለሱ
እዚህ “ወደ እግዚአብሔር ተመለስ” የሚለው እንደገና ለእርሱ መገዛትን ይወክላል ። ኣት: - “ለእግዚአብሔር እንደገና ብትሰጡ ” (ዘይቤያዊን ፡ ይመልከቱ)

ወንድሞቻችሁና ልጆቻችሁ ማርከው በሚወስዷቸው ፊት ምህረትን ያገኛሉ
እዚህ ላይ “ምህረትን ያገኛሉ” የሚለው ዘይቤአዊ አገላለጽ ሲሆን ምህረትን ይለማመዳሉ ማለት ነው ። እነርሱን “ማርከው በሚወስዷቸው ፊት .. ያገኛሉ” የሚለው ማርከው የሚወስዷቸው ምህረትን ያሳየዋቸዋል ማለት ነው። ኣት: - “ወንድሞችህና ልጆችህ በግዞት ከወሰዷቸው ሰዎች ርኅራሆ ያገኛሉ” ወይም “ወንድሞችህንና ሕፃናትን ግዞተኛ አድርገው የወሰዷቸው ሰዎች ርኅራሄ ያሳዮአቸዋል” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

ፊቱን ከአንተ አይርቅም
እዚህ “ፊቱን ከእናንተ ማራቅ” የሚለው አባባል እነርሱን አለመቀበልንና እነርሱን ለመጠበቅ ፈቃደኛ አለመሆንን ያሳያል። ኣት: - “አይጥልህም”(ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

ወደ እርሱ ብትመለሱ
እዚህ “ወደ እርሱ ተመለስ” የሚለው ለእግዚአብሔር መገዛትን ያሳያል ። ኣት: - “እንደገና ለእርሱ ብትገዙ” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 30:10

የኤፍሬምና የምናሴ ክልሎች
ኤፍሬምና ምናሴ በእስራኤል ሰሜናዊ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ሁለት ነገዶች ነበሩ። እዚህ ላይ “ኤፍሬም እና ምናሴ” የሚለው ሐረግ የሰሜናዊው እስራኤል አሥሩ ነገዶች አባላት የሆኑትን ሰዎች ሁሉ ያመለክታል። በ 2ኛ ዜና 30፡ 30 ውስጥ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። ኣት: - “የሰሜናዊ የእስራኤል ነገዶች ግዛቶች” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን :ይመልከቱ)

እስከ ዛብሎን ድረስ
ዛብሎን በእስራኤል ሰሜን ጫፍ ውስጥ ከሚገኙት ነገዶች መካከል አንዱ ነበር ፣ ነገር ግን ከእነርሱ አልፈው ወደ ሰሜን ጥግ የሚደርሱ ሌሎች ሦስት ነገዶች ነበሩ።

የእግዚአብሔርም እጅ በይሁዳ ላይ ወረደ
እዚህ“የእግዚአብሔር እጅ” የሚለው የእርሱን አመራር የሚወክል ሲሆን ልክ በእጁ እየመራቸው ያለ ይመስላል። ኣት:- “እግዚአብሔር የይሁዳን ሕዝብ መራ።” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

አንድ ልብ ለመስጠት
“አንድ ልብ” መኖሩ አንድነትን እና መስማማትን ያመለክታል ። ኣት: - “እንዲስማሙ ማድረግ” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

ትዕዛዙን እንዲያደርጉ
እዚህ “ትዕዛዙን ማድረግ” የሚለው አባባል የታዘዘውን ማድረግ የሚል ትርጉም አለው። ኣት: - “ትዕዛዙን መታዘዝ” (ፈሊጥን :ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ቃል የሆነውን የንጉሡንና የአለቆቹን ትዕዛዝ
“በእግዚአብሔር ቃል” የሚለው ሐረግ የሚያሳየው ንጉሡና መሪዎቹ ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ ትዕዛዙን እንደሰጡ ያሳያል ። ኣት: - “ንጉሡና መሪያዎቹ ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ የሰጧቸው ትእዛዝ” ወይም “እግዚአብሔር ከተናገረው ነገር የተነሳ ንጉሡና መኳንንቱ ያዘዙት”

2 Chronicles 30:13

በሁለተኛው ወር
ይህ በዕብራይስጥ የቀን መቁጠሪያ ሁለተኛ ወር ነው። ጊዜው በምዕራባዊያን ቀን መቁጠሪያዎች ላይ የሚያዚያ መጨረሻ እና የግንቦት የመጀመሪያ ክፍል ነው። (የዕብራዊያንን ወራት እና ሕገኛ ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

ተነሱና መሠዊያዎቹን አስወገዱ
እዚህ “ተነሱ” ማለት መሠዊያዎቹን ለማስወገድ መሥራት ጀመሩ ማለት ነው ። ኣት: - “መሥራት ጀመሩ ፣ መሠዊያዎቹንም አስወገዱ” ወይም “መሠዊያውን አራቁ”

በኢየሩሳሌም የነበሩትን መሠዊያዎችና ለጣዖታት የሚያጥኑበትን ዕቃ ሁሉ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚያመለክቱት ሰዎች ለሐሰት አማልክት የሠሯቸውን መሠዊያዎችን ነው ።

በቄድሮን ወንዝ
ይህ በቄድሮን ሸለቆ ውስጥ የነበረ ትንሽ የውሃ ጅረት ነው ። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

በሁለተኛው ወር በአሥራ አራተኛው ቀን
ይህ በምዕራባዊያን የቀን መቁጠሪያዎች ላይ የግንቦት መጀመሪያ አካባቢ ነው። (የዕብራዊያንን ወራት እና ሕገኛ ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 30:16

በየቦታቸው በየክፍላቸው ቆሙ
በተመደቡባቸው ቦታዎች ቆሙ ”

ከሌዋውያን እጅ የተቀበሉትን ደም
ይህ ሌዋውያን ያረዷቸውን የበግ ጠቦቶች ደም ያመለክታል። እዚህ ላይ “ከሌዋውያን እጅ የተቀበሉትን” የሚለው ሌዋውያኑ ደም ለካህናቱ መስጠታቸውን ለመግለጽ ነው ። ኣት: - “ከሌዋውያን የተቀበሉት ደም” ወይም “ሌዋውያኑ የሰጧቸው የበግ ጠቦት ደም” (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን እና የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

የፋሲካ-ጠቦት
“የፋሲካ የበግ ጠቦቶች”

2 Chronicles 30:18

ኤፍሬም ፣ ምናሴ ፣ ይሳኮር እና ዛብሎን
እነዚህ በሰሜናዊው የእስራኤል ክፍል ይኖሩ የነበሩ የአንዳንድ ነገዶች ስሞች ናቸው። በ 2ኛ ዜና 30 :10 ውስጥ “ዛቡሎን” የሚለውን እንዴት እንደተረጉምከው ተመልከት ። (የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)

የተጻፈውን ትዕዛዝ በመተላለፍ
መመሪያዎችን የሚቃወም ነገር ማድረግ ማለት ለመመሪያዎቹ ባለመታዘዝ አንድን ነገር ማድረግ ማለት ነው ። አስፈላጊ ከሆነ መመሪያዎቹ ግልጽ ሊደረጉ ይችላሉ ። ኣት: - “ምንም እንኳን የተፃፉት መመሪያዎች መጀመሪያ ራሳቸውን እንዲያነጹ ቢናገሩም” (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸን መረጃ : ይመልከቱ)

ቸሩ እግዚአብሔር
እዚህ “ቸር” የሚለው ቃል እግዚአብሔር ቸር መሆኑን ለህዝቡ የ ሚያሳስብ ነው ። ኣት: - “ቸር የሆነው እግዚአብሔር” (መለየትን ከማስታወቅ ወይም ከማስታወስ ጋር :ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን ለመፈለግ ልቡን የሚያቀናውን
እዚህ“ልቡን የሚያቀናው” የሚለው አንድን ነገር ለማከናወን ጽኑ ውሳኔ መኖርን የሚወክል ሲሆን ፣ “እግዚአብሔርን መፈለግ” የሚለው ደግሞ እርሱን ማወቅን ፣ ማምለክን እና መታዘዝን የሚያመለክት ነው ። ኣት: - “እግዚአብሔርን ለመታዘዝ የወሰነ ማንኛውም ሰው” ወይም “በእውነት እግዚአብሔርን ለማክበር የሚፈልግ ሁሉ” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

እግዚአብሔርም ሕዝቅያስን ሰማው
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ለሕዝቅያስ በጎ ምላሽ እንደሰጠ ያሳያል ። ኣት: - “እግዚአብሔርም ለሕዝቅያስ መልካም ምላሽ ሰጠው” ወይም “እግዚአብሔር ሕዝቅያስ የጠየቀውን አደረገ” (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን :ይመልከቱ)

ሕዝቡን ፈወሰ
እዚህ “ህዝቡን ፈወሰ” የሚለው ሰዎችን ይቅር ለማለቱ እና እነርሱን የማይቀጣ ለመሆኑ ምልክት ነው ። ኣት: - “ህዝቡን ይቅር አለ” ወይም “ሕዝቡን አልቀጣም” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 30:21

የቂጣውን በዓል ጠበቀ
እዚህ “በዓሉን ጠበቁ” የሚለው ፈሊጥ በበዓሉ ላይ ተሳተፉ ወይም በዓሉን አከበሩ የሚል ትርጉም አለው። ኣት: - “በዓሉን አከበሩ” (ፈሊጥን : ይመልከቱ)

ታላቅ ድምጽ ባላቸው የሙዚቃ መሣሪያዎች ለእግዚአብሔር መዘመር
“ለእግዚአብሔር ከፍተኛ ድምጽ ያላቸውን የሙዚቃ መሣሪያዎች መጫወት እና መዘመር”

የእግዚአብሔርን አገልግሎት የተረዳ
ያበረታታቸውም ለዚህ ነበር ። ኣት: - “የእግዚአብሔርን አገልግሎት ስለተረዱ” ወይም “ያህዌን በብቃት ስላገለገሉ” (መለየትን ከማስታወቅና ከማስታዎስ ጋር :ይመልከቱ)

ስለዚህ እነርሱ በበዓሉ ላይ ሁሉ በሉ
“እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው ።

ለእግዚአብሔር እየተናዘዙ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “እየተናዘዙ” የሚለው እዚህ ላይ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ታላቅ መሆኑን ማወጅን ነው ። ኣት: - “እግዚአብሔርን ማወደስ” ወይም 2) “መናዘዝ” እዚህ ላይ ኃጢአታቸውን መናዘዝን ያመለክታል። ኣት: - “ኃጢአታቸውን ወደ እግዚአብሔር መናዘዝ”

2 Chronicles 30:23

ሕዝቅያስም ማኅበሩን ... ወይፈኖችን በጎችን ደግሞ ስለ ቁርባን ሰጣቸው
ሕዝቅያስ ከብቶቹን ህዝቡ ይበሉ ዘንድ ለእግዚአብሔር እንደ መባ አድርጎ ሰጠ። አንድ ሺህ ወይፈኖች... ሰባት ሺህ በጎች... አንድ ሺህ ወይፈኖችና... አሥር ሺህ በጎችና ፍየሎች “1,000 ወይፈኖች... 7,000 በጎች... 1,000 ወይፈኖች... 10,000 በጎችና ፍየሎች” (ቁጥርን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 30:25

የይሁዳ ጉባኤ ሁሉ
እዚህ ላይ “ይሁዳ” ምናልባት የደቡቡን የእስራኤል ነገዶች ያመለክታል ።

ከእስራኤል የተሰበሰበ ሕዝብ ሁሉ
እዚህ “እስራኤል” የሚለው ምናልባት የሚያመለክተው ሰሜናዊያኑን የእስራኤል ነገዶች ነው ። ሰዎቹ የነዚያ ነገዶች አባላት ናቸው ። በይሁዳም ወደነበረው ወደ ኢየሩሳሌም መጡ ። ኣት: - “ከሰሜን እስራኤል በአንድነት የተሰበሰበ ሕዝብ ሁሉ” (የሚጠበቁ እውቀት ካልተገለጸ መረጃን : ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከእስራኤል ምድር የመጡ የባዕድ አገር ሰዎች
እዚህ “የእስራኤል ምድር” የሚለው ምናልባት በሰሜናዊ የእስራኤል ነገዶች የተያዙትን መሬት የሚያመለክት ሊሆን ይችላል ። ኣት: “ከሰሜን እስራኤል ምድር የመጡት የባዕድ አገር ሰዎች” (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን ፡ይመልከቱ)

በይሁዳ የኖሩት
እዚህ“ይሁዳ” የሚለው ምናልባት በደቡባዊው የእስራኤል ነገዶች የተያዙትን መሬት የሚያመለክት ሊሆን ይችላል ። ኣት: - “በይሁዳ የኖሩ የባዕድ አገር ሰዎች” (የሚጠበቁ እውቀቶችን እና ያልተገለጹ መረጃዎችን ፡ይመልከቱ)

ከእስራኤል ንጉሥ ከዳዊት ልጅ ከሰሎሞን ዘመን ጀምሮ
“የዳዊት ልጅ ሰሎሞን በእስራኤል ላይ ከነገሠበት ጊዜ አንስቶ” ወይም “የዳዊት ልጅ ሰሎሞን የእስራኤል ንጉሥ ንጉሥ ሳለ ህዝቡ ካከበሩት ከፋሲካ በዓል ጀምሮ”

በኢየሩሳሌምም እንደዚህ ያለ ነገር አልነበረም
“በኢየሩሳሌም በዚህ መልኩ የተከበረ የፋሲካ በዓል አልነበረም”

ድምፃቸው ተሰማ... ጸሎታቸውም እግዚአብሔር ወደሚኖርበት ወደ ቅድስት ሰማይ ወጣ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች አንድ ዓይነት ትርጉም ያላቸው ሲሆን የሚያመለክቱት እግዚአብሔር ለጸሎታቸው በጎ ምላሽ እንደሰጣ ነው ። ኣት: “እግዚአብሔር በሰማይ በተቀደሰ ማደሪያው ሆኖ ጸሎታቸው ሰማ በበጎም መለሰላቸው” ወይም “በቅዱሱ ሰማይ ውስጥ የሚኖር አምላክ ጸሎታቸውን ሰማ” (ምስስልን ፡ይመልከቱ)

ድምፃቸው ተሰማ
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: “እግዚአብሔር ድምፃቸውን ሰማ” ወይም “እግዚአብሔር የለመኑትን ሰማ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን፡ይመልከቱ)

ጸሎታቸው ወደ ሰማይ ወጣ
ጸሎታቸው ወደ ሰማይ መሄዱ በሰማይ ያለ እግዚአብሔር በምድር ላይ ለሚጸልዩ ለእነሱ ትኩረት እንደሚሰጥ የሚያመለክት ነው ። (ዘይቤያዊን ፡ ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 31

1 ሁሉም ነገር ከተጠናቀቀ በኋላ እዚያ የተገኙት የእስራኤል ሰዎች ሁሉ ወደ ይሁዳ ከተሞች ወጥተው የአምልኮ ድንጋይ ምሶሶዎችን ሰባበሩ፤ የማምለኪያ
ዐፀዶቹን ቆረጡ፤ በይሁዳና በብንያም ሁሉ መስገጃዎችንና መሠዊያዎችን ሰባበሩ፤ ሁሉንም እስኪያጠፉ ድረስ ይህንኑ በኤፍሬምና በምናሴም ጭምር
አደረጉት። ከዚያም የእስራኤል ሰዎች ሁሉ እያንዳንዱ ወደ ገዛ ምድሩና ወደ ገዛ ከተማው ተመለሰ። 2 ሕዝቅያስም ካህናቱንና ሌዋውያኑን በየሥራ ክፍል
በማደራጀት ለካህናቱና ለሌዋውያኑ ለእያንዳንዱ ሥራ በመስጠት በየአገልግሎታቸው መደባቸው። የሚቃጠል መሥዋዕትና የሕብረት መሥዋዕት እንዲያቀርቡ፥
እንዲያገለግሉ፥ እንዲያመሰግኑና በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በሮች እንዲያወድሱ መደባቸው። 3 በእግዚአብሔር ሕግ ተጽፎ እንደነበረውም ለሚቃጠል
መሥዋዕት ማለትም ለጠዋትና ለማታ የሚቃጠል መሥዋዕት፥ ለሰንበት ቀናት፥ ለመባቻዎቹና ለመደበኛ በዓላትም የሚቃጠል መሥዋዕት ከንጉሡ ከገዛ ራሱ
ሃብት ድርሻውን መደበ። 4 በተጨማሪም ካህናቱና ሌዋውያኑ የእግዚአብሔርን ሕግ በመታዘዝ ላይ እንዲያተኩሩ በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎች ለካህናቱና
ሌዋውያኑ ድርሻቸውን እንዲሰጡ አዘዘ። 5 ትእዛዙ እንደወጣም የእስራኤል ሕዝብ የእህሉን፥ የአዲሱን ወይን፥ የዘይቱን፥ የማሩን እንዲሁም ከእርሻው መከር ሁሉ
በኩራት አትረፍርፈው ሰጡ፤ የሁሉንም ነገር አሥራትም አትረፍርፈው አመጡ። 6 በይሁዳ ከተሞች የሚኖሩ የእስራኤልና የይሁዳ ሕዝብ የበሬዎቹንና በጎቹን
አሥራት፥ ለአምላካቸው ለእግዚአብሔር የተሰጡ ነገሮችን ጭምር አሥራት አምጥተው ከምረው አስቀመጡት። 7 በሦስተኛው ወር መከመር ጀምረው በሰባተኛው
ወር ጨረሱ። 8 ሕዝቅያስና መሪዎቹ መጥተው ክምሮቹን ሲያዩ እግዚአብሔርንና ሕዝቡን እስራኤልን ባረኩ። 9 ሕዝቅያስም ካህናቱንና ሌዋውያኑን ስለ ክምሩ
ጠየቀ። 10 የሳዶቅም ቤት የሆነው ሊቀ ካህን ዓዛርያስ፦" ሕዝቡ ሥጦታዎቻቸውን ወደ እግዚአብሔር ቤት ማምጣት ከጀመሩ አንስቶ በልተናል፤ ጠግበናልም፤
እግዚአብሔርም ሕዝቡን ስለባረከ ብዙ ተርፎአል። የተረፈውም ነገር ይህ እዚህ ያለው ታላቅ መጠን ነው" ብሎ መልስ ሰጠ። 11 ከዚያም ሕዝቅያስ
በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ መጋዘኖች እንዲዘጋጁ አዘዘ፤ እነርሱም አዘጋጇቸው። 12 ሥጦታዎቹን፥ አሥራቱንና የእግዚአብሔር የሆኑትን ነገሮች በታማኝነት
አመጡ። ሌዋዊው ኮናንያ የበላያቸው አስተዳዳሪ ነበር፤ ወንድሙም ሰሜኢ በደረጃ ከእርሱ ቀጥሎ ሁለተኛ ነበረ። በንጉሡም በሕዝቅያስና በእግዚአብሔር ቤት
ላይ ባለ ሥልጣን በነበረው በዓዛርያስ የተሾሙ፥ ከኮናንያና ከወንድሙ ከሰሜኢ እጅ በታች 13 ይሒዒል፥ ዓዛዝያ፥ ናሑት፥ አሣኤል፥ ይሬሞት፥ ዮዛባት፥ ኤሊኤል፥
ሰማኪያ፥ መሐት፥ በናያስ አስተዳዳሪዎች ነበሩ። 14 ሌዋዊው የይምና ልጅ የምሥራቁ በር ጠባቂ ቆሬ ለእግዚአብሔር የተቀደሱትን ሥጦታዎችና በእግዚአብሔር
የበጎ ፈቃድ ሥጦታዎች ላይ የበላይ ሆኖ ለእግዚአብሔር የቀረቡ ሥጦታዎችን ለማከፋፈል አዛዥ ነበር። 15 ከበታቹም በካህናቱ ከተሞች ውስጥ ዔድን፥
ሚንያሚን፥ ኢያሱ፥ ሸማያ፥ አማርያና ሴኬንያ ነበሩ። እነዚህን ሥጦታዎች ለታላላቆቹና ለታናናሾቹ ወንድሞቻቸው እንደየሥራ ክፍላቸው ለመስጠት በመታመን
ሥልጣን ተሰጣቸው። 16 በዕለታዊ የጊዜ ሰሌዳ እንደሚጠበቅባቸው ወደ እግዚአብሔር ቤት የሚገቡ ሁሉ በቦታቸው ሆነው በየሥራ ክፍላቸው ሥራቸውን
ለመሥራት በዘር ሐረጋቸው ተቆጥረው የነበሩ ሦስት ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆኑ ወንዶችም ሰጡ። 17 በቦታቸው ሆነው በየሥራ ክፍላቸው ሥራቸውን ለመሥራት
በአባቶቻቸው ቤቶች በዘር ሐረጋቸው ተቆጥረው የነበሩ ሌዋውያን ሃያ ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆኑትም ሰጡ። 18 በዘር ሐረጋቸው ተቆጥረው ለነበሩ ለሕፃናቱ፥
ለሚስቶቻቸው፥ ለወንዶችና ለሴቶች ልጆቻቸው ሁሉ በመላው ሕዝብ መካከል በተቀደሰ ሁኔታ በአመኔታ ለተሰጣቸው ሥልጣን ራሳቸውን ለእግዚአብሔር
ስለቀደሱ ለእነርሱም ሰጡ። 19 በየከተማቸው ወይም በከተሞቹ ሁሉ ባሉ መንደሮች መስኮች ላይ ለነበሩ ለአሮን ዝርያዎች በካህናቱ መካከል ለሁሉም ወንዶች
በስማቸው ድርሻቸውን ለመስጠትና በሌዋውያን መካከል እንደሆኑ በትውልድ ሐረጋቸው ለተቆጠሩ ሁሉ የተመደቡላቸው ሰዎች ነበሩ። 20 ሕዝቅያስም ይህንን
በይሁዳ ሁሉ አደረገ። በእግዚአብሔር በአምላኩ ፊት መልካም፥ ትክክለኛና ታማኝ ነገርን አከናወነ። 21 በእግዚአብሔር ቤት አገልግሎት በጀመረው በየትኛውም
ሥራ በሕጉና በትዕዛዛቱ አምላኩን ለመፈለግ በሙሉ ልቡ አከናወነው፤ እርሱም ተሳካለት።

---

2 Chronicles 31:1

እዚያ ነበሩ
“በኢየሩሳሌም የነበሩት”

ለገዛ ንብረቱ
እዚህ “ንብረት” የሚለው በድፍኑ ንብረቶች ማለት ነው ። ኣት: - “ለገዛ ንብረቱ” ወይም “በገዛ ቤቱ” (አጠቃላይ ስማዊ ግስን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 31:2

ሕዝቅያስም የካህናትንና የሌዋውያኑን በየክፍላቸውና በየአገልግሎታቸው አደራጀ ፤ እያንዳንዱም ሰው በሥራው ተመደበ ፣ካህናቱም ለሌዋውያኑም ።
ይህ በንቃት ቅርፅ ለገለፅ ይችላል ። ኣት: “ሕዝቅያስ ካህናቱንና ሌዋውያኑን በቡድን በቡድን አደራጀ። እያንዳንዱን ካህን እና ሌዋዊ በስራው መደበ። ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን:ይመልከቱ)

ከገዛ ንብረቱ ለሚቃጠለው መስዋዕት የንጉሡን ድርሻ ሰጠ
ሕዝቅያስ ለሚቃጠሉ መባዎች የሚጠቀምበትን ሥጋና እህል ከራሱ ንብረቱ ወሰደ።

መባቻ
ይህ ከጨረቃ እንቅስቃሴ ጋር የተጣመረ በዓል ነበር ።

በዓላት
ይህ ለበዓል በተለዩ ቀናት ላይ የሚደረጉ በዓላትን ይመለከታል።

በእግዚአብሔር ሕግ እንደ ተጻፈ
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ለገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ሙሴ በእግዚአብሔር ሕግ እንደ ጻፈው” ወይም “እግዚአብሔር በሕጉ እንዳዘዘው” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 31:4

ትዕዛዙ እንደላከ ወዲያውኑ
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ለገለጽ ይችላል ። ኣት: - “ህዝቡ ትዕዛዙን እንደሰማ ወዲያው” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

የሁሉም ነገር አሥራት ነው
“ከእሕሎቻቸው ሁሉ አንድ አሥረኛ”

2 Chronicles 31:6

ሦስተኛ ወር
ይህ በዕብራይስጥ የቀን መቁጠሪያ ሦስተኛ ወር ነው። ይህ በመከር ወቅት መጨረሻና በበጋ ወቅት መጀመሪያ ላይ ነው ። ይህ በምዕራባዊያን የቀን መቁጠሪያዎች ላይ የግንቦት የመጨረሻ እና የሰኔ የመጀመሪያ ክፍል ነው። (የዕብራዊያንን ወራት እና ሕገኛ ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሰባተኛ ወር
ይህ በዕብራይስጥ የቀን አቆጣጠር ሰባተኛ ወር ነው። ይህ ቀዳሚው የዝናብ ወቅት ሲሆን መሬቱ የሚዘራበት እንዲሆን ያለሰልሰዋል። ጊዜው በምዕራባዊያን ቀን መቁጠሪያዎች ላይ በመስከረም ወር መጨረሻ እና በጥቅምት ወር መጀመሪያ ላይ ነው ። (የዕብራዊያንን ወራትንና ሕገኛ ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 31:9

የሳዶቅ ቤት
እዚህ “ቤት” የሚለው ቤተሰብን ወይም ዘሮችን ይወክላል ። ኣት: - “የሳዶቅ ዘሮች” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

የተረፈው ይህ ክምር ትልቅ ነው
ሊቀ ካህኑ ወደ ትላልቅ ክምሮች እየጠቆመ ነበር።

ሕዝቅያስ መጋዘኖች እንዲዘጋጁ አዘዘ
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: “ሕዝቅያስ ካህናቱና ሌዋውያኑ መጋዘኖችን እንዲያዘጋጁ አዘዙ” (ገቢራዊ ወይም ተብሮአዊ : ይመልከቱ)

ኮናንያ... ሰሜኢ.... ይሒዒል ፣ ዓዛዝያ ፣ ናሖት ፣ አሣሄል ፣ ይሬማት ፣ ዮዛባት ፣ ኤሊኤል ፣ ሰማክያ ፣ መሓት ፣ እና በናያስ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው ። (ገቢራዊ ወይም ተብሮአዊ :ይመልከቱ)

በኮናንያና በወንድሙ በሰሜዒ እጅ በታች አስተዳዳሪዎች ነበሩ
እዚህ “እጅ” ኃይልን ወይም ቁጥጥርን ይወክላል ። “ከእጅ ስር” የሚለው ሐረግ ማለት በአንድ ሰው ስልጣን ስር መሆን ማለት ነው ። ኣት: “ኮናንያ እና ወንድሙ ሰሜኢ በበላይነት የሚቆጣጠሯቸው አስተዳዳሪዎች ነበሩ” (የባህሪ ስምን እና ፈሊጥን :ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ቤት ላይ ተሾመ
እዚህ “ላይ” የሚለው አባባል ሲሆን ኃላፊ ማለት ነው ። ኣት: - “በእግዚአብሔር ቤት የሚያገለግሉ ሰዎች ሁሉ አለቃ” (ፈሊጥን : ይመልከቱ)

2 Chronicles 31:14

የይምና ልጅ ቆሬ... ዔድን ፣ ሚንያሚን ፣ ኢያሱ ፣ ሸማያ ፣ አማርያ እና ሴኬኒያ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው ። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

የምሥራቅ በር ጠባቂ
በቤተ መቅደሱ የምሥራቅ በር “በር ጠባቂ”

በካህናቱም ከተሞች ውስጥ ከእርሱ ሥር ዔድን ነበር
እዚህ “ስር” የሚለው ቃል በአንድ ሰው ስልጣን ስር መሆን ማለት ነው ። ኣት: - “ዔድን... በካህናቱ ከተሞች ውስጥ ቆሬን ረድቶታል” (ፈሊጥን: ይመልከቱ)

ለመስጠት እንዲችሉ በፈቃድ ባቀረቡት ላይ ተሾመ
ተግባራቸው መስጠት ወይም ”በታማኝነት መስጠት” ነበር

ለወንድሞቻቸው
እዚህ “ወንድሞች” የሚለው ምሳሌ “ሌሎች ካህናትን ” የሚያመለክት ነው ። ኣት: - “ባልደረቦቻቸው ለሆኑ ካህናት” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

ክፍል በክፍል
“በቡድን በቡድን”

ለታላላቆችና ለታናናሾች
እዚህ “ታላላቆች” እና “ታናናሾች” አንድ ላይ “ሁሉም ሰው ” ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል ። “ኣት” “ ለሁሉም ሰው ታላላቆችን እና ታናናሾችን ጨምሮ” (ሜሪዝምን :ይመልከቱ)

ታላላቆችና እና ታናናሾች
ይህ ያረጀውንና እና ወጣቱን የሚያመለክት ይመስላል። ይህ አላስፈላጊ ተቀጽላዎችን በማስወገድ በሌላ መልኩ ሊገለጽ ይችላል። ኣት: - “በዕድሜ የገፉ እና ወጣቶች” (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን እና ስማዊ ቅጽሎችን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 31:16

በተጨማሪም ሰጡ
የነፃ ፈቃድ መባዎችን እንደሰጡ ይታወቃል። ኣት: - “ደግሞም በፈቃዳቸው መባዎችን አቀረቡ” (የፊደል ግድፈትን :ይመልከቱ)

ዕድሜያቸው ሦስት ዓመትና ከዚያ በላይ
“ዕድሜያቸው ሦስት ዓመት የሆናቸውና ከዚያ በላይ የሆኑ”

በመዝገብ ውስጥ የተጻፉት
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ስማቸው በመዝገቦቹ ውስጥ ተመዝግቦ የለ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

በእለታዊ መርሃግብሩ እንደተጠየቁት ሥራቸውን በምድባቸውና በክፍሎቻቸው ለማከናወን
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ሊሠሩ የሚገባቸውን የዕለት ተዕለት ሥራ ለመሥራት” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን:ይመልከቱ)

2 Chronicles 31:17

አሰራጭተዋል
የነፃ ፈቃድ መባን ማሰራጨታቸው ይታወቃል። ኣት: - “የነፃ ፈቃድ ስጦታዎችን አከፋፈሉ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

ጭድሜው ሃያ ዓመት እና ከዚያ በላይ
“ዕድሜው 20 ዓመትና ከዛ በላይ” (ቁጥሮችን:ይመልከቱ)

ድርሻቸውን ለመስጠት በስም የተመደቡ ሰዎች ነበሩ
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ድርሻዎችን የመስጠት ኃላፊነት ያላቸው ሰዎች ነበሩ” (ገቢራዊ ወይም ተብሮአዊ :ይመልከቱ)

በመዝገቡ ውስጥ ለተዘረዘሩት ሁሉ
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “በመዝገቦቹ ውስጥ ስማቸው ለነበረ ሁሉ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 31:20

አምላኩን ለመፈለግ
እግዚአብሔርን መፈለግ እርሱን ለማወቅ ፣ ለማምለክ እና ለመታዘዝ መምረጥን ያመለክታል ። ኣት: - “አምላኩን መታዘዝ” (ዘይቤያዊን : ይመልከቱ)

ይህን ያደረገው በሙሉ ልቡ ነው
እዚህ “ልብ” የሚለው ቃል የአንድን ሰው ፍላጎት እና ፈቃድ ያመለክታል ። ኣት: - “እርሱ ይህን ያደረገው በፍጹም ፈቃድ ነው ” ወይም “ እርሱ ለሥራው ሙሉ በሙሉ የተሠጠ ነበር” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 32

1 ከእነዚህ ነገሮችና ከእነዚህ የታማኝነት ድርጊቶች በኋላ የአሦር ንጉሥ ሰናክሬም መጥቶ ወደ ይሁዳ ገባ፤ ለራሱ ሊይዛቸው ያሰባቸውን የተከበቡ ከተሞች ሊያጠቃ ሰፈረ። 2 ሕዝቅያስም ሰናክሬም እንደ መጣ ኢየሩሳሌምንም ሊዋጋ እንዳሰበ ባየ ጊዜ 3 ከከተማው በስተውጪ የነበሩትን የምንጭ ውሃዎች ለመድፈን ከመሪዎቹና ከኃያላን ሰዎቹ ጋር ተመካከረ፤ እነርሱም እንደዚህ ለማድረግ ረዱት። 4 በመሆኑም በርካታ ሰዎች በአንድነት ተሰብስበው ምንጮቹን ሁሉና በምድሪቱ መካከል አልፎ ይፈስ የነበረውን ጅረት አስቆሙ። እነርሱም "የአሦር ነገሥታት መጥተው ለምን ብዙ ውሃ ያገኛሉ?" አሉ። 5 ሕዝቅያስም ተደፋፈረና የፈረሰውን ቅጥር ሁሉ ጠገነ፤ እስከ ማማዎቹ ድረስ ሠራው፤ በስተውጪ ሌላ ግንብም ሠራ። በዳዊትም ከተማ ውስጥ የነበረችውን ሚሎንም አጠነከረ፤ ከፍተኛ መጠን ያላቸውን የጦር መሣርያዎችንና ጋሻዎችንም ሠራ። 6 በሕዝቡ ላይም የጦር አዛዦችን አስቀመጠ። በአንድነትም በከተማይቱም በር በሰፊ ቦታ ወደራሱ ሰብስቦአቸው በማበረታታት ተናገራቸው። 7 "በርቱ አይዞአችሁ። ከእርሱ ጋር ካሉት ከእኛ ጋር ያለው እርሱ እግዚአብሔር የሚበልጥ ስለሆነ ከአሦር ንጉሥና ከእርሱ ጋር ካለው ሠራዊት የተነሳ እንዳትፈሩ ወይም እንዳትደነግጡ። 8 ከእርሱ ጋር ያለው የሥጋ ክንድ ብቻ ነው፤ ከእኛ ጋር ግን ሊረዳንና ጦርነታችንን ሊዋጋልን ያለው አምላካችን እግዚአብሔር ነው" አላቸው። ሕዝቡም በይሁዳ ንጉሥ በሕዝቅያስ ቃል ራሳቸውን አጽናኑ። 9 ከዚህ በኋላ የሦርያ ንጉሥ ሰናክሬም (በዚህ ጊዜ በለኪሶ ፊት ለፊት ነበረ፤ ሠራዊቱም ሁሉ ከእርሱ ጋር ነበሩ) አገልጋዮቹን ወደ ኢየሩሳሌም ወደ ይሁዳ ንጉሥ ወደ ሕዝቅያስና በኢየሩሳሌም ወደነበሩት ወደ ይሁዳ ሁሉ ላከ፤ 10 "የአሦር ንጉሥ ሰናክሬም የሚለው ይህንን ነው፦'በኢየሩሳሌም የተከበባችሁበትን ለመቋቋም የምትደገፉት በምን ላይ ነው? 11 ሕዝቅያስ፦ 'አምላካችን እግዚአብሔር ከአሦር ንጉሥ እጅ ይታደገናል' ብሎ ሲነግራችሁ በረሃብና በጥማት እንድትሞቱ አሳልፎ ሊሰጣችሁ እያሳሳታችሁ አይደለምን? 12 የኮረብታ መስገጃዎቹንና መሠዊያዎቹን ያስወገደና 'በአንድ መሠዊያ ላይ ታመልካላችሁ፤ በእርሱም ላይ መሥዋዕታችሁን ታቃጥላላችሁ' ብሎ ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን ያዘዘው ይኸው ሕዝቅያስ አይደለምን? 13 እኔና አባቶቼ በሌሎች ምድሮች ሕዝቦች ሁሉ ላይ ያደረግነው ምን እንደሆነ አላወቃችሁምን? የእነዚህ ምድሮች ሕዝቦች አማልክት በየትኛውም መንገድ ምድራቸውን ከኃይሌ ሊታደጉ ችለው ነበርን? 14 አባቶቼ ሙሉ በሙሉ ካጠፏቸው ከእነዚያ ሕዝቦች አማልክት ሁሉ መካከል ሕዝቡን ከእጄ መታደግ የቻለ አምላክ ነበርን? አምላካችሁስ እናንተን ከኃይሌ ሊታደጋችሁ እንዴት ይችላል? 15 አሁንም ሕዝቅያስ በዚህ መንገድ አያታልልላችሁ ወይም አያሳምናችሁ። የየትኛውም ሕዝብ ወይም መንግሥት አማልክት ሕዝቡን ከእጄ ወይም ከአባቶቼ እጅ ሊታደግ ስላልቻለ አትመኑት። ይልቁንም አምላካችሁ ከእጄ እንዴት ሊያድናችሁ ይችላል?" አለ። 16 የሰናክሬም አገልጋዮችም እግዚአብሔር አምላክና አገልጋዩ ሕዝቅያስ ላይ ይበልጥ የተቃውሞ ነገር ተናገሩ። 17 ሰናክሬም በእስራኤል አምላክ በእግዚአብሔር ላይ ለማፌዝና እርሱንም በመቃወም ለመናገር ደብዳቤዎችንም ጻፈ። "የምድሪቱ ሕዝቦች አማልክት ሕዝባቸውን ከእጄ እንዳልታደጉ እንደዚሁ የሕዝቅያስም አምላክ ሕዝቡን ከእጄ አይታደግም" አለ። 18 ከተማይቱን ለመያዝም በቅጥሩ ላይ የነበሩትን የኢየሩሳሌም ሰዎች ለማስፈራራትና ለማስጨነቅ በአይሁድ ቋንቋ በጎላ ድምጽ ይጮሁ ነበር። 19 የሰዎች የእጅ ሥራ ብቻ በነበሩት በምድር ሌሎች ሕዝቦች አማልክት ላይ እንደተናገሩት በኢየሩሳሌም አምላክም ላይ ተናገሩ። 20 ንጉሡ ሕዝቅያስና የአሞጽ ልጅ ነቢዩ ኢሳይያስ ከዚህ ጉዳይ የተነሳ ፀለዩ፤ ወደ ሰማይም ጮኹ። 21 እግዚአብሔርም መልአክን ላከ፤ እርሱም ተዋጊዎቹን ሰዎች፥ አዛዦቹንና የንጉሡን ባለሥልጣናት በሰፈሩበት ቦታ ገደላቸው። በመሆኑም ሰናክሬም አፍሮ ወደ ገዛ ምድሩ ተመለሰ። ወደ አምላኩ ቤት በገባ ጊዜ እዚያ ከገዛ ራሱ ልጆች አንዳንዱ በሰይፍ ገደሉት። 22 በዚህ መንገድ እግዚአብሔር ሕዝቅያስንና የኢየሩሳሌምን ነዋሪዎች ከአሦር ንጉሥ ከሰናክሬም እጅና ከሌሎች ሁሉ እጅ አዳናቸው፤ በሁሉም መንገድም መራቸው። 23 በርካቶችም ለእግዚአብሔር ሥጦታዎችን፥ የከበሩ ነገሮችንም ለይሁዳ ንጉሥ ለሕዝቅያስ ወደ ኢየሩሳሌም ያመጡ ነበር። እርሱም ከዚያን ጊዜ አንስቶ በሕዝቦች ሁሉ ፊት ከፍ ከፍ አለ። 24 በዚያን ወቅት ሕዝቅያስ ለመሞት እስኪቀርብ ድረስ ታምሞ ነበር። ወደ እግዚአብሔርም ፀለየ፤ እርሱም ተናገረው፤ እንደሚፈወስም ምልክትን ሰጠው። 25 ሕዝቅያስ ግን ልቡ ታብዮ ስለ ነበር እግዚአብሔር ለሰጠው እርዳታ ውለታ ቢስ ሆነ። በመሆኑም በእርሱ፥ በይሁዳና በኢየሩሳሌም ላይ ቁጣ መጣባቸው። 26 ቢሆንም ግን በኋላ ላይ ሕዝቅያስ ስለ ልቡ ትዕቢት እርሱና የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ሁለቱም ራሳቸውን አዋረዱ። የእግዚአብሔርም ቁጣ በሕዝቅያስ ዘመን አልመጣባቸውም። 27 ሕዝቅያስ እጅግ ብዙ ባለጠግነትና ብዙ ክብር ነበረው። ለራሱም ለብር፥ ለወርቅ፥ ለከበሩ ድንጋዮችና ለቅመማ ቅመሞች እንዲሁም ለጋሻዎችና ዋጋ ላላቸው ነገሮች ሁሉ መጋዘኖችን ሠራ። 28 ለእህል፥ ለአዲስ ወይንና ዘይት መጋዘኖች፥ ለሁሉም ዓይነት እንስሳት ጋጣዎችም ነበሩት። 29 በተጨማሪም እግዚአብሔር እጅግ ብዙ ሃብት ስለሰጠው ለራሱ ከተሞችን፥ የተትረፈረፉ የበጎችና የከብቶች መንጋዎች ንብረት አዘጋጀ። 30 የግዮንን የላይኛውን ውሃ ምንጮች የደፈነና በዳዊትም ከተማ በምዕራብ በኩል በቀጥታ ቁልቁል እንዲመጡ ያደረጋቸው ይኸው ሕዝቅያስ ነው። ሕዝቅያስም በሠራው ሥራ ሁሉ ተሳካለት። 31 ነገር ግን በምድሪቱ ስለተደረገው ተዓምራዊ ምልክት የሚያውቁ ሰዎችን ጥያቄ ለመጠየቅ የተላኩትን የባቢሎን መሳፍንት መልዕክተኞችን በተመለከተ ጉዳይ እግዚአብሔር ሊፈትነውና በልቡ ያለውን ለማወቅ ለራሱ ተወው። 32 ሕዝቅያስን በተመለከተ ሌሎቹ ጉዳዮች የቃል ኪዳን ታማኝነት ድርጊቶቹን ጨምሮ በአሞጽ ልጅ በነቢዩ በኢሳይያስ ራዕይና በይሁዳና በእስራኤል ነገሥታት መጽሐፍ መጻፋቸውን መመልከት ትችላላችሁ። 33 ሕዝቅያስ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ በዳዊትም ዝርያዎች መቃብር በኮረብታው ላይ ቀበሩት። የይሁዳና የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ሁሉ በሞቱ ጊዜ አከበሩት። ልጁ ምናሴ በእርሱ ቦታ ነገሠ።

---

2 Chronicles 32:1

ከነዚህ ነገሮች እና ከእነዚህ የታማኝነት ሥራዎች በኋላ
የረቂቅ ስሙ “ታማኝነት” የሚለው “በታማኝነት” ተብሎ ሊገለፅ ይችላል። ኣት: “ ሕዝቅያስ እግዚአብሔር ያዘዘውን ሁሉ በታማኝነት ከፈጸመ በኋላ ” (የረቂቅ ስሞችን:ይመልከቱ)

የአሦር ንጉሥ ሰናክሬም መጣ ፣ እርሱም ሰፈረ
እዚህ ሰናክሬም ሠራዊቱን ይወክላል :: ኣት: - “የአሦር ንጉሥ ሰናክሬም እና ሠራዊቱ መጡ... ሰፈሩ” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከል)

ወደ ይሁዳም ገባ
እዚህ “መጥቷል” ማለት “እንደ ሄደ” ሊገለፅ ይችላል። ኣት: “ሄዶ ወደ ይሁዳ ገባ” (ሂዱ እና ኑን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 32:2

ሰናክሬም መጥቷል ብሎ አሰበ
እዚህ ሰናክሬም ሠራዊቱን ይወክላል :: ኣት: - “ሰናክሬም እና ሠራዊቱ መጥተው አሰቡ” (ሁሉን በአንዱ አንዱን በሁሉ መወከልን :ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ኢየሩሳሌም ለመውጋት
እዚህ “ኢየሩሳሌም” የሚለው እዚያ ያሉትን ሰዎች ይወክላል ። ኣት: - “የኢየሩሳሌምን ሰዎች ለመውጋት” ወይም “በኢየሩሳሌምን ሠራዊት ለመውጋት” (የባህሪ ስሞችን :ይመልከቱ)

ከከተማይቱ ውጭ የነበሩትን የውሃ ምንጮችን ለማቆም
የከተማይቱ ሰዎች ጉድጓዶችንና ምንጮቹን በአፈርና በድንጋይ በመሸፈን ውሃውን ከአሦራውያን ይደብቃሉ ፣ ነገር ግን ህዝቡ ውሃውን በስውር መንገዶች ወደ ከተማው ያስገባሉ ። (አወያይ መጠይቅን :ይመልከቱ)

የአሦር ነገሥታት መጥተው ብዙ ውሃ ስለ ምን ያገኛሉ?
ሰዎቹ የአሦር ነገሥታት ውሃቸውን እንዲያገኙ እንዳልፈለጉ ለማጉላት አወያይ መጠይቅ ይጠቀማሉ ። ጥያቄው እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: - “የአሦር ነገሥታት ወደዚህ እንዲመጡ እና ብዙ ውሃ እንዲያገኙ አንፈልግም።” (አወያይ መጠይቅን :ይመልከቱ)

የአሦር ነገሥታት
ለ “ነገሥታት” ለሚለው ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን አንዱን የአሦር ንጉሥ የሚያመለክት ነው ። ኣት: “የአሦር ንጉሥ” ወይም 2) ይህ ምናልባት ንጉሡንና ሌሎች መሪዎቹን ሊያመለክት ይችላል ። ኣት: - “ንጉሡ እና ሌሎቹ የአሦር መሪዎች” (ፈሊጥን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 32:5

ሕዝቅያስም በድፍረት ሠራ . . . ሠራ ... ሠራ ... ደግሞም ሠራ
አንባቢያን ሕዝቅያስ ምናልባት ሌሎች ሰዎች ሥራውን እንዲሰሩ አዞ ሊሆን እንደሚችል አንባቢዎች ሊገነዘቡ ይገባል ። ኣት: “ሕዝቅያስ በድፍረት ፣ ሕዝቡም እንዲገነቡ አዘዘ ፣ ሠሩ... ደግሞም ሠሩት” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን :ይመልከቱ)

ሕዝቅያስ ደፋር ሆነ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሕዝቅያስ ህዝቡ የከተማይቱን ግንቦች እንዲጠግኑ በማዘዝ አቋሙን አጠናከረ ። አያያዥ የሆነውን “በ” በመጠቀም ይህንን ትርጉም የበለጠ ግልጽ ማድረግ ትችላለህ ። “ኣት” “ሕዝቅያስ ከተማይቱን በመጠገን አጠናከረ” ወይም 2) እርሱ ተበረታታ ። ኣት.: - “ሕዝቅያስ ተበረታቶ ጠገነ ” (አያያዥ ቃላትን :ይመልከቱ)

ሚሎን
ይህ ከኢየሩሳሌም በስተ ሰሜን በኩል የሚገኘው ግድግዳ ክፍል ነው።

2 Chronicles 32:6

በሕዝቡ ላይ የጦር አዛዦችን አስቀመጠ
“ላይ አስቀመጠ” የሚለው ፈሊጥ እርሱ በኃላፊነት ሾመ ማለት ነው። “በሕዝቦች ላይ የጦር አዛዦችን አለቃ አድርጎ ሾመ” (ፈሊጥን :ይመልከቱ)

ከእኛም ጋር ያለው ከእርሱ ጋር ካለው ይበልጣል
“አምላካችን ከእኛ ጋር ስለሆነ ከአሦር ንጉሥ ጋር ካሉት የበለጠ ኃያል ነው”

የሥጋ ክንድ ብቻ ነው
እዚህ “ክንድ” ጥንካሬን ይወክላል ፣ “ሥጋ” ደግሞ ሰብአዊነትን ይወክላል ። ኣት: - “ሰብአዊ ኃይል ያላቸው ብቻ ናቸው” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 32:9

አሁን እርሱ ... ከእርሱ ጋር ነበር
“አሁን” የሚለው ቃል በዋናው የታሪክ መስመር መቋረጡን ለማመልከት እዚህ ጥቅም ላይ ውሏል ። እዚህ ላይ ተራኪው ስለሰናክሬም እና ሠራዊቱ ያሉበትን ቦታ ዳራዊ መረጃ ይነግረናል ። (ዳራዊ መረጃን :ይመልከቱ)

በለኪስ
ይህ በይሁዳ የሚገኝ ከተማ ነበር። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

በኢየሩሳሌም ላይ የተከበበውን ከበባ ለመቋቋም ምን ያህል ትተማመናለህ?
ሰናክሬም ህዝቡ ስለሁኔታቸው እንዲያስቡ ለማድረግ አወያይ ጥያቄ ይጠቀማል ። ጥያቄው እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: - “የኢየሩሳሌምን ከበባ መቋቋም አልቻልክም።” (አወያይ መጠይቅን : ይመልከቱ)

2 Chronicles 32:11

የሚያስታችሁ ሕዝቅያስ አይደለምን .. . የአሦርን ንጉሥ?
ሰናክሬም የኢየሩሳሌም ሰዎች ስላሉበት ሁኔታ እንዲያስቡ አወያይ መጠይቅ ይጠቀማል ። እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: - “ሕዝቅያስ እያሳታችሁ ነው....የአሦር ንጉሥ ።” (አወያይ መጠይቅን :ይመልከቱ)

በራብ እና በጥም እንድትሞቱ ያድርግህ ዘንድ
“በምግብና በውሃ እጥረት ትሞታለህ”

ከአሦር ንጉሥ እጅ
እዚህ “እጅ” ኃይልን ወይም ቁጥጥርን ይወክላል ። ኣት: - “ከአሦር ንጉሥ ኃይል” ወይም “ከአሦር ንጉሥ” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

መሠዊያዎችን ያስወገደ ይሄው ሕዝቅያስ አይደለምን... መሠዊያ?
ሰናክሬም የኢየሩሳሌም ሰዎች ያሉበትን ሁኔታ እንዲያስቡ ለማድረግ አወያይ መጠይቅ ይጠቀማል ።ይህ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: - “መሠዊያዎቹን የፈረሰ ይሄው ሕዝቅያስ ነው።” ”ወይም “ ሕዝቅያስ መሠዊያዎቹን አስወገደ....”

ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን አዘዘ
እዚህ “ይሁዳ” እና “ኢየሩሳሌም” የሚሉት ቃላት የሚቀመጡትን የሚያመለክቱ ናቸው ። ኣት: - “የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን ሕዝብ አዘዘ” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 32:13

አገሮች....ምን እንደሆኑ አታውቁምን?
ሰናክሬም የኢየሩሳሌም ሰዎች ስላላቸው ሁኔታ እንዲያስቡ አወያይ መጠይቅ ይጠቀማል ። እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: - “አገሮች ....ምን እንደሆኑ በደንብ ታውቃላችሁ!” (አወያይ መጠይቅን :ይመልከቱ)

አማልክቱ... ኃይል?
ሰናክሬም የኢየሩሳሌም ሰዎች ስለ ንግግራቸው እንዲያስቡ ለማድረግ አወያይ መጠይቅ ይጠቀማል ። እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: - “ከአማልክት ሁሉ አምላክ የለም... ማን ... ከኃይሌ!” (አወያይ መጠይቅን :ይመልከቱ)

ከአማልክት ሁሉ መካከል... አምላክ አለን...እጅ?
ሰናክሬም የኢየሩሳሌም ሰዎች ስለሁኔታቸው እንዲያስቡ አወያይ መጠይቅ ይጠቀማል ። እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: - “በአማልክት ሁሉ መካከል አምላክ የለም... የሚገዛ... በእጅ...!” (አወያይ መጠይቅን : ይመልከቱ)

ከእጄ
እዚህ “እጅ” ኃይልን ወይም ቁጥጥርን ይወክላል ። ኣት: - “ከኃይሌ” ወይም “ከእኔ”(የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

አምላካችሁ እንዴት ይችላል ....ኃይል ?
ሰናክሬም የኢየሩሳሌም ሰዎች ስለ ንግግራቸው እንዲያስቡ አወያይ መጠይቅ ይጠቀማል ። እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: - “አምላካችሁ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የሚቻልበት ምንም ምክንያት የለም... ኃይል !” (አወያይ መጠይቅን ፡ ይመልከቱ)

አሁን
እዚህ “አሁን” የሚለው ቃል ወደሚቀጥለው አስፈላጊ ነጥብ ትኩረትን ለመሳብ ይጠቅማል ።

አምላክሽ ከእጄ የማዳኑ እድል እጅግ ያነሰ ነው?
ሰናክሬም የኢየሩሳሌም ሰዎች ያሉበትን ሁኔታ እንዲያስቡ ለማድረግ አወያይ መጠይቅ ይጠቀማል ። እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። አት: - “አምላክህ በእርግጥ ከእጄ ሊያድንህ አይችልም!” (አወያይ መጠይቅን ፡ ይመልከቱ)

2 Chronicles 32:16

ከእጄ ውጪ
እዚህ “እጅ” ኃይልን ወይም ቁጥጥርን ይወክላል ። አት: - “ከኃይሌ” ወይም “ከእኔ”(የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 32:18

ጮኹ
“የሰናክሬም አገልጋዮች ጮክ ብለው ጮኹ”

እነርሱን ለማስፈራራት እና እነርሱን ለማስጨነቅ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ አንድ ዓይነት ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ የፍርሃትን ጥልቀት አፅንዖት ይሰጣሉ ። አት: - “እነርሱን በጣም እንዲፈሩ ለማድረግ” (ድግግሞሽን ፡ይመልከቱ)

ሊይዙ ይችላሉ
“የአሦራውያን ሠራዊት ሊይዝ ይችላል”

በምድር አሕዛብ አማልክት ላይ እንደሚናገሩ መጠን በኢየሩሳሌም አምላክ ላይ ተናገሩ
“በሌሎች አገር ሕዝቦች አማልክት ላይ እንዳተሳለቁት የኢየሩሳሌምን አምላክ አፌዙበት”

የሰዎች እጅ ሥራ ብቻ ናቸው
ይህ የሰዎች እነዚህን ጣዖታት በገዛ እጆቻቸው እንደሠሩ እና በዚህም ምክንያት ዋጋ ቢስ እንደሆኑ አጽንዖት ይሰጣል ። አት: - “ሰዎች የሰሯቸው ጣዖታት ናቸው” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 32:20

ወደ ሰማይ ጮኸ
እዚህ “ሰማይ” የሚለው እግዚአብሔርን ይወክላል ። አት: - “እግዚአብሔር እንዲረዳቸው ወደ እግዚአብሔር ጮኹ” ወይም “ወደ እግዚአብሔር ተማጸኑ” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

በፊቱ ላይ በሃፍረት
“አፈሩ” ወይም “ተሳቀቁ”

የአምላኩ ቤት
'የአምላኩ ቤተ መቅደስ'

2 Chronicles 32:22

ከሰናክሬም እጅ ... ከሌሎች ሁሉ እጅ
እዚህ “እጅ” ኃይልን ወይም ቁጥጥርን ይወክላል ። አት: - “ከሰናክሬም ኃይል... ከሌሎቹ ሁሉ ኃይል” ወይም “ከሰናክሬም... ከሌሎቹ ሁሉ” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

በሁሉም ወገን እረፍት ሰጣቸው
“እረፍት” የሚለው ረቂቅ ስም “ሰላም” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። አት “በዙሪያቸው ካሉ አገራት ሁሉ ጋር በሰላም እንዲኖሩ አድርጓቸዋል” (የረቂቅ ስሞችን ፡ይመልከቱ)

በሁሉም አገራት ፊት ከፍ ከፍ አለ
እዚህ “ከፍ ከፍ” የሚለው ፈሊጥ ሲሆን ክብር ማለት ነው ። ደግሞም “ፊት” ፍርድን ወይም ምዘናን የሚወክል ዘይቤ ነው ። አት: - “የሁሉም አገራት ሰዎች አከበሩት” (ፈሊጥን እና ዘይቤያዊን ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 32:24

እንዲድን
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “ሕዝቅያስን እንዲፈውሰው” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ይመልከቱ)

ሕዝቅያስ ግን እንደ ተቀበለው ቸርነት መጠን ለእግዚአብሔር አላደረገም
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። አት : “ግን ሕዝቅያስ እግዚአብሔር ከረዳው በኋላ እንደ አመስጋኝ ሰው አልኖረም” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ይመልከቱ)

ልቡ ከፍ ከፍ አለ
እዚህ “ልብ” የሚለው ዘይቤአዊ አነጋገር ሲሆን የሰውን ውስጣዊ ማንነት የሚያመለክት ነው ። እዚህ “ልብ ከፍ ከፍ ብሏል” ማለት ኩራት ማለት ነው ። አት: “ትዕቢተኛ ሆነ” (የባህሪ ስምን እና ፈሊጥን፡ይመልከቱ)

ስለዚህ በእርሱ ላይ እና በይሁዳና በኢየሩሳሌም ላይ ቁጣ ሆነባቸው
እግዚአብሔር ተቆጥቶ ሕዝቡን መቅጣቱ “ቁጣ እንደወረደባቸው” ተደርጎ ተነግሯል። “ይሁዳ” እና “ኢየሩሳሌም” በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች የሚወክሉ መግለጫዎች ናቸው ። አት: ስለዚህ “እግዚአብሔርም ተቆጣ እርሱንም የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ቀጣ” (ዘይቤያዊን እና የባህሪ ስምን ፡ ይመልከቱ)

በሕዝቅያስ ዘመን
“በሕዝቅያስ የሕይወት ዘመን” ወይም “ሕዝቅያስ በገዛበት ዘመን”

2 Chronicles 32:27

ጋጣ
ይህ ፈረሶችን ማሳደሪያ አነስተኛ ቦታ ነው ። ይህንን በ 2 ኛ ዜና መዋዕል 9 ፡ 25 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

በረት ሠራ
አነስተኛ እንስሳትን ማሳደሪያ ቦታ ነው።

2 Chronicles 32:30

ሕዝቅያስ ደግሞ ደፈነ .....እርሱ አቅንቶ አወረደው
ምናልባት ሕዝቅያስ ሌሎች ሰዎች ሥራውን እንዲሰሩ አዞ ሊሆን እንደሚችል አንባቢዎቹ ሊገነዘቡ ይገባል ። አት: - “ሕዝቅያስ ሠራተኞቹ ውሃውን እንዲደፍኑ እና ... ውሃው እንዲወርድ ቱቦ እንዲሰሩ አዘዘ ” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

የጊዮንን ውሃ
ይህ በኢየሩሳሌም አቅራቢያ ያለ ዥረት ስም ነው። (የስሞችን አተረጓጎም ፡ ይመልከቱ)

በምድሪቱ የተከናወነው ተአምራዊ ምልክት
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “እግዚአብሔር በምድሪቱ ላይ ያደረገውን ተአምር” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ይመልከቱ)

በልቡ ውስጥ ያለውን ሁሉ ለማወቅ
እዚህ “ልብ” የሰውን ውስጣዊ ማንነት ያሳያል ። ኣት: - “የሕዝቅያስን እውነተኛ ባሕርይ ለመግለጥ” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 32:32

ሕዝቅያስ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ
ይህ ስለ ሞቱ የሚነገርበት ትህትና ያለው መንገድ ነበር ። ይህንን በ 2 ኛ ዜና መዋዕል 9፡ 31 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። ኣት: “ሕዝቅያስ ሞተ” (ዘወርዋራን :ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 33

1 ምናሴ መንገሥ በጀመረ ጊዜ አሥራ ሁለት ዓመቱ ነበር፤ በኢየሩሳሌም ሃምሳ አምስት ዓመት ነገሠ። **2** እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ፊት እንዳስወጣቸው ሕዝቦች ዓይነት አስጸያፊ ነገር በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገር አደረገ። **3** አባቱም ሕዝቅያስ ያፈረሳቸውን የኮረብታውን መስገጃዎች እንደገና ገነባ፤ ለበኣልም መሠዊያዎችን ሠራ፤ የማምለኪያ ዐፀዶችንም አቆመ፤ ለሰማይም ከዋክብት ሁሉ ሰገደ፤ አመለካቸውም። **4** ምንም እንኳን እግዚአብሔር፦ "ስሜ ለዘላለም የሚኖረው በኢየሩሳሌም ነው" ብሎ ያዘዘ ቢሆንም በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ለጣዖታት መሠዊያዎችን ገነባ። **5** በእግዚአብሔር ቤት ሁለቱ አደባባዮች ውስጥ ለሰማይ ከዋክብት ሁሉ መሠዊያዎችን ሠራ። **6** በሄኖም ልጅ ሸለቆ ውስጥ ልጆቹን በእሳት ውስጥ እንደሚቃጠል መሥዋዕት አቀረበ፤ ሞራ ገላጭ ሆነ፤ አስማት አደረገ፤ መተተኛም ነበረ፤ ከሙታን ጋር ከሚነጋገሩና ከመናፍስት ጋር ከሚነጋገሩ ጋር ይማከር ነበር። በእግዚአብሔር ፊት እጅግ ክፋት በመለማመድ እግዚአብሔርን ለቁጣ አነሳሳ። **7** የአሼራን የተቀረጸ ምስል ሠርቶ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ አኖረው፤ እግዚአብሔር ለዳዊትና ለልጁ ለሰለሞን ሲናገር፦" ከእስራኤል ነገዶች ሁሉ ስሜ ለዘላለም እንዲኖርበት የመረጥኩት በዚህ ቤትና በኢየሩሳሌም ነው" ብሎ የነበረው ስለዚህ ቤት ነበር። **8** በሙሴ አማካይነት የሰጠኋቸው ሕግ፥ ደንቦችና ድንጋጌዎች በመከተል ያዘዝኳቸውን ሁሉ ለመጠበቅ ቢጠነቀቁ ለአባቶቻቸው ከመደብኩላቸው ምድር የእስራኤልን ሕዝብ ከዚህ በኋላ አላወጣም" ብሎ ነበር። **9** ምናሴም የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን ነዋሪዎች እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ፊት ካጠፋቸው ሕዝቦች የበለጠ ክፋትን እንዲያደርጉ መራቸው። **10** እግዚአብሔርም ምናሴንና ሕዝቡን ተናገራቸው፤ ነገር ግን አልሰሙትም። **11** በመሆኑም የአሦርን ንጉሥ ሠራዊት አዛዦች አመጣባቸው፤ ምናሴንም በእግር ብረት ያዙት፤ በሰንሰለት አሰሩት፤ ወደ ባቢሎንም ወሰዱት። **12** ምናሴ በተጨነቀ ጊዜ አምላኩን እግዚአብሔርን ተማፀነ፤ በአባቶቹም አምላክ ፊት ራሱን እጅግ አዋረደ። **13** ወደ እርሱም ፀለየ፤ እግዚአብሔርም ተለመነው። እግዚአብሔር ልመናውን ሰምቶ ወደ ኢየሩሳሌም ወደ ንግሥናው መለሰው። ምናሴም እግዚአብሔር እርሱ አምላክ እንደሆነ አወቀ። **14** ከዚህ በኋላ ምናሴ በዳዊት ከተማ በግዮን ምዕራብ በኩል በሸለቆው ውስጥ እስከ ዓሣው በር መግቢያ ድረስ የውጫዊውን ግንብ ገነባ። የኦፌልንም ኮረብታ በእርሱ ከበበው። ግንቡንም እጅግ ታላቅ ከፍታ ድረስ አነሳው። በተመሸጉት በይሁዳ ከተሞች ሁሉ ደፋር አዛዦችን አኖረ። **15** የባዕድ አማልክትን ጣዖቱንም ከእግዚአብሔር ቤት አስወገደ፤ በእግዚአብሔር ቤት ተራራ ላይና በኢየሩሳሌም ውስጥ የገነባቸውን መሠዊያዎች ከከተማው ውጪ ወረወራቸው። **16** የእግዚአብሔርም መሠዊያ አደሰ፤ የሕብረት መሥዋዕትና የምሥጋናን መሥዋዕት ሥጦታዎች አቀረበበት፤ የይሁዳ ሕዝብ የእስራኤልን አምላክ እንዲያገለግሉ አዘዘ። **17** ነገር ግን ሕዝቡ እስከ አሁንም በኮረብታው መስገጃዎች ላይ ይሰዋ ነበር፤ ነገር ግን ለአምላካቸው ለእግዚአብሔር ብቻ ነበር። **18** ምናሴን የሚመለከቱት ሌሎች ነገሮች ወደ አምላኩ የፀለየው ፀሎትና በእስራኤል አምላክ በእግዚአብሔር ስም የተናገሩት የነቢያት ቃል እነሆ በእስራኤል ነገሥታት ድርጊቶች መካከል ተጽፈዋል። **19** ፀሎቱም እግዚአብሔርም እንዴት እንደተለመነው፥ ኃጢአቱና መተላለፉ ሁሉ ራሱንም ከማዋረዱ በፊት የኮረብታ መስገጃዎች የገነባባቸው፥ የማምለኪያ አጸዶችንና የተቀረጹትን ምስሎች ያቆመባቸው ቦታዎች በባለ ራዕዮቹ ታሪክ መጽሐፍ ተጽፎአል። **20** ምናሴም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ በገዛ ራሱ ቤት ውስጥ ቀበሩት። ልጁም አሞጽ በእርሱ ቦታ ነገሠ። **21** አሞጽ መንገሥ በጀመረ ጊዜ እድሜው ሃያ ሁለት ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ሁለት ዓመት ነገሠ። **22** አባቱ ምናሴ እንዳደረገ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገር አደረገ። አሞጽ አባቱ ምናሴ ለሠራቸው ለተቀረጹ ምስሎች ሁሉ ሠዋ፤ አመለካቸውም። **23** አባቱ ምናሴ እንዳደረገ በእግዚአብሔር ፊት ራሱን አላዋረደም። ይልቁንም ይኸው አሞጽ መተላለፉን ይበልጥ ጨመረው። **24** አገልጋዮቹ በእርሱ ላይ አሲረው በገዛ ቤቱ ውስጥ ገደሉት። **25** የምድሪቱ ሕዝብ ግን በንጉሡ በአሞጽ ላይ ያሴሩበትን ሰዎች ሁሉ ገደሉ፤ ልጁንም ኢዮስያስን በእርሱ ቦታ አነገሡት።

---

2 Chronicles 33:1

በእግዚአብሔርም ፊት ክፉ የሆነውን ነገር
እዚህ የእግዚአብሔር “እይታ” የሚያመለክተው የእርሱን ፍርድ እና ምዘና ነው። በ 2 ኛ ዜና 14 ፡ 2 ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት ። ኣት: - “እግዚአብሔር ከፉ ነው ያለው ነገር” ወይም “እግዚአብሔር ክፋት እንደሆኑ የቆጠራቸው ነገሮች” (ዘይቤያዊን ፡ይመልከቱ)

እንደ አስጸያፊ ነገሮች
ሌላ አማራጭ ትርጉም “አስጸያፊ ነገሮችን” ጨምሮ ።

በኮረብታ ላይ የነበሩትን መስገጃዎች ሠራ ፤ መሠዊያዎችን ሠራ ፤ መሠዊያዎችን ሠራ ፤ የማምለኪያ ዐፀዶችንም ተከለ
ምናሴ ሠራተኞቹን ግንባታውን እንዲሠራለት አዞ ይሆናል ። ኣት: - “የኮረብታውን መስገጃዎች መልሶ አሠራ ፣ መሠዊያዎችን አወራ… የማምለኪያ አጸዶቹንም አሠራ” ወይም “ሠራተኞቹ የኮረብታውን መስገጃዎች እንዲሠሩ ፣ መሠዊያውንም እንዲሠሩለት አደረገ … የማምለኪያ አጸዶቹንም እንዲሠሩለት አደረገ” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 33:4

ስሜ ለዘላለም በኢየሩሳሌም ይኖራል
ስሙ ግለሰቡን የሚተካ ነው። ኣት: - “በኢየሩሳሌም ለዘላለም ማን እንደ ሆንኩ እገልጣለሁ” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ቤት በሁለቱ አደባባዮች ላይ ለሰማይ ኮከቦች ሁሉ መሠዊያዎችን ሠራ
ሰዎች ከዋክብትን እንዲያመልኳቸውና እና እንዲሰውላቸው እእነዚህን መሠዊያዎች ማሠራቱ ተጠቁሟል። ደግሞም ፣ እነዚህን መሠዊያዎች ራሱ አልሠራም ፣ ይልቁንም ሠራተኞቹን እንዲሠሩ አዝዞ ነበር ። ኣት: “ሰዎቹ ከዋክብትን ማምለክ እንዲችሉና መስዋዕት እንዲያቀርቡላቸው በእግዚአብሔር ቤት በሁለቱ ግቢዎች ውስጥ ሠራተኞቹ መሠዊያ እንዲሠሩ አደረገ” (የሚጠበቅ እውቀትን ፣ ያልተገለጸ መረጃን እና የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

በሄኖምም ሸለቆ
ይህ በገሃነም ተብሎም የሚታወቅ በኢየሩሳሌም አቅራቢያ የሚገኝ ቦታ ነው። (የስሞች አተረጓጎም ፡ይመልከቱ)

ልጆቹን በእሳት እንዲያልፉ አደረገ
ልጁን ለምን ወደ እሳት እንዳስገባ እና ይህን ካደረገ በኋላ ምን እንደ ሆነ ግልፅ ማድረግ ሊኖርብህ ይችላል ። ኣት: “ልጆቹን ለአምላኩ መሥዋዕት አድርጎ ልጆቹን በእሳት አቃጠላቸው” (የሚጠበቅ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ፡ይመልከቱ)

አማካሪ
መረጃ ጠይቋል

ሙታን
ይህ የሞቱ ሰዎችን ያመለክታል ። ኣት: - “የሞቱ ሰዎች” ወይም “ሙታን”(ስማዊ ቅጽልን ፡ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምናሴ በእግዚአብሔር ፊት እጅግ ክፉ ነገር አደረገ
እዚህ የእግዚአብሔር “እይታ” የሚለው የሚያመለክተው እርሱ አንድን ነገር እንዴት እንደሚመዝን ነው። በ 2 ኛ ዜና 14፡ 2 ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት ። ኣት: - “ምናሴ እግዚአብሔር ክፉ ነው ብሎ የተናገራቸውን ብዙ ነገሮች አደረገ” ወይም “እግዚአብሔር ክፉ እንደሆኑ የወሰናቸውን ነገሮች አደረገ” (ዘይቤያዊን ፡ይመልከቱ)

አስቆጣው
“ምናሴ እግዚአብሔርን እጅግ አሳዘነ”

2 Chronicles 33:7

እርሱ ሠራው
ምናሴ ሥራውን አልሠራ ይሆናል። አገልጋዮቹ ሥራውን ሠርተው ይሆናል። ኣት: - “ምናሴ ሠራተኞቹን እንዲሠሩ አዘዘ” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

ስሜን ለዘላለም አኖራለሁ
እዚህ እግዚአብሔር “በስሙ” ተወክሏል። ኣት: “ሰዎች ለዘላለም እንዲያመልኩኝ በፈለግኩበት ቦታ” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

ለአባቶቻቸው ሰጠኋቸው
ለአባቶቻቸው የሰጠኋቸው ”

ይሁዳ እና የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች
እዚህ “ኢየሩሳሌም”የ “ይሁዳ” አንድ አካል ነው። ኣት: “የይሁዳና የኢየሩሳሌም ሰዎች” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን ፡ ይመልከቱ)

እግዚአብሔር በእስራኤል ፊት ካጠፋቸው ከአሕዛብ ይልቅ
እዚህ “አገራት” የሚለው ቃል እስራኤል ከመምጣቱ በፊት በከነዓን ምድር ይኖሩ የነበሩትን ሰዎች ያመለክታል ። ኣት: “እግዚአብሔር የእስራኤልን ህዝብ ወደ ምድሪቱ ሲገባ እና እየተስፋፉ ሲሄዱ ካጠፋቸው እጅግ የበለጡ ሰዎች” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 33:10

በእነሱ ላይ አመጣ
እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን እንዲያጠቃ ሰራዊቱን ላከ ። ኣት: “በእነርሱ ላይ ጥቃት አመጣባቸው” (የሚጠበቅ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃን ፡ ይመልከቱ)

የአሦር ንጉሥ ሰራዊት አዛዦች
አዛዦች ከወታደሮቻቸው ጋር ነበሩ ። ኣት: - “የአሦር ንጉሥ ሠራዊት አዛዦችና ወታደሮቻቸው” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከል፡ይመልከቱ)

ምናሴን በሰንሰለት አስረው ወደ ባቢሎን ወሰዱት
እዚህ ላይ ምናሴ ወደ ግዞት የተወሰደው እግሩ ታስሮ ነበር።ሰንሰለቶች በእግሮቹ ዙሪያ የተቀመጡ ማሰሪያዎች ነበሩ። ኣት: “ምናሴን ያዘው ፣ በሰንሰለት አሰረው ወደ ባቢሎን እስረኛ አድርገው ወሰዱት።" (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 33:12

ተማጸነ
እርዳታ መለመን

ወደ እርሱም ጸለየ ። እግዚአብሔርም ተለመነው
ሁለተኛው ሐረግ የመጀመሪያው ሐረግ በማጠናከር የምናሴን ጸሎት እውነተኛነት ያስረግጣል ። ይህ በገቢራዊ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: - “ወደ እግዚአብሔር ጸለየ እርሱም ተለመነው” (ድግግሞሽን ፣ ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን፡ይመልከቱ)

ወደ ንግሥናው ገባ
“እንደ ንጉሥ እንደገና ለመግዛት”

2 Chronicles 33:14

አጠቃላይ መረጃ
የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ

ምናሴ ሠራ ... ከበበው ... ወሰደው .... በተራራ ላይ ሠራ
ምናሴ ሕንጻውንና ግንባታውን አልሠራም ፣ይልቅ ሠራተኞቹን እንዲሠሩት አዘዛቸው ። ኣት: “ምናሴ ሠራተኞቹን እንዲሠሩ ... ዙሪያውን ከበቡ... ሠራተኞቹንም እንዲያስወግዱ .....ከዚህ በፊት በተራራው ላይ የሠሩትን ።(የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

ግዮን
ይህ ምንጭና እና የጅረት ስም ነበር ። በ 2ኛ ዜና 32 ፡30 ውስጥ ‹የጊዮን ውኃዎች› የሚለውን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። ኣት: - “የጊዮን ውኃዎች” (የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)

የኦፌል ኮረብታ
በ 2 ኛ ዜና 27፡3 እንዳለው የዚህን ኮረብታ ስም ይተረጉሙ ። (የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)

ግድግዳውን ከፍ አደረጉ
“ግድግዳውን ከፍ አድርጎ ገነባ ”

የተመሸጉ ከተሞች
ይህ በዙሪያቸው ግንብ ያሉባቸውን ከተሞች ያመለክታል ።

ባዕዳን አማልክቱ
'ከሌሎች አገሮች የመጡ የሐሰት አማልክት'

2 Chronicles 33:16

እንደገና ገነባ
ምናሴ ሕንጻውንና ግንባታው አልሠራም ፣ ይልቅ ሠራተኞቹን እንዲሠሩት አዘዘ ። ኣት: - “እንደገና እንዲገነቡ አዘዛቸው” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

ይሁዳን አዘዘ
እዚህ ላይ “ይሁዳ” የሚያመለክተው በዚያ አገር የሚኖሩትን ሰዎች ነው ። ኣት: - “የይሁዳን ሕዝብ አዘዘ” (የባህሪ ስሞችን ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 33:18

እነሆ ፣ በእስራኤል ሥራዎች ... ተጽፈው ነበር
“ማንኛውም ሰው ሥራዎቹን ማየት ይችላል ... እስራኤልን እዚያ እንደተጻፈ ማየት ይችላል”

ተጽፈዋል... ተጽፈውባቸዋል
እነዚህ ሐረጎች በገቢራዊ አረፍተነገሮች ሊገለጹ ይችላሉ። ኣት: - “ሰዎች ጻፏቸው ... ሰዎች ስለእነርሱ ጻፉ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ ይመልከቱ)

የእስራኤል ነገሥታት ሥራ
ይህ በእስራኤል የታሪክ መዝገብ ውስጥ አሁን የማይገኝ ነው ።

በኮረብታው ላይ የነበሩትን መስገጃዎች የሠራበት ፣ የማምለኪያ አጸዶችን እና የተቀረጹ ምስሎችን ያቆመበት ቦታ
ምናሴ ሕንጻውንና ግንባታውን አልሠራም ፣ ይልቅ ሠራተኞቹን እንዲሠሩ አዟል ። ኣት: - “የኮረብታው መስገጃዎች ያሠራበት ፣ እና የማምለኪያ አጸዶቹን እና የተቀረጹ ምስሎችን ያስቆመበት ሥፍራ ፤” ወይም “ሠራተኞቹን የኮረብታ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መስገጃዎቹን እንዲገነቡና የማምለኪያ አጸዶቹን እና የተቀረጹ ምስሎችን እንዲያቆሙ ” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

በባለ ራእዩ ታሪክ መጽሐፍ
ይህ የማይገኝ መጽሐፍ ነው።

ምናሴ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ
ይህ አክብሮት ያለው አገላለጽ ነው። አት: - “ምናሴ ሞተ” (ዘወርዋራን ፡ ይመልከቱ)

በገዛ ቤቱ
“በቤተ መንግሥቱ”

አሞጽ
ይህ የሰው ስም ነው ። (የስሞችን አተረጓጎም ፡ይመልከቱ)

በእርሱ ቦታ ነገሠ
ይህ ፈሊጥ ነው ። ኣት: - “ቀጣዩ ንጉሥ ሆነ” ወይም “የይሁዳ ንጉሥ ሆነ” (ፈሊጥን ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 33:21

ዕድሜ ሃያ ሁለት ዓመት
“ዕድሜው 22 ዓመት” (ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)

በእግዚአብሔርም ፊት ክፉ የሆነውን ነገር አደረገ
እዚህ የእግዚአብሔር “እይታ” የሚያመለክተው አንድን ነገር እንዴት እንደሚመዝን ነው። በ 2 ኛ ዜና 14 ፡ 2 ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት ። ኣት: - “እግዚአብሔር ክፉ ናቸው ያላቸው ነገሮች” ወይም “እግዚአብሔር ክፋ እንደሆኑ የቆጠራቸው ነገሮች” (ዘይቤያዊን ፡ ይመልከቱ)

ይህ አምኖን እጅግ ብዙ ተላለፈ
“አሞን ደጋግሞ ኃጢአት ሠራ” ወይም “አሞጽ ኃጢአት በመሥራት ቀጠለ ”

2 Chronicles 33:24

ለሞት አበቁት
ይህ ፈሊጥ ነው ። ኣት: “እርሱን ገደለው” (ፈሊጥን ፡ይመልከቱ)

በእርሱ ላይ አመፁ
እሱን ለመግደል በስውር ታቅዶ ነበር ”

በእርሱ ቦታ ነገሠ
ይህ ፈሊጥ ነው ። ኣት: - “ቀጣዩ ንጉሥ ሆነ” ወይም “የይሁዳ ንጉሥ ሆነ” (ፈሊጥን ፡ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 34

1 ኢዮስያስ መንገሥ በጀመረ ጊዜ እድሜው ስምንት ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ሠላሳ አንድ ዓመት ነገሠ። 2 በእግዚአብሔር ፊት ትክክለኛውን ነገር አደረገ፤ በአባቱም በዳዊት መንገድ ሄደ፤ ከእርሱም ወደ ቀኝም ወደ ግራም አላለም። 3 በነገሠም በስምንተኛው ዓመት ገና ወጣት እያለ የአባቱን የዳዊትን አምላክ መፈለግ ጀመረ። በአሥራ ሁለተኛው ዓመትም ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን ከኮረብታው መስገጃዎች፥ ከማምለኪያ ዐፀዶቹ፥ ከተቀረጹት ምስሎችና ቀልጠው ከተሠሩት ምስሎች ማጽዳት ጀመረ። 4 ሕዝቡ የበኣሊምን መሠዊያዎች በእርሱ ፊት አፈረሱ፤ እርሱ ከበላያቸው የነበሩትን የዕጣን መሠዊያዎች ሰባበረ። የማምለኪያ ዐፀዶቹንም ሰባበረ፤ የተቀረጹትን ምስሎች፥ ቀልጠው የተሠሩትንም ምስሎች አፈር እስኪሆኑ ድረስ አደቀቃቸው። ትቢያውንም መሥዋዕት ይሰዉላቸው በነበሩ ሰዎች መቃብር ላይ በተነው። 5 የካህናቶቻቸውንም አጥንቶች በመሠዊያቸው ላይ አቃጠለ። በዚህ መንገድ ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን አጸዳ። 6 በምናሴ፥ በኤፍሬም፥ በስምዖን ከተሞችም እስከ ንፍታሌም ድረስና በዙሪያቸው ባሉት ፍርስራሾች ሁሉ ተመሳሳይ ነገር አደረገ። 7 መሠዊያዎቹን አፈረሰ፤ የማምለኪያ ዐፀዶቹንና የተቀረጹትን ምስሎች አደቀቃቸው፤ በእስራኤል ምድር ሁሉ የዕጣን መሠዊያዎችን ሁሉ ቆራረጠ፤ ከዚያም ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ። 8 ኢዮስያስ ምድሪቱንና ቤተ መቅደሱን ካጸዳ በኋላ በነገሠ በአሥራ ስምንተኛው ዓመት የኤዜልያስን ልጅ ሳፋን፥የከተማይቱንም ገዢ መዕሤያ፥ የታሪክ ጸሐፊውንም የኢዮአካዝን ልጅ ኢዮአክን የአምላኩን የእግዚአብሔርን ቤት እንዲያድሱ ላካቸው። 9 እነርሱም ወደ ሊቀ ካህኑ ወደ ኬልቅያስ ሄደው ሌዋውያኑ፥ የበሮቹ ጠባቂዎች ከምናሴና ከኤፍሬም፥ ከእስራኤል ቅሬታዎች ሁሉ፥ ከይሁዳና ከብንያም ሁሉ፥ ከኢየሩሳሌምም ነዋሪዎች የሰበሰቡትን ወደ እግዚአብሔር ቤት የመጣውን ገንዘብ አደራ ሰጡት። 10 ገንዘቡን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ሥራ በበላይነት ለሚቆጣጠሩት ሰዎች ሰጧቸው። እነዚህ ሰዎች ቤተ መቅደሱን ለሚጠግኑና ለሚያድሱ ሠራተኞች ከፈሏቸው። 11 የተጠረበውን ድንጋይ፥ ለማጋጠሚያ ጣውላ እንጨትና አንዳንድ የይሁዳ ነገሥታት እንዲፈርስ ለተዉት መዋቅር ወራጆች እንዲገዙ ለአናጢዎቹና ግንበኞቹ ከፈሏቸው። 12 ሰዎቹም ሥራውን በታማኝነት ሠሩ። ሥራውን በበላይነት የሚቆጣጠሯቸው ሌዋውያኑ ከሜራሪ ልጆች ኢኤትና አብድዩ፥ ከቀዓትም ልጆች ዘካርያስና ሜሱላም ነበሩ። ሁሉም መልካም የሙዚቃ መሣሪያ ተጫዋቾች የነበሩ ሌሎች ሌዋውያንም ሠራተኞቹን በቅርበት አቅጣጫ ይመሯቸው ነበር። 13 እነዚህ ሌዋውያን የግንባታ ዕቃ የሚሸከሙትንና በሌላም መንገድ የሚሠሩትን ሌሎች ሰዎች ሁሉ ይቆጣጠሩ ነበር። ጸሐፊዎች፥ አስተዳዳሪዎችና የበር ጠባቂዎች የነበሩ ሌሎች ሌዋውያንም ነበሩ። 14 ወደ እግዚአብሔር ቤት የመጣውን ገንዘብ ወደ ውጪ ሲያመጡት ካህኑ ኬልቅያስ በሙሴ በኩል የተሰጠውን የእግዚአብሔርን ሕግ መጽሐፍ አገኘ። 15 ኬልቂያስም ጸሐፊውን ሳፋንን፦" በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የሕጉን መጽሐፍ አግኝቼአለሁ" አለው። ኬልቅያስም መጽሐፉን ወደ ሳፋን አመጣው። 16 ሳፋንም መጽሐፉን ወደ ንጉሡ ወስዶ፦"አገልጋዮችህ በኃላፊነት የተሰጣቸው ማናቸውንም ነገር እያደረጉ ናቸው። 17 በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የተገኘውን ገንዘብ ወደ ውጪ አውጥተው ለተቆጣጣሪዎቹና ለሠራተኞቹ አደራ ሰጥተዋል" በማለት ነገረው። 18 ጸሐፊውም ሳፋን ለንጉሡ ፦"ካህኑ ኬልቅያስ አንድ መጽሐፍ ሰጥቶኛል" ብሎ ነገረው። ከዚያም ለንጉሡ አነበበለት። 19 ንጉሡ የሕጉን ቃላት በሰማ ጊዜ ልብሱን ቀደደ። 20 ንጉሡም ኬልቅያስን፥ የሳፋንንም ልጅ አኪቃምን፥ የሚክያስንም ልጅ ዓብዶንን፥ ጸሐፊውንም ሳፋንን የራሱንም አገልጋይ ዓሳያን፦ 21 "ሄዳችሁ ከተገኘው መጽሐፍ ቃል የተነሳ ለእኔና በእስራኤልና በይሁዳ ለተረፉት ሰዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ጠይቁ። በእኛ ላይ የፈሰሰው የእግዚአብሔር ቁጣ ታላቅ ስለሆነ፥ በውስጡ የተጻፈውን ሁሉ ለመታዘዝ አባቶቻችን የዚህን መጽሐፍ ቃላት ስላልሰሙ ቁጣው ታላቅ ነው። 22 በመሆኑም ኬልቅያስና ንጉሡ ያዘዛቸው ሰዎች (በኢየሩሳሌም በሁለተኛው ክፍል ትኖር ወደ ነበረችው) ወደ ልብሰ ተክህኖ ጠባቂው ወደ ሐስራ ልጅ፥ ወደ ቲቁዋ ልጅ፥ ወደ ሴሌም ሚስት ወደ ነቢይቱ ወደ ሕልዳና ሄዱ፤ እንዲህም ብለው አናገሯት። 23 እርሷም፦"የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር የሚለው ይህንን ነው፦ወደ እኔ ለላካችሁ ሰው ንገሩት፥ 24 "እግዚአብሔር የሚለው ይህንን ነው፦ 'እነሆ በይሁዳ ንጉሥ ፊት ባነበቡት መጽሐፍ ውስጥ የተጻፉትን እርግማን ሁሉ በዚህ ቦታና በነዋሪዎቹ ላይ ጥፋትን ላመጣ ነው። 25 ባደረጓቸው ተግባራት ሁሉ ለቁጣ ሊያነሳሱኝ እኔን ትተው ለሌሎች አማልክት ዕጣንን ከማጠናቸው የተነሳ ስለዚህ ቁጣዬ በዚህ ሥፍራ ላይ ይነድዳል፤ ምንም ነገርም አያቆመውም'" አለቻቸው። 26 ነገር ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመጠየቅ ለላካችሁ ለይሁዳ ንጉሥ የምትሉት ይህ ነው፦" የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ስለ ሰማኸው ቃል፦ 27 ' ልብህ ለስላሳ ስለ ነበርና በዚህ ቦታና በነዋሪዎቹ ላይ እንደሚመጣ የተነገረውን ቃሉን ስትሰማ በእግዚአብሔር ፊት ራስህን ስላዋረድህ፥ ራስህንም በፊቴ አዋርደህ ልብስህንም ቀድደህ በፊቴ ስላለቀስህ እኔም ሰምቼሃለሁ' እግዚአብሔር የሚናገረው ይህ ነው፤ 28 'እነሆ ወደ ዝርያዎችህ እሰበስብሃለሁ፤ በሰላምም ወደ መቃብርህ ትሰበሰባለህ፤ በዚህ ቦታና በነዋሪዎቹ ላይ የማመጣውን የትኛውንም ጥፋት ዓይኖችህ አያዩም'" በመሆኑም ሰዎቹ ይህንን መልዕክት ለንጉሡ መልሰው ወሰዱለት። 29 ከዚያም ንጉሡ መልዕክተኞችን ልኮ የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን ሽማግሌዎች ሁሉ በአንድነት ሰበሰበ። 30 ንጉሡም የይሁዳ ወንዶችና የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ሁሉ፥ ካህናቱም፥ ሌዋውያኑና ከትልቅ እስከ ትንሽ ሕዝቡ ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ቤት ወጡ። በእግዚአብሔርም ቤት የተገኘውን የቃል ኪዳኑን መጽሐፍ ቃል ሁሉ እየሰሙት አነበበላቸው። 31 ንጉሡም በቦታው ቆሞ እግዚአብሔርን ተከትሎ ለመሄድ፥ ትዕዛዛቱን፥ የቃል ኪዳን ድንጋጌዎቹንና ደንቦቹን ለመጠበቅ፥ በሙሉ ልቡና በሙሉ ነፍሱ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጻፉትን የቃል ኪዳኑን ቃላት ለመታዘዝ በእግዚአብሔር ፊት ቃል ኪዳን አደረገ። 32 በኢየሩሳሌምና በብንያም የሚገኙትን ሁሉ በቃል ኪዳኑ እንዲቆሙ አደረጋቸው። የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ለአባቶቻቸው አምላክ ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን በመታዘዝ አደረጉ። 33 ኢዮስያስም የእስራኤል ሕዝብ ከነበረው ምድር ላይ አስጸያፊውን ነገር ሁሉ አስወገደ። በእስራኤልም የነበሩት ሰዎች ሁሉ አምላካቸው እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ አደረጋቸው። በእርሱ ዘመን ሁሉ የአባቶቻቸውን አምላክ እግዚአብሔርን ከመከተል ዘወር አላሉም።

---

2 Chronicles 34:1

ሠላሳ አንድ ዓመት
“31 ዓመት” (ቁጥሮች ፡ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ፊት ትክክል የሆነውን ነገር
እዚህ የእግዚአብሔር “እይታ” የሚያመለክተው በአንድ ነገር ምንነት ላይ እንዴት እንደሚፈርድ ወይም እንደሚወስን ነው። በ 2 ኛ ዜና 14 ፡ 2 ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት ። ኣት: - “እግዚአብሔር ትክክል ያላቸው ነገሮች” ወይም “እግዚአብሔር ትክክል እንደሆኑ የቆጠራቸው ነገሮች” (ዘይቤያዊን ፡ይመልከቱ)

በአባቱም በዳዊት መንገድ ሄደ
ኢዮስያስ የዳዊትን ባሕርይ ማሳየቱ እንደ ዳዊት በአንድ ዓይነት መንገድ ወይም አካሄድ እንደሄደ ተደርጎ ተገልጻል ። ኣት: - “አኗናሩን እንደ አባቱ እንደ ዳዊት አደረገ” ወይም “የአባቱን የዳዊትን ምሳሌ ተከተለ” (ተመልከት/ች: ዘይቤአዊን ፡ይመልከቱ)

ወደ ቀኝም ሆነ ወደ ግራ አልተመለሰም
እግዚአብሔርን ሙሉ በሙሉ መታዘዝ አንድ ሰው በትክክለኛው መንገድ ላይ እንደነበረና ፈጽሞ ከእርሷ እንደማያፈነግጥ ሆኖ ተገልጾአል ። ኣት: - “እግዚአብሔርን የማያስደስተውን ነገር አላደረገም” ወይም “የእግዚአብሔርን ሕግጋት ሙሉ በሙሉ ታዘዙ” (ዘይቤያዊን ፡ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ስምንተኛው ዓመት ... አሥራ ሁለተኛው ዓመት
በ 2 ኛ ዜና 14:2 ይህንን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። (ሕገኛ ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

እስራኤልንና ኢየሩሳሌምን ከተቀረጹትና ከብረት ቀልጠው ከተሠሩት ማጽዳት ጀመረ
ይህ የሚናገረው ኢዮስያስ በይሁዳና በኢየሩሳሌም የሐሰት አማልክትን ለማምለክ ያገለገሉትን ስለማስወገዱ ሲሆን ቦታዎቹን በአካል እንዳፀዳ ተደርጎ ተነግሯል። ኢዮስያስ ሠራተኞቹን እነዚህን ነገሮች እንዲያስወግዱ አዞ ነበር ። ኣት: - “ሠራተኞቹ ከፍ ያሉ የማምለኪያ ሥፍራዎችን ፣የማምለኪያ አጸዶችን፣ የተቀረጹትን እና ቀልጠው የተሠሩትን ምስሎች በማስወገድ ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን በእግዚአብሔር ዘንድ እንደገና ተቀባይነት እንዲያገኙ አደረገ” (ዘይቤያዊን እና የባሕሪ ስምን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 34:4

በፊቱ
“በኢዮስያስ ፊት”

ቆራረጠው... ሰባበረ... በታተነ... አቃጠለ
ኢዮስያስ ሠራተኞቹን እነዚህን ነገሮች እንዲያደርግ አዞ ነበር ። ኣት: - “እንዲቆራርጡ አደረጋቸው... እንዲሰባብሩ አዘዛቸው... እንዲበታትኑ አደርጋቸው... እንዲያቃጥሉ አዘዛቸው” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

አቧራ
በነፋሱ ሊወሰዱ የሚችሉ በጣም ትንሽ ቁርጥራጮች

የካህናታቸውን አጥንቶች በመሠዊያዎቻቸው ላይ አቃጠላቸው
ይህ ማለት በመሠዊያው ላይ ለሐሰት አማልክት መሠዊያ የሚሠዉ ካህናት አጥንቶቻቸው ከዚህ በፊት በሠሯቸው መሠዊያዎች ላይ ይቃጠላሉ ማለት ነው ።

ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን አነጻ
ይህ የሚናገረው ኢዮስያስ ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኙ ስለማድረጉ ሲሆን በአካላዊ ሁኔታ እንዳነጻቸው ተደርጎ ተነግሯል። ኣት: - “ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን እንደገና በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኙ አደረገ” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 34:6

መሠዊያዎችን አፍርሷል ... በታተነ....ቆራረጠ
ኢዮስያስ ሠራተኞቹን እነዚህን ነገሮች እንዲያደርግ አዞ ነበር ። ኣት: - “ሠራተኞቹን መሠዊያዎች እንዲሰባብሩ ፣ እንዲበታትኑ... እንዲቆራርጡ አዘዘ” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

ወደ ዱቄት
“ወደ አፈር” ማለትም ዱቄት እስኪሆኑ ድረስ መከስከስ ማለት ነው ።

2 Chronicles 34:8

አሥራ ስምንተኛው ዓመት
“18ኛ ዓመት” (ህገኛ ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

ኢዮስያስ ምድሪቱንና ቤተ መቅደሱን አነፃ
ይህ የሚናገረው ኢዮስያስ ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኙ ስለማድረጉ ሲሆን በአካላዊ ሁኔታ እንዳነጻቸው ተደርጎ ተነግሯል። ኣት: - “ኢዮስያስ ምድሪቱንና ቤተ መቅደሱን እንደገና በጌታ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኙ አደረገ” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

የኤዜልያስ ልጅ ሳፋን ፣ መዕሤያ ... የኢዮአካዝ ልጅ ኢዮአክ ... ኬልቅያስ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው ። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

በአደራ ተሰጥቶታል
“ገንዘቡን እንዲጠቀምበት ኃላፊነት ሰጠው”

በበሩ ጠባቂዎች በሌዋውያን ተሰብስቦ ወደ እግዚአብሔር ቤት ይገባ ነበር
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ለገለፅ ይችላል ። ኣት: - “በሮቹን የሚጠብቁት ሌዋውያን ያከማቹትን ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ቤት ያመጡ ነበር” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 34:10

በአደራ ሰጡ
“እነርሱ” የሚለው ቃል ኢዮስያስ ወደ ሊቀ ካህኑ ወደ ኬልቅያስ የላከላቸውን ሰዎች ያመለክታል ። በመጀመሪያ ገንዘቡን ሰጡት ከዚያም ሕንፃውን ለሚቆጣጠሩት ሰዎች አከፋፈለ ። ኣት: - “ከኬልቅያስ በአደራ የተሰጠ” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

ገንዘቡ
ይህ ለኬልቅያስ በአደራ በተሰጠ ገንዘብ ላይ የተወሰነውን ይመለከታል ። ኣት: - “የተወሰነ ገንዘብ” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን : ይመልከቱ)

አናጢዎች
እንጨት የሚሰሩ ሠራተኞች

ሰረገሎች
ትላልቅ ቢሞችን ለማገናኘት ያገለግላሉ

ተበላሽቶ ነበር
“እንዲበሰብስ አድርገውት ነበር”

2 Chronicles 34:12

ኢኤት... ሜሱላም
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው ። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

ከሜራሪ
በ 2 ኛ ዜና 29 :12 እንዳለው የዚህን ሰው ስም ተርጉም ። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

ቀዓትም
በ 2 ኛ ዜና 20 :19 እንዳለው የጎሳውን ስም ተርጉም ። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

አብድዩ... ዘካርያስ
በ 2 ኛ ዜና 17 ፡ 7 ውስጥ የእነዚህን ሰዎች ስሞች ለሌሎች ሰዎች እንደተረጎምከው ተመሳሳይ ስም አድርገህ ተርጉም ። (የስሞችን አተረጓጎም : ይመልከቱ)

እነዚህ ሌዋውያን የግንባታ ቁሳቁሶችን የሚሸከሙትን እንዲሁም በማንኛውም መንገድ የሚሰሩትን ሰዎች ሁሉ ይቆጣጠሩ ነበር
ይህ ማለት ማንኛውንም ዓይነት የግንባታ ሥራ ለሚያደርጉ ወንዶች ሁሉ ኃላፊ ነበሩ ማለት ነው ። ኣት: - “እነዚህ ሌዋውያን ማንኛውንም ዓይነት የግንባታ ሥራ በሚሠሩ ሰዎች ሁሉ ላይ ተሾመው ነበር” (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 34:14

አጠቃላይ መረጃ
የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እነርሱ ወደ እግዚአብሔርም ቤት የቀረበውን ገንዘብ ባመጡ ጊዜ
“እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኬልቅያስንና እሱን የሚረዳውን ሰው ነው ። ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ለተቆጣጣሪዎቹ ገንዘብ ባወጡ ጊዜ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

በሙሴ በኩል የተሰጠው
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “እግዚአብሔር በሙሴ በኩል ለሕዝቡ በሰጣቸው ጊዜ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

ሳፋን
ይህ የሰው ስም ነው ። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

የሕጉ መጽሐፍ
እነዚህ ሕጎች በአንድ ጥቅልል የመጻፍ እድላቸው ከፍተኛ ነው። ጥቅልል የመጽሐፍ ዓይነት ሲሆን ከአንድ ጊዜ የተጠቀለለ ፓፒረስ ወይም ቆዳ የሚሠራ ነበር።

በአደራ የተሰጣቸውን ነገር ሁሉ
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “አንተ እንዲያደርጉት በአደራ የሰጠሃቸውን ነገሮች ሁሉ” ወይም “እንዲሠሩ ኃላፊነት የሰጠሃቸውን ነገሮች ሁሉ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 34:17

ባዶ አደረጉ
ይህ ፈሊጥ ነው ። ኣት: - “ሁሉንም ሰብስበዋል” (ፈሊጥን :ይመልከቱ)

በአለቆችና በሠራተኞቹ እጅ
የእነርሱን ንብረት አፅንዖት ለመስጠት ተቆጣጣሪዎችና ሠራተኞች በ “እጅ” ተወክለዋል ። ኣት: - “ለአለቆችና ለሠራተኞቹ” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን ሁሉ መወከልን :ይመልከቱ)

ይህ በሆነ ገዜ
ይህ ሐረግ በታሪኩ ውስጥ አንድን አስፈላጊ ክስተት ለማመልከት እዚህ ጥቅም ላይ ውሏል ። ቋንቋህ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ መጠቀም ትችላለህ ።

ልብሱን ቀደደ
ይህ የከባድ ሀዘን ወይም መከፋት አመልካች ድርጊት ነው። ኣት: “በጣም ስለተበሳጨ ልብሱን ቀደደ” (ምሳሌያዊ ድርጊት :ይመልከቱ)

2 Chronicles 34:20

የሳፋን ልጅ አኪቃም ፣ የሚክያስ ልጅ አብዶን ፣ ሳፋንን ... አሳያ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው ። (የስሞች አተረጓጎም :ይመልከቱ)

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለእኔ ጠይቁ
“ፈቃድ” የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል ። ደግሞም ፣ በ 2 ኛ ዜና 34 ፡22 በግልፅ እንደተጠቀሰው ንጉሡ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ነብያት ሄደው የጌታን ፈቃድ ለይተው እንዲያውቁ ረዱቷቸዋል ። ኣት: - “ምን እንዳደርግ እንደሚፈልግ እግዚአብሔርን ጠይቅ” (የረቂቅ ስሞችን : ይመልከቱ)

ስለተገኘው ቃል
“ስለተገኘው ቃል ”

የተገኘው የመጽሐፉ ቃል
እዚህ “ቃል” ህግጋትን ይወክላል ። ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ኬልቅያስ በገኘው መጽሐፉ ውስጥ ያሉ ሕግጋት” (የረቂቅ ስሞችን እና ገቢራዊ ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

በእኛ ላይ የፈሰሰው የእግዚአብሔር ቁጣ ታላቅ ነውና። ታላቅ ነው
እንደ ቁጣ ያሉ ስሜቶች ብዙውን ጊዜ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እንደ ፈሳሽ ይናገራሉ ። ኣት: - “ የእግዚአብሔር ቁጣ በእኛ ላይ ታላቅ ነው፣ እንደ ውኃ ጠራርጎ ሊወስደን ይችል ነበር። በእኛ ላይ ታላቅ ነው ፣ እንደ ውሃ ሙሉ በሙሉ አጥቦ ሊወስደን ይችላል”ወይም“ እግዚአብሔር እኛን ይቀጣበት ቁጣው ታላቅ ነውና ” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

የተጻፈውም ሁሉ በእርሱ ነው
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “በእርሱ ላይ የተጻፈው ሁሉ” ወይም “በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያለው ሁሉ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 34:22

ሕልዳና
ይህ የሴት ስም ነው ። (የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)

ሴሉም... ቲቁዋ... ሓስራ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው ። (የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)

የልብስ ጠባቂ
ይህ ሴሌምን ይመለከታል ። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) በቤተመቅደስ ውስጥ ካህናት የሚለብሱትን ልብስ የሚጠብቅ ሰው ወይም 2) የንጉሡን ልብስ በአግባቡ የሚጠብቅ ።

ሁለተኛው አውራጃ
ይህ የኢየሩሳሌም ክፍል ነው። ምናልባት አዲስ ክፍል ሊሆን ይችላል። ኣት: “ሁለተኛው ክፍል” (ሕገኛ ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

በዚህ መንገድ አነጋገራት
“የሚከተለውን ውይይት ከእርሷ ጋር አደረጉ”

2 Chronicles 34:23

ወደ እኔ የላከውን ሰው
እዚህ ላይ “ሰው” የሚለው የሚያመለክተው ንጉሥ ኢዮስያስን ነው።

እነሆ
እዚህ ቃሉ ጥቅም ላይ የዋለው እንደ አነጋገር ዘይቤ ሆኖ ሲሆን የአድማጮቹን ትኩረት ቀጥሎ ወደ ተናገረው ለመሳብ አገልግሏል ። ኣት: - “አዳምጥ” (ፈሊጥን :ይመልከቱ)

በዚህ ስፍራና በነዋሪዎቿ ላይ ጥፋት አመጣለሁ
እግዚአብሔር አስከፊ ነገሮችን እንዲከሰት ስለማድረጉ ሲነገር ጥፋት ወደ አንድ ቦታ ሊያመጣው የሚችል ነገር እንደሆነ ተደርጎ ተገልጾአል ። ኣት: - “በቅርቡ በዚህ ቦታ እና በነዋሪዎቹ ላይ አስከፊ ነገሮች እንዲደርሱ አደርጋለሁ” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

እዚህ ቦታ ላይ
“በኢየሩሳሌም” ይህ የይሁዳን ምድር በሙሉ የምትወክለውን የኢየሩሳሌምን ከተማ ያመለክታል ። ኣት: - “በይሁዳ ላይ” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን :ይመልከቱ)

የተጻፉትን እርግማኖች ሁሉ
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “የተጻፉን እርግማኖች ሁሉ” ወይም “እርግማኖችን ሁሉ ” (ገቢራዊ ወይም ተብሮአዊ :ይመልከቱ)

እንድቆጣ አድርገውኛል
“አስቆጡኝ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ስለዚህ ቁጣዬን በዚህ ስፍራ ላይ ይፈሳል ፣ ደግሞም አይጠፋም
እንደ ቁጣ ያሉ ስሜቶች ብዙውን ጊዜ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እንደ ፈሳሽ ይናገራሉ ። ኣት: - “ስለዚህ በዚህ ስፍራ ላይ ቁጣዬ እንደ እሳት ነው ፣ ምንም ነገር አያቆመውም” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

ቁጣዬ ይፈስሳል
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ቁጣዬን አወርዳለሁ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን:ይመልከቱ)

እዚህ ቦታ ላይ
እዚህ “እዚህ ቦታ” የሚያመለክተው እዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ነው ። ኣት: - “በእነዚህ ሰዎች ላይ” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 34:26

ስለ ሰማኸው ቃል
“ስለ ሰማኸው መልእክት”

ልብህ ገር ሆኗልና
እዚህ “ልብ” የሰውን ውስጣዊ ማንነት ይወክላል ። የሚያዝን ልብ ገር ተብሏል ። ኣት: - “ስለተጸጸትክ” ወይም “ንስኃ ስለገባህ”(የባህሪ ስምን እና ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

ልብሶቻችሁን ቀደዳችሁ
ይህ ከባድ ሀዘንን ወይም መከፋትን የሚያመለክቱ ምሳሌያዊ ድርጊቶች ነው። (ምሳሌያዊ ድርጊትን :ይመልከቱ)

ይህ የእግዚአብሔር ቃል ነው
እርሱ ስለሚናገረው ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ እግዚአብሔር ስለ ራሱ በስሙ ይናገራል ። ኣት: - “እግዚአብሔር ያወጀው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርኩት የህ ነው” (አንደኛ ፣ ሁለተኛና ሦስተኛ መደብ ሰብዓዊን :ይመልከቱ)

እነሆ ወደ አባቶችህ እሰበስብሃለሁ። በሰላም ወደ መቃብርህ ትሰበሰባለህ
ሁለቱም መግለጫዎች በመሠረቱ አንድ ዓይነት ናቸው ። ይሞታል የሚለውን በአክብሮት የሚገልጹ ናቸው ። ኣት: - “ስለሆነም እንድትሞት እና በሰላም እንድትቀበር እፈቅድልኃለው” (ምስስልን እና ዘወርዋራን :ይመልከቱ)

ወደ መቃብርህ ትሰበሰባለህ
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ወደ መቃብርህ እሰበስብሃለሁ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

ዓይኖችህ አያዩም
እዚህ “ዐይን” ሙሉ ሰውን ይወክላል ። ደግሞም “አያዩም” የሚለው ሐረግ የሆነን ነገር አለመለማመድን ያሳያል ። ኣት: - “አይደርስብህም”(ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን እና የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

በዚህ ስፍራ የማመጣው ጥፋት
እግዚአብሔር አስከፊ ነገሮችን እንዲከሰቱ የሚያደርግ መሆኑ ጥፋት እግዚአብሔር ወደ አንድ ቦታ የሚያመጣ ቁስ እንደሆነ ተደርጎ ተገልጻል ። ኣት: - “በዚህ ስፍራ ላይ አስከፊ ነገሮችን እንዲከሰቱ አደርጋለሁ” (ዘይቤያዊን : ይመልከቱ)

2 Chronicles 34:29

የይሁዳ ሰዎች ሁሉ እና የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ሁሉ
ይህ አጠቃላይ ነው ። ኣት: - “ሌሎች ብዙ ሰዎች” (ግነትን እና አጠቃላይን : ይመልከቱ)

ከታላቅ እስከ ትንሽ
ይህ በመካከላቸው ያሉትን ሁሉ የሚያካትት አገላለጽ ነው። ኣት: - “ከታላላቆች እስከ ታናናሾች ድረስ” (ሜሪዝምን :ይመልከቱ)

ከዚያም በችሎታቸው አነበበ
“ከዚያም ንጉሡ መስማት እንዲችሉ ጮክ ብሎ ያነባል”

የተገኘውን
ይህበገቢራዊቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። ኣት: - “ኬልቅያስ እንዳገኘው” ወይም “ያገኘውን”(ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 34:31

በእርሱ ቦታ ቆመ
ይህ ንጉሡ በቤተ መቅደሱ የቆመበትን ቦታ ያመለክታል ። ኣት: - “በቤተ መቅደሱ መግቢያ በር ሊቆም በተገባው ቦታ ቆመ” (የሚጠበቅ እውቀትን ወይም ያልተገለጸ መረጃን :ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን ተከተል
የአንድ ሰው አኗኗር የሚጓዝበት መንገድ እንደሆነ ተደርጎ ተገልጾአል አንድን ሰው “እየተከተሉ መጓዝ” ያ ሰው የሚያደርገውን ነገር ለማድረግ መፈለግን ወይም ሌሎች እንዲያደርጉ የሚፈልገውን ነገር የሚያሳይ ነው ። ኣት: - “እግዚአብሔርን በመታዘዝ ኑሩ” (ዘይቤያዊን ወይም የባህሪ ስምን : ይመልከቱ)

ትእዛዛቱን ፣ ሥርዓቱንና ደንቦቹን
እነዚህ ቃላት ሁሉም ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው ። በአንድነት እግዚአብሔር በሕጉ ውስጥ ያዘዛቸውን ነገሮች ሁሉ ያጎላሉ ። (ድግግሞሽን :ይመልከቱ)

በፍጹም ልቡ እና በሙሉ ነፍሱ
የቃሉ ፈሊጥ “በፍጹም ልቡ” ማለት “ሙሉ በሙሉ” ማለት ሲሆን “በሙሉ ነፍሱ” ማለት ደግሞ “በሁለንተናው” ማለት ነው ። እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው ። ኣት: - “በሁለንተናው” ወይም “በሙሉ ኃይሉ” (ፈሊጥን እና ድግግሞሽን :ይመልከቱ)

በዚህ መጽሐፍ የተጻፈውን
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። ኣት: - “ይህ መጽሐፍ እንደያዘ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

በኢየሩሳሌምም ሆነ በብንያም የተገኙት ሁሉ
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “በኢየሩሳሌምና በቢንያም የሚኖሩ ሁሉ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

በቃል ኪዳኑ ቆሙ
ይህ ፈሊጥ ነው ። ኣት: - “የቃል ኪዳኑን ውል ተቀበሉ” ወይም “ቃል ኪዳኑን ለመታዘዝ ቃል ገቡ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 34:33

ኢዮስያስ ሁሉንም አስወገደ
ኢዮስያስ ሠራተኞቹን ይህን እንዲያደርጉ አዞ ነበር ። ኣት : - “ኢዮስያስ ሠራተኞቹን ሁሉ እንዲያስወግዱ አዘዘ” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

አስጸያፊ ነገሮች
ለእግዚአብሔር አጸያፊ የነበሩት ጣዖታት እነዚህ ናቸው ። ኣት: - “አስጸያፊዎቹ ጣዖታት” (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን :ይመልከቱ)

ለዘመኑ ሁሉ
የኢዮስያስ ሕይወት በ “ቀኖቹ” ተወክሏል። ኣት: “በሕይወቱ ዘመን ሁሉ” ወይም “ኢዮስያስ በሕይወት እስካለ ድረስ” (ሁለን በአንድ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን :ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 35

1 ኢዮስያስ በኢየሩሳሌም ለእግዚአብሔር የፋሲካን በዓል አከበረ፤ በመጀመሪያው ወር በአሥራ አራተኛው ቀን የፋሲካ ጠቦቶቹን አረዱ። 2 ካህናቱን በየሥራ
ቦታቸው አድርጎ በእግዚአብሔር ቤት አገልግሎት አበረታታቸው። 3 እስራኤልንም ሁሉ ያስተምሩ ለነበሩት ለእግዚአብሔር ለተሰጡት ሌዋውያን ፦ "ቅዱሱን ታቦት
የእስራኤል ንጉሥ የዳዊት ልጅ ሰለሞን በገነባው ቤት ውስጥ አስቀምጡት። ከዚህ በኋላ በትከሻችሁ እየተሸከማችሁ አታዟዙሩት፤ አሁንም አምላካችሁን
እግዚአብሔርን አምልኩ፤ ሕዝቡንም እስራኤልን አገልግሉ። 4 በእስራኤል ንጉሥ ዳዊት የተጻፈና በልጁም በሰለሞን ጭምር የተሰጠውን መመሪያ በመከተል
በየአባቶቻችሁ ቤቶችና በየሥራ ክፍላችሁ ስም ራሳችሁን አደራጁ። 5 በሕዝቡ ዝርያዎች በወንድሞቻችሁ የአባቶች ቤቶች ውስጥ በየሥራ ክፍላችሁ የኃላፊነት
ቦታችሁን በመያዝና በሌዋውያን አባቶች ቤቶች ውስጥ በየሥራ ክፍላችሁ ቦታችሁን በመያዝ በተቀደሰው ሥፍራ ቁሙ። 6 የፋሲካውን ጠቦቶች እረዱ፤ እናንተም
ራሳችሁን ለእግዚአብሔር ስጡ። ለወንድሞቻችሁ ለእስራኤል ጠቦቶቹን ዝግጁ አድርጉላቸው፤ በሙሴ አማካይነት ለተሰጠው ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ
አድርጉት። 7 ኢዮስያስ ለፋሲካው መሥዋዕት እንዲሆን እዚያ ለነበሩት ሕዝብ ሁሉ ከመንጋው ሠላሳ ሺህ የበግና የፍየል ጠቦቶች ሰጠ። ሦስት ሺህ
ወይፈኖችንም ሰጠ፤ እነዚህም የንጉሡ ኃብት ከነበሩት ነበሩ። 8 መሪዎቹም ለህዝቡ፥ ለካህናቱና ለሌዋውያኑ የበጎ ፈቃድ ሥጦታዎችን ሰጡ። በእግዚአብሔር
ቤት ባለሥልጣናት የነበሩት ኬልቅያስ፥ ዘካርያስና ይሒኤል ለፋሲካው መሥዋዕት እንዲሆን ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ትንንሽ ከብቶችና ሦስት መቶ በሬዎች
ለካህናቱ ሰጡ። 9 የሌዋውያኑ አለቆች ኮናንያ፥ ወንድሞቹም ሸማያና ናትናኤል፥ ሐሸቢያ፥ ይዒኤልና ዮዛባት ለፋሲካው መሥዋዕት አምስት ሺህ ትንንሽ ከብቶችና
አምስት መቶ በሬዎች ለሌዋውያኑ ሰጡ። 10 በመሆኑም አገልግሎቱ ዝግጁ ነበረ፤ ካህናቱም ለንጉሡ ትዕዛዝ ምላሽ በመስጠት በየሥራ ክፍላቸው ከሆኑት
ከሌዋውያኑ ጋር በየቦታቸው ቆመው ነበር። 11 የፋሲካ ጠቦቶቹንም አረዱ፤ ካህናቱም ከሌዋውያኑ እጅ የተቀበሉትን ደም ረጩ፤ ሌዋውያኑም የጠቦቶቹን
ቆዳቸውን ገፈፉ። 12 በሙሴ መጽሐፍ እንደተጻፈ ለእግዚአብሔር ለማቅረብና በሕዝቡ የአባቶች ቤቶች መሠረት በየሥራ ክፍላቸው ሊያድሏቸው የሚቃጠለውን
መሥዋዕት ለይተው አስቀመጡ። በወይፈኖቹም ላይ እንደዚሁ አደረጉ። 13 መመሪያዎቹን በመከተል የፋሲካውን ጠቦቶች በእሳት ጠበሷቸው። የተቀደሱትን
ሥጦታዎች በምንቸቶች፥ በሰታቴዎችና በመጥበሻዎች ቀቀሏቸው፤ ለሕዝቡም ሁሉ በፍጥነት አዳረሷቸው። 14 ከዚያም በኋላ ለራሳቸውና ለካህናቱም
መሥዋዕቱን አዘጋጁ፤ የአሮን ልጆች ካህናቱ የሚቃጠለውን መሥዋዕትና ስቡን በማቅረብ እስከ ምሽት ድረስ በሥራ ተጠምደው ስለነበር ሌዋውያኑ ለራሳቸውና
ለአሮን ልጆች ለካህናቱ መሥዋዕቱን አዘጋጁ። 15 ዳዊት፥ አሳፍ፥ ኤማንና የንጉሡ ባለ ራዕይ ኤዶታም በሰጡት መመሪያ መሠረት የአሳፍም ዝርያዎች መዘምራኑ
በሥፍራቸው ቆመው ነበር። ጠባቂዎቹም በየበሮቹ ላይ ነበሩ፤ ወንድሞቻቸው ሌዋውያን መሥዋዕቱን ያዘጋጁላቸው ስለነበር የሥራ ቦታቸውን መልቀቅ
አያስፈልጋቸውም ነበር። 16 ስለዚህ ንጉሡ ኢዮስያስ ባዘዘው መሠረት በእግዚአብሔር መሠዊያ ላይ የሚቃጠለውን መሥዋዕት ለማቅረብ፥ በዚያን ጊዜ መላው
የእግዚአብሔር አገልግሎት የፋሲካን በዓል ለማክበር ተፈፀመ። 17 በዚያን ቦታ ተገኝተው የነበሩ የእስራኤል ሕዝብ በዚያን ጊዜ ፋሲካውንና ከዚያም ለሰባት
ቀናት የቂጣ በዓልን አከበሩ። 18 ከነቢዩ ከሳሙኤል ዘመን ጀምሮ እንደዚህ ያለ የፋሲካ በዓል በእስራኤል ተከብሮ አያውቅም፤ ከእስራኤልም ሌሎች ነገሥታት
ሁሉ የትኛውም ኢዮስያስ ከካህናቱ፥ ከሌዋውያኑና ከይሁዳና እዚያ ከነበሩ ከእስራኤል ሕዝብና ከኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ሁሉ ጋር እንዳደረገው ያለ ፋሲካ አክብሮ
አያውቅም። 19 ይህ ፋሲካ የተከበረው ኢዮስያስ በነገሠ በአሥራ ስምንተኛው ዓመት ነበር። 20 ከዚህ ሁሉ በኋላ ኢዮስያስ ቤተ መቅደሱን ካስተካከለ በኋላ
የግብጽ ንጉሥ ኒካዑ በኤፍራጥስ ወንዝ ከርከሚሽን ለዋጋ ወጣ፤ ኢዮስያስም ለዋጋው ሄደ። 21 ኒካዑ ግን ወደ እርሱ ፦" የይሁዳ ንጉሥ ሆይ ካንተ ጋር ምን
አለኝ? ጦርነት የምዋጋው በሌላ ቤት ላይ ነው እንጂ በአንተ ላይ ዛሬ ለጦርነት አልመጣሁብህም። እግዚአብሔር እንድፈጥን አዝዞኛል፤ ስለዚህ ከእኔ ጋር
በሆነው በእግዚአብሔር ላይ ጣልቃ አትግባ፤ አለበለዚያ ያጠፋሃል" በማለት መልዕክተኞችን ላከበት። 22 ነገር ግን ኢዮስያስ ከእርሱ መመለስን እምቢ አለ።
ከእርሱ ጋር ለመዋጋት ራሱን በሌላ መልክ ሸፈነ። ከእግዚአብሔር አፍ የመጣውን የኒካዑን ቃል አልሰማም፤ ስለሆነም በመጊዶ ሸለቆ ውስጥ ሊዋጋ ሄደ። 23
ቀስተኞችም ንጉሥ ኢዮስያስን ወጉት፤ ንጉሡም ለአገልጋዮቹ፦" ክፉኛ ቆስያለሁና ወደዚያ ውሰዱኝ" አላቸው። 24 ስለዚህ አገልጋዮቹ ከሰረገላው አውርደው
በሌላኛው ተጨማሪ ሰረገላ ውስጥ አስቀመጡት። ወደ ኢየሩሳሌምም ወሰዱት፤ በዚያም ሞተ። በአባቶቹም መቃብር ተቀበረ። ይሁዳና ኢየሩሳሌም ሁሉ
ለኢዮስያስ አለቀሱለት። 25 ኤርምያስም ለኢዮስያስ የሐዘን እንጉርጉሮ አወጣለት፤ እስከ ዛሬም ድረስ ውንዶችና ሴቶች መዘምራን ሁሉ ስለ ኢዮስያስ የሐዘን
እንጉርጉሮ ያወጣሉ። እነዚህ መዝሙሮች በእስራኤል ልማድ ሆኑ፤ እነሆ በሐዘን እንጉርጉሮ መዝሙር ውስጥ ተጽፈዋል። 26 ኢዮስያስን በተመለከተ ሌሎቹ
ጉዳዮችና በእግዚአብሔር ሕግ ለተጻፈው ነገር በመታዘዝ ያደረጋቸው መልካም ድርጊቶች፥ 27 የእርሱ ድርጊቶች ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በይሁዳና
በእስራኤል ነገሥታት መጽሐፍ ተጽፈዋል።

---

2 Chronicles 35:1

ኢዮስያስም ለእግዚአብሔር ፋሲካ አደረገ
ኢዮስያስ ህዝቡ እግዚአብሔር አባቶቻቸው እንዲያከብሩት ያዘዘውን ፋሲካ እንዲያከብሩ ሕዝቡን አዘዘ ::

በኢየሩሳሌም
የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ፋሲካን ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም እንዲወጡ እግዚአብሔር ለሙሴ አዝዞት ነበር።

በመጀመሪያው ወር በአሥራ አራተኛው ቀን
ይህ በዕብራይስጥ የቀን አቆጣጠር የመጀመሪያ ወር ነው። አሥራ አራተኛው ቀን በምዕራባዊ የቀን መቁጠሪያዎች የመጋቢት ወር መጀመሪያ ነው። (የዕብራዊያንን ወራት እና ሕገኛ ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

ካህናቱን በየምድባቸው አኖራቸው
ካህናቱን በየምድባቸው ማስቀመጡ ለካህናቱ ምን ዓይነት ሥራ መሥራት እንዳለባቸው ለመንገር ምሳሌ ነው :: አንባቢው ኢዮስያስ ለካህናቱ መመሪያ እንዲሰጥ ሰራተኞቹን ትእዛዝ እንደሰጠ አንባቢው መረዳት አለበት :: ኣት: - “ሰዎች ለካህናቱ የትኛውን ሥራ እንደሚሰሩ እንዲነግራቸው አደረገ (ዘይቤያዊን እና የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

አገልግሎት ላይ
“አገልግሎት” የሚለው የረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። ኣት: - “በያአገልግሎታቸው” ወይም “በጥሩ ሁኔታ ለማገልገል” (የረቂቅ ስሞችን ፡ ይመልከቱ)

2 Chronicles 35:3

የእስራኤል ንጉሥ የዳዊት ልጅ ሰሎሞን ሠራ
ሰሎሞን ምናልባት ሌሎች ሰዎች ት ሥራውን እንዲሰሩ እንዳዘዘ አንባቢዎቹ ለጊነዘቡት ይገባል :: ኣት - “የእስራኤል ንጉሥ ሰሎሞን ህዝቡ እንዲሠሩ አዝዞ ነበር” (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን :ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በአባቶቻችሁ ቤቶችና በየክፍላችሁ
“ስም” የሚለው ቃል እያንዳንዱን የዘር ሐረግ እያንዳንዱን ቤት እና እያንዳንዱን ምድብ የሚያመለክት የጋራ ስም ነው። ቋንቋህ “እንደ አባቶቻችሁ ቤቶች ስሞችና እንደ ክፍሎቻችሁ ሁሉ” ማለት ያስፈልገው ይሆናል ።

የዘርህ ቤቶች
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ ለሚኖሩት ቤተሰቦች የሚወክል ስም ነው ። ኣት: - “የአባትህ ዘሮች ቤተሰቦች” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

ክፍሎች
ህዝቡ ካህናትንና ሌዋውያንን የተከፋፈሉባቸው ቡድኖች

የዳዊትን ሕግ እና የልጁ የሰሎሞንን ቃሎች
“ዳዊትና ልጁ ሰሎሞን የጻፏቸው መመሪያዎች”

2 Chronicles 35:5

ቦታችሁን ይዛችሁ በቅዱሱ ስፍራው ቆሙ
“በቤተ መቅደሱ ውስጥ ቦታችሁን ጠብቁ”

በክፍሎቻችሁ
ይህ ህዝቡ እያንዳንዱን ሌዋዊ የሾመበትን የሥራ ቡድንን ይመለከታል ። ይህንን በ 2 ኛ ዜና መዋዕል 35 ፡ 4 እንዴት እንደተረጉሙት ይመልከቱ ።

የዘር ሐረግ ቤቶች
ይህ በሌዋውያን መካከል ያሉትን የተለያዩ ነገዶች ይመለከታል ። ለእያንዳንዱ ነገድ ወይም ቅድመ አያት ቤት በተሰየመው ዓይነት ሥራ መሠረት ሌዋውያን ለተለያዩ የሥራ ቡድኖች የተመደቡ ይመስላል ። ይህንን በ 2 ኛ ዜና 35፡4 እንዴት እንደተረጎምከ ተመልከት ።

ራሳችሁን ቀድሱ
ይህ ምናልባት ካህናቱና ሌዋውያኑ በቤተመቅደሱ ውስጥ ከመሥራታቸው በፊት ራሳቸውን የሚያጥቡትን ሊያመለክት ይችላል።

በሙሴ እጅ እንደ ተሰጠው እንደ እግዚአብሔር ቃል ይደረግ ዘንድ
እዚህ “እጅ” የሚለው ቃል ራሱ ሙሴን ያመለክታል። ትዕዛዙን ለመስጠት እግዚአብሔር እንደ ወኪሉ ሙሴን ተጠቅሟል ። ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። ኣት: - “እግዚአብሔር በሙሴ በኩል ለሕዝቡ የሰጣቸውን ትእዛዛት ሁሉ ለመታዘዝ” ወይም “እግዚአብሔር ሙሴን ለሕዝቡ እንዲናገር ያዘዘውን ሁሉ ለመፈጸም” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን እና ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 35:7

አጠቃላይ መረጃ
ቁጥሮችን እና የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ

ሠላሳ ሺህ ጠቦቶች ነበሩ
“30,000 በጎች” (ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

ልጆች
የፍየል ግልገሎች

ሦስት ሺህ ወይፈኖች
“3,000 ወይፈኖች” (ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

እነዚህ ከንጉሡ ንብረቶች ነበሩ
“እነዚህ ሁሉ የበግ እና የፍየል ግልገሎች ፣ እና በሬዎች የሰጣቸው እርሱ ነበር”

2,600 በጎችና ፍየሎች
“ሁለት ሺህ ስድስት መቶ በጎችና ፍየሎች” (ቁጥሮችን:ይመልከቱ)

ሦስት መቶ በሬዎች
“300 በሬዎች” (ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

ኬልቅያስ... ዘካርያስ... ይሒኤል... ለፋሲካው... ሸማያ... ናትናኤል... ሓሻቢያ... ይዒኤል ...ዮዛባት
እነዚህ ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው ። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

አምስት ሺህ በጎችና ፍየሎች
“5,000 ፍየሎችና በጎች” (ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

አምስት መቶ በሬዎች
“500 በሬዎች” (ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 35:10

አገልግሎቱ ተዘጋጅቶ ነበር
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። ኣት: - “ፋሲካውን ለማከናወን የሚያስፈልጉትን ነገሮች ሁሉ አዘጋጁ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ ይመልከቱ)

ክፍሎቻቸው
ሕዝቡ ካህናቱንና ሌዋውያኑን የከፋፈሉባቸው ቡድኖች ነበሩ። ይህንን በ 2 ኛ ዜና 35 ፡ 4 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ።

ከሌዋውያን እጅ የተቀበሉትን ደም
እዚህ “እጅ” የሚለው ቃል ሌዋውያንን ያመለክታል። ኣት: - “ሌዋውያኑ የሰጧቸው ደም” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን ፡ ይመልከቱ)

በየአባቶቻቸው ቤቶች
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚወክል ስም ነው ። ኣት: - “የአባቶቻቸው ዘሮች ቤተሰቦች” (የባህሪ ስምን ፡ ይመልከቱ)

2 Chronicles 35:13

አጠቃላይ መረጃ
“እነርሱ” እና “ራሳቸው” የሚሉት ምሳሌዎች በሙሉ ሌዋውያንን ያመለክታሉ (2ኛ ዜና መዋዕል 35:10)።

የፋሲካውን የበግ ግልገል በእሳት ጠበሱት
“የፋሲካውን የበግ ግልገል በእሳት አበሰሉት”

እነርሱም በምንቸት ፣ በሰታቴ እና በድስትም ቀቀሉ
“የተለያየ መጠን ባለው ዕቃዎች ውስጥ በውኃ አበሰሏቸው”

ለእራሳቸው እና ለካህናቱ የተቀደሰውን ቁርባን ያዘጋጁ ነበር
“ የሚበሉትንም የተቀደሰውን ቁርባን ለራሳቸውና ለካህናቱ አዘጋጁ”

2 Chronicles 35:15

በዳዊት ፣ በአሳፍ ፣ ኤማን እና በንጉሡም ባለ ራእይ ኤዶታም መመሪያ መሠረት
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - እንደ “ዳዊት ፣ አሳፍ ፣ ኤማን እና የንጉሡ ባለ ራእዩ ኤዶታም እንደመራቸው” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

ኤማን...ኤዶታም
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው ። (የስሞች አተረጓጎምን:ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Chronicles 35:16

የእግዚአብሔር አገልግሎት ሁሉ ተፈጸመ
ይህ በፋሲካ በዓል ዝግጅት ፣ ከቅዱሳኑ እና ከእግዚአብሔር አምልኮ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ሁሉ ይመለከታል ። “አገልግሎት” የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊገለጽ ይችላል እና ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል ኣት: - “እግዚአብሔርን ለማገልገል መከናወን የነበረበትን ነገር ሁሉ አከናወኑ” (የረቂቅ ስሞችን እና ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ይመልከቱ)

ፋሲካውን ጠበቁ
ይህ ፈሊጥ ነው ። ኣት: - “ፋሲካውን አደረጉ” ወይም “ፋሲካውን አከበሩ” (ፈሊጥን ፡ይመልከቱ)

የቂጣ በዓል
ይህ በዓሉን ማክበርን ያመለክታል ።ኣት - “ከዚያም ያቂጣ በዓልን ጠበቁ” ወይም “ከዚያ በኋላ ያቂጣ በዓልን አከበሩ” (የቃላት ግድፈትን ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 35:18

እንዲህ ዓይነቱ የፋሲካ በዓል በእስራኤል ፈጽሞ ታይቶ አይታወቅም
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። ኣት: - “በእስራኤል ውስጥ እንዲህ ያለ የፋሲካ በዓል አከባበር ኖሮ አያውቅም” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ ይመልከቱ)

በእስራኤል ተካሄደ
ይህ ያልተከፈለቺውን እስራኤልን ይመለከታል፣ ይህ የሰሜናዊው መንግሥት እና የደቡባዊው መንግሥት ተበብሎ ከመከፋፈሉ በፊት የነበረውን እስራኤል ያመለክታል ።

ከቀናቱ
“ከጊዜው”

ሌሎቹ የእስራኤል ነገሥታት
እዚህ“እስራኤል” የሚያመለክተው የሚያመለክተው የሰሜናዊውን የእስራኤልን መንግሥት ነው ።

ይህ ፋሲካ ተጠበቀ
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ይህን ፋሲካ አከበሩ” (ገቢራዊ ወይም ተብሮአዊ ፡ይመልከቱ)

ተጠበቀ
ይህ ፈሊጥ ነው ። ኣት: “ጠደረገ” ወይም “ተከበረ” (ፈሊጥ፡ይመልከቱ)

አሥራ ስምንተኛው ዓመት
“18ኛው ዓመት” (ሕገኛ ቁጥሮች ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 35:20

ቤተ መቅደሱን አሰናዳ
ይህ ማለት በቤተ መቅደሱ ውስጥ የነበረውን አምልኮ በማደስ እንደ እግዚአብሔር ኃሳብ እንዲሆን አድርጎታል ። ኣት: “የቤተመቅደሱን አምልኮ ወደ ተገቢው መንገድ መልሶታል” (የሚጠበቁ እውቀቶችን ወይም ያልተገለጹ መረጃዎችን ፡ይመልከቱ)

የግብፅ ንጉሥ ኒካዑ ወጣ
ይህ የግብፅ ንጉሥ ስም ነው ። እዚህ ንጉሡ ራሱን እና ሠራዊቱን ይወክላል ። ኣት: “የግብፅ ንጉሥ ኒካዑ ከሠራዊቱ ጋር ወጣ” (የስሞች አተረጓጎምን እና ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱሰን በሁሉ መወከልን ፡ይመልከቱ)

በከርከሚሽ ላይ
ይህ የከተማ ስም ነው ። እዚህ ከተማዋ የሚኖሩትን ሰዎች ትወክላለች ። ኣት: - “በከርከሚሽ ሰዎች ላይ” (የስሞችን አተረጓጎም እና የባህሪ ስምን ፡ ይመልከቱ)

ኢዮስያስ እርሱን ለዋጋ ሄደ
እዚህ ሁለቱም ኢዮስያስ እና ኒካዑ ራሳቸውን እና የጀባቸውን ሠራዊቶቻቸውን ይወክላሉ ። ኣት: “ኢዮስያስና ሠራዊቱ ኒካዑ እና በሠራዊቱን ለዋጉ ሄዱ” (ሁሉን በአንዱ መወከልን ፡ይመልከቱ)

የይሁዳ ንጉሥ ሆይ ፣ ከአንተ ጋር ምን አለኝ?
ኒካዑ ይህን አወያይ መጠይቅ ተጠቅሞ ለኢዮስያስ ከእሱ ጋር ግጭት እንደሌለው እና ኢዮስያስም እርሱን ማጥቃት እንደሌለበት ይነግረዋል። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊጻፍ ይችላል ።ኣት፡ “የይሁዳ ንጉሥ ሆይ ፣ እኔን ለማጥቃት ምክንያት የለህም።” (አወያይ መጠይቅን ፡ይመልከቱ)

በአንቺ ላይ አልመጣሁም
እዚህ ንጉሡ ኢዮስያስ መንግሥቱን ይወክላል ። ኣት: - “የንተን መንግሥት እየተዋጋሁ አይደለም” (ሁሉን በአንዱ መወከልን ፡ይመልከቱ)

ከቤቱ ጋር
እዚህ “ቤት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የባቢሎንን ቤት ሲሆን “ቤት” ማለት መንግስቱን የሚወክል ነው ። መንግሥቱ የሚለው የባቢሎናውያንን ሰራዊት የሚያወሳ ዐውደ-ጽሑፍ ነው ። ኣት: - “ከባቢሎን ቤት ጋር ” (የባህሪ ስም እና ሁሉን በአንዱ መወከልን ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 35:22

እራሱን ሌላ አስመሰለ
ሌሎቹ ወታደሮች እንዳያስተውሉት ኢዮስያስ ሌላ ሰው መስሎ ራሱን ገለጠ ።

ከእርሱ ጋር ለዋጋ
“እርሱ” የሚለው ቃል ራሱን እና ሰራዊቱን የሚወክለውን ኒካዑን ያመለክታል ። ኣት: - “ከግብጽ የጦር ሠራዊት ጋር ለዋጋ” (ሁሉን በአንዱ መወከልን ፡ ይመልከቱ)

ከእግዚአብሔር አፍ የመጣውን
እዚህ የእግዚአብሔርን ንግግር አፅንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር በ “አፉ” ተወክሏል ። ኣት: “ከእግዚአብሔር የመጣውን” ወይም “እግዚአብሔር የተናገረውን” (ሁሉን በአንዱ መወከልን ፡ይመልከቱ)

ስለዚህ እርሱ ሄደ
“እርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢዮስያስን እና ሠራዊቱን ነው ። ኣት: - “እርሱና ሠራዊቱ ሄዱ” (ሁሉን በአንዱ መወከልን ፡ይመልከቱ)

የመጊዶ ሸለቆ
ይህ የቦታ ስም ነው ። (የስሞችን አተረጓጎም፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 35:23

መላው ይሁዳና ኢየሩሳሌም
“ይሁዳ” እና “ኢየሩሳሌም” በዚያ የሚኖሩትን የሚያመለክቱ ናቸው ። ኣት: - “የይሁዳና የኢየሩሳሌም ሰዎች ሁሉ” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 35:25

እስከዛሬ
ይህ ማለት ጸሐፊው የጻፈበትን ቀን ነው ። ይህንን በ 2 ኛ ዜና ምዕራፍ 5 9 ውስጥ እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እነሆ ፣ እነርሱ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች-1) “እነርሱ ያሉት እዚህ ነው፡ እነርሱ” ወይም 2) “እነርሱ አሁንም አሉ ፣ እነርሱ” ።

የልቅሶ ግጥም
ይህ የጥንት የቀብር መዝሙሮች ጥቅል ነው ።

የደረጋቸው መልካም ሥራዎቹ
ይህ በንቃት ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ያከናወናቸውን መልካም ሥራዎች” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

የተጻፈው
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: “ቃላቶቹ”(ገቢራዊን ወይም ተቢሮአዊን :ይመልከቱ)

ሥራውም ... በመጽሐፉ ተጽፎአል
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ሰዎችም ስለ ሥራዎቹ ሁሉ... በመጽሐፉ ላይ ጻፉ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

የፊተኛውና የኋለኛውም ሥራው
ይህ የሚያመለክተው ከንግሥና ጀምሮ እስከ ሕይወቱ መጨረሻ ድረስ ያከናወናቸውን ታላላቅ ነገሮችን ሁሉ ነው ። ኣት: - “ያደረገው ነገር ሁሉ” ወይም “ከንግሥናው መጀመሪያ አንስቶ እስከሞተበት ጊዜ ድረስ ያከናወናቸውን ነገሮች ሁሉ” (ሜሪዝምን:ይመልከቱ)

የይሁዳና የእስራኤል ነገሥታት መጽሐፍት
ይህ የማይገኝ መጽሐፍ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 36

1 የምድሪቱም ሰዎች የኢዮስያስን ልጅ ኢዮአክስን ወስደው በአባቱ ቦታ በኢየሩሳሌም አነገሡት። **2** ኢዮአክስም መንገሥ በጀመረ ጊዜ ሃያ ሦስት ዓመቱ ነበር፤ በኢየሩሳሌምም ሦስት ወር ነገሠ። **3** የግብጽ ንጉሥ ከኢየሩሳሌም ከመንግሥቱ አስወገደው፤ ምድሩንም አንድ መቶ መክሊት ብርና አንድ መቶ መክሊት ወርቅ ቅጣት ጣለባት። **4** የግብጽ ንጉሥ ወንድሙን ኤልያቄምን በይሁዳና በኢየሩሳሌም ላይ ንጉሥ አደረገው፤ ስሙንም ኢዮአቄም ብሎ ለወጠው። የኤልያቄምን ወንድሙን ኢዮአክስን ወሰደና ወደ ግብጽ አመጣው። **5** ኢዮአቄም መንገሥ በጀመረ ጊዜ ሃያ አምስት ዓመቱ ነበር፤ በኢየሩሳሌምም አሥራ አንድ ዓመት ነገሠ። በአምላኩ በእግዚአብሔር ፊት ክፉውን ነገር አደረገ። **6** ከዚያም የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ጦርነት ከፍቶበት በሰንሰለት አስሮ ወደ ባቢሎን ወሰደው። **7** ናቡከደነፆር ከእግዚአብሔር ቤት ዕቃዎችም አንዳንዶቹን ወደ ባቢሎን ወሰደ፤ በባቢሎንም በቤተ መንግሥቱ ውስጥ አስቀመጣቸው። **8** ኢዮአቄምን በተመለከተ ሌሎቹ ጉዳዮችና ያደረጋቸው አስጸያፊ ድርጊቶች፥ በእርሱ ላይ በክፉነት የተያዙበት ድርጊቶች እነሆ በይሁዳና በእስራኤል ነገሥታት መጽሐፍ ተጽፈዋል። ልጁም ዮአኪን በእርሱ ቦታ ነገሠ። **9** ዮአኪን መንገሥ በጀመረ ጊዜ ስምንት ዓመቱ ነበር፤ በኢየሩሳሌምም ሦስት ወርና አሥር ቀን ነገሠ። በእግዚአብሔር ፊት ክፉውን ነገር አደረገ። **10** በፀደይ ወራት ንጉሥ ናቡከደነፆር ሰዎችን ልኮ ከእግዚአብሔር ቤት ከተወሰዱ የከበሩ ነገሮች ጋር ወደ ባቢሎን አመጣው፤ ዘመዱንም ሴዴቅያስን በይሁዳና በኢየሩሳሌም ላይ አነገሠው። **11** ሴዴቅያስ መንገሥ በጀመረ ጊዜ ሃያ አንድ ዓመቱ ነበር፤ በኢየሩሳሌምም አሥራ አንድ ዓመት ነገሠ። **12** በእግዚአብሔር በአምላኩ ፊት ክፉውን ነገር አደረገ። ከእግዚአብሔርም አፍ በተናገረው በነቢዩ በኤርምያስ ፊት ራሱን አላዋረደም። **13** ሴዴቅያስም ታማኝ እንዲሆንለት በእግዚአብሔር እንዲምል ባደረገው በንጉሡ በናቡከደነፆር ላይ አመፀ። ሴዴቅያስ ግን ወደ እስራኤል አምላክ ወደ እግዚአብሔር ላለመመለስ አንገቱን አደነደነ፤ ልቡንም አጠነከረ። **14** በተጨማሪም የካህናቱ መሪዎችና ሕዝቡ የሌሎችን ሕዝቦች አስፀያፊ ነገሮች ምሳሌነት በመከተል እጅግ በጣም መተላለፍ አበዙ። እግዚአብሔር ለራሱ በኢየሩሳሌም የቀደሰውን የእግዚአብሔርን ቤት በከሉት። **15** የአባቶቻቸው አምላክ እግዚአብሔር ለሕዝቡና ለማደሪያው ሥፍራ ከመራራቱ የተነሳ ደግሞ ደጋግሞ በመልዕክተኞቹ በኩል ቃል ይልክላቸው ነበር። **16** እነርሱ ግን የእግዚአብሔር ቁጣ በሕዝቡ ላይ እስኪነሳ ድረስ፥ መሸሻ መንገድ እስከማይኖር ድረስ የእግዚአብሔርን መልዕክተኞች ይሳለቁባቸው፥ ቃሉንም ያቃልሉና በነቢያቱም ላይ ያፌዙ ነበር። **17** ስለዚህም እግዚአብሔር የከለዳውያንን ንጉሥ አመጣባቸው፤ እርሱም በቤተ መቅደሱ ውስጥ ወጣቶቻቸውን በሰይፍ ገደላቸው፤ ለወጣቶቻቸው ወይም ለደናግልቱ፥ ለሽማግሌዎች ወይም ለሽበቶዎች አልራራም። እግዚአብሔር ሁሉንም በእጁ አሳልፎ ሰጠው። **18** የእግዚአብሔርንም ቤት እቃዎች ሁሉ ትልልቁንም ትንንሹንም የእግዚአብሔርንም ቤት ሃብትና የንጉሡንና የመሪዎቹን ሃብት እነዚህን ሁሉ ወደ ባቢሎን ወሰደ። **19** የእግዚአብሔርን ቤት አቃጠሉ፤ የኢየሩሳሌምን አጥር አፈረሱ፤ ቤተ መንግሥቶቹን ሁሉ አቃጠሉ፤ በውስጧ ያሉትን ውብ ነገሮች ሁሉ አጠፉ። **20** ከሰይፍም ያመለጡትን ንጉሡ ወደ ባቢሎን አጋዛቸው። የፋርስ መንግሥት አገዛዝ እስኪደርስ ድረስ ለእርሱና ለልጆቹ አገልጋዮች ሆኑ። **21** ይህ የሆነው ምድሪቱ የሰንበት እረፍትዋን እስክታገኝ ድረስ በነቢዩ በኤርምያስ አፍ የተነገረውን የእግዚአብሔር ቃል እንዲፈፀም ነው። በዚህ መንገድ ሰባ ዓመት በማሳለፍ ተትታ በነበረበት ጊዜ ሁሉ ሰንበቷን አከበረች። **22** በኤርምያስ አፍ የተነገረው የእግዚአብሔር ቃል እንዲፈፀም በፋርስ ንጉሥ በቂሮስ በመጀመሪያው ዓመት እግዚአብሔር የፋርስን ንጉሥ የቂሮስን መንፈስ አነሳሳ። እርሱም በመንግሥቱ ሁሉ አዋጅ አስነገረ፤ በጽሑፍም አደረገው። **23** "የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ የሚለው ይህ ነው፦ 'የሰማይ አምላክ እግዚአብሔር የምድርን መንግሥታት ሁሉ ሰጥቶኛል፤ በይሁዳም ባለችው በኢየሩሳሌም ለእርሱ ቤት እንድሠራለት አዝዞኛል። በመካከላችሁ ከእርሱ ሕዝብ መካከል ማንም ቢሆን አምላካችሁ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ይሁን፤ እርሱም ወደ ምድሪቱ ይውጣ" አለ።

---

2 Chronicles 36:1

ኢዮአክስ
ይህ የወንድ ስም ነው። (የስሞችን አተረጓጎም፡ይመልከቱ)

በአባቱ ቦታ
“በእርሱ ቦታ” የሚለው ሐረግ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው ፣ትርጉሙ “በእርሱ ፋንታ” ማለት ነው።

ዕድሜው ሃያ ሦስት ዓመት... ሦስት ወር
“ዕድሜው 23 ዓመት... 3 ወር” (ዘይቤያዊን ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 36:3

የግብፅ ንጉሥ በኢየሩሳሌም አወጣው
የሚለው አገላለጽ “በኢየሩሳሌም አስወግዶታል” ማለት በኢየሩሳሌም ላይ ንጉሥ እንዳይሆን አደረገው ማለት ነው። ኣት: - “የግብፅ ንጉሥ በኢየሩሳሌም ንጉሥ እንዳይሆን አግዶታል” (ፈሊጥን ፡ይመልከቱ)

ምድሪቱን ዕዳ ጣለባት
እዚህ “መሬት” የሚለው ቃል በዚያ የሚኖሩትን ያመለክታል ። ኣት: - “የአገሩን ሰዎች ዕዳ ጣለባቸው” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

አንድ መቶ መክሊት ብርና አንድ መክሊት ወርቅ
ይህንን ወደ ዘመናዊ ልኬት ሊለውጡት ይችላሉ። አንድ መክሊት 33 ኪሎ ግራም ያህል ነበር። ኣት: - “ሠላሳ ሦስት መቶ ኪሎ ግራም ብር ፣ ሠላሳ ሦስት ኪሎግራም ወርቅ” ወይም “3,300 ኪሎ ግራም ብር እና 33 ኪሎ ግራም ወርቅ” (መጽሐፍ ቅዱሳዊ ገንዘብን እና ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)

ኤልያቄም... ኢዮአክስ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው ። (የስሞችን አተርጓጎም ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 36:5

ዕድሜው ሃያ አምስት ዓመት... አሥራ አንድ ዓመት
“25 ዓመት... የ 11 ዓመት ልጅ” (ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)

በአምላኩ በእግዚአብሔር ፊት መጥፎ የሆነውን ነገር አየ
እዚህ “እይታ” የሚለው ቃል ፍርድን ያመለክታል ። እግዚአብሔር የኢዮአቄምን ድርጊት አየ ፣ አልተቀበለውም። ኣት: - “እግዚአብሔር እንደሆነ የወሰነው” ወይም “እግዚአብሔር እንደ ክፉ አድርጎ የሚቆጠረው” (የባህሪ ስምን፡ ይመልከቱ)

እርሱን መታው
“እርሱ” የሚለው ቃል ኢዮአክስም ያመለክታል ። ኢዮአክስም ኢየሩሳሌምን ወይንም የይሁዳን ህዝብ ይወክላል ። ኣት: - “ኢየሩሳሌምን አጠቃ” ወይም “ይሁዳን አጠቃ” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

እንዲሁ ናቡከደነፆር ወሰደ
ናቡከደነ ፆር ንጉሥ ስለነበረ ወታደሮቹ ይህን እንዲፈጽሙ አድርጎ ይሆናል። ኣት: - “ናቡከደነፆር ወታደሮቹን ተሸክመው እንዲወስዱ አደረገ” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የእግዚአብሔር ቤት
እዚህ “ቤት” የሚለው ቃል ቤተመቅደሱን ይወክላል ። ኣት: - “የእግዚአብሔር መቅደስ” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 36:8

ያደረጋቸው ርኩሰ ነገሮች
ይህ ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር የሚጠላውን የሐሰት አማልክትን ማምለክን ያመለክታል ።

በእርሱም የተገኘው ሁለ
ይህ ፈሊጥ የሚያመለክተው ሰዎች ጥፋተኛ ብለው እርሱን ሊከሱት ስለሚችሉት ድርጊቶቹ ነው ። ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ሰዎች በእርሱ ላይ ያገኙትን” ወይም “በሰዎች ሊያስከስሰው የሚችል ድርጊት” (ፈሊጥን እና ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ይመልከቱ)

እነሱ የተጻፉ ናቸው
“ማንም ሰው በመጽሐፉ ውስጥ ... እስራኤልን ማየትና እዚያ እንደተጻፈ ማየት ይችላል” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ይመልከቱ)

እነርሱ በመጽሐፉ ተጽፈዋል
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። ኣት: “አንድ ሰው በመጽሐፉ ውስጥ ጻፋቸው” ወይም “ስለ እነርሱ በመጽሐፉ ውስጥ ማግኘት ትችላለህ” (ገቢራዊ ወይም ተብሮአዊ፡ይመልከቱ)

የይሁዳና የእስራኤል ነገሥታት መጽሐፍ
ይህ የማይገኝ መጽሐፍ ነው። በ 2 ኛ ዜና 35፡ 27 ውስጥ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ።

በእርሱ ቦታ ነገሠ
“በእርሱ ቦታ” የሚለው ሐረግ ስእላዊ አገላለጽ ሲሆን “በእርሱ ፋንታ” የሚል ትርጉም አለው ። “በኢዮአቄም ፋንታ ነገሠ” (ዘይቤያዊን፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 36:9

የስምንት ዓመት ልጅ... ሦስት ወር እና አስር ቀናት
“ዕድሜው 8 ዓመት... 3 ወር እና 10 ቀን” (ቁጥሮችን፡ይመልከቱ)

በእግዚአብሔርም ፊት ክፉ የሆነውን ነገር
እዚህ “እይታ”የሚለው ፍርድን ይወክላል ። እግዚአብሔር የዮአኪን ድርጊት አይቷል እናም አልተቀበለውም ። ኣት:- “እግዚአብሔር ክፋ እንደሆነ የወሰነው” ወይም “እግዚአብሔር ክፉ እንደሆነ የቆጠረው” (ዘይቤያዊን፡ ይመልከቱ)

ወደ ባቢሎን አመጣው
ዮአኪንን ወደ ባቢሎን አመጣ ”

የእግዚአብሔር ቤት
እዚህ “ቤት” የሚለው ቤተመቅደሱን ይወክላል ። ኣት: - “የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ” (የባህሪ ስምን፡ይመልከቱ)

ዘመዱ
“ዮአኪንን ዘመድ”

2 Chronicles 36:11

ሃያ አንድ አመት... አሥራ አንድ ዓመት
“ዕድሜው 21 ዓመት... 11 ዓመት” (ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)

በአምላኩ በእግዚአብሔር ፊት መጥፎ የሆነውን ነገር
እዚህ “ፊት” የሚለው ፍርድን ያመለክታል ። እግዚአብሔር የሴዴቅያስን ሥራ አየ ፤ አልተቀበለውምም። ኣት: “አምላኩ እግዚአብሔር ክፉ እንደ ሆነ የወሰነው ወይም “አምላኩ እግዚአብሔር ክፉ እንደሆነ የቆጠረው” (ዘይቤያዊን ፡ይመልከቱ)

ከእግዚአብሔር አፍ የተናገረ
እዚህ “አፍ” የሚለው ቃል እግዚአብሔር የተናገረውን ቃል ይወክላል ። ኣት: - “እግዚአብሔር ለእርሱ የተናገረውን ቃል የተናገረው ” (የባህሪ ስምን ፡ ይመልከቱ)

2 Chronicles 36:13

ሴዴቅያስም ወደ እግዚአብሔር እንዳይመለስ አንገቱን አደነደነ ልቡንም አደነደነ
“አንገቱን አደነደነ” እና “ልቡን አደነደነ” የሚሉት ኃረጎች ሁለቱም እምቢተኝነትን የሚወክሉ ንግግሮች ናቸው ። ሴዴቅያስ እግዚአብሔርን ለማምለክ ፈቃደኛ አለመሆኑ ወደ እግዚአብሔር ዘወር ለማለት እንቢ ማለት እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል ። ኣት: - “ሴዴቅያስ እግዚአብሔርን ለማምለክ እምቢ አለ” (ድግግሞሽን እና ዘይቤያዊን ፡ይመልከቱ)

የአሕዛብን ርኩስ ልምምዶች ተከትለዋል
“ልምምዶች መከተል” የሚለው ፈሊጥ እነዚህን ነገሮች ማድረግ ማለት ነው። ኣት: - “አሕዛብ ያደረጉትን አስጸያፊ ተግባር አደረጉ” (ፈሊጥን ፡ይመልከቱ)

አስጸያፊ ልምዶች
ይህ ሐረግ ሌሎች አማልክትን ማምለክን ያመለክታል ።

የእግዚአብሔርንም ቤት አረከሱ
ለእግዚአብሔር አገልግሎት ጥቅም ላይ የማይውል ቦታ ቆሻሻ እንደሆነ ተደርጎ ተገልጾአል ። “ቤት” የሚለው ቃል ቤተመቅደሱን ይወክላል ። ኣት: - “የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አረከሱ” (ዘይቤያዊን እና የባህሪ ስምን ፡ ይመልከቱ)

2 Chronicles 36:15

ደግመው ደጋግመው
"ብዙ ጊዜ"

የሚኖርበት ቦታ
ይህ ቤተመቅደሱን ያመለክታል ።

የእግዚአብሔር ቁጣ በሕዝቡ ላይ ተነሳ
እዚህ “ተነሳ” የሚለው ቃል የድርጊትን መጀመር ያመለክታል ። እግዚአብሔር ሕዝቡን በቁጣው መቅጣቱ ቁጣው በእነርሱ ላይ እርምጃ እንደሚወስድ ሰው ሆኖ ተቆጥረዋል። ኣት: - “እግዚአብሔር በቁጣው ሕዝቡን መቅጣት ጀመረ” (ዘይቤያዊን ፡ይመልከቱ)

ፈውስም አልተገኘለትም
ይህ ፈሊጥ ሲሆን የተከሰተውን ለመከላከል ማንም ምንም ነገር ማድረግ አይችልም ማለት ነው ። ኣት: - “እርሱን ማስቀረት የሚቻልበት ምንም መንገድ አልነበረም” (ፈሊጥን፡ይመልከቱ)

2 Chronicles 36:17

እግዚአብሔር የከለዳውያንን ንጉሥ በእነሱ ላይ አመጣባቸው
“በእነሱ ላይ አመጣባቸው”የሚለው ፈሊጥ ማለት ከሠራዊቱ ጋር ጥቃት እንዲሰነዝር ማድረግ ማለት ነው ። ኣት: - “እግዚአብሔር የከለዳውያንን ንጉሥ ጥቃት እንዲፈጽምባቸው አመጣባቸው እርሱም” (ፈሊጥን ፡ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወጣቶቻቸውን በሰይፍ ገደለ
ምናልባት ንጉሡ ወጣቶቹን በግል አልገደላቸውም ይሆናል። ይልቁንም ሠራዊቱ ገድሏቸዋል ። ኣት: - “ሠራዊቱ ወጣቶቻቸውን በሰይፍ ገድለዋቸዋል” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ሁሉንም በእጁ አሳልፎ ሰጣቸው
እዚህ “እጅ” እነርሱን ለማሸነፍ የሚያስችል የኃይል መገለጫ ነው ። ኣት: - “የከለዳውያን ሠራዊት ድል እንዲያደርግ እግዚአብሔር ፈቅዷል” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 36:18

የእግዚአብሔር ቤት... የእግዚአብሔር ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል ቤተመቅደሱን ይወክላል ። ኣት: - “የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ... የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

እነርሱ አቃጠሉ
“እነርሱ” የሚያመለክተው የባቢሎናውያንን ወታደሮች ነው።

2 Chronicles 36:20

ንጉሡ ወደ ባቢሎን ተወሰደ
እዚህ “ንጉሡ” የሚለው ሥራውን እንዲሠሩ ያዘዛቸውን ይርሱን ወታደሮቹ ያመለክታል ። “ተወስዷል ” የሚለው ፈሊጥ ሲሆን እነርሱን በኃይል ወደ ባቢሎን ማምጣት ማለት ነው ። ኣት: - “ንጉሡ ሠራዊቱን በኃይል ወደ ባቢሎን ወሰደው” (የባህሪ ስምን እና ፈሊጥን :ይመልከቱ)

እስከ ፋርስ መንግሥት አገዛዝ ድረስ
“የፋርስ መንግሥት ወደ ሥልጣን እስኪመጣ ድረስ”

የእግዚአብሔር ቃል በኤርምያስ አፍ
እዚህ “ቃል” የሚለው ስም “ተናገር” ከሚለው ግስ ጋር መተርጎም ይችላል ። “አፍ” የሚለው ቃል ኤርሚያስን ይወክላል ። ኣት: - “እግዚአብሔር በኤርምያስ በኩል የተናገረው” ወይም “ኤርምያስ የተናገረው የእግዚአብሔር ቃል” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከል :ይመልከቱ)

ምድሪቱ ሰንበትን በማድረግዋ እስክታርፍ ድረስ
ሰዎቹ በየሰባት ዓመቱ መሬቱን ባለማረስ የሰንበትን ሕግ መታዘዝ ነበረባቸው። ይህ ሐረግ ስለዚህ ሲናገር ምድርን እንደሰው የሰንበትን ሕግ የምትታዘዝ እና የምታርፍ አስመስሏታል ። ኣት: - “ምድሪቱ በሰንበት ሕግ እስክታርፍ ድረስ” ወይም “በሰንበት ሕግ በተደነገገው መሠረት ምድሪቱን ማንም ገና እስከማያርስ ድረስ” (የባህሪ ስም: ተስብአትን :ይመልከቱ)

በተተወችበት ዘመን ሁሉ ሰንበትን አከበረች
“እርሷ” የሚለው ቃል መሬትን ያመለክታል ። ምድሪቱ ሰንበትን የምታከብር ሰው እንደ ሆነች ተደርጋ ተገልጻለች ። ኣት: - “ምድሪቱ እስከተፈታች ድረስ የሰንበት ሕግ መስፈርቶች ተፈጽመዋል ማለት ነው ” (የባህሪ ስምን: ተስብአትን :ይመልከቱ)

በዚህ መንገድ ሰባ ዓመት ለማለፍ ነው
ምድሪቱ ባድማ ሆና ለ 70 ዓመት ቆየች (ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 36:22

በመጀመሪያው ዓመት
ይህ የንጉሥ ቂሮስ የአገዛዝ ዘመን መጀመሪያን ያመለክታል ። (ሕገኛ ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

በኤርምያስ አፍ የተነገረው የእግዚአብሔር ቃል ይፈጸም ዘንድ ነው
እዚህ “ቃል” የሚለው ስም “ተናገር” ከሚለው ግስ ጋር መተርጎም ይችላል ። “አፍ” የሚለው ቃል ኤርሚያስን ይወክላል ። ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል ። ኣት: - “እግዚአብሔርም በኤርምያስ የተናገረው ነገር እንዲፈጸም” ወይም “ኤርምያስ የተናገረው የእግዚአብሔር ቃል ይፈጸም ዘንድ” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን እና ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

እግዚአብሔር የፋርስ ንጉሥ የሆነውን የቂሮስን መንፈስ አነሳሳ
መንፈስን ማነሳሳት አንድን ሰው እርምጃ መውሰድ እንዲፈልግ ማድረግ ነው። ኣት: - “እግዚአብሔር የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ እርምጃ ለውሰድ እንዲፈልግ አደረገው” (አንዱን በሁሉ ወይም ሁሉን በአንዱ መወከልን :ይመልከቱ)

የምድር መንግሥታት ሁሉ
ቂሮስ የማይገዛባቸው መንግስታት ስለነበሩ ይህ ግነት ነው ። (ግነትን እና አጠቃላይን :ይመልከቱ)

ለእርሱ ቤት ይሠሩ ዘንድ
እዚህ “ቤት” የሚለው ቃል ቤተ መቅደስን ይወክላል ። ኣት: - “ለእርሱ ቤተ መቅደስ ለመሥራት” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

የእርሱ ህዝብ
“የእግዚአብሔር ሕዝብ”

ወደ ምድሪቱ ይሂድ
“ያ ሰው ወደ ይሁዳ ምድር ይሂድ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Ezra

Ezra

Chapter 1

1 የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ በነገሠበት የመጀመሪያው ዓመት እግዚአብሔር በኤርምያስ አፍ የተነገረውን ቃሉን ፈጸመና የቂሮስን መንፈስ አነሣሣ። የቂሮስ ድምጽ
በመንግሥቱ ሁሉ ላይ ተሰማ። የተነገረውና የተጻፈው እንዲህ የሚል ነው፤ 2 "የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ እንዲህ ይላል፤ የሰማይ አምላክ እግዚአብሔር የምድር
መንግሥታትን ሁሉ ሰጥቶኛል፥ በይሁዳ ባለች በኢየሩሳሌም ቤት እንድሠራለት አዞኛል። 3 ማንም ከሕዝቡ ጋር የሚመጣ ቢኖር አምላኩ ከእርሱ ጋር ይሁን፥ ወደ
ኢየሩሳሌም ይውጣና የኢየሩሳሌም አምላክ ለሆነው ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር ቤት ይሥራ። 4 የሚቀሩት በሚኖሩባቸው በመንግሥቱ በየትኛውም
አካባቢ የሚገኙ ሰዎች ብርና ወርቅ፥ ንብረትና እንስሳ በተጨማሪም በኢየሩሳሌም ላለው የእግዚአብሔር ቤት የበጎ ፈቃድ ቁርባን ይስጡ"። 5 ከዚያም የይሁዳና
የብንያም ነገድ የቤተሰብ አለቆች፥ ካህናቱ፥ ሌዋውያኑና እንዲሄዱና ቤቱን እንዲሠሩለት እግዚአብሔር መንፈሳቸውን ያነሣሣ ሁሉ ተነሡ። 6 በዙሪያቸው ያሉትም
ሥራቸውን በብርና ወርቅ ዕቃ፥ በቁሳቁስ፥ በእንስሳ፥ በጠቃሚ ዕቃዎችና በበጎ ፈቃዳቸው በሰጡት መባ አገዟቸው። 7 ደግሞም ናቡከደነፆር ከኢየሩሳሌም
አምጥቶ በአማልክቶቹ ቤቶች ያኖራቸውን የእግዚአብሔርን ቤት ዕቃዎች ንጉሡ ቂሮስ አወጣቸው። 8 ቂሮስ በግምጃ ቤቱ ኃላፊ በሚትሪዳጡ እጅ ሰጠ፥
እርሱም ለይሁዳው አለቃ ለሰሳብሳር ቆጥሮ አስረከበው። 9 ብዛታቸው እንደሚከተለው ነበር፤ ሠላሳ የወርቅ ሳሕን፥ አንድ ሺህ የብር ሳሕን፥ ሃያ ዘጠኝ ሌሎች
ሳሕኖች። 10 ሠላሳ ጎድጓዳ የወርቅ ሳሕን፥ 410 ትናንሽ ጎድጓዳ የብር ሳሕኖችና ሌሎች አንድ ሺህ ዕቃዎች ነበርሩ። በአጠቃላይ 5400 የብርና የወርቅ
ዕቃዎች ነበሩ። 11 ምርኮኞቹ ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌም በሄዱ ጊዜ እነዚህን ሁሉ ሰሳብሳር አመጣቸው።

Ezra 1:1

የመጀመሪያ ዓመት
ይህ የሚያሳየው የቂሮስን የመጀመሪያ የንግሥ ዓመት ነው።

በኤርምያስ አፍ የተነገረውን ቃሉን እግዚአብሔር ፈጸመው
እዚህ ላይ ‹‹አፍ›› የሚለው የተነገረውን ለማለት ነው። ‹‹ ኤርምያስ እግዚአብሔር ያደርገዋል ብሎ የተነበየውን እግዚአብሔር አደረገው።››

ያሕዌ
ይህ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ለሕዝቡ ራሱን የገለጠበት የእግዚአብሔር ስም ነው። ይህንን ስለመተርጎም በትራንስሌሽን ወርድ ፔጅ ላይ የተጻፈውን ተመልከት።

እግዚአብሔር---የቂሮስን መንፈስ አስነሣ
እዚህ ላይ ቂሮስ የተገለጸው በመንፈሱ ነው። ይህም የሚናገረው እግዚአብሔር ቂሮስን መንፈሱን ‹‹በማስነሣት›› ፈቃዱን እንዲያደርግ መፈለጉን ነው። ‹‹እግዚአብሔር --- ቂሮስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ እንዲወድ አደረገው››

የቂሮስ አዋጅ በግዛቱ ሁሉ ላይ ተነገረ
አዋጁ የሚነገረውን መልእክት ምንነት የሚወክል ሲሆን ፣ በግዛቱ ሁሉ ላይ የሚለው ደግሞ በሚገዛው ምድር ላይ የሚኖሩትን ሰዎች ሁሉ ይወክላል። ‹‹ ቂሮስ በመንግሥቱ ሁሉ ላይ አዋጅ አስነገረ።››

የተጻፈውና የተነገረው ምንድን ነው
ይህ በአድራጊ ግስነት ሊተረጎም ይችላል። ቂሮስ ያወጀውን አዋጅ በሚገዛው ግዛት ሁሉ ላ ሰዎች እንዲደርስ ሌሎች ሰዎች እንደረዱት ተደርጎ ቢተረጎም የተሻለ ነው። ‹‹ቂሮስ የጻፈውን መልእክተኞቹ ሲያነቡ ሕዝቡ ሰሙአቸው››

የምድርን መንግሥታት ሁሉ
እዚህ ላይ ‹‹ሁሉ›› የሚለው ቃል የተጋነነ ነው፤ ቂሮስ የማይገዛቸውን ግዛቶች ሁሉ ያጠቃለለ ይመስላል።

በይሁዳ --- ቤት ለእርሱ
ይህ ቤት ሕዝቡ እግዚአብሔርን የሚያመልኩበት ቤት እንደሆነ ግልፅ ማድረግ ያስፈልጋል። ‹‹ በይሁዳ --- ሕዝቡ እግዚአብሔርን የሚያመልኩበት ቤት ››

Ezra 1:3

የእርሱ ሕዝብ
የእግዚአብሔር ሕዝብ

በሚኖርበትም ስፍራ ሁሉ ለቀረው ሰው --- ይርዱት
ባሉበት ለመቅረት የመረጡት እስራኤላውያን ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ የመረጡትን በገንዘብና በቁሳቁስ ይርዱአቸው።

Ezra 1:5

ሥራቸው
ቀደም ባለው ቁጥር እንደተጠቀሰው እግዚአብሔር ያነሣሣቸው ሰዎችን ሥራ ያመለክታል።

እግዚአብሔር እንዲሄድ መንፈሱን ያነሣሣው እያንዳንዱ
ያነሣሣው የሚለው ቃል አንድን ሰው የሥራው ተሳታፊ እንዲሆን ማድረግን ያመለክታል። ዕዝራ 1:1 እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት። ‹‹እግዚአብሔር እንዲሄድ ያደረገው እያንዳንዱ››

Ezra 1:7

ሚትሪዳጡ --- ሰሳብሳር
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው

በመዝገብ ቤት ኃላፊው በሚትሪዳጡ እጅ አወጣቸው
ዕቃዎቹን በአንድ ሰው እጅ አስቀመጡአቸው የሚለው አባባል ያ ሰው በእጁ የገባውን ዕቃ እንደወደደው ለማድረግ ይፈቀድለታል ማለት ነው። ‹‹ሚትሪዳጡን በንብረቶቹ ላይ ኃላፊ አደረገው›› ወይም ‹‹ ሚትሪዳጡን በዕቃዎቹ ላይ ኀላፊነት ሰጠው..

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሂሳብ ሹም
በገንዘብ ላይ የተሾመ ባለሥልጣን

ሰላሣ--- አንድ ሺህ --- ሃያ - ዘጠኝ --- **410**
‹‹30 --- 1,000 --- 29 --- አራት መቶ አሥር››

Ezra 1:9

ሰሐኖች --- ጎድጓዳ ሰሐኖች
ለእግር መታጠቢያ የሚያገለግሉ ውኃ የሚይዙ ዕቃዎች

አጠቃላይ መረጃ፡
እነዚህ ቁጥር የተሰጣቸው የዕቃዎች ዝርዝር ናቸው።፡

5,400 --- ጠቅላላ
‹‹ አምስት ሺህ አራት መቶ --- ጠቅላ።።›› እነዚህ ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱ፣ ከዚህ በላይ በተናጠል የተዘረዘሩ ጠቅላላ ዕቃዎች ቁጥር ነው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 ንጉሡ ናቡከደነፆር ማርኮ ወደ ባቢሎን ካፈለሳቸው ምርኮኞች ወደ ኢየሩሳሌምና በይሁዳ ወዳሉ ወደየከተሞቻቸው የተመለሱት እነዚህ ናችው፤ **2** እነርሱም ከዘሩባቤል፥ ከኢያሱ፥ ከነህምያ፥ ከሠራያ፥ ከረዕላያ፥ ከመርዶክዮስ፥ ከበላሳን፥ ከመሴፋር፥ ከበጉዋይ፥ ከሬሁምና ከበዓና ጋር መጡ። የሚከተለው የእስራኤል ሰዎች የወንዶቹ ዝርዝር ነው፤ **3** የፋሮስ ተወላጆች 2172። **4** የሰፋጥያስ ተወላጆች 372። **5** የኤራ ተወላጆች 775። **6** በኢያሱና በኢዮአብ በኩል የፌሐት ሞዓብ ተወላጆች 2812። **7** የኤላም ተወላጆች 1254። **8** የዛቱዕ ተወላጆች 945። **9** የዘካይ ተወላጆች 760። **10** የባኒ ተወላጆች 642። **11** የቤባይ ተወላጆች 623። **12** የዓዝጋድ ተወላጆች 1222። **13** የአዶኒቃም ተወላጆች 666። **14** የበጉዋይ ተወላጆች 2056። **15** የዓዲን ተወላጆች 454። **16** በሕዝቅያስ በኩል የአጤር ሰዎች 98። **17** የቤሳይ ተወላጆች 323። **18** የዮራ ተወላጆች 112። **19** የሐሱም ሰዎች 223። **20** የጋቤር ሰዎች 95። **21** የቤተልሔም ሰዎች 123። **22** የነቶፋ ሰዎች 56። **23** የዓናቶት ሰዎች 128። **24** የዓዝሞት ሰዎች 42። **25** የቂርያት ይዓሪም፥ የከፊራና የብኤሮት ሰዎች 743። **26** የራማና የጌባ ሰዎች 621። **27** የማክማስ ሰዎች 122። **28** የቤቴልና የጋይ ሰዎች 223። **29** የናባው ሰዎች 52። **30** የመጌብስ ሰዎች 156። **31** የሌላው ኤላም ሰዎች 1254። **32** የካሪም ሰዎች 320። **33** የሎድ፥ የሐዲድና የኦኖም ሰዎች 725። **34** የኢያሪኮ ሰዎች 345። **35** የሴናዓ ሰዎች 3630። **36** ካህናቱ፤ ከኢያሱ ቤተሰብ የዮዳኤ ተወላጆች 973። **37** የኢሜር ተወላጆች 1052። **38** የፋስኮር ተወላጆች 1247። **39** የካሪም ተወላጆች 1017። **40** ሌዋውያኑ፤ በሆዳይዋ በኩል የኢያሱና የቀድምኤል ተወላጆች 74። **41** የቤተ መቅደሱ መዘምራን፤ የአሳፍ ተወላጆች 128። **42** የበረኞቹ ተወላጆች፤ የሴሎም፥ የአጤር፥ የጤልሞን፥ የዓቁብ፥ የሐጢጣና የሶባይ ተወላጆች በአጠቃላይ 139። **43** በቤተ መቅደስ ውስጥ እንዲያገለግሉ ተመድበው የነበሩት፤ የሲሐ፥ ሐሡፋ፥ ጠብዖት፥ **44** ኬራስ፥ ሲዓ፥ ፋዶን፥ **45** ልባና፥ አጋባ፥ ዓቁብ፥ **46** አጋብ፥ ሰምላይና ሐናን ተወላጆች፤ **47** የጌዴል፥ ጋሐር፥ ራያ፥ **48** ረአሶን፥ ኔቆዳ፥ ጋሴም፥ **49** ዖዛ፥ ፋሴሐ፥ ቤሳይ፥ **50** አስና፥ ምዑናውያንና ንፉሰሲም ተወላጆች፤ **51** የበቅቡቅ፥ ሐቁፋ፥ ሐርሑር፥ **52** በስሎት፥ ምሒዳ፥ ሐርሳ፥ **53** በርቆስ፥ ሲሣራ፥ ቴማ፥ **54** ንስያና ሐጢፋ ተወላጆች። **55** የሰለሞን አገልጋዮች ተወላጆች፤ የሶጣይ፥ ሶፌሬት፥ ፍሩዳ፥ **56** የዕላ፥ ደርቆን፥ ጌዴል፥ **57** ሰፋጥያስ፥ ሐጢል፥ ፈክራት፥ ሐፂቦይምና አሚ ተወላጆች። **58** በቤተ መቅደስ እንዲያገለግሉ የተመደቡት ተወላጆችና የሰለሞን አገልጋዮች ተወላጆች በድምሩ 392 ነበሩ። **59** ቴልሜላን፥ ቴላሬሳን፥ ክሩብን፥ አዳንና ኢሜርን ትተው የመጡ፥ ነገር ግን አባቶቻቸው እስራኤላውያን ስለመሆናቸው ማስረዳት ያልቻሉ **60** 652 የዳላያ፥ የጦብያና የኔቆዳ ተወላጆች ተካተቱ። **61** የካህናቱ ተወላጆችም፤ የኤብያ፥ የአቆስና የቤርዜሊ (እርሱም ከገለዓዳዊው ከቤርዜሊ ሴቶች ሚስት በማግባቱ በስማቸው የተጠራው ነው) ተወላጆች። **62** እነዚህ በመዝገቡ ውስጥ የትውልዳቸውን ሐረግ ቢፈልጉም ለማግኘት ስላልቻሉ ከክህነት አገልግሎት ታገዱ። **63** በኡሪምና በቱሚም የሚዳኝ ካህን እስኪገኝ ድረስ ከማንኛውም የተቀደሰ መሥዋዕት እንዳይበሉ አስተዳዳሪው አዘዛቸው። **64** ጠቅላላ ሕዝቡ7337 **65** ወንድና ሴት አገልጋዮቻቸውን እኔዲሁም 200 ወንድና ሴት የቤተ መቅደስ መዘምራኖቻቸውን ሳይጨምር 42360 ነበር። **66** 736 ፈረሶች፥ 245 በቅሎዎች፥ **67** 435 ግመሎችና 6720 አህዮች ነበሯቸው። **68** በኢየሩሳሌም ወዳለው የእግዚአብሔር ቤት በሄዱ ጊዜ የአባቶች አለቆች ለቤቱ መሥሪያ የበጎ ፈቃድ ስጦታዎቻቸውን ሰጡ። **69** ለሥራው የሚያስፈልገውን እንደ ችሎታቸው መጠን ሰጡ፤ የሰጡትም ስልሳ አንድ ሺህ የወርቅ ዳሪክ፥ አምስት ሺህ ምናን ብርና አንድ መቶ የክህነት ልብስ ነበር። **70** ካንናቱና ሌዋውያኑ፥ ሕዝቡ፥ የቤተ መቅደስ መዘምራን፥ በረኞቹና በቤተ መቅደስ እንዲያገለግሉ የተመደቡት በየከተሞቻቸው ተቀመጡ። የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ በከተሞቻቸው ነበሩ።

Ezra 2:1

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ክፍል ከስደት የተመለሱትን ሰዎች ስም ዝርዝር በመግለጽ ይጀምራል።

ወጡ
ይህ ወደ ኢየሩሳሌም መጓዛቸውን የሚያመለክት ነው። ‹‹ተመለሱ›› ወይም ‹‹ተመልሰው መጡ››

ሠራያ፣ ረዕላያ፣ መረዶክዮስ፣ በላሳን፣ መሴፋር፣ በጉዋይ፣ ሬሁም፣ እና በዓና
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው።

ቁጥራቸውም ይህ ነው
ይህ የሚያሳየው የሰዎቹን የስም ዝርዝር ነው 2:3-35

Ezra 2:3

አጠቃላይ መረጃ፡
ይህ ከምርኮ የተመለሱትን ሰዎች ቀጣይ የስም ዝርዝር እና እያንዳንዱን ቡድን ከነቁጥራቸው የሚያቀርብመረጃ ነው።

Ezra 2:7

አጠቃላይ መረጃ፡
ይህ ከምርኮ የተመለሱትን ሰዎች ቀጣይ የስም ዝርዝር እና እያንዳንዱን ቡድን ከነቁጥራቸው የሚያቀርብመረጃ ነው።

ዛቱዕ --- ዘካይ --- ባኒ
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው።

Ezra 2:11

አጠቃላይ መረጃ፡
ይህ ከምርኮ የተመለሱትን ሰዎች ቀጣይ የስም ዝርዝር እና እያንዳንዱን ቡድን ከነቁጥራቸው የሚያቀርብመረጃ ነው።

ቤባይ --- ዓዝጋድ --- አዶኒቃም
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው።

በጉዋይ
ይህ የሰው ስም ነው። ዕዝራ 2:02ን እንደተ እንደተረጎምከው ተመልከት

Ezra 2:15

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ከምርኮ የተመለሱትን ሰዎች ቀጣይ የስም ዝርዝር እና እያንዳንዱን ቡድን ከነቁጥራቸው የሚያቀርብ መረጃ ነው።

ዓዲን --- አጤር --- ቤሳይ
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው።

ዘጠና-ስምንት
‹‹98››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ezra 2:19

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ከምርኮ የተመለሱትን ሰዎች ቀጣይ የስም ዝርዝር እና እያንዳንዱን ቡድን ከነቁጥራቸው የሚያቀርብ መረጃ ነው። ከምዕራፍ 2:21 ጀምሮ የተጠቀሱት ከመጀመሪያው ከመጡበት ስፍራ ጋር የተዘረዘሩ ስሞች ናቸው።

ሐሱም --- ጋቤር
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው።

ዘጠና-አምስት --- ሃምሳ-ስድስት
‹‹95 --- 56››

የቤተልሔም ልጆች
ዘሮቻቸው በይሁዳ ከተሞች ይኖሩ የነበሩት ሰዎች ስም ዝርዝር እና ቁጥራቸው ከዚህ ይጀምራል።

ነጦፋ
ይህ በይሁዳ ያለ ከተማ ስም ነው።

Ezra 2:23

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ ከምርኮ የተመለሱትን ሰዎች ዘሮቻቸው ይኖሩበት ከነበረው ስፍራ ጋር የተጠቀሱ የእያንዳንዱ ቡድን ስም ዝርዝር ቀጣይ ክፍል ነው።

ዓናቶት --- ዓዝሞት --- ቂርያትይዓሪም --- ከፊራ --- ብኤርትም --- ጌባ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው።

አርባ-ሁለት
‹‹42››

Ezra 2:27

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ ከምርኮ የተመለሱትን ሰዎች ዘሮቻቸው ይኖሩበት ከነበረው ስፍራ ጋር የተጠቀሱ የእያንዳንዱ ቡድን ስም ዝርዝር ቀጣይ ክፍል ነው።

ማክማስ --- ናባው --- መጌብስ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው።

ሃምሳ-ሁለት
‹‹52››

Ezra 2:31

አጠቃላይ መረጃ:-
ይህ ከምርኮ የተመለሱትን ሰዎች ዘሮቻቸው ይኖሩበት ከነበረው ስፍራ ጋር የተጠቀሱ የእያንዳንዱ ቡድን ስም ዝርዝር ቀጣይ ክፍል ነው።

ካሪም --- ሎድ --- ሐዲድ ---- ኦኖ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው።

Ezra 2:34

አጠቃላይ መረጃ:-
ይህ ከምርኮ የተመለሱትን ሰዎች ዘሮቻቸው ይኖሩበት ከነበረው ስፍራ ጋር የተጠቀሱ የእያንዳንዱ ቡድን ስም ዝርዝር ቀጣይ ክፍል ነው።

ሴናዓ
ይህ የቦታ ስም ነው።

Ezra 2:36

አጠቃላይ መረጃ:-
ይህ ከምርኮ የተመለሱትን ካህናት ዘሮቻቸው ይኖሩበት ከነበረው ስፍራ ጋር የተጠቀሱ የእያንዳንዱ ቡድን ስም ዝርዝር ቀጣይ ክፍል ነው።

ዮዳኤ --- አሜር --- ፋስኮር --- ካሪም
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው።

ኢያሱ
ይህ የሰው ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 2:06 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ካሪም
በዕዝራ 2:32 የተጠቀሰው ‹‹ካሪም›› የቦታ ስም ነው፣ ነገር ግን እዚህ የተጠቀሰው ‹‹ካሪም ›› የሰው ስም ነው።

Ezra 2:40

አጠቃላይ መረጃ:-
ይህ ከምርኮ የተመለሱትን ሌዋውያን ዘሮቻቸው ይኖሩበት ከነበረው ስፍራ ጋር የተጠቀሱ የእያንዳንዱ ቡድን ስም ዝርዝር ቀጣይ ክፍል ነው።

ቀድምኤል --- ሆዳይዋ --- ሰሎም --- ጤልሞን፣ ዓቁብ፣ ሐጢጣ፣ እና ሶባይ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው።

ሰባ-አራት
‹‹74››

በር ጠባቂዎች
እነዚህ በቤተ መቅደሱ በሮች ለመግባት ኃላፊነት የተሰጣቸው ናቸው።

አጤር
ይህ የሰው ስም ነው። ይህን ስም በዕዝራ 2:16 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Ezra 2:43

አጠቃላይ መረጃ:-
ይህ ክፍል ዘሮቻቸው ከምርኮ የተመለሱትን የሌዋውያን ስም ዝርዝር በቀጣይነት የያዘ ነው።

ሲሐ፣ ሐሱፋ፣ ጠብዖት፣ ኬራስ፣ ሲዓ፣ ፋዶን፣ ልባና፣ አጋባ፣ --- አጋብ፣ ሰምላይ፣ እና ሐና
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው።

ዓቁብ
ይህን በዕዝራ 2:42 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Ezra 2:47

አጠቃላይ መረጃ:-
ይህ ክፍል ዘሮቻቸው ከምርኮ የተመለሱትን የሌዋውያን ስም ዝርዝር በቀጣይነት የያዘ ነው። እነዚህ ሁሉ የሰዎች ስሞች ናቸው።

Ezra 2:51

አጠቃላይ መረጃ:-
ይህ ክፍል ዘሮቻቸው ከምርኮ የተመለሱትን የሌዋውያን ስም ዝርዝር በቀጣይነት የያዘ ነው። እነዚህ ሁሉ የሰዎች ስሞች ናቸው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ezra 2:55

አጠቃላይ መረጃ፦
ይህ ክፍል ዘሮቻቸው ከምርኮ የተመለሱትን የሌዋውያን ስም ዝርዝር በቀጣይነት የያዘ ነው።

392 ጠቅላላ ዝርያዎች
‹‹ ሦስት መቶ ዘጠና-ሁለት ጠቅላላ ዝርያዎች።›› ይህ በዚህ ቡድን ከምርኮ የተመለሱትን ሰዎች ቁጥር ነው።

Ezra 2:59

አጠቃላይ መረጃ፦
ይህ ከልዩ ልዩ የባቢሎን ከተማዎች ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱ ነገር ግን ዝርያቸውን ማረጋገጥ ያልቻሉ ሰዎች ዝርዝር ነው።

ቴልሜላ፣ ቴላሬሳ፣ ክሩብ፣ አዳን፣ እና ኢሜር
እነዚህ በባቢሎን የነበሩ አሁን ግን የማይገኙ ከተሞች ስሞች ናቸው።

652 ዝርያዎች
‹‹ስድስት መቶ ሃምሳ-ሁለት ዝርያዎች››

ዳላያ፣ ጦብያ፣ ኔቆዳ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው።

Ezra 2:61

ኤብያ --- አቆስ --- ቤርዜሊ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው።

የዘር ሐረጋቸው ዘገባ
ዘገባው ዘሮቻቸው እነማን እንደነበሩ የሚናገር ነው

ሊያገኙ አልቻሉም
‹‹በካህናቱ የስም ዝርዝር ውስጥ ስማቸውን ሊያገኙ አልቻሉ››

እንዳልተቀደሱ ከክህነት ተከለከሉ
ይህ እንደ ተግባራዊ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። ‹‹ ክህነት ›› የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ‹‹ እንደ ካህን መሥራት›› በሚል ግስ ሊተረጎም ይቻላል። ‹‹ ሌሎቹ ካህናት እንደረከሱ ስለቆጠሩአቸው እንደ ካህናት እንዲሠሩ አልፈቀዱላቸውም››

ያልተቀደሰ
ለክህነት ብቁ ያልሆነ

ኡሪም ኣና ቱሚም
ካህናት እግዚአብሔር እንዲያደርጉ የሚፈቅደውን ለመለየት የሚጠቀሙበት ሁለት ትናንሽ ኩብ የሚመስሉ ነገሮች ናቸው

Ezra 2:64

ጠቅላላ ቡድን
ይህ ማለት ከምርኮ ወደ ይሁዳ የተመለሱት ጠቅላላ ቡድን ማለት ነው።

42,360
‹‹አርባ-ሁለት ሺህ ሦስት መቶ ስድሳ››

የእነርሱ የቤት ሠራተኞች
‹‹ የእነርሱ ሴት ሠራተኞቻቸው››

እነዚህ **7,337** ነበሩ
‹‹እነዚህ ሰባት ሺህ ሦስት መቶ ሰላሳ-ሰባት ነበሩ››

ሁለት መቶ
‹‹200››

Ezra 2:66

አጠቃላይ መረጃ፦
እነዚህ የእንስሳቱ ዝርዝር ከአይነታቸው ቁጥር ጋር እንዲሁም አብረዋቸው ከስደት ከተመለሱት ሰዎች ጋር የቀረበ ነው።

Ezra 2:68

ስድሳ-አንድ ሺህ --- አምስት ሺህ --- አንድ መቶ
‹‹ 61,000 ... 5,000 ... 100”

የወርቅ ዳሪክ
‹‹ ዳሪክ ›› በፋርስ ግዛት ውስጥ ጥቅም ላይ ይውል የነበረ ትንሽ የወርቅ ሳንቲም ነው።

ምናን
ምናን የአንድ ነገር መስፈሪያ ወይን መመዘኛ ነው። አንድ ምናን 550 ግራም ይሆናል። ምናን በተለምዶ ብርን ለመለካት ጥቅም ላይ የሚውል ነበር።

ቱኒክስ
የውስጥ አልባሳት

Ezra 2:70

በእስራኤል ያሉ ሰዎች ሁሉ በከተማዎቻቸው ነበሩ
እያንዳንዱ በይሁዳ ወዳለው ወደየቤቱ ተመለሰ። እንዳንዱ በየሩሳሌም መኖሪያውን አላደረገም።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 የእስራኤል ሕዝብ በኢየሩሳሌም እንደ አንድ ሰው ሆነው በሚሰበሰቡበት ጊዜ ወደ ከተሞቻቸው ከመጡ ሰባት ወር ሆኗቸው ነበር። 2 የኢዮሴዴቅ ልጅ ኢያሱና
ካህናት ወንድሞቹ፥ የሰላትያል ልጅ ዘሩባቤልና ወንድሞቹ ተነሥተው በእግዚአብሔር ሰው በሙሴ ሕግ እንደታዘዘው የሚቃጠለው መሥዋዕት የሚቀርብበትን
የእስራኤልን አምላክ መሠዊያ ሠሩ። 3 ከዚያም በምድሪቱ ከሚኖሩ ሰዎች የተነሣ ሥጋት ስለነበረባቸው መሠዊያውን በሥፍራው አቆሙት። የሚቃጠለውንም
መሥዋዕት በጠዋትና በማታ ለእግዚአብሔር አቀረቡ። 4 ደግሞም የዳሱን በዓል እንደተጻፈው አከበሩ፥ ለየዕለቱ እንደታዘዘው የሚቃጠለውን መሥዋዕት ዕለት
በዕለት አቀረቡ። 5 እንዲሁም በበጎ ፈቃድ ከሚቀርበው መባ ሁሉ ጋር ለዕለት፥ ለወርና ለተደነገጉት የእግዚአብሔር በዓላት ሁሉ መሥዋዕት ይቀርብ ነበር። 6
የቤተ መቅደሱ መሠረት ባይጣልም በሰባተኛው ወር የመጀመሪያ ቀን የሚቃጠለውን መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ማቅረብ ጀመሩ። 7 እንዲሁም ለድንጋይ
ጠራቢዎችና ለአናጺዎች ብር ሰጧቸው፤ የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ እንዳዘዘላቸው የዝግባ ዛፎችን ከሊባኖስ በባህር ወደ ኢዮጴ እንዲልኩላቸው ለጢሮስና ለሲዶና
ሰዎች ምግብ፥ መጠጥና ዘይት ሰጧቸው። 8 ከዚያም ዘሩባቤል፥ የኢዮሴዴቅ ልጅ ኢያሱ፥ የቀሩት ካህናቱ፥ ሌዋውያኑና ከምርኮ ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱት
በኢየሩሳሌም ወዳለው ወደ እግዚአብሔር ቤት በመጡ በሁለተኛው ዓመት በሁለተኛው ወር ሥራውን ጀመሩ። ሃያ ዓመትና ከዚያም በላይ የሆኑትን ሌዋውያን
የእግዚአብሔርን ቤት ሥራ እንዲቆጣጠሩ መደቧቸው። 9 ኢያሱም ወንዶች ልጆቹንና ወንድሞቹን፥ ቀድምኤልና ወንዶች ልጆቹን፥ እንዲሁም የይሁዳን ተወላጆች
የእግዚአብሔርን ቤት የሚሠሩትን ሰዎች ለእንዲቆጣጠሩ ደለደላቸው። ከእነርሱም ጋር የኤንሐዳድ ተወላጆች፥ ደግሞም ተወላጆቻቸውና ባልደረቦቻቸው
ሌዋውያን ነበሩ። 10 ግንበኞቹ የእግዚአብሔርን ቤት መሠረት ጣሉ። ይህ ካህናቱ ልብሰ ተክህኗቸውን ለብሰው መለከቶችን ይዘው እንዲቆሙና ሌዋውያኑ
የአሳፍ ወንዶች ልጆች በእስራኤል ንጉሥ በዳዊት እጅ እንደታዘዘው በጸናጽል እግዚአብሔርን ለማመስገን አስቻላቸው። 11 እነርሱም፥ "ቸር ነው! ለእስራኤልም
የቃል ኪዳን ታማኝነቱ ለዘላለም ነው" እያሉ በምስጋናና በውዳሴ ለእግዚአብሔር ዘመሩ። የቤተ መቅደሱ መሠረት ስለተጣለ ሕዝቡ ሁሉ እግዚአብሔርን
እያመሰገኑ በታላቅ የደስታ ድምጽ እልል አሉ። 12 ነገር ግን በርካታ ካህናት፥ ሌዋውያን፥ የአባቶች አለቆችና የመጀመሪያውን ቤት ያዩ አዛውንቶች የዚህኛው ቤት
መሠረት ሲጣል ባዩ ጊዜ በታላቅ ድምጽ አለቀሱ። ብዙዎቹ ግን የመደነቅና የደስታ ጩኸት ይጮሁ ነበር። 13 ሰዎች የደስታውንና የሐሴቱን ድምጽ ክሕዝቡ
የልቅሶ ድምጽ ለመለየት አልቻሉም፥ ሕዝቡ በታላቅ ደስታ ይጮኹ ስለነበር ድምጻቸው ከሩቅ ተሰማ።

Ezra 3:1

ሰባተኛው ወር
በዕብራውያን የዘመን አቆጣጠር ይህ ሰባተኛው ወር ነው። ይህ የደረቁ ወቅት መጠናቀቂያ እና የዝናቡ ወቅት መጀመሪያ ነው። ይህ በምራባውያን የዘመን አቆጣጠር የመስከረም ወር መጨረሻ እና የጥቅምት ወር መጀመሪያ ነው።

እንደ አንድ ሰው
አንድ ሰው በአንድ ቦታ ብቸ ሲሆን አንድ አላማ ብቻ አለው። ‹‹ ለአንድ ዓላማ››

ኢያሱ
ይህ የአንድ ሰው ስም ነው። ይህን ስም በዕዝራ 2:36 እንደተተረጎመው ይሁን።

ሰላትያል
ይህ የአንድ ሰው ስም ነው።

ተነሡ እና ገነቡ
ተነሡ የሚለው ሥራን ለመጀመር መነሣትን የሚያመለክት ነው። ‹‹ሊሠሩ ጀመሩ››

በሙሴ ሕግ እንደተጻፈው
ይህ እንደ ተግባራዊ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። እግዚአብሔር ያዘዘውን በመጥቀስ የበለጠ ግልፅ ማድረግ ትችላለህ። ‹‹እግዚአብሔር በሙሴ ሕግ እንዲሠሩ እንዳዘዛቸው››

Ezra 3:3

መሰዊያውን በሥፍራው ላይ አስቀመጡት
‹‹ መሰዊያውን በመቆሚያው ላይ ከፍ አደረጉት›› ወይም ‹‹ መሰዊያውን በመቆሚያው ሥፍራ አስቀመጡት››

ፍርሃት ነበረባቸው
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ‹‹በጣም ፈርተው ነበር››

በምድሪቱ ሰዎች ምክንያት
አይሁድ የፈሩበትን ምክንያት ግልፅ ለማድረግ ስለ ሰዎቹ የተነገረውን መግለጽ ያስፈልግህ ይሆናል። ‹‹ የምድሪቱ ሰዎች ሊያጠቁአቸው እንደሚፈልጉ ስላሰቡ››

በጥዋትና በማታም የሚቃጠለውን መሥዋዕት ለእግዚአብሔር አቀረቡበት
ሰዎቹ ማድረግ ከሚገባቸው ነገሮች አንዱ የሚቃጠል መሥዋዕት ማቅርብ ነበር። ይህ ቤተ መቅደሱ ከመሠራቱ አስቀድሞ ነበር።

የዳስ በዓል
በዕብራውያን ዘመን አቆጣጠር በሰባተኛው ወር ይህ የዳስ በዓል ለስምንት ቀናት ይከበራል። በዘፀአት ጊዜ እስራኤላውያን በዳስ ይኖሩ የነበረበትን ወቅት የሚያስታውስ በዓል ነው።

Ezra 3:6

የሰባተኛው ወር የመጀመሪያው ቀን
ይህ በዕብራውያን የዘመን መቁጠሪያ ሰባተኛው ወር ነው። የመጀመሪያው ቀን በምዕራባውያን ዘመን አቆጣጠር የመስከረም ወር አጋማሽ ላይ ይውላል።

ቤተ መቅደሱ ገና አልተመሠረተም
አይሁድ ቤተ መቅደሱ ከመመሥረቱ አስቀድሞ የአምልኮ ሥርዓቱን ጀምረው ነበር። ‹‹ቤተ መቅደሱ ገና አልተመሠረተም››

በፋርስ ንጉሥ በቂሮስ በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት
ከቂሮስ የተሰጣቸው ደብዳቤ አይሁድ የሚያስፈልጋቸውን ዕቃ እንዲገዙና ቤተ መቅደሱን መገንባት እንዲችሉ ፈቃድ የሚጣቸው ነው።

Ezra 3:8

ሁለተኛ ወር
ይህ በዕብራውያን ዘመን መቁጠሪያ ሁለተኛው ወር ነው። ይህ ሰዎች ሰብላቸውን የሚሰበስቡበት ሞቃታማ ወቅት ነው። ይህም በምዕራባውያን ዘመን አቆጣጠር የሚያዝያ ወር መጨረሻው ጊዜ እና የግንቦት ወር የመጀመሪያው ክፍል ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሁለተኛው ዓመት
ይህ ከተመለሱበት ዓመት ቀጥሎ ያለው ዓመት ነው።

ለእግዚአብሔር ቤት
እነርሱ በደረሱ ጊዜ የእግዚአብሔ ቤት እንዳልነበረ ግልጽ ማድረግ አለብህ። ‹‹የእግዚአብሔር ቤት በነበረበት ሥፍራ ›› ወይም የእግዚአብሔር ቤትን ሊሰሩበት ወደአሰቡት ስፍራ››

ኢያሱ --- ኢዮሴዴቅ --- ኤንሐዳድ
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው።

ሃያ ዐመቱ
‹‹20 ዓመቱ››

ቀድምኤል
ይህ የሰው ስም ነው። ይህንን ዕዝራ 2:40 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Ezra 3:10

መሠረት መጣል
‹‹መሠረት›› ይህ ቤተ መቅደሱን የሚሸከሞ የድንጋይ መሠረት ከማስቀመጥ የላቀ ነው። የቤተ መቅደሱን ጠቅላላ ወለል በድንጋይ መገንባትን ይጨምራል። ይህም በቤተመቅደሱ ገብተው የሚያመልኩት ሁሉ ልብሳቸውን ለመልበስ እና ንጽሕናቸወን ለመጠበቅ የሚያስችላቸው ነው።

ልብሳቸውን
‹‹የእነርሱ ልዩ አልባሳት››

ከነሐስ የተሠሩ ሁለት ሰሐን መሰል የሙዚቃ መሣሪያዎች
ሁለት ቀጭን፣ ክብ የሆኑ የብረት ሰሐኖች እርስ በርሳቸውን በማጋጨት ከፍተኛ ድምፅ የሚያወጡባቸው የሙዚቃ መሣሪያዎች።

የዳዊት እጅ --- እንዳዘዘው
የንጉሥ እጅ ትእዛዝን ለመስጠት ያለውን ሥልጣን ለማሳየት ጥቅም ላይ የሚውል ምሳሌአዊ አነጋገር ነው።

ማመስገን
ሌሎች ላሳዩን መልካምነት አድናቆታችንን እና ምስጋናችንን የምንገልጥበት ስሜት ነው።

የእርሱ የቃል ኪዳኑ ታማኝነት ለእስራኤል የጸና ነው
‹‹ታማኝነት›› የሚለው ረቂቅ ስም ‹‹በታማኝነት›› ወይም ‹‹ ታማኝ›› በሚለው ቃል ሊገለጽ ይችላል። ‹‹እርሱ እስራኤልን በታማኝነት ለዘላለም ወድዶአል›› ወይም ‹‹ እርሱ ሁልጊዜ ለእስራኤል ለገባው ቃል ኪዳን ታማኝ ነው››

Ezra 3:12

የመጀመሪያ ቤት
ይህ ሰሎሞን ያሰራውን የመጀመሪያውን የእግዚአብሔር ቤት ያመለክታል።

በአይናቸው ፊት
ሰዎቹ የተገለጹት ‹‹በዓይናቸው›› መሆኑ ያዩት ላይ ትኩረት ለማድረግ ነው። ‹‹በዓይናቸው ፊት›› ወይም ‹‹አና አዩት››

በታላቅ ድምፅ አለቀሱ
ይህ ሐዘንን በእንባና በጩኸት መግለጽን ያመለክታል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 አንዳንድ የይሁዳና የብንያም ጠላቶች ከምርኮ የተመለሱት ሰዎች ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በመሥራት ላይ መሆናቸውን ሰሙ። 2 እነርሱም ወደ ዘሩባቤልና ወደ አባቶቻቸው የነገድ አለቆች መጡ። እነርሱም፥ "እንደናንተው አምላካችሁን እንፈልገዋለንና የአሶር ንጉሥ አስራዶን ወደዚህ ስፍራ ካመጣን ጊዜ ጀምሮም ስንሠዋለት ነበርና አብረናችሁ እንሥራ"አሏቸው። 3 ዘሩባቤል፥ ኢያሱና የአባቶቻቸው የነገድ አለቆች ግን፥ "የአምላካችንን ቤት መሥራት የሚገባን እኛ እንጂ እናንተ አይደላችሁም፥ የፋርስ ንጉሥ እንዳዘዘው ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር የምንሠራው እኛ ነን" አሏቸው። 4 ስለዚህ የምድሩ ሕዝብ የይሁዳን ሰዎች እጅ አደከሙ፤ እንዳይሠሩም የይሁዳን ሰዎች አስፈራሩ። 5 ደግሞም ዕቅዳቸውን ለማጨናገፍ ለአማካሪዎች ጉቦ ሰጡ። ይህንንም በቂሮስ ዘመን ሁሉና እስከ ፋርስ ንጉሥ ዳርዮስ እስከ ነገሠበት ጊዜ ድረስ አደረጉ። 6 ከዚያም አርጤክስስ መንገሥ በጀመረበት ዘመን በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ነዋሪዎች ላይ ክስ ጻፉባቸው። 7 በአርጤክስስ ዘመን ቢሽላም፥ ሚትሪዳጡ፥ ጣብኤልና ተባባሪዎቻቸው ነበር ለአርጤክስስ የጻፉት። ደብዳቤውም በአረማይስጥ ቋንቋ ተጽፎ የተተረጎመ ነበር። 8 አዛዡ ሬሁምና ጸሐፊው ሲምሳይ ስለ ኢየሩሳሌም ለአርጤክስስ እንዲህ ብለው ጻፉ፤ 9 ከዚያም ዳኞች የነበሩት ሬሁም፥ ሲምሳይና ተባባሪዎቻቸው እንዲሁም በአርክ፥ በባቢሎንና በኤላሙ ሱሳ የነበሩ ሌሎች የመንግሥት ኃላፊዎች ደብዳቤውን ጻፉ - 10 እነርሱንም ታላቁና ኃያሉ አሹርባኒጳል በወንዙ ማዶ ባለው አውራጃ ከቀሩት ከሌሎቹ ጋር በሰማርያ እንዲሰፍሩ ያስገደዷቸው ሰዎች ደገፏቸው። 11 ለአርጤክስስ የላኩት የደብዳቤው ግልባጭ ይህ ነው፤ "ይህንን የሚጽፉት ከወንዙ ማዶ ያሉት ሰዎች፥ አገልጋዮችህ ናቸው፤ 12 ካንተ ዘንድ የወጡት አይሁድ እኛን በመቃወም አመጸኛይቱን ከተማ በኢየሩሳሌም ውስጥ ለመሥራት መጀመራቸውን ንጉሡ ይወቅ። እነርሱም ቅጥሮቹን ጨርሰው መሠረቶቹን አድሰዋል። 13 ይህቺ ከተማ ከተሠራችና ቅጥሯም ከተጠናቀቀ ምንም ዓይነት እጅ መንሻና ቀረጥ እንደማይሰጡና ንጉሡን እንደሚጎዱት ንጉሡ ይወቅ። 14 በርግጥ የቤተመንግሥቱን ጨው ስለ በላን በንጉሡ ላይ ማናቸውም ዓይነት ውርደት ሲደርስበት ማየት አይገባንም። 15 ለዚህም ነው የአባትህን መዛግብት እንድትመረምርና ነገሥታትንና አውራጃዎችን የምትጎዳ አመጸኛ ከተማ መሆኗን እንድታረጋግጥ ለንጉሡ ያስታወቅነው። በነገሥታትና በአውራጃዎች ላይ ብዙ ችግር የፈጠረች ነች። ከብዙ ዘመን ጀምሮም የአመጽ ማዕከል ነች። ከተማይቱ ተደምስሳ የነበረችውም በዚሁ ምክንያት ነበር። 16 ይህቺ ከተማ ከቅጥሯ ጋር ከተሠራች ከዚህ በኋላ ከታላቁ ከኤፍራጥስ ወንዝ ማዶ ምንም የሚቀርልህ ነገር እንደማይኖር ለንጉሡ እናስታውቃለን"። 17 ስለዚህ ንጉሡ ለሬሁም፥ ሲምሳይ፥ በሰማሪያ ላሉ ተባባሪዎቻቸውና ከወንዙ ማዶ ላሉት ለቀሩት ምላሽ ላከ፤ "ሰላም ይሁንላችሁ። 18 የላካችሁልኝ ደብዳቤ ተተርጉሞ ተነቦልኛል። 19 በመሆኑም ምርመራ እንዲደረግ አዘዝኩኝና ባለፉት ዘመናት በነገሥታት ላይ ስታምጽ የኖረች አመጸኛ መሆኗ ታውቋል። 20 በኢየሩሳሌም ላይ ኃያላን ነገሥታት ገዝተዋል፥ ከወንዙ ማዶ ባለው ሁሉ ላይም ሥልጣን ነበራቸው። እጅ መንሻና ቀረጥም ይሰጣቸው ነበር። 21 አሁንም እነዚህ ሰዎች ሥራውን እንዲያቆሙና እኔ እስከማዝዝ ድረስ ይህቺን ከተማ እንዳይሠሩ ትዕዛዝ ስጡ። 22 ይህንን ማድረጉን ቸል እንዳትሉ ተጠንቀቁ። ነገሥታቱን የሚጎዳው ጥፋት ለምን ይጨምራል?" 23 የንጉሡ የአርጤክስስ ትዕዛዝ በሬሁም፥ በሲምሳይና በተባባሪዎቻቸው ፊት በተነበበ ጊዜ በፍጥነት ወደ ኢየሩሳሌም ሄዱና አይሁድ ሥራውን እንዲያቆሙ አስገደዷቸው። 24 ስለዚህ በኢየሩሳሌም ያለው የእግዚአብሔር ቤት ሥራ የፋርስ ንጉሥ ዳርዮስ እስከ ነገሠበት እስከ ሁለተኛው ዓመት ድረስ ተቋረጠ።

Ezra 4:1

አጠቃላይ መረጃ፦
አይሁድ-ያልሆኑ ሰዎች በቤተ መቅደሱ ግንባታ ላይ ለመሳተፍ ጠየቁ።

ተሰድደው የነበሩ
ይህ በተግባራዊ ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። ‹‹ባቢሎናውያን በምርኮ የወሰዱአቸው››

ዘሩባቤል
የሰው ስም። ይህንን በዕዝራ 2:2 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

አስራዶን፣ የአሦር ንጉሥ
ቂሮስ በፋርስ ከመግዛቱ በፊት አስራዶን በአሦር ይገዛ ነበር።

Ezra 4:3

ኢያሱ
የሰው ስም። ይህን በዕዝራ 2:06 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

እናንተ አይደላችሁም፣ ነገር ግን እኛ እንሠራዋለን
የሚከተሉት ተገቢ ትርጉሞች ናቸው፦ 1. የአይሁድ አለቆች ቂሮስ እንዳዘዛቸው እነርሱ ብቻ መገንባት እንዳለባቸው ተሰማቸው ወይም 2. ቤተ መቅደሱን መገንባት ሙሉ ለሙሉ የአይሁድ ተግባር ነው እንጂ አይሁድ ያልሆኑትን ሰዎች ማሳተፍ አይፈቀድም።

Ezra 4:4

የምድሩ ሰዎች
‹‹ በዚያን ዘመን በምድሩ ላይ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች፣›› አየሁድ ያልሆኑና ባቢሎናውያን በምርኮ ያልወሰዱአቸው አይሁዶች ጭምር››

የየይሁዳን ሕዝብ እጅ ያደክሙ ነበር
ይህ የሚገልጸው በምድሩ ላይ ይኖሩ የነበሩት ሰዎች የይሁዳን ሕዝብ እጃቸውን ያደክሙ እንደነበር ነው። ‹‹ አይሁድን ተስፋ ያስቆርጡ ነበር››

አይሁዶች
ከባቢሎን የተመለሱ እና በይሁዳ ምድር የሰፈሩ ሕዝቦች

እቅዳቸውን ለማጣጣል
‹‹ አይሁዶች እንዳቀዱት ቤተ መቅደሱን ሊሰሩ እንዳይችሉ ማድረግ››

በይሁዳ እና በኢየሩሳሌም በሚኖሩት ሰዎች ላይ የክስ ጽሕፈት ጻፉ
‹‹ክስ›› የሚለው ረቂቅ ስም ‹‹ከሰሰ›› እንደሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። እዚህ ላይ ጠላቶች አይሁድን ምን ሠሩ ብለው እንደከሰሱአቸው ግልፅ ማድረግ ያስፈልግሃል። ‹‹ በይሁዳ እና በኢየሩሳሌም የሚኖሩት ንጉሡን እንደማይታዘዙ ጠቅሰው የክስ ጽሕፈት ጻፉባቸው።››

Ezra 4:7

ቢሽላም --- ሚትሪዳጡ --- ጣብኤል --- ሲምሳይ
የሰው ስሞች

ደብዳቤው
ይህ ደብዳቤ በዕዝራ 4:6 የተነገረው ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አረማይክ
ለይፋ የንግድ ሥራ በዚያን ዘመን ጥቅም ላይ ይውል የነበረ ቋንቋ

ተተረጎመ
ወደ ፋርስ ቋንቋ

ሬሁም
የሰው ስም። ይህንን በዕዝራ 2፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Ezra 4:9

አርካ --- ሱሳ
የከተሞች ስሞች

አስናፈር
ይህ የአንድ ሰው ስም ነው።

ከወንዙ ማዶ ላለው ክፍለ ሐገር
ይህ ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተምዕራብ የሚገኘው ከተማ መጠሪያ ነው። ከሱሳ ከተማ አንፃር ከወንዙ ማዶ የሚገኝ ነው።

Ezra 4:11

ይህ ግልባጭ ነው
ዕዝራ በጽሑፉ ለንጉሥ አርጤክስስ የተጻፈውን ደብዳቤ ይዘት አስፍሮአል።

ከወንዙ ማዶ ላለው ክፍለ ሐገር
ይህ ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተምዕራብ የሚገኘው ከተማ መጠሪያ ነው። ከሱሳ ከተማ አንፃር ከወንዙ ማዶ የሚገኝ ነው። ይህንንበዕዝራ 4፡10 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሃይማታዊ ከተማ
ይህ ከተማ በውስጧ የሚኖሩትን ሰዎች ማንነት በፈሊጣዊ አነጋገር የሚገልጽ ነው። ‹‹ ሊኖሩበት ያቀዱት ከተማ ነገር ግን በአንተ ላይ የምታምጽ ናት››

መሠረቱን አደሱ
‹‹መሠረቱን አስተካከሉ›› ወይም ‹‹ መሠረቱን ጠገኑ››

Ezra 4:13

ይህች ከተማ ከተገነባች ቅጥሮቿም ተሠርተው ካለቁ
ይህ በተግባራዊ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። ‹‹ ከተማዋን ከገነቡ ቅጥሯንም ሠርተው ከፈጸሙ››

ነገር ግን ንጉሡን ይጎዳሉ
‹‹ይጎዳሉ›› የሚለው ቃል አይሁድ ለንጉሡ ገንዘብ መስጠታቸውን እንደሚያቆሙ የሚያመለክት ነው።

Ezra 4:14

የቤተ መንግሥቱን ጨው እንበላለንና
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች:- 1. ጸሐፊዎቹ ለንጉሡ ታማኞች ናቸው ወይም 2. ንጉሡ ለጸሐፊዎቹ የተለየ ክብር ሰጥቶአቸዋል። ‹‹እኛ ለአንተ ታማኞች ነን ›› ወይም ‹‹ እኛን የአንተ ባለሟሎች በማድረግህ አክብረኸናል››

አመጸኛ ከተማ
ከተማዋ በውስጧ የሚኖሩትን ሰዎች ማንነት ትወክላለች:- ‹‹ በዚህች ከተማ የሚኖሩ ሰዎች በአባትህም ላይ ያመጹ ነበሩ››

ከተማዋ ጠፍታ ነበር
ይህ በተግባራዊ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል፣ ከተማዋን ምን እንዳጠፋት ግልጽ ማድረግ ያስፈልግሃል። ‹‹ከተማዋ›› በውስጧ የሚኖሩትን ሰዎች ትወክላለች። ‹‹ ባቢሎናውያን ከተማዋን አጥፍተዋታል››

ይህች ከተማ ቅጥሮቿም ከተሠሩ
ይህ በተግባራዊ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። ይህን በዕዝራ 4፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ‹‹ከተማዋንና ቅጥሮቿን ከገነቡ››

ለአንተ ምንም አይቀርልህም
እዚህ ላይ ‹‹ምንም›› የሚለው ቃል አይሁድ በንጉሡ ላይ ካመጹ ንጉሡ ብዙ የታክስ ገንዘብ እንደሚቀርበት የሚያሳይ የሚያጋንን ቃል ነው።

ከወንዙ ማዶ ላለው ክፍለ ሐገር
ይህ ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተምዕራብ የሚገኘው ከተማ መጠሪያ ነው። ከሱሳ ከተማ አንፃር ከወንዙ ማዶ የሚገኝ ነው። ይህንንበዕዝራ 4፡10 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Ezra 4:17

ከወንዙ ማዶ ላለው ክፍለ ሐገር
ይህ ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተምዕራብ የሚገኘው ክፍለ ሀገር መጠሪያ ነው። ከሱሳ ከተማ አንፃር ከወንዙ ማዶ የሚገኝ ነው። ይህንንበዕዝራ 4፡10 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

ወደ እኔ የላካችሁት ደብዳቤ ተተርጉሞ ተነቦአል
ይህ በተግባራቂ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል፣ በመሆኑም ደብዳቤውን ማን እንደተረጎመውና ለንጉሡ እንደነበበለት ማባራራት ያስፈልግህ ይሆናል። ‹‹ ወደ እኔ የላካችሁትን ደብዳቤ አገልጋዮቼ ተርጉመው አንብበውልኛል››

ሬሁም
የወንድ ስም። ይህንን በዕዝራ 2፡2 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሲምሳይ
የወንድ ስም። ይህንን በዕዝራ 4፡8 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ወንዙ
የኤፍራጥስ ወንዝ

Ezra 4:20

ከወንዝ ማዶ ያለው ክፍለ ሀገር
ይህ ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተምዕራብ የሚገኘው ክፍለ ሀገር መጠሪያ ነው። ከሱሳ ከተማ አንፃር ከወንዙ ማዶ የሚገኝ ነው። ይህንን በዕዝራ 4፡10 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

ቀረጥ እና ግብር ይከፈለቸው ነበር
ይህ ተግባራዊ በሆነ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። ‹‹በኢየሩሳሌም የነበሩ ሰዎች በዚያ ለነበሩ ነገሥታት ቀረጥ እና ግብር ይከፍላሉ። ወይም ‹‹ እነዚያ ነገሥታት ቀረጥና ግብር ማስከፈል ይችሉ ነበር››

አዋጅ አወጀ
‹‹ ሕግ አወጣ››

ይህን ቸል እንዳትሉ ተጠንቀቁ
‹‹ቸል እንዳትሉ›› የሚለው አባባል ፀሐፊዎቹ ንጉሥ አርጤክስስ የነገሩትን እንዲያደርግ የሚፈልጉትን ነገር የሚያሳስብ ነው። ‹‹ቸልም እንዳትሉ ተጠንቀቁ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለነገሥታቱ ጉዳትና ጥፋት እየበዛ ስለምን ይሄዳል?
አርጤክስስ ይህን ጥያቄ በመጠየቁ ቀረጥና ክብር ቢቀርበት ምን ያህል ጉዳት እንደሚሆን መገንዘቡን ነገራቸው። ‹‹ለነገስታቱ ቀረጥና ክብር በመቅረቱ ጉዳት እንዳይሆን ጉዳዩን በጥብቅ መከታተላቸሁን እርግጠኞች መሆን አለባችሁ።››

የጉዳት መብዛት
አደጋው ልክ እንደ እጽዋት እድገት እያሰፋ እና እያደገ እንደሚሄድ ተገልፆአል። ‹‹አደጋ እየከፋ ይሄዳል››

ጉዳቱ በነገሥታቱ ገቢ ላይ የበለጠ ይከፋል
‹‹የነገሥታቱ ገቢ›› የሚለው አባባል የሚያመለክተው የንጉሡን ገቢ ነው። ‹‹ለነገሥታቱ ጉዳትና ጥፋት እየበዛ ስለ ምን ይሄዳል››

Ezra 4:23

የንጉሥ አርጤክስስ አዋጅ ተነበበ
ይህ በተግባራዊ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል፣ በዚህም መሠረት አዋጁን ከንጉሡ ተቀብሎ ለባለ ሥልጣኖቹ ማን እንዳነበበው ግልጽ ማድረግ ያስፈልግሃል። ‹‹የንጉሥ አርጤክስስ መልእክተኞች የእርሱን አዋጅ አነበቡ››

ሬሁም
ይህንን ዕዝራ 2፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሲምሳይ
ይህንን በዕዝራ 4፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

በኢየሩሳሌም ያለው የእግዚአብሔር ቤት ሥር እስከ ዳርዮስ ዘመነ መንግስት ሁለተኛ ዓመት ድረስ ተቋረጠ
ይህ መስተጓጎል 16 ዓመታት ያህል ቆይቶአል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 5

1 ከዚያም ነቢዩ ሐጌና የአዶ ልጅ ንቢዩ ዘካርያስ በይሁዳና በኢየሩሳሌም ለሚኖሩ አይሁድ በእስራኤል አምላክ ስም ትንቢት ተናገሩ። **2** የሰላትያል ልጅ ዘሩባቤልና የኢዮሴዴቅ ልጅ ኢያሱ ካደፋፈሯቸው ነቢያት ጋር በመሆን በኢየሩሳሌም ያለውን የእግዚአብሔር ቤት መሥራት ጀመሩ። **3** ከወንዙ ማዶ ያለው አውራጃ አስተዳዳሪ ተንትናይ፥ ሰተር ቡዝናይና ተባባሪዎቻቸው መጥተው፥ "በማን ትዕዛዝ ነው ይህንን ቤት የምትሠሩትና የቅጥሮቹን ጥገና እየጨረሳችሁ ያላችሁት?" አሏቸው። **4** ደግሞም፥ "ይህን ሕንፃ የሚሠሩት ሰዎች ስም ማን ማን ነው?" አሏቸው። **5** ነገር ግን የእግዚአብሔር ዓይን በአይሁድ አለቆች ላይ ነበር፥ ጠላቶቻቸውም አላስቆሟቸውም። እነርሱም በዚህ ጉዳይ ለንጉሡ ደብዳቤ ለመጻፍና ትዕዛዝ እስኪመጣላቸው ይጠብቁ ነበር። **6** ተንትናይ፥ ሰተር ቡዝናይና ተባባሪዎቻቸው የሆኑት አለቆች ለንጉሡ ለዳርዮስ የጻፉት ደብዳቤ ይህ ነበር፤ **7** እንዲህ ሲሉ ለንጉሡ ዳርዮስ ጻፉለት፤ "ሙሉ ሰላም ለአንተ ይሁን። **8** ወደ ይሁዳ ወደ ታላቁ አምላክ ቤት ሄደን እንደነበረ ንጉሡ ይወቅ። እርሱም በታላላቅ ድንጋዮች እየተሠራና በቅጥሮቹም መሐል እንጨቶችን እያስገቡበት ነው። ሥራው በትጋት እየተሠራና በእጆቻቸው ላይ በመከናወን ላይ ይገኛል። **9** አለቆቹንም፥ "ይህንን ቤትና ቅጥሮቹን እንድትሠሩ የፈቀደላችሁ ማነው?" ብለን ጠየቅናቸው። **10** ደግሞም የሚመሯቸውን ሰዎች የእያንዳንዳቸውን ስም ታውቅ ዘንድ ስሞቻቸውን እንዲነግሩን ጠየቅናቸው። **11** እነርሱም መልሰው፤ "እኛ የሰማይና የምድር አምላክ አገልጋዮች ነን፥ ከብዙ ዓመታት በፊት ታላቁ የእስራኤል ንጉሥ የሠራውንና የጨረሰውን ይህንን ቤት በማደስ ላይ ነን። **12** ይሁንና አባቶቻችን የሰማይን አምላክ ባስቆጡት ጊዜ ይህንን ቤት ባፈረሰውና ሕዝቡን ማርኮ ወደ ባቢሎን በወሰዳቸው በባቢሎን ንጉሥ በናቡከደነፆር እጅ አሳልፎ ሰጣቸው። **13** ሆኖም ቂሮስ በባቢሎን ላይ በነገሠ ጊዜ በመጀመሪያው ዓመት የእግዚአብሔር ቤት እንዲሠራ ትዕዛዝ ሰጠ። **14** ደግሞም ንጉሥ ቂሮስ ናቡከደነፆር ከኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ በባቢሎን ወደሚገኘው መቅደስ ያመጣቸውን የእግዚአብሔር ቤት መገልገያ የሆኑትን የወርቁንና የብሩን ዕቃዎች መለሰ። አስተዳዳሪ እንዲሆን ለሾመው ለሰሳብሳር አስረከበው። **15** እርሱንም፥ "እነዚህን ዕቃዎች ውሰድ። ሂድና በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ውስጥ አኑራቸው። በዚያም የእግዚአብሔር ቤት ይሠራ" አለው። **16** ከዚያም ይህ ሰሳብሳር ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ የእግዚአብሔርን ቤት መሠረት ጣለ፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በመሠራት ላይ ነው፥ ይሁን እንጂ እስካሁን አላለቀም። **17** አሁንም ንጉሡ መልካም መስሎ ከታየው በኢየሩሳሌም የእግዚአብሔር ቤት እንዲሠራ ንጉሥ ቂሮስ ያዘዘው ትዕዛዝ በባቢሎን መዝገብ ቤት ይገኝ እንደሆን ይመርመር፤ ከዚያም ንጉሡ ውሳኔውን ይላክልን።

Ezra 5:1

አዶ --- ኢያሱ --- ኢዮሴዴቅ
የሰዎች ስም

ሰላትያል
የወንድ ስም። ይህንን በዕዝራ 3፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

የእግዚአብሔርን ቤት ለመሥራት
ይህ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነበረ

Ezra 5:3

ተንትናይ --- ሰተርቡዝናይ
የሰዎች ስሞች

ከወንዙ ማዶ ያለ ክፍለ ሐገር
ይህ ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተምዕራብ የሚገኘው ክፍለ ሀገር መጠሪያ ነው። ከሱሳ ከተማ አንፃር ከወንዙ ማዶ የሚገኝ ነው። ይህንን በዕዝራ 4፡10 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

የእግዚአብሔር ዓይን በላዩ
ዓይን የሚለው የሚያሳየው አንድን ሰው የሚጠብቅ ሌላ ሰው እንዳለ ነው። ‹‹እግዚአብሔር ይጠብቅ ነበር››

አንድ ደብዳቤ ወደ ንጉሡ እንዲላክ እና አዋጁ ወደ እነርሱ እንዲመለስ
ይህ በተግባራዊ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። ‹‹ አንድ ባለ ሥልጣን ደብዳቤ ወደ ንጉሡ እንዲልክ ንጉሡም ደብዳቤውን መልሶ ከአዋጅ ጋር ወደ እነርሱ እንዲልክ››

Ezra 5:6

ይህ የደብዳቤው ግልባጭ ነው
ዕዝራ በቤተ መቅደሱ ስላለው የእነርሱ ሥራ ለንጉሡ ለዳርዮስ በተጻፈው ደብዳቤ ውስጥ ያለውን ይዘት ጠቅሶአል።

ከወንዙ ማዶ ያለ ክፍለ ሐገር
ይህ ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተምዕራብ የሚገኘው ክፍለ ሀገር መጠሪያ ነው። ከሱሳ ከተማ አንፃር ከወንዙ ማዶ የሚገኝ ነው። ይህንን በዕዝራ 4፡10 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Ezra 5:8

አጠቃላይ መረጃ
ከተንትናይ የተጻፈ ደብዳቤ ከዕዝራ 5፡7 ጀምሮ ለተጠቀሰው ንጉሡ ይቀጥላል

ግንዶች
ለግንባታ የሚሆኑ እንጨቶች

ማን አወጀላችሁ
‹‹ማን ፈቀደላችሁ››

Ezra 5:11

አጠቃላይ መረጃ:
ከተንትናይ የተጻፈ ደብዳቤ ከዕዝራ 5፡7 ጀምሮ ለተጠቀሰው ንጉሡ ይቀጥላል።

የአንዱ አገልጋዮች ነን
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1. የአይሁድን ሰዎች የእግዚአብሔር ባሪያዎች ብለው ይጠሩአቸዋል ወይም 2. መልስ የሰጡአቸው ለቤተ መውደሱ የአምልኮ እና የመስዋዕት አገልግሎት ኃላፊዎች ከሌዊ እና ከአሮን ወገን ስለሆኑ ነው።

ከብዙ ዘመናት በፊት ታላቁ የእስራኤል ንጉሥ ሠርቶ የጨረሰው ነው
ይህ ተግባራዊ በሆነ ቅርጽ ሊተረጎም የሚችል ነው። ‹‹ የእስራኤል ታላቁ ንጉሥ ሊገነባው የሚያስፈልገውን ዕቃ ሁሉ ሰጠ››

ሠርቶ ፈጸመው
‹‹የሚያስፈልገውን ዕቃ ሁሉ ሰጠ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ezra 5:12

አጠቃላይ መረጃ፡-
ከተንትናይ ለንጉሡ የተጻፈ ደብዳቤ ይቀጥላል። ከዕዝራ 5፡11 ጀምሮ ተንትናይ አይሁድ የነገሩትን ሁሉ ለንጉሡ መንገሩን ቀጥሎአል።

የሰማይን አምላክ አስቆጡ
‹‹ የሰማይ አምላክ በእኛ እጅግ እንዲቆጣ አደረገው››

በባቢሎን ንጉሥ በከለዳዊው በናቡከደነፆር እጅ አሳልፎ ሰጣቸው፣ እርሱም ይህን ቤት አወደመው ሕዙንም ወሰዳቸው
እጅ የሚለው ቃል ኃይልንና ሥልጣንን የሚያመለክት አባባል ነው፣ እንዲሁም፣ ‹‹ናቡከደነፆር›› ሠራዊቱን ይወክላል። ‹‹የከለዳዊው የባበሊሎን ንጉሥ የናቡከደነፆር ሠራዊት ይህንን ቤት እንዲያወድም እና ሕዝቡን እንዲወስድ ፈቀደለት››

ይህን ቤት እንዲያወድም
‹‹ይህን ቤት እንዲያፈርሰው››

ቂሮስ የእግዚአብሔር ቤት እንደገና እንዲሠራ ፈቃድ ሰጠ
ቂሮስ ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ እንደገና እንዲሰሩ አዘዘ።

Ezra 5:14

አጠቃላይ መረጃ
ከተንትናይ በዕዝራ 5፡7 ጀምሮ ለተገለጸው ንጉሡ የተጻፈ ደብዳቤ ይቀጥላል። ከዕዝራ 5፡11 ጀምሮ ተንትናይ አይሁድ የነገሩትን ሁሉ ለንጉሡ መንገሩን ቀጥሎአል።

ሰሳብሳር
ይህንን በዕዝራ 1፡7 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

እርሱ መለሳቸው
ንጉሥ ቂሮስ የቤተ መቅደሱን ዕቃዎች መለሳቸው

የእግዚአብሔር ቤት እንደገና ይሠራ
ይህ በተግባራዊ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። ‹‹ አይሁዶች የእግዚአብሔርን ቤት እንደገና እንዲሠሩ እፈልጋለሁ..

Ezra 5:16

አጠቃላይ መረጃ፡-
ከተንትናይ በዕዝራ 5፡7 ጀምሮ ለተገለጸው ንጉሡ የተጻፈ ደብዳቤ ይቀጥላል። ከዕዝራ 5፡11 ጀምሮ ተንትናይ አይሁድ የነገሩትን ሁሉ ለንጉሡ መንገሩን ቀጥሎአል።

እየተገነባ ነው፣ ነገር ግን አልተጠናቀቀም
ይህ እንደ ተግባራዊ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። ‹‹ሕዝቡ እየገነባው ነው፣ ነገር ግን ሥራውን ፈጽመው አላጠናቀቁትም››

ተገንብቷል
ታንጾአል

Ezra 5:17

አጠቃላይ መረጃ፡-
ተንትናይ ከዕዝራ 5፡7 ጀምሮ ለተጠቀሰው ንጉሥ የጻፈው ደብዳቤ ቀጥሏል። ተንትናይ አየሁዶች የነገሩትን ለንጉሡ መንገሩን ጨርሶአል አሁን ንጉሡን የሚጠይቀው አይሁዶች የነገሩት ሁሉ ትክክል መሆኑን እንዲያጣራ ነው።

ነገሩ ይመርመር
ይህ እንደ ተግባራዊ ቅርጽ ሊተረጎመ ይችላል። ‹‹አንድ ሰው አዝዘህ ይህን ጉዳይ እንድታስመረምር እፈልጋለሁ››

የንጉሥ ቂሮስ ፍርድ በዚያ ለመኖሩ
‹‹ንጉሥ ቂሮስ ይህን አዋጅ ስለማውጣቱ የተመዘገበ ነበር ካለ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 6

1 ስለዚህ ንጉሥ ዳርዮስ በባቢሎን ባሉት ቤተ መዛግብት ምርመራ እንዲደረግ አዘዘ። **2** በሜዶን አገር ቅጥር ባላት ኤክባታና ከተማ አንድ የመጽሐፍ ጥቅልል ተገኝ፥ ጽሑፉም የሚለው እንዲህ ነበር፤ **3** "ንጉሡ ቂሮስ በነገሠ በመጀመሪያው ዓምት በኢየሩሳሌም ስላለው የእግዚአብሔር ቤት ቂሮስ እንዲህ የሚል ትዕዛዝ ሰጥቷል፤ የመሥዋዕቱ ቤት ይሠራ። ቅጥሩም ስልሳ ክንድ ከፍታ፥ ስልሳ ክንድ ወርድ ተደርጎ **4** በሦስት ዙር ትላልቅ ድንጋዮችና በአንድ ዙር አዲስ እንጨት ይሠራ። ወጪውም በንጉሡ ቤት ይሸፈን። **5** ደግሞም ናቡከደነፆር ከኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ወደ ባቢሎን ቤተ መቅደስ ያመጣቸውን የእግዚአብሔር ቤት የወርቅና የብር ዕቃዎች መልሱላቸው። በኢየሩሳሌም ወዳለው ቤተ መቅደስ ላኩና በዚያ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ይቀመጥ። **6** አሁንም በወንዙ ማዶ ያላችሁት ተንትናይ፥ ሰተር ቡዝናይና ተባባሪዎቻችሁ ከእነርሱ ራቁ። **7** ይህንን የእግዚአብሔር ቤት ሥራ ለእነርሱ ብቻ ተዉላቸው። ይህንን የእግዚአብሔር ቤት አስተዳዳሪውና የአይሁድ አለቆች በዚያው ሥፍራ ላይ ይሠሩታል። **8** ለእነዚህ የእግዚአብሔርን ቤት ለሚሠሩት ይህንን እንድታደርጉላቸው አዝዣለሁ፤ ሥራቸውን እንዳያስተጓጉሉ በወንዙ ማዶ ካሉት ለንጉሡ ከሚሰበሰበው ገቢ ላይ ወጪ እየተደረገ ይከፈላቸው። **9** ለሰማይ አምላክ ለሚቃጠለው መሥዋዕት የሚፈለገው ሁሉ ወይፈኖችን፥ አውራ በጎችን ወይም ጠቦቶችን እንዲሁም በኢየሩሳሌም ባሉት ካህናት ትዕዛዝ መሠረት ስንዴ፥ ጨው፥ ወይን ወይም ዘይት እነዚህን ነገሮች ሳታቋርጡ በየዕለቱ ስጧቸው። **10** ለሰማይ አምላክ መሥዋዕት እንዲያቀርቡና ለእኔ ለንጉሡና ለልጆቼም እንዲጸልዩ ይህንን አድርጉላቸው። **11** ይህንን ትዕዛዜን የሚተላለፍ ማንም ቢሆን የቤቱ ምሶሶ ተነቅሎ እርሱ እንዲሰቀልበት አዝዣለሁ። በዚህ ምክንያት መኖሪያ ቤቱ የቆሻሻ መጣያ ይሁን። **12** በኢየሩሳሌም የሚገኘውን የእግዚአብሔር ቤት ለማፍረስ የሚነሳውን ንጉሥና ሕዝብ በዚያ የሚኖረው አምላክ ያጥፋው። እኔ ዳርዮስ ይህንን አዝዣለሁ። ሙሉ በሙሉ ይፈጸም። **13** ከዚያም ተንትናይ፥ ሰተር ቡዝናይና ተባባሪዎቻቸው ንጉሡ ዳርዮስ ያዘዘውን ሁሉ ፈጸሙ። **14** ስለዚህ የአይሁድ አለቆች ሐጌና ዘካርያስ በትንቢት በነገሯቸው መሠረት ሥራውን ሠሩ። እነርሱም በእስራኤል አምላክ በእግዚአብሔር እና በፋርስ ነገሥታት በቂሮስ፥ በዳርዮስና በአርጤክስስ ትዕዛዝ መሠረት ሠሩ። **15** ቤቱም ንጉሡ ዳርዮስ በነገሠ በስድስተኛው ዓመት አዳር በሚባለው ወር በሦስተኛው ቀን ተጠናቀቀ። **16** የእስራኤል ሕዝብ፥ ካህናቱ፥ ሌዋውያኑና የቀሩት ምርኮኞች የዚህን የእግዚአብሔር ቤት ምረቃ በደስታ አከበሩ። **17** እነርሱም ለእግዚአብሔር ቤት ምረቃ አንድ መቶ ወይፈኖችን፥ ሁለት መቶ አውራ በጎችንና አራት መቶ ጠቦቶችን አቀረቡ። ለእያንዳንዱ የእስራኤል ነገድ አንድ፥ ለእስራኤል ሁሉ የኃጢአት መሥዋዕት አሥራ ሁለት ወንድ ፍየሎች ቀረቡ። **18** ደግሞም ካህናቱና ሌዋውያኑ በሙሴ ሕግ እንደተጻፈው በኢየሩሳሌም ያለውን የእግዚአብሔር ቤት አገልግሎት በየተራቸው እንዲፈጽሙ ተመደቡ። **19** እንዲሁም በምርኮ የነበሩት በመጀመሪያው ወር በአሥራ አራተኛው ቀን የፋሲካን በዓል አከበሩ። **20** ካህናቱና ሌዋውያኑ ሁሉ ራሳቸውን አነጹና እራሳቸውን ጨምሮ በምርኮ ለነበሩት ሁሉ የፋሲካውን መሥዋዕቶች አረዱ። **21** የፋሲካውን ሥጋ ከበሉት እስራኤላውያን ውስጥ አንዳንዶቹ ከምርኮ የተመለሱና ራሳቸውን ከሚኖሩበት ምድር ሰዎች እርኩሰት በመለየት የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን የሚፈልጉ ነበሩ። **22** እግዚአብሔር ደስታን ስለ ሰጣቸውና በቤቱ፥ በእስራኤል አምላክ ቤት ሥራ ላይ እጆቻቸውን እንዲያበረቱ የአሶር ነገሥታትን ልብ መልሶላቸው ስለነበረ የቂጣውን በዓል ለሰባት ቀናት በደስታ አከበሩ።

Ezra 6:1

ምርመራው እንዲደረግ ታዘዘ
‹‹ምርመራ›› የሚለው ረቂቅ ስም ‹‹መመርመር›› ወይም ‹‹መፈለግ›› በሚሉት ቃላት ሊገለጽ ይችላል። ‹‹በለሟሎቹ ነገሩን እንዲመረምሩ አዘዘ›› ወይም ‹‹ባለሟሎቹ ጉዳዩን እንዲፈልጉ አዘዘ››

ምርመራ እንዲደረግ አዘዘ
ምን ይመረምሩ እንደነበር በግልጽ ሊብራራ ይችላል። ‹‹መዛግብቱን እንዲመረምሩ ባለሟሎቹን አዘዛቸው›› ወይም ‹‹ንጉስ ቂሮስ አይሁድ በኢየሩሳሌም የእግዚአብሔርን ቤት እንዲሠሩ አዝዞአቸው እንደሆነ መርምረው እንዲያገኙ ባለሟሎቹን አዘዛቸው››

ቤተ መዛግብት
ይህ ሕንፃ የንጉሡ አስፈላጊ የሆኑ የመንግሥት መዛግበት የሚቀመጡበት ሕንፃ ነው።

አሕምታ
ይህ የከተማ ስም ነው።

አንድ ጥቅል መጽሐፍ ተገኝቷል
ይህ በተግባራዊ ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። ‹‹አንድ ጥቅል መጽሐፍ አገኙ›› ወይም ‹‹ስለ ዳርዮስ እና ኢየሩሳሌም የሚናገር አንድ ጥቅል መጽሐፍ አገኙ››

Ezra 6:3

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ንጉሥ ቂሮስ አይሁድ በኢየሩሳሌም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ እንዲሠሩ ያዘዘበት መዝገብ ጅማሬ ነው።.

በንጉሥ ቂሮስ የመጀመሪያው ዓመት
ይህ ዓመት ንገሡ የነገሠበት የመጀመሪያው ዓመት እንደሆነ ግልጽ መደረግ ይችላል። ‹‹ንጉሥ ቂሮስ በነገሠበት በመጀመሪያው ዓመት››

ቤቱ እንደገና ይገንባ
ይህ በተግባራዊ ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። ‹‹አይሁዶች ቤቱን ይገንቡይት›› ወይም ‹‹አየሁዶች ቤቱን መገንባት አለባቸው››

ስድሳ ኩቢት
‹‹ስድሳ ኩቢት›› ይህንን ወደ ዘመናዊው መለኪያ መለወጥ ትችላለህ። ‹‹ሃያ ሰባት ሜትር››

ኩቢት፣ ሦስት ረድፍ ረጃጅም ድንጋዮች እና አንድ ረድፍ አዲስ ግንድ
ይህ እንደ አዲስ አረፍተ ነገር ሊቀርብ ይችላል። የሚከተሉት ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች ናቸው 1. ይህ የሚገልጸው መሠረቱ እንደሚጣል ነው ‹‹ኩቢት። መሠረቱን በሦስ ረድፍ ረጃጅም ድንጋዮችና በላዩም አንድ ረድፍ ግንድ በማድረግ ገንቡት›› ወይም 2. ይህ ግድግደዎቹ እንዴት እንደሚገነቡ ይገልጻል። ‹‹ኩቢት። የቤቱን ግድግዳዎች በሦስት ረድፍ ረጃጅም ድንጋዮች ከእያንዳንዱ ረገድፍ ቀጥሎ አንድ ረድፍ ግንድ በማድረግ ገንቡአቸው››

ወጪው ከንጉሡ ቤት ይከፈል
‹‹ከንጉሡ ቤት›› የሚለው ሐረግ የሚወክለው በነገሥታቱ ንብረት የሚገኘውን የንጉሥ ቂሮስን የግል ሀብት ነው። ይህ በአድራጊ ቅርጽ ሊቀርብ ይችላል። ‹‹ከነገሥታቱ ንብረት ወጪውን እኔ እከፍላለሁ››

Ezra 6:6

አጠቃላይ መረጃ፡-
ይህ ንጉሥ ቂሮስ አይሁድ በኢየሩሳሌም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ እንዲገነቡ ያዘዘበት በዕዝራ 6፡3 ላይ የተገለጸው ዘገባ ቀጣይ ክፍል ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ተንትናይ --- ሰተርቡዝናይ
ዳርዮስ በቀጥታ የጻፈው ለእነዚህ ሰዎች ነው። በዕዝራ 5:3 እንደተገለጸው ስማቸውን ተርጉም።

ከወንዙ ማዶ ያለው ክፍለ ሐገር
x

Ezra 6:8

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ንጉሥ ቂሮስ አይሁድ በኢየሩሳሌም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ እንዲገነቡ ያዘዘበት በዕዝራ 6:3 ላይ የተገለጸው ዘገባ ቀጣይ ክፍል ነው።

አስፈላጊው ገንዘብ በወንዙ ማዶ ከሚገኘው አገር ከንጉሡ የግብር ገቢ ለእነዚህ ሰዎች እንዲከፈል
ይህ እንደ አድራጊ ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። ‹‹በወንዝ ማዶ ካለው አገር ከሚመጣው ግብር ከንጉሡ ገንዘብ ለእነዚህ ሰዎች ወጪውን በትጋት እንድትሰጡአቸው››

በወንዙ ማዶ ከሚገኘው አገር ከንጉሡ የግብር ገቢ
‹‹የንጉሡ የግብር ገቢ›› የሚያመለክተው ሰዎች ለንጉሡ የሚከፍሉትን ቀረጥ ነው። ‹‹ከወንዙ ማዶ ከለው አገር ከሚኖሩ ሰዎች ለንጉሡ በቀረጥ ከምትሰበስቡት ገንዘብ››

የሚያስፈልገውን
ይህ እንደ አድረጊ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። ‹‹የሚያስፈልጋቸውን››

Ezra 6:11

አጠቃላይ መረጃ፡-
ይህ ንጉሥ ቂሮስ አይሁድ በኢየሩሳሌም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ እንዲገነቡ ያዘዘበት በዕዝራ 6:3 ላይ የተገለጸው ዘገባ ቀጣይ ክፍል ነው።

ምሰሶው ከቤቱ ተነቅሎ እርሱ ይሰቀልበት ቤቱም የጉድፍ መጣያ ይደረግ
ይህ በአድራጊ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። ‹‹ምሰሶውን ከቤቱ ነቅለው እርሱን ይሰቀልበት ዘንድ ባለሥልጣኖቼን አዝዣለሁ። ቤቱንም የጉድፍ መጣያ ያደርጉታል››

ምሰሶ
ትልቅ እና ቀጥ ያለ የቤትን ጣሪያ የሚደግፍ እንጨት

ይሰቀልበት
ይጠረቅበት

ለመለወጥ እጃቸውን ያነሡትን --- ወይም ለማፍረስ
እጃቸውን ማንሳት የሚለው የሚወክለው አነድ ነገር ለማድረግ መሞከር። ‹‹ለመለወጥ የሚሞክር --- ወይም ለማጥፋት›› ወይም ‹‹እለውጣለሁ የሚል --- ወይም የሚያጠፋ››

ይህን ድንጋጌ ሊለውጥ
‹‹ድንጋጌ›› የሚለው የስውር ስም ‹‹እኔ የደነገግሁትን›› በሚለው ሐረግ ሊገለጽ ይችላል። ‹‹ እኔ የደነገግሁትን ለመለወጥ›› ወይም ‹‹እኔ ከደነገግሁት የተለየ የሚናገር››

Ezra 6:13

ተንትናይ --- ሰተርቡዝናይ
በዕዝራ 5:03 ላይ እነዚህን ስሞች እንደተረጎምከው አስቀምጣቸው

ቤቱ ተጠናቀቀ
ይህ በአድራጊ ቅርጹ ሊተረጎም ይችላል። የትኛውን ቤት ሠርተው እንዳጠናቀቁ ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። ‹‹የእግዚአብሔርን ቤት ሠርተው አጠናቀቁ›› ወይም ‹‹ቤተ መቅደሱን መገንባት አጠናቀቁ››

በአዳር ወር በሦስተኛው ቀን
‹‹አዳር›› በዕብራውያን የዘመን አቆጣጠር የአሥራ ሁለተኛውና የመጨረሻው ወር መጠሪያ ነው። ይህ ቀዝቃዛው ወቅት ነው። በምርአባውያን የዘመን አቆጣጠር ሦስተኛው ቀን ወደ ፌብሩዋሪ መካከለኛው ቀን ይጠጋል።

ስድስተኛ ዓመት
ንጉሥ ዳርዮስ የነገሠው ለአምስት አመታት ነበር፣ አሁን ስድሰተኛ አመቱን ይዞአል።

Ezra 6:16

የቀሩት ምርኮኞች
እነዚህ ሰዎች የተማረኩና ወደ ባቢሎን ተወስደው የነበሩ፣ ነገር ግን ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱ ናቸው። ‹‹የቀሩት ምርኮኞች ወደ በምርኮ ተወስደው የነበሩ ሲሆኑ በኋላ ግን ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱ ናቸው›› ወይም ‹‹የተቀሩት ሰዎች ከምርኮ የተመለሱ ናቸው››

መቶ ወይፈኖች --- አራት መቶ ጠቦቶች
‹‹100 ወይፈኖች --- 400 ጠቦቶች›› በንግግር ሐረግ መገለጽ ይቻላል።

የሥራ ክፍፍል
ስውር ስም የሆነው ‹‹የሥራ ክፍፍል›› በንግግር ሐረግ ሊገለጽ ይችላል። ‹‹በቡድን እንዲሠሩ››

የሥራ ክፍፍል
‹‹በጋራ የሚሠሩ ቡድኖች››

Ezra 6:19

የመጀመሪያው ወር አስራ አራተኛ ቀን
ይህ በዕብራውያን ዘመን አቆጣጠር የመጀመሪያው ወር ነው። አስራአራተኛው ቀን በምዕራባውያን ዘመን አቆጣጠር ለኤፕሪል ወር መጀመሪያ ይቀርባል።

ራሳቸውን አነጹ
‹‹ራሳቸውን ንጹህ አደረጉ።›› ራስን ንጹህ ማድረግ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ማግኘትን ያመለክታል። ‹‹ራሳቸውን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኙ አደረጉ››

Ezra 6:21

በምድሩ ላይ ከሚኖሩ ካልነጹ ሰዎች ራሳቸውን ለዩ
ራስን ከርኩሰት መለየት የሚያሳየው የሚያረክሱ ነገሮችን አለማድረግን ነው። ‹‹እነርሱ በምድሩ ላይ የሚኖሩት ሰዎች የሚያደርጉትን ነገር ግን የሚያረክሳቸውን ነገር ማድረግ እምቢ አሉ››

የምድሩ ሰዎች ርኩሰት
እዚህ ላይ ‹‹ርኩሰት›› የሚያመለክተው በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን አለማግኘትን ነው። ‹‹ በምድሩ ላይ የሚኖሩት ሰዎች በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዳያገኙ ያደረጋቸው የሚያደርጉት ርኩሰት የሞላበት ሥራ ነው

እግዚአብሔርን መፈለግ
እግዚአብሔርን መፈለግ የሚያመለክተው እርሱን ለማወቅ፣ ለማምለክ፣ እና ለመታዘዝ መምረጥ ነው። ‹‹ እግዚአብሔርን መታዘዝ መምረጥ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የአሦርን ንጉሥ ልብ መመለስ
የንጉሡን ልብ መመለስማለት ስለ ቤተ መቅደሱ ሥራ ሲያስብ ከነበረው የተለየ እንዲያስብ ማድረግ ነው። ‹‹የአሦር ንጉስ የነበረውን ዝንባሌ መለወጥ›› ወይም ‹‹የአሦርን ንጉሥ ፈቃደኛ ማድረግ››

ለቤቱ ሥራ እጃቸውን ያበረታ ዘንድ
ለሥራው እጃቸውን ያበረታ ዘንድ የሚለው የሚያመለክተው እንዲሠሩ መርዳትን ነው። የአሦር ንጉሥ ይህን ያደረገው እንዲሠሩ በመናገር እና ለሥራውም የሚያስፈልገውን ገንዘብ በመድጠት ነው። ‹‹ ቤቱን እንዲሠሩ ለመርዳት›› ወይም ቤቱን እንዲሠሩ ለማስቻል››

የቤቱ ሥራ
ይህ የሚያመለክተው የቤተ መቅደሱን ሥራ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 7

1 ከእነዚህ ነገሮች በኋላ በንጉሡ በአርጤክስስ ዘመነ መንግሥት በትውልዱ የሠራያ፥ ዓዛርያስ፥ ኬልቅያስ፥ **2** ሰሎም፥ ሳዶቅ፥ አኪጦብ፥ **3** አማርያ፥ ዓዛርያስ፥ መራዮት፥ **4** ዘራአያ፥ ኦዚ፥ ቡቂ፥ **5** አቢሱ፥ ፊንሐስ፥ አልዓዛር ከዚያም የታላቁ ካህን የአሮን ልጅ የሆነው ዕዝራ - **6** ዕዝራ ባቢሎንን ለቆ ወጣ። እርሱም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ለሙሴ በሰጠው ሕግ በሚገባ የተካነ ጸሐፊ ነበር። የእግዚአብሔር እጅ ከእርሱ ጋር ስለነበረ የጠየቀውን ሁሉ ንጉሡ ሰጠው። **7** ደግሞም በንጉሥ አርጤክስስ በሰባተኛው ዓመት አንዳንድ የእስራኤል ተወላጆችና ካህናቱ፥ ሌዋውያን፥ የቤተ መቅደስ መዘምራን፥ በር ጠባቂዎችና በቤተ መቅደስ እንዲያገለግሉ የተመደቡት ወደ ኢየሩሳሌም ወጡ። **8** እርሱም በዚያው ዓመት በአምስተኛው ወር ኢየሩሳሌም ደረሰ። **9** በመጀመሪያው ወር በመጀመሪያው ቀን ባቢሎንን ለቀቀ። መልካሚቱ የእግዚአብሔር እጅ ከእርሱ ጋር ስለነበረ ኢየሩሳሌም የደረሰው በአምስተኛው ወር የመጀመሪያ ቀን ነበር። **10** ዕዝራም የእግዚአብሔርን ሕግ ለማጥናት፥ ለመተግበርና ሥርዓትና ትዕዛዙን ለማስተማር ልቡን አዘጋጅቶ ነበር። **11** ንጉሡ አርጤክስስ ለካህኑና እግዚአብሔር ለእስራኤል በሰጠው ትዕዛዝና ሥርዓት ጸሐፊና ለሆነው ለዕዝራ የሰጠው ትዕዛዝ ይህ ነበር፤ **12** ከንጉሠ ነገሥት አርጤክስስ፥ የሰማይ አምላክ ሕግ ጸሐፊ ለሆነው ለካህኑ ዕዝራ፤ **13** በመንግሥቴ ውስጥ እስራኤላዊ የሆነ ማንም ቢሆን ከካህናቶቻቸውና ከሌዋውያኖቻቸው ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ የሚወዱ ካንተ ጋር እንዲሄዱ አዝዣለሁ። **14** ይሁዳና ኢየሩሳሌምን በሚመለከት በምታውቀው በእግዚአብሔር ሕግ እንድትመረምር፥ **15** ለእስራኤል አምላክ በፈቃዳቸው ያቀረቡትን ብርና ወርቅ ወደ ኢየሩሳሌም ወደ ቤቱ እንድትወስድ እኔ ንጉሡና ሰባቱ አማካሪዎቼ ልከንሃል። **16** ሕዝቡና ካህናቱ በኢየሩሳሌም ለሚገኘው የእግዚአብሔር ቤት በፈቃዳቸው ካቀረቡት በተጨማሪ ባቢሎናዊያን በሙሉ የሰጡትን ወርቅና ብር ሁሉ በነጻ ስጥ። **17** ስለዚህ በሬዎችን፥ አውራ በጎችንና ጠቦቶችን፥ ስንዴና የመጠጥ ቁርባኑን በርከት አድርገህ ግዛ። በኢየሩሳሌም በሚገኘው በአምላክህ ቤት መሠዊያ ላይ ሠዋቸው። **18** በቀረው ብርና ወርቅ አምላክህን ለማስደሰት አንተና ወንድሞችህ መልካም መስሎ የታያችሁን ሁሉ አድርጉበት። **19** በፈቃደኝነት የተሰጡህን ዕቃዎች በኢየሩሳሌም በሚገኘው በአምላክህ ቤት ለአገልግሎት እንዲሆን በፊቱ አስቀምጥ። **20** ለአምላክህ ቤት ያስፈልጋል ብለህ ለምትጠይቀው ለየትኛውም ተጨማሪ ወጪ ገንዘቡን ከግምጃ ቤቴ ውሰድ። **21** እኔ ንጉሥ አርጤክስስ በወንዙ ማዶ ላላችሁት የግምጃ ቤት ኃላፊዎች በሙሉ፥ ዕዝራ የሚጠይቃችሁን ማናቸውንም ነገር በዛ አድርጋችሁ እንድትሰጡት አዝዣለሁ፥ **22** እስከ አንድ መቶ መክሊት ብር፥ አንድ መቶ ቆሮስ ስንዴ፥ አንድ መቶ የባዶስ መስፈሪያ ወይንና አንድ መቶ የባዶስ መስፈሪያ ዘይት፥ ደግሞም ያለ መጠን የሆነ ጨው ስጡአቸው። **23** ከሰማይ አምላክ የሚመጣውን ማንኛውንም ነገር ለቤቱ በትጋት አድርጉት። በእኔና በልጆቼ መንግሥት ላይ ቁጣው ለምን ይምጣብን? **24** በካህናቱ፥ በሌዋውያኑ፥ በሙዚቀኞቹ፥ በበር ጠባቂዎቹ ወይም ለቤተ መቅደሱ አገልግሎት በተመደቡት ሰዎችና የዚህ አምላክ ቤት አገልጋዮች በሆኑት ላይ ምንም ዓይነት እጅ መንሻም ሆነ ቀረጥ እንዳይጥሉ ስለ እናንተ እናስታውቃቸዋለን። **25** አንተም ዕዝራ፥ እግዚአብሔር በሰጠህ ጥበብ መሠረት በወንዙ ማዶ ያሉትን ሰዎች ሁሉ እና የአምላክህን ሕግ የሚያውቀውን ማንኛውንም ሰው እንዲያገለግሏቸው ፈራጆችንና አስተዋዮችን ሰዎች መሾም አለብህ። አንተ ደግሞ እነዚያን ሕጉን የማያውቁትን ሰዎች አስተምራቸው። **26** የእግዚአብሔርን ሕግ ወይም የንጉሡን ሕግ ሙሉ በሙሉ የማይፈጽመውን ማንኛውንም ሰው በሞት፥ በስደት፥ ንብረቱን በመውረስ ወይም በእስራት ቅጣው።" **27** ዕዝራም አለ፥ "በኢየሩሳሌም ያለውን የእግዚአብሔርን ቤት ለማስዋብ ይህንን ሁሉ በንጉሡ ልብ ያኖረና ደግሞም በንጉሡ፥ **28** በአማካሪዎቹና በኃያላን አለቆቹ ሁሉ ፊት የቃል ኪዳን ታማኝነቱን በእኔ ላይ ያበዛ የአባቶቻችን አምላክ እግዚአብሔር ይመስገን። በአምላኬ በእግዚአብሔር እጅ በረታሁኝ፥ ከእኔ ጋር እንዲሄዱም የእስራኤልን አለቆች ሰበሰብሁ።

Ezra 7:1

አጠቃላይ መረጃ:-
የዕዝራ የዘር ግንድ፣ ወደ ኋላ ሲቆጠር የመጀመሪያ ሊቀ ካህን ከሆነው ከአሮን ጋር ይገናኘዋል።

ዕዝራ ከባቢሎን መጣ
ዕዝራ ከየት እንደመጣ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። ‹‹ዕዝራ ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌን መጣ››

ሠራያ
የዚህን ሰው ስም በዕዝራ 2:2 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

ሰሎም
የዚህን ሰው ስም በዕዝራ 2:42 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

አዛርያ፣ ኬልቅያስ፣ --- ሳዶቅ፣ አኪጦብ፣ አማርያ፣ ዓዛርያስ፣ መራዮት፣ ዘራአያ፣ ኦዚ፣ ቡቂ፣ አቢሱ፣ ፊንሐስ፣ አልዓዛር
እነዚህ ሁሉ የወንዶች ስም ዝርዝር ነው።

Ezra 7:6

ንጉሡ የጠየቀውን ሁሉ ሰጠው
‹‹ንጉሡ የጠየቀውን ሁሉ ለዕዝራ ሰጠው››

የእግዚአብሔር እጅ ከእርሱ ጋር ነበረች
የእግዚአብሔር ‹‹እጅ›› የሚያሳየው የእግዚአብሔርን በረከት ወይም እርዳታ ነው። ‹‹ የእግኢአብሔር በረከት ከዕዝራ ጋር ነበር›› ወይም ‹‹እግዚአብሔር ዕዝራን ይባርከው ነበር››

በንጉሥ አርጤክስስ ሰባተኛው ዓመት።
ይህ የሚያሳየው የንጉሡን ሰባተኛ ዓመት ንግስ ነው። ‹‹ ንጉሥ አርጤክስስ በነገሠ በሰባተኛው ዓመት››

Ezra 7:8

አምስተኛው ወር
ይህ በዕብራውያን ዘመን አቆጣጠር አምስተኛው ወር ነው። ይህም በምዕራባውያነ ዘመን አቆጣጠር የጁላይ መጨረሻው ክፍልን እና የኦገስት የመጀመሪያውን ክፍል የሚያሳይ ነው።

የመጀመሪያው ወር የመጀመሪያው ቀን
ይህ በምዕራባውያን ዘመን አቆጣጠር የማርችን/መጋቢትን ወር መካከለኛ ጊዜ የሚያመለክት ነው።

የአምስተኛው ወር የመጀመሪያ ቀን
ይህ በምዕራባውያን ዘመን አቆጣጠር የጁላይ/ሐምሌ ወርን አካፋይ የሚያመለክት ነው።

የእግዚአብሔር መልከሚቱ እጅ
‹‹እጅ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ለመልካም ውጤት ሥልጣኑን እና ቁጥጥሩን መጠቀሙን ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ዕዝራ ልቡ ለማጥናት አዘጋጅቶ ነበር
ማዘጋጀት የሚያመለክተው ቁርጠኛ መሆንን ወይም አንድን ነገር ለማድረግ ራሱን መስጠቱን ነው። ‹‹ ዕዝራ ሕይወቱን ለጭናት ሰጥቶ ነበር››

ማድረግ
‹‹መታዘዝ››

የእግዚአብሔር ሥርዓት፣ ፍርድና ሕግ
እነዚህ እግዚአብሔር በሙሴ በኩል ለእስራኤል ያስተላለፈላቸው ሕጎች ናቸው

Ezra 7:11

ድንጋጌው ይህ ነበር
ከዚህ ዓረፍተ ነገር ቀጥሎ የሚገኘው ምንባብ በንጉሥ አርጤክስስ የተሰጠ ድንጋጌ ነው።

የነገሥታት ንጉሥ አርጤክስስ
‹‹ የነገሥታት ንጉሥ›› የሚለው ማዕረግ እርሱ ከነገሥታት ሁሉ ታላቅ መሆኑን የሚያሳይ ነው፣ ንጉሡ ሌሎች ነገሥታት ይታዘዙታል። ‹‹ታላቁ ንጉሥ አርጤክስስ›› ወይም ‹‹አርጬክስስ፣ ከሁሉም ታላቅ የሆነ ንጉሥ››

ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ የሚወድ ሁሉ --- እኔ አዝዤአለሁ
በዚያን ዘመን ሰዎች በሌሎች መንግሥታት በተወረሩና በወደሙ ምድሮች ላይ እንደገና ለመኖር ከንጉሡ ፈቃድ መጠየቅ ይጠበቅባቸዋል።

ከአንተ ጋር ለመሄድ ይችላሉ
‹‹ከአንተ›› የሚለው የሚያመለክተው ዕዝራን ነው።

Ezra 7:14

አገናኝ መግለጫ:-
ይህ ንጉሥ አርጤክስስ ለዕዝራ የሰጠው ድንጋጌ ቀጣይ ክፍል ነው።

እኔ፣ ንጉሡ፣ እና ሰባቱ አማካሪዎቼ
‹‹እኔ›› የሚለው ቃል እና ‹‹ንጉሡ›› የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው አንድን ሰው ነው። ንጉሡ ሕዝቡን ሊያስታውሳቸው የሚፈልገው የዚህ ደብዳቤ ጸሐፊ እርሱ መሆኑን ነው።

ስለ ይሁዳ እና ኢየሩሳሌም በእግዚአብሔር ሕግ መሠረት መጠየቅ
ስለ ምን እንደሚጠይቁ የበለጠ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። ‹‹በይሁዳ እና በኢየሩሳሌም ያለውን ሁኔታ ለመመርመር የፈለጉት እነርሱ የእግዚአብሔርን ሕግ ታዝዘው እንደሆነና እንዳልሆነ ለማወቅ ነው››

ብሩንና ወርቁን ታመጣ ዘንድ
ወዴት እንደሚያመጡ በግልጽ ሊብራራ ይችላል። ‹‹ ብሩንና ወርቁን ወደ ኢየሩሳሌም ታመጣ ዘንድ››

በፈቃዳቸው የሚያቀርቡትን ብሩንና ወርቁን
‹‹በፈቃዳቸው›› ማለት ገንዘቡን እንዲሰጡ አልተገደዱም ማለት ነው። የሰጡት መስጠት ስለፈለጉ ነው።

በሕዝቡና በካህናቱ በፈቃዳቸው የተበረከተው
ይህ በድርጊታዊ ቅረጹ ሊብራራ ይችላል። ‹‹ ሕዝቡና ካህናቱ በፈቃዳቸው የሰጡት››

Ezra 7:17

አገናኝ መግለጫ
ይህ ንጉሥ አርጤክስስ ለዕዝራ የሰጠው ድንጋጌ ቀጣይ ክፍል ነው።

ቁርባኑን --- በተሟላ ሁኔታ ግዛ
‹‹በተሟላ ሁኔታ›› ማለት ኃላፊነቱን ለመወጣት መግዛት የቻለውን ያህል ማለት ነው። ብሩንና ወርቁን በቤተ መቅደሱ እግዚአብሔርን ለማምለክ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ለመግዛት ጥቅም ላይ ያውሉታል። ‹‹ ስለዚህ በዚህ ገንዘብ ወይፈኖችንና አውራ በጎችን ጠቦቶችንም እህላቸውንና የመጠጣቸውን ቁርባን ተግተህ ግዛ››

አንተና የአንተ ወንድሞች
‹‹የአንተ ወንድሞች›› የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ከዕዝራ ጋር ይህን ሥራ የሚሠሩትን ሰዎች ነው። ‹‹ከአንተ ጋር የሚሠሩ›› ወይም ‹‹የሥራ ባልደረቦችህ››

Ezra 7:19

አገናኝ መግለጫ
ይህ ንጉሥ አርጤክስስ ለዕዝራ የሰጠው ድንጋጌ ቀጣይ ክፍል ነው።

ለእንተ በነፃ የተሰጡህን ዕቃዎች
ይህ በተግባራዊ ቅርጹ ሊገለጽ ይችላል። ‹‹ ለአንተ በነፃ የሰጠንህን ዕቃዎች ሁሉ››

ዕቃዎቹን --- በፊቱ አስቀምጣቸው
‹‹በፊቱ›› የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው።

ለአምላክህ ቤት አገልግሎት ይሆን ዘንድ
የስውር ስም የሆነው ‹‹አገልግሎት›› ‹‹አገልግል›› ወይም ‹‹ተጠቀም›› ‹‹ በአምላክህ ቤት አገልግሎት ላይ ጥቅም ላይ እንዲውል›› ወይም ‹‹በአምላክህ ቤት አገልግሎት ላይ እንዲያገለግሉ››

ግምጃ ቤት
ገንዘብ የሚቀመጥበት የተጠበቀ ሥፍራ

Ezra 7:21

አገናኝ መግለጫ
ይህ ንጉሥ አርጤክስስ ለዕዝራ የሰጠው ድንጋጌ ቀጣይ ክፍል ነው።

ከወንዙ ማዶ ያለው ክፍለ ሐገር
ይህ ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተምዕራብ የሚገኘው ክፍለ ሀገር መጠሪያ ነው። ከሱሳ ከተማ አንፃር ከወንዙ ማዶ የሚገኝ ነው። ይህንን በዕዝራ 4፡10 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ካህኑ ዕዝራ ከእናንተ የሚፈልገውን ነገር ሁሉ በሙሉ ስጡት
ይህ በተግባራዊ ቅርጹ ሊገለጽ ይችላል። ‹‹ካህኑ ዕዝራ ከእናንተ የሚፈልገውን ነገር ሁሉ በሙሉ ስጡት››

በሙሉ ሊሰጠው ይገባል
‹‹በሙሉ›› የሚለው ሐረግ የሚወክለው ሥራውን ለመሥራት የሚያስፈልገውን መጠን ያህል የሚለውን ነው ‹‹የሚያስፈልገውን ያህል ሊሰጠው ይገባል።››

አንድ መቶ መክሊት ብር
‹‹100 መክሊት ብር›› ይህንን ወደ ዘመናዊ መለኪያ መለወጥ ትችላለህ። ‹‹ 3,300 ኪሎ ግራም ሲልቨር ››

መቶ የቆሮስ መስፈሪያ ስንዴ
ይህንን ወደ ዘመናዊ መለኪያ መለወጥ ትችላለህ። ‹‹22,000 ሊትር ስንዴ›› ወይም ‹‹ሃያ ሁለት ሊትር ስንዴ››

አንድ መቶ የባዶስ መስፈሪያ ዘይት
ይህንን ወደ ዘመናዊ መለኪያ መለወጥ ትችላለህ። ‹‹2,200 ሊትር ዘይት›› ወይም ሁለይ ሺህ ሊትር ዘይት››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የእርሱ ቤት
ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ነው።

የእርሱ ቁጣ በመንግሥቴና በልጆቼ ላይ ስለምን ይመጣል?
ንጉሡ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው የእግዚአብሔር ቁጣ በእነርሱ ላይ እንዲመጣ ስለማይፈልግ ነው። ይሽም የሚያመለክተው ለዕዝራ የሚያስፈልገውን ካልሰጡ እግዚአብሔር መንግሥቱን እንደሚቀጣ ነው። ‹‹ የእግዚአብሔር ቁጣ በመንግሥቴ እና በልጆቼ ላይ እንዲመጣ አንፈልግም

የእርሱ ቁጣ በመንግሥቴና በልጆቼ ላይ ስለምን ይመጣል?
የእግዚአብሔር ቁጣ የሚያመለክተው እግዚአብሔር እንደሚቀጣቸው ነው። ‹‹የእግዚአብሔር ቁጣ በመንግሥቴና በልጆቼ ላይ ስለምን ይመጣል?›› ወይም እነዚህን ነገሮች የማታደርጉ ከሆነ እግዚአብሔር መንግሥቴንና ልጆቼን ይቀጣ።››

Ezra 7:24

አገናኝ መግለጫ
ይህ ንጉሥ አርጤክስስ ለዕዝራ የሰጠው ድንጋጌ ቀጣይ ክፍል ነው።

ማንኛውንም ግብር ወይም ታክስ በአንተ ላይ እንደይጥሉ አስታውቀናቸዋል
‹‹ማንኛውንም ግብር ወይም ታክስ በአንተ ላይ እንደይጥሉ ነግረናቸዋል››

ሙዚቀኞች
የሙዚቃ መሣሪያዎችን የሚጫወቱ ሰዎች

Ezra 7:25

አገናኝ መግለጫ
ይህ ንጉሥ አርጤክስስ ለዕዝራ የሰጠው ድንጋጌ ፍጻሜ ነው።

እግዚአብሔር እንደሰጠህ ጥበብ መጠን ዳኞችንና ፈራጆችን ሹም
ስውር ስም የሆነው ‹‹ጥበብ›› በንግግር ሐረግ ሊገለጥ ይችላል። ‹‹እግዚአብሔር ጥበበኛ አድርጎሃል፣ ስለዚህ በጥበብ ዳኞችንና ፈራጆችን መሾም አለብህ››

በሞት ወይም በስደት ወይም ገንዘብን በመውረስ ወይም በግዞት
ረቂቅ ስሞቹ በግስ ሊተረጎሙ ይችላሉ። ‹‹ እነርሱን በመግደል፣ በማሳደድ፣ ገንዘባቸውን በመውረስ፣ ወይም ወደ እስር ቤት በማስገባት›› ወይም ‹‹ልትገድሉአቸው ፣ ልታሳድዱአቸው፣ ያላቸውን ንብረት ሁሉ ልትወስዱባቸው፣ ወይም ወደ እስር ቤት ልታስገቡአቸው ትችላላችሁ››

Ezra 7:27

አገናኝ መግለጫ
ዕዝራ ንጉሥ አርጤክስስ በሰጠው ድንጋጌ ምክንያት እግዚአብሔርን ያመሰግናል።

በኢየሩሳሌም ያለውን የእግዚአብሔርን ቤት ያሳምር ዘንድ ይህን ሁሉ በንጉሡ ልብ አስቀመጠ
በንጉሡ ልብ ነገሮችን ማስቀመጥ የሚለው አነጋገር የሚያመለክተው አንድን አሳብ ወይም ፍላጎት እንዲኖረው ማድረግን ነው ‹‹በኢየሩሳሌም ያለውን የእግዚአብሔርን ቤት እንዲያከብር አደረገው››

የእግዚአብሔር ቤት
ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ነው

ለእኔ የቃል ኪዳኑን ታማኝነት አድርጎልኛል
‹‹ታማኝነት›› የሚለው ረቂቅ ስም ‹‹ታማኝ›› ወይም ‹‹የታመነ›› በሚል ሊገለጽ ይችላል። ‹‹ለእኔ ታማኝ የሆነው›› ወይም ‹‹ለእኔ የታመነው›› / ምሥጢራዊ ስሞችን ተመልከት/

እኔም በረታሁ
በረታሁ የሚለው ቃል የሚያመለክተው መበረታታትን ነው።

በአምላኬ በእግዚአብሔር እጅ
እዚህ ላይ የእግዚአብሔር እጅ የሚያመለክተው ለዕዝራ ያደረገውን እርዳታ ነው። ‹‹ እግዚአብሔር ስለረዳኝ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 8

1 በንጉሡ አርጤክስስ የንግሥና ዘመን ከእኔ ጋር ከባቢሎን የወጡት የአባቶች ቤት አለቆች እነዚህ ናቸው፤ **2** ከፊንሐስ ተወላጆች ጌርሶን። ከኢታምር ተወላጆች
ዳንኤል። ከዳዊት ተወላጆች ሐጡስ። **3** ከሴኬንያ ተወላጆች፥ ከፋሮስ ተወላጆች ዘካርያስ። ከእርሱ ጋር የተመዘገቡት ወንዶች 150 ነበሩ። **4** ከፋሐት ሞዓብ
ተወላጆች የዘራእያ ልጅ ኤሊሆዔናይ። ከእርሱ ጋር የተመዘገቡት ሁለት መቶ ወንዶች ነበሩ። **5** ከሴኬንያ ተወላጆች የየሕዚኤል ልጅ። ከእርሱ ጋር የተመዘገቡት
ሦስት መቶ ወንዶች ነበሩ። **6** ከዓዲን ተወላጆች የዮናታን ልጅ ዔቤድ። ከእርሱ ጋር የተመዘገቡት ሃምሳ ወንዶች ነበሩ። **7** ከኤላም ተወላጆች የጎቶልያ ልጅ
የሻያ። ከእርሱ ጋር የተመዘገቡት ሰባ ወንዶች ነበሩ። **8** ከሰፋጥያስ ተወላጆች የሚካኤል ልጅ ዝባድያ። ከእርሱ ጋር የተመዘገቡት ሰማንያ ወንዶች ነበሩ። **9**
ከኢዮአብ ተወላጆች የይሒኤል ልጅ አብድዩ። ክእርሱ ጋር የተመዘገቡት218 ወንዶች ነበሩ። **10** ከሰሎሚት ተወላጆች የዮሲፍያ ልጅ። ከእርሱ ጋር
የተመዘገቡት 160 ወንዶች ነበሩ። **11** ከቤባይ ተወላጆች የቤባይ ልጅ ዘካርያስ። ከእርሱ ጋር የተመዘገቡት ሃያ ስምንት ወንዶች ነበሩ። **12** ከዓዝጋድ
ተወላጆች የሃቃጣን ልጅ ዮሐናን። ከእርሱ ጋር የተመዘገቡት 110 ወንዶች ነበሩ። **13** የአዶኒቃም ተወላጆች ዘግይተው መጡ። ስማቸው እንደሚከተለው ነው፤
ኤሊፋላት፥ ይዑኤል፥ ሸማያ። ከእነርሱ ጋር ስልሳ ወንዶች መጡ። **14** ከበጉዋይ ተወላጆች ዑታይና ዘቡድ። ከእነርሱ ጋር የተመዘገቡት ሰባ ወንዶች ነበሩ። **15**
ዕዝራም አለ፥ "መንገደኞቹን ወደ አሳዋ በሚወርደው ወንዝ አጠገብ ሰበሰብኋቸው፥ በዚያም ሦስት ቀን ቆየን። ሕዝቡንና ካህናቱን ተመለከትኩ፥ ከሌዊ
ተወላጆች ግን በዚያ አንድም አላገኘሁኝም። **16** እኔም አለቆች ወደነበሩት ወደ አልዓዛር፥ አርኤል፥ ሸማያ፥ ኤልናታን፥ ያሪብ፥ ኤልናታን፥ ናታን፥ ዘካርያስ፥
ሜሱላምና አስተማሪዎች ወደነበሩት ዮያሪብና ኤልናታን መልዕክት ላክሁ። **17** በመቀጠልም በካሲፍያ አለቃ ወደ ሆነው ወደ አዶ ላክኋቸው። ለአዶ፥
ለወንድሞቹና በካሲፍያ ለሚኖሩ የቤተ መቅደስ አገልጋዮች ምን ማለት እንዳለባቸው አስታወቅኋቸው፤ ይኸውም ለእግዚአብሔር ቤት አገልጋዮችን እንዲልኩልን
ነበር። **18** ስለዚህ በመልካሚቱ በእግዚአብሔር እጅ ምክንያት ሰራብያ ተብሎ የሚጠራውን አስተዋይ ሰው ላኩልን። እርሱም ከእስራኤል ልጅ፥ ከሌዊ ልጅ፥
ከሞሖሊ ተወላጆች አንዱ ነበር። እርሱም ከአሥራ ስምንት ወንዶች ልጆቹና ወንድሞቹ ጋር መጣ። **19** ሐሸብያም ከእርሱ ጋር መጣ። ደግሞም ከሜራሪ ወንዶች
ልጆች አንዱ የሆነው የሻያን ከወንድሞቹና ከወንዶች ልጆቹ ጋር በድምሩ ሃያ ወንዶች ነበሩ። **20** በቤተ መቅደስ ውስጥ እንዲያገለግሉ ከተመደቡት ውስጥ
ዳዊትና ሹማምንቱ ሌዋውያኑን ለማገልገል የሰጡት 220 ነበሩ፥ እያንዳንዳቸው በየስማቸው ተመደቡ። **21** ራሳችንን በእግዚአብሔር ፊት ለማዋረድ፥ ለእኛ፥
ለታናናሽ ልጆቻችንና ለንብረታችን ሁሉ መንገዳችንን እንዲያቃናልን በአሳዋ ወንዝ አጠገብ ጾም አወጅኩ። **22** ንጉሡን፥ 'የአምላካችን እጅ ለመልካም
በሚፈልጉት ሁሉ ላይ ናት፥ ቁጣውና ኃይሉ ግን እርሱን በሚተዉት ሁሉ ላይ ነው' ብለን ስለነበር በመንገድ ላይ ከጠላቶቻችን የሚጠብቁንን ሠራዊት ወይም
ፈረሰኞችን እንዲሰጠን ንጉሡን ለመጠየቅ አፈርኩኝ። **23** ስለዚህ በእግዚአብሔ ፊት ጾምንና ጸለይን፥ ስለዚህም ጉዳይ ለመንነው። **24** ከዚያም ከካህናቱ ዋና
ዋናዎቹን ሰራብያን፥ ሐሸቢያንና አሥር ወንድሞቻቸውን፥ አሥራ ሁለት ሰዎች መረጥኩ። **25** ንጉሡ፥ አማካሪዎቹ፥ አለቆቹና በዚያ የነበሩ እስራኤል ሁሉ
ለእግዚአብሔር ቤት በፈቃዳቸው ያቀረቡትን ብር፥ ወርቅ፥ ቁሳቁስና መባ መዝኜ ሰጠኋቸው። **26** ስለዚህ 650 መክሊት ብር፥ አንድ መቶ መክሊት የብር
ዕቃዎች፥ አንድ መቶ መክሊት ወርቅ፥ አንድ ሺህ ዳሪክ የሚያወጡ **27** ሃያ ጎድጓዳ የወርቅ ሳሕኖች፥ የወርቅ ያህል የከበሩ ሁለት አብረቅራቂ የነሐስ ዕቃዎች
መዝኜ በእጃቸው ሰጠኋቸው። **28** ከዚያም እንዲህ አልኳቸው፥ 'እናንተና እነዚህ ዕቃዎች ለእግዚአብሔር ተቀድሳችኋል። ይህ ብርና ወርቅ ለአባቶቻችሁ አምላክ
ለእግዚአብሔር በፈቃደኝነት የቀረበ መባ ነው። **29** በካህናቱ ኃላፊዎች፥ በሌዋውያኑና በእስራኤል የነገድ አለቆች ፊት በኢየሩሳሌም በእግዚአብሔር ቤት
ክፍሎች ውስጥ እስክትመዝኑት ድረስ በጥንቃቄ ጠብቁት። **30** ካህናቱና ሌዋውያኑ የተመዘነውን ብር፥ ወርቅና ቁሳቁስ ወደ ኢየሩሳሌም ወደ አምላካችን ቤት
ለመውሰድ ተረከቡት። **31** በመጀመሪያው ወር በአሥራ ሁለተኛው ቀን ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ከአሳዋ ወንዝ አጠገብ ተነሣን። የአምላካችን እጅ በእኛ ላይ
ነበረች፤ እርሱም ከጠላቶቻችን እጅና በመንገድ ላይ አድፍጠው ሊያጠቁን ከፈለጉት አዳነን። **32** ወደ ኢየሩሳሌም ደርስንና ሦስት ቀን በዚያ ቆየን። **33** ከዚያም
በአራተኛው ቀን ብሩ፥ ወርቁና ቁሳቁሱ በአምላካችን ቤት ውስጥ በካህኑ በኦርዮ ልጅ በሜሪሞት እጅ ተመዝነው ተሰጡ። የፊንሐስ ልጅ አልዓዛር፥ ሌዋውያኑ
የኢያሱ ልጅ ዮዛባትና የቢንዊ ልጅ ኖዓድያ ከእርሱ ጋር ነበሩ። **34** የሁሉም ነገር ቁጥሩና ክብደቱ ታወቀ፤ በዚያኑ ጊዜም ጠቅላላ የክብደቱ መጠን ተጻፈ። **35**
ተማርከው የነበሩት፥ ከምርኮም የተመለሱት ለእስራኤል አምላክ የሚቃጠል መሥዋዕት አቀረቡ፤ ለእስራኤል ሁሉ አሥራ ሁለት ወይፈኖችን፥ ዘጠና ስድስት
አውራ በጎችን፥ ሰባ ሰባት ጠቦቶችንና ለኃጢአት መሥዋዕት አሥራ ሁለት አውራ ፍየሎችን አቀረቡ። ሁሉም ለእግዚአብሔር የሚቃጠል መሥዋዕት ነበር። **36**
ከዚያም የንጉሡን ትዕዛዝ በወንዙ ማዶ ላሉት የንጉሡ ሹማምንትና አስተዳዳሪዎች ሰጧቸው፥ እነርሱም ሕዝቡንና የእግዚአብሔርን ቤት አገዙ።

Ezra 8:1

አጠቃላይ መረጃ:
ከዚህ ምዕራፍ ጀምሮ ግልጽ የሆነ የደረሲ ልዩነት እንመለከታለን። ከምዕራፍ 1-7 ጸሐፊው ስለ ዕዝራ የጻፈው ነው። ምዕራፍ 8 ግን ጸሐፊው ራሱ ዕዝራ እንደሆነ ያመለክታል።

አጠቃላይ መረጃ:
ከቁጥር 2-14 የመሪዎችና የአባቶቻቸው ስም ዝርዝር ነው። ሁሉም ወንዶች ናቸው።

ከፊንሐስ ልጆች፣ ጌርሶን
በዝርዝሩ ውስጥ ይህ የመጀመሪያው ነው። ‹‹ነበር›› በሚለው ግስ መጻፍ ይቻላል። ‹‹ የፊንሐስ ዝርያ መሪ ጌርሶን ነበር›› ወይም ‹‹ ጌርሶን የፊንሐስ ዝርያ መሪ ነበር››

ከኢታምር ልጆች ዳንኤል
ይህ በስም ዝርዝር ውስጥ በሁለተኛ ደረጃ የተጠቀሰ ነው። ይህም ‹‹ነበር›› በሚለው ግስ ሊጻፍ ይችላል። ‹‹ የኢታምር ዝርያዎች መሪ ዳንኤል ነበር›› ወይም ‹‹ ዳንኤል የኢታምር ዝርያዎች መሪነበር››

ፋሮስ
የዚህን ሰው ስም በዕዝራ 2:3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ከዳዊት ልጆች ሐጡስ --- ፋሮስ እና ዘካርያስ
ይህ በዝርዝሩ ውስጥ ሦስተኛው ነው። ይህም ‹‹ነበሩ›› በሚለው ግስ ሊጻፍ ይችላል። ‹‹የዳዊት ልጆች መሪዎች ሐጡስ እርሱም --- ፋሮስ እና ዘካርያስ ነበሩ›› ወይም ‹‹ የዳዊት ልጆች መሪዎች ሐጡስ እና ዘካርያስ ነበሩ--- ሐጡስ ከፋሮስ --- ወገን ነበረ››

ሐጡስ፣ የሴኬንያ ዘር የነበረ፣ ከፋሮስ ነገድም የነበረ ነው።
ይህ ‹‹ከዘካርያስ›› በኋላ ለብቻው ሊጻፍ የሚችል ዐረፍተ ነገር ነው። ‹‹ሐጡስ የሴኬንያ ዝርያ ነበረ። እርሱም የፋሮስ ዝርያ ነው››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከእርሱ ጋር በእርሱ የዘር ሐረግ የተመዘገቡ **150** ወንዶች ነበሩ።
‹‹ ከዘካርያስ ጋር በእርሱ የዘር ሐረግ የተመዘገቡ 150 ወንዶች ነበሩ››

150 ወንዶች
‹‹ አንድ መቶ ሃምሳ ወንዶች››

Ezra 8:4

አጠቃላይ መረጃ
የወንዶቹ ስም ዝርዝር ይቀጥላል።

ከፋሐት ሞዓብ ልጆች የዘራእያ ልጅ፣ ኤሊሆዔናይ
ይህ በስም ዝርዝር ውስጥ ቀጣዩ ክፍል ነው። ‹‹ነበ›› በሚል ግስ ሊጻፍ ይችላል፡ ‹‹የፋሐት ሞዓብ ዝርያዎች መሪ የዘራእያ ልጅ አሊሆዔናይ ነበር›› ወይም ‹‹ የዘራእያ ልጅ ኤሊሆዔናይ የፋሐት ሞዓብ ዝርያዎች መሪ ነበረ››

ከእርሱ ጋር ሁለት መቶ ወንዶች ነበሩ
‹‹ከኤሊሆዔናይ ጋር ሁለት መቶ ወንዶች ነበሩ››

ዘራእያ
የዚህን ሰው ስም በዕዝራ 7:4 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

ዓዲን
የዚህን ሰው ስም በዕዝራ 2:15 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

ሁለት መቶ --- ሦስት መቶ --- ሃምሳ -- ሰባ
‹‹ 200 --- 300 --- 50 --- 70››

Ezra 8:8

አጠቃላይ መረጃ፡-
የወንዶቹ ስሞች ዝርዝር ይቀጥላል።

የሰፋጥያስ ልጆች የሚካኤል ልጅ ዝባድያ
ይህ በዝርዝሩ ውስጥ የሚቀጥለው ክፍል ነው። ‹‹ነበር›› በሚል ግስ ሊጻፍ የሚችል ነው። ‹‹ የሰፋጥያስ ዝርያዎች መሪ የሚካኤል ለጅ ዝባድያ ነበረ›› ወይም የሚካኤል ለጅ ዝባድያ የሰፋጥያስ ዝርያዎች መሪ ነበር

ሰፋጥያስ
የዚህን ሰው ስም በዕዝራ 2:2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

ሚካኤል
ይህ የአንድ ሰው ስም ነው።

ከእርሱ ጋር የሰማንያ ወንዶች ስም ተጠቅሶአል።
‹‹ ከዝባድያ ጋር ሰማንያ ወንዶች ተጠቅሰዋል››

218 ወንዶች
‹‹ ሁለት መቶ አሥራ ስምንት ወንዶች››

160 ወንዶች
‹‹አንድ መቶ ስድሳ ወንዶች››

ቤባይ
ይህንን በዕዝራ 2:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሰማንያ --- ሃያ-ስምንት
‹‹80 --- 28››

Ezra 8:12

አጠቃላይ መረጃ
ይህ የወንዶቹ የስም ዝርዝር መጨረሻ ነው።

ከዓዝጋድ ልጆች የሃቃጣን ልጅ ዮሐናን
ይህ በስም ዝርዝር ውስጥ የሚቀጥለው ክፍል ነው። ‹‹ነበር›› በሚለው ግስ ሊጻፍ ይችላል። ‹‹ ይህ የአዝጋድ ልጆች መሪ የሃቃጣን ልጅ ዮሐናን ነበር›› ወይም ‹‹ የሃቅጣን ልጅ ዮሐናን የዓዝጋድ ልጆች መሪ ነበር››

ከእርሱም ጋር **110** ወንዶች ተመዝዝግበዋል
‹‹ ከዮናታን ጋር የተመዘገቡ 110 ወንዶች ነበሩ››

110 ወዶች
‹‹ አንድ መቶ አሥር ወንዶች››

እነርሱ የአዶኒቃም ልጆች ናቸው
‹‹እነርሱ›› የሚለው ቃል የሚያመለክተው አለቆችን ነው። ‹‹ የአዶኒቃኽ ልጆች መሪዎች››

አዝጋድ
ይህንን ስም በዕዝራ 2፡12 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

አዶኒቃም
የዚህን ሰው ስም በዕዝራ 2፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

በጉዋይ
የዚህን ሰው ስም በዝራ 2፡2 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ስድሳ --- ሰባ
‹‹60 --- 70››

Ezra 8:15

አጠቃላይ መረጃ
በምዕራፉ ውስጥ ‹‹እኔ›› የሚለው ቃል የሚያመለክተው ዕዝራን ነው።

አጠቃላይ መረጃ
ቁጥር 16 የወንዶችን ስም ዝርዝር ይዞአል።

ወደ ካሲፍያ የሚወስደው ቦይ
‹‹ቦይ›› ለሚለው ቃል የሚከተሉት ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች ናቸው 1. ሰዎች የሠሩት የውኃ ቦይ ወይም 2. አንድ ተራ ወንዝ። በአጠቃላይ መልኩ ሊተረጎም ይችላል። ‹‹ወደ አሳዋ ወንዝ የሚወርድ የውኃ መንገድ››

አሳዋ
ይህ የቦታ ስም ነው

ሸማያ
የዚህን ሰው ስም በዕዝራ 8፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ኤልናታን --- ኤልናታን --- ኤልናታን
በተመሳሳይ ስም የሚጠሩ ሦስት ሰዎች እንደነበሩ ግልጽ ነው

Ezra 8:17

አዶ
ይህ የአንድ ወንድ ስም ነው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በመቀጠል እነርሱን ወደ አዶ ላክኋቸው
‹‹እነርሱን›› የሚለው ቃል በዕዝራ 8፡16 ስለ እነርሱ የተጻፈላቸው ዘጠኝ መሪዎችና ሁለት አስተማሪዎች ናቸው። ‹‹በመቀጠል እነዚያን ሰዎች ወደ አዶ ላክኋቸው”

ካሲፍያ
ይህ የአንድ የቦታ ስም ነው

ለአዶ ምን ማለት እንዳለባቸው ነገርኳቸው --- ይኸውም፣ ለአምላካችን ቤት አገልጋዮችን እንዲልክልን ነው
‹‹ይኸውም›› የሚለው ቃል ምን እንዲናገሩ እንዳስታወቃቸው ያመለክታል። ‹‹ ለአዶ --- ለአምላካችን ቤት አገልጋዮችን እንዲልክልን እንዲነግሩት ነገርኳቸው።

Ezra 8:18

ሰራብያ --- ሞሖሊ --- ሐሸብያን --- የሻያን --- ሜራሪ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

ስለዚህ በአምላካችን መልካም እጅ አንድ ሰው ላኩልን
የአምላካችን ‹‹መልካም እጅ›› የሚለው የሚያመለክተው ኪሰጣቸው ቸር መሆናቸውን ነው። ‹‹ አምላካችን ለእኛ መልካም ስለሆነ፣ አንድ ሰው ላኩልን››

አንድ ጠንቃቃ ሰው
ይህ የእውቀት እና የጥበብ ሰው ነው።

የሌዊ ልጅ የእስራኤል ልጅ
እዚህ ላይ ‹‹እስራኤል‹‹ የሰው ስም ነው። እግዚአብሔር ለያዕቆብ የሰጠው ስም ነው።

አስራ ስምንት --- ሃያ
18 -- 20

የሻያን
የዚህን ሰው ስም በዕዝራ 8፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ባለስልጣኖች
በመንግሥት አሠራር ውስጥ የተወሰነ ኃላፊነት የተሰጣቸው ሰዎች።

Ezra 8:21

የአሳዋ ሸለቆ
ይህ አሳዋ ተብሎ ወደ ሚጠራው ወንዝ የሚፈስሰው የሸለቆ ስም ነው። አሳዋነና ሸለቆውን በዕዝራ8፡15 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

ከእርሱም የቀናውን መንገድ ለእኛና ለልጆቻችን ለንብረታችንም ሁሉ እንለምን ዘንድ
‹‹መለመን›› የሚለው ቃል መልካም ነገር እንዲያደርግላቸው እግዚአብሔርን መጠየቅን የሚያመለክት ነው። ‹‹የቀናውን መንገድ›› የሚለው ቃል የሚያመለክተው በሚጓዙበት ጊዜ ከክፉ እንዲጠበቁ ነው። ‹‹ በምንጓዝበት ጊዜ እኛ እና ልጆቻችን ንብረታችንም ሁሉ ከክፉ እንድንጠበቅ እግዚአብሔርን ጠይቀን ነበር››

የአምላካችን እጅ እርሱን በሚፈልጉ ሁሉ ላይ ነች
የእግዚአብሔር እጅ በሕዝቡ ላይ ናት የሚለው አባባል በሕዝቡ ላይ ያለውን የእግዚአብሔር እርዳታ ያመለክታል፣፣ እግዚአብሔርን መፈለግ እርሱን የማገልገል ምሳሌአዊ አነጋገር ነው። ‹‹እግዚአብሔር እርሱን የሚያገለግሉትን ሁሉ ይረዳቸዋል››

ነገር ግን ኃይሉና ቁጣው እርሱን በሚተዉ ሁሉ ላይ ነው
የእግዚአብሔር ኃይልና ቁጣው በሕዝቡ ላይ ይሆናል የሚለው አባባል የሚያመለክተው እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚቀጣ ነው። እግዚአብሔርን መርሳት እግዚአብሔርን ለማገልገል እምቢ ማለትን የሚያመለክት አባባል ነው።

ስለዚህ ጾምን እግዚአብሔርንም ፈለግን
እዚህ ላይ እግዚአብሔርን ፈለግን ማለት አንድ ነገር እንዲያደርግልን እግዚአብሔርን ጠየቅን ማለት ነው። ‹‹ስለዚህ ጸምን እግዚአብሔር እንዲረዳንም ጠየቅነው››

Ezra 8:24

ሰራብያ፣ ሐሸቢያ
የእነዚህ ሰዎችን ስም በዕዝራ 8፡19 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

Ezra 8:26

650 መክሊት ብር
‹‹ ስድስት መቶ ሃምሳ መክሊት ብር›› አንድ መክሊት ሠላሳ ሦስት ኪሎ ግራም ይመዝናል ይህንን ወደ ዘመናዊው የክብደት መለኪያ መለወጥ ትችላለህ። ‹‹ 22,000 ኪሎ ግራም ብር››

አንድ መቶ መክሊት የብር ዕቃዎች
‹‹ 100 መክሊት የብር ዕቃዎች›› ይህንን ወደ ዘመናዊው የክብደት መለኪያ መቀየር ትችላለህ። ‹‹3,300 ኪሎግራም የብር ዕቃዎች››

አንድ መቶ መክሊት ወርቅ
‹‹100 መክሊት ወርቅ›› ይህንን ወደ ዘመናዊ የክብደት መለኪያ መለወጥ ትችላለህ። ‹‹3,300 ኪሎ ግራም ወርቅ››

አንድ ሺህ ዳሪክ
‹‹1,000 ዳሪክ›› ‹‹ዳሪክ›› በፋርስ ግዛት ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ይጠቀሙበት የነበረ ትንሽ የወርቅ ሳንቲም ነው። ይህንን በሳንቲሞቹ ብዛት ወይም በሚመዝኑት ክብደት ልክ መተርጎም ትችላለህ። ‹‹ አንድ ሺህ የፋርስ የወርቅ ሳንቲሞች›› ወይም ‹‹ ስምንት ነጥ አምስት ኪሎ ግራም ወርቅ››

የናስ ዕቃዎች
ናስ ከመዳብ እና ከሌላ ብረት ቅልቅል የሚገኝ ብረት ነው። ከንጹህ መዳብ ይልቅ ጠንካራ ነው።

Ezra 8:28

በመቀጠልም እንዲህ አልኳቸው
‹‹ በመቀጠልም ለአሥራ ሁለቱ የካህናት አለቆች እንዲህ አልኳቸው››

በሌዋውያን አለቆች እና በሕዝቡ መሪዎች ፊት እስክትቆጥሩአቸው ድረስ
ወደ ኢየሩሳሌም በደረሱ ጊዜ፣ ብሩንና ወርቁን ናሱንም መቁጠራቸው ከእነዚህ ዕቃዎች ምንም እንዳላጎደሉ ያሳያል።

ካህናቱና ሌዋውያን
በሙሴ ሕግ መሠረት፣ የሌዊ ነገዶች የቤተ መቅደሱን ሥራ ንበረቱንና መባዉን በማስተባበር ያገለግላሉ።

Ezra 8:31

ወደ ኢየሩሳሌም እንሄድ ዘንድ ከአሳዋ ወንዝ ተነሣን
‹‹የአሳዋ ወንዝን ትተን ተጓዝን›› ወይም‹‹ከአሳዋ ወንዝ ጀምረን ተጓዝን››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የአሳዋ ወንዝ
ይህ አሳዋ ወደሚባል ቦታ የሚፈስ ወንዝ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 8፡2 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የመጀመሪያው ወር አሥራ ሁለተኛው ቀን
ይህ በዕብራውያን የዘመን መቁጠሪያ የመጀመሪያው ወር ነው። አሥራ ሁለተኛው ቀን በምዕራባውያን አቆጣጠር ወደ መጋት መጨረሻ የሚቃረብ ነው።

የአምላካችን እጅ በላያችን ነበረች
የአምላክ እጅ በሕዝቡ ላይ ነው ማለት የእግዚአብሔር እርዳታ ከእነርሱ ጋር ነው የሚል ማሳሌአዊ አነጋገር ነው። ‹‹ እግዚአብሔር እየረዳን ነበር››

በመንገድም ላይ ከጠላት እና ከ---- ሰው እጅ አዳነን
እጅ የሚለው እነዚያ ሰዎች ሊያደርጉ የሚችሉትን የሚያመለክት ነው። እነርሱም የሚጓዙትን ቡድኖች የሚያጠቁትን በቀጥታ የሚመለከት ነው። ‹‹ ከጠላታችን ጥቃት እና በመንገድ ላይ ከሚሸምቅብን አዳነን›› ወይም ‹‹ ጠላቶችና ዘራፊዎች በመንገድ ላይ እንዳያጠቁን ከእኛ አራቃቸው››

ሊያጠቁን ከሚሸምቁብን
ይህ የሚያመለክተው ተጓዦቹ የያዙትን ዕቃዎች ለመዝረፍ በመመኘት ሊያጠቁአቸው የሚፈልጉትን ሌቦችንና ዘራፊዎችን ነው።

Ezra 8:33

ብሩ፣ ወርቁ ሌሎችም ዕቃዎች ተመዘኑ
ይህ በተግባራቂ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። ‹‹ አሥራ ሁለቱ የካህናት አለቆች ብሩንና ወርቁን ሌሎችንም ዕቃዎች መዘኑአቸው››

ብሩ፣ ወርቁ ሌሎችም ዕቃዎች በሜሪሞት እጅ ተመዘኑ
እዚህ ላይ ‹‹ በሜሪሞት እጅ›› የሚለው የሚያመለክተው ብሩና ወርቁ ሌሎችም ዕቃዎች በእርሱ ቁጥጥር ሥር መቆጠራቸውን ነው። ሰዎቹ ዕቃዎቹን ከቆጠሩ በኋላ በእርሱ ቁጥጥር ሥር እንዲጠበቁ ለሜሪሞት ሰጡት።

ሜሪመፐት ---- ኦሪዮ --- አልዓዛር --- ፊንሐስ ---ዮዛባት ---ኢያሱ ---ኖዓድያ ---ቢንዊ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

ኢያሱ
የዚህን ሰው ስም በዕዝራ 2፡6 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Ezra 8:35

ከምርኮ የወጡት ምርኮኞች --- የተሰደዱ ሰዎች
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች በባቢሎን ይኖሩ የነበሩ እና ባቢሎንን ትተው የወጡትን፣ ወደ ይሁዳ ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱትን የአይሁድ ምርኮኞችን የሚያመለክቱ ናቸው። ‹‹ከባቢሎን ምርኮኛነት ወደ ይሁዳ ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱት ስደተኛ ሕዝቦች››

አሥራ ሁለት --- ዘጠና ስድስት --- ሰባ ሰባት --- አሥራ ሁለት
‹‹12 --- 96 --- 77 --- 12››

በወንዙ ማዶ ላሉት ለንጉሡ ሹማምንቶች
እነዚህ ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተ ምዕራብ የሚገኙትን ሰዎች የሚያስተዳድሩ ባለ ሥልጣኖች ናቸው። በይሁዳ የሚኖሩትን ሰዎች ይጨምራል።

ከወንዙ ማዶ ያለ ክፍለ ሐገር
ይህ ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተ ምዕራብ የሚገኘው ክፍለ ሐገር ስም ነው። ሱሳ ከምትባለው ከተማ ባሻገር ወንዙን ተሻግሮ ያለው ከተማ ነው። ይኽም ይሁዳን ይጨምራል። ይህንን በዕዝራ 4፡10 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 9

1 "እነዚህ ነገሮች በተደረጉ ጊዜ አለቆቹ ወደ እኔ መጥተው፥ 'የእስራኤል ሕዝብ፥ ካህናቱና ሌዋውያኑ ራሳቸውን ከሌላው ምድር ሕዝብ፤ ከከነዓናውያን፥ ኬጢያውያን፥ ፌርዛውያን፥ ኢያቡሳውያን፥ አሞናውያን፥ ሞዓባውያን፥ ግብፃውያንና አሞራውያን እና ከርኩሰቶቻቸው አልለዩም። 2 ከወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸው ጋር በመጋባት ቅዱሱን ሕዝብ ከሌላው ምድር ሕዝብ ጋር ደባልቀዋል። በዚህ እምነት የለሽነት ቀዳሚዎቹ ሹማምንቱና አለቆቹ ናቸው።' 3 ይህንን በሰማሁ ጊዜ፥ ልብሴንና ካባዬን ቀደድሁ፥ ከራሴና ከፂሜም ላይ ፀጉሬን ነጨሁ። አፍሬም ተቀመጥኩ። 4 ከእስራኤል አምላክ ከእግዚአብሔር ቃል የተነሣ ስለዚህ እምነት የለሽነት በፍርሃት የተንቀጠቀጡ ሁሉ እስከ ምሽቱ መሥዋዕት ማቅረቢያ ጊዜ ድረስ በእፍረት ተቀምጬ ሳለሁ ወደ እኔ መጡ። 5 የምሽት መሥዋዕት በማቅረቢያ ጊዜ ግን የተቀደደ ልብሴንና ካባዬን ለብሼ በእፍረት ከተቀመጥኩበት ተነሣሁ፥ ተንበርክኬም እጆቼን ወደ አምላኬ ወደ እግዚአብሔር ዘረጋሁ። 6 እንዲህም አልኩ፥ 'አምላኬ ሆይ፥ ኃጢአታችን በራሳችን ላይ በዝቷል፥ በደላችንም እስከ ሰማያት ደርሷልና ፊቴን ወደ አንተ ለማቅናት እፈራለሁ፥ እጅግም አፍራለሁ። 7 ከአባቶቻችን ዘመን ጀምሮ እስካሁን ድረስ በታላቅ በደል ውስጥ አለን። ዛሬ እንደሆነብን ሁሉ በበደላችን ምክንያት ነገሥታቶቻችንና ካህናቶቻችን በዚህ ዓለም መንግሥታት እጅ ለሰይፍ፥ ለምርኮ፥ ለመበዝበዝና ለእፍረት ፊት ተሰጡ። 8 አሁንም ገና ለጥቂት ጊዜ የተረፍነው እኛ ጥቂቶቹ በሕይወት እንድንኖርና በዚህም ቅዱስ ሥፍራ የእግር መቆናጠጫ ሊሰጠን ከእግዚአብሔር ከአምላካችን ቸርነት መጥቶልናል። ዓይኖቻችንን ለማብራትና በባርነት እያለን ጥቂት እረፍት ሊሰጠን ይህ የአምላካችን ሥራ ነበር። 9 ባሪያዎች ነንና፥ አምላካችን ግን የቃል ኪዳን ታማኝነቱን ለእኛም አስረዘመልን እንጂ አልረሳንም። ፍርስራሹን እንድናነሣና የአምላካችንን ቤት እንደገና መሥራት እንድንችል አዲስ ጉልበት ሊሰጠን በፋርስ ንጉሥ ፊት ይህንን አድርጓል። በኢየሩሳሌምና በይሁዳ የመከላከያ ቅጥር ሊሰጠን ይህንን አደረገ። 10 አሁን ግን አምላካችን ሆይ፥ ከዚህ በኋላ ምን ማለት እንችላለን? ትዕዛዝህን እረስተናል፥ 11 የረሳነውም፤ "ልትወርሷት የምትገቡባት ይህቺ ምድር የረከሰች ምድር ናት። በምድሪቱ በሚኖሩት ሰዎች እርኩሰት ረክሳለች። ከአንደኛው ጫፍ እስከ ሌላኛው ጫፍ ድረስ በእርኩሰታቸው ሞልተዋታል። 12 አሁንም፥ እንድትበረቱና የምድሪቱን ፍሬ እንድትበሉ፥ ለልጆቻችሁም ለዘላለም እንድታወርሷቸው ሴቶች ልጆቻችሁን ለወንዶች ልጆቻቸው አትስጡ፤ ለወንዶች ልጆቻችሁም ሴቶች ልጆቻቸውን አትውሰዱ፥ ሰላምና ደኅንነታቸው እንዲቀጥልም አትፈልጉ ብለህ ለአገልጋዮችህ ለነቢያት የሰጠኸውን ትዕዛዝ ነው።" 13 ይሁን እንጂ በክፉ ሥራችንና በብዙ በደላችን ምክንያት ከደረሱብን ነገሮች በኋላ አንተ አምላካችን ለኃጢአታችን የሚገባውን ተውክልንና የተረፍነውን በሕይወት እንድንኖር ፈቀድክ። 14 ታዲያ እንደገና ትዕዛዝህን መጣስና ከእነዚህ ከረከሱ ሕዝቦች ጋር በጋብቻ መደባለቅ ነበረብን? አንተስ አንድም የሚቀር ወይም የሚያመልጥ እስከማይኖር ድረስ ታጠፋን ዘንድ ልትቆጣን አይገባህምን? 15 የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፥ አንተ ጻድቅ ነህ፥ እኛም ጥቂቶች ተርፈን በሕይወት አለን። እነሆ፥ ከበደላችን ጋር በፊትህ ነን፥ ከዚህ የተነሣ በፊትህ ለመቆም የሚችል ማንም የለም።"

Ezra 9:1

ራሳቸውን አልለዩም ነበር
ከባዕድ ምድር ሴቶችን አግብተዋል የእነርሱንም ሃይማኖት የራሳቸው አድርገዋል።

Ezra 9:3

እኔም ይህን በሰማሁ ጊዜ
አያሌ እስራኤላውያን የባዕድ ሴቶችን እንዳገቡ፣ የእነርሱንም አማልክት እንደሚያመልኩ ዕዝራበሰማ ጊዜ

ልብሴንና መጎናጸፊያዬን ቀደድሁ፣ የራሴንና የጺሜን ጠጉር ነጨሁ
ዕዝራ ሰዎቹ እግዚአብሔርን የሚያሳዝን ተግባር በመፈጸማቸው እጅግ ማዘኑን ለሁሉም አሳየ

እስከ ሠርክ መሥዋዕት
ካህናቱ ፀሐይ በገባች ጊዜ የሚያቀርቡት መሥዋዕት

Ezra 9:5

የተዋረደበት ሁኔታ
በሌላ አባባል ‹‹በሐፍረት ተቀመጦ›› ነበር (ዕዝራ 9፡4)። ‹‹ ምን ያህል እንዳዘንኩ ለማሳየት በመሬት ላይ ተቀመጥኩኝ››

ተንበርክኬም እጆቼን ዘረጋሁ
‹‹በጉልበቴ ተንበርክኬ እጆቼን ወደ ሰማይ ዘረጋሁ››

Ezra 9:7

የአባቶቻችን ቀናት
‹‹አባቶቻችን ይኖሩበት ከነበረ ዘመን ጀምሮ››

በከፍተኛ በደል ---- በኃጢአታችን ምክንያት
‹‹ በደል›› እና ‹‹ኃጢአት›› የሚሉት ምስጢራዊ ስሞች እንድ ቅጽል ስም እና ግስ በተከታታይ ሊተረጎሙ ይችላሉ። ‹‹ በጣም በደለኛ --- ከሠራነው ከፉ ሥራችን የተነሣ››

ለ---- ለነገሥታት እጅ አሳልፈን ተሰጠን
ይህ በተግባራዊ ቅርጹ ሊተረጎም ይችላል። ‹‹ ለነገሥታት እጅ --- አሳልፈህ ሰጠኸን››

ለዚህ ዓለም ነገሥታት አልፈን ተሰጠን
እዚህ ላይ ‹‹እጅ›› የሚለው ሥልጣንን ወይም ቁጥጥርን ያመለክታል። ‹‹ ለዚህ ዓለም ነገሥታት ቁጥጥር አልፈን ተሰጠን›› ወይም ‹‹ ለዚህ ዓለም ነገሥታት አልፈን ተሰጠን››

ለሰይፍና ለምርኮ ለብዝበዛ እና ለእፍረት
ሰይፍ ሰዎች ሌሎች ሰዎችን አንደሚገድሉ የሚያመለክት ቃል ነው። ‹‹ ምርኮ›› እና ‹‹ብዝበዛ›› የሚሉት ረቂቅ ስሞች እንደ ግስ ሐረጎች ሊገለጹ ይችላሉ። እንዲሁም ‹‹በእፍረት ፊት›› የሰውን ሁለንተና የሚያመለክት ሁኔታ ነው። ‹‹ለጠላቶቻችን ይገድሉን ዘንድ፣ ይይዙን ዘንድ፣ ይዘርፉን ዘንድ እና ያሳፍሩን ዘንድ››

Ezra 9:8

ከአምላካችን ከእግዚአብሔር ምሕረት መጣልን
እግዚአብሔር ምሕረት ለማድረግ መወሰኑ የሚያመለክተው ያ ምሕረት የተደረገለት መንቀሳቀስና መጓዝ የሚል መሆኑን ነው። ‹‹ አምላካችን እግዚአብሔር በእኛ ላይ ምሕረቱን ያደርግ ዘንድ ወሰነ››

የቃል ኪዳኑን ታማኝነት በእኛ ላይ አበረታ
‹‹ታማኝነት›› የሚለው ረቂቅ ስም ‹‹ታማኝ›› ወይም ‹‹የታመነ›› በማለት ሊገለጽ ይችላል። የዚህን ተመሳሳይ ሐረግ በዕዝራ 7:28 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ‹‹እርሱ ግን ለእኛ ታማኝ ነበር›› ወይም ‹‹እርሱ ለእኛ የታመነ ነበረ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በፋርስ ነጉሥ ፊት
ንጉሡ በቀጥታ ቤተ መቅደሱን ሊያይ አይችልም፣ ነገር ግን በኢየሩሳሌም ምን እየተሠራ እንዳለ ያውቃል። እዚህ ላይ ‹‹ፊት›› የሚለው ቃል በእርሱ እውቀት ፊት ለማለት ጥቅም ላይ የዋለ አባባል ነው። ‹‹ ስለዚህ የፋርስ ንጉሥ ይህንን ያውቃል።

የእግዚአብሔር ቤት
ቤተ መቅደሱ

የምንጠበቅበት ቅጥር ይሰጠናል
ሕዝቡ የሚጠበቅበት ቅጥር እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚጠብቅ ስለመሆኑ ምሳሌአዊ አነጋገር ነው። ‹‹ሊጠብቀን ይችላል››

Ezra 9:10

ለዘላለም
‹‹እስከ ዘመናት መጨረሻ››

Ezra 9:13

ለክፉ ሥራችንና ለበደላችን
‹‹ሥራችን›› እና ‹‹በደላችን›› የሚሉት ረቂቅ ስሞች እንደ ስም እና ቅጽል በቅደም ተከተላቸው ሊተረጎሙ ይችላሉ። ‹‹ስላደረግናቸው መጥፎ ተግባሮች በደለኞችም ስለሆንን››

ለበደላችን የሚገባው ሊደርግብን ሲገባ አኛን አተረፍከን
‹‹ልትገድለን ሲገባ፣ አልቀጣኸንም ይልቁንም አንዳዶቻችንነ በሕይወት እንኖር ዘንድ ተውከን››

ትእዛዛትህን እንደገና መተላለፍ ነበረብን እናም ---- ከአሕዛብ ጋር እንጋባ ዘንድ ይገባናልን?
ይህ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። ‹‹ ትእዛዛትህን መተላለፋችን ፈሞ ስህተት ነው ከአሕዛብም ጋር እንጋባ ዘንድ አይገባም››

አትቆጣንምን--- እናመልጣለንን?
ይህ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። ‹‹ ትቆጣናለህ --- ዘናመልጥም ብዬ እፈራለሁ።››

Ezra 9:15

ተመልከት
‹‹የምናገረውን በአንክሮ ተመልከት››

በበደላችን በፊትህ አለን
‹‹ እኛ ሁላችን በደለኞች መሆናችንን ታያለህ››

በፊትህ ሊቆም የሚችል አንድም ሰው የለም
‹‹ማንም ሰው ከበደል ነፃ የሆነ እንዳለ አታስብም››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 10

1 ዕዝራ እየጸለየና እየተናዘዘ በእግዚአብሔር ቤት ፊት ተደፍቶ አለቀሰ። ወንዶች፥ ሴቶችና ልጆች ያሉበት እጅግ ታላቅ የእስራኤል ጉባዔ በዙሪያው ተሰበሰቡ፥ ሕዝቡም ታላቅ ልቅሶ አለቀሱ። 2 የኤላም ተወላጅ የይሒኤል ልጅ ሴኬንያ ዕዝራን እንዲህ አለው፥ "እኛ ራሳችን በአምላካችን ላይ ክህደት ፈጽመናል፥ ከሌላ ምድር ሰዎችም ሚስቶችን አግብተናል። ይሁን እንጂ በዚህ ጉዳይ ላይ አሁንም ለእስራኤል ተስፋ አለ። 3 አሁንም ጌታዬና የአምላካችንን ትዕዛዝ የሚፈሩት በምትሰጡን መመሪያ መሠረት ሴቶቹን ሁሉ ከልጆቻቸው ጋር ለማሰናበት ከአምላካችን ጋር ቃል ኪዳን እናድርግ፥ ይህም በሕጉ መሠረት ይፈጸም። 4 ይህ አንተ ልታደርገው የሚገባህ ጉዳይ ነውና ተነሥ፥ እኛም አብረንህ ነን። በርታና አድርገው። 5 ዕዝራ ተነሣና የካህናቱን ዋነኞች፥ ሌዋውያኑንና እስራኤላውያኑን በሙሉ በዚሁ መሠረት ተግባራዊ እንዲያደርጉ ቃል አስገባቸው። እነርሱም ቃል ገቡ። 6 ከዚያም ዕዝራ ከእግዚአብሔር ቤት ፊት ተነሥቶ ወደ ኤልያሴብ ልጅ ወደ ዮሐናን ክፍል ገባ። በምርኮ የነበሩት እምነት የለሽ ስለመሆናቸው ያለቅስ ነበርና ምንም ዓይነት ምግብ አልተመገበም አንዳች ውሃም አልጠጣም ነበር። 7 በይሁዳና በኢየሩሳሌም የሚገኙ ከምርኮ የተመለሱት ሰዎች ሁሉ በኢየሩሳሌም እንዲሰበሰቡ መልዕክት ላኩ። 8 በሦስት ቀን ውስጥ የማይመጣ ማንም ቢኖር በሹማምንቱና በሽማግሌዎቹ ውሳኔ መሠረት ንብረቱ ይወረሳል፥ እርሱም ከምርኮ ከተመለሰው ታላቅ የሕዝብ ጉባዔ ይለያል። 9 ስለዚህ የይሁዳና የብንያም ሰዎች በሙሉ በሦስት ቀናት ውስጥ በኢየሩሳሌም ተሰበሰቡ። ይህም የሆነው በዘጠነኛው ወር ከወሩም በሃያኛው ቀን ነበር። ሕዝቡ ሁሉ በእግዚአብሔር ቤት ፊት ባለው አደባባይ ላይ ቆመው ነበር፥ ከሚሰሙት ቃልና ከዝናቡ የተነሣም ይንቀጠቀጡ ነበር። 10 ካህኑ ዕዝራም ተነሥቶ እንዲህ አለ፥"እናንተ ራሳችሁ ክህደት ፈጽማችኋል። የእስራኤልን በደል ለማብዛት ባዕዳን ሴቶችን አግብታችኋል። 11 አሁን ግን ለአባቶቻችሁ አምላክ ክብርን ስጡ፥ ፈቃዱንም አድርጉ። ከምድሩ ሰዎችና ከባዕዳን ሴቶች ተለዩ።" 12 ጉባዔውም ሁሉ በታላቅ ድምጽ፥ "እንደ ተናገርከው እናደርጋለን። 13 ይሁንና ሕዝቡ ብዙ ነው፥ ወቅቱም የዝናብ ጊዜ ነው። እንዲህ ሜዳው ላይ ለመቆም አቅም የለንም፥ በዚህ ጉዳይ እጅግ ተላልፈናልና ሥራው የአንድ ወይም የሁለት ቀን ብቻ አይደለም። 14 ስለዚህ ሹማምንቶቻችን ጉባዔውን በሙሉ ይወክሉ። የአምላካችን ብርቱ ቁጣ ከእኛ እስኪመለስ ድረስ ባዕዳን ሴቶች በከተሞቻችን እንዲኖሩ የፈቀዱ ሁሉ የከተማው ሽማግሌዎችና የከተማው ዳኞች በሚወስኑት ቀን ይምጡ።" 15 የአሣሄል ልጅ ዮናታንና የቴቁዋ ልጅ የሕዝያ ይህንን ሃሳብ ተቃወሙ፥ ሌዋውያኑ ሜሱላምና ሳባታይም ደገፉአቸው። 16 ስለዚህ ከምርኮ የተመለሱት ሰዎች እንዲህ አደረጉ። ካህኑ ዕዝራም ከነገድ አባቶችና ከቤተሰቡ መሪዎች የሚሆኑ ሰዎችን ሁሉንም በየስማቸው መረጠ፥ እነርሱም በዘጠነኛው ወር በመጀመሪያው ቀን ጉዳዩን መመልከት ጀመሩ። 17 በመጀመሪያው ወር የመጀመሪያው ቀን ባዕዳን ሴቶችን ያገቡት እነማን እንደሆኑ ምርመራቸውን ጨረሱ። 18 ከካህናቱ ወገን ባዕዳን ሴቶችን ያገቡ ነበሩ። ከኢዮሴዴቅ ልጅ ከኢያሱና ከወንድሞቹ ተወላጆች መካከል መዕሤያ፥ አልዓዛር፥ ያሪብና ጎዶልያስ። 19 እነዚህ ሚስቶቻቸውን ለመፍታት ወሰኑ። በደለኞች ነበሩና ከመንጋዎቻቸው ስለ በደል መሥዋዕት አንዳንድ አውራ በግ አቀረቡ። 20 ከኢሜር ተወላጆች አናኒና ዝባድያ። 21 ከካሪም ተወላጆች መዕሤያ፥ ኤልያስ፥ ሸማያ፥ ይሒኤልና ዖዝያ። 22 ከፋስኩር ተወላጆች ኤልዮዔናይ፥ መዕሤያ፥ ይስማኤል፥ ናትናኤል፥ ዮዛባትና ኤልዓሣ። 23 ከሌዋውያኑ መካከል፤ ዮዛባት፥ ሰሜኢ፥ ቆለጣስ የሚባለው ቆልያ፥ ፈታያ፥ ይሁዳና አልዓዛር። 24 ከመዘምራኑ መካከል፤ ኤልያሴብ። በር ከሚጠብቁት መካከል፤ ሰሎም፥ ጤሌምና ኡሪ። 25 ከተቀሩት እስራኤላውያን መካከል፤ ከፋሮስ ተወላጆች መካከል፥ ራምያ፥ ይዝያ፥ መልክያ፥ ሚያሚን፥ አልዓዛር፥ መልክያና በናያስ። 26 ከኤላም ተወላጆች መካከል፤ ሙታንያ፥ ዘካርያስ፥ ይሒኤል፥ አብዲ፥ ይሬሞትና ኤልያ። 27 ከዛቱዕ ተወላጆች መካከል ዔሊዮዔናይ፥ ኢልያሴብ፥ ሙታንያ፥ ይሬሞት፥ ዛባድና ዓዚዛ። 28 ከቤባይ ተወላጆች መካከል፤ ይሆሐናን፥ ሐናንያ፥ ዘባይና አጥላይ። 29 ከባኒ ተወላጆች መካከል፤ ሜሱላም፥ መሉክ፥ ዓዳያ፥ ያሱብና ሸዓል ራሞት። 30 ከፈሐት ሞዓብ ተወላጆች መካከል፤ ዓድና፥ ክላል፥ በናያስ፥ መዕሤያ፥ ሙታንያ፥ ባስልኤል፥ ቢንዊና ምናሴ። 31 ከካሪም ተወላጆች መካከል፤ አልዓዛር፥ ይሺያ፥ መልክያ፥ ሸማያ፥ ስምዖን፥ 32 ብንያም፥ መሉክና ሰማራያ። 33 ከሐሱም ተወላጆች መካከል መትናይ፥ መተታ፥ ዛባድ፥ ኤሊፋላት፥ ይሬማይ፥ ምናሴና ሰሜኢ። 34 ከባኒ ተወላጆች መካከል፤ መዕዳይ፥ ዓምራም፥ ኡኤል፥ 35 በናያስ፥ ቤድያ፥ ኬልቅያ፥ 36 ወንያ፥ ሜሪሞት፥ ኤሌያሴብ፥ 37 መታንያ፥ መትናይ፥ የዕሡ፥ 38 ባኒ፥ ቢንዊ፥ ሰሜኢ፥ 39 ሰሌምያ፥ ናታን፥ ዓዳያ፥ 40 መክነድባይ፥ ሴሴይ፥ ሸራይ፥ 41 ኤዝርኤል፥ ሰምምያ፥ ሰማራያ፥ 42 ሰሎም፥ አማርያና ዮሴፍ። 43 ከናባው ተወላጆች መካከል፤ ይዔኤል፥ መቲትያ፥ ዛባድ፥ ዘቢና፥ ያዳይ፥ ኢዮኤልና በናያስ። 44 እነዚህ ሁሉ ባዕዳን ሴቶችን ያገቡና አንዳንዶቹም ከእነርሱ የወለዱ ነበሩ።

Ezra 10:1

ዕዝራ ሲጸልይ እና ሲናዘዝ --- ራሱን ዝቅ አድርጎ ነበር
ዕዝራ ስለራሱ ሲናገር ራሱን እንደ ተራ ሰው በመቁጠር ነበር

ራሱን እየጣለ እየወደቀ
እየተነሣ እና በግምባሩ እየወደቀ

በእግዚአብሔር ቤት ፊት
በቤተ መቅደሱ ትይዩ

ሴኬንያ
ይህንን በዕዝራ 8:5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

ይሒኤል
ይህንን በዕዝራ 8:9 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

ለአምላከችን ታማኞች አልሆንንም
ይህ ለጉራ ሳይሆን፣ በሕዝብ ፊት የተደረገ ኑዛዜ ነው።

Ezra 10:3

ከአንተ ጋር ነን
‹‹እንረዳሃለን››

Ezra 10:5

የሐናን --- ኤልያሴብ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

Ezra 10:7

ማንም የማይመጣ --- ንብረቱ ሁሉ እንዲወረስ እርሱም ከምርኮው ጉባዔ እንዲለይ
‹‹ምርኮኛቹም ሁሉ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሰበሰቡ እንደ አለቆቹና እንደ ሽማግሌዎቹ ምክር --- ምብረቱ እንዲወረስ›› ወይም ‹‹የይሁዳ እና የኢየሩሳሌም ሰዎች የማይመጣውን ሰው ንብረት እንዲወስዱ--- ከጉባዔም እንዲለዩት››

ሦስት ቀናት
3ቀናት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ezra 10:9

በሦስት ቀናት ውስጥ
‹‹ከሦስት ቀናት በኋላ››

ዘጠነኛው ወር የወሩም አሥራ ሁለተኛው ቀን
ይህ በዕብራውያን ዘመን አቆጣጠር ዘጠነኛው ወር ነው። አሥራ ሁለተኛው ቀን በምዕራባውያብ ዘመን አቆጣጠር የታህሳስ አጋማሽ ነው።

በአደባባዩ
በቤተ መቅደሱ ፊት ለፊት የሚፈኝ ሰፊ ቦታ

ሕግህን ተላለፍን
‹‹መተላለፍ›› የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። ‹‹ የሕዝብህን ጠላቶች ረዳን››

የእስራኤልን በደል ከፍ ለማድረግ
‹‹ካሁን ቀድም ካደረግነው በደል የከፋ በደል ማድረጋችንን እግዚአብሔር ቆጠረው››

Ezra 10:11

ከ--- መለየት
ከ---ራቀ፣ ከ--- የተለየ ሆነ

Ezra 10:12

ይህ የአንድ እና ሁለት ቀናት ሥራ ብቻ አይደለም።
ይህ ውስጠ ምስጢር አነጋገር በሆነ መንገድ ሊተረጎም ይችላል። ‹‹ይህንን ሥራ ሁሉ ለማከናወን ብዙ ጊዜ ያስፈልገናል››

Ezra 10:14

የከተማው አለቆችና ሽማግሌዎች በቀጠሩት ጊዜ
ይህ በተግባራዊ ቅርጹ ሊተረጎም እንዲሁም በተለያዩ አረፍተ ነገሮች ሊቀመጡ ይችላሉ። ‹‹እናንተ በወሰናችሁት ጊዜ። ከከተማው አለቆችና ሽማግሌዎች ጋር ይምጡ››

ዮናታን --- አሣሄል --- የሕዝያ --- ቴቁዋ --- ሜሱላም --- ሳባታይ
የወንዶች ስሞች

የአሣሄል ልጅ ዮናታን እና የቴቁዋ ልጅ የሕዝያ ይህንን ተቃወሙ
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1. እነዚህ ሰዎች የከተማው ባለስልጣኖች ጥፋቱን እንዲመረምሩ አልፈለጉም ይም 2. የሰዎቹን ጋብቻ ማንም እንዲመረምር አልፈለጉም።

Ezra 10:16

ይህን አደረጉ
አይሁድ ያልሆኑትን ሴቶች ያገቡትን ሕዝቡ መረመራቸው።

የአሥረኛው ወር የመጀመሪያው ቀን
ይህ በዕብራውያን የዘመን አቆጣጠር አሥረኛው ወር ነው። በምዕራባውያን የዘመን አቆጣጠር የመጀመሪያው ቀን ወደ ታህሳስ አጋማሽ ይጠጋል።

የመጀመሪያው ወር የመጀመሪያ ቀን
ይህ በምዕራባውያን የዘመን አቆጣር ወደ መጋቢት አጋማሽ የሚቀርብ ነው።

Ezra 10:18

ኢያሱ
ይህንን በዕዝራ 2፡2 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

ኢዮሴዴቅ
ይህንን በዕዝራ 3፡2 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

መልሜያ --- ጎዶልያስ
የወንዶች ስም

አልዓዛር --- ያሪብ
ይህንን በዕዝራ 8፡16 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

Ezra 10:20

አጠቃላይ መረጃ
ዕዝራ አይሁድ ያልሆኑ ሴቶች ያገቡትን ወንዶች በዝርዝር መግለጹን ይቀጥላል።

አሜር --- ፋስኩር
የወንዶች ስሞች። ይህንን በዕዝራ 2:37 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

አናኒ --- ኤልዮዔናይ --- ናትናኤል --- ኤልዓሣ
የወንዶች ስሞች

ዝባድያ
የወንድ ስም። ይህንን በዕዘራ 8 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

ካሪም
የወንድ ስም። ይህንን በዕዝራ 2፡32 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

መዕሤያ
የወንድ ስም። ይህንን በዕዝራ 10፡18 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሸማያ --- ይሒኤል
የወንዶች ስሞች። ይህንን እንዴት በዕዝራ 8፡13 እንደተረጎምከው ተመልከት።

ዮዛባት
የወንድ ስም። ይህንን በዕዝራ 8፡33 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Ezra 10:23

አጠቃላይ መረጃ
ዕዝራ አይሁድ ያልሆኑ ሴቶች ያገቡትን ወንዶች በዝርዝር መግለጹን ይቀጥላል።

ዮዛባት
የወንድ ስም። ይህንን በዕዝራ 8፡33 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ኤልያሴብ
የወንድ ስም። ይህንን በዕዝራ 10፡6 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሰሎም
የወንድ ስም። ይህንን በዕዝራ 2:42 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ፋሮስ
የወንድ ስም። ይህንን በዕዝራ 2:03 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

አልዓዛር
የወንድ ስም። ይህንን በዕዝራ 2:03 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ezra 10:26

አጠቃላይ መረጃ
ዕዝራ አይሁድ ያልሆኑ ሴቶች ያገቡትን ወንዶች በዝርዝር መግለጹን ይቀጥላል።

ኤላም --- ዛቱስ --- ባኒ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። ይህንን በዕዝራ 2:7 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ይሒኤል
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 8:09 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ዔሊዮዔናይ
የወንድ ስም። ይህንን በዕዝራ 10:22 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ኤልያሴብ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:06 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ቤባይ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 2:11 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ይሆሐናን
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:06 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሜሱላም
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:16 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Ezra 10:30

አጠቃላይ መረጃ
ዕዝራ አይሁድ ያልሆኑ ሴቶች ያገቡትን ወንዶች በዝርዝር መግለጹን ይቀጥላል።

ፈሐት ሞዓብ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 8:04 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

በናያስ --- መልኪያ
የወንዶች ስሞች። ይህንን በዕዝራ 10:25 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

መዕሤያ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:18 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሙታንያ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:26 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ቢንዊ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 8:33 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ካሪም
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 2:32 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

አልዓዛር
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 8:16 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

መሉክ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:29 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Ezra 10:33

አጠቃላይ መግለጫ
ዕዝራ አይሁድ ያልሆኑ ሴቶች ያገቡትን ወንዶች በዝርዝር መግለጹን ይቀጥላል።

ሐሱም
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 2:19 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ዛባድ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:27 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ኤሊፋላት
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 8:13 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ምናሴ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:30 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሰሜኢ --- በናያስ
የወንዶች ስሞች።ይህንን በዕዝራ 10:23 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ባኒ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 2:10 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሜሪሞት
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 8:33 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ኤልያሴብ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:06 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Ezra 10:37

አጠቃላይ መረጃ
ዕዝራ አይሁድ ያልሆኑ ሴቶች ያገቡትን ወንዶች በዝርዝር መግለጹን ይቀጥላል።

መታንያ --- ዓዳያ
የወንዶች ስሞች። ይህንን በዕዝራ 10:26 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መታንያ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:33 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ቢንዊ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:06 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሰሌምያ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:23 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Ezra 10:41

አጠቃላይ መረጃ
ዕዝራ አይሁድ ያልሆኑ ሴቶች ያገቡትን ወንዶች በዝርዝር መግለጹን ጨረሰ

ሰሌመያ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:39 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሰማራያ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:32 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሰሎም
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 2:42 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

አማርያ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 7:03 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ናባው
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 2:29 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ይዔኤል
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 8:13 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ዛባድ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:27 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ዘቢና -- ያዳይ --ኢዮኤል
የወንዶች ስሞች።

በናያስ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:25 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

እነዚህ ሁሉ
እነዚህ ከዕዝራ 10:20 ጀምሮ በዝርዝሩ ውስጥ ያሉት ናቸው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Nehemiah

Nehemiah

Chapter 1

1 እኔ የሐካልያ ልጅ ነህምያ ነኝ። ንጉስ አርጤክስስ የፋርስን መንግስት መግዛት በጀመረበት በሃያኛው አመት፣ ካሴሉ በተባለው ወር፤ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሼ
ያደረግሁትን ይህን ነገር ጻፍሁ። እኔም በፋርስ ዋና ከተማ በሱሳ ነበርሁ። 2 ወንድሜ አናኒ እኔን ለማየት መጣ። እርሱና ሌሎች ጥቂት ሰዎች ከይሁዳ መጥተው
ነበር። ከባቢሎን ምርኮ ስላመለጡ ጥቂት አይሁዶች፣ እና ስለ ኢየሩሳሌም ከተማ ጥያቄዎችን ጠየቅኳቸው። 3 እነርሱም እንዲህ አሉኝ፣ “ከምርኮ ያመለጡት
አይሁዶች በዚያ በታላቅ መከራ እና ውርደት እየኖሩ ይገኛሉ። የከተማዋ ቅጥሮች በብዙ ስፍራዎች ተገፍተው ስለወደቁ ጠላት በቀላሉ ይገባባታል፣ ይህም ብቻ
ሳይሆን፣ ነገር ግን የከተማዋ በሮች ሙሉ በሙሉ በእሳት ተቃጥለዋል።” 4 ይህንን በሰማሁ ጊዜ፣ ተቀምጬ አለቀስኩ። ለብዙ ቀናት በሰማይ ወዳለው አምላክ
በለቅሶ ጾምኩ ጸለይኩ። 5 እንዲህ ስል ጸለይኩ፣ “ያህዌ፣ አንተ በሰማይ ያለህ አምላክ ነህ። አንተ ታላቅና አስደናቂ አምላክ ነህ፣ ለሚወዱህና ህግጋትህንና
ትዕዛዛትህን ለሚጠብቁ ሁሉ የተቀደሰውን አብሮነትህንና ቃልኪዳንህን ትጠብቃለህ። 6 እባክህ አሁን ወደ እኔ ተመልከት ወደ ጸሎቴም አድምጥ። በቀንና
በለሊት ለህዝብህ ለእስራኤል እጸልያለሁ። ኃጢአት መስራታችንን እናዘዛለሁ። እኔና ቤተሰቤ ጭምር አንተን በድለናል። 7 በጣም ክፉ አድርገናል። ከብዙ
አመታት አስቀድሞ ባሪያህ ሙሴ አንተ እናደርገው ዘንድ ያዘዝከውን ህግጋትና ስርዓቶች ሰጥቶናል፣ እኛ ግን ህግጋትህን አልጠበቅንም። 8 እባክህ ለአገልጋይህ
ለሙሴ የተናገርከውን አስብ። እንዲህ ብለሃል፣ ‘በፊቴ በታማኝነት እና በመታዘዝ ባትመላለሱ በአገራት መሃል እበትናችኋለሁ። 9 ነገር ግን ወደ እኔ ብትመለሱ
እና ትዕዛዞቼን ብትጠብቁ፣ ወደ ሩቅ ሥፍራዎች ብትጋዙም እንኳን፣ ሁላችሁንም ሰብስቤ የእኔን ታላቅነትና ክብር ወደማሳያችሁ ወደዚህ ስፍራ እመልሳችኋለሁ።
10 እኛ የአንተ አገልጋዮች ነን። በታላቁ ሀይልህ ከባርነት ነጻ ያወጣኸን ህዝብ ነን። አንተ ያንን ያደረግከው ማድረግ የምትፈልገውን ሁሉ ማድረግ ስለምትችል
ነው። 11 ያህዌ፣እባክህ የእኔን የአገልጋይህን ፀሎት ስማ። እባክህ በማንነትህና በስራህ አንተን ሲያከብሩ፣ ታላቅ ሀሴት የሚያደርጉትን የህዝብህን ሁሉ ጸሎት
ስማ። ወደ ንጉሱ ፊት ስቀርብ መከናወንን እንድትሰጠኝ እጸልያለሁ፤ ለንጉሱ ጥያቄዬን ሳቀርብ ህይወቴ አደጋ ላይ እንዳትወድቅ ጠብቃት። ምህረትህ
ይከተለኝ።” እኔ ለንጉሱ እጅግ ከታመኑት አገልጋዮች አንዱ ሆኜ አገለግል ነበር።

Nehemiah 1:1

ነህምያ ... ሐካልያ ... አናኒ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ተመልከት)

በካሴሉ ወር
“ካሴሉ” በዕብራውያን የቀን መቁጠርያ ዘጠነኛው ወር ነው። ይህ ወር በምዕራባውያኑ የቀን መቁጠርያ በህዳር ወር መጨረሻ እና በታህሳስ ወር መጀመርያ ላይ የሚገኝ ነው። (የዕብራውያን ወራት እና ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚሉትን ተመልከት)

በሀያኛው ዓመት
ነህምያ የሚያመለክተው አርጤክስስ ንጉስ ሆኖ የገዛበትን የዓመታት ቁጥር ነው። አማራጭ ትርጉም:- “የፋርስ ንጉስ የሆነው አርጤክስስ ይገዛ በነበረበት በሃያኛው ዓመት” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ እና ደረጃ የሚያሳዩ ቁጥሮች የሚሉትን ተመልከት)

ሱሳ ግንብ
ይህ በኤላም አገር የሚገኝ የፋርስ ነገስታት ንጉሳዊ ከተሞች ከሆኑት አንዱ ነበር:: ይህ ስፍራ እጅግ በጣም ትልቅና ከፍ ባለ ጠንካራ ግንብ ዙርያውን የታጠረ ከተማ ነበር።

ከወንድሞቼ አንዱ አናኒ
አናኒ የነህምያ የስጋ ወንድሙ ነበር።

አናኒ ከሌሎች ሰዎች ጋር በመሆን ከይሁዳ መጣ።
“አናኒ ከሌሎች ጥቂት ሰዎች ጋር ከይሁዳ መጣ”

ከምርኮ የተረፉት አይሁድ፣ በዚያ የነበሩት የአይሁድ ቅሬታዎች
እነዚህ ሁለት ሀረጎች የሚናገሩት ስለ ተለያዩ ሰዎች ሳይሆን ስለ ተመሳሳይ ሰዎች ነው። የሚከተሉት አማራጭ ትርጉም ሊሆኑ ይችላሉ:- 1) ምሮኮኞች ሆነው ወደ ባቢሎን የተወሰዱ ነገር ግን ከዚያ አምልጠው በኢየሩሳሌም ለመኖር የተመለሱ ጥቂት አይሁዳውያን ወይም 2) ወደ ባቢሎን ምርኮኛ አድርገው ሊወስዱአቸው ከሞከሩ ሰዎች አምልጠው በኢየሩሳሌም የቀሩት ጥቂት አይሁዳውያን። እነዚህ ሰዎች ከየት እንዳመለጡ ግልጽ ስላይደለ በትርጉም ላይ በግልጽ ለይቶ አለማስቀመጡu የተሻለ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ከምርኮ ያመለጡትና በኢየሩሳሌም የቀሩት አይሁዳውያን” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

Nehemiah 1:3

እነርሱም እንዲህ አሉኝ
በዚህ “እነርሱም” የሚለው ቃል የሚያመለክተው አናኒ እና ከይሁዳ የመጡትን ሌሎች ጥቂት ሰዎችን ነው።

ክፍለ ሀገር
በዚህ “ክፍለ ሀገር” የሚለው ቃል ይሁዳ በፋርስ ግዛት ስር የምትገኝ አንዲት የአውራጃ አስተዳደራዊ መዋቅር እነደሆነች ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም:- “የይሁዳ ክፍለ ሀገር” ወይም “ይሁዳ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

የኢየሩሳሌምም ቅጥር ፈርሶአል፥ በሮችዋም በእሳት ተቃጥለዋል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ሰራዊቱ የኢየሩሳሌምን ቅጥር አፈራርሰውታል፣ በሮቿን ደግሞ አቃጥለውታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ተመልከት)

Nehemiah 1:4

ከዚያም እንዲህ አልሁ
ነህምያ የተናገረው የጸለየውን ነገር ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ከዚያም ለያህዌ እንዲህ አልሁ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ያህዌ
ይህ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ራሱን ለሕዝቡ የገለጠበት የእግዚአብሔር ስም ነው። ስለ ያህዌ እና ይህን ቃል እንዴት መተርጎም እንደሚገባ ትራንስሌሽን ወርድ የሚለውን ድህረ ገጽ ተመልከት።

እርሱን ለሚወድዱትና የእርሱን ትእዛዝ ለሚጠብቁ
ነህምያ የሚናገረው ለያህዌ ስለሆነ “እርሱ” እና “የእርሱ” የሚሉት ተውላጠ ስሞች “አንተ” እና “የአንተ” ተብለው ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “አንተን ለሚወዱና የአንተን ትእዛዝ ለሚጠብቁ” (አንደኛ መደብ፣ ሁለተኛ መደብ እና ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

Nehemiah 1:6

ዓይኖችህ ይከፈቱ
“ተመልከተኝ።” በዚህ ክፍል “ዓይኖችህ ይከፈቱ” የሚለው ሀሳብ በዘይቤአዊ መንገድ የተገለጸ ሲሆን ለአንድ ሰው ትኩረት መስጠትን የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ትኩረትህን በኔ ላይ አድርግ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የባርያህን ጸሎት ትሰማ ዘንድ
“እኔ ባርያህ፣ የምጸልየውን ጸሎት ትሰማ ዘንድ።” “ባርያ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ነህምያን ነው። አንድ ሰው ትህትና እና አክብሮት ለማሳየት ሲል ከአለቃው ጋር የሚነጋገረው እንዲህ ነበር።

ቀንና ለሊት
ይህን በማለቱ ቀንም ሌሊትም ይጸልያል፤ ነህምያ የጸሎቱን ድግግሞሽ አጉልቶ ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሁልጊዜ” (ወካይ ዘይቤ ይመልከቱ)

እኔና የአባቴ ቤት
በዚህ ክፍል “ቤት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ቤተሰብን ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔና ቤተሰቤ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 1:8

አገናኝ አርፍተ ነገር
ነህምያ ወደ እግዚአብሔር መጸለዩን ቀጠለ።

እባክህ አስብ
“ማሰብ” የሚለው ፈሊጥ ማስታወስ የሚለውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “እባክህ አስታውስ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ለባርያህ ሙሴ ያዘዝከውን ቃልህን
“ያዘዝከውን” እና “ቃልህን” በሚሉት ቃላት ውስጥ ያሉት ተውላጠ ስሞች እግዚአብሔርን ያመለክታሉ።

ታማኝ ባትሆኑ ... እበትናችኋለሁ ... ብትመለሱ ... የእናንተን ሕዝብ
“እበትናችኋለሁ” እና “የእናንተ” የሚሉት ቃላት ተውላጠ ስሞች የብዙ ቁጥር መግለጫ ሲሆኑ የሚያመለክቱት ደግሞ እስራኤላውያንን ነው።

በአሕዛብ መካከል እበትናችኋለሁ
ያሕዌ ሰው ዘርን ሲዘራ እንደሚበትን እንዲሁ እስራኤላውያንን በአሕዛብ መካከል እንዲኖሩ እንደሚበትናቸው ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “በአሕዛብ መካከል እንድትኖሩ አደርጋችኋለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የእናንተ ሕዝብ ተበትነው ቢሆኑም እንኳ
ይህ ዓርፍተ ነገር በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ምንም እንኳ የእናንተ ሕዝብ ብበትናቸውም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እስከ ሰማይ ዳርቻ ደረስ
ያሕዌ በምድር ላይ በጣም ሩቅ ያሉትን ቦታዎች “እስከ ሰማይ ዳርቻ” ብሎ ይጠራቸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ “በጣም ሩቅ ወደሆኑ ቦታዎች” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ይኖርበት ዘንድ ወደ መረጥኩት ቦታ
ይህ ሐረግ የሚያመለክተው ቤተ መቅደሱ የሚገኝበትን ኢየሩሳሌምን ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “... ይኖርበት ዘንድ ወደ መረጥኩት ወደ ኢየሩሳሌም” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ስሜ ይኖርበት ዘንድ ወደ መረጥኩት ቦታ
በዚህ ክፍል “ስሜ” የሚለው ቃል የሚያሳየው ራሱን ያሕዌን ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እኖርበት ዘንድ የመረጥኩት ቦታ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 1:10

አጠቃላይ መረጃ፦
ነህምያ ጸሎቱን ቀጠለ።

አሁን
ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው ነህምያ ወደ ሌላ የጸሎት ሃሳብ መሸጋገሩን ለማሳየት ነው። እዚህ ላይ ነህምያ በያሕዌ ተስፋ ቃል ላይ ተመስርቶ ጥያቄውን ያቀርባል።

እነርሱ ባርያዎችህ ናቸው
“እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እስራኤላውያንን ነው።

በታላቅ ሃይልህና በብርቱ እጅህ
እዚህ ላይ “እጅህ” የሚለው ቃል ጥንካሬንና ሃይልን ያመለክታል። እነዚህ ሁለት ሐረጎች አንድ ላይ በመሆን የያሕዌን ሃይል ታላቅነት ለማጉላት ጥንድ ሃሳቦችን መስርተዋል። አማራጭ ትርጉም፦ “በታላቅ ኃይልህ እና ከፍ ባለው ብርታትህ” ወይም “በጣም ኃያል በሆነው ብርታትህ” (ምትክ ስም እና ተመሳሳይ ጥንድ ሃሳብ የሚለውን ይመልከቱ)

የባርያህ ጸሎት
እዚህ ላይ “ባርያህ” የሚለው የሚያመለክተው ነህምያን ነው። አንድ ሰው ትህትና እና አክብሮት ለማሳየት ሲል ከአለቃው ጋር የሚነጋገረው እንዲህ ነበር። ነህምያ 1:6ን እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።

የባርያዎችህ ጸሎት
እዚህ ላይ “ባርያዎችህ” የሚለው የሚያመለክተው ያህዌ ስለ ሕዝቡ እና ስለ ኢየሩሳሌም እንዲነሳ ይጸልዩ የነበሩትን የቀሩትን የእስራኤል ሕዝቦች በሙሉ ነው።

ስምህን በማክበር ደስ የሚሰኙትን
እዚህ ላይ “ስም” የሚለው የሚያሳየው ያሕዌን ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “አንተን ለማክበር ደስ የሚሰኙትን” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በዚህ ሰው ፊት ምህረትን ስጠው
“ስጠው” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ነህምያን ሲሆን በእግዚአብሔር ፊት ያለውን ትህትና ለመግለጽ ራሱን በሶስተኛ መደብ ያመለከተበት ነው፤ “በዚህ ሰው” የሚለው የሚያመለክተው የፋርስን ንጉስ አርጤክስስን ነው።

በዚህ ሰው ፊት
ነህምያ የሚናገረው ንጉሱ በሚያይበት እይታ ላይ ተመስርቶ ስለ ንጉሱ ዝንባሌ ወይም አመለካከት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ንጉሱ በእኔ ላይ ምህረቱን ያሳይ ዘንድ አድርግ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የንጉሱ ጠጅ አሳላፊ ሆኜ አገለግለው ነበር
ይህ ነህምያ በንጉሱ ቤተ መንግስት ምን ይሰራ እንደነበር የሚያሳይ የዳራ መረጃ ነው። የአንተ ቋንቋ የዳራ መረጃ የሚያሳዩበት የራሳቸው የተለየ መንገድ ሊኖረው ይችላል። (የዳራ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 በንጉስ አርጤክስ፣ አገዛዝ ሃያኛ ዓመት፣ ኒሳን ተብሎ በሚጠራው ወር፣ በክብረ በዓሉ ለንጉሱ ወይን ጠጅ የሚቀርብበት ሰዓት ነበር። ወይን ወስጄ ለንጉሱ አቀረብኩ። ከዚያ አስቀድሞ በንጉሱ ፊት እንዲህ አዝኜ ቀርቤ አላውቅም ነበር። 2 በዚያን ቀን ግን፣ ንጉሱ እኔን ተመልክቶ እንዲህ አለኝ፣ “ለምን እንዲህ እጅግ አዘንህ? የታመምክ አትመስልም። ምናልባት መንፈስህ ታውኮ ይሆንን?” እኔም በጣም ፈርቼ ነበር። 3 እንዲህ ስል መለስኩ፣ “ንጉስ ሆይ፣ ለዘለዓለም ንገስ! ያዘንኩት ያለ ምክንያት አይደለም፣ አባቶቼ የተቀበሩባት ከተማ ፍርስራሽ ሆናለች፣ በከተማዋ ዙሪያ ያሉ በሮቿ በሙሉ ተቃጥለው አመድ ሆነዋል።” 4 ንጉሱ እንዲህ ሲል መለሰልኝ፣ “ምን እንዳደርግልህ ትፈልጋለህ?” እናም ለእርሱ መልስ ከመስጠቴ አስቀድሞ፣ በሰማይ ወዳለው አምላክ ጸለይኩ። 5 ከዚያ እንዲህ ሲል ምላሽ ሰጠሁ፣ “ታደርገው ዘንድ ፈቃድህ ከሆነ፣ እኔም አንተን ደስ አሰኝቼ ከሆነ፣ አባቶቼ የተቀበሩባትን ከተማ ኢየሩሳሌምን መልሼ እንድገነባ ወደዚያ እንድሄድ ፈቀድልኝ።” 6 ንጉሱ (ንገስቲቱ አጠገቡ ተቀምጣ ሳለ) እንደህ ሲል ጠየቀኝ፣ “እንድትሄድ ብፈቅድልህ፣ ለስንት ጊዜ በዚያ ትቆያለህ? ደግሞስ መቼ ትመለሳለህ?” እርሱም፣ ወደዚያ የምሄድበትንና ተመልሼ የምመጣበትን ቀን እንዳሳወቅሁት፣ ወዲያውኑ እንድሄድ ፈቃድ ሰጠኝ። 7 ደግሞም ለንጉሱ እንዲህ አልኩት፣ “ለአንተ ለሰጠሁት ታማኝ አገልግሎቴ እንደ ሸልማት አድርገህ፣ ከአፍራጦስ ወንዝ ባሻገር ለሚያስተዳድሩ ገዥዎች ደብዳቤ ስጠኝ። ወደ ይሁዳ ስገባና ስወጣ በግዛቶቻቸው በደህንነት መጓዝ እችል ዘንድ እንዲፈቅዱልኝ እባክህን ትዕዛዝ ስጣቸው። 8 እንዲሁም፣ እባክህን ደኖችህን ለሚያስተዳድረው ለአሳፍ ደብዳቤ ፃፍልኝ፣ ደግሞም በቤተ መቅደሱ አጠገብ የሚገኘውን ግንብ በሮች አምዶቹን ለማበጀት፣ የከተማዋን ቅሮች ለመጠገን፣ እና የምኖርበትን ቤት እንዲሰጠኝ ፃፍለት።” እግዚአብሔር ለዚህ ስራ የሚያስፈልገኝን እንዳገኝ እየረዳኝ ስለነበር፣ ንጉሱ እንዲያደርግ የጠየቅኩትን አደረገልኝ ። 9 ወደ ይሁዳ ለመሄድ ተነሳሁ። ንጉሱ፣ እኔን እንዲያጅቡኝና እንዲጠብቁኝ አንዳንድ ፈረሰኛ የጦር መኮንኖችንና ወታደሮችን ላከ ። ገዥዎቹ ወደሚያስተዳድሩት ግዛት ስንደርስ፣ ከንጉሱ ዘንድ የተላከውን ደብዳቤ ሰጠኋቸው። 10 ነገር ግን ሁለቱ የመንግስት ባለስልጣናት፣ ሖሮናዊው ሰንበላጥና አሞራዊው አገልጋይ ጦቢያ፣ እኔ መድረሴን ሲሰሙ የእስራኤልን ህዝብ የሚረዳ በመምጣቱ በጣም ተቆጡ። 11 ስለዚህም እኔ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቼ በዚያ ለሶስት ቀናት ቆየሁ። 12 በምሽት ከከተማ ወጣሁ፣ ከእኔ ጋርም ጥቂት ሰዎች ነበሩ። እኛ የነበረን እኔ የተቀመጥኩበት አንድ እንስሳ ብቻ ነበር። በኢየሩሳሌም አደርገው ዘንድ እግዚአብሔር በልቤ ስላስቀመጠው ነገር ለማንም ሰው ምንም አልተናገርኩም። 13 በሸለቆው መግቢያ አለፍኩና ከከተማው ቅጥር ውጭ ሄድኩ። ከዚያ በከተማዋ ዙሪያ ተዟዙሬ የቀበሮዎች ጉድጓድ በሚባለው ጉድጓድ በኩል አለፍኩ። ከዚያ ወደ ፋንድያ መድፊያ በር አለፍኩ። በኢየሩሳሌም ዙሪያ የሚገኙ ቅጥሮችን ሁሉ ዞሬ ተመለከትኩ፣ እናም ሁሉም በሮች ተሰባብረው ቅጥሮቹ ክፍት መሆናቸውን አየሁ፣ ደግሞም በቅጥሩ ዙሪያ የነበሩ የእንጨት በሮች ሁሉ አመድ እስኪሆኑ ተቃጥለው ነበር። 14 ከዚያ ወደ ፏፏቴ በር እና የንጉስ ገንዳ ወደሚባለው ገንዳ ሄድኩ፣ ነገር ግን የተቀመጥኩበት አህያ በጠባቡ መተላለፊያ ማለፍ አልቻለችም። 15 ስለዚህ ወደ ኋላ ዞሬ ወደ በቄድሮን ሸለቆ አጠገብ እያለፍኩ ወደ ኋላ ከመመለሴና ወደ ሸለቆው በር ወደ ከተማዋ ከመግባቴ አስቀድሞ በዚያ የነበሩ ቅጥሮችን ተመለከትኩ። 16 የከተማዋ ባለስልጣናት እኔ ወዴት እንደሄድኩ ወይም ምን እንዳደረግኩ አላወቁም ነበር። ለአይሁድ መሪዎች ወይም ለባለስልጣናቱ ወይም ለካህናቱ ወይም በእድሳቱ ስራ ለሚሳተፉ ለማናቸው ሌሎች ሰዎች ስለዚህ ምንም ነገር አልተናገርኩም። 17 እንዲህ አልኩ፣ “በከተማችን ላይ የደረሰውን መጥፎ ነገሮች ሁሉ ሁላችሁም በሚገባ ታውቃላችሁ። ከተማዋ ፍርስራሽ ሆናለች፣ ሌላው ቀርቶ በሮቿ ተቃጥለው ወድቀዋል። ኑ፣ የኢየሩሳሌምን ቅጥር እንደገና ለመገንባት ስራውን እንጀምር። እኛ ያንን ብናደርግ፣ ከዚህ በኋላ በከተማችን አናፍርም።” 18 ከዚያ ከንጉሱ ጋር በተነጋገርኩ ጊዜ እግዚአብሔር እንዴት በመልካምነቱ እንዲረዳንና ንጉሱ ምን እንዳለኝ ነገርኳቸው። እነርሱም እንዲህ ሲሉ መለሱ፣ “ተነስተን የእድሳቱን ስራ እንጀምር!” ስለዚህም ይህን መልካም ሥራ ለመስራት ተነሱ። 19 ነገር ግን ሰንበላጥ፣ አሞናዊው አገልጋይ ጦቢያ፣ እና አረባዊው ጌሻም፣ እኛ ለመስራት ያቀድነውን ሰሙ። በእኛ ላይ ቀለዱ አፌዙብንም፤ እንዲህም አሉ፣ “ይህ እናንተ የምትሰሩት ስራ ምንድን ነው? በንጉሱ ላይ እያመጻችሁ ነውን?” 20 እኔ ግን እንዲህ አልኳቸው፣ “በሰማይ ያለው አምላክ ስኬት ይሰጠናል። እናንተ ግን በዚህ ከተማ ላይ መብት የላችሁም፣ ተሳትፎ የላችም፣ በዚህ ላይ ህጋዊ መብት የላችሁም፣ በኢየሩሳሌም ከተማ ላይ ምንም ታሪካዊ መታሰቢያ የላችሁም።”

Nehemiah 2:1

በኒሳን ወር
“ኒሳን” በዕብራይስጥ የቀን መቁጠርያ የመጀመርያው ወር ስም ነው። (የዕብራይስጥ ወራቶች የሚለውን ይመልከቱ)

በንጉስ አርጤክስስ በሃያኛው አመት
“አርጤክስስ ንጉስ በሆነበት በ20ኛው አመት (ደረጃ የሚያሳይ ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

አሁን
ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው ከዋናው የታሪክ ፍሰት ወጣ ብሎ ሌላ ነገር መጀመሩን ለማሳየት ነው። እዚህ ላይ ነህምያ በንጉሱ ፊት ስለነበረው መልክ የዳራ መረጃ ይሰጣል። (የዳራ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሱ ግን
“ስለዚህም ንጉሱ”

ፊትህ ለምን አዘነ
እዚህ ላይ ነህምያ የተገለጸው በፊቱ ነው ምክንያቱም ፊት የሰውን ስሜት ሰለሚያሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ለምን አዘንህ” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ተመልከት) (ወካይ ዘይቤ ይመልከቱ)

ይህ የልብ ሐዘን መሆን አለበት
ይህ ነህምያ ልቡ እንዳዘነ እርሱም እንደዛው እንዳዘነ ያሳያል፣ ምክንያቱም ልብ የስሜቶች ሁሉ ማዕከል እንደሆነ ተደርጎ ስለሚታሰብ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “በጣም አዝነሃል” (ወካይ ዘይቤ ይመልከቱ)

ከዚያም እጅግ በጣም ፈራሁ
ነህምያ ንጉሱ ለጠየቀው ነገር መልስ ለመስጠት ሲዘጋጅ በጣም ፈራ ምክንያቱም ንጉሱ እንዴት እንደሚመልስለት አያውቅም ነበር።

Nehemiah 2:3

ንጉሱ ለዘላለም ይኑር
ነህምያ ለንጉስ አርጤክስስ ክብርን እያሳየ ነው። እዚህ ላይ “ለዘላለም” የሚለው ቃል ረዥም እድሜን የሚያሳይ የግነት ቃል ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ንጉሱ ረዥም አመት ይኑር” (ግነት እና ጅምላ ምልከታ የሚለውን ተመልከት)

ለምን ፊቴ አይዘን?
እዚህ ላይ ነህምያ የሚያዝንበት ምክንያት እንዳለው ለንጉሱ ለመንገር ይህን መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ ተጠቀመ። ይህን በዓርፍተ ነገር ቅርጽ ሊጸፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “እንዳዝን የሚያደርጉኝ በቂ ምክንያቶች አሉኝ።” (መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የአባቶቼ መቃብር ያለበት ቦታ
“አባቶቼ የተቀበሩበት ቦታ”

በሮቹ በእሳት ተቃጥለዋል
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እሳት በሮችዋን አፈራርሶታል” ወይም “ጠላቶቻችን በሮችዋን አቃጥለውታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ተመልከት)

Nehemiah 2:4

ለንጉሱም ... አልሁት
“ከዚያም ለንጉሱ .... መለስኩለት”

ባርያህ
ነህምያ ለንጉሱ ያለውን አክብሮት ለመግለጽ ራሱን በዚህ መንገድ ገለጸ።

በፊትህ
እዚህ ላይ በፊትህ ሲል ፍርድን ወይም ግምገማን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በአንተ ፍርድ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የአባቶቼ መቃብር ከተማ
“አባቶቼ የተቀበሩበት ከተማ”

እንደገና እሰራው ዘንድ
ነህምያ ግንባታውን በሙሉ ራሱ ለመስራት አላሰበም፣ ነገር ግን የስራው መሪ ይሆናል። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔና ሕዝቤ እንሰራው ዘንድ” (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 2:7

ደብዳቤ ይሰጠኝ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ደብዳቤ ስጠኝ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ከወንዙ ማዶ ያለው ግዛት
ይህ ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተ ምዕራብ በኩል የነበረው ግዛት ስም ነው። በሱሳ ከተማ ከነበረው ወንዝ ባሻገር ያለ ቦታ ነበር።

አሳፍ
ይህ የአንድ ወንድ ስም ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር መልካሚቱ እጅ በእኔ ላይ ነበረች
የእግዚአብሔር “መልካሚቱ እጅ” የሚያሳየው የእግዚአብሔርን “ሞገስ” ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የእግዚአብሔር ሞገስ በእኔ ላይ ነበር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 2:9

ሖሮናዊው ሰንባላጥ
ሰንባላጥ የአንድ ወንድ ስም ነው፣ ሖሮናውያን ደግሞ የአንድ ሕዝብ ወገን ነበሩ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ተመልከት)

አገልጋዩ አሞናዊው ጦቢያ
ይህ ሰው ባርያ የነበረ ነገር ግን ነጻ ወጥቶ በአሞን ከተማ ሹም ሆኖ እያገለገለ የነበረ ሰው እንደሆን ይታመናል። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ይህን ሰሙ
“መድረሴን ሰሙ”

Nehemiah 2:11

በልቤ አኖረው
እዚህ ላይ የነህምያ “ልብ” የሚያመለክተው ሃሳቡንና ፈቃዱን ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “አነሳሳኝ” ወይም “መራኝ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ምንም እንስሳ አብሮኝ አልነበረም
“ከኔ ጋር ምንም እንስሶች አልነበሩም”

Nehemiah 2:13

አጠቃላይ መረጃ፦
በዚህ ጉብኝቱ ጥቂት ሰዎች ከነህምያ ጋር አብረው ነበሩ፣ ነገር ግን ነህምያ የሚናገረው በአንደኛ መደብ ነው ምክንያቱም ቀዳሚው ሰው እርሱ ሰለነበር ነው። (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

በምሽትም በሸለቆ በር ወጣሁ
“ሲመሽ፣ በሸለቆ በር በኩል ወጣሁ”

ቀበሮ
የበረሃ ውሻ

ቆሻሻ መጣያ በር
ይህ በር ቆሻሻ ከከተማው የሚወገድበት እንደነበር ይገመታል

ፈርሰው ክፍት የነበሩትን፣ የእንጨት በሮቹ ደግሞ በእሳት ተቃጥለው ነበር
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የእስራኤል ጠላቶች ሰብረው የከፈቱትን፣ ጠላቶቻቸው በእሳት አቃጥለው ያፈረሷቸውን የእንጨት በሮች። (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 2:15

... ስለዚህ ወጥቼ ... እንዲሁም ተመለስሁ
ከነህምያ ጋር የነበሩት ሰዎችም ተከትለውት ነበር። አማራጭ ትርጉም፦ “ስለዚህ ወጥተን ... እንዲሁም ተመለስን” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

በሸለቆው በር
“በሸለቆ በር በኩል”

ስራውን ይሰሩ የነበሩት ሌሎች
ይህ የሚያመለክተው በኋላ ላይ ቅጥሩን በማደስ ሰራ ላይ የሚሳተፉትን ሰዎች ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በኋላ ቅጥሩን የማደስ ስራ የሚሰሩት ሌሎች” (ግምታዊ እውቀትና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 2:17

ችግሩን ታያላችሁ
እዚህ ላይ “ታያላችሁ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ሲሆን ጥቅም ላይ የዋለው በነህምያ 2:16 ላይ የተገለጹትን ሰዎች በሙሉ ለማመልከት ነው። (የሁለተኛ መደብ ቅርጾች የሚለውን ይመልከቱ)

በሮችዋ በእሳት ተቃጥለዋል
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ጠላቶቻችን በሮችዋን በእሳት እንዴት እንዳቃጠሉት” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህ ወዲያ መሳለቂያ እንዳንሆን
“ከእንግዲህ ወዲያ እንዳናፍር”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የአምላኬ መልካሚቱ እጅ በእኔ ላይ ነበረች
የእግዚአብሔር “መልካሚቱ እጅ” የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን “ሞገስ” ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የእግዚአብሔር ሞገስ በእኔ ላይ ነበር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እንነሳና እንስራ
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “መገንባት እንጀምር” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህ ለመልካም ስራ እጃቸውን አጠነከሩ
“እጃቸውን አጠነከሩ” የሚለው ሐረግ አንድን ስራ ለመስራት ተዘጋጁ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ይህን መልካም ስራ ለመስራት ተዘጋጁ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 2:19

ሰንባላጥ ... ጦብያ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። እነዚህን በነህምያ 2:9-10 ላይ እንዴት እንደተተረጎሙ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ጌሳም
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ምን እያደረጋችሁ ነው? ንጉሱ ላይ እያመጻችሁ ነውን?
እነዚህ መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች ጥቅም ላይ የዋት ነህምያ ላይ ለመሳለቅ ነው። ይህ በዓርፍተ ነገር ቅርጽ ሊጻፉ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሞኝነት ስራ እየሰራችሁ ነው! በንጉሱ ላይ ልታምጹ አይገባም! (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሱ
ይህ የሚያመለክተው የፋርስ ንጉስ አርጤክስስን ነው።

ተነስተን እንሰራለን
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም “እንደገና መገንባት እንጀምራለን” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ ግን በኢየሩሳሌም ድርሻ፣ መብትና የኛ የምትሉት የታሪክ መታሰቢያም የላችሁም
“እናንተ ግን በኢየሩሳሌም ምንም ድርሻ፣ ሕጋዊ መብት ወይም ሃይማኖታዊ ባለቤትነት የላችሁም“

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 ከዚያ የእስራኤል ሊቀ ካህን የሆነው ኤልያብ፣ ከሌሎች ካህናት ጋር የበጎች በር የተባለውን እንደገና ሰሩ። ይህንንም ለያህዌ ክብር ለዩት፣ እናም የመግቢያውን በሮች በስፍራው አቆሙ ቀጥሎ ቅጥሩን የመቶ ማማ እስከሚባለው ድረስ መልሰው ገነቡ፣ እናም ያህዌን ለማክበር ለዩት። እንዲሁም የሐንኤልን ማማ መልሰው ገነቡ። **2** ከእነርሱ ቀጥሎ፣ የኢያሪኮ ሰዎች መልሰው ይገነቡ ነበር። ከእነርሱ ቀጥሎ፣ የአምሪ ልጅ ዘኩር መልሶ ይገነባ ነበር። **3** የአሳ በር የሚባለውን የሃስና ልጆች ገነቡት። እነርሱ የእንጨት አምዶቹን ከመግቢያዎቹ በላይ አጋደሙ፣ ደግሞም በሮቹን በስፍራቸው አኖሩ። ከዚያ ጠንካራ ቁልፍ እንዲኖር መቀርቀሪያ እና መወርወሪያዎችን አበጁ። **4** ከእነርሱ ቀጥሎ፣ የአቆስ የልጅ ልጅ፣ የአርዮ ልጅ የሆነው ሜርሞት ቅጥሮቹን ለማጠናከር ጠገናቸው። ከእርሱ ቀጥሎ፣ የሜሴዜቤል የልጅ ልጅ፣ የበራክየ ልጅ የሆነው ሜሱላም የቅጥሩን ከፊል ጠገነ። ከእርሱ ቀጥሎ፣ የበዓና ልጅ ሳዶቅ የቅጥሩን ከፊል ጠገነ። **5** ከእርሱ ቀጥሎ፣ የተቁሖ ሰዎች ቅጥሩን በከፊል ጠገኑ፣ ነገር ግን የቴቁ መሪዎች አሰሪዎቻቸው እንዲሰሩ የሰጣቸውን ለመስራት አልፈለጉም። **6** የፋሴሐ ልጅ ዮዳሄ እና የበሶድያ ልጅ ሜሱላም አሮጌውን መግቢያ ጠገኑ። ከመግቢያው በላይ ያሉትን አምዶችም በስፍራቸው አደረጉ፣ እንዲሁም መቀርቀሪያዎችንና መወርወሪያዎችን መግቢያውን ለመቆለፍ አስገቡ። **7** ከእነርሱ ቀጥሎ፣ የገባኦንና ከምጽጳ ሰዎች የሆኑት ገባኦናዊው መልጥያ እና ሜሮኖታዊው ያዶን፣ ከባህሩ ማዶ የሚገኘው አውራጃ ገዢ የሚኖርበትን ክፍል ጠገኑ። **8** ከእርሱ ቀጥሎ፣ የሖርሃያ ልጅ ዑዝኤል፣ እና ሐናንያ ነበሩ፣ ነገር ግን እነርሱ እስከ ሰፊው ቅጥር ድረስ ያለውን ክፍል ሰሩ። ሐርሃያ ወርቅ አንጥረኛ፣ ሐናንያ ደግሞ ሽቶ ቀማሚ ነበሩ። **9** ከእርሱ ቀጥሎ፣ የኢየሩሳሌምን ከፊል አውራጃ የሚገዛው የሆር ልጅ ረፋ የቅጥሩን ከፊል መልሶ ሰራ። **10** ከእርሱ ቀጥሎ፣ የኤርማፍ ልጅ ይዳያ ከቤቱ አጠገብ የሚገኘውን ቅጥር ከፊሉን መልሶ ሰራ። ከእርሱ ቀጥሎ የአሰቦንያ ልጅ ሐጡስ የቅጥሩን ከፊል መልሶ ሰራ። **11** የሃሪም ልጅ መልክያ፣ እና የፈሐት ሞዓብ ልጅ አሱብ የቅጥሩን ከፊል ጠገነ፣ እንዲሁም የእቶን ማማ የተባለውን መልሶ ሰራ። **12** ከእርሱ ቀጥሎ፣ ሌላውን የኢየሩሳሌም ከፊል አውራጃ የሚገዛው የአጦሎኤስ ልጅ ሰሎም የቅጥሩን ከፊል መልሶ ሰራ። ሴት ልጆቹ በስራው ረዱት። **13** ሐኖንና የዛኖ ከተማ ሰዎች የሸለቆ መግቢያ ተብሎ የሚጠራውን መልሰው ሰሩ። እነርሱም መግቢያዎቹን መልሰው በስፍራቸው አቆሙ፣ ደግሞም መወርወሪያዎቹንና መቀርቀሪያዎቹን በሮቹን ለመቆለፊያ አበጁ። ቅጥሩን የቆሻሻ መጣያ በር እስከሚባለው ድረስ 460 ሜትር መልሰው ሰሩ። **14** የበት ሐካሪም አውራጃ ገዢ የሆነው የረካብ ልጅ መልክያ የቆሻሻ መጣያ በር ተብሎ የሚጠራውን መልሶ ሰራ። መግቢያውን ለመቆለፊያ መወርወሪያዎቹንና ፍርግርጎቹን መልሶ ሰራ። **15** የምጽጳ አውራጃን የሚገዛው የኮልሐዜ ልጅ ሰሎም የፏፏቴ በር ተብሎ የሚጠራውን መግቢያ መልሶ ሰራ። ከመግቢያው በላይ ጣራ አበጀ፣ በሩን ለመቆለፍ መግቢያዎቹንና መቀርቀሪያዎቹን እንዲሁም ፍርግርጎቹን አበጀ። ከዳዊት ከተማ ተነስቶ ቁልቁል እስከ ሼላን ገንዳ አጠገብ ከንጉሱ መናፈሻ ቀጥሎ ቅጥሩን ገነባ። **16** ከእርሱ ቀጥሎ፣ የቤት ዱር አውራጃን በከፊል የሚገዛው የዓዝቡቅ ልጅ ነህምያ፣ በዳዊት ከተማ ውስጥ እስከ መቃብር ስፍራ ያለውን ቅጽር፣ ሰው ሰራሽ እስከ ሆነው መዋኛ እና እስከ ፈረስ ቤቶች ድረስ መልሶ ሰራ። **17** ከእርሱ ቀጥሎ፣ ካህናቱን የረዱት ብዙ የሌዊ ትውልዶች የቅጥሩን ክፍሎች መልሰው ሰሩ። የባኒ ልጅ ሬሁ አንዱን ክፍል መልሶ ሰራ። የቅኢላን ግማሽ አውራጃ የሚገዛው ሐሸብያ የአውራጃውን ህዝብ ወክሎ ቀጣዩን ክፍል መልሶ ሰራ። **18** የቅዒላን ቀሪውን ግማሽ አውራጃ የሚገዛው የኤንሐዳድ ልጅ በዋይና ከሌሎች የሌዊ ትውልዶች ጋር ቀጣዩን ክፍል መልሶ ሰራ። **19** ከእርሱ ቀጥሎ፣ የምጽጳ ከተማን የሚገዛው የኢያሱ ልጅ ኤጽር እስከ ጦር መሣሪያ ግምጃ ቤት ደጃፍ፣ መአዘን ላይ እስከ ሚገኘው የቅጥሩ ቅስት ድረስ ያለውን ሌላውን ክፍል መልሶ ሰራ። **20** ከእርሱ ቀጥሎ፣ የዘባይ ልጅ ባሮክ የቀረውን የቅጥሩን ክፍል በታላቅ ትጋት መልሶ ሰራው። ከሊቀ ካህኑ ከኤልያሴብ ቤት በር እስከ ራሱ እስከ ባሮክ ቤት መጨረሻ ድረስ ያለውን ክፍል መልሶ ሰራ። **21** ከእርሱ ቀጥሎ፣ የአቆስ የልጅ ልጅ፣ የኦርዮ ልጅ የሆነው ሜሪሞት ከኤልያሴብ ቤት በር እስከ ራሱ እስከ ሜሪምት ቤት መጨረሻ ያለውን ክፍል መልሶ ሰራ። **22** ከእርሱ ቀጥሎ፣ ብዙ ካህናት የቅጽሩን ክፍሎች መልሰው ሰሩ። በኢየሩሳሌም አቅራቢያ ያሉ ካህናት አንድ ክፍል መልሰው ሰሩ። **23** ከእነርሱ ቀጥሎ፣ ብንያምና አሱብ ከቤታቸው ፊት ለፊት ያለውን አንድ ክፍል መልሰው ሰሩ። የሖናንያ የልጅ ልጅ፣ የመፅሤያ ልጅ የሆነው ዓዛርያስ ቀጣዩን ክፍል መልሶ ሰራ። **24** ከእርሱ ቀጥሎ፣ ከዓዛርያስ ቤት ቅጽሩ በጥቂቱ ዞር እስከሚልበት ድረስ ያለውን አንዱን ክፍል የኤንሐዳድ ልጅ ቢንዊ መልሶ ሰራ። **25** ከእርሱ ቀጥሎ፣ ቅጥሩ ከሚዞርበትና የመጠበቂያ ማማው ከላይኛው ቤተ መንግስት ከፍ ብሎ እስከሚታይበት ድረስ ያለውን አንድ ክፍል የኡዛይ ልጅ ፉላል መልሶ ሰራ። መጠበቂያ ማማው ጠባቂዎቹ ከሚኖሩበት አደባባይ አጠገብ ይገኛል። ከፉላል ቀጥሎ፣ የፋሮስ ልጅ ፈዳ ቅጥሩን መልሶ ሰራ። **26** ከእርሱ ቀጥሎ የቤተ መቅደስ አገልጋዮች በትልቁ ማማ ምስራቅ አቅጣጫ ፊቱን ወደ ውሃ በር ያደረገውን አንድ ክፍል መልሰው ጠገኑ። **27** ከእርሱ ቀጥሎ፣ የተቁሐ ሰዎች ከትልቁ ማማ ፊት ለፊት እስከ ኦፌል ቅጥር ድረስ ያለውን ሁለተኛውን ክፍል መልሰው ሰሩ። **28** ከፈረስ መግቢያ ሰሜን አንስቶ ያለውን ቅጽር አንድ የካህናት ቡድን መልሶ ሰራው። እያንዳንዱ ካህን ከቤቱ ፊት ለፊት ያለውን ክፍል መልሶ ሰራ። **29** ከእነርሱ ቀጥሎ፣ የአሜር ልጅ ሳዶቅ ከቤቱ ፊት ለፊት ያለውን ክፍል መልሶ ሰራ። ከእርሱ ቀጥሎ፣ በስተምስራቅ የሚገኘው በር ጠባቂ የነበረው የሴኬንያ ልጅ ሸማያ ቀጣዩን ክፍል መልሶ ሰራ። **30** ከእርሱ ቀጥሎ፣ የሰሌምያ ልጅ ሐናንያ፣ እና የሴሌፍ ስድስተኛ ልጅ አንድ ክፍል መልሰው ሰሩ። ያም እነርሱ መልሰው የጠገኑት ሁለተኛው ክፍል ነበር። ከእርሱ በኋላ የበራክያ ልጅ ሜሱላም እርሱ ይኖርበት በነበረው ቤት ፊት ለፊት የሚገኙትን ቅጥሮች ክፍል መልሶ ሰራ። **31** ከእነርሱ ቀጥሎ፣ ወርቅ አንጣሪው መልክያ ከቀጠሮ በር ማዕዘን ላይ እስከሚገኘው የላይኛው መኖሪያዎች የሚገኙትን የቤተ መቅደስ አገልጋዮችና ነጋዴዎች እስከ ሚገለገሉባቸው ህንጻዎች ድረስ ያለውን ክፍል መልሶ ሰራ። **32** ሌሎች ወርቅ አንጥረኞች፣ ከነጋዴዎች ጋር ሆነው የቅጥሩን የመጨረሻ ክፍያ እስከ በጎች በር ድረስ መልሰው ሰሩ።

Nehemiah 3:1

ታላቁም ካህን ኤልያሴብ ከካህናት ወንድሞቹ ጋር ተነሳ
“ከዚያም ታላቁ ካህን ኤልያሴብ ከካህናት ወንድሞቹ ጋር መጣ”

ኤልያሴብ ... የአምሪ ልጅ ዙኩር
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

የመቶ ግንብ ግንብ
“የመቶ ግንብ ግንብ” (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

የሐናንኤል ግንብ
ይህ የግንብ ስም ነው። አንድ “ሐናንኤል” በሚባል ሰው ስም ስያሜ እንደተሰጠው መገመት ይቻላል። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

የኢያሪኮ ሰዎች
ይህ ማለት እነዚህ ሰዎች ከኢያሪኮ የመጡ ናቸው ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ከኢያሪኮ የመጡ ሰዎች” (የንብረት ባለቤትነት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Nehemiah 3:3

ሃስናአ ... ሜሪሞት ... ኦርዮ ... አቆስ ... ሜሱላም ... በራክያ ... ሜሴዜቤል ... ሳዶቅ ... በዓና
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

በሮችን አቆሙ
“በሮችዋን አስገቡ” ወይም “በሮችዋን በቦታው አስቀመጡ”

መቀርቀርያዎቹንና መወርወርያዎቹን
“ቁልፎቹንና መቀርቀሪያዎቹን።” እነዚህ በሮቹን በአስተግንብኝ ሁኔታ እንዲቆለፉ ያደርጉ ነበር።

የሚቀጥለውን ክፍል ሜሪሞት አደሰ .... ሜሱላም አደሰ ... ሳዶቅ አደሰ ... ቴቁሐውያን አደሱ ...
እነዚህ ሐረጎች የሚያመለክቱት ቅጥሩን ስለ መገንባት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ሜሪሞት የሚቀጥለውን ክፍል አደሰ ... ሜሱላምም ቅጥሩን አደሰ ... ሳዶቅ ቅጥሩን አደሰ ... ቴቁሐውያን ቅጥሩን አደሱ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ቴቁሐውያን
እነዚህ ቴቁሐ ከሚባል ከተማ የመጡ ሰዎች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

በአለቆቻቸው የታዘዙትን
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አለቆቻቸው አድርጉ ብለው ያዘዟቸውን” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 3:6

ዮዳሔ ... ፋሴሐ እና ሜሱላም ... በሶድያ ... መልጥያ ... ያዶን
እነዚህ ሁሉም የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

በሮችዋን አቆሙ
“በሮቹን አስገቡ” ወይም “በሮቹን በቦታቸው አስቀመጡ”

መቀርቀርያዎቹንና መወርወርያዎቹን
“ቁልፎቹንና መቀርቀሪያዎቹን።” እነዚህ በሮቹን በአስተግንብኝ ሁኔታ እንዲቆለፉ ያደርጉ ነበር።

ገባዖናዊ ... ሜሮኖታዊ
ገባዖናውያንና ሜሮኖታውያን ሕዝቦች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ገባዖንና ምጽጳ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ከወንዙ ማዶ ያለው ግዛት
ይህ ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተ ምዕራብ በኩል የነበረው ግዛት ስም ነው። በሱሳ ከተማ ከነበረው ወንዝ ባሻገር ያለ ቦታ ነበር። ይህ በነህምያ 2:7 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 3:8

ዑዝኤል ... ሐርሃያ ... ሐናንያ ... ረፋያ ... ሆር ... ይዳያ ... ኤርማፍ ... ሐጡስ ... ሐሰበንያ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ወርቅ አንጥረኛ
ወርቅ አንጥረኛ ማለት የወርቅ ጌጣጌጥና ሌሎች የወርቅ እቃዎችን የሚሰራ ሰው ነው።

ወርቅ አንጥረኛው አደሰ ... ሆር አደሰ ... ኤርማፍ አደሰ ... ሐሰበንያ አደሰ
እነዚህ ሐረጎች የሚያመለክቱት ቅጥሩን ስለማደስ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ወርቅ አንጥረኞች ቅጥሩን አደሱ ... ኤርማፍ ቅጥሩን አደሰ ... ሐሰበንያ ቅጥሩን አደሰ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

በአጠገቡም የሸቶ ቀማሚ የነበረው ሐናንያ ነበር
ሐናንያም ቅጥሩን አደሰ። አማራጭ ትርጉም፦ “በአጠገቡም የሸቶ ቀማሚ የነበረው ሐናንያ ቅጥሩን አደሰ።” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ሸቶ
ሰዎች ጥሩ መዓዛ እንዲኖራቸው በሰውነታቸው ላይ በትንሽ መጠን የሚያደርጉት ፈሳሽ ቅመሞች ናቸው።

አለቃ
መሪ ወይም ዋና ገዢ

የግዛት እኩሌታ
“እኩሌታ” ማለት ከሁለት እኩል መጠን ያላቸው ነገሮች አንዱ ማለት ነው። (ክፍልፋዮች የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 3:11

መልክያ ... ካሪም ... አሱብ ... ፈሐት ሞዓብ ... ሰሎም ... ኤሎኤስ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 3:13

ሐኖን
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

የዛኖዋ ነዋሪዎች
“ከዛኖዋ የመጡ ሰዎች”

ዛኖዋ
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

የሸለቆ በር
“የሸለቆ በር” ወይም “ወደ ሸለቆ የሚወስደው በር።” ይህን እንደ ማብራሪያ ሳይሆን እንደ ስም ለመተርጎም ይሞከር።

በሮችዋን አስገቡ
“በሮችዋን አስገቡ” ወይም “በሮችን በቦታቸው አደረጉ”

መቀርቀሪያዎቹና መወርወሪያዎቹ
“ቁልፎቹንና መቀርቀሪያዎቹን።” እነዚህ በሮቹ በአስተግንብኝ ሁኔታ ተዘግተው እንዲቆዩ ያደርጉ ነበር።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እስከ ቆሻሻ መጣያ በሩ ድረስ አንድ ሺህ ክንድ የሚሆን ቅጥር አደሱ
ከሸለቆ በር እስከ ቆሻሻ መጣያ በር መካከል ያለውን የቅጥር ክፍል አደሱት። አማራጭ ትርጉም፡- “ከሸለቆ በር እስከ ቆሻሻ መጣያ በር አንድ ሺህ ክንድ ርዝመት ያለው የቅጥር ክፍል አደሱ” (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ሺህ ክንድ ርዝመት ያለው አደሱ
የኢየሩሳሌምን ቅጥር እያደሱ እንደነበር ግልጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ሺህ ክንድ ርዝመት ያለው የቅጥር ክፍል አደሱ” ወይም “ከሸለቆ በር ባሻገር ሌላ አንድ ሺህ ክንድ የቅጥሩን ክፍል አደሱ” (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ሺህ ክንድ
“አንድ ሺህ ክንድ።” ይህ በዘመናዊ የርዝመት መለኪያ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “460 ሜትር” (መጽሐፍ ቅዱሳዊ ርቀት እና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ቆሻሻ መጣያ በር
ቆሻሻ ከከተማይቱ ይወገድ የነበረው በዚህ በር በኩል እንደነበር መገመት ይቻላል። ይህንን መግለጫ እንደ እንደ ማብራርያ ከመተርጎም ይልቅ እንደ ስም ለመተርጎም ይሞከር።

Nehemiah 3:14

መልክያ ... ሬካብ ... ሰሎም .... ኮልሖዜ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

አለቃው፣ የሬካብ ልጅ መልክያ
የግዛቱ አለቃ መልክያ ነበር፣ ሬካብ አልነበረም።

አለቃ
መሪ ወይም ዋና ገዢ። ይህንን በነህምያ 3:9 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።

ቤትሐካሪም
ይህ የአንድ ቦታ ስም ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ... በሮቹን ሰራ
“በሮቹን አስገባ” ወይም “በሮቹን በቦታቸው አደረጋቸው”

መቀርቀሪያዎቹና መወርወሪያዎቹ
“ቁልፎችንና መቀርቀሪያዎች።” እነዚህ በሮቹ በአስተግንብኝ ሁኔታ እንዲዘጉ ያደርጋሉ።

የግዛቱ አለቃ የኮልሖዜ ልጅ ሰሎም
የግዛቱ አለቃ የነበረው ሰሎም ነው፣ ኮልሖዜ አልነበረም።

የሼላን መዋኛ ቅጥር
ይህ ማለት ቅጥሩ ከሼላን መዋኛ አጠገብ ነበር የሚገኘው ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የሼላን መዋኛን የከበበው ቅጥር” (የንብረት ባለቤትነት የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 3:16

ነህምያ ... ዓዝቡቅ ... ሬሁም ... ባኒ ... ሐሸብያ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

አለቃው፣ የዓዝቡቅ ልጅ ነህምያ
አለቃ የነበረው ነህምያ ነው፣ አዝቡቅ አልነበረም።

ነህምያ
እዚህ የተጠቀሰው ነህምያ ይህን መጽሐፍ ከጻፈው ሰው የተለየ ነው።

አለቃ
መሪ ወይም ዋና ገዢ። ይህንን በነህምያ 3:9 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።

የግዛቱ እኩሌታ
“እኩሌታ” ማለት ከሁለት እኩል መጠን ያላቸው ነገሮች አንዱ ማለት ነው። (ክፍልፋዮች የሚለውን ይመልከቱ)

ቤት-ጹር
እነዚህ የቦታ ስያሜዎች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

... እስካለው ስፍራ አደሱ ... ሌዋውያን አደሱ
እነዚህ ሐረጎች የሚያመለክቱት ስለ ቅጥሩ እድሳት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “... እስካለው ስፍራ ቅጥሩን አደሱ ... ሌዋውያን ቅጥሩን አደሱ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ኃያላን ሰዎች
“ተዋጊዎች”

ለግዛቱ
“ግዛቱን ወክሎ” ወይም “ግዛቱን በመወከል”

Nehemiah 3:18

ከእርሱም በኋላ የአገሩ ሰዎች አደሱ ... ሌላ ክፍልም አደሱ
እነዚህ ሐረጎች የሚያመለክቱት ቅጥሩን ስለማደስ ነው ። አማራጭ ትርጉም፡- “ከእርሱም በኋላ የሃገራቸው ሰዎች ቅጥሩን አደሱ ... የቅጥሩን ሌላ ክፍልም አደሱ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእርሱ በኋለ
“ከእርሱ ቀጥሎ”

በዋይ ... ኤንሐዳድ ... ኤጽር ... እያሱ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

አለቃው፣ የኤንሐዳድ ልጅ በዋይ
የግዛቱ አለቃ የነበረው በዋይ ነው፣ ኤንሐዳድ አልነበረም።

ቅዒላ ... ምጽጳ
እነዚህ የቦታ ስያሜዎች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

አለቃው፣ የኢያሱ ልጅ ኤጽር
አለቃ የነበረው ኤጽር ነው፣ ኢያሱ አልነበረም።

በጦር መሳርያ ቤት አንጻር
“ወደ ጦር መሳርያ ቤት ከሚያመሩት ደረጃዎች ፊት ለፊት የሚገኘው”

የጦር መሳርያ ቤት
የጦር መሳርያዎች የሚቀመጡበት ስፍራ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Nehemiah 3:20

ከእርሱ በኋላ
“ከእርሱ ቀጥሎ”

ባሮክ ... ዘባይ ... ኤልያሴብ ... ሜሪሞት ... ኦርዮ ... አቆስ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ሌላውን ክፍል አደሰ
ይህ የሚያመለክተው ቅጥሩን ሰለማደስ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የቅጥሩን ሌላ ክፍል አደሰ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 3:22

ኢየሩሳሌም ዙሪያ፣ አደሱ ... ብንያምና አሱብ አደሱ ... ዓዛርያስ .. አደሰ ... ቢንዊ ... አደሰ
እነዚህ ሐረጎች የሚያመለክቱት የቅጥሩን መታደስ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በኢየሩሳሌም ዙሪያ ቅጥሩን አደሱ፣ ብንያምና አሱብ ቅጥሩን አደሱ ... ዓዛርያስ ቅጥሩን አደሰ ... ቢንዊ ቅጥሩን አደሰ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ብንያም ... አሱብ ... ዓዛርያስ ... መዕሤያ ... ሐናንያ ... ቢንዊ ... ኤንሐዳድ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ከእነርሱ በኋላ ... ከእርሱ በኋላ
“ከእነርሱ ቀጥሎ ... ከእርሱ ቀጥሎ”

በቤታቸው አንጻር
“ከቤታቸው ፊት ለፊት”

Nehemiah 3:25

ፋላል ... አደሰ ... ፋሮስ ... አደሰ ... ባርያዎቹ አደሱ ... ሌላውን ክፍል አደሱ
እነዚህ ሐረጎች የሚያመለክቱት የቅጥሩን መታደስ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ፋላል ... ቅጥሩን አደሰ ... ፋሮስ ቅጥሩን አደሰ ... ባርያዎቹ ... ቅጥሩን አደሱ ... የቅጥሩን ሌላኛ ክፍሎች አደሱ።

ፋላል ... ኡዛይ ... ፈዳያ ... ፋሮስ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ወደላይ ከፍ ያለውን ግንብ
“ወደላይ የሚወጣውን ግንብ”

የላይኛው የንጉስ ቤት
“የእስራኤል መሪ ታላቁ ቤተመንግስት”

የዘበኞች አደባባይ
ይህ ጠባቂዎቹ ይኖሩበት የነበረው ቦታ ነው።

ከእርሱ በኋላ
“ከእርሱ ቀጥሎ”

ጶፌል
ይህ የቦታ ስያሜ ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

በውሃው በር አንጻር
“ከውሃው በር ፊት ለፊት”

ታላቁ ግንብ ... የቆመው ታላቅ ግንብ
“ታላቁ ግንብ ... ታላቁ ግንብ።” “የቆመው ግንብ” የሚለው ሐረግ ከቅጥሩ ወጣ በሎ የሚታየው ረጅሙ ግንብ ነው። ሁለቱም ሐረጎች ስለ አንድ ግንብ እንደሚያወሩ ይገመታል።

ቴቁሐውያን
እነዚህ ቴቁሐ ከሚባል ከተማ የመጡ ሕዝቦች ናቸው። ይህ በነህምያ 3:5 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 3:28

ካህናት አደሱ ... በቤታቸው አንጻር አደሱ ... የምስራቁን በር .. አደሰ ... ሌላውን ክፍል አደሱ ... ትይዩውን አደሱ
እነዚህ ሐረጎች የሚያመለክቱት ስለ ቅጥሩ መታደስ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ካህናት ቅጥሩን አደሱ ... የቅጥሩን ክፍል አደሱ ... የቅጥሩን የምስራቅ በር ክፍል አደሱ ... የቅጥሩን ሌላ ክፍል አደሱ ... የቅጥሩን ተቃራኒ ክፍል አደሱ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ከፈረሱ በር በላይ
“በላይ” የሚለው ቃል እዚህ ጥቅም ላይ የዋለው የካህናቱ ቤት በከፍታ ከፈሱ በር በላይ ከፍ በሎ ይገኝ ሰለነበር ይመስላል።

ከራሱ ቤት አንጻር
“ከራሱ ቤት ፊት ለፊት”

ከእነርሱ በኋላ ... ከእርሱ በኋላ
“ከእነርሱ ቀጥሎ ... ከእርሱ ቀጥሎ”

ሳዶቅ ... አሜር ... ሸማያ ... ሴኬንያ ... ሐናንያ ... ሰሌምያ ... ሐኖን ... ሴሌፍ ... ሜሱላም ... በራክያ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

የምስራቁ በር ጠባቂ የሴኬንያ ልጅ ሸማያ
የምስራቁ በር ጠባቂ የነበረው ሸማያ ነው፣ ሴኬንያ አልነበረም።

የምስራቁ በር ጠባቂ
“የምስራቁን በር ይጠብቅ የነበረው ሰው” ወይም “የምስራቁን በር ይከፍትና ይዘጋ የነበረው ሰው”

ስድስተኛው ወንድ ልጅ
“ስድስተኛ የወንድ ልጅ” ወይም “በቁጥር ስድስተኛ የነበረው ወንድ ልጅ” (ደረጃ የሚያሳይ ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

በጓዳው አንጻር
“አርሱ ይኖርበት ከነበረበት ክፍሎች ፊት ለፊት።” “እርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሜሱላምን ነው።

Nehemiah 3:31

ከእርሱ በኋላ
“ከእርሱ ቀጥሎ”

መልክያ
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ወርቅ አንጥረኛ
ወርቅ አንጥረኛ ማለት የወርቅ ጌጣጌጥና ሌሎች የወርቅ እቃዎችን የሚሰራ ሰው ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እስከ ... ቤት ድረስ አደሰ ... ነጋዴዎች አደሱ
እነዚህ ሐረጎች የሚያመለክቱት ቅጥሩን ስለማደስ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እስከ ነጋዴዎቹ ቤት ድረስ ያለውን ቅጥሩን አደሰ ... ነጋዴዎች ቅጥሩን አደሱ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ነጋዴዎች
“ሻጮች” ወይም “ነጋዴዎች”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 ሰንበላጥ የከተማዋን ቅጥር እንደገና እየሰራን መሆኑን በሰማ ጊዜ፣ እኛ ኢየሩሳሌምን እንደ ገና መገንባታችን በውስጡ እንደ እሳት አቃጠለው፣ እናም በጣም ተቆጥቶ በአይሁዶች ላይ በጥላቻ ተሞልቶ ተናገረ። **2** ከሰማርያ በመጡት አማካሪዎቹና የጦር አለቆቹ ፊት እንዲህ አለ፣ “እነዚህ አይሁዶች ራሳቸውን ችለው መቆም አይችሉም፣ ምን እያደረጉ ያሉ መስሏቸዋል? ከተማዋን እንደገና ገንብተው ራሳቸው ሊኖሩባት ነውን? ቤተ መቅደሱን እንደገና ገንብተው ካህናቱ ለያህዌ የሚያቀርቡትን መስዋእት ሁሉ ሊያቀርቡ ነውን? በአንዲት ቀን እንዲህ ያለውን ታላቅ ሥራ ይጨርሳሉን? እነዚህን የተቃጠሉና ከጥቅም ውጭ የሆኑ ድንጋዮች ቅጥሩን እንደገና ለመገንባት ሊጠቀሙበትና ለከተማዋ ዳግም ሕይወት ሊሰጧት ይችላሉን? **3** ጦቢያ ከሰንበላጥ አጠገብ ቆሞ ነበር። እርሱም እንዲህ አለ፣ “ያ እነርሱ የሚገነቡት ቅጥር እጅግ ደካማ ነው፤ ትንሽ ቀበሮዎች ቢወጡበት እንኳን ይፈርሳል፤ የእነርሱ የድንጋይ ቅጥር ቀበሮ ቢወጣበት ይፈርሳል!” **4** ከዚያ እኔ እንዲህ ስል ጸለይኩ፣ “አምላካችን ሆይ፣ ስማን፣ እነርሱ እየቀለዱብን ነው! የስድባቸውን ቃል ወደ ራሳቸው እንዲመለስ አድርግ! ጠላቶቻቸው እንዲመጡባቸውና እንዲይዟቸው ወደ ባዕድ ምድርም እንዲያሳድዷቸው አድርግ! **5** እነርሱ በደለኞች ናቸው። በደላቸውን ከእነርሱ አታርቅ በፊትህ ለሰሩት ኃጢአት ዋጋ ይክፈሉ። በስድቦቻቸው፣ ቅጥሩን መልሰው የሚገነቡትን በጣም አስቆጥተዋል!” **6** ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን፣ ሰራተኞቹ ከጠቅላላው በከተማይቱ ዙሪያ ከሚገኘው የቅጥሩ ከፍታ ግማሽ ያህሉን ሰሩ። ይህን ማከናወን የቻሉት ሊሰሩ የሚችሉትን በሙሉ ልባቸው ለመስራት ስለፈለጉ ነበር። **7** ነገር ግን ሰንበላጥ፣ ጦብያ፣ ዐረቦች፣ አሞናዊያን፣ እና አሽዶዳዊያን የቅጥሩ ስራ መሰራቱ እንደ ቀጠለና የፈረሰውን ቅጥር እየጠገንን መሆኑን ሲሰሙ በጣም ተቆጡ። **8** እነርሱም መጥተው የኢየሩሳሌምን ሰዎች ለመውጋት እና በከተማይቱ ውስጥ ሀብት ለመፍጠር በአንድነት ዕቅድ አወጡ። **9** እኛ ግን ቅጥሩን መልሰን በመገንባታችን እጅግ በተቆጡት በእነዚህ ሰዎች ምክንያት ወደ አምላካችን ጸለይን፣ ደግሞም ከተማዋን ቀንና ሌሊት ይጠብቁ ዘንድ ወንዶችን በቅጥሮቹ ዙሪያ አቆምን። **10** ከዚያ የይሁዳ ሰዎች እንዲህ ማለት ጀመሩ፣ “ቅጥሩን የሚሰሩት ወንዶች መላ አቅማቸውን እየተጠቀሙ ነው። ልናነሳው የሚገባ እጅግ ብዙ ፍርስራሽ አለ፤ እኛ ይህን ስራ መጨረስ አልቻልንም ስራው እጅግ በዝቶብናል። **11** ከዚህም ባሻገር፣ ጠላቶቻችን እንዲህ እያሉ ነው! ‘አይሁዶች እኛን ከማየታቸው አስቀድሞ፣ በእነርሱ ላይ እንውጣባቸውና እንግደላቸው፣ የቅጥሩን ስራቸውንም እናስቁማቸው!” **12** በጠላቶች አቅራቢያ ይኖሩ የነበሩ አይሁዶች ብዙ ጊዜ ወደ እኛ እየመጡ ጠላቶቻችን በእኛ ላይ ሊፈጽሙ የሚያስቡትን ክፉ እቅድ ይነግሩን ነበር። **13** ስለዚህ ከእያንዳንዱ ቤተሰብ ቅጥሩን እንዲጠብቁ ሰዎችን አቆምኩ። እነዚህ ሰዎች ቅጥሩን በቀላሉ መሻገር በሚቻልባቸው በቅጥሩ ዝቅተኛ ስፍራዎች እንዲቆሙ ተደረገ። እነርሱም ሰይፎቻቸውን ጦሮቻቸውን፣ እና ደጋኖቻቸውንና ቀስቶቻቸውን ይዘው ይጠብቁ ነበር። **14** ከዚያ እያንዳንዳቸውን ከተመለከትኩ በኋላ፣ መሪዎችንና ሌሎች ሹማምንቶችን እንዲሁም ሌሎች ብዙ ሰዎችን ሰብስቤ እንዲህ አልኳቸው፣ “ጠላቶቻችንን አትፍሯቸው! እግዚአብሔር ታላቅና በክብር የተሞላ እንደሆነ አስቡ! እናም ቤተሰባችሁን፣ ወንድና ሴቶች ልጆቻችሁን፣ ሚስቶቻችሁን እና ቤቶቻችሁን ለመጠበቅ ተዋጉ!” **15** ጠላቶቻችን፣ ዕቅዶቻቸውን እንደሰማን አወቁ፣ እግዚአብሔርም ስራችንን ለማስቆም ያወጡትን ዕቅድ ከንቱ አደረገባቸው። ስለዚህ እኛ ሁላችንም ወደ ፊት እንሰራበት ወደነበረው ወደዚያው ስፍራ ቅጥሩን ለመገንባት ተመለስን። **16** ነገር ግን ከዚያ በኋላ፣ በዚያ ከነበሩት ወንዶች ግማሾቹ ብቻ የቅጥሩን ሥራ ይሰሩ ነበር። ሌሎቹ ጦሮቻቸውን፣ ጋሻዎቻቸውን፣ ደጋኖቻቸውንና ቀስቶቻቸውን ይዘውና የጦር ልብሶቻቸውን ለብሰው ይጠብቁ ነበር። መሪዎቹ የይሁዳን ሕዝብ ይጠብቁ ነበር። **17** መሪዎች ቅጥሩን የሚሰሩትንና የጉልበት ሥራ የሚሰሩትን ይጠብቁ ነበር። እያንዳንዱ ሰው በአንድ እጁ ቅጥሩን ሲገነባ በሌላው እጁ መሳሪያ ይይዛል። **18** ቅጥሩን የሚገነባ ሁሉ በወገቡ ሰይፍ ይታጠቃል። ጠላቶቻችን ቢመጡ መለከት የሚነፋው ሰው ከእኔ አጠገብ ይሆናል። **19** ከዚያ ለባለስልጣናቱ፣ ለሌሎች ታላላቅ ሰዎች፣ እና ለሌሎች ሰዎች እንዲህ አልኳቸው፣ “ይህ ሥራ ታላቅ ነው፣ እኛ በቅጥሩ ዙሪያ የምንገኝ አንዳችን ከሌላችን ተራርቀን እንገኛለን። **20** የመለከት ድምጽ ስትሰሙ፣ መለከቱ በሚነፋበት ስፍራ ተሰብሰቡ። አምላካችን ለእኛ ይዋጋልናል!” **21** ስለዚህም ስራችንን መስራት ቀጠልን። ከህዝቡ እኩሌታው ቀኑን ሙሉ ጦሩን ይዞ፣ ጠዋት ጸሀይ ስትወጣ አንስቶ ምሽት ከዋክብት እስኪታዩ ድረስ ጥበቃ ያደርጋል። **22** በዚያን ጊዜ፣ እኔ ለህዝቡ፣ “ለእያንዳንዱ ሰራተኛ እና ለረዳቱ በምሽት ኢየሩሳሌም ውስጥ እንዲቆዩ ይነገራቸው። ያንን በማድረግ፣ በምሽት እኛን መጠበቅና በቀን ቅጥሩን መገንባት ይችላሉ” በማለት እናገራሁ። **23** በእነዚያ ጊዜያት፣ ልብሴን አላወልቅም፣ የጦር መሳሪያዬንም ሁልጊዜ እይዛለሁ። ወንድሞቼ፣ አገልጋዮቼ እና እኔን የሚከተሉ ወንዶች እና ዘብ ሆነው የሚያገለግሉ ሁሉ ይህንኑ ያደርጋሉ። ሁላችንም ውሃ ለመጠጣት ስንሄድ እንኳን የጦር መሳሪያዎችንን እንደያዝን ነበር።

Nehemiah 4:1

አሁን ሰንባላጥ
እዚህ ላይ ነህምያ አዲስ የታሪኩን አዲስ ክፍል መጀመሩን ለማመልት ሲል “አሁን” የሚለውን ቃል ይጠቀማል።

ሰንባላጥ ... ጦብያ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። ይህ በነህምያ 2:10 ላይ እንዴት እንደተተረጎሙ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

በውስጡም እጅግ ነደደ፣ እጅግም ተበሳጨ
እዚህ ላይ “ነደደ” ተብሎ የተገለጸው አይሁዳውያን የፈረሰውን ቅጥር እያደሱ መሆኑን ሰንባላጥ መገንዘቡ ነው። ይህ ደግሞ የሰንባላጥ ንዴት እንደሚንድድ እሳት እንደሆነ በጣም እንደተበሳጨ የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እጅግ በኃይል ተናደደ” ወይም “በጣም ተናደደ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በወንድሞቹ ፊት
“በዘመዶቹ ፊት” ወይም “በወገኖቹ ፊት”

እነዚህ ደካሞች መምድን ናቸው ... ያድኑታልን ... ይሰዋሉን ... ስራውን በአንድ ቀን ይጨርሳሉን
ሰንባላጥ እነዚህን ጥያቄዎች የሚጠይቀው በአይሁዳውያን ላይ ለመሳለቅ ነው። እነዚህ በዓርፍተ ነገር መልክ ሊጻፉ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህ ደካማ አይሁዳውያን ምንም ነገር ሊያሳኩ አይችሉም። ከተማቸውን ከጥፋት አድነው ለራሳቸው ሊያደርጉ አይችሉም። መስዋዕት አያቀርቡም። (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ደካማ አይሁዶች
“አቅመ ቢስ አይሁዶች”

በአንድ ቀን
በአንድ ቀን ስራው ሊያልቅ አይችልም ሲል አንድን ነገር ቶሎ ሰርቶ መጨረስ አለመቻልን ለማሳየት ነው።” አማራጭ ትርጉም፡- “በቶሎ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ድንጋዮቹ ከተቃጠሉ በኋላ ከፍርስራሽ ክምር መካከል ነፍስ ይዘሩባቸው ይሆን?
ሰንባላጥ ይህንንም ጥያቄ የሚጠይቀው በአይሁዳውያን ላይ ለመሳለቅ ነው። ይህ በዓርፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከተቃጠለው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የፍርስራሽ ክምር መካከል ለድንጋዮቹ እንደገና ነፍስ ሊዘሩባቸው አይችሉም።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ድንጋዮቹ ከተቃጠሉ በኋላ ከፍርስራሽ ክምር መካከል ነፍስ ይዘሩባቸዋል
ይህ ሰዎቹ ከተማውን ነፍስ እንደዘሩበት ያህለ ደግመው ስለመስራታቸውና ስለመገንባታቸው ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከተቃጠሉትና ወደ ፍርስራሽነት ከተለወጡት የማይጠቅሙ ድንጋዮች ከተማይቱን ያድሳሉ ደግሞም ቅጥሩን እንደገና ይሰራሉ።” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከተቃጠሉ በኋላ የፍርስራሽ ክምር ከሆኑት
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች አቃጥለው የፍርስራሽ ክምር ካደረጉት ድንጋይ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በሚገነቡት ላይ ቀበሮ ቢወጣበት የድንጋይ ቅጥራቸውን ያፈርሰዋል
ሰንባላጥ የሚሰራው ቅጥር ደካማ እንደሆነ ለማሳየትና በእነርሱ ላይ ለመሳለቅ ቀበሮ ቢወጣበት እንደሚያፈርሰው ግነት በተሞላበት ንግግር ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሚገነቡት ቅጥር በጣም ደካማ ከመሆኑ የተነሳ ትንሽ ቀበሮ እንኳን ቅጥሩ ላይ ቢወጣ የድንጋዩ ቅጥራቸው ይፈራርሳል።” (ግነትና ጅምላ መግለጫየሚለውን ይመልከቱ)

አምላካችን ሆይ ስማ ... ሰራተኞቹን አበሳጭተዋልና
እዚህ ላይ ነህምያ ወደ እግዚአብሔር ይጸልያል። ይህ በግልጽ ሊብራራና በትምህርተ ጥቅስ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ ከዚያም ጸለይሁ፣ “አምላካችን ስማ ... ሰራተኞችን አስቆጥተዋቸዋልና። ስለዚህም ...” (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ ተንቀናልና አምላካችን ስማ
እዚህ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው አይሁዳውያንን ነው። ይህ በዓረፍተ ነገር ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላቶቻችን ንቀውናልና አምላካችን ስማ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ለብዝበዛ አሳልፈህ ስጣቸው
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላቶቻቸው እንዲበዘብዙአቸው አድርግ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ስድባቸውን በራሳቸው ላይ መልስባቸው
“ስድባቸውን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሰንባላጥና የጦብያን ስድብ ነው። “በራሳቸው ላይ” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ጠቅላላ ሕዝቡን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ስድባቸው በራሳቸው ላይ ይሁንባቸው” ወይም “ስድባቸው በራሳቸው ላይ መሳለቂያ እንዲሆኑ ያድርጋው።” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

አትክደን
ይህ በአካል ሊከደኑ እንደሚችሉ እቃዎች እንዲሁ የአንድ ሰው ኃጢአት እንደሚከደንና ይቅር እንደሚባል ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይቅር አትበል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በደላቸውም በፊትህ አትደምሰስ
ይህ ሊሰረዝ እንደሚችል አንድ ጽሑፍ የአንድን ሰው ኃጢአት እንደሚወገድና እንደሚረሳ የሚያሳይ ው። አማራጭ ትርጉም፡- “በደላቸውን አትርሳ”

የሚገነቡትን ሰዎች አበሳጭተዋልና
“ገንቢዎቹን አናድደዋቸዋል”

ቅጥሩንም ሰራን
“ቅጥሩን ደግመን ገነባን”

ቅጥሩም በሙሉ እስከ ቁመቱ አጋማሽ ድረስ ተጋጠመ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ቅጥሩን አንድ ላይ አጋጠምነው፤ ከጠቅላላ ቁመቱም ግማሹን ያህል ነበር” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ግማሽ ቁመት የሚያክል
“እኩሌታ” ማለት ከሁለት ሁለት እኩያ መጠን ካላቸው ነገሮች አንዱ ማለት ነው። (ክፍልፋዮች የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 4:4

አምላካችን ሆይ ስማ ... ሰራተኞቹን አበሳጭተዋልና
እዚህ ላይ ነህምያ ወደ እግዚአብሔር ይጸልያል። ይህ በግልጽ ሊብራራና በትምህርተ ጥቅስ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ ከዚያም ጸለይሁ፣ “አምላካችን ስማ ... ሰራተኞችን አስቆጥተዋቸዋልና። ስለዚህም ...” (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ ተንቀናልና አምላካችን ስማ
እዚህ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው አይሁዳውያንን ነው። ይህ በዓረፍተ ነገር ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላቶቻችን ንቀውናልና አምላካችን ስማ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ለብዝበዛ አሳልፈህ ስጣቸው
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላቶቻቸው እንዲበዘብዙአቸው አድርግ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ስድባቸውን በራሳቸው ላይ መልስባቸው
“ስድባቸውን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሰንባላጥና የጦብያን ስድብ ነው። “በራሳቸው ላይ” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ጠቅላላ ሕዝቡን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ስድባቸው በራሳቸው ላይ ይሁንባቸው” ወይም “ስድባቸው በራሳቸው ላይ መሳለቂያ እንዲሆኑ ያድርጋው።” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

አትክደን
ይህ በአካል ሊከደኑ እንደሚችሉ እቃዎች እንዲሁ የአንድ ሰው ኃጢአት እንደሚከደንና ይቅር እንደሚባል ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይቅር አትበል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በደላቸውም በፊትህ አትደምሰስ
ይህ ሊሰረዝ እንደሚችል አንድ ጽሑፍ የአንድን ሰው ኃጢአት እንደሚወገድና እንደሚረሳ የሚያሳይ ው። አማራጭ ትርጉም፡- “በደላቸውን አትርሳ”

የሚገነቡትን ሰዎች አበሳጭተዋልና
“ገንቢዎቹን አናድደዋቸዋል”

ቅጥሩንም ሰራን
“ቅጥሩን ደግመን ገነባን”

ቅጥሩም በሙሉ እስከ ቁመቱ አጋማሽ ድረስ ተጋጠመ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ቅጥሩን አንድ ላይ አጋጠምነው፤ ከጠቅላላ ቁመቱም ግማሹን ያህል ነበር” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ግማሽ ቁመት የሚያክል
“እኩሌታ” ማለት ከሁለት ሁለት እኩያ መጠን ካላቸው ነገሮች አንዱ ማለት ነው። (ክፍልፋዮች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Nehemiah 4:7

ታላቅም ንዴት በውስጣቸው ነደደ
ይህ ሕዝቡ ንዴታቸው አንድ ነገር በውስጣቸው የሚነድድ እስከሚመስል ድረስ በጣም ተናድደው እንደነበር የሚያሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በጣም ተናደዱ” ወይም “ሃይለኛ ንዴት ተፈጠረባቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ኢየሩሳሌምን ይወጉ ዘንድ
እዚህ ላይ “ኢየሩሳሌም” የሚለው በዚያ የሚኖሩ ሕዝብን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሕዝብን ይወጉና ያሸብሩ …” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ለጥበቃ ዘቦችን አደረግን
“ከተማው ለመጠበቅ በቅጥሩ ዙሪያ ዘቦችን አቆምን”

Nehemiah 4:10

ብዙ ፍርስራሽ አለ
ፍርስራሽ “የተቃጠለ ድንጋይ” ወይም “የተሰባበረ ድንጋይ” ወይም “የማይጠቅም ድንጋይ” ነው።

በመካከላቸው እስክንመጣ ድረስ አያውቁም ወይም አያዩምም
“አጠገባቸው እስክንደርስ ድረስ ስንመጣ አያዩንም”

Nehemiah 4:12

ከሁሉም አቅጣጫዎች
ይህ ብዙ አቅጣጫዎችን ይወክላል። “ሁሉም” የሚለው ቃል “ብዙ” ይወክላል የሚለውን የሚያጋንን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ከብዙ አቅጣጫዎች” (ግነትና ጅምላ መግለጫየሚለውን ይመልከቱ)

አስር ጊዜ ነገሩን
እዚህ ላይ 10 ቁጥር “ብዙ” የሚለውን ቃል የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ብዙ ጊዜ ነገሩን” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በተከፈቱ ስፍራዎች
“ለአደጋ በተጋለጡ ቦታዎች”

እያንዳንዱን ቤተሰብ አቆምኳቸው
ይህ ከእያንዳንዱ ቤተሰብ የተመረጡ ብዙ ሰዎችን ያመለክታል፣ ምርጫው ሴቶችንና ሕጻናትን እንደማይጨምር ይገመታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከያንዳንዱ ቤተሰብ ሰዎችን አቆምኩ” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ጌታን አስቡ
“አስቡ” የሚለው ቃል ማስታወስ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ጌታን አስታውሱ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 4:15

እንዲህም ሆነ
“እንዲህ ሆነ”

ሃሳባቸው በእኛ የታወቀ ነበር
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለ ሃሳባቸው አውቀናል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ባርያዎቼ ይሰሩ ነበር
“ወጣት ልጆቼ ይሰሩ ነበር”

ከባርያዎቼ እኩሌታዎቹ ... እኩሌታዎቹ
“እኩሌታ” ማለት ከሁለት እኩል መጠን ያላቸው ነገሮች አንዱ ማለት ነው። (ክፍልፋዮች የሚለውን ይመልከቱ)

አለቆቹ ከሕዝቡ ጀርባ ይቆሙ ነበር
“መሪዎቹ ከሕዝቡ ሁሉ ጀርባ ይሆኑ ነበር”

Nehemiah 4:17

ሁሉም በአንድ እጁ እየሰራ በሌላኛው እጁ የጦር መሳሪያውን ይይዝ ነበር
ይህ ግነት ነው። በሚሰሩበት ጊዜ ሁሉ በአንድ እጅ ብቻ አይሰሩም ነበር፣ ነገር ግን ራሳቸውንና በዙሪያቸው ያሉትን ሰዎች ለመከላከል ዝግጁ ለመሆን የጦር መሳሪያቸው ሁልጊዜ ከነሱ ጋር ነበር። (ግነትና ጅምላ መግለጫየሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 4:19

እኔም አልኳቸው
እዚህ ላይ “እኔ” የሚለው ቃል የሚያሳየው ነህምያን ነው።

ታላላቆቹን .... ሹማምንቱ
እነዚህ በነህምያ 4:16 ላይ የተገለጹት መሪዎች ናቸው።

ሥራው ታላቅ ነው
እዚህ ላይ “ታላቅ” የሚለው ቃል “መጠነ ሰፊ” ወይም “ትልቅ” ለማለት ነው።

የቀንደ መለከቱ ድምጽ
ይህ አንድ ሰው መለከትን ሲነፋ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ሰው ቀንደ መለከቱን ሲነፋ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 4:21

እኩሌታዎቹ
“እኩሌታ” ማለት ከሁለት እኩል መጠን ያላቸው ነገሮች አንዱ ማለት ነው። (ክፍልፋዮች የሚለውን ይመልከቱ)

ጎህ ሲቀድ ጀምሮ እስከ ከዋክብት መውጫ ድረስ
ይህ ሙሉ ቀንን፣ ብርሃን ባለበት ጊዜ ሁሉ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከቀን ጅማሬ እስከ ምሽቱ ጅማሬ ድረስ”

ጎህ ሲቀድድ
ይህ የማለዳ ጸሐይ የሚወጣበት ጊዜ ማለትም “ንጋት” ነው። እዚህ የጸሐይ መውጫ ጊዜ “ንጋት” ተብሎ ይጠራል። አማራጭ ትርጉም፡- “የጸሐይ መውጫ” ወይም “ንጋት” (ተዛምዶአዊ ዘይቤ ይመልከቱ)

በኢየሩሳሌም መካከል
“ኢየሩሳሌም ውስጥ”

ልብስ አልለወጥንም
“ልብስ አላወለቅንም”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 5

1 ቆይቶ፣ ሌሎቹ አንዳንድ አይሁዶች በሚያደርጉት ብዙዎቹ ወንዶችና ሚስቶቻቸው ፍትህ ለማግኘት ጮኹ። 2 አንዳንዶቹ እንዲህ አሉ፣ “እኛ ብዙ ልጆች አሉን። በልተን ለማደርና በህይወት ለመቆየት እንኳን ብዙ እህል ያስፈልገናል።” 3 ሌሎቹ ደግሞ እንዲህ አሉ፣ “በዚህ የረሃብ ወቅት የምንበላው እህል ለማግኘት የእርሻ መሬታችንን፣ የወይን ተክላችንንና ቤቶቻችንን ማስያዝ ግድ ሆኖብናል። 4 ሌሎቹም እንዲህ አሉ፣ “ለእርሻ መሬቶቻችንና ለወይን ተክላችን ለንጉሱ ግብር ለመክፈል ገንዘብ መበደር የግድ ሆኖብናል። 5 እኛም እንደ ሌሎቹ አይሁዶች አይሁዳውያን ነን። የእነርሱ ልጆች ለእነርሱ ጠቃሚ እንደሆኑ ሁሉ፤ የእኛም ልጆች ለእኛ እንደዚያው ናቸው። ነገር ግን መክፈል የሚገባንን ለመክፈል ስንል ልጆቻችንን ለባርነት ለመሸጥ ተገደናል። አንዳንድ ሴት ልጆቻችንን አሁን ለባርነት ሸጠናል። የእርሻ መሬቶቻችንና የወይን ተክሎቻችን ከእኛ ተወስደዋል፣ ስለዚህም መክፈል ያለብንን ገንዘብ ለመክፈል ገንዘቡ የለንም።” 6 እነዚህን እነርሱ የተጨነቁባቸውን ነገሮች በሰማሁ ጊዜ በጣም ተቆጣሁ። 7 ስለዚህም ማድረግ ያለብኝን ነገር አሰብ። ለመሪዎችና ለሹማምንቱ እንዲህ አልኳቸው፣ “ገንዘብ ሲበደሯችሁ የገዛ ዘመዶቻችሁን ወለድ ታስከፍላላችሁ። ይህ ልክ እንዳልሆነ ታውቃላችሁ!” ከዚያም ክስ እንዲያቀርቡባችሁ ብዙ ሰዎችን በእነርሱ ላይ ሰብስቤ ጠራሁ። 8 እንዲህም አልኳቸው፣ “አንዳንድ አይሁዳዊ ወገኖቻችን የአህዛብ ባሪያዎች ለመሆን ራሳቸውን ለመሸጥ ተገደው ነበር። የቻልነውን ያህል፣ መልሰን ገዝተናቸው ነበር። ነገር ግን አሁን እናንተ የገዛ ወገኖቻሁን እንኳን እየሸጣችሁ ነው፤ ይኸውም የገዛ ወገኖቻቸው ወደ ሆኑ አይሁዶች ተመልሰው ይሸጡ ዘንድ ነው!” ይህን ስናገራቸው፣ ምላሽ አልሰጡም። አንዲት ቃል እንኳን አልመለሱም። 9 ከዚያ እንዲህ አልኳቸው፣ “የምታደርጉት ነገር ክፉ ነው። እግዚአብሔርን ልትታዘዙና ትክክል የሆነውን ልታደርጉ አይገባችሁምን? ይህን ብታደርጉ፣ ጠላቶቻችን በንቀት እንዳያዩን ማድረግ ትችላላችሁ። 10 እኔና አይሁዳዊ ወገኖቼ እንዲሁም አገልጋዮቼ ለህዝቡ ገንዘብና እህል አበደርን። ነገር ግን ሁላችንም ከእነዚህ ብድሮች በአንዱም ወለድ መቀበል እናቁም። 11 እንደዚሁም፣ የወሰዳችሁባቸውን የእርሻ መሬቶቻቸውን፣ የወይን ስፍራቸውን፣ የወይራ ዛፍ ቦታቸውን እንዲሁም ቤቶቻቸውን ልትመልሱላቸው ይገባል። እንደዚሁም ገንዘብ፣ እህል፣ ወይን፣ እና የወይራ ዘይት ሲበደሯችሁ ያስከፈላችኋቸውን ወለዶች ልትመልሱላቸው ይገባል። ይህን ዛሬውን ልታደርጉ ይገባል!” 12 መሪዎች እንዲህ ሲሉ መለሱ፣ “ያልከንን እናደርጋለን። እንዲሰጡን ያስገደድናቸውን ነገር ሁሉ እንመልስላቸዋለን፣ ደግም ሌላ ተጨማሪ ነገር እንዲሰጡን አንጠይቅም።” ከዚያ ካህናቱን ሰበሰብኩ፣ እናም ቃል የገቡትን እንዲያደርጉት አስማልኳቸው። 13 የክህነት ልብሴን እጥፋት አራገፌ እንዲህ አልኳቸው፣ “ልታደርጉት አሁን ቃል የገባችሁትን ባታደርጉ፣ እኔ ልብሴን እንዳራገፍኩ እግዚአብሔር ያራግፋችኋል።” እነርሱም “አሜን እንዳልከው ይሁን!” ሲሉ መለሱ፤ ደግሞም ያህዌን አወደሱ። ከዚያ ለማድረግ ቃል የገቡትን አደረጉ። 14 አርጤክስስ የፋርስ ንጉስ በነበረበት በሀያኛው ዓመት የይሁዳ ገዥ ሆኜ ተሹሜ ነበር። ከዚያን ጊዜ አንስቶ እስከ ሰላሳ ሁለተኛው የንግስናው አመት ድረስ እኔም ሆንኩ የእኔ ሹማምንት ገዥ በመሆኔ ለቀለብ የተፈቀደልኝን ገንዘብ አልተቀበልንም። 15 ከእኔ አስቀድሞ ገዥ የነበሩ ሰዎች በየቀኑ አርባ የብር ሳንቲሞች ለምግብና ለወይን በመጠየቅ በህዝቡ ላይ ሸክም አክብደውበት ነበር። አገልጋዮቻቸው ጭምር ህዝቡን ይጨቁኑ ነበር። እኔ ግን ያን አላደረግኩም፣ ምክንያቱም ለእግዚአብሔር ክብር መስጠት እፈልግ ነበር። 16 በዚህ ቅጥር ላይ መስራቴንም ቀጠልኩ፣ እኛም ከህዝቡ ምንም መሬት አልገዛንም። ለእኔ የሚሰሩት ሁሉ በቅጥሩ ስራ ተባበሩን። 17 እንዲሁም፣ በየዕለቱ ከገበታችን አይሁዶችንና ሹማምንቱን፣ አንድ መቶ ሀምሳ ሰዎችን፣ እና በዙሪያችን ካሉ አገሮች የመጡ ጎብኚዎችን እንመግብ ነበር። 18 በየቀኑ አገልጋዮቼ አንድ በሬ፣ ስድስት ሙክቶች እና የዶሮዎች ስጋ እንዲያቀርቡ አደርግ ነበር። በየአስሩ ቀን ብዙ የሆነ አዲስ ወይን ጠጅ አቀርብላቸው ነበር። ነገር ግን ህዝቡ እጅግ ብዙ ግብር በመክፈል ጫና እንደሚበዛበት አውቅ ነበር፣ ስለዚህም እንደ አገረ ገዥ የተፈቀደልኝን ገንዘብ እንኳን አልቀበልም ነበር። 19 አምላኬ፣ አስበኝ፣ እናም ለዚህ ህዝብ ላደረግኩት ሽልማት ስጠኝ።

Nehemiah 5:1

ከዚያም ሕዝቡና ሚስቶቻቸው በአይሁድ ወንድሞቻቸው ላይ ታላቅን ጩኸት አሰሙ
እነርሱ ቅጥሩን በማደስ ላይ ስለነበሩ ሰራተኞቹ ስራ ለመስራት፣ ለመግዛትና ለማረስ ለቤተሰባቸው የሚያስፈልግ ምርት ለማቅረብ በቂ ጊዜ አልነበራቸውም። የዚህ ዓርፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም ጥርት ባለ መልኩ መጻፍ ይቻላል። (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሕዝቡና ሚስቶቻቸው
ይህ የሚያመለክተው ቅጥሩን በማደስ ላይ ተሰማርተው የነበሩትን ወንዶች ነው።

ታላቅ ጩኸት አሰሙ
“ጩኸት” የሚለው ቃል እንደ ግስ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በታላቅ ድምጽ ጮኹ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እርሻችንን አስይዘናል
“እንደ ማስያዣ እርሻችንን ሰጥተናል” ወይም “እርሻችንን በማስያዣ እንድንሰጥ ሆነናል”

Nehemiah 5:4

አሁንም ስጋችንና ደማችን እንደወንድሞቻችን ስጋና ደም ነው፣ ልጆቻችንም እንደ ልጆቻቸው ናቸው
እዚህ ስፍራ አይሁዳውያኑ ከሌሎች አይሁዳውያን ጋር በዘር አንድ እንደሆኑና እንደሌሎቹ አይሁዳውያን እነርሱም እንደሚጠቅሙ ይናገራሉ። የዚህ ትርጉም በግልጽ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የኛ ቤተሰቦችም እንደሌሎች አይሁዳውያን ቤተሰቦች አይሁዳውያን ናቸው፣ የእነርሱ ልጆች ለእነርሱ እንደሚጠቅሙ ሁሉ የኛም ልጆች ለእኛ በጣም ጠቃሚ ናቸው” (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ስጋና ደማችን
ይህ እነርሱ የቤተሰብ አባላትን የሚያመለክት ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ቤተሰባችን” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ከሴቶች ልጆቻችንም የተወሰኑት በባርነት እየኖሩ ያሉ አሉ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከሴት ልጆቻችን ውስጥ አንዳንዶችን ለባርነት ሸጠናቸዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን ሌሎች የኛን እርሻና የወይን ማሳ ይዘዋልና እነሱን ማዳን ከአቅማችን በላይ ነበር
የሰዎቹ እርሻና የወይን ማሳ በማስያዣ ተይዞ የእነርሱ ሰላልነበረ ምርት አምርተውና ገንዘብን አግኝተው ቤተሰባቸውን መደገፍ አይችሉም ነበር። የዚህ ሙሉ ትርጉም በግልጽ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን ይህንን ሁኔታ መቀየር አልቻልንም፣ ምክንያቱም ሕይወታችንን መምራት የምንችልበት እርሻችንና የወይን ማሳችን አሁን ሌሎች ሰዎች በንብረትነት ይዘውታል” (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከአቅማችን በላይ ነው
ይህ የሚያሳየው አንድን ነገር ለማድረግ ተገቢው ግብአት እንደሌላቸው ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እኛ ማድረግ አልቻልንም” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Nehemiah 5:6

ጩኸታቸውን በሰማሁ ጊዜ
“ጩኸት” የሚለው ቃል በግስ መልክ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሲጮኹ በሰማሁ ጊዜ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እያንዳንዳችሁ ከወንድማችሁ ላይ ወለድ ትወስዳላቸሁ
አንድ አይሁዳዊ ለሌላ አይሁዳዊ በወለድ ማበደር እንደማይችል እያንዳንዱ አይሁዳዊ ሊያውቀው የሚገባ ነገር ነበር። የዚህ ትርጉም በግልጽ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እያንዳንዳችሁ ከወንድሞቻችሁ ወለድ ትወስዳላችሁ፣ እርሱ ደግሞ በሕጉ መሰረት ትክክል አይደለም” (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ትልቅ ጉባኤ ሰበሰብሁባቸው
ይህ ማለት ብዙ ቁጥር ያላቸው ሰዎችን ሰብስቦ እነዚህን ክሶች በእነርሱ ላይ አቀረበ ማለት ነው። የዚህ ትርጉም በግልጽ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ትልቅ ጉባዔ ሰብስቤ በእነርሱ ላይ እነዚህን ክሶች ተናገርኩባቸው” ወይም “በጉባዔ ፊት ከሰስኳቸው” (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ ግን የገዛ ወንድሞቻችሁንና እህቶቻችሁን ሸጣችሁ እነርሱ ደግመው ለእኛ እንዲሸጡልን አደረጋችሁ
ይህ ማለት እነርሱ የቤተሰብ አባሎቻቸውን ባርያ እንዲሆኑ ለሌሎች አይሁዶች እየሸጧቸው ነበር ማለት ነው። የዚህ ትርጉም በግልጽ ሊቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የራሳችሁን ሰዎች ወገኖቻችሁ ለሆኑት ለአይሁዳውያን ባርያ እንዲሆኑና መልሰውም ለእኛ እንዲሸጡልን ሸጣችኋቸው” (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለአሕዛብ የተሸጡትን
ይህ በገቢር/አድርጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ባርያ እንዲሆኑ ሰዎች ለአሕዛብ የሸጧቸውን” (ገቢር/አድርጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 5:9

እኔ ደግሞ አልኩ
“እኔ” የሚለው ቃል የሚወክለው ነህምያን ነው።

እናንተ እያደረጋችሁ ያላችሁት
“እናንተ” የሚለው ቃል የሚወክለው የአይሁድ አለቆችን ነው።

ጠላቶቻችን የሆኑትን የአሕዛብን ስድብ ለመከላከል እግዚአብሔር አምላካችንን በመፍራት ልትመላለሱ አይገባም?
ይህ ነህምያ አለቆቹን ለመገሰጽ የተጠቀመበት መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ ነው። በዓርፍተ ነገር መልክ መተርጎም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላቶቻችን አሕዛብ እንዳይሰድቡን እግዚአብሔርን በመፍራት መመላለስ አለባችሁ” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

አምላካችን እግዚአብሔርን በመፍራት ተመላለሱ
ይህ ፈሊጥ ነው። እዚህ ላይ “ተመላለሱ” የሚያመለክተው ስለ ሰው ባሕርይ እና የአኗኗር ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሕይወታችሁን እግዚብሔርን በሚያከብር መንገድ ኑሩ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

የጠላቶቻችን የአህዛብ ስድብ
“ስድብ” የሚለው ቃል “ስላቅ” እና “ሹፈት” ማለት ነው፣ በግስ መልክም መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላቶቻችን ከሆኑት ከአህዛብ ስድብ” ወይም “የጠላቶቻችን የአህዛብ ስድብ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ማበደር
ማዋስ ወይም ተመልሶ እንዲሰጠን በመጠበቅ ለአንድ ሰው አንድ ነገር መስጠት

ብድሮች
ይህ አንድ ሰው ካለበት ብድር እንዲወጣ ወይም ብድሩን እንዲከፍል ከሌላ ሰው የሚዋሰው ብር፣ ምግብ ወይም ቁሳቁስ ነው። ስለዚህም ተበዳሪው የአበዳሪው ባለእዳ ይሆናል ማለት ነው።

ከመቶ እጅ
ተበዳሪው ወለድ የሚጠየቅበት የብድሩ መጠን የተወሰነ ክፍል ነው።

ከእነርሱ ወሰዳችሁ
“አስከፈለችኋቸው” ወይም “እንዲከፍሉ አደረጋችኋቸው”

Nehemiah 5:12

ከዚያም እነርሱ ...
እዚህ ላይ “እነርሱ” የሚለው ቃል የሚወክለው የአይሁድ አለቆችን ነው።

ከእነርሱ የወሰድነውን እንመልስላቸዋለን
የአይሁድ አለቆች ድሃ የሆኑ ሌሎች አይሁዶች በወለድ የከፍሏቸውን ገንዘብ እንመልስላቸዋለን እያሉ ነው።

አማልኋቸው
“አማልኋቸው” በሚለው ቃል ውስጥ ያለው የድርጊት ተቀባይ አመልካች የሚወክለው የአይሁድ አለቆችን ነው።

ከዚያም ጠርቼ
“ጠርቼ” በሚለው ቃል ውስጥ ያለው የባለቤት አመልካች የሚወክለው ነህምያን ነው።

የልብሴን ዘርፍ አራግፌ
“የልብሴን ኪሶች አራገፍኩ።” ብዙ ጊዜ በብሉይ ኪዳን ዘመን መኃላዎች በሚፈጸሙበት ጊዜ ቃል ለተገበው ነገር እንደ ምስክር እንዲሆን በአንዳድ አካላዊ እንቅስቃሴ ወይም ድርጊቶች ይገለጻሉ። ነህምያ የአይሁድ አለቆች የገቡትን ቃል ባይፈጽሙ የሚደርስበቸውን ነገር ልብሱን በማራገፍ አሳያቸው። (ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ቤቱን ያራገፈው ... ይርገፍ ባዶም ይሁን
እዚህ ላይ ነህምያ ልብሱን እንዳራገፈው ሁሉ እግዚአብሔር መሃላውን ያልፈጸመውን ሰው እግዚአብሔር ከቤቱ እንዲያራግፈውና ሃብቱን በሙሉ እንዲወስድበት ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ በልብሴ ኪስ ውስጥ የነበረውን ማንኛውንም ነገር እንዳረገፍሁ እንደዚሁ መሃላውን ከማይጠብቀው ከእያንዳንዱ ሰው እግዚአብሔር ንብረቱንና ቤቱን በሙሉ ይውሰድበት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 5:14

ከተሾምኩ ጀምሮ
እዚህ ላይ “ከተሾምኩ” የሚለው ቃል ላይ ያለው የባለቤት አመላካች የሚወክለው ነህምያን ነው።

ከሃያኛው አመት እስከ ሰላሳ ሁለተኛው አመት
“ከ20ኛው ዓመት እስከ 32ኛው ዓመት” (ደረጃ የሚያሳዩ ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሱ አርጤክስስ
“አርጤክስስ ንጉስ በሆነበት”

አስራ ሁለት ዓመታት
“12 ዓመታት” ወይም “በአስራ ሁለት አመታት ውስጥ።” ነህምያ የዓመታቱን ቁጥር ደጋግሞ የሚናገረው እርሱ ገዢ በነበረበት ጊዜ በሙሉ ያለማቋረጥ የሰራውን ስራ አጽንዖት ለመስጠት ነው። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለአለቃ የሚገባውን ምግብ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሕዝቡ ለአለቃ የሚያቀርበውን ምግብ በላ”

ለየዕለታቸው
“በየቀኑ ለሚያስፈልጋቸው”

የቀድሞ ገዢዎች
“የቀድሞ ገዢዎች” ወይም “ቀድሞ ይገዙ የነበሩ ገዢዎች።” ነህምያ የይሁዳ የመጀመርያ ገዢ አልነበረም።

አርባ ሰቅል
“40 ሰቅል” ወይም “40 የብር ሳንቲሞች” (ቁጥሮችና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መገበያያ ገንዘቦች የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ግን እግዚአብሔርን ስለፈራሁ አላደረግኩም
“እኔ ግን እግዚአብሔርን ስለምፈራ ምግቡን አለወሰድኩም” ወይም “እኔ ግን እግዚአብሔርን ስለፈራሁ ምግቡን አልወሰድኩም”

Nehemiah 5:16

እኔም ቀጠልኩኝ
“እኔ” የሚለው የሚያመለክተው ነህምያን ነው።

አልገዛንም
“አልገዛንም” የሚለው ቃል ውስጥ የባለቤት አመልካቹ የሚወክለው ነህምያና ሰራተኞቹን ነው።

ሰራተኞቼም ወደ ስራው ተሰበሰቡ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰራተኞቼን በሙሉ ወደዚያ ሰበሰብኳቸው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ለስራው
“ቅጥሩን ለመገንባት”

150 ሰዎች
“አንድ መቶ አምሳ ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በገበታዬ አይሁዶች ነበሩ ... በዙሪያችን ከነበሩ ከአሕዛብ መካልም ነበሩ
ነህምያ ለእነዚህ ሰዎች በሙሉ ምግብ የማቅረብ ኃላፊነት ነበረበት። ይህ በግልጽ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ከዚህ በተጨማሪ በየቀኑ ከገበታችን 150 ሰዎች ከአይሁድና ከሹማምንት የመመገብ ኃላፊነት ነበረብኝ፤ እንዲሁም በዙሪያችን ካሉ አሕዛብ ሃገሮች የመጡ እንግዶችን እንግብ ነበር” (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ገበታዬ
ይህ የገዢውን ገበታ ያመለክታል። ይህም ለማህበረሰቡና በተለያዩ ሃሳቦች ዙሪያ ለመወያየትም የሚጠቅም ገበታ ነበር።

ሹማምንት
የመንግስት መሪዎች

Nehemiah 5:18

በየቀኑም ... ይዘጋጅ ነበር
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በየቀኑም ሰራተኞቼን ... እንዲያዘጋጁ እነግራቸው ነበር” ወይም “በየቀኑ ለሰራተኞቼ ... ከመዓዱ እንዲያስተናግዱን እነግራቸው ነበር” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ስድስት የተመረጡ ... አስር ቀናት
“6 የተመረጡ ... 10 ቀናት” (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ብዙ ወይን
“ለሁሉም ሰው የሚበቃ ወይን”

ቢሆንም ግን ለአለቃ የሚገባውን የምግብ አበል አልሻም ነበር
“ቢሆንም ግን ለአለቃ የሚሰጠውን የምግብ አበል ፈጽሞ አልጠየቅሁም”

አስበኝ
ይህ ፈሊጥ ነው። ይህ እግዚአብሔር እንዲያስበውና እንዲያስታውሰው የቀረበ ልመና ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “አስታውሰኝ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ለመልካም
ይህ ፈሊጥ ነህምያ ለሕዝቡ ስላደረገው መልካም ነገር በሙሉ እግዚአብሔር ዋጋ እንዲሰጠው የሚለምንበት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ዋጋዬን ስጠኝ” ወይም “መልካም ነገሮችን እንዲሆኑልኝ አድርግ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 6

1 ምንም እንኳን እስከ አሁን በሮቹን በመግቢያዎቹ ላይ ገና ባንገጥምም፣ የቅጥሩን ሥራ መጨረሳችንንና ያልተጠገነ የፈረሰ ስፍራ አለመኖሩን ሰንበላጥ፣ ጦቢያ፣ ጌሳምና ሌሎች ጠላቶቻችን ሰሙ። **2** ስለዚህ ሰንበላጥና ጌሳም እንዲህ የሚል መልዕክት ወደ እኔ ላኩ፣ “ከኢየሩሳሌም በስተሰሜን በሚገኘው ኦኖ በሚባለው ሜዳ መጥተህ እንነጋገር።” ነገር ግን ይህን ያሉት እኔን ለመጉዳት አስበው እንደነበር ግልጽ ነው። **3** ስለዚህም እንዲህ ብለው እንዲነግሯቸው መልዕክተኞችን ላክሁ፣ “ከፍ ያለ ስራ እየሰራሁ ነው፣ እናም ወደዚያ ልሄድ አልችልም። እኔ ከእናንተ ጋር ለመነጋገር ወደዚያ በመሄድ ይህ ስራ መስተጓጎል አይኖርበትም። **4** እነርሱ ይህንኑ መልዕክት አራት ጊዜ ወደ እኔ ላኩ፣ እኔም በእያንዳንዱ ወቅት ተመሳሳይ መልስ ሰጠኋቸው። **5** ከዚያም ሰንበላጥ አምስተኛውን መልዕክት አስይዞ አንዱን አገልጋዩን ወደ እኔ ላከ። ይህኛው መልዕክት በጽሁፍ ነበር፣ በእርግጥ ማህተም ያልተደረገበትና ያልታሸገ ደብዳቤ ነበር። **6** በመልዕክቱ የተጻፈው ይህ ነበር፡ “በባቢሎን ንጉስ ላይ አመጽ ለማስነሳትና አንተም የእስራኤል ንጉስ ለመሆን አቅደህ አንተና ሌሎች አይሁዶች ቅጥሩን እንደገና እየገነባችሁ እንደሆነ በአቅራቢያ ባሉ አገሮች ያሉ አንዳንድ ሰዎች ወሬ ሰምተዋል። እውነቱ ይህ መሆኑን ጌሳም ነግሮናል። **7** ደግሞም ሰዎች፣ አንተ ነህምያ፣ አሁን የአይሁድ ንጉስ መሆንህን እንዲያውጁ ነቢያትን መሾምህን እየተናሩ ነው። ንጉስ አርጤክስስ በእርግጥ ይህን ወሬ መስማቱ አይቀርም፣ ያን ጊዜ ትልቅ ችግር ላይ ትወድቃለህ። ስለዚህ ተገናኝተን በዚህ ጉዳይ ላይ መነጋገር እንደሚኖርብን አሳስባለሁ።” **8** ያን መልዕክት ካነበብኩ በኋላ መልዕክተኛው ወደ ሰንበላጥ ይህን መልዕክት መልሶ እንዲያደርስ ላክሁ፣ “ከምትናገረው ውስጥ አንዱም እውነት አይደለም። ይህን የምትለው ከገዛ ልብህ ፈጥረህ ነው።” **9** ይህንን የምለው እነርሱ እኛን ለማስፈራራት እየሞከሩ እንደነበር ስለማወቅ ነው፣ ስለዚህም እንዲህ ብለው ያስባሉ፣ “ከዚህ በኋላ ቅጥሩን ለመስራት ፍጹም ተስፋ ይቆርጣሉ፣ ስራውም በፍጹም ከፍጻሜ አይደርስም።” ስለዚህም እኔ፣ “አምላኬ ሆይ፣ ብርታትን ስጠኝ።” ስል ጸለይኩ። **10** አንድ ዕለት የመሔጣብኤል የልጅ ልጅ፣ የድልያ ልጅ፣ ከሆነው ከሸማያ ጋር ለመነጋገር ሄድኩ። ከእርሱ ጋር ለመነጋገር ወደ ቤቱ ሄድኩ። ከቤቱ እንዳይወጣ ትዕዛዝ ተሰጥቶት ነበር። እርሱም እንዲህ አለኝ፣ “አንተና እኔ ከቤተ መቅደሱ ውስጠኛ ክፍሎች ወደ አንዱ መግባትና በሮቹን መቆለፍ አለብን። ዛሬ ምሽት ሊገድሉህ ይመጣሉ።” **11** እኔም እንዲህ ስል መለስኩለት፣ “እኔ እንዲያ ያለ ሰው አይደለሁም! ህይወቴን ለማትረፍ ራሴን ቤተመቅደስ ውስጥ ሸሽቼ ገብቼ አልደብቅም! አይ፣ ያንን አላደርግም!” **12** የተናገረውን አሰላሰልኩ፣ ሸማያ እግዚአብሔር ያላለውን እንደነገረኝ አወቅሁ። ጦቢያ እና ሰንበላጥ ቀጥረውት ነበር። **13** እንዲያስፈራራኝ እነርሱ ቀጥረውት ነበር። እነርሱ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት እንዳልጠብቅ በመቅደስ ውስጥ በመደበቅ እንድበድል ይፈልጉ ነበር። ያንን ባደርግ፣ ስሜን ያጠፉና ከዚያም ያዋርዱኛል። **14** ስለዚህም እንዲህ ስል ጸለይኩ “አምላኬ ሆይ፣ ጦቢያና ሰንበላጥ ያደረጉትን አትርሳ። ነቢይቱ ኖዓድያ እና ሌሎች ነቢያት ሊያስፈራሩን የሞከሩትን አትርሳ።” **15** በኤሉል ወር በወሩ ሃያ አምስተኛው ቀን የቅጥሩን ጥገና አጠናቀቅን። ጠቅላላውን ስራ በሀምሳ ሁለት ቀናት አጠናቀቅን። **16** በአቅራቢያችን በሚገኙ አገሮች የሚኖሩ ጠላቶቻችን ይህንን ሲሰሙ፣ በጣም ፈሩ፣ ዕፍረትም ተሰማቸው ምክንያቱም ይህን ሥራ እንድናጠናቅቅ የረዳን እግዚአብሔር እንደሆነ አውቀው ነበር። **17** በዚህ ጊዜ ውስጥ፣ የአይሁድ መሪዎች ብዙ መልዕክቶችን ወደ ጦቢያ ይልኩ ነበር፣ ጦቢያም መልሶ መልዕክቶችን ወደ እነርሱ ይልክ ነበር። **18** በይሁዳ ያሉ ብዙ ሰዎች ታማኝታቸውን በመሀላ ለጦቢያ አረጋግጠውለት ነበር። እርሱም የኤራ ልጅ የሴኬንያ አማት ሲሆን፣ የጦቢያ ወንድ ልጅ የቤሪክያን ልጅ የሆሐና የሚሹ ሀላምን ሴት ልጅ አግብቶ ነበር። **19** ሰዎች ብዙ ጊዜ እኔ ባለሁበት ጦቢያ ስለ ሰራቸው መልካም ስራዎች ይናገሩና፣ ከዚያ እኔ የተናገርኩትን እያንዳንዱን ነገር ይነግሩታል። ስለዚህም ጦቢያ እኔን ለማስፈረራት በርካታ ደብዳቤዎችን ወደ እኔ ይልክልኝ ነበር።

Nehemiah 6:1

ሰንባላጥ፣ ጦብያ እና ጌሳም

እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። እነዚህ በነህምያ 2:9-10 ላይ እንዴት እንደተተረጎሙ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ቅጥሩን ሰራሁ ... አላቆምሁም ነበር

ነህምያ የቅጥሩን ደግሞ መገንባት ይቆጣጠር ነበር ነገር ግን እርሱ ራሱ አልገነባውም። አማራጭ ትርጉም፡- “ቅጥሩን ገነባን ... አላቆምንም ነበር” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ማንኛውንም ክፍል

ይህ የቅጥሩን ክፍሎች ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ማንኛውንም የቅጥሩ ክፍል” ወይም “በከተማው ቅጥር ላይ ማንኛውም ክፍተት” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ላከብኝ

ይህ ማለት ከመልዕክቱ ጋር መልዕክተኛን ላኩ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “መልዕክተኛ ወደ እኔ ላኩ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ኦኖ

ይህ የቦታ ስያሜ ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 6:3

ታላቅ ስራ እየሰራሁ ነው

ነህምያ የቅጥሩን መገንባት ተቆጣጥሮአል። እርሱ ብቻውን አልገነባውም። አማራጭ ትርጉም፡- “ታላቅ ስራ እየሰራን ነው” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ስራውን ትቼ ወደ እናንተ በመውረዴ ስራው ለምን ይቋጣል?

ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ የሰንባላጥን ጥያቄ ለመሞገት የተጠየቀ ነው። ይህ በዓረፍተ ነገር ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስራውን አቋርጬ ወደ እናንተ ልወርድ አልችልም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እናንተ ልወርድ

“ልወርድ” የሚለው ቃል እዚህ ላይ ጥቅም ላይ የዋለው ነህምያን የጠሩበት ቦታ ማለትም የኦኖ ሜዳ ከኢየሩሳሌም ዝቅ ብሎ የሚገኝ ስለሆነ ነው።

Nehemiah 6:5

ሰንባላጥ በተመሳሳይ ሁኔታ ለአምስተኛ ጊዜ መልዕክተኛ ላከብኝ

ይህ መልዕክት ለብቻው መነገሩ ቀድሞ ከነበሩ ከሌሎቹ መልዕክቶች በተወሰነ መልኩ ለየት እንደሚል ለማሳየት ነው፤ ስለዚህ መልዕክቱም ትኩረት ሊደረግበት ይገባል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰንባላጥ መልዕክተኛውን እንደቀደመው እንደገና ወደ እኔ ላከ” ወይም “ሰንባላጥ መልዕክተኛው በመላክ አምስተኛውን መልዕክት ላከብኝ” (ደረጃን የሚያሳዩ ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ክፍት ደብዳቤ
ደብዳቤው ያለታሸገ የዲፕሎማሲያዊ መልዕክት ነበር። ይህ ደግሞ ለተቀባዩ ስድብ ነው ምክንያቱም መልዕክቱን ይዞ የሚንቀሳቀሰው ሰው በቀላሉ ሊያነበውና በአካባቢው ላለው ሕዝብ የደብዳቤውን ይዞታ ማካፈል ስለሚችል ነው።

በእጁ ውስጥ
ይህ ማለት ደብዳቤው ከእርሱ ጋር ነበር ነገር ግን ሁልጊዜ በእጁ ይዞት ይንቀሳቀሳል ማለት አይደለም። አማራጭ ትርጉም፡- “ከእርሱ ጋር ነበር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በአህዛብ ዘንድ ተሰምቷል
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የዚህ ወሬ ጭምጭምታ በአካባቢው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ልታምጹ ማሰባችሁን
ይህ በጊዜው አይሁዳውያንን ይገዛ የነበረው የፋርስ ንጉስ አርጤክስስ ላይ አመጽ ያስባሉ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በአርጤክስስ ላይ አመጽን ልታስነሱ ማሰባችሁን …” (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 6:7

ንጉሱ ይሰማል
“ንጉስ አርጤክስስ ይሰማል”

ስለዚህ ና
“ስለዚህም ና እንገናኝ”

Nehemiah 6:8

ከዚያ እኔ ለእርሱ መልእክት ላክሁበት
እዚህ ላይ “እኔ” የሚለው የሚወክለው ነህምያን ሲሆን “እርሱ” የሚለው ደግሞ ደግሞ ሰንባላጥን ነው።

ካልካቸው ነገሮች አንተ እንዳልከው ምንም አልተከሰተም
“ከጻፍካቸው ነገሮች አንዱም አልተከሰተም”

አንተ በልብህ ውስጥ ፈጥረሃቸዋልና
እዚህ ላይ “ልብ” የሚያመለክተው “አእምሮ”ን ነው፣ አእምሮም የአንድ ሰው ፍላጎትና አሳብ ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ በአእምሮህ ውስጥ ፈጥረሃቸዋልና” ወይም “አንተ በራስህ ሃሳብ ውስጥ ፈጥረሃቸዋልና” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ እኛን ሊያስፈራሩን ፈልገዋልና
እዚህ ላይ “እነርሱ” የሚለው የነህምያ ጠላቶች የነበሩትን ሰንባላጥ፣ ጦብያ ጌሳምና የእነርሱን ተከታዮች የሚያመለክት ነው። “እኛ” የሚለው ደግሞ አይሁዳውያንን ያመለክታል።

እጃቸውን ስራውን ከመስራት ያነሳሉ
ይህ ቅጥሩን የመገንባት ስራቸውን ያቆማሉ የሚለውን ሃሳሳ ገላጭ ሐረግ ነው። አማራጭ ትርጉም “በቅጥሩ ላይ የተሰማሩት ሰራተኞች ቅጥሩን መገንባት ያቆማሉ” (ግምታዊ እውቀት እና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እጆቼን አጠንክር
እዚህ ላይ ነህምያ “እጆቹን” እንዲያጠነክር በመጠየቅ እርሱን እንዲየጠነክረው እግዚአብሔርን ይለምናል። አማራጭ ትርጉም፡- “አበርታኝ” ወይም “ድፍረት ስጠኝ” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 6:10

ሸማያ … ድላያ … መሔጣብኤል
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

በቤቱ ውስጥ ተዘግቶ ተቀምጦ የነበረው
በቤት ውስጥ ተዘግቶ ለመቀመጡ ጸሃፊው ምክንያት አያቀርብም፣ ስለዚህ ጠቅላላ ቃላትን በመጠቀም ሰውየው በቤት ውስጥ ተቀምጦ ነበር ማለት ይሻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ቤቱን ለቅቆ መውጣት የማይችለው” ወይም “በአለቆች ከቤት እንዳይወጣ የታዘዘው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደኔ ዓይነት ሰው ይሸሻል? እንደኔ ዓይነት ሰው ነፍሱን ለማዳን ወደ መቅደስ ይገባል?
ነህምያ እነዚህን መልስ የማይሰጥባቸውን ጥያቄዎች የተጠቀመው ሸማያ ያቀረበለትን ሃሳብ እንደማያደርገው አስረግጦ ለመናገር ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እንደኔ ዓይነት ሰው አይሸሽም። እንደኔ ዓይነት ሰው ነፍሱን ለማትረፍ ብሎ መቅደስ አይገባም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 6:12

እርሱ ግን በእኔ ላይ ትንቢት ተናገረ
“እኔን ለመቃወም ትንቢት ተናገረ”

እበድል ዘንድ
ቤተ መቅደስን እንደ መሸሸጊያ ቦታ መጠቀም በደል ነበር። ይህንን ግልጽ ማድረግ ጠቃሚ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “መቅደስን በማይገባ መንገድ በመጠቀም እበድል ዘንድ”

መጥፎ ስም
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ ለእኔ መጥፎ ስም መስጠት እንዲችሉ” ወይም “ስለ እኔ መጥፎ የሆነ ነገር እንዲናገሩ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

አስብ
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አስታውስ”

ኖዓድያ
ይህ የሴት ስም ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 6:15

ቅጥሩም … ተጨረሰ
ይህንን በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ቅጥሩን ገንብተን ጨረስን” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በኤሉል ወር በሃያ አምስተኛው ቀን
“በኤሉል ወር በ25ኛው ቀን።” ኤሉል በዕብራይስጥ የቀን መቁጠርያ ስድስተኛው ወር ነው። (የዕብራይስጥ ወራት እና ደረጃ የሚያሳዩ ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

አምሳ ሁለት ቀን
“52 ቀናት” (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በራሳቸው ዓይን ወርደው ታዩ
“ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ማየት ጀመሩ” ወይም “በራሳቸው መተማመን አልቻሉም”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ስራው በእግዚአብሔር እርዳታ እንደተሰራ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ይህን ስራ እንድንጨርስ የረዳን እግዚአብሔር ነው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከተው)

Nehemiah 6:17

ብዙ ደብዳቤዎች ይልኩ ነበር
አለቆቹ ደብዳቤዎችን ወደ ጦብያ እንዲያደርሱ መልዕክተኞችን ልከው ነበር። አማራጭ ትርጉም፦ “ብዙ መልዕክተኞችን ከደብዳቤዎች ጋር ላኩ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የጦብያ ደብዳቤዎችም ይመጡ ነበር
እዚህ ላይ የጦብያ ደብዳቤዎች በመልእክተኞች በኩል መጥተው ሳለ በራሳቸው እንደመጡ ተደርጎ ተጽፏል። አማራጭ ትርጉም፦ “ጦብያ ደብዳቤዎችን ላከ” ወይም “ጦብያ ደብዳቤ የያዙ ብዙ መልዕክተኞችን ላከ” (ሰውኛ የሚለውን ይመልከቱ)

ጦብያ
ይህ በነህምያ 2፡10 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ከእርሱ ጋር በመኃላ ተሳስረው የነበሩ
ይህ የሚናገረው ለጦብያ ታማኝ ስለነበሩ ሰዎች ነው ምክንያቱም ከእርሱ ጋር መኃላ ገብተው ነበር፤ መኃላቸው ደግሞ ሰውነታቸውን አጥብቆ እንዳሰረ ገመድ ተደርጎ የሚቆጠር ነበር። አማራጭ ትርጉም፦ “ከእርሱ ጋር በቃልኪዳን ተማምለው ነበር” ወይም “ከእርሱ ጋር ቃልኪዳን አድርገው ታማኝ ሆነውለት ነበር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሴኬንያ አማት ነበር
ይህ ማለት ጦብያ ከሴኬንያ ሴት ልጅ ጋር ተጋብቶ ነበር ማለት ነው። “ሴኬንያ” በነህምያ 3፡29 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ኤራ ... ይሆሐናን
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ሜሱላም ... በራክያ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ እርሱ መልካም ነገሮችን ለእኔ ያወሩ ነበር የኔንም የምለውንም ተከታትለው ይነግሩት ነበር
“የአይሁድ አለቆች ስለ ጦብያ መልካም ስራዎች ለእኔ ይነግሩኝ ነበር እኔ የነበረኝን ምላሽም ለእርሱ ይነግሩት ነበር።”

ከጦብያም ደብዳቤዎች ይላኩልኝ ነበር
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል። ጦብያ ደብዳቤዎችን ወደ ነህምያ እንዲያደርሱ መልዕክተኞችን ይልክ ነበር። አማራጭ ትርጉም፦ “ጦብያ ደብዳቤዎችን ወደ እኔ ይልክ ነበር” ወይም “ጦብያ ደብዳቤዎችን ወደ እኔ እንዲያደርሱ መልዕክተኞችን ይልክ ነበር” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 7

1 ቅጥሩ ተሰርቶ ከተጠናቀቀና በሮቹም በስፍራቸው ከቆሙ በኋላ፣ የቤተ መቅደሱ ጠባቂዎችና የዝማሬ አባላቱ እንዲሁም የተቀሩት የሌዊ ትውልዶች በየስራ መደባቸው ተመደቡ። **2** ወንድሜን አናኒን የኢየሩሳሌም ገዥ አድርጌ ሾምኩት። እርሱ ከብዙ ሌሎች ሰዎች ይልቅ ታማኝና እግዚአብሔርን የሚፈራና የሚያከብር ሰው ነበር። በተጨማሪም ሐናንያ በኢየሩሳሌም ለሚገኘው የከተማይ ግንብ አዛዥ ሆኖ ተሾሙ። **3** እነርሱን እንዲህ አልኳቸው፣ “ፀሀይ ሞቅ እስክትል የኢየሩሳሌምን መግቢያ በሮች አትክፈቱ። በሮችን የምትቆልፉትና የበሮችን መቀርቀሪያዎች የምትዘጉት በር ጠባቂዎች መግቢያዎችን እየጠበቁ ሳለ ነው።” አንዳንድ በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎችን ዘቦችና በከተማዋ ዙሪያ ያሉ ማረፊያዎችን ጠባቂዎች እንዲያደረጓቸው፤ እንዲሁም አንዳንዶችን ከራሳቸው ቤቶች አቅራቢያ ጠባቂ እንዲያደረጓቸው ነገርኳቸው። **4** የኢየሩሳሌም ከተማ ሰፊ ናት፣ ነገር ግን በዚያን ጊዜ በከተማዋ ብዙ ህዝብ አይኖርም ነበር፣ እንዲሁም ከቤቶቹ አንዱንም እንደገና አልገነቡም ነበር። **5** እግዚአብሔር መሪዎችንና ሹማምንቱን እንዲሁም ሌሎች ሰዎችን እንድሰበስብ እና በየቤተሰባቸው መዛግብት እንድጽፍ አሳብ በልቤ አኖረ። እንደዚሁም ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱትን የመጀመሪያዎቹን ተመላሾች ዝርዝር አገኘሁ። በእዚያ መዛግብት ተጽፎ ያገኘሁት ይህንን ነው። **6** ”ወደ ኢየሩሳሌምና ወደ ይሁዳ ሌሎች ስፍራዎች የተመለሱ ሰዎች ዝርዝር ይህ ነው። እነርሱ ባቢሎን ውስጥ ይኖሩ ነበር። ናቡከደነጾር ወደዚያ ወስዷቸው ነበር። እነርሱ ወደ ኢየሩሳሌምና ይሁዳ ተመለሱ። እያንዳንዱ ተመላሽ አባት ከልደት በፊት ይኖርበት ወደነበረበት ወደ ራሱ ከተማ ተመልሶ ሄደ። **7** እነርሱ ከዘሩባቤል፣ ከኢያሱ፣ ከነህምያ፣ ከአዛርያስ፣ ከረዓምያ፣ ከነሐማኒ፣ ከመርዶክዮስ፣ ከላሶን፣ ከሚስጴሬት፣ ከጉዋይ፣ ከነሑም፣ እና ከባና ጋር ተመልሰው መጡ። ከህዝቡ የተመለሱት የወንዶች ቁጥር ዝርዝር እንደሚከተለው ነበር: **8** ከፋሮስ ትውልዶች 2172 **9** ከሰፋጥያስ ትውልዶች 372 **10** ከኤራ ትውልዶች፣ 652 **11** ሞዓብ ትውልዶች፣ የኢያሱና ኢዮብአብ ትውልዶች 2818 **12** ከኤላም ትውልዶች 1254፣ **13** ከዛቱዕ ትውልዶች፣ 845፣ **14** ከዘካይ ትውልዶች፣ 845፣ **15** ትውልዶች፣ 648፣ **16** ከቤባይ ትውልዶች፣ 628፣ **17** ከዓዝጋድ ትውልዶች፣ 2322፣ **18** ከአዶኒቃም ትውልዶች፣ 667፣ **19** ከበጉዋይ ትውልዶች፣ 2067፣ **20** ከዓዲን ትውልዶች፣ 655፣ **21** ከአጤር ትውልዶች ሌላ ስማቸው ሕዝቅያስ ከሚባለው፣ 98፣ **22** ከሐሱም ትውልዶች፣ 328 **23** ከቤሳይ ትውልዶች፣ 324፣ **24** ከሐሪፍ ትውልዶች፣ ሌላ ስማቸው ጆራህ ከሚባለው፣ 112 **25** ከገባዖን ትውልዶች 95 **26** አባቶቻቸው በእነዚህ ከተሞች የኖሩ ወንዶችም ደግሞ ተመለሱ ከቤተልሔምና ከነጦፋ የመጡ ወንዶች፣ 188። **27** ከዓናቶት የመጡ ወንዶች፣ 128 ነበሩ **28** ከቤት አዛምት የመጡ ወንዶች 42፣ **29** ከቂርያት ይዓሪም ከከፈሪና ከብኤሮት 743 ወንዶች **30** ኮራማና ከጌባ 621 ወንዶች **31** 122 ወንዶች ነበሩ **32** ከቤቴልና ከጋይ፣ 123 ወንዶች **33** ከናባው፣ 52 ወንዶች **34** ከኤላም፣ 1254 ወንዶች **35** ከካሪም 320 ወንዶች ነበሩ **36** ከኢያሪኮ፣ 345 ወንዶች **37** ከሎድ፣ ሐዲድና አኖ 721 ወንዶች ነበሩ እነዚህ ካህናትም ደግሞ ተመልሰዋል **38** ከሴናዓ ትውልድ 3930 ነበሩ **39** የኢያሱ ቤተሰብ የሆኑ፣ የዮዳኤ ትውልዶች፣ 973 **40** ከኢሜር ትውልዶች 1052፣ **41** ከፋስኮር ትውልዶች፣ 1247፣ **42** ከካሪም ትውልዶች፣ 1017 **43** ከሌዋውያን ትውልዶች የተመለሱት እነዚህ ነበሩ፣ የኢያሱ፣ ቀደምኤል፣ ቤትኢ እና የሆዳይዋ ትውልዶች 74 ናቸው **44** ከመዘምራኑ ትውልዶች የተመለሱት እነዚህ ነበሩ ከኤሳፍ ትውልድ 148 **45** እንዲሁም ከሰሎም፣ አጤር፣ ጤልሞን፣ ዓቁብ፣ ሐጢጣ፣ እና ሶባይ ትውልዶች የተመለሱ 138 የቤተ መቅደሱ በር ጠባቂዎች ናቸው። **46** የተመለሱት የቤተ መቅደሱ ሰራተኞች የእነዚህ ሰዎች ትውልዶች ነበሩ የሲሐ፣ ሐሡፋ፣ ጠብዖት **47** የኬረስ፣ ሲዓዓ ሩዶን **48** የልባና አጉባ፣ ሰሞላይ **49** የሐናን ጌዱል፣ ጋሐር፣ **50** ራያ፣ ራአሰን፣ ኔቆዳ **51** ጋሴም፣ አዛ፣ ፋሴሐ **52** ቤሳይ፣ ምዑኒም፣ ንፉሰሊም፣ እነዚህ ንፉሰሲም ተብለውም ይጠራሉ **53** በቅቡቅ፣ ሐቀፋ፣ ሐርሑር፣ **54** በሰሎት፣ እነዚህ በሰሉት ተብለውም ይጠራሉ ምሒዳ፣ ሐርሻ **55** ቦርቆስ፣ ሲሣራ፣ ቴማ **56** ንስያ፣ ሐጢፋ **57** ከንጉስ ዳዊት አገልጋዮች ትውልዶች የተመለሱት እነዚህ ነበሩ፣ ሶጣይ፣ ሶፌሬት፣ ፍሩዳ **58** የዕላ፣ ደርቆን፣ ጊዴል **59** ሰፋጥያስ፣ ሐጢል፣ ፈከራት፣ ሐፂቦይምና አሞን **60** በአጠቃላይ፣ 392 የቤተ መቅደስ ሰራተኞችና የሰለሞን ትውልዶች አገልጋዮች ተመላሾች ነበሩ። **61** ከዳላያ፣ ጦብያ እና ኔቆዳ ጎሣዎች **62** ሰዎች ያሉት ሌላ ቡድን ከቴልሜላ ቴላሬሳ፣ ከክሩብ፣ አዳን፣ በባቢሎን አዳን እና አሜር ተብሎም ይታወቃል፤ ከእነዚህ ከተሞች ይመለሳሉ። ነገር ግን እነርሱ እስራኤላዊያን መሆናቸውን ማረጋገጥ አልቻሉም። **63** የኤብያ፣ አቆስ፣ እና ቤርዜሊ ትውልድ የሆኑ ካህናትም ደግሞ ተመለሱ። ቤርዜሊ ከገለዓድ አካባቢ የቤርዜሊ ትውልድ የሆነችን አንዲት ሴት አገባ፤ እርሱም የሚስቱን ቤተሰቦች ስም መጠሪያው አድርጎ ወሰደ። **64** እነዚህ የአባቶችን ስሞች በያዙ መዛግብቶች ውስጥ የትውልድ ሀረጋቸውን ፍለጋ አደረጉ፣ ነገር ግን የቤተሰቦቻቸውን ስሞች ማግኘት አልቻሉም፤ ስለዚህ ካህናት ያሏቸውን መብቶችና ግዴታዎች ማግኘት አልተፈቀደላቸውም። በመሆኑም ንጹህ እንዳልሆኑ ስተቆጠረ ካህናት ለመሆን አልበቁም ምክንያቱም የትውልድ ሀረጋቸውን ማመላከት አልቻሉም። **65** ስለዚህ አገረ ገዥው በኡሪምና ቱሚም የሚያገለግል ከህን እስኪነሳ ድረስ ከመስዋዕቱ ከተወሰደው እጅግ ከተቀደሰው ከካህናቱ ድርሻ ምግብ እንዳይበሉ አዘዛቸው። **66** በአጠቃላይ፣ ከይሁዳ የተመለሱት ሰዎች 42360 ነበሩ። **67** እንደዚሁም 7337 አገልጋዮቻቸውና 245ዘማሪዎች ከወንዶችም ከሴቶችም በአንድነት ተቆጠሩ። **68** እስራኤላዊያኑ ከባቢሎን 736 ፈረሶችና 245 በቅሎዎች፣ **69** አራት መቶ ሰላሳ አምስት ግመሎችና 6720 አህዮችንም ጭምር ይዘው ተመለሱ። **70** አንዳንዶቹ የጎሣው መሪዎች ለመቅደሱ ግንባታ ሠራተኞች ስጦታዎችን ሰጡ። አገረ ገዥው 8. 5 ኪሎግራም ወርቅ ለመቅደስ አገልግሎት ሀምሳ ጎድጓዳ ሳህኖች፣ እና 530 የክህነት ልብሶችን ለካህናቱ ሰጠ። **71** ሌሎቹ መሪዎች ለግምጃ ቤት ሀላፊው 170 ኪሎግራም ወርቅ ሰጡ፣ የጎሣው መሪዎች በአጠቃላይ 1. 2 ሜትሪክ ቶን ብር ሰጡ። **72** ሌላው ህዝብ 170 ኪሎግራም ወርቅ፣ እና 1. 1 ሜትሪክ ቶን ብር እንዲሁም 67 የክህነት ልብስ ለካህናቱ ሰጡ። **73** ስለዚህም ካህናቱ፣ ካህናቱን የሚረዱ ሌዋውያን፣ የቤተመቅደሱ ጠባቂዎች፣ ዘማሪዎቹ፣ የቤተ መቅደሱ ሰራተኞች፣ እና በርካታው ተራ ህዝብ እንዲሁም እስራኤላዊ የሆኑ ሁሉ አባቶቻቸው ይኖሩባቸው በነበሩ በይሁዳ ከተሞች መኖር ጀመሩ።

Nehemiah 7:1

ቅጥሩ ተሰርቶ ካለቀ በኋላ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ቅጥሩን ሰርተን ስንጨርስ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በሮቹን በቦታቸው አደረግሁ
ይህ በሌላ ሰው እርዳታ የተደረገ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔና ሌሎቹ በሮቹን ሰቀልን” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

በር ጠባቂዎቹ ዘማሪዎቹና ለሌዋውያን ተሾሙ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። የሚከተሉት አማራጭ ትርጉሞች ሊሆኑ ይችላሉ፡- 1) ነህምያ ሾማቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “በር ጠባቂዎቹን ዘማሪዎቹንና ሌዋውያኖቹን ለስራቸው ሾምኳቸው። ወይም 2) ሌላ ሰው ሾማቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “በር ጠባቂዎቹን ዘማሪዎቹንና ሌዋውያንን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለስራቸው ሾሙአቸው።” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በር ጠባቂዎች
ወደ ከተማውና ወደ መቅደሱ የሚገባውን ሰው ለመቆጣጠርና ገዢው በወሰነው ምክንያት በትክክለኛው ጊዜ በሩን እንዲከፍቱና እንዲዘጉ የተወሱ ሰዎች በእያንዳንዱ በር ላይ ተመደቡ።

ዘማሪዎች
አምልኮ ላይ፣ ጉዞ ላይና የተለያዩ ዝግጅቶች ላይ ሙዚቃና ዜማን በድምጻቸው በመፍጠር ዝግጅቱ ትኩረት እንዲሰጠው የሚያደርጉ ወይም የሚያደምቁ ሰዎች።

አናኒ ... ሐናንያ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ወንድሜን አናኒን ... ሾምሁት
“ወንድሜ አናኒ አስተዳዳሪ እንዲሆን አዘዝኩት”

የቅጥሩን አለቃ
“ቅጥሩን ይቆጣጠር የነበረው”

ከብዙዎች ይልቅ እግዚአብሔርን ይፈራ ነበር
“ከሌሎች ብዙ ሰዎች የበለጠ እግዚአብሔርን ይፈራ ነበር”

Nehemiah 7:3

እኔም ... ለእነርሱ አልኳቸው
“አልኳቸው” የሚለው ቃል ውስጥ ያለው የድርጊት ተቀባይ አመልካች “አናኒ” እና “ሐናንያ” ያመለክታል።

ጸሐይ እስኪሞቅ ድረስ የኢየሩሳሌምን በሮች አትክፈቱ። በር ጠባቂዎቹ ዘብ በሚቆሙበት ጊዜ በሮቹን ልትዘጓቸውና ልትቆልፏቸው ትችላላችሁ።
የዚህ አማራጭ ትርጉም ሊሆን የሚችለው፦ 1) እነዚህ ድርጊቶች ይሰሩ የነበረው በአናኒና ሐናንያ ነው። ወይም 2) እነዚህ ድርጊቶች ይሰሩ የነበረው በበር ጠባቂዎች እርዳታ በአናኒና ሐናንያ ነው። 3) እነዚህን ድርጊቶች ይሰሩ የነበረው በአናኒና ሐናንያ ትዕዛዝ በበር ጠባቂዎቹ ነው።

ፀሐይ እስኪሞቅ
“ፀሐይ በሰማይ ላይ ከፍ እስክትል ድረስ”

በር ጠባቂዎቹ እየጠበቁ እያለ በሩን ዝጉት ቀርቅሩትም
“በር ጠባቂዎች በመጠበቅ ስራቸው ላይ እያሉ በሩን ዝጉና ቀርቅሩት”

በር ጠባቂዎች
ይህ በነህምያ 7፡1 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ

በሮችን ዝጉና ቀርቅሯቸው
“በሮችን ዝጉና ቆልፏቸው”

በኢየሩሳሌም ከሚኖሩት ሰዎች መካከል ጠባቂዎችን አስቀምጡ
“በኢየሩሳሌም ከሚኖሩ ሰዎች ጠባቂዎችን ሹሙ”

የጥበቃ ጣቢያ
“የጥበቃ ስፍራ” ወይም “የጥበቃ ስራ ቦታ”

ምንም ቤቶችም ደግመው አልተሰሩም ነበር
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰዎቹ ቤቶቹን ደግመው አልሰሩም ነበር” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 7:5

በልቤ አደረገ
እዚህ ላይ የነህምያ “ልብ” የሚወክለው ሃሳቡንና ፈቃዱን ነው። ይህ በነህምያ 2:12 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ። አማራጭ ትርጉም፦ “አነሳሳኝ” ወይም “መራኝ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እቆጥራቸው ዘንድ
“ዝርዝራቸውን ሰርቼ ለመመዝገብ”

የትውልድ ሐረግ መጽሐፍ
ይህ መጽሐፍ በወቅቱ ያልነበረ ነው።

እንደዚህ ተጽፎ አገኘሁ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አንድ ሰው የሚከተሉትን ጽፎ አገኘሁ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 7:6

የአገሩ ሰዎች እነዚህ ናቸው
“እዚህ ቦታ ቀድሞ ይኖሩ የነበሩት እነዚህ ናቸው”

የመጡ
“የተመለሱ” ወይም “እንደገና የመጡ”

የወጡት
ይህ ፈሊጥ ወደ ኢየሩሳሌም መጓዛቸውን ያሳያል፣ ይሄም በዙሪያው ካሉ ከተሞች ይልቅ በከፍታ ቦታ ላይ የሚገኝ ነበር። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

የባቢሎን ንጉስ ናቡከደነፆር የማረካቸው
“የባቢሎን ንጉስ ናቡከነደነፆር ከትውልደ ሃገራቸው የወሰዳቸው።” ይህን ያደረገው በናቡከደነፆር ትእዛዝ የባቢሎን ሰራዊት ነው። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ዘሩባቤል ... ኢያሱ ... ነህምያ .. አዛርያስ ... ረዓምያ ... ነሐማኒ ... መርዶክዮስ ... በላሳን ... ሚስጴሬት ... በጉዋይ ... ነሑም ... በዓና
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

የሕዝቡ ቁጥር
እስራኤላውያን ከምርኮ በኋላ በመጀመርያ ወደ ኢየሩሳሌም በተመሰሉ ጊዜ የሕዝብ ቆጠራ ተደርጎ ነበር። እነዚህ ቁጥሮች በእያንዳንዱ ቤተሰብ ምን ያህል ወንዶች እንዳሉ ያሳያል። ይህ ዓርፍተ ነገር በሚከተሉት ጥቅሶች ለሚቀርበው መረጃ መግቢያ ይሰጣል።

Nehemiah 7:8

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፦
ነህምያ ከግዞት የተመለሱትን የሕዝብ ቁጥር ድጋሚ እየቆጠረ ነው። ሕዝቡ በቤተሰቡ የጎሳ መሪዎች ስም መሰረት እንደየቤተሰቡ ተመድቧል። ቁጥሮቹ በየቤተሰቡ ውስጥ የሚገኙትን የወንዶች ቁጥር ይወክላል። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ፋሮስ ... ሰፋጥያስ ... ኤራ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Nehemiah 7:11

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፡
ነህምያ ከግዞት የተመለሱትን ሕዝብ ቁጥር ድጋሚ መቁጠሩን ቀጠለ። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ከኢያሱና ከእዮአብ ልጆች የነበሩ
“የኢያሱና የእዮአብ ዘሮች የነበሩ”

ፋሐት-ሞዓብ ... ኢያሱ ... እዮአብ ... ኤላም ... ዛቱዕ ... ዘካይ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 7:15

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፡-
ነህምያ ከግዞት የተለመለሱትን ሕዝብ ቁጥር ደግሞ መቁጠሩን ቀጠለ። (ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

ቢንዊ ... ቤባይ ... ዓዝጋድ ... አዶኒቃም
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 7:19

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፡-
ነህምያ ከግዞት የተመለሱትን ሕዝብ ቁጥር ደግሞ መቁጠሩን ቀጠለ። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በጉዋይ ... ዓዲን ... አጤር ... ሐሱም
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

የሕዝቅያስ ወገን የአጤር ልጆች
ጸሀፊው ይህንን ዓርፍተ ነገር አሳጥሮታል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሕዝቅያስ ዘር የሆነው የአጤር ልጆች” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 7:23

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፡-
ነህምያ ከግዞት የተመለሰውን ሕዝብ ቁጥር ደግሞ መቁጠሩን ቀጠለ። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ቤሳይ ... ሐሪፍ ... ገባዖን
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ቤተልሔም እና ነጦፋ
እነዚህ በይሁዳ የሚገኙ ቦታዎች ስያሜ ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 7:27

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፡-
ነህምያ ከግዞት የተመለሱትን ሕዝብ ቁጥር ደግሞ መቁጠሩን ቀጠለ። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ዓናቶች ... ቤትዓዝሞት ... ቂርያትይዓሪም ... ከፊራ እና ብኤሮት ... ራማ እና ጌባ
እነዚህ የቦታ ስያሜዎች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 7:31

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፡-
ነህምያ ከግዞት የተመለሰውን ሕዝብ ቁጥር ደግሞ መቁጠሩን ቀጠለ። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ማክማስ ... ቤቴል እና ጋይ ... ናባው ... ኤላም
እነዚህ የቦታ ስያሜዎች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 7:35

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፡-
ነህምያ ከግዞት የተመለሱትን ሕዝብ ቁጥር ደግሞ መቁጠሩን ቀጠለ። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ካሪም ... ኢያሪኮ ... ሎድ፣ ሐዲድ እና ኦኖ ... ሴናዓ
እነዚህ የቦታ ስያሜዎች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 7:39

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፡-
ነህምያ ከግዞት የተመለሰውን ሕዝብ ቁጥር ደግሞ መቁጠሩን ቀጠለ። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

የዳኤ ... አሜር ... ፋስኮር ... ካሪም
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

የኢያሱ ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል ለቤተሰብ ምትክ ሆኖ የገባ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ከኢያሱ ቤተሰብ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 7:43

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፡-
ነህምያ ከግዞት የተመለሰውን ሕዝብ ቁጥር ደግሞ መቁጠሩን ቀጠለ። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ኢያሱ ... ቀድምኤል ... ቢንዊ ... ሆዳዋይ ... አሳፍ ... ሰሎም ... አጤር ... ጤልሞን ... ዓቁብ ... ሐጢጣ ... ሶባይ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ዘማሪዎች
ይህ በነህምያ 7:1 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።

የበር ጠባቂዎች
ይህ በነህምያ 7:1 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።

Nehemiah 7:46

አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ቁጥሮች ወላጆቻቸው ከግዞት የተመለሱትን ሕዝብ ስም መዘርዘር ይቀጥላል።

ሲሃ ... ሐሱፋ ... ጠብዖት ... ኬራስ ... ሲዓ ... ፋዶን ... ልባና ... አጋባ ... ሰምላይ ... ሐናን ... ጌዴል ... ጋሐር
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሲዓ
ይህ ሰው በዕዝራ 2፡44 ላይ ሲዓ ተብሎ የተጠራው ሰው ነው።

Nehemiah 7:50

አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ቁጥሮች ወላጆቻቸው ከግዞት የተመለሱትን ሕዝብ ስም መዘርዘር ይቀጥላል።

ራያ ... ረአሶን ... ኔቆዳ ... ጋሴም ... ዖዛ ... ፋሴሐ ... ቤሳይ ... ምዑናውያን ... ንፉስሲም
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 7:53

አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ቁጥሮች ወላጆቻቸው ከግዞት የተመለሱትን ሕዝብ ስም መዘርዘር ይቀጥላል።

በቅቡቅ ... ሐቀፋ ... ሐርሑር .... በስሎት ... ምሒዳ ... ሐርሻ ... በርቆስ ... ሲሣራ ... ቴማ ... ንስያ ... ሐጢፋ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 7:57

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፡-
ነህምያ ከግዞት የተመለሰውን ሕዝብ ቁጥር ድጋሚ መቁጠሩን ቀጠለ። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሶጣይ ... ሶፌሬት ... ፍሩዳ ... የዕላ ... ደርቆን ... ጌዴል ... ሰፋጥያስ ... ሐጢል ... ፈከራት ሐዚቦይም ... አሞን
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ሶፌሬት
ይህ ሰው በዕዝራ 2፡55 ላይ ሶፌሬት ተብሎ የተጠራው ነው።

ፍሩዳ
ይህ ሰው በዕዝራ 2፡55 ላይ ፍሩዳ ተብሎ የተጠቀሰው ነው።

Nehemiah 7:61

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፡-
ነህምያ ከግዞት የተመለሰውን ሕዝብ ቁጥር ድጋሚ መቁጠሩን ቀጠለ። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ወጡ
ይህ በዙረያዋ ከነበሩት አካባቢዎች ይልቅ በከፍታ ስፍራ ወደምትገኘው ወደ ኢየሩሳሌም መጓዝን የሚያመለክት ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ተመለሱ” ወይም “እንደገና መጡ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ቴል ሜላ ... ቴላ ሬሳ ... ክሩብ ... አዳን ... አሜር
እነዚህ የቦታ ስያሜዎች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ዳላያ ... ጦብያ ... ኔቆዳ ... ኤቢያ ... አቆስ ... ቤርዜሊ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 7:64

እነዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከተጻፉት መካከል ትውልዳቸውን ፈለጉ
“እነርሱ በጽሑፍ የተቀመጠውን የትውልድ ሐረግ መዝገብ ፈለጉ”

እነዚህ ... ፈለጉ
“እነዚህ” የሚለው የሚያመለክተው የኤብያ፣ አቆስና ቤርዜሊ ልጆችን ነው።” ነህም 7:63

ነገር ግን ሊገኙ አልቻሉም
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን የትውልዳቸውን ጽሁፍ አላገኙም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱም ንጹህ ስላልሆኑ ከክህነት ተከለከሉ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። “ክህነት” የሚለው ረቂቅ ስም “በክህነት መስራት” በሚለው ግስ መለወጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ገዢው ንጹህ እንዳልሆኑ ስላሰበ በክህነት እንዲሰሩ አልፈቀደላቸውም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በኡሪምና ቱሚም የሚፈርድ ካህን እስኪነሳ ድረስ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በኡሪምና ቱሚም አገልግሎት የሚሰጥ ካህን ማረጋገጫ እስኪሰጥ ድረስ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ኡሪምና ቱሚም
እነዚህ ሊቀ ካህኑ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ የሚጠቀምባቸው በደረት ኪሱ ይዞአቸው የሚገባ የተቀደሱ ድንጋዮች ናቸው። (የማይታወቁ ነገሮች መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 7:66

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፡-
ነህምያ ከግዞት የተመለሰውን ሕዝብ ቁጥር ዲጋሚ መቁጠሩን ቀጠለ። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ጉባዔው ሁሉ በአንድነት
“ሙሉ ጉባዔው በአንድነት”

42,360 ነበር
“አርባ ሁለት ሺህ ሶስት መቶ ስልሳ ሕዝብ ነበር”

ወንዶችና ሴቶች መዘምራን ነበሩ
“ወንድና ሴት ዘማሪያን”

Nehemiah 7:68

736 ... 245 ... 435 ... 6,720
“ሰባት መቶ ሰላሳ ስድስት ... ሁለት መቶ አርባ አምስት ... አራት መቶ ሰላሳ አምስት .... ስድስት ሺህ ሰባት መቶ ሃያ“ (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 7:70

የአባቶች ቤት አለቆች
“ዋና የቤተሰብ አባቶች” ወይም “የጎሳ መሪዎች”

ለግምጃ ቤት ሰጡ
“ወደ ግምጃ ቤት አስገቡ”

አንድ ሺህ ዳሪክ
“1000 ዳሪክ” (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የወርቅ ዳሪክ
ዳሪክ የፋርስ መንግስት የሚጠቀምበት ትንሽ የወርቅ ሳንቲም ነው። (መጽሐፍ ቅዱሳዊ የመገበያያ ገንዘቦች የሚለውን ይመልከቱ)

ድስቶች
“አምሳ ድስቶች።” እነዚህ ትልቅ ጎድጓዳ ሳህኖች ናቸው። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

530 የካህናት ልብስ
“አምስት መቶ ሰላሳ የካህናት ልብሶች።” እነዚህ በካህናት የሚደረጉ የልብስ ዓይነቶች ናቸው። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሃያ ሺህ ዳሪክ
“20,000 ዳሪክ” (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

2,200 የብር ምናን
“ሁለት ሺህ ሁለት መቶ የብር ምናን።” ምናን ማለት በክብደት ከግማሽ ኪሎግራም ጋር ተቀራራቢ የሆነ ነው። (ቁጥሮችና መጽሐፍ ቅዱሳዊ የክብደት መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

ብር
የሚያንጸባርቅ፣ ግራጫ የከበረ ብረት ሳንቲሞችን፣ ጌጦችንና፣ እቃ መያዣዎችንና ማጌጫዎችን ለመስራት ያገለግላል።

ሁለት ሺህ ምናን
“2,000 ምናን” (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ስልሳ ሰባት የካህናት ልብስ
“67 የካህናት ልብስ” (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 7:73

የበር ጠባቂዎች
ይህ በነህምያ 7:1 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።

መዘምራን
ይህ በነህምያ 7:1 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።

ከሕዝቡም አንዳንዶቹ
ይህ ቀጥተኛ ያልሆነ መረጃ እስራኤላውያን ሆነው ካህናትና የመቅደስ ሰራተኞች ያልሆኑትን ይወክላል። (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እስራኤልም ሁሉ
የሚከተሉት አማራጭ ትርጉሞች ናቸው፡- 1) በዚህ ቁጥር ላይ የተዘረዘሩት እስራኤላውያን ወገኖች በሙሉ ወይም 2) በመቅደስ ውስጥ የማያገለግሉት እስራኤላውያን።

ሰባተኛው ወር
“7ኛው ወር።” ይህ በዕብራይስጥ የቀን መቁጠርያ ሰባተኛው ወር ነው። በምዕራባውያን ቀን መቁጠርያ በመስከረም ወር መጨረሻና በጥቅምት ወር መጀመርያ አካባቢ ያለው ጊዜ ነው። (ደረጃን የሚያሳዩ ቁጥሮች እና የዕብራይስጥ ወራት የሚለውን ይመልከቱ)

በከተሞቻቸው ተቀመጡ
“በከተሞቻቸው ኖሩ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 8

1 ህዝቡ ሁሉ በውሃ በር አጠገብ በሚገኘው አደባባይ በአንድነት ተሰበሰቡ። የሚነገረውን መረዳት የሚችሉ ወንዶችና ሴቶች እንዲሁም ልጆች በአንድነት
ተሰበሰቡ። እነርሱም ህግጋቱንና ትዕዛዛቱን ይጠብቁ ዘንድ፣ ያህዌ ለእስራኤል ህዝብ መመሪያ አድርጎ የሰጠውን ሙሴ የፃፈውን የህግ ጥቅልል መጽሐፍ
እንዲመያጣ ዕዝራን ጠየቁት። 2 በቤተ መቅደስ መስዋዕቶችን በማቅረብ እግዚአብሔርን የሚያገለግለው ዕዝራ፣ ለወንዶችና ለሴቶች እንዲሁም ለማናቸውም
የሚነበበውን መረዳት ለሚችሉ ህጉን አውጥቶ በህዝቡ ሁሉ ፊት አነበበ። ይህንን በዚያ አመት በሰባተኛው ወር በወሩ በመጀመሪያው ቀን አደረገ። 3 ስለዚህም
መጽሐፉን አውጥቶ ለህዝቡ አነበበ። ጠዋት ከማለዳ አንስቶ እስከ እኩለ ቀን ድረስ የህጉን መጽሐፍ አነበበ። ወንዶና ሴቶች እንዲሁም የሚያነበውን መረዳት
የሚችሉ ሁሉ ሰሙት። ዕዝራ ከህጉ መጽሐፍ የሚያነበውን፣ ህዝቡ በታላቅ ፍላጎት አደመጠ። 4 ዕዝራ ለዚህ ተግባር በህዝቡ በተዘጋጀ ከፍ ያ የእንጨት መድረክ
ላይ ቆመ። ከእርሱ በስተቀኝ መቲትያ፣ ሸማዕ፣ ዓናያ፣ ኦርዮ፣ ኬልቅያስ እና መዕሤያ ቆመው ነበር። በስተግራው በኩል ደግሞ ፈዳያ፣ ሚሳኤል፣ መልክያ፣
ሐሱም፣ ሐሸበዳ፣ ዘካርያስና ሜሱላም ቆመው ነበር። 5 ዕዝራ በመድረኩ ላይ ሁሉም ሰዎች ሊያዩት በሚችሉት ቦታ ቆሞ ጥቅልሉን ተረተረው፣ እርሱ መጽሐፉን
ሲከፍት ህዝቡ ሁሉ ተነስቶ ቆመ። 6 ከዚያም ዕዝራ ታላቁን አምላክ ያህዌን አመሰገነ፣ ህዝቡም ሁሉ እጆቻቸውን አንስተው፣ “አሜን! አሜን!” አሉ። ከዚያም
ሁሉም በግምባራቸው ወደ ምድር እየሰገዱ ያህዌን አመለኩ። 7 ኢያሱ፣ ባኒ፣ ሰራብያ፣ ያሚን፣ ዓቁብ፣ ሳባታይ፣ ሆዲያ፣ መዕሤያ፣ ቆሊጣስ፣ ዓዛርያስ፣ ዮዛባት፣
ሐናን እና ፌልያ ሁሉም ሌዋውያን ነበሩ። እነርሱም የሙሴን ህግጋት ትርጉም በዚያ ቆመው ለነበሩ ህዝቦች አብራሩ። 8 እንደዚሁም እግዚአብሔር ለሙሴ
የሰጠውን ህግ ከመጽሐፉ ጥቅልሎች አነበቡ፣ ደግም ወደ አረማይክ ቋንቋ እየተረጎሙ ህዝቡ ሊረዱት እንዲችሉ ትርጉሙን ግልጽ አደረጉ። 9 ከዚያ አገረ
ገዥው ነህምያ እና ጸሓፊውና ካህኑ ዕዝራ፣ እንዲሁም የተነበበውን ለህዝቡ ይተረጉሙ የነበሩ ሌዋውያን፣ እንዲህ አሏቸው፣ “ያህዌ አምላካችሁ ይህን ቀን
ከሌሎች ቀናት ለይቶታል። ስለዚህ በዚህ ቀን አትዘኑ ወይም አታልቅሱ!” ይህን የተናገሩት፣ ዕዝራ ህጉን ሲያነብ፤ የሚሰሙት ሁሉ ያለቅሱ ስለነበር ነው። 10
ከዚያም ነህምያ እንደዚህ አላቸው፣ “አሁን ወደየቤታችሁ ሄዳችሁ መልካም ምግብ ተመገቡ ደስ የሚያሰኝ ጣፋጭ መጠጥም ጠጡ። ከምትበሉትና
ከምትጠጡት የሚበሉትና የሚጠጡት ለሌላቸው አካፍሉ። ይህ ቀን፣ ጌታችንን ለማምለክ የተለየ ቀን ነው። ሀዘን አይሙላባችሁ! ያህዌ የሚሰጣችሁ ደስታ
ብርቱ ያደርጋችኋል።” 11 ሌዋውያኑም ህዝቡን “ዝም በሉ አታልቅሱ፣ ይህ ቀን ለያህዌ የተለየ ቀን ነው። አትዘኑ!” በማለት ፀጥ አሰኙ። 12 ስለዚህም ህዝቡ
ተነስቶ ሄደ፤ በሉም ጠጡም፣ እንዲሁም ምንም ለሌላቸው ከምግባቸው አካፈሉ። የተነበባላቸውን ቃላት ትርጉሙን ስለተረዱ በጣም ደስተኞች ነበሩ። 13
በማግስቱ፣ የየቤተሰቡ አባወራዎች እና ካህናቱ እንዲሁም ሌዋውያኑ የህጉን ቃላት ይበልጥ ለመረዳት በአንድነት ወደ ዕዝራ መጡ። 14 አያቶቻቸው በበረሃ
ሲጓዙ በዳሶች ውስጥ እንደኖሩ ያስታውሱ ዘንድ፣ በእነዚያ ወራት ሁሉ የእስራኤል ህዝብ እንዴት በጊዜያዊ ዳሶች ውስጥ መኖር እንደሚገባቸው ያህዌ ለሙሴ
የሰጠውን ተዕዛዝ በህጉ ውስጥ ተጽፎ አገኙ። 15 እንደዚሁም ህዝቡ ወደ ኮረብቶች ሄዶ፤ ከወይራ ዛፎች ቅርንጫፎችን፣ ከበረሃ ወይራ ዛፎችና ከባርሰነት
ዛፎች፣ ከዘንባባ ዛፎችና ሰፊ ጥላ ከሚሰጡ ዛፎች ዝንጣፊዎችን እየቆረጡ እንዲያመጡና በኢየሩሳሌምና በሌሎች ከተሞች ማወጅ እንዳለባቸው ተረድተዋል።
ሙሴ እንደፃፈው፣ በበዓላቱ ወቅቶች ለመኖሪያነት የሚገለገሉባቸውን እነዚህን ዳሶች ከእነዚህ ዛፎች ቅርንጫፎች ማበጀት አለባቸው። 16 ስለዚህም ህዝቡ
ከከተማ ወጥቶ ቅርንጫፎችን ቆርጦ ዳሶችን ለመስራት ተጠቀመባቸው። ዳሶችንም በየቤቶቻቸው ሰገነቶችት በየአደባባዮቻቸው፣ በቤተ መቅደስ አደባባዮች፣
እና በውሃ በር አጠገብ በሚገኘው አደባባይና በኤፍሬም መግቢያ ሰሩ። 17 ከባቢሎን የተመለሱ እስራኤላዊያን ሁሉ ዳሶችን ገንብተው ለአንድ ሳምንት
ኖሩባቸው። እስራኤላዊያን ያንን በዓል ከኢያሱ ዘመን አንስቶ እስከዚያ ጊዜ ድረስ እንዲህ አላከበሩም። ህዝቡ በጣም ተደስቶ ነበር። 18 ዕዝራ በዚያን ሳምንት
በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ህግ ለህዝቡ ያነብ ነበር። ከዚያ በስምንተኛው ቀን፣ ድንጋጌውን ተከትለው ህዝቡ እንዲሰበሰብ አደረጉ፣ ይህም የበዓሉ ፍጻሜ ነበር።

Nehemiah 8:1

ህዝቡም ሁሉ እንደ አንድ ሰው ሆነው ተሰበሰቡ
“ሁሉም” የሚለው ቃል የነበረው ሰው አንድ ላይ መሰብሰቡን የሚያሳይ ጅምላ ቃል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሕዝቡ በአንድ ላይ ተሰበሰበ” (ግነትና ጅምላ ፈረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የውሃው በር
ይህ በቅጥሩ ላይ የነበረ ታላቅ መግቢያ በር ነበር።

የሙሴ የሕግ መጽሐፍ
ይህ የብሉይ ኪዳን የመጀመርያ አምስት መጻሕፍት በሙሉ ወይም ከፊል ሊሆን ይችላል።

በሰባተኛው ወር የመጀመርያው ቀን
ይህ በዕብራይስጥ ቀን አቆጣጠር የመጀመርያው ወር ነው። የሰባተኛው ወር የመጀመርያ ቀን በምዕራባውያን አቆጣጠር የመስከረም ወር አጋማሽ ላይ ያለ ጊዜ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በ7ኛው ወር በ1ኛው ቀን” (የዕብራይስጥ ወራት እና ደረጃ የሚያሳዩ ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሕጉን ... አመጣ
“የሕግ መጽሐፍ አመጣ”

ሊሰሙና ሊያስተውሉ በሚችሉ ሁሉ ፊት
ይህ የሚነበበውን ለመረዳት ዕድሜአቸው የደረሱ ሕጻናትንም ይጨምራል።

... በፊት ባለው አደባባይ ቆሞ
“ወደ አደባባዩ ዞሮ”

ከዚያ አነበበው
“ከዚያ” የሚለው የሚያመለክተው የተነበበው የሙሴ የሕግ መጽሐፍን ነው።

Nehemiah 8:4

መቲትያ ... ሸማዕ ... ዓናያ ... ኦርዮ .. ኬልቅያስ ... መዕሤያ ... ፈዳያ ... ሚሳኤል ... መልክያ ... ሐሱም ... ሐሸበዳና ... ዘካርያስ ... ሜሱላም
እነዚህ ሁሉም የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ዕዝራ በሰዎች ሁሉ ፊት መጽሐፉን ከፈተ
“ፊት” የሚለው ረቂቅ ስም የሚናገረው “ተመለከቱ” በሚለው ግስ ሊተካ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሁሉም ሰዎች ዕዝራ መጽሐፉን ሲከፍተው ተመለከቱት” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

መጽሐፉ
“የሕጉ መጽሐፍ”

በሕዝቡ ላይ ከፍ ብሎ ቆሞ
“ከሰዎቹ ከፍ ብሎ ቆሞ ነበር”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በገለጠው ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ ተነስቶ ቆመ
ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ቃል ያለውን አክብሮት ለመግለጽ ተነስቶ ቆመ። (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 8:6

ዕዝራም እግዚአብሔርን ባረከ
“ባረከ” የሚለው ረቂቅ ስም በግስ መልክ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ዕዝራ ያሕዌን አመሰገነ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እያሱ፣ ባኒ፣ ሰራብያ፣ ያሚን፣ ዓቁብ፣ ሳባታይ፣ ሆድያ፣ መዕሤያ፣ ቆሊጣስ፣ ዓዛርያስ፣ ዮዛባት፣ ሐናን፣ ፌልያ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱም ከመጽሐፉ አነበቡ
“እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሌዋውያንን ነው።

ፍቺውን በማሳየትና ትርጉሙን በመስጠት ግልጽ አደረገው
“ፍቺ” እና “ትርጉም” የሚሉት ረቂቅ ቃላት በድርጊት ቃላት መተካት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በግልጽ በመፍታትና በማብራራት” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ንባቡን
“ይነበብ የነበረውን”

Nehemiah 8:9

ሕዝቡ ሁሉ ያለቅሱ ነበርና
ይህ በሕዝቡ ዘንድ ታላቅ ለቅሶ እንደነበር የሚያሳይ ጅምላ ገለጻ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሕዝቡ በጣም ያለቅስ ነበርና” (ግነትና ጅምላ መግለጫ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰባውን ብሉ ጣፋጩንም ጠጡ
ይህ በተዛዋሪ የቀረበ መረጃ የሚያሳየው ሕዝቡ በጥሩ ምግብና መጠጥ እንዲያከብሩ እንደተነገራቸው የሚያሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥሩ የሆነ ምግብና ጣፋጭ መጠጥ ተመገቡ” (ግምታዊ እውቀትና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አትዘኑ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አትዘኑ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የያሕዌ ደስታ ኃይላችሁ ነውና
እዚህ ላይ “ደስታ” እና “ኃይል” የሚሉት ረቂቅ ቃላት በግስና ገላጭ መልክ መቀመጥ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “በያሕዌ ሐሴት ማድረግ ይጠብቃችኋል” ወይም “በያሕዌ መደሰት ብርቱ መጠጊያ ይሆናችኋል” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 8:11

ጸጥ በሉ
“ጸጥ በሉ!” ወይም “ዝም በሉ!”

አትዘኑ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አትዘኑ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በታላቅ ደስታ ለያከብሩ
“ደስታ” የሚለው ረቂቅ ቃል በግስ መልክ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እጅግ ሊደሰቱ” (ረቂቅ ግሶች የሚለውን ይመልከቱ)

ለእነርሱ ተነግሮአቸው የነበሩት ቃላቶች
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ ለእነርሱ የነገራቸውን ነገር” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 8:13

በሁለተኛው ቀን
“በ2ኛው ቀን” ወይም “በሚቀጥለው ቀን” (የመቁጠርያ ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ይተረጎምላቸው ዘንድ
“ይተረጎምላቸው” የሚለው ቃል በግስ መልክ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለመረዳት” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በዳስ ይቀመጡ ዘንድ
እነዚህ ሰዎች ከዛፍ ቅርንጫፎችና ከቅጠሎች ይሰሯቸው የነበሩ ጊዜያዊ መጠለያዎች ነበሩ።

ሰባተኛው ወር
“ወር 7።” ይህ የዕብራይስጥ ቀን መቁጠሪያ ሰባተኛ ወር ነው። በምዕራባውያን አቆጣጠር በመስከረም መጨረሻና በጥቅምት ወር መጀመርያ አካባቢ ያለው ጊዜ ነው። (ደረጃ የሚያሳዩ ቁጥሮች እና የዕብራይስጥ ወራት የሚለውን ይመልከቱ)

... ብለው ያውጁ ዘንድ
“... ብለው ይናገሩ ዘንድ”

ባርሰነት
ባለ ቀለም አበቦች ያለው ትንሽ የዛፍ ዓይነት። (የማይታወቁ ነገሮች ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ለምለም ዛፎች
“ብዙ ቅጠል ያላቸው ዛፎች”

እንደተጻፈ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሙሴ ስለዚህ ነገር እንደ ጻፈው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 8:16

እያንዳንዱም ለራሱ ዳስን ሰራ
“እያንዳንዱ የራሱን ዳስ ገነባ”

በውኃው በር ... በኤፍሬምም በር
እነዚህ በቅጥሩ ላይ የነበሩ የታላላቅ መግቢያዎች ወይም የበሮችን ስም ናቸው።

በኤፍሬም በር አደባባይ ውስጥ
“በኤፍሬም በር በኩል በነበረው ክፍት ቦታ”

ከኢያሱ ዘመን ጀምሮ
“ከኢያሱ ዘመን ጀምሮ”

የነዌ ልጅ
“ነዌ” የወንድ ስም ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ደስታቸው እጅግ ታላቅ ነበር
“ደስታ” የሚለው ረቂቅ ቃል በገላጭ ቃል መተካት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሕዝቡ በጣም ተደስተው ነበር” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 8:18

ዕለት ዕለት
ይህ ፈሊጥ “እያንዳንዱ ቀን” ማለት ነው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ከመጀመርያው ቀን እስከ መጨረሻው ድረስ
ይህ በተዛዋሪ የተገለጸ መረጃ በዓሉ በተከበረበት ሳምንት ሙሉ እንድተደረገ ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከሳምንቱ መጀመርያ እስከ ሳምንቱ መጨረሻ ድረስ” (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በዓሉን አደረጉ
“ድግሱን አደረጉ” ወይም “በዓሉን አከበሩ”

በስምንተኛው ቀን
“በ8ኛው ቀን” (ደረጃን የሚያሳዩ ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

የተቀደሰ ጉባዔ
ይህ የተለየ ኃይማኖታዊ መሰባሰብ ነበር።

ሕጉን በመታዘዝ
ይህ በተዛዋሪ የተገለጸ መረጃ የዳስ በዓል እንዴት መጠናቀቅ እንዳለበት የሚያሳየው “ሕግ” በያሕዌ የታዘዘ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር እንዳዘዘው” (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 9

1 በዚያው ወር በሃያ አራተኛው ቀን፣ ህዝቡ በአንድነት ተሰበሰበ። ለጥቂት ጊዜ አልበሉም፣ ሰንዴና ሌላ እህል ለመያዣ የተዘጋጁ ጆንያዎችን ልብስ አደርገው
ለበሱ፣ በራሳቸው ላይ የምድር ትቢያ ነሰነሱ። 2 የእስራኤል ትውልዶች ራሳቸውን ከሌሎች መጻተኞች ሁሉ ለዩ። በዚያ ቆመው የራሳቸውን ኃጢአትና አባቶቸው
የሰሯቸውን ክፉ ነገሮች ተናዘዙ። 3 ቆመው ለሶስት ሰዓቶች ከያህዌ ህግ አነበቡ፣ ደግሞም ለሌላ ሶስት ሰዓቶች በያህዌ ፊት ኃጢአቶቻቸውን ድምጻቸውን ከፍ
አድርገው ተናገሩ፣ ከዚያ በመሬት ላይ ተደፍተው እርሱን አመለኩ። 4 ሌዋውያኑ በደረጃው ላይ ቆመው ነበር። እነርሱም ኢያሱ፣ ባኒ፣ ቀድምኤል፣ ሰበንያ፣ ቡኒ፣
ሰራብያ፣ ባኒ፣ እና ከናኒ ነበሩ። 5 ከዚያ የሌዋውያኑ መሪዎች በህዝቡ ፊት ተሰየሙ። እነርሱም ኢያሱ፣ ባኒ፣ አሰበንያ፣ ሰራብያ፣ ሆዲያ፣ ሰበንያና ፈታያ ነበሩ።
እነርሱም እንዲህ አሉ፣ “ቁሙና ከዘለዓም እስከ ዘለዓለም ለነበረውና ለሚኖረው ለአምላካችሁ ለያህዌ ምስጋና አቅርቡ! ያህዌ፣ የከበረውን ስምህን እናወድሳለን!
መልካምና ድንቅ ከሆነው ነገር ሁሉ ስምህ የበለጠ ጠቃሚ ነው! 6 አንተ ያህዌ ነህ፣ ሌላ ማንም ዘለዓለማዊና በራሱ ህልውና ያለው የለም። አንተ ሰማይንና
ሰማያትን ከሁሉም በላይ ሰራህ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፈጽሙትን መላዕክት ሁሉ ፈጠርህ። ምድርንና በላይዋ ያሉትን አንተ አበጀህ፣ ባህሮችንና
በውስጣቸው የሚገኙትን ሰራህ። አንተ ለሁሉም ነገር ህይወት ሰጠህ። በሰማይ ያሉ የመላዕክት ሰራዊት ሁሉ አንተን ያመልኩሃል። 7 ያህዌ፣ አንተ እግዚአብሔር
ነህ። አንተ አብራምን መርጠህ ከኡር ከከለዳኖ አወጣኸው። አብርሃም የሚል ስም ሰጠኸው። 8 አንተ የእርሱን ልብ አየህ፣ የታመነ ሰው እንደነበረ ታውቅ
ነበር። ከዚያ ከእርሱ ጋር በደም ቃል ኪዳን አደረግህ፣ የከነዓናዊያንን፣ የኬጢያውያንን፣ የአሞራውያንን፣ የፌርዛውያንን፣ የኢያቡሳውያንንና የጌርሳውያንን ምድር
ለትውልዶች እንደምትሰጠው ቃል ገባህለት። እና አንተ ያህዌ፣ ቃል የገባኸውን ፈጸምክ፣ ምክንያቱም አንተ ሁልጊዜም ትክክል የሆነውን ታደርጋለህ። 9
አባቶቻችን በግብጽ ምን ያህል ይሰቃዩ እንደ ነበር አንተ አይተሃል። ቀይ ባህር አጠገብ በነበሩ ጊዜ ወደ አንተ ለእርዳታ ሲጮኹ ሰማሃቸው። 10 ንጉሱ፣
አገልጋዮቹና የእርሱ ህዝቦች ሁሉ እንዲጨነቁ የሚያደርግ ብዙ አይነት ተአምራቶችን አደረግህ። በዚህም፣ አንተ፣ ያህዌ፣ ለራስህ ስም አደረግህ፣ እናም ዛሬም
ድረስ ስምህ ታላቅ መሆኑ ይታወቃል! 11 ለሁለት ክፍል ከፈልህ፣ እናም ህዝብህ በደረቅ ምድር በመሀሉ ተራመደ። አንተ የግብጽን ወታደሮች በውሃዎች ስር
አሰመጥክ፣ ድንጋይ በጥልቅ ውሃ እንደሚሰምጥ ሰመጡ! 12 በቀን ደመና እንደ አምድ እየተከተላቸው መራሃቸው፣ በምሽት ወዴት እንደሚሄዱ ልታሳያቸው
የእሳት አምድ ብርሃን ሰጠሃቸው። 13 አንተ ከሰማይ ወርደህ በሲና ተራራ ላይ አናገርካቸው። የታመኑና እውነተኛ የሆኑ ብዙ ድንጋጌዎችንና ደንቦችን ሰጠሃቸው፣
መልካም የሆኑ ትዕዛዛትንና ህግጋትንም ሰጠሃቸው። 14 ስለ ቅዱሱ ሰንበትህ አስተማርካቸው፣ ትዕዛዛትንና ህግጋትን እንዲሁም ይፈጽሟቸው ዘንድ የህግጋት
አይቶችን በአገልጋይህ በሙሴ በኩል ሰጠሃቸው። እርሱ ለህዝቡ ይነግራቸዋል። 15 በተራቡ ጊዜ፣ ከሰማይ እንጀራ ሰጠሃቸው። በተጠሙ ጊዜ፣ ከአለት ውሃ
አጠጣሃቸው። ትሰጣቸው ዘንድ በመሀላ ቃል የገባህላቸውን ምድር ሄደው እንዲወርሱ ነገርካቸው። 16 ነገር ግን አባቶቻችን በጣም ኩራተኞችና ግትሮች ነበሩ።
እንዲያደርጉት ያዘዝካቸውን ለማስማት እንኳን ተቃወሙ። 17 አንተን ለመስማት አልወደዱም። ለእነርሱ ያደረግከውን ተአምራቶች ሁሉ ረሱ። ደንዳኖች ሆኑ፣
በአንተ ላይ ስለመጹ፣ ዳግም ባሪያዎች ወደሚሆኑበት! ወደ ግብጽ የሚመልሳቸውን መሪ መረጡ። ነገር ግን አንተ ደግመህ ደጋግመህ ይቅር የምትል አምላክ
ነህ። ለመቆጣት አትቸኩልም፣ ለእነርሱ ያለህ ፍቅርም በፍጹም የማያልቅና ታላቅ ነው። እነርሱን አልተውካቸውም። 18 ስለዚህ፣ ምንም እንኳን የከበሩ
ማዕድናትን አቅልጠው ጥጃ የሚመስል ጣኦት ቢቀርጹም ሙሉ ለሙሉ አልተወካቸውም። እግዚአብሔርን በመራገምና እርሱ የከለከለውን በማድረግ፣ ይህን
ጥጃ ወደ ህዝቡ አቅርበው፣ ‘ይህ እናንተን ከግብጽ ያወጣችሁ አምላካችሁ ነው’ አሉ። 19 አንተ ሁልጊዜም መሃሪ ነህ፣ በበረሃ በነበሩ ጊዜም አልተውካቸውም።
እንደ ታላቅ አምድ የሆነው ብሩህ ደመና በቀን ይመራቸው ነበር፣ የእሳት ደመናው በምሽት የሚሄዱበትን ይመራቸው ነበር። 20 መልካሙን መንፈስህን
እንዲመራቸው ላክህላቸው። በተራቡ ጊዜ መናውን አልከለከልካቸውም፣ በተጠሙ ጊዜ ውሃ ሰጠሃቸው። 21 ለአርባ አመታት በበረሃ ተጠነቀቅክላቸው። በነዚያ
ጊዜያት ሁሉ፣ የአንዳች ነገር ጉድለት አልነበረባቸውም። ልብሳቸው አላረጀም፣ እግሮቻቸው አላበጡም። 22 የአህዛብን ነገስታትና መንግስታት ሰጠሃቸው። በዚህ
ምድር እጅግ ሩቅ የሆነውን ስፍራ እንኳን ርስት አድርገው ወሰዱ። ንጉስ ሴዎን የሚገዛውን ምድር ከሐሴቦን ወሰዱ እንዲሁም የንጉስ ዐግን ግዛት ባሳንን
ወረሱ። 23 አባቶቻችንን በሰማይ እንዳሉ ከዋክብት እንዲበዙ ረዳሃቸው፣ አባቶቻቸው ይገቡባትና ይኖሩባት ዘንድ ወደ ነገርካቸው ወደዚህ ምድር አመጣሃቸው።
24 የእስራኤል ህዝቦች ገብተው በዚያ ከሚኖሩ ህዝቦች ምድሪቱን ወሰዱ። አንተ ከነአናዊያንንና ነገስታቶቻውን እንዲያሸንፉ ረዳሃቸው፣ አንተም በዚይ ምድር
ህዝቦች ላይ ገዛህ። በእነዚያ ህዝቦች ላይ ማድረግ የሚፈልጉትን ሁሉ እንዲያደርጉ አንተ ረዳሃቸው። 25 አባቶቻችን ዙሪያቸው የተቀጠሩትን ከተሞች ያዙ።
የለምለሚቱን ምድር ሀብት ወረሱ። በመልካም ነገሮች የተሞሉትን ቤቶችና የተቆፈሩ የውሃ ጉድጓዶችን ወረሱ። የወይን እርሻዎችን፣ የወይራ ዛፎችን እና የፍራፍሬ
ዛፎችን ወረሱ። የፈለጉትን ሁሉ በልተው ረኩ። አንተ በሰጠሃቸው ብዙ ስጦታዎች ራሳቸውን ደስ አሰኙ። 26 ነገር ግን አልታዘዙህም በአንተ ላይም አመጹ።
በህግጋትህ ላይ ጀርባቸውን ሰጡ። ወደ አንተ መመለስ እንዳለባቸው ያስጠነቀቋቸውን ነቢያት ገደሉ። ስምህን ተራገሙ። 27 ስለዚህም ያሸንፏቸው ዘንድ
ለጠላቶቻቸው አሳልፈህ ሰጠሃቸው። ነገር ግን ጠላቶቻቸው ባሰቃይዋቸው ጊዜ፣ ወደ አንተ ጮኹ። አንተ ከሰማይ ጩኸታቸውን ሰማህ፣ አንተ እጅግ መሃሪ
ስለሆንክ ከጠላቶቻቸው ነጻ የሚያወጧቸውን ሁሉ ላክህላቸው። እነርሱም ነፃ አወጧቸው። 28 ነገር ግን እንደገና የሰላም ጊዜ ከሆነ በኋላ፣ አባቶቻችን ዳግም
አንተ የምትጠላውን ክፉ ነገሮች አደረጉ። ስለዚህ ጠላቶቻቸው እንዲያሸንፏቸውና እንዲገዟቸው ፈቀድህ። ነገር ግን እንደገና እንድትረዳቸው በጮኹ ጊዜ ሁሉ
አንተ ከሰማይ ሆነህ ትሰማቸዋለህ፣ አንተ በምህረት የተሞላህ ስለሆንክ ትታደጋቸዋለህ። 29 አንተ እንደገና ህግጋትህን እንዲታዘዙ ታስጠነቅቃቸዋለህ፣ ነገር ግን
እነርሱ ኩራተኞችና ግትሮች ይሆናሉ፣ ድንጋጌዎችህንም ይጥሳሉ። እንዲያደርጉ ያዘዝካቸውን ሳይታዘዙ ይቀራሉ። ለትዕዛዛትህ አንዳች ትኩረት አይሰጡም።
አንተን መስማትን በግትርነት ይቃወማሉ። 30 አንተ ለብዙ አመታት ታግሰሃቸው ነበር። መንፈስህ ለነቢያት በሚሰጣቸው መልዕክት አማካይነት
ታስጠነቅቃቸዋለህ። ነገር ግን እነርሱን እነዚያን መልዕክቶች አይሰሙም። ስለዚህ እንደገና በአጠገባቸው ያሉ የአህዛብ ነገስታት እንዲያሸንፏቸው ትፈቅዳለህ።
31 ነገር ግን አንተ በይቅርታ ስለተሞላህ ሙሉ ለሙሉ አታጠፋቸውም ወይም ለዘለዓለም አትተዋቸውም አንተ መሀሪና ይቅር ባይ አምላክ ነህ! 32 አምላካችን
ሆይ፣ አንተ ታላቅ ነህ! አንተ ሃያል ነህ! አንተ አስደናቂ ነህ! አንተ እንደምታደርግልን በኪዳንህ ቃል እንደ ገባህልን በታማኝነት ትወደናለህ! ነገር ግን እኛ በእነዚህ
ነገሮች ሁሉ ታላቅ ችግሮች አሉብን። መከራችን በፊትህ እንደ ቀላል አይታይ! ይህ በእኛ ነገስታት ልዑላን፣ ካህናት፣ ነቢያት፣ አባቶች እና በመላው ህዝብህ ላይ
ከአሶር ነገስታት ዘመን አንስቶ እስከ ዛሬ ደርሷል። 33 በቀጣኸን ጊዜ ሁሉ በጥፋታችን እንደተቀጣን እናውቃለን። እጅግ በድለናል፣ አንተ ግን በምህረትህ
አይተኸናል እኛ ክፉ አድርገናል። 34 ንጉሶቻችን እና ሌሎች መሪዎች፣ ካህኖቻችን እና የእኛ አባቶች ህግህን አልጠበቁም። እነርሱ ትዕዛዛትን ወይም
የሰጠኃቸውን ማስጠንቀቂያዎች አልሰሙም። 35 የራሳቸው ነገስታት በኖራቸው ጊዜ እንኳን፣ በዚህ በሰጠሃቸው ሰፊና ለም ምድር ለእነርሱ ባደረግካለቸው
መልካም ነገሮች በተደሰቱ ጊዜ እንኳን፣ አንተን አላገለገሉህም ደግሞም ክፉ ማድረጋቸውን አላቆሙም። 36 ስለዚህ አሁን ምድሪቱ በምታበቅለው መልካም
ነገሮች ሁሉ ደስ እንዲሰኙ ለአባቶቻችን በሰጠሃቸው በዚህች ምድር ባሮች ነን። እነሆ ዛሬም በዚህ ባሮች ነን! 37 ስለበደልን ምድሪቱ የምታበቅለውን ነገሮች
መብላት አልቻልንም። አሁን እኛን የሚገዙ ነገስታት በዚህ በሚበቅሉ ነገሮች ደስ እየተሰኙ ነው። እነርሱ ይገዙናል ከብቶቻችንንም ይወስዳሉ። እኛ እነርሱን
የማገልገልና ደስ የሚያሰኛቸውን ነገሮች የማድረግ ግዴታ አለብን። በታላቅ ጉስቁልና ውስጥ እንገኛለን። 38 ከዚህ ሁሉ የተነሳ፣ እኛ የእስራኤል ሰዎች
በጥቅልል ጽሁፍ ታላቅ ስምምነት እናደርጋለን። በጥቅልሉ ላይ የመሪዎቻችንን፣ የሌዋውያንን፣ የካህናትን ስሞች እንጽፍና ማህተም እናደርግበታለን።”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Nehemiah 9:1

በዚህም ወር በሃያ አራተኛው ቀን
“በሰባተኛው ወር በሃያ አራተኛው ቀን” ይህ በምዕራባውያን ቀን መቁጠርያ በጥቅምት ወር አጋማሽ አካባቢ ነው። (የዕብራይስጥ ወራት እና ደረጃ የሚያሳዩ ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ልጆች ተከማቹ
“የእስራኤል ሕዝብ አንድ ላይ ተሰበሰቡ”

ማቅ ለብሰው፣ በራሳቸውም ላይ ትቢያን ነስንሰው
እንዲህ ያደረጉት እነርሱና አባቶቻቸው ላደረጉት ትክክል ያልሆነ ነገር ምን ያህል እንዳዘኑ ለማሳየት ነው። (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ዘር
“እስራኤላውያን”

ከእንግዶች ሁሉ ራሳቸውን ለዩ
“እስራኤላዊ ካልሆኑ ሰዎች ጋር ህብረታቸውን አቋረጡ”

ቆመው የራሳቸውን ኃጢአትና አባቶቻቸውንም የፈጸሙትን ክፉ ስራ ተናዘዙ
“ራሳቸውና የቀደሙ አባቶቻቸው የሰሯቸውን ክፉ ስራዎች ተናዘዙ”

Nehemiah 9:3

ቆሙ
ሁሉም እስራኤላውያን ተነሱ

ተናዘዙ
“ያደረጉትን ኃጢአት በመቀበል ይናዘዙ ነበር”

በፊቱ ሰገዱ
“አምልኮን አደረጉ” ወይም “አመሰገኑ”

ሌዋውያኑ እያሱና ባኒ ... በደረጃዎች ላይ ቆመው
አንዳንድ ትርጉሞች “እያሱ፣ ባኒ ... ለሌዋውያን በተሰራው ደረጃ ላይ ቆሙ” ብለው ይተረጉሙታል።

እያሱ፣ ባኒ፣ ቀድምኤል፣ ሰበንያ፣ ቡኒ፣ ሰራብያ፣ ባኒ እና ክናኒ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 9:5

ከዚያም ሌዋውያን ቆማችሁ ... እስከ ዘላለም ... አሉ
እዚህ ላይ ሌዋውያን የሚናሩት ለእስራኤል ሕዝብ ነው።

ለያሕዌ ምስጋናን ስጡ
“ያሕዌን ባርኩ”

ኢያሱ ... ቀድምኤል ... ባኒ ... ሰራብያ ... ሰበንያ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። ይህ በነህምያ 9:3-4 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

አሰበንያ ... ሆዲያ ... ፈታያ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ክቡር ስምህን ይባርኩ
እዚህ ላይ ሌዋውያን ለእግዚአብሔር እየተናገሩ ነው። “ያሕዌ ሆይ፣ የይሁዳ ሕዝብ የከበረው ስምህን ይባርክ”

ከፍ ያሉት ሰማያት፣ ከሰራዊቶቻቸው ጋር ... የሰማይ ሰራዊት አንተን ያመልኩሃል
ሰራዊት ጦር ነው። “የሰማይ ሰራዊት” የሚናገረው በተለዋጭ ዘይቤ እንደ ጦር ሰራዊት በማሰብ ስለ ብዙ ከዋክብት ነው። ከዋክብቶቹ ደግሞ በሌላ መልኩ ለብዙ መላእክት ተለዋጭ ዘይቤ ናቸው። ከዋክብት ያሕዌን ያመልካሉ የሚለው መላእክት ያሕዌን ያመልካሉ ለሚለው ተለዋጭ ዘይቤ ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 9:7

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፡-
ሌዋውያን በሕዝቡ ፊት እያደረጉ ያሉትን ጸሎት ቀጠሉ።

ከዑር ከላውዴዎንም
“ዑር የተባለው የከላውዴዎን ሕዝብ ይኖርበት የነበረ ስፍራ ነው”

ልቡም በአንተ ፊት የታመነ ሆኖ አገኘኸው
የአንድ ሰው ውስጣዊ ማንነት የሆነው ልብ አንድን ሰው ይወክለዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለአንተ ሙሉ በሙሉ ታማኝ መሆኑን ተመለከትክ” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ከነዓናውያን ... ኬጢያውያን ... አሞራውያን ... ፌርዛውያን ... እያቡሳውያን ... ጌርጌሳዊያን
እነዚህ የሕዝብ ስሞች ናቸው (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 9:9

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፡-
በእነዚህ ቁጥሮች ሌዋውያን በእስራኤል ሕዝብ ፊት ያሕዌን ማመስገናቸውን ቀጠሉ።

አየህ
ያሕዌ ተመለከተ

ጩኸታቸውን ሰማህ
ይህ በተዛዋሪ የተተገለጸ መረጃ እስራኤላውያን ለእርዳታ ያለቀሱትን በማየት እግዚአብሔር እርምጃ እንደወሰደ ያሳያል። (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በፈርዖን ላይ ምልክትና ተዓምራትን
መቅሰፍቶቹ የፈርዖንን ልብ ፈተኑት፣ እነርሱም ለልቡ ደንዳናነትም ምስክር ሆኑ። አማራጭ ትርጉም፡- “በፈርዖን ላይ የመሰከሩ ተዓምራትና ምልክቶች” ወይም “ፈርዖንን የኮነኑ ተዓምራትና ምልክቶች” (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ ምድር ሕዝብ ሁሉ
“ግብጻውያን ሁሉ”

በአእነርሱ ላይ እንደታበዩባቸው
“እስራኤላውያን ላይ ትዕቢተኞች ሆኑባቸው” ወይም “የእግዚአብሔርን የተመረጠ ሕዝብ አሰቃዩ”

እስከዚህ ቀን ድረስ ያለውን ስምህን ለራስህ አስጠራህ
እዚህ ላይ “ስም” የሚለው የሚናገረው ስለ “ዝና” ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ራስህን የታወቅህ አደረግህ ስለዚህም ሰዎች ዛሬም ያስታውሱሃል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Nehemiah 9:11

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፡-
በእነዚህ ቁጥሮች ሌዋውያን በእስራኤል ሕዝብ ፊት ያሕዌን ማመስገን ቀጠሉ።

ባህሩን ከፈልክ
እግዚአብሔር ባህሩን ከፈለ

አንተ ... ያሳደዷቸውን ድንጋይ በውሃ ውስጥ እንደሚጣል ወደ ጥልቅ ውስጥ ጣልካቸው
በዚህ ንጽጽር ላይ ጸሃፊው አንድ ሰው በቀላሉ ድንጋይን በውሃ ውስጥ ጥሎ ድንጋዩ በውኃው ውስጥ ተሰውሮ ከእይታ እንደሚጠፋ እግዚአብሔር ግብጻውያንን በቀላሉ በባህር ውስጥ እንደጣላቸው ይገልጻል። (ተነጻጻሪ የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 9:12

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፡-
በእነዚህ ቁጥሮች ሌዋውያን በእስራኤል ሕዝብ ፊት ያሕዌን ማመስገን ቀጠሉ።

መራሃቸው
ያሕዌ እስራኤላውያንን መራ

ወረድክ
እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ሲነጋገር ብዙ ጊዜ “ወረደ” ወይም “ከሰማይ ወረደ” ተብሎ ይነገራል። ይህ እግዚአብሔር ለአንድ ሰው እንደተገለጠለት መግለጫ መንገድ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ተገለጥክ” ወይም “ከሰማይ ወረድክ” (ፈሊጥ እና ግምታዊ እውቀትና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ጻድቁን ትዕዛዝና እውነቱን ሕግ፣ መልካሙን ሥርዓትና ትዕዛዝ
ሁለቱም ጥንድ ሐረጎች ተመሳሳይ ነገርን ይገልጻሉ እርሱም የሙሴን ሕግ ነው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 9:14

አያያዥ አርፍተ ነገር፡-
በእነዚህ ቁጥሮች ሌዋውያን በእስራኤል ሕዝብ ፊት ያሕዌን ማመስገን ቀጠሉ።

ትዕዛዝ ... ሥርዓት ... ሕግ
እነዚህ ሶስት ቃላት እያንዳንዳቸው ስለ ሙሴ ሕግ ያወራሉ። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 9:16

አያያዥ ዓርፍተ ነገሮች፡-
በእነዚህ ቁጥሮች ሌዋውያን በእስራኤል ሕዝብ ፊት ያሕዌን ማመስገን ቀጠሉ።

እነርሱና አባቶቻችን
በሙሴ ጊዜ የነበሩት እስራኤላውያን እና ከሙሴ ጊዜ በኋላ የነበሩት እስራኤላውያን

እነርሱ ግን ደንዳና ነበሩ ... ደንዳና ሆኑ
ቀጥተኛ አባባሉ “እንገታቸውን አደነደኑ” የሚለው ነው። ቋንቋችሁ ደንዳና ስለመሆን የተለየ ፈሊጣዎ መግለጫ ካለው እርሱን መጠቀም ይቻላል። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

በመካከላቸው ያደረግኸው ተዓምራት
“በመካከላቸው ያደረግኸው ድንቆች”

ወደ ባርነት ለመመለስ መሪ ሾሙ
እስራኤላውያን የቀደሙት አባቶቻቸው ወደ ግብጽ ለመመለስ መፈለጋቸውን ሊያውቁ እንደሚገባቸው ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ባርያ ወደነበሩበት ወደ ግብጽ እንዲመልሳቸው መሪን ሾሙ” (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በይቅርታ የተሞላ
ይቅርታን መፈለጉ የውሃ መያዣን እንደሚሞላ ፈሳሽ ተመስሎ ቀርቧል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይቅር ለማለት ዝግጁ የሆነ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጽኑና የማያወላውል ፍቅር የተሞላ
እዚህ ላይ ፍቅር ያሕዌ ለሕዝቡ እንደሚያካፍለው እንደ ምግብ እህል ተደርጎ ቀርቧል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሕዝቡን በጣም ይወድዳል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 9:18

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፡-
በእነዚህ ቁጥሮች ሌዋውያን በእስራኤል ሕዝብ ፊት ያሕዌን ማመስገን ቀጠሉ።

አንተ ... አልተውካቸውም
ያሕዌ እስራኤላውያንን አልተዋቸውም።

ከቀለጠ ብረት እንቦሳ ሰርተው
ብረትን አቅልጠው በእንቦሳ ቅርጽ ቀረጹት

የደመና አምድ ... የእሳት አምድ
ይህ በነህምያ 9:12 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ

Nehemiah 9:20

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፡-
በእነዚህ ቁጥሮች ሌዋውያን በእስራኤል ሕዝብ ፊት ያሕዌን ማመስገን ቀጠሉ።

መልካሙን መንፈስህን ... መናህን ... ውሃ
ጸሐፊው ያሕዌ ለሕዝቡ ያደረገውን መልካም ነገር ላይ ትኩረት ለመስጠት የተለመደውን የቃላት አገባብ ስርዓት ይቀይረዋል። የእናንተ ቋንቋ እነዚህ ነገሮችን የበለጠ ትኩረት እንዲሰጣቸው ለማድረግ የተለየ መንገድ ሊኖረው ይችላል።

እንዲመራቸው
እንዲያስተምራቸው

መናህን ከአፋቸው አልከለከልክም
ይህ ተቃራኒውን የመካድ አገላለጽ በአዎንታዊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “መናን በልግስና ሰጠሃቸው” (ተቃራኒን በመካድ መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ከአፋቸው
አፍ የሚለው አንድን ሙሉ ሰው ወካይ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ከእነርሱ” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Nehemiah 9:22

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፡-
በእነዚህ ቁጥሮች ሌዋውያን በእስራኤል ሕዝብ ፊት ያሕዌን ማመስገን ቀጠሉ።

መንግስታትን ሰጠሃቸው
ያሕዌ ለእስራኤላውያን መንግስታትን ሰጣቸው

መንግስታትንና ሕዝቦችን ሰጠሃቸው
“መንግስታትንና ሕዝቦችን እንዲያሸንፉ አደረግሃቸው”

የየምድሩን ዳርቻ እየሰጠሃቸው
“የምድሩን ሁሉንም ቦታ እንዲወስዱ እያደረገካቸው”

ሴዎን ... ዐግ
እነዚህ የነገስታት ስሞቸች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ሐሴቦን ... ባሳን
እነዚህ የቦታ ስያሜዎች ናቸው (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 9:23

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፡-
በእነዚህ ቁጥሮች ሌዋውያን በእስራኤል ሕዝብ ፊት ያሕዌን ማመስገን ቀጠሉ።

ልጆቻቸውን አበዛህ
ያሕዌ በሙሴ ጊዜ የእስራኤላውያንን ዘር አበዛ።

በእጃቸው ሰጣቸው
ከናዓናውያን አንድ ሰው በሌላ ሰው እጅ ላይ እንደሚጥለው ልክ እንደ አንድ ትንሽ ቁስ ተደርገው ተጽፈዋል። አነድን ነገር ለሌለው በእጁ መስጠት ማለት ተቀባዩ ሰው በተቀበለው እቃ ላይ ሙሉ ቁጥጥር እንዲኖረው ለዚያ ሰው ስልጣን መስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እስራኤላውያን ሙሉ በሙሉ እንዲቆጣጠሯቸው አደረግክ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 9:25

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፡-
በእነዚህ ቁጥሮች ሌዋውያን በእስራኤል ሕዝብ ፊት ያሕዌን ማመስገን ቀጠሉ።

ተቆጣጠሩ
በሙሴ ጊዜ የነበሩ እስራኤላውያን ተቆጣጠሩ

ፍሬያማ ምድር
“ለምለም ምድር”

የውሃ ምንጭ
ሰዎች ውሃ የሚያስቀምጡባቸው ጉድጓዶች

ወፈሩ
ይህ “ያሕዌን ማሰብ ተዉ” ወይም “በራሳቸው ረኩ” የሚለውን ለመናገር ጥቅም ላይ የዋለ ተለዋጭ ዘይቤ ይሆናል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 9:26

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፡-
በእነዚህ ቁጥሮች ሌዋውያን በእስራኤል ሕዝብ ፊት ያሕዌን ማመስገን ቀጠሉ።

እነረሱ ሕግህን ከጀርባቸው ጣሉ
ሕጉ አንድ ሰው እንደሚጥለው እንደማይረባ ነገር ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሕግህን ጥቅም እንደሌለው አሰቡ ከዚህ የተነሳ ለሕጉ ትኩረት አልሰጡትም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሕግህን ጣሉ
እስራኤላውያን የያሕዌን ሕግ ጣሉ

ላሰቃዩአቸው ለጠላቶቻቸው እጅ አሳልፈህ ሰጠሃቸው
እዚህ ላይ “እጅ” የሚያመለክተው ኃይል እና በቁጥጥር ስር ማድረግን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላቶቻቸው እንዲያሸንፏቸውና እንዲያሰቃዩአቸው ፈቀድክ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ከጠላቶቻቸው እጅ ያዳኗቸውን ታዳጊዎች ላክህላቸው
እዚህ ላይ “እጅ” የሚያመለክተው ኃይልና በቁጥጥር ስር ማድረግን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላቶቻቸው እንዳይጎዷቸው ሰዎችን ላክህላቸው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 9:28

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፡-
በእነዚህ ቁጥሮች ሌዋውያን በእስራኤል ሕዝብ ፊት ያሕዌን ማመስገን ቀጠሉ።

እነርሱ ባረፉ ጊዜ ደግመው በአንተ ፊት ክፉን አደረጉ
“እነርሱ” የሚለው ቃል የሚወክለው እስራኤላውንን ሲሆን “አንተ” የሚለው ደግሞ ያሕዌን ይወክላል።

አንተ በጠላቶቻቸው እጅ ተውካቸው
እዚህ ላይ “እጅ” የሚለው ኃይል እና በቁጥጥር ስር ማድረግን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ ተውኻቸው ጠላቶቻቸውም እንዲያሸንፏቸው አደረግህ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ትዕዛዝህን አልሰሙም
“መስማት” ለሚለው ቃል “መታዘዝ” የሚል ተመሳሳይ ትርጉም ያለው ቃል በቋንቋችሁ ካለ እዚህ ላይ እሱን መጠቀም ትችላላችሁ።

ለሚታዘዛቸው ለማንኛውም ሰው ሕይወትን የሚሰጡት ትዕዛዞችህ
እዚህ ክፍል ላይ ያሕዌ ራሱ እንደ ሕግጋቱና ትዕዛዛቱ ተደርጎ ነው የተነገረው። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ ትዕዛዝህን ለሚጠብቁ ሁሉ ሕይወትን የምትሰጥ ነህ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እምቢተኛ ሆነው ጀርባቸውን አዞሩብህ፤ አንገታቸውን አደነደኑ
እነዚህ መግለጫዎች አንድ በሬ ባለቤቱ በጫንቃው ላይ ቀንበር ሊያስረው ሲሞክር እምቢተኛ መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው። እዚህ ላይ ያሉት ተለዋጭ ዘይቤዎች ሕዝቡ አንገተ ደንዳና እንደሆነ የሚያሳዩ ናቸው።

Nehemiah 9:30

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፡-
በእነዚህ ቁጥሮች ሌዋውያን በእስራኤል ሕዝብ ፊት ያሕዌን ማመስገን ቀጠሉ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በዙሪያቸው ባሉ አሕዛብ እጅ አሳልፈህ ሰጠሃቸው
እዚህ ላይ “እጅ” የሚለው የሚያሳየው ኃይልንና በቁጥጥር ስር ማዋልን ነው። ይህ በነህምያ 9:27 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ። አማራጭ ትርጉም፡- “በዙሪያቸው ያሉ አሕዛብ እንዲያሸንፏቸው አደረግህ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ሰጠህ
ያሕዌ ሰጠ

ፈጽመህ አላጠፋሃቸውም
“አላጠፋሃቸውም”

Nehemiah 9:32

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፡-
በእነዚህ ቁጥሮች ሌዋውያን በእስራኤል ሕዝብ ፊት ያሕዌን ማመስገን ቀጠሉ።

እስከዛሬ ድረስ ... የደረሰብን መከራ ሁሉ በፊትህ ጥቂት መስሎ አይታይህ
ይህን ዓርፍተ ነገር ለሁለት መክፈል ይቻላል። “ለአንተ መከራው ጥቂት መስሎ አይታይህ። መከራው እስከዛሬ ድረስ በእኛ ላይ እየደረሰብን ነው።”

መከራ ... የደረሰብን ... የደረሰብን ሁሉ
“የደረሰብን” የሚለው ሐረግ እነዚህን መጥፎ ነገሮች የሚያደርሷቸው ሰዎች እንደሆኑ የሚናገር ነው።አማራጭ ትርጉም፡- “ጉዳት ... የተሰቃየነው ... የተሰቃየነው ሁሉ” (ሰውኛ የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 9:35

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፡-
በእነዚህ ቁጥሮች ሌዋውያን በእስራኤል ሕዝብ ፊት ያሕዌን ማመስገን ቀጠሉ።

ለእነርሱ ባደረግኸው ባንተ ታላቅ መልካምነት እየተደሰቱ
“በሰጠሃቸው መልካም ነገሮች እየተደሰቱ”

አላገለገሉህም
“ለሕግህና ለትምህርትህ ታዛዥ አልነበሩም”

Nehemiah 9:36

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፡-
በእነዚህ ቁጥሮች ሌዋውያን በእስራኤል ሕዝብ ፊት ያሕዌን ማመስገን ቀጠሉል።

መልካም ስጦታዋን
“በውስጧ ያለውን መልካም ነገር በሙሉ” ወይም “ከእርሷ የምናገኘውን መልካም ነገር በሙሉ”

Nehemiah 9:38

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፡-
በእነዚህ ቁጥሮች ሌዋውያን በእስራኤል ሕዝብ ፊት ያሕዌን ማመስገን ቀጠሉ።

በእነዚህ ምክንያት
ሕዝቡ ያሕዌን ባለመታዘዙ እና ያሕዌም ሕዝቡን ስለቀጣ

በታሸገው ሰነድ ላይ ስሞች አሉ
ሰነዱ ከመታሸጉ በፊት ሰዎቹ ስማቸውን በሰነዱ ላይ ጽፈው እንደነበር አንባቢው መረዳት አለበት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 10

1 በስምምቱ ላይ የፈረሙት የስማቸው ዝርዝር ይህ ነው፡ 2 በጽሁፉ ላይ የፈረሙ ካህናት እነዚህ ናቸው፡ ሠራያ፣ ዓዛርያስ፣ ኤርምያስ 3 ፉስኮር፣ አማርያ፣ መልክያ፣ 4 ሐጡስ፣ ሰበንያ፣ መሉክ 5 ካሪም፣ ሜሪምት፣ አብድዩ 6 ዳንኤል፣ ጌንቶን፣ ባሮክ 7 ሜሱላም፣ አብያ፣ ሚያሚን፣ 8 መዓዝያ፣ ቤልጋይ፣ ሸማያ እነዚህ ካህናት ነበሩ። 9 የፈረሙት ሌዋውያን ትውልዶች እነዚህ ነበሩ፡ የአዛንያ ልጅ ኢያሱ፣ ቤንዊ፣ ከኤንሐዳድ፣ ቀድምኤል፣ 10 ሰባንያ፣ ሆዲያ፣ ቆሊጣስ፣ ፈልያ፣ ሐናን 11 ሚካ፣ ሪአብ፣ ሐሸብያ፣ 12 ዘኩርር ሰራብያ፣ ሰበንያ፣ 13 ሆዲያ፣ ባኒ፣ ብኒኑ። 14 በመጽሐፍ ጥቅሉ ላይ የፈረሙት የእስራኤል መሪዎች እነዚህ ነበሩ፡ ፋሮስ፣ ፈሐት፣ ሞዓብ፣ ኤላም፣ ዛቱዕ፣ ባኒ። 15 ቡኒ፣ ዓዝጋድ፣ ቤባይ፣ 16 አዶንያስ፣ በጉዋይ፣ ዓዲን 17 አጤር፣ ሕዝቅያስ፣ ዓዙር፣ 18 ሆዲያ፣ ሐሱም፣ ቤሳይ 19 ሐሪፍ፣ ዓናቶት፣ ኖባይ፣ 20 መግጲዓስ፣ ሜሱላም፣ ኤዘር 21 ሜሴዜቤል፣ ሳዶቅ፣ ያጹአ፣ 22 ፈለጥያ፣ ሐናን፣ ዓናያ፣ 23 ሆሴዕ፣ ሐናንያ፣ አሱብ፣ 24 አሎኤስ፣ ፈልሃ፣ ሶቤቅ 25 ሬሁም፣ ሐሰብና፣ መዕሤያ፣ 26 አኪያ፣ ሐናን፣ ዓናን፣ 27 ሙሉክ፣ ካሪምና በዓና። 28 ካህናቱን በር ጠባቂዎቹን፣ ዘማሪዎቹን እና የመቅደስ ሰራተኞቹን ጨምሮ የቀረው ሕዝብ የከበረ ስምምነት አደረጉ። እንደዚሁም አገራቸውን ለቀው የወጡትንና በእስራኤል ይኖሩ የነበሩትን ጎረቤቶቻቸው ከሆኑ ከሌሎች ህዝቦች ወንዶችን ሁሉ ጨመሩ። እነዚህ ወንዶች ከሚስቶቻቸውና የሚያደርጉትን ለይተው ከሚያውቁ ከፍ ካሉ ወንድና ሴት ልጆቻቸው ጋር ሆነው የእግዚአብሔርን ህግ እንደሚጠበቁ ቃል ገቡ። 29 ይህን የከበረ ስምምነት ተግባራዊ ለማድረግ ሁሉም ከመሪዎቻቸው ጋር ተባበሩ። እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠውን ህግጋት ሁሉ ለመታዘዝ ተስማሙ። ያህዌ አምላካችን ያዘዘውን፣ ድንጋጌዎቹንና ትዕዛዛቱን ሁሉ ለመከተልና ለመፈፀም ተስማሙ። ተከታዩን ለማድረግ ቃል ገቡ። 30 “ሴቶች ልጆቻችን ያህዌን የማያመልኩትን የዚህ ምድር ሰዎች እንዲያገቡ አንሰጥም፣ ወንድ ልጆቻችን ሴት ልጆቻቸውን እንዲያገቡም አንፈቅድም። 31 ምድር የሚኖሩ የሌላ አገር ሰዎች በሰንበት ወይም በሌላ በተቀደሰ ቀን እህል ወይም ሌሎች ነገሮችን ሊሸጡልን ቢያመጡ፣ አንዳች ነገር አንገዛቸውም። እናም በየሰባት አመቱ አንዴ ለምድሪቱ እረፍት እንሰጣለን፤ በዚያን አንድ አመት ምንም አይነት እህል አንዘራም፤ እንዲሁም ለሌሎች አይሁዶች እዳቸውን ሁሉ እንሰርዛለን። 32 እንዲሁም እያንዳንዳችን ቤተ መቅደሱን ለሚያገለግሉና ለሚንከባከቡ በየአመቱ 5 ግራም ብር ለመክፈል ቃል ገባን። 33 በዚያ ገንዘብ እነዚህን ነገሮች መግዛት ይችላሉ፡ በእግዚአብሔር ፊት በገበታው ላይ የሚቀርብ ዳቦ፣ በእያንዳንዱ ቀን በመሰዊያው ላይ የሚቀርብ የእህል ቁርባን፣ በመሰዊያ ላይ ታርደው ሙሉ ለሙሉ የሚቃጠሉ እንስሳት፣ ለእግዚአብሔር በሰንበት የሚርቡ የተቀደሱ መስዋዕቶች እና የአዲስ ጨረቃ በዓልን ለማክበርና ለሌሎች በዓላት መስዋዕቶች፣ ለእስራኤል ህዝቦች ኃጢአት መስዋዕት የሚሆኑ እንስሳት፣ እና ማናቸውም የቤተመቅደሱን ሥራ ለመንከባከብ የሚያስፈልጉ ሌሎች ነገሮች መግዛት ይችላሉ። 34 በየአመቱ ካህናቱ፣ ካህናቱን የሚረዱ የሌዊ ትውልዶች እና የተቀረነው በእግዚአብሔር ሕግ እንደተፃፈው በዚያ አመት ከሌዋውያን መሃል የትኛው ቤተሰብ በአምካላችን በእግዚአብሔር ቤት መስዋዕቶቹን ለማቅረብ በመሰዊያው ላይ የሚነደውን እንጨት እንደሚያቀርቡ ለመወሰን እጣዎችን እንጥላለን። 35 በእያንዳንዱ አመት እያንዳንዱ ቤተሰብ በእርሻችን ካበቀልነውና ለምግብ ካጨድነው እንዲሁም በዚያ አመት ከፍራፍሬ ዛፎች የተገኘውን በኩራት መስዋዕት አድረገን ወደ ቤተ መቅደስ ለማምጣት ቃል እንገባለን። 36 የበኩር ወንድ ልጆችንና የላም፣ የበግና የፍየል በኩሮችን ለእግዚአብሔር መታሰቢያ አድርገን ወደ እግዚአብሔር ቤት እናመጣለን። ማድረግ የሚገባን፣ በእግዚአብሔር ሕግጋት የተፃፈው ይህ ነው። 37 በየአመቱ ካመረትነው እህል ከበኩራቱ የተዘጋጀ ዱቄት ለካህናቱ ወደ ቤተ መቅደስ እናመጣለን፣ እንዲሁም ሌሎች የወይን፣ የወይራ ዘይትና የፍራፍሬ መስዋዕቶችንም ከበኩራቱ እናመጣለን። ካህናቱን ለሚረዱ የሌዊ ትውልዶች አስራቶችንም እናመጣለን። 38 የአሮን ትውልድ የሆነ አንድ ካህን፣ ከሌዋውያን ጋር ሆኖ አስራቶችን ሲሰበስቡ አብሮ ይገኛል። ከዚያ የሌዊ ትውልዶች ድርሻቸውን ይወስዳሉ፤ ህዝቡ ካመጣው ነገሮች አንድ አስረኛውን ይወስዱና በቤተ መቅደስ በግምጃ ቤት ያስቀምጣሉ። 39 የሌዊ ትወልዶችና አንዳንድ የእስራኤል ሰዎች በቤተ መቅደስ ለሚያገለግሉ የእህል፣ የወይን፣ እና የወይራ ዘይት ስጦታዎችን የተለያዩ መገልገያዎች ወደ ሚከማቹበት ግምጃ ቤቶች መውሰድ አለባቸው። በዚያን ጊዜ የሚያገለግሉ ካህናት፣ በር ጠባቂዎች፣ እና በቤተ መቅደስ የሚዘምሩ የዝማሬ ቡድን የሚኖሩበት ስፍራ ይህ ነው። “የአምላካችንን ቤተ መቅደስ ከመጠበቅ ቸል እንደማንል ቃል እንገባለን።”

Nehemiah 10:1

በታሸገው ላይ የነበሩት ነህምያ ... መልክያ
የእነዚህ ሰዎች ስም በሰነዱ ላይ ተጽፎ ነበር። ይህ በግልጽ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በታሸገው ሰነድ ላይ የነህምያ ... መልክያ ስሞች ነበሩ” ወይም “በታሸገው ሰነድ ላይ የሚከተሉት ሰዎች ስም ነበር፡- እነርሱም፡ ነህምያ ... መልክያ” (ግምታዊ እውቀት እና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የታሸጉ ሰነዶች
ስሞቹ በሰነዶቹ ላይ ከተጻፉ በኋላ ሰነዶቹ ታሽገዋል።

የታሸጉ ሰነዶች
ስሞቹ በሰነዶቹ ላይ ከተጻፉ በኋላ ሰነዶቹ ታሽገዋል።

ነህምያ
አንዳንዶች ይህን መጽሐፍ የጻፈው ነህምያ እንደሆነ ያምናሉ ለዚህም ነው ስለ ራሱ ሌላ ሰው እንደሆነ አድርጎ የሚናገረው ምክንያቱም ይህ ሰነድ ሕጋዊ የስም ዝርዝር ስለሆነ ነው። (ተውላጠ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ሐካልያ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህ በነህምያ 1፡1 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ሴዴቅያስ፣ ሠራያ ... ኤርምያስ፣ ፋስኮር፣ አማርያ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ዓዛርያስ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህ በነህምያ 3፡23 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

መልክያ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህ በነህምያ 3፡11 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 10:4

አጠቃላይ መረጃ፡-
በእነዚህ ጥቅሶች ነህምያ በታሸገው ሰነድ ላይ የፈረሙትን የካህናት ስም ዝርዝሯል (ነህምያ 10፡1 ን ይመልቱ)

ሐጡስ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህ በነህምያ 3፡10 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሰበንያ ... ሜሱላም
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። ይህ በነህምያ 9:4 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

መሉክ ... አብድዩ፣ ዳንኤል፣ ጌንቶን ... አብያ፣ ሚሚን፣ መዓዝያ፣ ቤልጋል
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ካሪም
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህ በነህምያ 3:11 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ሜሪሞት
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህ በነህምያ 3:4 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ባሮክ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህ በነህምያ 3:20 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ሸማያ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህ በነህምያ 3:29 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ ካህናት ነበሩ
ይህ ከላይ የተዘረዘሩት ስማቸው በታሸገው ሰነድ ላይ የፈረሙት ሰዎች ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እነዚህ በሰነዱ ላይ የፈረሙት ካህናት ስሞች ናቸው” (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 10:9

አጠቃላይ መረጃ፦
በእነዚህ ቁጥሮች ነህምያ በታሸገው ሰነድ ላይ የፈረሙትን የካህናት ስም መዘርዘር ቀጠለ።

ሌዋውያኑም ... ነበሩ
ይህ ስማቸው በታሸገው ሰነድ ላይ ስማቸውን ያስቀመጡትን ሰዎች ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “በታሸገው ሰነድ ላይ ስማቸውን ያስቀመጡ ሌዋውያን እነዚህ ነበሩ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ኢያሱ ... ኤንሐዳድ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። ይህ በነህምያ 3:18-19 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

አዛንያ ... ረአብ ... ቢንዊ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ቢንዊ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህ በነህምያ 3:24 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ቀድምኤል
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህ በነህምያ 7:43 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባንያ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህ በነህምያ 9:4 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ሆዲያ ... ቆሊጣስ ... ፌልያ ... ሰራብያ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። ይህ በነህምያ 8:7 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ሐናን
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህ በነህምያ 7:49 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ሚካ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህ በነህምያ 10:11 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ሐሸብያ ... ባኒ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። ይህ በነህምያ 3:17 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ዘኩር
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህ በነህምያ 3:2 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

የሕዝቡ መሪዎቹም
ይህ በታሸገው ሰነድ ላይ ስማቸው ያሰፈሩትን ሰዎች ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “በታሸገው ሰነድ ላይ ስማቸው ያሰፈሩት የሕዝቡ መሪዎች እነዚህ ናቸው” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ፋሮስ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህ በነህምያ 3:25 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ፈሐት ሞዓብ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህ በነህምያ 3:11 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ኤላም ... ዛቱዕ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። ይህ በነህምያ 7:12 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 10:15

አጠቃላይ መረጃዎች፦
በእነዚህ ቁጥሮች ነህምያ በታሸገው ሰነድ ላይ የፈረሙትን ሰዎች ስም መዘርዘር ቀጠለ።

ቡኒ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህ በነህምያ 9:4 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ዓዝጋድ፣ ቤባይ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። ይህ በነህምያ 7:16-17 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

አዶንያስ ... ዓዙር ... ኖባይ ... መግጲዓስ ... ኤዚር .. ያዱአ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

በጉዋይ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህ በነህምያ 7:7 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ዓዲን፣ አጤር፣ ሕዝቅያስ፣ ... ሐሱም
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። ይህ በነህምያ 7:20 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ሆዲያ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህ በነህምያ 8:7 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ቤሳይ፣ ሐሪፍ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። ይህ በነህምያ 7:23 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ዓናቶት
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህ በነህምያ 7:27 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ሜሱላም ... ሜሴዜቤል፣ ሳዶቅ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። ይህ በነህምያ 3:4 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 10:22

አጠቃላየ መረጃዎች፡-
በእነዚህ ቁጥሮች ነህምያ በታሸገው ሰነድ ላይ የፈረሙትን ሰዎች ስም መዘርዘር ቀጠለ።

ፈላጥ ... ሆሴዕ ... ፈለሃ ... ሶቤቅ .. ሐሰብና ... አኪያ ... ዓናን ... ካሪም .. በዓና
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ሐናን
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህ በነህምያ 7:49 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ዓናያ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህ በነህምያ 8:4 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ሐናንያ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህ በነህምያ 3:8 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

አሱብ ... ኤሎኤስ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። ይህ በነህምያ 3:11 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ሬሁም
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህ በነህምያ 3:17 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

መዕሤያ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህ በነህምያ 3:23 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

መሉክ፣ ካሪም
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። ይህ በነህምያ 10:4 ላይ እንዴ እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

በዓና
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 10:28

በር ጠባቂዎች
ይህ ወደ ከተማው ወይም ወደ መቅደሱ የሚገባውን ሰው ለመቆጣጠርና ገዢው በወሰነው ምክንያት በተወሰነ ጊዜያቶች በሩን እንዲከፍቱና እንዲዘጉ በእያንዳንዱ በር ላይ የተመደቡትን ሰዎች ያመለክታል። ይህ በነህምያ 7:1 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።

ዘማሪዎች
እነዚህ በመቅደስ ውስጥ ይዘምሩ የነበሩ ሰዎች መሆናቸውን ግልጽ ማድረግ ያስፈልግ ይሆናል። አማራጭ ትርጉም፡- “የመቅደስ ዘማሪዎች”

የሚያውቁትና የሚያስተውሉት
ይህ ሐረግ ትርጉሙ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔርን መታዘዝ ምን እደሆነና የሚከተለው ተስፋ ምን ማለት እንደሆነ ለመረዳት እድሜአቸው የደረሰ በሙሉ” (ግምታዊ እውቀትና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ወንድሞቻቸው፣ አለቆቻቸው
“አለቃ የሆኑ ወንድሞቻቸው” ወይም “መሪዎች የሆኑ ወንድሞቻቸው” እነዚህ ሐረጎች የሚያመለክቱት ስለተመሳሳይ ሰው ነው።

በእርግማንና በመሃላ ራሳቸውን አሰሩ
ይህ መኃላና እርግማን ስለወሰዱ ሰዎች ይናገራል፣ መኃላቸው ደግሞ ሰውነታቸውን አጥብቆ እንዳሰረ ገመድ ተደርጎ የሚቆጠር ነበር። አማራጭ ትርጉም፡- “ለመኃላና ለእርግማን ማረጋገጫ ሰጡ” ወይም “ቃላቸውን ባይጠብቁ እርግማን ወደራሳቸው ለመጥራት መኃላ ገቡ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ሕግ ለመራመድ **to**
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በእግዚአብሔር ሕግ ለመኖር” ወይም “የእግዚአብሔርን ሕግ ለመታዘዝ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ባርያ በሙሴ የተሰጠው
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእግዚአብሔር ባርያ ሙሴ ለእስራኤል የሰጠው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ለመከታተል
“ለመከተል”

Nehemiah 10:30

አጠቃላይ መረጃ፡-
በእነዚህ ቁጥሮች ሕዝቡ በነህምያ 10:29 ላይ የገቡትን ቃልኪዳን ይዞታ ይዘረዝራሉ።

ሴት ልጆቻችንን በምድሪቱ ለሚኖሩ አሕዛብ አንሰጥም ወይም የእነርሱንም ሴት ልጆቻቸውን ለወንድ ልጆቻችን አንወስድም
ይህ ማለት ወንድና ሴት ልጆቻቸው እነርሱን እንዲያቡ አይፈቅዱም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሴት ልጆቻችንን በምድሪቱ የሚኖሩ አሕዛብ እንዲያገቧቸው አንሰጥም ወይም ወንድ ልጆቻችን እንዲያገቧቸው የእነርሱ ሴት ልጆቻቸው አንወስድም” (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለምድሪቱ ሕዝበ
ይህ በምድራቸው እየኖሩ ግን ያሕዌን የማያመልኩትን ሕዝቦች ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ያሕዌን የማያመልኩ የምድሪቱ ሕዝቦች” (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ቃል ገብተናል ... አንሰጥም ... አንገዛም ... እናደርጋለን ... እናጠፋለን
በዚህ ያለው “እኛ” የሚለው ተወላጠ ስም ነህምያና አይሁዳውያንን የሚያካትት ነው ነገር ግን የዚህን መጽሐፍ አንባቢዎችን አይጨምርም። (አካታችና ኢ-አካታች “እኛ” የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባተኛው አመት
“7ኛ አመት” (ደረጃን የሚያሳዩ ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

እርሻዎቻችንን እናሳርፋለን
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እርሻዎቻችንን አናርስም” ወይም “በእርሻዎቻችን ላይ ምንም ነገር አንዘራም” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

እዳን በሙሉ ማስከፈል እንተዋለን
ይህ ማለት ሰዎች በእነርሱ ላይ ያለባቸውን እዳ እንዲከፍሉ አያስገድዱም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰዎች በእኛ ላይ ያለባቸውን እዳ እንሰርዛለን” ወይም “ለሰዎች እዳቸውን እንደተውነውና መክፈል እንደማይጠበቅባቸው እንነግራቸዋለን”

Nehemiah 10:32

አጠቃላይ መረጃ፦
በእነዚህ ቁጥሮች ሕዝቡ በነህምያ 10፡29 ላይ የገቡትን ቃልኪዳን ይዘታ መዘርዘር ይቀጥላሉ።

ትዕዛዙን ተቀበልን
“ትዕዛዙን ለመታዘዝ ቃል ገባን”

ተቀበልን
በዚህ ላይ ያለው “እኛ” የሚለው ተውላጠ ስም ከካህኑና ከሌዋውያኑ በስተቀር ሁሉንም እስራኤላውያንንና ነህምያን ያካትታል። የዚህን መጽሐፍ አንባቢ አያካትትም። (አካታች እና ኢ-አካታች “እኛ” የሚለውን ይመልከቱ)

የሰቅል ሲሶ
“የሰቅል አንድ ሶስተኛ።” “አንድ ሶስተኛ” ማለት ከሶስት እኩል መጠን ያላቸው ነገሮች መካከል አንዱ ማለት ነው። ይህ በዘመናዊ መለኪያዎች መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “5 ግራም ብር” (መጽሐፍ ቅዱሳዊ መገበያያ ገንዘቦች እና ክፍልፋዮች የሚለውን ይመልከቱ)

ለአገልግሎት
“ለእንክብካቤው መክፈል”

ለገጸ ሕብስቱም
ይህ የሚናገረው እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር መሆኑን ለማሳየት በምሳሌነት ጥቅም ላይ የሚውሉት በመቅደስ ውስጥ ስለሚቀመጡት ያለ እርሾ ስለሚጋገሩት ስለ 12 ሕብስቶች ነው።

ለአዲስ ጨረቃ በዓላት
እነዚህ ጨረቃ በሰማይ ላይ ትንሽ ሆና በምትታይበት ጊዜ የሚከበሩ በዓላት ነበሩ።

Nehemiah 10:34

አጠቃላይ መረጃ፦
በእነዚህ ቁጥሮች ሕዝቡ በነህምያ 10፡29 ላይ የገቡትን ቃልኪዳን ይዘታ መዘርዘር ይቀጥላሉ።

እንዲቃጠል
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሌዋውያን እንዲያቃጥሉት” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደተጻፈው
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እንደሚናገር” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተግብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ከመሬታችን
“በመሬታችን” ወይም “በምድራችን”

Nehemiah 10:37

አጠቃላይ መረጃዎች፦
በእነዚህ ቁጥሮች ሕዝቡ በነህምያ 10፡29 ላይ የገቡትን ቃልኪዳን ይዘታ መዘርዘር ይቀጥላሉ።

እኛ እናመጣለን ... እኛ እናመጣለን
እዚህ ላይ “እኛ” የሚለው ተውላጠ ስም ከካህኑና ከሌዋውያኑ በስተቀር ሁሉንም እስራኤላውያንና ነህምያን ይወክላል። የዚህን መጽሐፍ አንባቢ አይጨምርም። (አካታችና ኢ-አካታች “እኛ” የሚለውን ይመልከቱ)

ቡሆአችንን
ለዚህ አማራጭ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት 1) ከሸካራ ዱቄት የተሰራ ሊጥ 2) ሸካራ ዱቄት ወይም 3) የተፈጨ እህል

አዲሱን ወይንና ዘይቱን
“በኩራት” የሚለው ቃል ከዓርፍተ ነገሩ መጀመርያ ጀምሮ ገልጽ ነው። እነዚህ ሊደጋገሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ከአዲሱ ወይንና ዘይት የመጀመርያውን” ወይም “ከአዲሱ ወይንና ዘይት ምርጡን” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ አምላካችን ቤት እቃ ቤቶች
“በመቅደስ ውስጥ እቃዎች የሚቀመጡበት ክፍል”

የመሬታችንን አስራት
እዚህ ላይ “መሬታችን” የሚለው በመሬት ላይ የሚበቅለውን ነገር በሙሉ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በመሬታችን ከምናበቅለው ነገር አስራት” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

አስራት ይቀበላሉ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሕዝቡ አስራቱን ይሰጣቸዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ አስረኛ
ይህ ከአስር እኩል መጠን ያላቸው ክፍሎች አንዱ ክፍል ማለት ነው። (ክፍልፋዮች የሚለውን ይመልከቱ)

በማከማቻ ቤት ያሉ ዕቃ ቤቶች
“በመቅደስ ውስጥ ያሉ እቃ ቤቶች”

Nehemiah 10:39

አጠቃላይ መረጃ፦
በእነዚህ ቁጥሮች ላይ ሕዝቡ በነህምያ 10፡29 ላይ የገቡትን መሃላ ይዘታ ዝርዝር በመናገር ጨረሰ።

የመቅደስ እቃዎች የሚቀመጡበት ማከማቻ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ለመቅደስ የሚጠቀሙበትን እቃዎች ካህናቱ የሚያስቀምጡበት እቃ ማስቀመጫ ክፍል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የአምላካችንን ቤት አንተውም
ይህ በአዎንታዊ መንገድ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ እንጠብቃለን”

እኛ እናደርጋለን
በዚህ ውስጥ ያለው “እኛ” የሚለው ተውላጠ ስም ነህምያንና ሁሉንም የእስራኤል ሕዝቦችን ያካትታል ነገር ግን የዚህን መጽሐፍ አንባቢ አይጨምርም። (አካታችና ኢ-አካታች “እኛ” የሚለውን ይመልከቱ)

ሕዝቡ ዕጣ ተጣጣሉ
ሕዝቡ ባለቀለም ጠጠሮችን ጣሉ።

ከአስሩ ሕዝቦች አንዱን ለመውሰደ
“ከአስር ቤተሰብ አንዱን ቤተሰብ ለመውሰድ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 11

1 የእስራኤል መሪዎችና ቤተሰቦቻቸው በኢየሩሳሌም ተቀመጡ። ለእግዚአብሔር በተለየችው ከተማ የሚኖሩትን ከአስሩ ቤተሰብ አንዱን ለመለየት የተቀሩት
ሰዎች እጣ ተጣጣሉ። 2 በኢየሩሳሌም ለመኖር ፈቃደኛ የሆኑትን ሰዎች እግዚአብሔር እንዲባርካቸው ጸለዩላቸው። 3 እነዚህ ቢየሩሳሌም ለመኖር የመጡት
የአውራጃው ባለስልጣናት ናቸው። ነገር ግን በይሁዳ ከተሞች እያንዳንዱ በየራሱ ቤተሰብ ንብረት በየራሱ ከተማ ኖረ። አንዳንዶች ካህናት፣ ሌዋውያን፣
የቤተመቅደስ አገልጋዮች እና የሰለሞን አገልጋዮች ትውልዶች የሆኑ እስራኤላውያን በኢየሩሳሌም ውስጥ ለመኖር መጡ። 4 ነገር ግን አንዳንድ የይሁዳ ሰዎች
እና የብንያም ሰዎች በኢየሩሳሌም ቆዩ በዚያም ኖሩ። እነዚህ ከይሁዳ ወገን ናቸው። የፋሬስ ትውልድ፣ የመላልኤል ልጅ፣ የሶፋጥያስ ልጅ፣ የአማርያ ልጅ፣
የዘካርያስ ልጅ፣ የኦዝያ ልጅ አታያ ናቸው። 5 እና የይሁዳ ልጅ ሴሎ ትውልድ የሆነው የዘካርያስ ልጅ፣ የዮያሪብ ልጅ፣ የዓዳያ ልጅ፣ የኦዛያ ልጅ፣ የኮልሖዜ ልጅ
የባሮክ ልጅ መዕሤያ ነበር። 6 በኢየሩሳሌም የተቀመጡት የፋሬስ ትውልዶች 468 ወንዶች ነበሩ። 7 ከብንያም ትውልድ በኢየሩሳሌም ለመኖር ከወሰነው ጎሳ
ሰዎች መሀል አንዱ የየሻያ ልጅ፣ የኢቲኤል ልጅ የመዕሤያ ልጅ፣ የቆላያ ልጅ፣ የፈዳያ ልጅ፣ የዮእድ ልጅ፣ የሜሱላም ልጅ ሰሉ ነው። 8 የሳሉ ሁለቱ ቤተ ዘመዶች
ጌቤ እና ሳላይም በኢየሩሳሌም ተቀመጡ። በአጠቃላይ ከብንያም ጎሣ 928 ሰዎች በኢየሩሳሌም ተቀመጡ። 9 መሪያቸው ዝክሪ ነበር። በኢየሩሳሌም
በሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው ሹም ሐስኑአ ነበር። 10 በኢየሩሳሌም የተቀመጡት ካህናት የዮያሪብ ልጅ ዮዳኤ፣ 11 አስቀድሞ የካህናቱ ሁሉ መሪ የነበረው
የአኪጦብ ልጅ የመራዮት ልጅ፣ የሳዶቅ ልጅ የሜሱላም ልጅ የኪልቅያስ ልጅ ሠራያ ነበር። 12 በአጠቃላይ ከዚያ ነገድ የቤተ መቅደሱ ሠራተኞች 822 ሰዎች
ናቸው። በኢየሩሳሌም የተቀመጠ ሌላው ካህን የመልክያ ልጅ፣ የፋስኮር ልጅ፣ የዘካርያስ ልጅ የአማሲ ልጅ፣ የፈለልያ ልጅ የይሮሐም ልጅ ዓዳያ ነበር። 13
በኢየሩሳሌም የተቀመጡ የዚያ ነገድ መሪዎች በጠቅላላው 242 አባላት ነበሩ። በኢየሩሳሌም የተቀመጠው ሌላው ካህን የአሜር ልጅ፣ የምሺሌሞት ልጅ፣
የአሕዛይ ልጅ፣ የኤዝርኤል ልጅ፣ አማስያ ነበር። 14 ከዚያ ነገድ ደፋር የሆኑ 128 ወታደሮች በኢየሩሳሌም ተቀመጡ። የእነርሱ መሪ የሐግዶሊም ልጅ
ዘብድኤል ነበር። 15 በኢየሩሳሌም የተቀመጠው ሌላው የሌዊ ትውልድ የቡኒ ልጅ የአሳብያ ልጅ፣ የዓዝሪቃም ልጅ፣ የአሱብ ልጅ ሻማያ ነበር። 16 ከቤ
ተመቅደሱ ውጭ ያለውን ሥራ የሚከታተሉ ሁለቱ ሌዋውያን ታላላቅ ሰዎች ሳባታይ እና ዮዛባት ነበሩ። 17 ሌላው የአሳፍ ልጅ፣ የዘብዲ ልጅ፣ የሚካ ልጅ መታንያ
ነበር። መታንያ የቤተ መቅደሱ የመዘምራን ቡድን እግዚአብሔርን ለማመስገን ዝማሬ ሲያቀርብ ቡድኑን ይመራ ነበር። ረዳቱ በቅበቃር ነበር። ሌላው በኢየሩሳሌም
የተቀመጠው የኤዶታም ልጅ፣ የጋላል ልጅ፣ የሳሙኤል ልጅ አብድያ ነበር። 18 በጠቅላላው፣ ለእግዚአብሔር በተለየችው ከተማ 284 ሌዋውያን ነበሩ። 19
በኢየሩሳሌም የተቀመጡት በር ጠባቂዎች ዓቁብ እና ጤልሞን ነበሩ። እነርሱና በአጠቃላይ በኢየሩሳሌም የተቀመጡ ቤተሰቦቸው 172 ነበሩ። 20 ሌሎቹ
የእስራኤል ትውልዶች የሌዊና ካህናትን ትውልዶች ጨምሮ በገዛ ይዞታቸውና በሌሎች ከተሞችና በይሁዳ ከተማዎች ተቀመጡ። 21 የቤተ መቅደሱ ሰራተኞች
ግን በኦፌል ኮረብታ ኢየሩሳሌም ውስጥ ተቀመጡ። እነርሱን የሚያዙት ሲሐ እና ጊሽጳ ነበሩ። 22 በኢየሩሳሌም የሚኖሩት የሌዊ ትውልዶች አለቃ የሚካ ልጅ፣
የመታንያ ልጅ፣ የሐሻብ ልጅ፣ የባኒ ልጅ ኦዚ ነበር። ኦዚ የአሳፍ ነገድ፣ በቤተ መቅደስ የዝማሬ ክፍሉ ሀላፊ ወገን ነበር። 23 የፋርስ ንጉስ እያንዳንዱ ነገድ
በእያንዳንዱ ቀን በቤተ መቅደስ በሚቀርበው ዝማሬ እያንዳንዱ ነገድ የሚሰራውን ነገዶቹ እንዲወስኑ ትዕዛዝ ሰጠ። 24 የይሁዳ ትውልድ የዛራ ነገድ የሆነው
የሜሴዜቤል ልጅ ፈታያ በፋርስ መንግስት የእስራኤል አምባሳደር ነበር። 25 በኢየሩሳሌም ያልተቀመጡት አንዳንድ ሰዎች በእርሻቸው አቅራቢያ በሚገኙ
መንደሮች ይኖሩ ነበር። ከይሁዳ ነገድ የሆኑ አንዳንዶች በቂርያት አርባቅ፣ በዲቦን፣ እና በይቀብጽኤል አጠገብ በሚገኙ መንደሮች ኖሩ። 26 አንዳንዶቹ በኢያሱ፣
በምላዳ፣ በቤትጳሌጥ፣ 27 በሐጸርሹዓል እና በቤርሳቤህ እንዲሁም በአቀራቢያው ባሉ መንደሮች ኖሩ። 28 ሌሎቹ በጺቅላግ፣ በምኮና እና በአካባቢው ባሉ
መንደሮች፣ 29 በዓይንሪሞን፣ በጸርዓ፣ በየርሙት፣ 30 በዛኖዋ፣ በዓዶላም፣ እና በእነዚያ ከተሞች አቅራቢያ ተቀመጡ። አንዳንዶቹ በለኪሶ እና በአካባቢ ባሉ
መንደሮች፣ እንዲሁም አንዳንዶች በዓዜቃና በአካባቢዋ ባሉ መንደሮች ተቀመጡ። እነዚህ ሁሉ ህዝቦች በደቡብ በቤርሳቤህ መሀል ባሉ ስፍራዎች እና በሰሜን
ቦኖም ሸለቆ በኢየሩሳሌም ዳርቻ በይሁዳ ተቀመጡ። 31 የብንያም ጎሣ ሰዎች በጌባ፣ ማክማስ፣ በጋያ ይህ አይ ቤቴል ተብሎም ይታወቃል፣ እና በአካባቢው
ባሉ መንደሮች፣ 32 በዓናቶች፣ በኖብ፣ በሐናንያ፣ 33 በሐጾር፣ በራማ፣ በጊቴም፣ 34 በሐዲድ፣ በስቦይም፣ በንቦላት፣ 35 በሎድ፣ በአኖ፣ እና የእጅ ጥበብ
ባለሙያዎች ሸለቆ በሚባሉ ቦታዎች ተቀመጡ። 36 በይሁዳ የኖሩ አንዳንድ ሌዋውያን ከብንያም ሰዎች ጋር ለመኖር ሄዱ።

Nehemiah 11:1

ሕዝቡ ዕጣ ተጣጣሉ
ሕዝቡ ባለቀለም ጠጠሮችን ጣሉ።

ከአስሩ ሕዝቦች አንዱን ለመውሰደ
“ከአስር ቤተሰብ አንዱን ቤተሰብ ለመውሰድ”

Nehemiah 11:3

በየመሬታቸው እስራኤላውያንንም ጨምሮ
“በየመሬታቸው:- እስራኤላውን”

ከይሁዳ ዘሮች አንዳንዶችና ከብንያም ዘሮች አንዳንዶች
“አንዳንድ የይሁዳ ሰዎችና አንዳንድ የብንያም ሰዎች”

የይሁዳ ሰዎች እነዚህን ያካትታሉ:-
“ከይሁዳ ዘር የነበሩት እነዚህ ነበሩ”

ይሁዳ ... ብንያም ... አታያ ... ዖዝያ .... ዘካርያስ ... አማርያ ... ሰፋጥያስ ... መላልኤል ... ፋሬስ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

የፋሬስ ልጆች
“ከፋሬስ ዘር የሆኑ”

Nehemiah 11:5

አያያዥ ዓርፍተ ነገር:-
በእነዚህ ቁጥሮች ነህምያ በኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩትን የግዛት ሹማምንትን መዘርዘር ይቀጥላል።

መዕሤያ ... ባሮክ ... ኮልሖዜ ... ዖዛያ ... ዓዳያ ... ዮያሪብ ... ዘካርያስ ... ፋሬስ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ሴሎናዊ
ይህ የሚያመለክተው ሴሎን ከሚባል መንደር የመጣ ሰውን ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሁሉ **468** ነበሩ
“ሁሉም አራት መቶ ስልሳ ስምነት ነበሩ።” ፋሬስ በኢየሩሳሌም የሚኖሩ 468 ዘሮች ነበሩት። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ብርቱ ሰዎች ነበሩ
“ጽኑዓን ሰዎች ነበሩ” ወይም “ቆራጥ ሰዎች ነበሩ”

Nehemiah 11:7

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፡-
በእነዚህ ቁጥሮች ነህምያ በኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩትን የግዛት ሹማምንትን መዘርዘር ይቀጥላል።

ልጆች እነዚህ ናቸው
“ከዘሮቹ የተወሰኑት እነዚህ ናቸው” የእናንተ ቋንቋ ይህ የእየያንዳንዱ ዘር ዝርዝር እንዳልሆነ ግልጽ ማድረግ አለበት።

ብንያም ... ሰሉ ... ሜሱላም ... ዮእድ ... ፈዳያ ... ቆላያ ... መዕሤያ ... ኢቲኤል ... የሻያ ... ጌቤና ... ሳላይ ... አዩኤል ... ዝክሪ ... ይሁዳ ... ሐስኑአ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

928 ሰዎች
“ዘጠኝ መቶ ሃያ ስምንት ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ነህምያ **11**:**10**-**12** የትርጉም ማስታወሻዎች ዮዳኤ ... ዮያሪብ ... ያኪን ... ሠራያ ... ኬልቅያስ ... ሜሱላም ... ሳዶቅ ... መራዮት ... አኪጦብ ... ዓዳያ ... ይሮሐም ... ፈላልያ ... አማሲ ... ዘካርያስ ... ፋስኮር ... መልክያ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ተባባሪዎቻቸው
“ወንድሞቻቸው” ወይም “ዘመዶቻቸው”

የቤቱን ስራ የሰሩ የነበሩ
“በቤተ መቅደሱ ይሰሩ የነበሩ።” “ቤቱ” የሚለው ቃል የሚናገረው በቀደመው ቁጥር ላይ ስለተነገረው ስለ “እግዚአብሔር ቤት” ነው።

822 ሰዎች
“ስምንት መቶ ሃያ ሁለት ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 11:10

ወንድሞቹ
የይሮሐም ልጅ ዓዳያ (ነህምያ 11:12)

ወንድሞች
ይህ ቃል ተለዋጭ ዘይቤ ነው፣ የሚወክለው ከሚከተሉት አንዱን ነው፡- 1) እስራኤላውያን የሆኑ ወገኖች ወይም 2) ተመሳሳይ ስራን ይሰሩ የነበሩ ሰዎች። አማራጭ ትርጉም፡- “ተባባሪዎች” ወይም “አብረው ይሰሩ የነበሩ ሰራተኞች” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

242 ሰዎች
“ሁለት መቶ አርባ ሁለት ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

አማስያ ... ኤዝርኤል ... አሕዛይ ... ምሺሌሞት ... አሜር ... ዘብድኤል ... ሐግዶሊም
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

128 ብርቱ ተዋጊ ሰዎች **128**
“አንድ መቶ ሃያ ስምንት ብርቱ ተዋጊ ሰዎች” እነዚህ እጅግ “ብርቱ” እና “ደፋር” ተዋጊዎች ነበሩ። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 11:13

ሻማያ ... አሱብ ... አሳብያ ... ቡኒ ... ሳባታይ ... ዮዛባት
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

የሌዋውያን መሪዎች የነበሩና ይቆጣጠሩ የነበሩ
“ከሌዋውያን መሪዎች የነበሩ ተቆጣጣሪዎች ነበሩ”

Nehemiah 11:15

ሻማያ ... አሱብ ... አሳብያ ... ቡኒ ... ሳባታይ ... ዮዛባት
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

የሌዋውያን መሪዎች የነበሩና ይቆጣጠሩ የነበሩ
“ከሌዋውያን መሪዎች የነበሩ ተቆጣጣሪዎች ነበሩ”

Nehemiah 11:17

መታንያ ... ሚካ ... ዘብዲ ... አሳፍ ... በቅበቃር ... አበድያ ... ሳሙስ ... ጋላል ... ኤዶታም
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ምስጋናንም በጸሎት የሚጀምሩ
ይህ ማለት ዘማርያኑን የሚመሩ ነበሩ ማለት ነው።

በወንድሞቹ መካከል ሁለተኛ የነበረ በቅበቃር
ለዚህ አማራጭ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት 1) በቅበቃር የመታንያ ዘመድ የነበረና በስልጣን ከመታንያ ቀጥሎ ሁለተኛ ሰው ነበር ወይም 2) “ሌሎች ሁለተኛውን የመዘምራንን ቡድን ይመራ የነበረ በቅበቃር”

ወንድሞች
ሌላ አማራጭ ትርጉም የሚከተሉት ሊሆኑ ይችላ “ተባባሪዎች” እና “አብረው የሚሰሩ ሰራተኞች።”

ቅድስቲቱ ከተማ
ይህ መግለጫ የሚወክለው የኢየሩሳሌምን ከተማ ነው።

ቁጥራቸው **284** ነበር
“ቁጥራቸው ሁለት መቶ ሰማንያ አራት ነበር።” በኢየሩሳሌም 284 ሌዋውያን ነበሩ። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 11:19

የበር ጠባቂዎች
ወደ ከተማውና ወደ መቅደሱ የሚገባውን ሰው ለመቆጣጠርና ገዢው በወሰነው ሰዓትና ምክንያት በሩን እንዲከፍቱና እንዲዘጉ ኃላፊነት የተሰጣቸው በእያንዳንዱ በር ላይ የተመደቡ ሰዎች። ይህ በነህምያ 7:1 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።

ዓቁብ ... ጤልሞን ... ሲሐ ... ጊሸጳ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

172 ሰዎች
“አንድ መቶ ሰባ ሁለት ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ኦፌል
ይህ የቦታ ስያሜ ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 11:22

ዋና አለቃ
“ኃላፊ”

ኦዚ ... ባኒ ... ሐሸብያ ... መታንያ ... ሚካ ... አሳፍ ... ፈታያ ... ሜሴዜቤል ... ዛራ ... ይሁዳ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

በንጉስ ትዕዛዝ ስር ነበሩ
“ንጉሱ ምን እንደሚሰሩ ነግሮአቸው” ለዘማሪዎቹ ጠንካራ ትዕዛዝ ተሰጥቶ ነበር ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ንጉሱ በተለይም ደግሞ ስለ ዘማሪዎች ምን መደረግ እንዳለበት ነግሮአቸው ነበር” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ ሕዝቡ ነገር ከንጉስ አጠገብ ነበር
“የአይሁድ ሕዝብን በሚመለከት ሁሉንም ጉዳዮች በተመለከተ የፋርስ ንጉስ አማካሪ ነበር”

Nehemiah 11:25

ቂርያት አርባቅ ... ዲቦን ... ይቀብጽኤል ... ኢያሱ ... ሞላዳ ... ቤት ጳሌጥ ... ሐጸርሹዓል ... ቤርሳቤህ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 11:28

ጺቅላግ ... ምኮና ... ዓይንሪሞን ... ጾርዓ ... የርሙት ... ዛኖዋ ... ዓዶላም ... ለኪሶ ... ዓዜቃ ... ቤርሳቤህ ... ሄኖም ሸለቆ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ተቀመጡ
እዚህ “እነርሱ” የሚለው የሚወክለው የይሁዳ ሕዝብን ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 12

1 ብዙ ካህናትና የሌዊ ትውልዶች ከዘሩባቤል እና ከኢያሱ ጋር ከባቢሎን ተመለሱ። እነዚህም፡ ሠራያ፣ ኤርምያስ፣ ዕዝራ፣ 2 አማርያ፣ ሙሉክ፣ ሐጡስ፣ 3 ሴኬንያ፣ ሬሁም፣ ሜሪሞት፣ 4 አዶ፣ ጌንቶን፣ አብያ፣ 5 ሚያሚን፣ መዓድያ፣ ቢልጋ፣ 6 ሸማያ፣ ዮያሪብ፣ ዮዳኤ፣ 7 ሰሉ፣ ዓሞቅ፣ ኬልቅያስና ዮዳኤ ነበሩ። እነዚህ በኢያሱ ዘመን የካህናቱና የወንድሞቸው አለቆች ነበሩ። 8 የተመለሱት የሌዊ ትውልዶች ዝርዝር ይህ ነው። እነርሱም ኢያሱ፣ ቢንዊ፣ ቀድምኤል፣ ሰራብያ፣ ይሁዳ እና መታንየ ነበሩ። የእነዚህ ሀላፊነት ለእግዚአብሔር የምስጋና ዝማሬ ማቅረብ ነበር። 9 በቅቡቅያ፣ ዑኒም እና ሌሎች የሌዊ ትውልዶች በዝማሬ ወቅት በትይዩ የሚቆሙ የዝማሬ ቡድን አበጁ። 10 ከብዙ አመታት አስቀድሞ አያሱ ሊቀ ካህን ነበር። ኢያሱ የዩአቂም አባት ነበረ፣ ዮአቄም የኤልያሴብ አባት ነበረ፣ ኤልያሴብ የዩአዳን አባት ነበረ፣ 11 ዩአዳ የዮናታን አባት ነበረ፣ ዮናታን የያዱአን አባት ነበረ። 12 ዮአቂም የካህናቱ ሁሉ መሪ ነበረ። የካህናቱ ቤተሰቦች መሪዎች እነዚህ ነበሩ፡ የሠራያ ቤተሰብ መሪ ምራያ፣ የኤርምያስ ቤተሰብ መሪ ሐናንያ፣ 13 የዕዝራ ቤተሰብ መሪ ሜሱላም፣ የአማርያ ቤተሰብ መሪ ይሆሐናን 14 የሙሊኪ ቤተሰብ መሪ ዮናታን፣ የሰብንያ ቤተሰብ መሪ ዮሴፍ 15 ከካሪም ቤተሰብ ብዙዎቹ መሪዎች ዓድና ነበሩ፣ ከመራዮት ቤተሰብ ሔልቃይ 16 ከአዶ ቤተሰብ ዘካርያስ ከጌንቶን ቤተሰብ ሜሱላም 17 ከአብያ ቤተሰብ ዝክሪ መሪዎች ነበሩ። ከሚያሚን ቤተሰብም አንድ መሪ ነበር። ከሞዓድያ ቤተሰብ ፈልጣይ ነበር። 18 ከቢልጋ ቤተሰብ ሳሙስ፣ ከሸማያ ቤተሰብ ዮናታን 19 ከዮያሪብ ቤተሰብ መትናይ፣ ከዮዳኤ ቤተሰብ ኦዚ፣ 20 ከሳላይ ቤተሰብ ቃላይ፣ ከዓምቅ ቤተሰብ ዔቤር፣ 21 ከኬልቅያስ ቤተሰብ ሐሸብያ፣ 22 ኤሊያሴብ ሌዋውያንን በሚመራበት ወቅት፣ የእነርሱ ሁሉ ዝርዝር ይህ ነው፡ ኤሊያሴብ፣ ዮአዳ፣ ዮሐና እና ያዱአ የካህናቱ ሁሉ መሪዎች ነበሩ። እነርሱ የሌዊ ትውልድ የሆኑትን ቤተሰቦች ስሞች መዘገቡ።ዳርዮስ የፋርስ ንጉስ በነበረበት ዘመን የየቤተሰቡን መሪዎች የመመዝገቡ ሀላፊነት የካህናቱ ነበር። 23 የሌዊ ትውልድ የሆኑ የቤተሰብ መሪዎችን ስሞች ዝርዝር በታሪክ መጽሐፍ ጽፈው ነበር። የኤልያሴብ የልጅ ልጅ የሆነው ዮሐና የካህናት ሁሉ መሪ እስከ ሆነበት ጊዜ ድረስ ያሉትን ክንዋኔዎች መዝግበው ነበር። 24 እነዚህ የሌዋውያን መሪዎች ነበሩ፡ ሐሸብያ፣ ሰራብያ፣ የቀድመኤል ልጅ ኢያሱ፣ እና ለእግዚአብሔር ውዳሴና ምስጋና ለማቅረብ ከእነርሱ ፊት ለፊት የቆሙ ወንድሞቸው። ይህንንም የእግዚአብሔር አገልጋይ የሆነው ንጉስ ዳዊት እንዳዘዛቸው እንደዚያው አደረጉ። 25 በር ጠባቂዎቹ፣ መታንያ፣ በቅቡቅያ፣ አብድዩ፣ ሜሱላም ጤልሞንና ዓቁብ ነበሩ። 26 አገረ ገዢው ነህምያ እና ካህኑ ዕዝራ በነበሩበት ወቅት፣ በኢዮሴዴቅ የልጅ ልጅ በኢያሱ ልጅ በዮቂም ዘመን ይህንን ሥራ ሰሩ። ዕዝራ የአይሁድን ህግጋትም በሚገባ ያውቅ ነበር። 27 የኢየሩሳሌምን ቅጥር ስንመርቅ፣ የሌዊን ትወልዶች ከሚኖሩባቸው የእስራኤል አካባቢዎች የቅጥሩን ምርቃት ያከብሩ ዘንድ ጠራናቸው። እነርሱም እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ብዙዎቹም በጽናጽልና፣ በበገና፣ በክራርና በሌሎች የክር ሙዚቃ መሳሪያዎች በመጫወት ይዘምሩ ነበር። 28 በህብረት ያለማቋረጥ የሚዘምሩትን የሌዊ ወገኖች ሰበሰብን። ከሰፈሩበት ከኢየሩሳሌም ዙሪያ ከነጦፋውያን መንደሮችና ከደቡብ ምስራቅ ኢየሩሳሌም ወደ መሃል ኢየሩሳሌም መጡ። 29 ከሰሜን ምስራቅ የኢየሩሳሌም ሶስት ቦታዎችም ከቤት ጌልገላ፣ ከጌባ አካባቢና ከዓዝሞት አካባቢ መጡ። መዘምራኑ ኢየሩሳሌም አቅራቢያ መንደሮችን መሰረቱ። 30 ካህናቱና የሌዊ ወገኖች ራሳቸውን በእግዚአብሔር ፊት የመንጻት ሥርዓት አደረጉ፣ ለህዝቡም ይህንኑ ስርዓት አደረጉ፣ ለከተማዋ መግቢያዎችና በመጨረሻም ለቅጥሩ ጭምር ስርዓቱን ፈጸሙ። 31 ከዚያ በቅጥሩ ጫፍ የይሁዳ መሪዎችን በአንድነት ሰበሰብኩ፣ እግዚአብሔርን እያገገኑ በቅጥሩ ላይ በከተማዋ ዙሪያ በሰልፍ እንዲዞሩ ሁለት ትላልቅ ቡድኖችን እዲመሩ ሾምኳቸው። በከተማይቱ ትይዩ ሲሆኑ፣ አንዱ ቡድን ወደ ቀኝ የቆሻሻ መጣያው በር ወደሚባለው ሄደ። 32 ከመሪዎቻቸው በኋላ ሆሻያና የይሁዳ እኩሌቶቹ መሪዎች ተሰለፉ። 33 ከእነርሱ በኋላ የተከተሏቸው ዓዛርያስ፣ ዕዝራ፣ ሜሱላም፣ 34 ይዳ፣ ብንያም፣ ሸማያ፣ ኤርምያስ፣ 35 እና መለከት የሚጫወቱ አንዳንድ የክህናቱ ወንዶች ልጆች ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ የአሳፍ ትውልድ የሆኑት የዘኩር ልጅ፣ የሚካያ ልጅ፣ የመታንያ ልጅ፣ የሸማያ ልጅ፣ የዮናታን ልጅ ዘካርያስ ይገኙበታል። 36 ከእነዚህ በኋላ የሚገዙት የዘካርያስ ቤተሰቦች ሌሎች አባላት ነበሩ። ከእነዚህም ሸማያ፣ ኤዝርኤል፣ ሚላላይ፣ ጊላላይ፣ መዓይ፣ ናትናኤል፣ ይሁዳ፣ እና አናኒምን ያካትታል። ሁሉም ንጉስ ዳዊት ከብዙ አመታት አስቀድሞ ይጫወትበት የነበሩ እነዚያኑ አይነት የሙዚቃ መሳሪያዎችን ይጫወቱ ነበር። የአይሁድን ህግጋት በሚገባ የሚያውቀው ሰው ዕዝራ፣ ከዚህ ቡድን ፊት ሰልፉን ይመራ ነበር። 37 የፋቷቴ በር ሲደርሱ፣ ወደ ዳዊት ከተማ ደረጃዎችን ወጡ፣ የዳዊትን ቤተ መንግስት አልፈው፣ ከዚያ ውሃ በር አጠገብ ወደሚገኘው ቅጥር በከተማዋ ምስራቅ አቅጣጫ ሄዱ። 38 ለያህዌ ይዘምርና ያመሰግን የነበረው ሌላው የዝማሬ ቡድን በቅጥሩ ላይ በግራ በኩል በሰልፍ አለፈ። እኔ ከህዝቡ ከፊሉን ይዤ ተከተልኳቸው። እኛ የእቶን ግንቡን አልፈን ወደ ሰፊው ቅጥር አለፍን። 39 ከዚያ ተነስተን የኤፍሬምን በር፣ የጄሻናን በር፣ የአሣን በር፣ የሐናንኤልን ግንብ፣ የመቶ ወታደሮችን በር አልፈን ወደ በጎች በር ተጓዝን። ወደ ቤተ መቅደሱ በር ስንቃረብ ሰልፋችንን ጨረስን። 40 ሁለቱም ቡድኖች እየዘመሩና እርሱን እያመሰገኑ ወደ እግዚአብሔር ቤት ደረሱ። በዚያም በየስፍራቸው ቆሙ። እኔና ከእኔ ጋር የነበሩ መሪዎችም በስፍራችን ቆምን። 41 የእኔ ቡድን መለከት የሚነፉትን እነዚህን ካህናት ያጠቃልላል፡ ኤልያቄም፣ መዕሤያ፣ ሚንያሚን፣ ሚካያ፣ ኤልዮዔናይ፣ ዘካርያስ እና ሐናንያ፣ 42 ሌሎቹም መዕሤያ፣ ሸማያ፣ አልዓዛር፣ ኦዚ፣ ይሆሐናን፣ መልክያ፣ ኤላም እና ኤድር ናቸው። መሪያቸው ይዝራሕያ የሆነው መዘምራኑ ድምቸውን ከፍ አድርገው ዘመሩ። 43 ከቤተ መቅደሱ ውጭ ከሄድን በኋላ ብዙ መስዋዕቶችን አቀረብን። እኛ ወንዶች ሁላችን እግዚብሔር በጣም ደስተኞች ስላደረገን ደስ አለን። ሴቶቹና ልጆችም እንደዚሁ ደስ አላቸው፤ በሩቅ ያሉ ሰዎች እኛ በኢሩሳሌም ውስጥ ሆነን የምናሰማውን ድምጽ መስማት ይችሉ ነበር። 44 በዚያን ቀን ህዝቡ ለቤተ መቅደስ የሰጠውን ገንዘብ ለሚያስቀምጡበት ግምጃ ቤት ሀላፊ የሚሆኑ ወንዶች ተሾሙ። እነዚህ ሰዎች ለአስራትና በየአመቱ ለሚሰበሰበው እህልና ፍራፍሬ በኩራቶችም ሀላፊዎች ነበሩ። እነዚሁ ሰዎች ወደ ግምጃ ቤቶቹ ከእርሻዎች ምርት ለካህናቱና ለሌዊ ትውልዶች ያመጡ ነበር። ይህ የተደረገው የይሁዳ ሰዎች በያህዌ ቤት የሚያገለግሉ አገልጋዮች እንዲኖር ይፈልጉ ስለነበር ነው። 45 ካህናቱና ሌዋውያኑ ነገሮችን ለማንጻት፣ በማንጻት ስርዓቱ ያህዌን ያገለግሉ ነበር፤ መዘምራኑ በቤተ መቅደስ፣ እንዲሁም በር ጠባቂዎቹ ንጉስ ዳዊትና ልጁ ሰለሞን እንዲደረግ እንደ ደነገጉት ስራቸውን ያከናውኑ ነበር። 46 ከዳዊትና ከአሳፍ ዘመን አንስቶ፣ የዘማሪዎች መሪዎች ነበሩ፤ መዘምራኑም እግዚአብሔርን ለማወደስና ለማመስገን ይዘምሩ ነበር። 47 ዘሩባቤል በነበረበት አመታትና በአገረ ገዥው ነህምያ ዘመን፣ ዘማርያኑና የቤተ መቅደስ በር ጠባቂዎች በየዕለቱ የሚያስፈልጋቸውን ምግብ መላው እስራኤል ያወጣ ነበር። ህዝቡ ለሌዋውያን ኑሮ የሚያስፈልገውን ያስቀምጡላቸውና ሌዋውያኑ ደግሞ ከካህናቱ ቀዳሚ መሪ ለሆኑት ለአሮን ትውልዶች የሚያስፈልገውን ያስቀምጡላቸው ነበር።

Nehemiah 12:1

ከዘሩባቤል ጋር
“በዘሩባቤል መሪነት”

የወጡት
“ከባቢሎን ተመልሰው የመጡት”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ዘሩባቤል ... ሰላትያል ... ኢያሱ ... ሠራያ ... ኤርምያስ ... ዕዝራ ... አማርያ ... መሉክ ... ሐጡስ ... ሴኬንያ ... ሬሁም ... ሜሪሞት
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ኢያሱ
የመጽሐፉ የመጀመርያ አንባቢዎች ኢያሱ ሊቀ ካህን እንደነበረ በሚገባ ይረዳሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ሊቀ ካህኑ ኢያሱ” (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 12:4

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፦
በነህምያ 12:1 ላይ የጀመረው የስም ዝርዝር ይቀጥላል።

እነዚህ ነበሩ
እነዚህ ቃላት የተጨመሩት ለዚህ ትርጉም ነበር። በነህምያ 12:1 ላይ የጀመረውን ዝርዝር ከቀጠላችሁ እነዚህን ቃላት መጠቀም አስፈላጊ አይሆንም።

አዶ ... ጌንቶን ... አብያ ... ሚንያሚን ... መዓድያ ... ቢልጋ ... ሸማያ ... የያሪብ ... ዮዳኤ ... ሰሉ ... ዓሞቅ ... ኬልቅያስ ... ዮዳኤ ... ኢያሱ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ጌንቶን
ጌንቶይ “ጌንቶን” ለሚለው ሌላኛው አማራጭ ስም ሳይሆን አይቀርም።

Nehemiah 12:8

ኢያሱ ... ቢንዊ ... ቀድምኤል ... ሰራብያ ... ይሁዳ ... መታንያ ... በቅበቁያ ... ዑኒ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

በአገልግሎት ጊዜም በተቃራኒያቸው ቆሙ
ለዚህ አማራጭ ትርጉም ሊሆኑ የሚቸሉ የሚከተሉት ናቸው፦ 1) ይህ በአምልኮ ጊዜ ነበርና እነዚህም ደግሞ ሁለት የዘማርያን ቡድኖች ነበሩ፣ ወይም 2) እነዚህ ቡድኖች በተለያዩ ጊዜያት መቅደሱን ይጠብቁ ነበር፣ ወይም “በየተራ መቅደሱን ይጠብቁ ነበር”

Nehemiah 12:10

ኢያሱ ... ዮአቂም ... ኤልያሴብ ...ዮአዳ ... ዮናታን ... ያዱአ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ኢያሱ የዮአቂም አባት ነበር
ይህ በነህምያ 12:1 ላይ የተጠቀሰው ኢያሱ ነው። የመጽሐፉ የመጀመርያ አንባቢዎች ኢያሱ ሊቀ ካህን እንደነበረ ይረዳሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ሊቀ ካህኑ ኢያሱ የዮአቂም አባት ነበረ” (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 12:12

ዮአቂም ... ምራያ ... ሐናንያ ... ሜሱላም ... ይሆሐናን ... ዮናታን ... ዮሴፍ እነዚህ
የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ሠራያ ... ኤርምያስ ... ዕዝራ ... አማርያ ... መሉክ ... ሰበንያ
እነዚህ በወንድ ስም የተጠሩ የቤተሰብ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 12:15

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፦
በነህምያ 12:12 የጀመረው የስም ዝርዝር ይቀጥላል።

ዓድና ... ሔልቃይ ... ዘካርያስ ... ሜሱላም ... ዚክሪ ... ፈልጣይ ... ሳሙስ ... ዮናታን ... መትናይ ... ኦዚ ... ቃላይ ... ዔቤር ... ሐሸብያ ... ናትናኤል
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ካሪም ... ሜሪሞት ... አዶ ... ጌንቶን ... አብያ ... ሚንያሚን ... ሞዓድያ ... ቢልጋ ... ሸማያ ... የያሪብ ... ዮዳኤ ... ሳላይ ... ዓሞቅ ... ኬልቅያስ ... ዮዳኤ
እነዚህ በወንድ ስም የተጠሩ የቤተሰብ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

የ ... አለቃ ነበር
“የ ... ቤተሰብ አለቃ ነበር” ወይም “የ ... ዘሮች አለቃ ነበር”

ሜሱላም የጌንቶን አለቃ ነበር
ጌንቶይ “ጌንቶን” ለሚለው ሌላኛው አማራጭ ስም ሳይሆን አይቀርም።

የሚያሚን
የዕብራይስጡን ጽሁፍ ያባዙ የነበሩት ሰዎች በስህተት የሚንያሚን ቤተሰብ አለቃ የነበረውን ሳይጽፉት ቀርተዋል። ተርጓሚዎች እንደ ሕዳግ መረጃ አድርገው ይህንን ያብራራሉ። የተባበሩት ሕያው ቃል ትርጉም ይህን ለማሳየት “ ... “ ይጠቀማል። ይህን የሚጠቀመው የመሪው ስም እንደተዘለለ ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “አንድ ሰው የሚያሚን ቤተሰብ አለቃ ነበር”

ሞዓድያ
ማዓድያ “ሞዓዓያ”ለሚለው ሌላኛው አማራጭ ስም ሳይሆን አይቀርም።

Nehemiah 12:22

ኤልያሴብ ... ዮአዳ፣ ዮሐናን ... ያዱአ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

በዳርዮስ መንግስት ዘመን
“እስከ ዳርዮስ የመንግስት ዘመን” የሚለው ሌላ ትርጉም መሆን ይችላል።

በታሪክ መጻሕፍት ተጻፉ
ይህ የዜና መዋዕልን ያመለክታል። ጸሐፊዎች ከላይ ባሉት ቁጥሮች ውስጥ እነዚህን ቃላት በየዕለቱ ምን እንደተፈጠረ በሚጽፉበት መጽሐፍ ላይ ጽፈዋቸው ነበር።

እስከ ... ቀናት ድረስ ለዳዊት ትዕዛዝ በመታዘዝ
ንጉስ ዳዊት ሌዋውያንን አምልኮን እንዴት እንደሚመሩና እንደሚያስተባብሩ አዝዞአቸው ነበር።

በዮአቂም ... ኤዮሴዴቅ ዘመን ... እና በአለቃው በነህምያና በጸሐፊውም በዕዝራ ዘመን
ይህ ቀን የተወሰነው በጊዜው አይሁዳውያንን እየመራ የነበረው ማን ነበር የሚለውን በመመልከት ነው። “ዮአቂም ... ኢዮሴዴቅ ሊቀ ካህን በነበረ ጊዜ፣ ነህምያ አለቃ በነበረ ጊዜ እና ዕዝራ ጸሐፊ በነበረ ጊዜ”

Nehemiah 12:27

የኢየሩሳሌም ቅጥር በተመረቀ ጊዜ
አማራጭ ትርጉም ሊሆን የሚችሉ፦ 1) “እነርሱ የኢየሩሳሌምን ቅጥር በመረቁ ጊዜ” ወይም 2) “የኢየሩሳሌም ቅጥር ምረቃ ይከናወን ዘንድ።”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጽናጽል
ሁለት ቀጭን ክብ ብረት ያለው፣ አብሮ ሲመታ ጮክ ያለ ድምጽ የሚያወጣ መሳሪያ። (የማይታወቁ ነገሮች ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 12:29

ቤት ጌልገላ ... ጌባ እና ዓዝሞት
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 12:31

የይሁዳ አለቆች
በይሁዳ ይኖሩ የነበሩትን ሕዝቦች ይመሩ የነበሩ ሰዎች

Nehemiah 12:32

ሆሻያ ... ዓዛርያስ ፣ ዕዝራ፣ ሜሱላም፣ ይሁዳ፣ ብንያም፣ ሸማያ፣ ኤርምያስ፣ ዘካርያስ፣ ዮናታን፣ ሸማያ፣ መታንያ ... ሚካያ ... ዙኩር ... አሳፍ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ከእነርሱ ኋላ ሄዱ
“ከእነርሱ በኋላ ተከተሉ”

አንዳንድ መለከት የያዙ የካህናት ወንዶች ልጆችና፣ ዘካርያስም **some of the priests’**
አንዳንድ ትርጉሞች “መለከት ይዘው ከነበሩት የካህናት ልጆች ውስጥ ዘካርያስ” ብለው ይተረጉሙታል።

የአሳፍ ልጅ የዘኩር ልጅ የሚካያ ልጅ የመታንያ ልጅ የሸማያ ልጅ የዮናታን ልጅ ዘካርያስ
“ዘካርያስ” ከሚለው ስም በፊት የተጻፉት በሙሉ የዘካርያስ ዘሮች ናቸው። ይህ ዝርዝር ዘካርያስን ታዋቂ ዘማሪ ከነበረው ከአሳፍ ጋር ያለውን ዝምድና ያሳያል። “የዮናታን ልጅ የነበረው፣ የሸማያ ልጅ የነበረው፣ የመታንያ ልጅ የነበረው፣ የሚካያ ልጅ የነበረው፣ የዘኩር ልጅ የነበረው የአሳፍ ልጅ ዘካርያስ”

Nehemiah 12:36

እነዚህም ነበሩ
“ከእነርሱ ጋርም እነዚህ ነበሩ”

ዘካርያስ ... ሸማያ፣ ኤዝርኤል፣ ሚላላይ፣ ጊላላይ፣ መዓይ፣ ናትናኤል፣ ይሁዳ፣ አናኒ .. ዳዊት ... ዕዝራ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ጸሐፊው ዕዝራ በፊታቸው ነበር
“ጸሐፊው ዕዝራ እየመራቸው ነበር”

በምንጭ በር ... በውኃ በር
እነዚህ በቅጥሩ ላይ የነበሩ በሮች ስም ናቸው።

Nehemiah 12:38

መዘምራን
የዘማሪዎች ስብስብ

ተከተልኳቸው
ነህምያ ተከትሏቸው ሄደ

የእቶኑ ግንብ ... የሐናኤል ግንብ ... የመቶ ግንብ
እነዚህ ሰዎች አደጋ ካለ መከታተል እንዲያመቻቸው ወጥተው የሚመለከቱባቸው ግንብዎች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ሰፊው ቅጥር
ይህ የቅጥሩ የአንዱ ክፍል ስም ነው።

በኤፍሬም በር ... በአሮጌው በር ... በዓሣ በር ... በበግ በር ... በዘበኞች በር
እነዚህ በቅጥሩ ላይ የነበሩ በሮች ስም ናቸው።

Nehemiah 12:40

እኔም በቦታዬ ላይ ቆምኩኝ
እዚህ የሚናገረው ነህምያ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ ነህምያ በቦታዬ ላይ ቆምኩ”

ኤልያቄም ... መዕሤያ ... ሚንያሚን ... ሚካያ ... ኤልዮዔናይ ... ዘካርያስ ... ሐናንያ ... መዕሤያ ... ሸማያ ... አልዓዛር ... ኦዚ ... ይሆሐናን ... መልክያ ... ኤላም ... ኤጽር
እነዚህ በጊዜው ካህናት የነበሩ ወንዶች ስም ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ይዝረሕያ
ይህ የዘማሪዎች መሪ የነበረ የወንድ ሰው ስም ነው።

በመለከቶች
አማራጭ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፡- 1) ከኤልያቄም እስከ ሐናንያ ድረስ የተዘረዘሩት ሰባት ካህኒናት መለከቶችን ተሸክመዋል ወይም 2) ከኤልያቄም እስከ ኤጽር ድረስ የተዘረዘሩት 15 ካህናት በሙሉ መለከቶችን ተሸክመዋል።

ድምጻቸው እንዲሰማ አደረጉ
“በጩኸት ዘመሩ”

Nehemiah 12:43

በታላቅ ደስታ ደስ መሰኘት
“እጅግ በጣም መደሰት” ከዚህ የተነሳ የኢየሩሳሌም ደስታ ከሩቅ መሰማት ይችል ነበር በዚህ ክፍል “የኢየሩሳሌም ደስታ” የሚለው “በኢየሩሳሌም ያሉ ሕዝቦች ያሰሙትን ድምጽ” የሚወክል ነው። ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከኢየሩሳሌም በጣም ርቀው የሚኖሩ ሕዝቦች የእስራኤል ሕዝብ በዓሉን በሚያከብሩበት ጊዜ ያሰሙትን ድምጽ መስማት ይችሉ ነበር” (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 12:44

ተቆጣጣሪ እንዲሆኑ ሰዎች ተሾሙ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። ሰዎቹን ማን እንደሾማቸው ግን የተገለጸ ነገር የለም። አማራጭ ትርጉም፡- “ተቆጣጣሪ ይሆኑ ዘንድ ሰዎችን ሾሙ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

መዋጮ
ሕዝቡ ለካህናት የሰጡት ነገሮች

ይሁዳ በካህናቱና በሌዋውያን ተደስቶ ነበርና
ሕዝቡ እነዚህን ሰዎች የሾሙአቸው የይሁዳ ሕዝብ ያገለግሉ በነበሩት በካህናቱና በሌዋውያኑ በመደሰታቸው ነው።

በፊታቸው ቆመው የነበሩት
ሌዋውያንኑና ካህናቱ ቆመው ብቻ አልነበረም፣ በተሰጣቸው ኃላፊነት እያገለገሉ ነበር። የዚህ ትርጉም ግልጽ ተደርጎ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡-

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

“በፊታቸው ቆመው እግዚአብሔርን ሲያገለግሉ የነበሩት” (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የበር ጠባቂዎች
ወደ ከተማውና ወደ መቅደሱ የሚገባውን ሰው ለመቆጣጠርና ገዢው በወሰነው ሰዓትና ምክንያት በሩን እንዲከፍቱና እንዲዘጉ ኃላፊነት የተሰጣቸው በእያንዳንዱ በር ላይ የተመደቡ ሰዎች። ይህ በነህምያ 7:1 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።

Nehemiah 12:46

የመዘምራን አለቆች ነበሩ
ይህ ዓርፍተ ነገር በነህምያ 12:45 ላይ ሰዎቹ ያደረጉትን ነገር ያደረጉበትን ምክንያት ይናገራል፣ ከዚህ በተጨማሪ ዳዊት በመቅደስ ውስጥ እንዴት አምልኮ መደረግ እንዳለበት ለሕዝቡ ስለ ተናገረበት ጊዜ መረጃ የይሰጠናል።

በዘሩባቤል ዘመን
ዘሩባቤል የንጉስ ዳዊት ዘር ሲሆን በይሁዳ ክልል ውስጥ ከገዢዎቹ ውስጥ አንዱ ነው።

ፋንታቸውን ይሰጡ ነበር
“እስራኤል ሁሉ ድርሻውን ያስቀምጡ ነበር”

የአሮን ዘሮች
ከሙሴ ወንድም ከአሮን ዘር የመጡ በእስራኤል የነበሩ ካህናት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 13

1 በዚያን ቀን እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠውን አሞናዊያን ወይም ሞአባዊያን የእግዚአብሔር ህዝቦች ወደሚያመልኩበት ስፍራ አይግቡ የሚለውን የህጉን ክፍል
ካህናቱ ለህዝቡ አነበቡ፤ ህዝቡም አደመጠ። 2 ይህ የሆነው የአሞንና የሞአብ ሰዎች እስራኤላዊያን ከግብጽ ወጥተው ወደሚገቡበት አገር ሲጓዙ ምንም ምግብ
ወይም ውሃ ስላልሰጧቸው ነበር። ይልቁንም፣ የአሞንና የሞብ ሰዎች በለዓም እስራኤላዊያንን እንዲረግም ገንዘብ ከፈሉት። እግዚአብሔር ግን እስራኤልን
ለመርገም የተደረገውን ያን ጥረት ወደ በረከት ለወጠው። 3 ስለዚህም ህዝቡ እነዚያ ህጎች ሲነበቡላቸው በሰሙ ጊዜ፣ አባቶቻቸው ከሌሎች አገሮች የሆኑትን
ሰዎች ሁሉ አስወጡ። 4 አስቀድሞ፣ ካህኑ ኤልያሴብ በቤተ መቅደሱ የግምጃ ቤቱ ኃላፊ ሆኖ ተሹሞ ነበር። እርሱም የጦቢያ ቤተዘመድ ነበር። እነርሱም የእህል
ቁርባኖቹንና እጣኑን በዚያ ስፍራ አከማቹ። 5 ለቤተ መቅደስ የሚያገለግሉ ዕቃዎችን በዚያ አስቀመጡ። ህዝቡ ለሌዋውያን የሰጠውን ስጦታዎች በግምጃ ቤት
አስቀመጡ። እግዚአብሔር ለሌዋውያኑ፣ ለዘማሪዎቹና ለበር ጠባቂዎች እንዲሰጡ ያዘዘውን የእህል፣ የወይንና የወይራ ዘይት አስራት አመጡ። ሌሎች ካህናትን
ለመደገፍም ስጦታዎቹን አመጡ። 6 በዚያን ጊዜ እኔ ኢየሩሳሌም ውስጥ አልነበርኩም። አርጤክስስ የባቢሎን ንጉስ በነበረበት በሰላሳ ሁለተኛው አመት
ያከናወንኩትን ለንጉሱ ለመናገር ተመለስኩ። ለጥቂት ጊዜ በዚያ ከቆየሁ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም እንድመለስ እንዲፈቅደልኝ ንጉሱን ጠየቅሁት። 7 ስመለስ፣
ኤልያሴብ ያደረገውን ክፉ ነገር አወቅሁ። ጦቢያ ለእግዚአብሔር የተለየውን አንድ ክፍል ቤት ለገዛ ጥቅሙ እንዲያውለው ትቶለት ነበር። 8 እኔም በጣም
ተቆጣሁ። ወደዚያ ክፍል ገብቼ የጦቢያ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ አውጥቼ ጣልኩ። 9 ከዚያ ያንን ክፍል እንደገና ለማንጻት የማንጻት ሥርኣት እንዲደረግ አዘዝኩ።
እንደዚሁም ደግሞ ለቤተ መቅደሱ አገልግሎት የሚውሉ ማናቸውም ዕቃዎችና የእህል ቁርባኖችን እንዲሁም እጣኑ ወደነበሩበት ወደዚያ ክፍል እንዲመለሱ
አዘዝኩ። 10 የእስራኤል ሰዎች የሚያስፈልጋቸውን ቀለብ ወደ ግምጃ ቤት ስላላመጡአቸው፣ የቤተ መቅደሱ ዘማሪዎችና ሌሎች ሌዋውያን ኢየሩሳሌምን ለቀው
ወደ እርሻዎቻቸው መመለሳቸውን ተረዳሁ። 11 ስለዚህ ሹማምንቱን እንዲህ ስል ገሰጽኳቸው፣ “በቤተ መቅደስ ለሚካሄደው አገልግሎት ጥንቃቄ
ያላደረጋችሁት ለምንድን ነው?” ስለዚህም እነርሱን በአንድነት ሰብስቤ ወደ መጀመሪያ ስፍራቸው መለስኳቸው። 12 ከዚያ የይሁዳ ሰዎች በሙሉ የእህል፣
የወይንና የወይራ ዘይት አስራታቸውን ወደ ቤተ መቅደሱ ግምጃ ቤት ዳግም ማምጣት ጀመሩ። 13 እኔም እነዚህን ሰዎች የግምጃ ቤቶቹ ሀላፊዎች አድርጌ
ሾምኳቸው። እነርሱም ካህኑ ሰሌምያ፣ የአይሁድ ህግ አዋቂው ሳዶቅ፣ እና ከሌዊ ወገን የሆነው ፈዳያ ናቸው። እነርሱን እንዲረዳ የመታንያን የልጅ ልጅ የዘኩርን
ልጅ ሐናን ሾምኩት። እነዚያ ሰዎች ለሠራተኞቹ ወገኖቹ ስጦታዎችን በትክክል እንደሚያከፋፍሉ ልተማመንባቸው እንደምችል አውቅ ነበር። 14 አምላኬ ሆይ፣
ለአንተ ቤተ መቅደስ የሰራኋቸውን እነዚህን መልካም ሥራዎችና እዚህ ለተሰራው ሰራ ሁሉ ያደረኩትን አትርሳ! 15 በእነዚያ ጊዜያት፣ ይሁዳ ውስጥ አንዳንዶች
በሰንበት ቀን ሲሰሩ አየሁ። አንዳንዶች ወይን ለመጥመቅ የወይን ፍሬ ይረግጡ ነበር። ሌሎች እህል፣ የወይን አቁማዳዎች፣ የወይን ፍሬ የሞሉ ቅርንጫፎች፣
በለስ፣ እና ሌሎች ብዙ ነገሮች በአህዮቻቸው ጭነው ወደ ኢየሩሳሌም ይወስዱ ነበር። በሰንበት ለይሁዳ ሰዎች ምንም ነገር እንዳይሸጡ አስጠነቀቅኳቸው። 16
ደግሞም በኢየሩሳሌም የሚኖሩ አንዳንድ የጢሮስ ሰዎች በሰንበት ቀን አሳና ሌሎች ነገሮችን ለአይሁድ ሰዎች ለመሸጥ ወደ ኢየረሳሌም ሲያመጡ አይሁ። 17
ስለዚህ የአይሁድን መሪዎች በመገሰጽ እንዲህ አልኳቸው፣ “ይህ የምታደርጉት በጣም ክፉ ነገር ነው! በሰንበት ቀን እግዚአብሔር በፍጹም እንዲሆን
የማይወደውን ነገር እያደረጋችሁት ነው። 18 አባቶችሁ እንደዚህ ያለ ነገሮችን አደረጉ፣ ስለዚህም እግዚአብሔር ቀጣቸው። በእነርሱ ኃጢአት ምክንያት ይህች
ከተማ እንድትጠፋ ፈቅዶ ነበር! እና አሁን የሰንበት ቀን ህግጋትን በመተላፍ እግዚአብሔር በእኛ ላይ እንዲቆጣ ምክንያት እየሆናችሁ ነው፣ እናም የከፋ ቅጣት
ይቀጣናል!” 19 ቀኑ ሲመሸ በኢየሩሳሌም መግቢያ ላይ አንዳንድ የራሴን ሰዎች አቆምኩ፣ ስለዚህ እነዚህ ሰዎች በዚያን ቀን ምንም አይነት የሚሸጥ ዕቃ
ማንም ሰው ወደ ከተማይቱ እንዳያስገባ ያደርጋሉ። 20 ነጋዴዎችና ሻጮች የተለያዩ አይነት ዕቃዎችና ሸቀጦች እንዲሁም አንዳንድ ነገሮችን በማግስቱ ለመሸጥ
ተስፋ አድርገው ሰንበት ከሚጀምርበት ከአርብ ምሽት አንስቶ ከኢየሩሳሌም ውጭ ለጥቂት ጊዜ ይሰፍራሉ። 21 እኔም እንዲህ ስል አስጠነቀቅኳቸው፣ “ዓርብ
ምሽት ከቅጥሩ ውጭ በዚህ ማደራችሁ አይጠቅማችሁም! ይህን ደግማችሁ ብታደርጉ፣ እኔ ራሴ አስወጣችሁና አባርራችኋለሁ!” ስለዚህ ከዚያ በኋላ፣
ዳግመኛ በሰንበት ቀናት ተመልሰው አልመጡም። 22 እንደዚሁም ደግሞ የሌዊ ትውልዶች፤ ራሳቸውን ለማንጻት የማንጻት ሥርዓቱን እንዲፈጽሙና የከተማዋን
በሮች ለመጠበቅ ስፍራቸውን እንዲይዙ፣ በዚያ የተቀደሰ ቀን ነጋዴዎች እንዳይገቡ በመከልከል ሰንበት ቅዱስ ሆኖ መጠበቁን እንዲያረጋግጡ አዘዝኳቸው።
አምላኬ ሆይ፣ ስለዚህም ደግሞ አሰበኝ! እንደ ታላቅ ፍቅርህ መጠን ምህረትህን አድርግልኝ። 23 በዚያን ጊዜ ብዙዎቹ የአይሁድ ወንዶች ከአሽዶድ፣ አሞንና
ሞዓብ ሴቶች ጋር መጋባታቸውን አወቅሁ። 24 ከልጆቻቸው እኩሌቶቹ የኖሩበትን ህዝብ የአሽዶድ ሰዎችን ቋንቋ ወይም ሌላ ቋንቋ ይናገሩ እንጂ የአይድን ቋንቋ
መናገር አይችሉም ነበር። 25 ስለዚህም እነዚያን ሰዎች ገስጽኳቸው፣ እግዚአብሔር የተረገሙ እንዲያደርጋቸው ጠየቅኩት፤ አንዳንዶቹን በቡጢ መታኋቸው፤
የአንዳንዶቹንም ጸጉር ነጨሁ! ከዚያ እግዚአብሔር እንደሚሰማ በማወቅ ዳግመኛ ባዕዳንን እንዳያገቡና ልጆቻቸውም ከባዕዳን ጋር እንዲጋቡ እንዳይፈቅዱ
ጥብቅ ቃል ኪዳን እንዲገቡ አስገደድኳቸው። 26 እንዲህ አልኳቸው፣ “የእስራኤል ንጉስ፣ ሰለሞን፣ ከባዕድ ሴቶች ጋር በመጋባቱ ምክንያት ኃጢአት ሰራ።
እርሱ ከሌሎች መንግስታት ነገስታት ሁሉ ታላቅ ነበር። እግዘአብሔር ወዶት በመላው የእስራኤል ህዝብ ላይ ንጉስ አደረገው። ነገር ግን ባዕዳን የሆኑት ሚስቶቹ
ኃጢአት እንዲሰራ ምክንያት ሆኑ። 27 እናንተ ስህተት መሆኑን እያወቃችሁ ባዕድ ሚስቶችን እንዳገባችሁና ጣኦት አምላኪ የሆኑ ባዕድ ሴቶችን በማግባት
በአምላካችሁ ላይ ታላቅ ኃጢአት እንደፈፀማችሁ እኛም ያንን ማድረግ ያለብን ይመስላችኋልን?” 28 ከዮአዳ ልጆች አንዱ፣ የሊቀ ካህኑ የአልያሴብ ልጅ
የሰንበላጥን ልጅ አገባ። ስለዚህ የዮአዳን ልጅ ከኢየሩሳሌም አባረርኩት። 29 አምላኬ ሆይ በክህነት ማዕረግ ላይ ዕፍረት ያስተሉትን አስብ፣ እናም በስራቸው
የክህነትንና የሌዋዊነትን ቃል ኪዳን ተላልፈዋል! 30 ከሌሎች አገሮችና ሀይማኖቶች ካመጧቸው ማናቸውም ነገር አነፃኋቸው፣ እንደዚሁም ለካህናቱና ለሌዊ
ወገኖች ደንቦችን ሰጠሁ፣ ስለዚህም እያንዳንዳቸው ማድረግ የለባቸውን ያውቃሉ። 31 በተወሰነው ጊዜና ቀናት በመሰዊያው ላይ የሚነድ ማገዶ ስለመኖሩ
አረጋገጥሁ። ህዝቡ ከምርቱ በኩራቱን ወደ ግምጃ ቤት እንዲያመጣ መመሪያ ሰጠሁ። አምላኬ ሆይ፣ እዚህን ሁሉ ነገሮች ማድረጌን አትርሳ፣ እነዚህን
በማድረጌም ባርከኝ።

Nehemiah 13:1

ለሕዝቡ አነበቡ
“ሕዝቡ እንደሚሰሙት ሆኖ”

ወደ እግዚአብሔር ጉባዔ ለዘላለም እንዳይገቡ
“ወደ እግዚአብሔር ጉባዔ ፈጽሞ እንዳይገቡ”

ይህም ምክንያቱ
“ወደ እግዚአብሔር ጉባዔ በፍጹም እንዳይገቡ የሆነበት ምክንያቱ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Nehemiah 13:4

ካህኑ ኤልያሴብ ተሾሞ ነበር
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል:: አማራጭ ትርጉም:- “እነርሱ ካህኑ ኤልያሴብን ሾሙት” ወይም “መሪዎቹ ካህኑ ኤልያሴብን ሾሙት” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ከጦብያ ጋር ተወዳጅቶ ነበር
“ኤልያሴብና ጦብያ በቅርበት አብረው ይሰሩ ነበር”

ኤልያሴብ ... ጦብያ
እዚህ የወንድ ስሞች ናቸው

ኤልያሴብ ለጦብያ ትልቅ ማከማቻ ክፍል አዘጋጅቶለት ነበር
“ኤልያሴብ ጦብያ እንዲጠቀምበት ትልቅ የእቃ ማከማቻ ክፍል አዘጋጅቶለት ነበር”

የበር ጠባቂዎች
ወደ ከተማውና ወደ መቅደሱ የሚገባውን ሰው ለመቆጣጠርና ገዢው በወሰነው ሰዓትና ምክንያት በሩን እንዲከፍቱና እንዲዘጉ ኃላፊነት የተሰጣቸው በእያንዳንዱ በር ላይ የተመደቡ ሰዎች:: ይህ በነህምያ 7:1 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ::

Nehemiah 13:6

ነገር ግን በዚህ ጊዜ ሁሉ እኔ ኢየሩሳሌም አልነበርኩም
“ይህ በተከሰተ ጊዜ እኔ ከኢየሩሳሌም ውጪ ነበርኩ”

እኔ አልነበርኩም
እዚህ ላይ “እኔ” የሚለው ቃል ነህምያን ያመለክታል::

በእግዚአብሔር ቤት አደባባይ የእቃ ማከማቻውን
ይህ ክፍል ለቤተ መቅደስ ቁርባን አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ለማስቀመጥ የተቀደሰ ክፍል ነበር:: (ነህምያ 13:5)

Nehemiah 13:10

የሌዋውያን ድርሻቸው አልተሰጣቸውም ነበር
የዚህ ዓርፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ ማድረግ ይቻላል:: አማራጭ ትርጉም:- “ሕዝቡ አስራታቸውንና ለቤተ መቅዱሱ ካህናት ለቁርባን የሚሆነውን የምግብ መስዋዕት ወደ ግምጃ ቤቱ አያስገቡም ነበር::” (ግምታዊ እውቀትና ያልተገለጸ መረጃ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ስራውን ይሰሩ የነበሩት ሌዋውያንና ዘማሪያን እያንዳንዳቸው ወደ እርሻቸው ሄዱ
“ስራውን ይሰሩ የነበሩ ሌዋውያንና ዘማርያን መቅደሱን ጥለው እያንዳንዳቸcው ወደ እርሻቸው ሄዱ

የእግዚአብሔር ቤት ለምን ተተወ?
ነህምያ ስራቸውን ያልሰሩትን አለቆች ለመሞገትና በእነርሱ ላይ ለመሳለቅ ይህን መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ ተጠቀመ:: አማራጭ ትርጉም:- “የእግዚአብሔር ቤት ትታችሁታል?” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 13:12

ይሁም ሁሉ
የሃገሩ ስም በሃገሩ ለሚኖሩ ሕዝቦች ወካይ ሆኖ ያገለግላል:: ይህ ማስፋፊያ ነው:: አማራጭ ትርጉም:- “በይሁዳ ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦች በሙሉ” (ምትክ ስም እና ግነትና ማስፋፊያ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰሌምያ ... ሳዶቅ ... ፈዳያ ... ሐናን ... ዘኩር ... መታንያ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው:: (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

የታመኑ ሆነው ተገኙ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል:: “የታመነ” የሚለው ረቂቅ ቃል በግስ መልክ መጻፍ ይቻላል:: አማራጭ ትርጉም:- “እምነቴን ልጥልባቸው የምችል ሰዎች አውቅ ነበር” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ይህን አስመልክቶ አምላኬ አስበኝ
“አምላኬ ይህን በተመለከተ አስበኝ”

Nehemiah 13:15

የወይን መጥመቂያ የሚረግጡትን
“የወይን መጥመቂያዎች” የሚለው ቃል በመጥመቂያዎች ውስጥ ለነበሩት የወይን ፍሬዎችን ወካይ ነው:: ሕዝቡ ጭማቂ እንዲያወጡ በወይን ፍሬዎቹ ላይ በላያቸው ይራመዱባቸው ነበር:: አማራጭ ትርጉም:- “በወይን መጥመቂያዎች ላይ የነበሩትን የወይን ፍሬዎችን ይረግጣሉ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ይረግጡ
አንድን ነገር ለመጨፍለቅ ወይም ለመጭመቅ በላዩ ላይ መራመድ

Nehemiah 13:16

ጢሮስ
ይህ የአንድ ከተማ ስም ነው (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የምታደርጉት ክፉ ነገር ምንድን ነው፣ ሰንበትንስ ታረክሳላችሁን?
ነህምያ ይህን መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ የይሁዳን አለቆች ለመገሰጽ ተጠመበት:: ይህ በዓርፍተ ነገር መልክ መተርጎም ይቻላል:: አማራጭ ትርጉም:- “የሰንበትን ቀን በማርከስ ክፉ ስራን እየሰራችሁ ነው” ወይም “የሰንበትን ቀን በማርከስ ለሰራችሁት ክፉ ስራ እግዚአብሔር ይቀጣችኋል” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

አባቶቻችሁ ይህን አድርገው አልነበረም? እግዚአብሔር በእኛና በከተማዋ ላይ ክፉ ነገርን ሁሉ አላመጣም?
ነህምያ እነዚህን መልስ የማይሰጥባቸውን ጥያቄዎች የይሁዳን አለቆች ለመገሰጽ ተጠቀመባቸው:: እነዚህ ጥያቄዎች በአንድ ላይ በማያያዝና በመተርጎም በአንድ ዓረፍተ ነገር መጻፍ እንችላለን:: አማራጭ ትርጉም:- “አባቶቻችሁ ይህን እንዳደረጉ ታውቃላችሁ፣ እግዚአብሔር ይህን ሁሉ ክፉ ነገር በእኛና በዚህች ከተማ ላይ ያመጣው ለዚህ ነው” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 13:19

በመሸ ጊዜ ... ከሰንበት በፊት
“ፀሐይ በገባች ጊዜ ... ሰንበት ሊጀምር ሰዓቱ ደርሶ ነበር”

በሮችዋ እንዲዘጉና እንዳይከፈቱ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል:: አማራጭ ትርጉም:- “ጠባቂዎቹ በሮቹን እንዲዘጉና እንዳይከፍቱአቸውም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ሸክም ወደ ውስጥ እንዳይገባ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል:: አማራጭ ትርጉም:- “ማንም መሸጥ የሚፈልገውን ነገር ይዞ መግባት አይችልም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የሁሉም ዓይነት እቃ ሻጮች
“መሸጥ የፈለጉአቸውን ብዙ የተለያዩ እቃዎችን ይዘው የመጡ ሰዎች”

Nehemiah 13:21

ከቅጥሩ ውጪ ለምን ታድራላችሁ?
ነህምያ ነጋዴዎችን ለመገሰጽና ትዕዛዙን አጠንክሮ ለመናገር ይህን መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ በዓርፍተ ነገር መልክ መተርጎም ይቻላል። የዚህ ዓርፍተ ነገር ሙሉ ትርጉምም ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ካዘዝኩት ነገር በተቃራኒ ከቅጥሩ ውጪ እያደራችሁ ነው” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች እና ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እጄን በእናተ ላይ አደርጋለሁ!
“እጅ” የሚለው ቃል በሃይል የተሞላ እርምጃን የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በኃይል አስነስቼ አባርራችኋለሁ!” ወይም “በኃይል አስወግዳችኋለሁ!” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

አምላኬ ሆይ ስለዚህ ደግሞ አስበኝ
“አምላኬ ሆይ፣ ይህንን አስመልክቶ እኔን አስበኝ” እንደዚህ ዓይነት ተመሳሳይ ሐረግ በነህምያ 13:14 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።

Nehemiah 13:23

አያያዥ ዓርፍተ ነገር፦
እነዚህ ቁጥሮች ተከትለው ለሚመጡት ድርጊቶች እንደ መግቢያ ያገለግላሉ።

የአዛጦን፣ የአሞንና የሞዓብ ሴቶችን ያገቡት አይሁዳውያን
“አይሁውያን ያልሆኑ ሴቶችን ያገቡ አይሁዳውያን” እግዚአብሔር ከዘራቸው ውጪ መጋባትን ከልክሎ ነበር። የዚህ ዓረፍተ ነገር ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አዛጦን
ይህ የከተማ ስም ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

አሞን ... ሞዓብ
እነዚህ የሕዝብ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ከልጆቻቸውም ግማሾቹ
“ከዚህም የተነሳ ከልጆቻቸው ግማሾቹ”

Nehemiah 13:25

ተከራከርኳቸው
“ስለሰሩት ነገርም በቀጥታ ተናገርኳቸው”

አንዳንዶቹን መታኋቸው
ነህምያ አንዳንዶቹን በእጁ መታቸው።

በእግዚአብሔር አስማልኳቸው
“በእግዚአብሔር ፊት ቃል አስገባኋቸው”

የእስራኤል ንጉስ ሰሎሞን በእነዚህ ሴቶች ምክንያት አልሳተምን?
ነህምያ ይህን መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ ሰዎቹን ለመገሰጽ ተጠቀመ። ይህ በዓርፍተ ነገር ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የእስራኤል ንጉስ ሰሎሞን በእነዚህ ሴቶች ምክንያት ኃጢአትን ማድረጉን ታውቃላችሁ” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ታዲያ እናንተን ሰምተን ይህንን ታላቅ ኃጢአት እናድርግ፣ እነዚህን እንግዳ ሴቶች በማግባትም አምላካችን ላይ በደል እናድርግ?
ነህምያ ሰዎቹን ለመገሰጽ ይህን መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ ተጠቀመ። ይህ በዓርፍተ ነገር መልክ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እናንተን አንሰማም ወይም ይህን ታላቅ ኃጢአት አናደርግም ወይም እነዚህን እንግዳ ሴቶችም በማግባት አምላካችንን አንበድልም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 13:28

ዮአዳ ... ኤልያሴብ ... ሰንባላጥ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ሖሮናዊው
ይህ የሚያመለክተው ከቤት ሖሮን ከተማ የመጣ ሰውን ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

እኔም ከአጠገቤ አባረርኩት
“አባረርኩት” ወይም “ኢየሩሳሌምን እንዲለቅቅ አደረግኩት”

አስባቸው
“ስለ እነርሱ አስብ” ወይም “ያደረጉትን አስታውስ።” እንደዚ አይነት ተመሳሳይ ሐረግ በነህምያ 13:14 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ

ክህነትን ስላረከሱ የካህናትንና የሌዋውያንን ቃልኪዳንም ስላፈረሱ
ክህነትን ማርከስ እና ቃልኪዳኑን ማፍረስ ክህነቱንና ቃልኪዳኑን በአካል እንዳረከሱት ተደርጎ ቀርቧል። አማራጭ ትርጉም፦ “የክህነቱን ክብር አጉድለዋል፣ ከካህናቱና ከሌዋውያኑ ጋር ያደረግኸውን ቃልኪዳን አፍርሰዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 13:30

ስለዚህ አነጻኋቸው
“በዚህም መንገድ አነጻኋቸው”

የካህናትና የሌዋውያንን ሥርዓት አደረግሁ
“ካህናቱና ሌዋውያኑን ምን ማድረግ እንደነበረባቸው ነገርኳቸው”

የእንጨት ቁርባንን አደረግኩኝ
“የእንጨት ቁርባን የቀርብበትን እንጨት አዘጋጀሁ”

ለበኩራቱም
“በመኸር ጊዜ የሚቀርበው የመጀመርያው ምርት”

አስበኝ፣ አምላኬ፣ በመልካም አስበኝ
“አምላኬ፣ የሰራሁትን ነገር ሁሉ አስብ ደግሞ ስላደረግሁት መልካም ነገር ባርከኝ” ይህ በነህምያ 13:14 ለይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Esther

Esther

Chapter 1

1 በአርጤክስስ ዘመን (እርሱም ከህንድ እስከ ኢትዮጵያ ድረስ በአንድ መቶ ሃያ ሰባት አገሮች የነገሠው ነው) **2** በእነዚያ ጊዜያት ንጉሡ አርጤክስስ በሱሳ
ግንብ ውስጥ ባለው የመንግሥቱ ዙፋን ላይ ተቀመጠ። **3** በነገሠ በሦስተኛው ዓመት ለሹማምንቱና ለአገልጋዮቹ በሙሉ ግብዣ አደረገላቸው። የፋርስና የሜዶን
የጦር አዛዦች፥ ባላባቶችና የአውራጃ አስተዳዳሪዎችም በፊቱ ነበሩ። **4** የመንግሥቱን ውበት ባለጸግነትና የግርማውን ክብር ታላቅነት ለብዙ ቀናት ማለትም
ለ180 ቀናት አስጎበኛቸው። **5** እነዚህ ቀናት ካበቁ በኋላ ንጉሡ ለሰባት ቀናት የሚቆይ ግብዣ አዘጋጀ። ግብዣው የተዘጋጀው ከታላቁ ጀምሮ እስከ ታናሹ ድረስ
በሱሳ ቤተመንግሥት ውስጥ ለነበሩት ሰዎች ሁሉ ነበር። ይህም የተደረገው በንጉሡ ቤተመንግሥት መናፈሻ በሚገኘው አደባባይ ውስጥ ነበር። **6** ከጥጥ
የተሠሩ ነጭና ሰማያዊ መጋረጃዎች ነጭና ሐምራዊ ገመድ በብር ቀለበቶቹ ውስጥ አልፈው በእምነበረዳ ቋሚዎች ላይ በመሰቀላቸው የመናፈሻው አደባባይ
ተውቦ ነበር። በቀይ ዓለት፥ በእምነበረድ፥ በእንቁ እናትና የተለያየ ቀለም ባላቸው የንጣፍ ድንጋዮች ባሉት ሥዕላዊ ወለል ላይ የወርቅና የብር ድንክ አልጋዎች
ነበሩ። **7** መጠጡ በወርቃማ መጠጫዎች ይቀርብ ነበር። እያንዳንዱ መጠጫ የተለያየ ነበር፥ ከንጉሡ ለጋስነት የተነሣም የቤተመንግሥቱ ወይን የተትረፈረፈ
ነበር። **8** መጠጡ ይቀርብ የነበረውም፥ "ግዴታ መኖር የለበትም" የሚለውን መመሪያ በመከተል ነበር። እንግዶቹ እያንዳንዳቸው በሚፈልጉት መጠን
እንዲቀርብላቸው ንጉሡ የቤተመንግሥቱን ሠራተኞች አዝዞ ነበር። **9** ንግሥት አስጢን በበኩሏ በንጉሡ አርጤክስስ ንጉሣዊ ቤተመንግሥት ለሴቶች ግብዣ
አደረገች። **10** በሰባተኛው ቀን ንጉሡ ከወይን ጠጅ የተነሣ ልቡን ደስታ በተሰማው ጊዜ ምሁማንን፥ ባዛንን፥ ሐርቦናን፥ ገበታን፥ ዘቶልታን፥ ዜታርንና ከርከስን
(በፊቱ የሚያገለግሉትን ሰባቱን ሹማምንት) ንግሥት አስጢን ዘውዷን ደፍታ በፊቱ እንድትቀርብ አዘዛቸው። **11** ተክለ ሰውነቷ ያማረ ነበርና ውበቷን ለሕዝቡና
ለሹማምንቱ ለማሳየት ፈለገ። **12** ንግሥት አስጢን ግን ንጉሡ በሹማምንቱ በላከባት ቃል መሠረት ለመምጣት እምቢ አለች። ከዚያም ንጉሡ በጣም ተቆጣ፥
ቁጣውም በውስጡ ነደደ። **13** ስለዚህ ንጉሡ ዘመኑን ከሚመረምሩ ጥበበኞች ሰዎች ጋር ተመካከረ (ሕግንና ዳኝነትን ስለሚያውቁት ሰዎች ሁሉ የንጉሡ
ልምድ እንዲህ ነበርና) ። **14** የቅርቦቹ የነበሩትም ሰባቱ የፋርስና የሜዶን መሳፍንት የሆኑት አርቄስዮስ፥ ሼታር፥ አድማታ፥ ተርሺሽ፥ ሜሬስ፥ ማሌሴዓርና
ምሙካን ነበሩ። እነዚህ ለንጉሡ የሚቀርቡና በመንግሥቱ ውስጥ ከፍተኛውን ሥልጣን የያዙ ናቸው። **15** "በሹማምንቱ የተላከባትን የንጉሡን የአርጤክስስን
ትዕዛዝ አልታዘዘችምና በሕጉ መሠረት በንግሥት አስጢን ላይ መደረግ ያለበት ምንድነው?" **16** ምሙካንም በንጉሡና በመኳንንቱ ፊት እንዲህ አለ፥
"ንግሥቲቱ አስጢን የበደለችው መኳንንቱን ሁሉና በንጉሡ በአርጤክስስ ግዛቶች ሁሉ የሚገኘውን ሕዝብ በሙሉ ደግሞ እንጂ ንጉሡን ብቻ አይደለም። **17**
የንግሥቲቱ ጉዳይ በሁሉም ሴቶች የሚታወቅ ይሆናል። ይህም ባሎቻቸውን እንዲንቁ ያደርጋል። እነርሱም፥ 'ንግሥት አስጢንን በፊቱ እንዲያቀርቧት ንጉሡ
አርጤክስስ አዘዘ፥ እርስዋ ግን እምቢ አለች' ይላሉና። **18** የንግሥቲቱን ጉዳይ የሰሙ የመኳንንቱ ሚስቶችም ይህ ቀን ከማለፉ በፊት ለንጉሡ መካንንቶች
በሙሉ ተመሳሳዩን ቃል ይናገራሉ። ብዙ ንቀትና ቁጣም ይሆናል። **19** ንጉሡን ደስ የሚለው ከሆነ፥ አስጢን ዳግመኛ በፊቱ እንዳትቀርብ ንጉሣዊ ትዕዛዝ
ያውጣ፥ ሊለወጥ የማይቻል ሆኖም በፋርስና በሜዶን ሕግ ውስጥ ይጻፍ። የንግሥትነቷን ክብርም ንጉሡ ክእርስዋ ለምትሻል ለሌላይቱ ይስጥ። **20** የንጉሡ
ትዕዛዝ በሰፊው መንግሥቱ ሁሉ በሚታወጅበት ጊዜ፥ ከታላቁ እስከ ታናሹ ድረስ ሚስቶች ሁሉ ባሎቻቸውን ያከብራሉ።" **21** ንጉሡና መካንንቶቹ በዚህ ምክር
ተደሰቱ፥ ንጉሡም የምሙካንን ምክር ተግባራዊ አደረገው። **22** እርሱም ደብዳቤዎችን ለእያንዳንዱ አውራጃ በየራሱ ጽሕፈትና ለእያንዳንዱ ሕዝብ በየራሱ ቋንቋ
አድርጎ ወደ መንግሥቱ አውራጃዎች በሙሉ ላከው። እርሱም እያንዳንዱ በቤተሰቡ ላይ ገዥ እንዲሆን አዘዘ። ይህም ትዕዛዝ በመንግሥቱ ውስጥ ላለ
ለእያንዳንዱ ሕዝብ በየቋንቋው ተሰጠው።

Esther 1:1

በጠረክሲስ ዘመን
"ጠረክሲስ በሚገዛበት ዘመን" ወይም "ጠረክሲስ ንጉሥ ሆኖ ይገዛ በነበረበት ጊዜ"

ይህ ጠረክሲስ ከህንድ አንስቶ እስከ ኩሽ/ ኢትዮጵያ ድረስ ከ**127** ግዛቶች በላይ ይገዛ ነበር።
ይህ የመረጃ ዳራ የቀረበው አንባቢ ጠረክሲስን ለማወቅ ይረዳው ዘንድ ነው። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

ግዛቶች
ግዛት አንዳንድ አገራት ለአስተዳደር ሲባል የሚከልሉት ሰፊ አካባቢ/ስፍራ ነው።

በንጉሣዊ ዙፋኑ ላይ ተቀመጠ
እዚህ ስፍራ "ንጉሣዊ ዙፋን" የሚለው በግዛቱ ላይ ያለውን አገዛዝ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። "መንግሥቱን አስተዳደረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት- የሚለውን ይመልከቱ)

ምሽግ/ግንብ
ይህ የቤተመንግሥት ግንብን፣ ጠንካራ ይዞታን ወይም የተመሸገ ከተማን ያመለክታል።

ሱሳ
ይህ የፋርስ ነገስታት መናገሻ ከተማ ነበር (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ፤ የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 1:3

በግዛቱ ሶስተኛ አመት
"ለ2 አመታት ከገዛ በኋላ" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰራዊቱ
ይህ ምናልባት የሰራዊቱን መሪዎች ሊያመለክት የሚችል ነው። " የሰራዊቱ መኳንንት " በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሲኔክቲኪ/ ዘይቤያዊ አነጋጋር- የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ፤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የግዛቱ ብልጽግና ታላቅነት
እነዚህ ቃላቶች ግዛቱ ምን ያህል ታላቅ እንደነበር አጉልተው የሚገልጹ እና ተመሳሳይ ትርጉም የያዙ ናቸው። (ደብሌት/ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

የታላቅነቱ ግርማ ክብር
እነዚህ ቃላት ምን ያህል ታላቅ እንደነበር የሚያጎሉ እና ተመሳሳይ ትርጉም የያዙ ናቸው። "የታላቅነቱ ክብር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

180 ቀናት
"አንድ መቶ ሰማንያ ቀናት" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 1:5

እነዚህ ቀናቶች በተፈጸሙ ጊዜ
"በዚያ ክብረ በዓል ማብቂያ"

ሰባት ቀናት የወሰደ በዓል
በሱሳ ለነበሩ መኳንንት ብቻ የተደረገ ሁለተኛው ክብረ በዓል ነበረር። "ሰባት ቀናት የፈጀ ሌላ ክብረ በዓል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ምሽግ/ግንብ
ይህ የቤተመንግሥት ግንብን፣ ጠንካራ ይዞታን ወይም የተመሸገ ከተማን ያመለክታል። በአስቴር 1:1 ይህንን እንዴት እንደተረጎሙት ተመልሰው ይመልከቱ።

ሱሳ
በአስቴር 1:2 ላይ የዚህን ስፍራ ስያሜ እንዴት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ፤ የሚለውን ክፍል ይመልከቱ)

በሞዛይክ (በጠጠር) የሚሰራ የእግረኛ መንገድ/ወለል
"ሞዛይክ" - ለዐይን ማራኪ በሆነ የአሰራር መንገድ የተለያዩ ቀለማት ያላቸውን ድንጋዮች በመጠቀም ይቀርባል

ፓርፊሪ/ ለጌጥ መስሪያ የሚያገለግል ቀይ/ሐምራዊ አለት
ይህ ቀይ እና ሐምራዊ መልክ ያለው አለት ሲሆን መስታወት የመሰለ ድንጋይ/የክርስታል ቁርጥራጮች አሉት።

Esther 1:7

መጠጥ በወርቅ ዋንጫ ይቀርብ ነበር።
በአድራጊ ዐረፍተ-ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እንግዶች ከወርቁዋንጫ ወይን ጠጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ገቢር/ተገቢሮ ወይም አድራጊ/ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ከንጉሡ ልግስና የተነሳ ብዙ የንጉሣዊ ክብር መገለጫ የሆነ ወይን ይቀርብ ነበር።
"ንጉሡ በንጉሳዊ ክብር መግለጫ ረገድ እጅግ ለጋስ ነበር"

ለጋስነት
"ለመስጠት ታላቅ ፈቃደኝነት"

አንዳች ግዴታ አይጣልም ነበር
"ማንም ወይን ለመጠጣት አይገደድም ነበር"

ንጉሡ ለቤተ መንግስቱ መኳንንት በሙሉ ለእያንዳንዱ ሰው የፈለገውን ያህል እንዲያቀርቡለት ትዕዛዝ አስተላለፈ።
ይህ ሃሳብ፤ ንጉሡ ለባለሟሎቹ ለሁሉም ታዳሚየሚፈልገውን ያህል ወይን እንዲሰጠው ትዕዛዝ ሰጥቶ ነበር ማለት ነው።

Esther 1:9

በሰባተኛው ቀን
"ከ6 ቀናት በኋላ" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

የንጉሡ ልብ ከወይን ጠጅ የተነሳ ደስ ተሰኝቶ ነበር።
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚለው ቃል ንጉሡን ያመለክታል፣ "ደስታ ተሞልቶ" የሚለው ደግሞ በፈሊጣዊ አገላለጽ ሰክሮ ነበር የሚል ትርጉም አለው። "ንጉሡ ወይን ጠጥቶ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሴኔክቲክ/ዘይቤያዊ አነጋገር እና ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ምሁማን፣ ባዛን፣ ሐርቦና፣ ገበታ፣ ዘቶሊያ፣ ዜታር እና ከርከስ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ፤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሚያገለግሉት ሰባቱ ሹማምንት
ይህ እነዚህ ሰዎች እነማን እንደነበሩ ለመግለጽ የቀረበ የመረጃ ዳራ ነው። (መረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

ተክለ ሰውነቷና ውበቷ አስደናቂ ነበር
"በጣም ውብ ነበረች"

Esther 1:12

በመኳንንቱ በደረሳት የንጉሡ ቃል መሰረት
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ-ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የንጉሡ ሹማምንት ስለ ንጉሡ ትዕዛዝ በነገሯት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ- ገቢር/ተገቢሮ የሚለውን ይመልከቱ)

በቃሉ
"በትዕዛዙ"

ቁጣው በውስጡ ነደደ
ይህ ጠንካራ የንጉሡ ቁጣ የተገለጸው በውስጡ እንደሚነድ እሳት ነው። "ቁጣው በውስጡ እንዳለ እሳት የበረታ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 1:13

ወቅቱን የተረዱ
"በህይወታቸው ውስጥ የሚፈጸመውን ነገር የሚረዱ" ንጉሡ በህግና በፍርድ ዐዋቂ ከሆኑ ጋር የመመካከር ልማድ ነበረው። ይህ የመረጃ ዳራ ንጉሡ እነዚህን ሰዎች ለምን እንደጠራ ያብራራል። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

አርቄስዮስ፣ ሼታር፣ አድማታ፣ ተርሺሽ፣ ማሬስ፣ ማሌሴዓር እና ምሙካ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ፤ የሚለውን ይመልከቱ

ህጉ እንዲከበር...በሹማምንነቱ ምን ቅሬታ ቀረበ?
ይህንን ጥያቄ ማን እንዳቀረበ መግለጹ ሊጠቅም ይችላል። ንጉሡ እንዲህ አላቸው፣ "ህጉ በመጣሱ ... በመኳንንት?" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ህጉ እንዲከበር
"ህጉን በማጤን" ወይም "ህጉን በመታዘዝ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Esther 1:16

ምሙካ
በአስቴር 1:14 በሚገኘው መሰረት ስሙን ይተርጉሙ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ፤የሚለውን ይመልከቱ)

መላው መኳንንት እና መላው ህዝብ... መላው ግዛት... ሴቶቹ ሁሉ
እነዚህ ሁሉ ግነቶች የተደረጉት የንግስቲቱ አለመታዘዝ የሚያስከትለውን ነገር ለማጉላት ነው። (ግነት እና ድምዳሜ የሚለውን ይመልከቱ)

ግዛቶች
ግዛት አንዳንድ አገራት ለአስተዳደር ሲባል የሚከልሉት ሰፊ አካባቢ/ስፍራ ነው። ይህንን በአስቴር 1:1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

ብዙ ንቀትና ቁጣ ይሆንል
"ባሎቻቸውን የማይታዘዙ ይሆናሉ፤ በንቀትም ያይዋቸዋል።

Esther 1:19

አያያዥ ሃሳብ፡
ምሙካ ለንጉሠ ጥያቄ ምላሽ መስጠቱን ቀጠለ

ንጉሠን ደስ የሚያሰኝ ከሆነ ...ወደ ንጉሡ... በፊቱ....ንጉሡ... የንጉሡ አወጅ... ታላቅ ግዛቱ
ምሙካ በሶስተኛ መደብ የተናገረው ንጉሠን በማክበር ነው። "ንጉሠን ደስ የሚያሰኝ ከሆነ... ከእርሱ...በፊቱ... ካስደተ... አዋጁ... በሰፊ ግዛቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

የማይሻር ሆኖ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ማንም ሊሽረው የማይችል ሆኖ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የንጉሠ አዋጅ ሲታወጅ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የንጉሠን አዋጅ በሰሙ ጊዜ" ወይም "ንጉሠ ያዘዘውን በሰሙ ጊዜ" በሚለው ውሰስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ታላቅ
በጣም ሰፊ

ከታላቁ እስከ ታናሹ
ይህ ሁለቱንም ጽንፎች እና በመሃል የሚገኘውን ሁሉ ከዳር ስስከ ዳር የሚገልጽ ነው። ይህ ምናልባትም ባሎችን ሊመለከት ይችላል፣ ነገር ግን ሚስቶችን ማመላከት ይችላል። (ጽንፍ/ሜሪዝም የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 1:21

ምሙካ
ስሙን በአስቴር 1:14 ውስጥ በሚገኘው መሰረት ይተርጉሙ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ፤ የሚለውን ይመልከቱ)

ግዛት
ግዛት አንዳንድ አገራት ለአስተዳደር ሲባል የሚከልሉት ሰፊ አካባቢ/ስፍራ ነው። ይህንን በአስቴር 1:1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

እያንዳንዱ ሰው የቤቱ ገዢ መሆን አለበት
" ሁሉም ወንዶች በሚስቶቻቸው እና በልጆቻቸው ላይ ሙሉ ስልጣን ሊኖራቸው ይገባል"

ይህ አዋጅ ተሰጥቶ የነበረው
ይህ በአድራጊ ጊዜ እንዲህ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። " እነርሱ ይህንን አዋጅ ጻፉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ- ገቢር/ተገቢሮ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 ከእነዚህ ነገሮች በኋላ የንጉሡ አርጤክስስ ቁጣ በበረደለት ጊዜ ንግሥት አስጢንን፥ እርሷም ያደረገችውን አሰበ። እንዲሁም በእርሷ ላይ ያስተላለፈውን የፍርድ ውሳኔ አሰበ። **2** ከዚያም ያገለግሉት የነበሩት የንጉሡ ወጣቶች፥ "የተዋቡ ልጃገረዶች ለንጉሡ ይፈለጉለት። **3** የተዋቡ ልጃገረዶችን በሙሉ በሱሳ ቤተመንግሥት ወደሚገኘው የሴቶች መኖሪያ እንዲሰበስቧቸው በመንግሥቱ አውራጃዎች ሁሉ ንጉሡ ኃላፊዎችን ይሹም። እነርሱም የሴቶች ኃላፊ በሆነው የንጉሡ ሹም በሄጌ ጥበቃ ሥር ይደረጉ፥ እርሱም መዋቢያዎቻቸውን ይስጣቸው። **4** ንጉሡን ደስ የምታሰኘው ልጃገረድ በአስጢን ፈንታ ንግሥት ትሁን።" ይህም ምክር ንጉሡን አስደሰተው፥ እርሱም እንደዚሁ አደረገ። **5** በሱሳ ከተማ መርዶክዮስ የሚባል አንድ አይሁዳዊ ነበር፥ እርሱም ብንያማዊ ሲሆን የቂስ ልጅ፥ የሰሜኢ ልጅ፥ የኢያዕር ልጅ ነበር። **6** እርሱም የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ከማረከው ከይሁዳ ንጉሥ ከኢኮንያን ጋር ተማርኮው ከተወሰዱት ምርኮኞች ጋር ከኢየሩሳሌም ተወስዶ ነበር። **7** እርሱም አባትም ሆነ እናት አልነበራትምና የአጎቱን ልጅ ሀደሳ የተባለችውን አስቴርን ያሳድግ ነበር። ልጃገረዲቱም የተዋበ ተክለሰውነትና ማራኪ ገጽታ ነበራት። መርዶክዮስ እንደ ራሱ ልጅ አድርጎ ወስዷት ነበር። **8** የንጉሡ መመሪያና ትዕዛዝ በታወጀ ጊዜ ብዙ ልጃገረዶችን ወደ ሱሳ ቤተመንግሥት ሰበሰቧቸው። እነርሱም ከሄጌ ጥበቃ ሥር ተደረጉ። አስቴርም ደግሞ ወደ ቤተመንግሥቱ ተወስዳ ከሴቶቹ ተቆጣጣሪ ከሄጌ ሥር ተደረገች። **9** ልጃገረዲቱ ደስ አሰኘችው፥ በፊቱም ሞገስን አገኘች። ወዲያውም የምግብ ድርሻዋንና መዋቢያዎቿን ሰጣት። ለእርሷም ከንጉሡ ቤተመንግሥት የሚያገለግሏትን ሰባት ልጃገረዶች መደበላት፥ እርሷንና የሚያገለግሏትን ልጃገረዶች በሴቶቹ መኖሪያ ውስጥ ወደ ተሻለው ክፍል አዛወራቸው። **10** መርዶክዮስ እንዳትናገር አዝዟት ስለ ነበር፥ አስቴር ሕዝቧንም ሆነ ወገንዋን ለማንም አልተናገረችም ነበር። **11** መርዶክዮስ የአስቴርን ደኅንነትና ያለችበትን ሁኔታ ለማወቅ በየዕለቱ በሴቶቹ መኖሪያ በስተውጭ ባለው አደባባይ ይመላለስ ነበር። **12** እያንዳንዷ ልጃገረድ ወደ ንጉሡ አርጤክስስ የምትሄድበት ተራ በደረሰ ጊዜ - ለሴቶቹ በወጣው ደንብ መሠረት እያንዳንዷ ልጃገረድ ስድስት ወር በከርቤ ዘይት፥ ስድስት ወር ደግሞ በሽቶዎችና በመዋቢያዎች ለአሥራ ሁለት ወራት የውበት አያያዝ ጊዜአቸውን ማጠናቀቅ ነበረባቸው - **13** አንዲት ልጃገረድ ወደ ንጉሡ በምትሄድበት ጊዜ ወደ ቤተመንግሥት እንድትወስደው የፈለገችው ሁሉ ከሴቶቹ መኖሪያ ይሰጣት ነበር። **14** ሲመሽ ትገባና ሲነጋ ወደ ሁለተኛው የሴቶች መኖሪያ፥ በቁባቶቹ ላይ ኃላፊ ወደሆነው የንጉሥ ሹም ወደ ሻአሸጋዝ ጥበቃ ሥር ትመለስ ነበር። ንጉሡ ተደስቶባት ዳግም ካልጠራት በስተቀር ሁለተኛ ወደ እርሱ መመለስ አትችልም ነበር። **15** ወደ ንጉሡ ለመግባት የአስቴር (መርዶክዮስ እንደ ራሱ ልጅ አድርጎ የወሰዳት የአቢካኤል ልጅ) ተራ በደረሰ ጊዜ በሴቶች ላይ ኃላፊ የሆነው የንጉሡ ሹም ሄጌ ከነገራት በቀር ምንም ነገር አልጠየቀችም። አስቴርም በሚያዩዋት ሁሉ ፊት ሞገስን ታገኝ ነበር። **16** አስቴርም ንጉሡ አርጤክስስ በነገሠ በሰባተኛው ዓመት፥ ቴቤት ተብሎ በሚጠራው በአሥረኛው ወር፥ ወደ ንጉሣዊ መኖሪያው ተወሰደች። **17** ንጉሡም ከሌሎቹ ሴቶች ሁሉ ይልቅ አስቴርን ወደዳት፥ ከደናግሉም ሁሉ ይልቅ በፊቱ ሞገስንና መወደድን አገኘች፥ ስለዚህ የእቴጌነትን ዘውድ በራሷ ላይ አደረገላት፥ በአስጢንም ምትክ ንግሥት አደረጋት። **18** ንጉሡም "የአስቴር ግብዣ" ብሎ የጠራውን ታላቅ ግብዣ ለሹማምንቱና ለአገልጋዮቹ ሁሉ አደረገ፥ አውራጃዎቹንም ከቀረጥ አሳረፋቸው። ደግሞም በንጉሣዊ ልግስናው ስጦታዎችን ሰጠ። **19** ደናግሎቹ ለሁለተኛ ጊዜ በተሰበሰቡ ጊዜ መርዶክዮስ በንጉሡ በር ይቀመጥ ነበር። **20** አስቴር ሕዝቧን ወይም ወገኗን መርዶክዮስ ባዘዛት መሠረት ገና ለማንም አልተናገረችም ነበር። እርሷም በልጅነትዋ ጊዜ ታደርግ አንደነበረው የመርዶክዮስን ምክር መከተልዋን ቀጠለች። **21** በእነዚያም ቀናት መርዶክዮስ በንጉሡ በር ተቀምጦ እያለ በሩን ይጠብቁ የነበሩት ሁለቱ የንጉሡ ሹማምንት ገበታና ታራ ተቆጡ፥ ንጉሡን አርጤክስስንም ለመግደል ፈለጉ። **22** መርዶክዮስ ጉዳዩን ባወቀ ጊዜ ለንግሥት አስቴር ነገራት፥ እርሷም በመርዶክዮስ ስም ለንጉሡ ነገረችው። **23** መረጃው ሲመረመር እውነት ሆኖ ተገኝ፥ ሁለቱም ሰዎች በስቅላት ተቀጡ። ታሪኩም በንጉሡ ፊት በታሪክ መዝገብ ላይ ተጻፈ።

Esther 2:1

ከእነዚህ ነገሮች በኋላ
ይህ ጥቂት ቆየት ብሎ የሆነን አዲስ ትዕይንት ያስተዋውቃል። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

የንጉሥ ጠረክሲስ ቁጣ በረደ
" ንጉሡ ቁጣው ቀነሰ"

አዋጁ
ይህ በአስቴር 1፡19-20 ያለውን አዋጅ ያመለክታል

ፍለጋ ይደረግ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አገልጋዮችህ እንዲፈልጉ እዘዛቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ- ገቢር/ተገቢሮ የሚለውን ይመልከቱ)

በንጉሡ ፈንታ
ሰዎቹ ንጉሡን በሶስተኛ መደብ የሚናገሩት ለአክብሮት መግለጫ ነው። "በአንተ ፈንታ" (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 2:3

አያያዥ ሃሳብ፡
ወጣቶቹ አገልጋዮች ለንጉሡ ገለጻቸውን ቀጠሉ

ንጉሡ... የንጉሡ ሹማምንት... ንጉሡ ቢፈቅድ
አገልጋዮቹ ንጉሡን በሶስተኛ መደብ የሚያናግሩት አክብሮታቸውን ለመግለጽ ነው። "ማድረግ ያለበት... ሹማምንቱ... ንጉሡ ቢፈቅድ" (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ግዛቶች
ግዛት አንዳንድ አገራት ለአስተዳደር ሲባል የሚከልሉት ሰፊ አካባቢ/ስፍራ ነው። ይህንን በአስቴር 1፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

የሴቶች ቤት/ ሃሬም
የአንድ ወንድ ሚስቶች ከብዙ ሚስቶቹ ጋር የሚኖሩበት ቤት

ግንቡ/ምሽጉ
ይህ የቤተመንግሥት ግንብን፣ ጠንካራ ይዞታን ወይም የተመሸገ ከተማን ያመለክታል። በአስቴር 1፡2 ይህንን እንዴት እንደተረጎሙት ተመልሰው ይመልከቱ።

ሱሳ
በአስቴር 1፡2 ላይ የዚህን ስፍራ ስያሜ እንዴት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ክፍል ይመልከቱ)

የሴቶች የበላይ ሃላፊ በሆነው በንጉሡ አገልጋይ በሄጌ እንክብካቤ ስር ይሁኑ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ-ነገር ሊገለጽ ይችላል። " የሴቶች ሃላፊ የሆነው፣ የንጉሡ ሹም ሄጌ፣ እነርሱን ይንከባከባል" (አድራጊ እና ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሄጌ
ይህ የወንድ ስም ነው።(ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ፤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሴቶች መኳኳያ
"መኳኳያ"- እንደ የፊት ዱቄት/ፓውደር፣ ፊትን ለማውዛት የሚረዳ ቅባት/ሎሽን፣ ክሬም/ጭቃ ቅባት የመሰለ ሲሆን ብዙውን ጊዜ ሴቶች ውበታቸውን ለማውጣት በፊታቸው ወይም በአካላቸው ላይ የሚቀቡትነው።

Esther 2:5

አንድ አይሁዳዊ ነበር
ይህ መርዶክዮስን እንደ አዲስ ገጸባህሪይ ያስተዋውቃል። (አዲስ እና አሮጌ ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

ሱሳ
የዚህን ከተማ ስም በአስቴር 1:2 ላይ በተረጎሙት መሰረት ይተርጉሙት። (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ክፍል ይመልከቱ)

የኢያዕር ልጅ የሰሜኢ ልጅ የቂስ ልጅ
"ኢያዕር፣ "ሰሜኢ፣" እና "ቂስ" እነዚህ ወንዶች ሲሆኑ እነርሱም የ"መርዶክዮስ" አባቶች ናቸው። (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ፤ የሚለውን ክፍል ይመልከቱ)

ብንያማዊ
"የብንያም ነገድ"

እርሱ ተወስዶ ነበር... የባቢሎን ንጉሥ ማረኮት ነበር
ይህ የመረጃ ዳራ መርዶክዮ ወደ ሱሳ ለመኖር እንዴት እንደመጣ ያብራራል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ- ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር እርሱን እና ሌሎች ምርኮኞችን ከይሁዳ ነጉሥ ከኢኮንያን ጋር ማረኮ ወሰዳቸው" (የመረጃ ዳራ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ከኢየሩሳሌም ተማርኮ ነበር
የዕብራይስጡ ትርጉም እዚህ ስፍራ ስለማን እንደሚነገር ግልጽ አላደረገውም። ምናልባት የመርዶክዮስ ቅድም አያት የሆነው ቂስ ሊሆን ይችላል። ራሱ መርዶክዮስ ከሆነ ግን አስቴርን በተመለከተ የሆነው ትዕይንቶች ሲፈጸሙ እጅግ አርጅቶ ነበር ማለት ነው። በርካታ አዳዲስ ትርጉሞች ይህንን ጉዳይ ግልጽ አያደርጉትም። ጥቂት ትርጉሞች ፣ ዩዲቢን (አንሎክ ዳይናሚክ ባይብል) ጨምሮ ከኢየሩሳሌም የተማረከው መርደኪዮስ እንደሆነ አድርገው ማቅረብን ይመርጣሉ።

ኢኮንያን፣ የይሁዳ ንጉሥ
(ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ክፍል ይመልከቱ)

Esther 2:7

አያያዥ ሃሳብ፡
ይህ ስለ መርዶክዮስ የመረጃ ዳራ ማቅረብን ይቀጥላል እንደዚሁም ከአስቴር ጋር ያለውን ግንኙነት ያብራራል። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

ሀደሳ
ይህ የአስቴር የእብራዊ ስሟ ነው። (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ክፍል ይመልከቱ)

የአጎቱ ሴት ልጅ
"ለእርሱ የአጎቱ ልጅ ናት"

እናትም ሆነ አባት አልነበራትም
"እናቷ እና አባቷ ሞተው ነበር"

እንደ ራሱ ልጅ አድርጎ ወስዷት ነበር
የራሱ ልጅ የሆነች ያህል ይንከባከባት ነበር"

Esther 2:8

የንጉሡ ትዕዛዝ እና አዋጅ በታወጀ ጊዜ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ-ነገር ሊገለጽ ይችላል። " ንጉሠ ውብ የሆነች ሴት እንዲፈልጉ ካዘዘ በኋላ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(አድራጊ እና ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ታወጀ
"ተነገረ"

ብዙ ወጣት ሴቶች ቀረቡ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ-ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ብዙ ወጣት ሴቶችን አቀረቡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(አድራጊ እና ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በሄጌ እንክብካቤ ስር ሆኑ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ-ነገር ሊገለጽ ይችላል።"ሄጌ እነርሱን መንከባከብ ጀመረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(አድራጊ እና ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አስቴርም ጭምር ሴቶችን በሚንከባከብበው በሄጌ እንክብካቤ ለመሆን ወደ ንጉሡ ቤተመንግት ተወሰደች
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ-ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሄጌ፣ የሴቶቹ ተንከባካቢ ወደ ንጉሡ ቤተመንግሥት ባመጧት ጊዜ አስቴርንም መንከባከብ ጀመረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(አድራጊ እና ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ቤተመንግት
ይህንን በአስቴር 1:5 ውስጥ እንዴት እንተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ

ወጣቷ ልጃገረድ አስደሰተችው፣ ደግሞም በእርሱ ዘንድ ሞገስን አገኘች
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ነገር ይናገራሉ፤ ደግሞም ምን ያህል ንጉሡን ደስ እንዳሰኘች ትኩረት ያደርጋሉ። "ወጣቷ ልጃገረድ እጅግ ደስ አሰኘችው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ወጣቷ ልጃገረድ
"አስቴር"

Esther 2:10

ስለ አስቴር ደህንነት
"አስቴር እንዴት እንደሆነች" ወይም "ስለ አስቴር በመልካም ሁኔታ መገኘት"

Esther 2:12

አጠቃላይ መረጃ:
ከቁጥር 12-14 ያለው፣ የንጉሡ ሚስቶች ስለሚሆኑ ሴቶች ያሉ ልምዶችን የሚገልጹ የመረጃ ዳራዎች ናቸው። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

ለሴቶቹ የሚደረጉ ደንቦች ከተፈጸሙ
"ለሴቶቹ መደረግ ያለበት በስርዓቱ መሰረት ከተከናወነ"

የውበት እንክብካቤ
ልጃገረዶቹ ውብ ሆነው እንዲታዩ እና መልካም መዓዛ እንዲኖራቸው የሚደረጉ ነገሮች።

መኳኳያ
በአስቴር 2:3 ውስጥ የተጠቀሙበትን ያንኑ ቃል ወይም ሀረግ ይጠቀሙ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የምትፈልገው ሁሉ ይሰጣት ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ-ነገር ሊገለጽ ይችላል::"የምትፈልገውን ሁሉ መውሰድ ትችል ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው::(አድራጊ እና ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ቤተመንግሥት
በአስቴር 1:5 ይህንን እንዴት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ::

Esther 2:14

አያያዥ ሃሳብ፡
ይህ በአስቴር 2:12 የተጀመረውን የንጉሡ ሚስቶች በሚሆኑ ሴቶች ላይ ስላለው ስርአት የመረጃ ዳራ ማቅረብን ይቀጥላል:: (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

በጠዋት
ይህ በማግስቱ ያለውን ማለዳ ያመላክታል:: ይህ መረጃ ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: "በማግስቱ ጠዋት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሁለተኛ ቤት
"የተለየ ቤት" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ) ወደ ሻሺጋዝ ጥበቃ... ዕቁባቶች "ሻሺጋዝ ወዳለበት... ቁባቶች ይንከባከቧት ነበር"

ተንከባካቢ
"ጉብኝት" ወይም "ጥበቃ"

ሻሺጋዝ
ይህ የወንድ ስም ነው:: (ስሞች እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ክፍል ይመልከቱ)

Esther 2:15

አሁን ጊዜው ሲደርስ
ይህ የታሪኩን አዲስ ክፍል ያስተዋውቃል:: (አዲስ ትዕይንት ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

የመርዶክዮስን አጎት የሆነውን፣ የአቢካኢልን ሴት ልጅ፣ ሴት ልጅ፣ እንደ ራሱ ልጅ አድርጎ የወሰዳት
ይህ የመረጃ ዳራ ለአንባቢው አስቴር ከመርዶክዮስ ጋር ያላትን ዝምድና ያስታውሰዋል:: (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ክፍል ይመልከቱ)

አቢካኢል
የአስቴር አባት እና የመርዶክዮስ አጎት (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ክፍል ይመልከቱ) አንዳች ነገር አልጠየቀችም ነገር ግን ምንን ጠየቀች ይህ በአዎነታዊ መልክ ሊጻፍ ይችላል:: "ምንን ብቻ ጠየቀች"

ሄጌ
በአስቴር 2:3 ውስጥ ይህ የወንድ ስም እንዴት እንደት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ:: (ስሞች እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ክፍል ይመልከቱ)

በሁሉም ዘንድ ሞገስ አገኘች
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው:: "ሁሉንም ደስ አሰኘች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

አስረኛው ወር፣ ይህም የቴቤት ወር ነው
"ቴቤት" በዕብራዊያን ወር አቆጣጠር አስረኛው ወር ነው:: በምዕራባዊያን ወር አቆጣጠር የታህሳስ መጨረሻ የጥር መጀመሪያ ነው:: (የዕብራዊያን ወሮች እና ተከታታይነትን የሚያሳይ ቁጥር እንዲሁም ስሞች እንዴት ይረረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባተኛው ወር
"7 ተኛው አመት" (ተከታታይነትን የሚያሳይ ቁጥር)

Esther 2:17

ንጉሡ ወደዳት
ይህ "ፍቅር" የሚለው ቃል አስደሳች/ሮማቲክ አጠቃቀም ነው::

ተቀባይነትን አገኘች፣ በፊቱም ሞገስን አገኘች
እነዚህ ፈሊጦች ተመሳሳይ ነገርን ይገልጻሉ፣ ደግሞም አስቴር ምን ያህል ንጉሡን ደስ እንዳሰኘች ትኩረት ይሰጣሉ::"እጅግ ደስ አሰኘችው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ፈሊጥ እና ጥንድ ትረጉም የሚሉተን ይመልከቱ)

የእቴጌነት ዘውድ በራሷ ላይ ጫነላት
ንጉሡ ይህንን ያደረገው እርሷን ንግሥት ማድረጉን ለማሳየት ነው:: (ተምሳሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

"የአስቴር ክብረ በዓል፣"
ይህ የክብረ በዓሉ ስያሜ መሆኑን መግለጹ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል:: "የአስቴር ክብረ በዓል ብሎ ጠራው፣" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለግዛቶች ከግብር እፎይታን ሰጠ
"ከዚያ እቀድሞ ከግዛቶች ይሰበስብ ከነበረው አነስ ያለ ግብር ሰበሰበ"

ግዛቶች
ግዛት አንዳንድ አገራት ለአስተዳደር ሲባል የሚከልሉት ሰፊ አካባቢ/ስፍራ ነው:: ይህንን በአስቴር 1:1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ::

ንጉሣዊ ልግስና
" ንጉሥ ብቻ ሊያደርገው የሚችለው ልግስና"

Esther 2:19

ደናግልቱ ለሁለተኛ ጊዜ በአንድነት ተሰብበው በነበረ ወቅት
ይህ ሁለተኛው መሰባሰብ መቼ እና ለምን እንደተደረገ ግልጽ አይደለም:: ለዚህም አንዳንድ ትረጉሞች ክፍሉን ለወጥ አድርገው ያቀርቡታል:: ምናልባትም ባለበት ሁኔታ መተርጎሞ እጅግ የተሻለ ሳይሆን አይቀርም::

ለሁለተኛ ጊዜ
"ለአንድ ተጨማሪ ጊዜ" ወይም "ለተጨማሪ ጊዜ" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

መርዶክዮስ በንጉሡ በር ይቀመጥ ነበር
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) መርደክዮስ በዚያ የሚቀመጠው አስቴር ምን እያደረገች እንደሆነ በበሩ በኩል ከሚያልፉ ብዙ ሰዎች መስማት ይችል ዘንድ ነው በሚል ሊተረጎም ይችላል ወይም 2) " በንጉሡ በር መቀመጥ" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን መርዶክዮስ በንጉሡ ስልጣን ተሰጥቶት ነበር ማለት ሊሆን ይችላል::

የንጉሡ በር
"ወደ ንጉሡ ቤተመንግሥት መግቢያ በር"

መርዶክዮስ እንዳዘዛት
መርዶክዮስ ስለ ቤተሰቧ ለማንም እንዳትናገር ነግሯት ነበር

በእነዚያ ቀናት
ይህ በታሪኩ ውስጥ አዲስ ትዕይነትን ያስተዋውቃል:: (አዲስ ትዕይነትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ገበታ እና ታራ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 2:22

ነገሩ ለመርዶክዮስ በተገለጸ ጊዜ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "መርዶክዮስ ምን እንዳሴሩ ባወቀ ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ እና ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በመርዶክዮስ ስም
ይህ ፈሊጥ ነው። "በመርዶክዮስ ምትክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ዘገባው ተመርምሮ ተረጋገጠ፣ በመሆኑም ሁለቱም ሰዎች በስቅላት ተቀጡ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ንጉሡ መርምሮ ዘገባውን አረጋገጠ፣ ደግሞም አገልጋዮቹ ሁለቱን ሰዎች እንዲሰቅሏቸው ትዕዛዝ ሰጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ እና ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው መስቀያ እንጨት
ይህ ሰዎችን ለመስቀል ያገለግል የነበረ አሰራር ሲሆን፣ የገመዱ አንዱ ጫፍ በመስቀያው እንጨት ላይ ሲታሰር ሌላኛው የገመዱ ጫፍ በሚሰቀሉት ሰዎች አንገት ዙሪያ በማድረግ ይንጠለጠላሉ። "ሰዎችን ለመስቀል የሚዋቀር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የማይታወቁትን መተረጎም የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ጉዳይ ተመዝግቦ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እነርሱ ይህንን ጉዳይ መዘገቡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ እና ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 ከእነዚህ ነገሮች በኋላ ንጉሡ አርጤክስስ አጋጋዊውን የሐመዳቱን ልጅ ሐማን በሹመት አላቀው፥ የሥልጣኑንም ወንበር ከእርሱ ጋር ከነበሩት ሹማምንት ሁሉ በላይ አደረገለት። **2** በንጉሡ በር የሚጠብቁ የንጉሡ አገልጋዮች ሁሉ ንጉሡ በሰጣቸው ትዕዛዝ መሠረት ሁልጊዜ ለሐማ በመንበርከክ አክብሮታቸውን ያሳዩት ነበር። መንዶክዮስ ግን አልተንበረከከለትም፥ አክብሮትም አላሳየውም። **3** ከዚያም በንጉሡ በር የሚጠብቁት የንጉሡ አገልጋዮች መርዶክዮስን፥ "የንጉሡን ትዕዛዝ የማታከብረው ለምንድነው?" አሉት። **4** ይህንን በየቀኑ ቢናገሩትም እርሱ ግን ቃላቸውን ለመቀበል እምቢ አለ። አይሁዳዊ መሆኑን ነግሯቸው ስለነበረ መርዶክዮስ በዚህ ሁኔታ እንዴት እንደሚቀጥል ለማየት ጉዳዩን ለሐማ ነገሩት። **5** ሐማም መርዶክዮስ ተንበርክኮ እንዳልሰገደለት ባየ ጊዜ ሐማ በንዴት ተሞላ። **6** የመርዶክዮስን የዘር ማንነት የንጉሡ አገልጋዮች ነግረውት ስለ ነበረ መርዶክዮስን ብቻ የመግደልን ሃሳብ ናቀው። በመላው አርጤክስስ መንግሥት ውስጥ የነበሩትን የመርዶክዮስ ወገን የሆኑትን አይሁድ በሙሉ ለመደምሰስ ፈለገ። **7** ንጉሡ አርጤክስስ በነገሠ በአሥራ ሁለተኛው ዓመት፥ በመጀመሪያው ወር (እርሱም የኒሳን ወር ነው) ፥ ፉር የሚባለውን፥ ቀኑንና ወሩን ለመምረጥ የሚያስችላቸውን የእያንዳንዱን ቀንና ወር ዕጣ በሐማ ፊት ጣሉ። በዕጣው መሠረት የአዳርን (አሥራ ሁለተኛውን ወር) መረጡ። **8** ከዚያም ሐማ ንጉሡን አርጤክስስን፥ "በመንግሥትህ አውራጃዎች ሁሉ ተበታትኖና ተሠራጭቶ የሚኖር አንድ ሕዝብ አለ። ሕጋቸው ከሌላው ሕዝብ የተለየ ነው፥ የንጉሡንም ሕጎች አያከብሩም፥ ስለዚህ ንጉሡ በሕይወት እንዲኖሩ ሊተዋቸው አይገባውም። **9** ንጉሡ ደስ የሚለው ከሆነ እንዲገደሉ ትዕዛዝ ይስጥ፥ እኔም ወደ ንጉሡ ግምጃ ቤት ገቢ እንዲያደርጉት በንጉሡ ንብረት ኃላፊዎች በሆኑት እጅ አሥር ሺህ መክሊት ብር መዝኜ እሰጣለሁ"አለው። **10** ከዚያም ንጉሡ ማኅተም ያለበትን ቀለበት ከጣቱ አውልቆ ለአይሁዶቹ ጠላት፥ ለአጋጋዊው ለሐመዳቱ ልጅ ለሐማ ሰጠው። **11** ንጉሡም ሐማን፥ "ገንዘቡ ለአንተና ለሕዝብህ ተመልሶ ማየት እፈልጋለሁ። አንተም በእርሱ የፈለግኸውን ሁሉ ታደርግበታለህ" አለው። **12** ከዚያም በመጀመሪያው ወር በአሥራ ሦስተኛው ቀን የንጉሡ ጸሐፊዎች ተጠሩ፥ ለንጉሡ የአውራጃ አስተዳዳሪዎች፥ በአውራጃዎቹ ሁሉ ላይ ለነበሩት፥ ልዩ ልዩ ሕዝቦችን ለሚያስተዳድሩትና ለሕዝቡ ሁሉ ሹማምንት፥ ለየአውራጃዎቹ በየራሳቸው ጽሑፍና ለእያንዳንዱም ሕዝብ በየራሱ ቋንቋ ሐማ ያዘዘው ሁሉ በዐዋጁ ውስጥ ተጻፈ። ዐዋጁም በንጉሡ አርጤክስስ ስም ተጽፎ በቀለበቱ ታተም። **13** በአሥራ ሁለተኛው ወር (እርሱም የአዳር ወር ነው) ፥ በአሥራ ሦስተኛው ቀን፥ በአንድ ቀን ውስጥ አይሁዶችን በሙሉ፥ ከወጣት እስከ ሽማግሌ፥ ልጆችንና ሴቶችን በአንድ ቀን እንዲያጠፉ፥ እንዲገድሉና እንዲደመስሱና ንብረታቸውንም እንዲዘርፉ ደብዳቤዎቹም በመልዕክተኞቹ እጅ ለንጉሡ አውራጃዎች ሁሉ ተላከ። **14** የደብዳቤው ቅጅም በየአውራጃው ሕግ ተደረገ። ለዚያ ቀን ይዘጋጁ ዘንድ በየአውራጃው ያሉ ሕዝቦች ሁሉ እንዲያውቁት ተደረገ። **15** መልዕክተኞቹም የንጉሡን ዐዋጅ ለማሰራጨት በጥድፊያ ሄዱ። አዋጁ በሱሳ ቤተመንግሥት ውስጥም ደግሞ ተሰራጨ። ንጉሡና ሐማ ለመጠጣት ተቀመጡ፥ የሱሳ ከተማ ግን ተበጥብጣ ነበር።

Esther 3:1

ከእነዚህ ነገሮች በኋላ
ይህ በታሪኩ ውስጥ አዲስ ትዕይነትን ያስተዋውቃል። (አዲስ ትዕይነትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

የአጋጋዊው የሐማዳቱ ልጅ ሐማ
ይህ ከንጊሡ መኳንንት አንዱ የሆነው የሐማ ስም እና ገለጻ ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የስልጣኑን ስፍራ ከእርሱ ጋር ከነበሩ መኳንንት ሁሉ በላይ ከፍ ከፍ አደረገ
እዚህ ስፍራ "የባለስልጣናት ስፍራ" የሚለው የሚገልጸው በመንግስት ውስጥ ያለውን ስፍራ ወይም ደረጃ ነው። "ከሌሎች መኳንንት በላይ ከፍ አደረገው" ወይም "ከሌሎች መኳንንት ሁሉ በላይ ይበልጥ ስልጣን ሰጠው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

መንበርከክ... መስገድ
እነዚህ ድርጊቶች ለሐማ ስልጣን መገዛትን ይገልጻሉ። (ተምሳሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ለሐማ ሰገዱ
"ራሳቸውን ዝቅ አድርገው በሐማ ፊት ለጥ ብለው ሰገዱ"

Esther 3:3

ስለ መርዶክዮስ ያለው ጉዳይ እንደዚያ ሆኖ መቅረቱን ለማየት
"ሐማ ስለ መርዶክዮስ ድርጊቶች ምን እንደሚያደርግ ለማየት"

Esther 3:5

አልተንበረከከም ወድቆም አልሰገደም
መርዶክዮስ እነዚህን ድርጊቶች ባለማድረግ ሐማ በመንግስት ውስጥ ላለው ደረጃ ክብር አለመስጠቱን አሳየ።(ተምሳሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ሐማ በቁጣ ተሞልቶ ነበር
እዚህ ሰፍራ የሐማ ቁጣ እጅግ እንደሚሞላው ነገር ተደርጎ ተነግሯል። "ሐማ እጅግ ተቆጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መርዶክዮስን ብቻ የመግደልን ሃሳብ ትንሽ ነገር አድርጎ አየው
"መርዶክዮስን ብቻ የመግደልን ሃሳብ አልተቀበለም።" ይህ በአዎንታዊ መልክም ሊገለጽ ይችላል። "መርዶክዮስን ብቻ ከመግደል ያለፈ ለማድረግ ወሰነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

መላውን አይሁድ ማጥፋት
"ሁሉንም አይሁድ ማስወገድ" ወይም "መላውን አይሁድ መግደል"

Esther 3:7

በመጀመሪያው ወር
" በአንደኛው ወር" (ተከታታይነትን የሚያሳይ ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

ኒሳን የትኛው ወር ነው
"ኒሳን" በዕብራዊያን ወር አቆጣጠር የመጀመሪያው ወር ስያሜ ነው። በምዕራባዊያን ቀን መቁጠሪያ የመጋቢት መጨረሻ እና የሚያዚያ መጀመሪያ ላይ ነው። (የዕብራዊያን ወራት እና ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሥ ጠረክሲስ በነገሠ አስራ ሁለተኛ አመት
"በንጉሥ ጠረክሲስ በ12ኛ አመት" ወይም "ንጉሥ ጠረክሲስ ወደ አስራ ሁለት አመት ያህል ከገዛ በኋላ" (ተከታታይነትን የሚያሳይ ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

ፉር - ያም ዕጣ ነው- ይጣላል
"ፉሩን ያወጣሉ - ያም ዕጣ ነው - " (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አስራ ሁለተኛው ወር
"አስራ ሁለተኛ ወር" (ተከታታይነት ን የሚያሳይ ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

የአዳር ወር
"አዳር" በዕብራዊያን የወር አቆጣጠር አስራ ሁለተኛው እና የመጨው ወር ነው። በምዕራባዊያኑ አቆጣጠር የየካቲት ወር መጨረሻ እና የመጋቢት መጀመሪያ ነው። (የዕብራዊያን ወራት እና ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 3:8

አንድ ህዝብ
" አንድ የህዝብ ወገን" ይህ አይሁድን እንደ አንድ ነገድ ያመላክታል።

ተበትኖ የሚኖር
"በብዙ የተለያዩ ስፍራዎች የሚኖር"

ግዛቶች
ግዛት አንዳንድ አገራት ለአስተዳደር ሲባል የሚከልሉት ሰፊ አካባቢ/ስፍራ ነው። ይህንን በአስቴር 1:1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

የንጉሡ ... ንጉሡ
ሐማ ለአክብሮት መግለጫ ምልክትነት ንጉሡን በሶስተኛ መደብ ይናገረዋል። "የእርሱ ... እርሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱን መተዉ ለንጉሡ ጠቃሚ አይደለም
"ንጉሡ እነርሱ እንዲተርፉ መፍቀድ የለበትም።" ይህ በአዎንታዊ መልክም ሊገለጽ ይችላል። "ንጉሡ ሊያስወግዳቸው ይገባል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

በእነርሱ እጅ... እኔ እመዝናለሁ
እዚህ ስፍራ "እጆች" የሚለው ወንዶች የሚለውን ይወክላል። "መመዘን" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ለእነርሱ መክፈል ማለት ነው። " ለሰዎቹ ... እኔ እከፍላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሲኔክቲኪ/ ዘይቤያዊ አነጋጋር- የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ፤ እና ፈሊጣዊ አነጋጋር/ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

አስር ሺህ መክሊት ብር
"330 ሜትሪክ ቶን ብር" መጽሐፍ ቅዱሳዊ ገንዘብ እና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 3:10

የቀለበት ማህተም
በአዋጅ ላይ የንጉሡን ይፋ ማህተም ለማሳረፍ የሚያገለግል የተለየ ቀለበት

ገንዘቡ ተመልሶ ለአንተ ሲሆንልህ አያለሁ
የዚህ ሐረግ ትርጉም ግልጽ አይደለም። ትርጉሙ 1) "እኔ ለአንተ ገንዘቡን እመልስልሃለሁ" ወይም 2) " ልክ እንደተናገርከው ገንዘቡን ወስደህ ለሰዎቹ ስጣቸው።" ማለት ሊሆን ይችላል። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 3:12

የንጉሡ ጸሐፍት ተሰበሰቡ... ሐማ ያዘዘውን ሁሉ የያዘ አዋጅ ተጻፈ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ንጉሡ ጸሐፍቱን ሰበሰበ ... እነርሱ ሐማ ያዘዘውን ሁሉ የያዘ አዋጅ ጻፉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የመጀመሪያው ወር አስራ ሶስተኛው ቀን
ይህ በዕብራዊያን አቆጣጠር የመጀመሪያው ወር ነው። አስራ ሶስተኛው ቀን በምዕራባዊያኑ አቆጣጠር ወደ ሚያዝያ መጀመሪያ ላይ ነው። (የዕብራዊያን ወሮች እና ደረጃን የሚያሳዩ ቁጥሮች)

የንጉሡ ግዛቶች ገዢዎች
"የግዛቶች ገዢዎች።" በአስቴር 1:1 ውስጥ በተረጎሙት መሰረት ይተርጉሙ። የተጻፈው በንጉሡ ጠረክሲስ ስም ነበር ደግሞም በእርሱ ማህተም ታትሞ ነበር ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እነርሱ አዋጁን በንጉሡ ጠረክሲስ ስም ጻፉ ሐማም በንጉሡ ቀለበት አተመው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በ...ስም
እዚህ ስፍራ "ስም" የንጉሡን ስልጣን ይወክላል። "በ... ስልጣን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት- የሚለውን ይመልከቱ)

ሰነዶቹ በመልዕክተኞች እጅ ተላኩ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። " መልዕክተኞች ሰነዶቹን በእጅ አደረሱ" ወይም "መልዕክተኞች ሰነዶቹን በቀጥታ አደረሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲጠፉ፣ እንዲገደሉ፣ እና እንዲደመሰሱ
እነዚህ ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ ጥፋቱ በሙላት እንዲደረግ ትኩረት የሚሰጡ ናቸው። "ሙሉ ለሙሉ መደምሰስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም/ደብሌት የሚለውን ይመልከቱ)

የአስራ ሁለተኛው ወር አስራ ሶተኛ ቀን
"የአስራ ሁለተኛው ወር አስራ ሶስተኛ ቀን" (ተከታታይነትን የሚያሳዩ ቁጥሮች)

አዳር የትኛው ወር ነው
አዳር" በዕብራዊያን የወር አቆጣጠር አስራ ሁለተኛው እና የመጨው ወር ነው። በምዕራባዊያኑ አቆጣጠር የየካቲት ወር መጨረሻ እና የመጋቢት መጀመሪያ ነው። (የዕብራዊያን ወራት እና ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ዝርፊያ
በሃይል መቀማት

Esther 3:14

የደብዳቤው ቅጂ በእያንዳንዱ ግዛት ህግ ተደርጎ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በእያንዳንዱ ግዛት የሚገኙ መኳንንት የደብዳቤውን ቅጅ ህግ አድርገው ተቀብለውት ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ግዛት
ግዛት አንዳንድ አገራት ለአስተዳደር ሲባል የሚከልሉት ሰፊ አካባቢ/ስፍራ ነው። ይህንን በአስቴር 1:1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

በእያንዳንዱ ግዛት ለሁሉም ህዝብ እንዲታወቅ ተደርጎ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በእያንዳንዱ ግዛት ለሚኖረው ህዝብ አሳውቀው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ቀን
"ያ ቀን"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አዋጁም ተልኮ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እነርሱም አዋጁን ልከው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ግንብ/ምሽግ
ይህ የቤተመንግሥት ግንብን፣ ጠንካራ ይዞታን ወይም የተመሸገ ከተማን ያመለክታል። በአስቴር 1:2 ይህንን እንዴት እንደተረጎሙት ተመልሰው ይመልከቱ።

ሱሳ
የዚህን ስፍራ ስም በአስቴር 1:2 ላይ እንዴት እንደ ተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ተንጣ ነበር
"በታላቅ ግራ መጋባት ውስጥ ነበረች"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 መርዶክዮስ የተደረገውን ሁሉ ባወቀ ጊዜ ልብሶቹን ቀደደ፥ ማቅ ለብሶም በራሱ ላይ አመድ ነሰነሰ። ወደ ከተማይቱ መካከል በመሄድም በታላቅ ጩኸት መራራ ልቅሶ አለቀሰ። **2** ማቅ ለብሶ በንጉሡ በር በኩል ማለፍ አይፈቀድም ነበርና እስከ አቅራቢያው ድረስ ብቻ ሄደ። **3** የንጉሡ ዐዋጅና ትዕዛዝ በደረሰበት አውራጃ ሁሉ በአይሁድ መካከል ከጾም፥ ከልቅሶና ከዋይታ ጋር ታላቅ ሀዘን ሆነ። ብዙዎቹም በማቅና በአመድ ላይ ተኙ። **4** የአስቴር ወጣት ሴቶችና አገልጋዮቿ መጥተው ስለ ሁኔታው በነገሯት ጊዜ ንግሥቲቱ እጅግ አዘነች። እርሷም መርዶክዮስን እንዲያለብሱት (ማቁን አውጥቶ እንዲጥል ነበር) ልብሶችን ላከችለት፥ እርሱ ግን አልተቀበለም። **5** ከዚያም አስቴር እርሷን ለማገልገል የተመደበውንና ከንጉሡ ሹማምንት አንዱ የሆነውን ሀታክን ጠራችው። ምን እንደ ተፈጠረና ምን ማለትም እንደሆነ ያጣራ ዘንድ ወደ መርዶክዮስ እንዲሄድ አዘዘችው። **6** ስለዚህ ሀታክ በንጉሡ በር ፊት ለፊት ወደሚገኘው የከተማው አደባባይ ወደ መርዶክዮስ ሄደ። **7** መርዶክዮስም የገጠመውን ነገር ሁሉ፥ አይሁድን ለመግደል ሐማ ወደ ንጉሡ ግምጃ ቤት ለማስገባት ቃል የገባውን የገንዘብ መጠን አስታወቀው። **8** በተጨማሪም አይሁድን ለማጥፋት በሱሳ የታወጀውን የዐዋጁን ቅጅም ሰጠው። ይህንንም ያደረገው ሀታክ ለአስቴር እንዲያሳያትና ወደ ንጉሡ ሄዳ ስለ ሕዝቧ ምህረት እንዲያደርግ እንድትለምነውና እንድትማልደው ኃላፊነት እንዲሰጣት ነበር። **9** ሀታክ ሄደና መርዶክዮስ ነግሮት የነበረውን ለአስቴር ነገራት። **10** ከዚያም አስቴር ሀታክ ተመልሶ ወደ መርዶክዮስ እንዲሄድ ነገረችው። **11** እንዲህም አለችው፥ "ወንድ ሆነ ሴት ማንኛውም ሰው ሳይጠራ ወደ ውስጠኛው አደባባይ ቢገባ አንድ ሕግ ብቻ እንዳለ የንጉሡ አገልጋዮች ሁሉና በንጉሡ አውራጃዎች የሚኖሩ ሕዝቦች ያውቃሉ፥ ሕጉም በሕይወት እንዲኖር ንጉሡ የወርቅ በትሩን ከሚዘረጋለት በስተቀር መገደል አለበት የሚል ነው። እነዚህን ሠላሳ ቀናት ወደ ንጉሡ ለመቅረብ አልተጠራሁም።" **12** ስለዚህ ሀታክ የአስቴርን ቃል ለመርዶክዮስ አስታወቀው። **13** መርዶክዮስም እንዲህ የሚል መልዕክት መለሶ ለከባት፥ "በንጉሡ ቤተመንግሥት ውስጥ ስለሆንሽ ከሌሎቹ አይሁዶች ሁሉ ይልቅ እንደምትድኚ ማሰብ የለብሽም። **14** አንቺ በዚህ ጊዜ ዝምታን ብትመርጪ ለአይሁድ እርዳታና መዳን ከሌላ ሥፍራ ይነሣላቸዋል፥ አንቺና የአባትሽ ቤት ግን ትጠፋላችሁ። ወደ ንግሥትነት የመጣሽው እንደዚህ ላለው ቀን እንደሆነስ ማን ያውቃል?" **15** ከዚያም አስቴር ይህን መልዕክት ወደ መርዶክዮስ ላከች፥ **16** "ሂድ፥ በሱሳ የሚኖሩትን አይሁድ ሁሉ በአንድ ላይ ሰብስባቸውና ስለ እኔ ጹሙ። ለሦስት ቀንና ሌሊት አትብሉ፥ አትጠጡም። እኔና ወጣት ልጃገረዶቼም እንደዚሁ እናደርጋለን። ከዚያም ከሕጉ ውጪ ቢሆንም ወደ ንጉሡ እገባለሁ፥ ከጠፋሁም እጠፋለሁ።" **17** መርዶክዮስም ሄዶ አስቴር ያለችውን ሁሉ አደረገ።

Esther 4:1

የተደረገውን ሁሉ አውቆ ነበር
"ስለነዚያ ደብዳቤዎች ደርሶበት ነበር" ልብሱን ቀደደ ደግሞም ማቅ ለብሶ በራሱ ላይ አመድ ነሰነሰ እነዚህ ድርጊቶች የታላቅ ሃዘን ምልክቶች ናቸው። " ሃዘኑን ለመግለጽ ልብሶቹን ቀደደ ደግሞም ማቅ ለብ አመድ ነሰነሰ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተምሳሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ግዛት
ግዛት አንዳንድ አገራት ለአስተዳደር ሲባል የሚከልሉት ሰፊ አካባቢ/ስፍራ ነው። ይህንን በአስቴር 1:1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

በአይሁዳዊያን መካከል ታላቅ ለቅሶ ነበር
"አይሁዳዊያን እጅግ አለቀሱ"

ብዙዎቹ ማቅ ለበሱ በላያቸውም አመድ ነሰነሱ
"ብዙዎቹ መሬት ላይ ተቀምጠው ነበር፣ ማቅ ለብሰው አመድ ላይም ተቀምጠው ነበር"

Esther 4:4

ወጣት ሴቶች እና ወንድ አገልጋዮች
"ሴት አገልጋዮች እና ወንድ አገልጋዮች"

መርዶክዮስን ለማልበስ
"መርዶክዮስ እንዲለብሰው"

ሀታክ
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሷን እንዲያገለግሏት ከተመደቡት የንጉሡ ባለሟሎች አንዱ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ንጉሡ እርሷን እንዲያገለግሉ ከመደባቸው ባለሟሎች አንዱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 4:6

ሀታክ
በአስቴር 4:5 ውስጥ ይህንን የወንድ ስም እንዴት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የከተማው አደባባይ
"በከተማው መሃል"

ሐማ
በአስቴር 3:1 ውስጥ ይህንን የወንድ ስም እንዴት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱም ሰጠው
" መርዶክዮስም ለሀታክ ሰጠው"

ከእርሱ ዘንድ ምህረትን እንድትለምን
"የንጉሡን ምህረት እንድትለምን"

Esther 4:9

ማንም ወንድ ወይም ሴት ወደ ንጉሡ ቢሄድ... ንጉሡ የወርቅ ዘንጉን/በትረ መንግሥቱን ይዘረጋል
ይህ ሁኔታዊ አባባል ሙሉ ሃሳብ/መግለጫ ተደርጎ ሊተረጎም ይችላል። ይህንን አገላለጽ በሁለት ዐረፍተ ነገሮች መክፈሉም ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። "ንጉሡ ካልጠራቸው በስተቀር ማንም ወንድ ወይም ሴት ወደ ውስጠኛው አደባባይ ወደ ንጉሡ መግባት አይፈቀድለትም። ይህንን ህግ የጣሰ ሰው ንጉሡ ወደዚያ ሰው የወርቅ ዘንጉን/በትረ መንግሥቱን ካልዘረጋለት በስተቀር ይገደላል።"

ሰላሳ ቀናት
"30 ቀናት" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Esther 4:13

ደህንነት እና መዳን ለአይሁድ ከሌላ ስፍራ ይሆናል
እዚህ ላይ "ደህንነት" እና "መዳን" ማንሳት እንደሚችሉ ህያዋን ነገሮች ሆነው ተነግረዋል። "አንድ ሌላ ሰው ከሌላ ስፍራ ተነስቶ አይሁድን ያድናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ/ፐርሶኒፊኬሽን የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህ ላለው ጊዜ ወደዚህ የንግስትነት ደረጃ መጥተሽ እንደሆነስ ማን ያውቃል?
የዚህ ጥያቄ አላማው አስቴር በዚህ ሁኔታ ልትጫወት ስለምትችለው ሚና በጥልቀት እንድታስብ ማድረግ ነው። "ማን ያውቃል፣ ንግስት የሆንሽው ምናልባትም ልክ እንዲህ ላለው ጊዜ ሊሆን ይችላል።" (ንግግራዊ/ሬቶሪካል ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 4:15

ሱሳ
የዚህን ስፍራ ስም በአስቴር 1:2 ላይ እንዴት እንደ ተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእኔ ጹሙ... እንጾማለን
ጾም አይሁዳዊያን በጥብቅ ሲጸልዩ የሚያደርጉት ተምሳሌታዊ ድርጊት ነው። ይህ ይበልጥ ግለጽ ሊደረግ ይችላል። "ለእኔ ጹሙ ጸልዩ.. እንጾማለን እንጸልያለን" (ተምሳሌታዊ ድርጊት)

ሶስት ቀናት
"3 ቀነናት" (ቁጥሮች እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት እውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 5

1 ከሥስት ቀን በኋላ አስቴር የንግሥትነትዋን ልብስ ለብሳ በንጉሡ መኖሪያ ፊት ለፊት፥ በንጉሡ ቤተመንግሥት ውስጠኛው አደባባይ ልትቆም ሄደች። ንጉሡም በቤቱ መግቢያ በር ትይዩ በንጉሣዊ ዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ነበር። **2** ንጉሡ ንግሥት አስቴርን አደባባዩ ላይ ቆማ ባያት ጊዜ፥ በፊቱ ሞገስን አገኘች። እርሱም የወርቁን በትር አንስቶ ዘረጋላት። ስለዚህ አስቴር ቀረበችና የበትሩን ጫፍ ነካች። **3** ከዚያም ንጉሡ፥ "ንግሥት አስቴር! ምንድነው የምትፈልጊው? ጥያቄሽስ ምንድነው? የመንግሥቴን ግማሽ ከሆነም ይሰጥሻል።" **4** አስቴርም፥ "ንጉሡን ደስ የሚለው ከሆነ ንጉሡ ከሐማ ጋር ወዳዘጋጀሁለት ግብዣ ዛሬ ይምጣ" አለችው። **5** ከዚያም ንጉሡ፥ "አስቴር ያለችው እንዲደረግ፥ በአስቸኳይ ሐማን ጥሩት" አለ። ስለዚህ ንጉሡና ሐማ አስቴር ወዳዘጋጀችው ግብዣ ሄዱ። **6** በግብዣው ላይ ወይኑ እየቀረበ እያለ ንጉሡ አስቴርን፥ "ልመናሽ ምንድነው? ይሰጥሻል። ጥያቄሽ ምንድነው? እስከ መንግሥቴ ግማሽ ይሰጥሻል" አላት። **7** አስቴርም፥ "በንጉሡ ዓይን ሞገስን ካገኘሁ፥ **8** የለመንኩትን ሊሰጠኝና ጥያቄዬን ሊያከብርልኝ ንጉሡን ደስ የሚለው ከሆን ልምናዬና ጥያቄዬ ይህ ነው። ነገ በማዘጋጅልህ ግብዣ ላይ ንጉሡ ከሐማ ጋር ይምጣ፥ እኔም የንጉሡን ጥያቄ እመልሳለሁ" አለችው። **9** ሐማ በዚያን ቀን ደስ ብሎት፥ ልቡም ሐሴት አድርጎ ሄደ። ነገር ግን ሐማ መርዶስዮስን በፊቱ ሳይፈራና ሳይንቀጠቀጥ፥ ከተቀመጠበትም ሳይነሳ በንጉሡ በር ባየው ጊዜ በመርዶክዮስ ላይ እጅግ ተናደደ። **10** ሆኖም ሐማ ራሱን ተቆጣጠረና ወደ ራሱ ቤት ሄደ። **11** ጓደኞቹን አስጠራና ከሚስቱ ዘሳራ ጋር በአንድ ላይ ሰበሰባቸው። ሐማም የብልጽግናውን ክብርና የልጆቹን ብዛት፥ ከንጉሡ አገልጋዮችና ከሹማምንቱ ሁሉ በላይ እንዴት በማዕረግ አንደበለጣቸው አወራላቸው። **12** ሐማም፥ "ንግሥት አስቴር ወዳዘጋጀችው ግብዣ እንኳን ከእኔ በቀር ከንጉሡ ጋር እንዲመጣ የጋበዘችው የለም። ነገም ደግሞ ከንጉሡ ጋር ግብዣዋ ላይ እንድገኝ ጋብዛኛለች። **13** ነገር ግን አይሁዳዊው መርዶክዮስ በንጉሡ በር ተቀምጦ ካየሁት ይህ ሁሉ ልምምዴ ምንም አይጠቅመኝም።" **14** ከዚያም ሚስቱ ዘሳራ ሐማንና ጓደኞቹን ሁሉ፥ "ቁመቱ ሃምሳ ክንድ የሆነ መስቀያ ያዘጋጁ። መርዶክዮስን በዚያ ላይ እንዲሰቅሉት ነገ ጠዋት ለንጉሡ ንገረው። ከዚያም ደስ ብሎህ ከንጉሡ ጋር ወደ ግብዣው ሂድ" አለቻቸው። ይህም ሐማን አስደሰተው፥ መስቀያው እንዲዘጋጅም አስደረገ።

Esther 5:1

ወደ ቤቱ መግቢያ ፊቷን መልሳ
"ከቤቱ መግቢያ ትይዩ " ወይም "ወደ ቤቱ መግቢያ አንጻር"

በዐይኖቹ ተቀባይነት አገኘች
"ዐይኖች" የሚለው የሚያመለክተው የእርሱን መመለክት ሲሆን እርሱ ለእሷ ያለውን ሚዛን የሚገልጽ ዘይቤ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። " በእርሷ ተደስቶ ነበር" ወይም "እርሷን ተቀበላት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በእጁ ያለውን የወርቅ ዘንግ/በትረ መንግሥት ዘረጋላት
ይህንን ያደረገው በእርሷ ደስ መሰኘቱን ለማሳየት ነው።

የዘንጉን/ በትረ መንግሥቱን ጫፍ ነካች
ምናልበትም ይህንን ያደረገችው ስልጣኑን ማክበሯን እና ለእርሷ ላሳየው በጎነት ምስጋና ለማቅረብ ሳይሆን አይቀርም

Esther 5:3

እስከ መንግቴ እኩሌታ ድረስ ቢሆን እንኳን ይሰጥሻል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የመንግሥቴን አኩሌታ እንኳን ብትጠይቂ፣ እሰጥሻለሁ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሡን ደስ የሚያሰኘው ከሆነ፣ ንጉሡ እና ሐማ ይምጡ.. ለእርሱ
ለንጉሥ ክብር ለማሳየት፣ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ እርሱን "አንተ" ብለው አይጠሩም። ይህ "አንተ" የሚለው ቃል ከሌሎች ቃላት ጋር አክብሮትን ለማሳየት ሊተረጎም ይችላል። "ንጉሥ ሆይ፣ ይህ ንጉሡን ደስ የሚያሰኘው ከሆነ፣ ንጉሡ ... ከሐማ ጋር" (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ሐማ
በአስቴር 3:1 ውስጥ ይህንን የወንድ ስም እንዴት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 5:5

ጥያቄሽ ምንድን ነው
"ጥያቄ" የሚለው ረቂቅ ስም "ጠየቀ" ወይም "ፈለግ" በሚሉ ግሶች ሊገለጽ ይችላል። "ምን ትጠይቂያለሽ" ወይም "ምን ትፈልጊያለሽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ለአንቺ ይሰጥሻል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የምትጠይቂውን እሰጥሻለሁ" ወይም "የምትጠይቂውን ለአንቺ አደርገዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የምትፈልጊው ምንድን ነው
"መፈለግ" የሚለው ረቂቅ ስም "መጠየቅ" ወይም "መሻት" በሚል ግስ ሊገለጽ ይችላል። "ምን ትጠይቂያለሽ" ወይም "ምን ትፈልጊያለሽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እስከ መንግስቴ እኩሌታ፣ ይሰጥሻል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እስከ መንግሥቴ እኩሌታ እንኳን ቢሆን ብትጠይቂ፣ እሰጥሻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 5:7

የእኔ አቤቱታ/ልመና እና ጥያቄዬ/መሻት
"አቤቱታ/ልመና" እና "ጥያቄ/መሻት" የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ይዘዋል። እነዚህን ቃላት በአንድነት የተጠቀመችባቸው ምናልባት ለንጉሡ በጣም ስርዓት በጠበቀ እና ክብር በሞላበት መንገድ ለመናገር ይሆናል። (ጥንድ ትረጉም የሚለውን ይመልከቱ)

በንጉሡ ዐይኖች ሞገስ አግኝቼ ከሆነ እና ንጉሡን ደስ ካሰኘሁ
ለአንድ ንጉሥ ክብር ለማሳየት፣ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ "አንተ" ብለው አይጠሩትም። ይህ "አንተ" ከሚለው ቃል ጋር ሌሎች ማክበርን የሚገልጹ ቃላት ተጨምረውበት ሊተረጎም ይችላል። "ንጉሡ በእኔ ደስ ተሰኝቶ ከሆነ፣ ንጉሥ ሆይ፣ ደግሞም ንጉሡን ደስ የሚያሰኝ ከሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በንጉሡ ዐይኖች ሞገስ አግኝቼ ከሆነ
"ሞገስ ማግኘት" የዚህ ትርጉም በፈሊጥ ተቀባይነት ማግኘት ወይም ንጉሡ በእርሷ ደስ መሰኘቱን የሚገልጽ ነው። "በንጉሡ ዐይን " የሚለው የእርሱን ሚዛን የሚገልጽ ዘይቤ ነው። "በንጉሡ ፊት ተቀባይነት ካገኘሁ" ወይም "ንጉሡ በእኔ ደስ ከተሰኘ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጥ እና ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ንጉሡ እና ሐማ ይምጡ
ይህ "አንተ" ከሚለው ቃል እና ክብርን ከሚገልጹ ሌሎች ቃላት ጋር አብሮ ሊተረጎም ይችላል። "ንጉሡ ይገኝ ደግሞም ሐማንም ይዞት ይገኝ" ወይም " ንጉሡ ይምጣ ሐማም ከንጉሱ ጋር ይምጣ" (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

የንጉሡን ጥያቄ እመልሳለሁ
ይህ "አንተ" ከሚለው ቃል እና ክብርን ከሚገልጹ ሌሎች ቃላት ጋር አብሮ ሊተረጎም ይችላል። "የንጉሡን ጥያቄ እመልሳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 5:9

መርዶክዮስ አይነሳለትም ነበር
መነሳት ክብርን የመግለጫ ምልክት ነበር። መርዶክዮስ ለሐማ የተለየ ክብር አይሰጠውም ነበር። (ተምሳሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

በቁጣ ይሞላ ነበር
"በቁጣ መሞላት" እጅግ በጣም መናደድን ያመለክታል። "እጅግ ተቆጥቶ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሆነ ሆኖ/ምንም አንኳን
ይህ በሐረግ ሊተረጎም ይችላል። "ምንም እንኳን እጅግ ቢበሳጭም

ሐማ ራሱን ተቆጣጠረ
ራሱን ተቆጣጠረ የሚለው የሚገልጸው ሊያደርግ እጅግ ፈልጎ ያለውን ነገር ከማድረግ መገታቱን ነው። ሐማ እጅግ መናደዱን ለመርደክዮስ ማሳየት ፈልጎ ነበር። "ሐማ ምን ያህል እንደ ተናደደ ላለማሳየት ራሱን ተቆጣጠረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ዞሳራ
ይህ የሴት ስም ነው። (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሐማ የሃብቱን ታላቅነት እያጋነነ ዘረዘረላቸው
"እያጋነነ" እና "ሃብቱን" የሚሉት ቃላት ሁለቱም ረቂቅ ስሞች ናቸው። "ሐማ ሃብቱ ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ነገረቸው" ወይም "ሐማ ስላሉት ብዙ ታላላቅ ነገሮች ነገራቸው" (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሡ ሊያከብረው የሰጠው እድገቶች ሁሉ
"እድገት" የሚለው ረቂቅ ስም "አደገ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። ንጉሡ ይበልጥ ከፍ ያለ ደረጃ ሰጠው ማለት ሊሆን ይችላል። "ንጉሡ እንዴት ብዙ ጊዜ ከፍ እንዳደረገው እና እንዳከበረው" ወይም "ንጉሡ እንዴት ብዙ ጊዜ ይበልጥ ከፍ ያለ ደረጃ በመስጠት እንዴት እንዳከበረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እንዴት ከሁሉም መኳንንት እና ከንጉሡ አገልጋዮች በላይ ከፍ ከፍ እንዳለ
ከሰዎች በላይ ከፍ ከፍ ማለት የሚለው የሚገልጸው ከሌሎቹ በላይ ጠቃሚ መሆኑን ነው። "ከሁሉም መኳንንት እና ከንጉሡ አገልጋዮች በላይ እንዴት ጠቃሚ እንደሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 5:12

ሌላ ማንም ሳይሆን እኔን
ይህ በአዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኔ ብቻ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ለእኔ አንዳች አይጠቅመኝም
"እኔን ደስ አያሰኘኝም" ወይም "እኔን አያረካኝም"

Esther 5:14

የሰው መስቀያ እንጨት
ይህ አንድን ሰው ለመስቀል የገመዱ አንዱ ጫፍ በመስቀያው እንጨት ላይ ሲታሰር ሌላኛው የገመዱ ጫፍ በሚሰቀለው ሰው አንገት ዙሪያ በማድረግ ሰውየው ይሰቀላል። በአስቴር 2:3 ላይ ይህንን እንዴት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ። (የማይታወቁትን መተረጎም የሚለውን ይመልከቱ)

ሃምሳ ክንድ ቁመት
"50 ክንድ ቁመት።" ይህንን ወደ ዘመናዊ መለኪያ መለወጥ ይችላሉ። ወደ” ሃያ ሶስት ሜትር ከፍታ" (ቁጥሮች እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ርቀት የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ መስቀያውን አሰራ
"ሰዎች መስቀያውን እንዲያበጁ አዘዘ"

ይህ ሐማን ደስ አሰኘው
"ይህ ሃሳብ ሐማን ደስ አሰኘው"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 6

1 በዚያ ሌሊት ንጉሡ እንቅልፉን መተኛት አልቻለም። እርሱም በዘመነ መንግሥቱ የተከናወኑ ሁነቶች በታሪክነት የተመዘገቡበትን መዝገብ እንዲያመጡለት አገልጋዮቹን አዘዛቸው፥ እነርሱም ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ለንጉሡ ያነቡለት ነበር። **2** ገበታና ታራ፥ ሁለቱ በር ጠባቂ የንጉሥ ሹሞች ንጉሥ አርጤክስስን ለመግደል ማቀዳቸውን መርዶክዮስ መናገሩ ተመዝግቦ ተገኘ። **3** ንጉሡም፥ "ይህንን ስላደረገ ለመርዶክዮስ ክብርና እውቅና ለመስጠት ምን ተደረገለት?" ብሎ ጠየቀ። ከዚያም ንጉሡን የሚያገለግሉ ወጣቶች፥ "ምንም አልተደረገለትም" አሉት። **4** ንጉሡም፥ "በአደባባዩ ውስጥ ያለው ማነው?" አለ። በዚያን ጊዜ ሐማ መርዶክዮስን ባዘጋጀለት መስቀል ላይ ለማሰቀል ለንጉሡ ለመንገር ወደ ውጪኛው አደባባይ ገብቶ ነበር። **5** የንጉሡም አገልጋዮች፥ "ሐማ አደባባዩ ውስጥ ቆሟል" አሉት። ንጉሡም፥ "ይግባ" አለ። **6** ሐማ በገባ ጊዜም ንጉሡ፥ "ንጉሥ ሊያከብረው ለሚወደው ሰው ምን ይደረግለት?"አለው። ሐማም በልቡ፥"ከእኔ የበለጠ ንጉሡ ሊያከብረው የሚወደው ማን ይኖራል?" ብሎ አሰበ። **7** ሐማም ንጉሡን፥ "ንጉሡ ሊያከብረው ለሚወደው ሰው፥ **8** ንጉሡ ይለብሰው የነበረ ንጉሣዊ ልብስ ይምጣለት፥ ንጉሡ ይቀመጥበት የነበረና በራሱ ላይ የክብር ጌጥ የተደረገለት ፈረስ ይምጣለት። **9** ከዚያም ልብሶቹና ፈረሱ ከንጉሡ ሹማምንት እጅግ በተመረጡት በአንደኛው እጅ ይሰጡ፥ እነርሱም ንጉሡ ሊያከብረው የወደደውን ሰው ያልብሱት፥ በፈረሱ ላይ በማስቀመጥም በከተማው ዋና ዋና ጎዳናዎች ይምሩት፥ በፊቱም "ንጉሡ ሊያከብረው ለሚወደው ሰው የሚደረግለት እንዲህ ነው!" እያሉ ያውጁ" አለ። **10** ከዚያም ንጉሡ ሐማን፥ "ፍጠን፥ እንደተናገርከው ልብሶቹንና ፈረሱን ውሰድ፥ በንጉሡ በር ለሚቀመጠው ለአይሁዳዊው ለመርዶክዮስ ይህንኑ አድርግለት። ከተናገርከውም አንድ አንዳይጎድል" አለው። **11** ከዚያም ሐማ ልብሱንና ፈረሱን ወሰደ። መርዶክዮስን አልብሶና ፈረስ ላይ አስቀምጦ በከተማው ዋና ዋና ጎዳናዎች አዟዟረው። በፊቱም፥ "ንጉሡ ሊያከብረው ለሚወደው ሰው የሚደረግለት እንዲህ ነው!" እያለ ዐወጀ። **12** መርዶክዮስ ወደ ንጉሡ በር ተመለሰ። ሐማ ግን ፊቱን ሸፍኖና አዘኖ በጥድፊያ ወደ ቤቱ ሄደ። **13** ሐማም ለሚስቱ ለዞሳራና ለጓደኞቹ ሁሉ የገጠመውን ነገር በሙሉ ነገራቸው። በጥበባቸው የታወቁት ሰዎቹና ምስቱ ዞሳራም፥ "በፊቱ መውደቅ የጀመርከለት መርዶክዮስ አይሁዳዊ ከሆነ በርግጥ በፊቱ ትወድቃለህ እንጂ አታሸንፈውም" አሉት። **14** ከእርሱ ጋር እየተነጋገሩ እያሉ የንጉሡ ሹማምንት መጡ። እነርሱም አስቴር ወዳዘጋጀችው ግብዣ ሐማን አቻኮሉት።

Esther 6:1

ገበታ እና ታራ
እነዚህ የሁለት ወንዶች ስሞች ናቸው። ስሞቻቸውን በአስቴር 2:21 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ተመዝግቦ ተገኘ
እዚህ ስፍራ "ተገኘ" የሚለው ማወቅ ለሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "ተገኘ" እና "ተመዝግቦ" የሚሉት ሁለቱም በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጹ ይችላሉ። "ጸሐፍቱ በዚያ እንደመዘገቡት አገኙ" ወይም "ጸሐፍቱ እንደጻፉ አወቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ክብር ለመስጠት ምን ተደረገ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ክብር ለመስጠት ምን አደረግኩ" ወይም "ክብር ለመስጠት ምን አደረግን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእርሱ ምንም አልተደረገለትም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። የሆነ ሆኖ አገልጋዮች ንጉሡን እየከሰሱ እንደሆነ የማያስመስል መንገድ መፈለጉ መልካም ሊሆን ይችላል። "ማንም ለመርዶክዮስ ምንም አላደረገም" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 6:4

ሐማ
ይህንን የወንድ ስም በአስቴር3:1 ውስጥ እንዴት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ

ውጫዊው አደባባይ
"ከውጭ የመጀመሪያው አደባባይ"

መርዶክዮስን ለመስቀል
እርሱን ለመስቀል ተፈልጎ የነበረበትን ምክንያት ግልጽ ማድረግ ይቻላል። "መርዶክዮስን በመስቀል ለመግደል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የሚገመት ዕውት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእርሱ ያዘጋጀው መስቀያ
መስቀያ እንጨት ሰዎችን በዚያ ላይ ለመግደል የሚዘጋጅ ነበር። በአስቴር 5፡ 14 ላይ "መስቀያ እንጨት" የሚለውን እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። "ሐማ መርዶክዮስን ለመስቀል ያዘጋጀው ግንድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የማይታወቁትን መተረጎም የሚለውን ይመልከቱ)

አዘጋጀ
"ሰራ"

ንጉሡ ሊያከብረው ለወደደው ሰው ምን መደረግ አለበት
እዚህ ስፍራ ላይ ንጉሡ በሶስተኛ መደብ ራሱ እየተናገረ ነው። ይህ በአንደኛ መደብ እና በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እኔ ለወደድኩት እና ላከብረው ለምፈልገው ሰው ምን ማድረግ ይኖርብኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሡ ሊያከብረው ለወደደ
አንዳች ነገር በማድረግ ደስ መሰኘት፤ አንድ ነገር በመደረጉ ምክንያት አንድ ነገር ለማድረግ ደስ መሰኘትን ወይም አንድ ነገር ለማድረግ መፈለግን የሚገልጽ ፈሊጥ ነው። "ንጉሡ ሊያከብረው ደስ ተሰኝቷል" ወይም "ንጉሡ ሊያከብረው ፈልጓል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

በልቡ እንዲህ አለ
ልቡ የሚለው አስተሳሰብን እና ዝንባሌን ይወክላል። "ሃሳብ" ወይም "ለራሱ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሡ ከእኔ ይልቅ ሊያከብረው የሚወደው ማን አለ?
ይህ እንደ ሙሉ አሳብ/መግለጫ ሊገለጽ ይችላል። "በእርግጥ ንጉሡ ከእኔ ይልቅ ሊያከብረው የሚወደው ማንም የለም!" (ሬቶሪካል/ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Esther 6:7

ንጉሡ የሚጎናጸፈው ልብስ ይምጣ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንድ ሰው ንጉሣዊ መጎናጸፊያዎችን ያምጣ" ወይም "አገልጋዮችህ ንጉሣዊ መጎናጸፊያዎችን እንዲያመጡ እዘዝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ) ንጉሣዊው ባርኔጣ/ክሪስት በማን ራስ ላይ ነው "በማን" የሚለው ቃል ፈረሱን ያመለክታል። ንጉሣዊው ባርኔጣ የንጉሡን ቤተሰብ የሚወክል ልዩ ምልክት ነው።

ከዚያም የንጉሡልብሶ እና ፈረስ ይሰጠው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ከዚያም ልብሶቹን እና ፈረሱን ይስጡት" ወይም "ከዚያም ልብሶቹን እና ፈረሱን እንዲሰጡት እዘዝ" ጨ

ያልብሱት... በማክበር፣ ደግሞም ከፊቱ እየሄዱ ይምሩ
"እንዲያለብሱ እዘዝ... በማክበር ደግሞም እየመሩ"

ያውጁ
"የከበሩ መኳንንት እና አገልጋዮች እንዲያውጁ እዘዝ"

Esther 6:10

ከተናገርከው አንዳች ነገር አይጉደል
"አንዳች ነገር" የሚለው ሐረግ የተናገረውን ሁሉ አንዳች ሳያስቀር እንዲያድግ ትኩረት የሚሰጥ ነው። በአዎንታዊ ሊጻፍ ይችላል። "የተናገርከውን ሁሉ ሙሉለሙሉ ማድረግህን እርግጠኛ ሁን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

Esther 6:12

ራሱን ተከናንቦ
ሰዎች ብዙውን ጊዜ ራሳቸውን የሚሸፍኑት እጅግ ማዘናቸውን ወይም ማፈራቸውን ለመግለጽ ነበር። (ተምሳሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ዘሳራ
ይህን የሴት ስም በእስቴር 5:10 ውስጥ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በፊቱ መውደቅ የጀመርክለት... በእርግጥ በፊቱ ትወድቃለህ
የሚናገሩት ሐማ እና መርዶክዮስ ልክ በጦርነት ውስጥ እንደሚገኙ አድርገው ነው፣ ደግሞም ሐማ በጦርነቱ ተሸናፊ መሆን ጀምሮ ነበር። እዚህ ስፍራ "መውደቅ" የሚለው ቃል የሚወከወለው ክብርን ማጣትን እና መሸነፍን ነው። "በፊቱ መውደቅ የጀመርክለት... በእርግጥ ያሸንፍሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አታሸንፈውም
"ልትቋቋመው አትችልም።" የሚናገሩት ሐማ እና መርዶክዮስ ልክ በጦርነት ውስጥ እንደሚገኙ አድርገው ነው። እዚህ ስፍራ ላይ አንድን ሰው ማሸነፍ የሚለው የሚገልጸው ከዚያ ሰው ይልቅ የበለጠ ክብር ማግኘትን ነው። "እርሱ ካለው ክብር በላይ ትልቅ ክብር አይኖርህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 7

1 ስለዚህ ንጉሡና ሐማ በንግሥት አስቴር ለመጋበዝ ሄዱ። **2** በዚህ በሁለተኛው ቀን፥ ወይን እየጠጡ እያሉ፥ ንጉሡ አስቴርን፥ "ልመናሽ ምንድነው ንግሥት አስቴር? እርሱ ይሰጥሻል። ጥያቄሽስ ምንድነው? እስከ መንግሥት አጋማሽ ድረስ ይሰጥሻል?" አላት። **3** ንግሥት አስቴርም መልሳ፥ "ንጉሥ ሆይ፥ በዓይንህ ፊት ሞገስ አግኝቼ ከሆነና ደስ የምትሰኝበትም ከሆነ ሕይወቴ እንድትሰጠኝ ልመናዬ ይህ ነው፥ ስለ ሕዝቤም የምጠይቀው ይህንኑ ነው። **4** እኔና ሕዝቤ ለመጥፋት፥ ለመሞትና ለመደምሰስ ተሸጠናልና። ወንድና ሴት ባሪያዎች እንድንሆን ለባርነት ብቻ ተሸጠን ቢሆን ኖሮ ዝም ባልኩኝ ነበር፥ ይህንን በመሰለው ጭንቀት ንጉሡን ማወክ አይገባምና። **5** ከዚያም ንጉሥ አርጤክስስ ንግሥት አስቴርን፥ "ማነው እርሱ? እንዲህ ያለውን ነገር ለማድረግ ልቡ የሞላ ያ ሰው የት ነው የሚገኘው?" አላት። **6** አስቴርም፥ "ያ ጠላትና ባላጋራው ሰው ይህ ክፉው ሐማ ነው!" ሐማም በንጉሡና በንግሥቲቱ ፊት ደነገጠ። **7** ንጉሡም በቁጣ ወይን ከሚጠጣበት ግብዣ ተነሥቶ ወደ ቤተመንግሥቱ መናፈሻ ሄደ፥ ሐማ ግን ንግሥት አስቴር ሕይወቱን እንድትታደገው ሊለምናት በዚያው ቆይቶ ነበር። ከንጉሡ ጥፋት እንደተወሰነበት አይቷልና። **8** ከዚያም ንጉሡ ከቤተመንግሥቱ መናፈሻ ወደ ወይን መጠጫው ክፍል ተመለሰ። ሐማ አስቴር በነበረችበት ድንክ አልጋ ላይ ልክ መደፋቱ ነበር። ንጉሡም፥ "በገዛ ቤቴ፥ በእኔው ፊት ንግሥቲቱን ሊደፍራት ነው እንዴ?" አለ። ልክ ይህ ቃል ከንጉሡ አፍ እንደወጣ፥ አገልጋዮቹ የሐማን ፊት ሸፈኑት። **9** ከዚያም ንጉሡን ከሚያገለግሉት ሹማምንቶች አንዱ የሆነው ሐርቦና፥ "ሃምሳ ክንድ ቁመት ያለው መስቀያ በሐማ ቤት ቆሟል። ያቆመውም ንጉሡን ለመታደግ የተናገረውን መርዶክዮስን ለመስቀል ነው" አለ። ንጉሡም "በእርሱ ላይ ስቀሉት" አላቸው። **10** ስለዚህ ሐማን ለመርዶክዮስ ባዘጋጀው መስቀያ ላይ ሰቀሉት። ከዚያም የንጉሡ ቁጣ በረደ።

Esther 7:1

ሐማ
ይህንን የወንድ ስም በአስቴር3:1 ውስጥ እንዴት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚህ በሁለተኛው ቀን
"በዚህ በበዓሉ ሁለተኛ ቀን"

ወይን ጠጅ እያቀረቡ ሳለ
"አገልጋዮች ወይን እየቀዱ እና እነርሱን እያስተናገዷቸው ሳለ"

ልመናሽ ምንድን ነው
"ልመና" የሚለው ረቂቅ ስም "መጠየቅ" ወይም "መፈለግ" በሚል ግስ ሊገለጽ ይችላል። "ምን ትጠይቂያለሽ" ወይም "ምን ትፈልጊያለሽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ለአንቺ ይሰጥሻል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የጠየቅሽውን እሰጥሻለሁ" ወይም "የምትጠይቂውን አደርግልሻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እስከ መንግሥቴ እኩሌታም ቢሆን ይሰጥሻል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የመንግሥቴን እኩሌታ እንኳን ቢሆን ብትጠይቂ፣ እሰጥሻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 7:3

ንጉሥ ሆይ፣ በፊትህ ሞገስ አግኝቼ ከሆነ
"ሞገስ ማግኘት" ይህ ፈሊጥ ሲሆን ተቀባይነት ማግኘት ወይም ንጉሡ በእርሷ ደስ መሰኘቱን የሚገልጽ ነው። "በዐይኖችህ" የእርሱን ሚዛን የሚገልጽ ዘይቤያው አነጋገር ነው። "መዝነህ ከተቀበልከኝ" ወይም "በእኔ ደስ ከተሰኘህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጥ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ህይወቴ ትትረፍ
"ህይወት መስጠት" የሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር የሚገለልጸው አንድን ሰው ከመገደል ማዳንን ነው። ይህ አባባል በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ህይወቴን አድን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ልመናዬ ይህ ነው
"ልመና" የሚለው ረቂቅ ስም "መጠየቅ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "የምጠይቀው ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ተሸጠን ቢሆን ኖሮ
"ተሸጠን ቢሆን" የሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር መካድን ይገልጻል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እኛን የካደን አለ" ወይም "ለጠላቶቻችን ለአደጋ አሳልፍ የሰጠን አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እንድንጠፋ፣ እንዲንገደል፣ እና እንድንደመሰስ
እዚህ ስፍራ እነዚህ ሶስት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ሲይዙ አገልግሎት ላይ የዋሉት ትኩረት ለመስጠት ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ጠላቶቻችን እንዲያጠፉን፣ እንዲገድሉን፣ እና እንዲደመስሱን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትረጉም እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህ ያለውን ነገር ለማድረግ ልቡን የሞላው ይህ ሰው ወዴት አለ
አንድ ነገር ለማድረግ ልብን መሙላት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው ትረጉሙም አንዳች ነገር ለማድረግ መፈለግ ማለት ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እንዲህ ያለ ነገር ለመስራት የደፈረው ሰው ወዴት አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጥ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 7:6

በፍርሃት ተዋጠ
"እጅግ ፈራ"

ንጉሡ በቁጣ ብድግ አለ
በቁጣ መሆን የሚለው እጅግ መቆጣትን ለመግለጽ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ንጉሡ እጅግ ተቆጥቶ ነበር እናም በቁጣ ብድግ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ ህይወቱ ንግስት አስቴርን ለመማጸን
"ህይወቱን እንድታድንለት ንግሥት አስቴርን ለመማጸን"

ጥፋት እንደተወሰነበት አየ
እዚህ ስፍራ ማየት የሚገልጸው ማወቅን ወይም መረዳትን ነው። "ጥፋት እንደተወሰነበት አወቀ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በእርሱ ላይ ከንጉሡ ዘንድ ጥፋት ተወስኖበት ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ጥፋት" የሚለው ረቂቅ ስም ይበልጥ ተጨባጭ በሆነ "ጠፋ" ወይም "ተገደለ" በሚል ግስ ሊገለጽ ይችላል። " ንጉሱ በእርሱ ላይ ጥፋት እንዲፈጸም ወስኖ ነበር" ወይም "ንጉሡ ሊያጠፋው ወስኖ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 7:8

ወይን ጠጅ በሚታደልበት ጊዜ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አገልጋዮች ወይን ጠጅ በሚያቀርቡበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ድንክ አልጋ
ሰው ሊቀመጥበት ወይም ሊጋደምበት የሚችል ተለቅ ያለ የቤት ዕቃ

እኔ እያለሁ በገዛ ቤቴ ንግሥቲቱን ያስነውራልን?
ንጉሡ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት ሐማ ያደርግ በነበረው ነገር መረበሹን እና መቆጣቱን ለማሳየት ነው። ይህ ጥያቄ ሙሉ ሃሰብ/መግለጫ ተደርጎ ሊተረጎም ይችላል። " እኔ ባለሁበት እና በገዛ ቤቴ ንግሥቲቱን ሊያስነውር ጭምር ያስባል!" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ንግሥቲቱን ያስነውራል
"ንግሥቲቱን ያጠቃል።" ይህ ሐረግ በጨዋ አገላለጽ ጾታዊ መድፈርን መግለጫ ነው። (አስነዋሪ/ጸያፍ ቃልን ሻል ባለ ቃል መጠቀም/ዩፊምዝም የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ዐረፍተ ነገር ከንጉሡ አፍ እንደ ወጣ ወዲያውኑ
ንግግሩ ከአፉ እንደ ወጣ የሚለው ንግግርን የሚወክል ሜቶኖሚ (ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት ነው)። "ንጉሡ ይህንን እንደተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት- የሚለውን ይመልከቱ)

አገልጋዮች የሐማን ፊት ሸፈኑ
ይህንን ያደረጉት ሐማ እንዲገደል ንጉሡ መፈለጉን ስለተረዱ መሆኑ ግልጽ ነው። "አገልጋዮቹ የሐማን ፊት መሸፈናቸው እንደሚገደል ምልክት ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ እና ተምሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 7:9

ሐርቦና
ይህ የወንድ ስም ነው።(ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሃምሳ ክንድ ርዝመት ያለው መስቀያ
"ሃምሳ ክንድ ቁመት።" የሚለውን ወደ ዘመናዊ መለኪያ መለወጥ ይችላሉ። በአስቴር 5:14 ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። ወደ፡ "አንድ የሰው መስቀያ ሃያ ሶስት ሜትር ከፍታ" (ቁጥሮች እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ርቀት የሚለውን ይመልከቱ)

የንጉሡ ቁጣ በረደ
የንጉሡ ቁጣ የተገለጸው ታላቅ እሳት እንደነበረ እና እየቀነሰ እንደመጣ ነው። "የንጉሡ ቁጣ በረደ" ወይም "ከዚያ ንጉሡ እጅግ አልተቆጣም ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 8

1 በዚያም ቀን ንጉሡ አርጤክስስ የአይሁዶችን ጠላት፥ የሐማን ንብረት፥ ለንግሥት አስቴር ሰጣት። መርዶክዮስ እንዴት እንደሚዛመዳት ለንጉሡ ነግራው ስለ ነበረ፥ መርዶክዮስ በንጉሡ ፊት ማገልገል ጀመረ። **2** ንጉሡ ከሐማ መልሶ የወሰደውን ማኅተም ያለበትን ቀለበት አውልቆ ለመርዶክዮስ ሰጠው። አስቴርም መርዶክዮስን በሐማ ይዞታ ላይ ኃላፊ አድርጋ ሾመችው። **3** ከዚያም አስቴር ንጉሡን ደግማ ተናገረችው። እርሷም በምድር ላይ ተደፍታ አጋጋዊው ሐማ በአይሁድ ላይ ያሴረውን የጥፋት ዕቅድ ማብቂያ እንዲያደርግለት እያለቀሰች ለመነችው። **4** ከዚያም ንጉሡ የወርቁን በትረ መንግሥት ለአስቴር ዘረጋላት። እርሷም ተነሥታ በንጉሡ ፊት ቆመች። **5** እርሷም፥ "ንጉሡን ደስ የሚለው ከሆነና በፊትህ ሞገስን ካገኘሁ፥ ነገሩም በንጉሡ ፊት ትክክል መስሎ ከታየውና እኔም በዓይንህ ፊት ተወድጄ ከሆነ፥ በአጋጋዊው በሐመዳቱ ልጅ በሐማ የተጻፈውን፥ በንጉሡ አውራጃዎች ሁሉ የሚኖሩትን አይሁድ ለማጥፋት የጻፈውን ድብዳቤ የሚሽር አዋጅ ይጻፍ። **6** በሕዝቤ ላይ የሚደርሰውን እልቂት ለማየት እንዴት መታገሥ እችላለሁ? የዘመዶቼን ጥፋት መመልከቱንስ እንዴት መቋቋም እችላለሁ?" አለችው። **7** ንጉሥ አርጤክስስ ንግሥት አስቴርንና አይሁዳዊውን መርዶክዮስን፥ "ተመልከቱ፥ የሐማን ቤት ለአስቴር ሰጠኋት፥ አይሁድን ሊያጠቃ ስለነበርም እርሱን በመስቀያው ላይ ሰቀሉት። **8** ለአይሁዶች በንጉሡ ስም ሌላ ዐዋጅ ጻፉ፥ በንጉሡም የቀለበት ማኅተም አትሙበት። ቀደም ሲል በንጉሡ ስም የተጻፈውና በንጉሡ ቀለበት የታተመው ዐዋጅ ሊሻር አይቻልምና።" **9** በሦስተኛው ወር፥ እርሱም የኒሳን ወር ነው፥ ከወሩም በሃያ ሦስተኛው ቀን በዚያን ጊዜ የንጉሡ ጸሐፊዎች ተጠርተው ነበር። ዐዋጁም አይሁድን በሚመለከት መርዶክዮስ ያዘዘው ሁሉ ተካትቶ ተጽፎበት ነበር። ለየአውራጃው አስተዳዳሪዎች ተጽፎ ነበር፥ ከህንድ እስከ ኢትዮጵያ ለሚዋሰኑት 127 የአውራጃ አስተዳዳሪዎችና አለቆች፥ ለእያንዳንዱ አውራጃ በየራሱ ጽሑፍና ለእያንዳንዱ ሕዝብ በየራሱ ቋንቋ፥ ደግሞም ለአይሁድ በራሳቸው ጽሑፍና ቋንቋ ተጻፈ። **10** መርዶክዮስ በንጉሥ አርጤክስስ ስም ጽፎ በንጉሡ የቀለበት ማኅተም አተመው። ደብዳቤዎቹንም ለንጉሡ አገልግሎት በሚውሉና ለዚሁ በተገሩ ፈጣን ፈረሶች በሚጋልቡ መልዕክተኞች ላከው። **11** በየከተማው ያሉ አይሁዶች በአንድ ላይ እንዲሰባሰቡና ሕይወታቸውን እንዲከላከሉ፤ ልጆችንም ሆነ ሴቶችን ጨምሮ ከየትኛውም ሕዝብም ሆነ አውራጃ እነርሱን ለማጥቃት መሣሪያ የሚያነሣውን ኃይል ሁሉ እንዲያጠፉ፥ እንዲገድሉና እንዲደመስሱ ንብረታቸውንም እንዲበዘብዙ ንጉሡ ፈቃድ ሰጣቸው። **12** ይህ በንጉሥ አርጤክስስ አውራጃዎች ሁሉ በአሥራ ሁለተኛው ወር፥ እርሱም አዳር የሚባለው ወር ነው፥ በአሥራ ሦስተኛው ቀን ተግባራዊ የሚደረግ ነበር። **13** የዐዋጁ ቅጅ ሕግ ሆኖ በመውጣት ሕዝብ ሁሉ እንዲያውቀው ተደረገ። አይሁድ በዚያን ቀን ጠላቶቻቸውን ለመበቀል ዝግጁዎች መሆን ነበረባቸው። **14** ስለዚህ መልዕክተኞቹ ለንጉሡ አገልግሎት በሚውሉ የቤተመንግሥት ፈረሶች ላይ ተቀመጡባቸው። እነርሱም ፈጥነው ሄዱ። ደግሞም የንጉሡ ዐዋጅ ከሱሳ ቤተመንግሥት ተነገረ። **15** ከዚያም መርዶክዮስ ንጭና ሰማያዊ የክብር ልብስ ለብሶ፥ ታላቅ የወርቅ አክሊልም ደፍቶ፥ ከሐምራዊና ከጥሩ የተልባ እግር የተሠራ መጎናጸፊያ ደርቦ ከንጉሡ ፊት ወጣ። የሱሳ ከተማም ደስ አላት፥ እልልም አለች። **16** ለአይሁድም ብርሃንና ፈንጠዚያ፥ ደስታና ክብር ሆነላቸው። **17** የንጉሡ ዐዋጅ በደረሰበት ሁሉ፥ በየአውራጃውና በየከተማው በአይሁድ መካከል ደስታና ፈንጠዚያ፥ ግብዣና በዓል ሆነ። አይሁድን መፍራት በላያቸው ላይ ወድቆ ስለነበረ በምድሩ ከሚኖሩ ልዩ ልዩ ሕዝቦች ብዙዎቹ አይሁድ ሆኑ።

Esther 8:1

ሐማ
በአስቴር 3:1 ላይ ይህን የወንድ ስም እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ

የቀለበት ማህተም
ይህ ቀለበት የንጉሡ ስም ወይም ምልክት በላዩ አለበት። ጠቃሚ በሆኑ ሰነዶች ላይ የሰም ማህተም ሲያሳርፍ፣ በማህተሙ ላይ ምልክቱን ያኖር ነበር። አንድ ሰነድ በማህተሙ ላይ ይህ ምልክት ካለበት፣ ሰዎች በወረቀቱ ላይ የተጻፈው ነገር በንጉሡ ስልጣን የተጻፈ መሆኑን ይረዱና ለዚያም መታዘዝ ይኖርባቸው ነበር። ይህንን በአስቴር 3:10 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ። (የማይታወቁትን ስለ መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

ለመርዶክዮስ ሰጠው
ለመርዶክዮስ የማህተም ቀለበቱን በመስጠት፣ ንጉሡ ለመርዶክዮስ ህዝቡ የሚታዘዘው ሰነድ መጻፍ የሚያስችለውን ስልጣንን ሰጠው

የሐማን ቤት ንብረት
ይህ የሚያመለክተው የሐማ የነበሩና ንጉሡ ለአስቴር የሰጣቸውን ሃብት ንብረቶችን ነው።

Esther 8:3

ከተማጽኖ ጋር
"ለመነች"

የአጋጋዊውን የሐማን ክፉ እቅድ ለማስወገድ
"ማብቂያው እንዲሆን" ይህ ፈሊጣው አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ አንድን ነገር ማስቆም ማለት ነው። " የአጋጋዊውን የሐማን ክፉ እቅድ ለማስቆም" ወይም " አጋጋዊውን ሐማ ያቀደውን ክፉ እቅድ ለመከላከል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አጋጋዊው
ይህንን በአስቴር 3:1 ውስጥ እንዴት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ።

ያዘጋጀው ሴራ
"የፈጠረው ተንኮል" ወይም "ሐማ የፈጠረው ሴራ"

ንጉሡ ለአስቴር በትረ መንግሥቱን/የወርቅ ዘንጉን ዘረጋላት
ይህንን ያደረገው በእርሷ ደስ መሰኘቱን ለማሳየት ነው። በአስቴር 5:2 ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ።

Esther 8:5

ንጉሡን ደስ ካሰኘው
"እኔ የምጠይቀው ንጉሡን ደስ ካሰኘው"

በንጉሡ በዐይኖች ሞገስ አግኝቼ ከሆነ
እዚህ ስፍራ "ሞገስ ማግኘት" የሚለው ፈሊጣው አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ ተቀባይነት ማግኘት ወይም በእርሷ ደስ መሰኘቱ የሚል ነው። "ዐይኖች " የሚለው ማየት ለሚለው ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት ሲሆን እይታ የሚለው የንጉሱን ሚዛን የሚገልጽ ዘይቤ ነው። "መዝነኸኝ ተቀባይነትን አግኝቼ ከሆነ" ወይም "በእኔ ደስ ተሰኝተህ ከሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጥ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት እንዲሁም ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በንጉሡ ፊት ነገሩ ትክክል ሆኖ ከታየ
"በንጉሡ ፊት" ይህ የእርሱን ምዘና የሚገልጽ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "የጠየቅኩት በንጉሡ ሚዛን ትክክል መስሎ ከታየ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በዐይኖችህ ፊት ደስ አሰኝቼ ከሆነ
እዚህ ስፍራ "በዐይኖችህ ፊት " የሚለው ማየት ለሚለው ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት ሲሆን/ እይታ የሚለው የንጉሱን ሚዛን የሚገልጽ ዘይቤ ነው።"መዝነኸኝ ተቀባይነትን አግኝቼ ከሆነ" ወይም "በእኔ ደስ ተሰኝተህ ከሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

የሚሸር
ወደ ኋላ መመለስ እና የማይሰራ ማድረግ

ሐማዳት
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ግዛቶች
ግዛት አንዳንድ አገራት ለአስተዳደር ሲባል የሚከልሉት ሰፊ አካባቢ/ስፍራ ነው። ይህንን በአስቴር 1፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

በህዝቤ ላይ የሚደርሰውን ጥፋት እያየሁ እንዴት ልታገስ እችላለሁ? የቤተ ዘመዶቼን ጥፋት እንዴት እያየሁ እንዴት መቋቋም እችላለሁ?
አስቴር እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመችባቸው ህዝቧ የሚጠፋ ከሆነ እጅግ እንደምታዝን ለማሳየት ነው። "በአይሁድ ላይ የሚደርሰውን ጥፋት እያየሁ እንዴት መቋቋም እችላለሁ። ቤተዘመዶቼ ሲገደሉ እንዴት ልታገስ እችላለሁ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 8:7

የሐማ ቤት
ይህ የሚገልጸው ሐማ የነበረውን ሁሉ ነው። "የሐማ የነበረው ሁሉ" ወይም "መላው የሐማ ንብረት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሲኔክቲኪ/ ዘይቤያዊ አነጋጋር- የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ፤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው መስቀያ እንጨት
ይህንን በአስቴር 6፡4 እንዴት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመለከቱ

በንጉሡ ስም... የተጻፈ
አንደን ነገር በንጉሥ ስም መጻፍ በእርሱ ስልጣን መጻፍን ያመላክታል፣ ወይም የእርሱ ወኪል ሆኖ መጻፍን ያሳያል። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት- የሚለውን ይመልከቱ)

በማህተም... የወጣ አዋጅ ሊሻር አይችልም
ይህ በአድርጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በንጉሱ ቀለበት ...ማንም አዋጁን ሊሸር ስለማይችል" ወይም " በቀለበት የታተመውን...ማንም አዋጁን ሊሰርዝ ስለማይችል" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በማህተም... የወጣ አዋጅ ሊሻር አይችልም
"አዋጅ" እና "አይቻልም" በሚሉት ቃላት መሃል የተሰጠው መረጃ ንጉሡ የሐማን አዋጅ መሻር ያልቻለበትን ምክንየት ያሳያል። "ምክንያቱም" በሚለው ቃል በግልጽ የማይችልበት ምክንያት ሊታይ ይችላል። "ቀደም ሲል የተጻፈውን አዋጅ ልሸር አልችልም፣ ምክንያቱም በንጉሡ ስምና ማህተም ከንጉሡ ቀለበት የታተመ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆና ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አስቀድሞ በንጉሡ ስም የወጣ አዋጅ
አንድን ነገር በንጉሥ ስም መጻፍ በእርሱ ስልጣን መጻፍን ያመላክታል፣ ወይም የእርሱ ወኪል ሆኖ መጻፍን ያሳያል። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት- የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 8:9

የንጉሡ ጸሐፊዎች ተጠርተው ነበር
ይህ በአድርጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ንጉሡ የእርሱን ጸሐፊት ጠራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። አንባቢ መረዳት የሚገባው ንጉሡ ምናልባት ለአንዱ ሹም ሰነዱን እንዲያመጣ ያዘዘው መሆኑን ነው። ንጉሡ ሰነዱን እንዲያመጡለት ምናልናት ጮክ ብሎ አልተጣራም ይሆናል። (አድርጊ ወይም ተደራጊ እና ይሆና ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሶስተኛው ወር፣ በኒሳን ወር፣ በወሩ ሃያ ሶስተኛ ቀን በዕብራዊያን ቀን አቆጣጠር "ኒሳን" በተባለው
"ኒሳን" በዕብራዊያን ቀን አቆጣጠር የሶስተኛው ወር ስም ነው። ሃያ ሶስተኛው ቀን በምዕራባዊያኑ ወር አቆጣጠር ወደ ሰኔ አጋማሽ ላይ ነው። (የዕብራዊያን ወራት እና ተከታታይነትን የሚያሳዩ ቁጥሮች እና ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚሉትን ይመልከቱ)

አዋጅ ተጻፈ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አዋጅ ጻፉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

127 ግዛቶች
"አንድ መቶ ሃያ ሰባት ግዛቶች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ግዛቶች
ግዛት አንዳንድ አገራት ለአስተዳደር ሲባል የሚከልሉት ሰፊ አካባቢ/ስፍራ ነው። ይህንን በአስቴር 1፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

በራሳቸው ጽህፈት ተጻፈ
"በራሳቸው ፊደል ተጻፈ።" በዓለም ዙሪያ የተለያዩ የአጻጻፍ ስርአቶች አሉ።

Esther 8:10

በንጉሥ ጠረክሲስ ስም ተጻፈ
አንድን ነገር በንጉሥ ስም መጻፍ በእርሱ ስልጣን መጻፍን ያመላክታል፣ ወይም የእርሱ ወኪል ሆኖ መጻፍን ያሳያል። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት- የሚለውን ይመልከቱ)

የቀለበት ማህተም
ይህንን ሀረግ በአስቴር 8፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ

መልዕክተኞች
መልዕክትየሚያደርሱ ሰዎች

ከንጉሡ ፈረሶች ዝርያ
የንጉሡ ምርጥ ወንድ ፈረሶች ዝርያ። ለንጉሡ አገልግሎት የሚውሉት ምርጥ ዝርያዎች ነበሩ። "የንጉሡ ምርጥ ፈረሶች ዝርያዎች። "የንጉሡ ምርጥ ፈረሶች ዝርያዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆና ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለአይሁድ እንዲሰበሰቡ... ፈቃድ ሰጣቸው
"እንዲሰበሰቡ እንደፈቀደላቸው...ለአይሁድ ነገራቸው"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ዝግጁ እንደሆኑ
ይህ መልሰው እንዲያጠቁ እንጂ እንዳይሸሹ የሚገልጽ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "ራሳቸውን ከጥቃት እንዲከላከሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የአስራ ሁለተኛው ወር አስራ ሶስተኛ ቀን፣ ይህም የአዳር ወር ነው
ይህንን በአስቴር 3:13 እንዴት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ።

Esther 8:13

ጠላቶቻቸውን እንዲበቀሉ
"ጠላቶቻቸውን እንዲበቀሉ" የዚህ ፈሊጥ ትረጉሙ የጎዳን ሰው መልሶ መጉዳት የሚል ነው። "ጠላቶቻቸውን መልሰው እንዲበቀሉ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሳይዘገዩ ወጡ
"ሳይዘገዩ" የዚህ ፈሊጥ ትረጉም አልዘገዩም ወይም አልጠበቁም ማለት ነው። "ወዲያውኑ ወጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሱሳ
የንጉሡ ቤተመንግስት የነበረባት ከተማ ናት። በአስቴር 1:2 ይህንን እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 8:15

የሱሳ ከተማ ተደሰተች ሀሴት አደረገችም
"ከተማይቱ" የሚለው በከተማዋ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን ይገልጻል። "የሱሳ ከተማ ሰዎች በደስታ ጮሁ ሃሴትም አደረጉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት- የሚለውን ይመልከቱ)

በደስታ ጮሁ፣ ሃሴትም አደረጉ
"ሃሴት አደረጉ" የሚለው ቃል እንዱት እንደጮሁ ይገልጻል። "በደስታ ጮሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ብርሃን እና ደስታ ሆነላቸው
አማራጭ ትርጉሞች ሊሆኑ የሚችሉት 1) ብርሃን የሚለው ደስተኛ ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "በደስታ እና ሃሴት ተሞሉ" ወይም 2) ብረሃን ወጣላቸው የሚለው እንደ በለጸጉ እና ደህንነት እንደተሰማቸው የሚገልጽ ፈሊጥ ነው። "ደህንነት ተሰማቸው ደግሞም ድተኞች ሆኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ክብር
አማራጭ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት 1) ሌሎች ህዝቦች አይሁዶችን አከበሯቸው። "ሌሎች ህዝቦች እነርሱን አከበሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) አይሁዶች እንደተከበሩ ተሰማቸው "እንደ ተከበሩ ተሰማቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆና ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ግዛት
ግዛት አንዳንድ አገራት ለአስተዳደር ሲባል የሚከልሉት ሰፊ አካባቢ/ስፍራ ነው። ይህንን በአስቴር 1:1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

የንጉሡ አዋጅ በየደረሰበት ስፍራ
የደረሰበት ቦታ የሚለው የሚገልጸው ወደየ ስፍራው መድረስን ነው። " የንጉሡ ሰዎች አዋጁን ይዘው ወጡ" ወይም "የንጉሡ አዋጅ በተነበበት ስፍራ ሁሉ" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ክብረ በዓል
ሰዎች ልዩ ትዕይንቶችን የሚያከብሩበት ቀን

አይሁዶችን መፍራት ወደቀባቸው
በሰዎች ላይ ፍርሃት ወደቀ የሚለው የሚገልጸው ሰዎች በጣም እየፈሯቸው መምጣቱን ነው። "አይሁዶችን በጣም ፈሯቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 9

1 አዳር ተብሎ በሚጠራው በአሥራ ሁለተኛው ወር፥ በአሥራ ሦስተኛውም ቀን የንጉሡ ሕግና ዐዋጅ ተግባራዊ በሚደረግበት፥ የአይሁድ ጠላቶች ሊያጠፏቸው
ተስፋ ባደረጉበት ቀን ነገሩ ተቀየረ። አይሁዶች በሚጠሏቸው ላይ የበላይነትን አገኙ። 2 አይሁድ ሊያጠፏቸው በሞከሩት ላይ እጆቻቸውን ለማንሣት ከንጉሥ
አርጤክስስ አውራጃዎች ሁሉ ወደ ከተሞቻቸው ተሰበሰቡ። እነርሱን መፍራት በሕዝብ ሁሉ ላይ ወድቆ ስለነበረ ማንም ሊቃወማቸው አልቻለም። 3
የአውራጃዎቹ አለቆች፥ የአውራጃ ገዢዎች፥ መኳንንቶችና የንጉሡ አስተዳዳሪዎች መርዶክዮስን በመፍራት ተይዘው ስለነበር አይሁድን አገዟቸው። 4
መርዶክዮስ በንጉሡ ቤት ታላቅ ነበር፥ ዝናውም በአውራጃዎቹ ሁሉ ተሰራጨ፥ መርዶክዮስ የተባለውም ሰው ታላቅ ሆነ። 5 አይሁድም ጠላቶቻቸውን በሰይፍ
አጠቋቸው፥ ገደሏቸው፥ አጠፏቸውም፥ በእነዚያ ይጠሏቸው በነበሩት ላይ ደስ ያሰኛቸውን አደረጉባቸው። 6 አይሁድ በራሱ በሱሳ ግንብ አምስት መቶ ሰዎችን
ገደሉ፥ አጠፉም። 7 የአይሁድ ጠላት የሐመዳቱን ልጅ 8 የሐማን አሥሩን ወንዶች ልጆቹን፥ ፓርሻንዳታን፥ ደልፎንን፥ አስፓታን፥ 9 ፖራታን፥ አዳልያን፥ አሪዳታን፥
10 ፓርማሽታን፥ አሪሳይን፥ አሪዳይንና ዋይዛታን ገደሉ። ነገር ግን ምንም ዝርፊያ አልፈጸሙም። 11 በተመሸገችው ከተማ፥ በሱሳ፥ በዚያን ቀን የተገደሉት ሰዎች
ብዛት ለንጉሡ ተነገረው። 12 ንጉሡም ንግሥት አስቴርን፥ "አይሁድ አሥሩን የሐማ ወንዶች ልጆች ጨምሮ በሱሳ ከተማ ውስጥ አምስት መቶ ሰዎችን ገደሉ።
በቀሩት የንጉሡ አውራጃዎች ምን አድርገው ይሆን? አሁን የምትለምኚው ምንድነው? እርሱም ይሰጥሻል። የምትጠይቂውስ ምንድነው? እርሱም
ይደረግልሻል" አላት። 13 አስቴርም፥ "ንጉሡን ደስ የሚለው ከሆነ፥ በሱሳ የሚገኙ አይሁዶች ዛሬ ያደረጉትን ነገም ደግሞ እንዲያደርጉ ይፈቀድላቸው፥ አሥሩ
የሐማ ልጆች ሬሳም በመስቀያ ይሰቀል" አለችው። 14 ስለዚህ ንጉሡ ይህ እንዲፈጸም አዘዘ። ዐዋጁም በሱሳ ተሰራጨ፥ አሥሩን የሐማ ወንዶች ልጆች
ሰቀሏቸው። 15 በአዳር ወር በአሥራ አራተኛው ቀን በሱሳ ይኖሩ የነበሩ አይሁድ አንድ ላይ ተሰብስበው ሦስት መቶ ተጨማሪ ሰዎችን ገደሉ፥ እጆቻቸውን ግን
ለመበዝበዝ አልዘረጉም። 16 በንጉሡ አውራጃዎች ይኖሩ የነበሩት፥ የቀሩት አይሁድ ሕይወታቸውን ለመከላከል በአንድ ላይ ተሰባሰቡ፥ ይጠሏቸው የነበሩትን
ሰባ አምስት ሺህ ሰው ገደሉ፥ ከጠላቶቻቸውም ዐረፉ። ነገር ግን ወደ ገደሏቸው ሰዎች ጠቃሚ ቁሳቁስ እጆቻቸውን አልዘረጉም። 17 በአዳር ወር በአሥራ
ሦስተኛው ቀን ይህ ሆነ፥ በአሥራ አራተኛው ቀን ዐረፉ፥ ቀኑንም የግብዣና የደስታ አደረጉት። 18 በሱሳ ይኖሩ የነበሩ አይሁድ ግን በአሥራ ሦስተኛውና በአሥራ
አራተኛው ቀን በአንድ ላይ ተሰባሰቡ። በአሥራ አምስተኛው ቀን ዐረፉ፥ የግብዣና የደስታም ቀን አደረጉት። 19 በገጠር ከተሞች የሚኖሩ የመንደሩ አይሁድ
የአዳርን ወር አሥራ አራተኛውን ቀን የግብዣና የደስታ ቀን አድርገው የሚያከብሩትና እርስ በርሳቸው የምግብ ስጦታ መለዋወጫ ቀን ያደረጉት ለዚህ ነው። 20
መርዶክዮስ እነዚህን ነገሮች ሁሉ በመጻፍ በንጉሥ አርጤክስስ አውራጃዎች ሁሉ በቅርብና በሩቅ ለሚኖሩ አይሁዶች በሙሉ በየዓመቱ በአዳር ወር 21 አሥራ
አራተኛውንና አሥራ አምስተኛውን ቀን እንዲጠብቁት በማዘዝ ደብዳቤዎችን ጻፈላቸው። 22 እነዚህ ቀናት አይሁድ ከጠላቶቻቸው ያረፉባቸው፥ ሀዘናቸው ወደ
ደስታ፥ ልቅሶአቸውም ወደ ደስታ በዓል የተለወጠባቸው ቀናት ነበሩ። እነርሱም ቀኖቹን የግብዣና የደስታ፥ ለእርስ በርሳቸውም የምግብ ስጦታ የሚለዋወጡበት፥
ለድሆችም ስጦታ የሚያበረክቱባቸው መሆን ነበረባቸው። 23 ስለዚህ አይሁድ መርዶክዮስ በጻፈላቸው ደብዳቤ መሠረት የጀመሩትን በዓል ማክበራቸውን
ቀጠሉ። 24 በዚያን ጊዜ የአይሁዶች ሁሉ ጠላት፥ የሐመዳቱ ልጅ ሐማ፥ አይሁድን ለማጥፋት አሢሮ ነበር፥ ሊሰባብርና ሊያፈርሳቸውም ፉር የተባለውን ዕጣ
ጥሎ ነበር። 25 ጉዳዩ ወደ ንጉሡ ፊት በቀረበ ጊዜ ግን ሐማ በአይሁድ ላይ ያዘጋጀው ክፉ ዕቅድ በእርሱ በራሱ ላይ እንዲመለስበትና ወንዶች ልጆቹ በስቅላት
እንዲቀጡ በደብዳቤ አዘዘ። 26 ስለዚህ ፉር ከሚለው ስም በመነሣት አነዚህን ቀናት ፉሪም ብለው ጠሯቸው። በዚህ ደብዳቤ በተጻፉት፥ እነርሱም ባዩትና
በደረሰባቸው ነገር ምክንያት አይሁድ አዲስ ልማድና አደራረግን ተቀበሉ። 27 ይህም ልማድ ለእነርሱ፥ ለትውልዳቸውና እነርሱን ለተጠጋ ሁሉ የሚቀጥል ነበር።
በየዓመቱ እነዚህ ሁለት ቀናት መከበር ነበረባቸው። ቀኖቹንም በየዓመቱ በተመሳሳይ ጊዜ፥ በአንድ ዓይነት መንገድ ማክበር ነበረባቸው። እነዚህ ቀኖች
በየትውልዱ፥ በየቤተሰቡ፥ በየአውራጃውና በየከተማው መታሰብና መከበር ይኖርባቸዋል። 28 እነዚህ አይሁዶችና ትውልዶቻቸው እነዚህን የፉሪም ቀናት
ፈጽመው እንዳይረሷቸው፥ በታማኝነት መጠበቃቸውንም በፍጹም ማቋረጥ አይኖርባቸውም። 29 የአቢካኢል ልጅ ንግሥት አስቴርና አይሁዳዊው መርዶክዮስ
ስለ ፉሪም ይህንን ሁለተኛ ደብዳቤ በሙሉ ሥልጣን ጽፈው አጸኑት። 30 በአርጤክስስ መንግሥት በ127 አውራጃዎች ውስጥ ለሚኖሩ አይሁድ በሙሉ
ደኅንነትንና እውነትን የሚመኙላቸው ደብዳቤዎች ተጻፉላቸው። 31 አይሁዳዊው መርዶክዮስና ንግሥት አስቴር አይሁድን እንዳዘዙት የፉሪም ቀናት
በተወሰነላቸው ጊዜያት እንዲደረጉ እነዚህ ደብዳቤዎች አጸኑት። አይሁድ ልክ የጾሙንና የለቅሶውን ጊዜ አንደተቀበሉት ይህንን ትዕዛዝ ደግሞ ለራሳቸውና
ለልጆቻቸው ተቀበሉት። 32 ፉሪምን በሚመለከት የአስቴር ትዕዛዝ እነዚህን መመሪያዎች አጸና፥ እርሱም በመጽሐፍ ተጻፈ።

Esther 9:1

አዳር በተባለው በአስራ ሁለተኛው ወር፣ በአስራ ሶስተኛ ቀን
በአስቴር 3፡13 ተመሳሳይ የሆነውን ሀረግ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ

የንጉሡ ህግ እና አዋጅ ሊፈጸም ባለበት ወቅት
"ሊፈጸም" የዚህ ፈሊጥ ትርጉም የታዘዘን ወይም የታቀደን ነገር ማድረግ ማለት ነው።ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች የንጉሡን ህግና አዋጅ የሚፈጽሙበት ጊዜ ሲደርስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በእነርሱ ላይ ስልጣን ለማግኘት
በሰዎች ላይ ሃይል ማግኘት እነርሱን ለማሸነፋቸው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "አይሁዶችን ለማሸነፍ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ተቀለበሰ
"ሁኔታው ተቀለብሶ ነበር።" ሁኔታው ተቀልብሶ የሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር ትርጉሙ ሊሆን ከሚጠበቀው ተቃራኒው ሲሆን ማለት ነው። "ተቃራኒው ሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ግዛቶች
ግዛት አንዳንድ አገራት ለአስተዳደር ሲባል የሚከልሉት ሰፊ አካባቢ/ስፍራ ነው። ይህንን በአስቴር 1፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

የእነርሱን ጥፋት በሚፈልጉ ወገኖች ላይ አደጋ ለመጣል
በሰዎች ላይ አደጋ መጣል የሚለው ከእነርሱ ጋር መዋጋት ለሚለው ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት/ ነው። "ጠላቶቻቸውን ለመዋጋት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት- የሚለውን ይመልከቱ)

በእነርሱ ላይ ጥፋት ለማምጣት የሞከረው ማን ነው
በሰዎች ላይ ጥፋት ማምጣት የሚለው ፈሊጥ ትርጉሙ በእነርሱ ላይ ጥፋት እንዲደርስ ምክንያት መሆን ማለት ነው። በዚህ ሁኔታ እነርሱን ማጥፋት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የሚለውን ያመላክታል። "እነርሱን ለማጥፋት የሞከረው ማን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ማንም ሊቋቋማቸው አልቻለም
ሰዎችን ተቃውሞ መቆም የሚለው የሚወክለው ጥቃታቸውን መቋቋምን ነው። "ማንም የአይሁዳዊያንን ጥቃት መቋቋም አይችልም" ወይም "ማንም በስኬት ከአይሁዶች ጋር መዋጋት አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት- የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱን መፍራት በሁሉም ላይ ህዝቦች ላይ ወደቀ
ፍርሃት በሰዎች ላይ ወደቀ የሚለው የሚወክለው ሰዎች እጅግ ፈሩ የሚለውን ነው። "ሁሉም ህዝብ አይሁዶችን እጅግ ፈራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 9:3

የአውራጃ ገዢዎች
"የአውራጃዎች ገዢዎች"

መርዶክዮስን መፍራት በእነርሱ ላይ ወደቀ
ፍርሃት በሰዎች ላይ ወደቀ የሚለው የሚገልጸው ሰዎች እጅግ ፈሩ የሚለውን ነው። "መርዶክዮስን ፈርተው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በንጉሡ ቤት ታላቅ ሰው ነበር
"በንጉሡ ቤተ መንግስት እጅግ ጠቃሚ ሰው ነበር"

ዝናው በሁሉም አውራጃዎች ተሰራጨ
በየስፍራው ዝናው ተሰራጨ የሚለው የሚገጸው፣ በእነዚያ ስፍራዎች የሚገኙ ሰዎች ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ አወቁ የሚለውን ነው። "በየአውራጃዎቹ ሰዎች እርሱ ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ አወቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 9:6

ምሽጎች
ምሽግ የቤተመንግሥት ግንብን፣ ጠንካራ ይዞታን ወይም የተመሸገ ከተማን ያመለክታል። በአስቴር 1:2 ይህንን እንዴት እንደተረጎሙት ተመልሰው ይመልከቱ።

ሱሳ
ይህ ከተማ የፋርስ ነገሥታት መናገሻ ከተማ ነበር። በአስቴር1:2 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አምስት መቶ ወንዶች
"500 ወንዶች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ፓርሻንዳታ፣ ደልፎን፣ አስፓታ፣ ፓራታ፣ አዳልያ፣ አረዳታ፣ፓርማታ፣ አሪሳይ፣ አሪዳይ፣ ዋይዛታ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አስር ወንድ ልጆች
"10 ወንድ ልጆች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሐማ
ይህ የንጉሡ ባለሟል የሆነው የሐማ ስም እና ለ እርሱ ገለጻ ነው። ይህንን በአስቴር 3:1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሐመዳቱ
የዚህን ሰው ስም በአስቴር 3:1 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የአይሁዶች ጠላት
ይህ ሀረግ ስለ ሐማ ይነግረናል

Esther 9:11

አምስት መቶ ወንዶች
"500 ወንዶች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ፓርሻንዳታ፣ ደልፎን፣ አስፓታ፣ ፓራታ፣ አዳልያ፣ አረዳታ፣ፓርማታ፣ አሪሳይ፣ አሪዳይ፣ ዋይዛታ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አስር ወንድ ልጆች
"10 ወንድ ልጆች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያ እነርሱ በተቀረው በንጉሡ አውራጃዎች ምን አደረጉ?
ንጉሡ ይህንን ጥያቄ ያነሳው አይሁድ በሌሎች አውራጃዎችም የሚገኙ ጠላቶቻቸውን መግደል እንደለባቸው ማመኑን ለማሳየት ነው። "በሌሎቹ በንጉሡ ግዛቶች ማድረግ ያለባቸው" ወይም "በተቀሩትም የንጉሡ ግዛቶች ተጨማሪ ብዙ ጠላቶቻቸውን እንዲገድሉ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሬቶሪካል/ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

አቤቱታሽ/ልመናሽ ምንድን ነው?
"አቤቱታ/ልመና" የሚለው ረቂቅ ስም "ጠየቀ" ወይም "ለመነ" በሚል ግስ ሊገለጽ ይችላል። "የምትለምኚው ምንድን ነው?" ወይም "ምን ትፈልጊያለሽ?" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ይሰጥሻል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የምትለምኚውን እኔ እሰጥሻለሁ" ወይም "የምጠይቂውን እኔ ለአንቺ አደርገዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የምትጠይቂው ምንድን ነው?
"ጥያቄ" የሚለው ረቂቅ ስም "ጠየቀ" ወይም "ፈለገ" በሚል ግስ ሊገለጽ ይችላል። " ምን ትጠይቂያለሽ?" ወይም "ምን ትፈልጊያለሽ?" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 9:13

የዚህ ቀን አዋጅ ነገም ጭምር እንዲቀጥል
"እንዲቀጥል" የዚህ ፈሊጥ ትረጉም አስቀድሞ የተፈቀደ ወይም የታቀደ ነገርን ማድረግ የሚል ነው። "የዛሬም አዋጅ ነገም ደግሞ እንዲቀጥል" ወይም "ዛሬ እንዲፈጽሙት ታውጆ የነበረውን ነገም ደግሞ እንዲያደርጉት። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አስር ወንድ ልጆች
"10 ወንድ ልጆች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው መስቀያ እንጨት
ይህ ሰዎችን ለመስቀል ያገለግል የነበረ አሰራር ሲሆን፣ የገመዱ አንዱ ጫፍ በመስቀያው እንጨት ላይ ሲታሰር ሌላኛው የገመዱ ጫፍ በሚሰቀሉት ሰዎች አንገት ዙሪያ በማድረግ ይንጠለጠላሉ። በአስቴር 2:23 ይህንን እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። "ሰዎችን ለመስቀል የሚዋቀር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የማይታወቁትን መተረጎም የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 9:15

በአዳር ወር በአስራ አራተኛው ቀን
በአስቴር 3፡13 ተመሳሳዩን ሀረግ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

በምርኮው ላይ እጃቸውን አልጫኑም
በነገሮች ላይ እጆቻቸውን መጫን የሚለው የሚያመለክተው ነገሮቹን መውሰድን ነው። "ከምርኮው አንዳች አልወሰዱም" ወይም "ከምርኮው አንዳች እንኳን አልወሰዱም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት- የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባ አምስት ሺህ
"75፣000" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

እጆቻቸውን በገደሏቸው ሰዎች ንብረት ላይ አልጫኑም
በነገሮች ላይ እጆቻቸውን መጫን የሚለው የሚገልጸው ነገሮቹን መውሰድን ነው። " ከገደሏቸው ሰዎች አንዳች ንብረት አልወሰዱም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት- የሚለውን ይመልከቱ)

ዋጋ ያላቸው
"ዋጋ ያላቸው ነገሮች" ወይም "ንብረቶች"

Esther 9:17

በአዳር ወር በአስራ ሶስተኛው ቀን
በአስቴር 3፡13 ተመሳሳዩን ሀረግ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

በአስራ አራተኛው ቀን አረፉ
"በአዳር ወር በአስራ አራተኛው ቀን በየአውራጃዎቹ የሚኖሩ አይሁዶች አረፉ

በሱሳ የሚኖሩ አይሁዶች ተሰበሰቡ
የተሰበሰቡበት ምክንያት በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። " በሱሳ የሚኖሩ አይሁዶች ከጠላቶቻቸው ጋር ለመውጋት በአንድነት ተሰበሰቡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆና ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 9:20

በየአመቱ የአዳርን ወር አስራ ሁለተኛ እና አስራ ሶስተኛ ቀን ለመጠበቅ
ቀንን መጠበቅ የሚለው ፈሊጣው አነጋገር ቀኑን ማክበር ማለት ነው። "በየአመቱ የአዳርን ወር አስራ አራተኛ እና አስራ አምስተኛ ቀን ለማክበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሀዘናች ወደ ደስታ ዞረ
ዞረ የሚለው መለወጥን ያመለክታል። ሀዘን እና ደስታ የሚሉት ረቂቅ ስሞች "መከፋት" እና "በደስታ መሞላት" በሚል ሊገለጹ ይችላሉ። " እጅግ ሀዘንተኛ ከመሆን ወደ ደስተኛነት ተለወጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 9:23

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ ምንባብ ለፉሪም በዓል መከበር ምክንያት የሆነውን ጉዳይ ለማብራራት የአስቴርን አመዛኙን ታሪክ በአጭሩ ያቀርባል።

የአጋጋዊው የሐመዳቱ ልጅ ሐማ
ይህ ከንጉሡ ሹማምንት አንዱ የሆነው የሐማ ስም እና ገለጻ ነው። ይህን በአስቴር 3፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ፉር አወጣ/ጣለ (ይህ ማለት፣ ዕጣ አወጣ ማለት ነው)
"ፉር" በፋርስ ቋንቋ "ዕጣ" የሚል ቃል ነው። "ጣለ/አወጣ" የሚለው ሀረግ "ፉር ጣለ/አወጣ" የሚለው ምን ማለት እንደሆነ ያብራራል።

ፉር አወጣ/ጣለ (ይህ ማለት፣ ዕጣ አወጣ ማለት ነው)
ለምን ፉር፣ ወይም ዕጣ ጣለ የሚለው በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "አይሁድን ለማጥቃት የተሻለው ቀን የትኛው እንደሆነ ለማወቅ እጣ ጣለ (ዕጣ አወጣ)" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆና ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን ጉዳዩ ወደ ንጉሡ ፊት ስትቀርብ
የዕብራይስጡ ጽሁፍ "አስቴር ግን ንጉሡ ፊት ስትቀርብ" ተብሎም ሊተረጎም ይችላል። አንዳድ ዘመናዊ ቅጂዎች ይህንን ትረጉም ይመርጡታል።

ሐማ በአይሁዳች ላይ ያወጣው ክፉ እቅድ በገዛ ራሱ ላይ ተመለሰበት
"በራሱ አናት ላይ ተመለሰ" ማለት በሐማ ላይ ይፈጸም ማለት ነው። "ሐማ በአይሁድ ላይ ያዘጋጀው ክፉ እቅድ በራሱ ላይ መፈጸም አለበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 9:26

እነዚህን ቀናት፣ ፉር ከሚለው ስም በመነሳት ፉሪም ብለው ጠሯቸው
አንድን ነገር ከሌላ አንድ ለነገር በመነሳት መሰየም ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ ያም ማለት አንድ አይነት ስም መስጠት ወይም ተመሳሳይ ስም መስጠት ነው። "እነዚህን ቀናት፣ ፉር ከሚለው ቃል በመነሳት ፉሪም ብለው ጠሯቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ፉሪም
ይህ የአይሁድ ህዝብ በጥንቱ ፋርስ በሐማ ሴራ በአንዲት ቀን ውስጥ ከመደምሰስ እና ከእልቂት የተረፈበት መታሰቢያ በዓል ስያሜ ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የፉር ስያሜ
"ፉር" ማለት ምን ማለት እንደሆነ በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "ፉር የሚለው ቃል፣ 'ዕጣ' ማለት ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆና ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ ቀናት ሊከበሩ እና ሊተሰቡ ይገባል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አይሁዳች እነዚህን ቀናት ያከብራሉ ያስቧቸዋልም" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በታማኝነት ከማክበር በፍጹም አያቋርጡም
ይህ በአዎንታዊ ሊጻፍ ይችላል። "ሁሌም በታማኝነት ያከብሩታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

Esther 9:29

ይህንን ሁለተኛውን ደብዳቤ .... የአቢካኢል ሴት ልጅ ንግሥት አስቴር እና አይሁዳዊው መርዶክዮስ ጻፉ
አስቴር የአቢካኢል ሴት ልጅ ናት። አስቴር እና መርዶክዮስ ደብደቤውን ጻፉ።

አቢካኢል
የአስቴር አባት እና የመርዶክዮስ አጎት። ይህንን በአስቴር 2፡15 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሁለተኛ ደብዳቤ
"ተጨማሪ ደብዳቤ" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 9:30

ደብዳቤዎች ወደ ሁሉም አይሁዶች ተላኩ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ወደ ሁሉም አይሁዳዊያን ደብዳቤዎች ላኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

127 አውራጃዎች
"አንድ መቶ ሃያ ሰባት አውራጃዎች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ) ለአይሁድ ደህንነት እና እውነት መመኘት ረቂቅ ስሞች የሆኑት "ደህንነት" እና "እውነት በሀረግ ሊገለጽ ይችላል። "አይሁድ ሰላም እንዲሆኑ እና ሌላው ህዝብ ለአይሁድ ታማኝ እንዲሆን መመኘት" (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

አይሁዳዊያን ይህንን ግዴታ ለራሳቸው እና ለትውልዳቸው ተቀበሉ
ግዴታን መቀበል ከተሰጡትን ግዴታዎች ጋር መስማማትን ለመግለጽ የሚውል ፈሊጥ ነው። "ግዴታ የሚለው ረቂቅ ስም "ታዘዘ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "አይሁዶች ተስማምተው እነርሱ እና የእነርሱ ትውልዶች የፉሪምን ቀናት ለማክበር ግዴታ እንዳለባቸው ተነገሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የጾም እና የሰቆቃ ጊዜያነትን ተቀበሉ
የጾም እና የሰቆቃ ጊዜያነትን መቀበል የሚለው ለተወሰነ ጊዜ ለመጾም እና ለማልቀስ መስማማትን የሚገልጽ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "ለተወሰነ ጊዜ ለመጾም እና በለቅሶ ለመጸለይ ተስማሙ" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 10

1 ከዚያም ንጉሥ አርጤክስስ እስከ ባህር ጠረፍ ባለው ሀገር ላይ ግብር ጣለ። **2** የኃይሉና የብርታቱ ሥራ ሁሉ፥ ንጉሡ ከፍ ከፍ ካደረገው ከመርዶክዮስ የታላቅነቱ ሙሉ ታሪክ ጋር በፋርስና በሜዶን ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ላይ ተጽፏል። **3** አይሁዳዊው መርዶክዮስ ከንጉሥ አርጤክስስ ቀጥሎ በማዕረግ ሁለተኛ ነበር። የሕዝቡን ደኅንነት የፈለገና ስለ ሕዝቡም ሁሉ ሰላም የተናገረ፥ በብዙ አይሁድ ወንድሞቹም የታወቀና በአይሁድ መካከል ታላቅ የሆነ ሰው ነበር።

Esther 10:1

እስከ ባህር ዳርቻ በሚዘልቀው ግዛቱ ግብር ጣለ
ግብር መጣል ማለት ህዝቡ ግብር እንዲከፍል ማድረግ ማለት ነው። ምድሩ እና የባህር ዳርቻ የሚለው የሚገልጸው በዚያ የሚኖረውን ህዝብ ነው። "በምድሩ እና በባህር ዳርቻ የሚኖረው ህዝብ ግብር እንዲከፍል አደረገ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት- የሚለውን ይመልከቱ)

የሃይሉ እና የብርታቱ ስኬቶች ሁሉ
"ስኬቶች" የሚለው ረቂቅ ስም "ተሳከ" በሚል ግስ ወይም "ታላላቅ ነገሮችን ማድረግ" በሚል ሀረግ ሊገለጽ ይችላል። "ሃይል" እና "ብርታት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች በቅጽል ሊገለጹ ይችላሉ። "ያደረገው ሁሉ ታላቅ እና ብርቱ ስለነበረ ነው። ወይም "ያደረጋቸው ታላላቅ ነገሮች ሁሉ ከሀይሉና ከታላቅነቱ የተነሳ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሡ ከፍ ከፍ ያደረው የመርደክዮስ ታላቅነት ሙሉ ታሪክ
የንጉሡ መርዶክዮስን ማክበር የተገለጸው ንጉሡ በአካል ያነሳው ያህል ተደርጎ ነው። "ንጉሡ እንዴት መርዶክዮስ ታላቅ መሆኑ እንዲታወቅ እንዳደረገ ያለው ሙሉ ታሪክ" ወይም "መርዶክዮስ ላደረጋቸው ነገሮች ንጉሡ እንዴት እንዳከበረው ሙሉው ታሪክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 10:3

ከንጉሡ ከጠረክሲስ ቀጥሎ በደረጃ ሁለተኛ
"ከንጉሥ ጠረክሲስ ቀጥሎ እጅግ ጠቃሚው ሰው"

አይሁዳዊ ወንድሞች
ወንድሞች የሚለው ቃል እንደ እርሱ ያሉ ሰዎችን ይወክላል። "አይሁዳዊ ወገኖች" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የህዝቡን ደህንነት ፈለገ
አንድን ነገር መፈለግ ለአንድ ነገር በጥንካሬ መስራትን የሚገልጽ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ደህንነት" የሚለው ረቂቅ ስም "በለጸገ" በሚለው ግስ ወይም "ደህንተነት" በሚል ቅጽል ሊተረጎም "ህዝቡ ይበለጽግ ዘንድ በጥንካሬ ሰራ" ወይም "የህዝቡ ደህንነት ይጠበቅ ዘንድ በጥንካሬ ሰራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

ለመላው ህዝቡ ሰላም ተናገረ
" ሰላም ይኖራቸው ዘንድ፣ እርሱ ህዝቡን ይወክላል

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Job

Job

Chapter 1

1 ፆጽ በሚባል ምድር ኢዮብ የሚባል አንድ ሰው ነበረ፤ ኢዮብም በደል የማይገኝበት፤ ትክክለኛ፤ እግዚአብሄርን የሚፈራና ከክፋት የራቀ ሰው ነበረ። **2** ለእርሱም ሰባት ወንዶችና ሶስት ሴቶች ልጆች ተወልደውለት ነበር። **3** ሰባት ሺህ በጎች፤ ሶስት ሺህ ግመሎች፤ አምስት ሺህ ጥንድ በሬዎችና አምስት ሺህ አህዮች እንዲሁም እጅግ ብዙ ሰራተኞች ነበሩት። ይህም ሰው በምስራቅ ካሉ ሰዎች ሁሉ ይልቅ ታላቅ ሰው ነበር። **4** ወንዶች ልጆቹም በየተመደበላቸው ተራ በያንዳንዳቸው ቤት ግብዣ ያደርጉ ነበር፤ ሦስቱ እኅቶቻቸውም ከእነርሱ ጋር እንዲበሉና እንዲጠጡ ልከው ይጠሩአቸው ነበር። **5** የግብዣቸውም ቀናቶች ሲያበቁ ኢዮብ፦ ያስጠራቸውና ለእግዚአብሔር መልሶ ይቀድሳቸው ነበር።ማልዶ በጠዋት ተነስቶ “ምናልባት ልጆቼ በድለው፥ እግዚአብሔርንም በልባቸው ረግመው ይሆናል” ብሎ ፤ ለልጆቹ ለእያንዳንዳቸው የሚቃጠል መሥዋዕት ያቀርባል። ይህንንም ኢዮብ ሁልጊዜ ያደርግ ነበር። **6** በኋላም የእግዚአብሔር ልጆች በያህዌ ፊት ራሳቸውን የሚያቀርቡበት ቀን ነበረ ፥ ሰይጣንም ደግሞ ከእነርሱ ጋር መጣ። **7** እግዚአብሔርም ሰይጣንን፦“ ከወዴት እየመጣህ ነው?” አለው። ሰይጣንም ለእግዚአብሔር ሲመልስ፦ “ምድርን ሁሉ ዞርሁ፥ በእርስዋም ላይ ወዲህና ወዲያ ተመላልሼ መጣሁ” አለ። **8** እግዚአብሔርም ሰይጣንን፦”በውኑ ባሪያዬን ኢዮብንስ ተመለከትኸውን? በምድር ላይ እንደ እርሱ ያለ በደል የማይገኝበት ትክክለኛ ሰው ፥ እግዚአብሔርንም የሚፈራ፥ ከክፋትም የራቀ ሰው የለም“ አለው። **9** ሰይጣንም ለእግዚአብሔር ሲመልስ እንዲህ አለ፦ “ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚፈራው እንዲሁ ነውን? **10** በእርሱና በቤቱ ባለውም ነገር ሁሉ ዙሪያ በየአቅጣጫው አጥር አላደረግህለትምን? የእጁን ሥራ ባርከህለታል፥ ሐብቱም በምድር ላይ በዝቶአል። **11** ነገር ግን አሁን እጅህን ዘርግተህ ያለውን ሀብት ሁሉ አውድም ፤ ፊትለፊት ይክድሃል።” **12** እግዚአብሔርም ሰይጣንን፦ “እነሆ እርሱ ያለው ነገር ሁሉ በስልጣንህ ስር ነው፥ በእርሱ ላይ ግን ጉዳት እንዳታደርስ” አለው። ሰይጣንም ከእግዚአብሔር ፊት ወጥቶ ሄደ። **13** ወንዶችና ሴቶች ልጆቹ በታላቅ ወንድማቸው ቤት በሚበሉበትና የወይን ጠጅ በሚጠጡበት ቀን እንዲህ ሆነ፤ **14** መልክተኛ ወደ ኢዮብ መጥቶ፦”በሬዎች እርሻ እያረሱ፥ በአጠገባቸውም አህዮች ተሰማርተው ነበር፤ **15** የሳባም ሰዎች አደጋ አድርሰው ወሰዱአቸው፥ ሰራተኞቹንም በሰይፍ ስለት ገደሉ፤ እኔም እንድነግርህ ብቻዬን አመለጥሁ“ አለው። **16** እርሱም ገና እየተናገረ ሳለ ሌላ መጥቶ፦“ የእግዚአብሔር እሳት ከሰማይ ወደቀ፥ በጎቹንና ጠባቂዎችን አቃጥሎ በላቸው፤ እኔም እንድነግርህ ብቻዬን አመለጥሁ“ አለው። **17** እርሱም ገና እየተናገረ ሳለ ሌላ መጥቶ፦”ከለዳውያን በሦስት ቡድን ተከፍለው በግመሎች ላይ አደጋ ጥለው ወሰዱአቸው ፥ ሰራተኞቹንም በሰይፍ ስለት ገደሉ፤ እኔም እንድነግርህ ብቻዬን አመለጥሁ“ አለው። **18** እርሱም ገና እየተናገረ ሳለ ሌላ መጥቶ፦ ወንዶችና ሴቶች ልጆችህ በታላቅ ወንድማቸው ቤት እየበሉና የወይን ጠጅ እየጠጡ ነበር፤ **19** ታላቅ ነፋስ ከምድረ በዳ መጥቶ የቤቱን አራቱን ማዕዘን መታውና በልጆቹ ላይ ወደቀ፥ እነርሱም ሞቱ፤ እኔም እንድነግርህ ብቻዬን አመለጥሁ“ አለው። **20** ኢዮብም ተነሣ ልብሱንም ቀደደ፥ ራሱንም ተላጨ፥ በምድርም ላይ በፊቱ ተደፍቶ እግዚአብሔርን አመለከ፤ **21** እንዲህም አለ፦”ከእናቴ ማኅፀን ራቁቴን ወጥቻለሁ፥ ራቁቴንም ወደዚያ እመለሳለሁ፤ እግዚአብሔር ሰጠ፥ እግዚአብሔርም ወሰደ፤ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን።“ **22** በእነዚህ ነገሮች ሁሉ ኢዮብ ሐጢያት አላደረገም፥ በስንፍናም እግዚአብሔርን አልከሰሰም።

Job 1:1

በፆጽ ምድር
ይህ ስፍራ ሊገኝ የሚችለው 1) በአሁኗ ዮርዳኖስ፣ ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምስራቅ ጥንት ኤዶም በምትባል ስፍራ ወይም 2) በአሁኗ ኢራን ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተ ምስራቅ ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ነቀፋ የሌለበት እና ትክክለኛ
"ነቀፋ የሌለበት" እና "ትክክለኛ" የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ ደግሞም ቃላቱ ኢዮብ ጻድቅ ሰው መሆኑን ትኩረት ይሰጣሉ። "በእግዚአንሔር ፊት ትክክል የሆነውን የሚያደርግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን የሚፈራ
"እግዚአብሔርን የሚያከብር"

ከክፉ የራቀ
እዚህ ስፍራ ክፉ የተገለጸው ሰው ወደዚያ ስፍራ ሄዶ ክፉ ከማድረግ ይልቅ ወደዚያ ከመሄድ ራሱን እንደሚያቅብበት ስፍራ ተደርጎ ነው። "ክፉ ማድረግን አሻፈረኝ ማለት/ከክፋት የራቀ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባት ወንዶች ልጆች እና ሶስት ሴቶች ልጆች
"7 ወንዶች ልጆች እና 3 ሴቶች ልጆች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባት ሺህ በጎች ነበሩት
"7,000 በጎች ነበሩት" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሶስት ሺህ ግመሎች
"3,000 ግመሎች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

አምስት መቶ ጥማድ/ጥንድ በሬዎች
"500 ጥማድ/ጥንድ በሬዎች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

እጅግ ታላቅ
"ከሁሉም ባለጸጋ"

በምስራቅ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ
ከከነዓን በስተ ምስራቅ የሚገኝን ስፍራ ያመለክታል። "ከከነዓን በስተ ምስራቅ በሚገኝ ምድር የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ" (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 1:4

በእያንዳንዱ ልጅ ተራ፣ እርሱ ያቀርብ ነበር
"ቀን" የሚለው ቃል ምናልባት የአንዱን ልጅ ልደት የሚያከብሩበት ቀን ማለት ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ቢያንስ ልጆቹ በየተራ ድግስ እንደሚያደርጉ ያመለክታል። "በእያንዳንዱ ልጅ የልደት ቀን፣ ልጁ ያቀርብ ነበር" ወይም "እያንዳንዱ ልጅ በተራው ያቀርብ ነበር"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እርሱ ያቀርብ ነበር... እነርሱ ልከው... ይጠሩ ነበር... ኢዮብ ይልክ ነበር... እርሱ ይሳል ነበር... በጥዋት ማልዶ ተነስቶ መስዋዕት ያቀርብ ነበር... እንዲህ ይል ነበር
"ሁሌም ያቀርብ ነበር...እነርሱ ሁሌም... ልከው ይጠሩ ነበር... ኢዮብ ሁሌም ይልክ... ሁሌም ይሳል... እርሱ ሁሌም ማልዶ ይነሳ እና ይሰዋ... እርሱ ሁሌም እንዲህ ይል ነበር"

ከእነርሱ ጋር
"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰባቱን ወንዶች ልጆች እና ሶስቱን ሴት ልጆች ሲሆን ኢዮብን ግን አይጨምርም።

የድግሱ ዕለት ሲያልፍ
"ድግሱ ሲጠናቀቅ" ወይም "ከድግሱ በኋላ"

ኢዮብ ወደ እነርሱ ይልክና
"ኢዮብ ዘወትር እነርሱ ወደ እርሱ እንዲመጡ አንድ ሰው ይልክ ነበር"

እነርሱን ያነጻ ነበር
እዚህ ስፍራ "ማንጻት" ማለት የኢዮብ ልጆች በደስታ በአንድነት ተሰብስበው ግብዣ ሲያደርጉ የፈጸሙት የምልኮ ነቀፊታ ቢኖር ጥፋት እንዳይደርስባቸው እግዚአብሔርን ይቅርታ መለመን ማለት ነው። ኢዮብ ስለ እነርሱ መስዋዕት በማቅረብ ይህን ያደርግ ነበር።

በልባቸው እግዚአብሔርን ረግመው ቢሆን
"በልባቸው" የሚለው የሚወክለው ሃሳባቸውን ነው። ብዙውን ጊዜ እንዲህ ያሉ ሃሳቦች አንድ ሰው ነገሩን ሊያስበው ሳይፈልግ ከፈቃዱ ውጭ ሊመጡ ይችላሉ። "በሃሳባቸው እግዚአብሔርን ረግመው ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 1:6

ከዚያም ... የሚደረግበት ቀን ነበር
"በ...በሚሆንበት ጊዜ" ወይም "አንድ ዕለት... በ...ጊዜ።" ይህ በአንድ የተለየ ቀን ብቻ የተደረገ አይደለም፣ ይልቁንም ስብሰባው ብዙውን ጊዜ እንደሚደረግ ግልጽ ነው።

የእግዚአብሔር ልጆች
ይህ ሰማያዊ ፍጥረታትን፣ መላዕክትን ያመለክታል።

ራሳቸውን በያህዌ ፊት ለማቅረብ
"ያደርጉት ዘንድ እርሱ እንዳዘዛቸው በያህዌ ፊት በአንድነት ለመቆም"

ያህዌ
ይህ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ራሱን ለህዝቡ የገለጸበት ስም ነው። ስለ ያህዌ ይህ እንዴት እንደሚተረጎም የቃል ትርጉም ገጽን ይመልከቱ።

በምድር ከመዞር፣ በላይዋ ከመመላለስ
"መዞር" እና "መመላለስ" የሚሉት ሀረጋት በምድር ሁሉ የመጓዝን ድርጊት በሙላት ለማጉላት የዋለ ነው። "በምድር ላይ በሁሉም ስፍራ መዞር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ጽንፍ የሚሉትን ይመልከቱ)

ባሪያዬን ኢዮብን አይተኸዋልን?
"ስለ ባሪያዬ ኢዮብ አውቀሃልን?" እዚህ ስፍራ እግዚአብሔር ስለ ኢዮብ ከሰይጣን ጋር መነጋገር ይጀምራል። "ባሪያዬን ኢዮብን አይተኸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ነቀፋ የሌለበት እና ቅን ሰው
"ነቀፋ የሌለበት" እና "ቅን" የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉሞችን ሲይዙ ኢዮብ ጻድቅ ሰው መሆኑን አጉልተው ያሳያሉ። ይህ በኢዮብ 1:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "በእግዚአብሔር ፊት መልካም የሆነውን የሚያደርግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን የሚፈራ
"እግዚአብሔርን የሚያከብር።" ይህ በኢዮብ 1:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

Job 1:9

ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚፈራው ያለ ምክንያት ነውን?
"ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚያከብረው ያለ ምክንያት ነውን?" ሰይጣን ለእግዚአብሔር ጥያቄ አቅርቦ ራሱ መልስ ይሰጣል። ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚታዘዘው እግዚአብሔር ስለባረከው ብቻ ነው ይላል። "ኢዮብ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ምክንያት አለው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በዙሪያው፣ በቤቱ ዙሪያ እና ባለው ነገር ሁሉ ዙሪያ ቅጥር አላኖርክለትምን?
ሰይጣን ክርክሩን ለማጠናከር የሚረዱትን መረጃዎች ሁሉ ይናገራል። "አንተ እርሱን፣ ቤተሰቡን እና ያለውን ነገር ሁሉ ጠብቀሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በዙሪያው፣ በቤቱ ዙሪያ እና ባለው ነገር ሁሉ ዙሪያ ቅጥር አድርገህለታል
እንደ ግርግዳ ወይም አጥር ያለ መከላከያ የአንድን ሰው ይዞታ ዙሪያውን እንደሚከብ እና እንደሚጠብቅ፣ እግዚአብሔር ኢዮብን በጥበቃው ከቦታል። "እርሱን እና ቤቱን እንዲሁም የእርሱ የሆነውን ሁሉ ጠብቀሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእጆቹን ስራዎች
"የሚሰራውን ነገር ሁሉ"

በምድር ላይ ከብቱ በዝቶለታል
"በምድር ላይ ከብቱ ተትረፍርፏል"

ነገር ግን አሁን እጅህን ዘርግተህ ያለውን ሁሉ ንካበት፣ በዚያን ጊዜ ፊት ለፊት እንደማይረግምህ ታያለህ
ሰይጣን ይህንን ማለቱ እግዚአብሔር ኢዮብን ቢነካው፣ የኢዮብ ምላሽ ምን እንደሚሆን ይመለከታል ማለቱ ነው። "ነገር ግን አሁን፣ እጅህን ብትዘረጋ እና ያለውን ሁሉ ብትነካ ፊት ለፊት እንደሚረግምህ ታያለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ነገር ግን አሁን፣ እጅህን ዘረጋ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚወክለው የእግዚአብሔርን የማድረግ አቅም ነው። "ነገር ግን አሁን ሀይልህን ተጠቀም" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ያለውን ሁሉ ንካ
እዚህ ስፍራ "መንካት" የሚወክለው ጉዳት የማድረስ ወይም የማጥፋት ድርጊትን ነው። "ያለውን ሁሉ አጥፋ" ወይም "ያለውን ሁሉ ደምስስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በፊትህ
"እየሰማኸው።" ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ትኩረት የሚሰጥበትን ጊዜ ነው።

እነሆ
"እነሆ" ወይም "የምናገረውን ትኩረት ሰጥተህ ብትሰማኝ"

እርሱ ያለው ሁሉ በእጅህ ነው
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚወክለው አንድ ሰው አንድን ነገር ለመቆጣጠር ያለውን አቅም/ሀይል ነው። "እርሱ ባለው ነገር ላይ ሁሉ አቅም ተሰጥቶሃል" በሚለው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ በራሱ ላይ
"በህይወቱ ላይ"

ያህዌ ከሚገኝበት ወጥቶ ሄደ
"ከያህዌ ፊት ወጥቶ ሄደ" ወይም "ያህዌ ካለበት ለቆ ሄደ"

Job 1:13

ሳባውያን
ይህ በዛሬ ዘመን በየመን አካባቢ የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታል። እዚህ ስፍራ ይህ የሚወክለው የፈረሰኞችን ቡድን ወይም ሽፍቶችን ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

በእነርሱ ላይ ወደቁባቸው
እዚህ ስፍራ "መውደቅ" የሚለው የሚገልጸው ማጥቃትን ነው። "እነርሱን አጠቋቸው/አደጋ ጣሉባቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መቷቸው
እዚህ ስፍራ ማጥቃት የሚለው የሚገልጸው መግደልን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የሰይፍ ስለት
እዚህ ስፍራ "የሰይፍ ስለት" የሚለው የሚወክለው ሰው ለመግደያነት የሚውለውን የሰይፉን ክፍል ነው፤ ይህም ማለት አንድም የሰይፉን ጫፍ ወይም የተሳለውን ጠርዝ ማለት ነው። እንደዚሁም ደግሞ፣ የሳባውያን ሰይፎች ሁሉ እንደ አንድ ሰይፍ ብቻ ተደርጎ ተገጽዋል። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና የስማዊ ሀረጋት ክፍል የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 1:16

እርሱ ገና እየተናገረ ሳለ
"እርሱ" የሚለው የሚያመለክተው የመጀመሪያውን መልዕክተኛ ነው።

ሌላው ደግሞ መጣ
ይህ የሚያመለክተው ሌላውን መልዕክተኛ ነው። "ሌላው መልዕክተኛ ደግሞ መጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ብቻዬን አመልሁ፤ ልነግረህም መጣሁ
ይህ በኢዮብ 1:15 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

አገልጋዮችህንም በሰይፍ ስለት መቷቸው። እኔ ብቻ ልነግርህ አመለጥሁ
እዚህ ስፍራ "የሰይፍ ስለት" የሚለው የሚወክለው ሰው ለመግደያነት የሚውለውን የሰይፉን ክፍል ነው፤ ይህም ማለት አንድም የሰይፉን ጫፍ ወይም የተሳለውን ጠርዝ ማለት ነው። እንደዚሁም ደግሞ፣ የከለዳውያን ሰይፎች ሁሉ እንደ አንድ ሰይፍ ብቻ ተደርጎ ተገጽዋል። ይህ በኢዮብ 1:15 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና የስማዊ ሀረጋት ክፍል የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 1:18

ወንዶች እና ሴቶች ልጆችህ በታላቅ ወንድማቸው ቤት ይበሉና ወይን ይጠጡ ነበር
ይህ በኢዮብ 1:13 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

አውሎ ነፋስ
"አውራቂስ/ቶርኔዶ" ወይም "የበረሃ ማዕበል"

የቤቱ አራት ማዕዘኖች
"ቤቱን ያቆመው መዋቅር/ቤቱ የተዋቀረበት ድጋፍ"

በወጣቶቹ ላይ ወደቀ
"ቤቱ በወንዶች እና ሴቶች ልጆችህ ላይ ወደቀ"

እኔ ብቻዬን አመልሁ፤ ልነግረህም መጣሁ
ይህ በኢዮብ 1:15 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

Job 1:20

ልብሱን ቀደደ፣ ራሱን ተላጨ
እነዚህ ሀዘንን የመግለጫ ስርዓቶች ነበሩ፤ ጥልቅ ሀዘንን መድረሱን ያመለክታሉ። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊቶች የሚለውን ይመልከቱ)

ከእኔቴ ማህጸን ስወጣ እርቃኔን ነበር፣ ደግሞም እርቃኔን እመለሳለሁ
"ስወለድ፣ ወደዚህ ዓለም አንዳች ይዤ አልመጣሁም፤ ስሞትም ምንም ሳልይዝ ወደ ምድር እመለሳሉ"

በዚህ ሁሉ ነገር
"በሆነው ነገር ሁሉ"

እግዚአብሔርን አጥፍተሃል ብለህ ክሰስ
"እግዚአብሔርን ተሳስተሃል በለው"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 በድጋሚ የእግዚአብሔር ልጆች በያህዌ ፊት ራሳቸውን በሚያቀርቡበት ቀን ፥ ሰይጣንም ደግሞ አብሮ መጣ። **2** እግዚአብሔርም ሰይጣንን፦“ ከወዴት እየመጣህ ነው?” አለው። ሰይጣንም ለእግዚአብሔር ሲመልስ፦ “ምድርን ሁሉ ዞርሁ፥ በእርስዋም ላይ ወዲህና ወዲያ ተመላልሼ መጣሁ” ብሎ አለ። **3** እግዚአብሔርም ሰይጣንን፦”በውኑ ባሪያዬን ኢዮብንስ ተመለከትኸውን? በምድር ላይ እንደ እርሱ ያለ በደል የማይገኝበት ትክክለኛ፥ እግዚአብሔርንም የሚፈራ፥ ከክፋትም የራቀ ሰው የለም። ምንም እንኳ ያለምክንያት በእርሱ ላይ በከንቱም ጥፋት እንዲመጣበት ግፊት ብታደርግብኝም ፥ እርሱ ግን እስከ አሁን በታማኝነቱ ጸንቷል“ አለው። **4** ሰይጣንም መልሶ እግዚአብሔርን፦ “ቆዳ በርግጥ ስለ ቆዳ ነው፤ ሰው ያለውን ነገር ሁሉ ሕይወቱን ለማዳን ሲል ይሰጣል” አለው። **5** ነገር ግን አሁን እጅህን ዘርግተህ አጥንቱንና ሰውነቱ ላይ ጉዳት ብታደርስ ፊተ ለፊት ይክድሃል” አለው። **6** እግዚአብሔርም ሰይጣንን፦” ሕይወቱን ብቻ ተው፤ እነሆ፥ እርሱ በእጅህ ነው“ አለው። **7** እናም ሰይጣን ከእግዚአብሔር ፊት ወጥቶ ሄደ። ኢዮብንም ከውስጥ እግሩ እስከ ራስ ጸጉሩ ድረስ በሚያሰቃይ ቍስል መታው። **8** ኢዮብም ሰውነቱን ለመፋቅ የሸክላ ስባሪ ወሰዶ በአመድ ላይ ተቀመጠ። **9** በኋላም ሚስቱ ፦”እስከ አሁን በታማኝነት ጸንተሃል እንዴ? እግዚአብሔርን እርገምና ሙት“ አለችው። **10** እርሱ ግን መልሶ”አንቺ እንደ ሰነፍ ሴቶች ተናገርሽ፤ ከእግዚአብሔር እጅ መልካሙን ብቻ እንጂ ክፉን አንቀበልም ብለሽ ነው የምታስቢው? “ አላት። በእነዚህ ነገሮች ሁሉ ኢዮብ በአፉ ቃል ሐጢያት አላደረገም። **11** ይህን የደረሰበትን ክፉ ነገር ሁሉ በሰሙ ጊዜ ሦስቱ የኢዮብ ወዳጆች ከየስፍራቸው መጡ፤ እነርሱም ቴማናዊው ኤልፋዝ፥ ሹሐዊው በልዳዶስ፥ ነዕማታዊው ሶፋር ነበሩ። እነርሱም ከኢዮብ ጋረ ሊያለቅሱና ሊያጽናኑት በአንድነት ጊዜ አመቻችተው መጡ። **12** ከሩቅ ዓይናቸውን አማትረው ሲመለከቱ በትክክል ሊለዩት አልቻሉም፤ ድምፃቸውንም ከፍ አድርገው አለቀሱ፤ እያንዳንዳቸውም ልብሳቸውን ቀደዱ፥ አቧራ ወደ ላይ እየበተኑ ራሳቸው ላይ ነሰነሱ። **13** ሰባት ቀንና ሰባት ሌሊት ከእርሱ ጋር መሬት ላይ ተቀመጡ፤ ሕመሙም እጅግ ከባድ እንደነበረ ስላዩ ከእርሱ ጋር አንድ ቃል ለመናገር የደፈረ አልነበረም።

Job 2:1

አጠቃላይ መረጃ:
እነዚህ ሀረጋት በኢዮብ 1፡1-6 ውስጥ ካለው ጋር ፍጹም ተመሳሳይ ናቸው፤ እናም ምናልባትም በተመሳሳይ መንገድ ሊተረጎሙ ይችላሉ።

ከዚያም ዕለቱ ያ ነበር
ይህ በኢዮብ 1፡6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ

አንድ ዕለት
ይህ አንድ ውሱን ቀን አይደለም። መሰባሰቡ ብዙ ጊዜ ይደረጋል። "በ...ጊዜ" ወይም "በ...አንድ ዕለት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

የእግዚአብሔር ልጆች
ይህ በኢዮብ 1፡6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ

ራሳቸውን በያህዌ ፊት አቀረቡ/በእግዚአብሔር ፊት መጡ
ይህ በኢዮብ 1፡6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ

በምድር ላይ ከመዞር፣ በላይዋ ወዲያና ወዲህ ከመመላለስ
ይህ በኢዮብ 1፡7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ

Job 2:3

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ ሀረግ "አንተ ያለ ምክንያት እንዳጠፋው በእርሱ ላይ ብታነሳሳኝም እርሱ ታማኝነቱን እንዳጸና ነው" የሚለው ከመጨመሩ በስተቀር ከኢዮብ 1፡8 ጋር ተመሳሳይ ነው።

አገልጋዬን ኢዮብን ተመለከትከውን?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በእርግጥ ዐረፍተ ነገርን ይመሰርታል። ይህ በኢዮብ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "አገልጋዬን ኢዮብን ተመለከትከው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ነቀፋ የሌለበት እና ቅን ሰው
"ነቀፋ የሌለበት" እና "ቅን" የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉሞችን ሲይዙ ኢዮብ ጻድቅ ሰው መሆኑን አጉልተው ያሳያሉ። ይህ በኢዮብ 1፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "በእግዚአብሔር ፊት መልካም የሆነውን የሚያደርግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን የሚፈራ እና ከክፋት የራቀ
ይህ በኢዮብ 1፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

እስከ አሁን ታማኝነቱን ጠብቋል
"መልካም እና ትክክል የሆነውን ለማድረግ እስከ አሁን ሙሉ ለሙሉ ራሱን ሰጥቷል"

በእርሱ ላይ በክፉ ብትገፋፋኝም
"ያለ ምክንያት እርሱን እንዳጠፋው ብትገፋፋኝም"

እርሱን እንዳጠፋው
እዚህ ስፍራ "ማጥፋት" የሚለው የሚገልጸው "ማደህየት" የሚለውን ነው። "ደሃ ሰው እንዳደርገው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

Job 2:4

በእርግጥ ቆዳ ስለ ቆዳ ነው
እዚህ ስፍራ "ቆዳ" የሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሚገልጸው የኢዮብን ህይወት ነው። "ሰው ህይወቱን ለማዳን ሀብቱን እና የሚወዳቸውን ሰዎች ማጣትን መቀበልን ጨምሮ ማናቸውንም ዐይነት ነገር ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን አሁን እጅህን ዘርግተህ አጥንት እና ስጋውን ብትነካ፣ በፊትህ በእርግጥ የማይራገም ስለመሆኑ እስኪ ተመልከት
ሰይጣን ይህን ማለቱ፣ እግዚአብሔር ኢዮብን ቢጎዳው ኢዮብ እንዴት ምላሽ እንደሚሰጥ ይመለከታል ማለቱ ነው። "ነገር ግን አሁን፣ እጅህን ብትዘረጋ እና አጥንቱን እና ስጋውን ብትነካ በፊትህ እንደሚረግምህ ትመለከታለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እጅህን ዘርጋ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን የማድረግ ሀይል ነው። "ነገር ግን አሁን ሀይልህን ተጠቀም" ይህ በኢዮብ 1፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መንካት
እዚህ ስፍራ "መንካት" የሚያመለክተው መጉዳትን ነው። "አጥቃው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አጥንቱ እና ስጋው
ይህ አገላለጽ የሚወክለው የኦዮብን አካል ነው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በፊትህ ይረግምሃል
ይህ በኢዮብ 1:11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

በፊትህ
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር በትኩረት ነገሩን የሚመለከትበትን ጊዜ ነው። "እየሰማህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 2:7

ከዚያም ሰይጣን ከእግዚአብሔር ፊት ወጥቶ ሄደ
ይህ በኢዮብ 1:12 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

እርሱ ኢዮብን በቁስል መታው
"በከባድ ቁስል አሰቃየው"

የስቃይ ቁስል
ትልቅ፣ የሚያሳክክ እና ስቃይ የሞላበት የቆዳ ቁስል

ገላውን የሚያክበት ገል/የሸክላ ስባሪ
ማከኪያው ስቃዩን ለመቀነስ ቆዳውን የሚያክበት ነው

በአመድ መሃል ተቀመጠ
ይህ ምናልባት አመድና ቆሻሻ ተጥሎ የሚቃጠልበትን ስፍራ ሊያመለክት ይችላል። እንዲህ ባለው ስፍራ መቀመጥ ጥልቅ ሀዘን መድረሱን የሚያመለክት ነበር። "በቆሻሻ ክምር ላይ ተቀመጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት እና ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊቶች የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 2:9

እስከ አሁን ታማኝነትህን ጠብቀሃል?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ ዐረፍተ ነገርን ይገልጻል። "እሰከ አሁን ታማኝነትህን መጠበቅ አልነበረብህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን ተራገም
"እግዚአብሔርን ተው"

አንቺ እንደ ሞኝ ሴት ተናገርሽ
"የማይረቡ ሴቶች እንደሚናገሩት ተናገርሽ"

መልካሙን ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ተቀበልን ክፉውንስ አንቀበልምን?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ ዐረፍተ ነበርን ይገልጻል። "መልካሙን ከእግዚአብሔር እንደተቀበልን ሁሉ ክፉውንም በእርግጥ መቀበል ይገባናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

መልካሙን መቀበል
"መልካም ከሆኑ ነገሮች ሁሉ ተጠቃሚ መሆን"

መልካም የሆነው
ይህ የሚወክለው እግዚአብሔር የሰጠንን መልካም ነገሮች ሁሉ ነው። (የስማዊ ሀረጋት ክፍሎች)

ክፉ የሆነውን መቀበል
"ሳያማርሩ ክፉ የሆነውን ሁሉ መቀበል"

ክፉ የሆነው
ይህ የሚወክለው እግዚአብሔር እንድናልፍበት የፈቀደቀውን ወይም ያደረገውን ክፉ ነገሮች ሁሉ ነው። (የስማዊ ሀረጋት ክፍሎች)

ከከንፈሮቹ በደል
እዚህ ስፍራ "ከንፈሮች" የሚወክለው የንግግርን ነው። "በንግግር እግዚአብሔርን መበደል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 2:11

ቴማናዊው ኤልፋዝ፣ ሹሐዊው በልዶስ፣ እና ናዕማታዊው ሶፋር
ኤልፋዝ፣ በልዶስ እና ሶፋር የወንድ ስሞች ናቸው። ቴማን በኤዶም ውስጥ የምትገኝ ከተማ ናት። ሹሐዊያን የአብርሃም እና የኬጡራ ትውልዶች ናቸው። ናዕማ በከነዓን ውስጥ የምትገኝ ከተማ ናት። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ጊዜ ወሰኑ
"በጊዜው ላይ ስምምነት ላይ ደረሱ)

ከእርሱ ጋር ለማልቀስ እና እርሱን ለማጽናናት
እዚህ ስፍራ "አብሮ ለማልቀስ" እና "ለማጽናናት" የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ወዳጆቹ ኢዮብን ለማጽናናት የሞከሩት ከእርሱ ጋር በማዘን ነው። "መከራውን እንዲረሳ" ከኢዮብ ጋር አዘኑ በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

Job 2:12

ዐይኖቻቸውን አነሱ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙም "በትኩረት ተመለከቱ" ወይም "በጥንቃቄ አዩ" ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አላወቁትም
ይህ ምናልባት የኢዮብ ጠያቂዎች ከሩቅ ሲመለከቱት በመጀመሪያ በቶሎ አላወቁትም ማለት ሊሆን ይችላል። ኢዮብ ከሀዘኑ እና ገላውን ከወረሰው ህመም የተነሳ ከወትሮው በጣም የተለየ ሆኖ ይታይ ነበር። "ለይተው ሊያውቁት አልቻሉም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ድምጻቸውን አንስተው አለቀሱ
እዚህ ስፍራ "ድምጻቸውን አንስተው" የሚለው ጮኸው ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ጮኸው አለቀሱ" ወይም "ድምጻቸውን ከፍ አድርገው አለቀሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ልብሱን ቀደደ
ይህ የሀዘን ምልክት ነው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ትቢያ ወደ ላይ እየበተነ እና በራሱ ላይ እየነሰነሰ
እነዚህ የሀዘን መግለጫዎች ነበሩ። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 ከዚህም በኋላ ኢዮብ አፉን ከፍቶ የተወለደበትን ቀን ረገመ። **2** እንዲህም አለ፦ **3** “ያ የተወለድሁበት ቀን ፤ 'ወንድ ልጅም ተፀነሰ' የተባለበት ሌሊት ይጥፋ” **4** ያ ቀን ጨለማ ይሁን እግዚአብሔርም ከላይ አያስበው ፤ የጸሀይ ብርሀንም አያግኝው። **5** ጨለማና የሞት ጥላ የራሳቸው እንደሆነ ይቁጠሩ፤ ዳመናም ይኑርበት፤ ቀኑን የሚያጨልሙ ነገሮች ሁሉ በርግጥ ያስደንግጡት። **6** ያንን ሌሊት ድቅድቅ ጨለማ ይያዘው፤ በዓመቱ ካሉት ቀኖች ጋር ደስ አይበለው፤ በወራት ውስጥ ገብቶ አይቈጠር። **7** ያቺ ምሽት መካን ትሁን፤ ወደ እርሷም የደስታ ድምጽ አይግባበት። **8** ሌዋታንን እንዴት ማንቃት እንዳለባቸው የሚያውቁ ያንን ቀን ይርገሙት። **9** አጥቢያ ኮከቦች ይጨልሙ፤ ያ ቀን ብርሃንን ሲጠባበቅ አያግኝ፥ የንጋትንም ወገግታ አይመልከት፤ **10** ምክንያቱም የእናቴን ማኅፀን ደጅ አልዘጋምና፥ መከራንም ከዓይኔ አልሰወረምና። **11** ከማኅፀን ስወጣ ስለ ምን አልሞትሁም? እናቴ ስትወልደኝስ ስለምን አልጠፋሁም? **12** ጕልበቶቿ ስለ ምን ተቀበሉኝ? ጡቶቿስ እንድጠባ ስለ ምን ተቀበሉኝ? **13** ይሄኔ በጸጥታ በተጋደምሁ፤ **14** አሁን ፈርሶ ያለውን መቃብር ለራሳቸው ከገነቡት የምድር ነገሥታትና አማካሪዎች ጋር፥ አንቀላፍቼም ባረፍሁ ነበር፤ **15** ወይም ባንድ ወቅት ቤታቸውን በብር ከሞሉ ወርቅም ከነበራቸው መኳንንት ጋር በተጋደምሁ ነበር፥ **16** ወይም ያለጊዜያቸው እንደተወለዱ፥ ብርሃንንም አይተው እንደማያውቁ ሕፃናት በሆንሁ ነበር። **17** በዚያ ክፉዎች ረብሻቸውን ያቆማሉ፤ የደከሙትም በዚያ ያርፋሉ። **18** በዚያ እስረኞች አርፈው በአንድነት ይቀመጣሉ፤ የአስጨናቂውን ጠባቂ ድምፅ አይሰሙም። **19** ታናናሽና ታላላቅ ሰዎች በዚያ አሉ፤ በዚያም ባሪያ ከጌታው ነጻ ወጥቶአል። **20** በመከራ ላለ ሰው ብርሃን ፤ ነፍሳቸው መራራ ለሆነችባቸውስ ህይወት፤ **21** የተሰወረን ሀብት ከሚፈልጉ ይልቅ ሞትን እየተመኙ ላልመጣላቸው ህይወት ለምን ተሰጠ? **22** መቀበሪያቸውን ባገኙ ጊዜ እጅግ ደስ ለሚላቸው፥ ሐሤትንም ለሚያደርጉ ሕይወት ለምን ተሰጠ? **23** መንገዱ ለጠፋበት ሰው፥ እግዚአብሔርም አጥር ላጠረበት ሰው ብርሃን ለምን ተሰጠ? **24** በመመገብ ምትክ ሲቃዬ ፈጥኖ ይመጣልና፥ መቃተቴም እንደ ውኃ ፈስሶአል። **25** የፈራሁት ነገር መጥቶብኛልና፥ የደነገጥሁበትም ደርሶብኛል። **26** በእርጋታና በጸጥታ አልተቀመጥሁም፥ አላረፍሁም ይልቅ መከራና ችግር መጣብኝ።

Job 3:1

አፉን ከፈተ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ንግግርን መጀመር ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የተወለድኩባት ቀን እና ምሽት ይጥፉ/መታሰቢያ ይጡ
ኢዮብ ስለዚያ ቀን እና ምሽት የሚናገረው ሰዎች እንደሆኑ አድርጎ ነው። "ምነው ባልተወለድኩ ኖሮ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

‘ወንድ ልጅ ተጸነሰ' የተባለበት ምሽት
ይህ አገላለጽ የኢዮብን ሀዘን ከተወለደበት እስከ ተጸነሰበት ቀን ድረስ ወደ ኋላ በመመለስ አጠንክሮ ይገልጻል። ‘ወንድ ልጅ ተጸነሰ የተባለበት ዕለት ይጥፋ' በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

የተባለበት ምሽት
እዚህ ስፍራ ምሽት የተገለጸው መናገር የሚችል ሰው ተደርጎ ነው። ሆኖም ተርጎሚው ከዚህ ዝቅ ባለ ዘይቤያዊ አገላለጽ ሊተረጉመው ይችላል። "ሰዎች … ያሉበት ምሽት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወንድ ልጅ ተጸንሷል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እናቱ ወንድ ልጅ ጸንሳለች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

Job 3:4

አጠቃላይ መረጃ፡
በዚህነዚህ ሀረጋት ውስጥ የሚገኙት አገላለጾች ኢዮብ የተወለደበት ቀን ከእንግዲህ እንዳይኖር ያለን ምኞት የሚገልጹ ናቸው። ይህ ምናልባት የቀደመው ቀን በአንድ መንገድ የሚቀጥል መሆኑን የሚጠቁም ሊሆን ይችላል። ዩዲቢ ቀኑ ምን ይመስል እንደነበር የሀዘን መግለጫ አድርጎ ይተረጉማቸዋል።

ያ ቀን ጨለማ ይሁን… ፀሐይም አይውጣበት።
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ኢዮብን ጸጸት በመደጋገም የተወለደበትን ቀን ጨለማነቱ ይገልጻሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ያ ቀን ጨለማ ይሁን
ይህ ያዚያችን ቀን ከእንገዲህ ያለመኖር የሚገልጽ ምኞት ነው። "ያቺ እለት ትጥፋ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጨለማ እና የሞት ጥላ እርሱን ይውረሱት
እዚህ ስፍራ ጨለማ እና የሞት ጥላ የተገለጹት አንድን ሰው ወይም አንድን ነገር የራሱ እንደሚያደርግ ሰው ተደርገው ነው። "እርሱን" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የኢዮብን የልደት ቀን ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሞት ጥላ
እዚህ ስፍራ ጥላ የሚወክለው ሞትን ነው። "ሞት እንደ ጥላ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ደመና በላዩ ይኑር
እዚህ ስፍራ ደመና የተገለጸው በኢዮብ የልደት ቀን ላይ መኖር እንደሚችል ሰው ተደርጎ ነው። "ማንም ሊመለከተው እንዳይችል ደመና ይሸፍነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ቀኑን ጨለማ የሚያደርግ ነገር ሁሉ
ይህ የሚያመለክተው የፀሐይን ብርሃን የሚጋርድን እና መለማ የሚፈጥርን ነገር ሁሉ ነው። እዚህ ስፍራ "ጥቁር" የሚወክለው ጨለማን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ያስፈራሩት
"ያንን ቀን ያስፈራሩት።" ቀኑ የተገለጸው በጨለማ ፍርሃት እንደሚውጠው ሰው ተደርጎ ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 3:6

ድቅድቅ ጨለማ ይያዘው
ይህ ጨለማ የተገለጸው ምሽቱን እንደሚይዝና እንደሚጨብጥ አንድ ሰው ተደርጎ ነው። "ከባድ ጨለማ ጨርሶ ያጥፋው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥቅጥቅ ጨለማ
"ጥልቅ ጨለማ" ወይም "ድፍን ጨለማ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እርሱን ደስ አይበለው
"እርሱን" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢዮብ የተወለደበትን ወይም የተጸነሰበትን ምሽት ነው። ኢዮብ የተጸነሰበት ምሽት የተገለጸው ደስታ ማግኘት እንደማይገባው ሰው ተደርጎ ነው። "ያ ምሽት ከቀኖች መሀል ተለይቶ ይጥፋ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አይቆጠር/ወደ ቁጥር አይምጣ
ምሽቱ የተገለጸው መራመድ የሚችል ሰው ተደርጎ ነው። "ማንም በቁጥር ውስጥ አስገብቶ አይቁጠረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ያ ቀን መሃን ይሁን
ኢዮብ የተወለደበት ምሽት አንዲት ሴት ሆኖ ተገልጽዋል። "በዚያ ምሽት አንድም ልጅ አይወለድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የደስታ ድምጽ ወደ እርሱ አይምጣ/አይሰማበት
እዚህ ስፍራ ኢዮብ የተወለደበት ምሽት የተገለጸው በዚያ ዕለት ወንድ ልጅ በመወለዱ ደስ የተሰኘ ሰው እንደነበር ተደርጎ ነው። "ወንድ ልጅ ሲወለድ የተሰማውን የደስታ ጩኸት ድምጽ/እልልታ ማንም አይስማው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የደስታ ጩኸት ደረሰ
እዚህ ስፍራ ድምጽ የሚለው ሚገልጸው ደስተኛ የሆነን ሰው ነው። "በእርሱ ማንም ደስተኛ አይሁን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 3:8

ሌዋታንን መቀስቀስ የሚችሉ
እዚህ ስፍራ ኢዮብ ጥፋትን በማስፋፋት ሌዋታንን ሳይቀር ለመቀስቀስ ይችሉ ይሆናል የሚላቸውን ጠንቆዮችን እና አስማተኞችን እያመላከተ ሊሆን ይችላል። ሌዋታን ሁሉንም አይነት ጥፋት፣ ስርአት ማጣትና ምስቅልቅል ያደርሳል ተብሎ የሚታሰብ በቅርብ ምስራቅ አገራት አፈታሪክ ውስጥ የሚታወቅ እንስሳ ነበር።

የዚያን ዕለት የንጋት ከዋከወበት ይጨልሙ
ይህ የሚያመለክተው ብዙውን ጊዜ ንጋት ላይ የሚታዩትን ፕላኔቶች ነው። "ከዚያን ቀን ከሚፈነጥቀው ብርሃን አስቀድሞ የሚታዩ ከዋክብት ይጨልሙ"

ያ ቀን ብርሃን ቢፈልግን አንዳች አያግኝ
የኢዮብ ልደት ቀን የተገለጸው አንዳች ነገር እንደሚፈልግ ሰው ተደርጎ ነው። "ያ ቀን ብሃንን ተስፋ ቢያደርግም፣ ነገር ግን አንዳች አያግኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የንጋት ሽፋሽፍቶች አይመልከቱ
ንጋቱ የተገለጸው እንደ ሰው ሁሉ ሽፋሽፍቶች እንዳሉት ተደርጎ ነው። "የንጋቱን የብርሃን ፍንጣቂ አይመልከት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ምክንያቱም የእናቴን ማህጸን አልዘጋምና
ማህጸን የተገለጸው በሮች እንዳሉት መያዣ ተደርጎ ነው። "ምክንያቱም ያ ቀን የእናቴን ማህጸን አልዘጋምና" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ምክንያቱም ከዐይኖቼ ችግርን አላራቀምና
እዚህ ስፍራ የኢዮብ ልደት ቀን የተገለጸው አንድን ነገር ሊደብቅ እንደሚችል ሰው ተደርጎ ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዐይኖቼ
እዚህ ስፍራ "ዐይኖች" የሚለው የሚወክለው የሚመለከትባቸውን ሰው ነው። "ከእኔ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 3:11

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ የንባብ ክፍል ኢዮብ የተለያዩ ተከታታይ ሃሳቦችን ለማቅረብ የሚጠይቃቸውን አራት ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎችን ይይዛል

ከማህጸን ሳልወጣ ሞቼ በቀረሁ?
"ለምን በምወለድበት ጊዜ ሳልሞት ቀረሁ?" ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚያቀርበው የተወለደበትን ቀን ለመርገን እና ጭንቀቱን ለመግለጽ ነው። "ምነው በተወለድኩበት ቀን በሞትኩ ኖሮ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ምነው እናቴ በወለደችኝ ቀን ነፍሴን ሳልሰጥ ቀረሁ?
ኢዮብ ይህንን የሚለው በህይወት መወለድ አልነበረብኝም ለማለት ነው። "ምነው ከማህጸን በመጣሁበት ሰአት በሞትኩ ኖሮ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ነፍሴን ብሰጥ
ይህ ሞትን ያመለክታል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለምን ጉልበቶቿ ታቀፉኝ
ይህ ምናልባት የኢዮብን እናት ጭኖች ሊያመለክት ይችላል። የእናቱ ጉልበቶች የተገለጹት አዲስ የተወለደን ህጻን እንደሚቀበሉ ሰዎች ተደርጎ ነው። "እኔን የሚታቀፉ የእናት ጭኖች/ጉልበቶች ባይኖሩ በመደድኩ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

እጠባቸው ዘንድ ስለምን የእናቴ ጡቶች ተቀበሉኝ?
የኢዮብ እናት ጡቶች የተገለጹት አዲስ የተወለደን ህጻን እንደሚቀበሉ ሰዎች ተደርጎ ነው። "የምጠባቸው ጡቶች ባይኖሩ በወደድኩ " በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 3:13

አሁን በጸጥታ ባረፍኩ ነበር። በዚህን ጊዜ ተኝቼ በእረፍት ላይ በሆንኩ ነበር።
ኢዮብ ሁለቱን ዐረፍተ ነገሮች የተጠቀመው ከነጭርሱ ሳይወለድ ቢቀር ኖሮ ወይም በሚወለድበት ሰአት ሞቶ ቢሆን ኖሮ ምን ይሆን እንደነበር ለማሰብ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት/ የሚሉትን ይመልከቱ)

በሰላም አንቀላፋ ነበር
ኢዮብ ከላይ እንደተጠቀሰው ሳይሆን ስለቀረው ነገር ግን ባለፈው ዘመን ሊሆን ይችል ስለነበረው ነገር ያሰላስላል። "በፀጥታ በተኛሁ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በፀጥታ መተኛት
"መተኛት፣ ማረፍ፣ በሰላም"

በዕረፍት መሆን
እዚህ ስፍራ "ዕረፍት" ማለት በሰላም መተኛት ማለት ሲሆን ነገር ግን ኢዮብ የገጠመውን ስቃይ አይኖረውም ነበር ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከምድር ነገሥታት እና አማካሪዎች ጋር
"ከነገሥታት እና አማካሪዎቻቸው ጋር"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Job 3:15

አጠቃላይ መረጃ
ኢዮብ ከመወለዱ አስቀደሞ ስለመሞቱ ያለውን ሀሳብ ይቀጥላል።

ወይ እተኛ ነበር...ብርሃን በፍጹም እንዳላየ
ይህ ሊሆን የሚችል ነገር ግን ያልሆነ ነገርን ይገልጻልለለ (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ከልዑላን ጋር አርፍ ነበር
" ከልዑላን ጋር አርፍ ነበር" በዚህ ሀረግ፣ "መተኛት" እና "ማረፍ" የሚሉት ቃላት በትሁት/በተሻለ አገላለጽ "ከዚያ ወዲያ በህይወት አለመኖር" የሚሉ ናቸው። (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

በአንድ ወቅት ወርቅ የነበራቸው፣ ቤቶቻቸውንም በብር የሞሉ
ኢዮብ ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን የተጠቀመው እየተናገረ የሚገኘውን ነገር ለማጉላት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወይም ምናልባት ብርሃን ፈጽሞ አይቶ እንደማያውቅ፣ ሞቶ የተወለደ ጭንጋፍ እሆን ነበር
ኢዮብ ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን የተጠቀመው እየተናገረ የሚገኘውን ነገር ለማጉላት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሞቼ በተወለድሁ
"በእናቴ ማህጸን ሳለሁ በሞትኩ"

ብርሃን ፈጽሞ እንዳላየ ጨቅላ
"እንዳልተወለዱ ህጻናት"

ጨቅላ ህጻናት
"ህጻናት" ወይም "በጣም ትንንሽ ልጆች"

Job 3:17

አጠቃላይ መረጃ:
ኢዮብ ንግግሩን ከሞት ወደ ከሞት በኋላ ያለ ህይወት ይለውጠዋል።

በዚያ ክፉዎች ማስቸገር ያቆማሉ፤ በዚያ የደከሙ በዕረፍተ ላይ ይሆናሉ።
ኢዮብ ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የተጠቀመው የተጨቆኑ ከመከራ እንደሚያርፉ አጉልቶ ለማሳየት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚያ የክፉዎች ማወክ ያበቃል
ኢዮብ እየተናገረ የሚገኘው ሰዎች በምድር መኖር ካቆሙ በኋላ ስለሚሄዱበት ስፍራ ነው። "ክፉ ሰዎች ችግር ማድረሳቸው በሚያበቃበት በዚያ ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የባሪያ አሳዳሪዎች/ገዢዎች ድምጽ
እዚህ ስፍራ "ድምጽ" የሚለው የባሪያ ጌቶች በባሪያዎቻቸው ላይ ያላቸውን ሀይል የሚገልጽ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። "ከእንግዲህ ወዲያ በባሪያ ገዢዎች ቁጥጥር ስር አይሆኑም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ታናናሾች እና ታላላቆች
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን "ሁሉም ሰው፣ ደሃውም ሆነ ባለጸጋው" የሚል ትርጉም አለው። (ጽንፍ የሚለውን ይመልከቱ)

አገልጋይ ከጌታው ነጻ ነው
ከዚያ በኋላ አንድ አገልጋይ ጌታውን ለማገልግል አይገደድም

Job 3:20

በመከራ ውስጥ የሚኖር ለምን ብርሃን ያያል? ነፍሱ የተመረረች ለምን ህይወት ይሰጠዋል?
ሁለቱ የኢዮብ ጥያቄዎች በመሰረቱ አንድ አይነት ናቸው። በመከራ ውስጥ የሚገኙ ለምን በህይወት እንደሚቀጥሉ ይገረማል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በመከራ ውስጥ የሚኖር ለምን ብርሃን ይሰጠዋል?
እዚህ ስፍራ ኢዮብ ሰዎች ለምን በህይወት ቆይተው እንደሚሰቃዩ በመገረም ይጠይቃል። "እግዚአብሔር ስለምን በመከራ ውስጥ ለሚኖረው ህይወት እንደሚሰጠው ለገባኝ አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ብርሃን
እዚህ ስፍራ ብርሃን የሚወክለው ህይወትን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የተደበቀ ሀብት....በነፍሱ ለተመረረ ለምን ህይወት ይሰጠዋል የተደበቀ ሀብት?
"እግዚአብሔር ለመከረኛው ሰው ለምን ህይወት ይሰጠዋል?" "እግዚአብሔር እጅግ ሀዘንተኛ ለሆነ ሰው ለምን ህይወት እንደሚሰጠው አይገባኝም... የተደበቀ ሀብት..." በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ሞትን እየተመኘ ለማያገኘው ሰው
እዚህ ስፍራ ሞት የተገለጸው ወደ አንድ ሰው እየመጣ እንሚገኝ ቁስ ነው። "ለመኖር ለማይፈልግ ሰው፣ ነገር ግን አሁንም በህይወት ለሚገኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የከበረ ሀብትን በቁፋሮ ከሚፈልግ ሰው ይልቅ ሞትን ለሚፈልግ ሰው
ሞትን ተስፋ የሚያደርግ ሰው የተገለጸው የተቀበረ ውድ ሀብትን ለማግኘት እንደሚቆፍር ሰው ተደርጎ ነው። "የተደበቀ ውድ ሀብትን ከሚፈልግ ሰው ይልቅ መሞትን በብርቱ የሚፈልግ ሰው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መቃብርን ሲያገኝ እጅግ ደስ ለሚሰኝ ለምን ብርሃን ይሰጠዋል
እዚህ ስፍራ ኢዮብ ጥያቄ የሚጠይቀው ዐረፍተ ነገር ለማበጀት ነው። "ሰውየው ሞቶ መቀበር እጅግ ደስ የሚያሰኘው ከሆነ እግዚአብሔር ለዚያ ሰው መኖርን ለምን እንደሚፈቅድ አይገባኝም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በጣም ደስ የሚሰኝ እና ደስተኛ የሆነ
"በጣም ደስ የሚሰኝ" የሚለው ሀረግ "ደስተኛ የሆነ" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው። ሁለቱ አገላለጾች በአንድነት ሆነው የደስተኝነትን መጠን ያጎላሉ። "እጅግ ደስ የተሰኘ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

መቃብርን ሲያገኝ
ይህ ሞትን ሻል ባለ መንገድ መግለጫ ነው። "በሚሞትበት እና ሊቀበር በሚችልበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

መቃብር
እዚህ ስፍራ መቃብር የሚወክለው ሞትን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 3:23

መንገዱ ለተደበቀችበት እግዚአብሔር ላጠረበት ሰው፣ ለምን ብርሃን ተሰጠው?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ዐረፍተ ነገር ለማበጀት ነው። "እግዚአብሔር ለሰው ህይወት ከሰጠው በኋላ የወደፊቱን ነጥቆ ሊያጥርበት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አይገባም" በሚለው ወስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ለሰው ለምን ብርሃን ተሰጠው
እዚህ ስፍራ ብርሃን የሚወክለው ህይወትን ነው። "እግዚአብሔር ለምን አንድን ሰው በህይወት ያኖረዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መንገዱ ለተደበቀችበት
እዚህ ስፍራ ኢዮብ አስቀድሞ ስለማያውቀው ስለ ወደፊቱ እግዚአብሔር እንደሰወረበት አድርጎ ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር መንገዱን ያጠረበት
እዚህ ስፍራ በችግር ውስጥ መሆን እና አደጋዎች የተገለጹት በጠባብ ስፍራ እንደመወሰን ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ትካዜ ምግብ ሆኖኛል፣ የስቃይ ጩኸቴ/መቃተቴ እንደ ውሃ ይፈሳል
ኢዮብ ጭንቀቱን በሁለት መንገዶች ይገልጻል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ትካዜ ምግብ ሆኖኛል
"ከመመገብ ይልቅ፣ ሀዘንተኛ ሆኛለሁ"

የስቃይ ጩኸቴ/መቃተቴ እንደ ውሃ ይፈሳል
እንደ ሀዘን የመሰሉ የስነምግባር ባህሪያት እና ስሜቶች ብዙውን ጊዜ በውሃ ይገለጻሉ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 3:25

የፈራኋቸው ነገሮች በላዬ መጡብኝ፣ የፈራሁት ደረሰብኝ
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። "በጣም ሰግቻለሁ" ወይም "እጅግ የፈራሁት ነገር ደረሰ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ተዘልዬ የተቀመጥኩ አይደለሁም፣ አላረፍኩም፣ ደግሞም እረፍት የለኝም
ኢዮብ ጭንቀቱን በሶስት የተለያዩ ሀረጋት ይገልጻል። "በጣም ሰግቻለሁ" ወይም "በስሜትም በአካልም ተሰቃይቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 ቴማናዊውም ኤልፋዝ እንዲህ ሲል መለሰ ፦ **2** አንድ ሰው ከአንተ ጋር ለመነጋገር ቢሞክር ታዝናለህን? ነገር ግን ከመናገር ራሱን ሊገታ የሚችል ማን ነው? **3** እነሆ፥ አንተ ብዙዎችን ታስተምር ነበር፥ የደከሙትንም እጆች ታበረታ ነበር፥ **4** ቃልህ ሊወድቅ የተሰናከለውን ያስነሣ ነበር፥ አንተም የሚብረከረከውን ጕልበት ታጸና ነበር። **5** አሁን ግን ጥፋት በአንተ ላይ መጥቶአል፥ አንተም ደከመህ፤ በርግጥ ደረሰብህ፥ አንተም ታወክህ። **6** እግዚአብሔርን መፍራትህ ድፍረትን፥ ያካሄድህስ ቀናነት ተስፋን አይሰጥህምን? **7** እባክህ ይህን እንድታስብ እለምንሃለሁ፥ ንጹሕ ሆኖ የጠፋ ማን አለ? ልበ ቅንስ ሆኖ የተደመሰሰ ማን ነው? **8** እኔ እንዳየሁ፥ ኃጢአትን የሚያርሱ፥ ሁከትንም የሚዘሩ መልሰው ያንኑ ያጭዳሉ። **9** በእግዚአብሔር እስትንፋስ ይጠፋሉ፥ በቍጣውም ንዳድ ያልቃሉ። **10** የአንበሳ ግሳት፥ የቁጡ አንበሳ ድምፅ፥ የደቦል አንበሳ ጥርስ ተሰባብረዋል። **11** ያረጀ አንበሳ አደን አጥቶ ይሞታል፥ የአንበሳይቱም ግልገሎች የትም ይበተናሉ። **12** ለእኔም ነገሩ በምሥጢር መጣልኝ፥ ጆሮዬም ስለነገሩ ሹክሹክታን ሰማች። **13** ከባድ እንቅልፍ በሰው ላይ በሚሆንበት ጊዜ፥ በሃሳብ ብዛት በሌሊት ሕልም ሲመጣ፥ **14** ድንጋጤና መንቀጥቀጥ መጡብኝ አጥንቶቼም ሁሉ ተንቀጠቀጡ **15** በፊቴም መንፈስ አለፈ የሰውነቴም ጠጕር ቆመ። **16** መንፈሱም ቆመ፥ መልኩን ግን ለመለየት አልቻልሁም፥ ቅርጹ በዓይኔ ፊት ነበረ፤ ጸጥታም ሆነ እንዲህም የሚል ድምፅ ሰማሁ፤ **17** “በውኑ ሥጋ የለበሰ ሰው ከእግዚአብሔር ይልቅ ጻድቅ ሊሆን ይችላልን ሰውስ ከፈጣሪው ይልቅ ንጹህ ሊሆን ይችላልን?” **18** እነሆ፥ እግዚአብሔር በአገልጋዮቹ ካልተማመነ፤ መላእክቱንም በስህተት ከወቀሳቸዋል፤ **19** ይልቁንስ በሸክላ ቤቶች ውስጥ በሚኖሩ፥ መሠረታቸውም በትቢያ ውስጥ ለሆነ፥ ከብል ቀድመው በሚጠፉት ዘንድ ይህ እንዴት እውነት ይሆን? **20** በጥዋትና በማታ መካከል ይጠፋሉ፤ ማንም ሳያውቀው እስከ ወዲያኛው ይጠፋሉ። **21** የድንኳናቸው ገመድ ከመካከላቸው የተነቀለ አይደለምን? ይሞታሉ፦ ያለጥበብም ይሞታሉ።

Job 4:1

ኤልፋዝ
ኤልፋዝ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ቴማናዊ
ቴማናዊ ከተምና ነገድ የሆነ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ትታገሳለህን?
ኤልፋዝ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው በዐረፍተ ነገር ሃሳቡን ለመግለጽ ነው። "በእርግጥ ልትታገስ ይገባል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ትታገሳለህን?
"ይህ ነገር ያስከፋሃልን?"

ነገር ግን ማን ከመናገር ራሱን ሊገታ ይችላል?
ኤልፋዝ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው የወዳጁን መጨነቅ እየተመለከተ ማንም ዝም ማለት አይችልም ለማለት ነው። "ወዳጁ አንተ በምትገኝበት ሁኔታ ሆኖ ማንም ከመናገር ራሱን መግታት አይችልም" ወይም "አንተ በጭንቀት ውስጥ ሆነህ እኔ ከመናገር ዝም ማለት አልችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ብዙዎቹን አስተምረሃል፣ የላሉ እጆችን አጽንተሃል
ይህ ስንኝ አንድን ሃሳብ በሁለት የተለያዩ መንገዶች ይገልጻል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ የላሉ እጆችን አጽንተሃል
እዚህ ስፍራ "የላሉ/ደካማ እጆች" የሚለው የሚወክለው እርዳታ የሚፈልጉ ሰዎችን ነው። "ሌሎች እርዳታ በሚፈልጉ ጊዜ አንተ ረድተሃቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 4:4

አጠቃላይ መረጃ:
ጸሐፊው ሁለት ሃሳቦችን በመጠቀም አንድ ሃሳብ ለመመስረት ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን በእያንዳንዱ ሀረግ ውስጥ የሚጠቀመው 1) በቀደመው ጊዜ ኢዮብ ለሌሎች የሰጠውን ድጋፍ፣ 2) በአሁኑ ችግሩ ላይ ያሳደረውን ተጽዕኖ፣ እና 3) በእግዚአብሔር ፊት የእርሱን ንጽህና ለማጉላት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ትደግፍ
የተበረታታ አንድ ሰው የተገለጸው ወደ ታች ከመውደቅ እንደተጠበቀ ተደርጎ ነው

መውደቅ
እዚህ ስፍራ ተስፋ መቁረጥ የተገለጸው ወደ ታች መውደቅ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የተብረከረኩ ጕልበታችን ታጠነክር ነበር
እዚህ ስፍራ ተስፋ መቁረጥ የተገለጸው ደካማ ጕልበቱ ተሸክሞ ሊያቆመው እንዳልቻለ አንድ ሰው ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አሁን ግን መከራ ወደ አንተ መጥቷል
እዚህ ስፍራ መከራ የተገለጸው ወደ አንድ ሰው እንደሚመጣ ቁስ ተደርጎ ነው። "ነገር ግን አንተ አሁን ከውድቀት የተነሳ ትጨነቃለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ዝለሃል
"አንተ ተስፋ ቆርጠሃል"

የምትፈራው
"አንተ እግዚአብሔርን ማክበርህ"

ፍርሃትህ ልበ ሙሉነትህ አይደለምን፣ ደግሞስ የመንገዶችህ ጽናት ተስፋህ አይደለምን?
ኤልፋዝ እነዚህን ጥያቄዎች የሚጠይቀው ኢዮብን የምትሰቃየው ከኃጢአትህ የተነሳ ነው ሊለው ፈልጎ ነው። "ሁሉም ሰው አንተ እግዚአብሔርን እንደምታከብር ያስባል፣ ሁሉም ሰው አንተ እውነተኛ ሰው እንደሆንክ ያስባል። እነዚህ ነገሮች ግን እውነት ሊሆኑ አይችሉም፣ ምክንያቱም አንተ እግአብሔርን ተስፋ ማድረግ አቁመሃ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ፍርሃትህ
ኤልፋዝ የኢዮብን እግዚአብን መፍራት ማለቱ ነው። "የአንተ እግዚአብሔርን መፍራት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መንገዶችህ
እዚህ ስፍራ "መንገዶችህ" የሚለው የሚወክለው "ባህሪህ፣" "አደራረግህ፣" የሚለውን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Job 4:7

ንጹህ ሆኖ ሳለ የጠፋ ማን ነው?
ኤልፋዝ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው ኢዮብ ህይወቱን ከኃጢአት እንዲመረምር፣ የእግዚአብሔርን ጻድቅ ፈራጅነት እንደዚሁም ሁሉን ሊያጣ የቻለበትን ምክንያት አንዲ ሊያነሳሳው ነው። "ንጹህ ሆኖ ሳለ የጠፋ ማንም የለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ትክክለኛ ሰዎች መች ተቆርጠው ጠፍተው ያውቃሉ?
ይህም ጥያቄ ሃሳብን ለማቅረብ የተሰነዘረ ነው፤ በአድራጊ ዐረፍት ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ትክክለኛ ሰው ሆኖ ሳለ ተቆርጦ የቀረ ሰው የለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ተቆርጦ የጠፋ
እዚህ ስፍራ ተቆርጦ መጥፋት የሚለው የሚገልጸው መደምሰስን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኩልነት ማጣትን ያርሳል... ችግርን ይዘራል... ያጭዳል
እዚህ ስፍራ የማረስ እና መዝራት ድርጊቶች የመወክሉት ለሌላው ሰው ለችግር ምክንያት መሆንን ነው። የማጨድ ድርጊት የሚወክለው አንድ ሰው ራሱ ባመጣው ችግር ምክንያት በመከራ መሰቃየትን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር እስትንፋስ ይጠፋሉ፣ በቁጣው መአት ይበላሉ
ጸሐፊው አንድን ሀሳብ ሁለት አይነት አገላለጽ በመጠቀም ያብራራል። ይህ በዕብራውያን ስነግጥም ትኩረት ለመስጠት፣ ሀሳብን ግልጽ ለማድረግ፣ ለማስተማር ወይም ለእነዚህ ለሶስቱም ጉዳዮች የሚውል ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር እስትንፋስ
ይህ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የመስጠት ድርጊት የሚወክል ሊሆን ይችላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የቁጣው መአት
ይህ አገላለጽ የሚጠቁመው አንዳንድ ጊዜ ሰው በጣም ሲቆጣ በአፍንጫው በከባዱ የሚተነፍሰውን አተነፋፈስ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የቁጣ... አተነፋፈስ
አንደኛው ቃል በሌላኛው ላይ ይመሰረታል። ውጤቱን ከፍ የሚያደርግ ትርጉሞችን በመጠቀም አንድን ነጥብ ይገልጻሉ። "ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው ትንፋሽ ይሞታሉ፤ የቁጣው አውሎ ነፋስ ያጠፋቸዋል።" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይጠፋሉ... ይበላሉ
ሁለተኛው ሀረግ በመጀመሪያው ላይ የተመሰረተ ነው። ሁለቱም ተመሳሳይ ነጥብን ይገልጻሉ። "ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው ትንፋሽ ይሞታሉ፤ የቁጣው አውሎ ነፋስ ያጠፋቸዋል።" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ይበላሉ
እዚህ ስፍራ መፈጀት ወይም መበላት የሚለው የሚወክለው መገደልን ነው።

Job 4:10

አጠቃላይ መረጃ:
ጸሐፊው በእነዚህ ስንኞች ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን የሚጠቀመው፣ በተለያየ አገላለጽ እግዚአብሔር ክፉ ሰዎችን የሚያጠፋ መሆኑን አጉልቶ ለማሳየት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የአንበሳ ግሳት፣ የተቆጣ አንበሳ ድምጽ፣ የአንበሳው ጥርሶች ¬- ተሰብረዋል።
እዚህ ስፍራ የአንበሳ ግሳት፣ ድምጹ፣ እና የጥርሱ መሰበር ክፉዎች እንደሚጠፉ መገለጫ ሆኖ አገልግሏል። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ተሰብረዋል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንድ ነገር ሰብሯቸዋል" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ያረጀ አንበሳ የሚያድነው በማጣቱ ይጠፋል፣ የአንበሳ ደቦሎች በየስፍራው ይበተናሉ
ኤልፋዝ ያረጀ አንበሳን በረሃብ መሞት እና የአንበሳ ቤተሰብ የመበተንን ዘይቤያዊ አገላለጾች የተጠቀመው ክፉዎች የሚጠፉ መሆኑን ለመግለጽ ነው።

የአንበሳ ደቦሎች ተበተኑ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የአንበሳ ደቦሎችን አንድ ነገር በተናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 4:12

አሁን አንድ ነገር በድብቅ ወደ እኔ መጥቷላ... ስለዚያም ነገር ጆሮዎቼ ሹክሹክታ ሰምተዋል
እነዚህ ሀረጋት አንድን ሀሳብ በተለያየ መንገድ ይገልጻሉ። ኤልፋዝ በሹክሹክታ መልእክት የመቀበሉን ሀሳብ ያስተላልፋሉ። የዚህ አይነቱ መደጋገም በዕብራውያን ሰነ ግጥም ውስጥ ትኩረት ለመስጠት፣ ለማስተማር ወይም ሃሳብን ግልጽ ለማድረግ አዘውትሮ በተግባር ላይ ይውላሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሌት በራዕይ
"ህልም"

በሰዎች ላይ ከባድ እንቅልፍ ሲወድቅ
"ሰዎች ከባድ እንቅልፍ ሲተኙ"

Job 4:14

አጠቃላይ መረጃ:
ጸሐፊው በእነዚህ ቁጥሮች የኤልፋዝን ስጋት ለማጉላት አንድን ሀሳብ የተለያዩ አገላለጾች በመጠቀም ለማስተላለፍ ንጽጽራዊ ዘይቤን ይጠቀማል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ፍርሃት እና መንቀጥቀጥ በላዬ መጡ
እዚህ ስፍራ ፍረሃት እና መንቀጥቀጥ የተገለጹት ወደ አንድ ሰው እንደሚመጡ ቁሶች ተደርገው ነው። "መፍራት እና መንቀጥቀጥ ጀመርኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰውነቴ ፀጉር ቆመ
ይህ ታላቅ ፍርሃትን ያመለክታል

የሰውነቴ ፀጉር
"በሰውነቴ ላይ የሚገኝ ፀጉር"

Job 4:16

አጠቃላይ መረጃ:
ጸሐፊው በቁጥር 17 ላይ ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን የተጠቀመው አንድን ሀሳብ በሁለት የተለያዩ አገላለጾች በእግዚአብሔር ፊት የሰውን ንጹህ አለመሆን ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ቅርጽ/መልክ በፊቴ ነበረ
"አንድ ነገር በዐይኔ ፊት ነበር፣" "አንድ ነገር ተመለከትኩ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ደግሞም ሰማሁ
"ከዚያም ሰማሁ"

ሟች የሆነ የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ይልቅ ጻድቅ ይሆናልን?
ኤልፋዝ ይህንን ጥያቄ የሚያቀርበው ኢዮብ "ራሴን ከእግዚአብሔር ይልቅ ጻድቅ አድርጌ ቆጥሬያለሁን?" ብሎ እንዲጠይቅ ለማድረግ ወይም "ሟች የሆነ የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ይልቅ ጻድቅ ሊሆን አይችልም" እንዲል ለማድረግ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ስርሱን ያበጀው
"የእርሱ ፈጣሪ"

Job 4:18

በሸክላ ቤት ውስጥ የሚኖሩ፣ መሰረታቸው አፈር የሆነ
ይህ ከምድር አፈር የተፈጠሩና አካላቸው እንደቤቶች የሆነ፣ ከሸክላ የተሰሩ መሰረታቸው ትቢያ የሆነ ሰዎችን በዘይቤያዊ መንገድ መግለጫ ነው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ከብል ይልቅ ፈጥነው የሚጨፈለቁ
የዚህ ዘይቤያዊ አነጋገር ትረጉሞች ሊሆኑ የሚችሉት 1) "እግዚአብሔር ብልን ሊጨፈልቅ የሚችለውን ያህል በቀላሉ የሚያጠፋቸው" ወይም 2) "ዘመናቸው የብልን እድሜ ያህል አጭር የሆነ።" (ዘይቤያዊ አገላለጽ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 4:20

አጠቃላይ መረጃ፡
እነዚህ ቁጥሮች ቀደም ሲል ያገለገሉት ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ ቀጣዮች ናቸው፣ እዚህ ስፍራ ሰዎች በድንገት ጥበብ ሳያገኙ እና ከሌሎችም ይሁንታ ሳይኖራቸው መሞታቸው በተለያየ መንገድ ትኩረት ተሰጥቶታል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በቀንና በምሽት መሃል ይጠፋሉ
ይህ የሚያመለክተው በፍጥነት የሚሆንን ነገር ነው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ጠፍተዋል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እነርሱ ሞቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የድንኳኖቻቸው ማሰሪያዎች/ገመድ ከመሃላቸው አልተነቀለምን?
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ጠላቶቻቸው የድንኳኖቻቸውን ማሰሪያ ከመሃላቸው ስበው አልጣሉምን?" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የድንኳኖቻቸው ማሰሪያ/ገመድ
እዚህ ስፍራ የድንኳኖች ማሰሪያ የሚወክለው ድንኳኖችን ነው። አንዳንድ ጊዜ የአንድ ሰው ቤት እና ቤተሰብ እንደ ድንኳኑ ተደርጎ ይገለጻል፤ ይህ ሰውየው ያለውን ንብረት ሁሉ የሚወክል ሊሆንም ይችላል። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 5

1 አሁን እስቲ ተጣራ፤ የሚመልስ አንድ እንኳ አለ? ከቅዱሳንስ ወደየትኛው ትዞራለህ? **2** ሰነፍን ሰው ቍጣ ይገድለዋል፥ ሞኙንም ቅንዓት ያጠፋዋል። **3** ቂል ሰው ሥር ሲሰድድ አየሁ፥ ነገር ግን በድንገት ቤቱን ረገምሁት። **4** ልጆቹም ከደኅንነት ከለላ ውጪ ናቸው፥ በከተማም አደባባይ የተረገጡ ናቸው፥ አንድም የሚያድናቸው የለም። **5** የተሰበሰበውን ሰብል በተራቡ በሌሎች ተበላ፥ ከእሾህ ውስጥ እንኳ የወጡ ሰዎች ወሰዱት፤ ያለውም ሁሉ ሀብትን በተጠሙ ሰዎች ተዋጠ። **6** ችግር እንዲሁ ከአፈር አይመጣም፥ መከራም ከመሬት አይመነጭም፤ **7** ነገር ግን የእሳት ፍንጣሪዎች ወደ ላይ እንደሚበርሩ፥ እንዲሁ ሰው መከራን በራሱ ላይ ያመጣል። **8** እኔ ግን እግዚአብሔርን ወደራሱ፥ ጉዳዬን ወደ ማቀርብለት ወደ እግዚአብሔር እመለስ ነበር። **9** እርሱ ታላቅና የማይመረመሩ ዋና ነገሮችንና የማይቈጠሩ አስደናቂ ነገሮችን ያደርጋል። **10** በምድር ላይ ዝናብን ይሰጣል፥ በእርሻም ላይ ውኃ ይልካል። **11** የተዋረዱትን በከፍታ ሊያኖር ፥ ኀዘንተኞችንም ለደኅንነት ከፍ ለማድረግ ይህንን ያደርጋል። **12** እጆቹው እቅዳቸውን እንዳይፈጽም የተንኰለኞችን ወጥመድ ከንቱ ያደርጋል። **13** ጠቢባንን በተንኰላቸው ይይዛቸዋል የተንኮለኞችንም ዕቅድ ያጠፋል። **14** በቀን ከጨለማ ጋር ይጋጠማሉ፥ በዕኩለቀንም በሌሊት እንዳሉ ያክል በዳበሳ ይሄዳሉ። **15** ነገር ግን ድሀውን ከአፋቸው ሰይፍ፤ ችግረኛውንም ከኃያላን እጅ ያድነዋል። **16** ስለዚህ ድሀው ተስፋ አለው፤ ፍትህ አልባነት ግን አፍዋን ትዘጋለች። **17** እነሆ፥ እግዚአብሔር የሚያርመው ሰው ምስጉን ነው፤ ስለዚህ ሁሉን የሚችለውን አምላክንተግሣጽ አትናቅ። **18** ምክንያቱም እርሱ ይሰብራል፥ ይጠግናል ያቈስላል በኋላም በእጆቹ ይፈውሳል። **19** እርሱ ከስድስት ክፉ ነገሮች ውስጥ ያወጣሃል፥ በርግጥ በሰባተኛው ክፋት አይነካህም። **20** በራብ ጊዜ ከሞት፥ በጦርነትም ከሰይፍ ስለት ያድንሃል። **21** ከምላስ ጅራፍ ትሰወራለህ፤ ጥፋትም ሲመጣ አትፈራም። **22** በጥፋትና በራብ ላይ ትስቃለህ፤ የምድር አውሬዎችንም አትፈራም፤ **23** ከምድርህ ድንጋይ ጋር ኪዳን ይኖርሃል ከምድር አራዊትም ጋር በሰላም ትሆናለህ። **24** ድንኳንህም በደህንነት እንዳለ ታውቃለህ፤ በረትህን ትጐበኛለህ አንድም አይጠፋብህም። **25** ዘሮችህም ታላቅ እንደሚሆኑ፥ ትውልድህም እንደ ምድር ሣር እንደሚበዙ ታውቃለህ። **26** የእህሉ ነዶ ደርሶ በወቅቱ ወደ አውድማ እንደሚገባ፥ ዕድሜን ጠግበህ ወደ መቃብር ትሄዳለህ። **27** እነሆ፥ ይህንን ነገር መረመርን፥ ነገሩ እውነት ነው፤ ልብ በለው፤ የራስህም እውቀት አድርገው።

Job 5:1

ወዴትኛው ቅዱስ ፊትህን ትመልሳለህ?
ኤልፋዝ ይህንን ጥያቄ የሚያነሳው ኢዮብ ለእርዳታ ፊቱን ሊያቀና የሚችልበት ማንም እንደሌለ ለመግለጽ ነው። "ፊትህን ወደ እርሱ ልትመልስ የምትችለው ቅዱስ አለን?" ወይም "እርዳታ ፍለጋ ወደ እርሱ ፊትህን ልታቀና የምትችልበት አንዳችም ቅዱስ የለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ቅዱስ የሆነ
ይህ መልአክንም ሆነ ሌላ መንፈሶች፣ አንድ እጅግ ሉዓላዊ የሚባልን ማንነት ያመለክታል።

በቅናት እዚህ ግባ የማይባለውን/ሞኙን መግደል
"በሞኝነት እና በስሜት በመገፋፋት የሚያደርገውን ማናቸውንም በቅናት መግደል"

እዚህ ግባ የማይባል... ሞኝ ሰው
ይህ የሚያመለክተው ማናቸውንም የማይረባ ሰው እና ማናቸውንም ሞኝ ሰው ነው። (የስማዊ ሀረግ ክፍል የሚለውን ይመልከቱ)

ሞኝ ሰው በሞኝነቱ ስር ይሰዳል
እዚህ ስፍራ ሞኝ ሰው የተገለጸው እርሱ ራሱ ተክል እንደሆነ፣ ምናልባትም በጊዜ ውስጥ ይበልጥ ሞኝ እየሆነ እንደሚሄድ ነው። "ሞኝ ሰው በሞኝነት ስር እየሰደደ ይሄዳለል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ቤቱ
ይህ የሰውየውን ቤተሰብ እና ንብረቱን ሁሉ ያመለክታል

Job 5:4

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ቁጥር ቀደም ሲል ያገለገለ ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ ቅጥያ ነው፣ እዚህ ስፍራ የሞኝ ሰው ልጆች በፍጹም ደህንተታቸው የተጠበቀ እንዳልሆነ በተለያዩ መንገዶች በትኩረት ተገልጽዋል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ ልጆች ደህንነትን/ጥበቃ ከማግኘት የራቁ ናቸው
"የእርሱ" የሚለው የሚያመለክተው በኢዮብ 5:2 ላይ የሚገኘውን ሞኙን ሰው ወይም ሞኝ ሰዎችን ነው። "ልጆቻቸው ፈጽሞውን ደህንነታቸው የተጠበቀ አይደለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ይፈጫሉ
እዚህ ስፍራ መፈጨት የሚለው የሚወክለው በፍትህ አደባባይ በጭቆና ስር መሆንን እና ጥቅምን መቀማትን ነው። ይህ ሀሳብ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንድ ሰው ያደቅቃቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

የከተማ በር
የከተማ በር፣ ክርክሮች የሚፈቱበት እና ፍትህ የሚሰጥበት ስፍራ ሆኖ ያገለግል ነበር።

የሚታደጋቸው ማንም የለም
"የሞኝ ሰዎችን ልጆች ከመከራቸው ለማውጣት ሊረዳቸው የሚችል ማንም የለም"

ሌላው ቀርቶ ከእሾህ መሃል ይህን ይወስዳሉ
ምናልባት ይህ የሚያመለክተው የእሾህ ተክል ከመኖሩ የተነሳ የከፋው ተክል የሚበቅልበትን ስፍራ ነው

ሃብታቸውን ተጠምቶ የሚፈልግ
እዚህ ስፍራ ስግብግብ ሰዎች የተገለጹት እንደ ተጠሙ ሲሆን፣ የሞኝ ሰው ሃብት ደግሞ እነርሱ ሊጠጡት እንደሚችሉት ነገር ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 5:6

ችግር ከአፈር ውስጥ አይወጣም፣ አሊያም መከራ ከምድር አይበቅልም
እዚህ ስፍራ ችግር እና መከራ የተገለጹት ተክል እንደሆኑ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የእሳት ፍንጣሪ ወደ ላይ እንደሚወጣው ሁሉ የሰው ልጅ የተወለደው ለመከራ ነው
ከእሳት ፍንጣሪው ወደላይ እንደሚወጣ ሁሉ ለሰው ልጆችም አንዴ ከተወለዱ በኋላ ችግር ማጋጠሙ ተፈጥሯዊ ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Job 5:8

አጠቃላይ መረጃ:
በእነዚህ ቁጥሮች፣ ኤልፋዝ ንግግሩን ከኢዮብ 4:1 ጀምሮ ይቀጥላል። ጸሐፊው ኢዮብ አስደናቂ ነገሮች የሚያደርገውን እግዚአብሔርን መለመን እንደሚገባው አጉልቶ ለማሳየት አንድን ሀሳብ ሁለት የተለያዩ አገላለጾች በመጠቀም ለማስተላለፍ በእያንዳንዱ ቁጥር ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ መጠቀሙን ይቀጥላል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ታላቅ እና የማይመረመሩ ነገሮች፣ ቁጥር የሌላቸው አስደናቂ ነገሮች
"ከመረዳት ባሻገር የሆኑ ታላላቅ ነገሮች፣ ሊቆጠሩ የማይችሉ አስደናቂ ነገሮች"

የማይመረመሩ ነገሮች
ይህ የሚያመለክተው የሰው ልጅ ሊረዳቸው የማይችሉ ነገሮችን ነው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ታላቅ እና የማይመረመሩ ነገሮች
እዚህ ስፍራ ጸሐፊው "እና" በሚል የተያያዙ ሁለት ራሳቸውን የቻሉ ቃላትን የሚጠቀመው የእግዚአብሔርን ስራ ታላቅነት ለማጉላት ነው። "በታላቅነት ጥልቅ/መሰረታዊ የሆኑ ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሄንዲየዲስ/ሁለት ቃላት 'እና' በሚል አያያዥ ቃል የሚገኙኙበትና አንድን ጥልቅ ሀሳብ ለመግለጽ የሚያገለግል ዘይቤያዊ አነጋገር)

አስደናቂ ነገሮች
"አስገራሚ ነገሮች" ወይም "አስደናቂ ነገሮች"

Job 5:11

አጠቃላይ መረጃ:
ጸሐፊው በእያንዳንዱ ቁጥር ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን አንድን ሀሳብ ሁለት የተለያዩ መግለጫዎችን በመጠቀም የሚያስተላልፈው እግዚአብሔር የተጠቁትን ከወደቁበት እንደሚየነሳ እና ተንኮለኞችን እንደሚያወርድ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ይህንን የሚያደርገው ዝቅ ባለ ስፍራ ያሉትን ከፍ ለማድረግ ነው
የትሁታን መጎዳት የተገለጸው በዝቅተኛ ስፍራ እንደ ተቀመጡ ተደርጎ ነው። እግዚአብሔር በሚታደጋቸው ጊዜ፣ ክብርን ይቀበላሉ። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ከፍ ተደርገው በከበረ ስፍራ እንደተቀጡ ተደርጎ ይነገርላቸዋል። "እግዚአብሔር ይሰቃዩ የነበሩ ትሁታንን ለማዳን እና እነርሱን ለማክበር ይህንን ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

እቅዳቸውን ይሰብራል
እዚህ ስፍራ የተንኮለኞችን እቅድ ማስቆም የተገለጸው እነርሱ በአካል እንክት ተደርገው እንደሚሰበሩ ነገሮች ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ተንኮለኛ ሰዎችን በራሳቸው ክፉ ስራ ያጠምዳቸዋል
እዚህ ስፍራ ተንኮለኞችን በራሳቸው ክፉ ስራ እንዲጨነቁ ማድረግ የተገለጸው እነርሱን በወጥመድ እንመያዝ ተደርጎ ነው። የራሳቸው ድርጊቶች የተነገሩት እነዚያ ወጥመዶች እንደሆኑ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ጠመዝማዛ ሰዎች
እዚህ ስፍራ በብልጣብልጥነት የሚደረግ ክፋት የተገለጸው ጠመዝማዛ መሆን ተደርጎ ነው። "ብልጣብልጥ የሆኑ" ወይም "ቅን ያለሆኑ" ወይም "ብልጦች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 5:14

አጠቃላይ መረጃ:
ጸሐፊው በእያንዳንዱ ቁጥር ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን አንድን ሀሳብ ሁለት የተለያዩ መግለጫዎችን በመጠቀም የሚያስተላልፈው እግዚአብሔር ክፉ ሰዎችን እንሚያዋርድ እና ድሆችን እንደሚያድን ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በቀን ብርሃን ጨለማ ይገጥማቸዋል
እዚህ ስፍራ ለእግዚአብሔር የማይመቹ ክፉዎች እና ጨካኝ ሰዎች ፀሐይ በአናት ትክክል ሳለች፣ በቀን ብርሃን እነርሱ ግን በጨለማ ውስጥ እንደሚገኙ ይናገራል። ማድረግ የሚፈልጉትን አንዳች ነገር ማድረግ አይችሉም፣ ምክንያቱም ማየት አይችሉም። "ተንኮለኞች፣ በእኩለ ቀን እንኳን በጨለማ ውስጥ ናቸው" (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ዳበሳ
እንደ ዐይነ ስውር ዙሪያን መዳሰስ

እኩለ ቀን
የቀኑ እኩሌታ፣ ፀሐይ በአናት ትክክል የምትሆንበትና ከፍተኛ ብርሃኗን የምትሰጥበት ጊዜ

እርሱ ግን ደሃውን ከአንደበታቸው ካለ ሰይፍ ያድነዋል
እዚህ ስፍራ ሰዎች የሚናገሯቸው ስድቦች እና ማስፈራሪያዎች በአንደበታቸው ለይ የሚገኝ ሰይፍ እንደሆነ ተደርጎ ተገልጽዋል። "እርሱ ግን ደሃውን ከታላላቆች ማስፈራራት ያድነዋል" ወይም "እርሱ ግን ደሃውን ታላላቆች ሲያስፈራሩት ወይም ሰድቡት ይታደገዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ፍትህ አልባነት አንደበቷን ትዘጋለች
ፍትህ አልባ ሰዎች የተገለጹት መናገርን ማቆም ያለባቸው ተደርገው እና ራሱን ፍትህ አልባነትን ሆነው ነው። "ይህ ፍትህ አልባነት የራሷን አንደበት እንደምትዘጋ ያህል ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 5:17

አጠቃላይ መረጃ:
ጸሐፊው በቁጥር 18 እና 19 ላይ ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን አንድን ሀሳብ ሁለት የተለያዩ መግለጫዎችን በመጠቀም የሚያስተላልፈው የእግዚአብሔርን ቅጣት እና ፈውስ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ያስተካክላል... ሁሉን ቻይ የሆነው ይቀጣል
እዚህ ስፍራ እግዚአብሔር የቀረበው እንደሚያርም ወላጅ ወይም ልጅን እንደሚመራ ወላጅ ሆኖ ነው። እግዚአብሔር የሚያርመው ሰው የተባረከ ነው "እግዚአብሔር እርሱ የሚያርመውን ሰው በእርግጥም ተቀብሎታል"

አታቃል
"አትቃወም" ወይም "ጥቅም እንደሌለው ነገር አድርገህ አትቁጠር"

መቅጣት
"መምራት" ወይም "ማረም" ወይም "ስርአት ማስያዝ"

እርሱ ያቆስላል እርሱ ይጠግናል፣ እርሱ ያቆስላል ደግሞም የእርሱ እዶች ይፈውሳሉ
"እርሱ ቢያቆስልም እርሱ ይጠግናል፣ እርሱ ያደቃል የእርሱ እጆች ይፈውሳሉ"

እጆቹ ይፈውሳሉ
እዚህ ስፍራ "የእርሱ እጆች" የሚለው የሚገልጸው እግዚአብሔርን ነው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እርሱ ከስድስት ችግሮች ያድንሃል፤ በእርግጥ በሰባተኛው ችግር የትኛውም ክፉ አያገኝህም
ቁጥሮችን ከፍ እያደረጉ "ስድሰት" እና "ሰባት" እንደሚለው መጠቀም ብዙ ብዙ ጊዜ የሚለውን ሀሳብ ይወክላል። "እርሱ ደግሞ ደጋግሞ ከችግር ያወጣሃል፣ በእርግጥ፣ ከጊዜ ጊዜ አንዳች ክፉ አይነካህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 5:20

አጠቃላይ መረጃ:
በኢዮብ 5:19 የሚጀምረው "እርሱ" ከሚለው "አንተ" ወደሚለው የተዋላጠ ስም/የስም ምትክ ሽግግር ማድረግ እሰከ ኢዮብ 5:29 ማለትም የኤልፋዝ ንግግር እስከሚያልቅበት ድረስ ይቀጥላል። በረሃብ ጊዜ ይቤዥሃል እዚህ ስፍራ ማዳን የተገለጸው መቤዤት፣ መልሶ መግዛት እንደሆነ ተደርጎ ነው። "በርሃብ ጊዜ እግዚአብሔር ከአደጋ ያድንሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰይፍ እጆች
እዚህ ስፍራ "እጆች" ምናልባት የሚወክለው ሰይፎችን ጨምሮ በመሳሪያ ጥቃት የሚያደርሱ ሰዎችን ሊሆን ይችላል። "ጥቃት የሚያደርሱ ሰዎች" ወይም "አንተን የሚያጠቁ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ከጥፋት
እዚህ ስፍራ "ጥፋት" የሚለው የሚያመለክተው በጠላት መደምሰስን ነው። "ያገኘህ ማንኛውም ጠላት ያጠፋሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በጥፋት እና ረሃብ ላይ ትስቃለህ
እዚህ ስፍራ "ሳቅ" የሚለው የሚገልጸው አለመፍራትን ነው። "ማናቸውንም የጥፋት አደጋ ወይም ረሃብ አትፈራም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምልክታዊ/ትዕምርታዊ ቋንቋ የሚለውን ይመልከቱ)

የምድር አራዊት
ይህ የሚያመለክተው የዱር አራዊት ነው።"የዱር እንስሳት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 5:23

አጠቃላይ መረጃ:
ጸሐፊው በእያንዳንዱ ቁጥር ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን አንድን ሀሳብ ሁለት የተለያዩ መግለጫዎችን በመጠቀም ማቅረቡን የሚቀጥለው ደህንነትን ከተፈጥሮ ዓለም፣ ከቤት እና ከአንድ ሰው ትውልዶች ጋር በማያያዝ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በማሳህ ከሚገኙ ድንጋዮች ጋር ትዋዋላለህ
እዚህ ስፍራ በገበሬ ማሳ ውስጥ የሚገኙ ድንጋዮች የተገለጹት አንድ ሰው አብሯቸው የሚዋዋላቸው ሰዎች ተደርገው ነው። "በእርሻህ ውስጥ የሚገኙ ድንጋዮች በአንተ ላይ አንዳችም ችግር ላያመጡ ቃል እንደገቡ ሰዎች ይሆናሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የዱር አራዊት
ይህ አደገኛ የዱር አራዊትን ያመለክታል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ድንኳንህ በሰላም እንዳለ ታውቃለህ
እዚህ ስፍራ "ድንኳን" የሚወክለው የአንድን ሰው ቤተሰብ፣ ቤቱን፣ እና ያለውን ሀብት ሁሉ ነው። "ቤተሰብህ፣ አገልጋዮችህ፣ እና ያለህ ሁሉ በሰላም መጠበቁን ታውቃለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በረትህን ስትቃኝ አንዳች አይጎድልም
"ምሽት በረትህን ስትመለከት፣ መንጋህን በሙሉ በዚያ ታገኛለህ"

ዘርህ ታላቅ ይሆናል
እዚህ ስፍራ "ዘር" የሚለው የሚወክለው የአንድን ሰው ትውልዶች ነው። "ዘርህ ብዙ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ትውልድህ በምድር ላይ እንዳለ ሳር ይሆናል
እዚህ ስፍራ "ትውልድ" የሚለው የተገለጸው ታጭዶ እንደተከመረ ሳር ብዙ ተደርጎ ነው፤ ምናልባትም በብዙ እንዳደገ ሳር ተደርጎ ተገልጽዋል። "ትውልድህ እንደ ሚያድግ ሳር ብዙ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 5:26

እድሜ ጠግበህ ወደ መቃብር ትመጣለህ
"እጅግ አርጅተህ ትሞታለህ"

በጊዜው እንደሚሰበሰብ የእህል ነዶ
በዚህ ተነጻጻሪ ዘይቤ ሰብል የሚለው በሚገባ ደርሶ መታጨዱን ግልጽ ማድረግ ይቻላል። በእርጅና እድሜው ሲሞት በጣም ደካማ አይሆንም ወይም ደግሞ ያለ ጊዜውም እንደማይሞት። (ቅጽ 1 የትርጉም ማብራሪያ) እና (ቅጽ 1 የተነጻጻሪ ዘይቤ ትርጉም የሚሉትን ይመልከቱ)

እነሆ፣ ይህንን ጉዳይ እኛ መርምረነዋል፤ ነገሩ ይህን ይመስላል፣ አድምጥ መርምረህ ድረስበት
"እኛ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የኢዮብን ወዳጆች እንጂ ኢዮብን አይደለም። "እነሆ፣ እኛ ስለዚህ ጉዳይ አስበንበታል። የምነግርህን አድምጥና ነገሩ እወነት መሆኑን ተረዳ" (የሚያጠቃልል እና የማያጠቃልል "እኛ" የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 6

1 ኢዮብም ሲመልስ እንዲህም አለ፦ **2** ኦ ስቃዬ ምነው በተመዘነ ኖሮ! መከራዬም ሁሉ ምነው በሚዛን ላይ በተደረገ ኖሮ! **3** ከባሕር አሸዋ ይልቅ ይከብድ ነበርና ለዚህ ነው ቃሎቼ የድፍረት ቃላት የሆኑት። **4** ሁሉን የሚችል አምላክ ቀስት በውስጤ ነው፥ መርዙንም ነፍሴ ትጠጣለች፤ የእግዚአብሔር ማስደንገጥ በእኔ ላይ ተሰልፎአል። **5** በውኑ የሜዳ አህያ ሣር እያለው በዝለት ያናፋልን? በሬስ ገለባ እያለው በረህብ ይጮኻልን? **6** ጣዕም የሌለው ነገርስ ያለ ጨው ይበላልን? ወይስ በእንቁላል ውኃ ውስጥ ጣዕም አለን? **7** ለመንካት ሰውነቴ እምቢ አላቸው፤ እንደሚያስጸይፍ ምግብ ሆኑብኝ። **8** ምነው ልመናዬ በደረሰልኝ! እግዚአብሔርም መሻቴን ምነው በሰጠኝ! **9** እግዚአብሔርም አንድ ጊዜ እኔን ማጥፋት ደስ ቢያሰኘው እጁንም ዘርግቶ ከዚህ ሀይወት ቢያስወግደኝ! **10** ይህም መጽናናት ይሆንልኛል፤ በማይበርድ ሕመም ውስጥ ብሆንም፥ የቅዱሱን ቃል አልክድምና። **11** እድጠብቅ አቅሜ ምንድን ነው? የምታገሰውስ የህይወቴ ፍጻሜ ምን ስለሆነ ነው? **12** ጕልበቴ የድንጋይ ጕልበት ነውን? ወይስ ሥጋዬ የተሰራው ከናስ ነውን? **13** በእኔ ውስጥ ሊረዳኝ የሚችልነገር እንደሌለ ጥበብም ከእኔ እንደ ተባረረ እውነት አይደለምን? **14** ሁሉን የሚችል አምላክን መፍራት የተወ ሰው፥ በዝለት ሊወድቅ ለቀረበ ስንኳ ታማኝነት ከወዳጁ ሊሆንለት ይገባል። **15** ነገር ግን ወንድሞቼ ጥቂት ቆይቶ ውሃ እንደማይኖረው ɾ እንደ በረሃ ወንዝ የማይታመኑ ሆኑብኝ። **16** ከበረዶ የተነሣ ፥በውስጡም ከተሰወረው አመዳይ፤ **17** ሙቀትበመጣ ጊዜ ይደርቃሉ፤ በበጋም ወቅት ከስፍራቸው ይጠፋሉ። **18** ተጌዙ ነጋዴዎች ውሃ ፍለጋ መንገዳቸውን ሲቀይሩ፤ ወደ በረሃ ገብተው ተቅበዝብዘው ይጠፋሉ። **19** የቴማን ነጋዴዎች በዚያ ተመለከቱ፥ የሳባ መንገደኞችም ተስፋ አደረጉ። **20** ውሃ እንደሚያገኙ ተማምነው ነበርና አፈሩ፤ ወደዚያ ደረሱ፥ ነገር ግን ተታልለው ነበር። **21** አሁንም እናንተ እንዲሁ ደረቅ ሆናችሁብኝ መከራዬን አይታችሁ ለራሳችሁ ፈራችሁ። **22** በውኑ እኔ፦”አንዳች ነገር ስጡልኝ? ፤ ከሃብታችሁ ስጦታ አቅርቡልኝ? **23** ወይስ፦ ከጠላቴ እጅ አድኑኝ? ከአስጨናቂዎቼ እጅ ተቤዙኝ“ ብያችኋለሁን? **24** አስተምሩኝ፥ እኔም ዝም እላለሁ፤ ምን ጋር እንደተሳሳትሁ አስረዱኝ። **25** የእውነት ቃል እንዴት ያማል! ነገር ግን የእናንተ ሙግት እንዴት እኔን ይገሥጻል? **26** ተስፋ እንደ ሌለው ሰው ንግግር ቃሌን እንደ ነፋስ ችላ ለማለት ታስባላችሁን? **27** በርግጥ አባት አልባ በሆኑ ልጆች ላይ ዕጣ ትጣጣላላችሁ፤ ለወዳጆቻችሁም ጕድጓድ ትቈፍራላችሁ። **28** አሁንም፥ እባካችሁ፥ ወደ እኔ ተመልከቱ፤ በእርግጥ በፊታችሁ አልዋሸም። **29** እባካችሁ፥ ተመለሱ፤ ፍትህ አልባነት በእናንተ መካከል አይሁን፤ በርግጥ ምክንያቴ ጽድቅ ነውና መለስ በሉ። **30** በውኑ በምላሴ ክፋት አለን? አፌስ ተንኰልን መለየት አይችልምን?

Job 6:1

ምነው ጭንቀቴ ቢመዘን፣ ስጋቴ በሚዛን ላይ ቢቀመጥ
እዚህ ስፍራ ጸሐፊው አንድ ሃሳብን፣ ይኸውም የኢዮብን መከራ ሸክም ለመግለጽ ሁለት የተለያዩ አገላለጾችን ይጠቀማል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "መከራዬን መመዘን ብችል፣ ደግሞም ስጋቴን ሁሉ በሚዛን ላይ ባስቀምጥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

በሚዛን ላይ
"በመለኪያ ላይ"

ከባህር አሸዋ የከበደ ይሆናል
ኢዮብ የመከራውን ክብደት ከአሸዋ ክብደት ጋር ያነጻጽራል፤ ሁለቱም አንድን ሰው ማድቀቅ የሚችሉ ናቸው። "ጭንቀቴ እና ስጋቴ በባህር ዳር ካለ አሸዋ ይከብዳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ንግግሬ የማያስገርሙ ነበሩ
"በግዴለሽነት ተናገርኩ" ወይም "በችኮላ ተናገርኩ"

Job 6:4

አጠቃላይ መረጃ፡
ጸሐፊው በእያንዳንዱ ቁጥር አንድን ሃሳብ ለማስተላለፍ ሁለት የተለያዩ አገላለጾችን በመጠቀም የኢዮብን ከባድ መከራ ለማማረሩ መነሻ ምክንያት አድርጎ ለማጉላት ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን መጠቀሙን ይቀጥላል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ ቀስቶች በእኔ ስጋ ውሰጥ ናቸው
ይህ የኢዮብን መከራ የሚገልጽ ዘይቤ ነው። ብዙ መከራውን እግዚአብሔር በቀስቱ ገላውን እንደ ወጋበት ቀስት አድርጎ ያነጻጽረዋል። "መከራዬ ሁሉን ቻይ የሆነው ቀስቶችን ወደ አካሌ እንደወረወረ ያህል ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ነፍሴ መርዝ ተጎነጨች
"ነፍሴ የቀስቱን መርዝ ጠጣች።" ይህ መርዝ ያለባቸው መሆኑን በማመልከት እና ኢዮብ በመንፈሱ ስቃዩ የተሰማው መሆኑን በመግለጽ በቀስቱ የተነገረውን ዘይቤ ይቀጥላል። መከራውን ሲናገር መንፈሱ መርዝ እንደጠጣ አድርጎ ይገልጻል። "በውስጠኛው ሰውነቴ የመርዛቸው ስቃይ ይሰማኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር አስጨናቂነት በእኔ ላይ በተራ ተሰልፎብኛል
እግዚአብሔር ብዙ ነገሮች ኢዮብን እንዲያስጨንቅ ማድረጉ የተገለጸው፤ የእግዚአብሔር ማሰጨነቅ ኢዮብን ለማጥቃት እንደ ተሰለፉ ወታደሮች ተደርጎ ነው። "በሰራዊት ውስጥ እንደሚገኝ ወታደር የእግዚአብሔር ማስጨነቅ ራሱን አሰልፎብኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የሜዳ አህያ ሳር እያለው ያናፋል ወይስ በሬ ድርቆሽ እያለው እምቧ ይላል?
ኢዮብ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚያቀርበው ለማመረር ምክንያት እንዳለው ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። ይህ ጥያቄ በገለጻ መልክ ሊቀርብ ይችላል። "የሜዳ አህያ ሳር እያለው ካለ ምክንያት እንደማያናፋ ወይም በሬ ድርቆሽ/ገለባ እያገኘ በረሃብ እምቧ እንደማይል እኔም ምክንያት ባይኖረኝ ኖሮ ባላጉረመረምኩ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ማናፋት
አህያ የሚያሰማው ድምጽ

እምቧ ማለት
በሬ የሚያሰማው ድምጽ

ድርቆሽ/ገለባ
የእንስሳ ምግብ

ጣዕም የሌለው ካለ ጨው ሊበላ ይችላልን? ወይስ የእንቁላል ውሃ ይጣፍጣልን?
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ኢዮብ ባለበት ሁኔታ ደስ አለመሰኘቱን የሚያነጻጽረው ሰዎች ጣዕም የሌለውን ምግብ ካለመውደዳቸው ጋር ነው ወይም 2) ኢዮብ በወዳጆቹ ምክር ደስ አለመሰኘቱን የሚያነጻጽረው ሰዎች ደስ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የማያሰኝን ምግብ ካለመውደዳቸው ጋር ነው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ጣዕም የሌለው ካለ ጨው ሊበላ ይችላልን? ወይስ የእንቁላል ውሃ ይጣፍጣልን?
ኢዮብ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠቀመው የራሱን ደስ አለመሰኘት ለማጉላት ነው። ይህ ጥያቄ በገለጻ መልክ ሊቀርብ ይችላል። "በእንቁላል ውሃ ውስጥ ጣዕም እንደሌለ፣ ጣዕም የሌለው ምግብ ካለ ጨው ሊበላ አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ጣዕም የሌለው ሊበላ ይችላልን?
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ጣዕም የሌለውን መብላት ትችላለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 6:7

አጠቃላይ መረጃ:
ኢዮብ ስለ መከራው መናገሩን እና መሞት መፈለጉን በገለጸ መጠን በእነዚህ ቁጥሮች ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን መጠቀሙን ይቀጥላል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱን መንካት አልፈልግም
"እነርሱ" የሚለው የሚያመለክተው መጥፎ ጣዕም ያላቸውን ምግቦች ነው።

እኔን ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ለማድቀቅ
ይህ ማለት እግዚአብሔር እርሱ/ኢዮብ እንዲሞት ቢፈቅድ ማለቱ ነው። "ቢያደቀኝ እና እንድሞት ቢተወኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

ምነው ፈጥኖ እጆቹን ቢያነሳ እና ከዚህ ህይወት ቢቆርጠኝ
"ፈጥኖ እጆቹን ቢያነሳ" የሚለው ሀረግ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን በፍጥነት ማድረግን ይገልጻል። እንደዚሁም፣ "ከዚህ ህይወት ቢቆርጠኝ" የሚለው ሀረግ መግደል ለሚለው ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት/ ነው። "ምነው ፈጥኖ ህይወቴን በአጭር ቢቆርጠው" ወይም "ፈጥኖ መጨረሳዬን ቢያደርገው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት እና የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 6:10

ይህ እንኳን መጽናናት በሆነኝ ነበር
"ይህ መጽናናት ያምጣልኝ።" "ይህ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔር እርሱ/ኢዮብ እንዲሞት መፍቀድን ነው። "ሞቴ መጽናናት በሆነኝ" ወይም "መሞቴ ያጽናናኝ" (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በመከራዬ ብፈነድቅ እንኳን ይህም ጭምር ስቃዬን አይቀንሰውም
"ማብቂያ በሌለው ስቃይ ደስታን ላገኝ እቸኩላለሁ" ወይም "የማይጠፋ መከራ በጽናት እታገሳለሁ"

መፈንደቅ
"መደሰት"

አይቀንስም
"አይጠፋም"

የቅዱሱን ትዕዛዝ አልተላለፍኩም
"እግዚአብሔርን አልካድኩምና።" ይህ በአዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሁልጊዜም ቅዱሱን ታዝዣለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እታገስ ዘንድ ብርታቴ ምንድን ነው? ህይወቴ ይረዝም ዘንድ መጨረሻዬ ምንድን ነው?/ ህይወቴ ስለ ምን ይቀጥላል?
ኢዮብ እነዚህን ጥያቄዎች የሚያነሳው መኖርን እንዲቀጥል የሚያደርግ ምንም ምክንያት እንደሌለው ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። እነዚህ ጥያቄዎች ሁሉም ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። በገለጻ መልክ ሊጻፉ ይችላሉ። "በህይወት ለመቀጠል በቂ ጥንካሬ የለኝም፤ ህይወቴ የሚቀጥልበት ምንም ምክንያት የለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 6:12

አጠቃላይ መረጃ:
ጸሐፊው በእነዚህ በእያንዳንዳቸው ቁጥሮች ትይዩ ንጽጽራዊ ጥያቄዎችን የተጠቀመው ኢዮብ መከራውን ለመቋቋም አቅም ማጣቱን ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ብርታቴ የድንጋይ ጥንካሬ ነውን? ወይንስ ስጋዬ የተሰራው ከነሀስ ነው?
ኢዮብ የሰውነቱን ደካማነት ለማጉላት እንደ አለት እና ነሀስ ጠንካራ አይደለሁም በማለት ይገልጻል። እነዚህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች በገለጻ መልክ ሊቀርቡ ይችላሉ። "እንደ አለት ጠንካራ አይደለሁም። ስጋዬ እንደ ብረት ጠንካራ አይደለም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ.... በውስጤ እርዳታ የሚሆነኝ አለመኖሩ እውነት አይደለምን?
ኢዮብ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠቀመው እውቀት እንዳጣ እና ደካምነቱን አጉልቶ ለማሳየት ነው። እንደዚሁም ደግሞ፣ "በውስጤ እርዳታ የሚሆነኝ የለም" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። " እኔ...የቀረ አቅም የሌለኝ መሆኑ እውነት ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥበብ ከውስጤ ተሟጦ ወጥቷል
"ስኬቴ ከእኔ ተወስዷል።" ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ጥበቤ ከእኔ ርቋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 6:14

እያበቃለት/እየደከመ ላለ ሰው፣ ወዳጆቹ ታማኝነትን ሊያሳዩት ይገባል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አበቃልኝ/ደከምኩ ላለ ሰው ወዳጁ ታማኝ ሊሆንለት ይገባል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እየደከመ ያለ ማን ነው
ይህ የሚናገረው፣ በአካል እየደከመ የመጣ ስለሚመስል፣ ተስፋ ስለ ቆረጠ እና በችግሩ ስለተዋጥ ሰው ነው። "ተስፋ የቆረጠ ማን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉን ቻይ የሆነውን ፍርሃት ለሚፈልግ እንኳን
"ሁሉን ቻይ የሆነውን አምላክ መፍራት ቢያቆም እንኳን።" ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የደከመ/ያበቃለት ሰው እግዚአብሔርን አይፈራም ወይም 2) የእርሱ ወዳጆች እግዚአብሔርን አይፈሩም

ወንድሞቼ ለእኔ የነበራቸው ታማኝነት እንደ በረሃ ጅረት ነበር
ኢዮብ ወዳጆቹ ለእርሱ ታማኝ አለመሆናቸውን የሚገልጸው በድንገት እንደሚደርቅ "በክረመት እንደሚሞላ ደረቅ ወንዝ" ነው። እንደዚሁም ኢዮብ እዚህ ስፍራ ወዳጆቹን በምጽት "ወንድሞች" እያለ ይገልጻቸዋል። "ወዳጆቼ ለእኔ ታማኝ አይደሉም። እነርሱ እንደ በረሃ ጅረት ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ምጽት የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወዴትም እንደማይደርስ የውሃ ቦይ
"እንደሚደርቅ ጅረት ውሃ።" ኢዮብ ስለ ወዳጆቹ እንደ ሚደርቅ ወራጅ ሊታመኑባቸው የማይቻል መሆኑን መናገሩን ይቀጥላል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ደግሞም ራሱን በውስጣቸው ከሚደበቀው በረዶ የተነሳ...በላያቸው ካለው በረዶ የተነሳ የሚጠቁሩ/የሚደፈርሱ
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ወራጁ ውሃ/ትንሽ ወምዝ በክረምት እንዴት በበረዶ እንደተሞላ ይገልጻሉ። "በክረምት በበረዶ በመሸፈናቸው ጠቁረው/ደፍርሰው ይታያሉ፤ ደግሞም በቀለጠው በረዶ/አመዳይ ይሞላሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከበረዶው የተነሳ ራሱን በእነርሱ ውስጥ የሚደብቅ
ይህ የሚናገረው በረዶው እየቀለጠ ራሱን በወራጁ እንደሚደብቅ ውሃው ወደ ወንዙ እንደሚሄድ ነው። "ምክንያቱም በረዶው እየቀለጠ ወደ እነርሱ ይሄዳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አየሩ ሲሞቅ/በጋ ሲመጣ፣ ይጠፋሉ... ሞቃት ሲሆን ከስፍራቸው ይቀልጣሉ
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሰይ ትርጉም አላቸው። በበጋ/በሞቃቱ ወቅት ወራጁ ወንዝ እንዴት እንደሚደርቅ ይገልጻሉ። "በጋ ሲመጣ፣ በረዶ ይቀልጣል ወራጁም ወንዝ ይደርቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 6:18

አያያዥ ሀሳብ
ኢዮብ ወዳጆቹ እንደሚደርቅ ወራጅ ውሃ ሊታመኑባቸው የማይቻል መሆኑን መግለጹን ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሲራራ/ተጓዥ ነጋዴዎች ውሃ ፍለጋ መንገዳቸውን ይቀይራሉ
"ሲራራ ነጋዴዎች መንገዳቸውን የሚቀይሩት ውሃ ፍለጋ ነው" ወይም "ሲራራ ነጋዴዎች ውሃ ለማግኘት የሚጓዙበትን መንገድ ይቀይራሉ"

ሲራራ ነጋዴዎች
በረሃ አቋርጠው ግመል እየነዱ በርካታ የሆኑ ተጓዦች ናቸው

በረሃ
"ጠፍ መሬት" ወይም "ምንም የሌለበት መሬት"

ቴማን..ሳባ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። የእነዚህ ስፍራዎች ሰዎች በሌላ አገር ከሚኖሩ ሰዎች ጋር ነገሮችን ለመነገድ ቅፍለት/ብዙ ግመሎች ይጠቀማሉ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የሳባ መንገደኞች
"ከሳባ የሚመጡ መንገደኞች"

በእነርሱ ተስፋ ያደረጉ
"በእነርሱ ላይ ተስፋ ያደረጉ" ወይም "ተስፋቸውን በእነርሱ ላይ የጣሉ"

ነገር ግን ተታለው ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ነገር ግን እነርሱ ተስፋ ቆርጠው ነበር" ወይም "ነገር ግን እነርሱ አልረኩም ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 6:21

አጠቃላይ መረጃ:
በእነዚህ ቁጥሮች ኢዮብ ወዳጆቹን ለመገሰጽ እና ከእነርሱ አንዳች እርዳታ አለመጠየቁን ለማጉላት አራት ጥያቄዎችን ያነሳል። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

አሁንም
ኢዮብ ይህንን ሀረግ የሚጠቀመው እየተናገረ የሚገኘውን ነገር ዋና ክፍል ለመጀመር ነው

እናንተ ወዳጆቼ ለእኔ አንዳች አላደረጋችሁም
"የእናንተ ወዳጅነት ለእኔን ምንም አልባችም"

ፈርታችኋል
ይህ ማለት ኢዮብ ያለበትን ችግር አይተዋል፤ እናም በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ እንዳይገቡ ፈርተዋል። "እግዚአብሔር ተመሳሳይ ነገር ያደርስብናል ብላችሁ ፈርታችኋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተን ‘አንዳች ነገር አድርጉልንኝ ብያችኋለሁ?' ወይስ፣ ‘ከሀብታችሁ ስጦታ ስጡኝ ብያችኋለሁ?' ወይስ፣ ‘ከጠላቴ እጅ አድኑኝ ብያችኋለሁ?' ወይስ ‘ከጨቆነኝ እጅ ተቤዙኝ ብያችኋለሁ?'
ኢዮብ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው እርሱን ወዳዶቹ አንድም ነገር እንዲሰጡት ወይም እንዲያደርጉለት አለመጠየቁን ለማጉላት ነው። "ገንዘብ ወይም ስጦታ እንድትሰጡን ጠየቅኳችሁን። ወይንስ ከጠላቶቼ ወይም ከጨቋኞቼ እንድታድኑኝ ጠይቄያችኋለሁ።በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ከጠላቶቼ እጅ እንድኑኝ...ከጨቋኞቼ እጅ ተቤዙኝ
እነዚህ ሁለቱም አገላለጾች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። እንደዚሁም፣ እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚወክለው ሃይልን ወይም መቆጣጠርን ነው። "ከጠላቶቼ ወይም ከጨቋኞቼ አድኑኝ" ወይም "ከባላኝጣዎቼ አድኑኝ" በሚው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ዘይቤያዊ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

ተቤዙኝ
"አድኑኝ"

Job 6:24

አስተምሩኝ...አድርጉልኝ
እዚህ ስፍራ "አስተማረ" እና "አደረገ" የሚሉት ግሶች የተጻፉት በሁለተኛ መበድ ብዙ ቁጥር ሲሆን የሚገልጹትም የእርሱን/ኢዮብ መዳጆች ነው። (አንተ የሚለው ተውላጠ ስም ልዩ ልዩ መለኮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰላሜን እይዛለሁ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ዝም እላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእውነት ቃላት ምን ያህል ይከብዳሉ! የእናንተ ንግግር ግን እንዴት አድርጎ በእርግጥ እኔን ሊቃወም/ሊወቅስ ይችላል?
የመገኛ ቋንቋው/ዋናው ቋንቋ ትክክለኛ ትርጉም በእርግጠኝነት አይታወቅም። አንዳንድ ቅጂዎች "እንዴት ያስጨንቃሉ" ብለው የሚተረጉሙት "እንዴት ደስ ያሰኛሉ" እንደማለት ነው። "አንድ ሰው እውነቱን ሲፈልግ፣ ይህ ማንንም አይጎዳም። የእናንተ ክርክር ግን ዕውነት አይደለም ስለዚህም እንዴት አድርጎ እኔን ሊገስጸኝ ይችላል?" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ነገር ግን የእናንተ ክርክር፣ በእርግጥ እንዴት እኔን ሊገስጸኝ ይችላል?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ወዳዶቹን ለመገሰጽ እና እነርሱ የሚናገሩት ነገር በእርሱ ላይ እንደማይሰራ/ትክክለኛ እንዳልሆነ ትኩረት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ በገለጻ መልክ ሊጻፍ ይችላል። "እናንተ እኔን ለመገሰጽ

በምታቀርቧቸው ምክንያቶች ምንም እንኳን በጥብቅ ልታርሙኝ ብትሞክሩም በእኔ ላይ ግን አይሰሩም/እውነትነት የላቸውም::" ወይም "በእኔ ላይ የምታቀርቡት ክርክር ዕውነት አይደለም፣ ስለዚህም ነገራችሁ በእርግጥ ሊገስጸኝ አይችልም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በእርግጥ ይቅር በሉኝ
x

የእናንተ ክርክር
"የምታቀርቧቸው ምክንያቶች" ወይም "እናንተ ነው የምትሉት"

Job 6:26

ቃሌን ቸል ልትሉ ታስባላችሁ፣ ተስፋ የቆረጠውን ሰው ቃል እንደ ነፋስ ታዩታላችሁን/ ትቆጥራላችሁን?
ኢዮብ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ወዳጆቹን ለመገሰጽ ነው:: የእርሱን ቃላት ከነፋስ ጋር የሚያነጻጽረው፣ የወዳጆቹን ድርጊት እንደ እርሱ ቃላት ባዶ እና ረብ የሌላቸው መሆኑን ለማብራራት ነው:: "እናንተ ቃሌን ቸል ብላችኋል! እኔ ተስፋ የቆረጥኩ ሰው ነኝ፣ እናንተ ደግሞ ቃሎቼን እንደ ነፋስ እርባና ቢስ አድርጋችሁ ታያላችሁ::" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

እናንተ
"እናንተ" ሁለተኛ መደብ ብዙ ቁጥር ነው:: (አንተ የሚለው ተውላጠ ስም ልዩ ልዩ መለኮች የሚለውን ይመልከቱ)

አባት በሌላቸው ልጆች ላይ ዕጣ ትጣጣላላችሁ
"ወላጅ አልባን ለማሸነፍ ቁማር እንኳን ትጫወታላችሁ"

እጣ ትጥላላችሁ... በወዳጆቻችሁ ላይ ትከራከራላችሁ
እዚህ ስፍራ "እናንተ" እና "የእናንተ" የሚሉት በሁለተኛ መደብ ብዙ ቁጥር የተጻፉ ናቸው:: (አንተ የሚለው ተውላጠ ስም ልዩ ልዩ መለኮች የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ሸቀጥ ንግድ በወዳጆቻችሁ ላይ ትከራከራላችሁ
ይህ አንድ ሰው ሸቀጥ እንደሚሸጥ እንዴት ወዳጁን እንደሚሸጠው ያነጻጽራል:: "ወዳጆቻችሁን በገንዘብ ለመሸጥ ትከራከራላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 6:28

አሁን
ኢዮብ ይህንን ቃል የተጠቀመው አዲስ መረጃ ለመስጠት/ለማስተዋወቅ ነው::

እባካችሁ ተመልከቱ
"ተመለከተ" የሚለው ግስ በሁለተኛ መደብ ብዙ ቁጥር የተጻፈ ነው:: (አንተ የሚለው ተውላጠ ስም ልዩ ልዩ መለኮች የሚለውን ይመልከቱ)

በፊታችሁ አልዋሸም
"እናንተ" የሚለው ቃል የኢዮብን ወዳጆች ያመለክታል:: እዚህ ስፍራ የእርሱ ወዳጆች የተወከሉት በእነርሱ ፊት በሚለው ነው፤ ይህም ያገለገለው እርሱን እየተመለከቱት መሆኑን አጉልቶ ለመግለጽ ነው:: "ፊት ለፊት እየተመለከትኳችሁ ልዋሻችሁ አልችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ይቅር እንድትሉኝ እለምናችኋለሁ
"እባካችሁ ይቅር በሉኝ" ወይም "እባካችሁ እኔ የምለምናችሁ፣ እንዲህ መናገራችሁን እንድታቆሙ ነው"

ፍርደ ገምድልነታችሁን ከእናንተ አስወግዱ
ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊጻፍ ይችላል:: "ቅን ፍረዱ" (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 7

1 ለእያንዳንዱ ሰው ህይወት በምድር ብርቱ ልፋት አይደለምን ቀኖቹስ እንደ ተቀጣሪ ሰራተኛ ቀኖች አይደሉምን **2** የምሽት ጥላን እንደሚመኝ አገልጋይ፤ደመወዙንም በጽኑ እንደሚፈልግ ቅጥረኛ፤ **3** እንዲሁ የጉስቁልና ወራትና፤ መከራ የተሞሉ ለሊቶችን በጽናት እንዳልፍ ተሰጡኝ። **4** በተኛሁ ጊዜ፦ መቼ እነሣለሁ? ሌሊቱስ መቼ ያልፋል እላለሁ። እስኪነጋ ድረስም ወዲያና ወዲህ እገላበጣለሁ። **5** ሥጋዬ ትልና የአመድ ቅርፊት ለብሶአል፤ ደርቆ የነበረው የቆዳዬም ቁስል እንደ ገና ያመረቅዛል። **6** ቀኖቼ ከሸማኔ መወርወርያ ይልቅ ፈጣን ናቸው፥ ያለ ተስፋም ያልፋሉ። **7** ሕይወቴ አንድ ትንፋሽ እንደ ሆነ፤ ዓይኔም መልካም ነገርን ከእንግዲህ አንደማያይ አሳሰበኝ። **8** የሚያየኝ የእግዚአብሔር ዓይን ከእንግዲህ ወዲህ አያየኝም፤ ዓይኖችህ በእኔ ላይ ይሆናል፥ እኔ ግን አልገኝም። **9** ደመና ተበትኖ እንደሚጠፋ፥ እንደዚሁ ወደ ሲኦል የሚወርድ ተመልሶ አይወጣም። **10** ወደ ቤቱ ዳግመኛ አይመለስም፥ የነበረበት ስፍራውም ዳግመኛ አያውቀውም። **11** ስለዚህም አፌን አልገድበውም፤ በመንፈሴ ስቃይ ሆኜ እናገራለሁ፤ በነፍሴ ምሬት በጎዘን አቤቱታዬን አቀርባለሁ። **12** ጠባቂ በላዬ ትቀጥርብኝ ዘንድ፥ እኔ ባሕር ወይስ የባህር አውሬ ነኝን? **13** እኔም፦ "አልጋዬ ያጽናናኛል፥ መቀመጫዬም የጎዘን እንጒርጒሮዬን ያቀልልኛል" ባልሁ ጊዜ፥ **14** አንተ በሕልም ታስፈራራኛለህ፥ በራእይም ታስደነግጠኛለህ፤ **15** ስለዚህም እኔ አጥንቴን ከምታገስ ይልቅ መታነቅንና ሞትን እመርጣለሁ። **16** ለዘላለም መኖርን እንዳልመኝ፤ ሕይወቴን ናቅኋት። ቀኖቼ ዋጋ ቢስ ናቸውና እባካችሁ ተዉኝ። **17** ትኩረት ትሰጠው ዘንድ ፥ልብህንስ ትጥልበት ዘንድ ሰው ምንድር ነው፥ **18** ማለዳ ማለዳስ ትጐበኘው ዘንድ፥ በየጊዜውስ ትፈትነው ዘንድ? **19** የማትተወኝ እስከ መቼ ነው? ምራቄንስ እስክውጥ ድረስ የማትለቅቀኝ እስከ መቼ ነው? **20** ሰውን የምትጠብቅ ሆይ፥ ኀጢያትንስ አድርጌ እንደ ሆነ ይህ ላንተ ምንድን ነው? ሸክም እ ሆንብህ ዘንድ? ስለ ምን የኢላማህ ግብ አደረግኸኝ? **21** መተላለፌን ይቅር ብለህ ስለ ምን ጉስቁልናዬን አታስወግድልኝም? አሁን በምድር ውስጥ እተኛለሁ፤ በጥንቃቄም ትፈልገኛለህ፥ አታገኘኝም።

Job 7:1

አጠቃላይ መረጃ:
ጸሐፊው በእነዚህ በእያንዳንዳቸው ቁጥሮች ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚጠቀመው አንድን ሀሳብ በሁለት የተለያዩ ገለጻዎች ለማስተላለፍ ሲሆን፣ የእርሱ ግላዊ መከራ ሁሉም ሰው የሚደርስበት የጋራ መከራ ክፍል መሆኑን ትኩረት ለመስጠትም ይጠቀምበታል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰው በምድር ላይ ከባድ ስራ የለበትምን?
ኢዮብ ይህንን አሉታዊ ጥያቄ የሚያቀርበው፣ ሁሉም ሰው ከባድ ስራ እንደሚሰራ የእርሱን ግንዛቤ ለማጉላት ነው። ይህ በአዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "በምድር ላይ እያንዳንዱ ሰው የሚሰራው ከባድ ስራ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በምድር ላይ
ይህ ሰው በምድር ላይ በሚኖርበት ጊዜ ለሚለው አጠቃላይ አስተያየት ነው። "በምድር በሚኖርበት ዘመን" (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

ዘመኑ እንደ ምንደኛ/ለእለት ስራ ተቀጣሪ/ ዘመን አይደለምን?
ኢዮብ ይህንን አሉታዊ ጥያቄ የሚያቀርበው ሁሉም ሰው በህይወት ውስጥ ትግል እንዳለበት ያለውን ግንዛቤ በትኩረት ለማቅረብ ነው። "ቀናቸው እንደ የእለት ተቀጣሪ ሰው ቀናት ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

እንደ አንድ ባሪያ... ልክ እንደ የእለት ተቀጣሪ ሰው... እኔ እንደዚያ ነበርኩ...በመከራ የተሞሉ ምሽቶች የተሰጡኝ
ኢዮብ መከራውን እና ችግሩን ከባሪያና ከተቀጣሪ ሰው ጋር ያነጻጽራል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የምሽት ጥላ
"ቀዝቃዛ ጥላ።" በስውር የተጠቆመው መረጃ የምሽት ጥላ ቅዝቃዜን ይሰጣል፣ ደግሞም ከፀሐይ ይከልላል የሚለው ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የተቀጠረ ሰው/ተቀጣሪ
"የቀን ሰራተኛ።" ይህ ለአንድ ቀን ስራ የተቀጠረ እና በእያንዳንዱ በሰራበት ቀን መጨረሻ ላይ የሚከፈለው ሰው ነው።

የሰራበትን እንደሚጠብቅ
"ክፍያውን እንደሚጠብቅ"

እኔም፣ መከራ የበዛባቸውን ምሽቶች አግኝተውኛል፣ የወራት መከራን እንድታገስ ተደርጌያለሁ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ስለዚህም የወራት መከራ ታግሻለሁ፤ መከራ የባዘባቸው ምሽቶች ገጥመውኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ እና ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የመከራ ወራት/ጊዜያት
"መከራ" የሚለው ረቂቅ ስም "መከረኛ" በሚል ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። "የመከራ ወራት/ጊዜያት" ወይም "ከንቱ ወራት/ጊዜያት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 7:4

ጋድም በምልበት ጊዜ
በውስጠ ታዋቂነት የቀረበው መረጃ ኢዮብ በምሽት ለመተኛት ጋድም በሚልበት ጊዜ ማለት ነው። "ለመተኛት ጋደም በምልበት ጊዜ" (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለራሴ እንዲህ እላለሁ
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ በተለይ ለሌላ ለማንም ሰው አያቀርብም። "እኔ እጠይቃለሁ" ወይም "እኔ እገረማለሁ" (ከባለቤቱ ጋር የሚጣቀስ ተውላጠ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

መቼ ከመኝታዬ እነሳለሁ መቼ ለሊቱ ይነጋል?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው መተኛት ባለበት ሰአት ምን ያህል መከራው ጽኑ እንደሆነ አጉልቶ ለመግለጽ ነው። "ከመኝታዬ መነሳት ብችል እወዳለሁ፣ ነገር ግን ምሽቱ አይነጋም/ይቀጥላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ፊት እና ወደ ኋላ ስገላበጥ
"ወደ ኋላ እና ወደፊት ስዘዋር።" ይህ የሚያመለክተው ኢዮብ ካለ አንዳች እንቅልፍ ሌሊቱን በመኝታው ላይ ሲገላበጥ እንደሚያድር ነው።

ስጋዬ በትሎች እና በአቧራ ጓል ተሸፍኗል
ትሎቹ እና የአቧራው ጓል ብዛት የተገለጸው ልብስ ሆነው እንደ ሸፈኑት ተደርጎ ነው። "ስጋዬ በትሎች እና በአቧራ ተሸፍኗል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ስጋዬ
ይህ መላ አካሉን ያመለክታል። "መላ አካሌ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የአቧራ ጓል
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ አማራጭ ትርጉሞች 1) የእድፍ ቅርፊት ወይም ጓል ወይም 2) በቆዳ ላይ ቅርፊት/ማፈክፈክ

አመርቅዟል
"ዳግም ቆስሏል"

Job 7:6

አጠቃላይ መረጃ:
ጸሐፊው የኢዮብን የእድሜ ጥቂትነት ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ እንዲሁም አንድን ሀሳብ ሁለት የተለያዩ ገለጻዎችን በመጠቀም ለማስተላለፍ በእነዚህ በእያንዳንዳቸው ቁጥሮች ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ መጠቀሙን ይቀጥላል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀኖቼ/ዘመኔ ከሸማኔ መወርወሪያ ይልቅ ፈጣኖች ናቸው
ኢዮብ ህይወቱን ከሸማኔ መወርወሪያ ፈጣንነት ጋር ያነጻጽራል። "ህይወቴ በጣም በቶሎ ያልፋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሸማኔ
ክር በማዳወር ልብስ የሚሰራ ሰው

የሸማኔ መወርወሪያ
ክሩን የሚይዘው ተንቀሳቃሽ ክፍል፣ ወይም ልብሱ ሲሰራ ከሸማኔው ዕቃ ውስጥ ክሩ ወደፊት እና ወደ ኋላ በፊጥነት እንዲንቀሳቀስ የሚያደርግ

አስብ
"አስታውስ።" "አስብ" የሚለው ሀረግ እግዚአብሔር ይረሳል ማለት አይደለም። ኢዮብ የህይወቱ ዘመን ጥቂት መሆኑን እግዚአብሔር እንዲያይለት እየጠየቀ ነው።

ህይወቴ የእስትንፋስ ያህል ናት
ኢዮብ የህይወቱን ጥቂትነት ከእስትንፋስ አጭርነት ጋር ያነጻጽራል። "ህይወቴ የአንዲት እስትንፋስ ያህል አጭር ናት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህ ዐይኖቼ አንዳች መልካም ነገር አያዩም
እዚህ ስፍራ "ዐይኖቼ" የሚለው የሚወክለው የኢዮብን መላ ሰውነት እና ነገሮችን የማየት ወይም የማድረግ ችሎታ ነው። "ዳግም በፍጹም መልካም ነገር አላይም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 7:8

አጠቃላይ መረጃ:
ጸሐፊው ኢዮብ ከሞት በኋላ እግዚአብሔርም ሆነ እርሱን የሚያውቁት ሰዎች ዳግም እንደማያዩት ያለውን ሀሳብ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ እንዲሁም አንድን ሀሳብ ሁለት የተለያዩ ገለጻዎችን በመጠቀም ለማስተላለፍ በእነዚህ በእያንዳንዳቸው ቁጥሮች ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ መጠቀሙን ይቀጥላል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሚመለከተኝ የእግዚአብሔር ዐይን ከእንግዲህ አያየኝም
በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ይህንን "የሚመለከቱኝ ዐይኖች ከእንግዲህ አያዩኝም" በሚል ተርጉመውታል። "የእግዚአብሔር" ቃሎች በዚህ ሀረግ ላይ የተጨመሩት በይዘቱ ውስጥ የተካተቱ/የተጠቆሙ በመሆኑ ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የሚመለከተኝ የእግዚአብሔር ዐይን... የእግዚአብሔር ዐይን በእኔ ላይ ይሆናል
እዚህ ስፍራ እግዚአብሔር ምን እንደሚመለከት ትኩረት ለመስጠት የተወከለው በእርሱ "ዐይን" ነው። "እኔን የሚመለከት እግዚአብሔር... እግዚአብሔር ይመለከተኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ደመና እንደሚበን እና እንደሚጠፋ፣ ወደ ሲኦል የሚወርድ ዳግም አይመለስም
ኢዮብ ሞትን የሚገልጸው በኖ እንደሚጠፋ ደመና ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚልን ይመልከቱ)

ደመና እንደሚበተን
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ደመና እንደሚበን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ሲኦል የሚወርድ ዳግም አይመለስም
"የሞተ ተመልሶ አይመጣም"

በእርሱ ስፍራ/በስፍራው
"በእርሱ ስፍራ" የሚሉት ቃላት በእርሱ ስፍራ የሚኖሩትን ይወክላል። "በእርሱ ስፍራ የሚኖሩ ሰዎች" ወይም "የእርሱ ቤተሰቦች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 7:11

በመንፈሴ ጭንቀት እናገራለሁ፣ በነፍሴን መራርነት አማርራለሁ
ኢዮብ ዝም የማይልበትን ምክንያት ለማጉላት ሁለት የተለያዩ ገለጻዎችን በመጠቀም አንድን ሃሳብ ያስተላልፋል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አፌን አላቅብም
እዚህ ስፍራ አፍ የሚወክለው ንግግርን ነው። "ንግግሬን አልገድብም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በመንፈሴ ምሬት
"በመንፈሴ ሀዘንተኝነት" ወይም "በመከራዬ ስቃይ።" "ጭንቀት" የሚለውን ረቂቅ ስም "ስቃይ" የሚለውን ተውሳከ ግስ ተጠቅሞ መተርጎም ይቻላል። "መንፈሴ ተጨንቆ ሳለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በነፍሴን መራርነት
እዚህ ስፍራ ሀዘን የተገለጸው መራራ ጣዕም እንዳለው ተደርጎ ሲሆን፣ "ነፍስ" ደግሞ የሰውን ሁለንተና የሚያመለክት ሆና ተነግራለች። "በቁጣ እና ቅር በመሰኘት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

በእኔ ላይ ጠባቂ ታኖር ዘንድ እኔ ባህር ነኝ፣ ወይንስ የባህር አውሬ ነኝ?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚያቀርበው በእግዚአብሔር ላይ ማዘኑን ለመግለጽ ነው። ኢዮብ ራሱን ከባህር ወይም ከባህር አውሬ ጋር በማነጻጸር እግዚአብሔር እርሱን አሰቃቂ ፍጥረት አድርጎ እንደቆጠረው ይናገራል። ይህ በገለጻ ሊተረጎም ይችላል። "እኔ ጠባቂ የሚያስፈልገው የባህር አውሬ ወይም ባህሩን አይደለሁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Job 7:13

አጠቃላይ መረጃ፡
ጸሐፊው የኢዮብን ጥልቅ መከራ ለማጉላት ሁለት የተለያዩ አገላለጾችን በመጠቀም እንድን ሃሳብ ለማስተላለፍ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ቁጥሮች ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን መጠቀሙን ይቀጥላል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መኝታዬ ያጽናናኛል፣ መከዳዬ ማጉረምረሜን ቀለል ያደርግልኛል
እዚህ ስፍራ "መኝታ/አልጋ" እና "መከዳ" የሚሉት "እንቅልፍ" ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ኢዮብ ለመተኛት ጋደም ሲል አረፍ ለማለት ተስፋ ያደርጋል። ይህ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሰብአዊ ባህሪያትም ደግሞ አሉት፤ የማጽናናት እና ሰውን አረፍ የማድረግ አቅም አላቸው። "መኝታዬ እና መከዳዬ እንደ ሰው ያሉ ነገሮች ናቸው።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

አልጋዬ/መኝታዬ... መከዳዬ
እነዚህ ሀረጋት ተመሳሳይ ነገርን ያመለክታሉ፡ "አልጋዬ...መኝታዬ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

አንተ አሰደነገጥከኝ/አስፈራኸኝ
እዚህ ስፍራ "አንተ" የሚለው የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው

ማነቅ
አንድን ሰው ጉሮሮውን ጨምቆ እና ትንፋሹን አቁሞ መግደል

እነዚህ የእኔ አጥንቶች/አጥንቶቼ
እዚህ ስፍራ ኢዮብ "አጥንቶች" የሚለውን ቃል የተጠቀመው አካሉን ለማመልከት ነው። "ይህ የእኔ አካል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስነክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 7:16

አያያዥ ሃሳብ፡
ጸሐፊው የኢዮብ መከራ በእርሱ ማንነት እርባና ግንዛቤ ላይ ትኩረት ለመሰጠት ሁለት የተለያዩ አገላለጾችን በመጠቀም እንድን ሃሳብ ለማስተላለፍ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ቁጥሮች ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን መጠቀሙን ይቀጥላል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ህይወቴን ጠላሁ
"ህይወቴን ናቅኩት"

ሁሌም በህይወት ለመኖር
"ለዘለአለም ለመኖር"

ቀናቴ/ዘመኔ እርባና ቢስ ናቸው
"ዘመኔ አለ ፍሬ ነው" ወይም "የህይወቴ ቀናት ከንቱ/ባዶ ናቸው"

ትከታተለው ዘንድ .... ሰው ምንድን ነው?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው እግዚአብሔር ለሰው ለምን ትኩረት እንደሚሰጥ መደነቁን ለማጉላት ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ትከታተለው ዘንድ...ሰው ምንድን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ልብህን ታሳርፍበት ዘንድ
እዚህ ስፍራ ልብ/አእምሮ የመሚለው የሚወክለው ሃሳብን እና ትኩረት መስጠትን ነው። "ልብህን ታሳርፍበት ዘንድ" ማለት ትኩረት መስጠት ማለት ነው። "ትኩረትህን ወደ እርሱ ታደርግ ዘንድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

እርሱን ተመልከተው
"እርሱን በጥንቃቄ መርምረው"

Job 7:19

ምራቄን ለመዋጥ...ይህ ለምን ያህል ጊዜ ይሆና?
እዚህ ስፍራ ኢዮብ ሁለት የተለያዩ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎችን በመጠቀም አንድን ሀሳብ የሚገልጸው እግዚአብሔር እርሱን መከታተሉን ቢያቆም ደስ እንደሚለው ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። "እኔን መከታተልህን አቁም! የራሴን ምራቅ የምውጥበትን ያህል ጊዜ እንኳን ፋታ ስጠኝ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

ምራቅ
አፍ እርጥበቱን እንዲጠብቅ እና ምግብን ለመዋጥ የሚረዳ በሰዎች አፍ ውስጥ የሚፈጠር ፈሳሽ

ኃጢአት ብሰራ እንኳን ... ሸክም ሆንኩብህ?
ኢዮብ እነዚህን ጥያቄዎች የሚያቀርበው እግዚአብሔር የማይገባ ነገር እንዳደረሰበት ከእርሱ ጋር ለመከራከር ነው። " ኃጢአት ብሰራ እንኳን፣ አንተ ሰዎችን ሁሉ ስለምታይ ያ በአንተ ላይ አንዳች አያደርግም። ሸክም እሆንብህ ዘንድ፣ ለምን ኢለማህ እንዳደረግከኝ ንገረኝ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 7:21

ስለ ምን መተላለፌን ይቅር ብለህ በደሌን ከእኔ አታርቅም?
እዚህ ስፍራ ኢዮብ ከቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ ጋር ሃሳቡን ለማጉላት ሁለት ተመሳሳይ ሐረጎችን ይጠቀማል። ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች፡ 1) ኢዮብ ለምን እግዚአብሔር ይቅር እንደማይለው ይጠይቃል። "መተላለፌን ለምን ይቅር እንደማትለኝ እና ኃጢአቴን እንደማታርቅልኝ ንገረኝ።" ወይም 2) ኢዮብ እግዚአብሔርን ምናልባት በድዬ ቢሆን እንኳን ለምን ስህተቴን እንዳላየህ ሆነህ አታልፈኝም። "በደሌን እና መተላለፌን ለምን እንዳልተውክልኝ ንገረኝ።" በሚሉት ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

ውሰድ/አርቅ
"አስወግድ"

አሁን በአፈር ውስጥ እጋደማለሁን
"በአፈር ውስጥ መጋደም" የሚለው ሀረግ ሞትን የሚወክል ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "እኔ አሁን እሞታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በህይወት አልኖርም
"እዚህ አልሆንም" ወይም "እኔ እሄዳለሁ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 8

1 ሹሐዊውም በልዳዶስ መለሰ እንዲህም አለ፦ **2** እስከ መቼ እነዚህን ነገሮች ትናገራለህ? የአፍህስ ቃል እስከ መቼ እንደ ብርቱ ነፋስ ይሆናል? **3** በውኑ እግዚአብሔር ፍትህን ያቃውሳልን? ሁሉንም የሚችል አምላክ ጽድቅን ያጣምማልን? **4** ልጆችህ በድለውት እንደ ሆነ፥ እርሱም በበደላቸው እጅ አሳልፎ እንደሰጣቸው እናውቃለን። **5** ነገር ግን እግዚአብሔርን በትጋት ብትፈልገውና፥ ሁሉንም ለሚችለው አምላክ ልመናህን ብታቀርብ፥ **6** ንጹሕና ቅን ብትሆን፥ በእውነት እርሱ ስለ አንተ ይቆማል፥ በርግጥ የታመነ መኖሪያ ያደርግልሃል። **7** ጅማሬህ ትንሽ ቢሆንም እንኳ ፍጻሜህ እጅግ ታላቅ ይሆናል። **8** ስለ ቀደመው ዘመን ትውልድ ትጠይቅ ዘንድ እለምንሃለሁ፥ አባቶቻቸውም ከመረመሩና ካገኙት ነገር ለመማር ትጋ፤ **9** (ዘመናችን በምድር ላይ እንደ ጥላ ስለሆነ እኛ ትናንት ተወለድን፤ ምንም አናውቅም) ፤ **10** እነዚህ የሚነግሩህና የሚያስተምሩህ አይደሉምን? ቃልንም ከልባቸው የሚያወጡ አይደሉምን? **11** በውኑ ረግረግ በሌለበት ደንገል ሳር ይበቅላልን? ወይስ ቄጠማ ውኃ በሌለበት ቦታ ይለመልማልን? **12** ገና ለምለም አረንጓዴ ሆኖ ሳይቈረጥ፥ ከአትክልት ሁሉ በፊት ይጠወልጋል። **13** እግዚአብሔርን የሚረሱ ሁሉ የመንገዳቸው ፍጻሜ እንዲሁ ነው፤ አምላክ የሌለው ሰው ተስፋም ይጠፋል። **14** መታመኛቸው እንደሚናድባቸው፥ እምነቱም የሸረሪት ድር አይነት የሆነበት። **15** እዲህ አይነት ሰው ቤቱን ይደገፋል፥ነገር ግን አይቆምለትም፤ደግፎም ይይዘዋል፥ አይጸናለትም። **16** ፀሐይም እንደወጣች ይለመልማል፥ ጫፉም በአትክልቱ ቦታ ጎልቶ ይወጣል። **17** ሥሮቹ በድንጋይ ክምር ላይ ይጠመጠማሉ፤ በድንጋዮቹም መካከል መልካም ቦታን ይፈልጋሉ። **18** ነገር ግን ይህ ሰው ከቦታው ቢጠፋ፦ ስፍውም "ፈጽሞ አቼህ አላውቅም" ብሎ ይክደዋል። **19** እነሆ፥ የደስእንደዚህ አይነትሰው ደስታ ይህ ነው፤ ሌሎች ተክሎች ከዚያው አፈር በፋንታው ይበቅላሉ። **20** እነሆ፥ እግዚአብሔር ንጹሁን ሰው አይጥለውም፥ የክፉ አድራጊውንም እጅ አያበረታም። **21** አፍህን እንደ ገና ሳቅ፥ ከንፈሮችህንም በደስታ ጩኹት ይሞላል። **22** የሚጠሉህ እፍረትን ይለብሳሉ፤ የአመጸኞችም ድንኳን አይገኝም።

Job 8:1

አያያዥ ሃሳብ
በዚህ ምዕራፍ፣ በልዳዶስ ስለ ኢዮብ ማማረር መናገር ይጀምራል።

አጠቃላይ መረጃ:
ቁጥር 2 እና ቁጥር 3 እያንዳንዳቸው ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሁለት የተለያዩ ጥያቄዎችን ይይዛሉ። በልዳዶስ እነዚህን ጥያቄዎች የሚያውላቸው/የሚጠቀምባቸው ኢዮብን ለመገሰጽ ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከዚያም ሹሐዊው በልዳዶስ እንዲህ ሲል መለሰ
"በልዳዶስ" የሹሐ ነገድ አባል የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እስከ መቼ የአፍቃል እንደ ታላቅ ነፋስ ይሆናል
በልዳዶስ የኢዮብን ቃል የሚገልጸው ባዶ እና እንደ ነፋስ በውስጣቸው ምንም ፍሬ ነገር እንደሌለባቸው አድርጎ ነው። ይህ በገለጻ አይነት ሊተረጎም ይችላል። "የአፍህ ቃላት እንደ ታላቅ ነፋስ ምንም ጥቅም የሌላቸው ናቸው።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያው አነጋገር እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ፍትህን ይከለክላልን? ሁሉን ቻይ የሆነው ጽድቅን ያጣምማልን?
እዚህ ስፍራ "እግዚአብሔር" እና "ሁሉን ቻይ የሆነው" የሚሉት ሁለቱም ያህዌን የሚያመለክቱ ናቸው። እነዚህ ጥያቄዎች በመግለጫ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "እግዚአብሔር ፍትህን አያጣምምም፤ ሁሉን ቻይ የሆነው ጽድቅን አያጣምም።" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ፍትህን ያጣምማልን?... ጽድቅን ያጣምማልን?
"ትክክል ያለሆነውን ማረጋገጫ ሰጥቶ ያደርጋልን?.. ጽድቅ ያልሆነውን ማረጋገጫ ሰጥቶ ይፈጽማልን?"

Job 8:4

ለእጆቸው ኃጢአት አሳልፎ ሰጥቷቸው ከሆነ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚወክለው የኃጢአትን ሀይል ወይም ውጤት ነው። በልዳዶስ እግዚአብሔር የኢዮብን ልጆች የገደላቸው በኃጢአታቸው ምክንያት እንደሆነ ያመለክታል። "የልጆችህ ኃጢአት እግዚአብሔር እንዲገድላቸው ምክንያት ሆኖታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ነገር ግን አንተ ምናልባት እግዚአብሔርን በትጋት ፈልገህ ጥያቄህንም ሁሉን ቻይ ለሆነው አቅርበህ ይሆናል
በልዳዶስ ኢዮብ ከእግዚአብሔር ጋር በትክክል ቢስማማ ምን ሊሆን ይችል እንደ ነበረ እየተናገረ ነው፤ ነገር ግን በልዳዶስ ኢዮብ ይህንን ማድረጉን አያምንም። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በትጋት እግዚአብሔርን መፈለግ... ሁሉን ቻይ ለሆነው ጥያቄህን ማቅረብ
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ኢዮብ እግዚአብሔርን እርዳታ ወይም ምህረት መጠየቁን ያመለክታሉ። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

በትጋት እግዚአብሔርን መፈለግ
"ከልብ እግዚአብሔርን እርዳታ መጠየቅ"

Job 8:6

አጠቃላይ መረጃዎች:
በልዳዶስ ኢዮብ ንጹህ ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር ይረዳው ነበር ይላል፥ ነገር ግን በልዳዶስ ኢዮብ ንጹህ መሆኑን አያምንም። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ንጹህ እና ትክክለኛ ብትሆን
"ንጹህ እና ጻድቅ ሰው ብትሆን ኖሮ" ወይም "እግዚአብሔርን ታዝዘህ ቢሆን እና ትክክለኛ የሆነውን ነገር የምታደርግ ቢሆን ኖሮ"

እርሱ ስለ አንተ ይነሳል
እዚህ ስፍራ ያህዌ የተገለጸው ኢዮብን ለመርዳት ከእንቅልፉ እንደተነሳ ተደርጎ ነው። "አንተን ሊረዳህ" ወይም "ለአንተ መልካም ነገሮችን ለማድረግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አንተን ወደ ትክክለኛ ስፍራ ይመልስሃል
ይህ የሚያመለክተው ኢዮብ ያጣቸውን ነገሮች፤ ቤተሰቡን ጨምሮ፣ ሀብቱን እና ክብሩን መልሶ እንደሚሰጠው ነው።

ምንም እንኳን ጅማሬህ እጅግ ታናሽ ቢሆንም፣ ፍጻሜህ ግን እጅግ ታላቅ ይሆናል
እዚህ ስፍራ ሀብትን ማጣት የተገለጸው "ታናሽ ጅማሬ" እንደሆነ ተደርጎ ነው። "በህይወትህ መነሻ ላይ ደሃ ብትሆንም፣ በዕድሜህ የኋልኛ ዘመን እግዚአብሔር እጅግ ባለጠጋ ያደርግሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Job 8:8

አጠቃላይ መረጃ:
በልዳዶስ አባቶቻቸው እርሱ ለኢዮብ ከሚነግረው ሃሳቦች ጋር የሚስማሙ መሆኑን አጉልቶ ለመግለጽ ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን በእነዚህ ቁጥሮች ሁሉ መጠቀሙን ይቀጥላል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አባቶቻችን ያስተምሯቸው ለነበሩ ነገሮች ዋጋ ስጥ
"አባቶቻችን ይናገሩ የነበረውን በጥንቃቄ ተረዳ" ወይም "አባቶቻችን የተዉልንን ትምህርቶች ስፍራ ስጣቸው"

በምድር ላይ የሰው ዘመን ጥላ ነው
የህይወት አጭርነት የተገለጸው በፍጥነት የሚጠፋ ጥላ እንደሆነ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ አያስተምሩህምን፣ ደግሞስ አይነግሩህምን? እነርሱ ከልባቸው ቃል አይነግሩህምን?
በልዳዶስ እነዚህን ቃለ
ምልልሳዊ ጥያቄዎች የሚጠቀመው ኢዮብን ከእርሱ እና ከአባቶቻቸው ጋር ባለመስማማቱ ሊወቅሰው ነው። ይህ በገለጻ ሊተረጎም ይችላል። "እነርሱ ያስተምሩሃል፣ ደግሞም ይነግሩሃል፤ በእውነት የሚያምኑበትንም ይነግሩሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ከልባቸው
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚወክለው ውስጣዊ እምነትን ነው። "እነርሱ በእውነተኝነት የሚያምኑበትን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 8:11

አጠቃላይ መረጃ:
ከቁጥር 11-14 ያለው የበልዳዶስ ትምህርቶች ስለመሆኑ ግልጽ አይደለም፣ ወይም በልዳዶስ ከኢዮብ 8:8-10 ያለውን የአባቶች ትምህርት ጠቅሶ ሊሆን ይችላል።

ረግረግ በሌለበት ደንገል ይበቅላልን? ውሃ በሌለበት ቄጠማ ይድጋልን?
በልዳዶስ እነዚህን ትይዩ ንጽጽራዊ ጥያቄዎች የሚጠቀመው ሰዎች ያለ እግዚአብሔር መኖር እንደማይችሉ ይህን አንድ ሀሳብ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። እዚህ ስፍራ ተክሎች ሰውን ሲወክሉ፣ ውሃ ደግሞ እግዚአብሔርን ይወክላል። ጥያቄው በግልጽ ሊተረጎም ይችላል። "የደንገል ተክል ከረግረግ ርቆ ሊያድግ አይችልም። ቄጠማም ያለ ውሃ ሊያድግ አይችለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለምልልሳዊ ጥያቄ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እንደዚሁም ዘይቤያው አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ደንገል
ጥልቀት በሌለው ውሃ ላይ የሚያድግ ረጅም ቄጠማ መሰል ተክል

ገና አረንጓዴ ሳሉ እና ሳይቆረጡ ከሌላው ተክል ፈጥነው ይደርቃሉ
ውሃ በሚያጥርበት ጊዜ እንደሚደርቁ ተጠቁሟል። ይህ ይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ማንም ባይቆርጣቸውም እንኳን እነዚህ ተክሎች ውሃ በሚያጥርበት ጊዜ ማደግ አይችሉም፤ ደግሞም ፈጥነው ይደርቃሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ይጠፋሉ
"ይደርቃሉ"

Job 8:13

አጠቃላይ መረጃ:
ከቁጥር 11-14 ያለው የበልዳዶስ ትምህርት ስለመሆኑ ግልጽ አይደለም፣ ወይም በልዳዶስ የአባቶችን ትምህርት ከኢዮብ 8:8-10 ካለው ክፍል ጠቅሶ ሊሆን ይችላል።

አጠቃላይ መረጃ:
ከቁጥር 14-18፣ "እርሱ" እና "የእርሱ" የሚሉት ተውላጠ ስሞች የሚያመለክቱት በአጠቃላይ እግዚአብሔር የለሽ ሰዎችን የሚወክል እግዚአብሔር የለሽ ሰውን ነው። "እነርሱ" እና "የእነርሱ" የሚሉትን የብዙ ቁጥር ተውላጠ ስሞች/የስም ምትኮች/ መጠቀም አንባቢያንን ሊያግዝ ይችላል። (የስማዊ ሀረግ ክፍሎች የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን የሚረሱ/የሚተዉ ሁሉ መንገዳቸው እንዲህ ነው
እዚህ ስፍራ "መንገድ" የሚወክለው የአንድን ሰው የወደፊት ጊዜ እና በእርሱ ላይ የሚደርሱ ነገሮችን ነው። "እግዚአብሔርን በሚረሱ ሁሉ ላይ ተመሳሳይ ነገር ይደርሳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር የለሾች ተስፋ ይጠፋል
"አምላክ የለሽ ሰው የሚሻቸው ነገሮች አይጸሙም"

የእርሱ ልበ ሙሉነት የንኮታኮታል/ይሰበራል... መታመኛው እንደ ሸረሪት ድር ደካማ ነው
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳሳ ትርጉም አላቸው፤ ደግሞም አገላለጾቹ አምላክ የለሽ ሰው ሊያድነው በማይችል ነገር እንደሚታመን ትኩረት ይሰጣሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እምነቱ እንደ ሸረሪት ድር ደካማ ነው
እዚህ ስፍራ በልዳዶስ የአምላክ የለሽ ሰዎችን እምነት ከሸረሪት ድር ጋር ያነጻጽራል፤ ሁለቱንም ጥቂት ሀይል ያፈራርሳቸዋል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በቤቱ ላይ ይደገፋል፣ ነገር ግን ይህ አይደግፈውም፤ እርሱ ይህን ይይዛል፣ ነገር ግን የያዘው ጸንቶ አይቆምም።
ይህ ሀሳብ የሚያመለክተው ምናልባት ለደህንነቱ ንብረቱን እና ሀብቱን መታመኛ ያደረገን ሰው ሊሆን ይችላል። እንዲህ ከሆነ ደግሞ እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚወክለው የባለቤቱን ንብረት እና ሀብት ነው። "ሀብት ስላለው በደህንነት የሚጠበቅ እንደሆነ ያስባል፣ ነገር ግን ደህንነቱ አይጠበቅም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሀብቱ አይደግፈውም
ይህ አሉታዊ ሀሳብ ተቃራኒውን ነገር ያጎላል። ይህ በአዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እርሱ ይወድቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምፀት/ ላይዶክስ የሚለውን ይመልከቱ)

አይቆምም
ይህ አሉታዊ ሀሳብ ተቃራኒውን ነገር ያጎላል። ይህ በአዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ይህ ይወድቃል"

Job 8:16

አጠቃላይ መረጃ:
እዚህ ስፍራ "እርሱ" እና "የእርሱ" የሚሉት ተወላጠ ስሞች የሚያመለክቱት በአጠቃላይ እግዚአብሔር የለሽ ሰዎችን የሚወክል እግዚአብሔር የለሽ ሰውን ነው። "እነርሱ" እና "የእነርሱ" የሚሉትን የብዙ ቁጥር ተውላጠ ስሞች/የስም ምትኮች/ መጠቀም አንባቢያንን ሊያግዝ ይችላል። (የስማዊ ሀረግ ክፍሎች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከፀሐይ በታች አረንጓዴ ነው፣ ቅርንጫፉ ሁሉ በስፍራ ሁሉ ይስፋፋል
እዚህ ስፍራ በልዳዶስ እግዚአብሔር የለሽ ሰውን ከጤናማ ተክል ጋር ያነጻጽራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከፀሐይ በታች አረንጓዴ ነው
የዕብራይስጡ ጽሁፍ ትርጉም ግልጽ አይደለም። ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትረጉሞች 1) በቀን ጤናማ ነው ወይም 2) ፀሐይ ከመውጣቱ አስቀድሞ ውሃ ይጠጣል

ስሮቹ በድንጋይ ክምር ላይ ይጠመጠማሉ... በአለት መካከል መልካም ስፍራ ይፈልጋል
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ሆኖም ትርጉማቸው ግልጽ አይደለም። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እያንዳንዱን ቀዳዳ በሚገባ በመጠቀም በአለት ላይ ስር የሰደደ ይመስላል ወይም 2) ስሩ ለም መሬት ማግኘት ስላልቻለ በአለቶች መሃል አልሚ ምግብ ለማግኘት መሞከር አለበት። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ይህ ሰው ከስፍራው ከተደመሰሰ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንድ ሰው ከስፍራው አስለቅቆታል" ወይም "አትክልተኛው ከስፍራው ከነቀለው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ስፍራው
"አለታማው መሬት" ወይም "የተተከለበት ስፍራ"

ስፍራው ሊክደው እና እንዲህ ሊለው ይችላል 'በፍጹም አይቼህ አላውቅም'
የአትክልቱ/የተተከለበት ስፍራ የተገለጸው የመናገር ችሎታ እንዳለው ተደርጎ ነው። ስፍራው ወዲያውኑ የእርሱን መኖር ረስቷል። (ሰውኛ ዘይቤ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 8:19

ይህ እንዲህ ያለው ሰው የ"ደስታ" ባህሪይ ነው
በልዳዶስ እግዚአብሔር የለሽ ሰው አንዳች ደስታ እንደሌለው በምጸት እየተናገረ ነው። "እግዚአብሔር የለሽ ከሆነው ድርጊታቸው የሚያተርፉት ደስታ ቢኖር ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምፀት የሚለውን ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ።

በተመሳሳይ አፈር ላይ በስፍራው ሌሎች ተክሎች ይበቅላሉ
በልዳዶስ ከኢዮብ 8:16-18 ዘይቤውን ይቀጥላል። ሌሎች እግዚአብሔር የለሽ ሰዎች የተገለጹት የመጀመሪያው አምላክ የለሽ ሰው ሲሞት የስርሱን ስፍራ እንደወሰዱ ተክሎች ተደርገው ነው። "አንድ ክፉ ሰው ሲሞት፣ ሌላው የእርሱን ስፍራ ይወስዳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይበቅላል
"ያድጋል"

በዚያው አፈር
"አለታማ ምድር" ወይም "ስፍራው/የአትክልቱ ቦታ"

በስፍራው
"አምላክ የለሽ በሆነው ሰው ቦታ"

እግዚአብሔር ንጹሁን ሰው አያጠፋም
ይህ በአዎንታዊ አረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር ንጹሁን ሰው ይቀበላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እርሱ የክፉ አድራጊዎችን እጅ አይዝም
እዚህ ስፍራ "እጅ መያዝ" የሚለው የሚያመለክተው መርዳት ወይም መደገፍ የሚለውን ነው። "እግዚአብሔር ክፉ የሚያደርጉ ሰዎችን አይደግፍም/አይረዳም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 8:21

እርሱ ገና የአንተን አፍ በሳቅ፣ ከንፈሮችህን በእልልታ/በደስታ ጩኸት ይሞላዋል
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው ኢዮብ ትሁት መሆን ቢችል እንደምን ተመልሶ ደስተኛ ሊሆን እንደሚችል ትኩረት ይሰጣሉ። "እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ሲሆን "የአንተ" ሚለው ኢዮብን ያመለክታል። "ንጹህ ብትሆን እግዚአብሔር ዳግም በጣም ደስተኛ ያደርግሃል" (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

አፍህን በሳቅ ይሞላል
እግዚአብሔር ኢዮብን በሳቅ እንዲሞላ ደርጋል የሚለው ሀሳብ የተገለጸው እግዚአብሔር በኢዮብ አፍ ሳቅ እንደሚጨምር ተደርጎ ነው። "ሳታቋርጥ እንድትስቅ ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከንፈሮችህን በእልልታ/በደስታ ጩኸት
"ይሞላል" የሚለው ግስ በውስጠ ታዋቂነት በቀደመው ሀረግ ውስጥ ይገኛል። እግዚአብሔር የደስታ ጩኸት/ እልልታ እንዲያሰማ ማድረጉ የተገለጸው እግዚአብሔር በኢዮብ አፍ ደስታን እንደሚጨምር ተደርጎ ነው። "እግዚአብሔር በደስታ እንድትጮህ/እልል እንድትል ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

አንተን የሚጠሉ ሀፍረት ይለብሳሉ
እዚህ "ሀፍረት" የሚለው ቃል የተገለጸው እግዚአብሔር የኢዮብ ጠላቶች እንዲለብሱት እንደሚያደርገው ልብስ ተደርጎ ነው። ይህ ማለት እነርሱ በጣም ያፍራሉ ማለት ነው። "እግዚአብሔር አንተን የሚጠሉትን በጣም እንዲያፍሩ ያደርጋቸዋል" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህ የክፉዎች ድንኳን አይገኝም
እዚህ "ድንኳን" የሚያመለክተው የክፉዎችን ቤት ነው። "የክፉዎች ቤት ይደመሰሳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ከእንግዲህ አይገኝም
"አይቀጥልም" ወይም "ይደመሰሳል"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 9

1 ኢዮብም ሲመልስ እንዲህም አለ፦ **2** “ እንዲህ እንደ ሆነ በእውነት አውቃለሁ፤ ነገር ግን ሰው በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ መሆን እንዴት ይችላል? **3** ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ለመከራከር ቢፈልግ፥ ከሺህ ነገር አንዱን እንኳ መመለስ አይችልም። **4** እግዚአብሔር በልቡ ጠቢብ ነው፥ ኃይሉም ታላቅ ነው፤ እርሱን ተዳፍሮ በደኅና የተሳካለት ማን ነው? **5** በቍጣው ተራሮችን ሲገለብጣቸው፤ ተራሮችን ሲነቅላልቸው ለማን አስቀድሞ ተናገረ። **6** ምድርን ከስፍራዋ ያሚያናውጣት እርሱ፥ ምሰሶዎችዋንም ያንቀጠቅጣቸዋል። **7** ይኸው እግዚአብሔር ፀሐይን እንዳትወጣ ያዝዛታል፥ አትወጣምም፤ ከዋክብትንም ይከልላቸዋል። **8** ሰማያትን በራሱ ይዘረጋል፥ የባሕሩን ማዕበል የሚገዛ በላዩም ይራመዳል። **9** ድብና ኦሪዮን የሚባሉትን ኮከቦች፥ ሰባቱንም ከዋክብት፥ በደቡብም በኩል ያሉትን የከዋክብት ስብስቦች ሠርቶአል። **10** ይኸው እግዚአብሔር የማይመረመሩ ታላላቅ ነገሮችን፥ በርግጥ የማይቈጠሩ ተአምራቶችን ያደርጋል። **11** እነሆ፥ ወደ እኔ ቢመጣ አላየውም፤፤ በአጠገቤም ቢያልፍ አላውቀውም። **12** እነሆ አንድን ሰው ነጥቆ ቢወስድ የሚከለክለው ማን ነው? ምን እያደረግህ ነው? የሚለውስ ማን ነው? **13** እግዚአብሔር ቊጣውን አይመልስም፤ የረዓብ ረዳቶች ከእርሱ በታች ይሰግዳሉ። **14** ይልቁንስ መልስ ልመልስለት፥ ከእርሱ ጋርስ ለክርክር ቃልን እመርጥ ዘንድ እኔ ማን ነኝ? **15** ጻድቅ ብሆን ኖሮ እንኳ ልመልስለት አልችልም፤ የምችለው ዳኛዬን ምህረት መለመን ብቻ ነው ። **16** ብጠራውና እርሱ ቢመልስልኝ ም ኖሮ፥ ድምጼን ይሰማ እንደ ነበር አላምንም ። **17** በዐውሎ ነፋስ ይሰብረኛል፥ ቍስሌንም ያለ ምክንያት ያበዛዋል። **18** ትንፋሽ እድወስድ እንኳ ፋታ አልሰጠኝም፥ ይልቅ በመራራነት አጠገበኝ። **19** ስለ ኃይል ከተናገርን እንደ እርሱ ኃያል ማን ነው፤ የፍርትህ ነገር ከተነሳ፦”የሚጠይቀኝ ማን ነው? “ ይላል። **20** ጻድቅ ብሆን እንኳ አንደበቴ ይወቅሰኛል፤ ሰበብ ባይገኝብኝ እንኳ ጥፋተኛ ያደርገኛል። **21** ያለነቀፋ ብሆንም ከእንግዲህ ለራሴ ግድ የለኝም፤ ሕይወቴንም እንቃታለሁ። **22** ልዩነት የለውም፤ እርሱ “ጻድቁንና ሃጥኡን ባንድነት ያጠፋል" የምለው ለዚህ ነው። **23** መቅሠፍ በድንገት ቢገድል፥ በንጹሐን ሰዎች ችግር ይስቃል። **24** ምድር ለኃጥአን እጅ ታልፋ ተሰጥታለች፤ እግዚአብሔርም የዳኞችዋን ፊት ሸፍኖአል፤ ይህን ያረገው እርሱ ካልሆነ ታድያ ማን ነው? **25** ዘመኔ ከመልክተኛ ሰው ሩጫ ይልቅ ይፈጥናል፤ ቀኖቼ፥ መልካምን ሳያዩ ይከንፋሉ። **26** የደንገል ጀልባ እንደሚፈጥን፥ ንስርም ወደሚነጥቀው ግዳይ እንደሚበርር ፈጣን ናቸው። **27** “አቤቱታዬን እረሳለሁ፤ ሐዘንተኛ ፊቴን ትቼ ደስተኛ እሆናለሁ” ብዬ ብል፥ **28** ንጹሕ አድርገህ እንደማትቆጥረኝ ስላወቅሁ መከራዬን ሁሉ እፈራዋለሁ። **29** ጥፋተኛ ሆኜ መቀጣቴ ላይቀር፤ ለምን በከንቱ እደክማለሁ? **30** ራሴን በአመዳይ ውሃ ባጥብና እጆቼንም እጅግ ባነጻቸው፥ **31** የገዛ ልብሴ እስኪጸየፈኝ ድረስ እግዚአብሔር በአዘቅት ውስጥ ይመልሰኛል። **32** መልስ እድሰጠው ፥ አብረን ወደ ፍርድ ችሎት እንዳንገባ፥ እርሱ እንደ እኔ ሰው አይደለም። **33** እጁን በሁለታችንም ላይ የሚያኖር ፈራጅ፤ በመካከላችንም የሚዳኝ የለም! **34** የእርሱን በትሩ ከእኔ ላይ የሚያነሳ፥ ማስደንገጡንም ከኔ የሚያርቅ ሌላ ፈራጅ የለምን **35** በሚገባ በተናገርሁ፥ ባልፈራሁም ነበር፤ ነገር ግን አሁን ነገሮች እንዲህ ባሉበት አልችልም።

Job 9:1

ይህ እንዲህ እንደሆነ በእውነት አውቃለሁ
"አንተ እምትናገረው እውነት እንደሆነ ያንን አውቃለሁ"

ይህ እንዲህ ነው
እዚህ ስፍራ "ይህ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው በልዳዶስ የተናገረውን ነው።

ሰው በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ትክክል/ጻድቅ ሊሆን ይችላል?
"ማንስ ቢሆን እንዴት በእግዚአብሔር ፊት ንጹህ ሊሆን ይችላል?"

ክርክር
"ጠብ"

ከአንድ ሺህ ጊዜ አንዱም ሊመልስለት አይችልም
"ከሺህ አንዱ" የዚህ ፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉም "በፍጹም" ማለት ነው። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች፡ 1) "ለእግዚአብሔር ምንም መልስ መስጠት አይችልም" ወይም 2) "እግዚአብሔር በፍጹም መልስ አይሰጠውም" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ሺህ ጊዜ
"1,000 ጊዜ"

Job 9:4

በልቡ ጠቢብ
እዚህ ስፍራ ልብ የሚለው የሚወክለው ውስጣዊ ፍጥረትን ወይም ሀሳብን ነው። "በውሳኔው ጠቢብ የሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በጥንካሬቀው ታላቅ
"ጥንካሬ" የሚለው ረቂቅ ስም "ጠንካራ" በሚለው ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። "በጥንካሬው እንዴት ታላቅ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ ላይ ደንድኖ ስኬት ያገኘ ማን ነው?
ይህ "ማንም" የሚል ምላሽ የሚጠበቅበት ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ ነው። በገለጻ እንደገና ሊጻፍ ይችላል። "ማንም በእርሱ ላይ ራሱን አደንድኖ ፍሬያማ የሆነ የለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ ላይ ራሱን አደንድኖ
ራስን ማደንደን ማለት ግትር መሆን ማለት ነው። "እርሱን ተቃውሞ" ወይም "እርሱን ሳያከብር" (ከባለቤቱ ጋር የሚጣቀስ ተውላጠ ስም)

ተራሮችን ከስፍራቸው የሚያስወግድ
"እግዚአብሔር ተራሮችን ያስወግዳል"

በእርሱ ቁጣ
"ቁጣ" የሚለው ረቂቅ ስም "መቆጣት" በሚለው ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። "እርሱ ስለተቆጣ/እርሱ በመቆጣቱ ምክንያት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ምድርን የሚያናውጠው እርሱ
"እግዚአብሔር ምድርን ያናውጣል"

ምሰሶዎቿን ያንቀጠቅጣል
"መሰረቶቿ እንዲንቀጠቀጡ ያደርጋል"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Job 9:7

ከዋክብትን የጋረደ ማን ነው?
"ከዋክብትን ከመታየት የሚከለክል ማን ነው"

በራሱ ችሎታ ሰማያትን የዘረጋ ማን ነው
እግዚአብሔር ሰማያትን ካለ ማንም እርዳት እንደፈጠረ፣ ሰማያት እርሱ የዘረጋቸው ስራዎቹ መሆኑ ተነግሯል። (ከባለቤቱ ጋር የሚጣቀስ ተውላጠ ስም እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

የባህር ማዕበልን የሚከለክል
እግዚአብሔር ባህርን ጸጥ እንደሚያደርግ ተገልጽዋል። "እግሮቹን በባህረ ማዕበል ላይ ያሳርፋል" ወይም "የባህር መዕበልን ጸጥ ያደርጋል በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ድብ፣ ኦሪዮን፣ ፕልያዲስ
እነዚህ በሰማይ ላይ የተለየ ቅርጽ የሚሰሩ የሚመስሉ የከዋክብት ስብስብ ስሞች ናቸው። (የማይታወቀውን መተረጎም የሚለውን ይመልከቱ)

ኦሪዮን
በግሪኮች አፈታሪክ ውስጥ ዝነኛ የሆነ አዳኝ

ፕልያዲስ
በሰማይ የተቀራረቡ የሚመስሉ በርካታ ብሩህ ከዋክብት

የከዋክብት ስብስብ
በሰማይ ላይ የተለየ ቅርጽ የሚሰሩ የሚመስሉ የከዋክብት ስብስቦች

Job 9:10

አጠቃላይ መረጃ:
ጸሐፊው በእነዚህ በእያንዳቸው ቁጥሮች ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን በመገልገል ድርብ ሃሳቦችን ተጠቅሞ የእግዚአብሔርን ታላቅነት፣ የማይታይ መሆኑን እና ሉዓላዊነቱን በአንድ ሃሳብ ለማስተላለፍ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የማይደረስባቸው/የማይመረመሩ ነገሮች
"ለመረዳት የማይቻሉ ነገሮች"

እነሆ
"ተመልከት" ወይም "አድምጥ" ወይም "ልነግርህ የተዘጋጀሁትን ለመስማት ትኩረት ስጥ::"

እርሱ አለፈ
"እርሱ በዚያ አለፈ" ወይም "እርሱ ተንቀሳቀሰ"

እርሱ አንዳች ነገር ቢነጥቅ፣ ማን ሊያስቆመው ይችላል? እርሱን 'ምን እያደረግህ ነው' ብሎ ሊጠይቀው የሚችል ምን ነው?
እነዚህ "ማንም" የሚል ምላሽ ሚጠበቅባቸው ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች ናቸው። በገለጻ መልክ ሊጻፉ ይችላሉ። "እርሱ አንድ ነገር ቢወስድ፣ ማንም ሊያስቆመው አይችልም። ማንም 'ምን እያደረግህ ነው?' ሊለው አይችልም። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ አንዳች ነገር ቢነጥቅ
"እርሱ አንድ ነገር ቢወስድ" ወይም "እርሱ አንድ ነገር መንጠቅ ቢፈልግ"

Job 9:13

ረዓብን የሚረዱ ከእርሱ በታች ይሰግዳሉ
እዚህ ስፍራ "ከእርሱ በታች መስገድ" የሚለው መገዛትን ወይም መሸነፍን ይወክላል። "እርሱ የረዓብን ረዳቶች ያደቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመለከቱ)

ረዓብ
እዚህ ስፍራ "ረዓብ" የሚለው ቃል የባህር አውሬን ያመለክታል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ታዲያ ከእርሱ ጋር እሟገት ዘንድ ፣ ለእርሱስ ምክንያት ለማቅረብ ቃላት ማግኘት እችላለሁን?
ኢዮብ እግዚአብሔርን ለመግጠም አቅም እንደሌለው ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ሁለት ተመሳሳይ ጥያቄዎችን ያቀርባል። እነዚህ ጥያቄዎች በገለጻ መልክት እንደገና ሊጻፉ ይችላሉ። "ስለዚህ በእርግጥ እኔ ለእርሱ መልስ ልሰጥ አልችልም ወይም ለእርሱ ምክንያት ለማቅረብ/ከእርሱ ጋር ለመከራከር ቃላት ልመርጥ አልችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 9:16

በአውሎ ነፋስ ሰብሮኛልና
ኢዮብ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣበትን መከራ ከአውሎ ነፋስ ተጽዕኖ ጋር ያነጻጽረዋል። "በአውሎ ነፋስ እንደተጎዳሁ ጎድቶኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አውሎ ነፋስ
ጥቃት የሚያደርስ ሀያለኛ ነፋስ

ቁስሌን አበዛው
"ብዙ ቁስሎች አደረገብኝ" ወይም "ደጋግሞ አቆሰለኝ"

ያለ ምክንያት
"ምንም እንኳን እንዲህ እንዲያደርግ የሚያበቃ ጥፋት ባልሰራም" ወይም "ምንም እንኳን ንጹህ ብሆንም"

ትንፋሽ እንዳገኝ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ "ደግሜ መተንፈስ እንድችል" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ በመራራነት ሞላኝ
ይህ ቁጥር እግዚአብሔር የኢዮብን ህይወት እንዲመረር በሚያደርጉ ነገሮች እንደሞላው ይናገራል። "መራርነት" የሚለው ረቂቅ ስም "መራራ" በሚለው ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። "በመራራ ነገሮች ሞላኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 9:19

ይህ የጥንካሬ ጉዳይ ቢሆንም
"የጥንካሬ መፎካከሪያ ቢኖርም"

እነሆ፣ እርሱ ታላቅ ነው
"ተመልከት እርሱ ታላቅ መሆኑን ትረዳለህ" ወይም "እኔ ልነግርህ ለተዘጋጀሁት ነገር ትኩረት ስጥ፡ እርሱ ታላቅ ነው"

እርሱ ታላቅ ነው
"እርሱ ከሁሉ ታላቅ ነው"

ለእርሱ ማን የክስ መጥሪያ ሊያቀርብለት ይችላል?
ይህ ጥያቄ "ከቶ ማንም" የሚል ምላሽ እግዚአብሔርን ወደ ፍርድ ቤት ሊያቀርበው አይችልም የሚል ምላሽ ያሰጣል። ይህ በገለጻ መልክ ሊጻፍ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይችላል። "ማንም ለእርሱ መጥሪያ ሊያቀርብለት አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ምንም እንኳን ጻድቅ/ትክክለኛ ብሆንም፣ የገዛ አንደበቴ ይፈርድብኛል፤ እንከን የለሽ ብሆንም ቃሎቼ ይኮንኑኛል።
ይህ ሀረግ ተመሳሳይ ሃብን ሁለት ጊዜ ደግሞ በማቅረብ አጽንኦት ይሰጣል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ትክክለኛ/ጻድቅ ብሆንም
እዚህ ስፍራ "እኔ ትክክለኛ ነኝ" የሚለው ትክክለኛ የሆነውን ያረግኩት እኔ ነኝ ማለት ነው። "ምንም እንኳን ትክክለኛ ነገሮችን ባደርግም" ወይም "ምንም እንኳን እኔ ንጹህ ብሆንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ስማዊ ቅጽሎች የሚሉትን ይመልከቱ)

የገዛ አንደበቴ ይኮንነኛል/በደለኛ ያደርገኛል
እዚህ ስፍራ "አንደበት" የሚለው የኢዮብን ቃላት ነው። "የራሴ ቃላት ይከሱኛል" ወይም " የተናገርኩት ይኮንነኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ነውር ባይኖርብኝም
"ጥፋት/እንከን ባይኖርብኝም"

የራሴ ቃሎች ጥፋተኛ መሆኔን ያሳያሉ
እዚህ ስፍራ "የራሴ ቃሎች" የሚለው የተገለጸው ቃላቶቹ ራሳቸው እርምጃ መውሰድ እንደሚችሉ ተደርጎ ነው። "እግዚአብሔር እኔ የተናገርኩትን የእኔኑ ጥፋተኝነት ለማረጋገጥ ይጠቀምበታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጥፋተኛ
እዚህ ስፍራ ይህ ቃል "ገልበጥባጣ" ወይም "ጠማማ" የሚል ትርጉም አለው።

Job 9:21

እኔ ነውር አልባ ነኝ
"እኔ ጥፋት የለብኝም"

ስለ ራሴ
"በእኔ ላይ የደረሰው"

ምንም ልዩነት አያመጣም
"ልዩነት የለውም" ወይም "ምንም ማለት አይደለም"

ጥፋት የሌለበትን እና ንጹሁን ሰው በአንድነት ያጠፋል
እዚህ ስፍራ "ነውር/ጥፋት የሌለበት" እና "ክፉ" የሚሉት ቃላት በመሃል ያሉትን ሁሉ የሚያካትት ሁለት ጽንፍ ነው። "እንከን የሌለውን እና ክፉውንም ሁሉንም ወደ ፍጻሜ ያመጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጽንፍ የሚለውን ይመልከቱ)

መቅሰፍት በድንገት ሲገድል
እዚህ ስፍራ "መቅሰፍት" የሚለው ቃል ለማኛቸውም አይነት ጥፋት ዘይቤ ነው። "በእንገት ጥፋት ሲደርስ እና ሰዎች ሞቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (በ ተመልከቱ)

የንጹህ ሰው ተስፋ መቁረጥ
"ተስፋ መቁረጥ" የሚለው ቃል ረቂቅ ስም ሲሆን "ተስፋ ቆረጠ" በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። እዚህ ስፍራ ተስፋ እየቆረጠ ለሚገኝ ንጹህ ሰው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ተስፋ የቆረጡ ንጹህን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (በ ተመልከቱ)

ንጹህ
ይህ ስማዊ ቅጽል ነው። "ንጹህ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (በ ተመልከቱ)

ምድር ተሰጥታለች
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር ምድርን ሰጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ምድር
እዚህ ስፍራ "ምድር" የሚለው የሚወክለው በምድር ላይ የሚኖሩ ዎችን ነው። "የዓለም ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በ...እጅ ውስጥ
እዚህ ስፍራ "እጅ" "መቆጣጠር ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "በ...ቁጥጥር ስራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር የፈራጆቿን ፊት ሸፍኗል
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር እግዚአብሔር የምድር ፈራጆችን/ዳኞችን እውነት እና ሀሰት በሆነው መሃል መለየት እንዳይችሉ ከልክሏቸዋል። "እግዚአብሔር ፈራጆቿን አሳውሯል" ወይም "እግዚአብሔር ፈራጆቿ/ዳኞቿ በትክክል እንዳይፈርዱ ከልክሏቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህንን ያደረገው እርሱ ካልሆነ፣ ታዲያ ይህንን ያደረገው ማን ነው?
"እነዚህን ነገሮች ያደረገው እግዚአብሔር ካልሆነ፣ ማን አደረጋቸው ይባላል?"

Job 9:25

ቀኖቼ ከሯጭ መልዕክተኛ ይልቅ ፈጣኖች ናቸው
ኢዮብ ቀኖቹ እንዴት በፍጥነት እያለፉ እንደሆነ የገለጸው ከፈጣን ሯጭ ጋር በማወዳደር ነው። "ቀኖቼ በፍጥነት ያልፋሉ" (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሯጭ መልዕክተኛ
"ሯጭ" ወይም "የሚሮጥ ሰው"

ቀናቶቼ ይበራሉ
ይህ የኢዮብ የህይወቱ ቀናት እንደ ሰው መሮጥ እንደሚችል ተደርጎ ተስሏል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የትም ስፍራ መልካምን ማየት አልቻሉም
ይህ የኢዮብን የህይወቱን ቀናት እንደ ሰው የሚያዩ ሆነው ተስለዋል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አንዳች መልካም
"አንዳች መልካም ነገር"

እንደ ደንገል ታንኳ ፈጣኖች ናቸው
ኢዮብ ቀኖቹ እንዴት በፍጥነት እያለፉ እንደሆነ ከፈጣን ታንኳ ፍጥነት ጋር ያነጻጽራል። "እንደ ደንገል ታንኳ በፍጥነት ያልፋሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የቄጠማ ደንገል ታንኳ
"ከቄጤማ የተሰራ ታንኳ።" ደንገል ቄጠማ ውስጡ ክፍት የሆነ በወንዝ ዳርቻ የሚበቅል ሳር መሰል ተክል ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ንስር ወደ ሚያድነው በፍጥነት ቁልቁል እንደሚወርድ
ኢዮብ ቀናቱ እንዴት በፍጥነት እንደሚያልፉ ትልቁ ወፍ ንስር ወደሚያድነው ነገር ቁልቁል እንዴት እንደሚወረወር በማነጻጸር ይናገራል። "ንስር ምግቡን ለማግኘት/ለመያዝ ከላይ ቁልቁል በፍጥነት ወደ ታች እንደሚወርድ/ እንደሚበር" (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በፍጥነት ወደታች መውረድ
"በፍጥነት ቁልቁል መውረድ"

Job 9:27

ስለ ማማርርባቸው ነገሮች እረሳለሁ
"ምሬት" የሚለው ረቂቅ ስም "ማማረር" በሚለው ግስ መተርጎም ይችላል። "ማማረሬን አቆማለሁ" ወይም "በእግዚአብሔር ላይ ማማረሬን አቆማለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ማማረሬን
ኢዮብ በማን ላይ እንደሚያማርር በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "በእግዚአብሔር ላይ ማማረሬን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሃዘንተኛ ፊቴን መልሼ ደስተኛ እሆናለሁ
የኢዮብ ሀዘንተኛ ገጽ የተገለጸው አንድ ዞር ሊደረግ እንደሚችል ነገር ተደርጎ ነው። ሀዘንተኛ ሆኜ መታጠቴን አቁሜ ፈገግ እላለሁ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሀዘኖቼ ሁሉ ያስፈሩኛል
ኢዮብ በቁጥር 27 የተናገረውን ቢያደርግ ሊከተል የሚችለውን ውጤት ቁጥር 28 እና 29 ይገልጻሉ። ይህ "ከዚያ" የሚለውን ቃል በመጨመር ለገለጽ ይችላል። "ከዚያም ከሀዘኖቼ ሁሉ የተነሳ እፈራለሁ" (አያያዝ ቃለት/ መስተጻምር የሚለውን ይመልከቱ)

ከሀዘኔ ሁሉ የተነሳ
"ሀዘን" የሚለው ረቂቅ ስም በግስ መልኩ ለገለጽ ይችላል። "ከጎዱኝ ነገሮች ሁሉ የተነሳ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እኮነናለሁ
"ተጠያቂ እሆናለሁ ደግሞም እቀጣለሁ።" ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ለገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር ይፈርድብኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይምተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ታዲያ ስለምን በከንቱ እደክማለሁ?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው የእግዚአብሔርን ፊት ለማግኘት የሚያደደርገው ሙከራ ምንም ጥቅም እንደማያስገኝለት ማሰቡን በትኩረት ለመግለጽ ነው። ኢዮብ ሊያደርግ እየሞከረ ስለሚገኘው ነገር በውስጠ ታዋቂነት የሚገኘው መረጃ ግልጽ ሊደረግ ይቻላል። "የእግዚአብሔርን ፊት ለማግኘት መሞከሬ አንዳች ጥቅም የለውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 9:30

ፊቴን በበረዶ ውሃ ብታጠብ እንኳን
"ሰውነቴን በንጹህ፣ የተራ ውሃ ብታጠብ"

የበረዶ ውሃ
ከሟሟ በረዶ የተገኘ ውሃ

በረዶ
ከደመና የሚወርድ የአየር ጸባዩ ቀዝቃዛ በሆነ ቦታ የሚወርድ ደቃቅ የቀዘቀዘ ውሃ

እጆቼን እጅግ ባነጻ
"እጆቼን ፍጹም ባነጻ።" አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች "በጣም ጠንካራ በሆነ ሳሙና እጆቼን ባነጻ" ብለው ይተረጉሙታል።

በዘአቅት ውስጥ ታሰምጠኛለሁ
"ወደ ጉድጓድ ትወረውረኛለህ"

የገዛ ልብሶቼ ይጸየፉኛል
እግዚአብሔር ወደ ጉድጎድ ከጣለው በኋላ የኢዮብ ልብሶች የተገለጹት ለኢዮብ አሉታዊ ምላሽ እንዳላቸው ተደርጎ ነው። "ገዛ ልብሶቼ እጅግ ይጸየፉኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 9:32

እመልስለታለሁ
ኢዮብ እግዚአብሔር ስህተት ሰርተሃል ብሎ እንደከሰሰው ያመለክታል፣ እርሱም ለክሶቹ መልስ መስጠት እንደሚፈልግ ይናገራል። "ላቀረበብኝ ክስ ምላሽ እንድሰጥ" ወይም "እራሴን እንድከላከል" ወይም "ከእርሱ ጋር ስለ ንጹህነቴ እንድከራከር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አብረን ወደ ፍርድ/ችሎት እንግባ
"ወደ ፍርድ/ችሎት አብረን እንግባ።" እዚህ ስፍራ "ፍርድ ቤት" የሚለው ሰዎች ቀርበው ዳኛ ለክርክራቸው መፍት የሚሰጥበትን ቦታ ነው። "አብሮ ወደ ፍርድ ቤት መግባት" እርስ በእርስ ተካሶ ወደ ፍርድ ቤት መሄድን የሚያመለክት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "እውነቱ እንዲወጣ በዳኛ ፊት አንዱ ከሌላው ጋር መከራከር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በመካከላችን ዳኛ የለም
ይህ ማለት በኢዮብ እና በእርሱ መሃል ከእግዚአብሔር የሚበልጥ ምን ትክክል እንደሆነ ሊወስን የሚችል ዳኛ የለም ማለት ነው።

በሁለታችንም ላይ እጁን የሚጭን
እዚህ ስፍራ "እጁን የሚጭን" ማለት የበለጠ ስልጣን ወይም ሃይል ያለው ማለት ነው። "እጁን በሁለታችንም ላይ የሚያኖር" ወይም "በሁለታችንም ላይ ስልጣን ያለው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 9:34

አያያዥ ሃሳብ፡
እነዚህ ቁጥሮች በኢዮብ እና በእግዚአብሔር መካከል ገብቶ ሊዳኝ የሚችል ከእግዚአብሔር የሚበልጥ ማንም እንደሌለ ቀደም ሲል የቀረበውን ክርክር ይቀጥላሉ

የእግዚአብሔርን በትር ከእኔ ውሰድ
እዚህ ስፍራ "የእግዚአብሔር በትር" የሚለው እግዚአብሔር ኢዮብን መቅጣቱን ወይም ማረሙን የሚገልጽ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "እግዚአብሔር እኔን መቅጣቱ ይቁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ማስፈራራቱ ከእኔ ይቁም
"ፍርሃት" የሚለው ረቂቅ ስም "አስፈራራ" በሚል ግስ ሊተረጎም ይችላል። "እርሱ እኔን ማስፈራራቱን እና ማስፈራቱን ማን ባስቆመልኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያ እኔም እናገራለሁ
"ቀጥሎ እናገራለሁ"

ነገሮች አሁን ባሉበት
"ምክንያቱም አሁን ነገሮች እንዲህ ናቸውና"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 10

1 በራሴ ሕይወት ዝያለሁ፤ አቤቱታዬን ያለመቆጠብ እገልጻለሁ፤ በነፍሴም ምሬት እናገራለሁ። **2** እግዚአብሔርን እንዲህ እለዋለሁ፦ ለምን እንደ ከሰሰከኝ ንገረኝ እንጂ እንዲያው አትፍረድብኝ። **3** የእጅህን ሥራ መናቅ፤እኔንስ ማስጨነቅ የኃጥአንን እቅድ ግን በፈገግታ ስትተወው ይህ በአንተ ዘንድ መልካም ነውን? **4** በውኑ አይኖችህ የሥጋ ለባሽ ዓይኖች ናቸውን? ሰውስ እንደሚያይ ታያለህን? **5** በደሌን ትከታተል ዘንድ፥ ኃጢአቴንም ትመረምር ዘንድ፥ **6** ቀኖችህ እንደ ሰው ቀኖች ናቸውን? ዓመታትህስ እንደ ሰው ዓመታት ናቸውን? **7** በደለኛ እንዳልሆንሁ ብታውቅም እንኳ፥ ከእጅህ ሊያድነኝ የሚችል የለም። **8** እጆቸህ አበጃጁኝ አሳምረህም ሠራኸኝ፤ መልሰህ ግን እያታጠፋኸኝ እኮ ነው። **9** እለምንሃለሁ፤ እንደ ሸክላ አበጃጅተህ እንደ ሰራኸኝ አስብ፤ እንደገናስ ወደ ትቢያ ትመልሰኛለህን? **10** እንደ ወተት አላፈሰስኸኝምን? እንደ እርጎስ አላረጋኸኝምን? **11** ስጋን አደረክልኝ ቁርበትንም አለበስኸኝ፥ በአጥንትና በጅማትም አቀናብረህ አጠነከርኸኝ። **12** ሕይወትና የታመነ ኪዳን ሰጠኸኝ፤ እርዳታህም መንፈሴን ጠበቀ። **13** ነገር ግን እነዚህንም ነገሮች በልብህ ሰወርህ፤ ይህንንም ታስብ እንደነበር አውቃለሁ። **14** ኃጢአትም ባደርግ አንተ ታውቀዋለህ፤ ከአመጻዬም ነጻ አትለቀኝም። **15** በደለኛ ብሆን ወየልኝ፤ ጻድቅ ብሆንም ራሴን ቀና አላደርግም፤ በሃፍረት ተሞልቼአለሁና፥ መከራዬንም እያየሁ ነውና። **16** ራሴንም ቀና ባደርግ እንደ አንበሳ ታድነኛለህ፤ እንደገና ሃያል መሆንህን ታሳየኛለህ፤ **17** አዲስ ምስክሮችህን ታቆምብኛለህ ቊጣህንም በላዬ ታበዛብኛለህ፤ በአዲስ ሰራዊትም ታጠቃኛለህ። **18** ታዲያ ለምን ከማኅፀን አወጣኸኝ? ምነው ያኔ ነፍሴ በጠፋችና የሰው ዓይን ባላየኝ። **19** ኖሮ እንደማያውቅ በሆንሁና፤ ከማኅፀን ቀጥታ ወደ መቃብር በወሰዱኝ። **20** የቀሩኝ ቀናቶች ጥቂት አይደሉምን? ታዲያ ጥቂት እንዳርፍ ተወት አድርገኝ፤ **21** ወደማልመለስበት ከመሄዴ በፊት፥ ወደ ጨለማና ወደ ሞት ጥላ ምድር፥ **22** እንደ እኩለ ለሊት ወደ ጨለመች ምድር፥ ሥርዓትም ወደሌለበት ወደ ሞት ጥላ፥ ብርሃንዋም እንደ ጨለማ ወደ ሆነ ምድር ሳልሄድ፥ ጥቂት እጽናና ዘንድ ተወኝ።

Job 10:1

ህይወቴ ዝላለች
"መኖር ሰልችቶኛል/ደክሜያለሁ"

የማማርርበትን ምክንያት በግልጽ እናገራለሁ
"መግለጽ" እና "ማማረር" የሚሉት ረቂቅ ስሞች "ገለጸ" እና "አማረረ" በሚሉ ግሶች ሊተረጎሙ ይችላሉ። "የማማርርበትን ነገር በግልጽ እናገራለሁ" ወይም "በግልጽ እከራከራለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በነፍሴ ምሬት እናገራለሁ
ኢዮብ እንዴት እንደተሰማው የተገለጸው የተነጻጸረው ከመራራ ጣዕም ጋር ነው። "መራርነት" የሚለው ረቂቅ ስም "በመራርነት" በሚለው ተውሳክ ግስ ሊተረጎም ይችላል። "ውስጣዊ ማንነቴ በመራርነት ይናገራል" ወይም "እኔ በመራርነት እናገራለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

እኔን መጨቆንህ ለአንተ መልካም ነገር ማድረግ ነውን፣ በክፉዎች እቅድ ፈገግ እያልክ የእጆችህን ስራዎች መናቅህስ መልካም ነውን?
ይህ ጥያቄ "አይደለም" የሚል ምላሽ ይጠበቅበታል፤ ደግሞም በገለጻ መልክ ሊቀርብ ይችላል። "በክፉዎች ስራ ፈገግ እያልክ፣ እኔን መጨቆንህ መልካም አይደለም፤ የእጆችህን ስራ መናቅህ ትክክልአይደለም። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይልከቱ)

የእጆችህ ስራዎች
እዚህ ስፍራ እግዚአብሔር የተወከለው በእርሱ "እጆች" ነው። "አንተ የፈጠርከው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በክፉዎች እቅድ ይስቃል
እዚህ ስፍራ "ይስቃል" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር የሚወክለው የእግዚአብሔርን መስማማት። "የክፎዎችን እቅድ ያጸድቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 10:4

የስጋ ዐይን አለህን? ሰው እንደሚያይ ታያለህን?
እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች ታራራቢ ትርጉም አላቸው። እነዚህ ጥያቄዎች እግዚአብሔር ሰው እንደማያይ ወይም ሰው በሚረዳበት መንገድ ነገሮችን እንደማይረዳ ትኩረት ለመስጠት አሉታዊ ምላሽ ይጠብቃሉ። ጥያቄዎቹ በገለጻ መልክ ሊገለጹ ይችላሉ። "አንተ የስጋ ዐይን የለህም፣ አንተ ሰው እንደሚያይ አታይም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

የአንተ ቀኖች እንደ ሰው ቀናት ናቸውን ወይስ የአንተ አመታት እንደ ሰው አመታት ናቸው... ደግሞም ከእጆችህ የሚያድነኝ ማንም የለም?
እነዚህ ጥያቄዎች እግዚአብሔር ዘለዓለማው መሆኑን እና የሰው ዘመን ጥቂት መሆኑን ትኩረት ለመስጠት አሉታዊ ምላሽ ይጠብቃሉ። ይህ በገለጻ መልክ ሊቀርብ ይችላል። "የአንተ ቀናት እንደ ሰው ቀናት አይደሉም የአንተ አመታት እንደ ሰው አመታት አይደሉም...ደግሞም ከአንተ እጅ የሚያድነኝ ማንም የለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ ቀናት እንደ ሰው ቀናት...የአንተ አመታት እንደ ሰው አመታት
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተቀራራቢ ትርጉም አላቸው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ ቀናት
"የአንተ ቀናት ቁጥር"

የአንተ አመታት
"የአንተ አመታት ቁጥር"

በእኔ ስህተት ላይ ጥያቄ ታነሳለህ... ኃጢአቴን ትከታተላለህ
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተቀራራቢ ትርጉም አላቸው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥያቄ ታነሳለህ
"ትከታተለኛለህ"

ከእጆችህ
እዚህ ስፍራ "እጆችህ" የሚለው የሚወክለው የእግዚአብሔርን ሀይል ነው። "ከአንተ ሃይል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 10:8

የአንተ እጆች
እዚህ ስፍራ "እጆች" የሚለው የሚወክለው የእግዚአብሔርን እና የእርሱን የመፍጠር ድርጊት ነው። "አንተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የአንተ እጆች አበጁን ሰሩኝም
ኢዮብ እግዚአብሔር እንዴት በጥንቃቄ እርሱን እንደፈጠረው ለመግለጽ ሸክላ ሰሪ ሸክላውን የሚያበጅበትን አሰራር በዘይቤ ይጠቀማል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አበጀኝ ሰራኝም
"ቅርጽ ሰጠኝ ሰራኝ" "ቅርጽ ሰጠኝ" እና "አበጀኝ" የሚሉት ቃላት በትርጉም ተመሳሳይ ናቸው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ልብ በል
"አስታውስ"

ዳግም ወደ አፈር አምጣኝ
"እንደገና ወደ አፈር መልሰኝ"

Job 10:10

አጠቃላይ መረጃ:
በእነዚህ ሀረጋት፣ ኢዮብ እግዚአብሔር እንዴት በእናቱ ማህጸን ውስጥ እንዳበጀመው ለመግለጽ የሸክላ ሰራተኛን ቋንቋ ይጠቀማል። (ስነ ግጥም የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ወተት አላፈሰስከኝምን፣ እንደ እርጎስ አላረጋኸኝምን?
ይህ አዎንታዊ ምላሽ የሚጠብቅ ጥያቄ ነው። "እንደ ወተት አፈሰስከኝ እንደ እርጎ አረጋኸኝ" ወይም "ፈሳሽ ወተት እርጎ እንደሚሆን በማህጸን አበጀኸኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

አንተ
እዚህ ስፍራ "አንተ" የሚለው የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው

እኔ
እዚህ ስፍራ "እኔ" የሚለው የሚያመለክተው ኢዮብን ነው።

ቆዳ እና ስጋ አለበስከኝ
እግዚአብሔር የኢዮብን አካል በቆዳ እና ስጋ መሸፈኑ የተገለጸው እግዚአብሔር ኢዮብን እንዳለበሰው ተደርጎ ነው። "ሰውነቴን በቆዳ እና ስጋ ሸፈንክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በአንድነት አገጣጠምከኝ
"በአንድነት ሸመንከኝ።" እግዚአብሔር የኢዮብን አካል በማህጸን ማዋደዱ የተገለጸው እግዚአብሔር ጨርቅን እንደሸመነ ተደርጎ ነው። "አዋደድከኝ/ በአንድነት አደረግከኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጅማቶች
ጡንቻን ከአጥንት ወይም ከሌላ የሰውነት ክፍል ጋር የሚያያይዝ እና ነጭ ጠንካራ ማስተሳሰሪያ

Job 10:12

ህይወት እና የቃል ኪዳን ታማኝነት ሰጠኸኝ
"ህይወት" እና "ታማኝነት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች "ህያው" እና "ታማኝ" በሚል ሊገለጹ ይችላሉ። "አንተ ለቃል ኪዳንህ ታማኝ ነበርክ ደግሞም ህያው እንድሆን ፈቅደሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ እርዳታ
"የአንተ እንክብካቤ"

መንፈሴን ጠበቀ
እዚህ ስፍራ ኢዮብ የተወከለው "በመንፈሱ" ነው። "ጠበቅከኝ" ወይም "እኔን በጥንቃቄ ተመለከትክ" ወይም "በደህንነት/በሰላም ጠበቅከኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ አንተ በልብህ የሰወርካቸው ነገሮች
እዚህ ስፍራ "እነዚህ ነገሮች" የሚለው የሚያመለክተው ከተከታዩ ቁጥር ላይ የሚገኘውን ነገር ነው

እነዚህ አንተ በልብህ የሰወርካቸው ነገሮች
እዚህ ስፍራ "አንተ በልብህ የሰወርካቸው" ማለት እግዚአብሔር ምስጢር አድርጓቸዋል ወይም ደብቆታል ማለት ነው። "አንተ ምስጢር ያደረካቸው እነዚህ ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ታውቀዋለህ
"አንተ ትጠብቀኛለህ"

Job 10:15

በክፋት አንድ ነገር ባደርግ
"ክፉ ነገሮችን ባደርግ"

ወዮው ለእኔ
"ለእኔ ይህ እደምን መጥፎ ይሆናል"

ራሴን ቀና ባደርግ
ይህ ፈሊጥ እርግጠኛ ወይም ልበ ሙሉ መሆን ማለት ነው። "ራስን ቀና ባደርግ" ወይም "ልበ ሙሉ መሆን" ወይም "ስለ ራሴ እርግጠኛ ብሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በሀፍረት ተሞላሁ - መከራዬን ተመልከት
ሌላው ሊሰጥ የሚችል ትርጉም፣ "ውርደት ተሞልቻለሁ በመከራዬ ተይዣለሁ"። ውርደቱ መጥፎ ሆነ ሳለ መከራው ደግሞ የከፋ ነው።

በውርደት ተሞልቻለሁ
"ሙሉ ለሙሉ አፍሬያለሁ" ወይም "ከዚህ በኋላ የሚያከብረኝ ማንም አይኖርም"

ውርደት
ሀፍረት

የደረሰብኝን ውርደት ተመልከቱ
"ተዋረደ" የሚለው ረቂቅ ስም "ውርደት" በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። "እግዚአብሔር እንዴት እንዳዋረደኝ ተመልከቱ" (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ራሴን ቀና ባደርግ፣ አንተ እንደ አንበሳ ታደባብኛለህ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1)ይህ ያልሆነ መላምታዊ ሁኔታ ነው ወይም 2) ይህ በተደጋጋ የተፈጸመ ሁኔታ መግለጫ ነው። "ራሴን ቀና ሳደርግ፣ እንደ አንበሳ ታደባብኛለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መላምታዊ ሁኔታ የሚለውን ይመልከቱ)

ራሴ ቀና ባደርግ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር በራስ መተማመን ወይም ኩራት ማለት ነው። "ብኮራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ከባለቤቱ ጋር የሚጣቀስ ተውላጠ ስም የሚለውን ይመለከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Job 10:17

አንተ በእኔ ላይ አዲስ ምስክር ታመጣለህ
ኢዮብ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚደርስበት መከራ የተገለጸው በእርሱ ላይ ምስክር የሚሆኑ ሰዎች እንደሆኑ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእኔ ላይ ቁጣህ ይጨምራል
"ቁጣ" የሚለው ረቂቅ ስም "ቁጡነት" በሚል ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። "በእኔ ላይ ቁጡነቱ እየጨመረ መጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በአዲስ ሰራዊት/ሀይል ታጠቃኛለህ
እግዚአብሔር ወደ ኢዮብ መከራ መላኩ የተገለጸው እግዚአብሔር ሳያቋርጥ በኢዮብ ላይ አዲስ ሰራዊት እንደሚልክ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 10:18

ከማህጸን አወጣኸኝ
እዚህ ስፍራ ከማህጸን ማውጣት የሚወክለው ወደዚህ ዓለም መምጣትን/መወለድን ነው። "ከእናቴ ማህጸን አወጣኸኝ" ወይም "ወደዚህ ዓለም አመጣኸኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መንፈሴን እሰጣለሁ
አንድ ሰው መንፈሱን መስጠቱ የሚወክለው መሞትን ነው። "ሞተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ዐይኖች ለዘለአለም አይመለከቱኝም
እዚህ ስፍራ ኢዮብ "ዐይን" የሚለውን የተጠቀመበት ሰውን ሁሉ ለመጥቀስ ነው። ማንም ሰው ከማየቱ አስቀድሞ በተወለደበት ጊዜ ቢሞት ይመኛል። " አስቀደሞ ማንም ሰው ሳይመለከተኝ" ወይም "ከመወለዴ አስቀድሞ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ያልተፈጠርኩ ያህል ነው
"በፍጹም አልኖርኩም"

በወሰዱኝ ኖሮ/ወደ መቃብር
"አካሌ ወደ መቃብር ይወሰድ ነበር"

Job 10:20

ቀኖቼ ጥቂት አይደሉምን?
እዚህ ስፍራ "ቀኖቼ" የሚለው የሚወክለው የኢዮብን የህይወት ዘመን መጠን ነው። ይህ ጥያቄ ኢዮብ ጥቂት የቀናት እድሜ ብቻ እንዳለው ለማጉላት አዎንታዊ ምላሽ ይጠብቃል። ይህ በገለጻ መልክ ሊቀርብ ይችላል። "ከእንግዲህ በህይወት ለመቆየት የቀሩኝ ጥቂት ቀናት ብቻ ናቸው" ወይም "ህይወቴ በቅርቡ ያበቃለታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሩ
እዚህ ስፍራ የሞቱ ሰዎች መንፈስ የሚሄድበት ቦታ የተገለጸው ምድር እንደሆነ ተደርጎ ነው። "ስፍራው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጨለማው እና የሞት ጥላው
"የሞት ጥላ" የሚለው ሀረግ "ጨለማ" የሚለውን ሀሳብ ያጠናክራል። ሁለቱም ሀረጎች የሞቱ ሰዎች መንፈስ ወዴት እንደሚሄድ ይገልጻሉ። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

የሞት ጥላ
ይህ በኢዮብ 3:5 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።

እንደ እኩለ ለሊት የጨለመ
የሞቱ ሰዎች መንፈስ የሚሄድበት ስፍራ ጥቁረት የተነጻጸረው ከእኩለ ለሊት ጨለማ ጋር ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ያለ አንዳች ስርአት
ይህ አሉታዊ ሀረግ በአዎንታዊ መልክ ሊገለጽ ይችላል። "ግራ በመጋት የተሞላ" ወይም "ሁሉም ግራ የተጋባበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምፀት/ላይዶክስ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ እኩለ ለሊት የጨለመ
የሞቱ ሰዎች ነፍስ የሚሄድበት ስፍራ መጨለም የተነጻጸረው ከእኩ ለሊት ጋር ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 11

1 ነዕማታዊውም ሶፋር እንዲህ በሎ መለሰ፦ **2** ለዚህ ሁሉ ቃል መልስ መስጠት አይገባምን? በንግግር የተማላው ይህ ሰው እንዲያው ይታመናልን? **3** ትምክህትህስ ሌሎችን ሁሉ ዝም ያሰኛቸዋልን? ትምህርታችንን ስትሳለቅበት፤ የሚያሳፍርህ ማንም የለምን? **4** ለእግዚአብሔር ስትናገር “ትምህርቴ የተጣራ ነው፥በዓይንህም ፊት ነቀፋ የለብኝም” ትላለህ። **5** ምነው እግዚአብሔር ቢናገርህ! በአንተም ላይ ከንፈሩን ቢከፍት! **6** በማስተዋሉ ታላቅ ነውና፤ የጥበቡን ምሥጢር ምነው ገልጦ ቢያሳይህ! እግዚአብሔር ለበደልህ ከሚገባው አሳንሶ እንደሚያስከፍልህ ታውቅ ነበር። **7** እግዚአብሔርን መርምረህ ልትረዳው ትችላለህን? ሁሉን የሚችል አምላክን በሙላት ልታውቀው ትችላለህን? **8** ነገሩ እንደ ሰማይ ከፍ ይላል፤ ምን ልታደርግ ትችላለህ? ከሲኦልም ይልቅ ይጠልቃል፤ ምን ልታውቅ ትችላለህ? **9** ርዝመቱ ከምድር ይልቅ ይረዝማል፥ ከባሕርም ይልቅ ይሰፋል። **10** እርሱ በመካከልህ ቢያልፍ፥ የፈለገውን በግዞት ቢዘጋ፥ ለፍርድ የወደደውን ቢጠራ፥ የሚከለክለው ማን ነው? **11** እርሱ ሃሰተኛ ሰዎችን ያውቃልና፥ አመጻንም ሲመለከት እንዳላየ ያልፋልን **12** የሜዳ አህያ ሰው በወለደ ጊዜ ካልሆነ በቀር፥ ሞኞች ሊረዱት አይችሉም። **13** ነገር ግን ልብህን በትክክል ብታቀና፤ እጅህንም ወደ እግዚአብሔር ብትዘረጋ፥ **14** በደልንም ከእጅህ እጅግ ብታርቀው፤ በድንኳንህም ኃጢአት ባይኖር፤ **15** ያን ጊዜ በእርግጥ ያለ እፍረት ቀና ትላለህ፤ ጠንክረህም ትቆማለህ፥ አትፈራምም። **16** መከራህንም ትረሳዋለህ፤ እንዳለፎ እንደሔደም ውኃ ታስበዋለህ። **17** ሕይወትህ ከቀትር ይልቅ ይበራል፤ ጨለማም ቢኖር እንኳ እንደ ጥዋት ይሆናል። **18** ተስፋ ስላለህ ተማምነህ ትቀመጣለህ፤ በዙሪያህ ሁሉ ደኅንነትን ታያለህ፥ በእረፍትም ትቀመጣለህ። **19** ለማረፍ ትተኛለህ፥ የሚያስፈራህም የለም፤ ብዙዎችም ያንተን እርዳታ ይሻሉ። **20** ነገር ግን የክፉዎች ዓይን ግን ትጨልማለች፤ የሚያመልጡበትም መንገድ የላቸውም፥ ያላቸው ተስፋም የመጨረሻ ትንፋሻቸውን መስጠት ብቻ ነው።

Job 11:1

ነዕማታዊው ሶፋር
ይህ ስም በኢዮብ 2፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ከነዕማታ ግዛት የሆነው ሶፋር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደዚህ የበዙ ጥያቄዎች/ቃላት መልስ ሊያገኙ አይገባምን?
ሶፋር ጥያቄውን በአሉታ የሚያቀርበው የኢዮብ ቃላት/ንግግር መገታት አለበት የሚለውን ለማጉላት ነው። "ለእነዚህ ንግግሮች ሁሉ እኛ መልስ ልንሰጥ ይገባል!" ወይም "አንድ ሰው ለዚህ ሁሉ ንግግር መልስ መስጠት ይኖርበታል!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ እንዲህ ንግግር የሚያበዛ ሰው ሊታመን ይገባዋልን?
ሶፋር ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው ኢዮብ የሚናገረውን ማመን እንደማይኖርባቸው ትኩረት ለመስጠት ነው። "ይህ ሰው በንግግር የተሞላ ነው፣ ነገር ግን ሰዎች ሊያምኑት አይገባም!" ወይም "ብዙ ንግግርህ ብቻውን አንተ ንጹህ መሆንህን አያሳይም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ መዘላበድ ሌሎች ዝም እንዲሉ ያደርጋልን?
ሶፋር ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው ኢዮብን ለመገሰጽ ነው። "አንተ ብዙ ስለተናገርክ ብቻ፣ ሌሎች ዝም ማለት አለባቸው ማለት አይደለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ስትቀልድ፣ እንድታፍር የሚያደርግህ ሰው የለምን?
ሶፋር ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው ኢዮብን ለመገሰጽ ነው። ኢዮብ ቀለደ የተባለውን ይበልጥ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። "እኛ በተናገርነው ላይ አንተ ትቀልዳለህ/ታሾፋለህ። አሁን እኛ አንተን እናሳፍርሀለን!" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን እና (በ ተመልከቱ)

Job 11:4

እምነቴ ንጹህ ነው
"መረዳቴ ትክክል ነው"

በአንተ ዐይኖች ንጹህ ነኝ
ዐይኖች አመለካከትን ይወክላል፣ ይህም እግዚአብሔርን የሚመዝንበት ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ኢዮብ እግዚአብሔር ነውር አልባ አድርጎ እንደሚያየው መናገሩ። "አንተ ነውር እንደሌለብኝ ትናገራለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው ወይም 2) ኢዮብ ነውር እንደሌለበት እግዚአብሔር እንደሚፈርድላት እንደሚያምን። "እኔ ነውር/ እንከን እንደሌለብኝ እውቅና መስጠት ይገባሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር እንዲህ ይናገራል... ከንፈሩን ከፍቶ በእናንተ ላይ ይናገራል
"ከንፈሩን ይከፍታል" የሚሉት ቃላት ንግግር ለሚለው ሜቶኖሚ /ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ በአንድነት ሆነው ሶፋር እግዚአብሔር በኢዮብ ላይ በሀይል ይናገራል የሚለውን ፍላጎቱን ያጎላሉ። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

እርሱ የሚያሳየው... የጥበብ ምስጢር
"የጥበብ ምስጢር" የሚለው በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "በኃጢያትህ ምክንያት መከራን እንደምትቀበል ያስረዳሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ከአንተ የሚጠብቀው/ለአንተ የከፈለው/ ለኃጢአትህ ከሚገባህ ያነሰውን ነው
ከኢዮብ የሚጠበቀው የሚለው የሚወክለው የኢዮብን መቅጣትን ነው። "እግዚአብሔር እየቀጣህ ያለው ልትቀጣ ከሚገባህ ያነሰውን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 11:7

እግዚአብሔርን በመፈለግ ልትረዳው ትችላለህ/መርምረህ ትደርስበታለህ? ሁሉን ቻይ የሆነውን ሙሉ ለሙሉ ልታውቀው ትችላለህ?
እነዚህ ሁለት ትይዩ ጥያቄዎች ተመሳሳይ ነገርን ይጠይቃሉ። ጸሐፊው የጥያቄ መልክን የተጠቀመው ትኩረት ለመስጠት ነው። "እግዚአብሔርን በመመርመር/በመፈለግ እርሱን መረዳት አትችልም፣ ሁሉን ቻይ የሆነውን ሙሉ ለሙሉ ልትረዳው አትችልም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

ጉዳዩ
ይህ እግዚአብሔርን ማወቅ/ መረዳትን ያመለክታል። "እግዚአብሔርን ማወቅ/ መረዳት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንደ መንግስተ ሰማይ ሩቅ ነው...ከሲኦል ይጠልቃል
እግዚአብሔርን መረዳት አለመቻል ወደ እነዚህ እጅግ ሩቅ ወደሆኑ ስፍራዎች መሄድ እንደማይቻለው አይነት ተደርጎ ተነግሯል። "በሰማይ ወዳለው ከፍ ያለ ስፍራ እንደማይደረስ... በሲኦል ካዳለው ጥልቅ ስፍራ ይልቅ የማይደረስበት ነው" (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ምን ማድረግ ትችላለህ?
ሶፋር ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው አንድ ሰው እግዚአብሔርን ሙሉ ለሙሉ ለመረዳት አንዳች ነገር ማድረግ አይችልም የሚለውን ለማሳየት ነው። "አንዳች ነገር ማድረግ አትችልም" ወይም "በዚያ መታወቅ ያለበትን ሁሉ ማወቅ አትችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

መጠኑ
ይህ ሊያመለክት የሚችለው አማራጭ ትርጉሞች 1) የእጋዚአብሔርን ታላቅነት 2) የእግዚአብሔርን ጥበብ ታላቅነት

ከምድር ይረዝማል... ከባህር ይሰፋል
የእግዚአብሔር ታላቅነት ወይም ጥበብ የተገለጸው በርቀት እንደሚለካ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 11:10

እርሱ.. በማንንም ላይ ቢዘጋ
"እግዚአብሔር... ማንንም በእስርቤት አስገብቶ ቢዘጋበት"

ማንንም ወደ ፍርድ ቢጠራ/ቢሰበስብ
"ፍርድ" የሚለው ረቂቅ ስም "ዳኘ" በሚል ግስ ሊተረጎም ይችላል። "እግዚአብሔር ሊፈርድበት ፈልጎ ማንንም ወደ እርሱ ቢጠራ/ቢሰበስብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ማን ሊያስቆመው ይችላል?
ይህ ጥያቄ ማንም እግዚአብሔርን ማስቆም እንደማይችል ትኩረት ይሰጣል። "ማንም ሊያስቆመው አይችልም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ይህን አያስተውልምን?
ይህ እግዚአብሔር ኃጢአትን እንደሚያይ ትኩረት ይሰጣል። "እርሱ በእርግጥ ይህንን ያያል!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ሞኝ ሰዎች ግን ማስተዋል/መረዳት የላቸውም
"መረዳት" የሚለው ረቂቅ ስም "ተረዳ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "ሞኝ ሰው ግን ይህንን አይረዳም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የሜዳ አህያ ሰው ሲወልድ እነርሱ ይህን መረዳት ይችላሉ
የሜዳ አህያ በፍጹም ሰው መውለድ እንደማይችል ሁሉ ሞኝ ሰውም ይህን መረዳት ማግኘት አይችልም። "የሜዳ አህያ ሰው ከወለደ ብቻ ያን ጊዜ ሞኝ ሰው መረዳትን/ጥበብን ያገኛል" ወይም "አህያ ሰው ሊወልድ አንደማይችል ሁሉ ሞኝ ሰውም መረዳት/ጥበብን ማግኘት አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 11:13

ምናልባት ልብህን ቀና ብታደርግ
ልብ የሚወክለው አስተሳሰብን እና ዝንባሌን ነው። ልብን ማስተካከል የሚለው የሚወክለው ልብን ማረምን ነው። "ዝንባሌህን ብታስተካክል እንኳን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እጅህን ወደ እግዚአብሔር ብትዘረጋ
ይህ እግዚአብሔርን እርዳታ መጠየቅን የሚወክል ድርጊት ነው። "ወደ እግዚአብሔር ጸልይ ወደ እርሱ ልመናህን አቅርብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ምናልባት ያ ኃጢአት በእጅህ ይገኛል
እጅ የሚወክለው እንድ ሰው የሚያደርገውን ነገር ነው። "ባለፈው ዘመን ክፉ ነገር አድርገህ ቢሆን እንኳን" ሚለው ውሰጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን ከዚያ በኋላ ይህንን ከአንተ ታርቃለህ
ኃጢአትን ከኋላ መተው የሚወክለው ኃጢአትን መስራትን ማቆምን ነው። "ነገር ግን ከዚያ በኋላ ክፉ ነገሮችን ማድረግ ታቆማለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርክሰት በድንኳንህ እንዲኖር አትፍቀድ
እርክሰት እንዲኖር የሚለው የሚወክለው ጽድቅ ያልሆነ ነገር የሚያደርጉ ሰዎችን ነው። "በቤትህ የሚኖሩ የረከሱ ነገሮችን እንዲያደርጉ አትፍቀድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 11:15

ያለ ሀፍረት ምልክት ፊትህን ወደ ላይ አንሳ
"ፊትህን ወደ ላይ አንሳ" የሚለው የሚወክለው ልበ ሙሉ እና ጀግና የሆነ ሰውን ዝንባሌ ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

እንዳለፈ ውሃ ብቻ ታስታውሰዋለህ
ሶፋር መከራን አልፎ ከሄደ ወራጅ ውሃ ጋር ያነጻጽረዋል። "ታስታውሰዋለህ፣ ነገር ግን መከራው አልፎ እንደሄደ ውሃ ይረሳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ህይወትህ እንደ ማለዳ...ይሆናል
ሶፋር ትኩረት ለመስጠት ተመሳሳይ የሆነን ሃሳብ ይደግማል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ህይወትህ ከቀትር ብርሃን ይልቅ ብሩህ ይሆናል
ብሩህነት የሚወክለው ባለጸጋ እና ደስተኛ መሆንን ነው። "ህይወትህ ልክ እንደ እኩለ ቀን የብልጽግና እና የደስታ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ምንም እንኳን ጨለማ ቢኖርም
ጨለማ እግርን እና ሃዘንን ይወክላል። "ምንም እንኳን ከባድ ችግር እን ሀዘን ቢኖርም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ማለዳ ይሆናል
ማለዳ የሚወክለው ብርሃን፣ ብልጽግናን እና ደስታን ይወክላል። "እንደ ማለዳ ብልጽግና እና ደስታ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 11:18

ደህንነትህ የተጠበቀ ይሆናል...በሰላምም ታርፋለህ
ሶፋር ተመሳሳይ ሃሳብን ትኩረት ለመስጠት እና የሚቻል መሆኑን ለመግለጽ ሲል ይደግማል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና መላምታዊ ሁኔታዎች የሚሉትን ይመልከቱ)

በሰላም ታርፋለህ
እዚህ ስፍራ "በሰላም ማረፍ" የሚለው "ዕረፍት" ማለት ነው። "በሰላም" የሚለው ሀረግ "በደህና/በአስተማማኝ" በሚለው ቃል ሊገለጽ ይችላል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

"በሰላም ማረፍ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስም የሚሉትን ይመልከቱ)

የአንተ ስጦታ...ደግሞም በሰላም ትተኛለህ
ሶፋር ተመሳሳይ የሆነ ሃሳብ የሚደግመው ትኩረት ለመስጠት እና የሚቻል መሆኑን ለመግለጽ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና መላምታዊ ሁኔታዎች የሚሉትን ይመልከቱ)

በሰላም ትተኛለህ
"ረፍት" የሚለው ረቂቅ ስም "አረፈ" ከሚለው ግስ ጋር ሊገለጽ ይችላል። "ጋድም ትላለህ ደግሞም ታርፋለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Job 11:20

የክፉ ሰዎች ዐይኖች ይጨልማሉ
የእነርሱ ዐይኖች የሚወክሉት መረዳታቸውን ነው። "የክፉ ሰዎች መረዳት ይጨልማል" ወይም "ክፉ ሰዎች መረዳት/እውቀት ማግኘት አይችሉም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 12

1 በመቀጠልም ኢዮብ መለሰ እንዲህም አለ፦ **2** በእርግጥ እናንተ አዋቂ ሰዎች ናቸሁ፤ ጥበብ ከእናንተ ጋር ትሞታለች። **3** ነገር ግን እኔ እንደ እናንተው ማስተዋል አለኝ፤ ከእናንተም የማንስ አይደለሁም፤ በእርግጥ እንደ እነዚህ ያሉትን ነገሮች የማያውቅ ማን ነው? **4** እግዚአብሔርን ሲጠራ የሚመልስለት ሰው የነበርሁ እኔ አሁን ለጎረቤቶቼ መሳለቅያ ሆኛለሁ፤ ጻድቅና ነቀፋ የሌለበት የነበርሁ እኔ አሁን ማሾፊያ ሆኛለሁ። **5** በደላው ሰው ሃሳብ ውስጥ መከራ የተናቀ ነው፤ እግሩ ለሚሸራተት ሰው ችግሩን ሊጨምርበት ያስባል። **6** የዘራፊዎች ድንኳን ይበለጥጋል፥ እግዚአብሔርንም የሚያስቈጡ በደህና ተቀምጠዋል፤ የገዛ እጃቸውን አምላካቸው አድርገዋል። **7** አሁን ግን እንስሶችን ጠይቁ፥ ያስተምሯችኋል፤ የሰማይንም ወፎች ጠይቁ፥ ይነግሯችኋል። **8** ወይም ለምድር ተናገሩ፥ እርስዋም ታስተምራችኋለች፤ የባሕርም ዓሣዎች በግልጥ ይነግሯችኋል። **9** ከእነዚህ ሁሉ እንስሳት የእግዚአብሔር እጅ ይህን እንዳደረገ፤ የሕያዋን ሁሉ ህይወት፤ **10** የሰው ልጆችንም ሁሉ እስትንፋስ በእጁ እንደያዘ የማያውቅ ማን ነው?። **11** ምላስ የምግብን ጣዕም እንደሚቀምስ፥ ጆሮ ቃላትን አይለይምን? **12** እድሜ በገፉት ዘንድ ጥበብ፥ በዘመን ርዝማኔም ማስተዋል ይገኛል። **13** በእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ኃይል አለ ምክርና ማስተዋልም በእርሱ ዘንድ ይገኛሉ። **14** እነሆ፥ እርሱ ያፈርሳል፥ ተመልሶም አይሠራም፤ አንድን ሰው ቢያስር ሊፈታው የሚችል የለም። **15** እነሆ፥ ውኖቹን ቢከለክል፥ እነርሱ ይደርቃሉ፤ እንደ ገናም ቢለቃቸው፥ ምድርን ያጥለቀልቃሉ። **16** ብርታትና ጥበብ በእርሱ ዘንድ ናቸው፤ የሚስተውና የሚያስተው በእርሱ ስልጣን ስር ናቸው። **17** መካሪዎችንም ባዶአቸውን በሃዘን ይሰዳቸዋል፥ ፈራጆችንም አላዋቂ ያደርጋቸዋል። **18** የነገሥታትንም የስልጣን ሰንሰለት ይፈታል፥ ወገባቸውንም በመታጠቂያ ልብስ ያስርላቸዋል። **19** ይሸራል ባዶአቸውንምይሰዳቸዋል፥ ኃያላንንም ይገለብጣቸዋል። **20** የታመኑ ሰዎችንም ንግግረ ያስወግዳል፥ የሽማግሌዎችንም ማስተዋል ይወስድባቸዋል። **21** በአለቆች ላይ ንቀትን ያፈሳል፥ የብርቱ ሰዎችንም ቀበቶ ይፈታል። **22** ከጨለማ ውስጥ ጥልቅ ነገሮችን ይገልጣል፥ ከሙታንም ሰፈር የመታየትን ጥላ ወደ ብርሃን ያወጣል። **23** ህዝቦችን ብርቱ ያደርጋል፥ ደግሞም ያጠፋቸዋል፤ ህዝቦችንም ያበዛል፥ ደግሞም ወደ ግዞት ይልካቸዋል። **24** ከምድር ሕዝብ አለቆች ማስተዋልን ይወስዳል፥ መንገድም በሌለበት ምድረበዳ ያቅበዘብዛቸዋል። **25** ብርሃን በሌለበት በጨለማ ይዳክራሉ፤ እንደ ሰካራምም ይንገዳገዳሉ።

Job 12:1

እናንተ እንደነዚህ አይነት ሰዎች መሆናች አያጠያይቅም፣ ጥበብ በእናንተ ዘንድ ትሞታለች
ኢዮብ በድርጊታቸው ይሳለቃል፣ ሀሳባቸው ምን ያህል የማይረባ እንደሆነ ያሳያቸዋል። "በእርግጥ እናንተ እንዲህ ያላችሁ ቁምነገረኞች ናችሁ፣ እውቀት ካለ እናንተ መኖር አትችልም" ወይም "እናንተ ብቸኛ ጥበብ ያላችሁ ሰዎች አድርጋችሁ ራሳችሁን ታሳያላችሁ፣ እናንተ በሞታችሁ ጊዜ ጥበብ ትጠፋለች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምፀት የሚለውን ዘይቤ ይመልከቱ)

አያጠራጥርም
"በእርግጥ"

እናንተ
በቁጥር 2 እና 3 ይህ ብዙ ቁጥር ነው። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)

እናንተ እነዚያ ሰዎች ናችሁ
"እናንተ ሁሉንም ነገር የምታውቁ ጠቃሚ ሰዎች ናችሁ"

በእርግጥ፣ እንደ እነዚህ ያሉ ነገሮችን የማያውቅ ማን ነው?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው ለአድማጮቹ ግልጽ መሆን ያለበትን እውነት ለመግለጽ ነው። ይህ በገለጻ መልክ ሊቀርብ ይችላል። " በእርግጥ እንደ እነዚህ ያሉ ነገሮችን የማያውቅ ሰው የለም" ወይም "በእርግጥ እያንዳንዱ ሰው እነዚህን ነገሮች ያውቃል።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 12:4

ለወዳጆቼ መሳለቂያ ሆኛለሁ - እግዚአብሔርን የምጠራ እና እርሱም ምላሽ ይሰጠኝ የነበረ እኔ፣
በእነዚህ ሀረጎች መሃል ያለው ግንኙነት "ምንም እንኳን" በሚሉት ቃላት ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ምንም እንኳን እግዚአብሔርን ጠርቼ የመለሰልኝ ብሆንም፣ አሁን ግን የወዳጆቼ መሳለቂያ ሆኛለሁ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አያያዥ ቃላት የሚለውን ይመልከቱ)

ትክክለኛ እና ያለ ነቀፋ የሆንኩት እኔ - አሁን መሳለቂያ ሆኛለሁ
በእነዚህ ሀረጋት መሃል ያለው ግንኙነት "ምንም እንኳን" በሚሉት ቃላት ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ምንም ያለ ነቀፋ እና ትክክለኛ ሰው ብሆንም፣ አሁን ግን የሰው መሳለቂያ ሆኛለሁ" (አያያዥ ቃላት የሚለውን ይመልከቱ)

በተመቸው ሰው አስተሳሰብ፣ መከራ የደረሰበት ሰው ይናቃል
"ሃሳብ"፣ "ምኞት"፣ "ንቀት"፣ "መከራ የደረሰበት/ዕደለ ቢስ" የሚሉት በሌሎች ሀረጋት ለገለጹ ይችላሉ። "ቀላል ህይወት የሚመራ ሰው መከራ የሚቀበለውን ሰው ይንቀዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ብዙ መከራ ያመጣል
መከራ ማምጣት የሚወክለው ነገሩ እንዲሆን ምክንያት መሆንን ነው። "ብዙ መጥፎ ነገሮች እንዲፈጸሙ ምክንየት መሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እግራቸው ለሚንሸራተት
የእግር መንሸራተት የሚወክለው በአደጋ ወይም ችግር ውስጥ መሆንን ነው። "አሁንም በችግር ውስጥ ለሚገኙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የዘራፊዎች ድንኳን ይበለጽጋል
የእነርሱ ድንኳን ይበለጽጋል የሚለው የሚወክለው ዘራፊዎች በድንኳናቸው ባለጸጋ እንደሚሆኑ ነው። "ዘራፊዎች በራሳቸው ድንኳን ውስጥ በብልጽግና ይኖራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

የገዛ እጃቸው አማልክቶቻቸው ናቸው
"የገዛ እጃቸው" የሚለው ለጥንካሬ ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሲሆን፤ "አማልክቶቻቸው" የሚለው ለኩራታቸው ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። "በችሎታቸው እጅግ ይመካሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Job 12:7

ነገር ግን አሁን ጠይቁ...ለእናንተ ያሳውቋችኋል
እነዚህ 4 ሃሳቦች፤ አውሬዎች፣ ወፎች፣ ምድር እና አሶች ሁሉም ከኢዮብ ወዳጎች ይልቅ እግዚአብሔርን መረዳት እንደሚችሉ ይገልጻሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ምፀት የሚሉትን ይመልከቱ)

እናንተ
ይህ በኢዮብ ቁጥር 7 እና 8 ላይ ብዙ ቁጥር ነው። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)

ነገር ግን አሁን አውሬዎችን ጠይቁ እነርሱም ያስተምሯችኋል
በዐረፍተ ነገሩ የመጀመሪያ ክፍል ላይ የሚገኘው ትዕዛዝ እንደ መላምታዊ ሁኔታ ሆኖ ያገለግላል። "አውሬዎችን ብትጠይቁ ኖሮ፣ እነርሱ ባስተማሩዋችሁ ነበር።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስልጣን እና ሃላፊነቶች - ሌሎች ጥቅሞች እንዲሁም መላምታዊ ሁኔታዎች የሚሉትን ይመልከቱ)

የሰማይ ወፎችን ጠይቁ፣ እነርሱም ይነግሯችኋል
በዐረፍተ ነገሩ የመጀመሪያ ክፍል ላይ የሚገኘው ትዕዛዝ እንደ መላምታዊ ሁኔታ ሆኖ ያገለግላል። የሰማይ ወፎችን ብትጠይቁ ኖሮ፣ እነርሱ ባስተማሩዋችሁ ነበር።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስልጣን እና ሃላፊነቶች - ሌሎች ጥቅሞች እንዲሁም መላምታዊ ሁኔታዎች የሚሉትን ይመልከቱ)

ወይም ከምድር ጋር ተነጋገሩ፣ እርሷ ታስተምራችኋለች
በዐረፍተ ነገሩ የመጀመሪያ ክፍል ላይ የሚገኘው ትዕዛዝ እንደ መላምታዊ ሁኔታ ሆኖ ያገለግላል። "ወይም ከምድር ጋር ብትነጋገሩ ኖሮ፣ ባስተማረቻችሁ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስልጣን እና ሃላፊነቶች - ሌሎች ጥቅሞች እንዲሁም መላምታዊ ሁኔታዎች የሚሉትን ይመልከቱ)

የባህር አሶች ያሳውቋችኋል
"የባህር አሶችን ጠይቁ" የሚለው ትዕዛዝ ከቀደሙት ዐረፍተ ነገሮች ለማለት የተፈለገው ይታወቃል። እንደ መላምታዊ ሁኔታ ሆኖ ይሰራል። "የባህር አሶችን ብትጠይቁ ኖሮ፣ ለእናንተ ያሳውቋችሁ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ እና ስልጣንና ሃላፊነቶች - ሌሎች ጥቅሞች እንዲሁም መላምታዊ ሁኔታዎች የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 12:9

ይህንን... ከእነዚህ ሁሉ እንስሳት የማያውቅ የትኛው ነው?
ይህ ጥያቄ ሁሉም እንስሳት ያህዌ ይህን እንዳደረገ ያውቃሉ የሚለውን ያጎላል። ይህ ጥያቄ በገለጻ መለክ ሊጻፍ ይችላል። " ይህን... ከእነዚህ ሁሉ መሃል እያንዳንዱ እንስሳ ያውቃል።"በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌ እጆች ይህን አድርጓል
የያህዌ እጅ የሚወክለው የእርሱን ሀይል ነው። "ያህዌ ይህንን በሀይሉ አድርጓል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

በእርሱ እጅ ህይወት... እና የሰው ሁሉ እስትንፋስ አለ
የያህዌ እጅ የሚወክለው የእርሱን ሀይል ወይም መቆጣጠር/መግዛት ነው። "እግዚአብሔር እስትንፋስ ያለውን ነገር ሁሉ ህይወት ይቆጣጠራል፤ ደግሞም ለሰው ሁሉ እስትንፋስን ይሰጣል።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

የሰው ሁሉ እስትንፋስ
እዚህ ስፍራ "እስትንፋስ" የሚወክለው ህይወትን ወይም ለመኖር ያለ አቅምን/ችሎታ ነው።

Job 12:11

ላንቃ ጣዕምን እንደሚለይ ጆሮስ ቃላትን አይለይምን?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው ሰዎች ሌሎች የሚናገሩትን በስማት ነገሩ መልካም መሆኑን ወይም አለመሆኑን እንደሚመዝኑ/እንደሚፈርዱ ትኩረት ለመስጠት ነው። ጆሮ እና ላንቃ ለመስማት እና ጣዕም ለመለየት ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ናቸው። "ሰዎች የሚናገሩትን እንሰማለን ደግሞም ምግብን እንደምቀምስ እንቀምሰዋለን ደግሞም እናጣጥመዋለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር እንደዚሁም ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ጥበብ ከእድሜ ባለጸጎች ጋር ናት
"የእድሜ ባለጸጎች ጥበብ አላቸው።" "ጥበብ" የሚለው ረቂቅ ስም "ብልህ" በሚለው ሊገለጽ ይችላል። "ወንዶች" የሚለው ቃል በአጠቃላይ ሰዎች የሚለውን ያመለክታል። "አዛውንቶች ብልህ ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ጥንካሬን የሚገልጹ ቃላት ሴቶችን ሲያካትቱ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀናት ሲጨምሩ መረዳት/ዕውቀት ይገኛል
ይህ የሚገልጸው ሰዎች ረጅም እድሜ በኖሩ መጠን እውቀት/መረዳትን እያገኙ ይሄዳሉ የሚለውን ነው። "መረዳት" የሚለው ረቂቅ ስም "ብዙ መረዳት" በሚለው ሀረግ ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች ረጅም እድሜ ሲኖሩ መረዳት ይጨምራሉ/ያገኛሉ" ወይም "ብዙ ዘመን የኖሩ ሰዎች ብዙ መረዳት አላቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Job 12:13

አጠቃላይ መረጃ:
ኢዮብ12:13 እግዚአብሔር ጠቢብ እና ታላቅ ነው ይላል። የምዕራፉ ቀሪ ክፍል እግዚአብሔር ስለ ሰራቸው በጥበብ የተሞሉ እና ታላላቅ ስራዎች በመናገር ይህ እውነት መሆኑን ያሳያል።

ጥበብ እና ታላቅነት የእግዚአብሔር ናቸው
"ጥበብ" እና "ታላቅነት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች "ጠቢብ" እና "ታላቅ" በሚሉ ቅጽሎች ሊገለጹ ይችላሉ። "እግዚአብሔር ጠቢብ እና ታላቅ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ/ተመልከት
"እይ" ወይም "አድምጥ" ወይም "ልነግርህ ስላለው ነገር ትኩረት ስጥ"

ይህ ዳግም ሊገነባ አይችልም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ይህን ማንም ዳግም ሊገነባው አይችልም" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ያሰረውን፣ ሊፈታው የሚችል የለም
"መፍታት" የሚለው ረቂቅ ስም "ነጻ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር ያሰረውን፣ ማንም ነጻ ሊያወጣው አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ውሆችን ከገደበ፣ ይደርቃሉ
ውሃን መገደብ/መያዝ የሚለው ሊኖረው የሚችለው ትርጉሞች 1) ዝናብ እንዳይዘንብ ቢከለክል። "ዝናብ እንዳይዘንብ ቢከለክል ምድር ትደርቃለች" ወይም 2) ወራጅ ውሃን ከመፍሰስ ቢያስቆም። "ውሃ እንዳይወርድ ቢያግድ ምድር ትደርቃለች" በሚሉት ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ቢለቃቸው፣ ምድሩን ያጥለቀልቃሉ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች፤ እነርሱን መልቀቅ የሚለው ዘይቤ ነው ትርጉሙም 1) ዝናብ እንዲዘንብ ቢያደርግ/ዝናብን ቢያዘንብ። "ብዙ ዝናብ ቢያዘንብ፣

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምድሪቱ ትጥለቀለቃለች" ወይም 2) ውሃ እንዲወርድ/እንዲፈስ ቢያደርግ። "ብዙ ውሃ እንዲወርድ ቢያደርግ፣ ምድር ትጥለቀለቃለች" በሚሉት ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 12:16

ብርታት/ሀይል እና ጥበብ የእርሱ ናቸው
"ብርታት" እና "ጥበብ" የሚሉት ረቂቅ ስሞች "ብርቱ" እና "ጠቢብ" በሚሉ ቃላት ሊገለጹ ይችላሉ። "እግዚአብሔር ብርቱ እና ጠቢብ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የተታለሉ እና የሚያታልሉ ሰዎች ሁለቱም ከእርሱ ሀይል ስር ናቸው
በእግዚአብሔር ሀይል ስር የሚለው የሚገልጸው እግዚአብሔር በሁሉም ላይ ገዢ መሆኑን ነው። "በሀሰት የሚያምኑ እና ለሌሎች የሚዋሹ ሰዎች ሁለቱም በእርሱ ሀይል ስራ ናቸው" ወይም "እግዚአብሔር በሃሰት በሚያምኑ እና ለሌሎች ሃሰትን በሚናገሩ በሁለቱም አይነት ሰዎች ላይ ገዢ ነው" በሚሉት ውስጥ እንደሚገኘው።

እርሱ አማካሪዎችን በባዶ እግራቸው ይሰዳቸዋል
አማካሪዎችን በባዶ እግር መላክ የእነርሱን ጥበብና ስልጣን መቀማት ማለት ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በሀዘን
"ሀዘን" የሚለው ረቂቅ ስም "መመረር" ወይም "ማዘን" በሚሉ ቃላት ሊገለጽ ይችላል። "ደግሞም በጣም ያዝናሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ፈራጆችን ሞኞች ያደርጋቸዋል
"እርሱ ፈራጆች ሞኞች እንዲሆኑ ያደርገል"

እርሱ የነገሥታት በሰንሰለት የማሰር ስልጣን ይወስድባቸዋል
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ነገሥታት ከዚህ በኋላ ስልጣን እንዳይኖራቸው ያደርጋል ለሚለው ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "የነገሥታትን ስልጣን ይቀማቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) ሰዎችን ነገስታት ከጫኑባቸው ቀንበር ነጻ ማውጣት ለሚለው ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት ነው። "እርሱ ነገሥታት በህዝቡ ላይ የጫኑትን ቀንበር ያነሳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እስከ ወገባቸው ድረስ ያለብሳቸዋል/ከወገባቸው በላይ ይራቆታሉ
ይህ ልብስ ምናልባት ባርያ የሚለብሰው ልብስ ይሆናል። ይህንን ልብስ ንጉሦችን ማልበስ የሚገልጸው ንጉሦችን ባሮች ማድረግን ነው። "እርሱ ነገሥታት የባሮችን ልብስ እንዲለብሱ ያደርጋል" ወይም "እርሱ ባሮች ያደርጋቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 12:19

ካህናቱን ባዶ እግራቸውን ይሰዳቸዋል
ካህናትን ባዶ እግራቸውን መስደድ ስልጣናቸውን መቀማትን ያመለክታል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በሀዘን
"ሀዘን" የሚለው ረቂቅ ስም "መመረር" ወይም "ማዘን" በሚሉ ቃላት ሊገለጽ ይችላል። "ደግሞም በጣም ያዝናሉ" ወይም "ደግሞም ይመረራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ታላላቆችን ያዋርዳል
"ሀይለኞችን ያሸንፋል"

ይታመኑ የነበሩትን ንግግራቸውን ያቀላል/ያርቃል
ንግግራቸውን ያቀላል/ያርቃል የሚለው የሚገልጸው መናገር እንዳይችሉ ያደርጋቸዋል ማለትን ነው። "ይታመኑ የነበሩትን መናገር የማይችሉ ያደርጋቸዋል" ወይም "ሌሎች ያምኗቸው የነበሩትን ጸጥ ያሰኛቸዋል" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የሽማግሌዎችን እውቀት/መረዳት ይወስድባቸዋል
መረዳታቸውን ይወስዳል የሚለው የሚገልጸው መረዳት ወይም ጥሩ ውሳኔ መስጠት እንዳይችሉ ማድረግ ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሽማግሌዎች
ሊሰጡ የሚችሉ ትረጉሞች 1) በእድሜ ትልቅ የሆኑ ሰዎች ወይም 2) መሪዎች የሚሉ ናቸው።

በልዑላን ላይ ንቀትን ያፈሳል
በልዑላን ንቀት ማፍሰስ ህዝቡ እንዲንቃቸው ማድረግ ለሚለው (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የሃያላንን ቀበቶ/ወገብ ይፈታል
ቀበቶ የጥንካሬ ምልክት ነው። የሀያልን ሰው ቀበቶ መፍታት የሚወክለው አቅሙን ከእርሱ መንጠቅ እና ሰውየወን ደካማ ማድረግን ነው። "ሃያልንን ደካማ ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 12:22

የጨለማን ጥልቅ ነገሮች ይገልጣል
ነገሮችን መግለጽ የሚወክለው እነርሱን እንዲታወቁ ማድረግን ነው። "በጨለማ ያሉ ጥልቅ ነገሮች" የሚወክለው ሰዎች የማያውቋቸውን ነገሮች ነው። "እርሱ ሰዎች የማያውቋቸውን ምስጢሮች እንዲታወቁ ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጥልቅ ጥላዎችን ወደ ብርሃን ያመጣል
ነገሮችን ወደ ብርሃን ማምጣት የሚወክለው እንዲታወቁ ማድረግን ሲሆን፣ እዚህ ስፍራ "ጥላዎች" በጥላ ውስጥ ለተደበቁ ነገሮች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት ነው። ይህም በተራው እግዚአብሔር ከሰዎች ለደበቀው እውነት ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። "ማንም ሊመለከተው የማይችለውን ነገር እንዲታወቅ ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

መንግሥታትን ታላቅ ያደርጋል
"እርሱ መንግሥታትን ትልቅ ያደርጋል" ወይም "እርሱ መንግሥታት ብዙ መሬት እንዲኖራቸው ያደርጋል"

እንደዚሁም እርሱ ከእስረኞች ጋር ይመራቸዋል
እግዚአብሔር አህዛብን ይመራል የሚለው የሚወክለው እግዚአብሔር ጠላቶቻቸው እንዲመሯቸው ያደርጋል የሚለውን ነው። "እነርሱ" የሚለው ቃል የሚወክለው ህዝቦችን ነው፤ እዚህ ስፍራ እነዚያን አገራት ሰዎች ነው። "እንደዚሁም እርሱ ጠላቶቻቸው እንደ እስረኛ እንዲመሯቸው ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 12:24

ከምድር ህዝቦች መሪዎች ዘንድ ሁሉ እርሱ ማስተዋልን ይወስዳል
ማስተዋላቸውን መውሰድ የሚለው የሚወክለው እንዳያስተውሉ ማድረግን ነው። "እርሱ የምድር ህዝቦች መሪዎች እንዳያስተውሉ ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መንገድ በሌለበት በረሃ መንከራተት

መንገድ በሌለበት በበረሃ መንከራተት የሚለው የሚወክለው በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ መሆንን እና መሄጃን አለማወቅን ነው። "መንገድ በሌለበት ጠፍ መሬት እንደሚንከራተት ምን ማድረግ እንዳለበት እንደማያውቅ ሰው እርግጠኛ አለመሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ብርሃን በሌለበት በጨለማ ይርመሰመሳሉ

ብርሃን በሌለበት በጨለማ መሆን የሚወክለው እውቀት ማጣትን ነው። "ሰዎች ያለ ብርሃን በጨለማ ለመራመድ እንደሚታገሉ እነርሱም ያለ እውቀት ውሳኔ ለመስጠት ይታገላሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንደሰከረ ሰው እንዲንገዳገዱ ያደርጋቸዋል

እንደጠጣ/እንደሰከረ ሰው መንገዳገድ የሚለው የሚወክለው ያለ አላማ መኖርን ነው። "ሲራመድ እንደሚነገዳገድ የሰከረ ሰው ያለ አላማ እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል" ወይም "ወደ ፊት እና ወደ ኋላ እንደሚንገዳገድ እንደ ሰከረ ሰው ያለ አላማ ይንከራተታሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 13

1 እነሆ፥ ይህን ሁሉ ዓይኔ አይቷል፤ ጆሮዬም ሰምቶ አስተውያለሁ። **2** እናንተ የምታውቁትን እኔም ደግሞ አውቀዋለሁ ከእናንተ የማንስ አይደለሁም። **3** ቢሆንም ግን ሁሉን ከሚችል አምላክ ጋር መነጋገር እመርጣለሁ፥ ከእግዚአብሔርም ጋር መዋቀስ እፈልጋለሁ። **4** እናንተ ግን እውነትን በሐሰት ለባጮች ናችሁ፤ ሁላችሁ ዋጋ የሌላችሁ ሃኪሞች ናችሁ። **5** ምነው ሁላችሁ ዝም ብትሉ! ይህም ጥበብ ይሆንላችሁ ነበር። **6** እንግዲህ ክርክሬን ስሙ፥ የከንፈሬንም ሙግት አዳምጡ። **7** ለእግዚአብሔር ጽድቅ የሌለበትን ነገር ትናገሩለታላችሁን? ለእርሱስ በማታለል ታወሩለታላችሁን? **8** ቸርነትንስ ታደርጉለታላችሁን? ለእግዚአብሔርስ በሸንጎ ጠበቃ ትሆኑለታላችሁን? **9** እንደ ዳኛ ወደ እናንተ ቢዞርና ቢመረምራችሁ ይህ መልካም ይመስላችኋልን? ወይስ አንዱ ሌላውን ሰው እንደሚያታልል፣ በሸንጎ ትሳለቁበታላችሁን? **10** በስውር ወደ እርሱ ብታደሉ እንኳ፤ እርሱ በእርግጥ ይገስጻችኋል። **11** ግርማዊነቱ አያስፈራችሁምን? ማስደንገጡስ በላያችሁ አይወድቅምን? **12** አስገራሚ ንግግራችሁ ከአመድ የተሰሩ ምሳሌዎች ናቸው፤ ምላሻችሁም ከሸክላ የተሰሩ መመከቻዎች ናቸው። **13** ዝም በሉ፥ እኔም እንድናገር ተዉኝ፤ የሚመጣው ነገር ይምጣብኝ። **14** ሥጋዬን በጥርሴ እይዛለሁ፥ ሕይወቴንም በእጆቼ አኖራታለሁ። **15** እነሆ ቢገድለኝ የሚቀርልኝ ተስፋ የለኝም፤ ቢሆንም ስለ መንገዴ በፊቱ እሟገታለሁ። **16** አምላክ እንደሌለው ሰው ወደ ፊቱ አልቀረብኩምና፤ለደህንነቴ ይሆንልኛል። **17** አምላኬ፡ንግግሬን በሚገባ አድምጥ፥ አስረግጬ የምለውም ለጆሮህ ይድረስ። **18** እነሆ አሁን፥ ሙግቴን አሰናድቻለሁ፤ ነጻ እንደምወጣም አውቃለሁ። **19** በሸንጎስ ቆሞ የሚከራከረኝ ማን ነው? ጥፋተኛ ሆኜ ከተገኘሁ፤ በዝምታ ህይወቴን ለሞት እሰጣለሁ። **20** አምላኬ ሁለት ነገር ብቻ አድርግልኝ፤ እኔም ራሴን ከፊትህ አልሸሸግም፤ **21** ጠንካራ እጅህን ከእኔ አርቅ፤ በማስደንገጥህም አታስፈራኝ። **22** ከዚያም ጥራኝ፥ እኔም እመልስልሃለሁ። ወይም እኔ ልናገር፥ አንተም መልስልኝ። **23** በደሌና ኃጢአቴ ምን ያህል ሆነ? መተላለፌንና ኃጢአቴን አስታውቀኝ። **24** ፊትህን ከእኔ ለምን ትሰውራለህ፥ እንደ ጠላትህስ ለምን ታደርገኛለህ? **25** የረገፈን ቅጠል ታሳድደዋለህን? ወይስ የደረቀን ገለባ ትከታተለዋለህ? **26** የመረረ ነገር ስለጻፍህብኝ፤ የወጣትነቴን ኃጢአት ታወርሰኛለህ። **27** እግሬንም በእግር ግንድ አስገባኸው፥ መንገዶቼን ሁሉ በቅርበት አየኻቸው፤ የእግሬ መርገጫ የተራመደበትን መሬት ሁሉ መረመርህ። **28** ምንምእንኳ እኔ እንደሚጣል ብስባሽ፥ ብልም እንደበላው ልብስ ብሆንም።

Job 13:1

አያያዥ ሃሳብ
ኢዮብ ለወዳጆቹ መናገሩን ይቀጥላል።

እነሆ/እይ
"ተመልከት" ወይም "አድምጥ" ወይም "ለምናገረው ትኩረት ስጥ"

ዐይኔ ይህን ሁሉ ተመልክቷል
ኢዮብ እነዚህን ነገሮች በዐይኑ በማየቱ ራሱን የሚገልጸው ዐይኖቹን አድርጎ ነው። "ይህንን ሁሉ አይቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ጆሮዎቼ ሰምተው ተረድተዋል
ኢዮብ እነዚህን ነገሮች በጆሮው በመስማቱ ራሱን የሚገልጸው ጆሮቹን አድርጎ ነው። "ይህን ሰምቼ ተረድቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ የምታውቁትን፣ ያንኑ እኔም አውቃለሁ
"የምታውቁትን፣ እኔም አውቃለሁ" ወይም " እናንተ የምታውቁትን ያህል እኔም አውቃለሁ"

Job 13:3

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ ለወዳጆቹ መናገሩን ይቀጥላል

ከእግዚአብሔር ጋር መከራከር እፈልጋለሁ
የኢዮብ ወዳጆች እየፈረዱበት ነው፣ ነገር ግን እውነት እየተናገሩ አይደለም። ይልቁንም ኢዮብ ቅሬታውን እያቀረበ ከእግዚአብሔር ጋር እየተከራከረ ነው።

እናንተ እውነትን በውሸት ኖራ ትሸፋፍናላችሁ
ኖራ መቀባት ወይም እውነትን መሸፈን የሚገልጸው እውነትን መተውን ነው። "እውነትን በሀሰት ትደብቃላችሁ" ወይም "ትዋሻላችሁ ደግሞም እውነትን ተዋላችሁ/ትጥላላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ ሁላችሁም ምንም የማትጠቅሙ ባለ መድሀኒቶች ናችሁ
ባለ መድሃኒት መሆን የሚወክለው ሌላውን የሚያጽናና ሰው መሆንን ነው። ምንም የማትጠቅሙ ማለት ማድረግ ያለባቸውን እንዴት እንደሚያደርጉ አያውቁም ማለት ነው። "ሰው እንዴት እንደሚፈውሱ እንደማያውቁ ባለመድሀኒቶች ናችሁ" ወይም "እናንተ ልታጽናኑኝ መጣችሁ፣ ነገር ግን ያልሰለጠነ መድሃኒተኛ እንዴት እንደሚፈውስ እንደማያውቅ ሁላችሁም እንዴት እንደምታጽናኑ አታውቁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእናንተ ሰላም ለእናንተ ይሁን/ሰላማችሁን ያዙት
ይህ አገላለጽ "ዝም በሉ" ወይም "መናገራችሁን አቁሙ" ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ያንን ብታደርጉ ይህ ለእናንተ ጥበብ ይሆናል
እነርሱ ጥበብ የሞላበትን ነገር እየተናገሩ ይመስላቸዋል፣ ኢዮብ ግን መናገራቸውን አቁመው ዝም ቢሉ የበለጠ ጥበበኞች እንደሚሆኑ ይነግራቸዋል። "ጥበብ" የሚለው ረቂቅ ስም "ጠቢብ" በሚለው ቃል ሊገለጽ ይችላል። "ያንን ብታደርጉ ጠቢብ ትሆናላችሁ" ወይም "መናገራችሁን ብታቆሙ፣ ጠቢብ መስላችሁ ትታያላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Job 13:6

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ ለወዳጆቹ መናገሩን ይቀጥላል

የከንፈሮቼን ልመና ስሙ
እዚህ ስፍራ "ከንፈሮች" የሚለው የሚወክለው ተናጋሪውን ሰው ነው። "እኔ ራሴ የምለውነውን ነገር አድምጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእርሱ በሸንገላ ... ያለ ጽድቅ/በክፉ ትናከራላችሁን?
ኢዮብ እነዚህን ሁለት ጥያቄዎች የሚጠቀመው ወዳጆቹ ያለ ጽድቅ/በክፉ በመናገራቸው ሊወቅሳቸው ነው። "እናንተ ለእግዚአብሔር የምትናገሩ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይመስላችኋላ፣ ነገር ግን በክፋት/ጽድቅ የሌለበትን ነገር እየተናገራችሁ ነው። በማታለል እየተናገራችሁ ነው።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

በማታለል መናገር
"መዋሸት" ወይም "ውሸት መናገር"

ለእርሱ ወገንተኝነትን ታሳያላችሁን? ለእግዚአብሔር ትከራከራላችሁን?
ለእግዚአብሔር ደግነትን ማሳየት የሚወክለው እግዚአብሔርን መርዳትን ወይም እግዚአብሔርን ከኢዮብ ማማረር መከላከልን ነው። ኢዮብ እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመባቸው ወዳጆቹ ለእግዚአብሔር እንቆምለታለን ብለው በማሰባቸው ሊወቅሳቸው ነው። "እግዚአብሔር እንድትከራከሩለት ይፈልጋል ብላችሁ ታስባላችሁን? ጠበቃ በፍርድ ቤት እንደሚካከር ለእግዚአብሔር እንደምትከራከሩለት ታስባላችሁ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እንዳሁም ምፀት የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 13:9

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ ለወዳጆቹ መናገሩን ይቀጥላል

እርሱ መርምሮ በደረሰባችሁ ጊዜ ይህ ለእናንተ መልካም ይሆንላችኋልን?
እዚህ ስፍራ "ከውጭ ሲያገኛችሁ" በዘይበያዊ አነጋገር "ሲመረምራችሁ" የሚል ትርጉም አለው። ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው እግዚአብሔር ወዳጆቹን በመረመራቸው ጊዜ ስህተተኞች ሆነው ስለሚያገኛቸው ሊያስጠነቅቃቸው ፈልጎ ነው። "እግዚአብሔር በመረመራችሁ ጊዜ፣ ለእናንተ መልካም አይሆንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተን ይወቅሳል
"እናንተን ይገስጻል"

በድብቅ ወገናዊነትን/አድልዎ ብታሳዩ
"ለሌላው በድብቅ አድልዎ ብታደርጉ።" ወገናዊነትን ማሳየት የሚመለክተው፣ ዳኛው ያ ሰው መልካም ነው እንዲል ስለ አንድ ሰው መልካሙን ብቻ መናገርን ነው። ይህንን በድብቅ ማድረግ ማለት በትክክል የተናገሩ ማስመሰል ሲሆን፣ በእርግጥ ግን ሲታይ ከአንዱ ሰው ይልቅ ለሌላው ማድላት ነው።

Job 13:11

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ ለወዳጆቹ መናገሩን ይቀጥላል

የእርሱ ግርማ አያስፈራችሁምን፣ ደግሞስ የእርሱ ፍራሃት አይወድቅባችሁምን?
ኢዮብ እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመው ወዳጆቹን ለመገሰጽ ነው። ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ኢዮብ አግዚአብሔርን መፍራት አለባችሁ እያላቸው ነው። "ግርማው ሊያስፈራችሁ፣ እርሱን መፍራት ሊወድቅባችሁ ይገባል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) ኢዮብ ወዳጆቹን እግዚአብሔርን ፍሩት ይላቸዋል። "ግርማው ያስፈራችኋል፣ ደግሞም የእርሱ ማስደንገጥ በላያችሁ ይወድቃል!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ ማስደንገጥ በላያችሁ ይወድቃል
ማስደንገጥ በሰዎች ላይ መውደቅ የሚለው የሚወክለው እነርሱ እጅግ ይፈራሉ የሚለውን ነው። "እናንተ እጅግ አትደነግጡምን" ወይም "ደግሞስ እጅግ አትፈሩም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእናንተ ምርጥ ንግግሮች/ምሳሌዎች የሚባሉት ከአመድ የተበጁ ናቸው
አመድ የሚወክለው ጥቅም እና እድሜ የሌላቸውን ነገሮች ነው። "የእናንተ ምርጥ አባባሎች እንደ አመድ እርባና ቢሶች ናቸው" ወይም "የእናንተ ምርጥ አባባሎች/ምሳሌዎች ነፋስ ጠርጎ እንደሚወስዳቸው አመድ ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መከላከያዎቻችሁ
ይህ የሚያመለክተው ሊሰጥ የሚችለው ትርጉም 1) ራሳቸውን ለመከላከል የሚናገሩት ወይም 2) ለእግዚአብሔር ጥብቅና ለመቆም የሚናገሩት

Job 13:13

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ ለወዳጆቹ መናገሩን ይቀጥላል

የእናንተ ሰላም ለእናንተ ይሁን/ሰላማችሁን ያዙት
ይህ ፈሊጣው አገላለጽ ነው "ዝም በሉ" ወይም "መናገራችሁን አቁሙ" ማለት ነው።(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔን ብቻዬን ተዉኝ
ይህ ፈሊጣው አገላለጽ ነው "እኔኝ መሳሰጨነቃችሁን አቁሙ" ወይም "እኔን ማስተጓጎላችሁን አቁም" ነው።(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእኔ ላይ የሚደርሰው ይድረስብኝ/ይምጣብኝ
በአንድ ሰው ላይ የሚመጡ ነገሮች የሚወክሉት በዚያ ሰው ላይ የሚሆኑ ነገሮችን ነው። ይህ አገላለጽ የሚጀምርበት "ይሁን" የሚለው አባባል በእርሱ ላይ ስለሚደርሰው ነገር ግድ የለውም ማለት ነው። "በእኔ ላይ ሊደርስ ያለው ማናቸውም ነገር ይድረስብኝ" ወይም "በእኔ ላይ ስለሚደርሰው ነገር ግድ አይለኝም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ስጋዬን ... በእጆቼ አይዛለሁ
እዚህ ስፍራ "ስጋ" የሚለው ለህይወት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ጥርስ" እና "እጆች" የሚሉት ራሱን ስለ መግዛቱ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ናቸው። እነዚህ ሁለት ሀረጋት በአንድነት ኢዮብ ከእግዚአብሔር ጋር በመከራከር ህይወቱን አሳልፎ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆኑን ያጎላሉ። "ህይወቴን አሳልፌ ለመስጠት ዝግጁ ነኝ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 13:16

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ ለወዳጆቹ መናገሩን ጨርሶ በቀጥታ ከእግዚአብሔር ጋር መናገር ይጀምራል።

ይህ ለእኔ ነጻ መውጣት ምክንያት ይሆናል
"ነጻ መውጣት" የሚለው ረቂቅ ስም "ነጻነት" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር እኔን ነጻ የሚያወጣበት ምክንያት ይህ ነው" ወይም "እግዚአብሔር እኔን ከችግሮቼ የሚያድነኝ ከዚህ የተነሳ ነው" በሚሉት ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ሆይ፣ ስማኝ
ኢዮብ ንግግሩን የሚጀምረው በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር በመጮህ/በመናገር ነው።

ንግግሬን እድምጥ፣ የምናገረው ወደ ጆሮህ ይድረስ
እነዚህ ሁለት መስመሮች በመሰራታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ ደግሞም ኢዮብ እግዚአብሔር እንዲሰማው የሚያቀርበውን ጥያቄ አጉልተው ይገልጻሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የምናገረው ወደ ጆሯችሁ ይድረስ
"መናገር/ማወድ" የሚለው ረቂቅ ስም "ተናገረ/አወጀ" በሚል ግስ ሊገለጽ ይችላል። ጆሯችሁ የሚለው የሚወክለው መስማትን ነው። "የምናገረውን ስሙ" ወይም "የምለውን ስሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ስሞች እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 13:18

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ ለእግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል

እነሆ አሁን ተመልከት
ይህ ተከትሎ የሚነገረውን ያጎላል። "እነሆ አሁን ስማ" ወይም "እባክህ ስማኝ"

መከላከያዬን በስርአት አቀርባለሁ
መከላከያውን በስርአት ማቅረብ የሚወክለው ራሱን ለመከላከል የሚያቀርበውን መወሰንን ያመለክታል። "እርሴን እንዴት እንደምከላከል በሚገባ አስቤበታለሁ" ወይም "ያለኝን ሀሳብ እንዴት እንደምገልጽ ወስኛለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በፍርድ ቤት እኔን በደለኛ አድርጎ መከራከር የሚችል ማን ነው?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀምበት ትክክለኛ እስከሆነ ድረስ ከእርሱ ጋር ማንም ሊከራከር እንደማይችል ያለውን እምነት ለመግለጽ ነው። "በፍርድ ቤት ማንም ከእኔ ጋር ይከራከራል ብዬ አላምንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህንን ለማድረግ ብትመጡ
"ከእኔ ጋር ለመከራከር ብትመጡ"

አንተ ብትመጣ እዚህ ስፍራ "አንተ" የሚለው እግዚአብሔርን ራሱን ነው
ስህተተኛ መሆኑ ከተረጋገጠ ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ስህተተኛ መሆኔን አንተ ካረጋገጥህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ህይወቴን አሳልፌ እሰጣለሁ
አንድ ሰው ህይወቱን አሳልፎ መስጠቱ ለሞት ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "እሞታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 13:20

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ ለእግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል

ከአንተ ፊት
"ፊት" የሚገለጸውን አካል ይወክላል። "ከአንተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ከባድ እጅህን ከእኔ ላይ አንሳ
ከባድ/የሚጫን እጅ አንድን ሰው የሚጫን ነገር ማድገረግን የሚገልጽ ሜቶኖሚ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። እጅን ማንሳት እነዚያ ነገሮችን ማድረግ ማቆምን የሚገልጽ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "እኔን መጫንህን አቁም/እጅህን ከእኔ አንሳ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ማስጨነቅህ እንድፈራ አያድርገኝ
"ማስጨነቅህ" የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲፈሩ የሚያደርጋቸውን ምክንያት ነው። "አታስጨንቀኝ/አታስፈራኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 13:23

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ ለእግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል

እንደ ጠላትህ ....ስለምን ከእኔ ትደበቃለህ?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው እግዚአብሔር እያደረሰበት ስላለው ነገር ለማማረር ነው። ምናልባትም መልስ ለማግኘት ተስፋ እያደረገ ይሆናል። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ፊትህን ከእኔ ደበቅህ/ሰወርክ
ፊትን ከሌላው መደበቅ የሚወክለው ለመመልከት አለመፈለግን ወይም ለማየት መቃወምን ነው። "እኔን ማየት አልፈለግክም" ወይም "ተውከኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ታሰቃያለህን...የደረቀውንስ እብቅ ትከታተላለህን?
ኢዮብ እነዚህን ጥያቄዎች የሚጠቀምባቸው እርሱ እዚህ ግባ የማይባል እና ደካማ ሳለ እግዚአብሔር ኢዮብን መከታተሉና ማሳደዱ ዋጋ እንደሌለው ለእግዚአብሔር ለመናገር ነው። "ቅጠል" እና "የደረቀ እብቅ" የኢዮብን ደካማነት፣ አቅመቢስነት እና ተሰባሪነት የሚገልጹ ዘይቤዎች ናቸው። "አንተ ታሳድደኛለህ፣ እኔ ግን ነፋስ እንደሚጠርገው ቅጠል እና እንደ ደረቅ እብቅ ደካማነኝ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እንደዚሁም ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 13:26

አጠቃላይ መረጃ፡
ኢዮብ ጉዳዩን ለእግዚአብሔር ማቅረቡን ያበቃል

አንተ በእኔ ላይ መራራ ነገሮችን ታቀርባለህ/ትጽፋለህ
"መራራ ነገሮች" የሚለው የሚወክለው መክሰስን ነው። "አንተ በእኔ ላይ ክስን ታቀርባለህ/ትጽፋለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መልካም ያልሆኑትን የወጣትነቴን ታማኝነት ማጣት/ኃጢአት እንድወርስ አደረግህ
የወጣትነቱን ታማኝነት ማጣት መውረስ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች፡ 1) በወጣትነቱ ታማኝነት ማጣት/ኃጢአት በደለኛ መሆን። "በወጣትነቴ ኃጢአት አሁንም ድረስ በደለኛ አደርገኸኛል" ወይም 2)በወጣትነት ኃጢአቱ እየተቀጣ ይገኛል። "በወጣትነቴ በሰራሁት ኃጢአት እየቀጣኸኝ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የወጣትነቴ ኃጢአት
"ወጣት" የሚለው ረቂቅ ስም "ታዳጊ" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። "ታዳጊ ሳለሁ የሰራሁት ኃጢአት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እግሮቼንም ደግሞ በእግር ግንድ ታጣብቃለህ
ይህንን ማድረግ የሚወክለው ወንጀል የሰራ እና እስረኛ የሆነ ይመስል፣ ኢዮብን መቅጣትን እና በነጻነት እንዳይኖር መከልከልን ነው። "እግሮቼን በእግር ግንድ ያጣበቅከኝ ያህል ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእግር ግንድ
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች፡ 1) የእስረኞን እግሮች በፍጹም መንቀሳቀስ እንዳይችል አድርጎ በአንድ ስፍራ የሚይዝ ማሰሪያ ወይም 2) መንቀሳቀሱን ከባድ የሚያደርግበት በእስረኛ እግሮች ዙሪያ የሚደረግ ሰንሰለት። እነዚህ እንደ ቅጣት መልክ የሚያገለግሉ ናቸው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መንገዶቼ ሁሉ
"መንገዶች" የሚለው የሚወክለው ኢዮብ ያደረጋቸውን ነገሮች ነው። "ያደረግኳቸው ነገሮች በሙሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እግሮቼ የረገጡትን ስፍራ/ዱካዬን ሁሉ መረመርህ/ተከታተልክ
የእግሩ ጫማ የሚወክለው የሚራመደውን ሰው ነው። "የተራመድኩባቸውን ስፍራዎች ሁሉ መረመርህ/ተከታተልህ" ወይም "አንድ ሰው የረገጣቸው ቦታዎች ሁሉ እንደሚታዩ የሰራኋቸውን ነገሮች ሁሉ ተከታተልክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደተበላሸ/ እንደበሰበሰ እና እንደተጣለ ነገር
ኢዮብ ህይወቱን ከበሰበሰ ነገር ጋር ያነጻጽራል። ቀስ በቀስ ወደ ሞት እየሄደ ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አይጦች እንደበሉት ጨርቅ
ኢዮብ ራሱን አይጦች በልተው ከቀዳደዱት ጨርቅ ጋር ያመነጻጽራል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 14

1 ከሴት የተወለደ ሰው ጥቂት ቀናት ቢኖርም፥ በመከራ የተሞሉ ሆኑ። **2** እንደ አበባ ከመሬት ይወጣል፥ ይረግፋልም፤ እንደ ጥላም ይፈጥናል፥ ነገር ግን አይቆይም። **3** እንደዚህ ያለውን ሰው ትመለከታለህን? ከአንተስ ጋር እኔን ወደ ፍርድ ታመጣኛለህን? **4** ከርኩስ ነገር ንጹሕን ማውጣት ማን ይችላል? ማንም የለም። **5** የሰው ዕድሜ የተወሰነ ነው፥ የወራቶቹም ቍጥር በአንተ እጅ ነው፥ እርሱም ሊያልፈው የማይችለውን ገደብ ቀጠርህለት። **6** እንደ ተቀጣሪ ሰው የቀሩትን ቀኖች እዲደሰትባቸው፤ እዲያርፍም ከእርሱ ዘወር በል። **7** ዛፍ ቢቈረጥ ደግሞ ሊያቈጠቍጥ፥ ቅርንጫፉም ማደግ እንዳያቆም ተስፋ ሊኖረው ይችላል። **8** ምንምእንኳ ሥሩ በምድር ውስጥ ቢያረጅ፥ ግንዱም በመሬት ውስጥ ቢሞት፥ **9** የውኃ ሽታ ሲያገኝ ዳግም ያቈጠቍጣል እንደ አትክልትም ቅርንጫፍ ያወጣል። **10** ሰው ግን ይሞታል፤ ይደክማል፤ በርግጥ ሰው እስትንፋሱን ይሰጣል፥ እርሱስ ወዴት አለ? **11** ውኃ ከሐይቅ እንደሚያልቅ፤ ወንዙም እንደሚቀንስና እንደሚደርቅ፤ **12** እንዲሁ ሰዎች ይተኛሉ ዳግም አይነሱም፤ ሰማይ እስኪያልፍ ድረስ አይነቁም፥ ከእንቅልፉቸውም አይነሱም። **13** በሲኦል ውስጥ ምነው በሰወርኸኝ ኖሮ! ቍጣህ እስኪያልፍ ድረስ በሸሸግኸኝ ኖሮ! ቀጠሮም አድርገህ ምነው ባሰብኸኝ ኖሮ! **14** በውኑ ሰው ከሞተ ተመልሶ ሕያው ይሆናልን? መለወጤ እስኪመጣ ድረስ፥ የሰልፌን ዘመን ሁሉ በትዕግሥት በተጠባበቅሁ ነበር። **15** በጠራኸኝና በመለስሁልህ ነበር፤ የእጅህንም ሥራ በተመኘኸው ነበር። **16** ለእርምጃዬ ጥንቃቄንና ገደብን ታደርግለታለህ፤ ኃጢአቴንም አትቆጣጠርብኝም። **17** መተላልፌን በከረጢት ውስጥ ታትመዋለህ፥ ኃጢአቴንም ትሸፍንልኛለህ። **18** ነገር ግን ተራራ እንኳ ይወድቃል ይጠፋልም፥ ዓለቶችም እንዲሁ ከስፍራቸው ይለቃሉ፤ **19** ውኖች በድንጋዮቹ ላይ ይወርዳሉ፤ ጎርፎቹም የምድሩን አፈር ይወስዳሉ፤ እንዲሁ የሰውን ተስፋ ታጠፋዋለህ። **20** ሁልጊዜ ታሸንፈዋለህ፥ እርሱም ያልፋል፤ፊቱን ትለውጣለህ፥ እርሱንም ወደ ሞት ትሰድደዋለህ። **21** ልጆቹ ወደ ክብር ቢመጡም አያውቅም፤ ቢዋረዱም ይህ ሲሆን አያይም። **22** ነገር ግን የራሱ ሰውነት ሕመም ብቻ ይሰማዋል፥ ለራሱም በሃዘን ያለቅሳል።

Job 14:1

አጠቃላይ መረጃ:
በዚህ ምዕራፍ በኢዮብ 12:1 የተጀመረው የኢዮብ ንግግር ይቀጥላል፣ ኢዮብ ከእግዚአብሔር ጋር ይነጋገራል።

ከሴት የተወለደ፣ ሰው
ይህ ወደዚህ ዓለም የተወለደውን ሁሉ፣ ወንድንም ሴትንም በአጠቃላይ ሰውን ያመለክታል። (ጉልበትን/ጠንቻቻማነትን የሚያመለክቱ ቃላት ሴቶችን ሲያካትቱ የሚለውን ይመልከቱ)

ለጥቂት ቀናት የሚኖር
ይህ ሰው አጭር እድሜ እንዳለው በማጋነን የቀረበ አገላለጽ ነው። "በጣም አጭር ጊዜ ብቻ የሚኖር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

በችግር የተሞላ
"በችግር የተሞላ" መሆን የሚወክለው ብዙ ችግር ማጋጠሙን ነው። "ብዙ ችግር አለው" ወይም "ብዙ ተሰቃየ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ አበባ ከምድር ይበቅላል፣ ደግሞም ይቆረጣል
የሰው እድሜ እንደ አበባ እድሜ አጭር ነው፣ ደግሞም በቀላሉ ይሞታል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ጥላ ይሸሻል፣ ደግሞም አይቆይም
የሰው አጭር ህይወት በፍጥነት ከሚጠፋ ጥላ ጋር ተነጻጽሯል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእነዚህ አንዱን ተመልክተሃል?
ኢዮብ እግዚአብሔር በእርሱ ላይ እንዲህ እንዲያተኩር አለመፈለጉን ይጠቁማል። "ከእነዚህ አንዱን አልተመለከትክም" ወይም "ለእነዚህ ብዙ ትኩረት አልሰጠህም። እባክህ በእኔ ላይ ብዙ አታተኩር።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ተመልከት
እዚህ ስፍራ አንድን አካል መመልከት የሚወክለው በእርሱ ላይ ለመፍረድ ትኩረት መስጠትን ነው። "ትኩረት ስጥ" ወይም "ከዚያ ላይ ስህተትን መፈለግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እኔን ከአንተ ጋር ወደ ፍርድ ታመጣለህን?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው ኢዮብ እንደ አበባ በቶሎ ጠፊ ሆኖ ሳለ እግዚአብሔር በእርሱ ላይ መፍረዱ እንዳስደነቀው ለመግለጽ ነው። "ነገር ግን አንተ በእኔ ላይ ፈረድክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 14:4

አጠቃላይ መረጃ:
ኢዮብ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገሩን ይቀጥላል።

ማን ንጹህ ካልሆነ ነገር ንጹህ የሆነ ነገርን ማውጣት ይችላል? ማንም
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው እርሱ ንጹህ ስላልሆነ ነገር የሚያውቀውን እግዚአብሔር በኢዮብ ላይ እንዲያደርግ ለመገፋፋት ነው። "ማንም ንጹህ ካልሆነ ነገር ንጹህ ነገርን ማምጣት አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ቀኖች የተወሰኑ ናቸው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንተ የሰውን ቀናት ትወስናለህ" ወይም "አንተ ሰው የሚኖርበትን ዘመን ትወስናለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የወራቱ ቁጥር በአንተ ዘንድ ነው
ሰው የሚኖርበት ወራት ቁጥር በእግዚአብሔር ዘንድ መሆኑ የሚወክለው ሰው የሚኖርበትን ወራት ቁጥር የሚወስነው እግዚአብሔር መሆኑን ነው። "ምን ያህል ወራት እንደሚኖር አንተ ትወስናለህ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሊያልፍ የማይችልበትን ገደብ አንተ ወስነህል
ገደብን ማለፍ የሚለው የሚወክለው አንድ ሰው እንዲኖር እግዚአብሔር አስቀድሞ የወሰነለት ዘመን መኖር ነው። "አንተ የሚሞትበትን ጊዜ ወስነሃል፣ እናም ሰው ያንን አልፎ መኖር አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የተቀጠረ ሰው/ቅጥረኛ
አንድን ስራ ለመስራት የተቀጠረ እና ከዚያ ወደ ቤቱ የሚሄድ ሰው

Job 14:7

ለዛፍ ተስፋ ሊኖረው ይችላል
"ተስፋ" የሚለው ረቂቅ ስም "ተስፋ" በሚል ግስ ሊገለጽ ይችላል። ተስፋ ከቁር 7-9 ባለው ውስጥ ተብራርቷል። "ዛፍ ዳግም እንደሚኖር ተስፋ ልናደርግ እንችላለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ዳግም ሊበቅል ይችላል
"እንደገና መብቀል ሊጀምር /ሊያቆጠቁጥ ይችላል"

ስለዚህም ቅርንጫፉ ሊጠፋ አይችልም
መጥፋ የሚወክለው መሞትን ነው። "ስለዚህም አዳዲሶቹ ቅርንጫፎች አይደርቁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ምንም እንኳን
"ቢሆንም እንኳን"

ጉቶ
ዛፉ ከተቆረጠ በኋላ ታች ከመሬቱ ላይ ብቅ ብሎ የሚቀረው ክፍል

የውሃ ሽታ ቢያገኝ ብቻ
ይህ የሚገልጸው የሞተው ጉቶ ልክ ውሃ ማሽተት እንደሚችል እና ውሃ በአቅራቢያው እንደሚገኝ ተደርጎ ነው። "ጥቂት ውሃ እንኳን በአቅራቢያው ቢኖር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ የሚለውን ዘይቤ ይመልከቱ)

ያቆጠቁጣል
"ማደግ/ማቆጥቆጥ ይጀምራል"

እንደ ተክል ቅርንጫፍ ያወጣል
ዛፍ ቅርንጫፍ ማውጣቱ የሚወክለው ቅርንጫፎች በዛፍ ላይ ማደጋቸውን ነው። "ቅርንጫፎች በጉቶው ላይ እንደ ተክል ማደግ ይጀምራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ የሚለውን ዘይቤ ይመልከቱ)

Job 14:10

ከእንግዲህ የት ይገኛል?
ኢዮብ ይህንን ጥጣቄ የተጠቀመው ሰው በሞተ ጊዜ፣ እንደማይገኝ አጉልቶ ለማሳየት ነው። "የት እንደሆነ ማንም አያውቅም" ወይም "ላይመለስ ሄዷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ውሃ ከሐይቅ እንደሚተን... ደግሞም ዳግምም እንደማይነሳ
ሞት ዳግም የሚከናወን ነገር አለመሆኑ የተነጻጸረው አንዴ የተነነ ውሃ ዳግም ሊመለስ ካለመቻሉ ጋር ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ውሃ እንደሚተን... ከወንዝ እንደሚነሳ
እነዚህ ሁለት ሀረጋት አንድ አይነት ሀሳብን ይገልጻሉ፤ ይህም መደጋገም የተደረገው ሞት የመጨረሻ ነገር መሆኑን ለማጉላት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደዚሁም ሰዎች ይጋደማሉ
መጋደም የሚለው የሚወክለው መሞትን ነው። "እንደዚሁም ሰዎች ይሞታሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ዳግም አይነሱም
ዳግም መነሳት የሚወክለው ዳግም መኖር የሚለውን ነው። "ዳግም አይኖርም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ዳግም አይነቁም አሊያም ከተኙበት አይነሱም
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ በአንድነት ያገለገሉት ሞት የመጨረሻ መሆኑን ለማጉላት ነው። መተኛት የሚለው የሚወክለው መሞትን ሲሆን መንቃት ደግሞ የሚወክለው ዳግም መኖርን ነው። "የሞቱ ሰዎች ዳግም አይኖሩም፣ እናም ከሞት አይነሱም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 14:13

አጠቃላይ መረጃ:
ኢዮብ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገሩን ይቀጥላል።

አቤቱ፣ እባክህ ሰውረኝ
ይህ ኢዮብ በጣም የሚፈልገውን ነገር ግን በእርግጥ ይሆናል ብሎ የማይጠብቀውን ነገር የሚያሳይ ቃለ አጋኖ ነው። "ብትሰውረኝ በወደድሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ አጋኖ የሚለውን ይመልከቱ)

ለብቻዬ አግልለኝ
"በእኔ ላይ ቆልፍ" ወይም "ሰውረህ አስቀምጠኝ"

አትርሳኝ
አንድን ሰው አለመርሳት/ማስታወስ ስለዚያ ሰው ማሰብን የሚገልጽ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ስለ እኔ አስብ" ወይም "እኔን አስታውስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሞተ ሰው ዳግም ይኖራልን?
በውስጠ ታዋቂነት የተሰጠ ምላሽ "አይ" የሚል ነው። "የሞተ ሰው፣ ዳግም በህይወት አይኖርም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህ ከሆነ
"ከሆነ" የሚለው ምን እንደሚያመለክት ከቀደመው ሀረግ ይታወቃል። "እርሱ ዳግም ቢኖር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የድካም ጊዜያቶቼን ሁሉ በዚያ ለመቆየት
"ብደክም እንኳን ዘመኔን ሁሉ በዚያ ለመቆየት"

የመለቀቅ/የመታደስ ጊዜዬ እስኪደርስ
"መለቀቅ/መታደስ" የሚለው ረቂቅ ስም "ተለቀቀ/ታደሰ" በሚል ግስ ሊገለጽ ይችላል። "እስከምለቀቅ ድረስ" ወይም "አንተ እስከምትለቀኝ/እስክታድሰኝ ድረስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Job 14:15

አጠቃላይ መረጃ:
ኢዮብ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገሩን ይቀጥላል።

እኔ መልስ እሰጣለሁ
"እኔ ምላሽ እሰጣለሁ"

ትፈልገኛለህ/ትናፍቃለህ
"ፍላጎት" የሚለው ስም "ፈለገ" ወይም "ወደደ" በሚል ግስ ሊገለጽ ይችላል። "አንተ ትፈልጋለህ/ትናፍቃለህ" ወይም "አንተ ትወዳለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የእጆችህ ስራ
እዚህ ስፍራ የእግዚአብሔር እጆች የሚወክሉት እርሱ ነገሮችን መስራቱን ነው። ኢዮብ ራሱን የእግዘአብሔር የእጆቹ ስራ አድርጎ ይገልጻል። "አኔን ያበጀኸኝ አንተ ነህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሶስተኛ መደብ የሚሉትን ይመልከቱ)

ቁጥር እና መቆጣጠር/መከታተል
እነዚህ ሁለት ግሶች ሁለቱ በአንድነት አንድን ድርጊት ይገልጻሉ። "በንቃት ትከታተላለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሄንዲየዲስ/ሁለት ቃላት 'እና' በሚል አያያዥ ቃል የሚገኙኙበትና አንድን ጥልቅ ሀሳብ ለመግለጽ የሚያገለግል ዘይቤያዊ አነጋገር)

የእግሬ ኮቴ/እርምጃዬ
እርምጃ/ኮቴ የሚለው የሚወክለው ህይወቱን ወይም ያደረገውን ነው። "ህይወቴ" ወይም "ያደረግኳቸው ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አትቆጥርብኝም... መተላለፌን ይቅር ትላለህ...አንተ ትሸፍንልኛለህ
እነዚህ ሶስት ሀረጎች ተመሳሳይ ሀሳብን ይገልጻሉ፣ በአንድነት የዋሉት እግዚአብሔር ይቅር እንደሚለው ያለውን እርግጠኝነት/ልበሙሉነት ለመግለጽ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ኃጢአቴን አትቆጥርብኝም
የኢዮብን ኃጢአት አለመቁጠር የሚወክለው ስለ እርሱ ኃጢአት አለማሰብን ነው። "ኃጢያቴን አትመለከትም" ወይም "ስለ እኔ ኃጢአት አታስብም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መተላለፌን በከረጢት ውስጥ ታትምበታለህ
መተላለፍን በከረጢት ማተም የሚለው የሚገልጸው ኃጢአትን መሸፈን እና ስለ እርሱ ማሰብን አለመፍቀድ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንድን ነገር በከረጢት ውስጥ እንደደበቀ ሰው መተላለፌን ማሰብ አትፈቅድም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በደሌን ትሸፍናለህ/ይቅር ታላለህ
እንዳይታይ የአንድን ሰው በደል መሸፈን የሚወክለው ስለዚያ ማሰብን አለመፍቀድን ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በደሌን ትሸፍናለህ" ወይም "ኃጢአቴን ትተውልኛለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 14:18

አጠቃላይ መረጃ:
ኢዮብ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገሩን ይቀጥላል።

ተራሮች ይወድቃሉ ከስፍራቸውም ይጠፋሉ
እዚህ ላይ "ከስፍራቸው ይጠፋሉ/መታሰቢያ ያጣሉ" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ ሙሉ ለሙሉ ይደመሰሳሉ ማለት ነው። ይህ ሀረግ "መውደቅ" የሚለውን ቃል በማብራራት ጥፋቱ ሙሉ ለሙሉ መሆኑን ያጎላል። "ታራሮች ሙሉ ለሙሉ ይፈራርሳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

አለቶች ከስፍራቸው ይወገዳሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አለቶች ከስፍራቸው ቁልቁለል ይንከባለላሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ልክ እንደዚህ፣ የሰውን ተስፋ ትደመስሳለህ
ኢዮብ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠቀመው ወዳጆቹ እርሱን ሰለሚያስተናግዱበት መንገድ ምሬቱን ለመግለጽ ነው። "ስጋዬን እስከሚበቃ ድረስ ፈጅታችኋል/ በልታችኋል!" ወይም "ስጋዬን መብላታችሁን አቁሙ!"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በስጋዬ ስቃይ መቼ እርካታ ታገኛላችሁ?
ኢዮብ የጓደኞቹን ጭካኔ የተሞላበት ንግግር የገለጸው የዱር አውሬ ሌላ እንስሳን እንደሚበላ ባለ መልክ ነው። "በሀይል ስሜን ማጥፋታችሁን አቁሙ።" ወይም "በቃላቶቻችሁ እኔን ማጥቃታችሁን አቁሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 19:23

አጠቃላይ መረጃ:
ኢዮብ ከሶስቱ ወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።

አወይ፣ ምነው ቃሎቼ በተጻፉ
ይህ አጋኖ የሚናገረው ኢዮብ ምን እንደሚፈልግ ነው። በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንድ ሰው ቃሎቼን ቢጽፍ በወደድኩ" (ቃለ አጋኖ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

የእኔ ቃሎች/ቃሎቼ
"እኔ የምናገረው"

አወየው፣ ምነው በመጽሐፍ በተጻፉ
ይህ አጋኖ የሚናገረው ኢዮብ ምን እንደሚፈልግ ነው። በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንድ ሰው በመጽሐፍ ቢጽፋቸው በወደድኩ" (ቃለ አጋኖ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

አወይ፣ በብረት ብዕር እና እርሳስ ለዘለዓለም በአለት ላይ በተቀረጹ
ይህ አጋኖ የሚናገረው ኢዮብ ምን እንደሚፈልግ ነው። በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንድ ሰው የብረት ብዕር እና እርሳስ ተጠቅሞ ለዘለዓለም በአለት ላይ ቢቀርጻቸው በወደድኩ" (ቃለ አጋኖ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

የብረት ብዕር
"ጠብረት መሮ።" ይህ ለመጻፊያ ያገለግል ነበር። ሰዎች ቃላቶችን በአለት ላይ እንዲቀርጹ ከብረት የተሰራ ነበር።

እርሳስ
እርሳስ ለስላሳ ብረት ነው። ሰዎች አለት ሲጠርቡ አንዴት እርሳን ይጠቀሙ እንደነበር አናውቅም። ምናልባት ጽሁፉ ለረጅም ጊዜ እንዲቆይ የጽሁፉን ፊደላት በእርሳስ ይሞሉት ይሆናል

Job 19:25

አጠቃላይ መረጃ:
ኢዮብ ከሶስቱ ወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።

እኔን ነጻ የሚያወጣኝ
"እኔን የሚከላከል።" እዚህ ስፍራ "ነጻ አውጪ" የሚለው የሚያመለክተው የኢዮብን ንጹህነት በማረጋገጥ ነጻ የሚያወጣውን፣ ክብሩን የሚመልስለትን፣ እና ፍትህ የሚሰጠው አካል ማለት ማለት ነው።

በመጨረሻ እርሱ በምድር ላይ ይቆማል
ይህ የሚያመለክተው በፍርድ ቤት ለመናገር መቆምን ነው። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1)ነጻ አውጪው በፍርድ ቤት ቆሞ ለመናገር የመጨረሻው ሰው ይሆናል። "እርሱ እኔ ጥፋተኛ መሆን አለመሆኔን ይፈርዳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) ነጻ አውጪው ኢዮብን ለመከላከል በዚህ በመጨረሻው ፍርድ ቤት ይቆማል። "በመጨረሻ እርሱ በፍርድ ቤት ቆሞ ለእኔ ይከላከላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ስጋዬ... ከጠፋ በኋላ
ይህ ሊያመለክት የሚችለው ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የእርሱ አካል በበሽታ መጥፋትን/መጎዳቱን ወይም 2) ከሞተ በኋላ አካሉ መበስበሱን

በስጋዬ እግዚአብሔርን አየዋለሁ
ስጋው የሚወክለው አካሉን ነው፣ ደግሞም "በስጋዬ" የሚለው በህይወት መኖርን ይወክላል። "በስጋዬ ውስጥ እየኖርኩ ሳለ፣ እግዚአብሔርን አየዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የገዛ ዐይኖቼ/የራሴ ዐይኖች - እኔ፣ ራሴ ሌላ ሰው ሳይሆን
"የገዛ ዐይኖቼ/የራሴ" የሚለው ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ የሚያመለክተው ኢዮብን ነው። "የገዛ ዐይኖቼ" እና "ሌላ ማንም ሳይሆን" የሚሉት ሀረጎች የሚያጎሉት በእርግጥ ኢዮብ ራሱ እግዚአብሔርን እንደሚመለከት ነው። እግዚአብሔርን የሚመለከተው እና ስለ እር የሚነግረው ሌላ ማንም አይደለም። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ልቤ በመናፈቅ ዝሏል
ሰዎች ስሜታቸው ባለበት በዚያ ልባቸው እንዳለ ያስባሉ። ስለዚህ የልብ መውደቅ የሚወክለው/የሚገልጸው እርሱ የተለያዩ ስሜቶች እንዳሉት ነው። "ስለዚህ ጉዳይ በጣም ስሜታዊ ነኝ" ወይም "ስለዚህ ሁኔታ ሳስብ ስሜቴ ሁለንተናዬን ይወርሰዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ልቤ በመናፈቅ ዝሏል
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ኢዮብ በተስፋ፣ በምስጋና ተሞልቷል ደግሞም ተድቷል ወይም 2) ኢዮብ አዳኙን በመጠበቅ ደክሟል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 19:28

አጠቃላይ መረጃ:
ኢዮብ ከሶስቱ ወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።

እንዴት እናሳድደዋለን
ይህ ቃለ አጋኖ ነው። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እነርሱ በእርግጥ ኢዮብን ያሳድዱታል ወይም 2) በከፋ ሁኔታ እነርሱ ያሳድዱታል። (ቃለ አጋኖ የሚለውን ይመልከቱ)

የችግሩ ስር በእርሱ ላይ አለ
"ስር" የሚወክለው መነሻን/መገኛን ነው። "እርሱ የችግሮቹ ሁሉ መገኛ/ምክንያት ነው" ወይም "ይህ ሁሉ ችግር ያጋጠመው ከሰራው ስራ/ካደረገው ነገር የተነሳ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንግዲህ ሰይፍን ፍሩ
ሰይፍ ሊወክለው የሚችላቸው ትርጉሞች 1) እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ይፈርዳል "እንግዲህ እግዚአብሔር ይፈርድብናል ብላችሁ ፍሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) እግዚአብሔር እነርሱን ይገድላቸዋል። "እንግዲህ እግዚአብሔር ይገድለናል ብላችሁ ፍሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ምክንያቱም ቁጣ በሰይፍ መቅጣትን ያመጣል
"ቁጣ" እና "ቅጣት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች "ተቆጣ" እና "ተቀጣ" በሚሉ ግሶች ሊገለጹ ይችላሉ። ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የእግዚአብሔር ቁጣ ቅጣት ያስከትላል። "ምክንያቱም እግዚአብሔር በእናንተ ሊቆጣ እና ሊቀጣችሁ ይችላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) የኢዮብ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወዳጆች ቁጣ ቅጣትን ያስከትላል።" ምክንያቱም እናንተ በእኔ ላይ እጅግ ብትቆጡ፣ እግዚአብሔር እናንተን ይቀጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ያመጣል
"ምክንያት ይሆናል" ወይም "ያስከትላል"

ፍርድ አለ
"ፍርድ" የሚለው ረቂቅ ስም "ፈረደ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር በሰዎች ላይ ይፈርዳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 20

1 ናዕማታዊውም ሶፋር ሲመልስ እንዲህ አለ፦ 2 ከውስጤ ጭንቀት የተነሳ አሳቤ መልስ እንድሰጥ አስቸኮለኝ። 3 የሚያሳፍረኝን ተግሣጽ ከአንተ ሰምቻለሁ፥ ነገር ግን ከመረዳቴ የሚያልፍ መንፈስ ይመልስልኛል። 4 እግዚአብሔር ሰውን በምድር ላይ ካኖረበት፥ ከጥንት ጀምሮ እንዴት እንደ ነበር አታውቅም? 5 የኃጢአተኛ መፈንጨት አጭር ፣ የአመጸኛም ደስታ ለቅጽበት መሆኑን አታውቅምን? 6 ቁመቱ እስከ ሰማይ ቢደርስ፥ ራሱም እስከ ደመና ቢሆን፥ 7 እንዲህ ያለ ሰው እንደ ምናምን ፈጽሞይጠፋል፤ አይተውት የነበሩም፦ ወዴት ነው? ይላሉ። 8 እንደ ሕልም ይበርራል፥ እርሱም አይገኝም፤ በርግጥ እንደ ሌሊት ራእይ በርሮ ይጠፋል። 9 ያየውም ዓይን ዳግመኛ አያየውም፤ የነበረበት ስፍራም እንደገና አይመለከተውም። 10 ልጆቹ ድሆችን ይቅርታ ይላሉ፤ እጆቹም ሀብቱን መመለስ ይገባቸዋል። 11 አጥንቶቹ በወጣትነት ጉልበት ተሞልተዋል፤ ነገር ግን ከእርሱ ጋር በአፈር ውስጥ ይተኛል። 12 ክፋት በአፉ ውስጥ ቢጣፍጥ፥ ከምላሱም በታች ቢደብቀው፥ 13 ምንም እንኳ እዚያው ቢያቆየው ባይለቅቀውም፥ በአፉ ውስጥ ቢይዘው፥ 14 ምግቡ በአንጀቱ ውስጥ ወደ መራራነት ይለወጣል፤ በውስጡ እንደ እባብ መርዝ ይሆንበታል። 15 የዋጠውን ሀብት መልሶ ይተፋል፤ እግዚአብሔርም ከሆዱ ያስወጣዋል። 16 የእባብን መርዝ ይመጣል፤ የእፉኝትም ምላስ ይገድለዋል። 17 በማርና በቅቤ ፈሳሾች፥ በወንዞችም ተደስቶ አይኖርም። 18 የደከመበትንም ሳይበላው መልሶ ይሰጣል፤ ባገኝውም ሃብት ደስ አይለውም። 19 ድሆችን አስጨንቆአልና፥ ትቷቸዋልም፤ ያልሠራውንም ቤት በጉልበት ነጥቋል። 20 በራሱ እርካታን ስለማያውቅ፤ የሚደሰትበትን አንድ ነገር ሊያስቀምጥ አይችልም። 21 ሳያጠፋ የሚያስቀረው ነገር ስለማይኖር የሚዘልቅ ብልጽግና አይኖረውም። 22 በሃብት ጠግቦ እያለ ይቸገራል፤ በድህነት ያሉ እጆች ሁሉ ይነሱበታል። 23 ሆዱን ለሞላ ሲዘጋጅ እግዚአብሔር ብርቱ ቊጣውን ይሰድበታል፥ እየበላም ሳለ ያዘንብበታል። 24 ከብረት መሣርያ ይሸሻል፥ የናስ ቀስት ግን ይወጋዋል። 25 በርግጥ ቀስቱም ከኋላ ይወጋዋል፤ የጫፉም ብልጭታ በጉበቱ በኩል ይወጣል፤ ፍርሃትም ይመጣበታል። 26 ለከበረ ዕቃው ፍጹም ጥፋት ተዘጋጅቶለታል፤ ያልተራገበ እሳት ይበላዋል፤ በድንኳኑም የተረፈውን ይጨርሰዋል። 27 ሰማያት ኃጢአቱን ይገልጡበታል፥ ምድርም ምስክር ሆና ትነሣበታለች። 28 የቤቱም ባለጠግነት ይጠፋል፤ በእግዚአብሔር ቊጣ ቀን የቤቱን ዕቃ ጎርፍ ይወስድበታል። 29 ይህም ከእግዚአብሔር ዘንድ የበደለኛ ሰው እድል ፈንታ፥ ከእግዚአብሔርም የተመደበለት ርስቱ ይህ ነው።

Job 20:1

አጠቃላይ መረጃ:
ሶፋር ለኢዮብ እንዲህ ሲልመለሰ።

ናዕማታዊው ሶፋር
ይህንን ወንድ ስም በኢዮብ 2:11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። ይህ ሶፋር የሚናገርበት ሁለተኛ ጊዜ እንደመሆኑ፣ አንዳንድ ቅጂዎች/ትርጉሞች እዚህ ስፍራ "ናዕማታዊው" የሚለውን ይተዉታል።

ሃሳቤ በፍጥነት እንድመልስ ያደርገኛል
የሶፋር ሃሳብ የሚለው አስተሳሰብ አንዳች ነገር ለማድረግ ያለውን ጠንካራ ፍላጎት ይወክላል። "በፍጥነት ልመልስልህ እጅግ እፈልጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በውስጤ ባለው ጭንቀት ምክንያት
"ጭንቀት" የሚለው ረቂቅ ስም "ተጨነቀ" በሚለው ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። ለመጨነቅ ምክንያት የሆነው ነገር በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "ምክንያቱም እኔ ስለአንተ በጣም ተጨንቄያለሁ" ወይም "ምክንያቱም አንተ በተናገርከው ነገር እኔ በጣም ከመጨነቄ የተነሳ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

እኔን የሚያዋርድ ግሳጼ ሰምቻለሁ
"ግሳጼ" የሚለው ረቂቅ ስም "ገሰጸ" በሚል ግስ ሊገለጽ ይችላል። "ስትገስጸኝ እና እኔን በማቃለል ስትናገሩ ሰማኋችሁ" ወይም "በስድብ አቃለላችሁኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

መረዳት/ግንዛብ የሚሰጠኝ መንፈስ መልስ ይሰጠኛል
እዚህ ስፍራ "መንፈስ" የሚለው ምናልባት ሃሳብን ወይም አስተሳሰብን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። "መረዳት የሚሰጠኝ አስተሳሰብ መልስ ይሰጠኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

መረዳት/ግንዛብ የሚሰጠኝ መንፈስ መልስ ይሰጠኛል
እዚህ ስፍራ "መንፈስ" ወይም አስተሳሰብ የሚለው ቃል የተነገረው ለሶፋር መልስ ሊሰጥ እንደሚችል ሰው ተደርጎ ነው። ከመረዳቴ የሚመነጭ ሀሳብ አለኝ፤ እናም አሁን ማወቅ የምፈልገው ምን እንደሆነ አውቃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መረዳት/ግንዛብ የሚሰጠኝ መንፈስ መልስ ይሰጠኛል
የመረዳቴ ይዘት በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "ከመረዳቴ የሚመነጨው አስተሳሰብ ለአንተ እንዴት መልስ እንደምሰጥ ያሳውቀኛል" ወይም "ከመረዳቴ የሚመነጭ አስተሳሰብ አለኝ፣ እናም አሁን ለአንተ እንዴት ምላሽ እንደምሰጥ አውቃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መረዳት/ግንዛብ የሚሰጠኝ መንፈስ መልስ ይሰጠኛል
"መንፈስ" እና "መረዳት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች "አሰበ" እና "ተረዳ" በሚሉ ግሶች ሊገለጹ ይችላሉ። "ነገሮችን ስለምረዳ፣ ሃሳብ አለኝ እናም አሁን እንዴት ለአንተ እንደምመልስ አውቃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Job 20:4

አጠቃላይ መረጃ:
ሶፋር ለኢዮብ መልስ መስጠቱን ቀጠለ።

ለቅጽበት...ይህንን እውነታ ከጥንት ጀምሮ ታውቅ ነበርን?
ሶፋር ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው እርሱ አሁን የሚናገረውን ነገር ኢዮብ በጥልቀት እንዲያስብበት ለማድረግ ነው። ይህ በገለጻ ሊተረጎም ይችላል። "ለአፍታ...አንተ በእርግጥ ከጥንት ጀምሮ ያለውን ታውቃለህ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የክፉ ሰው ድል ለአጭር ጊዜ ነው
"ድል" የሚለው ረቂቅ ስም "ድል አደረገ" ወይም "ግብዝ አደረገ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "ክፉ ሰው የሚያሸንፈው ለአጭር ጊዜ ብቻ ነው" ወይም "ክፉ ሰው ግብዝ የሚያደርገው ለአጭር ጊዜ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

አምላክ የለሽ የሆነ ሰው ደስታ የሚቆየው ለአጭር ጊዜ ብቻ ነው
"ደስታ" የሚለው ረቂቅ ስም "ሀሴት" ወይም "ደስታ" በሚለው ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። "አፍታ/ቅጽበት" የሚለው ቃል ጊዜው በጣም አጭር መሆኑን ለማጉላት የዋለ ግነት ነው። "አምላክ የለሽ ሰው ደስታው ለቅጽበት ነው" ወይም "አምላክ የለሽ ሰው ደስ የሚሰኘው ለአጭር ጊዜ ብቻ ነው" በሚለው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ኩሸት እንደዚሁም አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 20:6

አጠቃላይ መረጃ:
ሶፋር ለኢዮብ መልስ መስጠቱን ቀጠለ።

እስከ ሰማይ ከፍ ቢል እንኳን
"የክፉ ሰው ከፍታ እስከ ሰማይ ቢደርስ እንኳን" "ከፍታ" የሚለው ረቂቅ ስም "ትልቅ/ረጅም" በሚል ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። "ምንም እንኳን እርሱ እስከ ሰማይ ቢረዝም/ቢተልቅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እስከ ሰማይ ከፍ ቢል እንኳን
የክፉ ሰው ከፍታ የሚለው የሚወክለው ክብሩን ወይም ኩራቱን ነው። እንደዚሁም እዚህ ስፍራ እስከ ሰማይ መድረስ" የሚወክለው በጣም ትልቅ መሆንን ነው። "ምንም እንኳን ክብሩ ታላቅ ቢሆንም" ወይም "ምንም እንኳን ኩራቱ ታላቅ ቢሆንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ራሱ እስከ ደመና ይደርሳል
"ደግሞም ምንም እንኳን ራሱ እስከ ደመና ከፍ ቢልም" ይህም የሚወክለው ክብሩን ወይም ትልቅ በመሆኑ መኩራቱን ነው። ይህ ማለት ከቀደመው ሀረግ ጋር ተመሳሳይ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

እንደ ራሱ እዳሪ ለዘለዓለም ይጠፋል
እዳሪ ከመሬት ጋር ተደባልቆ ይጠፋል። ክፉ ሰው ከእዳሪ ጋር መነጻጸሩ እርባና ቢስ/ጥቅም የለሽ መሆኑን የሚጠቁም ነው። "በአፈር ውስጥ ሙሉ ለሙሉ እንደሚጠፋ እንደ ራሱ እዳሪ በዘላቂነት ይጠፋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ራሱ እዳሪ ለዘለዓለም ይጠፋል
ሰዎች እዳሪ በሚለው ቃል ደስ የማይሰኙ/የሚያሳፍር ከሆነ ሙሉ ለሙሉ ከሚጠፋ ሌላ ነገር ጋር ማመሳሰል ይቻላል። "ንፋስ እንደ በተነው አቧራ ለዘለዓለም ይጠፋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 20:8

አጠቃላይ መረጃ:
ሶፋር ለኢዮብ መልስ መስጠቱን ቀጠለ።

እርሱ
"ክፉ ሰው"

እንደ ህልም ይጠፋል... እንደ ምሽት ህልም ተሰዶ ይጠፋል
እዚህ ስፍራ "መጥፋት" እና "መባረር/መሰደድ" የሚሉት ቃላት የሚወክሉት መጥፋትን ነው። ህልሞች እና ራዕዮች በረስዋቸው ጊዜ እንደሚጠፉ ሁሉ፣ እነዚህም ክፉዎች እንደሚረሱ ያመለክታል። "እንደ ህልም ይረሳሉ... በምሽት እንደ ታየ ህልም ይረሳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

አይገኝም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ማንም ሊያገኘው አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የተመለከቱት ዐይኖች
ዐይን ሰውየውን ይወክላል። "እርሱን የተመለከተ ማንም ሰው" ወይም "እርሱን የተመለከቱ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ስፍራው
"ስፍራው/የእርሱ ስፍራ" የሚለው ሀረግ የሚወክለው በእርሱ ስፍራ የሚኖሩትን ነው። "በእርሱ ስፍራ የሚኖሩ ሰዎች" ወይም "ቤተሰቦቹ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 20:10

አጠቃላይ መረጃ:
ሶፋር ለኢዮብ መልስ መስጠቱን ቀጠለ።

ልጆቹ
"የክፉ ሰው ልጆች"

እጆቹ ብልጽግናውን መልሰው ያመጡለታል
እዚህ ስፍራ "እጆች" የሚለው የሚወክለው የክፉ ሰው ልጆችን ነው። እርሱ በሚሞትበት ጊዜ፣ ልጆቹ እርሱ ከሌሎች ሰዎች የወሰደውን ለመመለስ ይገደዳሉ። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አጥንቶቹ በጥንካሬ የተሞሉ ናቸው
"አጥንቶቹ" የሚለው የሚወክለው አካሉን/ሰውነቱን ነው። "ጠቃሚ በሆነ ጥንካሬ ሙሉ መሆን" የሚለው የሚወክለው እንደ ወጣት ሰው ጠንካራ መሆንን ነው። "ሰውነቱ እንደ ወጣት ሰውነት ጠንካራ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ነገር ግን ይህ ከእርሱ ጋር አፈር ውስጥ ይገባል
"ይህ" የሚለው የሚያመለክተው የእርሱን ጠቃሚ ጥንካሬ ነው። "አፈር ውስጥ... ይጋደማል" የሚለው ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሚወክለው ሞትን ነው። የሞት ጥንካሬ የሚለው መጥፋት ለሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "ነገር ግን ጠቃሚ ጥንካሬው ከእርሱ ጋር አብሮ ይሞታል" ወይም "ነገር ግን የእርሱ ጠቃሚ ጥንካሬ/የሚመካበት እርሱ ሲሞት አብሮት ያከትማል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 20:12

አጠቃላይ መረጃ:
ሶፋር ለኢዮብ መልስ መስጠቱን ቀጠለ።

ምንም እንኳን ክፋት በአፉ ላይ ጣፋጭ ቢሆንለትም
እዚህ ስፍራ "ክፋት ጣፋጭ ቢሆንለትም" የሚለው የሚወክለው ክፉ ነገር በማድረግ ደስ የሚሰኝ ሰውን ነው። " ምንም እንኳን ክፉ ነገሮችን ማድረግ ጣፋጭ ምግብን እንደ መቅመስ ደስ የሚያሰኘው ቢሆንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ምንም እንኳን ቢደብቅም ... እንዲሄድ አይፈቅድም
አንድ ሰው ጣፋጭ ምግብን በመቅመስ ደስ መሰኘቱን መቀጠል እንደሚፈልግ ክፉ ሰው ክፉ በማድረግ ደስታ ለማግኘት መፈለጉን ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በአንጀቱ ውስጥ ያለ ምግብ መራራ ይሆንበታል
ምግብ በአንጀት ውስጥ ወደ መራራነት ሲቀየር፣ ስቃይን ያስከትላል ደግሞም መራራ ጣዕም ያመጣል። ይህ ክፉ በማድረጉ ምክንያት መጥፎ

ለሚገጥመው የዋለ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "እነዚያ ክፉ ነገሮች በሆድ ውስጥ ወደ መራራነት እንደ ተለወጠ ምግብ ይሆናሉ" ወይም "የእነዚያ ክፉ ነገሮች ውጤታቸው በሆድ ውስጥ ጎምዛዛ እንደሆነ ምግብ ስቃይ የሚፈጥሩ ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በውስጡ እንደ እባብ መርዝ ይሆናል
ምግብ በሆድ ውስጥ ወደ መራራነት ሲቀየር፣ ስቃይን ይፈጥራል ደግሞም መራራ ጣዕምን ያመጣል። ይህ ክፉ ነገሮችን በማድረግ መከራ ለሚቀበል ሰው የዋለ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "እነዚያን ክፉ ነገሮች ማድረግ ውጤቱ በውስጡ የእባብ መርዝ የገባ ያህል መሰቃየት ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መርዘኛ
"መርዛማ እባቦች

Job 20:15

አጠቃላይ መረጃ:
ሶፋር ለኢዮብ መልስ መስጠቱን ቀጠለ።

ባለጸግነትን ይውጣል... መልሶ ከሆዱ ያስወግዳቸዋል
ሶፋር ሀብት ማግኘትን እና ማጣትን የሚገልጸው አንድ ሰው በልቶ መልሶ እንደሚያስመስለው ምግብ አድርጎ ነው። "ክፉ ሰው ባለጸጋ ይሆናል፣ ነገር ግን የበላውን እንደሚያስመልስ ሰው ሀብቱን ያጣዋል። እግዚአብሔር ሃብቱን በሙሉ እንዲያጣ ያደርገዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሃብትን ይውጣል
"ሃብትን ይውጣል" ለሚለው ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሀብት ያሰበስባል፣ ደግሞም በስስት ያከማቻል። "ክፉ ሰው ብዙ ሃብት ያገኛል፣ ደግሞም ሁሉንም ለራሱ ያደርገዋል" ወይም 2) ከክፋት መንገዶች ሀብት ማከማቸት። "ክፉ ሰው ብዙ ሀብት ይሰርቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ከሆዱ ያስተፋዋል
"ከሆዱ ያስተፋዋል" የሚለው ሰውየው ያገኘውን በማስመለስ ያወጣዋል ለሚለው ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ይህ ክፉ ሰው ሃብቱን ለሚያጣበት ምክንያት ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ያስወግዳል
ያስወጣል

እዚህ ስፍራ "የእባብ መርዝ ይጠባል"
የሚለው የሚወክለው ክፉ ነገር ማድረግን ነው። ሁለቱም በጣም አደገኛ ናቸው። "ክፉ ነገሮችን ማድረግ የእባብ መርዝን እንደ መጥባት ነው" ወይም "ክፉ ነገሮችን ያደርጋል ደግሞም የእባብ መርዝን እንደሚጠባ ሰው ህይወቱን አደጋ ላይ ይጥላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መርዛም እባብ
መርዘኛ እባብ

የእፍኝት ምላስ ይገድለዋል
እፍኝት መርዛም እባብ ነው። ምላሱ የሚወክለው መርዛም ንክሻውን ነው። "የእፍኝት መርዛማ ንክሻ እርሱን ይገድለዋል" ወይም "እፍኝት ይነክሰዋል ከዚያም ይሞታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የእፍኝት ምላስ ይገድለዋል
እፍኝት የሚወክለው የሰውየውን ክፉነት ነው። "ክፋቱ እንደ እፍኝት ንክሻ ይገድለዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 20:17

አጠቃላይ መረጃ:
ሶፋር ለኢዮብ መልስ መስጠቱን ቀጠለ።

ጅረቶች፣ የቅቤ እና ማር ጎርፍ
"ጅረቶች" እና "ጎርፍ" ብዛትን የሚወክሉ ዘይቤያዊ አነጋገሮች ናቸው። "ማር" እና "ቅቤ" እግዚአብሔር ለሰዎች የሚሰጠውን መልካም ነገሮች የሚወክሉ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ናቸው። "እግዚአብሔር ለህዝቡ የሚሰጠው መልካም ነገሮች ብዛት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

የስራው ፍሬ
በተለመደው አነጋገር "የስራው ፍሬ" በቀጥታ የሚያመለክተው የስራውን ውጤት ነው። በዚህ ሁኔታ ግን ክፉ ሰው የሰረቃቸውን ነገሮች ያመለክታል። "ለማግኘት የሰራቸው ነገሮች" ወይም "የሰረቃቸው ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ሊመገበው አይችልም
እዚህ ስፍራ የስራውን ፍሬ "ሊመገብ" የሚለው የሚወክለው በሰረቀው ነገር ደስ መሰኘቱን ይወክላል። "በእነርሱ ደስ ሊሰኝ አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 20:20

ሳይበላ የሚያስተርፈው ምንም ነገር የለም
ይህ ከአሉታዎቹ አንዱ ብቻ ተቀይሮ ሊጻፍ ይችላል። "ሁሉንም ነገር ፈጅቷል፣ ያስቀረው እንድም የለም" ወይም "የቀረ ምንም ነገር የለም ምክንያቱም እርሱ ሁሉንም በልቷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ አሉታ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ያልበላው የቀረ ምንም ነገር የለም
እዚህ ስፍራ "መብላት" የሚለው የሚወክለው ነገሮችን ለራሱ መውሰድን ነው። "ለራሱ ያልወሰደው፣ ምንም የቀረ ነገር የለም" ወይም "እርሱ ሁሉንም ለራሱ ወስዷል፣ እናም ምንም ነገር አልቀረም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ችግር ላይ ይወድቃል
"በድንገት ችግር ያጋጥመዋል"

በችግር ላይ ያለ እጅ ሁሉ በእርሱ ላይ ይነሳሉ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚወክለው ሀይልን ነው፣ ደግሞም "እጅ... በእርሱ ላይ ይነሳል" የሚለው የሚወክለው እርሱን የሚያጠቁ ሰዎችን ነው። "ድህነት" የሚለው ረቂቅ ስም "ድህ" በሚለው ቅጽል ይገለጻል። "በድህነት ውስጥ ያለ ሁሉ እርሱን ያጠቃዋል" ወይም "ደሀ የሆነ ሁሉ እርሱን ያጠቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 20:23

አጠቃላይ መረጃ:
ሶፋር ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጠለ።

ሆዱን ለመሙላት
እዚህ ስፍራ "ሆዱን መሙላት" የሚለው ብዙ መብላት የሚል ትረጉም የሚሰጥ ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር በእርሱ ላይ የቁጣውን መአት ያወርድበታል
"የቁጣው መአት" የሚለው የሚወክለው የእግዚአብሔርን ቁጣ እና ቅጣት ነው። ቁጣውን ያወርድበታል የሚለው በከፍተኛ ደረጃ ይቀጣዋል ማለት ነው። "እግዚአብሔር ይቆጣል ደግሞም ቁጣውን ያወርድበታል" ወይም "እግዚአብሔር ይቆጣል ደግሞም እጅግ ይቀጣዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ይህን ያዘንብበታል
"እግዚአብሔር ይህን በእርሱ ላይ እንዲዘንብ ያደርጋል።" እዚህ ስፍራ "ይህን በእርሱ ላይ ያዘንባል" የሚለው የሚገልጸው በሰውየው ላይ ብዙ ጥፋት እንደሚደርስ ነው። "እግዚአብሔር እጅግ ይቀጣዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከብረት መሳሪያ ያመልጣል
የብረት መሳሪያ የሚለው የሚወክለው መሳሪያውን የያዘውን ሰው ነው። "የብረት መሳሪያ ከያዘ ሰው ያመልጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የነህስ ደጋን ይወጋዋል
ደጋኑ የሚወክለው በእርሱ ቀስት የሚወረውረውን ሰው ነው። "የነህስ ደጋን የያዘ ሰው እርሱን ይወጋዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ጉበት
ይህ ትልቅ እና ጠቃሚ የሆነ የሰውነት ክፍል ነው። አንድ ሰው በቀስት ይህን የሰውነት ክፍል ቢወጋ፣ የተወጋው ሰው ይሞታል።

ፍርሃት ይወርድበታል
በድንገት በጣም ይፈራል። "በፍርሃት ተዋጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 20:26

ሀብቱ ለድቅድቅ ጨለማ ተዳርጓል
እዚህ ስፍራ "ድቅድቅ ጨለማ" የሚለው ለጥፋት ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "ሀብቱ ለጥፋት ተዳርጓል " ወይም "ሀብቱ ይጠፋል/ይደመሰሳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ያልተራበ እሳት ይበላዋል
እዚህ ስፍራ "መብላት/መፍጀት" የሚለው ዘይቤ ትርጉሙ መጥፋት/ መደምሰስ ማለት ነው። "የልተራበ እሳት ያጠፋዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ያልተራበ እሳት ይበላዋል
"ያልተራበ" የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው ማንም ሰው እሳቱን እንደማይጀምር ነው። ይልቁንም፣ እግዚአብሔር እሳቱን ይፈጥራል። "በሰው ያልተጀመረ እሳት እርሱን ይበላዋል" ወይም "እግዚአብሔር እርሱን የሚበላ አሳት ያመጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ይበላዋል/ይፈጀዋል
እዚህ ስፍራ "መብላት/መፍጀት" የሚለው ዘይቤያዊ ትርጉም መጥፋት/ መደምሰስ ነው። "እሳቱ ይደመስሰዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሰማያቱ... ምድሪቱ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) በሰማያት እና በምድር የሚኖሩት ወይም 2) ሶፋር ሰማያትን እና ምድርን የሚገልጻቸው በፍርድ ቤት ቀርበው በክፉዎች ላይ ምስክር እንደሚሆኑ ሰዎች አድርጎ ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 20:28

አጠቃላይ መረጃ፡
ይህ ሶፋር ከኢዮብ ጋር የሚያደርገውን ንግግር ያጠቃልላል።

ጠፋ
ተደመሰሰ

ንብረቶቹ ተጠራርገው ይሄዳሉ
እዚህ ስፍራ "ተጠራርገው ይሄዳሉ" የሚለው የሚወክለው ከእርሱ ይወሰዳሉ የሚለውን ነው። "ንብረቶቹ፣ በጎርፍ ላይ እየተንሳፈፉ እንደሚወሰዱ ነገሮች ከእርሱ ይወሰዳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ንብረቶቹ
"ያለው ሃብት"

የእግዚአብሔር የቁጣ ቀን
እዚህ ስፍራ "ቁጣ" የሚለው የሚወክለው ቅጣትን ነው። "ቁጣ" የሚለው ረቂቅ ስም "ቀጣ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር ሰዎችን በሚቀጣበት ቀን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ከእግዚአብሔር ዘንድ የክፉ ሰው እድል ፈንታው/ድርሻው ነው
እዚህ ስፍራ "ከእግዚአብሔር ዘንድ እድል ፈንታው/ድርሻው" የሚለው የሚወክለው እግዚአብሔር የወሰነው በሰውየው ላይ መድረሱ አይቀርም የሚል ነው። ይህ ተገለጸው እግዚአብሔር ለሰውየው እንደሚሰጠው ነገር ተደርጎ ነው። "እግዚአብሔር በክፉ ሰው ላይ እንዲደርስ የወሰነው ነገር ይህ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ለእርሱ የተጠበቀለት ቅርስ
ይህ እግዚአብሔር ለአንድ ሰው እንዲሆንለት የወሰነውን ይወክላል/ይገልጻል። ይህ የተነገረው እግዚአብሔር እንደ ውርስ አድርጎ የሚሰጠው ነገር ተደርጎ ነው። "እግዚአብሔር ለእርሱ ሊሰጠው ያቀደው" ወይም "እግዚአብሔር ለእርሱ ይሁን ብሎ ያቀደው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 21

1 ቀጥሎም ኢዮብ ሲመልስ እንዲህ አለ፦ **2** ንግግሬን በጥንቃቄ ስሙ፤ የምታጽናኑኝም እንደዚህ ይሁን። **3** እንድናገር ፍቀዱልኝ፤ ከተናገርሁም በኋላ ተሳለቁ። **4** ቅሬታዬን የማሰማው ሰው ላይ ነውን? ትዕግስት ባጣስ፤ አይገባኝምን? **5** እስቲ ተመልከቱኝና ተደነቁ፤ አፋችሁንም በእጃችሁ ያዙ። **6** እኔ ስቃዬን ባሰብሁ ቍጥር እጨነቃለሁ፥ በፍርሃትምሥጋዬ ይንቀጠቀጣል። **7** ለምን ኃጢአተኞች በሕይወት እስከ እርጅና ይኖራሉ? ለምን በሃይልስ ይበረታሉ? **8** ዘራቸው ከእነርሱ ጋር ተደላድለዋል፥ ልጆቻቸውም በአይናቸው ፊት ጸንተው ይኖራሉ። **9** ቤቶቻቸው ያለስጋት ናቸው፥ የእግዚአብሔርም በትር በላያቸው የለም። **10** ኮርማቸው ይወልዳል፥ ዘሩም በከንቱ አይወድቅም፤ ላማቸውም አትጨነግፍም በጊዜዋ ትወልዳለች፥ ። **11** ሕፃናቶቻቸውን እንደ መንጋ ያሰማራሉ፥ ልጆቻቸውም ይቦርቃሉ። **12** በከበሮና በክራር ይዘምራሉ፥ በእምቢልታም ሙዚቃ ይደሰታሉ። **13** ዕድሜያቸውንም በብልጥግና ይፈጽማሉ፤ በጸጥታም ወደ ሲኦል ይወርዳሉ። **14** እግዚአብሔርንም፦" ከእኛ ራቅ፤ የመንገድህን እውቀት አንፈልግም' ይሉታል። **15** እናመልከው ዘንድ ሁሉን የሚችል አምላክ ማን ነው? ወደ እርሱ በመጸለይስ ምን ጥቅም ይገኛል? ይላሉ። **16** እነሆ፥ ሀብታቸው በእጃቸው ውስጥ አይደለምን? ከኃጥአን ምክር ጋር ምንም አይነት ህብረት የለኝም። የኃጥአን መብራት የጠፋው፥ **17** መቅሠፍትም በላያቸው የመጣባቸው ስንት ጊዜ ነው ፥ እግዚአብሔርም በቍጣው መከራ የከፈለቸው መቼ ነው፥ **18** በነፋስ ፊት እንደ ገለባ፥ በዐውሎ ነፋስም እንደ ተወሰደ ትቢያ የሆኑ ስንት ጊዜ ነው? **19** እናንተ፦ 'እግዚአብሔር የበደለኛውን ቅጣት ለልጆቹ ይጠብቃል' ብላችኋል። ጥፋቱን እንዲያው ቅጣቱን ራሱ ይክፈል። **20** የገዛ ዓይኖቹ ጥፋቱን ይዩ፥ ሁሉን የሚችል አምላክን ቍጣ ራሱ ይጠጣ። **21** ወራቶቹስ ካለቁ በኋላ፥ ከራሱ ሌላ ስለቤተሰቦቹ ምን ገዶት? **22** በከፍታ ያሉትን ለሚፈርድ ለእግዚአብሔር ማን እውቀትን ሊያስተምረው ይችላል? **23** አንድ ሰው በፍጹም ሰላምና ጤና ሲቀመጥ በሙሉ ብርታቱ ሳለ ይሞታል። **24** በሰውነቱ ወተት ሞልቶአል፥ የአጥንቶቹም መቅን እርጥብና በጤንነት ናቸው። **25** ሌላው ሰው ደግሞ መልካምን ነገር ፈጽሞ ሳይቀምስ፤ በተመረረች ነፍስ ይሞታል። **26** በአፈር ውስጥ በአንድ ላይ ይጋደማሉ፥ ሁለቱንም ትል ይጨርሳቸዋል። **27** አሳባችሁን፥ያሴራችሁብኝንም ክፉ ምክር አውቄዋለሁ። **28** እናንተ፦ 'የልኡሉ ቤት የት አለ? ኃጢአተኛውም ሰው ይኖርበት የነበረ ድንኳን የት ነው?" ብላችኋል። **29** መንገድ ተጓዦችን አልጠየቃችሁምን? ሊናገሩ የሚችሉትን ማስረጃ አታውቁምን? **30** ኃጢአተኛው ከመቅሠፍት ቀን እንደ ተጠበቀ፥ ከቍጣው ቀን ዘወር እንደተደረገ። **31** የሃጥያተኛውን መንገድ ፊት ለፊት1 የሚቃወም ማን ነው? በሠራው ስራ የሚቀጣው ማን ነው? **32** እርሱን ግን ወደ መቃብር ይሸከሙታል፥ ሰዎቹም መቃብሩን ይጠብቃሉ። **33** የተቀበረበት አፈር እንኳ ይጣፍጥለታል፤ ሰዎች ሁሉ ይከተሉታል፥ እጅግ ብዙ ሕዝብም ከፊቱ ይሄዳል። **34** መልሳችሁ ከውሸት በቀር ምንም ስለሌለበት፤ በከንቱ ነገር እንዴት ልታጽናኑኝ ትችላላችሁ?

Job 21:1

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ ለሶፋር ክስ ምላሽ መስጠት ይጀምራል።

ታገሰኝ
"ፍቀዱልኝ" ወይም "ትዕግስት ይኑራችሁ"

መሳለቅ
"በእኔ ላይ መሳለቃችሁን መቀጠል ትችላላችሁ።" ኢዮብ ምጸት የተጠቀመው ጓደኞቹ የሚናገረውን ቸል በማለታቸው እና በእርሱ ላይ መሳለቅ በመቀጠላቸው ነው። (ምጸት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 21:4

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ ከወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ይቀጥላል።

ቅሬታዬ በሰው ላይ ነውን? ትዕግስት ማጣት አይገባኝምን?
ኢዮብ ጥያቄዎችን የሚጠቀመው ቅር መሰኘቱን ለእግዚአብሔር መናገሩ ተገቢ መሆኑን ለማጉላት ነው። "ቅሬታዬን የማቀርበው ለሰው አይደለም። ትዕግስት ለማጣት መብቱ አለኝ/ትዕግስት ባጣም ይገባኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

እጃችሁን በአፋችሁ ላይ አድርጉ
"አፋችሁን በእጃችሁ ሸፍኑ።" ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ ለመገረም ምላሽ ነው። "አፋችሁን በእጃችሁ ሸፍኑ" እንደሚለው ወይም 2) ይህ አንድ ሰው እንደማይናገር ምልክት ነው። "አንዳች ነገር አትናገር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

አካሌን መንቀጥቀጥ ያዘው
"ፍርሃት ሰውነቴን አራደው/አንቀጠቀጠው" ወይም "በፍርሃት ተንቀጠቀጥኩ"

Job 21:7

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ ከወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ይቀጥላል።

ክፉ ሰዎች ለምን ህልውናቸው ይቀጥላል፣ ለምን እስከ እርጅናቸው ይኖራሉ፣ ለምንስ ሀይላቸው እየጨመረ ይሄዳል?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ወዳጆቹ ክፉ ሰዎች ሁሌም ስቃይ ይደርስባቸዋል ብለው ማሰባቸው ስህተት መሆኑን ሊያሳያቸው ነው። "በእርግጥ ክፉ ሰዎች መኖራቸውን ይቀጥላሉ፣ ያረጃሉ፣ ይበልጥ ባለጸጋም እየሆኑ ይሄዳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

በአይናቸው እየተመለከቱ ከእነርሱ ጋር ትውልዳቸው ይታነጻል... ትውልዳቸው በዐይናቸው ፊት ጸንቶ ይኖል
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ ይህ እውነት መሆኑንም ያጎላሉ ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እየተመለከቱ... በዐይናቸው ፊት
እነዚህ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው ምክንያቱም "ዐይኖች" እይታን ያመለክታሉ። ክፉ ሰዎች ትውልዳቸው እያየለ እና እየበለጸገ ሲሄድ ያያሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

ቤቶቻቸው
እዚህ ስፍራ "ቤቶች" በእነርሱ ውስጥ የሚኖሩ የቤተሰብ አባላትን ያመለክታሉ። "ቤተሰቦቻቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር በትር
ይህ የእግዚአብሔርን ቅጣት ያመለክታል። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Job 21:10

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ ከወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ይቀጥላል።

ላማቸው አትጨነግፍም
"ላማቸው አትጨነግፍም" ወይም "ጥጃዋ ጤናማ እና ጠንካራ ሆኖ ይወለዳል"

ህጻናቶቻቸው እንደ መንጋ ናቸው
ኢዮብ እነዚህን ህጻናት ከጥጆች ጋር የሚያነጻጽረው ህጻናቶቻቸው እንደሚቦርቁ፣ እንደሚጫወቱ እና ደስተኞች እንደሆኑ ለማጉላት ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከበሮ መሰል የሙዚቃ መሳሪያ/ታምብሪን
ላዩ ከበሮ የሚመስል በብረት ቁራጭ የሚመታ እና በዙሪያው ያሉ ቁርጥራጭ ብረቶች ሲርገፈገፉ ድምጽ የሚሰጥ የሙዚቃ መሳሪያ። (ማይተወቀውን መተረጎም የሚለውን ይመልከቱ)

Job 21:13

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ ከወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ይቀጥላል።

ቀናቸው
"የህይወት ዘመናቸው"

በሰላም ወደ መቃብር/ሲኦል ይወርዳሉ
ይህ ትሁት በሆነ መንገድ ሞታቸውን መግለጽ ነው። "በሰላም ይሞታሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ መንገዶች/መንገድህን
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ሰዎች ምን ማድረግ እንዳለበቸው እንደሚፈልግ ነው

እናመልከው ዘንድ፣ ሁሉን ቻይ የሆነው ምንድን ነው? ወደ እርሱ ብንጸልይ ምን ጥቅም እናገኛለን?
ክፉ ሰዎች እነዚህ ጥያቄዎች የሚጠይቁት በእግዚአብሔር ላይ ለመዘበት ነው። "ይህ ሁሉን ቻይ አምላክ የእኛ አምልኮ ይገባዋል ብለን አናምንም። እርሱ ለእኛ ምንም ሊያደርግ አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

Job 21:16

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ ከወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ይቀጥላል።

እነሆ፣ ብልጽግናቸው በገዛ እጃቸው ላይ አይደለምን?
እዚህ ስፍራ "እጆች" የሚለው የሚያመለክተው ሀይላቸውን ወይም አቅማቸውን ነው። ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው ወዳጆቹን ለመገዳደር ነው። "እነሆ፣ እነዚህ ክፉ ሰዎች ራሳቸውን ባለጸጋ እንዳደረጉ ይናገራሉ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

መቅሰፍት በላያቸው የሚመጣው... እስከ መቼ ነው?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ ክፉዎችን አይቀጣም ብሎ የሚያስበውን ለማጉላት ነው። "ብዙ ጊዜ መቅሰፍት... አያጋጥማቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

የክፉ ሰዎች መብራት ይጠፋል
ኢዮብ መብራት ማትፋትን ከሰው ሞት ጋር ያነጻጽራል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር በድንገት ይገድላቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

የክፉ ሰዎች መብራት
ኢዮብ የክፉ ሰዎችን ህይወት እየነደደ ከሚገኝ መብራት ጋር ያነጻጽራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በቁጣው... ይህ ለምን ያህል ጊዜ ይሆናል?
ኢዮብ ይህን ሁለተኛ ጥያቄ የሚጠይቀው እግዚአብሔር ክፉዎችን ብዙ ጊዜ አይቀጣም ብሎ ስለሚያስብ ይህንን ለማጉላት ነው። "በቁጣው... ይህ ብዙ ጊዜ አይሆንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ማዕበል የሚወስዳቸው ...ይህ ለምን ያህል ጊዜ ነው?
ኢዮብ ይህን ሦስተኛ ጥያቄ የሚጠይቀው እግዚአብሔር ክፉዎችን ብዙ ጊዜ አይቀጣም ብሎ ስለሚያስብ ይህንን ለማጉላት ነው። "ማዕበል የሚወስዳቸው...ይህ ብዙ ጊዜ አይሆንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

በነፋስ ፊት እንደሚጠረግ ገለባ ይሆናሉ ወይም ዐውሎ ነፋስ ጠርጎ እንደሚወስደው እብቅ ይሆናሉ
የክፉ ሰው ሞት የተነገረው ከገለባ ይልቅ እርባና ቢስ እንደሆኑ እና በቀላሉ ተጠርጎ እንደሚወሰድ እብቅ ተደርጎ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ነፋስ ገለባን ጠርጎ እንደሚወስድ እግዚአብሔር ይወስዳቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 21:22

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ ከወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ይቀጥላል።

እርሱ ከፍ ባሉት ላይም ፈረጅ ስለሆነ እግዚአብሔርን የሚያስተምረው አለን?
ኢዮብ ይህንን የሚጠይቀው እግዚአብሔር ሁሉን እንደሚያውቅ ለማጉላት ነው። "እርሱ በሰማያት ባሉት ላይ እንኳን የሚፈርድ ስለሆነ፣ በእርግጥ ማንም እግዚአብሔርን ማስተማር አይችልም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ከፍ ያሉት
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "በሰማያት ያሉት" ወይም 2) "ሀያላን ሰዎች"

አንዱ በሙሉ ሀይሉ ሳለ ይሞታል
ኢዮብ በጤና እና በሰላም ኖሮ የሞተውን ይህንን ሰው በሀዘን እና በስቃይ ከሞተው በበኢዮብ 21:25 ከተጠቀሰው ሰው ጋረ ያነጻጽራል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰውነቱ ወተት ጠግቧል ... የአጥነቱ መቅኔ እርጥብ ነው
እነዚህ ሁለቱም ሀረጎች ሰውየው በጣም ጤነኛ ነው የሚል ትርጉም አላቸው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰውነቱ ወተት ጠግቧል
"ወተት" የሚለው ቃል "ስብ" ለማለት ይሆናል። ተሸፍኗል/የተሞላ ማለት በሚገባ ተመግቧል ማለት ነው። "ሰውነቱ በስብ የተሞላ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የአጥንቶቹ መቅኔ እርጥብ ነው
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሰውነቱ ብርቱ እና ጤናማ ነው ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 21:25

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ ከወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ይቀጥላል።

ሌላው ሰው ይሞታል
ኢዮብ ይህንን ሰው በኢዮብ 21:23 ላይ ከተጠቀሰው በሰላም ከሞተው ሰው ጋር ያነጻጽራል

በነፍስ መራራነት
እዚህ ስፍራ ሀዘን የተገለጸው መራራ ጣዕም እንዳለው ነገር ተደርጎ ነው፣ "ነፍስ" ደግሞ መላ የሰውን ማንነት ታመለክታለች። "በቁጣ እና በንዴት" ወይም "አሳዛኝ ህይወት ከመኖር በኋላ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

አንዳች መልካም ነገር ሳያገኝ/ሳያይ
ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊገለጽ ይችላል። "መጥፎ ነገሮችን ብቻ አይቶ" እንደሚለው።

እነርሱም እንደዚው በአፍር ውስጥ ተጋደሙ
ይህ እነርሱም ሞቱ የሚለው በትህትና መግለጫ መንገድ ነው። "እነዚህ ሁለቱም ሞተው ሰዎች ይቀብሯቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

ሁለቱንም ትል ይሸፍናቸዋል
ትሎች የተያያዙት ከሞተ ሰውነት መበስበስ ጋር ነው። "በአፍር ውስጥ የሚገኙ ትሎች የሞቱ አካሎቻቸውን ይመገባሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 21:27

አያያዥ ሃሳብ፡
x

Job 21:29

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ ከወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ይቀጥላል።

መንገደኞችን አልጠየቃችሁምን? በቁጣው ቀን...እነርሱ የመሚናገሩትን አታውቁምን?
ኢዮብ እነዚህን ጥያቄዎች የሚያነሳው ወዳጆቹ ከመንገደኞች መማር ባለመቻላቸው ሊወቅሳቸው ነው። "ወደ ሩቅ አገር የተጓዙትን ልታደምጧቸው ይገባል። በቁጣው ቀን ... የሆነውን ጭምር ይነግሯችሁኋል።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉ ሰው ከቁጣ ቀን ይጠበቃል... በቁጣ ቀን ከጥፋት ይርቃል
እነዚህ ሀረጎች ተመሳሳይ ትረጉም አላቸው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር በአንድ ስፍራ ጥፋት ሲያደርስ ክፉውን ሰው ይጠብቀዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 21:31

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ ከወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ይቀጥላል።

የክፉውን ሰው መንገድ በፊቱ የሚወቅስ ማን ነው?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚያነሳው ክፉዎች ሁልጊዜም እንደሚፈረድባቸው የወዳጆቹን አስተሳሰብ ለመቃወም ነው። "ማንም ሰው ከፉ ሰውን በፊቱ አይኮንነውም/አይወቅሰውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በፊቱ
ይህ ማለት ማንም ሰው በቀጥታ ወደ ክፉ ሰው ሄዶ ፊት ለፊት አይወቅሰውም። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለሰራው ስራ መልሶ የስራውን የሚከፍለው ማን ነው?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው ከፉ ሰዎች ይፈረድባቸዋል የሚለውን የወዳጆቹን እምነት ለመቃወም ነው። "ለሰራቸው መጠፎ ነገሮች ማንም ሰው መልሶ አይከፍለውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ድጋፍ ያገኛል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች ይደግፉታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የሸለቆ ጓል ለእርሱ ጣፋጭ ይሆንለታል
ኢዮብ የሞተው ክፉ ሰው በላዩ የተጫነው አፈር እንኳን ደስ እንደሚያሰኘው ይገምታል። ይህ ማለት ክፉ ሰው ሞቱ እንኳን መልካም እንደሚሆንለት እና ዘመኑ ሲያበቃ መልካም ቀበር ይደረግለታል ይላል። "ጓል" የሚያመለክተው መቃብር የሚሸፍን አፈርን ነው። "በሸለቆ አፈር መሸፈኑን ደስ ይሰኝበታል" ወይም "በሸለቆ አፈር መቀበሩ ደስ ያሰኘዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእርሱ በፊት አያሌ ሰዎች እንደነበሩ፣ ሰው ሁሉ እርሱን የከተለዋል
ኢዮብ ብዙ የህዝብ ስብስብ በክፉ ሰው ቀብር ላይ እርሱን ለማክበር እንደሚገኙ አጉልቶ ይናገራል። "ወደ ቀብሩ ስፍራ ብዙ ህዝብ ከፊሉ ከፊት፣ ከፊሉ ከኋላ አጅቦት ይሄዳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Job 21:34

አያያዥ ሃሳብ፡
ይህ ኢዮብ ለወዳጆቹ የሚያደርገውን ንግግር ያጠቃልላል።

በመልሶቻችሁ ውስጥ ከሀሰት በስተቀር ሌላ ነገር ሳይኖር እንዴት በማይረባ ነገር ልታጽናኑኝ ትችላላችሁ?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው ወዳጆቹን ለመገሰጽ ነው። "በማይረባ ነገር ልታጽናኑኝ አትችሉም። መልሶቻችሁ ሁሉ ሀሳት ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 22

1 ቴማናዊውም ኤልፋዝ ሲመልስ እንዲህ አለ፦ **2** ሰው እግዚአብሔርን መጥቀም ይችላልን? ጥበበኛ ቢሆን እንኳ ይጠቅመዋልን? **3** ጻድቅ መሆንህስ ሁሉን ለሚችለው አምላክ የሚጨምረው ደስታ አለን? መንገድህ ፍጹም ቀና ቢሆን የሚጠቅመው ነገር አለን? **4** የሚገስጽህና ወደ ፍርድስ ስፍራ የሚያመጣ፥ እርሱን ስለፈራህ ነውን? **5** በደልህ እጅግ የበዛ፣ ኃጢአትህም ፍጻሜ የሌለው አይደለምን? **6** ያለምክንያት ከወንድሞችህን መያዣን ወስደሃል፥ ሰዎችን ልብሳቸውን ገፈህ እርቃናቸውን አስቀረሃቸው። **7** ለዛሉም ሰዎች ውኃ አልሰጠሃቸውም፥ ከራብተኛ ሰዎችም እንጀራን ከልክለሃል። **8** ምድርን የገዛህ ሃያል፤ ክቡር ሰው ብትሆንም። **9** መበለቶን ባዶአቸውን ሰድደሃቸዋል አባት የሌላቸው ልጆችም ክንድ ተሰብሮአል። **10** ስለዚህ ወጥመድ በዙሪያህ አለ፥ ድንገተኛ ፍርሃት ያናውጥሃል። **11** እንዳታይም ጨለማ ሆነብህ፥ የጎርፍ ውሃም አሰጠመህ። **12** እግዚአብሔር በሰማያት ከፍታ ላይ አይልምን? የዋክብትን ከፍታ ተመልከት ምን ያህል ከፍ ይላሉ! **13** አንተም፦ 'እግዚአብሔር ምን ያውቃል? በድቅድቅ ጨለማ ሆኖ ሊፈርድ ይችላልን? **14** እንዳያየን ጥቅጥቅ ደመና ጋርዶታል፤ በሰማይም ክበብ ላይ ይራመዳል' አልህ። **15** እነዚያ ኃጢአተኞች የሄዱበትን፥ የቀድሞውን መንገድ አንተ ደግሞ ትደግመዋለህን? **16** ጊዜያቸው ሳይደርስ ተነጠቁ፤ መሠረታቸውም እንደ ወንዝ ፈሳሽ ተወሰደ። **17** እግዚአብሔርንም፦ “ከእኛ ዘንድ ራቅ ሁሉንም የሚችል አምላክ ምን ሊያደርግልን ይችላል?” አሉት። **18** ነገር ግን እርሱ ቤታቸውን በመልካም ነገር ሞላ፤ የኃጥአን ምክር ከእኔ ይራቅ። **19** ጻድቃን የነዚህን ፍጻሜ ያያሉ፥ ደስም ይላቸዋል፤ ንጹሐንም በንቀት እዲህ በማለት ይስቁባቸዋል። **20** 'በእርግጥ በእኛ ላይ የተነሱ ጠፍተዋል፥ ሃብታቸውንም እሳት በልቶታል።' **21** አሁን ከእግዚአብሔር ጋር ተስማማ፥ ሰላምም ይኑርህ፤ በዚያም መንገድ መልካም ነገር ያገኝሃል። **22** እለምንሃለሁ፥ ከእርሱ አፉ መመሪያ ተቀበል፥ በልብህም ቃሉን አኑር፤ **23** ሁሉን ወደሚችል አምላክ ብትመለስ፥ እንደገና ትሰራለህ፥ ኃጢአትንም ከድንኳንህ አርቀህ ብትጥል፥ **24** የከበረ ሃብትህን በአፈር ውስጥ፥ የኦፊርንም ወርቅ በጅረት ድንጋይ መካከል ብትጥል፥ **25** ሁሉን የሚችል አምላክ የከበረ ሃብትና የተመረጠ ብር ይሆንልሃል። **26** በዚያን ጊዜ ሁሉን በሚችል አምላክ ደስ ይልሃል፥ ፊትህንም ወደ እግዚአብሔር ታነሣለህ። **27** ወደ እርሱ ትጸልያለህ፥ እርሱም ይሰማሃል፤ ስእለትህንም ለእርሱ ትሰጣለህ። **28** በማናቸውም ነገር አዋጅ ትናገራለህ፥ እርሱም ይጸናልሃል፤ ብርሃንም በመንገድህ ላይ ይበራል። **29** እግዚአብሔር ትዕቢተኛን ሰው ያዋርዳል፤ ትሑቱንም ሰው ያድነዋል። **30** ንጹሕ ያልሆነውን ሰው እንኳ፤ በእጅህ ንጽሕና በኩል ይታደገዋል።

Job 22:1

ቴማናዊው ኤልፋዝ
ይህ የወንድ ስም በኢዮብ 2:11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰው እግዚአብሔርን ሊጠቅመው ይችላልን? ብልህ ሰው ለእርሱ ጠቃሚ ሊሆን ይችላልን?
ሁለቱ ጥያቄዎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ኤልፋዝ ጥያቄዎቹን የተጠቀመባቸው የሰው ድርጊት እና ጥበብ እግዚአብሔርን እንደማይጠቅመው ለማጉላት ነው። "ሰው እግዚአብሔርን ሊጠቅም አይችልም። ጥበበኛ ሰው እርሱን ሊጠቅመው አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

አንተ ጻድቅ ብትሆን ሁሉን ቻይ ለሆነው አንዳች ደስታ ነውን? መንገድህን ያለ ነቀፋ ብታደርግ ለእርሱ ጥቅም ነውን?
ሁለቱ ሃሳቦች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ኤልፋዝ ጥያቄዎቹን የተጠቀመባቸው የኢዮብ ድርጊት እግዚአብሔርን እንደማይረዳው ለማጉላት ነው። "አንተ ጻድቅ ብትሆን ሁሉን ቻይ የሆነው አንዳች ደስታ አይቀበልም። አንተ መንገዶችህን ያለ ነቀፋ ብታደርግ እርሱ አንዳች ነገር አያገኝም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 22:4

አያያዥ ሃሳብ፡
ኤልፋዝ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጠለ

ወደ ፍርድ የሚያቀርብህ እና የሚገስጽህ አንተ ለእርሱ ካለህ አምልኮ የተነሳ ነውን? ኃጢአትህ/ክፋትህ ታላቅ
አይደለምን? ለበደልህ ዳርቻ የለውምን? ኤልፋዝ እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመው ኢዮብን ለመገሰጽ እና አስከፊ ኃጢአት ስለመስራቱ ሊከሰው ነው። "በእርግጥ እግዚአብሔር አንተን የገሰጸህ እና ወደ ፍርድ ያቀረበህ ለእርሱ የተሰጠህ ስለነበርክ አይደለም! አይደለም፣ እንደምታውቀው፣ የፈረደብህ ክፋትህ/ኃጢአትህ ታላቅ ስለሆነ እና በኃጢአተኛነትህ ስለቀጠልክበት/ከኃጢአትህ ስላልተመለስክ ነው!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 22:6

አያያዥ ሃሳብ፡
ኤልፋዝ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጠለ

ላበደርከው መያዣ ጠይቀሃል
ይህ የሚያመለክተው አበዳሪ ከተበዳሪው መልሶ መክፈል መቻሉን ለማረጋገጥ አንድ ነገር እንደሚወስድ ነው።

የተራቆቱትን/ድሆችን ልብሳቸውን ገፈሃል
ኤልፋዝ ኢዮብን የሚከሰው ከእርሱ ከተበደሩ ድሆች ላይ መያዣ አድርጎ ልብሳቸውን እንደወሰደ አድርጎ ነው።

እንጀራቸውን ከልክለሃል
እዚህ ስፍራ "እንጀራ" የሚያመለክተው በአጠቃላይ ምግብን ነው። " ምግብ ከልክለሃል" (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

መሬታቸውን ወርሰሃል/ቀምተሃል... በላይዋ ኖረሃል
ኤልፋዝ ኢዮብን የሚከሰው ከድሃ ሰዎች መሬታቸውን እንደ ቀማ እና በመሬታቸው እንዳይኖሩ እንደከለከላቸው አድርጎ ነው። ይህንን ነጥብ የሚያጎላው ነገሩን ሁለት ጊዜ ደጋግሞ በመናገር ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መሬታቸውን ወርሰሃል/ቀምተሃል
ኤልፋዝ ኢዮብ የያዘውን መሬት መጠን የሚያጋንነው ኢዮብን ራስ ወዳድ አድርጎ ለማሳየት ነው። "እጅግ ሰፊ መሬት ይዘሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 22:9

አያያዥ ሃሳብ፡
ኤልፋዝ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጠለ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ባሎቻቸው የሞቱባቸውን መበለቶች ባዷቸውን ሰደሃል
"መበለቶች ባዷቸውን እንዲሄዱ አድርገሃል"

መበለቶች
ባሎቻቸው የሞቱባቸው ሴቶች

አባት የሌላቸው ክንዳቸው ተሰብሯል
እዚህ ስፍራ "ክንዶች" የሚለው የሚያመለክተው ሀይልን ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ወላጅ የሌላቸውን ሳይቀር ጨቁነሃል" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

በዙሪያህ ወጥመድ አለ... ጨለማ ሆኗል... ብዙ ውሃ ሸፍኖሃል
እያንዳንዳቸው እነዚህ ዘይቤያዊ አነጋገሮች፣ ከኃጢአቱ የተነሳ ኢዮብን ችግር እና አደጋ ዙሪያውን እንደከበቡት ይገልጻሉ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ብዙ ውሃ
"ጎርፍ"

Job 22:12

አያያዥ ሃሳብ፡
ኤልፋዝ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጠለ

እግዚአብሔር በሰማያት ከፍታ አይደለምን?
ኤልፋዝ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው እግዚአብሔር የኢዮብን ኃጢአት እንደሚመለከት እና እንደሚፈርድበት ለመናገር ነው። "እግዚአብሔር በሰማያት ከፍታ ነው፤ በምድር የሚሆነውን ሁሉ ይመለከታል።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ወደ ከዋክብት ከፍታ ተመልከት፣ እንደምን ከፍ ያሉ ናቸው!
ኤልፋዝ እግዚአብሔር ከከዋክብትም በላይ ከፍ ብሎ እንደሚገኝ እያመለከተ ነው። ይህ ይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ከዋክብት እንዴት ከፍ ብለው እንደሚገኙ ተመልከት። እግዚአብሔር ከከዋክብትም በላይ ከፍ ያለ ነው!"በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ምን ያውቃል? እርሱ በድቅድቅ ጨለማ ሊፈርድ ይችላልን?
ኤልፋዝ እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመው ኢዮብ በእግዚአብሔር ላይ እነዚህን ነገሮች ተናግሯል ለማለት ነው። "እግዚአብሔር በምድር ላይ የሚሆነውን አያውቅም። እሱ በጥቁር ደመና ላይ ስለተቀመጠ በእኛ ላይ ለመፍረድ ሊመለከተን አይችልም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ በሰማያት ከፍታ ይራመዳል
እዚህ ስፍራ "ከፍታ፣ጣሪያ" የሚለው የሚያመለክተው የጥንት ሰዎች ምድርን እና ሰማይን ይለያል ብለው የሚያስቡትን መለያ ነው። "እርሱ እዚህ የሚሆነውን እጅግ ሩቅ በሰማያት ሆኖ ይመለከታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 22:15

አያያዥ ሃሳብ፡
ኤልፋዝ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጠለ

ኃጢአተኞች በሚሄዱበት አሮጌ መንገድ መሄድህን ትቀጥላለህ
ክፉ ስራ መስራት የተነጻጸረው በመንገድ ላይ ከመሄድ ጋር ነው። "ክፉ ሰዎች የሚያደርጉትን ማድረግህን ትቀጥልበታለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ተቀሙት እንደ እነርሱ
ሞት የተነጻጸረው እግዚአብሔር እነርሱን እንደ ቀማቸው ተደርጎ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ለገለጽ ይችላል። "የሞቱት እነርሱ" ወይም "እግዚአብሔር የወሰዳቸው እነርሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

መሰረታቸው እንደ ወንዝ ተጠርጎ የተወሰደው
የክፉ ሰዎች ሞት የተነጻጸረው መሰረታቸው በጎርፍ ከተወሰደ ህንጻዎች ጋር ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉን ቻይ የሆነው በእኛ ላይ ምን ማድረስ ይችላል?
ኤልፋዝ የሚጠቅሰው ክፉዎች በእግዚአብሔር ላይ ለመሳለቅ የሚያነሱትን ጥያቄ ነው። "ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ በእኛ ላይ አንዳች ማድረግ አይችልም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 22:18

አያያዥ ሃሳብ፡
ኤልፋዝ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጠለ

ሆኖም እርሱ ይሞላዋል
"ሆኖም እግዚአብሔር ይሞላዋል"

የክፉ ሰዎች እቅድ ከእኔ የራቀ ነው
"ከእኔ የራቀ" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉሙ ኤልፋዝ እነርሱን ይቃወማል ማለት ነው። "እኔ ግን ክፉ እቅዳቸውን አልሰማም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እድል ፈንታቸውን ያያሉ
"በክፉዎች ላይ የሚደርሰውን ያውቃሉ"

በንቀት ይስቁባቸዋል
"በክፉዎች ላይ ይሳለቃሉ"

እነርሱ እንዲህ ይላሉ
"ጻድቃን እንዲህ ይላሉ"

በእርግጥ በእኛ ላይ ሚነሱ ይቆረጣሉ/ይጠፋሉ
እዚህ ስፍራ "እነርሱ የሚነሱብን" የሚለው የሚያመለክተው ክፉ ሰዎችን ነው።ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በእርግጥ እግዚአብሔር እኛን የጎዱትን ክፉ ሰዎች ያጠፋቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 22:21

አያያዥ ሃሳብ፡
ኤልፋዝ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጠለ

እነሆ
ኤልፋዝ ይህንን ቃል የተጠቀመው ሊናገር የፈለገውን ጠቃሚ ነገር ለማስተዋወቅ ነው።

ከአፉ የወጣው ትዕዛዝ
እዚህ ስፍራ "ከአፉ የወጣው" የሚለው የሚወክለው እግዚአብሔር የተናገረውን ነው። "እግዚአብሔር የሰጠው/የተናገረው ትዕዛዝ" በሚለው

ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ቃሉን አከማችቷል
የእግዚአብሔር ቃሎች የተነጻጸሩት ኢዮብ በግምጃ ቤት ሊያጠራቅመው ከሚችለው ሀብት ጋር ነው። "ትዕዛዛቱን ማከማቸት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ልብህ
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚያመለክተው የኢዮብን አስተሳሰብ ነው። "የአንተ አእምሮ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 22:23

አያያዥ ሃሳብ፡
ኤልፋዝ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጠለ

አንተ ትጸናለህ
ኤልፋዝ የኢዮብን መታደስ የሚያነጻጽረው ከወደቀ ቤት መልሶ መገንባት ጋር ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እርሱ ይፈውስሀል፣ ደግሞም መልሶ ባለጠጋ ያደርግሀል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከጎጆች ጽድቅ ያልሆውን ብታርቅ
ጽድቅ ያልሆነ የሚለው የተገለጸው ሊርቅ እንደሚገባው በኢዮብ ጎጆ እንደሚኖር ሰው ተደርጎ ነው። "አንተ እና በቤትህ የሚኖሩ ሁሉ ኃጢአት መስራትን ብታቆሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሀብትህን በአፈር ውስጥ ቅበር
ሀብትን በአፈር ውስጥ መቅበር፣ ሀብትን ጥቅም እንደሌለው ማድረግ ነው። "ብልጽግናህን እንደ አፈር ጥቅም የሌለው አድርገህ ቁጠረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የኦፊርን ወርቅ በጅረቶች ድንጋይ መሃል
ወርቅን በወራጅ ውስጥ መጣል ከደንጋይ የተሻለ ምንም ጥቅም እንደሌለው አድርጎ መቁጠር ነው። "የኦፊር ወርቅ በወራጅ ውስጥ እንደሚገኝ ድንጋይ ጥቅም የሌለው ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኦፊር
ይህ በወርቁ የታወቀ ቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉን ቻይ የሆነው ብልጽግና፣ እና ውድ ብር ይሆንልሃል
ይህ ማለት እግዚአብሔር ለኢዮብ ከማንኛውም ሀብት ይልቅ ዋጋ ያለው ይሆንለታል ማለት ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 22:26

አያያዥ ሃሳብ፡
ኤልፋዝ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጠለ

ፊትህን ወደ እግዚአብሔር ታነሳለህ
ይህ ማለት ኢዮብ ከእንግዲህ አያፍርም፣ ይልቁንም በእግዚአብሔር ይታመናል። "በሙሉ ልን ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይሆንልሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ለአንተ ይረጋገጥልሃል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር ፍሬያማ ያደርግሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በመንገዶችህ ብርሃን ይሆናል/ይበራል
የእግዚአብሔር በረከት የተነጻጸረው በኢዮብ መንገድ ላይ ሁሉ እንደሚሆን ብርሃን ነው። "በፊትህ በሚገኝ መንገድ ላይ እንደሚበራ ብርሃን ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 22:29

አያያዥ ሃሳብ፡
ይህ ኤልፋዝ ከኢዮብ ጋር ያለውን ንግግር ያጠቃልላል

ዝቅ ያሉ/የተዋረዱ ዐይኖች ያሉት
እዚህ ስፍራ "ዝቅ ያሉ ዐይኖች" የሚለው የሚያመለክተው ትህትናን ነው። "ትሁቱ ሰው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ትህት ያልሆነውን ሰው እንኳን ያድናል፤ በአንተ እጅ ንጽህና ግን የሚድነው ማን ነው
የኢዮብ ንጹህ መሆን የተነገረው አካላዊ እጁ ንጹህ እንደሆነ ተደርጎ ነው። "ማን ይድናል" የሚለው ሀረግ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንተ ትክክል የሆነውን ስታደርግ ያኔ ያህዌ ንጹህ ያልሆውን ሰው እንኳን ያድናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

እርሱ ትህት ያልሆነውን ሰው እንኳን ያድናል፤ በአንተ እጅ ንጽህና ግን የሚድነው ማን ነው
አንዳንድ ቅጂዎች እንዲህ ይላሉ፣ "እርሱ ትሁቱን ሰው ያድናል፤ ስለዚህ የአንተ እጆች ንጹህ በሆኑ ጊዜ አንተን ያድንሃል"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 23

1 ኢዮብም ሲመልስ እንዲህ አለ፦ 2 ዛሬም ቢሆን የኅዘን አቤቱታዬ መራራ ነው፤ መከራዬም ማቃሰት ከምችለው በላይ ይከብዳል። 3 ኦ! እርሱን ወዴት እንደማገኘው ምነው ባውቅ! እርሱ ወዳለበት ስፍራ በሔድሁ! 4 ጕዳዬን በፊቱ በተገቢ ሁኔታ ባቀረብሁ፥ አፌንም ለሙግት ሞልቼ አዘጋጅ ነበር። 5 የሚመልስልኝን ቃሎች አውቅ ነበር፥ የሚለኝንም በተረዳሁ ነበር። 6 በኃይሉ ብዛት ከእኔ ጋር ይምዋገት ነበርን? እንኳን! ያደምጠኝ ነበር። 7 ጻድቅ ሰው ከእርሱ ጋር በዚያ ይዋቀሳል፤ እንደዚህም በዳኛዬ በእርሱ ለዘላለም ነጻ እወጣ ነበር። 8 ነገር ግን፥ ወደ ምስራቅ ብሄድ፥ በዚያ የለም፤ ወደ ምዕራብም ብሔድ ላየው አልቻልኩም፤ 9 ወደሚሠራበት ወደ ሰሜን ብሄድ አላየሁትም፤ ራሱን ወደሚሰውርበት በደቡብም፥ላየው አልቻልኩም፤ 10 ነገር ግን የምሄድበትን መንገድ ያውቃል፤ ከፈተነኝም በኋላ እንደ ወርቅ እወጣለሁ። 11 እግሮቼ እርምጃውን በጽናት ተከተሉ፤ ውልፍት ሳልል መንገዱን ጠብቄአለሁ። 12 ከከንፈሩም ትእዛዝ አላፈገፈግሁም፤ የአፉን ቃል በልቤ ሰውሬአለሁ። 13 እርሱ ግን በአይነቱ ብቸኛ ነው፤ እርሱንስ ማን ሊመልሰው ይችላል? እርሱ የወደደውን ነገር ያደርጋል። 14 በእኔ ላይ የተወሰነብኝን ይፈጽማል፤ እንደነዚህም አይነት ብዙ አለ። 15 ስለዚህ በእርሱ ፊት ደነገጥሁ፤ ስለእርሱም ባሰብሁ ጊዜ እፈራዋለሁ። 16 እግዚአብሔር ልቤን አድክሞታል፥ ሁሉንም የሚችል አምላክ አስደንግጦኛል። 17 እንጂ ጨለማ ወይም ድቅድቁ ጨለማ ፊቴን ከመክደኑ የተነሣ አልጠፋሁም።

Job 23:1

ዛሬም እንኳን ሀዘኔ መራራ ነው
እዚህ ስፍራ "ዛሬም እንኳን" የሚለው የወዳጆቹ ክርክር የኢዮብን ሁኔታ ምንም እንዳለወጠው የሚያጎላ ነው። "እንንተ ከተናገራችሁት ሁሉ ባሻገር፣ የእኔ ሀዘን ዛሬም መራራ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ሀዘኔ መራራ ነው
ኢዮብ ስላልተመለሱ ጥያቄዎቹ በአፉ ውስጥ እንዳለ መራራ ጣዕም አድርጎ እግዚአብሔርን ተቃውሞ ይናገራል። "ያልተመለሱ ጥያቄዎቼ በአፌ ውስጥ እንደሚገኝ መራራ ምግብ ሆኖብኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእኔ እጅ ... ከማቃሰቴ የተነሳ ከብዷል
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ከማቃሰቴ የተነሳ እጄን ማንሳት እንኳን አልቻልኩም" ወይመም 2) "ከማቃሰቴ ባሻገር የእግዚአብሔር እጅ እኔን ማሰቃየቱን ቀጥሏል" እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው የሚያመለክተው እግዚአብሔር ለመቅጣት ያለውን ሀይል ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 23:3

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል

አወይ፣ ያ የት እንደሆነ አውቃለሁ... አወይ፣ እኔ ወደዚያ እመጣለሁ
እነዚህ ሁለት መስመሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ የሚያጎሉትም ኢዮብ ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ያለውን ፍላጎት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አገኘው ይሆናል
"እግዚአብሔርን አገኘው ይሆናል"

ጕዳዬን በፊቱ አቀርብ... አፌን በሞላው
እነዚህ ሁለት መስመሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ የሚያጎሉትም ኢዮብ ለእግዚአብሔር ሁኔታውን ለማስረዳት ያለውን ፍላጎት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አፌን በክርክር ሞላው
እዚህ ስፍራ "አፌን ሞላው" የሚለው የሚያመለክተው ንግግርን ነው። "ክርክሬን ሁሉ አቀርባለሁ/እናገራለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ቃሎቹን እማራለሁ... እረዳቸዋለሁ
እነዚህ ሁለት መስመሮች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትረጉም አላቸው፤ የሚያተኩሩትም ኢዮብ የእግዚአብሔርን መልስ ለመስማት ባለው ፍላጎት ላይ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእኔ የሚሰጠኝን መልስ
"እርሱ ለእኔ የሚሰጠውን መልስ"

Job 23:6

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል

እርሱ ...ይሆን
"እግዚአብሔር...ይሆን"

በዚያ
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር የሚገኝበትን ስፍራ ነው

ፈራጁ/ዳኛዬ ለዘለዓለም ነጻ ያወጣኛል
ይህ በዐድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የእኔ ዳኛ ለዘለአለም ነጻ ያወጣኛል" ወይም "የእኔ ዳኛ የሆነው እግዚአብሔር፣ ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ንጹህ መሆኔን ይናገራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 23:8

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል

ወደ ምስራቅ... ወደ ምዕራብ... ሰሜን....ደቡብ
እነዚህን አራት አቅጣጫዎች በመጥራት፣ ኢዮብ ወደ ሁሉም ስፍራ መመልከቱን ያተኩራል

ራሱን የት እንደ ሰወረ
ኢዮብ ስለ እግዚአብሔር ራሱን እንደ ሰወረ ሰው አድርጎ ይናገራል

Job 23:10

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እርሱ እኔ የምወስደውን መንገድ ያውቃል
የኢዮብ ድርጊቶች የተገለጹት በመንገድ እንደሚሄድ ተደርገው ነው። "እግዚአብሔር የማደርገው ምን እንደሆነ ያውቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ወርቅ ነጥሬ እወጣለሁ
ኢዮብ መከራው እርሱ እንደ ነጠረ ወርቅ መሆኑን እንደሚያረጋግጥ ያምናል። "ማናቸውም ንጹህ ያልሆነ ነገር በእሳት ተፈትኖ ሲወገድ፣ እኔ እንደ ወርቅ ንጹህ መሆኔን ይመለከታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እግሮቼ የእርሱን መንገድ ጠብቀዋል
እዚህ ስፍራ "እግሬ" የሚለው የሚያመለክተው ኢዮብን ነው። "እርሱ ያሳየኝን መንገድ ተከትያለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስነክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱን መንገድ ጠብቄያለሁ
የኢዮብ ታዛዥነት የተገለጸው እግዚአብሔር ባሳየው መንገድ እንደሄደ ተደርጎ ነው። "እርሱ አደርገው ዘንድ የነገረኝን አድርጌያለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያ ፈቀቅ አላልኩም
ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊጻፍ ይችላል። "በትክክል ተከትያለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ከዚያ ወደ ኋላ አልልኩም/አላፈገፈግኩም
ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ሁልጊዜም ታዝዣለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

የእርሱ ከንፈሮች
ይህ ሀረግ የሚያመለክተው እግዚአብሔር የተናገረውን መልዕክት ነው። "እርሱ የተናገረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የአፉ ቃል
እዚህ ስፍራ እግዚአብሔር የተገለጸው በ "አፉ" ነው። "እርሱ የተናገረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስነክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 23:13

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል

እርሱ ብቻውን ነው፣ ማን ሊመልሰው ይችላል?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም እንደሌለ እና እርሱን ይለውጠው ዘንድ የሚችል ማንም እንደሌለ ትኩረት ሰጥቶ ለመናገር ነው። "ነገር ግን እንደ እርሱ ያለ ማንም የለም፣ ማንም ሀሳቡን ሊያስለውጠው አይችልም።" ወይም " ነገር ግን እርሱ ብቻ አምላክ ነው፣ ማንም ተጽኖ ሊያሳድርበት አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ የወደደውን ያደርጋል
"እርሱ ማድረግ የፈለገውን ሁሉ ያደርጋል"

በእኔ ላይ ትዕዛዙን አወጣ
"በእኔ ላይ አደርጋለሁ ያለውን አደረገ"

እንደነዚህ ያሉ ሌሎች ብዙዎች አሉ
"እርሱ ለእኔ ሌሎች ብዙ ተመሳሳይ እቅዶች አሉት"

Job 23:15

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል

አጠቃላይ መረጃ፡
እነዚህ እያንዳንዳቸው ሀረጋት ኢዮብ በዚያ ያደረጋቸውን ዋና ዋና ነጥቦች ለማጉላት የትይዩ ንጽጽር ዘይቤ መልኮች አላቸው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ ሚለውን ይመልከቱ)

ልቤን ደካማ አደረገው
ልቡ የደከመ ሰው ድንጉጥ ወይም በፍርሃት የተሞላ ነው። "እንድፈራ አደረግኸኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በጨለማ ወደ ፍጻሜ አልመጣሁም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ከፊቴ ያለው ድቅድቁ ጨለማ ዝም አላሰኘኝም" ወይም 2) "ጨለማ አላስቆመኝም" ወይም " እግዚአብሔር እንጂ ጨለማ አላስቆመኝም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የፊቴ ትካዜ
እዚህ ስፍራ ኢዮብ ራሱን የሚገልጸው በ"ፊቱ/ገጹ" ነው። "ትካዜዬ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስነክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 24

1 ሁሉን ከሚችል አምላክ ሃጢያተኛ የሚፈረድበት ጊዜ ለምን አልተወሰነም? ለእርሱስ ታማኝ የሆኑት የፍርዱ ቀን እንደመጣ ለምን አያዩም? 2 የድንበር
ምልክትን የሚያፈርሱ ኅጢያተኛ ሰዎች አሉ፤ የሌሎችን መንጋ በግፍ ወስደው የሚያሰማሩ አመጸኞች አሉ። 3 የድሀ አደጎችን አህያ ቀምተው ይነዳሉ ፤
የመበለቲቱንም በሬ በመያዣ ይወስዳሉ። 4 ድሆችን ከመንገዳቸው ያስወጣሉ፤ የምድርም ችግረኞች ሁሉ ከእነርሱ ይሸሸጋሉ። 5 እነዚህ ችግረኞች፥ በምድረ
በዳ እንዳሉ የሜዳ አህዮች ወደ ስራቸው ይወጣሉ፥ ምግብን ፍለጋ በጥንቃቄ ይሄዳሉ፤ ምንአልባት ምድረ በዳው ለልጆቻቸው መብልን ይሰጣቸዋል። 6
ድሆቹም በሌሎች ሰዎች በእርሻ ውስጥ በምሽት ያጭዳሉ፤ ከበደለኞችም መከር ወይንን ይቃርማሉ። 7 ራቁታቸውን ያለ ልብስ ምሽቱን ሁሉ ይተኛሉ፥ በብርድም
ጊዜ መጐናጸፊያ የላቸውም። 8 ከተራሮች በሚወርድ ዝናብ ይረጥባሉ፤ መጠለያም ስለሌላቸው ከቋጥኝ ስር ይጋደማሉ። 9 ድሀ አደጉን ህጻን ከእናቱ ጡት
የሚነጥሉ ኅጢያተኞች አሉ፤ በደለኞችም ልጆችን በመያዣነት ይወስዳሉ። 10 ነገር ግን ድሃዎቹ ያለ ልብስ ራቁታቸውን ይሄዳሉ፤ ተርበውም ቢሆን የሌሎችን
እህል ነዶ ይሸከማሉ፤ 11 ድሃ ሰዎች በጐጢአን አጥር ውስጥ ዘይት ይሰራሉ፤ ወይንም ይጠምቃሉ፥ ነገር ግን እነርሱ በጥም ይሰቃያሉ። 12 በከተማ ውስጥ
ሰዎች ያቃስታሉ ፤ የቆሰሉም ለእርዳታ ይጮኻሉ፤ እግዚአብሔር ግን ልመናቸውን አይመለከትም። 13 እነዚህ ኅጢያተኞች በብርሃን ላይ ያምጻሉ፤ መንገዱን
አያውቁም፥ በጎዳናውም አይጸኑም። 14 ነፍሰ ገዳዩም ማልዶ ይነሣል፤ ችግረኞችንና ድሆችን ይገድላል፤ በሌሊትም እንደ ሌባ ነው። 15 የአመንዝራም ዓይን
ድግዝግዝታን ይጠብቃል። "የማንም ዓይን አያየኝም" ይላል፥ ፊቱንም እንደሌላ ይለውጣል። 16 አመጸኞች ቤቶችን በጨለማ ይሰረስራሉ፤ በቀን ግን
ይሸሸጋሉ፤ ለብርሃንም ግድ የላቸውም። 17 ለእነርሱ ጥዋት እንደ ድቅድቅ ጨለማ ነውና፤ ከድቅድቅ ጨለማ ሽብር ጋርም ተወዳጅተዋል። 18 ይሁን እንጂ
በውኃ ላይ እንዳለ አረፋ በርረው ይጠፋሉ፤ የርስት እድል ፈንታቸውም የተረገመ ነው፤ በወይን ቦታቸውም ላይ ለመስራት ማንም አይሄድም። 19 ድርቅና ሙቀት
በረዶውን እንደሚያቀልጥ፤ እንዲሁ ሲኦል ሃጢያተኞችን ታጠፋለች። 20 የተሸከመችው ማኅፀን ትረሳዋለች፤ ትልም በደስታ ይበላዋል፤ ዳግመኛም አይታሰብም፤
በዚህ ሁኔታ ዓመጸኝነት እንደ ዛፍ ይሰበራል። 21 የማትወልደውን መካኒቱን ሃጥያተኛው ይጎዳታል፤ ለመበለቲቱም ምንም አይነት በጎነት አያደርግም። 22 ነገር
ግን እግዚአብሔር በኃይሉ ኃያላንን ጎትቶ ይጥላል፤ እርሱም ይቆማል በሕይወቱ ግን አይጠነክርም። 23 እግዚአብሔር በደኅንነት እንዳሉ እንዲያስቡ
ይፈቅዳል፥ በዚያም ደስ ይላቸዋል፤ ነገር ግን ዓይኖቹ በመንገዳቸው ላይ ናቸው። 24 እነዚህ ሰዎች ለጥቂት ጊዜ ከፍ ከፍ ይላሉ፤ በርግጥ ግን፥ ይዋረዳሉ፤
እንደ ሌሎች ሁሉ ተሰብስበው፤ እንደ እሸት ራስ ጫፍ ይቈረጣሉ። 25 እንደዚህስ ባይሆን ሐሰተኛ የሚያደርገኝ፥ ንግግሬንም ከንቱ የሚያደርግ ማን ነው?

Job 24:1

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል

ሁሉን ቻይ በሆነው አምላክ የክፉ ሰዎች የፍርድ ጊዜ ለምን አይወሰንም
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው እግዚአብሔር በክፉዎች ላይ አይፈርድም የሚለውን መረበሹን ለመግለጽ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር በክፉ ሰዎች ላይ ሚፈርድበትን ጊዜ ለምን እንደማይወስን አይገባኝም" ወይም "ሁሉን ቻይ የሆነው በክፉ ሰዎች ላይ መቼ እንደሚፈርድ መወሰን አለበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ለእግዚአብሔር ተማኝ የሆኑ ለምን የፍርዱ ቀን ሲመጣ/ ሲደርስ አይመለከቱም?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው ጻድቃን እግዚአብሔር በኃጢአተኞች ላይ ሲፈርድ ባለመመልከታቸው የሚሰማቸውን መረበሽ ለመግለጽ ነው። "እርሱን የሚታዘዙ እርሱ በኃጢአተኞች ላይ ሲፈርድ የሚመለከቱ አይመስልም" ወይም "እግዚአብሔር በኃጢአተኞች ላይ ሲፈርድ እርሱን የሚያውቁ ይህንን የሚመለከቱበትን ቀን ማሳየት/ማምጣት አለበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 24:2

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል

ዳርቻን አመልካቾች
እነዚህ በተለያዩ ሰዎች የተያዙ መሬቶችን ድንበር የሚለዩ ድንጋዮች ወይም ሌሎች ቁሳቁሶች ናቸው።

የግጦሽ መሬት
እንስሳት ለግጦሽ የሚሰማሩበት መሬት

ይነዷቸዋል
"ይሰርቃሉ"

አባቶች የሌሏቸውን
"የሙት ልጆች" ወይም "ወላጆቻቸው የሞቱባቸው ልጆች"

የመበለቶችን በሬዎች መያዣ አድርገው ይወስዳሉ
"የመበለቶችን በሬዎች ለተበደሩት ገንዘብ መያዣ አድርገው ይወስዳሉ"

መበለት
ባሏ የሞተባት ሴት

መያዣ አድርገው
አበዳሪው ከተበዳሪው መልሶ መክፈሉን ለማረጋገጥ አንድ ነገር ይወስዳል።

ከመንገዳቸው ወጥተው
"ከመንገዳቸው ውጭ" ወይም "ከመንገዱ ውጭ"

የምድር ድሆች ሁሉም ራሳቸውን ይደብቃሉ
"ሁሉም" የሚለው ቃል ብዙ ድሆች እነዚህን ክፉ ሰዎች እንደሚፈሯቸው የሚያሳይ ግነት ነው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 24:5

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል

የሜዳ አህዮች ወደ በረሃ ምግብ ፍለጋ በጥንቃቄ እንደሚወጡ፣ እነዚያ ድሃ ሰዎች ወደ ስራቸው ይወጣሉ
እነዚህ ድሃ ሰዎች የተገለጹት ምግባቸውን ከየት ማግኘት እንደሚችሉ እንደማያውቁ የሜዳ አህዮች ነው። "እነዚህ ድሃ ሰዎች ምግብ ፍለጋ የሚወጡት በበረሃ እንደሚኖሩ የሜዳ አህዮች ባለ ሁኔታ ነው።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሜዳ አህዮች
"ባለቤት ወይም ተንከባካቢ የሌላቸው አህዮች"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ድሆች በምሽት ያጭዳሉ...ወይን ይለቅማሉ
እነዚህ ሁለት መስመሮች ተመሳሳይ ነገርን ይገልጻሉ፤ በአንድነት የዋሉት እነዚህ ሰዎች እጅግ የተራቡ እና በምሽት ምግብ ለመስረቅ የተገደዱ መሆናቸውን ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ ሚለውን ይመልከቱ)

እርቃናቸውን ተጋድመዋል... የሚለብሱት የላቸውም
እነዚህ ሁለት መስመሮች ተመሳሳይ ነገርን ይገልጻሉ፤ በአንድነት የዋሉት እነዚህ ሰዎች ራሳቸውን ከብርድ ለመከላከል ምንም ልብስ እንደሌላቸው ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ ሚለውን ይመልከቱ)

Job 24:8

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል

ከተራሮች በሚወርድ ዝናብ ርሰዋል
"በተራሮች ሲዘንብ ርሰዋል"

የሙት ልጆችን ከእናታቸው ጡት ያስጥላሉ
እዚህ ስፍራ "ጡት" የሚያመለክተው እናትን ነው። ይህ የሚያመለክተው እነዚህ ወላጅ የሞተባቸው ገና ልጆች መሆናቸውን ነው። ይህ ይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ወላጆች የሞቱባቸው ልጆች ከእናቶቻቸው እቅፍ ሲወጡ" ወይም "አባቶቻቸው የሞቱባቸው ጨቅላ ልጆች ከእናቶቻቸው ተነጠሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ወላጅ የሞተባቸው
ይህ በአጠቃላይ ወላጅ የሌላቸውን ልጆች ያመለክታል። ሆኖም እዚህ ስፍራ በተለይ እናት ያላቸውን ነገር ግን አባት የሌላቸውን ልጆች ያመለክታል።

ከድሆች ልጆቻቸውን በመያዣነት ይወስዳሉ
"የድሆችን ልጆች ድሆቹ ከክፉ ሰዎች የተበደሩትን መልሰው እንዲከፍሉ በመያዣነት ይወስዳሉ"

በመያዣነት
አበዳሪው ተበዳሪው መልሶ መክፈል መቻሉን ለማረጋገጥ ከተበዳሪው አንድ ነገር ይወስዳ/ ይይዛል። ይህ በኢዮብ 24፡3 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ወደዚያ ሄደ
"ተዘዋወረ"

ያለ ልብስ የተራቆተ
"ያለ ልብስ" የሚለው ሀረግ "እርቃን" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው። "ሙሉ ለሙሉ እርቃን" ወይም "አንዳች ልብስ ስላልነበራቸው እርቃናቸውን ነበሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

የሌሎችን ነዶ ይሸከማሉ
ይህ ማለት ድካማቸው/ስራች የሚጠቅመው/ምግብ የሚያስገኘው ለእነርሱ ሳይሆን ለሌሎች ነው

Job 24:11

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል

ድሆች ዘይት ያዘጋጃሉ
ከወይራ ዘይት ለእነርሱ ዘይት ይጨምቃሉ

በክፉ ሰዎች አጥር ውስጥ
እዚህ ስፍራ "አጥር" የሚለው የሚወክለው በአጠቃላይ ቤቱን ነው። "በእነዚያ ክፉ ሰዎች ቤት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በክፉዎች ወይን መጭመቂያ ይረግጣሉ
ወይን ለማዘጋጀት ይህንን እንደሚያደርጉ መግለጽ ሊያስፈልግ ይችላል። "ወይን ለማዘጋጀት የወይን ፍሬ ይረግጣሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ራሳቸው በጥም ይሰቃያሉ
"ከጥማት የተነሳ ይሰቃያሉ" ወይም "ተጠምተዋል"

Job 24:13

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል

ብርሃን ላይ ማመጽ
ለ"ብርሃን" ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የሚታይ ብርሃን ወይም 2) መንፈሳዊ ብርሃን፣ ይህ እግዚአብሔርን ሊያመለክት ወይም በጽድቅ መኖርን ሊያመለክት ይችላል። "የቀን ብርሃንን ጠላ" ወይም "ነገሮችን በገሃድ ለማድርግ አለመፈልግ" ወይም "በእግዚአብሔር ላይ ማመጽ" በሚሉት ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ መንገዱን አላወቁም፣ አሊያም በመንገድ አልቆዩም
እነዚህ ሁለት ምመሮች ተመሳሳይ ነገርን ይገልጻሉ፣ በአንድነት የዋሉት የብርሃንን መንገድ ለመከተል አለመፈለጋቸውን አጉልቶ ለመግለጽ ነው። "ስነ ምግባር ያለው ህይወት እንዴት እንደሚኖሩ አያውቁም፤ የጽድቅ ህይወት ከመኖር የራቁ ናቸው" በሚሉት ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ድሆች እና ጎስቋላ ሰዎች
"ድሃ" እና "ጎስቋላ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክተው ተመሳሳይ ሰዎችን ነው፤ አጉልቶ የሚገልጸውም እነዚህ ሰዎች ራሳቸውን መርዳት አለመቻላቸውን ነው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ እንደ ሌባ ነው
ሌባ ማንም ሳያየው እንደሚሰርቅ ሁሉ ነብሰ ገዳዩም በድብቅ ይገድላል። "ሌባ በድብቅ እንደሚሰርቅ ሁሉ እርሱ/ነብሰ ገዳዩ ሰዎችን በድብቅ ይገድላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 24:15

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል

የዘማዊ ዐይን
እዚህ ስፍራ "ዐይን" የሚለው የሚያመለክተው በጠቅላላ ሰውየውን ነው። "ዘማዊው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ጀንበር ስትጠልቅ
"ፀሐይ ስትጠልቅ"

የማንም ዐይን አያየኝም
እዚህ ስፍራ "ዐይን" የሚለው የሚያመለክተው በጠቅላላ ሰውየውን ነው። "ማንም አያየኝም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ክፉ ሰዎች ቆፍረው ወደ ቤት ይገባሉ
ወደ ቤቶች ቆፍረው የሚገቡት ከእነርሱ ለመስረቅ ነው። ይህ ይበልጥ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "ክፉ ሰዎች ወደቤቶች ቆፍረው የሚገቡት ከእነርሱ ለመስረቅ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በራሳቸው ላይ ይዘጋሉ
"እነርሱ በውስጥ ይደበቃሉ"

ለእነርሱ ለሁሉም፣ ድቅድቅ ጨለማ እንደ ንጋት ነው
ለጤናማ ሰው የንጋት ብርሃን ምቹ እንደሚሆንለት ለክፉዎች ድቅድቅ ጨለማ ምቹ ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የድቅድቅ ጨለማ ፍርሃት
"በጨለማ የሚሆኑ አስፈሪ ነገሮች"

Job 24:18

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል

በውሃ ላይ እንዳለ አረፈ
አረፋ የሚቆየው ለአጭር ጊዜ ብቻ ነው። ይህ እግዚአብሔር ክፉዎችን አንደምን በቶሎ እንደሚያጠፋ አጎልቶ ያሳያል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ምድራቸው የተረገመ ነው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር ምድራቸውን ይረግማታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ድርቅ እና በረሃማነት/ሙቀት እንደሚያጠፉ... ኃጢአት የሰሩ
ኢዮብ፣ በሙቀት ጊዜ በረዶ እንደሚቀልጥ እና እንደሚጠፋ ኃጢአተኞች በሲኦል ይጠፋሉ ይላል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ድርቅ እና በረሃማነት/ሙቀት
እነዚህ ሁለት ቃላት በመሰረቱ ተመሳሳይ የአየር ንብረትን ይገልጻሉ፤ በአንድነት የቀረቡት ነገሩን በሙላት ለመግለጽ ነው። (ሄንዲየዲስ/ሁለት ቃላት 'እና' በሚል አያያዥ ቃል የሚገኙኙበትና አንድን ጥልቅ ሀሳብ ለመግለጽ የሚያገለግል ዘይቤያዊ አነጋገር)

Job 24:20

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል

ማህጸን
ይህ የሚያመለክተው እናትን ነው። "እናት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ትሎች በደስታ ይመገቡታል
ይህ ማለት ይሞትና ትሎች በድኑን ይበሉታል ማለት ነው። "ትሎች በድኑን በመብላት ይረካሉ" ወይም "እርሱ ይሞታል ደግሞም በድኑ በትል ይበላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚህ ወዲያ መታሰቢያ አይኖረውም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ከዚህ በኋላ ማንም አያስታውሰውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ክፋት እንደ ዛፍ ይቆረጣል
እግዚአብሔር በክፉ ሰው ላይ የሚያደርሰው ጥፋት የተገለጸው ዛፍን ቆርጦ እንደሚጥል ተደርጎ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር ከፉ ሰውን የሚያጠፋው/ቆርጦ የሚጥለው ዛፍ እንደነበር አድርጎ ነው።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ክፉዎች ይበላሉ
ይህ ዘይቤ ክፉ ሰው ምን ያህል ስር የለሽ እንደሆነ ያሳያል። "የዱር አውሬ የሚያድነውን እንደሚገድል፣ ክፉ ሰውም እንደዚያው ጉዳት ይደርስበታል" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መሃኒቱ ወለደች
የዚያን ዘመን ሰዎች መሀን ሴት በእግዚአብሔር እንደ ተረገመች አድርገው ይቆጥሩ ነበር። ስለዚህም ይህ እጅግ እድለቢስ የሆነችን ሴት ይወክላል።

መበለት/ጋለሞታ
ባሏ የሞተባት ሴት

Job 24:22

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል

በእርሱ ሀይል
"ሀይሉን በመጠቀም" ወይም "ሀይለኛ በመሆኑ ምክንያት"

እርሱ ይነሳል ደግሞም በህይወት አያበረታቸውም
"በህይወት አያበረታቸውም" ማለት እግዚአብሔር በህይወት አያኖራቸውም/ ህይወት አይሰጣቸውም ማለት ነው። "እግዚአብሔር ይነሳል፣ ክፉዎች በህይወት እንዲኖሩ አቅም አይሰጣቸውም" ወይም "እግዚአብሔር ይነሳል ደግሞም በህይወት እንዳይኖሩ ይገድላቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን ዐይኖቹ በመንገዳቸው ላይ ነው
እዚህ ስፍራ "ዐይኖች" የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው። "ነገር ግን ሁልጊዜም የሚያደርጉትን ይመለከታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 24:24

አያያዥ ሃሳብ፡
ይህ የኢዮብን ንግግር ያጠቃልላል

ወደ ህግ ይቀርባሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር ወደ ህግ ያቀርባቸዋል" ወይም "እግዚአብሔር ያጠፋቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደሌሎቹ ሁሉ ይሰበሰባሉ
አንዳንድ ትርጉሞች በተለየ ጥንታዊ ጽሁፍ/ጥቅስ ላይ የተመሰረቱ ናቸው፣ "እንደ አረም ጠውልገው ይጠፋሉ" እንደሚለው። (የጽሁፍ/ጥቅስ ልዩነቶች የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱም እንደ ሌሎቹ ሁሉ ይሰበሰባሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሌሎች" የሚለው ምን እንደሚያመለክት በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር ሌሎች ክፉ ሰዎችን እንደሰበሰበ እነዚህንም ይሰበስባል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በምድር ገጽ ላይ እንደሚገኝ ቅንጣት እነርሱም ይቀረጣሉ
እነዚህ ክፉ ሰዎች በአዝመራ ወቅት እንደሚታጨድ ሰብል በተመሳሳይ መንገድ ይቆረጣሉ። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ገበሬ የእህልን አገዳ አናት እደሚቆርጥ እግዚአብሔር እነርሱን ይቆርጣቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

እንደዚህ ካልሆነ፣ የእኔን ሀሰተኝነት ማን ማረጋገጥ ይችላል፣ ማነድ ንግግሬን እርባና ቢስ ያደርገዋል?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት የክርክሩን እርግጠኝነት ለመግለጽ ነው። በውስጠ ታዋቂነት የቀረበው መልስ፡ "ማንም የለም" የሚል ነው። "ይህ እውነት ነው፣ ደግሞም ማንም እኔ ሀሰተኛ ሊያደርገኝ አይችልም፤ ማንም እኔ ስህተተኛ መሆኔን ማረጋገጥ አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ንግግሬን እርባና ቢስ የሚያደርግ
"የተናገርኩት ስህተት መሆኑን ማረጋገጥ የሚችል"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 25

1 ሹሐዊው በልዳዶስ ሲመልስ እንዲህ አለ፦ **2** ገዢነትና መፈራት የእርሱ ናቸው፤ በሰማይ ከፍታውም ስርአትን ያደርጋል። **3** በውኑ ለሠራዊቶቹ ቍጥር ፍጻሜ አላቸውን? ብርሃኑስ የማይወጣው በማን ላይ ነው? **4** እንግዲህ ሰው በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ጻድቅ ይሆናል፥ ከሴትስ የተወለደ እንዴት ንጹሕና በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት ይኖረዋል? **5** ጨረቃ እንኳ ለእርሱ ብሩህ አይደለም፥ ከዋክብትም በፊቱ ንጹሐን አይደሉም። **6** ይልቁንስ ትል የሆነ ሰው፥ የሰው ልጅ ምንኛ ያንስ!

Job 25:1

ሹሐዊው በልዳዶስ
ይህ የወንድ ስም በኢዮብ 2፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ

ገናንነት እና መፈራት የእርሱ ናቸው
እዚህ ስፍራ "እርሱ" የሚለው የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው። "ገናና/የበላይ" እና "ፍርሃት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች በግስ መልክ ሊጻፉ ይችላሉ። "እግዚአብሔር በሁሉም ላይ ይገዛል፣ እናም ሰዎች እርሱን ብቻ ይፍሩት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ በሚገኝበት በከፍታ ስፍራ በላይ በሰማይ ስርአትን አበጅቷል
"በላይ በሰማይ ሰላምን አድርጓል"

ለሰራዊቱ ቁጥር ልክ/መጠን አለውን?
በልዳዶስ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው እግዚአብሔር ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ አጉልቶ ለመግለጽ ነው። በውስጠ ታዋቂነት ለጥያቄው የተሰጠው ምላሽ "የለውም" የሚል ነው። ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ሰራዊት የሆኑተን መልአክትን ነው። "በእርሱ ሰራዊት ውስጥ የመላዕክቱ ቁጥር መጠን የለውም።" ወይም "የእርሱ ሰራዊቶች ማንምሊቆጥራቸው የማይቻለው እጅግ ብዙ ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

የእርሱ ብርሃን የማያበራው በማን ላይ ነው?
በልዳዶስ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው እግዚአብሔር ለሁሉም ሰው ብርሃን እንደሚሰጥ አጉልቶ ለመግለጽ ነው። "የእርሱ ብርሃን በላዩ የማያበራለት ማንም የለም" ወይም "እግዚአብሔር ብርሃኑ በሁሉም ላይ እንዲበራ አድርጓል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 25:4

አያያዥ ሃሳብ፡
በልዳዶ መናገሩን ቀጥሏል

ታዲያ ሰው እንዴት... በእግዚአብሔር ፊት...? ከ...የተወለደ ሰው እርሱ እንዴት?
እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች በአንድነት የዋሉት ሰው በእግዚአብሔር ፊት ፍጹም ሊሆን እንደማይችል አጉልቶ ለመግለጽ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

ሰው እንዴት በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ሆኖ ሊገኝ ይችላል?
በውስጠ ታዋቂነት የሚሰጠው ምላሽ አይችልም የሚል ነው። "አንድ ሰው በፍጹም በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ሊሆን አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ከ.. የተወለደ ... በእርሱ ፊት እንዴት ተቀባይነት ያገኛል?
በውስጠ ታዋቂነት የጥያቄው ምላሽ አይችልም የሚል ነው። "ከሴት የተወለደ ሰው በእግዚአብሔር ፊት በፍጹም ንጹህ ሊሆን ወይም ተቀባይነት ሊያገኝ አይችልም" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ከሴት የተወለደ እርሱ/ሰው
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሁሉንም ሰው ያካትታል። "ማንኛውም ሰው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ
እዚህ ስፍራ "እነሆ" የሚለው ቃል ተከትሎ በሚመጣው ላይ ትኩረት ይጨምራል። "በእርግጥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

በእርሱ ፊት ጨረቃ ብሩህነት የላትም
"ብሩህ" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል መልክ ሊገለጽ ይችላል። "በእግዚአብሔር ፊት ጨረቃ በቂ ብሩህነት የላትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ እይታ ከዋክብት ንጹሃን አይደሉም
እዚህ ስፍራ "ንጹህ" ማለት ፍጹም ማለት ነው። "እርሱ ከዋክብትን እንኳን ፍጹም አድርጎ አያያቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ትል የሆነ፣ የሰው ልጅ ... ሰው ምን ያህል ያንሳል
እነዚህ ሁለት መስመሮች ተመሳሳይ ነገር ይናገራሉ፤ በአንድነት ሆነው የሚያጎሉትም ሰው ፍጹም አለመሆኑን ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ትል ማን ነው
በልዳዶስ የሰው ልጆች እንደትሎች እርባና ቢስ መሆናቸውን ይገልጻል። "እንደ ትል እርባና ቢስ የሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ
ይህ ሰው የተገለጸበት ሌላ መንገድ ነው። "አንድ ሰው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 26

1 ኢዮብም ሲመልስ እንዲህ አለ፦ **2** ኃይል የሌለውን እንዴት ረዳኸው! ብርታት የሌለውን ክንድ ምንኛ አዳንኸው! **3** ጥበብስ የሌለውን እንዴት መከርኸው! መልካም እውቀትንስ ምንኛ ገለጥህለት! **4** እነዚህን ቃሎች በማን እርዳታ ተናገርህ? ስትናገርስ ከአንተ የወጣው መንፈስ የማን ይሆን? **5** በልዳዶ ስ መለሰ “ሙታን ሰዎች ከውሃዎች በታች የሚኖሩ፥ጥላዎ ቻቸውም ይንቀጠቀጣሉ። **6** ሲኦል በእግዚአብሔር ፊቱ ራቁትዋን ናት፥ ጥፋትም ቢሆን ራሱን መሸፈኛ የለውም። **7** ሰሜንን በባዶ ሕዋ ውስጥ ዘረጋው፥ ምድርንም እንዲያው ባዶ ላይ አንጠለጠላት። **8** ውሃዎችን በደመናዎች ውስጥ ያስራል፥ ደመናውም ከታች አልተቀደደችም። **9** የጨረቃን ፊት ይጋርዳል፥ ደመናውንም በላይዋ ይዘረጋበታል። **10** በብርሃንና በጨለማ መካከል እንዳለ መስመር፥ በውሃዎች ላይ ድንበርን አደረገ። **11** የሰማይ አዕማድ ተንቀጠቀጡ፥ ከተግሣጹም የተነሣ ደነገጡ። **12** በኃይሉ ባሕርን ጸጥ አደረገ፥ በማስተዋሉም ረዓብን መታ። **13** በእስትንፋሱ የሰማያትን ማዕበል ያነጻል፤ ሰማያትም ውበትን አገኙ፥ እጁም በራሪይቱን እባብ ወጋች። **14** እነዚህም ገና የመንገዱ መጀመሪያ ብቻ ናቸው፤ ከእርሱ የሰማነው ይህ ነገር ምንኛ ጥቂት ነው! የኃይሉን ነጐድጓድ ሊረዳ የሚችል ማን ነው?

Job 26:1

አቅም የሌለውን ክንድ ... እርሱን እንዴት ረዳኸው
በዚህ ዐረፍተ ሀሳብ፣ ኢዮብ በልዳዶስን እየነቀፈው/እየከሰሰው ነው። "እርሱን" የሚለው የሚያመለክተው ኢዮብን ነው። "ክንድ" የሚለው ቃል ደግሞ የሚወክለው በአጠቃላይ ሰውየውን ነው። "እኔ አቅም የለኝም፤ ደግሞም አንዳች ጥንካሬ የለኝም፣ ነገር ግን አንተ እንደረዳኸኝ ያህል ትሆናለህ፣ ነገር ግን በእርግጥ አንተ ምንም አልረዳኸኝም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምፀት እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

ጥበብ የሌለውን እንዴት መከርከው፤ እንዴት ጠቃሚነት ያለው እውቀት ሰጠው
ኢዮብ በልዳዶስ መልካም ምክር እና እውቀት እንዳልሰጠው እየተናገረ ነው። "አንተ የሚምልህ እኔ አንዳች ጥበብ እንሌለኝ እና አንተ እንደመከርከከኝ፤ ደግሞም ጥሩ ምክር እንደሰጠኸኝ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

ለእርሱ ተሰሚነት ያለው እውቀት ሰጠው
"ጥሩ ምክር ሰጠው"

እነዚህን ቃላት በማን እርዳታ ተናገርክ? አንተ...ይህ የማን መንፈስ ነበር?
በእነዚህ ጥያቄዎች ኢዮብ በበልዳዶስ ላይ መሳለቁን ይቀጥላል። ሁለቱም ጥያቄዎች ቃለ ምልልሳዊ ናቸው፤ ትርጉማቸውም በመሰረታዊነት አንድ ነው። በአንድነት የቀረቡት አንዱ ሀሳብ ሌላውን ለማጠንከር ነው። "እነዚህን ቃላት እንድትናገር እርዳታ ሳታገኝ አልቀረህም። ምናልባት እነዚህን ነገሮች እንድትናገር አንድ መንፈስ ሳይረዳህ አልቀረም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 26:5

የሞቱት
ይህ የሚያመለክተው የሞቱ ሰዎችን ነው። "እነዚያ የሞቱት" ወይም "የሞቱት መንፈስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

መንቀጥቀጥ
እግዚአብሔርን ስለፈሩ ተንቀጠቀጡ። ይህ ይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "በፍርሃት ተንቀጠቀጡ" ወይም "እግዚአብሔርን በመፍራት ተንቀጠቀጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከውሆች በታች የሚኖሩ
ይህ በፍርሃት የተንቀጠቀጡትን ሙታን ያመለክታል

በእነርሱ የሚኖሩ ሁሉ
ይህ የሚያመለክተው በውሆች ውስጥ የሚኖሩ የሞቱ ሰዎችን ነው

በእግዚአብሔር ፊት ሲኦል እርቃኑን ነው፤ ጥፋት ራሱ ምንም መሸፈኛ የለውም
ሲኦል የተገለጸው ሰው እንደሆነ ተደርጎ ነው። እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። "ራቁት" መሆን ወይም "መሸፈኛ" ማጣት አንዳች ነገር ለመደበቅ አለመቻል እና ሙሉ ለሙሉ መጋለጥ ማለት ነው። "ሲኦል በእግዚአብሔር ፊት የተራቆተ እንደሆነ ሁሉ፣ በሲኦል አንዳች ነገር እንደሌለ፣ የጥፋት ስፍራ እንደሆነ፣ ከእግዚአብሔር ፊት የራቀ/የተደበቀ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይልከቱ)

ጥፋት
ይህ የሲኦል ሌላው ስሙ ነው። "የጥፋት ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

Job 26:7

እርሱ ሰሜናዊውን ሰማይ በህዋው ላይ ዘረጋው
ሰሜናዊ ሰማይ የሚለው የሚወክለው፣ እግዚአብሔር እርሱ ከፈጠራቸው ፍጥረታት ጋር የሚኖርበትን ስፍራ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ በእነዚህ ከባድ ደመናዎች ውሆችን ቋጥሯል
ደመናዎች የተነጻጸሩት እግዚአብሔር የዝናብን ውሃ ከጠቀለለበት ትልቅ ብርድ ልብስ ጋር ነው። "እርሱ ውሆችን በከባድ ደመናዎች ጠቅልሏል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 26:9

ደግሞም በእርሷ ላይ ደመናዎችን ዘርግቷል
ይህ ሀረግ የጨረቃን ገጽ እንዴት እንደሸፈነ ይገልጻል። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። "ደመናዎቹን በእርሷ ፊት በመዘርጋት"

እርሱ በውሆች ገጽ ዙሪያ ክብ ዳርቻዎችን አበጅቷል
ይህ እግዚአብሔር በውቅያኖስ ላይ የዳርቻ ምልክት ያደረገ የሚመስልበትን ምድር ከሰማይ ጋር የገጠመ ሆኖ ስለሚታይበት ስለ አድማስ ይናገራል

Job 26:11

የሰማይ አምዶች ተናወጡ፣ በቁጣውም ራዱ
ሰዎች ሰማያት ወይም ሰማይ በአምዶች ላይ እንደቆሙ ያስባሉ። ኢዮብ ሰዎች እግዚአብሔር ሲቆጣ የሚርዱ አምዶች እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። "ሰማይን የተሸከሙ አምዶች እግዚአብሔር ሲቆጣቸው በፍርሃት ይናወጣሉ" ወይም "ሰማይን የተሸከሙ አምዶች እግዚአብሔር ሲገስጻቸው እንደሚርዱ ሰዎች ይናወጣሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ረአብን ይቆራርጣል/ይሰባብራል
"ረአብን ያጠፋል"

ረአብ
ይህ በውሃ ውስጥ የሚኖር አስፈሪ የሆነ አውሬ ስም ነው። ይህ በኢዮብ 9:13 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 26:13

በእስትንፋሱ ሰማያትን ያነጻል
"እስትንፋስ" የሚለው ስም "ተነፈሰ" ወይም "እፍ አለ" በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። ይህ ምሳሌ የሚወክለው እግዚአብሔር ደመናትን ለመበተን እግዚአብሔር ነፋሳትን እንደሚያነፍስ ነው። "እግዚአብሔር ሰማያት ንጹህ ይሆኑ ዘንድ ደመናዎችን ይበትናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እጆቹ በራሪውን አውሬ ወጋ
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር በእጆቹ ሰይፍ እንደ ያዘ እና እዚህ ስፍራ "የእርሱ እጅ" የሚለው ደግሞ የሚያመለክተው ያንን ሰይፍ ነው። "በሳው" መግደልን ያሳያል። "በሰይፉ በራሪ አውሬውን ወጋ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

በራሪው አውሬ
"አውሬው ከእርሱ ለማምለጥ በሞከረ ጊዜ።" ይህ በውሃ ውስጥ የሚኖረውን ረአብን ያሳያል። ኢዮብ 26:12 ይመልከቱ።

እነሆ፣ ይህ የመንገዱ ዘርፍ ነው
እዚህ ስፍራ "ዘርፍ" የሚወክለው ትልቅ ከሆነ ነገር ውስጥ አነስተኛ የሆነውን ክፈል ነው። "እነሆ፣ እነዚህ እግዚአብሔር የሰራቸው ነገሮች የሚያመለክቱት ከታላቅ ሀይሉ ውስጥ ጥቂቱን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከእርሱ ምንኛ ታናሽ ሹክሹክታውን እንሰደማለን!
ይህ እኛ ስለመኖሩ እንኳን ከነጭርሱ የማናውቀው የኢዮብን አድናቆት አጋኖ የሚገልጽ እግዚአብሔር ከሰራቸው ታላላቅ ነገሮች አንዱ ነው። እግዚአብሔር ያደረገውን ማየት የተገለጸው የእግዚአብሔርን ድምጽ እንደመስማት ተደርጎ ነው። "ይህ የእርሱን ጸጥ ያለ ማንሾካሾክ እንደመስማት ነው!" (ቃለ አጋኖ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 27

1 ኢዮብም መናገሩን ቀጠለ እንዲህም አለ፦ **2** ፍርዴን ያስወገደ ሕያው እግዚአብሔርን! ነፍሴንም መራራ ያደረገ ሁሉን የሚችል አምላክን! **3** ነፍሴ በእኔ ውስጥ፥ የእግዚአብሔርም እስትንፋስ በአፍንጫዬ እስካለ ድረስ፥ **4** በርግጥ ከንፈሬ ኃጢአትን አይናገርም፥ ምላሴም ሽንገላን አያወራም። **5** እናንተን ትክክል አድርጎ መቀበል ከእኔ ይራቅ፤ እስክሞት ድረስ ትክክለኛነቴን በፍጹም አልጥልም። **6** ጽድቄን አጥብቄ እይዛለሁ እርሱንም አለቅም፤ ከኖርኩባቸው ቀኖቼ ስለ አንዱም ህሊናዬ አይወቅሰኝም። **7** ጠላቴ እንደ በደለኛ ሰው ይሁን፥ በእኔ ላይም የሚነሣ እንደ ኃጢአተኛ ይሁን። **8** እግዚአብሔር ባጠፋውና ነፍሱን በለየ ጊዜ፥ አምላክ የሌለው ሰው ተስፋው ምንድር ነው? **9** መከራ በመጣበት ጊዜ፥ እግዚአብሔር ጩኸቱን ይሰማልን? **10** ሁሉንስ በሚችል አምላክ ደስ ይለዋልን? እግዚአብሔርንስ ሁልጊዜ ይጠራልን? **11** ስለ እግዚአብሔር እጅ አስተምራችኋለሁ፤ የሁሉን ቻይ አምላክን ሃሳብ አልሸሸግም። **12** እናንተ ሁላችሁ ይህንን አይታችሁ፤ ለምን ይህን ሁሉ ከንቱ ነገር ተናገራችሁ? **13** ይህ እግዚአብሔር ለክፉ ሰው ያቆየው እድል ፈንታ፥ ግፈኛም ሁሉን ከሚችል አምላክ የሚቀበለው ርስት ነው፤ **14** ልጆቹ ቢበዙ ለሰይፍ ይዳረጋሉ፤ ዘሩም በቂ እንጀራን አያገኝም። **15** የተረፉለትም በመቅሰፍት ምክንያት ይቀበራሉ፤ መበለቶቻቸውም አያለቅሱላቸውም። **16** አመጸኛ ሰው ብርን እንደ አፈር ቢከምር፥ ልብስንም እንደ ሸክላ ቢያከማች፥ **17** እርሱ ያከማቸውን ልብስ፥ ጻድቃን ይለብሱታል፤ ብሩንም ንጹሐን ሰዎች ይከፋፈሉታል። **18** ቤቱን እንደ ሸረሪት ይሠራል፥ ጠባቂም እንደሚቀልሰው ጎጆ ይመስላል። **19** ባለጠጋ ሆኖ ይተኛል፥ ነገር ግን አይዘልቅበትም፤ ዓይኑን በከፈተ ጊዜ፥ ሃብቱ ሁሉ የለም። **20** ድንጋጤ እንደ ጐርፍ ያገኘዋል፤ ማዕበልም በሌሊት ይወስደዋል። **21** የምሥራቅ ነፋስ ይወስደዋል፥ እርሱም ይለቃል፤ ከስፍራውም ይጠርገዋል። **22** ከነፋሱ ሊያመልጥ ይሞክራል፥ ነገርግን ሳያቋርጥ እየተወረወረ ይደርስበታል። **23** በመሳለቅም እጁን ያጨበጭብበታል፤ በፉጨትም ከስፍራው ያስወጣዋል።

Job 27:1

እንደ እግዚአብሔር ህልውና እርግጠኝነት ያለው
ይህ ሀረግ የሚያመለክተው ኢዮብ ማሃላ ማድረጉን ነው። ኢዮብ የእግዚአብሔርን ህልውና እርግጠኝነት የሚያነጻጽረው እርሱ ከተናገረው ነገር እርግጠኝነት ጋር ነው። ይህ በመሃላ ነገርን የማረጋገጥ መንገድ ነው። "ህያው እግዚአብሔርን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ፍትህን ከእኔ አራቀው
ፍትህ የተገለጸው ሊወሰድ ወይም ሊሰጥ እንደሚችል አካል/ቁስ ነው። መውሰድ የሚለው የሚገልጸው ለኢዮብ ተገቢውን ፍትህ መንፈግን ነው። "ለእኔ ፍትህ መስጠትን አልወደደም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ህይወቴን መራራ አደረገ
የኢዮብ "ህይወት" መራራ መሆን የሚወክለው ኢዮብ ለእግዚአብሔር ያለውን በቅሬታ የተሞላ ስሜት ነው። "ህይወቴ በቅሬታ የተሞላ እንዲሆን አደረገ" ወይም "በአግባብ ስላልተመለከተኝ በሀዘን ሞላኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ህይወቴ ገና በውስጤ እስካለች ድረስ
ይህ የሚያመለክተው በህይወት ለመኖር የቀረውን እድሜ ነው። "ህይወቴ በውስጤ በምትኖርበት በቀሪው ዘመን ሁሉ" ወይም "ህይወቴ በእኔ ውስጥ እስካለች ድረስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ህይወቴ ገና በውስጤ እስካለች ድረስ
"ህይወት" የሚለው ረቂቅ ስም "መኖር" በሚል ቅጽል ወይም "ኖረ" በሚል ግስ ሊገለጽ ይችላል። "በህይወት እስካለሁ ድረስ" ወይም "በህይወት እስከ ኖርኩ ድረስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር እስትንፋስ በአፍንጫዬ ውስጥ አለ
"እስትንፋስ... በአፍንጫዬ አለ" የሚለው የሚወክለው መተንፈስ መቻልን ነው። "እስትንፋስ ከእግዚአብሔር ዘንድ" የሚለው የሚገልጸው እግዚአብሔር እርሱን መተንፈስ ማስቻሉን ነው። "እግዚአብሔር እስትንፋስ ሰጠኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አፍንጫዎች
"አፍንጫ"

Job 27:4

ከንፈሮቼ ክፋትን አይናገሩም፣ ምላሶቼም ሽንገላን አያወሩም
እነዚህ ሁለት ሀረጋት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ በአንድነት የቀረቡት በዚህ አይነት መንገዶች እንደሚናገር በትኩረት ለመግለጽ ነው። "ከንፈሮቼ" እና "ምላሴ" የሚሉት የሚወክሉት ራሱን ኢዮብን ነው። "ክፋትን አልናገርም ወይም አላታልልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

ክፋትን መናገር... ማታለል/ሀሰትን መናገር
"ክፋት" እና "ማታለል" የሚሉት ረቂቅ ስሞች "በክፋት" እና "በማታለል" በሚሉት ቃላት ሊገለጽ ይችላል። "በክፋት መናገር... በማታለል መናገር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

መቼም ቢሆን እናንተ ሶስታችሁ ትክክል ናቸው ብዬ መናገር አልችልም
"መቼም ቢሆን ሶስታችሁ ትክክል ናችሁ ስል ከእናንተ ጋር አልስማማም"

እናንተ ሶስታችሁ ትክክል ናችሁ
"እናንተ" የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ነው። የሚያመለክተውም የኢዮብን ወዳጆች ነው። (አንተ የሚለው ቃል ልዩ ልዩ መልኮች)

ቅንነቴን አልጥልም
"በፍጹም ትሁት መሆኔን ልክድ አልችልም" ወይም "ሁልጊዜም ቢሆን ትሁት መሆኔን እናገራለሁ"

Job 27:6

ጽድቄን አጥብቄ እይዛለሁ
እዚህ ስፍራ "አጥብቄ እይዛለሁ" የሚለው አንድን ነገር አጥብቆ ይዞ መቀጠል ለሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "ጽድቅ" የሚለው ረቂቅ ስም "ጻድቅ" በሚለው ሊገለጽ ይችላል። "ጻድቅ ነኝ የሚለውን አጥብቄ ይዤ ለመቀጠል ወስኛለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

እንዲሄድ አልፈቅድም
እዚህ ስፍራ "እንዲሄድ አልፈቅድም" የሚለው አንድን ነገር ለመተው/ለማቆም አለመፍቀድን የሚገልጽ ዘይቤ ነው። "ጻድቅ መሆኔን መናገርን አላቆምም" ወይም "እንደዚያ ማለቴን አላቆምም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሀሳቤ አይዘልፈኝም
እዚህ ስፍራ "ሀሳቤ/አስተሳሰቤ" የሚለው የሚወክለው ኢዮብን ነው። "በሃሳቤ እንኳን፣ ራሴን አልዘልፍም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ጠላቶቼ እንዲህ ይሁኑ... በእኔ ላይ የሚነሱ እንዲህ ይሁኑ
በእነዚህ ቃላት የሚጀምሩት እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። በአንድነት የቀረቡት ይህ እንዲሆን ኢዮብ ያለውን ጠንካራ ፍላጎት በትኩረት ለመግለጽ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጠላቶቼ እንደ ኃጢአተኛ ሰው ይሁኑ
እርሱ ጠላቶቹ እንዴት እንደ ኃጢአተኛ ሰው እንዲሆኑ እንደሚፈልግ ግልጽ ተደርጎ ለገለጽ ይችላል። "ጠላቶቼ እንደ ኃጢአተኛ ሰው ይቀጡ" ወይም "እግዚአብሔር ኃጢአተኛ ሰዎችን እንደሚቀጣ ጠላቶቼን ይቅጣቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በእኔ ላይ የሚነሳ እንደ ኃጢአተኛ ሰው ይሁን
ኢዮብ ይህ ሰው/ጠላቱ/ እንዴት እንደ ኃጢአተኛ ሰው ሊሆን እንደሚፈልግ ግልጽ ተደርጎ ለገለጽ ይችላል። "በእኔ ላይ የሚነሳብኝ እርሱ ኃጢአተኛ ሰው እንደሚቀጣ ይቀጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በእኔ ላይ የሚነሳብኝ እርሱ
እዚህ ስፍራ "በእኔ ላይ የሚነሳብኝ" የሚለው ዘይቤያዊ አገላለጽ ሲሆን ትርጉሙ "የሚቃወመኝ" ማለት ነው። መላው ሀረግ የሚያመለክተው የኢዮብን ተቃዋሚዎች ነው። "እኔን የሚቃወመኝ እርሱ" ወይም "የእኔ ተቃዋሚ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 27:8

እግዚአብሔር ህይወቱን በሚሰበስባት/በሚወስድ ጊዜ... እግዚአብሔር የለሽ የሆነ ሰው ተስፋው ምንድን ነው?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው እንዲህ ያለው ሰው ምንም ተስፋ የለውም ለማለት ነው። ይህ ጥያቄ በቀላል ሀሳብ ሊገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር ነፍሱን ሲወስዳት... እግዚአብሔር የለሽ ለሆነ ሰው አንዳች ተስፋ የለውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ሲቆርጠው፣ እግዚአብሔር ህይወቱን ሲወስዳት
ሁለቱ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። "እግዚአብሔር እርሱን በሚቆርጠው እና ህይወቱን በሚወስድ ጊዜ" ወይም "እግዚአብሔር እርሱን ሲገድለው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱን ሲቆርጠው
የዚህ ዘይቤያዊ አነጋገር ትርጉም "እርሱን ሲገድለው" ወይም "እንዲሞት ሲያደርግ" ማለት ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ህይወቱን ሲወስድ
የዚህ ዘይቤያዊ አነጋገር ትርጉም "እርሱን ሲገድለው" ወይም "መኖሩ እንዲያበቃ ሲያደርግ" ማለት ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ችግር ደርሶበት ሲጮህ እግዚአብሔር ይሰማው ይሆን?
x

Job 27:11

እኔ አስተምርሃለሁ
በእነዚህ ሀረጎች "እናንተ" የሚለው በተገለጸ ጊዜ ሁሉ ብዙ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተውም የኢዮብን ሶስት ጎደኞች ነው።

የእግዚአብሔር እጅ
የእግዚአብሔር "እጅ" የሚያመለክተው ሀይሉን ነው። "የእግዚአብሔር ሀይል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉን ቻይ የሆነውን ሀሳብ አልሸሸግም
"ሀሳብ" የሚለው ረቂቅ ስም "አሰበ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "ሁሉን ቻይ የሆነውን ሀሳብ ከእናንተ አልደብቅም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ታዲያ ለምን ይህንን የማይረባ ነገር ሁሉ ትናገራላችሁ?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው ወዳጆቹ እንደዚህ ያሉ የማይረቡ ነገሮችን ስለተናገሩ ሊገስጻቸው ነው። ይህ ጥያቄ በቀላል ሀሳብ ሊተረጎም ይችላል። "እንዲህ ያለ የማይረባ ነገር መናገር አልነበረባችሁም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 27:13

ይህ ከእግዚአብሔር ዘንድ የኃጢአተኛ ሰው አድል ፈንታው/ድርሻ ነው።
"ይህ እግዚአብሔር ለኃጢአተኛ ሰው ያቀደለት ነው"

ሁሉን ቻይ ከሆነው ዘንድ የሚቀበለው የጨቆኝ ሰው/ሰውን የሚያሳዝን ሰው ድርሻው
እዚህ ስፍራ "የጨቆኝ/ ሰውን የሚያሳዝን ሰው ድርሻው" የሚለው በጨቆኝ ሰው/ሰውን በሚያሳዝን ሰው ላይ የሚደርሰውን ነገር የሚገልጽ ዘይቤ ነው። በዚህ ሰው ላይ እግዚአብሔር የሚያደርገው ነበር የተገለጸው እግዚአብሔር ለእርሱ የሚሰጠው ነገር ተደርጎ ነው። "ሁሉን ቻይ የሆነው በጨቆኝ ሰው/ ሰውን በሚያሳዝን ሰው ላይ የሚያደርገው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለሰይፍ ይሆናል
እዚህ ስፍራ "ለሰይፍ" የሚወክለው በጦርነት መሞትን ነው። "በጦርነት ይሞታሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 27:15

ከእርሱ ልጆች በህይወት የሚኖሩት ይህ የኃጢአተኛውን ሰው ልጆች ያመለክታል። ይህ ይበልጥ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "ክፉ የሆኑት
አባቶቻቸው ከሞቱ በኋላ የሞኖሩት ልጆቻቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በመቅሰፍት ይቀበራሉ
እዚህ ስፍራ "ይቀበራሉ" የሚለው የሚወክለው ሞትን ነው። "በመቅሰፍት ይሞታሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የእነርሱ መበለቶች...እነርሱ
"የእነርሱ" እና "እነርሱ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክተው "ከእርሱ በኋላ የሚኖሩትን" ይኸውም የክፉ ሰውን ልጆች ነው።

ብር እንደ አፈር መከመር
እዚህ ስፍራ "መከመር" የሚለው "ብዙ መሰብሰብ" ለሚለው ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ኢዮብ ብር ማግኘት አፈር የማግኘት ያህል እንደሚቀላቸው ይናገራል። "የብር ቁልል ይሰበስባሉ"

ወይም "አፈር መሰብሰብ የሚችሉትን ያህል በቀላሉ ብር ይሰበስባሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ልብስ እንደ ሸክላ ይከምራሉ
እዚህ ስፍራ "መከመር" የሚለው "ብዙ መሰብሰብ" ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ኢዮብ ልብስ ማግኘት አፈር የማግኘት ያህል እንደሚቀላቸው ይናገራል። "የልብስ ቁልል ይሰበስባሉ" ወይም "አፈር መሰብሰብ የሚችሉትን ያህል በቀላሉ ልብስ ይሰበስባሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 27:18

ቤቱን እንደ ሸረሪት ይሰራል/ይገነባል
"ከሸረሪት" በኋላ "ድሯን ማድራት" የሚለው ሀረግ በግልጽ የሚታወቅ ነገር ነው። ይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ሸረሪት ድሯን እንደምታደራ ኃጢአተኛው ቤቱን ይሰራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

ቤቱን እንደ ሸረሪት ይሰራል
የሸረሪት ድር በቀላሉ ይበጣጠሳል፣ ደግሞም በቀላሉ ይጠፋል። "ሸረሪት ድሯን እንደምትሰራ ቤቱን ይገነባል" ወይም "የሸረሪት ድር በቀላሉ እንደሚበጣጠስ፣ ቤቱን እንደዚያው ይገነባል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ጎጆ
ጎጆ በጣም ጠንካራ ያልሆነ ጊዜያዊ ቤት ነው። "እንደ ጊዜያዊ ጎጆ/ድንኳን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በባለጸጋ አልጋ ይተኛል
"በመኝታው ሲጋደም ባለጸጋ ነው።" ይህ የሚያመለክተው በምሽት በአልጋው ላይ መጋደሙን እና መተኛቱን ነው።

ነገር ግን ይህንን ማድረጉን አይቀጥልም
"ነገር ግን በባለጸጋ አልጋ ላይ መተኛቱን አይቀጥልም" ወይም "በአልጋው ላይ በሚተኛበት ጊዜ ባለጸጋነቱ አይቀጥልም/ከመኝታው ሳይወርድ ባለጸጋነቱ ያበቃል"

ዐይኖቹን ሲከፍት
ዐይኖቹን ሲከፍት የሚለው የሚወክለው በጠዋት ሲነሳ የሚለውን ነው። "ከእንቅልፉ ሲነቃ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ያለውን ሁሉ አጥቶታል/ያለው ሁሉ ሄዷል
"ሀብቱ ሁሉ ጠፍቷል" ወይም "ሁሉም ነገር ከእርሱ ርቋል"

Job 27:20

ፍርሃት ውጦታል
እዚህ ስፍራ "እርሱን ውጦታል" የሚለው የሚወክለው በድንገት የሚደርስበትን ነው። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች "ጭንቀት/መሸበር" ለተከታዮቹ ሀሳቦች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። 1) ሰዎች እንዲፈሩ የሚያደርጉ ነገሮች። "በድንገት በኃጢአተኛው ላይ የሚደርሱ ነገሮች" ወይም 2) ፍርሃት። "በድንገት ፍርሃት ዋጠው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እንደ ውኖች
"ውኖች" የሚለው ቃል ጎርፍን ያመለክታል። ጎርፍ ሰዎች ሳይጠብቁት በድንገት ሊደርስ ይችላል፤ ደግሞም አደገኛ እና አስፈሪም ነው። "እንደ ጎርፍ" ወይም "በድንገት እንደሚሞላ ደራሽ ውሃ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አውሎ ነፋስ ይወስደዋል
"ሃይለኛ ነፋስ ጠርጎ ይወስደዋል"

ከስፍራው ይጠርገዋል
ኢዮብ ኃጢአተኛውን ሰው ከቤቱ ጠርጎ የሚወስደውን ነፋስ የገለጸው፣ ነፋስን እንደ ሰው በመግለጽ እና አቧራን ከቤት ከሚያስወግድ መጥረጊያ ጋር በማነጻጸር ነው። "ሴት ቆሻሻን በመጥረጊያ ጠርጋ እንደምታስወጣ ነፋስ ከስፍራው ይጠርገዋል" ወይም "ነፋስ በቀላሉ ከስፍራው ይጠርገዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ስፍራው
"ቤቱ"

Job 27:22

አጠቃላይ መረጃ:
በኢዮብ 27፡ 22-23 ላይ ኢዮብ ስለ ነፋስ የሚናገረው ክፉዎችን እንደሚያጠቃ ሰው አድርጎ ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በኃጢአተኛው ላይ ይወድቅበታል
" በኃጢአተኛው ላይ ይወድቅበታል" የሚለው ሀረግ የሚወክለው ነፋሱ በኃጢአተኛው ላይ አደጋ እንደሚጥል ሰው ሆኖ በሃይል ይነፍስበታል ማለትን ነው። "አደጋ እንደሚጥል ሰው በእርሱ ላይ በሃይል ይነፍስበታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእጁ አምልጦ ለመብረር ይሞክራል
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚወክለው ነፋስ በክፉ ሰው ላይ ያለውን ሀይል ወይም አቅም ነው። "ከእርሱ ቁጥጥር ለማምለጥ ይሞክራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

በፌዝ እጆቹን ያጨበጭብበታል
እጆችን ማጨብጨብ በሌላ ሰው ላይ የማፌዝ መንገድ ነው። እዚህ ስፍራ ይህ የሚወክለው ነፋስ ከፍ ያለ ድምጽ ማሰማቱን/መስጠቱን ነው። "በእርሱ ላይ ለማፌዝ አንድ ሰው እጆቹን እንደሚያጨበጭብ ከፍ ያለ ድምጽ ያወጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 28

1 በእርግጥ ብር የሚወጣበት፥ ወርቅም የሚነጠርበት ስፍራ አለ። **2** ብረት ከመሬት ውስጥ ይወሰዳል፥ መዳብም ከድንጋይ ቀልጦ ይወጣል። **3** ሰው የጨለማ መጨረሻ ድረስ ይወርዳል፤ በጨለማና ባስፈሪ ስፍራ ውድ ድንጋይ ይፈላልጋል። **4** ሰው ከሚኖርበት ርቆ መውረጃ ይቈፍራሉ፤ ከሁሉ እግር በተረሳ ስፍራ፥ ከሰዎችም ሩቅ ሆኖ እየተንጠላጠለ ይወዛወዛል። **5** ከምድር እንጀራ ቢገኝም፤ ከታችኛው ክፍል ግን እሳት ይገላበጣል። **6** ድንጋይዋ ሰንፔር የሚገኝበት ስፍራ ነው፥ አፈሯም ወርቅን ይዟል። **7** ያን መንገድ ጭልፊት አያውቀውም፥ የአሞራም ዓይን አላየውም። **8** ኩሩ እንስሶች ይህን መንገድ አልሄዱበትም፥ አስፈሪው አንበሳም በዚያ አላለፈም። **9** ሰው ቡላድ ድንጋይ ላይ እጁን ይጭናል፥ ተራራዎችንም ከሥራቸው ይገለብጣል። **10** በድንጋይ ውስጥ መንዶልዶያን ፈልፍሎ ይሰራል፤ በዚያም ዓይኑ የከበሩ ነገሮችን ሁሉ ያያል። **11** ፈሳሹም እንዳያልፉ ይገድባል፤ በዚያም የተሰወሩትን ወደ ብርሃን ያወጣቸዋል። **12** ጥበብ ግን የት ትገኛለች? የማስተዋልስ ስፍራ ወዴት ነው? **13** ሰው ዋጋዋን አላወቀም በሕያዋንም ምድር አትገኝም። **14** ከምድር ጥልቅ ያለ ውሃ፦ "በእኔ ውስጥ የለችም' አለ፤ ባሕርም፦ "እኔ ጋር የለችም" አለ። **15** ወርቅ ሊገዛት አይችልም፥ ዋጋዋም በብር አይመዘንም። **16** በኦፊር ወርቅ፥ በከበረም መረግድና በሰንፔር አትገመትም። **17** ወርቅና ብርሌ አይተካከሉአትም፥ በነጠረ ወርቅ ጌጥም አትለወጥም። **18** ዛጐልና አልማዝ ከቁጥር አይገቡም። በርግጥ የጥበብ ዋጋ ከቀይ ዕንቍ ይበልጣል። **19** የኢትዮጵያ ቶጳዝዮን አይስተካከላትም፥ በንጹህ ወርቅም አትገመትም። **20** ታዲያ ጥበብ ከወዴት ትመጣለች? የማስተዋልስ ስፍራ የት ነው? **21** ጥበብ ሕይወት ካላቸው ነገሮች ሁሉ ዓይን ተሰውራለች፥ ከሰማይ ወፎችም ተሸሽጋለች። **22** ጥፋትና ሞት፦ “ወሬዋን ብቻ በጆሮቻችን ሰምተናል” አሉ። **23** እግዚአብሔር ወደ እርሷ የሚወስደውን መንገድ ያስተውላል፥ስፍራዋንም ያውቃል። **24** ምክንያቱም እርሱ የምድርን ዳርቻ፥ ከሰማይም በታች ያለውን ሁሉ ያያል። **25** እርሱ አስቀድሞ ለነፋስ ሃይል መጠንን አደረገ፥ ውኖችንም በስፍር ሰፈረ፥ **26** እርሱ ለዝናብ ሥርዓትን፥ ለነጐድጓድ መብረቅም መንገድን አደረገ፥ **27** በዚያን ጊዜ ጥበብን አያት፥ ገለጣትም አጸናት፥ በርግጥም መረመራት። **28** ለሰዎችም፦ እነሆ፥ “እግዚአብሔርን መፍራት ጥበብ ነው፤ ከክፋትም መራቅ ማስተዋል ነው” አለ።

Job 28:1

የማዕድን ስፍራ
ይህ ሰዎች ከመሬት የተለያዩ አለቶችን የሚያወጡበት ስፍራ ነው። አለቶች በውስጣቸው ብረት አላቸው።

ማጣራት
ይህ በብረት ውስጥ የሚገኘውን አፈር ለማጣራት ብረትን የማቅለጥ ሂደት ነው

ብረት ከአፈር ውስጥ ይወጣል
ይህ በአድርጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች ብረትን ከመሬት ያወጣሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድርጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

መዳብ ከማዕድን ድንጋይ ቀልጦ ይወጣል
ይህ በአድርጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች መዳብን ከመሬት ያወጣሉ" ወይም "ሰዎች መዳብን ለማውጣት ድንጋይ ያቃጥላሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድርጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

መዳብ
ጠቃሚ የሆነ ቀይ ቡኒ ቀለም ያለው ብረት

ማቅለጥ
ይህ በአለቶች ውስጥ የሚገኘውን ብረት ለማግኘት ሲባል አለቶችን የማቃጠል ሂደት ነው

Job 28:3

ሰው ለጨለማ ዳርቻ ያበጅለታል
እዚህ ስፍራ "ለጨለማ ዳርቻ ማበጀት/ጨለማ ማስወገድ" የሚለው የሚወክለው በጨለማ ማብራትን ነው። ሰዎች ብርሃን ለማግኘት ፋኖስን ወይም ችቦን ይጠቀማሉ። "ሰው ወደ ጨለማ ስፍራ ብርሃን ይዞ ይሄዳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሩቅ ወደሆነው ስፍራ
"ወደ ማዕድን ቁፋሮው ሩቅ ስፍራ"

ድብቅነት...ድቅድቅ ጨለማ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በአንድነት አገልግሎት ላይ የዋሉት ማዕድን የሚገኝበት ስፍራ እጅግ ጨለማ መሆኑን ለመግለጽ ነው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

የጉድጓድ መግቢያ/አፍ
ወደ መሬት ወደ አለት ውስጥ የተቆፈረ ጠባብ ጥልቅ ጉድጓድ። ሰዎች ማዕድን ለማውጣት ወደ ጉድጓዱ ውስጠኛ ክፍል ይገባሉ።

በማንም እግር ያልታወሱ ስፍራዎች
እግር የተገለጸው ማስታወስ እንደሚችል ሰው ተደርጎ ነው። "ሰዎች ያልሄዱባቸው ስፍራዎች" ወይም "ማንም ተራምዶባቸው የማያውቁ ስፍራዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ከሰዎች ርቆ ይቆያል
እንዴት እና የት እንደ ራቀበግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "በጉድጓዱ ውስጥ በገመድ ታስሮ ከሰዎች ርቆ ያቆያል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 28:5

ከመሬት እንጀራ ይወጣል
እዚህ ስፍራ "እንጀራ" የሚወክለው በአጠቃላይ ምግብን ነው። እንጀራ ከመሬት ይወጣል የሚለው እንጀራ ከመሬት ይበቅላል የሚል ዘይቤ ነው። "እንጀራ የሚወጣበት መሬት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

በእሳት እንደሆነ ነገር ከስር ተገልብጧል
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) አለቶችን ለመሰባበር ሰዎች ከምድር በታች እሳት አንድደዋል። "መአድን ቆፋሪዎች ባነደዱት እሳት ከምድር በታች ያለው ተንኮታኩቷል" ወይም 2) "ተገልብጧል" የሚለው ተለውጧል ለሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "ከስር በእሳት የጠፋ ያህል በከፍተኛ ደረጃ ተንኮታኩቷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እርሷ ተገልብጧለች.. የእርሷ አለቶች/ደንጋይ ... የእርሷ አብዋራ/አፈር
"እርሷ" የሚለው የሚያመለክተው መሬትን ነው።

ሰንፔር
በጥቂቱ ብቻ የሚገኝ ዋጋው የከበረ ሰማያዊ ቀለም ያለው ድንጋይ

Job 28:7

የትኛውም አዳኝ ወፍ ወደዚያ የሚወስደውን መንገድ አያውቅም... አሊያም የጭልፊት ዐይንም አላየውም
እነዚህ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። "የትኛውም አዳኝ ወፍ ወይም ጭልፊት ወደ ማዕድን ስፍራ የሚወስደውን መንገድ አይቶት አያውቅም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አዳኝ ወፍ
"ሌሎች እንስሳትን የሚበላ ወፍ"

ጭልፊት
ይህ "አሞራ" ተብሎም ሊተረጎም ይችላል። እነዚህ ሁለቱም የሚያድኑ እና ሌሎች እንስሳት የሚመገቡ ወፎች ናቸው። ይህንን በባህላችሁ ውስጥ በሚገኝ አነስተኛ ወፍ ተክታችሁ መተረጎም ትችላላችሁ።

ኩሩዎቹ እንስሳት በዚህ መንገድ አልሄዱም... አሊያም ሀይለኞቹ አንበሶች በዚያ አላለፉም
እነዚህ ሀረጎችም ደግሞ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ኩሩዎቹ እንስሳት
ይህ የሚያመለክተው በጣም ጠንካራ የሆኑ የዱር አራዊትን ነው

Job 28:9

በባልጩት/ጠንካራ አለቶች ላይ እጆቹን ያሳርፋል
ይህ የሚወክለው አለቶችን መሰባበርን ነው። "ጠንካራ አለት መቆፈር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ጠንካራ አለት
"ጠጣር አለት"

እርሱ ተራሮችን ከስራቸው ይገለብጣል
ተራሮችን እና ከስራቸው የሚገኘውን መሬት መቆፈር የሚለው አረምን ወይም ዛፎችን ከስራቸው መንቀል ለሚለው ዘይቤያዊ አገላለጽ ሲሆን ማዕድኖችን ከመሬት ቆፍሮ ማውጣትን አጋኖ ለመግለጽ የዋለ ነው። "እርሱ ስራቸውን ቆፍሮ በማውጣት ተራሮችን ከስራቸው ገለበጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት እንዲሁም ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

የእርሱ ዐይኖች
እዚህ ስፍራ "የእርሱ ዐይኖች" የሚለው የሚወክለው እርሱን ነው። "እርሱ ይመለከታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ጅረቶች እንዳይፈሱ/እንዳይወርዱ ያግድ ነበር
እዚህ ስፍራ " ጅረቶች እንዳይወርዱ" የሚለው ጅረቶችን ማገድ ወይም እንዳይፈሱ መከልከል ማለት ነው። "እርሱ ጅረቶች እንዳይወርዱ ያግዳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በዚያ የተደበቀው
ይህ የሚያመለክተው ሰዎች ከምድር በታች ወይም ከውሃ ስር በመሆናቸው ምክንያት ሊመለከቱ የማይችሉትን ነገር ነው።

Job 28:12

አጠቃላይ መረጃ:
በኢዮብ 28:12-28 እውቀት እና ግንዛቤ ማግኘት በአንድ ስፍራ የሚገኙ እና ሰዎች የሚፈልጓቸው ውድ ሀብቶች እንደሆኑ ተደርጎ ተገልጽዋል። እውቀት እና ግንዛቤ ማግኘት የሚወክሉት ብልህ መሆንንና ነገሮችን በሚገባ መረዳትን መማርን ነው። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጥበብ ከወዴት ይገኛል? የመረዳትስ ስፍራው የት ነው?
እነዚህ ጥያቄዎች ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው፤ የዋሉትም ጥበብን እና መረዳትን ማግኘት በጣም አስቸጋሪ መሆኑን ለማሳየት ነው። "ጥበብን እና መረዳትን ማግኘት በጣም አስቸጋሪ ነው።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

ጥበብ ከወዴት ይገኛል?የመረዳትስ ስፍራው የት ነው?
ብልህ መሆን እና ግንዛቤ ማግኘት የተገለጹት ጥበብን እና መረዳትን እንደ ማግኘት ተደርጎ ነው። "ሰዎች ብልህ የሚሆኑት እንዴት ነው? ሰዎች ነገሮችን በሚገባ መረዳት የሚችሉት እንዴት ነው?" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሰው ዋጋዋን አያውቅም
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ጥበብ የተገለጸችው ሰዎች ሊገዟት እንደሚችሉት ነገር ተደርጋ ነው። "ሰዎች የሚረባው ምን እንደሆነ አያውቁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) "ዋጋ" ተብሎ የተተረጎመው ቃል "ስፍራ" ማለት ነው። "ሰዎች የት እንደምትገኝ አያውቁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በህያዋን ምድር አትገኝም
"እናም በህያዋን ምድር አትገኝም።" የህያዋን ምድር" የሚለው የሚያመለክተው ሰዎች የሚኖሩበትን ይህንን ምድር ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እናም ማንም በዚህ ምድር ጥበብን ሊያገኝ አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥልቅ ውኖች... 'በእኔ ውስጥ አትገኝም' ይላሉ፤ ባህር 'በእኔ ውስጥ አትገኝም' ይላል።
ጥልቅ ውኖች እና ባህር የቀረቡት መናገር እንደሚችል ሰው ተደርገው ነው። "ጥበብ ከምድር በታች ባለው በጥልቅ ውኖች ውስጥ አትገኝም፣ አሊያም በባህር ውስጥ አይደለችም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 28:15

በወርቅ አትገኝም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። ይህ የሚያመለክተው ጥበብ ከወርቅ ይልቅ ጠቃሚ እንደሆነ ነው። "ሰዎች እውቀትን በወርቅ መግዛት አይችሉም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ብር ዋጋዋ ተደርጎ ሊመዘንላት አይችልም
ይህ የሚያመለክተው ጥበብ ከብር ይልቅ ጠቃሚነት እንዳላት ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች ለእውቀት በቂየሆነ ብር መክፈል/መመዘን አይቻላቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ዋጋዋ በሰንፔር... ሊመዘን/ሊለካ አይችልም
ይህ የሚያመለክተው ጥበብ ከኦፌር ወርቅ፣ ከከበረ መረግድና ሰንፔርና የበለጠ ዋጋ እንዳላት ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ኦፌር
ይህ የተጣራ ወርቅ የሚገኝበት ምድር ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

መረግድ የከበረ ድንጋይ
ጥቁር የከበረ ድንጋይ

ሰንፔር
ሰማያዊ የከበረ ድንጋይ

ወርቅ እና አብረቅራቂ መአድን/ብርሌ የእርሷን ያህል ዋጋ የላቸውም
ይህ የሚያመለክተው ጥበብ ከወርቅ እና ከከበረ ድንጋይ/አብረቅራቂ መአድን እጅግ እንደምትበልጥ ነው

የከበረ ድንጋይአብረቅራቂ መአድን/ብርሌ
ዋጋ ያለው የከበረ እንደ ብርጭቆ ንጹህ ቀለም ያለው ድንጋይ

በጠራ ወርቅ በተሰራ ጌጥም ቢሆን ልትለወጥ አትችልም
"እናም በጠራ ወርቅ በተሰራ ጌጥ አትለወጥም።" ይህ የሚያመለክተው ጥበብ በጠራ ወርቅ ከተሰራ ጌጥ የሚበልጥ ዋጋ ያላት መሆኑን ነው።

መለወጥ/መቀየር
"መነገድ"

Job 28:18

ዛጎል፣ ኢያስፔር እና አልማዝ ከእርሷ ጋር አይስተካከሉም
"እርሷን ከዛጎል እና ሰንፔር ጋር ማነጻጸር አይቻልም" ይህ የሚያመለክተው ጥበብ ከዛጎል እና ኢያስፔር እጅግ እንደምትበልጥ ነው፤ ስለዚህም ኢዮብ ስለነዚህ ነገሮች መናገር አላስፈለገውም። "ስለ ዛጎል ወይም ኢያስፔር መናገር አያስፈልገኝም" ወይም "ዛጎል፣ ኢያስፔር እና አልማዝ ከጥበብ ጋር ሲነጻጸሩ እርባና እንደሌለው ነገር ይቆጠራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ዛጎል
ይህ ውብ የሆነ፣ ጠንካራ እና በውቅያኖስ ዳርቻ የሚገኝ ቁስ ነው።

ኦፌር...ቀይ እንቁ...ቶጳዝዮን
እነዚህ የከበሩ ድንጋዮች/ማዕድናት ናቸው

የኩሽ ቶጳዝዮን አይስተካከሏትም
ይህሚያመለክተው ጥበብ ምርጥ ከተባለው ቶጳዝዮን እንደምትሻል ነው

ከንጹህ ወርቅ ጋርም ልትመዘን/ዋጋዋ ሊተመን አይችልም
"እናም ጥበብ በንጹህ ወርቅ ዋጋዋ ሊለካ አይችልም።" ይህ ጥበብ ከንጹህ ወርቅ እጅግ እንደምትበልጥ ያሳያል።

Job 28:20

ታዲያ ጥበብ ከወዴት ትገኛለች? የእውቀትስ ስፍራዋ የት ነው?
ኢዮብ እነዚህን ጥያቄዎች የሚጠቀመው ሰዎች ጥበብን እና እውቀትን ሰዎች ከየት እንደሚያገኙ ለመናገር ነው። "ጥበብ ከየት እንደምትገኝ እነግራችኋለሁ ደግሞም እውቀት ከወዴት እንደሆነች አስታውቃችኋል።" ወይም "እንዴት ጥበበኛ መሆን እንደሚቻል እንደዚሁም ደግሞ እንዴት ነገሮችን መረዳት እንደሚቻል እነግራችኋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ታዲያ ጥበብ ከወዴት ትገኛለች
ጥበብ የተገለጸችው በአንድ ስፍራ እንደሆነችና ወደ ሰዎች እንደምትመጣ ተደርጎ ነው። የእርሷ መምጣት የሚወክለው ሰዎች ብልህ ሊሆኑ እንደሚችሉ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የመረዳት/እውቀት ስፍራዋ የት ነው
መረዳት/እውቀት የተገለጸችው በአንድ ስፍራ እንደምትገኝ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጥብብ ከህያዋን ዐይኖች ሁሉ ተሰውራለች
ይህ ማለት ህያዋን ነገሮች ጥበብን ማየት አልቻሉም ማለት። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ማናቸውም ህያው ነገር ጥበብን ማየት/ ማግኘት አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከሰማይ ወፎች ተደብቃ ተቀምጣለች
ይህ ማለት ወፎች ጥበብን ማየት አይችሉም ማለት ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በሰማያት የሚበሩ ወፎች እንኳን ጥበብን ማየት አይችሉም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥፋት እና ሞት እንዲህ ይላሉ
እዚህ ስፍራ "ጥፋት" እና "ሞት" መናገር የሚችሉ ነገሮች ተደርገው ቀርበዋል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 28:23

እግዚአብሔር የእርሷን መንገድ ያውቃል፤ እርሱ ስፍራዋን ያውቃል
ጥበብ የተገለጸችው በአንድ ስፍራ እንደምትገኝ ተደርጎ ነው። "እግዚአብሔር ጥበብ እንዴት እንደምትገኝ ያውቃል። እርሱ ጥበብ የት እንዳለች ያውቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የምድራ ዳርቻ
"የምድር የመጨረሻው ሩቅ ስፍራ"

ውኆችን ይሰፍራል
ይህ የሚገልጸው እግዚአብሔር በእያንዳንዱ ስፍራ መገኘት ያለበትን የውሃ መጠን የወሰነ መሆኑን ነው። ይህ ለመወሰን የሚያመለክተው አማራጭ ትርጉም 1) በእያንዳንዱ ደመና ምን ያህል ዝናብ መገኘት እንዳለበት ወይም 2) በእያንዳንዱ ባህር የሚገኘውን ውሃ መጠን። "በእያንዳንዱ ስፍራ የሚኖረውን ውሃ ወስኗል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 28:26

ለመብረቅ መንገድን
"እርሱ መብረቅ እንዴት መሰማት እንዳለበት ውስኗል" ወይም "እርሱ የመብረቅን መሄዳ ወስኗል"

እነሆ፣ እግዚአብሔርን መፍራት - ይህ ጥበብ ነው።
"ፍርሃት" የሚለው ረቂቅ ስም "ፈራ" ወይም "አከበረ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "ጥበብ" የሚለው ረቂቅ ስም "ጠቢብ" በሚለው ቃል ሊገለጽ ይችላል። "አድምጡ፣ ጌታን ብትፈሩ ጥበበኛ ትሆናላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ከክፉ መራቅ ጥበብ/መረዳት ነው
እዚህ ስፍራ "ከክፉ መለየት" ክፉ ነገሮችን ለማድረግ አሻፈረኝ ማለት ነው። "መረዳት" የሚለው ረቂቅ ስም "ተረዳ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል።

"ክፉ ማድረግን ባትፈቅድ፣ ከዚያ በኋላ ብዙ ነገሮችን ትገነዘባለህ" በሚለው
ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 29

1 ኢዮብም መናገሩን ቀጠለ፥ እንዲህም አለ፦ **2** እግዚአብሔር ይጠብቀኝ እንደ ነበረው ጊዜ፥ እንዳለፉት ወራት ምነው በሆንሁ! **3** መብራቱ በራሴ ላይ እንደበራበት ወቅት፥ በጨለማ ውስጥ በብርሃኑ አልፌ እንደሄድሁበት ጊዜ፥ **4** ቀኖቼ ወደ ሙላታቸው በደረሱ ጊዜ፥ የእግዚአብሔር ወዳጅነት በድንኳኔ በነበረ ጊዜ፥ **5** ሁሉን የሚችል አምላክ ገና ከእኔ ጋር በነበረ ጊዜ፥ ልጆቼም በዙሪያዬ እያሉ፥ **6** መንገዴ በቅቤ ይታጠብ በነበረ ጊዜ፥ ድንጋዩ የዘይት ፈሳሽ ያፈስስልኝ በነበረ ጊዜ። **7** ወደ ከተማው በር በወጣሁ ጊዜ፥ በአደባባዩ መሃል ወንበሬ ላይ በተቀመጥሁ ጊዜ፥ **8** ወጣቶች አይተው በአክብሮት ገለል አሉ፥ ሽማግሌዎችም ተነሥተው ቆሙ። **9** በመጣሁ ጊዜ ልኡላን ከመናገር ይቆጠባሉ፥ እጃቸውንም በአፋቸው ላይ ይጭኑ ነበር። **10** የብልሆች ድምፅ ጸጥ ይል፤ ምላሳቸውም በላንቃቸው ተጣበቀች። **11** በጆሮአቸው ከሰሙኝ በኋላ ይባርኩኝ ነበር፥` በአይናቸው ዓይተው ያሞግሱኝና ይመሰክሩልኝ ነበር፤ **12** ምክንያቱም የሚጮኽውን ችግረኛ፥ ድሀ አደጉንና ረዳት የሌላቸውን አድን ነበረና። **13** ሊጠፋ የቀረበ በረከት ወደ እኔ ይመጣል፤ ባል የሞተባትንም ሴት ልብ በደስታ እንድትዘምር አደርግ ነበርና። **14** ጽድቅን ለበስሁ እርስዋም ለበሰችኝ፤ ፍትሃዊነቴም እንደ መጐናጸፊያዬና ጥምጣሜ ነበረ። **15** ለአይነ ስውራን ዓይናቸው፥ መራመድ ለማይችሉም ሰዎች እግር ነበርሁ። **16** ለችግረኞች አባት ነበርሁ፤ የማላውቀውንም ሰው ሙግት እመረምር ነበር። **17** የኃጢአተኛውን መንጋጋ ሰበርሁ፥ የያዘውንም ከጥርሱ ውስጥ አስጣልሁ። **18** እንዲህም አልሁ፦ “በጎጆዬ ሆኜ እሞታለሁ፥ ቀኖቼን እንደ አሸዋ አበዛለሁ፤ **19** ሥሮቼ ወደ ውኃ ይሰራጫሉ፥ ጠልም ምሽቱን ሁሉ በቅርንጫፎቼ ላይ ያድራል፤ **20** በእኔ ዘንድ ያለው ክብር ሁልጊዜ ትኩስ ነው፥ በእጄ ያለው የብርታቴ ቀስት አዲስ ነው። **21** ሰዎች እኔን ለመስማት በትዕግሥት ተጠባበቁ፥ ምክሬንም ለማዳመጥ በጸጥታ ተቀመጡ። **22** ንግግሬንም ከጨረስኩ በኋላ መልሰው አልተናገሩም፤ ቃሎቼም በላያቸው እንደ ውሃ ተንጠባጠበ። **23** ዝናብን እንደሚጠብቁ ሁልጊዜ ይጠብቁኛል፤ የበልግ ዝናብን እንደሚሹት፥ ከቃሎቼ ለመጠጣት አፋቸውን ከፈቱ ። **24** እነርሱ ባልጠበቁተ ጊዜ ሳቅሁላቸው፤ የፊቴንም ብርሃን ቸል አላሉትም። **25** መንገድን እመርጥላቸውና አለቃቸው ሆኜ እቀመጣለሁ፤ ኅዘነተኞችን በቀብር ጊዜ እንደሚያጽናና ሰው፥ በሠራዊቱም መካከል እንዳለ ንጉሥ በመካከላቸው ኖርሁ።

Job 29:1

አወይ፣ ምነው ባለፉት ወራት እንደነበርኩት በሆንኩ ኖሮ
ኢዮብ ይህንን አጋኖ የተጠቀመው ምኞትን ለመግለጽ ነው። "በቀደሙት ወራት እንደነበርኩት ብሆን በወደድኩ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አጋኖ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ ብርሃን በእኔ ራስ ላይ ሲበራ
የእግዚአብሔር ብርሃን በኢዮብ ላይ ማብራቱ የሚወክለው እግዚአብሔር ኢዮብን ያለውን መባረኩን ነው። "የእግዚአብሔር በረከት እንደ መብራት በላዬ በሚያበራበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ ብርሃን በጨለማ ውስጥ በማልፍበት ጊዜ
በጨለማ ውስጥ ማለፍ የሚወክለው አስቸጋሪ ሁኔታን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 29:4

በመልካም ቀናቶቼ/በአጨዳ ቀናቶቼ
ኢዮብ ጠንካራ እና ወጣት ስለነበረበት ጊዜ የተናገረው እነዚያን ጊዜያት አዝመራ እንደሚታጨድበት ጊዜ አድርጎ ነው። "ወጣትና ጠንካራ በነበርኩበት ወቅት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ወዳጅነት በጎጆዬ በነበሩበት ወቅት
"ወዳጅነት" የሚለው ረቂቅ ስም "ወዳጅ" በሚለው ስም ሊገለጽ ይችላል። "ጎጆ" የሚለው ቃል የኢዮብን ቤት ይወክላል። "እግዚአብሔር የእኔ ወዳጅ በነበረበት እና እኔን በሚጠብቅበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

መንገዴ በቅባት/ወተት እና የወተት ተዋጽኦ በተሸፈነበት ጊዜ
"መንገዴ በቅባት በተጥለቀለቀ ጊዜ" ኢዮብ ይህንን አጋኖ የተጠቀመው ብዙ ላሞች እንደመበሩት እና ላሞቹ ለእርሱ እና ለቤተሰቡ ከሚያስፈልገው ያለፈ ብዙ ቅባት ይሰጡት እንደነበረ ለመግለጽ ነው። "ላሞቼ እጅግ የበዛ ቅባት ይሰጡኝ በነበረ ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚለውን ይመልከቱ)

ደግሞም አለቱ የዘይት ፈሳሽ ይሰጠኝ ነበር
"ደግሞም አለቱ የዘይት ፈሳሽ ይሰጠኝ ነበር።" ኢዮብ ይህንን አጋኖ የተጠቀመው ብዙ የወይራ ተክል እንደነበረው እና ብዙ የወይራ ዘይት ያመርት እንደነበር ለመግለጽ ነው። አለቱ አገልጋዮቹ ከወይራ ፍሬ ዘይት ይጨምቁበት የነበረበት ስፍራ ነው። "አገልጋዮቼ እጅግ ብዙ የወይራ ዘይት ይጨምቁ በነበረበት ጊዜ" ወይም "ዘይት እንደ ወንዝ ዘይት ከሚጨመቅበት አለት ይፈስ በነበረበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 29:7

የከተማ አደባባይ
ይህ በመንደር ወይም በከተማ ውስጥ ሁለት ወይም ከዚያ የበለጡ መንገዶች የሚገናኙበት ስፍራ ነው።

ለእኔ ተነስተው ይቆሙ ነበር
ይህ የአክብሮት ምልክት ነው። ይበልጥ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "ለእኔ በአክብሮት ተነስተው ይቆሙ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 29:9

ልዑላን እኔ ስመጣ ንግግራቸውን ያቋርጡ ነበር
ይህ የአክብሮት ምልክት ነበር። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

እጃቸውን በአፋቸው ላይ ይጭኑ ነበር
ይህን የሚያደርጉት እንደማይናገሩ ለማሳየት ነው። ይህ ለኢዮብ ያላቸውን አክብሮት የሚያሳዩበት ምልክት ነበር። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

የተከበሩ ሰዎች ድምጽ ጭጭ ይል ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የተከበሩ ሰዎች ጸጥ ይሉ ነበር" ወይም "የተከበሩ ሰዎች መናገራቸውን ያቆሙ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምላሳቸው ከትናጋቸው ጋር ይጣበቅ ነበር
ይህ እነርሱ ለኢዮብ ካላቸው እጅግ ከፍ ያለ አክብሮት የተነሳ አንዳች የሚናገሩት ነገር እንዳልነበረ ያሳያል። "መናገር የማይችሉ ሆኖ ይሰማቸው ነበር" ወይም "አንዳች የሚሉት አልነበራቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 29:11

ጆሯቸው እኔን ካደመጠ በኋላ ... ዐይናቸው እኔን ካደመጠ በኋላ
ጆሮዎች የሚለው የሚወክለው እርሱን የሰሙትን ሰዎች ሲሆን፣ ዐይኖች የሚለው ደግሞ የሚወክለው እርሱን ያዩተን ሰዎች ነው። "የነገርኳቸውን ከሰሙ በኋላ... እኔን ከተመለከቱ በኋላ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእኔ ምስክርነት ይሰጡ፤ ደግሞም ያልኩትን ይቀበሉ ነበር
"የተናገርኩት ትክክል ነው በማለት ይመሰክሩ ነበር"

ድሃው ሲጮህ ካለበት ሁኔታ አወጣው ነበር
እዚህ ስፍራ "ድሃ የሆነው/ድሃው" የሚለው የሚያመለክተው ማንኛውንም ድሃ ሰው ነው። "ድሆች ሲጮሁ ደርሼ ካሉበት ችግር አወጣቸው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የስማዊ ሀረግ ክፍል የሚለውን ይመልከቱ)

በሞት አፋፍ ላይ የደረሰው መርቆኛል
የአንድ ሰው ምርቃት/በረከት ወደ ሌላው መድረሱ የሚወክለው ያ ሰው ሌላውን መባረኩን ነው። "ሞት አፋፍ ላይ ደርሶ ነበረው ስረዳው ይባርከኝ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በሞት አፋፍ ላይ የደረሰው/ለመጥፋት የተቃረበው
ይህ የሚወክለው ለሞት የተቃረበውን ማናቸውንም ሰው ነው። "ለሞቱ የተቃረቡ/በሞት አፋፍ ላይ ያሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የስማዊ ሀረግ ክፍል የሚለውን ይመልከቱ)

የመበለቶች ልብ በሀሴት እንዲዘምር አድርጌያለሁ
እዚህ ስፍራ "የመበለቶች ልብ" የሚለው የሚወክለው ማንኛይቱንም መበለት ነው። "መበለቶች በደስታ እንዲዘምሩ ምክንያት ሆኛለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና የስማዊ ሀረግ ክፍል የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 29:14

ጽድቄን አበዛለሁ፤እንደልብስ ይሸፍነኛል
ብዙውን ጊዜ ሰዎች ጽድቅን እንደ ልብስ አድርገው ይገልጽዋታል። "ጽድቅ የሆነውን አደርግ ነበር፣ እርሷም ለእኔ እንደ ምለብሰው ልብስ ነበረች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ፍርዴ እንደ ልብስ እና እንደ ጥምጥም ነበረች
ብዙውን ጊዜ ሰዎች ጽድቅን እንደ ልብስ አድርገው ይገልጽዋታል። "ትክክል የሆነውን አደርግ ነበር፣ ፍትህ በእኔ ላይ እንደ ልብስ እና እንደ ጥምጥም ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤያዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥምጥም
ወንዶች በራሳቸው ላይ የሚጠመጥሙት እና እንደ ኮፍያ የሚያደርጉት ረጅም ጨርቅ

ለዐይነ ስውራን ዐይን ነበርኩ
ይህ የሚወክለው ዐይነ ስውር የሆኑ ሰዎችን መርዳትን ነው። "ለዐይነ ስውራን ዐይን ነበርኩ" ወይም "ዐይነ ስውራንን እመራ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለአንካሶች እግር ነበርኩ
ይህ አካል ጉዳተኞችን መርዳትን ያመለክታል። "ለአንካሶች እግር ነበርኩ" ወይም "አንካሶችን እደግፍ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለችግረኞች አባት ነበርኩ
እዚህ ስፍራ "አባት ነበርኩ" የሚለው የሚወክለው ለሰዎች የሚያስፈልጋቸውን ማቅረብን ነው። "አባት ለልጆቹ የሚያስፈልጋቸውን እንደሚያቀርብ ለችግረኞች አቀርብላቸው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 29:17

አጠቃላይ መረጃ:
ከቁጥር/ስንኝ 18-20 ባለው ክፍል ኢዮብ በእርሱ ላይ መከራ ከመድረሱ በፊት ይናገራቸው ስለነበሩ ነገሮች ይገልጻል።

የ... መንጋጋ እሰብር ነበር፣ ...ምርኮኞችን ነጻ አወጣ ነበር
ኢዮብ ኃጢአተኞችን በጥርሳቸው ያደኑትን እንደሚነክሱ የዱር አራዊት ይገልጻቸዋል። "አንድ ሰው የዱር አውሬን መንጋጋ ሰብሮ ያደነውን ከጥርሶቹ መሃል እንደሚያስጥለው፣ እኔም ኃጢአተኞች ሰዎችን እንዳያሳድዱ እከልክላቸው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በጎጆዬ ውስጥ እሞታለሁ
እዚህ ስፍራ "ጎጆ" የሚወክለው የኢዮብን ቤት እና ቤተሰብ ነው። ኢዮብ እርሱን እንደ ወፍ ልጆቹን ደግሞ እንደ ወፍ ጫጩቶች አድርጎ ይናገራል። "ከቤተሰቦቼ ጋር በቤቴ ውስጥ እሞታለሁ" ወይም "በቤቴ በሰላም እሞታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እድሜዬን እንደ ምድር አሸዋ አበዛለሁ
በወንዝ ዳርቻ ማንም ሊቆጥረው የማይችለው አሸዋ አለ። ማንም ሊቆጥረው ከሚችለው በላይ እድሜ እኖራለሁ ማለቱ ረጅም እድሜ እንደሚኖር አጋኖ መናገሩ ነው። "በጣም ዘመን እኖራለሁ" ወይም "ብዙ አመታት እኖራለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት እንዲሁም ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

የእኔ ስር... የእና ቅርንጫፍ
ኢዮብ ስለ ጥንካሬው በሚገባ ውሃ እንዳገኘ ዛፍ አድርጎ ይናገር ነበር። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 29:20

በውስጤ ያለው ክብር ሁሌም አዲስ ነው
" ክብር" የሚለው ረቂቅ ስም "ከበረ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። እዚህ ስፍራ "አዲስ/ትኩስ" የሚለው የሚወክለው ያለማቋረጥ የሚሰጥን ክብር ነው። "ሰዎች ሁሌም/ሳያቋርጡ ክብር ይሰጡኝ ነበር" ወይም "ሰዎች ሁሌም ያከብሩኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በእጄ ያለው ቀስት ሁሌም በእጄ ላይ አዲስ ነው
አዲስ ቀስት በጣም ጠንካራ ነው። የኢዮብ በእጁ የሚገኘው ቀስት ጥንካሬ የሚወክለው የእርሱን አካላዊ ብርታት ነው። "እኔ ሁልጊዜም እንደ አዲስ ቀስት ጠንካራ ነኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ንግግሬ እንደ ውሃ በላያቸው ይንጠባጠባል
እዚህ ስፍራ "እንደ ውሃ በላያቸው ይንጠባጠባል" የሚለው የሚወክለው እርሱን የሚሰሙ ሰዎች መታደሳቸውን ነው። "ንግግር" የሚለው ረቂቅ ስም "ተናገረ" ወይም "አለ" በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። "ውሃ ሲፈስበት የሰዎች አካል እንደሚታደስ ንግግሬ ልባቸውን ደስ ያሰኝ ነበር" ወይም "እኔ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እምናገራቸው ነገር በአካላቸው እንደሚፈስ ውሃ ያድሳቸው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 29:23

ዝናብን እንደሚጠባበቅ ንግግሬን ይጠባበቁ ነበር
ሰዎች ኢዮብን በትግስት ይጠባበቁት ነበር፤ ደግሞም ከእርሱ መልካም ነገርን ለመስማት ይጠባበቁ ነበር። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእኔ ቃላት ለመጠጣት አፋቸውን በሰፊው ይከፍታሉ
ይህ የሚወክለው ኢዮብ ከሚናገረው ተጠቃሚ ለመሆን በጉጉት መጠባበቅን ነው። "ከምናገረው ለመጠቀም እኔ እስከምናገር ድረስ በጉጉት ይጠባበቁ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የኋለኛውን ዝናብ እንደሚጠባበቁ
"ገበሬዎች የኋለኛውን ዝናብ በጉጉት እንደሚጠባበቁ"

የኋለኛው ዝናብ
ይህ ዝናብ የሌለበት/ደረቅ ወቅት ከመግባቱ አስቀድሞ የሚዘንበውን ብዙ መጠን ያለውን ዝናብ ያመለክታል።

ፈገግ አልላቸው/አስቅላቸው ነበር
ፈገግ የሚልበት ምክንያት እነርሱን ለማበረታታት በመሆኑ፣ ይህ ይበልጥ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "እነርሱን ለማበረታታት ፈገግ አልላቸው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የፊቴ ብርሃን
ይህ የሚወክለው በኢዮብ ገጽ ላይ የሚመለከቱትን ደግነት ነው። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 29:25

መንገዳቸውን እመርጥላቸው ነበር
እዚህ ስፍራ "መንገዳቸውን እመርጥላቸው" የሚለው የሚገልጸው ምን ማድረግ እንዳለባቸው መወሰንን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አለቃቸው ሆኜ እቀመጥ ነበር
እዚህ ስፍራ "መቀመጥ" የሚወክለው መግዛትን ወይም መምራትን ነው። አለቆች ከፍ ያለ ውስኔ የሚሰጡት ተቀምጠው ነው። "አለቃቸው ሆኜ እመራቸው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አለቃቸው ሆኜ እቀመጥ ነበር
ኢዮብ የእነርሱ አለቃ ነበር። "አለቃቸው ስለነበርኩ እመራቸው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በሰራዊቱ መሃል እንደሚገኝ ንጉሥ እኖር ነበር
ኢዮብ ሰዎቹን እንዴት ይመራ እንደነበር፤ ራሳቸውን እንደ ሰራዊቱ፣ እርሱንም እንዴት እንደ ንጉሳቸው ያህል ቆጥረው ይታዘዙት እንደነበር ይናገራል። (ተነጻጻሪ ዘይቤያዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ያዘኑትን አጽናና ነበር
ይህ ሀረግ ኢዮብ በእርግጥ ሰዎችን ያጽናና ነበር ማለት ነው። "ባዘኑ ጊዜ አጽናናቸው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 30

[1] አሁን ግን በዕድሜ ከእኔ የሚያንሱ፥ አባቶቻቸውን ከመንጋዬ ጠባቂ ውሾች ጎን እንዳይሰሩ ልከለክላቸው የምችል የነበሩ እነዚህ ወጣቶች፥ በእኔ ላይ
ተሳለቁብኝ። [2] በርግጥ የአባቶቻቸው ክንድ ጥንካሬ ምን ሊፈይድልኝ ይችል ነበር? የጉልምስናቸው ጥንካሬ ጠፍቶባቸው ነበርና። [3] በድህነትና በራብ የመነመኑ
ናቸው፤ በደረቅ መሬት በምድረ በዳ ጨለማና ጥፋት ይሰቃያሉ። [4] ከቍጥቋጦ አጠገብ ያለውን ጨው ጨው የሚሉትን ቅጠሎች ይለቅማሉ፤ የክትክታ ሥራሥር
ምግባቸው ነበር። [5] ሌባን እየተከታተሉ እንደሚጮኹበት፤ ከሚጮኹባቸው ሰዎች ተለይተው ተሰደዱ። [6] በወንዝ ሸለቆ በምድር ጕድጓድና በድንጋይም ዋሻ
ውስጥ ይኖራሩ ነበር። [7] በቍጥቋጦ መካከል እንደ አህያ ይጮኻሉ፤ ከቁጥቋጦ በታች በጋራ ተሰብስበዋል። [8] በርግጥ የሰነፎችና ዋጋ የሌላቸው ሰዎች
ልጆች ናቸው፤ እየተገረፉ ከምድሪቱ ተባረዋል። [9] አሁን ግን ለልጆቻቸው የስላቅ ዘፈን ሆንኩላቸው፤ በርግጥም የነሱ መቀለጃ ሆኛለሁ። [10] ተጸየፉኝ፥ ከእኔም
ርቀው ይቆማሉ፤ ፊቴም ላይ መትፋትን አያቆሙም። [11] እግዚአብሔር የቀስቴን መወጠሪያ አላልቶብኛል፥ መከራም አሳይቶኛል፤ እነርሱም በፊቴ ይሉኝታ
የላቸውም። [12] በቀኜ በኩል ዱርዬዎች ተነሥተዋል፥ ያሳድዱኛል፤ ለእግሬም የጥፋትን ወጥመድ ያደርጋሉ። [13] መንገዴን ያበላሻሉ፤ ከልካይ እንደሌላቸው
ሰዎች ጥፋትን ገፍተው ያመጡብኛል። [14] በሰፊ ፍራሽ ቀዳዳ እንደሚመጣ ሰራዊት ይመጡብኛል፤ በጥፋት ላይ ተንከባልለው መጡብኝ። [15] ድንጋጤ በላዬ
መጥቶብኛል፥ ክብሬም በነፋስ ያሳደዱት ያክል በነነ፤ ብልጥግናዬም እንደ ደመና ተበተፈ። [16] አሁንም ነፍሴ በውስጤ ፈሰሰች፤ የብዙ ቀናት መከራም ያዘኝ።
[17] በሌሊት አጥንቶቼ በውስጤ ተወጉ፥ የሚያሰቃየኝ ህመም ፋታ አይሰጠኝም። [18] ከእግዚአብሔር ታላቅ ኃይል የተነሣ ልብሴ ተያዘ፥ እንደ ቀሚስ መቀነት
ተጠቀለለብኝ። [19] እርሱ ጭቃ ውስጥ ወረወረኝ፥ አፈርና አመድም መሰልሁ። [20] ወደ አንተ ጮኽሁ እግዚአብሔር፥ አንተም አልመለስህልኝም ቆምሁኝ፥
አልተመለከትኸኝም። [21] ተለወጥህብኝ ፤ ጨካኝም ሆንህብኝ፤ በእጅህም ሃይል አሳደድኸኝ። [22] በነፋስ አነሣኸኝ፥ በላዩም አስቀምጠኸ ወሰድኸኝም፤
በማእበልም ውስጥ አቀለጥኸኝ። [23] ለሕያዋን ሁሉ ወደተወሰነው ቤት፤ ወደ ሞት እንደምትወስደኝ አውቄአለሁ። [24] ነገር ግን ሰው ሲወድቅ እጁን እርዳታ
ፍለጋ አይዘረጋምን? በችግር ውስጥ ያለ ማንም ለእርዳታ አይጮኽምን? [25] በችግር ላለ ሰው አላለቀስሁምን? ለድሆችስ ነፍሴ አላዘነችምን? [26]
መልካምን በተጠባበቅሁ ጊዜ ክፉ መጣብኝ፤ ብርሃንን ስጠባበቅ፥ ጨለማ መጣ። [27] ልቤ ታወከ፥ እረፍትም አላገኘም የስቃይም ቀናቶች መጡብኝ። [28] ያለ
ፀሐይ በጨለመ ሰማይ በትካዜ ሄድሁ፤ በጉባኤም መካከል ቆሜ ለእርዳታ እጮኻለሁ። [29] ለቀበሮ ወንድም፥ ለሰጐንም ጓደኛ ሆንሁ። [30] ቆዳዬ ጠቈረ፥
ከላዬም ተቀርፎ ወደቀ፤ አጥንቶቼም በትኵሳት ተቃጠሉ። [31] ስለዚህ በገናዬ ለኀዘን እንጉርጉሮ ፥ እምቢልታዬም ለለቅሶ ጩኸት ተቃኙ።

Job 30:1

በእኔ ላይ ይሳለቃሉ
"መሳለቅ" የሚለው ረቂቅ ስም "ተሳለቁ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "በእኔ ላይ ተሳለቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

አባቶቻቸው መንጋዎቼን ከሚጠብቁ ውሾች ጋር እንዲቀመጠ/እንዲሰሩ እንኳን ያላፈቀድኩላቸው
ይህ የሚያመለክተው እነዚያን አባቶች ምን ያህል ይንቃቸው እንደነበረ ነው። መንጎቼን ከሚጠብቁ ከውሾቼ ጋር ለመሆን እንኳን የሚበቁ አልነበሩም። "እኔ የናቅኳቸው አባቶቻቸው፤ ከመንጎቼ ውሾቼ ጋር እንዲሆኑ ያልፈቀድኩላቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የመንጎቼ ውሾች
ውሾቹ ከመንጎቹ ጋር ያላቸው ግንኙነት ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "መንጎቼን የሚጠብቁ ውሾች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በእርግጥ፣ የአባቶቻቸው እጆች ጥንካሬ፣ እንዴት እኔን ሊያግዝ ይችላል... አልጠፋምን?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት በእነዚያ ሰዎች ጥንካሬ ላይ ለማፌዝ ነው። "የአባቶቻቸው ክንዶች ጥንካሬ ሊረዳኝ አልቻለም... ጠፍቷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የብስለት እድሜ ሃይላቸው የጠፋባቸው ሰዎች
የሃይላቸው መጥፋት ከእንግዲህ እየደከሙ እንጂ እየበረቱ እንደማይሄዱ የመሚገልጽ ዘይቤ ነው። "የብስለት እድሜ" የሚለው ማርጀታቸውን ያመለክታል። "ያረጁ እና ሀይላቸው የደከመ ሰዎች" ወይም "ያረጁ እና የደከሙ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ከድህነት እና ከረሀብ የተነሳ ከስተዋል
"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሚያለግጡ/የሚቀልዱ ወጣቶችን አባቶች ነው።

ከድህነት እና ከረሀብ የተነሳ ከስተዋል
"ረሃብ" የሚለው ረቂቅ ስም "ድሃ" በሚለው ቃል ሊገለጽ ይችላል። "ረሃብ" የሚለው ረቂቅ ስም "መራብ" ወይም "ችጋር" በሚለው ቃል ሊገለጽ ይችላል። "በጣም ከሲታ የነበሩት ድሆች እና የተራቡ ስለነበሩ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በደረቁ ምድር ላይ ያገኙትን ይቆረጣጥማሉ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ደረቅ ምድር" በደረቅ ምድር ላይ የሚበቅሉ ደረቅ ስሮች ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት ነው። "ከምድር ያገኙትን ደረቅ ስራስሮችን ይቆረጣጥማሉ" ወይም2) "ከደረቁ መሬት ላይ ያገኙትን ይቆረጣጥማሉ/ይበላሉ" የሚለው በደረቁ ምድር ያገኙትን ለመመገባቸው ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 30:4

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ ስለሚሳለቁበት ሰዎች አባቶች መናገሩን ቀጥሏል በረሃብ ጊዜ ብቻ የሚበላ ጨው ጨው የሚል ተክል... የቁጥቋጦ ቅጠል... የክትክታ ዛፍ/ችፍርግ እነዚህ ሰዎች ሌላ የሚበላ ነገር ባጡ ጊዜ የሚበሏቸው ቅጠላቅጠሎች ናቸው።

የክትክታ ስር ምግባቸው ነበር
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሰዎች የክትክታ ቅጠል/ችፍርግ ይበሉ ነበር ወይም 2) ሰዎች የክትክታ ስራ ስሮችን በማንደድ ይሞቁ/ሙቀት ያገኙ ነበር

እንደ ሌባ... እየተከታተሉ ከሚጮሁባቸው ሰዎች ይሸሹ ነበር
"ይሸሹ ነበር" የሚለው ሀረግ "ለመሸሸ ይገደዱ ነበር" ማለት ነው። ይህ ሀረግ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች እንደ ሌባ እያባረሩ ይጮሁባቸው ነበር... ደግሞም ለቀው እንዲሄዱ ያስገድዷቸው ነበር"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ሰው ሌባን እንደሚያበርር እየጮሁ ያሳድዷቸው ነበር
"ሌባ የሆኑ ያህል ይጮሁባቸው ነበር"

Job 30:7

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ ስለሚሳለቁበት ሰዎች አባቶች መናገሩን ቀጥሏል

እንደ አህዮች ያናፉ ነበር
ኢዮብ በረሃብ ይጮሁ የነበሩ ሰዎችን ከፍ ያለ ድምጽ እንደሚያሰሙ የሜዳ አህዮች ይገልጻቸዋል። "ከረሃባቸው የተነሳ እንደ ሜዳ አህያ ይጮሁ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤያዊ የሚለውን ይመልከቱ)

በሳማ ስር በአንድነት ይሰባሰቡ ነበር
"ሳማ" ሹል እሾህ ያለው እጅብ ብሎ የሚበቅል ተክል ነው። ይህ የሚያመለክተው ቤት እንደሌላቸው ነው።

የማይረቡ ሰዎች ልጆች ናቸው
እዚህ ስፍራ "የማርረቡ ሰዎች ልጆች" የሚለው የሚገልጸው የማይረባ/ጅል ባህሪይ እንዳላቸው ነው። "እንደ ጅሎች ነበሩ" ወይም "ሞኞች ነበሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእርግጥ፣ ስም የለሽ ሰዎች ልጆች ነበሩ
"በእርግጥ" የሚለው ቃል ቀጥሎ የሚመጣውን ሀሳብ የሚያጠናክር ነው። እዚህ ስፍራ " የስም የለሽ ሰዎች ልጆች" የሚለው የሚገልጸው ስም እዚህ ግባ የሚባል ባህሪ እንዳሌላቸው ነው። "በእርግጥ፣ የሚረቡ ሰዎች አልነበሩም" ወይም "በእርግጥ፣ እርባና ቢስ ሰዎች ነበሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ስም የለሽ ሰዎች
እዚህ ስፍራ "ስም የለሽ" የሚለው የሚገልጸው አንዳች ክብር ወይም ከበሬታ የሌለው ማለት ነው። ይህ ማለት እርባና ቢስ ነበሩ ማለት ነው። "እርባና ቢስ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በአለንጋ እየተገረፉ ከምድሪቱ ይባረሩ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) አለንጋ የሚለው እንደ ወንጀለኛ ይቀጡ እንደነበር ያመለክታል። "ሰዎች እንደ ወንጀለኞች ይመለከቷቸው እና ከአገራቸው በግድ ያስወጧቸው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) ሰዎች በአለንጋ እየገረፉ በግድ ያስወጧቸው ነበር። "ሰዎች ይገርፏቸው እና ምድሪቱን ለቀው እንዲወጡ ያስገድዷቸው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከምድሪቱ ይባረሩ ነበር
እዚህ ስፍራ "ምድሪቱ" የሚለው የሚያመለክተው ወደ በረሃ ከመሰደዳቸው አስቀድሞ የሚኖሩበትን ምድር ነው።

Job 30:9

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ እንደገና ስለሚሳለቁበት ሰዎች መናገሩን ቀጥሏል ነገር ግን አሁን ለሚያንጓጥጥ ዘፈናቸው ሆኛለሁ "ዘፈን" የሚለው ረቂቅ ስም "ዘፈነ" በሚል ግስ ሊገለጽ ይችላል። "በእኔ ላይ ለማንጓጠጥ ይዘፍናሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ለእነርሱ መተረቻ ሆኛለሁ
እዚህ ስፍራ "መተረቻ" የሚለው ሰዎች በጭከና ለማፌዛቸው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት ነው። "አሁን እነርሱ በጭካኔ የሚዘባበቱብኝ ሆኛለሁ" ወይም "ስለ እኔ በፌዝ ጭካኔ የተሞላበት ነገር ይናገራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በፊቴ ላይ ምራቃቸውን ጠቅ ለማለት ወደኋላ አይሉም
ይህ በአዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በፊቴ ላይ አንኳን ይተፉብኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምጸት የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ከእኔ ቀስቴን ሰብሮታል
የተሰበረ ቀስት ጥቅም የለውም። "ቀስቴን ሰብሮታል" የሚለው ሀረግ ኢዮብን አቅመቢስ ስለ ማድረግ ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። "እግዚአብሔር እራሴን እንዳልከላከል አቅሜን ከእኔ ወስዶታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእኔ ላይ የሚያላግጡት
"በእኔ የሚቀልዱ"

በፊቴ ያለገደብ ክፉ ያደርጋሉ
ገደብ አንድ ሰው በነጻነት አንዳይንቀሳቀስ እና የሚፈልገውን እንዳያደርግ ያግዳል። እዚህ ስፍራ "መቆጠብ" የሚለው የሚገልጸው አንድ ነገር ከማድረግ መገታተትን፣ ሲሆን "ገደብን መስበር" የሚለው ደግሞ አንድ ነገር ከማድረግ አለመከልከልን ነው። በዚህ ሁኔታ ፌዘኞቹ በኢዮብ ላይ ክፉ ነገርን ከማድረግ አልተቆጠቡም። "ለእኔ ክፉ ከመሆን አልተገቱም" ወይም "በእኔ ላይ ማድረግ የሚፈልጉትን የጭካኔ ተግባር ሁሉ ያደርጋሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 30:12

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ እንደገና ስለሚሳለቁበት ሰዎች መናገሩን ቀጥሏል

አጠቃላይ መረጃ፡
ኢዮብ ክፉ የሚያደርጉበትን ፌዘኞች በቡድን እንደሆኑ እና እንደ ሰራዊት በአንድላይ ሆነው እንደሚያጠቁት አድርጎ ይገልጻል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በቀኜ ጀሌዎች ተነሱብኝ
"በቀኜ ጀሌዎች ተነሱብኝ" የሚለው በሚከተሉት መንገዶች ሊተረጎም ይችላል 1) በኢዮብ ቀኝ እጅ ላይ መነሳት በእርሱ ጥንካሬ ላይ መነሳትን ሊወክል ይችላል። "ወሮበሎች አቅሜን መቱት/አጠቁኝ" ወይም በኢዮብ ቀኝ እጅ ላይ መነሳት የእርሱን ክብር ማጥቃትን ይወክላል። "ጀሌው ክብሬን አጠፋ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

አሳደዱኝ
"እንድሸሽ አስገደዱኝ"

የዐፈር ድልድል አዘጋጁብኝ
ሰራዊት አንዲትን ከተማ በቅጥሯ ላይ ተንጠላጥሎ ወጥቶ ለማጥቃት በቅጥሩ ስር አፈር ይከምራል። ኢዮብ በእርሱ ላይ የሚያፌዙት እንዲህ ያለ ነገር እንዳደረጉ ይናገራል። "ሰራዊት አንዲትን ከተማ ለማጥቃት እንደሚዘጋጅ እነርሱ እኔን ለማጥቃት ተዘጋጁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መንገዴን ደመሰሱ
ይህ የሚገልጸው ኢዮብ ከጥቃታቸው እንዳያመልጥ ማድረጋቸውን ነው። "ከእነርሱ እንዳላመልጥ ከለከሉኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጥፋትን ወደ እኔ አመጡ
እዚህ ስፍራ "ክፋትን ማምጣት" የሚለው የሚገልጸው ጥፋት እንደሆን ማድረግን ነው። "በእኔ ላይ ጥፋት እንዲደርስ ተጣጣሩ" ወይም "እኔን ለማጥፋት ሞከሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ማንም ሊያግዳቸው/ወደ ኋላ ሊመልሳቸው የማይችላቸው ሰዎች
እዚህ ስፍራ "ወደ ኋላ መመለስ/ማገድ" የሚለው የሚገልጸው አንድ ነገር እንዳያደርጉ እነርሱን መከልከልን/ማስቆምን ነው። "እኔን ከማጥቃት ማንም የማያስቆማቸው ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 30:14

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ እንደገና ስለሚሳለቁበት ሰዎች መናገሩን ቀጥሏል

አጠቃላይ መረጃ፡
ኢዮብ ክፉ የሚያደርጉበትን ፌዘኞች በቡድን እንደሆኑ እና እንደ ሰራዊት በአንድላይ ሆነው እንደሚያጠቁት አድርጎ ይገልጻል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በአንዲት ከተማ ትልቅ የቅጥር ፍራሽ/ብስ አልፎ እንደሚገባ ሰራዊት በእኔ ላይ መጡብኝ
ይህ የሚገልጸው ኢዮብን በሃይል ማጥቃታቸውን ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በላዬ በሃይል መጡብኝ
ይህ የሚገልጸው ታላቅ የውቅያኖስ ማዕበል በእርሱ ላይ እንደመጣበት ብዙ ሆነው በአንድነት መጥተው እንዳጠቁት ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ፍርሃት በላዬ ወረደ/መጣ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ኢዮብ እጅግ ፈራ ወይም 2) ኢዮብ ኢንዲፈራ የሚያደርጉ ነገሮች እየሆኑ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በነፋስ ተጠርጎ እንሚወሰድ ክብሬ ተወሰደ
ኢዮብ ነፋስ በድንገት ጠርጎ እንደወሰደው ነገር ክብሩ ከእርሱ መወሰዱን ይናገራል። "ማንም እኔን አያከብርም" ወይም "እኔ አሁን ማንም የማያከብረው ሰው ሆኛለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ብልጽግናዬ/ሀብቴ እንደ ደመና አለፈ
ኢዮብ የሃብቱን መጥፋት በነፋስ እንደተጠረገ ደመና ይገልጻል። እዚህ ስፍራ "ሀብት/ብልጽግና" ደህንነትን ወይም ጥበቃን ሊያመለክት ይችላል። "ከእንግዲህ አንዳች የለኝም" ወይም "ከእንግዲህ ሰላም አይደለሁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 30:16

አሁን ህይወቴ ከውስጤ ይፈሳል
ኢዮብ ህይወቱ ፈሳሽ እንደሆነ እና አካሉን ህይወቱን እንደያዘ እቃ/መያዣ አድርጎ ይገልጻል። መሞቻው እንደደረሰ ይሰማዋል። "አሁን እሞትኩ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ብዙ የመከራ ቀናት ይዘውኛል
ኢዮብ የማያቆርጥ መከራውን የሚገልጸው የመከራ ቀናቱ እርሱን አንቀው እንደያዙት አድርጎ ነው። "ለብዙ ቀናት ተሰቃየሁ፣ መከራው ግን አላበቃም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በውስጤ አጥንቴ ይወጋኛል
ኢዮብ በአጥንቱ ውስጥ የሚሰማውን ስቃይ የሚገልጸው አጥንቶቱ እየተበሱ እንደሚገኙ አድርጎ ነው። "አጥንቶቼን እጅግ ይቆረጥመኛል" ወይም "በአጥንቶቼ ውስጥ እጅግ አስጨናቂ ስቃይ ይሰማኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ካለ ማቋረጥ ይቆረጥመኛል
ኢዮብ የማያቋርጥ ስቃዩን ህይወት እንዳለው እና እንደሚነክሰው ደግሞም ለማቆም እምቢ እንዳለ ነገር አድርጎ ይገልጸዋል። "የሚያሰቃየን መከራ አያቋርጥም" ወይም "በማያቋርጥ ስቃይ ውስጥ ነኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 30:18

የእግዚአብሔር ታላቅ ሀይል በልብሴ አንቆ ይዞኛል
ኢዮብ፣ የእግዚአብሔር ሀይል አንዳች ነገር እያደረገ እንደሆነ እና እግዚአብሔር ሀይሉን እየተጠቀመ እንደሆነ ይናገራል። እዚህ ስፍራ "የእግዚአብሔር... ሀይል" የሚለው የቆመው/የሚገልጸው "እግዚአብሔርን" ነው። "እግዚአብሔር በታላቅ ሀይሉ በልብሴ አንቆ ይዞኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

መከራው እንደ ሸሚዜ ኮሌታ ዙሪያዬን አንቆታል
የእግዚአብሔር ሀይል በኢዮብ ዙሪያ መጠምጠሙ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የኢዮብን መከራ ይወክላል/ይገልጻል። "ስቃዬ እግዚአብሔር በሸሚዜ ኮሌታ አንቆ የያዘኝን ያህል ነው" ወይም 2) ይህ የሚገልጸው እግዚአብሔር በኢዮብ ላይ ብዙ መከራ እንዳደረሰበት ነው። "የሚሰማኝ እግዚአብሔር በታላቁ ሀይሉ በልብሴ አንቆ የያዘኝን ያህል ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ጭቃ ውስጥ ወረወረኝ
ኢዮብ እግዚአብሔር አዋርዶኛል እያለ ነው። "ያደረገኝ ልክ ጭቃ ውስጥ የመጣልን ያህል ነው" ወይም "እርሱ፣ ጭቃ ውስጥ የተጣለን ሰው ያህል አዋርዶኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ አዋራ እና አመድ ሆንኩ
ይህ የሚገልጸው ኢዮብ የተሰማውን እርባና ቢስነት ነው። "እንደ አብዋራ እና አመድ ጥቅም የማይሰጥ ሰው ሆንኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 30:20

ጨካኝ
ይህ ቃል ደግነት የሌለው ማለት ነው

በክንድህ ጥንካሬ አሳደድከኝ
"እጅ" የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ሀይል ይገልጻል/ይወክላል። "በሀይልህ አሳደድከኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 30:22

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ ለእግዚአብሔር መናገሩን ቀጥሏል።

በነፋስ አነሳኸኝ... በማዕበል አናወጥከኝ
እነዚህ አገላለጾች የሚወክሉት እግዚአብሔር ኢዮብ ጸንቶ እንዲያልፍበት ያደረገውን እጅግ ከፍ ያለ መከራ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲያንገላታኝ አደረግህ
"ነፋሱ/ማዕበሉ እንዲገፋኝ አደረግህ"

ወደ ሞት ታደርሰኛለህ/ትገድለኛለህ
እዚህ ስፍራ "ወደ ሞት ታደርሰኛለህ" የሚለው የሚወክለው ኢዮብ እንዲሞት ማድረጉን ነው። "እንድሞት ታደርጋለህ/ትገድለኛለህ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ህያው ለሆነው ሁሉ የተዘጋጀለት ቤት
ኢዮብ ይህ እግዚአብሔር ለህያዋን ነገሮች ሁሉ ይሄዱበት ዘንድ ያዘጋጀው ቤት ይህ እንደሆነ ስለ ሙታን ዓለም እየተናገረ ነው። "በህይወት የኖረ ሁሉ የሚሄድበት የሙታን ዓለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ህይወት ያለው ነገር ሁሉ
ይህ፣ አንድ ቀን የሚሞት ነገር ግን አሁን በህይወት ያለ ነገር ሁሉ።

Job 30:24

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ ለእግዚአብሔር መናገሩን ቀጥሏል።

ሲወድቅ እጆቹን አንስቶ የማይለምን አለን? በችግር የወደቀ ሰው ለእርዳታ አይጣራምን?
ኢዮብ እነዚህን ጥያቄዎች የሚያነሳው/የሚጠቀመው ለእርዳታ ወደ እግዚአብሔር መጮሁ ተገቢ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው። "ማንም ሰው በችግር ላይ በሚወድቅበት ጊዜ ለእርዳታ ወደ እግዚአብሔር እጆቹን ያነሳል። በችግር ውስጥ የሚገኝ ሁሉ እርዳታ ለማግኘት ይጣራል።" ወይም "እኔ ወድቄያለሁ፣ ስለዚህ እርዳታውን ስለምነው እግዚአብሔር እንደተሳሳትኩ ሊመለከተኝ አይገባውም። እኔ በመከራ ውስጥ እገኛለሁ፣ ስለዚህም በእርግጥ እርዳታ ለማግኘት እጣራለሁ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በችግር ...እኔ አላለቅስምን? ሰው... አያዝንምን?
ኢዮብ እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመው ለሌሎች ጥሩ ነገሮችን ያደርግ እንደነበረ ለመናገር ነው። "እኔ እንደማለቅስ አንተ ታውቃለህ... የተቸገረ እና ያዘነ...ሰው!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

መልካምን ነገር ተስፋ ሳደርግ፣ ክፉ ደረሰብኝ
መልካምን መጠባበቅ የሚገልጸው መልካም ነገሮችን ተስፋ ማድረግን ነው፣ ደግሞም የክፉ መድረስ/መምጣት የሚወክለው ክፉ ነገሮች እንደሚሆኑ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ብርሃንን ተጠባበቅኩ... ጨለማ መጣብኝ/ሆነ
እዚህ ስፍራ "ብርሃን" የሚወክለው የእግዚአብሔርን በረከት እና ሞገስ ሲሆን "ጨለማ" ደግሞ የሚወክለው ችግርን እና መከራን ነው። "የእግዚአብሔርን ብርሃን በረከት ተጠባበቅሁ፣ ነገር ግን በምትኩ የጨለማ መከራ ደረሰብኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 30:27

ልቤ ተጨነቀ እረፍት አላገኘም
ኢዮብ ልቡ ሰው እንደሆነ አድርጎ ይገልጻል። "በልቤ ታወክሁ/ተጨነቅሁ፣ ደግሞም መከራው ማብቂያ የለውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የመከራ ቀን መጣብኝ
የመከራ ቀን በኢዮብ ላይ መምጣቱ የሚወክለው ኢዮብ ለብዙ ቀናት በመከራ ውስጥ መቆየቱን ነው። "ለአያሌ ቀናት በመከራ ውስጥ ኖርኩ" ወይም "በየቀኑ መከራ ወረደብኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኖርኩ/ቆየሁ
እዚህ ስፍራ "ኖርኩ/ቆየሁ" የሚለቀው የሚገልጸው በህይወት መቆየቱን ነው። "ኖርኩ" ወይም "አለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ፀሐይ ሳይመለከት፣ በጨለማ ውስጥ እንደሚኖር ሰው
እዚህ ስፍራ "በጨለማ ውስጥ መኖር" የሚለው አገላለጽ እጅግ ማዘንን የሚገልጽ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "ነገር ግን ፀሐይን ሳይመለከት" የሚለው ሀረግ "በጨለማ ውስጥ መኖር" የሚለውን ፀሐይ ባለመውጣቷ ምክንያት ጨለማው አለመፈጠሩን የሚያብራራ ዘይቤ ነው። "እጅግ እንዳዘነ ሰው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የቀበሮዎች ወንድም፣ የሰጎን ወዳጅ
የእነዚህ እንስሳት ወንድም መሆን እንደ እነርሱ አይነት መሆን ለሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "በበረሃ እንደሚጮሁ ቀበሮዎች እና ሰጎኖች ሆንኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 30:30

አጥንቶቼ በሙቀት ተቃጠሉ
እዚህ ስፍራ "አጥንቶች" የሚያመለክተው በትኩሳት የሚሰቃየውን መላ አካልን ነው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በገናዬ ወደ ሀዘን እንጉርጉሮ ተለወጠ
እዚህ ስፍራ "በገናዬ" የሚለው የሚወክለው ኢዮብን ራሱን ነው፣ እንደዚሁም ደግሞ የሀዘን እንጉርጉሮ ብቻ መዘመር መፈለጉን ይወክላል። "በበገናዬ የሀዘን እንጉርጉሮ ብቻ እጫወታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ዋሽንቴ ለሙሾ ማውረጃ ሆነ
እዚህ ስፍራ "ዋሽንቴ" የሚለው የሚወክለው ኢዮብን ራሱን ነው፣ እንደዚሁም ደግሞ የሀዘን እንጉርጉሮ ብቻ መዘመር መፈለጉን ይወክላል። "በዋሽንቴ የሀዘን እንጉርጉሮ ብቻ እጫወታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ዋይታ/ለቅሶ
ዋይታ ከፍ ካለ ሀዘን ወይም ስቃይ የተነሳ ድምጽን በጣም ከፍ አድርጎ ማልቀስ ነው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 31

1 ከዓይኔ ጋር ቃል ኪዳን ስለገባሁ፤ እንዴት ድንግሊቱን በምኞት እመለከታለሁ? 2 ከላይ ከእግዚአብሔር የሆነው እድል ፈንታ ፥ ሁሉንም የሚችል አምላክስ
ርስት ከአርያም ምንድን ነው? 3 መዓት ለኃጢአተኛ፥ ጥፋትም ክፋትን ለሚያደርጉ ነው ብዬ አስብ ነበር። 4 እግዚአብሔር መንገዴን አያይምን? እርምጃዬንስ
ሁሉ አይቈጥርምን? 5 በሐሰት ሄጄ እንደ ሆነ እግሬም ለሽንገላ ቸኩሎ እንደ ሆነ፥ 6 በእውነተኛ ሚዛን ልመዘን፥ እግዚአብሔርም ትክክለኛቴን ይወቅ። 7
እርምጃዬ ከትክክለኛው መንገድ ፈቀቅ ብሎ፥ ልቤም የዓይኔን ምኞት ተከትሎ፥ ነውርም በእጄ ላይ ተጣብቆ እንደ ሆነ፥ 8 እኔ ልዝራ፥ ሌላ ሰውም ይብላው፤
መከሩም ከእርሻዬ ላይ ይነቀል። 9 ልቤ ወደ ሌላይቱ ሴት ጐምጅቶ እንደ ሆነ፥ የጎረቤቴን ሚስት ለማየት ደጃፉ አድብቼ እንደ ሆነ፥ 10 ሚስቴ ለሌላ ሰው እህል
ታዘጋጅ፥ ሌሎችም ከእርስዋ ጋር ይተኙ። 11 ይህ ክፉ ወንጀል ነውና፥ በፈራጆችም ሊቀጣ የሚገባው በደል ነውና፤ 12 ይህ እስከ ሲኦል ድረስ የሚበላ እሳት፥
ያመረትኩትን ሁሉ የሚያቃጥል ነውና። 13 ወንድ ወይም ሴት ባሪያዎቼ ከእኔ ጋር በተምዋገቱ ጊዜ፥ ሙግታቸውን በትክክል ሳላይ ቀርቼ እንደ ሆነ፥ 14
እግዚአብሔር ሊከሰኝ በተነሣ ጊዜ ምን አደርጋለሁ? ሊፈርደኝም በመጣ ጊዜ እንዴት እመልስለታለሁ? 15 እኔን በማኅፀን የሰራኝ እነርሱንስ የፈጠረ
አይደለምን? በማኅፀንስ ውስጥ ሁላችንን የሠራን አንድ አይደለምን? 16 ድሀዎችን ከፍላጎታቸው ከልክዬ፥ የመበለቲቱንም ዓይን በለቅሶ አጨልሜ እንደ ሆነ፥
17 እንጀራዬን ለብቻዬ በልቼ እንደ ሆነ፥ አባት የሌላቸውንም ከእርሱ እንዳይበሉ ከልክዬ እንደ ሆነ፤ 18 ይልቁን እርሱ ከታናሽነቴ ጀምሬ እንደ አባቱ ሆኜ ከእኔ ጋር
አሳድጌው ነበር፥ እናቱንም ከእናቴ ማኅፀን ጀምሬ መራኋት፤ 19 አንድ ሰው የሚለብሰው አጥቶ ሲጠፋ፥ ወይም ድሀ ያለ ልብስ ሲሆን እንዲያው አይቼ እንደ ሆነ፥
20 በበጎቼም ጠጕር ያልሞቀና፥ በልቡ ያልባረከኝ እንደ ሆነ፤ 21 በከተማው በር ረዳት ስላለኝ፥ አባት በሌላቸው ላይ እጄን አንሥቼ እንደ ሆነ፥ 22 ትከሻዬ
ከመጋጠሚያው ይውደቅ፥ ክንዴም ከመገናኛው ይሰበር። 23 ከእግዚአብሔር የሆነ ቁጣ ለእኔ አስደንጋጭ ነውና ከግርማውም የተነሳ እነዚህን ነገሮች ማድረግ
አልችልም። 24 ወርቅን ተስፋዬ አድርጌ፥ ጥሩውንም ወርቅ”በአንተ እታመናለሁ“ ብዬ እንደ ሆነ፤ 25 ሀብቴ ስለ በዛ፥ እጄም ብዙ ስላከማቸ ደስ ብሎኝ እንደ
ሆነ፤ 26 ፀሐይ ሲበራ ተመልክቼ፥ ጨረቃ በድምቀት ስትሄድ አይቼ፥ 27 ልቤ እነርሱን ለማምለክ በስውር ተስቦ፥ አፌም እጄን ስሞ እንደ ሆነ፤ 28 በላይ ያለውን
እግዚአብሔርን መካድ ነውና ይህም ዳኞች ሊቀጡት የሚገባ ወንጀል በሆነ ነበር። 29 በሚጠላኝ በማንም መጥፋት ደስ ብሎኝ ወይም ክፉ ነገር በሆነበት ጊዜ
ራሴን አስደስቼው እንደ ሆነ፤ 30 ለነፍሱ እርግማንን በመናገር፥ አንደበቴ ኃጢአት እንዲሰራ በርግጥ አልፈቀድኩለትም፤ 31 በድንኳኔ የሚኖሩ ሰዎች፦
“ከኢዩብ ማዕድ ያልጠገበ ማን ይገኛል?” ብለው ካልተናገሩ፤ 32 መጻተኛው በከተማ ጎዳና እንዳያድርም፥ ሁልጊዜ ደጄን ለመንገደኛ እከፍት ነበር፤ 33
በደሌንም በብብቴ በመሸሸግ ኃጢአቴን እንደ ሰዉ ሁሉ ደብቄ እንደ ሆነ፤ 34 የሕዝብን ብዛት ከመፍራቴ የተነሳ፥ የዘመዶቼም ንቀት አስደንግጦኝ፥ ዝም ብዬ
ከቤቴ ሳልወጣ ቀርቼ እንደ ሆነ፤ 35 ኦ የሚያዳምጠኝ አንድ ሰው ምነው በኖረኝ! ይኸው የእጄ ፊርማ ምልክት፤ ሁሉን የሚችል አምላክ ይመልስልኝ! ባላጋራዬ
የጻፈው የክስ ጽሑፍ ምነው በተገኘልኝ! 36 በግልጽ ትከሻዬ ላይ አድርጌ እሸከመው ነበር፥ እንደ አክሊልም ራሴ ላይ አስቀምጠው ነበር። 37 የእርምጃዎቼን
ቍጥር በግልጽ አስታውቀው፥ እንደ ተማመነ አለቃም ፊትለፊቱ እወጣ ነበር። 38 የእርሻዬ መሬት በእኔ ላይ ጮሆ እንደ ሆነ፥ ትልሞቹም አብረው አልቅሰው
እንደ ሆነ፤ 39 የምርቱን ዋጋ ሳልከፍል በልቼ፥ የባለቤቶቹንም ነፍስ አሳዝኜ እንደ ሆነ፥ 40 በስንዴ ፋንታ እሾኽ፥ በገብስም ፋንታ አረም ይብቀልበት።“
የኢዮብም ንግግር ተፈጸመ።

Job 31:1

አጠቃላይ መረጃ:
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል።

ከዐይኖቼ ጋር ቃል ኪዳን ገባሁ
ኢዮብ ዐይኖቹ ሰው የሆኑ ይመስል ስለሚመለከተው ነገር ከዐይኖቹ ጋር ቃል መግባቱን ይናገራል። "ስለምመለከተው ነገር ከዐይኖቼ ጋር ጽኑ ቃል ገባሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከዐይኖቼ ጋር ቃል ኪዳን ገባሁ
ኢዮብ ምን ቃል ኪዳን እንደገባ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "ድንግሊቱን በአምንዝራ አይን እንዳልመለከት የጸና ኪዳን ገባሁ" ወይም "ወደ አንዲት ድንግል በአመንዝራነት ላለመመልከት ቃል ገባሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ታዲያ እንዴት ወደ አንዲት ድንግል በአመንዝራነት ፍላጎት እመለከታለሁ?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀምበት ቃልኪዳኑን በምንም ምክንያት እንደማያፈርስ ትኩረት ለመስጠት ነው። "ስለዚህ በእርግጥ ወደ አንዲት ድንግል በአመንዝራነት ዐይን አልመለከትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ከላይ ከእግዘአብሔር ዘንድ ድርሻዬ፣ በከፍታ ካለው ሁሉን ቻይ ከሆነው ርስቴ ምንድን ነው?
ኢዮብ እግዚአብሔር ለሰዎች ባህሪ ያለውን ምላሽ የሚገልጸው እግዚአብሔር ለሰዎች የሚሰጠው ርስት ክፍል አድርጎ ነው። "በሰማይ የሚኖር አምላክ ለእኔ የሚመልሰው እንዴት ነው? በላይ የሚኖረው ሁሉን ቻይ አምላክ ምን ይፈጽማል? በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከላይ ከእግዘአብሔር ዘንድ ድርሻዬ፣ በከፍታ ካለው ሁሉን ቻይ ከሆነው ርስቴ ምንድን ነው?
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች፤ ኢዮብ እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመባቸው ተከታዬቹን ነጥቦች ለማጉላት ነው 1) እግዚአብሔር መጥፎ ባህሪ ያለውን አይባርከውም። "ወደ አንዲት ሴት በአመንዝራነት ዐይን ብመለከት፥ በላይ በሰማይ የሚኖር ሁሉን ቻይ አምላክ አይባርከኝም።" ወይም 2) እግዚአብሔር መጥፎ ባህርይን ይቀጣል። "ወደ ሴት በአመንዝራነት ብመለከት፣ በሰማይ የሚኖር ሁሉን ቻይ አምላክ በእርግጥ ይቀጣኛል።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 31:3

አጠቃላይ መረጃ:
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል።

እግዚአብሔር መንገዴን አይመለከትምን ደግሞስ እርምጃዬን አይቆጥርምን?
እዚህ ስፍራ "መንገዶቼ" እና "እርምጃዎቼ" የሚሉት ለኢዮብ ባህርይ መግለጫነት የቀረቡ ዘይቤዎች ናቸው። እዚህ ስፍራ "መንገዶቼን ተመልከት" እና "እርምጃዎቼን ሁሉ ቁጠር" የሚሉት ኢዮብ የሚያደርገውን ሁሉ እግዚአብሔር እንደሚያው ለመግለጽ የቀረቡ ዘይቤዎች ናቸው። ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት እግዚአብሔር እርሱ ያደረገውን ሁሉ እንደሚያውቅ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። "በእርግጥ እግዚአብሔር ይመለከተኛል፣ ደግሞም ያደረግሁትን ነገር በሙሉ ያውቃል።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እግዚአብሔር መንገዶቼን አይመለከትምን ደግሞስ እርምጃዎቼን ሁሉ አይቆጥርምን?
ኢዮብ ምናልባትም እግዚአብሔር የእርሱን ጻድቅነት ማወቅ እንደሚገባው እና መቅሰፍት እና ጥፋት ለእርሱ እንደማይገባው እያመላከተ ሊሆን ይችላል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 31:5

አጠቃላይ መረጃ:
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል።

እንዲህ አድርጌ ቢሆን
በኢዮብ 31፡ 5-40 ውስጥ የእግዚአብሔር ቅጣት እንደሚይገባው የተለያዩ ሁኔታዎችን ይገልጻል። ይልቁንም፣ ጥፋት እንደሌለበት እና ንጹህ እንደሆነ ያውቃል። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በሀሰት መንገድ ተመላልሼ እንደሆነ፣ እግሮቼ ወደ ማታለል ፈጥነው እንደሆነ
እዚህ ስፍራ "መመላለስ" እና "መፍጠን" የሚሉት ኢዮብ እንዴት እንደኖረ የሚገልጹ ዘይቤዎች ናቸው። "አንዳች ሀሰት የሆነ ነገር አድርጌያለሁን ወይስ ይሁን ብዬ የፈጸምኩት ማታለል አለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በትክክለኛ ሚዛን ልመዘን
ሰዎች ነገሮችን ለመለካት እና ዋጋቸውን ለመወሰን ሚዛን ይጠቀማሉ። ይህ ምስል በንጹህነት መበየንን ይወክላል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በንጹህነት ልመዘን" ወይም "እግዚአብሔር እንደ ንጽህናዬ ይፍረድብኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 31:7

አጠቃላይ መረጃ:
ኢዮብ የእግዚአብሔር ቅጣት እንደማይገባው ሁኔታዎችን መግለጹን ቀጥሏል፣ ይልቁንም፣ ጥፋት እንደሌለበት እና ንጹህ እንደሆነ ያውቃል። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

እርምጃዎቼ ከመንገድ ፈቀቅ ብለው ቢሆን
እዚህ ስፍራ "እርምጃዎቼ" የሚለው የኢዮብን ባህርይ የሚገልጽ ዘይቤ ሲሆን "ከመንገድ ፈቀቅ ብለው ቢሆን" የሚለው ከትክክለኛ አኗኗር መውጣትን የሚያሳይ ዘይቤ ነው። "ከጽድቅ ህይወት ዘወር ብዬ ቢሆን" ወይም "ትክክለኛ የሆነውን ማድረግ አቁሜ ቢሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ልቤ ዐይኖቼን ተከትሎ ሄዶ ቢሆን
እዚህ ስፍራ "ልቤ" እና "ዐይኖቼ" የሚሉት ኢዮብ ለሚፈልጋቸው እና ለሚያያቸው ነገሮች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ናቸው። ልብ ዐይንን ተከትሎ መሄድ የሚለው የተመለከተውን ለማድረግ መፈለግን የሚገልጽ ዘይቤ ነው። ይህ ኢዮብ የተመለከተውን በኃጢአት የተሞሉ ነገሮች ያመለክታል። "ከተመለከትኳቸው ክፉ ነገሮች አንዱን ለማድረግ ፈልጌ ቢሆን ኖሮ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

በእጄ ላይ አንዳች በደል ተገኝቶ ቢሆን
ይህ ጥፋተኝነትን ለማመልከት የሚውል ዘይቤ ነው። "በአንዳች በደል ውስጥ ብገኝ ኖሮ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህ ቢሆን፣ እኔ የዘራሁትን ሌላው ይብላው፣ ደግሞም የተከልኩት ከስሩ ይነቀል
ኢዮብ በእርግጥ በደል ፈጽሞ ቢሆን እነዚህ ክፉ ነገሮች ይድረሱብኝ እያለ ነው። በደል ፈጽሞ ቢሆን ከባድ የሆነውን የመዝራት ተግባር በእርሻው ላይ ያከናውናል ነገር ግን ከዚያ አንዳች መቅመስ አይችልም።

የተከልኩት ከስሩ ተነቅሎ ይጥፋ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሌላ ሰው መጥቶ ከእርሻዬ አዝመራዬን ይውሰድ። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 31:9

አጠቃላይ መረጃ:
ኢዮብ የእግዚአብሔር ቅጣት እንደማይገባው ሁኔታዎችን መግለጹን ቀጥሏል፣ ይልቁንም፣ ጥፋት እንደሌለበት እና ንጹህ እንደሆነ ያውቃል። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ልቤ በሴት ተታሎ ቢሆን
እዚህ ስፍራ "ልቤ" የሚለው የሚወክለው ኢዮብን ነው። "ተታሎ" የሚለው ቃል "ማማለልን/የዐይን ዐምሮትን" የሚገልጽ ሃሳብ ነው። "ሴት" የሚለው ቃል "የሌላ ሰው ሚስት የሆነችን ሴት" ይገልጻል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የሌላ ሰው ሚስት ብትስበኝ" ወይም "የሌላ ሰውን ሚስት ብመኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

በወዳጄ በር አድብቼ ብጠባበቅ
በወዳጁ በር ለምን አድብቶ እንደሚጠባበቅ በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "ከሚስቱ ጋር ለመተኛት በወዳጄ በር አድብቼ ብጠባበቅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ቢሆን የእኔ ሚስት ለሌላው ወፍጮ ትፍጭ
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ኢዮብ ሚስቴ ከሌላ ሰው ጋር ትተኛ የሚለውን በዩፊምዝም/ በማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት/ እየተናገረ ነው። 2) ይህ ማለት ሚስቱ ባሪያ ሆና ለሌላ ሰው ታገለግላለች። (ዩፊምዝም/ የማያስደስት ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 31:11

አጠቃላይ መረጃ:
ኢዮብ የእግዚአብሔር ቅጣት እንደማይገባው ሁኔታዎችን መግለጹን ቀጥሏል፣ ይልቁንም፣ ጥፋት እንደሌለበት እና ንጹህ እንደሆነ ያውቃል። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ክፉ ወንጀል በሆነብኝ ነበር
"ይህ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የኢዮብ ከሌላ ሴት ጋር የመተኛትን ክፉ በደል ነው።

ይህ በዳኞች ቅጣት የሚያስጥል ወንጀል ይሆናል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ይህ ዳኞች በእኔ ላይ ቅጣት ቢጥሉ/ቢፈጽሙ ትክክለኛ ናቸው የሚያሰኝ ወንጀል ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ እሳት ያለውን ሁሉ ይፍጀው፣ አዝመራዬንም ከስሩ ጭምር ያቃጥለው
ኢዮብ ከሌላ ሰው ሚስት ጋር መተኛት የሚያስከትለውን ጥፋት እሳት ሁሉንም ነገር ከማጥፋቱ ጋር ያነጻጽረዋል። "ይህ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከሌላ ሰው ሚስት ጋር መተኛትን ነው። "ማመንዘር ሁሉንም ነገር ከጫፍ ጫፍ እንደሚያጠፋ እና አዝመራን ሁሉ እንደሚያቃጥል እሳት ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከዳር እዳር ይፍጅ/ያቃጥል
እነዚህ ቃላት ምናልባት "ለቀሪው ዘመኔ አንዳች ሳያስቀር ሁሉንም ነገር ያጥፋ" ለሚለው ሀሳብ ዘይቤያዊ አገላለጽ ሊሆን ይችላል። ምናልባትም ደግሞ ይህንን ቃል በቃል መተረጎም ያስፈልጋል። ተከታዩን ይመልከቱ ([[:en: ta: vol1: translate: figs:-metaphor]])

አዝመራዬን ከስሩ ያቃጥል
እዚህ ስፍራ "ይህ" የሚለው ቃል ከሌላ ሰው ጋር የመተኛትን ድርጊት ያመለክታል። ይህ ድርጊት ኢዮብ ነገሩን አድርጎት ቢሆን ሊቀበለው ስለሚገባው ቅጣት በዘይቤ የቀረበ ነው። አዝመራውን የሚያቃጥል እሳት የደከመበትን ሁሉ ማጣት ለሚለው ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ነው። "እኔን የሚቀጡ የደከምኩበትን ሁሉ ይውሰዱት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።ተከታዩን ይመልከቱ ([[:en: ta: vol2: translate: figs:-metonomy]]) እና([[:en: ta: vol2: translate: figs:-synecdoche]])

Job 31:13

አጠቃላይ መረጃ:
ኢዮብ የእግዚአብሔር ቅጣት እንደማይገባው ሁኔታዎችን መግለጹን ቀጥሏል፣ ይልቁንም፣ ጥፋት እንደሌለበት እና ንጹህ እንደሆነ ያውቃል። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ኢዮብ እነዚህን ጥያቄዎች የሚያነሳው እግዚአብሔር በእርሱ ላይ እንዲፈርድ የሚያደርግ በደል ሰርቶ ራሱን ንጹህ
አድርጎ እንደማያቀርብ በትኩረት ለመግለጽ ነው። "እንዲህ ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር ሊፈርድብኝ ሲመጣ ራሴን ለመከላከል የማቀርበው አንዳች ነገር አይኖርም ነበር።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በማህጸን ያበጀኝ እነርሱንስ አላበጀምን? ሁላችንንም በማህጸን የሰራን እርሱ አይደለምን?
ኢዮብ እነዚህን ጥያቄዎች የሚያነሳው ከእርሱም አገልጋዮቹ እንደማይለይ በትኩረት ለመግለጽ ነው። አገልጋዮቹን ከራሱ ዝቅ አድርጎ ቢመለከት እግዚአብሔር እንደሚቆጣ ይናገራል። "በማህጸን የሰራኝ እርሱ፣ አነርሱንም ፈጥሯል። እርሱ ሁላችንንም በማህጸን ሰርቶናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 31:16

አጠቃላይ መረጃ:
ኢዮብ የእግዚአብሔር ቅጣት እንደማይገባው ሁኔታዎችን መግለጹን ቀጥሏል፣ ይልቁንም፣ ጥፋት እንደሌለበት እና ንጹህ እንደሆነ ያውቃል። ሀሳቡን በቁጥር 16 እና 17 ላይ አይጨርስም። ይልቁንም በቁጥር 18 ላይ እነዚህ ለምን ጥፋተኛ እንዳልሆነ ያብራራል። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ለድሆች የሚያስፈልጋቸውን ከልክዬ ከሆነ
"ድሆች የሚፈልጉትን እንዳያገኙ ከልክዬ ከሆነ"

የመበለቲቱ ዐይኖች በለቅሶ እንዲፈዙ አድርጌ ከሆነ
እዚህ ስፍራ "እየፈዘዙ እንዲሄዱ/እንዲፈዙ" የሚለው የሚያመለክተው መበለት ብዙ በማንባት ዐይኖቿ ሊፈዙ መቻላቸውን ነው። "አንዲት መበለት በታላቅ ሀዘን እንድታለቅስ ምክንያት ሆኜ ቢሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ቁራሼን
"ምግቤን"

ምክንያቱም ከልጅነቴ አንስቶ አባት ለሌላቸው እንደ አባት ሆኜ አሳድጌያለሁ
እዚህ ስፍራ "ወላጅ የሌላቸው" የሚለው የሚያመለክተው በአጠቃላይ ወላጆቻቸው ሞቱባቸውን ነው። ኢዮብ ወላጅ የሌላቸውን እንዴት ይረዳ እንደነበር ይናገራል። "ምክንያቱም ገና ወጣት ሳለሁ እንኳን ወላጅ የሌላቸውን እንደ አባት ሆኜ እንከባከባቸው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የስማዊ ሀረግ ክፍል የሚለውን ይመልከቱ)

በወጣትነቴ ምክንያት
"ከእነዚህ ነገሮች ውስጥ አንዱንም አልፈጸምኩም" የሚለው ሀረግ ትርጉም ከአውዱ/አገባቡ ግልጽ ነው። "ነገር ግን ከእነዚህ ነገሮች ውስጥ አንዱንም አልፈጸምኩም፣ ምክንያቱም ከወጣትነቴ አንስቶ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእናቴ ማህጸን አንስቶ መበለቲቱን ደግፌያለሁ
ኢዮብ መበለቶችን በእውነት እንዴት እንደ ደገፈ ይናገራል። "ከእናቴ ማህጸን አንስቶ" የሚለው ይህንን በህይወት ዘመኑ ሁሉ ማድረጉን በማጋነን ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። "ዘመኔን በሙሉ አባት የሌላቸውን ልጆች እናቶች ደግፌያለሁ" ወይም "ዘመኔን በሙሉ መበለቶችን ደግፌያለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 31:19

አጠቃላይ መረጃ:
ኢዮብ የእግዚአብሔር ቅጣት እንደማይገባው ሁኔታዎችን መግለጹን ቀጥሏል፣ ይልቁንም፣ ጥፋት እንደሌለበት እና ንጹህ እንደሆነ ያውቃል። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ልቡ ባርኮኝ ካልሆነ
"ልቡ/የእርሱ ልብ" የሚለው ሀረግ የሚወክለው ልብስ የሚፈልገውን የተራቆተ ድሃ ነው። "እርሱ አመስግኞኝ/ባርኮኝ ካልሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ከበጎቼ ፀጉር ከተሸለተው ለብሶ ሞቆት ካልሆነ
እዚህ ስፍራ "የበጎቼ ፀጉር" የሚለው የሚገልጸው ከኢዮብ በጎች ፀጉር የተሰራን ብርድ ልብስ ወይም ልብስ ነው። ይህ በአድርጊ ዐረፍተ ነገር ሊጸፍ ይችላል። "ከበጎቼ ሱፍ የተሰራው ልብስ ሳያሞቀው ቀርቶ ቢሆን" ወይም "ከበጎቼ ሲፍ የተሰራ ልብስ ሳልሰጠው ቀርቼ ቢሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

አባት በሌላቸው ላይ እጆቼን አንስቼ ቢሆን
በአንድ ሰው ላይ እጅን ማንሳት ማለት ያንን ሰው መጉዳትን ይገልጻል። "አባት የሌላቸውን አግባብ የሌለው ሁኔታ አድርሼባቸው ቢሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ድጋፌን በከተማ መግቢያ አይቻለሁ
እዚህ ስፍራ "ማየት" የሚለው "ማወቅ፣" ለሚለው ዘይቤ ሲሆን "ድጋፍ" የሚለው "ማረጋገጫ" ለሚለው ዘይቤ ነው። "የከተማ መግቢያ/በር" የሚለው ደግሞ በከተማዋ በር ለሚቀመጡ መሪዎች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ/ ነው። "በከተማዋ በር የሚቀመጡ መሪዎች ስለ እኔ እንደሚመሰክሩ አውቃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

በከተማይቱ በር
ይህ የከተማይቱ ታላላቅ ሰዎች ውሳኔ ለመስጠት የሚቀመጡበት ስፍራ ነው

በእኔ ላይ ክሳችሁን አቅርቡ
ይህ ሀረግ በመጀመሪያው ጽሁፉ በቀረበበት ቋንቋ ወይም በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች ውስጥ የለም። እዚህ የተጨመረው በኢዮብ ረዘም ያለ ንግግር ውስጥ ያለውን ሀሳብ ላለማጉደል ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Job 31:22

አጠቃላይ መረጃ፡
እንዲህ ከሆነ ትከሻዬ ከመጋጠሚያው ይነቀል፣ ክንዴም ደግሞ ከመታጠፊያው ይሰበር ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል፡፡ "እንዲህ ከሆነ አንድ ሰው ትከሻዬን ከመጋጠሚያው ይንቀለው ደግሞም ክንዴን ከመታጠፊያው ይስበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱን ግርማ ... ፈርቻለሁና
ኢዮብ ከቁጥር 7 አንስቶ እስከ 21 ድረስ ከተናገረው ውስጥ በአንዱም እንዳልበደለ የተናገረበት ምክንያት ይህ/የእርሱን ግርማ/ መፍራቱ ነው

Job 31:24

አጠቃላይ መረጃ፡
ኢዮብ የእግዚአብሔር ቅጣት እንደማይገባው ሁኔታዎችን መግለጹን ቀጥሏል፣ ይልቁንም፣ ጥፋት እንደሌለበት እና ንጹህ እንደሆነ ያውቃል፡፡ (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ወርቅን ተስፋ አድርጌ ቢሆን
"ተስፋ" የሚለው ረቂቅ ስም "ታመነ" ወይም "ተስፋ አደረገ" በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል፡፡ "በወርቅ ታምኜ ቢሆን" ወይም "የብዙ ወርቅ ባለቤት መሆን ይጠብቀኛል ብዬ ተስፋዬን ጥዬበት ቢሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ምርጥ የሆነውን ወርቅ 'የታመንኩት በአንተ ነው' ብዬው ቢሆን
ይህ ስንኝ/ቁጥር ከላይኛው ቁጥር ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እጄ ብዙ ሀብት ነበረው
እዚህ ስፍራ "እጄ" የሚለው የሚገልጸው የኢዮብን ነገሮችን የማከናወን አቅም ነው፡፡ "በችሎታዬ ብዙ ሀብት አከማችቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህ ከሆነ በእኔ ላይ ክስ አቅርቡ
ይህ ሀረግ በመጀመሪያው ጽሁፉ በቀረበበት ቋንቋ ወይም በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች ውስጥ የለም፡፡ እዚህ የተጨመረው በኢዮብ ረዘም ያለ ንግግር ውስጥ ያለውን ሀሳብ ላለማጉደል ነው፡፡

Job 31:26

አጠቃላይ መረጃ፡
ኢዮብ የእግዚአብሔር ቅጣት እንደማይገባው ሁኔታዎችን መግለጹን ቀጥሏል፣ ይልቁንም፣ ጥፋት እንደሌለበት እና ንጹህ እንደሆነ ያውቃል፡፡ (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የጨረቃ አካሄድ
እዚህ ስፍራ "አካሄድ" የሚወክለው ቀስ ብሎ መንቀሳቀስን ነው፡፡ "ጨረቃ ሰማይን እያቋረጠች ስትንቀሳቀስ"

ጨረቃ በድምቀቷ ስትራመድ
"ድምቀት" የሚለው ረቂቅ ስም "ብሩህ" ወይም "በብሩህነት" በሚሉ ቃላት ሊገለጽ ይችላል፡፡ "ብሩኋ ጨረቃ ሰማይን እያቋረጠች ስትንቀሳቀስ" ወይም "ጨረቃ ብሩህ ሆና በሰማይ ስትንቀሳቀስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ልቤ በስውር ተስቦ ቢሆን
እዚህ ስፍራ "ልቤ" የሚለው የሚወክለው ኢዮብን ነው፡፡ ይህ ሀረግ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል፡፡ "በድብቅ ወደ እነርሱ ተስቤ ቢሆን" ወይም "በድብቅ እነርሱን ለማምለክ ፈልጌ ቢሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

በዚህም ምክንያት አፌ እጄን ስሞ ቢሆን
እዚህ ስፍራ "አፌ" የሚለው የሚወክለው ኢዮብን ነው፡፡ ይህ የፍቅር እና የተመስጦ ምልክት ነው፡፡ "ስለዚህም እጄን ስሜ ቢሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱን ለማምለክ
"ፀሐይን እና ጨረቃን ለማምለክ"

በዳኞች መቀጣት
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል፡፡ "የትኛዎቹ ዳኞች እኔን ቢቀጡኝ ትክክለኛ ይሆናሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰማይ ያለውን አምላክ ክጄ ቢሆን
"በላይ ላለው እግዚአብሔር አምላክ ታማኝ ሳልሆን ቀርቼ ቢሆን"

Job 31:29

አጠቃላይ መረጃ፡
ኢዮብ የእግዚአብሔር ቅጣት እንደማይገባው ሁኔታዎችን መግለጹን ቀጥሏል፣ ይልቁንም፣ ጥፋት እንደሌለበት እና ንጹህ እንደሆነ ያውቃል፡፡ (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

እኔን የሚጠሉ ሁሉ በሚጠፉበት ጊዜ
"ጥፋት" የሚለው ረቂቅ ስም "ጠፋ" በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል፡፡ "እኔን የሚጠላ ማንም ቢሆን በሚጠፋበት ጊዜ" ወይም "እኔን በሚጠላ ማንም ሰው ክፉ ነገር በሚደርስበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱን ጥፋት በሚውጠው ጊዜ
"ጥፋት ሲደርስበት"

እንዲህ ከሆነ/በዚይን ጊዜ በእኔ ላይ ክስ አቅርቡ
ይህ ሀረግ በመጀመሪያው ጽሁፉ በቀረበበት ቋንቋ ወይም በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች ውስጥ የለም፡፡ እዚህ የተጨመረው በኢዮብ ረዘም ያለ ንግግር ውስጥ ያለውን ሀሳብ ላለማጉደል ነው፡፡

በእርግጥ፣ አፌ እንኳን ኃጢአት እንዲናገር አልፈቀድኩም
እዚህ ስፍራ "አፌ/አንደበቴ" የሚለው የሚወክለው የኢዮብን ንግግር ነው፡፡ "በእውነት ራሴን ለኃጢአት አሳልፌ አልሰጠሁም" ወይም "በእውነት፣ ኃጢአት አልሰራሁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ ህይወት እንዲረገም በመጠየቅ
እዚህ ስፍራ "የእርሱ ህይወት እንዲረገም በመጠየቅ" የሚለው የሚገልጸው አንድ ሰው እንዲሞት መራገምን ነው፡፡ "ይሞት ዘንድ እርሱን በመርገም" ወይም "ህይወቱን በመርገም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 31:31

አጠቃላይ መረጃ፡
ኢዮብ የእግዚአብሔር ቅጣት እንደማይገባው ሁኔታዎችን መግለጹን ቀጥሏል፣ ይልቁንም፣ ጥፋት እንደሌለበት እና ንጹህ እንደሆነ ያውቃል፡፡ (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የጎጆዬ/የቤቴ ሰዎች
ጎጆው የሚወክለው የኢዮብን ቤት ነው። የጎጆው ሰዎች የሚያጠቃልለው የቤተሰቡን አባላት እና አገልጋዮቹን ነው። እነዚህ ሁሉ ኢዮብን በሚገባ ያውቁታል። "የቤቴ ሰዎች" ወይም "የቤተሰቤ አባላት እና አገልጋዮቼ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ማን ከኢዮብ ገበታ ያልጠገበን ሰው ማግኘት ይችላል?
የኢዮብ ሰዎች ይህንን ጥያቄ ኢዮብ ለጋስ ሰው እንደሆነ በትኩረት ለመግለጽ ሊያነሱ ይችላሉ። "ሁሉም ከኢዮብ ገበታ በልቶ ጠግቧል!" ወይም "እኛ የምናውቀው ሁሉ የፈለገውን ያህል ከኢዮብ ምግብ ተመግቧል!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ባዕድ እንኳን በከተማ አደባባይ አይረሳም ነበር
ኢዮብ እንግዶችን እንዴት ይንከባከብ እንደነበር ተገልጽዋል። እዚህ ስፍራ "በከተማ አደባባይ መቀመጥ" የሚለው የሚገልጸው በከተማ አደባባይ ምሽቱን ማደርን ነው። "እንግዶች ፈጽሞውኑ በከተማይቱ አደባባይ በሜዳ ላይ አያድሩም ነበር" ወይም "እንግዶች/ባዕዳን ውጭ አያድሩም ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሌም በሮቼን ለመንገደኞች ክፍት አደርግ ነበር
እዚህ ስፍራ "ለመንገደኞች በሬን እከፍት ነበር" የሚለው የሚወክለው ወደ ቤቱ መንገደኞችን መቀበሉን ነው። "ሁሌም መንገደኞችን በቤቴ እቀበል ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እናም ነገሩ ይህ ባይሆን፣ በዚያን ጊዜ በእኔ ላይ ክስ አቅርቡ
ይህ ሀረግ በመጀመሪያው ጽሁፉ በቀረበበት ቋንቋ ወይም በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች ውስጥ የለም። እዚህ የተጨመረው በኢዮብ ረዘም ያለ ንግግር ውስጥ ያለውን ሀሳብ ላለማጉደል ነው።

Job 31:33

አጠቃላይ መረጃ:
ኢዮብ የእግዚአብሔር ቅጣት እንደማይገባው ሁኔታዎችን መግለጹን ቀጥሏል፣ ይልቁንም፣ ጥፋት እንደሌለበት እና ንጹህ እንደሆነ ያውቃል። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ኃጢአቴን... ደብቄ/ሰውሬ ቢሆን
እዚህ ስፍራ "ኃጢአቴን ሰውሬ ቢሆን" የሚለው የሚወክለው እርሱ ኃጢአት መስራቱን ሰዎች እንዳያውቁበት ለመደበቅ ሞክሮ ያውቅ እንደሆነ ነው። "ኃጢአቴን... ሰዎች እንዳያውቁ ለመደበቅ ሞክሬ እንደሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኃጢአቴን በካቦርቴ ውስጥ በመሰወር
ይህ የሚወክለው እርሱ በደለኛ መሆኑን ሰዎች እንዳያውቁ ለመደበቅ መሞከርን ነው። "የበደሎቼን ማስረጃዎች በካቦርቴ ውስጥ በመሸሸግ" ወይም "በካቦርቴ ውስጥ የበደሉን ማስረጃዎች እንደሚሸሸግ ሰው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ብዙ ህዝብ በመፍራት፣ ከቤተሰብ የሚመጣን ንቀት በመፍራት
ኃጢአቱን ለመደበቅ ምክንያት ሊሆን የሚችለው ይህ ነው። እነዚህ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ትኩረት የሚሰጡት አንድ ሰው ኃጢአቱን የሚሸሸገው ሰዎች ስለ እርሱ የሚኖራቸውን አስተሳሰብ በመፍራት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚያን ጊዜ በእኔ ላይ ክስ አቅርቡ
ይህ ሀረግ በመጀመሪያው ጽሁፉ በቀረበበት ቋንቋ ወይም በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች ውስጥ የለም። እዚህ የተጨመረው በኢዮብ ረዘም ያለ ንግግር ውስጥ ያለውን ሀሳብ ላለማጉደል ነው።

Job 31:35

አወይ፣ ምነው የሚሰማኝ ባገኘሁ!
ይህ አጋኖ የኢዮብን ፍላጎት/የሚመኘውን ይገልጻል። "የሚሰማኝ ባገኝ በመደድሁ" ወይም "የሚሰማን ሰው ባገኝ እወዳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ አጋኖዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ፊርማዬ እነሆ
እዚህ ስፍራ "ፊርማዬ" የሚለው የሚገልጸው፣ ኢዮብ የተናገረው ነገር ሁሉ እውነት መሆኑን ቃል መግባቱን ነው። ስለ ደረሰበት ነገር ህጋዊ ሰነድ እንደጻፈ አድርጎ ይናገራል። "የተናገርኩት እውነት መሆኑን በእርግጥ ቃል እገባለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉን ቻይ የሆነው እርሱ ይመልስልኝ!
እዚህ ላይ ምላሽ የሚለው የሚያመለክተው ምናልባት ኢዮብ ምን ስህተት እንደፈጸመ የሚከሰስበትን የሚነግረውን መፈለጉን ይሆናል። "ሁሉን ቻይ የሆነው እርሱ የሰራሁትን በደል ይንገረኝ" ወይም "ሁሉን ቻይ የሆነው የሰራሁት በደል ምን እንደሆነ ቢነግረኝ እወዳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ተቃዋሚዎቼ በእኔ ላይ የጻፉትን የክስ ማስረጃ ባውቅ በወደድኩ!
ይህ የኢዮብን ፍላጎት ይገልጻል። ኢዮብ አንድ ሰው እርሱን ኃጢአተኛ አድርጎ ለመክሰሱ ማስረጃ አድርጎ የሚያቀርበው የደረሰበትን ችግር ነው። "የትኛውም ተቃዋሚ የሚያቀርብብኝ ክስ ቢኖር በወደድኩ" ወይም "ምነው ተቃዋሚዬ የሚያቀርብብኝን ክስ ማንበብ በቻልኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ተቃዋሚዬ/ባለጋራዬ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ እግዚአብሔርን ሊያመለክት ይችላል ወይም 2) ሌላ አካልን ሊያመለክት ይችላል

በእርግጥ ክሱን በግልጽ በትክሻዬ እሸከመዋለሁ፤ እንደ ዘውድ በራሴ ላይ እጭነዋለሁ
ይህ የሚወክለው ክሱን ማንም ሊያነበው በሚችለው ስፍራ ማስቀመጥን/ማድረግን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ልበ ሙሉ ልዑል ወደ እርሱ ዘንድ እሄዳለሁ
ይህ ማለት ኢዮብ ኃጠአት ባለመስራት አንዳች ፍራቻ ወደ እግዚአብሔር እንደሚቀርብ ይናገራል። ኢዮብ ይህን ማድረግ እንደሚችል የሚናገረው ጥፋተኛ ስላልሆነ ነው። "በድፍረት ወደ እርሱ እቀርባለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 31:38

አጠቃላይ መረጃ:
ኢዮብ የእግዚአብሔር ቅጣት እንደማይገባው ሁኔታዎችን መግለጹን ያጠቃልላል፣ ይልቁንም፣ ጥፋት እንደሌለበት እና ንጹህ እንደሆነ ያውቃል። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሬ በእኔ ላይ ቢያለቅስብኝ፣ እርሻዩ በአንድነት ቢያለቅስ
ኢዮብ ጥፋተኛ ስላለመሆኑ የሚናገረው ምድሩ ሰው እንደሆነ እና እርሻውን በመበደሉ ምክንያት በእርሱ ላይ እንደሚያለቅስበት አድርጎ ነው። "እርሻዬን በሚመለከት አንዳች ስህተት ሰርቼ ቢሆን" ወይም "እርሻዬን/ መሬት ከሌላ ሰው ሰርቄ ቢሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ህይወታቸው እንዲያልፍ
ይህ ሞትን ያመለክታል። "እንዲሞት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በገብስ ፈንታ አረም
"ይሁን" እና "ይብቀል" የሚሉት ከቀደመው ሀረግ ይታወቃሉ። "በገብስ ፈንታ አረም ይብቀል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 32

1 ኢዮብም ራሱን ጻድቅ አድርጎ ስላስቀመጠ እነዚያ ሦስቱ ሰዎች ምላሽ መስጠት አለብህ። **2** ከራም ቤተሰብ የሆነ የቡዛዊው የባርክኤል ልጅ ኤሊሁ እጅግ ተቆጣ፤ ከእግዚአብሔር ይልቅ ራሱን ስላጸደቀ ኢዮብን ተቈጣው። **3** ደግሞም በኢዮብ ፈረዱበት እንጂ የሚገባ መልስ ስላልሰጡት በሦስቱ ጓደኞቹ ላይ ተቈጣ። **4** ከእርሱ ይልቅ ሰዎቹ ሽማግሌዎች ስለነበሩ ኤሊሁ ከኢዮብ ጋር ለመነጋገር ተራውን ይጠብቅ ነበር። **5** ቢሆንም ግን ኤሊሁም በእነዚህ በሦስቱ ሰዎች አፍ መልስ እንደሌለ ሲያይ በጣም ተቆጣ። **6** ቡዛዊውም የባርክኤል ልጅ ኤሊሁ መናገር ሲጀምር እንዲህም አለ፦ እኔ በዕድሜ ወጣት ነኝ፥ እናንተም ሽማግሌዎች ናችሁ፤ ስለዚህም ሰጋሁ፤ እውቀቴን እንዳልናገር ራሴን ገታሁ። **7** እንደዚህም አልሁ፦ የቀናት ርዝመት ንግግርን፥ የዓመታትም ብዛት ጥበብን ሊያስተማሩ ይገባ ነበር። **8** ነገር ግን በሰው ውስጥ መንፈስ አለ፤ የሁሉን ቻዩ እስትንፋስ ማስተዋልን ይሰጠዋል። **9** ታላላቅ ሰዎች በመሆናቸው ብቻ ጥበበኞች አይደሉም፣ በእድሜ የገፉ ስለሆኑ ብቻም ፍትሕን አያስተውሉም። **10** ስለዚህ እንዲህ እላችኋለሁ፥ 'አድምጡኝ፤ እኔም ደግሞ የማውቀውን እነግራችኋለሁ'። **11** ተመልከቱ፥ እስክትናገሩ ጠበቅኋችሁ፥ ምን መናገር እንዳለባችሁ በማሰብ ላይ እያላችሁም ክርክራችሁን አዳመጥኩኝ። **12** በርግጥ ትኩረቴን ሰጠኻችሁ፥ ነገር ግን፥ ተመልከቱ፥ አንዳችሁም ኢዮብን ማስረዳት ወይም ለቃሎቹ ምላሽ መስጠት አልቻላችሁም። **13** 'ጥበብን አግኝተናል!' እንዳትሉ ተጠንቀቁ ኢዮብን ማሸነፍ ያለበት እግዚአብሔር ነው፤ ተራ ሰው ይህንን ለማድረግ አይችልም። **14** ኢዮብ እኔን በመቃወም አልተናገረምና እኔም የእናንተን በሚመስል ቃል አልመልስለትም። **15** እነዚህ ሦስት ሰዎች ዲዳ ሆነዋል፤ ከዚህ በኋላ ለኢዮብ ሊመልሱለት አይችሉም፤ ቀጥለው የሚናገሩት አንድም ቃል የላቸውም። **16** እዚያ በዝምታ ስለቆሙና ከእንግዲህ ስለማይመልሱ፥ ስለማይናገሩም፥ መጠበቅ አለብኝ? **17** አይሆንም፥ እኔም ደግሞ የበኩሌን እመልሳለሁ፤ እኔም ደግሞ ዕውቀቴን እነግራቸዋለሁ። ቃል **18** ተሞልቻለሁና፤ በውስጤ ያለው መንፈስም ይገፋፋኛል። **19** ተመልከቱ፥ ውስጤ ተከድኖ እንደሚብላላ ወይን ነው፤ ሊፈነዳ እንደተቃረበ አዲስ የወይን ጠጅ አቁማዳም ነው። **20** አርፍ ዘንድ እናገራለሁ፤ አፌንም ከፍቼ መልስ እሰጣለሁ። **21** አድልዎ አላደርግም፤ የትኛውንም ሰው አላቆላምጥም። **22** እንዴት እንደማቆላምጥ አላውቅምና፤ እንዲህ ባደርግ ኖሮ ፈጣሪዬ ፈጥኖ ያስወግደኝ ነበር።

Job 32:1

እርሱ በራሱ ዐይኖች ፊት ጻድቅ ነበር
ዐይኖች የሚመክሉት ማየትን ስሆን፣ ማየት የሚወክለው ሃሳብን ወይም ፍርድን ነው። "ራሱን ጻድቅ አድርጎ ቆጥሯል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያም የራም ቤተሰብ የሆነው የቡዛዊው የባሮክ ልጅ የኤሊሁ ቁጣ ነደደ፤ ቁጣው የነደደው በኢዮብ ላይ ነበር
ይህ የሚያነጻጽረው የኤሊሁን ቁጣ አንድ ሰው እሳት ከመለኮሱ ጋር ነው። እንደዚሁም፣ ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ከዚያም የራም ቤተሰብ የሆነው የቡዛዊው የባሮክ ልጅ የኤሊሁ ቁጣ በኢዮብ ላይ እጅግ ነደደ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ኤሊሁ... ባሮክ...ራም
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ቡዛዊ
ይህ የህዝብ የወል/የቡድን ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ሳይለው ራሱን ጻድቅ አድረጓል
ይህ ማለት፣ ራሱን ንጹህ አድርጎ፤ እርሱን በመቅጣቱ እግዚአብሔር ጥፋተኛ እንደሆነ አምኗል። "ራሱን አጽድቆ እርሱን ስለቀጣው እግዚአብሔርን ጥፋተኛ ነው ብሏል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 32:3

የኤሊሁ ቁጣ የነደደው በሶስቱ ወዳጆቹም ላይ ጭምር ነበር
ይህ የኤሊሁን ቁጣ እሳትን ከመለኮስ ጋር ያነጻጽራል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እንደዚሁም ደግሞ ኤሊሁ በሶስቱ ወዳጆቹ ላይ እጅግ ተቆጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

እነሆ/አሁን
ይህ ቃል በዚህ ስፍራ የዋለው በዋናው ታሪክ ላይ ማረፊያ ለማበጀት ነው። ይህ ስለ ኤሊሁ የመረጃ ዳራ/የቀደመ ማስረጃ ይሰጣል። (የመረጃ ዳራ/የቀደመ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በእነዚህ ሶስት ሰዎች አፍ አንዳች መልስ አልተገኘም
ይህ ማለት ሰዎቹ ከኢዮብ ጋር መነጋገራቸውን ጨርሰው/አብቅተው ነበር። ይህ፣ መልስ በሰዎቹ አፍ ላይ የሚገኝ ነገር ቢሆን ኖሮ ምናልባት መልስ ያገኙ እንደ ነበር ይገልጻል። "እነዚህ ሶስት ሰዎች ሌላ የሚናገሩት ነገር የላቸውም" ወይም "እነዚህ ሶስት ሰዎች ለኢዮብ የሚሰጡት ሌላ ምንም ተጨማሪ መልስ የላቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ቁጣው ነድዶ ነበር
ይህ የኤሊሁን ቁጣ እሳትን ከመለኮስ ጋር ያነጻጽራል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በጣም ተቆጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 32:6

እናንተ አዛውንቶች ናችሁ/በጣም ሽማግሌዎች ናችሁ
እዚህ ስፍራ "እናንተ" የሚለው ብዙ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተውም ኢዮብን እና ሶስቱን ወዳጆቹን ነው። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመለከቱ)

የቀናት እርዝመት መናገር መቻል አለበት፣ የአመታት ብዛት እውቀትን መስጠት አለበት
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ኤሊሁ ትኩረት የሰጠው ከወጣቶች ይልቅ አዛውንቶች ጥበብ የቀሰሙ በመሆናቸው የሚያውቁትን አስቀድሞ መናገር እንደሚገባቸው ነው። "ብዙ ዘመናትን የኖረ እርሱ መናገር አለበት፤ አዛውንት የሆነው እርሱ ጥበብን ማስተማር ይገባዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 32:8

አጠቃላይ መረጃ:
ኤሊሁ ለኢዮብ እና ለእርሱ ወዳጆች መናገሩን ቀጥሏል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሁሉን ቻይ የሆነው እስትንፋስ፤ በሰው ውስጥ መንፈስ አለ
ሁለቱ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አቸላቸው። ኤሊሁ የሰው ጥበብ ከእግዚአብሔር እንደሚመጣ ትኩረት ይሰጣል። "በሰው ውስጥ መንፈስ አለ፣ ይህም፣ ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ እስትንፋስ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ እስትንፋስ
እዚህ መንፈስ የሚለው የተወከለው በ"እስትንፋስ" ነው። "ሁሉን ቻይ የሆነው የእርሱ መንፈስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 32:11

እነሆ
ኤሊሁ እዚህ ስፍራ ይህንን ቃል የተጠቀመው የሰዎቹን ትኩረት ቀጥሎ ወደሚናገረው ነገር ለመሳብ ነው። "አድምጡኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ቃላችሁን አደመጥኩ
"የተናገራችሁትን ስሰማ ቆየሁ።" "እናንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የኢዮብን ወዳጆች ነው። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)

ለእርሱ ቃላት ማን ምላሽ ሊሰጥ ይችላል
እዚህ ስፍራ "ምላሽ" የሚለው ቃል መልስ ማለት ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን ጠቃሚ የሆነ ምላሽ መስጠት ነው።

Job 32:13

አጠቃላይ መረጃ:
ኤሊሁ ለኢዮብ ወዳጆች መናገሩን ቀጥሏል

እኛ እውቀት አግኝተናልን/አለን
ይህ ማለት ጠቢብ ምን እንደሆነ ለይተው እንደሚያውቁ ያምናሉ ማለት ነው። "ጠቢብ ምን እንደሆነ እኛ አውቀናል/ደርሰንበታል"

ኢዮብን ለማሸነፍ
ይህ የሚገልጸው እግዚአብሔር ለኢዮብ ምላሽ እንደሚሰጥ እና እርሱን በጦርነት እንዳሸነፈ አድርጎ እንደሚያስተካክለው ነው። "ኢዮብን ለመቃወም" ወይም "ለኢዮብ መልስ ለመስጠት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በበአፍህ ቃል
"ያልከውን በማለትህ"

Job 32:15

አጠቃላይ መረጃ:
ኤሊሁ መናገሩን ቀጥሏል

እጅግ መገረም
መደነቅ፣ መናገር አለመቻል

እነርሱ ስላልተናገሩ፣ በዚያ በጸጥታ ስለቆሙ እና መልስ መስጠት ስላቆሙ እኔ ዝም ማለት ይኖርብኛል?
ኤሊሁ ጥያቄውን የሚጠቀምበት ከእንግዲህ በኋላ ዝም ብሎ እንደማይቆይ ትኩረት ለመስጠት ነው። ኤሊሁ በቀጣዩ ቁጥር ለጥያቄው ራሱ መልስ ይሰጣል። "ነገር ግን እናንተ ዝም ስላላችሁ፣ እኔ በእርግጥ ከእንግዲህ ዝም አልልም፤ እናንተ ዝም ብላችሁ ቆማችኋል ምላሽ መስጠትም አቁማችኋል።"

በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 32:17

አጠቃላይ መረጃ:
ኤሊሁ ትይዩ ተነጻጻሪ ዘይቤን በመጠቀም መናገሩን ቀጥሏል።

እኔም የበኩሌን መልስ እሰጣለሁ
"እኔ አሁን በተራዬ መልስ እሰጣለሁ"

በቃላት ተሞልቻለሁ
ኤሊሁ በቃላት እንደመሞላቱ መጠን የሚናገረው ብዙ እንዳለው ይገልጻል። "ብዙ የምናገረው አለኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በውስጤ ያለው መንፈስ ግድ ይለኛል
"መንፈሴ እንድናገር ያስገድደኛል"

ደረቴ መተንፈሻ እንዳጣ እንደ ፈለ ወይን፣ እንደ አዲስ የወይን አቁማዳ፣ ለመፈንዳት ተዘጋጅቷል
ወይን በሚፈለበት ጊዜ፣ በመያዣው ውስጥ አየር ይታመቃል። አየሩ መውጫ ካላገኘ አቁማዳው ይፈነዳል። ኤሊሁ ይህንን ሲል ብዙ የሚናገረው እንዳለው እና ይህንን ካልተናገረ የሚፈነዳ ሆኖ እንደተሰማው መግለጹ ነው፤ ምንም እንኳን እነዚህ ሁለት ሃሳቦች ትይዩ ቢሆኑና ትርጉማቸው ግን ተመሳሳይ ቢሆንም። "የሚተመፍስበት እንዳጣ የፈለ ወይን ጠጅ እንደያዘ አቁማዳ ደረቴ የሚፈነዳ ሆኖ ይሰማኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ትይዩ ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ደረቴ ... ነው
ይህ የሚገልጸው ኤሊሁን ሲሆን፣ በተለይም መንፈሱን ነው። "መንፈሴ...ነው" ወይም "እኔ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 32:20

አጠቃላይ መረጃ:
ኤሊሁ ትኩረት ለመስጠት ትይዩ ተነጻጻሪ ዘይቤን በመጠቀም መናገሩን ቀጥሏል።

እታደስ ይሆናል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የተሸለ /እፎይታ ሊሰማኝ ይችላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ከንፈሮቼን አንቀሳቅሳለሁ
እዚህ ስፍራ "ከንፈሮች" የሚለው የሚወክለው አፍን/አንደበትን ነው። "አፌን እከፍታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ለማንም ሰው የከበረ መጠሪያ አልሰጥም
"ማንንም አላወድስም ወይም ለማንም የክብር ስም አልሰጥም"

ያበጀኝ/የሰራኝ
ይህ እግዚአብሔርን የሚያመለክት ስም ነው። "ያበጀኝ እርሱ እግዚአብሔር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ይወስደኛል
ይህ ማለት እርሱ ያጠፋዋል ማለት ነው። "ያጠፋኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 33

1 አሁንም ኢዮብ ሆይ፥ ቃሎቼን እንድትሰማ፥ ንግግሬንም እንድታደምጥ እለምንሃለሁ። 2 ይኸው አሁን አፌን ከፍቻለሁ፤ ምላሴም በአፌ ውስጥ ተናግሯል። 3 ቃሎቼ የልቤን ቅንነት ይናገራሉ፤ ከንፈሮቼ የሚያውቁትን በታማኝነት ይናገራሉ። 4 የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጠረኝ፤ የሁሉን ቻዩ እስትንፋስ ሕይወትን ሰጠኝ። 5 ከቻልክ መልስልኝ፤ በፊቴም ቃሎችህን በቅደም ተከተል አዘጋጅና ቁም። 6 ተመልከት፥ በእግዚአብሔር ፊት አንተ እንደሆንከው እንዲሁም እኔም ነኝ፤ እኔም ደግሞ ከጭቃ ተሠርቻለሁ። 7 ተመልከት፥ ማስፈራራቴ አያስፈራህም፤ ተጽዕኖዬም ቢሆን አይከብድብህም። 8 በእርግጥ በጆሮዬ ተናግረሃል፤ እንዲህ የሚለውንም የቃልህን ድምፅ ሰምቻለሁ፥ 9 ንጹሕ ነኝ መተላለፍም የለብኝም፤ አልበደልኩም፥ ኃጢአትም የለብኝም። 10 ይኸው፥ እግዚአብሔር ሊያጠቃኝ አጋጣሚ ይፈልጋል፤ እንደ ጠላቱ አድርጎ ይቆጥረኛል። 11 እግሮቼን በግንድ ውስጥ ያስገባቸዋል፤ መንገዶቼንም ሁሉ ይመለከታል። 12 እግዚአብሔር ከሰው ይበልጣልና እንደዚህ መናገርህ ትክክል አይደለም ብዬ እመልስልሃለሁ። 13 ለየትኛውም ሥራው ትኩረት አይሰጠውም በማለት ከእርሱ ጋር ለምን ትታገላለህ? 14 ሰው ባያስተውለውም እግዚአብሔር አንድ ጊዜ፥ አዎን፥ ሁለት ጊዜ ይናገራል። 15 ሰዎች አልጋቸው ላይ ተኝተው ከባድ እንቅልፍ በሚወድቅባቸው ጊዜ በህልም፥ በሌሊት ራዕይ ይናገራቸዋል። 16 በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር የሰዎችን ጆሮ ይከፍትና በማስጠንቀቂያው ያስፈራራቸዋል፤ 17 ይህንን የሚያደርገውም ሰውን ከኃጢአታዊ ዓላማው ሊመልሰውና ከትዕቢት ሊጠብቀው ነው። 18 እግዚአብሔር የሰውን ሕይወት ከጉድጓድ ይጠብቃል፥ ሕይወቱንም ወደ ሞት ከመውረድ። 19 ደግሞም ሰው በአልጋው ላይ በሕመም ይቀጣል፥ በአጥንቶቹም ውስጥ በማያቋርጥ ስቃይ፤ 20 ሕይወቱ ምግብን፥ ነፍሱም ጣፋጩን መብል እስክትጠላ ድረስ። 21 ሥጋው ሊታይ እስከማይችል ድረስ ጠፍቷል፥ የማይታዩ የነበሩት አጥንቶቹም አሁን ገጠው ወጥተዋል። 22 በርግጥ ነፍሱ ወደ ጉድጓድ ቀርባለች፥ ሕይወቱም ሊያጠፏት ወደሚፈልጉት። 23 ነገር ግን መካከለኛ ሊሆንለት የሚችል አንድ መልአክ ቢኖር፥ የትኛውን መልካም ነገር ማድረግ እንዳለበት የሚያሳየው፥ መካከለኛ የሚሆንለት ከሺህ መላእክት አንድ ቢገኝለት፥ 24 መልአኩም ለእርሱ ደግ ቢሆንና እግዚአብሔርን፥ 'ቤዛ የሚሆንለት አግኝቻለሁና ይህንን ሰው ወደ ጉድጓድ ከመውረድ አድነው' ቢለው 25 በዚያን ጊዜ ሥጋው ከሕፃን ገላ ይልቅ ይታደሳል፤ ወደ ወጣትነት የብርታቱ ዘመንም ይመለሳል። 26 እርሱ ወደ እግዚአብሔር ይጸልያል፥ እግዚአብሔርም ይራራለታል፥ እርሱም የእግዚአብሔርን ፊት በደስታ ያያል። እግዚአብሔርም ለሰውየው ድልን ይሰጠዋል። 27 ከዚያም ያ ሰው በሌሎች ሰዎች ፊት እንዲህ ሲል ይዘምራል፥ 'ኃጢአትን ሠርቻለሁ፥ ትክክለኛ የሆነውንም አጣምሜአለሁ፥ ይሁን እንጂ ስለኃጢአቴ አልተቀጣሁም። 28 እግዚአብሔር ነፍሴን ወደ ጉድጓድ ከመውረድ አዳናት፤ ሕይወቴም ብርሃን ማየቷን ትቀጥላለች"። 29 ተመልከቱ፥ እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች ሁሉ በሰው ሕይወት ሁለት ጊዜ፥ አዎን፥ እንዲያውም ሦስት ጊዜ ያደርጋቸዋል፤ 30 ይኸውም የሕይወት ብርሃን ይበራለት ዘንድ ነፍሱን ከጉድጓድ ለመመለስ ነው። 31 ኢዮብ ሆይ አስተውለህ ስማኝ፤ ዝም በል፥ እኔም እናገራለሁ። 32 የምትናገረው ነገር ካለህ መልስልኝ፤ ትክክለኛ መሆንህን ለማረጋገጥ እፈልጋለሁና ተናገር። 33 ካልሆነ ግን ጸጥ ብለህ ስማኝ፤ እኔም ጥበብን አስተምርሃለሁ“።

Job 33:1

አጠቃላይ መረጃ:
ኤሊሁ መናገሩን ቀጥሏል።

ንግግሬን አድምጡ፤ ቃሎቼን ሁሉ ስሙ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርም አላቸው። ኤሊሁ ኢዮብ በጥንቃቄ ሊያደምጥ እንደሚገባው ትኩረት ሰጥቶ ይናገራል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ አፌን እከፍታለሁ... ምላሶቼ የአንደበቴን ቃል ይናገራሉ
እነዚህ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ኤሊሁ አሁን ለመናገር ዝግጁ መሆኑን በትኩረት ይገልጻል። የእርሱ "ምላስ" ንግግር የሚወክለው የራሱን ንግግር ነው። "አፌን ከፍቼ መናገር ጀምሬያለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

ቃሎቼ ከልቤ ቅንነት ይፈልቃሉ
እዚህ ስፍራ ኤሊሁ ትክክል መሆኑን የሚገልጸው በ"ልቡ" ቅንነት ነው። "በጽድቅ እናገራለሁ" ወይም "በሙሉ ቅንነት እናገራለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ከንፈሮቼ መልካም እውቀት ይናገራሉ
እዚህ ስፍራ ኤሊሁ በ"ከንፈሮቹ" ራሱን የሚወክለው ለንግግሩ ትኩረት ለመስጠት ነው። "በትክክለኛ አቋም እናገራለሁ" ወይም "በፍጹም ቅንነት እናገራለሁ" (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 33:4

አጠቃላይ መረጃ:
ኤሊሁ ለኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል።

የእግዚአብሔር መንፈስ ... ህይወት ሰጠኝ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ኤሊሁ እግዚአብሔር እርሱን እንደሰራው እና ለሚናገረው ሀላፊነትን እንደሰጠው ትኩረት ይሰጣል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቃሎችን አሰናድተህ በፊቴ ለመቆም ተዘጋጅ
ይህ የሚገልጸው ኢዮብ የሚናገረውን አካላዊ ቁሶችን እንደሚደረድር እንዲያሰናዳ ነው። "የምትናገረውን አሰናዳ፣ ከዚያም ቆመህ/ታጥቀህ መልስልኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 33:6

አጠቃላይ መረጃ:
ኤሊሁ ለኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል።

እነሆ
ኤሊሁ እዚህ ስፍራ ይህንን ቃል የተጠቀመው የኢዮብን ትኩረት ቀጥሎ ወደሚናገረው ነገር ለመሳብ ነው። "አድምጡኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

በእግዚአብሔር እይታ እኔም ልክ እንደ አንተ ነኝ
እዚህ ስፍራ እይታ የሚወክለው ፍርድን ወይም ሚዛንን ነው። "በእግዚአብሔር ፍርድ እኔም ልክ እንደ አንተ ነኝ" ወይም "እግዚአብሔር በአንተ ላይ በሚፈርድበት ተመሳሳይ መንገድ በእኔም ላይ ይፈርዳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እኔም ደግሞ የተበጀሁት ከሸክላ ነው
ምንም እንኳን ሰዎች ከሸክላ ባይሰሩም፣ ሸክላ ሰራተኛ ነገሮችን በጥንቃቄ ከሸክላ እንደሚያበጅ እግዚአብሔር ሁሉንም አበጅቷል። "ሸክላ ሰራተኛ ነገሮችን ከሸክላ እንደሚሰራ እግዚአብሔር ሁለታችንንም ሰርቶናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔም ደግሞ ተሰርቻለሁ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር እኔንም ደግሞ አበጅቶኛል" ወይም "እግዚአብሔር ሁለታችንንም አበጅቶናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የእኔ ማስደንገጥ አንተን አያስፈራህም
"እኔን ልትፈራ አያስፈልግም"

የእኔ ጫና በአንተ ላይ ሊከብድ አያስፈልግም
ይህ ማለት እርሱ ኢዮብን አያግደውም ወይም ሸክም አይጭንበትም። እርሱ ስሜታዊውን ሸክም የሚናገረው እንደ ከባድ አካላዊ ሸክም አድርጎ ነው። "እኔ በአንተ ላይ ሸክም አልጭንም" ወይም "በምናገረው ነገር ጫና አላሳድርብህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 33:8

አጠቃላይ መረጃ:
ኤሊሁ ለኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል።

እኔ ስሰማህ
"እኔ ልሰማህ በምችልበት"

አንደበትህ ሲናገር የሰማሁት
"ስትናገር የሰማሁህ"

ንጹህ
እግዚአብሔር በመንፈስ ተቀባይነት አለው ያለው ሰው፤ በአካል ንጹህ እንደነበረ ሰው ተደርጎ ይገለጻል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኃጢአት የለብኝም
"ኃጢአት አልሰራሁም"

Job 33:10

አጠቃላይ መረጃ:
ኤሊሁ ኢዮብ የተናገረውን መጥቀሱን ቀጥሏል።

እነሆ
ተናጋሪው እዚህ ስፍራ ይህንን ቃል የተጠቀመው ቀጥሎ ወደሚናገረው ትኩረት ለመሳብ ነው። "አድምጠኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። እግሮቼን በግንድ አጣበቀ "ከግንድ ጋር ማሰሪያ" ይህ ከግንድ ጋር ተጣብቆ ማሰሪያ ሲሆን አሳሪው በእስረኛው እግር ዙሪያ እንቅስቃሴውን ለመገደብ የሚያደርገው ነው። ኢዮብ እስረኛ እንደሆነ የሚሰማው በግንድ ተጣብቆ እንደታሰረ በመናገር ነው። "እስረኛ እንዳደረገኝ ይሰማኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእኔ መንገዶች
እነዚህ ቃላት ወዴት እንደሚሄድ ያመለክታሉ። እዚህ ስፍራ ወዴት እንደሚሄድ የሚለው የሚገልጸው ምን እንደሚያደርግ ነው። "የማደርገው ነገር ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ እመልስልሃለሁ
ኤሊሁ ለኢዮብ እየተናገረ ነው

Job 33:13

አጠቃላይ መረጃ:
ኤሊሁ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።

ለምን እርሱን በመቃወም ትታገላለህ?
ኤሊሁ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀምበት ኢዮብ ከእግዚአብሔር ጋር መታገል እንደሌለበት ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ከእግዚአብሔር ጋር መታገል የለብህም" ወይም "ከእግዚአብሔር ጋር ለመከራከር መሞከር የለብህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይልከቱ)

እርሱ በሚያደርገው ሁሉ አይጠየቅም
"እርሱ የሚያደርገውን ማናቸውንም ነገር ለእኛ ማብራራት አይኖርበትም"

እግዚአብሔር በአንድም- በሌላም መንገድ ይናገራል
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "እግዚአብሔር በተለያየ መንገድ ደግሞ ደጋግሞ ይናገራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በህልም... በምሽት በራዕይ
እነዚህ ሀረጎች አንድ አይነት ትርጉም አላቸው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰዎች ላይ ከባድ እንቅልፍ ሲወድቅ፣ በአልጋ ላይ አንቀላፍተው ሳሉ
ይህ ሰዎች በከባድ እንቅልፍ ላይ ሳሉ፣ እንቅልፍ በእነርሱ ላይ እንደ ወደቀባቸው ወይም እነርሱን እንዳሸነፈ አድርጎ ይናገራል። "ሰዎች በአልጋቸው ላይ ተኝተው ሙሉ እንቅልፍ ወስዷቸው ሳለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 33:16

አጠቃላይ መረጃ:
ኤሊሁ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።

በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር የሰዎችን ጆሮ ይከፍታል
ይህ የሚናገረው እግዚአብሔር ይሰሙ ዘንድ ጆሯቸውን በመክፈት ሰዎች ስለ ነገሮች እንዲረዱ ማድረጉን ነው። "በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር ነገሮችን ለሰዎች ይገልጻል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሰውን ከሄደበት ለመመለስ
ይህ የሚናገረው እግዚአብሔር አንድ ሰው ክፉ ነገር እንዳይሰራ በአካል ወደ ኋላ የመጎተትን ያህል እየከለከለ ከክፉ ተግባሩ እንደሚጠብቀው ነው። "እርሱን ከ... ይጠብቅ ዘንድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር የሰውን ህይወት ከጉድጓድ ይጠብቃል... ህይወቱ ወደ ሞት እንዳይሻገር ይጠብቀዋል
እነዚህ ሁለቱም ሃሳቦች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። "እግዚአብሔር ሰዎችን ከመቃብር እና ከሞት ያድናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጉድጓድ
ሰዎች ሲሞቱ የሚሄዱበት ስፍራ እዚህ ላይ "ጉድጓድ" ተብሎ ተጠቅሷል። "የሞቱ ሰዎች የሚገኙበት ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ህይወት ይመለሳል...የእርሱ ህይወት
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ሰው ከመሞት እና...እርሱ ይጠብቀዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወደ ሞት ከመሻገር
እዚህ ስፍራ "ሞት" የሚወክለው ሰዎች ሲሞቱ የሚሄዱበትን ስፍራ፣ ይኸውም፣ ሲኦልን ነው። "ወደ ሲኦል ከመሄድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 33:19

አጠቃላይ መረጃ:
ኤሊሁ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።

እንደዚሁም ደግሞ ሰው ይቀጣል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር ደግሞ ሰውን ይቀጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በአልጋው ላይ ሳለ በህመም
ይህ ማለት ሰው በአልጋው ላይ ታሞ ይተኛ ዘንድ እንዲህ ያለው መከራ ይደርስበታል። "በአልጋው ላይ በስቃይ ይተኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህም ህይወቱ ምግብ ትጸየፋለች፣ ደግሞም ነፍሱ ምኞትን ትጠላለች
በመሰረቱ እነዚህ ሁለቱ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ይኸውም ሰውየው መመገብ እንኳን እስከሚያቅተው ድረስ በታላቅ ስቃይ ውስጥ ነው ማለት ነው። ሰውየው የተገለጸው በ"ህይወቱ" እና በ"ነፍሱ" ነው። "ውጤቱ አንዳች የሚበላ አይፈልግም፣ እጅግ ምርጥ የሆነውን ምግብ እንኳን አይፈልግም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

ምኞትን መጸየፍ
"እጅግ ምርጥ የሆነውን ምግብ እንኳን መጥላት"

Job 33:21

አጠቃላይ መረጃ:
ኤሊሁ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።

ስጋው በአካሉ ላይ እስከማይታይ ድረስ ይሟሸሻል፣ በአንድ ወቅት የማይታዩ የነበሩ አጥንቶቹ አሁን ወጥተው ይታያሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ስጋው" የሚለው የሚያመለክተው ውፍራቱን እና ጡንቻዎቹን እንጂ የውጭ ሰውነቱን ቆዳ አይደለም። "በሽታ አጥንቶቹ እስኪታዩ ድረስ ሰውነቱን ደካማ እና ከሲታ አድርጎታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ እና ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ነፍሱ ወደ ጉድጓድ ተቃርባለች
እዚህ ስፍራ ሰውየው የተገለጸው በ"ነፍሱ" ነው። "ወደ መቃብር ሊወርድ ተቃርቧል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ጉድጓድ
ሰዎች ሲሞቱ የሚሄዱበት ስፍራ እዚህ ላይ "ጉድጓድ" ተብሎ ተጠቅሷል። "የሞቱ ሰዎች የሚገኙበት ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ህይወቱ ሊያጠፏት ለሚፈልጉ
እዚህ ስፍራ ሰውየው የተገለጸው በ"ነፍሱ" ነው። "ህይወቱ ሊያጠፏት ለሚፈልጉ" የሚለው ሀረግ ሰዎች ከሞቱ በኋላ የሚሄዱበትን ስፍራ ያመለክታል። "እናም የሞቱ ሰዎች ወደሚሄዱበት ስፍራ ለመሄድ ቅርብ ነው" ወይም "እናም በቅርቡ ወደ ሙታን ስፍራ ይሄዳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 33:23

አጠቃላይ መረጃ:
ኤሊሁ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።

ለእርሱ
ይህ አንድን የተለየ ሰው አያመለክትም። ኤሊሁ ስለማንኛውም ሰው በአጠቃላይ መናገሩን ይቀጥላል።

ከሺህ መላዕክት መሃል
በአንዳንድ ቋንቋዎች "በብዙ ሺህ" ከማለት ይልቅ "ብዙ/አእላፋት" ማለቱ ይበልጥ ተገቢ ይሆናል። "ከብዙ መላዕክት መሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ጉድጓድ
ሰዎች ሲሞቱ የሚሄዱበት ስፍራ እዚህ ላይ "ጉድጓድ" ተብሎ ተጠቅሷል። "የሞቱ ሰዎች የሚገኙት ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለእርሱ መቤዣ አገኛለሁ
ይህ ማለት መላዕክት ሰውየው እንዳይሞት ለኃጢአቱ ክፍያ የሚያደርጉበት መንገድ ያገኛሉ ማለት ነው። "እርሱ እንዳይሞት የምታደርግበትን መንገድ እኔ ለአንተ አግኝቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 33:25

አጠቃላይ መረጃ:
ኤሊሁ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።

ከዚያም
"ከዚይም" የሚለው ቃል እዚህ ስፍራ የዋለው እግዚአብሔር ለመላዕክቱ ጥያቄ ምላሽ ቢሰጥ ምን እንደሚሆን ለማመልከት ነው። "ከዚይም በውጤቱ" ወይም "መላዕክቱ ለእግዚአብሔር ከሚያቀርቡት ጥያቄ የተነሳ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ስጋው ከትንሽ ልጅ ገላ ይልቅ አዲስ ይሆናል
ይህ የሚናገረው የተፈወሰው ሰው አካሉ እንደ ህጻን አካል ታድሰሶ ዳግም እንደሚታደስ ነው። "የታመመው ሰው አካል ዳግም እንደ ወጣት ሰው አካል ይታደሳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከልጅ ይልቅ ታድሶ
በዚህ ንጽጽር፣ "አዲስ" የሚለው ቃል ግነት ነው። "እንደ ልጅ አዲስ ገላ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

የልጅ
ይህ የሚያመለክተው የልጅን ገላ ነው። "የልጅ ገላ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ወጣትነቱ ቀናት ጥንካሬ ይመለሳል
ይህ የሚናገረው ሰውየው ዳግም ወጣት እንደነበረበት ዘመኑ ጥንካሬ ያንኑ የወጣትነት ዘመኑን ብርታት እንደሚይዝ ነው። "ወጣት እንደነበረበት ዘመን ዳግም ብርቱ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የእግዚአብሔርን ፊት በደስታ ይመለከታል
ይህ ፈሊጥ ነው። "በደስታ እግዚአብሔርን ያመልካል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ፊት
እዚህ ስፍራ እግዚአብሔር የተገለጸው በ "ፊቱ" ነው። "እግዚአብሔር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ለሰው ድል ይሰጣል
"እግዚአብሔር ሰውን ያድናል" ወይም "እግዚአብሔር ለሰው ነገሮችን ዳግም ያስተካክላል"

Job 33:27

አጠቃላይ መረጃ:
ኤሊሁ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።

ነገር ግን ኃጢአቱ አልተቀጣም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ነገር ግን እግዚአብሔር ለሰራሁት ኃጢአት አልቀጣኝም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ነፍሴን ወደ ጉድጓድ ከመውረድ አዳናት
እዚህ ስፍራ ሰውየው የተገለጸው በ"ነፍሱ" ነው። "ከሞት እና ወደ ጉድጓድ ከመውረድ አዳነኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ጉድጓድ
ሰዎች ሲሞቱ የሚሄዱበት ስፍራ እዚህ ላይ "ጉድጓድ" ተብሎ ተጠቅሷል። "የሞቱ ሰዎች የሚገኙት ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ህይወቴ ብርሃን ማየቱን ይቀጥላል
እዚህ ስፍራ ሰውየው የተገለጸው በ"ህይወቱ" ነው። መኖር ደግሞ የተነገረው ብርሃንን ማየት ተደርጎ ነው። "መኖሬን እና የቀን ብርሃን ማየቴን እቀጥላለሁ" ወይም "መኖሬ ይቀጥላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 33:29

አጠቃላይ መረጃ:
ኤሊሁ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።

እነሆ
ኤሊሁ እዚህ ስፍራ ይህንን ቃል የሚጠቀመው ቀጥሎ ለሚናገረው ነገር ኢዮብ ትኩረት እንዲሰጠው ለማድረግ ነው። "አድምጠኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ሁለቴ፣ አዎን፣ ሶስቴ አንኳን
ይህ ፈሊጥ ነው። "ደግሞ ደጋግሞ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ ነፍስ
ሰውየው የተገለጸው በ"ነፍሱ" ነው። "እርሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ነፍሱን ዳግም ከጉድጓድ ለመመለስ
ይህ የሚናገረው አንድ ሰው ሞቶ እንደ ነበረ እና ዳግም ከሞት አድኖ ወደ ህይወት እንደመመለስ አድርጎ ነው። "እርሱን ከሞት እና ወደ ጉድጓድ ከመውረድ መጠበቅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጉድጓድ
ሰዎች ሲሞቱ የሚሄዱበት ስፍራ እዚህ ላይ "ጉድጓድ" ተብሎ ተጠቅሷል። "የሞቱ ሰዎች የሚገኙት ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ምናልባት እርሱ የህይወት ብርሃን ይበራለት ይሆናል
ይህ ፈሊጥ ነው፤ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽም ይችላል። "ምናልባት አስካሁን በህይወት በመቆየቱ ደስተኛ ሊሆን ይችላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 33:31

አጠቃላይ መረጃ:
ኤሊሁ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።

ኢዮብ ሆይ ልብ በል፣ ደግሞም አድምጠኝ
እነዚህ ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። "ኢዮብ ሆይ፣ በጥንቃቄ አድምጠኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ትክክል እንደሆንክ
ይህ ፈሊጥ ነው። "አንተ ቅን ነህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 34

1 ኤሊሁም በመቀጠል እንዲህ አለ፥ 2 ”እናንተ ጥበበኞች፥ ቃሎቼን አድምጡ፤ እውቀት ያላችሁ እናንተ ስሙኝ። 3 ምላስ ምግብን እንደሚያጣጥም ጆሮም
ቃላትን ያመዛዝናል። 4 ትክክለኛ የሆነውን ለራሳችን እንምረጥ፤ መልካም የሆነውንም በመካከላችን እንፈልገው። 5 ኢዮብ 'እኔ ጻድቅ ነኝ እግዚአብሔር ግን
መብቴን ነፍጎኛል። መብት ቢኖረኝም እንደ ሐሰተኛ ተቆጥሬአለሁ። 6 ምንም እንኳን ኃጢአት ባይኖርብኝም ቁስሌ የማይፈወስ ነው' ብሏልና። 7 ስድብን እንደ
ውሃ የሚጠጣ፥ 8 ክፋትን ከሚያደርጉት ጋር እንደሚወዳጅ፥ ከአመጸኞችም ጋር እንደሚመላለስ እንደ ኢዮብ ያለ ማነው? 9 እርሱ፥ 'ሰው እግዚአብሔር
የሚፈልገውን በማድረግ መደሰቱ ምንም አይጠቅምም' ብሏልና። 10 ስለዚህ እናንተ አዋቂዎች ስሙኝ፤ አመጻን ማድረግ ከእግዚአብሔር ይራቅ፤ ኃጢአትን
ማድረግም ሁሉን ቻይ ከሆነው ይራቅ። 11 ለሰው እንደ ሥራው ይከፍለዋልና፤ እያንዳንዱም በየራሱ መንገድ ወደ ብድራቱ እንዲመጣ ያደርገዋል። 12 በእርግጥ
እግዚአብሔር አንዳችም አመጻን አያደርግም፥ ደግሞም ሁሉን ቻዩ ከቶም ፍትሕን አያዛባም። 13 በምድር ላይ እርሱን ፈራጅ ያደረገው ማነው? ዓለሙንስ በሙሉ
ከእርሱ በታች ያደረገው ማነው? 14 እርሱ ፍላጎቱን በራሱ ላይ ብቻ ቢያደርግና መንፈሱንና እስትንፋሱን ወደ ራሱ ቢመልስ ኖሮ 15 ያን ጊዜ ሥጋን የለበሰ ሁሉ
በጠፋ፥ ሰውም እንደገና ወደ ዐፈር በተመለሰ ነበር። 16 አሁን እንግዲህ ማስተዋል ካለህ ይህንን ስማ፤ የቃሌንም ድምፅ አድምጥ። 17 ፍትሕን የሚጠላ
ማስተዳደር ይችላል? ጻድቅና ሁሉን ቻይ የሆነውን አምላክ ትኮንነዋለህ? 18 እግዚአብሔር ንጉሡን፥ 'በደለኛ ነህ' ወይም ባለስልጣኖችን፥ 'አመጸኞች ናችሁ'
አይልምን? 19 እግዚአብሔር ለመሪዎች አያዳላም፤ ባለጸጋዎችንም ከድኾች አስበልጦ አይመለከታቸውም፤ ሁሉም የእጁ ሥራዎች ናቸውና። 20 በቅጽበት
ይሞታሉ፤ እኩለ ሌሊት ላይ ሰዎች ይንቀጠቀጣሉ፥ ይሞታሉም፤ ኃያላን ሰዎች ይወሰዳሉ፥ በሰው እጅ ግን አይደለም። 21 የእግዚአብሔር ዐይኖች በሰው አካሄድ
ላይ ናቸው፤ እርምጃዎቹንም ሁሉ ያያቸዋል። 22 ክፉ አድራጊዎች የሚደበቁበት ጨለማ ወይም ድቅድቅ ጭጋግ የለም። 23 እግዚአብሔር ከዚህ በላይ ሰውን
መመርመር አይፈልግም፥ የትኛውም ሰው በእርሱ ፊት ቆሞ መሟገት አያስፈልገውም። 24 ስለ አካሄዳቸው ተጨማሪ ምርመራ እንዳያስፈልጋቸው ኃያላኑን ሰዎች
ይሰባብራቸዋል፤ በስፍራቸውም ሌሎችን ይሾማል። 25 እንዲህ ባለ መንገድ ሥራቸውን ያውቃል፤ እነዚህን ሰዎች በጨለማ ይጥላቸዋል፤ እነርሱም ይጠፋሉ።
26 በሌሎች ፊት፥ በአደባባይ ስለ ክፉ ሥራቸው እንደ ወንጀለኛ ይገድላቸዋል፥ 27 እርሱን ከመከተል ተመልሰዋልና፥ ከመንገዶቹም የትኛውንም ለመቀበል
ፈቃደኞች አልሆኑምና። 28 እንዲህ ባለ መንገድ የድኾች ጩኸት በፊቱ እንዲወጣ አደረጉ፤ እርሱም የተጨነቁትን ሰዎች ጩኸት ሰማ። 29 በዝምታ
በሚቆይበት ጊዜ ማን ሊወቅሰው ይችላል? ፊቱንስ ቢሰውር ማን ሊገነዘበው ይችላል? 30 አመጸኛው ሰው ገዢ እንዳይሆን፥ በሕዝቡም ላይ ወጥመድን
የሚያደርግ እንዳይገኝ እርሱ በሀገሮችና በግለሰቦች ላይ ይገዛል። 31 አንድ ሰው እግዚአብሔርን እንዲህ እንደሚለው ገምቱ፥ 'በርግጥ በድያለሁ፥ 32 ከዚህ
በኋላ ግን ከቶ ኃጢአትን አላደርግም፤ ላየው የማልችለውን አስተምረኝ፤ ኃጢአትን ሠርቻለሁ፥ ከእንግዲህ ግን አላደርግም'። 33 እግዚአብሔር የሚያደርገውን
የምትጠላ ሰው ብትሆንም፥ እግዚአብሔር የዚያን ሰው ኃጢአት የሚቀጣ ይመስልሃል? እኔ ሳልሆን አንተው መምረጥ አለብህ። ስለዚህ ትክክል ነው ብለህ
የምታውቀውን ተናገር። 34 ዐዋቂዎች ሰዎችም እንዲህ ይሉኛል፥ በእርግጥ የሚሰማኝ ጥበበኛ ሰው ሁሉ የሚለው እንዲህ ነው፥ 35 'ኢዮብ የሚናገረው
የማያውቀውን ነው፤ ቃሎቹም ጥበብ የለባቸውም'። 36 እንደ አመጸኞች ሰዎች ተናግሯልና ምነው ኢዮብ ብቻውን ከጉዳዮቹ ስለ ጥቂቶቹ በዝርዝር በተመረመረ።
37 በኃጢአቱ ላይ አመጽን ጨምሯልና፤ በመካከላችን እጆቹን እያጨበጨበ ተሳድቧልና፤ እግዚአብሔርን በመቃወምም ብዙ ቃል ተናግሯል።"

Job 34:1

ኤሊሁም ቀጠለ
"ከዚያም፣ ኤሊሁ"

ኤሊሁ
ይህ የወንድ ስም በኢዮብ 32:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ቃሌን አድምጥ
"የምናገረውን ስማ"

እናንተ ጠቢባን ... እናንተ አዋቂዎች
ኤሊሁ ኢዮብን እና ወዳጆቹን እየተቸ ነው። በእርግጥ ጠቢባን ናቸው ብሎ አያስብም። (ምጸት የሚለውን ይመልከቱ)

ላንቃ/ምላስ የምግብ ጣዕም እንደሚለይበት ጆሮም ነገርን ይለያል
ኤሊሁ ይህንን ማለቱ ሰዎች የምግብን ጣዕም ለመለየት ምግቡን እንደሚቀምሱ ሁሉ ትክክል የሆነውን ከስህተት ለመለየት በጥንቃቄ ያደምጣሉ ማለቱ ነው። እዚህ ስፍራ ሰዎች የተጠቀሱት በ"ጆሯቸው" እና በ"ላንቃቸው/ምላሳቸው" የሆነው ሰዎች እንደሚያጣጥሙ እና እንደሚያደምጡ ትኩረት ለመስጠት ነው። "መልካም የሆነውን ምግብ ለመለየት እንደምንቀምስ ሁሉ፣ መልካም የሆነውን ቃል ከክፉው ለመለየት እናደምጣለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 34:4

አጠቃላ መረጃ:
ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ።

እኛ
እዚህ ስፍራ "እኛ" የሚለው የሚያመለክተው ኤሊሁን፣ ኢዮብን፣ እና ሶስቱን ወዳጆቻቸውን ነው። (አካታች "እኛ" የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ መብቴን ገፎኛል/ቀምቶኛል
"ፍትህ ሊሰጠኝ አልፈቀደም"

ሀሰተኛ ተደርጌ ተቆጠርኩ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር ሀሰተኛ አድርጎ ቆጥሮኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ቁስሌ የማይድን ነው
እዚህ ስፍራ የኢዮብ ህመም እና መከራ የተወሰደው እንደ "ቁስል" ተደርጎ ነው። "እኔ ታምሜያለሁ ማንም ሊፈውሰኝ አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 34:7

አጠቃላ መረጃ:
ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንደ ኢዮብ ያለ ሰው ማን ነው
ኤሊሁ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚያነሳው ኢዮብን ለመገሰጽ ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊቀርብ ይችላል። "እንደ ኢዮብ ያለ ሌላ ማንም ሰው የለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ፌዝን እንደ ውሃ የሚጨልጥ/የሚጠጣ ማን ነው
ኤሊሁም ሰው ውሃ እንደሚጠጣ ያህል ኢዮብን በፌዝ እየከሰሰው ነው። "ውሃ እንደሚጠጣ ሰው ያህል እንደ ኢዮብ ማን አዘውትሮ በሌሎች ላይ ያፌዛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ማን ከኃጢአተኛ ሰው ጋር ይሄዳል/ይራመዳል
እዚህ ስፍራ "መራመድ" የሚለው አንድ ሰው ለሚያደርገው ነገር ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ማን እንደ ኃጢአተኛ ሰው ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 34:10

አጠቃላ መረጃ:
ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ። እነዚህ እያንዳንዳቸው ቁጥሮች ትይዩ ሀረጎችን ይዘዋል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ አዋቂዎች
ኤሊሁ ኢዮብን እና ወዳጆቹን እየነቀፈ ነው። በእርግጥ ጠቢባን ናቸው ብሎ አያስብም። (ምፀት የሚለውን ዘይቤ ይመልከቱ)

ይህ ከእግዚአብሔር የራቀ ይሁን... ሁሉን ቻይ ከሆነው በደል የራቀ ይሁን
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው ደግሞም በአንድ ላይ የቀረቡት እግዚአብሔር እንደማይሳሳት ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። "ከእርሱ የራቀ ይሁን" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ሁሉን ቻይ የሆነው እግዚአብሔር ስህተት ወይም ክፉ የሆነ ነገር አያደርግም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ምፀት የሚሉትን ይመልከቱ)

እርሱ ለሰው ዋጋውን መልሶ ይከፍለዋል
ይህ ማለት እርሱ ለአንድ ሰው ለሰራው ስራ የሚገባውን ይከፍለዋል ማለት ነው። እዚህ ስፍራ "ስራ" የሚለው ቃል አንድ ሰው ለሰራው ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። "እርሱ ለአንድ ሰው ለሰራው ስራ የሚገባውን መልሶ ይከፍለዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ እያንዳንዱ ሰው የራሱን መንገዶች ላይ ያለውን ዋጋ እንዲያገኝ ያደርጋል
"በራሱ መንገዶች" የሚለው ሀረግ አንድ ሰው ህይወቱን እንዴት እንደሚኖር ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኤሊሁ ያንን እግዚአብሔር ለሰዎች የሚገባቸውን እንደሚሰጥ በትኩረት ይናገራል። "እርሱ እያንዳንዱ በኖረበት መሰረት ዋጋውን እንዲቀበል ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 34:13

አጠቃላ መረጃ:
ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ።

በምድር ላይ እርሱን የሚከስ ማን አለ? ማን መላዋን ምድር በእርሱ ስር አደረገ?
እነዚህ ሁለቱም ቃለምልልሳዊ ጥያቄዎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ እናም፣ ቀድሞኑ የተረጋገጠ በመሆኑ ማንም የእግዚአብሔርን ስልጣን እንደማያረጋግጥለት ትኩረት ሰጥተው ይገልጻሉ። እነዚህ ጥያቄዎች በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፉ ይችላሉ። "በመላው ምድር ላይ ያሻውን እንዲያደርግ ማንም ለእግዚአብሔር ፈቃድ ሊሰጠው አያስፈልግም። እርሱ ምድርን ለመግዛት ሙሉ ስልጣን አለው።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

መቼም ቢሆን
ኤሊሁ እርሱ የማያምንበት ሁኔታ በፍጹም ሊሆን እንደማይችል ይገልጻል። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ መንፈስ እና እስትንፋሱ
ሁሉንም ህያዋን ነገሮች በህይወት የሚያኖረው የእግዚአብሔር "መንፈስ" እና "እስትንፋስ" ነው። "ለእኛ ህይወት የሰጠን የእርሱ መንፈስ እና እስትንፋስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ስጋ ለባሽ ሁሉ
እዚህ ስፍራ ህይወት ያላቸው ነገሮች ሁሉ የተወከሉት በ"ስጋቸው" ነው። "ህይወት ያላቸው ነገሮች ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰው የሆነ ሁሉ/ የሰው ልጅ ወደ አፈር ይመለሳል
ይህ ማለት ሁሉም ሰው ይሞታል፤ አካሉም በስብሶ አፈር ይሆናል። በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው ከአፈር ነው። "የሰው ልጅ አካል በቶሎ ተመልሶ አፈር ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 34:16

አጠቃላ መረጃ:
ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ።

እነሆ
ኤሊሁ ይህንን ቃል የተጠቀመው ቀጥሎ ወደሚናገረው ጠቃሚ ነገር ትኩረት ለመሳብ ነው።

አንተ አለህ
እዚህ ስፍራ "አንተ" የሚለው ተውላጠ ስም ነጠላ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተው ኢዮብን ነው። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)

የቃሌን ድምጾች ስማ
"የምናገረውን ስማ" ይህ ማለት ከዐረፍተ ነገሩ የመጀሪያ ክፍል ጋር ተመሳሳይ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ፍትህን የሚጠላ ያስተዳድራልን? አንተ ጻድቅ እና ታላቅ የሆነውን እግዚአብሔርን ትከሳለህን?
ኤሊሁ ይህንን ጥያቄ የሚያነሳው እግዚአብሔር ፍትህን ይጠላል ብለሃል በማለት ኢዮብን ለመገሰጽ ነው። "ፍትህን የሚጠላ በሰዎች ላይ ይገዛል ተብሎ ሊጠበቅ አይችልም። ስለዚህም አንተ ጻድቅ እና ሃያል የሆነውን እግዚአብሔርን በእርግጥ ልትወቅስ አትችልም፤ ደግሞም እርሱ የሚያደርገውን ስህተት ነው ልትል አትችልም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ፍትህን የሚጠላ ያስተዳድራልን?
ለዚህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በውስጠታዋቂነት የተሰጠው ምላሽ "አይችልም" የሚል ነው። ይህ ጥያቄ የሚያሳየው እግዚአብሔር ፍትህን ቢጠላ ኖሮ አለምን ለጊዛ አይችልም ነበር የሚል ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ፍትህን የሚጠላ ዓለምን ለጊዛ አይችልም" ወይም "በእርግጥ እግዚአብሔር በፍጹም ትክክል የሆነውን ሊጠላ እና ዓለምን ለጊዛ አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ጻድቅ እና ታላቅ የሆነውን እግዚአብሔርን ትወቅሳለህን?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የዋለው ኢዮብ እግዚአብሔርን ለመውቀስ ስልጣን ወይም ምክንያት እንደሌለው ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። "ጻድቅ እና ታላቅ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የሆነውን እግዚአብሔርን ልትወቅስ አትችልም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 34:18

አጠቃላ መረጃ:
ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ።

እንደ እግዚአብሔር ንጉሡን 'አንተ የማትረባ ነህ' ወይም ከበርቴውን 'አንተ ደካማ ነህ' የሚል ማን ነው?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ ኢዮብ እግዚአብሔርን ሊወቅስ እንደማይችል ትኩረት ለመስጠት ከቀደመው ጥቅስ ይቀጥላል። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "እርሱ ንጉሡን 'አንተ የማትረባ ነህ' ይላል ከበርቴውንም 'አንተ ደካማ ነህ' ይለዋል።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሡን የሚናገር፣ እግዚአብሔር
ይህ የቀደመው ጥያቄ ክፍል ነው። ከቀደመው ክፍል መረዳት እንደሚቻለው "አንተ እግዚአብሔርን ትውቀሳለህን" የሚለው ሊጨመር ይችላል። "አንተ ንጉሡን የሚናገረውን እግዚአብሔርን ትወቅሳለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

የማይረባ
"ክፉ" ወይም "ዋጋ የሌለው"

እነርሱ የእጆቹ ስራዎች ናቸውና
እዚህ ስፍራ "እጆች" የሚለው የሚወክለው ሀይልን ነው። "እግዚአብሔር ሁሉንም አበጅቷልና" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በእኩለ ሌሊት
እኩለ ሌሊት አንዱ ቀን የሚያበቃበት እና ሌላው ቀን የሚጀምርበት ጊዜ ነው። እዚህ ስፍራ "እኩለ ሌሊት" የሚለው ያገለገለው እንደ ፈሊጣዊ አነጋገር ሆኖ ነው። "በምሽት" ወይም "ድንገት በምሽት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሰዎች ይርዳሉ/ይንቀጠቀጣሉ ደግሞም ያልፋሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ይንቀጠቀጣሉ" የሚለው ሀረግ "ይመታሉ" ለሚለው ፈሊጣዊ አገላለጽ ነው። "እግዚአብሔር ይመታቸዋል ይሞታሉም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ታላላቅ ሰዎች ይወሰዳሉ፣ ነገር ግን በሰዎች እጆች አይደለም
ይህ ማለት ሰዎች የሚሞቱት በእግዚአብሔር እንጂ በሰዎች አይደለም ማለት ነው። ይህም ደግሞ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ብዙ ሰዎች እንዲሞቱ ምክንያቱ እግዚአብሔር እንጂ ሰዎች አይደሉም" (ዩፊምዝም/የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

በሰዎች እጅ አይደለም
እዚህ ስፍራ ሰዎች የተወከሉት በ"እጆቻቸው" ነው። "በሰውልጅ አይደለም" ወይም "በሰዎች አይደለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 34:21

የእግዚአብሔር ዐይኖች በሰው መንገዶች ላይ ነው
የእግዚአብሔር "ዐይኖች" የሚወክለው የእርሱን እይታ ነው። "የሰው መንገዶች" የሚለው ሀረግ ለሚያደርገው እና ለአኗኗሩ ፈሊጥ ነው። "እግዚአብሔር ሰው የሚያደርገውን ነገር ሁሉ ይመለከታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

እርሱ እርምጃዎቹን ሁሉ ይመለከታል
ይህ ማለት እርሱ ሁሌም አንድ ሰው የት እንደሚገኝ እና ወዴት እንደሚሄድ ያውቃል። "እርሱ ሰው ወዴት እንደሚሄድ ይመለከታል/የሰውን መንገድ ይመለከታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ጨለማ የለም፣ ጥልቅ ጨለማም የለም
"ጥልቅ ጨለማ" የሚሉት ቃላት "ጨለማ" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ለጨለማው ጥልቀት ሰጥቶ ለመግለጽ የዋለ ነው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

በፍርድ
"ስለዚህ እርሱ ይፈርድበታል" ወይም "ፍርድ ለመቀበል"

Job 34:24

አጠቃላ መረጃ:
ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ።

እርሱ ታላላቅ ሰዎችን ይሰባብራቸዋል
ይህ የሚገልጸው እግዚአብሔር እነዚህን ሰዎች አጥንታቸውን እንደሚሰባብር አድርጎ እንደሚያጠፋቸው ነው። "እርሱ ታላላቅ ሰዎችን ይደመስሳል" ወይም "እርሱ ከፍ ያሉትን ይደመስሳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለመንገዳቸው ተጨማሪ ምርመራ አያስፈልገውም
እርሱ ያደረጉትን ጨምሮ መመርመር አያስፈልገውም ምክንያቱም ስለ እነርሱ ሁሉንም አስቀድሞ ያውቃል። "መንገዳቸውን አስቀድሞ ስለሚያውቅ፣ ተጨማሪ ምርመራ ማድረግ ሳያስፈልግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መንገዶቻቸውን
ይህ ፈሊጥ ነው። "እነርሱ ያደረጓቸው ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ሌሎችን በእነርሱ ስፍራ ያስቀምጣል
ይህ ማለት ሌሎች ሰዎች በእነርሱ ስፍራ ተቀምጠው እንዲመሩ ይሾማል። "እናም ሌሎች ሰዎች በእነርሱ ስፍራ እንዲመሩ ይመርጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በምሽት
ይህ ፈሊጥ ነው። "እነርሱ ነገሩን በማይጠብቁበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ይጠፋሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እናም ያጠፋቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 34:26

አጠቃላ መረጃ:
ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ።

ሌሎች በግልጽ እየተመለከቱ፣ እንደ ወንጀለኛ ስለ ክፉ ስራቸው እርሱ ይገድላቸዋል
ይህ ሀረግ እነዚህ ሰዎች የሚሞቱበትን መንገድ ወንጀለኞች ከሚሞቱበት ሁኔታ ጋር ያነጻጽራል። "ወንጀለኞች የሆኑ ያህል በሰዎች ፊት እነርሱን ስለ ክፉ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ስራቸው ይገድላቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሌሎች በግልጽ እየተመለከቱ
ይህ ፈሊጥ ነው። "ሁሉም ሰው ሊመለከተው በሚችለው ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ይገድላቸዋል
ይህ ምንም እንኳን እግዚአብሔር ራሱ በሰይፍ ባይመታቸውም፣ እነዚህን ሰዎች እርሱ እንደሚገድላቸው ይገልጻል። ሌሎች ሰዎች እንዲገድሏቸው ሊያደርግ ወይም ጥፋት በላያቸው እንዲመጣባቸው ይችላል። "እንዲሞቱ ያደርጋል" ይህ ምንም እንኳን እግዚአብሔር ራሱ በሰይፍ ባይመታቸውም፣ እነዚህን ሰዎች እርሱ እንደሚገድላቸው ይገልጻል። ሌሎች ሰዎች እንዲገድሏቸው ሊያደርግ ወይም ጥፋት በላያቸው እንዲመጣባቸው ይችላል። "እንዲሞቱ ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ መንገዶች
ይህ ሰዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው የእግዚአብሔርን ትዕዘዛ ያመለክታል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ የድሆች ጩኸት ወደ እርሱ እንዲመጣ አድርገዋል
"ጩኸት" የሚለው ቃል በግስ መልኩ ሊገለጽ ይችላል። ይህ የሚናገረው እግዚአብሔር ጩኸታቸውን የሚሰማው ጩኸቱ ራሱ ሰው ሆኖ ወደ እርሱ እንደመጣ አድርጎ ነው። "እነርሱ ድሆችን አስለቅሰዋል፣ እግዚአብሔርም የድሆችን ጩኸት ሰምቷል።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 34:29

አጠቃላ መረጃ:
ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ።

እርሱ ዝም ሲል፣ ማን ሊወቅሰው ይችላል?
ኤሊሁ ይህንን ቃል ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ኢዮብን ለማስተማር ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እርሱ ዝም ለማለት ከወሰነ ማንም እግዚአብሔርን ሊተቸው አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ ፊት
እዚህ ስፍራ እግዚአብሔር የተገለጸው በ"ፊቱ" ነው። "እርሱ ራሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ማንም ሰዎችን አያጠምድም
ይህ አዳኝ እንስሳ እንደሚያድን ሁሉ አምላክ የለሽ መሪ ሰዎችን ከመጉዳቱ ጋር ያነጻጽራል። "ማንም ሰዎችን እንዳይጎዳ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 34:31

አጠቃላ መረጃ:
ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ።

ማየት የማልችለውን አስተምረኝ
እዚህ ስፍራ "ማየት" ማለት ማወቅ ማለት ነው። "ሳላውቅ የሰራሁትን ስህተት አሳየኝ/አስተምረኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ እግዚአብሔር የሚያደርገውን እስከጠላህ ድረስ እርሱ የዚያን ሰው ኃጢአት ይቀጣል ብለህ ታስባለህን?
"እግዚአብሔር የሚያደርገውን እስከጠላህ ድረስ፣ እግዚአብሔር የዚህን ሰው ኃጢአት መቅጣት ይገባዋል ብለህ ታስባለህን?" ኤሊሁ ይህን ቃለምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው እግዚአብሔር ይህንን ሰው አይቀጣውም ብሎ ማሰብ አይኖርበትም የሚለውን ለማጉላት ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ምንም እንኳን እግዚአብሔር ያደረገውን አንተ ባትወደውም፣ በእርግጥ ምንም እንኳን እግዚአብሔር ይህንን ሰው ይቀጣዋል ብለህ ባታስብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የዚያ ሰው ኃጢአት
እዚህ ስፍራ ሰውን በኃጢአቱ ምክንያት መቅጣት የተጠቀሰው "የሰውየውን ኃጢአት" መቅጣት ተደርጎ ነው። "ያ ሰው በኃጢአቱ ምክንያት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ እስካልወደድክ ድረስ
"አንተ ባለመውደድህ ምክንያት"

ይህ አንተ የምታውቀው ምንድን ነው
"ስለዚህ አንተ የምታስበው"

Job 34:34

አጠቃላ መረጃ:
ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ።

እኔን የሚሰሙኝ
"ስናገር የሚሰሙን እነርሱ"

Job 34:36

ኢዮብ በፈተና ቢቀመጥ ኖሮ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እኛ ኢዮብን በፈተና ለናስቀምጠው ብንችል ኖሮ" ወይም "ኢዮብን ወደ ፍርድቤት ልናቀርበው ብንችል እና ዳኛ ሊያደምጠው ቢችል ኖሮ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በትናንሽ ዝርዝር ጉዳዮቹ
ይህ ፈሊጥ ነው። "ጉዳዮቹን በጥልቀት ለመስማት" ወይም "የእርሱን ጉዳዮች በሙሉ በዝርዝር ለመስማት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ ንግግር የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ክፉ ሰዎች የሆነውን ንግግሩን
"እንዴት እንደ ክፉ ሰው እንደተናገረ"

አመጽን ጨምሯል
ይህ በእግዚአብሔር ላይ ማመጽን ያመለክታል። "እርሱ በእግዚአብሔር ላይ አመጽ ጨምሯል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በመሃከላችን ሆኖ በፌዝ እጆቹን አጨብጭቧል
በዚህ ክስ፣ ኢዮብ አጨበጨበ የተባለው በእግዚአብሔር ላይ አፊዟል የሚባለውን ለማጠናከር ነው። "በመካከላችን ሆኖ በእግዚአብሔር ሲያፌዝ እጆቹን አጨብጭቧል" ወይም "በፊት ለፊታችን በእግዚአብሔር ላይ አፊዟል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ እንዲሁም ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚሉትን ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ላይ ብዙ ተናግሯል
ኤሊሁ ስለ "ቃላት" ሲናገር ቁሶች እንደሆኑ አድርጎ ነው፤ ብዙ ቃላትን ስለመናገር ሲናገርም እነዚያን ቁሶች አንዱን በሌላው ላይ እንደመከምር አድርጎ ነው። "እርሱ በእግዚአብሔር ላይ ብዙ ቃላትን ተናግሯል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 35

1 ኤሊሁ እንዲህ ሲል ንግግሩን ቀጠለ፥ **2** “ንጹሕ ነኝ ብለህ ታስባለህ? 'ከእግዚአብሔር ይልቅ ጻድቅ ነኝ' ብለህስ ታስባለህ? **3** ጻድቅ መሆኔ ምን ይጠቅማል? ኃጢአት አድርጌ ቢሆን ኖሮ ከዚህ የሚበልጥ ምን ያገኘኝ ነበር?' ብለሃልና። **4** ለአንተና ለወዳጆችህ ምላሽ እሰጣለሁ። **5** ወደ ሰማይ ቀና በሉና ተመልከቱት፤ ከእናንተ ከፍ የሚለውን ሰማይ ተመልከቱ። **6** ኃጢአትን ብታደርግ እግዚአብሔርን ምን ትጎዳዋለህ? መተላለፍህ እጅግ የበዛ ቢሆን ለእርሱ ምኑ ነው? **7** ጻድቅ ብትሆንስ ምን ልትሰጠው ትችላለህ? ከእጅህስ ምን ይቀበላል? **8** አንተም ሰው ነህና ክፋትህ ሌላውን ይጎዳ ይሆናል፤ ጽድቅህም ሌላውን የሰው ልጅ ይጠቅመው ይሆናል። **9** በብዙ በደል ምክንያት ሰዎች ይጮኻሉ፤ ከኃያላኑ እጅ የሚያድናቸውን ፍለጋ ይጣራሉ። **10** ነገር ግን 'በሌሊት ዝማሬን የሚሰጥ፥ **11** የምድር አራዊትን ከሚያስተምርበት በበለጠ የሚያስተምረን፥ ከሰማይ አዕዋፍም ይልቅ ጥበበኞች የሚያደርገን ፈጣሪያችን እግዚአብሔር የት አለ?' ማንም አላለም። **12** በዚያን ጊዜ ይጮኻሉ፥ ነገር ግን በክፉ ሰዎች ትዕቢት ምክንያት እግዚአብሔር ምንም ምላሽ አይሰጣቸውም። **13** ያለጥርጥር እግዚአብሔር የሞኞችን ጩኸት አይሰማም፤ ሁሉን ቻዩም ትኩረት አይሰጠውም። **14** ጉዳይህን በፊቱ አቅርበህ እየተጠባበቅኸው እያለህ እንዳላየኸው ከተናገርክ እንዴት አድርጎ መልስ ይሰጥሃል! **15** ማንንም ተቆጥቶ አይቀጣም፥ በሰዎች ትዕቢት እምብዛም ግድ አይለውም ካልክ እንዴት አድርጎ መልስ ይሰጥሃል? **16** ስለዚህ ኢዮብ አፉን የሚከፍተው ስንፍናን ለመናገር ብቻ ነው፤ ዕውቀት የሌለበትን ቃል መናገርንም ያበዛል"።

Job 35:1

ይህ ፍትህ ነው... ‘በእግዚአብሔር ፊት ያለኝ መብት ነው' ብለህ ታስባለህ?
ኤሊሁ ኢዮብን ለመገዳደር ጥያቄዎችን ያነሳል። "አንተ ትክክል እንደሆንክ ታስባለህ… ‘በእግዚአብሔር ፊት መብቴ ነው'" ትላለህ ወይም "ይህ ልክ አይደለም…‘በእግዚአብሔር ፊት መብቴ ነው'" ትላለህ። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህን በማለትህ ልክ የሆንክ ይመስልሃል
"አንተ ይህን ማለትህ ልክ ይመስልሃል"

ይመስልሃል/እንዲህ ታስባለህ
እዚህ ስፍራ "አንተ" የሚለው ነጠላ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተውም ኢዮብን ነው። (አንተ የሚለው ተውላጠ ስም መልኮች የሚለውን ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ፊት ያለኝ መብት
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ኢዮብ በእግዚአብሔር ፊት ንጹህ መሆኑን እየተናገረ ነው። ወይም 2) ኢዮብ ከእግዚአብሔር ይልቅ እኔ ትክክል ነኝ እያለ ነው።

አንተ ‘ይህ ለእኔ ምን ጥቅም አለው?' ብለህ ጠይቀሃል። ደግሞም፣ ‘ኃጢአት ባለመስራቴ ምን አተረፍኩ?' ብለሃል።
ኤሊሁ ኢዮብ እነዚህን ሁለት ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች እንዳነሳ ይጠቅሳል። "አንተ እንዲህ ብለሃል፣ ‘ይህ እኔን አልጠቀመኝም' ደግሞም፣ ‘ኃጢአት ብሰራ ከሚደርስብኝ ምንም የተሻለ አልሆነልኝም/ኃጢአት ባለመስራቴ አልተጠቀምኩም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 35:4

አጠቃላ መረጃ:
ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ።

Job 35:6

አጠቃላ መረጃ:
ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ።

ኃጢአት ብትሰራ... በእርሱ ላይ ምን ታደርጋለህ/ትጨምራለህ?
እነዚህ ሁለት መስመሮች ተመሳሳይ ትርጉም ይጋራሉ። ሁተኛው መስመር የመጀመሪያውን መስመር ትርጉም ያጠናክራል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ኃጢአት ብትሰራ፣ እግዚአብሔርን ምን ተጎዳዋለህ?
ኤሊሁ ይህንን ጥያቄ የሚያነሳው የኢዮብ ኃጢአት በእግዚአብሔር ላይ አንዳች ነገር እንደማያመጣ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። "ኃጢአት ብትሰራ፣ እግዚአብሔርን አንዳች አትጎዳውም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

መተላለፍህ ወደ ላይ ቢከመር፣ እርሱን ምን ታደርገዋለህ?
ኤሊሁ ስለ "መተላለፎች" የሚናገረው ቁሶች እንደሆኑ አድርጎ ነው፤ ብዙ መተላለፎችን ማድረግ ደግሞ እነዚህን ቁሶች አንዱን በሌላው ጫፍ ወደ ላይ መከመር እንደሆነ አድርጎ ይገልጻል። ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ኢዮብ በመተላለፉ በእግዚአብሔር ላይ አንዳች ማምጣት ማድረግ እንደማይችል ትኩረት ለመስጠት ነው። "አንተ ብዙ ታላላቅ መተላለፎችን ብትፈጽም፣ በእርሱ ላይ አንዳች ማድረግ አትችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

ጻድቅ ብትሆን፣ ለእርሱ ምን ልትሰጠው ትችላለህ? እርሱ ከአንተ እጅ ምን ይቀበላል?
ሁለቱ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ናቸው፤ ሁለቱም የሚገልጹት የኢዮብ ጽድቅ ለእግዚአብሔር አንዳች ነገር እንደማይጨምር ነው። "አንተ ጻድቅ ብትሆን፣ ይህ አንተ ለእርሱ አንዳች ነገር እንድትሰጠው አያበቃህም፤ ደግሞም እርሱ ከአንተ እጅ የሚቀበለው አንዳች ነገር የለም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከአንተ እጅ መቀበል
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል የሚወክለው ኢዮብን ነው። "ከአንተ እጅ መቀበል"

ሌላ የሰው ልጅ
"ሌላ የሰው ልጅ" ወይም "ሌላ ሰው"

Job 35:9

አጠቃላ መረጃ:
ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ።

በብዙ የተጽዕኖ ድርጊቶች ምክንያት
"ተጽዕኖ" የሚለው ቃል በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "ሰዎች ሌሎችን ለመጨቆን በሚያደርጓቸው በርካታ ነገሮች ምክንያት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ከታላላቅ ሰዎች ክንዶች እርዳታን ይፈልጋሉ
እዚህ ስፍራ "ክንዶች" የሚለው የሚያመለክተው ሀይልን ወይም ጥንካሬን ነው። "ከታላላቅ ሰዎች ሀይል ለማግኘት ጥሪ ያደርጋሉ" በሚለው ውስጥ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በምሽት ዝማሬዎችን የሚሰጥ ማን ነው
ኤሊሁ እግዚአብሔር ለሰዎች በችግር ጊዜ፣ በምሽት ሰአት የሚዘምሩት ዝማሬ አድርጎ ተስፋን እንደሚሰጥ ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 35:12

አጠቃላ መረጃ:
ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ።

እነርሱ ይጮሃሉ
"የተጨቆኑ ሰዎች ይጮሃሉ"

አንተ እርሱን ከምትጠባበቅበት... ምን ያህል ያነሰ ነገር ይመልስልሃል!
እግዚአብሔር የትዕቢተኞችን እና የክፉዎችን ጸሎት ስለማይሰማ፣ ይልቁንም ሙሉ ለሙሉ በእግዚአብሔር ላይ የተነሳውን የኢዮብን ጸሎት ይሰማል አይባልም። "ስለዚህ አንተ በትጠባበቀውም...እርሱ በእርግጥ ምላሽ አይሰጥህም!" (ቃለ አጋኖ የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ ጉዳይ በፊቱ ነው
"አንተ ጉዳይህን ለእርሱ አቅርበሃል"

አንተ እርሱን እየጠበቅህ ነው
" አንተ እርሱን እንዲመልስልህ እየጠበቅህ ነው"

Job 35:15

አጠቃላ መረጃ:
ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ።

አሁን አንተ የእርሱ ቁጣ ቅጣት አያደርስም ብለሃል፣ ስለ መተላለፍ ጥቂት እርምጃ እንኳን አይወስድም ብለሃል
ኢዮብ ስለ እግዚአብሔር እውነት ያልሆኑ እነዚህን ነገሮች በመናገሩ ምክንያት፤ እግዚአብሔር ለኢዮብ ጸሎት ምላሽ አይሰጥም።

የእርሱ ቁጣ ቅጣት አያስከትልም
እዚህ ስፍራ "የእርሱ ቁጣ" የሚለው "እርሱ" ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "እርሱ በመቆጣቱ ምክንያት በፍጹም ማንንም አይቀጣም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይመልከቱ)

ያለ ዕውቀት ቃሎችን ደርድሯል/ብዙ ቃሎችን ተናግሯል
ኤሊሁ ስለ "ቃላት" ሲናገር ቁሶች እንደሆኑ አድርጎ ነው፤ ብዙ ቃላትን ስለመናገር ሲናገርም እነዚያን ቁሶች አንዱን በሌላው ላይ እንደመከምር አድርጎ ነው። "እውቀት" የሚለው ቃል በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "ስለ ምን እንደሚናገር ሳያውቅ ብዙ ቃላትን ተናግሯል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 36

1 ኤሊሁ እንዲህ በማለት ንግግሩን ቀጠለ፥ 2 "ትንሽ ጨምሬ እንድናገር ፍቀድልኝ፥ እግዚአብሔርን በመወገን ትንሽ አክዬ የምናገረው አለኝና ጥቂት ነገሮችን
አሳይሃለሁ። 3 ዕውቀቴን ከሩቅ አመጣለሁ፤ ጽድቅ የፈጣሪዬ ነው እላለሁ። 4 በርግጥ ቃሎቼ ሐሰት አይደሉም፤ አንድ በዕውቀት የበሰለም ከአንተ ጋር ነው። 5
ተመልከት፥ እግዚአብሔር ኃያል ነው፥ ማንንም አይንቅም፤ እርሱ በማስተዋል ብርታቱም ኃያል ነው። 6 እርሱ የአመጸኞች ሰዎችን ሕይወት አይጠብቅም ነገር ግን
ከዚያ ይልቅ መከራ ለሚቀበሉት ትክክል የሆነውን ነገር ያደርግላቸዋል። 7 ፊቱን ከጻድቃን አይመልስም ነገር ግን ከዚያ ይልቅ እንደ ነገሥታት በዙፋኖች ላይ
ያስቀምጣቸዋል፥ እነርሱም ይከብራሉ። 8 ይሁንና፥ በሰንሰለት ቢገቡ፥ በመከራም ገመድ ቢታሰሩ 9 ያን ጊዜ ያደረጉትን መተላለፋቸውንና በግፍ እንደተመላለሱ
ይገልጥላቸዋል። 10 ደግሞም እርሱ ጆሮዎቻቸውን ለትምህርቱ ይከፍታቸዋል፥ ከክፋታቸው እንዲመለሱም ያዛቸዋል። 11 ቢሰሙትና ቢያመልኩት ቀኖቻቸውን
በብልጽግና ዓመቶቻቸውንም በእርካታ ያሳልፋሉ። 12 ይሁን እንጂ፥ ባይሰሙት በሰይፍ ይጠፋሉ፤ ዕውቀት ስለሌላቸው ይሞታሉ። 13 ልባቸው ከእግዚአብሔር
የራቀ እነዚያ ቁጣቸውን ያከማቻሉ፤ እግዚአብሔር በሚያስራቸው ጊዜ እንኳን ለዕርዳታ አይጮኹም። 14 በወጣትነታቸው ይሞታሉ፤ ሕይወታቸውም በቤተ ጣዖት
ዝሙት አዳሪዎች መካከል ይጠፋል። 15 የሚሰቃዩትን ሰዎች በስቃያቸው አማካይነት ያድናቸዋል፤ በመከራቸው አማካይነትም ጆሮዎቻቸውን ይከፍታል። 16
በእርግጥ እርሱ ከጭንቀት አውጥቶ የሰባ ምግብ የሞላበት ጠረጴዛ በፊትህ ወደሚቀመጥበትና ስቃይ ወደሌለበት ሰፊ ስፍራ ሊያወጣህ ይፈልጋል። 17 ነገር
ግን አንተ በክፉ ሰዎች ፍርድ ተሞልተሃል፤ ፍርድና ፍትሕም ይዘውሃል። 18 ብልጽግና ወደ መታለል እንዲስብህ እትፍቀድለት፤ መጠኑ የበዛ ጉቦም ፍትሕን
እንድታዛባ እንዲያደርግህ አትፍቀድለት። 19 ብልጽግናህ ከሐዘን ሊያርቅህ ይችላል? ወይም የኃይልህ ብርታት ሁሉ ሊረዳህ ይችላል? 20 ሰዎች በየስፍራቸው
በሚወገዱበት ጊዜ በሌሎች ላይ ኃጢአትን ለመሥራት ጨለማን አትመኝ። 21 ኃጢአትን ከማድረግ ትርቅ ዘንድ በመከራ ተፈትነሃልና ወደ ኃጢአት እንዳትመለስ
ተጠንቀቅ። 22 ተመልከት፥ እግዚአብሔር በኃይሉ ከፍ ያለ ነው፤ እንደ እርሱስ ያለ አስተማሪ ማነው? 23 ስለ መንገዱ ከቶ ማን አስተምሮታል? 'በደለኛ ነህ'
ሊለውስ ከቶ ማን ይችላል? 24 ሰዎች የዘመሩለትን ሥራዎቹን ለማወደስ አስታውስ። 25 እነዚያን ሥራዎች ሰዎች ሁሉ አይተዋል፥ ነገር ግን እነዚያን ሥራዎች
የሚያዩት ከርቀት ብቻ ነው። 26 ተመልከት፥ እግዚአብሔር ትልቅ ነው፤ እኛም በሚገባ አናውቀውም፤ ዘመኖቹም አይቆጠሩም። 27 እርሱ እንፋሎቱ ዝናብ ሆኖ
ይወርድ ዘንድ የውሃ ነጠብጣቦችን ወደ ላይ ስቦ ያከማቻል፥ 28 ደመናዎች ወደ ታች ያፈስሱታል፥ በሰዎች ላይም በብዙ ያንጠባጥቡታል። 29 በርግጥ
የደመናዎቹን መዘርጋትና ከድንኳኑ የሚወጣውን መብረቅ ሊያስተውል የሚችል አለ? 30 ተመልከት፥ መብረቁን በዙሪያው ይበትናል፤ ባህሩን በጨለማ
ይከድነዋል። 31 በዚህ መንገድ ሰዎችን ይመግባቸዋል፥ ብዙ ምግብንም ይሰጣቸዋል። 32 ዒላማቸውን እንዲመቱ እስኪያዛቸው ድረስ እጆቹን በመብረቅ
ነጓድጓድ ይሸፍናቸዋል። 33 ዐውሎ ነፋስ እንደሚመጣ ድምፁ ለሰዎች ይነግራቸዋል፤ መቃረቡንም እንስሶች ደግሞ ያውቃሉ።

Job 36:1

ጥቂት ነገሮችን አሳይሃለሁ
ኤሊሁ ለኢዮብ ነገሮችን ማስረዳትን የሚገልጸው እነዚያን ነገሮች ለኢዮብ እንደሚያሳየው አድርጎ ነው። "ጥቂት/አንዳንድ ነገሮችን አሳይሃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እውቀት ከሩቅ ስፍራ አገኛለሁ
ኤሊሁ ስለ ተለያዩ ነገሮች እውቀትን ከሩቅ ስፍራ እንዳገኘ አድርጎ ይገልጻል። "ታላቁን እውቀቴን አሳይሃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጽድቅ የሰራኝ/የፈጠረኝ የእርሱ መሆኑን
እዚህ ስፍራ "ጽድቅ" የሚለው በቅጽል መልኩ ሊተረጎም ይችላል። "ፈጣሪዬ/የሰራኝ ጻድቅ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Job 36:4

ቃሎቼ ሀሰት አይሆኑም
"እኔ የምናገረው ሀሰት አይሆንም"

በእውቀት የበሰለ አንድ ሰው ከአንተ ጋር አለ
"አንድ ሰው" የሚለው ቃል ኤሊሁ ራሱን ያመለክታል። በእውቀት የበሰለ በጣም አዋቂ ስለ መሆን ይናገራል። "እኔ፣ ከአንተ ጋር ያለሁት፣ በጣም በእውቀት የላቅሁ ነኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ
"ተመልከት" ወይም "ስማ" ወይም "ልነግርህ ላለው ነገር ትኩረት ስጥ"

እርሱ በመረዳት ባለጸጋነቱ ሃያል ነው።
"በጥንካሬ ሃያል" የሚለው ሀረግ ጥንድ ትርጉም ይሰጣል፤ ይህም "በጣም ጠንካራ" ማለት ነው። ኤሊሁ ስለ እግዚአብሔር መረዳት/እውቀት ሁሉንም ነገር በፍጹምነት የሚናገረው የእርሱ መረዳት በጣም ጠንካራ እንደሆነ አድርጎ ነው። "እርሱ በመረዳቱ በጣም ጠንካራ ነው" ወይም "እርሱ ሁሉንም ነገር ሙሉ ለሙሉ ያውቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 36:6

እርሱ ዐይኖቹን ከጻድቅ ሰው ላይ አያነሳም
ኤሊሁ እግዚአብሔር ለጻድቅ ሰው ሚያደርገውን ጥበቃ የመገልጸው እግዚአብሔር በዐይን እንደሚከታተላቸው አድርጎ ሲሆን እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ የሚያደርገውን ጥበቃ ማቆሙን ደግሞ ዐይኖቹን ከላያቸው ማንሳት አድርጎ ይገልጸዋል። "እርሱ ጻድቃን ሰዎችን መጠበቁን አያቆምም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ንጉሥ በዙፋን ላይ ያስቀምጣቸዋል
ኤሊሁ እግዚአብሔር ለጻድቃን የሚሰጠውን ክብር የሚገልጸው እንደ ንጉሥ በዙፋን ላይ እንደሚያስቀምጣቸው አድርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ከፍ ይላሉ
ኤሊሁ እግዚአብሔር ጻድቃንን የሚያከብራቸው ከፍ ወዳለ ስፍራ እንደሚያወጣቸው አድርጎ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍት ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እርሱ ወደ ላይ ከፍ ያደርጋቸዋል" ወይም "እርሱ ያከብራቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Job 36:8

እነርሱ በሰንሰለት ቢታሰሩ እንኳን
እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው የሚያመለክተው ኃጢአት ቢሰሩ እግዚአብሔር ለእርማት የሚቀጣቸውን ጻድቃን ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንዱ በሰንሰለት ቢያስራቸው" ወይም "አንዱ እስረኛ ቢያደርጋቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በመከራ ገመድ ቢያጠምዳቸው
ኤሊሁ በስቃይ ውስጥ እንዲገባ የተደረገን ሰው የሚገልጸው፤ ያ ሰው በገመድ እንደተያዘ እና እንዲሰቃይ እንደተደረገ ነው። "አንዱ ሰው እነርሱ እንዲሰቃዩ አድርጓል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

የእነርሱ መተላለፍ እና የእነርሱ ኩራት
ግሱ ከቀደመው ሀረግ ሊገኝ ይችላል። "መተላለፋቸውን እና ኩራታቸውን ለእነርሱ ይገልጥላቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 36:10

እርሱ ጆሯቸውንም ደግሞ ይከፍታል
ኤሊሁ የሚናገረው የአንድን ሰው ጆሮ መክፈት ሰውየው እንዲሰማ ማድረግ መሆኑን ነው። "እርሱ እንዲሰሙም አድርጓል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ ትዕዛዝ
"ትዕዛዝ" የሚለው ስም በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "እርሱ ለሚያዛቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ከክፋት መመለስ
ኤሊሁ አንድን ድርጊት ማቆም ከዚያ መመለስ አድርጎ ይናገራል። "ክፉ ከማድረግ መመለስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ቀኖቻቸውን በብልጽግና ይፈጽማሉ፣ አመቶቻቸውንም በእርካታ
"ቀናት" እና "አመታት" የሚሉት ቃላት ሁለቱም የሚያመለክቱት የአንድን ሰው የህይወት ዘመን ነው። "ዘመናቸውን/እድሜያቸውን በብልጽግና እና በእርካታ ይፈጽማሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ በሰይፍ ይጠፋሉ
ኤሊሁም የሚናገረው በሀይል በሰይፍ ስለሚጠፋ ሰው፣ በሰይፍ አንድ ሰው ስለገደላቸው ሰዎች ነው። "በአመጽ ይገደላሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 36:13

በልባቸው አምላክ የለሽ የሆኑ
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚለው የሚያመለክተው ሃሳብን እና ስሜትን ነው። ይህ ሀረግ ሰውየው እግዚአብሔርን ማመንን በግትርነት መቃወሙን ነው።"በእግዚአብሔር ማመንን ማን ይቃወማል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር በአንድ ላይ በሚያስራቸው ጊዜ እንኳን
ኤሊሁ እግዚአብሔር ሰዎችን መቅጣቱን በገመድ እንደሚያስራቸው አድርጎ ይገልጸዋል። "እግዚአብሔር በሚቀጣች ጊዜ እንኳን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ህይወታቸው በቤተ ጣኦት አመንዝሮች መሃል ያከትማል
እዚህ ስፍራ "የቤተ ጣኦት አመንዝሮች" የሚለው የሚያመለክተው በጣኦት አምልኮ ቤተመቅደስ ውስጥ የሚያገለግሉ ወጣት ወንዶች የአምልኳቸው ክፍል አድርገው የሚፈጽሙትን ስነምግባር የሌለው ወሲባዊ ድርጊት ነው። ለዚህ ሀረግ ሊሰጡ የሚችሉ አማራጭ ትርጉሞች 1) አምላክ የለሾች ስነምግባር በሌለው ባህሪያቸው መሞታቸውን ወይም 2) አምላክ የለሾች በሀፍረት እና በውርደት ይሞታሉ።

Job 36:15

እርሱ ጆሮዎቻቸውን ከፍቷል
ኤሊሁ ያለ ችግር በሰፊ መከራ በሌለበት በሰፊ መኖርን ይገልጻል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ገበታህ ስብ በበዛበት ማዕድ ይሞላል
ኤሊሁ የሚናገረው ገበታ በምርጥ ምግቦች ተሞልቶ በብልጽግና ስለመኖር ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ገበታህ ይዘጋጃል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አገልጋዮችህ ገበታህን ያዘጋጃሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በስብ የተሞላ ምግብ
ብዙ ስብ ያለው ስጋ የብልጽግና ምልክት ነበር፣ ምክንያቱም እንስሳቱ ጤናማ እና በሚገባ የተመገቡ እንደነበሩ ያሳያል። "እጅግ ምርጥ የሆነ ምግብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 36:17

አንተ እንደ ክፉ ሰዎች በፍርድ ስር ነህ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "እግዚአብሔር ክፉዎችን እንደሚቀጣ አንተንም እየቀጣ ነው" ወይም 2) "ክፉዎች በሚቀጡበት ቅጣት እየተቀጣህ ነው"

ፍርድ እና ብይን ይዘውሃል
ኤሊሁ እግዚአብሔር በኢዮብ ላይ እየፈረደበት እንደሆነ እና ፍርድ እና ብይን ኢዮብን እንደያዙት ሰዎች አድርጎ ይናገራል። "እግዚአብሔር ወደ ፍርድ አምጥቶሃል ደግሞም ብይን ሰጥቶሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቁጣህ ወደ ፌዝ አይምራህ
አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች ይህንን "በሀብት አለመማለልህን ተጠንቀቅ" ይላሉ።

Job 36:19

እንዳትጎዳ ሀብትህ ሊረዳህ ይችላልን፣ ወይም የጥንካሬህ ሀይል ሁሉ ሊያግዝህ ይችላል?
ኤሊሁ እነዚህን ጥያቄዎች የሚጠይቀው ገንዘብ እና ሀይል በትክክለኛ መንገድ እስካልሄደ ድረስ ኢዮብን ሊረዱት እንደማይችሉ ለመግለጽ ነው። "ሀብት ከመከራ ሊያወጣህ አይችልም፣ ደግሞም የትኛውም ሀይልና ጥንካሬ በሙሉ ሊረዳህ አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄየሚለውን ይመልከቱ)

የአቅምህ ጥንካሬ በሙሉ
"የታላቅ አቅምህ ጥንካሬ በሙሉ" ወይም "ታላቅ ጥረትህ በሙሉ"

ሰዎች ከስፍራቸው ሲወገዱ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ "ሰዎች" የሚለው በአጠቃላይ ሰዎችን ያመለክታል፣ "ከስፍራቸው ይቆረጣሉ" የሚለው ደግሞ ሌሎችን ከቤታቸው በሀይል ማስወገድን የሚገልጽ ዘይቤ ነው። "ሰዎች ሌሎችን ከቤታቸው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጎትተው ሲያስወጡ" ወይም 2) ይህ "ሰዎች" የሚለው የሚገልጸው አገርን ሲሆን "ከስፍራቸው ይቆረጣሉ" የሚለው ህዝቦች እንዲጠፉ መደረጋቸውን ይገልጻል። "አገራት ሲጠፉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ በመከራ እየተፈተንክ ነው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "መከራ እንድትቀበል በማድረግ እግዚአብሔር እየፈተነህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 36:22

እነሆ፣ እግዚአብሔር
"ይህንን አስቀድሞውኑ ታውቃለህ፡ እግዚአብሔር"

እግዚአብሔር በሀይሉ ከፍ ያለ ነው
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "እግዚአብሔር እጅግ ሀያል ነው" ወይም 2) "ሰዎች እግዚአብሔርን ከፍ ያደርጋሉ ምክንያቱም እርሱ ሀያል ነው"

እንደ እርሱ አስተማሪ ማን ነው?
ኤሊሁ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠይቀው እንደ እግዚአብሔር ያለ አስተማሪ የለም የሚለውን ለማጉላት ነው። "እንደ እርሱ ያለ አስተማሪ የለም" ወይም "እርሱ እንደሚያስተምር የሚያስተምር ማንም የለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄየሚለውን ይመልከቱ)

Job 36:25

እነርሱ እነዚያን ድርጊቶች የተመለከቱት ከርቀት ብቻ ነው
ኤሊሁም የእግዚአብሔርን ስራዎች ከርቀት ብቻ በመመልከታቸው፣ ስራዎቹን በሙላት ሊረዱ ስላልቻሉ ሰዎች ይናገራል። "እነርሱ ስራዎቹን በሙላት አልተረዱም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ
"ተመልከት" ወይም "ስማ" ወይም "ልነግርህ ለተዘጋጀሁት ነገር ትኩረት ስጥ"

የእርሱ ዘመናት ቁጥር አይሰላም
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ከመቼ አንስቶ እንደነበር ነው። "ሰዎች እርሱ ለምን ያህል ጊዜ እንደኖረ ማወቅ አይችሉም" ወይም "ሰዎች የእርሱን እድሜ ሊያውቁ አይችሉም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 36:27

እርሱ ከእንፋሎቱ ዝናብ ያዘንባል/ያነጥራል
"ማንጠር" የሚለው ቃል "ማጥራት" ወይም "ማጣራት" ማለትም ሊሆን ይችላል። ኤሊሁ እግዚአብሔር እንዴት የውሃ ጠብታን፣ ወይም ተንን እንዴት ወደ ዝናብነት እንደሚለውጥ ይገልጻል። "እርሱ ተኑን ወደ ዝናብ ይለውጠዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የደመናዎችን ታላቅ መበተንት፣ ከእርሱ ጎጆ የሚወጣውን መብረቅ የሚረዳ አለን?
ኤሊሁ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠይቀው ማንም እነዚህን ነገሮች ማድረግ እንደማይችል ትኩረት ለመስጠት ነው። "ማንም የደመናን መበተን እና ከእርሱ ጎጆ የሚወጣውን መብረቅ ሊረዳ አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄየሚለውን ይመልከቱ)

የደመናዎችን ታላቅ መበተንት
"ታላቅ መበተንት" የሚለው ሀረግ በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "በሰማይ ሁሉ ላይ ደመና እንዴት እንደሚበተን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ከእርሱ ጎጆ
ኤሊሁ ሰማይን እግዚአብሔር እንደሚኖርበት "ጎጆ" አድርጎ ይገልጸዋል። "እግዚአብሔር ከሚኖርበት፣ ከሰማይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 36:30

እነሆ፣ እርሱ ይበትናቸዋል
"በጥንቃቄ ተመልከት፣ ደግሞም እንዴት እንደሚበትናቸው እይ"

እናም የባህርን ስሮች ይሸፍናል
ኤሊሁ ባህር ተክል እንደሆነ እና ጥልቅ ስፍራው ስሩ እንደሆነ አድርጎ ስለባህር ጥልቅ ክፍል ይናገራል። ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ምንም እንኳን መብረቅ በሰማይ ብርሃን እንዲታይ ቢያደርግም፣ የባህር ጥልቅ ክፍሎች ግን ጨለማ እንደሆኑ ይቀራሉ። "ነገር ግን የባህር ጥልቅ ክፍል ጨለማ ሆኖ ይቀራል" ወይም 2) የሰማይ መብረቅ የባህር ጥልቅ ስፍራ ጭምር ብርሃን እንዲያገኝ ያደርጋል። "እናም ብርሃናት የባህርን ጥልቅ ስፍራ ያበራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 36:32

እጆቹን በመብረቅ ይሞላል
ኤሊሁ ነጎድጓድ ስለሚያመጣው መብረቅ እግዚአብሔር መብረቅን በእጆቹ እንደያዛቸው እና እርሱ ወደ ፈለገው አቅጣጫ እንደሚጥላቸው ይናገራል። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እግዚአብሔር የመብረቅን ሀይል ሊወረውራቸው በእጆቹ ይዟል፣ ወይም 2) እግዚአብሔር የመብረቅን ሀይል እስከሚጠቀምባቸው ድረስ በእጆቹ ደብቆ ይዟል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መብረቆቹ
"በብልጭታ የሚፈጠረው መብረቅ" ወይም "መብረቁ"

አድምጥ እየመጣ ነው
"ሞገዱ እየመጣ መሆኑን ስማ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 37

1 በርግጥ በዚህ ጉዳይ ልቤ ተናውጧል፤ ስፍራውንም ለቋል። 2 ኦ እስቲ አድምጡ፤ የድምፁን ሁካታ፥ ከአፉም የሚወጣውን ድምፅ አድምጡ። 3 እርሱ
ድምፁን ከሰማይ በታች ወዳለ ስፍራ ሁሉ ይልካል፥ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስም መብረቁን ይልካል። 4 ከእርሱ በኋላ ድምፅ ይጮኻል፤ በግርማዊ ድምፁም
ያንጎደጉዳል፤ ድምፁ በሚሰማበት ጊዜ የመብረቁን ብልጭታ አይከለክልም። 5 እግዚአብሔር በድምፁ በሚያስደንቅ ሁኔታ ያንጎደጉዳል፤ ልናስተውላቸው
የማንችላቸውን ታላላቅ ነገሮችንም ያደርጋል። 6 በረዶውን፥ 'በምድር ላይ ውደቅ'፤ እንዲሁም ዝናቡን፥ 'ብርቱ ዝናብ ሆነህ ውረድ' ይለዋል። 7 ሰዎች ሁሉ
ያደረገውን ሥራውን እንዲያዩ የእያንዳንዱን ሰው እጅ ከመሥራት ይከለክላል። 8 ከዚያም አራዊት ወደ መደበቂያቸው ይሄዳሉ፥ በዋሻዎቻቸውም ውስጥ ይቆያሉ።
9 ዐውሎ ነፋስ ከደቡብ መኖሪያው ይመጣል፤ ቅዝቃዜም በሰሜን ከተበተነው ነፋስ። 10 በእግዚአብሔር እስትንፋስ በረዶ ይገኛል፤ የውኆቹም ስፋት እንደ ብረት
ይቀዘቅዛል። 11 በርግጥ ጥቅጥቁን ደመና በሙቀት ይበትነዋል፤ መብረቆቹን በደመናዎች መካከል ይበትናቸዋል። 12 በመላው ዓለም ላይ ፈቃዱን ያደርጉ
ዘንድ በአመራሩ ደመናትን ያሸከረክራቸዋል። 13 እነዚህ ሁሉ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፤ ይህንን የሚያደርገው አንዳንድ ጊዜ ለማቅናት፥ አንዳንዴም ምድሩን
ለማጠጣት፥ አንዳንዴም የቃል ኪዳን ታማኝነቱን ለማሳየት ነው። 14 ኢዮብ ሆይ፥ ይህንን ስማ፤ ቆም በልና የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራዎች አስብ። 15
እግዚአብሔር እንዴት ፈቃዱን በደመናት ላይ እንደሚፈጽም፥ የመብረቁንም ብልጭታ በእነርሱ ውስጥ እንዲበራ እንደሚያደርግ ታውቃለህ? 16 በዕውቀቱ
ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራዎች፥ የደመናትንም መንሳፈፍ ታስተውላለህ? 17 ከደቡብ በሚመጣው ነፋስ ምክንያት ምድር ጸጥ በምትልበት
ጊዜ ልብስህ እንዴት እንደሚሞቅ ታስተውላለህ 18 ከብረት የተሠራ ጠንካራ መስታወት የሚመስለውን ሰማይ እንደ እርሱ መዘርጋት ትችላለህ? 19
አዕምሮአችን ከመጨለሙ የተነሣ ክርክራችንን በሥርዓት ማቅረብ አልቻልንምና ምን እንደምንመልስለት አስተምረን። 20 ላነጋግረው እንደምፈልግ ይነገረው
ዘንድ ይገባል? አንድ ሰው እንዲዋጥ ይፈልጋል? 21 እነሆ፥ ነፋስ በውስጡ ካለፈና ደመናውን ካጠራው በኋላ በሰማይ ላይ የሚያበራውን ፀሐይ ሰዎች ለማየት
አይችሉም። 22 እንደ ወርቅ የሚያብረቀርቅ ብርሃን ከሰሜን ይመጣል- በእግዚአብሔር ዘንድ አስፈሪ ግርማ አለ። 23 ሁሉን ቻዩን በሚመለከት እኛ ልናገኘው
አንችልም፤ እርሱ በጽድቁና በኃይሉ ታላቅ ነው። ሰዎችን አያስጨንቅም። 24 ስለዚህ፥ ሰዎች ይፈሩታል። ጥበበኞች ነን ብለው የሚያስቡትን
አይመለከታቸውም"።

Job 37:1

ልቤ ተንቀጠቀጠ... ከስፍራው ሸሸ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ ደግሞም የፍርሃቱን ክብደት ያጎላሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚህ ነገር ልቤ ራደ/ተንቀጠቀጠ
"ይህ" የሚለው የሚያመለክተው በኢዮብ 36:33 ላይ የሚገኘውን ነጎድጓ ነው

ከስፍራው ሸሽቷል
ኤሊሁ ስለ ልቡ የሚናገረው ከደረቱ የሚወጣ እስኪመስል በሃይል እንደሚመታ ነው። "ከስፍራው ለቀቀ" ወይም "በሃይል ይመታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

የድምጹ ነጎድጓድ፣ ከአፉ የሚወጣው ድምጽ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ነገሮችን ይናገራሉ። ኤሊሁ መብረቅን የእግዚአብሔር ድምጽ እንደሆነ አድርጎ ይገልጻል። (ዘይቤያዊ አነጋገር እናትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ
ኤሊሁ በምድር ሩቅ ስፍራ የሚገኘውን ቦታ የምድር ዳርቻ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። "በምድር በሁሉም ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 37:4

ከዚህ በኋላ ከፍ ያለ ድምጽ ይሰማል... የግርማው ድምጽ ይሰማል
ኤሊሁ ስለ ነጎድጓዱን እንደ እግዚአብሔር ድምጽ አድርጎ መግለጹን ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚህ በኋላ ያጉረመርማል
"ከብልጭታው በኋላ ያጉረመርማል"

የግርማዊነቱ ድምጽ
"የእርሱ ግርማዊነት ድምጽ"

ድምጹ በሚሰማበት ጊዜ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች ድምጹን በሚሰሙበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ልክ እንደዚሁ ለዶፍ ዝናብ
ግሱ ከቀደመው ሀረግ ሊወሰድ ይችላል። "ልክ እንደዚሁ፣ ለዶፍ ዝናብ ይናገረዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ ሚለውን ይመልከቱ)

Job 37:7

እርሱ የሁሉንም ሰው እጅ ያቆማል
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል የሚወክለው መላውን ሰውነት ነው። "እርሱ ሁሉንም ሰው ያስቆማል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ሀይለኛው ዝናብ በደቡብ ካለው ማደሪያው ይወጣል፣ በረዶም/ቅዝቃዜ በሰሜን ካለው የተበታተነ ነፋስ ይወጣል
በእስራኤል፣ ጠንካራ የነፋስ ማዕበል ከደቡብ ይነፍሳል፤ ቀዝቃዛ አየር ደግሞ ከሰሜን ይመጣል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ማዕበል በደቡብ ካለው ማደሪያው ይመጣል
ኤሊሁ አውሎ ነፋሱ እስኪመጣ ድረስ ማደሪያ ስፍራ እንዳለው አድርጎ እና ከደቡብ እንደሚነፍስ ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 37:10

በእግዚአብሔር እስትንፋስ በረዶ ይሆናል
ኤሊሁ ቀዝቃዛው የሰሜን ነፋስ የእግዚአብሔር እስትንፋስ እንደሆነ ይናገራል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የእግዚአብሔር እስትንፋስ በረዶ

ይሰጣል/ይፈጥራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድርጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

እንደ ብረት ይጋገራል
ኤሊሁ የበረዶን ጥንካሬ ከብረት ጥንካሬ ጋር ያነጻጽራል። "እንደ ብረት ይጋገራል" (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ክምሩን ደመና እርጥበት ያሸክመዋል
ኤሊሁ እግዚአብሔር የደመናው ማዕበል እርጥበቱ ከብዶ በውሃ እንዲሞላ ማድረጉን ይናገራል። "እርሱ ከባዱ ደመና በእርጥበት እንዲሞላ ያደርጋል" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 37:12

አንዳንድ ጊዜ ይህ ለእርማት ይሆናል
"እርማት/ቅጣት" የሚለው ቃል በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "የሚያርመው" አካል ሰዎች ናቸው። "አንዳንድ ጊዜ ህዝቡን ለመቅጣት ይህ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

አንዳንድ ጊዜ ለምድሩ
ይህ ማለት ዝናብ ምድሩን አጠጥቶ ሰብል እንዲበቅል ያደርጋል። "አንዳንድ ጊዜ ምድሩን ለማጠጣት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አንዳንድ ጊዜ እንደ ቃል ኪዳን ታማኝነት ተግባር
"ታማኝነት" የሚለው ረቂቅ ስም "ታማኝ"ነ ወይም "በታማኝነት" ተብሎ ሊጻፍ ይችላል። "አንዳንድ ጊዜ በታማኝነት ለቃል ኪዳኑ ለማድረግ" ወይም "አንዳንድ ጊዜ ለህዝቡ ታማኝ ለመሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Job 37:14

እግዚአብሔር ደመናትን እንዴት እንደሰራ ደግሞም የመብረቆችን ብልጭታ እንዳበጀ ታውቃለህን?
ኤሊሁ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ኢዮብ ይህን ማወቅ እንደማይችል ትኩረት ለመስጠት ነው። "እግዚአብሔር እንዴት ደመናትን እንደሚያበጅ እና እንዴት መብረቅን እንደሚያበርቅ ልታውቅ አትችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ደመናትን መስራት
"ደመናትን መቆጣጠር" ወይም "ደመናት እርሱን እንዲታዘዙለት እንደሚያደርግ"

Job 37:16

በእውቀቱ ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔርን አስደናቂ ስራዎች፣ የደመናትን መንሳፈፍ ማወቅ ትችላለህ?
ኤሊሁ ይህን ጥያቄ የሚጠይቀው ኢዮብ እነዚህን ነገሮች ማወቅ እንደማይችል ትኩረት ለመስጠት ነው። "በእውቀት ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔርን አስደናቂ ስራዎች፣ የደመናትን መንሳፈፍ፣ መረዳት አትችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

የደማናትን መንሳፈፍ
"ደመናት እንዴት እንደሚንሳፈፉ"

የእግዚአብሔርን አስደናቂ ስራዎች
ግሱ ከቀደመው ሀረግ ለገኝ ይችላል። "ወይስ የእግዚአብሔርን አስደናቂ ስራዎች ትረዳለህን?" ወይም "ደግሞም የእግዚአብሔርን አስደናቂ ስራዎች ልተረዳ አትችልም" (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

ከደቡብ በሚመጣ... እንዴት ልብስህ እንደሚወብቅህ/እንደሚሞቅህ ትረዳለህ?
ኤሊሁ ይህን ጥያቄ የሚጠይቀው ኢዮብ እነዚህን ነገሮች እንደማያውቅ ትኩረት ለመስጠት ነው። "ከደቡብ በሚመጣ...ልብሶችን እንዴት እንደሚወብቁህ አታውቅም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ልብሶችህ እንዴት እንደሚወብቁህ/እንደሚሞቁህ
"የለበስከው እንዴት ወበቅ እንደሚፈጥርብህ" ወይም "በልብስህ ውስጥ እንዴት እንደሚያልብህ"

ነፋሱ ከደቡብ እቀጣጫ ከመምጣቱ/ከመንፈሱ የተነሳ
በእስራኤል፣ ሞቃት ነፋስ የሚፍሰው ከደቡብ በረሃ ሲሆን ይህም ሞቃት የሙቀት መጠን ይፈጥራል። "ከሙቀቱ የተነሳ፣ ከደቡብ ደረቅ ነፋስ ይነፍሳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 37:18

ከብረት እንደተሰራ መስታወት...ሰማይን ልትዘረጋ ትችላለህ?
ኤሊሁ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ኢዮብ ይህን ማድረግ እንደማይችል ትኩረት ሰጥቶ ለመናገር ነው። ከብረት የተሰራ መስታወት የሚመስለውን ሰማይ... አንተ ሰማይን ልትረረጋ አትችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ከብረት እንደ ተደተሰራ መስታወት ጥንካሬ ያለው
መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈባቸው ዘመናት፣ መስታወት የሚሰራው ከብረት ነበር። ኤሊሁ ሰማዩ እንደ ብረት ከመጠንከሩ የተነሳ ዝናብ አለመስጠቱን ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የነጠረ ብረት
ይህ የሚያመለክተው፣ በማቅለጫ ውስጥ ተጨምሮ የቀለጠ እና ከዚያም ሲቀዘቅዝ የጠነከረ ብረትን ነው።

እኛን ለእርሱ መናገር የሚገባንን ለእኛ አስተምረን
እዚህ ስፍራ "እኛን" እና "እኛ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ኤሊሁን፣ ኤልፋዝን፣ በልዳዶስን እና ሶፋርን ሲሆን ኢዮብን አይጨምርም። ኤሊሁ ይህን ሀረግ የተጠቀመው በምጸት ነው። (አካታች የሆነ እና አካታች ያልሆነ "እኛ" የሚለውን ይመልከቱ)

ከአእምሯችን መጨለም የተነሳ
ኤሊሁ መረዳት አለመቻልን በአንድ ሰው አይምሮ ውስጥ እንደሚገኝ ጨለማ አድርጎ ይገልጻል። "እኛ ስለማንረዳ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከእርሱ ጋር መናገር እንደምፈልግ ለእርሱ ሊነገረው ይገባልን?
ኤሊሁ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠይቀው ማንም ይህን ማድረግ እንደማይችል ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። "ከእርሱ ጋር መነጋገር እንደምፈልግ ለእርሱ የሚነግረው ሰው ማግኘት አልችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ለእርሱ ሊነገረው ያስፈልጋል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ለእርሱ የሚነግረው ሰው ሊኖረኝ ያስፈልጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ሰው መዋጥ ሊፈልግ ያስፈልገዋልን?
ኤሊሁ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠይቀው ማንም ሰው ይህ እንዲደርስ እንደማይፈልግ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። "ማንም ሰው ሊዋጥ አይፈልግም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለመዋጥ
ኤሊሁ አንድ እየጠፋ ያለን ሰው እየተዋጠ እንደሚገኝ ሰው ይገልጸዋል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል።"እግዚአብሔር እርሱን ስለሚያጠፋው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 37:21

ከሰሜን ወርቃማ ድምቀት ይመጣል
"ወርቃማ ድምቀት" የሚለው ሀረግ የሚገልጸው የወርቅን ክብር/ድምቀት ነው። ይህ በትርጉም ውስጥ ይበልጥ ግልጽ መደረግ ይችላል። "እግዚአብሔር ከሰሜን በመርቃማ ክብር/ድምቀት ይመጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ላይ አስፈሪ ግርማ አለ
"አስፈሪ" የሚለው ቃል ትርጉሙ ፍርሃት ይፈጥራል ማለት ነው። ኤሊሁ ስለ እግዚአብሔር ግርማ የሚገልጸው በእግዚአብሔር ላይ እንዳረፈ ነገር አድርጎ ነው። "የእግዚአብሔር ግርማ ሰዎች እንዲፈሩ ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 37:23

እኛ እርሱን ልናገኘው አንችልም
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ወደ እርሱ ልንቀርብ አንችልም" ወይም 2) ይህ ዘይቤ ኤሊሁ ሰው እግዚአብሔርን ማግኘት እንደማይችል አድርጎ ቢያቀርብም ሰው እግዚአብሔርን ሙሉ ለሙሉ ሊረዳ እንደማይችል የገለጸበት ነው። "ሙሉ ለሙሉ ልናውቀው አንችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በራሳቸው አዕምሮ ጠቢባን ነን የሚሉ
እዚህ ስፍራ "አዕምሮ" የሚወክለው የሰውን ሀሳብ ነው። "በራሳቸው አስተሳሰብ ጠቢባን የሆኑ" ወይም "ራሳቸውን ጠቢባን አድረገው የቆጠሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 38

1 ያን ጊዜ እግዚአብሔር ከብርቱ ዐውሎ ነፋስ ውስጥ ኢዮብን ጠራውና እንዲህ አለው፥ **2** "ዕውቀት በጎደለው ቃል ዕቅዴን የሚያጨልም ይህ ማነው? **3** ጥያቄዎችን እጠይቅሃለሁና አሁን እንደ ሰው ወገብህን ታጠቅ፥ አንተም ልትመልስልኝ ይገባሃል። **4** የምድርን መሠረቶች ባቆምኩ ጊዜ አንተ የት ነበርክ? ከፍ ያለ ማስተዋል ካለህ ነገረኝ። **5** መጠኑን የወሰነው ማነው? የምታውቅ ከሆነ ንገረኝ። በላዩ ላይስ የመለኪያ ገመድ የዘረጋ ማነው? **6** መሠረቶቹስ የቆሙት በምን ላይ ነው? **7** የንጋት ከዋክብት በአንድነት በዘመሩና የእግዚአብሔር ልጆች ሁሉ በደስታ በዘመሩ ጊዜ የማዕዘኑን ድንጋይ ያስቀመጠ ማን ነበር? **8** ደመናትን ልብሱ፥ ድቅድቁንም ጨለማ መጠቅለያው ባደረግሁ ጊዜ **9** ከማኅፀን የሚወጣ ይመስል ፈንድቶ በወጣ ጊዜ የባህሩን መዝጊያ የዘጋ ማነው? **10** ያን ጊዜ ነበር ለባህሩ ገደብን ያደረግሁለት፥ በሮችንና መወርወሪያዎችን ባደረግሁለት ጊዜ፥ **11** እንዲህም ባልኩት ጊዜ፥ 'እስከዚህ ድረስ መምጣት ትችል ይሆናል፥ ከዚህ ግን አትለፍ፤ ለሞገድህ ትዕቢት ገደብ የማደርግለት እዚህጋ ነው'። **12** ከተወለድክበት ጊዜ ጀምሮ ንጋት እንዲጀምር ከቶ ትዕዛዝ ሰጥተኸዋል? ወጋገኑስ በነገሮች መካከል ስፍራውን እንዲያውቅ አድርገኸዋል? **13** የምድርን ማዕዘናት በመያዝ ክፉዎች ሰዎች ከእርሱ ላይ እንዲራገፉ አድርገሃል? **14** ጭቃው ከማኅተም በታች እንደሚለወጥ የምድርም መልክ ተለውጧል፤ በእርሱ ላይ ያለው ነገር ሁሉ በግልጽ እንደ ቁራጭ ጨርቅ ተጠቅልሎ ቆሟል። **15** ከክፉ ሰዎች 'ብርሃናቸው' ተወስዷል፤ ወደ ላይ የተነሣው ክንዳቸውም ተሰብሯል። **16** ወደ ባህሩ መገኛ ሄደህ ታውቃለህ? ዝቅ ወዳለው ጥልቅ ስፍራስ ወርደህ ታውቃለህ? **17** የሞት በሮች ተገልጠውልሃል? የሞት ጥላ በሮችንስ አይተኻቸዋል? **18** ምድርን በስፋቱ ታውቀዋለህ? ይህንን ሁሉ የምታውቅ ከሆነ ንገረኝ። **19** ብርሃን የሚያርፍበት ስፍራ መንገዱ የት ነው? የጨለማውስ ስፍራው የት ነው? **20** ብርሃንና ጨለማን ወደ ሥራቸው ስፍራ ልትመራቸው ትችላለህ? ወደ መኖሪያቸው የሚመለሱበትን መንገድስ ልትፈልግላቸው ትችላለህ? **21** ያን ጊዜ ተወልደህ ስለነበርና የዕድሜህም ቁጥር ታላቅ ስለሆነ ያለጥርጥር ታውቃለህ! **22** ወደ በረዶው መጋዘን ገብተሃል? ወይም የአመዳዩን ማከማቻ አይተሃል? **23** እነዚህን ነገሮች ለመከራ ጊዜ፥ ለጦርነትና ለውጊያ ቀናት ያስቀመጥኳቸው ናቸው። **24** የመብረቅ ብልጭታ የሚሰራጭበት መንገድ የትኛው ነው? ወይም ነፋሳት ከምስራቅ በምድር ላይ የሚበተኑበት መንገድ የቱ ነው? **25** ለዶፍ ዝናብ መውረጃን ያበጀለት ወይም ለመብረቅ ብልጭታ መንገድ ያዘጋጀለት ማነው? **26** ሰው በሌለበት ምድር፥ ማንም በሌለበት ምድረ በዳ ላይ እንዲዘንብ ያደረገ ማነው? **27** ሰው የሌለበትንና የባድማውን አካባቢ ፍላጎት የሚያረካ፥ ሣር እንዲበቅልበትስ የሚያደርግ ማነው? **28** ዝናብ አባት አለው? የጤዛን ጠብታ የወለደው ማነው? **29** በረዶስ የመጣው ከማን ማኅፀን ነው? የሰማዩን አመዳይ ማን ወለደው? **30** ውኆች ራሳቸውን ይደብቁና እንደ ድንጋይ ይጠነክራሉ፤ የጥልቁም ገጽታ ግግር ይሆናል። **31** ኀልያዲስ የተባለውን ኮከብ በሠንሰለት ልታስረው ወይም የኦሪዮንን እስራት ልትፈታ ትችላለህ? **32** የከዋክብት ክምችት በተገቢው ጊዜአቸው እንዲታዩ ልትመራቸው ትችላለህ? ድብ የተባለውን ከነልጆቹ ልትመራቸው ትችላለህ? **33** የሰማይን ሥርዓት ታውቃለህ? የሰማይን ሥርዓት በምድር ላይ መተግበር ትችላለህ? **34** ብዙ የዝናብ ውሃ እንዲያጥለቀልቅህ ድምፅህን ወደ ደመናት ማሰማት ትችላለህ? **35** 'ይኸው እዚህ አለን' ብለው ይላኩህ ዘንድ የመብረቅ ብልጭታዎችን ልትልካቸው ትችላለህ? **36** በደመናት ውስጥ ጥበብን ያኖረ ወይም ለእርጥበት ዕውቀትን የሰጠ ማነው? **37** በጥበቡ ደመናትን ለመቁጠር የሚችል ማነው? **38** ብናኙ ዐፈር ተበጥብጦ ጠንካራ ጓል በሚሆንበትና ጭቃው አፈር በአንድ ላይ በሚጣበቅበት ጊዜ **39** የሰማይን የውሃ መያዣ አዘንብሎ ማፍሰስ የሚችል ማነው? **39** በዋሻዎቻቸው በሚያደቡበትና በመኖሪያቸው ተጋድመው በሚጠባበቁበት ጊዜ **40** ለአንበሳዪቱ አደን ልታድንላት ወይም ግልገሎቿን ልታጠግብላት ትችላለህ? **41** ጫጩቶቻቸው ወደ እግዚአብሔር በሚጮኹበትና ምግብ በማጣት በሚንከራተቱበት ጊዜ ለቁራዎች ምግብ የሚሰጣቸው ማነው?

Job 38:1

ከዚያም ያህዌ መናገር ጀመረ
እዚህ ስፍራ "ከዚያም" የሚለው ቃል የመጽሐፉን አዲስ ክፍል መጀመር ያሳያል። በእናንተ ቋንቋ አዲስ ትዕይንትን ለመጀመር ተመሳሳይ ቃል ካለ ያንን መጠቀም ትችላላችሁ። "ያ ሁሉ ከሆነ በኋላ፣ ያህዌ መናገር ጀመረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ለኢዮብ ተናገረ
"ለኢዮብ መለሰለት" ወይም "ለኢዮብ ምላሽ ሰጠው"

ያለ እውቀት በቃላት ጨለማን ወደ እቅድ የሚመለስ/የሚያመጣ እርሱ ማን ነው?
ያህዌ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት ኢዮብ ስለማያውቀው ነገር መናገሩን ትኩረት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጽ ይችላል። "አንተ ጨለማን ያለ እውቀት በቃላት አማካይነት ወደ እቅዴ አስገብተሃል/አምጥተሃ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ይህን የሚያመጣ እርሱ ማን ነው
"ይህ ለማምጣት አንተ ማን ነህ"

ወደ እቅዶች ጨለማ የሚያመጣ
"እቅዴን የሚያበለሽ" ወይም "ተግባሬን ግራ የሚያጋባ።" ኢዮብ የእግዚአብሔርን እቅድ እንዴት እንዳበላሸ የተገለጸው የእግዚአብሔርን እቅድ ለማየት ይበልጥ ከባድ እንዳደረገ ተደርጎ ነው። "ጨለማ" የሚለው ረቂቅ ስም "አጨለመ" በሚል ግስ ሊተረጎም ይችላል። "እቅዶችን አጨለመ" ወይም "እቅዶች መታየት እንዳይችሉ ከባድ አደረገ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

ያለ እውቀት በቃላት አማካይነት
"ስለማታውቃቸው ነገሮች በመናገር"

ያለ እውቀት በመናገር
"እውቀት" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል መልኩ ሊገለጽ ይችላል። "የማይታወቁ ቃላት" ወይም "እውቀት የሌለባቸው ቃላት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ወንድ ወገብህን ታጠቅ
"ቀበቶህን እንደ ወንድ በወገብህ ዙሪያ እሰር።" ወንዶች ከባድ ስራ ሲሰሩ በነጻነት እግራቸውን ማንቀሳቀስ እንዲችሉ በወገባቸው ዙሪያ ቀበቷቸውን ይታጠቃሉ። "እንደ ወንድ ወገብህን ታጠቅ" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር እንደ ስራ፣ ውድድር፣ ወይም ጦርነትን የመሰለ አንድ ነገር ለማድረግ ተዘጋጅ የሚል ትርጉም አለው። ኢዮብ ለእግዚአብሔር መልስ መስጠትን ለመሰለ ከባድ ስራ መዘጋጀት ነበረበት። "ለከባድ ስራ ራስህን አዘጋጅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 38:4

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ እርሱ እንጂ ኢዮብ ምድርን አለመፍጠሩን ትኩረት ሰጥተው በሚገልጹ በርካታ ጥያቄዎች ኢዮብን መገዳደር ጀመረ። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እኔ የምድርን መሰረቶች መሰረትኩ
ያህዌ መሬትን መፍጠሩን የሚገልጸው መዋቅሮችን ይገነባ እንደነበረ አድርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንግዲህ አንተ እጅግ ብዙ መረዳት ካለህ
"መረዳት" የሚለው ረቂቅ ስም "ተረዳ/አወቀ" በሚል ግስ ሊተረጎም ይችላል። "እጅግ ብዙ አውቀህ ከሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

መጠኗን የወሰነው ማን ነው? ይህ ታውቅ እንደሆነ ንገረኝ
ይህንን በዐረፍተ ነገር መልክ መግለጽ ይቻለል። "የምታውቅ ከሆነ፣ መጠኗን ማን እንደወሰነ ንገረኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

መጠን
"ልክ"

በላይዋ የመለኪያ ገመዷን የዘረጋ ማን ነው?
ይህን ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ መግለጽ ይቻለል። "በላይዋ የመለኪያ ገመድ ማን እንደዘረጋ ንገረኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

የመለኪያ ገመድ
ሰዎች የአንድን ነገር ትክክለኛ መጠን እና ቅርጽ ለመለካት የሚጠቀሙበት ገመድ ወይም ሲባጎ

Job 38:6

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

አጠቃላይ መረጃ:
"የእርሷን" የሚለው ቃል መሬተን ያመለክታል፤

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ታላቅነቱን ለማጉላት ብዙ ጥያቄዎችን ይጠቀማል። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

መሰረቷ የተጣለው በምን ላይ ነበር?
ይህ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "መሰረቷ በምን ላይ እንደተጣለ ንገረኝ" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

መሰረቷ የተጣለው በምን ላይ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እኔ መሰረቷን በምን ላይ መሰረትኩ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ልጆች በደስታ ሲጮኹ... በዚያን ጊዜ ማን ማዕዘኖቿን መሰረተ?
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። " የእግዚአብሔር ልጆች በደስታ ሲጮኹ... ያን ጊዜ ማን ማዕዘኖቿን እንደመሰረተ ንገረኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

የማለዳ ከዋክብት በአንድነት ሲዘምሩ ደግሞም የእግዚአብሔር ልጆች በደስታ ሲጮሁ
እነዚህ ሁለት መስመሮች በትርጉም ተመሳሳይ ናቸው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የማለዳ ከዋክብት በአንድነት ሲዘምሩ
የማለዳ ከዋክብት የተገለጹት ሰዎች እንደሚዘምሩ የሚዘምሩ ተደርገው ነው። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) በቀጣዩ መስመር እንደተገለጸው "የማለዳ ከዋክብት" ከ "እግዚአብሐር ልጆች" ጋር ተመሳሳይ ናቸው ወይም 2) "የማለዳ ከዋክብት" የሚለው የሚያመለክተው በሰማይ የሚገኙ ከዋክብትን ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የማለዳ ከዋክብት
"በማለዳ የሚያበሩ ደማቅ ከዋክብት"

የእግዚአብሔር ልጆች
ይህ የሚያመለክተው ሰማያዊ ፍጥረታት የሆኑተን መላዕክትን ነው። ይህ በኢዮብ 1:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

በደስታ ሰጮኹ
"ደስታ" የሚለው ረቂቅ ስም "ደስተኛነት" በሚል ተውሰከ ግስ ሊተረጎም ይችላል። "በደስተኝነት ጮኹ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በደስታ
"በደስታ ተሞልተው ስለነበር"

Job 38:8

አያያዥ ሀሳብ:
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ሌላ ጥያቄ የተጠቀመው እርሱ እንጂ ኢዮብ ምድርን አለመፍጠሩን ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

በባህር ላይ በር የዘጋ ማን ነው... ደግሞስ ከባድ ጨለማን መጠቅለያው ያደረገለት ማን ነው?
ይህ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ማን በባህ ላይ በሮችን እንደዘጋበት ንገረኝ...ከባድ ጨለማንስ ማን መጠቅለያው እንዳደረገ ንገረኝ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

በባህር ላይ በሮችን የዘጋ
ያህዌ ባህር መላውን ምድር እንዳይሸፍን የከለከለበት መንገድ በባህሩ ላይ በር ከመዝጋት ጋር ተነጻጽሯል። "ውሃ ምድርን እንዳያጥለቀልቅ ከልክሏል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከማህጸን የወጣ ይመስል
ያህዌ ባህርን የፈጠረበትን ሁኔታ ከልጅ መወለድ ጋር ያነጻጽረዋል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ልብሱ
"ለባህር ልብስ ሆኖ"

ጥልቅ ጨለማ መጠቅለያው ሆኖ
"ጨለማ" የሚለው ረቂቅ ስም "ጨለመ" በሚል ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። "ከባድ ጨለማን መጠቅለያው አደረግሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

መጠቅለያ ጨርቅ/መጠምጠሚያ
ልጆች እንደተወለዱ የሚጠቀለሉበት ረጅም ቁራጭ ጨርቅ

Job 38:10

ለባህር የእኔን ዳርቻን በጀሁለት
"ለባህር ዳርቻ አበጀሁለት"

ዳርቻ
ያህዌ ባህር እንዲያልፍ ያልተፈቀደለትን ድንበር አበጀለት"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መቀርቀሪያዎቹን እና በሮቹን አደረግሁለት
ያህዌ ለባህር ዳርቻ ያበጀበትን መንገድ የሚያነጻጽረው መቀርቀሪያ እና በሮች እንዲኖር ከማድረግ ጋር ነው። "መቀርቀሪያ አበጀሁለት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መቀርቀሪያዎች
በር ለመዝጊያ የሚያገለግል ረጅም የአንጨት ቁራጭ ወይም ብረት

እኔ ስናገረው/ሳዝዘው
"እኔ ባህሩን ስናገረው።" ያህዌ ባህሩን የሚናገረው/የሚያዘው ሰው እንደሆነ አድርጎ ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህን ያህል መቅረብ ትችላለህ፣ ከዚህ ወዲያ ግን አታልፍም
"ይህን ያህል" የሚለው ቃል ያህዌ እስከፈቀደለት ስፍራ ድረስ ማለት ነው። "እስከዚህ ድንበር ድረስ ልትመጣ ትችላለህ፣ ነገር ግን ከዚህ አታልፍም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የማዕበልህ ኩራት
"ለማዕበልህ ሀይል።"ማዕበል የተገለጸው ኩራት እንዳለው ተደርጎ ነው። "ኩራት" የሚለው ረቂቅ ስም "ኩሩ" በሚል ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። "ለኩሩ ማዕበልህ" ወይም "ለሀይለኛው ማዕበልህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 38:12

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ይህን ጥያቄ የተጠቀመው እርሱ እንጂ ኢዮብ ብርሃንን አለመፍጠሩን ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ክፉው ከእርሱ እንዲወገድ ... አንተ ነቅንቀኸዋልን?
ይህ ጥያቄ አሉታዊ ምላሽ ይጠበቅበታል። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንተ ፈጽሞውኑ ክፉውን ... ከእርሱ ነቅንቀህ አላስወገድክም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ለማለዳ ትዕዛዝ መስጠት
ያህዌ ማለዳ ትዕዛዝን መቀበል እንደሚችል እና እንደ ሰው ነገሮችን ማወቅ እንደሚችል ይናገራል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይልከቱ)

ንጋት ስፍራውን እንዲያውቅ ማድረግ
"ንጋት ስፍራው የት እንደሆነ እንዲያውቅ ማድረግ"

ንጋት
በማለዳ ሰማይ ላይ ፀሐይ ከመውጣቷ አስቀድሞ የቀኑ ብርሃን መታየት

የምድርን ዳርቻ መያዝ
የንጋት ብርሃን የተገለጸው የምድርን አድማስ እንደያዘ ተደርጎ ነው። "የምድርን ዳርቻዎች መያዝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያው አነጋገር እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ክፉውን ከውስጧ ነቅንቆ ማስወገድ
የቀን ብርሃን የተገለጸው የማያስፈልጉ ነገሮች በመነቅነቅ እንደሚወገዱ ክፉ ሰዎችን እንደሚያስወግድ ተደርጎ ነው። "ክፉ ሰዎችን ከምድር ነቅንቆ ማስወገድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 38:14

ከማህተም በታች እንዳለ ጭቃ/ሸክላ የምድር መልኳ ይለወጣል
በምሽት፣ ሰዎች በግልጽ መመልከቱ አይችሉም፣ ማለዳ ግን ማህተም በሸክላ ላይ ግልጽ ምስልን እንደሚፈጥር ብርሃን የሁሉንም ነገር ቅርጽ በግልጽ መለየት ያስችላል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ቁራጭ ጨርቅ እጥፋት በእርሷ ላይ የሚገኙ ነገሮች ሁሉ በግልጽ ይታያል
እዚህ ስፍራ "እርሷ" የሚለው የሚያመለክተው ምድርን ነው። ይህ ሀረግ በዚህ ስንኝ ከሚገኘው የመጀመሪያው ሀረግ ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከክፉ ሰዎች "ብርሃናቸው" ይወሰዳል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ማለዳ የክፉ ሰዎችን ‘ብርሃን' ይወሰዳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የእነርሱን ‘ብርሃን'
ክፉዎች ጨለማን ብርሃናቸው አድርገው ይቆጥራሉ፣ ምክንያቱም ክፉ ስራቸውን ሚሰሩት በጨለማ ሲሆን ደግሞም ከጨለማ ጋር ቅርርብ አላቸው። (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

የተነሳው ክንዳቸው ይሰበራል
የተነሳው የክፉዎች እጅ የሚለው የሚወክለው ሀይላቸውን እና ክፉ ለማድረግ ያላቸውን ፍላጎት ነው። ነገር ግን የማለዳው ብርሃን ስወጣ ክፉዎች እነዚያን ክፉ ነገሮች ማድረጋቸውን ያቆማሉ። (ዘይቤያው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 38:16

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ አምስት ጥያቄዎችን የተጠቀመው እርሱ እንጂ ኢዮብ ምድርን እና ባህርን አለመፍጠሩን ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ፡
ቁጥር 16 እና 17 አያንዳንዳቸው ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሀረጎችን ይዘዋል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በስፋቷ... ሄደህባታል?
እነዚህ ጥያቄዎች አሉታዊ ምላሽ ይጠብቃሉ። ጥያቄዎቹ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጹ ይችላሉ። "ወደ ባህር ውሃ መሰረት አልሁድክም፣ ወይም በጥልቁ ታችኛ ክፈል አልተራመድክም። የሞት ደጆች ለአንተ አልተገለጹም፤ ደግሞም የሞት ጥላ ደጆችን አላየህም። ምድርን በስፋቷ አላወቅካትም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

የውኖች መሰረትን/መገኛ
"ምንጮች"

ጥልቅ
ይህ ጥልቅ ውሃ የሚገኝበትን ባህርን ወይም ውቅያኖስን ያመለክታል። "ጥልቁ ባህር" ወይም "የውቅያኖስ ጥልቀት" ወይም "ጥልቁ ውሀ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)

የሞት ደጆች ለአንተ ተገልጸውልሃል
x

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Job 38:19

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ሶስት ጥያቄዎችን የተጠቀመው እርሱ እንጂ ኢዮብ ብርሃንን እና ጨለማን እንደማይረዳ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ፡
እነዚህ ሁለቱ ሀረጎች እያንዳንዳቸው ሁለት ትይዩ ሀረጎች አላቸው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ብርሃን ማረፊያ ስፍራ ደግሞም ወደ ጨለማ የሚወስደው መንገድ የት ነው?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ወደ ብርሃን ወይም ወደ ጨለማ ስፍራ የሚወስደውን መንገድ አታውቅም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

የብርሃን ማረፊያ ስፍራ
"የብርሃን መኖሪያ።" ብርሃን የተገለጸው ለእያንዳንዱ ቀን ተነስቶ የሚመጣበት ማረፊያ ስፍራ እንዳለው ተደርጎ ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ብርሃን
"የቀን ብርሃን" ወይም "የፀሐይ ብርሃን"

ብርሃንን እና ጨለማን ወደ ስራ ስፍራቸው ልትመራቸው ትችላለህን? ለእነርሱ ወደ ሆነው ቤታቸው መልሶ
የሚወስዳቸውን መንገድ ልታገኝ ትችላለህ? እነዚህ ጥያቄዎች አሉታዊ ምላሽ እንዲሰጥባቸው ይጠበቃል። እነዚህ ጥያቄዎች በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጹ ይችላሉ። "ብርሃንን እና ጨለማን ወደ ስራ ስፍራቸው ልትመራቸው አትችልም ወይም ደግሞ የእነርሱ ወደ ሆነ ቤታቸው የሚመለሱበትን መንገድ ልታገኝ አትችልም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ወደ ስራ ስፍራቸው
"ወደ አካባቢያቸው/መኖሪያቸው።" ብርሃን እና ጨለማ የተነገሩት በእየዕለቱ የያህዌን ተግባር ለማከናወን እንደሚወጡና እንደሚገቡ ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ያለ ጥርጥር... እጅግ ትልቅ
ያህዌ ምፀታዊ ቀልድ የተጠቀመው ኢዮብ ብርሃንን እና ጨለማን እንደማይረዳ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። "አንተ እንደማታውቅ ግልጽ ነው፣ ምክንያቱም እነርሱን ስፈጥራቸው አንተ ገና አልተወለድክም ነበር፣ ደግሞም አንተ በጣም አላረጀህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

በዚይን ጊዜ ተወልደህ እንደሆነ
"በዚያን ጊዜ አንተ ትኖር ነበር።" "በዚያን ጊዜ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ብርሃን የተፈጠረበትን እና ከጨለማ የተለየበትን ጊዜ ነው። "እነርሱን በፈጠርኩበት ጊዜ አንተ ተወልደህ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

የቀኖችህ ቁጥር እጅግ ትልቅ ነው
"እጅግ ረጅም አመታት ኖረሃል"

Job 38:22

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ይህን ጥያቄዎችን የተጠቀመው እርሱ እንጂ ኢዮብ በተፈጥሮ ላይ እንደማይገዛ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ወደ በረዶ ቤተመዛግብት/መጋዘን ገብተሃል፣ ወይም የበረዶ ውሽንፍሩን ቤተመዛግብት አይተሃል... ደግሞስ ለጦርነት ቀን?
እነዚህ ጥያቄዎች አሉታዊ ምላሽ እንዲሰጥባቸው ይጠበቃል። እነዚህ ጥያቄዎች በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጹ ይችላሉ። "አንተ በፍጹም ወደ በረዶ ቤተመዛግብት አልገባህም፣ ወይም የበረዶ ውሽንፍሩን ቤተመዛግብት... እና ለጦርነት ቀን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

የበረዶ ግምጃ ቤት ገብተሃል... የበረዶውን ውሽንፍርን ቤተመዛግብት
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በትርጉም ተመሳሳይ ናቸው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የበረዶ ቤተ ማዛግብት... የበረዶ ውሽንፍር ቤተመዛግብት
በረዶ እና የበረዶ ወሽንፍራ ያህዌ የእርሱን ፈቃድ ሊፈጽምባቸው ያጠራቀማቸው ተደርገው ተገልጸዋል። (ዘይቤያው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የበረዶ ውሽንፍር
የበረዶ ኳስ (ብዙ ጊዜ ትንንሽ ናቸው) አንዳንድ ጊዜ በሃይለኛ ዝናብ ወቅት ከሰማይ ይወርዳል።

የመብረቅ ብልጭታ መንገዱ ወዴት ነው ወይም ከምስራቅ በምድር ላይ ሁሉ የነፋስ መሄጃው ወዴት ነው?
እነዚህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፉ ይችላሉ። "የመብረቅን ብልጭታ የምልክበት መንገድ ወዴት ነው ወይም ከምስራቅ በምድር ላይ ሁሉ ነፋሳትን የምበትነው ወዴት ነው?" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ነፋሳት ይበተናሉ
"ነፋሳት ይነፍሳሉ"

Job 38:25

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ይህን ጥያቄ ኢዮብን የጠየቀው እርሱ እንጂ ኢዮብ ዝናብ እንዲዘንብ እና መብረቅ እንዲበርቅ እንደማያደርግ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ለዝናብ መውረጃውን የሚፈጥርለት ወይም...ሳር እንዲበቅል የሚያደርገው ማን ነው?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፈ ይችላል። "ለዝናብ መውረጃውን የማበጅለት፣ ሳር እንዲበቅል የማደርግ እኔ ብቻ ነኝ፣... እኔ ብቻ ይህንን አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

የዝናብ መውረጃ
"የዝናብ ጎርፍ"

የመብረቅ መንገድ
"የመብረቅ ጉርምርምታ የሚሰማበት መንገድ"

ማንም ሰው በማይኖርበት መሬት፣ ማንም በማይኖርበት ምድረበዳ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተቀራራቢ ትርጉም አላቸው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ማንም ሰው በማይኖርበት
"ሰዎች በሌሉበት"

ለማርካት
በውስጠ ታዋቂነት የቀረበው መረጃ ምድር ሳር እንድታበቅል የሚያደርገው ዝናብ ነው። "ስለዚህ ዝናብ ምድር እንድታበቅል ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አጠፋ ደግሞም አወደመ
"የፈራረሰ እና የተበላሸ።" እነዚህ ሁለት ቃላት ተቀራራቢ ትርጉም አላቸው፤ ደግሞም የእነዚህን አካባቢዎች የፈራረሰ እና ባዶ ተፈጥሮ ትኩረት ይሰጣሉ። (ሄንዲያዲስ/ሁለት ቃላት 'እና' በሚል አያያዥ ቃል የሚገኛኙበትና አንድን ጥልቅ ሀሳብ ለመግለጽ የሚያገለግል ዘይቤያዊ አነጋገር)

በሣር
"እየበቀለ ያለ ሣር" ወይም "በመብቀል ላይ የሚገኝ ሣር።" ማደግ የጀመረ ይህ ሣር።

ምድርን በአዲስ ሣር የሚሞላ
"ምድር አዲስ ሳር እንድታበቅል የሚያደርግ"

Job 38:28

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ኢዮብን አራት ጥያቄዎችን የጠየቀው እርሱ እንጂ ኢዮብ ዝንብን እንደማያዘንብ፣ ጤዛና እና በረዶን እንደማይፈጥር እንደዚሁም አመዳይን እንደማያበጅ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ፡
በእነዚህ ሶስት ስንኞች ውስጥ የሚገኙ እያንዳንዳቸው መስመሮች ተመሳሳይ ነገሮችን ይገልጻሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ፡
ዝናብ፣ ጤዛ፣ በረዶ፣ እና አመዳይ የተገለጹት እንደ ሰዎች እንደሚወለዱ ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዝናብ አባት አለውን፣ ወይስ፣ የጤዛ ጠብታ አባቱ ማን ነው? በረዶ ከማን ማህጸን መጣ? የሰማይን ነጭ አመዳይ ማን ወለደው?
እነዚህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "ዝናብ አባት እንዳለው፣ የዝናብ ጠብታዎችን ማን እንዳስገኘ ንገረኝ። በረዶ ከማን ማህጸን እንደወጣ፣ ደግሞም የሰማይን ነጭ አመዳይ ማን እንደወለደው ንገረኝ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ለጤዛ ጠብታ አባቱ
ለጤዛ አባቱ የሆነው የሚለው ለመፈጠሩ ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። "የጤዛ ጠብታ እንዲኖር ምክንያት የሆነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በረዶ
"ቀዝቅዞ ጠጣር የሆነ/የረጋ ውሃ"

መውለድ
"ልጅ መስጠት"

ነጭ አመዳይ
በቅዝቃዜ መሬት ላይ በረዶ/ጠጣር የሆነ ጤዛ፣ ደማና በሌለበት ምሽቶች ራሳቸውን የደበቁ እና እንደ ድንጋይ ጠጣር የሆኑ ውኖች
ውኖች የተገለጹት መደበቅ እንደሚችሉ ተደርጎ ነው። በክረምት በረዶ ከስሩ ውሃ ይደብቃል። (ሰውኛ እና ከባለቤቱ ጋር የሚጣቀስ ተውላጠ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

እንደ ድንጋይ ሆነ
የበረዶው ጠጣርነት የተገለጸው ድንጋይ እንደሆነ ተደርጎ ነው። "እንደ ድንጋይ ጠጣር/ጠንካራ ሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥልቁ
ይህ የሚያመለክተው ውሃው በጣም ጥልቅ የሆነን፣ ባህርን ወይም ውቅያኖስን ነው። "ጥልቁ ባህር" ወይም "የውቅያኖስ ጥልቀት" ወይም "ጥልቁ ውሃ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይምለከቱ)

Job 38:31

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ኢዮብን አምስት ጥያቄዎችን የጠየቀው እርሱ እንጂ ኢዮብ ሰማያትን እንደማይገዛ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ፡
በእነዚህ ሶስት ስንኞች ውስጥ የሚገኙ እያንዳንዳቸው ሁለት መስመሮች ተመሳሳይ ነገሮችን ይገልጻሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በምድር ላይ ሁሉ...በሰንሰለቶች መቆለፍ ትችላለህ
እነዚህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "ፕልያዲስ የተባለውን ኮከብ በሰንሰለት ማሰር ትችል እንደሆነ፣ ወይም ኦርዮን የተባለውን ኮከብ ገመድ መበጠስ ትችል እንደሆነ ንገረኝ። የከዋክብት ክምችትን በተገቢው ጊዜያቸው እንዲታዩ መምራት ትችል እንደሆነ ነገረኝ፤ ወይም ድብ የተባለውን ኮከብ ከልጆቹ ጋር መምራት ትችላለህ። የሰማይን ስርአት የምታውቅ ከሆነ፣ ወይም የሰማይን ህግ በምድር ላይ ማድረግ ትችል እንደሆነ ንገረኝ። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ሰንሰለት መፍታት
"የሰንሰለት እስራት ልጥበጥስ" ወይም "ሰንሰለት መበጠስ"

ፕልያዲስ...ኦርዮን... ድብ
እነዚህ የከዋክበት ክምችቶች ስሞች ናቸው። እነዚህ በኢዮብ 9:9 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

የኦርዮንን ገመዶች ልትበጥስ
"ኦርዮን የተባለውን ኮከብ ያሰሩትን ገመዶች ልትፈታ"

የከዋክብት ክምችት
በሰማይ ላይ አንድ የተለየ ቅርጽ ሚፈጥሩ የከዋክብት ክምችት

በተገቢ ጊዜያቸው መታየት
"በትክክለኛ ጊዜያቸው ይታዩ ዘንድ"

ልጆቹ
"ግልገሎቹ"

Job 38:34

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ኢዮብን ሁለት ጥያቄዎችን የጠየቀው እርሱ እንጂ ኢዮብ የዝናብ ደመናዎችን እና መብረቅን እንደማይገዛ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

‘እኛ በዚህ አለን’ ...አንተ ልትነሳ ትችላለህ?
እነዚህ ጥያቄዎች በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "ብዙ የዝናብ ውሃ ይሸፍንህ ዘንድ ድምጽህን እሰከ ደመናት ድረስ ማሰማት ትችል እንደሆነ ንገረኝ። የመብረቅ ብልጭታን ይወጣ ዘንድ ልታዘው ትችል እንደሆነ ንገረኝ፤ እነርሱም ‘እዚህ አለን!' ይሉህ እንደሆነ ተናገር።" በሚለው ውስጥ እንሚገኘ። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ብዙ የዝናብ ውሃ
"ብዙ/የተትረፈረፈ" የሚለው ረቂቅ ስም "የበዛ" በሚል ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። "ብዙ የዝናብ ውሃ" ወይም "የውኖች ጎርፍ" በሚለው ውስጥ እንሚገኘ። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን መልከቱ)

እዚህ አለን
ይህ የሚያሳየው የመብረቅ ብልጭታዎች እንደ አገልጋይ ትዕዛዝ ለመቀበል ዝግጁ ነን ማለታቸውን ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 38:36

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ኢዮብን ሶስት ጥያቄዎችን የጠየቀው እርሱ እንጂ ኢዮብ ደመናዎችን እና ዝናብን እንደማይገዛ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ጥበብን በአንድነት አጥብቆ የያዘ...ማን ነው?
እነዚህ ጥያቄዎች በዐረፍተ ነገር ሊተረጎሙ ይችላሉ። "ጥበብን በደመናዎች ያኖረ ማን እንደሆነ ደግሞም ለብዝታ መረዳትን የሰጠ ማን ነው። ማን በችሎታው ደመናትን ሊቆጥር እንደሚችል ንገረኝ። አፈር ወደ ጠጣርነት ሲለወጥ እንዲሁም የምድር ጓል በአንድነት ሲጣበቅ የሰማይ የውሃ አቁማዳን ማን ማንቆርቆር እንደሚችል ንገረኝ።" በሚለው ውስጥ እንሚገኘ። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ጥበብን በደመናት ውስጥ ያስቀመጠ ማን ነው ወይም ለብዝታ መረዳትን የሰጠ ማን ነው?
እነዚህ ሁለት መስመሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ደመናት እና ብዝታን ማስወገድ ያህዌ ለሰዎች የሚያደርጉትን ነገር ይረዱ ዘንድ የሰጣቸው ጥበብ እና መረዳት ተደርገው ተገልጸዋል። "ጥበብ" እና "መረዳት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች "ጠቢብ" በሚል ቅጽል እና "ተረዳ" በሚል ግስ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "ደማናትን ጠቢብ ያደረገ ማን ነው ወይም ብዥታን ግልጽ ያደረገ ማን ነው?" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ሰውኛ ዘይቤ እንዲሁም ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

በደማናት ውስጥ ጥብን ያኖረ
"ለደማናት ጥበብን የሰጠ"

በራሱ ጥበብ ደማናት መቁጠር የሚችል ማን ነው?
"ደማናትን መቁጠር የሚችል ማን ነው?"

የውሃ አቁማዳዎች
እነዚህ ሰዎች በአንድነት የሚሰፏቸው ሲሆኑ ውሃ ለመያዝ የሚያገለግሉ ናቸው። ያህዌ ከባድ ደማናዎችን ከ"ውሃ አቁማዳ" ጋር ያስተያያቸዋል፣ ምክንያቱም እንደ ውሃ አቁማዳ ብዙ ውሃ መያዝ ይችላሉ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አፈር ወደ ጠጣርነት ሲለወጥ እና የምድር ጓል በአንድነት ሲጣበቅ
እነዚህ ሁለት መስመሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አፈር ወደ ጠጣርነት ሲለወጥ
ዝናብ የላመውን ደረቅ አፈር በአንድነት ያጣብቀዋል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ዝናብ አፈሩን በአንድ ላይ አጣብቆ ሲያድበለብለው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የምድር ጓል በአንድነት ሲጣበቅ
"የአፈር ጓል በአንድነት ሲጣበቅ"

Job 38:39

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ኢዮብን ይህን ጥያቄ የጠየቀው እርሱ እንጂ ኢዮብ አንበሶችን እንዴት እንደሚመግብ አለማወቁን ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

አንተ አድብተህ ጠብቀህ... ማደን ትችላለህ?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "አድብተህ ጠብቀህ... ማደን ትችል እንደሆን ንገረኝ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

የሚታደን
"ታዳኝ።" ይህ አንድ አንበሳ አድኖ የሚበላው እንስሳ ነው።

ሴት አንበሳ
ይህች ሴት አንበሳ ናት

የምግብ ፍላጎት
ረሃብ

የእርሷ የአንበሳ ግልገል
"የአንበሳ ግልግል/ደቦል" ለራሳቸው አድነው መመገብ የጀመሩ ደቦል አንበሶች

ዋሻ
"ዋሻ" አንበሳ የሚጠለልበት መኖሪያ/የአውሬ ዋሻ/ ነው

በሚደበቅበት ጊዜ የሚጠለልበት
"በቁጥቋጦ ውስጥ መደበቅ።" አንበሶች ሲያድኑ ጥቅጥቅ ባለ ሳር ቅጠል ውስጥ ይደበቃሉ

አድብቶ መጠበቅ
በውስጠ ታዋቂነት የሚገኘው መረጃ አንበሶች ተደብቀው የሚያድኑት እንስሳ እስኪቀርብ ይጠብቃሉ። "ታዳኙን ተጋድሞ/አድፍጦ መጠበቅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 38:41

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ኢዮብን ይህን ጥያቄ የጠየቀው እርሱ እንጂ ኢዮብ ለአሞሮች ምግብ እንደማይሰጣቸው ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ምግብ ላጡ... ምግባቸውን የሚሰጣቸው ማን ነው?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ምግብ ላጡ... ለተጠቁት ማን ምግባቸውን እንደሚሰጣቸው ንገረኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ለተራቡት ምግብ የሚሰጥ
"ምግብ የሚሰጥ።" ይህ የሚያመለክተው ቁራዎች ለምግብነት የሚፈልጓቸውን እንስሳት ነው።

ቁራዎች/ቁራ መሰል አሞራ
የሞቱ እንስሳትን የሚመገቡ የሚያብረቀርቅ ጥቁር ላባ ያላቸው ትላልቅ ወፎች

ወደ እግዚአብሔር መጮህ
በውስጠ ታዋቂነት የሚገኘው መረጃ ቁራዎች ምግብ ለማግኘት ይጮሃሉ የሚል ነው። "ለእርዳታ ወደ እግዚአብሔር መጮህ" ወይም "ምግብ እንዲሰጣቸው ወደ እግዚአብሔር ይጮሃሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መንገዳገድ
ይህ ማለት ወዲያ ወዲህ በመንገዳገድ መራመድ

ምግብ በማጣት
"በምግብ በማጣት ምክንያት" ወይም "የሚበሉት በማጣታቸው ምከንያት"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 39

1 የበረሃ ፍየሎች በዐለቶች መካከል የሚወልዱበትን ጊዜ ታውቃለህ? አጋዘኖችስ ግልገሎቻቸውን በሚወልዱበት ጊዜ ልታያቸው ትችላለህ? **2** የእርግዝናቸውንስ ወራት ለመቁጠር ትችላለህ? የሚወልዱበትንስ ጊዜ ታውቃለህ? **3** ይንበረከኩና ግልገሎቻቸውን ይወልዳሉ፤ የምጣቸውንም ሕመም ያበቃሉ። **4** ግልገሎቻቸው ይጠነክራሉ፥ በገላጣው መስክ ላይም ያድጋሉ፤ ርቀው ይሄዳሉ፥ ወደ ወለዷቸውም አይመለሱም። **5** የሜዳ አህያው በነጻነት እንዲሄድ የፈቀደለት ማነው? **6** አራባህን ቤቱ፥ የጨውንም ምድር መኖሪያው ያደረግሁለትን የፈጣኑንስ አህያ እስራት የፈታ ማነው? **7** በከተማ ባለው ሁካታ በንቀት ይስቃል፤ የነጂውንም ጩኸት አይሰማም። **8** በመሰማሪያዎቹ በተራሮች ላይ ይንከራተታል፤ በዚያም የሚመገበውን የለመለመ ሣር ሁሉ ይፈልጋል። **9** ጎሽ ሊያገለግልህ ይፈቅዳል? በበረትህስ አጠገብ ለማደር ይስማማል? **10** ጎሽ ትልሞችህን እንዲያርስልህ በገመድ ልትቆጣጠረው ትችላለህ? ጓሉንስ ይከሰክስልሃል? **11** ጉልበቱ ብርቱ ስለሆነ ትታመነዋለህ? እርሱ እንዲያከናውንልህ ተግባርህን ትተውለታለህ? **12** ምርትህን ዐውድማ ላይ እንዲያከማችልህ፥ እህልህንም ወደ ቤት እንዲያገባልህ ትተማመነዋለህ? **13** የሰጎን ክንፎች በደስታ ይራገባሉ፤ ነገር ግን እነርሱ የፍቅር ክንፎችና ላባዎች ናቸው? **14** እንቁላሎቿን በአፈር ውስጥ ትጥላለች፥ እንዲሞቃቸውም በትቢያ ውስጥ ትተዋቸዋለች። **15** እግር እንዲረግጣቸው ወይም የዱር አውሬ እንዲጨፈልቃቸው ትረሳቸዋለች። **16** የእርስዋ ያልሆኑ ይመስል በጫጩቶቿ ትጨክናለች፤ ድካሟ ሁሉ ከንቱ እንደሚሆን በማሰብ አትፈራም፤ **17** እግዚአብሔር ጥበብን ነፍጓታልና አንዳች ማስተዋልንም አልሰጣትም። **18** በፍጥነት በምትሮጥበት ጊዜ በፈረሱና በጋላቢው ላይ በንቀት ትሥቃለች። **19** ለፈረስ ኃይሉን ሰጥተኸዋል? አንገቱንስ በጋማው አልብሰኸዋል? **20** እንደ አንበጣ እንዲዘል አድርገኸዋል? የማንኮራፋቱ ገናናነት አስፈሪ ነው። **21** በኃይል ይጎደፍራል፥ በብርታቱም ደስ ይለዋል፤ የጦር መሳሪያዎችን ለመገናኘት ይፈጥናል። **22** በፍርሃት ላይ ይሳለቃል፥ አይደነግጥምም፤ ከሰይፍም ወደ ኋላ አይመለስም። **23** ከሚብለጨለጨው ፍላጻና ጦር ጋር የፍላጻዎች መያዣ ጎኑ ላይ ይንኳኳል። **24** በቁጣና በጭካኔ መሬትን ይውጣል፤ የመለከት ድምፅ ሲሰማ ይቁነጠነጣል። **25** የመለከት ድምፅ በሚሰማበት ጊዜ ሁሉ 'አሃ!' ይላል፤ ጦርነትን፥ የአዛዦችን የሚንጎደጎድ ጩኸትና ሁካታ ከሩቅ ያሸታል። **26** ጭልፊት ርቆ የሚመጥቀው፥ ክንፎቹንም ወደ ደቡብ የሚዘረጋው ባንተ ጥበብ ነው? **27** ንስር ወደ ላይ የሚበረውና ጎጆውን ከፍ ባሉ ስፍራዎች የሚሠራው ባንተ ትዕዛዝ ነው? **28** በገደል ላይ ይኖራል፥ መኖሪያ ምሽጉንም በገደሉ ጫፍ ላይ ያደርጋል። **29** እዚያ ላይ ሆኖ የሚነጥቀውን ይቃኛል፤ ዐይኖቹም ከርቀት ይመለከቱለታል። **30** ጫጩቶቹ ደግሞ ደም ይጠጣሉ፤ በድን ባለበት እርሱም በዚያ አለ"።

Job 39:1

አያያዥ ሀሳብ:
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ኢዮብን አራት ጥያቄዎች የጠየቀው እርሱ ከኢዮብ ታላቅ እንደሆነ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። ምክንያቱም ለእነዚህ የተራራ ዱር ፍየሎች እና አጋዘኖች እንክብካቤ የሚያደርገው እርሱ እንጂ ኢዮብ አይደለም። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ልጆቻቸውን ምን ጊዜ እንደሚወልዱ... አንተ ታውቃለህን?
ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንተ በእርግጥ መቼ ነገሮች ምቹ እንደሚሆኑ ...አጋዘኖች መቼ ግልገሎቻቸውን እንደሚወልዱ ማወቅ አትችልም!"

አጋዘኖች መቼ ልጆቻቸውን እንደሚወልዱ መጠባበቅ ትችላለህ?
ይህ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። አጋዘኖች ግልገሎቻቸውን የሚወልዱበትን ሁሉም ነገር ምቹ የሚሆንበትን ገዜ በእርግጠኝነት መጠባበቅ አትችልም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ግልገሎች የሚኖሩት
"ግልገሎቻቸውን የመወልዱበት"

የእርግዝና ወራቶቻቸውን መቁጠር ትችላለህ?
ይህ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እርጉዝ የሚሆኑበትን ወራት መቁጠር አትችልም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

እርጉዝ የሚሆኑበት
"እርግዝናቸው የሚያበቃበት"

እነርሱ
"እነርሱ" የሚለው ቃል ፍየሎችን እና አጋዘኖችን ያመለክታል

እርጉዞች
"እርጉዝ የሆኑ"

ግልገሎቻቸውን መቼ እንደሚወልዱ ጊዜውን ታውቃለህ?
ይህ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "በእርግጥ መቼ ግልገሎቻቸውን እንደሚወልዱ አታውቅም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

Job 39:3

አያያዥ ሀሳብ:
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

እነርሱ ወደ ታች ቁጢጥ ይላሉ
"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሜዳ ፍየሎችን እና አጋዘኖችን ነው።

ግልገሎቻቸውን ይወልዳሉ
"ዘራቸውን ይሰጣሉ"

ከዚያም የምጣቸው ስቃይ ያጨርሳሉ
የሚሰጡ ትርጉሞች 1) ወልደው ሲጨርሱ የምጣቸው ስቃይ ያልፋል ወይም 2) "የምጥ ስቃይ" የሜዳ ፍየሎች እና የአጋዘኖች ግልገሎችን የሚያመለክት ሜቶኖሚ/ ነው። ምክንያቱም እነርሱ የእናቶቻቸው ምጥ እና ስቃይ ውጤቶች ናቸው። "ከማህጸናቸው ግልገሎቻቸውን ይወልዳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ባዶ ሜዳዎች
"ገጠራማ አካባቢ" ወይም "ጫካ"

ተመልሰው አይመጡም
"ወደ እነርሱ አይመለሱም" ወይም "ወደ እናቶቻቸው አይመለሱም"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Job 39:5

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

የጨው ምድሩን...ማን ሰጠው?
ያህዌ ከኢዮብ ይልቅ ታላቅ መሆኑን በትኩረት ለመግለጽ ሁለት ጥጣቄዎችን ይጠቀማል፤ ምክንያቱም ያህዌ ለሜዳ አህዮች እንክብካቤ የሚያደርገው ያህዌ እንጂ ኢዮብ አይደለም። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

የሜዳ አህያን በነጻነት እንዲፈነጭ ያደረገው ማን ነው?
ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "የሜዳ አህያን በነጻነት እንዲፈነጭ ያደረግኩት እኔ ነኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

የሜዳ አህያ...የዱር አህያ
ይህ ተመሳሳይ ለሆነ የአህያ አይነት የተሰጠ ስም ነው

በጨው ምድር ...እስራቱን የፈታ ማን ነው?
ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "በጨው ምድር...እስራቱን የፈታሁለት እኔ ነኝ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ማሰሪያዎች
እንስሳት ሮጠው እንዳይሄዱ የሚታሰሩባቸው ገመዶች፣ ሰንሰለቶች፣ ወይም ማሰሪያዎች

በምድረበዳ የማንን ቤት ሰራሁ
ያህዌ አህያ ቤት እንዳለው ሰው አድርጎ ይገልጻል። "ምድረበዳን መኖሪያ አድርጌ ሰጠሁት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የጨው ምድር
በጨው ባህር አካባበ ያለው ምድር ብዙ ጨው ይገኝበታል

Job 39:7

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

እርሱ
"እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሜዳ አህያን ነው

በንቀት ይስቃል
ያህዌ አህያን እንደ ሰው ይስቃል በማለት ይገልጻል። አህያው የሚስቀው በከተማ የሚኖሩ ከፍ ያለ ድምጹን እንዲሰሙ ሲሆን፣ እርሱ ግን በጸጥታ ስፍራ ይኖራል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚልውን ይመልከቱ)

ነጂዎች
እንስሳው እንዲሰራ የሚያስገድድ

መሰማሪያ
እንስሳት በሜዳ የበቀለውን የሚግጡበት ስፍራ

Job 39:9

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

አጠቃላይ መረጃ፡
እዚህ ስፍራ ያህዌ አራት ጥያቄዎች የጠየቀው ኢዮብ እንደ ያህዌ እንዳልሆነ ትኩረት ለመስጠት ነው፤ ምክንያቱም ኢዮብ ጎሽን ሊቆጣጠር አይችልም። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ጎሽ
ሊሰጡ የሚችለሁ ምክንያቶች 1) በጫካ የሚኖር የበሬ ዝርያ/አይነት ወይም 2) በሬ የሚመስል የጎሽ አይነት

ደስተኛ መሆን
"ፈቃደኛ መሆን"

በግርግምህ ሊቆይ ይፈቅዳልን?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "በግርግምህ ሊቆይ አይፈቅድም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በግርግምህ ሊቆይ ይፈቅዳል
"ምሽቱን በበረትህ ለማደር"

ግርግም
እንስሳት መመገብ እንዲችሉ ምግባቸውን መያዣ

በእርሻ ስፍራ ጎሽን ለማሰር ገመድ መጠቀም ትችላለህ?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ጎሽ የእርሻህን ትልም እንዲያርስ በገመድ ጠምደህ ልትቆጣጠረው አትችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ገመድ
ገበሬዎች እንስሳትን ለመምራት በጭንቅላታቸው ወይም ጫንቃቸው/አንገት ላይ ገመድ ያስራሉ

ትልሞች
እነዚህ በእርሻ ላይ ያሉ ረጃጅም ቦዮች ናቸው። ትልም የሚለው በኢዮብ 31፡38 እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ሸለቆውን አንተን እየተከተለ ይከሰክስልሃል?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "በፍጹም አንተን እየተከተለ ሸለቆውን አይከሰክስልህም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

መከስከስ
አፈርን ማለስለስ

Job 39:11

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

አጠቃላይ መረጃ፡
እዚህ ስፍራ ያህዌ ሶስት ጥያቄዎች የጠየቀው ኢዮብ እንደ ያህዌ እንዳልሆነ ክርክሩን ለመቀጠል ነው፤ ምክንያቱም ኢዮብ ጎሽን ሊቆጣጠር አይችልም። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ሀይሉ ታላቅ ስለሆነ እርሱን ትተማመናለህን?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ሀይሉ ታላቅ ስለሆነ በእርሱ ልትተማመን አትችልም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱን ታምናለህ
"እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው "ጎሽ"ን ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይሰራው ዘንድ ስራህን በእርሱ ላይ ትጥላለህ/ትተዋለህ?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ለአንተ ይሰራልህ ዘንድ ስራህን ለእርሱ መተው አትችልም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ይሰራልህ ዘንድ ስራህን ለእርሱ መተው
"ከባዱን ስራህን ይሰራልህ ዘንድ"

እህልህን ይወቃልህ/ያበራይልህ ዘንድ...በእርሱ ትታመናለህ?
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ይይዛሉ። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "እህልህን እንዲወቃልህ ...በእርሱ ላይ ልትታመን አትችልም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 39:13

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

የሰጎን ክንፎች...የፍቅር ላባዎች እና ክንፎች ናቸው?
ያህዌ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው ኢዮብ ሰጎኖች የሚያደርጉትን ለምን እንደሚያደርጉ ኢዮብ እንደማየውቅ ትኩረት ለመስጠት ነው። "የሰጎን ክንፎች እና ላባዎች በኩራት ሲቀዝፉ ይህን የሚያደርጉት በፍቅር ይሁን አይሁን አንተ አታውቅም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰጎን
በጣም በፍጥነት መሮጥ የምትችል ነገር ግን የማትበር በጣም ትልቅ ወፍ

በኩራት ማርገብገብ
"በደስታ መንቀሳቀስ"

ክንፍ
በወፍ ክንፍ ላይ የሚገኝ በጣም ረጃጅም ላባዎች

ላባ
የወፍ አካልን የሚሸፍኑ አነስተኛ ላባዎች

የፍቅር
የዕብራይስጡ ቃል እርግጠኛ አይደለም። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "የታማኝነት" ወይም 2) "የሺመላ።" ማለት ሊሆን ይችላል። የሸመላ ስም ትርጉሙ "ታማኝ የሆነው" ወይም "አፍቃሪ የሆነ" ማለት ነው፤ ምክንያቱም ሰዎች ሸመላ ለጫጩቶቻቸው በጣም መልካም ተንከባካቢ እንደሆኑ ያውቃሉ።

በመሬት ላይ
"በምድር"

እነርሱን ያደቋቸዋል/ይቸጫቸዋል
"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው እንቁላሎችን ነው

ይረጋግጧቸዋል
"በላያቸው ይቆማሉ/ይራመዱባቸዋል"

Job 39:16

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

እርሷ በጭካኔ ትተዋቸዋለች
"እርሷ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሴቷን ሰጎን ነው

የእርሷ ምጥ
እንቁላሏን ስትጥል የምትሰራው ስራ

በከንቱ ሊሆን ይችላል
ጫጩቶቹ ከሞቱ፣ ስራዋ ሁሉ ዋጋ ቢስ ነበር። "ጫጩቶቹ የሚሞቱ ከሆነ ልፋቷ ከንቱ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከጥበብ ተነጥላለች
"ጥበብን እንድትዘነጋ ተደርጋለች" ወይም "ጥበብ አልተሰጣትም"

የጥበብ ምስጢር
ይህ ቃል በኢዮብ 11፡ ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

እርሷ ስትሮጥ
ይህ ስንኝ ጫጩቶቿን ከመንከባከብ ከድካሟ ጋር በንጽጽር ይታያል። "ሆኖም፣ በምትሮጥበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እርሷ በጋላቢው...ትስቃለች
በጋላቢው የምትስቀው ከፈረስ ፈጣን በመሆኖ እንደሆነ ተጠቁሟል። "በጋላቢው የምትስቀው... ከፈረስ ይልቅ ፈጣን በመሆኗ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 39:19

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

አጠቃላይ መረጃ፡
እዚህ ስፍራ ያህዌ ሶስት ጥያቄዎች የጠየቀው ኢዮብ እንደ ያህዌ እንዳልሆነ ትኩረት ለመስጠት ነው፤ ምክንያቱም ኢዮብ የዱር/ያልተገራ ፈረስን ሊቆጣጠር አይችልም። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

አንገቱን በጋማ ትሸፍናለህን?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "አንገቱን በጋማ ልትሸፍን አትችልም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

አንገቱን በጋማ ልትሸፍን
የፈረስ "ጋማ" የተገለጸው የፈረስን አንገት እንደሚሸፍን ልብስ ተደርጎ ነው። "ጋማው አንገቱን እንደ ልብስ ይሸፍናል" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በአንገቱ ላይ የወረደው ጋማ
በፈረሱ አንገት ላይ የሚገኘው ረጅም ፀጉር

በእውኑ አንተ እንደ አንበጣ እንዲፈናጠር ልታደርገው ትችላለህን?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "አንተ እንደ አንበጣ እንዲዘል ልታደርገው አትችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ትልቅ አንበጣ
በጣም በፍጥነት እና በጣም ሩቅ ሊዘል የሚችል ትልቅ የአንበጣ አይነት

ማሸካካት/ማንኮራፋት
ፈረሶች በአፍንጫቸው የሚያወጡት በጣም ጉልህ ድምጽ

Job 39:21

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

እርሱ ይጎደፍራል/መሬቱን ይመታል
"እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ፈረስን ነው። ፈረሱ ምድርን በእግሩ ይመታል/ይጎደፍራል ምክንያቱም ምግያው እንዲጀምር በጣም ቸኩሏል። "በጉጉት መሬቱን ይመታል ደግሞም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መጎድፈር
"በኮቴው መሬቱን መቆፈር/መምታት"

መሳሪያውን ለማግኘት
እዚህ ስፍራ "መሳሪያ" የሚለው የሚወክለው ለጦርነቱ የሚጠቀሙበትን ነው። "ወደ ጦርነት ለመግባት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በፍርሃት ላይ ያፌዛል
"በፍጹም አይፈራም"

ያፌዛል
"ይስቃል"

መጨነቅ
"ተስፋ መቁረጥ"

ወደ ኃላ አይመለስም
"አይሸሸም"

ኮሮጆ
ፍላጻዎችን መያዣ

ማስፈራራት
መርገፍገፍ እና ድምጽ ማሰማት

ሸንጥ
የፈረሱ ጎን

ጦር
ሰዎች በጠላቶቻቸው ላይ የሚወረውሩት ጫፉ ሹል የሆነ ብረት ያለው ረጅም በትር

Job 39:24

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

እርሱ
"እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ፈረስን ነው።

ምድርን ይውጣል
የፈረሱ በምድር ላይ በፍጥነት መሮጥ ሰው ውሃን ሲጠጣ በፍነት ጭልጥ እንደሚያደርግ ፍጥነቱ ተገልጽዋል። "በምድር ላይ በፍጥነት ይሮጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመለከቱ)

በሃይል እና በቁጣ
ፈረሱ ስለጓጓ በፍጥነት እና በጥንካሬ ይንቀሳቀሳል

በመለከት ድምጽ
አንድ ሰው መለከት እንደሚነፋ ተደርጎ ሊገለጽ ይችላል። "ጦርነት መጀመሩን ለማወጅ አንድ ሰው መለከት ሲነፋ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በአንድ ስፍራ መቆም አይችልም
"በአንድ ስፍራ ተረጋግቶ መቆም አይችልም/ይቅበጠበጣል"

አሃ፣ ይላል
"አሃ" የሚለው ቃል ሰዎች አንድ ነገር ሲያገኙ የሚያወጡት ድምጽ ነው። ፈረስ ድምጽ የሚያወጣው ጦርነት መኖሩን በማወቁ ምክያት ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ነጎድጓዳዊ ጩኸት
ይህ የሚያመለክተው ፈረሱ እነዚህን ነገሮች መስማቱን ነው። "እርሱ ነጎድጓዳዊ ጩኸቱን ሰምቷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ፉከራ
"የጦርነት ጩኸት።" ሰዎች በጦርነት ጊዜ ጅግንነታቸውን እና ብርታታቸውን ለማሳየት እንዲሁም ጠላቶቻቸውን ለማስፈራራት የሚያሰሙት የተለየ ጩኸት አለ

Job 39:26

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

ወደ ደቡብ... ይህ በአንተ ጥበብ ነውን?
ያህዌ ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ኢዮብ እንደ ያህዌ ታላቅ አለመሆኑን ለማረጋገጥ ነው። ለዚህ ጥያቄ በውስጠ ታዋቂነት የሚሰጠው ምላሽ "አይደለም" የሚል ነው። "ወደ ደቡብ...ይህ በአንተ ጥበብ አይደለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ክንፎቹን ወደ ደቡብ የሚዘረጋው
እዚህ ስፍራ ክንፎችን መዘርጋት የሚያመለክተው መብረርን ነው። "ወደ ደቡብ መብረር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ደቡብ
በመጽሐፍ ቅዱሳዊው መልከአምድር ወፎች በክረምት በሞቃታማ የአየር ንብረት ለመኖር ወደ ደቡብ ይበራሉ።

Job 39:27

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

ጎጆቸውን በከፍታ ስፍራ የሚሰሩት ... በአንተ ትዕዛዝ ነውን?
ያህዌ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው ኢዮብ ንስሮችን ለማዘዝ አቅም እንደሌለው ለማረጋገጥ ነው። ለዚህ ጥያቄ በውስጠ ታዋቂነት የሚሰጠው ምላሽ "አይደለም" የሚል ነው። "አንተ ንስር በከፍታ ስፍራ ቤቱን እንዲሰራ ልታዝዘው አትችልም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በአንተ ትዕዛዝ
"ትዕዛዝ" የሚለው ረቂቅ ስም በግስ መልኩ ሊጻፍ ይችላል። "እንዲህ እንዲያደርግ አንተ ስለ ነገርከው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ከፍ ብሎ እንዲወጣ
ይህ ማለት ወደ ላይ ይበራል ማለት ነው። "ወደ ሰማይ ይበራል" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጠንካራ ምሽግ
ታላቁ ገደል ለንስር ጠንካራ ምሽጉ ነው፤ ምክንያቱም ሊበላው የሚፈልገው እንስሳ ወደዚያ ስፍራ ሊደርስ አይችልም።

Job 39:29

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

እርሱ የሚያድነውን ይፈልጋል
እዚህ ስፍራ "እርሱ" የሚለው የሚያመለክተው ንስርን ነው።

የሚያድነው
"ገድሎ የሚመገበው እንስሳ"

የእርሱ ዐይኖች ይመለከቷዋል
እዚህ ስፍራ "የእርሱ ዐይኖች" የሚለው የሚያመለክተው ንስሩን ነው። "እርሱ ይመለከታቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ጫጩቶቹ
"ትንንሽ ንስሮች።" ይህ የሚሆነው ንስር አድኖ ከገደለ በኋላ መሆኑን መግለጹ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። "ንስሩ አድኖ ከገደለ በኋላ፣ ጫጩቶቹ ንስሮች"

ደም ይጠጣል
"የገደለውን እንስሳ ደም ይጠጣል"

በድን ባለበት
"የሞቱ ሰዎች ባሉበት።" ይህ ሀረግ የሚያመለክተው ምድር ውስጥ የተቀበሩትን ሳይሆን በሜዳ ላይ የወደቁትን በድኖች ነው።

በዚያ እርሱ ይገኛል
ይህ በድን ለመብላት እንደሚመጣ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "እነርሱን ለመብላት በዚያ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 40

1 እግዚአብሔር ኢዮብን እንዲህ ሲል መናገሩን ቀጠለ፥ **2** "ማንም መተቸት የሚፈልግ ሁሉን ቻዩን አምላክ ማረም አለበት? ከእግዚአብሔር ጋር የሚከራከር እርሱ ምላሹን ይስጥ"። **3** ኢዮብም ለእግዚአብሔር እንዲህ ሲል መለሰ፥ **4** "ተመልከት፥ እኔ ከምንም የማልቆጠር ነኝ፤ እንዴትስ መልስ ልሰጥህ እችላለሁ? እጄን በአፌ ላይ እጭናለሁ። **5** አንድ ጊዜ ተናገርኩ፥ መልስ መስጠትም አልችልም፤ በእርግጥ ሁለተኛ ተናግሬ ይሆናል፥ ከዚህ በኋላ ግን አልቀጥልም"። **6** ከዚያም እግዚአብሔር ከኃይለኛ ዐውሎ ነፋስ ውስጥ ሆኖ ኢዮብን እንዲህ ሲል ተናገረው፥ **7** "እንግዲህ እንደ ወንድ ወገብህን ታጠቅ፥ እጠይቅሃለሁና አንተም ልትመልስልኝ ይገባል። **8** ፍትሐዊ ስላለመሆኔ ትናገራለህ? ራስህን ትክክለኛ አድርገህ ለመቁጠር እኔን ትኮንናለህ? **9** የእግዚአብሔርን የሚያክል ክንድ አለህ? እንደ እርሱስ ድምፅህን ልታንጎደጉድ ትችላለህ? **10** አሁንም ክብርንና ልዕልናን ልበስ፤ ክብርንና ግርማንም ታጠቅ። **11** የቁጣህን ብዛት በዙሪያህ አፍስስ፤ ትዕቢተኛ የሆነውን ሁሉ ተመልከተውና አዋርደው። **12** ትዕቢተኛ የሆነውን ሁሉ ተመልከተውና ዝቅ አድርገው፤ ክፉዎችንም ሰዎች በቆሙበት ስፍራ አድቅቃቸው። **13** አንድ ላይ ዐፈር ውስጥ ቅበራቸው፤ በተሰወረ ስፍራም ፊታቸውን ደብቀው። **14** ያን ጊዜ እኔ ደግሞ የገዛ ክንድህ ሊያድንህ እንደቻለ ዐውቃለሁ። **15** አሁንም አንተን እንደፈጠርኩህ የፈጠርኩትን ጉማሬ ተመልከት፤ እርሱ እንደ በሬ ሣር ይበላል። **16** ተመልከት፥ ኃይሉ በወገቡ፥ ብርታቱም በሆዱ ጡንቻ ውስጥ ነው። **17** ጭራውን እንደ ጥድ ያወዛውዛል፤ የወርቹ ጅማቶችም እርስ በእርሳቸው የተገጣጠሙ ናቸው። **18** አጥንቶቹ እንደ ነሐስ ቱቦ ናቸው፤ እግሮቹም እንደ ብረት ዘንግ ናቸው። **19** እርሱ እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጥረታት ዋነኛው ነው። እርሱን የፈጠረው እግዚአብሔር ብቻ ሊያሸንፈው ይችላል። **20** ኮረብታዎች ምግቡን ያዘጋጁለታልና፤ በመስክ ላይ ያሉት አራዊትም በአቅራቢያው ይጫወታሉ። **21** በረግረጉ ስፍራ ከደንገል ተክሎች ስር ይተኛል። **22** በውሃ ዳር የሚበቅሉ ዛፎች በጥላዎቻቸው ይሸፍኑታል፤ የአኻያውም ዛፍ ሁሉ በዙሪያው ነው። **23** ተመልከት፥ ወንዙ ቢጎርፍም እርሱ አይፈራም፤ የዮርዳኖስ ወንዝ እስከ አፉ ቢሞላም እርሱ ተማምኖ ይኖራል። **24** በወጥመድ ሊይዘው ወይስ አፍንጫውን በወጥመድ ሊበሳው የሚችል አለ?

Job 40:1

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

ሁሉን ቻይ የሆነውን እንዲህ አድርግ ለማለት መድፈር የሚችል አለን?
ያህዌ ኢዮብን እየገሰጸው ነው፡፡ ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል፡፡ "ማንም ቢሆን እኔን ለመንቀፍ ወይም ከእኔ ጋር ለመከራከር መሞከር የለበትም፣ እኔ ሁሉን ቻይ አምላክ ነኝና፡፡" ወይም "አንተ ሰው ሆነህ ሳለ፣ ሁሉን ቻይ አምላክ የሆንኩትን እኔን ለመንቀፍ ትፈልጋለህ፤ ደግሞም እኔን ለማረም መሞከር የለብህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእግዚአብሔር ጋር የሚከራከር፣ እርሱ ምላሽ ይስጥ
ያህዌ ስለ ራሱ እና ስለ ኢዮብ ሌሎች ሁለት ሰዎች እንደሆኑ እና በየትኛውም ስፍራ የሚገኝ ማንኛም ሰው ከእግዚአብሔር ጋር መከራከር እንደሌለበት አድርጎ ይናገራል፡፡ "ከእኔ ጋር ትከራከራለህን፣ እንግዲያውስ መልስልኝ" (ተውላጠ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Job 40:3

እነሆ እኔን ተመልከት
"እኔ መሆኔን ስትናገር አልተሳሳትክም" ወይም "እኔን ተመልከት እኔ መሆኔን ታያለህ"

እኔ ዋጋ የለኝም
"እኔ ጠቃሚ አይደለሁም"

እንዴት መልስ ልሰጥህ እችላለሁ?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው እግዚአብሔርን በመሟገቱ/በመጠየቁ ምህረት ለመለመን ነው፡፡ "እኔ መልስ ልሰጥህ አልችልም፡፡" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 40:6

እንደ ወንድ ወገብህን ታጥቀህ ተዘጋጅ
ቀበቶውን የታጠቀ ወንድ ለብርቱ ስራ የተዘጋጀ ነው፤ ኢዮብ ለእግዚአብሔር መልስ መስጠትን ለመሰለ ከባድ ስራ መዘጋጀት ነበረበት፡፡ ይህ በኢዮብ 38፡3 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ተመልከቱ፡፡ (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 40:8

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

በእርግጥ እኔን ትክክል አይደለህም ትላለህን?
"በእርግጥ" የሚለው ቃል ኢዮብ እርሱን ትክክል አይደለህም በማለቱ መደነቁን እና በእርግጥም ይህን ለማለት መፈለጉን እንዲያረጋግጥ እየጠየቀው መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል፡፡ "እኔን ትክክል አይደለህም በማለትህ ተገርሜያለሁ" ወይም "እኔን ትክክል አይደለህም ለማለት መፈለግህን እርግጠኛ መሆን አለብህ፣ ምክንያቱም እያልክ ያለኸው ያንን ነው፡፡" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ራስህን ትክክለኛ አድርገህ እኔን ትኮንናለህን?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል፡፡ "ራስህን ንጹህ አድርገህ በመቁጠር እኔን መኮነን ትችላለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔርን ክንድ የመሰለ
ክንድ የሚለው በክንድ ውስጥ ለሚገኝ ጥንካሬ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው፡፡ "እንደ እግዚአብሔር ጥንካሬ ብርቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚውን ይመልከቱ)

እንደ እርሱ በድምጽ መብረቅ ታወጣለህ?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል፡፡ "እግዚአብሔር በድምጹ እንደሚያርደው አንተ በእርግጥ በድምጽህ መብረቅ ማብረቅ አትችልም፡፡" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

እንደ እርሱ ድምጽ ያለ
"እርሱ በሚያደርግበት መንገድ እንዳለ ድምጽ" ወይም "እንደ እርሱ ድምጽ ያለ ድምጽ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Job 40:10

ሰው እንደሚለብሰው ልብስ አድርገህ ራስህን በክብር እና በማዕረግ አጎናጽፍ፤ በሞገስ እና ግርማ አዘጋጅ
"ክብር፣" "ማዕረግ፣" "ሞገስ፣" እና "ግርማ" የሚሉት ረቂቅ ስሞች የተነገሩት ሰው እንደሚጎናጸፈው ልብስ ተደርገው ነው። እንደ ቅጽሎች እና ግሶች ሆነው ሊተረጎሙ ይችላሉ። "ራስህን ክቡር አድርግ፤ ሰዎች ያከብሩህ እና ከፍ ከፍ ያደርጉህ ዘንድ አንዳች ታላቅ ነገር አድርግ፤ ደግሞም ሰዎች እንደ ታላቅ ንጉስ እንዲመለከቱህ አድርግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

የበዛውን ቁጣህን አፍስስ
"ቁጣ" የሚለው ረቂቅ ስም ብዙጊዜ የሚገለጸው በአንዳች መያዣ ነገር እንደሚያዝ ተደርጎ ነው፣ በዚህ ሁኔታ ግን አብሮ ሊሄድ የማይችለው በዙሪያ የሚፈስ ብዙ ነገር እንዳለው ተደርጎ። ይህ ሲበሳጭ ለሚወስደው እርምጃ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ለምን እንደሚቆጣ ግልጽ ማድረግ ሊያስፈልግ ይችላል። "ሰዎች ስለሚኮሩ እና ስለሚቀጣቸው በዚህ ምክንያት ይቆጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች እንዲሁም ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

አዋርደው
"የሚኮራበትን ነገር ሁሉ ውሰድበት"

Job 40:12

የእነርሱን ፊቶች
"ፊት" የሚለው የሚወክለው ሰውየውን ነው። "እነርሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ስውር ስፍራ
ሰዎች ሲሞቱ መንፈሳቸው ስለሚሄድበት ስፍራ በዩፊሚዝም/የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት/ የቀረበ አገላለጽ። (ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 40:15

ብሄሞት
ትልቅ ውሃ ውስጥ የሚኖር እንስሳ፣ ምናልባት ጉማሬ ሊሆን ይችላል

እርሱ ይበላል
ብሄሞት ይበላል

እንደ በሬ ሳር ይበላል
ብሄሞትም በሬም ሁለቱም ሳር ይበላሉ። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የወገብ... የሽንጥ/ሆድ ጡንቻዎች
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ የሰውነት ክፍልን ይገልጻሉ

Job 40:17

እንደ ጥድ
ጥድ በጣም ጠንካራ እንጨት ነው፣ እናም የጉማሬው ጭራ እንደ ጥድ በጣም ጠንካራ ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ናስ ቱቦዎች
እዚህ ስፍራ፣ የእንስሳውን ጥንካሬ ለመግለጽ አጥንቶቹ የተነጻጸሩት ከናስ ከተሰራ ቱቦ ጋር ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ብረት መቀርቀሪያዎች
ይህ የመጨረሻው ማነጻጸሪያ የሚገልጸው የዚህን ትልቅ እንስሳ ጥንካሬ ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 40:19

የፍትረት አለቃ/ዋና
"ከፍጥረታት ሁሉ ዋናው" ወይም "ከፍጥረታት በጣም ጠንካራው"

የፍጥረታት አምላክ። እግዚአብሔር ብቻ
ያህዌ ራሱን እንደ ሌላ አካል አድርጎ ይናገራል። "የእኔ ፍጥረቶች። እኔ ብቻ፣ እግዚአብሔር" (ተውላጠ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ኮረብቶች ምግብ ያበቅሉለታል
ኮረብቶች የተገለጹት ምግብ መስጠት እንደሚችሉ ሰዎች ተደርገው ነው። "ለእርሱ በኮረብቶች ምግብ ይበቅላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አስደሳች ተክሎች
በረግረጋማ አካባቢዎች በውሃ ላይ የሚበቅሉ አበባማ ተክሎች

ቄጠማ
በረግረጋማ ወይም አረንቋማ ስፍራ የሚገኝ ረጅም ሳር

Job 40:22

አስደሳች ተክሎች
በረግረጋማ አካባቢዎች በውሃ ላይ የሚበቅሉ አበባማ ተክሎች። ይህ በኢዮብ 40፡19 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

የወንዝ ዳርቻ ዛፍ
የወንዝ ዳርቻ ዛፎች በረግረጋማ ስፍራ የሚበቅሉ ትላልቅ ዛፎች ናቸው። በእናንተ ባህል ውስጥ የማይታወቁ ከሆኑ፤ በውሃ ዳር የሚበቅል ዛፍን ስም መጠቀም ትችላላችሁ።

የወንዝ ዳርቻ
በወንዝ ዳርና ዳር

ዮርዳኖስ ከአፍ እስከ ገደፉ ቢሞላም
"ምንም እንኳን የዮርዳኖስ ወንዝ እስከ አፉ ቢሞላም"

አጥምዶ...በመንጠቆ ሊይዘው የሚችል አለን?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጽ ይችላል። "ማንም በመንጠቆ ወይም በወጥመድ አፍንጫውን ሊይዝ አይችልም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 41

1 ሌዋታንን በዓሳ መንጠቆ ልትይዘው ትችላለህ? ወይስ መንጋጋዎቹን በገመድ ታስራለህ? **2** በአፍንጫው ገመድ ልታስገባ ወይም አገጩን በችካል ልትበሳው ትችላለህ? **3** አብዝቶስ ይለምንሃል? በለሰለሱ ቃላትስ ያናግርሃል? **4** የሁልጊዜ አገልጋይህ ለመሆን እንድትወስደው ከአንተ ጋር ስምምነት ያደርጋል? **5** ከወፍ ጋር እንደምትጫወት ከእርሱ ጋር ትጫወታለህ? ሴት አገልጋዮችህ እንዲጫወቱበት ታስርላቸዋለህ? **6** ዓሳ አጥማጆችስ በእርሱ ላይ ይደራደራሉ? ለነጋዴዎችስ ያከፋፍሉታል? **7** ቆዳውን በአንካሴ ወይም ራሱን በዓሳ መውጊያ ጦር ልትበሳው ትችላለህ? አንድ ጊዜ ብቻ **8** እጅህን በላዩ ላይ አድርግ፥ ያን ጊዜ ግብግቡን አትረሳውም፥ እንዲህ ያለውን ተግባርም አትደግመውም። **9** ተመልከት፥ ማንም ይህንን ለማድረግ ተስፋ ቢያደርግ ሐሰተኛ ነው፤ እርሱን በማየቱ ብቻ በድንጋጤ የማይወድቅ ማነው? **10** ሌዋታንን ለመቀስቀስ የሚደፍር የለም፤ ማንስ በፊቱ ሊቆም ይችላል? **11** እንድመልስለት ማንኛውንም ነገር አስቀድሞ ለእኔ የሰጠኝ ማነው? ከሰማይ በታች ያለው ሁሉ የእኔ ነው። **12** ስለ ሌዋታን እግሮች፥ ስለ ብርታቱና ስለተዋበው ቅርጹ ከመናገር ዝም አልልም። **13** ቆዳውን ማን ሊገፈው ይችላል? ድርብ መከላከያውንስ ማን ሊበሳው ይችላል? **14** አስፈሪ ጥርሶቹ የተገጠገጡበትን የፊቱን ደጆች ማን ሊከፍት ይችላል? **15** ጀርባው ተቀራርበው ከተጣበቁ ንብርብር ጋሻዎች የተሠራ ነው። **16** አንደኛው ከሌላኛው ጋር እጅግ ከመቀራረቡ የተነሣ በመካከላቸው ነፋስ አያስገባም። **17** እርስ በእርስ ተገናኝተዋል፥ ሊነቅሏቸው እስከማይቻልም ድረስ በአንድነት ተጣብቀዋል። **18** ከእንጥሽታው የብርሃን ብልጭታ ይወጣል፤ ዓይኖቹ እንደ ንጋት ጮራ ያበራሉ። **19** የሚነድ ፍም፥ የእሳትም ትንታግ ከአፉ ይወጣል። **20** በእሳት ላይ ተጥዶ በኃይል እንደሚንተከተክ ድስት ከአፍንጫው ጢስ ይወጣል። **21** እስትንፋሱ ከሰሉን እንዲቀጣጠል ያደርገዋል፤ ከአፉም እሳት ይወጣል። **22** ብርታት በአንገቱ ውስጥ አለ፥ ሽብርም በፊት ለፊቱ ይጨፍራል። **23** የሥጋው እጥፋቶች እርስ በእርሳቸው የተገጠገጡ ናቸው፤ በእርሱ ላይ ጸንተዋል፤ ሊያነቃንቋቸውም አይቻልም። **24** ልቡ እንደ ድንጋይ የጠነከረ ነው፤ በእርግጥም እንደ ወፍጮ መጅ ጠንካራ ነው። **25** ቀና በሚልበት ጊዜ አማልክት እንኳ ይፈራሉ፤ ከፍርሃታቸውም የተነሣ ወደኋላቸው ይመለሳሉ። **26** ሰይፍ ቢቆርጠው አንዳች አይሰማውም፤ ጦር፥ ቀስት፥ ወይም የትኛውም የጦር መሣሪያ ቢነጣጠርበት አይሰጋም። **27** ብረትን እንደ አገዳ፥ ናስንም እንደ ነቀዘ እንጨት ይቆጥረዋል። **28** ቀስት እንዲሸሽ አያደርገውም፥ የወንጭፍ ድንጋይም ለእርሱ እንደ ገለባ ነው። **29** ዱላ እንደ አገዳ ተቆጥሯል፤ በሚወረወርበት ጦር ላይም ይስቃል። **30** የሆዱ ስር እንደ ገል ስብርባሪ የሾለ ነው፤ የእህል መውቂያ መሣሪያ ይመስል በጭቃው ላይ ምልክት ትቶ ያልፋል። **31** በድስጥ ውስጥ ያለ ውሃ እንደሚፈላ የጥልቁን ውሃ ያናውጠዋል፤ ባህሩንም እንደ ሽቶ ቢልቃጥ ያደርገዋል። **32** የሄደበት መንገድ ከበስተኋላው እንዲያበራ ያደርጋል፤ ይህንን ያየም ጥልቁን ነጭ ነው ብሎ ያስባል። **33** ያለ ፍርሃት እንዲኖር የተፈጠረ በምድር ላይ እርሱን የሚያክል የለም። **34** ኩሩ የሆነውን ሁሉ ያያል፤ እርሱ በትዕቢት ልጆች ሁሉ ላይ ንጉሥ ነው።"

Job 41:1

አጠቃላ መረጃ፡
እግዚአብሔር መናገሩን ቀጥሏል። ኢዮብን ለመገገዳደር ብዙ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎችን ይጠቀማል

አሳ በሚያዝበት መንጠቆ ሌዋታንን አጥምደህ ልታወጣው ትችላለህ?
እግዚአብሔር ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው ኢዮብ እንደ ሌዋታን ጠንካራ አለመሆኑን ሊያስታውሰው ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጽ ይችላል። "አሳ በሚጠመድበት መንጠቆ ሌዋታንን ማጥመድ እንደማትችል ታውቃለህ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

አጥምደህ ልታወጣው
ከውሃ ውስጥ ልታወጣው

የእርሱ...እርሱ
"የእርሱ" እና "እርሱ" የሚሉት ቃላት ሌዋታንን ያመለክታሉ።

ወይስ በገመድ/ሲባጎ መንጋጋውን ታስራለህ?
"አንተ ትችላለህን?" የሚሉት ቃላት ከቀደመው ጥያቄ በመነሳት ሊታወቁ የሚችሉ ናቸው። እዚህ ስፍራ ሊደገሙ ይችላሉ። እግዚአብሔር ይህንን ጥያቄ ኢዮብ እንደ ሌዋታን ጠንካራ አለመሆኑን ሊያስታውሰው ተጠቅሞበታል። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ወይንስ መንጋጋውን በሲባጎ ልታስር ትችላለህን?" ወይም "ደግሞም መንጋጋውን በሲባጎ ማሰር እንደማትችል ታውቃለህ።" (የተዘለለ/የተተወ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

በአፍንጫው ውስጥ ገመድ ማስገባት... በመንጠቆ ልታጠምደው ትችላለህን?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ኢዮብ እንደ ሌዋታን ሀይለኛ አለመሆኑን ሊያስታውሰው ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "በመንጠቆ እንደማትይዘው...በሌዋታን አፍንጫ ገመድ ማስገባት እንደማትችል ታውቃለህ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ለአንተ ብዙ ልመና ያቀርባልን?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ኢዮብ እንደ ሌዋታን ሀይለኛ አለመሆኑን ሊያስታውሰው ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። " ለአንተ ልመና እንደማያቀርብልህ ታውቃለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ለአንተ ለስላሳ ቃላትን ይናገራል?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ኢዮብ እንደ ሌዋታን ሀይለኛ አለመሆኑን ሊያስታውሰው ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ለአንተ ለስላሳ ቃላትን እንደማይናገር ታውቃለህ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 41:4

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገሰጹን ቀጥሏል። እርሱ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ኢዮብ እንደ ሌዋታን ጠንካራ አለመሆኑን ሊያስታውሰው ነው።

ለዘለዓለም አገልጋዩ እንድታደርገው እርሱ ከአንተ ጋር ቃለኪዳን ይገባል?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ለዘለአለም አገልጋይህ እንድታደርገው ከአንተ ጋር ቃለኪዳን እንደማይገባ ታውቃለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ... የእርሱ
"እርሱ" እና "የእርሱ" የሚሉት ቃላት ሌዋታንን ያመለክታሉ።

ከወፍ ጋር እንደሚጫወት ከእርሱ ጋር ትጫወታለህን?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ከወፍ ጋር እንደምትጫወት ከእርሱ ጋር መጫወት እንደማትችል ታውቃለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለአገልጋይ ልጃገረዶችህ እርሱን ማሰር ትችላለህን?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ለአገልጋይ ልጃገረዶችህ እርሱን ማሰር እንደማትችል ታውቃለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

አሳ አጥማጆች ከእርሱ ጋር መደራደር ይችላሉን?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "አሳ አጥማጆች ከእርሱ ጋር ሊደረደሩ እንደማይችሉ ታውቃለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በነጋዴዎች መሃል ሊነግዱበት እርሱን ይከፋፈላሉን?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "እርሱን ሊነግዱት በማህላቸው እንደማይከፋፈሉት ታውቃለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ይከፋፈሉታል
"አሳ አጥማጅ ቡድኖች ይከፋፈሉታል"

Job 41:7

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገሰጹን ቀጥሏል። እርሱ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ኢዮብ እንደ ሌዋታን ጠንካራ አለመሆኑን ሊያስታውሰው ነው።

ቆዳውን በአንካሴ ወይም ጭንቅላቱን በአሳማጥመጃ ጦር ልትወጋው ትችላለህ?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ቆዳውን በአንተ ማደኛ መሳሪያ ልትበሳው አትችልም፣ አሊያም ጭንቅላቱን በአሳ ማጥመጃ ጦር ልትበሳው አትችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ... የእርሱ
"እርሱ" እና "የእርሱ" የሚሉት ቃላት ሌዋታንን ያመለክታሉ።

አንካሴዎች
ሰዎች ትላልቅ የውሃ ውስጥ ፍጥረታትን ለማደን የሚጠቀሙባቸው ሹል ጫፍ ያላቸው ረጃጅም ጦሮች

እነሆ
"ተመልከት" ወይም "ስማ" ወይም "ቀጥሎ ለምነግርህ ትኩረት ስጥ"

በእይታው ብቻ ማንም ቢሆን ምድር ላይ አይወድቅምን?
ይህ ማጠቃለያ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ወደ እርሱ የሚመለከት ምድር ላይ እስኪወድቅ ድረስ እጅግ በፍርሃት ይዋጣል" (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

እርሱን ማየት
"ወደ እርሱ በመመልከት" ወይም "እርሱን በማየት"

Job 41:10

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በመጠየቅ ኢዮብን መገሰጹን ቀጥሏል። እርሱ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ያህዌ ከሌዋታንም ሆነ ከኢዮብ ይልቅ እጅግ ጠንካራ መሆኑን ሊያስታውሰው ነው።

ማን ሌዋታንን ሊደፍር ይችላል፣ ታዲያ ይልቁን በእኔ ፊት ማን ሊቆም ይችላል?
በያህዌ ፊት ከመቆም ሌዋታንን መንካት ቀላል ይሆናል። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ማንም ሌዋታንን ሌዋታንን ለመንካት እንደማይደፍር ታውቃለህ፣ ይልቁንም ማንም በፊቴ ሊቆም እንደማይደፍር በእርግጠኝነት ማወቅ ይኖርብሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእርሱ እመልስለት ዘንድ አስቀድሞ አንዳች ነገር ለእኔ የሰጠኝ ማን ነው?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ማንም ለእኔ አስቀድሞ አንዳች ነገር እንዳልሰጠኝ ታውቃለህ፣ ስለዚህም እኔ መልሼ ልከፍለው የሚገባኝ ማንም የለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ... የእርሱ
"እርሱ" እና "የእርሱ" የሚሉት ቃላት አንድን ሰው ያመለክታሉ።

... በተመለከተ ዝም አልልም...አሊያም ስለ... አሊያም ስለ
ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊተረጎም ይችላል። "በእርግጥ እኔ ስለ... በእርግጠኝነት እናገራለሁ... እና ስለ...እና ስለ..." (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

የሌዋትንን እግሮች በተመለከተ፣ አሊያም ስለ እርሱ ጥንካሬ፣ አሊያም ስለ አስፈሪ መልኩ
እነዚህ እግዚአብሔር ዝም የማይልባቸው ነገሮች ናቸው

የእርሱ
"የእርሱ" የሚለው ቃል ሌዋታንን ያመለክታል

Job 41:13

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በመጠየቅ ኢዮብን መገሰጹን ቀጥሏል።

ውጫዊ ሽፋኑን ማን ሊያስወልቀው ይችላል?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ማንም ውጫዊ ልብሱን ሊያስወልቀው አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ
"የእርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሌዋታንን ነው።

ድርብ የጦር ልብሱን ማን ሊበሳው ይችላል?
"የጦር ልብስ" የሚለው ጠንካራ ቅርፊች ወይም የጀርባው ቆዳ ለሚለው ዘይቤ ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ማንም ቢሆን በጣም ወፍራም ቆዳውን ሊበሳ አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

አስፈሪ የሆነውን...ማን የአፉን ደጅ ሊከፍት ይችላል?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ማንም አስፈሪ... መንጋጋውን መክፈት አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ጋሻዎች
"ጋሻዎች" የሚለው ቃል ለሌዋታን ጠንካራ ቆዳ ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። ጋሻዎች እና የሌዋታን ቆዳ የሚሉት ሁለቱም ቀስቶችን የሚመክቱ እና ከሌሎችም መሳሪያዎች የሚከላከሉ ናቸው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ተገጣጥመው እርስ በእርስ የተቀራረቡ ናቸው
ይህ ማለት "ጋሻዎቹ" እርስ በእርሳቸው የተቀራረቡ በመሆናቸው በመሃላቸው ምንም ነገር ሊገባ አይችልም።

Job 41:16

አንዱ ወደ ሌላው እጅግ የቀረበ ነው
በአንዱ ረድፍ ሚገኙት ጋሻዎች ከሌላው ጋር እጅግ ቅርብ ነው። (ኢዮብ 41፡15)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የእነርሱ...እነርሱ
"የእነርሱ" እና "እነርሱ" የሚሉት ቃላት በመስመር የተደረደሩ ጋሻዎችን ያመለክታሉ። (ኢዮብ 41:15)

ለየብቻ ሊለያዩ አይችሉም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ማንም ሊገነጣጥላቸው አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ከመደንፋቱ/ከማሸካካቱ
"ሲደነፈፉ/ሲያሸካካ።" በመኝታ ከሚሰማ አጭር ማንኮራፋት ጋር ይመሳሰላል። ሊሰጥ የሚችለው ሌላ ትርጉም "ከማስነጠሱ ጋር" ወይም "ሲያስነጥስ" የሚል ነው።

ዐይኖቹ የንጋት ሽፋሽፍትን ይመስላሉ
ይህ ማለት ዐይኖቹ የማለዳ ሰማይ እንደሚቀላ የቀሉ ናቸው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ
"የእርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሌዋታንን ነው።

Job 41:19

ከአፉ የሚነድ ችቦ ይወጣል፣ የእሳት ብልጭታ ይፈናጠራል
እግዚአብሔር በሌዋታን አስፈሪ መልክ ላይ ትኩረት ለመስጠት ተመሳሳይ ሀሳብን በሁለት የተለያዩ መንገዶች ይገልጻል። ይህንን የተተወውን ቃል በመጨመር ግልጽ ማድረግ ትችላላችሁ። "ከአፉ የሚነድ ችቦ ይወጣል እና የእሳት ብልጭታ ይወጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና የተዘለለ/የተተወ የሚሉትን ይመልከቱ)

የእርሱ
"የእርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሌዋታንን ነው።

አፍንጫዎቹ
የአፍንጫው ሁለቱ ቀዳዳች

እንደሚፈለ ገንቦ የሚጤስ
ጢስ እና የሚፈለ ገንቦ ሁለቱም በጣም ሞቃት ናቸው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከሰል ወደ ፍምነት ይቀጣጠላል
"ከሰል ፍም እንዲሆን"

Job 41:22

የእርሱ...እርሱ
"የእርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሌዋታንን ነው።

ፍርሃት በፊቱ ያሸበሸባል
"ፍርሃት" የሚለው ረቂቅ ስም "ፈራ" በሚል ግስ ሊተረጎም ይችላል። "ሰዎች እርሱ ሲመጣ ሲመለከቱ፣ በጣም ይፈራሉ" (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ሊንቀሳቀሱ አይችሉም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ማንም ሊያንቀሳቅሳቸው አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ልቡ እንደ ድንጋይ ጠንካራ ነው
አለት ወይም ድንጋይ ተለውጦ ለስላሳ አይሆንም። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1)የሌዋታን ደረቱ እና በውስጡ ያሉ አካላት ጠንካራዎች ናቸው ወይም 2)ሌዋታን አንዳች ነገር አይፈራም ወይም 3) ሌዋታን የተገለጸው ያለ አንዳች ርህራሄ እንደሚገድል ሰው ተደርጎ ነው። (ተነጻጻሪ እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

የታችኛው ድርብርብ አለት
"ከአለቶች ሁሉ ይበልጥ ጠንካራ የሆነው።" የታችኛው አለት ትልቅ እና ለእህል ወፍጮነት የሚያገለግል ከሁለቱ የላይኞቹ አለቶች ጠንካራ የሆነው ነው። ሰዎች ሊያገኙ ከሚችሏቸው አለቶች እጅግ ጠንካራዊ ነው።

Job 41:25

እርሱ... እርሱ ራሱ...የእርሱ
"እርሱ፣" "እርሱ ራሱ" እና "የእርሱ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ሌዋታንን ነው።

አማልዕክቱ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ታላላቅ ሰዎች" ወይም 2) "በጣም ጠንካራ ሰዎች"

ብረትን እንደ ገለባ ይቆጥራል
"ከብረት የተሰሩ መሳሪያዎችን ከገለባ እንደተሰሩ ይቆጥራቸዋል።" ገለባ ቆዳውን አልፎ ሊገባ እንደማይችል ያህል፣ የብረት መሳሪያዎች ቆዳውን ሊበሱት አይችሉም/ ብረትን እንደ ገለባ ይቆጥራል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ነሐስን ብል እንደበላው እንጨት ይቆጥራል
ይህንን የተተዉ ቃላትን በመጨመር ግልጽ ማድረግ ይቻላል። "ከነሐስ የተሰሩ መሳሪያዎችን ብል በበላው እንጨት እንደተሰሩ ይቆጥራቸዋል" (የተዘለለ/የተተወ እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 41:28

ለእርሱ የወንጭፍ ድንጋይ ገለባ ይሆንለታል
ገለባ ሌዋታንን ለጎዳው አይችልም፣ እንደዚሁም የወንጭፍ ድንጋይ ልክ እንደ ገለባ ሁሉ የማይጎዳው ይሆናል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ... እርሱ ራሱ...የእርሱ
"እርሱ፣" "እርሱ ራሱ" እና "የእርሱ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ሌዋታንን ነው።

በትርን እንደ ገለባ ይቆጠራል
ከገለባ የተሰራ መምቻ እርሱን ሊጎዳው እንደማይችል ሁሉ ከእንጨት የተሰራም በትር አይጎዳውም። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ዱላን እንደ ገለባ ይቆጥራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በተሰበቀ ጦር ላይ ይስቃል
ጦር የወረወረ ሰው ጦሩ ሌዋታንን እንደሚገድል ተስፋ ያደርጋል፣ ነገር ግን ጸሐፊው የሚገልጸው ሌዋታን ጦሩ እንደማይገድለው እንደሚያውቅ እና በተወረወረው ጦር እንደሚስቅ አድርጎ ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ መውቃያ መሳሪያ በጭቃ ውስጥ ምልክት ጥሎ ያልፋል
የመውቂያ መሳሪያ የሚወቃውን እህል እንደሚያደቅ፣ ሌዋታ ጭራውን እያወዛወዘ ሲራመድ በጭቃ ላይ ምልክት እያደረግ ያልፋል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 41:31

ጥልቁን በማሰሮ እንደሚፈለ ውሃ አረፋ ያደርገዋል
"በውሃ ውስጥ ሲያልፍ፣ ከኋላው በማሰሮ እንደሚፈለ ውሃ አረፋ እየተው ይሄዳል"

እርሱ
"እርሱ" የሚለው ቃል ሌዋታንን ያመለክታል።

ባህሩን በገንቦ እንዳለ ቅባት ያደርገዋል
በገንቦ ውስጥ ያለ ቅባት አንድ ሰው ቢበተብጠው ይደፈርሳል፣ እንደዚሁ ሌዋታን ሲዋኝበት ባህሩ ይደፈርሳል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ሰው ጥልቁ ሸበት እንዳለው አድርጎ ሊያስብ ይችላል
ይህ የሚሆንበት ምክንያት ያንቀሳቀሰው ውሃ አረፋ ስለሚነጣ ነው

Job 41:33

ለእርሱ አቻ የለውም
"የትኛውም ፍጥረት እንደ ሌዋታን አይደለም"

እርሱ ኩራተኛ የሆነውን ነገር ሁሉ ይመለከታል
"እርሱ በጣም፣ በጣም ኩራተኛ ነው"

የእርሱ... እርሱ
"የእርሱ" እና "እርሱ" የሚሉት ቃላት ሌዋታንን ያመለክታሉ።

እርሱ በኩራት ልጆች ላይ ሁሉ ንጉሥ ነው
ሌዋታን የተገለጸው ንጉሥ ሊሆን እና ሊኮራ እንደሚችል ሰው ተደርጎ ነው። "ሌዋታን በምድር ላይ ከማንም ይልቅ ሊኮራ የሚችልበት የበለጠ ምክንያት አለው" (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 42

1 ኢዮብም ለእግዚአብሔር እንዲህ ሲል መለሰ፥ **2** "ሁሉን ለማድረግ እንደምትችል፥ ዓላማህ ሊደናቀፍ እንደማይችል አውቃለሁ። **3** 'ያለዕውቀት ዕቅዴን የሚያጨልም ይህ ማነው?' ብለህ ጠይቀኸኛል። ስለዚህ የማላውቀውን፥ ያልተረዳሁትን፥ ለማወቅም እጅግ አስቸጋሪ የሆነውን ነገር ተናግሬአለሁ። **4** አንተም፥ 'አሁንም፥ አድምጥ፥ እኔ እናገራለሁ፤ አንዳንድ ነገሮችን እጠይቅሃለሁ፥ አንተም ትነግረኛለህ' አልከኝ። **5** ስለአንተ መስማትን በጆሮዬ ሰምቼ ነበር፥ አሁን ግን ዓይኖቼ አዩህ። **6** ስለዚህ ራሴን እንቃለሁ፤ በአመድና በትቢያ ላይ ተቀምጬ ንስሓ እገባለሁ"። **7** እግዚአብሔር ኢዮብን ይህን ቃል ከተናገረው በኋላ ቴማናዊውን ኤልፋዝን እንዲህ አለው፥ "አንተና ሁለቱ ጓደኞችህ አገልጋዬ ኢዮብ እንዳደረገው ስለ እኔ ትክክለኛውን ነገር አለተናገራችሁምና ቁጣዬ በእናንተ ላይ ነዶባችኋል። **8** አሁን እንግዲህ ሰባት ወይፈኖችንና ሰባት አውራ በጎችን ለራሳችሁ ይዛችሁ ወደ አገልጋዬ ኢዮብ ሂዱ፤ ለራሳችሁም የሚቃጠል ምስዋዕት አድርጋችሁ አቅርቡ። እኔም እንደ ስንፍናችሁ እንዳላደርግባችሁ አገልጋዬ ኢዮብ ይጸልይላችኋል፤ እኔም ጸሎቱን እቀበላለሁ። አገልጋዬ ኢዮብ እንዳደረገው ስለ እኔ ትክክለኛውን ነገር አልተናገራችሁምና።" **9** ስለዚህ ቴማናዊው ኤልፋዝ፥ ሹሐዊው በልዳዶስና ናዕማታዊው ሶፋር እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው ሄደው አደረጉ፤ እግዚአብሔርም ኢዮብን ተቀበለው። **10** ኢዮብ ስለ ጓደኞቹ በጸለየ ጊዜ እግዚአብሔር እንደገና አበለጸገው። ቀድሞ ከነበረው በላይ እግዚአብሔር ዕጥፍ አድርጎ ሰጠው። **11** ከዚያም የኢዮብ ወንድሞቹና እህቶቹ ሁሉ፥ ቀድሞ ያውቁት የነበሩትም ሁሉ እርሱ ወደነበረበት መጡ፤ ከእርሱም ጋር ምግብ በሉ። እነርሱም ሐዘኑን ተጋሩት፤ እግዚአብሔር አምጥቶበት ስለነበረው መከራ ሁሉ አጽናኑት። እያንዳንዳቸውም ለኢዮብ ጥሬ ብርና የወርቅ ቀለበት ሰጡት። **12** እግዚአብሔር ከመጀመሪያው ይልቅ የኢዮብን የኋለኛውን ዘመን ባረከለት፤ እርሱም ዐሥራ አራት ሺህ በጎች፥ ስድስት ሺህ ግመሎች፥ አንድ ሺህ ጥማድ በሬዎች፥ አንድ ሺህም ሴት አህዮች ነበሩት። **13** ደግሞም ሰባት ወንዶችና ሦስት ሴቶች ልጆች ነበሩት። **14** የመጀመሪያ ሴት ልጁን ይሚማ፥ ሁለተኛዋን ቃሥያ፥ ሦስተኛዋን አማልቶያስ ቂራስ ብሎ ሰየማቸው። **15** በሀገሩ ሁሉ እንደ ኢዮብ ሴቶች ልጆች የተዋቡ ሴቶች አልተገኙም። አባታቸውም ከወንድሞቻቸው እኩል ርስትን ሰጣቸው። **16** ከዚህ በኋላ ኢዮብ 140 አመት ኖረ፤ እርሱም ወንዶች ልጆችን፥ የወንዶች ልጆቹን ወንዶች ልጆች እስከ አራት ትውልድ ድረስ አየ። **17** ከዚያም ኢዮብ አርጅቶ፥ ዕድሜንም ጠግቦ ሞተ።

Job 42:1

አንተ ሁሉንም ነገሮች መስራት እንደምትችል አውቃለሁ፣ ከስራዎችህ አነዱም ሊገታ አይችልም "እኔ አውቃለሁ" የሚሉትን ቃላት መድገም ልትፈልግ ትችላለህ። "ሁሉንም ነገሮች መስራት እንደምትችል አውቃለሁ። የትኛውም ተግባርህ ሊገታ እንደማይችል አውቃለሁ" (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

የትኛውም ተግባርህ ሊገታ አይችልም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ማንም ከእቅዶችህ አንዱንም ማስቆም አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ማን ነው
ዩኤልቢ እና በርካታ ዘመናዊ ቅጅዎች ኢዮብ ከ መጽሐፈ ኢዮብ 38:2 ላይ እንደጠቀሰ ይስማማሉ። እናንተም ሃሳቡን ግልጽ ለማድረግ በዩዲቢ እንደቀረበው እግዚአብሔር ኢዮብን ይህንን ጥያቄ እንደ ጠየቀው እና ኢዮብ አሁን ይህንን እንደሚያስታውስ መወሰን ትችላላችሁ። "አንተ ለእኔ፣ ‘ይህ ማን ነው' ብለሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 42:4

ነገር ግን አሁን ዐይኖቼ አንተን አይተዋል
ዐይኖች ማየትን ይወክላሉ፣ ማየት ደግሞ መረዳትን ይወከወላል። "ነገር ግን አሁን እኔ በእርግጥ አንተን እረዳለሁ/አውቃለሁ" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይምልከቱ)

ራሴን እንቃለሁ
የኢዮብ እኔነት/ራሱ ለተናገረው ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ / ነው። "የተናገርኳቸውን ነገሮች እንቃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

መናቅ
ጥልቅ የሆነ መጥላት

በአፈር እና በአመድ ላይ ተቀምጬ ንስሃ እገባለሁ
በአፈር እና በአመድ ላይ መቀመጥ ሰውየው ማዘኑን የሚገልጽ ምልክታዊ ድርጊት ነው። (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 42:7

እንዲህም ሆነ
ይህ ሀረግ እዚህ ስፍራ የዋለው ጠቃሚ የሆነ ትዕይንት ወደ ታሪኩ ውስጥ መግባቱን ለማመልከት ነው። በእናንተ ቋንቋ ይህን መግልጽ የምትችሉበት መንገድ ካለ ይህን እዚህ ላይ መጠቀም ትችላላችሁ።

ቴማናዊው ኤልፋዝ
ይህ የወንድ ስም በኢዮብ 2፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ቁጣዬ በእናንተ ላይ ነድዷል
እሳት ቁጣን ለመግለጽ የዋለ ዘይቤ ነው። እሳት መለኮስ ለመቆጣት ዘይቤ ነው። "እኔ በእናንተ ላይ እጅግ ተቆጥቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይምልከቱ)

ሰባት ኮርማዎች
"7 ኮርማዎች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

የሰራችሁትን አሳፋሪ ጥፋት እምር ዘንድ
"አሳፋሪ ጥፋት" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ምንም እንኳን ያደረጋችሁት ሞኝነት ቢሆንም፣ የሚገባችሁን ቅጣት አልቀጣችሁም" (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ሹሐዊው በልዳዶስ
ይህ የወንድ ስም በኢዮብ 2፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ናዕማታዊው ሶፋር
ይህ የወንድ ስም በኢዮብ 2፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ያህዌ ኢዮብን ተቀበለው
ሰውየው ለጸለየው ጸሎት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "እግዚአብሔር ኢዮብ ለሶስቱ ወዳጆቹ የጸለየውን ጸሎት ተቀበለ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Job 42:10

ያህዌ እድል ፈንታውን አደሰለት
"ያህዌ ሀብቱን መለሰለት" ወይም "ያህዌ ሀብቱን አደሰለት"

አስቀድመው ያውቁት የነበሩ ሁሉ
"አስቀድሞ ያውቃቸው የነበሩ ሰዎች"

Job 42:12

ከመጀመሪያው ይልቅ
"እርሱ ባረከው" እና "የኢዮብ ህይወት" የሚሉት ቃላት ከቀደመው ሀረግ የሚታወቁ ናቸው። እዚህ ስፍራ ሊደገሙ ይችላሉ። "የመጀመሪያውን የኢዮብ የህይወት ምዕራፍ ከባረከው ይልቅ" (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

አስራ አራት ሺህ በጎች
14,000 በጎች (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ስድስት ሺህ ግመሎች
6,000 ግመሎች (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ሺህ ጥማድ በሬዎች
1,000 ጥማድ በሬዎች (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባት ወንዶች ልጆች እና ሶስት ሴቶች ልጆች
7ወንዶች እና 3 ሴቶች (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ይማሚ... ቃሥያ... አማልቶያስ ቂራስ
የሴቶች ስሞች (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 42:15

እንደ ኢዮብ ሴቶች ልጆች ያሉ ውብ ሴቶች አልነበሩም
"የኢዮብ ሴቶች ልጆች ከሌሎች ሴቶች ሁሉ የተዋቡ ነበሩ"

140 አመታተት ኖረ
"140 አመታት ኖረ" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

እድሜ ጠገበ ደግሞም አርጅቶ
"እድሜ ጠግቦ" የሚሉት ቃላት "አረጀ" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው። ሁለቱ ሀረጎች የጋራ ፈሊጥ አላቸው። "በጣም ያረጀ ሰው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Psalms

Psalms

Chapter 1

1 በክፉዎች ምክር የማይሄድ በኃጢአተኞች መንገድ የማይቆም በፌዘኞች ወንበር የማይቀመጥ ምስጉን ነው። **2** ነገር ግን ደስ የሚሰኘው በያህዌ ሕግ ነው ሕጉንም ቀንና ሌሊት ያሰላስላል። **3** እርሱም ፍሬዋን በየወቅቱ እንደምትሰጥ፣ ቅጠሏም እንደማይጠወልግ፣ በወራጅ ውሆች እንድ ተተከለች ዛፍ ይሆናል፤ የሚሠራውም ሁሉ ይከናወንለታል። **4** ኃጢአተኞች ግን እንዲህ አይደሉም ነገር ግን ነፋስ ጠራርጎ እንደሚወስደው ገለባ ናቸው። **5** ስለዚህ ክፉዎች በፍርድ ኃጢአተኞችም በጻድቃን ጉባኤ አይቆሙም። **6** ያህዌ የጻድቃንን አካሄድ ይጠብቃልና የክፉዎች መንገድ ግን ትጠፋለች።

Psalms 1:1

አጠቃላይ ሃሳብ፡
በዕብራይስጥ ቅኔ ትይዩነት የተለመደ ነው። (ቅኔ እና ትይዩነትን ይመልከቱ)

በክፉዎች ምክር ያልሄደ
የ“ክፉዎች ምክር” የቀረበው እንደ መንገድ ነው። አማራጭ ትርጉም፤ “በክፉዎች ምክር ያልሄደ” ወይም “የክፉዎችን ምክር ያልተገበረ” (ዘይቤን ይመልከቱ)

በኃጢአተኞች መንገድ የልቆመ
እዚህ ጋር “መንገድ” የሚለው ቃል የሚወክለው የሰዎችን የአኗኗር ዘይቤ ነው። “መቆም” የሚለው ቃል ደግሞ “መራመድ” ከሚለው ቃል ጋር ትይዩ ነው። አማራጭ ትርጉም፤ “የኃጢአተኞችን ባህሪ ማስመሰል”። (ዘይቤን ይመልከቱ)

ወይም በዋዘኞች መንገድ ያልተቀመጠ
በእግዚአብሔር ላይ ከሚያፌዙ (ዋዘኞች) ጋር መቀመጥ የሚያመለክተው ከዋዘኞች ጋር ማበርን ነው። አማራጭ ትርጉም፤ “ከዋዘኞች ጋር ማበር” ወይም “ከሌሎች ፊዘኞች ጋር እግዚአብሔር ላይ ማፌዝ”። (ድጋሚ መሰየም (Metonymy)ን ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለዋል
“መደሰት” የሚለው ቃል ከረቂቅ ስም የወጣ ግስ ነው። አንድ ግለሰብ በሕግ ሊደሰት ይችላል ማለትም ሕጉ መልካም ስለሆነ እና ስለሚታዘዘው ደስተኛ ይሆናል። አማራጭ ትርጉም፤ “የእውነት የሚያስደስተው የእግዚአብሔር ሕግ ነው” ወይም “የእውነት የሚያስደስተው የእግዚአብሔርን ሕግ አየታዘዘ እንደሆነ ማወቁ ነው” (ረቂቅ ስምን ይመልከቱ)

Psalms 1:3

አጠቃላይ ሃሳብ
ይህ ክፍል አንድ ጻድቅ ሰው ምን እንደሚመስል አንድ በአበበ ዛፍ ምስል ያብራራል።

እርሱም ... ፍሬዋን በየጊዜው እንደምትሰጥ ዛፍ ነው
በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ አንድ ጊዜ ሰዎች እንደ ዛፍ ይመሰላሉ። በእግዚአብሔር ሕግ ደስ የሚሰኙ ሰዎች እግዚአብሔር እንዲሰሩ የሚፈልገውን ሁሉ በውሃ ዳር የተተከለ ዛፍ መልካም ፍሬን እንደሚያፈራ መስራት ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፤ “ዛፍ በየወቅቱ እንደሚያራ የበለጸገ ይሆናል” (አነጻጻሪ ዘይቤን ይመልከቱ)

በውሃ ዳር እንደተተከለ
ከውሃ ዳር የተተከለ ዛፍ ጤነኛ ሆኖ እንዲቆይ የሚያደርገውን የውሃ መጠን ያገኛል።

ፍሬውን በየጊዜው እንደሚሰጥ
ጤነኛ ዛፎች መልካም ፍሬን በወቅቱ ያፈራሉ።

ቅጠልዋም እንደማይረግፍ
በቂ ውሃ የሚያገኝ ዛፍ ቅጠሎቹ ደርቀው አይሞቱም።

የሚሰራው ሁሉ ይከናወንለታል
“በሚሰራው ሁሉ ስኬታማ ይሆናል”

Psalms 1:4

ክፉዎች እንዲህ አይደሉም
እንዴት እንዳልሆኑ በግልጽ መጥቀስ ይቻላል። “ክፉዎች እንዲህ አይበለጥጉም” ወይም “ክፍዎች እይበለጽጉም” (ድብቅ ሃሳብ ወይም ግምታዊ እውቀትን ይመልከቱ)

ነገር ግን እንደ ትብያ ናቸው
እንደ ትብያ የሆኑበትን መንገድ በግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፤ “እንደ ትብያ ጥቅም የለሾች ናቸው” (አነጻጻሪ ዘይቤን ይመልከቱ)

በፍርድ ፊት አይቆሙም
ያሉት አማራጭ ፍችዎች፡ 1) በፍርድ አለመቆም በእግዚአብሔር መፈረድን እና ከመገኘቱ መውጣትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፤ “እግዚአብሔር በሚፈርድባቸው ጊዜ በፊቱ አይቆዩም`` ወይም ጥፋተኛ እንደሆኑ እግዚአብሔር እንደወሰነባቸው ከመገኘቱ ዞር ማለት አለባቸው ወይም 2) በፍርድ ፊት አለመቆም በፍርዱ የሚፈረድበት መሆንን የሚያመለክት አባባል ነው. አማራጭ ትርጉም በፍርድ ይፈረድባቸዋል ወይም እግዚአብሔር በሚፈርድበት ጊዜ ይፈረድባቸዋል (ምሳሌያዊ አባባን ይመልከቱ)

በፍርድ
ፍርድ የሚለው ስም እንደ ግስም ሊሆን ይችላል። ይህ የሚያመለክተው የመጨረሻውን ፍርድ እግዚአብሔር በሁሉም ላይ የሚፈርድበትን ነው። አማራጭ ትርጉም፡ እግዚአብሔር በሁሉም በሚፈርድበት ጊዜ

ኃጣንም በፃድቃን ማህበር
‘መቆም’ የሚለውን ግስ ተርጓሚው ሊጨምር ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡ “ኃጣን በጻድቃን ማህበር አይቆሙም” ወይም “እግዚአብሔር ኃጣን ከጻድቃን ጋር እንዲቆሙ አይፈቅድም”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ኃጥአንም በፃድቃን ማህበር
ተርጓሚዎች አይዎሙም የሚለውን ግስ ሊጨምሩበት ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም እግዚአብሔርም ኃጥአንን ከፃድቃን ጋር አብሮ አይቀበልም (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

Psalms 1:6

እግዚአብሔር የፃድቃንን መንገድ ያውቃልና፤ የኃጥአን መንገድ ግን ትጠፋለች
እነዚህ ሁለት ስንኞች የሚያወዳድሩት በፃድቁ እና በኃጥአኑ ላይ የሚደርሰውን ነው። (ትይዩነትን ይመልከቱ)

የፃድቁ መንገድ
የሰዎች ሕይወት እንደ ምንሄድበት መንገድ ይገለጻል። አማራጭ ትርጉም፡ የፃድቁ ሕይወት (ዘይቤን ይመልከቱ)

የኃጥአን መንገድ ግን ትጠፋለች
የሰዎች ሕይወት እንደ ምንሄድበት መንገድ ይገለጻል። አማራጭ ፍችዎች 1)የሚጠፋው መንገድ የሚያመለክተው ከአኗኗሩ የተነሣ የፃድቁን መጥፋት ነው። አማራጭ ትርጉም፡ ‹‹ኃጥአን ከአኗኗራቸው የተነሣ ይጠፋሉ›› ወይም 2) የመንገድ መጥፋት መኖር ማቆምን የሚያሳይ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትጉም፡ ‹‹ኃጥአን የሚኖሩት አኗኗር መኖር መቀጠል አየችሉም›› (ዘይቤን እና ድጋሚ መሰየምን ይመልቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 አሕዛብ ለምን ያሤራሉ? ሕዝቦችስ ለምን በከንቱ ያድማሉ? **2** የምድር ነገሥታት በአንድነት ተነሡ ገዦችም በአንድነት አሤሩ እንዲህ በማለትም በያህዌና በመሲሑ ላይ አሤሩ **3** «እግር ብረታቸውን ከእግራችን እንቁረጥ፣ ሰንሰሰታቸውንም በጥሰን እንጣል።» **4** በሰማያት የሚቀመጥ እርሱ ያፌዝባቸዋል ጌታም ይሳለቅባቸዋል። **5** ከዚያም በቁጣው ያናግራቸዋል እንዲህ በማለትም በመዐቱ ያስፈራቸዋል **6** «እኔ ራሴ በጽዮን፣ በተቀደሰውም ተራራዬ ንጉሤን ሾምሁ።» **7** የያህዌን ዐዋጅ ዐውጃለሁ። እርሱም እንዲህ አለኝ፣ «አንተ ልጄ ነህ! በዚህ ቀን አባትህ ሆኛለሁ። **8** ለምነኝ፤ አሕዛብን ለርስትህ የምድር ነገሥታትንም ለግዛትህ እሰጥሃለሁ። **9** በብረት በትር ትቀጠቅጣቸዋለህ ሸክላ ሠሪው እንዳበጀው ዕቃ ታደቃቸዋለህ።» **10** ስለዚህ አሁን እናንት ነገሥታት ተጠንቀቁ እናንት የምድር ገዦች አስተውሉ። **11** ያህዌን በፍርሃት አምልኩት በመንቀጥቀጥ ተገዙለት። **12** እንዳይቆጣ በመንገድም እንዳትጠፉ ልጁን ሳሙት። ቁጣው ፈጥኖ ይነዳልና። እርሱን መጠጊያ የሚያደርጉ ሁሉ የተባረኩ ናቸው።

Psalms 2:1

አጠቃላይ ሃሳብ፡
ትይዩነት በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው። (ቅኔ እና ትይዩነትን ይመልከቱ)

አሕዛብ ለምን አጉረመረሙ፣ ሕዝቦችስ ለምን ከንቱ ሴራ ያሴራሉ?
እነዚህ ጥያቄዎች የተጠየቁት ሕዝቡ ምን ያህል የተሳሳተ እና የሞኝ ነገሮች እንደሚያደርጉ ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም፡ ‹‹አሕዛብ ግራ ተጋብተዋል ሕዝቦችም ከንቱ ሴራ ያሴራሉ›› (መልስ አዘል ጥያቄዎችን ይልከቱ)

አሕዛብ ለምን ያጉረመርማ
ይህ የሚያመለክተው ምንአልባት አሕዛብ የንዴት ጩኸት እያሰሙ እንደነበር ነው።

አሕዛብ
ይህ የሚወክለው መሪዎቹን ወይም ሕዝቦቹን ነው። (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

ከንቱ ሴራ
ምን አልባት በእግዚአብሔር እና በሕዝቡ ላይ የተሴረ ሴራ ነው።

የምድር ነገሥታት ተነሱ፤ አለቆችም ... እንዲህ ሲሉ ተማከሩ
እነኚህ ሁለት ስንኞች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። (ትይዩነትን ይመልከቱ)

ተነሱ ... ተማከሩ
እነዚህ ቃላት አንድ ዓይነት ትርጉም አላቸው። የሚያመለክቱም፤ መሪዎች በአንድ ላይ እግዚአብሔርን እና መሲሁን ለመዋጋት እንደ ተነሱ። ይህ በግልጽ ሊፃፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፤ ‹‹ለመዋጋት መሰባሰብ ... ለማመጽ በጋራ ማቀድ›› (ድብቅ ሃሳብ ወይም ግምታዊ እውቀትን ይመልከቱ)

መሳርያቸውን እንበጥስ... ገመዳቸውንም እንጣል
ሌሎች ሕዝቦች ስለ የያህዌን እና የመሲሁን በእነርሱ ላይ መንገስ እንደ መሳርያ እና ሰንሰለት ይገልጹታል። አማራጭ ትርጉም፡ ‹‹ከእነርሱ ቁጥጥር ራሳችንን ነፃ ማውጣት አለብን፤ በእኛ ላይ እንዲሰለጥኑ ልንፈቅድላቸው አይገባም›› (ዘይቤን ይመልከቱ)

Psalms 2:4

እርሱ... ጌታ
እነዚህ ቃላት ያህዌን ያመለክታሉ። ያህዌ ብዙውን ጊዜ ‹‹ጌታ›› ተብሎ ይገለጻል። ነገር ግን ያህዌ እኛ ጌታ የተለያዩ ቃላ ናቸው።

በሰማይ የሚኖር
በዚህ ስፍራ መኖር የሚያመለክተው መግዛትን ነው። የሚኖበት በግልጽ ሊጠቀስ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፤ ‹‹በሰማይ ይገዛል›› ወይም ‹‹በሰማይ በዙፋኑ ይኖራል›› (ድብቅ ሃሳብ ወይም ግምታዊ እውቀትን ይመልከቱ)

ጌታም ይሳለቅባቸዋል
‹‹እንደነዚህ ባሉት ጌታ ይሳለቅባቸዋል።›› ለምን እንደሚሳለቅባቸው በግልጽ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡ ‹‹ጌታ ከሞኝ አቅዳቸው የተነሣ ይሳለቅባቸዋል። (ድብቅ ሃሳብ ወይም ግምታዊ እውቀትን ይመልከቱ)

በመአቱ ያውካቸዋል
‹‹መአት›› ረቂቅ ስም ነው ‹‹በቁጣ›› ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፤ ‹‹ይቆጣና ያውካቸዋል›› (ረቂቅ ስምን ይመልከቱ)

መታወክ
ታላቅ ፍርሃት

Psalms 2:6

እኔ ግን
የህዌ የሚያተኩረው ሌላ ሳይሆን እርሱ ራሱ ንጉሡን አንደሚሾም ነው።

ንጉሤን ሾምሁ
‹‹ንጉሤ እንዲነግስ አደረግሁ››

ትእዛዙን እናገራለሁ
ይህን የሚናገረው ንጉሡ ነው። ይህ በግልጽ ቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡ ‹‹ንጉሡም እንዲህ አለ፣ ‹‹የያህዌን ትእዛዝ እናገራለሁ›› (ድብቅ ሃሳብ ወይም ግምታዊ እውቀትን ይመልከቱ)

እንዲህ አለኝ
‹‹ያህዌ እንዲህ አለኝ››

አንተ ልጄ ነህ፤ ዛሬ እኔ ወለድሁህ
በዚያን ዘመን እና የዓለም ክፍል ከብዙ ሰዎች መካከል ሰዎች ወራሽ የሚሆናቸውን በሕግ በጉዲፈቻነት ለመውሰድ ይወስኑ ነበር። እዚህ ጋር ያህዌ አንድ ሰው በጉዲፈቻ ይወስድ እኛ በእስራኤል ላይ ንጉሥ ያደርገዋል። አማራጭ ትርጉም፡ ‹‹ልጄ አደረግሁህ። ዛሬ አባት ሆኜሃለሁ›› ወይም ‹‹አሁን አንተ ልጄ ነህ አኔም አባትህ››

Psalms 2:8

አያያዥ ዓረፍተ-ነገር፡
ያህዌ ለአዲሱ የእስራኤል ንጉሥ መናገሩን ይቀጥላ።

ሕዝቡን ለርስትህ፣ የምድርንም ዳርቻ ለግዛትህ
እነዚህ ሁለት ስንኞች አንድ አይነት ሃሳብን ያመለክታሉ። (ትይዩነትን ይመልከቱ)

የምድርም ዳርቻ
‹‹እሩቅ የሚገኙ ቦታዎች››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በብረት በትር ትሰባብራቸዋለህ፤ እንደ ሸክላ ሰሪ ዕቃዎች ትቀጠቅጣቸዋለህ
እነዚህ ሁለት ስንኞች አንድ አይነት ሃሳብን ያመለክታሉ። (ትይዩነትን ይመልቱ)

በብረት በትር ትሰባብራቸዋለህ
ሕዝቡን ማሸነፍ እንደ መሰበበር ተገልጧል የንጉሡም ኃይል እንደ ብረት ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም፤ ‹‹በኃይልህ ሙሉ ለሙሉ ታሸንፋቸዋለህ።›› (ዘይቤን ይመልከቱ)

ትቀጠቅጣቸዋለህ
ሕዝቦችን መሸነፍ እንደ ሸክላ ዕቃ መሰባበር ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም: ‹‹ሙሉ ለሙሉ እንደ ሸክላ ዕቃ ታጠፋቸዋለህ›› (ዘይቤን እና አነጻጻሪ ዘይቤን ይመልክቱ)

እንደ ሸክላ ሰሪ ዕቃዎች
የሸክላ ሰሪ ዕቃዎች በቀላሉ ተሰባሪ ዕቃዎች ናቸው። አማራጭ ትርጉም: ‹‹ሸክላ›› ወይም ‹‹የሸክላ ዕቃ›› (የማይታወቁን መተርጎምን ይመልክቱ)

Psalms 2:10

ስለዚህ እናንተ ነገሥታት ልብ በሉ፤ እናነት የምንር ገዥዎችም፤ ተጠንቀቁ።
እነዚህ ሁለት ስንኞች አንድ አይነት ትርጉም አላቸው። አማራጭ ትርጉም: ‹‹ስለዚህ እናንተ ነገሥታት እና የዓለም መሪዎች ልብ በሉ እና ታረሙ›› (ትይዩነትን ይመልከቱ)

ልብ በሉ
በቀጥተኛ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም: ‹‹ይህን ማስጠንቀቂያ አድምጡ›› ወይም ‹‹ጥበበኞች ሁኑ›› (ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪን ይመልከቱ)

ተጠንቀቁ
በቀጥተኛ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም: ‹‹ይህን ማስጠንቀቅያ አድምጡ›› ወይም ‹‹ጥበበኞች ሁኑ›› (ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪን ይመልከቱ)

Psalms 2:12

ልጁን ሳሙት
ሰዎች ታማኝነታቸውን ለመግለጽ ንጉሡን ይስሙታል ምን አልባትም እግሩን። አማራጭ ትርጉም: ‹‹የእውነት መገዛታችሁን ለልጁ አሳዩት›› ወይም ‹‹በልጁ ፊት ዝቅ ብላችሁ ስገዱ›› (አመልካች ድርጊትን ይመልከቱ)

በመንገዱ እንዳትጠፉ
አንድ ሰው ከመንገዱ ዞር ማለት ሳይችል እዚያው እና ወድያው መሞትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም ‹‹ወድያው ትሞታላችሁ››

ቁጣው ፈጥኖ ይነዳል እና
የንጉሡ ቁጣ እንደ እሳት ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም: ‹‹ድንገት በተናደደ ጊዜ›› (ዘይቤን ይመልከቱ)

እርሱን መጠጊያ የሚያደርጉ
ክለላን ከንጉሡን መፈለግ መጠጊያ እንደመፈለግ ይገለጻል። አማራጭ ትርጉም: ‹‹ንጉሡ እንዲጠብቃቸው የሚጠይቁ›› (ዘይቤን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 ያህዌ ሆይ፣ ጠላቶቼ ምንኛ በዙ! በእኔ ላይ የተነሡ ብዙዎች ናቸው። **2** ብዙ ሰዎች፣ «እግዚአብሔር አያድነውም» እያሉ ስለ እኔ ይናገራሉ። **3** አንተ ግን ያህዌ ሆይ፣ ዙሪያዬን እንደ ጋሻ ትከልለኛለህ፣ ክብሬንና ራሴንም ከፍ የምታደርግ አንተ ነህ። **4** ድምፄን ወደ ያህዌ አነሣለሁ እርሱም ከተቀደሰው ተራራው ይመልስልኛል። ሴላ **5** በሰላም እተኛለሁ፤ እንቀላፋለሁ ያህዌ ስለ ጠበቀኝ ከእንቅልፌ ተነሣሁ። **6** በየአቅጣጫው ከተነሡብኝ ሰዎች ብዛት አልፈራም። **7** ያህዌ ሆይ ተነሥ፤ አምላኬ ሆይ አድነኝ! አንተ የጠላቶቼን መንጋጋ መታህ የክፉዎችን ጥርስ ሰበርህ። **8** መዳን ከያህዌ ነው በረከትህ በሕዝብህ ላይ ይሁን።

Psalms 3:1

አጠቃላይ ሃሳብ፡
x

Psalms 3:3

አንተ ግን ያህዌ ጋሻዬ ነህ
ጋሻ ተዋጊን ይከላከላል። ዳዊት እግዚአብሔርን እንደ ገሻው ይገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም፡ አንተ ግን ያህዌ እንደ ጋሻ ትከልከኛለህ›› (ዘይቤን ይመልከቱ)

ክብሬ
እግዚአብሔርን ክብሬ ብሎ በመጥራት ዳዊት ክብር የሚሰጠው እግዚአብሔር እንደሆነ ይናገራል። ዳዊት ስለጠላቶቹ ስለተናገረ እና እግዚአብሔርን ጋሻዬ ስላለ፣ ክብሬ ሲል ደግሞ ምን አልባት በጠላቶቹ ላይ እንዲያሸንፍ በማድረግ ክብር እንደሚሰጠው ለማመልከት ነው። አማራጭ ትርጉም፡ “ክብር የምትሰጠኝ አንተ ነህ” ወይም “ድልን የምትሰጠኝ አንተ ነህ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

ራሴን ከፍ ከፍ የምታደርገው አንተ ነህ
“ራሴን ከፍ ክፍ የምታደርገው አንተ ነህ” አንድን ሰው ማበረታታት ራስን ከፍ እንደ ማድረግ ይገለጣል። አማራጭ ትርጉም “የምታበረታታኝ” (ዘይቤን ይመልከቱ)

ድምፄን ከፍ አደርጋለሁ
ለመጮህ ድምፅን መጠቀም ድምፅን ከፍ እንደማድረግ ይገለፃል። አማራጭ ጥርጉም፡ “እጮሃለሁ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

ሴላ
ይህ ምንአልባት ሰዎች እንዴት መዘመር ወይም የሙዚቃ መሳርያ እንዴት መጫወት እንደሚገባቸው የሚያሳይ የሙዚቃ ቃል ነው። አንድ አንድ ትርጉሞች የዕብራይስጥ ቃሉን ሲጽፉት ሌሎች ደግሞ በትርጉም ውስጥ እንደውም አያካትቱትም። በመዝ 3፡1 ይህን እንዴት እደተረጎሙት ይመልከቱ። (ቃላት መዋስን ይመልከቱ)

Psalms 3:5

የሚከቡኝን
“ከየአቅጣጫው የከበበኝን”

Psalms 3:7

ተነሥ
ዳዊት አንድን ነገር ለማድረግ መጀመር መነሳት ብሎ ይገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም፡ “እርምጃ ውሰድ” ወይም “አንድ ነገር አድርግ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

የጠላቶቼን መንጋጋ መትተሃልና የክፉዎችነም ጥርስ ሰብረሃል
እነዚህ ሁለት አገላለጾች ተመሳሳይ ናቸው። “ጠላቶቼ” እና “ክፉዎች” የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ሰዎችን ይወክላሉ። (ትይዩነትን ይመልከቱ)

የጠላቶቼን መንጋጋ መትተሃልና
ይህ ሰዎችን የመሳደብ መንገድ ነው። ዳዊት እየተናገረ ያለው ያህዌ እራሱ መጥቶ ጠላቶቹን እንደሚመታ ነው አማራጭ ትርጉም፡ “መንጋጋችን እንደሚመታ ጠላቶቼን ታዋርዳቸዋለህ” (ምስላዊ እንቅስቃሴን እና ዘይቤን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 የጽድቄ አምላክ ሆይ፣ በጠራሁህ ጊዜ መልስልኝ ከጭንቀቴም አሳርፈኝ ማረኝ ጸሎቴንም ስማ። **2** እናንተ ሰዎች እስከ መቼ ክብሬን ታወርዳላችሁ? እስከ መቼ ከንቱ ነገር ትወዳላችሁ፤ ሐሰትንስ ትፈልጋላችሁ? ሴላ **3** ያህዌ ጻድቁን ለራሱ እንደ ለየ ዕወቁ። በጠራሁት ጊዜ ያህዌ ይሰማኛል። **4** የቱንም ያህል ብትፈሩ ኃጢአት አትሥሩ! በመኝታችሁ እያላችሁ በልባችሁ አሰላስሉ፤ ጸጥም በሉ። ሴላ **5** ለያህዌ የጽድቅ መሥዋዕት አቅርቡ እምነታችሁንም እርሱ ላይ አድርጉ። **6** ብዙዎች፣ «መልካሙን ማን ያሳየናል?» ይላሉ። ያህዌ ሆይ፣ የፊትህን ብርሃን እኛ ላይ አብራ። **7** ብዙ እህልና ወይን ካገኙ ሰዎች ይበልጥ አንተ ልቤን በታላቅ ሐሤት ሞልተኸዋል። **8** በሰላም የምታኖረኝ አንተ ብቻ ስለሆንህ በሰላም እተኛለሁ አንቀላፋለሁም።

Psalms 4:1

አጠቃላይ መረጃ:
ትይዩነት በዕብራይስጥ የቅኔ ጽሑፍ የተለመደ ነው። (ቅኔና ትይዩነትን ይመልከቱ)

ለመዘምራን አለቃ
“ይህ ለመዘምራን አለቃ በአምልኮ ለመምራት ነው”

በበገናዎች የሚዜም
“ከመዝሙሮች ጋር ሰዎች በመሳርያዎችን/በገናዎችን ሊጫወቱ ይገባል”

የዳዊት መዝሙር
አማራጭ ፍችዎች: 1) ዳዊት ዝማሬውን ጽፎታል ወይም 2) ዝማሬው ስለዳዊት ነው ወይም 3) ዝማሬው የተዘመረው በዳዊት የአዘማመር ስልት ነው

በጠራሁህ ጊዜ መልስልኝ
“ስጠራህ መልስልኝ” ወይም “ስጠራህ እርዳኝ”

የጽድቄ አምላክ
“ጻድቅ እንደሆንሁ የሚያሳይ አምላክ”

በጭንቀቴ አሰፋልኝ
በችግር ውስጥ መሆን በጠባብ ስፍራ እንደመሆን ይገለጻል። አማራጭ ትርጉም: “በችግር ጊዜ አድነኝ” (ዘይቤን ይመልከቱ)

Psalms 4:2

አጠቃላይ መረጃ:
ይህን የመዝሙር ክፍል ዳዊት ለጠላቶቹ እንደሚያወራ ይዘምረዋል።

እናንተ ሰዎች ሆይ እስከ መቼ ድረስ ክብሪን ዝቅ ታደርጋላችሁ?
ዳዊት ይህን ጥያቄ ጠላቶቹን ለመገሰጽ ይጠቀምበታል። አማራጭ ትርጉም: “እናንተ ሰዎች ባለማቋረጥ ክብሪን ወደ ውርደት ትለውጣላችሁ!” (መልስ አዘል ጥያቄዎችን ይልከቱ)

ክብሬን ወደ ውርደት
በማክበር ፈንታ እርሱን ማዋረድ ክብርን ወደ ውርደት እንደመቀየር ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም: “በማክበር ፈንታ ታዋርዱኛላችሁ” ወይም “ክብርን በመስጠት ፈንታ ውርደት ትሰጡኛላችሁ”

እስከ መቼ ድረስ ከንቱ ነገርን ትወዳላችሁ? ሐሰትንስ ትሻላችሁ?
ዳዊት ይህን ጥያቄ ጠላቶቹን ለመገሰጽ ይጠቀምበታል። አማራጭ ትርጉም: “ከንቱ ነገር በመውደድ ትቀጥላላችሁ ውሸትንም ትሻላችሁ” (መልስ አዘል ጥያቄዎችን ይልከቱ)

ከንቱ ነገርን ትወዳላችሁ? ሐሰትነስ ትሻላችሁ?
እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች ተመሳሳይ ትርጉም አዝለዋል። ሐሰት ከንቱ ነገር ነው። አማራጭ ትርጉም: “ከንቱ ሐሰትን ትወዳላችሁ” (ትይዩነትን ይመልከቱ)

ያህዌ ለራሱ ጻድቁን እንደለየ ዕወቁ
“ያህዌ እግዚአብሔራዊ ሰዎችን ለራሱ ይመርጣል”

Psalms 4:4

በፍርሃት መርበትበት
የ”ፍርሃት” እና የ”መርበትበት” ግንኙነት እና ሰዎች ማንን መፍራት እንዳለባቸው በግልጽ መጠቀስ ይችላል።አማራጭ ትርጉም: “ያህዌን እስክትርበተበቱ ድረስ ፍሩት” ወይም “በያህዌ በመደነቅ ቁሙ” (ድብቅ ሃሳብ ወይም ግምታዊ እውቀትን ይመልከቱ)

መርበትበት
በፍርሃት መንቀጥቀጥ

በልብ አሰላስል
ልብ የሰውን ሃሳብ ይወክላል። በጥንቃቄ ማሰብ አንደ ማሰላለሰል ይገለጻል። አማራጭ ትርጉም: “በጥንቃቄ አስብ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

የጽድቅን መስዋዕት ሰዉ
“ጻድቅ መስዋዕትን ሰዉ”

እግዚአብሔርን ታመኑ
እዚህ ጋር እምነት አንድ ቦታ ማስቀመጥ እደምንምችለው ቁስ አቃል ተገልጧል። “መታመን” የሚለው ስምም በግስ መልክ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም: “በያህዌ ታመን” ወይም “ያህዌን ታመን” (ዘይቤን እና ረቂቅ ስምን ይመልከቱ)

Psalms 4:6

በጎውን ማን ያሳየናል?
አማራጭ ፍችዎች 1) መልካም ነገር ማሳየት መልካም ነገር ማምጣትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም: “መልካም ነገር ማን ያመጣልናል?” ወይም 2) ምልካም ነገር ማሳየት መልካም ነገር እንደሆነ መናገር። አማራጭ ትርጉም: “መልካም ነገር ሆንዋል ብሎ ምን ይነገረናል?” (ድጋሚ መሰየምን ይመለክቱ)

የፊትህ ብርሃን በላያችን ያብራ
ጸሐፊው ያህዌ በአድሎ ወደነሱ ሲመለከት ፊቱን እንደ ማብራት ይገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም: “ለኛ በአድሎ እርምጃ ውሰድ” (ዘይቤን ይመልከቱ)

በልቤ ደስታን ጨመርህ
ልብ ግለሰቡን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም: “የበለጠ ደስታን ሰተኸኛል” (በአንድ ክፍል ሙሉ አካልን መሰየም Synecdocheን ይመልከቱ)

ከሌሎች ይልቅ ደስታን አብዝተህ ሰጠኸኝ
እዚህ ጋር “ደስታ” ሊሰጥ እንደሚችል ቁስ አካል ተገልቷል። “ደስታ” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ “መደሰት” ለገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም: “ከሌሎች ይልቅ ደስተኛ አድርገኸኛል” (ዘይቤን እና ረቂቅ ስምን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ስንዴና አዲስ ወይን ይልቅ
“አዲስ ወይን” የወይን ፍሪን ሊያመለክት ይችላል። አማራጭ ትርጉም “የስንዴ እና የወይን መኸሩ ብዙ በሆነ ጊዜ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

በሰላም እና ያለስጋት
እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው በመደገማቸው ፍጹም ደህንነትን ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጉም፡ “ፍጹም ደህና እንድሆን ያደርገኛል”

በሰላም እተኛለሁ አንቀላፋለሁም
ሰላም የተገለፀው እንደ ስፍራ ነው። ይህ ወደ ረቂቅ ስም ወደ መሆን ይቀይረዋል። አማራጭ ትርጉም፡ “ስተኛ እና ሳንቀላፋ ሰላማዊ እሆናለሁ” ወይ “ስተኛ እና ሳንቀላፋ አደጋን አልፈራም” (ዘይቤን እና ረቂቅ ስምን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 5

1 ያህዌ ሆይ ወደ አንተ ስጣራ ስማኝ መቃተቴንም አስብ። **2** ንጉሤና አምላኬ ወደ አንተ እጸልያለሁና የልመናዬን ጽምፅ አድምጥ **3** ያህዌ ሆይ በማለዳ ድምፄን ትሰማለህ በማለዳ ልመናዬን ወደ አንተ አቀርባለሁ፤ እጠባበቃለሁም። **4** በእርግጥ አንተ በክፋት ደስ የምትሰኝ አምላክ አይደለህም ክፉ ሰዎች ከአንተ አያድሩም። **5** እብሪተኛ በፊትህ አይቆምም ዐመፃን የሚያደርጉትህን ሁሉ ጠላህ። **6** ሐሰተኞችን ታጠፋለህ ደም የተጠሙትን አታላዮችን ያህዌ ይጸየፋል። **7** እኔ ግን በኪዳናዊ ታማኝነትህ ብዛት ወደ ቤትህ እገባለሁ፤ በአክብሮት ፍርሃትም የተቀደሰ ማደሪያህ ውስጥ እሰግዳለሁ። **8** ጌታ ሆይ፣ በጠላቶች ምክንያት በጽድቅህ ምራኝ መንገድህንም በፊቴ አቅና። **9** በአፋቸው እውነት የለም ልባቸው ተንኰለኛ ነው። ጕሮሮአቸው እንደ ተከፈተ መቃብር ነው። በአንደበታቸው ይሸነገላሉ። **10** እግዚአብሔር ሆይ፣ የእጃቸውን ስጣቸው ተንኰላቸው መጥፊያቸው ይሁን! አንተ ላይ ዐምፀዋልና ከኃጢአታቸው ብዛት የተነሣ አስወግዳቸው። **11** በአንተ የተማመኑ ሁሉ ደስ ይበላቸው አንተ ከለላ ሁነሃቸዋልና ለዘላለም ሐሤት ያድርጉ። ስምህን የሚወዱ በአንተ ደስ ይበላቸው **12** ያህዌ ሆይ፣ አንተ ጻድቁን ትባርካለህ እንደ ጋሻ በሞገስ ትከልላቸዋለህ።

Psalms 5:1

አጠቃላይ ሃሳብ፡
በዕብራይስጥ ቅኔ ትይዩነት የተለመደ ነው። (ቅኔ እና ትይዩነትን ይመልከቱ)

ለመዘምራን አለቃ
“ይህ ለመዘምራን አለቃ ለአምልኮ እንዲጠቀምበት ነው”

በዋሽንት
“ይህ መዝሙር በዋሽንት በሚጠቀሙ መታጀብ አለበት”

የዳዊት መዝሙር
አማራጭ ፍችዎች፡ 1) ዳዊት ዝማሬውን ጽፎታል ወይም 2) ዝማሬው ስለዳዊት ነው ወይም 3) ዝማሬው የተዘመረው በዳዊት የአዘማመር ስልት ነው።

ቃሌን አድምጥ
ይህ እርዳታን ፍለጋ የሚደረግ ጥሪ ነው። አማራጭ ትጉም፡ “ለእርዳታ ወደ አንተ ስጣራ ስማኝ”(ድብቅ ሃሳብ ወይም ግምታዊ እውቀትን ይመልከቱ)

መቃተቴን
ሰዎች በስቃይ ጊዜ የሚያሰሙት ዝግ ያለ ድምጽ

በማለዳ ድምፄን ትሰማለህ፤ በማለዳ ልመናዬን በፊትህ አቀርባለሁ
እነኚህ ሁለት ስንኞች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። (ትይዩነትን ይመልከቱ)

ልመናዬን በፊትህ አቀርባለሁ
“ጥያቄዬን አቀርባለሁ” ወይም “የሚያስፈልገኝን እጠይቅሃለሁ”

በጥሞና እጠባበቃለሁ
“የጠየኩትን እንደምታደርግልኝ እጠብቃለሁ”

Psalms 5:4

ያህዌ ክፉ እና ሐሰተኛ ሰዎችን ይቃወማል
በዚህ መዝሙር ዳዊት ወደ እግዚአብሔር እየተናገረ ስለሆነ፣ ይህ ስንኝ አንተ በሚል መተካ ይችላል። አማራጭ ትርጉም “ያህዌ፣ አንተ ክፉ እና ሐሰተኛ ሰዎችን ትቃወማለህ” ወይም “ያህዌ፣ አንተ ክፉ የሚሰሩ ሰዎችን እና የሚዋሹ ሰዎችን ትጠላለህ” (አንደኛ፥ ሁለተኛ እና ሦስተኛ መደብን ይመልከቱ)

Psalms 5:7

በምሕረትህ (በታማኝነትህ) ብዛት
“ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ገላጭ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፤ “ለቃልኪዳንህ ታማኝ ስለሆንክ” (ረቂቅ ስምን ይመልከቱ)

ቤትህ
ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ቤተመቅደስ ነው። አማራጭ ትርጉም፡ “ቤተ መቅደስህ”

በጽድቅህ ምራኝ
ዳዊት ጽድቅን እንደ መንገድ ማስተማርንም እንደ መምራት ይገልጻል። “ጽድቅህ” የሚለው ሀረግ እግዚአብሔር ጻድቅ መሆኑን ያመለክታል አማራጭ ትርጉም፡ “ትክክል የሆነውን ማድረግ እንድችል አስችለኝ” (ምሳሌያዊ አባባልን ይመልከቱ)

መንገድህን በፊቴ አቅና
ዳዊት ጽድቅን እንደ መንገድ ይገልጸዋል። የቀና መንገድ ለማየትም ለመራመድም ቀላል ነው። አማራጭ ትርጉም፡ “በትክክለኛ መንገድ መኖርን አሳየኝ” ወይም “ትክክለ የሆነውን ማድረግ ቀላል አድርግልኝ” (ምሳሌያዊ አባባልን ይመልከቱ)

Psalms 5:9

አጠቃላይ ሃሳብ፡
ዳዊት ስለ ጣቶቹ ይናገራል።

በአንደበታቸው ምንም እውነት ስለሌለ
እውነት በአንደበት መኖር እውነትን መናገር ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡ “እውነት የሆነውን መቼም ስለማይናገሩ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

Psalms 5:11

አንተን መጠግያ ያደረጉ ሁሉ ደስ ይበላቸው
እግዚአብሔር እንደ መጠግያ ተገልጸዋል፣ ሰዎች ከጥፋት ሊጠበቁበት የሚችሉበት ቦታ። አማራጭ ትርጉም፡ “ከክፋት ለመጠለል ወደ አንተ የሚመጡ ሁሉ ደስ ይበላቸው” (ምሳሌያዊ አባባልን የመልከቱ)

... ደስ ይበላቸው፤ ዘላለም በደስታ ይዘምሩ፤
እነዚህ ሁለት ሃረጎች ተመሳሳይ ሃሳብ አላቸው. (ትይዩነትን ይመልከቱ)

አንተን መጠግያ ያደረጉ
ለመጠለያነት ወደ ያህዌ መሄድ እርሱን መጠግያ እንደማድረግ ይገለፃል። አማራጭ ትርጉም፡ “ወደ አንተ መለጠለያነት የሚሄዱ” (ምሳሌያዊ አባባልን የመልከቱ)

ስምህን የሚወዱ
የእግዚአብሔር ስም እራሱን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም “አንተን የሚወዱ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንደ ጋሻ በጸጋህ ትከልላቸዋለህ
የእግዚአብሔር ጸጋ እንደ ጋሻ ተመስሏል። አማራጭ ትርጉም፡ “ወታደር አራሱን እንደሚጠብቀው በ ጸጋህ ትጠብቃቸዋለህ፣ ትከልላቸዋለህ” ወይም “እንተ ለእነርሱ መልካም ስለሆንህ ትጠብቃቸዋለህ” (አነጻጻሪ ዘይቤን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 6

1 ያህዌ ሆይ፣ በቁጣህ አትገሥጸኝ በመዐትህም አትቅጣኝ፡ **2** ያህዌ ሆይ፣ ደካማ ስለሆንሁ ምሕረት አድርግልኝ። አምላኬ ሆይ፣ አጥንቶቼ ተናውጠዋልና፣ ፈውሰኝ። **3** ነፍሴም ታወካለች፤ ያህዌ ሆይ፣ ይህ እስከ መቼ ይቀጥላል? **4** ወደ እኔ ተመለስ፤ አድነኝም። ከታማኝ ኪዳንህ የተነሣ አድነኝ **5** በሞት የሚያስታውስህ የለም መቃብር ውስጥ ሆኖ፣ የሚያመሰግንህ ማን ነው? **6** ከመቃተቴ የተነሣ ዝዬአለሁ ሌሊቱን ሁሉ በልቅሶ አልጋዬን በእንባ አርሳለሁ መኝታዬንም በእንባ አረጥባለሁ። **7** ከሐዘን የተነሣ ዐይኖቼ ፈዘዙ፤ ከባላጋራዎቼ የተነሣ ደከሙ። **8** እናንት ዐመፃን የምታደርጉ ሁሉ ከእኔ ራቁ ያህዌ የለቅሶዬን ድምፅ ሰምቷልና **9** እንዲምረኝ ወደ እርሱ ያቀረብኩትን ልመና አድምጧል፤ ያህዌ ጸሎቴን ተቀብሏል። **10** ጠላቶቼ ሁሉ ይፈሩ፤ እጅግም ይታወኩ ወደ ኋላ ይመለሳሉ፤ በድንገትም ይዋረዳሉ።

Psalms 6:1

አጠቃላይ ሃሳብ፡
በዕብራይስጥ ቅኔ ትይዩነት የተለመደ ነው። (ቅኔ እና ትይዩነትን ይመልከቱ)

ለመዘምራን አለቃ
“ይህ ለመዘምራን አለቃ ለአምልኮ እንዲጠቀምበት ነው”

በዋሽንት
“ይህ መዝሙር በዋሽንት በሚጠቀሙ መታጀብ አለበት”

በሺሚኒት
ይህ የሙዚቃውን ስልት ሊያመለክት ይችላል

የዳዊት መዝሙር
አማራጭ ፍችዎች፡ 1) ዳዊት ዝማሬውን ጽፎታል ወይም 2) ዝማሬው ስለዳዊት ነው ወይም 3) ዝማሬው የተዘመረው በዳዊት የአዘማመር ስልት ነው።

አጥንቶቼ ታውከዋል/ይንቀጠቀጣሉ
x

Psalms 6:3

እጅግ ታወከች
“ፍራች” ወይም “ተጨነቀች”

እስከ መቼ ይቀጥላሉ?
ዳዊት ይህን ጥያቄ መበጠቀም እየፈራ እና እየተጨነቀ መቀጠል እንደማይፈልግ ይገልፃል። አማራጭ ትርጉም፡ “እባክህ እንዲቀጥሉ አትፍቀድ!” (መልስ አዘል ጥያቄን ይመልከቱ)

ተመለስ ያህዌ
እግዚአብሔር ወደ እርሱ ሲመለስ ለእርሱ መልካም እንደሆነ ይገልፃል። አማራጭ ትርጉም፡ “ያህዌ ወደኔ ተመለስ” ወይም “ያህዌ፣ምሕረት አድርግልኝ” (ምሳሌያዊ አባባልን የመልከቱ)

ስለኪዳን ታማኝነትህ ስትል አድነኝ
“ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ገላጭ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡ “ለኪዳንህ ታማኝ ስለሆንህ አድነኝ” (ረቂቅ ስምን ይመልከቱ)

በሞት መታሰብያ የለህምና፣ በሲዖልም የሚያመሰግን ማን ነው?
እነዚህ ሁለት ሃረጎች ተመሳሳይ ሃሳብ አላቸው። (ትይዩነትን ይመልከቱ)

በሞት መታሰብያ የለህምና
“መታሰብያ” የሚለው ረቂቅ ስም ምስጋናን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም “ምክንያቱም ሰዎች በሚሞቱበት ጊዜ፥ ሊያመሰግኑህ አይችሉም።” (ድጋሚ መሰየም እና ረቂቅ ስምን ይመልከቱ)

በሲዖል ማን ያመሰግንሃል?
ዳዊት ይህን ጥያቄ በመጠየቅ ትኩረት እየሰጠ ያለው በሲዖል እግዚአብሔርን የሚያመሰግን እንደሌለ ነው። አማራጭ ትርጉም፡ “በሲዖል ማንም አያመሰግንህም” ወይም “ሙታን ሊያመሰግኑህ ይችሉም” (መልስ አዘል ጥያቄን ይመልከቱ)

Psalms 6:6

በሰቆቃዬ ደክሚያለሁ
ይህ ሰቆቃ የሚያመለክተው የሚሰማውን ህመምን እና ጭንቀት ነው። አማራጭ ትርጉም፡ “ከህመም የተነሣ ደክምያለሁ” (ድጋሚ መሰየም ይመልከቱ)

አልጋዬን በእንባ አረጠብኩ፥ ትራሴን በእንባ አጠብኩ
እነዚህ ሁለት ሃረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ያስተላልፋሉ(ትይዩነትን ይመልከቱ)

አልጋዬን በእንባ አረጠብኩ፥
“አልጋዬን በእንባዬ አረጠብኩት” ወይም “አልጋዬ ከእንባዬ የተነሣ ረጠበ”

ትራሴን በእንባ አጠብኩ
“ትራሴን ከእንባዬ የተነሣ አረጠብኩት”

ዓይኖቼ ፈዘዙ
የማየት አቅም በዓይኖች ይመሰላል። አማራጭ ትርጉም “እይታዬ ፈዘዘ” ወይም “በግልጥ ማየት አልቻልኩም” (ድጋሚ መሰየም ይመልከቱ)

ከሃዘን
እዚህ ጋር ሃዘን ለቅሶን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡ “ከለቅሶ” ወይም “ከለቅሶ ብዛት” (ድጋሚ መሰየም ይመልከቱ)

Psalms 6:8

ያህዌ የምሕረት ልመናዬን ሰምቷል.... ያህዌ ፀሎቴን ተቀብሏል
እነዚህ ሁለት ሃረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ያስተላልፋሉ(ትይዩነትን ይመልከቱ)

ያህዌ ፀሎቴን ተቀብሏል
ዳዊት የፀለየውን ለማድረግ ፈቃደኛ መሆን ፀሎትን እንደ መቀበል ተለግጧል። አማራጭ ትርጉም፡ “ያህዌ ፀሎቴን ይመልሳል” (ድጋሚ መሰየም ይመልከቱ)

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 7

1 ያህዌ አምላኬ ሆይ፣ አንተ መጠጊያዬ ነህ! ከሚያሳድዱኝ ሁሉ አድነኝ ታደገኝም **2** አለበለዚያ እንደ አንበሳ ይዘነጣጥሉኛል የሚያድነኝ በሌለበት ሁኔታ
ያደቁኛል። **3** አምላኬ ያህዌ ሆይ፣ ጠላቶቼ አድርጓል የሚሉትን አላደረግሁም በእኔ ላይ ምንም በደል የለም። **4** በጐ ለዋለልኝ ክፉ አልመለስሁም።ጠላቶቼን
በከንቱ አልጐዳሁም። **5** የምናገረው እውነት ካልሆነ ጠላቴ አሳድዶ ይያዘኝ ሕይወቴን ከምድር ይቀላቅል ክብሬንም ከትቢያ ጋር ይደበልቅ። ሴላ **6** ያህዌ ሆይ፣
በቁጣህ ተነሥ በጠላቶቼ ዛቻ ፍረድ አምላኬ ሆይ ንቃ ትእዛዝም አስተላልፍ። **7** ሕዝቦችን ሁሉ በዙሪያህ ሰብስብ ከላይም ሆነህ ግዛቸው። **8** ያህዌ በሕዝቦች
ላይ ይፈርዳል ያህዌ ሆይ፣ እንደ ጽድቄ ፍረድልኝ ልዑል ሆይ፣ እንደ ንጽሕናዬ መልስልኝ። **9** ልብንና አእምሮን የምትመረምር ጻድቅ አምላክ ሆይ፣ የክፉዎችን
ዐመፅ አጥፋ፤ ጻድቃንን ግን አጽና። **10** ጋሻዬ ልዑል እግዚአብሔር ነው፤ እርሱ ልበ ቅኖችን ያድናቸዋል። **11** እግዚአብሔር ጻድቅ ዳኛ ነው፤ ቁጣውንም በየዕለቱ
የሚገልጥ አምላክ ነው። **12** ሰው በንስሐ የማይመለስ ከሆነ እግዚአብሔር ሰይፉን ይስላል፤ ለውጊያም ቀስቱን ይገትራል **13** የሚገደሉ ጦር ዕቃዎቹን
አዘጋጅቷል የሚንበለበሉትን ፍላጻዎቹንም አሰናድቶአል። **14** ክፋትን ያረገዘ፣ ክፉ ዕቅዶችን የፀነሰና አጥፊ ሐሰቶችን የወለደ ሰውን አስቡ። **15** ጥልቅ ጉድጓድ
ይቆፍራል በቆፈረው ጉድጓድ እርሱ ይገባበታል። **16** ለሌሎች ያዘጋጀው ክፉ ዕቅድ ወደ ራሱ ይመለሳል፤ ዐመፃውም በገዛ ዐናቱ ላይ ይወርዳል። **17** ስለ ጽድቁ
ያህዌን አመሰግናለሁ ለልዑል አምላክም እዘምራለሁ።

Psalms 7:1

አጠቃላይ መረጃ
ትይዩነት በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው። (ቅኔ እና ትይዩነትን ይመልከቱ)

ዳዊት የዘመረው መዝሙር
“ይህ ዳዊት የጻፈው መዝሙር ነው”

ስለ ብንያማዊ ሰው ስለ ኩሽ ቃል
“ብንያማዊው ኩሽ ስለተናገረው” ወይም “ኩስ፤ የቢንያም ሰው ስለተናገረው”

በአንተ እታመናለሁ
ለጥበቃ ወደ ያህዌ መሄድ በእርሱ እንደመታመን ይገለጻል። አማራጭ ትርጉም፡ “ለጥበቃ ወደአንተ አመጣለሁ” (ቅኔን ይመልከቱ)

ነፍሴን እንደ አንበሳ ነጥቀው እነዳይሰብሩዋት
ዳዊት ስለ ጠላቶቹ ሲናገር ሰውነቱን እንደሚገለጣጥሉ አናብስት ይገልፃቸዋል። አማራጭ ትርጉም “አንበሳ የሚያጠቃውን እንስሳ እንደሚገነጣጥል በጭካኔ ይገድሉኛል” ወይም “በጭካኔ ይገድሉኛል” (አነጻጻሪ ዘይቤን ይመልከቱ)

ማንም የሚያድነኝ በሌለበት
“ማንም ሊያድነኝ አይችልም”

Psalms 7:3

አመፃ በእጁ ቢኖር
እጅ ሰው የሚያደርገውን ይወክላሉ። አመፃ በእጅ መኖር የተሳሳተ ነገርን ማድረግ ይወክላል. አማራጭ ትርጉም “የተሳሳተ ነገር በማድረግ አጥፍቻለሁ” ወይም “ኃጢአትን ሰርቻለሁ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

Psalms 7:5

ሕይወቴ
ሕይወት ሰውየውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም “እራሴ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

ይይዙኛል
መማረክን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡ “ይማርኩኛል” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

ሕይወቴን ከምድር ይቀላቅላል
እዚህ ጋ ‘ሕይወቴ’ የሚወክለው ጸሐፊውን ነው። አማራጭ ትርጉም፡ “ሊያጠፋኝ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

ክብሬን ከዐፈር ይደባልቃል
ይህ የሚያለክተው መሞትን እኛ በክብር አለመቀበርን ነው።

Psalms 7:6

እግዚአብሔር ሆይ በቁጣህ ተነስ
መነሳት እንድን ነገር ማድረግ ወይም እርምጃ መውሰድን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡ “በቁጣህ አንድ ነገር አድርግ” ወይም “በጠላቶቼ ላይ ተቆጣ እና እርምጃ ውሰድ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

በቁጣ በተነሱብኝ ላይ ተነስ
ከሰዎች ጋር መጣላት ወይም መዋጋት በእነርሱ ላይ እንደ መነሳት ይገለጻል። አማራጭ ትርጉም፡ “በቁጣ የሚዋጉኝን ተዋጋቸው” ወይም “የተቆጡኝ ጠላቶች አጥቃቸው” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

የጠላቶቼ ቁጣ
የጠላቶች ቁጣ ማጥቃታቸውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡ “የጠላቶቼ ጥቃት” ወይም “የሚያጠቁኝ ጠላቶቼ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

ተነስ
መነሳት አንድ ነገር ማድረግ መጀመር ወይም እርምጃ መውሰድ ያመለክታል። አማራጭ ተርጉም፡ “እርምጃ ውሰድ ” ወይም “አንድ ነገር አድርግ” (ቅኔን ይመልከቱ)

ስለ እኔ ስትል
“ለእኔ” ወይም “እኔን ለመርዳት”

አገሮች ተሰባሰቡ
አገር የሚለው ቃል የሚወክለው ለማጥቃት የተሰባሰቡትን ጦሮችን ነው

በእነርሱ ላይ ለአንድ ጊዜ የሚገባህን ስፍራ ውሰድ
ሰዎችን መግዛት በእነርሱ ላይ እንደመሆን ይገለጻል። የያህዌ የሚገባ ስፍራ ሰማያትን ወይም በአጠቃላይ መግዛትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም: “ከሰማይ በእነርሱ ላይ ግዛ” ወይም “በእነርሱ ላይ ግዛ” (ቅኔን ይመልከቱ)

Psalms 7:8

አክብረኝ
“ጥፋተኛ እንዳልሆንኩ አሳያቸው”

ጻድቃንን አጽና
“ጻድቅ የሆኑ ሰዎችን አጠንክር” ወይም “ጻድቅ የሆኑ ሰዎችን እንዲበለጽጉ አድርግ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አንተ ልብን እና አእምሮን የምትመረምር
ልብ እና እእምሮ የሰውን ፍላጎት እና ሃሳብን ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም፡ “አንተ የውስጥ ሃሳባችንን የምታውቅ” (ቅኔን ይመልከቱ)

Psalms 7:10

ጋሻዬ ከእግዚአብሔር ይመጣል
‘ጋሻ’ የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ጥበቃ ያመለክታል። (ቅኔን ይመልከቱ)

በየቀኑ ንዴቱ ይነዳል
ይህን ሃሳብ በግልጽ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡ “ኃጢአተኛውን በየቀኑ የሚቆጣ” (ድብቅ ሃሳብ ወይም ግምታዊ እውቀትን ይመልከቱ)

Psalms 7:12

እግዚአብሔር ሰይፉን ይስላል ቀስቱንም ይገትራል
በቁጥ 12 እና 13፣ ዳዊት እግዚአብሔር ክፉዎችን እንደ ተዋጊ በጦር መሳርያ ሊቀጣ እንደ ተዘጋጀ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡ “እግዚአብሔር ሰይፉን እንደ ሳለ ቀስቱንም እንደ ገተረ ጦረኛ እርምጃ ይወስዳል።” (ቅኔን ይመልከቱ)

Psalms 7:14

ክፋትን ጸንሷል ቅጥፈትን አርግዟል ሐሰትን ይወልዳል
x

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 8

1 ክብርህን በላይ በሰማያት የምትገልጥ አንተ ጌታችን ያህዌ፣ ስምህ በምድር ሁሉ ምንኛ ገናና ነው። **2** ከጠላትህ የተነሣ፤ ባላንጣንና ቂመኛን ጸጥ ለማሰኘት
ከልጆችና ጡት ከሚጠቡ ሕፃናት አፍ ምስጋናን አዘጋጀህ። **3** ጣቶችህ የሠሯቸው ሰማያትን፣ በየቦታቸው ያደርግሃቸው ጨረቃና ከዋክብትን ስመለከት **4**
በአሳብህ ስፍራ ትሰጠው ዘንድ ሰው ምንድነው? ትጠነቀቅለትስ ዘንድ የሰው ልጅ ምንድነው? **5** ከመላእክት በጥቂት አሳነሰኸው የክብርና የሞገስ ዘውድ
አቀዳጀኸው። **6** በእጆችህ ሥራ ሁሉ ላይ ሾምኸው ሁሉንም ከእግሮቹ በታች አደረግህለት **7** በጐችና በሬዎችን፣ የዱር አራዊትን፣ **8** የሰማይ ወፎችን፣ የባሕር
ዓሦችን ባሕር ውስጥ የሚርመሰመሱትን ሁሉ አስገዛህለት። **9** ጌታችን ያህዌ፣ ስምህ በምድር ሁሉ ላይ ምንኛ ገነነ!

Psalms 8:1

አጠቃላይ ሃሳብ
ትይዩነት በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው (ቅኔ እና ትይዩነትን ይመልከቱ)

ለመዘምራን አለቃ
“ይህ ለመዘምራን አለቃ ለአምልኮ እንዲጠቀምበት ነው”

በዋሽንት
“ይህ መዝሙር በዋሽንት በሚጠቀሙ መታጀብ አለበት”

የዳዊት መዝሙር
አማራጭ ፍችዎች፡ 1) ዳዊት ዝማሬውን ጽፎታል ወይም 2) ዝማሬው ስለዳዊት ነው ወይም 3) ዝማሬው የተዘመረው በዳዊት የአዘማመር ስልት ነው።

ስምህ በምድር ላይ እንዴት ታላቅ ነው
የእግዚአብሔር ስም ማንነቱን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡ “በምድር ያሉ ሰዎች ሁሉ ታላቅነትህን ያውቃሉ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

ከሕጻናት እና ከሚጠቡ አፍ ምስጋናን አዘጋጀህ
አማራጭ ፍችዎች 1) ምስጋና እንደ ቁስ አካል ተገልጧል። እግዚአብሔር ከህጻናት እና ከሚጠቡ አፍ ያወጣው እና እንደ መከላከያ ግንብ ያኖረዋል ወይም 2) እግዚአብሔር አለምን የፈጠረው ምስጋና ህጻናት እንደበት እንዲወጣ ነው። አማራጭ ትርጉም፡ “ለህጻናት እና ለሚጠቡ አንተን የማመስገን ብቃት ሰጥተሃቸዋል” ወይም “በእውነት የሚያመሰግኑህ ህጻናት እና የሚጠቡት ናቸው” (ቅኔን ይመልከቱ)

Psalms 8:3

ጣቶችህ ያመጁት ሰማያትህ
የእግዚአብሔር ጣቶች እርሱን ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም፡ “አንተ የሰራሃቸው ሰማያት”

በሐሳብህ ስፍራ ትሰጠው ዘንድ ሰው ምንድን ነው? ትጠነቀቅለትም ዘንድ የሰው ልጅ ምንድን ነው?
እነዚህ ሃሳቦች ትኩረትን ለመስጠት በጥያቄ መልክ ተቀምጠዋል። አማራጭ ትርጉም፡ “ሰለሰዎች ማሰብህ እና መጠንቀቅህ አስገራሚ ነው!” (መልስ አዝል ጥያቄን ይመልከቱ)

የሰው ዘር.... የሰው ልጅ
ሁለቱም ሃረጎች በአጠቃላይ ሰዎችን ይወክላሉ።

የክብር እና የሞገስ ዘውድ ደፋህላቸው
ክብር እና ሞገስ እንደ ዘውድ ተገልጸዋል። ‘ክብር’ እና ‘ሞገስ’ የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ አላቸው። አማራጭ ትርጉም፡ “ክብር እና ሞገስ ሰጥተሃቸዋል” ወይም “እንደ ንጉሥ እንዲሆኑ እድርገሃቸዋል” (ቅኔ እና መድገምን ይመልከቱ)

Psalms 8:6

ሾምህው... ሁሉንም ከእግሩ በታች አደረግህ
ሁለቱ ሃረጎች ተመሳሳይ ፍቺ አላቸው። (ትይዩነትን ይመልከቱ)

የእጆችህን ስራ
እጆች እግዚአብሔርን የሰራውን ይወክላሉ። አማራጭ ጥርጉም፡ “አንተ የሰራሃቸው ነገሮች” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዛህለት
ነገሮች መግዛት እና መቆጣጠር ከእግር በታች እንደማድረግ ይገለጣል። ይህም ማለት እግዚአብሔር ለሰዎች በፍጥረት ሁሉ ላይ እንዲገዙ ስልጣን ሰጣቸው። አማራጭ ትርጉም “በሁሉ ነገሮች ላይ ስልጣንን ሰተሀዋል” (ቅኔን ይመልከቱ)

Psalms 8:9

ስምህ በምድር ሁሉ ምንኛ ግርማዊ ነው
በነዚህ የአጋኖ ቃላት፣ ዳዊት በእግዚአብሔር ታላቅነት መደሰቱን እና መደነቁን ይገልጣል። አማራጭ ትርጉም፡ “ስምህ በሚያስደንቅ መልኩ በአለም ሁሉ ታላቅ ነው” ወይም “በምድር ያሉ ሰዎች ሁሉ ምንያህል ታላቅ እንደሆንህ ያውቃሉ” (አጋንኖን ይመልከቱ)

ስምህ
የእግዚአብሔር ስም አራሱን ወይም ስለሱ የሚባለውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡ “ስለአንተ የሚባለው” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

ግርማዊ
ታላቅ፣ ፍጹም

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 9

1 በፍጹም ልቤ ያህዌን አመሰግናለሁ ስለ ድንቅ ሥራዎችህም እናገራለሁ። **2** በአንተ ደስ ይለኛል፤ ሐሤትም አደርጋለሁ ልዑል ሆይ፣ ለስምህ እዘምራለሁ! **3** ጠላቶቼ ወደ ኋላ በተመለሱ ጊዜ ተሰነካክለው በፊትህ ይጠፋሉ። **4** በዙፋንህ ላይ ተቀምጠህ ጻድቅ ፈራጅ ነህ! የእኔን ጉዳይም ትፈርድልኛለህ። **5** ሕዝቦችን ገሠጽህ ክፉዎችን አጠፋህ ስማቸውን ከዘላለም እስከ ዘላለም ደመሰስህ። **6** ጠላቶች ለዘላለም ጠፍተዋል ከተሞቻቸውንም ገለባበጥሃቸው መታሰቢያቸውንም አጠፋህ። **7** እግዚአብሔር ግን ለዘላለም ዙፋኑ ላይ ነው ዙፋኑንም ለፍርድ አጽንቶአል። **8** ዓለምን በጽድቅ ይዳኛል ለሕዝቦችም በፍትሕ ይፈርዳል። **9** ያህዌ ለተጨቆኑት ዐምባ ነው። በመከራም ጊዜ መጠጊያ ይሆናቸዋል። **10** ስምህን የሚያውቁ በአንተ ይታመናሉ አንተ ያህዌ፣ የሚፈልጉህን አትተዋቸውም። **11** በጽዮን ለሚገዛ ለያህዌ ምስጋና ዘምሩ ድንቅ ሥራውን ለሕዝቦች ተናገሩ። **12** ደም ተበቃዩ አስቦአቸዋልና የጭቁኖችን ጩኸት አልዘነጋም። **13** ያህዌ ሆይ፣ ማረኝ በሚጠሉኝ የደረሰብኝን ጭቆና ተመልከት አንተ ከሞት አፋፍ ነጥቀህ አድነኝ። **14** ይህን ብታደርግልኝ፣ በጽዮን አደባባይ ምስጋናህን ሁሉ ለሕዝብ እናገራለሁ በማዳንህም ደስ እሰኛለሁ! **15** ሕዝቦች ባዘጋጁት አዘቅት ሰጠሙ እግሮቻቸውም በሰወሩት ወጥመድ ተያዙ። **16** እግዚአብሔር በእውነተኛ ፍርዱ ታወቀ ክፉዎችም በእጃቸው ሥራ ተጠመዱ። **17** ክፉዎች ተመልሰው ወደ ሲኦል ይወርዳሉ። እግዚአብሔርን የሚዘነጉ ሰዎች ሁሉ ፍጻሜ ይኸው ነው። **18** ችግረኞች መቼም ቢሆን አይዘነጉም የድኾችም ተስፋ ከንቱ ሆኖ አይቀርም። **19** ያህዌ ሆይ ተነሥ፣ ሰውም አያይል ሕዝቦችም በፊት ይፈረድባቸው። **20** ያህዌ ሆይ፣ አስደንግጣቸው ሕዝቦች ሰዎች ብቻ መሆናቸውን ይወቁ። ሴላ

Psalms 9:1

አጠቃላይ መረጃ:
በዕብራይስጥ ቅኔ ትይዩነት የተለመደ ዘይቤ ነው። (ቅኔ እና ትይዩነትን ይመልከቱ)

ለመዘምራን አለቃ
“የመዘምራን አለቃ በጋራ አምልኮ ጊዜ የሚጠቀምበት”

በሙትላቤን ቅኝት
ይህ ምንአልባት የቅኝትን አይነት ያመለክታል

የዳዊት መዝሙር
አማራጭ ፍችዎች፡ 1) ዳዊት ዝማሬውን ጽፎታል ወይም 2) ዝማሬው ስለዳዊት ነው ወይም 3) ዝማሬው የተዘመረው በዳዊት የአዘማመር ስልት ነው።

በሙሉ ልቤ ያህዌን አመሰግናለሁ
ይህ መዝሙር ለያህዌ የተደረሰ ስለሆነ፣ ያህዌ ‘አንተ’ ሊባል ይችላል። አማራጭ ተርጉም “ያህዌ፥ በሙሉ ልቤ አንተን አመሰግንሃለሁ” (አንደኛ ሁለተኛ እና ሦስተኛ መደብን ይመልከቱ)

ድንቅ ስራዎችህ
ስራ የሚለው ስም በግስ መልክ ሊተካ ይችላል። አማራጭ ትርጉም: “ያደረካቸው አስደናቂ ነገሮች ሁሉ” ወይም “የሰራሃቸው አስደናቂ ነገሮች ሁሉ” (ረቂቅ ስምን ይመልከቱ)

ለስምህ ምስጋናን እዘምራለሁ
የእግዚአብሔር ስም እራሱን እግዚአብሔርን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም: “ለአንተ ምስጋናን አዘምራለሁ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

Psalms 9:3

ወደ ኋላ መመለስ
“ማፈግፈግ” ወይም “በፍርሃት መመለስ”

አንተ ጻድቅ ፈራጅ በዙፋንህ ተቀምጠሃል
ንጉሦች በሰዎች ላይ የመፍረድ ሥልጣን ነበራቸው፣ ሲፈርዱም በዙፋናቸው ይቀመጣሉ። ዳዊት ስለ እግዚአብሔር በምድር እንዳለ ንጉሥ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም: “በዙፋኑ እንደቀመጠ ንጉሥ ትፈርዳለህ፥ ጻድቅም ነህ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

Psalms 9:5

ስማቸውን እስከ ወዲያኛው ደመሰስህ
ሰዎች እንዲረሱ ማድረግ ስማቸውን እንደ መደምሰስ ይገለጣል። አማራጭ ትርጉም: “ስማቸው እንደተደመሰሰ እንዲረሱ አደረግህ” ወይም “ማንም መቼም አያስታውሳቸውም” (ቅኔን ይመልከቱ)

ደመሰስህ
“ሰረዝህ”

ጠላቶች እንደ ፍርስራሽ ወደቁ
ጠላት ልክ እንደ ፈራረሰ ህንጻ እንዳለው ከተማ ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም: “ጠላቶቻችን ተደምስሰዋል” (አነጻጻሪ ዘይቤን ይመልከቱ)

ከተማዎቻቸውን ገለበጥሃቸው
“ከተማዎቻቸውን ደመሰስህ”

ዝክራቸውም በአንድነት ጠፋ
“ዝክር” በህይወት እንዳለ ነገር እና ለሞት እንደሚችል ነገር ነው የተገለጸው። አማራጭ ትርጉም: “እነርሱም የሚያስታስ ነገር ሁሉ ቆሟል” ወይም “ምንም እነርሱን ማስታወስ የለም” (ምሳሌያዊ አነጋገርን ይመለክቱ)

መታሰቢያዎቻቸውም ተደምስሰዋል
“መታሰቢያዎቻቸው” የሚለው ቃል በሕይወት እንደለ ነገር ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም: “እነርሱን ማስታወስ ቆምዋል” ወይም “እነርሱን የሚያስታውስ ምንም ነገር የመልም” (ረቂቅ ስምን ይመልከቱ)

Psalms 9:7

ያህዌ ለዘላለም ይኖራል
“ይኖራል” የሚለው ቃል የሚወክለው በዙፋኑ እንደ ንጉሥ መኖርን ነው። አማራጭ ትርጉም: “ያህዌ ለዘላለም በዙፋኑ ይቀመጣል” ወይም “ያህዌ ለዘላለም ይገዛል” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

መንበሩንም ለፍርድ አፍንቶአል
“መንበሩ” የሚለው ቃል ዙፋኑን ወይም አገዛዙን ይወክላል። አማራጭ ፍቺ 1) “በሰዎች ለመፍረድ ይገዛል” ወይም “በጽድቅ በሰዎች ላይ ይገዛል” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

በዓለም በጽድቅ ይፈርዳል ... በፍትህ በሕዝቦች ላይ ይፈርዳል
እነዚህ ሁለት ሃረጎች ተመሳሳይ ሃሳብ አላቸው (ትይዩነትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በጽድቅ በዓለም ላይ ይፈርዳል
“ዓለም” የሚለው ቃል እዚህ ጋር የሚወክለው በዓለም ያሉትን ሰዎች ነው። አማራጭ ትርጉም: “በጽድቅ በዓለም ያሉትን ሰዎች ሁሉ ላይ ይፈርዳል” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

Psalms 9:9

ያህዌ ለተጨነቁ ዐምባ ነው
እግዚአብሔር ሰዎች ለማለጥ የሚሸሸጉበት አንድ ስፍራ እንደሆነ ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም: “ያህዌ የተጨነቁትን የጠብቃል” ወይም “ያህዌ ለተጨነቁ መሸሸግያ ይሆናል” (ቅኔን ይመልከቱ)

ስምህን የሚያውቁ
ስምህ የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም: “አንተን የሚያውቁ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

አትተዋቸውም
“ብቻቸውን አትተዋቸውም” ወይም “ያለ ረዳት አትተዋቸውም”

Psalms 9:11

በጽዮን የሚገዛ
“በኢየሩሳሌም የሚኖር”

ለሕዝቦች አውሩ
“ሕዝቦች” የሚለው ቃል ከተለያዩ ቦታ የሆኑ ሰዎችን ያመለክታል። (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ደም ተበቃዮ አስታውሶዋቸዋል እና
አስታውሷል የሚለው ቃል በግልጽ ሊቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም: ”የተገደሉትን ደም የሚበቀለው እግዚአብሔር አስታውሷቸዋል” ወይም “የተገደሉትን እግዚአብሔር አስታውሷቸዋል ገዳዮችንም ይቀጣል” (ግምታዊ እውቀትን እና ድብቅ ሃሳብ ይመልከቱ)

ለቅሶዋቸውን አይረሳም
“ለቅሶዋቸውን አይዘነጋም”

Psalms 9:13

በሚጠሉኝ እንዴት እንደተጨቆንኩ ተመልከት
በቀጥተኛ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም: “የሚጠሉኝ እንዴት እንደጨቆኑኝ ተመልከት” ወይም “የሚጠሉኝ እንዴት በመጥፎ ሁኔታ አንደሚያንገላቱኝ ተመልከት” (ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪን ይመልከቱ)

አንተ ከሞት ደጃፍ ልትነጥቀኝ የምትችል
ሞት ሰዎች ለሊገቡበት እንደሚችሉ ደጃፍ አንዳለው ከተማ ተገልጧል። አንድ ሰው ከደጃፉ ቅርብ ከሆነ ለሞት ቀርቧል ማለት ነው። ሰውን ከሞት መጠበቅ ከሞት ደጆች እንደ መመለስ ይገለጻል። አማራጭ ትርጉም: “ከሞት ልትታደገኝ የምትችል አንተ” ወይም “ከመሞት የምትጠብቀኝ አንተ” (ቅኔን ይመልከቱ)

Psalms 9:15

አሕዛብ በቆፈሩት ጉድጓድ ገቡ
ሰዎች እንስሳትን ለማጥመድ ጉድጓድ ይቆፍራሉ። እዚህ ጋር ጉድጓድ መቆፈር ሰዎችን ለማጥፋት ማቀድን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም: “አሕዛብ ለሉሎች ጉድጓድን ይቆፍራሉ እራሳችው ይገቡበታል” (ቅኔን ይመልከቱ)

እግቸውም እራሳቸው በስውር ባስቀመጡት ወጥመድ ተያዘ
ሰዎች እንስሳትን ለማጥመድ ወጥመድ ይዘረጋሉ። እዚህ ጋር ወጥመድ በስውር ባስቀመጥ ሰዎችን ለማጥፋት ማቀድን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም: “በደበቁት ወጥመድ እንደሚያዙ ሰዎች ናቸው” (ቅኔን ይመልከቱ)

ክፉዎች በእራሳቸው ስራ ተጠመዱ
እዚህ ጋ ክፉዎች የሚለው ቃል ማንኛውም ኃጢአተኛ ሰውን ይወክላል። አንድ ክፉ ሰው ሌላ ሰውን ለመጉዳት የሚሰራ ስራ ሌሎች እንዲያዙበት ወጥመድ እንደማዘጋጀት ተገልጧል። ይህ በቀጥተኛ መንገድ ሊገለጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም: “አንድ ክፉ ሰው ሌሎች ሰዎችን ለመጉዳት ሲሞክር፥ የእራሱ ስራ መልሶ ይጎዳዋል”

ተጠመዱ
“ወጥመድ ውስጥ ገቡ”

Psalms 9:19

ተነሣ
መነሣት የሚያመለክተው አንድ ነገር ለማድረግ መጀመርን ነው። አማራጭ ትርጉም: “አንድ ነገር አድርግ” ወይም “እርምጃ ውሰድ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

ሰው
ሰዎች

ይፍረድ
መፍረድ መቅጣትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም: “ይቅጣ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

በፊትህ
መገኘትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም: “በመገኘትህ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

አሕዛብ በፊትህ ይፈረድባቸው
በቀጥተኛ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም: “በፊትህ አሕዛብ ፍረድባቸው” ወይም “አህዝብን ወደ ፊትህ አምጣቸው እና ፍረድባቸው” (ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 10

1 ያህዌ ሆይ፣ ለምን ርቀህ ቆምህ? በመከራ ጊዜ ለምን ራስህን ሰወርህ? **2** በእብሪት ተነሳሥተው ክፉዎች ጭቁኖችን ያሳድዳሉ እባክህ ክፉዎች ባጠመዱት ወጥመድ ይጠመዱ። **3** ክፉ ሰው በልቡ ምኞት ይኩራራል ስግብግቡን ይባርካል፤ ያህዌን ይሰድባል። **4** ክፉ ሰው በራሱ ይመካል፤ እግዚአብሔርንም አይፈልግም። ስለ እርሱ ምንም ደንታ ስለሌለው ስለ እግዚአብሔር አያስብም። **5** ነገሩ ዘወትር ለእርሱ የተሳካ ነው የእግዚአብሔርን ፍርድ ግን ሊረዳ አይችልም። በጠላቶቹ ላይ ይሳለቃል። **6** በልቡም፣ «በፍጹም አልወድቅም ከትውልድ እስከ ትውልድ መከራ አያገኘኝም» ይላል። **7** አፉ መርገምን፣ ሸፍጥንና ግፍን የተሞላ ነው፤ በምላሱ ይጐዳል፤ ይገድላልም። **8** መንደሮች አጠገብ አድፍጦ ይጠብቃል በሰዋራ ቦታ ንጹሐንን ይገድላል ዐይኖቹም ምስኪኖች ላይ ያነጣጥራሉ። **9** ደን ውስጥ እንዳለ አንበሳ በስውር ያደባል ረዳት የሌለውን ለመያዝ ያሸምቃል። መረቡን ዘርግቶ ጭቁኖችን ያጠምዳል። **10** እርሱ መትቶ ይጥላቸዋል፤ ረዳት የሌላቸው ደካሞች ምስኪኖችም የእርሱ ሰለባ ሆነው ይወድቃሉ። **11** በልቡም፣ «እግዚአብሔር ረስቶአል እንዳያይም ፊቱን ሸፍኖአል» ይላል። **12** ያህዌ ሆይ፣ ተነሥ! አምላክ ሆይ ኃያል ክንድህ ይነሣ! የተጨቆኑትን ችላ አትበላቸው። **13** ክፉ ሰው ለምን እግዚአብሔርን ይንቃል? በልቡም ለምን፣ «እግዚአብሔር አይቀጣኝም» ይላል? **14** አንተ ግን መከራንና ሐዘንን ታያለህ ምስኪኑም ራሱን በአንተ ላይ ይጥላል፤ ለድኻ አደጉም አንተ ረዳቱ ነህ። **15** የክፉና የበደለኛውን ክንድ ስበር አንተ እንደማታገኘው አስቦ ነበር የእጁንም ሰጠው። **16** ያህዌ ከዘላለም እስከ ዘላለም ንጉሥ ነው ሕዝቦችም ከምድሩ ይወገዳሉ። **17** ያህዌ የጭቁኖቹን ጩኸት ሰምቷል ልባቸውን ታበረታለህ፤ ጸሎታቸውንም ትሰማለህ **18** ከእንግዲህ ማንም በምድር ላይ ሽብር እንዳያደርግ አንተ አባት ለሌላቸውና ለጭቁኖች መከታ ሆንህላቸው።

Psalms 10:4

ክፉው ሰው
ይህ ሁሉንም ክፉ ሰው ይወክላል። አማራጭ ትርጉም: “ክፉ ሰዎች” (አጠቃላይ ስያሜን ይመልከቱ)

የተነሣ ፊት
የተነሣ ፊት ትዕቢትን ይወክላል። አማራጭ እርጉም: “የንቀት ሃሳብ አለው” ወይም “ጉረኛ ነው” (ቅኔን ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን አይፈልግም
እግዚአብሔርን መፈለግ 1) እግዚአብሔርን እርዳታ መጠየቅ ወይም 2) እግዚአብሔርን ማሰብ እና መታዘዝ። አማራጭ ትርጉም: “እግዚአብሔርን ዕርዳታ አይጠይቅም” ወይም “ስለ እግዚአብሔር አያስብም” (ቅኔን ይመልከቱ)

መንገዱ የተሳካ ነው
“ሁልጊዜ የተጠበቀ ነው”። በእውነትም የተጠበቀ አይደለም ነገር ግን የተጠበቀ እንደሆነ ይመስለዋል።

ከጻድቅ ሕግህ የራቀ ነው
ለመረዳት የሚከብድ ነገር ለመድረስ የራቀ እንደሆነ ይገለጻል። አማራጭ ትርጉም: “ጻድቅ ሕግህን ለመረዳት አይችልም።” (ቅኔን ይመልከቱ)

በጠላቶቹ ላይ ያፌዛል
ይህን የሚያደርገው ጠላቶቹ ደካማ እና አላስፈላጊ እንደሆኑ ስለሚያስብ ነው። አማራጭ ትርጉም: “ጠላቶቹ ሁሉ ደካማ እና ጥቅም የለሽ እንደሆኑ ያስባል” ወይም “በጠላቶቹ ሁሉ ላይ ያሾፋል” (አመልካች ድርጊትን ይመልከቱ)

ያፌዛል
x

Psalms 10:6

ይላል
“ክፉው ሰው እንዲህ ይላል”

ከትውልድ እስከ ትውልድ
ምናልባትም ለዘላለም ማለት ሊሆን ይችላል።

መከራ አያገኘኝም
መከራ በሕይወት መለማመድ እንደ መገናኘት ይገለጻል። አማራጭ ትርጉም: “ምንም አይነት ችግር አይኖርብኝም” (ቅኔን ይመልከቱ)

አፉ መርገምን፣ ቅጥፍትንኣ ግፉን የተሞላ ነው
ሰዎች የሚናገሩት ነገር በአፋቸው እንዳለ ይገለጻል። አማራጭ ትርጉም: “ሁልጊዜ ሰዎችን ይረግማል አና የሚጎዳ ውሸት ይናገራል” ወይም “ሰዎችን ሁልጊዜ ይረግማል፣ ይዋሻል አና እንደሚጎዳቸው በማስፈራራት ይናገራል” (ቅኔን ይመልከቱ)

ሸንገላ እና ክፋት ከምላሱ ስር ይገኛሉ
ምላስ መናገርን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም: “የሚናገረው ሰዎችን የሚያጠፋ እና የሚጎዳ ነው” ወይም “ሰዎችን የሚያስፈራራ እና የሚጎዳ ነገር ይናገራል” (ቅኔን ይመልከቱ)

Psalms 10:8

ያደፍጣል
ይህ ድርጊት በክፉው ሰው ይደረጋል።

ዐይኖቹ በምስኪኖች ላይ ያነጣጥራል
ዐይኖቹ እርሱን ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም: “ረዳት የሌላቸው ምስኪኖችን ይመለከታል” (በአንድ ክፍል ሙሉ አካልን መሰየምን ይመልከቱ)

በደኑ ውስጥ እንዳለ አንበሳ በስውር ያደባል
ይህ ሃሳብ ክፉው ሰው ልክ እንደ አንበሳ ይገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም: “ደካሞች እስቀሚቀርቡት ድረስ አንበሳ እንስሳን ለማጥቃት በዝምታ እንደሚያደባ ይደበቃል” (አነጻጻሪ ዘይቤን ይመልከቱ)

ያደባል
ለመጉዳት ወይም ለመግደል ተደብቆ መቆየት ማለት ነው።

Psalms 10:11

ይላል
የሚናገር ክፉው ሰው ነው። ክፉው ክፉ ሰዎችን የሚወክል ስም ነው። (አጠቃላይ ስያሜን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ረስቷል
ለማሰብ አለመፍቀድ እንደመርሳት ተገልጿል። አማራጭ ትርጉም: “እግዚአብሔር ሰዎችን አያስብም” ወይም “እግዚአበሔር ስለ እኔ ግድ አይለውም” (ቅኔን ይመልከቱ)

ፊቱን ይሸፍናል
አንድ ሰው ምን እያደረገ እንዳለ ለመመልከት አለመፍቀድ ፊትን እንደመሸፈን ይገለጻል። አማራጭ ትርጉምኘ “እየሆነ ያለውን ለመመልከት እግዚአብሔር አይፈልግም” (ቅኔን ይመልከቱ)

ፈጽሞም አያይም
አንድን ነገር ማሰብ እንደ ማየት ይገለጻል። አማራጭ ትርጉም፡ “እግዚአብሔር እየሆነ ያለውን ለማየት ፈቃደኛ እይደለም።” (ቅኔን ይመልከቱ)

ተነሣ
መነሣት የሚያመለክተው አንድ ነገር ለማድረግ መጀመርን ነው። አማራጭ ትርጉም፡ “አንድ ነገር አድርግ” ወይም “እርምጃ ውሰድ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

እጅህን አንሣ
አንድን ሰው ለመምታት እጅን ማንሣት መቅጣትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡ “በሃይል መምታት” ወይም “ክፉውን ሰው መቅጣት” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

Psalms 10:13

ክፉ ሰው በእግዚአብሔር ላይ ለምን ክፉ ይናገራል? “ስለ ስራዬ አይጠይቀኝም” ለምን ይላል?
ተናጋሪው እነዚህ ጥያቄዎች በመጠየቅ ክፉ ሰዎች በሚያደርጉት ነገር ማዘኑን ይገልጻል። አማራጭ ትርጉም፡ “ክፉ ሰዎች ሁልጊዜ ‘በስራቻን ተጠያቂ አይደለንም’ በማለት እግዚአብሔርን እየተቃወሙ ነው” (መልስ አዘል ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

ስለ ስራዬ ተጠያቂ አይደለሁም
“የማደርገውን ለምን አንደማደርግ አትጠይቀኝም” አንድ ሰው ተጠያቂ ማድረግ መቅጣትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡ “አትቀጣኝም” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

Psalms 10:17

የተጨቆኑትን ፍላጎት ሰምተሃል
የተጨቆኑ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መጮሃቸው የልተገለጸ ሃሳብ ነው። አማራጭ ትርጉም፡ “የተጨቆኑ ሰዎች ወደ አንተ ሲጮሁ እና ፍላጎታቸውን ሲነግሩህ ሰምተሃቸዋል” (ግምታዊ እውቀትን እና ድብቅ ሃሳብ ይመልከቱ)

ልባቸውን ታጠነክራለህ
ጠንካራ ልብ ድፍረትን ያመለክታለ የሰዎችን ልብ ማጠንከር ደግሞ ሰዎችን ማበረታታት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡ “ታበረታታቸዋለህ” ወይም “ደፋር ታረጋቸዋለህ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

ማንም ሰው ከእንግዲህ አያስጨንቃቸውም
“ማንም ሰው ከእንግዲህ እንዲፈሩ አያደርጋቸውም”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 11

1 ያህዌ ሆይ፣ አንተን መጠጊያ አደረግሁ ታዲያ፣ ነፍሴ፣ «እንደ ወፍ ወደ ተራሮች ብረሪ» እንዴት ትሏታላችሁ? **2** ደግሞም ለምን እንዲህ ትሉኛላችሁ? ልበ ቅኖችን በጨለማ ለመግደል ክፉዎች ቀስታቸውን ገትረዋል፤ ፍላጻቸውንም በአውታሩ ላይ ደግነዋል። **3** ያህዌ ሆይ፣ አንተን መጠጊያ አደረግሁ ታዲያ፣ ነፍሴ፣ «እንደ ወፍ ወደ ተራሮች ብረሪ» እንዴት ትሏታላችሁ? ደግሞም ለምን እንዲህ ትሉኛላችሁ? **4** ልበ ቅኖችን በጨለማ ለመግደል ክፉዎች ቀስታቸውን ገትረዋል፤ ፍላጻቸውንም በአውታሩ ላይ ደግነዋል። **5** ያህዌ ጻድቁንና ኃጢአተኛውን ይመለከታል ዐመፅን ማድረግ የሚወዱትን ግን ይጠላቸዋል። **6** እርሱ በክፉዎች ላይ የእሳት ፍምና ዲን ያዘንባል፤ የሚለበልብ ዐውሎ ነፋስም የእነርሱ ዕጣ ፈንታ ነው። **7** ያህዌ ጻድቅ ስለ ሆነ የጽድቅን ሥራ ይወዳል፤ ቅኖችም ፊቱን ያያሉ።

Psalms 11:1

አጠቃላይ ሃሳብ፡
ትይዩነት በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው። (ቅኔ እና ትይዩነትን ይመልከቱ)

ለመዘምራን አለቃ
“የመዘምራን አለቃ በጋራ አምልኮ ጊዜ የሚጠቀምበት”

የዳዊት መዝሙር
አማራጭ ፍችዎች፡ 1) ዳዊት ዝማሬውን ጽፎታል ወይም 2) ዝማሬው ስለዳዊት ነው ወይም 3) ዝማሬው የተዘመረው በዳዊት የአዘማመር ስልት ነው።

በያህዌ ታምኛለሁ
ለእርዳታ ወደ ያህዌ መሄድ በእርሱ እንደ መታመን ይገለጻል። አማራጭ ትርጉም፡ “ለጥበቃ ወደ ያህዌ ሄጃለሁ” (ቀኔን ይመለክቱ)

“እንደ ወፍ ወደ ተራራ ብረሪ” ለምን ትላላችሁ?
ይህ ጥያቄ የተጠቀው ትኩረትን ለመሳብ ነው። እንደ ዓረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ተርጉም፡ “እንዳመልጥ ትጠይቁኛላችሁ!” (መልስ አዘል ጥያቄን ይመልከቱ)

እነሆ፣ ክፉዎች ቀስታቸውን ገትረዋል፣ የቅኑን ሰው ልብ በጨለማ ለመንደፍ ፍላጻቸውን በአውታሩ ላይ ደግነዋል
“ተመልከት! ክፉዎች ቅኖችን ለማጥቃት ተዘጋጅተዋል”

ቅን ልብ
ቅን ልብ የሚወክለው ጻድቅ ወይም እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎችን ነው።

Psalms 11:3

መሰረቱ ከተናደ ጻድቅ ምን ማድረግ ይችላል?
“መሰረት” የሚወክለው ሕግ እና ስርዓትን ነው። መልስ አዘል ጥያቄው የተጠየቀው ትኩረት ለመጨመር ነው። ዓረፍተ ነገር ማናድረግ መተርጎም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡ “ክፉ ሰዎች ሕጉን ባለመታዘዛቸው ምክንያት ሳይቀጡ ሲቀሩ ጻድቃን ምንም ማድረግ አይችሉም።” (መልስ አዘል ጥያቄን ይመልከቱ)

Psalms 11:5

ያህዌ ይፈትናል
“ያህዌ በጥንቃቄ ይመለከታል”

ዐመጻ የሚያደርጉ
“ሌሎችን የሚጎዱ”

እርሱ በክፉዎች ላይ የእሳት ፍምና ዲን ያዘንባል፥ የጽዋቸውም ዕጣ ፈንታ የሚለበልብ ዐውሎ ነፋስ ነው
የእግዚአብሔር ቅጣት እንደሚነድ ፍም እና እንደ እሳተ ጎመራ ዲን ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም፡ “ክፉውን ይቀጣል፥ ምንም እረፍት አይሆንላቸውም።” (ቅኔን ይመልከቱ)

ዲን
ሰልፈር

ፊቱን ያያሉ
“በመገኘቱ ይሆናሉ”

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 12

1 ያህዌ ሆይ፣ ደግ ሰው የለምና አንተው እርዳኝ ከሰው ዘር መካከል አንድ ታማኝ አይገኝም። **2** እያንዳንዱ ሰው ለባልንጀራው ባዶ ቃላት ይናገራል በሸንገላ ከንፈርና በሁለት ልብ ይናገራል። **3** ሸንጋይ ከናፍርቶችንና በትምክህት የሚናገሩ አንደበቶችን ያህዌ ያጥፋ። **4** እነዚህም፣ «በአንደበታችን እንበረታለን የምንናገረውንስ ማን ማስተባበል ይችላል?» የሚሉ ናቸው። **5** «ስለ ድኾች መከራ፣ ስለ ችግረኞች ጩኸት ያህዌ አሁን እነሣለሁ፤ የናፈቁትንም ሰላም እሰጣቸዋለሁ» ይላል። **6** የያህዌ ቃሎች የነጹ ቃሎች ናቸው በእሳት ምድጃ ሰባት ጊዜ እንደ ነጠረ ብር የጠሩ ናቸው። **7** ያህዌ ሆይ፣ አንተ ትጠብቀናለህ ከዚህ ዐመፀኛ ትውልድ ለዘላለም ጻድቃንን ትጠብቃለህ። **8** በሰው ልጆች መካከል ክፋት በገነነበት ጊዜ ዐመፀኞች እንዳሻቸው በየቦታው ይዘራሉ።

Psalms 12:1

አጠቃላይ ሃሳብ፡
በዕብራይስጥ ቅኔ ትይዩነት የተለመደ ነው። (ቅኔ እና ትይዩነትን ይመልከቱ)

ለመዘምራን አለቃ
“ይህ ለመዘምራን አለቃ ለአምልኮ እንዲጠቀምበት ነው”

በሸሚኒት
ይህ የሙዚቃውን ስልት ሊያመለክት ይችላል

የዳዊት መዝሙር
አማራጭ ፍችዎች፡ 1) ዳዊት ዝማሬውን ጽፎታል ወይም 2) ዝማሬው ስለዳዊት ነው ወይም 3) ዝማሬው የተዘመረው በዳዊት የአዘማመር ስልት ነው።

ያህዌ ሆይ ድረስልኝ
“ያህዌ ለችግሬ ድረስልኝ”

ታማኝ ሰው የለም
“ታማኝ ሰዎች ሁሉ ጠፍተዋል”

Psalms 12:2

ያወራሉ ይነጋገራሉ
በተደጋጋሚ ይህ ሃሳብ መጠቀሱ ግነትን ያመለክታል፥ ለብዙ ሰዎችም እውነት መሆኑን ያሳያል። (አጠቃላይነትን እና ግነትን ይመልከቱ)

በሸንገላ ከንፈር እና በሁለት ልብ ይናገራሉ
‘ክንፈር’ ለሰዎች ንግግር ቅያሪ ስያሜ ነው። ‘ሁለት ልብ’ ለሃሰተኝነት ቅኔያዊ ገለጻ ነው። አማራጭ ትርጉም፡ “ሁሉም ሰው በሃሰት እና በአታላይ ከንፈር ይናገራል” ወይም “ሁሉም ሰው በውሸት ሰዎችን እያመሰገነ ይዋሻል።” (ድጋሚ መሰየም እና ቅኔን ይመልከቱ)

ሸንጋዩን ከንፈር እግዚአብሔር ቆርጣል
x

Psalms 12:5

ጩኸት
በህመም ጊዜ በታላቅ ስሜት ሰዎች የሚያሰሙትን ስቃ ያመለክታል።

ያህዌ “እነሳለሁ” ይላል
ያህዌ ሰዎቹን ለመርዳት አንድ ነገር ያደርጋል ማለት ነው።

Psalms 12:6

በምድር ላይ እነደ ተፈተነ ሰባት ጊዜ እነደ ተጣራ ብር
የያህዌ ቃላት ከተጣራ ብር ጋር ተወዳድሯል። አማራጭ ትርጉም፡ “ያለምንም አንከን ናቸው” (አነጻጻሪ ዘይቤን ይመልከቱ)

አንተ ትጠብቃቸዋለህ
“ጻድቃንን ትጠብቃቸዋለህ”

በየአቅጣጫው ይሄዳሉ
“ይዞራሉ”

ዐመጻ በሰዎች ዘንድ ከፍ ከፍ ባለ ጊዜ
በቀጥታ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡ “ሰዎች ሀሉም ቦታ ዐመጻን ከፍ ከፍ ባደረጉ ጊዜ” (ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪን ይመልከቱ)

የሰው ልጆች
“ሰዎች”

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 13

1 ያህዌ ሆይ፣ እስከ መቼ ድረስ ለዘላለሙ ትረሳኛለህ? ፊትህን ከእኔ የምትሰውረውስ እስከመቼ ድረስ ነው? **2** በስጋት የምኖረው ልቤስ ቀኑን ሙሉ የሚያዝነው
እስከ መቼ ነው? ጠላቴ እኔ ላይ የሚያይለው እስከ መቼ ነው? **3** ያህዌ አምላኬ ሆይ፣ ወደ እኔ ተመልከት መልስልኝም! **4** የሞት እንቅልፍ እንዳይወስደኝ
ዐይኖቼን አብራ። ጠላቴ፣ «አሸነፍሁት» እንዳይል ባላጋራዎቼም በውድቀቴ ደስ እንዳይላቸው ርዳኝ። **5** እኔ ግን ወሰን በሌለው ፍቅርህ እተማመናለሁ ልቤም
በማዳንህ ደስ ይለዋል። **6** ቸርነቱ በዝቶልኛልና ለያህዌ እዘምራለሁ።

Psalms 13:1

አጠቃላይ ሃሳብ፡
በዕብራይስጥ ቅኔ ትይዩነት የተለመደ ነው። (ቅኔ እና ትይዩነትን ይመልከቱ)

ለመዘምራን አለቃ
“ይህ ለመዘምራን አለቃ ለአምልኮ እንዲጠቀምበት ነው”

የዳዊት መዝሙር
አማራጭ ፍችዎች፡ 1) ዳዊት ዝማሬውን ጽፎታል ወይም 2) ዝማሬው ስለዳዊት ነው ወይም 3) ዝማሬው የተዘመረው በዳዊት የአዘማመር ስልት ነው።

እስከ መቼ፣ ያህዌ ትረሳኛለህ?
ይህ ጥያቄ የተጠየቀው የአንባብያንን ትኩረት ለመሳብ እና ለመጨመር ነው። እንደ ዓረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡ “ያህዌ፣ ስለ እኔ የረሳህ ይመስላል!” (መልስ አዘል ጥያቄን ይመልከቱ)

ፊትህንም ከእኔ የምትመልሰው እስከ መቼ ድረስ ነው?
“ፊትህ” የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ሁለመና ያመለክታል። መልስ አዝል ጥያቄ የተጠየቀው ትቁረት ለመስጠት ነው። እንደ ዓረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡ “ከእኔ እየተደበክ ይመስላል” (በአንድ ክፍል ሙሉ አካልን መሰየምን እና መልስ አዘል ጥያቄን ይመልከቱ)

ጠላቴስ በእኔ ላይ የሚያይለው እስከ መቼ ድረስ ነው?
መልስ አዝል ጥያቄ የተጠየቀው ትቁረት ለመስጠት ነው። እንደ ዓረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡ “በእርግጥ ጠላቶቼ ሁልጊዜ አያሸንፉኝም” (መልስ አዘል ጥያቄን ይመልከቱ)

Psalms 13:3

ተመልከተኝ ስማኝም
“ትኩረትህን ስጠኝ እና ስማኝ”

ዐይኖቼን አብራ
ይህ ኃይልን የመጠየቅያ መንገድ ነው። አማራጭ ትርጉም፡ “በድጋሚ ኃይለኛ አድርገኝ” (ፈሊጥን ይመለክቱ)

የሞት እንቅልፍ እንዳልተኛ
“የሞት እንቅልፍ” ማለት መሞት ማለት ነው።

ጠላቶቼ እንዳይሉ ... ጠላቶቼ እንዳይሉ
“ጠላቶቼ ስለ እኔ እንዲህ አንዲሉ አትፍቀድላቸው ... ጠላቶቼ በእኔ ላይ እንዳይሉ”

ወደ ታች በወረድሁ ጊዜ
“ስወድቅ” ወይም “ሲያሸንፉኝ”

Psalms 13:5

በቃል ኪዳን ታማኝነትህ እታመናለሁ
“ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ገላጭ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡ “ለቃል ኪዳንህ ታማኝ እንደሆንህ አምናለሁ” ወይም “ለቃል ኪዳንህ ታማኝ ስለሆንህ በአንተ እታመናለሁ” (ረቂቅ ስምን ይመልከቱ)

በማዳንህ ልቤ ደስ ይለዋል
“ልቤ” የሚለው ቃል መላ ሰውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡ “ስላዳንከኝ ደስ ይለኛል” (በአንድ ክፍል ሙሉ አካልን መሰየምን ይመልከቱ)

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 14

1 ሞኝ በልቡ፣ «እግዚአብሔር የለም» ይላል። ብልሹዎች ናቸው፤ አስጸያፊ ተግባርም ይፈጽማሉ። መልካም የሚያደርግ አንድም የለም። **2** የሚያስተውል፣ እርሱንም የሚፈልግ መኖሩን ለማየት ያህዌ ከሰማይ ወደ ምድር ተመለከተ። **3** ሁሉም ከመንገድ ወጥተዋል፤ ሁሉም ብልሹዎች ሆነዋል ከእነርሱ አንድ እንኳ መልካም የሚያደርግ የለም። **4** እነዚያ ዐመፃ የሚያደርጉ ሕዝቤን እንደ እንጀራ የሚበሉ፣ የያህዌን ስም የማይጠሩ ሰዎች ዕውቀት የላቸውምን? **5** እግዚአብሔር በጻድቃን መካከል ይገኛልና እነርሱ በፍርሃት ተርበደበዱ! **6** ምንም እንኳ ያህዌ መጠጊያው ቢሆንም እናንተ ግን ድኻውን ማዋረድ ትፈልጋላችሁ። **7** ያህዌ ሕዝቡን ከምርኮ ሲመለስ ለእስራኤል መዳን ከጽዮን ይመጣል ያኔ ያዕቆብ ደስ ይለዋል እስራኤልም ሐሤት ያደርጋል።

Psalms 14:1

አጠቃላይ ሃሳብ፡
በዕብራይስጥ ቅኔ ትይዩነት የተለመደ ነው። (ቅኔ እና ትይዩነትን ይመልከቱ)

ለመዘምራን አለቃ
“ይህ ለመዘምራን አለቃ ለአምልኮ እንዲጠቀምበት ነው”

የዳዊት መዝሙር
አማራጭ ፍችዎች፡ 1) ዳዊት ዝማሬውን ጽፎታል ወይም 2) ዝማሬው ስለዳዊት ነው ወይም 3) ዝማሬው የተዘመረው በዳዊት የአዘማመር ስልት ነው።

ሞኝ በልቡ እግዚአብሔር የለም ይላል
ይህ ፈሊጥ ለራስ መናገር ወይም ማሰብን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡ “ሞኝ ሰው ለራሱ ይናገራል” (ፈሊጥን ይመለክቱ)

ብልሹዎች ናቸው
“ናቸው” የሚለው የሚያመለክተው እግዚአብሔር የለም የሚሊትን ሞኝ ሰዎችን ነው።

Psalms 14:2

የሰው ልጆች
ይህ ሃረግ ሰዎችን ሁሉ ይወክላል

እርሱን የሚፈልግ
ይህ የሚገልጠው እግዚአብሔርን ለማወቅ የሚፈልጉትን በመንገድ እንደሚከተሉት የሚፈልጉትን ነው። አማራጭ ትርጉም፡ “እርሱን ለማወቅ የሚፈልጉ” (ቅኔን ይመልከቱ)

ሁሉም ከመንገድ ወጥተዋል
እግዚአብሔርን የሚቃወሙ ሰዎችን በትክክለኛ መንገድ መሄድ አቁመው በተሳሳተ አቅጣጫ አንደሚሄዱ የሚገልጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡ “ሁሉም ከያህዌ ዞር ብለዋል” (ቅኔን ይመልከቱ)

Psalms 14:4

የእግዚአብሔርን ስም የማይጠሩት ዕውቀት የላቸውምን?
መልስ አዝል ጥያቄ የተጠየቀው ትቁረት ለመስጠት ነው። እንደ ዓረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡ “ያህዌን የማይጠሩ ምንም እንደማያውቁ ይሆናሉ። የሚያደርጉትን ግን ያውቃሉ” (መልስ አዘል ጥያቄን ይመልከቱ)

ክፋት አድራጊዎች
“ክፉት” የሚለው ረቂቅ ስም “ክፉ አድራጊዎች” በማለት ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡ “ክፉ የሚያደርጉ” (ረቂቅ ስምን ይመልከቱ)

ሕዝቤን እንደ እንጀራ የሚበሉ
የሚያመለክተው ክፉ አድራጊዎችን እና የእግዚአብሔርን ሕዝብ ምግብ እንደሚበሉ የሚያጠፉትን ነው። (ቅኔን ይመልከቱ)

Psalms 14:5

ይደነግጣሉ
ክፉ የሚያደርጉትን ያመለክታል።

እግዚአብሔር በጻድቃን ጉባኤ ይገኛል
እግዚአብሔር ከጻድቃን ጋር ነው ማለት ይረዳቸዋል ማለት ነው። ይህ ሃሳብ በግልጽ ሊቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡ “በጽድቅ የሚኖሩትን እግዚአብሔር ይረዳል” ወይም “ትክክለኛ ነገር የሚያደርጉትን እግዚአብሔር ይረዳል” (ግምታዊ እውቀትን እና ድብቅ ሃሳብ ይመልከቱ)

ትሻለህ
የሚያመለክተው ክፉ ሰዎችን ነው።

ድሃውን ለማዋረድ
“ድሃ የሆነው ሰው ውርደት እንዲሰማው ለማድረግ”

ያህዌ መጠግያው ነው
ያህዌ የሚሰጠውን ጥበቃ ያመለክታል። እንድ ሰው ከማዕበል እንደሚጠለልበት መጠግያ። አማራጭ ትርጉም፡ “ያህዌ እንደሚጠብቀው ጋሻ ነው” (ቅኔን ይመልከቱ)

Psalms 14:7

ምን ነው እስራኤልን መዳን ከጺዮን በመጣ!
ይህ ማጋነን ነው። ጸሐፊው እግዚአብሔር እንዲያደርገው የሚፈልገውን አየገለጸ ነው። አማራጭ ተርጉም፡ “የእስራኤል መዳን ከጺዮን እንዲመጣ እመኛለሁ!” (አጋኖን ይመልከቱ)

ምን ነው እስራኤልን መዳን ከጺዮን በመጣ!
“እስራኤልን መዳን” የሚለው የያህዌ ሌላ ስም ነው። እስራኤልን የሚያድን እርሱ። አማራጭ ትርጉም፡ “ያህዌ ከጺዮን መጥቶ እስራኤልን ያድናል።” ወይም “ያህዌ ከጺዮን መጥቶ የእስራኤልን ህዝብ እንዲያድን አመኛለሁ።” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

ያዕቆብም ደስ ይበለው፥ እስራኤልም ሐሴት ያድርግ
እነዚህ ሁለት ሃረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። “ያዕቆብም” “እስራኤልም” የሚወክሉት የእስራኤልን ሕዝብ ነው። በትርጉም ወቅት ሁለቱን ሃረጎች ማጣመር ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡ “ሁሉም የእስራኤል ሕዝቦች ሐሴት ያድርጉ” (ትይዩነትን እና በአንድ ክፍል ሙሉ አካልን መሰየምን ይመልከቱ)

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 15

1 ያህዌ ሆይ፣ በድንኳንህ ውስጥ የሚያድር ማን ነው? በተቀደሰው ኮረብታህስ የሚኖር ማን ነው? **2** አካሄዱ ንጹሕ የሆነ፣ ጽድቅን የሚያደርግ ከልቡ እውነትን
የሚናገር፤ **3** በአንደበቱ የማይሸነግል ሌሎች ሰዎችን የማይጐዳ፤ በጐረቤቱ ላይ አሉባልታ የማያሰራጭ **4** ነውረኛውን የሚንቅ፣ ያህዌን የሚፈሩትን ግን
የሚያከብር። ዋጋ ቢያስከፍለው እንኳ የገባውን ቃል የሚፈጽም **5** ገንዘቡን በወለድ የማያበድር ንጹሕ ሰው ላይ ለመመስከር ጉቦ የማይበላ፤ እነዚህን የሚያደርግ
ከቶውንም አይናወጥም።

Psalms 15:1

አጠቃላይ ሃሳብ:
በዕብራይስጥ ቅኔ ትይዩነት የተለመደ ነው። (ቅኔ እና ትይዩነትን ይመልከቱ)

የዳዊት መዝሙር
አማራጭ ፍችዎች: 1) ዳዊት ዝማሬውን ጽፎታል ወይም 2) ዝማሬው ስለዳዊት ነው ወይም 3) ዝማሬው የተዘመረው በዳዊት የአዘማመር ስልት ነው።

በተቀደሰው ተራራህ ማን መኖር ይችላል?
የእግዚአብሔር “ተራራ” የሚወክለው በጺዮን ተራራ የነበረውን የእግዚአብሄር መቅደስን ነው። አማራጭ ተርጉም: “በተቀደሰው ስፍራህ ማን ሊኖር ይችላል?” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

ከልቡ እውነትን የሚናገር
“በታማኝነት የሚናገር”

Psalms 15:3

በምላሱ የማይሸነግል
“ምላስ” የሚወክለው ሰውን ነው። የማይሸነግለው ሰው “ጻድቁ ሰው” ነው (መዝሙር 15:02)። አማራጭ ትርጉም: “በንግግሩ አይሸነግልም” ወይም “ስለ መልካም ሰዎች ክፉ አይናገርም” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

ጉዳት
“መጉዳት”

Psalms 15:4

ነውረኛ በፊቱ የተናቀ፥ እግዚአብሔርን የሚፈሩትን ግን የሚያከብር
“ጻድቅ ሰዎች እግዚአብሔርን የሚቃወሙትን ይጠላሉ፥ ነገር ግን እግዚአብሔርን የሚያከብሩትን ያከብራሉ”

የተናቀ
“ክፉ ሰው” ወይም “ያህዌን የሚቃወም ሰው”

“ከቶ አይናወጥም”
“ከቶ አይናወጥም” የሚለው ሃረግ በሰላም ረዥም እድሜ መኖርን ያመለክታል። በሌላ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም: “በሰላይ ይኖራል” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 16

1 በአንተ ተማምኛለሁና ያህዌ ሆይ ጠብቀኝ። **2** ያህዌን፣ «አንተ ጌታዬ ነህ፤ ከአንተ ውጪ መልካም ነገር የለኝም» አልሁት። **3** በምድር የሚኖሩ ቅዱሳን የተከበሩ ናቸው፤ በእነርሱም ደስ ይለኛል። **4** ሌሎች አማልክትን የሚከተሉ መከራቸው ይበዛል እኔ ግን ለአማልክቶቻቸው የደም ቁርባን አላፈስም፤ ስማቸውንም በአፌ አልጠራም። **5** ያህዌ የርስት ድርሻዬና ጽዋዬ ነው፤ ፍጻሜዬም በአንተ እጅ ነው። **6** መለኪያ ገመድ ባማረ ስፍራ ተጥሎልኛል በእርግጥም የተዋበች ርስት አግኝቻለሁ። **7** የሚመክረኝን ያህዌን እባርካለሁ፤ ሌሊት እንኳ ልቦናዬ ያስተምረኛል። **8** ሁልጊዜ እግዚአብሔርን አስቀድማለሁ፤ እርሱ በቀኜ ስለሆነ አልናወጥም! **9** ስለዚህ ልቤን ደስ አለው፤ ክብሬም ሐሤት አደረገ። በእርግጥ ያለ ስጋት እኖራለሁ። **10** ምክንያቱም አንተ ነፍሴን በሲኦል አትተዋትም ታማኝህ መበስበስ እንዲደርስበት አታደርግም። **11** የሕይወትን መንገድ ታሳየኛለህ በአንተ ዘንድ የደስታ ሙላት፣ በቀኝህም የዘላለም ፍስሐ አለ።

Psalms 16:1

አጠቃላይ ሃሳብ:
በዕብራይስጥ ቅኔ ትይዩነት የተለመደ ነው። (ቅኔ እና ትይዩነትን ይመልከቱ)

የዳዊት ቅኔ
ቅኔ በሚለው ፋንታ ያለው የዕብራይስጡ ቃል ትርጉም በእርግጠኝነት አይታወቅም። በምትኩ “መዝሙር” ወይም “ቅኔ” የሚለውን ቃል መጠቀም ይቻላል። እንዲህ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል: “ይህ መዝሙር ዳዊት የጻፈው ነው”

መጠጊያዬ ነህ
ለመሸሸግ ወደ ያህዌ መሄድ እርሱን መጠግያ እንደ ማድረግ ይገለጻል። አማራጭ ትርጉም: “ለመሸሸግ ወደ አንተ እመጣለሁ” (ቅኔን ይመልከቱ)

በምድር ያሉ ቅዱሳን ሁሉ
“ቅዱሳን” የሚወክለው በእርሱ የሚታመኑትን የእግዚአብሔር ሕዝብን ነው። አማራጭ ትርጉም: “በዚህ ምድር የሚኖሩ ሕዝብህ” (ግምታዊ እውቀትን እና ድብቅ ሃሳብ ይመልከቱ)

Psalms 16:4

ሌሎች አማልክት የሚከተሉ ሀዘናቸው ይበዛል
በቀጥተኛ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም: “ሌሎች አማልክት የሚያመለኩ ሰዎች ሀዘን እበዛ ይሄዳል” (ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪን ይመልከቱ)

ደም ለአማልክቶቻቸው ያፈሳሉ
“ደም እንደ ቁርባን ለአማልክቶቻቸው ያቀርባሉ”

ስማቸውን በአፌ አልጠራም
ስማቸውን መጥራት የሚያመለክተው እነርሱን ማወደስ ነው። “በአፌ” ሰው የሚናገርውን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም: “በቃላቴ አላወድሳቸውም” ወይም “አማልክቶቻቸውን አላወድስም” (የተጋነነ ቅኔ እና ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

Psalms 16:5

የርስቴ ድርሻዬ
ዳዊት ስለ ያህዌ እንደ ተሰጠው የመሪት ድርሻ ይናገራል። (ቀኔን ይመልከቱ)

ጽዋዬ
ዳዊት ስለ ያህዌ ብዙ በረከትን እንደያዘ ጽዋ ይገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም: “የሚባርከኝ” (ቀኔን ይመልከቱ)

ዕጣዬ በእጅህ ናት
“የወደፊቴን የምትወስን አንተ ነህ” ወይም “በእኔ የሚሆነውን ትቆጣጠራለህ”

ገመድ ባማረ ስፍራ
ገመድ መጣል መሪትን ለመለካት እና ለሰው ለመስጠት ሌላ ስያሜ ነው። ዳዊት ከእግዚአብሔር በተለዩ ታላላቅ መንገዶች ስላገኘው በረከት ቅኔያዊ መግለጫ ነው። በቀጥታ ሊገለጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም: “በመልካም ስፍራ መሪት ወስነህልኛል” ወይም “በመልካም ስፍራ መሪት ሰተኸኛል” ወይም “በመልካም ስፍራ መሪት እንደሚሰጥ ባርከኸኛል” (ድጋሚ መሰየም፥ ቅኔ፥ ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪን ይመልከቱ)

ገመድ
ገመድ በዚያን ጊዜ መሪትን ለመለካት አና ድንበር ለመከለል ይጠቀሙበት ነበር።

በርግጥም የተዋበች ርስት አግኝቻለሁ
ዳዊት የያህዌን በረከት እንደተቀበለው ርስት አድርጎ ይገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም: “በሰጠኝ ነገር ሁሉ ደስተኛ ነኝ” (ቀኔን ይመልከቱ)

Psalms 16:7

ያህዌ ሁልጊዜ በፊቴ ነው
“ያህዌ ከእኔ ጋር እንዳለ ሁል ጊዜ አስታውሳለሁ”

እርሱ በቀኜ ስላለ አልናወጥም
በቀጥተኛ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም: “ከአጠገቡ ምንም ሊወስደኝ የሚችል ነገር የለም” (ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪን ይመልከቱ)

Psalms 16:9

አጠቃላይ ሃሳብ
ዳዊት ስለ እግዚአብሔር መናገር ይቀጥላል

ልቤ ሐሴት ያደርጋል
“ልብ” የሚወክለው የተናጋሪውን ሀሳብ እና ስሜትን ነው። አማራጭ ትርጉም: “ስለዚህ ደስተኛ ነኝ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

ክብሬ ይደሰታል
አማራጭ ፍቺዎች 1) “ክብር” የሚለው ቃል የሚወክለው አንድ ሰው የሚሰማውን ክብር። አማራጭ ትርጉም: “በእግዚአብሔር በመደሰቴ ክብር ይሰማኛል” ወይም 2) “ክብር” ለሚለው ቃል የተጠቀመው የዕብራይስጥ ቃል “ጉበት” ማለት ነው፥ ይህም የሰውን ስሜት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም: “ደስተኛ ነኝ”

Psalms 16:11

የደስታ ሙላት
“ታላቅ ደስታ” ወይም “እጅግ ብዙ የሆነ ደስታ”

በአንተ ዘንደ ደስታ
ጸሐፊው “ደስታን” እንደ ግለሰብ ይገልጻታል። (ሰውኛ ዘይቤ ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በቀኝህ
“በቀኝህ” የሚለው ቃል የሚወክለው በእግዚአብሔር ዘንድ የተለየ ስፍራን
ነው። አማራጭ ትርጉም፡ “በቅርብህ ስሆን” (ፈሊጥን ይመልከቱ)

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 17

1 ያህዌ ሆይ፣ ትክክለኛ ፍርድ ለማግኘት የማቀርበውን ጸሎት ስማ ጩኸቴንም አድምጥ። ከሐሰተኛ ከንፈር ያልወጣውን ጸሎቴን አድምጥ። 2 ጽድቄ ከአንተ
ዘንድ ይምጣ፤ ዐይኖችህም ፍትሕን ይመልከቱ። 3 ልቤን ብትመረምር፣ በሌሊትም ብትጐበኘኝ፣ ብትፈትነኝም ከእኔ ዘንድ ክፋት አታገኝም፤ አንደበቴም
አይስትም። 4 የሰው ልጆችን ተግባር በተመለከተ አንተ በተናገርኸው ቃል መሠረት ከዐመፀኞች መንገድ ራሴን ጠብቄአለሁ። 5 አረማመዱ በመንገድህ
ጸንቶአል እግሮቼም አልተንሸራተቱም። 6 ያህዌ ሆይ፣ ስለምትመልስልኝ ወደ አንተ እጣራለሁ፤ ጆሮህን ወደ እኔ አዘንብል፤ ጸሎቴንም ስማ። 7 የሚተማመኑብህን
በቀኝህ ከጠላቶቻቸው የምታድናቸው አንተ ታማኝነትህን ድንቅ አድርገህ ግለጠው። 8 እንደ ዐይንህ ብሌን ጠብቀኝ፤ በክንፎችህ ጥላ ሥር ሰውረኝ። 9
ከሚያስጨንቁኝ፣ ከከበቡኝም አደገኛ ጠላቶቼ ጋርደኝ። 10 እነርሱ ማንንም አይምሩም፤ አንደበታቸው ትዕቢትን ይናገራል። 11 ጠላቶቼ አስጨነቁኝ፤ ከበባም
አደረጉብኝ መሬት ላይ ሊዘርሩኝም አፈጠጡብኝ። 12 እነርሱ ለንጥቂያ እንደሚጓጓ፣ አድፍጦም እንደሚጠብቅ ደቦል አንበሳ ናቸው። 13 ያህዌ ሆይ፣ ተነሣና
አጥቃቸው፤ በአፍጢማቸው ድፋቸው! በሰይፍህ ከክፉዎች አድነኝ። 14 ያህዌ ሆይ፣ እንዲህ ካሉ ሰዎች፣ ብልጽግናቸው በዚህ ሕይወት ብቻ ከሆነ ከዚህ ዓለም
ሰዎች በቀኝህ አድነኝ። የአንተ የሆነ ሰዎችን ሆድ በመልካም ነገር ትሞላለህ እነርሱም ብዙ ልጆች ይኖሩዋቸዋል፤ ሀብታቸውንም ለልጆቻቸው ያወርሳሉ። 15 እኔ
ግን በጽድቅ ፊትህን አያለሁ ስነቃም ክብርህን ዐይቼ እረካለሁ።

Psalms 17:1

አጠቃላይ ሃሳብ፡
በዕብራይስጥ ቅኔ ትይዩነት የተለመደ ነው። (ቅኔ እና ትይዩነትን ይመልከቱ)

የዳዊት ጸሎት
“ይህ ዳዊት የጻፈው ጸሎት ነው”

ከአታላይ ከንፈር ያልወጣውን ጸሎቴን አድምጥ
“ጆሮ ስጥ” ስማ ለሚለው ቅኔ ነው። “ከአታላይ ከንፈር ያልወጣ” ከማይዋሽ ሰው ለሚለው ወካይ ነው። አማራጭ ትርጉም፡ “ያለሸንገላ የሆነ ጸሎቴን አድምጥ” (ቅኔን እና በአንድ ክፍል ሙሉ አካልን መሰየምን ይመልከቱ)

ጽድቄ ከአንተ ዘንድ ይምጣ
ጽድቅ ከእግዚአብሔር ዘንድ መምጣት የሚያመለክተው እግዚአብሔር ፈርዶ አንድን ሰው ጻድቅ ሲለው ነው። የእግዚአብሔር መገኘት ለእግዚአብሔር ለራሱ ገላጭ ነው። አማራጭ ተርጉም፡ “ጽድቄ ከአንተ ዘንድ ይምጣ” ወይመ “ንጹህ እንደሆነሁ ተናገር” (ቅኔ እና ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

ዐይኖችህም ፍትህን ይዩ
ዐይኖችህ የሚወክለው እራሱ እግዚአብሔርን ነው። “ይዩ” የሚለው ሃሳብ ትኩረትን መስጠት እና አንድ ነገር ለማድረግ መወሰን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡ “አባክህ ትክክል የሆነውን ተመልከት” ወይም “ትክክል የሆነው አድርግ” (ቅኔን እና በአንድ ክፍል ሙሉ አካልን መሰየምን ይመልከቱ)

Psalms 17:3

ልቤን መረመርኸው በሌሊት ጠጋ ብለህ ፈትነኸኝ
“ልቤን መረመርኸው” ማለት ሀሳቤን እና ስሜቴን መርምር ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡ “ሀሳቤን በሌሊት ብትመረምር” (ፈሊጥን ይመልክቱ)

አንደበቴ እላፊ አይሄድም
እዚህ ጋር አንደበት በራሱ መንቀሳቀስ እንደሚችል ነው የተገለጸው። የሚወክለውም ሰው የሚናገረውን ቃላት ነው። አማራጭ ትርጉም፡ “ውሸትን አልናገርም ወይም በቃላቴ ኃጢአትን አልሰራም” (ሰውኛ ዘይቤ እና በአንድ ክፍል ሙሉ አካልን መሰየምን ይመልከቱ)

Psalms 17:4

በከንፈርህ ቃል ከዐመጸኞች መንገድ ራሴን ጠብቄአለሁ
“በከንፈርህ ቃል” የሚለው ሃረግ ለእግዚአብሔር ትዕዛዝ ሌላ ስያሜ ነው። “የዐመጸኞች መንገድ” ዐመጸኞች የሚያደርጉትን የሚያመለክት ቅኔ ነው። አማራጭ ትርጉም፡ “ትዕዛዛትህን በመታዘዝ እራሴን ዐመጸኞች የሚያደርጉትን ከማድረግ ጠበቅሁ” ወይም “ትዕዛዛትህ ክፉ ነገር ማድረግን እንዳሶግድ አድርገውኛል” (ድጋሚ መሰየምን እና ቅኔን ይመልከቱ)

አረማመዴ በመንገድህ ጸንቶአል፥ እግሮቼም ኣልተንሸራተቱም
ሁለቱም ሃረጎች ተመሳሳይ ትርጓሜ አላቸው። መደገማቸው ትኩረትን ይጨምራል። (ትይዩነትን ይመልከቱ)

Psalms 17:6

ስለምታደምጠኝ አንተን እጣራለሁ
እነዚህ ሃረጎች ተመሳሳይ ትርጓሜ አላቸው። “ስለምታደምተኝ” የሚለው ሃሳብ የእግዚአብሔርን ጸሎተ ለመስማት እና ለመመለስ ፈቃደኝነት ይገልጻት። አማራጭ ትርጉም፡ “ስናገር ትሰማለህ፤ ትኩረትን ትሰጠኛለህ” (ትይዩነትን እና ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

የቃል ኪዳን ታማኝነትህን በአስደናቂ ሁኔታ ግለጽ
“ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ገላጭ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡ “በአስደናቂ መንገድ ለቃልኪዳንህ ታማኝ መሆንህን ግለጥ።”(ረቂቅ ስምን ይመልከቱ)

ቀኝህ
ቀኝ እጅ የእግዚአብሔርን ኃይል ታመለክታለች። አማራጭ ትርጉም፡ “ኃይልህ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

መተገኛ
ለጥበቃ ወደ ያህዌ መሄድ በእርሱ እንደ መጠለል ይገለጻል። አማራጭ ትርጉም፡ “ለመከለል ወደ አንተ መምጣት” (ቅኔን ይመልከቱ)

Psalms 17:8

እንደ ዐይንህ ብሌን ጠብቀኝ
“የዐይን ብሌን” የከበረን ነገር ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡ “ውድ እና የከበረን ነገር እንደምትጠብቅ ትጠብቀኛለህ” (አነጻጻሪ ዘይቤ ይመልከቱ)

በክንፎችህ ጥላ ሰውረኝ
ዳዊት ስለ እግዚአብሔር ጥበቃ ሲናገር ወፍ ጫጩቶቿን በክንፎቿ ስር እንደምትጋርድ ነው። አማራጭ ትርጉም፡ “እናት ወፍ ጫጩቶቿን በክንፏ ስር እንደምትጋርድ ጠብቀኝ።” (ቅኔን ይመልከቱ)

በአፋቸው ትዕቢትን ይናገራሉ
“በአፋቸው” የሚለው ቃል የሚወክለው የጠላቶችን ንግግር ነው። አማራጭ ትርጉም፡ “በትዕቢት ይናገራሉ” ወይም “ሁልጊዜ ይታበያሉ” (በአንድ ክፍል ሙሉ አካልን መሰየምን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 17:11

ከበቡኝ
“ከበቡኝ” የሚለው ቃል ዳዊት ጠላቶቹ እንዴት በሁሉም ስፍራ ሊይዙት እንደተከታተሉት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡ “ጠላቶቼ ከበውኛል” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

እነርሱ ለንጥቂያ እንደሚጓጓ አንበሳ በስውርም እነደሚያደባ ደቦል አንበሳ ናቸው
ሁለቱም ሃረጎች ተመሳሳይ ትርጓሜ አላቸው። መደገማቸው ትኩረትን ይጨምራል። (ትይዩነትን ይመልከቱ)

አንበሳ ... ደቦል
ጸሐፊው አንበሳ የሚበላውን እነደሚያሳድድ እየተሰደደ አንደሆነ ተሰምቶታል። (አነጻጻሪ ዘይቤ ይመልከቱ)

Psalms 17:13

ያህዌ በሰይፍም ከክፉዎች ታደገኝ ... እንዲህ ካሉት ሰዎች በክንድህ አድነኝ
ሁለቱም ሃረጎች ተመሳሳይ ትርጓሜ አላቸው። መደገማቸው ትኩረትን ይጨምራል። (ትይዩነትን ይመልከቱ)

በሰይፍህ ... በክንድህ
“ሰይፍ” የሚለው ቃል እና “ክንድ” የሚለው ቃል የያህዌን ኃይል ያመለክታሉ። (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

የመዝገቦችህን ሆዳቸውን ሙላ
የጥንቱ ጽሑፍ ለመረዳት አስቸጋሪ ነው። አማራጭ ፍቺዎች 1) “መዝገብ” ለፍቅር ቅኔያዊ መግለጫ ነው፥ ስለዚህ “መዝገብ” በእግዚአብሔር የተወደዱትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡ “የምትወዳቸውን ሰዎች ሆድ በፍቅርህ ተሞላለህ” ወይም 2) “የመዝገቦችህ” የሚያመለክተው እግዚአብሔር ለዚህ ዓለም ህዝብ የሚሰጠውን መዝገብ ነው፥ አማራጭ ትርጉም፡ “ሆዳቸውን በሀብት መዝገብ ትሞላለህ” (ቅኔን ይመልከቱ)

የመዝገቦችህን ሆዳቸውን ሙላ
“የመዝገቦችህን ሆዳቸውን ሙላ” የሚያመለክተው ብዙ ውድ ነገሮቸን መስጠትን ነው። አማራች ፍቺዎች 1) “ለምትወዳቸው ሰዎች ብዙ ሀብትን ትሰጣቸዋለህ” ወይም 2)”ለዚህ ዓለም ሰዎች ብዙ ሀብትን ትሰጣቸዋለህ” (ቅኔን ይመልከቱ)

Psalms 17:15

እኔ ግን በጽድቅ ፊትህን አያለሁ
“ፊት” የሚወክለው የያህዌን ሁለመና ነው። ዳዊት ያህዌን እንደሚያይ እርግጠኛ ነው። አማራጭ ትርጉም፡ “በትክክለኛ መንገድ ስለምሄድ፥ አንድ ቀን ፊትህን አያለሁ” (በአንድ ክፍል ሙሉ አካልን መሰየምን ይመልከቱ)

ስነቃም ክብርህን አይቼ እረካለሁ
ዳዊት ከሞተ በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚሆን እርግጠኛ ነው። ይህ ሃሳብ በትርጉም ውስጥ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡ “ከሞትኩ በኋላ በመገኘትህ ውስጥ በመንቃት ደስ ይለኛል” (ግምታዊ እውቀትን እና ድብቅ ሃሳብ ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 18

1 ጉልበት የሆንኸኝ ያህዌ እወድሃለሁ። **2** ያህዌ ዐለቴ፣ መጠጊያዬና ታዳጊዬ ነው። እርሱ አምላኬ የምሸሸግበት ዐለቴ፣ ጋሻዬ፣ የድነቴ ቀንድና ዐምባዬ ነው። **3** ምስጋና የሚገባውን ያህዌን እጠራለሁ፤ ከጠላቶቼም እድናለሁ። **4** የሞት ገመድ አነቀኝ፤ የጥፋት ጐርፍም አጥለቀለቀኝ። **5** የሲኦል ማሰሪያ ተጠመጠመብኝ የሞት ወጥመድም ተጠመደብኝ። **6** በጨነቀኝ ጊዜ ያህዌን ጠራሁት፤ እንዲረዳኝም ወደ አምላኬ ጮኽሁ፤ ከመቅደሱ ድምፄን ሰማ፤ ጩኸቴም ከፊቱ ደረሰ፤ ወደ ጆሮውም ገባ። **7** ምድር ተንቀጠቀጠች ተናወጠችም፤ የተራሮችም መሠረት ተናጋ፤ ጌታ እግዚአብሔር ተቆጥቶአልና ተንቀጠቀጡ። **8** ከአፍንጫው ጢስ፣ ከአፉም የሚባላ እሳት ወጣ፤ የፍም ነበልባል ከእርሱ ፈለቀ። **9** ሰማያትን ከፍቶ ወረደ፤ ከእግሮቹም በታች ድቅድቅ ጨለማ ነበረ። **10** በኪሩቤል ላይ ተቀምጦ በረረ፤ በነፋስም ክንፍ መጠቀ። **11** ጨለማን እንደ ድንኳን፣ ዝናብ አዘል ጥቁር ደመናን በዙሪያው አደረገ። **12** በፊቱ ካለው መብረቅ የተነሣ የበረዶ ድንጋይና የእሳት ፍም ወጣ። **13** ያህዌ ከሰማያት አንጐደጐደ! የልዑልም ድምፅ አስተጋባ። **14** ቀስቱን አስፈንጥሮ ጠላቶቹን በተናቸው፤ መብረቅ አዥጐድጉዶ አሳደዳቸው። **15** ያህዌ ሆይ፣ ከቁጣህ የተነሣ፣ ከአፍንጫህም እስትንፋስ የተነሣ፣ የባሕር ወለል ታዬ የዓለምም መሠረት ተገለጠ። **16** ከላይ እጁን ዘርግቶ ያዘኝ፤ ከጥልቅ ውሃም ስቦ አወጣኝ። **17** ከኃያላን ጠላቶቼ፣ ከሚጠሉኝ ከዐቅሜ በላይ ከሆኑ ባላንጣዎቼ ታደገኝ። **18** በመከራዬ ቀን መጡብኝ፤ ያህዌ ግን ድጋፍ ሆነኝ። **19** በጣም ሰፊ ወደ ሆነ ቦታ አወጣኝ፤ ወዶኛልና አዳነኝ። **20** ያህዌ እንደ ጽድቄ ከፍሎኛል፤ እጆቼ ንጹሕ ስለ ነበሩ ታድጐኛል። **21** የያህዌን መንገድ ጠብቄአለሁና፤ በዐመፅ ተነሣሥቼ ከእርሱ ዘወር አላልሁም። **22** ሕጐቹ ሁሉ በፊቴ ናቸው፤ ሥርዐቱንም ከፊቴ አላራቅሁም። **23** በእርሱ ፊት ንጹሕ ነበርሁ፤ ከኃጢአትም ራሴን ጠብቄአለሁ። **24** ያህዌ እንደ ጽድቄ መጠን፤ በዐይኖቹ ፊት ንጹሕ እንደ ነበሩት እጆቼ መጠን ከፍሎኛል። **25** አንተ ታማኝ ለሆኑት ታማኝ ነህ እውነተኞች ለሆኑት እውነተኛ ነህ **26** ለንጹሖች ንጹሕ ነህ። ለጠማሞች ግን ጠማማ ትሆንባቸዋለህ። **27** አንተ ትሑታንን ታድናለህ ትዕቢተኛውን ዐይን ግን ታዋርዳለህ። **28** አንተ መብራቴን ታበራለህ፤ አምላኬ ያህዌ ጨለማዬን ብርሃን ታደርገዋለህ። **29** በአንተ ጉልበት በሰራዊት እረማመዳለሁ፤ በአምላኬም ኃይል ቅጥሩን እዘላለሁ። **30** የእግዚአብሔር መንገድ ፍጹም ነው፤ የያህዌ ቃል የነጠረ ነው። መጠጊያ ለሚያደርጉት ሁሉ እርሱ ጋሻ ነው። **31** ከእግዚአብሔር በቀር ማን አምላክ አለ? ከአምላካችንስ በቀር ዐምባ ማን ነው? **32** ኀይልን የሚያስታጥቀኝ፣ መንገዴንም የሚያቃና እግዚአብሔር ነው። **33** እርሱ እግሮቼን እንደ ብሖር እግሮች ያጠነክራል፣ በከፍታዎችም ላይ ያቆመኛል። **34** እጆቼን ለጦርነት ያሠለጥናቸዋል የናስ ቀስቶች መሳብ እንዲችሉ ክንዶቼን ያበረታል። **35** የማዳን ጋሻህን ሰጠኸኝ፤ ቀኝ እጅህ ደግፎኛል፤ ሞገስህም ታላቅ አድርጐኛል። **36** እግሮቼ እንዳይንሸራተቱ ከበታቼ ያለውን ቦታ አሰፋህልኝ። **37** ጠላቶቼን አሳድጄ እይዛቸዋለሁ፤ እስኪጠፉ ድረስ ወደ ኋላ አልልም። **38** እንዳያንሰራሩ አድርጌ አደቀቅኋቸው ከእግሬም ሥር ወደቁ። **39** አንተ ለጦርነት ኀይልን አስታጠቅኸኝ፤ በእኔ ላይ የተነሡትንም ከበታቼ አደረግህልኝ። **40** ጠላቴቼ ወደ ኋላ እንዲሸሹ አደረግህ የሚጠሉኝንም አጠፋኋቸው። **41** ለእርዳታ ጮኹ፤ ግን ማንም አላዳናቸውም ወደ ያህዌ ጮኹ፤ እርሱ ግን አልመለሰላቸውም። **42** ነፋስ ጠርጐ እንደሚወስደው ትቢያ አደቀቅኋቸው መንገድ ላይ እንዳለ ጭቃ ረጋገጥኋቸው። **43** ከሕዝብ ክርክር ታደገኸኝ፤ መንግሥታት ላይ መሪ አደረግኸኝ፤ የማላውቀውም ሕዝብ ያገለግለኛል። **44** ዝናዬን እንደ ሰሙ ታዘዙልኝ፤ ባዕዳንም በፊቴ ራሳቸውን ዝቅ አደረጉ። **45** ባዕዳን በፍርሃት ተዋጡ እየተንቀጠቀጡም ከምሸጋቸው ወጥተው መጡ። **46** ያህዌ ሕያው ነው፤ ዐለት የሆነልኝ ይባረክ የድነቴ አምላክ ከፍ ከፍ ይበል። **47** እርሱ ጠላቶቼን ይበቀልልኛል፤ ሕዝቦችን ከእግሬ ሥር የሚያስገዛልኝም እርሱ ነው። **48** ከጠላቶቼም የሚታደገኝ እርሱ ነው! በእርግጥም አንተ ከተነሡብኝ በላይ ከፍ አደረግኸኝ! ከጨካኞችም አዳንኸኝ። **49** ያህዌ ሆይ፣ ስለዚህ ለአንተ ውዳሴ እሰጣለሁ በሕዝቦች መካከል አመሰግንሃለሁ፤ ለስምህም እዘምራለሁ። **50** እግዚአብሔር ለንጉሡ ታላቅ ድል ይሰጠዋል ለቀባው ለዳዊትና ለዘሮቹም ለዘላለም ታማኝነቱን ይገልጣል።

Psalms 18:1

አጠቃላይ መረጃ
ተጓዳኝ ሐሳቦች በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመዱ ናቸው።

ለመዘምራን አለቃ
‹‹ይህ የመዘምራን መሪው በአምልኮ ጊዜ የሚጠቀምበት ነው››

የዳዊት መዝሙር
እንዲህም ማለት፤ 1) መዝሙሩን የጻፈ ዳዊት ነው፤ ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው፤ ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት ነው ማለት ሊሆን ይችላል።

ለያህዌ እንዲህ ሲል የዘመረው ነው
‹‹ይህን መዝሙር ለያህዌ ዘመረ››

ያህዌ በታደገው ቀን
‹‹ያህዌ ከታደገው በኋላ››

ከሳዖል እጅ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› የሳዖልን ኀይል ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከሳዖል ኀይል››

Psalms 18:2

ያህዌ ዐለቴ ነው
ዳዊት ያህዌ ዐለት እንደሆነ ይናገራል። ‹‹ዐለት›› የምቹ ቦታ ምሳሌ ነው።

ዐለቴ መሸሸጊያዬ
እዚህ ላይ ‹‹ዐለት›› እና፣ ‹‹መሸሸጊያ›› ተመሳሳይ ነገሮች ቢሆኑም፣ ያህዌ ከጠላት ማምለጫ ቦታ እንደሚያዘጋጅ አጽንዖት ይሰጣል።

የምሸሸግበት
መከላከያ ለማግኘት ወደ ያህዌ መሄድ በእርሱ ውስጥ መሸሸግ ማለት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንድከለል ወደ እርሱ እሄዳለሁ››

ጋሻዬ፣ የድነቴ ቀንድና ዐምባዬ ነው
ያህዌ፣ ‹‹ጋሻው›› የድነቱ፣ ‹‹ቀንድ›› እና፣ ‹‹ዐምባው›› እንደሆነ ዳዊት ይናገራል። ከጉዳት የሚጠብቀው ያህዌ ነው። እዚህ ላይ አጽንዖት ለመስጠት ተመሳሳይ ሐሳቦች በሦስት የተለያዩ መንገዶች ቀርበዋል።

ከጠላቶቼ እድናለሁ
‹‹ከጠላቶቼ አመልጣለሁ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 18:4

የሞት ገመድ ከበበኝ
ዳዊት ሞት በገመድ ከያዘ በኃላ የሚያስር ሰው እንደሆነ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ልገደል ነበር››

የጥፋት ጐርፍ አጥለቀለቀኝ
ዳዊት ጐርፍ እንደሚወስደው ሰው ዐቅም አጥቶ እንደ ነበር ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ፍጹም ዐቅመ ቢስነት ተሰማኝ››

የሲኦል ገመድ ከበበኝ፤ የሞት ወጥመድ ያዘኝ››
እዚህ ላይ የሙታን ቦታ የሆነው፣ ‹‹ሲኦል›› እና፣ ‹‹ሞት›› እንደ ሰው እንደ ከበቡትና እንዳጠመዱት ተነግሯል። ሁለቱም ቃሎች ተመሳሳይ ነገር ቢሆኑም፣ የተደገሙት አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በወጥመድ እንደ ተያዝሁ ተሰማኝ፤ ልሞት ነው በማለት አሰብሁ››

Psalms 18:6

በጨነቀኝ ጊዜ
‹‹በቸገረኝ ጊዜ›› ወይም፣ ‹‹ተስፋ ስቆርጥ››

የርዳታ ጥሪዬ ወደ ፊቱ ሄደ
እዚህ ላይ ዳዊት፣ ‹‹የርዳታ ጥሪው›› ሰው ይመስል ወደ ያህዌ ፊት እንደ ሄደ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወደ እርሱ ጸለይሁ››

ወደ ጆሮው ገባ
ዳዊት የርዳታውን ጩኸት ያህዌ እንደ ሰማው ይናገራል። ሐሳቡ የተደገመው አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ልመናዬን ሰማ››

Psalms 18:7

ያህዌ ስለ ተቆጣ... ምድር ተናወጠ
የእግዚአብሔር ቁጣ ከባድ የመሬት መናወጥ እንዳመጣ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔር በጣም ስለ ተቆጣ... ምድር ተናወጠ››

ምድር ተንቀጠቀጠ ተናወጠም
‹‹መንቀጥቀጥ›› እና፣ ‹‹መናወጥ›› በመሠረቱ ተመሳሳይ ቢሆኑም፣ አጽንዖት የተሰጠው ምድር በኀይል እንደ ተንቀጠቀጠ ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምድር ወደ ፊት ወደ ኃላ ተንቀሳቀሰ›› ወይም፣ ‹‹ምድር ወደ ላይ ወደ ታች ተንቀሳቀሰ›› ወይም፣ ‹‹ከባድ የምድር መናወጥ ሆነ››

የተራሮች መሠረትም ተንቀጠቀጠ፤ ተናወጠ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የተራሮች መሠረትም ተንቀጠቀጠ ተናወጠ››

ከአፍንጫው ጢስ ወጣ... ፍም ከእርሱ ወጣ
ዳዊት ያህዌ እሳት እየተነፈሰ እንደሆነ ይናገራል። ይህም እግዚአብሔር ምን ያህል እንደ ተቆጣ ያሳያል።

ከአፉ የሚባላ እሳት ወጣ፤ ከእርሱም እሳት ነደደ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሚባላ እሳት ከአፉ ወጣ፤ ከዚያም እሳት ነደደ››

Psalms 18:9

ከፈተ
እርሱ የሚያመለክተው ያህዌን ነው።

ከእግሮቹም በታች ድቅድቅ ጨለማ ነበረ
ምንም እንኳ እግሮች ባይኖሩትም፣ ዘማሪው የሰው ባሕርይ ሰጥቶታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከበታቹ ድቅድቅ ጨለማ ነበረ››

የነፋስ ክንፎች
እዚህ ላይ ዘማሪው ነፋስ እንደ መልአክ ዐይነት ክንፎች እንዳሉት ይናገራል

Psalms 18:11

ጨለማን ሠራ... የእርሱ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እርሱ›› እና፣ ‹‹የእርሱ›› ያህዌን ያመለክታል።

ጨለማን ድንኳን አደረገ
ጨለማ እንደ ድንኳን እንደሆነ ተነግሮአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጨለማን መሸፈና አደረገ›› ወይም፣ ‹‹ጨለማን መደበቂያ ቦታ አደረገ››

ጥቁር ደመና
‹‹ዝናብ የከበደው ደመና›› ወይም፣ ‹‹ጥቅጥቅ፣ ጥቁር ጨለማ››

የበረዶ ድንጋይ
ከበረዶ የተሠራ ድንጋይ

Psalms 18:13

ያህዌ በሰማያት አንጐዳጐደ
የያህዌ ድምፅ እንደ መብረቅ ተሰማ

ልዑል
‹‹ልዑል›› የተባለው ያህዌ ነው።

ፍላጻውን አስፈንጥሮ ጠላቶቹን በተናቸው... መብረቅ አዥጐድጉዶ አሳደዳቸው
ሁለቱም ዐረፍተ ነገር ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው።

ፍላጻውን አስፈንጥሮ ጠላቶቹን በተናቸው
እዚህ ላይ መብረቅ እንደ ፍላጻ ተነግሮአል።

በተናቸው
‹‹በተለያየ አቅጣጫ አባረራቸው››

Psalms 18:15

አጠቃላይ መረጃ
ጸሐፊው ስለ ያህዌ ታላቅ ኀይል መናገር ቀጥሏል።

ከዚያም የባሕር ወለል ተገለጠ፤ የዓለምም መሠረት ራቁቱን ቀረ
ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከዚያም የባሕሩ ታችኛው ክፍል ተገለጠ፤ አንተም የዓለምን መሠረት እርቃኑን አስቀረህ።››

ከአፍንጫው ታላቅ እስትንፋስ የተነሣ
እዚህ በተነገረው መሠረት እግዚአብሔር ሰብዓዊ ባሕርያት ባይኖሩትም፣ ይህ ታላቅ ኀይሉን ያመለክታል። ነፋስ ከእግዚአብሔር ትንፋሽ የሚወጣ ታላቅ እስትንፋስ እንደሆነ ተነግሯል።

Psalms 18:16

እጁን ወደ ታች ሰደደ... እኔን ያዘኝ... ጐትቶ አወጣኝ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እርሱ›› የሚያመለክተው ያህዌን ነው።

የሚናወጥ ውሃ
እዚህ ላይ ዘማሪው ጠላቶቹ እንደ ግዙፍና ኀይለኛ ውሃ እንደሆኑ ይናገራል፤ ያህዌ ያዳነው ከዚያ ውስጥ ነበር።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 18:18

መጡብኝ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እነርሱ›› የሚያመለክተው ቁጥር 17 ላይ የተጠቀሱትን ጠላቶቹን ነው።

በመከራዬ ቀን መጡብኝ፤ ያህዌ ግን ድጋፍ ሆነልኝ
‹‹መከራ›› የሚለውን የነገር ስም ቅጽል ማድረግ ይቻላል፤ ‹‹ድጋፍ›› የሚለውን ስም ‹‹ከለላ›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ብርቱዎቹ ጠላቶቼ ጭንቀት ውስጥ ባለሁበት ቀን መጡብኝ፤ ያህዌ ግን ከለላ ሆነኝ››

Psalms 18:20

እጆቼ ንጹሕ ነበሩ
የእጅ ንጽሕና የሚያመለክተው በደል አለማድረግን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በደል አልነበረብኝም›› ወይም፣ ‹‹ያደረግሁት ትክክል ነበር››

የያህዌን መንገዶች ጠብቄአለሁ
የያህዌ ሕጐች ሰው ሊመላለስባቸው የሚገባ መንገዶች እንደሆኑ ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለያህዌ ሕጐች ታዝዣለሁ››

በዐመፅ ከያህዌ አልራቅሁም
እዚህ ላይ ዐመፅ ትክክለኛውን መንገድ በመተው ትክክል ባልሆነው መንገድ መሄድ ማለት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከአምላኬ በመራቅ ዐላመፅሁም››

Psalms 18:22

ጻድቅ ሕጐች ሁሉ... ከእነርሱ አልራቅሁም
ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። ጸሐፊው የደጋገማቸው አጽንዖት ለመስጠት ነው።

በፊቴ ነበሩ
‹‹መርተውኛል›› ወይም፣ ‹‹አስታውሻለሁ››

ነቀፋ አልነበረብኝም... ራሴን ከኀጢአት ጠብቄአለሁ
ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ትርጒም አላቸው። ጸሐፊው የደጋገማቸው አጽንዖት ለመስጠት ነው።

በፊቱ ነቀፋ አልነበረብኝም
‹‹በእርሱ ዘንድ ንጹሕ››

ራሴን ከኀጢአት ጠብቄአለሁ
‹‹ኀጢአት አላደረግሁም››

እጆቼ ንጹሕ ነበሩ
‹‹ንጹሕ እጆች›› ምንም በደል አለማድረግ ማለት ነው። መዝሙር 18፥20 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በደል አልነበረብኝም›› ወይም፣ ‹‹ሥራዬ ትክክል ነበር››

በዐይኖቹ ፊት
ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር መገኘት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በፊቱ›› ወይም፣ ‹‹በእርሱ ዘንድ››

Psalms 18:25

አጠቃላይ መረጃ
ጸሐፊው ለያህዌ ይናገራል

ታማኝ ለሆነ ሁሉ
‹‹ታማኝ›› መሆን እግዚአብሔር ያዘዘውን ማድረግ ማለት ነው። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በታማኝነት ትእዛዞችህን የሚጠብቁ›› ወይም፣ ‹‹በታማኝነት ኪዳንህን ለሚያደርጉ››

ከንጹሑ ጋር... አንተም ንጹሕ ትሆናለህ
ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ትርጒም አላቸው። ጸሐፊው የደጋገማቸው አጽንዖት ለመስጠት ነው።

ለጠማማው ጠማማ ትሆንበታለህ
‹‹ቅን›› ላልሆነው አንተም አትሆንለትም››

Psalms 18:27

አወረድሃቸው
‹‹ዝቅ አደረግሃቸው››

የትዕቢተኛውን፣ የንቀት ዐይን
ፈሊጣዊው አነጋገር ትዕቢተኛ ሰውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የታበዬ››

ለመብራቴ ብርሃን ሰጠኸኝ፤ ያህዌ አምላኬ ጨለማዬን ያበራል
ጸሐፊው የያህዌ መገኘት ብርሃን እንደሆነ ይናገራል። እነዚህ አነጋገሮች ተመሳሳይ ትርጒም አላቸው።

በአንተ ቅጥሩን እዘላለሁ
‹‹በአንተ ርዳታ እንቅፋትን እሻገራለሁ››

Psalms 18:30

ለሚጠጉት ሁሉ ጋሻ ነው
ጋሻ ወታደሩን ይከልላል። ዳዊት ያህዌ የሚከልለው ጋሻ እንደሆነ ይናገራል። መዝሙር 3፥3 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ ሆይ፣ ወደ አንተ የሚጠጉትን እንደ ጋሻ ትከልላቸዋለህ››

ከያህዌ በቀር አምላክ ማነው? ከአምላካችን በቀር ዐለት ማን ነው?
የሚጠበቀው መልስ ማንም የለም የሚል ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ ብቻ አምላክ ነው፤ አምላካችን ብቻ ዐለት ነው››

ዐለት
ያህዌ ከጠላቶቹ ለማምለጥ የሚወጣበት ዐለት እንደ ሆነ ዳዊት ይናገራል። መዝሙር 18፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

ኀይልን አስታጠቅኸኝ
እግዚአብሔር ለዳዊት ትጥቅ የሚሆነው ኀይል ሰጠው

ቀናውን ሰው በመንገዱ አደረገ
እዚህ ላይ ዳዊት በትክክለኛው መንገድ በመሄድ ያህዌን ደስ ሚያሰኝ ሕይወት እየኖረ እንደሆነ ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ቀናውን ሰው የጽድቅ ሕይወት እንዲኖር አደረገ››

Psalms 18:33

እግሮቼን አፈጠነ
ይህ የሚያመለክተው በፍጥነት መሮጥን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በፍጥነት እንድሮጥ አደረገ››

እንደ ብሖር ከፍታ ላይ አደረገኝ
ብሖር ፈጣን ነው፤ ተራሮችም ላይ ጸንቶ ይቆማል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እጆቼን ያሠለጥናል
‹‹እጆቼ›› ሰውየውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያሠለጥነኛል››

ክንዶቼን
ይህ ሰውየውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እኔን››

Psalms 18:35

የድነት ጋሻ
እዚህ ላይ ጸሐፊው የእግዚአብሔር ጥበቃ እንደ ጋሻ እንደሆነ ይናገራል። ‹‹ድነት›› የሚለውን፣ ‹‹መዳን›› በማለት መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጥበቃህ አዳነኝ››

ቀኝ እጅህ ደገፈኝ
የእግዚአብሔር ቀኝ እጅ ኀይሉን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ኀይልህ ደገፈኝ›› ወይም፣ ‹‹አንተ በኀይልህ ደገፍኸኝ››

ሞገስህ ታላቅ አደረገኝ
እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ሞገስ እንደ እርሱ ሞገስ ያደረገውን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እንደ ሞገስህ ታላቅ አደረግኸኝ›› ወይም፣ ‹‹በቸርነትህ ታላቅ አደረግኸኝ››

ከእግሮቼ በታች ያለውን ቦታ አሰፋህልኝ
እግዚአብሔር ያደረገለት ጥበቃ የሚቆምበት ሰፊ ቦታ እንደ መስጠት መሆኑን ጸሐፊው ይናገራል። እዚህ ላይ፣ ‹‹እግሮቼ›› ሰውየውን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለእኔ ደህና ቦታ››

እግሮቼ አልተንሸራተቱም
‹‹እግሮቼ›› ሰውየውን ይወክላል። እግዚአብሔር ያደረገለት ጥበቃ ተንሸራትቶ እንዳይወድቅ ደህና ቦታ መቆም ማለት እንደሆነ ጸሐፊው ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አልተንሸራተትሁም›› ወይም፣ ‹‹በደንብ ቆሜአለሁ››

Psalms 18:37

አደቀቅኃቸው
‹‹ፈጨኃቸው›› ወይም፣ ‹‹ሰባበርኋቸው››

መነሣት አይችሉም
‹‹መቆም አይችሉም››

በእግሮቼ ሥር ወደቁ
አነጋገሩ ዘማሪው ጠላቶቹን አሸነፈ ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሁሉንም አሸነፍኋቸው››

ኀይልን አስታጠቅኸኝ
ዘማሪው እርሱን ለመደገፍ ወገቡ ላይ እንደሚታጠቀው ቀበቶ ያህዌ ኀይል እንደ ሰጠው ይናገራል።

ከእግሬ ሥር አደረግህልኝ
እዚህ ላይ ዘማሪ የጠላቶቹ መሸነፍ እነርሱ ላይ መቆም ማለት እንደሆነ ይናገራል፤ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አንተ አሸነፍህልኝ››

በእኔ ላይ የተነሡትን
ይህ የሚያመለክተው ዘማሪውን የሚቃወሙትን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጠላቶቼን››

Psalms 18:40

የጠላቶቼን ማጅራት ሰጠኸኝ
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ለዳዊት ጠላቶቹ ላይ ድል እንደ ሰጠው ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በጠላቶቼ ላይ ድል ሰጠኸኝ››

የጠላቶቼን ማጅራት ሰጠኸኝ
ይህም የሚያመለክተው እግዚአብሔር ለዳዊት ጠላቶቹ ላይ ድል እንደ ሰጠው ነው። 1) ዳዊት የጠላቶቹን ራስ ከአንገታቸው መቁረጥ ይችላል፣ ወይም 2) ዳዊት እግሩን ጠላቶቹ ላይ ማድረግ ይችላል፤ ወይም 3) ዳዊት ከእርሱ ሲሸሹ የጠላቶቹን ጀርባ ማየት ይችላል።

የሚጠሉንን አጠፋኃቸው
‹‹የሚጠሉንን አሸነፍሁ›› ወይም፣ ‹‹የሚጠሉኝን ፈጽሞ ደመሰስሁ››

እርሱ ግን አልመለሰላቸውም
ይህ ማለት ያህዌ አልረዳቸውም ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እርሱ ግን አልረዳቸውም››

ነፋስ ፊት እንዳለ ትቢያ አደቀቅኃቸው
ምን ያህል እንደ ተሸነፉ ለማሳየት የዘማሪው ጠላቶች ከትቢያ ጋር ተመሳስለዋል።

እንደ መንገድ ላይ ጭቃ ረገጥኃቸው
ምን ያህል እንደ ተሸነፉ ለማሳየት የዘማሪው ጠላቶች በመንገድ ላይ ጭቃ ተመስለዋል።

Psalms 18:43

ፀብ
አለመግባባት፤ ግጭት

በሕዝቦች ላይ ራስ አደረገኝ
‹‹ራሱ›› የሚወክለው መሪን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የብዙ ሕዝብ መሪ አደረግኸኝ››

ባዕዳን በፊቴ ዝቅ አሉ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እግዚአብሔር ባዕዳን በፊቴ ዝቅ እንዲሉ አደረገ››

የሌላ አገር ሰዎች እየተንቀጠቀጡ መጡ
‹‹መንቀጥቀጥ›› የሚያመለክተው መፍራታቸውን ነው። ትርጒሙ ውስጥ ይህን ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሌላ አገር ሰዎች ፍርሃታቸውን ለማሳየት እየተንቀጠቀጡ መጡ››

Psalms 18:46

ዐለቴ ይመስገን
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እርሱ ዐለቴ ነው፤ መመስገን ይገባዋል›› ወይም፣ ‹‹ሕዝቦች ዐለቴን ያመስግኑት››

ዐለቴ
እዚህ ላይ ጸሐፊው ጠላቶቹ እንዳያገኙት ያህዌ መከላከያ ዐለት እንደሆነለት ይናገራል። መዝሙር 18፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

የድነቴ አምላክ ከፍ ይበል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰዎች የድነቴን አምላክ ከፍ ያድርጉት››

የድነቴ አምላክ
‹‹ድነት›› የሚለው ስም፣ ‹‹መዳን›› ወይም፣ ‹‹መታደግ›› ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የታደገኝ አምላክ››

የሚበቀልልኝ አምላክ
‹‹የሚበቀልልኝ›› ማለት ሰዎችን በክፉ ሥራቸው የሚቀጣ ማለት ነው። ‹‹በቀል›› የሚለውን ቃል ማውጣት ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እኔ ላይ ባደረጉት ክፉ ሥራ ሰዎችን የሚቀጣ አምላክ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 18:48

ነጻ ወጣሁ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እግዚአብሔር ነጻ አደረገኝ››

ወደ ላይ ከፍ አደረግኸኝ
x

Psalms 18:50

ድል ለንጉሡ
ዳዊት፣ ‹‹ለንጉሡ›› የሚለው ራሱን ነው።

እርሱ ለቀባው የኪዳኑን ታማኝነት ያሳየዋል... ለዘሩም ለዘላለም
‹‹በኪዳኑ ባገባው ቃል መሠረት በታማኝነት ወደደኝ፤ ዘሮቼንም ለዘላለም ወደደ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 19

1 ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፤ የሰማይ ጠፈርም የእጁን ሥራ ያውጃል። **2** አንዱ ቀን ለሌላው ቀን ቃል ይናገራል፤ አንዱም ሌሊት ለሌላው ሌሊት ዕውቀትን ይገልጣል። **3** ንግግር የለም፤ ቃልም የለም፤ ድምፃቸውም አልተሰማም። **4** ያም ሆኖ ቃላቸው ወደ ምድር ሁሉ ወጣ፣ ንግግራቸውም ወደ ዓለም ዳርቻ ወጣ። በመካከላቸውም ለፀሐይ ድንኳኑን ተከለ **5** ፀሐይ ከእልፍኙ እንደሚወጣ ሙሽራ ይወጣል ወደ ግቡም እንደሚሮጥ ብርቱ ሰው ደስ ይለዋል። **6** ፀሐይ ከአንዱ አድማስ ሰማይን አቋርጦ ወደ ሌላው አድማስ ይወጣል፤ ከሙቀቱም የሚሰወር የለም። **7** የያህዌ ሕግ ፍጹም ነው፤ ነፍስን መልሶ ያለመልማል፤ የያህዌ ምስክር የታመነ ነው፤ ዐላዋቂውን ጥበበኛ ያደርጋል። **8** የያህዌ ሕግ ትክክል ነው፤ ልብን ደስ ያሰኛል። የያህዌ ትእዛዝ ንጹሕ ነው፤ ዐይንንም ያበራል። **9** ያህዌን መፍራት ንጹሕ ነው፤ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል። የያህዌ ፍርድ የታመነ ነው፤ ሁለንተናውም ጽድቅ ነው። **10** ከወርቅ ይልቅ የከበረ፤ እጅግ ከጠራ ወርቅም የበለጠ ነው። ከማር ይልቅ ይጣፍጣል፤ ከማር ወለላም ይበልጥ ይጥማል። **11** እንዲሁም አገልጋይህ በእርሱ ይመከራል፤ ሕግህን በመጠበቁም ወሮታ አለው። **12** ስሕተቱን ሁሉ ማን ማስተዋል ይችላል? ከተሰወረ ኃጢአት አንጻኝ። **13** ባርያህን ከድፍረት ኃጢአት ጠብቅ ያኔ ፍጹም እሆናለሁ ከታላቅ በደልም እነጻለሁ። **14** ዐለቴና አዳኜ ያህዌ ሆይ፣ የአፌ ቃልና የልቤም ሐሳብ በፊትህ ያማረ ይሁን።

Psalms 19:1

አጠቃላይ መረጃ
ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው።

ለመዘምራን አለቃ
‹‹ይህ በአምልኮ የመዘምራን መሪ የሚጠቀምበት ነው››

የዳዊት መዝሙር
ይህም ማለት፣ 1) መዝሙሩን የጻፈው ዳዊት ነው ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው፤ ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት መሠረት ነው።

ሰማያት ይናገራሉ
ሰማያት እንደ ሰው እንደሆኑ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰማያት ያሳያሉ›› ወይም፣ ‹‹ሰማያት ያውጃሉ››

የሰማያትም ጠፈር የእጁን ሥራ ያሳውቃሉ
ሰማያት አስተማሪ እንደሆኑ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰማያት የእግዚአብሔርን እጅ ሥራ ያስታውቁናል››

የእጁ ሥራ
‹‹ፍጥረቱ›› ወይም፣ ‹‹እርሱ የሠራው ዓለም››

ድምፃቸው ወጣ
የፍጥረት ውበት ፍጥረት የሚናገር ሰው እንደሆነ ያመለክታል። እነዚሁ ቃሎች በየቦታው ከሚፈስስ ውሃ ጋር ተመሳስለዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ፍጥረት ለሁሉም እንደሚናገር ሰው ነው››

ንግግር የለም፤ ቃል የለም፤ ድምፃቸውም አልተሰማም
እነዚህ ሐረጎች የመጀመሪያዎቹ ሁለት ቁጥሮች ምሳሌያዊ አነጋገር መሆናቸውን በግልጽ ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ድምፅ ወይም ቃል የለም፤ በጆሮው ድምፅ የሰማ ሰው የለም››

ድምፃቸው አልተሰማም
ሌሎች ትርጉሞች፣ ‹‹ድምፃቸው ባልተሰማበት›› ይላሉ፤ ይህም የፍጥረት፣ ‹‹ድምፅ›› በየቦታው እንደሚሰማ አጽንዖት ይሰጣል።

Psalms 19:4

አጠቃላይ መረጃ
ዳዊት ፍጥረት የእግዚአብሔርን ክብር እንደሚያሳይ ያመለክታል።

ቃላቸው... ድምፃናቸው
ይህ የሚያመለክተው ‹‹በቃላት›› የማይነገረውን የእግዚአብሔርን ክብር የሚያሳየውን ፍጥረት ነው።

ቃላቸው ወጣ
ቃላቸው መልእክት ይዞ እንደ ወጣ ሰው መሆኑ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ፍጥረት የሚናገረው ቃል ይዞ እንደ ወጣ ሰው ነው››

ንግግራቸው እስከ ዓለም ዳርቻ
ይህ ትርጉም ውስጥ ቃሎች መግባት እንዳለበት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ንግግራቸው እስከ ዓለም ዳርቻ ወጣ››

ለፀሐይ ድንኳን ተከለ
ያህዌ ለፀሐይ ያዘጋጀለት ስፍራ እንደ ድንኳን መሆኑን ጸሐፊው ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለፀሐይ ስፍራ አዘጋጀ››

በመካከላቸው
‹‹እነርሱ›› የሚያመለክተው ምናልባት ሰማያትን ነው።

ፀሐይ ከእልፍኙ እንደሚወጣ ሙሽራ ነው።
የፀሐይ መውጣት እንደ ሙሽራ እንደሆነ ጸሐፊው ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ፀሐይ ደስ እያለው ወደ ሙሽራዪቱ እንደሚሄድ ሙሽራ ነው››

ወደ ግቡ እንደሚሮጥ ብርቱ ሰው ደስ ይለዋል
ብርታትና ድምቀቱን ለማሳየት ጸሐፊው ፀሐይን ከሯጭ ጋር ያመሳስለዋል።

ብርቱ ሰው
‹‹ፈጣን ሯጭ››

አድማስ
ምድርና ሰማይ የሚገናኙበት መስመር

ወደ ሌላው
ወደ ‹‹ሌላው›› የሚያመለክተው ሌላውን አድማስ ነው። ትርጉሙ ውስጥ ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወደ ሌላው አድማስ››

ከሙቀቱ የሚያመልጥ የለም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሙቀቱ ለሁሉም ይደርሳል››

Psalms 19:7

ነፍስ... ልብ... ዐይኖች
ሦስቱም የሚያመለክቱት መላውን ሰው ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰው››

አላዋቂ
‹‹ልምድ የሌለው›› ወይም፣ ‹‹ያልተማረ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ትክክል
‹‹እውነት›› ወይም፣ ‹‹ተገቢ››

ብሩህ
‹‹ማስተዋል የሚሰጥ››

Psalms 19:9

የታመነ
‹‹ፍጹም ትክክል››

ከወርቅ ይልቅ ዋጋው የከበረ... ከማር ይልቅ የጣፈጠ
የያህዌ ሕግ የሚገዛና የሚቀመስ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከገዛኸው ከወርቅ ይበልጣል... ከቀመስኸው ከማር ይበልጥ ይጣፍጣል››

ከጠራ ወርቅ እንኳ ይበልጣል
‹‹ዋጋው›› የሚለው ቃል ካለፈው ሐረግ ውስጠ ታዋቂ ነው፤ መደገምም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከብዙ የጠራ ወርቅ ዋጋው ይበልጣል››

የጠራ ወርቅ
‹‹ንጹሕ ወርቅ›› ወይም፣ ‹‹ውድ ወርቅ››

Psalms 19:11

አዎን
ይህ ቃል ከተነገረው በላይ እውነት መሆኑን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የበለጠ››

በእነርሱ ባርያህ ጥንቃቄ ያደርጋል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ባርያህን ያስጠነቅቁታል›› ወይም፣ ‹‹ለባርያህ ማስጠንቀቂያ ናቸው››

ለእነርሱ... በመታዘዝ
‹‹በእነርሱ›› የሚለው የያህዌን ቅዱስ ትእዛዞች ያመለክታል።

ባርያህ ይጠነቀቃል
አክብሮቱን ለማሳየት ዳዊት ለእግዚአብሔር ሲናገር ራሱን ባርያ በማለት ይጠራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እጠነቀቃለሁ››

ስሕተቱን ማን ሊያስተውል ይችላሉ?
በጥያቄ ያቀረበው አጽንዖት ለመስጠት ነው፤ ጠንከር ተደርጐ በዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የራሱን ስሕተት ማስተዋል የሚችል የለም››

ከተሰወረ በደል
‹‹ካደረግሁት ስውር በደል››

Psalms 19:13

ባርያህን ጠብቀው
ፈሊጣዊው አነጋገር ባርያው ማድረግ ከማይፈልገው ኀጢአት መራቅ እንደሚፈልግ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ባርያህን ከማድረግ ጠብቀው›› ወይም፣ ‹‹እንዳላደርግ ርዳኝ››

ባርያህ
አክብሮቱን ለማሳየት ለእግዚአብሔር ሲናገር ዳዊት ራሱን ባርያ በማለት ይጠራል። መዝሙር 19፥11 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

አይግዙኝ
ኀጢአት ሰውን የሚገዛ ንጉሥ እንደ ሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኀጢአቶቼ እንደ ንጉሥ አይግዙኝ››

ከብዙ መተላለፍ አንጻኝ
‹‹አንተ ላይ እንዳላምፅ አድነኝ›› ወይም፣ ‹‹ብዙ ኀጢአት ከማድረግ››

የአፌ ቃልና የልቤ ሐሳብ
እነዚህ ቃሎች በአንድነት ሲወሰዱ አንድ ሰው የሚናገረውና የሚያስበው ሁሉ ማለት ናቸው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የምናገረውና የማስበው ሁሉ››

በፊትህ የተወደደ ይሁን
‹‹በፊትህ ተቀባይነት ያለው›› ወይም ‹‹ደስ የሚያሰኝህ››

በፊትህ
ፊት ፍርድና ሚዛንን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በአንተ ፍርድ››

ያህዌ ዐለቴ
ጸሐፊው ያህዌ ከጠላቶቹ የሚሸሸግበት ዐለት እንደሆነ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ፣ አንተ ለእኔ እንደ ዐለት ነህ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 20

1 በመከራ ቀን ያህዌ ይስማህ የያዕቆብም አምላክ ይጠብቅህ። **2** ከመቅደሱ ረድኤት ይላክልህ ከጽዮንም ደግፎ ይያዝህ **3** መባህን ሁሉ ያስብልህ የሚቃጠል መሥዋዕትህን ይቀበልልህ። **4** የልብህን መሻት ይስጥህ ዕቅድህንም ሁሉ ያሳካልህ። **5** በአንተ ደስ ይለናል በአምላካችንም ስም ዐርማችን ከፍ ከፍ እናደርጋለን። ያህዌ የለመንኸውን ሁሉ ይፈጽምልህ። **6** ያህዌ የቀባውን እንደሚያድን አሁን ዐወቅሁ፤ ማዳን በሚችለው ቀኝ እጁ ከተቀደሰው ሰማይ ይመልስለታል። **7** አንዳንዶች በሰረገላ ሌሎች በፈረስ ይታመናሉ እኛ ግን የያህዌን ስም እንጠራለን። **8** እነርሱ ተሰነካክለው ወደቁ እኛ ግን ተነሣን፤ ቀጥ ብለንም ቆምን! **9** ያህዌ ሆይ፣ ንጉሡን አድን ስንጠራህ እኛንም ሰማን።

Psalms 20:1

አጠቃላይ መረጃ
ይህ መዝሙር የሚጀምረው ሰዎች ለእስራኤል ንጉሥ እየተናገሩ ነው።

አጠቃላይ መረጃ
ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው።

ለመዘምራን አለቃ
‹‹ይህ በአምልኮ ጊዜ ለመዘምራን መሪ የሚሆን ነው››

የዳዊት መዝሙር
ይህም ማለት 1) መዝሙሩን የጻፈ ዳዊት ነው፤ ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው፤ ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት ነው።

ይረዳሃል
እዚህ ላይ፣ ‹‹አንተን›› የሚለው ንጉሡን ነው።

በመከራ ቀን
‹‹በችግር ቀን›› ወይም፣ ‹‹ችግር ሲገጥምህ››

የያዕቆብ አምላክ ስም ይጠብቅህ
ይህም ማለት፣ 1) እዚህ ላይ፣ ‹‹ስም›› የያህዌን ኀይል ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የያዕቆብ አምላክ ኀይል ይጠብቅህ›› ወይም፣ ‹‹የያዕቆብ አምላክ በኃይሉ ይጠብቅህ›› ወይም 2) እዚህ ላይ፣ ‹‹ስም›› እግዚአብሔርን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የያዕቆብ አምላክ ይጠብቅህ››

ከመቅደሱ ረድኤት ይላክልህ
እግዚአብሔር በመቅደሱ ሆኖ መርዳቱ ርዳታ መላክ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ ከመቅደሱ ረድኤት ይላክልህ››

መቅደሱ... ጽዮን
ሁለቱም ቃሎች የሚያመለክቱት በኢየሩሳሌም ያለውን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነው።

Psalms 20:3

ያስብህ
‹‹ያስብህ›› የተባለው እግዚአብሔር ስለሚረሳ አይደለም። ያስታውስህ ወይም ያስብልህ ለማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እርሱ ያስታውስህ››

እርሱ
ይህ ቃል የሚያመለክተው ያህዌን ነው።

ሴላ
ይህ ቃል እንዴት እንደሚዘምሩ ወይም የሙዚቃ መሣሪያቸውን እንደሚጫወቱ ለሕዝብ የሚናገር የሙዚቃ አገላለጽ ነው። አንዳንድ ትርጕሞች የዕብራይስጡን ቃል ይጽፋሉ፤ አንዳንድ ትርጕሞች ያንን አያደርጉም። መዝሙር 3፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

ይስጥህ
‹‹ይለግሥህ››

የልብህን መሻት
‹‹ልብ›› የሰውን ሁለንተና ይወክላል። ‹‹መሻት›› የሚለውን ስም ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የምትሻውን›› ወይም፣ ‹‹የምትፈልገውን››

ዕቅድህን ሁሉ ያሳካልህ
‹‹ዕቅድ›› የሚለውን የነገር ስም ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያቀድኸውን ሁሉ ለማሳካት ይርዳህ››

Psalms 20:5

በአንተ ድል ደስ ይለናል
‹‹እኛ›› የሚለው ሕዝቡን ነው። በንጉሡ ድል ደስ ይላቸዋል።

በአምላካችን ስም
እዚህ ላይ፣ ‹‹ስም›› ክብርንና ዝናን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ለአምላካችን ክብር›› ወይም፣ ‹ለአምላካችን ዝና››

ዐርማ እናነሣለን
‹‹የድል ባንዲራ እናነሣለን›› እንዲህ የሚያደርጉት በጠላቶቻቸው ላይ ድል ስለሰጣቸው እግዚአብሔርን ለማመስገን ነው።

ልመናህን ሁሉ ይፈጽምልህ
‹‹የለመንኸውን ሁሉ ይስጥህ››

እነሆ
ቃሉ እዚህ ጥቅም ላይ የዋለው መዝሙሩ ቆም የሚልበትን ቦታ ለማመልከት ነው። ንግግሩ ከሕዝቡ ወደ ንጉሡ እንዲሸጋገር።

አውቃለሁ
‹‹እኔ›› የሚለው ምናልባት በዚህ ክፍል እየተናገረ ያለውን ንጉሡን ያመለክት ይሆናል።

የቀባውን... ይመልስለታል... ይታደገዋል
ንጉሡ በሦስተኛ ሰው ደረጃ ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በመጀመሪያ ሰው ደረጃ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የቀባውን እኔን... ይመልስልኛል... ይታደገኛል››

ከሰማይ መቅደሱ
በኢየሩሳሌም እንዳለው ቤተ መቅደስ ሁሉ፣ እግዚአብሔር በሰማይም ይኖራል (መዝሙር 20፥2 ይመ.)።

በቀኝ እጁ ብርታት ይታደገዋል
የእግዚአብሔር ቀኝ እጅ ኀይሉን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በታላቅ ብርታቱ ይታደገዋል››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 20:7

አንዳንዶች በሰረገላ ሌሎች በፈረስ ይታመናሉ
‹‹ሰረገላ›› እና፣ ‹‹ፈረስ›› የንጉሡን ሰራዊት ይወክላሉ።

ሌሎች በፈረሶች
‹‹ይታመናሉ›› ውስጠ ታዋቂ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሌሎች በፈረስ ይታመናሉ››

እንጠራለን... እንነሣለን
‹‹እኛ›› የሚያመለክተው ጸሐፊውንና አንባቢዎቹን ነው።

እነርሱ ተሰነካክለው ወደቁ
‹‹እነርሱ›› የሚያመለክተው በሰረገሎችና በፈረሶች የሚተማመኑትን ሰዎች ነው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔር ያሰነካክላቸዋል፤ ይጥላቸዋል››

ተሰነካክለው ወደቁ
ሁለቱም ግሦች ተመሳሳይ ናቸው። ሁለቱም የሚያመለክቱት በጦርነት መሸነፍን ነው።

እኛ ተነሣን ጸንተንም ቆምን
‹‹እኛ ተነሥተን ቀጥ ብለን እንቆማለን›› ሁለቱን ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው። ሁለቱም የሚያመለክቱት በጦርነት ድል ማድረግን ነው።

Psalms 20:9

ያህዌ ንጉሡን ያድነዋል
ይህም ማለት፣ 1) ንጉሡን እንዲጠብቀው ሕዝቡ እግዚአብሔርን እየለመኑ ነው። ወይም 2) ንጉሡ በሦስተኛ ሰው ደረጃ ስለ ራሱ መናገር ቀጥሏል።

ንጉሡ፣ እኛም ስንጠራህ ስማን
አንዳንድ ትርጉሞች ዕብራይስጡን በተለየ ሁኔታ ይተረጉሙታል። አንዳንዶች ሕዝቡ ለንጉሣቸው ለያህዌ እየተናገሩ እንደሆነ ተርጉመውታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ንጉሥ፣ ስንጠራህ ሰማን››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 21

1 ያህዌ ሆይ፣ ንጉሥ በኃይልህ ደስ ይለዋል! በምትሰጠውም ድል እጅግ ሐሤት ያደርጋል። **2** የልቡን መሻት ሰጠኸው፤ የለመንህንም አልከለከልኸውም። ሴላ **3** ብዙ በረከት ሰጠኸው፤ በራሱ ላይ የንጹሕ ወርቅ ዘውድ አደረግህለት። **4** ሕይወትን ለመነህ አንተም ረጅም ዘመንን ለዘላለም ሰጠኸው **5** ከሰጠኸው ድል የተነሣ ክብሩ እጅግ በዛ ክብርንና ሞገስንም አጐናጸፍኸው። **6** ዘላለማዊ በረከት ሰጠኸው በፊትህ ባለው ፍስሐም ደስ አሰኘኸው። **7** ንጉሡ በያህዌ ተማምኖአልና ከልዑል ታማኝነት የተነሣ ከቶውንም አይናወጥም። **8** እጅህ ጠላቶችህን ትይዛቸዋለች ቀኝ እጅህም የሚጠሉህን ሁሉ ታገኛቸዋለች። **9** በቁጣህ ቀን እሳት በሚንቀለቀልበት ምድጃ ታቃጥላቸዋለህ፤ ያህዌ በመዓቱ ይፈጃቸዋል፤ እሳትም ይበላቸዋል። **10** ትውልዳቸውን ከምድር ላይ ታጠፋለህ ዘራቸውንም ከሰዎች መካከል ለይተህ ትደመስሳለህ። **11** በአንተ ላይ ክፋት ቢያስቡም፣ ሤራ ቢያውጠነጥኑም፣ አይሳካላቸውም። **12** በመጡበት ትመልሳቸዋለህና ቀስትህንም በእነርሱ ላይ ታነጣጥራለህ። **13** ያህዌ ሆይ፣ በብርታትህ ከፍ ከፍ በል እኛም ኃይልህን እንዘምራለን፤ እንወድሳለንም።

Psalms 21:1

አጠቃላይ መረጃ
ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው።

ለመዘምራን አለቃ
‹‹ይህ በአምልኮ እንዲጠቀምበት ለመዝሙር መሪው ነው››

የዳዊት መዝሙር
ይህም ማለት፣ 1) መዝሙሩን የጻፈው ዳዊት ነው፤ ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው፤ ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት ነው።

ያህዌ ሆይ፣ በኀይልህ
ይህ ጠላቶቹን እንዲያሸንፍ ያህዌ ለንጉሡ የሰጠው ኀይል መሆኑ ግልጽ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ ሆይ፣ ጠላቶቹን እንዲያሸንፍ አንተ ኀይል ስለ ሰጠኸው››

ምንኛ ደስ አለው
‹‹በጣም ደስ አለው››

በምትሰጠው መዳን
እግዚአብሔር ንጉሡን ከጠላቶቹ እንዳዳነው ግልጽ ነው። ‹‹መዳን›› የሚለውን የነገር ስም ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከጠላቶቹ ስላዳንኸው››

ልቡ ደስ ይለዋል
‹‹የልቡ መሻት›› እዚህ ላይ ‹‹ልብ›› የሰውን ሁለንተና ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የልቡ መሻት›› ወይም፣ ‹‹እርሱ የተመኘው››

አልከለከልኽውም
‹‹እንቢ አላልኸውም›› ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰጠኸው››

የከንፈሮቹን ልመና
‹‹ከንፈሮች›› የሰውን ሁለንተና ይወክላሉ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የለመነህን›› ወይም፣ ‹‹የጠየቀህን››

ሴላ
ይህ እንዴት እንደሚዘምሩ ወይም የሙዚቃ መሣሪያ እንደሚጫወቱ ለማሳሰብ የተሰጠ የሙዚቃ አገላለጽ ነው። አንዳንድ ትርጒሞች የዕብራይስጡን ቃል ጽፈዋል። ሌሎች ግን ያንን አላደረጉም። መዝሙር 3፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

Psalms 21:3

ብዙ በረከት አመጣህለት
‹‹በረከት›› የሚለውን የነገር ስም፣ ‹‹በበረከት›› ወይም፣ ‹‹መልካም ነገር›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በብዛት ባረክኸው›› ወይም፣ ‹‹ብዙ መልካም ነገር ሰጠኸው››

ራሱ ላይ የንጹሕ ወርቅ ዘውድ ደፋህለት
አንድ ሰው ራስ ላይ ዘውድ መድፋት፣ እርሱን ንጉሥ ማድረግ ማለት ነው።

የንጹሕ ወርቅ ዘውድ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ንጹሕ ወርቅ›› ለንጉሡ የተሰጠውን ታላቅ ክብር ይወክላል።

ሕይወትን ለመነህ አንተም ሰጠኸው
‹‹ሕይወት›› የሚለውን ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ረጅም ዘመን እንዲኖር ለመነህ አንተም ያንኑ አደረግህለት››

ከዘላለም እስከ ዘላለም ረጅም ዘመን
ይህም ማለት፣ 1) በጣም ረጅም ዘመን፤ ወይም 2) የዘላለም ሕይወት፤ ወይም 3) ረጅም የትውልድ ሐረግ ማለት ሊሆን ይችላል።

Psalms 21:5

ክብሩ
‹‹የንጉሡ ክብር›› ወይም፣ ‹‹የንጉሡ ዝና››

ክብርና ሞገስን አጐናጸፍኸው
‹‹እርሱ ላይ ክብርና ሞገስ አደረግህ።›› ንጉሡን ሀብታምና ኀያል ማድረግ፣ እርሱ ላይ ክብርና ሞገስ ማድረግ ማለት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሀብታምና ኀያል አደረግኸው››

ሰጠኸው
‹‹ፈቀድህለት›› ወይም፣ ‹‹ልትሰጠው ፈቀድህ››

ዘላቂ በረከት
‹‹የማይጠፉ በረከት›› ወይም፣ ‹‹ሁሌም የሚኖር በረከት››

የፊትህ ደስታ
‹‹በፊትህ የመሆን ደስታ›› ወይም፣ ‹‹ወደ አንተ በመቅረብ የሚገኝ ደስታ››

Psalms 21:7

ከልዑል ታማኝነት ኪዳን የተነሣ
‹‹ታማኝነት›› የሚለውን መለወጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ልዑል ለኪዳኑ ታማኝ በመሆኑ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አይናወጥም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከንጉሥነቱ ማንም አይነቀንቀውም››

እጅህ ትይዛለች
‹‹እጅ›› ኃይልን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ኀይልህ ትይዛለች›› ወይም፣ ‹‹በኀይል ትይዛለህ››

እጅህ... የሚጠሉህን
‹‹የአንተ›› እና፣ ‹‹አንተ›› ሲል፣ 1) ንጉሡን ነው ወይም 2) እግዚአብሔርን ነው።

ቀኝ እጅህ የሚጠሉህን ፈልጋ ትይዛለች
ይህ ከዐረፍተ ነገሩ የመጀመሪያ ክፍል ጋር ተመሳሳይ ነው። እግዚአብሔር ጠላቶቹን የሚቋቋምበት ኀይል ለንጉሡ እንደሚሰጠው አጠንክሮ ይናገራል።

Psalms 21:9

በተቆጣህ ጊዜ
‹‹በቁጣህ ስትገለጥ››

በቁጣህ... ታጠፋለህ
‹‹የአንተ›› እና፣ ‹‹አንተ›› ሲል፣ 1) እግዚአብሔርን ነው ወይም 2) ንጉሡን ማለቱ ነው።

እንደ ምድጃ እሳት ታቃጥላቸዋለህ
ያህዌ ወይም ንጉሡ ጠላቶቻቸውን መደምሰሳቸው ጠላቶቻቸው ያህዌ ወይም ንጉሡ ምድጃ ውስጥ የሚጥሏቸው እንጨት እንደሆኑ ተነግሮአል።

ያህዌ በመዓቱ ያቃጥላቸዋል፤ እሳት ይበላቸዋል
ሁለቱም ሐረጎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው። ያህዌ ጠላቶቹን ጨርሶ መደምሰሱ የእርሱ መዓት እነርሱን ፈጽሞ የሚያጠፋ እሳት እንደሆነ ተነግሯል።

ከምድር... ከሰው ዘር መካከል
ሁለቱም ሐረጎች ተመሳሳይ ናቸው። ከጠላቶቻቸው አንድ እንኳ እንደማይቀር ነው አጽንዖት የሚሰጡት።

Psalms 21:11

ያውጠነጥናሉ
‹‹ያቅዳሉ›› - ‹‹እነርሱ›› የሚያመለክተው የእግዚአብሔርንና የንጉሡን ጠላቶች ነው።

በአንተ ላይ ክፉ
‹‹አንተ ላይ ክፉ ነገር ለማድረግ››

ተንኰል አውጠነጠኑ
‹‹ዕቅድ አወጡ›› ወይም፣ ‹‹አሤሩ››

Psalms 21:13

ያህዌ ሆይ፣ በብርታትህ ከፍ በል
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ያህዌ ብርታትህን አሳየን›› ወይም 2) ‹‹ያህዌ አንተ ብርቱ በመሆንህ እኛም ከፍ እንላለን›› ማለት ሊሆን ይችላል።

እንዘምራለን ኀይልህን እናመሰግናለን
‹‹መዘመር›› እና፣ ‹‹ማመስገን›› ተመሳሳይ ትርጒም አላቸው። ‹‹ኀይል›› የሚለው እግዚአብሔርንና ኀይሉን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አንተ ኀይል ስለሆንህ በዝማሬ እናመሰግንሃለን››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 22

1 አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ? እኔን ለማዳን፣ ከመቃተቴም ቃል ለምን ራቅህ? **2** አምላኬ ሆይ፣ በቀን ወደ አንተ እጮኻለሁ፣ አንተ ግን አልመለሰህልኝም
በሌሊት እንኳ አላረፍሁም። **3** አንተ ቅዱስ ነህ በእስራኤል ምስጋና ውስጥ እንደ ንጉሥ ትቀመጣለህ። **4** አባቶቻችን በአንተ ተማመኑ፣ በአንተ ተማመኑ አንተም
ታደግሃቸው። **5** ወደ አንተ ጮኹ፤ እነርሱም ዳኑ በአንተ ተማመኑ፤ እነርሱም አላፈሩም። **6** እኔ ግን ትል እንጂ፣ ሰው አይደለሁም ለሰዎች ማላገጫ፣ በሕዝብም
ዘንድ የተናቅሁ ነኝ። **7** የሚያዩኝ ሁሉ ይሣለቁብኛል ራሳቸውንም እየነቀነቁ ያፌዙብኛል። **8** «በያህዌ ተማምኖአል፤ ያህዌ ያድነው፤ በእርሱ ደስ ተሰኝቶበታልና
እስቲ ይታደገው» ይላሉ። **9** አንተ ከእናቴ ማሕፀን አወጣኸኝ በእናቴም ጡት ሳለሁ በአንተ እንድታመን አደረግኸኝ። **10** ከማሕፀን ጀምሮ በአንተ ተጣልሁ
በእናቴ ማሕፀን ከነበርኩበት ጊዜ ጀምሮ አንተ አምላኬ ነህ! **11** መከራ እየተቃረበ ነው የሚረዳኝም የለምና ከእኔ አትራቅ። **12** ብዙ ኮርማዎች ከበቡኝ ኃይለኛ
የባሳን ኮርማዎች ዙሪያዬን ቆመዋል። **13** እንደሚያገሣና እንደሚቦጫጭቅ አንበሳ አፋቸውን ከፈቱብኝ። **14** እንደ ውሃ ፈሰሰሁ አጥንቶቼም ሁሉ
ከመጋጠሚያቸው ወለቁ ልቤ እንደ ሰም ሆነ በውስጤም ቀጠለ። **15** ጉልበቴ እንደ ሸክላ ደረቀ ምላሴም ከላንቃዬ ጋር ተጣበቀ። እንደ ሞተ ሰው ትቢያ ላይ
አደረግኸኝ። **16** ውሾች ከበቡኝ የክፉዎች ስብስብ በዙሪያዬ ሰፈሩ፤ እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩ **17** ዐጥንቶቼን ሁሉ አንድ አንድ መቁጠር እችላለሁ እነርሱም
አፍጥጠው ይመለከቱኛል። **18** ልብሶቼን ተከፋፈሉ በእጄ ጠባቤም ዕጣ ተጣጣሉ። **19** ያህዌ ሆይ፣ ከእኔ አትራቅ ብርታቴ ሆይ፣ እባክህ እኔን ለመርዳት
ፍጠን! **20** ነፍሴን ከሰይፍ ታደጋት ውድ ሕይወቴንም ከክፉ ውሾች አድናት። **21** ከአንበሳ አፍ አድነኝ፣ ከተዋጊ ጐሽ ቀንዶችም ታደገኝ። **22** ስምህን
ለወንድሞቼ እናገራለሁ፤ በጉባኤም መካከል አመሰግንሃለሁ። **23** እናንት ያህዌን የምትፈሩ አመስግኑት። እናንት የያዕቆብ ዘሮች ሁሉ አክብሩት! እናንት
የእስራኤል ልጆች ሁሉ እርሱን ፍሩት! **24** ጭንቀት የደረሰበትን ሰው አልናቀም፤ መከራ ላይ ያለውን አልተጸየፈም፤ ነገር ግን የድረሱልኝ ጩኸቱን ሰማው። **25**
ስለ ሠራኸው መልካም ሥራ፣ ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት ስፍራ አመሰግንሃለሁ፤ በሚፈሩህ ሰዎችም ፊት ስእለቴን እፈጽማለሁ። **26** ችግረኞች ይበላሉ፤
ይጠግባሉም ያህዌን የሚፈልጉም ያመሰግኑታል። ልባችሁ ለዘላለም ሕያው ይሁን። **27** የምድር ሕዝቦች ሁሉ ያስታውሳሉ ወደ ያህዌም ይመለሳሉ፤ የምድር
ወገኖች ሁሉ በፊትህ ወድቀው ይሰግዳሉ። **28** መንግሥት የያህዌ ነውና ሕዝቦችንም የሚገዛ እርሱ ነው። **29** የምድር ከበርቴዎች ሁሉ ይበላሉ፤ እርሱንም
ያመልካሉ በሕይወት ማቆየት የማይችሉ ወደ አፈር ተመላሽ የሆኑ ሰዎች ሁሉ በፊቱ ይንበረከካሉ። **30** የሚመጣው ትውልድ ያገለግለዋል ለቀጣዩ ትውልድም
ስለ ጌታ ይነግረዋል **31** የጽድቅ ሥራውን በማወጅ ገና ላልተወለደ ሕዝብ ጽድቁን፣ እርሱ ያደረገውንም ይነግራሉ።

Psalms 22:1

አጠቃላይ መረጃ
ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው።

ለመዘምራን አለቃ
‹‹ይህ የመዘምራን መሪ በአምልኮ ጊዜ የሚጠቀምበት ነው››

የንጋት አጋዘን
ይህ የሚያመለክተው የዜማውን ስልት ሊሆን ይችላል።

የዳዊት መዝሙር
ይህም ማለት፣ 1) መዝሙሩን የጻፈው ዳዊት ነው ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት ነው ማለት ሊሆን ይችላል።

አምላኬ፣ አምላኬ
ጸሐፊው፣ ‹‹አምላኬ›› የሚለውን የደገመው እግዚአብሔር እንዲሰማው አጥብቆ መፈለጉን አጽንዖት ለመስጠት ነው።

አምላኬ ለምን ተውኸኝ?
ጸሐፊው ጥያቄውን ያነሣው እግዚአብሔር እንደ ተወው ስለ ተሰማው ነው። ይህን ጥያቄ እንደሆነ መተው ይሻላል። እንደ ዐረፍተ ነገር መተርጐምም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አምላኬ ሆይ፣ አንተ እንደ ተውኸኝ ይሰማኛል!››

ተውኸኝ
‹‹ብቻዬን ተውኸኝ››

እኔን ከማዳን፣ ከመቃተቴ ቃል ለምን ራቅህ?
ጸሐፊው ጥያቄውን ያነሣው እግዚአብሔር ከእርሱ በጣም እንደ ራቀ ስለ ተሰማው ነው። ይህን ጥያቄ እንደሆነ መተው ይሻላል። በዐረፍተ ነገር መተርጐምም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተ እኔን ከማዳንና ከመቃተቴ ቃል ርቀሃል››

ከመቃተቴ ቃል ርቀሃል
እግዚአብሔር እንዳልሰማው ጸሐፊው የነበረው ስሜት እግዚአብሔር ከመቃተቱ ቃል በጣም የራቀ ያህል መሆኑን ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለሚሰማኝ ጭንቀት ስናገር የማትሰማኝ ለምንድነው?›› ወይም ‹‹ስለ መከራዬ ነገርሁህ አንተ ግን ወደ እኔ አልመጣህም››

በቀን... በሌሊት
ጸሐፊው፣ ‹‹ቀን›› እና፣ ‹‹ሌሊት›› በተሰኙ ቃሎች የተጠቀመው ዘወትር ወደ እግዚአብሔር እንደሚጸልይ ለማመልከት ነው።

ዝም አላልሁም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አሁንም እየተናገርሁ ነው››

Psalms 22:3

በእስራኤል ምስጋና እንደ ንጉሥ ተቀመጥህ
‹‹የእስራኤል ምስጋና አንተ እንደ ንጉሥ የምትቀመጥበት ዙፋን ነው›› የእስራኤል ምስጋና እግዚአብሔር ተቀምጦ የሚገዛበት ዙፋን ወይም እግዚአብሔር የሚኖርበት ቤት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተ ንጉሥ ነህ፤ የእስራኤል ሕዝብ ያመሰግንሃል››

የእስራኤል
እዚህ ላይ፣ ‹‹የእስራኤል›› የእስራኤልን ሕዝብ ይወክላል።

አላፈሩም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አላሳፈርሃቸውም›› ወይም ‹‹አልጣልሃቸውም››

አላፈሩም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አዳንሃቸው›› ወይም ‹‹የለመኑህን አደረግህላቸው››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 22:6

እኔ ትል ነኝ፤ ሰው አይደለሁም
ጸሐፊው እርሱ ትል እንደሆነ ይናገራል። ይህም እርሱ ከንቱ እንደሆነ ወይም ሰዎች እንደ ከንቱ ነገር እንደሚቆጥሩት አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ እንደ ትል ነኝ እንጂ፣ ሰው አይደለሁም››

ሰው ያላገጠብኝ፤ ሕዝብም የናቀኝ ነኝ
ሁለቱም ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው። ‹‹ሕዝብም የናቀኝ›› የሚለውን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ሁሉ ዋጋ እንደሌለኝ በመቁጠር ይጠሉኛል››

ያላግጡብኛል፤ ይሣለቁብኛል፤ ራሳቸውንም ይነቀንቁብኛል
እነዚህ ሦስት ሐረጐች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ ሰዎች ምን ያህል እንዳዋረዱት አጽንዖት ይሰጣሉ።

ራሳቸውንም ይነቀንቁብኛል
ይህ ሰውን የመናቅ ምልክት ነው።

በያህዌ ተማምኖአል... በእርሱ ደስ የተሰኘበትን
ሰዎች እንዲህ ያሉት በጸሐፊው ለማፌዝ ነው። ያህዌ እንደሚታደገው በእርግጥ አያምኑም።

እስቲ ይታደገው
‹‹እስቲ ያህዌ ይታደገው››

በእርሱ ደስ የተሰኘበትን
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ያህዌ በእርሱ ደስ ተሰኝቶአልና›› ወይም 2) ‹‹እርሱ በያህዌ ደስ ተሰኝቶአልና››

Psalms 22:9

አንተ ግን
ጸሐፊው፣ ‹‹ግን›› በሚል ቃል የተጠቀመው ለምን እርሱን ለመርዳት እንደማይመጣ ግራ መጋባቱን ለማሳየትና እግዚአብሔር ለመጠየቅ ነው።

ከማሕፀን አወጣኸኝ
ይህ ‹‹እንድወለድ አደረግህ›› ማለት ነው።

በእናቴ ጡት ሳለሁ
ይህ ማለት ገና ሕፃን እያለ በያህዌ ይተማመን ነበር ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእናቴ ጡት እጠባ በነበረበት ጊዜ እንኳ››

ከእናቴ ማሕፀን ስወጣም በአንተ ተጣልሁ
‹‹ተጣልሁ›› የሚለው ቃል ያህዌ እንደራሱ ልጅ ተቀብሎ ተጠነቀቀለት ለማለት ጥቅም ላይ የዋለ ቃል ነው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ተወለድሁ አንተ ተቀበልኸኝ››

አንተ አምላኬ ነህ
ይህ የሚያመለክተው ያህዌ ዘወትር ለጸሐፊው ይጠነቀቅለት እንደ ነበር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ ተጠነቀቅህልኝ››

በእናቴ ማሕፀን ሳለሁ
‹‹ከመወለዴ በፊት››

Psalms 22:11

ከእኔ አትራቅ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወደ እኔ ቅረብ›› መከራ እየተቃረበ ነውና
ጸሐፊው፣ ‹‹መከራ ወደ እርሱ እየቀረበ ያለ ነገር እንደሆነ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጠላቶቼ ወደ እኔ እየቀረቡ ነውና››

የሚረዳ የለም
‹‹ረዳት የለም››

ብዙ ኮርማዎች ከበቡኝ፣ ጎይለኛ የባሳን በሬዎችም በዙሪያየ ቆሙ
ጸሐፊው ጠላቶቹ እንደ ኮርማ እንደሆኑ ይናገራል። ይህ የሚያሳየው ጠላቶቹ ምን ያህል አደገኛና ብርቱ መሆናቸውን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ኮርማዎች የከበቡኝ ብዙ ጠላቶች አሉኝ እነርሱ ዙሪያዬን እንደ ቆሙ ጎይለኛ የባሳን በሬዎች ናቸው››

አፋቸውን አስፍተው ከፈቱብኝ
ጸሐፊው ጠላቶቹ እርሱን ለመብላት አፋቸውን እንደ ከፈቱ አንበሶች እንደሆኑ ይናገራል። ጠላቶቹ እርሱን ለማዋረድ ሐሰት እየተናገሩ ይሆናል። ወይም እንደሚያጠቁት እየዛቱበት ይሆናል።

እንደሚነጥቅና እንደሚያገሣ አንበሳ
ጸሐፊው ጠላቶቹ እንደ አንበሳ እንደሆኑ ይናገራል። ይህም ጠላቶቹ ምን ያህል ጎይለኞችና አደገኞች መሆናቸውን አጽንዖት ይሰጣል።

Psalms 22:14

እንደ ውሃ ፈሰስሁ
ይህን በሌለ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ውሃ የፈሰሰሁ መሰለኝ››

እንደ ውሃ ፈሰስሁ
ከእንስራ ወደ ውጭ እንደ ፈሰሰ ውሃ ያበቃለትና ፍጹም ደካማነት እንደ ተሰማው ጸሐፊው ይናገራል።

ዐጥንቶቼ ሁሉ ከመጋጠሚያቸው ወለቁ
‹‹ዐጥንቶቼ ሁሉ ተናጉ›› ጸሐፊው አንድ ዐይነት የአካል ሕመም ደርሶበት ይሆናል። ወይም ስሜታዊውን ሕመም እንደ አካላዊ ሕመም እያመለከተ ይሆናል።

ልቤ እንደ ሰም... ውስጤ
ልቡ እንደ ሰም እንደ ቀለጠ ሰው፣ ጸሐፊው ከእንግዲህ ምንም ወኔ እንደሌለው ይናገራል። እዚህ ላይ፣ ‹‹ልብ›› የሚያመለክተው፣ ‹‹ወኔን›› ነው።

ሰም
በአንጻራዊ በጣም ዝቅ ባለ ሙቀት እንኳ የሚቀልጥ ነገር

በውስጤ
‹‹እኔ ውስጥ››

ብርታቴ እንደ ገል ደረቀ
ጸሐፊው በቀላሉ እንደሚሰበር የደረቀ ሸክላ ስባሪ ዐቅመ ቢስነት እንደ ተሰማው ይናገራል።

የሸክላ ስባሪ
እቤት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል ከሸክላ የተሠራ ነገር

ምላሴ ከላንቃዬ ጋር ተጣበቀ
‹‹ምላሴ ከትናጋዬ ጋር ተጣበቀ›› ምናልባትም ጸሐፊው በጣም ጠምቶት እንደ ነበር እየተናገረ ይሆናል። ወይም መድከሙ የመድረቅ ያህል እንደሆነበት እየተናገረ ይሆናል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በሞት ዐፈር አጋደምኸኝ
‹‹የሞት ዐፈር›› ማለት 1) ከሞተ በኃላ ወደ ዐፈር የተለወጠ ሰው ማለት ይሆናል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንድሞትና ዐፈር እንድሆን አደረግኸኝ›› ወይም 2) ስለ መቃብርና በዚያም አማካይነት እግዚአብሔር ጸሐፊው እንዲሞት እንዳደረገ መናገሩ ይሆናል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በመቃብሬ አጋደምኸኝ››

አጋደምኸኝ
‹‹አንተ›› የሚለው የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው።

Psalms 22:16

ውሾች ከበቡኝ
ጸሐፊው ጠላቶቹ እንደ ውሾች እንደሆኑ ይናገራል። ጠላቶቹ የሞተ እንስሳ እንደሚበሉ የዱር ውሾች ወደ እርሱ እየቀረቡ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጠላቶቼ እንደ ውሾች ከበቡኝ››

የክፉዎች ሸንጎ
‹‹የክፉዎች ጉባኤ›› ወይም፣ ‹‹የክፉዎች ቡድን››

በዙሪያዬ
ክብ ሠርተው ቆሙ

እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩ
ይህም ስለ ውሾቹ ነው የሚናገረው ጸሐፊው ጠላቶቹ እንደሚናከሱና በጥርሳቸው እጆችና እግሮቹን እንደ ቸነከሩ ይናገራል።

ቸነከሩኝ
ስል በሆነ ነገር ወጉኝ

ዐጥንቶቼን መቁጠር እችላለሁ
ይህም ማለት፣ 1) ጸሐፊው በጣም ከሲታ ስለ ነበር ዐጥንቶቹን ማየት ይችላል ማለት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዐጥንቶቼን ሁሉ ማየት እችላለሁ›› ወይም፣ ‹‹ዐጥንቶቼን መንካት እችላለሁ›› ወይም 2) ይህ የሚናገረው ስለ ውሾቹ ሲሆን፣ ሥጋውን ከገነጣጠሉ በኃላ ዐጥንቶቼን ማየት ቻሉ ማለት ሊሆን ይችላል።

አፍጥጠው ያዩኛል፤ ይመለከቱኛል
‹‹ያዩኛል›› እና፣ ‹‹ይመለከቱኛል›› በመሠረቱ አንድ ቢሆኑም፣ ሰዎች በፍርሃት እንደሚያዩትና እንደሚቀልዱበት አጽንዖት ይሰጣል።

Psalms 22:18

በእጅ ጠባቤ
‹‹በልብሴ››

አትራቅ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወደ እኔ ቅረብ››

ብርታቴ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ብርታት›› የሚያመለክተው ብርታት የሚሰጠውን ያህዌን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ብርታት ሰጠኸኝ››

Psalms 22:20

ነፍሴን ታደጋት
‹‹ነፍስ›› የሰውን ሁለንተና ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ታደገኝ››

ከሰይፍ
ሰይፍ ለአደገኛ ጠላት የሚሰጥ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለገድሉኝ የሚፈልጉ›› ወይም፣ ‹‹ጠላቶቼ››

ውድ ሕይወቴን
‹‹የከበረች ሕይወቴን›› ወይም፣ ‹‹ያለችኝን ብቸኛ ሕይወቴን››

ከዱር ውሾች ጥፍር... ከአንበሶች አፍ... ከዱር በሬዎች ቀንድ
ጸሐፊው ጠላቶቹ ምን ያህል አደገኞች መሆናቸውን አጽንዖት ለመስጠት የዱር ውሾች፣ አንበሶችና የዱር በሬዎች እንደሆኑ ይናገራል። በተጨማሪም ጥፍር፣ አፍና ቀንድ በምሳሌያዊ አነጋገር እንስሳትን ሁሉ ያመለክታል። ጸሐፊው ለእነዚህ ነገሮች አጽንዖት የሰጠው እንስሶች ሌላውን ለመግደል የሚጠቀሙት በእነዚህ ነገሮች በመሆኑ ነው።

የዱር ውሾች... የዱር በሬዎች
እዚህ ላይ ‹‹ዱር›› የሚለው ቃል እንስሶቹን ማንም ይዞአቸው ወይም አልምዶአቸው። እንደማያውቅ ለማመልከት ነው።

Psalms 22:22

ስምህን እናገራለሁ
‹‹ስምህን አሳውቃለሁ›› እዚህ ላይ፣ ‹‹ስም›› የእግዚአብሔርን ባሕርይና ማንነት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለ ባሕርይህ እናገራለሁ››

ለወንድሞቼ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ወንድሞቼ›› ማለት፣ ‹‹እስራኤላውያን ወገኖቼ›› ወይም፣ ‹‹እንደ እኔ ያህዌን ለሚያመልኩ›› ማለት ነው።

በጉባኤ መካከል
‹‹እኔና እስራኤላውያን ወገኖቼ በአንድነት ስንሰባሰብ›› ወይም ‹‹ያህዌን በሚያመልኩ ሰዎች ስከበብ››

የምትፈሩት
እዚህ ላይ፣ ‹‹አንተ›› በነጠላ ቁጥር ሳይሆን የተነገረው በብዙ ቁጥር ነው።

እናንት የያዕቆብ ዘር... የእስራኤልም ዘር
ሁለቱም የሚያመለክቱት አንድን ሕዝብ ነው።

እርሱን ፍሩት
‹‹እርሱን በጣም ፍሩት›› ወይም፣ ‹‹የእግዚአብሔር ኀይል ያስደንቃችሁ››

Psalms 22:24

የተጨነቀውን ሰው ጭንቀት አልናቀም፤ ቸልም አላለምና
ይህም ማለት፣ 1) መከራ ላይ ስለሆነ የተጨነቀውን ሰው አልናቀም ወይም 2) የተጨነቀውን ሰው መከራ አቅልሎ አላየም ማለት ሊሆን ይችላል።

አልናቀም ወይም አልተጸየፈም
በመሠረቱ ሁለቱም ተመሳሳይ ናቸው፤ የተጨነቀውንና በመከራ ያለውን እግዚአብሔር አለመርሳቱን አጽንዖት ይሰጣሉ።

አልናቀም
አጥብቆ አልጠላም

የተጨነቀውን ሰው መከራ... አልተጸየፈም
እዚህ ላይ፣ መከራ የሚያመለክተው ሰውየውን ነው። አንድን ነገር መጸየፍ አጥብቆ መጥላት ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የተጨነቀውን ሰው መከራ አጥብቆ አልጠላም››

የተጨነቀው ሰው መከራ... ከእርሱ... የተጨነቀው ጮኸ
ይህም ማለት፣ 1) ጸሐፊው እግዚአብሔር መከራ ውስጥ ያሉትን እንዴት እንደሚያይ እየተናገረ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መከራ ውስጥ ያሉት... ከእነርሱ... መከራ ውስጥ ያሉት ጮኹ›› ወይም 2) ጸሐፊው በተለይ እርሱን እንዴት እንደሚያይ እየተናገረ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከመከራዬ የደረሰብኝ ጭንቀት... ከእኔ... ጮኽሁ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ፊቱን ከእርሱ አልሰወረም
ከሰው ፊትን መሰወር እርሱን ችላ ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ትኩረቱን ከእርሱ አላነሣም›› ወይም፣ ‹‹ችላ አላለውም››

ሰማ
‹‹አደመጠ›› ጩኸታቸውን ሲሰማ ምላሽ መስጠቱ ግልጽ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹መለሰ›› ወይም፣ ‹‹ረዳ››

በአንተ
‹‹አንተ›› የሚለው ያህዌን ነው።

ስዕለቴን እፈጽማለሁ
ይህ የሚያመለክተው ጸሐፊው ለእግዚአብሔር እንደሚያቀርብ ቃል የገባውን ነው።

እርሱን በሚፈሩት ፊት
‹‹እርሱ›› የሚያመለክተው ያህዌን ነው። ‹‹አንተ›› ሊባልም ይችላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አንተን በሚፈሩ ፊት››

Psalms 22:26

ችግረኞች ይበላሉ ይጠግባሉ
ይህ የሚያመለክተው ጸሐፊው ቃል የገባውን መሥዋዕት ካቀረበ በኋላ የሚኖረውን የኅብረት ምግብ ነው። እርሱ ለመሥዋዕት ያቀረበውን እንስሳ ክፍል እንዲበሉ ችግረኞችን ይጋብዛል።

ያህዌን የሚፈልጉት
ያህዌን ማወቅና እርሱን ደስ ማሰኘት የሚፈልጉ እርሱን ራሱን ለማግኘት እንደሚፈልጉ ተነግሯል።

ልባችሁ ለዘላለም ሕያው ይሁን
እዚህ ላይ፣ ‹‹ልብ›› የሰውን ሁለንተና ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለዘላለም ሕያው ሁኑ››

ልባችሁ ለዘላለም
እዚህ ላይ፣ ‹‹የእናንተ›› የሚለው ችግረኞቹን ነው።

ያስታውሳሉ ወደ ያህዌ ይመለሳሉ
ለያህዌ መታዘዝ የሰዎች ወደ ያህዌ መመለስ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌን ያስታውሱታል ይታዘዙለታል››

የሕዝቦች ወገኖች ሁሉ በፊትህ ወድቀው ይሰግዳሉ
ይህ ከመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ክፍል ጋር ተመሳሳይ ነገር ነው የሚናገረው። ጸሐፊው በየቦታው ያሉ ሰዎች ሁሉ ያህዌን እንደሚያመልኩና እንደሚታዘዙለት አጽንዖት ይሰጣል።

በፊትህ ወድቀው ይሰግዳሉ
ይህ የሚያመለክተው ክብርንና ምስጋናን መስጠትን ነው።

በፊትህ
እዚህ ላይ፣ ‹‹አንተ›› የሚያመለክተው ያህዌን ነው። ከመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ክፍል ጋር እንዲጣጣም በሦስተኛ ሰው ደረጃ መተርጐም አለበት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በፊቱ››

Psalms 22:28

መንግሥት የያህዌ ነው
‹‹መንግሥት የሚገባው ለያህዌ ነው›› እዚህ ላይ፣ ‹‹መንግሥት›› የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን እንደ ንጉሥ መግዛት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ ንጉሥ ነውና››

ሕዝቦችንም የሚገዛ እርሱ ነው
‹‹ሕዝቦች›› የሚያመለክተው ሰዎችን ሁሉ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በየአገሩ ያሉ ሰዎች››

ይበላሉ
ሰዎቹ በአንድነት በደስታ ይበላሉ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አብረው ይበላሉ›› ወይም፣ ‹‹የደስታ ምግብ አብረው ይበላሉ››

ወደ ዐፈር የሚወርዱ ሁሉ... ራሳቸውን ማዳን የማይችሉ
ሁለቱም ሐረጐች የሚያመለክቱት ስለ አንድ ወገን ነው። ሰዎች ሁሉ ሟች ስለ ሆኑ ሁለቱም የሚናገሩት ስለ ሰዎች ሁሉ ነው።

ወደ ዐፈር የሚወርዱ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ዐፈር›› የሚያመለክተው መቃብርን ነው። ‹‹ወደ ዐፈር የሚወርዱ›› የሚለው የሚያመለክተው የሚሞቱ ሰዎችን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እየሞቱ ያሉ›› ወይም፣ ‹‹የሚሞቱ››

ራሳቸውን ማዳን የማይችሉ
‹‹ሕይወታቸውን ማዳን የማይችሉ›› ወይም፣ ‹‹ራሳቸውን ከሞት የማያድኑ››

Psalms 22:30

የሚመጣ ትውልድ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ትውልድ›› የሚያመለክተው ትውልዱ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ነው። ‹‹የሚመጣ›› የሚያመለክተው የወደ ፊቱን ጊዜ ሲሆን እንደሚሄድና አንድ ቦታ እንደሚደርስ ነገር አድርጐ ይናገራል።

የሚቀጥል ትውልድ
‹‹ትውልድ›› የሚያመለክተው ትውልዱ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሚቀጥለው ትውልድ ሰዎች›› ወይም፣ ‹‹ልጆቻቸው››

ስለ ጌታ
‹‹ጌታን በተመለከተ›› ወይም፣ ‹‹ጌታ ስላደረገው››

ጽድቁን ይነግራሉ
‹‹ጽድቁ›› የሚለውን የነገር ስም፣ ቅጽል ማድረግ ይቻላል። ‹‹እርሱ ያደረገውን የጽድቅ ሥራ ይነግራሉ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 23

1 ያህዌ እረኛዬ ነው፤ ምንም አላጣም። **2** በለመለመ መስክ ያሳድረኛል ፀጥ ባለ ውሃ ዘንድ ይመራኛል። **3** ነፍሴን ይመልሳታል፤ ያድሳታል። ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ ይመራኛል። **4** በጨለማው የሞት ሸለቆ ውስጥ እንኳ ባልፍ አንተ ከእኔ ጋር ስለ ሆንህ ጉዳት ይደርስብኛል ብዬ አልፈራም። **5** በጠላቶቼ ፊት ለፊት በፊቴ ገበታ አዘጋጀህልኝ ራሴን በዘይት ቀባህ ጽዋዬ ሞልቶ ተርፏል። **6** በሕይወት ዘመኔ ሁሉ ደግነትና ፍቅር ዘወትር ከእኔ ጋር ይሆናሉ፤ በያህዌም ቤት ለዘላለም እኖራለሁ።

Psalms 23:1

አጠቃላይ መረጃ
ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው።

አጠቃላይ መረጃ
በአብዛኛው በዚህ መዝሙር ክፍል ራሱን እንደ በግ ጌታን ደግሞ እንደ እረኛ አድርጐ ዳዊት ይጽፋል።

የዳዊት መዝሙር
ይህም ማለት፣ 1) መዝሙሩን የጻፈ ዳዊት ነው ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት ነው ማለት ሊሆን ይችላል።

ያህዌ እረኛዬ ነው
ጸሐፊው ያህዌ እንደ እረኛ እንደሆነ ይናገራል። ይህም እረኛ ለበጐቹ እንደሚያስብ ያህዌም ለሰዎች እንደሚያስብ ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ እንደ እረኛዬ ነው›› ወይም፣ ‹‹እረኛ ለበጐቹ እንደሚያስብ ያህዌ ለእኔ ያስብልኛል››

አንዳች አይጐድልብኝም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሚያስፈልገኝ ሁሉ አለኝ››

በለመለመ መስክ ያሳርፈኛል
ጸሐፊው ራሱን እንደ በግ ያህዌን እንደ እረኛ ያቀርባል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በጉን በለመለመ መስክ እንደሚያሳርፍ እረኛ ዕረፍት ይሰጠኛል››

በዕረፍት ውሃ ዘንድ ይመራኛል
ጸሐፊው ራሱን እንደ በግ ያህዌን እንደ እረኛ ያቀርባል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በጉን በዕረፍት ውሃ ዘንድ እንደሚመራ እረኛ የሚያስፈልገኝን ሁሉ ያቀርብልኛል።››

የዕረፍት ውሃ
‹‹ረጋ ያለ ውሃ›› ወይም፣ ‹‹ረጋ ብሎ የሚወርድ ውሃ›› ይህ ውሃ ለመጠጥ ተስማሚ ነው።

Psalms 23:3

አጠቃላይ መረጃ
ይህ መዝሙር እረኛ ለበጐቹ እንደሚያስብ እግዚአብሔርም ለእኛ እንደሚያስብ መናገር ቀጥሏል።

ነፍሴን መለሳት
ይህ ማለት ደካማውን ሰው እግዚአብሔር ብሩቱ ያደርገዋል ያሳርፈዋል ማለት ነው።

በትክክለኛው መንገድ መራኝ
እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕይወት መኖርን ለአንድ ሰው ማሳየት በጉን በትክክለኛ መንገድ እንደሚመራ እረኛ መሆን እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በትክክል መኖርን ያሳየኛል››

ስለ ስሙ ሲል
‹‹ስለ ስሙ›› የሚለው ሐረግ የእርሱን ማንነት ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ስለ ማንነቱ›› ወይም፣ ‹‹ሰዎች እንዲያከብሩት››

Psalms 23:4

አጠቃላይ መረጃ
ይህ መዝሙር እረኛ ለበጐቹ እንደሚያስብ እግዚአብሔርም ለእኛ እንደሚያስብልን መናገር ቀጥሏል።

በሞት ጥላ ሸለቆ ውስጥ ብሄድ እንኳ
ከባድ መከራ የደረሰበት ሰው በጨለማና አደገኛ ሸለቆ ውስጥ እንደሚሄድ ሰው መሆኑን ጸሐፊው ይናገራል። በዚያ በጐች ይጠፋሉ፤ በአደገኛ አውሬ ይጠቃሉ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሕይወቴ በሞት ጥላ ሸለቆ ውስጥ እንደሚሄድ ቢሆን እንኳ››

ጉዳት ይደርስብኛል ብዬ አልፈራም
‹‹ጉዳት›› የሚለውን የነገር ስም ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አንዳች ነገር ይጐዳኛል ብዬ አልፈራም››

አንተ ከእኔ ጋር ስለሆንህ
‹‹አንተ›› የሚያመለክተው ያህዌን ነው።

በትርህና ምርኩዝህ ያጽናኑኛል
በትርና ምርኩዝ እረኞች በጐቻቸውን ከአደጋ ለመጠበቅ የሚጠቀሙባቸው ስለሆነ ጥበቃን ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በበትርና በምርኩዙ በጐቹ እንደሚጠብቅ እረኛ እኔንም ስለምትጠብቀኝ አልፈራም››

Psalms 23:5

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር በቤቱ እንግድነት ተቀብሎ እንደሚጠብቀው ሰው እንደሆነ ጸሐፊው ይናገራል።

ገበታ አዘጋጀህልኝ
ገበታ ግብዣን ያመለክታል፤ ሰዎች ምግቦችን ሁሉ ገበታው ላይ ይኖራሉ።

በጠላቶቼ ፊት
የዚህ ትርጒም ጸሐፊው እርሱ የተከበረ የጌታ እንግዳ እንደሆነና እርሱም ከአደጋ ስለሚጠብቀው እንደማይሰጋ ጸሐፊው ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ጠላቶቼ እያዩ››

ራሴን በዘይት ቀባህ
ሰዎች ለእንግዳው ክብር ራሱን በዘይት ይቀቡት ነበር።

ጽዋዬም ሞልቶ ይፈስሳል
ወይን ሞልቶ የሚፈስስ ጽዋ ብዙ በረከትን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሞልቶ እስኪፈስ ድረስ ጽዋዬን ሞላኸው›› ወይም፣ ‹‹ብዙ በረከት ሰጠኸኝ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 23:6

በጐነትና ኪዳናዊ ታማኝነት በእርግጥ ይከተሉኛል
ያህዌ ለሰው ደግና ታማኝ መሆኑ በጐነትና ኪዳናዊ ታማኝነት ያንን ሰው እንደሚከተሉት ተደርጐ ተነግሯል። ‹‹በጐነት›› እና፣ ‹‹ታማኝነት›› የተሰኙ የነገር ስሞች እንደ ቅጽል መተርጐም ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለእኔ አንተ በእርግጥ መልካምና ታማኝ ነህ››

በሕይወቴ ዘመን ሁሉ
‹‹ሕይወት›› የሚለውን የነገር ስም ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሕይወት እስካለሁ ድረስ››

በያህዌ ቤት
ይህም ማለት፣ 1) የያህዌን ዘላለማዊ ቤት ያመለክታል ወይም 2) በኢየሩሳሌም ያለውን የያህዌን ቤቴ መቅደስ ያመለክታል። ከተቻለ ሁለቱንም ሐሳቦች በሚያካትት ሁኔታ ተርጉመው።

ለረጅም ዘመን
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ለዘላለም›› ወይም 2) ‹‹በሕይወት እስካለሁ ድረስ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 24

1 ምድርና በእርሷ ያለው ሁሉ፣ ዓለምና በውስጧ የሚኖር ሁሉ የያህዌ ነው። **2** እርሱ ባሕር ላይ መሥርቶአታልና በውሆችም ላይ አጽንቶአታል። **3** ወደ ያህዌ ተራራ ማን ይወጣል? በተቀደሰ ስፍራውስ ማን ይቆማል? **4** ንጹሕ እጅና ንጹሕ ልብ ያለው፣ ነፍሱን ለሐሰት ያላስገዛ በሐሰት የማይምል፣ **5** እርሱ ከያህዌ ዘንድ በረከትን፣ ከመድኃኒቱም አምላክ ጽድቅን ይቀበላል። **6** እርሱን የሚፈልግ ትውልድ የያዕቆብ አምላክን ፊት የሚፈልግ እንዲህ ያለ ነው። ሴላ **7** እናንተ ደጆች ራሳችሁን ቀና አድርጉ እናንተ የዘላለም በሮች የክብር ንጉሥ እንዲገባ ብድግ በሉ! **8** ይህ የክብር ንጉሥ ማን ነው? ብርቱና ኃያል የሆነው ያህዌ፣ በጦርነት አሸናፊ የሆነው ያህዌ ነው። **9** እናንተ ደጆች ራሳችሁን ቀና አድርጉ እናንተ የዘላለም በሮች የክብር ንጉሥ እንዲገባ ብድግ በሉ! **10** ይህ የክብር ንጉሥ ማን ነው? የሰራዊት ጌታ ያህዌ እርሱ የክብር ንጉሥ ነው። ሴላ

Psalms 24:1

አጠቃላይ መረጃ
ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው።

የዳዊት መዝሙር
ይህም ማለት፣ 1) መዝሙሩን የጻፈው ዳዊት ነው ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት ነው።

ሞላዋ
‹‹ሞላዋ›› የሚለው የነገር ስም፣ ‹‹የሞላት›› በሚል ግሥ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እርሷን የሞላ ሁሉ››

እርሱ በባሕር ላይ መሥርቶአታልና በውሆችም ላይ አጽንቶአታል
እዚህ ላይ፣ ‹‹በባሕር ላይ መሠረታት›› እና፣ ‹‹ውሆች ላይ አጸናት›› ማለት በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው በዚያ ዘመን የነበሩ ዕብራውያን ምድራቸው በባሕር እንደ ተመሠረተችና በጥልቅ ውሆች ላይ እንደ ጸናች ያምኑ ነበር። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹መሠረቷን ባሕር ላይ አደረገ፤ ጥልቅ ውሆችም ላይ አጸናት››

ባሕር... ውሆች
እነዚህ ሐረጎች በአንድነት ጥቅም ላይ የዋሉት ከምድር በታች ያለውን ግዙፍና ጥልቅ ውቅያኖስ ለማመልከት ነው።

በውሆች ላይ
‹‹ከታች ጥልቅ ውስጥ ያለው ውሃ››

Psalms 24:3

ወደ ተራራው ማን ይወጣል... በተቀደሰ ስፍራውስ?
ሁለቱም ጥያቄዎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው። ጸሐፊው ወደዚያ ሄዶ ያህዌን የሚያመልክ ማን ሊሆን እንደሚችል እየጠየቀ ነው።

ማን ሊወጣ ይችላል
‹‹ማን ወደ ላይ ይሄዳል›› ወይም፣ ‹‹ማን መውጣት››

የያህዌ ተራራ
ይህ የሚያመለክተው ኢየሩሳሌም ያለው የጽዮን ተራራ ነው።

የተቀደሰ ስፍራ
ይህ የሚያመለክተው የያህዌን ቤተ መቅደስ ነው። ቤተመቅደሱ ያለው በኢየሩሳሌም በጽዮን ተራራ ላይ ነው።

ያለው... የማያስገዛ... የማይምል
‹‹እርሱ›› ሲል አንድ ግለ ሰብ ማመልከቱ አይደለም። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያላቸው... የማያስገዙ... የማይምሉ››

Psalms 24:5

እርሱ ከያህዌ ዘንድ በረከት ይቀበላል
‹‹እርሱ›› ሲል አንድ ግለ ሰብ ማመልከቱ አይደለም። ባለፈው ቁጥር የተጠቀሱትን ንጹሕ ልብ ያላቸውን እያመለከተ ነው። ‹‹በረከት›› የሚለውን የነገር ስም፣ ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ ይባርካቸዋል››

ጽድቅን ከአዳኝ አምላኩ
‹‹ጽድቅ›› የሚለውን የነገር ስም፣ ‹‹በጽድቅ›› በማለት መግለጽ ይቻላል። ‹‹አዳኝ›› የሚለውን፣ ‹‹መዳን›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እግዚአብሔር በጽድቅ ይፈርድለታል ደግሞም ያድነዋል››

እርሱን የሚፈልግ ትውልድ እንዲህ ነው።
‹‹ትውልድ›› ሰዎችን ሁሉ ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እነርሱን የሚፈልጉ ሰዎች እንዲህ ናቸው››

እርሱን የሚፈልጉ፣ የያዕቆብን አምላክ ፊት የሚፈልጉ
ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች የሚያመለክቱት ተመሳሳይ ነገር ነው። ሁለቱም የሚናገሩት እግዚአብሔርን ለማምለክ ወደ ቤተ መቅደስ የሚሄዱትን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡ የእስራኤልን አምላክ የሚያመልኩ ናቸው››

እርሱን የሚፈልጉ
ያህዌን ለማምለክ ወደ ቤተ መቅደስ መሄድ እርሱን መፈለግ እንደሆነ ተነግሯል።

የያዕቆብ አምላክ ፊት
‹‹ፊት›› ሙሉውን ሰው ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የያዕቆብን አምላክ››

Psalms 24:7

እናንተ ደጆቸ ቀና በሉ፤ እናንተም የዘላለም በሮች ብድግ በሉ
የሁለቱም ሐረጎች ትርጒም በጣም ተቀራራቢ ነው። ‹‹ደጆች›› እና፣ ‹‹በሮች›› የሚያመለክቱት የቤተ መቅደሱን ደጆች ነው። ጸሐፊው ደጆቹ ሰው እንደሆኑ አድርጐ ይናገራል። ደጆቹን የሚከፍት ጠባቂው ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እናንት የጥንት ደጆች ተከፈቱ›› ወይም፣ ‹‹እነዚህን የጥንት ደጆች ክፈቱ››

ራሳችሁን ቀና አድርጉ
እንደ፣ ‹‹ራስ›› ቀና የሚል የደጃፉ ክፍል ግልጽ አይደለም። ግን የሚወክለው ደጁን ሁሉ ነው።

ያህዌ ብርቱና ኀያል፣ ያህዌ በጦር ኀያል
ጸሐፊው ያህዌ ጦርነት የሚዋጋ ብርቱ ጦረኛ እንደሆነ ይናገራል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 24:9

እናንት ደጆች ቀና በሉ፤ የዘላለም በሮች ብድግ በሉ
የሁለቱም ሐረጐች ትርጕም ተመሳሳይ ነው። ‹‹ደጆች›› እና፣ ‹‹በሮች›› የሚያመለክቱት የቤተ መቅደሱን ደጆች ነው። ጸሐፊው ደጆቹ ሰው እንደሆኑ አድርጐ ይናገራል። ደጆቹን የሚከፍት ጠባቂው ነው። መዝሙር 24፥7 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እናንት የዘላለም ደጆች ተከፈቱ›› ወይም፣ ‹‹እነዚህ የዘላለም ደጆችን ክፈቱ››

ራሳችሁን ቀና አድርጉ
ቀና የሚለው የደጃፉ ‹‹ራስ›› ግልጽ አይደለም። ሆኖም ደጃፉን ሁሉ ይወክላል።

ሴላ
እንዴት እንደሚዘምሩ ወይም ሙዚቃ እንደሚጫወቱ ለሰዎች የሚያመለክት ሙዚቃዊ አገላለጽ ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ትርጕሞች የዕብራይስጡን ቃል ይጽፋሉ፤ ሌሎች ግን ይተውታል። መዝሙር 3፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 25

1 ያህዌ ሆይ፣ ነፍሴን ወደ አንተ አነሣለሁ! **2** አምላኬ ሆይ፣ በአንተ እታመናለሁ። እባክህ አታሳፍረኝ፤ አታዋርደኝ ጠላቶቼም በእኔ ላይ ደስ እንዲላቸው አታድርግ። **3** አንተን ተስፋ የሚያደርጉ ከቶ አያፍሩም፤ እንዲያው ያለ ምክንያት የሚያታልሉ ግን ያፍራሉ። **4** ያህዌ ሆይ፣ አካሄድህን አሳውቀኝ መንገድህንም አስተምረኝ። **5** በእውነትህ ምራኝ አስተምረኝም፤ አንተ የድነቴ አምላክ ነህና ቀኑን ሙሉ በአንተ ታመንሁ። **6** ያህዌ ሆይ፣ ከጥንት ጀምሮ የነበሩ ምሕረትህንና ፍቅርህን አስብ። **7** የልጅነቴን ኃጢአት፣ መተላለፌንም አታስብብኝ፤ ያህዌ ሆይ፣ እንደ ቸርነትህ ብዛት እንደ ምሕረትህም መጠን አስበኝ። **8** ያህዌ መልካም ቅን ነው፤ ስለዚህ ኃጢአተኞችን መንገድን ያስተምራቸዋል። **9** ትሑታንን በትክክለኛው መንገድ ይመራቸዋል መንገዱንም ያስተምራቸዋል **10** ኪዳኑንና ሥርዐቱን ለሚጠብቁ የያህዌ መንገድ ሁሉ ቸርነትና እውነት ነው። **11** ያህዌ ሆይ፣ ኃጢአቴ እጅግ ብዙ ነውና ስለ ስምህ ይቅር በለኝ **12** ያህዌን የሚፈራ ሰው ማን ነው ጌታ በመረጠው መንገድ ያስተምረዋል። **13** ዘመኑን በተድላ ደስታ ያሳልፋል ዘሮቹም ምድርን ይወርሳሉ። **14** ያህዌ ለሚታዘዙት ሁሉ ወዳጃቸው ነው ለእነርሱ የገባውንም ኪዳን ያጸናል። **15** ዐይኖቼ ዘወትር ወደ ያህዌ ናቸው እግሮቼን ከወጥመድ የሚያላቅቃቸው እርሱ ነው። **16** እኔ ብቸኛና ምስኪን ነኝና ወደ እኔ ተመለስ ማረኝም። **17** የልቤ ሐዘን በዝቶአል ከጭንቀቴ አወጣኝ። **18** መከራዬንና ጭንቀቴን ተመልከት ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር በል። **19** ጠላቶቼ እንዴት እንደ በዙ እይ፤ እንዴት አምርረው እንደሚጠሉኝ ተመልከት። **20** ነፍሴን ጠብቃት፤ ታደገኝም በአንተ ተማምኛለሁና አልዋረድ፤ አልፈር። **21** አንተን ተስፋ አድርጌአለሁና ታማኝነትና ቅንነት ይጠብቁኝ **22** ያህዌ ሆይ፣ እስራኤልን ከመከራው ሁሉ አድነው።

Psalms 25:1

አጠቃላይ መረጃ
ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው።

ሕይወቴን አነሣለሁ
‹‹ሕይወቴን አነሣለሁ›› ምሳሌያዊ አባባል ነው። ይህም ማለት፣ 1) ጸሐፊው ራሱን ለያህዌ እየሰጠ ነው፤ ማለት ሙሉ በሙሉ በያህዌ ይታመናል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ራሴን ለአንተ እሰጣለሁ›› ወይም 2) የምስጋና ጸሎት ለያህዌ ማቅረቡ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አመልክሃለሁ፤ ከፍ አደርግሃለሁ››

አታሳፍረኝ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጠላቶቼ እንዲያሳፍሩኝ አትተዋቸው››

በድል አድራጊነት በእኔ ላይ ደስ አይበላቸው
‹‹እኔን በማሸነፍ ደስ አይበላቸው›› - ‹‹በእኔ ላይ›› የሚለው ሐረግ ጠላቶቹ እንዳሸነፉትና በድል እንደ ቆሙ ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እኔን በማሸነፍ ደስ አይበላቸው››

አንተን ተስፋ የሚያደርጉ አያፍሩም
‹‹አንተን ተስፋ የሚያደርጉ አይፈሩ›› በጠላት መሸነፍ እፍረት ያመጣል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አንተን ተስፋ የሚያደርጉን ጠላት አያሸንፋቸው››

አንተን ተስፋ የሚያደርጉ
‹‹የሚታመኑብህ››

ከሐዲዎች የሆኑ
‹‹አታላዮች›› ወይም፣ ‹‹የሚያጭበረብሩ››

ያለ ምክንያት
‹‹ምንም ምክንያት ሳይኖር››

Psalms 25:4

ያህዌ ሆይ፣ አካሄድህን አሳወቀኝ መንገድህንም አስተምረኝ
ሁለቱም ሐረጐች ተመሳሳይ ናቸው። እንዴት እንደሚኖር እግዚአብሔርን ሰውን ማስተማሩ እርሱን በትክክለኛው መንገድ መምራት ማለት እንደሆነ ተነግሯል።

አንተን ተስፋ አድርጌአለሁ
‹‹በአንተ ታምኛለሁ›› ወይም ‹‹አንተን በትዕግሥት እጠብቃለሁ››

በእውነትህ ምራኝ አስተምረኝም
መመራትና ማስተማር ተመሳሳይ ሲሆኑ፣ መመሪያ መስጠት ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለአንተ እውነት በመታዘዝ ሕይወቴን እንዴት እንደምመራ አስተምረኝ››

የመዳኔ አምላክ
‹‹መዳኔ›› የሚለውን ‹‹የምታድነኝ›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የምታድነኝ››

Psalms 25:6

አስበኝ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። እግዚአብሔር ይረሳል ማለት አይደለም። ጸሐፊው እግዚአብሔርን እየጠየቀ ያለው የርኅራኄና የታማኝነት ሥራውን እንዲያስብ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አስታውስ›› ወይም፣ ‹‹አስብ››

የርኅራኄና የኪዳናዊ ታማኝነት ሥራህን
‹‹ርኅራኄ›› እና፣ ‹‹ታማኝነት›› የተሰኙትን የነገር ስሞች ቅጽል ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለኪዳንህ ርኅሩኅና ታማኝ መሆንህን››

እነርሱ ከጥንት የነበሩ ናቸውና
እዚህ ላይ፣ ‹‹እነርሱ›› በማለት ሰውኛ የሚያደርገው የእግዚአብሔርን ርኅራኄና ኪዳናዊ ታማኝነት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አንተ ሁሌም እንደዚያ ነበርህ››

የልጅነቴን ኀጢአት አታስብብኝ
‹‹ኀጢአት›› የሚለውን የነገር ስም፣ ‹‹ኀጢአቴን›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በልጅነቴ ጊዜ አንተ ላይ የፈጸምሁትን በደል››

መተላለፌንም
‹‹መተላለፌንም›› የሚለውን፣ ‹‹ዐመፃየንም›› ማለት ይቻላል። ‹‹አንተ ላይ የፈጸምሁትን ዐመፅ››

አስበኝ
ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። እግዚአብሔር ይረሳል ማለት አይደለም። ጸሐፊው እግዚአብሔርን እየጠየቀ ያለው እንዲያስበው ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አስበኝ›› ወይም፣ ‹‹አስብ››

እንደ ቸርነትህ ብዛት በኪዳናዊ ታማኝነትህ
‹‹ታማኝነት›› እና፣ ‹‹ቸርነት›› የሚለውን ትጽል ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ አንተ ቸር ስለሆንህ በኪዳንህ ታማኝ ሁንልኝ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 25:8

መንገድ... መንገዱ
እግዚአብሔር ከሰው የሚፈልገው አኗኗር እርሱ እንዲሄድ የሚፈልገው መንገድ እንደሆነ ተነግሯል።

ትሑት
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ትሑት ሰዎች›› ወይም፣ ‹‹ትሑት የሆኑ››

Psalms 25:10

የያህዌ መንገድ ሁሉ ቸርነትና እውነት ነው።
‹‹መንገድ›› የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከኪዳኑና ከታማኝነቱ የተነሣ ያህዌ ሁሌም ይወደናል››

በስምህ ምክንያት
‹‹በስምህ›› የሚለው የያህዌን ማንነት ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በማንነትህ›› ወይም፣ ‹‹ሰዎች እንዲያከብሩህ››

ኀጢአቴ ታላቅ ነውና ይቅር በለኝ
‹‹ኀጢአት›› የሚለውን፣ ‹‹ያደረግሁት ኀጢአት›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያደረግሁት ኀጢአት ብዙ ስለሆነ ይቅር በለኝ››

Psalms 25:12

ያህዌን የሚፈራ ሰው ማን ነው?
ይህ ጥያቄ፣ ‹‹ያህዌን የሚፈራውን ሰው›› እንደ አዲስ ርዕሰ ጉዳይ ያስተዋውቃል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌን ስለሚፈራ ሰው እነግራችኃለሁ››

የሚፈራ ሰው... ያስተምረዋል... በመረጠለት... ሕይወቱ... ዘሮቹ
ይህ የሚናገረው ስለ አንድ ሰው አይደለም። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሚፈሩ... ያስተምራቸዋል... በመረጠላቸው... ሕይወታቸው... ዘሮቻቸው››

በመረጠው መንገድ ጌታ ያስተምረዋል
እንዴት መኖር እንዳለበት ያህዌ ሰውን ማስተማሩ መሄድ የሚገባውን መንገድ ለእርሱ መምረጡ እንደሆነ ተነግሯል።

ሕይወቱን በተድላ በደስታ ያሳልፋል
‹‹እግዚአብሔር ያበለጽገዋል›› ወይም፣ ‹‹ጌታ ያበለጽጋቸዋል››

Psalms 25:14

የያህዌ ወዳጆች
‹‹ያህዌ... ወዳጅ ነው›› አንዳንዶች፣ ‹‹ያህዌ ምስጢሩን›› በማለት ተርጉመውታል። ምስጢሩን ለእነርሱ መናገሩ ምን ያህል የጠበቀ ወዳጃቸው መሆኑን ያመለክታል።

ዐይኖቼ ዘወትር ያህዌ ላይ ናቸው
‹‹ዐይኖች›› ማየትን ይወክላሉ። እንዲረዳው ያህዌን እንደሚያይ ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እንዲረዳኝ ሁሌም ያህዌን እመለከታለሁ›› ወይም ‹‹እንዲረዳኝ ሁሌም በያህዌ እታመናለሁ››

እግሮቼን ከመረብ ነጻ ያደርጋልና
መረብ ወጥመድ ነው። አደጋ ላይ ያሉ ሰዎች እግሮቻቸው በመረብ እንደ ተጠላለፉ ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከአደጋ ያወጣኛል››

ወደ እኔ ተመለስ
ያህዌ ትኩረቱን ሰው ላይ ማድረጉ ወደ እርሱ መመለስ እንደሆነ ተነግሯል።

Psalms 25:17

የልቤ መከራ በዝቶአል
‹‹ልብ›› የሰውን ስሜት ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በጣም ከባድ ችግር ደርሶብኛል››

ከጭንቀቴ አውጣኝ
‹‹ከጭንቀቴ አድነኝ›› ይህ ጭንቀት ሰው ከውስጡ የሚወጣበት ነገር እንደሆነ ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከጭንቀቴ ታደገን›› ወይም፣ ‹‹ከጭንቀቴ ፋታ ስጠኝ››

ጭንቀቴ
‹‹ጭንቀት›› የሚለው ቃል የነገር ስም ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሚያስጨንቁኝ ነገሮች›› ወይም፣ ‹‹የሚያስፈሩኝ ነገሮች››

መከራዬን ተመልከት
‹‹መከራዬን ልብ በል››

መከራዬ
‹‹መከራ›› የሚለውን የነገር ስም ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያስጨነቀኝ ነገር›› ወይም፣ ‹‹ምን ያህል እንደ ተጐዳሁ››

ስቃዬ
‹‹ስቃይ›› የሚለውን የነገር ስም ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያስቸገሩኝ ነገሮች››

አምርረው ጠሉኝ
‹‹በጣም ጠሉኝ›› ወይም፣ ‹‹አጥብቀው ጠሉኝ››

Psalms 25:20

አታሳፍረኝ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጠላቶቼ እንዲያሳፍሩኝ አትተዋቸው››

ወደ አንተ እጠጋለሁ!
ለጥበቃ ወደ ያህዌ መሄድ ወደ እርሱ መጠጋት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጥበቃ እንድታደርግልኝ ወደ አንተ እጠጋለሁ››

ታማኝነትና ቅንነት ይጠብቁኝ
‹‹ታማኝነት›› እና፣ ‹‹ቅንነት›› እንደ ሰው የሚጠብቁ ነገሮች እንደሆኑ ተነግሯል። እነዚህን የነገር ስሞች ቅጽል ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ታማኝ መሆኔና ቅን የሆነውን ነገር ማድረጌ ይጠብቁኝ›› ወይም፣ ‹‹ጌታ ሆይ፣ ታማኝና ቅን ስለሆንሁ ጠብቀኝ››

ጠብቀኝ
‹‹አድነኝ››

Psalms 25:22

እስራኤልን ታደገው
‹‹እስራኤልን አድነው›› ‹‹ወይም እስራኤልን ዋጀው››

እስራኤልን... ከመከራዎቹ
እዚህ ላይ ‹‹እስራኤል›› የእስራኤልን ሕዝብ ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የእስራኤልን ሕዝብ... ከመከራዎቻችን››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 26

1 ያህዌ ሆይ፣ ያለ ነቀፋ ተመላልሻለሁና አንተው ፍረደኝ፤ ያለ ማወላውል በያህዌ ተማምኛለሁ። **2** ያህዌ ሆይ፣ ፈትነኝ መርምረኝም የልቤንና የውስጤን ንጽሕና ፈትን! **3** የኪዳን ታማኝነትህ ዘወትር በፊቴ ነው በታማኝነትህም ተመላለስሁ። **4** ከአታላይ ሰዎች ጋር አልተባበርሁም ከማይታመኑ ሰዎችም ጋር አልተቀላቀልሁም። **5** የክፉዎችን ኅብረት ጠላሁ ከዐመፀኞችም ጋር አልተቀመጥሁም። **6** እጆቼን በየዋህነት እታጠባለሁ ያህዌ ሆይ፣ መሠዊያህንም እዞራለሁ **7** የምስጋናህን መዝሙር እየዘመርሁ ድንቅ ሥራዎችህን ሁሉ አወራለሁ። **8** ያህዌ ሆይ፣ የምትኖርበትን ቤት፣ የክብርን ማደሪያ ቦታ ወደድሁ። **9** ነፍሴን ከኃጢአተኞች ጋር፣ ሕይወቴንም ደም ከተጠሙ ጋር አታጥፋ **10** በእነርሱ እጅ የተንኰል ዕቅድ አለ ቀኝ እጃቸውም ጉቦ ያጋብሳል። **11** እኔ ግን በታማኝነት እጓዛለሁ አድነኝ፤ ምሕረትም አድርግልኝ። **12** እግሮቼ በተስተካከለ ምድር ላይ ቆመዋል በጉባኤ ፊት ያህዌን እባርካለሁ።

Psalms 26:1

አጠቃላይ መረጃ
ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው።

የዳዊት መዝሙር
ይህም ማለት፣ 1) መዝሙሩን የጻፈ ዳዊት ነው ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት ነው።

ተመላለስሁ
‹‹መመላለስ›› አኗኗርን የሚያመለክት ምሳሌ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንደ ኖርሁ››

በያህዌ
‹‹ያህዌን›› በተመለከተ በሦስተኛ ሰው ደረጃ የተነገረውን በሁለተኛ ሰው ደረጃ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በአንተ››

ያለ መናወጥ
መጠራጠር ሚዛን መሳትና ወዲያ ወዲህ ማለት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያለ መጠራጠር››

ፈትነኝ
‹‹መርምረኝ››

ልቤንና የውስጤን ንጽሕና መርምር
እዚህ ላይ፣ ‹‹የውስጤ›› እና፣ ‹‹ልቤ›› ዝንባሌን ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ዝንባሌዬ መልካም መሆን አለመሆኑን መርምር››

ኪዳናዊ ታማኝነትህ በዐይኔ ፊት ነውና
እዚህ ላይ፣ ‹‹ዐይን›› የሰውን ሐሳብና አንድን ነገር ዐይን ፊት ማድረግ ስለዚያ ነገር መገንዘብን ያመለክታል። ‹‹ታማኝነት›› የተሰኘውን የነገር ስም እንደ ቅጽል መተጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እኔ ሁልጊዜም ኪዳናዊ ታማኝነትህን እገነዘባለሁ›› ወይም፣ ‹‹አንተ ለኪዳንህ ታማኝ መሆንህን ሁሌም እገነዘባለሁ››

በታማኝነትህ ተመላለስሁ
‹‹መመላለስ›› አኗኗርን ይወክላል። ‹‹ታማኝነት›› የተሰኘውን የነገር ስም እንደ ቅጽል መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሕይወቴን እንደ አንተ ታማኝነት እኖራለሁ›› ወይም፣ ‹‹አሁን እንደምኖረው የምኖረው አንተ ታማኝ ስለሆንህ ነው››

Psalms 26:4

ከ... አልተባበርም
‹‹...ወዳጅ አልሆንም›› ወይም፣ ‹‹ከ... አልቀመጥም››

ከአታላይ ሰዎች
‹‹ሌሎችን ከሚያታልሉ››

ከክፉዎች ሸንጐ ጋር አልተባበርሁም
ይህም ማለት ከዐረፍተ ነገሩ የመጀመሪያ ክፍል ጋር ተመሳሳይ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከሐሰተኞች ጋር አልተባበርሁም››

ሐሰተኞች ሰዎች
‹‹ግብዞች›› ወይም፣ ‹‹የሚዋሹ››

የክፉዎች ሸንጐ
‹‹ክፉ ለማድረግ የሚሰበሰቡ››

ዐመፀኞች
ይህ ቅጽል ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ዐመፀኛ ሰዎች›› ወይም፣ ‹‹ዐመፅ የሚያደርጉ››

Psalms 26:6

እጆቼን በየዋህነት እታጠባለሁ
ይህ ምንም ጎጢአት ወይም በደል አለማድረግን ለማመልከት እጅ የመታጠብን ሥርዐት የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።

መሠዊያህን እዞራለሁ
ይህ እስራኤላውያን የለመዱት አምልኮ ነው።

የምትኖርበትን ቤት
ይህም ማለት፣ 1) ይህ የተጻፈው ከዳዊት ዘመን በኋላ ቢሆን ኖሮ፣ በኢየሩሳሌም ያለውን ቤተ መቅደስ ያመለክት ነበር። ወይም 2) ይህን የጻፈው ዳዊት ከሆነ እርሱን የሚያመልኩበትን ቦታ እንዲሠሩለት ለሕዝቡ የተናገረው ድንኳን ነው ማለት ነው።

ክብርህ የሚኖርበትን
‹‹ክብር›› የሚወክለው የእግዚአብሔርን ሐልዎትና ኀይል ሲሆን፣ በጣም ደማቅ ብርሃን ጋር ይመሳሰላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሕዝብህ የሓልዎትህን ክቡር ብርሃን የሚያዩበትን ቦታ››

Psalms 26:9

ከኀጢአተኞች ጋር አታስወግደኝ
‹‹ማስወገድ›› መደምሰስ ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከኀጢአተኞች ጋር አታጥፋኝ››

ወይም ሕይወቴን
‹‹አታስወግድ›› የሚለው ውስጠ ታዋቂ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ወይም ሕይወቴን አታስወግድ››

ደም ከጠማቸው ጋር
‹‹ደም የጠማቸው›› ሰው መግደል የሚፈልጉ ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የሌሎችን ደም ማፍሰስ ደስ የሚላቸው›› ወይም፣ ‹‹ነፍሰ ገዳዮች››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በእጃቸው
‹‹እጅ›› መላውን ሰው ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የደም ሰዎች››

ሄራ
‹‹ክፉ ዕቅድ››

Psalms 26:11

እኔ ግን
ይህ ሐረግ ጸሐፊው ስለ ክፉ ሰዎች ከመናገር ስለ ራሱ ወደ መናገር መመለሱን ያመለክታል።

በተአማኒ ሕይወት እመላለሳለሁ
‹‹መመላለስ›› አኗኗርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በተአማኒ ሕይወት እኖራለሁ››

እግሮቼ ቆመዋል
‹‹እግሮች›› መላውን ሰው ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እቆማለሁ››

ደልዳላ ስፍራ
‹‹እግሮች›› መላውን ሰው ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እቆማለሁ››

ደልዳላ ስፍራ
‹‹ደልዳላ ስፍራ፣ 1) ደህና ቦታ ማለት ሊሆን ይችላል ወይም 2) መልካም ፀባይ ማለት ሊሆን ይችላል።

በጉባኤ ውስጥ ያህዌን እባርካለሁ
‹‹ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ስሰበሰብ አመሰግንሃለሁ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 27

1 ያህዌ ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው የሚያስፈራኝ ማን ነው? ያህዌ የሕይወቴ መታመኛዋ ነው የሚያስደነግጠኝ ማን ነው? **2** ክፉ አድራጊዎች ሥጋዬን ለመብላት
በቀረቡኝ ጊዜ፣ ባላጋራዎቼና ጠላቶቼ ተሰነካክለው ወደቁ። **3** ሰራዊት ቢከብበኝ እንኳ፣ ልቤ አይፈራም ጦርነት ቢነሣብኝ እንኳ ልበ ሙሉ ነኝ። **4** ያህዌን አንዲት
ነገር ለመንሁት፣ እርሷንም እሻለሁ፤ ያም በሕይወቴ ዘመን ሁሉ በያህዌ ቤት እንድኖር፣ የመቅደሱን ውበት እንዳይና መቅደሱ ውስጥ አሰላስል ዘንድ ነው። **5**
በመከራዬ ቀን በድንኳኑ ይሰውረኛናል በዐለትም ላይ ያቆመኛል። **6** ያኔ በዙሪያዬ ባሉ ጠላቶቼ ላይ ራሴ ከፍ ከፍ ይላል በድንኳኑም የደስታ መሥዋዕት እሠዋለሁ
ለያህዌ እቀኛለሁ፤ እዘምርለታለሁም። **7** ያህዌ ሆይ፣ ወደ አንተ ስጮኽ ድምፄን ስማ ማረኝ መልስልኝም። **8** «ፊቴን ፈልጉ» ባልህ ጊዜ ልቤ፣ «የያህዌን ፊት
እፈልጋለሁ» አለች። **9** ፊትህን ከእኔ አትሰውር ተቆጥተህም ባርያህን ገሸሽ አታድርገው! መቼም አንተ ረዳቴ ነህና የመድኃኒቴ አምላክ ሆይ፣ አትተወኝ፣
አትጣለኝም **10** አባትና እናቴ ቢተውኝ እንኳ ያህዌ ይቀበለኛል። **11** ያህዌ ሆይ መንገድህን አስተምረኝ ስለ ጠላቶቼም በቀናች መንገድ ምራኝ። **12** ሐሰተኛ
ምስክሮች ተነሥተውብኛልና ጠላቶቼ እንደ ፈለጉ እንዲያደርጉብኝ አትተወኝ። እነርሱ ዐመፃን ይረጫሉ! **13** በሕያዋን ምድር የያህዌን መልካምነት እንደማይ
ባላምን ኖሮ ምን እሆን ነበር? **14** እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ አይዞህ በርታ እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ

Psalms 27:1

አጠቃላይ መረጃ
ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው።

የዳዊት መዝሙር
ይህም ማለት፣ 1) መዝሙሩን የጻፈ ዳዊት ነው ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት ነው።

ያህዌ ብርሃኔ ነው
እዚህ ላይ ‹‹ብርሃን›› ሕይወትን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ የሕይወቴ ምንጭ ነው››

ማንን እፈራለሁ?
ጥያቄው ዳዊት የሚፈራው አለመኖሩን አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ማንንም አልፈራም››

ያህዌ የሕይወቴ መጠጊያ ነው
ይህ ያህዌ ሰዎች የሚጠጉበት ቦታ እንደሆነ ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በሰላም እንድኖር የሚጠብቀኝ ያህዌ ነው››

የሚያስደነግጠኝ ማን ነው?
ጥያቄው ዳዊትን የሚያስደነግጠው ነገር አለመኖሩን አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የሚያስደነግጠኝ የለም››

Psalms 27:2

ሥጋዬን ለመብላት
አንድን ሰው ጨርሶ ማጥፋት የእርሱን ሥጋ መብላት እንደሆነ ተነግሯል። ቃል በቃል ሥጋውን ይበላሉ ማለት አይደለም። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሊያጠፉኝ››

ባላጋራዎቼና ጠላቶቼ
ሁለቱም ቃሎች ተመሳሳይ ናቸው። እነዚህ ወደ እርሱ የቀረቡ ክፉ አድራጊዎች ናቸው።

ተሰናክለው ወደቁ
ይህ የሚያመለክተው የጸሐፊው ጠላቶች እርሱን የማጥፋት ዕቅዳቸው አለመሳካቱን ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አልተሳካላቸውም›› ወይም፣ ‹‹ፈረሰባቸው››

ሰራዊት ቢሰፍርብኝ እንኳ
‹‹ሰራዊት ቢከበኝ እንኳ›› ወይም ‹‹ሰራዊት ድንኳኑን በዙሪያየ ቢያደርግ እንኳ››

ልቤ አይፈራም
‹‹ልብ›› መላውን ሰው ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አልፈራም››

ጦርነት ቢነሣብኝ እንኳ
የጸሐፊው ጠላቶች ራሳቸው ጦርነት እንደሆኑ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጠላቶቼ ሊወጉኝ ቢመጡ እንኳ››

ልበ ሙሉ ነኝ
‹‹እግዚአብሔር እንደሚረዳኝ እተማመናለሁ››

Psalms 27:4

ያህዌን እጠይቀዋለሁ
‹‹ያንን እንዳገኝ ያህዌን እጠይቀዋለሁ››

እርሷን እሻለሁ
አጥብቆ አንድን ነገር የሚፈልግና ያንን እንዲሰጠው ዘወትር ያህዌን የሚለምን ሰው አንድን ነገር ማግኘት እንደሚፈልግ ሰው እንደሆነ ተነግሯል።

የያህዌን ውበት ለማየት
አስደናቂው የእግዚአብሔር ባሕርይ ውበት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ እጅግ ድንቅ መሆኑን እንዳይ››

መቅደሱ ውስጥ እንዳሰላስል
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ያህዌ ከእኔ የሚፈልገውን ለመጠየቅ›› ወይም 2) ‹‹መቅደሱ ውስጥ ስለ እግዚአብሔር ረጋ ብዬ እንዳስብ››

Psalms 27:5

በመከራ ቀን
‹‹በመከራ ጊዜ›› ወይም፣ ‹‹መከራ ሲደርስብኝ››

እንዲሰውረኝ
‹‹እንዲደብቀኝ››

መሸሸጊያው... ድንኳኑ
ሁለቱም የሚያመለክቱት ጸሐፊው እግዚአብሔርን የሚያመልክበትን መገናኛ ድንኳን ነው።

በድንኳኑ መሸፈኛ
‹‹መሸፈኛ›› የሚለው ቃል የሚያመለክተው መደበቂያና መሸሸጊያ ቦታ ነው።

በዐለት ላይ ያነሣኛል
እግዚአብሔር ጸሐፊውን ከጠላቶቹ ማዳኑ ጠላቶቹ የማይደርሱበት ከፍ ያለ ዐለት ላይ እንዳደረገው መሆኑ ተነግሯል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ራሴ ከጠላቶቼ በላይ ከፍ ይላል
ይህ የሚያመለክተው ጠላቶቹን ሲያሸንፍ ጸሐፊው ያገኘውን ኩራት ወይም ክብር ነው። በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጠላቶቼን ሳሸንፍ ሰዎች ያከብሩኛል›› ወይም፣ ‹‹ጠላቶቼን እንዳሸንፍ በማድረግ እግዚአብሔር ያከብረኛል።››

Psalms 27:7

ያህዌ፣ ድምፄን ስማ
‹‹ድምፅ›› የሚናገር ወይም የሚጣራ ሰውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ሰማኝ››

መልስልኝ
ይህ የሚያመለክተው ያህዌ የጸሐፊውን ጸሎት እንደሚሰማና የለመነውን እንደሚያደርግለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጸሎቴን መልስ›› ወይም፣ ‹‹የለመንሁህን አድርግልኝ››

ልቤ ይላል
‹‹ልብ›› የሰውን አእምሮና ሐሳብ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በልቤ አልሁ›› ወይም፣ ‹‹ለራሴ አልሁ››

ፊቱን ፈለግሁ
ወደ ያህዌ ለመጸለይ ወደ ቤተ መቅደስ የሚሄድ ሰው ያህዌን ለመፈለግ እንደሚሄድ ሰው እንደሆነ ተነግሯል። እዚህ ላይ፣ ‹‹ፊት›› የእግዚአብሔርን ሁለንተና ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለጸሎት ወደ ቤተ መቅደስህ እመጣለሁ››

ያህዌ ሆይ ፊትህን እሻለሁ
ወደ ያህዌ ለመጸለይ ወደ ቤተ መቅደስ የሚሄድ ሰው ያህዌን እንደሚፈልግ ተነግሯል። እዚህ ላይ ‹‹ፊት›› የእግዚአብሔርን ሁለንታ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወደ አንተ ለመጸለይ ወደ ቤተ መቅደስህ እመጣለሁ››

Psalms 27:9

ፊትህን ከእኔ አትሰውር
እዚህ ላይ፣ ‹‹ፊት›› የያህዌን ትኩረት ይወክላል፤ ፊትን መሰወር ችላ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ችላ አትበለኝ›› ወይም፣ ‹‹ለእኔ ማሰብህን አትተው››

ተቆጥተህ ከባርያህ ዘወር አትበል
ዳዊት ትሕትናውን ለማሳየት ራሱን፣ ‹‹ባርያህ›› ይላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አትቆጣኝ››

አትጣለኝ፤ አትተወኝ
‹‹መጣል›› እና፣ ‹‹መተው›› ሁለቱም ተመሳሳይ ናቸው። ጸሐፊው እግዚአብሔር እንዲተወው እንደማይፈልግ አጥብቆ ይናገራል።

ወይም አትተወኝ
‹‹እኔን›› የሚለው ውስጠ ታዋቂ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔን አትተወኝ›› ወይም፣ ‹‹እኔን አትጣለኝ››

የመዳኔ አምላክ
‹‹መዳኔ›› የሚለውን፣ ‹‹የምታድነኝ›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የምታድነኝ አምላክ›› ወይም፣ ‹‹የምታድነኝ አንተ ስለሆንህ››

አባትና እናቴ ቢተውኝ እንኳ
‹‹አባትና እናቴ የሚተውኝ ቢሆን እንኳ››፤ እንዲህ አድርገዋል ወይም ያደርጋሉ ማለቱ አይደለም። ዋናው ነጥብ ያንን ቢያደርጉ እንኳ እግዚአብሔር እንደማይተወው መናገሩ ነው።

ያህዌ ይቀበለኛል
‹‹ያህዌ ይጠብቀኛል›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ይጠነቀቅልኛል››

Psalms 27:11

መንገድህን አስተምረኝ
የሰው አኗኗር የሚሄድበት መንገድ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንድኖር የምትፈልገውን አስተምረኝ›› ወይም፣ ‹‹እንዳደርግ የምትፈልገውን አስተምረኝ››

በደልዳላ መንገድ ምራኝ
ያህዌ ጸሐፊውን ከጠላቶቹ መጠበቁ መሰናከል ወይም መውደቅ በማይችልበት መንገድ እርሱን መምራት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጠብቀኝ››

ለጠላቶቼ ፍላጎት አሳልፈህ አትስጠኝ
ፍላጎት የሚለውን የነገር ስም ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጠላቶቼ የሚፈልጉትን እንዲያደርጉብኝ አሳልፈህ አትስጠኝ››

ተነሥተውብኛል
እዚህ ላይ ‹‹መነሣት›› ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን፣ ከሳሾች ክስ ለማቅረብ ፍርድ ቤት ውስጥ ቆመዋል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ ላይ ክፉ ለመናገር ቆመዋል››

ዐመፅን ይረጫሉ
ዐመፅ የሚረጭ ነገር እንደሆነ እዚህ ላይ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ ላይ ክፉ ነገር እንደሚያደርጉ ይናገራሉ››

Psalms 27:13

እኔ ላይ ምን ይሆናል
ጥያቄውን በሌላ መልኩ ማቅረብ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንድ ክፉ ነገር ይደርስብኛል››

የያህዌን ቸርነት
‹‹ቸርነት›› የሚለውን እንደ ቅጽል ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ የሚያደርገው መልካም ነገር››

በሕያዋን ምድር
ይህ የሚያመለክተው በሕይወት መኖርን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሕይወት እያለሁ››

ያህዌን ጠብቅ... ያህዌን ጠብቅ!
በዚህ ጥቅስ፣ 1) ጸሐፊው ለራሱ እየተናገረ ነው ወይም 2) ጸሐፊው ለሌሎች እየተናገረ ነው ወይም 3) ሌላ ሰው ለጸሐፊው እየተናገረ ሊሆን ይችላል።

ልብህ ይበርታ
‹‹ልብ›› መላውን ሰው ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በርታ››

ያህዌን ጠብቀው!
የመዝሙሩ መደምደሚያ እንዲሆን ይህ ቃል መጨረሻ ላይ ተነግሯል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 28

1 ያህዌ ሆይ፤ ወደ አንተ እጣራለሁ፤ ዐለቴ ሆይ፣ ችላ አትበለኝ። አንተ ዝም ካልኸኝ ወደ መቃብር ከሚወርዱ ጋር እሆናለሁ። **2** እንድትረዳኝ ወደ አንተ በጮኽኩ
ጊዜ እጆቼን ወደ ቅዱስ ማደሪያህ በዘረጋሁ ጊዜ የልመኛዬን ቃል ስማ። **3** ከዐመፀኞች ጋር፣ ክፋትን ከሚያደርጉ ጋር፣ በልባቸው ክፉ ሐሳብ እያለ
ከባልንጀራቸው ጋር በሰላም ከሚናገሩ ጋር ጐትተህ አትውሰደኝ። **4** የእጃቸውን ስጣቸው፣ እንደ ዐመፃቸውም ክፈላቸው እንደ ክፉ ተግባራቸው መልስቸው። **5**
ለያህዌ ሥራ ግድ ስለሌላቸው፣ ለእጆቹም ተግባር ስፍራ ስላልሰጡ እርሱ ያፈርሳቸዋል፤ መልሶም አይሠራቸውም። **6** የልመናዬን ቃል ሰምቶአልና ያህዌ
ይባረክ። **7** ያህዌ ብርታቴና ጋሻዬ ነው ልቤ በእርሱ ይተማመናል፤ እርሱም ረዳኝ። ስለዚህ ልቤ ሐሤት አደረገ፤ በዝማሬም አመሰግነዋለሁ። **8** ያህዌ የሕዝቡ
ብርታታቸው ነው ለቀባውም የመዳን ዐምባ ነው። **9** ሕዝብህን አድንን ርስትህንም ባርክ እረኛ ሁናቸው፤ ለዘላለሙም ተንከባከባቸው።

Psalms 28:3

አታርቀኝ
እግዚአብሔር ሰዎችን መቅጣቱ እነርሱን ማራቅ እንደሆነ ተነግሯል። በዚህ ምሳሌያዊ ቋንቋ ያህዌ ወደ እስር ቤት፣ ምርኮ ወይም ሞት እያራቃቸው እንደሆነ ሊያመለክት ይችላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አታስወግደኝ››

ከባልንጀሮቻቸው ጋር ሰላም ከሚናገሩ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ባልንጀራ›› ሰዎችን ሁሉ ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከሰዎች ጋር ሰላም ከሚናገሩ››

በልባቸው ተንኰል እያለ
‹‹ልብ›› የሰውን አእምሮና ሐሳብ ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ግን ስለ እነርሱ ክፉ ከሚያስቡ››

እንደ ተግባራቸው ስጣቸው... እንደ ክፋታቸው መጠን ክፈላቸው
ሁለቱም ሐረጐች ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። በአንድነት የተነገሩት እግዚአብሔር ሊቀጣቸው እንደሚገባ አጽንዖት ለመስጠት ነው።

እንደ እጆቻቸው ሥራ
‹‹እጅ›› ሰው የሚያደርገውን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንዳደረጉት ነገር››

አጸፋውን መልስላቸው
‹‹የሚገባቸውን ሰጣቸው››

አልተረዱምና... አይገነባቸውም
ይህም ማለት፣ 1) እግዚአብሔር ክፉዎች ላይ ስለሚያደርገው ነገር ዳዊት እርግጠኛ ነው ወይም 2) ዳዊት እግዚአብሔር ክፉዎችን እንዲያጠፋ እየለመነ ነው።

የያህዌን ሥራ አልተረዱምና
‹‹አልተረዱምና›› ሲል ችላ ብለዋል ወይም የያህዌን ሥራ ማክበር አልፈለጉም ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ ያደረገውን በክብር አላዩምና››

የእጆቹን ሥራ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጆች›› ያህዌ ያደረገውን ወይም የፈጠረውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እርሱ የፈጠረውን››

ያፈርሳቸዋል፤ መልሶም አይገነባቸውም
የክፉ ሰዎች መቀጣት እነርሱ እግዚአብሔር የሚያፈርሰው ሕንፃ ወይም ከተማ እንደሆኑ ተነግሯል።

Psalms 28:6

የልመናዬን ድምፅ ሰምቷል
እዚህ ላይ፣ ‹‹ድምፅ›› ጸሐፊው የተናገረውን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እርሱን ስለምን የተናገርሁትን ሰማ››

ያህዌ ብርታቴ ነው
‹‹ብርታት›› የሚለውን የነገር ስም፣ ‹‹ብርቱ›› በማለት መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ ብርቱ ያደርገኛል››

ጋሻዬ
ይህ የሚያመለክተው ያህዌ ጸሐፊውን ይጠብቀው እንደ ነበር ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እርሱ ይጠብቀኛል››

ልቤ ይታመናል
‹‹ልብ›› መላውን ሰው ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እታመናለሁ››

ተረዳሁ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እርሱ ረዳኝ››

ልቤ ሐሤት አደረገ
‹‹ልብ›› መላውን ሰው ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በጣም ደስ አለኝ››

ያህዌ ለሕዝቡ ብርታታቸው ነው
‹‹ብርታት›› የሚለውን የነገር ስም፣ ‹‹ብርቱ›› በማለት መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ ሕዝቡን ብርቱ ያደርጋል››

ለቀባውም የመዳን ዐምባ ነው
ያህዌ ንጉሡን በሰላም መጠበቁ ያህዌ ንጉሡ ሄዶ የሚሸሸግበት ቦታ እንደ ሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እርሱ ንጉሥ እንዲሆን የቀባውን በደህና ይጠብቀዋል››

ለቀባው
ይህ የሚያመለክተው ንጉሡን ነው።

Psalms 28:9

ርስትህ
ይህ የእግዚአብሔር ሕዝብ የእግዚአብሔር ርስት እንደሆነ ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ንብረትህ›› ወይም፣ ‹‹የአንተ የሆኑት››

እረኛ ሁናቸው ለዘላለሙም ዐቅፈህ ያዛቸው
ጸሐፊው ያህዌ እረኛቸው ሕዝቡ ደግሞ በጐቹ እንደሆኑ ይናገራል። በጉ ርዳታ ወይም ጥበቃ ከፈለገ እረኛው ይሸከመዋል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንደ እረኛ ሆነህ ለዘላለሙ ጠብቃቸው››

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 29

1 እናንተ የእግዚአብሔር ልጆች ለያህዌ ምስጋና ስጡ ስለ ክብሩና ስለ ብርታቱ ለያህዌ ምስጋና ስጡ። **2** ለስሙ የሚገባውን ክብር ለያህዌ ስጡ በቅድስናው
ውበት ለያህዌ ስገዱ **3** የያህዌ ድምፅ በውሆች ላይ ያስተጋባል የክብር አምላክ ያንጐዳጉዳል ያህዌ በብዙ ውሆች ላይ ድምፁን ያሰማል። **4** የያህዌ ድምፅ
ኃያል ነው የያህዌ ድምፅ ባለ ግርማ ነው። **5** የያህዌ ድምፅ የሊባኖስን ዝግባ ይሰብራል **6** ሊባኖን እንደ ጥጃ፣ ስርዮንን እንደ ኮርማ ያዘልላል። **7** የያህዌ ድምፅ
የእሳት ነበልባል ይረጫል **8** የያህዌ ድምፅ ምድረ በዳውን ያናውጣል የያህዌ ድምፅ የቃዴስን ምድረ በዳ ያናውጣል። **9** የያህዌ ድምፅ ወርካዎችን ይወዘውዛል
ጫካዎችን ይመነጥራል። ሁሉም በእርሱ ቤተ መቅደስ፣ «ክብር!» ይላል። **10** ያህዌ በጐርፍ ላይ ዙፋኑን ዘርግቶ ተቀምጧል ያህዌ ለዘላለም ይነግሣል። **11**
ያህዌ ለሕዝቡ ብርታት ይሰጣል ያህዌ ሕዝቡን በሰላም ይባርካል።

Psalms 29:1

አጠቃላይ መረጃ
ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው።

የዳዊት መዝሙር
ይህም ማለት፣ 1) መዝሙሩን የጻፈ ዳዊት ነው ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት ነው ማለት ሊሆን ይችላል።

እናንት የእግዚአብሔር ልጆች
‹‹ልጆች›› የሚለው፣ ‹‹ባሕርዩ ያላችሁ›› እንደ ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እናንት ኀያላን››

ለያህዌ ክብርንና ብርታትን ስጡ
‹‹ክብር›› እና፣ ‹‹ብርታት›› የተሰኙትን የነገር ስሞች እንደ ቅጽል ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እርሱ የከበረና ብርቱ ስለሆነ ያህዌን አመስግኑ››

ለስሙ የሚገባውን ክብር ለያህዌ አምጡ
‹‹ክብር›› የሚለውን የነገር ስም ግሥ ወይም ቅጽል ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ለስሙ እንደሚገባው ያህዌን አክብሩ›› ወይም፣ ‹‹ለስሙ እንደሚገባው ያህዌ ክቡር መሆኑን ተናገሩ››

ለስሙ የሚገባውን
‹‹ለስሙ›› የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ያህዌን ወይም ማንነቱን ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ለማንነቱ ተገቢ የሆነው››

ለያህዌ ዝቅ በሉ
ይህ ሕዝቡ ለአምልኮ ዝቅ ማለት እንዳለባቸው ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌን ለማምለክ ዝቅ በሉ››

በቅድስናው ግርማ
‹‹ቅድስና›› እና፣ ‹‹ግርማ›› የተሰኙትን የነገር ስሞች እንደ ቅጽል መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እርሱ የከበረ ውብና ቅዱስ በመሆኑ››

Psalms 29:3

አጠቃላይ መረጃ
መዝሙሩ የያህዌን ኀይልና ክብር ያሳያል።

የያህዌ ድምፅ በውሆች ላይ ይሰማል
የእግዚአብሔር ድምፅ ከሌሎች ጫጫታዎች ሁሉ ይልቅ ጮኽ ያለና ጥርት ያለ ነው። የውሆችን ድምፅ ከመሳሰሉ ሌሎች ድምፆች በላይ ከፍ ብሎ ይሰማል። ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ በሚናገርበት ጊዜ ድምፁ ከባሕር ድምፅ ይልቅ ጮኽ ብሎ ይሰማል››

በውሆች ላይ
ይህ ባሕሮችን ወይም ውቅያኖሶችን ያመለክታል። ማዕበሉ ሲነሣና ሲወድቅ እነዚህ ውሆች በጣም ከፍ ያለ ድምፅ ይኖራቸዋል።

የያህዌ ድምፅ
እዚህ ላይ ያለ፣ ‹‹ድምፅ›› ሁሉ የያህዌን ንግግር ይወክላል። ያህዌ ሲናገር ድምፁ ከፍ ያለ በመሆኑ በውሆች ላይ እንደሚሰማና ኀያል በመሆኑም ታላላቅ ዛፎችን እንደሚሰብር ጸሐፊው አጽንዖት ሰጥቶ ይናገራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ ሲናገር ድምፁ››

የክብር አምላክ አንጐዳጐደ
ይህ እግዚአብሔር ሲናገር ድምፁ እንደ መብረቅ ድምፅ እንደሆነ ያመለክታል። እንደ መብረቅ ድምፅ የያህዌም ድምፅ በጣም ከሩቅ ይሰማል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የክብር አምላክ ድምፅ እንደ መብረቅ ድምፅ ከፍ ያለ ነው›› ወይም፣ ‹‹ክቡር አምላኬ ሲናገር እንደ መብረቅ ያንጐዳጉዳል››

በብዙ ውሆች ላይ
‹‹በሰፊ ውሆች አካል ላይ››

Psalms 29:6

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር ድምፅ ኀይል መናገር ቀጥሏል።

ሊባኖስን እንደ ጥጃ ያዘልለዋል
የሊባኖስ ምድር መናወጥ እንደሚዘልል ጥጃ ተደርጐ ተነግሯል። ይህ አጽንዖት የሚሰጠው ያህዌ ሲናገር የድምፁ ኀይል ምድሩን እንደሚያናውጥ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የሊባኖስን ምድር እንደ ጥጃ ያዘልለዋል››

መዝለል
ወደ ፊትና ወደ ኃላ ቀለል ያለ ዝላይ

ሰርዮንንም እንደ ኮርማ
‹‹ያደርገዋል›› እና፣ ‹‹ያዘልለዋል›› የሚለው ከመጀመሪያው ሐረግ ውስጠ ታዋቂ ነው። እዚህ ላይ መደገም ይችላሉ። የሰርዮን ምድር መናወጥ እንደሚዘልል ኮርማ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሰርዮንን እንደ ኮርማ ያዘልለዋል››

ሰርዮን
ይህ ሊባኖስ ውስጥ ያለ ተራራ ነው። የሄርሞን ተራራ ተብሎም ይጠራል።

የያህዌ ድምፅ የእሳት ነበልባል ይረጫል
እዚህ ያለ ‹‹ድምፅ›› ሁሉ የያህዌን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ ሲናገር ሰማዩ ላይ መብረቅ እንደሚያበራ ያደርጋል››

የእሳት ነበልባል
ይህ የሚያመለክተው መብረቅን ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 29:9

የያህዌ ድምፅ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ድምፅ›› የያህዌን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ ሲናገር ድምፁ››

ወርካዎችን ይወዘውዛል
‹‹ትልልቅ ዛፎች ይናወጣሉ››

ጫካዎችን ያራቁታል
የዛፎቹ ቅጠሎች መወገድ እነርሱን መመንጠር ወይም ልብስ ማስወለቅ እንደ ሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ቅጠሎቹ ከዛፎቹ ላይ እንዲረግፉ ያደርጋል።››

ያህዌ እንደ ንጉሥ ተቀምጧል
ይህ ያህዌ ይገዛል ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ ይገዛል›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ንጉሥ ነው››

በጐርፍ ላይ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ጐርፍ›› ምድርን የሚሸፍን ውሃ ነው።

Psalms 29:11

ያህዌ ሕዝቡን በሰላም ይባርካል
‹‹ሰላም›› የሚለው ቃል የነገር ስም ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እነርሱን በማበልጸግና በሰላም እንዲኖሩ በማድረግ ያህዌ ሕዝቡን ይባርካል››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 30

1 ያህዌ ሆይ፣ አንተ አንሥተኸኛልና ጠላቶቼም በእኔ ላይ ደስ እንዲላቸው አላደረግህምና ከፍ ከፍ አደርግሃለሁ። **2** ያህዌ ሆይ፣ እንድትረዳኝ ወደ አንተ ጮኽሁ አንተም ፈውሰኸኝ። **3** ያህዌ ሆይ፣ ነፍሴን ከሲኦል አወጣሃት ወደ መቃብር ከመውረድም አዳንኸኝ። **4** እናንት የእርሱ ታማኝ ሕዝቦች ለያህዌ የምስጋና መዝሙር አቅርቡ፤ ቅድስናውን ስታስታውሱ፣ ውዳሴ ስጡ። **5** ቁጣው ለአጭር ጊዜ ነው ሞገሱ ግን ለዕድሜ ልክ ነው። ሌሊት ሲለቀስ አድሮ ማለዳ ደስታ ይሆናል። **6** በልበ ሙሉነት «አልናወጥም!» አልሁ። **7** ያህዌ ሆይ በሞገስህ እንደ ተራራ ብርቱ አደረግኸኝ ፊትህን ስትሰውር ግን ውስጤ ታወከ። **8** ያህዌ፣ ወደ አንተ ጮኽሁ፤ ከጌታም ዘንድ ሞገስ ፈለግሁ። **9** እኔ ብሞት፣ ወደ መቃብርም ብወርድ ምን ጥቅም አለው? አፈር ያመሰግንሃልን? ታማኝነትህንስ ይናገራልን? **10** ያህዌ ሆይ፣ ስማኝ ማረኝም፣ ያህዌ ረዳት ሁነኝ። **11** ዋይታዬን ወደ ሸብሸባ ለወጥህልኝ ማቄን አስወግደህ ደስታን አለበስከኝ። **12** እንግዲህ፣ ነፍሴ ታመስግንህ፤ ዝምም አትበል። አምላኬ ያህዌ ሆይ፣ ለዘላለም አመሰግንሃለሁ።

Psalms 30:1

አጠቃላይ መረጃ
ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው

በቤተ መቅደሱ ምረቃ ጊዜ የተዘመረ
‹‹ይህ መዝሙር የተዘመረው ቤተ መቅደሱ የተመረቀ ጊዜ ነበር››

የዳዊት መዝሙር
ይህም ማለት 1) መዝሙን የጻፈ ዳዊት ነበር፣ ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት ነው።

አንሥተኸኛልና
እግዚአብሔር እርሱን መታደጉና ከሞት ማዳኑ እርሱን ከጥልቅ ጉድጓድ ማውጣት እንደሆነ ጸሐፊው ይናገራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አንተ ታደግኸኝ››

ነፍሴን ከሲኦል አወጣት
‹‹ሲኦል›› የሞቱ ሰዎች የሚሄዱበት ስፍራ ስለሆነ ሞትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከሞት አዳነኝ››

ነፍሴን አወጣት
‹‹ነፍሴ›› የሚለው የሚያመለክተው ጸሐፊውን ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አወጣኝ››

ወደ መቃብር ከመውረድ
‹‹መቃብር›› ሞትን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከመሞት››

Psalms 30:4

ቅድስናውን ስታስታውሱ አመስግኑ
‹‹ቅድስና›› እና፣ ‹‹ማመስገን›› የተሰኙትን የነገር ስሞች፣ ‹‹ምስጋና›› እና፣ ‹‹ቅዱስ›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እግዚአብሔር ቅዱስ መሆኑን አስታውሱ ስለዚህ አመስግኑ›› ወይም፣ ‹‹ቅዱስ ከመሆኑ የተነሣ እግዚአብሔር ያደረገውን አስታውሱ፤ ስለዚህ አመስግኑት››

ቁጣው ለአጭር ጊዜ ነው
‹‹ቁጣው የሚቆየው ለአጭር ጊዜ ነው›› ‹‹ቁጣ›› የሚለውን የነገር ስም፣ ‹‹መቆጣት›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የሚቆጣው ለአጭር ጊዜ ብቻ ነው››

ለአጭር ጊዜ
‹‹ለአጭር ጊዜ›› ለጊዜው ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ለጊዜው››

ሞገሱ ግን ለሕይወት ዘመን ነው
‹‹ሞገስ›› የሚለውን የነገር ስም፣ ‹‹ቸርነት›› በሚል ቅጽል መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በሕይወት ዘመናችን ሁሉ እርሱ ቸር ነው››

ለቅሶ ማታ ይመጣል፤ ደስታ ግን ጠዋት ይመጣል
ይህ፣ ‹‹ለቅሶ›› እና ‹‹ደስታ›› በተወሰነ ጊዜ የሚመጡ ነገሮች እንደሆነ ተነግሯል›› አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ማታ እናለቅስ ይሆናል ጠዋት ግን ደስ ይለናል››

Psalms 30:6

ተረጋጋሁ
‹‹መረጋጋት›› የሚለው ቃል የነገር ስም ነው። ጸሐፊው የበለጸገበትንና ሁሌም መልካም የነበረበትን ጊዜ ያስታውሳል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በተረጋጋሁ ጊዜ›› ወይም፣ ‹‹የተረጋጋሁ በመሰለኝ ጊዜ››

አልናወጥም
‹‹መናወጥ›› መሸነፍን የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ማንም አያሸንፈኝም››

በሞገስህ
‹‹በሞገስህ›› የተሰኘውን የነገር ስም፣ ‹‹ሞገስ›› ወይም፣ ‹‹ቸርነት›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሞገስ ስለሆንኸኝ›› ወይም፣ ‹‹ለእኔ ቸር ስትሆን››

እንደ ብርቱ ተራራ አጸናኸኝ
ጸሐፊው የሚሰማውን ደህንነት ከብርቱ ተራራ ጋር አመሳስሎታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከፍ እንዳለ ተራራ ደህንነት እንዲሰማኝ አደረግህ››

ፊትህን በሰወርህ ጊዜ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እኔን መርዳት በተውህ ጊዜ›› ወይም፣ ‹‹ችላ ያልኸኝ ጊዜ››

ታወክሁ
‹‹ፈራሁ›› ወይም፣ ‹‹ተጨነቅሁ››

ከጌታዬ ሞገስ ፈለግሁ
‹‹ሞገስ ፈለግሁ›› የሚለው ርዳታ ለመንሁ ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንድትረዳኝ ለመንሁ››

ከጌታዬ
ጸሐፊው ያህዌን በሦስተኛ ሰው ደረጃ ያመለክታል። በሁለተኛ ሰው ደረጃ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጌታዬ ሆይ፣ ከአንተ››

Psalms 30:9

በመሞቴና ወደ መቃብር በመውረዴ ምን ጥቅም ይገኛል?
ጸሐፊ ይህን ጥያቄ ያቀረበው የእርሱ መሞት ለእግዚአብሔር ጥቅም እንደሌለው አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ብሞትና ወደ መቃብር ብወርድ ምንም ጥቅም የለም››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ዐፈር ያመሰግንሃልን? ታማኝነትህንስ ይናገራልን?
ጸሐፊው ይህን ጥያቄ ያቀረበው የእርሱ መሞትና መበስበስ እግዚአብሔርን እንደማያመሰግን አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ዐፈር በእርግጥ አያመሰግንህም፤ ታማኝ መሆንህንም ለሌሎች አይናገርም››

ዐፈር
ይህ የሚያመለክተው ሲሞት ዐፈር የሚሆነውን የጸሐፊውን ሰውነት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሚበሰብስ አካሌ››

Psalms 30:11

ዋይታዬን ወደ ሽብሸባ ለወጥህልኝ
በጣም ደስ ሲለቸው ማሸብሸብ በአይሁድ ባሕል የተለመደ ነበር። ‹‹ዋይታ›› እና ‹‹ማሸብሸብ›› እንደ ግሥ ማቅረብ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ዋይታዬን ትቼ ደስ ብሎኝ እንዳሸበሸብ አደረግህ››

ማቄን አስወገድህ
ማቅ ከዋይታና ከሐዘን ጋር የተያያዘ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከእንግዲህ እንዳላዝን አደረግህ››

ደስታን አለበስኸኝ
ደስታ እንደ ልብስ የሚለበስ ነገር እንደሆነ ጸሐፊው ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ደስ አሰኘኸኝ››

ክብሬ ምስጋናህን ይዘምራል
‹‹ክብሬ›› የሚለው የጸሐፊውን ነፍስ፣ ልብ ወይም ውስጣዊ ሰውነት ያመለክታል። ይህ ደስ ስላሰኘው እግዚአብሔርን እያመለከ ያለውን የጸሐፊውን ሙሉ ሰውነት ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ምስጋና እዘምርልሃለሁ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 31

1 ያህዌ ሆይ፣ አንተን ተማጽኛለሁና እፍረት ከቶ አይድረስብኝ፤ በጽድቅህም ታደገኝ። **2** ጌታ ሆይ፣ አድምጠኝ ፈጥነህም ታደገኝ የመማጸኛ ዐለት፣ የመዳኛም ምሽግ ሁነኝ። **3** አንተ ዐለቴና ዐምባዬ ነህ ስለ ስምህ ስትል ምራኝ መንገዱንም አሳየኝ። **4** አንተ መታመኛዬ ነህና በስውር ከተዘረጋብኝ ወጥመድ አውጣኝ። **5** መንፈሴን በእጅህ ዐደራ እሰጣለሁ የእውነት አምላክ ያህዌ ሆይ፣ ተቤዠኝ። **6** ከንቱ ጣዖታትን የሚያገለግሉትን ጠላሁ እኔ ግን በያህዌ እታመናለሁ። **7** መከራዬን አይተሃልና የነፍሴን ጭንቀት ዐውቀሃልና እኔ በኪዳን ታማኝነትህ ደስ ይለኛል፤ ሐሤትም አድርጋለሁ። **8** በጠላቴ እጅ አሳልፈህ አልሰጠኸኝም እግሮቼን ሰፊ ቦታ ላይ አቆምሃቸው። **9** ያህዌ ሆይ፣ ጭንቀት ውስጥ ነኝና ማረኝ ዐይኖቼ በሐዘን ደክመዋል፤ ነፍስና ሥጋዬም ዝለዋል። **10** ሕይወቴ በጭንቀት ዕድሜዬም በመቃተት አለቀ። ከኃጢአቴ የተነሣ ጉልበቴ ከዳኝ ዐጥንቴም ደቀቀ። **11** ከጠላቶቼ ሁሉ የተነሣ ለጐረቤቶቼ መዘባበቻ ለሚያውቁኝ ሰዎች መሳለቂያ ሆኛለሁ መንገድ ላይ የሚያገኙኝም ይሸሹኛል። **12** ማንም እንደማያስበው እንደ ሞተ ሰው ተረሳሁ እንደ ተሰበረ የሸክላ ዕቃም ተቆጠርሁ። **13** የብዙዎችን ሹክሹክታ ሰምቻለሁ በዙሪያዬም የሸብር ወሬ አለ በእኔ ላይ ባሤሩ ጊዜ ሕይወቴን ለማጥፋት ዶለቱ። **14** እኔ ግን ያህዌ ሆይ፣ በአንተ እተማመናለሁ «አንተ አምላኬ ነህ» አልሁ። **15** ዘመኔ ሁሉ በእጅህ ነው። ከጠላቶቼና ከሚያሳድዱኝ ሰዎች እጅ አድነኝ። **16** ፊትህን ባርያህ ላይ አብራ፤ በኪዳን ታማኝነትህ አድነኝ። **17** ያህዌ ሆይ፣ አንተን ጠርቻለሁና ለእፍረትና ለውርደት አትዳርገኝ። ክፉዎች ግን ይፈሩ፤ ይዋረዱ ሲኦል ገብተው ጸጥ ይበሉ። **18** ጻድቁ ላይ በእብሪት የሚናገሩ ትዕቢትና ንቀትን የተሞሉ ከንፈሮች ድዳ ይሁኑ። **19** ለሚፈሩህ የሰወርኸው፣ በአንተም ለሚታመኑ በሰው ልጆች ሁሉ ፊት የምታደርገው እንዴት ታላቅ ነው! **20** ከሰዎች ሤራ በማደሪያህ ውስጥ ትሸሸጋቸዋለህ። **21** በተከበበች ከተማ ለእኔ ድንቅ ታማኝነቱን የገለጠ ያህዌ ይባረክ። **22** እኔ ግን ባለ ማስተዋል፣ «ከእንግዲህ ከዐይንህ ፊት ተወግጃለሁ» ብዬ ነበር፤ ሆኖም፣ አንተ እንድትረዳኝ ስጮኽ ሰማኸኝ። **23** እናንተ ታማኝ ተከታዮቹ ሁሉ ያህዌን ወደዱት ያህዌ ታማኞችን ይጠብቃል ለእብሪተኞች ግን የእጃቸውን ይሰጣቸዋል። **24** እግዚአብሔርን ተስፋ የምታደርጉ ሁሉ በርቱ ልባችሁም ይጽና።

Psalms 31:1

አጠቃላይ መረጃ
ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው።

ለመዘምራን አለቃ
‹‹ይህ በአምልኮ ጊዜ ለመዘምራን መሪ ነው››

የዳዊት መዝሙር
ይህም ማለት፣ 1) መዝሙሩን የጻፈ ዳዊት ነው ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት ነው።

ያህዌ ሆይ፣ በአንተ እሸሸጋለሁ
ጥበቃ እንዲደረግለት ወደ ያህዌ መሄድ እርሱ ውስጥ መሸሸግ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንድትጠብቀኝ ያህዌ ሆይ፣ ወደ አንተ እሄዳለሁ››

አታሳፍረኝ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሌሎች እንዲያሳፍሩኝ አታድርግ››

መጠጊያ ዐለቴና የምታድነኝ ምሽግ ሁነኝ
‹‹መጠጊያ ዐለቴ›› ማለት ጥበቃ እንዲያገኝ መለመን ማለት ነው። ሁለተኛው ሐረግ የመጀመሪያውን ሐረግ ያጠናክራል።

መጠጊያ ዐለቴ
የሚያድን ታላቅ ዐለት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እኔን እንደሚያድን ግዙፍ ዐለት››

የምታድነኝ ምሽግ
ያህዌ ጸሐፊው ከጠላቶቹ የሚድንበት ጠንካራ ምሽግ እንደሆነ ተነግሯል።

Psalms 31:3

ዐለቴ
ያህዌ ጸሐፊውን ከጥቃት የሚያድን ግዙፍ ዐለት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የምድንበት ግዙፍ ዐለት››

ምሽጌ
ያህዌ ጸሐፊው ከጠላቶቹ የሚድንበት ጠንካራ ምሽግ እንደሆነ ተነግሯል።

ስለ ስምህ ስትል
‹‹ስም›› የሚወክለው ያህዌን ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ስምህ እንዲከበር›› ወይም፣ ‹‹እኔ እንዳመልክህ››

ምራኝ መንገዱን አመልክተኝ
‹‹ምራኝ›› እና፣ ‹‹አመልክተኝ›› በመሠረቱ ተመሳሳይ ቢሆኑም፣ ያህዌ እንዲረዳው ያቀረበውን ልመና ያጠነክራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንድሄድ ወደምትፈልገው ምራኝ››

ከሰወሩብኝ መረብ አወጣኝ
ጸሐፊው በተሰወረ መረብ እንደ ተያዘ ወፍ እንደሆነና ያህዌ ከወጥመዱ ነጻ እንዲያደርገው እንደሚጠብቅ ይናገራል።

አንተ መጠጊያዬ ነህ
ያህዌ ሰዎች ጸሐፊውን እንዳያጠቁ የሚደበቅበት ቦታ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አንተ ሁሌም ትጠብቀኛለህ›› ወይም፣ ‹‹ዘወትር ጥበቃ ታደርግልኛለህ››

Psalms 31:5

በእጆችህ
እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ እዚህ ላይ ግን እጅ እንዳሉት ተነግሯል። ‹‹እጆችህ›› የሚለው የያህዌን ጥበቃ ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹ለጥበቃህ››

መንፈሴን እሰጣለሁ
‹‹መንፈሴ›› የሚለው የሚያመለክተው ጸሐፊውን ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ራሴን አኖራለሁ››

የሚታመን አምላክ
‹‹አንተ የምታመንብህ አምላክ ነህ››

ከንቱ ጣዖቶች የሚያገለግሉትን ጠላሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ከንቱ›› የሚለው ጣዖቶችን ሁሉ ይመለከታል። ይህን በትርጕም ማብራራት ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጣዖቶች ከንቱ ናቸው፤ እነርሱን የሚያገለግሉትን ጠላሁ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በኪዳናዊ ታማኝነትህ ደስ ይለኛል፤ ሐሤት አደርጋለሁ
‹‹ደስታ›› እና፣ ‹‹ሐሤት›› የተሰኙት ቃሎች ተመሳሳይ ትርጉም ቢኖራቸውም፣ የደስታውን ታላቅነት አጽንዖት ይሰጣሉ። ‹‹ታማኝነት›› የሚለውን የነገር ስም እንደ ቅጽል መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተ ለኪዳንህ ታማኝ ስለሆንህ በጣም ደስ ይለኛል››

መከራዬን አይተሃል... የነፍሴንም ጭንቀት አውቀሃል
ሁለቱም ሐረጐች እግዚአብሔር የጸሐፊውን መከራ እንደሚያውቅ ያመለክታሉ።

የነፍሴን ጭንቀት
‹‹ነፍሴ›› ጸሐፊውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹‹‹ጭንቀቴን››

Psalms 31:8

እግሮቼን አቆምሃቸው
‹‹እግሮቼ›› ጸሐፊውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አቆምኸኝ››

በሰፊ ቦታ
በዕብራይስጥ ሰፊ ቦታ ደህንነትንና ነጻነትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ነጻ ወደምሆንበት ቦታ››

ጭንቀት ውስጥ ነኝ
‹‹ትልቅ መከራ ደርሶብኛል››

ነፍሴ እና ሥጋዬ
‹‹ነፍስ›› እና፣ ‹‹ሥጋ›› ሙሉውን ሰው ያመለክታሉ።

Psalms 31:10

ሕይወቴ በመጨነቅ
‹‹ሕይወቴ›› ጸሐፊውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጣም ደከምሁ››

በሐዘን... በመቃተት
‹‹በሐዘኔ ምክንያት... በመቃተቴ ምክንያት››

ዕድሜዬ በመቃተት
‹‹አለቀ›› የሚለው ቃል ባይጠቀስም በውስጠ ታዋቂነት ይታወቃል። ‹‹ዕድሜዬ በመቃተት አለቀ››

ጉልበቴ ከዳኝ
‹‹ጉልበቴ›› ጸሐፊውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጣም ደከምሁ››

ዐጥንቴ በውስጤ ሟሟ
‹‹ዐጥንት›› የጸሐፊን አካል ጤንነት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጤና አጣሁ››

ሰዎች ይንቁኛል
‹‹ሰዎች ይሰድቡኛል››

የሚያገኙኝም ይሸሹኛል
‹‹በሁኔታዬ ይደነግጠቃሉ››

Psalms 31:12

እንደ ሞተ ሰው ተረሳሁ
ሰዎች ለሞተ ሰው አያስቡም። ጸሐፊው ሰዎች ስለ እርሱ እንደሚያስቡ አያስብም

እንደ ተሰበረ የሸክላ ዕቃ
ጸሐፊው ጨርሶ ከጥቅም ውጪ እንደሆነ ያስባል። ‹‹እንደ ተሰበረ የሸክላ ዕቃ ጥቅም የለሽ››

የብዙዎችን ሹክሹክታ
‹‹ብዙ›› የሚለው ሰዎችን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ብዙዎች ስለ እኔ ያወራሉ››

በዙሪያዬ አስፈሪ ወሬ
‹‹ከብዙ አቅጣጫዎች አስፈሪ ወሬ››

ሕይወቴን ለመውሰድ
ይህ ማለት መግደል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሊገድሉኝ››

Psalms 31:14

ዘመኔ ያለው በእጅህ ነው
‹‹በእጅህ›› የያህዌን ጎይል ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የወደ ፊት ሕይወቴን ለመወሰን ጎይል አለህ››

ለሚያሳድዱኝ
‹‹ሊይዙኝ ለሚሞክሩ››

ባርያህ ላይ ፊትህን አብራ
ያህዌ ለእርሱ መልካም ነገር ማድረጉ እርሱ ላይ ፊቱን ማብራት እንደሆነ ጸሐፊው ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለባርያህ መልካም አድርግ››

በኪዳናዊ ታማኝነትህ አድነኝ
‹‹ታማኝነት›› የሚለውን የነገር ስም እንደ ቅጽል መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለኪዳንህ ታማኝ በመሆንህ አድነኝ››

Psalms 31:17

አልፈር
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሌሎች እንዲያሳፍሩኝ አታድርግ››

ክፉዎች ይፈሩ
‹‹ክፉ ሰዎችን እግዚአብሔር እንዲያሳፍራቸው እፈልጋለሁ››

ክፉዎች
ይህ የሚመለክተው፣ ‹‹ክፉ ሰዎችን›› ነው።

Psalms 31:19

በጐነትህ
ይህን ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተ የምታደርገው መልካም ነው››

ያስቀመጥሃት
የያህዌ በጐነት እንደ አንዳች ነገር የሚቀመጥ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተ ለሚያስፈልግ ጊዜ ያስቀመጥኸው››

ለሚፈሩህ
‹‹አንተን በጣም ለሚያከብሩ››

ወደ አንተ ለሚጠጉ
ጥበቃ ለማግኘት ወደ ያህዌ መሄድ ወደ እርሱ መጠጋት እንደሆነ ተነግሯል። መዝሙር 31፥1 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጥበቃ እንድታደርግላቸው ወደ አንተ ለሚመጡ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በማደሪያህ ውስጥ ትሸሸጋቸዋለህ... በመጠለያህ ውስጥ ትደብቃቸዋለህ
ሁለቱም ሐረጎች እግዚአብሔር ይጠብቃቸዋል ማለት ናቸው።

በመጠለያህ
የያህዌ ማደሪያ ጸሐፊው ደህንነት የሚያገኝበት ትልቅ ግንብ እንደሆነ ተነግሯል

በመጠለያህ ትደብቃቸዋለህ
እዚህ ላይ፣ ‹‹መጠለያ›› አደጋ የሌለበት ቦታ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አደጋ የሌለበት ቦታ ታዘጋጅላቸዋለህ››

ከአንደበት ጭቅጭቅ
እዚህ ላይ፣ ‹‹አንደበት›› ጸሐፊው ላይ ክፉ የሚናገሩ ሰዎችን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጠላቶቻቸው ክፉ መናገር የማይችሉበት››

Psalms 31:21

የሚያስደንቅ ኪደናዊ ታማኝነቱን አሳየኝ
‹‹ታማኝነት›› የሚለውን የነገር ስም እንደ ቅጽል መተርጎም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱ ለኪዳኑ ታማኝ መሆኑን በአስደናቂ ሁኔታ አሳየኝ››

ከዐይንህ ፈት ተወገግጃለሁ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከፊትህ አስወገድከኝ››

ከዐይንህ
ያህዌ፣ ‹‹በዐይኖቹ›› ተወክሏል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተ››

የርዳታ ልመናዬን ሰማህ
‹‹ልመና›› የሚለውን ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለርዳታ ስለምን ሰማኸኝ››

Psalms 31:23

ታማኞች
ይህ የሚያመለክተው ታማኝ ሰዎችን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ታማኝ የሆኑ ሰዎች››

ለእብሪተኞች የሚገባውን ይከፍላቸዋል
እዚህ ላይ፣ ‹‹ይከፍላቸዋል›› ቅጣትን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለትዕቢተኞች የሚገባቸውን ቅጣት ሁሉ ይሰጣቸዋል››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 32

1 መተላለፉ ይቅር የተባለለት ኃጢአቱም የተሸፈነለት ሰው ቡሩክ ነው። **2** ያህዌ በደሉን የማይቆጥርበት በመንፈሱም ሸንገላ የሌለበት ሰው ቡሩክ ነው። **3** ቀኑን ሙሉ በመቃተቴ ዝም ባልሁ ጊዜ፣ አጥንቶቼ ተበላሹ። **4** ቀኑን ሙሉ እጅህ ከብዳኛለች ብርታቴም የበጋ ትኩሳት እንደ መታው ነገር ከውስጤ ተሟጠጠ። ሴላ **5** በዚያን ጊዜ ኃጢአቴን ለአንተ ተናዘዝሁ በደሌንም ከአንተ አልሰወርሁም ደግሞም፣ «መተላለፌን ለያህዌ እናዘዛለሁ» አልሁ አንተም የኃጢአቴን በደል ይቅር አልህ። ሴላ **6** ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው በጭንቅ ጊዜ ወደ አንተ ይጸልይ ብርቱ ጐርፍ ሞልቶ ቢያጥለቀቅ እንኳ፣ ወደ እነዚህ ሰዎች አይቀርብም። **7** አንተ መሸሸጊያዬ ነህ፤ ከመከራም ታወጣኛለህ። በድል ዝማሬ ትከበኛለህ። ሴላ **8** አስተምርሃለሁ፤ በምትሄድበት መንገድ እመራሃለሁ እመክርሃለሁ ዐይኔንም አንተ ላይ አደርጋለሁ። **9** ወደምትፈልጉት ቦታ እንዲሄዱላችሁ በልጓምና በልባብ እንደሚገሩት ማስተዋል እንደሌለው ፈረስና በቅሎ አትሁኑ። **10** የክፉዎች ሐዘን ይበዛል በያህዌ የሚታመነውን ግን የእርሱ ኪዳን ታማኝነት ይከብበዋል። **11** ጻድቃን ሆይ፣ በእግዚአብሔር ደስ ይበላችሁ ልበ ቅኖች ሆይ፣ እልል በሉ።

Psalms 32:1

አጠቃላይ መረጃ
ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው።

የዳዊት መዝሙር
ይህም ማለት 1) መዝሙሩን የጻፈ ዳዊት ነው። ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት ነው ማለት ሊሆን ይችላል።

ማስቺል
ይህ የአዘማመርን ስልት የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።

መተላለፉ ይቅር የተባለለት፣ ኀጢአቱም የተሸፈነለት
እነዚህ ሐረጐች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔር መተላለፉን ይቅር ያለው፣ ኀጢአቱንም የሸፈነለት››

ኀጢአቱ የተሸፈነለት
ይቅር የተባለ ኀጢአት ከእንግዲህ ማንም እንዳያየው የተሸፈነ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኀጢአቱ የታለፈለት›› ወይም፣ ‹‹ሆን ተብሎ ኀጢአቱ የተረሳለት››

ያህዌ በደሉን የማይቆጥርበት
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ እንደ ንጹሕ የሚያየው›› ወይም፣ ‹‹በያህዌ ፊት በደለኛ ያልሆነ››

በመንፈሱም ሸንገላ የሌለበት
‹‹መንፈስ›› የሚያመለክተው ሰውየውን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሸንገላ የሌለበት›› ወይም፣ ‹‹ፍጹም ቅን የሆነ››

Psalms 32:3

ዐጥንቶቼ ተበላሹ
‹‹ዐጥንቶቼ›› የሚያመለክተው ጸሐፊውን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እየተጐዳሁ ነው›› ወይም፣ ‹‹የበለጠ እየደከምሁ ነው››

ቀኑን ሙሉ
ይህም ማለት ‹‹ዘወትር›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሁልጊዜ››

ቀንና ሌሊት
እነዚህ ሁለት ጽንፎች በመካከል ያለውን ሁሉ ይጨምራሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሁልጊዜ››

እጅህ ከብዳኛለችና
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› የሚያመለክተው ያህዌን ነው። ይህ ሐረግ በሙሉ፣ ‹‹ጐዳኸኝ›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጣም አሰቃየኸኝ››

ጎይሌም የበጋ ድርቅ እንዳገኘው ተሟጠጠ
የዳዊት ጎይል በድርቅ ጊዜ እንደሚጠወልግ ትንሽ ለምለም ተክል ጋር ተመሳስሎአል።

ሴላ
ይህ እዚህ ላይ እንዴት እንደሚዘምሩ ወይም የሙዚቃ መሣሪያ እንደሚጫወቱ የሚያመለክት ሙዚቃዊ አገላለጽ ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል ይጽፋሉ ሌሎች ትርጉሞች ግን ትተውታል። መዝሙር 3፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

በታላቅ ጭንቅ ጊዜ
‹‹በጣም በተጨነቁ ጊዜ››

ጎይለኛ ጐርፍ አካባቢውን ቢያጥለቀልቅም፣ እነርሱ አጠገብ አይደርስም
አስቸጋሪ ሁኔታዎች እንደ ጐርፍ እንደሆኑ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ችግሮች እንደ ጐርፍ ሲመጡ እነዚህ ሰዎች ምንም አይሆኑም››

Psalms 32:7

አንተ መሸሸጊያዬ ነህ
ጸሐፊው ከጠላቶቹ ከደረሰበት ጥቃት ያህዌ መሸሸጊያ እንደሆነው ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተ ከጠላቶቼ የምደበቅበት ቦታ ነህ››

በድል ዝማሬ ትከበኛለህ
ምሳሌው የሚያመለክተው ያህዌ ለጸሐፊው ጥበቃ ማድረጉ የድል ዝማሬ እንዲያቀርብ ምክንያት እንደሆነው ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከአንተ የተነሣ የድል ዝማሬ አቀርባለሁ››

ሴላ
ይህ እዚህ ላይ እንዴት እንደሚዘምሩ ወይም የሙዚቃ መሣሪያቸውን እንደሚጫወቱ ለሰዎች የሚናገር ሙዚቃዊ አገላለጽ ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል ይጽፋሉ፤ ሌሎች ግን ይተውታል። መዝሙር 3፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

አስተምርሃለሁ በምትሄድበት መንገድ እመራሃለሁ
‹‹ማስተማር›› እና፣ ‹‹መምራት›› ተመሳሳይ ነገሮች ቢሆኑም፣ ጠበቅ ያለ ትምህርትን ለማመልከት አጽንዖት ተሰጥቷቸዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መንገዱን በተመለከተ ማንኛውንም ነገር አስተምርሃለሁ››

አስተምርለሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እኔ›› ሲል ያህዌ በቀጥታ ለዳዊት እየተናገረ ሊሆን ይችላል።

በምትሄድበት መንገድ
በትክክለኛው መንገድ መኖር ጸሐፊው የሚሄድበት መንገድ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕይወትህን እንዴት እንደምትኖር››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በዐይኔ እከታተልሃለሁ
‹‹ዐይኔ›› የሚለው የያህዌ ትኩረት ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ትኩረቴን አንተ ላይ አደርጋለሁ›› ወይም፣ ‹‹እጠብቅሃለሁ››

Psalms 32:9

ማስተዋል እንደሌላቸው... እንደ ፈረስ አትሁኑ
ጸሐፊው ማስተዋል የሌላቸውን ሰዎች ከፈረስና ከበቅሎ ጋር ያመሳስላቸዋል። ይህም ማለት፣ 1) ጸሐፊው ለአንባቢዎቹ የያህዌን ቃል እየተናገረ ነው፤ ‹‹ሁላችሁም ማስተዋል እንደሌላቸው... እንደ ፈረስ አትሁኑ›› ወይም 2) ለብዙዎች እንደሚናገር ያህዌ ለጸሐፊው እየተናገረ ነው።

በልባብና በልጓም
ሁለቱም ነገሮች ፈረሶችና በቅሎዎች እንዲሄዱ ወደሚፈልጉት ቦታ ለመምራት የሚጠቀሙባቸው ናቸው።

እንዲሄዱ የምትፈልገው
‹‹ሰው ሁሉ እንዲሄዱ የሚፈልገው›› እዚህ ላይ፣ ‹‹አንተ›› ነጠላ ቁጥር ቢሆንም፣ አንድን ሰው ነጥሎ እየተናገረ አይደለም።

የያህዌ ኪዳናዊ ታማኝነት የሚታመንበትን ይከብበዋል
ያህዌ ለሰው ታማኝ መሆኑና እርሱንም መጠበቁ የያህዌ ኪዳናዊ ታማኝነት ያንን ሰው እየከበበው እንደሆነ ተነግሯል። ‹‹ታማኝነት›› የሚለው የነገር ስም እንደ ቅጽል ሊተረጐም ይችላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ ለኪዳኑ ታማኝ በመሆኑ፣ በእርሱ የታመነውን ይጠብቀዋል››

Psalms 32:11

በያህዌ ደስ ይበላችሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹በያህዌ›› ያህዌ ያደረገውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ ባደረገው ደስ ይበላችሁ››

ጻድቃን ሆይ
ይህ ሰዎችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እናንት ጻድቃን ሰዎች››

በደስታ እልል በሉ
‹‹ደስ እያላችሁ ጩኹ›› ወይም፣ ‹‹ከደስታ የተነሣ ጩኹ››

ቅን ልብ ያላችሁ
‹‹ልብ›› ሰውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ቅን ልብ ያላችሁ ሰዎች››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 33

1 ጻድቃን ሆይ፣ በያህዌ ደስ ይበላችሁ ቅኖች ሊያመሰግኑት ይገባል። **2** ያህዌን በመሰንቆ አመስግት ዐሥር አውታር ባለው በገና ዘምሩለት። **3** አዲስ ዝማሬ አቅርቡለት ባማረ ቅኝት በገና ደርድሩ፤ እልልም በሉ። **4** የያህዌ ቃል እውነት ነው ሥራውም ሁሉ የታመነ ነው። **5** እርሱ ጽድቅንና ፍትሕን ይወዳል ምድር በያህዌ ኪዳን ታማኝት ተሞልታለች። **6** ያህዌ ሰማያትን በቃሉ የሰማይ ሰራዊትን በአፉ እስትንፋስ ፈጠረ። **7** የባሕርን ውሆች እንደ ክምር ቀላዩንም በመከማቻ ስፍራ አኖረ። **8** ምድር ሁሉ ያህዌን ትፍራው በዓለም ያሉ ሁሉ በፊቱ ይንቀጥቀጥ። **9** እርሱ ተናግሮአልና ሆኑ፤ እርሱ አዞአልና በስፍራቸው ጸኑ። **10** ያህዌ የሕዝቦችን ምክክር ያጨናግፋል ዕቅዳቸውንም ከንቱ ያደርጋል። **11** የያህዌ ዕቅድ ግን ለዘላለም ይኖራል የልቡም ሐሳቡም ለትውልድ ሁሉ ነው። **12** ያህዌ አምላኩ የሆነለት፣ ርስቱ እንዲሆን የመረጠውም ሕዝብ ቡሩክ ነው። **13** ያህዌ ከሰማይ ይመለከታል የሰው ልጆችንም ሁሉ ያያል። **14** ከማደሪያው ሆኖ፣ በምድር የሚኖሩትን ሁሉ ይመለከታል። **15** የሁሉንም ልብ የሠራ እርሱ ነው የሚያደርጉትንም ሁሉ ይመለከታል። **16** ንጉሥ በሰራዊቱ ብዛት አይድንም፤ ጀግናም በኃይሉ ብርታት አያመልጥም። **17** በፈረስ ድል አደርጋለሁ ማለት ከንቱ ተስፋ ነው፤ በብርቱ ጉልበቱም ማንም አይድንም **18** እነሆ፣ የያህዌ ዐይኖች በሚፈሩት ላይ ናቸው፤ በኪዳን ታማኝነቱ በሚታመኑት ላይ አትኩረዋል። **19** ይህም የሚሆነው ከሞት ሊያድናቸውና ከራብ ዘመንም ሊጠብቃቸው ነው። **20** ያህዌን በተስፋ እንጠብቃለን እርሱ ረድኤታችንና ጋሻችን ነው። **21** በቅዱስ ስሙ ተማምነናልና ልባችን በእርሱ ደስ ይለዋል። **22** ያህዌ ሆይ፣ ተስፋችንን አንተ ላይ አድርገናልና ምሕረትህ በእኛ ላይ ይሁን።

Psalms 33:1

አጠቃላይ መረጃ
ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው።

በያህዌ ደስ ይበላችሁ
‹‹በያህዌ›› የሚለው ያህዌ ለእነርሱ ያደረገውን ያመለክታል። ‹‹ያህዌ ባደረገላችሁ ደስ ይበላችሁ››

ቅኖች ሊያመሰግኑት ይገባል
‹‹ያህዌን ማመስገን ለቅኖች የተገባ ነው››

Psalms 33:4

አጠቃላይ መረጃ
እያንዳንዱ ቁጥር በጣም ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሁለት መስመሮች አሉት።

የያህዌ ቃል የቀና ነው
‹‹የቀና›› የሚለው እውነተኛ የሆነ ነገርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ሁሌም አደርጋለሁ ያለውን ያደርጋል››

ጽድቅንና ፍትሕን ይወድዳል
እነዚህን የነገር ስሞች በተግባር መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጽድቅና እውነት የሆነውን ነገር ማድረግ ይወድዳል›› ወይም፣ ‹‹ጽድቅና እውነት የሆነውን ነገር የሚያደርጉትን ይወድዳል››

ምድር በያህዌ ኪዳናዊ ታማኝነት ተሞልታለች
በዓለም ማንኛውም ቦታ ያሉ ሰዎች የያህዌን ኪዳናዊ ታማኝነት ማስረጃ ማየት መቻላቸው ኪዳናዊ ታማኝነቱ ምድርን እንደ ሞላ ተነግሯል። ‹‹ኪዳናዊ ታማኝነት›› የሚለውን የነገር ስም እንደ ቅጽል መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በምድር የትኛውም ቦታ ያሉ ሰዎች ያህዌ ለኪዳኑ ታማኝ መሆኑን ማየት ይችላሉ›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ለኪዳኑ ታማኝ ስለ መሆኑ በምድር ሁሉ ማስረጃ አለ››

በያህዌ ቃል ሰማያት ተሠሩ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በቃሉ አማካይነት ያህዌ ሰማያትን ሠራ››

በአፉ እስትንፋስ
ይህ የሚያመለክተው የያህዌን ቃል ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በቃሉ››

Psalms 33:7

አጠቃላይ መረጃ
እያንዳንዱ ቁጥር በጣም ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሁለት መስመሮች ይዞአል።

እንደ ክምር
‹‹ግድብ ውሰጥ እንዳለ›› ጸሐፊው ስለ ባሕር መፈጠር ሲናገር ያህዌ ውሆችን በክምር እንዳደረገ ይናገራል።

ውቅያኖሱን በአንድ ስፍራ ያከማቻል
ጸሐፊው ስለ ውቅያኖስ መፈጠር ሲናገር እግዚአብሔር በአንድ ስፍራ እንዳከማቸው ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰው እህልን በጐተራ እንደሚያከማች እርሱም ውቅያኖስን በአንድ ስፍራ አከማቸ››

ምድር ሁሉ
ይህ መላው ምድርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በምድር ያለ ሁሉ››

በፊቱ በፍርሃት ይቁም
‹‹በፍርሃት ይቁም›› ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን፣ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያክብሩት››

በቦታቸው ሆኑ
‹‹በቦታቸው ሆኑ›› ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን፣ ‹‹ተፈጠሩ›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መሆን ጀመሩ››

Psalms 33:10

አጠቃላይ መረጃ
እያንዳንዱ ቁጥር በጣም የሚመሳሰሉ ትርጉሞች ያሏቸው ሁለት መስመሮች ይዞአል።

ያህዌ ያጨናግፋል
‹‹ያህዌ ያጠፋል›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ይሰብራል››

የሕዝቦች ወገን
‹‹ሕዝቦች›› የአነዚህ አገሮችን ሰዎች ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የተለያዩ ሕዝቦች ወገን››

ጎብረት
ጎብረት በጦርነት ጊዜ አብረው የጋራ ጠላት እንዲወጉ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ወገኖች መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የሕዝቦች ምክክር
‹‹የሰዎች ፍላጐት›› አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሰዎች ክፉ ምክክር››

ለዘላለም ይጸናል
‹‹ይጸናል›› ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን፣ ‹‹ይኖራል›› ማለት ነው።

ለትውልዶች ሁሉ የልቡ ሐሳብ
‹‹ይጸናል›› የሚለው ቃል ውስጠ ታዋቂ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የልቡም ሐሳብ ለትውልዶች ሁሉ ይጸናል››

የልቡም ሐሳብ
‹‹ልብ›› የሚያመለክተው ያህዌን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የእርሱ ሐሳብ››

ለትውልዶች ሁሉ
‹‹ወደ ፊት ለሚኖሩ ትውልዶች ሁሉ›› ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን፣ ‹‹ለዘላለም›› ማለት ነው።

ሕዝብ የተባረከ ነው
‹‹ሕዝብ›› ሲል ሰዎችን ሁሉ ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰዎች የተባረኩ ናቸው››

ያህዌ አምላኩ የሆነ
‹‹ያህዌን የሚያመልክ››

እንደ ራሱ ርስት
እዚህ በተገለጸው መሠረት የእርሱ ርስት የሆኑ ይመስል ሕዝቡ ያህዌን እንዲያመልኩ ተመርጠዋል።

Psalms 33:13

ወደ ታች ይመለከታል
ያህዌ የሚኖርበት ቦታ ከሰዎች መኖሪያ በላይ እንደሆነ ተነግሯል።

የሁሉንም ልብ የሠራ
‹‹ልብ›› የእነዚህን ሰዎች አስተሳሰብ ያመለክታል። እርሱ የሸክላውን ዕቃ ቅርጽ የሚያስይዝ ሸክላ ሠሪ ይመስል ያህዌ የሕዝቡን አስተሳሰብ እንደሚመራ ጸሐፊው ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሸክላ ሠሪ ዕቃውን ቅርጽ እንደሚያስይዝ አስተሳሰባቸውን የሚመራ››

Psalms 33:16

ንጉሥ በሰራዊቱ ብዛት አይድንም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ንጉሥን የሚያድነው የሰራዊቱ ብዛት አይደለም››

በፈረስ ጉልበት ድል አደርጋለሁ ማለት አይቻልም
‹‹ፈረስ›› የአንድን ሰራዊት ብርቱ ክፍል ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጠንካራ ፈረሰኞች ያሉት ሰራዊት ባለቤት መሆን ደህንነት ለመኖሩ ማረጋገጫ አይደለም››

Psalms 33:18

እነሆ
ይህ ቃል የሚያመለክተው በዚህ መዝሙር አዲስ ዐቢይ ሐሳብ መጀመሩን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ተመልከቱ›› ወይም፣ ‹‹ስሙ›› ወይም፣ ‹‹የምነግራችሁን ልብ በሉ››

የያህዌ ዐይኖች
እዚህ ላይ፣ ‹‹ዐይኖች›› የያህዌን ትኩረት ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የያህዌ ትኩረት››

በኪዳኑ ታማኝነት የሚተማመኑ
‹‹የሚተማመኑ›› የሚለው ቃል፣ ‹‹የሚጠብቁ›› ወይም ‹‹ተስፋ የሚያደርጉ›› ማለት ነው። ‹‹ታማኝነት›› የሚለውን የነገር ስም ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ከኪዳኑ የተነሣ በታማኝነት እንዲያደርግላቸው የሚጠብቁት››

ሕይወታቸውን ከሞት ለማዳን
‹‹ሕይወታቸውን›› የሚለው የሚያመለክተው ሕዝቡን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከሞት እንዲያድናቸው››

Psalms 33:20

ያህዌን እንጠባበቃለን
‹‹መጠባበቅ›› መተማመን ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በያህዌ እንታመናለን›› ወይም፣ ‹‹ያህዌን ተስፋ እናደርጋለን››

እርሱ ረዳታችን፣ ጋሻችንም ነው
እዚህ ላይ ያህዌ ሰራዊትን ከጥቃት የሚከልል ጋሻ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እርሱ ረዳታችንና እንደ ጋሻ የሚከልለን ነው››

ልባችን ደስ ይለዋል
‹‹ልብ›› የሚያመለክተው ሕዝቡን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ደስ ይለናል››

በቅዱስ ስሙ
‹‹ቅዱስ ስሙ›› የያህዌን ቅዱስ ባሕርይ ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ቅዱስ ባሕርዩ›› ወይም፣ ‹‹እርሱ ቅዱስ ስለሆነ በእርሱ››

Psalms 33:22

ያህዌ ሆይ፣ የኪዳን ታማኝነትህ ከእኛ ጋር ይሁን
ያህዌ ለሕዝቡ ታማኝ መሆኑ የኪዳኑ ታማኝነት ከእነርሱ ጋር እንደ ሆነ ተናግሯል። ‹‹ታማኝነት›› የሚለውን የነገር ስም ቅጽል ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ ሆይ፣ ከኪዳንህ የተነሣ አንተ ሁሌም ታማኝ ሁንልን››

ተስፋችንን በአንተ ላይ አድርገናል
‹‹አንተ እንደምትረዳን ተስፋ አለን››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 34

1 ያህዌን ሁልጊዜ አመሰግናለሁ ምስጋናውም ዘወትር በአፌ ነው። **2** ያህዌን አመሰግናለሁ! ትሑታን ይህን ሰምተው ደስ ይበላቸው። **3** ያህዌን ከእኔ ጋር
አመስግኑት በአንድነት ስሙን ከፍ ከፍ እናድርግ። **4** ያህዌን ፈለግሁ እርሱም መለሰልኝ ከፍርሃቴም ሁሉ አዳነኝ። **5** ወደ እርሱ የሚመለከቱ ያበራሉ ፊታቸውም
በፍጹም አያፍርም። **6** ይህ ችግረኛ ጮኸ እግዚአብሔርም ሰማው ከመከራውም ሁሉ አዳነው። **7** የያህዌ መልአክ በሚፈሩት ዙሪያ ይሰፍራል ያድናቸዋልም። **8**
ያህዌ መልካም መሆኑን ቀምሳችሁ እዩ። በእርሱ የተማመነ ሰው ቡሩክ ነው። **9** እናንተ ቅዱሳን ያህዌን ፍሩ እርሱን የሚፈሩ አንዳች አያጡምና። **10** አንበሶች
ሊያጡ ሊራቡም ይችላሉ ያህዌን የሚሹ ግን መልካም ነገር አይጐድልባቸውም። **11** ልጆቼ ሆይ፣ ኑ ስሙኝ ያህዌን መፍራት አስተምራችኋለሁ። **12** ሕይወትን
የሚወድ፣ መልካም ነገርን ለማየት ረጅም ዕድሜ የሚፈልግ ማነው? **13** እንግዲያስ አንደበትህን ከክፉ ከልክል ከንፈርህንም ከውሸት ጠብቅ። **14** ከክፉ ሽሽ፤
መልካሙንም አድርግ ሰላምን ፈልጋት ደግሞም ተከተላት። **15** የያህዌ ዐይኖች ጻድቃን ላይ ናቸው፤ ጆሮዎቹም ለጩኸታቸው ተከፍተዋል። **16** መታሰቢያቸውን
ከምድር ላይ ለማጥፋት የያህዌ ፊት ክፉ በሚያደርጉ ላይ ነው። **17** ጻድቃን ወደ ያህዌ ይጮኻሉ እርሱም ይሰማቸዋል፤ ከመከራቸውም ሁሉ ያድናቸዋል። **18**
ያህዌ ልባቸው ለተሰበረ ቅርብ ነው መንፈሳቸው የደቀቀውንም ያድናቸዋል። **19** የጻድቅ መከራው ብዙ ነው ያህዌ ግን ከሁሉም ያድነዋል። **20** ዐጥንቶቹን ሁሉ
ይጠብቃል ከእነርሱ አንዱ እንኳ አይሰበርም። **21** ኃጢአተኛን ክፋት ይገድለዋል ጻድቃንን የሚጠሉ ይፈርድባቸዋል። **22** ያህዌ የባርያዎቹን ነፍስ ይታደጋል
እርሱንም መጠጊያ ያደረገ አይፈረድበትም።

Psalms 34:1

አጠቃላይ መረጃ
ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው።

የዳዊት መዝሙር
ይህም ማለት፣ 1) መዝሙሩን የጻፈ ዳዊት ነው ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት ነው ማለት ሊሆን ይችላል።

እንደ እብድ ሆኖ
‹‹እብድ በመምሰል››

አቢሜሌክ ፊት
ይህ የሚናገረው አይሁዳውያን በሚገባ የሚያውቁትን ታሪክ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አቢሜሌክ ቤት በነበረ ጊዜ›› ወይም፣ ‹‹የአቢሜሌክ እስረኛ ሳለ››

ተባርሮ በወጣ ጊዜ
‹‹በግድ የወጣ ጊዜ››

ምስጋናውም ዘወትር በአፌ ነው
እዚህ ላይ፣ ‹‹በአፌ›› የሚለው ዳዊት ለያህዌ ሲናገር ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ዘወትር አመሰግነዋለሁ››

Psalms 34:2

የተጨቆኑ
ይህ የሚያመለክተው የተጨቆኑ ሰዎችን ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የተጨቆኑ ሰዎች››

ያህዌን ከእኔ ጋር አመስግኑ
‹‹አመስግኑ›› የሚለው ግሥ ሕዝቡን ማዘዝ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሰው ሁሉ ከእኔ ጋር ያህዌን ያመስግን››

ስሙን ከፍ አድርጉ
‹‹ከፍ አድርጉ›› ማለት ያህዌን አክብሩት ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ታላቅነቱን ለሰዎች ተናገሩ››

ስሙ
‹‹ስሙ›› የያህዌን ባሕርይ ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ባሕርዩ››

Psalms 34:4

ያህዌን ፈለግሁት
‹‹ፈለግሁት›› የሚለው ዳዊት ያህዌ እንዲረዳው መለመኑን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ወደ ያህዌ ጸለይሁ›› ወይም፣ ‹‹እንዲረዳኝ ያህዌን ለመንሁ››

ወደ እርሱ የሚመለከቱ
‹‹መመልከት›› ከእርሱ ርዳታ መለመንን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንዲረዳቸው ወደ እርሱ የሚመለከቱ›› ወይም፣ ‹‹ከእርሱ ብቻ ርዳታ የሚጠብቁ››

ያበራሉ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ደስ ይላቸዋል ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ደስ ይላቸዋል››

ፊታቸውም አያፍርም
‹‹ፊታቸው›› ወደ ያህዌ የሚመለከቱ ሰዎችን ያመለክታል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አያፍሩም›› ወይም፣ ‹‹ይኮራሉ››

ይህ ችግረኛ
ዳዊት ራሱን እንደ ችግረኛ ይቆጥራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ተቸግሬ ነበር››

ያህዌ ሰማው
‹‹ሰማኝ›› ያህዌ ረዳኝ ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ ረዳው››

Psalms 34:7

በዙሪያቸው ይሰፍራል
የእግዚአብሔር መልአክ ሰዎችን ለመጠበቅ በዙሪያቸው እንደሚሰፍር በዳዊት ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሊጠብቃቸው››

ያህዌ መልካም መሆኑን ቀምሳችሁ እዩ
የያህዌ መልካምነት ተቀምሶ እንደሚታይ ነገር እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ መልካም መሆኑን በሕይወታችሁ እዩ››

ወደ እርሱ በሚጠጉ
ያህዌ ሕዝቡ ከጠላቶቻቸው ለመዳን የሚደበቁበት ቦታ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንዲጠብቃችሁ በእርሱ የሚተማመኑ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የሚፈሩ አንዳች አያጡም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሚፈሩት የሚያስፈልጋቸው ሁሉ ይኖራቸዋል››

Psalms 34:10

ምንም አያጡም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሚያስፈልጋቸው መልካም ነገር ሁሉ ይኖራቸዋል››

ልጆቼ
እዚህ ላይ የጸሐፊውን ልጆች ሳይሆን፣ ስለ ያህዌ የሚያስተምራቸውን ሰዎች ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ተማሪዎቼ››

Psalms 34:12

መልካምን እንዲያይ ሕይወትን የሚፈልግና ረጅም ዘመን መኖር የሚፈልግ ማን ነው?
ለዚህ ጥያቄ መልሱ፣ ‹‹ሰው ሁሉ›› የሚል ነው። ይህን ዐረፍተ ነገር ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰው ሁሉ ሕይወትንና ረጅም ዕድሜ መኖርን እንዲሁም መልካምን ነገር ማየትን ይፈልጋል››

አንደበትህን ከክፉ ጠብቅ... ከንፈሮችህን ሐሰት ከመናገር ከልክል
እነዚህ ሁለት ሐረጐች ተመሳሳይ ነገር ማለት ቢሆኑም ለአስፈላጊነቱ አጽንዖት ለመስጠት በሁለት የተለያዩ መንገዶች ቀርቧል።

አንደበትህን ከክፉ ጠብቅ
‹‹አንደበት›› መላውን ሰው ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ክፉ አትናገር››

ከንፈሮችህን ሐሰት ከመናገር ከልክል
‹‹ከንፈር›› የሚናገረውን ሰው ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሐሰት አትናገር››

ከክፉ ሽሽ
‹‹ሽሽ›› ከክፉ ራቅ ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ክፉ አታድርግ››

ሰላምን እሻ
‹‹እሻ›› ስለ ሰላም አስብ ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከሰዎች ጋር በሰላም ለመኖር አጥብቀህ ፈልግ››

Psalms 34:15

የያህዌ ዐይኖች ወደ ጻድቃን ናቸው
‹‹የያህዌ ዐይኖች›› በጥንቃቄ መጠበቁን ያመለክታል። ‹‹ጻድቃን›› ጻድቅ ሰዎችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ ጻድቅ ሰዎችን በጥንቃቄ ይጠብቃል››

ጆሮዎቹም ለጩኸታቸው ክፍት ናቸው
ያህዌ፣ ‹‹በጆሮዎቹ›› ተወክሏል። ለአንድ ነገር ክፍት መሆን ለዚያ ነገር ትኩረት መስጠትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለጩኸታቸው ትኩረት ይሰጣል›› ወይም፣ ‹‹ለጩኸታቸው መልስ ይሰጣል››

መታሰቢያቸውን ከምድር ይቆርጣል
ልክ በቢላ ተቆርጦ የተጣለ ይመስል እነርሱ ሲሞቱ ያህዌ መታሰቢያቸውን ጨርሶ ያጠፋል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሲሞቱ ሰዎች ጨርሶ ይረሷቸዋል››

ያህዌ ይሰማል
‹‹ይሰማል›› ማለት ምላሽ ይሰጣቸዋል ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ ትኩረት ይሰጣቸዋል››

Psalms 34:18

ያህዌ ቅርብ ነው
‹‹ቅርብ›› ማለት ‹‹ለመርዳት ዝግጁ›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ ዘወትር ለመርዳት ዝግጁ ነው››

ልባቸው የተሰበረ
ይህ ልባቸው የተሰበረ ሰዎችን የማያመለክት አነጋገር ነው። ጥልቅ ሐዘን የሰውን ልብ መሰበር ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በጣም ያዘኑ ሰዎች››

መንፈሳቸው የደቀቀ
በጣም ተስፋ የቆረጡ ሰዎች መንፈሳቸው የደቀቀ ሰዎች እንደሆኑ ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በጣም ተስፋ የቆረጡ ሰዎች››

ጻድቃን
ይህ የሚያመለክተው ጻድቅ ሰዎችን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጻድቅ ሰዎች››

ዐጥንቱን ሁሉ ይጠብቃል፤ ከእነርሱ አንዱ እንኳ አይሰበርም
‹‹ዐጥንቱ ሁሉ›› ቃል በቃል ቢሆንም፣ ያህዌ መላውን ሰው እንደሚጠብቅም ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ ፈጽሞ ይጠብቀዋል፤ በምንም መንገድ ጉዳት አያገኘውም››

Psalms 34:21

ክፋት ክፉውን ይገድላል
ክፋት ሰውን መግደል የሚችል ሰው እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የክፉ ሰዎች ሥራ እነርሱን ይገድላቸዋል››

ክፉዎች
ይህ የሚያመለክተው ክፉ ሰዎችን ነው።

ጻድቃንን የሚጠሉ ይፈረድባቸዋል
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጻድቃንን በሚጠሉ ላይ ያህዌ ይፈርድባቸዋል››

ጻድቃን
ይህ የሚያመለክተው ጻድቅ ሰዎችን ነው።

ወደ እርሱ የሚጠጉ አይፈረድባቸውም
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። ቀጥተኛ በሆነ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ወደ እርሱ የሚጠጉትን ሁሉ ያህዌ ይቅር ይላቸዋል››

ወደ እርሱ የሚጠጉ
ጥበቃ ለማግኘት ወደ ያህዌ መሄድ ወደ እርሱ መጠጋት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጥበቃ ለማግኘት ወደ እርሱ መሄድ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 35

1 ያህዌ ሆይ፣ የሚቃወሙኝን ተቃወማቸው፤ የሚዋጉኝንም ተዋጋቸው። **2** ትልቁንና ትንሹን ጋሻ ያዝ እኔንም ለመርዳት ተነሥ። **3** በሚያሳድዱኝ ላይ ጦርና ሰይፍህን ምዘዝና ነፍሴን «እኔ አዳኝሽ ነኝ» በላት። **4** ሕይወቴን የሚፈልጓት ይፈሩ ይዋረዱም እኔን ለመጉዳት የሚያደቡ አፍረው ወደ ኋላቸው ይመለሱ፤ ግራ ይጋቡ። **5** በነፋስ ፊት እንዳለ እብቅ ይሁኑ የያህዌም መልአክ ያሳድዳቸው። **6** መንገዳቸው ጨለማና ድጥ ይሁን የያህዌ መልአክ ያባርራቸው። **7** ያለ ምክንያት ወጥመድ ዘርግተውብኛል ያለ ምክንያት ሕይወቴን ለማጥፋት ጉድጓድ ቆፍረዋል። **8** ጥፋት በድንገት ይምጣባቸው የዘረጉት ወጥመድ ይያዛቸው ጉድጓድ ውስጥ ወድቀው ይጥፉ። **9** እኔ ግን በያህዌ ደስ ይለኛል በማዳኑም ሐሤት አደርጋለሁ። **10** ዐጥንቶቼ ሁሉ፣ «ያህዌ ሆይ፣ ድኻውን ከእርሱ ከሚበረቱ፣ ችግረኛውንና ምስኪኑን ከቀማኞች እጅ የሚያድን እንደ አንተ ያለ ማን ነው?» እለዋለሁ። **11** ሐሰተኛ ምስክሮች ተነሥተውብኛል በሐሰትም ይከስሱኛል። **12** እኔን ብቸኛ አድርገው በመልካም ፈንታ ክፉ መለሱልኝ። **13** እኔ ግን እነርሱ በታመሙ ጊዜ ማቅ ለበስሁ፤ ለእነርሱ ጾምሁ፤ አንገቴን ደፋሁ። **14** ለወንድሙ እንደሚያለቅስ ሰው አዘንሁ ለእናቱ ልጅ እንደሚያዝን ሰው ሆንሁ። **15** እኔ በተሰናከልሁ ጊዜ ደስ ብሎአቸው ተሰበሰቡ ግፈኞች በድንገት ተሰበሰቡብኝ ያለ ዕረፍትም ቦጫጨቁኝ። **16** እንደ ምናምንቴዎች አፌዙብኝ ጥርሳቸውንም አፋጨብኝ። **17** ጌታ ሆይ፣ እስከ መቼ ዝም ብለህ ታያለህ? ነፍሴን በእነርሱ ከመጠቃት ሕይወቴንም ከአንበሶች አድናት። **18** በታላቅ ጉባኤ መካከል አመሰግንሃለሁ ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበትም እወድስሃለሁ። **19** ያለ ምክንያት የሚጠሉኝ ጠላቶቼ በእኔ ላይ ደስ እንዲላቸው፣ ተንኰላቸውንም እንዲፈጽሙብኝ አታድርግ። **20** የሰላም ቃል ከአፋቸው አይወጣም ነገር ግን በምድሪቱ በጸጥታ በሚኖሩት ላይ ተንኮል ይሸርባሉ። **21** አፋቸውን አስፍተው በመክፈት፣ «እሰይ! እሰይ! በዐይናችን አየነው» አሉ። **22** ያህዌ ሆይ፣ ይህን አይተሃልና ዝም አትበል ጌታ ሆይ፣ ለእኔም አትራቅ። **23** አምላኬ ጌታዬ፣ ለእኔ ለመሟገት ተነሥ ልትከራከርልኝም ተንቀሳቀስ፤ **24** ያህዌ ሆይ፣ በጽድቅህ ፍረድልኝ በእኔም ላይ ደስ አይበላቸው። **25** በልባቸው፣ «እሰይ፣ ያሰብነው ተሳካ» አይበሉ፤ «ዋጥ አደረግነውም» አይበሉ። **26** በጭንቀቴ ደስ የሚላቸው ይፈሩ፤ ግራም ይጋቡ። በእኔ ላይ የሚያፌዙ፤ እፍረትና ውርደት ይልበሱ። **27** ፍትሕ ማግኘቴን የሚፈልጉ እልል ይበሉ ሐሤትም ያድርጉ፣ ዘወትርም፣ «የባርያው ሰላም ደስ የሚለው ያህዌ ይመስገን» ይበሉ። **28** ያኔ የአንተን ጽድቅ እናገራለሁ ቀኑን ሙሉ አመሰግንሃለሁ።

Psalms 35:1

አጠቃላይ መረጃ
ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው።

የዳዊት መዝሙር
ይህም 1) መዝሙሩን የጻፈ ዳዊት ነው ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት ነው ማለት ሊሆን ይችላል።

ትንሹንና ትልቁን ጋሻህን ያዝ... ጦርህንና ጭሬህን ምዘዝ
ይህ ሐረግ እግዚአብሔር ለጦርነት የተዘጋጀ ጦረኛ እንደሆነ ያመለክታል

Psalms 35:4

ሕይወቴን የሚሹ ይፈሩ ይዋረዱ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እኔን ለመጉዳት የሚያቅዱትን ያህዌ ይመልሳቸው ግራ ያጋባቸው››

ወደ ኋላ ይመለሱ
‹‹ወደ ኋላ መመለስ›› ዕቅድን ለመፈጸም አለመቻልን የሚያሳይ ምሳሌ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አይሳካላቸው››

ግራ ይጋቡ
‹‹የሚያደርጉ ይጥፋቸው››

በነፋስ ፊት እንዳለ እብቅ
የጸሐፊው ጠላቶች በቀላሉ እንደሚበንን ነፋስ ፊት እንዳለ እብቅ እንደ ሆኑ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንደ እብቅ ነፋስ ያብንናቸው››

በመንገዳቸው
‹‹መንገዳቸው›› ሕይወታቸውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሕይወታቸው››

ጨለማና ድጥ
ይህ ድብቅና አደገኛ መንገድን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ድብቅና አደጋ የሞላበት››

ያሳደዳቸው
ይህ የሚያመለክተው የያህዌ መልአክ የጸሐፊው ጠላቶችን መቃወም ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እነርሱ ላይ ይነሣ›› ወይም፣ ‹‹እነርሱን ይቃወም››

Psalms 35:7

መረብ አኑረውብኛል
የክፉዎች አድማ ጸሐፊውን ለማጥመድ መረብ መጣል እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንደ ትንሽ እንስሳ በመረብ ሊይዙኝ ፈልገዋል››

ለሕይወቴ ጉድጓድ ቆፍረዋል
የክፉዎች አድማ ጸሐፊውን ለማጥመድ ጉድጓድ መቆፈር እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንደ ትልቅ እንስሳ ሊይዙኝ ጉድጓድ ቆፍረዋል።

ሕይወቴን
ይህ የሚያመለክተው ጸሐፊውን ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እኔን››

ጥፋት በድንገት ይምጣባቸው
ጥፋት በድንገት የሚያጠቃ አደገኛ አውሬ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በድንገት ይጥፉ›› ወይም፣ ‹‹በድንገት ስታጠፋቸው ይደነቁ››

ያስቀመጡት መረብ
የክፉዎች ሤራ ጸሐፊውን ለመያዝ ያስቀመጡት መረብ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንደ እንስሳ እኔን ለመያዝና ለመጉዳት ያስቀመጡት መረብ››

በውስጡ ይውደቁ
ይህ ቁጥር 7 ላይ እንዳለው ምሳሌያው አነጋገር ነው። መረቡ ጸሐፊውን ለመያዝ የታሰበ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ለእኔ የቆፈሩት ጉድጓድ ውስጥ ይውደቁ››

ውስጡ ይውደቁ
ይህም ማለት፣ 1) ቁጥር 7 ላይ ያለው ጉድጓድ ውስጥ ይውደቁ ወይም 2) ጥፋት ውስጥ ይወደቁ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለጥፋታቸው
‹‹ጥፋት›› የሚለውን የነገር ስም ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንዲጠፉ›› ወይም፣ ‹‹አንተ የምታጠፋቸው እንደዚያ ነው››

Psalms 35:9

በማዳኑ
‹‹ማዳን›› የሚለውን የነገር ስም እንደ ግሥ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አንተ ስላዳንኸኝ››

ዐጥንቶቼ ሁሉ
‹‹ዐጥንት›› የሰውየውን ጥልቅ ውስጣዊ ማንነት ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጠቅላላ ውስጣዊ ማንነቴ››

ያህዌ እንደ አንተ ማን አለ... ሊቀሟቸው ከሚሞክሩ?
የዚህ ጥያቄ መልስ እንደ ያህዌ ማንም የለም የሚል ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ እንደ አንተ ማንም የለም ሊቀሟቸው ከሚሞክሩ››

ድኾችና ችግረኞች
‹‹ድኾች›› እና፣ ‹‹ችግረኞች›› በመሠረቱ ተመሳሳይ ቢሆኑም፣ አጽንዖት የተሰጠው ርዳታውን የሚፈልጉትን ብዙዎች ያህዌ እንደሚያድናቸው ነው።

Psalms 35:11

ተነሡ
ይህ ፍርድ ቤት መመስከርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ለመመስከር ፈቃደኛ የሆነ››

ለመልካም ክፉ ከፈሉኝ
ይህ ማለት ለተቀበሉት መልካም ነገር ለውጥ ክፉ የሚመልሱ ሰዎችን የሚያመለክት ምሳሌ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ላደረግሁላቸው መልካም ክፉ አደረጉብኝ››

ክፉ... መልካም
እነዚህን የነገር ስሞች በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ክፉ ነገሮች... መልካም ነገሮች››

አዝኛለሁ
‹‹በጣም አዝኛለሁ››

Psalms 35:13

እነርሱን ባመማቸው ጊዜ
‹‹እነርሱ›› የሚያመለክተው፣ ‹‹ክፉ ምስክሮችን ነው›› (መዝሙር 35፥11)

ማቅ ለበስሁ
‹‹ማዘኔን አሳየሁ››

ራሴን ዝቅ አደረግሁ
ይህ የጸሎት ምሳሌ ነው። ‹‹ራሴን ለጸሎት ዝቅ አደረግሁ››

ለወንድሜ እንደማዝን ሆንሁ
ጸሐፊው የራሱ ወንድም የሞተ ያህል አዝኗል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የገዛ ወንድሜ የታመመ ያህል አዘንሁ››

ለእናቴ እንደማለቅስ አንገቴን ደፋሁ
ጸሐፊው የራሱ እናት የሞተች ያህል አልቅሷል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እናቴ የሞተች ያህል አለቀሰሁ››

አንገቴን ደፋሁ
ይህ የሕመምና የመከራ ምልክት ነው።

Psalms 35:15

ተሰበሰቡ
‹‹በአንድነት ተሰባሰቡ›› ወይም ‹‹ተገናኙ››

እኔ ላይ
ይህ ማለት ጸሐፊውን ለማጥቃት በአንድነት ተሰባሰቡ ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እኔ ላይ ተማከሩ›› ወይም፣ ‹‹ሊያጠፉኝ ለመማከር››

ቦጫጨቁኝ
ጸሐፊው ጨርቅ ይመስል ቆራርጠው ቦጫጨቁት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ክፉዎች አጠቁኝ››

እንደ ምናምንቴዎች አፌዙብኝ
‹‹ከከንቱ ሰዎች ጋር አብረው አፌዙብኝ›› ወይም 2) ‹‹ያለ አንዳች አክብሮት ቀለደብኝ››

ጥርሳቸውን በቁጣ አፏጩብኝ
ይህ የቁጣና የጥላቻ ምልክት ነው። ‹‹እኔ ላይ ጥርሳቸውን የማፏጩት ድምፅ አሰሙ››

Psalms 35:17

እስከ መቼ ዝም ብለህ ታያለህ?
ይህ ጥያቄ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ዝም ብሎ ማየቱን ትቶ እርሱን መርዳት እንዲጀምር መፈለጉን ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንዲህ ሲያደርጉ ዝም ብለህ የምታያቸው እስከ መቼ ነው?›› ወይም፣ ‹‹የምትረዳኝ መቼ ነው?

ነፍሴን ታደጋት
‹‹ነፍስ›› ጸሐፊውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ታደገኝ››

ሕይወቴን ከአንበሶች
‹‹አድን›› የሚለው ውስጠ ታዋቂ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሕይወቴን ከአንበሶች አድን››

ሕይወቴን
ይህ ጸሐፊውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እኔን››

ከአንበሶች
ጸሐፊው ጠላቶቹ አደገኛ አንበሶች እንደሆኑ ይናገራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንደ ዱር አራዊት ከሚያጠቁኝ ጠላቶቼ››

Psalms 35:19

ከውሸታም ጠላቶቼ
‹‹እኔ ላይ ሐሰት እንዲናገሩ ጠላቶቼን አትተዋቸው››

ክፉ ሤራቸው
‹‹ክፉ ዕቅዳቸው››

ሰላም አይናገሩም
‹‹ሰላም›› የሚለውን ቃል ‹‹ሰላማዊ›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ለሰዎች ሰላማዊ ቃል አይናገሩም››

ክፉ ቃሎች ይሸርባሉ
‹‹ሐሰት መናገር ይፈልጋሉ››

በሰላም በሚኖሩት
‹‹ሰላም›› የሚለውን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከሌሎች ጋር ሰላማዊ ሆኖ መኖር›› ወይም፣ ‹‹ማንንም ሳይጐዱ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 35:21

አፋቸውን አስፍተው የከፈቱት ጸሐፊውን ለመክሰስ ነበር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔን ለመክሰስ ጮኹብኝ››

አሃ፣ አሃ
ይህ አንድነ ነገር በድንገት ሲታይ ወይም ግልጽ ሲሆን የሚባል ቃለ አጋኖ ነው፤ ለሚከተለው ዐረፍተ ነገር አጽንዖት ይሰጣል።

በዐይናችን ዐየነው
‹‹ዐይናችን›› የሚያመለክተው የጠላቶቹን ዐይን ነው። እንዲህ ያሉት ጸሐፊው አንዳች መጥፎ ነገር ሲያደርግ ስላዩ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዐየነው›› ወይም ያደረግኸውን መጥፎ ነገር ዐየን››

አንተ አይተሃልና
‹‹ያየው›› የጸሐፊው ጠላቶችን ሐሰተኛ ክስ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሐሰት እየከሰሱኝ እንደሆነ ዐየህ››

ዝም አትበል
‹‹ያደረጉትን ቸል አትበል›› ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ባደረጉት መሠረት ፍረድባቸው››

ከእኔ አትራቅ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወደ እኔ ቅረብ››

ተነሥ፣ ንቃ
እንዲህ ማለት እግዚአብሔር ተኝቶአል ማለት አይደለም። ጸሐፊው እግዚአብሔር ጣልቃ እንዲገባ ይፈልጋል። ሁለቱም ቃሎች ተመሳሳይ ቢሆኑም የልመናውን አጣዳፊነት አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተ ያንቀላፋህ ይመስለኛል! ንቃ››

ልትከራከርልኝ
‹‹መከራከር›› የሚለውን የነገር ስም፣ ‹‹ተከራከር›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለእኔ ተከራከር››

ነገሬን
ይህ የሚያመለክተው ጸሐፊውን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለእኔ››

Psalms 35:24

በእኔ ላይ ደስ አይበላቸው
‹‹በእኔ መከራ ደስ አይበላቸው››

በልባቸውም አይበሉ
ይህ ለራስ መናገርን የሚያመለክት ምሳሌ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለራሳቸው አይበሉ››

አሃ
ይህ አንድ ነገር በድንገት ሲደረግ ወይም መግለጽ ሲያቅት የሚባል ቃለ አጋኖ ነው። ለሚከተለው ነገር አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አዎን››

የፈለግነውን አገኘን
ይህ የሚያመለክተው የጸሐፊው ጠላቶች በደለኛ እንዲባል ፈልገው እንደ ነበር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ፈለግነው በደለኛ ተባለ››

ዋጥነው
የጸሐፊው ጠላቶች የእርሱን ውድቀት እንደ ዱር እንስሳት እርሱን እንደበሉት ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጨርሶ ዋጥነው›› ወይም፣ ‹‹አጠፋነው››

በጭንቀቴ ደስ የሚላቸው ይፈሩ፣ ግራም ይጋቡ
‹‹የእኔ መጨነቅ ደስ የሚላቸው ይፈሩ ግራ ይጋቡ››

ይፈሩ
‹‹እፍረት ይከናነቡ››

ግራ ይጋቡ
‹‹የሚያደርጉት ይጥፋቸው›› ወይም፣ ‹‹ይዋረዱ››

ራሳቸውን ከፍ የሚያደርጉብኝ እፍረትና ውርደት ይከናነቡ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ ላይ ከፍ ማለት የሚፈለጉትን አንተ እፍረትና ውርደት አከናንባቸው››

እኔ ላይ ከፍ ማለት የሚፈልጉ
‹‹ከእኔ የበለጠ እንደሆኑ የሚቆጥሩ›› ወይም፣ ‹‹እኔ ላይ ክፉ የማድረግ መብት እንዳላቸው የሚያስቡ››

እፍረትና ውርደት ይከናነቡ
እፍረትና ውርደት እንደ ልብስ እንደሆኑ ተነግሯል። እነዚህን የነገር ስሞች እንደ ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይፈሩ ይዋረዱ››

እፍረት ውርደት
እነዚህ ቃሎች የሚናገሩት ስለ ተመሳሳይ ነገር ቢሆንም፣ ጥቅም ላይ የዋሉት ወርደታቸው የከፋ መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት ነው።

Psalms 35:27

ፍረድልኝ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ፍረድ›› ሲል ዘማሪው ንጹሕ መሆኑን ያህዌ እንዲፈርድለት መፈለጉን ያመለክታል።

ዘወትር እንዲህ ይበሉ
‹‹ሁሌም እንዲህ ይበሉ››

ያህዌ ይመስገን
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌን እናመስግን››

በእርሱ ደስ ይበላቸው
‹‹ደስ የሚላቸው›› ወይም፣ ‹‹ደስ ያላቸው››

ሰላም
ደህንነት፣ ደስታ

ጽድቅህን ይናገራል
‹‹ጽድቅ›› የሚለውን የነገር ስም፣ ‹‹ትክክል›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሥራህ ትክክል መሆኑን ይናገሩ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 36

1 ክፉ ሰው በልቡ፣ ክፋትን ያስባል በዐይኖቹም ፊት እግዚአብሔርን መፍራት የለም። **2** በደሉ ግልጽ ወጥቶ እንዳይጠላ እያሰበ ራሱን ይሸነግላል። **3** ንግግሩ ተንኰልንና ሐሰትን የተሞላ ነው፤ አስተዋይ መሆንንና መልካም ማድረግን አይፈልግም። **4** በመኝታው ላይ ክፋት ያውጠነጥናል ራሱን ወደ ክፉ መንገድ ይመራል ክፉውንም ነገር አያርቅም። **5** ያህዌ ሆይ፣ ታማኝነትህ እስከ ሰማይ እውነተኛነትህም እስከ ደመናት ይደርሳል። **6** ጽድቅህ እንደ እግዚአብሔር ተራራ ነው ፍርድህም እጅግ ጥልቅ ነው። ያህዌ ሆይ፣ አንተ ሰውንም እንስሳንም ትጠብቃለህ። **7** እግዚአብሔር ሆይ፣ ታማኝነትህ እንዴት ክቡር ነው! የሰው ልጆች ሁሉ በክንፎችህ ጥላ ሥር መጠጊያ ያገኛሉ። **8** ከቤትህ ሲሳይ ተመግበው ይጠግባሉ፤ ከበረከትህም ወንዝ ይጠጣሉ። **9** በአንተ ዘንድ የሕይወት ምንጭ አለ በአንተ ብርሃን ብርሃን እናያለን። **10** ለሚያውቁህ ምሕረትህ፣ ልባቸውም ለቀና ጽድቅህ አይቋረጥባቸው። **11** የእብሪተኛ እግር አይቅረበኝ የክፉ ሰው እጅም አያሳድደኝ። **12** ክፉ አድራጊዎች እንዴት እንደ ወደቁ መነሣትም እንደማይችሉ ተመልከት።

Psalms 36:1

አጠቃላይ መረጃ
ተጓዳኝ ሐሳብ በዕራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው።

ለመዘምራን አለቃ
‹‹ይህ የመዝሙር መሪው በአምልኮ የሚጠቀምበት ነው››

የያህዌ ባርያ የዳዊት መዝሙር
ይህም ማለት፣ 1) መዝሙሩን የጻፈ ዳዊት ነው ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት ነው ማለት ሊሆን ይችላል።

ክፉ ሰው
ይህ በአጠቃላይ ስለ ክፉ ሰዎች እንጂ፣ ስለ አንድ ሰው የተነገረ አይደለም። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ክፉ ሰዎች››

በጥልቅ ልቡ
‹‹ልብ›› የሰውን ጥልቅ ማንነት ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከጥልቅ ልቦናው››

በዐይኑ ፊት
‹‹ዐይኑ›› ክፉውን ሰው ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በእርሱ ዘንድ››

እንዲህ በማሰብ ራሱን ያጽናናል
‹‹ይህን ማመን ይመርጣል›› ወይም፣ ‹‹እንዲህ ማሰብ ይፈልጋል››

ኀጢአቱ የሚታወቅና የሚጠላ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እግዚአብሔር ኀጢአቱን የሚያውቅና የሚጠላ››

Psalms 36:3

ቃሎቹ
‹‹እርሱ የሚለው››

በጐ ማድረግ
‹‹መልካም ነገር ማድረግ››

በክፉ መንገድ ይሄዳል
የሰው ክፉ ሥራ በክፉ መንገድ መሄድ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ክፉ ነገር ያደርጋል››

ክፋትን አያርቅም
‹‹ክፋት›› የሚለውን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ክፉ ተግባርን አይንቅም››

Psalms 36:5

የኪዳን ታማኝነትህ… ወደ ሰማያት ይደርሳል
የእግዚአብሔር ኪዳን ታማኝነት ወደ ሰማይ የሚደርስ አንዳች ነገር እንደሆነ ተነግሯል። ‹‹ታማኝነት›› የሚለውን የነገር ስም በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የኪዳን ታማኝነትህ… በጣም ትልቅ ነው›› ወይም፣ ‹‹ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል አንተም… ለኪዳንህ ታማኝ ነህ››

ወደ ደመናት ይደርሳል
የእግዚአብሔር ታማኝነት ትልቅነት በጣም ከፍ ያለ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንደ ደመናት ከፍ ያለ ነው›› ወይም፣ ‹‹እጅግ ታላቅ ነው››

እንደ የእግዚአብሔር ተራሮች… እንደ ታላቁ ጥልቅ
የእግዚአብሔር ጽድቅና ፍርድ ታላቅነት በጣም ከፍ ያለና የጠለቀ መሆኑን ይህ ሐረግ ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንደ ተራሮች ከፍ ያለ… እንደ ባሕር የጠለቀ››

የጠበቅኸው
‹‹የረዳኸው›› ወይም፣ ‹‹ያዳንኸው››

Psalms 36:7

የኪዳን ታማኘነትህ ምንኛ የከበረ ነው
‹‹የከበረ›› የሚለው ጸሐፊው የያህዌን ኪዳን ታማኝነት ምን ያህል ታላቅ ዋጋ እንደሚሰጠው ያመለክታል›› ‹‹ታማኝነት›› የሚለውን የነገር ስም በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ለኪዳንህ ታማኝ መሆንህን ታላቅ ዋጋ እሰጣለሁ››

በቤትህ ሙላት ደስ ይላቸዋል።
ቤት ውስጥ በእንግድነት መመገብ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚያስፈልገውን ሁሉ መስጠት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አንተ ስለምትሰጣቸው ሁሉም አላቸው›› ወይም፣ ‹‹ብዙ የምትሰጠው አለህ፤ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ታዘጋጅላቸዋለህ››

ከደስታህ ወንዝ እንዲጠጡ አደረግህ
እዚህ ላይ ሁለት ምሳሌያዊ ገለጻዎች ቀርበዋል። የእግዚአብሔር በረከት ሙላት ወንዝ ውስጥ እንደሚፈስስ ውሃ እንደሆነ ተነግሯል። እነዚህን በረከቶች የሚቀበሉ እንደ ውሃ እየጠጧቸው እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የከበሩ በረከቶችህ እንደሚጠጡት የወንዝ ውሃ ነው››

የሕይወት ምንጭ
‹‹የሕይወት መገኛ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በብርሃንህ ብርሃን እናያለን
‹‹ብርሃን›› የእውነተኛ ዕውቀት ምሳሌ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አንተ ስታበራልን እውነትን እናውቃለን›› ወይም፣ ‹‹ስለ አንተ እውነቱን ማወቅ የሚስችለን የአንተ ብርሃን ነው››

Psalms 36:10

አንተን ለሚያውቁ የኪዳንህን ታማኝነት በሙላት ይድረሳቸው
ያህዌ ዘወትር ለሕዝቡ ታማኝ መሆኑን ወደ እነርሱ እስኪደርስ የሚረዝም ነገር እንደሆነ ጸሐፊው ይናገራል። ‹‹ታማኝነት›› የሚለውን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለሚያውቁህ በታማኝነት ፍረድላቸው››

ልባቸው ለቀና መከታ ሁንላቸው
‹‹መከታ›› የሚለውን እንደ ግሥ ማድረግ ይቻላል። ካለፈው ሐረግ፣ ‹‹ዘወትር›› የሚለው ውስጠ ታዋቂ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ልባቸው የቀናውን ዘወትር መከታ ሁንላቸው››

ልባቸው የቀና
‹‹ልብ›› ሰዎችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ቅኖች›› ወይም፣ ‹‹በጽድቅ የሚኖሩ ሰዎች››

የእብሪተኛ እግር… የክፉ ሰው እጅ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እግር›› እና፣ ‹‹እጅ›› ክፉ ሰዎችን ያመለክታሉ። እነዚህ ክፉ ሰዎችን በአጠቃላይ እንጂ፣ የተወሰኑ ሰዎችን ብቻ የሚመለከቱ አይደሊም። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እብሪተኛ ሰዎች… ክፉ ሰዎች››

አያሳድደኝ
‹‹አያባርረኝ›› ወይም፣ ‹‹ስፍራዬን እንድተው አያድርገኝ››

ክፉ አድራጊዎች ወድቀዋል፤ ተፈጥፍጠዋል መነሣትም አይችሉም
ሦስቱም ሐረጐች የሚያመለክቱት የተሸነፉትን ክፉ አድራጊዎች ነው

ተፈጥፍጠዋል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ፈጥፍጠሃቸዋል›› ወይም፣ ‹‹አጥፍተሃቸዋል››

መነሣትም አይችሉም
‹‹ከእንግዲህ አይነሡም››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 37

1 በክፉዎች ምክንያት አትበሳጭ ኃጢአት በሚሠሩም አትቅና፤ **2** እንደ ሣር ቶሎ ይደርቃሉና እንደ ለመለመ ቅጠልም ይጠወልጋሉ። **3** በያህዌ ተማመን፤ መልካምንም አድርግ በምድሪቱ ተቀመጥ፤ ታምነህም ተሰማራ። **4** በያህዌ ደስ ይበልህ የልብህንም ፍላጐት ይሰጥሃል። **5** መንገድህን ለያህዌ አደራ ስጥ በእርሱ ታመን እርሱም ያከናውንልሃል። **6** ጽድቅህን እንደ ብርሃን ያንተንም ንጽሕና እንደ ቀትር ፀሐይ ያበራዋል። **7** በያህዌ ፊት ጸጥ በል፤ በትዕግሥትም ተጠባበቀው። ነገር በተሳካለት፣ ክፋትንም በሚሸርብ ሰው አትቅና **8** አትቆጣ፤ ተስፋም አትቁረጥ መከራን ከማብዛቱ ውጪ ምንም ስለማይጠቅምህ አትከፋ። **9** ክፉ አድራጊዎች ይጠፋሉ ያህዌን የሚጠባበቁ ግን ምድሪቱን ይወርሳሉ። **10** ብዙም ሳይቆይ ክፉ ሰው ይጠፋል ብትፈልግም ቦታውን አታገኘውም። **11** ገሮች ግን ምድርን ይወርሳሉ በታላቅ ሰላምም ደስ ይላቸዋል። **12** ክፉዎች ጻድቃን ላይ ያሤራሉ ጥርሳቸውንም ያፋጩባቸዋል። **13** መጥፊያ ቀናቸው እንደ ደረሰ ስለሚያውቅ ጌታ ይስቅባቸዋል። **14** ድኾችንና ችግረኞችን ለመጣል ልበ ቅኖችንም ለመግደል ክፉዎች ሰይፋቸውን መዘዙ፤ ቀስታቸውንም ገተሩ። **15** ሰይፋቸው የገዛ ልባቸውን ይወጋል ቀስታቸውም ይሰበራል። **16** ከክፉ ሰው ብዙ ሀብት ይልቅ፣ የጻድቅ ጥቂት ሀብት ይበልጣል። **17** የክፉዎች ክንድ ይሰበራልና ያህዌ ግን ጻድቃንን ይደግፋቸዋል። **18** ያህዌ ያለ ነቀፋ የሚመላለሱትን ዕለት ዕለት ይጠብቃቸዋል። ርስታቸውም ለዘላለም ይኖራል። **19** በክፉ ቀን አያፍሩም በራብ ዘመንም የሚበሉትን አያጡም። **20** ክፉዎች ግን ይጠፋሉ የያህዌ ጠላቶች እንደ መስክ ውበት ይሆናሉ። እንደ ጢስም በንነው ይጠፋሉ። **21** ኃጢአተኛ ይበደራል፣ ግን መልሶ አይከፍልም ጻድቅ ግን በልግስና ይሰጣል። **22** እግዚአብሔር የባረካቸው ምድርን ይወርሳሉ እርሱ የረገማቸው ግን ይጠፋሉ። **23** የሰውን አካሄድ የሚያጸና ያህዌ ነው በመንገዱም ደስ ይለዋል። **24** ያህዌ በእጁ ደግፎ ስለሚይዘው ቢሰናከል እንኳ አይወድቅም። **25** ጐልማሳ ነበርሁ፤ አሁን አርጅቻለሁ ጻድቅ ሲጣል፣ ዘሩም እንጀራ ስለምን አላየሁም። **26** ጻድቅ ሁልጊዜ በልግሥና ይሰጣል፣ ደግሞም ያበድራል ልጆቹም የተባረኩ ይሆናሉ። **27** ከክፉ ራቅ መልሙንም አድርግ ለዘላለምም በሰላም ትኖራለህ። **28** ያህዌ ፍትሕ ይወዳልና ታማኞቹንም በፍጹም አይጥልም፤ ለዘላለምም ይጠብቃቸዋል። የኃጢአተኛው ዘር ግን ይጠፋል። **29** ጻድቃን ምድርን ይወርሳሉ በእርሷም ለዘላለም ይኖራሉ። **30** የጻድቅ አፍ ጥበብን ይናገራል አንደበቱም ፍትሕን ያወራል። **31** የአምላኩ ሕግ ልቡ ውስጥ ነው አካሄዱም አይሰናከልም። **32** ኃጢአተኛው ጻድቅን ይመለከተዋል ሊገድለውም ይፈልጋል። **33** እግዚአብሔር ግን በእጁ አይጥለውም ፍርድ ፊት ሲቀርቡም አይረታም። **34** ያህዌን ደጅ ጥና፤ መንገዱንም ጠብቅ እርሱም ምድርን እንድትወርስ ከፍ ከፍ ያደርግሃል። ክፉዎች ሲጠፋ ታያለህ። **35** ክፉና ጨካኙን ሰው ምቹ መሬት ላይ እንዳለ ዛፍ ለምልሞ አየሁት **36** ተመልሼ ስመጣ ግን በቦታው አልበረም፤ ፈለግሁ ላገኘው ግን አልቻልሁም። **37** ጻድቅን ሰው ተመልከት ቅን የሆነውንም ሰው እይ የሰላም ሰው ተስፋ አለውና። **38** ኃጢአተኞች ግን ፈጽሞ ይደመሰሳሉ ዘራቸውም ይወገዳል። **39** የጻድቃን ድነት ከያህዌ ዘንድ ነው በመከራም ጊዜ ይጠብቃቸዋል። **40** ያህዌ ይረዳቸዋል፤ ደግሞም ይታደጋቸዋል። ከክፉዎች እጅ ነጥቆ ያወጣቸዋል እርሱን መጠጊያ አድርገዋልና ያድናቸዋል።

Psalms 37:1

የዳዊት መዝሙር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) መዝሙሩን ዳዊት ጽፎታል ወይም 2) መዝሙሩ የሚመለከተው ዳዊትን ነው ወይም 3) መዝሙሩ የዳዊትን መዝሙሮች ዘይቤ የተከተለ ነው የሚሉት ናቸው።

በክፉ አድራጊዎች ምክንያት አትበሳጭ
“አመፀኞች ሰዎች እንዲያናድዱህ አትፍቀድላቸው” ወይም “አመፀኞች ሰዎች በሚያደርጉት ነገር አሳብ አይግባህ”

እንደ ሣር ይደርቃሉ ... እንደ አረንጓዴ ተክሎች ይጠወልጋሉ
ክፉ አድራጊዎች በሞቃት የአየር ጠባይ እንደሚደርቅና እንደሚሞት ሣርና ተክል ተደርገው ተነግረዋል። የእነዚህ የሁለቱም ማነጻጸሪያዎች ትርጉም ይሞታሉ የሚል ነው። አ.ት፡ “ይሞታሉ” ወይም “ፍጻሜአቸው ይሆናል” (See: Simile and Parallelism)

Psalms 37:3

በታማኝነት ተሰማራ
ታማኝነት በመልካም መሰማሪያ የሚያሳድጉት እንስሳ በሚመስል መልኩ ተነግሮለታል። አ.ት፡ “ታማኝነትን ተመገብ” ወይም “ታማኝነትህን አብዛ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የልብህን ፍላጎት
እዚህ ጋ “ልብ” የሚወክለው የሰውየውን ውስጣዊ ማንነትና አሳብ ነው። አ.ት፡ “ጥልቅ የሆነ ውስጣዊ ፍላጎትህን” ወይም “እጅግ የምትፈልጋቸውን ነገሮች” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 37:5

መንገድህን ለእግዚአብሔር ስጥ
እዚህ ጋ “መንገድህን ስጥ” የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን እግዚአብሔር ሕይወትህን እንዲቆጣጠር ጠይቀው ማለት ነው። አ.ት፡ “እግዚአብሔር አኗኗርህን እንዲመራ ጠይቀው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ስለ አንተ ሆኖ ያደርጋል
ይህ በሕግ ጉዳዮች ሌላውን ሰው መወከል ነው። እዚህ ጋ፣ አንድ ሰው በእግዚአብሔር በሚታመንበት ጊዜ እርሱ ለዚያ ሰው ተከላካይ ይሆናል፣ ፍትሕ እንዲያገኝም ያደርጋል። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

እንደ ቀን ብርሃን ... ቀትሩም እንደ ቀን
እነዚህ ሁለቱም ሐረጎች የሚሉት ስለ አንድ ነገር ነው። (See: Parallelism)

እንደ ቀን ብርሃን
ይህ “ሁሉም በሚያየው ሁኔታ” ማለት ነው። አ.ት፡ “እንደ ቀን ብርሃን በግልጽ የሚታይ” (See: Simile)

ቀትሩም እንደ ቀን
ይህ “የቀትር ፀሐይ እንደሚታይ” ማለት ነው። አ.ት፡ “በቀን ውስጥ ብርሃኑ ብሩህ ሆኖ እንደሚታይ” (See: Simile)

Psalms 37:7

ጸጥ በል
“ዝም በል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 37:8

ይቆረጣሉ
የአመፀኛው መጥፋት ተቆርጦ እንደሚጣል የተክል ቅርንጫፍ ሆኖ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔርን ተስፋ የሚያደርጉ ግን
“በእግዚአብሔር የሚታመኑ ግን”

ምድሪቱን ይወርሳሉ
ምድሪቱን መውረስ ርስትን እንደ መቀበል ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “ምድሪቱን እንደ ራሳቸው ንብረት አድርገው ይቀበላሉ” ወይም “በምድሪቱ ላይ በሰላም እንዲኖሩ ይፈቀድላቸዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ይጠፋሉ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ የክፉውን ሰው ሞት ያመለክታል። አ.ት፡ “ይሞታል፣ ዳግመኛም አታየውም” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Psalms 37:11

የዋሁ
ይህ የሚያመለክተው የዋህ የሆኑትን ሰዎች ነው። አ.ት፡ “የዋህ ሰዎች” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

ምድሪቱን ይወርሳል
ምድሪቱን መውረስ ርስትን እንደ መቀበል ሆኖ ተነግሯል። ይህንን በመዝሙር 37:9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ምድሪቱን እንደ ራሳቸው ንብረት አድርገው ይቀበላሉ” ወይም “በምድሪቱ ላይ በሰላም እንዲኖሩ ይፈቀድላቸዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ክፉው ሰው
ይህ አንድን የተለየን ሰው አያመለክትም። የሚያመለክተው በአጠቃላይ ክፉ ሰዎችን ነው። አ.ት፡ “ክፉው ሰውዬ” (See: Generic Noun Phrases)

ጻድቃን
ይህ አንድን የተለየን ሕዝብ አያመለክትም። የሚያመለክተው ጻድቅ የሆኑ ሕዝቦችን ነው። አ.ት፡ “ጻድቁ ሰውዬ” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

ጥርሱን ያፋጫል
ክፉው ሰው ጻድቁን እጅግ ይጠላዋል፣ ንዴቱን ለማሳየትም ጥርሶቹን ያፋጫል። (See: Symbolic Language)

ቀኑ ቀርቧል
“ቀኑ” የፍርድ ቀን እንደሚሆን ያመለክታል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር በእርሱ ላይ የሚፈርድበትና የሚቀጣበት ቀን ቀርቧል” ወይም “እግዚአብሔር በክፉው ሰው ላይ የሚፈርድበትና የሚቀጣበት ቀን ቀርቧል” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

Psalms 37:14

ክፉው
ይህ ክፉዎቹን ሰዎች ያመለክታል። አ.ት፡ “ክፉዎቹ ሰዎች” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

ሰይፋቸውን መዘዋል ... ቀስታቸውን ገትረዋል
“ሰይፍ” እና “ቀስት” ሁለቱም ሰዎችን ለማጥቃት ጥቅም ላይ የሚውሉ የጦር መሣሪያዎች ናቸው። “መዘዋል” እና “ገትረዋል” የሚሉት የእርግጠኝነት ቃላት ውጊያውን ለመጀመር ዝግጁ ናቸው ማለት ነው። (See: Synecdoche)

ለመጣል
የእነዚህ ችግረኞች ጥፋት፣ መሬት ላይ ሲጣል ስብርብሩ እንደሚወጣ ሸክላ ማሰሮ ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ለማጥፋት” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የተጨቆኑና የተቸገሩ
እነዚህ ሁለቱም ቃላት የሚያመለክቱት ራሳቸውን ለመከላከል አቅም የሌላቸውን ሰዎች ነው። አ.ት፡ “ሊቋቋሟቸው የማይችሏቸው ሰዎች” (See: Doublet)

ሰይፋቸው የገዛ ልባቸውን ይወጋል
ሰይፍ የጦር መሣሪያዎች ምሳሌ ሲሆን “ልብ” የሚወክለው ሕዝቡን ነው። “ልብን መውጋት” በአነጋገር ዘይቤ “መግደል” የሚል ትርጉም አለው። አ.ት፡ “ሰይፋቸው በራሳቸው ላይ ይመለሳል፣ ራሳቸውንም ይገድላሉ” (Synecdoche እና የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Psalms 37:16

ከብዙ ክፉ ሰዎች ሀብት ይልቅ ለጻድቁ ያለው ትንሹ ይሻላል
“ከብዙ ብልጽግና ጋር ክፉ ከመሆን ጻድቅ ሆኖ ድኻ መሆን ይሻላል”

ለጻድቁ ያለው ትንሹ ይሻላል
“ትንሹ” የሚለው ስማዊ ቅጽል የሚያመለክተው ጥቂት ሀብትን ነው። “ጻድቁ” የሚለው ስማዊ ቅጽል የሚያመለክተው ደግሞ ጻድቁን ሰው ነው። አ.ት፡ “ጻድቅ ሰው ያለው ጥቂት ሀብት ይሻላል” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

ብዙ
ይህ የሚያመለክተው የክፉ ሰዎችን ብልጽግና ነው። (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

የክፉ ሰዎች ክንድ ይሰበራል
እዚህ ጋ “ክንድ” የሚወክለው የክፉ ሰዎችን ኃይል ነው። ክንዳቸውን መስበር ሥልጣናቸውን መውሰድን ይወክላል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር የክፉ ሰዎችን ብርታት ያስወግዳል” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Psalms 37:18

ነቀፋ የሌለባቸውን ይመለከታል
“መመልከት” አንድን ሰው መጠበቅ ማለት ነው። እዚህ ጋ “ነቀፋ የሌለባቸው” የሚያመለክተው የማይነቀፉትን ሰዎች ነው። አ.ት፡ “ነቀፋ የሌለባቸውን ሰዎች ይጠብቃል” (የአነጋገር ዘይቤ እና ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

ዕለት በዕለት
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ትርጉሙም “ባለማቋረጥ” የሚል ነው። አ.ት፡ “በየቀኑ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ቀኖቹ ክፉዎች በሚሆኑበት ጊዜ
ይህ ሐረግ እንደ ረሃብ ያለውን ጥፋት ያመለክታል። አ.ት፡ “መቅሰፍት በሚሆንበት ጊዜ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Psalms 37:20

የእግዚአብሔር ጠላቶች እንደ ሳር ክብር ይሆናሉ
ጸሐፊው የእግዚአብሔርን ጠላቶች መስክ ላይ ከሚያብቡ አበባዎች ጋር ያነጻጽራቸዋል። (See: Simile)

በእሳት ይቃጠላሉ፣ በንነውም ይጠፋሉ
ጸሐፊው የክፉዎችን መጥፋት ከመከር በኋላ በሚቃጠል አረም ወይም መስክ ላይ ጠውልገው ባሉ አበቦች መስሎ ይናገራል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይችላል። አ.ት፡ “እሳት የመስኩን አረም ወደ ብናኝነት እንደሚቀይረው እግዚአብሔር ያጠፋቸዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ለጋስ ነው፣ ይሰጣልም
የሁለቱም ትርጉም አንድ ሲሆን አጽንዖት የሚሰጡት ስለ ጻድቁ ልግስና ነው። (See: Doublet)

Psalms 37:22

እነዚያ በእግዚአብሔር የተባረኩ ምድርን ይወርሳሉ፤ በእርሱ የተረገሙት እነዚያ ይቆረጣሉ
ይህ የሁለት ተመሳሳይ አሳቦች ንጽጽር ነው። እነዚያ በእግዚአብሔር የተባረኩት በእግዚአብሔር ከተረገሙት ጋር ተነጻጽረዋል። (See: Parallelism)

እነዚያ በእግዚአብሔር የተባረኩ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እነዚያ እግዚአብሔር የሚባርካቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ምድርን ይወርሳሉ
ምድርን መውረስ ርስትን እንደ መቀበል ሆኖ ተነግሯል። ይህንን በመዝሙር 37:9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ምድሪቱን እንደ ግል ንብረታቸው አድርገው ይቀበላሉ” ወይም “ምድሪቱ ላይ በሰላም እንዲኖሩ ይፈቀድላቸዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እነዚያ በእርሱ የተረገሙት
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እነዚያ እግዚአብሔር የሚረግማቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ይቆረጣሉ
የአመፀኛው መጥፋት ተቆርጦ እንደሚጣል የተክል ቅርንጫፍ ሆኖ ተነግሯል። ይህንን በመዝሙር 37:9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የሰው አካሄድ የሚጸናው በእግዚአብሔር ነው ... በእግዚአብሔር ፊት ይመሰገናል
እነዚህ የአስተሳሰቡን ተገቢነት በሚያሳዩበትና ተደራጊ አንቀጹን በሚያብራሩበት ሁኔታ ሊነገሩ ይችላሉ። አ.ት፡ “አንድ ሰው በእግዚአብሔር ፊት በሚመሰገንበት ሁኔታ ከኖረ እግዚአብሔር አካሄዱን ያጸናለታል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የሰው አካሄድ የሚጸናው በእግዚአብሔር ነው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አንድ ሰው ስኬታማ እንዲሆን የሚያስችለው እግዚአብሔር ነው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

አንድ ሰው ... ሰውየው
ይህ ሰዎችን በአጠቃላይ እንጂ አንድን የተለየን ሰው አያመለክትም። (See: Generic Noun Phrases)

የሰው አካሄድ
አካሄድ የሚወክለው የአንድን ሰው አኗኗር ነው። አ.ት፡ “አንድ ሰው የሚኖርበት አኗኗር” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ቢደናቀፍም አይወድቅም
እዚህ ጋ “መደናቀፍ” እና “መውደቅ” የሚያመለክቱት ሰውየው በአስቸጋሪ ጊዜ የሚኖረውን ምላሽ ነው። አ.ት፡ “አስቸጋሪ ጊዜዎች ቢገጥሙትም ፈጽሞ አይወድቅም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእጁ ይይዘዋል
እዚህ ጋ “በእጁ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ኃይል ሲሆን “ይይዘዋል” የሚያመለክተው የሚያደርግለትን ጥበቃ ነው። አ.ት፡ “በኃይሉ ይጠብቀዋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 37:25

ጻድቁ ሰው ተረስቷል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ጻድቁን ሰው ረስቶታል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ጻድቁ ሰው
ይህ አጠቃላይ ንግግር እንጂ አንድን የተለየን ሰው አያመለክትም። (See: Generic Noun Phrases)

እንጀራ ሲለምን
እዚህ ጋ “እንጀራ” የሚለው ቃል በአጠቃላይ ምግብን ይወክላል። አ.ት፡ “ምግብ ሲለምን” (See: Synecdoche)

ዕድሜውን ሙሉ
በዚህ የአነጋገር ዘይቤ ይህ አድራጎት የሕይወት ዘመን ልምምዱ ነው የሚል ትርጉም አለው። አ.ት፡ “እርሱ ሁሌም” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ልጆቹ በረከት ይሆናሉ
“ልጆቹ ሌሎችን ለመባረክ ያድጋሉ”

ከ -- ራቅ
አንድ ነገር ማድረግን መተው ሰውየው ከድርጊቱ እንደ ራቀ ተደርጎ ተናግሯል። አ.ት፡ “ማድረግን ተው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 37:28

ለዘላለም ይኖራሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ለዘላለም ይጠብቃቸዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ይቆረጣሉ
የአመፀኛው መጥፋት ተቆርጦ እንደሚጣል የተክል ቅርንጫፍ ሆኖ ተነግሯል። ይህንን በመዝሙር 37:9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)።

ጻድቁ
ይህ ጻድቅ የሆኑትን ሰዎች ያመለክታል። አ.ት፡ “ጻድቅ ሰዎች” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

ምድሪቱን ይወርሳሉ
ምድሪቱን መውረስ ርስትን እንደ መቀበል ሆኖ ተነግሯል። ይህንን በመዝሙር 37:9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ምድሪቱን እንደ ራሳቸው ንብረት አድርገው ይቀበላሉ” ወይም “በምድሪቱ ላይ በሰላም እንዲኖሩ ይፈቀድላቸዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የጻድቅ ሰው አፍ
እዚህ ጋ “አፍ” የሚወክለው የተናጋሪውን ሰው ሁለንተና ነው። አ.ት፡ “ጻድቁ ሰው” (See: Synec- doche)

ጥበብን ይናገራል
የነገር ስም የሆነው “ጥበብ” “ጠቢብ” ተብሎ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ለሌሎች ጥበብ ያለበትን ምክር ይሰጣል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ፍትሕን ያበዛል
የነገር ስም የሆነው “ፍትሕ” እንደ ድርጊት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሌሎች ሰዎች በጽድቅ እንዲኖሩ ያበረታታል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 37:31

የእግዚአብሔር ሕግ በልቡ አለ
እዚህ ጋ “በልቡ ውስጥ” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ጥልቅ የሆነውን ውስጣዊ ማንነቱን ነው። አ.ት፡ “የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት በውስጣዊ ማንነቱ ውስጥ ያስቀምጠዋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እግሮቹም አይንሸራተቱም
እዚህ ጋ እግዚአብሔርን ያለመታዘዝ ከትክክለኛው መንገድ መንሸራተትና መውደቅ እንደሆነ ተቆጥሮ ተነግሯል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር እንዲሄድበት በሚፈልገው መንገድ በሰላም ይሄዳል” ወይም “እግዚአብሔር እንዲያደርግ የፈለጋቸውን ነገሮች በሰላም ያደርጋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አመጸኛው ሰው ... ጻድቁን ሰው ... ክፉው ሰው
እነዚህ ተለይተው የታወቁ ሰዎች አይደሉም። በጥቅሉ እንዲህ ዓይነቶቹን ሰዎች የሚያመለክቱ ናቸው። (See: Generic Noun Phrases)

ጻድቁን ሰው ይመለከተዋል
እዚህ ጋ መመልከት ጻድቅ የሆኑትን ሰዎች ለመጉዳት መከታተልን ያመለክታል። አ.ት፡ “ጻድቁን ሰው አድፍጦ ይጠብቀዋል” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

Psalms 37:34

ምድሪቱን እንድትወርስ ያነሣሃል
እዚህ ጋ “ያነሣሃል” የሚያመለክተው እግዚአብሔር እርሱን ተስፋ ለሚያደርጉት ክብርን እንደሚሰጣቸው ነው። አ.ት፡ “ምድሪቱን ለአንተ በመስጠት ያከብርሃል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ክፉዎች
ይህ ክፉ ሰዎችን ያመለክታል። አ.ት፡ “ክፉዎች ሰዎች” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

ይቆረጣሉ
የአመፀኛው መጥፋት ተቆርጦ እንደሚጣል የተክል ቅርንጫፍ ሆኖ ተነግሯል። ተመሳሳዩን ሐረግ በመዝሙር 37:9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 37:35

ክፉውንና ጨካኙን ሰው
ይህ አንድን የተለየን ሰው አያመለክትም። ይህ ጥቅል አነጋገር ነው። (See: Generic Noun Phrases)

በራሱ ዐፈር ላይ እንደ ለመለመ ዛፍ ተስፋፍቶ
እዚህ ጋ የክፉው ሰው መበልጸግ በጥሩ ዐፈር ላይ በሚበቅል ጤናማ ዛፍ ተመስሎ ተነግሮለታል። (See: Simile)

ሊገኝ አይችልም
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ላገኘው አልቻልኩም” ወይም “እግዚአብሔር እርሱን አስወግዶታል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Psalms 37:37

ቅኑን ሰው
ይህ አንድን የተለየን ሰው አያመለክትም። ይህ ጥቅል አነጋገር ነው። (See: Generic Noun Phrases)

ትክክለኞቹን ልብ በላቸው
“ደግ ሰዎችን በጥንቃቄ አስተውላቸው” ወይም “ደግ ሰዎችን አስተውላቸው”

የክፉ ሰው ተስፋው ይቆረጣል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር የትውልድ ሐረጉ እንዳይቀጥል ያደርጋል” ወይም “አንድም ዘር አይኖረውም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ተስፋው
ይህ የሚያመለክተው ዘሩን ነው። አ.ት፡ “ዘሩ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ክፉው ሰው
ይህ አንድን የተለየን ሰው አያመለክትም። ይህ ጥቅል አነጋገር ነው። (See: Generic Noun Phrases)

ይቆረጣል
የአመፀኛው መጥፋት ተቆርጦ እንደሚጣል የተክል ቅርንጫፍ ሆኖ ተነግሯል። ተመሳሳዩን ሐረግ በመዝሙር 37:9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 37:39

የጻድቃን ድነት የሚመጣው ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው
የነገር ስም የሆነው “ድነት” እንደ ድርጊት ሊገለጽ ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ጻድቅ የሆነውን ሕዝብ ይታደገዋል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ጻድቃን
ይህ የሚያመለክተው ጻድቅ የሆኑትን ሰዎች ነው። አ.ት፡ “ጻድቃን” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

ይረዳል ... ይታደጋል ... ያድናል
ይህ ተመሳሳይ አሳብ እግዚአብሔር የሚታመኑበትና ለመርዳት የሚችል መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት በብዙ የተለያዩ መንገዶች ተደጋግሟል። (See: Parallelism)

እርሱን መጠጊያ አድርገዋል
ጥበቃ ለማግኘት ወደ እግዚአብሔር መሄድ በእርሱ መጠጊያ ማግኘት እንደሆነ ተነግሯል። አ.ት፡ “ጥበቃ ለማግኘት ወደ እርሱ ሄደዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 38

1 ያህዌ ሆይ፣ በቁጣህ አትገሥጸኝ በመዓትህም አትቅጣኝ። **2** ፍላጻዎችህ ወግተውኛልና እጅህ ተጭናኛለች። **3** ከቁጣህ የተነሣ መላው አካሌ ታመመ
ከኃጢአቴ የተነሣም ዐጥንቶቼ ጤና የላቸውም። **4** በደሌ ውጦኛል እንደ ከባድ ሸክምም ተጭኖኛል። **5** በሞኝነት ካደረግሁት የተነሣ ቁስሌ መገለ፤ ሸተተም።
6 ጐበጥሁ፤ በየቀኑም እያጐነበስኩ ሄድሁ ቀኑን ሙሉ በትካዜ ዋልሁ። **7** ውስጤ እንደ እሳት ይቃጠላል ሥጋዬም ጤና የለውም። **8** እንደ ዲዳ ሆንሁ፤
ፈጽሞም ደቀቅሁ ከልቤ ምሬት የተነሣ እቃትታለሁ። **9** ጌታ ሆይ፣ የጥልቅ ልቤን ናፍቆት አንተ ታውቃለህ መቃተቴም ከአንተ የተሰወረ አይደለም። **10** ልቤ
በኃይል ይመታል፤ ጉልበት ከድቶኛል የዐይኔም ብርሃን ፈዝዞአል። **11** ካለሁበት ሁኔታ የተነሣ፣ ወዳጆቼም ባልንጀሮቼም ሸሹኝ ጐረቤቶቼም ርቀው ቆሙ። **12**
ሕይወቴን ማጥፋት የሚወዱ ወጥመድ ዘረጉብኝ ሊጐዱኝ የሚፈልጉም በዛቻ ተናገሩኝ፤ በእኔም ላይ ቀኑን ሙሉ ያሤራሉ። **13** እኔ ግን እንደማይሰማ ደንቆሮ
ምንም መናገር እንደማይችል ዲዳ ሰው ሆንሁ። **14** ጆሮው እንደማይሰማ አንደበቱም መልስ መስጠት እንደማይችል ሰው ሆንሁ። **15** ያህዌ ሆይ፣ በፍጹም ልቤ
አንተን እጠብቃለሁ ጌታ ሆይ፣ አንተ መልስ ትሰጠኛለህ። **16** ይህን የምለው ጠላቶቼ በእኔ ላይ ደስ እንዳይላቸው ነው፤ እግሬ ቢንሸራተት ክፉ ነገር
ያደርጉብኛል። **17** ልወድቅ ተቃርቤአለሁ ሕመሜም ፋታ አልሰጠኝም። **18** በደሌን እናዘዛለሁ ኃጢአቴም አስጨንቆኛል። **19** ጠላቶቼ እጅግ ብዙ ናቸው ያለ
ምክንያት የሚጠሉንም በዝተዋል። **20** በመልካም ፈንታ ክፉ መለሱልኝ መልሙን እየተከተልሁ ቢሆንም፣ እነርሱ ግን እኔ ላይ የሐሰት ክስ ደረደሩ። **21** ያህዌ
ሆይ፣ አትተወኝ አምላኬ ሆይ፣ ከእኔ አትራቅ **22** ጌታ መድኃኒቴ እኔን ለመርዳት ፍጠን።

Psalms 38:1

የዳዊት መዝሙር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) መዝሙሩን ዳዊት ጽፎታል ወይም 2) መዝሙሩ የሚናገረው ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) የመዝሙሩ ስልት የዳዊትን መዝሙር ይመስላል የሚሉት ናቸው።

በቁጣህ አትገስጸኝ ... በመዓትህ አትቅጣኝ
በመሠረቱ የእነዚህ ሐረጎች ትርጉም ተመሳሳይ ሲሆን አሳቡ የተደጋገመው አጽንዖት ለመስጠት ነው። (See: Paral- lelism)

ፍላጻዎችህ ወግተውኛል
በጸሐፊው ላይ የእግዚአብሔር ቅጣት ከባድነት ልክ እግዚአብሔር በጸሐፊው ላይ ቀስት የወረወረበት ያህል ተቆጥሮ ተነግሯል። አ.ት፡ “ቅጣትህ በቀስት የወጋኸኝ ያህል አሳምሞኛል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እጅህ ወደ ታች ይጫነኛል
እግዚአብሔር ጸሐፊውን የቀጣበት መንገድ ልክ በእጁ የመታው ያህል ተቆጥሮ ተነግሯል። እዚህ ጋ “እጅ” የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ኃይል ነው። አ.ት፡ “ኃይልህ መትቶ ይጥለኛል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 38:3

በኃጢአቴ ምክንያት አጥንቶቼ ምንም ጤና የላቸውም
እዚህ ጋ “አጥንቶቼ” የሚወክለው የጸሐፊውን አካል ነው። አ.ት፡ “በኃጢአቴ ምክንያት መላው አካላቴ ታሞአል” (See: Synecdoche)

በደሌ አጥለቅልቆኛል
የጸሐፊው በደል በሚሸፍነው ጎርፍ ተመስሎ ተነግሯል። አ.ት፡ “በደሌ እንደ ጎርፍ ሸፍኖኛል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እንደ ከባድ ሸክም ሆነውብኛል
የጸሐፊው በደል ሊያነሣው በማይችል ከባድ ሸክም ተመስሎ ተነግሯል። አ.ት፡ “እርሱ ላነሣው እጅግ እንደሚከብድ ሸክም ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 38:5

ቁስሎቼ አመረቀዙ፣ ሸተቱም
እዚህ ጋ፣ “ሸተቱ” የሚለው ቃል ከሥጋው መበስበስ የተነሣ ቁስሎቹ መጥፎ ጠረን እንዳወጡ ያመለክታል። አ.ት፡ “ቁስሌቼ አመርቅዘዋል፣ በመበስበሳቸውም ይገማሉ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ጎበጥሁ
በቁስሎቹ ምክንያት የጸሐፊው ሕመም እንደ ሸመገለ ደካማ ሰው እንዲጎብጥ አድርጎታል። አ.ት፡ “በሕመም ጎብጫለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 38:7

በቃጠሎ ተሞልቻለሁ
ጸሐፊው ውስጡ የሚቃጠል እስኪመስለው ድረስ በትኩሳት ታሟል። አ.ት፡ “ሰውነቴ በትኩሳት ነዶአል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሥጋዬ ጤና የለውም
እዚህ ጋ “ሥጋዬ” የሚያመለክተው ጸሐፊውን ነው። አ.ት፡ “ሙሉ በሙሉ ታምሜአለሁ” (See: Synecdoche)

ፈጽሞ ደቅቄአለሁ
ከባድ ሸክም የተጫነው ያህል የጸሐፊው ሕመም እጅግ ብርቱ ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የልቤ ጭንቀት
እዚህ ጋ “ልቤ” የሚያመለክተው ጸሐፊውን ነው። አ.ት፡ “ጭንቀቴ” (See: Synecdoche)

Psalms 38:9

የልቤ ጥልቅ ናፍቆት
እዚህ ጋ “ልቤ” የሚያመለክተው ጸሐፊውን ነው። ጸሐፊው ጤንነቱ እንዲስተካከልለት መመኘቱን መናገር ሊጠቅም ይችላል። አ.ት፡ “ታላቁ ምኞቴ” ወይም “እንድትፈውሰኝ እመኝሃለሁ” (Synecdoche and Assumed Knowl- edge and Implicit Information የሚለውን ተመልከት)

ማቃሰቴ ከአንተ አልተሰወረም
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የሐዘን እንጉርጉሮዬንም ሁሉ ማየት ትችላለህ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ልቤ ይመታል
የዚህ የአነጋገር ዘይቤ ትርጉም ልቡ በፍጥነት ይመታል የሚል ነው። አ.ት፡ “ልቤ በኃይል ይመታል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጉልበቴ ይከዳኛል
“በጣም ደካማ ሆንኩ”

ዕይታዬ ጨልሞአል
“ከእንግዲህ በአግባቡ ማየት አልችልም”

Psalms 38:11

ወጥመድ አጠመዱብኝ
የጸሐፊው ጠላቶች ሤራ እንደ እንስሳ በእርሱ ላይ ወጥመድ እንደዘረጉበት ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “እኔን ለመያዝ ወጥመድ አጠመዱ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የሚያፈርስ ቃል ያወራሉ፣ የሚያታልል ቃልም ይናገራሉ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ የሚናገሩት ተመሳሳይ ነገር ሲሆን እነዚህ ሰዎች የሚናገሩት የመጉዳት ባህርይ እንዳለው አጽንዖት ይሰጣሉ። (See: Parallelism)

Psalms 38:13

እኔ መስማት እንደ ተሣነው ሰው ነኝ ... ምንም እንደማይሰማ ... አይሰማም
የቁጥር 13 እና 14 የመጀመሪያ ስንኞች ተመሳሳዩን መስማት የተሣነውን ሰው ምስል ለማቅረብ ንጽጽርን ይጠቀማሉ። ጸሐፊው መስማት እስከማይችል ድረስ በጣም ታሟል። (See: Parallelism and Simile)

እኔ እንደ ዲዳ ሰው ነኝ ... ምንም እንደማይናገር ... ምንም እንደማይመልስ
የቁጥር 13 እና 14 ሁለተኛ ስንኞች የዲዳን ሰው ምስል ለማቅረብ ንጽጽርን ይጠቀማሉ። ጸሐፊው መናገር እስከማይችል ድረስ በጣም ታሟል። (See: Parallelism and Simile)

ዲዳ ሰው
መናገር የማይችል ሰው

Psalms 38:15

አንተ ትመልሳለህ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ትመልስልኛለህ” ወይም 2) “ለጠላቶቼ ትመልስላቸዋለህ” የሚሉት ናቸው።

በእኔ ላይ አይፈነድቁም
“በመከራዬ አይደሰቱም”

እግሬ ቢንሸራተት
እዚህ ጋ “እግሬ” የሚወክለው ጸሐፊውን ነው። የእግሩ መንሸራተት የጸሐፊውን መከራና መጥፎ አጋጣሚ የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ስሕተትን ብሠራ መከራን ያመጣብኛል” (Synecdoche እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 38:17

ለመሰናከል ተቃርቤአለሁ
ለዚህ ዘይቤአዊ አነጋገር ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ለመሞት እስክቃረብ ድረስ በጣም ታምሜአለሁ” ወይም 2) “በቶሎ የተረሳሁ እሆናለሁ” የሚሉት ናቸው። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ያለው ዘይቤአዊ አነጋገር ባይተረጎም ተመራጭ ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በማያቋርጥ ሕመም ውስጥ ነኝ
“ሁሌም በሕመም ውስጥ ነኝ”

Psalms 38:19

ነገር ግን ጠላቶቼ እጅግ ብዙ ናቸው ... በጣም ብዙ ናቸው
እነዚህ ሁለትም ሐረጎች በመሠረቱ የሚናገሩት ተመሳሳይ ነገር ነው። (See: Parallelism)

መልካም ባደረግሁ ክፉ ይመልሱልኛል
የጸሐፊው ጠላቶች ድርጊት፣ እንደ ገንዘብ ግብይት፣ ባደረገው መልካም ነገሮች ምትክ ክፉ ነገሮችን እንደመለሱለት ተደርጎ ተነግሯል። የነገር ስም የሆነው “ክፉ” እና “መልካም” እንደ ቅጽል ሊነገሩ ይችላሉ። አ.ት፡ “መልካም ከሆንኩላቸው በኋላ ክፉን ነገር ያደርጉብኛል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

ክሶችን ይወረውሩብኛል
የጸሐፊው ጠላቶች እርሱን የሚከሱበት መንገድ ክሶቹ ድንጋዮች የሆኑ ይመስል በእርሱ ላይ እንደወረወሩበት ሆኖ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መልካሙን ተከተልሁ
ጸሐፊው መልካምን ነገር መመኘቱ ከመልካም ነገሮች በስተኋላ እንደሮጠ ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 38:21

አትተወኝ ... ከእኔ አትራቅ
እነዚህ ሁለቱም ሐረጎች በጣም ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም አላቸው። (See: Parallelism)

ከእኔ አትራቅ
እግዚአብሔር ለጸሐፊው ጥያቄ ምላሽ ሳይሰጥ በመቆየቱ ምክንያት እግዚአብሔርን ከእርሱ እንደራቀ አድርጎ ጸሐፊው ይናገራል (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እኔን ለመርዳት ፈጥነህ ና
እግዚአብሔር ጸሐፊውን ለመርዳት እንደሚሮጥ ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ድነቴ
የነገር ስም የሆነው “ድነት” እንደ ድርጊት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እኔን የምታድነኝ አንተ ነህ” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 39

1 እኔ፣ «በአንደበቴ እንዳልበድል ለምናገረው እጠነቀቃለሁ፣ በክፉዎችም ፊት እስካለሁ ድረስ፣ በአፌ ልጓም አደርጋለሁ» አልሁ። **2** አንድ ቃል እንኳ ሳልናገር
ዝም አልሁ ለመልካም ነገር እንኳ አፌን ዘጋሁ፤ ያም ሆኖ ጭንቀቴ ባሰ። **3** ልቤ በውስጤ ጋለ ስለ እነዚህ ነገሮች ሳስብ እንደ እሳት ነደደ። ከዚያም መናገር
ጀመርሁ። **4** «ያህዌ ሆይ፣ የሕይወቴ መጨረሻ መቼ እንደ ሆነና የዕድሜዬን ልክ አሳውቀኝ አላፊ ጠፊ መሆኔን አሳየኝ። **5** እነሆ፣ ዘመኔን በስንዝር ለክተህ
አኖርህ ዕድሜዬም በፊትህ እንደ ኢምንት ነው። በእርግጥ የሰው ሁሉ ሕይወት ጥላ ነው። ሴላ **6** በእርግጥ ሰው ሁሉ እንደ ጥላ ይመላለሳል። ለማን
እንደሚሆን ሳያውቅ ሀብት ንብረት ያከማቻል። **7** ጌታ ሆይ፣ አሁንስ ማንን ልጠብቅ? ተስፋዬ አንተ ብቻ ነህ። **8** ከኃጢአቴ አድነኝ የሞኞች መዘባበቻ
አታድርገኝ። **9** ይህን ያደረግህ አንተ ነህና ዝም እላለሁ አፌንም አልከፍትም። **10** ክንድህን አንሣልኝ ከእጅህ ምት የተነሣ ዝዬአለሁ። **11** ሰውን በኃጢአቱ
ትገሥጸዋለህ፤ ትቀጣዋለህም የሚወደውንም ነገር እንደ ብል ታጠፋበታለህ። በእርግጥ ሰው ሁሉ ተን ነው። ሴላ **12** ያህዌ ሆይ፣ ጸሎቴን ስማ፤ ጩኸቴንም
አድምጥ ለቅሶየንም ቸል አትበል። በአንተ ፊት እንደ መጻተኛ ነኝና እንደ አባቶቼም እንግዳ ነኝ። **13** ከመሞቴ በፊት ዳግመኛ ደስ እንዲለኝ ዐይንህን ከላዬ
አንሣ።

Psalms 39:1

ለሙዚቀኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”

ኤዶታም
ከዳዊት የሙዚቃ አለቆች ለአንዱ ይህ ተመሳሳይ ስም ነበረው። ይህ ምናልባት እርሱን ያመለክት ይሆናል። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የዳዊት መዝሙር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) መዝሙሩን ዳዊት ጽፎታል ወይም 2) መዝሙሩ የሚናገረው ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) የመዝሙሩ ስልት የዳዊትን መዝሙር ይመስላል የሚሉት ናቸው።

የምናገረውን አያለሁ
እዚህ ጋ “ማየት” የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን “ልብ ማለት” የሚል ትርጉም አለው። አ.ት፡ “ለምናገራቸው ነገሮች ትኩረት እሰጣለሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በምላሴ ኃጢአትን እንዳልሠራ
እዚህ ጋ “ምላስ” የሚያመለክተው የጸሐፊውን ንግግር ነው። አ.ት፡ “እግዚአብሔርን የሚያስቆጣ ነገር እንዳልናገር” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ልጓም
“መለጎም” ማለት አፍን መዝጋት ነው። ዳዊት እዚህ ጋ የሚናገረው ከክፉ ሰው ጋር ሲሆን እንደማይናገር ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 39:2

ዝም አልኩ፤ ቃሌን መለስኩ
የእነዚህ የሁለቱም ሐረጎች ትርጉም አንድ ሲሆን ጸሐፊው ፈጽሞ እንደማይናገር አጽንዖት ይሰጣል። አ.ት፡ “ፈጽሞ ጸጥ ብዬ ነበር” (See: Doublet)

ቃሌን መለስኩ
“አልተናገርኩም”

ልቤ ሞቀ ... እንደ እሳትም ነደደ
እዚህ ጋ “ልብ” የሚወክለው የሰውን ሁለንተናውን ነው። የጸሐፊው አስጨናቂ አሳብ በውስጡ እንደሚነድ እሳት ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ስለ እነዚህ ነገሮች ባሰብኩ ጊዜ በጣም ተጨነቅኩኝ” (See: Synecdoche እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 39:4

የሕይወቴ ማብቂያ ... የቀኖቼ ርዝመት
በመሠረቱ እነዚህ ሐረጎች የሚሉት ተመሳሳይ ነገር ነው። (See: Parallelism)

አላፊ ጠፊ መሆኔን አሳየኝ
“ሕይወቴ ምን ያህል አጭር እንደሆነ አሳየኝ” ወይም “በቶሎ የምሞትበትን ጊዜ አሳየኝ”

የእጄን እርዝመት ያህል ብቻ
ጸሐፊው የሕይወት ዘመኑ በእጁ እርዝመት ሊለካ እንደሚችል አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “በጣም አጭር ጊዜ ብቻ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የሕይወት ዘመኔ በፊትህ እንደ ኢምንት ነው
ይህ ንጽጽር የሚናገረው የጸሐፊው የሕይወት ዘመን እርዝማኔ የማይሰነብት፣ አጭር መሆኑን ነው። ይህ ዕድሜው ምን ያህል አጭር እንደሚሆን አጽንዖት ለመስጠት የተነገረ ግነት ነው። አ.ት፡ “የሕይወቴ እርዝመት በየትኛውም ጊዜ ሊያበቃ የሚችል ነው” (Simile፣ ግነትና ጥቅል አስተያየት የሚለውን ተመልከት)

በእርግጥ እያንዳንዱ ሰው እስትንፋስ ብቻ ነው
ሕይወት አጭር ነው፤ ዘማሪው በዚህ ስፍራ ዕጥረቱ አንድ ሰው ትንፋሹን አንድ ጊዜ የሚተነፍስበትን ያህል እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “የሰዎች የሕይወት ዘመን ልክ አንድ ሰው ከሚተነፍሰው አጭር እስትንፋስ ጋር አንድ ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 39:6

በእርግጥ እያንዳንዱ ሰው እንደ ጥላ ይመላለሳል
የሰዎች ሕይወት ምንም ያህል እንደማይቆይ ጥላ ተደርጎ ተነግራል። አ.ት፡ “ጥላ እንደሚጠፋ እያንዳንዱ ይጠፋል” (See: Simile)

ማን እንደሚቀበላቸው ባያውቁም
እዚህ ጋ እነርሱ ከሞቱ በኋላ ሀብታቸው ምን እንደሚሆን እንደማያውቁ ያመለክታል። የዚህ አነጋገር ሙሉ ትርጉም ሊብራራ ይችላል። (See: Assumed Knowledge and Implicit Informa- tion)

ጌታ ሆይ፣ አሁን እኔ የምጠብቀው ምንድነው?
ጸሐፊው ይህንን የሚጠይቀው ሰዎች ሊረዱት እንደማይችሉ አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህ ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እንደ ንግግር ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እንግዲህ እግዚአብሔር ሆይ፣ ከማንም ምንም ነገር አልጠብቅም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 39:8

ዝም እላለሁ ... አፌን አልከፍትም
በመሠረቱ እነዚህ ሐረጎች የሚሉት ተመሳሳይ ነገር ነው። (See: Parallelism)

ይህንን ያደረግኸው አንተ ነህና
“ቅጣቴ የሚመጣው ከአንተ ነውና”

Psalms 39:10

እኔን ማቁሰልህን ተው
እግዚአብሔር ጸሐፊውን መቅጣቱ ልክ በጦር መሣሪያ እግዚአብሔር እንዳቆሰለው ተደርጎ ተነግራል። አ.ት፡ “እባክህን እኔን መቅጣትህን ተው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እኔ ዝዬአለሁ
“ፈጽሞ ተሸንፌአለሁ”

የእጅህ ምት
እግዚአብሔር ጸሐፊውን መቅጣቱ ልክ እግዚአብሔር በቡጢ እንደመታው ተደርጎ ተነግራል። እዚህ ጋ “እጅ” የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ፍርድ ነው። አ.ት፡ “ፍርድህ በእኔ ላይ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እንደ ብል የተመጀቸውን ነገሮች በላህ
ብል የጨርቅን ቁራጭ እንደሚበላው እግዚአብሔር የከበረ የሚሉትን ነገራቸውን ይወስድባቸዋል። አ.ት፡ “ብል ጨርቅን እንደሚበላ የሚመጀቸውን ነገሮች ይበላል” (See: Simile)

ሰዎች ሁሉ እንደ ተን ብቻ ናቸው
ጸሐፊው የሰዎችን ደካማነት ፈጥኖ ከሚጠፋ ጭጋግ ጋር በማመሳሰል ይናገራል። አ.ት፡ “ሁሉም ፈጽሞ ተሰባሪ ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 39:12

ጸሎቴን ስማ ... አድምጠኝ ... ለቅሶዬን አድምጥ
የእነዚህ ሦስት ሐረጎች ትርጉማቸው በመሠረቱ ተመሳሳይ ሲሆን እግዚአብሔር ምላሽ እንዲሰጠው እንዴት አጥብቆ እንደሚፈልግ ያሳያል። (See: Parallelism)

ደንቆሮ አትሁንብኝ
ጸሐፊው እግዚአብሔር ለእርሱ ምላሽ አለመስጠቱን እንደ ደነቆረ አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “ልትሰማኝ የማትችል ይመስል ዝም አትበለኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እኔ ከአንተ ጋር እንደ እንግዳና ስደተኛ ነኝ
ጸሐፊው እግዚአብሔር ለእርሱ ምላሽ አለመስጠቱን እግዚአብሔር ለእርሱ ፈጽሞ እንግዳ እንደሆነበት አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “እኔ ፈጽሞ እንደ እንግዳ ሆኜብሃለሁ” (See: Simile)

ዐይንህን ከእኔ ላይ አንሣ
እዚህ ጋ “ዐይንህን” የሚወክለው የእግዚአብሔርን ቅጣት ነው። አ.ት፡ “እባክህን እኔን መቅጣትህን ተው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እንደገና እንድስቅ
እዚህ ጋ “መሳቅ” ደስተኛ ከመሆን ጋር ተያይዟል። አ.ት፡ “እንደገና ደስተኛ መሆን እንድችል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 40

1 በትዕግሥት ያህዌን ደጅ ጠናሁት እርሱም ዘንበል አለልኝ፤ ጩኸቴንም ሰማኝ። **2** ከአደገኛ ጉድጓድ፣ ከሚያዘቅጥም ጭቃ አወጣኝ፤ እግሮቼን፣ በዐለት ላይ አቆመ አካሄዴንም አጸና። **3** ለአምላካችን ምስጋና አዲስ መዝሙር በአፌ አኖረ። ብዙዎች ዐይተው ያከብሩታል፤ በያህዌም ይታመናሉ። **4** ያህዌን መታመኛው ያደረገ ወደ ትዕቢተኛው የማይመለከት የሐሰት አማልክት ወደሚከተሉት የሚያይ ቡሩክ ነው። **5** ያህዌ አምላኬ ሆይ፣ ያደረግኸው ድንቅ ነገር ብዙ ነው ለእኛ ያለህም ሐሳብ ከቁጥር በላይ ነው፤ ላወራው ልናገረው ብል ስፍር ቁጥር አይኖረውም። **6** መሥዋዕትንና መባን አልፈለግህም ጆሮዎቼን ግን ከፈትህ፤ የሚቃጠል መሥዋዕትንና የኃጢአት መሥዋዕትን አልጠየቅህም። **7** እኔም እንዲህ አልሁ፣ «እነሆ፣ መጥቻለሁ በመጽሐፍ ጥቅልል ስለ እኔ ተጽፎአል፤ **8** አምላኬ ሆይ ፈቃድህን ለማድረግ ወደድሁ ሕግህም ልቤ ውስጥ ነው። **9** በታላቅ ጉባኤ ውስጥ ጽድቅህን ዐወጅሁ ያህዌ ሆይ፣ ይህን ከማድረግ ወደ ኋላ አለማለቴንም አንተ ታውቃለህ። **10** ጽድቅህን በልቤ ውስጥ አልሸሸግሁም፤ ታማኝነትህንና ማዳንህን ተናገርሁ ምሕረትህንና እውነትህን ከታላቅ ጉባኤ አልደበቅሁም። **11** ያህዌ ሆይ ምሕረትህን አትንፈገኝ ቸርነትህና ታማኝነትህ ዘወትር ይጠብቁኝ። **12** ስፍር ቁጥር የሌለው ችግር ከብቦኛል የኃጢአቴ ብዛት ስለ ያዘኝ ማየት ተስኖኛል፤ ከራሴ ጠጉር ይልቅ በዝቶአል፤ ልቤም ከድቶኛል። **13** ያህዌ ሆይ፣ እኔን ለማዳን ፈቃድህ ይሁን እኔን ለመርዳትም ፍጠን። **14** ነፍሴን ለመንጠቅ የሚፈልጉ ይፈሩ፤ ይዋረዱም። ጉዳቴን የሚሹ ተዋርደው በመጡበት ይመለሱ። **15** በእኔ ላይ፣ «እሰይ! እሰይ!» የሚሉ በራሳቸው እፍረት ይደንግጡ **16** አንተን የሚፈልጉ ሁሉ ደስ ይበላቸው ሐሤትም ያድርጉ፤ ማዳንህን የሚወዱ ዘወትር፣ «ያህዌ ከፍ ከፍ ይበል» ይበሉ። **17** እኔ ችግረኛና ምስኪን ነኝ ጌታ ግን ያስብልኛል። አንተ ረዳቴ ነህ እኔን ለማዳን ፍጠን አምላኬ ሆይ አትዘግይ።

Psalms 40:1

ለሙዚቀኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”

የዳዊት መዝሙር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) መዝሙሩን ዳዊት ጽፎታል ወይም 2) መዝሙሩ የሚናገረው ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) የመዝሙሩ ስልት የዳዊትን መዝሙር ይመስላል የሚሉት ናቸው።

እግዚአብሔርን በትዕግስት ጠበቅሁት
ይህ ማለት ጸሐፊው እግዚአብሔር እንዲረዳው ሲጠብቀው ነበር።

እርሱ ሰማኝ ... ጩኸቴንም አደመጠ
እነዚህ ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ በአንድ ዐረፍተ ነገር ሊጣመሩም ይችላሉ። አ.ት፡ “በጠራኹት ጊዜ ሰማኝ” (See: Doublet)

ከአስከፊ ጉድጓድ፣ ከረግረጉም ጭቃ
እነዚህ ሁለት ዘይቤአዊ አነጋገሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ጸሐፊው የነበረበት አደገኛ ሁኔታ ጭቃ በተሞላና ለሞት በሚያበቃ ጉድጓድ ተመስሎ ተነግሯል። ይህ አደገኛነቱ ላይ አጽንዖት ይሰጣል። አ.ት፡ “የሚያጣብቅ ጭቃ በሞላበት አስከፊ ጉድጓድ ከመጠመድ” (Parallelism እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እግሮቼን በዐለት ላይ አቆማቸው
እዚህ ጋ “እግሮቼን” የሚያመለክተው የጸሐፊውን ሲሆን “ዐለት” የሚያመለክተው ሰላማዊ ስፍራን ነው። አ.ት፡ “ሰላማዊ ስፍራን አዘጋጀልኝ” (Synecdoche and ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 40:3

አዲስን መዝሙር በአፌ ጨመረ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ለአዲስ መዝሙር የሚሆን ቃል አስተማረኝ” ወይም 2) “ለመዘመር አዲስ ምክንያትን ሰጠኝ” የሚሉት ናቸው።

በአፌ
እዚህ ጋ “አፌ” የሚያመለክተው ጸሐፊውን ነው። አ.ት፡ “በውስጤ” (See: Synecdoche)

ለአምላካችን ምስጋና
“ምስጋና” የሚለው ስም እንደ ግሥ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አምላካችንን የምናመሰግንበትን ዝማሬ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ብዙዎች ያዩታል
እዚህ ጋ “ያዩታል” እግዚአብሔር ስላደረገለት ነገር ጸሐፊው ሲዘምር እንደሚሰሙት ያመለክታል። አ.ት፡ “ብዙ ሰዎች እግዚአብሔር ያደረገልኝን ስናገር ይሰሙኛል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔርን መታመኛው የሚያደርግ ሰው የተባረከ ነው
“በእግዚአብሔር የሚታመን ሰው የተባረከ ነው” ወይም “በእግዚአብሔር የሚታመኑ እነርሱ የተባረኩ ናቸው’

ኩሩው
ይህ ኩሩ የሆኑትን ሰዎች ያመለክታል። አ.ት፡ “ኩሩ ሰዎች” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

ለውሸት
የዕብራይስጡ ቃል ግልጽ አይደለም። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ውሸት” ወይም 2) “ሐሰተኞች አማልክት” የሚሉት ናቸው።

Psalms 40:5

ስለ እኛ የምታስባቸው አሳቦች ሊቆጠሩ አይችሉም
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ለእኛ የምታስባቸውን ነገሮች በሙሉ ማንም ሊቆጥራቸው አይችልም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ሊቆጠሩ አይችሉም ... ሊቆጠሩ ከሚችሉ በላይ ናቸው
በመሠረቱ የእነዚህ ሐረጎች ትርጉም አንድ ነው። የመጀመሪያው በአሉታዊነት ሲነገር ሁለተኛው በአዎንታዊነት ተነግሯል። (See: Parallelism and Litotes)

በመሥዋዕት ወይም በቁርባን ደስ አይልህም
ይህ ሌሎች ነገሮች ለእግዚአብሔር በይበልጥ አስፈላጊ ስለመሆናቸው በግነት የተነገረበት ነው። አ.ት፡ “አንተን እጅግ የሚያስደስትህ መሥዋዕቶችና ሌሎች ቁርባኖች አይደሉም” (ግነት እና ጥቅል አስተያየት የሚለውን ተመልከት)

ጆሮዎቼን ከፍተሃቸዋል
እዚህ ጋ “ጆሮዎቼ” የሚያመለክተው የመስማትን ችሎታ ነው። አ.ት፡ “ትዕዛዝህን ለመስማት አስችለኸኛል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የሚቃጠሉ ቁርባኖችን ወይም የኃጢአት ቁርባኖችን አልፈለግህም
ይህ፣ እነዚህ ነገሮች ለእግዚአብሔር እጅግ አስፈላጊዎች እንዳልሆኑ ለማሳየት የተነገረ ግነት ነው። አ.ት፡ “አንተ አብልጠህ የምትፈልጋቸው በመሰዊያ ላይ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የሚቃጠሉ እንስሶችንና ሌሎች ስለ ኃጢአታችን የሚቀርቡ ቁርባኖችን አይደለም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

Psalms 40:7

የመጽሐፍ ጥቅልል
ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ቃል የተጻፈበትን ጥቅልል ነው። አ.ት፡ “የተጻፈበት ጥቅልል” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ሕግጋቶችህ በልቤ ውስጥ ናቸው
እዚህ ጋ “ልቤ” የሚያመለክተው የጸሐፊውን ውስጣዊ ማንነት ነው። አ.ት፡ “በውስጣዊ ማንነቴ ሁልጊዜ ስለ ሕግህ አስባለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የጽድቅህን የምስራች በታላቅ ጉባዔ ተናግሬአለሁ
“ስለ ጽድቅህ የምስራች በታላቅ ጉባዔ ለነበሩ ሰዎች ተናግሬአለሁ”

የጽድቅህን የምስራች
ይህ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚታደጋቸው የሚነገረውን የምሥራች ያመለክታል። አ.ት፡ “አንተ ጻድቅ ስለሆንክ ሕዝብህን ስለማዳንህ የምሥራችን” (See: Ellipsis)

ከንፈሮቼ ይህንን ከማድረግ አለተቆጠቡም
እዚህ ጋ “ከንፈሮቼ” ንግግሩ ላይ አጽንዖት በመስጠት ጸሐፊውን ይወክላሉ። አ.ት፡ “እነዚህን ነገሮች ከማብሰር ራሴን አልገታሁም” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 40:10

ጽድቅህን በልቤ አልደበቅሁም
“ጽድቅህን ምስጢር አድርጌ አልያዝሁትም”። ይህ ደግሞ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ስለ ጽድቅህ ለሁሉም በግልጽ ተናግሬአለሁ” (See: Litotes)

በልቤ
እዚህ ጋ ይህ የሚያመለክተው የጸሐፊውን ውስጣዊ ማንነት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የቃል ኪዳን ታማኝነትህንና አለኝታነትህን ከታላቁ ጉባዔ አልደበቅሁም
ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በታላቁ ጉባዔ ውስጥ ለነበሩት ሁሉ ስለ ቃል ኪዳን ታማኝነትህ ወይም ስለ አለኝታነትህ ነግሬአቸዋለሁ” (See: Litotes)

የቃል ኪዳን ታማኝነትህ
የነገር ስም የሆነው “ታማኝነት” የሚለው ቃል “ታማኝ” ተብሎ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አንተ ለቃል ኪዳንህ ታማኝ ነህ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

አለኝታነትህ
ይህ የነገር ስም የሆነው “አለኝታነት” እንደ “አለኝታ” ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አንተ አለኝታ ነህ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

የቃል ኪዳን ታማኝነትህና አለኝታነትህ ሁልጊዜ ይጠብቁኝ
እዚህ ጋ “የቃል ኪዳን ታማኝነት” እና “አለኝታነት” ጸሐፊውን ሊጠብቁት እንደሚችሉ ሕያዋን ሰዎች ተደርገው ተነግረዋል። አ.ት፡ “የቃል ኪዳን ታማኝነትህ እና አለኝታነትህ ሁልጊዜ እንዲጠብቁኝ እፈልጋለሁ” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

Psalms 40:12

ሊቆጠር የማይቻል መከራ ከቦኛል
እዚህ ጋ መከራ ተናጋሪውን ከቦ እንደሚያጠምደው ቁስ ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ልቆጥረው ከምችለው በላይ የበዛ መከራ በዙሪያዬ አለ” ወይም “ልቆጥረው የማልችለው መከራ መጣብኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሊቆጠር የማይቻል
ይህ ቁጥሩን ለማጉላት በአሉታዊነት ተነግሯል። ይህንን በመዝሙር 40:5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “በቁጥር ብዙ ናቸው” (See: Litotes)

ኃጢአቴ
ይህ የኃጢአቱን ውጤት ያመለክታል። አ.ት፡ “የኃጢአቴ ውጤት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ይዞኛል
የጸሐፊው ኃጢአት እንደሚያጠቃው ጠላት ተደርጎ ተነግሯል። (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

ከእንግዲህ ምንም ነገር ማየት አልችልም
የተለያዩ ትርጉሞች በዚህ አስቸጋሪ ምንባብ ላይ ይለያያሉ። ምናልባት ተናጋሪው እጅግ ከመጮኹ የተነሣ በዕንባው ምክንያት ምንም ነገር ለማየት አልቻለም ይሆናል።

ልቤ ከድቶኛል
እዚህ ጋ “ልብ” የሚያመለክተው የጸሐፊውን ውስጣዊ መተማመን ነው። አ.ት፡ “በጣም ተስፋ ቆርጫለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 40:14

ነፍሴን ለመውሰድ የሚከታተሉኝ እነርሱ ... ይሁኑ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊጻፍና ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እነዚያን ሊገድሉኝ የሚሞክሩትን እንዲያፍሩና እንዲዋረዱ አድርጋቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ነፍሴን ለመውሰድ የሚከታተሉኝ
እዚህ ጋ “ነፍሴን ለመውሰድ የሚከታተሉኝ” ማለት ጸሐፊውን ለመግደል ይመኛሉ ማለት ነው። ጸሐፊው “በነፍሱ” ተወክሏል። አ.ት፡ “ሊገድሉኝ የሚሞክሩ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እኔን በመጉዳት የሚደሰቱ እነርሱ ... ይሁኑ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊጻፍና ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እኔን በመጉዳት የሚደሰቱትን ከልክላቸው፣ አዋርዳቸውም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ወደ ኋላ ይመለሱ
መከልከላቸው ወይም መታገዳቸው ከማጥቃታቸው ወደ ኋላ እንዲመለሱ እንደተደረጉ ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “ተከልክለዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእኔ ላይ “እንኳን፣ እንኳን!” የሚሉ እነርሱ ... ይሁኑ
“በእኔ ላይ ‘እንኳን፣ እንኳን!’ የሚሉ በእፍረታቸው ምክንያት ይንቀጥቀጡ”

በእፍረታቸው ምክንያት ይደንግጡ
“በምታሳፍራቸው ጊዜ እንደሚደነግጡ ተስፋ አደርጋለሁ”

በእኔ ላይ “እንኳን፣ እንኳን!” የሚሉ
“እንኳን፣ እንኳን!” ሰዎች በሌላው ላይ በሚስቁበት ጊዜ የሚሉት ነገር ነው። የአንተ ቋንቋ ሰዎች በሌላው ላይ ሲስቁ የሚናገሩት የተለየ ቃል ካለው እዚህ ጋ

መጠቀም ይቻላል። ይህ ታዲያ “መሳቅ” ከሚል ግሥ ጋር ሊተረጎም ይችላል።

Psalms 40:16

ደስ ይበላቸው፣ ሐሴትም ያድርጉ
የእነዚህ ሁለት ሐረጎች ትርጉም ተመሳሳይ ሲሆን የደስታው ጥልቀት ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ። አ.ት፡ “በጣም ደስ ይበላችሁ” (See: Doublet)

ማዳንህን ይወዳል
የነገር ስም የሆነው “ማዳን” እንደ ድርጊት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ስላዳንካቸው ይወዱሃል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ድኻና ችግረኛ
እነዚህ ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ ጸሐፊው ምን ያህል ምስኪን እንደሆነ አጽንዖት ይሰጣሉ። አ.ት፡ “በጣም ችግረኛ” (See: Doublet)

ጌታ ስለ እኔ ያስባል
“ጌታ ስለ እኔ ይገደዋል”

አንተ ረዳቴ ነህ ... ልትታደገኝ መጣህ
እነዚህ ሐረጎች የሚሉት ተመሳሳይ ነገር ነው። (See: Parallelism)

አንተ ረዳቴ ነህ
“እኔን የምትረዳኝ አንተ ነህ”

ልትታደገኝ መጣህ
“ልታድነኝ መጣህ”

አትዘግይ
ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ፈጥነህ መልስ” (See: Litotes)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 41

1 ለድኾች የሚያስብ ቡሩክ ነው እርሱንም በመከራ ቀን ያህዌ ያድነዋል። **2** ያህዌ ይጠብቀዋል፤ በሕይወትም ያኖረዋል በምድርም ላይ ይባርከዋል ለጠላቶቹ ምኞትም አሳልፎ አይሰጠውም። **3** ታሞ በተኛበት አልጋ ያህዌ ይንከባከበዋል በበሽታውም ጊዜ መኝታውን ያነጥፍለታል። **4** እኔም፣ «ያህዌ ሆይ፣ ማረኝ! በአንተ ላይ ኃጢአት አድርጌአለሁና ፈውሰኝ» አልሁ። **5** «የሚሞተው መቼ ነው፤ ስሙ የሚደመሰሰውስ መቼ ነው?» እያሉ ጠላቶቼ እኔ ላይ ክፉ ይናገራሉ። **6** ሊጠይቀኝ ቢመጣ እንኳ በልቡ ስድብ እያመቀ ከአንገት በላይ ይናገራል ወጥቶም ወሬ ይነዛል። **7** ጠላቶቼ ሁሉ ተባብረው እኔ ላይ ያሾኮሽካሉ የክፋ ነገርም በላዬ ያውጠነጥናሉ **8** «ክፉ ደዌ ይዞታል፤ አልጋ ላይ ወድቋል ከእንግዲህ ከተኛበት አይነሣም» ይላሉ። **9** እንጀራዬን ተካፍሎ የበላ የተማመንሁበት የቅርብ ወዳጄ በእኔ ላይ ተረከዙን አነሣ። **10** አንተ ግን ያህዌ ሆይ ማረኝ፤ የእጃቸውን እንድሰጣቸውም አስነሣኝ። **11** ጠላቴ በእኔ ላይ ድል አላገኘምና እንደ ወደድከኝ በዚህ ዐወቅሁ። **12** ስለ ቅንነቴ እኔን ትረዳኛለህ በፊትህም ለዘላለም ታኖረኛለህ። **13** የእስራኤል አምላክ ያህዌ ከዘላለም እስከ ዘለላለም ይመስገን። አሜን አሜን።

Psalms 41:1

ለሙዚቃቹቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”

የዳዊት መዝሙር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) መዝሙሩን ዳዊት ጽፎታል ወይም 2) መዝሙሩ የሚናገረው ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) የመዝሙሩ ስልት የዳዊትን መዝሙር ይመስላል የሚሉት ናቸው።

እርሱ ... እርሱን ... የእርሱ
እነዚህ ቃላት ስለ ደካሞች የሚገደውን ማንኛውንም ሰው ያመለክታሉ።

ደካማው
“ደካሞች ሰዎች” ወይም “ድኾች ሰዎች”

በመከራው አልጋ ላይ እግዚአብሔር ይደግፈዋል
“የመከራ አልጋ” የሚለው ሐረግ አንድ ሰው ታሞ በአልጋው ላይ የሚተኛበትን ጊዜ ያመለክታል። አ.ት፡ “ታሞ አልጋው ላይ በሚሆንበት ጊዜ እግዚአብሔር ይደግፈዋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የሕመም አልጋውን የፈውስ አልጋ ታደርግለታለህ
“የፈውስ አልጋ” የሚለው ሐረግ አንድ ሰው በአልጋው ላይ በማረፍ ከሕመሙ የሚያገግምበትን ጊዜ ያመለክታል። አ.ት፡ “አንተ እግዚአብሔር፣ ከሕመሙ ትፈውሰዋለህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 41:4

ስሙ የሚደመሰሰው
የአንድ ሰው ስም ሞተ ማለት ሰዎች በሕይወት ኖሮ እንደነበር ይረሱታል ማለት ነው። አ.ት፡ “ስሙ የሚደመሰሰው መቼ ነው” ወይም “ሰዎች ስለ እርሱ የሚረሱት መቼ ነው” (Ellipsis እና የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ጠላቴ ሊያየኝ ከመጣ
“ጠላቴ” የሚለው ቃል አንድን የታወቀውን ጠላት ማለት ሳይሆን በጥቅሉ የትኛውንም ጠላት ያመለክታል።

እርሱ ከንቱ ነገሮችን ይናገራል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) ትርጉም የለሽ ነገሮችን ይናገራል” ወይም 2) ጠላቶቹ ወዳጆቹ ሳይሆኑ እንደሆኑ እንዲያስብ የሚያስደርገውን ነገር ይናገራሉ የሚሉት ናቸው። አ.ት፡ “የሚያሳስቱ ነገሮችን ይናገራል” ወይም “ስለ እኔ የሚገዳቸው ያስመስላሉ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ልቡ ለጥፋቴ የሚሆነውን ለራሱ ያከማቻል
ጠላቶቹ የእርሱን ክፉ ነገሮች ሁሉ ለማጥናት ይሞክራሉ። እዚህ ጋ “ልብ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሙሉውን ሰው ነው። መጥፎ ሁኔታዎች ሊከማቹ እንደሚችሉ ቁሶች ተደርገው ተነግሮላቸዋል። አ.ት፡ “ለጥፋቴ የሚሆነውን ሁሉ ለማጥናት ይሞክራሉ” (Synecdoche እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 41:7

መጎዳቴን ተስፋ ያደርጋሉ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “በጣም መጥፎ የሆኑ ነገሮች እንደሚደርሱብኝ ተስፋ ያደርጋሉ” ወይም 2) “እኔን ለመጉዳት እያቀዱ ነው” የሚሉት ናቸው።

በእርሱ ላይ ክፉ በሽታ ...
ጠላቶቹን እርሱን በሚይዘው ሰው በመመሰል ስለ “በሽታ” ይናገራሉ። አ.ት፡ “በአደገኛ በሽታ ታሞአል” (ሰውኛ እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ክፉ በሽታ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “አደገኛ በሽታ” ወይም 2) “ክፉ የሆነ ነገር” የሚሉት ናቸው።

አሁን ወድቋል፣ ከእንግዲህ አይነሣም
እዚህ ጋ “ወድቋል” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ከሕመም የተነሣ አልጋ ላይ መተኛትን ነው። “አይነሣም” ማለት መተኛቱን ይቀጥላል ማለት ሲሆን ይሞታል የሚለውን በጨዋነት የመግለጽ አሳብ ነው። አ.ት፡ “አሁን ታሞ አልጋ ላይ ነው፣ በዚያ ይሞታል” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information and Euphemism)

ተረከዙን በእኔ ላይ አንሥቶአል
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ባልንጀራው አሳልፎ ሰጥቶታል ማለት ነው። አ.ት፡ “አሳልፎ ሰጠኝ” ወይም “በእኔ ላይ ተቃዋሚ ሆነ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Psalms 41:10

እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ ግን ማረኝ፣ አንሣኝም
ይህ ልመና ነው። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ሆይ፣ እባክህን ማረኝና አንሣኝ” (See: Statements - Other Uses)

አንሣኝ
ይህ ማለት ከአልጋው ላይ እንዲያነሣው ወይም ከበሽታው እንዲያገግም እንዲያደርገው ነው። አ.ት፡ “ጤነኛ አድርገኝ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

መልሼ እንድከፍላቸው
ጸሐፊው የሚናገራው የተበዳራቸውን ይመልስላቸው ይመስል ጠላቶቹን ስለ መበቀል ነው። አ.ት፡ “እንድበቀላቸው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጠላቴ ድል አላደረገኝምና በእኔ ደስ እንደተሰኘህ በዚህ አውቃለሁ
“በዚህ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጸሐፊው ቀጥሎ የሚናገረውን ነው። ለግልጽነት እንዲረዳ ሐረጉ ቦታው ሊቀያየር ይችላል። አ.ት፡ “ጠላቴ ድል ስለማያደርገኝ በእኔ ደስ እንደሚልህ አውቃለሁ” (የሁነቶች ቅደም ተከተል የሚለውን ተመልከት)

ጠላቴ ድል አላደረገኝምና በእኔ ደስ እንደተሰኘህ በዚህ አውቃለሁ
እግዚአብሔር ገና ስላልፈወሰው ይህ የወደፊቱን በሚያመለክት ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ጠላቶቼ ድል እንዳያደርጉኝ ካስቻልከኝ በእኔ እንደተደሰትክ አውቃለሁ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

በቅንነቴ ትደግፈኛለህ
“በቅንነቴ ምክንያት ትደግፈኛለህ”

በፊትህ ትጠብቀኛለህ
ጸሐፊው እግዚአብሔር እርሱን ማየት በሚችልበትና እርሱም የእግዚአብሔርን ፊት ለማየት በሚችልበት ስፍራ እንደተገኘ ያህል በእግዚአብሔር ሀልዎት ውስጥ ስለመሆን ይናገራል። አ.ት፡ “ከአንተ ጋር ታቆየኛለህ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 41:13

መዝሙር **1** መዝሙር **41** ላይ ያበቃል።
መዝሙር 1 መዝሙር 41 ላይ ያበቃል።

ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም
ይህ ሁለቱን ጽንፍ የሚያመለክት ሲሆን ትርጉሙ ሁልጊዜ ማለት ነው። አ.ት፡ “ለዘለዓለም” (See: Merism)

አሜን፣ አሜን
“አሜን” የሚለው ቃል የተነገረውን ከማጽደቅ አንጻር አጽንዖት ለመስጠት ተደግሟል። አ.ት፡ “እንደዚሁ ይሁን” (See: Doublet)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 42

1 ዋላ የምንጭ ውሃ እንደሚናፍቅ አምላኬ ሆይ፣ እኔም እግዚአብሔርን ተጠማሁ። **2** መቼ ደርሼ ነው የአምላክን ፊት የማየው? **3** ጠላቶቼ ዘወትር፣ «አምላክህ የት አለ?» ስለሚሉኝ እንባዬ ቀንና ሌሊት ምግቤ ሆነ። **4** ነፍሴ በውስጤ እየፈሰሰች እነዚህን ነገሮች አስታውሳለሁ፣ ታላቅ ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር ቤት እየመራሁ በአእላፍ ሕዝብ መካከል በእልልታና በምስጋና መዝሙር እንዴት ከሕዝቡ ጋር እሄድ እንደ ነበር ትዝ አለኝ። **5** ነፍሴ ሆይ፣ ለምን ታዝኛለሽ? በውስጤስ ለምን ትታወኪያለሽ? የመድኃኒቴን አምላክ ዳግመኛ እንዳመሰግነው እግዚአብሔርን ተስፋሽ አድርጊ። **6** አምላኬ ሆይ፣ ነፍሴ በውስጤ አዝናለች ስለዚህ በዮርዳኖስ ምድር፣ ከአርሞንኤም ተራራ ጫፍ በሚዛር ተራራ አስብሃለሁ። **7** በፏፏቴህ ድምፅ ጥልቁ ጥልቁን ይጠራል ማዕበልህና ሞገድህ ሁሉ በእኔ ላይ አለፈ። **8** ያም ሆኖ፣ ያህዌ ምሕረቱን በቀን ያዛል በሌሊትም ዝማሬው በእኔ ዘንድ አለ ይህም ለሕይወቴ አምላክ የማቀርበው ጸሎት ነው። **9** እግዚአብሔር ዐለቴን፣ «ለምን ረሳኸኝ? ጠላቴ ከደረሰብኝ ጭንቀት የተነሣ ለምን በሐዘን እመላለሳለሁ?» እለዋለሁ። **10** ጠላቶቼ ቀኑን ሙሉ፣ «አምክህ የት አለ?» እያሉ የሚያደርሱብን ፌዝ ዐጥንቶቼ ውስጥ እንደ ሰይፍ ሆነ። **11** ነፍሴ ሆይ፣ ለምን ታዝኛለሽ? ለምንስ በውስጤ ትታወኪያለሽ? የመድኃኒቴን አምላክ ዳግመኛ እንዳመሰግነው እግዚአብሔርን ተስፋሽ አድርጊ።

Psalms 42:1

ለሙዚቀኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”

ማስኪል
ይህ ምናልባት የሙዚቃን ስልት ያመለክት ይሆናል። ይህንን በመዝሙር 32፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ዋላ ወደ ውሃ ምንጮች እንደምታለከልክ፣ አምላክ ሆይ አንተን እጠማለሁ
ደራሲው ለእግዚአብሔር ያለውን ናፍቆት የተጠማች ዋላ ለውሃ ካላት ናፍቆት ጋር ያነጻጽረዋል።

ማለክለክ
ሰው ወይም እንስሳ በጣም ደክሞ ወይም ተጠምቶ በከባዱ ሲተነፍስ

እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተን ተጠማሁ ... እግዚአብሔርን መጠማት
ደራሲው ለእግዚአብሔር ያለውን ብርቱ ናፍቆት ውሃን በብርቱ ከመጠማት ጋር አመሳስሎ ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መጥቼ በእግዚአብሔር ፊት የምቀርበው መቼ ነው?
ደራሲው ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው በእግዚአብሔር ፊት ለመሆን ያለውን ብርቱ ናፍቆት ለማሳየት እንጂ ምላሽ ፈልጎ አይደለም። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

Psalms 42:3

ዕንባዬ ምግብ ሆነኝ
የሚመገበው ምግብ ይመስል ደራሲው ወደ ዕንባው ያመለክታል። ይህ ማለት መብላት እስከማይችል ድረስ አዝኗል። አ.ት፡ “ዕንባዬ እንደ ምግብ ስለሆነኝ ሌላ ምንም ነገር አልበላም” (ዘይቤአዊ አነጋገር፣ Assumed Knowledge እና Implicit Information የሚለውን ተመልከት)

ቀንና ሌሊት
ይህ ሐረግ ጅማሬውንና መጨረሻውን በመጠቆሙ የሚያመለክተው ሙሉውን ቀን ነው። አ.ት፡ “ቀኑን ሙሉ” (See: Merism)

ጠላቶቼ ሁልጊዜ እንዲህ ይሉኛል
ይህ ግነት ነው። ጠላቶቹ ይህንን የሚሉት አልፎ አልፎ እንጂ ሁልጊዜ አይደለም። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

አምላክህ የት አለ?
x

Psalms 42:5

ነፍሴ ሆይ፣ ለምን አቀረቀርሽ? ለምንስ በውስጤ ተረበሸሽ?
ደራሲው ራሱን ወደሚወክልበት “ነፍሱ” ይኸውም ውስጣዊ ማንነቱ ያመለክታል። ራሱን ለመውቀስ እነዚህን ጥያቄዎች ይጠይቃል። አ.ት፡ “ማቀርቀር አልነበረብኝም። መጨነቅ አልነበረብኝም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እና Synecdoche የሚለውን ተመልከት)

ማቀርቀር
ጸሐፊው ነፍሱ የጎበጠች ይመስል የሚናገረው ስለ መጫጫን ወይም ተስፋ መቁረጥ ነው። አ.ት፡ “ተስፋ ቆርጫለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእግዚአብሔር ተስፋ አድርጊ
ጸሐፊው ለነፍሱ መናገሩንና በእግዚአብሔር እንድትታመን ማዘዙን ቀጥሏል። (See: Imperatives - Other Uses)

አምላኬ ሆይ፣ ነፍሴ
ጸሐፊው ስለ ነፍሱ ለእግዚአብሔር መናገር ይጀምራል።

አስብሃለሁ
የዚህ ሐረግ ትርጉም ማስታወስ ወይም ስለ አንድ ነገር ማሰብ ማለት ነው። አ.ት፡ “ስለ አንተ አስባለሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የዮርዳኖስ ምድር
ይህ ምናልባት የዮርዳኖስ ወንዝ መነሻ የሆነውን ሰሜናዊ እስራኤል ያመለክት ይሆናል። አ.ት፡ “የዮርዳኖስ ወንዝ መነሻ ምድር” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ጫፍ
የተራራ ጫፍ

የሚዛር ኮረብታ
ይህ በአርሞንኤም ተራራ ስር ያለ የኮረብታ ስም ነው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Psalms 42:7

በፏፏቴህ ድምፅ አንዱ ጥልቅ ሌላውን ጥልቅ ይጣራል
“ጥልቅ” የሚለው ቃል ጥልቅ የሆነውን የውሃ አካል የሚያመለክት ሲሆን እዚህ ጋ ሊሆን የሚችለው ከአርሞንኤም ተራራ ወደ ታች የሚወርደውን ምንጭ ነው። ሰዎች ከተራራው ላይ ሲወርዱ የሚያሰሙትን እንቅስቃሴ ለእርስ በእርስ እንደሚያወሩ አድርጎ ጸሐፊው ስለ ውሃው አወራረድ ይናገራል። (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሞገድህና ... ሁሉ በላዬ ላይ አልፏል
ደራሲው እጅግ አስከፊ የሆነበትን አጋጣሚና ሐዘኑን አንዱ ሞገድ ከሌላው ሞገድ ጋር እያላጋው ጥልቅ ውሃ እንዳሰጠመው ያህል አድርጎ ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሞገድህና ማዕበልህ
“ማዕበል” የሚለው ቃል “ሞገድ” ለሚለው ተለዋጭ ቃል ነው። ሁለቱ ቃላት በአንድነት በሞገዱ ታላቅነት ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ። አ.ት፡ “ታላላቅ ሞገዶችህ ሁሉ” (See: Doublet)

እግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታማኝነቱን በቀን ያዛል
ከእርሱ ጋር እንዲኖር የሚያዘው ሰው የሆነ ይመስል ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታማኝነት ይናገራል። የነገር ስም የሆነው “ታማኝነት” እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታማኝነቱን በቀን ያሳየኛል” ወይም “እግዚአብሔር ለቃል ኪዳኑ ምን ያህል ታማኝ እንደሆነ በቀን ያሳየኛል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መዝሙሩን
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “የሚሰጠኝ መዝሙር” ወይም “ስለ እርሱ የሆነውን መዝሙር” የሚሉት ናቸው።

የሕይወቴ አምላክ
“ሕይወት የሚሰጠኝ አምላክ”

Psalms 42:9

ለእግዚአብሔር፣ ለዐለቴ እናገራለሁ
ጸሐፊው ከጠላት ጥቃት ሊከላከል በሚችል በትልቅ ዐለት መስሎ ስለ እግዚአብሔር ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ለምን እያለቀስኩ እሄዳለሁ
“እያለቀሱ መሄድ” በጣም ከማዘን ጋር የተያያዘ ሥርዓት መፈጸም ነው።

በአጥንቴ ውስጥ እንደገባ ሰይፍ
ጸሐፊው የባላጋራዎቹን ወቀሳ በብርቱ እንዳቆሰሉት ይህል አድርጎ ይናገራል። (See: Simile)

ሁልጊዜ እንዲህ ይሉኛል
ይህ ግነት ነው፤ ጠላቶቹ አልፎ አልፎ እንጂ ሁልጊዜ እንዲህ አይሉትም። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

አምላክህ የት አለ?
የደራሲው ጠላቶች እንዲህ በማለት የሚጠይቁት ሊሰለቁበትና እግዚአብሔር ሲረዳው እንዳላዩ ለመግለጽ ነው። አ.ት፡ “የሚረዳህ አምላክህ በዚህ የለም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

Psalms 42:11

ነፍሴ ሆይ፣ ለምን አቀረቀርሽ? ለምንስ በውስጤ ተረበሸሽ?
ደራሲው ራሱን ወደሚወክልበት “ነፍሱ” ይኸውም ውስጣዊ ማንነቱ ያመለክታል። ራሱን ለመውቀስ እነዚህን ጥያቄዎች ይጠይቃል። ይህንን በመዝሙር 42:5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ማቀርቀር አልነበረብኝም። መጨነቅ አልነበረብኝም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እና Synecdoche የሚለውን ተመልከት)

ማቀርቀር
ጸሐፊው ነፍሱ የጎበጠች ይመስል የሚናገረው ስለ መጫጫን ወይም ተስፋ መቁረጥ ነው። ይህንን በመዝሙር 42:5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ተስፋ ቆርጫለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእግዚአብሔር ተስፋ አድርጊ
ጸሐፊው ለነፍሱ መናገሩንና በእግዚአብሔር እንድትታመን ማዘዙን ቀጥሏል። ይህንን በመዝሙር 42:5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (See: Imperatives - Other Uses)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 43

1 አምላክ ሆይ፣ ፍረድልኝ ከጽድቅ ከራቀ ሕዝብ ጋር ተሟገትልኝ። **2** አምላክ ሆይ፣ አንተ ብርታቴ ነህ ለምን ተውኸኝ? ጠላት እያስጨነቀኝ ለምን በሐዘን እመላለሳለሁ? **3** ብርሃንህንና እውነትህን ላክ፤ እኔንም ይምሩኝ። ወደ ቅዱስ ኮረብታህና ወደ ማደሪያህ ያድርሱኝ። **4** እኔም ወደ እግዚአብሔር መሠዊያ እሄዳለሁ ፍጹም ደስታዬ ወደ ሆነው አምላኬ አቀናለሁ። እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፣ በበገና አመሰግንሃለሁ። **5** ነፍሴ ሆይ፣ ለምን ታዝኛለሽ? ለምንስ በውስጤ ትታወኪያለሽ? የመድኃኒቴን አምላክ ዳግመኛ እንዳመሰግነው እግዚአብሔርን ተስፋሽ አድርጊ።

Psalms 43:1

የብርታቴ አምላክ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “የሚጠብቀኝ አምላክ” ወይም 2) “ብርታት የሚሰጠኝ አምላክ” የሚሉት ናቸው።

ለምን ተውከኝ? በጠላት ጭቆና ምክንያት ለምን እያለቀስኩ እሄዳለሁ?
ጸሐፊው እነዚህን ጥያቄዎች የሚጠይቀው ምላሽ ለማግኘት ሳይሆን በእግዚአብሔር ላይ ያለውን ቅሬታና ስሜቱን ለመግለጽ ነው። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ለምን እያለቀስኩ እሄዳለሁ
“እያለቀሱ መሄድ” በጣም ከማዘን ጋር የተያያዘ ሥርዓት መፈጸም ነው።

በጠላት ጭቆና ምክንያት
“ጭቆና” የሚለው ቃል እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ጠላቴ ስለሚጨቁነኝ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

Psalms 43:3

ብርሃንህን እና እውነትህን ላክ
ብርሃን ሆኖ መንገዱን ያሳየው፣ እውነት ሆኖም እንዴት መኖር እንዳለበት ያስተምረው ይመስል ጸሐፊው የሚናገረው ስለ እግዚአብሔር ታዳጊነት ነው። አ.ት፡ “በብርሃንህ እና በእውነትህ ምራኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ቅዱስ ኮረብታ
ይህ መቅደሱ የሚገኝበትን የኢየሩሳሌም ኮረብታና መቅደሱን ራሱን ያመለክታል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ወደ ማደሪያህ
“አንተ ወደምትኖርበት ስፍራ”

ፍጹም ደስታዬ እግዚአብሔር
“ታላቅ ደስታዬ የሆነው እግዚአብሔር” ወይም “ታላቅ ደስታን የሚሰጠኝ እግዚአብሔር”

Psalms 43:5

ነፍሴ ሆይ፣ ለምን አቀረቀርሽ? ለምንስ በውስጤ ተረበሸሽ?
ደራሲው ራሱን ወደሚወክልበት “ነፍሱ” ይኸውም ውስጣዊ ማንነቱ ያመለክታል። ራሱን ለመውቀስ እነዚህን ጥያቄዎች ይጠይቃል። ይህንን በመዝሙር 42:5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ማቀርቀር አልነበረብኝም። መጨነቅ አልነበረብኝም” (See: Imperatives - Other Uses)

ማቀርቀር
ጸሐፊው ነፍሱ የጎበጠች ይመስል የሚናገረው ስለ መጫጫን ወይም ተስፋ መቁረጥ ነው። ይህንን በመዝሙር 42:5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ተስፋ ቆርጫለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእግዚአብሔር ተስፋ አድርጊ
ጸሐፊው ለነፍሱ መናገሩንና በእግዚአብሔር እንድትታመን ማዘዙን ቀጥሏል። ይህንን በመዝሙር 42:5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

አምላኬና ድነቴ
“ድነቴ” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ያመለክታል። አስፈላጊ ከሆነ ሁለቱ ሐረጎች ሊጣመሩ ይችላሉ። አ.ት፡ “የሚያድነኝ አምላኬ” (See: Doublet)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 44

1 አምላክ ሆይ፣ በጆሮአችን ሰምተናል በቀድሞ ዘመን እነርሱ በነበሩበት ዘመን ያደረግኸውን አባቶቻችን ነግረውናል። **2** ሕዝቦችን በእጅህ አሳድደህ አስወጣህ የእኛን ሕዝብ ግን ተከልህ ሕዝቦችን አደቀቅህ የእኛ ሕዝብ ግን በምድሩ እንዲኖር አደረግህ። **3** ምድሪቱን የወረሳት በሰይፋቸው አልነበረም፣ ያዳናቸውም የገዛ ክንዳቸው አልነበረም አንተ ወደድሃቸውና ቀኝ እጅህ፣ ክንድህና የፊትህ ብርሃን ይህን አደረገ። **4** እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ ንጉሤ ነህ ያዕቆብ ድል እንዲያገኝ የወሰንህ አንተ ነህ። **5** በአንተ ርዳታ ጠላቶቻችንን ድል እንነሣለን በስምህም ተቃዋሚዎቻችንን እንረግጣለን። **6** በቀስቴ አልተማመንምና ሰይፌም አያድነኝም። **7** አንተ ግን ከጠላቶቻችን አዳንኸን የሚጠሉንንም አሳፈርሃቸው። **8** ዘወትር በእግዚአብሔር እንመካለን ለዘላለምም ስምህን እንወድሳለን። ሴላ **9** አሁን ግን ትተኸናል ለውርደትም ዳርገኸናል ከሰራዊታችንም ጋር አትወጣም። **10** ከጠላት ፊት እንድንሸሽ አደረግህ ባላንጣዎቻችንም ዘረፉን። **11** እንደሚታረዱ በጐች አደረግኸን በሕዝቦችም መካከል በተንኸን። **12** ሕዝብህን በርካሽ ዋጋ ሸጥኸው ከሽያጩም ያተረፍኸው የለም። **13** ለጐረቤቶቻችን ማፈሪያ በዙሪያችን ላሉትም መሣቂያና መዘባበቻ አደረግኸን። **14** በሕዝቦች ዘንድ ስድብ፣ በሰዎችም መካከል ራስ የሚነቀነቅብን አደረግኸን። **15** ውርደቴ ዘወትር በፊቴ ነው ፊቴም እፍረትን ተከናንቦአል። **16** ይህም ከዘላፊውና ከተሳዳቢው ድምፅ የተነሣ ከጠላትና ከተበቃይ የተነሣ ነው። **17** ይህ ሁሉ ቢደርስብንም፣ አንተን ግን አልረሳንም ለኪዳንህ ታማኝ መሆንንም አልተውንም። **18** ልባችን ከአንተ አልተመለሰም ርምጃችንም ከመንገድህ ወደ ኋላ አላለም። **19** አንተ ግን ተኩላዎች በሚውሉበት ቦታ ሰባብረህ ጣልኸን፤ በሞት ጥላም ሸፈንኸን። **20** የአምላካችንን ስም ረስተን፣ እጆቻችንን ለባዕድ አማልክት ዘርግተን ቢሆን ኖሮ፣ **21** እግዚአብሔር ይህን ማወቅ ይሣነዋልን? እርሱ የሰውን ልብ ምስጢር የሚረዳ ነውና። **22** ያም ሆኖ፣ ቀኑን ሙሉ ስለ አንተ እንገደላለን እንደሚታረዱ በጐችም ተቆጠርን። **23** ጌታ ሆይ ንቃ፣ ለምንስ ትተኛለህ? ተነሥ፣ ለዘላለምም አትተወን። **24** ፊትህን ለምን ከእኛ ትሰውራለህ? መከራና ጭንቀታችን ለምን ችላ ትላለህ? **25** እስከ ምድር ትቢያ ድረስ ወርደናል አካላችን ከምድር ጋር ተጣብቆአል። **26** እኛን ለመርዳት ተነሥ ስለ ኪዳን ታማኝነትህ ስትል ተቤዠን።

Psalms 44:1

ለሙዚቀኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”

የቆሬ ልጆች መዝሙር
x

Psalms 44:3

በገዛ ሰይፋቸው
“ሰይፍ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ወታደራዊ ኃይልን ነው። አ.ት፡ “በገዛ ሰይፋቸው በመዋጋት” ወይም “በገዛ ሰራዊታቸው ጉልበት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የገዛ ክንዳቸው
እዚህ ጋ “ክንድ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኃይልን ነው። አ.ት፡ “የገዛ ኃይላቸው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የፊትህ ብርሃን
ለዚህ ሐረግ ግሥ ልትጨምርበት ትችላለህ። አ.ት፡ “የፊትህ ብርሃን ምድሪቱን የእነርሱ እንድትሆን አደረገ” (See: Ellipsis)

ቀኝ እጅህ፣ ክንድህ
እዚህ ጋ “እጅ” እና “ክንድ” የሚሉት ቃላት ሁለቱም የእግዚአብሔርን ኃይል ያመለክታሉ። ተጣምረው ለእግዚአብሔር ኃይል ታላቅነት አጽንዖት ይሰጣሉ። አ.ት፡ “ታላቅ ኃይልህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና Doublet የሚለውን ተመልከት)

የፊትህ ብርሃን
የእግዚአብሔር ፊት በእነርሱ ላይ ያበራ ይመስል ጸሐፊው እግዚአብሔር በሞገስ እንዳያቸውና ቸር እንደሆነላቸው ይናገራል። አ.ት፡ “ደግነትህ” ወይም “ሞገስህ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ለያዕቆብ ድልን
የእስራኤል ሕዝብ በአባታቸው በ “ያዕቆብ” ስም ተጠርቷል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 44:5

በአንተ አማካይነት ... የአንተ በሆነው አማካይነት
“በአንተ... የአንተ በሆነው”

ይወድቃሉ ... ይረገጣሉ ... አይነሡም
ጸሐፊው ጠላቶቹ “የወደቁ” እና ለጦርነት ለመዘጋጀት “የተነሡ” ይመስል የሚናገረው ስለመሸነፋቸው ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በስምህ
እዚህ ጋ “ስም” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ኃይልና ሥልጣን ነው። አ.ት፡ “በኃይልህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ይረገጣሉ
“በእግሮቻችን ይረገጣሉ” ወይም “በላያቸው ላይ እንረማመዳለን”

Psalms 44:7

ፎክረናል
“መፎከር” የሚለው ቃል ከግሥ ጋር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ፎክረናል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ለስምህ ምስጋናን እናቀርባለን
እዚህ ጋ “ስም” የሚለው ቃል ራሱን እግዚአብሔርን ያመለክታል። አ.ት፡ “ለአንተ ምስጋናን እናቀርባለን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 44:9

ጥለኸናል
ጸሐፊው እግዚአብሔር የማይፈለግን ቁራጭ ጨርቅ እንደሚጥል እስራኤልን እንደ ተወው ይናገራል። አ.ት፡ “ትቶናል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ዘረፉ
ሰራዊት ጦርነቱን ካሸነፈ በኋላ የሚሰበስበው ሀብትና ንብረት

እንደሚታረዱ በጎች አድርገኸናል
ጸሐፊው እስራኤላውያኑን ሰዎች አርደው ከሚበሏቸው በጎች ጋር ያነጻጽራቸዋል። በጎች በአራዶቻቸው ፊት ተስፋ እንደሌላቸው እስራኤላውያንም

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በጠላቶቻቸው ፊት ተስፋ የላቸውም። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “በጎችን አርደው እንደሚበሉ ጠላቶቻችን እንዲገድሉን ፈቅደህላቸዋል” (Simile እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በሕዝቦች መካከል በተንከን
“በተለያዩ ሕዝቦች መካከል እንድንኖር አደረግኸን”

Psalms 44:12

ሕዝብህን በከንቱ ሸጥከው
እግዚአብሔር፣ የእስራኤል ጠላቶች እነርሱን እንዲያሸንፏቸው ማድረጉን ምንም ክፍያ ሳይጠይቃቸው የእስራኤልን ሕዝብ ለጠላቶቻቸው እንደሸጣቸው አድርጎ ጸሐፊው ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ለጎረቤቶቻችን ተግሳጽ፣ በዙሪያችን ላሉትም መሳቂያና መሳለቂያ ታደርገናለህ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመካከላቸው የሚኖሩባቸው ሕዝቦች እንዴት እንደሚሳለቁባቸው አጽንዖት የሚሰጡ ተመሳሳዮች ናቸው። (See: Parallelism)

ለጎረቤቶቻችን ተግሳጽ ታደርገናለህ
“ተግሳጽ” የሚለው ቃል እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ጎረቤቶቻችን እንደሚገስጹት አንዳች ነገር ታደርገናለህ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

በዙሪያችን ላሉትም መሳቂያና መሳለቂያ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በዙሪያችን ያሉ ይስቁብናል፣ ይሳለቁብናልም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በመካከላቸው ስድብ ... የራስ መነቅነቅ
እነዚህ ሐረጎች ተመሳሳዮች ሲሆኑ በዙሪያቸው ያሉ ሕዝቦች ምን ያህል አብዝተው እንደ ተሳለቁባቸው አጽንዖት ይሰጣሉ። (See: Parallelism)

በሕዝቦች መካከል ስድብ ታደርገናለህ
“ስድብ” የሚለው ቃል እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “በዙሪያችን ያሉ ሕዝቦች እንዲሰድቡን አደረግሃቸው” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

በሰዎች መካከል ለራስ መነቅነቂያ
“ራስን መነቅነቅ” የሚለው ሐረግ በግሥነት ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ሰዎች ራሳቸውን የሚነቀንቁበት አንዳች ነገር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ለራስ መነቅነቂያ
ሰዎች ሌሎች ላይ ያላቸውን ንቀት ለማሳየት የሚጠቀሙበት የሰውነት እንቅስቃሴ ነው።

Psalms 44:15

ውርደቴ በፊቴ ነው
ጸሐፊው እንደ ቁስ ፊት ለፊቱ ይታየው ይመስል ስለ ውርደቱ ይናገራል። የሐረጉ ትርጉም፣ ‘ሁልጊዜ ስለ ውርደቱ ያስባል’ ማለት ነው። አ.ት፡ “ስለ ውርደቴ አስባለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የእፍረት ፊቴ ጋርዶኛል
ጸሐፊው እንደ ብርድ ልብስ የሚሸፍነው ቁስ ይመስል የሚናገረው ስለ እፍረቱ ነው። አ.ት፡ “የፊቴ እፍረት ውጦኛል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የፊቴ እፍረት
“በፊቴ ላይ የሚታየው እፍረት”። ይህ እፍረቱ በፊት ገጽታው ላይ እንዴት እንደሚንጸባረቅ ያመለክታል።

ከዘላፊውና ከተሳዳቢው ድምፅ የተነሣ
እዚህ ጋ “ድምፅ” የሚለው ቃል እርሱን የሚሰድበውን ሰው ይወክላል። አ.ት፡ “እኔን ከሚዘልፈኝና ከሚሰድበኝ ሰውዬ ንግግር የተነሣ” (See: Synecdoche)

የሚዘልፍና የሚሳደብ
እነዚህ ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ ይህ ሰው ባለው ብልሹ ጸባይ ላይ አጽንዖት ያደርጋሉ። (See: Doublet)

Psalms 44:18

ልባችን ወደ ኋላ አልተመለሰም ... ከመንገድህ አልራቀም
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች ተመሳሳዮች ናቸው። ጸሐፊው እግዚአብሔርን መከተልን እንደ ታማኝነት፣ ከእርሱ መለየትን ደግሞ ታማኝነትን እንደ ማጉደል በመቁጥር ይናገራል። (Parallelism እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ልባችን ወደ ኋላ አልተመለሰም
እዚህ ጋ “ልብ” የሚለው ቃል ስሜትን፣ በተለይም ደግሞ ታማኝነትን እና ፍቅርን ያመለክታል። አ.ት፡ “ለአንተ ያለንን ታማኝነት አላቋረጥንም” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ክፉኛ ሰብረኸናል
ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር ቅጣት የሚናገረው ተሰባሪውን ዕቃ እንደሚሰብር አድርጎ ነው። አ.ት፡ “ክፉኛ ቀጣኸን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በቀበሮዎች ስፍራ
ጸሐፊው እግዚአብሔር ከቀጣቸው በኋላ ሰዎች እንደማይኖሩበት እንደ ኦና ስፍራ በመቁጠር ስለ እስራኤል ይናገራል። አ.ት፡ “ምድራችንን እንደ ቀበሮዎች መኖሪያ አደረገ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ቀበሮዎች
የዱር ውሾችን የሚመስሉ

በሞት ጥላ ሸፈንከን
ጸሐፊው ለሞቱ ባሉት ላይ ጥላውን እንደ ዘረጋ ቁስ አካል አድርጎ የሚናገረው ስለ ሞት ነው። አ.ት፡ “እንድንሞት አደረገን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የአምላካችንን ስም ረስተን ከሆነ
እዚህ ጋ “ስም” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ራሱን እግዚአብሔርን ነው። እግዚአብሔርን መርሳት ማለት እርሱን ማምለክ ማቆም ማለት ነው። ይህ ያልሆነ ነገር ነው። አ.ት፡ “አምላካችንን ረስተን ከነበረ” ወይም “አምላካችንን ማምለክ ትተን ከነበረ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና Hypothetical Situations የሚለውን ተመልከት)

ወደ ባዕድ አማልክት እጆቻችንን ዘርግተን
እጆችን መዘርጋት ሰዎች ወደ አምላክ በሚጸልዩበት ጊዜ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ነው። አ.ት፡ “ባዕድን አምላክ አምልከን” ወይም “ወደ ባዕድ አምላክ ጸልየን” (See: Symbolic Action)

እግዚአብሔር ይህንን አያየውም?
ጸሐፊው ሌላ አምላክ አምልከው ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር ያውቀው እንደነበር ለመግለጽ ይህንን ጥያቄ ይጠቀማል። አ.ት፡ “በእርግጥ እግዚአብሔር ያውቀዋል” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

እርሱ የልብን ምስጢር ያውቃል
እዚህ ጋ “ልብ” የሚለው ቃል አዕምሮንና አሳብን ያመለክታል። አ.ት፡ “አንድ ሰው በምስጢር የሚያስበውን እርሱ ያውቃል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ቀኑን ሁሉ እንገደላለን
“ቀኑን ሁሉ” የሚለው ሐረግ ሕዝባቸው ባለማቋረጥ መገደላቸውን አጽንዖት ለመስጠት የተደረገ ግነት ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ከሚገድሉን ሰዎች የተነሣ ሁሌም አደጋ ውስጥ ነን” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እንደሚታረዱ በጎች ተቆጥረናል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሰዎች እንደሚታረዱ በጎች ይቆጥሩናል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የሚታረዱ በጎች
ጸሐፊው እስራኤላውያኑን ሰዎች አርደው ከሚበሏቸው በጎች ጋር ያነጻጸራቸዋል። በጎች በአራጆቻቸው ፊት ተስፋ እንደሌላቸው ሁሉ እስራኤላውያኑም በጠላቶቻቸው ፊት ተስፋ የላቸውም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 44:23

ጌታ ሆይ ንቃ፣ ለምንስ ትተኛለህ?
እግዚአብሔር በእርግጥ ተኝቷል ማለት አይደለም። ጸሐፊው እግዚአብሔር ፈጥኖ አለመመለሱን እንደ ተኛ ቆጥሮት ይናገራል። እግዚአብሔር ስለ መከራቸው ግድ ያለው መስሎ ስላልታየው እርሱን ለመውቀስ ጥያቄውን ይጠይቃል። አ.ት፡ “ጌታ ሆይ! የተኛህ መስሎ ይሰማኛልና ንቃ!” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አትጣለን
ጸሐፊው እግዚአብሔር የማይፈለግን ቁራጭ ጨርቅ እንደሚጥል እስራኤልን እንደተወው ይናገራል። ተመሳሳዩን ሐረግ በመዝሙር 44:9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “አትተወን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከመጠቃታችን ፊትህን ለምን ትሰውራለህ?
እግዚአብሔር ዝም ያላቸው መስሎ ስለታየው ቅሬታውን ለማቅረብ ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። አ.ት፡ “ከመጠቃታችን ፊትህን አትሰውር” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ፊትህን ሰወርክ
ጸሐፊው እግዚአብሔር እነርሱን መተዉን እንዳያያቸው ፊቱን እንደሰወረባቸው አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “ተውከን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ስቃያችንን እና መጠቃታችንን ረሳህ
በመሠረቱ “ስቃይ” እና “መጠቃት” የሚሉት ቃላት ትርጉማቸው አንድ ሲሆን የስቃያቸው ክብደት ላይ አጽንዖት ይሰጣል። እነዚህ ቃላት እንደ ግሥ ሊተረጎሙም ይችላሉ። አ.ት፡ “ሰዎች እንደሚያሰቃዩንና እንደሚያጠቁን ረሳህ” ወይም “ሰዎች እጅግ እንዳሰቃዩን ረሳህ” (የነገር ስም እና Doublet የሚለውን ተመልከት)

Psalms 44:25

ዐፈር ውስጥ ቀልጠናል፤ ሥጋችን ከምድር ጋር ተጣብቋል
እነዚህ ተመሳሳይ ሐረጎች ተመሳሳዩን ትርጉም ይጋራሉ። ጸሐፊው የራሱን ሕዝብ በተሸናፊነትና በውርደት መሬት ላይ እንደ ተጋደመ ይገልጸዋል። (See: Parallelism)

ዐፈር ውስጥ ቀልጠናል
ጸሐፊው በረዶ ቀልጦ ወደ ዐፈር ውስጥ እንደሚሰርግ አካላቸው ቁስ የሆነ ይመስል ስለ መዋረዳቸው ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሥጋችን ከምድር ጋር ተጣብቋል
ጸሐፊው ራሳቸውን ወደ ላይ ማንሣት እስከማይቻላቸው ድረስ ሥጋቸው ከመሬት ጋር እንደተጣበቀ አድርጎ ስለ መዋረዳቸው ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ተነሥ
ይህ እንዲነሣ የተሰጠ ትዕዛዝ ነው። ይህ ሐረግ በአንድ ነገር ላይ እርምጃ ለመውሰድ መጀመርን ያመለክታል። አ.ት፡ “እርምጃ ውሰድ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ስለ ቃል ኪዳን ታማኝነትህ ስትል
የነገር ስም የሆነው “ታማኝነት” እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ለቃል ኪዳንህ ታማኝ መሆንህን ለማሳየት” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 45

1 ልቤ መልካም ሐሳብ አፈለቀ ለንጉሡ የተቀኘሁትን ቅኔ አሰማለሁ አንደበቴ እንደ መልካም ጸሐፊ ብዕር ነው። **2** አንተ ከሰዎች ሁሉ ይልቅ ውብ ነህ ከከንፈሮችህ ጸጋ ይፈስሳል፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ለዘላለም ባርኮሃል። **3** ኃያል ሆይ፣ ሰይፍህን በወገብህ ታጠቅ ግርማ ሞገስንም ተላበስ **4** ስለ እውነት ስለ ፍትሕ ግርማን ተጐናጸፈህ ድል ለማድረግ ገሥግሥ ቀን እጅህ ድንቅ ነገር ታሳይ። **5** ፍላጻዎችን የሾሉ ናቸው ሕዝቦች ከእግርህ በታች ይወድቃሉ። ፍላጻዎችህ የንጉሡ ጠላቶችን ልብ ይወጋል። **6** አምላክ ሆይ፣ ዙፋንህ የዘላለም ዙፋን ነው በትረ መንግሥትህም የፍትሕ በትረ መንግሥት ነው። **7** ጽድቅን ወደድህ፤ ዐመፃንም ጠላህ ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክህ ከባልንጀሮችህ ይልቅ በደስታ ዘይት ቀባህ። **8** ልብስህ ሁሉ ከከርቤ፣ ከእሬትና ከብርጉድ በተቀመመ ሽቱ ያውዳል፤ በዝሆን ጥርስ ከተዋቡ ቤተ መንግሥቶች የሚወጣ የበገናና የመሰንቆ ድምፅ ደስ ያሰኝሃል። **9** በቤተ መንግሥትህ ከሚገኙ ወይዛዝርት መካከል፤ የነገሥታት ልጆች ይገኛሉ፤ ንግሥቲቱም በንጹሕ ወርቅ ያሸበረቀ ጌጤኛ ልብስ ተጐናጽፋ በቀኝህ በኩል ትቆማለች። **10** ልጄ ሆይ፣ አድምጪ አስተውይ፣ ጆሮሽንም አዘንብይ ሕዝብሽንና የአባትሽን ቤት እርሺ። **11** ንጉሥ በውበትሽ ተማርኮአል እርሱ ጌታሽ ነውና አክብሪው። **12** የጢሮስ ሴት ልጅ ስጦታ ይዛ ትመጣለች፤ ሀብታሞች ደጅ ይጠኑሻል። **13** በቤተ መንግሥት ያለችው ልዕልት አጊጣለች ልብሷም በወርቅ አሸብርቋል። **14** ጌጠኛ ልብሷን ለብሳ ወደ ንጉሡ ትገባለች፤ ደናግል ጓደኞቿም አጅበዋት ወደ አንተ ይመጣሉ። **15** በደስታና በሐሤትም አብረው ወደ ንጉሡ ቤት ይገባሉ። **16** ወንዶች ልጆችህ በአባቶችህ እግር ይተካሉ በምድር ሁሉ ላይ ገዦች አድርገህ ትሾማቸዋለህ። **17** ስምህን በትውልድ ሁሉ ዘንድ ለመታሰቢያ አደርጋለሁ ስለዚህ ሕዝቦች ከዘላለም እስከ ዘላለም ይወድሱሃል።

Psalms 45:1

ለሙዚቀኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”

ለሾሻኒም የተዘጋጀ
ለሾሻኒም የተዘጋጀ

የቆሬ ልጆች መዝሙር
“ይህ የቆሬ ልጆች የጸፉት መዝሙር ነው” ይህ አንድን ሙዚቃ ስልት ወይም ቅኝት ሳያመለክት አይቀርም። አንዳንድ ጊዜ “ለ’ጽጌረዳ’ ቅኝት የተዘጋጀ” ተብሎ ተተርጉሟል። ይህንን በመዝሙር 32፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የፍቅር መዝሙር
“የፍቅር መዝሙር”

ልቤ መልካም አሳብ ሞልቶት ያፈስሳል
ጸሐፊው ፈሳሽ ሞልቶት እንደሚያፈስ ዕቃ ስለ ልቡ ይናገራል። “ልብ” የሚለው ቃል በሚዘምረው መዝሙር የተደሰተ ስሜቱን ይወክላል። አ.ት፡ “ስለ መልካሙ አሳብ ደስታ ተሰምቶኛል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መልካም አሳብ
“የከበረ ርዕሰ ጉዳይ” ወይም “ያማረ ቃል”። ይህ የሚያመለክተው እርሱ የጻፈውን መዝሙር ነው።

የተቀናበረ
የተጻፈ ወይም የተደረሰ መዝሙር

ምላሴ የዝግጁ ጸሐፊ እስክሪብቶ ነው
ጸሐፊው እስክሪብቶ ብሎ የሚናገረው ስለ ምላሱ ነው። ልምድ ያለው ጸሐፊ ቃላትን እንደሚጽፍ እርሱ ቃላትን በብልሃት ይናገራል። አ.ት፡ “ምላሴ በደንብ እንደሚጽፍ ሰው እስክሪብቶ ነው” ወይም “ልምድ ያለው ጸሐፊ ቃላትን መጻፍ እንደሚችል ሁሉ እኔም ቃላትን በብልሃት እናገራለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከሰው ልጆች ይልቅ ውብ ነህ
ይህ ሐረግ ንጉሡ ከማንም ይልቅ ማራኪ ስለመሆኑ አጽንዖት ለመስጠት የተነገረ ግነት ነው። “የሰው ልጆች” የሚለው ሐረግ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ሰዎችን ሁሉ ያመለክታል። አ.ት፡ “አንተ ከየትኛውም ወንድ ይልቅ መልከ መልካም ነህ” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እና የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በከንፈሮችህ ላይ ጸጋ ይፈስሳል
አንድ ሰው የንጉሡን ከንፈሮች ለመቀባት የተጠቀመበትን ዘይት በሚመስል መልኩ ጸሐፊው የሚናገረው ስለ ጸጋ ነው። “ከንፈሮች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የንጉሡን ንግግር ነው። የሐረጉ ትርጉም፣ ንጉሡ አንደበተ ርቱዕ ነው የሚል ነው። አ.ት፡ “አንድ ሰው ከንፈሮችህን በዘይት የቀባቸው ይመስላል” ወይም “አንደበተ ርቱዕ ነህ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 45:3

ሰይፍህን በጎንህ ታጠቀው
ተዋጊዎች ሰይፋቸውን በወገባቸው ዙሪያ ባለው ቀበቶ በሚንጠለጠለው ሰገባ ውስጥ ይታጠቁት ነበር። ሰይፉ በጎናቸው በኩል ይቀመጣል። ይህ ሐረግ አንድ ሰው ለጦርነት የሚያደርገውን ዝግጅት ይገልጻል። አ.ት፡ “ራስህን ለጦርነት አዘጋጅ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

በድል አድራጊነት ገስግስ
ጸሐፊው ንጉሡ በፈረሱ ወይም በሰረገላው ላይ ተቀምጦ ወደ ድል እንዲገሰግስ ይነግረዋል

በእውነተኝነትህ፣ በየዋህነትህና በጽድቅህ ምክንያት
የነገር ስም የሆኑት “እውነተኝነት”፣ “የዋህነት” እና “ጽድቅ” እንደ ቅጽል ሊነገሩ ይችላሉ። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) እነዚህ የኃያል ሰው መለያ ናቸው። አ.ት፡ “አንተ እውነተኛ፣ የዋህና ጻድቅ ስለሆንክ” ወይም 2) እነዚህ ለሚያስተዳድረው ሕዝብ ሊያቆይላቸው የሚዋጋላቸው መልካም ባህርያት ናቸው። አ.ት፡ “ለእውነተኝነት፣ ለየዋህነትና ለትክክለኝነት ለመዋጋት” የሚሉት ናቸው። (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ቀኝ እጅህ አስፈሪ ነገሮችን ያስተምርሃል
አብዛኞቹ ወታደሮች በሚዋጉበት ጊዜ ሰይፋቸውን በቀኝ እጆቻቸው ይይዙ ነበር። እዚህ ጋ “ቀኝ እጅ” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ጸሐፊው ስለ አንድ፣ ከጦርነት ያገኘውን ልምድ ለንጉሡ ሊያስተምር ስለ ቻለ ሰው፣ የተናገረውን ነው። አ.ት፡ “በብዙ ጦርነቶች በመዋጋት ታላላቅ ወታደራዊ ጀብዱዎችን ለመፈጸም ትማራለህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

አስፈሪ ነገሮች
“አስደናቂ ሥራዎችን”። ይህ ጠላቶቹ እንዲፈሩትና ተባባሪዎቹ እንዲያከብሩት የሚያስደርጋቸውን ወታደራዊ ድሎች ያመለክታል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 45:5

ሕዝቦች ከበታችህ ይወድቃሉ
ይህ ሐረግ የሚያመለክተው ንጉሡ ጠላቶቹን ማሸነፉን ነው። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “ሕዝቦች ተማርከው እግርህ ላይ ይወድቃሉ” ወይም 2) “ሕዝቦች እግርህ ስር ይሞታሉ” የሚሉት ናቸው።

ቀስቶችህ በንጉሡ ጠላቶች ልብ ውስጥ ናቸው
“ቀስቶችህ የጠላቶችህን ልብ ወግቷል”። ጸሐፊው ንጉሡን በማመልከት በሦስተኛ መደብ የሚናገረው ለንጉሡ ነው።

. . . ዙፋንህ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ነው
“ዙፋን” የሚለው ቃል የንጉሡን መንግሥትና አገዛዝ ይወክላል። አ.ት፡ “መንግሥትህ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ነው” ወይም “ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ትነግሣለህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር ሆይ ዙፋንህ
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፣ “እግዚአብሔር” የሚለው ቃል 1) የእግዚአብሔር ወኪል የሆነው የንጉሡ መጠሪያ ነው ወይም 2) “ዙፋን” የሚለውን ቃል “እግዚአብሔር የሰጠህ መንግሥት” ለሚለው ተስማሚ ያደርገዋል የሚሉት ናቸው።

በትረ - መንግሥትህ የፍትሕ በትረ - መንግሥት ነው
“በትረ - መንግሥት” የሚለው ቃል መንግሥቱን ለማስተዳደር ያለውን የንጉሡን ሥልጣን ይወክላል። አ.ት፡ “መንግሥትህን በፍትሓዊነት ታስተዳድራለህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አምላክህ እግዚአብሔር በደስታ ዘይት ቀብቶሃል
ጸሐፊው ስለ ደስታ ሲናገር እግዚአብሔር ንጉሡን ለመቀባት እንደተጠቀመበት ዘይት አድርጎ ይገልጸዋል። እግዚአብሔር እርሱን መቀባቱ ንጉሥ እንዲሆን እንደ መረጠው ምልክታዊ ድርጊት ነው። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ንጉሥ አድርጎ በሾመህ ጊዜ በጣም ደስ አሰኘህ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና Symbolic Action የሚለውን ተመልከት)

Psalms 45:8

ከርቤ፣ አደስ፣ እና ጥንጆት
እነዚህ ሰዎች ሽቶ ለመሥራት የሚጠቀሙባቸው መዓዛ ያላቸው እጽዋት ናቸው። (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)

በዝሆን ጥርስ የተዋቡ ቤተ መንግሥቶች
የዝሆን ጥርስ ከእንስሳ የሚገኝ ነጭና ጠንካራ ነገር ነው። ይህ ሐረግ የሚገልጸው ሰዎች ግድግዳዎቹንና ቁሳቁሶቹን በዝሆን ጥርስ ስላስዋቡት ቤተ መንግሥት ነው።

ባለ አውታር የሙዚቃ መሣሪያዎች ደስ አሰኝተውሃል
“ባለ አውታር የሙዚቃ መሣሪያዎች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰዎች ባለ አውታር የሙዚቃ መሣሪያ በመጠቀም የሚጫወቱትን ሙዚቃ ነው። አ.ት፡ “የባለ አውታሩ ሙዚቃ ደስ አሰኝቶሃል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የተከበሩ ሴቶች
እነዚህ ሴቶች የንጉሡን ፈቃድ የሚቀበሉ ሚስቶቹ ናቸው።

ንግሥቲቱ
ይህ ንግሥት ልትሆን ያለችውን ሴት ማመላከቻ ነው። አ.ት፡ “ንግሥቲቱ ሙሽራህ” ወይም “ንግሥት የምትሆነው ሙሽራህ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ኦፊር
ይህ በጥሩ ወርቁ የተመሰከረለት የቦታ ስም ነው። ስፍራው አይታወቅም። (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Psalms 45:10

ልጄ ሆይ፣ ስሚ
ንግሥቲቱ ወጣት ሴት በመሆኗ ምክንያት ጸሐፊው “ልጄ” በማለት ሊያነጋግራት ይጀምራል።

ጆሮሽን አዘንብዪ
ጸሐፊው አንድን ነገር በጥንቃቄ መስማቱን ለመግለጽ በተናጋሪው ሰው አቅጣጫ ጎንበስ ከማለት ጋር ያገናኘዋል። አ.ት፡ “በጥንቃቄ አድምጪ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የገዛ ሕዝብሽን እርሺ
ንግሥቲቱ ልክ ልትረሳቸው በምትችልበት መልኩ ከእንግዲህ የወገኖቿን እምነትና ልማድ መከተል እንደማይኖርባት ጸሐፊው ይናገራል። አ.ት፡ “ከእንግዲህ የሕዝብሽን ልማድ መከተል አይኖርብሽም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የአባትሽን ቤት
እዚህ ጋ “ቤት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ቤተሰብን ነው። አ.ት፡ “ዘመዶችሽን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በዚህ መልኩ
“እና” ወይም “እንደዚህ”

ንጉሡ ውበትሽን ይመኛል
ይህ ንጉሡ ሚስቱ አድርጓት ከንግሥቲቱ ጋር ለመተኛት መፈለጉ በጨዋነት የተነገረበት ነው። (See: Eu- phemism)

Psalms 45:12

የጢሮስ ሴት ልጅ
ጸሐፊው በጢሮስ ስለሚኖሩ ሰዎች ሲናገር እንደ ጢሮስ ልጆች ይቆጥራቸዋል። አ.ት፡ “የጢሮስ ሕዝብ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የንጉሥ ሴት ልጅ
ይህ ንጉሡ የሚያገባትን ሴት ማንነት የሚያመላክት ነው። አ.ት፡ “የንጉሡ ሙሽራ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ሁለንተናዋ ያሸበረቀ
“በጣም ውብ”። ይህ የሴቲቱን ገጽታ ያመለክታል።

ልብሷ በወርቅ የተሠራ ነው
ልብሷ በወርቅ ያጌጠ ወይም የተጠለፈ ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አንድ ሰው በወርቃማ ክር የጠለፈውን ልብስ ትለብሳለች” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Psalms 45:14

የተጠለፈበትን ልብስ ለብሳ ወደ ንጉሡ ትወሰዳለች
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የተጠለፈበትን ልብስ እንደ ለበሰች ሰዎች ወደ ንጉሡ ይወስዷታል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ጥልፍ
የተለያየ ቀለም ያሏቸውን ክሮች ወደ ጨርቅነት ለመስፋት የተዘጋጀ ንድፍ

አጅበው የሚከተሏትን ደናግል ወደ አንተ ያመጣሉ
እዚህ ጋ፣ “አንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ንጉሠን ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሰዎች እርሷን አጅበው የሚከተሏትን ደናግል ያመጡልሃል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ደስታና ሐሴት ይመሯቸዋል
ይህ ሐረግ “ደስታና ሐሴት”ን ሌሎች እንዲደሰቱ የሚመራቸው ዓይነት ሰው ተደርጎ ተገልጿል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ደስታና ሐሴት እነርሱን ይመሯቸዋል” ወይም “በደስታና በሐሴት ወደፊት ይሄዳሉ” (ሰውኛ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ደስታና ሐሴት
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ቃላት ትርጉማቸው አንድ ሆኖ ሳለ የደስታው ጥልቅነት ላይ አጽንዖት የሚሰጡ ናቸው። አ.ት፡ “በታላቅ ደስታ” (See: Doublet)

Psalms 45:16

በአባቶቻችሁ ቦታ ልጆቻችሁ ይሆናሉ
ይህ ማለት እርሱ ነገሥታት የነበሩ አባቶቹን እንደተካቸው የንጉሠ ወንዶች ልጆች ንጉሥ በመሆን ይተኩታል ማለት ነው።

በምድር ሁሉ ላይ ገዦችን ታደርጋለህ
“በምድር ሁሉ ላይ” የሚለው በብዙ ሀገሮች እንደሚያስተዳድሩ አጽንዖት ለመስጠት እንጂ ግነት ነው። አ.ት፡ “በብዙ ሀገሮች ላይ ገዢዎች እንዲሆኑ ታደርጋቸዋለህ” (ግነት እና ጥቅል አስተያየት የሚለውን ተመልከት)

ትውልድ ሁሉ ስምህን እንዲያስታውስ አደርጋለሁ
እዚህ ጋ በውስጠ ታዋቂነት “እኔ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጸሐፊውን ነው። “ስም” የሚለው ቃል የንጉሠን ጸባይና ምስክርነት ያመለክታል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በየትውልዱ የሚኖሩ ሰዎች ስለ ታላቅነትህ እንዲያውቁ አደርጋቸዋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 46

1 እግዚአብሔር መጠጊያችንና ኃይላችን፣ በመከራም ቀን ረዳታችን ነው። **2** ስለዚህ ምድር ብትናወጥ ተራሮችም ወደ ባሕር ልብ ቢወሰዱ፣ አንፈራም። **3** ውሆች ቢያስገመግሙ፣ ዐረፋ ቢደፍቁም፣ ከውሃው ሙላት የተነሣ ተራሮች ቢንቀጠቀጡም አንደነግጥም። ሴላ **4** የእግዚአብሔርን ከተማ የልዑልንም የተቀደሰ ማደሪያ ደስ የሚያሰኙ ወራጅ ወንዞች አሉ። **5** እግዚአብሔር በመካከሏ ነውና አትናወጥም ጠዋት በማለዳ እግዚአብሔር ይረዳታል። **6** ሕዝቦች በዐመፅ ተነሡ፤ መንግሥታት ወደቁ ድምፁን ከፍ አድርጐ አሰማ ምድርም ቀለጠች። **7** የሰራዊት ጌታ ያህዌ ከእኛ ጋር ነው የያዕቆብ አምላክ መጠጊያችን ነው። ሴላ **8** ኑ የእግዚአብሔርን ሥራ በምድር ላይ የደረሰውን ጥፋት ተመልከቱ። **9** ከምድር ዳር እስከ ዳርቻ ጦርነትን ያስወግዳል ቀስትን ይሰብራል፤ ጦርንም ያነክታል ጋሻዎችንም በእሳት ያቃጥላል። **10** ጸጥ በሉ፤ እኔም አምላክ እንደ ሆንሁ ዕወቁ በሕዝቦች ዘንድ ከፍ ከፍ እላለሁ በምድርም ላይ ከፍ ከፍ እላለሁ። **11** የሰራዊት አምላክ ያህዌ ከእኛ ጋር ነው፤ የያዕቆብ አምላክ መጠጊያችን ነው። ሴላ

Psalms 46:1

ለሙዚቀኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”

የቆሬ ልጆች መዝሙር
“ይህ የቆሬ ልጆች የጻፉት መዝሙር ነው”

ለአላሞስ የተዘጋጀ
ይህ ምናልባት አንድን ዓይነት የሙዚቃ ስልት ያመለክት ይሆናል። (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር መጠጊያችንና ኃይላችን ነው
ጸሐፊው ሰዎች ደህንነታቸውን ለማስጠበቅ እንደሚሄዱበት ስፍራ አድርጎ ስለ እግዚአብሔር ይናገራል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ደህንነትንና ኃይልን ይሰጠናል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ተራሮች ተንቀጥቅጠው ወደ ባህር ልብ ቢሰጥሙ
ጸሐፊው የባህሩን ጥልቅ ክፍል እንደ ባህሩ ልብ ቆጥሮት ይናገራል። እዚህ ጋ፣ ተራሮችን ገለባብጦ ባህር ውስጥ ስለሚጥላቸው የመሬት መንቀጥቀጥ ያብራራል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ተራሮች ወደ ባህሩ ጥልቀት እስኪወድቁ ድረስ በኃይል ይንቀጠቀጣሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ውኖቹ ቢቆጡና ቢጮኹም
“የባህሩ ውሃ ቢቆጣና ቢጮህም”። “ቁጣ” እና “ጩኸት” የሚሉት ቃላት በብርቱ ማዕበል ወቅት ባህሩ የሚኖረውን ኃይለኛ እንቅስቃሴ ይገልጻሉ።

ተራሮች ከነእብጠታቸው ይንቀጠቀጣሉ
“እብጠታቸው” የሚለው ቃል ከባህሩ ላይ እየተነሣ ከተራሮች ጋር የሚጋጨውን ውሃ ያመለክታል። አ.ት፡ “ያበጡ ውኖች ተራሮቹ እንዲንቀጠቀጡ ያደርጓቸዋል” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

Psalms 46:4

በምንጮቹ የእግዚአብሔርን ከተማ ደስ የሚያሰኝ ወንዝ አለ
የወራጅ ወንዝ ሥዕል የእግዚአብሔርን ከተማ ሰላምና ብልጽግና ያሳያል። (See: Symbolic Language)

የእግዚአብሔርን ከተማ ደስ የሚያሰኝ
“የእግዚአብሔር ከተማ” የሚለው ሐረግ ኢየሩሳሌምን ሲያመለክት በከተማይቱ የሚኖሩትን ሰዎችም ይወክላል። አ.ት፡ “በኢየሩሳሌም የሚኖሩትን ሰዎች ደስ ያሰኛቸዋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ልዑሉ የሚያድርበት ቅዱሱ ስፍራ
ይህ ሐረግ “የእግዚአብሔር ከተማ”ን ያብራራል። አ.ት፡ “ልዑሉ የሚኖርበት ቅዱሱ ስፍራ” (See: As- sumed Knowledge and Implicit Information)

በመካከሏ፤ ... ይረዳታል፣ አትናወጥም
“እርሷን” እና “እርሷ” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት “የእግዚአብሔር ከተማ”ን ነው።

አትናወጥም
እዚህ ጋ፣ “አትናወጥም” የሚለው ቃል በመዝሙሩ ቁጥር 2 ላይ “አትነቀነቅም” ተብሎ ከተተረጎመው ቃል ጋር አንድ ነው። ጸሐፊው፣ ኢየሩሳሌም በወታደሮች መፍረሷን የመሬት መንቀጥቀጥ እንዳጠፋት አድርጎ ይናገራል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ምንም ነገር እርሷን ሊያጠፋት አይችልም” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Psalms 46:6

ሕዝቦች ተቆጡ
እዚህ ጋ፣ “ተቆጡ” የሚለው ቃል ጸሐፊው በመዝሙሩ ቁጥር 3 ላይ የባህሩን ውሃ ከገለጸበት ቃል ጋር አንድ ነው። ታላቅ ማዕበል በሚሆንበት ጊዜ የባህሩ ውሃ በኃይል እንደሚንቀሳቀስ ስለ ሕዝቦች ፍርሐት ይናገራል። አ.ት፡ “ሕዝቦች ፈርተዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መንግሥታቱ ተነቀጥቅጠዋል
እዚህ ጋ፣ “ተንቀጥቅጠዋል” የሚለው ቃል ጸሐፊው በመዝሙሩ ቁጥር 2 ላይ የመሬት መንቀጥቀጡ በተራሮቹ ላይ ያስከተለውን ለመግለጽ ከተጠቀመበት ቃል ጋር አንድ ነው። ጸሐፊው በሰራዊት አማካይነት የሚወድቀውን መንግሥት ልክ የመሬት መንቀጥቀጥ እንዳጠፋው አድርጎ ይናገራል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሰራዊቱ መንግሥቱን ገለበጠው” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ድምፁን አነሣ
“እግዚአብሔር ድምፁን አነሣ”። ጸሐፊው “ድምፅ”ን አንድ ሰው ከመሬት አንሥቶ ወደ ሰማይ ከፍ እንደሚያደርገው ቁስ አድርጎ ይናገራል። ይህ ድምፁ ከፍ ያለ ይሆናል ማለት ነው። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ጮኸ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ምድሪቱ ቀለጠች
ጸሐፊው መሬትን እንደ አንዳች ነገር፣ ለምሳሌ ሊቀልጥ እንደሚችል በረዶ አድርጎ ይናገራል። እዚህ ጋ፣ “ምድሪቱ” የሰው ዘርን ስትወክል፣ መቅለጥ ደግሞ ፍርሐትን ይወክላል። አ.ት፡ “በምድር ላይ የሚኖሩ ሰዎች በፍርሃት ይንቀጠቀጣሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የያዕቆብ አምላክ መጠጊያችን ነው
ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር ሲናገር ሰዎች ደህንነት ፍለጋ እንደሚሄዱበት ስፍራ አድርጎ ይገልጸዋል። አ.ት፡ “የያዕቆብ አምላክ ደህንነትን ይሰጠናል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የያዕቆብ አምላክ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ያዕቆብ ያመለከው አምላክ” ወይም 2) “ያዕቆብ” የእስራኤል ሕዝብ የሚገለጽበት ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ “የእስራኤል አምላክ” ማለት ነው የሚሉት ናቸው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 46:8

ጦርነቶችን ያስቀራል
“ሀገራት እንዳይዋጉ ያግዳቸዋል”

እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን በዓለም ላይ በሁሉም ስፍራ ማለት ነው። አ.ት፡ “በዓለም ላይ በሁሉም ስፍራ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ቀስትን ይሰብራል ... ጋሻዎችን ያቃጥላል
እግዚአብሔር ጦርነቶችን ሁሉ ከሚያስቀርባቸው መንገዶች አንዱ ወታደሮች እርስ በርሳቸው የሚዋጉባቸውን የጦር መሣሪያዎች በማጥፋት ነው።

Psalms 46:10

ዝም በሉና እኔ አምላክ መሆኔን ዕወቁ
እዚህ ጋ እግዚአብሔር መናገር ይጀምራል።

ዝም በሉ
በዚህ ዐውድ፣ እነዚህ ቃላት ሀገራት ጦርነቶቻቸውን እንዲያቆሙ የተሰጣቸው ትዕዛዝ ሊሆን ይችላል። አ.ት፡ “መዋጋት አቁሙ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

እኔ አምላክ መሆኔን ዕወቁ
እዚህ ጋ፣ “ዕወቁ” የሚለው ቃል ትርጉም እግዚአብሔር እውነተኛ አምላክ መሆኑን መረዳትና መመስከር ነው።

በሕዝቦች መካከል እከብራለሁ፤ በምድር ላይ እከብራለሁ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ በዓለም ላይ ያሉ ሀገራት ሕዝቦች ሁሉ እግዚአብሔርን እንደሚያከብሩት አጽንዖት ይሰጣሉ። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ከሀገራት ሁሉ ሰዎች ያከብሩኛል፤ በምድር ሁሉ ላይ የሚኖሩ ሰዎች ያከብሩኛል” (Parallelism እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የሰራዊት አምላክ ከእኛ ጋር ነው፤ የያዕቆብ አምላክ መጠጊያችን ነው
ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር ሲናገር ሰዎች ደህንነት ፍለጋ እንደሚሄዱበት ስፍራ አድርጎ ይገልጸዋል። እነዚህን በመዝሙር 46፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 47

1 ሕዝቦች ሁሉ እጆቻችሁን አጨብጭቡ ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር እልል በሉ። **2** በምድር ሁሉ ላይ ታላቅ ንጉሥ የሆነው ልዑል ያህዌ እጅግ አስፈሪ ነው። **3** ሕዝቦችን ከእኛ በታች አደረገ፣ መንግሥታትንም ከእግራችን ሥር አስገዛልን። **4** ለሚወደው ለያዕቆብ ክብር የሆነችውን ርስታችንን እርሱ መረጠልን። **5** እግዚአብሔር በእልልታ፣ ያህዌም በመለከት ድምፅ ዐረገ **6** ዘምሩ ለአምላካችን ዘምሩ ዘምሩ ለንጉሣችን ዘምሩ **7** እግዚአብሔር የምድር ሁሉ ንጉሥ ነውና ስለዚህ በማስተዋል ዘምሩለት። **8** እግዚአብሔር በሕዝቦች ሁሉ ነግሦአል እግዚአብሔር በተቀደሰ ዙፋኑ ላይ ተቀምጧል። **9** ከአብርሃም አምላክ ሕዝብ ጋር የሕዝቦች መኳንንት ተሰበሰቡ የምድር ነገሥታት የእግዚአብሔር ናቸውና እርሱ እጅግ ከፍ ያለ ነው።

Psalms 47:1

ለሙዚቀኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”

የቆሬ ልጆች መዝሙር
“ይህ የቆሬ ልጆች የጻፉት መዝሙር ነው”

እጆቻችሁን አጨብጭቡ
“እጆቻችሁን አጨብጭቡ” ከደስታ ጋር ተዛምዷል። አ.ት፡ “በደስታ እጆቻችሁን አጨብጭቡ” (Assumed Knowledge and Implicit Information የሚለውን ተመልከት)

በድል አድራጊነት ድምፅ ወደ እግዚአብሔር ጩኹ
“በደስታ ድምፅ ወደ እግዚአብሔር ጩኹ”። እዚህ ጋ፣ “በድል አድራጊነት” የሚለው ቃል ከድል ጋር የተዛመደውን ደስታ ያመለክታል።

Psalms 47:3

ሕዝቦችን ከበታቻችን፣ ሀገራትንም ከእግሮቻችን በታች ያስገዛል
እነዚህ ሁለቱም ሐረጎች ተመሳሳዮች ናቸው፤ ትርጉሙም፣ እስራኤል ጠላቶቻቸውን እንዲያሸንፉ እግዚአብሔር አስችሏቸዋል ማለት ነው። (See: Parallelism)

ያስገዛል
ድል ማድረግና በሌላው ሥልጣን ሥር እንዲሆኑ ማድረግ

ከበታቻችን ... ከእግሮቻችን በታች
ጸሐፊው ሌሎች ሕዝቦችን ስለ ማሸነፍ ሲናገር እነዚያ ሕዝቦች ከእግሮቻቸው ሥር እንደተደረጉ ያህል አድርጎ ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ርስታችንን ይመርጥልናል
ጸሐፊው የእስራኤልን ምድር ቋሚ ንብረት እንዲሆናቸው እግዚአብሔር ለሕዝቡ በርስትነት እንደሰጣቸው አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “ይህችን ምድር ርስት እንዲሆነን ይመርጥልናል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የያዕቆብ ክብር
እዚህ ጋ፣ “ክብር” የሚለው ቃል የኩራትን ምንጭ ያመለክታል፣ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ርስት አድርጎ የሰጣቸውን ምድርም ይወክላል። አ.ት፡ “ያዕቆብ የሚኮራበት ምድር” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የወደደውን ያዕቆብን
“ያዕቆብ” የሚለው ቃል የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አምላክ በዕልልታ ዐረገ
ጸሐፊው እግዚአብሔር ሕዝቦችን ድል ስለማድረጉ ሲናገር እግዚአብሔር እንደ ንጉሥ በቤተ መቅደስ በሚገኘው ዙፋን ላይ እንደሚቀመጥ አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “ሕዝቡ ዕልል እያሉ እግዚአብሔር ወደ መቅደሱ ዐረገ” ወይም “ሕዝቡ ዕልል እያሉ እግዚአብሔር ዙፋኑ ላይ ተቀመጠ” (ዘይቤአዊ አነጋገር፣ እና Assumed Knowledge and Implicit Information የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር በመለከት ድምፅ
ይህ ሐረግ ቀደም ሲል ከነበረው ሐረግ ጋር ተመሳሳይ ነው። ለግልጽነቱ ግሥ ሊጨመርበት ይችላል። አ.ት፡ “ሕዝቡ መለከቶቹን እየነፉ እግዚአብሔር ዐረገ” (See: Parallelism and Ellipsis)

Psalms 47:6

ምስጋናን ለእግዚአብሔር ዘምሩ፣ ምስጋናን ዘምሩ፤ ምስጋናን ለንጉሣችን ዘምሩ፣ ምስጋናን ዘምሩ
“ምስጋናን ዘምሩ” የሚለው ሐረግ አጽንዖት ለመስጠት ተደግሟል። ድግግሞሹ በአንተ ቋንቋ የማይመች ከሆነ ልትተወው ትችላለህ። አ.ት፡ “ዘምሩ፣ ለእግዚአብሔር ምስጋናን ዘምሩ፤ ዘምሩ፣ ለንጉሣችን ምስጋናን ዘምሩ” (See: Parallelism)

Psalms 47:8

የሕዝቦች ልዑላን
“የሕዝቦች ሁሉ ገዢዎች”

ከሕዝቡ ጋር በአንድነት ተሰበሰቡ
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፣ የሕዝቦቹ ገዢዎች 1) “በሕዝቡ ፊት ለፊት ተሰበሰቡ” ወይም 2) ሁሉም እግዚአብሔርን እንደ ንጉሥ ሊያመልኩት “ከሕዝቡ ጋር በአንድነት ተሰበሰቡ” የሚሉት ናቸው።

የምድር ጋሻዎች የእግዚአብሔር ናቸው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ “ጋሻዎች” 1) የጦር መሣሪያዎችን ያመለክታል። አ.ት፡ “በምድር ካሉ ነገሥታት የጦር መሣሪያዎቻቸው ይልቅ እግዚአብሔር የበለጠ ኃይል አለው” ወይም 2) ሕዝባቸውን ለመጠበቅ እንደ ጋሻ የተነገረላቸውን የሕዝቦቹን ገዢዎች ያመለክታል። አ.ት፡ “የምድር ነገሥታት ለእግዚአብሔር ተገዢዎች ናቸው” የሚሉት ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 48

1 ያህዌ ታላቅ ነው፣ በአምላካችን ከተማ በተቀደሰ ተራራው ላይ ከፍ ያለ ምስጋና ሊቀርብለት ይገባል። **2** የምድር ሁሉ ደስታ የሆነው በሰሜን በኩል በርቀት
የሚታየው በከፍታ ላይ አምሮ የደመቀው የጽዮን ተራራ የታላቁ ንጉሥ ከተማ ነው። **3** እግዚአብሔር በቤተ መንግሥት ውስጥ ሆኖ ብርቱ ምሽጓ መሆኑን
አስመስክሮአል። **4** እነሆ፣ ነገሥታት ተባብረው መጡ በአንድነትም ገሠገሡ። **5** ዐይተው ተደነቁ ደንግጠውም ፈረጠጡ። **6** በዚያ ፍርሃትና ድንጋጤ ያዛቸው
ምጥ እንደያዛት ሴት ብርክ ያዛቸው። **7** የምሥራቅ ነፋስ የተርሴስን መርከብ እንደሚሰባብር አንተ አንበረከክሃቸው **8** በጆሮአችን እንደ ሰማን በሰራዊት አምላክ
ከተማ በአምላካችን ያህዌ ከተማ በዐይናችን አየን። **9** አምላክ ሆይ፣ በቤተ መቅደስ ውስጥ ሆነን ታማኝነትህን እናስባለን። **10** እግዚአብሔር ሆይ፣ እንደ
ስምህ ምስጋናህም እስከ ምድር ዳርቻ ነው፤ ቀኝ እጅህም ጽድቅን የተሞላች ናት። **11** ስለ ጽድቅህ የጽዮን ተራራ ደስ ይበላት የይሁዳም ልጅ ሐሤት ታድርግ።
12 በጽዮን ተራራ፣ በዙሪያዋም ተመላለሱ፣ ማማዎቿን ቁጠሩ፤ **13** ለሚቀጥለው ትውልድ ትናገሩ ዘንድ ጠንካራ ቅጥሮቿን አስተውሉ ምሽጐችዋንም
ተመልከቱ። **14** ይህ አምላክ ከዘላለም እስከ ዘላለም አምላካችን ነው፤ እስከ መጨረሻው መሪያዎችንም እርሱ ነው።

Psalms 48:1

የቆሬ ልጆች መዝሙር
“የቆሬ ልጆች የጻፉት መዝሙር ይህ ነው”

ከፍ ያለ ምስጋና ይገባዋል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሰዎች ከፍ ያለ ምስጋና ያቅርቡለት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የአምላካችን ከተማ በተቀደሰው ተራራው ላይ
ይህ በጽዮን ተራራ ላይ የተሠራችውን ኢየሩሳሌምን ያመለክታል።

የአምላካችን ከተማ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “አምላካችን የሚኖርበት ከተማ” ወይም 2) “የአምላካችን የሆነው ከተማ” የሚሉት ናቸው።

በከፍታው ላይ የተዋበው
“የተዋበና ከፍ ያለ”። “ከፍታ” የሚለው ቃል የጽዮን ተራራ ምን ያህል ከፍ ያለ መሆኑን ያመለክታል።

የምድር ሁሉ ደስታ ጽዮን ናት
እዚህ ጋ፣ “ምድር” የሚለው ቃል በምድር ላይ የሚኖሩትን ሁሉ ያመለክታል። “ደስታ” የሚለው ቃል እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “የጽዮን ተራራ በምድር ለሚኖሩ ሁሉ ደስታን ይሰጣል” ወይም “በጽዮን ተራራ ምክንያት በምድር የሚኖሩ ሁሉ ይደሰታሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

በሰሜን በኩል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ ይህ ሐረግ 1) የሰሜንን አቅጣጫ ያመለክታል ወይም 2) “የእግዚአብሔር ተራራ” የሚል ትርጉም ላለው የጽዮን ተራራ ሌላኛው ስሙ ነው የሚሉት ናቸው።

እንደ መሸሸጊያ በሆኑት ቤተ መንግሥቶቿ እግዚአብሔር ራሱን ገልጧል
ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር ሲናገር ሰዎች ለደህንነታቸው እንደሚደበቁበት ስፍራ አድርጎ ይገልጸዋል። አ.ት፡ “በጽዮን ተራራ ቤተ መንግሥቶች ውስጥ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ደህንነትን የሚሰጥ ሆኖ ራሱን ገልጧል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 48:4

ተመልከቱ
እዚህ ጋ፣ “ተመልከቱ” የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚመጣው አስደናቂ መረጃ ትኩረት እንድንሰጥ ያነቃናል።

ራሳቸውን አከማቹ
እዚህ ጋ፣ ነገሥታቱ ሰራዊታቸውን ይወክላሉ። አ.ት፡ “ሰራዊታቸውን አከማቹ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በአንድነት አለፉ
“በኢየሩሳሌም በኩል በአንድነት አለፉ”

አዩአት
“ኢየሩሳሌምን አዩአት”

ሰጉ
እጅግ ተረበሹ

በዚያ መንቀጥቀጥ ያዛቸው
x

Psalms 48:7

በምስራቁ ንፋስ የተርሴስን መርከቦች ትሰብራለህ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) እግዚአብሔር በታላቅ ንፋስ ስለሚያጠፋቸው እንደሚናወጡ መርከቦች፣ ይህ ጸሐፊው የንጉሡን መፍራት የሚገልጽበት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “በምስራቁ ንፋስ በሰባበርካቸው ጊዜ የተርሴስ መርከቦች እንደተናወጡ አነርሱ በፍርሐት ተናወጡ” ወይም 2) ይህ ደራሲው የእግዚአብሔርን ታላቅ ኃይል የሚገልጽበት ምልክት ነው የሚሉት ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር እና Apostrophe የሚለውን ተመልከት)

የምስራቅ ንፋስ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “ከምስራቅ የሚነፍሰው ንፋስ” ወይም 2) “ከባድ ንፋስ” የሚሉት ናቸው።

የተርሴስ መርከቦች
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ ይህ የሚያመለክተው 1) ወደዚያ የሚጓዙ ወይም በተርሴስ የሚሠሩ መርከቦችን ወይም 2) የትኛውንም በውቅያኖስ ላይ መጓዝ የሚችል ትልቅ መርከብን ነው የሚሉት ናቸው።

እንደ ሰማነው
እግዚአብሔር ባለፉት ዘመናት ያደረጋቸውን ታላላቅ ነገሮች መስማታቸውን ያመለክታል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ስላደረጋቸው ታላላቅ ነገሮች እንደሰማነው” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

እኛም ደግሞ አይተናል
ይህ ማለት የሰሟቸው ነገሮች እውነት ስለመሆናቸው ማረጋገጫውን አይተዋል። አ.ት፡ “አሁንም እግዚአብሔር ታላላቅ ነገሮችን ሲሠራ አይተናል” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በሰራዊት ጌታ ከተማ፣ በአምላካችን ከተማ
እነዚህ ሁለቱም ሐረጎች የሚያመለክቱት ኢየሩሳሌምን ነው። አ.ት፡ “በሰራዊት ጌታ፣ በአምላካችን ከተማ” (See: Paral- lelism)

ያጸናታል
“የተጠበቀች ያደርጋታል”። እዚህ ጋ፣ “ማጽናት” የሚለው ቃል ትርጉም አንድን ነገር ማቆየት እና መጠበቅ ማለት ነው።

Psalms 48:9

የቃል ኪዳን ታማኝነትህ
የነገር ስም የሆነው “ታማኝነት” እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ለቃል ኪዳንህ ምን ያህል ታማኝ እንደሆንክ” ወይም “ከቃል ኪዳንህ የተነሣ ለእኛ ምን ያህል ታማኝ እንደሆንክ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

በመቅደስህ መካከል
“በመቅደስህ ውስጥ እያለን”

እንደ ስምህ ሁሉ ... ምስጋናህም እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ነው
እዚህ ጋ፣ “ስም” የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ባህርይና ዝና ይወክላል። ሁለቱ ሐረጎች የእግዚአብሔርን የታላቅነቱን ዝና ሰዎች እርሱን እንዴት ከፍ ባለ ሁኔታ ያመሰግኑት እንደሆነ ያነጻጽራሉ። አ.ት፡ “ስምህ እጅግ ታላቅ ነው ... በዓለም የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ከፍ ያለ ምስጋና ያቀርቡልሃል” ወይም “በዓለም ዙሪያ ያሉ ሰዎች ስለ አንተ ሰምተዋል ... ስለዚህ በዓለም ዙሪያ ያሉ ሰዎች ያመሰግኑሃል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን በዓለም ላይ በሁሉም ስፍራ ማለት ነው። ይህንን በመዝሙር 46:9 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ቀኝ እጅህ በጽድቅ ተሞልቷል
ጸሐፊው ጽድቅን እግዚአብሔር በእጁ ሊይዘው እንደሚችለው ቁስ አድርጎ ይናገራል። እዚህ ጋ፣ “እጅ” የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ኃይልና የመግዛት ሥልጣኑን ያመለክታል። አ.ት፡ “በጽድቅ ትገዛለህ” ወይም “አንተ ስትገዛም ጻድቅ ነህ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 48:11

የጽዮን ተራራ ደስ ይበለው
ጸሐፊው የጽዮንን ተራራ ሊደሰት እንደሚችል ሰው አድርጎ ይናገርለታል። ሐረጉ በኢየሩሳሌም የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታል። አ.ት፡ “በጽዮን ተራራ የሚኖሩ ደስ ይበላቸው” (ሰውኛ እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የይሁዳ ሴቶች ልጆች ደስ ይበላቸው
ጸሐፊው በይሁዳ የሚገኙትን ከተሞች እንደ ይሁዳ ልጆች አድርጎ ይናገራል። ሐረጉ በእነዚያ ከተሞች የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታል። አ.ት፡ “በይሁዳ ከተሞች የሚኖሩ ሰዎች ደስ ይበላቸው” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 48:12

በጽዮን ተራራ አካባቢ ተመላለሱ፣ በዙሪያዋም ሂዱ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ናቸው። አ.ት፡ “በጽዮን ተራራ ዙሪያ ሁሉ ተመላለሱ” (See: Parallelism)

በሚገባ ተመልከቱ
“በዝርዝር ተመልከቱ”

Psalms 48:14

እርሱ መሪያችን ይሆናል
“መሪ” የሚለው ቃል እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እርሱ ይመራናል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

እስከ ሞት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “እስክንሞት ድረስ” ወይም 2) “ለዘላለም” የሚሉት ናቸው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 49

1 ሕዝቦች ሁሉ ይህን ስሙ በዓለም የምትኖሩ ሁሉ ይህን አድምጡ። **2** ዝቅተኞችና ከፍተኞች ሀብታሞችና ድኾች ይህን በአንድነት አድምጡ። **3** አፌ ጥበብን ይናገራል የልቤ ሐሳብም ማስተዋልን ይሰጣል። **4** ጆሮዬን ወደ ምሳሌ አዘነብላለሁ በበገናም የምሳሌዎቹን ትርጕም እገልጣለሁ። **5** ክፉ ቀን ሲመጣና አታላዮች ሲከብቡኝ ለምን እፈራለሁ? **6** በሀብታቸው የሚመኩትንና በብልጽግናቸው የሚተማመኑትን ለምን እፈራለሁ? **7** ማንም ወንድሙን መቤዠት ለእርሱም ቤዛ የሚሆነውን ዋጋ ለእግዚአብሔር መክፈል አይችልም። **8** የነፍስ ቤዛ ውድ ነውና በቂ ዋጋ ሊገኝለት አይችልም። **9** እንዳይሞትና ወደ መቃብር እንዳይወርድ ማንም ለዘላለም መኖር አይችልም። **10** ሰዎች ሁሉ ይሞታሉ፤ ጠቢባን እንኳ ከሞኞችና ከሞኞች እኩል በአንድት ይጠፋሉ ሀብታቸውንም ለሌላው ጥለው ይሄዳሉ። **11** እነርሱ የሚያስቡት ቤተ ሰባቸው ለዘላለም እንደሚኖር፣ መኖሪያ ስፍራቸውም ለትውልድ ዘመን እንደማይጠፋ በመሆኑ መሬቶቻቸውን በስማቸው ይሰይማሉ። **12** ግን ሰው በሀብቱ እንደ ተከበረ አይዘልቅም አሁን ታይተው በኃላ እንደሚጠፉ እንስሳት ይመስላል። **13** ይህ የምኞት ዕድል ፈንታ የእነርሱንም አባባል የሚከተሉ ሰዎች መጨረሻ ግብ ነው። **14** እንደ በጎች ለሞት የተመደቡ ናቸው እረኛቸውም ሞት ነው በማለዳ ቅኖች ይገዟቸዋል፤ መኖሪያ ቦታ አጥቶ አካላቸው ሲኦል ውስጥ ይፈራርሳል። **15** እግዚአብሔር ግን ሕይወቴን ከሲኦል ኃይል ይቤዣልኛል፤ እርሱም ይቀበለኛል። ሴላ **16** ሰው ባለጠጋ ቢሆን፣ የቤቱም ክብር ቢበዛለት አትፍራ። **17** በሚሞትበት ጊዜ ምንም ይዞ አይሄድም ክብሩም አብሮት አይወርድም። **18** ሰው በሕይወቱ ዘመን ቢደሰትም፣ ሁሉም ነገር ስለ ተሳካለት ቢመሰገንም፣ **19** በሞት ተለይቶ ከእንግዲህ ብርሃን ወደሚያይበት ወደ አባቶች ትውልድ ይሄዳል። **20** ሁሉም ነገር እያለው ማስተዋል የጐደለው ሰው ታይተው የሚጠፉ እንስሳትን ይመስላል።

Psalms 49:1

ለሙዚቀኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”

የቆሬ ልጆች መዝሙር
“ይህ የቆሬ ልጆች የጻፉት መዝሙር ነው”

ሕዝቦች ሁሉ ይህንን ስሙ፤ የምትኖሩባትም ሁሉ ጆሮአችሁን ስጡ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳዮች ናቸው። በአንድ ላይ ሰዎች ሁሉ እንዲሰሙ የተሰጠውን ትዕዛዝ ያጠናክራሉ። (See: Parallelism)

ጆሮአችሁን ስጡ
የዚህ የአነጋገር ዘይቤ ትርጉም አንድ ሰው ለመስማት ጆሮውን ማዘጋጀቱ ነው። አ.ት፡ “ስሙ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ዝቅተኞችና ከፍተኞች
ጸሐፊው ደካሞች ወይም በማኅበረሰቡ ውስጥ ቦታ የማይሰጣቸውን ሰዎች እንደ ዝቅተኞች፣ አስፈላጊዎችና ብርቱዎቹን ሰዎች እንደ ከፍተኞች በመቁጠር ይናገራል። “ዝቅተኛ” እና “ከፍተኛ” የሚሉት ቃላት በአንድነት ሰዎችን ሁሉ ይወክላሉ። አ.ት፡ “አስፈላጊ የሆኑና ያልሆኑ ሰዎች ሁሉ” ወይም “በየትኛውም የማኅበራዊ ደረጃ ያሉ ሰዎች” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና Merism የሚለውን ተመልከት)

ሀብታሙና ድኻው በአንድነት
“ሀብታም” እና “ድኻ” የሚሉት ቃላት በአንድነት የብልጽግናቸውን ልክ ሳይሆን ሰዎችን ሁሉ ያመለክታል። አ.ት፡ “ሰዎች ሁሉ” (See: Merism)

Psalms 49:3

አፌ ጥበብን ይናገራል
እዚህ ጋ፣ “አፍ” የሚለው ቃል የሚናገረውን ሰው ሁለንተና ያመለክታል። አ.ት፡ “የጥበብን ቃል እናገራለሁ” (See: Synecdoche)

የልቤም ጥልቅ አሳብ ማስተዋልን
እዚህ ጋ፣ “ልብ” የሚለው ቃል አዕምሮንና አሳብን ይወክላል። የነገር ስም የሆነው “ጥልቅ አሳብ” እና “ማስተዋል” እንደ ግሥ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አ.ት፡ “በጥልቀት የማስበው አሳብ እንድታስተውል ይረዳሃል” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ጆሮዬን አዘነብላለሁ
ጸሐፊው በጥንቃቄ መስማትን አጎንብሶ፣ ጆሮን ወደሚናገረው ሰው እንደ ማቅረብ አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “በጥንቃቄ ስማ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በበገና
“በገና ስደረድር”

ተረከዜን ... ለምን እፈራለሁ?
ጸሐፊው ክፉ ነገር በሚመጣበት ጊዜ የሚፈራበት ምክንያት ሊኖር እንደማይገባ አጽንዖት ለመስጠት ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። አ.ት፡ “ተረከዜን ... የምፈራበት ምክንያት የለኝም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ክፉ ቀናትን
“ክፉ ነገሮች በሚመጡበት ጊዜ”። እዚህ ጋ “ቀናት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጥቅሉን የጊዜ ክፍልፋይ ነው።

ኃጢአት ተረከዜን በከበበኝ ጊዜ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) ጸሐፊው የጠላቶቹን ክፉ ምኞት ሊቀማው እንደተዘጋጀ ዘራፊ በመቁጠር ይናገራል። አ.ት፡ “የኃጢአተኞች ኃጢአት ሊያሸንፈኝ በሚዘጋጅበት ጊዜ” ወይም 2) የጸሐፊው ጠላቶች ኃጢአት በመሥራት ላይ እያሉ እርሱን ከበውታል” የሚሉት ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 49:6

በብልጽግናቸው የሚታመኑ
እነዚህ ሰዎች ብልጽግናቸው መከራ እንዳይደርስባቸው እንደሚያደርግ ይታመናሉ። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ስለ ሀብታቸውም ብዛት
የአንድ ነገር በብዛት መኖር

አንድም እንደሌለ የታወቀ ነው
“ማናቸውም የሚችሉበት መንገድ የለም” ወይም” ወይም አ.ት፡ “ማንም አይችልም”

ማንም ወንድሙን ማዳን አይችልም ወይም ስለ እርሱ ለእግዚአብሔር ዋጋ አይሰጥም
እነዚህ ሁለቱም ሐረጎች የሚገልጹት አንድ ሰው ሞትን ለማስቀረት ለእግዚአብሔር በቂ ገንዘብ መስጠት እንደማይችል ነው። አ.ት፡

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

“ወንድሞቻቸው እንዳይሞቱ ለእግዚአብሔር ገንዘብ መክፈል የሚችል ማንም የለም” (See: Assumed Knowl- edge and Implicit Information and Parallelism)

የአንድን ሰው ሕይወት መቤዠት ዋጋው ውድ ነው
“መቤዠት” የሚለው ቃል ከግሥ ጋ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “የአንድን ሰው ሕይወት መቤዠት ከፍ ያለ ዋጋ ያስከፍላል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

Psalms 49:9

ሰውነቱ እንዳይበሰብስ
ይህ በመቃብር ውስጥ የሚበሰብሰውን ሰውነት ያመለክታል።

መበስበስን ያያል
ጸሐፊው አንድን ነገር መለማመድ ያንን ነገር እንደማየት እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “ይሞትና ሰውነቱ ይበሰብሳል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ጠቢባን ይሞታሉ፤ ሰነፎችና ጨካኞችም እንደዚሁ ይጠፋሉ
ጸሐፊው እጅግ ጠቢብ የሆኑትና ከዚያም የሚያንሱትን በመጥቀሱ ሰዎችን ሁሉ ያመላክታል። (See: Merism)

ጨካኝ
ይህ ማለት የማይረባና ብልሃት የጎደለው ሰው ማለት ነው።

Psalms 49:11

የውስጥ አሳባቸው
“እምነታቸው”

ከትውልድ እስከ ትውልድ የሚኖሩባቸው ስፍራዎች
ቀደም ብሎ ካለው ሐረግ ግሡ ሊጨመርበት ይችላል። አ.ት፡ “የሚኖሩባቸው ስፍራዎች ለትውልዶች ሁሉ ይተላለፋሉ” (See: Ellipsis)

ምድራቸውን በስሞቻቸው ይጠራሉ
“በስሞቻቸው ይጠራሉ”። ይህ ሐረግ ባለቤትነትን ይገልጻል። አ.ት፡ “ምድራቸውን የራሳቸው ያደርጋሉ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Psalms 49:12

ሰው ግን ሀብት ያለው
“ሰው ግን፣ ሀብት እንኳን ቢኖረው”

ይህ መንገዳቸው የጅልነታቸው ነው
ጸሐፊው የሞኞችን ዕጣ ፈንታ የሚራመዱበት የመንገዳቸው መጨረሻ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “በጅልነት የሚኖሩ ዕጣ ፈንታቸው ይህ ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሆኖም ከእነርሱ በኋላ
“ሆኖም ከሞቱ በኋላ”

Psalms 49:14

እንደ በጎች
ጸሐፊው የሚሞቱትን ሰዎች ሁሉ ከበግ መንጋ ጋር ያነጻጽራቸዋል። ልክ አራጁ ሊያርዳቸው በሚወስንበት ጊዜ በጎች ማምለጥ እንደማይችሉ ሰዎችም የሚሞቱበት ጊዜ ሲደርስ አያመልጡም። (See: Simile)

ተወስነዋል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ወስኗቸዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ሞት እረኛቸው ይሆናል
ጸሐፊው ሞትን ወደ መቃብር እንደሚመራቸው ሰው በመቁጠር ስለሚሞቱ ሰዎች ይናገራል። አ.ት፡ “እረኛ በጎችን ወደሚታረዱበት እንደሚወስዳቸው ሞት ይወስዳቸዋል” (ሰውኛ እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በጠዋት
እዚህ ጋ “ጠዋት” የሚለው ቃል ዘይቤአዊ አነጋገር ሲሆን እግዚአብሔር ጻድቃንን ነጻ የሚያወጣበትንና ከክፉ ሰዎች የሚያድንበትን ጊዜ ያመለክታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሰውነታቸው በሲዖል ይቃጠላል
ሲዖል ሰው ወይም እንስሳ የሆነ ይመስል ጸሐፊው የሙታን ስፍራ ስለሆነው ስለ እርሱ ይናገራል። ስለ ሬሳ መበስበስ ሲናገርም ሲዖል እነርሱን እንደሚበላቸው አድርጎ ይናገራል። (ሰውኛ እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር ሕይወቴን ከሲዖል ኃይል ያድናታል
ጸሐፊው ስለ ሲዖል ሲናገር በሚሞቱት ላይ ኃይል እንዳለው ሰው አድርጎ ይገልጸዋል። ከዐውዱ አንጻር ይህ ኃይል የሙታንን አካል እንደሚበላ ያመለክታል። (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር ሕይወቴን ያድናታል
እዚህ ጋ “ሕይወት” የሚለው ቃል የሰውን ሁለንተና ያመለክታል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ያድነኛል” (See: Synecdoche)

Psalms 49:16

የቤቱ ክብር ይጨምራል
እዚህ ጋ፣ “ክብር” የሚለው ቃል ሀብትን ወይም ብልጽግናን ያመለክታል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “በቤቱ የበለጠ ሀብት በሚያገኝበት ጊዜ” ወይም 2) “ቤተሰቡ በሚበለጽጉበት ጊዜ” የሚሉት ናቸው።

ምንም ነገር አይወስድም
“ምንም ነገር ከራሱ ጋር ወደ መቃብር አይወስድም”

ክብሩ ተከትሎት አይወርድም
“መውረድ” የሚለው ቃል ሰው የሚሞትበትን ጊዜ ያመለክታል። አ.ት፡ “እርሱ በሚሞትበት ጊዜ ክብሩ ከእርሱ ጋር አይሄድም” ወይም “በሚሞትበት ጊዜ ዝናውን አያቆይም” (See: Euphemism)

Psalms 49:18

ነፍሱን ባርኳል
እዚህ ጋ “ነፍስ” የሚለው ቃል የሰውን ሁለንተና ያመለክታል። የዚህ ሐረግ ትርጉም፣ በሀብቱ ምክንያት ራሱን ደስተኛና ስኬታማ አድርጎ ይቆጥራል የሚል ነው። አ.ት፡ “ራሱን ‘እንኳን ደስ ያለህ’ ብሏል” (See: Synecdoche እና የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ለራስህ በምትኖርበት ጊዜ ሰዎች ያመሰግኑሃል
እዚህ ጋ፣ ጸሐፊው ሰዎች በዓለማዊው መስፈርት ስኬታማ ስለሆኑ ስለ ሌሎች ሰዎች እንዴት እንደሚናገሩ ጠቅለል ያለ አባባል አቅርቧል።

ለራስህ ስትኖር
ይህ ሐረግ በዓለማዊው መስፈርት በስኬታማነት መኖርን ያመለክታል። አ.ት፡ “ለራስህ መልካሙን አድርግ” ወይም “በስኬት ኑር” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ወደ አባቶቹ ትውልድ ይሄዳል
“የአባቶቹ ትውልድ ወዳለበት ይሄዳል”። ይህ የተሻለ ቃል ሲሆን ትርጉሙ ሀብታሙ ሰው ይሞትና በመቃብር ውስጥ ከአባቶቹ ጋር ይገናኛል የሚል ነው። አ.ት፡ “መቃብር ውስጥ ከአባቶቹ ጋር ይገናኛል” (See: Euphemism)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ዳግመኛ ብርሃንን ከቶ አያዩም

በውስጠ ታዋቂ ያለው “እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሀብታሞችንና አባቶቻቸውን ነው። “ብርሃን” የሚለው ቃል ፀሐይን ያመለክት ይሆናል ወይም በዘይቤአዊ አነጋገር ሕይወት ሊሆን ይችላል። አ.ት፡ “ዳግመኛ ፀሐይን ከቶ አያዩም” ወይም “ዳግመኛ ከቶ በሕይወት አይኖሩም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 50

1 ኃያሉ አምላክ ያህዌ ተናገረ ከፀሐይ መውጫ እስከ መጥለቂያዋ ድረስ ምድርን ተናገረ። **2** ፍጹም ውብ ከሆነችው ከጽዮን እግዚአብሔር አበራ። **3** አምላካችን ይመጣል ዝምም አይልም የሚባላ እሳት በፊቱ ነው ኃይለኛ ዐውሎ ነፋስም በዙሪያው ነው። **4** ሕዝቡ ላይ ይፈርድ ዘንድ በላይ ያሉ ሰማያትንና ምድርን፣ «በመሥዋዕት ከእኔ ጋር ኪዳን የገቡትን **5** ቅዱሳኔን ሁሉ ወደ እኔ ሰብስቡ» ብሎ ይጣራል። **6** ሰማያት ጽድቁን ያውጃሉ። እግዚአብሔርን ራሱ ፈራጅ ነው። ሴላ **7** «ሕዝቤ ሆይ፣ ስማኝ ልንገርህ እስራኤል ሆይ፣ በአንተ ላይ ልመስክር፤ አምላክህ እኔ እግዚአብሔር ነኝ። **8** ስለ መሥዋዕትህ አልነቅፍህም የሚቃጠል መሥዋዕትህ ሁልጊዜ በፊቴ ነው። **9** ከበረትህ ኮርማዎችን፣ ከጉሮኖህም አውራ ፍየሎችን አልወስድም **10** የዱር አራዊት ሁሉ፣ በሺ ተራሮች ያለው እንስሳ ሁሉ የእኔ ነውና። **11** በየተራሮች ያሉ ወፎችን ሁሉ ዐውቃለሁ። በመስክ የሚገኙ እንስሶች ሁሉ የእኔ ናቸው። **12** ብራብ እንኳ ለአንተ አልናገርም ዓለምና በውስጧ ያለው ሁሉ የእኔ ነውና። **13** የኮርማዎችን ሥጋ እበላለሁን? ወይስ የፍየሎችን ደም እጠጣለሁን? **14** የምስጋና መሥዋዕት ለእግዚአብሔር አቅርብ፤ ስእለትህንም ለልዑል አምላክ ክፈል። **15** በመከራ ቀን ጥራኝ እኔ እታደግሃለሁ፤ አንተም ታከብረኛለህ። **16** ዐመፀኛውን እግዚአብሔር እንዲህ ይለዋል ሕጌን ለማነብነብ፣ ኪዳኔንም በአፍህ ለመናገር ምን መብት አለህ? **17** ትምህርቴን ጠልተሃል፤ ቃሌንም ወደ ኃላህ ጥለሃል። **18** ሌባውን ባየህ ጊዜ ከእርሱ ጋር ሮጥህ፣ ዕድል ፈንታህንም ከአመንዝሮች ጋር አደረግህ። **19** አፍህን ለክፋት፣ አንደበትህንም ሸንገላ ለመናገር አዋልህ። **20** ተቀምጠህ ወንድምህን አማኸው የእናትህንም ልጅ ስም አጠፋህ። **21** ይህን ሁሉ ስታደርግ ዝም አልሁህ ስለዚህ እኔም እንዳንተው የሆንሁ መሰለህ። አሁን ግን ፊት ለፊት ነገርህን ገልጬ እገሥጽሃለሁ። **22** እናንት እግዚአብሔርን የምትረሱ ይህን አስተውሉ፤ አለበለዚያ ብትንትናችሁን አወጣለሁ! የሚያስጥላችሁም የለም! **23** የምስጋና መሥዋዕት የሚያቀርብልኝ ያከብረኛል፤ መንገዱን ቀና ለሚያደርግ የእግዚአብሔር ማዳን አሳየዋለሁ።

Psalms 50:1

የአሳፍ መዝሙር
“ይህ አሳፍ የጻፈው መዝሙር ነው”

ኃያሉ አምላክ፣ እግዚአብሔር
ደራሲው ስለ እግዚአብሔር ለመናገር የተለያዩ ሦስት ስሞችን ይጠቀማል።

ምድርን ጠርቷል
እዚህ ጋ፣ “መሬት” የሚለው ቃል በምድር ላይ የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታል። አ.ት፡ “ሰዎችን ሁሉ ጠርቷል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከፀሐይ መውጫ እስከ መግቢያው ድረስ
ይህ ሐረግ ፀሐይ የምትወጣበትን የምስራቅ አቅጣጫና የምትገባበትን የምዕራብ አቅጣጫ ያመለክታል። ጸሐፊው በምድር ላይ ሁሉን ስፍራ እንዲወክል እነዚህን ሁለት ጽንፎች ይጠቀማል። አ.ት፡ “በምድር ላይ በሁሉም ስፍራ” (See: Merism)

የውበት መደምደሚያ ጽዮን
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “ውበቷ ፍጹም የሆነ ጽዮን” ወይም 2) “እጅግ የተዋበችው ከተማ ጽዮን” የሚሉት ናቸው።

እግዚአብሔር አበራ
ጸሐፊው እግዚአብሔርን እንደሚያበራ ብርሃን አድርጎ ይናገራል። ይህ ሰዎች ስለ ክብሩ እንዲያውቁ እግዚአብሔር እንደሚያደርግ ያመለክታል። አ.ት፡ “የእግዚአብሔር ክብር እንደ ብርሃን ያበራል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 50:3

ዝም አይልም
ጸሐፊው አዎንታዊው ንግግር ላይ አጽንዖት ለመስጠት አሉታዊውን ይጠቀማል። አ.ት፡ “ሁሉም ሊሰማው እንዲችል አድርጎ ይናገራል” (ምጸት የሚለውን ተመልከት)

በፊቱ እሳት ይበላል
ይበላቸው ይመስል ጸሐፊው የሚናገረው ነገሮችን ስለሚያቃጥል እሳት ነው። አ.ት፡ “በፊት ለፊቱ እሳት ይቃጠላል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ብርቱ ዐውሎ ነፋስም በዙሪያው ነው
“ታላቅ ዐውሎ ነፋስ በዙሪያው አለ”

በላይ ያሉ ሰማያትንና ምድርን ይጠራል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ በሚፈርድበት ጊዜ በሰማይና በምድር ላይ የሚኖሩትን ሁሉ ምስክሮች እንዲሆኑ ይጠራቸዋል ወይም 2) እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ በሚፈርድበት ጊዜ ልክ እንደ ሰዎች ምስክር እንዲሆኑ ለሰማይና ለምድር ይናገራል የሚሉት ናቸው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

Psalms 50:6

ሰማያት ያውጃሉ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) ጸሐፊው “ሰማያት” በሚለው ቃል በዚያ የሚኖሩትን መላእክት ለማመልከት ይጠቀማል ወይም 2) ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር ጽድቅ እንደሚመሰክር ሰው በመቁጠር ስለ “ሰማያት” ይናገራል የሚሉት ናቸው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

Psalms 50:7

ስለ መሥዋዕቶችህ አልነቅፍህም
“እነቅፍሃለሁ፣ ስለ መሥዋዕቶችህ ግን አይደለም”። እግዚአብሔር የሚወቅሳቸው በመሥዋዕቶቻቸው ምክንያት እንዳልሆነ ያስታውቃቸዋል።

መንቀፍ
አንድ ሰው የማይገባውን ነገር እንዳደረገ ለእርሱ መንገር

የሚቃጠሉ መሥዋዕቶችህ ሁልጊዜ በፊቴ ናቸው
እግዚአብሔር ስለ መሥዋዕታቸው ለምን እንደማይወቅሳቸው ይኼ ያብራራል። “ሁልጊዜ በፊቴ ናቸው” የሚለው ሐረግ በእግዚአብሔር መገኘት ውስጥ መሆንን የሚያመለክት ሲሆን ትርጉሙም የእርሱ የሆነው ሕዝብ የሚቃጠሉ መሥዋዕቶችን ሁልጊዜ እያቀረቡለት ነው የሚል ይሆናል። አ.ት፡ “እናንተ ሁልጊዜ የሚቃጠል መሥዋዕት እያቀረባችሁልኝ ነው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Psalms 50:9

በረት
በጎችና ፍየሎች የሚጠበቁበት፣ ዙሪያው የታጠረ አካባቢ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በሺህ ኮረብታ ላይ ያሉ የቀንድ ከብቶች
“በሺህ ኮረብታዎች ላይ” የሚለው ሐረግ በአጠቃላይ የእግዚአብሔር የሆኑትን የቀንድ ከብቶች ቁጥር አይወክልም። ቁጥሩ የተጋነነ ሲሆን በዓለም ላይ ያሉት የቀንድ ከብቶች ሁሉ የእግዚአብሔር ስለመሆናቸው አጽንዖት ይሰጣል። ቀደም ብሎ ካለው ቁጥር ግሥ ሊጨመርበት ይችላል። አ.ት፡ “በዓለም ላይ ያሉት የቀንድ ከብቶች ሁሉ የእኔ ናቸው” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እና Ellipsis የሚለውን ተመልከት)

አንድ ሺህ ኮረብታዎች
“1000 ኮረብታዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ወፎችን ሁሉ አውቃቸዋለሁ
እዚህ ጋ “አውቃለሁ” የሚለው ቃል ባለቤትነትን ያመለክታል። አ.ት፡ “ወፎች ሁሉ የእኔ ናቸው” (የአነጋገር ዘይቤ፣ Assumed Knowledge እና Implicit Information የሚለውን ተመልከት)

Psalms 50:12

ቢርበኝም እንኳን
ይህ እግዚአብሔር ስለማይቆጣ ሊሆን ያልቻለን አንድን ነገር ያብራራል። (See: Hypothetical Situations)

የኮርማዎችን ሥጋ እበላለሁ ወይስ የፍየሎችን ደም እጠጣለሁ?
እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች እንደማያደርግ፣ በመሆኑም መሥዋዕታቸው እንደማያስፈልገው አጽንዖት ለመስጠት ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ይጠይቃል። አ.ት፡ “የኮርማዎችን ሥጋ አልበላም ወይም የፍየሎችን ደም አልጠጣም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

Psalms 50:14

ለእግዚአብሔር አቅርብ
እዚህ ጋ እግዚአብሔር የሚያመለክተው ወደ ራሱ ነው። አ.ት፡ “አቅርብልኝ” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

ስእለትህን ለልዑሉ ክፈል
ጸሐፊው አንድ ሰው ለእግዚአብሔር የሚከፍለው ገንዘብ በሚመስል መልኩ ስለ “ስእለት” ይናገራል። አ.ት፡ “ለልዑሉ ስእለትህን ፈጽም” ወይም “ለልዑሉ ለማድረግ ቃል የገባኸውን አድርግ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በመከራ ቀን
እዚህ ጋ፣ “ቀን” የሚለው ቃል የትኛውንም የጊዜ ክፍል የሚያመለክት ነው። አ.ት፡ “መከራ በሚገጥምህ ጊዜ ሁሉ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Psalms 50:16

ለክፉው ሰው ግን እግዚአብሔር እንዲህ ይለዋል
እዚህ ጋ፣ እግዚአብሔር ገና እየተናገረ ነው፣ ስለ ራሱ የሚናገረውም በሦስተኛ መደብ አድርጎ ነው። አ.ት፡ “ለክፉው ግን እንዲህ እለዋለሁ” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

ለክፉው ሰው
“ክፉ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ክፉ የሆኑትን ሰዎች በአጠቃላይ ነው። አ.ት፡ “ለክፉ ሰዎች” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

ቃሌን ወዲያ ትጥላለህና . . . ሕጌን ለማወጅ ምን መብት አለህ?
እግዚአብሔር ክፉ ሰዎችን ለመውቀስ ይህንን ጥያቄ ይጠቀምበታል። ይህ ጥያቄ ወደ ንግግር ሊቀየር ይችላል። አ.ት፡ “ትምህርቴን ስለምትጠላና ቃሌን ወዲያ ስለምትጥል ሕጌንና ቃል ኪዳኔን ማወጅህ ትርጉም አይኖረውም” ወይም “ሕጌን ማወጅ ለአንተ ተገቢህ አይደለም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

በአፍህ ቃል ኪዳኔን መውሰድህ
ክፉ ሰዎች የቃል ኪዳን ቃሉን ማነብነባቸውን እግዚአብሔር ኪዳኑን በአፋቸው እንዳስቀመጡት አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “ስለ ቃል ኪዳኔ መናገርህ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ቃሌን ወዲያ ጥለሃል
ክፉ ሰዎች ቆሻሻን እንደሚጥሉ እርሱ የሚናገረውን መጣላቸውን እግዚአብሔር ይናገራል። አ.ት፡ “እኔ የምናገረውን ጥለሃል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 50:18

ከእርሱ ጋር ትስማማለህ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) የሌባውን ተግባር ያጸድቃሉ። አ.ት፡ “ታጸድቁታላችሁ” ወይም 2) በተግባራቸው ሌባውን ይተባበሩታል። አ.ት፡ “ትተባበሩታላችሁ” የሚሉት ናቸው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

አፍህን ለክፋት ሰጠህ
ክፉ ነገርን ስለሚናገር ሰው፣ የዚያ ሰው አፍ፣ ክፉ ነገርን እንዲያደርግ ለሚልከው ለእርሱ መልዕክተኛ እንደሚሆን እግዚአብሔር ይናገራል። አ.ት፡ “አንተ ሁሌም የምትናገረው ክፉ ነገርን ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና Synec- doche የሚለውን ተመልከት)

ምላስህ ማታለልን ይገልጣል
“ምላስ” የሚለው ቃል የሚወክለው ተናጋሪውን ሰው ነው። አ.ት፡ “አንተ ሁልጊዜ ትዋሻለህ” (See: Synecdoche)

ተቀምጠህ ወንድምህን አማኽው፤ የገዛ እናትህን ልጅ ስም አጠፋህ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች የተለያየ ቃል ቢጠቀሙም ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። በቤተሰብ አባሎቻቸው ላይ በሐሰት ስለመናገራቸው እግዚአብሔር ይወቅሳቸዋል። (See: Parallelism)

ተቀምጠህ ተናገርክ
በአንድ ሰው ላይ “ተቀምጠህ ተናገርክ” ማለት ይህ ሰው ስለሌላው ሰው ሆነ ብሎ ክፉ ነገሮችን ያወራል ማለትን ያመለክታል። አ.ት፡ “ሁሌም ስለምትናገርባቸው መንገዶች ታስባለህ” (የአነጋገር ዘይቤ፣ Assumed Knowledge and Implicit Information የሚለውን ተመልከት)

Psalms 50:21

እኔም ልክ እንዳንተው እንደሆንኩ አሰብክ
እግዚአብሔር ክፉ ሰዎችን ሳይገስጻቸው ዝም በማለቱ ምክንያት እያደረጉት ያሉትን እግዚአብሔር እንዳጸደቀላቸው አሰቡ። አ.ት፡ “ልክ አንተ እንደምታደርገው እኔም እንደማደርግ አሰብክ” (See: Assumed Knowledge እና Implicit Information የሚለውን ተመልከት)

መውቀስ
ለአንድ ሰው የማይገባውን በማድረጉ በደለኛ ስለ መሆኑ መንገር

ያደረግከውን ነገር ሁሉ ... አምጣ
ያደረጉትን ክፉ ነገር ሁሉ እግዚአብሔር እንደሚዘረዝራቸው ይናገራል። አ.ት፡ “ያደረግከውን ነገር ሁሉ ... ዘርዝር” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በዐይኖችህ ፊት መልካም
እዚህ ጋ “በዐይኖችህ ፊት” መሆን ማለት ሊያዩት በሚችሉበት ቦታ ማለት ነው። ይህ ማለት እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ የሚያቀርበውን ክስ ለመካድ አይችሉም ማለት ነው። አ.ት፡ “ልክ በፊት ለፊታችሁ” ወይም “ልትክዷቸው በማትችሉባቸው ሁኔታዎች” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

እናንተ እግዚአብሔርን የምትረሱ
እግዚአብሔርን የተዉትን ክፉዎች እርሱን እንደረሱት አድርጎ ይናገራል። ስለ ራሱ በሦስተኛ መደብ ይናገራል። አ.ት፡ “እኔን የምትተዉኝ እናንተ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

እሰባብራችኋለሁ
ያደነውን እንደሚበላ አንበሳ እግዚአብሔር ክፉዎችን እንደሚያጠፋቸው ይናገራል። አ.ት፡ “አጠፋችኋለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 50:23

መንገዱን ቀና ለማድረግ ያቅዳል
እግዚአብሔር አንድ ሰው የሚኖርበትን የሕይወት አኳኋን ሰውዬው እንደሚጓዝበት መንገድ አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “ሕይወቱን በትክክለኛው መንገድ ይመራል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የእግዚአብሔርን ድነት አሳየዋለሁ
የነገር ስም የሆነው “ድነት” እንደ “ማዳን” ተደርጎ ሊነገር ይችላል። እግዚአብሔር በሦስተኛ መደብ ወደ ራሱ ያመለክታል። አ.ት፡ “አድነዋለሁ” (የነገር ስም እና አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 51

1 እግዚአብሔር ሆይ፣ እንደ ቸርነትህ መጠን ማረኝ፤ እንደ ርኅራኄም ብዛት መተላለፌን ደምስስ። **2** በደሌን ፈጽሞ እጠብልኝ ከኃጢአቴም አንጻኝ። **3** መተላለፌን ዐውቃለሁና ኃጢአቴም ዘወትር በፊቴ ነው። **4** አንተን፣ በእርግጥ አንተን ብቻ በደልሁ ስትናገር ትክክል ነህ፤ ስትፈርድም ትክክል ነህ። **5** ስወለድ ጀምሮ በደለኛ ነህ ገና እናቴም ስትወልደኝ ኃጢአተኛ ነኝ። **6** እነሆ፣ አንተ ልቤ ውስጥ እውነትን ትሻለህ ስለዚህ ጥልቅ ጥበብን በውስጤ አስተምረኝ። **7** በሂሶጵ እርጨኝ እኔም እነጻለሁ። እጠበኝ፤ ከበረዶም ይልቅ እነጻለሁ። **8** ያደቀቅሃቸው አጥንቶቼ ደስ እንዲላቸው ደስታንና ሐሤትን አሰማኝ። **9** ፊትህን ከኃጢአቴ መልስ፣ በደሌን ሁሉ ደምስስልኝ። **10** አምላኬ ሆይ፣ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ ቀና የሆነውንም መንፈስ በውስጤ አድስ **11** ከፊትህ አትጣለኝ ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ አትውሰድብኝ። **12** የማዳንህን ደስታ መልስልኝ በእሺታ መንፈስም ደግፈኝ ያዘኝ። **13** በዚያ ጊዜ፣ ለሕግ ተላላፊዎች መንገድህን አስተምራለሁ። ኃጢአተኞችም ወደ አንተ ይመለሳሉ። **14** የድነቴ አምላክ ሆይ፣ ደም አፍሳሽነቴን ይቅር በል አንደበቴም በደስታ ስለ ጽድቅህ በእልልታ ይዘምራል። **15** ጌታ ሆይ፣ ከንፈሮቼን ክፈት አፌም ምስጋናህን ያውጃል። **16** መሥዋዕትን ብትወድ ኖሮ፣ እሰጥህ ነበር፤ የሚቃጠል መሥዋዕትም ደስ አያሰኝህም። **17** የእግዚአብሔር መሥዋዕት የተሰበረ መንፈስ ነው አንተ፣ የተሰበረውን የተዋረደውን መንፈስ አትንቅም። **18** በበጐነትህ ለጽዮን መልካም አድርግ የኢየሩሳሌምንም ቅጥሮች ሥራ። **19** በዚያ ጊዜ የጽድቅ መሥዋዕት፣ የሚቃጠል መሥዋዕትና ፈጽሞ የሚቃጠል መሥዋዕት ደስ ያሰኝሃል። እኛም በመሠዊያህ ላይ እንደ ገና ኮርማዎችን እናቀርባለን።

Psalms 51:1

ለሙዚቀኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”

የዳዊት መዝሙር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) መዝሙሩን ዳዊት ጽፎታል ወይም 2) መዝሙሩ የሚመለከተው ዳዊትን ነው ወይም 3) መዝሙሩ የዳዊትን መዝሙሮች ዘይቤ የተከተለ ነው የሚሉት ናቸው።

ነቢዩ ናታን ወደ እርሱ በመጣ ጊዜ
ናታን ወደ ዳዊት በመጣ ጊዜ ያደረገው ነገር በግልጽ ሊነገር ይችላል፣ ምክንያቱም ይህ መዝሙር ለዚያ ምላሽ ነውና። አ.ት፡ “ነቢዩ ናታን ወደ ዳዊት መጥቶ በገሰጸው ጊዜ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ከቤርሳቤህ ጋር ከተኛ በኋላ
“ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር ከተኛ በኋላ”

ስለ ቃል ኪዳን ታማኝነትህ
የነገር ስም የሆነው “ታማኝነት” እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “አንተ ለኪዳንህ ታማኝ ስለሆንክ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

እጅግ ብዙ ስለሆኑት ምሕረትን የተሞሉ ሥራዎች
“እጅግ ብዙ የምሕረት ሥራዎችን ታደርጋለህና”

መተላለፌን ደምስሰው
ኃጢአትን ይቅር ማለት 1) እንደ መደምሰስ ወይም 2) በጽሑፍ የተመዘገበውን ኃጢአት እንደ መሰረዝ ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “አንድ ሰው አንድን ነገር ጠርጎ እንደሚያስወግደው ኃጢአቴን ይቅር በለኝ” ወይም “አንድ ሰው የተመዘገበውን ኃጢአት እንደሚሰርዝ ኃጢአቴን እርሳው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከበደሌ ፈጽመህ እጠበኝ ... ከኃጢአቴ አንጻኝ
እነዚህ ሁለቱም ሐረጎች የሚሉት አንድ ነገር ነው። (See: Parallelism)

ከበደሌ ፈጽሞ እጠበኝ
በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ማግኘት ንጹሕ እንደ መሆን ተደርጎ ተነግሯል። እግዚአብሔር የሰዎችን ኃጢአት ይቅር በማለት ተቀባይነት እንዲኖራቸው ያደርጋል። አ.ት፡ “ኃጢአቴን ሁሉ እጠብልኝ” ወይም “በአንተ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረኝ ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር በለኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ፈጽሞ
ሙሉ በሙሉ፣ ጨርሶ

ከኃጢአቴ አንጻኝ
በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ማግኘት ንጹሕ እንደ መሆን ተደርጎ ተነግሯል። እግዚአብሔር የሰዎችን ኃጢአት ይቅር በማለት ተቀባይነት እንዲኖራቸው ያደርጋል። አ.ት፡ “ከኃጢአቴ አንጻኝ” ወይም “ንጹሕ እንድሆን ኃጢአቴን ይቅር በለኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 51:3

ኃጢአቴ ሁልጊዜ በፊቴ ነው
ኃጢአቱን ለመርሳት አለመቻሉ ሁልጊዜ ሊያየው በሚችልበት በፊት ለፊቱ እንዳለ ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “ስለ ኃጢአቴ ሁልጊዜ አውቃለሁ” ወይም “ኃጢአቴን ልረሳው አልችልም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በፊትህ ክፉ የሆነውን
እዚህ ጋ “ፊት” የሚለው ቃል የሚወክለው ፍርድን ነው። እግዚአብሔር የዳዊትን ድርጊት ተመልክቶ አልተቀበለውም። አ.ት፡ “አንተ ክፉ ነው ያልከውን” ወይም “አንተ ክፉ እንደሆነ የቆጠርከውን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 51:5

እይ፣ የተወለድኩት በአመፅ ነው ... እይ፣ አንተ ታማኝነትን ትፈልጋለህ
እዚህ ጋ፣ ሁለቱ የ “እይ” አጠቃቀሞች ትኩረታችንን በሁለቱ ሁኔታዎች መካከል ወዳለው ንጽጽር ይስቡታል። አ.ት፡ “በእውነት እኔ የተወለድኩት በአመፅ ነው ... አንተ ግን ታማኝነትን ትፈልጋለህ”

እይ፣ የተወለድኩት በአመፅ ነው ... እናቴ እንደ ፀነሰችኝ በኃጢአት ውስጥ ነበርኩኝ
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚሉት አንድ ነገር ሲሆን በአንድ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት አጽንዖት ለመስጠት ነው። (See: Paral- lelism)

የተወለድኩት በአመፅ ነው
ኃጢአተኛ መሆን በደለኛ እንደመሆን ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “በተወለድኩ ጊዜ ወዲያው ኃጢአተኛ ሆንኩኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እናቴ እንደ ፀነሰችኝ በኃጢአት ውስጥ ነበርኩኝ
ኃጢአተኛ መሆን በኃጢአት ውስጥ እንደመሆን ተቆጥሮ ተነግሯል። አ.ት፡ “እናቴ በፀነሰችኝ ጊዜ እንኳን እኔ ኃጢአተኛ ነበርኩ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በውስጡ ማንነቴ ታማኝ እንድሆን ትፈልጋለህ
“ውስጣዊ ማንነት” የሚወክለው 1) የሰውየውን ፍላጎት ወይም 2) ሙሉዉን ሰው ነው። አ.ት፡ “ታማኝነትን እንድመኝ ትፈልጋለህ” ወይም “ታማኝ እንድሆን ትፈልጋለህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና Synecdoche የሚለውን ተመልከት)

Psalms 51:7

አንጻኝ ... እነጻለሁ ... እጠበኝ ... ከበረዶ ይልቅ ነጭ እሆናለሁ
በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ማግኘት ንጹሕ ወይም ነጭ እንደመሆን ተቆጥሮ ተነግሯል። እግዚአብሔር የሰዎችን ኃጢአት ይቅር በማለት ተቀባይነት እንዲኖራቸው ያደርጋቸዋል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በሂሶጵ አንጻኝ
ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር ሲናገር፣ እርሱን ለእግዚአብሔር ለማቅረብ ውሃ እንደሚረጭበት ካህን አድርጎ ይገልጸዋል። አ.ት፡ “ውሃውን በሂሶጵ ነክረህ በእኔ ላይ በመርጨት ተቀባይነት እንዲኖረኝ አድርገኝ” ወይም “በአንተ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረኝ ኃጢአቴን ይቅር በለኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሂሶጵ
ይህ ካህናት ለማንጻት ሥርዓት፣ ይኸውም ለእግዚአብሔር ተቀባይነት እንዲኖራቸው ለማድረግ፣ በሰዎች ወይም በሌሎች ነገሮች ላይ ውሃ ወይም ደም ለመርጨት የሚጠቀሙበት ተክል ነው። (See: የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)

ከበረዶ ይልቅ ነጭ
ኃጢአት የሌለበት መሆን ነጭ እንደ መሆን ተቆጥሯል። አ.ት፡ “እጅግ፣ በጣም ነጭ” (See: Simile)

ደስታና ሐሴት
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ቃላት የሚሉት አንድ ነገር ሆኖ አስደሳች ነገሮችን ለመስማት ባለው ምኞት ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ። (See: Doublet)

የሰበርካቸው አጥንቶቼ ደስ ይሰኙ ዘንድ
ስለ ተሰማው አስከፊ ሐዘን ሲገልጽ አጥንቶቹ እንደተሰበሩ አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “በውሳጣዊው ማንነቴ ላይ የከፋ ሐዘን እንዲደርስብኝ አድርገሃልና። እንደገና ደስ ይበለኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከኃጢአቴ ፊትህን መልስ
ስለ አንድ ሰው ኃጢአት ማሰብ ኃጢአቱን እንደ ማየት ሆኖ ተነግሯል። ይቅር ማለት ወይም ኃጢአቱን ለማሰብ አለመፍቀድ ለማየትም እንዳለመፍቀድ ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ኃጢአቴን አትመለከት” ወይም “ኃጢአቴን አታስታውሰው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ኃጢአቴን ሁሉ ደምስስልኝ
የአንድን ሰው ኃጢአት ይቅር ማለት ወይም ለማሰብ አለመፍቀድ 1) እንደ መደምሰስ ወይም 2) በጽሑፍ የተመዘገበውን ኃጢአት እንደ መሰረዝ ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ 1) “አንድ ሰው አንድን ነገር ጠርጎ እንደሚያስወግደው ኃጢአቴን ይቅር በለኝ” ወይም “አንድ ሰው የተመዘገበውን ኃጢአት እንደሚሰርዝ ኃጢአቴን እርሳው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 51:10

በውስጤ ንጹህ ልብን ፍጠርልኝ
እዚህ ጋ፣ “ልብ” ምኞትንና ስሜትን ይወክላል። ለእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ መሰጠትና መታዘዝ ንጹሕ ልብ እንዳለው ሰው ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ሙሉ በሙሉ ለአንተ የተሰጠ ሰው አድርገኝ” ወይም “ሁልጊዜ አንተን ለመታዘዝ እንድፈልግ አድርገኝ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ትክክለኛውን መንፈስ በውስጤ አድስ
እዚህ ጋ “መንፈስ” የሚወክለው የዳዊትን ጠባይና ምኞት ነው። አ.ት፡ “ጠባዬን ትክክለኛ አድርገው” ወይም “ሁልጊዜ ትክክል የሆነውን እንዳደርግ አድርገኝ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከሀልዎትህ አታርቀኝ
“ከአንተ ተለይቼ እንድሄድ አታስገድደኝ”። በእግዚአብሔር የተተወ መሆን ከእርሱ ተለይቶ እንዲሄድ እንደመገደድ ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ከሕዝብህ እንደ አንዱ አትተወኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 51:12

ደግፈኝ
“ከፍ አድርገኝ” ወይም “አግዘኝ”

መንገድህን
“ሰዎች እንዲኖሩት የምትፈልገውን መንገድ” ወይም “ሰዎች እንዲያደርጉት የምትፈልገውን”

ተላላፊዎች ... ኃጢአተኞች
እዚህ ጋ፣ እነዚህ ሁለት ቃላት የሚያመለክቱት አንዱን ዓይነት ሰዎች ነው።

Psalms 51:14

ደም ከማፍሰስ
ይህ ሐረግ ሌላውን ሰው መግደልን ያመለክታል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ጌታ ሆይ፣ ከንፈሮቼን ክፈታቸው፣ አፌም ምስጋናህን ይናገራል
እዚህ ጋ፣ ሰውዬው በ”አፍ” ተወክሏል። መናገር መቻል እንደ ከንፈሮች መከፈት ተነግሯል። እዚህ ጋ መናገር አለመቻል በኃጢአት ምክንያት በደለኛና መከላከል የማይችል የመሆን ምልክት ነው። አ.ት፡ “ጌታ ሆይ፣ መናገር እንድችል አድርገኝ፣ እኔም አመሰግንሃለሁ” (See: Synecdoche)

በመሥዋዕት ደስ አትሰኝም ... የሚቃጠል መሥዋዕትም አያስደስትህም
ይህ ማለት እግዚአብሔር ከእነዚህ ነገሮች ይልቅ በይበልጥ የሚፈልገው ነገር አለ። አ.ት፡ “አንተን ለማስደሰት መሥዋዕት በቂ አይደለም... አንተ ከሚቃጠል መሥዋዕት ይልቅ አብልጠህ የምትፈልገው ነገር አለ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

Psalms 51:17

የእግዚአብሔር መሥዋዕት
“እግዚአብሔርን የሚያስደስት መሥዋዕት”

የተሰበረ መንፈስ
የተሰበረ መንፈስ ትሁት ጠባይን ይወክላል። አ.ት፡ “ትህትና” ወይም “ትሁት የሆነ ሰው” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የተሰበረና የተጸጸተ ልብ
ትሁት መሆንና ስለ ኃጢአት ማዘን የተሰበረና የተጸጸተ ልብ እንዳለው ሰው መሆን ተደርጎ ተነግሯል። ልብ ስሜትንና ፈቃድን ይወክላል። አ.ት፡ “ሀዘንና ትህትና” ወይም “ስለ ኃጢአቱ የሚያዝንና ትሁት የሆነ ሰው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የኢየሩሳሌምን ግንቦች አድስ
የአንድ ከተማ ግንቦች ከተማይቱንና በውስጧ የሚኖሩትን ሰዎች ይጠብቃሉ። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “የኢየሩሳሌምን ግንቦች እንድናድስ አስችለን” ወይም 2) “ኢየሩሳሌምን ጠብቃትና አበርታት” የሚሉት ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሕዝባችን በመሰዊያህ ላይ ኮርማዎችን ያቀርባሉ
ኮርማ ወደ በሬነት እያደገ ያለ ነው። እግዚአብሔር በሰጠው መመሪያ መሠረት
ኮርማዎች አብዛኛውን ጊዜ ለመሥዋዕት የሚቀርቡ እንስሶች ናቸው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 52

1 ኃያል ሆይ፣ ሁከት በመፍጠር ለምን ትኩራለህ? የእግዚአብሔር ኪዳን ታማኝነት ዕለት ዕለት ነው። **2** አንደበትህ እንደ ሰላ ምላጭ ጥፋትን ያውጠነጥናል። **3** ከመልካም ይልቅ ክፋትን፣ እውነትን ከመናገር ይልቅ ሐሰትን ወደድህ። **4** አንተ አታላይ አንደበት ሆይ፣ ሌሎችን የሚያጠፋ ቃል ወደድህ። **5** ስለዚህ እግዚአብሔር ለዘላለም ያጠፋሃል ይነጥቅሃል፤ ከድንኳንህም መንጥቆ ያወጣሃል፤ ከሕያዋን ምድር ይነቅልሃል። **6** ጻድቃን ይህን ዐይተው ይፈራሉ እንዲህ እያሉም ይሥቁበታል፤ **7** «ተመልከቱ፣ እግዚአብሔርን መጠጊያ ያላደረገ፣ ነገር ግን በሀብቱ ብዛት የተመካ በክፋቱም የበረታ ያ ሰው እነሆ!» **8** እኔ ግን በእግዚአብሔር ቤት እንደ ለመለመ የወይራ ዛፍ ነኝ፤ ከዘላለም እስከ ዘላለም፣ በእግዚአብሔር ምሕረት እታመናለሁ። **9** ስላደረግኸው ነገር ለዘላለም አመሰግንሃለሁ፤ ስምህ መልካም ነውና ስምህን ተስፋ አደርጋለሁ፤ በቅዱሳንም መካከል አመሰግንሃለሁ።

Psalms 52:1

ለሙዚቀኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”

ማሺል
ይህ ምናልባት አንድን ዓይነት የሙዚቃ ስልት ያመለክት ይሆናል። ይህንን በመዝሙር 32፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ዶይቅ ... አቢሜሌክ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

አንተ ኃያል ሰው፣ ችግር በመፍጠርህ ለምን ትኩራራለህ?
ይህ ጥያቄ ዳዊት ችግር በፈጠረው ላይ እንዴት እንደተቆጣ ያሳያል። አ.ት፡ “አንተ ኃያል ሰው፣ ችግር በመፍጠርህ መኩራራት አልነበረብህም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

አንተ ኃያል ሰው
ዳዊት ዶይቅን እንዲህ ብሎ በሚጠራበት ጊዜ ምጸትን ሳይጠቀም አይቀርም። አ.ት፡ “ኃያል እንደሆንክ የምታስብ ሰው ሆይ” (See: Irony)

የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታማኝነት በየቀኑ ይመጣል
ዳዊት፣ ሊመጣ እንደሚችል አንዳች ነገር አድርጎ የሚናገረው ስለ እግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታማኝነት ነው። የነገር ስም የሆነው “ታማኝነት” እንደ ቅጽል ወይም ተውሳከ ግሥ ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር የሰጠውን የቃል ኪዳን ተስፋ ለመጠበቅ በየዕለቱ ታማኝ ነው” ወይም “እግዚአብሔር በየዕለቱ ሕዝቡን እንዳንተ ካሉ ክፉ ሰዎች ይጠብቃል” (ዘይቤአዊ አነጋገር፣ Assumed Knowledge፣ Implicit Information እና የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ስል መቁረጫ
ስል ምላጭ

እንደ ስል መቁረጫ ምላስህ በማታለል እየሠራ ጥፋትን ያቅዳል
እዚህ ጋ ምላስ ትልቅ ጉዳት ሊያስከትል ከሚችል ስል መቁረጫ ጋር ተነጻጽሯል። አ.ት፡ “ጥፋትን በምታቅድበትና ሌሎችን በምታታልልበት ጊዜ ምላስህ እንደ ስል መቁረጫ ሰዎችን ይጎዳል” (See: Simile)

ምላስህ
እዚህ ጋ “ምላስህ” ዳዊት እየተናገረው ያለውን ሰው ያመለክታል። አ.ት፡ “አንተ” (See: Synecdoche)

Psalms 52:3

ጽድቅን ከመናገር ይልቅ መዋሸትን
“ትክክል የሆነውን ከመናገር የበለጠ መዋሸትን ትወዳለህ”

Psalms 52:4

ሌሎችን የሚበሉ ቃላቶችን
እዚህ ጋ ሌሎችን የሚጎዱ ቃላት ሰዎችን እንደሚበሉ የዱር እንስሶች ተደርገው ተነግረዋል። አ.ት፡ “ሌሎችን የሚጎዱ ቃላት” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አንተ አታላይ ምላስ ሆይ
ይህ ደራሲው የሚናገረውን ሰውዬ ያመለክታል። አ.ት፡ “የማታለልን ቃል የምትናገር አንተ” ወይም “አንተ ውሸታም” (See: Synecdoche)

መንጥቆ ያወጣሃል ... ይጎትትሃል ... ይነቅልሃል
እነዚህ ሦስቱም ሐረጎች በተለያየ መንገድ “ያስወግድሃል” የሚል ትርጉም አላቸው። (See: Parallelism)

ከሕያዋን ምድር ይነቅልሃል
በምድር ላይ ሕያው ሆኖ መኖር፣ ሥራቸውን በመሬት ውስጥ በሚያደርጉ ተክሎች ተመስለው ስለ ሰዎች ተነግሯል። እግዚአብሔር አንድን ሰው መግደሉ ልክ የተክልን ሥር ከመሬት ውስጥ እንደ መንቀል ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ከሕያዋን ምድር ይወስድሃል” ወይም “ከሕያዋን ሰዎች ጋር በምድር ላይ እንዳትኖር ይገድልሃል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሴላ
ይህ ሰዎች እንዴት መዘመር ወይም የሙዚቃ መሣሪያ መጫወት እንዳለባቸው የተነገራቸው ሙዚቃዊ ቃል ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል ሲጽፉ አንዳንድ ትርጉሞች ደግሞ ይህንን አያካትቱም። (ቃላትን ቅዳ ወይም ተዋስ የሚለውን ተመልከት)

Psalms 52:6

ጻድቃን ይህንን አይተው ይፈራሉ
“ጻድቃን ደግሞ እግዚአብሔር እርሱን ሲያስወግደው ያዩና ይፈራሉ”

እነሆ
“እዩ” ወይም “ስሙ” ወይም “የምነግራችሁን ልብ በሉ”

እግዚአብሔርን መጠጊያው ያላደረገ
እዚህ ጋ “መጠጊያ” የሚወክለው ተከላካይን ነው። አ.ት፡ “እግዚአብሔርን ተከላካዩ ያላደረገ” ወይም “እግዚአብሔር እንዲከላከልለት ያልጠየቀ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 52:8

የለመለመ የወይራ ዛፍ
የለመለመ የወይራ ዛፍ ጠንካራና አስተማማኝ ነው፤ ተሰብሮ አይወድቅም።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እኔ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ እንደ ለመለመ የወይራ ዛፍ ነኝ
ጉዳት በማያገኘውና በአስተማማኝ ሁኔታ ውስጥ መሆን ጠንካራ ዛፍ እንደ መሆን ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “እኔ እንደ ለመለመ የወይራ ዛፍ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ጠንካራ ነኝ” ወይም “በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ስለማመልክ እንደ ለመለመ የወይራ ዛፍ አስተማማኝ ጥበቃ አለኝ” (See: Simile)

በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ
ይህ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ያመለክታል።

ከዘላለም እስከ ዘላለም በእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታማኝነት ላይ እታመናለሁ
የነገር ስም የሆነው “ታማኝነት” ከቅጽል ጋር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እርሱ ለኪዳኑ ታማኝ ስለሆነ ከዘላለም እስከ ዘላለም በእግዚአብሔር እታመናለሁ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

በስምህ ተስፋ አደርጋለሁ፣ እርሱ መልካም ነውና
የእግዚአብሔር ስም ራሱን እግዚአብሔርን ይወክላል። እግዚአብሔርን ተስፋ ማድረግ የሚወክለው እግዚአብሔር እንዲረዳው እርሱን ተስፋ ማድረግን ነው። አ.ት፡ “አንተ መልካም ስለሆንክ ተስፋ አደርግሃለሁ” ወይም “አንተ መልካም ስለሆንክ እንድትረዳን ተስፋ አደርግሃለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 53

1 ሞኝ በልቡ፣ «እግዚአብሔር የለም» ይላል ብልሹዎች ናቸው፤ ጸያፍ ነገርም አድርገዋል መልካም የሚያደርግ አንድ እንኳ የለም። **2** አስተዋዮችና እርሱን የሚፈልጉ ሰዎች ለማግኘት፣ እግዚአብሔር ከሰማይ ወደ ሰው ልጆች ተመለከተ። **3** ሁሉም ወደ ሌላ ዘወር ብለዋል፤ በአንድነትም ብልሹዎች ሆነዋል። መልካም የሚያደርግ አንድ እንኳ የለም። **4** ክፉ አድራጊዎች ከቶ አያስተውሉምን እንጀራ እንደሚበላ ሰው ሕዝቤን የሚበሉ፣ እግዚአብሔርንም ጠርተው የማያውቁት ሰዎች አይማሩምን? **5** ምንም የሚያስፈራ ነገር ሳይኖር እጅግ ፈሩ፤ የዘመቱብህን ሰዎች ዐጥንት እግዚአብሔር በተነ፤ እግዚአብሔር ስለ ናቃቸው እንዲህ ያሉ ሰዎች ያፍራሉ። **6** ምነው ለእስራኤል የሚሆን መዳን ከጽዮን በመጣ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከምርኮ በመለሰ ጊዜ ያዕቆብ ደስ ይለዋል፤ እስራኤልም ሐሤት ያደርጋል!

Psalms 53:1

ለሙዚቀኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”

ለማሃላዝ የተዘጋጀ
ይህ ምናልባት አንድን የሙዚቃ ስልት ዓይነት ያመለክት ይሆናል። (ቃላትን ቅዳ ወይም ተዋስ የሚለውን ተመልከት)

ማሺል
ይህ ምናልባት አንድን የሙዚቃ ስልት ዓይነት ያመለክት ይሆናል። ይህንን በመዝሙር 32፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የሰው ልጆች
ይህ ሰዎችን ሁሉ ያመለክታል።

እርሱን የሚፈልግ
እግዚአብሔርን እንደ ሰው መፈለግ እርሱን እንደ “መፈለግ” ሆኖ ተነግሯል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) እግዚአብሔርን ለማወቅ መፈለግ። አ.ት፡ “እርሱን ለማወቅ የሚፈልግ” ወይም 2) እግዚአብሔርን ማምለክ። አ.ት፡ “እርሱን የሚያመለክ” የሚሉት ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሁሉም ወደ ኋላ ተመልሰዋል
እግዚአብሔርንና ትክክል የሆነውን መተው ወደ ኋላ እንደ መመለስ ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “ሁሉም ትክክል የሆነውን ከማድረግ ወደ ኋላ ተመልሰዋል” ወይም “ሁሉም እግዚአብሔርን ትተውታል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 53:4

እግዚአብሔር ... ለእነዚያ ... ኃጢአትን ለሚሠሩ ማስተዋል የላቸውም?
ሕዝቡ እጅግ ኃጢአተኞች በመሆናቸው ጸሐፊው የተሰማውን ድንጋጤ ለማሳየት ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ እንደ ሁለት ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። “እነዚያ ኃጢአትን የሚሠሩ ሰዎች ምንም ነገር እንደማያውቁ ያህል ያደርጋሉ። እንጀራን እንደሚበሉ ሕዝቤን ይበላሉ፣ እግዚአብሔርንም አይጠሩም!” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

እንጀራን እንደሚበሉ ሕዝቤን የሚበሉ እነዚያ
ሕዝብን ማጥፋት እነርሱን እንደመብላት ተደርጎ ተነግሯል። እንጀራን በሚበሉበት መልኩ ማድረጋቸው የሚያመለክተው ያንን ያደረጉት በቀላሉ ወይም በደለኝነት ሳይሰማቸው መሆኑን ነው። አ.ት፡ “እንጀራን የሚበሉ ያህል በነጻነት ሕዝቤን የሚያጠፉ እነዚያ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና Simile የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር፣ ማንንም በአንተ ላይ የሚሰፍረውን አጥንቱን ይበታትነዋል
የሰዎችን አጥንት መበታተን የሚወክለው እነርሱን መግደልንና በአግባቡ እንዳይቀበሩ አጥንቶቻቸው በሞቱበት ስፍራ ሁሉ እንዲቀመጥ መተውን ነው። “እግዚአብሔር ማንንም በአንተ ላይ የሚሰፍረውን ፈጽሞ ያጠፋዋል፣ አጥንቶቻቸውም በምድር ላይ ተበታትነው ይቀራሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ማንንም በአንተ ላይ የሚሰፍረውን
በሰዎች ላይ መስፈር እነርሱን መውጋትን ይወክላል። የጠላት ሰራዊት ሊወጋው ወደሚፈልገው ሕዝብ በመጓዝ በአቅራቢያው በጊዜያዊነት የሚኖርበትን የጦር ሰፈር ይሠራል። አ.ት፡ “አንተን የሚወጋህ ማንም ቢሆን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 53:6

ምነው የእስራኤል ድነት በመጣ!
እዚህ ጋ “ምነው” የሚለው ቃል ተስፋን ወይም ጸሎትን የሚገልጽ ቃለ አጋኖን ያስተዋውቃል። አ.ት፡ “የእስራኤል ድነት እንደሚመጣ ተስፋ አደርጋለሁ” ወይም “ድነት እንዲመጣ እጸልያለሁ” (ቃለ አጋኖ የሚለውን ተመልከት)

የእስራኤል ድነት ከጽዮን ይመጣል
ድነት መቅደሱ በጽዮን የሆነውን፣ አዳኙን እግዚአብሔርን ይወክላል። አ.ት፡ “የእስራኤል አዳኝ ከጽዮን ይመጣል” ወይም “እግዚአብሔር ከጽዮን ይመጣና እስራኤልን ያድናል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር ሕዝቡን ከምርኮ በሚመልስበት ጊዜ
“እግዚአብሔር የተማረከ ሕዝቡን በሚያድንበት ጊዜ”

ያዕቆብ ደስ ይለዋል፣ እስራኤልም ሐሴትን ያደርጋል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች አንድ ዓይነት ትርጉም አላቸው። (See: Parallelism)

ያዕቆብ
እዚህ ጋ “ያዕቆብ” የሚያመለክተው የያዕቆብ ዘር የሆኑትን እስራኤላውያንን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 54

1 እግዚአብሔር ሆይ፣ በስምህ አድነኝ በኃይልህም ፍረድልኝ። **2** እግዚአብሔር ሆይ፣ ጸሎቴን ስማልኝ የአፌንም ቃል አድምጥ። **3** ባዕዳን ተነሥተውብኛልና ጨካኞችም ነፍሴን ይፈልጓታል እግዚአብሔርንም ከምንም አልቆጠሩትም። ሴላ **4** እነሆ እግዚአብሔር ረዳቴ ነው ጌታም ደግፎ ይይዘኛል። **5** ክፋታቸውን በጠላቶቼ ላይ መልስባቸው በቃልህ ታማኝ ነህና አጥፋቸው። **6** በበጐ ፈቃድ መሥዋዕት አቀርብልሃለሁ መልም ነውና ያህዌ ሆይ፣ ስምህን አመሰግናለሁ። **7** ከመከራ ሁሉ ታድጐኛልና ዐይኔም የጠላቶቼን ውድቀት ለማየት በቅቶአል።

Psalms 54:1

ለሙዚቀኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”

አውታር ባላቸው የሙዚቃ መሣሪያዎች
“ሰዎች ከዚህ መዝሙር ጋር አውታር ያላቸውን የሙዚቃ መሣሪያዎች መጫወት አለባቸው”

ማሺል
ይህ አንድ የሙዚቃ ስልት ዓይነትን ያመለክት ይሆናል። ይህንን በመዝሙር 32፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ዜፋውያን
ከኬብሮን ደቡባዊ ምስራቅ፣ በይሁዳ ተራሮች ላይ ያለው የዚፍ ከተማ ሰዎች። (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ዳዊት በእኛ ዘንድ ተደብቆ የለምን?
ሳዖል ሊያውቀው የሚገባው አስፈላጊ ነገር መሆኑን ለማሳየት ይህ ዓይነቱ ጥያቄ ጥቅም ላይ ውሏል። አ.ት፡ “ዳዊት በእኛ ዘንድ ተደብቋል”። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር ሆይ፣ በስምህ አድነኝ
እዚህ ጋ፣ የእግዚአብሔር ስም ባህርዩን ይወክላል። በተለይም ኃይሉንና ፍትሐዊነቱን ሊወክል ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ሆይ፣ በኃይልህ አድነኝ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በብርታትህ ፍረድልኝ
እዚህ ጋ ለዳዊት መፍረድ፣ እርሱ በደለኛ አለመሆኑን ለሕዝብ ማሳየትን ይወክላል። እግዚአብሔር ዳዊትን ለማዳን ብርታቱን በሚጠቀምበት ጊዜ ዳዊትን በደለኛ አድርጎ እንዳልፈረደበት ሰዎች ያውቃሉ። አ.ት፡ “በደለኛ አለመሆኔን በብርታትህ ለሕዝቡ አሳያቸው” ወይም “እኔን ለመታደግ ኃይልህን በመጠቀም በደለኛ አለመሆኔን ለሕዝቡ አሳያቸው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ለቃሌ ጆሮህን ስጥ
የአንድ ሰው ጆሮ መስጠት መስማትን ይወክላል። አ.ት፡ “ቃሌን ስማ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የአፌን ቃል
እዚህ ጋ ተናጋሪው በአፉ ተወክሏል። አ.ት፡ “ቃሎቼን” ወይም “እኔ የምነግርህን” (See: Synecdoche)

በእኔ ላይ ተነሥተዋል
በአንድ ሰው ላይ መነሣት እርሱን ለማጥቃት መዘጋጀትን ወይም ማጥቃትን ይወክላል። አ.ት፡ “እኔን ለማጥቃት ተዘጋጅተዋል” ወይም “እያጠቁኝ ነው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ጨካኞች ሰዎች
“ምንም ርኅራኄ የሌላቸው ሰዎች”

ሕይወቴን ፈልገዋታል
የአንድን ሰው ሕይወት መፈለግ እርሱን ለመግደል መሞከርን ይወክላል። አ.ት፡ “ሊገድሉኝ ሞክረዋል” ወይም “ሊገድሉኝ ይፈልጋሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔርን በፊታቸው አላስቀመጡትም
እግዚአብሔርን በፊታቸው ማስቀመጥ ለእግዚአብሔር ትኩረት መስጠትን ይወክላል። አ.ት፡ “ለእግዚአብሔር ትኩረት አይሰጡም” ወይም “እግዚአብሔርን ቸል ብለዋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 54:4

ደግፎ የሚይዘኝ
ለዳዊት መከላከልና ጥበቃ ማድረግ ደግፎ እንደ መያዝ ወይም እርሱን እንደ ማገዝ ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “የሚከላከልልኝ” ወይም “ጥበቃ የሚያደርግልኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ለጠላቶቼ በክፋት ይከፍላቸዋል
ቅጣት እንደ ክፍያ ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “ጠላቶቼ ክፋትን ስላደረጉብኝ እርሱም ክፉን ያደርግባቸዋል” ወይም “ጠላቶቼ በእኔ ላይ ያደረጉትን ክፋት በእነርሱም ላይ እንዲደረግ ያደርጋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በታማኝነትህ አጥፋቸው
እዚህ ጋ፣ ዳዊት ስለ እግዚአብሔር ከመናገር ለእግዚአብሔር ወደ መናገር ይቀይረዋል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ ለእኔ ታማኝ ነህና አጥፋቸው”

Psalms 54:6

እግዚአብሔር ሆይ፣ መልካም ነውና ለስምህ ምስጋናን አቀርባለሁ
የእግዚአብሔር ስም እርሱን ይወክለዋል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ መልካም ነህና ምስጋናን አቀርብልሃለሁ” (See: Synecdoche)

ዐይኔ ተመልክቷል
ዐይን ሰውዬውን ይወክላል። አ.ት፡ “ተመልክቻለሁ” (See: Synecdoche)

ዐይኔ በጠላቶቼ ላይ በድል አድራጊነት ተመልክቷል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ጠላቶቹ ድል ሲደረጉ መመልከትን። አ.ት፡ “ጠላቶቼ ድል ሲደረጉ ተመልክቻለሁ” ወይም 2) ጠላቶቹን ድል ማድረጉን። አ.ት፡ “ጠላቶቼን ድል አድርጌአቸዋለሁ” የሚሉት ናቸው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 55

1 እግዚአብሔር ሆይ፣ ጸሎቴን ስማ ልመናዬንም ቸል አትበል። **2** ችግሬ ዕረፍት ነስቶኛልና ወደ እኔ ተመልከት መልስልኝም። **3** ከጠላቶቼ ዛቻ የተነሣ፣ ፈርቼአለሁ፤ በክፉዎችም ጭቄና ደቅቄአለሁ። መከራ አምጥተውብኛልና፤ በቁጣም ያሳድዱኛል። **4** ልቤ በውስጤ ተሸበረብኝ የሞት ድንጋጤም መጣብኝ። **5** ፍርሃትና እንቅጥቅጥ መጡብኝ ሸብርም በረታብኝ። **6** እኔም እንዲህ አልሁ፣ «ምነው የርግብ ክንፍ በኖረኝ! በርሬ ሄጄ ዐርፍ ነበር። **7** እነሆ፣ ኮብልዬ በራቅሁ ነበር በምድረ በዳ በሰነበትሁ ነበር። ሴላ **8** ከዐውሎ ነፋስና ከውሽንፍር ሸሽቼ ወደ መሸሸጊያ ፈጥኜ በደረስሁ ነበር።» **9** ግፍና ሁከት በከተማዪቱ ዐይቻለሁና ጌታ ሆይ ግራ አጋባቸው፤ ቋንቋቸውንም ደበላልቅ! **10** ቀንና ሌሊት ቅጥሮቿን ይዞራሉ ተንኰልና መከራ በውስጧ አሉ። **11** ዐመፃ በመካከልዋ ነው፤ ግፍና አታላይነት ከጐዳናዋ አይጠፋም። **12** የሰደበኝ ጠላት አይደለም ያማ ቢሆን በታገሥኩ ነበር፤ የሚታበይብኝ፣ ራሱንም ቀና ቀና ያደረገብኝ ባላንጣ አይደለም፤ ያማ ቢሆን፣ ከእርሱ በተሸሸግሁ ነበር። **13** ነገር ግን ያን ያደረግህ አንተ እኩያየ፣ ባልንጀራዬና የቅርብ ወዳጄ ነህ። **14** ደስ የሚል ኅብረት በአንድነት ነበረን በሕዝቡ መካከል በእግዚአብሔር ቤት አብረን ተመላልሰን ነበር። **15** በድንገት ሞት ይምጣባቸው ክፋት በመካከላቸው ናትና በሕይወታቸው እያሉ ወደ ሲኦል ይወረዱ። **16** እኔ ግን እግዚአብሔርን እጣራለሁ ያህዌም ያድነኛል። **17** በማታ፣ በጧትና በቀትር አቃሥታለሁ እቃትታለሁም እርሱም ድምፄን ይሰማል። **18** ከእኔ ጋር የሚዋጉት ብዙ ናቸውና እርሱ፣ ከተከፈተብኝ ጦርነት በሰላም ይታደገኛል። **19** ስለማይለወጡና አምኬንም ስለማይፈሩ ከዘላለም እስከ ዘላለም ዙፋኑ ላይ ያለው እግዚአብሔር ሰምቶ ያዋርዳቸዋል። ሴላ **20** ጓደኛዬ የምለው ሰው እጁን በወዳጆቹ ላይ ሰነዘረ፤ ቃል ኪዳኑንም አፈረሰ። **21** አፉ ከቅቤ ይልቅ የለዘበ ነው በልቡ ግን ጦርነት አለ፤ ቃሉ ከዘይት ይልቅ የለሰለሰ ነው ሆኖም የተመዘዘ ሰይፍ ነው። **22** የከበድህን ነገር በያህዌ ላይ ጣል እርሱ ደግፎ ይይዝሃል፤ የጻድቁን መናወጥ ከቶ አይፈቅድም። **23** አንተ ግን እግዚአብሔር ሆይ፣ ዐመፀኞችን ወደ ጥፋት ጕድጓድ ታወርዳቸዋለህ ደም የተጠሙና አታላዮች የዕድሜያቸውን ግማሽ እንኳ አይኖሩም። እኔ ግን በአንተ እታመናለሁ።

Psalms 55:1

ለሙዚቀኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”

አውታር ባላቸው የሙዚቃ መሣሪያዎች
“ሰዎች ከዚህ መዝሙር ጋር አውታር ያላቸውን የሙዚቃ መሣሪያዎች መጫወት አለባቸው”

ማሺል
ይህ አንድ የሙዚቃ ስልት ዓይነትን ያመለክት ይሆናል። ይህንን በመዝሙር 32፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ለጸሎቴ ጆሮህን ስጥ
የአንድ ሰው ጆሮ መስጠት የሚወክለው መስማትን ነው። አ.ት፡ “ጸሎቴን ስማ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከልመናዬ ራስህን አትሰውር
ለልመናው ትኩረትን አለመስጠት ራሱን እንደ ሰወረ ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ልመናዬን ቸል አትበል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከጠላቶቼ ድምፅ የተነሣ
እዚህ ጋ፣ “ድምፅ” የሚወክለው እነርሱ የሚናገሩትን ነው። አ.ት፡ “ጠላቶቼ ከሚናገሩት ነገር የተነሣ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መከራን ያመጡብኛል
መከራ እንዲሆን ማድረግ መከራን እንደማምጣት ተቆጥሮ ተነግሯል። አ.ት፡ “ታላቅ መከራ እንዲደርስብኝ ያደርጋሉ” ወይም “እኔ እንድሰቃይ ክፉ ነገሮችን ያደርጉብኛል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 55:4

ልቤ በውስጤ ይንቀጠቀጣል
እዚህ ጋ፣ “ልብ ይንቀጠቀጣል” ስቃዩንና የሕመም ስሜቱን ያመለክታል። ይህ ስቃይ የሆነበት ከፍርሐት የተነሣ ነው። አ.ት፡ “እጅግ ስለ ፈራሁ እየተሰቃየሁ ነው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የሞት ድንጋጤ በላዬ ወደቀብኝ
በጣም መፍራትን ወይም መሸበርን ለመግለጽ ድንጋጤን በአንድ ሰው ላይ እንደሚወድቅበት አንዳች ነገር ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “እሞታለሁ ብዬ በጣም ፈርቻለሁ” ወይም “እሞታለሁ ብዬ ተሸብሬአለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ፍርሃትና መንቀጥቀጥ መጥተውብኛል
ፈሪ መሆንና መንቀጥቀጥ ልክ ፍርሃትና መንቀጥቀጥ በሰው ላይ እንደሚመጣ እንደ አንዳች ነገር ተቆጥሮ ተነግሯል። አ.ት፡ “በጣም ፈርቼ እንቀጠቀጣለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሸብር ዋጠኝ
የመሸበር ስሜት ሰዎችን እንደሚሸፍናቸው እንደ አንዳች ነገር ተቆጥሮ ተነግሯል። አ.ት፡ “ከባድ ሽብር ይሰማኛል” ወይም “እጅግ ፈርቻለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 55:6

ምነው እንደ እርግብ ክንፍ ብቻ በኖረኝ!
ይህ ጩኸት ጸሐፊው በጣም የተመኘውን ነገር ይገልጻል። አ.ት፡ “እንደ እርግብ ክንፍ እንዲኖረኝ በጣም እመኛለሁ” (See: Exclamations)

በርሬ እሄድ ነበር
“ክንፍ ቢኖረኝ ኖሮ በርሬ እሄድ ነበር”

እነሆ፣ ከዚያ እቅበዘበዝ ነበር
“ይህንን እና ሌላም አደርግ ነበር፤ እቅበዘበዝ ነበር”

ሴላ
ይህ ሰዎች እንዴት መዘመር ወይም የሙዚቃ መሣሪያ መጫወት እንዳለባቸው የተነገራቸው ሙዚቃዊ ቃል ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል ሲጽፉ አንዳንድ ትርጉሞች ደግሞ ይህንን አያካትቱም። (ቃላትን ቅዳ ወይም ተዋስ የሚለውን ተመልከት)

Psalms 55:8

አውሎ ንፋስ
ብርቱ አውሎ ንፋስ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ዋጣቸው
አንድን ነገር ማጥፋት ጨርሶ እንደ መብላት ተደርጎ ተነግሯል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ “የጠላቶቼን ዕቅድ አጥፋው’ ወይም “ጠላቶቼን አጥፋቸው” የሚሉት ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ቋንቋቸውን ደበላልቀው
እዚህ ጋ፣ “ቋንቋ” የሚወክለው ሰዎች እርስ በርሳቸው ይነጋገሩት የነበረውንና በተለይም ክፉ ስለማድረግ ዕቅድ ይነጋገሩ የነበሩትን ያመለክት ይሆናል። ያንን መደበላለቅ የሚወክለው እርስ በርሳቸው እንዳይግባቡ ማድረግን ነው። አ.ት፡ “እርስ በርስ በሚነጋገሩበት ጊዜ አደናግራቸው” ወይም “ዕቅዳቸውን አደናግረው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 55:10

በግምቦቹ ላይ ይወጣሉ
“ግፍና ሁከት በግምቦቿ ላይ ይወጣሉ”። (መዝሙር 55፡9ን ተመልከት) ግፍና ሁከት እንደ ሰዎች ተቆጥረው ተነግሮላቸዋል። ግፍና ሁከትን ስለሚፈጥሩ ሰዎች ይህንን በመናገር መግለጽ ይቻላል። አ.ት፡ “በከተማይቱ ግምቦች ላይ ሰዎች እየተዋጉና እያወኩ ይመላለሳሉ” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

በግምቦቿ ላይ
“በከተማይቱ ግምቦች አናት ላይ”። ከተሞች ከጠላቶቻቸው የሚጠበቁባቸው ጠንካራ ግምቦች በዙሪያቸው ይኖራቸው ነበር። የትኛውም ጠላት ወደ ከተማይቱ በመምጣት ላይ መሆኑን ለማየት ሰዎች በግምቦቹ አናት ላይ መመላለስ ይችሉ ነበር።

ኃጢአትና ተንኮል በመካከሏ ነው
ኃጢአትና ተንኮል እንደ ሰዎች ተቆጥረው ተነግሮላቸዋል። ይህንን፣ ኃጢአትንና ተንኮልን ስለሚያደርጉ ሰዎች በመናገር መግለጽ ይቻላል። አ.ት፡ “በከተማይቱ መካከል ሰዎች ኃጢአትን ይሠራሉ፣ ተንኮልንም ያደርጋሉ” ወይም “በውስጧ ሰዎች በኃጢአት የተሞሉ ነገሮችን ይሠራሉ፣ ችግርም ይፈጥራሉ” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

ተንኮል
ችግር

ክፋት በመካከሏ ነው
ክፋት እንደ ሰው ተቆጥሮ ተነግሮለታል። ይህንን፣ ክፉ ነገሮችን ስላደረጉ ሰዎች በመናገር መግለጽ ይቻላል። አ.ት፡ “በከተማይቱ መካከል ሰዎች ክፉ ነገሮችን ያደርጋሉ” ወይም “ሰዎች በከተማይቱ ውስጥ ያሉትን ነገሮች ያጠፋሉ” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

ግፍና ማታለል ከጎዳናዎቿ አይርቁም
ግፍና ማታለል እንደ ሰዎች ተቆጥረዋል። ይህንን በሌሎች ላይ ግፍ ስለሚያደርጉና ስለሚያታልሉ ሰዎች በመናገር መግለጽ ይቻላል። አ.ት፡ “በከተማይቱ ጎዳናዎች ሰዎች በሌሎች ላይ ግፍና ማታለልን ይፈጽማሉ፣ ከዚያም አይርቁም” ወይም “በከተማይቱ ጎዳናዎች ላይ ሰዎች ሁልጊዜ በሌሎች ላይ ግፍ ይፈጽማሉ፣ ያታልላሉ” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

በጎዳናዎቿ ላይ
ይህ ምናልባት በከተማይቱ ውስጥ ያለውን የገበያ ስፍራ ያመለክት ይሆናል።

Psalms 55:12

ልሸከመው እችል ነበር
ተግሳጽን መታገስና መጽናት እርሱን ይዞ እንደመቆየትና እንደ መሸከም ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ተግሳጹን መታገስ በቻልኩ ነበር” ወይም “ስለ ተግሳጹ እምብዛም አላዝንም ነበር” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ራሱን በእኔ ላይ ቀና አደረገ
ኩሩ መሆንና ሌላውን መሳደብ ራስን በሌላው ላይ ቀና አንደማድረግ ተቆጥሮ ተነግሯል። አ.ት፡ “ሰደበኝ” ወይም “ናቀኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ነገር ግን አድራጊው አንተ ነህ
እርሱን የሚገስጸውና የሚያንጓጥጠው ሰውዬ በዚያ ሆኖ ይሰማው ይመስል ዘማሪው ይናገረዋል። (See: Apostrophe)

እኔ ራሴ፣ ባልንጀራዬና የቅርብ ጓደኛዬ
ይህ ተከፋፍሎ አዲስ ዐረፍተ ነገር ሊጀመር ይችላል። አ.ት፡ “እኔ ራሴ። አንተ ባልንጀራዬና የቅርብ ጓደኛዬ ነበርክ”

እኛ
“እኛ” የሚለው ቃል ዘማሪውንና ጓደኛውን ያመለክታል።

ከተሰበሰበው ጋር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “በአንድነት” ወይም 2) “ከሕዝቡ ጋር” የሚሉት ናቸው።

Psalms 55:15

ሞት በድንገት ይምጣባቸው
ሞት ሰዎችን ሊያጠቃ እንደሚችል ሰው ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ጠላቶቼ በድንገት ይሙቱ” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

ሕያዋን ሳሉ ወደ ሲዖል ይውረዱ
በድንገት መሞት ሰዎች መሞታቸው እንኳን በአግባቡ ሳይረጋገጥ በፍጥነት ወደ ሲዖል እንደሚሄዱ ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “በድንገት ወደ ሲዖል ይሂዱ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ክፋት መኖሪያቸው ነው
ክፋት በሆነ ቦታ ላይ ሊቀመጥ እንደሚችል ነገር ተደርጎ ተነግሯል። የጠላቶቹ የተለመደው ክፋት ከእነርሱ ጋር ወይም አጠገባቸው እንደሚኖር ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “በሚኖሩበት ስፍራ ሁልጊዜ ክፉ ነገሮችን ያደርጋሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እዚያው በመካከላቸው
ይህ ሐረግ፣ ክፋት በጣም በቅርባቸው አለ የሚለውን አሳብ ያጠናክራል። እዚህ ጋ፣ ክፋት በቤቶቻቸው ብቻ ሳይሆን ባሉበት ቦታ ሁሉ እንዳለ ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “ባሉበት ቦታ ሁሉ ክፉ ነገሮችን ሁልጊዜ ያደርጋሉ” ወይም “ባሉበት ቦታ ሁሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 55:16

ለእኔ ግን
ይህ ሐረግ የሚያሳየው ጸሐፊው ስለ አንድ ነገር መናገሩን አቁሞ ስለ ራሱ ሊናገር መሆኑን ነው። አ.ት፡ “እኔ ግን”

ማቃሰት
ሰዎች ወይም እንስሳት በህመማቸው ጊዜ የሚያሰሙት ድምፅ

እርሱ ድምፄን ይሰማኛል
እዚህ ጋ፣ “ድምፅ” የሚወክለው 1) ዘማሪውን ወይም 2) የዘማሪውን ቅሬታና ማቃሰት ይሆናል። አ.ት፡ “እርሱ ይሰማኛል” ወይም “እርሱ ማቃሰቴን ይሰማል” (See: Synecdoche እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሕይወቴ
እዚህ ጋ፣ “ሕይወቴ” የሚወክለው ዘማሪውን ነው። አ.ት፡ “እኔን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የሚዋጉኝ ብዙዎች ነበሩ
“ብዙ ሰዎች ተዋግተውኛል”

የሌሎቹን ግማሽ እንኳን
“ሌሎች ሰዎች ከሚኖሩት ግማሹን እንኳን”

Psalms 55:19

ይሰማቸዋል
“ጠላቶቼን ይሰማቸዋል” ወይም “ጠላቶቼ የሚሉትን ይሰማል”። አንዳንድ ትርጉሞች “ይሰማኛል” ይላሉ።

አዋርዳቸው
እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያዋርዳቸው በግልጽ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ያሸንፋቸዋል፣ ያዋርዳቸዋልም” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

Psalms 55:20

በእነዚያ ላይ እጆቹን አንሥቷል
በሰዎች ላይ እጅን ማንሣት እነርሱን ማጥቃትን ይወክላል። ይህ ሰዎችን አደጋ ላይ ስለ መጣል ወይም እንዲቸገሩ ስለ ማድረግ ለሚነገሩ ነገሮች ዘይቤአዊ አነጋገር ሊሆኑ ይችላሉ። አ.ት፡ “እነዚያን አጥቅቷል” ወይም “እነዚያን ክዷል” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 55:22

ሸክምህን አስቀምጥ
እዚህ ጋ ዘማሪው የሚናገረው ለሌሎች እግዚአብሔርን ለሚፈሩ ሰዎች ነው።

ሸክማችሁን በእግዚአብሔር ላይ አስቀምጡት
እዚህ ጋ፣ ችግሮች ሰዎች እንደሚሸከሟቸው ሸክሞች ተደርገው ተነግረዋል። በችግራችን ጊዜ እግዚአብሔር እንዲረዳን በእርሱ መታመናችን እርሱ ስለ እኛ እንዲሸከማቸው ሸክሞቻችንን በእርሱ ላይ እንደ መጣል ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ችግሮችህን ለእግዚአብሔር ስጠው” ወይም “አንዱ፣ ብርቱ የሆነውን ሰው ‘ሸክሜን ሊሸከምልኝ ይችላል’ ብሎ እንደሚታመነው፣ አንተም በችግሮችህ ሁሉ እግዚአብሔር እንደሚረዳህ ታመነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እርሱ ይደግፍሃል
አንድ ሰው ችግር በሚገጥመው ጊዜ እርሱን መንከባከብ ወይም መርዳት እርሱን እንደ መርዳት ተቆጥሮ ተነግሮለታል። አ.ት፡ “እርሱ ይጠነቀቅልሃል” ወይም “እርሱ ይረዳሃል”

ጻድቁ እንዲንገዳገድ እርሱ በፍጹም አይፈቅድም
አንድ በሆነ ዓይነት አደጋ ክፉኛ የተጎዳ ሰው ለመውደቅ እንደሚንገዳገድ ወይም እንደሚወዛወዝ ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “ጻድቁን ሰው ተንገዳግዶ እንዲወድቅ አይተወውም” ወይም “ጻድቁ ሰው እንዲጠፋ አይተወውም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ ግን
አሁን ደራሲው የሚናገረው ለእግዚአብሔር ነው።

የጥፋት ጉድጓድ
ይህ ምናልባት መቃብርን ወይም ሲዖልን ያመለክታል።

ክፉዉን ወደ ጥፋት ጉድጓድ ውስጥ ያወርደዋል
ይህ ሰዎች እንዲሞቱ ማድረግን ይወክላል። አ.ት፡ “ክፉው እንዲሞት ያደርጋል” ወይም “ክፉ ሰዎች እንዲሞቱና ሙታን ወዳሉበት ስፍራ እንዲሄዱ ያደርጋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ደም የተጠሙና የሚያታልሉ ሰዎች
“የሚዋሹና ሌሎችን ለመግደል የሚፈልጉ ሰዎች” ወይም “አታላይ ነፍሰ ገዳዮች”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 56

1 እግዚአብሔር ሆይ፣ ሰዎች ስለሚያጠቁኝና ጠላቶቼም ቀኑን ሙሉ ስለሚያሳድዱኝ ማረኝ። **2** ጠላቶቼ ቀኑን ሙሉ በላዬ ቆሙ በእብሪት የሚዋጉኝ ብዙ ናቸውና። **3** እኔ ግን ፍርሃት ሲይዘኝ እምነቴን አንተ ላይ አደርጋለሁ **4** ቃሉን በማመሰግው አምላክ በእግዚአብሔር ታምኛሁና አልፈራም ከቶ ሰው ምን ሊያደርገኝ ይችላል? **5** ቀኑን ሙሉ ቃሌን ያጣምማሉ ሐሳባቸው ሁሉ እኔን መጉዳት ነው። **6** ይዶልታሉ፤ ያደባሉ ሕይወቴ ላይ እንደሚያደቡት ሁሉ ርምጃዬንም ይከታተላሉ። **7** አምላክ ሆይ፣ በምንም መንገድ እንዲያመልጡ አታድርጋቸው፤ በቁጣህ ሕዝቦችን አዋርዳቸው። **8** የመንከራተት ቀኖቼን ቆጥረሃል እንባዎቼን በመያዣህ አኑረሃል። ሁሉስ በመጽሐፍህ ያለ አይደለምን? **9** ወደ አንተ በተጣራሁ ቀን ጠላቶቼ ወደ ኋላቸው ይመለሳሉ። በዚህም እግዚአብሔር ከእኔ ጋር መሆኑን በእርግጥ ዐወቅሁ። **10** ቃሉን በማመሰግነው አምላክ ቃሉን በማመመሰግነው ያህዌ **11** በአምላክ ታምኛለሁና አልፈራም፤ ሰው ምን ሊያደርገኝ ይችላል? **12** አምላኬ ሆይ፣ የተሳልሁትን እፈጽማለሁ ለአንተም የምስጋና መሥዋዕት አቀርባለሁ። **13** ነፍሴን ከሞት፣ እግሬን ከመሰናከል አድነሃልና በሕያዋን ብርሃን፣ በእግዚአብሔር ፊት እመላለሳለሁ።

Psalms 56:1

ለሙዚቀኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”

ለዮናስ ኤሌም ሬሆኪም የተዘጋጀ
ይህ ምናልባት መዝሙሩን በሚዘምሩበት ጊዜ ምን ዓይነት የሙዚቃ ስልት ወይም ቅኝት መጠቀም እንዳለባቸው ሳይነግራቸው አይቀርም። አ.ት፡ “’የዮናስ ኤሌም ሬሆኪም’ን ቅኝት በመጠቀም ይህንን መዝሙር ዘምሩ” ወይም “የዮናስ ኤሌም ሬሆኪምን ስልት በመጠቀም ይህንን ዘምሩ”

ዮናስ ኤሌም ሬሆኪም
ይህ ምናልባት “በሩቅ የወርካ ዛፎች ላይ ያለች እርግብ” ማለት ሊሆን ይችላል። ተርጓሚዎች ትርጉሙን መጻፍ ወይም የዕብራይስጡን ቃላት መቅዳት ይኖርባቸው ይሆናል። (የማይታወቁትን ተርጉማቸው እና ቃላትን ቅዳ ወይም ተዋስ የሚለውን ተመልከት)

የዳዊት መዝሙር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) መዝሙሩን ዳዊት ጽፎታል ወይም 2) መዝሙሩ የሚመለከተው ዳዊትን ነው ወይም 3) መዝሙሩ የዳዊትን መዝሙሮች ዘይቤ የተከተለ ነው የሚሉት ናቸው።

ሚችታም
“ሚችታም” የሚለው ቃል ትርጉሙ በእርግጠኝነት አይታወቅም። በምትኩ “መዝሙር” የሚለውን ቃል መጠቀም ይኖርብህ ይሆናል። “ዳዊት የጻፈው መዝሙር ይህ ነው” ተብሎ ሊጻፍ ይችላል። ይህንን በመዝሙር 16፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ፍልስጤማውያን በጌት በያዙት ጊዜ
“ፍልስጤማውያን በጌት በማረኩት ጊዜ”

ከበባቸውን አጠናክረዋል
“ሊወጉኝ በጣም ተጠግተዋል”

ጠላቶቼ ረጋግጠውኛል
የጠላት ብርቱ ጥቃት በእርሱ ላይ በመሄድ ሰውነቱን የሰባበሩት በሚመስል መልኩ ተነግሯል። አ.ት፡ “ጠላቶቼ ክፉኛ እያጠቁኝ ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 56:3

አንተ
“አንተ” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ያመለክታል።

ሰው ምን ሊያደርገኝ ይችላል?
እዚህ ጋ ዘማሪው፣ ሰዎች በከፋ ሁኔታ ለጎዱት ስለማይችሉ እንዳልፈራቸው ለማሳየት ጥያቄው ጥቅም ላይ ውሏል። ይህ ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ሰው ብቻ የሆነ እርሱ ምንም ሊያደርገኝ አይችልም!” ወይም “ሰው ብቻ የሆነ እርሱ ከባድ ጉዳት ሊያደርስብኝ አይችልም!” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ሰው ብቻ የሆነ
“ሰብአዊ ፍጡር” ወይም “ሰዎች”። ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር እንጂ ሰዎች ብርቱዎች አለመሆናቸውን ነው።

Psalms 56:5

ቀኑን ሁሉ
“ሁልጊዜ”

ቃሌን ያጣምማሉ
አንድ ሰው የሚናገረውን ደግሞ መናገር፣ ነገር ግን ትንሽ ለውጥ በማድረግ ሌላ ትርጉም እንዲኖረው ማድረግ ቃላቸውን እንደማጣመም ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ያልተናገርኩትን እንደተናገርኩ አድርገው ይናገራሉ” ወይም “ነገሮቹን እኔ እንደ ተናገርኩ ይናገራሉ፣ ነገር ግን ይዋሻሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእኔ ላይ የሚያስቡት ሁሉ ለክፋት ነው
“በእኔ ላይ ሁልጊዜ ክፉ አሳብ አላቸው” ወይም “ክፉ ነገር ሊያደርጉብኝ ሁልጊዜ ያስባሉ”

እርምጃዬን ይከታተላሉ
ልክ አንድን ሰው ለመያዝ የሚፈልግ፣ ያ ሰው ወዴት እንደሚሄድ እንደሚመለካከት ሁሉ፣ አንድን ሰው ችግር ላይ ለመጣል እርሱ የሚያደርገውን መመልከት ርምጃውን እንደመመልከት ተቆጥሮ ተነግሯል። አ.ት፡ “የማደርገውን ሁሉ ይመለከታሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ልክ ሕይወቴን እንደሚጠባበቋት
አንድን ሰው ለመግደል መጠባበቅ ሕይወቱን እንደ መጠባበቅ ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “እኔን ለመግደል ሲጠብቁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 56:7

ኃጢአትን ሠርተው እንዲያመልጡ አትተዋቸው
ካመለጡ በግልጽ ይከሰሳሉ። አ.ት፡ “ስለ ኃጢአታቸው በአንተ ከመቀጣት እንዲያመልጡ አትተዋቸው” ወይም “ስለሚያደርጉት ክፉ ነገር አንተ በምትቀጣቸው ጊዜ እንዲያመልጡ አትተዋቸው” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሕዝቡን ጣላቸው
ጠላቶችን ማሸነፍ እነርሱን እንደ መጣል ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ሕዝቡን ድል አድርጋቸው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መንከራተቴን ትመዘግባለህ
እግዚአብሔር ስለ ዘማሪው ግድ መሰኘቱ፣ ዘማሪው ለመጽናናት የሚሄድበት ስፍራ ሳይኖረው በስጋት የተመላለሰበትን እያንዳንዱን ጊዜ እግዚአብሔር እንደቆጠረለት ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ብቻዬን ስለ ተንከራተትኩባቸው ጊዜያት ሁሉ አንተ ይገድሃል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ዕንባዬን በጠርሙስህ አስቀምጠው
እግዚአብሔር ለዘማሪው ግድ መሰኘቱ፣ እግዚአብሔር የዘማሪውን ዕንባ በጠርሙስ ውስጥ እንዳስቀመጠ ተደርጎ ተነግሯል። ዕንባ ለቅሶን ይወክላል። አ.ት፡ “ምን ያህል እንዳለቀስኩ ታውቃለህ፣ ስለ እኔም ይገድሃል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በመጽሐፍህ ውስጥ ያሉ አይደሉም?
እግዚአብሔር ለዘማሪው ግድ መሰኘቱ፣ እግዚአብሔር የዘማሪውን የዕንባ ቁጥር በመጽሐፉ ውስጥ እንደጻፈ ተደርጎ ተነግሯል። እግዚአብሔር ለዘማሪው እጅግ እንደሚጠነቀቅለት ለማሳሰብ ጥያቄው ጥቅም ላይ ውሏል። አ.ት፡ “ስለ እነርሱ በመጽሐፍህ ውስጥ ጽፈሃል!” ወይም “ለቅሶዬን ታስታውሳለህ!” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

Psalms 56:9

ወደ ኋላቸው ይመለሳሉ
“ያፈገፍጋሉ” ወይም “ተመልሰው ይሸሻሉ”

እግዚአብሔር ለእኔ ነው
ትርጉሙ እግዚአብሔር ለእርሱ ያደላል ማለት ነው። በዚህ ዐውድ፣ ዘማሪውን ለመጠበቅ እግዚአብሔር ከዘማሪው ጠላቶች ጋር እንደሚዋጋ ያመለክታል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ስለ እኔ ይዋጋል” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ማን ምን ሊያደርግብኝ ይችላል?
እዚህ ጋ ጥያቄው ጥቅም ላይ የዋለው ዘማሪው ብዙም ሊጎዱት ስለማይችሉ ሰዎችን እንደማይፈራቸው ለማሳየት ነው። ይህ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ ‘ሰዎች ምንም ሊያደርጉብኝ አይችሉም!” ወይም “ሰዎች በከፋ ሁኔታ ሊጎዱኝ አይችሉም!” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

Psalms 56:12

ስእለቴን የመፈጸም ኃላፊነት አለብኝ
አንድ ነገር ለማድረግ ግዴታ ውስጥ መሆን፣ መደረግ ያለበት ነገር በሰውየው ላይ እንደ ተቀመጠ ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ለአንተ የገባሁትን ስእለት መፈጸም አለብኝ” ወይም “ላደርገው ቃል የገባሁልህን ማድረግ አለብኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እግሮቼን ከመውደቅ አድነኻቸዋል
እዚህ ጋ እግር የሚወክለው ሰውዬውን ነው። መውደቁ ደግሞ በጠላቶቹ መገደልን ሊወክል ይችላል። አ.ት፡ “ከመውደቅ አድነኸኛል” ወይም “በጠላቶቼ እጅ ከመሞት አድነኸኛል” (Synecdoche የሚለውን ተመልከት)

በእግዚአብሔር ፊት እንድመላለስ
መኖርና በእግዚአብሔር መታየት በእግዚአብሔር ፊት እንደ መመላለስ ተወስዶ ተነግሯል። አ.ት፡ “በእግዚአብሔር ሀልዎት ውስጥ እንድኖር” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በሕያዋን ብርሃን ውስጥ
እዚህ ጋ “የሕያዋን ብርሃን” የሚወክለው ምናልባት ሰዎች በሕይወት እንዲኖሩ እግዚአብሔር የሚያስችላቸው መሆኑን ነው። አ.ት፡ “አንተ በምትሰጠው ሕይወት” ወይም “በሕይወት እንድኖር ስለምታስችለኝ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 57

1 እግዚአብሔር ሆይ ማረኝ አቤቱ ማረኝ የመከራው ጊዜ እስኪያበቃ ድረስ አንተን መጠጊያ አድርጌአለሁና። ጥፋት እስኪያልፍ ድረስ በክንፎችህ እጠለላለሁ። **2** ወደ ልዑል እግዚአብሔር የሚያስፈልገኝን ሁሉ ወደሚሰጠኝ አምላክ እጮኻለሁ። **3** ከሰማይ ልኮ ያድነኛል የሚያስጨንቁኝንም ያዋርዳቸዋል። እግዚአብሔር ፍቅሩንና ታማኝነቱን ይልካል። **4** ነፍሴ በአንበሶች ተከባለች፣ ሊውጡኝ በተዘጋጁ መካከል ወድቄአለሁ። እነዚህ ሰዎች ጥርሳቸው ጦርና ፍላጻ ምሳቸውም የተሳለ ሰይፍ ነው። **5** እግዚአብሔር ሆይ፣ ከሰማያት በላይ ከፍ ከፍ በል ክብርህም በምድር ሁሉ ላይ ይስፋፋ **6** ለእግሬ ወጥመድ ዘረጉ፣ ነፍሴንም አጐበጡአት፤ መንገዴ ላይ ጉድጓድ ቆፈሩ፤ ነገር ግን ራሳቸው ገቡበት። ሴላ **7** ልቤ ጽኑ ነው፤ እግዚአብሔር ሆይ ልቤ ጽኑ ነው እቀኛለሁ፤ እዘምራለሁ። **8** ነፍሴ ሆይ፣ ንቂ በገናና መሰንቆም ተነሡ እኔም በማለዳ እነሣለሁ። **9** ጌታ ሆይ፣ በሕዝቦች መካከል አመሰግንሃለሁ በመንግሥታት መካከል ምስጋና እዘምራለሁ። **10** ዘላለማዊ ፍቅርህ ከሰማያት በላይ ነው ታማኝነትህም እስከ ደመናት ይደርሳል። **11** እግዚአብሔር ሆይ፣ ከሰማያት በላይ ከፍ በል ክብርህም በምድር ሁሉ ላይ ይስፋፋ።

Psalms 57:1

ለሙዚቀኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”

ለአል ታሼዝ የተዘጋጀ
ይህ ምናልባት መዝሙሩን በሚዘምሩበት ጊዜ ምን ዓይነት የሙዚቃ ስልት ወይም ቅኝት መጠቀም እንዳለባቸው ሳይነግራቸው አይቀርም። አ.ት፡ “’የአል ታሼዝን ቅኝት በመጠቀም ይህንን መዝሙር ዘምሩ” ወይም “የአል ታሼዝን ስልት በመጠቀም ይህንን ዘምሩ”

አል ታሼዝ
ይህ “አታጥፋ” ማለት ነው። ተርጓሚዎች ትርጉሙን መጻፍ ወይም የዕብራይስጡን ቃል መቅዳት ይኖርባቸዋል። (የማይታወቁትን ተርጉማቸው እና ቃላትን ቅዳ ወይም ተዋስ የሚለውን ተመልከት)

የዳዊት መዝሙር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) መዝሙሩን ዳዊት ጽፎታል ወይም 2) መዝሙሩ የሚመለከተው ዳዊትን ነው ወይም 3) መዝሙሩ የዳዊትን መዝሙሮች ዘይቤ የተከተለ ነው የሚሉት ናቸው።

ሚችታም
“ሚችታም” የሚለው ቃል ትርጉሙ በእርግጠኝነት አይታወቅም። በምትኩ “መዝሙር” የሚለውን ቃል መጠቀም ይኖርብህ ይሆናል። “ዳዊት የጻፈው መዝሙር ይህ ነው” ተብሎ ሊጻፍ ይችላል። ይህንን በመዝሙር 16፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ከሳዖል ሸሽቶ በዋሻ ውስጥ በነበረ ጊዜ
የዚህ ሐረግ ዓላማ ሁኔታውን በዝርዝር ከሚያስረዱ አንዳንድ መሠረታዊ ነገሮች ጋር በግልጽ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ይህ ዳዊት ዋሻ ውስጥ ከሳዖል ስለተደበቀበት ጊዜ ነው” ወይም “ይህ ንጉሥ ሳዖል ዳዊትን ባሳደደው ጊዜ ዳዊት ዋሻ ውስጥ ስለተደበቀበት ወቅት ነው” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

አንተን መጠጊያዬ አድርጌአለሁ
ጥበቃ ለማግኘት ወደ እግዚአብሔር መሄድ በእርሱ መጠጊያ ማግኘት እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ጥበቃ ለማግኘት ወደ አንተ እመጣለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከለላ ለማግኘት በክንፎችህ ስር እቆያለሁ
ዘማሪው ስለ እግዚአብሔር ሲናገር ጫጩቶቿን በክንፎቿ ስር ከምትሰበስባቸው ወፍ ጋር ያነጻጽረዋል። አ.ት፡ “እንደምትጠብቀኝ እታመንሃለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ይህ ጥፋት እስኪያልፍ ድረስ
የነገር ስም የሆነው “ጥፋት” እንደ “አጥፊ” ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ይህ አጥፊ ማዕበል እስኪያልፍ ድረስ” (የነገር ስም እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 57:2

ሁሉን ነገር የሚያደርግልኝ
ወደ እግዚአብሔር የሚጮኸው ለምን እንደሆነ ይህ ያብራራዋል። “ምክንያቱም” ከሚል ቃል ጋር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ምክንያቱም እርሱ ሁሉን ነገር ያደርግልኛል”

እነዚያን የረጋገጡኝን
የጠላቶቹ ብርቱ ጥቃት በላዩ ላይ በመረማመድ ሰውነቱን እንደ ረጋገጡት ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “በከፋ ሁኔታ ያጠቁኝ እነዚያ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር ምህረቱንና ታማኝነቱን ይልክልኛል
የእግዚአብሔር መሐሪነትና ታማኝነት ምህረቱንና ታማኝነቱን እንደሚልክ ተደርጎ ተነግሯል። የነገር ስም የሆነው “ምህረት” እና “ታማኝነት” እንደ “መሐሪ” እና “ታማኝ” ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ለእኔ መሐሪና ታማኝ ይሆናል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

Psalms 57:4

ሕይወቴ በአንበሶች መካከል ነው
ዘማሪው ስለ ጠላቶቹ ሲናገር እንደ አንበሶች ይቆጥራቸዋል። አ.ት፡ “የምኖረው በጨካኝ ጠላቶች መካከል ነው” ወይም “ጨካኝ ጠላቶች እንደ አንበሳ ከብበውኛል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እነዚያ ሊውጡኝ የተዘጋጁት
ማጥፋት አንድን ነገር እንደ መዋጥ ወይም ጨርሶ እንደ መብላት ሆኖ ተነግሯል። አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡ ቃል “ጨካኝ አውሬዎች” ማለት እንደሆነ ይገነዘባሉ። ሁለቱም ሥዕሎች ጠላቶቹን እንደ ዱር አውሬ አድርገው ይገልጻሉ። አ.ት፡ “እነዚያ ሊያጠፉኝ የተዘጋጁት” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ጥርሶቻቸው ጦርና ቀስት የሆኑ ሕዝብ
የጠላት ቀስትና ጦር እንደ አንበሳ ጥርስ ተደርጎ ተነግሯል። ዘማሪው ጠላቶቹ እንደ አንበሳ እንደሆኑ መናገሩን ቀጥሏል። አ.ት፡ “አንበሳ በሹል ጥርሶቹ እንደሚገድል በቀስትና በጦር ሌሎችን ሰዎች የሚገድሉ ሕዝቦች” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጦርና ቀስት
የእነዚህ የሁለቱም ስያሜ የጦር መሣሪያ እስከሆነ ድረስ የአንተ ባህል አንዱን ብቻ የሚያውቅ ከሆነ እርሱን ብቻ ብትጠቀም ተቀባይነት አለው። (See: Doublet)

ምላሳቸው የተሳለ ሰይፍ ነው
ምላስ አንድ ሰው የሚናገረውን ይወክላል፣ ጭካኔን የተሞሉት የጠላቶች ቃላት እንደ ሰይፍ ተቆጥረው ተነግረዋል። አ.ት፡ “ጭካኔን የተሞሉት ቃሎቻቸው እንደ ተሳሉ ሰይፎች ናቸው” ወይም “በሚናገሩት ቃል የከፋ ችግር የሚያስከትሉብኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር ሆይ፣ ከሰማያት በላይ ከፍ ከፍ በል
እግዚአብሔር መክበሩን እንዲያሳይ ዘማሪው እየጠየቀው ነው። ከሰማያት በላይ ከፍ ማለት ታላቅ መሆንን ይወክላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ሆይ፣ ከሰማያት በላይ ከፍ ከፍ ማለትህን አሳይ” ወይም “እግዚአብሔር ሆይ፣ በሰማያት ላይ ታላቅ መሆንህን አሳይ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ክብርህ በምድር ሁሉ ላይ ይሁን
እግዚአብሔር ክብሩን እንዲያሳይ ዘማሪው እየጠየቀው ነው። አ.ት፡ “በምድር ሁሉ ላይ ክብርህን አሳይ”

Psalms 57:6

ለእግሮቼ መረብን ዘረጉ
ጠላቶቹ እርሱን ለመያዝ ማቀዳቸው እርሱን ለማጥመድ መሬት ላይ ወጥመድ እንደ ዘረጉ ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ነገሩ ጠላቶቼ እኔን ለማጥመድ መረብ የዘረጉ ይመስላል” ወይም “ሰዎች የዱር እንስሳ ለማጥመድ መረብ እንደሚዘረጉ እኔን ለመያዝ አቅደዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በፊት ለፊቴ ጉድጓድን ቆፍረዋል
ጠላቶቹ እርሱን ለመያዝ ማቀዳቸው ይወድቅበት ዘንድ ጉድጓድ እንደ ቆፈሩለት ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “እንድወድቅበት ጉድጓድ የቆፈሩልኝ ያህል ይመስላል” ወይም “ልክ ሰዎች የዱር እንስሳ ለማጥመድ ጉድጓድ እንደሚቆፍሩ እኔን ለመያዝ አቅደዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እነርሱ ራሳቸው በመካከሉ ወደቁ
ጠላቶቹ እርሱን ለመያዝ በሚሞክሩበት ጊዜ በእነርሱ ላይ የደረሰባቸው ጉዳት ለእርሱ ባጠመዱት ወጥመድ ውስጥ እንደ ወደቁ ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “በቆፈሩልኝ ጉድጓድ ውስጥ እነርሱ ራሳቸው ወደቁ” ወይም “ነገር ግን በእኔ ላይ ለማድረግ ባቀዱት በዚያ እነርሱ ራሳቸው ተጎዱበት” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 57:7

ልቤ ጽኑ ነው፣ እግዚአብሔር ሆይ፣ ልቤ ጽኑ ነው
ስለ መተማመን፣ የአንድ ሰው ልብ ከመንቀጥቀጥ ወይም በቀላሉ ከመነቅነቅ ይልቅ የጸና እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። በእግዚአብሔር ላይ ፍጹም መታመን እንዳለውና እንደማይለወጥ ለማሳየት ሐረጉ ተደግሟል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ሆይ፣ ሙሉ በሙሉ በአንተ እተማመናለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ምስጋናን እዘምራለሁ
የሚዘምረው ማን እንደሆነ በግልጽ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ሆይ፣ ምስጋናን እዘምርልሃለሁ” (Assumed Knowl- edge and Implicit Information የሚለውን ተመልከት)

ዕድለኛው ልቤ ተነሥ
የመነሣቱ ዓላማ ለእግዚአብሔር ምስጋናን ለመዘመር መሆኑ በግልጽ ሊነገር ይችላል። መነሣት አንድን ነገር ለማድረግ የመጀመር ወይም የመዘጋጀት ዘይቤአዊ አነጋገር ሊሆን ይችላል። ልብ ዘማሪውን ወይም የእርሱን ስሜት ይወክላል። አ.ት፡ “ዕድለኛው ልቤ ለእግዚአብሔር ምስጋናን ለመዘመር ተነሥ” ወይም “ለእግዚአብሔር የምስጋናን መዝሙር እንዲዘምር ዕድለኛውን ልቤን አዘጋጀዋለሁ” ወይም “ለመነሣትና ለእግዚአብሔር ምስጋናን ለመዘመር ታድያለሁ” (Assumed Knowledge and Implicit Information፣ዘይቤአዊ አነጋገር እና Synecdoche የሚለውን ተመልከት)

በገና እና መሰንቆም ተነሡ
የመነሣቱ ዓላማ ለእግዚአብሔር ምስጋናን ለመዘመር መሆኑ በግልጽ ሊነገር ይችላል። ዘማሪው በገናና መሰንቆ ለእግዚአብሔር ምስጋናን የሚዘምሩ ሰዎች እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “በገናና መሰንቆ ተነሡ፣ ለእግዚአብሔር ምስጋናን ዘምሩ” ወይም “ለእግዚአብሔር ምስጋናን በምዘምርበት ጊዜ በበገናና በመሰንቆ እጫወታለሁ” (Assumed Knowledge and Implicit Information፣ ሰውኛ እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ንጋትን እቀሰቅሰዋለሁ
ንጋት በራሱ ሕያው እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮለታል፣ ከመንጋቱ በፊት መነሣትም እርሱን እንደ መቀስቀስ ተደርጎ ተነግሯል። ከመንጋቱ በፊት የመነሣት ዓላማው እግዚአብሔርን ለማመስገን ነው። አ.ት፡ “ከመንጋቱ በፊት እነሣለሁ” ወይም “ፀሐይ ከመውጣቷ በፊት እነሣለሁ” (ሰውኛ፣ ዘይቤአዊ አነጋገር እና Assumed Knowledge and Implicit Information የሚለውን ተመልከት)

Psalms 57:9

እስከ ሰማያት ድረስ፣ ምህረትህ ታላቅ ነውና ... ታማኝነትህ እስከ ደመና ድረስ
የእነዚህ የሁለቱም ሐረጎች ትርጉም በጣም ተመሳሳይ ነው። የእግዚአብሔር ምህረትና ታማኝነት ታላቅነት መለካት በሚችል ርቀት ተመስሎ ተነግሯል። (Parallelism እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እስከ ሰማያት ድረስ፣ ምህረትህ ታላቅ ነውና
የእግዚአብሔር ምህረት ታላቅነት መለካት በሚችል ርቀት ተመስሎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ከመሬት እስከ ሰማያት ድረስ ያለውን ርቀት ያህል ምህረትህ ታላቅ ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ታማኝነትህ እስከ ደመና ድረስ
“ታላቅ ነው” እና “ድረስ” የሚሉትን ቃላት ቀደም ብሎ ካሉት ቁጥሮች መገንዘብ ይቻላል። አ.ት፡ “እስከ ደመናት የሚደርስ ታማኝነትህ ታላቅ ነው” ወይም “ታማኝነትህ ከመሬት እስከ ደመናት ድረስ ያለውን ርቀት ያህል ታላቅ ነው” (Ellipsis እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር ሆይ፣ ከሰማያት በላይ ከፍ ከፍ በል
እግዚአብሔር መክበሩን እንዲያሳይ ዘማሪው እየጠየቀው ነው። ከሰማያት በላይ ከፍ ከፍ ማለት ታላቅ መሆንን ይወክላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ሆይ፣ ከሰማያት በላይ ከፍ ከፍ ማለትህን አሳይ” ወይም “እግዚአብሔር ሆይ፣ በሰማያት ላይ ታላቅ መሆንህን አሳይ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ክብርህ በምድር ሁሉ ላይ ከፍ ከፍ ይበል
እግዚአብሔር ክብሩን እንዲያሳይ ዘማሪው እየጠየቀው ነው። አ.ት፡ “በምድር ሁሉ ላይ ክብርህን አሳይ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 58

1 እናንተ ገዢዎች እውነትን ትናገራላችሁ? እናንተ ሰዎች ቅን ፍርድ ትፈርዳላችሁ? **2** የለም፤ በልባችሁ ክፋት ታውጠነጥናላችሁ በእጃችሁም በምድር ሁሉ ላይ
በደል ትፈጽማላችሁ። **3** ክፉዎች በእናታቸው ማሕፀን እያሉ እንኳ ከመንገድ የወጡ ናቸው ሲወለዱ ጀምሮ የተሳሳቱና ውሸታሞች ናቸው። **4** መርዛቸው እንደ
እባብ መርዝ ነው **5** የአስማተኛውን ቃል አልሰማ እንዳለች እፉኝት ጆሮአቸውን ደፍነዋል። **6** እግዚአብሔር ሆይ፣ ጥርሳቸውን አፋቸው ውስጥ ስበር
የአንበሶችንም መንጋጋ አውላልቅ። **7** ፈስሶ እንደሚያልቅ ውሃ ይጥፉ የቀስታቸው ፍላጻ ዱልዱም ይሁን። **8** እየሄደ ሟምቶ እንደሚጠፋ ቀንድ አውጣ፣ ፀሐይ
እንደማያይም ጭንጋፍ ይሁኑ። **9** የሚነደው እሾኽ እሳት ገና ድስታችሁን ሳያሞቀው እርጥቡንም ደረቁንም እኩል በዐውሎ ነፋስ ጠራርጐ ይወስዳቸዋል። **10**
ጻድቃን የእግዚአብሔርን በቀል ሲያዩ ደስ ይላቸዋል እግሩንም በግፈኞች ደም ይታጠባል። **11** በዚህ ጊዜ ሰዎች፣ «በእርግጥ ለጻድቃን ዋጋ አላቸው፤
በእውነትም በምድር ላይ የሚፈርድ አምላክ አለ» ይላሉ።

Psalms 58:1

ለሙዚቀኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”

ለአል ታሼዝ የተዘጋጀ
ይህ ምናልባት መዝሙሩን በሚዘምሩበት ጊዜ ምን ዓይነት የሙዚቃ ስልት ወይም ቅኝት መጠቀም እንዳለባቸው ሳይነግራቸው አይቀርም። ይህንን በመዝሙር 57፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

አል ታሼዝ
ይህ “አታጥፋ” ማለት ነው። ተርጓሚዎች ትርጉሙን መጻፍ ወይም የዕብራይስጡን ቃል መቅዳት ይኖርባቸዋል። (የማይታወቁትን ተርጉማቸው እና ቃላትን ቅዳ ወይም ተዋስ የሚለውን ተመልከት)

የዳዊት መዝሙር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) መዝሙሩን ዳዊት ጽፎታል ወይም 2) መዝሙሩ የሚመለከተው ዳዊትን ነው ወይም 3) መዝሙሩ የዳዊትን መዝሙሮች ዘይቤ የተከተለ ነው የሚሉት ናቸው።

ሚችታም
“ሚችታም” የሚለው ቃል ትርጉሙ በእርግጠኝነት አይታወቅም። በምትኩ “መዝሙር” የሚለውን ቃል መጠቀም ይኖርብህ ይሆናል። “ዳዊት የጻፈው መዝሙር ይህ ነው” ተብሎ ሊጻፍ ይችላል። ይህንን በመዝሙር 16፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

እናንተ ገዢዎች ጽድቅን ትናገራላችሁ?
ደራሲው በጽድቅ ስለማይናገሩ ገዢዎቹን ለመገሰጽ ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። አ.ት፡ “እናንተ ገዢዎች ትክክለኛውን ነገር አትናገሩም!” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

እናንተ ... የእናንተ
“እናንተ” እና “የእናንተ” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ፈራጆች የሆኑ ኃያላን ሰዎችን ነው። እዚህ ጋ የእንግሊዝኛው “ዩ” ብዙ ቁጥር ነው። (Forms of You የሚለውን ተመልከት)

እናንተ ሰዎች፣ እናንተ በጽድቅ ትፈርዳላችሁ?
ደራሲው በጽድቅ የማይፈርዱትን ፈራጆች ለመገሰጽ ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። አ.ት፡ “እናንተ ሰዎች፣ በሕዝቡ ላይ በጽድቅ አትፈርዱም!” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

አይደለም
ደራሲው ጠይቋቸው የነበሩትን ሁለቱንም ጥያቄዎች ይመልሳል።

በልባችሁ ክፋትን ታደርጋላችሁ
ልብ የሕዝቡን አሳብ ወይም ዕቅድ ያመለክታል። አ.ት፡ “በአሳባችሁ ክፋትን ታደርጋላችሁ’ ወይም “ክፉ ነገሮችን ስለማድረግ ታስባላችሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በምድሪቱ ሁሉ ላይ በእጆቻችሁ ሁከትን ታከፋፍላላችሁ
በምድሪቱ ላይ በተለያየ ስፍራ ማወክ ልክ ሁከት ዕቃ ይመስል በምድሪቱ ሁሉ ላይ እንደ ማከፋፈል ወይም እንደ ማስፋፋት ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “እናንተ ራሳችሁ በምድሪቱ ሁሉ ላይ የሁከት ተግባር ትፈጽማላችሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 58:3

ክፉዎች በማህፀን እያሉ እንኳን መንገድ የሳቱ ናቸው ... ከመወለዳቸው ጀምሮ መንገድ ይስታሉ
ይህ በሁለት የተለያየ መንገድ የተገለጸ ተመሳሳይ አሳብ ነው። (Parallelism የሚለውን ተመልከት)

መንገድ መሳት
የተሳሳቱ ነገሮችን ማድረግ ልክ ሰዎች በመንገድ ላይ እየሄዱ እያሉ ታጥፈው በተሳሳተ መንገድ እንደሚሄዱ ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “የተሳሳተ ነገሮችን ያደርጋሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መርዛቸው ልክ እንደ እባብ መርዝ ነው
ሰዎች የሚናገሯቸው ክፉ ነገሮች መርዝ እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “የእባብ መርዝ ሰውን እንደሚጎዳ ሁሉ ክፉ ቃላቸውም ችግር ይፈጥራል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና Simile የሚለውን ተመልከት)

እነርሱ ልክ ጆሮዎቹን እንደሚያቆም ደንቆሮ እባብ ናቸው
ምክርን ወይም ተግሳጽን የማይሰሙ ክፉ ሰዎች ለደጋሚው ሙዚቃ ምላሽ እንደማይሰጡ እባቦች ተደርገው ተነግሮላቸዋል። አ.ት፡ “ጆሮዎቹን እንደሚያቆም ደንቆሮ እባብ ለመስማት አይፈልጉም” (Simile የሚለውን ተመልከት)

ጆሮዎቹን የሚያቆም ደንቆሮ እባብ
ለደጋሚው ሙዚቃ ምላሽ የማይሰጠው እባብ እንዳይሰማ ጆሮው ውስጥ የሆነ ነገር እንደ ከተተ ተደርጎ ተነግሮለታል። አ.ት፡ “የማይሰማ እባብ” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

እባብ
የመርዘኛ እባብ ዝርያ

ደጋሚዎች
እባቡን ለመቆጣጠር በሙዚቃ የሚጫወቱ ወይም የሚዘፍኑ ሰዎች

ምንም ያህል ብልሆች መሆናቸው ልዩነት የለውም
በእባብ ላይ ድግምት የሚያደርጉት ብልህ የሆኑት በምን እንደሆነ በግልጽ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እባቦቹን በመቆጣጠር ጉዳይ ደጋሚዎቹ ምንም

ያህል ብልኖች ቢሆኑም እንኳን” (Assumed Knowledge and Implicit Information የሚለውን ተመልከት)

Psalms 58:6

ጥርሶቻቸውን ስበር ... የአንበሳ ደቦሎቹን ታላላቅ ጥርስ ስበር
በእነዚህ በሁለቱም ሐረጎች ውስጥ ክፉ ሰዎች አንበሳ እንደሆኑ ተደርጎ የተነገረላቸው ሲሆን ሰዎችን እንዳይገድሉ እነርሱን አቅም ማሳጣት ደግሞ ጥርሶቻቸውን እንደ መስበር ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “የሚገድሉበትን ኃይል ውሰድባቸው። ጥርሶቻቸው ተሰብሮ እንደ ወደቀባቸው ደቦል አንበሶች አቅመ ቢስ አድርጋቸው” (Paral- lelism እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ፈጥኖ እንደሚያልፍ ወራጅ ውሃ ቀልጠው እንዲጠፉ አድርጋቸው
ክፉ ሰዎች እንደ በረዶ ወይም ውሃ ተመስለው ተነግሮላቸዋል። ዳግመኛ አለመኖር እንደ መቅለጥ ወይም ወደ መሬት ውስጥ እንደመስረግ ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “እንደ ወራጅ ውሃ እንዲጠፉ አድርጋቸው” ወይም “ልክ ቀልጦ ወደ መሬት ውስጥ እንደሚሰርግ በረዶ እንዲተኑ አድርጋቸው” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና Simile የሚለውን ተመልከት)

ምንም ዒላማ እንደሌላቸው ይሁኑ
“ቀስቶቻቸው ዒላማዎቻቸውን እንደሚስቱ ይሁኑ”

ቀልጦ እንደሚጠፋ ቀንድ አውጣ ይሁኑ
ዳግመኛ አለመኖር እንደ መቅለጥ ወይም መጥፋት ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ክፉዎች እንደሚቀልጥና ዳግመኛ እንደማይኖር ቀንድ አውጣ ተነው ይጥፉ” (Simile የሚለውን ተመልከት)

ቀንድ አውጣ
እስራኤላውያን እንደ እርኩስ የሚቆጥሩትና በሚያመነጨው ልጋግ መሰል ነገር ላይ ሲሄድ የሚቀልጥ የሚመስል ነፍሳት

ከሴት ተወልዶ የፀሐይን ብርሃን እንደማያይ ጭንጋፍ
አለመኖር ሞቶ የተወለደ ሕፃን መምሰል እንደሆነ ተነግሯል። አ.ት፡ “በሕይወት ለመኖርና የፀሐይን ብርሃን ለማየት እንዳይችል በጣም ቀድሞ እንደ ተወለደ ሕፃን” ወይም “ሞቶ እንደ ተወለደ ሕፃን” (Simile የሚለውን ተመልከት)

Psalms 58:9

የሚነደው እሾህ ድስታችሁን ሳያሰማው ... እርጥቡን እሾህና የሚነደውን እሾህ
ክፉዎች በእሾህ ቅርንጫፎች ተመስለዋል፤ በእነርሱ ላይ የእግዚአብሔር ፈጣን ቅጣትም ፈጥኖ እንደሚያነዳቸው ወይም ጠራርጎ እንደሚያስወግዳቸው ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “ከማብሰያው ድስት ስር በእሳት የተለኮሰውን የእሾህ ቅርንጫፍ ጠራርጎ ሊወስድ ከሚችል ዐውሎ ነፋስ ይልቅ እግዚአብሔር ክፉ ሰዎችን በፍጥነት ያጠፋቸዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የእናንተ
ዳዊት የሚናገረው ለእግዚአብሔር ሕዝብ ስለሆነ ይህ ብዙ ቁጥር ነው። (Forms of You የሚለውን ተመልከት)

የሚቃጠለው እሾህ ሳያሰማው ... እርጥቡን እሾህና የሚነደውን እሾህ
“የሚነድደው የእሾህ ቅርንጫፍ ሙቀት ... የእርጥቡ እሾህ ቅርንጫፍና የሚነደው እሾህ ቅርንጫፍ

ጻድቁ በሚያይበት ጊዜ ደስ ይለዋል
“ጻድቁ” የሚለው ቃል በጥቅሉ ጻድቅ የሆኑ ሰዎችን ያመለክታል። አ.ት፡ “ጻድቅ የሆኑ ሰዎች በሚያዩበት ጊዜ ደስ ይላቸዋል” (Generic Noun Phrases የሚለውን ተመልከት)

በክፉዎቹ ደም እግሮቹን ይታጠባል
በደም ላይ በመራመዱ የአንድ ሰው እግር መርጠቡ እግሩን በደም እንደ ታጠበ ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ጻድቃን እግሮቻቸውን በክፉዎች ደም ያረጥባሉ” ወይም “ጻድቃን በክፉዎች ደም ላይ ይረማመዳሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በክፉዎች ደም እግሮቹን ይታጠባል
ይህ ግነት ብዙ ቁጥር ያላቸው ክፉ ሰዎች እንደሚሞቱ ይገልጻል። አ.ት፡ “እጅግ ብዙ ሰዎች በመሞታቸው ጻድቃን በደማቸው ላይ በሚረማመዱበት ጊዜ እግሮቻቸውን በደም ያጠቡ እስኪመስሉ ድረስ ይደርሳሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና Hyperbole and Generalization የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 59

1 እግዚአብሔር ሆይ፣ ከጠላቶቼ አድነኝ በእኔ ላይ ከሚነሡ ሰዎችም ጠብቀኝ። **2** ከክፉ አድራጊዎች ታደገኝ፣ ደም ከተጠሙ ሰዎችም አድነኝ። **3** ሕይወቴን
ለማጥፋት አድብተዋልና ያህዌ ሆይ፣ ጨካኞች ያለ በደሌ፣ ያለ ኃጢአቴ በላዬ ተሰብስበው ዶለቱብኝ። **4** ምንም በደል ባይኖርብኝም ተዘጋጅተው መጡብኝ፤
አንተ ግን ሁኔታዬን ተመልከት እኔን ለመርዳትም ተነሥ። **5** የሰራዊት አምላክ የሆንህ ያህዌ አንተ የእስራኤልም አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፤ ሕዝቦችን
ለመቅጣት ተነሥ፣ ዐመፀኞችንም ያለ ምሕረት ቅጣቸው። ሴላ **6** እንደ ውሻ እያላዘኑ በምሽት ተመልሰው ይመጣሉ በከተማዪቱም ይራወጣሉ። **7** ከአፋቸው
የሚወጣውን ተመልከት ሰይፍ ከንፈራቸው ላይ አለ ደግሞም፣ «ማን ሊሰማን ይችላል?» ይላሉ። **8** አንተ ያህዌ ግን ትሥቅባቸዋለህ ሕዝቦችን ሁሉ በንቀት
ታያቸዋለህ። **9** እግዚአብሔር ብርታቴ ሆይ አንተን እጠብቃለሁ፤ አምላኬ ሆይ አንተ መጠጊያዬ ነህና። **10** እግዚአብሔር በምሕረቱ ይገናኘኛል አምላኬ
የጠላቶቼን ውድቀት ያሳየኛል። **11** እግዚአብሔር ጋሻችን ሆይ፣ ሕዝቤ እንዳይረሱ አትግደላቸው፤ በኃይልህ በትናቸው ዝቅ ዝቅም አድርጋቸው። **12** ከአፋቸው
ስለሚወጣው ኃጢአት ከከንፈራቸውም ስለሚሰነዘረው ቃል በትዕቢታቸው ይያዙ። ከአፋቸው ስለ ወጣው መርገምና ውሸት **13** በቁጣ አጥፋቸው፤ ፈጽመህም
አስወግዳቸው። እግዚአብሔር በያዕቆብና በምድር ዳርቻ ሁሉ ገዢ መሆኑን ይወቁ። **14** እንደ ውሻ እያላዘኑ፣ በምሽት ተመልሰው ይመጣሉ፤ በከተማዪቱም
ዙሪያ ይራወጣሉ። **15** ምግብ ፍለጋ ይራወጣሉ፤ ካልጠገቡም ያላዝናሉ። **16** እኔ ግን ስለ ኃይልህ እዘምራለሁ በማለዳም ስለ ዘላለማዊ ፍቅርህ እዘምራለሁ።
አንተ መጠጊያዬ፣ በመከራዬም ቀን ዐምባዬ ነህና። **17** ብርታቴ ሆይ፣ በዝማሬ አመሰግንሃለሁ፤ እግዚአብሔር መጠጊያዬ የምትወደኝም አምላኬ ነህና።

Psalms 59:1

ለሙዚቀኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”

ለአል ታሼዝ የተዘጋጀ
ይህ ምናልባት መዝሙሩን በሚዘምሩበት ጊዜ ምን ዓይነት የሙዚቃ ስልት ወይም ቅኝት መጠቀም እንዳለባቸው ሳይነግራቸው አይቀርም። አ.ት፡ “’የአል ታሼዝን ቅኝት በመጠቀም ይህንን መዝሙር ዘምሩ” ወይም “የአል ታሼዝን ስልት በመጠቀም ይህንን ዘምሩ”

የዳዊት መዝሙር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) መዝሙሩን ዳዊት ጽፎታል ወይም 2) መዝሙሩ የሚመለከተው ዳዊትን ነው ወይም 3) መዝሙሩ የዳዊትን መዝሙሮች ዘይቤ የተከተለ ነው የሚሉት ናቸው።

ሚችታም
“ሚችታም” የሚለው ቃል ትርጉሙ በእርግጠኝነት አይታወቅም። በምትኩ “መዝሙር” የሚለውን ቃል መጠቀም ይኖርብህ ይሆናል። “ዳዊት የጻፈው መዝሙር ይህ ነው” ተብሎ ሊጻፍ ይችላል። ይህንን በመዝሙር 16፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሳዖል በላካቸውና ሊገድሉት ቤቱን በከበቡት ጊዜ
“የሚገድሉበትን አጋጣሚ ለማግኘት የዳዊትን ቤት እንዲጠብቁ ሳዖል ወታደሮቹን በላካቸው ጊዜ”

በከፍታ አስቀምጠኝ
የከፍታ ስፍራ ጠላቶቹ ሊደርሱበት የማይችሉበትን አስተማማኝ ስፍራ ይወክላል። አ.ት፡ “በአስተማማኝ ስፍራ አስቀምጠኝ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእኔ ላይ ተነሥተዋል
በአንድ ሰው ላይ መነሣት እርሱን ማጥቃትን ይወክላል። አ.ት፡ “ሊያጠቁኝ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ደም የተጠሙ ሰዎች
“ደም የተጠሙ” የሚለው ቃል መግደልን የሚያመለክተውን “ደም” እና “ምኞትን የሚያመለክተውን “መጠማት” ይዟል። አ.ት፡ “ለመግደል የሚመኙ ሰዎች” ወይም “ሰዎችን መግደል ደስ የሚያሰኛቸው ሰዎች” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Psalms 59:3

ሕይወቴን ለመውሰድ አድብተው ይጠብቃሉ
የዳዊት ጠላቶች ተደብቀዋል፣ እርሱን የሚያጠቁበትን አጋጣሚም በመጠባበቅ ላይ ናቸው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ንቃ
አንድ ነገር ለማድረግ መወሰንና እርሱኑ ለማድረግ መጀመር እንደ መንቃት ተቆጥሮ ተነግሯል። አ.ት፡ “አንድ ነገር አድርግ” ወይም “እርምጃ ውሰድ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

እና ተመልከት
እግዚአብሔር ምን እንዲያይለት እንደ ፈለገ በግልጽ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ምን እየደረሰብኝ እንዳለ ተመልከት” ወይም “ምን እያደረጉብኝ እንዳሉም ተመልከት” (Assumed Knowledge and Implicit Information የሚለውን ተመልከት)

Psalms 59:5

ተነሥ
አንድ ነገር ለማድረግ መወሰንና እርሱኑ ለማድረግ መጀመር እንደ መነሣት ተቆጥሮ ተነግሯል። አ.ት፡ “አንድ ነገር አድርግ” ወይም “እርምጃ ውሰድ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ሕዝቦች ሁሉ
እዚህ ጋ፣ “ሕዝቦች” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን የማያከብሩትን የሀገራቱን ሕዝቦች ይወክላል። አ.ት፡ “የየሀገሩ ሕዝብ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 59:6

በምሽት ይመለሳሉ
በውስጠ ታዋቂነት ያለው “እነርሱ” የሚለው ቃል ክፉዎች ተላላፊዎችን ያመለክታል።

እንደ ውሻ ያላዝናሉ
ዘማሪው ለማጥቃት ስለሚያስፈራሩት ጠላቶቹ ሲናገር በሰዎች ላይ እንደሚያላዝኑ ወይም እንደሚጮኹ ውሾች አድርጎ ይገልጻቸዋል። አ.ት፡ “ሰዎችን ለማጥቃት ያስፈራራሉ” (Simile የሚለውን ተመልከት)

በከተማይቱ ዙሪያ ይሄዳሉ
በከተማይቱ ዙሪያ የሚሄዱበት ምክንያት በግልጽ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የሚያገኙትን የትኛውንም ሰው ለማጥቃት በከተማው ዙሪያ ይሄዳሉ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

(Assumed Knowledge and Implicit Information የሚለውን ተመልከት)

እነሆ
እዚህ ጋ፣ “እነሆ” የሚለው ቃል ትኩረትን ወደ አንድ ነገር ለመሳብ ጥቅም ላይ ውሏል። አ.ት፡ “ስማ”

በአፋቸው ያገሳሉ
መጥፎ ነገር መናገር እንደ ማግሳት ተቆጥሮ ተነግሯል። እነዚህ መጥፎ ነገሮች ስድብ ወይም ማስፈራራት ሊሆኑ ይችላሉ። አ.ት፡ “መጥፎ ነገሮችን ይናገራሉ” ወይም “መጥፎ ቃላት እየተናገሩ ይጮኻሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ማግሳት
ከፍ ባለ ድምፅ ማግሳት፤ የተቃጠለ አየር ከሆድ በአፍ በኩል ከፍ ባለና በሚረብሽ ድምፅ እንዲወጣ ማድረግ

በከንፈራቸው ውስጥ ሰይፍ አለ
ክፉ ሰዎች የሚናገሯቸው የጭከና ቃላት እንደ ሰይፍ ሆነው ተነግረዋል። አ.ት፡ “ሰይፍ ሰዎችን የሚያጠፋቸውን ያህል በሰዎች ላይ ችግር የሚፈጥሩ የጭካኔ ቃላት ይናገራሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ማን ይሰማናል?
እግዚአብሔር እንደማይሰማቸውና እንደማይቀጣቸው ማመናቸውን ለማሳየት ይህ ጥያቄ ጥቅም ላይ ውሏል። አ.ት፡ “ማንም ሊሰማን አይችልም!” ወይም “አምላክህ አይሰማንም!” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

Psalms 59:8

ትስቅባቸዋለህ
“በንቀት ትስቅባቸዋለህ” ወይም “ትሳለቅባቸዋለህ”። የማይረቡና አቅመ ቢሶች ስለሆኑ እግዚአብሔር ይስቅባቸዋል።

ሕዝቦችን ሁሉ በንቀት ታያቸዋለህ
“ሕዝቦችን ሁሉ ታሞኛቸዋለህ” ወይም “የየሀገሩ ሕዝብ ሞኝ እንደሆኑ ታውቃለህ”

ንቀት
ማሞኘት

ጉልበቴ
እግዚአብሔር የዘማሪው ጉልበት መሆኑ የእግዚአብሔርን ጥበቃ ይወክላል። አ.ት፡ “አንተ ጉልበቴ ነህ” ወይም “አንተ ጠባቂዬ ነህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አንተ ረጅም ማማዬ ነህ
ረጅም ማማ ሰዎች ከጠላቶቻቸው ለመከለል የሚሄዱበት ስፍራ ነው። ዘማሪው እግዚአብሔር እርሱን እንደሚጠብቀው ሲናገር እግዚአብሔር ብርቱና አስተማማኝ ከለላ እንደሆነው ይመሰክራል። አ.ት፡ “እንደ ረጅም ማማ ትከልለኛለህ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 59:10

እግዚአብሔር በቃል ኪዳን ታማኝነቱ ይገናኘኛል
ይህ ሐረግ እግዚአብሔር ሊያድነው እንደሚመጣ ያመለክታል። የነገር ስም የሆነው “ታማኝነት” ከቅጽል ጋር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ለቃል ኪዳኑ ታማኝ የሆነው አምላኬ ሊያድነኝ ይመጣል” ወይም “ለኪዳኑ ታማን ስለሆነ አምላኬ ሊያድነኝ ይመጣል” (Assumed Knowledge and Implicit Information እና የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

በጠላቶቼ ላይ የእኔ ምኞት
የነገር ስም የሆነው “ምኞት” ከግሥ ጋር “ፍላጎት” ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። አ.ት፡ “በጠላቶቼ ላይ እንዲደርስባቸው የምፈልገው” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

በትናቸው
“እንዲቅበዘበዙ አድርጋቸው”

ጋሻችን
የእግዚአብሔር ጻድቁን መጠበቅ፣ እግዚአብሔርን ጋሻ እንደሆነ ተደርጎ እንዲነገር አድርጓል። አ.ት፡ “የእኛ ጠባቂ” ወይም “እንደ ጋሻ የሚከላከልልን እርሱ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 59:12

ከአፋቸው ስለሚወጣው ኃጢአትና ስለ ከንፈሮቻቸው ቃል
አፍና ከንፈር ሰዎች የሚናገሩትን ነገር ይወክላል። አ.ት፡ “በሚናገሩት ኃጢአትን ስለሚያደርጉ” ወይም “በሚናገሩት የኃጢአት ንግግር ምክንያት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በትዕቢታቸው ይያዙ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በትዕቢታቸው ምክንያት ሰዎች ይያዟቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ስለሚገልጹት
“ስለሚሉት”

በቁጣ አቃጥላቸው፣ ከእንግዲህ እንዳይገኙ አቃጥላቸው
እነርሱን ሙሉ በሙሉ ማጥፋት እንደ ማቃጠል ወይም መብላት ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ተቆጣቸው፣ አንዳቸውም እንዳይቀሩ አድርገህ አጥፋቸው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በያዕቆብ
እዚህ ጋ፣ ያዕቆብ የሚያመለክተው እስራኤልን ነው። አ.ት፡ “በእስራኤል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እስከ ምድር ዳርቻ
“በምድር ላይ እጅግ ሩቅ እስከሆነው ቦታ እንኳን”። ይህ በምድር ላይ ሁሉን ስፍራ ይወክላል። አ.ት፡ “በምድር ላይ በሁሉም ቦታ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 59:14

እንደ ውሻ ማላዘን
ዘማሪው ሰዎችን ለማጥቃት ስለሚያስፈራሩ ጠላቶቹ ሲናገር በሰዎች ላይ እንደሚያላዝኑ፣ እንደሚያጉረመርሙ ወይም እንደሚጮኹ ውሾች አድርጎ ይገልጻቸዋል። አ.ት፡ “ሊያጠቁን ያስፈራራሉ” ወይም “እንደ ዱር ውሾች ሊያጠቁን ያስፈራሩናል” (Simile የሚለውን ተመልከት)

ርክተዋል
የሚፈልጉት ሁሉ ስላላቸው በቃኝ ማለት

Psalms 59:16

አንተ ለእኔ ረጅም ማማና መጠጊያ ነህና
ረጃጅም ማማዎችና መጠጊያዎች ሰዎች ከጠላቶቻቸው ለመከለል የሚሄዱባቸው ቦታዎች ናቸው። ዘማሪው ለእርሱ የሚያደርግለትን ጥበቃ እግዚአብሔር ብርቱና አስተማማኝ መጠለያ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “እንደ ረጅም ማማና መጠጊያ ጠብቀኸኛል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በጭንቀቴ ቀን
“በችግሬ ጊዜ ሁሉ”

ጉልበቴ ሆይ፣ ለአንተ ምስጋናን እዘምርልሃለሁ
“ጉልበቴ ሆይ፣ ለአንተ” እንደ አንድ አንቀጽ ሊጣመር ይችላል። አ.ት፡ “አንተ ጉልበቴ ነህ፣ ስለዚህ ምስጋናን እዘምርልሃለሁ” (Sentence Structure የሚለውን ተመልከት)

ጉልበቴ
እግዚአብሔር የዘማሪው ጉልበት መሆኑ እግዚአብሔር እርሱን መጠበቁን ይወክላል። አ.ት፡ “ጠባቂዬ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር ረጅም ማማዬ ነውና
ረጃጅም ማማዎች ሰዎች ከጠላቶቻቸው ለመከለል የሚሄዱባቸው ቦታዎች ናቸው። ዘማሪው፣ እግዚአብሔር ለእርሱ የሚያደርግለትን ጥበቃ እግዚአብሔር ብርቱና አስተማማኝ መጠለያ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “እንደ ረጅም ማማ ጠብቀኸኛል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የቃል ኪዳን ታማኝነት አምላክ
የነገር ስም የሆነው “ታማኝነት” ከቅጽል ጋር ሊተረጎም ይችላል። ይህ ለብቻው በሚቆም ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። አ.ት፡ “ለቃል ኪዳኑ ታማኝ የሆነው እርሱ እግዚአብሔር ነው” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 60

1 እግዚአብሔር ሆይ፣ ጣልኸኝ፣ ሰባበርኸን፤ ተቆጣኸንም፤ አሁን ግን መልስህ አብጀኝ። **2** ምድሪቱን አናወጥኃት፣ ፍርክስክስ አደረግኃት፤ ተንገዳግዳለችና ስብራቷን ጠግን። **3** ሕዝብህን መከራውን አሳየኸው የሚያንገዳግድ ወይን ጠጅ እንድንጠጣም ሰጠኸን። **4** ከጠላት ቀስት እንዲያመልጡ ለሚፈሩህ ምልክት አደረግህላቸው። ሴላ **5** የምትወደው ሕዝብህ ከጉዳት እንዲድን በቀኝህ ታደገን፤ መልስም ስጠን። **6** እግዚአብሔር በመቅደሱ ሆኖ እንዲህ አለ፣ «ሲኬምን እሸነሽናለሁ፤ የሱኮትንም ሸለቆ አከፋፍላለሁ። **7** ገለዓድ የእኔ ነው፤ ምናሴም የእኔ ነው፤ ኤፍሬም የራስ ቁሬ፣ ይሁዳም በትረ መንግሥቴ ነው። **8** ሞዓብ መታጠቢ ገንዳዬ ነው፤ በኤዶም ላይ ጫማየን እወረውራለሁ ፍልስጥኤማውያን ላይ በድል እልል እላለሁ። **9** ወደ ተመሸገችው ከተማ ማን ያመጣኛል? ማንስ ወደ ኤዶም ይመራኛል? **10** ነገር ግን እግዚአብሔር ሆይ፥ የጣልከን አንተ አይደለህምን? አምላክ ሆይ፥ ከሠራዊታችን ጋር አብረህ አልወጣህም **11** በጠላቶቻችን ላይ ድልን ስጠን የሰው ድጋፍ ከንቱ ነውና። **12** በእግዚአብሔር እርዳታ ድል እንቀዳጃለን እርሱ ጠላቶቻችንን ከእግሩ በታች ይረግጣቸዋል።

Psalms 60:1

አጠቃላይ መረጃ፡-
ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ለመዘምራን አለቃ
“ይህ አምልኮ ላይ እንዲጠቀምበት ለመዘምራኑ አለቃ ነው።”

የኪዳን ጽጌ ረዳ በምሚለው ቅኝት የሚዘመር
ይህ ምናልባትም መዝሙርን ስንዘምር ምን አይነት የዜማ ቅኝት ወይም ዘይቤ መጠቀም እንዳለብን ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይህንን መዝሙር “የኪዳን ፅጌሬዳ” ቅኝትን በመጠቀም ዘምር” ወይም “ይህንን መዝሙር የኪዳን ፅጌሬዳን ዘይቤ በመጠቀም ዘምር”

የኪዳን ጽጌሬዳ
ይህ “የኪዳን ፅጌሬዳ” ማለት ነው። ተርጓሚው ትርጉሙን መፃፍ ወይም ደግሞ የዕብራይስጡን ቃል መገልበጥ ይችላል። (የማይታወቁትን ተርጉም እና ቃላትን ገልብጥ ወይም ከሌላ ውሰድ የሚለውን ይመልከቱ)

ሚክታም
ሚክታም የሚለው የዕብራይስጥ ቃል ትርጉም በእርግጠኝነት አይታወቅም። በምትኩ “መዝሙር” የሚለውን ቃል መጠቀም ይቻላል። ይህ እንዲህ ተብሎ ሊፃፍ ይችላል፡- “ይህ ዳዊት የፃፈው መዝሙር ነው።” ይህንን በመዝሙረ ዳዊት 16:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

አራም ናሃራይም . . . አራም ዞባህ
“በሁለቱ ወንዞች መካከል የሚገኘው አራም . . . በዞባህ የሚገኘው አራማውያን ሕዝብ።” እነዚህ ቦታዎች ናቸው።(ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ኢዮአብ
ይህ ኢዮአብን እና እርሱ የሚመራውን የጦር ሰራዊት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ኢዮአብ እና የእርሱ የጦር ሰራዊት” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

አስራ ሁለት ሺህ ኤዶማውያን
“12,000 ኤዶማውያን” (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ጣልኸን
እግዚአብሔር ሰዎችን አለመቀበሉ እነእርሱን አንደጣላቸው ተደርጎ ተረግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ አልተቀበልከንም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ምሽጋችንን ጥሰህ ገባህ
እግዚአብሔር የእስራኤል ጠላቶች ምሽጋቸውን ጥሰው እንዲገቡ መፍቀዱ እርሱ ራሱ እንደፈፀመው ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ ጠላቶቻችን ምሽጋችንን ጥሰው እንዲገቡ ፈቅደሀል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 60:2

አያያዥ ሀሳብ፡-
ዘማሪው ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።

አንተ ምድሪቱ እንድትናወጥ አደረግህ፤ፍርክስክስክስም አደረግህት
ዘማሪው በሀገሩ ውስጥ ያለውን አደጋ የመሬት መንቀጥቀጥ እንደሆነ እንደዚያ አድርጎ ይናገራል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ስብራትዋን ጠግን
ህዝቡን እንደገና ጠንካራ ማድረግ የመሬትን ወይም የግድግዳን ውስጥ ስብራት መጠገን እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ስብራቶች
የመሬት ወይም የግድግዳ ውስጥ ሰፊ ስንጥቅ

ህዝብህ አስቸጋሪ ነገሮችን እንዲያይ አድርገህል
እዚህ ላይ “እንዲያይ” የሚለው ቃል “እንዲደርስበት” ወይም “እንዲሰቃይ” የሚለውን ይወክላል። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የሚያንገዳግድ የወይን ጠጅ መጠጣት
ረዳት ማጣት በዙሪያ እንደመንገዳገድ ተደርጎ ተነግሯል፣ እንደምንም ቀጥ ብሎ መቆም እንደመቻል። “መንገዳገድ” የሚለው ረቂቅ ስምን እንደግስ መግለፅ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እንድንገዳገድ የሚያደርግ የወይን ጠጅ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 60:4

አንተ ምልክትን አቆምህ
እግዚአብሔር ህዝቡን በጦርነት ውስጥ መምራቱ እግዚአብሔር ለጦር ሰራዊቱ ምልክትን ያቆመ ስጋለባሽ ንጉስ ወይም የጦር ዋና አዛዥ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ ምልክትን እንዳቆመ ንጉስ እንደዚያ ነህ” ወይም “ምልክትን ወደላይ ከፍ እንደአደረገ ንጉስ እንደዚያው አንተ በጦርነት ውስጥ ትዕዛዝ ትሰጠናለህ።” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ምልክት
“የጦርነት ሰንደቅ አላማ።” ይህ ንጉስ ወይም የጦር ዋና አዛዥ ሰራዊቱ መሰብሰብ እንዳለበት ለማሳየት በዋልታ ላይ ከፍ የሚያደርገው ሰንደቅ አላማ ነው።

ከቀስት ፊት ያመልጡ ዘንድ
ይህ በገቢር/አድራጊ ሀረግ መግለፅ ይቻላል። ነገር ግን አንዳንድ እትሞች ስለዚህ ሀረግ የተለያየ ፍቺ አላቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “ “ቀስትን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከተሸከሙ ሰዎች ፊት ያመልጡ ዘንድ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀስትን ከተሸከሙ ሰዎች ፊት ያመልጡ ዘንድ
“ቀስትን የተሸከሙ ሰዎች” የሚለው ሀረግ በጦርነት ውስጥ ያሉትን የጠላት ወታደሮችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ በጠላቶቻችሁ ላይ ወታደሮቹን ወደ ጦርነት ሲያሰማራ ያመልጡ ዘንድ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በአንተ ቀኝ እጅ
የእግዚአብሔር ቀኝ እጅ የእርሱን ስልጣን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በስልጣንህ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

መልስን ስጠኝ **answer me**
እዚህ ላይ መመለስ ለእርሱ ጥያቄ ምላሽ መስጠትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእኔን ጥያቄ መመለስ” ወይም “ፀሎቴን መመለስ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 60:6

ኤፍሬም ደግሞ የእኔ የብረት ባርኔጣ ነው
እግዚአብሔር የኤፍሬም ነገድን የእርሱ ሰራዊት እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። የብረት ባርኔጣ የጦርነት መሳሪያን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ኤፍሬም እንደመረጥኩት የብረት ባርኔጣ እንደዚያው ነው” ወይም “የኤፍሬም ነገድ የእኔ ሰራዊት ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የብረት ባርኔጣ
ወታደሮች ራሳቸውን ከጉዳት ለመከላከል የሚያደርጉት ጠንካራ ኮፍያ

ይሁዳ በትረ መንግስቴ ነው
እግዚአብሔር ከይሁዳ ነገድ ለእርሱ ህዝብ ንጉስ እንዲሆኑ ወንዶችን መርጧል እናም ያ ነገድ የእርሱ በትረ መንግስት እንደሆነ እንደዚያ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “የይሁዳ ነገድ እንደ በትረ መንግስቴ እንደዚያው ነው” ወይም “ይሁዳ በእርሱ አማካኝነት ህዝቤን የምመራበት ነገድ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 60:8

ሞዐብ የመታጠቢያ ገንዳዬ ነው
እግዚአብሔር ሞዐብ ጠቃሚ አለመሆኑን ሞዐብ የመታጠቢያ ገንዳ ወይም ተራ አገልጋይ እንደሆነ እንደዚያ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሞዐብ ለመታጠቢያ እንደምጠቀምበት ጎድጓዳ ሰሀን ልክ እንደዚያው ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በኤዶምያስ ላይ ጫማዬን እወረውራለሁ
እግዚአብሔር ምናልባትም የኤዶምያስ ባለቤትነትን መውሰዱ እርሱ ባለቤት እንደሆነ ለማሳየት በተምሳሌነት ጫማውን ወደ ምድሪቱ እንደወረወረ እንደዚያ አድርጎ እየተናገረ ነበረ። ነገር ግን አንዳንድ እትሞች ሌላ ትርጉሞች አሏቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “የኤዶምያስ ምድር ባለቤትነትን እኔ ወስጃለሁ” ወይም “የኤዶምያስ ምድር የእኔ እንደሆነ ለማሳየት ጫማዬን ወደ እርሱ ወረወርሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምሳሌያዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 60:10

እግዚአብሔር ግን፣ የጣልከን አንተ አይደለህምን?
መዝሙረኛው ይህንን ጥያቄ እግዚአብሔር የጣላቸው ስለሚመስል ስለዚያ ሀዘኑን ለመግለፅ ተጠቅሞበታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ግን እግዚአብሔር ሆይ አንተ እንደጣልከን እንደዚያ ይመስላል” ወይም “እግዚአብሔር አንተ የተውከን ይመስላል።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ከሰራዊታችን ጋር ወደ ጦርነት አትወጣህም
መዝሙረኛው እግዚአብሔር የእነርሱን ሰራዊት መርዳቱ እግዚአብሔር ሄዶ ከእነርሱ ጋር እንደሚዋጋ እንደዚያ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ወደ ጦርነት ስንሄድ ሰራዊታችንን አንተ አትረዳም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከንቱ ነው
“ዋጋቢስ ነው”

ድል ማድረግ ይሆናል
ጠላታችንን እናሸንፋለን

እርሱ ጠላቶቻችንን ይረጋግጣል
መዝሙረኛው እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን እንዲያሸንፉ የእነርሱን ሰራዊት መርዳቱ እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን እንደሚረጋግጥ እንደዚያ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ ጠላቶቻችንን እንድንረጋግጥ ያስችለናል” ወይም “እርሱ ጠላቶቻችንን ለማሸነፍ ብቁ ያደርገናል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 61

1 እግዚአብሔር ሆይ፣ ጩኸቴን ስማ ጸሎቴንም አድምጥ። **2** ልቤ በዛለ ጊዜ ከምድር ዳርቻዎች ወደ አንተ እጣራለሁ ከእኔ ይልቅ ከፍ ወዳለው ዐለት ምራኝ። **3** አንተ መጠጊያዬ ከጠላትም የምከለልብህ ፅኑ ግንብ ሆነኸኛልና። **4** በማደሪያህ ለዘላለም ልኑር በክንፎችህም ጥላ ልከለል። ሴላ **5** እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ ስእለቴን ሰምተሃል ስምህን የሚያከብሩ ሰዎችን ርስት ለእኔ ሰጠህ። **6** የንጉሡን ዕድሜ አርዝመው ዘመኑንም እስከ ብዙ ትውልዶች ድረስ ጨምርለት። **7** ለዘላለም በእግዚአብሔር ፊት ይንገሥ። **8** ስእለቴን በየቀኑ እንድፈጽም ለስምህ ለዘላለም የምስጋና መዝሙር አቀርባለሁ።

Psalms 61:1

አጠቃላይ መረጃ፡-
ትይዩነት/ተመሳሳይነት በዕብራውያን ግጥም የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ፡-
ይህ መዝሙር ስለ እግዚአብሔር ታማኝነት ነው።

ለመዘምራን አለቃ
“ይህ አምልኮ ላይ እንዲጠቀምበት ለመዘምራኑ አለቃ ነው።”

ክር ባለው የሙዚቃ መሳሪያ
“ሰዎች ይህንን መዝሙር ክር ባለው የሙዚቃ መሳሪያ መጫወት አለባቸው”

የዳዊት መዝሙር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ዳዊት መዝሙሩን ፅፎታል ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት ዘይቤ ነው

ጩኸቴን ስማ እግዚአብሔር ሆይ፣ ፀሎቴንም አድምጥ
እነዚህ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ሆይ አድምጠኝ ፀሎቴንም መልስ” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ከእኔ ይልቅ ከፈ ወዳለው አለት ምራኝ
እዚህ ላይ ጸሐፊው እግዚአብሔር እርሱ ለመጠለል ወደላይ ሊወጣ የሚችልበት ከፍ ያለ አለት እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በጠላት ፊት ፅኑ ግንብ
እዚህ ላይ ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር እርሱ ከጠላቶቹ መከለያን የሚያቀርብ “ፅኑ ግንብ” እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከጠላቶቼ የሚከልለኝ ፅኑ ግንብ” ወይም “ከጠላቶቼ ጠብቆ እንደሚያቆየኝ ፅኑ ግንብ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 61:4

በክንፎችህ ጥላ ስር መሸሸግ
ለጥበቃ ወደ እግዚአብሔር መሄድ በእርሱ ውሰጥ መሸሸግ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ጥበቃ እርሱ ህፃን ጫጩቷን በክንፎችዋ ስር እየጠበቀች እንዳለች ዶሮ እንደሆነ አድርጎ የሚናገር ሁለተኛ ተለዋጭ ዘይቤ አለ። አማራጭ ትርጉም፡- “የዶሮ ጫጩት በእናቱ ክንፎች ስር የተጠበቀ እንደሆነ እንደዚይ ወደ አንተ ለጥበቃ መሄድ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ርስትን ለእኔ ሰጠህ
ጸሐፊው የእግዚአብሔር በረከቶች እርሱ የተቀበላቸው ርስቶች እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “በረከቶችን አንተ ሰጥተኸኛል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ስምህን የሚያከብር
እዚህ ላይ “ስምህ” ማለት እግዚአብሔር ራሱ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተን የሚያከብር” ወይም “ለአንተ አስደናቂ አክብሮት ያለው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 61:6

ታረዝማለህ.....ብዙ ትውልዶችን
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ሀሳቡ የተደጋገመው ለአፅንኦት ነው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

የንጉሱን እድሜ ታረዝማለህ
“የንጉሱን ህይወት ትቀጥላለህ” ወይም “የንጉሱ ህይወት ለረጅም ጊዜ እንዲቆይ ታደርጋለህ”

የእርሱ አመታትም እንደ ብዙ ትውልዶች ይሆናሉ
እዚህ ላይ “አመታት” ምን ያህል ንጉሱ እንደሚኖር ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ ለብዙ ትውልዶች ይኖራል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ለዘልአለም በእግዚአብሔር ፊት ይኖራል
እዚህ ላይ “በእግዚአብሔር ፊት መኖር” በእግዚአብሔር ህልውና ውስጥ መሆን ወይም ከእግዚአብሔር ጋር መሆን ማለት ነው። ይህ በትርጉሙ ውስጥ በግልፅ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ለዘልአለም ከእርሱ ጋር ይሆናል” ወይም “እግዚአብሔር ለዘልአለም ከንጉሱ ጋር ይሆናል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 61:8

ለዘለአለም ለስምህ ምስጋናን እዘምራለሁ
እዚህ ላይ “ስምህ” እግዚአብሔርን ራሱን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሁልጊዜ ለአንተ ምስጋናን እዘምራለሁ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ስእለቴ
ይህ ዘወትር ለእግዚአብሔር መስእዋት የመስጠት ቃልኪዳንን ያመለክታል።

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 62

1 ድነቴ የሚመጣው ከእርሱ ስለሆነ እግዚአብሔርን ብቻ በጸጥታ እጠብቃለሁ። **2** ዐለቴና መድኃኒቴ እርሱ ብቻ ነው መጠጊያዬም እርሱ ነው፤ ከቶም አልናወጥም። **3** ሰውን የምታጠቁት እስከ መቼ ነው? ይህን የዘመመ ግድግዳ የተንጋደደ ዐጥር ሁላችሁ ገፍታችሁ ልትጥሉት ትፈልጋላችሁ? **4** እነርሱ የሚፈልጉት እርሱን ከክብሩ ለማዋረድ ስለሆነ በእርሱ ላይ ሐሰት መናገር ይወዳሉ፤ በአፋቸው ይመርቁታል፤ በልባቸው ግን ይረግሙታል። ሴላ **5** እግዚአብሔርን ብቻ በጸጥታ እጠብቃለሁ **6** ዐለቴና መድኃኒቴ እርሱ ብቻ ነው። መጠጊያዬም እርሱ ነው፤ ከቶም አልናወጥም። **7** ድነቴና ክብሬ ከእግዚአብሔር ነው እርሱ መጠጊያ ዐምባዬና መሸሸጊያ ነው። **8** ሰዎች ሆይ፣ ሁልጊዜ በእርሱ ታመኑ በፊቱም ልባችሁን አፍስሱ እግዚአብሔር ለእኛ መጠጊያችን ነውና። ሴላ **9** ከዝቅተኛ ወገን መወለድ ከንቱ ነው፣ ከከፍተኛ ወገን መወለድም ሐሰት ነው ሚዛን ላይ ከፍ ብለው ቢታዩም ሁሉም በአንድነት ከነፋስ የቀለሉ ናቸው። **10** በዝርፊያ አትተማመኑ በቅሚያ በተገኘ ሀብትም ተስፋ አታድርጉ በዚህ አትበለጽጉምና ልባችሁ እነርሱ ላይ አታድርጉ። **11** እግዚአብሔር አንዴ ተናገረ እኔም ይህን ሁለቴ ሰማሁ። ኃይል የእግዚአብሔር ነው። **12** ጌታ ሆይ፣ የኪዳን ታማኝነት የአንተ ነው አንተ ለእያንዳንዱ፣ እንደ ሥራው ትከፍለዋለህ።

Psalms 62:1

አጠቃላይ መረጃ፡-
ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ፡-
ይህ መዝሙር ስለ እግዚአብሔር ታማኝነት ነው።

ለመዘምራን አለቃ
“ይህ ለመዘምራኑ መሪ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ነው።”

ኤዶታም
አንዱ የዳዊት የመዘምራን አለቃ የዚህ አይነት ስም ነበረው። ይህ ምናልባት እርሱን ያመለክታል። ይህንን በመዝሙረ ዳዊት 39:1 እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

የዳዊት መዝሙር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ዳዊት መዝሙሩን ፅፎታል ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት ዘይቤ ነው

መድሀኒቴ ከእርሱ ዘንድ ይመጣል
“የሚታደገኝ እርሱ ነው” ወይም “የሚያድነኝ እርሱ ነው”

አለቴ እና መድሀኒቴ እርሱ ብቻ ነው
ጸሐፊው የእግዚአብሔር እርሱን የመከላከል ችሎታን እግዚአብሔር አለት እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔን ሊከላከልልኝ እና ሊያድነኝ የሚችለው እርሱ ብቻ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ከፍ ያለ ግንቤ ነው
ጸሐፊው የእግዚአብሔር እርሱን የመከላከል ችሎታን እግዚአብሔር ከፍ ያለ ግንብ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ ከጠላቶቼ እጅ ያስመልጠኛል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እጅግ አልናወጥም
ይህ በገቢር/አድራጊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ምንምነገር ከቶ ሊያናውጠኝ አይችልም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 62:3

እናንተ ሁላችሁ
“የእኔ ጠላቶች” ወይም “ሁሉም የእኔ ጠላቶች”

እስከ መቼ.....ሰውን ታጠቃላችሁ.....ወይም የተንጋደደ አጥርን
ዳዊት መደናገጡን ለመግለፅ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄን ይጠቀማል። መልስ አይጠበቅም። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላቶቼ እኔን ማጥቃት መቼም ቢሆን የሚያቆሙ አይመስልም። በአንተ ፊት ልክ እንደ አዘነበለ ግንብ ወይም እንደ ተሰበረ አጥር ደካማ እንደሆንሁ ይሰማኛል። (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰውን ማጥቃት
“እኔን ማጥቃት”

ከእርሱ ጋር መክረዋል
“እነርሱ አስበዋል” ወይም “እነርሱ አቅደዋል”

ከእርሱ ጋር መምከር ... እርሱን ማምጣት.....እርሱን መባረክ.... እርሱን መርገም
በእነኚህ ጥቅሶች ውስጥ ዳዊት ራሱን “እርሱ” እያለ ይጠቅሳል።

በአፋቸው
ይህ ንግግራቸውን ወይም ቃላታቸውን ያመለክታል። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በልባቸው ውስጥ
ይህ ሀሳባቸውን ያመለክታል። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 62:5

ተስፋዬ በአንተ ላይ ተቀምጧል
“ተስፋዬን በእርሱ ውስጥ ስለ አስቀመጥሁ”

አለቴ እና መድሀኒቴ እርሱ ብቻ ነው፤ እርሱ ከፍተኛ ግንቤ ነው
ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር እርሱ አለት እና ከፍተኛ ግንብ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። እነኚህ ሁለቱም ተለዋጭ ዘይቤዎች እግዚአብሔር ከአንድ ሰው ጠላቶች እንዴት ጥበቃን እንደሚሰጥ ያሳያሉ። እዚህ ላይ “መድሀኒት” እግዚአብሔር ጸሐፊውን አዳነው ማለት ነው። ይህ በ መዝሙረ ዳዊት 62:2 ላይ አንዴት ተተርጉሞ እንደሆነ ይመልከቱ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አልናወጥም
ይህ በገቢር/አድራጊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ምንም ነገር ሊያናውጠኝ አይችልም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 62:7

ብርቱ አለቴ እና መሸሸጊያዬ በእግዚአብሔር ነው
ጸሐፊው እግዚአብሔር አንድን ሰው ከጠላቶቹ በደህንነት እንደሚጠብቅ አለት እንደሆነ አድርጎ ይናገራል።ደግሞ እግዚአብሔር መከለያን የሚሰጥ መጠለያ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሁልጊዜ እግዚአብሔር ብርታትን እና መሸሸጊያን ይሰጠኛል”(ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ልባችሁን አፍስሱ
ይህ ፈሳሽን ወደ ውጪ እያፈሰሱ እንደሆነ እንደዚያ ለእግዚአብሔር ውስጣዊ ስሜትን መንገር ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥልቃዊ ሀሳብህን ለእግዚአብሄር መስጠት” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእኛ መሸሸጊይ
“እኛ” የሚለው ቃል ዳዊትን እና የሚናገራቸውን ሰዎች ያመለክታል። (አካታች “እኛ” የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 62:9

በዝቅተኛ ደረጃ ያለ ሰዎች ... በከፍተኛ ደረጃ ያለ ሰዎች ሁሉ ውሸት ናቸው
ይህ የሁሉም የሀብት እና ጠቃሚነት ደረጃ ሰዎችን ያመለክታል። ሀረጎቹ “ከንቱ ናቸው” እና “ውሸት ናቸው” አንድ ትርጉም አላቸው። አንድ ሰው በማንም ሰው ላይ በእርግጠኝነት እምነት መጣል አይችልም። አማራጭ ትርጉም፡- “ምንም ያህል አንድ ሰው ብርቱ ቢሆንም እንኳን እምነትህን በእነርሱ ላይ መጣል አትችልም” (ትይዩነት እና ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

ባንድነት ሲመዘኑ፣ ከምንም ነገር የቀለሉ ናቸው
ሁሉንም እንደዚህ አይነት ሰዎች ባንድነት ሚዛን ላይ ብታስቀምጥ ምንም ክብደት አይኖራቸውም። ይህ ምንም ተጨባጭ ዋጋ የላቸውም ማለት ነው።

በጭቆና ወይም በዝርፊያ
እነኚህ ሁለት ቃላት በመሰረቱ አንድ አይነት ትርጉም አላቸው። ከሌላ ሰዎች በመውሰድ ባገኛችሁት ገንዘብ ውስጥ እምነት መጣል አትችሉም። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ምንም ፍሬ አያፈሩምና
ጸሐፊው ሀብታሞች ፍሬ ማፍራት እንደሚችሉ ዛፎች ወይም ሀረግ እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለአንተ ምንም መልካም ነገር አይሰጡህም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ልብህ በእነርሱ ላይ አያተኩር
እዚህ ላይ “ልብ ማተኮር” አንድን ነገር በእጅጉ መመኘት የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱን አትመኝ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 62:11

እግዚአብሔር አንድ ጊዜ ተናገረ፤ እኔም ሁለት ጊዜ ይህን ሰማሁ
ይህ እግዚአብሔር ይህንን ከአንድ ጊዜ በላይ ተናግሯል ማለት ነው።

ሀይል የእግዚአብሔር ነው
እግዚአብሔር በሀይል መገለፁ ሀይል የእርሱ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። “ሀይል” የሚለው ረቂቅ ስም በቅፅል ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ሀያል ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልቱ)

ደግሞም ጌታ ሆይ የቃልኪዳን ታማኝነት የአንተ ነው
እግዚአብሔር በቃልኪዳን ታማኝነት መገለፁ የቃልኪዳን ታማኝነት የእርሱ እንደሆነ ተደርጎ ተረግሯል። “ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም በቅፅል ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ ጌታ ሆይ ለቃልኪዳንህም ደግሞ ታማኝ ነህ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልቱ)

አንተ ለእያንዳንዱ ሰው እንደ ስራው ስለምትከፍል
ጸሐፊው የእግዚአብሔርን ወሮታ መክፈል ለስራ ደሞዝ እንደመክፈል አድርጎ ይናገራል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 63

1 እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ አምላኬ ነህ! ከልቤ አንተን እሻለሁ ውሃ በሌለበት ደረቅና ጭው ያለ ምድረ በዳ ነፍሴ አንተን ተጠማች ሥጋዬም አንተን ናፈቀች። **2** ስለዚህ መቅደስህ ውስጥ አየሁህ ኃይልህንና ክብርህንም ተመለከትሁ። **3** ታማኝነትህ ከሕይወት ይበልጣልና ከንፈሮቼ ያመሰግኑሃል። **4** እንግዲህ በሕይወቴ ዘመን አመሰግንሃለሁ በስምህም እጆቼን አነሣሁ። **5** ሰው መልካም ምግብ በልቶ እንደሚጠግብ ነፍሴ በአንተ ትረካለች፤ ስለዚህ ደስ እያለኝ የምስጋና መዝሙር አቀርብልሃለሁ **6** በመኝታዬ ሆኜ አስታውስሃለሁ፤ ሌሊቱን ሁሉ የአንተን ነገር አስባለሁ። **7** አንተ ረዳቴ ነህና በክንፎችህ ጥላ ውስጥ ሐሤት አደርጋለሁ። **8** ነፍሴ አንተን የሙጥኝ ብላለች ቀኝ እጅህም ደግፋ ይዛኛለች። **9** ነፍሴን ማጥፋት የሚፈልጉ ግን ወደ ምድር ጥልቅ ይወርዳሉ፤ **10** በሰይፍ ይገደላሉ ለቀበሮችም ምግብ ይሆናሉ። **11** ንጉሥ ግን በእግዚአብሔር ደስ ይለዋል በእግዚአብሔ ስም የሚምሉ ሁሉ ይከብራ የሐሰተኞች አንደበትም ትዘጋለች።

Psalms 63:1

አጠቃላይ መረጃ፦
ትይዩነት/ተመሳሳይነት በዕብራውያን ግጥም የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

የዳዊት መዝሙር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) ዳዊት መዝሙሩን ፅፎታል ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት ዘይቤ ነው

በቅንነት
በእውነተኛነት

ነፍሴ አንተን ተጠማች፤ ስጋዬም አንተን ናፈቀች
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ አንድ አይነት ትርጉም አላቸው እንዴት ጸሐፊው ያለቅጥ ከእግዚአብሔር ጋር መሆን እንደሚሻ አፅንዶት ለመስጠትም ባንድነት ይጠቀማሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ሙሉ ሰውነቴ ያለቅጥ ከአንተ ጋር መሆንን ይሻል” (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

በደረቅ እና አድካሚ ምድር
“ሞቃት፣ ደረቅ በረሀ”

Psalms 63:3

የአንተ ቃልኪዳን ታማኝነት ከህይወት የተሻለ ስለሆነ ከንፈሮቼ
“ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም በተውሳከ ግስ ሊተረጎም ይችላል እና “ህይወት” የሚለው ረቂቅ ስም በግስ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አንተ ለቃልኪዳንህ ታማኝ መሆንህን በህይወት መኖርን ከምሰጠው በላይ ከፍ ያለ ቦታ እሰጠዋለሁ ስለዚህ ከንፈሮቼ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ከንፈሮቼ ያመሰግኑሀል
እዚህ ላይ “ከንፈሮቼ” ሙሉ ግለሰቡን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “አንተን አመሰግንሀለሁ” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

በአንተ ስም እጆቼን ወደላይ አነሳለሁ
እዚህ ላይ “በአንተ ስም” “ለአንተ” ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “አንተን አመልካለሁ ለአንተም እፀልያለሁ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 63:5

የመቅኒ እና ስብ ማዕድ እንደተመገብኩ እንደዚያ ይሆናል
እዚህ ላይ ጸሐፊው እግዚአብሔርን ማወቅ እና ማምለክ መልካም ማዕድን ከመብላት ይበልጥ የሚያረካ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “ስብ እና የተመረጠ ምግብን ከበላ ሰው ይበልጥ ደስተኛ እሆናለሁ” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በደስታ በተሞሉ ከንፈሮቼ አፌ አንተን ያመሰግናል
እዚህ ላይ “በደስታ የተሞሉ ከንፈሮቼ ኣአፌ” የሚለው እግዚአብሔርን በደስታ የሚያመሰግኑትን ግለሰቦች በሙሉ ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “በደስታ አመሰግንሀለሁ” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

በመኝታዬ ላይ ስለ አንደ ባሰብሁ ጊዜ....በለሊቱ ጊዜ ውስጥ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች አንደ አይነት ትርጉም አላቸው። ሀሳቦቹ ጸሐፊው ምን ያህል ስለ እግዚአብሔር እንደሚያስብ አፅንዖት ለመስጠት ነው የተደጋገሙት። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 63:7

በክንፎችህ ጥላ ስር ደስ ይለኛል
ጸሐፊው እግዚአብሔር ልጁን በክንፎቹ ስር የሚከላከል ወፍ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “አንተ ስለምትጠብቀኝ እደሰታለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተን አጥብቄ እይዛለሁ
“እፈልግሀለሁ” ወይም “አንተ ላይ እተማመናለሁ”

ቀኝ እጅህ ይደግፈኛል
እዚህ ላይ ቀኝ እጅ ለብርታት እና ሀይል ተምሳሌትነት ይጠቅማል። አማራጭ ትርጉም፦ “አንተ ትደግፈኛለህ” ወይም “አንተ ወደላይ ታነሳኛለህ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 63:9

ወደ ምድር ጥልቅ ክፍል ውሰጥ ይወርዳሉ
ይህ ማለት ይሞቱ እና ወደ ሙታን መኖሪያ ይሄዳሉ። ይህ በትርጉም ውስጥ በግልፅ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሞተው ወደ ሙታን መኖሪያ ይወርዳሉ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እጃቸው ሰይፍን ለሚጠቀሙ ለእነርሱ ታልፈው ይሰጣሉ
እዚህ ላይ “ሰይፍ” በጦርነት ውስጥ ሞትን ይወክላል እና “እጃቸው ሰይፍን ለሚጠቀሙ ለእነርሱ” በጦርነት ውስጥ የሚገሏቸውን ጠላቶቻቸውን ይወክላል። ይህ በገቢር/አድራጊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር በጦርነት ውስጥ እንዲሞቱ ያደርጋል” (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ለቀበሮዎች ምግብ ይሆናሉ
እዚህ ላይ “እነርሱ” በጦርነት የሞቱትን የእነርሱን ሬሳ ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ቀበሮዎች ሙት ሰውነታቸውን ይበሉታል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀበሮዎቹ **the**
እዚህ ላይ “ቀበሮዎች” ረጅም እግር ያላቸው የዱር ውሻ አይነት ናቸው። የበሰበሰ ስጋ፣ የአደን እንስሳትን እና ፍራፍሬ ይመገባሉ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 63:11

ንጉሱ . . . ይለዋል
ዳዊት ስለ ራሱ እየተናገረ ነው። ይህ በትርጉሙ ውስጥ በግልፅ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ የእስራኤል ንጉስ ይለኛል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ መማል.....በእርሱ መኩራት
“እርሱ” የሚለው ቃል “እግዚአብሔር”ን ያመለክታል።

ሀሰትን የሚናገሩ ሰዎች አፍ ግን ይዘጋል
እዚህ ላይ “አፍ” የሰውን ሁለንተና ይወክላል። ይህ በገቢር/አድራጊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ግን ውሸታሞቹን ዝም ያሰኛል” ወይም “እግዚአብሔር ግን የሚዋሹትን ሰዎች ዝም ያሰኛል” (ወካይ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 64

1 እግዚአብሔር ሆይ፣ ድምፄን ስማ የብሶቴን ቃል አድምጥ፤ ከሚያስፈራ የጠላት ዛቻ ሕይወቴን አድናት **2** ከክፉ አድራጊዎች ዐድማ ሰውረኝ ከዐመፀኞችም ሤራ አድነኝ። **3** እነርሱ ምላሳቸውን እንደ ሰይፍ ስለዋል መርዘኛ ቃላቸውንም እንደ ፍላጻ ያነጣጥራሉ **4** ካሸመቁበት ቦታ ሆነው ንጹሑን ሰው ይነደፋታል ድንገት ይነድፉታል፤ አይፈሩምም። **5** ክፉ ዕቅድ ለማውጣት እርስ በርስ ይመካከራሉ፤ ወጥመድ ለመዘርጋትም በምስጢር ይነጋገራሉ፤ «ማንስ ሊያድን ይችላል?» ይባባላሉ። **6** እነርሱ ክፉ ዕቅድ አወጡ፤ በሐሳባቸውም፣ «በጥንቃቄ ዕቅድ አውጥተናል» ይላሉ። የሰው ሐሳብና ልብ በጣም ጥልቅ ነው። **7** እግዚአብሔር ግን በፍላጻው ይነድፋቸዋል እነርሱም በድንገት ይቆስላሉ። **8** በገዛ ምላሳቸው ያሰናክላቸዋል ጥፋትንም ያመጣባቸዋል የሚያዩአቸው ሁሉ በመገረም ራሳቸውን ይነቀንቃሉ። **9** የሰው ልጆች ሁሉ ይፈራሉ የእግዚአብሔር ያደረገውንም በይፋ ይናገራሉ። **10** ጻድቅ በያህዌ ደስ ይለዋል፤ እርሱንም መጠጊያው ያደርጋል ልበ ቅኖችም ሁሉ በእርሱ ይመካሉ።

Psalms 64:1

አጠቃላይ መረጃ፡-
ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ፡-
ይህ መዝሙር ለእርዳታ ፀሎት ነው።

ለመዘምራን አለቃ
“ይህ ለመዘምራኑ መሪ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ነው።”

የዳዊት መዝሙር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ዳዊት መዝሙሩን ፅፎታል ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት ዘይቤ ነው

ማቆየት
ማዳን

ከክፉዎች ሚስጢራዊ ሴራ ሰውረኝ
እዚህ ላይ “መሰወር” ጥበቃን ይወክላል እናም “የክፉዎች ሚስጥራዊ ሴራ” ክፉዎች በሚስጥር ዳዊት ላይ ሊያረጉበት ያቀዱትን ጉዳት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉዎች በሚስጥር እኔ ላይ ሊያደርጉ ከአቀዱት ጉዳት ጠብቀኝ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ከአመፅ
“ሰውረኝ” የሚለው ቃል በፊተኛው ሀረግ ግልፅ ሆኗል እናም እዚህ መድገም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከአመፅ ሰውረኝ” ወይም “ከአመፅ ጠብቀኝ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

የጭካኔ አድራጊዎች አመፅ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- “አመፅ” የሚያመለክተው 1) በጩኸት የተሞላ ረብሻ አማራጭ ትርጉም፡- “ጭካኔ አድራጊዎች የሚያደርጉት በጩኸት የተሞላ ረብሻ” ወይም 2) በጩኸት የተሞላን ረብሻ የሚያደርግ ህዝብ ስብስብ። አማራጭ ትርጉም፡- “በጩኸት የተሞላ የጭካኔ አድራጊዎች ህዝብ ስብስብ”

Psalms 64:3

ምላሳቸውን እንደ ሰይፍ ስለዋል
ጸሐፊው የጠላቶቹ ምላስ እንደ ሰይፍ ሹል እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። እዚህ ላይ “ምላስ” ጠላቶች የሚናገሩትን መጥፎ ቃላት ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ የሚናገሩአቸው መጥፎ ነገሮች እንደ ሾለ ሰይፍ ያሳምሙኛል” (ተነፃፃሪ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ቀስት፣ መራራ ቃላት
ጸሐፊው የጠላቶቹ መራራ ቃላት እርሱ ላይ እየተተኮሱ እንዳሉ ቀስት አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “እንደ ቀስት እኔን የሚወጉ መራራ ቃላት”(ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 64:5

እኛን ማን ያየናል?
ክፉዎች ማንም እንደማያያቸው ስለሚያስቡ ለጥያቄያቸው መልስ አልጠበቁም። አማራጭ ትርጉም፡- “እኛ ምን እንደምናደርግ ማንም አያይም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው የውስጥ ሀሳቡና ልቡ ጥልቅ ናቸው
ጸሐፊው የሰው “የውስጥ ሀሳብ” እና “የሰው ልብ” ማንም እስከ መላ መነሻ መንገዱ ሊመረምር እንደማይችለው ጥልቅ የውሀ አካል እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ውስጣዊ ሀሳብ.... የሰው ልብ
እነኚህ ሁለቱም ሀረጎች የሰው የግል ወይም ውስጣዊ ሀሳቦችን ያመለክታሉ። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 64:7

አጠቃላይ መረጃ፡-
ጸሐፊው ለ”ክፉዎች” መናገሩን ቀጥሏል መዝሙረ ዳዊት 64:01።

እግዚአብሔር ግን ይመታቸዋል.... በእርሱ ቀስቶች
ጸሐፊው የእግዚአብሔር የክፉዎች ቅጣት እግዚአብሔር እነርሱ ላይ ቀስቶችን እየመታ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ እንዲሰናከሉ ይደረጋሉ
ጸሐፊው እግዚአብሔር የክፉዎችን እቅድ እንዲከሽፍ ማድረጉ እግዚአብሔር በጎዳናቸው ላይ እንዲሰናከሉ እንዳደረጋቸው አድርጎ ይናገራል። ይህ በገቢር/አድራጊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር እነርሱ እንዲሰናከሉ ያደርጋል” ወይም “እግዚአብሔር የእነርሱ እቅድ እንዲከሽፍ ያደርጋል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የገዛ ምላሳቸው እነርሱን ስለሚቃወም
እዚህ ላይ “ምላስ” እነርሱ የሚናገሩትን ቃላት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ የሚናገሩት ቃላቶች ራሳቸውን የሚቃወሙ ስለሆኑ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ምን እንዳደረገ
“እግዚአብሔር ምን እንዳደረገ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 64:10

በእርሱ ውስጥ መሸሸግ
ለጥበቃ ወደ እግዚአብሔር መሄድ በእርሱ ውስጥ መሸሸግ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ወደ እርሱ ለጥበቃ መሄድ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ልበ ቅኖችም ሁሉ በእርሱ ይኮራሉ
እዚህ ላይ “ልበ ቅኖች” የእግዚአብሔር ወይም ፃድቅ የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የእግዚአብሔር የሆኑ ሰዎች ሁሉ እርሱን ያመሰግናሉ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 65

1 እግዚአብሔር ሆይ፣ በጽዮን ለአንተ ምስጋና ይገባል፤ ለአንተ የተሳልነውንም እንፈጽማለን። **2** ሥጋ ለባሽ ሁሉ ጸሎትን ወደምትሰማ ወደ አንተ ይመጣል። **3** ኃጢአት በርትቶብን በነበረ ጊዜ አንተ መተላለፋችንን ይቅር አልህ። **4** አንተ የመረጥኸው፣ በአደባባይህም እንዲኖር ወደ አንተ ያቀረብኸው ሰው ቡሩክ ነው። ከተቀደሰው መቅደስህ፣ ከቤትህም በረከት እንጠግባለን። **5** የምድር ዳርቻዎችና ከባሕሩ ማዶ ርቀው ያሉ ሁሉ ተስፋ አዳኛችን እግዚአብሔር ሆይ፣ በጽድቅህ ድንቅ አሠራር መልስልን። **6** በኃይልህ ተራሮችን አጽንተሃል ብርታትንም ታጥቀሃል። **7** አንተ የባሕሮችን ማስገምገም የማዕበላቸውንም ጩኸት የሕዝቦችንም ውካታ ጸጥ ታሰኛለህ። **8** ርቀው በምድር ዳርቻዎች ያሉ ካደረግኸው ድንቅ ሥራህ የተነሣ ይደነግጣሉ። ምሥራቅና ምዕራብ በደስታ እልል እንዲሉ ታደርጋቸዋለህ። **9** ዝናብ በማዝነብ ምድርን ትጐበኛለህ፤ ፍሬያማ በማድረግም ታበለጽጋታለህ። ለሰው ልጆች እህልን ይሰጡ ዘንድ የእግዚአብሔር ወንዞች ውሃን የተሞሉ ናቸው። አንተ እንዲህ እንዲሆን ወስነሃል። **10** ትልሟን ታረሰርሳለህ ወጣ ገባውን ታስተካክላለህ ዐፈሩን በካፊያ ታለሰልሳለህ ቡቃያዋንም ትባርካለህ። **11** ለዓመቱ በጐነትህን ታቀዳጀዋለህ፤ ሰረገላህም በረከትን ሞልቶ ይፈስሳል። **12** የምድረ በዳው ግጦሽ ቦታ እጅግ ለመለመ ኮረብቶችም ደስታን ለበሱ። **13** መሰማሪያዎች መንጋ በመንጋ ሆኑ ሸለቆዎች በሰብል ተሞሉ እልል እያሉም ዘመሩ።

Psalms 65:1

አጠቃላይ መረጃ፡-
ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ፡-
ይህ መዝሙር የምስጋና መዝሙር ነው።

ለመዘምራን አለቃ
“ይህ ለመዘምራኑ መሪ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ነው።”

መዝሙር። የዳዊት መዝሙር
“ይህ ዳዊት የፃፈው መዝሙር ነው”

ለአንተ፣ በፅዮን ላለህ እግዚአብሔር፣ ምስጋናችን ይገባሀል
ይህ ምስጋና በገዛ ራሱ መተግበር የሚችል ግለሰብ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለአንተ ብቻ በፅዮን ላለህ እግዚአብሔር ምስጋናችንን እናቀርባለን” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ስዕለታችንን ለአንተ እናደርሳለን
ይህ በገቢር/አደራጊ መልኩ መገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እናደርጋለን ብለን ለአንተቃል የገባነውን እናደርጋለን” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ኀጢአት በእኛ ላይ በረታብን
ዳዊች ስለ ሀጢአት ሊያሸንፍ ወይም ሊጨቁን የሚችል ግለሰብ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “የገዛ ራሳችን ሀጢአት እንደሚያሸንፈን ልክ እንደዚያ ነው” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱን ይቅር ትላቸዋለህ
“እነርሱ” የሚለው ቃል የእኛ “ሀጢአትን” ያመለክታል።

Psalms 65:4

አንተ የመረጥከው... የአንተ ሕዝብ
አንተ እና የአንተ የሚሉት ቃላት በዚህ ጥቅስ ውስጥ እግዚአብሔርን ያመለክታሉ።

በአንተ ቤተ መንግስቶች ውስጥ መኖር
ይህ ግነት ያ ሰው እግዚአብሔርን ለማምለክ በጣም አዘውትሮ ቤተ መቅደስ ውስጥ እንደሚሆን ይገልፃል። አማራጭ ትርጉም፡- “ብዙ ጊዜ በአንተ ቤተ መንግስትህ ውስጥ ማምለክ” (ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከቤትህ በረከት እንረካለን፣ ከተቀደሰው ቤተ መቅደስህም
ይህ በገቢር/አድራጊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የቤትህ በረከት፣ የተቀደሰውም ቤተ መቅደስህ እኛን ያረካናል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ እንሆናለን
እዚህ ላይ እኛ የሚለው ቃል ዳዊት እና የእስራኤል ህዝብን ያመለክታል፣ እርሱ የሚያናግረውን እግዚአብሔርን ግን አይደለም። (አግላይ እና አካታች “እኛ” የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ ቤት፣ የአንተ ቅዱስ ቤተ መቅደስ
“የተቀደሰ ቤተ መቅደስህ የሆነው የአንተ ቤት”

Psalms 65:5

በፅድቅ
“ምክንያቱም አንደ ፃድቅ ስለሆንህ”

አንተ . . . የሆንከው
“አንተ ነህ”

በምድረ ዳርቻ ሁሉ... ባህር ዳር እስከ ዳር
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “ምድር ሙሉ በሙሉ እና ባህር ዳር እስከ ዳር ከሚኖር ሰዎች ሁሉ” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

በምድር ዳርቻ ሁሉ
ይህ በምድር ላይ ሁሉ የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታል። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 65:6

ብርታትን የታጠቅኸው አንተ
ጸሐፊው እግዚአብሔር እርሱ ብርታቱን ልክ እንደ ቀበቶ እንደለበሰው አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ በጣም ጉልበተኛ እንደሆንህ ማሳየት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የባህሮችን ማጓራት፣ የእነርሱ ሞገድ ማጓራት
እነዚህ ሁለት ሀረጎች አንድ አይነት ትርጉም አላቸው እናም አድማጩ ወይም አንባቢው ላይ ጉልህ አሻራ ለመፍጠር ባንድነት እንጠቀማቸዋለን። አማራጭ ትርጉም፡- “የማያቋርጥ የባህሮች ማጓራት” (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ማጓራት
በነፋስ እና በሞገድ የሚፈጠር ሀይለኛ ጩኸት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የህዝቦቹ አመፅ
ይህም ደግሞ እግዚአብሔር ፀጥ የሚያደርገው ነገር ነው።

አመፅ
ሀይለኛ ጩኸት

Psalms 65:8

ማስረጃ
ማረጋገጫ ወይም ሌላ ነገር ትክክል እንደሆነ የሚያሳይ ነገር

አንተ ምስራቅ እና ምዕራብ እንዲደሰቱ ታደርጋለህ
“ምስራቁ እና ምዕራቡ” የሚለው ሀረግ በአለም ዙሪያ ሁሉ የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ ሁሉም ቦታ ያሉ ሰዎች በደስታ እንዲጮሁ ታደርጋለህ” (ምትክ ስም እና ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

ምድርን መርዳት
ይህ የምድርን አፈር ያመለክታል።

አንተ በጣም አበለፀግኸው
“አንተ መልካም ነገሮች እርሱ ላይ እንዲበቅሉ አፈሩን በጣም መልካም አደረግኸው”

የእግዚአብሔር ወንዝ በውሀ የተሞላ ነው
ይህ በሰማይ ውስጥ ያለን እግዚአብሔር ምድርን ለማጠጣት እና ጅረትን ለመሙላት የሚልከውን የውሀ አቅርቦት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጅረቶችን በውሀ ሞላህ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 65:10

አንተ... የአንተ
x

Psalms 65:13

መስኮቹ መንጎችን ለብሰዋል
ጸሐፊው መስኮቹ በጣም በመንጋ መሸፈናቸው መስኮቹ ልብስ የለበሱ የሚመስል አንደሆነ ይናገራል።

መስኮቹ
እንስሳቶች ሳር ላይ የሚመገቡበት ሰፊ ማሳ

መንጋዎች
የእንስሳት ቡድን፣ በግ እና ፍየል የመሳሰሉት

እነርሱ በደስታ ይጮሀሉ፣ እናም ይዘምራሉ
መስኮቹ፣ ኮረብታዎቹ እና ሸለቆዎቹ እነርሱ በደስታ እየዘመሩ እና እየጮሁ እንደሚመስሉ ሁሉ በጣም ለጋስ ናቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ እንደ ደስተኛ የሚዘምሩ ሰዎች ናቸው” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ይጮሀሉ
እነርሱ የሚለው ቃል መስኮቹን እና ሸለቆዎቹን ያመለክታል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 66

1 ምድር ሁሉ ለእግዚአብሔር እልል በሉ **2** ለስሙ ክብር ዘምሩ ምስጋናውን አድምቁ። **3** እግዚአብሔርን፣ «ሥራህ እንዴት ድንቅ ነው! ከኃይልህ ታላቅነት የተነሣ ጠላቶችህ ይገዙልሃል። **4** ምድር ሁሉ ያመልክሃል በዝማሬም ያመሰግኑሃል ለስምህም ይዘምራሉ» ባሉት። ሴላ **5** ኑ የእግዚአብሔርን ሥራ እዩ ለሰው ልጅ ያደረገውስ አስፈሪ ነው። **6** ባሕሩን ደረቅ ምድር አደረገው ወንዙን በእግር ተሻገሩ እኛም እርሱ ባደረገው ነገር ደስ ብሎናል። **7** በኃይሉ ለዘላለም ይነግሣል ዐይኖቹ ሕዝቦችን ይመለከታሉ። እንግዲህ ዐመፀኞች ቀና ቀና አይበሉ። ሴላ **8** ሕዝቦች ሁሉ እግዚአብሔርን ባርኩ የምስጋናውንም ድምፅ አሰሙ። **9** በሕያዋን መካከል አኑሮናል እግራችን እንዲንሸራተት አልፈቀደም። **10** እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ ፈተንኸን ብር እንደሚፈተን እኛን ፈተንኸን **11** ወደ ወጥመድ አገባኸን በጀርባችንም ከባድ ሸክም ጫንህብን። **12** ሰዎች ራሳችን ላይ እንዲፈነጩ አደረግህ በእሳትና በውሃ መካከል አለፍን የኃላ ኃላ ግን ወደ ሰፊ ስፍራ አመጣኸን። **13** የሚቃጠል መሥዋዕት ይዤ ወደ ቤትህ እመጣለሁ ስእለቴንም ለአንተ እከፍላለሁ። **14** ይህም መከራ በደረሰብኝ ጊዜ ከአፌ የወጣ፣ በከንፈሮቼም የተናገርሁት ስእለት ነው። **15** የሰቡ እንስሶችን የሚቃጠል መሥዋዕት አድርጌ፣ እንዲሁም መዓዛው ደስ የሚያሰኝ የአውራ በግ መሥዋዕት አቀርብልሃለሁ። **16** እናንት እግዚአብሔርን የምትፈሩ ሁሉ ኑና ስሙ፣ ለነፍሴ ያደረገላትን እነግራችኃለሁ። **17** በአፌ ወደ እርሱ ጮኽሁ፤ በአንደበቴ አመሰገንሁት። **18** በውስጤ ኃጢአት ይዤ ቢሆን ኖሮ ጌታ አይሰማኝም ነበር። **19** አሁን ግን እግዚአብሔር በእርግጥ ሰምቶኛል ጸሎቴንም አድምጦአል። **20** ጸሎቴን ያልናቀ ምሕረቱንም ከእኔ ያላራቀ እግዚአብሔር ይመስገን።

Psalms 66:1

አጠቃላይ መረጃ፦
ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ፦
ይህ መዝሙር የምስጋና መዝሙር ነው።

ለመዘምራን አለቃ
“ይህ ለመዘምራኑ መሪ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ነው።”

Psalms 66:3

ስራህ እንዴት አስደናቂ ነው
የእግዚአብሔር ስራዎች እኛ በአክብሮት እና በፍርሀት ውስጥ እንድንሆን ያደርጉናል ምክንያቱም እርሱ ሀይለኛ እና ቅዱስ እንደሆነ እናውቃለን።

በሀይልህ ታላቅነት
“ምክንያቱም አንተ ትልቅ ሀይል አለህ”

ምድሩ ሁሉ አንተን ያመልካሉ
ይህ በምድር ላይ የሚኖሩ ሰዎችን ሁሉ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “በምድር ላይ ያሉ ሰዎች ሁሉ አንተን ያመልካሉ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ለአንተ ስም ይዘምራሉ
እዚህ ላይ “የአንተ ስም” እግዚአብሔር ራሱን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “እነርሱ አንተን ያመልካሉ ያከብራሉም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 66:5

እርሱ... የእርሱ... እርሱ
እዚህ ላይ እነኚህ ቃሎች ሁሉ እግዚአብሔርን ያመለክታሉ።

እርሱ ለሰው ልጆች ያደረገው ስራው አስፈሪ ነው
“እርሱ ሰዎች የእርሱን ስራ ሲያዩ ፍርሀት እና መደነቅ እንዲሰማቸው ያደርጋል”

የሰው ልጆች
“ሰብአዊነት”

እርሱ ባህሩን ወደ ደረቅ ምድር ቀየረ፤ እነርሱ በባርሩ ውስጥ በእግር ሄዱ
ይህ ቀይ ባህርን መሻገርን ያመለክታል። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 66:8

ለእግዚአብሔር በረከት መስጠት... የእርሱ ምስጋና ድምፅ ይሰማ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሰይ ትርጉም አላቸው። ሀሳቡ እግዚአብሔርን የማመስገን ጠቃሚነትን ለማጉላት ነው የተደገመው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ... የእኛ
እነዚህ ቃላቶች ዳዊትን እና እርሱ የሚያናግራቸው ሰዎችን ያመለክታሉ። (አካታች “እኛ” የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ እግራችን እንዲንሸራተት አልፈቀደም
ጸሐፊው የእግዚአብሔርን ጥበቃ ሲገልጽ ሕዝቡ ሲጓዙ ወይም ከገደል አፋፍ ሊወድቁ ሲሉ እርሱ እንዳይንሸራቱ ሕዝቡን እንደሚጠብቅ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “እርሱ ወደ አደጋ እንድንወድቅ አልፈቀደም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 66:10

አንተ ወደ መረብ አመጣኸን
ጸሐፊው የእግዚአብሄር ቅጣትን እግዚአብሔር ህዝቡን በመረብ እንደያዘ አድርጎ ይናገረዋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መረብ
ለወፍ ወይም ለእንስሳ ወጥመድ

አንተ በጀርባችን ላይ ከባድ ሸክምን አስቀመጥህ
ጸሐፊው ህዝቡ የተቋቋመውን በእነርሱ ጀርባ ላይ ከባድ ጭነት መሸከም እንዳለባቸው አድርጎ ይናገረዋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ሰዎች በራሳችን ላይ እንዲጋልቡ አደረግህ
ይህ በጦርነት ውስጥ ክፉኛ የመሸነፍ ምስል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ይህ የእኛ ጠላቶች በጦርነት አሸንፈውን እና ከዛም በወደቀው ሰውነታችን ላይ ሰረገላቸውን እንደነዱብን እንደዛ ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በእሳት እና በውሀ ውስጥ ማለፍ
እግዚአብሄር እነርሱን እንደ እሳት እና ጎርፍ ባሉ ተፈጥሮአዊ አደጋዎች ፈተናቸው። አማራጭ ትርጉም፦ “በእሳት እና ጎርፍ እንደሚሰቃዩ ሰዎች እኛም ተሰቃየን” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሰፊ ቦታ
ጸሐፊው የእስራኤል ህዝብ አሁን ስላለው በረከት ሲናገር አስተማማኝ ድነት በሚኖራቸው በሰፊና ክፍት ስፍራ እንዲመጡ እንደተደረገ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በደህንነት በምንኖርበት በክፍት ስፍራ”(ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 66:13

ከንፈሮቼ ቃል የገቡትንና አፌ የተናገረውን
እዚህ ላይ “ከንፈሮቼ” እና “አፍ” የተነገሩትን የተስፋ ቃላት የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ የሰጠሁትን ተስፋ ቃል” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

የሚቃጠል መስዋዕት
“ለመስዕዋት የቀረቡ በጎች ሲቃጠሉ የሚኖረው ሽታ”

Psalms 66:16

ለነፍሴ ያደረገላትን ነገር እናገራለሁ
“ነፍስ” የሚለው ቃል የሰውን ሁለንተና ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ ለእኔ የሰራውን ስራ እኔ እነግራችኋል” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ በአፌ ወደ እርሱ ጮኽኩኝ
“አፍ” የሚለው ቃል ወደ እግዚአብሔር የሚጮኹትን ሰዎች ሁለንተና የሚወክል ነው። (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ በአንደበቴ ተመሰገነ
እዚህ ላይ “አንደበት” ንግግርን ይወክላል። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱን በአንደበቴ አመሰገንሁት” ወይም “እርሱን አመሰገንሁት” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ሀጢአትን አይቼ
“ሀጢአትን ወድጄ” ወይም “በደልን ይዤ”

እኔን አይሰማኝም ነበር
እዚህ ላይ “አይሰማኝም ነበረ” የሚለው እግዚአብሔር ፀሎቱን አይመልስለትም ነበር የሚል ሀሳብ አለው። ይህ በትርጉሙ ውስጥ ግልፅ ሊደረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ወደ እርሱ ስጣራ አይሰማኝም ነበር ” ወይም “ፀሎቴን አይመልስልኝም ነበር” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 66:19

ነገር ግን እግዚአብሔር በእውነት ሰምቶኛል፤ ትኩረት ሰጥቶኛል
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን በአንድ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት እግዚአብሔር ፀሎቱን እንዲሰማለት አፅንኦት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን እግዚአብሔር በእውነት ፀሎቴን ሰምቷል” (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

የፀሎቴን ድምፅ
እዚህ ላይ የጸሐፊው ፀሎት የድምፅ ግላዊ ማንነት ተሰጥቶታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ፀሎቴ” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ፀሎቴን ያልከለከለኝ
እዚህ ላይ “ያልከለከለኝ” የሚለው ፀሎቱን ችላ ማለትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- ”ፀሎቴን ችላ ያላለ”

ወይም የቃል ኪዳን ታማኝነቱን ከእኔ
“ከእኔ አልከለከለም” የሚለው ሀረግ ከዚህ በፊት ከነበረው ሀረግ መረዳት ይቻላል፣ እዚህ ደግሞ ሊደገም ይችላል። “የቃል ኪዳን ታማኝነት” የሚለው ሀሳብ “ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ነው” በሚለው ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የቃል ኪዳኑን ታማኝነት ከእኔ አልመለሰም” ወይም” ከእኔ ጋር ለነበረው ቃል ኪዳን ታማኝ መሆኑን አላቆመም” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 67

1 እግዚአብሔር ይማረን ይባርከንም ፊቱንም በላያችን ያብራ። ሴላ **2** መንገድህ በምድር ላይ ማዳንህም በሕዝቦች ሁሉ መካከል ይታወቅ ዘንድ። **3** እግዚአብሔር ሆይ፣ ሕዝቦች ያመስግኑህ ሰዎች ሁሉ ምስጋና ያቅርቡልህ። **4** አንተ ለሕዝቦች ቅን ስለምትፈርድላቸው የምድር ሕዝቦችን ስለምትመራ ሕዝቦች ሁሉ ደስ ይበላቸው በእልልታም ይዘምሩ። ሴላ **5** እግዚአብሔር ሆይ፣ ሕዝቦች ያመስግኑህ ሰዎች ሁሉ ምስጋና ያቅርቡልህ። **6** ምድር ፍሬዋን ሰጠች አምላካችን እግዚአብሔር ባርኮናል። **7** እግዚአብሔር ባርኮናል የምድር ዳርቻዎች ሁሉ እርሱን ያከብሩታል።

Psalms 67:1

አጠቃላይ መረጃ፦
ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ለመዘምራን አለቃ
“ይህ አምልኮ ላይ እንዲጠቀምበት ለመዘምራኑ አለቃ ነው።”

በበገናዎች
“ሰዎች በገናዎችን ከዚህ መዝሙር ጋር ለጫወቱ ይገባቸዋል”

ፊቱን በላያችን ያብራ
ጸሐፊው እግዚአብሔር ለእነርሱ በቸርነት እንዳደረገላቸው ሲናገር የእግዚአብሔር ፊት በእነርሱ ላይ ብርሀን እንዳበራ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ለእኛ በቸርነት አድርጎልናል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መንገዶችህ በምድር ሁሉ ይታወቁ ዘንድ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰዎች መንገዶችህን በምድር ላይ ያውቁ ዘንድ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ማዳንህን በአህዛብ ሁሉ መካከል
ጸሀፊው እግዚአብሔር እነርሱን ለማዳን ሀይል እንዳለው እያንዳንዱ ሰው እንዲያውቅ ይፈልጋል። ይህ በትርጉሙ ግልፅ ሊደረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አንተ እነርሱን ለማዳን ሀይል እንዳለህ የሀሉም መንግስታት ህዝቦች በሙሉ ያውቁ ዘንድ” (አስጨምሬ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 67:3

አቤቱ አህዛብ ያመስግኑህ... አህዛብ ሁሉ ያመስግኑህ
እግዚአብሔርን የማመስገን አስፈላጊነት አፅንኦት ለመስጠት ሁለተኛው ሀረግ የመጀመርያውን ሀረግ ትርጉም ያጠነክራል። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

አህዛብ... አህዛብን ትመራለህ
እዚህ ላይ “አህዛብ” በምድር ላይ ባሉ መንግስታት በሙሉ የሚኖሩ ሰዎችን የሚወክል ነው። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በፍትህ
“በቅንነት” ወይም “በፍትሀዊነት”

Psalms 67:5

አህዛብ ያመስግኑህ... አህዛብ በሙሉ ያመስግኑህ
እግዚአብሔርን የማመስገን አስፈላጊነትን አፅንኦት ለመስጠት ሁለተኛው ሀረግ የመጀመርያውን ሀረግ ትርጉም ያጠናክራል። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ምድር ፍሬዋን ሰጠች
እዚህ ላይ ጸሐፊው ስለ “ምድር” ሲናገር ለህዝቡ ምርትን ለመስጠት እንደመረጠ አድርጎ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “እኛ ከሰብላችን ብዙ ምርት ሰብስበናል” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 67:7

የምድር ዳርቻ ሁሉ ያከብሩታል
ይህ በየትኛውም ስፍራ የሚገኙ ሰዎች በሙሉ ከእርሱ በረከት የተነሳ እግዚአብሔርን ሊያከብሩት ይገባል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በየትኛውም የምድር ገፅ የሚገኙ ሰዎች በሙሉ ለእርሱ ታላቅ አክብሮት እንዲኖራቸው እፈልጋለሁ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 68

1 እግዚአብሔር ይነሣ የሚጠሉትም ከፊቱ ይበተኑ። **2** ጢስ እንደሚበንን፣ እንዲሁ አብንናቸው፤ ሰም በእሳት ፊት እንደሚቀልጥ እንዲሁ ክፉች ከእግዚአብሔር ፊት ይጥፉ። **3** ጻድቃን ግን ደስ ይበላቸው በእግዚአብሔርም ፊት ሐሤት ያድርጉ ደስታንና ሐሤትን ይሞሉ። **4** ለእግዚአብሔር ዘምሩ፤ ለስሙም የምስጋና መዝሙር አቅርቡ በደመናት ላይ የሚሄደውን ከፍ አድርጉት። ስሙ ያህዌ ነው! በፊቱም ሐሤት አድርጉ። **5** በተቀደሰ ማደሪያው ያለው አምላክ አባት ለሌላቸው አባት ነው። ለመበለቶችም ዳኛ ነው። **6** እግዚአብሔር ብቸኞች በቤተ ሰብ መካከል ያኖራቸዋል፤ እስረኞችን ነጻ አውጥቶ ያስፈነድቃቸዋል፤ ክፉዎች ግን በምድረ በዳ ይኖራሉ። **7** እግዚአብሔር ሆይ፣ በሕዝብህ ፊት ባለፍህ ጊዜ በምድረ በዳ በተጓዝህ ጊዜ፣ **8** በሲና አምላክ በእግዚአብሔር ፊት ምድር ተንቀጠቀጠች ሰማያትም ዶፍ አወረዱ። **9** እግዚአብሔር ሆይ፣ በቂ ዝናብ አዘነብህ ደርቆ የነበረውን ርስትህን አረሰረስህ። **10** ሕዝብህ መኖሪያው አደረጋት፤ እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ ከመልካምነትህ ለድኾች ሰጠህ። **11** እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ቃሉን ሰጠ ቃሉን የሚያውጁትም ብዙ ሰራዊት ናቸው። **12-13** የሰራዊት ነገሥታት ፈጥነው ወደ ኋላ ሸሹ፤ በሰፈር የቀሩ ሴቶችም ምርኮ ተከፋፈሉ በበጎች በረት መካከል ብትገኙ እንኳ በቅጠልያ ወርቅ እንደ ተለበጡ ላባዎች ናችሁ። **14** ሁሉን ቻዩ በዚያ የነበሩትን ነገሥታት በበተነ ጊዜ፣ ከሰልሞን ተራራ እንደሚወርድ በረዶ አደረጋቸው። **15** አንተ ብርቱ የባሰን ተራራ ሆይ፤ እናንት ባለ ብዙ ጫፍ ተራሮች ሆይ፣ እግዚአብሔር ሊኖርበት የመረጠውን ተራራ፣ በእርግጥ እግዚአብሔር ለዘላለም **16** የሚኖርበትን ተራራ ለምን በምቀኝነት ትመለከቱታላችሁ? **17** የእግዚአብሔር ሰረገላዎች እልፍ አእላፍ ነቸው ሺህ ጊዜም ሺህ ናቸው ጌታ በተቀደሰው ቦታ በሲና በመካከላቸው ነው። **18** ወደ ላይ ዐረግህ፣ ምርኮን አጋበስህ እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ በዚያ ትኖር ዘንድ ከአንተ ጋር ከተዋጉት እንኳ ሳይቀር፣ ከሰዎች ስጦታን ተቀበልህ። **19** በየዕለቱ ሸክማችንን የሚሸከምልን መድኃኒታችን የሆነው እግዚአብሔር ይባረክ። ሴላ **20** አምላካችን የሚያድን አምላክ ነው ከሞት ሊታደገን የሚቻለው ጌታ ያህዌ ነው። **21** እግዚአብሔር የጠላቶችን ራስ በኃጢአታቸውም የሚጸኑትን ሰዎች ጠጉራም ዐናት ይፈነክታል። **22** ጌታ እንዲህ አለ፤ «ጠላቶቼን ከባሳን መልሼ አመጣቸዋለሁ፤ ከባሕርም ጥልቅ አውጥቼ አመጣቸዋለሁ፤ **23** እግርህ በጠላትህ ደም እንዲጠልቅ የውሻህም ምላሽ ከጠላትህ ድርሻውን እንዲያገኝ ነው።» **24** አምላክ ሆይ፣ የክብር አካሄድህን፣ አምላኬና ንጉሤ ወደ ቤተ መቅደሱ የሚያደርገውን የክብር አካሄድ አዩ። **25** የሚጫወቱ ከኋላ ሆነው ሲሄዱ መዘምራን ከፊት፤ መሣሪያ መካከላቸው ከበሮ የሚመቱ ደናግል ነበሩ። **26** እግዚአብሔርን በጉባኤ አመስግኑት በእውነት የእስራኤል ዘር የሆናችሁ ያህዌን አመስግኑት። **27** በመጀመሪያ በቁጥር ታናሽ የሆነው የብንያም ነገድ ታየ ቀጥሎም የይሁዳ መሪዎችና ሰራዊቶቻቸው ታዩ፤ በመጨረሻም የዛብሎንና የንፍታሌም መሪዎች ተከተሉ። **28** እግዚአብሔር ሆይ፣ በቀድሞ ዘመን እንደዳረግኸው ኃይልህን ግለጥ **29** ነገሥታት ስጦታቸውን ከሚያመጡልህ በኢየሩሳሌም ካለው ቤተ መቅደስህ ኃይልህን ግለጥ። **30** በሸምበቆ መካከል ያሉትን አራዊት ገሥጽ ኮርማዎችና ጥጆች የመሳሰሉትን መንግሥታት ገሥጻቸው። አዋርዳቸው ስጦታዎች እንዲመጡልህም አድርጋቸው ጦርነትን የሚወዱ ሕዝቦችንም በትናችው። **31** መሳፍንት ከግብጽ ይመጣሉ፤ ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች። **32** እናንት የምድር መንግሥታት ለያህዌ የምስጋና መዝሙር አቅርቡ። ሴላ **33** ከጥንት ጀምሮ ከነበሩት ሰማያት በላይ ለሚራመደው በኃያል ድምፁ ለሚያስገመግመው ዘምሩ። **34** ግርማው በእስራኤል ላይ ኃይሉም በሰማያት ላይ ስለሆነ የእግዚአብሔርን ኃይል ዐውጁ። **35** እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ በመቅደስህ ድንቅ ነህ፤ የእስራኤል አምላክ ለሕዝቡ ኃይልና ብርታት ይሰጣል። እግዚአብሔር ይባረክ!

Psalms 68:1

አጠቃላይ መረጃ፦
ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ለመዘምራን አለቃ
“ይህ አምልኮ ላይ እንዲጠቀምበት ለመዘምራኑ አለቃ ነው።”

የዳዊት መዝሙር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፦ 1) መዝሙሩን የፃፈው ዳዊት ነው ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት ዘይቤ የተፃፈ ነው

እግዚአብሔር ይነሳ
እግዚአብሔር መስራት መጀመሩ እርሱ እንደተነሳ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር መስራት ይጀምር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጠላቶቹ ይበተኑ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ጠላቶቹን ይበታትናቸው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ጢስ እንደሚበንን እንዲሁ ይብነኑ
የእግዚአብሔር ጠላቶች በነፋስ በቀላሉ እንደሚበንኑ ጢስ እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ነፋስ ጢስን እንደሚያበንን እንደዚሁ በትናቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰም በእሳት ፊት እንደሚቀልጥ
የእግዚአብሔር ጠላቶች በእሳት በቀላሉ እንደሚቀልጥ ሰም ተደርገው ተነግረዋል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰም በእሳት ፊት እንደሚቀልጥ እንዲጠፉ አድርጋቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉዎች
ይህ በአጠቃላይ ክፉ ሰዎችን የሚያመለክተ ነው። (የስም ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ፃድቅ
ይህ በአጠቃላይ ፃድቃን ሰዎችን የሚያመለክት ነው። (የስም ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ሀሴት ያድርጉ ደስም ይበላቸው
እነዚህ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን እነርሱ የሚሰማቸውን የደስታ መጠን አፅንኦት ይሰጣሉ። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 68:4

ለስሙ
ይህ እግዚአብሔርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ለእርሱ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በደመናት ላይ የሚሄደውን
የእግዚአብሔር ህልውና በህዝብ መካከል እርሱ በፈረስ ወይም በሰረገላ ላይ ሆኖ ወደ ምድር እንደሚሄድ ሆኖ ተነግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አባት ለሌላቸው አባት ነው
እግዚአብሔር ለወላጅ አልባዎች እንደ አባት የሚሆን ሩህሩህ አምላክ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ወላጆች ለሌላቸው ልጆች እንደ አባት የሚሆን አምላክ”” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለባልቴቶች ዳኛ
እግዚአብሔር ባልቴቶችን የሚጠብቅ ምህረት የተሞላ አምላክ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “የባልቴቶች ጠባቂ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ብቸኞችን በቤተሰብ መካከል ያኖራቸዋል
እግዚአብሔር ብቸኞችን በቤተሰብ መካከል እንደሚያኖራቸው ተደርጎ ተነግሯል። “እግዚአብሔር ቤተሰብ ለሌላቸው ቤተሰብ ይሰጣቸዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ እስረኞችን ከታሰሩበት እየዘመሩ እንዲወጡ ያደርጋቸዋል
እግዚአብሔር እስረኞችን ከታሰሩበት እንዲወጡ የሚመራቸው እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር እስረኞችን ነፃ ያወጣል፤ በደስታም እንዲዘምሩ ያደርጋቸዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አመፀኞች
ይህ የስም ቅፅል አመፀኛ ሰዎችን የሚያመለክተ ሲሆን በቅፅል ወይም በስም ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አመፀኛ ሰዎች” ወይም” በእርሱ ላይ የሚያምፁ ሰዎች” (የስም ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ምድረ በዳ
እግዚአብሔር አመፀኞችን ስለ መቅጣቱ ሲናገር እርሱ እጅግ በጣም ሞቃት የሆነ ምድረ በዳ እንዲኖሩ እንዳስገደዳቸው ተደርጎ ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም፡- “በጣም ሞቃት እና ደረቅ ምድር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 68:7

አጠቃላይ መረጃ፡-
ዳዊት እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በምድረ በዳ ወደ ሲና ተራራ የመራበትን ታሪክ መናገር ጀመረ።

እናንተ በወጣችሁ ጊዜ... እናንተ በዚያ ባለፋችሁ ጊዜ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ክስተት ያመለክታሉ። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ በህዝብህ ፊት ሄድህ
“አንተ ህዝብህን መራህ”

እናንተ በምድረ በዳ ባለፋችሁ ጊዜ
እግዚአብሔር በእስራኤል ህዝብ ቀድሞ የወጣ ወታደር እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰማያት ዝናብን አንጠባጠቡ... የእግዚአብሔር ህልውና
“እግዚአብሔር እንዲዘንብ አደረገ”

በእግዚአብሔር ህልውና ውስጥ
እዚህ ያለው ፈሊጥ እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ፊት መገለጡን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን በተገለጠ ጊዜ” (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 68:9

ርስትህ በደከመ ጊዜ አንተ አበረታኸው
የእስራኤል ምድር ሊደክም የሚችል ወይም ብርታት ሊያገኝ የሚችል ሰው እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ምድሪቱ መልካም እህል እድታመርት አድርገህታል።” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ርስትህ
እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰጣት ምድር አባት ለልጆቹ ያወረሳቸው ርስት እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለእስራኤላውያን የሰጠሀት ምድር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ደህው
ይህ በአጠቃላይ ደህ የሆኑ ሰዎችን የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ደሃ ሰዎች” (የስም ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 68:11

አጠቃላይ መረጃ፡-
ዳዊት እስራኤላውያን በምድረ በዳ የተጓዙት የጉዞ ታሪክ መናገር ቀጥሏል። በዚህ የታሪክ ክፍል ውስጥ እስራኤላውያን በጦርነት በጠላቶቻቸው ላይ ድል አድርገዋል።

ትእዛዙን የሚያውጁት ... ሰራዊት
እጅግ በጣም ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔርን መልእክት ለሌሎች ተናገሩ። እነርሱ እጅግ ታላቅ ሰራዊት እንደ ነበሩ ተደርጎ ተነግሯል። ሀረጉ በሴት ፆታ ስለተገለፀ አንዳንድ ትርጉሞች “ትእዛዙን ያወጁት ሴቶች... ሰራዊት” ብለው ተርጉመውታል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰራዊቶች ንጉስ... ለምን ይህን ታደርጋለህ?
በ መዝሙረ ዳዊት 68:12-13 ያለው መረጃ ትርጉሙን የበለጠ በቀላሉ መረዳት እንዲቻል ለማድረግ ቅደም ተከተሉ ተስተካክሏል። (የጥቅስ ድልድዮች የሚለውን ይመልከቱ)

የሰራዊት ነገስታት ፈጥነው ይሸሻሉ፣ እነርሱ ይሸሻሉ
ነገስታቱ ራሳቸውንና ሰራዊታቸውን በሙሉ ይወክላሉ። እነርሱ የሸሹት በእስራኤል ሰራዊት በመሸነፋቸው ምክንያት እንደሆነ ግልፅ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገስታቱና ሰራዊታቸው በሙሉ በመሸነፋቸው ምክንያት ከእኛ ሸሹ” (ወካይ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ምርኮ
ከተሸነፈው ሰራዊት የተወሰዱና ድል ወዳደረገው ሰራዊት ቤተ የተወሰዱ ነገሮች።

በብር የተሸፈኑ ርግቦች... ወርቅ
የዚህ ትርጉም አንዳንድ ምርኮዎች በከበሩ ብረቶች የተሸፈኑ ስለሆኑ በጣም ውድ ናቸው ማለት ነው።

እናንተ አንዳንድ ሰዎች በበጎች በረት መካከል ብትገኙ እንኳ፣ ይህንን ለምን ታደርጋላችሁ?
ይህ ጥያቄ ጥቅም ላይ የዋለው በጦርነት ውስጥ ያልተሳተፉትን ሰዎች ለመገሰፅ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በበጎች በረት መካከል የቆዩት ሰዎች በዚያ ሊቆዩ አይገባቸውም ነበር፤ ወደ ጦርነቱ መሄድ ነበረባቸው” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 68:14

በዚያ ያሉት የተበታተኑ ነገስታት ... በሰልሞን ላይ በረዶ ዘነበ
በተራራው ላይ በጣም ቡዙ የሞቱ ነገስታትና ወታደሮች ነበሩ፤ እነዚህ ተራራውን የሸፈኑ በረዶ እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡-

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

“በዚያ በጣም ቡዙ የጠላት ነገስታትና ወታደሮች ተሸንፈው ስለነበር እንደ በረዶ ሰልሞን ተራራን ሸፍነውት ነበር” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የተበታተኑ ነገስታት
እዚህ ላይ “ነገስታት” የሚያመለክተው ሰራዊታቸውንም ጭምር ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የጠላት ነገስታትና ሰራዊቶቻቸው ተበታተኑ” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰልሞን
ይህ የተራራ ስም ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ብርቱ ተራራ... ከፍ ያለ ተራራ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ በአንድ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት አንዱ ሌላውን ለማጠንከር ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ብርቱና ከፍ ያለው ተራራ የኮረብታማው አገር ባሰን ነው” (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ለምን በምቀኝነተ አይን ታያላችሁ... እርሱ ለዘላለም የሚኖርበትን ስፍራ?
ጥያቄው እንደ አረፍተ ሀሳብ ሊፃፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የባሳን ከፍ ያለው ኮረብታማ አገር እግዚአብሔር ሊኖርበት የሚፈልገው ስፍራ በሆነው በተራራው ላይ በምቀኝነት አይን ሊያየው አይገባም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 68:17

ሃያ ሺህ፣ ሺዎች እና ሺዎች
ይህ ምናልባት ትክክለኛው እቅጩን የሆነ ቁጥር ማለቱ ላይሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ብዙ ሺዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ከፍ አለ
“ከፍ ማለት” ወደ ላይ መንቀሳቀስ ነው፣ ወደ ሰማይ መሄድ ነው።

Psalms 68:19

ሸክማችንን በየእለቱ ይሸከማል
“የእኛን ከባድ ሸክም በየቀኑ ይሸከማል።” ጌታ ለህዝቡ የሚያደርገው እንክብካቤ እርሱ በአካል ችግሮቻቸውን እንደ ሸክም እንደሚሸከም ተደርጎ ተነግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ደህንነታችን የሆነው እግዚአብሔር... አምላካችን የሚያድን አምላክ ነው
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። እዚህ ላይ “ደህንነታችን” የሚለው “አዳነ” በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሚያድን አምላክ... አምላካችን እኛን የሚያድነን አምላክ ነው።” (ትይዩነት እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የጠላቶቹን ራስ ይቀጠቅጣል
እግዚአብሔር ጠላቶቹን ለመግደል ዓላማ በማድረግ የእነርሱን ራስ በመቀጥቀጥ የሚገድል ጦረኛ ተዋጊ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ራሳቸውን በመፈንከት ጠላቶቹን ይገድላል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ፀጉራም አናት
በጦርነት ጊዜ ወታደሮች ፀጉራቸውን አለመቆረጣቸው የሚዘወተር ልማድ የነበረ ይመስላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ረጅም ፀጉር ያለው አናት” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ ላይ በሀጢአት የሚሄዱትን
እግዚአብሔርን ማሳዘን በሀጢአት መካከል መሄድ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “በተለምዶ በእርሱ ላይ ሀጢአት ያደርጋሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 68:22

እነርሱን እመልሳቸዋለሁ
“እነርሱ” የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ጠላቶች ያመለክታል።

የባህር ጥልቆች
ይህ የሚናገረው የባህር ጥልቅ እንደሆነ ያህል በማሰብ ሰዎች ከእግዚአብሔር ለማምለጥ የሚሞክሩበት እጅግ በጣም ሩቅ የሆነ የምድር ክፍል ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ትጨፈልቃቸዋለህ
የእስራኤል ጠላቶች ሙሉ በሙሉ የሆነ ጥፋት እስራኤላውያን እነርሱን ከእግራቸው በታች እንደሚጨፈልቋቸው ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላቶቻችሁን ሙሉ በሙሉ ታሸንፏቸዋላችሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እግርህ በደም ውስጥ እንዲጠልቅ
ከጠላቶች ጥፋት የሚነሳው ብጥብጥ በጣም ስእላዊ በሆነ መልኩ ተነግሯል፣ እስራኤላውያን በሞቱት ጠላቶቻቸው ደም ውስጥ እንደቆሙ ተደርጎ ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም፡- “በደማቸው ውስጥ መረማመድ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የውሻህም ምላስ ከጠላትህ ድርሻውን ያገኛል
በእስራኤል ጠላቶች ላይ በተረገው ጦርነት ምክንያት የፈሰሰው ደም ውሾች በምላሳቸው የሚፈስሰውን ደም እስኪልሱ ድረስ እጅግ የከፋ እንደነበር ተደርጎ ተነግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 68:24

ሰልፍ
ሰልፍ የክብረ በአል መገለጫ ሆኖ ብዙ ሰዎች ስርአት ባለው ሁኔታ የሚራመዱበት ነው።

መዘምራን
የሙዚቃ መሳሪያዎች የሚጫወቱ ሰዎች።

Psalms 68:26

እግዚአብሔርን በጉባኤ አመስግኑት፣ ከእስራኤል ምንጭ የተገኛችሁ እግዚአብሔርን አመስግኑ።
የእነዚህን ሀረጎች ቅደም ተከተል መለወጥ ሊረዳ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከእስራኤል ምንጭ የተገኛችሁ እግዚአብሔርን አመስግኑት፣ እግዚአብሔርን በጉባኤ አመስግኑት”

ከእስራኤል ምንጭ
ምንጭ የሚለው ቃል እስራኤል የሚለው ሰው የብዙ ሰዎች አባት የመሆን ችሎታ የሚገልፅ ተለዋጭ ዜይቤ ነው፤ ከምንጭ ብዙ ውሀ እንደሚወጣ እስራኤልም ደግሞ የብዙ ሰዎች አባት ነው። ይህ በተጨማሪ የሚያሳየው እስራኤል የሚባለው ሰው እንዳደረገው እዚህ እየተደረገ ያለው ጥሪ እግዚአብሔርን ለሚያገግሉ ሰዎች ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የእስራኤል እውነተኛ ልጆች” ወይም “ከእስራኤል የተገኛችሁ ልጆች ሁላችሁም” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የእነርሱ በብዙ የሚቆጠሩ ህዝብ
“የእነርሱ ቡድን።” የእነርሱ የሚለው ቃል የይሁዳ መሪዎችን ያመለክታል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 68:28

እስራኤል ሆይ አምላክህ ሀይልህን አዝዞአል
አንዳንድ ትርጉሞች የእብራይስጡን ትርጉም በተለየ መንገድ ይረዱታል:- “እግዚአብሔር ሆይ፣ ሀይልህን እዘዝ” ወይም “እግዚአብሔር ሆይ ሀይልህን ተጠቀም”

እስራኤል ሆይ፣ አምላክህ አዝዞአል
“የእስራኤል ህዝብ ሆይ፣ አምላክህ አዝዞአል”

ለእኛ... ለእኛ
“እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጸሐፊውንና የእስራኤልን ህዝብ ነው ነገር ግን ጸሐፊው የሚናገረው እግዚአብሔርን አይደለም:: (አግላይ እና አካታች “እኛ” የሚለውን ይመልከቱ)

በኢየሩሳሌም ካለው ከቤተ መቅደስህ ብርታትህን ግለጥ
“በኢየሩሳሌም ባለው በቤተ መቅደስህ በምትገኝበት ጊዜ ሀይልህን አሳየን”

ሀይልህን ግለጥ
“ሀይል” የሚለው ረቂቅ ስም “ብርቱ” ተብሎ ሊብራራ ይችላል:: አማራጭ ትርጉም:- “አንተ ብርቱ እንደሆንህ አሳየን” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 68:30

በሸንበቆ መካከል ያሉት አራዊቶች
ብዙ የስነ መለኮት ምሁራን እነዚህ አራዊቶች የግብፅን ህዝብ የሚያመለክቱ ተለዋጭ ዘይቤዎች እንደሆኑ ያምናሉ:: ይህ ግልፅ ሊደረግ ይችላል:: አማራጭ ትርጉም:- “በሸንበቆ መካከል እንዳሉት አራዊቶች የመሰሉት የግብፅ ህዝብ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ህዝብ፣ የኮርማዎችና የወይፈኖች መንጋ
የሌሎች መንግስታት ሕዝቦች የከብቶች ትልቅ መንጋ እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሯል:: አማራጭ ትርጉም:- “እንደ ኮርማዎች መንጋ የሆኑ ኃያላን ሕዝቦች” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በትናቸው
አንድ ነገር እንዲበታተን ወይም ደግሞ በተለያየ አቅጣጫ በፍጥነት እንዲሰራጭ ማድረግ

መኳንንት ከግብፅ ይመጣሉ
ይህ የሚያመለክተው እነዚህ መኳንንቶች በኢየሩሳሌም ለእግዚአብሔር ስጦታ ለማቅረብ ከግብፅ እንደሚመጡ ነው:: አማራጭ ትርጉም:- “ከዚያም የግብፅ መሪዎች ለአንተ ስጦታ ያመጣሉ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ኩሽ
ይህ የኩሽን ህዝብ የሚያመለክት ነው:: አማራጭ ትርጉም:- “ኩሻውያን” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች
ይህ እግዚአብሔርን ማምለክ የሚወክል ምሳሌያዊ ድርጊት ነው:: አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔርን ለማመስገን እጆቿን ወደ ላይ ትዘረጋለች” (ምሳሌያዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 68:32

እናንተ የምድር መንግስታት ሆይ
እዚህ ላይ “መንግስታት” የሚለው የመንግስታቱን ዜጎች የሚያመለክት ነው:: አማራጭ ትርጉም:- “በአለም ዙሪያ ያላችሁ እናንተ የመንግስታቱ ዜጎች የሆናችሁ” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ሰማየ ሰማያት ለወጣ ለእርሱ ዘምሩ
“ዘምሩ” የሚለው ቃል የዚህ ጥቅስ መጀመሪያ እንደሆነ ይታሰባል:: እዚህ ላይ እግዚአብሔር በሰማይ ላይ በሰረገላ እንደሚነዳ ተደርጎ ተገልጧል:: አማራጭ ትርጉም:- “በሰረገላው ላይ ሆኖ ወደ ሰማይ ለሚወጣው ለእግዚአብሔር ዘምሩ” (አስጨምሬ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ድምፁን በሀይል ከፍ ያደርጋል
ይህ ፈሊጥ እርሱ በሀይል ይናገራል የሚል ትርጉም አለው:: አማራጭ ትርጉም:- “እርሱ በሀይል ይጮሀል” ወይም “እርሱ ከፍ ባለ ድምፅ ይናገራል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 68:34

ለእግዚአብሔር ክብርን አቅርቡ
“አቅርቡ” ለአንድ ሰው ተገቢውን ዝና ስጡ ማለት ነው:: አማራጭ ትርጉም:- “ክብር የእግዚአብሔር ነው”

ሀይሉ በሰማያት ላይ ነው
“ሀይል” የሚለው ረቂቅ ስም “ሀይለኛ” ተብሎ ሊብራራ ይችላል:: አማራጭ ትርጉም:- “እርሱ ሀይለኛ እንደሆነ በሰማያት ላይ ያሳያል” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ በተቀደሰ ስፍራህ የተፈራህ ነህ
እዚህ ላይ ጸሐፊው ለእግዚአብሔር በቀጥታ ይናገራል:: (እንቶኔ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ብርታትና ሀይል
እነዚህ ሁለት ቃላት በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው:: እግዚአብሔር ለህዝቡ ምን ያህል ብርታት እንደሚሰጥ አፅንኦት ይሰጣሉ:: (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 69

1 የውሃ ሙላት እስከ አንገቴ ደርሶአልና አምላክ ሆይ አድነኝ። 2 መቆሚያ ስላጣሁ በጥልቁ ረግረግ ውሃ ለመስጠም ተቃርቤአለሁ። 3 ብዙ ከመጮኼ የተነሣ
ዛልሁ ጕሮሮየም ደረቀ፤ አምላኬን በመጠባበቅ ዐይኖቼ ፈዘዙ። 4 ያለ ምክንያት የሚጠሉኝ ከራስ ጠጕሬ ይልቅ በዝተዋል፤ ብዙ ጠላቶቼ እኔን ማጥፋት
ይፈልጋሉ ያልሰረቅሁን ነገር መልሰህ አምጣ ተባልሁ። 5 እግዚአብሔር ሆይ አንተ ሞኝነቴን ታውቃለህ ኃጢአቴም ከአንተ የተሰወረ አይደለም። 6 የሰራዊት ጌታ
ያህዌ ሆይ፣ አንተን ተስፋ የሚያደርጉ በእኔ ምክንያት አይፈሩ። የእስራኤል አምላክ ሆይ፣ አንተን አጥብቀው የሚሹህ በእኔ ምክንያት አይዋረዱ። 7 ስለ አንተ
ስድብን ታግሼአለሁ እፍረትም ፊቴን ሸፍኖአል። 8 ለወንድሞቼ እንደ እንግዳ ለእናቴም ልጆች እንደ ባዕድ ሆንሁባቸው። 9 የቤትህ ቅናት በላችኝ ለአንተ
የተሰነዘረው ስድብ እኔ ላይ ዐረፈ። 10 በምጾምበት ጊዜ በጣም አለቀስሁ እነርሱም ሰደቡኝ። 11 ማቅ በለበስሁ ጊዜ መተረቻ አደረጉኝ። 12 በከተማው ቅጥር
ለሚቀመጡ የመነጋገሪያ ርእስ ለሰካራሞችም መዝፈኛ ሆንሁ። 13 ያህዌ ሆይ፣ እኔ ግን በወደድኸው ሰዓት ወደ አንተ እጸልያለሁ። በታላቅ ምሕረትህ፣
በማዳንህም ርግጠኝነት መልስልኝ። 14 ከረግረግ አውጣኝ እንድሰጥምም አትተወኝ። ከጥልቁ ውሃ ከእነዚያ ከሚጠሉኝም ታደገኝ። 15 ጐርፍ አያጥለቅልቀኝ
ጥልቁ ውሃም አይዋጠኝ ጕድጓዱም ተደርምሶ አይዘጋብኝ። 16 ያህዌ ሆይ፣ የኪዳንህ ታማኝነት በጐ ናትና ስማኝ እንደ ምሕረትህም ብዛት መልስልኝ 17
ከባርያህ ፊትህን አትሰውር ተጨንቄአለሁና ፈጥነህ መልስልኝ። 18 ወደ እኔ ቀርበህ አድነኝ ስለ ጠላቶቼም ተቤዠኝ። 19 የደረሰብኝን ስድብ፣ እፍረትና ውርደት
ታውቃለህ ጠላቶቼንም አንድ በአንድ ታውቃቸዋለህ። 20 ስድብ ልቤን ሰብሮታልና ተስፋ ቆረጥሁ። የሚያዝንልኝ ፈለግሁ ማንም አልነበረም የሚያጽናናኝም
ፈለግሁ ማንንም አላገኘሁም። 21 ምግቤን ከሐሞት ጋር ቀላቀሉ ለጥማቴም ሆምጣጤ ሰጠኝ። 22 በፊታቸው የቀረበው ማእድ ወጥመድ ይሁንባቸው ደኅና
ነን ሲሉ አሽክላ ይሁንባቸው። 23 ማየት እንዳይችሉ ዐይናቸው ይጨልም ጀርባቸውም ዘወትር ይጉበጥ። 24 መዓትህን በላያቸው አፍስስ፤ የቁጣህም
መቅሠፍት ድንገት ይድረስባቸው። 25 መኖሪያቸው ወና ይሁን! በድንኳኖቻቸውም የሚኖር አይገኝ። 26 አንተ የመታኸውን አሳደዋልና ያቆሰልሃቸውንም ሥቃይ
አባብሰዋል። 27 በበደላቸው ላይ በደልን ጨምርባቸው ወደ ጽድቅህ ድል አይግቡ። 28 ከሕይወት መጽሐፍ ይደምሰሱ ከጻድቃንም ጋር አይጻፉ። 29 እኔ ግን
ምስኪንና ሐዘነተኛ ነኝና አምላክ ሆይ፣ ማዳንህ ደግፎ ይያዘኝ። 30 የእግዚአብሔርን ስም በዝማሬ አመሰግናለሁ በውዳሴም ከፍ ከፍ አደርገዋለሁ። 31 ከበሬ
ይልቅ፣ ቀንድና ጥፍር ካበቀለ እንቦሳ ይበልጥ ይህ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋል። 32 ገሮች ይህን ባዩ ጊዜ ደስ ይላቸዋል እናንተ እግዚአብሔርን የምትሹ
በርቱ። 33 ያህዌ ችግረኞችን ይሰማልና በእስራት ያለውንም ሕዝቡን አይንቅም። 34 ሰማይና ምድር፣ ባሕሮችና በውስጡ የሚንቀሳቀሱ ሁሉ ያመስግኑት። 35
እግዚአብሔር ጽዮንን ያድናታልና የይሁዳንም ከተሞች መልሶ ይሠራቸዋልና ሕዝቡም በዚያ ይሰፍራል ይወርሷታልም። 36 የባርያዎቹም ዘሮች ይወርሷታል
ስሙንም የሚወዱ በዚያ ይኖራሉ።

Psalms 69:1

አጠቃላይ መረጃ፡-
ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ፡-
ይህ መዝሙር ለእርዳታ የሚደረግ መዝሙር ነው።

ለመዘምራን አለቃ
“ይህ አምልኮ ላይ እንዲጠቀምበት ለመዘምራኑ አለቃ ነው።”

በፅጌረዳ ዜማ
ይህ ምናልባትም የሚያመለክተው የሙዚቃ አይነትን ነው። ይህንን በ መዝሙረ ዳዊት 45:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የዳዊት መዝሙር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፦ 1) መዝሙሩን የፃፈው ዳዊት ነው ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት የመዝሙር ስልት የተቃኘ ነው።

አቤቱ ውሀ፣ ህይወቴን ለአደጋ ተጋላጭ አድርጎታል
ጸሐፊው በህይወቱ የገጠመውን ችግር በውሀ ጎርፍ እየሰመጠ እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በውሆች እየሰጠምሁ እንደሆነ ይሰማኛል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በጥልቅ ረግረግ ጠለቅሁ
ጸሐፊው በህይወቱ የገጠመውን ችግር በጥልቅ ረግረግ እየሰጠመ እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በጥልቅ ረግረግ እየሰጠምሁ እንደሆነና እንደምሞት ሆኖ ይሰማኛል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ረግረግ
ወፍራም ጭቃ

መቆምያ ስፍራ የለኝም
ጸሐፊው ያለበት ሁኔታ እንዴት ያልተረጋጋና እርግጠኝነተ የሌለበት እንደሆነ አፅንኦት ለመስጠት አሉታዊ አረፍተ ሀሳቦችን ይጠቀማል። (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

ጎርፍ በእኔ ላይ በሚፈስስበት ወደ ጥልቅ ወርጃለሁ
ጸሐፊው ችግሩን በጥልቅና አስፈሪ ወንዝ እየሰጠመ እንደሆነ እድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በጥልቅ ውሀ እንደሆንሁና የውሀ ጎርፍ በላዬ ላይ እየፈሰሰ እንደሆነ ይሰማኛል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 69:3

ደከምሁ
በጣም መዛል

አይኖቼ ፈዘዙ
ይህ ፈሊጥ ጸሐፊው እጅግ በጣም እንዳለቀሰና ከአሁን በኋላ አይኖቹ በሚገባ ማየት እንደማይችሉ ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፡- “አይኖቼ ከእንባ የተነሳ አብጠዋል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

በራሴ ካሉት ፀጕሮች የበለጠ
ይህ ጸሐፊው ምን ያህል ጠላቶች እንዳሉት ለመግለፅ የተጠቀመበት ግነት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በራሴ ላይ እንዳሉት ፀጕሮች እኔ ልቆጥራቸው ከምችላቸው በላይ ናቸው” (ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ቆረጡኝ
ይህ ፈሊጥ “ገደሉኝ” ማለት ነው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 69:5

ሞኝነቴ
“ሞኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም “ሞኝ” ተብሎ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ የሰራኋቸው ሞኝ ነገሮች” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ሀጢአቶቼ ከአንተ የተሰወሩ አይደሉም
ይህ በአዎንታዊ አረፍተ ሀሳብ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሀጢአቶቼን በሙሉ ታውቃቸዋለህ” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ አይፈሩ.. እነዚህ አይዋረዱ
“እነዚህን አታሳፍራቸው… እነዚህን አታዋርዳቸው”

በአንተ ተስፋ የሚያደርጉ ከእኔ የተነሳ አይፈሩ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህ አንተን የሚጠባበቁ ሰዎች ከእኔ የተነሳ አንዳቸውም ለሀፍረት ታልፈው እንዲሰጡ እባክህ አትፍቀድ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተን የሚፈልጉ ከእኔ የተነሳ አይዋረዱ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህ አንተን የሚፈልጉ ሰዎች ከእኔ የተነሳ አንዳቸውም ለውርደት ታልፈው እንዲሰጡ እባክህ አትፍቀድ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ አንተን የሚፈልጉ
እግዚአብሔርን መፈለግ የሚከተሉትን ሊወክል ይችላል፡- 1) እግዚአብሔርን ለእርዳታ መጠየቅ ወይም 2) ስለ እግዚአብሔር ማሰብና እርሱን መታዘዝ። አማራጭ ትርጉም፡- 1) “እነዚህ አንተን ለእርዳታ የመሚጠይቁህ ሰዎች” ወይም 2) “እነዚህ አንተን የሚያመልኩህና የሚታዘዙህ ሰዎች” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 69:7

ስለ አንተ
“ለአንተ ስል” ወይም “ለአንተ”

ስድብን ታግሻለሁ
የጸሐፊው ጠላቶች ስድቦች ሊሸከማቸው የሚገባው እጅግ በጣም ከባድ ሸክም እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል።አማራጭ ትርጉም፡- “የጠላቶቼን ስድቦች ተሸክሜአለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ፊቴን እፍረት ሸፍኖታል
ጸሐፊው የተሰማው እፍረት ማንኛውም ሰው በግልፅ ሊያየው የሚችለው በፊቱ ላይ የሚታይ መጥፎ ነገር እንደሆነ አድርጎ ተናግሮታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ ሙሉ በሙሉ ተዋርጃለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለወንድሞቼ እንደ እንግዳ ሆንኩኝ
ጸሐፊው ስለ ራሱ ሲናገር የቤተሰቡ አባል እንዳልሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ወንድሞቼ ከእንግዲህ ወዲህ ፈፅሞ አያውቁኝም ወይም አይቀበሉኝም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለወንድሞቼ እንደ እንግዳ… ለእናቴ ልጆች ደግሞ እንደ ባእድ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። የተደጋገሙት ከራሱ ቤተሰብ መለያየቱን አፅንኦት ለመስጠት ነው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ለእናቴ ልጆች እንደ ባእድ
እዚህ ላይ “ሆንሁኝ” የሚለው ሀሳብ ልንረዳው እንደሚገባ ታሳቢ ኖኗል። ጸሐፊው ስለ ራሱ ሲናገር የራሱ ቤተሰብ አባል እንዳልሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ወንድሞቼ ከእንግዲህ ወዲህ ፈፅሞ አያውቁኝም ወይም አያምኑኝም” (አስጨምሬ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የቤትህ ቅናት በላኝ
ጸሐፊው ለእዚአብሔር ቤተ መቅደስ ስላለው ቅናት ሲናገር ቅናቱ ጸሐፊውን የሚበላ አራዊት እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለአንተ ቤት ያለኝ ቅናት በላኝ” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በላኝ
ይህ ፈሊጥ ጸሐፊው ለቤተ መቅደሱ ያለው ቅናት ሀሳቡንና ድጊቱን በሙሉ ተቆጣጥሮታል ማለቱ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የማስበውንና የምሰራውን ነገር ሁሉ ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥሯል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

የሚሰድቡህ ስድብ… በላዬ ወድቋል
ጸሐፊው የእግዚአብሔር ጠላቶች ስድቦች በጸሀፊው ላይ እንደተጣሉ ድንጋዮች እንደሆኑ አድርጎ ተናግሯል።አማራጭ ትርጉም፡- “አንተን የሚሰድቡህ ስድባቸውን በእኔም ላይ ጥለዋቸዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 69:10

አለቀስሁ ምግብም አልበላሁም
ጸሐፊው የወፆሙ እውነታ ህዝቡ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ በአግባቡ ካለመያዙ የተነሳ በጣም አዝኖ እንደነበር ያመለክታል። (ምሳሌያዊ ድርጊት እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰደቡኝ
x

Psalms 69:13

አንተ በምትቀበልበት ጊዜ
“አንተ በምትወድደው ጊዜ” ወይም “አንተ ፈቃደኛ ስትሆን”

በማዳንህ እርግጠኝነት መልስልኝ
“እርግጠኝነት” እና “ማዳንህ” የሚሉት ረቂቅ ስሞች “በታማኝነት” እና “አድነኝ” በሚሉት ሊብራሩ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ በታማኝነትህ ስለምትወድደኝ፣ ለእኔ ቃል እንደገባኸው፣ አድነኝ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

አውጣኝ… እሰጥም ዘንድ አትተወኝ
አነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ከረግረግ አውጣኝ እሰጥም ዘንድ አትተወኝ
ጸሐፊው ከጠላቶቹ ስለሚገጥመው አደጋ ሲናገር ወደ ጭቃ ጉድጓድ እየሰጠመ እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከእንግዲህ ጭቃ ውስጥ እንድሰጥም አትፍቀድ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንድወጣ አድርገኝ
እዚህ ላይ “አውጣኝ” የሚለው ከአደጋ ስለማምለጥ ያመለክታል። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አውጣኝ” ወይም “አድነኝ” (ፈሊጥ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ታደገኝ
እዚህ ላይ “እኔን” የሚለው ሀሳብ ግልፅ እንደሆነ ታሳቢ ተደርጎ ነው። ይህ በገቢር ቅርፅ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እባክህ አድነኝ” (አስጨምሬ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥልቅ ውሀ… የውሀ ጎርፍ… ጥልቅ
እነዚህ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከጥልቅ ውሀ አድነኝ
ጸሐፊው ከጠላቶቹ ስለሚደርስበት አደጋ ሲናገር በጥልቅ ውሀ እየሰጠመ እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የውሀው ጎርፍ አስፈራኝ
ጸሐፊው ከጠላቶቹ ስለሚደርስበት አደጋ ሲናገር የውሀ ጎርፍ ሙሉ በሙሉ እንደሚሸፍነው አድርጎ ገልፆታል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥልቅ ይውጠኛል
ጸሐፊው ስለ ጥልቁ ሲናገር ጉድጓዱ እርሱን ሊበላው የተዘጋጀ ጨካኝ አውሬ እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥልቅ ውሀዎቹ እንደ አደገኛ አውሬ ዋጡኝ” (ሰውኛ ዘይቤ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጉድጓዱ አፉ በእኔ ላይ እንዲዘጋ አታድርግ
እዚህ ላይ “ጉድጓድ” እንደ ሰው አፍ እንዳለውና ጸሐፊውን መብላት እንደሚችል ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጉድጓዱ እንዲበላኝ አታድርግ” ወይም “የሞት ጉድጓድ በእኔ ላይ እንዲዘጋ አታድርግ” (ሰውኛ ዘይቤ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 69:16

የኪዳንህ ታማኝነት መልካም ነው
“ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ቅፅል ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ ለኪዳንህ መልካምና ታማኝ ነህ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ለእኔ ያለህ ምህረት ብዙ ነው
“አንተ ለእኔ በጣም መሀሪ ነህ”

ወደ እኔ ተመለስ
ወደ አንድ ሰው የመመለስ ሀሳብ ለእነርሱ ተገቢ ትኩረት መስጠት ወይም እነርሱን መርዳት ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እርዳኝ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከባሪያህ ፊትህን አትሰውር
የአንድ ሰው ፊት መሰወር ሌላ ሰውን ለመስማት ወይም ለመርዳት ፈቃደኛ አለመሆን ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እባክህ ባሪያህን እርዳ” ወይም “እባክህ እርዳኝ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ጭንቅ ውስጥ
“በታላቅ መከራ ውስጥ”

Psalms 69:18

ታደገኝ
ጸሐፊው እግዚአብሔር ሊታደገውና ነፃነቱን ሊመልስለት እንደሚችል ባሪያ እንደሆነ ራሱን በማሰብ እግዚአብሔርን እንዲታደገው ይጠይቀዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነፃ አውጣኝ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ተቤዠኝ
ጸሐፊው ነፃ ለመውጣት እዳው ሊከፈልለት የሚቻል እስረኛ እንደሆነ ራሱን በማሰብ እግዚአብሔርን እንዲቤዠው ይጠይቀዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “አድነኝ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ስድቤን፣ እፍረቴን እና ውርደቴን
እነዚህ ረቂቅ ስሞች እንደ ድርጊት ሊብራሩ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች እንዴት እንደሰደቡኝ፣ እንዳሳፈሩኝ እና እንዳዋረዱኝ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ጠላቶቼ ሁሉ በፊትህ ናቸው
እዚህ ላይ “በፊትህ” የሚለው እግዚአብሔር ስለ እነርሱ ሁሉን ያያል ደግሞም ያውቃል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላቶቼ ሁሉ እነማን እንደሆኑ አንተ ታውቃቸዋለህ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 69:20

ልቤን ሰበረው
ይህ ፈሊጥ ሰውየው እጅግ በጣም እንዳዘነ ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፡- “በጥልቀት ውስጤን አሳዘነኝ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ልቤ እጅግ በጣም ከብዶታል
የጸሐፊው ታላቅ ሀዘን እርሱ ትልቅ ክብደት እንደተሸከመ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ ሀዘን ከብዶኛል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አስተዛዛኝ
ሀዘንና ስብራት መጋራት

ለምግቤ መርዝ ሰጡኝ
ይህ ምናልባትም ዘይቤአዊ ንግግር ነው። ሰዎች ለጸሐፊው ይሰጡት የነበረው ምግብ እንደ መርዝ ጣእም ያለው በጣም መጥፎ ነበር። አማራጭ ትርጉም፡- “እንደ መርዝ ጣእም ያለው ምግብ ሰጡኝ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 69:22

በፊታቸው የቀረበው ማእዳቸው ወጥመድ ይሁንባቸው... እንቅፋት ይሁንባቸው
ጸሐፊው ጠላቶቹ በወጥመድ ወይም በመረብ እንደሚያዙ ትንንሽ እንስሳቶች የጠላቶቹ ምግብ ሙሉ በሙሉ እንዲያጠፋቸው ይፈልጋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ምግባቸው እንደ ወጥመድ ያጥፋቸው... እንደ መረብ ታውድማቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ማእዳቸው
ይህ ምናልባትም በግብዣ ላይ በማእድ የሚቀርበውን ምግብ የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የራሳቸው ምግብ ወይም ለመስዋእት የቀረበ ግብዣ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

አይኖቻቸው እንዳያዩ ይጨልሙ
ጸሐፊው በሚገባ ስለማያዩ አይኖች ሲናገር እንደጨለሙ አድርጎ ገልፆታል። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እባክህ አንድም ነገር ማየት እንዳይችሉ አድርጋቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ጀርባቸው እንዲጎብጥ አድርግ
ደካማ ጀርባዎች በድካም እንደሚንቀጠቀጡ ተደርገው ተነግረዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጀርባቸው አንድም ነገር መስራት እንዳይችሉ እጅግ ደካማ አድርጋቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጀርባቸው
“ጎናቸው” ወይም “ወገባቸው”

Psalms 69:24

መአትህ በእነርሱ ላይ ይፍሰስ
የእግዚአብሔር ቁጣውን መግለፅ እርሱ በጠላቶቹ ላይ አንደ ዉሀ እንደሚያፈስስ ተደርጎ ተገልጧል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መአት
ፍትህ ያጣ ሰው ቁጣ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የቁጣህ መቅሰፍት
“የሚነድ ቁጣህ” ወይም “ጠንካራ ቁጣህ”

ይድረስባቸው
በጠላቶቹ ላይ የሚገለጠው የእግዚአብሔር ቁጣ እነርሱን እየተከተለ እንደሚሮጥና እንደሚይዛቸው ተደርጎ ተገልጧል።(ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ባድማ ይሁን
ይህ ረቂቅ ስም “የተተዉ ይሁኑ” በሚለው ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የተተዉ ይሁኑ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 69:26

እርሱን አሳድደውታልና
“ሰውየውን አሳድደውታልና”

መታኻቸው
እዚህ ላይ “መመታት” ቅጣትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “አንተ ቀጣሀቸው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ያቆሰልካቸው
እዚህ ላይ “ማቁሰል” እነርሱ እንዲሰቃዩ ማድረግን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “እንዲሰቃዩ ያደረግኻቸው ሰዎች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በሀጢአታቸው ላይ ሀጢአት ጨመርክባቸው
“የሀጢአታቸውን በሙሉ መዝገብ ያዝክባቸው”

በሀጢአት ላይ ሀጢአት
“በጣም ብዙ ሀጢአት”

ወደ ፅድቅህ ድል አይግቡ
ወደ እግዚአብሔር ድል መምጣት ከእርሱ ዘንድ ሽልማት መቀበልን የሚያመለክት ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የአንተን የፅድቅ ሽልማት እንዲቀበሉ አታድርጋቸው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 69:28

እነርሱ ይደምሰሱ
እዚህ ላይ “እነርሱ” የሚለው የጠላቶቹን ስሞች ያመለክታል። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ስማቸውን ደምስስ” (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

አይጻፉ
“እነርሱ” የሚለው ሀሳብ ግልፅ እንደሆነ ታሳቢ ተደርጓል። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ስማቸውን አትፃፋቸው” (አስጨምሬ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ሆይ፤ የአንተ መድሀኒት በከፍታ ላይ ያድርገኝ
“መድሀኒት” የሚለው ረቂቅ ስም “አድነኝ” በሚለው ግስ ሊብራራ ይችላል። እዚህ ላይ “በከፍታ ላይ” የሚለው የደህንነት ስፍራን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ሆይ፤ አድነኝ ደግሞም በደህንነት ስፍራ አስቀምጠኝ” (ረቂቅ ስሞች እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 69:30

የእግዚአብሔር ስም
እዚህ ላይ “ስም” እግዚአብሔርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዝአብሔር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በምስጋና
ይህ ረቂቅ ስም ማመስገን በሚለው ግስ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እርሱን በማመስገን” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ከበሬና ከኮርማ ይልቅ የበለጠ
በሬና ኮርማ ለእግዚአብሔር እንደ መስዋእት ሊቀርቡ እንደሚገቡ ግልፅ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በሬ ከመሰዋትና ኮርማ ከመሰዋት ይበልጣል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀንድና ጥፍር ካለው ኮርማ
ይህ ሀረግ ሙሉ ለሙሉ ያደገ ኮርማና ሌሎች ያልደረሱ ላሞችን በአግባቡ ይለያል። አማራጭ ትርጉም፦ “ቀንድና ጥፍር ያለው ሙሉ በሙሉ ያደገ ኮርማ”

Psalms 69:32

የዋሆች
ይህ በአጠቃላይ “የዋህ” ሰዎችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “የዋህ ሰዎች” (የስም ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ እግዚአብሔርን የምትፈልጉ
እግዝአብሔርን መፈለግ የሚወክለው የሚከተሉትን ነው፦ 1) እግዚአብሔርን ለእርዳታ መጠየቅ ወይም 2) ስለ እግዚአብሔር ማሰብና እርሱን መታዘዝ። አማራጭ ትርጉም፦ “እናንተ እግዚአብሔርን ለእርዳታ የምትጠየቁት” ወይም “እናንተ ስለ እግዚአብሔር የምታስቡ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ልባችሁ ህያው ይሁን
እዚህ ላይ “ልባችሁ” የሚለው የሚያመለክተው ሰዎቹን ነው። እዚህ ላይ “ህያው” የሚለው ፈሊጥ ሲሆን መበረታታት ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የበረታችሁ ሁኑ” (ወካይ እና ግምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ይሰማል
እዚህ ላይ “ይሰማል” ማለት ይሰጣል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ይመልሳል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ችግረኞች
ይህ በአጠቃላይ ችግረኛ ሰዎችን ይመለከታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ችግረኛ ሰዎች” (የስም ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ እስረኞች
“ለእርሱ መከራ የተቀበሉት”

Psalms 69:34

ሰማይና ምድር፣ ባህርም... ያመሰግኑት
እዚህ ላይ ሰማይ፣ ምድርና ባህር እግዚአብሔርን ማመስገን እንደሚችሉ ሰዎች ተደርገው ተነግረዋል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ባህርና በውስጣቸው የሚንቀሳቀሱ ሁሉ
“ያመስግኑት” የሚለው ሀሳብ በውስጡ እንዳለ ግልፅ ሊሆን ይገባዋለው። አማራጭ ትርጉም፦ “ባህሮችና በውስጣቸውም የሚንቀሳቀሱ ማንኛውም ነገሮች ሀሉ ያመስግኑት” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ፅዮንን ያድናታል
እዚህ ላይ “ፅዮን” የሚለው በፅዮን የሚኖሩትን ህዝብ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር የፅዮንን ህዝብ ያድናል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እርሷን ይወርሳታል
“እርሷን” የሚለው ቃል የይሁዳን ምድር ያመለክታል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ስሙን የሚወድዱ
እዚህ ላይ “ስም” የሚለው እግዚአብሔርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦
“እግዚአብሔርን የሚወድዱ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 70

1 አምላክ ሆይ አድነኝ፤ ያህዌ ሆይ፣ ፈጥነህም እርዳኝ። **2** ሕይወቴን ማጥፋት የሚፈልጉ ይፈሩ ይዋረዱም፤ **3** በእኔ ስቃይ ደስ የሚላቸው ተሸማቅቀው ወደ ኋላ ይመለሱ። **4** ነገር ግን አንተን የሚፈልጉ ሁሉ ደስ ይበላቸው ሐሤትም ያድርጉ፤ ማዳንህን የሚወዱ ሁሉ ሁልጊዜ፣ «እግዚአብሔር ታላቅ ነው» ይበሉ። **5** እኔ ምስኪንና ችግረኛ ነኝ፤ አምላክ ሆይ ፈጥነህ ድረስልኝ፤ አንተ ረዳቴ ታዳጊዬም ነህና ያህዌ ሆይ አትዘግይ።

Psalms 70:1

አጠቃላይ መረጃ፦
ትይዩነት በዕብራይስጥ ግጥም በጣም የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ለመዘምራን አለቃ
“ይህ በአምልኮ ጥቅም ላይ እንዲውል ለመዘምራን አለቃ ነው”

የዳዊት መዝሙር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) መዝሙሩን የፃፈው ዳዊት ነው ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) የዳዊት አይነት መዝሙር ነው

ለመታሰቢያ
“ይህ መዝሙር የተፃፈው ሰዎች እንዲያስታውሱ ነው”

እነዚያ
“እነዚያ ሰዎች”

ነፍሴን ለመውሰድ
ይህ ፈሊጥ “ሊገድሉኝ” ማለት ነው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ይፈሩ ይዋረዱም
ይህ በገቢር ቅርፅ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “”እግዚአብሔር ያሳፍራቸው፣ በእነርሱም ላይ ውርደት ያምጣባቸው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ኋላቸው ይመለሱ፣ ይፈሩም
ይህ በገቢር ቅርፅ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ወደ ኋላቸው ይመልሳቸው፣ ስለ ሰሩት ስራ እንዲያፍሩ ይድጋቸው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ኋላቸው ይመሰሉ
እንዲቆሙ ወይም እንዳይንቀሳቀሱ መደረግ ከጥቃታቸው ወደኋላ እንዲመለሱ እንደማድረግ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “እንዲቆሙ ማድረግ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንኳ፣ እንኳ የሚሉኝ
ይህ የስላቅ ሳቅ መግለጫ ነው። “እንኳ እንኳ” የሚለውን በአንተ ቋንቋ በምትጠቀምበት በየትኛውም የሳቅ ድምፅ ልትተካው ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፦ “እነዚያ በእኔ ላይ የሚቀልዱና የሚስቁ”

Psalms 70:4

የሚፈልጉህ
እግዚአብሔርን መፈለግ የሚከተሉትን ሊወክል ይችላል፦ 1) እግዚአብሔርን ለእርዳታ መጠየቅ ወይም 2) ስለ እግዚአብሔር ማሰብና እርሱን መታዘዝ። አማራጭ ትርጉም፦ “አንተን ለእርዳታ እጠይቃለሁ” ወይም “ስለ አንተ አስባለሁ እታዘዛለሁም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሀሴት ማድረግና ደስ መሰኘት
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን የደስታውን ጥልቀት አፅንኦት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “በታላቅ ሁኔታ ሀሴት ማድረግ” ወይም “በጣም ደስ መሰኘት” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

መዳንህን የሚወድዱ
“መዳን” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ተግባር ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እነርሱን ስላዳንካቸው እወድሀለሁ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ሁልጊዜ ይበሉ
ይህ ግነት አፅንኦት የሚሰጠው እግዚአብሔርን ሁልጊዜ ማድነቅ አስፈላጊ እንደሆነ ነው። (ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ታላቅ ነው ይበሉ
ይህ በገቢር መልክ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሁሉም ሰው እግዚአብሔር ታላቅ ነው ይበል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ችግረኛና ምስኪን
እዚህ ላይ ችግረኛ እና ምስኪን የሚሉት ቃላቶች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ራሱን መርዳት እንደማይችል አፅንኦት የሚሰጡ ናቸው። አማራጭ ትርጉም፦ “በጣም ምስኪን” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ለእኔ ፍጠን
ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር ሲናገር እርሱን ለመርዳት ወደ ጸሐፊው እንደሚሮጥ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔን ለመርዳት ፈጥነህ ና” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ረዳቴ ነህ፣ እኔን ታድገኸኛል
እዚህ ላይ “እኔን ታድገኸኛል” የሚለው ሀረግ እግዚአብሔር እንዴት የእርሱ “ረዳት” እንደሆነ አፅንኦት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔን በመታደግ ትረዳኛለህ” (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

አትዘግይ
ይህ በገቢር ቅርፅ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እባክህ በፍጥነት ና” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 71

1 ያህዌ ሆይ፣ አንተን መጠጊያ አደረግሁ ፈጽሞ አልፈር። **2** በጽድቅህ ታደገኝ አስጥለኝም ጆሮህን ወደ እኔ አዘንብል አድነኝም። **3** በምሄድበት ቦታ ሁሉ አንተ መጠጊያ ዐምባ ሁነኝ። አንተ ዐለቴ፣ ምሽጌ ነህና እኔን ለማዳን ትእዛዝ ከአንተ ይውጣ። **4** አምላኬ ሆይ፣ ከዐመፀኛ ርኅራኄ ከሌለው ከጨካኝ እጅ ታደገኝ። **5** ጌታ ያህዌ ሆይ፣ አንተ ተስፋዬ ነህና ከልጅነቴ ጀምሮ በአንተ ታምኛለሁና። **6** ከተወለድሁ ጀምሮ በአንተ ተደገፍሁ ከእናቴ ማሕፀን ያወጣኸኝም አንተ ነህ ምስጋናዬ ዘወትር ለአንተ ነው። **7** አንተ ብርቱ መጠጊያየ ስለሆንህልኝ ሕይወቴ ለብዙዎች ምሳሌ ሆነ። **8** አፌ በምስጋናህ ተሞልቶአል ስለ ክብርህም ቀኑን ሙሉ እናገራለሁ። **9** በእርጅና ዘመኔ አትጣለኝ ጉልበቴም በደከመ ጊዜ አትተወኝ። **10** ጠላቶቼ ተነጋግረውብኛልና ሕይወቴን ማጥፋት የሚፈልጉም በእኔ በአንድነት አሢረዋል። **11** እነርሱም፣ «እግዚአብሔር ትቶታል፣ የሚያስጥለው የለምና ተከታትላችሁ ያዙት» አሉ። **12** አምላክ ሆይ፣ ከእኔ አትራቅ፣ አምላኬ ሆይ፣ እኔን ለማዳን ፍጠን። **13** ተቃዋሚዎቼ ይፈሩ፤ ይጥፉም ለጐዱኝ የሚፈልጉ ይፈሩ ይዋረዱም። **14** እኔ ግን ዘወትር አንተን ተስፋ አደርጋለሁ በምስጋና ላይ ምስጋና አቀርብልሃለሁ። **15** ምንም እንኳ ማስተዋል ቢያዳግተኝ አንደበቴ ዘወትር ስለ ጽድቅህና ስለ ማዳንህ ይናገራል። **16** መጥቼ የጌታ ያህዌን ብርቱ ሥራ ዐውጃለሁ የአንተን ጽድቅ ብቻ እናገራለሁ። **17** እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ ከልጅነቴ ጀምረህ አስተማርኸኝ እኔም እስከ ዛሬ ድረስ ድንቅ ሥራህን እናገራለሁ። **18** አምላክ ሆይ፣ ሳረጅና ስሸብትም አትተወኝ እኔም ኃያልነትህን ለመጪው ትውልድ ብርታህንም ኃላ ለሚነሣ ሕዝብ እናገራለሁ። **19** አምላክ ሆይ፣ ጽድቅህ እስከ ሰማያት ከፍ ያለ ነው አንተ ታላላቅ ነገሮችን አድርገሃል አምላክ ሆይ፣ እንደ አንተ ያለ ማን ነው? **20** ብዙ ችግርና መከራ ብታሳየኝም ሕይወቴን እንደ ገና ታድሳለህ። ከምድር ጥልቅም እንደ ገና ታወጣኛለህ **21** ክብሬን ትጨምራለህ ተመልሰህም ታጽናናኛለህ። **22** አምላኬ ሆይ፣ ስለ ታማኝነትህ በበገና አመሰግንሃለሁ፤ የእስራኤል ቅዱስ ሆይ፣ በመሰንቆ እዘምርልሃለሁ። **23** ለአንተ የምስጋና መዝሙር ሳቀርብ፣ ከንፈሮቼ በደስታ ይሞላሉ አንተ ያዳንሃት ነፍሴም እልል ትላለች። **24** አንደበቴ ቀኑን ሙሉ ስለ ጽድቅህ ያወራል፤ የእኔን መጐዳት የሚፈልጉ አፍረዋልና ተዋርደዋልምና።

Psalms 71:1

አጠቃላይ መረጃ፡-
ትይዩነት በዕብራይስጥ ግጥም በጣም የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ፡-
ይህ መዝሙር ለእርዳታ የተደረገ ፀሎት ነው።

እግዚአብሔር ሆይ፣ እኔ በአንተ እሸሸጋለሁ
ለጥበቃ ወደ እግዚአብሔር መሄድ በእርሱ እንደመሸሸግ ተደርጎ ተረግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ሆይ፣ ለጥበቃ ወደ አንተ መጣሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለዘላለም አልፈር
ይህ በገቢር ቅርፅ ሊብራራ ይችላል። “ለዘላለም አልፈር” የሚለው በ መዝሙረ ዳዊት 25:2 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላቶች ፈፅሞ ለሀፍረት አይዳርጉኝ” (ገቢር/አድርጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በፅድቅህ አድነኝ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) አድነኝ ምክንያቱም አንተ ሁልጊዜ የምትሰራው ትክክለኛ የሆነውን ነገር ነው” ወይም 2) አድነኝ እኔ የምሰራው አንተ ልሰራ የምትፈልገውን ነገር ነውና (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ጆሮህን ወደ እኔ መልስ
እዚህ ላይ ጆሮህ የሚለው የሚያመለክተው ወደ እርሱ የሚፀልየውን ሰው ለመስማት የእግዚአብሔርን ፈቃደኝነት ነው። ይህን በ መዝሙረ ዳዊት 17:6 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “ለእኔ ትኩረት ስጥ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ለእኔ የመሸሸጊያ አለት ሁነኝ
ዘማሪው ጠላቶች ሊያገኙት በማይችሉበት በትልቅ አለት ገደል ውስጥ ተደብቆ ደህና ሊሆን እንደሚችል ሁሉ እንደዚሁ በደህንነት እንዲጠብቀው እግዚአብሔርን ይጠይቃል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አለት... አለት
እነዚህ አንድ ሰው እጁን በሌላው ይዞ አስገብቶ የሚይዝባቸው ኮረብቶችና ተራሮች ናቸው፣ አለቶች አይደሉም።

አንተ ትእዛዝ ሰጥተሀል
“አንተ ለመላእክትህ ትእዛዝ ሰጥተሀል”

አድነኝ
“በደህንነት ጠብቀኝ”

አንተ አለቴ እና መጠጊያዬ ነህ
ዘማሪው እግዚአብሔር እንደሚጠብቀውና በትልቁ ተራራ ጫፍ ላይ እንደተደበቀና በሰው ሰራሽ መጠጊያ እንደተደበቀ ያህል እግዚአብሔር እንዲጠብቀውና ደህና እንዲያደርገው ያምናል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 71:4

ከክፉ እጅ፣ ከአመፀኛው እጅ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) “እጅ” የሚለው ቃል ለሀይል ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ከሀያላን እጅ፣ ከአመፀኞች እጅ” ወይም 2) “እጅ” ለራሱ ሰውየውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከክፉ ሰዎች፣ ከአመፀኞች ሰዎች” ወይም “ክፉ ሰዎች ወይም አመፀኞች ሰዎች እኔን መጉዳት እንዳይችሉ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉ፣ ከአመፀኛ እጅ
“ክፉ፣ ከአመፀኛ እጅ አድነኝ።” አማራጭ ትርጉም፡- “መረዳት የሚቻለውን መረጃ ግልፅ ልታደርገው ትችላለህ።” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉ... አመፀኛ... ጨካኝ
እነዚህ ቅፅሎች እንደ የስም ሀረጎች ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ሰዎች... አመፀኛ ሰውች... ጭካኝ ሰዎች” (የስም ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ተስፋዬ ነህ
እዚህ ላይ “ተስፋ” መዝሙረኛው ተስፋ ለሚያደርግበት ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ በእርግጠኝነት እንደምትረዳኝ የምጠብቀው አንተ ነህ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 71:6

ከማህፀን ጀምሮ በአንተ ተደገፍሁ
ይህ በገቢር ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከማህፀን ጀምሮ አንተ እኔን ደገፍከኝ” ወይም “ከእናቴ ማህፀን ከወጣሁበት ጊዜ ጀምሮ አንተ እኔን ተንከባከብከኝ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ አንተ ነህ
“አንተ ነህ”

እኔ ለብዙ ሰዎች ምሳሌ ነኝ
“ብዙ ሰዎች እንዴት እንደምኖር ይመለከታሉ እኔም እንደምኖረው መኖር ይፈልጋሉ”

Psalms 71:8

አፌ ሁልጊዜ በምስጋናህ ይሞላል... በክብርህ
ዘማሪው በሚናገረው ቃላቶች እግዚአብሔርን ለማመስገንና ለማክበር ያለውን ፍላጎት ሲናገር አፉ በምግብ እንደሚሞላ እንደዚሁ በቃላቶች እንደተሞላ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፡- “አፌ አንተን በሚያመሰግኑና በሚያከብሩ ቃላቶች ይሞላል” ወይም “እኔ ሁልጊዜ አመሰግንሀለሁ... እኔ ሁልጊዜ አከብርሀለሁ” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ ምስጋና
እዚህ ላይ “ምስጋና” የሚለው እግዚአብሔርን ለማመስገን የሚጠቀምባቸውን ቃላቶች ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ ምን ያህል ታላቅ እንደሆንህ ለሰዎች የሚናገሩ ቃላቶች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ ክብር
እዚህ ላይ ክብር የሚለው እግዚአብሔርን ለማክበር የሚጠቀምባቸውን ቃላቶች ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች አንተን እንዲያከብሩ የሚያደርጉ ቃላቶች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ቀኑን በሙሉ
“ቀኑን ሁሉ” ወይም “ሁልጊዜ”

አትጣለኝ... አትተወኝ
እነዚህ ሁለት ቃላቶች በመሰረታዊነተ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ጥቅም ላይ የዋሉት ለአፅንኦት ነው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

አትጣለኝ
“ከአንተ ርቄ እንድሄድ አታድርገኝ።” እግዚአብሔርን እርሱን መተዉ ከእርሱ ርቆ እንዲሄድ እግዚአብሔር እንዳስገደደው ተደርጎ ተነግሯል። ይህን በ መዝሙረ ዳዊት 51:11 እንዴት እደተረጎምከው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “አታስወግደኝ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አትተወኝ
“ሁልጊዜ አትልቀቀኝ”

Psalms 71:10

ህይወቴን ይፈልጓታል
እነርሱ ህይወቱን ለመውሰድ አጋጣሚ እየጠበቁ እንደሆነ ያመለክታል። ህይወት መውሰድ የሚለው ለስላሴ መግደል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ህይወቴን ለመውሰድ አጋጣሚ ይፈልጋሉ” ወይም “እኔን ለመግደል አጋጣሚ ይፈልጋሉ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ እና ለስላሴ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አሉ
ይህ እነርሱ ስለ እርሱ እያወሩ እንደሆነ ግልፅ ለማድረግ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለ እኔ ተናገሩ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ተከተሉና ያዙት
“ሲሮጥ ተከተሉትና ግደሉት”

Psalms 71:12

ከእኔ አትራቅ
እግዚአብሔር የጸሐፊውን ጥያቄ ገና ስላልመለሰለት እርሱ ስለ እግዚአብሔር ከጸሐፊው ርቆ እንደቆመ አድርጎ ተናግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 71:14

እጨምራለሁ
“ሁልጊዜ የበለጠ” ወይም “ሁልጊዜ ከዚህ በፊት ሳደርገው ከነበረው የበለጠ”

አፌ ፅድቅህ ይናገራ፣ ማዳንህን ደግሞ ቀኑን ሙሉ፣ ምንም እንኳ ሊገባኝ ባይችልም
“ፅድቅህን እና ማዳንህን ሙሉ በሙሉ አልተረዳሁትም፣ ነገር ግን አፌ ቀኑን ሙሉ ስለ እነርሱ ያወራል”

አፌ ይናገራል
አፍ ለሰው ሁለንተና ወካይ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እናገራለሁ” ወይም “በአፌ አወራለሁ እናገርማለሁ” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

ፅድቅህ
“ፅድቅ” የሚለውን ረቂቅ ስም ለማስወገድ ይህ እንደገና ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ እንዴት ፃድቅ ነህ” ወይም “የሰራሀቸው መልካም ነገሮች በሙሉ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ማዳንህ
“ማዳን” የሚለው ረቂቅ ስም አንደ ተግባር ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ እኔን እንዴት አዳንከኝ” ወይም “ሰዎችን እንዴት አዳንህ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እመጣለሁ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) “ሰዎች እግዚአብሔርን ወደሚያመልኩበት ስፍራ እሄዳለሁ” ወይም 2) “ወደ ጠላቶቼ እሄዳለሁ (ሂድ እና ና የሚለውን ይመልከቱ)

በጌታ በእግዚአብሔር ታላቅ ስራ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) “ጌታ እግዚአብሔር የሰራቸውን ታላላቅ ስራዎች ለእነርሱ እነግራቸዋለሁ” ወይም 2) ጌታ እግዚአብሔር ታላላቅ ስራዎችን ለመስራት ብርታት ስለሰጠኝ”

አስባለሁ
“ስለዚያ አወራለሁ”

Psalms 71:17

አስተማርኸኝ
ሊያመለክት የፈለገው መረጃ በግልፅ ሊብራራ ይችላል። “ብዙ ነገሮችን አስተማረኝ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ሆይ አትተወኝ
“እግዚአብሔር ሆይ እባክህ አትተወኝ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሀይልህን እየተናገርሁ ነበር
“ሀይል” የሚለው ረቂቅ ስም በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ እንዴት ብርቱ እንደሆንህ ስናገር ነበር” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ለሚመጣ ትውልድ
“ዛሬ ልጆች ለሆኑት”

ለሚመጣ ትውልድ ሁሉ ሀይልህን
የተዘለለው መረጃ በግልፅ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለሚመጣው ለማንኛውም ሰው ሀይልህን በምናገርበት ጊዜ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ለሚመጣው ትውልድ ሁሉ
ይህ ግነት የሚያመለክተው ጸሐፊው ሊነግራቸው ለሚችላቸው ሰዎች በሙሉ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ ልነግራቸው የምችላቸው ብዛት ያላቸው ሰዎች በሙሉ ያውቃሉ” (ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 71:19

እግዚአብሔር ሆይ ፅድቅህ ደግሞ እጅግ ታላቅ ነው
ዘማሪው እግዚአብሔር ስለሰራቸው መልካም ነገሮች ሲናገር እነዚያ ስራዎች አንድ ላይ ተሰባስበው እንደ ትልቅ ህንፃ ወይም ከፍ ያለ ተራራ እንደሆኑ ተደርጎ ተገልጧል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ አንተ ያለ ማን ነው?
ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ እንደ አረፍተ ሀሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እንደ አንተ ያለ አንድም የለም!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ህያው አደረግኸኝ
አበረታኸኝ ወይም እንደገና እንድኖር አደረግኸኝ

ከምድር ጥልቆች
እዚህ ላይ የምድር ጥልቆች የሚለው ሰዎች ሲሞቱ ለሚሄዱበት ስፍራ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። ዘማሪው በስጋ አልሞተም ነገር ግን ይህ እርሱ የሚናገረው ግነት እንደ ሞተ አድርጎ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ወደ ሞት በምንቀርብበት ጊዜ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 71:21

ትጨምራለህ... ተመልሰህ ታፅናናኛለህ
“እንድትጨምር እፈልጋለሁ... እንድትመለስና እንድታፅናና እፈልጋለሁ።”

ተመለስና አፅናናኝ
ይህ አንድን ተግባር በሁለት ሀረጎች ይገልፃል። አማራጭ ትርጉም፡- “እንደገና አፅናናኝ” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ለአንተ በበገና አመሰግንሀለሁ፣ የእስራኤል ቅዱስ ሆይ
“የእስራኤል ቅዱስ ለሆንህ ለአንተ በገና እየተጫወትሁ ምስጋና እዘምርልሀለሁ”

Psalms 71:23

ከንፈሮቼ በደስታ ይጮሀሉ
“ከንፈሮች” የሰውን ሁለንተና ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በደስታ እጮሀለሁ” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ የተቤዠሀት ነፍሴ
ዘማሪው የዘለላቸው ቃላቶች በግልፅ ሊብራሩ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ የተቤዠሀት ነፍሴ ምስጋናን ትዘምርልሀለች” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ነፍሴ
እዚህ ላይ “ነፍስ” የሰውን ሁለንተና ይወክላል። (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

አንደበቴ ያወራል
እዚህ ላይ አንደበት የሰውን ሁለንተና ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔም አወራለሁ” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

የእኔን መጎዳት የሚፈልጉ አፍረዋል፣ ግራም ተጋብተዋል
“የእኔን ጉዳት የፈለጉ ሰዎች ተዋርደዋል፤ ግራም ተጋብተዋል”

አፍረዋል፣ ግራም ተጋብተዋል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር አዋረዳቸው ደግሞም ግራ አጋባቸው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የእኔን መጎዳት የሚፈልጉ
ይህ የጸሐፊውን ጠላቶች ያመለክታል። (መዝሙረ ዳዊት 71:10)። “የእኔን መጎዳት የሚፈልጉ” በ መዝሙረ ዳዊት 71:13. ላይ እንዴት እደተረጎምከው ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 72

1 እግዚአብሔር ሆይ፣ ለንጉሡ ትክክለኛ ፍርድን ለንጉሡም ልጅ ጽድቅህን ስጠው። **2** እርሱም ሕዝብህን በጽድቅ፣ ይዳኛል ለተቸገሩትም በትክክል ይፈርዳል። **3** ተራሮች ሰላምን፣ ኮረብቶችም የጽድቅን ፍሬ ያመጣሉ። **4** ለተቸገረው ሕዝብ ይሟገታል የችግረኞችን ልጆች ያድናል ጨቋኙንም ያደቀዋል። **5** ፀሐይ እስካለች ድረስ፣ ጨረቃም እስከምትኖርበት ከትውልድ እስከ ትውልድ ድረስ፣ አንተን ያከብራሉ። **6** በታጨደ መስክ ላይ እንደሚዘንብ ዝናብ ይውረድ እንደ ካፊያም ምድርን ያረስርስ። **7** በዘመኑ ጽድቅ ይስፈን ጨረቃም ብርሃንዋ በምትሰጥበት ዘመን ሁሉ ብርልጽግና ይብዛለት። **8** ግዛቱም ከባሕር እስከ ባሕር ከታላቁም ወንዝ እስከ ምድር ዳርቻ ይሁን። **9** በምድረ በዳ የሚኖሩ በፊቱ ይስገዱ ጠላቶቹም ወደ መሬት ወድቀው ትቢያ ይላሱ። **10** የተርሴስ ነገሥታትና ደሴቶች ስጦታ ያምጡለት የሳባና የዐረብ ነገሥታት እጅ መንሻ ያቅርቡለት። **11** ነገሥታት ሁሉ ይስገዱለት ሕዝቦችም ሁሉ ያገልግሉት። **12** ወደ እርሱ የሚጮኸውን ችግረኛ ሌላ ረዳት የሌለውን ድኻ ይረዳልና። **13** ለድኻና ለችግረኛ ይራራል ምስኪኖችንም ከሞት ያድናል። **14** ሕይወታቸውን ከጭቆናና ከግፍ ያድናል ደማቸውም በፊቱ የከበረ ነው። **15** ዕድሜው ይርዘም፤ ከዐረብ ወርቅ ይምጣለት፤ ዘወትር ይጸልዩለት የእግዚአብሔር በረከት አይለየው። **16** በምድሪቱ እህል ይትረፍረፍ በተራሮች አናት ያለው ሰብል ይወዛወዝ። ፍሬው እንደ ሊባኖስ ይንዠርገግ፤ በከተማ ያለውም ሕዝብ እንደ ሜዳ ሣር ይብዛ። **17** ስሙ ለዘላለም ጸንቶ ይኑር ዝናውም ፀሐይ በሚወጣበት ዘመን ሁሉ ይሰማ፤ ሕዝቦች በእርሱ ይባረኩ ሰዎች ሁሉ ቡሩክ ነህ ይበሉት። **18** ብቻውን ድንቅ የሚያደርግ የእስራኤል አምላክ ያህዌ ይባረክ። **19** ክቡር ስሙ ለዘላለም ይባረክ ምድር ሁሉ በክብሩ ትሞላ። አሜን፤ አሜን **20** የእሴይ ልጅ የዳዊት ጸሎት እዚህ ላይ ተፈጸመ።

Psalms 72:1

አጠቃላይ መረጃ፡-
ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ፡-
የሰለሞን መዝሙር ለሚለው ርእስ አማራጭ ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፡- 1) ዳዊት ይህንን መዝሙር ስለ ሰለሞን ፃፈው (“የንጉሱ ወንድ ልጅ”) ወይም 2) ሰለሞን (እንደ ዳዊት ወንድ ልጅ “የንጉሱ ወንድ ልጅ” ነበር) ይህንን መዝሙር ስለ ራሱ እንደ ፀሎት ፃፈው ወይም 3) ሌላ ንጉስ በሰለሞን የአፃፃፍ ስልት ስለ ወንድ ልጁ ይህን መዝሙር ፃፈው። በእነዚህ ቀናቶች ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ብዙ ጊዜ ስለ ራሳቸው ሲናገሩ ሌላ ሰው እንደሆኑ አድርገው ይናገሩ ነበር። ይሁን እንጂ ዘማሪው ስለ ራሱ ሳይሆን ስለ ሌላ ሰው ይናገር አንደነበረ አድርጎ መተርጎም የበለጠ ተመራጭ ይሆናል። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ሆይ፣ የጽድቅ ስርአቶችህን ለንጉስ ስጥ፣ ፅድቅህን ለንጉስ ልጅ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፡- 1) “እግዚአብሔር ሆይ፣ ለእኔ ለንጉስ የፅድቅህን ስርአቶችህን ስጠኝ፣ ፅድቅህን ለልጄ” ወይም 2) “እግዚአብሔር ሆይ፣ ለእኔ ለንጉስ የፅድቅ ስርአቶችህን ስጠኝ፣ ፅድቅህን ለእኔ ለንጉስ ልጅ።” በእነዚህ ቀናቶች ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ብዙ ጊዜ ስለ ራሳቸው ሲናገሩ ሌላ ሰው እንደሆኑ አድርገው ይናገሩ ነበር። ይሁን እንጂ ዘማሪው ስለራሱ ሳይሆን ስለ ሌላ ሰው ይናገር እንደነበር አድርጎ መተርጎም የበለጠ ተማራጭ ይሆናል። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

የፅድቅ ስርአቶችህን ለንጉስ ስጥ
“ንጉስ በትክክል መፍረድ እንዲችል አድርገው”

ፅድቅህን ለንጉስ ልጅ
ግሱ ከቀደመው ሀረግ ሊወሰድ ይችላል። እዚህ ላይ ፅድቅ የሚለው ቃል ፅድቅ ያለበት ውሳኔ ማድረግን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ፅድቅህን ለንጉስ ልጅ ስጥ ወይም የንጉስ ልጅ በፅድቅ መምራት እንዲችል አድርገው” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ይፈርድ ዘንድ
ይህን የፃፈው ዳዊት ከሆነ የሚናገረው ስለ ልጁ ነው፣ “የንጉስ ልጅ” ፣ ልጁ ንጉስ የሚሆንበትን ጊዜ እየተናገረ ነው። ይህን የፃፈው ሰለሞን ከሆነ ምንም እንኳ የሚናገረው ስለ ራሱ ቢሆንም እርሱ ስለ ሌላ ሰው ይፅፍ እንደነበር አድርጎ መተርጎሙ የበለጠ ተማራጭ ነው። በየትኛውም መንገድ ቢሆን “ንጉስ ይፈርድ ዘንድ” የሚለው የተሻለ ትርጉም ነው።

ህዝብህን... ችግረኞችህን
ዘማሪው ለእግዚአብሔር እየተናገረ ነው።

ችግረኞችህ
ግሱ ከበፊተኛው ሀረግ ሊወሰድ ይችላል። “ችግረኞች” የሚለው ቅፅል የሚያመለክተው ድሆችን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ ችግረኞች ህዝብህን ይዳኝ ዘንድ” (አስጨምሬ እና የስም ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ተራሮች የሰላምን ፍሬ ይስጡ... ኮረብቶች የፅድቅን ፍሬ ይስጡ
ዘማሪው ስለ የእስራኤል ህዝብ ሲናገር እነርሱ የሚኖሩባቸው ተራሮችና ኮረብቶች እንደሆኑ አድርጎ ገልጧቸዋል። ተራሮቹና ኮረብቶቹ የእስራኤል መላው ምድር እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል፣ ይህ ምድር ደግሞ ፍሬ የሚያፈራ የአትክልት ስፍራ እንደሆነ አድርጎ በመናገር ፍሬው ደግሞ ሰላምና ፅድቅ እንደሆኑ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፡- “የምድሪቱ ህዝብ በሰላም ይኖሩ ዘንድ... ሁሉን ነገር በፅድቅ መንገድ ያደርጉ ዘንድ” (ምትክ ስም፣ ወካይ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 72:4

እርሱ... እርሱ
እነዚህ የሚያመለክቱት “የሚፈርደውን” ነው። (መዝሙረ ዳዊት 72:2)።

ጨቋኙን ያደቅቀዋል
ጸሀፊው ሌሎችን የሚጨቁኑ ህዝቦችን ስላሸነፈውና ስለቀጣው ንጉስ ሲናገር እነዚህ ህዝቦች ንጉሱ የሚያደንቃቸው ግኡዛን ነገሮች እንደሆኑ አድርጎ ገልጧቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሌሎችን የሚጨቁን ሰው ቅጣ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ፀሀይ እስካለች ድረስ፣ ጨረቃም በምትኖርበት ዘመን ሁሉ
ፀሀይና ጨረቃ በአንድ ላይ ሆነው ሁሉንም ጊዜ ስለሚወክሉት ቀንና ሌሊት ምትክ ስም ናቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “ለዘላለም፣ መጨረሻ የሌለው” (ምትክ ስም እና ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 72:6

እርሱ በታጨደ መስክ ላይ እንደሚወርድ ዝናብ ይምጣ
ንጉሱ መልካም ይሆናል፣ ደግሞም እርሱ አዲስ በታጨደ መስክ ላይ እንደሚዘንብ ዝናብ እንደሆነ በማሰብ ለህዝቡ መልካም የሆኑትን ነገሮች ያደርጋል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይመጣ ዘንድ
“እርሱ እንዲመጣ እፈልጋለሁ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንደሚያረሰርስ ውሀ
“እንደሚያረሰርስ ውሀ ወደታች ይምጣ።” ንጉሱ መልካም ይሆናል፣ ደግሞም እርሱ አዲስ በታጨደ መስክ ላይ እንደሚዘንብ ዝናብ እንደሆነ በማሰብ ለህዝቡ መልካም የሆኑትን ነገሮች ያደርጋል። (አስጨምሬ እና ተንጸጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ፃድቅ
“ፃድቅ” የሚለው ቅጽል እንደ ስም ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ፃድቅ ሰዎች” (የስም ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

በዘመኑ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፡- 1) “ንጉሱ በሚመራበት ዘመን” ወይም 2) “ፃድቅ ሰው እስከኖረ ድረስ” ወይም “ፃድቃን ሰዎች እስከኖሩ ድረስ”

Psalms 72:8

እርሱ ይግዛ
“ንጉሱ ይግዛ”

ከባህር እስከ ባህር ድረስ፣ ከታላቁም ወንዝ እስከ ምድር ዳርቻ
እነዚህ መግለጫዎች በሙሉ ወካዮቹ ሲሆኑ መላውን ምድር ያመለክታሉ። (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

ከባህር እስከ ባህር
ከሙት ባህር ጀምሮ በምስራቅ ከኪኔሬት ባህር ድረስ በምእራብ ደግሞ እስከ ሜዲቴራኒያን ባህር ድረስ።

ወንዝ
“የኤፍራጥስ ወንዝ”፣ ይህ እስራኤላውያን ወደ ሰሜን አቅጣጫ በምድር የሚጓዙበት ነው።

የምድር ዳርቻ
ይህ የሚያመለክተው ሰዎች ወደ ደቡብ አቅጣጫ በምድር ሊሄዱ የሚችሉበትን ርቀት በሙሉ ነው። እስራኤላውያን ምድር ዳርቻ ያላትና ዝርግ ገፅታ የያዘች እንደሆነች አድርገው ይናገራሉ። (ተለዋጭ ዘይቤ እና ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

አፈር ይልሳሉ
ይህ አባባል ተለዋጭ ዘይቤ ሲሆን ታላቅ ውርደትን የሚያሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እንዲኖሩ ይፈቅድላቸው ዘንድ ማድረግ የሚችሉትን ማንኛውንም ነገር ያደርጋሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ታርሴስ
የቦታ ስም ነው (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ይሰጣሉ
ይከፍላሉ

ስጦታ ያቀርባሉ
“ስጦታ ይሰጣሉ”

ሳባ
ይህ የአገር ስም ነው። ይህ ከአረብ አገር ጋር ተመሳሳይ አይደለም። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 72:11

በፊቱ ይሰግዳሉ
“በፊቱ ወድቀው ይሰግዳሉ” ወይም “እንደ ንጉሳቸው ያከብሩታል”

ህዝቦች ሁሉ
እዚህ ላይ “ህዝቦች” የሚለው በመንግስታቱ ውስጥ የሚኖሩትን ህዝቦች ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በሁሉም መንግስታት ውስጥ የሚኖሩት ህዝቦች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ሌላ ረዳት የለም
“እርሱን ለመርዳት ሌላ አንድም የለም”

Psalms 72:13

ለድኾችና ለችግረኛው ይራራል
“እርሱ ድሆችና ችግረኞች ስቃያቸውን ለማስቆም ይፈልጋል”

ድኾችና ችግረኞች
እዚህ ላይ “ድኾች” እና “`ችግረኞች” የሚሉት የስም ቅፅሎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ራሳቸውን መርዳት እንዳልቻሉ አፅንኦት የሚሰጡ ናቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህ ድኾችና እነዚህ ችግረኞች የሆኑ ሰዎች” (ጥምር ቃል እና የስም ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ህይወታቸውን ያድናል
እዚህ ላይ “ህይወት” የሚለው የሚያመለክተው የሰውን ሁለንተና ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱን አዳናቸው” ወይም “አዳናቸው” ወይም “ታደጋቸው” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

ጭቆናና ግፍ
እነዚህ ሁለት ቃላቶች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ችግረኞች ምን ያህል እንደሚሰቃዩ አፅንኦት የሚሰጡ ናቸው። እነዚህ ረቂቅ ስሞች እንደ ግስ ሊብራሩ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህ እነርሱን የሚጨቁኑና እነርሱን የሚጎዱ ሰዎች” (ጥምር ቃል እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ ፊት ደማቸው ክቡር ነው
እዚህ ላይ “ደማቸው” የሚለው ለደህንነታቸው ምትክ ስም ነው። የእግዚአብሔር ፊት ደግሞ የእርሱን ፍርድ ወይም ግምገማ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእነርሱ ደህንነት ለእርሱ በጣም ዋነኛ ነገር ነው” ወይም “እነርሱ በደህንነት እንዲኖሩ ይፈልጋል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በፊቱ
ይህ ቃል በ መዝሙረ ዳዊት 19:14 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።

Psalms 72:15

እድሜው ይርዘም!
ይህ አባባል ንጉሱ በጣም ረጅም ጊዜ እንዲኖር ምኞታቸውን በመግለጥ እርሱን ለማክበር ጥቅም ላይ ይውል ነበር። አማራጭ ትርጉም፡- “ንጉሱ ረጅም ዘመን ይኑር!” ወይም “ንጉሱ ረጅም ዘመን እንዲኖር እመኛለሁ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

የአረብ አገር ወርቅ ይምጣለት
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ የአረብ አገር ወርቅ ይስጡት” ወይም” እርሱ የአረብ አገር ወርቅ ይቀበል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀኑን ሙሉ
ይህ ፈሊጥ “ያለማቋረጥ” ማለት ሲሆን አንድ ቀን ብቻ የሚያመለክት አይደለም። አማራጭ ትርጉም፡- “ያለማቋረጥ” ወይም “ሁልጊዜ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የእህል ብዛት
“ብዛት” የአንድ ነገር መትረፍረፍ ነው። ይህ ረቂቅ ስም “ብዙ” ወይም “የተትረፈረፈ” በሚሉት ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ብዙ እህል” ወይም “የተትረፈረፈ እህል” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰብል
ሰዎች ለምግብነት የሚያበቅሏቸው ተክሎች።

ተወዛወዘ
ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው ረጅም ሳር ረጋ ያለ ነፋስ በላዩ ላይ ሲነፍስ የሚያሳየውን እንቅስቃሴ ለማሳየት ነው፤ በቀስታ ወደፊትና ወደኋላ ይንቀሳቀሳል።

አንደ ሊባኖስ
“እንደ ሊባኖስ የጥድ ዛፍ።” እነዚህ ዛፎች ውብና ለህንጻ በጣም ጥሩ ነበሩ። የዚህ አባባል ትርጉም ግልፅ ሊደረግ ይችላል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ህዝቡ በከተማ ውስጥ እንደ ሜዳ ሳር ይለምልም
በከተማ ስለሚኖረው ህዝብ ብልፅግና ሲናገር ህዝቡ በሜዳ ላይ በብዛት እንደሚበቅል ሳር ተደርገው ተገልፀዋል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 72:17

ስሙ ለዘላለም ፀንቶ ይኑር
ይህ አባባል ህዝቡ ሁልጊዜ እርሱን ለማሰብ ያላቸውን ፍላጎት በመግለፅ እግዚአብሔርን ለማክበር ጥቅም ላይ ውሏል።አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች ሁልጊዜ ስለ እርሱ ይወቁ” ወይም “ሰዎች እርሱ ማን እንደሆነ ፈፅሞ አይርሱ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ ስም
እዚህ ላይ “የእርሱ ስም” የሚለው የእግዚአብሔርን መልካም ስም የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የንጉሱ ስም” ወይም “የንጉሱ መልካም ስም” ወይም “የንጉሱ ዝና” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ፀሀይ የምትኖረውን ዘመን ያህል
ግሱ ከዚህ በፊት ከነበረው ሀረግ ሊወሰድ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ፀሀይ ፀንታ የምትኖረውን ያህል” ወይም “ፀሀይ እስከበራች ድረስ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ህዝቦች ሁሉ በእርሱ ይባረኩ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር እርሱ ለህዝብ መልካም ነገርን እንዲፈፅም ያድርገው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ብሩክ ነህ ይበለው
“እግዚአብሔር እንደባረከው ይወቅ”

Psalms 72:18

አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች የዚህ መዝሙር መጨረሻ ከመሆንም በላይ ጠቀሜታ አላቸው። የመዝሙረ ዳዊት ሁለተኛ መፅሀፍ የሆነው ከመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 42 እስከ መዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 72 ድረስ ያለው መፅሀፍ የመዝጊያ ሀሳብ ነው።

የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ህዝብ የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን ይባርክ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ክቡር ስሙ ለዘላለም ይባረክ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ህዝብ የተከበረ ስሙን ለዘላለም ይባርክ” ወይም “ስም” የሚለውን ለራሱ ለእግዚአብሔር ምትክ ስም እንደሆነ በማሰብ፣ “ህዝብ እርሱ እንዴት የከበረ እንደሆነ ለዘላለም ይወቅ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የተከበረ ስሙ ይባረክ
“ክቡር የሆነው እርሱ ይባረክ”

ምድር ሁሉ በክብሩ ይሞላ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክብሩ ምድርን ሁሉ ይሙላ” ወይም “እርሱ ምድርን ሁሉ በክብሩ ይሙላ ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

አሜን፤ አሜን
አሜን የሚለው ቃል የተደጋገመው ለተነገረው ነገር ማረጋገጫመስጠቱን አፅንኦት ለመስጠት ነው። ይህንን በመዝሙረ ዳዊት 41:13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “በእርግጥም እንዲህ ይሁን”

የእሴይ ልጅ የዳዊት ፀሎት እዚህ ላይ ተፈፀመ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ዳዊት የእሴይ ልጅ ፀሎቱን ፈፀመ” ወይም “ይህ የእሴይ ልጅ የዳዊት የመጨረሻው ፀሎት ነው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 73

1 ልባቸው ንጹሕ ለሆነ ለእስራኤል እግዚአብሔር ቸር ነው። **2** እኔ ግን እግሬ ሊሰናከል፣ አዳልጦኝም ልወድቅ ጥቂት ቀረኝ። **3** ክፉዎች ሲሳካላቸው ዐይቼ ቅናት አድሮብኝ ነበር። **4** እስኪሞቱ ድረስ ሕመም አያውቃቸውም ሰውነታቸውም ጤነኛና ጠንካራ ነው። **5** እንደ ሌሎች ሰዎች አይጨነቁም በሌሎች ላይ የሚደርሰው ስቃይ እነርሱ ላይ አይደርስም። **6** ትዕቢት የአንገት ጌጣቸው ነው ግፍን እንደ ልብስ ለብሰውታል። **7** የሰባ ዐይናቸውም ይጉረጠረጣል፣ ልባቸው ክፉ ሐሳብ ያፈልቃል። **8** በፌዝና በክፋት ይናገራሉ በእብሪት ተነሣሥተው ሌሎች ላይ ይዝታሉ። **9** አፋቸውን በሰማይ ያላቅቃሉ አንደበታቸውም ምድርን ያካልላል። **10** ስለዚህ ሕዝቡ ወደ እነርሱ ይመለሳል ውሃቸውንም በገፍ ይጠጣሉ። **11** «እግዚአብሔር እንዴት ሊያውቅ ይችላል በልዑልስ ዘንድ ዕውቀት አለ?» ይላሉ። **12** እንግዲህ ክፉዎች እንደዚህ ናቸው ሁልጊዜ እንደ ተዝናኑ ናቸው በሀብት ላይ ሀብት ይጨምራሉ። **13** ለካ ልቤን ንጹሕ ያደረግሁት እኔን በየዋህነት የታጠብሁት በከንቱ ኖሮአል! **14** ቀኑን ሙሉ ተሰቃየሁ በየማለዳውም ተቀጣሁ። **15** እኔ እንደዚህ እናገራለሁ ብል ኖሮ የልጆችህን ትውልድ በከዳሁ ነበር። **16** እነዚህን ነገሮች ለመረዳት ብሞክርም በጣም ከባድ ሆነብኝ። **17** ወደ መቅደስህ እስክገባ ድረስ ምንም ማወቅ አልቻልሁም በኋላ ግን በክፉዎች ላይ ምን እንደሚደርስባቸው ተረዳሁ። **18** በእርግጥ በሚያዳልጥ ስፍራ አኑረሃቸዋል ወድቀው እንዲጠፉም አድርገሃል። **19** እንዴት ፈጥነው በቅጽበት ጠፉ! በከባድ ድንጋጤ ፈጽመው ወደሙ። **20** ሰው ከሕልሙ ሲነቃ እንደሚሆነው፣ ጌታ ሆይ፣ አንተም በምትነሣበት ጊዜ፣ እነርሱ በማለዳ እንደሚረሳ ሕልም ይሆናሉ። **21** ልቤ በጣም ተማረረች፣ እኔም እጅግ ቆሰልሁ። **22** ስሜት የሌለው አላዋቂ ሆንሁ በፊትህም እንደ እንስሳ ሆንሁ። **23** ይህም ሆኖ ዘወትር ከአንተ ጋር ነኝ አንተም ቀኝ እጄን ይዘኸኛል። **24** በምክርህ ትመራኛለህ በመጨረሻም በክብር ትቀበለኛለህ። **25** በሰማይ ከአንተ በቀር ማን አለኝ? በምድርም ከአንተ ሌላ የምፈልገው የለኝም። **26** ሥጋዬና ልቤ ደከሙ እግዚአብሔር ግን ለዘላለም የልቤ ብርታትና አለኝታ ነው። **27** እነሆ፣ ከአንተ የሚርቁ ይጠፋሉ ለአንተ ያልታመኑትንም ታጠፋቸዋለህ። **28** ለእኔ ግን ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይሻለኛል፣ ጌታ ያህዌን መጠጊያዬ አድርጌዋለሁ ሥራህንም ሁሉ እናገራለሁ።

Psalms 73:1

አጠቃላይ መረጃ፦
ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

የአሳፍ መዝሙር
“ይህ አሳፍ የጻፈው መዝሙር ነው።” ይህ በ መዝሙረ ዳዊት 53:1 ላይ አንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።

እኔ ግን እግሬ ሊሰናከል፣ አዳልጦኝም ልወድቅ ጥቂት ቀረኝ
ዘማሪው የሚናገረው እግዚአብሔርን መታመን አንዳልቻለና በሚያዳልጥ መንገድ ሲራመድ ሊወድቅ እንደደረሰ አድርጎ ራሱን በማሰብ ሀጢአት ለመስራት እንደፈለገ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔ በእግዚአብሔር መታመን ለማቆም ደርሼ ነበር፤ በእርሱ ላይ ትልቅ ሀጢአት ለመስራትና በደለኛ ለመሆን ደርሼ ነበር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በአመፀኞች ቀንቼ ነበር
“አመፀኞች ቀናሁባቸው” ወይም “አመፀኞች ሰዎች የነበራቸው መልካም ነገር እንዲኖራቸው አልፈልግም”

አመፀኞች
“አመጸኞች” የሚለው ቅፅል እንደ ስም ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አመፀኞች ሰዎች” (የስም ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

የክፉዎች ባለጠግነት
“ባለጠግነት” የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ክፉዎች በጣም ብዙ መልካም ነገር እንዳላቸው አይቼ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉዎች
“ክፉዎች” የሚለው ቅፅል እንደ የስም ሀረግ ሊተረጎም ይቸላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ክፉ ሰዎች” (የስም ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 73:4

አጠቃላይ መረጃ፦
አሳፍ “አመፀኞች” እና “ክፉዎች” ስለሆኑ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ቅሬታ ማቅረብ እንዴት እንደሚፈልግ መግለፅ ይጀምራል። (መዝሙረ ዳዊት 73:3)።

የሌሎች ሰዎች ሸክም
ሸክም የሚለው ቃል ለእለት ከእለት የህይወት ትግል ምትክ ስም ነው(የምግብ፣ መጠለያ፣ ልብስ እና ጤና ፍላጎት) (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ሌሎች ሰዎች መከራ አይደርስባቸውም
“ሌሎች ሰዎች እንደሚሰቃዩት እነርሱ አይሰቃዩም”

Psalms 73:6

አጠቃላይ መረጃ፦
አሳፍ “አመፀኞች” እና “ክፉዎች” ስለሆኑ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ቅሬታ ማቅረብ እንዴት እንደሚፈልግ መግለፁን ቀጥሏል። (መዝሙረ ዳዊት 73:3)።

ስለዚህ ትዕቢት የአንገት ጌጣቸው ነው፤ አመፅንም እንደ ልብስ ተጎናፅፈዋል
ክፉዎች የአንገት ጌጥ እንዳደረጉና ውበት ያለው ልብስ እንደለበሱ ያህል ለእያንዳንዱ ሰው ምን ያህል ትእቢተኞችና አመፀኞች እንደሆኑ ያሳያሉ። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የአንገት ጌጥ... ልብስ
ይህ የሚያመለክተው ባለጠጋና ትልቅ ስፍራ ያላቸው ሰዎች የሚያጌጡበትና የሚለብሷቸው ነገሮች ናቸው።

የአንገት ጌጥ
ብዙ ጊዜ ከወርቅ የሚሰራ ሰንሰለት ወይም በአንገት ዙሪያ የሚደረግ ጌጣጌጥ ነው።

ከእንዲህ አይነት እውርነት ሀጢአት ይመጣል
የሚሄዱበትን ስፍራ ማየት እንደማይችሉ እንደ አይነ ስውራን ከመሆነቸው የተነሳ ሳያውቁት ሀጢአት ያደርጋሉ። እውር መሆን ምን ያህል ክፉ እንደሆነ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ማየት ያልቻለ ሰውን የሚያሳይ ምትክ ስም ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ልባቸው በክፉ ሀሳብ ተሞልቷል
እዚህ ላይ ዘማሪው የሰዎችን ሀሳብ ሰዎቹ እንደሆኑ አድርጎ ይገልፅላቸዋል። ከዚህ በተጨማሪ የክፉ ሰዎችን ውስጣዊ ማንነት ሲገልፅ ሰዎች ሊራመዱ የሚችሉበት ህንጻዎች እንደሆኑ አድርጎ አቅርቦታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በውስጣዊ ማንነታቸው ስለሚሰሯቸው ተጨማሪ ክፉ ነገሮች ሁልጊዜ ያስባሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 73:8

አጠቃላይ መረጃ፡-
አሳፍ “አመፀኞች” እና “ክፉዎች” ስለሆኑ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ቅሬታ ማቅረብ እንዴት እንደሚፈልግ መግለፁን ቀጥሏል (መዝሙረ ዳዊት 73:3)።

አፌዙ
በማን ላይ እንዳፌዙ በግልጥ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ በእግዚአብሔርና በህዝቡ ላይ አፌዙ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አፋቸውን በሰማይ ላይ ያላቅቃሉ
እዚህ ላይ አፋቸው “የሚለው” ለንግግራቸው ምትክ ስም ነው፣ “ሰማይ” የሚለው ደግሞ በሰማያት ላይ ለሚኖረው ለእግዚአብሔር ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በሰማያት ላይ በሚኖረው በእግዚአብሔር ላይ ተናገሩ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

አንደበታቸውም በምድር ላይ ተመላለሰ
“አንደበት” የሚለው ቃል ህዝቡን ይወክላል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፡- 1) ስለ እግዚአብሔር ክፉ ነገሮችን እየተናገሩ በምድር ዙሪያ ተመላለሱ” ወይም “ስለ ራሳቸው እየታበዩ በሁሉም ስፍራ ተመላለሱ“ (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 73:10

አጠቃላይ መረጃ፡-
አሳፍ “አመፀኞች” እና “ክፉዎች” ስለሆኑ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ቅሬታ ማቅረብ እንዴት እንደሚፈልግ መግለፁን ቀጥሏል (መዝሙረ ዳዊት 73:3)።

ህዝቡ ወደ እነርሱ ይመለሳሉ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፡- 1) “የእግዚአብሔር ህዝብ ክፉ ሰዎችን ወደደ” ወይም “ክፉ ሰዎች ወደዚህ ስፍራ ተመለሱ”

ብዙ ውሀ ፈሰሰ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፡- 1) “የእግዚአብሔር ህዝብ የክፉ ሰዎችን ቃላት በደስታ ያዳምጣሉ ወይም 2) “ክፉ ሰዎች የሚበሉት ብዙ ምግብና የሚጠጡት ብዙ ወይን ጠጅ አላቸው”

እንዲህ አሉ
ክፉ ሰዎች እንዲህ አሉ

እግዚአብሔር እንዴት ያውቃል? በልዑልስ ዘንድ እውቀት አለ?
እነዚህ መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች ለእግዚአብሔር ያለውን ንቀት ያሳያሉ። እነዚህ ጥያቄዎች እንደ አረፍተ ሀሳብ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር እኛ የምንሰራውን ስራ በእርግጠኝነት አያውቅም። ልዑል ስለዚህ ነገር እውቀት የለውም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 73:13

አጠቃላይ መረጃ፡-
በቁጥር 13 እና 14 አሳፍ “አመፀኞች” እና “ክፉዎች” ስለሆኑ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ቅሬታ ማቅረብ እንዴት እንደሚፈልግ መግለፁን ቀጥሏል (መዝሙረ ዳዊት 73:3)። በቁጥር 15 በእርግጥ ስለሚያስበው ነገር መናገር ጀምሯል።

እኔ አለኝ
“እኔ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው አሳፍን ነው።

ልቤን ጠበቅሁ
አሳፍ ልቡን ስለ መጠበቁ ሲናገር ከተማ ወይም ህንፃን ከጠላቶች እንደሚጠብቁት አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፡- “አሳቦቼን በንፅህና ጠበቅሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እጆቼን በየዋህነት ታጠብሁ
ጸሐፊው ስለ ንፅህናው ሲናገር እጆቹን በውሀ ከመታጠብ ይልቅ በየዋህነት እንደታጠበ አድርጎ ገልፆታል። ይህንን በ መዝሙረ ዳዊት 26:6 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “ድርጊቴ ንፁህ ነው” ወይም “እኔ እውነተኛ እንደሆንሁ ለማሳየት እጆቼን ታጠብሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀኑን ሙሉ
“ሁልጊዜ” ወይም “በየቀኑ”

ተቀሰፍሁ
“እኔ እንድሰቃይ አደረግኸኝ።”በ መዝሙረ ዳዊት 73:5 ላይ “እነርሱ መከራ አይደርስባቸውም” የሚለው እንዴት እነደተተረጎመ ተመልከት።

እኔ... ተቀጣሁ
“እኔ… ተገረፍሁ”

“እኔ እንደዚህ እናገራለሁ” ብልማ ኖሮ፤ የልጆችህን ትውልድ በከዳሁ ነበር
ይህ ግምታዊ ሁኔታ በተግባር አልተከሰተም። አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህን ነገሮች እናገራለሁ” ፈፅሞ አላልኩም፣” ስለዚህ የልጆችህን ትውልድ አልካድሁም” (ግምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 73:16

እነዚህ ነገሮች
በክፉዎች ላይ የተፈፀሙ መልካም ነገሮች (መዝሙረ ዳዊት 73:4-መዝሙረ ዳዊት 12)።

እጣ ፈንታቸው
“ክፉ ሰዎች ሲሞቱ የሚሆንባቸው ነገር” ወይም “ክፉ ሰዎች እንዴት እንደሚሞቱ”

Psalms 73:18

እነርሱን አስቀመጥከቸው
“እነርሱን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከፉ ሰዎችን ነው።

በሚያዳልጥ ስፍራ
“የማይመች ወይም የማይፀና መሬት። ”ማዳለጥ” በ መዝሙረ ዳዊት 73:2 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።

እንዴት በቅፅበት ምደረበዳ ሆኑ
“ምድረ በዳ” የሚለው ቃል መልካም የሆነውን ነገሩን ሁሉ ያጣ ሰው ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እንዴት በፍጥነት ጠፉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሰው ከህልሙ ሲነቃ እንደሚሆነው
ክፉዎች አንድ ሰው በህልም ከሚያየው የረዘመ ጊዜ አይቆዩም። ያ ሰው በነቃበት ቅፅበት ይጠፋል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 73:21

ልቤ አዘነች
“ልብ” የሚለው ቃል የሚወክለው ሰውየውን ሲሆን ሀሳባቸውንና ስሜታቸውን አፅንኦት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔ በጣም አዝኜ ነበር” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ በጣም ቆስያለሁ
ዘማሪው ስለ ስሜታዊ ህመም ሲናገር በቢላዋ ወይም በቀስት እደተወጋና አካላዊ ህመም እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፦ “አንድ ሰው እንዳቆሰለኝ ያህል ተሰማኝ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አላዋቂና ስሜት የሌለው
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን የሚያውቀው ምን ያህል ጥቂት እንደሆነ አፅንኦት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፦ “በጣም አላዋቂ” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ስሜት የሌለው
“ምንም የማይገባው”

አንተ
ይህ “አንተ” እግዚአብሔርን ያመለክታል።

Psalms 73:23

እኔ ሁልጊዜ ከአንተ ጋር ነኝ
እዚህ ላይ “እኔ” የሚለው ቃል የሚወክለው አሳፍን ነው። እዚህ ላይ “አንተ” የሚለው ቃል ደግሞ የሚወክለው እግዚአብሔርን ነው።

አንተ ቀኝ እጄን ያዝከኝ
የሰው “ቀኝ እጅ” የሰውን ሁለንተና ያመለክታል። ይህ ፅናትና ዋስትና የሚሰጠውን ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ፅኑ አብሮነት የሚያሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “አንተ አጥብቀህ ያዝከኝ” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ክብርህ ተቀበለኝ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፦ 1) “ሰዎች በሚያከብሩኝ ስፍራ አስቀምጠኝ” ወይም 2) “አንተ ወዳለህበት እኔን በመውሰድ አክብረኝ።” “ተቀበለኝ” የሚለው በ መዝሙረ ዳዊት 49:15 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።

Psalms 73:25

በሰማይ ከአንተ በቀር ማን አለኝ?
ይህንን እንደ አረፍተ ሀሳብ መተርጎም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፦ “በሰማይ ላይ ለእኔ ማንም የለኝም፣ አንተ ብቻ ነህ!” ወይም “በሰማይ ያለኸኝ አንተ ብቻ ነህ!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በሰማይ
“በአማልክት መካከል ወይም በልዕለ ተፈጥሮአዊ በሆኑ አካላት መካከል”

ስጋዬና ልቤ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ይጋራሉ። በአንድ ላይ እነዚህ ሀረጎች የሰውን ሀለንተና ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “የእኔ አካልና የእኔ አእምሮ” (ጥምር ቃል እና ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 73:27

አጠቃላይ መረጃ፦
አሳፍ ስለ እግዚአብሔር መናገር ቀጥሏል።

ከአንተ የሚርቁ
እዚህ ላይ ከእግዚአብሔር ርቆ መቆየት እርሱን ለመታዘዝ ፈቃደኝ ካለመሆን ጋር ተነፃፅሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “አንተን ለመታዘዝ የማይፈልጉ ሰዎች” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መጠጊያዬ
ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር ሲናገር እርሱ ሰው ለደህንነቱ ሸሽቶ የሚያመልጥበት ስፍራ እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 74

1 አምላክ ሆይ፣ ለዘላለም የጣልኸን ለምንድነው? በመሰማሪያህ በጎችህስ ላይ ቁጣህ የነደደው ለምንድነው? **2** ከጥንት ጀምሮ የመረጥኸውን ሕዝብ ርስትህ
እንዲሆን የዋጀኸውን ነገድ፣ መኖርያህ ያደረግሃትን የጽዮን ተራራን አስብ። **3** ጠላት ለዘለቄታው ባድማ ያደረገውን መቅደስህ ውስጥ ያወደመውን ሁሉ
ተመልከት። **4** ጠላቶችህ አንተ በመረጥኸው ቦታ መካከል ደነፉ፤ የጦርነት ዓርማቸውንም ምልክት አድርገው በዚያ አቆሙ። **5** እነርሱ ጥቅጥቅ ባለው ደን
ውስጥ እንጨቶችን በመጥረቢያ የሚቆርጥ ሰው ይመስላሉ። **6** በእደ ጥበብ ያጌጠውን ሥራ ሁሉ፣ በመጥረቢያና በመዶሻ ሰባብረው አደቀቁት። **7**
መቅደስህን አፍርሰው በእሳት አቃጠሉት የስምህን ማደሪ አረከሱ። **8** በልባቸውም፣ «ገና ሁሉንም እናጠፋቸዋለን!» አሉ። በምድሪቱ ያሉ የተቀደሱ ቦታዎችን
ሁሉ አቃጠሉ። **9** የምናየው ምልክት የለም ከእንግዲህ ወዲህ ነቢያትም አይኖሩም፤ ይህ እስከ መቼ እንደሚቀጥል ከእኛ መካከል የሚያውቅ የለም **10** አምላክ
ሆይ፤ ጠላት የሚሳደበው እስከ መቼ ነው? ባላንጣስ ለዘላለም በስምህ ያላግጣልን? **11** እጅህን፣ ቀኝ እጅህን የምትመልሰው ለምንድነው? ቀኝ እጅህን
ከብብትህ አውጥተህ አጥፋቸው። **12** እግዚአብሔር ሆይ፣ ከጥንት ጀምሮ አንተ ንጉሤ ነህ ማዳንህንም በምድር ላይ አደረግህ። **13** በኃይልህ ባሕሩን ከፈልህ
የባሕሩንም አውሬ ራስ ውሃ ውስጥ ቀጠቀጥህ። **14** የሌዋታንን ራሶች አደቀቅህ ሥጋውንም በምድረ በዳ ለሚኖሩ ምግብ አድርገህ ሰጠሃቸው። **15**
ምንጮችንና ፈሳሾችን አፈለቅህ ወራጅ ወንዞችን አደረቅህ **16** ቀኑ የአንተ ነው፣ ሌሊቱም የአንተ ነው፤ ፀሐይንና ጨረቃንም በቦታቸው አደረግህ። **17** የምድር
ዳርቻዎችን ሁሉ የወሰንህ አንተ ነህ ክረምትና በጋ እንዲፈራረቁ አደረግህ። **18** ያህዌ ሆይ፣ ጠላቶችህ በአንተ ላይ መሳለቃቸውን ጅል ሰዎችም ስምህን
መዳፈራቸውን ተመልከት። **19** የርግብህን ነፍስ ለዱር አራዊት አሳልፈህ አትስጥ፤ የተጨቆኑ ሕዝብህንም ለዘላለም አትርሳ። **20** የምድር ጨለማ ቦታዎች
በዐመፅ ተሞልተዋልና ኪዳንህን አስብ። **21** የተጨቆኑት አፍረው አይመለሱ ችግረኞችና ጭቁኖች ስምህን ያመስግኑ። **22** አምላክ ሆይ፣ ተነሥ ለክብርህ
ተሟገት ከንቱ ሰው ቀኑን ሙሉ አንተ ላይ ማላገጡን ተመልከት። **23** የባላጋራዎችህን ድንፋታ ዘወትር የሚሰነዝሩትን ስድብ አትርሳ።

Psalms 74:1

አጠቃላይ መረጃ፦
ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

የአሳፍ ትምህርት
“ይህ አሳፍ የፃፈው ትምህርት ነው”

ትምህርት
ይህ የሙዚቃ ስልትን ያመለክት ይሆናል። ይህ በ መዝሙረ ዳዊት 32:1 ላይ አንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።

እግዚአብሔር ሆይ፣ ለዘላለም የጣልኸን ለምንድን ነው?
ይህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ሆይ፤ እኛ የፈጸምነው ጥፋት የለም ነገር ግን አንተ ለዘላለም ጣልኸን!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በማሰማሪያህ ባሉ በጎችህስ ላይ ቁጣህ ለምን ነደደ?
ይህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እኛ አንተ ልትጠብቀን ቃል ኪዳን የገባህልን ሰዎች ነን፣ የፈፀምነው ጥፋት ደግሞ የለም ነገር ግን አንተ ግን በእኛ ላይ ተቆጥተሀል!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በማሰማሪያህ ላይ ያሉ በጎች
አሳፍ ስለ እስራኤል ህዝብ ሲናገር እነርሱ በጎች እንደሆኑ አድርጎ ይገልፃቸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ “እንደ በጎች የሆኑትንና በማሰማሪያ በምትመግባቸው በእስራኤል ላይ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አስብ
“ለእነርሱ ትኩረት ስጥ…” እግዚአብሔር ህዝቡን አልረሳም ነገር ግን ስለ እነርሱ የሚያስብ አይመስልም።

ገንዘብህ የሆነውን
“ለዘላለም የአንተ የሆነውን”

Psalms 74:3

አጠቃላይ መረጃ፦
እነዚህ ጥቅሶች በኢየሩሳሌም በሚገኘው በእስራኤል ቤተ መቅደስ ህንፃ ላይ የተፈፀመውን እውነተኛ ክስተት ይገልፃሉ።

ና ተመልከት
አሳፍ ለእግዚአብሔር በመናገር እርሱ እንዲመጣና ጥፋቱን እንዲመለከት ይጠይቀዋል።

ደነፋ
ጠላቶቹ በታላቅ የድል ጩኸት በጣም ይጮሁ ነበር።

የተቀረፁ ምልክቶች
ይህ የሚያመለክተው በቤተ መንግስት ውስጥ በእንጨት ፣ ብረት እና ድንጋይ የተቀረፁ ምስሎችን ነው።

Psalms 74:7

አጠቃላይ መረጃ፦
አሳፍ የቤተ መቅደሱን መፈራረስ መግለፅ ቀጥሏል።

እነርሱ… እነርሱ… እነርሱ… እነርሱ
እዚህ ላይ እነርሱ የሚለው የሚያመለክተው በ መዝሙረ ዳዊት 74:4 ላይ የተጠቀሱትን ጠላቶች ነው።

በልባቸው እንዲህ አሉ
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ለራሳቸው እንዲህ አሉ” ወይም “ለራሳቸው አሰቡ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 74:9

አጠቃላይ መረጃ፦
አሳፍ ስለተመለከተው ጥፋት ለእግዚአብሔር ይናገራል።

ምልክታችንን ከእንግዲህ ወዲህ አናይም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፦ 1) “ከእንግዲህ ወዲህ ከእግዚአብሔር ዘንድ ተአምራታዊ የሆኑ ምልክቶችን አናይም” ወይም 2) “የተቀደሱ ምልክቶቻችን በሙሉ ሄደዋል” ወይም 3) “ምልክቶቹ” ራሱን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሰራዊቱን የሚወክሉ የሰራዊት ሰንደቅ አላማዎችና ምልክቶች ናቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “የእኛን ጦር ሰራዊት ሙሉ በሙሉ አጥፍተውታል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እግዝአብሔር ሆይ፣ ጠላት በአንተ ላይ የሚሳደበው እስከ መቼ ነው?
ይህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ሆይ፣ ጠላት በአንተ ላይ ለረጅም ጊዜ ስድብን እየወረወረ ነበር!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ጠላት ለዘላለም በስምህ ላይ ያላግጣልን?
ይህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላት የአንተን ስም ከመሳደብ ፈፅሞ የምታስቆም አይመስልም!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ስምህን ይሳደባሉ
“ስም” የሚለው ቃል ለእግዚአብሔር ለራሱ ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ መጥፎ እንደሆንህ ይናገራሉ” ወይም “ይሰድቡሀል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እጅህን ለምን ትሰበስባለህ? ቀኝ እጅህን ለምን ትመልሳለህ?
ዘማሪው ስለ እግዚአብሔር ሲናገር ስጋዊ አካል እንዳለው አድርጎ ይገልፀዋል። ይህ እንደ አረፍተ ሀሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እጅህን፣ ቀኝ እጅህን አትሰብስብ!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች እና ሰውኛ የሚለውን ይመልከቱ)

እጅህን ሰብስብ
እዚህ ላይ “እጅ” የሚለው ቃል ለሀይል ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሀይልህን አትግለጥ” ወይም “ጠላቶችህን ለማጥፋት ሀይልህን አትጠቀም”(ምትክ ስም እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀኝ እጅህ
“ጠንካራ እጅህ”

ቀኝ እጅህን ከልብስህ አውጣ
ይህ ዘማሪ ስለ ዘማሪው ሲናገር ስጋዊ አካል እንዳለው አድርጎ ይገልፀዋል። “ሀይልህን ከመሰወር አቁምና እርምጃ ውሰድ” (ምትክ ስም እና ሰውኛ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 74:12

አጠቃላይ መረጃ፡-
ይህ አዲስ ርዕስ ይምራል፡- አሳፍ እግዚአብሔር በህዝቡ ታሪክ ውስጥ የሰራውን ታላቅ ስራዎች ያውጃል።

እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ ንጉሴ ነው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፡- 1) አሳፍ እንደ እስራኤል ወኪል ሆኖ ይናገራል፣ “እኛ እስራኤላውያን ህዝብ ከሆንንበት ከመጀመሪያ ጀምሮ ንጉሳችን ነበር” ወይም 2) “እግዚአብሔር አምላኬ ከጥንት ዘመን ጀምሮ ህያው ነው”

ድነትን አመጣህ
“ድነት” የሚለው ረቂቅ ስም “ማዳን” በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ሰዎችን ማዳን ሲገለፅ ድነት ከእርሱ ጋር ይዞት የሚመጣው እቃ እንደሆነ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ህዝብን ማዳን” (ረቂቅ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከፈልህ... በውሀ ውስጥ
አሳፍ እዚህ ላይ ምናልባት የሚናገረው እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ ማውጣቱን፣ ቀይ ባህርን መክፈሉን፣ እስራኤልን በደረቅ ምድር መምራቱን ከዚያም የፈርኦን ሰራዊትን በውሀ አሰጠማቸው። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ በሀይልህ ባህሩን ከፈልህ
አሳፍ ስለ እግዚአብሔር ሲናገር እርሱ ስጋዊ አካል እንዳለው አድርጎ ገልፆታል። “አንተ እጅግ በጣም ጠንካራ ነህ፣ በባህር መካከል ደረቅ መሬት ማድረግ ችለሀል” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ባህር
“ታላቁ ዉሀ”

የባህሩን አውሬ ራሶች በውሀ ውስጥ ቀጠቀጥህ
አሳፍ ምናልባት ስለ ፈርኦንና ሰራዊቱ የባህር አውሬዎች እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። የሚቻል ከሆነ እነዚህን ቃላቶች በቁሙ ተርጉማቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “የፈርኦንን ሰራዊት በገደልህባቸው ጊዜ የባህርን አውሬ ራሶች በውሀ ውስጥ እንደቀጠቀጥህባቸው ያህል ነው።” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 74:14

አጠቃላይ መረጃ፡-
አሳፍ እግዚአብሔር ከረጅም ጊዜ በፊት የሰራውን ስራ መናገሩን ቀጥሏል። እርሱ ምናልባት እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ ምድር ያወጣበትንና የፈርኦንን ሰራዊት በቀይ ባህር ያሰጠመበትን ጊዜ እየተናገረ ነው። የሚቻል ከሆነ እነዚህ ቃላቶች በቁሙ መተርጎም ይኖርባቸዋል።

ሌዋታን
ሌዋታን የባህር አውሬ ነው። ይህ ጨካኝ የሆነውን ጠላት ይወክላል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ምንጮችንና ፈሳሾችን ያፈለቅህ አንተ ነህ
እግዚአብሔር ምንጮችንና ፈሳሾችን ከምድር እንዲፈስሱ ማድረጉ እርሱ መሬትን ሰንጥቆ እንደመክፈትና ፈሳሾች እንዲፈስሱ እንደማድረግ ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ ምንጮችና ፈሳሾች ከምድር ፈልቀው እንዲፈስሱ አድርገሀል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 74:16

አጠቃላይ መረጃ፡-
አሳፍ የእግዚአብሔርን የመፍጠር ሀይል እንደገና ማሳሰቡን ቀጥሏል።

የምድር ዳርቻዎች
“የመሬትና የባህር ዳርቻዎች”

Psalms 74:18

አጠቃላይ መረጃ፡-
አሳፍ የእግዚአብሔርን እርዳታ እየጠየቀ ነው።

አስብ
“ትኩረት ስጥ።” ይህ በ መዝሙረ ዳዊት 74:2 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ጠላት በአንተ ላይ ስድብን አወረደ
አሳፍ ስለ ስድብ ቃላቶች ሲናገር ጠላት በእግዚአብሔር እንደሚወረውረው እንደ ድንጋይ ቁሳዊ ነገር እንደሆነ ተደርጎ ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላት አንተን ብዙ ጊዜ ሰደበህ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የርግብህን ህይወት
አሳፍ ስለ ራሱ ማንም ረዳት እንደሌላት ወፍ እንደ ርግብ አድርጎ ተናግሯል። ይህ ሀረግ ለእስራኤል ህዝብ ምናልባት ተለዋጭ ዘይቤ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ፣ የአንተ ርግብ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ርግብ
ራስዋን መከላከል የማትችልና እንደ ለማዳ እንስሳ የምትጠበቅ ትንሽ ወፍ ናት።

የዱር እንስሳ
ይህ ምናልባት ለእስራኤል ጠላት ተለዋጭ ዘይቤ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እንደ ዱር እንስሳ የመሰለ ጨካኝ ጠላት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የችግረኞች ህዝብህን ህይወት ለዘላለሙ አትርሳ
“የተቸገሩ ህዝብህን ለመርዳት ምንም ነገር ካለማድረግ ለዘላለል አትቀጥል።” ይህ በአዎንታዊ ቅርፅ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የተቸገሩ ህዝብህን ለመርዳት በፍጥነት ና” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 74:20

አጠቃላይ መረጃ፡-
አሳፍ ለእግዚአብሔር የሚያደርገውን ልመና ቀጥሏል።

የምድሪቱ የጨለማ አካባቢዎች የአመፅ ስፍራ ተሞልተዋል
አሳፍ ስለ አካባቢዎች ሲናገር አንድ ሰው የአመፅ ስፍራዎች ሊያስቀምጥበት እንደሚችለው ማስቀመጫ እቃ እንደሆኑ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “አመፀኞች ሰዎች በምድር ዙሪያ በሚችሉት ቦታ ሁሉ በጨለማ ስፍራ ክፉ ድርጊት ይሰራሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የምድሪቱ የጨለማ አካባቢዎች
“ጨለማ” የሚለው ቃል ምናልባት መጥፎ ነገሮች ለሚፈፅሙት ስፍራ ወይም እስራኤላውን ለግዞት ተልከው ለነበሩበት ምድር ተለዋጭ ዘይቤ ነው ነገር ግን እነዚህ ቃላቶች የሚቻል ከሆነ በቁሙ ሊተረጎሙ ይገባል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የተጨቆኑት አፍረው አይመለሱ
“ክፉ ሰዎች የተጨቆኑትን እንዲያሸንፉና እንዲያሳፍሯቸው አታድርጋቸው”

የተጨቆኑት
እነዚህ በሀይለኛ ሰዎች በጭካኔ የሚሰቃዩ ሰዎች ናቸው።

ድሆችና የተጨቆኑ
“ድሆች” እና “የተጨቆኑ” የሚሉት ቃላቶቹ በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን እግዚአብሔር የእርሱን እርዳታ የሚፈልጉትን ሰዎች እንደሚያድን አፅንኦት ይሰጣሉ። እነዚህ ቃላቶች በ መዝሙረ ዳዊት 35:10.ላይ እንዴት እንደተተረጎሙ ተመልከት። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 74:22

ለክብርህ ተሟገት
“አንተ ፃድቅ እንደሆንህ ለሁሉም አሳይ”

አስብ
“ትኩረት ስጥ።” እግዚአብሔር ሞኞች እርሱን እንደሚሰድቡት አልረሳም ነገር ግን ስለዚህ ነገር እርሱ የሚያስብ አይመስልም። ይህ በ መዝሙረ ዳዊት 2 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።

የባላጋራዎችህ ድምፅ
ድምፅ የሚለው ቃል ሰዎች ሲናገሩ ለሚጠቀሙባቸው ቃላቶች ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የአንተ ጠላቶች የሚናገሩት ነገር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ወይም በማያቋርጥ ሁኔታ የሚቃወሙህ ሰዎች ሁካታ
ዘማሪው እግዚአብሔርን ስለሚቃወሙት ሰዎች ቃላቶች ሲናገር ከእንስሳት ወይም እንደ ውሃና ነፋስ ከመሳሰሉ ሕይወት የሌላችው ቁሳቁሶች የሚወጣ ከባድ ጩኸት እንደሆኑ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህ ያለማቋረጥ በአንተ ላይ የሚቃወሙ ሰዎች ጩኸትና ትርጉም አልባ ቃላቶችን ትኩረት ስጥ” (አስጨምሬ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ተቃውሞ
በድፍረት መቃወም

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 75

1 አምላክ ሆይ፣ እናመሰግንሃለን ሐልዎትህን ስለ ገለጥህ ምስጋና ለአንተ እንሰጣለን፤ ሰዎች ድንቅ ሥራህን ይናገራሉ። **2** አንተም እንዲህ አልህ፣ «ለይቼ በወሰንሁት ሰዓት በቅን የምፈርድ እኔ ነኝ። **3** ምድር ብትናወጥ በውስጧ የሚኖሩትም ቢንቀጠቀጡ እኔ የምድርን መሠረት አጸናለሁ። ሴላ። **4** ትዕቢተኞችን፣ አትታበዩ ክፉዎችን ‹አታምፁ› እላቸዋለሁ፤ **5** ቀንድህን ወደ ሰማይ አታንሣ፤ ዐንገትህንም መዝዘህ አትናገር።» **6** ክብር ከምሥራቅ ወይም ከምዕራብ፣ ወይም ከምድረ በዳ አይመጣም። **7** ነገር ግን አንዱን ዝቅ፣ ሌላውን ከፍ በማድረግ በትክክል የሚፈርድ እግዚአብሔር ነው። **8** ያህዌ በእጁ የቁጣው ወይን ጠጅ የሞላበት ጽዋ ይዞአል ሲያፈስሰው ክፉዎች ሁሉ ጨልጠው ይጠጡታል። **9** እኔ ግን ዘወትር ሥራህን እናገራለሁ፤ ለያዕቆብ አምላክም ዝማሬ አቀርባለሁ። **10** እርሱ «የክፉዎችን ሁሉ ቀንድ እሰብራለሁ፤ የጻድቃን ቀንድ ግን ከፍ ከፍ አደርጋለሁ» ይላል።

Psalms 75:1

አጠቃላይ መረጃ፡-
ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ፡-
የእግዚአብሔር ህዝብ በ 75:1 ላይ ይናገራሉ፣ እና እግዚአብሔር ደግሞ በ 75:2-3 ውስጥ ይናገራል።

ለመዘምራን አለቃ
“ይህ አምልኮ ላይ እንዲጠቀምበት ለመዘምራኑ አለቃ ነው።”

“አታጥፋ” በሚለው ቅኝት የሚዜም
ይህ የሚያመለክተው የዜማ ስልትን ሊሆን ይችላል። ይህን በ መዝሙረ ዳዊት 57:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የአሳፍ መዝሙር
x

Psalms 75:4

አመፀኞችንና ክፉዎችን... እላቸዋለሁ
አመፀኞች እና ክፉዎች የሚሉት ቃላቶች የስም ቅፅሎች ሲሆኑ በስም ሊተረጎሙ ይችላሉ። ለሁለተኛው ሀረግ የሚያስፈልገው ግስ ከመጀመሪያው ሀረግ ሊወሰድ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለአመፀኞች ሰዎች... አልኋቸው... ለክፉዎች ሰዎች... አልኋቸው” (የስም ቅፅሎች እና አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

አልሁ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፡- 1) እግዚአብሔር እየተናገረ ነው ወይም 2) አሳፍ እየተናገረ ነው።

አመፀኞች አትሁኑ... አታንሱ... የአንተን ወደ ላይ አታንሳ... አትናገር
ተናጋሪው ለብዙ ክፉ ሰዎች እተናገረ ነው ስለዚህ እነዚህ ቅርፆች ሁሉም ብዙ ቁጥር ናቸው። (ተውላጠ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ቀንድህን ወደ ላይ አታንሳ
አሳፍ ስለ ክፉ ሰዎች ሲናገር በራሳቸው ላይ ቀንድ እንዳላቸው፣ አንገታቸውን እንደሚመዝዙና ሌሎች እንስሳትን ለማስፈራራት ራሳቸውን ወደ ላይ ከፍ አድርገው እንደሚያነሱ እንስሳት አድርጎ ገልጧቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “በራሳችሁ አትተማመኑ” ወይም “እንዴት ብርቱ ነኝ እያላችሁ በራሳችሁ አትመኩ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀንድህን ወደ ከፍታዎች አታንሳ
አሳፍ ስለ ክፉ ሰዎች ሲናገር ነራሳቸው ላይ ቀንድ እንዳላቸው፣ አንገታቸውን እንደሚመዝዙና ሎለሎች እንስሳትን ለማስፈራረራት ቻሉትን ያህል ራሳቸውን ወደ ላይ ከፍ አድርገው እንደሚያነሱ እንስሳት አድርጎ ገልጧቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “እናንተ በተለይም ደግሞ ከእግዚአብሔር በላይ ትልቅ እንደሆናችሁ በማሰብ ራሳችሁን ከፍ እንዳታደርጉ እርግጠኞች ሁኑ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በትዕቢተ በተሞላ አንገት
አሳፍ እግዚአብሔርን ስለሚቃወሙና ስለሚገዳደሩ ክፉ ሰዎች ሲናገር በራሳቸው ላይ ቀንድ እንዳላቸው፣ አንገታቸውን እንደሚመዝዙና ሌሎች እንስሳትን ለማስፈራራት ራሳቸውን ወደ ላይ ከፍ አድርው እንደሚያነሱ እንስሳት አድርጎ ገልጧቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “በትዕቢት” (ፈሊጥ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ክብር ከምስራቅ... አይመጣም
አሳፍ ራሱን ከፍ ስለሚደርግ ሰው ሲናገግ ራሱ ሰውየው ከፍ የማድረግ ተግባር እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። በተጨማሪ እርሱ እግዚአብሔር ለሰው ብርታትና ክብር ስለመስጠቱ ሲናገር እግዚአብሔር ሰውየውን በአካል ወደ ላይ ከፍ እንዳደረገው አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተን ወደ ላይ ከፍ የሚያደርግህ ከምስራቅ የሚመጣ ሰው አይደለም” ወይም “አንተን ብርቱ የሚያደርግህና ሰዎች እዲያከብሩህ የሚያደርግህ ከምስራቅ የሚመጣ ሰው አይደለም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 75:7

አጠቃላይ መረጃ፡-
አሳፍ ስለ እግዚአብሔር ይናገራል።

እርሱ ያዋርዳል፣ እርሱ ያከብራል
የግሱ ተሳቢ በግልፅ ሊብራራ ይችላል፡- “እርሱ አንዳንድ ሰዎችን ያዋርዳል፣ ሌሎች ሰዎችን ደግሞ ያከብራል። “ያዋርዳል” እና “ያከብራል የሚሉት ቃላቶች እግዚአብሔር ሰዎችን ባለስልጣን ስለማድረግና የሰዎችን ስልጣን ስለመውሰዱ ተለዋጭ ዘይቤዎች ናቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ አንዱን ሰው በሌላ ሰው ምትክ ንጉስ ያደርገዋል” ወይም “እርሱ የአንዱን ሰው ስልጣን ይወስድና ለሌላው ሰው ስልጣን ይሰጠዋል ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዐረፋ የሚወጣው የወይን ጠጅ የሞላበት ፅዋ... በቅመማ ቅመም የተቀመመ
እግዚአብሔር ሰዎችን ሲቀጣ ሰዎቹ ጠንካራ ወይን ጠጅ እንደጠጡና እንደታመሙ ሰዎች ይሆናሉ። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዐረፋ የሚወጣው የወይን ጠጅ
ዐረፋ ሰዎች እንዲሰክሩ ለሚያደርገው የወይን ጠጅ ጥንካሬ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠንካራ የወይን ጠጅ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቅመማ ቅመም
የደረቁ ቅጠላ ቅጠሎች ወይም መሬት ውስጥ የሚገኙ ዘሮች

ገለበጠው
ከትልቅ ፈሳሽ መያዣ ሰዎቹ ወደሚጠጡበት ፅዋዎች ገለበጠው

እስከ መጨረሻው ጠብታ ድረስ ጠጡት
“እያንዳንዱን የወይን ጠጅ ጠብታ ጠጧት”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 75:9

እርሱ ተናገረ
እግዚአብሔር ተናገረ

ቀንዶችን ሁሉ እሰብራለሁ
የእንስሳ ቀንዶች ለሰው ስልጣን ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ስልጣናቸውን ሁሉ ከእነርሱ እወስዳለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የፃድቃን ቀንድ ግን ከፍ ከፍ ይላል
የእንስሳት ቀንዶቸ ለሰው ስልጣን ተለዋጭ ዘይቤ ነው። ይህ በገቢር ቅርፅ እንደ አረፍተ ሀሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የፃድቃንን ቀንዶች ከፍ ከፍ አደርጋለሁ ወይም ፃድቃንን ባለ ስልጣን አደርጋቸዋለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 76

1 እግዚአብሔር በይሁዳ ታወቀ ስሙም በእስራኤል ታላቅ ነው። **2** ድንኳኑ በሳሌም መኖሪያውም በጽዮን ነው። **3** በዚያም የቀስቱን ፍላጻዎች ጋሻውን፣ ጦሩንና ሌሎች የጦር መሣሪያዎችን ሰበረ። ሴላ **4** ጠላቶችህን ካጠፋህበት ተራሮች ስትወርድ ደምቀህ አበራህ፤ ክብርህንም ገለጥህ። **5** ጀግኖች ተኝተው እያሉ የማረኩትን ተቀሙ ጦረኞችም ሁሉ ዐቅመ ቢስ ሆኑ። **6** የያዕቆብ አምላክ ሆይ፤ ከተግሣጽህ የተነሣ ፈረሱና ፈረሰኛው ጭልጥ ብለው ተኝተዋል። **7** መፈራት ያለብህ አንተ ብቻ ነህ፤ በተቆጣህ ጊዜ ፊትህ መቆም የሚችል ማነው? **8** አንተ ከሰማይ ፍርድህን አሰማህ ምድርም ፈርታ ጸጥ አለች **9** አንተ በምድር የተጨቆኑትን ለማዳን ለፍርድ ስትነሣ ዓለም ጸጥ አለ። **10** በእርግጥ የሰው ልጅ ላይ የሚወርደው ቁጣ ፍርድህ አንተን ያመሰግንሃል ከቁጣ የተረፉትንም ትገታቸዋለህ። **11** ለአምላካችሁ ለያህዌ ተሳሉ፣ ስእለቱንም አግቡ በእርሱ ዙሪያ ያሉ ሁሉ መፈራት ለሚገባው እጅ መንሻ ያምጡ። **12** እርሱ የገዦችን መንፈስ ይሰብራል በምድር ነገሥታትም ዘንድ የተፈራ ይሆናል።

Psalms 76:1

አጠቃላይ መረጃ፦
ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ለመዘምራን አለቃ
“ይህ አምልኮ ላይ እንዲጠቀምበት ለመዘምራኑ አለቃ ነው።”

በበገናዎች
“ሰዎች ይህንን መዝሙር በበገና ሊጫወት ይገባል”

የአሳፍ መዝሙር
“አሳፍ የፃፈው ይህ መዝሙር” ይህ በመዝሙር በ መዝሙረ ዳዊት 53:1 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።

ራሱን በይሁዳ እንዲታወቅ አደረገ
“እርሱ ማን እንደሆነ የይሁዳ ህዝብ እንዲያውቁት አደረገ”

ስሙ በእስራኤል ታላቅ ነው
“ስሙ” የሚለው ቃል ለመልካም ስሙ ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የእስራኤል ህዝብ እርሱን መልካምና ሀያል እንደሆነ ይቆጥሩታል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የማደሪያው ስፍራ
“እርሱ ሊኖርበት የመረጠው ስፍራ”

በዚያም ተወርዋሪውን ፍላፃ፣ ጋሻ፣ ሰይፉና ሌሎች የጦር መሳሪያዎችን ሰበረ
እነዚህ ቃላቶች ምናልባት የይሁዳ ህዝብ ጠላቶቻቸው በእነርሱ ላይ ጦርነት ይደፍቱብናል የሚል ፍርሀት ሳይኖራቸው በሰላም እንዲኖሩ ለማድረጉ ተለዋጭ ዘይቤ ናቸው ነገር ግን እነዚህ ቃላቶች በቁሙ ሊተረጎሙ ይገባል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሴላ
ይህ ምናልባትም ሰዎች እንዴት መዘመር እንዳለባቸው ወይም ከዚህ ላይ የሙዚቃ መሳርያዎቻቸውን እንዴት መጫወት እንዳለባቸው የሚናገር የሙዚቃ ቃል ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል በቀጥታ ይፅፋሉ፣ አንዳንድ ትርጉሞች ደግሞ ይህን አያካትቱም። ይህን በ መዝሙረ ዳዊት 3:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከተት። (ቃላቶችን ቅዳ ወይም ከሌላ ውሰድ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 76:4

አጠቃላይ መረጃ፦
አሳፍ ስለ እግዚአብሔር ሲናገር እግዚአብሔር ታላቅ ጦርነትን ካሸነፈ በኋላ ከተራራ እንደሚመለስ አድርጎ ገልፆታል።

አንተ ብርሀን ተላብሰህ ክብርህን ገልጠሀል
ሁለተኛው ሀረግ አንደኛውን ሀረግ ያጠናክራል ምክንያቱም የእግዚአብሔር ክብር ከእግዚአብሔር ብርሀን መላበስ ጋር ተያያዥነት ስላለው ነው። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ በድምቀት ታበራለህ
በድምቀት ታበራለህ የሚሉት ቃላት ታላቅ ለመሆን ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “አንተ እጅግ ታላቅ እንደሆንህ አሳይተሀል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ልበ ሙሉ የሆኑት ተዘረርፈዋል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የአንተ ህዝብ የጠላቶቻቸውን ደፋር ወታደሮች ገደሉና ንብረታቸውን በሙሉ ወሰዱባቸው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

አንቀላፍተው ተኝተዋል
እዚህ ላይ “አንቀላፍተው ተኝተዋል” የሚለው ሞተዋል ለማለት ለስላሴ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ሞተዋል” ወይም “ሞተው ወደቁ” (ለስላሴ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 76:6

ከተግሳፅህ የተነሳ
“ተግሳፅ” የሚለው ረቂቅ ስም የሚያመለክተው በቁጣ ወይም በጥልቅ መንገድ አንድ ነገር መናገርን ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “አንተ በገሰፅሀቸው ጊዜ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

አንቀላፍተው ተኝተዋል
ይህ ሀረግ እነርሱ ሞተዋል ብሎ ለመናገር ትህትና የተሞላበት መንገድ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ሞተዋል” ወይም “ሞተው ወደቁ” (ለስላሴ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በተቆጣህ ጊዜ ማን በፊትህ መቆም ይችላል?
ይህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አንተ በተቆጣህ ጊዜ አንድም ሰው በፊትህ ሊቆም አይችልም።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 76:8

አንተ ፍርድህ እንዲሰማ አደረግህ
“አንተ ፍርድን አስተላለፍህ” ወይም “አንተ ክፉ ሰዎችን እንዴት እንደምትቀጣ አወጅህ”

ምድር ነበረች
እዚህ ላይ “ምድር” በምድር ለሚኖሩ ሰዎች ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የምድር ሰዎች… ነበሩ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ፍርድን ፈፀምህ
“ፍርድን አስተላለፍህ” ወይም “ክፉ ሰዎችን ቀጣህ”

ሴላ
ይህ ምናልባት ሰዎች እንዴት መዘመር እንዳለባቸው ወይም እዚህ ላይ የሙዚቃ መሳርያዎቻቸውን እንዴት መጫወት እንዳለባቸው የሚናገር የሙዚቃ ቃል ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል በቀጥታ ይፅፋሉ፣ አንዳንድ ትርጉሞች ደግሞ ይህን አያካትቱም። ይህን በ መዝሙረ ዳዊት 3:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ቃላቶችን ቅዳ ወይም ከሌላ ውሰድ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 76:10

በእርግጥ የአንተ የቁጣ ፍርድ
“የአንተ የቁጣ ፍርድ እርግጠኛ ነው”

በሰው ልጆች ላይ የሚገለጠው የአንተ የቁጣ ፍርድ ለአንተ ክብርን ያመጣል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፦ 1) “ሰዎች አንተን ያመሰግኑሀል ምክንያቱም አንተ በክፉዎች ላይ ስለተቆጣህና በእነርሱ ላይ ስለፈረድህ ነው” ወይም 2) “ከአንተ ጋር የተቆጡ ሰዎች አንተን እንዲያመሰግኑ የሚያደርጉ ነገሮችን ያደርጋሉ።”

ከቁጣህ በተረፉት ራስህን ትታጠቃለህ
የእግዚአብሔር ቁጣ እርሱ በዙሪያው እንደ ቀበቶ ሊታጠቀው የሚችለው ነገር እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “የተረፈውን ቁጣህን እንደ ቀበቶ በዙሪያህ ትታጠቃለህ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 76:11

ሊፈራ ለሚገባው ለእርሱ
“ሊፈሩት የሚገባው እግዚአብሔር”

እርሱ የገዢዎችን መንፈስ ይሰብራል
“እርሱ… መንፈስ ይሰብራል” የሚለው ሀረግ ፈሊጥ ሲሆን እርሱ መንፈስን ይሰብራል ወይም ያዋርዳል ማለት ነው።አማራጭ ትርጉም፦ “እርሱ ገዢዎችን ያዋርዳል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

በምድር ነገስታት ዘንድ የተፈራ ነው
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የምድር ነገስታት እርሱን ይፈሩታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 77

1 ድምፄን ከፍ አድርጌ ወደ እግዚአብሔር እጮኻለሁ ይሰማኝ ዘንድ ድምፄን ከፍ አድርጌ እግዚአብሔርን እጠራለሁ። **2** በመከራዬ ቀን ጌታን ፈለግሁት በሌሊትም ያለ ዕረፍት እጆቼን ዘረጋሁ፤ ነፍሴ አልጽናና አለች። **3** አምላኬ ሆይ፣ አንተን ባሰብሁ ቁጥር ቃተትሁ ባወጣሁ ባወረድሁ መጠን መንፈሴ ዛለች። **4** ዐይኖቼ እንዳይከደኑ አደረግህ መናገር እስኪሳነኝ ድረስ ታወክሁ። **5** የቀድሞውን ዘመን አሰብሁ የድሮውን ዘመን አወጠነጠንሁ። **6** በሌሊት ዝማሬዬን አስታወስሁ በጥልቅ በማሰብ እየሆነ ያለውን መረዳት ሞከርሁ። **7** እግዚአብሔር ለዘላለም ጥሎኛልን? ከእንግዲህስ ቸርነት አያደርግልኝምን? **8** የኪዳን ታማኝነቱስ እስከ ወዲያኛው ተሻረን? የተስፋ ቃሉንስ ዘነጋ? **9** እግዚአብሔር ቸርነቱን ረሳ? ወይስ ከቁጣው የተነሣ መራራቱን ትቶአልን? ሴላ **10** እኔም፣ «የልዑል ቀኝ እጅ እንደ ተለወጠ ማሰቤ ይህ የእኔ ደካማነት ነው» አልሁ። **11** ያህዌ ሆይ፣ ሥራዎችህን ሁሉ አስታውሳለሁ ድሮ ያደረግኸውን ድንቅ ሥራ አስባለሁ። **12** ሥራዎችህን ሁሉ አሰላሰላለሁ ድንቅ ሥራህን ሁሉ አውጠነጥናለሁ። **13** አምላክ ሆይ፣ መንገድህ ቅዱስ ነው እንደ አምላካችን ያለ ታላቅ አምላክ ማን ነው? **14** እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ ድንቆችን የምታደርግ አምላክ ነህ በሕዝቦች መካከል ኃይልህን ገለጥህ። **15** በታላቅ ኃይልህ ለሕዝብህ ለያዕቆብና ለዮሴፍ ልጆች ድል ሰጠሃቸው። ሴላ **16** አምላክ ሆይ፣ ውሆች አዩህ ውሆች አንተን አይተው ፈሩ፤ ጥልቆችም ተነዋወጡ። **17** ደመኖች ውሃ አንጠባጠቡ። ሰማያት አንጐዳጐዱ ፍላጾችህም ዙሪያውን አንጸባረቁ። **18** የድምፅህ ነጐድጓድ ዐውሎ ነፋስ ውስጥ አስተጋባ የመብረቅ ብልጭታ ዓለምን አበራ ምድር ራደች ተንቀጠቀጠች። **19** መንገድህ በባሕር ውስጥ ነው መሄጃህም በታላቅ ውሃ ውስጥ ነው ዱካህንም ማንም አላየም። **20** በሙሴና በአሮን እጅ ሕዝብህን እንደ በግ መንጋ መራኸው።

Psalms 77:1

አጠቃላይ መረጃ፡-
ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ለመዘምራን አለቃ
“ይህ አምልኮ ላይ እንዲጠቀምበት ለመዘምራኑ አለቃ ነው።”

ኤዶታም
ከዳዊት ዋነኛ ሙዚቃ ተጫዋቾች መካከል አንዱ ይህ ተመሳሳይ ስም ነበረው። ይህ እሱነ ሊያመለክት ይችላል። ይህን በ መዝሙረ ዳዊት 39:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

የአሳፍ መዝሙር
“ይህ አሳፍ የፃፈው መዝሙር ነው።” ይህ በ መዝሙረ ዳዊት 53:1 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።

Psalms 77:2

እጆቼን ዘረጋሁ
“እጆቼን በመዘርጋት ፀለይኩኝ”

ነፍሴ አልፅናና አለች
ነፍስ ሰውየውን ትወክላለች። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ አንድም ሰው እኔን ለማፅናናት እንዲሞክር አልፈቅድለትም” (ወካይ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በጮኽሁ ጊዜ እግዚአብሔርን አሰብሁት፤ ነፍሴን በሳትሁ ጊዜ ስለ እግዚአብሔር አሰብሁ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ይጋራሉ፣ በአንድ ላይ የተጣመሩት ለአፅንኦት ነው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ነፍሴን ሳትሁ
“መንፈሴ በፈዘዘ ጊዜ” ወይም “መንፈሴ በደከመ ጊዜ“

ሴላ
ይህ ምናልባት ሰዎች እንዴት መዘመር እንዳለባቸው ወይም እዚህ ላይ የሙዚቃ መሳሪያዎቻቸውን እንዴት መጫወት እንዳለባቸው የሚናገር የሙዚቃ ቃል ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል በቀጥታ ይፅፋሉ፣ አንዳንድ ትርጉሞች ደግሞ ይህን አያካትቱም። ይህን በ መዝሙረ ዳዊት 3:2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ቃላቶችን ቅዳ ወይም ከሌላ ውሰድ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 77:4

አጠቃላይ መረጃ፡-
ስለ እግዚአብሔር ከተናገረ በኋላ አሳፍ በቁጥር 4 ላይ ለእግዚአብሔር ተናገረና እንደገና ተመልሶ ስለ እግዚአብሔር መናገር ቀጠለ።

አይኖቼ እንዳይከደኑ ያዝኸቸው
“ለእግዚአብሔር እንዲህ አልኩት፣ “አይኖቼ እዳይከደኑ ያዝኸቸው”

አይኖቼ እንዳይከደኑ ያዘ
ያልተከደነ አይን ለመተኛት አለመቻልን የሚያሳይ ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እንዳልተኛ ከለከለኝ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የድሮውን ቀናት... የጥንቶቹን ጊዜያት
አስፈላጊ ከሆነ “የድሮ ቀናት” እና “የጥንት ጊዜያት” የሚሉት ሊጣመሩ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “በጣም ረጅም ጊዜ በፊት ስለተከናወኑ ነገሮች” (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 77:6

ወደ አእምሮዬ ተመለስሁ
ይህ ማስታወስን የሚገልጽ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አስታወስሁ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

የሆነው ምን እንደሆነ
ሌላ አማራጭ ትርጉም፡- “ምን እየሆነ እንደነበረ” ነው።

ጌታ ለዘላለም ይጥለኛል? እርሱ እንደገና በጎነትን አያሳየኝም?
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በጌታ ዘንድ የተጣለ የመሆን ስሜትን የሚገልፁ ናቸው። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

በጎነት ያሳየኛል
“በእኔ እንደተደሰተ የሚያሳዩ ነገሮችን ያደርጋል”

Psalms 77:8

አጠቃላይ መረጃ፡-
አሳፍ ለእነዚህ ጥያቄዎች የሚሰጠው መልስ ምን እንደሆነ እርግጠኛ ስላልነበረ ምናልባት በቀጥታ የተጠየቁ ጥያቄዎች ሊሆኑ ይችላሉ ስለዚህ በቀጥታ ሊተረጎሙ ይገባል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የኪዳኑ ታማኝነት ለዘላለም ጠፋ ወይ?
አሳፍ እግዚአብሔር ለኪዳኑ በታማኝነት ከእንግዲህ ወዲህ ስላለመስራቱ ሲናገር የእግዚአብሔር የኪዳኑ ታማኝነት እንደጠፋ አድርጎ ገልፆታል። ታማኝነት የሚለው ረቂቅ ስም በቅፅል ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ ለኪዳኑ ታማኝ መሆን ለዘላለም አቆመን?” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ቸርነቱን ረሳን? ከቁጣው የተነሳ ርህራሄውን ነፈገ?
እነዚህ እግዚአብሔር ርህራሄ አለማሳየቱን ተመሳሳይ ሀሳብ የሚያብራሩ ሁለት መግለጫዎች ናቸው። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ከቁጣው የተነሳ ርህራሄውን ነፈገ?
አሳፍ ስለ ቁጣ ሲናገር ቁጣ ሌላ ሰው፣ ርህራሄ የሚባል፣ ወደ ውጭ እንዳይወጣ ለመጠበቅ በር የሚዘጋ ሰው እንደሆነ አደርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር በእኛ ላይ ከመቆጣቱ የተነሳ ርህራሄ ለእኛ ማሳየቱን አቆመን?” (ሰውኛ ዘይቤ እና መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 77:10

አልሁ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፡- 1) ዘማሪው የሚናገረው ለራሱ ይናገር ነበር ወይም 2) ዘማሪው ለእግዚአብሔር ይናገር ነበር።

የልዑል የቀኝ እጅ ለእኛ እንደተለወጠ
“ቀኝ እጅ” ለሀይል፣ ስልጣንና ብርታት ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ልዑል እኛን ለመርዳት ከእንግዲህ ወዲህ ሀይሉን አይተቀምም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 77:11

አጠቃላይ መረጃ፡-
ጸሐፊው ለእግዚአብሔር መናገር ጀምሯል።

ወደ አእምሮዬ ተመለስኩ
“አስታወስሁ” ይህን በ መዝሙረ ዳዊት 74:2 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

የጥንት አስደናቂ ስራዎችህን
“ከረጅም ጊዜ በፊት የሰራሀቸውን አስደናቂ ነገሮች”

ስራህን ሁሉ አሰላስላለሁ፣ በእነርሱ ላይ አውጠነጥናለሁ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች እግዚአብሔር በሰራው ስራ ላይ የማሰላሰልን ሀሳብ የሚገልፁ ናቸው። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

አሰላስላለሁ
በጥልቀት ስለ አንድ ነገር ማሰብ

በእነርሱ ላይ አውጠነጥናለሁ
“እነርሱ ምን ማለት እንደሆኑ ማሰብ”

Psalms 77:13

አጠቃላይ መረጃ፡-
ጸሐፊው ለእግዚአብሔር መናገሩን ቀጥሏል።

እንደ አምላካችን ያለ ታላቅ አምላክ ማን ነው?
ይህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከእኛ ታላቅ አምላክ ጋር የሚወዳደር ማንም አምላክ የለም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በህዝቦች መካከል ሀይልህን ትገልጣለህ
“ሀይል” የሚለው ረቂቅ ስም በቅፅል ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከብዙ የህዝብ ወገኖች ለህዝብ ምን ያህል እንደሆንህ አሳየህ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ለህዝብህ ድል ሰጠሀቸው... ለልጆች
“ለእኛ ለህዝብህ ድል ሰጠኸን... ለእኛ ለልጆች”

ለህዝብህ ድል ሰጠሀቸው
“ድል” የሚለው ረቂቅ ስም በቅፅል ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ህዝብህ አሸናፊ እንዲሆኑ አደረግህቸው” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የያዕቆብና የዮሴፍ ልጆች
ይህ መላው የእስራኤልን ህዝብ የሚያመለክት ነው።

Psalms 77:16

ውሆች አንተን አዩህ... ፈሩ... ጥልቆች ተነዋወጡ
አሳፍ ስለ ውሀ ሲናገር ውሀው እርሱን የሚያስፈራው ነገር እንዳየ ሰው አድርጎ ገልፆታል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ውሆች አንተን አዩህ፣ እነርሱም ፈሩ፤ ጥልቆችም ተነዋወጡ
“ውሀ” እና “ጥልቅ” ባህር እና ውቅያኖስ የመሳሰሉትን ትልቅ የውሀ አካል ያመለክታሉ። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ጥልቆች
ጥልቅ ውሀዎች

ደመናት ውሀን አንጠባጠቡ
አሳፋ ስለ ደመናት ሲናገር ውሀን ከማጠራቀሚያ እያወጡ የሚያፈስሱ ሰዎች እንደሆኑ አድርጎ ገልፆአቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ብዙ ዝናብ ወረደ” ወይም “በጣም ጠንካራ ዝናብ ዘነበ” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ፍላፃችህ ዙሪያውን አብለጨለጩ
ይህ የእግዚአብሔር ፍላጾች ማብለጭለጫቸውን የሚገልፅ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ከአንተ የወጣው መብረቅ እንደ ፍላጻዎች ያበራል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አብለጨለጩ
አንድ ሰው ፍላፃን ከወረወረ በኋላ ፍላፃው ምን እንደሚያደርግ የሚገልጽ በራስህ ቋንቋ ተጠቀም።

Psalms 77:18

የነጎድጓድ ድምፅ
ይህ ሰውኛ ዘይቤ ሲሆን ነጎድጓዱን እንደ እግዚአብሔር ድምፅ የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እንደ ነጎድጓድ የሚጮህ ድምጽ” ወይም “በጣም ታላቅ ድምፅ” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መብረቅህ አለምን አበራው
ይህ መብረቅ ጸሀፊው ሊያየው የሚችለውን ማንኛውንም ነገር እንዳበራው አፅንኦት ለመስጠት ጥቅም ላይ የዋለ ግነት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “መብረቅህ ልታየው የምትችለውን ያህል ያለ ማንኛውንም ነገር አበራው” (ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መንገድህ... መሄጃህ
እነዚህ ሁለት ቃላቶች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን አንድ ላይ የተጣመሩት ለአፅንኦት ነው። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የአንተ ዱካ
አሳፍ ስለ እግዚአብሔር ሲናገር እግዚአብሔር እግር ያለው ሰው እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። ይህ ሰውኛ ሆኖ ሳለ የሚቻል ከሆነ በቀጥታ ሊተረጎም ይገባል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ ዱካዎች አይታዩም
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “የአንተን ዱካ ማንም ሰው አላየም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ህዝብህን እንደ በግ መንጋ መራኸው
ይህ ተነፃፃሪ የእግዚአብሔርን ህዝብ ከእንስሳት መንጋ ጋር ያወዳድረዋል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በእጅ
እዚህ ላይ “በእጅ” የሚለው ቃል “በድርጊታቸው” ወይም “በድርጊታቸው በኩል” ማለት ነው።

እጅ
እዚህ ላይ “እጅ” የሚለው ለሰው ሁለንተና ወካይ ዘይቤ ነው። (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 78

1 ሕዝቤ ሆይ፣ ትምህርቴን ሰሙ የአፌንም ቃል አድምጡ። 2 አፌን በምሳሌ እከፍታለሁ ከጥንት ጀምሮ የተሰወረውን ምስጢር እገልጣለሁ። 3 ይህም
የሰማነውና ያወቅነው አባቶቻችንም የነገሩን ነው። 4 እኛም ከልጆቻቸው አንደብቀውም ስለ እግዚአብሔር ኃይል ስላከናወናቸውም ታላላቅ ሥራዎችና
ስላደረጋቸው ድንቅ ነገሮች ለተከታዩ ትውልድ እንገራለን። 5 ለያዕቆብ ሥርዐትን መሠረተ ለእስራኤልም ሕግን ደነገገ። ይህንንም ለሚቀጥለው ትውልድ
እንዲያስተምሩ አባቶቻችንን አዘዘ። 6 ይህም የሚመጣው ትውልድ ሥርዐቱን እንዲያውቅ እነርሱም በተራቸው ለልጆቻቸው ገና ለሚወለዱትም እንዲነግሩ ነው።
7 እነርሱም በእግዚአብሔር ይታመኑ የእግዚአብሔርን ሥራ አይረሱም ትእዛዞቹንም ይጠብቃሉ። 8 እንደ ቀድሞ አባቶቻቸው እልኸኛና ዐመፀኛ አይሆኑም፤
እነርሱ እግዚአብሔርን በማመን አልጸኑም ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነው አልኖሩም። 9 የኤፍሬም ሰዎች የታጠቁ ቀስተኖች ቢሆኑም በጦርነት ቀን ወደ ኋላ
ተመለሱ። 10 የእግዚአብሔርን ኪዳን አልጠበቁም፣ በሕጉ መሠረት መኖርም አልፈለጉም። 11 ሥራዎቹን ረሱ ያሳያቸውንም ድንቆች ዘነጉ። 12 በግብፅ ምድር፣
በዞዓር ምድር በአባቶቻቸው ፊት ያደረጋቸውን ድንቆች ዘነጋ። 13 ባሕሩን ከፍሎ አሻገራቸው ውሃውንም እንደ ግድግዳ አቆመው። 14 ቀን በደመና፣ ሌሊቱንም
ሁሉ በእሳት ብርሃን መራቸው። 15 በምድረ በዳ ዐለቱን ሰነጠቀ እንደ ባሕር የበዛ ውሃ ሰጣቸው። 16 ከዐለቱ ምንጭ አፈለቀ ውሃውም እንደ ወንዝ እንዲፈስ
አደረገ 17 እነርሱ ግን ኃጢአት ማድረጋቸውን ቀጠሉ፤ በምድረ በዳ በልዑል ላይ ዐመፁ። 18 የተመኙትን ምግብ በመጠየቅ፣ ሆን ብለው እግዚአብሔርን
ተፈታተኑት። 19 እንዲህ በማለትም በእግዚአብሔር ላይ ተናገሩ፣ «ለመሆኑ፣ እግዚአብሔር በምድረ በዳ ማዕድ ማዘጋጀት ይችላልን?» 20 ዐለቱን ሲመታው
ውሃ ተንዶለዶለ ጅረቶችም ጐረፉ። ታዲያ፣ እርሱ እንጀራንም መስጠት ይችላል? ለሕዝቡስ ሥጋ ማቅረብ ይችላል? 21 ያህዌ ይህን ሲሰማ እጅግ ተቆጣ
በያዕቆብ ላይ እሳት ነደደ በእስራኤልም ላይ ቁጣው ተቀጣጠለ። 22 በእግዚአብሔር አላመኑም በእርሱም ማዳን አልተማመኑም። 23 ሆኖም እርሱ ከላይ
ያሉትን ሰማያትን አዘዘ የሰማይንም በሮች ከፈተ 24 ይበሉ ዘንድ ለሕዝቡ መና አዘነበላቸው የሰማይንም ምግብ ሰጣቸው። 25 ሰዎች የመላእክትን እንጀራ በሉ።
ጠግበው እስከሚተርፍ ድረስ ምግብ ላከላቸው። 26 የምሥራቅን ነፋስ ከሰማይ አስነሣ የደቡብንም ነፍስ በኃይሉ አመጣ። 27 ሥጋን እንደ ዐፈር ብዙ
ውፎችንም እንደ ባሕር አሸዋ አዘነበላቸው። 28 ሰፈራቸው መሓል በድንኳኖቻቸውም ዙሪያ አወረደ። 29 ስለዚህ እስኪጠግቡ ድረስ በሉ አጥብቀው
የተመኙትን ሰጣቸው። 30 ነገር ግን ገና ምኞታቸውን ሳያረኩ፣ ምግቡ ገና አፋቸው ውስጥ እያለ፣ 31 የእግዚአብሔር ቁጣ እነርሱ ላይ ተነሣ የእስራኤልን ኃያላን
ሰዎች ገደለ ምርጥ ወጣቶችንም በአጭር ቀጨ። 32 ይህም ሆኖ፣ ኃጢአት ማድረጋቸውን ቀጠሉ፤ ድንቅ ሥራዎቹንም አላመኑም። 33 ስለዚህ ዘመናቸውን
አሳጠረ ዕድሜያቸውም በሽብር እንዲያልቅ አደረገ። 34 እርሱ በገደላቸው ጊዜ ፈለጉት ከልባቸው በመሻትም ወደ እርሱ ተመለሱ። 35 እግዚአብሔር
ዐለታቸው፣ ልዑል አምላክ ታዳጊያቸው እንደ ሆነ አስቡ። 36 ነገር ግን በአፋቸው ሸነገሉት በአንደበታቸውም ዋሹት። 37 ልባቸው በእርሱ የጸና አልነበረም
ለኪዳኑም ታማኞች አልነበሩም። 38 እርሱ ግን መሐሪ ስለሆነ ኃጢአታቸውን ይቅር አለ፤ እነርሱንም አላጠፋም ቁጣውን ብዙ ጊዜ ገታ መዐቱንም አላወረደም።
39 ካለፈ በኋላ እንደማይመለስ ነፋስ ሥጋ ለባሾች መሆናቸውን አሰበ። 40 በምድረ በዳ ስንት ጊዜ ዐመፁበት በበረሓስ ምን ያህል አሳዘኑት! 41 ደግመው
ደጋግመው እግዚአብሔርን ተፈታተኑት የእስራኤልንም ቅዱስ አስቆጡት። 42 ኃይሉን አላሰቡም፣ እነርሱን ከጠላቶቻቸው እጅ ያዳነበትን፣ ቀንና ታላቁን ኃይሉን
አላስታወሱም። 43 በግብፅ አገር፣ በዞዓር ሜዳ ያደረጋቸውን ታላላቅ ድንቆችና ምልክቶች ዘነጉ። 44 ከወንዞቻቸው ወሃ መጠጣት እንዳይችሉ የግብፃውያንን
ወንዞች ወደ ደም ለወጠ። 45 ተናዳፊ የዝንብ ሰራዊት ሰደደባቸው፣ ጓጉንቸርም ላከባቸው፤ ምድራቸውንም አጠፋ። 46 ሰብላቸውን ለኩብኩባ፣ ምርታቸውንም
ለአንበጣ ሰጠ። 47 የወይን ተክላቸውን በበረዶ የበለስ ዛፎቻቸውንም በውርጭ አጠፋ። 48 ከብቶቻቸውን በበረዶ በጐቻቸውንም በመብረቅ ገደለ። 49 ጽኑ
ቁጣውን በላያቸው ሰደደ መዓቱን፣ የቅናቱንም ቁጣና መቅሠፍት ላከባቸው አጥፊ የመላእክት ሰራዊትም ሰደደባቸው። 50 ለቁጣው መንገድ አዘጋጀ፤ ከሞትም
አላዳናቸውም። ነገር ግን ሕይወታቸውን ለመቅሠፍት አሳልፎ ሰጠ። 51 የዐፍላ ጉልበታቸው መጀመሪያ የሆኑትን በካም ድንኳኖች፣ በኩሮቻቸውንም ሁሉ
በግብፅ ምድር ፈጀ። 52 ሕዝቡን ግን እንደ በግ አሰማራቸው በምድረ በዳ እንደ መንጋ መራቸው 53 በሰላም ስለ መራቸው አልፈሩም ጠላቶቻቸውን ግን ባሕር
ዋጣቸው። 54 ከዚያም ወደ ተቀደሰች ምድሩ፣ ቀኝ እጁም ወዳስገኘው ወደዚህ ተራራ አመጣቸው። 55 ሕዝቦችን ከፊታቸው አባረረ ምድራቸውንም ርስት
አድርጐ አከፋፈላቸው። የእስራኤል ነገዶችን በጠላቶቻቸው ድንኳን አኖረ። 56 እነርሱ ግን አምላክን ተፈታተኑት በልዑልም ላይ ዐመፁ፤ ትእዛዞቹንም
አልጠበቁም። 57 እንደ አባቶቻቸው ዐመፀኞችና ከዳተኞች ሆኑ። እንደማያስተማምን ጠማማ ቀስት ተወላገዱ። 58 በኮረብታ ማምለኪያዎቻቸው አስቆጡት
በጣዖቶቻቸውም አስቀኑት። 59 እግዚአብሔር በሰማ ጊዜ እጅግ ተቆጣ እስራኤልንም ፈጽሞ ተወ። 60 በሰዎች መካከል የኖረባትን ድንኳን፣ በሴሎ የነበረች
ማደሪያውን ተዋት። 61 የኃይሉን ምልክት አስማረካት፣ ክብሩንም ለጠላቶች እጅ አሳልፎ ሰጠ። 62 ሕዝቡን ለሰይፍ ዳረገ በርስቱም ላይ እጅግ ተቆጣ። 63
ጐልማሶቻቸውን እሳት በላቸው ለልጃገረዶቻቸውም የሰርግ ዘፈን አልተዘፈነላቸውም። 64 ካህናቶቻቸው በሰይፍ ተገደሉ መበለቶቻቸው ማልቀስ ተሳናቸው። 65
ጌታም ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሣ የወይን ጠጅ ጠጥቶ ድፍረት እንደሚሰማው ጀግና ሆነ። 66 ጠላቶቹን መትቶ ወደ ኋላ መለሳቸው የዘላለም ውርደትንም
አከናነባቸው። 67 የዮሴፍን ድንኳን ተዋት፣ የኤፍሬምንም ነገድ አልመረጠም። 68 ነገር ግን የይሁዳን ነገድና የወደዳትን የጽዮን ተራራ መረጠ። 69 መቅደሱን
እንደ ሰማያት፣ እርሱ ለዘላለም እንደ መሠረታት ምድር ሠራት። 70 ባርያውን ዳዊትን መረጠ ከበጐች ጉረኖ ወሰደው፤ 71 ለሕዝቡ ለያዕቆብ፣ ለርስቱም
ለእስራኤል እረኛ ሊደርገው የሚያጠቡ በጐችን ከመከተል አመጣው። 72 ዳዊትም በፍጹም ቅንነት ጠበቃቸው፤ በእጁ ብልኃትም መራቸው።

Psalms 78:1

አጠቃላይ መረጃ፦
ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

የአሳፍ ትምህርት
“ይህ አሳፍ የፃፈው ትምህርት ነው።” “የአሳፍ ትምህርት” የሚለውን መዝሙረ ዳዊት 50:1 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።

ትምህርት
ይህ የሙዚቃ ስልትን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። ይህ በ መዝሙረ ዳዊት 32:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

ትምህርቴን ስማ
“ትምህርት” የሚለው ስም በግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔ የማስተምርህን ስማ” ወይም “ሳስተምርህ ስማ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የአፌን ቃላቶች
“አፍ” የሚለው ቃል ሰውየውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ቃሌን” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

አፌን በምሳሌ እከፍታለሁ
“አፌን እከፍታለሁ” የሚለው ፈሊጥ መናገር ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በምሳሌ እናገራለሁ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ... ዘምሩ
“ተናገሩ።” “ትናገራለች” የሚለውን በ መዝሙረ ዳዊት 19:2 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።

የተሰወሩ ነገሮችን
የአንተ ቋንቋ ሆን ተብሎ ለመረዳት አስቸጋሪ እንዲሆን የተደረጉትን አባባሎች የሚገልፅ ቃል ካለው እዚህ ላይ ልትጠቀምበት ትችላለህ።

Psalms 78:3

አጠቃላይ መረጃ፡-
ቁጥር 3 በቁጥር 2 ላይ የተጀመረውን አረፍተ ነገር ይቀጥላል።

እነዚህን ከልጆቻቸው አንሰውርም
ይህን በአዎንታዊ መልክ ልንፅፈው እንችላለን። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለ እነርሱ ለልጆቻችን በእርግጠኝነት እንነግራቸዋለን”

የእግዚአብሔርን ምስጋናውንና ያደረገውን ድንቅ ነገር
“እግዚአብሔርን የምናመሰግንባቸውን ነገሮች”

Psalms 78:5

መሰረተ
“እግዚአብሔር መሰረተ”

የቃል ኪዳን ስርአቶች
ሌሎች ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፡- “ምስክሮች” ወይም “ህጎች።”

Psalms 78:7

አጠቃላይ መረጃ፡-
ጸሐፊው የሚናገረው በ መዝሙረ ዳዊት 78:5-6 ስላሉት ልጆች ነው።

Psalms 78:9

የኤፍሬም ልጆች... የጦርነት ቀን
ይህ ምናልባት ቃል ኪዳኑን (ቁጥር 10) ላለመጠበቅ ተለዋጭ ዘይቤ ሊሆን ይችላል ነገር ግን ይህን በቀጥታ መተርጎም ይሻላል።

የኤፍሬም ልጆች
“የኤፍሬም ልጆች ወታደሮች”

ቀስት ታጥቀው ነበር
ወታደሮቹ ምናልባት ቀስት ጭምር ነበራቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “ለጦርነት የሚሆኑ ቀስትና ጦር ነበራቸው።” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 78:12

የጣኔዎስ ምድር
ይህ በግብፅ ምድር የነበረውን በጣኔዎስ ከተማ አካባቢ የነበረውን ስፍራ ያመለክታል። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 78:15

እርሱ ሰነጠቀ
“እግዚአብሔር ሰነጠቀ”

የባህሩን ጥልቅ ለመሙላት የሚበቃ
ይህ ምናልባት ግነት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሊጠጡት ከሚችሉት በላይ የሆነ ተጨማሪ ዉሀ” (ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ምንጮች
ትንንሽ ወንዞች

Psalms 78:17

እነርሱ እግዚአብሔርን ተፈታተኑት
እግዚአብሔር አደርገዋለሁ ብሎ የተናገረውን ነገር ማድረግ እንደሚችል እርሱን ከማመናቸው በፊት እንዲያረጋግጥላቸው ፈለጉ።

በልባቸው
“በሙሉ ልባቸው”

የምግብ ፍላጎታቸውን ለማርካት
“የተመኙትን ያህል መብላት እንዲችሉ”

Psalms 78:19

ተናገሩ
እስራኤላውያን ተናገሩ

በእውነት እግዚአብሔር በምድረ በዳ ማዕድ ለእኛ ማዘጋጀት ይችላልን?
ይህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኛ በእውነት እግዚአብሔር በምድረ በዳ ለእኛ ማእድ ሊያዘጋጅ ይችላል ብለን አናምንም!” ወይም “እግዚአብሔር፣ አንተ በእውነትም በምድረ በዳ ለእኛ ማእድ ማዘጋጀት የምትችል መሆንህን አረጋግጥልን!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ማእድ ማዘጋጀት
“ማእድ ማዘጋጀት” የሚለው ፈሊጥ ምግብ ለመብላት ማእድ ማዘጋጀት ማለት ነው። እዚህ ላይ “ማእድ” የሚለው ለሚበላው ምግብ ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ምግብ አዘጋጀልን” (ፈሊጥ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ውሃ ተንዶለዶለ
ብዙ ውሀ በፍጥነት ወጣ

ነገር ግን እንጀራ መስጠት ይችላልን? ለህዝቡስ ስጋን ሊያቀርብ ይችላልን?
ህዝቡ በእነዚህ ጥያቄዎች እርሱን እየሰደቡ በእግዚአብሔር ላይ ይስቃሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን እንጀራ እንደሚሰጠንና ለህዝቡ ስጋ ማቅረብ እንደሚችል ይህን ሰርቶ እስከሚያሳይ ድረስ አናምንም።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

እንጀራ... ስጋ
ከእፅዋት የሚገኝ ምግብ፣ ከእንስሳት የሚገኝ ምግብ። ምንም እንኳ ይህ ለሁሉም አይነት ምግብ ወካይ ቢሆንም የሚቻል ከሆነ በቀጥታ መተርጎም የተሻለ ነው። (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 78:21

በያዕቆብ ላይ እሳቱ ነደደ
ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር ቁጣ ሲናገር ቁጣው እሳት እንደሆነና እሳቱ ያዕቆብን እንዳቃጠለው ያህል እግዚአብሔር በያዕቆብ ላይ በቁጣ እርምጃ እንደወሰደበት አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ቁጣው ያዕቆብን እንደ እሳት አቃጠለው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ያዕቆብ
ይህ የሚያመለክተው የአስራኤልን ህዝብ ነው።

ቁጣው እስራኤልን አጠቃ
ጸሐፊው እግዚአብሔር በተቆጣ ጊዜ እስራኤልን ስለመቅጣቱ ሲናገር ቁጣው እስራኤልን ያጠቃ እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ ስለተቆጣ እስራኤልን አጠቃው” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ ማዳን አልታመኑም
“እነርሱን እንደሚያድናቸው አላመኑትም”

Psalms 78:23

እርሱ ሰማያትን አዘዘ
አሳፍ ስለ ሰማያት ሲናገር ሊሰማ የሚችልና የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የሚያደርግ ሰው እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ ለሰማይ ተናገረ” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰማያት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፡- 1) “ሰማይ” ወይም 2) “ደመናት።”

የሰማይንም ደጆች ከፈተ
አሳፍ ስለ ሰማይ ሲናገር በር ያለው መጋዘን እንደሆነ አድርጎ አቅርቦታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰማይን እንደ መጋዘን ከፈተው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይበሉም ዘንድ መና አዘነበላቸው፤ ከሰማይም መብልን ሰጣቸው
እነዚህ ሁለት መስመሮች ስለ ተመሳሳይ ክስተት ያወራሉ።

መና አዘነበላቸው
“መና ከሰማይ እንደ ዝናብ እንዲፈስስላቸው አደረገ”

የመላዕክት እንጀራ
ይህ እግዚአብሔር ለህዝቡ የሰጠውን መና የሚያመለክት ነው። “እንጀራ” የሚለው ቃል በአጠቃላይ ምግብን የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “መላዕክት የሚበሉት አይነት ተመሳሳይ ምግብ” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

የተትረፈረፈ ምግብ
“የተትረፈረፈ” የሚለው ረቂቅ ስም በቅፅል ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ብዙ ምግብ” ወይም “ትልቅ መጠን ያለው ምግብ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 78:26

አመጣ
“እግዚአብሔር አመጣ”

ስጋን እንደ አፈር አዘነበላቸው
ጸሐፊው እግዚአብሔር ወፎችን ከሰማይ እንዲወርዱ ስለማድረጉ ሲናገር ወፎቹ እግዚአብሔር ከሰማይ እንዲወርዱ ያደረጋቸው ዝናብ እንደሆኑ አድርጎ ገልፆአቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ ስጋ እንደ ዝናብ ከሰማይ እንዲወርድ አደረገ፣ ይህም እጅግ በጣም ብዙ ከመሆኑ የተነሳ ምድርን እንደ አፈር ሸፈነው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ተነጻጻሪ የሚለውን ይመልከቱ)

ስጋ
ወፎች

እንደ ባህር አሸዋ እጅግ ብዙ ናቸው
የባህርን አሸዋ መቁጠር የሚችል አንድም ሰው የለም። አንድም ሰው ሊቆጥራቸው ከሚችለው በላይ የሆኑ እጅግ ብዙ ወፎች ነበሩ፣ ነገር ግን ይህ መግለጫ ግነት ነው፡- ምናልባት ከባህር አሸዋ የሚበልጥ ቁጥር ያላቸው ወፎች ቃል በቃል አልነበሩም ይሆናል። (ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 78:29

ጎመጁ
በብርቱ ፈለጉ

Psalms 78:31

በዚያን ጊዜ
ምግቡ በአፋቸው እያለ (መዝሙረ ዳዊት 78:31)

የእግዚአብሔር ቁጣ በላያቸው ላይ መጣ
“እግዚአብሔር ተቆጣና በላያቸው መጣ።” “የእርሱ ቁጣ በእስራኤል ላይ መጣ “ የሚለውን በ መዝሙረ ዳዊት 78:21 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በላያቸው ላይ መጣ
ይህ ለስላሴ ዘይቤ ሲሆን ትርጉሙም እንዲሞቱ አደረጋቸው ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ገደላቸው” (ለስላሴ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አስደናቂ ስራውን አላመኑም
“ስራ” የሚለው ቃል ስራዎቹን ለሰራው ለእግዚአብሔር ምትክ ስም ነው። ያላመኑት ምን እንደሆነ በግልፅ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ምንም እንኳ እንዲህ አይነት አስደናቂ ስራ ቢሰራም እነርሱን እንደሚንከባከባቸውና እንደሚጠብቃቸው አላመኑም።” (ምትክ ስም እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 78:33

አጠቃላይ መረጃ፡-
ጸሐፊው እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰራውን ስራ መናገሩን ቀጥሏል።

ቀኖቻቸውን አሳጠረው
እዚህ ላይ “ቀኖች” የሚለው ቃል የህይወት ዘመናቸውን ያመለክታል። “ቀኖቻቸውን አሳጠረ” የሚለው ፈሊጥ ረጅም ዘመን ከመኖራቸው በፊት እንዲሞቱ አደረጋቸው የሚል ትርጉም አለው። አማራጭ ትርጉም፡- “ገና ወጣቶች ሳሉ ገደላቸው” (ለስላሴ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አመቶቻቸው በድንጋጤ የተሞሉ ነበሩ
አሳፍ ስለ “አመቶች” ሲናገር ማጠራቀሚያ እንደሆኑ አድርጎ ገልጧቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከአመት ወደ አመት ሁልጊዜ በፍርሀት ይኖሩ ነበር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱን ለመፈለግ
ይጠብቃቸው ዘንድ ሊያደርግላቸው የሚፈልጉትን ነገር ለመጠየቅ (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 78:35

አጠቃላይ መረጃ፦
እስራኤላውያን ስለ ሰሯቸው ስራዎች የሚናገሩ ንግርቶች።

አስብ
“አስታውስ።” ይህ በ መዝሙረ ዳዊት 20:3 ላይ እንዴት እደተተረጎመ ተመልከት።

እግዚአብሔር አለታቸው ነበር
ጸሀፊው ስለ እግዚአብሔር ሲናገር እርሱ ሰዎች ከጠላቶቻቸው እንዲድኑ ሄደው የሚጠጉበት ኮረብታ ወይም ተራራ እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፦ “እነርሱ የሚጠብቃቸው እግዚአብሔር ነበር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አዳኛቸው
“እነርሱን የሚያድናቸው”

ሸነገሉት
“በልባቸው ሳያምኑበት እርሱ አስደናቂ አምላክ እንደሆነ ነገሩት”

በአፋቸው
“አፍ” የሚለው ቃል አፋቸውን በመጠቀም እነርሱ ለሚናገሯቸው ቃላቶች ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የተናገሩትን በመናገር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ልባቸው በእርሱ የፀና አልነበረም
እዚህ ላይ ”ልባቸው” ለሀሳባቸው ምትክ ስም ነው። ለእርሱ ታማኝ መሆን ከእርሱ ጋር በአፅንኦት መጠበቅ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሀሳባቸው በእርሱ ላይ ያተኮረ አልነበረም” ወይም “ለእርሱ ታማኞች አልነበሩም” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 78:38

በደላቸውን ይቅር አላቸው
“ምንም እንኳ ክፉ ስራ ቢሰሩም ይቅር አላቸው”

ቁጣውን ገታ
አሳፍ ስለ እግዚአብሔር ቁጣ ሲናገር ቁጣው የተቆጣ ሰው እንደሆነና እግዚአብሔር እርሱን ያስቆጡትን ሰዎች እንዳያጠቃቸው እርሱን እንዲከለክለው ሀላፊነት የሰጠው ሰው እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ምንም እንኳ በእነርሱ ላይ የተቆጣ ቢሆንም አልቀጣቸውም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መአቱንም ሁሉ አላወረደም
አሳፍ ስለ እግዚአብሔር መአት ሲናገር መአቱ እግዚአብሔር እንዲተኛ የፈቀደለትና ከዚያ በኋላ ሳይነቃ የቀረ እንቅልፍ የወሰደው ሰው እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሙሉ በሙሉ በእነርሱ ላይ ቁጡ እንዳይሆን ራሱን ከለከለ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 78:39

አስብ
“አስታውስ።” “አስብ” የሚለውን በ መዝሙረ ዳዊት 20:3 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ስጋ ለባሾች ናቸው
“ስጋ” የሚለው ቃል፣ ደካማና ሟች የሆነው፣ ለሰው ልጅ ደካማነትና ሟችነት ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እስራኤላውያን ደካሞችና አንድ ቀን የሚሞቱ ናቸው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ምድረ በዳ
“አንድም ነገር የማይበቅልበት ስፍራ”

እግዚአብሔርን ተፈታተኑት
እግዚአብሔር አደርገዋለሁ ብሎ የተናገረውን ነገር ማድረግ እንደሚችል እርሱን ከማመናቸው በፊት እንዲያረጋግጥላቸው ፈለጉ። ይህን በ መዝሙረ ዳዊት 78:18 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

Psalms 78:42

አጠቃላይ መረጃ፦
ጸሐፊው እግዚአብሔር እስራኤላውያንን እንዴት እንዳዳናቸው ይናገራል።

ጣኔዎስ
በግብፅ የሚገኝ ከተማ (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 78:44

አጠቃላይ መረጃ፦
ጸሐፊው እግዚአብሔር የሰራውን ስራ ይገልጻል።

የዝንብ ሰራዊት
እንደ ደመና የሚመስል እጅግ ብዙ ዝንቦች።

እነርሱን ነደፏቸው
ዝንቦቹ ግብፃውያንን ቢበሏቸው ኖሮ ሊሰማቸው ይችል እንደነበር እንደዚሁ ግብፃውያንን እንዲያዝኑ አድርገዋቸዋል። (ተለዋጭ ዘይቤ እና ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አዝመራቸውን ለኩብኩባ፣ ሰብላቸውን ለአንበጣ ሰጠባቸው
“ኩብኩባ አዝመራቸውን በሙሉ እንዲበሉ አንበጣ ደግሞ ለማምረት ሲሉ እጅግ በጣም ደክመው የሰሩትን ማንኛውንም ነገር እንዲበሉ ፈቀደላቸው”

ምድራቸውን ወረሩት
“በምድራቸው በየትኛውም አቅጣጫ ሄዱ”

ኩብኩባ
ለመዝለል የሚረዱ ረጃጅም እግሮች ያሉት ዕፅዋት የሚበላ ነፍሳት

አዝመራቸውን ለኩብኩባ ሰጠ
አሳፍ ስለ አዝመራው ሲናገር እግዚአብሔር ለኩብኩባው የሰጠው ስጦታ እንደሆነ አደርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፦ “አዝመራቸውን እንዲበላባቸው እርሱ ለኩብኩባው ፈቀደለት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የደከሙበትን ሁሉ ለአንበጣ ሰጠ
“እርሱ የደከሙበትን ማንኛውም ነገር ለአንበጣ ሰጠ።” አሳፍ ሰዎቹ የደከሙበትን ነገር እግዚአብሔር ለአንበጣዎች የሰጠው ስጦታ እንደሆነ አድርጎ ተናግሯል።” “የደከሙበት ነገር” የሚለው ሀረግ በድካማቸው ለማምረት በተዘጋጀው እህል ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እጅግ በጣም ደክመው ለምርት የበቃውን እህል አንበጣዎች እንዲበሉት ፈቀደላቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 78:47

አጠቃላይ መረጃ፦
ጸሐፊው እግዚአብሔር ለግብጻውያን የሰራውን ስራ መግልጽ ቀጥሏል።

ወይን
ፍሬ የሚሰጥ ዛፍ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የመብረቅ እሳት
ትልቅ ነጎድጓድ የሚያስከትል መብረቅ

እርሱ በረዶ አዘነበባቸው
“እርሱ በረዶ አወረደ” ወይም “በረዶ እንዲወርድ አደረገ”

ፅኑ ቁጣውን በእነርሱ ላይ ሰደደ
አሳፍ ስለ እግዚአብሔር መቅሰፍት ሲናገር መቅሰፍቱ ሌላ ሰውን እንደሚያጠቃ ሰው እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፦ “እርሱ በእነርሱ ላይ ተቆጣ፣ ከዚህ የተነሳ በድንገት በመአቱ አጠቃቸው” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ፅኑ ቁጣ
“የእርሱ ፅኑ ቁጣ”

በእነርሱ ላይ ሰደደ
“በእነርሱ ላይ አንድም ነገር ይሆናል ብለው ሳያስቡት አጠቃቸው”

መከራ እንደሚያመጡ ወኪሎች ቁጣ፣ መአትና መቅሰፍት ላከባቸው
አሳፍ ስለ ቁጣ፣ መአትና መቅሰፍት ሲናገር እግዚአብሔር ስራውን ለእርሱ ለመስራት ሊልካቸው እንደሚችላቸው ሰዎች አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፦ “እርሱ በጣም ከመቆጣቱ የተነሳ ግብፃውያንን መጉዳት ፈለገ፣ ከዚህ የተነሳ በእነርሱ ላይ መከራ ላከባቸው፣ መቅሰፍት ደግሞ አመጣባቸው” (ሰውኛ ዘይቤ እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መአት
አንድ ሰው ሌሎችን ለመጉዳት የሚያነሳሳ ቁጣ

Psalms 78:50

አጠቃላይ መረጃ፦
ጸሐፊው እግዚአብሔር ለግብጻውያን የሰራውን ስራ መግለጽ ቀጥሏል።

ለቁጣው መንገድ ጠረገ
ዘማሪው ስለ ቁጣ ሲናገር እግዚአብሔር ህዝቡን እንዲቀጣ ለማመቻቸት ቀድሞ የሚወጣ ሰው እንደሆነና ሰዎች እንዲራመዱበት መንገዱን ደልዳላ የሚያደርግ እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፦ “እርሱ በጣም ስለተቆጣ እነርሱን ለመጉዳት ማድረግ የሚችለውን ማንኛውንም ነገር አደረገ” ወይም “ቁጣው ታላቅ ጦር ሰራዊት እነደሆነ ያህል ለጦርነት ለመዝመት ደልዳላ መንገድ ሰራ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ሰውኛ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱን ከሞት አላዳነም
“እርሱ ግብፃውያንን ከሞት አልጠበቃቸውም” ወይም “ግብፃውያን በህይወት እንዲኖሩ አልፈቀደላቸውም”

ህይወታቸውን ለመቅሰፍት አሳልፎ ሰጠ
አሳፍ ስለ መቅሰፍት ሲናገር ግብፃውያንን ለመጉዳት የሚሄድ ሰው እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሁሉም በመቅሰፍት በጣም እንዲታመሙ አደረጋቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ሰውኛ የሚለውን ይመልከቱ)

የአፍላ ጉልበታቸው በኩር
ይህ ሀረግ የእያንዳንዱን ቤተሰብ ወንድ ልጅ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “የመጀመሪያ ወንዶች ልጆች” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

በካም ድንኳኖች
እዚህ ላይ “ድንኳን” የሚለው ቃል ለቤተሰብ ምትክ ስም ነው። “ካም” የሚለው ቃል ደግሞ በቅድመ አያታቸው ስም ግብፃውያንን የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በግብጽ ቤተሰቦች መካከል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 78:52

አጠቃላይ መረጃ፦
ጸሐፊው እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰራውን ስራ መግለጽ ቀጥሏል።

እንደ በግ... እንደ መንጋ
ጸሐፊው እስራኤላውያን እንደ በግ እንደሆኑ አድርጎ ተናግሯል። ይህ የሚያሳየው እግዚአብሔር እረኛ ለበጎቹ እንደሚያደርገው ህዝቡን እንደሚንከባከብና እንደሚጠብቅ ነው። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዋጣቸው
ሙሉ በሙሉ ሸፈናቸው

Psalms 78:54

አጠቃላይ መረጃ፦
ጸሐፊው እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰራውን ስራ መግለጽ ቀጥሏል።

ቀኝ እጁ አባረረ
“ቀኝ እጅ” የሚሉት ቃላቶች ለሀይል ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እርሱ በራሱ ሀይል ለራሱ አሸነፈ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ርስታቸውን አከፋፈለላቸው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፦ 1) እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን በአንድ ወቅት ሌሎች ህዝቦች ይኖሩበት በነበረው ምድር ርስታቸውን አከፋፈለላቸው ወይም 2) እግዚአብሔር በአንድ ወቅት ከርስታቸው ወደ ሌላ አውጥቶ ለሰደዳቸው አህዛብ ርስታቸውን አካፈለላቸው። “ሁልጊዜ ለእነርሱ የሚሆን ምድር ሰጣቸው”

በድንኳናቸው ውስጥ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፦ 1) እርሱ እስራኤላውያንን በምድሪቱ በራሳቸው ድንኳኖች አኖራቸው ወይም 2) እርሱ እስራኤላውያንን ሌሎች ህዝቦችን አባርሮ ባወጣበት ድንኳኖች አኖራቸው። እነዚህ “ድንኳኖች” አብዛኛዎቹ እውነተኛ ቤቶች ነበሩ፣ እነዚህ ቤቶች ደግሞ ሌሎች ህዝቦች በውስጣቸው የኖሩባቸውና እስራኤላውያኑ ራሳቸው የኖሩባቸው ናቸው። አማራጭ ትርጉም፦ “በራሳቸው ቤት” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 78:56

አጠቃላይ መረጃ፦
ጸሐፊው እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰራውን ስራ መግለጽ ቀጥሏል።

ተፈታተኑት፣ አመፁ
እነዚህ ቃላቶች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ጸሐፊው እነዚህን የተጠቀመው እግዚአብሔር ለእነርሱ የሚያስፈልጋቸውን እንደሚያዘጋጅላቸው ወይም እንደተናገረው ክፉውን እንደሚቀጣ እስራኤላውያን ፈፅመው እንደማያምኑ አፅንኦት ለመስጠት ነው። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ተፈታተኑት
እግዚአብሔር አደርገዋለሁ ብሎ የተናገረውን ነገር ማድረግ እንደሚችል እርሱን ከማመናቸው በፊት እንዲያረጋግጥላቸው ፈለጉ። ይህን በ መዝሙረ ዳዊት 78:18 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

አመጹ
ለመታዘዝ እንቢ አሉ

ከዳተኞች ነበሩ፣ ክፋትንም አደረጉ
እነዚህ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ጸሐፊው ሁለቱንም ሀረጎች የተጠቀመባቸው እስራኤላውያን እናደርጋለን ብለው የተናገሩትን ነገር

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለእግዚአብሔር እንዳላደረጉ አፅንኦት ለመስጠት ነው። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 78:58

አጠቃላይ መረጃ፦
ጸሐፊው እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰራውን ስራ መግለጽ ቀጥሏል።

በኮረብታ ማምለኪያዎቻቸው አስቆጡት፤ ተቀርፀው በተሰሩ ጦኦቶቻቸው አስቀኑት
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ትይዩነት ያላቸው ሲሆን ሁለቱም ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 78:60

አጠቃላይ መረጃ፦
ጸሐፊው እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰራውን ስራ መግለጽ ቀጥሏል።

የሀይሉን ምልክት አስማረካት፤ ክብሩንም ለጠላቶቹ እጅ አሳልፎ ሰጠ
አሳፍ ስለ እግዚአብሔር ሀይልና ክብር ሲናገር እነዚህ ሁለቱ ሰዎች ሊይዟቸውና ሊሸከሟቸው የሚችሉ ቁሳዊ እቃዎች እንደሆኑ አድርጎ ገልጧቸዋል። “ሀይል” እና “ክብር” የሚሉት ቃላቶች ምናልባት ለቃል ኪዳኑ ታቦት ምትክ ስሞች ሊሆኑ ይችላሉ። “እጅ” የሚለው ቃል ለጠላት ሀይል ምትክ ስም ነው። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ጠላቶቹ የከበረውን የቃል ኪዳኑን ታቦት እንዲማርኩት ፈቀደ፤ ታቦቱን የፈለጉትን ማንኛውንም ነገር ሊያደርጉበት እንዲችሉ ለእነርሱ አሳልፎ ሰጣቸው” (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 78:62

አጠቃላይ መረጃ፦
ጸሐፊው እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰራውን ስራ መግለጽ ቀጥሏል።

ህዝቡን ለሰይፍ አሳልፎ ሰጠ
አሳፍ ስለ እግዚአብሔር ህዝብ ሲናገር እግዚአብሔር እንደ ስጦታ ለሌሎች የሚሰጣቸው ትንሽ እቃ እንደሆኑ፣ በጦርነት ለሚከሰት ሞት ምትክ ስም የሆነውን ሰይፍ ደግሞ ስጦታውን ሊቀበል የሚችል ሰው እንደሆነ አደርጎ ገልጧቸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ “እርሱ ሌሎች ሰዎች ህዝቡን በጦርነት ውስጥ እንዲገድሏቸው ፈቀደ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ሰውኛ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በርስቱ ላይ እጅግ ተቆጣ
“ለዘላለም የራሱ ይሆናል ብሎ የተናገረላቸው ህዝቡ ላይ ተቆጣ”

ጎልማሶቻቸውን እሳት በላቸው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፦ 1) “ጎልማሶቻቸውን በሙሉ ለመግደል ጠላት እሳት ተጠቀመ” ወይም 2) “ጎልማሶቻቸው በጦርነት ውስጥ እሳት ደረቅ ሳርን እንደሚያቃጥል እንደዚሁ በፍጥነት ሞቱ።” እነዚህ ሰዎች የጦር መሳሪያ እንደተጠቀሙ የሚያሳይ መልእክት አታስተላልፍ። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በላቸው
“መብላት” ማንኛውንም ነገር በጣም በፍጥነት መብላት ነው።

ሰርግ
ሰዎች ሲያገቡ የሚፈፀም ስርአት

Psalms 78:64

ካህናቶቻቸው በሰይፍ ወደቁ
እዚህ ላይ “ሰይፍ” የሚለው ቃል በሰይፍ የሚዋጉ ወታደሮችን የሚወክል ነው። “በሰይፍ ወደቁ” የሚለው ሀረግ ፈሊጥ ሲሆን በጦርነት መካከል መሞት ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ካህናቶቻቸው በጦርነት መካከል ሞቱ” ወይም “ጠላት ካህናቶቻቸውን በሰይፍ ገደላቸው” (ምትክ ስም እና ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

መበለቶቻቸው ማልቀስ ተሳናቸው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፦ 1) አንድ ሰው መበለቶች እንዳያለቅሱ አስገደዳቸው ወይም 2) ብዙ ካህናቶች ከመሞታቸው የተነሳ አግባብነት ያለው የቀብር ስርአት ለመፈፀም ጊዜ አልነበረም።

መበለቶች
ባሎቻቸው የሞቱባቸው ሴቶች

ጌታም ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሳ
ጌታ ለተወሰነ ጊዜ ስራ ስለ አለመስራቱ ሲናገር እርሱ ተኝቶ እንደነበረ ተደርጎ ሲገለፅ፣ ስራ መጀመሩ ደግሞ ከእንቅልፍ መነሳቱ ተደርጎ ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ከእንቅልፍ እንደነቃ ያህል ስራ መስራት ጀመረ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የወይን ጠጅ ስካር እንደ በረደለት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፦ 1) ብዙ የወይን ጠጅ እንደጠጣና እንደሰከረ ከስካሩም በመንቃቱ ምክንያት ለመዋጋት እንደፈለገ በቁጣም እንደተሞላ ተዋጊ ወይም 2) ብዙ የወይን ጠጅ እንደጠጣ ነገር ግን አሁን ማሰብ እንደቻለና ከመተኛቱ የተነሳ በሚገባ እንደተዋጋ ተዋጊ።

Psalms 78:67

አጠቃላይ መረጃ፦
ጸሐፊው እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰራውን ስራ መግለጽ ቀጥሏል።

የዮሴፍ ድንኳን
እዚህ ላይ “ድንኳን” የሚለው ቃል ለቤተሰብ ምትክ ስም ነው። በዚህ ሀረግ ድንኳን የዮሴፍን ልጆች ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “የዮሴፍ ልጆች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የሴፍ... ኤፍሬም
ኤፍሬም የዮሴፍ ልጅ ነበር።

ይሁዳ... የፅዮን ተራራ
የጽዮን ተራራ የሚገኘው የይሁዳ ነገድ ይኖርበት በነበረው ምድር ነው።

መቅደሱን እንደ ሰማያት ሰራት
የዚህ ንፅፅር ዘይቤ ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፦ 1) እግዚአብሔር መቅደሱን እንደ ሰማያት ከፍ አድርጎ ሰራት። አማራጭ ትርጉም፦ “መቅደሱን አንደ ሰማያት ከፍ አድርጎ ሰራት” ወይም 2) እግዚአብሔር መቅደሱን እንደ ሰማያት የማይናወጥ አድርጎ ሰራት። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰማያት ለዘላለም ፀንተው እንደሚኖሩ እንደዚሁ መቅደሱን ለዘላለም ፀንታ እንድቅቆም አድርጎ ሰራት” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ምድር
ይህ ግስ የተሰጠው ከቀደመው መስመር ሊሆን ይችላል። ጸሐፊው የእግዚአብሔርን መቅደስ ቋሚነት ከምድር ቋሚነት ጋር አነፃፅሮታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ምድር በቋሚነት እንደሚኖር እንዲሁ እርሱ መቅደሱን በቋሚነት እንዲኖር አድጎ ሰራት።” (አስጨምሬ እና ተንጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 78:70

አጠቃላይ መረጃ፦
ጸሐፊው እግዚአብሔር የሰራውን ስራ መግለጽ ቀጥሏል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የበጎች ጉረኖ
“በጎች በደህንነት እንዲጠበቁ የሚያደርግ በዙርያው ግድግዳ ያለው ስፍራ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ርስቱን
“ለዘላለም የራሱ ይሆኑ ዘንድ የመረጣቸው ህዝብ” ይህን በ መዝሙረ ዳዊት 78:62 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።

ለህዝቡ ለያዕቆብ፣ ለርስቱም ለእስራኤል እረኛ ይሆን ዘንድ
“እረኛ” የሚለው ቃል ሌሎች ሰዎችን ለሚመራና ለሚጠብቅ ሰው ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ህዝቡን የያዕቆብን ልጆች፣ ርስቱንም እስራኤልን ይመራና ይጠብቅ ዘንድ ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱን ዳዊት ጠበቃቸው
“ጠበቃቸው” የሚለው ቃል ለመምራትና ለመጠበቅ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ዳዊት እነርሱን መራቸው፣ እነርሱን ጠበቃቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 79

1 አምላክ ሆይ፣ ባዕድ ሕዝቦች ርስትህን ወረሩ! የተቀደሰ መቅደስህን አረከሱ ኢየሩሳሌምን የፍርስራሽ ክምር አደረጓት። **2** የባሪያዎችህን ሬሳ ለሰማይ ወፎች፣ የታማኞችህን ሥጋ ለምድር አራዊት ምግብ እንዲሆን ሰጡ። **3** ደማቸውን በኢየሩሳሌም ዙሪያ እንደ ውሃ አፈሰሱ የሚቀብራቸውም አልተገኘም። **4** እኛም ለጎረቤቶቻችን መዘባበቻ በዙሪያችን ላሉትም መሣቂያ መሣለቂያ ሆንን። **5** ያህዌ ሆይ፣ ይህ እስከ መቼ ነው? የምትቆጣው ለዘላለም ነውን? ቅናትህ እንደ እሳት ሲነድ ይኖራልን? **6** አንተን በማያውቁ ሕዝቦች ላይ፣ ስምህን በማይጠሩ መንግሥታት ላይ መዓትህን አፍስስ፤ **7** ያዕቆብን ውጠውታልና መኖሪያ ቦታውንም ባድማ አድርገዋል። **8** የአባቶቻችንን ኃጢአት እኛ ላይ አትቁጠርብን እጅግ ተዋርደናልና ምሕረትህ ፈጥና ወደ እኛ ትምጣ። **9** መድኃኒታችን እግዚአብሔር ሆይ፣ ስለ ስምህ ክብር ርዳን፤ ይቅርም በለን። **10** ሕዝቦች፣ «አምካቸው የት አለ?» ለምን ይበሉ? ስለ ፈሰሰው የባሪያዎችህ ደም፣ ዐይናችን እያየ ሕዝቦችን ተበቀል። **11** የእስረኞች ሰቆቃ ወደ አንተ ይድረስ በኃይልህ ብርታት ሞት የተፈረደባቸውን አድን። **12** ጌታ ሆይ፣ ጐረቤቶቻችን አንተ ላይ ስለ ሰነዘሩት ስድብ ሰባት ዕጥፍ ተበቀላቸው። **13** እኛ ሕዝብህ፣ የመሰማሪያ በጐችህ ለዘላለም ምስጋና እናቀርብልሃለን። ለትውልድ ሁሉ ምስጋናህን እንናገራለን።

Psalms 79:1

አጠቃላይ መረጃ፡-
ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

የአሳፍ መዝሙር
“ይህ አሳፍ የፃፈው መዝሙር ነው።” ይህ በ መዝሙረ ዳዊት 50:1 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።

ርስትህ
“ለአንተ ለዘላለም የሚሆን ምድር” ይህ በ መዝሙረ ዳዊት 68:9 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።

ደማቸውን እንደ ውሀ አፈሰሱ
“ደም” የሚለው ቃል ለንፁሀን ሰዎች ህይወት ተለዋጭ ዘይቤ ነው። ደም ማፍሰስ ንፁሀን ሰዎችን መግደል ነው። አብዛኛው ሰዎች ዉሀ በየቀኑ ያያሉ፣ ስለዚህ ደም እንደ ውሀ የተለመደ ነገር እንዲሆን ብዙ ንፁሀን ሰዎች መሞት ነበረባቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “እጅግ በጣም ብዙ ንፁሀን ሰዎች ከመግደላቸው የተነሳ ደማቸው ዝናብ ከዘነበ በኋላ እንደሚፈስስ ውሀ ደማቸው በየቦታው ፈሰሰ” (ምትክ ስም እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 79:4

እኛም ለጎረቤቶቻችን መዘባበቻ፤ በዙሪያችንም ላሉት መሳቂያና መሳለቂያ ሆንን
“መዘባበቻ እና መሳቂያ የሚሉት ቃላቶች ሌሎች ለሚዘባበቱባቸው፣ ለሚስቁባቸውና ለሚሳለቁባቸው ምትክ ስሞች ናቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “እኛ ጎረቤቶቻቸው የሚስቁባቸውን የሚሳለቁቸው ሰዎች ሆነናል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ሆነናል
“እኛ” የሚለው ተውላጠ ስም የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ህዝብ ነው።

መሳለቂያ
አንድን ሰው ለማዋረድ የሚደረግ ብርቱ ሳቅ ነው።

የቅናትህ ቁጣ እንደ እሳት የሚነደው እስከ መቼ ነው?
ይህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የቅናት ቁጣህ እንደ እሳት መንደዱን ፈፅሞ የሚቆም አይመስልም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የቅናትህ ቁጣ ይነድዳልን
“ቁጣ” የሚለው ረቂቅ ስም ቁጡ ተብሎ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ቀናተኛና ቁጡ ትሆናለህን” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ እሳት ይነድዳል
ይህ ተነፃፃሪ ዘይቤ የእግዚአብሔር ቁጣ መገለጠ ነገሮች ከሚያጠፋ እሳት ጋር ያነፃፅረዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “አጠፋን” (ተነጻጻሪ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 79:6

አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ሁለት ጥንድ ሀረጎች እያንዳንዳቸው ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን በአንድ ላይ የተጣመሩት አፅንኦት ለመስጠት ነው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

በህዝቦች ላይ መአትህን አፍስስ
አሳፍ ስለ እግዚአብሔር መአት ሲናገር ፈሳሽ እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ ስለተቆጣህ ህዝቦችን ቅጣቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ስምህን በማይጠሩ
“ስም” የሚለው ቃል ለሰውየው ሀይልና ስልጣን ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የአንተ ያልሆኑት ወይም እንድትረዳቸው ለማይጠይቁህ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ያዕቆብን በልተውታልና
“ያዕቆብ” የሚለው ቃል ልጆቹ ለሆኑት ለእስራኤል ህዝብ ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የእስራኤልን ህዝብ ሙሉ በሙሉ አጠፏቸው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 79:8

የአባቶቻችንን ሀጢአት በእኛ ላይ አትቁጠርብን
“የአባቶቻችንን ሀጢአት ማሰብህን አቁም፣ ስለ እነርሱም እኛን አትቅጣን” ወይም “ስለ አባቶቻችን ሀጢአት እኛን ይቅር በለን”

እኛ በጣም ተቸግረናል
ጸሐፊው ስለ ህዝቡ ደካማነትና ሀዘንተኛ መሆን ሲናገር በዝቅተኛ ስፍራ እንዳሉ አድርጎ ገልጧቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኛ በጣም ደካሞች ነን” ወይም “እኛ በጣም አዝነናል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የደህንነታችን አምላክ
“ደህንነት” የሚለው ቃል “አዳነ” በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል፡- “ያዳነን አምላክ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ ስምህ ክብር ብለህ
“ስም” የሚለው ቃል ለመልካም ስሙ፣ ስለእርሱ ሰዎች ለሚያውቁት ነገር ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች ስለ አንተ ክብር ያውቁ ዘንድ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ስለ ስምህ ብለህ
እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ስም ሁለንተናዊ ማንነቱንና የሚገባውን ክብር የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች አንተን ያከብሩ ዘንድ” ወይም “ስለ ራስህ ስም ብለህ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 79:10

ህዝቦች “አምላካቸው የት አለ?” ለምን ይበሉ?
ይህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ህዝቦች “አምላካቸው የት አለ?” ብለው መናገር መቻል የለባቸውም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

አምላካቸው የት አለ?
ይህ ማንጓጠጥ እንደ አረፍተ ሀሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አምላካቸው ምንም ሊያደርግ አይችልም!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የፈሰሰውን የአገልጋዮችህን ደም በቀል፣ አይናችን እያየ ህዝቦች ይወቁት
ደም ማፍሰስ ንፁሀን ሰዎችን ለመግደል ምትክ ስም ነው። ይህ በገቢር ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ህዝቦች የገደሏቸውን የንፁሀን አገልጋዮችህን በቀል አንተ ስታደርገው በአይናችን ፊት መመልከት መንገድ ተበቀልላቸው” (ምትክ ስም እና መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በአይናችን ፊት
“በአይናችን” ወይም “በአካል በተገኘንበት”

የእስረኞች ሰቆቃ በፊትህ ይድረስ
አሳፍ በመከራና በሀዘን ውስጥ የነበሩት እስረኞች ስላሰሙት ሰቆቃ ሲናገር በንጉስ ፊት እንደሚቀርብ ሰው አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእስረኞችን ሰቆቃ በጥንቃቄ አድምጥና እርዳቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ አና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የሞት ልጆች
ይህ ሞት የተፈረደባቸውን ሰዎች የሚያመለክት ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እንዲሞቱ የተፈረደባቸው ሰዎች” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 79:12

ጌታ ሆይ፤... የተዘባበቱበት መዘባበት... አንተ መልስላቸው
አሳፍ የጎረቤት አገሮች በእስራኤል ላይ የሰሩት ክፉ ስራ እንደ “መዘባበት” እንደሆነና እነዚህ ስድቦች እንደ ቁሳቁሶች እንደሆኑ አድርጎ ተናግሯል። እነዚህን ድርጊቶች እንዲቆጥርባቸው ጌታን ይጠይቃል፣ የጎረቤት አገሮች ስላደረጉት ሰለ እያንዳንዱ ድርጊት በእነዚህ የጎረቤት አገሮች ላይ ሌላ አካል አስነስቶ ሰባት እጥፍ ክፉ ስራ በእነርሱ ላይ እዲያደርግባቸው ጌታን ይጠይቃል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ክፈላቸው
“መልስላቸው” ወይም “መልሰህ ስጣቸው”

በጭናቸው ላይ
በተቀመጡበት በጉልበታቸውና በታፋቸው። ይህ “በቀጥታና በግለሰብ ደረጃ” ለመፈፀሙ ተለዋጭ ቀይቤ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ ህዝብህ፣ የማሰማሪያ በጎችህ፣ ለዘላለም ምስጋና እናቀርብልሀለን
“በጎች” የሚለው ቃል እረኛ ለሚጠብቃቸውና ለሚመራቸው ረዳት አልባ ሰዎች ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ የምትጠብቀንና የምትመራን እኛ ህዝብህ ለዘላለም እናመሰግንሀለን” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ምስጋናህን ለትውልድ ሁሉ እንናገራለን
“የሚመጣው ትውልድ በሙሉ የሰራኸውን መልካም ነገሮች በሙሉ እንዲያውቁ በእርግጠኝነት እናደርጋለን”

ምስጋናህን
ይህ ሰዎች ጌታን የሚያመሰግኑባቸው እርሱ የሰራቸው ነገሮችን የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ ስለ ሰራሀቸው ነገሮች አንተን ማመስገን እንዲቀጥሉ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 80

1 ዮሴፍን እንደ በግ መንጋ የምትመራ፣ የእስራኤል እረኛ ሆይ፣ ስማን። በኪሩቤል ላይ ባለው ዙፋን የምትቀመጥ ሆይ፣ ብርሃንህ ይብራልን! **2** በኤፍሬም፣ በብንያምና በምናሴ ፊት ኃይልህን ግለጥ፤ መጥተህም አድነን። **3** አምላክ ሆይ፣ መልሰን ፊትህን አብራልን እኛም እንድናለን። **4** የሰራዊት ጌታ ያህዌ ሆይ፣ በሕዝብህ ጸሎት ላይ የምትቆጣው እስከ መቼ ነው? **5** የእንባ እንጀራ አበላሃቸው ስፍር የሞላ እንባም አጠጣሃቸው። **6** የጐረቤቶቻችን መከራከሪያ አደረግኸን ጠላቶቻችንም ተሣሣቁብን። **7** የሰራዊት አምላክ ሆይ፣ ፊትህን አብራልን እኛም እንድናለን። **8** የወይን ግንድ ከግብፅ አመጣህ አሕዛብን አባርረህ እርሷን ተከልህ። **9** መሬቱን መነጠርህላት፣ እርሷም ሥር ሰድዳ መሬቱን ሞላች። **10** ተራሮችም በጥላዋ ተሸፈኑ የቅርንጫፎቿም ጥላ የሊባኖስን ዛፎች ሸፈነ። **11** ቅርንጫፎቿን እስከ ባሕሩ ቁጥቋጦዋንም እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ዘረጋች። **12** ታዲያ፣ አላፊ፣ አግዳሚው ፍሬዋን እንዲቀጥፍ በዙሪያዋ የነበሩ አጥሮችን ለምን አፈረስህ። **13** የዱር አሳማ ያበላሻታል በሜዳ የሚንጋጋም አራዊት ይበላታል። **14** የሰራዊት አምላክ ሆይ፣ ወደ እኛ ተመለስ፣ ከሰማይ ተመልከት እይም ይህችን የወይን ተክልም ተንከባከባት። **15** ይህች ቀኝ እጅህ የተከላት ተክል አንተም ያጸደቅሃት ተክል ናት። **16** ነገር ግን ቆራርጠው በእሳት አቃጠሏት ከቁጣህ የተነሣ ይጠፋሉ። **17** እጅህ የቀኝ እጅህ የሆነው ሰው ላይ፣ አንተ ራስህ ብርቱ ያደረግኸው የሰው ልጅ ላይ ትሁን **18** እኛም ከአንተ ወደ ኋላ አንልም፤ በሕይወት ጠብቀን፤ እኛም ስምህን እንጠራለን። **19** ሰራዊት አምላክ ያህዌ ሆይ፣ መልሰን ፊትህን አብራልን እኛም እንድናለን።

Psalms 80:1

አጠቃላይ መረጃ:
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነ ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

የመዘምራን አለቃ
"ይህ የመዘምራን አለቃ ሆኖ አምልኮ የሚመራውን ያመለክታል። ይህ በመዝሙር 4፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

"የኪዳን ጽጌሬዳ" በሚለው ቅኝት የሚዜም
ይህ የዝማሬን ዐይነት ሊያመለክት ይችላል። ይህ በመዝሙር 45፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

የአሳፍ መዝሙር
"ይህ አሳፍ የጻፈው መዝሙር ነው።"ይህ በመዝሙር 50፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

የእስራኤል እረኛ
አሳፍ እግዚአብሔር እርሱ እስራኤልን እንደሚመራና እንደሚጠብቅ አድርጎ ይጠቅሳል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ዮሴፍን እንደ መንጋ የምትመራ
"ዮሴፍ" የሚለው ቃል የእስራኤልን ያመለክታል። አሳፍ ስለ ህዝቡ እነርሱ በጎቹ እንደሆኑ እና እረኛቸው የሆነው ያህዌ ደግሞ እንደሚጠብቃቸው አድርጎ ይናገራል። "እንደ በግ መንጋ የዮሴፍን ትውልድ የምትመራ ሆይ" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ዮሴፍ
እዚህ ስፍራ ዮሴፍ እስራኤልን ይወክላል። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በኪሩብ ላይ የምትቀመጥ ሆይ
ኪሩቤል በቃል ኪዳኑ ታቦት ላይ የሚገኙ መሆናቸውን ግልጽ ማድረግ ሊያስፈልግ ይችላል። የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፍት ብዙውን ጊዜ የቃል ኪዳኑ ታቦት፣ በላይ በሰማይ በዙፋኑ የተቀመጠው የያህዌ የእግሩ መቆሚያ እንደሆነ አድርገው ይናገራሉ። "በቃል ኪዳኑ ታቦት ከኩሩቤል በላይ በዙፋንህ የተቀመጥህ ሆይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

በላያችን አብራ
አሳፍ ስለ እግዚአብሔር እርሱ ብርሃንን የሚሰጣቸው ፀሐይ እንደሆነ እና ለመልካምነት ዘይቤ አድርጎ ይናገራል። "ብርሃን ስጠን" ወይም "የምንኖርበትን ትክክለኛ ህይወት አሳየን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ኃይልህን አንቀሳቅስ
"አንቀሳቅስ" የሚለው ሀረግ "ወደ ድርጊት አምጣው" የሚል ትርጉም አለው።

ፊትህን በእኛ ላይ አብራ
ጸሐፊው ያህዌ ለእነርሱ የሚያሳየውን ሞገስ ያህዌ በላያቸው ብርሃን እንዳበራ አድርጎ ይገልጸዋል። "ለእኛ ሞገስ ስጠን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኛም እንድናለን
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። " እባክህ አድነን" ወይም "ስለሆነም ልታድነን ትችላለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 80:4

የአንተ ህዝብ
እስራኤል

የእንባ እንጀራ መገብካቸው፣ ብዙ እንባ ይጠጡ ዘንድ ሰጠሃቸው
"የእንባ እንጀራ" እና "ይጠጡ ዘንድ እንባ" የሚሉት ቃላት ለማያቋርጥ ሀዘን ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። "ሁሉም በመከራ ውስጥ እንዲኖሩ አደረግህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

Psalms 80:7

አጠቃላይ መረጃ:
አሳፍ በእስራኤል ህዝብ ምትክ ተናገረ። በቁጥር 8 እግዚአብሔር፣ ሰው ምድርን መንጥሮ የወይን ተክልን እንደሚተክልባት ሁሉ እስራኤልን በምድራቸው የመሰረተበትን መንገድ መናገር ይጀምራል። የወይን ተክሉ ምሳሌ እስከ ቁጥር 16 ድረስ ይቀጥላል።

በላያችን አብራ
ጸሐፊው እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ሞገሱን እንዳደረገ የሚገልጸው ያህዌ በላያች እንዳበራ አድርጎ ነው። ይህ በመዝሙር 80፡3 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "በእኛ ላይ ሞገስህን አደረግህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኛም እንድናለን
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንተ ታድነናለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አንተ የግብጽን ወይን ታመጣለህ
አሳፍ የእስራኤልን ህዝብ ወደ ሌላ ስፍራ ተወስዶ ሊተከል ከተዘጋጀ ወይን ጋር ያነጻጽራል። "አንተ እኛን፣ እንደ ወይን ከግብጽ አወጣኸን" (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

አንተ ህዝብን አውጥተህ በሌላ ስፍራ ተከልክ
ዘማሪው ስለ ህዝቡ ያህዌ በሌላ ስፍራ ወስዶ እንደ ተከለው ተክል አድርጎ ይናገራል። "አንተ ህዝብን፣ ከምድራቸው አውጥተህ ለእኛ ሰጠኸን እናም ወይንህን በዚያ ተከልክን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ህዝብን አወጣህ
"አንተ ህዝብ ለቆ እንዲወጣ አስገደድክ"

Psalms 80:9

አጠቃላይ መረጃ:
አሳፍ ስለ እስራኤል በምድራቸው የወይን እርሻ ውስጥ እንዳለ የወይን ተክል አድርጎ እስራኤልን መናገሩን ቀጥሏል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሩን መነጠርክለት
"ምድሩን ለወይን መነጠርክ"

ስር ሰደደ
"ወይኑ ስር ሰደደ" ወይም "የወይን ለክሉ ማደግ ጀመረ"

ምድሩን ሞላ
"ቅርንጫፉ ምድሩን ሸፈነ

ተራሮች በጥላዎቿ የእግዚአብሔር ዝግባ በቅርንጫፎቿ ተሸፍነው ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ጥላዎቿ ተራሮችን፣ ቅርንጫፎቿ የእግዚአብሔርን ዝግባ ሸፈኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔርን ዝግባዎች በቅርንጫፎቿ
"እግዚአብሔር ዝግባዎች በቅርንጫፎቿ ተሸፍነው ነበር፣" ግሱ የተወሰደው ከቀደመው ዐረፍተ- ነገር ነው።ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ቅርንጫፎቿ የእግዚአብሔርን ዝግባ ሸፈነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ዝግባ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ረጃጅሙ የዝግባ ዛፎች፣" ከእስራኤል በስተሰሜን በሊባኖስ ምድር "በተራሮች" ላይ ያደጉ የዝግባ ዛፎች፣ ወይም 2) "የእግዚአብሔር የራሱ የዝግባ ዛፎች"

ባህሩ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ረጃጅሙ የዝግባ ዛፎች፣" ከእስራኤል በስተሰሜን በሊባኖስ ምድር "በተራሮች" ላይ ያደጉ የዝግባ ዛፎች፣ ወይም 2) "የእግዚአብሔር የራሱ የዝግባ ዛፎች"

ባህሩ
ከእስራኤል ምዕራብ የሜድትራንያን ባህር

ቡቃያ
ከምድር መብቀል የጀመረ የአዲስ የተክል ክፍል

Psalms 80:12

አጠቃላይ መረጃ:
አሳፍ ስለ እስራኤል በምድራቸው የወይን እርሻ ውስጥ እንዳለ የወይን ተክል አድርጎ እስራኤልን መናገሩን ቀጥሏል።

ቅጥሯ
የድንጋይ ቅጥር፣ የእንጨት አይደለም

ከርከሮዎች
x

Psalms 80:14

አጠቃላይ መረጃ:
አሳፍ ስለ እስራኤል በምድራቸው የወይን እርሻ ውስጥ እንዳለ የወይን ተክል አድርጎ እስራኤልን መናገሩን ጨረሰ።

ወደኃላ ዙር/ተመለስ
ጸሐፊው እግዚአብሔር ይረዳው ዘንድ ዘወር እንዲልለት ይፈልጋል። ይህ ይበልጥ ግለጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "ወደ እኛ ዘወር በል" ወይም "ዳግም ወደ እኛ መጥተህ እርዳን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እይ
"ተመልከት"

ይህ ወይን
ጸሐፊው እስራኤልን ከወይን ተክል ጋር ማነጻጸሩን ቀጥሏል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ቀኝ እጅህ የተከላት ስር ይህች ናት
ቀኝ እጅ የሚወክለው የያህዌን ሀይል እና መቆጣጠር ነው። "ይህች አንተ ያህዌ የተከልካት ስር ናት" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ቡቃያ
ከምድር መብቀል የጀመረ የአዲስ የተክል ክፍል። ይህ በመዝሙር 80፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ወደቁ፤ ከግሳጼህ የተነሳ ጠፉ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ወደቁ፤ ከግሳጼህ የተነሳ ህዝብህ ጠፋ።" ወይም 2) "ወደቁ። ከግሳጼህ የተነሳ ጠላቶችህ ይጥፉ!"

Psalms 80:17

የአንተ እጅ
ይህ የያህዌን ሀይል እና መቆጣጠር ያመለክታል። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የቀኝ እጅህ ሰው
ያህዌ የራሱ አድርጎ የመረጠው፣ የእስራኤል ህዝብ። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀኝ እጅ
በእስራኤል አንድ ሰው ሌላውን ማክበር ሲፈልግ፣ ያሰው ወደ ቀኝ እጁ ተጠግቶ በቀኙ በኩል እንዲቆም ያደርጋል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከአንተ ዘወር አንልም
እዚህ ስፍራ "ዞር ማለት" የሚለው አንድን ሰው ላለመቀበል ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። ይህ በአዎንታዊ መልክም ሊገለጽ ይችላል። "አንተን መታዘዝ እና ማምለክ አናቆምም" ወይም "እኛ ሁልጊዜም አንተን እናመልካለን እንታዘዛለንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 80:19

በላያችን አብራ
ጸሐፊው ያህዌ ለእነርሱ ሞገስ መስጠቱን የሚገልጸው የያህዌ ፊት በላያቸው ብርሃን እንዳበራ አድርጎ ነው። ይህ በመዝሙር 80:3 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "በእኛ ላይ ሞገስህ አድርግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኛም እንድናለን
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንተ ታድነናለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 81

1 ብርታታችን ለሆነው አምላክ በደስታ ዘምሩ ለያዕቆብ አምላክ በደስታ እልል በሉ። **2** ለመዘመር ተነሡ፤ ከበሮም ምቱ በበገናና በመሰንቆ ደስ የሚል ዜማ አሰሙ። **3** በሙሉ ጨረቃ በክብረ በዓላችን ቀን በወሩ መግቢያ ጨረቃ ስትወለድ ቀንደ መለከት ንፉ። **4** ይህም ለእስራኤል የተደነገገ፣ የያዕቆብ አምላክ የሰጠው ሥርዐት ነው። **5** ግብፅን ለቅቆ በወጣ ጊዜ ይህን ለዮሴፍ ደነገገ፤ በማላውቀውም ቋንቋ እንዲህ ሲል ሰማሁ፤ **6** «ከትከሻው ሸክምን አስወገድሁ እጆቹንም ቅርጫት ከመያዝ አሳረፍሁ። **7** በመከራህ ጊዜ ጠራኸኝ፤ እኔም ረዳሁህ በነጐድጓድ መሰወሪያ ውስጥ መለስሁልህ በመሪባ ውሃ ዘንድ ፈተንሁህ። ሴላ **8** ሕዝቤ ሆይ፣ ሳስጠነቅቅህ ስማኝ እስራኤል ሆይ፣ ምነው ባደመጥኸኝ! **9** ባዕድ አምላክ በመካከልህ አይሁን ሌሎች አማልክት አታምልክ። **10** እኔ ከግብፅ ምድር ያወጣሁህ አምላክህ ያህዌ ነኝ። አፍህን በሰፊው ክፈት፤ እኔም እሞላዋለሁ። **11** ሕዝቤ ግን ቃሌን አልሰማም እስራኤልም ለእኔ አልታዘዝም። **12** ስለዚህ በእልከኝነት መንገዳቸው እንዲሄዱ፣ የፈለጉትንም እንዲያደርጉ ተውኳቸው። **13** ምነው ሕዝቤ ባደመጠኝ ኖሮ፣ እስራኤል በመንገዴ ሄዶ ቢሆን ኖሮ። **14** ፈጥኜ ጠላቶቻቸውን አስገዛላቸው ነበር እጄንም በጨቋኞቻቸው ላይ ባነሣሁ ነበር። **15** ያህዌን የሚጠሉ በፊቱ በፍርሃት ይሸማቀቃሉ! ለዘላለምም ያፍራሉ። **16** እስራኤልን ግን ምርጡን ስንዴ አበላዋለሁ ከዐለት ከሚገኘውም ማር አጠግባችኋለሁ።»

Psalms 81:1

አጠቃላይ መረጃ:
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነ ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ:
የአሳፍ መዝሙር።

ለመዘምራን አለቃ
"ይህ በመዘምራን አለቃ ለአምልኮ የሚዜም ነው"

ጊቶት በሚባል (ዋሽንት መሰል) የሙዚቃ መሳሪያ የሚቀርብ
ይህ ምናልባት የሙዚቃን/ዝማሬን አይነት ያመለክት ይሆናል። በመዝሙር 8:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

የአሳፍ መዝሙር
"ይህ አሳፍ የጻፈው ዝማሬ ነው"

እግዚአብሔር ሀይላችን
"ሀይል/ጥንካሬ" የሚለው ረቂቅ ስም "ጠንካራ" በሚል ሊገለጽ ይችላል። "እንድንጠነክር የሚያስችለን እግዚአብሔር/ እግዚአብሔር ሀይላችን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የያዕቆብ አምላክ
እዚህ ስፍራ "ያዕቆብ" የሚወክለው ትውልዶቹን ሁሉ ነው። "የእስራኤል አምላክ፣ የያዕቆብ ትውልድ ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ደስ የሚያሰኘውን ድምጽ በበገና እና በታምቡሪኒ/ከበሮ መሰል መሳሪያ/ አሰሙ
በገና እና ከበሮ መሰል የሙዚቃ መሳሪያ/ታምቡሪኒ/ የሙዚቃ መሳሪያ ናቸው

ታምቡሪኒ/ከበሮ መሰል የሙዚቃ መሳሪያ
አናቱ ከበሮ የሚመስል የምት መሳሪያሲሆን በዚሪያው ያሉ ቁርጥራጭ ብረቶች እየትርገፈገፉ ድምጽ የሚሰጥ የሙዚቃ መሳሪያ። (የማይታወቀውን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

አዲስ ጨረቃ
ይህ የጨረቃ ወር መጀመሪያ ነው

የሙሉ ጨረቃ ቀን
ይህ የጨረቃ ወር አጋማሽ ነው

የክብረ በዓላችን ዕለት ሲጀምር
"ክብረ በዓላችን በመጀምርበት ቀን"

Psalms 81:4

ለዚህ
እዚህ ስፍራ "ይህ" የሚለው የሚያመለክተው የክብረ በዓሉን ቀን ነው።

በያዕቆብ አምላክ የተሰጠ ሥርዐት
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የያዕቆብ አምላክ ይህን ሥርዐት ሰጠ" ወይም "የያዕቆብ አምላክ ይህን አዘዘ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የያዕቆብ አምላክ
እዚህ ስፍራ "ያዕቆብ የሚወክለው ትውልዱን ሁሉ ነው። "የእስራኤል አምላክ፣ የያዕቆብ ትውልድ ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ከግብጽ ምድር ለቆ በወጣ ጊዜ
ይህ የሚያመለክተው የእስራኤል ህዝብ ባሪያ ከነበሩበት ከግብጽ ምድር እግዚአብሔር ነጻ ያወጣቸውን ታሪካዊ ወቅት ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የግብጽ ምድር
እዚህ ስፍራ "ምድር"የሚወክለው ህዝቡን ነው። "የግብጽ ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 81:6

አጠቃላይ መረጃ:
እዚህ ስፍራ እግዚአብሔር መናገር ይጀምራል።

ከጫንቃው ሸክሙን አስወገደ
እዚህ ስፍራ "ከጫንቃው ሸክሙን" የሚለው የሚወክለው አስራኤላውያን በግብጽ ውስጥ በባርነት በነበሩበት ጊዜ ይሰሩት የነበረውን የግዴታ ስራ ነው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

እጆቹ ቅርጫት ከመሸከም ነጻ ወጡ
እዚህ ስፍራ "ቅርጫት መሸከም" የሚለው የሚወክለው አስራኤላውያን በግብጽ ውስጥ በባርነት በነበሩበት ጊዜ ይሰሩት የነበረውን የግዴታ ስራ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ነው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በጭንቀትህ
"በታላቁ መከራህ"

በጨለማና ነጎድጓዳማ ደመና ውስጥ ለጥያቄህ መልስ ሰጠሁህ
እግዚአብሔር ወደ እስራኤላውያን ሲመጣ፣ ሙሉ መገኘቱን እና ክብሩን፣ በጨለማ እና አስፈሪ ደመና ውስጥ ይሰውራል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በመሪባ ውኾች ፈተንኩህ
እግዚአብሔር የእስራኤልን ልጆች በመሪባ በረሃ ውሃ እንደሚሰጣቸው ያምኑ እንደሆነ ለማየት ፈተናቸው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 81:8

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ህዝቡን በበረሃ በነበሩ ጊዜ የተናገራቸውን አስታወሳቸው።

እኔ የማስጠነቀቅህ
"ማስጠንቀቂያ የምሰጥህ"

እስራኤል
እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚለው የሚወክለው የእስራኤልን ህዝብ ነው። "እስራኤላውያን" ወይም "የእስራኤል ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እኔን ብቻ ብትሰማኝ!
"እኔን ብትሰማኝ እንዴት በወደድኩ" ወይም "ነገር ግን እኔን መስማት መጀመር ይኖርብሃል!"

አፍህን በሰፊው ክፈት፣ እኔም እሞላዋለሁ
እግዚአብሔር የህዝቡን ፍላጎት ሁሉ እንደሚያሟላ የተገለጸው አንዲት እናት ወፍ ጫጩቶቿን በምትመግብበት ሁኔታ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 81:11

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ህዝቡን ካስጠነቀቀ በኋላ በእርግጥ የሆነውን ተናገረ

በእኔ ቃሎች
"እኔ እንደ ተናገርኩት" ወይም "በእኔ"

ለራሳቸው ግትር መንገድ/ደንዳናነት አሳልፎ ሰጠኋቸው
እግዚአብሔር ህዝቡን ለደንዳናነቱ እንዲቆይ መፍቀዱ የተገለጸው ጠላት እነርሱን እንዲጎዳቸው አሳልፎ እንደመስጠት ተደርጎ ነው። "ስለዚህ፣ ለደንዳናው ልባቸው አሳላፌ ሰጠኋቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 81:13

አወይ፣ ምነው ይህ ህዝቤ በመንገዶቼ ቢሄድ
እግዚአብሔር ህዝቡ እርሱን እንዲታዘዘው መፈለጉ የተገለጸው፣ ህዝቡ በእርሱ መንገድ ወይም ጎዳና እንዲሄድ እርሱ እንደሚፈልግ ተደርጎ ነው። "እነርሱ ለህጎቼን እንዲጠብቁ እሻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እጄን በእነርሱ ላይ አነሳሁ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚወክለው የያህዌን ሀይል ነው። "እኔ አጠፋለሁ" ወይም "እኔ አሸንፋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 81:15

ያህዌን የሚጠሉ... ከእኔ አስቀድሞ
ያህዌ ስለ እረሱ በሶስተኛ መደብ ይናገራል። "እኔን የሚጠሉ...ከእኔ አስቀድሞ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

በፍርሃት መሸማቀቅ
"በፍርሃት መጎንበስ" ወይም "በፍርሃት መውደቅ"

ለዘለዓለም የተዋረዱ ይሁኑ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኔ እነርሱን ለዘለዓለም አዋርዳቸዋለሁ" ወይም "እኔ እነርሱን ለዘለዓለም እቀጣቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ እስራኤልን ምርጥ የሆነውን ስንዴ እመግበዋለሁ
እግዚአብሔር ምርጥ የሆነው ስንዴ በእስራኤል እንዲበቅል ማድረጉ የተገለጸው እርሱ ስንዴውን በቀጥታ ለህዝቡ እንደሚያበላ ተደርጎ ነው። "እኔ እስራኤላውያን ምርጥ የሆነውን ስንዴ እንዲመገቡ አደርጋለሁ"በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እስራኤልን መመገብ...እናንተን ማርካት
"እስራኤል" እና "እናንተ" የሚሉት ሁለቱም የሚያመለክቱት እስራኤላውያንን ነው።

ከዓለቱ ውስጥ ማር
ይህ የጫካ ማርን ያመለክታል። ንቦች በዓለት ውስጥ በሚገኙ ቀዳዶች ቀፎ ሰርተው በዚያ ስፍራ ማር ያበጃሉ። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 82

1 እግዚአብሔር በአማልክት ጉባኤ ቆመ፤ በአማልክትም ላይ፣ ይፈርዳል እንዲህም ይላል፤ **2** ፍትሕ የምታጓድሉት እስከ መቼ ነው? ለክፉዎች የምታደሉትስ
እስከ መቼ ነው? ሴላ **3** ለድኾችና ለሙት ልጆች ተሟገቱ፤ የችግረኛውንና የምስኪኑን መብት አስከብሩ። **4** ድኾችንና ምስኪኖችን ታደጉ፤ ከዐመፀኞችም እጅ
አስጥሏቸው። **5** ዕውቀትም ሆነ ማስተዋል የላቸውም በጨለማ ውስጥ ወዲያ ወዲህ ይመላለሳሉ የምድር መሠረቶችም ተናወጡ። **6** እኔም፣ «እናንተ
አማልክት ናችሁ፤ ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ አልሁ። **7** ሆኖም፣ እንደ ማንኛውም ሰው ትሞታላችሁ እንደ ማንኛውም ገዥ ትወድቃላችሁ።» **8**
እግዚአብሔር ሆይ፣ ተነሥ፤ ሕዝቦች ሁሉ ርስትህ ናቸውና፤ በምድር ላይ ፍረድ።

Psalms 82:1

አጠቃላይ መረጃ:
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው

የአሳፍ መዝሙር
"ይህ አሳፍ የጻፈው ዝማሬ ነው"

መለኮታዊ ጉባኤ
"ሰማያዊው ምክር ቤት" ወይም "በሰማይ የተደረገ ስብሰባ"

እርሱ ፍርድ አደረገ
"እርሱ ፍርድ ሰጠ።" "ፍርድ" የሚለው ረቂቅ ስም በግስ መልክ ሊገለጽ ይችላል። "እርሱ ፈረደ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

አማልዕክት
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እነዚህ በሰማይ የሚኖሩ ሌሎች መንፈሳዊ አካላት ናቸው። "መለኮታዊ አካላት" ወይም "ሰማያዊ ፈራጆች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፤ ወይም 2) እነዚህ እግዚአብሔር ለዳኝነት የሾማቸው ሰዎች ናቸው። በማንኛውም መንገድ ቢሆን፣ ያህዌ እምላክ እንደሆነው ያሉ አማልዕክት ናቸው ማለት አይደለም። የዚህ ትርጉም እግዚአብሔር ታላቅ ስልጣን እና ሀይል ሰጥቷቸዋል ማለት ነው። "መሪዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እስከ መቼ ያለ ቅንነት ትፈርዳላችሁ፣ እስከ መቼስ ለክፉዎች ታደላላችሁ?
ያህዌ ጥያቄውን የተጠቀመበት ዳኞች ለህዝቡ በቅንነት ባለመፍረዳቸው ለመውቀስ ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ሴላ
ይህ ሰዎች የሙዚቃ መሳሪያቸውን እዚህ እንዴት እንደሚያዜሙበት ወይም እንደሚጫወቱበት የሚያሳይ ሙዚቃዊ ስያሜ ነው። አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል እንዳለ ይጠቀሙበታል፣ አንዳንድ ትርጉሞች ይተዉታል። ይህ በመዝሙር 3:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ቅጂ/እንዳለ መገልበጥ/ ወይም ቃላትን መዋስ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 82:3

ድሆች እና አባት የሌላቸው
እዚህ ስፍራ "ድሃ" እና "አባት የሌለው" የሚሉት ስማዊ ቅጽሎች ናቸው። በቅጽል መልክ ሊገለጹ ይችላሉ። "ድሆች የሆኑ እና ወላጅ የሌላቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

የ...መብት ጠብቁ
"ለ...ትክክል የሆነውን አድር/ ለ...በጽድቅ ፍረዱ

የተጠቁ እና ምስኪኖች
እዚህ ስፍራ "የተጠቁ" እና "ምስኪኖች" የሚሉት ስማዊ ቅጽሎች ናቸው። በቅጽል ሊገለጹ ይችላሉ። "መከራ የሚቀበሉ እና አንዳች ነገር የሌላቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ድሆች እና እረዳታ የሚሹ... ክፉዎች
እነዚህ ስማዊ ቅጽሎች ናቸው። እንደ ቅጽል ሊገለጹ ይችላሉ። "ድሆች እና እርዳታ ፈላጊ የሆኑ... ክፉ የሆኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱን ከክፉዎች እጅ አድኗቸው
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል ሀይልን ወይም መቆጣጠርን ይወከወላል። "ክፉ ሰዎች እነርሱን ማጥቃታቸውን ከልክሉ/አስቁሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 82:5

እነርሱም የላቸውም
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "እነርሱ" የሚለው አማልዕክትን ያመለክታል፤ ወይም 2) "እነርሱ" የሚለው ክፉ ሰዎችን ያመለክታል።

በጨለማ ውስጥ ይመላለሳሉ
ክፉ ነገር ማድረግ የተገለጸው በጣም ጨለማ በሆነ ስፍራ እንደሚመላለሱ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የምድር መሰረቶች ሁሉ ተናወጡ
ያህዌ የመሰረተውን የሞራል ስርዓትን የጣሱ ዳኞች የተገለጹት አማልዕክት ምድርን እንዳናወጡ እና ምድር እንደፈራረሰች ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ተናወጠ
ፈራረሰ

Psalms 82:6

እናንተ አማልዕክት ናችሁ፣ እናንተ ሁላችሁም የልዑሉ ወንዶች ልጆች ናችሁ
እዚህ ስፍራ "አማልዕክት" የሚለው የሚያመለክተው በመዝሙር 82:1 ላይ የሚገኙትን እነዚያኑ ወገኖች ነው። ይህ የሚያመለክተው መንፈሳዊ ፍጥረቶችንም ሆነ ሰዎችን፣ ያህዌ እንደሆነ ያሉ አምላክ አይደሉም። ቃል በቃል የእርሱ ወንዶች ልጆች ናቸው ማለትም አይደለም። "አማልዕክት" እና "የልዑሉ ወንዶች ልጆች" ብሎ በመጥራት ያህዌ ለእነርሱ ትልቅ ሀይል እና ስልጣን መስጠቱን ያረጋግጣል።

የልዑሉ ወንዶች ልጆች
ያህዌ ስለ እራሱ "ልዑሉ/ እጅግ ከፍ ያለው" በማለት ይገልጻል። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

የሆነ ሆኖ እናንተ
"ሆኖም እናንተም"

ትወድቃላችሁ
ይህ ሰው የሚሞት መሆኑ የሚገለጽበት መንገድ ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 82:8

አጠቃላይ መረጃ:
ጸሐፊው ዳግም ይናገራል

በምድሪቱ ላይ መፍረድ
እዚህ ስፍራ "ምድር" ህዝቡን ይወክላል። "በምድሪቱ ህዝብ ላይ ፍረድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ በምድር ወገኖች ላይ ሁሉ ርስት አለህና
"የምድር ወገኖች ሁሉ የአንተ ርስት ናቸውና።" ያህዌ ህዝብን በሙሉ የራሱ አድርጎ ይወስዳል ደግሞም በእነርሱ ላይ መግዛት የተገለጸው ህዝቦች ሁሉ የእርሱ የሚገዛቸው ሀብቱ ተደርገው ነው። "አንተ በአገራት ሁሉ ህዝብ ላይ ትገዛለህና" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አገራት ሁሉ
እዚህ ስፍራ "አገራት" የሚለው የሚወክለው የአገራትን ህዝብ ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 83

1 እግዚአብሔር ሆይ፣ ዝም አትበል አትተወን ችላ አትበል። **2** ጠላቶችህ እንዴት እንደ ተነሣሡ ባላንጣዎችህም እንዴት ራሳቸውን ቀና ቀና እንዳደረጉ
ተመልከት። **3** በሕዝብህ ላይ ያደባሉ፣ አንተ በምትጠብቃቸውም ላይ ያሤራሉ። **4** ‹የእስራኤል ስም ከእንግዲህ እንዳይታሰብ፣ ኑና ሕዝብ እንዳይሆኑ
እንደምስሳቸው› አሉ። **5** በአንድ ሐሳብ ተስማምተው ተማከሩ አንተም ላይ ተማማሉ። **6** የኤዶምና የእስማኤላውያን፣ የሞዓብና የአጋራውያን ድንኳኖች፣ **7**
ጌባል አሞንና አማሌቅ፣ ፍልስጥኤምም ከጢሮስ ሕዝብ ጋር አብረው ዶለቱ። **8** አሦርም ከእነርሱ ጋር ተባበረ የሎጥም ልጆች ረዳት ሆነ። ሴላ **9** ምድያም ላይ
እንዳደረግኸው አድርግባቸው በቂሶን ወንዝ በሲሣራና በኢያቢስ ላይ ያደረስኸው ይድረስባቸው። **10** እነርሱ በዐይንዶር ጠፉ እንደ ምድር ትቢያ ሆኑ። **11** እንደ
ሔሬብና እንደ ዜብ፣ መሳፍንቶቻቸውንም እንደ ዛብሄልና እንደ ስልማና አድርጋቸው፤ **12** እነርሱም፣ «የእግዚአብሔርን ግጦሽ ቦታ እንውሰድ» አሉ። **13** አምላኬ
ሆይ፣ በዐውሎ ነፋስ እንደሚወሰድ ትቢያ፣ ነፋስ ፊት እንዳለ ገለባ አድርጋቸው። **14** እሳት ደንን እንደሚያቃጥል ተራራውን እንደሚያዳርስ እሳት ነበልባል **15**
እንዲሁ በማዕበልህ አሳዳቸው በሞገድህም አስደንግጣቸው። **16** አምላኬ ያህዌ ሆይ፣ ስምህን ይሹ ዘንድ፣ ፊታቸውን በእፍረት ሙላ፤ **17** ለዘላለም ይፈሩ
ይታወኩም፤ በውርደትም ይጥፉ። **18** ስምህ ያህዌ የሆነው አንተ ብቻ በምድር ላይ ልዑል እንደ ሆንህ ይወቁ።

Psalms 83:1

አጠቃላይ መረጃ:
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነግጥም እና ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ዝማሬ። የአሳፍ ዝማሬ
"ይህ አሳፍ የጻፈው ዝማሬ ነው"

ጸንቶ/በዝምታ መቆየት
"እኛን ለመርዳት አንዳች አለማድረግ"

እነሆ፣ ጠላቶችህ ሁከት እየፈጠሩ ነው
እዚህ ስፍራ "ሁከት መፍጠር" ማለት እነርሱ አመጽ እያስነሱ እና በእግዚአብሔር ላይ እያመጹ ነው ማለት ነው። "እነሆ፣ ጠላቶችህ በአንተ ላይ አምጸዋል"

አንተን የሚጠሉ ራሳቸውን ቀና እያደረጉ ነው
"እራሳቸውን ቀና እያደረጉ" የሚለው ሀረግ በእግዚአብሔር ላይ እያመጹ ነው የሚለው መገለጫ ነው። "አንተን የሚጠሉ አንተን እየተቃወሙ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 83:3

በአንተ የተጠበቁ
"አንተ የጠበቅካቸው" ይህ እስራኤላውያንን ያመለክታል።

ከእንግዲህ የእስራኤላውያን ስም አይታወስም
እዚህ ስፍራ "ስም" የሚወክለው የአንድን ሰው ክብር ወይም መታሰቢያ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ማንም ከእንግዲህ የእስራኤላውያንን የቀድሞ ህልውና አያስታውስም" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

እነርሱ በአንድ ላይ በአንድ ሀሳብ አመጹ
"ጠላቶችህ በአንድ እቅድ ተስማሙ"

በአንተ ላይ በአንድነት ተስማምተው ተነሱ
"አንተን ለመቃወም ህብረት አደረጉ"

Psalms 83:6

አጠቃላይ መረጃ:
ጸሐፊው እስራኤልን ለማጥፋት የሚፈልጉ ወገኖችን መዘርዘሩን ይቀጥላል።

የኤዶም ድንኳኖች
ይህ የሚያመለክተው በድንኳን የሚኖሩ የኤዶም ሰዎችን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አጋራውያን
ይህ ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምስራቅ የሚኖሩ የህዝብ ወገኖች ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ጌባል፣ አሞን፣ አማሌቅ...ፍልስጥኤም
እነዚህ ሁሉ የሚወክሉት የእያንዳንዱን አካባቢ ሰዎች ወይም ነገድ ነው። "የጌባል ሰዎች፣ አሞናውያን፣ አማሌቃውያን...ፍልስጥኤማውያን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ጌባል
ይህ ከሙት ባህር በስተ ደቡብ የሚገኝ አካባቢ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 83:8

አሦር
ይህ የአሦር ህዝብን ይወክላል። "የአሦር ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የሎጥ ትውልድ
ይህ የሞዓብንና የአሞንን አገር ሰዎች ያመለክታል። መረጃውን ይበልጥ ግልጽ ማድረግ ትችላላችሁ። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሴላ
ይህ ሰዎች የሙዚቃ መሳሪያቸውን እዚህ እንዴት እንደሚያዜሙበት ወይም እንደሚጫወቱበት የሚያሳይ ሙዚቃዊ ስያሜ ነው። አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል እንዳለ ይጠቀሙበታል፣ አንዳንድ ትርጉሞች ይተዉታል። ይህ በመዝሙር 3:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ቅጂ/እንዳለ መገልበጥ/ ወይም ቃላትን መዋስ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 83:9

በእነርሱ ላይ አድርግ...በምድሪቱ
ጸሐፊው እግዚአብሔርን የእስራኤልን ጠላቶች በቀድሞ ጊዜ እንዳደረገው ድል እንዲያደርጋቸው ይጠይቃል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በምድያማውያን ላይ እንዳደረግኸው
እዚህ ስፍራ "ምድያም" የሚለው የሚወክለው የምድያምን ሰዎች ነው። "በምድያም ላይ እንዳደረግከም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሲሳራ...ኢያቢስ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። ኢያቢስ የሐሬብ ንጉሥ ነው። ሲሳራ የኢያቢስ ጦር አዛዥ ነበር። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የቂሶን ወንዝ
ይህ በሰሜን እስራኤል የሚገኝ ወንዝ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ዐይንዶር
ይህ በሰሜን እስራኤል የሚገኝ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ለምድር እንደ ፍግ ይሆናሉ
ይህ ማለት የሲሳራ እና ኢያቢስ በድኖች ሳይቀበሩ በሜዳ ወድቀው ይቀራሉ ማለት ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 83:11

አጠቃላይ መረጃ:
ጸሐፊው ወደ እግዚአብሔር ባለፉት እርሱ ድል ያደረጋቸውን ሌሎች ጠላቶቻቸውን ማስታወሱን ይቀጥላል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሔሬብ...ዜብ...ዛብሄል...ስልማና
እነዚህ ሁሉ የነገሥታት ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ እንዲህ አሉ
እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው የሚያመለክተው ሔሬብ፣ ዜብ፣ ዛብሄል እና ስልማን ነው።

የእግዚአብሔር የግጦሽ ስፍራ
ይህ የሚናገረው የእስራኤል ምድር በጎች የሚሰማሩበት የግጦሽ ስፍራ በማድረግ እና እግዚአብሔር በዚያ ላይ እረኛ እንደሆነ አድርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 83:13

አጠቃላይ መረጃ:
ጸሐፊው እግዚአብሔር የእስራኤልን ጠላቶች በጠቅላላ ማጥፋቱን ለመግለጽ ተነጻጻሪ ዘይቤን ይጠቀማል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በዐውሎ ነፋስ እንደሚነዳ ትቢያ፣ በነፋስ ፊት እንዳለ ገለባ አድርጋቸው
ሁለቱም ሀሳቦች ስለ እግዚአብሔር ጠላቶቹን እርሱ አውሎ ነፋስ እንደሆነ እና እነርሱን በቀላሉ እንደሚጠርጋቸው ይገልጻሉ። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ጫካን እንደሚያቃጥል እሳት፣ እና ተራሮችን እንደሚያነድ እሳት
ሁለቱም ሀሳቦች የእግዚአብሔር ቅጣት እሳት እንደሆነ እና የእግዚአብሔርን ጠላቶች ደግሞ በእሳቱ እንደሚቃጠሉ ነገሮች አድርገው ይናገራሉ። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

በዐውሎ ነፋስህ አባራቸው፣ በማዕበልህ አስደንግጣቸው
ሁለቱም ሀሳቦች እግዚአብሔር ጠላቶቹን በማዕበሎች እንዲያጠፋቸው ይጠጥቃሉ።(ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

Psalms 83:16

ፊታቸውን በሀፍረት ሙላው
እዚህ ስፍራ "ፊት" የሚወክለው ማለውን ማንነት/ሰው ነው።"በጣም አሳፍራቸው" (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ስምህን ይፈልጉ ይሆናል
እዚህ ስፍራ "ስም" የሚወክለው የእግዚአብሔርን ሀይል ነው። የእግዚአብሔር ጠላቶች እግዚአብሔር ሀያል ለመሆኑ እውቅና እንደሚሰጡ የተገለጸው ያህዌን ለማግኘት እንደሚፈልጉ ተደርጎ ነው። "አንተ ሀያል መሆንህን እውቅና ይሰጣሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ስምህን ይፈልጉ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የእግዚአብሔር ጠላቶች እግዚአብሔር ሀያል መሆኑን አምነው ተቀበሉ፤ ወይም 2) የእግዚአብሔር ጠላቶች እግዚአብሔርን እርዳታ ይለምናሉ፤ ወይም 3) የእግዚአብሔር ጠላቶች እርሱን ማምለክ እና መታዘዝ ይጀምራሉ።

እነርሱ ይፈሩ ለዘለዓለምም ይንቀጥቀጡ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እንዲያፍሩ እና ለዘለዓለም እንዲፈሩ አድርጋቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በሀፍረትም ይጥፉ
"በሀፍረታቸው ይወገዱ/ይሙቱ)

Psalms 83:18

ከዚያም እነርሱ ያውቃሉ
ይህ ጸሐፊው ለእግዚአብሔር ልመና በሚያቀርብበት ጊዜም ሊገለጽ ይችላል። "እንዲረዱ አድርጋቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እጅግ ከፍ ያለው በምድር ላይ ነው
እግዚአብሔር በምድር ላይ የሁሉም ገዢ መሆኑ የተገለጸው እርሱ ከማንኛውም ነገር በላይ ከፍ ብሎ እንደሚገኝ ተደርጎ ነው። " ከፍ ያልክ፣በምድር ላይ የሚገኙ ነገሮችን ሁሉ የምትገዛ ነህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 84

1 የሰራዊት ጌታ ያህዌ ሆይ፣ ማደሪያህ ምንኛ ያማረ ነው። **2** ነፍሴ የያህዌን አደባባዮች ትናፍቃለች እጅግም ትጓጓለች። ልቤና ሁለንተናዬ ሕያው እግዚአብሔርን ይጣራሉ። **3** ንጉሤና አምላኬ የሰራዊት አምላክ ሆይ፣ መሠዊያህ ባለበት ስፍራ ድንቢጥ እንኳ መኖሪያ ቤት ዋኖስም ጫጩቶችዋን የምታኖርበት ቦታ አገኘች። **4** በቤትህ የሚኖሩ የተባረኩ ናቸው፤ እነርሱ ለዘላለም ያመሰግኑሃል። ሴላ **5** አንተን ብርታታቸው ያደረጉ በልባቸው የጽዮንን መንገድ የሚያስቡ ቡሩካን ናቸው። **6** በልቅሶ ሸለቆ በሚያልፉበት ጊዜ የሚጠጡት የምንጭ ውሃ ያገኛሉ የበልግም ዝናብ ይሞላዋል። **7** ከኃይል ወደ ኃይል ይሸጋገራሉ እያንዳንዱም በጽዮን ባለው አምላክ ፊት ይቀርባል። **8** የሰራዊት አምላክ ያህዌ ሆይ፣ ጸሎቴን ስማ፣ የያዕቆብ አምላክ ሆይ፣ ቃሌን አድምጥ። ሴላ **9** አምላክ ሆይ፣ ጋሻችንን ጠብቅ፣ ለቀባኸውም ራራለት። **10** በሌላ ቦታ ሺህ ቀን ከመኖር፣ አንዲት ቀን በአደባባይህ መዋል ይሻላል። **11** አምላካችን ያህዌ ፀሐይና ጋሻችን ነውና፤ ያህዌ ጸጋንና ክብርን ይሰጣል፤ በቅንነት የሚሄዱትን መልካም ነገር አይነፍጋቸውም። **12** የሰራዊት ጌታ ያህዌ ሆይ፣ በአንተ የተማመነ ሰው ቡሩክ ነው።

Psalms 84:1

አጠቃላይ መረጃ:
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነግጥም እና ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ለመዘምራን አለቃ
"ይህ ለመዘምራን መሪ በአምልኮ ጊዜ የሚውል ነው"

ጊተት በሚባል (ዋሽንተ መሰል) የሙዚቃ መሳሪያ የሚቀርብ
ይህ ምናልባት የሙዚቃን/ዝማሬን አይነት ያመለክት ይሆናል። በመዝሙር 8፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

የቆሬ ልጆች መዝሙር
"ይህ የቆሬ ልጆች የጻፏቸው መዝሙሮች ናቸው"

እንዴት የተወደደ
"እንዴት ውብ"

የያህዌን አደባባይ እጠብቃለሁ
"በያህዌ አደባባይ መሆን እፈልጋለሁ"

የያህዌ አደባባይ
እዚህ ስፍራ "አደባባይ" የሚወክለው ቤተ መቅደስን ነው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ለዚህ ያለኝ ጥበቃ አጓጉቶኛል
"በጉጉት ዝያለሁ" ወይም "ይህን እጅግ ከመፈለጌ የተነሳ ደክሜያለሁ"

ልቤ እና ጠቅላላው ማንነቴ ይጣራሉ
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚወክለው ጠቅላላ ስብዕናን ነው። "በመላው ማንነቴ ፈለግሁ" (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ህያው አምላክ
ይህ ማለት እግዚአብሔር ህያው ነው፣ ደግሞም እርሱ ሌሎች ነገሮች ሁሉ አንዲኖሩ የማድረግ ሀይል አለው።

Psalms 84:3

ድንቢጥ...ዋኖስ
እነዚህ የወፍ አይነቶች ናቸው። (የማይታወቀውን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

እርሷ ማረፊያ/ማኖሪያ አገኘች
"ቤት አገኘች" ወይም "ቤት ሰራች"

የድንቢጥ ቤት
እዚህ ስፍራ "አገኘች" ወይም "ሰራች" የሚሉት ቃላት ባይጠቀሱም የታወቁ ናቸው። "ድንቢጥ እንኳን ቤቷን አገኘች" ወይም "ድንቢጥ እንኳን ቤቷን ሰራች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

ጫጩቶቿን የምኖርበት
"እንቁላልዋን የምትጥልበት እና ጫጩቶቿን የምትንከባከብበት"

እነርሱ በአንተ ቤት የሚኖሩ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "እነርሱ" የሚለው ቤተመቅደሱን በቋሚነት የሚያገለግሉ ካህናትን ያመልክታል፤ ወይም 2) "እነርሱ" የሚለው የሚያመለክተው በቤተ መቀደሱ መጥተው የሚያመልኩ ሰዎችን በአጠቃላይ ነው።

ሳያቋርጡ አንተን ያወድሳሉ
"አንተን ደግመው ደጋግመው ማወደሳቸውን ይቀጥላሉ"

Psalms 84:5

የተባረከ ሰው ነው
እዚህ ስፍራ "ሰው" የሚያመለክተው በአጠቃላይ ሰዎችን ነው። (የስማዊ ሀረግ ክፍል እና ወንዴ መጠሪያ/ቃላት ሴቶችን ሲያካለትት የሚለውን መልከቱ)

አንተ ብርታታቸው የሆንክ
ስለ እግዚአብሔር የተነገረው ሀይል በእርሱ እንደሚገኝ ተደርጎ ነው። "አንተ ያበረታሃቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የጽዮን መንገዶች በማን ልብ ይገኛል
ይህ አገላለጽ ልባዊ ምኞትን ያመለክታል። "እስከ ጽዮን መድረስ የሚወዱ" ወይም "በእውነት እስከ ጽዮን መድረስ የሚፈልጉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጎዳና
በዙሪያው ከሚገኘው መሬት ከፍ ብለው የተገነቡ መንገዶች

እስከ ጽዮን ድረስ
ቤተመቅደሱ የሚገኘው ጽዮን ተብሎ በሚጠራው በእየሩሳሌም በሚገኘው ከሁሉም ከፍ ባለው ኮረብታ ላይ ነበር

የእንባ ሸለቆ
ይህ የሚያመለክተው ደረቅ እና የማይታረስ ስፍራን ነው። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅጂዎች "የባካ ሸለቆ" የሚል ይጨምራሉ። "ባካ" ማለት "ለቅሶ" ማለት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የመጀመሪያ/ቀዳሚ ዝናብ
ይህ ማለት ከክረምቱ አስቀድሞ በበልግ የሚዘንበው ዝናብ ማለት ነው። ይህም በምዕራባውያን የወር አቆጣጠር በጥቅምት እና ህዳር ወራት ማለት ነው።

በረከቶች
እዚህ ስፍራ "በረከቶች" የሚለው ቃል በደረቅ ምድር የሚኖሩ ሰዎችን ደስተኛ ለሚያደርግ የኩሬ ውሃ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "እነርሱን ደስ የሚያሰኝ የኩሬ ውሃ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ([[rc://*/ta/vo12/translate/figs-metonomy]]) ይመልከቱ።

Psalms 84:7

ከሀይል ወደ ሀይል ይሄዳሉ
ይህ እየበረቱ ይሄዳሉ የሚለው የሚገለጽበት መንገድ ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይሄዳሉ
እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ለማምለክ ወደ ቤተመቅደስ ለመሄድ ብርቱ ፍላጎት ያላቸውን ነው።

ሴላ
ይህ ሰዎች የሙዚቃ መሳሪያቸውን እዚህ እንዴት እንደሚያዜሙበት ወይም እንደሚጫወቱበት የሚያሳይ ሙዚቃዊ ስያሜ ነው። አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል እንዳለ ይጠቀሙበታል፣ አንዳንድ ትርጉሞች ይተዉታል። ይህ በመዝሙር 3:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ቅጂ/እንዳለ መገልበጥ/ ወይም ቃላትን መዋስ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር፣ ከጋሻችን በላይ ይመለከታል
ህዝቡን የሚጠብቀው ንጉሥ የተገለጸው ጋሻ እንደሆነ ተደርጎ ነው። "እግዚአብሔር ከንጉሣችን በላይ ይመለከታል" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በአንተ አደባባዮች ለአንድ ቀን መሆንበሌላ ስፍራ ሺህ ቀን ከመኖር ይሻላል
ይህ በሚታወቅ መረጃ ሊገጽ ይችላል። "በሌላ ስፍራ ለሺህ ቀናት ከመሆን በአንተ አደባባዮች ለአንድ ቀን መሆን ይሻለኛል" (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ሺህ
"1,000" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ዘብ ጠባቂ መሆን
"በበር ላይ ጠባቂ መሆን" ወይም "በር ላይ መቆም"

ክፉዎች
ይህ ስማዊ ቅጽል እንደ ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። "ክፉ ሰዎች" ወይም "ክፉ የሆኑ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 84:11

ያህዌ አምላክ ፀሐያችን እና ጋሻችን ነው
ህዝቡን የሚጠብቀው እና የሚመራው ያህዌ የተገለጸው ፀሐይ እና ጋሻ እንደሆነ ተደርጎ ነው። "ያህዌ አምላክ ከፀሐይ እንደሚወጣ ብርሃን ይመራናል፣ ደግሞም እንደ ጋሻ ሆኖ ይጠብቀናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ ጸጋ እና ክብር ይሰጣል
"ጸጋ" እና "ክብር" የሚሉት ረቂቅ ስሞች በግሥ ሊገለጹ ይችላሉ። "ያህዌ ለእኛ መልካም ይሆንልናል ደግሞም ያከብረናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በቅንነት የሚራመድ
አንድ ሰው ህይወቱን የሚመራበት መንገድ ወይም ድርጊቱ የተገለጸው ያ ሰው እንደሚራመድ ተደርጎ ነው። "በሀቀኝነት የሚኖር" ወይም "ሀቀኛ የሆኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

የተባረከ ሰው ነው
እዚህ ስፍራ "ሰው" የሚያመለክተው በአጠቃላይ ሰዎችን ነው። (የስማዊ ሀረግ ክፍል እና ወንዴ መጠሪያ/ቃላት ሴቶችን ሲያካለትት የሚለውን መልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 85

1 ያህዌ ሆይ፣ ለምድርህ ሞገስ አሳየህ የያዕቆብን ምርኮ መለስህ። **2** የሕዝብህን ኃጢአት ይቅር አልህ በደላቸውንም ሸፈንህ። ሴላ **3** መዓትህን ሁሉ አራቅህ ከጽኑ ቁጣህም ተመለስህ። **4** አዳኛችን እግዚአብሔር ሆይ፣ መልሰን፤ በእኛ ያዘንህብንን ሁሉ አርቅልን። **5** የምትቆጣን ለዘላለም ነውን? ቁጣህንስ ከትውልድ ወደ ትውልድ ታስተላልፋለህን? **6** እኛ ሕዝብህ በአንተ ደስ እንዲለን እንደ ገና በሕይወት አታኖረንምን? **7** ያህዌ ሆይ፣ የኪዳን ታማኝነትህን አሳየን ማዳንህንም ስጠን። **8** ያህዌ አምላክ የሚናገረውን እሰማለሁ፤ እንደ ገና በስሕተት መንገድ ካልሄዱ በቀር ለሕዝቡና ለታማኞቹ ሰላምን ያደርጋል። **9** ክብሩ በምድራችን ይኖር ዘንድ ማዳኑ ለሚፈሩት በእርግጥ ቅርብ ነው። **10** ምሕረትና ታማኝነት ተገናኙ፡ ጽድቅና ሰላም ተሳሳሙ። **11** ታማኝነት ከምድር በቀለች ጽድቅ ከሰማይ ተመለከተች። **12** ያህዌ መልካም ነገር ይሰጣል ምድራችንም ፍሬዋን ትሰጣለች። **13** ጽድቅ በፊቱ ትሄዳለች ለአረማመዱም መንገድ ያዘጋጃል።

Psalms 85:1

አጠቃላይ መረጃ:
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነግጥም እና ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

የመዘምራን አለቃ
"ይህ የመዘምራን አለቃ ሆኖ አምልኮ የሚመራውን ያመለክታል።

የቆሬ ልጆች መዝሙር
"ይህ የቆሬ ልጆች የጻፏቸው መዝሙሮች ናቸው"

አንተ ለምድርህ ሞገስ ሰጠህ
እዚህ ስፍራ "ምድር" የሚወክለው የእስራኤልን አገር እና ህዝብ ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ደህንነት
ይህ የሚያመለክተው የአንድን ሰው ደስተኛ መሆን፣ ጤንነት እና ብልጽግና ነው።

የያዕቆብ
እዚህ ስፍራ "ያዕቆብ" የሚወክለው የያዕቆብን ትውልድ፣ እስራኤላውያንን ነው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ኃጢአታቸውን ሁሉ ከደንክ
እዚህ ስፍራ የኃጢአት ይቅርታ የተነገረው አንዳይታይ የተሸፈነ ተደርጎ ነው። "አንተ እያወቅህ ኃጢአታቸውን ረሳህላቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእነርሱን ኃጢአት
ይህ ጸሐፊ ስለ ራሱ የእግዚአብሔር ህዝብ ወገን አድርጎ ያስባል። "የእኛ ኃጢአት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ሴላ
ይህ ሰዎች የሙዚቃ መሳሪያቸውን እዚህ እንዴት እንደሚያዜሙበት ወይም እንደሚጫወቱበት የሚያሳይ ሙዚቃዊ ስያሜ ነው። አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል እንዳለ ይጠቀሙበታል፣ አንዳንድ ትርጉሞች ይተዉታል። ይህ በመዝሙር 3:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ቅጂ/እንዳለ መገልበጥ/ ወይም ቃላትን መዋስ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 85:3

ቁጣህን ሁሉ አስቀረህ
ከእንግዲህ እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ላይ ቁጣው እንደማይቀጥል የተገለጸው፣ ቁጣ እሳት እንደሆነ እናእግዚአብሔር ከዚያ ፊቱን እንደመለ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የደህንነታችን አምላክ
"ደህንነት" የሚለው ረቂቅ ስም በግሥ መልክ ሊገለጽ ይችላል። "ያዳነን እግዚአብሔር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በእኛ ደስ አለመሰኘትህ ያብቃ
እግዚአብሔር በእስራኤላውያን መቆጣቱ እንዲያበቃ መለመኑ የተገለጸው፣ ጸሐፊው ደስ አለመሰኘትን እግዚአብሔር እንዲወስደው የሚፈልገው ቁስ አካል እንደሆነ አድርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ በእኛ ላይ ለዘለዓለም ትቆጣለህን? ቁጣህ በሚቀጥለውም ትውለድ ዘመን ውስጥ ሁሉ ይቀጥላልን?
ጸሐፊው እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመው እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ መቆጣቱ እንዲያበቃ እየለመነ መሆኑን ለማጉላት ነው። እነዚህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "እባክህ በእኛ ላይ ለዘለዓለም አትቆጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 85:6

ዳግም አታድሰንምን?
ጸሐፊው ጥያቄውን ያዋለው የእስራኤልን ህዝብ ለማበልጸግ እና ዳግም ደስተኛ ለማድረግ ወደ እግዚአብሔር ለሚያቀርበውን ጥያቄ ትኩረት ለመስጠት ነው። ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "እባክህ ዳግም ባለጸጎች አድርገን።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የቃል ኪዳንህን ታማኝነት አሳየን
ዐረፍተ ነገሩ እንደገና ቢጻፍ፣ "የቃል ኪዳን ታማኝነት" የሚለው ረቂቅ ስም ሀሳብ "ለአንተ ቃል ኪዳን ታማኝ መሆን" በሚለው ሀረግ ሊገለጽ ይችላል። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተን ማዳን አረጋግጥልን
ይህ ጸሐፊው እግዚአብሔር ለህዝቡ ያለውን ታማኝነት እንዲያሳይ የፈለገው እንደዚህ ነው። ዐረፍተ ነገሩ እንደገና ቢጻፍ፣ "ደህንነት" በሚለው ረቂቅ ስም ውስጥ የሚገኘው ሀሳብ "ዳነ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "እናም አድነን" ወይም "እኛን በማዳን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 85:8

እርሱ ከህዝቡ ጋር ሰላም አደረገ
"ከህዝቡ ጋር ሰላማዊ ግንኙነት ይኑር" ወይም "ለህዝቡ ሰላም አመጣ"

ሆኖም ወደ ጥፋት መንገዳቸው ዳግም መዞር የለባቸውም
የአንድ ሰው የቀድሞ መንገዱን መቀየር የተገለጸው ሰውየው በአካል ወደ ሌላ አቅጣጫ እንደዞረ ተደርጎ ነው። "ሆኖም እነርሱ ዳግም ጥፋት መስራት መጀመር የለባቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በእርግጥ የእርሱ ማዳን ለእነርሱ ቅርብ ነው
እግዚአብሔር ለማዳን ዝግጁ መሆኑ የተገለጸው ደህንነት እግዚአብሔር በአንደ ሰው አጠገብ ያስቀመጠው ቁስ አካል እንደሆነ ተደርጎ ነው። "በእርግጥ እግዚአብሔር እነርሱን ለማዳን ዝግጁ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያም ክብር በምድራችን ይሆናል
እዚህ ስፍራ "ክብር" የሚወክለው የእግዚአብሔርን መገኘት ነው። "ከዚያም የክብሩ መገኘት በምድራችን ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 85:10

የቃል ኪዳን ታማኝነት እና እምነት የሚጣልበት የመሆን አስፈላጊነት በአንድነት ተገናኙ
"ታማኝነት" እና "እምነት የሚጣልበት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች የተገለጹት በአንድነት እንደተገኛኙ ሰዎች ተደርጎ ነው። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እግዚአብሔር በቃል ኪዳኑ ታማኝ ነው፤ እናም እርሱ ለማድረግ ቃል የገባወን ያደርገዋል። "እግዚአብሔር ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ነው፤ ሰዎች እርሱን ሊያምኑት እንደሚገባ አረጋግጦላቸዋል" ወይም 2) ከቃል ኪዳኑ የተነሳ እና ሰዎች ለእርሱ ታማኝነት መሆናቸውን ምልሽ በመስጠታቸው የእግዚአብሔር ታማኝነት ታይቷል። "እግዚአብሔር ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ነበር፣ ሰዎችም እርሱን በመታመን ምላሽ ሰጥተዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

በአንድነት ተገኛኙ...እርስ በእርሳቸው ተሳሳሙ
ምናልባት ተናጋሪው እግዚአብሔር ህዝቡን ወደፊት ዳግም ባለጸጋ የሚያደርግበትን ጊዜ እየገለጸ ሊሆን ይችላል። "በአንድነት ይገናኛሉ... እርስ በእርስ ይሳሳማሉ"

ጽድቅ እና ሰላም እርስ በእርሳቸው ተሳሳሙ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ህዝቡ ትክክለኛ የሆነውን ያደርጋል፣ እግዚአብሔርም ህዝቡ በሰላም እንዲኖር ያደርጋል፤ ወይም 2) እግዚአብሔር ትክክል የሆነውን ያደርጋል፣ ህዝቡም በሰላም እንዲኖር ያደርጋል። በየትኛውም መንገድ ቢሆን ጽድቅ እና ሰላም ረቂቅ ስሞች ናቸው፤ የተገለጹትም እርስ በእርሳቸው እንደሚሳሳሙ ሰዎች ተደርገው ነው። (ረቂቅ ስሞች እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

እርስ በእርስ ተሳሳሙ
ይህ ጓደኛሞች እርስ በእርስ ሰላምታ የሚለዋወጡበት የተለመደ መንገድ ነበር።

ታማኝነት ከምድር በቀለ
በምድር የሚገኙ ሰዎች ለእግዚአብሔር ያላቸው ታማኝነት የተገለጸው ታማኝነት ከምድር የሚበቅል ተክል ተደርጎ ነው። "ታማኝነት" የሚለው ቃል "ታዛዥ" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "እዚህ በምድር ላይ፣ ለእግዚአብሔር ታዛዥ እንሆናለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

ጽድቅ ከሰማ ሆኖ ወደታች ተመለከተ
"ጽድቅ" የሚለው ቃል ረቂቅ ስም ነው፣ የተገለጸውም እግዚአብሔር እንደሚያደርገው ከላይ ሆኖ ወደታች እንደሚመለከት ነው። "እግዚአብሔር ከሰማይ ወደ እኛ ይመለከታል፣ ደግሞም በእኛ ላይ በትክክል ይፈጽማል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

Psalms 85:12

ጽድቅ በፊቱ ይሄዳል፣ ለእግሩም እርምጃዎች መንገድን ያዘጋጃል
እግዚአብሔር እርሱ በሚሄድበት ስፍራ ሁሉ ትክክል እንደሚያደርግ የተገለጸው ጽድቅ ከእግዚአብሔር ፊት የሚሄድ እና እግዚአብሔር የሚራመድበትን መንገድ እንደሚያዘጋጅ ሰው ተደርጎ ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ የእግሩ እርምጃዎች/ኮቴ
እዚህ ስፍራ "የእግር ኮቴ" የሚወክለው የእግዚአብሔርን እርምጃዎች ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 86

1 ያህዌ ሆይ፣ እኔ ድኻና ምስኪን ነኝና እባክህ ስማኝ መልስልኝም። **2** እኔ ለአንተ ታማኝ ስለሆንሁ ጠብቀኝ አምላኬ ሆይ፤ በአንተ የታመነውን ባርያህን አድነው። **3** ጌታ ሆይ፣ ቀኑን ሙሉ ወደ አንተ እጮኻለሁና እባክህ ማረኝ። **4** ጌታ ሆይ፣ ወደ አንተ እጸልያለሁና ባርያህን ደስ አሰኘው። **5** ጌታ ሆይ፣ አንተ መልካምና ይቅር ባይ ነህ ለሚጠሩህ ሁሉ ምሕረትህ ወሰን የለውም። **6** ያህዌ ሆይ ጸሎቴን አድምጥ የልመናዬንም ጩኸት ስማ። **7** አንተ ስለምትመልስልኝ በመከራዬ ቀን ወደ አንተ እጣራለሁ። **8** ጌታ ሆይ፣ ከአማልክት መካከል እንደ አንተ ያለ የለም። ከአንተ ሥራ ጋር የሚወዳደር ሥራ የለም። **9** ጌታ ሆይ፣ የሠራሃቸው ሕዝቦች ሁሉ መጥተው በፊት ይሰግዳሉ። ስምህን ያከብራሉ። **10** አንተ ታላቅ ነህና ተአምራትን ታደርጋለህ አንተ ብቻህን አምላክ ነህ። **11** ያህዌ ሆይ፣ መንገድህን አስተምረን፤ እኔም በእውነትህ እሄዳለሁ። ባልተከፋፈለ ልብም እንዳከብርህ አድርገኝ። **12** ጌታ አምላኬ ሆይ፣ በፍጹም ልቤ አመሰግንሃለሁ ስምህንም ለዘላለም አከብራለሁ **13** ለእኔ የምታሳየው ዘላለማዊው ፍቅርህ እጅግ ታላቅ ነው። ነፍሴንም ከጥልቁ ሲኦል አወጣሃት። **14** አምላክ ሆይ፣ እብሪተኞች ተነሥተውብኛል የክፉዎች ጉባኤ ነፍሴን ይፈልጓታል። አንተንም ከምንም አልቆጠሩም። **15** አንተ ግን ጌታ ሆይ፣ መሐሪና ርኅሩኅ አምላክ ነህ ለቁጣ የዘገየህ፣ ምህረትህና ታማኝነትህ የበዛ ነው። **16** ወደ እኔ ተመለስ ማረኝም ለባሪያህ ብርታትህን ስጥ የሴት ባሪያህንም ልጅ አድን። **17** የሞገስህን ምልክት አሳየኝ አንተ ያህዌ ረድተኸኛልና አጽናንተኸኛልምና የሚጠሉኝ ይህን አይተው ያፍራሉ።

Psalms 86:1

አጠቃላይ መረጃ፡
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነግጥም እና ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ድሃ እና የተጨቆነ
"ደካማ እና እርዳታ ፈላጊ"

አገልጋይህን አድን
ዳዊት ራሱን "የአንተ አገልጋይ" በማለት ይጠቅሳል፣ ይህም ማለት የእግዚአብሔር አገልጋይ ማለት ነው። "እኔን አገልጋይህን አድነኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 86:3

ቀኑን በሙሉ
ይህ ማጋነን ነው። ዳዊት ያለማቋረጥ አልቅሷል፣ ነገር ግን ቃል በቃል ነግቶ እስኪመሽ ሁሉንም ሰአት ማለት አይደለም። "አለማቋረጥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ አጋኖ እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

አገልጋይህን ደስ አሰኝ
ዳዊት ራሱን "የአንተ አገልጋይ" በማለት ይጠቅሳል፣ ይህም ማለት የእግዚአብሔር አገልጋይ ማለት ነው። "እኔን የአንተ አገልጋይ አድርገኝ" ወይም "አድርገኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 86:5

በመከራዬ ቀናት
"በችግሬ ጊዜ"

ወደ አንተ እጣራለሁ
"ወደ አንተ እጸልያለሁ"

Psalms 86:8

በአማልክት መሃል
ጸሐፊው የእነዚህ ሌሎች አማልክት ህልውና እውቅና እየሰጠ አይደለም። ሌሎች አገራት የሚያመልኳቸውን ሀሰተኛ አማልክት እያመለከተ ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አገራት ሁሉ
እዚህ ስፍራ "አገራት" የሚለው የሚወክለው ሰዎችን ነው። "ከሁሉም አገራት ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ስምህን ያከብራሉ
እዚህ ስፍራ "ስም" የሚወክለው መላ ማንነትን ነው። "እነርሱ አንተን ያከብራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 86:10

አስደናቂ ነገሮች
"እኔን የሚያስደንቁ በጣም ጥሩ ነገሮች"

አንተ ብቻ እግዚአብሔር ነህ
"ብቸኛው አምላክ አንተ ነህ"

ያህዌ ሆይ፣ መንገዶችህን አስተምረኝ። ያን ጊዜ በእውነትህ እራመዳለሁ
እግዚአብሔር የሚፈልገውን የሚታዘዝ ሰው የተገለጸው በእግዚአብሔር መንገድ ወይም ጎዳና እንደሚራመድ ተደርጎ ነው። "ያህዌ ሆይ፣ እውነትህን አስተምረኝ። ይህ ሲሆን የተናገርከውን እታዘዛለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አንተን አከብር ዘንድ ልቤን አንድ አድርገው/ያልተከፋፈለ ልብ ስጠኝ
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚወክለው የአንድን ሰው ሀሳብ፣ ስሜት እና ሰበበ ምክንያት ነው። አንድ ሰው እርሱን በሙሉ ልቡ እንዲያከብር እግዚአብሔርን መጠየቅ የተገለጸው፣ የዚያ ሰው ልብ የተከፋፈለ እንደነበረ እና እግዚአብሔር እነዚያን ክፍልፋዮች እንደሚገጣጥማቸው ተደርጎ ነው። "በሙሉ ልቤ በቅንነት አንተን እንዳከብር አድርገኝ" ወይም "በቅንነት አንተን እንዳከብር አድርግ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ))

እኔ ስምህን አከብራለሁ
እዚህ ስፍራ "ስም" የሚወክለው መላ ማንነትን ነው። "እኔ አከብርሃለሁ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 86:13

አንተ ለእኔ ያለህ የቃልኪዳን ታማኝነት ታላቅ ስለሆነ
"ታማኝነት" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል መልክ ሊገለጽ ይችላል። "ከቃል ኪዳንህ የተነሳ አንተ ለእኔ በጣም ታማኝ ነህና" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለፍሴን ከሲኦል ጥልቅ አዳንካት
ይህ ማለት እርሱ ከሞተ በኋላ እግዚአብሔር ዳግም ወደ ህይወት መለሰው ማለት አይደለም። ሊሞት ከተቃረበበት እግዚአብሔር እርሱን አዳነው ማለት ነው።

እብሪተኛ
ይህ ስማዊ ቅጽል እንደ ቅጽል ሆኖ ሊገለጽ ይችላል። "እብሪተኛ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)

በእኔ ላይ ተነስተውብኛል
"እኔን ለመጉዳት በአንድነት እየመጡ ነው"

ነፍሴን ፈለጓት
ሊገድሉኝ ፈለጉ የሚለው የተገለጸበት መንገድ ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 86:15

በቃል ኪዳን ታማኝነት እና በታማኝነት የተትረፈረፈ
የእግዚአብሔር የማያቋርጥ ታማኝነት እና መታመን የተገለጸው ታማኝነት እና መታመን እግዚአብሔር በብዙ መጠን ያለው ቁሳዊ ነገር ተደርጎ ነው። ሁለቱ ረቂቅ ስሞች እንደ ቅጽል ሊተረጎሙ ይችላሉ። "ሁሌም ለቃል ኪዳንህ ታማኝ ደግሞም ሰዎች አንተን ለመታመን በጣም የተገባህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

ወደ እኔ ዘወር በል
እርሱን እንዲመለከት እግዚአብሔርን መጠየቅ የተገለጸው እግዚአብሔር ወደ እርሱ ዘወር ብሎ ሊመለከተው እንደሚፈልግ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ብርታትህን ለአገልጋይህ ስጥ
"ብርታት" የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ወይም እንደ ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። "አገልጋይህን አበርታው" ወይም "አገልጋይህን ጠንካራ አድርገው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ አገልጋይ...የሴት አጋልጋይህ ወንድ ልጅ
ጸሐፊው በሶስተኛ መደብ የሚናገረው ስለ እራሱ ነው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ይፈሩ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እነርሱ ይፈሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 87

1 እግዚአብሔር ከተማውን፣ በተቀደሰው ተራራ ላይ መሠረተ **2** ያህዌ የጽዮንን ደጆች ከያዕቆብ መኖሪያዎች ይበልጥ ይወዳል። **3** የእግዚአብሔር ከተማ ሆይ፣ ስለ አንቺ አስደናቂ ነገሮች ተነግረዋል። ሴላ **4** ከሚያውቁኝ መካከል ረዓብንና ባቢሎንን እጠቅሳለሁ፤ እነሆ ፍልስጥኤምና ጢሮስ ከኢትዮጵያ ጋር ሆነው፣ «ይህ ሰው የተወለደው በዚያ ነው› ይላሉ። **5** ስለ ጽዮን ግን፣ ልዑል እግዚአብሔር ራሱ ስለሚመሠርታት፣ «እነዚህ ሁሉ የተወለዱ እዚያ ነው» ይላሉ። **6** ያህዌ ሕዝቦችን ሲመሠርት «ይህ ሰው የተወለደው በዚያ ነው» ብሎ ይጽፋል። **7** ዘማሪዎችና መሣሪያ ተጫዋቾችም፣ «ምንጩ ሁሉ አንቺ ውስጥ ይገኛል» ይላሉ።

Psalms 87:1

አጠቃላይ መረጃ:
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነግጥም እና ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

የቆሬ ልጆች ዝማሬ፣ ዝማሬ
"ይህ የቆሬ ልጆች የጻፉት ዝማሬ ነው"

የጽዮን በሮች
እዚህ ስፍራ "የጽዮን በሮች" የሚለው የሚወክለው መላዋን የእየሩሳሌም ከተማ ነው። "የኢየሩሳሌም ከተማ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

መላው የያዕቆብ ድንኳኖች
በበረሃ በሚንከራተቱበት ወቅት በድንኳኖች የኖሩ ሰዎች። እዚህ ስፍራ ጸሐፊው "የያዕቆብ ድንኳኖች" የሚለውን የተጠቀመበት እስራኤላውያን አሁን የሚኖሩነትን ለመግለጽ ነው። "ማናቸውም አሁን እስራኤላውያን የሚገኙባቸው ሌሎች የመኖሪያ ስፍራዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ከተማ ሆይ፣ ስለ አንቺ አስደናቂ ነገሮች ተነግረዋል
ጸሐፊው ለእየሩሳሌም ከተማ እርሱን እንደምትሰማው አድርጎ ይናገራል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እናንተ በእየሩሳሌም የምትኖሩ ሰዎች ሆይ፣ ሌሎች ሰዎች ስለ እናንተ ከተማ አስደናቂ ነገሮችን ይናገራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አጋኖ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ሴላ
ይህ ሰዎች የሙዚቃ መሳሪያቸውን እዚህ እንዴት እንደሚያዜሙበት ወይም እንደሚጫወቱበት የሚያሳይ ሙዚቃዊ ስያሜ ነው። አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል እንዳለ ይጠቀሙበታል፣ አንዳንድ ትርጉሞች ይተዉታል። ይህ በመዝሙር 3:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ቅጂ/እንዳለ መገልበጥ/ ወይም ቃላትን መዋስ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 87:4

እኔ እጠቅሳለሁ
"እኔ ስለዚህ ተናገርኩ።" እዚህ ስፍራ "እኔ" የሚለው የሚያመለክተው ያህዌን ነው።

ረዓብ እና ባቢሎን
እዚህ ስፍራ "ረዓብ" ግብጽ የተጠቀሰችበት ስነግጥማዊ መንገድ ነው። "ረዓብ" እና "ባቢሎን" ሁለቱም ህዝቡን ይወክላሉ፤ "የግብጽ እና የባቢሎን ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚሉትን ይመልከቱ)

ለእኔ ተከታዮች
"እኔን ለሚያመልኩኝ"

ፍልስጤም፣ እና ጢሮስ፣ ከኩሽ ጋር
የእነዚህ አገራት ስሞች ህዝብን ይወክላል። ከፍልስጤም እና ጢሮስ እንዲሁም ከኩሽ ከመጣው ህዝብ ጋር"

ይህኛው የተወለደው በዚያ ነበር
"ይህኛው" የሚለው የሚያመለክተው ጸሐፊው ከጠቀሳቸው አገሮች የሆኑ ሰዎችን ነው። ምንም እንኳ እነርሱ በአካል በጽዮን ባይወለዱም፣ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ በመንፈስ የእየሩሳሌም ተወላጆች ናቸው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 87:5

የጽዮን የሆኑ ይባላል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች ስለ ጽዮን ይናገራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ እያንዳንዳቸው የተወለዱት በዚህ ነበር
ያህዌን የሚያመልኩ ከሌሎች አገራት የመጡ ሰዎች በእየሩሳሌም እንደ ተወለዱ ተደርጎ ይነገራል። "ይህም እነዚህ ሁሉ ሰዎች በእየሩሳሌም እንደተወለዱ ይቆጠራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በ እርሷ
ከተሞችን "እርሷ" ብሎ መጥራት የተለመደ ነበር። "በእየሩሳሌም" ወይም "በጽዮን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ከሁሉም ከፍ ያለው /ልዑሉ ራሱ
ጸሐፊው "እርሱ ራሱ" የሚለውን ደጋጋሚ ተውላጠ ስም የተጠቀመው ይህንን ያደረገው ልዑሉ ራሱ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። (ደጋጋሚ ተውላጠ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እርሷን ያጸናታል
"እየሩሳሌምን ጠንካራ ያደርጋታል"

ያህዌ በአገራት የህዝብ ቆጠራ መጽሐፍ ላይ ሲጽፍ
ያህዌ የሌላ አገር ሰዎችም የእርሱ እንደሆኑ እውቅና መስጠቱ የተገለጸው፣ በእርሱ ከተማ የሚኖሩ ሰዎችን ስሞች እንደጻፈ ንጉሥ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህኛው የተወለደው እዚህ ነበር
"ይህኛው" የሚለው የሚያመለክተው ጸሐፊው ከጠቀሳቸው አገራት የሆኑ ሰዎችን ነው። ምንም እንኳን በአካል በጽዮን ባይወለዱም፣ እግዚአብሔርን የሚከተሉ/የሚያመልኩ በመንፈስ የእየሩሳሌም ተወላጆች ናቸው። ይህ በመዝሙር 87:4 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 87:7

፯፮፰ዎቼ ሁሉ በአንቺ ውስጥ ይገኛሉ
እየሩሳሌም ሰዎች በረከቶቻቸውን ሁሉ የሚቀበሉባት ስፍራ መሆኗ
የተገለጸው፣ እየሩሳሌም ለህዝቡ ውሃ የምታቀርብ ምንጭ እንደሆነች ተደርጎ
ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 88

1 አዳኜ ያህዌ አምላክ ሆይ፤ ቀንና ሌሊት በፊትህ እጮኻለሁ። **2** እባክህ ጸሎቴን ስማ፤ ጩኸቴንም አድምጥ። **3** በመከራ ተሞልቻለሁና ነፍሴም ወደ ሲኦል ተቃርባለች። **4** ወደ መቃብር ከሚወርዱ ጋር ተቆጥሬአለሁ፤ ዐቅም አጣሁ። **5** በሙታን መካከል ፈጽሞ እንደ ተተዉ ሞተው መቃብር ውስጥ እንደ ተጋደሙ ከእንግዲህ ፈጽሞ እንደማታስታውሳቸውና ከእጅህ ወጥተው እንደ ተወገዱ ሆንሁ። **6** ጥልቁ አዘቅት ውስጥ ጣልኸኝ ጨለማ ጉድጓድ ውስጥ ከተትኸኝ። **7** ቁጣህ እጅግ ከብዶኛል ማዕበልህም ሁሉ አጥለቅልቆኛል። **8** ወዳጆቼን ሁሉ ከእኔ አራቅህ እንዲጸየፉኝም አደረግህ ዙሪያውን ተከብቤአለሁና ማምለጥ አልችልም። **9** ዐይኖቼ በሐዘን ፈዘዙ ያህዌ ሆይ፣ ቀኑን ሙሉ ወደ አንተ እጮኻለሁ እጆቼን ወደ አንተ ዘረጋሁ። **10** ለሙታን ተአምራት ታደርጋለህን? የሞቱትስ ተነሥተው ያመሰግኑሃልን? ሴላ **11** ምሕረትህ መቃብር ውስጥ ታማኝነትህስ በሙታን ዓለም ይነገራልን? **12** ድንቅ ሥራህ በጨለማ ስፍራ ጽድቅህስ በመረሳት ምድር ትቃወቃለችን? **13** ያህዌ ሆይ፣ እኔ ግን ወደ አንተ እጮኻለሁ በጧትም ጸሎቴን ወደ ፊት አቀርባለሁ። **14** ያህዌ ሆይ፣ ለምን ትተወኛለህ? ፊትህንስ ከእኔ ለምን ትሰውራለህ? **15** ከልጅነቴ ጀምሮ ችግረኛና ሞት አፋፍ ላይ ያለሁ ሰው ነበርሁ፤ ከማስደንገጥህ የተነሣ ተስፋ ቆርጫለሁ። **16** ቁጣህ እኔ ላይ ተከነበለ መዓትህም አጠፋኝ። **17** ቀኑን ሙሉ እንደ ጐርፍ ከበቡኝ ዙሪያውን አጥረው ያዙኝ። **18** ወዳጆቼንና የሚቀርቡኝን ሰዎች ሁሉ ከእኔ አራቅህ ጓደኛዬ ጨለማ ብቻ ሆኖ ቀረ።

Psalms 88:1

አጠቃላይ መረጃ:
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነግጥም እና ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ዝማሬ፣ የቆሬ ልጆች ዝማሬ
"ይህ የቆሬ ልጆች የጻፉት ዝማሬ ነው"

ለመዘምራን አለቃ
"ይህ በመዘምራን አለቃ ለአምልኮ የሚዜም ነው"

በማሕሌት የሚዘመር
ይህ የዝማሬ አይነትን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። (ቅጂ/እንዳለ መገልበጥ/ ወይም ቃላትን መዋስ የሚለውን ይመልከቱ)

ማኸላት
ይህ የዝማሬ አይነትን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። ይህ በመዝሙር 32፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ኤማን
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ይዝራኤላዊ
ይህ የህዝብ ወገን ስም ነው። የዛራን ወንድ ልጅ ወይም ትውልድ ያመለክታል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የደህንነቴ አምላክ
"ደህንነት" የሚለው ረቂቅ ስም በግስ መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ያዳንከኝ አንተ ነህ/አንተ አዳንከኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ቀንና ሌሊት
ጸሐፊው እነዚህን ተቃራኒ ትርጉሞች ያላቸው ቃላት የተጠቀመው ያለማቋረጥ እንደሚጮህ ለመናገር ነው። (ከጽንፍ ጽንፍ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 88:3

እኔ በመከራ ተሞልቻለሁና
ጸሐፊው ስለ እራሱ፣ እርሱ ዕቃ መያዣ እንደሆነ እና ችግር ደግሞ መያዣውን እንደሞላ ይዘት አድርጎ ይናገራል። "እኔ በጣም ተጨንቄያለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእኔ ህይወት ሲኦል ደረሰች
እዚህ ስፍራ "ህይወት" የሚወክለው ጸሐፊውን ነው። "ሲኦል" ደግሞ ሞትን ይወክላል። ጸሐፊው ስለ እራሱ ምናልባትም በቶሎ እንደሚሞት እና ሲኦል መድረሻ ስፍራው ሆኖ በዚያ እንደሚደርስ ይናገራል። "ልሞት ተቃርቤያለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ሰዎች እኔን የቆጠሩት ወደ ጉድጓድ እንደወረዱት አድርገው ነው
"ጉድጓድ" የሚለው ቃል "ሲኦል" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው። "ወደ ሲኦል መውረድ" የሚለው ሀረግ የሚወክለው መሞትን ነው። "ሰዎች የሞትኩ አድርገው ቆጠሩኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 88:5

በሞቱት መሃል ተተውኩ
ሰዎች ጸሐፊውን የሞተ አድርገው እንደቆጠሩት የተገለጸው ሳይቀበር እንደተጣለ በድን ነው። "የሞትኩ ያህል ብቻዬን ተተውኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በመቃብር እንደተጋደመ ሬሳ ነኝ
ጸሐፊው ሰዎች እና እግዚአብሔርም እንደተዉት የተሰማው ስሜት የተገለጸበት ሁኔታ ልክ ሞቶ በመቃብር እንደ ተጋደመ ሰው ነው።

ሞተው የተጋደሙ
"ሙታን" የሚለው ስማዊ ቅጽል እንደ ቅጽል ለገለጽ ይችላል። "ሞቶ የተጋደመ ሰው" ወይም "ሞተው የተጋደሙ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ከአንተ ሀይል ተቆርጠዋል/ጠፍተዋል
የእግዚአብሔር ሀይል ከእንግዲህ የሞቱ ሰዎችን እንደ ማይረዳቸው የተገለጸው፣ እግዚአብሔር እርሱን ቆርጦ እንደጣለው ወይም ከእርሱ ሀይል እንዳስወገደው ተደርጎ ነው። "ከእንግዲህ አነርሱን ለመርዳት ሀይልህን አትጠቀምም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ በጉድጓዱ ታችኛው ስፍራ፣ በጨለማውን እና በጥልቁ አስቀመጥከኝ
ጸሐፊው እግዚአብሔር እርሱን እንደ ተወው የተሰማውን ስሜት የገለጸው፣ እግዚአብሔር እርሱን በጥልቅ እና ጨለማ መቃብር ውስጥ እንዳስቀመጠው አድርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 88:7

ቁጣህ በላዬ በእጅጉ ወደቀ
ይህ የሚናገረው እግዚአብሔር በጸሐፊው ላይ በጣም እንደተቆጣ ሲሆን፣ የእግዚአብሔር ቁጣ ልክ እንደ ከባድ ቁስ ሆኖ በላዩ ላይ እንደወደቀበት አድርጎ ይገልጻል። "ታላቁ ቁጣህ ተሰማኝ" ወይም "አንተ በእኔ ላይ እንዴት በጣም እንደተቆጣህ ተሰማኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ማዕበልህ ሁሉ ሰባብሮኛል
ይህ እግዚአብሔር በጸሐፊው በጣም መቆጣቱን የሚገልጸው የእግዚአብሔር ቁጣ ከባህር የሚነሳ ትልቅ ማዕበል ሆኖ በእርሱ ላይ እንዳረፈበት አድርጎ ነው።

ሴላ
ይህ ሰዎች የሙዚቃ መሳሪያቸውን እዚህ እንዴት እንደሚያዜሙበት ወይም እንደሚጫወቱበት የሚያሳይ ሙዚቃዊ ስያሜ ነው። አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል እንዳለ ይጠቀሙበታል፣ አንዳንድ ትርጉሞች ይተዉታል። ይህ በመዝሙር 3:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ቅጂ/እንዳለ መገልበጥ/ ወይም ቃላትን መዋስ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 88:8

የቅርብ ወዳጆቼ
"እኔን የሚያውቁኝ እነርሱ"

ለእነርሱ ማስፈራሪያ አደረግከኝ
"ለዐይናቸው የሚጸየፉኝ አደረግከኝ" ወይም "ከአንተ ከደረሰብኝ ነገር የተነሳ፣ ሲመለከቱኝ ድንጋጤ ወደቀባቸው"

እኔ ተከብቤያለሁ
ጸሐፊው በጓደኞቹ ዘንድ ተቀባይነት ያሳጣው አካላዊ ሁኔታ የተገለጸው በተጣበበ ስፍራ እንደተቆለፈበት ሆኖ ነው። "በእስር ቤት ውስጥ እንዳለ ሰው ሆንኩ" ወይም "በወጥመድ ተያዝኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 88:9

ዐይኖቼ ከመከራ የተነሳ ደከሙ
እዚህ ስፍራ "ዐይኖች" የሚለው የሚወክለው የሰውን የማየት አቅም ነው። ዐይኖቹ ከመከራ የተነሳ መድከማቸው፣ የደረሰበት መከራ ብዙ እንዲያነባ እንዳደረገውና ከዚህም የተነሳ ማየት እንደከበደው የተገለጸበት መንገድ ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

እጆቼን ወደ አንተ ዘረጋሁ
"እጆቼን ወደ አንተ አነሳሁ።" ይህ እርሱ ሙሉ ለሙሉ በእግዚአብሔር ላይ መደገፉን የሚያሳይ ድርጊት ነው። (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት)

አንተ ለሙታን አስደናቂ ነገርን ታደርጋለህን?
ጸሐፊው ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት፣ እግዚአብሔር እርሱን ይሞት ዘንድ ቢተወው ከዚያ በኋላ ለእርሱ አስደናቂ ነገሮችን ለማድረግ እንደማይችል ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። "ለሙታን አስደናቂ ነገሮችን አታደርግም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የሞቱ ተነስተው ያመሰግኑሃልን?
ጸሐፊው ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት፣ እግዚአብሔር እርሱን ይሞት ዘንድ ቢተወው ከዚያ በኋላ ተነስቶ ሊያመሰግነው እንደማይችል ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው።(ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 88:11

የቃል ኪዳንህ ታማኝነት በመቃብር ፣ ወይንስ ታማኝነትህ በሙታን ስፍራ ይታወጃል?
ሁለቱም ጥያቄዎች ተመሳሳይ ነገርን ይገልጻሉ። ጸሐፊው ጥያቄዎቹን የተጠቀመባቸው የሞተ ሰው የእግዚአብሔርን ታማኝነት ማወደስ እንደማይችል ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። "ታማኝነት" እና "ትክክለኛነት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች በቅጽል መልካቸው ሊተረጎሙ ይችላሉ። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ማንም የቃል ኪዳንህን ታማኝነት እና ትክክለኛነት ከመቃብር ሊያውጅ/ሊናገር አይችልም።" ወይም "ማንም ከመቃብር ሆኖ አንተ ለቃል ኪዳንህ ወይም ለትክክለኛነትህ ታማኝ መሆንህን ለህዝብህ መናገር አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ቃለምልልሳዊ ጥያቄ እንዳሁም አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

መቃብር... የሙታን ስፍራ...በጨለማ...የመረሳ ስፍራ
እነዚህ ሁሉ ሰዎች ከሞቱ በኋላ የሚሄዱበትን ስፍራ ይወክላሉ።

በሙታን ስፍራ የአንተ ታማኝነት አለን?
ይህ የተለየ ዐረፍተ ነገር ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። "ታማኝነትህ በሙታን ስፍራ ሊታወጅ ይችላልን?" ወይም "ሙታን የአንተን ታማኝነት ሊናገሩ አይችሉም።" (የተተወ/የተዘለለ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

አስደናቂ ስራዎችህ በጨለማ ፣ ወይስ ጽድቅህ በመረሳት ስፍራ ይታወቀልን?
ሁለቱም ጥያቄዎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ጸሐፊው ጥያቄዎቹን የተጠቀመባቸው ሙታን የእግዚአብሔርን ስራ ታላቅነት ለመግለጽ ወይም ለማወጅ እንደማይችሉ ትኩረት ሰጥቶ ለመናገር ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች ስለ አንተ አስደናቂ ስራዎች እና ጽድቅ፣ በተረሱ/በተዘነጉት ሙታን መሃል አይናገሩም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች እንዲሁም አድራጊ ወይም ተደራጊ በሚሉት ውስጥ ይመልከቱ)

ወይስ ጽድቅህን በዝንጉነት ስፍራ ይናገራሉን?
ይህ የተለየ ዐረፍተ ነገር ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። "ጽድቅህ በዝንጉነት ስፍራ ይታወቃልን?" ወይም "በመረሳት ስፍራ የሚገኙ አንተ ስላደረግካቸው የጽድቅ ስራዎች አያውቁም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች በሚሉት ውስጥ ይመልከቱ)

Psalms 88:13

ጸሎቴ በፊትህ ይምጣ
ጸሐፊው ወደ ያህዌ የሚያደርሰው ጸሎት የተገለጸው ጸሎቱ ራሱ ከያህዌ ጋር ለመነጋገር እንደሚሄድ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለምን ፊትህን ከእኔ ትደብቃለህ?
ይህ የሚናገረው ጸሐፊው እግዚአብሔር እንደተወው ወይም እንዳልተቀበለው የተሰማውን ስሜት ሲሆን፣ እግዚአብሔር ፊቱን እንደደበቀበት ወይም ከጸሐፊው በአካል ፊቱን እንዳዞረ ተደርጎ ተገልጽዋል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 88:15

የአንተ የቁጣ ድርጊቶች በላዬ አለፉ
ይህ እግዚአብሔር ጸሐፊውን መቅጣቱን፣ የእግዚአብሔር ቅጣት ከባህር እንደሚነሳ እና በጸሐፊው ላይ ወድቆ እንደሚያፈራርስ ታላቅ ማዕበል ተደርጎ ተገልጽዋል። "ይህ የአንተ የቁጣ ድርጊቶች እኔን እንዳጠፋኝ ያህል ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ አስፈራ ድርጊቶች ራሴን አሳተኝ/አጠፋኝ
ይህ ግነት የሚናገረው እግዚአብሔር ጸሐፊውን የቀጣው ሙሉ ለሙሉ እንደሆነ አድረሰጎ ነው። "አንተ ያደረግካቸው አስፈሪ ነገሮች እኔን አጠፉኝ" ወይም "አንተ ያደረግካቸው አስፈራ ድርጊቶች እኔን አጠፉኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ግነት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 88:17

ቀኑን በሙሉ እንደ ውሃ ከበቡኝ
ጸሐፊው የእግዚአብሔርን ቁጣ ከውሃ ፈሳሽ/ጎርፍ "የቁጣ ድርጊት" እና "አስፈሪ ድርጊቶች" ጋር ያነጻጽራል። "እነርሱ ቀኑን በሙሉ ጎርፍ እንደሚያጠፋ ሊያጠፉኝ ያስፈራሩኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ
"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከቀደመው ቁጥር የእግዚአብሔርን "የቁጣ ድርጊቶች" እና "አስደንጋጭ ስራዎች" ነው።

እነርሱ ሁሉ እኔን ከበቡኝ
ጸሐፊው የእግዚአብሔርን "የቁጣ ድርጊቶች" እና "አስፈራ ተግባራት" የሚገልጸው እርሱን ለመያዝ እና ለመግደል እንደሚሞክሩ ጠላቶች አድርጎ ነው። "እነርሱ እንደ ጠላት ወታደሮች ከበቡኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እያንዳንዱ ወዳጅ እና የቅርብ ሰው
"እያንዳንዱ እኔ የምወደው እና የማውቀው ሰው"

ብቸኛው ወዳጄ ጨለማ ነው
ይህ ስለ ጨለማ የሚናገረው፣ ጨለማ ሰው እንደሆነ እና ከሌላ ሰው ጋር ጓደኛ ሊሆን እንደሚችል ነገር አድርጎ ነው። ጸሐፊው ሙሉ ለሙሉ ብቸኝነት እንደተሰማው ትኩረት ይሰጣል። "በደረስኩበት ሁሉ ጨለማ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 89

1 ስለ ያህዌ ምሕረት ለዘላለሙ እዘምራለሁ። ታማኝነትህንም ለሚመጣው ትውልድ እናገራለሁ። **2** ምሕረትህን ለዘላለም እንደምትመሠርት ታማኝነትህንም
በሰማያት እንደምታጸና እናገራለሁና **3** አንተም እንዲህ ብለሃል፣ «ከመረጥሁት ጋር ኪዳን አድርጌአለሁ፤ ለባርያዬ ለዳዊት ምዬአለሁ። **4** ዘርህን ለዘላለም
አተክላለሁ ዙፋንህንም በትውልድ ዘመን ሁሉ አጸናለሁ።» ሴላ **5** ያህዌ ሆይ፣ ሰማያት ድንቅ ሥራህን ያመሰግናሉ ጽድቅህም በቅዱሳን ጉባኤ ይወደሳል። **6**
በላይ በሰማያት ከያህዌ ጋር ማን ሊስተካከል ይችላል? ከአማልክት ልጆችስ መካከል እንደ ያህዌ ያለ ማን ነው? **7** እርሱ በቅዱሳኑ ጉባኤ መካከል እጅግ
የተፈራ ነው፤ በዙሪያው ካሉትም ሁሉ ታላቅና አስፈሪ ነው። **8** የሰራዊት ጌታ ያህዌ ሆይ፣ እንደ አንተ ያለ ኃያል ማነው? ታማኝነትህም ከቦሃል። **9** የባሕሩን ቁጣ
በሥልጣንህ ታዝዛለህ ማዕበሉንም ጸጥ ታደርጋለህ። **10** አንተ ረዓብን ቀጥቅጠህ ገደልኸው በታላቁ ኃይልህ ጠላቶችህን በተንሃቸው። **11** ሰማያት የአንተ
ናቸው ምድርም የአንተ ናት። አንተ ዓለምንና በውስጧ ያሉትን ሁሉ ፈጠርህ። **12** ሰሜኑን ደቡቡንም አንተ ፈጠርህ ታቦርና አርሞንዔም በስምህ ደስ ይላቸዋል።
13 አንተ ክንደ ብርቱ ነህ እጅህ ኃያል ናት፤ ቀኝ እጅህም ከፍ ከፍ ያለች ናት። **14** ጽድቅና ፍትሕ የዙፋንህ መሠረት ናቸው ምሕረትና ታማኝነት በፊት ይሄዳሉ።
15 ያህዌ ሆይ፣ በፊት ብርሃን የሚሄድ አንተንም የሚያመልክ ሕዝብ ቡሩክ ነው። **16** ቀኑን ሙሉ በስምህ ደስ ይላቸዋል በጽድቅህም ከፍ ከፍ ይላሉ። **17**
ገናናው ኃይልህ ብርታት ይሰጣቸዋል በሞገስህም ድል ተቀዳጀን። **18** ጋሻችን የያህዌ ነው ንጉሣችንም የራሱ የእስራኤል ቅዱስ ነውና። **19** ከረጅም ጊዜ በፊት
በራእይ ለሕዝብህ ተናገርህ እንዲህም አልህ፤ «ኃያሉን ሰው ሥልጣን አጐናጸፍሁ፤ ከሕዝብ መካከል እኔ የመረጥሁትን አስነሣሁ። **20** ባርያዬ ዳዊትን
መረጥሁት በተቀደሰው ዘይቴም ቀባሁት **21** እጄ ይደግፈዋል ክንዴም ያበረታዋል። **22** ጠላት አይረታውም ክፉ ሰውም አያሸንፈውም። **23** ጠላቶቹን በፊቱ
አደቃለሁ፤ ባላንጣዎቹንም እገድላለሁ። **24** እውነቴና ታማኝነቴ ከእርሱ ጋር ይሆናል በስሜ ድል ይቀዳጃል። **25** እጁን በባሕሮች ቀኝ እጁንም በወንዞች ላይ
አደርጋለሁ። **26** እርሱም፣ «አንተ አባቴ፣ አምላኬ የድነቴም ዐለት» ብሎ ይጠራኛል። **27** እኔም ደግሞ በኩሬ አደርገዋለሁ ከምድር ነገሥታትም ሁሉ በላይ ከፍ
ይላል። **28** ምሕረቴንም ለዘላለም ለእርሱ እዘረጋለሁ ለእርሱ ጋር ያደረግሁትም ኪዳን ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል። **29** የዘር ሐረጉን ለዘላለም ዙፋኑንም በሰማያት
ዕድሜ ልክ አጸናለሁ **30** ልጆቹ ሕጌን ቢተው፣ ሥርዐቴን ባይጠብቁ፣ **31** ደንቤን ቢተላለፉ፣ ትእዛዞቼ ባያከብሩ፣ **32** ኃጢአታቸውን በበትር፣ በደላቸውንም
በአለንጋ እቀጣለሁ። **33** ለእርሱ ያለኝ ፍቅር ግን አይቋረጥም ታማኝነቴንም አላጓድልበትም። **34** ኪዳኔን አላፈርስም ከአፌ የወጣውን አላጥፍም። **35** አንዴ
በቅድስናዬ ምያለሁና ለዳዊት አልዋሸም። **36** ልጆቹ ለዘላለም ዙፋኑም በፀሐይ ዕድሜ ልክ ጸንቶ ይኖራል። **37** በሰማይ ታማኝ ምስክር ሆና እንደምትኖረው
እንደ ጨረቃ እርሱም ለዘላለም ይመሠረታል። ሴላ **38** አሁን ግን ናቅኸው፤ ጣልኸውም በቀባኸውም ንጉሥ ላይ ተቆጣህ። **39** ለባርያህ የገባኸውን ኪዳን
አፈረስህ የክብር ዘውዱን መሬት ላይ ጣልህ። **40** ቅጥሮቹን ሁሉ አፈረስህ ምሽጉንም ደመሰስህ። **41** ዐላፊ አግዳሚ ሁሉ ዘረፈው ለጐረቤቶቹም መዘባበቻ
ሆነ። **42** የጠላቶቹን ቀኝ እጅ ከፍ አደረግህ ባላንጣዎቹም ሁሉ ደስ አላቸው። **43** የሰይፉን ስለት አጠፍህ በጦርነትም ጊዜ አልረዳኸውም። **44** የክብሩን
ውበት አጠፋህበት ዙፋኑንም መሬት ላይ ጣልህበት። **45** የወጣትነት ዘመኑን አሳጠርኸው ዕፍረትንም አከናነብኸው። **46** ያህዌ ሆይ፣ ይህ እስከ መቼ ነው?
ራስህንስ ለዘላለም ትሰውራለህን? ቁጣህስ እንደ እሳት የሚነደው እስከ መቼ ነው? **47** ዕድሜዬ ምን ያህል አጭር እንደ ሆነ አስብ፤ የሰውን ልጆች እንዲሁ
ለከንቱ ፈጠርሃቸው! **48** ሞትን ሳያይ ሕያው ሆኖ የሚኖር ማን ነው? ሕይወቱን ከሲኦል እጅ ማዳን የሚችል ማነው? ሴላ **49** ጌታ ሆይ፣ በታማኝነትህ ለዳዊት
የማልህለት የቀድሞ ምሕረትህ የታለ? **50** ጌታ ሆይ፣ ባርያህ ላይ የደረሰውን ፌዝ የብዙ ሰዎችንም ስድብ እንደ ታቀፍሁ አስብ። **51** ያህዌ ሆይ፣ ጠላቶችህ
የሚሳደቡትን፣ አንተ የቀባኸውን ሰው ርምጃ የነቀፉበትን ሁኔታ አስብ። **52** ያህዌ ለዘላለም ይባረክ። አሜን፣ አሜን

Psalms 89:1

አጠቃላይ መረጃ:
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነግጥም እና ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ማሸል
ይህ የዝማሬ ስልትን ሊያመለክት ይችላል። ይህ በመዝሙር 32:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ኤታን
ይህ የጸሐፊው ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ይዝራኤላዊው
ይህ የአንድ ወገን ህዝብ ስያሜ ነው። ይህ አንድን ወንድ ልጅ ወይም የየዛራን ትውልድ ሊያመለክት ይችላል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የቃል ኪዳን ታማኝነት ድርጊቶች
"ታማኝነት" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል መልክ ሊገለጽ ይችላል። "ታማኝ ድርጊቶች" ወይም "ተወዳጅ ድርጊቶች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የቃል ኪዳን ታማኝነት ለዘለዓለም ተመስርቷል
እግዚአብሔር ሁሌጊዜም ሊያደርግ ቃል የገባውን ማድረጉ የተገለጸው ታማኝነቱ እርሱ የገነባው እና ያጠነከረው/ያቆመው ህንጻ ተደርጎ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ከእኛ ጋር ቃል ኪዳን የተነሳ አንተ ሁልጊዜም ታማኝ ትሆናለህ" (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

አንተ እውነተኛነትህን በሰማያት መሰረትህ
እግዚአብሔር ሁሌጊዜም ሊያደርግ ቃል የገባውን ማድረጉ የተገለጸው ታማኝነቱ እርሱ የገነባው እና ያጠነከረው/ያቆመው ህንጻ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በሰማት
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ የእግዚአብሔርን መኖሪያ ስፍራ ያመለክታል። ይህ ማለት እግዚአብሔር በሰማይ ሆኖ ይገዛል፣ ደግሞም እርሱ ሁልጊዜም ቃል የገባውን ያደርጋል፤ ወይም 2) ይህ ሰማይን ያመለክታል። ይህም ማለት የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን እንደ ሰማይ የጸና እና ቋሚ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 89:3

እኔ ከመረጥኩት ጋር ቃል ሊዳኔን አድርጌያለሁ
"የመረጥኩት " የሚለው ዳዊትን እንደሚያመለክት ግልጽ ማድረግ ይቻላል። "እኔ ለመረጥኩተ ለዳዊት ቃል ኪዳን ገብቻለሁ" በሚለው ውስጥ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ አድርጌያለሁ
ያህዌ በመዝሙር 89:3-4 ባለው ውስጥ ይናገራል።

እኔ ተውልድህን ለዘለዓለም አጸናለሁ
ያህዌ ሁልጊዜ ከዳዊት ተውልዶች አንዱን እንደሚያነግስ የተገለጸው የዳዊት ትውልዶች የሚያንጸው እና አጠንክሮ የሚያቆመው ህንጻ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በትውልዶች ሁሉ ዙፋንህን አጸናለሁ
እዚህ ስፍራ "ዙፋን" የሚወክለው እንደ ንጉሥ የመምራትን ሀይል ነው። መዝሙረኛው ከዳዊት ትውልዶች ውስጥ አንዱ ሁልጊዜ ንጉሥ እንደሚሆን እና እንደሚመራ የሚናገረው እግዚአብሔር የዳዊትን ዙፋን እንደሚመሰርት እና እንደሚያጸና አድርጎ ነው። "ከትውልዶች ውስጥ አንዱ በህዝቤ ላይ በየትውልዱ ንጉሥ ሆኖ እንደሚመራ አረጋግጣለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ሴላ
ይህ ሰዎች የሙዚቃ መሳሪያቸውን እዚህ እንዴት እንደሚያዜሙበት ወይም እንደሚጫወቱበት የሚያሳይ ሙዚቃዊ ስያሜ ነው። አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል እንዳለ ይጠቀሙበታል፣ አንዳንድ ትርጉሞች ይተዉታል። ይህ በመዝሙር 3:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ቅጂ/እንዳለ መገልበጥ/ ወይም ቃላትን መዋስ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 89:5

ሰማያት ያወድሳሉ
እዚህ ስፍራ "ሰማየት" የሚወክሉት በሰማይ ያሉትን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ ሆይ፣ አስደናቂ ስራዎችህን አወድሳለሁ
"ያህዌ ሆይ፣ ከሰራሃቸው አስደናቂ ስራዎች የተነሳ አወድስሃሁ"

ታማኝነትህ በቅዱሳን ጉባኤ ይወደሳል
"ታማኝነት" የሚለው ረቂቅ ስም "አንተ ሁሌጊዜም ለማድረግ ቃል የገባኸውን ታደርጋለህ።" ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገርም ሊጻፍ ይችላል። "የቅዱሳኑ ጉባኤ አንተን ያወዱስሃል ምክንያቱም አንተ ሁልጊዜም ለማድረግ ቃል የገባኸውን ታደርጋለህ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ ሚለውን ይመልከቱ)

የቅዱሳኑ ጉባኤ
ይህ በሰማይ ያሉትን መላዕክት ያመለክታል።

በሰማይ ማን ከያህዌ ጋር ሊነጻጸር ይችላል? ከአማልክት ልጆች ያህዌን ይመስላል?
ሁለቱም ጥያቄዎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ጸሐፊው ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው በሰማይ እንደ ያህዌ ያለ ማንም እንደሌለ ትኩረት ለመስጠት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ቃለምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

የአማልክት
እዚህ ስፍራ "የልጆች" ማለት የ...ባህሪይ ያለው ማለት ነው። ይህ በሰማይ የሚኖሩ ሌሎች መንፈሳዊ ፍጥረታትን የማመላከቻ መንገድ ነው። "መላዕክት" ወይም "መለኮታዊ ፍጥረታት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 89:7

እርሱ በቅዱሳኑ ምክርቤት እጅግ የተከበረ አምላክ ነው።
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የቅዱሳኑ ምክርቤት እግዚአብሔርን እጅግ ያከብራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የቅዱሳኑ ምክር ቤት
"የሰማያዊ ፍጥረታት ስብሰባ" ወይም "የመላዕክት ስብሰባ"

ያህዌ ሆይ፣ እንደ አንተ ሀያል ማን ነው?
ጸሐፊው ጥያቄውን ያነሳው እንደ ያህዌ ያለ ሀያል እንደሌለ ትኩረት ለመስጠት ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ታማኝነትህ ከቦሃል
ያህዌ ሁልጊዜም ለማድረግ ቃል የገባውን ማድረጉ የተገለጸው የእርሱ ታማኝነት ዙሪያውን እንደ ጠቀለለው ልብስ ወይም እንደ ካባው ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 89:9

አንተ የባህሩን ቁጣ ትገዛለህ
"አንተ የባህሩን ቁጣ ትቆጣጠራለህ"

ረዐብን እንደ ተገደለ ያህል ታደቀዋለህ
እዚህ ስፍራ "ረዐብ" የሚለው ቃል የባህርን አውሬ ያመለክታል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ እና ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚሉትን ይመልከቱ)

በብረቱ ክንዶችህ
እዚህ ስፍራ "ክንድ" የሚወክለው ሀይልን ነው። "በታላቁ ሀይልህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 89:11

ሰሜኑ እና ደቡቡ
ጸሐፊው "ሰሜን" እና "ደቡብ" የሚሉትን ቃላት በአንድነት የተጠቀመባቸው፣ እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ የሚገኙትን ሁሉንም ነገሮች ፈጥሯል ለማለት ነው። (ከጽንፍ ጽንፍ የሚለውን ይመልከቱ)

ታቦር እና አርሞንዔም በስምህ ደስ ይሰኛሉ
ታቦር ከገሊላ በስተ ደቡብ ምዕራብ የሚገኝ ተራራ ሲሆን አርሞንዔም ከገሊላ ባህር በሰሜን ምስራቅ የሚገኝ ተራራ ነው። ጸሐፊው እነዚህን ተራሮች የሚገልጸው ደስ መሰኘት እንደሚችሉ ሰዎች አድርጎ ነው። "ይህ የታቦር ተራራ እና የአርሞንዔም ተራራ በስምህ ደስ እንደተሰኙ ሆኖ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ እና ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚሉትን ይመልከቱ)

በስምህ
እዚህ ስፍራ "ስም" የሚወክለው ጠቅላላ ሰውነትን ነው። " በአንተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 89:13

አንተ ታላቅ ክንድ እና ጠንካራ እጅ አለህ፣ ደግሞም ቀኝ እጅህ ከፍ ያለ ነው
"ታላቅ ክንድ፣" "ጠንካር እጅ፣" እና "ቀኝ እጅ" የሚሉት ሁሉም የእግዚአብሔርን ሀይል ይወክላሉ። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ቀኝ እጅህ ከፍ ያለ ነው
ቀኝ እጅን ወደ ላይ ከፍ አድርጎ ማንሳት፣ ሀይልን የሚያሳይ ምልክት ። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጽድቅ እና ፍትህ የዙፋንህ መሰረቶች ናቸው
የእግዚአብሔር በንግሥናው መግዛት እና ትክክልና ተገቢ የሆነውን ማድረግ የተገለጸው፣ የእግዚአብሔር ዙፋን ግንብ እንደሆነ እና ጽድቅና ፍትህ መሰረቶቹ እንደሆኑ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ዙፋንህ
ዙፋኑ የእግዚአብሔርን እንደ ንጉሥ መግዛት ይወክላል። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የቃል ኪዳን ታማኝነት እና ታማኝነት ከፊትህ ይወጣሉ
እግዚአብሔር ሁልጊዜም ታማኝ መሆኑ እና ቃል የገባውን መፈጸሙ የተገለጸው የቃል ኪዳን ታማኝነት እና ታማኝነቱ መጥተው ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚገኙ ተደርጎ ነው። ረቂቅ የሆኑት ስሞች በቅጽል መልክ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "አንተ ሁልጊዜም ለቃል ኪዳንህ ታማኝ ነህ ደግሞም አንተን ላመኑህ ትበጃቸዋለህ" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 89:15

አንተን የሚያመልኩ
እዚህ ስፍራ "አምልኮ" የሚለው የሚያመለክተው መጮህን እና መለከት/ቀንዶችን መንፋትን ነው። ይህ በእስራኤላውያን ክብረ በዓል የተለመደ ድርጊት ነበር። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ይሄዳሉ/ይራመዳሉ
እዚህ ስፍራ የሰዎች ኑሮ የተገለጸው እንደሚሄዱ/እንደሚራመዱ ተደርጎ ነው። "ይኖራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በፊትህ ብርሃን
ጸሐፊው ያህዌ ለእነርሱ ሞገስን እንደሚሰጥ የገለጸው፣ የያህዌ ፊት በእነርሱ ላይ ብርሃንን እንደሚያበራ አድርጎ ነው። "በእነርሱ ላይ ሞገስህን እንደምታደርግ ይወቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በስምህ
እዚህ ስፍራ "ስም" የሚወክለው ጠቅላላ ሰውነትን ነው። " በአንተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በጽድቅህ አንተን ከፈ ከፍ ያደርጋሉ
"ጽድቅ" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል መልክ ሊገለጽ ይችላል። "አንተ ሁልጊዜም ትክክል የሆነውን ስለምታደርግ እነርዱ ከፈ ከፍ ያየርጉሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። "ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 89:17

አንተ የእነርሱ ባለ ግርማ ሞገስ ብርታታቸው ነህ
"ብርታት/ጥንካሬ" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል መልክ ሊገለጽ ይችላል። "እጅግ ብርቱ ታደርጋቸዋልህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ የእነሱ ነህ
እዚህ ስፍራ "የእነሱ" የሚለው የሚያመለክተው እስራኤላውያንን ነው። ጸሐፊው የእስራኤላውያን አባል አድርጎ አካቷል። "አንተ የእኛ ነህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ ድል አድራጊ ነን
እዚህ ስፍራ "እኛ" የሚለው የሚያመለክተው ጸሐፊውን እና እስራኤላውያንን ነው፤ ጸሐፊው የሚያናግረውን ያህዌን አይጨምርም። (የማያካትት እና አካታች "እኛ" የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌ የሆነ የእኛ ጋሻ
ህዝቡን የሚጠብቀው እና ያህዌ የመረጠው ንጉሥ የተገለጸው የያህዌ ጋሻ እንደሆነ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 89:19

አጠቃላይ መረጃ:
ጸሐፊው፣ አንባቢው እንዴት ዳዊት የተመረጠው ንጉሥ እንደሆነ ታሪኩን እንደሚያውቅ ይገምታል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ሀያል በሆነው ላይ ዘውድ አደርጌያለሁ/ጭኛለሁ
በአንድ ሰው ራስ ላይ ዘውድ መጫን ሰውየውን ንጉሥ የማድረግ ምልክት ነው። "ታላቁን ሰው አነግሰዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በቅዱሱ ቅባቴ እርሱን ቀባሁት
እዚህ ስፍራ በአንድ ሰው ራስ ላይ ዘይት ማፍሰስ እግዝአብሔር ያንን ሰው ንጉሥ እንዲሆን መሾሙን የሚያሳይ ምልክት ነው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

የእኔ እጅ እርሱን ይደግፈዋል፣ ክንዴም ያበረታዋል
እዚህ ስፍራ "እጅ" እና "ክንድ" የሚሉት ሁለቱም የያህዌ ሀይል እና ቁጥጥር ማለት ነው። "እኔ እደግፈዋለሁ ደግሞም አበረታዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

የክፋት ወንድ ልጅ
ጸሐፊው የክፋት ተፈጥሮ ወይም ባህሪይ ያላቸውን "የክፋት ወንዶች ልጆች" በማለት ይገልጻቸዋል። "ክፉ ሰው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 89:24

አያያዥ ሃሳብ:
ያህዌ ስለ ዳዊት መናገሩን ቀጥሏል።የእግዚአብሔር የዘላለም ታማኝነት እና ለዳዊት የገባውን እንደሚፈጽምለት የተገለጸው፣ እውነት እና ታማኝነት ከዳዊት ጋር እንደሚሆኑ አካለት ተደርገው ነው። "እውነት" እና "ታማኝነት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች በቅጽል መልክ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "እኔ ለእርሱ ሁልጊዜም ታማኝ እሆናለሁ ደግሞም ለእርሱ ሁሌም በታማኝነት እፈጽምለታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

በስሜ ድል ይጎናጸፋል
እዚህ ስፍራ "ስም" የሚለው የሚወክለው የእግዚአብሔርን ሀይል ነው። "እኔ፣ እግዚአብሔር፣ድል አጎናጽፈዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እጆችን ከባህሮች በላይ፣ ቀኝ እጁንም ከወንዞች በላይ አደርጋለሁ
እዚህ ስፍራ "እጅ" እና "ቀኝ እጅ" የሚሉት የሚወክሉት ሀይልን እና ስልጣንን ነው። "ባህሩ" ከእስራኤል በስተ ምዕራብ የሜድትራኒያን ባህርን የሚያመለክት ይመስላል፤ "ወንዞች" የሚለው በስተ ምስራቅ የሚገኘውን የኤፍራጥስ ወንዝ ያመለክታል። ይህ ማለት ዳዊት ከባህሩ እስከ ወንዙ ድረስ

ባለው ማናቸውንም ነገር ላይ ስልጣን ይኖረዋል ማለት ነው። "እኔ ለእርሱ ከሜድትራኒያን ባህር እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ ባለው ማናቸውም ነገር ላይ ስልጣን እሰጠዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ከጽንፍ ጽንፍ /ከዳር ስስከ ዳር/ የሚሉትን ይመልከቱ)

እርሱ፣ 'አምላኬ ሆይ፣ አንተ አባቴ ፣ የደህንነቴ አለት ነህ' ብሎ ወደ እኔ ይጣራል።
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ ይዟል። ቀጥተኛ ባልሆነ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል። "እርሱ እኔን፤ አባቴ፣ አምላኬ፣ እና የደህንነቴ አለት እንደሆንኩ ይናገራል።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ እንደዚሁም ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያለሆኑ ጥቅሶች የሚለውን ይመልከቱ)

የደህንነቴ አለት
ያህዌ ዳዊትን መጠበቁ እና ማዳኑ የተገለጸው፤ ያህዌ፣ ዳዊት ከጠላቶቹ ለመዳን በላዩ ሊቆምበት እንደሚችል ከፍ ያለ አለት ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 89:27

አያያዥ ሃሳብ፡
ያህዌ ስለ ዳዊት መናገሩን ቀጥሏል።

እንደ በኩር ልጄ አድርጌ አስቀምጠዋለሁ
ያህዌ ለዳዊት ልዩ ማዕረግ መስጠቱ እና ኬሌሎች ሰዎች በላይ ለእርሱ ጥበቃ ማድረጉ የተገለጸው፣ ዳዊት የያህዌ የበኩር ልጅ እንደሚሆን ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ ሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ለእርሱ የቃል ኪዳኔን ታማኝነት ለዘለዓለም እቀጥላለሁ
የያህዌ የቃል ኪዳን ታማኝነቱን ለዳዊት እንደሚቀጥል የገለጸው የያህዌ ቃል ኪዳን ታማኝነት እርሱ እንደሚያሰፋው ወይም እንደሚያራዝመው አካል ተደርጎ ነው። "ታማኝነት" የሚለው ረቂቅ ስም በተውሳከ ግስ መለኩ ሊተረጎም ይችላል። "እኔ ለእርሱ ያለኝን ታማኝነት ለዘለዓለም እቀጥላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

የእርሱ ዙፋን በላይ እንደሚገኘው ሰማይ የጸና ነው
ከዳዊት ቤት ንጉሥ እንደማይታጣ የተገለጸው የእርሱ ዙፋን ሰማይ ለዘለዓለም የጸና እንደሆነ ዙፋኑ ለዘለዓለም እንደሚኖር ተደርጎ ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ ዙፋን
እዚህ ስፍረ "ዙፋን" የሚወክለው እንደ ንጉሥ የመግዛት ሀይልን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 89:30

የእርሱ ልጆች
"የዳዊት ልጆች"

አመጻቸውን በበትር እቀጣለሁ
እግዚአብሔር የዳዊትን ልጆች መቅጣቱ የተገለጸው እግዚአብሔር በቀጥታ እነርሱን በበትር እንደሚመታ ተደርጎ ነው። "አመጽ" የሚለው ረቂቅ ስም በግስ መልክ ሊገለጽ ይችላል። "በእኔ ላይ በማመጻቸው እቀጣቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

በደላቸውን በጅራፍ
እግዚአብሔር የዳዊትን ትውልዶች መቅጣቱ የተገለጸው እግዚአብሔር እነርሱን በቀጥታ እንደሚመታ ተደርጎ ነው። ይህ በሙሉ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኔን በድለዋልና እቀጣቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና የተዘለለ/የተተወ በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው)

Psalms 89:33

ጽኑ ፍቅሬን ከእርሱ አላርቅም ወይም የቃል ኪዳኔን ታማኝነቴን አላርቅም
ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊገለጽ ይችላል። "እኔ ዳዊትን ለዘለዓለም እወደዋለሁ፣ ደግሞም ለእርሱ ቃል የገባሁትን እፈጽማለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምጸት የሚለውን ይመልከቱ)

የከንፈሬ ቃሎች
እዚህ ስፍራ "ከንፈሮች/ከናፍርት" የሚለው የሚወክለው በጠቅላላው አፍን እና ንግግር ነው። "እኔ የተናገርኩት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 89:35

በቅዱስናዬ ማልኩ
ያህዌ ቅድስናውን ለመሃላው መሰረት አድርጎ ተጠቅሞበታል። ይህ እርሱ ለማድረግ ቃል የገባውን በእርግጥ እንደሚያደርግ የሚያረጋግጥበት መንገድ ነው።

የእርሱ ዙፋን እንደ ፀሐይ በፊቴ ለዘለዓለም ይሆናል/ይቀጥላል
"ይቀጥላል" የሚለው ቃል በውስጠ ታዋቂነት መኖሩ ይታወቃልለ። "የእርሱ ዙፋን ፀሐይ በፊቴ እስላለች ድረስ ይቀጥላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለየሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ለዘለዓለም የጸና ይሆናል
እዚህ ስፍራ "ይህ" የሚለው የሚያመለክተው የዳዊትን ዙፋን ወይም እንደ ንጉሥ የመግዛት ሀይሉን ነው። በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ለዘለዓለም የጸና እንዲሆን አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ጨረቃ ለዘለዓለም
እግዚአብሔር የዳዊትን ንጉሣዊ አገዛዝ ከጨረቃ ጋር ያነጻጸረው ከዳዊት ትውልዶች ውስጥ ሁልጊዜም የሚነግስ ሰው እንደሚኖር ትኩረት ለመስጠት ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጨረቃይቱ፣ በሰማይ ታማኝ ምስክር
ጨረቃይቱ የተገለጸችው ያህዌ ለዳዊት ቃልኪዳን ሲገባለት ምስክር ሆኖ እንደተገኘ ሰው ተደርጋ ነው። "ጨረቃይቱ፣ በሰማይ እንደ ታማኝ ምስክር የሆነች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሴላ
ይህ ሰዎች የሙዚቃ መሳሪያቸውን እዚህ እንዴት እንደሚያዜሙበት ወይም እንደሚጫወቱበት የሚያሳይ ሙዚቃዊ ስያሜ ነው። አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል እንዳለ ይጠቀሙበታል፣ አንዳንድ ትርጉሞች ይተዉታል። ይህ በመዝሙር 3:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ቅጂ/እንዳለ መገልበጥ/ ወይም ቃላትን መዋስ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 89:38

አንተ ተቃወምከው ተውከውም
"ንጉሡ" የሚለው ቃል በውስጠ ታዋቂነት አለ። "አንተ ንጉሠን ተቃወምከው ወይም ተውከውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/ የተዘለለየሚለውን ይመልከቱ)

የቀባኸው ንጉሥ
"አንተ የመረጥከው ንጉሥ"

አንተ ቃል ኪዳኑን ተውክ
"አንተ ቃል ኪዳኑን ጣልክ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አንተ የእርሱን ዘውድ በመሬት ላይ አረከስክ
ወደ መድር ወይም አፈር ላይ መጣል በታላቅ ሁኔታ ማዋረድን ያመለክታል። "አንተ የእርሱን ዘውድ ምድር ላይ ጥለህ አቆሸሸክ" ወይም "አንተ የእርሱ ዘውድ ቆሻሻ ላይ እንዲወድቅ አደረግህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ ዘውድ
ይህ የሚወክለው እንደ ንጉሥ የንጉሡን ሀይል እና የመግዛት መብት ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ የእርሱን ቅጥሮች ሁሉ አፈረስክ። ጠንካራ ምሽጎቹን ሁሉ አወደምክ
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ጠላቶች የእየሩሳሌም መከላከያ ሁሉ እንዲወድም መፍቀዱን ነው። "ጠላቶች የእርሱን ቅጥር እንዲያፈርሱ እና ጠንካራ ምሽጎቹን እንዲደመስሱ ፈቀድክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 89:41

ለጎረቤቶቹ
እዚህ ስፍራ "ጎረቤቶች" ማለት በአቅራቢያ አገራት የሚኖሩ ሰዎች ማለት ነው።

የጠላቶቹን ቀኝ እጅ አስነሳሁበት
እዚህ ስፍራ "ቀኝ እጅ" የሚለው የሚወከወለው ሀይልን ነው። "ቀኝ እጅን ማንሳት" ማለት ያህዌ እርሱ ራሱ የመረጠውን ንጉሥ ጠላቶቹ እንዲያሸንፉት አቅም ሰጣቸው ማለት ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚሉትን ይመልከቱ)

የሰይፉን ስለት አጠፍኩ
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚወክለው ንጉሡ በጦርነት ያለውን ሀይል ነው። ሰይፍን መመለስ/ማጠፍ የሚወክለው ንጉሡን በጦርነት ማሸነፍ እንዳይችል ማድረግን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

የሰይፉ ስለት/ጠርዝ
እዚህ ስፍራ "ስለት/ጠርዝ" የሚወክለው ጠቅላላ ሰይፉን ነው። "የእርሱ ሰይፍ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በጦርነት መሃል መቆም እንዳይችል ማድረግ
እዚህ ስፍራ "መቆም" የሚወክለው በጦርነት ወቅት አሸናፊ መሆንን ነው። "በጦርነት አሸናፊ እንዲሆን አንተ አልረዳኸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 89:44

ዙፋኑን ወደ ምድር ጣልክ
እዚህ ስፍራ "ዙፋን" የሚወክለው እንደ ንጉሥ የመግዛትን ሀይል ነው። "አንተ፣ ያህዌ፣ እንደ ንጉሥ ሆኖ የሚገዛበትን ዘመን አበቃህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የወጣትነት ቀናቱን አሳጠርክ
ይህ እግዚአብሔር ንጉሡ ወጣት ሆኖ ሳለ ሽማግሌ እንዲመስል አደረገ ማለት ነው። "ገና ወጣት ሳለ አንተ እርሱን እንደ ሽማግሌ ሰው ደካማ አደረግኸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእፍረት ሸፈንከው/ከደንከው
ያህዌ ንጉሡን ሙሉ ለሙሉ ማሳፈሩ የተገለጸው፤ እፍረት እግዚአብሔር ንጉሡን ለመሸፈን እንደ ተጠቀመበት ልብስ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 89:46

ያህዌ ሆይ፣ እስከመቼ ድረስ? ለዘለዓለም ራስህን ትሰውራለህን?
ጸሐፊው እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመባቸው እግዚአብሔርን ንጉሡን አለመቀበሉን እንዲቀጥልበት አለመፈለጉን ትኩረት ለመስጠት ነው። "ያህዌ ሆይ፣ እባክህ ንጉሡን ለዘለዓለም አትጣለው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ራስን ትደብቃለህን
እግዚአብሔር ንጉሡን አለመርዳቱ የተገለጸው እግዚአብሔር ራሱን ከእርሱ እንደሰወረ/እንደ ደበቀ ተደርጎ ነው። "ንጉሡን አትረዳውምን?" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ቁጣህ እስከ መቼ እንደ እሳት ይነዳል?
ጸሐፍው ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት እግዚአብሔር እንደ ተቆጣ እንዲቆይ እንደማይፈልግ ትኩረት ለመስጠት ነው። "እባከህ ቁጣህ ይብረድ/ ቁጣህ አይቀጥል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ቁጣህ እንደ እሳት ይነዳል
እግዚአብሔር በጣም መቆጣቱ የተገለጸው ቁጣዉ የሚነድ እሳት ተደርጎ ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለምን ረብ ለሌለው ነገር የሰው ልጆችን ሁሉ ፈጠርካቸው
"ረብ/ጥቅም የሌለው" የሚለው ረቂቅ ስም "ያለ ጥቅም" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎችን ሁሉ ያለ ጥቅም ይሞቱ ዘንድ ፈጠርካቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጆች
ይህ ሰዎችን ሁሉ በጠቅላላ ያመለክታል። "የሰው ልጆች" ወይም "ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጡንቻማነትን የሚገልጹ ቃላት ሴትን ሲያካትቱ የሚለውን ይመልከቱ)

ላይሞት ነዋሪ የሚሆን ማን ነው፣ ወይም ራሱን ከሲኦል እጅ የሚያድን ማን ነው?
ጸሐፊው እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመው ሰዎች ሟች እንደሆኑ ትኩረት ለመስጠት ነው። "ማንም ለዘለዓለም መኖር አይችልም ወይም ማንም ራሱን ከሞት በኋላ ወደ ህይወት መመለስ አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 89:49

ጌታ ሆይ፣ በእውነተኛነትህ ለዳዊት የማልክለት የቀድሞው የቃል ኪዳንህ ታማኝነት ወዴት አለ?
ጸሐፊው ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው ጌታ ከዳዊት ጋር የገባውን ኪዳን እንዲጠብቅ ለመጠየቅ ነው።"ጌታ ሆይ፣ በቀድሞው ጊዜ እንደ ነበርህ ከዳዊት ጋር የገባኸውን ኪዳን ጠብቅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የቀደመው የቃል ኪዳን ታማኝነትህ ድርጊቶች
"ድርጊቶች" እና "ታማኝነት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች በግስ እና ተውሳከ ግስ መልካቸው ሊረተጎሙ ይችላሉ። "አስቀድሞ ያደረግሃቸው ነገሮች አንተ ለቃል ኪዳንህ ታማኝ መሆንህን ያሳያሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አስታውስ
ጸሐፊው ያህዌን ይህንን እንዲያስትውስ ይጠይቃል። "አስታውስ" ወይም "ስፍራ ስጠው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አገልጋችህ መቀለጃ ሆነናል
እዚህ ስፍራ "አገልጋዮችህ" የሚለው የሚያመለክተው የእስራኤልን ሰዎች ነው። "እንደምን በእኛ በአገልጋዮችህ ላይ እንዳፌዙብን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እንደምን በልቤ ከአገራት ሁሉ እጅግ ብዙ ስድብን ተሸከምኩ
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚወክለው የሰውን ስሜቶች ነው። "ከአገራት ህዝቦች ብዙ ስድብን ተቋቋምኩ" ወይም "ከየአገራቱ ሰዎች በደረሰብኝ ስድብ ምክንያት ተሰቃየሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከየአገራቱ
እዚህ ስፍራ "አገራት" የሚለው የሚወክለው የተለያዩ አገራት ሰዎችን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ ጠላቶች ስድብ አወረዱብኝ
ጠላቶች በንጉሱ ላይ በጩኸት መሳደባቸው የተገለጸው ስድብ ጠላቶች በንጉሡ ላይ በሀይል እንደሚወረውሩት ነገር/ቁስ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ በቀባኸው እርምጃዎች ላይ አፌዙ
እዚህ ስፍራ "እርምጃዎች" የሚለው የሚወክለው ንጉሡ የሄደበትን ነው። "የቀባኸውን በሄደበት እየተከተሉ አፌዙበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 89:52

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ ቁጥር ከዚህ ዝማሬ መጨረሻነት/ማብቂያነት የላቀ ነው። በመዝሙር 73 ለሚጀምረው እና በመዝሙር 89 ለሚጨርሰው ለመጽሐፈ መዝሙር 3 የመዝጊያ ሀሳብ ነው።

ያህዌ ለዘለዓለም የተባረከ ይሁን
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ህዝቦች ያህዌን ለዘለዓለም ያወድሱት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አዎን እና አዎን /አሜን፤ አሜን
"አሜን" የሚለው ቃል የተወከለው እርሱ የተናገረውን ለማረጋገት ትኩረት ለመስጠት ነው። ይህ በመዝሙር 41:13 እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 90

1 ጌታ ሆይ፣ አንተ ከትውልድ እስከ ትውልድ መጠጊያችን ነህ። **2** ተራሮችን ከመሥራትህና ዓለምንም ከመፍጠርህ በፊት አንተ ከዘላለም እስከ ዘላለም አምላክ ነህ **3** ሰዎችን ወደ ዐፈር ትመልሳለህ፤ «የሰው ልጆች ሆይ ወደ ቦታችሁ ተመለሱ» ትላለህ። **4** ሺህ ዓመት በፊትህ፣ እንዳለፈው ትናንት ቀን እንደ ሌሊትም ጥቂት ሰዓቶች ነው። **5** እንደ ጐርፍ ጠርገህ ስትወስዳቸው እንደ ሕልም ይበናሉ በየማለዳው እንደሚታደስ የሣር ቡቃያ ይሆናሉ። **6** ሣር ወዲያው አድጐ ያብባል ሲመሽ ግን ጠውልጐ ይጠፋል። **7** እኛ በቁጣህ ጠፍተናል በመዓትህም ደንግጠናል። **8** ኃጢአታችንን በፊትህ፣ የተሰወረ ኃጢአታችንንም በግልጽ በሚታይ ቦታ ታኖራለህ። **9** ዘመናችን ሁሉ በቁጣህ ያልፋል ዕድሜያችንም በቅጽበት እንደሚያልፍ እስትንፋስ ነው። **10** ዕድሜያችን ሰባ፣ ጤነኞች ከሆንንም ሰማንያ ዓመት ነው። እነዚያም ቢሆኑ፣ በመከራና ሐዘን የተሞሉ ናቸው። ዕድሜያችን ቶሎ ያልቃል፤ እኛም ወዲያው እንነጉዳለን። **11** የቁጣህን ኃይል ማን ያውቃል? መዓትህም የመፈራትህን ያህል ታላቅ ነው። **12** ጥበበኞች መሆን እንድንችል ዕድሜያችን ምን ያህል መሆኑን አስተምረን። **13** ያህዌ ሆይ፣ ተመለስ፤ ይህ እስከ መቼ ይሆናል፤ ለባሪያዎችህም ራራላቸው። **14** በዘመናችን ሁሉ ደስ እንዲለን፣ ሐሤትም እንድናደርግ በማለዳ ምሕረትህን አጥግበን። **15** መከራ ባየንበት ዘመን መጠን ችግር ባየንባቸው ዓመታት ልክ ደስ አሰኘን። **16** እኛ ባርያዎችህ ታላቁን ሥራህን፣ ልጆቻችንም ግርማህን እንዲያዩ ፍቀድልን። **17** የጌታ አምላካችን ሞገስ እኛ ላይ ይሁን የእጆቻችንን ሥራ ፍሬያማ ያድርግልን አዎን ፍሬያማ ያድርግልን።

Psalms 90:1

አጠቃላ መረጃ:
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ሰው የሙሴ ጸሎት
"ይህ የእግዚአብሔር ሰው ሙሴ የጻፈው ጸሎት ነው"

ጌታ ሆይ፣ አንተ መጠጊያችን ነህ
እግዚአብሔር ለህዝቡ ያደረገው ጥበቃ የተገለጸው እግዚአብሔር መጠጊያ ወይም መጠለያ ተደርጎ ነው። "ጌታ ሆይ፣ አንተ ለእኛ መጠለያችን ሆንክልን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በትውልዶች ሁሉ ውስጥ
"ሁልጊዜም"

ተራሮች ከመመስረታቸው አስቀድሞ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገርሊገለጽ ይችላል።"አንተ ተራሮችን ከመፍጠርህ/ ከማበጀትህ አስቀድሞ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ተመስርተው ነበር/ተበጅተው ነበር
"ተፈጥረው ነበር" ወይም "ቅርጽ ተሰጥቷቸው ነበር"

ዓለም
ይህ በዓለም ውስጥ ያለውን ነገር ሁሉ ይወክላል። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም
ይህ ሀረግ የሚወክለው ያለፈውን፣ የአሁኑን እና መጪውን ዘመን ሁሉ ነው።

Psalms 90:3

አንተ ሰውን ወደ አፈር ትመልሰዋለህ
ይህ የሚያመለክተው፣ እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ሰው፣ አዳምን፣ ከአፈር እንደፈጠረው፤ ሰዎች ከሞቱ በኋላ እግዚአብሔር የሰው አካል ወደ አፈር እንዲመለስ እንደሚያደርግ ነው። "አንተ ሰዎችን ሲሞቱ ወደ ትቢያነት ትመልሳቸዋለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰውን ትመልሰዋለህ
እዚህ ስፍራ "ሰው" የሚለው በአጠቃላይ የሰው ልጅን ነው። (ጡንቻማነትን የሚገልጹ ቃላት ሴትን ሲያካትቱ የሚለውን ይመልከቱ)

አናንተ ትውልዶች/የሰው ልጆች ትመለሳላችሁ
"ወደ ትቢያ" ወይም "ወደ አፈር" የሚሉት ቃላት በውስጠ ታዋቂነት ይገኛሉ። "አናንተ ትውልዶች ወደ ትቢያ ትመለሳላችሁ" ወይም "እናንተ ትውልዶች ወደ አፈር ትመልሳላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ የሰው ልጆች
ይህ በአጠቃላይ የሰው ልጆችን መጥቀሻ መንገድ ነው። "እናንተ የሰው ልጆች" ወይም "እናንተ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በአንተ ዘንድ ሺህ አመት እንደ ትላንት፣ በምሽት እንዳለፈ አንድ ሰዓት ነው
ጸሐፊው ረጅም ጊዜ ለእግዚአብሔር እንደ አጭር ጊዜ ይቆጠራል ማለቱ ነው። "አንተ ሺህ አመትን እንዳለፈ አንድ ቀን ወይም በምሽት እንዳለፈ አጭር ጊዜ ትቆጥራለህ" ወይም "ለአንተ ሺህ አመት እንኳን ረጅም ጊዜ አይደለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ሺህ አመታት
"1,000 አመታት" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በአንተ ዐይኖች/እይታ
እዚህ ስፍራ እይታ የሚወክለው አስተያየትን ወይም ምዘናን ነው። "ለ አንተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 90:5

በጎርፍ ትጠርጋችለህ እነርሱም ይጠረጋሉ
እግዚአብሔር ሰዎችን በድንገት መግደሉ የተገለጸው እነርን በመጥረጊያ እንደመጥረግ ተደርጎ ነው። ይህ መጥረግ የተነገረው ሰዎችን ጠርጎ እንደሚወስድ ጎርፍ ተደርጎ ነው። "ጌታ ሆይ፣ አንተ ሰዎችን በጎርፍ እንደሚጠፉ አጠፋህ እነርሱም ሞቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

እነርሱ ተኙ
ይህ የሰዎች መሞት ሻል ባለ ቃል የተገለጸበት መንገድ ነው። (የፊምዝም/ሻል ያለ ቃል መጠቀም የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ በማለዳ እንደ ሳር ናቸው...በምሽት ይጠወልጋል ይደርቃልም
ሰዎቹ ከሳር ጋር የተነጻጸሩት ረጅም ጊዜ እንደማይኖሩ ትኩረት ለመስጠት ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይፈካል ያድግማል
እነዚህ ሁለቱም ሀረጎች ሳር እንዴት እንደሚያድግ ያመለክታሉ። "ማደግ እና መበልጸግ ይጀምራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ይጠወልጋል ይደርቅማል
እነዚህ ሁለቱም ሀረጎች ሳር እንዴት እንደሚያሞት/እንደሚደርቅ ያመለክታሉ። "ይጠወልጋል፣ ይደርቅማል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 90:7

እኛ በቁጣህ አልቀናል
የሰዎች በእግዚአብሔር ቁጣ ማለቅ የተገለጸው፣ የእግዚአብሔር ቁጣ ሰዎችን ሙሉ ለሙሉ የሚያጠፋ እሳት እንደሆነ ተደርጎ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንተ በቁጣህ አጠፋኸን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

እኛ ከቁጣህ የተነሳ ተሸብረናል
"አንተ በምትቆጣ ጊዜ እኛ እጅግ እንፈራለን"

በደላችንን በፊትህ፣ የተሰወሩ ኃጢአቶቻችን በመገኘትህ ብርሃንህ ውስጥ አኖርክ
እግዚአብሔር የሰዎችን ኃጢአት መመልከቱ የተገለጸው፣ ኃጢአት በራሱ ፊት እንደሚያስቀምጠው ቁስ እና እንደሚመለከተው ነገር ተደርጎ ነው። "አንተ እኛ የምናደርጋቸውን ክፉ ነገሮች ሁሉ፣ በስውር ያደረግናቸውን እንኳን ሳይቀር ታያለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 90:9

ህይወታችን በቁጣህ ስር አለፈ
"ምክንያቱም" የሚለው ቃል የእግዚአብሔር ቁጣ የሰው ህይወት እንዲያበቃለት እንደሚያደርግ ግልጽ ለማድረግ ሊውል ይችላል። "ከቁጣህ የተነሳ ህይወታችን አበቃለት/ሞትን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አያያዥ የሚለውን ቃላት የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ አንድ ትንፋሽ/ሳግ
ጸሐፊው የሰውን ህይወት ከአንድ ትንፋ ጋር የሚያነጻጽረው ህይወት በጣም አጭር መሆኗን ትኩረት ለመስጠት ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባ
"70" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰማንያ
"80" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ምርጥ የተባሉ ዘመናቻችን እንኳን ችግር እና ሀዘን ነበረባቸው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እጅግ የተሻሉ ዘመኖቻችን እንኳን በችግር እና ሀዘን ያለባቸው ነበሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እንወሰዳለን
ይህ የሰዎች መሞት ሻል ባለ ቃል የሚገለጽበት መንገድ ነው። "ሞትን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊምዝም/ሻል ያለ ቃል መጠቀም የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 90:11

የቁጣህን ክብደት ፣ አንተን መፍራትን ያሚተካለለውን መአትህንስ ማን ያውቃል?
ጸሐፊው ጥያቄውን የተጠቀመበት ማንም የእግዚብሔርን ቁጣ መቋቋም እንደማይችል ትኩረት ለመስጠት ነው። ስለዚህ ማንም እግዚአብሔር ከሚያደረገው ሊመልሰው አይችልም፣ ደግሞም ሰዎች ኃጢአት ባደረጉ ጊዜ ቁጣውን አልፈሩም። "ማንም የቁጣህን ክብደት አያውቀውም። ስለዚህ ኃጢአት ሲፈጽሙ አንዳቸውም የአንተን ቁጣ አልፈሩም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ ሆይ፣ ተመለስ! ይህ እስከ መቼ ይሆናል?
ያህዌን ቁጣው እንዳይቀጥል መለመን የተገለጸው ጸሐፊው እግዚአብሔር በአካል ከቁጣው ዞር እንዲል እንደፈለገ ተደርጎ ነው። "ያህዌ ሆይ፣ እባክህ ከእንግዲህ ቁጣህ አይቀጥል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ እስከ መቼ ይሆናል?
ጸሐፊው ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት እግዚአብሔር ቁጣውን እንዲያቆም መፈለጉን ለመግለጽ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለአገልጋዮችህ ምህረት አድርግ
እዚህ ስፍራ "የአንተ አገልጋዮች" የሚለው የሚያመለክተው የእስራኤልን ሰዎች ነው። "ለእኛ ለአገልጋዮችህ ምህረት አድርግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

Psalms 90:14

በማለዳ ደስ አሰኘን
"እኛን በየማለዳው/በየጠዋቱ ደስ አሰኘን"

በቃልኪዳንህ ታማኝነት
"ታማኝነት" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል መልኩ ሊገለጽ ይችላል። "ከእኛ ጋር ካለህ ቃል ኪዳን የተነሳ ታማኝ በመሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

መከራ ባሳየኸን ቀናት ችግር ባየንበት አመታት ፈንታ
እነዚህ ሁለቱም ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ጸሐፊው ያህዌን የሚጠይቀው እነርሱን በቀጣቸው ጊዜ መጠን ደስተኞች እንዲያደርጋቸው ነው። "መከራ ባሳየኸን እና ችግር ባየንባቸው ጊዜያት መጠን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተን አገልጋዮች
እዚህ ስፍራ "የአንተ አገልጋዮች" የሚለው የሚያመለክተው የእስራኤልን ሰዎች ነው። "እኛ አገልጋዮችህ" ወይም "እኛን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የእኛ ልጆች
እዚህ ስፍራ "ልጆች" ማለት ልጆች እና ትውልዶች ማለት ነው።

ክብርህን እናያለን
"ክብር" የሚለው ረቂቅ ስም "ታላላቅ ነገሮች" በሚለው ሊገለጽ ይችላል። "አንተ ያደረግሃቸውን ታላላቅ ነገሮች እንመለከታለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 90:17

የእግዚአብሔር የአምላካችን ሞገስ በላያችን ይሁን
"ሞገስ" የሚለው ረቂቅ ስም "መልካም መሆን" በሚለው ውስጥ ሊገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር አምላካችን ለእኛ መልካም ይሁን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 91

1 በልዑል መጠጊያ የሚኖር ሁሉን በሚችል አምላክ ጥላ ሥር ያድራል። **2** ያህዌን፣ «መጠጊያዬ፣ ምሽጌ፣ የምታመንብህ አምላኬ» እለዋለሁ። **3** ከአዳኝ ወጥመድ ከአደገኛም መቅሠፍት ያድንሃል **4** በላባዎቹ ይጋርድሃል በክንፎቹም ሥር መሸሸጊያ ታገኛለህ። ታማኝነቱም ጋሻና መከታ ይሆንልሃል። **5** የሌሊትን ሽብር፣ በቀን ከሚወረወር ፍላጻም አትፈራም **6** በጨለማ ከሚያደባ ቸነፈር በቀትርም ከሚወርድ መቅሠፍት አትሰጋም። **7** በአጠገብህ ሺህ በቀኝህም ዐሥር ሺህ ይወድቃሉ ወደ አንተ ግን አይቀርብም። **8** በዐይንህ ብቻ ታያለህ የክፉዎችንም መቀጣት ትመለከታለህ። **9** አንተ ያህዌን መሸሸጊያ ልዑል አምላክንም መጠጊያህ አድርገኸዋልና። **10** ክፉ ነገር አያገኝህም መቅሠፍትም ወደ ቤትህ አይጠጋም። **11** በመንገድህ ሁሉ እንዲጠብቁህ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋል። **12** እግሮችህ በድንጋይ እንዳይሰናከሉ በእጆቻቸው ያነሡሃል። **13** አንበሳና እፉኝት ላይ ትጫማለህ ደቦሉን አንበሳና ዘንዶውን ትረግጣለህ። **14** ወዶኛልና አታደገዋለሁ በእኔ ተማምኖአልና እጠብቀዋለሁ። **15** ይጠራኛል እኔም እመልስለታለሁ በመከራው ጊዜ ከእርሱ ጋር እሆናለሁ ድል አቀዳጀዋለሁ፤ አከብረውማለሁ። **16** ረጅም ዕድሜ አጠግበዋለሁ ማዳኔንም አሳየዋለሁ።

Psalms 91:1

አጠቃላይ መረጃ:
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ሁሉን ቻይ በሆነው ...ዘንድ የሚኖር እርሱ...ያድራል
"መጠጊያ/መጠለያ" እና "ጥላ" እንደሚሉት ለጥበቃ ዘይቤያዊ አገላለጽ እንዳላቸው ቃላት ሁሉ "መኖር" እና "ማደር" የሚሉት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ስለዚህም ሁለቱን ስንኞች በአንድ ላይ ማጣመር ይቻላል። "እጅግ ከፍ ያለው እና ሁሉን ቻይ የሆነው በእርሱ ጥበቃ ውስጥ ለሚኖሩ ጥንቃቄ ያደርግላቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ጥንድ ትርጉም የሚሉትን ይመልከቱ)

እጅግ ከፍ ባለው መጠለያ/ በልዑል መጠጊያ የሚኖር
"መጠለያ" የሚለው ቃል ያህዌን የሚያመለክት ዘይቤ ነው።"ልዑሉ ለእርሱ ጥበቃ በሚያደርግበት የሚኖር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እጅግ ከፍ ያለው /ልዑሉ
"ልዑል/እጅግ ከፍ ያለ" የሚለው ቃል ያህዌን ያመለክታል። ይህ በመዝሙር 18፡13 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ሁሉን ቻይ በሆነው ጥላ ስር ይቆያል/ያድራል
እዚህ ስፍራ "ጥላ" የሚለው ቃል ጥበቃ ለሚለው ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። "ሁሉን ቻይ የሆነው ሊጠብቀው በሚችልበት ስፍራ ይቆያል/ያድራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉን ቻዩ
ሀይል ያለው እና ሁሉን ነገር ሊቆጣጠር/ሊገዛ የሚችል። ይህ በመዝሙር 68፡14 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ያህዌን እንዲህ እለዋለሁ
"ስለ ያህዌ እንዲህ እላለሁ"

መሸሸጊያዬ እና ምሽጌ
"መሸሸጊያ" አንድ ሰው ሊሄድ የሚችልበት እና የሚሸሸገው ሰው ወይም ነገር የሚያገኝበት ስፍራ ነው። "ምሽግ" ሰዎች ራሳቸውን እና ያላቸውን ንብረት ለመጠበቅ የሚያበጁት ስፍራ ነው። እዚህ ስፍራ አሳፍ እነዚህን ለጥበቃ እንደ ዘይቤ ተጠቅሞባቸዋል። "እኔ ልሄድ የምችልበት እና እርሱም እኔን የሚጠብቅበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚውን ይመልከቱ)

Psalms 91:3

እርሱ ከአዳኝ ወጥመድ ደግሞም ከክፉ መቅሰፍት ያድንሃል
የተተዉት ቃላት ሊጨመሩ/ሊገቡ ይችላሉ። "እግዚአብሔር አንተን ከአዳኝ ወጥመድ እና ሊገድል ከሚችል መቅሰፍት ያድንሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

የአዳኝ ወጥመድ
"አዳኝ አንተን ለመያዝ ካስቀመጠው ወጥመድ"

በክንፎቹ ይጋርድሃል/ይሸፍንሃል፣ ከክንፉፎቹም በታች መሸሸጊያ ታገኛለህ
እዚህ ስፍራ የእግዚአብሔር ጥበቃ የተገለጸው ወፍ ጫጩቶቿን ከአደጋ እንደ ምትጋርድበት "ክንፎች" ተደርጎ ነው። "በክንፎቹ ይሸፍንሃል" እና "ከክንፎቹ በታች" የሚሉት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። "እርሱ በሰላም ይጠብቅሃል፣ ይጋርድህማል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

የእርሱ ታማኝነት ጋሻ እና ጥበቃ ነው
እዚህ ስፍራ የእግዚአብሔር ታማኝነት የሚለው የተገለጸው በእርሱ የሚታመኑ ሰዎችን መጠበቅ እንደሚችል "ጋሻ" ተደርጎ ነው። "ታማኝነት" የሚለው ረቂቅ ስም "መታመን" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "እርሱ እንደሚጠብቅህ ልትታመንበት ትችላለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

መከላከያ
የዚህ ቃል ትርጉም በእርግጠኝነት አይታወቅም። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ወታደሮች ራሳቸውን ከጠላት ቀስቶች እና ሰይፍ ለመከላከል በክንዳቸው የሚያዙት ትንሽ ጋሻ፤ ወይም 2) ወታደሮች በውስጡ ተሸሽገው ቀስት የሚወረውሩበት በክብ የተሰራ የድንጋይ ግርግዳ

Psalms 91:5

በምሽት ሽብር
ዘማሪው ስለ "ሽብር" የሚናገረው በምሽት ጥቃት እንደሚያደርስ መንፈስ ወይም አስፈሪ እንስሳ እና እጅግ አስፈሪ ሰዎች አድርጎ ነው። "በምሽት ከሚያጠቁህ ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በምሽት...በቀን
እነዚህ ሁለት ሀረጎች አንድ ላይ የተወሰዱት ማናቸውንም የምሽት ወይም የቀን ክፍለ ጊዜ ለማመልከት ነው። (ከጽንፍ ጽንፍ የሚለውን ይመልከቱ)

በቀን የሚበር/የሚፈናጠር ፍላጻ
እዚህ ስፍራ "ፍላጻ/ቀስት" ቀስት ለሚወረውሩ ሰዎች የዋለ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "በቀን በቀስት ጥቃት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከሚያደርሱብህ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ወይም ከሚከብህ መቅሰፍት
ዘማሪው ስለ ህመም የሚናገረው በሽታ ሰው ሆኖ ሰዎችን ለመግደል በምሽት እንደሚሄድ ሰው አድርጎ ነው። "በበሽታ የሚመጣ ሞት አያስፈራህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መንከራተት/መሄድ
በማናቸውም ጊዜ ወደሚፈልግበት ስፍራ ሁሉ መሄድ

በጨለማ...በቀትር ወቅት
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በአንድነት ሆነው የሚያመለክቱት ሁሉንም የምሽት እና ቀን ጊዜያት ነው። (ከጽንፍ ጽንፍ የሚለውን ይመልከቱ)

በሽታ
በተመሳሳይ ጊዜ ብዙ ሰዎችን ህመም ላይ የሚጥል

በሺህ የሚቆጠሩ በጎንህ፣ በአስር ሺህ የሚቆጠሩ በቀኝህ ሊወደወቁ ይችላሉ
"ብዙ ሰዎች በዙሪያህ ሊወድቁ ይችላሉ።" ትክክለኛውን ቁጥር መተርጎሙ አንባቢዎችን ግራ የሚያጋባ ከሆነ፣ እነርሱን መተው ይቻላል።

ይህ አይደርስብህም/አያገኝህም
"ክፉው አይጎዳህም"

Psalms 91:8

አንተ በዐይኖችህ ትመለከታለህ፣ ታያለህም
"አንተ ራስህ መከራ አትቀበልም፣ ነገር ግን በጥንቃቄ ታያለህ፣ ደግሞም ትመለከታለህ"

የክፉዎች መቀጣት
"ቅጣት" የሚለው ረቂቅ ስም በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "እግዚአብሔር ክፉዎችን እንዴት እንደሚቀጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ መሸሸጊያዬ ነው
ጸሐፊው፣ ከጠላቶቹ ጥበቃ ለማግኘት ያህዌ ለእርሱ አስተማማኝ ስፍራ እንደሆነ አደርጎ ይገልጻል። "አንድ ሰው በመሸሸጊያ ስፍራ ጥበቃ እንደሚያገኝ ያህዌ እኔን ይጠብቀኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ልዑሉንም መሸሸጊያህ አድርግ
"ልዑሉንም መሸሸጊያህ ማድረግ አለብህ ::" ዘማሪው ለእግዚአብሔር መናገሩን አቁሞ ለአንባቢው ይናገራል።

Psalms 91:10

የትኛውም ክፉ ነገር አያገኝህም
ጸሐፊው መጥፎ ወይም ክፉ ነገርን የሚለማመድን ሰው የሚገልጸው ክፉ ሰው እንደሆነና በሌላ ሰው ላይ መጥፎ ነገር እንደሚያደርስ አድርጎ ነው። "አንዳችም ክፉ በአንተ ላይ አይደርስም" (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሰውኛ የሚሉትን ይመልከቱ)

አንዳች መቅሰፍት ወደ ቤትህ አይቀርብም
ዘማሪው ሌላውን ሰው የሚበክሉ ራሳቸውን የሚያደርሱትን ጉዳት ራሱን አድርጎ ያቀርባቸዋል። "ማንም ቤተሰብህን ሊጎዳ አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

እርሱ ያዛል
"ያህዌ ያዛል"

በመንገድህ ሁሉ
ዘማሪው አንድ ሰው ህይወቱን የሚኖርበትን መንገድ ሰውየው እንደሚራመድበት ጎዳና አድርጎ ይገልጻል። "በምታደርገው ነገር ሁሉ" ወይም "በሁሉም ጊዜያት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 91:12

እነርሱ ያነሱሃል
"የያህዌ መላዕክት ያነሱሃል"

እግርህ በድንጋይ አይሰናከልም
መላዕክት የሚጠብቁት የአንባቢውን እግር ብቻ ሳይሆን ሌላውንም የሰውነቱን ክፍል ሁሉ ነው። "እግርህ በድንጋይ ...አይሰናከልም" የሚለው አንዳች ጉዳት አይደርስብህም የሚለው በግነት የተገለጸበት ሜቶኖሚ/ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ይህ ምናልባት አንዳች ክፉ ነገር ዳግም በፍጹም አይደረስም ለሚለው እንደ ቃል ኪዳን አይወሰድም። "እግርህን እንቅፋት አይመታውም" ወይም "ጥቂት ክፉ ነገር እንኳን በአንተ ላይ አይደርስም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት፣ አጠቃላይ አስተያየት እንዲሁም ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

አንበሳዎችን ሰባብረህ ከእግርህ በታች ታደርጋለህ፤ በደቦል አንቦች እና በእባቦች ላይ ትጫማለህ/ትረጋግጣቸዋለህ
"እግርህ በድንጋይ ይጋጫል/እንቅፋት እግርህን ይመታል" የሚለው አነስተኛ ችግርን ሲያሳይ፤ አንበሶች እና እባቦች የታላላቅ አደጋዎች ምልክቶች ናቸው። ዘማሪው ስለ አንበሶች እና እባቦች የሚናገረው በሰው እግር እንደሚረጋገጡ ትንንሽ እንስሳት አድርጎ ነው። "አንበሶችን እና ዘንዶውን እንደ ትናንሽ እንስሳት ከእግርህ በታች ትፈጫቸዋለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ዘንዶ/መርዘኛ እባብ
መርዘኛ የእባብ አይነት

መረጋገጥ
በሀይል በላዩ ላይ በመራመድ መፍጨት/መጨፍለቅ

Psalms 91:14

እርሱ ራሱን ለእኔ ሰጥቷልና
"ወዶኛልና"

በመከራው ጊዜ ከእርሱ ጋር እሆናለሁ
ይህ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "በችግሩ ጊዜ ከእርሱ ጋር እሆናለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ድል እሰጠዋለሁ
"ድል" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ድል ነሺ አደርገዋለሁ" ወይም "ጠላቶቹን ማሸነፍ እንዲችል አበቃዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ረጅም እድሜ አጠግበዋለሁ
ዘማሪው ስለ ህይወት የሚናገረው አንድ ሰው ሊመገበው እንደሚችለው ነገር አድርጎ ነው። "ረጅም እና ደስተኛ ህይወት እንዲኖር እፈቅድለታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ማዳኔን አሳየዋለሁ
"ማዳኔንም አሳየዋለሁ።" ዘማሪው እግዚአብሔር ሰዎችን ለማዳን ያደረገውን ስራ የሚናገረው እንደ ቁሳዊ አካል አድርጎ ነው። "ያዳንኩት እኔ መሆኔን ያውቅ

ዘንድ እታደገዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር
የሚለውን ይመልከቱ)

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 92

1 ያህዌን ማመስገን መልካም ነው፤ ልዑል ሆይ፣ ለስምህ መዘመር መልካም ነው። **2** ምህረትህን በማለዳ ታማኝነትህን በሌሊት ማወጅ መልካም ነው። **3** ዐሥር አውታር ባለው በገና ከመሰንቆም ጣዕመ ዜማ ጋር ማወጅ መልካም ነው። **4** ያህዌ ሆይ፣ በሥራህ ደስ ስላሰኘኸኝ ስለ እጅህ ሥራ በደስታ እዘምራለሁ። **5** ያህዌ ሆይ፣ ሥራህ እንዴት ታላቅ ነው? ሐሳብህ እጅግ ጥልቅ ነው። **6** ደነዝ ሰው ይህን አያስተውልም ሞኝም ይህን አይረዳም፣ **7** ክፉ ሰዎች እንደ ሣር ቢበቅሉ ተንኰለኞችም ቢለመልሙ ለዘላለሙ ይጠፋሉ። **8** አንተ ግን ያህዌ ሆይ፣ ለዘላለም ትነግሣለህ። **9** ጠላቶችህ ያህዌ ሆይ፣ ጠላቶችህ ይጠፋሉ ክፉ አድራጊዎችም ሁሉ ይበተናሉ። **10** እንደ ጐሽ ቀንድ ቀንዴን ከፍ ከፍ አደረግህ በትኩስ ዘይትም ቀባኸኝ። **11** ዐይኖቼ የባላንጣዎቹን ውድቀት አዩ ጆሮቼም የክፉ ጠላቶቼን ጥፋት ሰሙ። **12** ጻድቃን እንደ ዘንባባ ዛፍ ይለመልማሉ እንደ ሊባኖስ ዛፍም ያድጋሉ። **13** በያህዌ ቤት ተተክለዋል በአምላካችን አደባባይ ይንሰራፋሉ። **14** ባረጁ ጊዜ እንኳ ያፈራሉ እንደ ለመለሙና እንደ ጠነከሩም ይኖራሉ። **15** እግዚአብሔር ትክክለኛ ነው፤ እርሱ ዐለቴ ነው፤ በእርሱ ዘንድ እንከን የለም።

Psalms 92:1

አጠቃላይ መረጃ:
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ለስምህ ውዳሴ/ምስጋና ማቅረብ
"የአንተ ስም" የሚሉት ቃላት "አንተ" ለሚለው ሜቶኖሚ /ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ለአንተ በውዳሴ መዘመር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በማለዳ የቃል ኪዳንህን ታማኝነት እናገራለሁ/አውጃለሁ
"ታማኝነት" የሚለው ረቂቅ ስም "ታማኝ" በሚለው ቅጽል ሊተረጎም ይችላል።"አንተ ለቃል ኪዳንህ ታማኝ እንደሆንክ በማለዳ አውጃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በየምሽቱ የአንተን እውነተኝነት
ግሱ ከቀደመው ሀረግ ሊወሰድ ይችላል። "እውነተኝነት" የሚለው ረቂቅ ስም "እውነት" በሚለው ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። "አንተ የምትናገረው ነገር ሁሉ እውነት መሆኑን በየምሽቱ እናገራለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

Psalms 92:4

አስደሳች
ደስታ

በስራዎችህ
"የአንተ ስራዎች" የሚለው ረቂቅ ስማዊ ሀረግ "አንተ የሰራኸው" በሚለው ተዛማጅ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "አንተ በሰራኸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የእጆችህ ስራዎች
"የእጆችህ ስራዎች" የሚለው ረቂቅ ስማዊ ሀረግ "የአንተ እጆች የሰሩት" በሚለው ተዛማጅ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "እጆች" የሚለው ቃል ለጠቅላላው ማንነት ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ነው። "አንተ የሰራኸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

የአንተ ስራዎች
"የአንተ ስራዎች" የሚለው ረቂቅ ስማዊ ሀረግ በተዛማጅ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "አንተ የሰራኸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ሀሳቦችህ በጣም ጥልቅ ናቸው
"አንተ እስከ ምታደርገው ድረስ ለማድረግ ያቀድከውን መረዳት አንችልም"

የአንተ ሀሳቦች
"የአንተ ሀሳቦች" የሚለው ረቂቅ ስማዊ ሀረግ በተዛማጅ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "አንተ የምታስበው" ወይም "አንተ የምታቅደው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 92:6

ደነዝ
እንደ እንስሳ

ክፉዎች እንደ ሳር ሲበቅሉ
ይህ ክፉ ሰዎችን በፍጥነት ብዙ ስፍራ ከሚበቅል ሳር ጋር ያነጻጽራል። "ክፉ ሰዎች እንደ ሳር፣ በፍጥነት ሲታዩ እና በየስፍራው የሚገኙ ሲመስሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በዘለዓለም ጥፋት ይፈረድባቸዋል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እግዚአብሔር እነርሱን ሙሉ ለሙሉ ለማጥፋት ወስኗል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 92:8

ያህዌ ሆይ፣ በእርግጥ ጠላቶችህን ተመልከት
ብዙ ቅጂዎች እነዚህን ቃላት አያካትቱም

እነርሱ ይጠፋሉ
"እነርሱ ይሞታሉ" ወይም "አንተ ትገድላቸዋለህ"

ክፉ የሚያደርጉ ሁሉ ይበተናሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "አንተ ክፉ የሚያደርጉትን ሁሉ ትበትናቸዋለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ይበተናሉ
ብዙ ቅጂዎች "ተበትነዋል" ይላሉ

ይበተኑ
"ይወሰዱ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 92:10

ቀንዴን እንደ ዱር በሬ/አውራሪስ ቀንድ ከፍ ከፍ አደረግህ
ዘማሪው እግዚአብሔር እንደ ዱር እንስሳ ጠንካራ እንዳደረገው ይናገራል። እዚህ ስፍራ የእርሱ "ቀንድ" የሚወክለው ጥንካሬውን ነው። "እንደ ዱር በሬ/አውራሪስ ጠንካራ አደረግኸኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

በለጋ ዘይት ተቀብቻለሁ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች እግዚአብሔር በዘማሪው ላይ ያስቀመጠው ቅባት እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ለመሆኑ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው 1) እርሱን ደስ ማሰኘቱ "አንተ እኔን በጣም ደስ አሰኘኸኝ" ወይም 2) እርሱን ጠንካራ አደረገው "አንተ እኔን ጠንካራ አደረግኸኝ" ወይም 3) ጠናቶችን እንዲያሸንፍ አስቻለው፣ "አንተ ጠላቶቼን እንዳሸንፍ አስቻልከኝ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ዐይኖቼ የጠላቶቼን ውድቀት ተመለከቱ፤ ጆሮዎቼ የጠላቶቼን ክፉ ቀን ሰሙ
"ዐይኖች" እና "ጆሮዎች" የሚሉት ቃላት ለተመልካቹ እና ሰሚው ሰው ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ነው። ስንኞቹ ሊጣመሩ ይችላሉ። "የክፉ ጠላቶቼን ሽንፈት አየሁ ደግሞም ሰማሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 92:12

ጻድቅ እንደ ዘንባባ ዛፍ ያብባል
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች፤ ጻድቅ ሰዎች እንደ ጤናማ የዘንባባ ዛፍ ናቸው ምክንያቱም እነርሱ 1) ጠንካራ ይሆናሉ/ይበረታሉ ወይም 2) ሰዎች ያከብሯቸዋል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የተተከሉ ናቸው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ያህዌ ተክሏቸዋል" ወይም "ያህዌ እርሱ እንደ ተከላቸው ዛፎች ለእነርሱ እንክብካቤ ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

በያህዌ ቤት...በአምላካችን በእግዚአብሔር አደባባዮች
ዘማሪው በእውነት እግዚአብሔርን ስለሚያመልኩ ሰዎች በያህዌ ቤት እንደሚያድጉ ዛፎች አድርጎ ይገልጻል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ያብባሉ
ዘማሪው ስለ ጻድቅ ሰዎች ጤናማ ዛፎች እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። "በጥሩ ሁኔታ ያድጋሉ" ወይም "በጣም ጠንካራ ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በአምላካችን አደባባይ
በእየሩሳሌም ቤተመቅደስ በሚገኘው አደባባይ

Psalms 92:14

ፍሬ ያፈራሉ
ዘማሪው ጻድቅ ሰዎችን የሚበላ ፍሬ እንደሚያፈሩ ዛፎች አድርጎ ይገልጻቸዋል። "እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለምለም እና አረንጓዴ ሆነው ይቆያሉ
ዘማሪው ጻድቅ ሰዎችን ዛፎች እንደሆኑ አድርጎ ይገልጻቸዋል። "ጠንካራ እና ጤናማ ሆነው ይቆያሉ" ወይም "ሁልጊዜም እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን ያደርጋሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አረንጓዴ/ለምለም፣ ያንን ለመናገር
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "አረንጓዴ/ለምለም፣ እነርሱ ያንን መናገር ይችላሉ" ወይም 2) "አረንጓዴ/ለምለም። ይህ ያንን ያሳያል"

እርሱ አለቴ ነው
"እኔን የሚጠብቀኝ ያህዌ ነው።" ዘማሪው ስለ ያህዌ የሚናገረው እርሱን እንደሚጠብቀው አለት አድርጎ ነው። ይህ በመዝሙር 18:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 93

1 ያህዌ ነገሠ ግርማንም ለበሰ፣ ያህዌ ግርማን ተጐናጸፈ ብርታትንም ታጠቀ ዓለምን በአንድ ስፍራ አጸናት፤ ከቶም አትናወጥም። **2** ዙፋንህ ከጥንት ጀምሮ የጸና ነው አንተም ከዘላለም እስከ ዘላለም ነህ። **3** ያህዌ ሆይ፣ ባሕሮች ይነሣሉ ድምፃቸውንም ከፍ አድርገው ይጮኻሉ ወንዞች የሚያስገመግም ማዕበላቸውን ከፍ አደረጉ። **4** ከብዙ ውሆች ድምፅ ይልቅ ከባሕርም ሞገድ ይልቅ ከፍ ብሎ ያለው ያህዌ ብርቱ ነው። **5** ትእዛዛትህ ያጸኑ ናቸው ያህዌ ሆይ፣ ቤትህ ለዘላለም በቅድስና ይዋባል።

Psalms 93:1

አጠቃላይ መረጃ:
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ክብርን ተጎናጽፏል፤ ያህዌ ክብርን ለብሷል ብርታትንም ታጥቋል
ዘማሪው ስለ ያህዌ ጥንካሬ እና ክብር የሚናገረው ያህዌ እነዚህን ነገሮች እንደለበሳቸው አድርጎ ነው። "እርሱ ለእያንዳንዱ ሀያል ንጉሥ መሆኑን ያሳያል" ወይም "ግርማዊነቱን፣ ንጉሥ እንደሚጎናጸፈው ካባ ሁሉም ይመለከተዋል፤ ሁሉም ነገር የያህዌን ብርታት እና እርሱ ታላቅ ስራ ለመስራት መዘጋጀቱን ያሳያል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ግርማዊ
የንጉሥ ሀይል እና የንጉሥ አደራረግ

ራሱን አስታጠቀ
ቀበቶ መታጠቅ- አንድ ሰው ለስራ ወይም ለጦርነት ለመዘጋጀት በወገቡ ዙሪያ የሚታጠቀው ከቆዳ ወይም ሌላ ቁስ የተሰራ ማሰሪያ/መታጠቂያ

ዓለም በጽኑ ተመስርታለች
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንተ ዓለምን በጽኑ መሰረትክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ሊንቀሳቀስ/ሊናወጥ አትችልም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ማንም መቼም ሊያንሳቅሳት አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ከዘለዓለም ድረስ ነህ
"አንተ ለዘለዓለም አለህ"

Psalms 93:3

ውቅያኖሶች...የውቅያኖስ
አንዳንድ ቅጂዎች "ጎርፍ...የጎርፍ" ይላሉ። ቃሉ ብዙውን ጊዜ ወንዝን ያመለክታል (በመዝሙር 72:8 ላይ "ወንዝ" የሚለውን ይመልከቱ) ፣ ነገር ግን እዚህ ስፍራ የተመረጠው "ውቅያኖሶች...የውቅያኖሶች" የሚለው እንጂ ወንዞች የሚለው አይደለም፤ ምክንያቱም "የሚለተም እና የሚያጎራ" "ማዕበል" ያለው ውቅያኖስ እንጂ ወንዝ አይደለም

የውቅያኖስ ማዕበል እና ማጎራት፣ ድምጻቸውን አነሱ
ዘማሪው ማዕበልን የሚገልጸው መናገር እንደሚችል ሰው አድርጎ ነው። "ማዕበላቸው ሲጋጭ እን ሲያጓራ ታላቅ ድምጽ አሰሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ማጓራት
ረጅም እና ከፍተኛ ድምጽ ማሰማት

ከብዙ ማዕበል መጋጨት በላይ፣ የባህር ታላቅ ነውጥ
"የባህር ታላቅ ነውጥ" የሚለው ሀረግ "ብዙ ማዕበል" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖረው እነዚህ ማዕበሎች እንዴት ታላቅ እንደሆኑ ትኩረት ይሰጣል። "ከባህሩ ታላቅ ነውጦች ሁሉ በላይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ሞገድ
ከባህሩ ወደ ዳርቻ የሚመጣ ትልቅ ማዕበል

በላይ
ዘማሪው እግዚአብሔር የሚኖርበትን ከምድር በላይ ከፍ ብሎ እንደሆነ አድርጎ ይገልጻል። "በሰማያት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 93:5

የተከበረ
በጣም የተረጋጋ

በጣም የታመኑ ናቸው
"ተለዋዋጭ ያልሆነ" ወይም "በፍጹም የማይለወጥ"

ቅድስና ቤትህን ያስጌጠዋል
ዘማሪው ስለ ያህዌ ቤት ውብ ልብስ እንደለበሰች ወይም እንዳጌጠች ሴት ሲገልጸው የያህዌን ቅድስና እንዳማረ ልብስ ወይም ጌጥ አድርጎ ያናገራል። "አንተ ቅዱስ ነህና ቤትህ የተዋበ ነው" ወይም "አንዲትን ሴት ውብ ልብሶችና ጌጥ ይበልጥ ውብ እንደሚያደርጓት ቅድስናህ ቤትህን አስውቦታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ቤትህ/የአንተ ቤት
በእየሩሳሌም የሚገኘው ቤተመቅደስ

ይዋባል
ውብ ይደረጋል

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 94

1 የበቀል አምላክ አንተ ያህዌ ሆይ፣ የበቀል አምላክ ሆይ፣ ብርሃንህ ይብራልን። **2** የምድር ዳኛ ሆይ፣ ተነሥ ለትዕቢተኞች የእጃቸውን ስጣቸው። **3** ያህዌ ሆይ፣ ክፉዎች እስከ መቼ፣ ክፉዎች እስከ መቼ ነው የሚፈነጩት? **4** የእብሪት ቃሎች ያዥጐደጕዳሉ ክፉ አድራጊዎችም ሁሉ ጕራ ይነዛሉ። **5** ያህዌ ሆይ፣ ሕዝብህን ያደቅቃሉ የአንተን ወገኖች ይጨቁናሉ። **6** በአገራቸው የሚኖሩ መበለቶችንና መጻተኞችን ይገድላሉ፤ **7** «ያህዌ አያይም፤ የያዕቆብ አምላክም አያስተውልም» ይላሉ። **8** እናንት አላዋቂዎች ይህን አስተውሉ፤ እናንት ሞኞች ለመሆኑ፣ ጥበበኞች የምትሆኑት መቼ ነው? **9** ጆሮን የተከለ እርሱ አይሰማምን? ዐይንን የሠራ እርሱ አያይምን? **10** ሕዝቦችን የሚገሥጸው አይቀጣምን? ለሰው ዕውቀት የሚሰጥ እርሱ ነው። **11** ያህዌ የሰው ሐሳብ ከንቱ እንደ ሆነ ያውቃል። **12** ያህዌ ሆይ፣ አንተ የምትገሥጸው ሕግህንም የምታስተምረው ሰው ቡሩክ ነው። **13** ለክፉዎች ጉድጓድ እስኪቆፈር ድረስ አንተ እርሱን ከመከራ ታሳርፈዋለህ። **14** ያህዌ ሕዝቡን አይጥልምና ርስቱንም አይተውም። **15** ፍርድ ተመልሶ በጽድቅ አሠራር ላይ ይመሠረታል ልበ ቀናዎችም ሁሉ ይከተሉታል። **16** ክፉዎችን የሚቋቋምልኝ ማን ነው? ከክፉ አድራጊዎች የሚሟገትልንስ ማን ነው? **17** ያህዌ ረዳቴ ባይሆን ኖሮ ፈጥኜ ወደ ዝምታው ዓለም በወረድሁ ነበር። **18** እኔ፣ «እግሬን አዳለጠኝ» ባልሁ ጊዜ ያህዌ ሆይ፣ ምሕረትህ ደግፎ ያዘኝ። **19** ሐዘኔ በበዛ ጊዜ፣ ማጽናናትህ ደስ አሰኘኝ። **20** ዓመፅን ሕጋዊ የሚያደርግ የጥፋት ዙፋን ከአንተ ጋር ሊያብር ይችላልን? **21** ጻድቃንን ለማጥፋት ያሤራሉ በንጹሑን ሰዎች ላይ የሞት ፍርድ ይበይናሉ። **22** ለእኔ ግን ያህዌ ጠንካራ ምሽግ አምላኬም መጠጊያ ዐለት ሆኖኛል። **23** ኃጢአታቸውን ወደ ራሳቸው ይመልሳል በገዛ ክፋታቸውም ያጠፋቸዋል። ያህዌ አምላካችን ይደመስሳቸዋል።

Psalms 94:1

አቃላይ መረጃ:
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

በላያችን አብራ
እዚህ ስፍራ "አብራ" የሚለው እግዚአብሔር ራሱን ለመግለጹ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "ራስህን አሳይ" ወይም "ክብርህን ግለጽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የምድር ዳኛ ሆይ ተነስ፣ ለኩሩዎች የሚገባቸውን ስጣቸው
"የምድር ዳኛ ሆይ ና፣ ኩሩዎችን ቅጣቸው"

ተነስ
ዘማሪው አንድ ነገር ማድረግ መጀመርን እንደ መነሳት አድርጎ ይገልጸዋል። የእናንተ ቋንቋ አንድን ድርጊት ለመጀመር የሚጠቀምበት ቃል ካለው እዚህ ስፍራ ተጠቀሙበት። "እርምጃ ውሰድ" ወይም "አንድ ነገር አድርግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 94:3

ያህዌ ሆይ ክፉዎች እስከ መቼ፣ እስከ መቼ ክፉዎች ደስ ይሰኛሉ?
ዘማሪው ጥያቄውን የሚደግመው፣ ክፉዎች ደስ ይላቸው ዘንድ ያህዌ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚፈቅድላቸው በመጠየቅ ደስ አለመሰኘቱን ለማሳየት ነው። ቃለ ምልልሳዊው ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊቀርብ ይችላል። "ያህዌ ሆይ በጣም ለረጅም ጊዜ ዝም አልካቸው፤ ክፉዎች በጣም ደስ እየተሰኙ እነርሱን ከመከልከል እጅግ ዘገየህ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ለምን ክፉዎች ደስ ይሰኛሉ
ለምን የክፉዎች ደስ መሰኘት በግልጽ ይታያል። "ክፉዎች ባደረጉት አንተ ፍጹም ስላልቀጣሃቸው እነርሱ ደስ ይሰኛሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ያንቆረቁራሉ/ያፈሳሉ
"ክፉ የሚያደርጉ ሁሉ ያንቆረቁራሉ"

የትዕቢት ቃሎቻቸውን ያንቆረቁራሉ
ዘማሪው የክፉዎችን ንግግር እንደሚፈስ ፈሳሽ አድርጎ ይጽፋል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉ የሚያደርጉ ሁሉ ይኩራራሉ
እነዚህ ሰዎች በክፉ ድርጊቶቻቸው እንደሚኩራሩ ትርጉሙ ይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ክፉ የሚያደርጉ ሁሉ በክፉ ድርጊታቸው ይኩራራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 94:5

አገሪቱን ጎዱ
እዚህ ስፍራ "አገር" የሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የአገሪቱን ህዝብ ያመለክታል። "የአገሪቱን ህዝብ አደቀቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አደቀቁ
ዘማሪው ሀይል ያላቸው ሰዎች ደካሞችን እንዳጠቁ የሚናገረው እነርሱን እንደ ማድቀቅ ወይም እንደ መሰባበር አድርጎ ነው። "መሰባበር" የሚለው በመዝሙር 72:4 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሙሉ ለሙሉ አጠፉ" ወይም "በታላቅ ሁኔታ ጎዱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መበለቲቱን
"ባሏ የሞተባት ሴት

አባት የሌላቸው
"አባቶቻቸው የሞቱባቸው ልጆች"

የያዕቆብ አምላክ ይህንን አላየም
"የእስራኤል አምላክ ያደረግነውን አላየም"

Psalms 94:8

አጠቃላይ መረጃ:
ጸሐፊው አሁን ክፉ ሰዎችን ያስተምራቸዋል።

እናንተ መቼ ትምህርት ታገኛላችሁ?
ቃለ ምልልሳዊው ጥያቄ ትኩረት የሚሰጠው ጸሐፊው በክፉ ሰዎች ላይ መቆጣቱን ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጽ ይችላል። "ከክፉ መንገዳችሁ ተመለሱ!" ወይም "ከስህተቶቻችሁ ተማሩ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጆሮን ያበጀው እርሱ አይሰማምን? ዐይንን የፈጠረው እርሱ አይመለከትምን?
እነዚህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች በዐረፍተ ነገር ወይም በትዕዛዝ መልክ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "ጆሮን የፈጠረው እግዚአብሔር እርሱ ይሰማል። ዐይንን የፈጠረው እግዚአብሔር እርሱ ይመለከታል" ወይም "እግዚአብሔር ጆሮን አበጅቷል፣ ስለዚህ እርሱ እንደማይሰማ አድርጋችሁ የምትቆጥሩትን ነገር አቁሙ። እግዚአብሔር ዐይኖችን ፈጥሯል፣ ስለዚህ እርሱ እንደማያይ ይምትሆኑትን አቁሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 94:10

አጠቃላይ መረጃ:
ጸሐፊው ክፉ ሰዎችን ማስተማሩን ቀጥሏል።

አገራትን የሚገስጽ እርሱ አያስተካክልምን?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። ያህዌ ህዝቡን እንደሚቀጣ ተጠቁሟል። "ያህዌ ህዝቡን እንደሚገስጽ ታውቃላችሁ፣ ስለዚህ ህዝቡን እንደሚያስተካክል እርግጠኞች መሆን ትችላላችሁ!" ወይም "እርሱ ህዝቡን ይቀጣል!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

እርሱ አይገስጽምን
ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊገለጽ ይችላል። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እግዚአብሔር ይገስጻል። "እርሱ ይገስጻል/ያርማል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። 2) እግዚአብሔር ይቀጣል። "እርሱ ይቀጣል" (ምጸት የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ተን ናቸው
እዚህ ስፍራ የሰዎች አስተሳሰብ የተነጻጸረው በአየር ላይ ከሚጠፋው ከተን ወይም እንፋሎት ጋር ነው። ይህ ዘይቤ የሚያመለክተው እነርሱ ምን ያህል የማይጠቅሙ እና የማይረቡ መሆናቸውን ለማሳየት ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ተን
"ጭጋግ።" ይህ ቃል በመዝሙር 39፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

Psalms 94:12

አጠቃላይ መረጃ:
አሁን ጸሐፊው ዳግም ከያህዌ ጋር ይነጋገራል።

ለክፉዎች ጉድጓድ እስኪቆፈር ድረስ
ዘማሪው ያህዌ ክፉዎችን መቅጣቱን የሚነሰገረው እንስሳን በወጥመድ እንደሚይዝ አድርጎ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንተ ለክፉዎች ጉድጓድ እስክትቆፍር ድረስ" ወይም "ክፉዎችን እስክታጠፋ ድረስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Psalms 94:14

የእርሱ ርስት
"ከእርሱ ጋር ለዘለዓለም እንዲሆኑ የመረጣቸው"

ፍርድ ዳግም ጽድቅ ይሆናል
ዘማሪው ፈራጆችን እንደሚሰጡት ውሳኔ አድርጎ ይገልጻቸዋል። "ፍርድ" የሚለው ረቂቅ ስም "ፈረደ" በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። "ዳኞች ዳግም በጽድቅ ይፈርዳሉ" ወይም "ዳኞች ዳግም ትክክለኛ ውሳኔ ይሰጣሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

በልባቸው ትክክለኛ የሆኑ
" በልባቸው ትክክለኛ የሆኑ" የሚለው ቅጽላዊ ሀረግ በስማዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "ልባቸው ከእግዚአብሔር ጋር ትክክል የሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)

ይህን ይከተላል
" ዳኞች በጽድቅ እንዲፈርዱ ይፈልጋል"

ክፉ አድራጊዎችን ማን ይቋቋምልኛል? በክፉ አድራጊዎች ላይ ስለ እኔ የሚከላከል ማን ነው?
ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ማንም ለእኔ ክፉ አድራጊዎችን የሚከላከልልኝ የለም። ክፉዎችን በመዋጋት እኔን የሚረዳኝ የለም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉዎች
"ክፉዎች" የሚለው ቅጽል በስማዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "ክፉ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 94:17

ያህዌ ረዳቴ ባይሆን ኖሮ...ዝምታ
ይህ መላምታዊ ሁኔታ ነው። ያህዌ እርሱን ረድቶታል፣ ስለዚህም እርሱ በዝምታ ስፍራ አልተጋደመም። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ ረዳቴ ባይሆን ኖሮ
"እርዳታ" የሚለው ረቂቅ ስም በግስ መልክ ሊገለጽ ይችላል። "ያህዌ ባይረዳኝ ኖሮ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በቶሎ በዝምታ ስፍራ እጋደማለሁ
እዚህ ስፍራ "እጋደማለሁ" የሚለው የሚያመለክተው "ሞትን" ሲሆን "በዝምታ ስፍራ" የሚለው የሚያመለክተው መቃብርን ነው። "በአጭር ጊዜ ውስጥ፣ ሞቼ በዝምታ ስፍራ እጋደማለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የፊምዝም/ሻል ያለ ቃል መጠቀም የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ ሆይ፣ የአንተ የቃል ኪዳን ታማኝነት አቁሞኛል
"ታማኝነት" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል መልኩ ሊተረጎም ይችላል። "ያህዌ ሆይ፣ አንተ ለቃል ኪዳንህ ታማኝ ነህና እርዳኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በውስጤ ያለው ሀዘን ሲበዛ፣ የአንተ ማጽናናት ደስተኛ ያደርገኛል
ዘማሪው ስለ ሀዘን የሚናገረው መከራዎቹን እንደሚቆጥራቸው አድርጎ ነው። "ማጽናናት" የሚለው ረቂቅ ስም "ማስተዛዘን" ወይም "ማጽናናት" በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። "ስለ ብዙ ነገሮች በምጨነቅበት ጊዜ፣ አንተ ታጽናናኛለህ ደግሞም ደስተኛም ታደርገኛለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 94:20

አመጻን ህጋዊ የሚያደርግ የጥፋት ዙፋን ከአንተ ጋር ሊተባበር ይችላልን?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የዋለው አንድን ጉዳይ ግልጽ ለማድረግ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "አፍትሃዊ ህግ የሚያወጣ ክፉ መሪ የአንተ ወዳጅ አይደለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የጥፋት ዙፋን
እዚህ ስፍራ "ዙፋን" የሚለው ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ንጉሥን ወይም መሪን ያመለክታል። "ክፉ መሪ" ወይም "ብልሹ ዳኛ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አድማ/ሴራ
x

Psalms 94:22

ያህዌ ከፍ ያለ ማማዬ ነው
እዚህ ስፍራ "ማማ" ጥበቃ ለሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "ያህዌ ከጠላቶቼ ጠበቀኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር የመሸሸጊያ አለት ሆነኝ
ዘማሪው እግዚአብሔር እርሱን መጠበቁን የገለጸው፣ ደህንነት ለማግኘት እንደሚሄድበት ስፍራ አድርጎ ነው። "አለት" እና "መሸሸጊያ" የሚሉት ቃላት በመዝሙር 62:7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ። "እግዚአብሔርን እንዲጠብቀኝ ለመንኩት፣ እርሱም በሀይሉ ጠበቀኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የገዛ ክፋታቸውን በራሳቸው ላይ ያመጣባቸዋል
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "በሌሎች ላይ ክፉ እንዳደረጉት በእነርሱ ላይ ያደርግባቸዋል" ወይም 2) "በሌሎች ላይ ባደረጉት ክፉ ነገሮች ሁሉ ይቀጣቸዋል።"

ይቆርጣቸዋል
ይህ "ይገድላቸዋል" ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በራሳቸው ክፋት
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ክፉ ነገሮችን ሲያደርጉ" ወይም 2) "ክፉ ነገሮች በማድረጋቸው ምክንያት።"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 95

1 ኑ፣ ያህዌን እናመስግን የመዳን ዐለታችን ለሆነው ለእርሱ በደስታ እንዘምር። **2** ወደ ፊቱ በምስጋና እንግባ በዝማሬም እናወድሰው። **3** ያህዌ ታላቅ አምላክ ነውና ከአማልክትም ሁሉ የበለጠ ታላቅ ንጉሥ ነው። **4** የምድር ጥልቆች በእጁ ናቸው የተራራ ጫፎችም የእርሱ ናቸው። **5** ባሕር የእርሱ ነው፤ እርሱ ሠራው እጆቹም የብሱን አበጁ። **6** ኑ እናምልከው እንስገድለትም በፈጠረን በያህዌ ፊት እንንበርከክ **7** እርሱ አምላካችን ነውና እኛ የመሰማሪያው ሕዝብ የእጁም በጐች ነን። ዛሬ ድምፁን ብትሰሙ **8** «በምድረ በዳ በነበራችሁበት ቀን በማሳህ፣ በመረባም እንዳደረጋችሁት ልባችሁን አታደንድኑት። **9** ሥራዬን ቢያዩም አባቶቻችሁ ፈተኑኝ፤ ተፈታተኑኝም፤ **10** ያንን ትውልድ አርባ ዓመት ሙሉ ተቆጣሁት፣ እኔም፣ «ልቡ የሸፈተ ሕዝብ ነው፤ መንገዴንም አላወቁም» አልሁ። **11** ስለዚህ፣ «በፍጹም ወደ እኔ ዕረፍቴ ቦታ አይገቡም» ብዬ በቁጣየ ማልሁ።

Psalms 95:1

አጠቃላይ መረጃ:
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

የደህንነታችን አለት
ዘማሪው ስለ ያህዌ የሚናገረው፣ ያህዌን ሰዎች ለደህንነታቸው እንደሚወጡት ተራራ አድርጎ ነው። "አለት" እና "የእኔ ደህንነት" የሚሉት በመዝሙር 18፡46 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ። "እኛ ልንሄድ የምንችልበት አለት እና እግዚአብሔር እኛን የሚያድንበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እርሱ መገኛ ግቡ
ዘማሪው አንባቢ ወደ አንድ ንጉሥ ክፍል እንዲገባ እንደሚናገር አድርጎ ይገልጻል። "እርሱ ወደሚገኝበት ሂዱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከምስጋና ጋር
"ወደ እርሱ መገኘት ስንገባ እናመስግነው"

ከአማልዕክት ሁሉ ይልቃል
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች፣ ያህዌ ታላቅ ንጉሥ ነው የሚል ነው። 1) "በሌሎች አማልዕክቶች ላይ ሁሉ የሚገዛ፣" ወይም 2) "ከሌሎች አማልዕክት ሁሉ በጣም የተሻለ።"

Psalms 95:4

በእርሱ እጅ
"በእርሱ ቁጥጥር" ወይም "እርሱ ሃላፊ ይሆናል" ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጥልቆች
x

Psalms 95:6

መንበርከክ
ብዙውን ጊዜ መሸነፍን ለማሳየት ሁለቱንም ጉልበቶች በመሬት ላይ ማድረግ። (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ የመሰማሪያው ህዝብ
"መሰማሪያ" የሚለው ቃል እንስሳት በሚሰማሩበት ስፍራ ስለሚያገኙት ምግብ ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሲሆን ይህም ደግሞ በተራው ያህዌ ለህዝቡ ለሚያደርገው አቅርቦት ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ነው። "እኛ የሚያስፈልገንን የሚያሟላን ህዝቡ ነን" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

መሰማሪያ
እንስሳት ለመጋጥ ሳር የሚያገኙበት አካባቢ

የእጁ በጎች
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው እረኛ በጎችን እንደሚጠብቅበት መንገድ ያህዌ እንዴት ህዝቡን እንደሚጠብቅ ነው። "እረኛ በጎቹን እንደሚጠብቅ እርሱ የሚጠብቃቸው ህዝቦች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ዛሬ እነሆ፣ የእርሱን ድምጽ ትሰማላችሁ!
"እነሆ፣ ዛሬ ድምጹን ትሰማላችሁ!" ዘማሪው ይሁነኝ ብሎ የሚናገረውን ይተረጉመዋል።

የእርሱን ድምጽ ስሙ
እዚህ ስፍራ "የእርሱ ድምጽ" የሚለው የሚወክለው የእግዚአብሔርን ንግግር ወይም እርሱ የተናገረውን ነው። "እግዚአብሔር ሲናገር አድምጡ" ወይም "እግዚአብሔር የሚናገረውን ስሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 95:8

አጠቃላይ መረጃ:
እዚህ ላይ ጸሐፊው ያህዌ የተናገራቸውን ቃላት ይጽፋል

ልባችሁን አደነደናችሁ
"ግትር ሆናችሁ"

መሪባ፣...ማሳህ
እነዚህ እስራኤላውያን በማመጻቸው ምክንያት ሙሴ የሰየማቸው በበረሃ የሚገኙ ስፍራዎች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

እኔን ፈተኑኝ...ተፈታተኑኝ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ያህዌ እነረሱን ከመቅጣቱ አስቀድሞ ህዝቡ ምን ያህል ክፉ ነገር በያህዌ ፊት ሊያደርጉ እንደሚችሉ የሚገልጹ ዘይቤዎች ናቸው። በመሰረቱ ሀረጎቹ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ በአንድ ላይ ሊቀናጁ ይችላሉ። "እኔን ፈተኑኝ" ወይም "እኔ ቅጣት ሳላደርስባቸው ክፉ ነገሮችን ማድረግ ይችሉ እንደሆነ ማየት ፈለጉ...እነርሱን መታገሴ ይቀጥል እንደሆነ ለማየት ተፈታተኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ጥንድ ትርጉም የሚሉትን ይመልከቱ)

የእኔ ስራዎች
"እኔ ያደረግኳቸው አስደናቂ ነገሮች

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 96

1 ለያህዌ አዲስ መዝሙር ዘምሩ ምድር ሁሉ ለእግዚአብሔር ዘምሩ **2** ለያህዌ ዘምሩ፤ ስሙንም ባርኩ ማዳኑንንም ዕለት በዕለት ተናገሩ። **3** ክብሩን በሕዝቦች መካከል ድንቅ ሥራውንም በሕዝቦች መካከል ተናገሩ። **4** እግዚአብሔር ታላቅ ነው፣ ከፍ ያለ ምስጋናም ይገባዋል ከአማልክት ሁሉ በላይ ሊፈራ ይገባዋል። **5** የሕዝቦች አማልክት ሁሉ ጣዖቶች ናቸው ያህዌ ግን ሰማያትን ሠራ። **6** ክብርና ግርማ በፊቱ ናቸው ብርታትና ውበትም መቅደሱ ውስጥ አሉ። **7** የሕዝብ ወገኖች ሁሉ ለያህዌ ምስጋና ስጡ ክብርንና ብርታትን ለያህዌ ስጡ። **8** ለስሙ የሚገባውን ክብር ለያህዌ ስጡ ስጦታ ይዛችሁ ወደ አደባባዩ ግቡ። **9** ክብርን በተሞላ ቅድስና ለያህዌ ስገዱ ምድር ሁሉ በፊቱ፤ ተንቀጥቀጡ። **10** በሕዝቦች መካከል፣ «እግዚአብሔር ነገሠ» በሉ፤ ምድር በጽኑ ስለ ተመሠረተች አትናወጥም። እርሱ ሕዝቦች ላይ በጽድቅ ይፈርዳል። **11** ሰማያት ደስ ይበላቸው፤ ምድርም ሐሴት ታድርግ። ባሕርና በውስጧ ያለው ሁሉ እልል ይበል። **12** መስክና በላዩ ያለው ሁሉ ይፈንጥዝ ያን ጊዜ የዱር ዛፎች ሁሉ በደስታ ይዘምራሉ። **13** እርሱ ይመጣልና በያህዌ ፊት ይዘምራሉ በምድር ላይ ሊፈርድ ይመጣል በዓለም ላይ በጽድቅ፣ በሕዝቦችም ላይ በእውነት ይበይናል።

Psalms 96:1

አጠቃላይ መረጃ:
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

አዲስ ዝማሬ
ማንም አስቀድሞ ያልዘመረው ዝማሬ

መላው ምድር
ይህ የምድር ሰዎችን በሙሉ ያመለክታል። "በምድር የሚኖሩ ሰዎች በሙሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ስሙን ባርኩ
"ስም" የሚለው ቃል ለያህዌ ለራሱ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ያህዌን ባርኩ" ወይም "ያህዌን ደስ የሚያሰኘውን አድርጉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። "ክቡር ስሙ ይባረክ" የሚለው በመዝሙር 72:19 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ማዳኑን ተናገሩ/አውጁ
"ደህንነት" የሚለው ረቂቅ ስም "አዳነ" የሚለውን ግስ በመጠቀም መተርጎም ይቻላል። "እርሱ እኛን እንደ አዳነን ተናገሩ" ወይም "እኛን ያዳነን እርሱ እንደሆነ ለሰዎች ተናገሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 96:3

በአገራት መሃል ክብሩን አውጁ
"ስለ እርሱ ታላቅ ክብር በየአገራቱ ለሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ተናገሩ"

ያህዌ ታላቅ ነው እጅግ ሊከበር ይገባዋል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ያህዌ ታላቅ ነው። እጅግ አድርጋችሁ አወድሱት" ወይም "ያህዌ ታላቅ ነው፣ እናም ሰዎች እጅግ ሊያወድሱት ይገባል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ከሌሎች አማልዕክት ሁሉ በላይ ሊፈራ ይገባዋል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ከሌሎች አማልዕክት በላይ ፍሩት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 96:5

እርሱ በሚገኝበት
"እርሱ ባለበት"

ውበት እና ግርማ በእርሱ ዘንድ ናቸው
ዘማሪው ውበትን እና ግርማን በንጉሥ ፊት እንደሚቆሙ ሰዎች አድርጎ ያቀርባቸዋል። "እያንዳንዱ የእርሱን ውበት እና ግርማ ያውቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥንካሬ/ብርታት እና ውበት በቅድስናው ስፍራ ናቸው
"ጥንካሬ/ብርታት" እና "ውበት" የሚሉት ቃላት በተቀደሰው ስፍራ ለሚገኘው ለቃል ኪዳኑ ምስክር ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ናቸው። "የቃል ኪዳኑን ታቦት ህግ/ድንጋጌ የያዘው የእርሱ ቅዱስ ስፍራ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 96:7

ያህዌን እንዲህ በሉት...ስለ እርሱ ክብር እና ብርታት ያህዌን እንዲህ በሉት
"ውዳሴ፣" "ክብር፣" እና "ብርታት" የሚሉትን ረቂቅ ስሞች እንደገና መግለጽ ይቻላል። እነዚህ ቃላት በመዝሙር 29:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ። "ያህዌን አወድሱት...ያህዌን አወድሱት ምክንያቱም እርሱ ክቡር እና ብርቱ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ለያህዌ ስም የሚገባውን ክብር ስጡ
"ክብር" የሚለው ረቂቅ ስም በግስ ወይም ቅጽል መልክ ሊገለጽ ይችላል። እነዚህ ቃላት በመዝሙር 29:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ። "ስሙ እንደሚገባው ልክ ያህዌን አክብሩ" ወይም "እንደ ስሙ ታላቅነት ያህዌ ክቡር መሆኑን አውጁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ ስም የተገባው ነው
እዚህ ስፍራ "ስም" የእግዚአብሔርን ማንነት ያመለክታል። "እርሱ ይገባዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ አደባባይ
ካህናት ለያህዌ እንስሳትን የሚሰዉበት የቤተ መቅደሱ አደባባይ

Psalms 96:9

ለያህዌ ስገዱ
በውስጠ ታዋቂነት የተነገረው መረጃ ሰዎች በአምልኮ ጊዜ ጎነበስ በለው እንደሚሰግዱ ነው። "ያህዌን ለማምለክ ጎንበስ ብላችሁ ስገዱ" በሚለው

ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በቅድስና ውበት
"ውበት" እና "ቅድስና" የሚሉት በቅጽል መልክ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "እርሱ በክብር ውብ እና ቅዱስ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ተናወጠች
ከፍርሃት የተነሳ መንቀጥቀጥ

ምድር ሁሉ
እዚህ ስፍራ "ምድር" የሚለው የሚወክለው ሰዎችን ነው። "የምድር ህዝብ በሙሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ምድርም ደግሞ ተመሰረተች
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እርሱ ደግሞ ዓለምን መሰረታት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሷ ልትናወጥ አትችልም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ምንም ነገር ሊያናውጣት አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 96:11

ሰማያት ሀሴት ያድርጉ፣ ምድርም ደስ ይበላት
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሰማያት እና ምድር የተገለጹት እንደ ሰዎች ሁሉ ስሜት እንዳላቸው ተደርጎ ነው። "ሰማያት ሀሴትን እንዳደረጉ ምድርም ደስ እንዳላት ይሁን" ወይም 2) "ሰማያት" እና "ምድር" በእነዚያ ስፍራዎች ለሚኖሩ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ናቸው። "በሰማያት የሚኖሩ ሀሴት ያድርጉ በምድር የሚኖሩም ደስ ይበላቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

በደስታ ጩኽት የተሞላ
በውስጠ ታዋቂነት የተነገረው መረጃ በባህር ውስጥ የሚኖሩ ፍጥረታትን ያመለክታል። እነርሱ የተገለጹት እንደ ሰዎች በደስታ መጮህ እንዳለባቸው ተደርጎ ነው። "የባህር ፍጥረታት በደስታ ጮሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መስኮች እና በውስጣቸው የሚገኙ ሁሉ ደስ ይበላቸው
"መስኮች እና በውስጣቸው የሚገኙ ሁሉ ደስ ይበላቸው።" ዘማሪው የሚናገረው "መስኮች" እና በውስጣቸው የሚኖሩ እንስሳት እንደ ሰዎች ስሜት እንዳላቸው አድርጎ ነው። "መስኮች ራሳቸው እና በውስጣቸው የሚኖሩ እንስሳት ሁሉ ደስ እንደሚላቸው ይሁኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በዱር የሚገኙ ዛፎች በደስታ ይጩሁ
ይህ ስለ ዛፎች የሚናገረው በደስታ እንደሚጮሁ ሰዎች አድርጎ ነው። "በጫካ የሚገኙ ዛፎች ሁሉ በደስታ እንደሚጮሁ ይሁን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ በምድር ለመፍረድ ይመጣል። እርሱ በምድር ... እና በሰዎች ይፈርዳል
ሶስቱም ሀረጋት ተመሳሳይ ትጉም አላቸው፤ የመጨረሻዎቹ ሁለት ሀረጋት የመጀመሪያውን ለማጠናከር ውለዋል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለመፍረድ... ይፈርዳል
ሌላው ሊሰጥ የሚችለው ትርጉም "ለመግዛት...ይገዛል" የሚል ነው።

እርሱ በምድር ላይ በጽድቅ ይፈርዳል
እዚህ ስፍራ "ምድር" የሚለው በምድር ላይ ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። እነዚህ ቃላት በመዝሙር 9፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ። "እርሱ በምድር ሰዎች ላይ ሁሉ በጽድቅ ይፈርዳል። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሰዎች በእርሱ ታማኝነት
"እርሱ ይፈርዳል" የሚሉት ቃላት በውስጠ ታዋቂነት አሉ። "እርሱ በሰዎች ላይ በእርሱ ታማኝነት ይፈርዳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/ የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ ታማኝነት
"ታማኝነት" የሚለውን ረቂቅ ስም ለመተካት እንደገና ሊጸፍ ይችላል። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "በትክክል፣ እርሱ የሚያውቀው እውነት በመሆኑ" ወይም 2) "ለሁሉም ሰዎች ያለ አድልኦ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 97

1 እግዚአብሔር ነገሠ ምድር ደስ ይበላት፤ በሩቅ ያሉ የባሕር ጠረፎች ሐሤት ያድርጉ። **2** ደመናና ጥቅጥቅ ያለ ጭጋግ በዙሪያው አለ ጻድቅና ፍትሕ የዙፋኑ መሠረት ናቸው። **3** እሳት በፊቱ ይሄዳል በዙሪያው ያሉ ባላንጣዎቹን ይፈጃል። **4** መብረቁ ዓለምን አበራ ምድር ዐይታ ተንቀጠቀጠች። **5** ተራሮች ያህዌ ፊት የምድር ሁሉ ጌታ ፊት እንደ ሰም ቀለጡ **6** ሰማያት ጽድቁን ያውጃሉ ሕዝቦችም ሁሉ ክብሩን ያያሉ። **7** የተቀረጹ ምስሎች የሚያመልኩ፣ በጣዖቶች የሚመኩ ሁሉ ይፈሩ እናንት አማልክት ሁላችሁ ለእርሱ ስገዱ **8** ያህዌ ሆይ፣ ስለ ፍርድህ ጽዮን ሰምታ ደስ አላት የይሁዳም ከተሞች ሐሤት አደረጉ። **9** ያህዌ ሆይ፣ አንተ በምድር ሁሉ ልዑል ነህና ከአማልክት ሁሉ ይልቅ እጅግ ከፍ ያልህ ነህ። **10** ያህዌን የምትወዱ ክፋትን ጥሉ! እርሱ የቅዱሳኑን ሕይወት ይጠብቃል ከክፉዎችም እጅ ይታደጋቸዋል። **11** ብርሃን ለጻድቃን ሐሤትም ለልበ ቅኖች ወጣ። **12** እናንተ ጻድቃን በያህዌ ደስ ይበላችሁ ቅዱስ ስሙንም አመስግኑ።

Psalms 97:1

አጠቃላይ መረጃ:
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ምድር ደስ ይበላት፤ የባህር ዳርቻዎችም ሀሴት ያድርጉ
ምድር እና የባህር ዳርቻ እንደ ሰው ስሜት እንዲኖራቸው ተነግሯል። "በምድር ላይ እና በባህር ዳርቻ ያላችሁ ሰዎች ሁሉ ሀሴት አድርጉ ደስም ይበላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የባህር ዳርቻዎች
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "በባህር ዳርቻ የሚገኝ መሬት" ወይም 2) "ደሴቶች።"

ደመናዎች እና ጨለማ እርሱን ከቦታል
"በዙሪያው ደመና ከቦት በጨለማ እንደተቀመጠ ሁሉ፣ እርሱን ልንመለከተው አንችልም"

ጽድቅ እና ፍትህ የዙፋኑ መሰረቶች ናቸው
"ዙፋን" የሚለው ቃል በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ተግባራት እና ቃላት ሜቶኖሚ/ ነው። ዘማሪው ጽድቅ እና ፍትህ ዙፋኑን የሚጠብቁ ቁሳዊ አካሎች እንደሆኑ አድርጎ ይገልጻል። "እርሱ በስራዎቹ ሁሉ ጻድቅ እና ትክክለኛ ነው" ወይም "እርሱ መግዛት ይችላል ምክንያቱም እርሱ በጽድቅ እና በፍትሃዊነት ይመራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

የዙፋኑ መሰረቶች
እዚህ ስፍራ "የዙፋኑ መሰረቶች" የሚለው የሚያመለክተው ያህዌ መንግሥቱን እንዴት እንደሚገዛ ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 97:3

እሳት በፊቱ ይሄዳል
ዘማሪው እሳትን ከንጉሡ ያህዌ ፊት እንደሚሄድ ሰው እንደሆነ አድርጎ ይገልጻል፤ ደግሞም ለሰዎች ንጉሡ እየመጣ እንደሆነ ይናገራል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ተቃዋሚዎቹን ይበላል
"ጠላቶቹን ያቃጥላል"

ምድር ተመለከተች ተንቀጠቀጠችም
ጸሐፊው ስለ ምድር ያህዌ የሚያደርገውን የምትመለከት ሰው እንደሆነች እና በፍርሃት እንደምትንቀጠቀጥ አድርጎ ይገልጻታል። "ምድር እንደ ሰው ትመለከታለች ደግሞም ትንቀጠቀጣለች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ተናወጠች
ከፍርሃት የተነሳ መንቀጥቀጥ

ተራሮች በያህዌ ፊት እንደ ሰም ይቀልጣሉ
ጸሐፊው ተራሮች በያህዌ ፊት እሳት ፊት እንዳለ ሰም እንደሚቀልጡ ይናገራል። "ተራሮች ያህዌ ሲቀርባቸው በፊቱ ሊቆሙ አይችሉም" ወይም "ተራሮች በያህዌ መገኘት ይወድቃሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 97:6

ሰማያት የእርሱን ፍርድ ያውጃሉ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ዘማሪው ሰማያት የያህዌን ትክክለኛነት የሚናገሩ መልዕክተኞች አድርጎ ይገልጻል። "ሁሉም ሰማይን ቀና ብሎ ማየት የሚችለውን ያህል እግዚአብሔር ትክክለኛ መሆኑን ማየት ይችላል" ወይም 2) ሰማያት የሚለው የሚገልጸው በሰማይ የሚኖሩ ፍጥረታትን ነው። "በሰማይ የሚኖሩ ሁሉ ያህዌ ትክክለኛ መሆኑን ያውጃሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

የተቀረጹ ምስሎችን እና እርባ ቢስ የሆኑ ጣኦታትን የሚያመለኩ ሁሉ ያፍራሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እግዚአብሔር በእርባና ቢስ ጣኦቶች የሚመኩትን እና የተቀረጹ ምስሎችን የሚያመለኩት ያሳፍራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ እና ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ጽዮን ሰማች...የይሁዳ ከተሞች
ይህ የሚያመለክተው በእነዚህ ምድሮች የሚኖሩ ሰዎችን ነው። "የጽዮን ሰዎች ሰሙ...የይሁዳ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 97:9

ከሁሉ በላይ ከፍ ያሉ ናቸው
ዘማሪው ለመግዛት በጣም ጠንካራ የሆኑት በአካል ኬሎቹ ከፍ ያሉ እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። "በዚያ ከሚኖሩ ሰዎች በላይ ሆነው የሚገዙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

አንተ እሰከ ሩቅ ከፍ ብለሃል
ዘማሪው ለመግዛት በጣም ጠንካራ የሆኑት በአካል ኬሎቹ ከፍ ያሉ እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። "አንተ እስከ ሩቅ ከፍ ያልክ ነህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ከክፉዎች እጅ ያስጥላቸዋል
"እጅ" የሚለው ቃል የሚወክለው ሀይልን ነው። ያህዌ ሰዎችን ከክፉዎች ሀይል ማዳኑ የተገለጸው ከእጃቸው እንደሚወስዳቸው/እንደሚያስጥላቸው ተደርጎ ነው። "እርሱ ከክፉዎች ሀይል ያድናቸዋል" በሚለው ውስጥ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ብርሃን ለ...ይዘራል፣ ደስታ ደግሞ ለ...
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ደግሞም ትኩረት ለመስጠት በእንድነት ቀርበዋል። "ያህዌ ትክክለኛ ስራ ለሚሰሩ ብርሃን ያወጣላቸዋል/ይዘራል፤ እውነተኛ ልብ ላላቸው ደስታን ይጨምርላቸዋል/ ይዘራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ እንደዚሁም የተተወ/የተዘለለ የሚሉትን ይመልከቱ)

ለጻድቃን ብርሃን ይወጣላቸዋል/ይዘራል
"መውጣት/መዝራት" የሚለው ቃል ወደፊት ውጤቱ ለሚታወቅ ነገር ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "ብርሃን" ለመልካም ነገር ዘይቤ ነው። "ያህዌ ለጻድቃን መልካም እንደሚሆን ያስባል/ያቅዳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጻድቃን
"ጻድቅ" የሚለው ቅጽል በስማዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "ጻድቅ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)

ሀቀኛ/ትክክለኛ ልብ ላላቸው ደስታ ይሆናል
"ይዘራል/ይሆናል" የሚለው ቃል በውስጠ ታዋቂነት አለ። "መዝራት" የሚለው ቃል ወደፊት ውጤቱ ለሚታወቅ ነገር ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "ደስተኛነት" የሚለው ረቂቅ ስም "ደስታ" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "ደስተኝነት ሀቀኛ ልብ ላላቸው ይዘራል" ወይም "ያህዌ ሀቀኛ ልብ ያላቸው ወደፊት ደስተኛ ይሁኑ ዘንድ ያቅዳል/ያስብላቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ እና ዘይቤያዊ አነጋገር እንደዚሁም ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

ሀቀኛ ልብ ያላቸው
ልብ ለሰው ጠቅላላ ማንነት ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ነው። "ሀቀኛ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 97:12

አጠቃላይ መረጃ፡
ይህ ሀረግ ለትዕዛዙ ምክንያት የሆነውን ትዕዛዝ ይዟል። የእናንተ ቋንቋ ትዕዛዙን የሚከተል ምክንያት የሚፈልግ ከሆነ፡ "ያህዌ ለእናንተ ካደረገው ነገር የተነሳ፣ እናንተ ጻድቃን ሆይ፣ ቅድስናውን ስታስታውሱ ደስ ይበላችሁ ምስጋናም አቅርቡ"

በያህዌ ደስ ይበላችሁ
የዚህ ፈሊጥ ትርጉም ያህዌ ካደረገው ነገር የተነሳ ደስ መሰኘት ማለት ነው። "ያህዌ ካደረገው ነገር የተነሳ ደስ ይበላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ቅድስናውን ስታስታውሱ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "እርሱ ምን ያህል ቅዱስ እንደሆነ በምታስታውሱበት ጊዜ" ወይም 2) "ለቅዱሱ ስሙ፣" ይህም "ለእርሱ" ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 98

1 እርሱ ድንቅ ነገሮችን አድርጐአልና ለያህዌ አዲስ መዝሙር አቅርቡ ቀኝ እጁ፣ ቅዱስ ክንዱም ድል ሰጥተውታል። **2** ያህዌ ማዳኑን አሳወቀ ጽድቁንም ለሕዝቦች ሁሉ በግልጽ አሳየ። **3** ለእስራኤል ቤት ምሕረቱን ታማኝነቱንም አሰበ። የምድር ዳርቻዎች ሁሉ የአምላካችንን ድል አድራጊነት አዩ። **4** ምድር ሁሉ ለያህዌ እልል በሉ ውዳሴ አፍልቁ፤ በደስታና በዝማሬ አመስግኑ። **5** በገና በመደርደርና በመዝሙር ለያህዌ ምስጋና አቅርቡ። **6** በመለከትና በእምቢልታ ድምፅ በንጉሡ በያህዌ ፊት እልል በሉ። **7** ባሕርና በውስጡ ያለው ሁሉ ዓለምና የሚኖሩባትም ሁሉ ያስገምግሙ **8** ወንዞች ያጨብጭቡ ተራሮችም በደስታ እልል ይበሉ። **9** ያህዌ በምድር ላይ ለመፍረድ ይመጣል በዓለም ላይ በጽድቅ በሕዝቦችም ላይ በእውነት ይበይናል።

Psalms 98:3

አሰበ
"አስታወሰ።" በመዝሙር 20፡3 ላይ "አሰበ" የሚለው እንዴት እንደ ተተረጎመ ይልከቱ። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የምድር ዳርቻ ሁሉ...መላው ምድር
እነዚህ ለምድር ሰዎች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ናቸው። "ከመላው ምድር የሆኑ ሰዎች...በምድር ያሉ ሰዎች ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የአምላካችንን ድል ማድረግ ይመለከታሉ
"ድል" የሚለው ረቂቅ ስም "አሸነፈ" የሚለውን ግስ በመጠቀም ሊተረጎም ይችላል። "አምላካችን ጠላቶቹን ሲያሸንፍ ይመለከታሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በዝማሬ ይሞላሉ/እልል ይላሉ
"በድንገት በደስታ መዘመር ይጀምራሉ"

በደስታ ትዘምራላችሁ
"ከደስታ የተነሳ ትዘምራላችሁ"

በውዳሴ መዘመር
"ለእግዚአብሔር በውዳሴ መዘመር"

Psalms 98:5

ጣዕመ ዝማሬ
በደስታ የተሞላ ወይም ደስ የሚያሰኝ የሙዚቃ ድምጽ

የቀንድ መለከት
እንደ ሙዚቃ መሳሪያ የሚያገለግል የእንስሳ ቀንድ

ደስ የሚያሰኝ ድምጽ ማሰማት/ማውጣት
"ከፍ ያለ ድምጽ ማሰማት/እልል ማለት።" በመዝሙር 47፡1 ላይ "ጩኹት" የሚለው ድምጽ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

Psalms 98:7

ባህር እና በውስጡ የሚገኘው ሁሉ እልል ይበል
ዘማሪው ባህርን ወደ እግዚአብሔር እንደ ሚጮህ ሰው አድርጎ ይገልጸዋል። "ባህር እና በውስጡ የሚገኘው ሁሉ እልል ይበሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዓለም እና በውስጧ የሚኖሩ ሁሉ
ዘማሪው የሚነገረው ዓለም ሰው እንደሆነች አድርጎ ነው። "እናም ዓለም እና በውስጧ የሚኖሩ ሁሉ እልል ይበሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/ የተዘለለ እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ወንዞች በእጆቻቸው ያጨብጭቡ፣ ደግሞም ተራሮች በደስታ እልል ይበሉ
ዘማሪው ወንዞች እና ተራሮች ማጨብጨብ እና እልል ማለት እንደሚችሉ አድርጎ ይናገራል። "ወንዞች ማጨብጨብ እንደሚችሉ እና ተራሮች በደስታ እልል ማለት እንደሚችሉ ይሁኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዓለም... አገራት
እነዚህ ሀረጎች "በዓለም ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች" እና "በአገራት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች" ሜቶኖሚ ናቸው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አገራት በትክክለኝነት
ግሱ ከቀደመው ሀረግ ሊወሰድ ይችላል። "እርሱ አገራትን በትክክል ይዳኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/ የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

በትክክለኝነት
"በእውነተኝነት" ወይም "ያለ አድልኦ"

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 99

1 ያህዌ ነገሠ፤ ሕዝቦች ይንቀጥቀጡ በኪሩቤል ላይ በዙፋኑ ተቀምጧል፤ ምድር ትናወጥ። **2** ያህዌ በጽዮን ታላቅ ነው ከሕዝቦችም ሁሉ በላይ ከፍ ያለ ነው። **3** ታላቁንና አስፈሪውን ስምህን ይወድሱ እርሱ ቅዱስ ነው። **4** ፍትሕ የምትወድ ኃያል ንጉሥ ሆይ ጽድቅንና ፍትሕን ለያዕቆብ አደረግህ። **5** አምላካችን ያህዌን አመስግኑት በእግሩ መርገጫ ስገዱ። እርሱ ቅዱስ ነው። **6** ሙሴና አሮን ካህናቱ መካከል ነበሩ ሳሙኤልም ስሙን ከጠሩት መካከል ነበረ እነርሱ ወደ ያህዌ ጸለዩ እርሱም መለሰላቸው። **7** በደመና ዐምድ ውስጥ ተናገራቸው እነርሱም ሥርዐቱንና የሰጣቸውን ድንጋጌ ጠበቁ። **8** አምላካችን ያህዌ ሆይ፣ አንተ መለስህላቸው ይቅር ባይ አምላክ ሆንህላቸው ኃጢአታቸውን ግን ቀጣህ። **9** አምላካችን ያህዌን አመስግኑ አምላካችን ያህዌ ቅዱስ ነውና በቅዱስ ተራራው ሰገዱ።

Psalms 99:1

አጠቃላይ መረጃ፡
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

አገራት
ይህ የሁሉንም አገራት ሰዎች ያመለክታል። "የሁሉም አገራት ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

መናወጥ
በፍርሃት መንቀጥቀጥ

እርሱ ከኪሩቤል በላይ በዙፋኑ ተቀምጧል
ኪሩቤል በቃል ኪዳኑ ታቦት መክደኛ ላይ የሚገኙ መሆኑን ግልጽ ማድረግ ሊያስፈልግ ይችላል። የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፍት ብዙወን ጊዜ ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት፣ የያህዌ በላይ በሰማይ ተቀምጦ የቃል ኪዳኑ ታቦት የእግሩ ማረፊያ እንደሆነ አድርገው ይገልጻሉ። "እርሱ በዙፋኑ ላይ ከኪሩቤል በላይ በቃል ኪዳኑ ታቦት ተቀምጧል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ተናወጠ
ተንቀጠቀጠ

ያህዌ በጽዮን ታላቅ ነው፤ እርሱ ከአገራት ሁሉ በላይ ከፍ ብሏል
"ያህዌ ታላቅነቱ በጽዮን ብቻ አይደለም፣ በአገራት ሁሉ ላይ እርሱ ከፍ ያለ ነው" ወይም "ያህዌ የሚገዛው በጽዮን ላይ ብቻ አይደለም፣ እርሱ በአገራት ሁሉ ላይ ይገዛል"

እርሱ በአገራት ሁሉ ላይ ከፍ ያለ ነው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በሁሉም አገራት የሚኖሩ ሰዎች እርሱን ከፍ ያደርጉታል" ወይም "የአገራት ሁሉ ህዝቦች በታላቅ ሁኔታ ያወድሱታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ እና ተደራጊ እንደዚሁም ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

ታላቁን እና አስደናቂ ስምህን ያወድሱ
እዚህ ስፍራ ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር ከመናገር፣ ለእግዚአብሔር ወደ መናገር ዘወር ይላል። በእርግጥ ከዚህ ሀረግ በኋላ ዳግም ተመልሶ ስለ እግዚአብሔር ይናገራል።

Psalms 99:4

እርሱ ፍትህን ይወዳል
"ፍትህ" የሚለው ረቂቅ ስም ትክክለኛ ለሆኑ ህጎች ሜቶኖሚ/ ነው። "አንተ የመሰረትካቸው ህጎች ትክክለኞች ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

በእግሩ መቀመጫ ስር አምልኩት
"የእግር መቀመጫ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው፤ ብዙውን ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች የያህዌ በላይ በሰማይ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ፣ ያህዌ እግሩን የሚያሳርፍበት አድርገው የሚገልጹትን የቃል ኪዳኑን ታቦት ይሆናል። ሰዎች ያህዌን ሊያመልኩ እንደሚገባ ትርጉሙ ግልጽ ሊያደርግ ይችላል። "በእግሩ ማስቀመጫ ስር ሆናችሁ ያህዌን አምልኩት" ወይም "ያህዌን በመቅደሱ በዙፋኑ ፊት አምልኩት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 99:6

የከበረ
"ጠቃሚ፣ ትኩረት የተሰጠው"

Psalms 99:8

አንተ መለስክላቸው
"አንተ ለህዝብህ ምላሽ ሰጠህ"

የእርሱ ቅዱሱ ተራራ
"የጽዮን ተራራ"

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 100

1 ምድር ሁሉ ለያህዌ እልል በሉ **2** ያህዌን በደስታ አገልግሉት። በደስታ ዝማሬ ፊቱ ቅረቡ **3** ያህዌ አምላክ መሆኑን ዕወቁ እርሱ ፈጠረን፤ እኛም የእርሱ ነን። እኛ ሕዝቡ የመሰማሪያውም በጎች ነን። **4** በምስጋና ወደ ደጆቹ፣ በውዳሴም ወደ አደባባዮቹ ግቡ። አመስግኑት ስሙንም ባርኩ፤ **5** ያህዌ ቸር ነው፤ ምሕረቱም ለዘላለም ነው፤ ታማኝነቱም ከትውልድ እስከ ትውልድ ነው።

Psalms 100:1

አጠቃላይ መረጃ:
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

በደስታ ለያህዌ እልል በሉ
"ወደ ያህዌ እልልታ አሰሙ።" "እልልታ/የደስታ ጩኸት" የሚለው በመዝሙር 47፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

መላው ምድር
ይህ መላውን የምድር ህዝብ ያመለክታል። "በምድር ያለ ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

ወደ መገኙቱ ቅረቡ/ኑ
ዘማሪው አንባቢያን የንጉሡ ዙፋን ወደሚገኝበት ክፍል እንዲሄዱ እንደሚናገር አድርጎ ይገልጻል። "እርሱ በደስታ ዝማሬ ወደሚገኝበት ሂዱ" ወይም "እርሱ ይሰማችኋልና በደስታ ዘምሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 100:3

የመሰማሪያው በጎች
የእግዚአብሔር ህዝብ እንደ እርሱ በጎች ነው። "እግዚአብሔር አቅርቦት የሚያደርግለት እና የሚጠብቀው ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መሰማሪያ
እንስሳት የሚግጡበት/የሚሰማሩበት ሳራማ አካባቢ

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 101

1 ያህዌ ሆይ፣ ስለ ታማኝነትህና ስለ ትክክለኛ ፍርድህ ምስጋና እዘምራለሁ። **2** ነቀፋ በሌለበት መንገድ እሄዳለሁ አንተ ወደ እኔ የምትመጣው መቼ ነው? በቤቴ ውስጥ ያለ ነቀፋ እመላለሳለሁ። **3** በዐይኖቼ ፊት በደል አላኖርም የክፉዎችን ሥራ እጠላለሁ ከቶም አልተባበራቸውም። **4** ጠማማ ሰዎች ከእኔ ይርቃሉ ከክፋት ጋር ምንም ግንኙነት የለኝም። **5** ባልንጀራውን በስውር የሚያማውን አጠፋለሁ። ትዕቢተኛ ዐይንና እብሪተኛ ልብ ያለውን ሰው አልታገሠውም። **6** ከእኔ ጋር እንዲኖሩ፣ ዐይኖቼ በምድሪቱ ያሉ ታማኞች ላይ ናቸው በንጹሕና የሚሄድ እርሱ ያገለግለኛል። **7** አታላይ ሰው ቤቴ ውስጥ አይኖርም ሐሰተኛም በዐይኖቼ ፊት አይከብርም። **8** በምድሪቱ ያሉትን ክፉ አድራጊዎች በየማለዳው አጠፋቸዋለሁ፤ ክፉ አድራጊዎችን ሁሉ ከያህዌ ከተማ አስወግዳቸዋለሁ።

Psalms 101:1

አጠቃላይ መረጃ:
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

የቃል ኪዳን ታማኝነትን እና ፍትህን እዘምራለሁ
"ታማኝነት" እና "ፍትህ" የሚሉት ረቂቅ ስሞች በቅጽል መልክ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "አንተ ለቃል ኪዳንህ ታማኝ እንደሆንክ እና ፍትሃዊ እንደሆንክ እዘምራለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 101:2

በአንድነት መንገድ እሄዳለሁ
እዚህ ስፍራ ዳዊት ስለ "መኖር" የሚናገረው "መራመድ" እንደሆነ አድርጎ ነው። "እውነተኛ እና ትክክለኛ በሆነ መንገድ እኖራለሁ" ወይም "አንድነት/ሀቀኝነት የተሞላ ህይወትን እኖራለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በቤቴ ውስጥ በአንድነት/ሀቀኝነት እራመዳለሁ
እዚህ ስፍራ ዳዊት ስለ "መኖር" የሚናገረው መኖር "መራመድ" እንደሆነ አድርጎ ነው። ዳዊት አንድነትን በቤቱ ውስጥ ተወስኖ እንደሚኖር አካላዊ ቁስ አድርጎ ቢመለከትም፣ ቤቱን በአንድነት እንደሚቆጣጠር ይናገራል። "ቤቴን በአንድነት/በሀቀኝነት እቆጣጠራለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በዐይኖቼ ፊት ትክክለኛ ያልሆኑ ስራዎችን አላኖርም
"ትክክለኛ ያልሆኑ" የሚለውን ረቂቅ ስም ዳግም ማስተካከል ይቻላል። "ክፉ የሆነውን በዐይኖቼ ፊት ማኖር፣" የሚለው ፈሊጥ ትርጉም ይህ ማረጋገጥ ማለት ነው። "እኔ ባለሁበት ለማናቸውም ትክክለኛ ያልሆነ ድርጊት ለሚፈጽም ይሁንታ አልሰጥም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

በእኔ ላይ አይጣበቅም
ዳዊት "ክፉውን" በእርሱ ላይ ሊጣበቅ እንደማይችል ነገር አድርጎ ይናገራል። ይህም ማለት ክፉ ነገሮች እና ሰዎች ክፉ እንዳያደርጉ ይከለክላቸዋል ማለት ነው። "ክፉውን ፍጹም አስወግደዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መጣበቅ
ከአንድ ነገር ወይም ከአንድ ሰው ጋር በጣም በጥብቅ መያያዝ

Psalms 101:4

ለክፉ
"ክፉ ለሆነ ማናቸውም ነገር"

በትዕቢት የሚያዋርድ እና እብሪተኛ ዝንባሌ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው እንዲህ አይነት ሰዎች እንዴት እንደሚታበዩ ትኩረት ይሰጣሉ። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

በትዕቢት የሚያዋርዱ
"በግልጽ የሚታይ ትዕቢት።" ይህ ትዕቢቱን ማንም በግልጽ ሊመለከተው ስለሚችለው ሰው ይናገራል።

ትሁቱ ከጎኔ እንዲቀመጥ አደርጋለሁ
ይህ ማለት ዳዊት እንዲህ ያሉ ሰዎች በእርሱ ዙሪያ እንዲሆኑ እና ከእርሱ ጋር እንዲኖሩ ይፈቅዳል። "በምድሪቱ የሚገኙ ታማኝ ሰዎች ከእኔ ጋር እንዲኖሩ እፈቅዳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ታማኞች
ይህ ለእግዚአብሔር ታማኝ የሆኑ ሰዎችን ያመለክታል። "ታማኝ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

በአንድነት መንገድ የሚራመዱ
እዚህ ስፍራ ዳዊት ስለ "መኖር" የሚናገረው "መራመድ" እንደሆነ አድርጎ ነው። "ሀቀኛ እና ትክክለኛ በሆነ መንገድ መኖር" ወይም "በሀቅ የተሞላ ህይወትን መኖር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 101:7

አስመሳይ ሰዎች...ሀሰተኛ ሰዎች
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ሀሳብ ሲኖራቸው በአንድነት የዋሉት ዳዊት አስመሳዮችን እንደማይታገስ ትኩረት ለመስጠት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሀሰተኞች ተቀባይነት የላቸውም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሀሰተኞችን አልቀበላቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በዐይኖቼ ፊት
እዚህ ስፍራ "የእኔ ዐይኖች" የሚለው የሚያመለክተው ራሱን ዳዊትን ነው። "በእኔ ፊት" ወይም "እኔ በምገኝበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በየማለዳው
"በየዕለቱ)

ክፉዎች
ይህ የሚያመለክተው ክፉ ሰዎችን ነው። "ክፉ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከያህዌ ከተማ
ዳዊት እርሱ የሚገኝበትን ከተማ "የያህዌ ከተማ" በማለት ይጠራታል።ይህ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "የያህዌ ከተማ ከሆነችው፣ ከዚህች ከተማ"

በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 102

1 ያህዌ ሆይ ጸሎቴን ሰማ ጩኸቴንም አድምጥ። **2** በመከራዬ ጊዜ ፊትህን ከእኔ አትሰውር ጆሮህን ወደ እኔ አዘንብል ወደ አንተ ስጣራ ፈጥነህ አድምጠኝ። **3** ዘመኔ እንደ ጢስ እየበነነ ነው ዐጥንቶቼም እንደ እሳት እየነደዱ ነው። **4** ልቤ ተሰብሮአል፤ እኔም እንደ ደረቀ ሣር ሆኛለሁ። እህል መብላትንም ዘንግቻለሁ። **5** ዘወትር ከመቃተቴ የተነሣ ዐጥንቴ ከቆዳዬ ጋር ተጣበቀ። **6** በምድረ በዳ እንዳለ እርኩም መሰልሁ፤ በፍርስራሽ መካከል እንዳ ጉጉት ሆንሁ። **7** ያለ እንቅልፍ አድራለሁ፤ በቤት ጣራ ላይ እንዳለ ብቸኛ ወፍ ሆኛለሁ **8** ጠላቶቼ ቀኑን ሙሉ ይሳለቁብኛል የሚያፌዙብኝም ስሜን እንደ ርግማን ቆጥረውታል። **9** ዐመድ እንደ እህል ቅሜአለሁ! እንባዬም ከምጠጣው ነገር ጋር ተደባልቆአል። **10** ወደ ላይ አነሣኸኝ፤ ከቁጣህና ከመዓትህም የተነሣ መልሰህ ጣልኸኝ። **11** ዘመኖቼ ቶሎ እንደሚያልፍ ጥላ ናቸው እኔም እንደ ሣር ደረቅሁ **12** አንተ ግን ያህዌ ሆይ፣ ለዘላለም ትኖራለህ ስምህ ከትውልድ እስከ ትውልድ ገናና ነው። **13** ትነሣህ፤ ጽዮንንም ትምራታለህ ለእርሷ ርኅራኄህን የምታሳይበት ጊዜ ነው፤ **14** አገልጋዮችህ ድንጋዮዋን ወደዋልና ለፍርስራሾቿ ራርተዋል። **15** ሕዝቦች የያህዌን ስም የምድር ነገሥታትም ክብርህን ይፈራሉ። **16** ያህዌ ጽዮንን እንደ ገና ይሠራታልና በክብሩም ይገለጣል። **17** በዚያ ጊዜ እርሱ ለችግረኞች ጸሎት መልስ ይሰጣል፤ ልመናቸውንም አይንቅም። **18** ገና ያልተወለዱ ሰዎች እንዲያመሰግኑት ይህ ያህዌ ያደረገው ድንቅ ነገር ለሚመጣው ትውልድ ይጻፍ። **19** በከፍታ ካለው መቅደሱ ወደ ታች ተመልክቶአልና ያህዌ ከሰማይ ምድርን ዐይቶአል። **20** ይኸውም የእስረኞችን መቃተት ይሰማ ዘንድ ሞት የተፈረደባቸውን ያድን ዘንድ ነው። **21** ስለዚህ የያህዌ ስም በጽዮን፣ ምስጋናውም በኢየሩሳሌም ይነገራል። **22** ይህም የሚሆነው ሕዝቦችና መንግሥታት ያህዌን ለማምለክ በአንድት ሲሰበሰቡ ነው። **23** በሕይወቴ እኩሌታ ብርታቴን ቀጨው ዕድሜዬንም ባጭሩ አስቀረው። **24** እኔም፣ «አምላኬ ሆይ፣ የአንተ ዘመን ከትውልድ እስከ ትውልድ ስለሆነ በዕድሜዬ እኩሌታ አትውሰደኝ» አልሁ። **25** አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ ሰማያትም የእጆችህ ሥራ ናቸው። **26** እነርሱ ይጠፋሉ፤ አንተ ግን ጸንተህ ትኖራለህ እነርሱ እንደ ልብስ ያረጃሉ እንደ መጐናጸፊያ ትለውጣቸዋለህ እነርሱም ወዲያ ይጣላሉ። **27** አንተ ግን ያው አንተ ነህ ዘመኖችህም ፍጻሜ የላቸውም። **28** የአገልጋዮችህ ልጆች በሰላም ይኖራሉ ትውልዳቸውም በፊትህ ጸንቶ ይኖራል።

Psalms 102:1

አጠቃላይ መረጃ:
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

የተጎዳ
ይህ ጉዳት የደረሰበትን ሰው ያመለክታል። "ጉዳት የደረሰበት ሰው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰቆቃውን በያህዌ ፊት አፈሰሰ
ጸሐፊው ሰቆቃውን የገለጸበት መንገድ ፈሳሽን ከማንቆርቆር ጋር ተነጻጽሯል። "ሀዘኑን ለያህዌ በነጻነት/በሙሉ ልቡ ገለጸ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 102:3

ቀኖቼ እንደ ጪስ አለፉ
እዚህ ስፍራ "ቀኖቼ" የሚለው የሚያመለክተው የጸሐፊውን ህይወት ሲሆን "ጪስ" የሚለው ሀሳብ በፍጥነት የሚጠፋን ነገር የሚገለጽ ነው። "ህይወቴ በቶሎ ያልፋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አጥንቶቼ እንደ እሳት ይቃጠላሉ
እዚህ ስፍራ ጸሐፊው "አካሉን" እንደ "አጥንቶቹ" አድርጎ ይጠቅሳል። "ሰውነቴ እንደሚነድ ሆኖ ይሰማኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ልቤ ደቀቀ
እዚህ ስፍራ ጸሐፊው ራሱን እንደ ራሱ "ልብ" አድርጎ ይገልጻል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኔ ተስፋ ቆርጫለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

እኔ እንደ ጠወለገ ሳር ነኝ
ይህ ተስፋ መቁረጡን የገለጸበት ሌላው መንገድ ነው። "እንደ ጠወለገ ሳር እየደረቅኩ እንደሆነ ይሰማኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 102:5

እንደ በረሃ ቆልማሚት መሰልኩ
ብቸኝነቱን የሚያነጻጽረው ከቆልማሚት ጋር ነው፤ ቆልማሚት ከሌሎች ወፎች ጋር ከመሆን ይልቅ ብዙውን ጊዜ ብቻውን ይሆናል። "በበረሃ እንደሚገኝ ቆልማሚት ብቻዬን እና ተስፋ ቆርጬ እገኛለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቆልማሚት
ትልቅ አሳ የሚመገብ ወፍ

በፍርስራሽ ውስጥ እንደሚኖር ጉጉት ሆንኩ
ጸሐፊው ብቸኝነትን ራሱን በፍርስራሾች ውስጥ ከሚኖር ጉጉት ጋር በማነጻጸር መግለጹን ቀጥሏል። "በፍርስራሾች ውስጥ ተጥሎ እንደሚኖር ጉጉት ወፍ ብቻዬን ሆንኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጉጉት ወፍ
ይህ በምሽት ከተኛበት የሚነሳ ወፍ ነው። "የምሽት ወፍ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

Psalms 102:7

እንደ ብቸኛ ወፍ ብቻዬን ሆንኩ
ጸሐፊው የብቸንነት ስሜቱን በትኩረት ለመግለጽ ራሱን ከወፍ ጋር ያነጻጽራል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 102:9

አመድን እንደ ዳቦ ተመገብኩ
ዳዊት እንደ ሀዘን መግለጫ በአመድ ላይ ይቀመጣል፣ ስለዚህም አመድ በምግቡ ላይ ይወድቃል። "ዳቦ እንደምመገብ አመድ እመገባለሁ" ወይም

"በሀዘኔ በምመገበው ዳቦ ላይ አመድ ይወድቅበታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መጠጤን ከእንባ ጋር ቀላቀልኩ
ዳዊት ይሁነኝ ብሎ መጠጡን ከእንባው ጋር አልቀላቀለም፤ ይልቁንም እርሱ ሲያዝን እና ሲያለቅስ እንባው በሚጠጣበት ብርጭቆ ውስጥ ይገባል። "እንባዬ በምጠጣበት ብርጭቆ/ጽዋ ውስጥ ይንጠባጠባል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደታች ልትጥለኝ ወደላይ ከፍ አደረግከኝ
እግዚአብሔር በቀጥታ የዳዊትን አካል ወደ ላይ ከፍ አላደረገውም ደግሞም ወደ ታች አልጣለውም፤ ይልቁንም ዳዊት ይህንን የተናገረው ምን እንደተሰማው እና እንደገጠመው ለመግለጽ ነው። "ወደላይ ያነሳኸኝ ቁልቁል ልትወረውረኝ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 102:11

ቀናቶቼ እንደ ደበዘዘ ጥላ ናቸው
ዳዊት በምድር ላይ ለመኖር የቀሩትን ጊዜያት የሚያነጻጽረው እየደበዘዘ ከሚሄድ ጥላ ጋር ነው። "በህይወት ለመኖር የቀረኝ እድሜ ምሽት ላይ በቶሎ እንደሚጠፋ ጥላ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ሳር ጠውልጌያለሁ
የዳዊት አካል እየደከመ ሲሄድ እና ወደ ህይወቱ ማብቂያ ሲቃረብ፣ ራሱን ከሚጠወልግ ሳር ጋር ያነጻጽራል። "እንደ ሚጠወልግ ሳር ሰውነቴ ደከመ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መጠውለግ
መድረቅ እና መጨማደድ

ዝናህ ለትውልዶች ሁሉ ነው
"በሚመጡት ትውልዶች ሁሉ ትታወቃለህ"

ዝና
በብዙ ሰዎች መታወቅ

Psalms 102:13

በጽዮን ላይ ምህረት አድርግ
እዚህ ስፍራ "ጽዮን" የሚያመለክተው በጽዮን የሚኖሩ ሰዎችን ነው። "በጽዮን ሰዎች ላይ ምህረት አድርግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሷ ላይ
"እርሷ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጽዮንን ነው።

ድንጋዮቿን/ቅጥሮቿን በውዴታ ያዛቸው
"ድንጋዮች" የሚለው የሚያመለክተው ከመደምሰሷ አስቀድሞ የከተማይቱ ቅጥር ክፍል የሆኑን ድንጋዮች ነው። "አሁንም አስቀድሞ የከተማይቱ ቅጥር የነበሩትን ድንጋዮች ውደዳቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ስምህ
እዚህ ስፍራ "ስምህ" የሚለው የሚያመለክተው ያህዌን ነው። "አንተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ክብርህና ከፍ ከፍ ያደርጋሉ
ሰዎች ያህዌን ከክብሩ የተነሳ ከፍ ከፍ ያደርጋሉ። እዚህ ስፍራ ያህዌ የተገለጸው በክብሩ ነው። "አንተን ያከብራሉ፣ ምክንየቱም አንተ ክቡር ነህ" (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በክብሩ ይታያል
"በክብሩ ይታያል" ወይም "ሰዎች ክብሩን ያያሉ"

Psalms 102:17

ምሲኪኖች/ችግረኞች
ይህ ሚስኪናንን ያመለክታል። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ጸሎታቸውን አይንቅም
ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊገለጽ ይችላል። "ያህዌ ጸሎታቸውን ይቀበላል/ ይሰማል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም አሉታዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ለመጪው ትውልድ ይተላለፋል/ይጻፋል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኔ ይህንን ለመጪው ትውልድ አስተላልፈዋለሁ/እጽፈዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 102:19

እርሱ ከተቀደሰው ከፍ ካለው ስፍራው ሆኖ ወደ ታች ተመልክቷል፤ ያህዌ ከሰማይ ተመልክቷል
እነዚህ ሁለቱ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ በአንድነት የዋሉት እግዚአብሔር እንዴት ከሰማይ ወደ ታች እንደ ተመለከተ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የተቀደሱት ከፍታዎች
"ከምድር በላይ ከፍ ያለ የእርሱ ቅዱስ ስፍራ"

ሞት የተፈረደባቸው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ባለስልጣናት ሞት የፈረዱባቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

Psalms 102:21

በጽዮን ያለውን ስሙን፣ ደግሞም በእየሩሳሌም የሚወደሰውን የያህዌን ስም አውጁ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ ደግሞም የያህዌ ስም መወደሱን ትኩረት ይሰጣሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 102:23

ብርታቴን ወሰደ
ዳዊት እግዚአብሔር ደካማ እንዳደረገው የሚገልጸው የእርሱ ጥንካሬዎች ከእርሱ ሊወሰዱ እንደሚችሉ አካላዊ ቁስ አድርጎ ነው። "ደካማ አደረገኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ቀኖቼ
እዚህ ስፍራ "ቀኖች" የሚለው ቃል የእርሱን ህይወት ያመለክታል። "የእኔ ህይወት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔን አትውሰደኝ
ዳዊት እግዚአብሔርን የሚጠይቀው እንደሞት እንዳይፈቅድ/እንዳይገድለው ነው። "ከምድር አትውሰደኝ" ወይም "አትግደለኝ/እንድሞት አትፍቀድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ በትውልዶች ውስጥ ሁሉ በዚህ አለህ
"አንተ በትውልዶች ሁሉ መሃል አለህ"

Psalms 102:25

እነርሱ ሁሉም ያረጃሉ
"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው "መሬትን" እና "ሰማያትን" ነው

አመታትህ መጨረሻ አይኖራቸውም
እዚህ ስፍራ ዳዊት እግዚአብሔር ህያው የሚሆንበት የጊዜ ርዝመት እንደ እርሱ "አመታት" ይገልጻል። ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊጻፍ ይችላል። "አንተ ለዘለዓለም ትኖራለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ጥንድ አሉታዎች የሚሉትን ይመልከቱ)

Psalms 102:28

ይኖራል
"መኖሩ ይቀጥላል"

በአንተ መገኘት መኖር
እዚህ ስፍራ ዳዊት የሚገልጸው፣ ትውልዶች በያህዌ ተጠብቀው የሚኖሩት በመገኘቱ መሆኑን ነው። "በአንተ መገኘት ውስጥ ሲኖሩ ይጠበቃሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 103

1 ነፍሴ ሆይ፣ ያህዌ አመስግኚ የያህዌን ቅዱስ ስም በሙሉ ልቤ አመሰግናለሁ። **2** ነፍሴ ሆይ፣ ያህዌን አመሰግኚ ውለታውንም ሁሉ አትርሺ። **3** ኃጢአትሽን ሁሉ ይቅር ይላል ደዌሽንም ሁሉ ይፈውሳል። **4** ሕይወትሽንም ከጥፋት ጉድጓድ ያድናል ምሕረትና ርኅራኄውን ያቀዳጅሻል። **5** ወጣትነትሽ እንደ ንስር ይታደስ ዘንድ ሕይወትሽን በመልካም ነገር ያጠግባል። **6** ያህዌ ለተጨቆኑ ሁሉ፣ ቅን ፍርድንና ፍትሕን ይሰጣል። **7** መንገዱን ለሙሴ፣ ሥራውንም ለእስራኤል ልጆች አሳወቀ። **8** ያህዌ መሐሪና ይቅር ባይ ለቁጣ የዘገየ፣ ታማኝነቱም የበዛ ነው። **9** እርሱ ሁልጊዜ አይገሥጽም ለዘላለምም አይቆጣም። **10** እንደ ኃጢአታችን አላደረግብንም እንደ በደላችንም አልከፈለንም። **11** ሰማይ ከምድር ከፍ የማለቱን ያህል እንዲሁ ለሚፈሩት ምሕረቱ ታላቅ ነው። **12** ምሥራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ በደልና ኃጢአታችንን በዚያው መጠን ከእኛ አስወገደ። **13** አባት ለልጆቹ እንደሚራራ እንዲሁ ያህዌም ለሚፈሩት ይራራል። **14** እርሱ አፈጣጠራችንን ያውቃልና ትቢያ መሆናችንንም ይገነዘባል። **15** ሰው እኮ እንደ ሣር እንደሚያድግ የዱር አበባ ነው። **16** ነፋስ በሚነፍስበት ጊዜ ድራሹ ይጠፋል፤ የነበረበት ስፍራ እንኳ አይታወቅም። **17** የያህዌ ምሕረት ግን ከዘላለም እስከ ዘላለም በሚፈሩት ላይ ነው። ጽድቁም እስከ ልጅ ልጆቻቸው ዘመን በላያቸው ይሆናል፤ **18** ይህም ኪዳኑን በሚጠብቁት ላይ ትእዛዙንም በሚያከብሩት ላይ ይሆናል። **19** ያህዌ ዙፋኑን በሰማይ አጽንቶአል መንግሥቱም ሁሉን ትገዛለች። **20** እናንተ ለቃሉ የምትታዘዙ መላእክት ትእዛዙንም የምትፈጽሙ እናንተ ኃያላን፣ ያህዌን አመስግኑ። **21** አገልጋዩ የሆናችሁ፣ ፈቃዱንም የምትፈጽሙ እናንተ የሰማይ ሰራዊት ያህዌን አመስግኑ። **22** በግዛቱ ሁሉ የምትገኙ ፍጥረቶቹ ያህዌን አመስግኑ፤ ነፍሴ ሆይ ያህዌን አመስግኚ።

Psalms 103:1

አጠቃላይ መረጃ:
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

የዳዊት መዝሙር
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ዳዊት ዝማሬውን ጽፏል፤ ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው፤ ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት መዝሙር ስልት የተጻፈ ነው።

በህይወቴ ሁሉ ለያህዌ ውዳሴ አቀርባለሁ፣ ደግሞም በውስጤ ባለው ሁሉ ለቅዱስ ስሙ ውዳሴ አቀርባለሁ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው፣ ያህዌን እርሱ ምን ያህል እንደሚያወድስ ትኩረት ይሰጣሉ። "በውስጥ ሰውነቴ ሁሉ ያህዌን አወድሰዋለሁ"ነ በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለቅዱስ ስሙ ውዳሴ ስጡ
ይህ የሚያመለክተው ያህዌን ስም እንደ ያህዌነቱ ማወደስን ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በውስጥ ሰውነቴ ሁሉ/ባለኝ ሀይል ሁሉ
"በመላው ማንነቴ" ወይም "በሆንኩት ሁሉ።" ዳዊት ይህን ሀረግ የተጠቀመው ወደ ራሱ ለማመልከት እና ለያህዌ ያለውን መሰጠት ለማጉላት ነው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 103:3

የእናንተ...የአንተ
ዳዊት ስለ ራሱ ይናገራል፣ ስለዚህም "የአንቺ" እና "አንቺ" የሚሉትን ቃላት ራሱን ለማመልከት ይጠቀምባቸዋል። ብዙ ቅጂዎች/ትርጉሞች ይህንን በዩዲቢ ውስጥ እንደሚገኘው "የእኔ" እና "እኔ" በሚል ይገልጽዋቸዋል።

እርሱ የአንቺን ህይወት ከጥፋት ተቤዠቷል
ይህ ማለት ያህዌ እርሱን በህይወት ጠብቆታል። "እርሱ ከሞት ታድጎሻል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ በቃል ኪዳን ታማኝነት ዘውድ ጭኖብሻል ደግሞም ታላቅ ምህረት አድርጎልሻል
እዚህ ስፍራ አንድን ሰው መባረክ እና ታላቅ ክብር መስጠት የተገለጸው በሰው ራስ ላይ ዘውድ እንደ መድፋት ተደርጎ ነው። "ታማኝነት" እና "ምህረት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች በተውሳከ ግስ መልክ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "እርሱ አንቺን በታማኝነት እና በምህረቱ ይባርክሻል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

ህይወትሽን በመልካም ነገር ያረካል
"ህይወትሽን" የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው "አንቺ" የሚለውን ሲሆን፣ ነገር ግን ይህ በህይወት ዘመን ሁሉ ባርኮትን እንደሚሰጥ ትኩረት ያደርጋል። "እርሱ በመልካም ነገሮች በዘመንሽ ሁሉ ያረካሻል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ወጣትነትሽ እንደ ንስር ይታደሳል
"ወጣትነት ማደስ" የሚለው ዳግም ወጣት የመሆን ስሜት ማግኘት ማለት ነው። እዚህ ስፍራ ዳዊት ይህንን የወጣትነት ስሜት የሚያነጻጽረው ከንስር ፍጥነት እና ጥንካሬ ጋር ነው። "ወጣትነት ይሰማሻል ደግሞም እንደ ንስር ጠንካራ ትሆኛለሽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወጣትነትሽን
"ወጣትነት" የሚለው ቃል ጥንካሬን አንድ ሰው በጎልማሳነቱ የሚሰማውን ጥንካሬ ያመለክታል። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 103:6

ፍትህን ያደርጋል
"ፍትህን እውን ያደርጋል"

የተጨቆኑ ሁሉ
ጭቆናን የሚፈጽሙ በግልጽ ሊጠቀሱ ይችላሉ። "በሰዎች ጭቆና የሚደርስባቸው ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ለእስራኤል ትውልዶች ያደረገው
"እንዲታወቅ ያደርጋል" የሚሉት ቃላት ከቀደመው ሀረግ ይታወቃሉ። እዚህ ስፍራ ሊደገሙ ይችላሉ። "እርሱ ስራዎቹ ለእስራኤል ትውልዶች እንዲታወቁ አደረገ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

ታላቅ የቃል ኪዳን ታማኝነት አለው
"በምህረት እና ፍቅር የተሞላ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 103:9

እርሱ ሁልጊዜ አይቀጣም፣ ሁልጊዜም አይቆጣም
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ሁለተኛው የመጀመሪያውን ሃሳብ ያጠናክራል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ እኛን አይከታተልም...ወይም እንደ በደላችን አይከፍለንም
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ትይዩ ናቸው ደግሞም እግዚአብሔር እኛ መቀጣት የሚገባንን ያህል እንደማይቀጣን ትኩረት ይሰጣሉ። "በኃጢአታችን መቀጣት የሚገባንን ያህል አይቀጣንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ በደላችን አይከታተለንም
"አይቀጣንም"

Psalms 103:11

ሰማያት ሩቅ እንደሆኑ...እርሱን ለሚያከብሩት
ንጽጽሩ የሚያወዳድረው እግዚአብሔር ለህዝቡ ያለውን ታላቅ ፍቅር፤ በሰማይና በምድር መሃል ካለው ትልቅ ርቀት ጋር ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የቃል ኪዳኑ ታማኝነት እጅግ ታላቅ ነው
"ታማኝነት" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ስለዚህ እርሱ ለኪዳኑ በጣም ታማኝ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እስከ ምስራቅ ድረስ...በደላችንን ከእኛ አራቀው
በምስራቅ እና ምዕራብ መሃል ያለው ርቀት መለካት እስከማይቻል ድረስ እጅግ ሩቅ ነው። በዚህ ተነጻጻሪ ውስጥ፣ ርቀቱ የተወዳደረው እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ከእኛ ምን ያህል እንዳራቀው ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አባት እንደሚራራው... እርሱ በሚያከብሩት ላይ
እዚህ ስፍራ ጸሐፊው አባትለልጆቹ ያለውን ርህራሄ፣ ያህዌ እርሱን ለሚያከብሩ ካለው ርህራሄ ጋር ያነጻጽራል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 103:14

እኛ እንዴት እንደተሰራን/እንደተበጀን
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የእኛ አካል የሚመስለው" ወይም "እርሱ አካላችንን ያበጀው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

እርሱ አፈር መሆናችንን ያውቃል
ያህዌ የመጀመሪያውን ሰው አዳምን ሲፈጥር፣ የፈጠረው ከአፈር ነው። "እርሱ ከአፈር እንደ ፈጠረን ያውቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰው ቀናቱ እንደ ሳር ነው
በዚህ ንጽጽር፣ የሰው ህይወት ዘመን መጠኑ የተወዳደረው ሳር ከመጠውለጉ አስቀድሞ ከሚኖራት አጭር ጊዜ ጋር ነው። "የሰው የህይወት ዘመን እንደ ሳር እድሜ አጭር ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ሜዳ አበባ ያብባል
በዚህ ንጽጽር፣ ሰው እንዴት በጊዜ ውስጥ እንደሚያድግ የተወዳደረው ከአበባ እድገት ጋር ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ያብባል
"ማበብ" በሚገባ ወይም ውብ ሆኖ ማደግ ነው።

ነፋስ በላዩ ይነፍሳል፣ ከዚያም ይጠፋል...በቅሎበት ከነበረው ስፍራ
እነዚህ ሀረጋት ስለ አበቦች እና ሳር መናገራቸውን ይቀጥላሉ። አበቦች እና ሳር እንዴት እንደሚሞቱ ከሰው አሟሟት ጋር ያነጻጽራሉ። "ነፋስ በአበቦች እና ሳሮች ላይ ይነፍሳል፣ እነርሱም ይጠፋሉ፤ ማንም የት ስፍራ በቅለው እንደነበር መናገር አይችልም - የሰው ልጅም እንደዚሁ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 103:17

የያህዌ የቃል ኪዳኑ ታማኝነት
"ታማኝነት" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል መልኩ ሊተረጎም ይችላል። "ያህዌ ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ ነው
ይህ ማለት ያህዌ የያህዌ ፈቅር ለዘለዓለም ይቀጥላል ማለት ነው። "ለዘለዓለም ይቀጥላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ከጽንፍ ጽንፍ የሚለውን ይመልከቱ)

የእነርሱ ትውልዶች
"እርሱን የሚያከብሩ ትውልዶች"

እነርሱ የእርሱን ኪዳን ይጠብቃሉ፣ ደግሞም ትዕዛዛቱን መጠበቅን አይዘነጉም
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ ዙፋኑን በሰማያት ላይ መስርቷል
እዚህ ስፍራ የያህዌ እንደ ንጉሥ መግዛት የተገለጸው እንደ "ዙፋኑ" ተደርጎ ነው። "ያህዌ በሰማይ እንደ ንጉሥ በሚገዛበት በወንበሩ ላይ ተቀመጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

መስርቷል
"አበጅቷል"

መንግስቱ ይገዛል
እዚህ ስፍራ እንደ ንጉሥ ስልጣኑ ላይ ለማተኮር፣ ያህዌ የተጠቀሰው "በእርሱ መንግሥት" ነው። "እርሱ ይገዛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 103:20

ፈቃዱን ይፈጽማል
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ "ፈቃዱን ያደርጋል" ማለት ነው። "ፈቃዱን ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ በሚገዛባቸው ስፍራዎች ሁሉ
"እርሱ በሚገዛባቸው ስፍራዎች ሁሉ አመስግኑት"

በሙሉ ህይወቴ
የዚህ ሀረግ ትርጉም ያህዌን በሙሉ ልቡ ያወድሰዋል ደግሞም ለእርሱ ላለው መሰጠት ትኩረት ይሰጣል ማለት ነው። "በሙሉ ማንነቴ" ወይም "በሙሉ ነፍሴ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 104

1 ነፍሴ ሆይ፣ ያህዌን አመስግኚ አምላኬ ያህዌ ሆይ፣ አንተ እጅግ ታላቅ ነህ ውበትና ግርማን ለብሰሃል። **2** ብርሃንን እንደ ሸማ ተጐናጽፈሃል ሰማያትን እንደ ድንኳን መጋረጃ ዘረጋህ። **3** በጠፈር ላይ ካለው ውሃ በላይ ቤትህን ሠርተሃል ደመናትን ሰረገላህ አደረግህ በነፋስ ክንፎች ትሄዳለህ። **4** ነፋሶችን መልእክተኞቹ፣ ነበልባልንም አገልጋዮቹ አደረግ። **5** ምድርን መሠረት ላይ አጸና ከቶም አትናወጥም። **6** በጥልቁ እንደ ልብስ ሸፈንሃት ውሆችም ከተራሮች በላይ ቆሙ። **7** በገሠጸካቸው ጊዜ ግን ፈጥነው ሄዱ የነጐድጓድህንም ድምፅ በሰሙ ጊዜ ሸሹ። **8** በተራሮች ላይ ፈሰሱ አንተ ወዳዘጋጀህላቸው ስፍራ ወደ ሸለቆዎች ወረዱ። **9** ዳግመኛ ምድርን እንዳይሸፍኑም አልፈውም እንዳይመጡ ድንበር አበጀህላቸው። **10** ምንጮች በሸለቆው ውስጥ እንዲ ወንዞችም በተራሮች መካከል እንዲወርዱ አደረግህ። **11** የዱር እንስሳት ከዚያ ይጠጣሉ የሜዳ አህዮችም ጥማቸውን ያረካሉ። **12** ወንዙ ዳር ወፎች ጐጆአቸውን ይሠራሉ በቅርንጫፎቹም መካከል ይዘምራሉ። **13** ከላይ ከእልፍኙ ተራሮችን ያጠጣል፤ ምድርም በሥራው ፍሬ ትረካለች። **14** ከምድር ምግብን ታወጣ ዘንድ ለእንስሶች ሣርን ታበቅላለህ ለሰው ልጆች ሥራ አትክልቶችን ታበቅላለህ። **15** ስለዚህ ልቡን ደስ የሚሰኘውን ወይን ጠጅ፣ ፊቱን የሚያበራ ዘይትና በሕይወት የሚያኖረውን እህል ያዘጋጃል። **16** ደግሞም የያህዌ ዛፎች፣ እርሱ የተከላቸውም የሊባኖስ ዝግባዎች በቂ ዝናብ ያገኛሉ። **17** በዚያ ወፎች ጐጆአቸውን ይሠራሉ ሽመላዎችም በጥዶቹ ውስጥ ማደሪያ ያገኛሉ። **18** ረጃጅሙ ተራራ የዋልያ ተራራ የዐለቱም ዋሻዎች የሽኮኮ መሸሸጊያ ናቸው። **19** ጨረቃ የወቅቶች ምልክት እንድትሆን አደረገ ፀሐይም የምትጠልቀበትን ጊዜ ታውቃለች። **20** ጨለማን ፈጠርህ፤ ሌሊትም ሆነ፤ በጨለማም የዱር አውሬዎች ሁሉ ይወጣሉ። **21** የአንበሳ ግልግሎች ምግብ ለማግኘት ይጫኹሉ፤ ከእግዚአብሔር ዘንድ ምግባቸውን ይፈልጋሉ። **22** ፀሐይ በወጣች ጊዜ ሸሽተው ይሄዳሉ፤ በየመኖሪያቸው ውስጥ ይተኛሉ። **23** ሰውም ወደ ሥራው ይሄዳል እስኪመሽም ድረስ ሲሠራ ይውላል። **24** ያህዌ ሆይ፣ ሥራህ እንዴት ብዙ ነው! ሁሉን በጥበብ አደረግህ ምድርም በፍጥረትህ ተሞላች። **25** እዚያ ደግሞ ሰፊና የተንጣለለ ባሕር አለ ታላላቅና ታናናሽ እንስሳት፣ ስፍር ቁጥር የሌላቸውም ነፍሳት በውስጡ አሉ። **26** መርከቦች በላዩ ይመላለሳሉ አንተ የፈጠርኸው ሌዋታን በውስጡ ይፈነጫል። **27** እነዚህ ሁሉ በጊዜው ምግባቸውን እንድትሰጣቸው አንተን ተስፋ ያደርጋሉ። **28** በሰጠሃቸው ጊዜ አንድ ላይ ይከማቻሉ፣ እጅህንም ስትዘረጋ በመልካም ነገር ይጠግባሉ። **29** ፊትህን ስትሰውር፣ በጣም ይደነግጣሉ እስትንፋሳቸውን ስትወስድ ይሞታሉ፤ ወደ አፈርም ይመለሳሉ። **30** መንፈስህ ስትልክ እነርሱ ይፈጠራሉ የምድርንም ገጽ ታድሳለህ። **31** ለዘላለም ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን ያህዌ በፍጥረቱ ደስ ይበለው። **32** ከላይ ምድርን ሲመለከት ትንቀጠቀጣለች ተራሮችን ሲዳስሳቸው ይጨሳሉ **33** በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ለያህዌ እዘምራለሁ በሕይወትም እስካለሁ ድረስ ለአምላኬ የምስጋና መዝሙር አቀርባለሁ። **34** ደስታዬ በእርሱ ስለሆነ የልቤ ሐሳብ እርሱን ደስ ያሰኘው። **35** ኀጥአን ከምድር ይጥፉ ዐመፀኞች ከእንግዲህ አይኑሩ። ነፍሴ ሆይ፣ ያህዌን አመስግኚ። ያህዌ ይመስገን።

Psalms 104:1

አጠቃላይ መረጃ:
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ ዝማሬ የውዳሴ መዝሙር ነው

በሙሉ ህይወቴ
የዚህ ሀረግ ትርጉም ያህዌን በሙሉ ልቡ ያወድሰዋል ደግሞም ለእርሱ ላለው መሰጠት ትኩረት ይሰጣል ማለት ነው። "በሙሉ ማንነቴ" ወይም "በሙሉ ነፍሴ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ውበትን እና ግርማዊነትን ለብሰሃል
"ውበት" እና "ግርማ" የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው ለያህዌ ክብር ትኩረት ይሰጣሉ። የተገለጹትም ያህዌ እንደ ልብስ እንደተጎናጸፋቸው ተደርጎ ነው። "በአንተ ዙሪያ ውበት እና ግርማ አለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

አንተ ራስህን እንደ ልብስ በብርሃ ሸፍነሃል
ያህዌ የተገለጸው ብርሃን እንደ ልብስ በዙሪያው እንደሸፈነው ተደርጎ ነው። "አንተ በብርሃን ተሸፍነሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ሰማያትን እንደ ድንኳን መጋረጃ ዘርግተሃል
እዚህ ስፍራ እግዚአብሔር የተገለጸው ሰው በውስጡ የሚቀመጥበት መጋረጃ እንደሚዘረጋ፣ ያህዌ ሰማያትን እንደ ዘረጋ ተደርጎ ነው። "ሰው ድንኳን እንደሚዘረጋ አንተ ሰማያትን ዘረጋህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የአዳራሽህን አግዳሚ በደመናት ላይ ዘረጋህ
"አንተ ላይኛውን ክፍልህን በሰማያት ገነባህ።" ይህ የሚያመለክተው የእርሱ ቤት የላይኛው ወለል እጅግ ረጅም ከመሆኑ የተነሳ እስከ ደመናት እንደሚደርስ ነው።

አንተ ደመናትን ሰረገላህ አደረግህ
እዚህ ስፍራ ደመናት የተገለጹት ሰረገላ ሆነው ያህዌን እንደተሸከሙ ተደርጎ ነው። "አንተ ደመናት እንደ ሰረገላ እንዲሸከሙህ አደረግህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ በነፋሳት ክንፎች ላይ ትራመዳለህ
እዚህ ስፍራ የነፋስ መንፈስ የተገለጸው ያህዌ እንደሚራመድባቸው ክንፎች ተደርጎ ነው። "አንተ በነፋስ ላይ ትራመዳለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 104:4

እርሱ ነፋሳትን መልዕክተኞቹ አደረገ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እርሱ ነፋስ እንደ መልዕክተኛ መልዕክት እንዲያደርስ አደረገ፣ "እርሱ ነፋሳትን መልዕክተኞቹ አደረገ" ወይም 2) "እርሱ መልዕክተኞቹን እንደ ነፋስ ፈጣን አደረገ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

የእሳት ነበልባልን አገልጋዮቹ
ይህ በቀደመው ዐረፍተ ነገር ውስጥ በውስጠ ታዋቂነት ከቀረበው መረጃ ጋር ለገለጽ ይችላል። "እርሱ የእሳት ነበልባልን አገልጋዮቹ አደረገ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ የምድር መሰረቶችን መሰረተ
እዚህ ስፍራ "መሰረቶችን መሰረተ" የሚለው ሀረግ "ፈጠረ" ማለት ነው። "እርሱ መላዋን ምድር ፈጠረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 104:6

አንተ ምድርን እንደ ልብስ በውሃ ሸፈንክ
እዚህ ስፍራ ምድርን የሸፈነው ውሃ የተነጻጸረው ትልቅ ልብስ አንድን ነገር እንዴት ሙሉ ለሙሉ እንደሚሸፍን ከዚያ ጋር ነው። "አንተ ምድርን ሙሉ ለሙሉ በውሃ ሸፈንክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ ግሳጼ ውሆችን...እነርሱም ይሸሻሉ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው ደግሞም በአንድነት የዋሉት እግዚአብሔር እንዴት እንደተናገረ እና ውሆች እንደሸሹ ትኩረት ለመስጠት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይመለሳሉ
ወደ ኋላ መመለስ፣ ዝቅ ማለት

ይሸሻሉ
እዚህ ስፍራ ዘማሪው ስለ ውሆች መመለስ የሚናገረው የያህዌን ድምጽ ከሰሙ በኋላ ልክ እንደ አንስሳ እንደሚሸሹ አድርጎ ነው። "መሸሸ" የሚለው ቃል በፍጥነት መሮጥ ማለት ነው። "በችኮላ መሸሸ/ፈጥኖ መሄድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 104:8

ተራሮች ከፍ ይላሉ፣ ሸለቆችም ይስፋፋሉ
እዚህ ስፍራ ዘማሪው የሚናገረው፤ ተራሮች እና ሸለቆዎች ራሳቸውን ለማንቀሳቀስ የፈቀዱ ይመስል እግዚአብሔር እንዲንቀሳቀሱ እና እንዲለወጡ ማድረጉን ነው። እነርሱ በዚህ መንገድ የተገለጹት በእግዚአብሔር ሀይል ላይ ትኩረት ለመስጠት ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንዳያልፉ ድንበር አበጀላቸው
እዚህ ስፍራ ዘማሪው እግዚአብሔር ውሆች እርሱ የፈጠረላቸውን ድንበራቸውን እንዳያልፉ ማድረጉን የገለጸው ውሆች ራሳቸው ድንበራቸውን ላለማለፍ እንደመረጡ አድርጎ ነው። እነርሱ በዚህ መንገድ የተገለጹት እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ያለውን ስልጣን ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። "ሊያልፉት/ሊያቋርጡት የማይችሉት ድንበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ድንበር
ዳርቻ

ለእነርሱ
"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ውሆችን ነው።

Psalms 104:10

ወራጆች
አነስተኛ ወንዞች

የሜዳ አህዮች ጥማቸውን ቆረጡ
ይህ በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። እነርሱ ውሃ በመጠጣት ትማቸውን ቆረጡ/ጠጥተው ረኩ። "የዱር አህዮች ውሃ ጠጥተው ከጥማቸው ረኩ" (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የወንዝ ዳርቻዎች
በወንዝ ዳርቻ የሚገኝ መሬት

በቅርንጫፎች መሃል ይዘምራሉ
እዚህ ስፍራ ዳዊት የወፎችን ጭውጭውታ እንደ ሚዘምሩ አድርጎ ይገልጸዋል። "በዛፍ ቅርንጫፎች መሃል ጭውጭው ይላሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 104:13

በሰማይ ካለው የውሃ እልፍኙ ተራሮችን ውሃ ያጠጣል
ይህ ማለት እግዚአብሔር ዝናብ ያዘንባል ማለት ነው። ውሆች የተገለጹት በሰማይ ባለው እልፍኝ እንደሚኖሩ ተደርጎ ነው። "እርሱ ዝናብ ከሰማይ እንዲዘንብ በማድረግ ተራሮችን ውሃ ያጠጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ የስራ ፍሬ
"አንተ የፈጠርካቸው ብዙ መልካም ነገሮች"

ሰው እንዲንከባከባቸው ዕፅዋትን ታበቅላለህ
"እርሱ አደረገ" እና "በቀሉ" የሚሉት ቃላት በቀደመው ሀረግ ወስጥ በውስጠ ታዋቂነት ይገኛሉ፣ እናም እዚህ ስፍራ ሊደገሙ ይችላሉ። "እርሱ ሰው እንዲንከባከባቸው ተክሎች እንዲበቅሉ ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 104:16

የያህዌ ዛፎች ብዙ ውሃ ያገኛሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ያህዌ ለእርሱ ዛፎች ብዙ ውሃ ይሰጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚያ ወፎች ጎጆቸውን ይሰራሉ
እነርሱ ጎጆቸውን በጥድ ላይ ይሰራሉ። ይህ ይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ወፎች ጎጆዎቻቸውን በጥድ ላይ ይሰራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሽመላ
ይህ የወፍ ዐይነት ነው። "ወፍ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ሽኮኮ
ሽኮኮ የአይጥ መልክ ያለው ትንሽ እንስሳ ነው። "በቋጥኝ የሚሸሸግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

Psalms 104:19

ወቅቶች
ይህ ቃል የሚያመለክተው በአመት ውስጥ ስለሚለዋወጡት የተለያዩ የአየር ንብረት ነው። አንዳንድ ቦታዎች ዝናባማ ወቅት እና ደረቅ ወቅት ሲኖራቸው፣ ሌሎች ፀደይ፣ በጋ፣ በልግ እንዲዚሁም ክረምት አላቸው።

ፀሐይ ወቅቷን ታውቃለች
እዚህ ስፍራ ዳዊት ፀሐይን የሚገልጻት የቀኑን ሰዓት እንደምታውቅ አድርጎ ነው። "እርሱ በሰዓቱ ፀሐይ እንድትጠልቅ ያደርጋል" (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ታደርጋለህ
"ያህዌ ሆይ፣ አንተ ይህን ታደርጋለህ።" እዚህ ስፍራ ጸሐፊው ስለ ያህዌ ከመናገር ለያህዌ ወደ መናገር ዘወር ይላል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 104:21

ታዳኝ/ታድኖ ለምግብ የሚውል እንስሳ
ለሌላው እንስሳ ምግብ የሚሆን እንስሳ

ምግባቸውን ከእግዚአብሔር ዘንድ ያገኛሉ
"ምግባቸውን ለማግኘት እግዚአብሔርን ተስፋ ያደርጋሉ"

ማፈግፈግ
ወደ ጎሬ/ ዋሻቸው ይመለሳሉ

ጎሬ/ዋሻ
የትናንሽ ጡት አጥቢዎች እና ትንንሽ እንስሳት ቤቶች

Psalms 104:23

በስራዎችህ ታጥለቀልቃቸዋለህ
እዚህ ስፍራ ዳዊት ዳዊት የፈጠራቸውን ነገሮች ብዛት ከመያዝቸው እየወጡ እንደ ሚያጥለቀልቁ ፈሳሾች አድርጎ ይገልጻል። "በስራህ ተሞልቷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 104:25

ጥልቅ እና ሰፊ
"በጣም ጠልቅ እና ሰፊ ነው።" የባህር ጥልቀት እና ስፋት ይህ ምን ያህል ትልቅ እንደሆነ ትኩረት ይሰጣል። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ከቁጥር በላይ በሆኑ ፍጥረታት መሞላት
"ማንም ሊቆጥራቸው ከሚችለው በላይ የሆኑ ፍጥረታትን መያዝ"

የማይቆጠር
ማንም ሊቆጥረው ከሚችለው በላይ

ትናንሽ እና ታላላቅ የሆኑትን ሁሉ
ይህ ማለት ሁሉንም አይነት መጠን ያላቸው ፍጥረታት። (ከጽንፍ ጽንፍ የሚለውን ይመልከቱ)

መርከቦች በዚያ ይጓዛሉ/ይመላለሳሉ
"መርከቦች በባህር ላይ ይጓዛሉ/ይመላለሳሉ"

Psalms 104:27

እነዚህ ሁሉ
"እነዚህ ፍጥረታት ሁሉ"

በጊዜው ምግባቸውን ትሰጣቸዋለህ
"በሚያስፈልጋቸው ጊዜ ምግባቸውን ትሰጣቸዋለህ"

በምትሰጣቸው ጊዜ፣ እነርሱ ይሰበስባሉ
የሚሰጣቸው ምግብ መሆኑን መግለጽ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። "ምግብ በምትሰጣቸው ጊዜ፣ እነርሱ ይሰበስቡታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መሰብሰብ
ማከማቸት

እጆችህን ስትከፍት
ይህ ለፍጥረታቱ ምግብ ለመስጠት ያህዌ እጆቹን እንደሚከፍት ይገልጻል። "እነርሱን ለመመገብ እጆችህን በምትከፍትበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 104:29

ፊትህን ስትደብቅ
ይህ ማለት ያህዌ እነርሱን አይመለከትም ወይም ለእነርሱ ትኩረት አይሰጥም። "እነርሱን በማትመለከትበት ጊዜ" ወይም "ቸል ባልካቸው/በተውካቸው ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ አፈር ይመለሳሉ
ይህ ማለት አካላቸው ይበሰብሳል፤ ወደ አፈራቸውም ይመለሳሉ/ተመልሰውም አፈር ይሆናሉ። "አካላቸው ይበሰብሳል፣ ወደ ምድር ይመለሳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መንፈስህን ስትወስድ
ይህ የሚያመለክተው የእርሱ መንፈስ ለፍጥረታት ህይወት ለመስጠት እንደሚላክ ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ይፈጠራሉ
እነርሱን የፈጠረው የያህዌ መንፈስ ነው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ የአገር ዳርቻን ታድሳለህ
"አንተ ምድር በአዲስ ህይወት እንዲሞላ ታደርጋለህ"

Psalms 104:33

ሀሳቦቼ አስደሳች ይሁኑ
ሀሳቡን የሚያነጻጽረው ጣፋጭ ጣዕም ካለው ነገር ጋር ነው። "ሃሳቦቼ ደስ የሚያሰኙ ይሁኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 104:35

ይወገዱ
ይጥፉ

ክፉዎች ከእንግዲህ አይገኙ
"ክፉዎች" የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው ክፉ ሰዎችን ነው። "ክፉ ሰዎች ይጥፉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 105

1 ያህዌን አመስግኑ፣ ስሙንም ጥሩ ሥራውንም በሕዝቦች መካከል ግለጡ። 2 ለእርሱ የምስጋና መዝሙር አቅርቡ ድንቅ ሥራዎቹን ሁሉ ተናገሩ። 3 በቅዱስ
ስሙ ተጓደዱ ያህዌን የሚፈልግ ልብ ደስ ይበለው። 4 ያህዌንና ብርታቱን ፈልጉ ፊቱንም ዘወትር ፈልጉ። 5 ያደረጋቸውን ድንቅ ሥራዎች ተአምራቱንና ከአፉ
የወጣውን ፍርድ ፈልጉ። 6 እናንት የአገልጋዩ የአብርሃም ዘሮች እርሱ የመረጣችሁ የያዕቆብ ልጆች ሆይ አስታውሱ። 7 እርሱ አምላካችን ያህዌ ነው ፍርዱም
በምድር ሁሉ ላይ ነው። 8 ኪዳኑን ለዘላለም፣ ያዘዘውንም ቃል እስከ ሺህ ትውልድ ዘመን ያስታውሳል። 9 ከአብርሃም ጋር ያደረገውን ኪዳን ለይስሐቅም በመሐላ
የሰጠውን ተስፋ አይረሳም። 10 ይህን ለያዕቆብ ሥርዐት ለእስራኤልም የዘላለም ኪዳን አድርጐ አጸናው። 11 እንዲህም አለ፣ «የርስትህ ድርሻ እንዲሆን
የከነዓንን ምድር እሰጥሃለሁ። 12 ይህን ያለው እነርሱ በቁጥር አነስተኞች፣ እጅግ ጥቂትና ባይተዋሮች ሳሉ፣ 13 ከሕዝብ ወደ ሕዝብ ሲንከራተቱ፣ ከአንዱ
መንግሥት ወደ ሌላው መንግሥት ሲቅበዘበዙ ነበር። 14 ማንም እንዲጨቁናቸው አልፈቀደም ስለ እነርሱም ነገሥታትን ገሠጸ። 15 «የቀባኋቸውን አትንኩ፤
ነቢያቶቼንም አትጉዱ» አለ። 16 በምድር ላይ ችጋርን ጠራ የምግብንም አቅርቦት ሁሉ አቋረጠ። 17 ከእነርሱ አስቀድሞ በባርነት የተሸጠው ዮሴፍን ላከ። 18
እግሮቹ በእግር ብረት ተላላጡ አንገቱም ላይ የብረት ማነቆ ገባ። 19 የተናገረው እስኪፈጸም ድረስ የያህዌ ቃል ፈተነው። 20 እርሱን እንዲፈቱ ንጉሡ
አገልጋዮቹን ላከ፤ የሕዝቦችም ገዢ ነጻ አወጣው። 21 የቤቱ ጌታ የንብረቱም ሁሉ አስተዳዳሪ አደረገው። 22 በንጉሡ ባለ ሥልጣኖች ላይ አዛዥ ሆነ ለንጉሡም
አማካሪዎች ጥበብን እንዲያስተምር ሥልጣን ተሰጠው። 23 ከዚያም እስራኤል ወደ ግብፅ ሄደ እስከ ጊዜው ድረስ ያዕቆብ በካም ምድር ተቀመጠ። 24 ያህዌ
ሕዝቡን እጅግ አበዛ ከጠላቶቻቸውም ይልቅ ብርቱ አደረጋቸው። 25 ሕዝቡን እንዲጠሉ ባርያዎቹንም እንዲበድሉ ልባቸውን አስጨከነ። 26 ባርያውን ሙሴን
እርሱ የመረጠውንም አሮንን ላከ። 27 በግብፃውያን መካከል ምልክቶችን በካም ምድርም ድንቆችን አደረጉ። 28 ጨለማን ልኮ ምድርን ጽልመት አለበሳት ይሁን
እንጂ ትእዛዘቹን አልፈጸሙም። 29 ውሃቸውን ወደ ደም ለወጠ ዓሣዎቻቸውንም ፈጀ። 30 የነገሥታት እልፍኝ እንኳ ሳይቀር ምድራቸው በእንቁራሪት ተሸፈነች።
31 እርሱ ሲናገር ተናካሽ ዝንቦችና ተናዳፊ ትንኞች በአገራቸው ተርመሰመሱ። 32 በአገራቸው ላይ የበረዶ ድንጋይና መብረቅ አወረደ። 33 ወይናቸውንና
በለሳቸውን መታ ሌሎች ዛፎቻቸውንም ሰባበረ። 34 እርሱ ሲናገር አንበጣ መጣ ስፍር ቁጠር የሌለውም ኩብኩባ ከተፍ አለ። 35 አንበጣ የምድሪቱን ዕፅዋት
ሁሉ በላ እህላቸውንም ሁሉ ፈጀ። 36 ደግሞም የእያንዳንዱን ግብፃዊ በኩር ሁሉ የኃይላቸውንም ሁሉ በኩራት መታ። 37 እስራኤላውያንን ከወርቅና ከብር ጋር
ከዚያ መርቶ አወጣ፤ ከነገዶቻቸው አንዱ እንኳ አልተደናቀፈም። 38 እጅግ ፈርተዋቸው ነበርና እስራኤላውያን አገር ለቀው ሲወጡ ግብፅ ደስ አላት። 39
በሚሄዱበት ጊዜ በደመና ጋረዳቸው እሳትም በሌሊት አበራላቸው። 40 ምግብ እንዲሰጣቸው በለመኑት ጊዜ ድርጭት አመጣላቸው የሰማይንም እንጀራ
አጠገባቸው። 41 ዐለቱን ሰነጠቀ፤ ውሃም ተንዶለዶለ 42 ለባርያው ለአብርሃም የሰጠውን ቅዱስ የተስፋ ቃል አስታውሶአልና 43 ሕዝቡን በደስታ፣ ምርጦቹንም
በእልልታ መራቸው። 44 የሕዝቦችን ምድር ሰጣቸው የእነርሱንም ሀብት ወረሱ። 45 ይህም ሥርዐቱን ይጠብቁ ዘንድ ሕጉንም ይፈጽሙ ዘንድ ነው። ያህዌ
ይመስገን

Psalms 105:1

አጠቃላይ መረጃ
x

Psalms 105:4

እግዚአብሔርን እና ኃይሉን ፈልጉ
“የእግዚአብሔርን ኃይል ፈልጉ” ማለት እንዲያጸናችሁ ጠይቁ ማለት ነው። “እግዚአብሔርን ፈልጉ፤ ኃይሉንም እንዲሰጣችሁ ጠይቁ”

አስታሱ
አስታውሱ እና አስቡ

ተአምራቱንና
“አስቡ” የሚለው ቃል ቀድሞ ከነበረው ሐረግ ጋር በማያያዝ የምንረዳው ነው። “ተአምራቱን አስቡ እና”

ከአፉ የወጣውን ፍርድ
እዚህ ላይ “አፍ” የሚያመለክተው እግዚአብሔር የተናገረውን ነው። “የተናገረውን ፍርድ”

እናንተ የአብርሃም ዘሮች ... እናንተ የያዕቆብ ልጆች
ጸሐፊው ለእስራኤላውያን እነዚህን ስሞች በመጥራት ይናገራል።

የእርሱ አገልጋይ አብርሃም
“የእግዚአብሔር አገልጋይ አብርሃም”

Psalms 105:7

ያዘዘውን ቃሉን ... ያስባል
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ስለሆነም አጽንኦት ለመስጠት አንድ ላይ ጥቅም ላይ ውለዋል። “ቃሉ” የሚለው የሚያመለክተው ቃል ኪዳኑን ነው። “ለባሪያው የገባውን ቃል ኪዳን ለዘላለም ያስባል”

ያስባል
ይህ ማለት ስለ አንድ ነገር ማስታወስ እና ማሰብ ማለት ነው። “ያስታውሳል”

ለሺህ ትውልዶች
“1,000 ትውልዶች”

Psalms 105:9

አሰበ
“አሰበ” ማለት አንድን ነገር አስታወሰ ማለት ነው። “ያስታውሳል”

ከአብርሃም ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳን ... ለይስሐቅም የማለውን
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች “ቃል ኪዳኑ” እና “መሐላው” የሚያመለክቱት እግዚአብሔር ለሕዝቡ የገባውን ተመሳሳይ ቃል ኪዳኑን ነው።

ለይስሐቅ የማለውን
"ያደረገው" የሚለው ቃል በቀደመው ሐረግ ውስጥ ግንዛቤ ተወስዶበታል። እዚህ ላይም ሊደገም ይችላል። “ለይስሐቅ ያደረገው መሐላ” ወይም “ለይስሐቅ የሰጠው መሐላ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 105:12

አገናኝ መግለጫ
መዝሙረኛው ስለ እስራኤል ይጽፋል።

እነርሱ በቁጥር ጥቂቶች በነበሩ ጊዜ
“እነርሱ” የሚለው ቃል እስራኤላውያንን ያመለክታል።

በምድሪቱ ላይ ስደተኞች ነበሩ
“ምድሪቱ” የከነዓንን ምድር ያመለክታል። “በከነዓን ምድር ስደተኞች ነበሩ”

ከ ሄዱ
“መቅበዝበዛቸውን ቀጠሉ”

ከሕዝብ ወደ ሕዝብ እንዲሁም ከመንግሥትም ወደ ሌላው
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ስለሆነም አጽንኦት ለመስጠት አንድ ላይ ጥቅም ላይ ውለዋል።

Psalms 105:14

አገናኝ መግለጫ
መዝሙረኛው ስለ እስራኤል ይጽፋል።

ስለ እነርሱ ሲል
“ለእነርሱ መልካም እንዲሆን።” ይህም እስራኤልን የሚያመለክት ነው።

የቀባኋቸውን አትንኩ
እዚህ ላይ “አትንኩ” ማለት አትጉዷቸው ማለት ሲሆን፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዳይነኩ ማስጠንቀቂያ ለመስጠት የተጠቀመበት የተጋነነ ቃል ነው። “የቀባኋቸውን ሰዎች አትጉዱ”

Psalms 105:16

ጠራ
“ላከ።” ይህ ማለት በምድሪቱ ላይ ረሃብ እንዲሆን አደረገ።

የእህልን አቅርቦት ሁሉ
x

Psalms 105:18

የእግር ብረት
የእስረኛ እግሮች የሚታሰሩበት የብረት ሰንሰለት

እግሮቹ በእግር ብረት ታሰሩ፣ አንገቱም በብረት ታሰረ
እነዚህ መግለጫዎች እንደ ድርጊት ሊገለጹ ይችላሉ። “ግብፃውያን እግሮቹን በእግር ብረት አሰሯቸው፤ በአንገቱም ላይ የብረት ሰንሰለት አደረጉ።

የእግዚአብሔር ቃል ፈተነው
“የእግዚአብሔር መልእክት ፈተነው”

Psalms 105:20

ንጉሡም ይፈቱት ዘንድ ባሪያዎችን ላከ፤ የሕዝቡም ገዢ ከእስር ነፃ አደረገው
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ ስለሆነም ንጉሡ ዮሴፍን ነፃ እንዳደረገው አጽንኦት ለመስጠት በአንድ ላይ ጥቅም ላይ ውለዋል።

ከዚያም እስራኤል ወደ ግብፅ መጣ
እዚህ ላይ “እስራኤል” የተባለው ያዕቆብን ያመለክታል። ያዕቆብ ቤተሰቡን ከእርሱ ጋር ይዞ መጣ። “እስራኤልና ቤተሰቡም ወደ ግብፅ መጡ”

Psalms 105:24

እግዚአብሔር ሕዝቡን ፍሬያማ አደረጋቸው
ጸሐፊው የእስራኤልን መብዛት ብዙ ፍሬ እንዳፈራ ተክል አድርጎ ገልጾታል። “እግዚአብሔር የሕዝቡን ቁጥር እጅግ አበዛው”

ሕዝቡን ለመጥላት፣ አገልጋዮቹንም ለመበደል
“ሕዝቡን ለመጥላት እና አገልጋዮቹን ለመበደል”

ምልክቶቹን በግብፃውያን መካከል አደረጉ ... ተአምራቱንም በካም ምድር
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። “ሙሴና አሮን የእግዚአብሔርን ተአምራት በግብፅ ውስጥ በካም ዝርያዎች መካከል አደረጉ”

ድንቆቹን በካም ምድር
“አደረጉ” የሚለው ቃል ቀደም ሲል በነበረው ሐረግ ውስጥ ግንዛቤ ተገኝቶበታል። እዚህም ላይ በድጋሚ ሊገለጹ ይችላሉ። “ድንቆቹንም በካም ምድር አደረጉ”

Psalms 105:28

ያንን ምድር ጨለማ አደረገው
“ሰማዩን አጨለመ”

እንቁራሪቶች
ትናንሽ የሚዘሉ እንስሳት

በገዢዎቻቸው ክፍሎች ውስጥ እንኳ
“በገዢዎቻቸው ክፍሎች ውስጥ ነበሩ”

Psalms 105:31

አገናኝ መግለጫ
መዝሙረኛው በግብፅ ላይ የነበረውን የእግዚአብሔርን ፍርድ መግለጹን ቀጥሏል።

መንጋ
የዝንብ መንጋ

ትንኞች
ትናንሽ የሚበሩ ነፍሳት

በረዶ
እንደ ዝናብ ከሰማይ የሚወርድ በረዶ

አጠፋ . . . ሰበረ
እግዚአብሔር በረዶን፣ ዝናብን እና መብረቅን አድርጎ ወይኑንና ዛፎችን አወደማቸው። “አጠፋው እና ሰበረውም”

Psalms 105:34

እጅግ ብዙ አንበጣዎች
“እጅግ ብዙ አንበጣዎች”

አንበጣዎቹም እፅዋቱን ሁሉ በሉ . . . በመሬት ላይ ያለውን ሰብል ሁሉ በሉ
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ስለሆነም አጽንኦት ለመስጠት በአንድነት ጥቅም ላይ ውለዋል። “አንበጣዎቹ እፅዋቱንና በምድሩ ላያ ያለውን ሰብል ሁሉ በሉ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በምድራቸውም እያንዳንዱን በኩር ገደለ፣ የጉልበታቸው መጀመሪያ የሆነውን ፍሬ ሁሉ መታ
እዚህ ላይ በሁለተኛው ሐረግ ስለ “መጀመሪያ ፍሬ” የሚናገረው በመጀመሪያው ሐረግ ስለ መጀመሪያ ልጅ ወይም ስለ በኩር የተጠቀሰውን ለመግለጽ ነው። “በምድራቸውም በመጀመሪያ የተወለደውን ሁሉ ገደለ፣ ያም የጉልበታቸው የመጀመሪያ ፍሬ ነው” ወይም “ከዚያም እግዚአብሔር በግብፃውያን ቤት ውስጥ ያለውን የመጀመሪያ ልጅ ወይም ታላቅ ልጅ ገደለ”

Psalms 105:37

እስራኤላውያንን ከብርና ከወርቅ ጋር አወጣቸው
እስራኤላውያን ከግብፅ በወጡ ጊዜ ብርና ወርቅ ይዘው ወጡ። “እስራኤላውያንን ከግብፅ ባወጣቸው ጊዜ ብርና ወርቅን ከንብረቶቻቸው ጋር ይዘው እንዲወጡ አደረጋቸው”

ከወገኖቹም አንዳቸውም በመንገድ ላይ አልተሰናከለም
ወደ ኋላ የቀረ አንድም አልነበረም። ይህ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለጽ ይችላል። “ወገኖቹ ሁሉ ጉዞውን ማድረግ ችለዋል”

Psalms 105:40

ድርጭትን አመጣ
እዚህ ላይ ይህንን ግልጽ ማድረግ ጠቃሚ ነው። ድርጭቶች ማለት ትናንሽ ወፎች ሲሆኑ እግዚአብሔር ይበሉ ዘንድ የላከላቸው ናቸው። “እግዚአብሔር ትናንሽ ወፎችን ይበሉ ዘንድ ላከላቸው”

ምግብ ከሰማይ
እግዚአብሔር መናን፣ የምግብ ዓይነት፣ ከሰማይ እንዲወርድ አድረገ። “ከሰማይ የወረደ ምግብ”

ፈሰሱ
“ውሃዎች ፈሰሱ”

አሰበ
ይህ ማለት አስታወሰ ማለት ነው። “አስተዋሰ”

Psalms 105:43

ሕዝቡን መራቸው . . . የመረጣቸውንም በደል አድራጊነት ድምፅ
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብፅ አውጥቶ በመራቸው ጊዜ ደስተኞች እንደ ነበሩ አጽንኦት ለመስጠት በአንድነት ጥቅም ላይ ውለዋል። ሕዝቡ በደስታ ይጮኹ ነበር። “የተመረጡትን ሕዝቦቹን በደስታ እና በድል አድራጊነት ድምፅ መራቸው”

የመረጣቸው
እዚህ ላይ “የመረጣቸው” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን የተመረጠ ሕዝብ ነው። “የእርሱ የተመረጠ ሕዝብ”

የድል አድራጊነት ድምፅ
ጠላቶቻቸውን ስላሸነፉ ሕዝቡ በደስታ የሚያሰሙት የድል አድራጊነት ድምፅ ነው

ሥርዓቱን ጠብቁ ሕጎቹን ታዘዙ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ አንድ ዓይነት ትርጉም አላቸው፣ አጽንኦት ለመስጠት ግን በአንድነት ጥቅም ላይ ውለዋል። ሥርዓቱን “መጠበቅ” ማለት እነርሱን መታዘዝ ማለት ነው። “ሕጉንና ሥርዓቱን መታዘዝ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 106

1 ያህዌን አመስግኑ ቸር ነውና ያህዌን አመስግኑ ምሕረቱም ለዘላለም ነውና። 2 የያህዌን ብርቱ ሥራ ማን ሊናገር ይችላል? ምስጋናውንስ ሁሉ ማን ተናግሮ
ይጨርሳል? 3 ዘወትር መልካሙንና ትክክል የሆነውን የሚያደርጉ የተባረኩ ናቸው። 4 ያህዌ ሆይ፣ ለሕዝብህ ሞገስ ስታደርግ አስበኝ፤ በምታድናቸውም ጊዜ
ርዳኝ። 5 ይኸውም፣ አንተ የመረጥሃቸውን መበልጸግ እንዳይ፣ በሕዝብህ ደስ መሰኘት እኔንም ደስ እንዲለኝ በርስትህም ክብር መመካት እንድችል ነው። 6
እኛም እንደ አባቶቻችን ኃጢአት ሠራን፣ በደልን፣ ክፉም አደረግን። 7 አባቶቻችን በግብፅ ምድር ያደረግኸውን አላስተዋሉም። ብዙዎቹን የቸርነት ሥራዎቹን
አላስተዋሉም። በባሕሩ አጠገብ፣ ቀይ ባሕር አጠገብ ዐመፁብህ። 8 እርሱ ግን የኃይሉን ታላቅነት ለማሳየት ስለ ስሙ አዳናቸው። 9 ቀይ ባሕርን ገሠጸ፤
እርሱም ደረቀ በምድረ በዳ እንደሚታለፍ በጥልቅ ውሃ መካከል መራቸው። 10 ከባላጋራቸው እጅ አዳናቸው ከጠላትም እጅ ታደጋቸው። 11 ባላጋራዎቻቸውን
ውሃ ዋጣቸው ከእነርሱ አንድ አልተረፈም። 12 ከዚያ በኋላ የተስፋ ቃሉን አመኑ በዝማሬም አመሰገኑት። 13 ሆኖም፣ ወዲያውኑ እርሱ ያደረገውን ረሱ በምክሩም
ለመሄድ አልታገሡም። 14 በምድረ በዳ ብዙ ነገር ተመኙ፤ በበረሐም እግዚአብሔርን ተፈታተኑት። 15 እርሱም የለመኑትን ሰጣቸው ነገር ግን የሚያኮሰምን ደዌ
ሰደደባቸው። 16 ሰፈር ውስጥ በሙሴ ላይ የተቀደሰው የያህዌ ካህን ላይ ቀኑ። 17 ምድር ተከፍታ ዳታንን ዋጠች የአቤሮንንም ሰዎች ሰለቀጠች። 18
በመካከላቸው እሳት ነድዶ ነበልባልም ክፉዎችን ፈጅቶ አስወገደ። 19 በኮሬብ ጥጃ ሠሩ ቀልጦ ለተሠራ ምስል ሰገዱ። 20 ክብራቸውን ሣር በሚበላ የበሬ
ምስል ለወጡ። 21 በግብፅ ታላላቅ ነገሮች ያደረገውን ያዳናቸውን እግዚአብሔርን ረሱ። 22 እርሱ በካም ምድር ድንቅ ሥራ በቀይ ባሕርም አስደናቂ ነገር
አደረገ። 23 ቁጣውን እንዲመልስ እርሱ የመረጠው ሙሴ በመካከል ባይገባ ኖሮ እነርሱን ለማጥፋት ወስኖ ነበር። 24 መልካሚቱን ምድር ናቁ በተስፋ ቃሉም
አላመኑም። 25 ድንኳናቸው ውስጥ አጉረመረሙ ለያህዌም አልታዘዙም። 26 ስለዚህ በምድረ በዳ እንደሚያጠፋቸው እጁን አንሥቶ ማለ። 27 ዘሮቻቸውን
በአሕዛብ መካከል ለመጣል እነርሱንም ወደ ተለያየ አገሮች እንደሚበትናቸው ማለ። 28 ብዔል ፌጎርን አመለኩ ለሙታን የተሠዋውን በሉ። 29 በተግባራቸውም
እግዚአብሔርን አስቆጡት፤ በዚህም ምክንያት በመካከላቸው መቅሠፍት ተነሣ። 30 ፊንሐስ ተነሥቶ ጣልቃ ገባ፤ መቅሠፍቱም ተገታ። 31 ይህም ከትውልድ
እስከ ትውልድ ለዘላለም ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት። 32 ደግሞም በመሪባ ውሃ አጠገብ ያህዌን አስቆጡት ሙሴም በእነርሱም ምክንያት ችግር ላይ ወደቀ። 33
ሙሴን ስላስመረሩት ራሱን ባለ መቆጣጠር ተናገረ። 34 እግዚአብሔር ባዘዛቸው መሠረት ሕዝቦችን ከማጥፋት ወደ ኃላ አሉ። 35 እንዲያውም ከእነርሱ ጋር
በመደባለቅ የእነርሱን መንገድ ተማሩ። 36 ጣዖቶቻቸውን አመለኩ፤ ይህም ወጥመድ ሆነባቸው። 37 ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን ለአጋንንት ሠዉ። 38
የወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን ደም ለከነዓን ጣዖቶች መሥዋዕት በማቅረባቸው ንጹሕ ደም አፈሰሱ ምድሪቱንም አረከሱ። 39 እነርሱ በሥራቸው ረከሱ
በድርጊታቸውም አመንዝሮች ሆኑ። 40 ስለዚህ ያህዌ በሕዝቡ ላይ እጅግ ተቆጣ ርስቱንም ተጸየፈ። 41 ለአሕዛብ አሳልፎ ሰጣቸው ጠላቶቻቸውም በላያቸው
ገዢዎች ሆኑባቸው። 42 ጠላቶቻቸው ጨቆኑአቸው በሥልጣናቸውም ሥር አደረጓቸው። 43 እርሱ ብዙ ጊዜ ታደጋቸው እነርሱ ግን ዐመፅ ማድረጋቸውን ገፉበት።
በገዛ ኃጢአታቸው ተዋረዱ። 44 ይህም ሆኖ እንዲረዳቸው ወደ እርሱ ሲጮኹ ጩኸታቸውን ሰማ ጭንቀታቸውንም ተመለከተ። 45 ለእነርሱ ሲል ቃል ኪዳኑን
አሰበ እንደ ምሕረቱም ብዛት ከቁጣው ተመለሰ። 46 የሚጨቁኑአቸው ሁሉ እንዲራሩላቸው አደረገ። 47 አምላካችን ያህዌ ሆይ፣ አድነን፤ ለቅዱስ ስምህ
ምስጋና እንድናቀርብ፣ አንተን በመወደስ እንድንከብር ከሕዝቦች መካከል ሰብስበህ አምጣን። 48 የእስራኤል አምላክ ያህዌ ከዘላለም እስከ ዘለላም ይባረክ።
ሕዝብም ሁሉ አሜን ይበል። ያህዌ ይባረክ።

Psalms 106:1

አጠቃላይ መረጃ
በዕብራውያን የቅኔ አጻጻፍ ውስጥ ተመሳሳይነት የተለመደ አገላለጽ ነው።

የቃል ኪዳኑ ታማኝነት ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል
ስውር ስሙ “ታማኝነት” ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል። “ለቃል ኪዳኑ ለዘላለም ታማኝ ነውና”

የእግዚአብሔርን ኃያል ድርጊቶች . . . ሥራውንስ ማን ይናገራል?
ደራሲው ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው እግዚአብሔርን ለማመስገን ነው እንጂ መልስ ፈልጎ አይደለም። “ማንም የእግዚአብሔር ኃያላን ድርጊቶች . . . ሥራውንም መናገር አይችልም።”

የሚያስመሰግኑ ሥራዎች
“ምስጋና የሚገባቸው ሥራዎች”

Psalms 106:3

አስበኝ
“አስበኝ” የሚለው ሐረግ አንድን ነገር ማስታወስ ማለት ነው። “አስበኝ”

የመረጥከውን
“የመረጥከው” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በእግዚአብሔር የተመረጠውን ሕዝብ ነው። “የመረጥከውን ሕዝብህን”

በደስታ ደስ መሰኘት . . . እናም መክበር
እነዚህ ነገሮች ዳዊት “የመረጥካቸውን ብልጽግና በማየት” ከሚለው ጋር ስለሚያደርገው የሚናገረው ነው። “አደርጋለሁ” የሚለው ቃል እዚህ ጋ ሊደገም ይችላል። “በደስታ ደስ ይለኛል . . . እከብራለሁም”

መደሰት
ደስታ፣ ደስ መሰኘት

ከአንተ ርስት ጋር መክበር
እዚህ ላይ “የአንተ ርስት” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው በእግዚአብሔር የተመረጡ ሕዝቦች የሆኑትን እስራኤላውያንን ነው። “መክበር” ማለት “በአንድ ነገር መመካት” ማለት ነው። ከዚህ የተነሣ በእግዚአብሔር ይመካሉ። “በታላቅነትህ ከሕዝብህ ጋር እመካለን” ወይም “ከሕዝብህ ጋ ስለ አንተ እንመካለን”

Psalms 106:6

አስገራሚ ሥራዎችህን አላደነቁም
“ለሠራሃቸው አስደናቂ ሥራዎች አላመሰገኑም”

በቃል ኪዳን ታማኝነትህ የሠራሃቸውን ብዙ ሥራዎች ቸል አሉ
“ታማኝነት” የሚለው ስውር ስም ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል። “አንተ ለቃል ኪዳንህ ታማኝ ሆነህ ያደረግከውን ብዙ ሥራ ቸል አሉ”

በባህር ውስጥ . . . የመቃ ባህር
እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚያመለክቱት አንዱን ባህር ነው። ሁለተኛው የባህሩ ስም ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 106:8

የሆነ ሆኖ፣ እርሱ
“ምንም እንኳን አሁን የተናገርኩት እውነት ቢሆንም፣ እርሱ”

ስለ ስሙ
እዚህ ላይ “ስለ ስሙ” የሚይለው የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው። “ስለ ራሱ መልካም ስም ሲል”

በጥልቅ በምድረ በዳ ውስጥ
እዚህ ላይ ዳዊት እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በመቃ ባህር ውስጥ በደረቅ ምድረ በዳ እንደ መራቸው ይናገራል። “ጥልቁ” የሚያመለክተው የባህሩን ታችኛው ክፍል ሲሆን እግዚአብሔር ውሃውን በከፈለ ጊዜ የታየው ነው። “በመቃ ባህር ውስጥ በደረቅ ምድር”

Psalms 106:10

ከእጁ አዳናቸው ... እናም ከእጁ ታደጋቸው
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች በመሠረቱ አንድ ዓይነት ናቸው፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ከጠላቶቻቸው እንዳዳናቸው አጽንኦት ለመስጠት በአንድ ላይ ጥቅም ላይ ውለዋል።

ከሚጠሏቸው እጅ
እዚህ ላይ “እጅ” የሚያመለክተው ኃይልን ወይም ቁጥጥርን ነው። “ከሚጠሏቸውም ኃይል” ወይም “ከሚጠሏቸው ቁጥጥር”

ጠላቶቻቸውን ሸፈናቸው
ይህ ስለ ጠላቶቻቸው መስጠም ጨዋ በሆነ መንገድ መግለጽ ነው። “ጠላቶቻቸውን አሰጠመ”

ከዚያም እነርሱ የእርሱን ቃሎች አመኑ
እዚህ ላይ “እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው “ዘሮቻቸውን” እና “የእርሱ” የሚለው ቃል ደግሞ “እግዚአብሔርን” ነው።

Psalms 106:13

ምክሩን አልታገሱም
እግዚአብሔር እንዲሄዱበት የሚፈልገውን ከመጠበቅ ይቅል እርሱን ሳይጠብቁ ነገሮችን ሁሉ አደረጉ። “የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጀመሪያ ሳይጠብቁ ነገሮችን አደረጉ”

የማይረኩ ምኞቶች
“እርካታ ሊሰጡ የማይችሉ ምኞቶች”

እግዚአብሔርን ተፈታተኑ
“በእግዚአብሔር ላይ አመጹ”

ነገር ግን እርሱ እጅግ አስከፊ በሽታ ላከ
እዚህ ላይ ዳዊት እግዚአብሔር ሰዎቹ ይጎዱ ዘንድ ልክ አንድ ሰው ሌላን ሰው ወይም መልእክተኛን እንደሚልክ በሽታን እንደ ላከባቸው ይናገራል። “ነገር ግን እርሱ በአስከፊ በሽታ እንዲሠቃዩ አደረጋቸው።

አስከፊ በሽታ
ሰዎች ቀስ በቀስ እንዲዳከሙ እና የተወሰኑት እንዲሞቱ የሚያደርግ በሽታ ነው

Psalms 106:16

በሰፈር ውስጥ
ይህ በምድረ በዳ የሚገኘውን የእስራኤል ሰፈር ያመለክታል። “በምድረ በዳ ሰፈር ውስጥ”

ምድር ተከፍታ ዋጠቻቸው
እዚህ ላይ ምድር ተከፍታ ሰዎችን መቅበሯ ፍጥረት አንድ ነገር ከመዋጡ ጋር ይነጻጸራል። “ምድር ተከፈተች ቀበረቻቸውም”

ዳታን
ይህ በሙሴ ላይ ያመፀ የታወቀ ሰው ነበር።

የአቢሮን ተከታዮች ተሸፈኑ
የአቢሮን ተከታዮችም መሬቷ ተከፍታ ዳታንን ስትቀብረው አብረው ተቀብረዋል። “የአቢሮን ተከታዮች ተሸፍነዋል” ወይም “የአቢሮን ተከታዮች ተቀብረዋል”

አቢሮን
ይህ በሙሴ ላይ ያመፀ የታወቀ ሰው ነበር።

እሳት በመካከላቸው ተነሣ፤ ክፉዎችን በላች
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን፣ ክፉ ሰዎች በእሳት እንዴት እንደ ተገደሉ አጽንኦት ለመስጠት በአንድነት ተጽፈዋል።

Psalms 106:19

በኮሬብ የጥጃ ምስል ሠሩ ቀልጦ ለተሠራ ምስልም ሰገዱ
የጥጃው ምስል ከብረት ቀልጦ የተሠራ እንደ ነበር ይህ መረጃ ሊመዘገብ ይችላል። “በኮሬብ ቀልጦ የተሠራ የጥጃ ምስል አደረጉ ሰገዱለትም”

የእግዚአብሔርን ክብር በጥጃ አምሳያ ለወጡ
ይህ ማለት እግዚአብሔርን ከማምለክ ይልቅ የጥጃውን ምስል አመለኩ። “የእግዚአብሔርን ክብር ከማምለክ ይልቅ የጥጃውን ምስል አመለኩ”

የእግዚአብሔር ክብር
እዚህ ላይ እግዚአብሔር የተገለጠው በክብሩ ነው። “የተከበረው አምላካቸው” ወይም “የተከበረው አምላክ”

Psalms 106:22

የካም ምድር
ይህ የሚያመለክተው የካም ዝርያዎች የኖሩበትን ምድር ነው። “የካም ዝርያዎች የኖሩበት ምድር”

ታላላቅ ድርጊቶች
“አስደናቂ ነገሮች”

በቁጣው መቅሰፍት እንዳያጠፋቸው በመካከል ገብቶ በፊቱ ቆመ
እዚህ ላይ ዳዊት የሚናገረው ሙሴ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን እንዳያጠፋቸው በመካከል ገብቶ ስለ መቆሙ ነው። “እግዚአብሔር እንዳያጠፋቸው በእስራኤላውያንና በእግዚአብሔር መካከል ቆመ”

Psalms 106:24

አጉረመረሙ
ተነጫነጩ

ቃል ኪዳኑ
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር የከነዓንን ምድር እንደ ርስታቸው እንዲወስዱ የገባላቸውን ቃል ኪዳን ነው።

Psalms 106:26

የእርሱን እጅ ዘረጋ
“የእርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው። መሐላ በሚማልበት ጊዜ እጅን ማንሣት ደግሞ የተለመደ ነገር ነበር።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ዘሮቻቸውን . . . በባዕድ ምድር በተናቸው
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ አንድ ዓይነት ትርጉም አላቸው ነገር ግን ትኩረት ለመስጠት በአንድነት ጥቅም ላይ ውለዋል። “እናም ዘሮቻቸው በባዕድ ምድር እንዲኖሩ አደረጋቸው”

በተነ
ይህ ማለት መበታተን ወይም አንድን ነገር ማሰራጨት ማለት ነው።

Psalms 106:28

ለሙታን የሚደረግ መሥዋዕት
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለጽ ይችላል። “ለሙታን ያቀረቡት መሥዋዕት”

ለሙታን
“ሙታን” የተባሉት እስራኤላውያን ያመልኳቸው የነበሩት ጣዖታትና ባዕድ አማልክት ናቸው። “ለሞቱ አማልክት” ወይም “ሕይወት ለሌላቸው አማልክት”

መቅሰፍት መጣ
“መቅሰፍቱ ተሰራጨ”

እንዲናደድ አደረጉት
“አስቆጡት”

Psalms 106:30

ፊንሐስ ጣልቃ ለመግባት ተነሣ
x

Psalms 106:32

መሪባ
ይህ የቦታ ስም ነው።

ከእነርሱ የተነሣ ተሰቃየ
ሙሴ ከሕዝቡ ኃጢአት የተነሣ ተሰቃየ። እዚህ ላይ “እነርሱ” የሚለው ቃል ሕዝቡን የሚያመለክት ተውላጠ ስም ሲሆን ኃጢአታቸውንም ያመለክታል። “በድርጊታቸውም ምክንያት ተሰቃየ”

ከአሕዛብ ጋር ተቀላቀሉ
እዚህ ላይ ዳዊት የሚናገረው ሕዝቡ የአሕዛብን ሴቶች በማግባት ስለ “መቀላቀላቸው” ነው። “ነገር ግን ከአሕዛብ ጋር በጋብቻ ተደባለቁ”

ያም ለእነርሱ ወጥመድ ሆነባቸው
ጣዖቶቹ ወጥመድ ሆኑባቸው።

Psalms 106:37

የወንዶችና የሴቶች ልጆቻቸውን ደም፣ የንጹሐንን ደም አፈሰሱ
“ደም ማፍሰስ” የሚለው ሐረግ “መግደልን” ለመግለጽ ጥቅም ላይ የሚውል ገላጭ የአነጋገር ዘይቤ ነው። “ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን በገደሉበት ጊዜ የንጹሐንን ደም አፍስሰዋል”

በሥራቸው ረከሰዋል
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለጽ ይችላል። “ሥራቸው አርክሶአቸዋል”

በድርጊታቸውም እንደ አመንዝሮች ሆኑ
እዚህ ላይ ዳዊት ለእግዚአብሔር ታማኝ አለመሆናቸውን ከማይታመኑትን አመንዝሮች ጋር ያነጻጽረዋል። “እነርሱም እንደ አመንዝሮች ለእግዚአብሔር ታማኞች አልሆኑም”

Psalms 106:40

ስለዚህ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ተቆጣ . . . የራሱን ሕዝብ ናቃቸው
“ስለዚህ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ተቆጣ ናቃቸውም”

በአሕዛብ እጅ አሳልፎ ሰጣቸው
እዚህ ላይ “እጅ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኃይልን ወይም መቆጣጠርን ነው። “እግዚአብሔር ሕዝቡን ይቆጣጠሩ ዘንድ ለአሕዛብ ፈቀደላቸው”

የጠሏቸው
“የጠሏቸው ሰዎች”

Psalms 106:42

ለባለ ሥልጣኖቻቸው ተገዢዎች ሆኑ
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለጽ ይችላል። “ጠላቶቻቸው ለባለሥልጣኖቻቸው እንዲገዙ አደረጓቸው”

በራሳቸው ኃጢአት ሕግን አመጡ
እዚህ ላይ “ሕግን አመጡ” የሚለው ሐረግ በራሳቸው ላይ ጥፋትን አመጡ ማለት ነው። እንዲሁም፣ ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለጽ ይችላል። “ኃጢአታቸው አጠፋቸው”

Psalms 106:44

የሆነ ሆኖ፣ እርሱ
“ምንም እንኳን አሁን የተናገርኩት እውነት ቢሆንም፣ እርሱ” ይህንን በመዝሙር 106:8 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።

ጭንቀታቸው
“ስቃያቸው” ወይም “መከራቸው”

አሰበ
“አሰበ” የሚለው ቃል አንድን ነገር አስታወሰ ማለት ነው። “አስታወሰ”

እርሱ . . . ከጽኑ ፍቅሩ የተነሣ ተጸጸተ
“እርሱ . . . እስከ አሁን አጥብቆ ስለሚወዳቸው እንዲቀጣቸው አልወሰነም”

ያሸነፏቸው
“የማረኳቸው” ይህ የሚያመለክተው ምርኮኛ አድርገው የወሰዷቸውን የእስራኤላውያንን ጠላቶች ነው።

ምሕረት አደረገላቸው
“ራራላቸው”

Psalms 106:47

አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ላይ 106:48 ከዚህ መዝሙር መጨረሻ የሚበልጥ ነው። ከመዝሙር 90 እስከ መዝሙር 106 መጨረሻ ላሉት 4 መጽሐፍት በሙሉ የመዝጊያ መግለጫ ነው።

የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይመስገን
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “ሕዝቡ የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን ያመስግኑ”

ለቅዱሱ ስምህ
እዚህ ላይ እግዚአብሔር “በቅዱስ ስሙ” ተጠቅሷል። “ለአንተ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ
ይህ የሚያመለክተው ሁለት ጽንፎችን ሲሆን ትርጉሙም ለዘለዓለም ማለት
ነው። ይህንን በመዝሙር 41:13 እንዴት እንደ ተረጎምኸው ተመልከት።
“ለዘለዓለም”

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 107

1 ቸር ነውና ምሕረቱም ለዘላለም ነውና ያህዌን አመስግኑ። **2** ያህዌ የተቤዣቸው ከጠላትም እጅ የታደጋቸው ይናገሩ። **3** ለባዕድ ምድር፣ ከምሥራቅና ከምዕራብ፣ ከሰሜንና ከደቡብ ሰበሰባቸው። **4** በበረሐ መንገድ ጠፍቶአቸው በምድረ በዳ ተንከራተቱ የሚኖሩበትም ከተማ አላገኙም። **5** ተራቡ፤ ተጠሙ ከድካም የተነሣ ዛሉ። **6** በተጨነቁ ጊዜ ወደ ያህዌ ጮኹ እርሱም ከመከራቸው አዳናቸው። **7** ወደሚኖሩበት ከተማ በቀና መንገድ መራቸው። **8** ለሰው ልጆች ስላደረገው ድንቅ ነገርና ስለዘላለማዊ ፍቅሩ ሕዝቡ ያህዌን ያመስግኑ። **9** እርሱ የተጠማችውን ነፍስ አርክቶአልና የተራበችውን ነፍስ በመልካም ነገር አጥግቦአል። **10** አንዳንዶች በሰንሰለት ታስረው ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ይኖሩ ነበር። **11** ይህም የሆነው በእግዚአብሔር ቃል በማመፃቸው የልዑልንም ምክር በማቃለላቸው ነበር። **12** በከባድ ሥራ ልባቸውን አዛለ ተዘለፈለፉ፤ የሚረዳቸውም አላገኙም። **13** በተጨነቁ ጊዜ ወደ ያህዌ ጮኹ፤ እርሱም ከመከራቸው አዳናቸው። **14** ከነበሩበት ድቅድቅ ጨለማ አወጣቸው የታሰሩበትንም ሰንሰለት ሰባበረ። **15** ለሰው ልጆች ስላደረገው ድንቅ ነገርና ስለ ዘላለማዊ ፍቅሩ ሕዝቡ ያህዌን ያመስግኑ። **16** እርሱ የናሱን በሮች ሰብሮአልና የብረቱንም መወርወሪያ ቆርጦአል። **17** አንዳንዶች የዐመፃን መንገድ በመከተላቸው ቂሎች ሆኑ ከበደላቸው የተነሣ ችግር ውስጥ ወደቁ። **18** ምግብ የመብላት ፍላጐት አጡ፤ ወደ ሞት በሮችም ተቃረቡ። **19** በተጨነቁ ጊዜ ወደ ያህዌ ጮኹ እርሱም ከመከራቸው አዳናቸው። **20** ቃሉን ልኮ ፈወሳቸው። ከመቃብር አፋፍ መለሳቸው። **21** ለሰው ልጆች ስላደረገው ድንቅ ነገርና ስለ ዘላለማዊ ፍቅሩ ሕዝቡ ያህዌን ያመስግኑ። **22** የምስጋና መሥዋዕት ያቅርቡለት በዝማሬም ሥራውን ያውጁ። **23** አንዳንዶች በመርከብ እየተጓዙ ንግዳቸውን ያካሄዱ ነበር። **24** እነርሱ የያህዌን ሥራ አዩ ድንቅ አድራጐቱንም በጥልቅ ውስጥ ተመለከቱ። **25** ትእዛዝ በሰጠ ጊዜ ባሕሩን የሚያናውጥ ዐውሎ ነፋስ ነፈሰ። **26** ወደ ሰማይ ወጡ፤ ወደ ጥልቅም ወረዱ ከመከራቸው የተነሣ ልባቸው ቀለጠ። **27** እንደ ሰካራም ዞሮባቸው ወዲያ ወዲህ ተንገዳገዱ፤ መላው ጠፍቶባቸው የሚያደርጉትን አጡ። **28** በመከራቸው ጊዜ ወደ ያህዌ ጮኹ፤ እርሱም ከመከራቸው አዳናቸው። **29** ዐውሎ ነፋሱን ጸጥ አደረገ ሞገዱም ረጭ አለ። **30** ባሕሩ ጸጥ በማለቱ ደስ አላቸው ወዳሰቡትም ወደብ አደረሳቸው። **31** ለሰው ልጆች ስላደረገው ድንቅ ነገር ስለ ዘላለማዊ ፍቅሩ ሕዝቡ ያህዌን ያመስግኑ። **32** በሕዝቦች ጉባኤ መካከል ከፍ ከፍ ያደርጉት በሽማግሌዎችም ሸንጐ ያመስግኑት። **33** ወንዞችን ወደ ምድረ በዳ የውሃ ምንጮችንም ወደ ደረቅ ምድር ለወጠ። **34** ከነዋሪዎቿ ክፋት የተነሣ ፍሬያማዋን መሬት ደረቅ ምድር አደረገ። **35** ምድረ በዳውን ወደ ኩሬ ደረቁንም ምድር ወደ ውሃ ምንጭ ቀየረ። **36** የተራቡትን በዚያ አኖረ የሚኖሩበትንም ከተማ ሠሩ። **37** በእርሻዎች እህል ዘሩ ወይንን ተከሉ፤ ብዙ መከርም ሰበሰቡ። **38** ይባርካቸዋል፤ እነርሱም እጅግ ይበዛሉ የከብቶቻቸውም ብዛት እንዲያንስ አያደርግም። **39** በጭንቅ፣ በመከራና በሐዘን፣ ቁጥራቸው አንሶ ተዋርደው ነበር፤ በመኳንንቱም ላይ መናቅን አወረደባቸው **40** መውጪያ መግቢያው በማይታወቅ በረሐ ውስጥም አንከራተታቸው። **41** ሆኖም፣ ችግረኞችን ከስቃይ አወጣቸው ለቤተ ሰቡም እንደ በግ መንጋ ተጠነቀቀ። **42** ቅኖች ይህን ዐይተው ደስ ይላቸዋል ክፋትም አፏን ትዘጋለች። **43** አስተዋይ የሆነ ሰው ይህን ልብ ይበል፤ እርሱም የያህዌን ምሕረት ያስተውል።

Psalms 107:1

አጠቃላይ መረጃ
በዕብራውያን የቅኔ አጻጻፍ ውስጥ ተመሳሳይነት የተለመደ አገላለጽ ነው።

የቃል ኪዳኑ ታማኝነት ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል
“ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል። “ለቃል ኪዳኑ ለዘላለም ታማኝ ነው”

እግዚአብሔር የተቤዣቸው
“የተቤዣቸው” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔር ያዳናቸውን ሰዎች ነው። “እነርሱ እግዚአብሔር ያዳናቸው”

መናገር
ይህ ማለት ስለ አንድ ነገር ለሌሎች መናገር ማለት ነው። “እግዚአብሔር ስላደረገው ነገር ተናገሩ”

ከጠላት እጅ
እዚህ ላይ “እጅ” የሚለው የሚያመለክተው ኃይልን ነው። “ከጠላት ኃይል”

ከምሥራቅ . . . እና ከደቡብ
እዚህ ላይ አራቱ አቅጣጫዎች ትኩረት የተሰጣቸው ከሁሉም ስፍራ እንደ ሰበሰባቸው ለማመልከት ነው። “ከሁሉም አቅጣጫ” ወይም “ከሁሉም የዓለም ክፍል”

ከምሥራቅና ከምዕራብ፣ ከሰሜን እና ከደቡብ
ይህ የሚገልጸው እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚሰበስበባቸውን ስፍራዎች ነው። “እርሱ ከምሥራቅና ከምዕራብ፣ ከሰሜን እና ከደቡብ ሰበሰባቸው”

Psalms 107:4

ተቅበዘበዙ
“አንዳንድ ሰዎች ተቅበዝብዘዋል”

በምድረ በዳ መንገድ ላይ
“በምድረ በዳ በነበረው መንገድ ላይ”

በኖሩበት
“መኖር በቻሉበት”

በመከራቸው ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጮኹ
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር እንዲረዳቸው ወደ እርሱ መጸለያቸውን ነው። “በመከራቸው እንዲረዳቸው ወደ እግዚአብሔር ጸለዩ”

ጭንቀታቸው
“ችግራቸው” ወይም “ሥቃያቸው”

Psalms 107:8

ኦ እነዚያ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታማኝነቱ ሊያመሰግኑት ይገባል
እዚህ ላይ “ኦ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ ጠንከር ያለ ማሳሰቢያ መስጠትን ነው። “ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል። “እርሱ ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ስለ ሆነ ሕዝቡ እግዚአብሔርን ያመስግኑ” ወይም “ሕዝቡ እግዚአብሔርን ማመስገን ያለባቸው እርሱ ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ስለሆነ ነው”

ለሰብአዊነት
“ለሁሉም ሰዎች”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እርሱ የተጠሙትን ሰዎች ፍላጎት አርክቶአል
“ለሚፈልጉት ውሃን ሰጣቸው፣ ለተጠሙትም”

የተራቡትን ሰዎች ፍላጎት በመልካም ነገሮች አጥግቦአል
“እጅግ ለተራቡ እና ምግብ ላስፈለጋቸው፣ ይበሉ ዘንድ መልካምን ነገር ሰጣቸው”

አንዳንዶች ተቀመጡ
ይህ የሚያመለክተው እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔር ያዳናቸው መሆናቸውን ነው። “እግዚአብሔር የተቀመጡትን ሰዎች አድኖአቸዋል”

በጨለማ እና በድንግዝግዝ ውስጥ
“ጨለማ” እና “ድንግዝግዝ” በመሠረቱ አንድ አይነት ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ የነበሩበት ስፍራ ምን ያህል ጨለማ እንደነበረ ትኩረት ለመስጠት ጥቅም ላይ ውለዋል። “በፍጹም ጨለማ ውስጥ”

Psalms 107:11

በእግዚአብሔር ቃል ላይ አመፁ . . . የልዑሉንም ትእዛዝ አንቀበልም አሉ
እነዚህ ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አሏቸው ትኩረት የሚሰጡትም ምን ያህል በእግዚአብሔር ላይ እንዳመፁ ነው፤ ለዚህም ነው በእስር ቤት የተጣሉት።

በመከራ ጊዜ ልባቸውን ትሑት አደረገ
እዚህ ላይ ልብ የሚለው አንድን ሰው ይወክላል፣ ነገር ግን በተወሰነ ሁኔታ ፈቃዱን የሚያመለክት ነው። “መከራ እንዲቀበሉ በማድረግ ትሑት እንዲሆኑ አደረጋቸው”

ችግር
1) “መከራ” ወይም 2) “ከባድ ሥራ” የሚሉት ትርጉሞችም ተቀባይነት አላቸው።

ተሰናከሉ፤ የሚረዳቸውም አልነበረም
“ተሰናከሉ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እነዚህ ሰዎች እጅግ አስቸጋሪ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ የነበሩባቸውን ጊዜያት ነው። “መከራ ውስጥ ገቡ ማንም ከመከራ ውስጥ እንዲወጡ የሚረዳቸው አልነበረም”

በመከራቸውም ወደ እግዚአብሔር ጮኹ
ይህም ማለት እግዚአብሔር እንዲረዳቸው ወደ እርሱ ጸለዩ ማለት ነው። ይህንን በመዝሙር 107:6 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። “በመከራቸው እንዲረዳቸው ወደ እግዚአብሔር ጸለዩ”

ጭንቀታቸው
“ችግር” ወይም “ሥቃይ።” ይህንን በመዝሙር 107:6 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

አመጣ
እዚህ ላይ ዳዊት እግዚአብሔር ከጭንቀታቸው እንዳዳናቸው ጭንቀታቸውንም እርሱ እነርሱን አድኖ እንዳመጣበት ተጨባጭ ስፍራ አድርጎ ይገልጸዋል።

Psalms 107:14

አመጣቸው
“እግዚአብሔር በእስር ቤት ያሉትን አመጣ”

ጨለማ እና ድንግዝግዝ
“ጨለማ” እና “ድንግዝግዝ” በመሠረቱ አንድ አይነት ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ የነበሩበት ስፍራ ምን ያህል ጨለማ እንደነበረ ትኩረት ለመስጠት ጥቅም ላይ ውለዋል። ይህንን በመዝሙር 107:10 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። “ፍጹም ጨለማ”

ኦ እነዚያ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታማኝነቱ ሊያመሰግኑት ይገባል
እዚህ ላይ “ኦ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ ጠንከር ያለ ማሳሰቢያ መስጠትን ነው። “ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል። ይህንን በመዝሙር 107:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። “እርሱ ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ስለ ሆነ ሕዝቡ እግዚአብሔርን ያመስግኑ” ወይም “ሕዝቡ እግዚአብሔርን ማመስገን ያለባቸው እርሱ ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ስለሆነ ነው”

እርሱ
“ምክንያቱም እርሱ”

የነሐሱን በሮች ሰበረ፤ የብረቱንም ምሰሶዎች ቆረጠ
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች የሚያመለክቱት እግዚአብሔር ሕዝቡን ከእስር ነጻ ማውጣቱን ሲሆን አጽንኦት የሚሰጡትም እግዚአብሔር በእውነት ነጻ እንዳወጣቸው ነው። “ሕዝቡን ከእስር ነጻ አደረገ”

Psalms 107:17

በአመጻ መንገዳቸው ሞኞች ነበሩ
“በእግዚአብሔር ላይ በማመጻቸው ሞኞች ነበሩ”

እናም ተሰቃዩ
“እናም መከራ ተቀበሉ።” በልዩ ሁኔታ ስለ ታመሙ ተሰቃዩ። “እናም ሕመምተኞች ሆኑ”

ወደ ሞት በሮች ተጠጉ
ይህ “የመሞት” ተግባር እንደ “ሞት በሮች” ተገልጾአል። “የሞቱ ያህል ሆኑ”

በመከራቸውም ወደ እግዚአብሔር ጮኹ
ይህ ማለት እግዚአብሔር እንዲረዳቸው ወደ እርሱ ጸለዩ ማለት ነው። ይህንን በመዝሙር 107:6 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። “በመከራቸው እንዲረዳቸው ወደ እግዚአብሔር ጸለዩ”

Psalms 107:20

ቃሉን ላከ ፈወሳቸውም
እዚህ ላይ ዳዊት የሚገልጸው እግዚአብሔር ቃሎቹን እንደ መልእክተኛ ልኮ እንደሚናገር ነው። ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) “እንዲፈወሱ አዘዘ እነርሱም ተፈወሱ” ወይም 2) “አበረታታቸው ፈወሳቸውም”

ኦ እነዚያ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታማኝነቱ ሊያመሰግኑት ይገባል
እዚህ ላይ “ኦ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ ጠንከር ያለ ማሳሰቢያ መስጠትን ነው። “ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል። ይህንን በመዝሙር 107:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። “እርሱ ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ስለ ሆነ ሕዝቡ እግዚአብሔርን ያመስግኑ” ወይም “ሕዝቡ እግዚአብሔርን ማመስገን ያለባቸው እርሱ ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ስለሆነ ነው”

Psalms 107:23

እና በውጭ አገር ንግድ በማካሄድ
በዚያ ካሉ ሰዎች ጋር እቃዎችን ለመግዛትና ለመሸጥ በመርከብ ይሄዳሉ። “በሩቅ ካሉ ከተሞች ጋር ሸቀጦችን ይሸጣሉ”

Psalms 107:25

ባሕሩንም የሚያናውጥ አውሎ ነፋስ አዘዘ አስነሳባቸውም
“ነፋሱን አዘዘ፣ ባሕሩንም የሚያንቀሳቅስ ታላቅ ዐውሎ ነፋስ ሆነ”

አውሎ ንፋስ
ኃይለኛ ንፋስ፣ ውሽንፍር የሚያስከትል ኃይለኛ ንፋስ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ባሕሮችን የሚያንቀሳቅስ
እዚህ ላይ ዳዊት የሚገልጸው ነፋሱ ማዕበልን በማስነሣት ልክ አንድን ነገር እንደሚመታ ዕቃ ይሆናል ይላል። “የባሕሩን ማዕበል እጅግ ከፍ እንዲል አደረገው”

ወደ ሰማይ ከፍ አሉ፤ ወደ ታችም ወደ ጥልቁ ወረዱ
ይህ የሚያሳየው መርከቦቹ በማዕበሉ ወደ ላይ እና ወደ ታች ማለታቸውን ነው። ወደ ሰማይ ወጡ እንዲሁም ወደ ታች ወደ ጥልቁ ወረዱ የሚለው ማዕበሉ ምን ያህል ከፍተኛ እንደ ነበር የሚገልጽ የተጋነነ አባባል ነው። “መርከቦቻቸው በማዕበሎቹ ወደ ላይ እጅግ ከፍ አሉ እንዲሁም በማዕበሎቹ መካከል ወደ ታች ወረዱ።

ሕይወታቸው በጭንቀታቸው ምክንያት ቀልጦአል
x

Psalms 107:28

በመከራቸውም ወደ እግዚአብሔር ጮኹ
ይህ ማለት እግዚአብሔር እንዲረዳቸው ወደ እርሱ ጸለዩ ማለት ነው። ይህንን በመዝሙር 107:6 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። “በመከራቸው እንዲረዳቸው ወደ እግዚአብሔር ጸለዩ”

ከዚያም እነርሱ
“እነርሱ” የሚለው ቃል መርከበኞቹን ያመለክታል።

ማዕበሉን ጸጥ አደረገው
“ነፋሱን እንዲቆም አደረገው”

ማዕበሉ ጸጥ አለ
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “ማዕበሎቹን ጸጥ አደረጋቸው”

አመጣቸው
“መራቸው”

የሚፈልጉት ወደብ
“መሄድ ወደሚፈልጉበት ወደብ”

Psalms 107:31

ኦ እነዚያ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታማኝነቱ ሊያመሰግኑት ይገባል
እዚህ ላይ “ኦ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ ጠንከር ያለ ማሳሰቢያ መስጠትን ነው። “ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል። ይህንን በመዝሙር 107:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። “እርሱ ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ስለ ሆነ ሕዝቡ እግዚአብሔርን ያመስግኑ” ወይም “ሕዝቡ እግዚአብሔርን ማመስገን ያለባቸው እርሱ ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ስለሆነ ነው”

በሸማግሌዎች ሸንጎ ይወድሱት
“ሸማግሌዎች በአንድ ላይ ሲቀመጡ።” ሸማግሌዎች በጎብረተሰቡ መካከል ያለውን ጉዳይ ለመነጋገርና ውሳኔዎችን ለመስጠት በአንድነት ተቀምጠዋል።

Psalms 107:33

ለወጠ
እግዚአብሔር አደረገ

ስለ ሕዝቡ ክፋት የተነሣ
“በዚያ የሚኖሩት ሰዎች ክፉዎች ስለ ናቸው”

ምድረ በዳውን ወደ ውሃ ገንዳ፣ ደረቁን መሬት ወደ ውሃ ምንጮች ይለውጣል
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን አጽንኦት የሚሰጡት እግዚአብሔር በምድረ በዳ ውሃ እንዲገኝ ማድረግ እንደሚችል ነው። “በረሃ በነበረው ምድር ላይ ምንጮችና ሐይቆችን ያደርጋል”

Psalms 107:36

የተራቡትን በእዚያ ያሰፍራቸዋል
“እዚያ” የሚለው ቃል እግዚአብሔር ምንጮችን እና ሐይቆችን ያደረገበትን ስፍራ ያመለክታል። ደግሞም “የተራቡት” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው የተራቡትብን ሰዎች ነው። “እግዚአብሔር የተራቡትን ሰዎች እዚያ እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል”

የወይን እርሻዎችን ለመትከል
“የወይን እርሻዎችን በዚያ ለመትከል”

በዚያ የተትረፈረፈ ምርት ለመሰብሰብ
“በዚያ ብዙ እህል ማምረት ይችላሉ”

ስለዚህ እጅግ ብዙ ናቸው
“ሕዝባቸውም እጅግ ብዙ ነው”

ከብቶቻቸው በቁጥር እንዲቀንሱ አያደርግም
ይህ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። “ከብቶቻቸውን እጅግ ያበዛላቸዋል”

Psalms 107:39

እነርሱ
“እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔር በምድሪቱ ያሰፈራቸውን የተራቡትን ሰዎች ነው። ይህ ዐረፍተ ነገር የሚያመለክተው ሰዎቹ እግዚአብሔር በምድሪቱ ሳያሰፍራቸው በፊት የነበሩበትን ሁኔታ ነው።

እነርሱ እየቀነሱ እና እያነሱ ነበር
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “መሪዎቻቸው ቁጥራቸውን ቀንሱ አነስተኛም አደረጓቸው”

ቀንሰዋል
“በቁጥር አነስተኛ ሆኑ”

አነስተኛ
ይህ መዋረድ ማለት ነው። “ተዋረዱ”

መናቅን አዘነበባቸው
እዚህ ላይ ዳዊት የሚናገረው እግዚአብሔር በመሪዎች ላይ ንቀትን እንደ ዝናብ እንዳወረደባቸው ነው። “መናቅን አሳያቸው”

መሪዎቹ
“መሪዎቹ።” ይህ የሚያመለክተው ሕዝቡን የጨቆኑትን መሪዎች ነው። “የጨቆኗቸው መሪዎች”

መንገዶች በሌሉበት
“ሰዎች በጭራሽ የማይሄዱበት”

Psalms 107:41

ግን እርሱ
“እግዚአብሔር ግን”

ችግረኞች
ይህ ችግረኞችን ይመለከታል። “ችግረኞች” ወይም “ድኾች”

ቤተሰቡን እንደ መንጋ ይንከባከባል
እዚህ ላይ ዳዊት እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዴት እንደሚንከባከብ ሲገልጽ እረኛ ለበጎቹ ከሚያደርገው ጥንቃቄ ጋር ያወዳድራል። ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) “በእያንዳንዱ ቤተሰብ ያሉትን ሰዎች እንደ መንጋ ቁጥራቸውን ያበዛል ወይም 2) “እረኛ ለበጎቹ እንክብካቤ እንደሚያደርግ ይጠነቀቅላቸዋል”

ቅኖች
ይህ የሚያመለክተው በትክክለኛ መንገድ የሚመላለሱትን ሰዎች ነው። “ቅን ሰዎች” ወይም “ትክክል የሆነውን የሚያደርጉ ሰዎች”

ክፋት ሁሉ
እዚህ ላይ ክፉ ሰዎች እንደ “ክፋት” ተጠቅሰዋል። “ክፉ ሰዎች ሁሉ”

አፉን ይዝጋ
ይህ ማለት ምንም ምላሽ መስጠት አይችልም ማለት ነው። “በምላሹ እግዚአብሔርን በመቃወም መልስ መስጠት አይችልም”

እነዚህን ነገሮች ልብ በሉ
ይህ ማለት ስለ እነዚህ ነገሮች ማሰብ ማለት ነው። “ስለ እነዚህ ነገሮች አስቡ” ወይም “እነዚህን ነገሮች አስታውሱ”

ስለ እግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታማኝነት አሰላስሉ
“ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል። “እግዚአብሔር ለቃል ኪዳኑ ታማኝ መሆኑን ማሳየቱን አሰላስሉ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 108

1 እግዚአብሔር ሆይ፣ ልቤ ጽኑ ነው። እዘምራለሁ፤ በፍጹም ልቤም እዘምራለሁ። **2** በገናና መሰንቆም ተነሡ፤ እኔም ማልጄ እነሣለሁ። **3** ያህዌ ሆይ፣ በሕዝቦች መካከል አመሰግንሃለሁ በመንግሥታት መካከል የምስጋና መዝሙር አቀርብልሃለሁ **4** ምሕረትህ ከሰማያት በላይ ታላቅ ናትና ታማኝነትህም እስከ ጠፈር ይደርሳል። **5** አምላክ ሆይ፣ ከሰማያት በላይ ከፍ ከፍ በል ክብርህም በምድር ሁሉ ይንሰራፋ። **6** የምትወደው ሕዝብህ ይድን ዘንድ በቀኝ እጅህ ታደግ መልሰልኝም። **7** እግዚአብሔር በቅድስናው እንዲህ አለ፤ ደስ እያለኝ ሴኬምን እከፍላለሁ የሱኮትንም ሸለቆ እለካለሁ። **8** ገለዓድ የእኔ ነው፤ ምናሴም የእኔ ነው፤ ኤፍሬም የራስ ቁሬ፣ ይሁዳም በትረ መንግሥቴ ነው። **9** ሞዓብ መታጠቢያ ገንዳዬ ነው በኤዶም ላይ ጫማዬን እወረውራለሁ፤ በፍልስጥኤም ላይ በድል አድራጊነት እፎክራለሁ። **10** ወደ ተመሸገችው ከተማ ማን ይወስደኛል? ወደ ኤዶምስ ማን ያደርሰኛል? **11** እግዚአብሔር ሆይ፣ ያጣልኸን አንተ አይደለህምን? ከሰራዊታችንም ጋር ወደ ጦርነት አልወጣህም። **12** አሁንም የሰው ማዳን ከንቱ ነውና በጠላታችን ላይ ድል አቀዳጀን። **13** በእግዚአብሔር ረድኤት ድል እናደርጋለን ጠላቶቻችንንም ከእግሩ በታች የሚረግጥ እርሱ ነው።

Psalms 108:3

የቃል ኪዳንህ ታማኝነት ከሰማያት በላይ ታላቅ ነው፤ ታማኝነትህ እስከ ሰማይ ይደርሳል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። የሚናገሩት የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታማኝነት እና አስተማማኝነት ልክ እንደ አንድ ቁመቱ እስከ ሰማይ እንደሚደርስ ረጅም ነገር ታላቅ መሆኑን በመጥቀስ ነው። “ታማኝነት” እና “አስተማማኝነት” የሚሉት ረቂቅ ስሞች እንደ ቅፅል ሊተረጎሙ ይችላሉ። “የቃል ኪዳን ታማኝነትህ እና አስተማማኝነትህ ከመሬት እስከ ሰማይ እንዳለ ርቀት ታላቅ ነው” ወይም “አንተ ለቃል ኪዳንህ የበለጠ ታማኝ ነህ፣ እንዲሁም ሰዎች ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል በአንተ ሊታመኑብህ የሚገባ ነህ”

Psalms 108:5

አምላክ ሆይ፣ ከሰማያት በላይ ከፍ ከፍ በል
መዝሙረኛው እግዚአብሔር ከፍ ያለ መሆኑን እንዲያሳየው ይጠይቃል። ከሰማያት በላይ ከፍ ማለት የሚያመለክተው ታላቅ መሆኑን ነው። “እግዚአብሔር ሆይ፣ ከሰማያት በላይ ከፍ ያልክ መሆንህን አሳይ” ወይም “እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ በሰማያት ታላቅ እንደ ሆንክ አሳይ” (ሜታፎርን ተመልከት)

ክብርህ ከፍ ይበል
እዚህ ላይ እግዚአብሔር በ“ክብሩ” ተጠቅሷል። “አንተ ከፍ በል”

ስለዚህ የሚወድዱህ ይዳና
ይህ በአድራጊ ቅርፅ መገለጽ ይችላል። “ምክንያቱም የሚወድዱህ መታደግ ያስፈልጋቸዋል” ወይም “የወደዱህን ታደግ”

በቀኝ እጅህ
ይህ የእግዚአብሔር “ቀኝ እጅ” የሚያመለክተው ኃይሉን ነው። “በኃይልህ”

መልስልኝ
መመለስ የሚያመለክተው ለጥያቄው ምላሽ መስጠትን ነው። “ለጥያቄዬ መልስ ስጠኝ” ወይም “ጸሎቴን መልስ”

Psalms 108:7

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ቁጥሮች በመዝሙር 60:6-7 ካሉት ጋር ተመሳሳይ ናቸው።

እግዚአብሔር በቅድስናው ተናግሯል
እዚህ ላይ ዳዊት የሚገልጸው እግዚአብሔር እርሱ ቅዱስ ስለሆነ በ“ቅድስናው” እንደሚናገር ነው፤ ልክ ቅድስናውን እርሱ በውስጡ እንዳለ ነገር አድርጎ ይገልጸዋል። “እግዚአብሔር እርሱ ቅዱስ ስለሆነ ተናግሯል”

ሴኬምን እከፍላለሁ እንዲሁም የሱኮትን ሸለቆ አካፍላለሁ
እዚህ ላይ እግዚአብሔር የሴኬምን ምድር ስለ መከፋፈል እንዲሁም የሱኮትን ሸለቆ ስለ ማካፈል ይናገራል።

ማካፈል
በክፍሎች መከፋፈል

ኤፍሬም ደግሞ የራስ ቁሬ ነው
እግዚአብሔር የኤፍሬምን ነገድ የእርሱ ሰራዊት እንደ ሆነ አድርጎ ይናገራል። የራስ ቁር የጦር መሣሪያን ይወክላል። “ኤፍሬምን እንደ ራስ ቁር መርጬዋለሁ” ወይም “የኤፍሬም ነገድ ሠራዊቴ ነው”

የራስ ቁር
ወታደሮች ጭንቅላታቸውን ከጉዳት ለመጠበቅ የሚያደርጓቸው ጠንካራ ባርኔጣ

ይሁዳ በትሬ ነው
እግዚአብሔር ከይሁዳ ነገድ ወንዶችን በሕዝቡ ላይ ነገሥታት ይሆኑ ዘንድ መርጦአል፤ የሚናገረውም ስለእዚያ ነገድ እርሱም በትሩ እንደ ሆነ አድርጎ ነው። “የይሁዳ ነገድ እንደ በትሬ ነው” ወይም “ይሁዳ በእርሱ በኩል ሕዝቤን የምገዛበት በትር ነው”

Psalms 108:9

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ጥቅሶች በመዝሙር 60:8-9 ካሉት ጋር ተመሳሳይ ናቸው።

ሞዓብ መታጠቢያ ገንዳዬ ነው
እግዚአብሔር ስለ ሞዓብ አስፈላጊ እንዳልሆነ እንደ የመታጠቢያ ገንዳ ወይም ዝቅተኛ አገልጋይ እንደ ሆነ አድርጎ ይናገራል። “ሞዓብ ለመታጠቢያ እንደሚጠቀሙበት ሳህን ነው”

በኤዶምያስ ላይ ጫማዬን እወረውራለሁ
እግዚአብሔር ምናልባት የኤዶምያስ ላይ ያለውን ባለቤትነት በምሳሌነት ለመግለጽ ጫማውን ወደ ምድሩ በመወርወር የራሱ መሆኑን ያሳያል። የሆነ ሆኖ አንዳንድ ትርጉሞች ሌላ አይነት ትርጓሜ አሏቸው። “የኤዶምያስ ምድር ባለቤት ነኝ” ወይም “በኤዶምያስ ምድር የእኔ መሆኑን ለማሳየት ጫማዬን እጥላለሁ፣”

Psalms 108:11

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ቁጥሮች በመዝሙር 60:10-12 ካሉት ጥቅሶች ጋር ተመሳሳይ ናቸው፣ ነገር ግን እንደ 60:10 ጅማሬ መዝሙር 108:11 “ግን አንተ” የሚል ሐረግ እንደሌለው ልብ በሉ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እግዚአብሔር ሆይ፣ የጣልኸን አንተ አይደለህምን?
መዝሙረኛው ልክ እግዚአብሔር እንደ ጣላቸው ለመግለጽ ይህንን ጥያቄ ይጠቀማል። “ልክ እንደ ጣልኸን ይመስላል!” ወይም “እግዚአብሔር ሆይ ፣ አንተ የተውኸን ይመስላል!”

ከሠራዊታችን ጋር ወደ ውጊያ አትወጣም
መዝሙረኛው፣ እግዚአብሔር የእነርሱን ሠራዊት እንዲረዳ የሚናገረው እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ሆኖ እንዲዋጋ ነው። “ወደ ጦርነት በሄድን ጊዜ ሠራዊታችንን አላገዝክም”

ከንቱ ነው
“ዋጋ ቢስ ነው”

ያሸንፋል
“ጠላቶቻችንን ያሸንፋል”

ጠላቶቻችንን ይረግጣል
መዝሙረኛው፣ እግዚአብሔር ሠራዊታቸውን እንደሚረዳ ጠላቶቻቸውንም እንደሚያሸንፍ ወደ ታችም እንደሚረግጣቸው ይናገራል። “ጠላቶቻችንን እንድንረግጥ ይረዳናል” ወይም “ጠላቶቻችንን ማሸነፍ እንድንችል ያደርገናል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 109

1 የማመሰግንህ አምላክ ሆይ፣ ዝም አትበለኝ 2 ክፉዎችና አታላዮች አጥቅተውኛልና በእኔ ላይ ሐሰት ይናገራሉ። 3 በጥላቻ ዙሪያዬን ከበቡኝ ያለ ምክንያትም
በድለውኛል። 4 ስወዳቸው ይወነጅሉኛል፤ እኔ ግን ለእነርሱ እጸልያለሁ። 5 በመልካም ፈንታ ክፋትን በወደድኃቸው ፈንታ ጥላቻን ይመልሱልኛል። 6 በእንዲህ
ያለው ሰው፣ ክፉ ሰው በላዩ ሹም ከሳሽም በቀኙ ይቁም። 7 በተሟገተ ጊዜ ተረትቶ ይገባ ጸሎቱ እንኳ እንደ ኃጢአት ይቆጠርበት። 8 ዕድሜው ይጠር ሹመቱን
ሌላው ይውሰደው። 9 ልጆቹ ድኻ አደጐች ይሁኑ ሚስቱም መበለት ትሁን። 10 ልጆቹ ይንከራተቱ፤ ለማኞችም ይሁኑ ከፈረሰው ቤታቸው ይሰደዱ። 11 ንብረቱ
ሁሉ በዕዳ ይያዝበት ለፍቶ ያገኘውን ጥሪት ባዕዳን ሰዎች ይውሰዱበት። 12 ማንም ሰው ደግ አይሁንለት ለድኻ አደግ ልጆቹ የሚራራላቸው አይገኝ። 13 ዘሩ
ተለይቶ ይጥፋ ስማቸውም በሚቀጥለው ትውልድ ይደምሰስ። 14 የአባቶቹ ኃጢአት በያህዌ ፊት ይታሰብ የእናቱም ኃጢአት አይደምሰስ። 15 በደላቸው
ሁልጊዜ በያህዌ ፊት ይሁን የእነርሱ መታሰቢያ ግን ጨርሶ ይጥፋ። 16 ይህ ሰው ምሕረት ከማድረግ ይልቅ፣ ችግረኛውንና ምስኪኑን ልቡም የቆሰለውን እስከ
ሞት አሳድዶአልና ያህዌ ይህን ያደርግበት 17 መርገምን ወደደ፤ ወደ እርሱም መጣች መባረክ አልወደደም በረከት ከእርሱ ይራቅ። 18 መርገምን እንደ ልብስ
ለበሳት፤ ስለዚህ መርገም እንደ ውሃ ወደ ውስጥ ሰውነቱ፣ እንደ ዘይትም ወደ አጥንቱ ዘለቀች። 19 ገላውን እንደሚሸፍንበት ልብስ፣ ዘወትር እንደሚታጠቀውም
መቀነት ትሁነው። 20 ለሚወነጅሉኝ ሰዎች፣ እኔ ላይ ክፉ ለሚናገሩ ያህዌ የሚከፍለው ይኸው ይሁን። 21 አምላኬ ያህዌ ሆይ፣ ስለ ስምህ ስትል እኔን በበጐ
ተመልከተኝ። 22 እኔ ድኽና ችግረኛ ነኝ ልቤም በውስጤ ቆስሎአል። 23 እንደ ምሽት ጥላ ላልፍ ተቃርቤአለሁ እንደ አንበጣም ረግፌአለሁ። 24 በጾም
ምንያት ጕልበቴ ደከመ ሰውነቴም ከስቶ ዐመድ መሰለ። 25 ለጠላቶቼ መሣለቂያ ሆንሁላቸው ሲያዩኝም ራሳቸውን ይነቀንቁብኛል። 26 አምላኬ ያህዌ ሆይ፣
ርዳኝ ስለ ታማኝነትህም አድነኝ። 27 ያህዌ ሆይ፣ እጅህ ይህን እንዳደረገች አንተም ይህን እንደ ፈጸምህ ይወቁ። 28 እነርሱ ቢራገሙ እንኳ አንተ ግን ባርከኝ
እኔን ሲያጠቁኝ ይዋረዱ ባርያህ ግን ሐሤት ያደርጋል። 29 ባላንጣዎቼ ውርደትን እንደ ልብስ ይልበሱ እፍረትንም እንደ ሸማ ይጐናጸፉ። 30 በአንደበቴ ያህዌን
እጅግ አመሰግለሁ በጉባኤም መካከል እባርከዋለሁ። 31 በእርሱ ላይ ከሚፈርዱ ለማዳን እርሱ በችግረኛው ቀኝ ይቆማልና።

Psalms 109:1

አጠቃላይ መረጃ
በዕብራውያን የቅኔ አጻጻፍ ውስጥ ተመሳሳይነት የተለመደ አገላለጽ ነው።

ለመዘምራን አለቃ
“ይህ ለአምልኮ የሚጠቀሙበት የሙዚቃ አለቃ ነው።”

የዳዊት መዝሙር
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) ዳዊት መዝሙሩን ጽፎአል ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት የመዝሙር አጻጻፍ ዘይቤ ነው።

ለክፉዎች እና አታላዮች
“ክፉ” እና “አታላይ” የሚሉት ቃላት ሰዎችን ያመለክታሉ። ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን አጽንኦት የሚሰጡትም ሰዎቹ ምን ያህል መጥፎ እንደሆኑ ነው። “ለክፉ እና አታላይ ሰዎች”

Psalms 109:4

ለመውደዴ ምላሽ
“ምንም እንኳ ብወዳቸው”

ፍቅሬ
“ለእነርሱ ያለኝ ፍቅር”

እነርሱ ይከሱኛል
“እነርሱ” የሚለው ቃል ክፉ እና አታላይ የሆኑትን ሰዎች ያመለክታል። መዝሙረኛውን የሚከስሱ ሰዎች በሐሰት እንደሚሠሩ በግልጽ ማስረዳት ያስፈልግ ይሆናል። “በሐሰት ከሰሱኝ” ወይም “ሰደቡኝ”

Psalms 109:6

ክፉውን ሰው ሾሙ . . . ከሳሹን ሾሙ
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች ትይዩ ናቸው “ክፉ ሰው” እና “ከሳሽ” የሚሉት ሐረጎች የሚያመለክቱት አንድን ሰው ነው።

በቀኝ እጁ በኩል
“በጠላቴ ቀኝ እጅ በኩል”

በሚፈረድበት ጊዜ ጥፋተኛ ሆኖ ይገኝ
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “ለፍርድ በሚቀርብበት ጊዜ ዳኛው ጥፋተኛ ያድርገው”

Psalms 109:8

ዕድሜውም ይጠር
“ዕድሜው” የሚለው ሐረግ የሕይወቱን ርዝመት ያመለክታል። “ረጅም ዕድሜ አይኑር”

ሹመቱ
“የሥልጣን ደረጃው”

በእጅ የሚሰጥ
ለድኾች የሚሰጥ ምግብ ወይም ገንዘብ

የፈረሰው ቤታቸው
“የወደሙ ቤታቸው”

Psalms 109:11

አበዳሪው
ለሌላ ሰው ገንዘብ የሚያበደር ነገር ግን ያ ሰው ገንዘቡ እንዲመልስለት የሚጠብቅ

Psalms 109:14

የአባቶቹ በደል በእግዚአብሔር ፊት ይታሰብ
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “እግዚአብሔር ሆይ የአባቶቹን ኀጢአት አስታውስ”

የእናቱም ኀጢአት አይደምሰስ
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “እናቱም ያደረገችውን ኀጢአት አትረሳ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጎጢአታቸው ሁልጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ይኑር
እዚህ ላይ ዳዊት የሚናገረው እግዚአብሔር ስለ ጎጢአታቸው እንዲያስብ እንደ አንድ ቁስ አካል በፊቱ እንዲሆን ነው። “እግዚአብሔር ስለ ጎጢአታቸው ዘወትር ያስብ”

እግዚአብሔር መታሰቢያቸውን ከምድር ያጥፋ
ዳዊት በምድር ላይ የሚኖሩ ሰዎችን ሁሉ ለማመልከት “ምድር” የሚለውን ቃል ተጠቅሟል ። ደግሞም፣ “መታሰቢያቸው” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ከሞቱ በኋላ ሰዎች የሚያደርጉትን ማስታወሻ ነው። “እግዚአብሔር በምድር ላይ ማንም ሰው ስለ እነርሱ እንዳያስብ ያድርግ”

ይህ ሰው ምንም አይነት የቃል ኪዳን ታማኝነትን ለማድረግ ፈጽሞ አላሳበም
ይህ የሚያመለክተው ለሰዎች ሊደረግ የሚገባውን የቃል ኪዳን ታማኝነት ነው። “ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል። “ይህ ሰው ለሰዎች የቃል ኪዳን ታማኝነት ለማሳየት ፈጽሞም አላሰበም” ወይም “ይህ ሰው ለቃል ኪዳኑ ታማኝ መሆኑን ለማሳየት ምንም ያደረገው ነገር የለም”

የተጨቆኑትን፣ ችግረኞችንም
ይህ የተጨቆኑትንና የተቸገሩ ሰዎችን ይመለከታል። “የተጨቆኑ ሰዎች፣ ችግረኛ ሰዎች”

ልባቸው የቆሰለ
ይህ የሚያመለክተው ልባቸው የቆሰለ ሰዎችን ነው። “ልባቸው የቆሰለ ሰዎች” ወይም “ተስፋ የቆረጡ ሰዎች”

እስከ ሞት
“እስኪሞቱ ድረስ።” ይህ ማለት እስከሞቱበት ጊዜ ድረስ አሰቃይቷቸዋል ማለት ነው።

Psalms 109:17

በእርሱ ላይ ይምጣበት
“እርግማኑ በእርሱ ላይ ይምጣበት”

መርገምን እንደ ልብስ ለብሶታል
ዳዊት ስለ ክፉ ሰው ባህሪ ሲናገር ክፋቱ እንደ ልብሱ እንደ ሆነ አድርጎ ነው። “ልብስን እንደሚለብስ ሌሎች ሰዎችን ይራገማል” ወይም “ሁልጊዜ ሰዎችን ይራገማል”

እንደ ልብሱ
“ልብሶቹ እንደ ሆኑ”

እርግማኑ ወደ ውስጡ እንደ ውሃ ይመጣል እንደ ዘይትም ወደ አጥንቱ ይገባል
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች፦ 1) ሁል ጊዜ እርግማንን ከመናገሩ የተነሣ የእርሱ ማንነት ክፍል ሆኖአል። “የናገራቸው እርግማኖች የእርሱ አካል ናቸው” ወይም 2) የተናገረው እርግማን በእርሱ ላይ ደርሷል። “በተናገረው እርግማን የእርሱ መላ ማንነቱ ተረገመ”

እንደ ውሃ
ይህ አንድ ሰው ውሃን እንዴት እንደሚጠጣ ያሳያል። “ሰው እንደሚጠጣው ውሃ”

እንደ ዘይት ወደ አጥንቶቹ
ይህ የሚያመለክተው ዘይት በቆዳው ላይ በሚደረግበት ጊዜ ወደ አጥንቶች የሚገባ መሆኑን ነው። “በሰው ቆዳ ላይ በሚቀባበት ጊዜ ወደ አጥንቶቹ ዘልቆ እንደሚገባ የወይራ ዘይት ነው”

Psalms 109:19

ራሱን ለመሸፈን እንደሚለብሰው ልብስ እርግማኑ በእርሱ ላይ ይሁን
ሰዎች ልብሳቸውን በየቀኑ ይለብሳሉ። ዳዊት ስለ ክፉ ሰው ሲናገር ሁል ጊዜ እንደሚለብሰው ልብስ እርግማኑ በእርሱ ላይ ይሁን ይላል። “እርግማኑ እንደሚለብሰው ልብስ በየቀኑ በእርሱ ላይ ይሁን”

ሁል ጊዜ እንደሚታጠቀው ቀበቶ
“እርግማኑ ለእርሱ ይሁን” የሚሉት ቃላት ከቀዳሚው ሐረግ ጋር የምንረዳቸው ናቸው። እዚህ ላይ ሊደገሙ ይችላሉ። “እርግማኑ ሁል ጊዜ እንደሚታጠቀው ቀበቶ ለእርሱ ይሁን” ወይም “እርግማኑ ሁል ጊዜ እንደሚታጠቀው ቀበቶ በእርሱ ላይ ይሁን”

ይህ ሽልማቱ ይሁን
“እነዚህ እርግማኖች ሽልማቱ ይሁኑ”

Psalms 109:21

በበጎ ተመልከተኝ
ይህ እግዚአብሔር በበጎነት እንዲመለከተው የቀረበ ልመና ነው። “በበጎነት አስበኝ”

ስለ ስምህ
“ስለ በጎ ስምህ”

የቃል ኪዳንህ ታማኝነት መልካም ነውና
“ታማኝነት”የሚለው ረቂቅ ስም ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል። “አንተ መልካምና ለቃል ኪዳንህ ታማኝ ስለሆንክ”

የተጨቆነና የተቸገረ
እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን የሚያተኩሩትም እርሱ እራሱን መርዳት አለመቻሉ ላይ ነው።

ልቤ በውስጤ ቆሰለ
እዚህ ላይ ዳዊት ልቡ ስለ መቁሰሉና በከፍተኛ ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ስለ መሆኑ ይናገራል። “በሐዘንና በተስፋ መቁረጥ ተሞልቻለሁ”

እኔ እንደ ጥላ እየጠፋሁ ነው . . . እንደ አንበጣም
እዚህ ላይ ዳዊት በቶሎ እንደሚሞት ሲገልጽ እየጠፋ እንደሚሄድ ጥላ እና በነፋስ እንደሚወሰድ አንበጣ በምሳሌነት በመጠቀም ነው። “እንደ ምሽት ጥላ በቶሎ እንደሚወገድ፣ እንዲሁም በቀላሉ በነፋስ እንደሚጠረግ አንበጣ፣ እኔም እንዲሁ እንደምሞት ይሰማኛል”

Psalms 109:24

ጉልበቶቼ ደከሙ
ይህ ማለት እርሱ በጣም ደክሞአል ለመቆምም አልቻለም ማለት ነው። “ለመቆም ተቸገርኩ” ወይም “ሰውነቴ ደክሞአል”

ከጾም
“ምንም ምግብ ስላልበላሁ”

ቆዳ እና አጥንት ብቻ ቀረኝ
ይህ ማለት ክብደቱን በጣም ቀንሶአል ማለት ነው። “ሰውነቴ በጣም ቀጭን ሆነ”

በከሳሾቼ ተንቄአለሁ
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “ከሳሾቼ ተሳለቁብኝ”

ራሳቸውን ነቀነቁ
ይህ ያለመስማማት ምልክት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 109:26

በቃል ኪዳንህ ታማኝነት አድነኝ
“ታማኝነት” የሚረው ረቂስ ስም በቅፅል ሊተረጎም ይችላል። “ለቃል ኪዳንህ ታማኝ ስለሆንህ አድነኝ”

እነርሱ ያውቁ ዘንድ
“እነርሱ” የሚለው ቃል የዳዊትን ከሳሾች እና ስለ እርሱ መጥፎ ነገር የሚናገሩ ሰዎችን ያመለክታል።

ይህን አድርገዋል
“አድነኝ”

Psalms 109:28

እነርሱ ቢረግሙኝም
“እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ዳዊትን የከሰሱ እና መጥፎ ነገር የሚናገሩ ሰዎችን ነው ::

እነርሱ ይፈሩ
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “እነርሱ ያፍሩ ይሆናል” ወይም “እነርሱ ይፈሩ”

ባሪያህ ግን ሐሴት ያድርግ
“ነገር ግን እኔ የአንተ አገልጋይ ሐሴት ላድርግ” ወይም “እኔ የአንተ አገልጋይ ነኝ፣ ሐሴት ላድርግ።” ዳዊት “የአንተ ባሪያ” የሚለውን ሐረግ የሚጠቀመው ስለ ራሱ ነው።

ባላጋራዎቼ ይከናነቡ . . . ይልበሱ
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ በአንድነት ጥቅም ላይ የዋሉት እርሱ ጠላቶቹ ምን ያህል ማፈር እንዳለባቸው እንደሚመኝ አጽንኦት ለመስጠት ነው።

እፍረትን ይልበሱ
እዚህ ላይ ዳዊት ስለ እነርሱ የሚናገረው ልብስን እንደሚለብሱ እፍረትን እንዲለብሱ ነው። “በጣም ይፈሩ”

እፍረታቸውን እንደ ልብስ ይልበሱ
ዳዊት ስለ እነርሱ የሚናገረው እንደሚለብሱት ልብስ እፍረትን እንዲለብሱ ነው። “ልብሳቸው በዙሪያቸው እንደ ተሸፈነ፣ እፍረታቸው ይሸፍናቸው”

Psalms 109:30

በአንደበቴ
ይህ ማለት እርሱ ይናገራል ማለት ነው። “እናገራለሁ እሰጣለሁ”

በችግረኛው በቀኝ እጁ በኩል ይቆማል
ይህ ማለት ድኾችን ይረዳል እና ይጠብቃል ማለት ነው። “ለችግረኛው ይከላከላል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 110

1 ያህዌ ጌታዬን፣ «ጠላቶችህን ለእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ» አለው። **2** ያህዌ ብርቱ በትርህን ከጽዮን ወደ ውጭ ይሰዳል አንተም በጠላቶችህ መካከል ትገዛለህ። **3** በኃይልህ ቀን ተከታዮችህ የተቀደሰ ልብስ ተጐናጽፈው በፈቃዳቸው ይከተሉሃል። ከንጋት ማሕፀን ጐልማሳነትህ እንደ ጠል ይወጣል። **4** «እንደ መልከጼዴቅ ሥርዐት አንተ ለዘላለም ካህን ነህ» ብሎ ያህዌ ምሎአል፤ እርሱም ሐሳቡን አይለውጥም። **5** ጌታ በቀኝህ ነው በቁጣው ቀን ነገሥታትን ይገድላል። **6** በሕዝብ ላይ ይፈርዳል የጦር ሜዳዎችን ሬሳ በሬሳ ያደርጋል። የብዙ አገሮችን ነገሥታት ይደመሰሳል። **7** መንገድ ዳር ካለች ፈሳሽ ውሃ ይጠጣል ከድል በኃላ ራሱን ቀና ያደርጋል።

Psalms 110:1

አጠቃላይ መረጃ
በዕብራውያን የቅኔ አጻጻፍ ውስጥ ተመሳሳይነት የተለመደ አገላለጽ ነው።

የዳዊት መዝሙር
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች፦ 1) ዳዊት መዝሙሩን ጽፎአል ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት የመዝሙሮች አጻፋፍ ዘይቤ ነው።

በቀኝ እጄ በኩል ተቀመጥ
“በቀኝ እጄ” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው የክብር ቦታን ነው። “ለአንተ ባለኝ የክብር ስፍራ ተቀመጥ”

ጠላቶችህን የእግርህ መርገጫ እስከማደርግልህ
እዚህ ላይ ዳዊት የሚገልጸው እግዚአብሔር የጌታን ጠላቶች በኃይሉ ቁጥጥር ስር አድርጎ ለእግሩ ልክ እንደ እግር መርገጫ እንደሚያደርግለት ነው። “ጠላቶችህን ከኃይልህ በታች አድርግ”

Psalms 110:2

አጠቃላይ መረጃ
ዳዊት ለንጉሡ መናገሩን ቀጠለ።

እግዚአብሔር የኃይልህን በትር ይይዛል
ዳዊት እዚህ ላይ የሚናገረው እግዚአብሔር የንጉሡን የገዢነት በትሩን በመያዝ ግዛቱን እንደሚያሰፋለት ነው። “እግዚአብሔር በኃይል የምትገዛውን ስፍራ ያሰፋልሃል”

በጠላቶችህ መካከል ግዛ
“ንጉሥ፣ በጠላቶችህ መካከል ግዛ።” ይህ ለንጉሡ የተነገረው እንደ ትእዛዝ ነው።

በራሳቸው ነፃ ፈቃድ
“በራሳቸው ምርጫ።” ይህ ማለት ንጉሡን ለመከተል ይመርጣሉ ማለት ነው።

በኃይልህ ቀን
ይህ የሚያመለክተው ንጉሡ ሠራዊቱን ወደ ጦር ግንባር የሚመራበትን ቀን ነው። ይህ በግልጽ ሊብራራ ይችላል። “ሠራዊትህን ወደ ጦርነት በምትመራበት ቀን”

ከንጋት ማኅፀን . . . እንደ ጠል
ዳዊት ጠልን ንጋት እንደሚወልደው ሕፃን ይገልጸዋል። “በማለዳ . . . እንደ ጠል”

ከንጋት ማኅፀን፣ ጎልማሳነትህ እንደ ጠል ልምላሜ ይሆንልሃል
ዳዊት ንጉሡን የሚናገረው በየጠዋቱ የሚኖረውን የወጣትነት ጥንካሬ በየቀኑ ማለዳ ከሚታየው ጠል ጋር በማነፃፀር ነው። “በየማለዳው ምድርን ለማለምለም የጠዋት ጤዛ እንደሚታይ አንተም ለመጽናት በወጣትነት ኃይል በየማለዳው ትሞላለህ”

Psalms 110:5

ጌታ በቀኝህ ነው
ጌታ ወደ ጦርነት በሚሄድበት ጊዜ እግዚአብሔር ሊረዳው በቀኙ ይቆማል። “እግዚአብሔር በጦርነት ውስጥ ይረዳሃል”

ጌታ
“ጌታ” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ያመለክታል።

እርሱ ይገድላል
“እርሱ” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ያመለክታል። ነገሥታቱ እንዲሸነፉና እንዲሞቱ ያደርጋል፣ ነገር ግን የንጉሡን ሠራዊት የጠላት ነገሥታትን እንዲገድሉ ይፈቅድላቸዋል። “ነገሥታቱን እንዲሞቱ ያደርጋል” ወይም “ሠራዊትህ ነገሥታትን እንዲገድሉ ይፈቅድላቸዋል”

ነገሥታት
ይህ ጠላቶቹን ይመለከታል። “ጠላቶች ነገሥታት”

በቁጣው ቀን
እዚህ ላይ ዳዊት እግዚአብሔር በሚቆጣበት ጊዜ ነገሥታትን በ“ቁጣው ቀን” እንደሚያሸንፋቸው ይናገራል። “ትዕግሥቱ ወደ ቁጣ በሚለወጥበት የፍርድ ቀን”

የጦርነት ሜዳዎችን በሬሳዎች ይሞላል
ይህ ማለት እግዚአብሔር ይህ እንዲሆን ያደርጋል፣ በጦር ሜዳ የሞቱትን ሰዎች ሁሉ እርሱ በግል ገድሏቸዋል ማለት አይደለም። “የጦር ሜዳዎቹን በሬሳዎች እንዲሞላ ያደርጋል”

እርሱ በብዙ አገሮች ውስጥ መሪዎችን ይገድላል
ይህ ማለት እግዚአብሔር ይህ እንዲሆን ያደርጋል፣ መሪዎቹን በግል ይገድላል ማለት አይደለም። “በብዙ አገሮች ውስጥ መሪዎችን እንዲገደሉ ያደርጋል” ወይም “በብዙ አገሮች ውስጥ መሪዎች እንዲሞቱ ይፈቅዳል”

Psalms 110:7

መንገድ ዳር ካለች ፈሳሽ ውሃ ይጠጣል
ንጉሡ ለጥቂት ጊዜ ውሃ ለመጠጣት በመንገድ ላይ ይቆማል ከዚያም ጠላቶቹን ማሳደዱን ይቀጥላል። “ጠላቶቹን በማሳደድ ላይ እያለ ለጥቂት ጊዜ ከፈሳሽ ውሃ በፍጥነት ለመጠጣት ይቆማል”

ከፈሳሽ ውሃ
ይህ ማለት እርሱ ከመንገድ ዳር ፈሳሽ ውሃ ይጠጣል ማለት ነው። የመንገድ ዳር ፈሳሽ አነስተኛ ወንዝ ነው። “ከወንዙ ውሃ ይጠጣል”

እና ከዚያ
“እና እንደዚያ” ወይም “ስለዚህ”

እርሱ ራሱን ቀና ያደርጋል
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) ንጉሡ የራሱን ጭንቅላት ቀና ያደርጋል ወይም 2) እግዚአብሔር የንጉሡን ራስ ከፍ ያደርጋል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከድል በኋላ ራሱን ወደ ላይ ቀና ያደርጋል
x

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 111

1 ያህዌ ይመስገን። በቅኖች ሸንጎ በጉባኤም መካከል በፍጹም ልቤ ያህዌን አመሰግናለሁ። **2** የያህዌ ሥራ ታላቅ ናት፤ የሚፈልጓትም ሁሉ አጥብቀው ይናፍቋታል። **3** ሥራው ባለ ግርማና ባለ ክብር ነው ጽድቁም ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል። **4** ያህዌ ቸርና መሐሪ ነው ሲታወስ የሚኖር ድንቅ ሥራ አደረገ። **5** ለሚፈሩት ምግባቸውን ይሰጣል ኪዳኑንም ዘወትር ያስባል። **6** ለእነርሱ የአሕዛብን ርስት በመስጠት የአሠራሩን ብርታት አሳይቶአል። **7** የእጁ ሥራ እውነተኛና ቅን ነው ትእዛዞቹም የታመኑ ናቸው። **8** እነርሱም ለዘላለም የጸኑ ናቸው በታማኝነትና በቅንነት ይጠበቃሉ። **9** ለሕዝቡ ድልን ሰጠ ኪዳኑን ለዘላለም አዘዘ ስሙም የተቀደሰና የተፈራ ነው። **10** ያህዌን መፍራት የጥበብ መጀመሪያ ነው ትእዛዙንም የሚጠብቁ ጥሩ ማስተዋል አላቸው። ምስጋናውም ለዘላለም ይኖራል።

Psalms 111:1

አጠቃላይ መረጃ
በዕብራውያን የቅኔ አጻጻፍ ውስጥ ተመሳሳይነት የተለመደ አገላለጽ ነው።

በሙሉ ልቤ
“ልብ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የአንድ ሰው ውስጣዊ ማንነትና ስሜቱን ነው። አት: - “ከመላ ማንነቴ ጋር”

በቅኖች ሸንጎ፣ በጉባኤአቸውም
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በአንድ ላይ ሊሆኑ ይችላሉ። “በቅኖች ስብስባ ውስጥ”

በሁሉ ዘንድ የሚፈለጉት እነርሱ በናፍቆት ይጠበቃሉ
“እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው “የእግዚአብሔርን” ሥራዎች ነው። ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “የእግዚአብሔርን ሥራዎች የሚፈልጉ ሁሉ በጉጉት ይጠባበቋቸዋል”

በጉጉት መጠበቅ
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) “የሚፈለጉ” ወይም 2) “የሚጠኑ” ናቸው።

Psalms 111:4

ይታወሳል
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “ሰዎች ሁል ጊዜ የሚያስታውሱት”

አስታውስ
ይህ አስበኝ ለማለት ጥቅም ላይ የዋለ አባባል ነው። “አስታውስ”

ኃያል ሥራዎቹ
“ኃይሉን የሚገልጹ ሥራዎቹ”

የአሕዛብ ርስት
ጸሐፊው የሚናገረው በከነአን የሚኖሩ አሕዛብ ምድር የእነርሱ ርስት እንደሆነ አድርጎ ነው። “የሌሎች አሕዛብ ንብረት የሆነ ምድር”

Psalms 111:7

የእጆቹ ሥራዎች
እዚህ ላይ “እጆቹ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ራሱን ነው። አት: “እርሱ የሠራቸው ሥራዎች”

Psalms 111:10

የጥበብ መጀመሪያ
“ጥበብ” የሚለው ቃል “ጠቢብ” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። “ጠቢብ ለመሆን የመጀመሪያው እርምጃ” ወይም “ጥበበኛ ለመሆን በጣም አስፈላጊው ነገር”

የእርሱን ትእዛዛት የሚፈጽሙ
“የእርሱን ትእዛዛት የሚታዘዙ”

ምስጋውም ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል
“ምስጋና” የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። “ሰዎች ለዘላለም ያመሰግኑታል”

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 112

1 ያህዌ ይመስገን ያህዌን የሚፈራ በትእዛዞቹም እጅግ ደስ የሚሰኝ የተባረከ ነው። **2** ዘሩ በምድር ላይ ኃያል ይሆናል የቅኖች ትውልድ ይባረካል። **3** ሀብትና ብልጽግና ቤቱን ይሞላል ጽድቁም ለዘላለም ይኖራል። **4** ምሕረትና ቸርነት፣ ቅንነትንም ለሚያደርግ ደግ ሰው በጨለማ ውስጥ ብርሃን ይወጣለታል። **5** ሥራውን በትክክል የሚያከናውን፣ ለጋስና ሳይሰስት የሚያበድር ሰው መልካም ይሆንለታል። **6** እርሱ ከቶውንም አይናወጥምና ጻድቅ ሰው ሲታወስ ይኖራል። **7** እምነቱን ያህዌ ላይ ያደረገ ልበ ሙሉ ስለሆነ ክፉ ወሬ አያሸብረውም። **8** ልቡ እግዚአብሔርን በመተማመን የጸና ነው። በመጨረሻ የጠላቶቹን ውድቀት ያያል። **9** በልግስና ለድኾች ይሰጣል ጽድቁም ለዘላለም ይኖራል። በክብር ከፍ ከፍ ይላል። **10** ክፉ ሰው ይህን፤ በማየት ይበሳጫል ጥርሱን ያፋጫል፤ እየመነመነም ይጠፋል። የክፉዎች ምኞት ትጠፋለች።

Psalms 112:1

አጠቃላይ መረጃ
በዕብራውያን የቅኔ አጻጻፍ ውስጥ ተመሳሳይነት የተለመደ አገላለጽ ነው።

እጅግ ደስ ይለኛል
“እጅግ ደስ ይለዋል”

እግዚአብሔርን የሚፈራ የተባረከ ነው
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “እግዚአብሔር እርሱን የሚፈራውን ሰው ዘሮች ይባርካል”

Psalms 112:3

አጠቃላይ መረጃ
ይህን መዝሙር የሚዘምረው ሰው እግዚአብሔርን ስለሚያከብረው ሰው መግለጹን ይቀጥላል።

ሀብትና ብልጽግና በቤቱ ነው
x

Psalms 112:8

አጠቃላይ መረጃ
ይህን መዝሙር የሚዘምረው ሰው እግዚአብሔርን ስለሚያከብረው ሰው መግለጹን ይቀጥላል።

ልቡ ጽኑ ነው
“ልቡ ተደግፎአል።” እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ግለሰቡን ነው። ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) “እርሱ ሰላም ነው” ወይም 2) “እርሱ የተማመነ ነው”

ጽድቁ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል
“የጽድቅ ሥራው ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።” ይህንን በመዝሙር 112፡3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

በክብር ከፍ ከፍ ይላል
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “እግዚአብሔር ክብርን በመስጠት ከፍ ያደርገዋል”

Psalms 112:10

ይሄንን ያያል
“እግዚአብሔርን ለሚፈራ ሰው ነገሮች በመልካም እንደሚደረጉ ያያል።” “ይህን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጸሐፊው እግዚአብሔርን ስለሚፈራ ሰው ቀደም ባሉት ጥቅሶች ላይ የገለጻቸውን መልካም ነገሮችን ሁሉ ነው።

እርሱ በቁጣ ጥርሱን ያፋጫል
የጥርስ መፋጨት የከባድ ቁጣ መግለጫ ነው። ይህንን በመዝሙር 35:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ይቀልጣል
ጸሐፊው ስለ ክፉው ሰው ቀጣይ ሞት ሲናገር እንደ አንድ የሚቀልጥ ነገር ወይም በረዶ አድርጎ በመግለጽ ነው። “በመጨረሻም ይሞታል”

የክፉ ሰዎች ምኞት ይጠፋል
“ምኞት” ለሚለው ቃል ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች፦ 1) ክፉ ሰዎች ያላቸውን ስሜታዊ ፍላጎት። “ክፉ ሰዎች ሊያደርጉት የሚፈልጉት ነገር ፈጽሞ ሊሆን አይችልም” ወይም 2) እርሱ ክፉ ሰዎች ለሚፈልጉት ምሳሌያዊ መግለጫ ነው። “ክፉ ሰዎች የፈለጉትን ያጣሉ”

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 113

1 ያህዌ ይመስገን። የያህዌ አገልጋዮች ሆይ፣ የያህዌን ስም አመስግኑ። **2** ከአሁን እስከ ዘላለም የያህዌ ስም ይመስገን። **3** ከፀሐይ መውጫ እስከ መግቢያው ድረስ የያህዌ ስም ይመስገን። **4** ያህዌ ከሕዝቦች ሁሉ በላይ ከፍ ያለ ነው፤ ክብሩም ከሰማያት በላይ ነው። **5** እንደ አምላካችን እንደ ያህዌ በላይ በዙፋኑ የተቀመጠ ማን ነው? **6** ራሱን ዝቅ አድርጐ በሰማይና በምድር ያሉትንስ የሚያይ ማን ነው? **7** ድኻውን ከትቢያ ያነሣል ችግረኛውንም ከዐመድ ከፍ ከፍ ያደርጋል። **8** ከመኳንንት ጋር፣ ከሕዝቡም ሹማምንት ጋር ያስቀምጠዋል። **9** መካኒቱን በቤት ያኖራታል ደስ የተሰኘች የልጆች እናት ያደርጋታል። ያህዌ ይመስገን!

Psalms 113:1

አጠቃላይ መረጃ
በዕብራውያን የቅኔ አጻጻፍ ውስጥ ተመሳሳይነት የተለመደ አገላለጽ ነው።

የእግዚአብሔር ስም
እዚህ ላይ “ስም” የሚለው ቃል የሚወክለው እግዚአብሔርን እራሱን ነው። AT: “እግዚአብሔር”

Psalms 113:3

ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያው ድረስ
ይህ ሐረግ የሚያመለክተው ፀሐይ ወደምትወጣበት ምሥራቅ እና ወደምትጠልቅበት ምዕራብ ነው። ጸሐፊው እነዚህን ሁለት ጽንፎች የተጠቀመው በምድር ላይ የትኛውንም ስፍራ ለመወከል ነው። በመዝሙር 50፡1 ውስጥ ይህንን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። “በምድር ሁሉ ላይ”

የእግዚአብሔር ስም ሊመሰገን ይገባዋል
እዚህ ላይ “ስም” የሚለው ቃል እግዚአብሔር ራሱን ይወክላል። ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “ሰዎች እግዚአብሔርን ያመስግኑ”

ክብሩ ከሰማያት በላይ ይደርሳል
የእግዚአብሔር ክብር እጅግ ከፍ ያለ እንደ ሆነ ይነገራል። “ክብሩ ከሰማያት በላይ ነው” ወይም “ክብሩ እጅግ ታላቅ ነው”

Psalms 113:5

እንደ አምላካችን እንደ እግዚአብሔር ያለ . . . በምድር ላይ ማን ነው?
ጸሐፊው ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም እንደሌለ አጽንኦት ለመስጠት ነው። ይህ የአጻጻፍ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። “እንደ አምላካችን እንደ እግዚአብሔር ያለ . . . በምድር ላይ የለም።”

መቀመጫው በከፍታ ላይ የሆነ ማነው
“በከፍታ ላይ የነገሠው ማነው” ወይም “በከፍተኛው ሥልጣን ላይ የሚገዛው ማነው”

Psalms 113:9

መካን ለሆነች ሴት ቤተሰብን ይሰጣታል
እዚህ ላይ “ቤተሰብ” የሚያመለክተው በቤት ውስጥ የሚኖሩትን ልጆች ነው። “ምንም ለሌላት ሴት ልጆችን ይሰጣታል”

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 114

1 እስራኤል ከግብፅ ወጥቶ ሲሄድ የያዕቆብም ቤት ከባዕድ ሕዝብ ተለይቶ ሲወጣ **2** ይሁዳ ቅዱስ ማደሪያው እስራኤልም ግዛቱ ሆነ። **3** ባሕር ዐይታ ሸሸች
ዮርዳኖስም ወደ ላኋው ተመለሰ። **4** ተራሮች እንደ አውራ በግ ፈነጩ ኮረብቶችም እንደ ጠቦት ዘለሉ። **5** አንተ ባሕር ምን ሆነህ ሸሸህ? አንተስ ዮርዳኖስ ለምን
ወደ ኃላህ ተመለስህ? **6** እናንተ ተራሮች ስለምን እንደ አውራ በግ ፈነጫችሁ? ኮረብቶችስ ለምን እንደ ጠቦት ዘለላችሁ? **7** ምድር ሆይ፣ በጌታ ፊት በያዕቆብ
አምላክ ፊት ተንቀጥቀጪ። **8** እርሱ ዐለቱን ወደ ውሃ ኩሬ ቋጥኙንም ወደ ውሃ ምንጭ ለወጠ።

Psalms 114:1

አጠቃላይ መረጃ
በዕብራውያን የቅኔ አጻጻፍ ውስጥ ተመሳሳይነት የተለመደ አገላለጽ ነው።

እስራኤል ከግብፅ ሲወጣ ያዕቆብም ባዕድ ቋንቋ ከሚናገሩ ሰዎች መካከል
እነዚህ ሁለቱ መስመሮች “እስራኤል” እና “የያዕቆብ ቤት” አንድ አይነት ትርጉም ያላቸው ናቸው፤ “ግብፅ” እና “የባዕድ አገር ሰዎች” የሚያመለክተው ስለ አንድ ሕዝብ ነው።

የያዕቆብ ቤት ባዕድ ቋንቋ ከሚናገሩ ሰዎች
እዚህ ላይ “ቤት” የሚለው ቃል ቤተሰብን ወይም ዘሮችን ይወክላል። ግሱ ለዚህ ሐረግ ሊሆን ይችላል። “የያዕቆብ ዘሮች የማያውቁትን ቋንቋ ከሚናገሩ ሰዎች ትተው ወጡ”

ይሁዳ የተቀደሰ ስፍራው፣ እስራኤልም መንግሥቱ ሆነ
“ለይሁዳ” እና “እስራኤል” ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች፦ 1) መሬቱን ያመለክታሉ። “የይሁዳ ምድር የእግዚአብሔር የተቀደሰ ስፍራ ሆነ፣ የእስራኤልም ምድር የእርሱ መንግሥት ሆነ” ወይም (2) እነርሱ ለይሁዳ እና ለእስራኤል ሕዝብ መገለጫዎች ናቸው። “የይሁዳ ሕዝብ እግዚአብሔር በመካከላቸው የሚኖር ሕዝብ ሆኑ፣ የእስራኤልም ሕዝብ ደግሞ የሚገዛበት ሆኑ”

Psalms 114:3

ባሕሩ አየች ሸሸችም
ጸሐፊው የሚናገረው ባሕር ልክ እንደ ሰው ከእግዚአብሔር ፊት እንደ ሸሸች እና እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ በደረቅ ምድር እንደ መራው ነው። “ባሕር ልክ እንዳየችና እንደሸሸች ነበር”

ዮርዳኖስ ተመለሰ
ጸሐፊው የሚናገረው የዮርዳኖስ ወንዝ ልክ ሰው ወደ ኋላው እንደ ተመለሰና እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ በውስጡ በደረቅ ምድር እንደ መራው ነው። “ይህ ልክ ዮርዳኖስ ወደ ኋላው እንዳፈገፈገ ያህል ነበር”

ተራሮች እንደ ኮርማዎች፣ ኮረብቶችም እንደ ጠቦቶች ዘለሉ
ጸሐፊው ስለ ተራሮች እና ስለ ኮረብቶች ሕይወት እንዳላቸው አድርጎ ይናገራል። ምናልባትም የሚናገረው ስለ መሬት መንቀጥቀጥ ሆኖ የገለጸው ተራሮችና ኮረብቶች በእግዚአብሔር ፊት ፈርተው እንደ ኮርማዎችና ጠቦቶች እንደ ዘለሉ አድርጎ ነው። “ተራሮች ኮርማዎች እንደሚዘልሉ እንደ ተንቀጠቀጡ እና ኮረብታዎች ጠቦቶች እንደሚዘልሉ እንደንተንቀጠቀጡ ያህል ነበር”

Psalms 114:5

አጠቃላይ መረጃ
ከ5-6 ቁጥሮች አራት የአጻጻፍ ጥያቄዎችን ይይዛሉ። ለእያንዳንዱ ጥያቄ የሚጠበቀው መልስ “ከጌታ መገኘት የተነሣ” በቁጥር 7 ላይ ይገኛል።

እንደ ኮርማዎች ዘለሉ . . . እንደ ጠቦቶች ዘለሉ
ጸሐፊው ስለ ተራሮች እና ስለ ኮረብቶች ሕይወት እንዳላቸው አድርጎ ይናገራል። ምናልባትም የሚናገረው ስለ መሬት መንቀጥቀጥ ሆኖ የገለጸው ተራሮችና ኮረብቶች በእግዚአብሔር ፊት ፈርተው እንደ ኮርማዎችና ጠቦቶች እንደ ዘለሉ አድርጎ ነው። በመዝሙር 114:3-4 ላይ ተመሳሳይ ሐረጎችን እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት። “እንደ ኮርማዎች ዝላይ መንቀጥቀጥ . . . እንደ ጠቦቶች ዝላይ መንቀጥቀጥ”

ምድር በጌታ ፊት፣ በያዕቆብ አምላክ ፊት ተንቀጠቀጠች
x

Psalms 114:8

እርሱ ድንጋዩን ወደ ውሃ ፣ ዓለቱንም ወደ ውሃ ምንጭ ለወጠው
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች ትይዩ ናቸው። ጸሐፊው እግዚአብሔርን የሚገልጸው ውሃውን ከድንጋይ ውስጥ እንዲፈስ ያደረገው ልክ ዓለቱን ወደ ውሃ እንደ ቀየረው አድርጎ ነው።

ዓለቱን ወደ ውሃ ምንጭ
ግሱ ከቀዳሚው ሐረግ ሊገኝ ይችላል። “ዓለታማውን ድንጋይ ወደ ውሃ ምንጭ ቀየረው

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 115

1 ለእኛ ሳይሆን፣ ያህዌ ሆይ ለእኛ ሳይሆን ስለ ፍቅርህ፣ ስለ ታማኝነትህ ስምህን አክብረው። **2** ስለ ምን ሕዝቦች፣ «አምላካቸው የት አለ?» ይበሉ **3** አምላካችን በሰማይ ነው እርሱ ደስ የሚለውን አደረገ። **4** የአሕዛብ ጣዖቶች ብርና ወርቅ የሰው እጅ ሥራዎችም ናቸው። **5** አፍ አላቸው ግን አይናገሩም ዐይን አላቸው ግን አያዩም **6** ጆሮ አላቸው ግን አይሰሙም አፍንጫ አላቸው ግን አያሸቱም። **7** እጅ አላቸው ግን አይዳሰስም እግር አላቸው ግን አይራመዱም ድምፅም ማሰማት አይችሉም። **8** የሠሩአቸውና የሚታመኑባቸው ሁሉ እንደ እነዚህ ጣዖቶች ናቸው። **9** የእስራኤል ቤት ሆይ፣ በያህዌ ታመኑ ረዳታችሁና ጋሻችሁ እርሱ ነው። **10** የአሮን ቤት ሆይ፣ በያህዌ ታመኑ ረዳታችሁና ጋሻችሁ እርሱ ነው። **11** እናንት ያህዌን የምትፈሩ፣ በእርሱ ታመኑ ረዳታችሁና ጋሻችሁ እርሱ ነው። **12** ያህዌ ያስበናል፤ ይባርከናልም፤ እርሱ የእስራኤልን ቤት ይባርካል የአሮንንም ቤት ይባርካል። **13** ታላላቆችም ሆኑ ታናናሾች እርሱ የሚፈሩትን ሁሉ ይባርካል። **14** ያህዌ እናንተንና ልጆቻችሁን በባርኮቱ ይባርካችሁ። **15** ሰማይና ምድርን የፈጠረ ያህዌ ይባርካችሁ። **16** ሰማያት የእግዚአብሔር ናቸው ምድርን ግን ለሰው ልጆች ሰጣት። **17** ወደ ዝምታ ዓለም፣ ወደ መቃብር የወረዱ ሙታን ያህዌን ሊያመሰግኑ አይችሉም። **18** እኛ ግን፣ ከአሁን ጀምሮ እስከ ዘላለም ያህዌን እንባርካለን። ያህዌ ይመስገን።

Psalms 115:3

የሰዎች የእጆች ሥራ
እዚህ ላይ “እጆች” የሚለው ቃል ጣኦታትን የሠሩትን ሰዎች ይወክላል። “ሰዎች የሠሯቸው ነገሮች”

Psalms 115:5

እነዚያ ጣኦታት አፍ አላቸው
ጣኦታት እውነተኛ አፍ፣ ዐይን፣ ጆሮ ወይም አፍንጫ የላቸውም። ይልቁንም ሰዎች የአፍ፣ የአይኖች፣ የጆሮዎች እና የአፍንጫዎች አምሳያ አድረገው ይሠሩላቸዋል። ጸሐፊው አጽንኦት የሚሰጠው እነዚህ ጣኦታት በእውነት ሕያዋን አለመሆናቸውን ነው። የተሰጠውን መግለጫ ግልፅ ማድረግ ትችላለህ። “ሰዎች ለእነዚያ ጣኦታት አፎችን ሰጥተዋቸዋል”

Psalms 115:7

እነዚያ ጣኦታት እጅ አላቸው
ጣኦታት እውነተኛ እጆች፣ እግሮች ወይም አፎች የላቸውም። ይልቁንም ሰዎች የእጆች፣ የእግሮች እና የአፎች አምሳያ ይሠሩላቸዋል። ጸሐፊው አጽንኦት የሚሰጠው እነዚህ ጣኦታት በእውነት ሕያዋን አለመሆናቸውን ነው። ይህንን ስውር መረጃ ግልፅ ማድረግ ትችላለህ። “ሰዎች ለእነዚያ ጣኦታት እጆችን ሰጥተዋቸዋል”

ነገር ግን አይሰማቸውም
“እነዚያ እጆች ግን አይሰማቸውም”

Psalms 115:9

እስራኤል ሆይ፣ በእግዚአብሔር ታመን
“እስራኤል” የሚለው ቃል የእስራኤልን ህዝብ ይወክላል። “የእስራኤል ሕዝቦች፣ በእግዚአብሔር ታመኑ”

የእናንተ እርዳታ እና ጋሻ
ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር የሚናገረው እርሱ ለእስራኤል እንደ ጋሻ ሆኖ ሕዝቡን ከጉዳት እንደሚጠብቃቸው ነው። “የሚረዳችሁና የሚጠብቃችህ”

የአሮን ቤት
እዚህ ላይ “ቤት” የሚለው ቃል ቤተሰብን ወይም ዘሮችን ይወክላል። ይህ ሐረግ የአሮን ዘሮች የነበሩትን ካህናትን ያመለክታል። “የአሮን ዘሮች” ወይም “ካህናት”

Psalms 115:12

አሰበን
“ትኩረት ሰጠን”

የእስራኤል ቤተ ሰብ
ይህ የሚያመለክተው የያዕቆብ ዘሮች የሆኑትን እስራኤል ብሎ የሚጠራቸውን ሕዝብ ነው። “የእስራኤል ሕዝብ”

የአሮን ቤተ ሰብ
ይህ የሚያመለክተው የአሮን ዘሮች የሆኑትን ካህናትን ነው። “የአሮን ዘሮች” ወይም “ካህናቱ”

ወጣቶችና አዛውንት
“ታናሾችና ታላቆች።” ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች፦ ይህ የሚያመለክተው 1) የጎብረተሰብ ደረጃ ወይም 2) ዕድሜን። በየትኛውም ሁኔታ፣ ሁለቱም ጽንፎች የሚያመለክቱት እያንዳንዱን፣ ዕድሜን ወይም የጎብረተሰብ ደረጃን ሳይመለከት ነው።

እግዚአብሔር አብዝቶ አብዝቶ ቁጥራችሁን ይጨምር
ጸሐፊው የሚናገረው የእስራኤል ሕዝብ ስለሚኖራቸው ልጆች ቁጥር ነው። “እግዚአብሔር የልጆቻችሁን ቁጥር አብዝቶ አብዝቶ ይጨምር”

የእናንተ እና የዘሮቻችሁ
የእናንተ ልጆች እና የዘሮቻችሁ ልጆች። ጸሐፊው እዚህ ላይ ግልጽ የሚያደርገው ይህ ጥያቄ ለአሁኑ ትውልድ ብቻ ሳይሆን ለዘሮቻቸውም ጭምር መሆኑን ነው።

Psalms 115:15

ሰማይንና ምድርን በሠራ በእግዚአብሔር ተባረኩ
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “ሰማይንና ምድርን የሠራ እግዚአብሔር ይባርካችሁ”

ምድርን ለሰው ልጆች ሰጣት
ይህ ማለት ምድር የእግዚአብሔር አይደለችም ማለት አይደለም፣ ነገር ግን ምድርን ለሰው ልጆች የሰጣት መኖሪያቸው ትሆን ዘንድ ነው።

Psalms 115:17

ሙታን
“ሙታን” የሚለው ቅፅል ከስም ጋር ሊተረጎም ይችላል። “የሞቱ ሰዎች”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወደ ሲኦል የሚወርዱ ምንም አያደርጉም
ይህ ትይዩ ሐረግ ቀደም ሲል ከነበረው ሐረግ ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው።
ፍቺውን ግልፅ ለማድረግ ግሱ ከቀደመው ሐረግ ጋር ሊተያይ ይችላል። “ወደ
ሲኦል የሚወርዱ እግዚአብሔርን ማመስገን አይችሉም”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 116

1 የልመናዬን ድምፅ ስለ ሰማ ያህዌን ወደድሁት። **2** እርሱ ሰምቶኛልና በሕይወት ዘመኔ ሁሉ ወደ እርሱ እጣራለሁ። **3** የሞት ወጥመድ ያዘኝ የሲኦልም ጣር አገኘኝ ጭንቅና ሐዘን በረታብኝ። **4** እኔም የያህዌን ስም ጠራሁ «ያህዌ ሆይ፣ እባክህ ነፍሴን አድናት።» **5** ያህዌ ቸርና መሐሪ ነው። አምላካችን ርኅሩኅ ነው። **6** አምላካችን ገሮችን ይጠብቃል እኔም በተቸገርኩ ጊዜ አድኖኛል። **7** ያህዌ መልካም ነገር አድርጐልኛልና ከእንግዲህ ነፍሴ ወደ እረፍት ቦታ ትመለሳለች። **8** አንተ ነፍሴን ከሞት፣ ዐይኔን ከእንባ እግሮቼን ከመሰናክል አድነሃልና። **9** እኔም በሕያዋን ምድር ያህዌን አገለግላለሁ። **10** «እጅግ ተጨንቄአለሁ» ባልሁ ጊዜ እንኳ በእርሱ ማመኔን አልተውሁም። **11** ግራ በተጋባሁ ጊዜ፣ «ሰው ሁሉ ሐሰተኛ ነው» አልሁ። **12** ስላደረገልኝ መልካም ነገር ሁሉ ለያህዌ ምን ልክፈለው? **13** የመዳንን ጽዋ አነሣለሁ የያህዌንም ስም እጠራለሁ። **14** በሕዝቡ ሁሉ ፊት ስእለቴን ለያህዌ እፈጽማለሁ። **15** የቅዱሳኑ ሞት በያህዌ ፊት የከበረ ነው። **16** ያህዌ ሆይ፣ እኔ በእውነት ባርያህ ነኝ፣ የሴት ባርያህም ልጅ ነኝ። ከእስራቴም ፈታኸኝ። **17** ለአንተ የምስጋና መሥዋዕት አቀርባለሁ የያህዌንም ስም እጠራለሁ። **18** በሕዝቡ ሁሉ ፊት ስእለቴን ለያህዌ እፈጽማለሁ **19** ኢየሩሳሌም ሆይ፣ በመካከልሽ በያህዌ ቤት አደባባይ ይህን አደርጋለሁ።

Psalms 116:1

አጠቃላይ መረጃ
በዕብራውያን የቅኔ አጻጻፍ ውስጥ ተመሳሳይነት የተለመደ አገላለጽ ነው።

ለምሕረት ያደረግኩትን የልመናዬን ድምፅ ሰምቷል
እዚህ ላይ “ድምፅ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሚናገረውን ሰው ነው። “ልመና” እና “ምሕረት” የሚሉት ረቂቅ ስሞች “መለመን” እና “መሐሪ” ተብለው ሊገለጹ ይችላሉ። “ለእኔ መሐሪ እንዲሆንልኝ ወደ እርሱ ስለምን ይሰማኛል”

Psalms 116:3

አጠቃላይ መረጃ
ይህን መዝሙር ያቀናበረው ሰው መናገሩን ይቀጥላል።

የሞት ገመዶች ከበቡኝ
ጸሐፊው ስለ ሞት የሚናገረው አንድን ሰው እንደ ያዘና በገመድ እንዳሰረው አድርጎ ነው። መዝሙር 18:4ን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። “ልክ እንደምሞት ሆኖ ተሰማኝ”

የሲኦል ወጥመድ አገኘኝ
ጸሐፊው ስለ “ሲኦል” የሚናገረው የሙታን ስፍራ መሆኑን እና ልክ በወጥመድ እንደ ታያዘ ሰው አድርጎ ነው። “ልክ ወደ መቃብር ለመግባት ዝግጁ እንደሆንኩ ተሰማኝ”

የእግዚአብሔርንም ስም ጠራሁ
እዚህ ላይ “ስም” የሚለው ቃል የሚወክለው እግዚአብሔርን ራሱን ነው። “ወደ እግዚአብሔር ተጣራሁ”

ሕይወቴን አድናት
እዚህ ላይ “ሕይወት” የሚለው ቃል የሚወክለው ግለሰቡን ነው። “አድነኝ” ወይም “ከመሞት አድነኝ”

Psalms 116:7

አጠቃላይ መረጃ
ይህን መዝሙር ያቀናበረው ሰው መናገሩን ይቀጥላል።

ነፍሴ ወደ እረፍት ስፍራዋ መመለስ ትችላለች
ጸሐፊው ሰላምንና መተማመንን ማግኘት ልክ ነፍሱ የምታርፍበትን ስፍራ እንዳገኘች አድርጎ ይናገራል። “ነፍስ” የሚለው ቃል ግለሰቡን ይወክላል። “እንደገና በሰላም ማረፍ እችላለሁ”

አንተ ሕይወቴን ከሞት አዳንካት
እዚህ ላይ “እንተ” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ያመለክታል። “ሕይወት” የሚለው ቃል ግለሰቡን ይወክላል። “ከሞት አድነኸኛል” ወይም “ከመሞት ጠብቀኸኛል”

ዓይኖቼን ከእንባ
ትርጉሙን ግልፅ ለማድረግ የቃል ሐረግ ከቀዳሚው ሐረግ ሊወሰድ ይችላል። “ዓይኖቼን ከእንባ አዳንካቸው” ወይም “ከማልቀስ ጠብቀኸኛል”

እግሮቼን ከመሰናከል
ትርጉሙን ግልፅ ለማድረግ የቃል ሐረግ ከቀዳሚው ሐረግ ሊወሰድ ይችላል። እዚህ ላይ እግሮች ግለሰቡን ይወክላሉ። መሰናክል የሚለው ምናልባት በጠላቶቹ መገደልን ይወክላል። “ከመሰናክል አድነኸኛል” ወይም “በጠላቶቼ ከመገደል ጠብቀኸኛል”

Psalms 116:9

አጠቃላይ መረጃ
ይህን መዝሙር ያቀናበረው ሰው መናገሩን ይቀጥላል።

በሕያዋን ምድር
“ሰዎች በሚኖሩበት በዚህ ዓለም ውስጥ።” ይህ ከሙታን ስፍራ በተቃራኒ ነው።

እኔ በጣም ተሠቃይቼአለሁ
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “በጣም ተሠቃየሁ” ወይም “ሰዎች በጣም አሠቃዩኝ”

ግራ በመጋባት ውስጥ ተናገርሁ
“በፍጥነት እንዲህ አልሁ” ወይም “ሳላስብበት ተናገርሁ”

ሰው ሁሉ ሐሰተኛ ነው
“ሰው ሁሉ ሐሰተኛ ነው” ወይም “ሰዎች ሁሉ ሐሰተኞች ናቸው”

Psalms 116:12

አጠቃላይ መረጃ
ይህን መዝሙር ያቀናበረው ሰው መናገሩን ይቀጥላል።

ስላደረገልኝ ሁሉ ... ለእግዚአብሔር ምን እመልሳለሁ?
ጸሐፊው ይህንን መሪ ጥያቄ የጠየቀው እግዚአብሔር ላደረገው ነገር እንዴት ምላሽ እንደሚሰጥ ለማስተዋወቅ ነው። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። “ላደረገልኝ ሁሉ ... ለእግዚአብሔር የምመልሰው እንዲህ ነው”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እኔ የመድኃኒትን ጽዋ አነሣለሁ
ይህ ምናልባት የሚያመለክተው ስለ መጠጥ ቁርባን ሲሆን ይህም ወይንን በመሠዊያው ላይ ማፍሰስን ይጠይቃል፤ ጸሐፊው ይህንን ቁርባን የሚያደርገው እግዚአብሔር ላደረገለት ማዳን ምላሽ እንዲሆን ነው። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልፅ ሊደረግ ይችላል። “እርሱ ስላዳነኝ ለእግዚአብሔር የመጠጥ ቁርባንን አቀርባለሁ”

የእግዚአብሔርንም ስም እጠራለሁ
እዚህ ላይ “ስም” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ራሱን ይወክላል። “እግዚአብሔርን እጠራለሁ”

Psalms 116:16

አጠቃላይ መረጃ
ይህን መዝሙር ያቀናበረው ሰው መናገሩን ይቀጥላል።

የሴት ባሪያህ ልጅ
ይህ ምናልባት የሚያመለክተው የጸሐፊውን እናት ሲሆን እርሷም እግዚአብሔርን በታማኝነት የምታመልክ እንደ ሆነች ይጠቁማል። የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። “እናቴ እንደ ነበረች”

ሠንሠለቴን አስወገድህ
ጸሐፊው በእስር ቤት የታሰረ ያህል የመሞት አደጋ ላይ እንደነበረ ይናገራል። “ከሞት አድነኸኛል”

የምስጋና መሥዋዕት
“ምስጋናዬን የሚገልጽ መሥዋዕት”

የእግዚአብሔርንም ስም እጠራለሁ
እዚህ ላይ “ስም” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ራሱን ይወክላል። “የእግዚአብሔርን ስም እጠራለሁ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 117

1 አሕዛብ ሁላችሁ ያህዌን አመስግኑት ሕዝቦችም ሁሉ በምስጋና ከፍ ከፍ አድርጉት። **2** እርሱ ለእኛ ያሳየው ምሕረት ታላቅ ነውና የያህዌ ታማኝነት ጸንቶ ይኖራል። ያህዌ ይመስገን።

Psalms 117:1

አጠቃላይ መረጃ
በዕብራውያን የቅኔ አጻጻፍ ውስጥ ተመሳሳይነት የተለመደ አገላለጽ ነው።

ለእርሱ
“በእርሱ ምክንያት”

የቃል ኪዳኑ ታማኝነት በእኛ ዘንድ ታላቅ ነው
“ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል። “ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ስለ ሆነ ለእኛ ታላቅ ነገር ያደርጋል”

የእግዚአብሔር አስተማማኝነት ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል
“አስተማማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም ከቅፅል ጋር ወይም ከቃል ሐረግ ጋር ሊተረጎም ይችላል። “እግዚአብሔር ለዘላለም የታመነ ነው” ወይም “እግዚአብሔር በእርሱ ለሚታመኑ ሰዎች ለዘላለም የታመነ ነው”

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 118

1 ቸር ነውና ያህዌን አመስግኑት ምሕረቱም ለዘላለም ጸንታ ትኖራለች። **2** የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ «ምሕረቱ ለዘላለም ነው» ይበል። **3** የአሮን ቤት፣ «ምሕረቱ ለዘላለም ነው» ይበል። **4** ያህዌን የሚፈሩ ሁሉ፣ «ምሕረቱ ለዘላለም ነው» ይበሉ። **5** በተጨነቅሁ ጊዜ ያህዌን ጠራሁት እርሱም ሰማኝ፤ ነጻም አወጣኝ። **6** ያህዌ ከእኔ ጋር ነው፤ አልፈራም ሰው ምን ሊያደርገኝ ይችላል? **7** ይረዳኝ ዘንድ ያህዌ ከእኔ ጋር ነው የጠላቶቼንም ውድቀት አያለሁ። **8** በሰው ከመታመን ይልቅ ያህዌን መከታ ማድረግ ይሻላል። **9** በመሪዎች ከመመካት ይልቅ ያህዌን መጠጊያ ማድረግ ይሻላል። **10** ሕዝቦች ሁሉ ከበቡኝ ነገር ግን በያህዌ ስም አሸነፍኃቸው **11** መክበቡንስ፣ ዙሪያዬን ከበቡኝ ነገር ግን በያህዌ ስም አሸነፍኃቸው። **12** እንደ ንብ መንጋ ከበቡኝ ሆኖም፣ እንደሚነድ እሾኽ ከሰሙ በእርግጥም በያህዌ ስም አሸነፍኃቸው። **13** ሊጥሉኝ ገፈተሩኝ ያህዌ ግን ረዳኝ። **14** ያህዌ ብርታቴና ደስታዬ ነው፤ የሚታደገኝም እርሱ ነው። **15** በጻድቃን ድንኳን፣ የእልልታና የሆታ ድምፅ፣ እንዲህ እያለ ያስተጋባል የያህዌ ቀኝ እጅ አሸነፈ። **16** የያህዌ ቀኝ እጅ ከፍ ከፍ አለ፤ የያህዌ ቀኝ እጅ አሸነፈ። **17** በሕይወት እኖራለሁ እንጂ፣ አልሞትም የያህዌንም ሥራ ገና እናገራለሁ። **18** ያህዌ ክፉኛ ቀጥቶኝ ነበር ነገር ግን ለሞት አሳልፎ አልሰጠኝም። **19** የጽድቅን ደጆች ክፈቱልኝ ወደዚያ ገብቼ ያህዌን አመሰግናለሁ። **20** ይህች የያህዌ ደጅ ናት፤ ጻድቃንም በእርሷ በኩል ይገባሉ። **21** ሰምተህ መልሰህልኛና፣ አዳኝም ሆነኽኛልና አመሰግንሃለሁ። **22** ግንበኞች የናቁት ድንጋይ የማእዘን ራስ ሆነ። **23** ይህም የያህዌ ሥራ ነው ለዐይኖቻችንም ድንቅ ነው። **24** ያህዌ የሠራት ቀን ይህች ናት፣ በእርሷ ደስ ይለኛል፤ ሐሤትም እናደርጋለን። **25** ያህዌ ሆይ፣ እባክህ ድል አቀዳጀን! ያህዌ ሆይ፣ እባክህ አከናውንልን። **26** በያህዌ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው እኛም ከያህዌ ቤት ባረክናችሁ። **27** ያህዌ አምላካችን ነው፤ ብርሃኑንም በላያችን አበራ መሥዋዕቱን መሠዊያው ቀንዶች ላይ በገመድ እሰሩ። **28** አንተ አምላኬ ነህ፤ አመሰግንሃለሁ፤ አንተ አምላኬ ነህ፤ ከፍ ከፍ አደርግሃለሁ። **29** ቸር ነውና ያህዌን አመስግኑ ምሕረቱም ለዘላለም ጸንታ ትኖራለች።

Psalms 118:1

አጠቃላይ መረጃ
በዕብራውያን የቅኔ አጻጻፍ ውስጥ ተመሳሳይነት የተለመደ አገላለጽ ነው።

እግዚአብሔር መልካም ስለሆነ አመስግኑ
“እርሱ ከሚያደርጋቸው መልካም ነገሮች የተነሣ እግዚአብሔርን አመስግኑ”

የቃል ኪዳኑ ታማኝነት ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል
“ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል። “ለቃል ኪዳኑ ለዘላለም ታማኝ ነው”

እስራኤል እንዲህ ይበል
x

Psalms 118:3

የአሮን ቤት እንዲህ ይበል
እዚህ ላይ “ቤት” የሚለው ቃል የአንድን ሰው ቤተሰብ እና ዘሮቹን ይወክላል። ይህ ሐረግ የአሮን ዘሮች የነበሩትን ካህናትን ያመለክታል። “የአሮን ዘሮች እንዲህ ይበሉ” ወይም “ካህናቱ እንዲህ ይበሉ”

የቃል ኪዳኑ ታማኝነት ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል
“ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል። በመዝሙር 118፡1-2 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። “ለቃል ኪዳኑ ለዘላለም ታማኝ ነው”

የእግዚአብሔር ታማኝ ተከታዮች
“እግዚአብሔርን የሚፈሩ” ወይም “እግዚአብሔርን የሚያመልኩ”

Psalms 118:5

ነጻ አድርገኝ
ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር የሚናገረው ከአንድ ጠባብ እስር ቤት አውጥቶ በነፃነት መንቀሳቀስ ወደሚችልበት ሰፊ ስፍራ እንደ ወሰደው ልክ እንደዚሁ ከጭንቀት እንዳዳነው ነው።

ሰው ምን ያደርገኛል?
ጸሐፊው ይህንን የአጻጻፍ ጥያቄ የሚጠይቀው እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለሆነ ማንም ሰው ሊጎዳው እንደማይችል አፅንኦት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። “ሰዎች እኔን ለመጉዳት ምንም ማድረግ አይችሉም።”

እግዚአብሔር ረዳቴ ሆኖ ከአጠገቤ ነው
በአንድ ሰው አጠገብ መቆም ያንን ሰው ለመርዳት መወሰኑን የሚያመልክት ፈሊጣዊ አገላለፅ ነው። “እግዚአብሔር እኔን ለመርዳት ወስኖአል”

በሚጠሉኝ ሰዎች ላይ በድል አድራጊነት እመለከታለሁ
ይህ የሚያመለክተው ጸሐፊው እየተመለከተ ሳለ እግዚአብሔር ጠላቶቹን የሚያሸንፍለት እርሱ መሆኑን ነው። የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊሆን ይችላል። “እግዚአብሔር የሚጠሉኝን ሁሉ ሲያሸንፋቸው አይቻለሁ”

Psalms 118:10

አሕዛብ ሁሉ
እዚህ ላይ “አሕዛብ” የሚለው ቃል የእነዚህን አሕዛብ ሠራዊት ይወክላል። ጸሐፊው በዙሪያው የከበቧቸውን እጅግ ብዙ የሆኑ ሠራዊቶችን ለማጉላት ይህን መግለጫ ተጠቅሞአል። “የብዙ አሕዛብ ሠራዊቶች”

በእግዚአብሔር ስም
እዚህ ላይ “ስም” የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ኃይል ይወክላል። “በእግዚአብሔር ኃይል”

ቆረጥኳቸው
ጸሐፊው የሚናገረው የጠላቱን ሠራዊት ልክ አንድ ሰው የእፅዋትን ቅርንጫፎች እንደሚቆርጥ መቁረጡንና ማሸነፉን በመግለጽ ነው። “አሸንፍኳቸው”

እንደ ንቦች ከበቡኝ
ጸሐፊው የጠላትን ሠራዊት ከንብ ከበባ ጋር ያወዳድረዋል። “ንቦች አንድን ሰው እንደሚክብቡ እኔን ከበቡኝ”

በእሾህ መካከል እንደሚነድድ እሳት በፍጥነት ጠፉ
ልክ ደረቅ እሾህ በፍጥነት እንደሚቃጠል፣ የጠላት ሠራዊት ጥቃትም በፍጥነት ይጠፋል። “እሾህን የሚያቃጥለው እሳት ቶሎ አቃጥሎት እንደሚጠፋ የእነርሱም ጥቃት ለአጭር ጊዜ ብቻ ነው”

Psalms 118:13

ወደ ታች ልትጥለኝ
ጸሐፊው የሚናገረው የጠላት ጦር እርሱን ለማሸነፍ በምድር ላይ ለመጣል ወደ ታች ሊገፉት እንደሞከሩ ነው። “እኔን ለማሸነፍ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እግዚአብሔር ኃይሌና ደስታዬ ነው
“እግዚአብሔር ብርታትና ደስታ ሰጠኝ”

Psalms 118:15

የእልልታና የደስታ ድምፅ በጻድቃን ድንኳን ተሰማ
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “ሰዎች የደስታና የድል ድምፅ በጻድቃን ድንኳኖች ውስጥ ሰሙ” ወይም “ጻድቃን በድንኳኖቻቸው ውስጥ ስላገኙት ድል እልል አሉ”

የእግዚአብሔር ቀኝ እጅ ድል አደረገች
እዚህ ላይ “እጅ” የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ኃይል ይወክላል። “እግዚአብሔር በታላቅ ኃይሉ አሸነፈ”

የእግዚአብሔር ቀኝ እጁ ከበረ
እዚህ ላይ፣ እጅን ማንሣት የድል ምልክት ነው። ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “እግዚአብሔር ቀኝ እጁን አከበረ” ወይም “እግዚአብሔር ቀኝ እጁን በድል አነሣ”

Psalms 118:17

አልሞትም፣ በሕይወት እኖራለሁ
ጸሐፊው እርሱ በእርግጥ ሕያው መሆኑን አፅንኦት ለመስጠት አንድ ዓይነት ሀሳብ በአሉታዊም በአዎንታዊ መልኩ ገልጾታል።

እግዚአብሔር ቀጣኝ
“እግዚአብሔር ሥርዓት አስያዘኝ”

ለሞት አሳልፎ አልሰጠኝም
ጸሐፊው ስለ ሞት የተናገረው ልክ እንደ ሰው ሥልጣን እግዚአብሔር ጸሐፊውን ለእርሱ አሳልፎ እንደሚሰጠው አድርጎ ነው። “እንድሞት አልፈቀደም” ወይም “ጠላቶቼ እንዲገድሉኝ አልፈቀደላቸውም”

Psalms 118:19

የጽድቅ ደጆች ክፈቱልኝ
“ጻድቃን የሚገቡበትን በሮች ክፈቱልኝ።” ይህ የቤተ መቅደሱን በሮች የሚያመለክት ሲሆን ጸሐፊው የበር ጠባቂዎቹን እየተናገረ ነው። የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊሆን ይችላል። “የቤተ መቅደሱን በሮች ክፈቱልኝ”

የእግዚአብሔር በር
ወደ “እግዚአብሔር ሕልውና የሚያደርስ በር” ወይም “የእግዚአብሔር በር”

ምስጋናን ለአንተ እሰጣለሁ
እዚህ ላይ ጸሐፊው ለእግዚአብሔር መናገርን ይጀምራል።

አንተ ድነቴ ሆንህልኝ
“ድነት” የሚለው ቃል በቃል ሐረግ ሊተረጎም ይችላል። “አዳንኸኝ”

Psalms 118:22

ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ድንጋይ ሆነ
ይህ ጸሐፊው የተጠቀመበት ምሳሌ ንጉሡን ወይም የእስራኤልን መንግሥት የሚገልጽ ነው። ሌሎች እንደማይጠቅም የሚቆጥሩት እግዚአብሔር እጅግ የሚጠቅም አደረገው።

ይህ በዓይናችን ፊት ድንቅ ነው
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች፦ 1) “ለእኛ ይህንን ማየት ድንቅ ነው” ወይም 2) “እኛ እንደ ድንቅ ነገር እንቆጥረዋለን።”

Psalms 118:26

በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የተባረከ ነው
እዚህ ላይ ካህናቱ ለንጉሡ መናገር ይጀምራሉ።

በእግዚአብሔር ስም የሚመጣው
እዚህ ላይ “ስም” የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ኃይል የሚወክል ነው። “በእግዚአብሔር ኃይል የሚመጣው”

እኛ ከእግዚአብሔር ቤት ባረክናችሁ
እዚህ ላይ ካህናቱ ለሕዝቡ ይናገራሉ።

የእግዚአብሔር ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል ቤተ መቅደሱን ያመለክታል። “የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ”

እርሱ ብርሃን ሰጥቶናል
ጸሐፊው እግዚአብሔር ሕዝቡን ስለ መባረኩ ሲናገር ልክ እግዚአብሔር ብርሃንን በላያቸው እንዳበራ አድርጎ ነው። “ባርኮናል”

መሥዋዕቱን በገመድ እሰሩ
“መሥዋዕቱን በገመድ እሰሩ”

አንተ አምላኬ ነህ
እዚህ ላይ ጸሐፊው እግዚአብሔርን በቀጥታ መናገር ይጀምራል።

Psalms 118:29

ኦ
ይህ የቃለ አጋኖ ምልክት ሲሆን በቋንቋ ውስጥ በሚገኝ በየትኛውም የቃለ አጋኖ ትኩረት ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ ልትጠቀምበት ትችላለህ።

እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ እርሱ ቸር ነውና
“ስላደረገው መልካም ነገር እግዚአብሔርን አመስግኑ።” ይህንን መዝሙር 118፡1ን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የቃል ኪዳኑ ታማኝነት ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል
“ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል። ይህንን መዝሙር 118፡1-2 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። “ለቃል ኪዳኑ ለዘላለም ታማኝ ነው”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 119

1 መንገዳቸው ነቀፋ የሌለበት በያህዌም ሕግ የሚሄዱ የተባረኩ ናቸው። 2 ትእዛኣቹን የሚጠብቁ በሙሉ ልባቸውም የሚፈልጉት የተባረኩ ናቸው። 3 በመንገዱ ይሄዳሉ እንጂ ዐመፅ አያደርጉም። 4 ጠንቅቀን እንጠብቃት ዘንድ አንተ ሥርዐትን አዝዘሃል። 5 ሥርዐትህን እጠብቅ ዘንድ ምነው መንገዴ ጽኑ በሆነልኝ ኖሮ! 6 ትእዛዞችህን ሁሉ በጥንቃቄ ካስተዋልሁ እፍረት ከቶ አይደርስብኝም። 7 የጽድቅ ፍርድህን ስማር በቅን ልብ ምስጋና አቀርብልሃለሁ። 8 ሥርዐትህን እጠብቃለሁ አንተ ፈጽሞ አትተወኝ። ቤት 9 ጐልማሳ መንገዱን እንዴት ያነጻል? ቃልህን በመጠበቅ ነው። 10 በሙሉ ልቤ እፈልግሃለሁ ከትእዛዞችህ እንድርቅ አትተወኝ። 11 አንተን እንዳልበድል ቃልህን በልቤ አኖራለሁ። 12 ያህዌ ሆይ፣ አንተ ቡሩክ ነህ ሥርዐትህን አስተምረኝ። 13 አንተ የገለጥኸውን የጽድቅ ሥርዐት ሁሉ በአንደበቴ እናገራለሁ። 14 ከብዙ ሀብት ይልቅ በኪዳንህ ሥርዐት ደስ ይለኛል። 15 ድንጋጌህን አሰላስላለሁ መንገድህም ላይ አተኩራለሁ። 16 በሥርዐትህ ደስ ይለኛል ቃልህንም አልዘነጋም። ጋሜል 17 በሕይወት እንድኖርና ቃልህን እንድጠብቅ ለባርያህ መልካም አድርግ። 18 ከሕግህ ድንቅ ነገር እንዳይ ዐይኖቼን ክፈት። 19 በምድር ላይ መጻተኛ ነኝ ትእዛዞችህን ከእኔ አትሰውር። 20 ጻድቅ ሥርዐትህን ለማወቅ ዘወትር ከመናፈቄ የተነሣ ነፍሴ እጅግ ዛለች። 21 ከትእዛዞችህ የሳቱትን የተረጉሙ ዕቡያንን ገሠጽህ። 22 ሥርዐቶችህን ጠብቄአለሁና ስድብና ውርደትን ከእኔ አርቅ። 23 ገዦች ተሰብስበው በእኔ ላይ ቢዶልቱም እንኳ ባርያህ ሥርዐትህን ያሰላስላል። 24 ትእዛዝህ ለእኔ ደስታዬ ነው መካሪየም ነው። ዳሌጥ 25 ነፍሴ ከዐፈር ጋር ተጣበቀች በቃልህ ሕይወት ስጠኝ። 26 ስለ መንገዴ ገልጬ ነገርሁህ አንተም መልሰህልኝ ሥርዐትህን አስተምረኝ። 27 ድንቅ ሥራህን አሰላስል ዘንድ የድንጋጌህን መንገድ እንዳስተውል አድርገኝ። 28 ሐዘን በርትቶብኛል በቃልህ አበርታኝ። 29 የሸንገላን መንገድ ከእኔ አርቅ በቸርነትህ ሕግህን አስተምረኝ። 30 የእውነትን መንገድ መርጫለሁ ሕግህንም ፊት ለፊቴ አድርጌአለሁ። 31 ከሥርዐትህ ጋር ተጣብቄአለሁ ያህዌ ሆይ፣ ለውርደት አሳልፈህ አትስጠኝ። 32 ያን እንዳደርግ አንተ ልቤን አስፍተኸዋል በትእዛዞችህ መንገድ እሮጣለሁ። ሄ 33 ያህዌ ሆይ፣ የሥርዐትህን መንገድ አስተምረኝ እኔም እስከ መጨረሻው እጠብቀዋለሁ። 34 ሕግህን እንድጠብቅ፣ በፍጹም ልቤም እንድታዘዘው ማስተዋልን ስጠኝ። 35 በዚያ መሄድ ደስ ይለኛልና በትእዛዞችህ መንገድ ምራኝ። 36 ጽድቅ ከሌለበት ጥቅም ይልቅ ልቤን ወደ ሥርዐትህ አዘንብል። 37 ከንቱ ነገር ከማየት ዐይኖቼን መልስ በጽድቅህ ሕይወቴን አድስልኝ። 38 ለእኔ ለአገልጋይህና ለሚፈሩህ ሁሉ የሰጠኸውን ተስፋ ቃል ፈጽም። 39 ጻድቅ ፍርድህ መልካም ነውና የምፈራውን ስድብ አርቅልኝ። 40 እነሆ፣ ድንጋጌህን ናፈቅሁ በጽድቅህም ሕያው አድርገኝ። ዋው 41 ያህዌ ሆይ፣ ዘላለማዊ ፍቅርህን ስጠኝ በተስፋ ቃልህ መሠረት አድነኝ። 42 በቃልህ ታምኛለሁና ለሚሰድቡኝ መልስ እሰጣለሁ። 43 ሕግህን ተስፋ አድርጌአለሁና የእውነትን ቃል ከአፌ አታርቅ። 44 ከዘላለም እስከ ዘላለም ሕግህን ዘወትር እጠብቃለሁ። 45 ሥርዐትህን እሻለሁና በፍጹም ነጻነት እኖራለሁ። 46 ትእዛዞችህን በነገሥታት ፊት እናገራለሁ ይህን በማድረጌም እፍረት አይሰማኝም። 47 አጥብቄ እወደዋለሁና በትእዛዞችህ ደስ ይለኛል። 48 እጆቼን ወደምወዳቸው ትእዛዞችህ አነሣለሁ፤ ሥርዐትህንም አሰላስላለሁ። ዛይ 49 በዚያ ተስፋ ሰጥተኸኛልና ለባርያህ የገባኸውን ቃል አስብ። 50 የተስፋ ቃልህ ሕያው አድርጐኛልና ይህ በመከራዬ መጽናኛዬ ሆነ። 51 ትዕቢተኞች እጅግ ተሳለቁብኝ እኔ ግን ከሕግህ ንቅንቅ አላልሁም። 52 ያህዌ ሆይ፣ ከጥንት የነበረውን ድንጋጌህን አሰብሁ በዚህም ተጽናናሁ። 53 ሕግህን ከናቁ ክፉዎች የተነሣ እጅግ ተቆጣሁ። 54 በእንግድነቴ አገር ሥርዐትህ መዝሙሬ ሆነ። 55 ያህዌ ሆይ፣ ስምህን በሌሊት አስባለሁ ሕግህንም እጠብቃለሁ። 56 ሥርዐትህን ጠብቄአለሁና ይህ የሁልጊዜ ልምዴ ሆነ። ሔት 57 ያህዌ ዕድል ፈንታዬ ነው ቃልህን ለመታዘዝ ቆርጫለሁ። 58 በፍጹም ልቤ የአንተን ሞገስ እፈልጋለሁ እንደ ቃልህ ቸርነት አሳየኝ። 59 መንገዴን መረመርሁ አካሄዴንም ወደ ሥርዐትህ አቀናሁ። 60 ትእዛዝህን ለመጠበቅ ቸኮልሁ፤ አልዘገየሁም። 61 የክፉዎች ገመድ ተተበተበብኝ እኔ ግን ሕግህን አልረሳሁም። 62 ስለ ጻድቅ ሥርዐትህ አንተን ለማመስገን በእኩለ ሌሊት እነሣለሁ። 63 እኔ አንተን የሚፈሩና ሥርዐትህንም የሚጠብቁ ሁሉ ባልንጀራ ነኝ። 64 ያህዌ ሆይ፣ ምድር በምሕረትህ ተሞላች ሥርዐትህን አስተምረኝ።ጤት 65 ያህዌ ሆይ፣ እንደ ቃልህ ለአገልጋይህ መልካም አድርገሃል። 66 በትእዛዞችህ አምናለሁና ተገቢውን ማስተዋልና ዕውቀትን አስተምረኝ። 67 አንዳች ጉዳት ሳይደርስብኝ መንገድ ስቼ ሄድሁ አሁን ግን ቃልህን እጠብቃለሁ። 68 አንተ መልካም ነህ፤ የምታደርገውም መልካም ነው እንግዲህ ሥርዐትህን አስተምረኝ። 69 እብሪተኞች በሐሰት ስሜን አጠፉ እኔ ግን በፍጹም ልቤ ትእዛዝህን እጠብቃለሁ። 70 ልባቸው የሰባና የደነደነ ነው እኔ ግን በሕግህ ደስ ይለኛል። 71 ሥርዐትህን እማር ዘንድ በመከራ ውስጥ ማለፌ መልካም ሆነልኝ። 72 ከአእላፋት ወርቅና ብር ይልቅ የአፍህ ሕግ ይሻለኛል። ዮድ 73 እጆችህ ሠሩኝ፣ አበጃጁኝም ትእዛዞችህን እንድማር ማስተዋልን ስጠኝ። 74 ቃልህን ተስፋ አድርጌአለሁና የሚፈሩህ እኔን ዐይተው ደስ ይላቸዋል። 75 ያህዌ ሆይ፣ ፍርድህ እውነተኛ እንደ ሆነ ያስጨነቅኸኝም በታማኝነት እንደ ሆነ ዐውቃለሁ። 76 ለአገልጋይህ በገባኸው ቃል መሠረት ምሕረትህ መጽናኛዬ ይሁንልኝ። 77 ሕግህ ደስታዬ ነውና በሕይወት እንድኖር ራራልኝ። 78 በሐሰት የሚከሱኝ ትዕቢተኞች ይዋረዱ እኔ ግን ሥርዐትህን አሰላስላለሁ። 79 አንተን የሚፈሩህ ሥርዐቶችህንም የሚያውቁ ወደ እኔ ይመለሱ። 80 እፍረት እንዳይደርስብኝ ልቤ በሥርዐትህ ያለ ነቀፋ ይሁን። ካፍ 81 ነፍሴ ማዳንህን እጅግ ናፈቀች ቃልህንም ተስፋ አድርጌአለሁ። 82 «መቼ ታጽናናኛለህ?» እያልሁ በመጠባበቅ ዐይኖቼ ፈዘዙ። 83 ጢስ እንደ ጠገበ የወይን ጠጅ አቁማዳ ሆኛለሁ ሥርዐትህን አልረሳሁም። 84 እኔ አገልጋይህ እስከ መቼ ልቆይ? በሚያሳድዱኝ ላይ የምትፈርደው መቼ ነው? 85 ሕግህን የማያከብሩ፤ ትዕቢተኞች ጉድጓድ ቆፈሩልኝ። 86 ትእዛዞችህ ሁሉ አስተማማኝ ናቸው ሰዎች ያለ ምክንያት እያሳደዱኝ ስለሆነ ርዳኝ። 87 ከምድር ሊያጠፉኝ ጥቂት ቀራቸው እኔ ግን ትእዛዞችህን ችላ አላልሁም። 88 ሕግህን እጠብቅ ዘንድ በዘላለማዊ ፍቅርህ ሕያው አድርገኝ። ላሜድ 89 ያህዌ ሆይ፣ ቃልህ በሰማይ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል። 90 ታማኝነትህ ከትውልድ እስከ ትውልድ ሁሉ ነው ምድርን መሠረትሃት እርሷም ጸንታ ትኖራለች። 91 ነገሮች ሁሉ አገልጋዮችህ ስለሆኑ በሕግህ መሠረት እስከ ዛሬ ድረስ ጸንተው ይኖራሉ። 92 ሕግህ ደስታዬ ባይሆን ኖሮ፣ በደረሰብኝ መከራ በጠፋሁ ነበር። 93 በእርሱ ሕያው አድርገኸኛልና ትእዛዞችህን ከቶ አልረሳሁም። 94 እኔ የአንተ ነኝ፤ እባክህ አድነኝ ሕግህንም ፈልጌአለሁ። 95 ክፉዎች ሊያጠፉኝ አድብተዋል እኔ ግን ሕግህን መረዳት እፈልጋለሁ። 96 ማንኛውም ነገር የራሱ ወሰን እንዳለው አየሁ፤ ትእዛእህ ግን እጅግ ሰፊ ነው። ሜም 97 አቤቱ ሕግህን ምንኛ ወደዱሁ ቀኑን ሙሉ አሰላስለዋለሁ። 98 ዘወትር ከእኔ ጋር በመሆኑ፣ ሕግህ ከጠላቶቼ ይልቅ አስተዋይ አደረገኝ። 99 ሥርዐቶችህን አሰላስላለሁና ከአስተማሪዎቼ ሁሉ የበለጠ ማስተዋል አለኝ። 100 መመሪያህን ተከትዬ ስለምሄድ ከሽማግሌዎች ይልቅ አስተዋይ ሆንሁ። 101 ቃልህን እጠብቅ ዘንድ እግሬን ከክፉ መንገድ ከለከልሁ። 102 አንተው ራስህ አስተምረኸኛልና ከድንጋጌህ ዘወር አላልሁም። 103 ቃልህ ለምላሴ ምንኛ ጣፋጭ ነው ለአፌም ከማር ወለላ ይልቅ ጣዕም አለው። 104 ከመመሪያህ ማስተዋል አገኘሁ ስለዚህ የሐሰትን መንገድ ሁሉ ጠላሁ። ኖን 105 ቃልህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴም ብርሃን ነው። 106 ጻድቅ ትእዛዞችህን ለመጠበቅ በመሐላ የገባሁትን ቃል አጸናለሁ። 107 እጅግ ተጐድቻለሁና ያህዌ ሆይ፣ እንደ ቃል ሕያው አድርገኝ። 108 ያህዌ ሆይ፣ ፈቅጄ የማቀርበውን የአፌን ምስጋና መሥዋዕት ተቀበል። 109 ነፍሴ ዘወትር አደጋ ላይ ናት፤ እኔ ግን ሕግህን አልረሳሁም። 110 ክፉዎች ወጥመድ ዘረጉብኝ እኔ ግን ከመመሪያህ ፈቀቅ አላልሁም። 111 ሕግህ የዘላለም ውርሴ ነው የልቤም ደስታ ይኸው ነው። 112 ትእዛዝህን እስከ መጨረሻው ለዘላለም ለመፈጸም ልቤን ወደዚያው አዘነበልሁ። ሳምኬት 113 መንታ ልብ ያላቸው ወላዋዮችን ጠላሁ፤ ሕግህን ግን ወደድሁ። 114 አንተ ጋሻዬና መሸሸጊያ ነህ ቃልህን በተስፋ እጠብቃለሁ። 115 የአምላኬን ትእዛዞች እጠብቅ ዘንድ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እናንት ክፉ አድራጊዎች ከእኔ ራቁ 116 በሕይወት እኖር ዘንድ በቃልህ ደግፈኝ ተስፋዬም መና ቀርቶ አልፈር። 117 ያለ ስጋት እንድኖር ደግፈህ ያዘኝ
ሥርዐትህንም ዘወትር አሰላስላለሁ። 118 አታላዮችና የማያስተማምኑ ስለሆኑ ከሥርዐትህ የሚያፈነግጡትን ሁሉ ወዲያ አስወገድሃቸው። 119 የምድርን
ክፉዎች ሁሉ እንደ ጥራጊ አስወገድሃቸው። ስለዚህ እኔ ትእዛዞችህን ወደድሁ። 120 አንተን በመፍራት ሥጋዬ ተንቀጠቀጠ ፍርድህን እፈራለሁ። ዔ 121
ትክክልና መልም የሆነውን አድርጌአለሁና ለሚጨቁኑኝ አሳልፈህ አትስጠኝ። 122 ለባርያህ ደኅንነት ዋስትና ሁን ትዕቢተኛ እንዲረግጠኝ አትፍቀድለት። 123
ማዳንህንና የጽድቅ ቃልህን በመጠባበቅ ዐይኖቼ ደከሙ። 124 ለእኔ ለአገልጋይህ ታማኝትህን አሳይ፣ ሥርዐቶችህንም አስተምረኝ። 125 እኔ አገልጋይህ ነኝ፤
ሥርዐትህንም እንዳውቅ ማስተዋልን ስጠኝ። 126 ያህዌ ሆይ፣ ሕግህ እየተጣሰ ነውና ጊዜው አንተ የምትሠራበት ነው። 127 ከወርቅ፣ ከንጹሕም ወርቅ ይልቅ
በእውነት ትእዛዞችህን ወደድሁ። 128 ስለዚህ መመሪያዎችን በጥንቃቄ ጠበቅሁ የሐሰትንም መንገድ ጠላሁ። ፌ 129 ሥርዐቶችህ አስደናቂ ናቸው እኔም
በሙሉ ልቤ እታዘዛቸዋለሁ። 130 የቃልህ ፍቺ ያበራል አላዋቂዎችን አስተዋይ ያደርጋል። 131 ትእዛዝህን በመናፈቄ አፌን ከፊትሁ አለከለክሁም። 132
ስምህን ለሚፈሩ ዘወትር እንደምታደርገው ወደ እኔ ተመልሰህ ምሕረት አድርግልኝ። 133 እንደ ቃልህ አካሄዴን ቀና አድርግልኝ ኃጢአት እንዲሠለጥንብኝም
አትፍቀድ። 134 ትእዛዝህን መጠበቅ እንድችል ከሰዎች ጥቃት አድነኝ። 135 ፊትህ በባርያህ ላይ ያብራ ሥርዐትህንም አስተምረኝ። 136 ሰዎች ሕግህን ስለ
ጣሱ እንባዬ እንደ ወራጅ ውሃ ፈሰሰ። 137 ያህዌ ሆይ፣ አንተ ጻድቅ ነህ ፍርድህም ትክክል ነው። 138 ሕግህ በፍጹም እውነትና ትክክል ነው። 139 ጠላቶቼ
ቃልህን መዘንጋታቸው በጣም አበሳጨኝ። 140 ቃልህ እጅግ የነጠረ ነው ባርያህም ወደደው። 141 እኔ የማልጠቅምና የተናቅሁ ብሆን እንኳ፣ መመሪያህን
አልዘነጋሁም። 142 ጽድቅህ ለዘላለም ትክክል ነው ሕግህም የታመነ ነው። 143 መከራና ስቃይ ቢደርስብኝ እንኳ አሁንም ትእዛዝህ ደስታዬ ነው። 144
ሥርዐትህ ለዘላለም ጻድቅ ነው በሕይወት መኖር እንድችል ማስተዋል ስጠኝ። ቆፍ 145 ያህዌ ሆይ፣ በፍጹም ልቤ እጮኻለሁና መልስልኝ፤ ሥርዐትህንም
እጠብቃለሁ። 146 ወደ አንተ እጣራለሁና አድነኝ ሥርዐትህንም እጠብቃለሁ። 147 ጐሕ ከመቅደዱ በፊት ርዳታህን በመፈለግ ወደ አንተ እጮኻለሁ፤
ቃልህንም ተስፋ አደርጋለሁ። 148 ቃልህን አሰላስል ዘንድ ሌሊቱን ሙሉ ዐይኔ ሳይከደን ያድራል። 149 እንደ ቸርነትህ መጠን ድምፄን ስማ ያህዌ ሆይ፣
በትእዛዝህ መሠረት ሕይወቴን ጠብቅ። 150 የሚያሳድዱኝ ወደ እኔ ቀርበዋል ከሕግህ ግን ርቀዋል። 151 ያህዌ ሆይ፣ አንተ ቅርብ ነህ መመሪያዎችህም
የታመኑ ናቸው። 152 ለዘላለም እንደ መሠረትሃቸው ጥንት ከሥርዐትህ ተምሬአለሁ። ሬስ 153 ሕግህን አልረሳሁምና መከራዬን ተመልከት አድነኝም። 154
ተሟገትልኝ አድነኝም እንደ ተስፋ ቃልህም ጠብቀኝ። 155 ሥርዐትህን ስለማይፈልጉ ድነት ከክፉዎች የራቀ ነው። 156 ያህዌ ሆይ፣ ርኅራኄህ ታላቅ ነው፤ እንደ
ሁልጊዜው በሕይወት ጠብቀኝ። 157 አሳዳጆቼና ጠላቶቼ በዝተዋል፤ እኔ ግን ከሥርዐትህ ፈቀቅ አላልሁም። 158 ቃህን አልጠበቁም ከዳተኞችን ዐይቼ
ተጸየፍኃቸው። 159 መመሪያህን እንዴት እንደምወድ እይ፤ ያህዌ ሆይ፣ እንደ ምሕረትህ ሕያው አድርገኝ። 160 የቃልህ ሥረ መሠረት እውነት ነው ጻድቅ የሆነው
ሕግህም ዘላለማዊ ነው። ሳን 161 መመሪያህን እንዴት እንደምወድ እይ፤ ያህዌ ሆይ፣ እንደ ምሕረትህ ሕያው አድርገኝ። 162 የቃልህ ሥረ መሠረት እውነት ነው
ጻድቅ የሆነው ሕግህም ዘላለማዊ ነው። ሳን 163 ሐሰትን እጠላለሁ፤ እጸየፋለሁ ሕግህን ግን ወደድሁ። 164 ጻድቅ ስለሆነው ሕግህ በቀን ሰባት ጊዜ
አመሰግንሃለሁ። 165 ሕግህን ለሚወዱ ብዙ ሰላም አላቸው ዕንቅፋትም የለባቸውም። 166 ያህዌ ሆይ፣ ማዳንህን እጠብቃለሁ ትእዛዞችህንም እፈጽማለሁ።
167 ትእዛዝህን እጠብቃለሁ በሙሉ ልቤም እወዳቸዋለሁ። 168 ትእዛዝህንና ሕግህን አከብራለሁ አንተ የምሠራውን ሁሉ ታውቃለህ። ታው 169 ያህዌ ሆይ፣
እንድትረዳኝ ወደ አንተ ስጮኽ ስማኝ እንደ ቃልህም ማስተዋልን ስጠኝ። 170 ልመናዬ ወደ አንተ ይድረስ በተስፋ ቃልህም መሠረት አድነኝ። 171 ሥርዐትህን
አስተምረኸኛልና ከንፈሮቼ ምስጋናን አፈለቁ። 172 ትእዛዞችህ ሁሉ ትክክል ስለሆኑ ስለ ቃልህ እዘምራለሁ። 173 መመሪያህን መርጫለሁና እጅህ እኔን
ለመርዳት ዝግጁ ይሁን። 174 ያህዌ ሆይ፣ ማዳንህን ናፈቅሁ ሕግህም ደስታዬ ነው። 175 አመሰግንህ ዘንድ በሕይወት ልኑር ሕግህም ይርዳኝ። 176 እንደ
ጠፋ በግ ተቅበዘበዝሁ ትእዛዞችህን አልረሳሁምና ባርያህን ፈልገው።

Psalms 119:1

አጠቃላይ መረጃ
ትይዩነት በዕብራይስጥ ቅኔ ውስጥ የተለመደ ነው።

አሌፍ
ይህ በዕብራይስጥ ፊደላት የመጀመሪያው ፊደል ስም ነው።

እነዚያ የተባረኩ
“ለእነዚያ እንዴት መልካም ነው”

መንገዳቸው ነቀፋ የሌለበት
የአንድ ሰው ባሕርያት “መንገዶች” ወይም “ጎዳናዎች” ይባላሉ። “እነዚያ ባሕርያቸው ነቀፋ የሌለባቸው” ወይም “ስሕተት በማድረግ ማንም የማይወቅሳቸው”

በእግዚአብሔር ሕግ የሚመላለሱ
አንድ ሰው አካሔዱ ወይም ባሕርይው እንደ መመላለስ ተደርጎ ይነገራል። “እንደ እግዚአብሔር ሕግ የሚኖር” ወይም “የእግዚአብሔርን ሕግ የሚታዘዙ”። ይህ ሐረግ “መንዳቸው ነቀፋ የሌለበት” የሚለውን ትርጉሙ ግልፅ ያደርጋል።

በፍጹም ልባቸው እርሱን የሚፈልጉት
እግዚአብሔርን “መፈለግ” ማለት እርሱን ለማወቅ መፈለግ ማለት ነው።

በፍጹም ልባቸው
ይህ በጣም ወይም በእውነት ለማለት የምንጠቀምበት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። “በሁለንተናቸው” ወይም “በውስጣቸው ባለው ነገር ሁሉ” ወይም “በእውነት”

Psalms 119:3

አጠቃላይ መረጃ
የዚህ መዝሙር አብዛኛው ክፍል ለእግዚአብሔር የሚናገር ሲሆን “አንተ” እና “የአንተ” የሚሉት ቃላት ሁል ጊዜ የሚያመለክቱት እርሱን ነው።

እነርሱ ስሕተትን አያደርጉም
እግዚአብሔርን አንታዘዝም አይሉም።

በመንገዶቹ ይሄዳሉ
“በእግዚአብሔር መንገዶች ይሄዳሉ።” እዚህ ላይ ባሕርያቸው “መራመድ” ተብሎ ተጠርቷል፣ እንዲሁም እግዚአብሔር እንዲያሳዩ የሚፈልገውን ባሕርይ “መንገዶቹ” ተብሎ ተነግሮአል። “እግዚአብሔር የሚፈልገውን ባሕርይ ያሳያሉ”

ትእዛዛትህን ይጠብቃሉ
“እንድናደርገው የደነገግኸውን ትእዛዛትህን ሁሉ እንታዘዛለን”

በጥንቃቄ ይጠብቃሉ
ይህ በጥንቃቄ ትዕዛዛቱን ማወቅ እና መረዳት እንደዚሁም መታዘዝ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 119:5

እኔ በፅኑ ተመስርቻለሁ
ጸሐፊው የሚናገረው ልክ በአካል ማንም ሰው ሊያነቃንቀው እንደማይችል ሁሉ በእግዚአብሔር ትእዛዛት መመስረቱን ነው።

ትእዛዛትህን አከብራለሁ
“ትእዛዛትህን እታዘዛለሁ”

እኔ አላፍርም
ጸሐፊው በእግዚአብሔር ፊት ሲቀርብ ማፈር አይፈልግም።

ትእዛዛትህ ሁሉ
“ያዘዝከንን ሁሉ”

Psalms 119:7

ቅን ልብ
“እውነተኛ ልብ።” ቅን የሆነ ሰው ትክክለኛውን ነገር ያደርጋል። ልብ በአንድ ሰው ውስጥ የስሜቱ ማዕከል መሆኑን ያመለክታል። በመዝሙር 25:21 ላይ “ቅንነት” የሚለውን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ትእዛዛትህ
“ትእዛዛት” የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ሕጎችን ወይም ትእዛዞችን ነው።

Psalms 119:9

ቤት
ይህ የዕብራይስጥ ፊደላት ሁለተኛው የፊደል ስም ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ ከቁጥር 9 እስከ 16 ያለው እያንዳንዱ መስመር በዚህ ፊደል ይጀምራል።

ጎልማሳ መንገዱን በምን ያነጻል?
ይህ ጥያቄ ለእግዚአብሔር ቃል አዲስን እሴት ለማስተዋወቅ ይጠቅማል። ይህ የአጻጻፍ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። “ጎልማሳ መንገዱን የሚያነጻው እንዲህ ነው”

መንገዱን ንፁሕ ማድረግ
ጸሐፊው እንደ እግዚአብሔር ሕግ መኖርን ከወጥመድ ነጻ ከሆነ መንገድ ጋር ያነጻፅረዋል።

በሙሉ ልቤ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ጥ ነው። ልብ ሁሉንም የአንድን ሰው ስሜቶች፣ ፍላጎቶች እና ፍቃድ ያሳያል። “በሁለንተናዬ” ወይም “ውስጤ ባለው ነገር ሁሉ” ወይም “በእውነት”

ከትእዛዛትህ አታርቀኝ
እዚህ ላይ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት አለመታዘዝ ከመንገድ እንደ መውጣት ተገልጾአል። “ትእዛዛትህን የማልታዘዝ አታድርገኝ”

Psalms 119:11

ቃልህን በልቤ ውስጥ አሰውራለሁ
“ቃልህን በልቤ ውስጥ አኖርሁ።” "ቃልህን አሰላስላለሁ" ለማለት ጥቅም ላይ የዋለ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። ልብ ሰዎች የሚያስቡትን መያዝ የሚችል መያዣ ነገር ነው።

Psalms 119:13

ከባለጠግነት በላይ ነው
“ከሀብት ሁሉ በላይ”

Psalms 119:15

አሰላስላለሁ . . . እናም ትኩረት እሰጣለሁ
እነዚህ አጽንኦት ለመስጠት የሚደገሙ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ትይዩ ሀሳቦች ናቸው።

ትእዛዛትህን አሰላስላለሁ
“ያዘዝከንን በጥንቃቄ አስባለሁ”

ትኩረት እሰጣለሁ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር የሚያመለክተው እየተወያየበት ስላለው ነገር በግልጽ ማሰብን ነው። “በጥንቃቄ አስብ”

ደስ ይለኛል
ለመደሰት

Psalms 119:17

ጋሜል
ይህ በዕብራይስጥ ፊደል ሦስተኛው የፊደል ስም ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ ከቁጥር 17 እስከ 24 ያለው እያንዳንዱ መስመር በዚህ ፊደል ይጀምራል።

ባሪያ
ጸሐፊው ትሑት መሆኑን ለማሳየት ራሱን “ባሪያህ” ብሎ ጠርቷል።

ማየት እንድችል ዐይኖቼን ክፈት
ደራሲው መረዳትን፣ እውቀትንና ጥበብን ማግኘት ማየት እንደ መቻል ነው ብሎ ይናገራል። እንዳስተውል እርዳኝ

በሕግህ ውስጥ አስደናቂ ነገሮች
ደራሲው በሕጉ ውስጥ መረዳትን ማግኘት የሚያስደንቅ ነገር ነው ይላል።

በሕግህ ውስጥ
“በትእዛዛትህ” ወይም “በትእዛዛትህ”

Psalms 119:19

እኔ በምድሪቱ ላይ መጻእተኛ ነኝ
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች፦ 1) ጸሐፊው የሚናገረው በምድር ላይ ያለው ዘመኑ አጭር መሆኑን ለመግለጽ ሲሆን፣ በምድር ላይ እንደ መጻእተኛ ለአጭር ጊዜ እንደሚቆይ ይናገራል። “እኔ እንደ መጻእተኛ በምድር ላይ ለአጭር ጊዜ እንደሚኖር ነኝ” ወይም 2) ጸሐፊው የእግዚአብሔርን ቃል አለማወቁን ሲገልጽ የሚኖርበትን ምድር ሕግ እንደማያውቅ መጻእተኛ መሆኑን ይገልጻል። “እኔ በምድር ላይ እንዳለ መጻእተኛ አላዋቂ ነኝ”

ምኞቶቼ በመናፈቅ ተሰብረዋል
ጸሐፊው ስለ ምኞቶቹ ሲናገር ፍላጎቶቹ በሥቃይ ውስጥ ያሉ ያህል በጣም ጠንካራ እንደሆኑ ተናግሯል። “የውስጥ ማንነቴ ለማወቅ በጣም ይጓጓል” ወይም “ነፍሴ ሕመም እስከሚሰማት በጣም ለማወቅ ጓጓች”

Psalms 119:21

የተረገሙ
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) እግዚአብሔር ይረግማቸዋል ወይም 2) የእግዚአብሔር ቅጣት ይገባቸዋል። “የአንተ ቅጣት የሚገባው”

ከትእዛዛትህ የራቁ
ጸሐፊው የሚናገረው የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት አለመታዘዝ ከመንገድ ወጥቶ እንደ መባዘን ነው። “ከአንተ የትእዛዝ መንገድ ርቀው የሄዱ” ወይም “የአንተን ትእዛዛት የማይታዘዙ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አራቅኸኝ
“ጠበቅኸኝ” ወይም “ታደግኸኝ”

Psalms 119:23

ገዥዎች ቢያሴሩብኝና ቢሰድቡኝም
“ገዥዎች እኔን ለመጉዳት እና ስለ እኔ መጥፎ ነገር ለመናገር ቢያቅዱም”

የቃል ኪዳን ድንጋጌዎችህ ደስታዬ ናቸው
“የቃል ኪዳን ድንጋጌዎችህ በጣም ደስተኛ አደረጉኝ።”

እነርሱ አማካሪዎቼ ናቸው
የእግዚአብሔር ድንጋጌዎች ልክ ሰዎች እንደሆኑ ተነግሯል። “እነርሱ ለእኔ እንደ ጠቢባን አማካሪዎች ናቸው” ወይም “ጥሩ ምክር ለእኔ ይሰጡኛል”

Psalms 119:25

ዳሌጥ
ይህ የዕብራይስጥ ፊደላት አራተኛው የፊደል ስም ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ ከቁጥር 25 እስከ 32 ያሉት እያንዳንዱ መስመር በዚህ ፊደል ይጀምራል።

ሕይወቴ ከአፈር ጋር ተጣብቃለች
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) በቶሎ እንደሚሞት አሰበ፣ ወይም 2) በጣም ስላዘነ በአፈር ላይ ተኛ፣ ወይም 3) በምድር ላይ ያሉ ከንቱ ነገሮች እንደ ተመኘ ተገነዘበ።

በቃልህ ሕይወት ስጠኝ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። እዚህ ላይ “ሕይወት” ማለት ተፈጥሮአዊ ሕይወት ሳይህን ዓላማ ያለው እና አስፈላጊ የሆነ ሕይወትን የሚያመለክት ነው።

በቃልህ
“እንደ ተስፋ ቃልህ”

የእኔ መንገዶች
አንድ ሰው የሚያደርገው ወይም ባህሪው እንደ ጎዳና ወይም እንደ መንገድ ተደርጎ ተነግሮአል። “ያደረግኩት”

Psalms 119:27

አስደናቂ ትምህርቶች
“አስገራሚ ትምህርቶች”

በሐዘን
“በጣም ስለ አዘንሁ”

አበርታኝ
“አበረታታኝ።” ይህ አካላዊ ጥንካሬን ወይም መንፈሳዊ ጥንካሬን ሊያመለክት ይችላል።

Psalms 119:29

የማታለልን መንገድ ከእኔ አርቅ
እዚህ ላይ “መንገድ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ባህሪን ነው። “የአታላይነትን መንገድ ከመከተል ጠብቀኝ” ወይም “ከመታለል ጠብቀኝ”

ማታለል
x

Psalms 119:31

ከቃል ኪዳን ድንጋጌዎችህ ጋር ተጣብቄአለሁ
እነርሱን አጥብቆ መያዝ የሚያመለክተው እነርሱን ለመታዘዝ ቁርጠኛ መሆንን ነው። “የቃል ኪዳንህን ድንጋጌ አጥብቄ እይዛለሁ” ወይም “የቃል ኪዳን ድንጋጌዎችህን ለመታዘዝ ቁርጠኛ ነኝ”

የቃል ኪዳን ድንጋጌዎች
ይህ የሙሴን ሕግ ያመለክታል።

በትእዛዝህ መንገድ እሮጣለሁ
ጸሐፊው የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ለመታዘዝ ማተኮርና ቁርጠኛ መሆንን ልክ አንድ ሯጭ በመሮጫያው ላይ አተኩሮ እንደሚሮጥ ነው። “ትዕዛዛትህን ለመታዘዝ ቁርጠኛ ነኝ”

ልቤን አስፋው
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) “ስለ ትእዛዛትህ የበለጠ ግንዛቤ እንዳገኝ እርዳኝ” ወይም 2) “ትእዛዛትህን ለመታዘዝ ትልቅ ፍላጎት ስጠኝ”

Psalms 119:33

ሔ
ይህ የዕብራይስጥ ፊደላት አምስተኛው የፊደል ስም ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ ከቁጥር 33-40 ያሉት እያንዳንዱ መስመር በዚህ ፊደል ይጀምራል።

ሕጎችህ
ይህ የሙሴ ሕግ የሚገለጽበት ሌላው መንገድ ነው።

እስከ መጨረሻ
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) “ሙሉ በሙሉ” ወይም 2) “እስከ ሕይወቴ መጨረሻ” ወይም 3) “እስከ ዘመን መጨረሻ።”

ሕግህን መጠበቅ
“ሕግህን መታዘዝ”

በሙሉ ልቤ እመለከተዋለሁ
“ሕግህን በእርግጥ አከብራለሁ” ወይም “ሕግህ የሚለውን ሙሉ በሙሉ ለማድረግ ቁርጠኛ ነኝ”

በሙሉ ልቤ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። “በሙሉ ማንነቴ” ወይም “በውስጤ ባለው ነገር ሁሉ” ወይም “በቅን ልቦና”

Psalms 119:35

በትእዛዝህ መንገድ ምራኝ
“እንደ ትእዛዛትህ ምራኝ” ወይም “ትእዛዛትህን እንድታዘዝ አስተምረኝ።” የእግዚአብሔር ትእዛዛት አንድ ሰው እግዚአብሔርን በመታዘዝ ከሚራመድበት መንገድ ጋር ይነጻጸራሉ።

ልቤን አዘንብል
ይህ ፈሊጣዊ አባባል ነው። “ልብ” የሚያመለክተው የአንድን ሰው ሕይወት የሚመሩ ፍላጎቶችን፣ ምኞቶችን እና ምርጫዎችን ነው። “እንደፈልግ አድርገኝ”

የቃል ኪዳንህ ድንጋጌዎች
“የቃል ኪዳንህን ድንጋጌዎች እንድታዘዝ።” ይህ የሙሴን ሕግ መታዘዝን ያመለክታል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በጽድቅ ያልሆነ ትርፍ
“የብልጽግና ምኞት።” ይህ የሚያመለክተው ሕገ-ወጥ በሆኑ መንገዶች ወይም በሌሎች ላይ በደልን በማድረግ የሚገኝ ሀብትን ነው።

Psalms 119:37

ዓይኖቼን ከንቱ ነገሮችን ከማየት መልስ
ይህ ዘላለማዊ ዋጋ የሌላቸውን ነገሮች መመኘትን የሚያመለክት ምሳሌያዊ አነጋገር ነው።

በመንገዶችህ አነቃቃኝ
“አንተ እንድኖር እንደምትፈልገው መኖር እንድችል አድርገኝ”

አነቃቃኝ
“ሕይወቴን አበርታት” ወይም “ብርታት ስጠኝ”

አንተን ላከበሩህ የገባኸውን ቃል ኪዳን ለባሪያህም አድርግለት
“ለሚያከብሩህ ሁሉ ለማድረግ የገባኸውን ቃል ኪዳን ለባሪያህም አድርግለት”

ባሪያህ
ጸሐፊው ትህትናውን ለማሳየት ራሱን የእግዚአብሔር ባሪያ እንደ ሆነ ያመለክታል። “እኔ የአንተ ባሪያ”

Psalms 119:39

እፈራለሁ
“እኔ በጣም ፈርቻለሁ”

የጽድቅ ፍርዶችህ መልካም ናቸው
እግዚአብሔር በትክክል ይፈርዳል ውሳኔዎቹም መልካም ናቸው። “ፍርዶችህ ጽድቅና መልካም ናቸው”

ተመልከት
ይህ ሁኔታን መገንዘብን ያሳያል። ትኩረቱ ከመመልከት ይልቅ በእውቀት ወይም በማስተዋል ላይ ነው።

ትእዛዛትህን እናፍቃለሁ
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) “የአንተን ትእዛዛት ለማወቅ በጣም እፈልጋለሁ” ወይም 2) “ያስተማረከንን ለመታዘዝ በጣም እፈልጋለሁ።”

በጽድቅህ ሕያው አድርገኝ
“ጽድቅ” የሚለው ቃል ቀጥተኛ ያልሆነ ትርጉም ያለው ሲሆን ጻድቅ መሆንን ያመለክታል። “ጻድቅ ስለ ሆንህ ሕያው አድርገኝ”

አነቃቃኝ
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) “ሕያው አድርገኝ” ወይም 2) “አበርታኝ።”

Psalms 119:43

የእውነትን ቃል ከአፌ አትውሰድ
እዚህ ላይ ጸሐፊው “በአፉ” ተወክሏል። ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች፦ 1) “ስለ እውነት መልእክትን ከመናገር ፈጽሞ አታርቀኝ” ወይም 2) “እውነተኛውን መልእክት ከመናገር ፈጽመህ አታርቀኝ።”፡

አከብራለሁ
“እታዘዛለሁ”

Psalms 119:45

እኔ በደህንነት እሄዳለሁ
በደህንነት መመላለስ የአንድን ሰው ሕይወት በደህንነት መኖር ነው። “በእግዚአብሔር በደህንነት እኖራለሁ”

ትእዛዛትህን እፈልጋለሁ
“መፈለግ” ማለት አንድ ሰው ሊያያቸው እንደሚችል የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ማስተዋል ወይም መረዳት ነው።

በነገሥታት ፊት የጠበቀ ትእዛዝ
“ለነገሥታት ከባድ ትእዛዛት” ወይም “ለነገሥታት የሚሰጡ መመሪያዎች”

Psalms 119:47

በትእዛዛትህ ደስ ይለኛል
x

Psalms 119:49

ዛይ
ይህ የዕብራይስጥ ፊደላት ሰባተኛ የፊደል ስም ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ ከቁጥር 49-56 ያሉት እያንዳንዱ መስመር በዚህ ፊደል ይጀምራል።

ቃል ኪዳንህን አስታውስ
ቃል ኪዳንህን አስታውስ። በመዝሙር 20:3 ውስጥ ይህንን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

በስቃዬ ጊዜ መጽናኛዬ ይህ ነው - ቃል ኪዳንህ ሕያው አድርጎኛል
ይህ ክፍል እንደገና ቀለል ባለ ሁኔታ ሊጻፍ ይችላል። “ለመጽናናቴ ምክንያት የሆነው ቃል ኪዳንህ በስቃዬ ውስጥ ሕያው ስላደረገኝ ነው”

Psalms 119:51

ኩራተኞች
ይህ የስሜታዊ መግለጫ ጽሑፍ እንደ አንድ ቅፅል ተደርጎ ሊገለጽ ይችላል። “ኩሩ ሰዎች”

ማፌዝ
በአንድ ሰው ላይ ማፌዝ ወይም ዝቅ አድርጎ መመልከት፣ መጠራጠር ወይም አለማክበር

ከጥንት ጊዜያት ጀምሮ
ይህ ድንጋጌዎቹና ሕጉ ለሙሴ ከብዙ ዓመታት በፊት መሰጠታቸውን የሚያመለክት ነው።

Psalms 119:53

ከፍተኛ ንዴት ያዘኝ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። እዚህ ላይ ቁጣ አንድን ግለሰብ እንደ ያዘ ሰው ተደርጎ ተገልጾአል። “በጣም ተናደድኩ”

ትእዛዛትህ መዝሙሮቼ ናቸው
“ትእዛዛትህን ለመዝሙሮቼ እንደ ግጥም ትጠቅሜአለሁ” ወይም “ከመግለጫዎችህ መዝሙሮችን ደርሻለሁ”

Psalms 119:57

ሔት
ይህ የዕብራይስጥ ፊደላት ስምንተኛ የፊደል ስም ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ ከቁጥር 57-64 ያሉት እያንዳንዱ መስመር በዚህ ፊደል ይጀምራል።

እግዚአብሔር እድል ፈንታዬ ነው
ይህ ማለት ዋናው የሚፈልገው እግዚአብሔርን ነው ማለት ነው። ሌዋውያኑ ለጌታ ሰፊ መሬት ርስት እንዳልተቀበሉ፣ ጸሐፊውም ለሚያስፈልገው ነገር ሁሉ እግዚአብሔር እርካታው እንደሆነ ይናገራል።

Psalms 119:59

እግሮቼን መለሰ
እዚህ ላይ “እግሮች” መላውን ሰው ይወክላሉ። ንስሐ መግባት እና የእግዚአብሔርን ሕግ ለመታዘዝ መምረጥ እግርን ወደ ሌላ አቅጣጫ ከመሄድ መመለስ ነው። “አቅጣጫዬን ቀይሬያለሁ”

እፈጥናለሁ አልዘገይምም
እግዚአብሔር የሰጠውን ትእዛዝ የመታዘዝን አስፈላጊነት ለማጉላት ጸሐፊው ተመሳሳይ ሀሳብ በአዎንታዊ እና በአሉታዊ መልኩ ገልጾታል።

Psalms 119:61

የክፉዎች ገመድ ተበተበኝ
በዚህ ምሳሌያዊ አባባል፣ ኃጢአተኞች ወይም ክፉ ሰዎች አደን የሚያድን ሰው አንድን እንስሳ በወጥመድ ለመያዝ እንደሚፈልግ ጸሐፊውን ኃጢአት እንዲሠራ ለማድረግ ሞክረዋል። “ጠላቶቼ እኔን ለመያዝ ሞክረዋል”

Psalms 119:63

እኔ ለሚያከብሩህ ሁሉ ባልንጀራ ነኝ
“ለሚያከብሩህ ሁሉ ጓደኛ ነኝ”

Psalms 119:65

ጤት
ይህ የዕብራይስጥ ፊደላት ዘጠነኛው የፊደል ስም ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ ከ65-72 ያሉት ቁጥሮች እያንዳንዱ መስመር በዚህ ፊደል ይጀምራል።

ለባሪያህ
ጸሐፊው ራሱን “የአንተ ባሪያ” ብሎ ጠርቶታል። “ለእኔ ለባሪያህ” ወይም “ለእኔ”

በቃልህ አማካይነት
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። “ቃልህ” እግዚአብሔር ለጸሐፊው የገባውን ቃል ኪዳን ያመለክታል። “ቃል እንደገባኸው”

በትእዛዝህ ታምኛለሁና ትክክለኛ መረዳትንና ማስተዋልን አስተምረኝ
አንዳንድ ቋንቋዎች አመክንዮአዊ እድገት ለውጥ ይጠይቁ ይሆናል። “በትእዛዛትህ ስለ አመንሁኝ፣ ትክክለኛ መረዳትንና ማስተዋልን አስተምረኝ”

Psalms 119:67

እኔ ከመሰቃየቴ በፊት
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “ሳታሰቃየኝ በፊት” ወይም “ሳትቀጣኝ በፊት”

በስሕተት መንገድ ሄጃለሁ
እግዚአብሔር አለመታዘዝ ግለሰቡ በተሳሳተ ጎዳና ላይ እንደሄደ ተደርጎ ተገልጿል። “እንተን አልታዘዝኩም”

ቃልህን አከብራለሁ
እዚህ ላይ “ቃል” የሚለው ትእዛዛትን ይወክላል። “ትእዛዛትህን እታዘዛለሁ”

Psalms 119:69

እብሪተኞች
ይህ የስሜታዊ መግለጫ ጽሑፍ እንደ አንድ ገላጭ ተደርጎ ሊገለጽ ይችላል። “እብሪተኛ ሰዎች”

በሐሰት የተሞሉ
ስለ አንድ ሰው ብዙ ሐሰት የሚናገሩ ሰዎች ስለ እርሱ ውሸትን በማሰራጨት ሰውየውን እንደሚያቆሽሹት ተነግሯል።

በሙሉ ልቤ
እዚህ ላይ “ልብ” የሰውን ፈቃድ ይወክላል። “በሙሉ ቁርጠኝነት” ወይም “ሙሉ በሙሉ”

ልባቸው ደንድኖአል
እዚህ ላይ “ልብ” የሕዝቡን ፈቃድ ይወክላል። ግትር የሆነ ሰው ልቡ ወይም ፈቃዱ እንደ ዐለት ጠንካራ እንደሆነ ተደርጎ ይገለጿል። “እነርሱ ግትር ናቸው”

Psalms 119:73

ዮድ
ይህ የዕብራይስጥ ፊደላት አሥረኛው የፊደል ስም ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ ከ73-80 ያሉት እያንዳንዱ መስመር በዚህ ፊደል ይጀምራል።

እጆችህ ሠሩኝ አበጃጁኝም
እግዚአብሔር አንድን ሰው መፍጠሩ ልክ ሸክላ ሠሪ አንድን ዕቃ እንደሚቀርጸው እንዲሁ እግዚአብሔር ሰውን ከጭቃ እንዳበጀው ተገልጾአል።

እጆችህ
እዚህ ላይ “እጆች” የእግዚአብሔርን ኃይል ወይም ተግባር ይወክላሉ። “አንተ”

በቃልህ ተስፋ አደርጋለሁና
“አንተ ያልከውን አምናለሁ” ወይም “የተናገርከውን በእርግጠኝነት አምናለሁ”

Psalms 119:75

በታማኝነት አሰቃየኸን
እግዚአብሔር ጻድቁን እንደሚክሰው እንዲሁም ተላላፊዎችን እንደሚቀጣቸው ሊያደርግ ያቀደውን ለማድረግ ታማኝ መሆኑን ቃል ገብቷል፤ “ታማኝነት” የሚለው ረቂት ስም ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል። “አንተ ታማኝ ስለሆንክ ቀጣኸኝ”

የቃል ኪዳንህ ታማኝነት ያጽናናኝ
“ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል። “ለቃል ኪዳንህ ታማኝ መሆንህን በማሳየት አጽናናኸኝ”

ባሪያህ
ጸሐፊው ራሱን “ባሪያ” ብሎ ጠርቶታል። “እኔ የአንተ ባሪያ” ወይም “እኔ”

Psalms 119:77

ኩራተኞች ይፍሩ
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “ትዕቢተኞችን አሳፍራቸው” ወይም “ኩራተኞችን እዲያፍሩ አድርጋቸው”

ኩራተኞች
ይህ የስሜታዊ መግለጫ ጽሑፍ እንደ አንድ ገላጭ ተደርጎ ሊገለጽ ይችላል። “ኩሩ ሰዎች” ወይም “ኩራተኛ የሆኑ ሰዎች”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 119:79

ወደ እኔ ይመለሱ
ለጸሐፊው በወዳጅነት የሚመለሱ ሰዎች በአካል ወደ እርሱ ዘወር እንደሚሉ ተገልጿል። “ወደ እኔ ኑ” ወይም “ከእኔ ጋር አንድ ሁኑ”

የቃል ኪዳን ድንጋጌዎችህን የሚያውቁ
x

Psalms 119:81

ካፍ
ይህ የዕብራይስጥ ፊደላት አሥራ አንደኛው የፊደል ስም ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ ከ81-88 ያሉት እያንዳንዱ መስመር በዚህ ፊደል ይጀምራል።

በቃልህ ተስፋ አደርጋለሁ
“በተናገርከው ላይ ሙሉ በሙሉ አምናለሁ”

ዐይኖቼ ተስፋይን ለማየት ይናፍቃሉ
እዚህ ላይ “ዐይን” መላውን ሰው ይወክላል። “አንተ ለማድረግ ቃል የገባኸውን እንድታደርግ እኔ እጠብቃለሁ”

Psalms 119:83

በጭስ እንዳለ የወይን አቁማዳ ሆኛለሁ
በጭስ በተሞላ ቦታ የወይን አቁማዳ ለረጅም ጊዜ ሲሰቀል ይበላሻል። ጸሐፊው ራሱን በጭስ ከተበላሸ የወይን አቁማዳ ጋር በማነጻጸር የማይረባ ሆኖ እንደ ተሰማው አድርጎ ይናገራል።

ባሪያህ ይህንን እስከ መቼ ይታገሳል? በሚያሳድዱኝ ላይ መቼ ትፈርዳለህ?
ጸሐፊው የሚያሳድዱትን እግዚአብሔር እንዲቀጣቸው ጥያቄ ያቀርባል። ይህ የአጻጻፍ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። “እባክህ ከአሁን በኋላ ብዙ እንዳልጠብቅ አድርገኝ። “የሚያሳድዱኝን ቅጣቸው።”

የአንተ ባሪያ
ጸሐፊው ራሱን “የአንተ ባሪያ” ብሎ ጠርቷል። “እኔ ባሪያ እሆናለሁ” ወይም “ማድረግ አለብኝ”

Psalms 119:85

ኩራተኞች ጉድጓድ ቆፈሩብኝ
ኩራተኞች ጸሐፊውን ለመያዝ ወይም ስህተት እንዲሠራ ለማድረግ እየፈለጉ ነው። ይህ ጸሐፊውን እንደ እንስሳ ለማጥመድ ጉድጓድ የሚቆፍሩ አደን አዳኞች እንደሆኑ ተደርጎ ይገለጻል።

ኩራተኞች
ይህ የስሜታዊ መግለጫ ጽሑፍ እንደ አንድ ቅፅል ተደርጎ ሊገለጽ ይችላል። “ኩራተኛ ሰዎች” ወይም “ኩራተኛ የሆኑ”

Psalms 119:87

እነርሱ ለእኔ በምድር ላይ ፍጻሜን ሊያደርጉ ተቃርበዋል
ይህ ሌላን ሰው ስለ መግደል ትህትና በተሞላበት መንገድ የሚገልጽ ነው። “ሊገድሉኝ ተቃርበው ነበር”

በጽኑ ፍቅርህ
“እንደ ጽኑ ፍቅርህ።” “ጽኑ ፍቅር” ወይም “ታማኝነት” የሚለው ሐረግ እንደ ተውሳከ ግስ ሊገለጽ ይችላል። “አንተ በታማኝነት ስለ ወደድኸኝ”

Psalms 119:89

ላሜድ
x

Psalms 119:91

ሁሉም ነገሮች የአንተ አገልጋዮች ናቸው
ሁሉም የተፈጠሩ ነገሮች እንደ ሰዎች እግዚአብሔርን ማገልገል የሚችሉ እንደሆኑ ተደርገው ተነግሯል። “ሁሉም ነገሮች ያገለግልሃል” ወይም “ሁሉም ነገሮች የአንተን ትእዛዝ ይታዘዛሉ”

Psalms 119:93

መቼም አልረሳም
ይህ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። “እኔ ሁልጊዜ አስታውሳለሁ”

በእነርሱ አማካይነት በሕይወት ጠበቅኸኝ
ጸሐፊው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንደሚታዘዝ ያመለክታል። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልፅ ሊደረግ ይችላል። “ትእዛዛትህን ስለ ታዘዝኸቸው በሕይወት ጠበቅኸኝ”

ትእዛዛትህን ፈልጌአለሁና
የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ለመታዘዝ በጣም መፈለግ አንድ ሰው አንድን ዕቃ በብርቱ እንደሚፈልገው አይነት እንደሆነ ተነግሮአል።

Psalms 119:95

መረዳትን እፈልጋለሁ
“ለመረዳት ጠንክሬ እሞክራለሁ”

ሁሉም ነገር የራሱ የሆነ ገደብ አለው
“ሁሉ ነገር መጨረሻ አለው”

የአንተ ትእዛዛት ግን ገደብ የሌለው ሰፊ ነው
የእግዚአብሔር ትእዛዛት ሁል ጊዜም እውነተኛ እና ፍፁም መሆናቸውን ሲናገር የእግዚአብሔር ትእዛዛት ልክ እንደ አንድ ገደብ እንደሌለው እንደማያቆም ነገር አድርጎ ነው። “ትእዛዛትህ ግን ያለገደብ ናቸው” ወይም “ትእዛዛትህ ግን ዘላለማዊ ናቸው”

Psalms 119:97

ሜም
ይህ የዕብራይስጥ ፊደላት አሥራ ሦስተኛው የፊደል ስም ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ ከቁጥር 97-104 ያሉት እያንዳንዱ መስመር በዚህ ፊደል ይጀምራል።

ትእዛዛትህ ሁልጊዜ ከእኔ ጋር ናቸው
ስለ እግዚአብሔር ትእዛዛት ያለማቋረጥ ማሰቡን ጸሐፊው ሲገልጽ ትእዛዞቹን ከእርሱ ጋር ሁልጊዜ እንደሚጠብቃቸው ዕቃዎች አድርጎ ነው።

Psalms 119:101

እግሮቼን ከማንኛውም መጥፎ ጎዳና እጠብቃለሁ
ክፉ ነገሮች ማድረግን ማስወገድ በፉ ጎዳናዎች ላይ መራመድን እንደ ማስወገድ ይቆጠራል። “ክፉ ነገሮች ማድረግን አስወግጄአለሁ”

እግሮቼን ጠበቅሁ
እዚህ ላይ “እግሮች” መላውን ሰው ይወክላሉ። “ራሴን ጠበቅሁ”

ቃልህን ጠብቅሁ
“ቃልህን ታዘዝሁ” ወይም “ትእዛዛትህን ጠብቅሁ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከአንተ የጽድቅ ድንጋጌዎች ራሴን አላራቅሁም
የእግዚአብሔርን የጽድቅ ሕግጋት መታዘዝ መቀጠሉ ጸሐፊው በአካል ከጻድቁ ድንጋጌዎች እንዳልራቀ ተደርጎ ተገልጾአል። ይህ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። “እኔ ሁልጊዜ የጽድቅ ድንጋጌዎችህን እታዘዛለሁ”

Psalms 119:103

ቃልህ ለአፌ ጣፋጭ ነው፣ አዎ እንደ ማር ጣፋጭ ነው!
ጸሐፊው እግዚአብሔር በተናገረው ደስተኛ መሆኑን ሲገልጽ፣ የእግዚአብሔር ቃሎች እንደ ጣፋጭ ጣዕም ያለው ምግብ እንደሆኑለት ተናግሮአል። “ቃሎችህ መልካም እና የሚያስደስቱ ናቸው!”

ማስተዋልን አግኝቻለሁ
“ማስተዋል” የተባለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊገለጽ ይችላል። “ትክክል የሆነውን ማስተዋል ተማርኩ”

ስለዚህ ሁሉንም የሐሰት መንገድ ጠላሁ
መጥፎ ባህሪ እንደ ሐሰት መንገድ ወይም ጎዳና ተብሎ ተነግሮአል።

Psalms 119:105

ኖን
ይህ የዕብራይስጥ ፊደላት አሥራ አራተኛው የፊደል ስም ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ ከቁጥር 105 እስከ 112 ያሉት እያንዳንዱ መስመር በዚህ ፊደል ይጀምራል።

ቃልህ ለእግሬ መብራት፣ ለመንገዴም ብርሃን ነው
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። የሚናገሩትም እግዚአብሔር አንድ ሰው እንዴት መመላለስ እንዳለበት እንደነገረው ልክ ሰውየው በመንገድ ላይ ሲሄድ ቃሉ እንደ ብርሃን እንደሚሆንለት ወዴትም መሄድ እንዳለበት እንደሚመራው አድርጎ ነው። “ቃልህ ሕይወቴን እንዴት መምራት እንዳለብኝ ይነግረኛል”

ቃልህ
እዚህ ላይ “ቃል” የሚወክለው እግዚአብሔር ለሰዎች ያስተላለፈውን መልእክት ሁሉ ነው።

Psalms 119:107

በቃልህ እንደ ገባኸው ቃልኪዳን
x

Psalms 119:109

ሕይወቴ ሁል ጊዜ በእጄ ውስጥ ነው
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው የደራሲው ሕይወት ሁል ጊዜ አደጋ ላይ ነው ማለት ነው። “ጠላቶቼ ብዙውን ጊዜ ሊገድሉኝ ይሞክራሉ”

ሕግህን አልረሳም
ይህ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። “ሕግህን ሁል ጊዜ አስታውሳለሁ”

ክፉዎች ወጥመድ አዘጋጅተውብኛል
ጸሐፊውን ለመያዝ እና ለመግደል የሚሞክሩ ክፉ ሰዎች እንስሳትን ለመያዝ ወጥመድ እንዳደረጉ የአደን ሰዎች እንደሆኑ ተደርገው ተገልጿል።

ክፉዎች
ይህ የስሜታዊ መግለጫ ጽሑፍ እንደ አንድ ቅፅል ተደርጎ ሊገለጽ ይችላል። “ክፉ ሰዎች”

ከትእዛዛትህ አልራቅሁም
የእግዚአብሔርን ትእዛዛት አለማድረግን እንቢ ማለት ጸሐፊው ከእግዚአብሔር ትእዛዛት አልራቀም ማለት ነው። ይህ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። “ትእዛዛትህን እታዘዛለሁ”

Psalms 119:111

የቃል ኪዳኖችህን ድንጋጌዎች ለዘላለም እንደ ርስቴ እቆጥራለሁ
ጸሐፊው ሁል ጊዜ የእግዚአብሔርን ድንጋጌዎች እንደሚወድና እንደሚታዘዝ የገለጸው ልክ ድንጋጌዎቹን እንደ መሬት እና እንደ ንብረት እንደሚወርሳቸው አድርጎ ነው። “ሕጎችህ ለዘላለም የእኔ ናቸው” ወይም “የቃል ኪዳን ድንጋጌዎችህ ለእኔ ለዘላለም እንደምጠብቃቸው ርስቶቼ ናቸው”

እነርሱ የልቤ ደስታ ናቸው
እዚህ ላይ “ልብ” የሰውን ሁለንተና ይወክላል። “ደስ ያሰኙኛል” ወይም “በእነርሱ ደስ ይለኛል”

ልቤ ለመታዘዝ ዝግጁ ነው
እዚህ ላይ “ልብ” የጸሐፊውን ፈቃድ ይወክላል። “ልብ ዝግጁ ነው” የሚለው ሐረግ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ጸሐፊው ቁርጠኛ መሆኑን የሚናገርበት መንገድ ነው። “ለመታዘዝ ቁርጠኛ ነኝ”

እስከ መጨረሻው
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) “እያንዳንዳቸውም” 2) “እስከ ሕይወቴ መጨረሻ” ወይም 3) “እስከ ፍጻሜው ዘመን”

Psalms 119:113

ሳምኬት
ይህ የዕብራይስጥ ፊደላት አሥራ አምስተኛው የፊደል ስም ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ ቁጥር 113-120 ያለው እያንዳንዱ መስመር በዚህ ፊደል ይጀምራል።

ሁለት አሳብ ያላቸው
እግዚአብሔርን ለመታዘዝ እውነተኛና ቆራጥ ያልሆነ ሰው ሁለት አሳብ እንዳለው ተደርጎ ተገልጿል። “ሙሉ በሙሉ ለመታዘዝ ፈቃደኛ ያልሆኑ” ወይም “ከልብ ያለሆኑ”

መሸሸጊያዬ
እግዚአብሔር ጸሐፊውን በደህንነት እንደ ጠበቀው ሲገልጽ እግዚአብሔር እንደ መሸሸጊያ እንደ ሆነለት እና እርሱም በዚያ ሄዶ እንደሚሸሸግ በመግለጽ ነው።

ጋሻዬ
እግዚአብሔር ጸሐፊውን እንደ ጠበቀው የተገለጸው እግዚአብሔር ለጸሐፊው ጋሻ እንደ ሆን በመግለጽ ነው።

በቃልህ ተስፋ አደርጋለሁ
እዚህ ላይ “መጠበቅ” ማለት በተስፋ መጠባበቅ ማለት ነው። ይህ የተስፋ እና የመታመን ሀሳብ አለው። “በቃልህ እታመናለሁ”

ቃልህ
x

Psalms 119:115

በቃልህ አጠንክረኝ
“እንደተናገርከኝ ጥንካሬን ስጠኝ” ወይም “ቃል እንደገባኸው ጠንካራ እንድሆን አስችለኝ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በተስፋዬ አላፍርም
እዚህ ላይ “ተስፋዬ” የሚለው ቃል ጸሐፊው በእግዚአብሔር እና በሰጠው ተስፋዎች ላይ እምነት መጣሉን ያሳያል። ይህ እንደ ሙሉ ዓረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። “ተስፋ አታስቆርጠኝ” ወይም “ልታደርገው ቃል የገባኸውን ባለማድረግ እንዳፍር አታድርገኝ”

Psalms 119:117

ደግፈኝ
“እርዳኝ” ወይም “አበርታኝ”

እነዚያ ሰዎች አታላዮች እና የማይታመኑ ናቸው
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) “እነዚያ ሰዎች ይዋሻሉ ስለሆነም ማንም ሊያምናቸው አይችልም” ወይም 2) “እነዚያ ሰዎች የማታለያ ዕቅዶችን ያቅዳሉ ነገር ግን አይሳካላቸውም”

Psalms 119:119

አንተ ኃጢአተኞችን ሁሉ እንደ ምድር ቆሻሻ ታስወግዳቸዋለህ
ቆሻሻ የሚጣል ነገር ነው፤ ወርቅ ወይም ሌሎች ብረቶች ከነጠሩ በኋላ ከላያቸው የሚወገዱ ነገሮች ቆሻሻ ይባላሉ። እግዚአብሔር ክፉ ሰዎችን እንደ ቆሻሻ ነገር ያስወግዳቸዋል።

ክፉዎች
ይህ የስሜታዊ መግለጫ ጽሑፍ እንደ አንድ ቅፅል ተደርጎ ሊገለጽ ይችላል። “ክፉ ሰዎች”

እንደ ቆሻሻ
“እንደ ቆሻሻ” ወይም “እንደ ቆሻሻ”

አካሌ አንተን በመፍራት ይንቀጠቀጣል
እዚህ ላይ “አካል” የሰውን ሁለንተና ይወክላል።

የጽድቅ ድንጋጌዎችህን እፈራለሁ
ጸሐፊው የእግዚአብሔርን የጽድቅ ድንጋጌዎች የሚፈራበት ምክንያት እግዚአብሔር ድንጋጌዎቹን የማይፈጽሙ ሰዎችን እንደሚቀጣ ስለሚያውቅ ነው። የዚህን መግለጫ ሙሉ ትርጉም በግልፅ ማድረግ ትችላለህ።

Psalms 119:121

ዔ
ይህ የዕብራይስጥ ፊደላት አሥራ ስድስተኛው የፊደል ስም ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ ከቁጥር 121-122 ያሉት እያንዳንዱ መስመር በዚህ ፊደል ይጀምራል።

ለሚያስጨንቁኝ አሳልፈህ አትስጠኝ
“ሰዎች እንዲጨቁኑኝ አትፍቀድላቸው”

ለባሪያ የደህንነት ዋስትና
ጸሐፊው ስለ ራሱ “የአንተ ባሪያ” ብሎ ይናገራል። “ለደህንነቴ ዋስትና” ወይም “ባሪያህን እርዳ ጠብቀኝም”

ኩራተኞቹ
x

Psalms 119:123

ስጠብቅ ዓይኖቼ ደከሙ
እዚህ ላይ “ዐይኖች” የሰውን ሁለንተና ይወክላሉ። “ጠብቄ ጠብቄ ደክሞኛል”

ማዳንህንና የጽድቅ ቃልህን
“መዳን” የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊገለፅ ይችላል። “ለማድረግ እንደ ገባኸው ቃል ታድነኝ ዘንድ”

የጽድቅ ቃልህ
“የጽድቅ ኪዳንህ”

ለባሪያን አሳየው
ጸሐፊው ስለ ራሱ ሲናገር የአንተ “ባሪያ” ይላል። “አሳየኝ” ወይም “እኔን ባሪያህን አሳየኝ” (አንደኛ ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ሰው ተመልከት)

የቃል ኪዳንህን ታማኝነት
“ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ተውሳከ ግስ ወይም እንደ ቅፅል ሊገለጽ ይችላል። “አንተ በታማኝነት ወደኸኛል” ወይም “አንተ ለቃል ኪዳንህ ታማኝ ነህና”

Psalms 119:125

ማስተዋልን ስጠኝ
“ማስተዋል” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊገለፅ ይችላል። “እንዳውቅ የምትፈልገውን እንዳስተውል አስችለልኝ”

እግዚአብሔር እርምጃ የሚወስድበት ጊዜ ነው
ጸሐፊው እግዚአብሔርን እንደ ሦስተኛ ሰው አድርጎ ያነጋግራል። ይህ በሁለተኛ ሰው ሊገለፅ ይችላል። “እግዚአብሔር ሆይ፣ እርምጃ የምትወስድበት ጊዜ አሁን ነው”

ሰዎች ሕግህን ጥሰዋል
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። እዚህ ላይ “ጥሰዋል” ማለት “አልታዘዙም” ማለት ነው። ይህ ማለት ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ሕግ ጥሰዋል ማለት ነው።

Psalms 119:127

ሁሉንም ትእዛዛትህን በጥንቃቄ እከተላለሁ
አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ትእዛዛት በጥንቃቄ የሚታዘዝ ከሆነ ትእዛዛቱ ያንን ሰው ይመሩታል እርሱም ከኋላ ይከተላል ማለት ነው። እኔ ትእዛዛትህን ሁሉ በጥንቃቄ እከተላለሁ”

የሐሰተኝነት መንገድ ሁሉ
መጥፎ ነገር የሚያደርጉ ሰዎች በተሳሳተ ጎዳና ላይ እንደሚጓዙ ይነገራል። “አንዳንድ ሰዎች የሚኖሩበት መጥፎ መንገዶች ሁሉ”

Psalms 119:129

ፌ
ይህ የዕብራይስጥ ፊደላት አሥራ ሰባተኛው የፊደል ስም ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ ከቁጥር 129-136 ያሉት እያንዳንዱ መስመር በዚህ ፊደል ይጀምራል።

የቃልህ መገለጥ ብርሃን ይሰጣል
ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር ቃሎች ሲናገር እንደ ታጠፈ ጨርቅ ሲሆን ነገር ግን ቃሎቹን የሚያብራራ የታጠፈውን ጨርቅ እየከፈተ እንደሚገልጽ አድርጎ ነው። “የቃልህ ማብራሪያ ብርሃን ይሰጣል” ወይም “አንድ ሰው ቃሎችህን ሲያብራራ ብርሃን ይሰጣሉ”

የቃልህ መገለጥ ብርሃን ይሰጣል
ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር ቃሎች ሲናገር ለአንድ ሰው ብርሃንን በማብራት ጥበብን እንደሚሰጡት አድርጎ ይናገራል። “የቃሎችህ ማብራሪያ ለሰዎች ጥበብን ይሰጣሉ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 119:131

ቃልህን በመጠማት አፌን ከፈትሁ ትእዛዛትህን ናፍቄአለሁና
ጸሐፊው ለእግዚአብሔር ቃል ያለውን ፍላጎት ሲገልጽ ልክ የተጠማ ውሻ ውሃን እንደሚፈልግ አድርጎ ነው። “እኔ ከልቤ ትእዛዛትህን እጅግ ናፍቄአለሁ”

ወደ እኔ ተመልከት
ወደ አንድ ሰው መለስ ብሎ መመልከት ለዚያ ሰው ትኩረት መስጠት ማለት ነው። “ለእኔ ትኩረት ስጠኝ”

ስምህን መውደድ
እዚህ ላይ “ስም” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ራሱን ይወክላል። “እወድሃለሁ”

Psalms 119:133

እርምጃዎቼን አቅና
እዚህ ላይ “እርምጃዎች” የሚለው ቃል ጸሐፊውን እየተራመደ እንዳለ ይወክላል። እርሱ ስለሚኖርበት አኗኗር ወይም ስለ ምግባሩ፣ በመንገድ ላይ እንደሚጓዝ ያህል ይናገራል። “ምራኝ” ወይም “እንዴት እንደምኖር አስተምረኝ”

አንድም ኃጢአት አይግዛኝ
ጸሐፊው ስለ ኃጢአት ሲናገር በእርሱ ላይ ሥልጣን እንዳለው ሰው አድርጎ ነው። ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) “ማንኛውንም ኃጢአት እንደ ልማድ እንድሠራ አትተወኝ” ወይም 2) “ኃጢአተኛ ሰዎች እንዲገዙኝ አትፍቀድ”

ከሰው ጭቆና አድነኝ
x

Psalms 119:135

ፊትህ በባሪያህ ላይ አብራ
ጸሐፊው እግዚአብሔር ለእርሱ እንዲያደላለት ሲጠይቅ ልክ እግዚአብሔር ፊቱን በእርሱ ላይ እንደሚያበራለት አድርጎ ነው። “ለባሪያህ መልካምን አድርግ”

የእንባ ዘለላዎች
ጸሐፊው ብዙ ጊዜ እንዳነባ ሲናገር እንባዎቹን እንደ ውሃ ፈሳሽ አድርጎ ይገልጻቸዋል። “ብዙ እንባዎች”

ሕግህን እጠብቃለሁ
“ሕግህን እታዘዛለሁ”

Psalms 119:137

ጻዴ
ይህ የዕብራይስጥ ፊደላት አሥራ ስምንተኛው የፊደል ስም ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ ከቁጥር 137 እስከ 144 ያሉት እያንዳንዱ መስመር በዚህ ፊደል ይጀምራል

የቃል ኪዳን ድንጋጌዎች
ሌሎች ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች “ምስክርነቶች” ወይም “ሕጎች” ናቸው። በመዝሙር 78:5 ውስጥ ይህንን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Psalms 119:139

ንዴት አቃጠለኝ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ሐረጉ የሚገልጸው “እጅግ ተናድጃለሁ” የሚለውን በተጋነነ ሁኔታ ነው።

እጅግ የተፈተነ ነው
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “ቃልህን ብዙ ጊዜ ፈትኜዋለሁ”

ባሪያህ ይወደዋል
ጸሐፊው ራሱን እንደ ሌላ ሰው አድርጎ ይናገራል። “እኔ ባሪያህ ወደድሁ፣” ወይም “እኔ ወደድሁ”

Psalms 119:141

እኔ . . . ተናቅሁ
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “ሰዎች ይንቁኛል”

Psalms 119:143

መከራና ስቃይ አገኙኝ
መዝሙረኛው መከራና ስቃይን ልክ እንደ ሰዎች አድርጎ ይናገራል። “ተጨነቅሁ ተሰቃየሁም” ወይም “አካሌና አእምሮዬ እየተሠቃዩ ነው”

Psalms 119:145

ቆፍ
ይህ የዕብራይስጥ ፊደላት አሥራ ዘጠነኛ የፊደል ስም ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ ከቁጥር 145-152 ያሉት ቁጥሮች በዚህ ፊደል ይጀምራሉ።

በሙሉ ልቤ
መዝሙረኛው መላ ማንነቱን ልቡ ብቻ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። “ሙሉ በሙሉ”

የቃል ኪዳን ድንጋጌዎች
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች፦ “ምስክርነቶች” ወይም “ሕጎች” ናቸው። ይህንን በመዝሙር 78:5 ውስጥ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Psalms 119:149

በቃል ኪዳንህ ታማኝነት
“ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል። “ለቃል ኪዳኖችህ ታማኝ ስለሆንክ”

እነርሱ ከሕግህ የራቁ ናቸው
“ከሕግህ ርቀዋል” ወይም “ለሕጎችህ ትኩረት አይሰጡም”

Psalms 119:151

ትእዛዛትህ ሁሉ የታመኑ ናቸው
“በትእዛዛትህ እታመናለሁ”

የቃል ኪዳን ድንጋጌዎች
ሌሎች ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች “ምስክርነቶች” ወይም “ሕጎች” ናቸው። በመዝሙር 78:5 ውስጥ ይህንን እንዴት እንደተረጎመከው ተመልከት።

በቦታቸው ላይ አስቀምጣቸው
መዝሙረኛው ስለ እግዚአብሔር ትእዛዛት ሲናገር በምድር ላይ እንደ ተለጠፉ አድርጎ ይናገራል። “ሰዎች እንዲታዘዙ የሰጣቸው”

Psalms 119:153

ሬስ
ይህ የዕብራይስጥ ፊደላት ሃያኛው የፊደል ስም ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ ከቁጥር 153 እስከ 160 ያለው እያንዳንዱ መስመር በዚህ ፊደል ይጀምራል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወደ ስቃዬ ተመልከት
መዝሙረኛው ስለ ስቃይ ሲናገር ሰዎች ሊያዩት እንደሚችሉት እቃ እንደሆነ አድርጎ ነው። “ምን ያህል እንደተሠቃየሁ ተመልከት”

ተሟገትልኝ
“የሚከስሱኝን ሰዎች ተሟገታቸው”

ጠብቀኝ
“ሕይወቴን ጠብቅ” ወይም “ሕይወትን ስጠኝ”

Psalms 119:155

መዳን ከክፉዎች የራቀ ነው
እግዚአብሔር ያላዳነው ሰው ድነት ከእርሱ የራቀ ነው። “ድነት” የሚለው ረቂቅ ስም “መዳን” ሊባል ይችላል። “አንተ በእርግጥ ክፉዎችን አታድኑም”

ምሕረት የተሞሉ ድርጊቶችህ ታላቅ ናቸው
እዚህ ላይ “ታላቅ” ማለት “ብዙ” ማለት ነው። “ለሰዎች ምሕረትን ብዙ ጊዜ አደረግህ” ወይም “ብዙ ምሕረት የተሞሉ ነገሮችን አድርገሃል”

አንተ ሁልጊዜ እንደምታደርገው
ሌላ ተቀባይነት ያለው ትርጉም “የምታደርገው ትክክል ስለ ሆነ” ነው።

Psalms 119:157

አሳዳጆቼ
“የሚያሳድዱኝ”

ከዚያ አልራቅሁ
ይህ ፈሊጣዊ አባባል ነው። “መታዘዝን አላቆምሁም” ወይም “ማመንን አላቆምሁም”

የቃል ኪዳን ድንጋጌዎች
ሌሎች ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች “ምስክርነቶች” ወይም “ሕጎች” ናቸው። በመዝሙር 78:5 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።

ከዳተኞች
“ከዳተኞች” የሚለው እንደ ስም ሐረግ ሊተረጎም ይችላል። “ከዳተኞች ሕዝቦች” ወይም “አሳልፎ የሰጡኝ” ወይም “ጠላቶቼ”

አይጠብቁ
“አይታዘዙ”

Psalms 119:159

ተመልከት
“ወደ እኔ ተመልከት ስለዚህ ማየት ትችላለህ”

በቃል ኪዳንህ ታማኝነት
“ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል። “ለቃል ኪዳኖችህ ታማኝ ስለሆንክ”

የቃልህ መሠረት እውነት ነው
“ቃልህ ሙሉ በሙሉ እውነት ነው” ወይም “ቃልህ ሊታመን ይችላል”

Psalms 119:161

ሳን
ይህ የዕብራይስጥ ፊደላት ሐያ አንደኛው የፊደል ስም ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ ከቁጥር 161 እስከ 168 ያሉት እያንዳንዱ መስመር በዚህ ፊደል ይጀምራል።

ልቤ ቃልህን በማድነቅ ቆሟል
መዝሙረኛው ልብ መደነቅ እንደሚችል አድርጎ ይናገራል። ልብ ለመላው ሰውነት ስሜት ማዕከል ነው። “በቃልህ ተገርሜአለሁ”

ዘረፋ
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) ወታደሮች እና ዘራፊዎች በጦርነት ካሸነፏቸው የሚወስዷቸው እቃዎች ወይም 2) ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ወይም “ሀብቶች”።

Psalms 119:163

መጥላት እና መናቅ
x

Psalms 119:165

የሚያሰናክላቸው ምንም ነገር የለም
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) “መጥፎ ነገር እንዲያደርጉ ማንም ተጽእኖ አላደረገባቸውም” ወይም 2) “ችግር እንዲያስከትሉ ያደረጋቸው የለም።”

Psalms 119:167

ጥብቅ ትእዛዛትህን እጠብቃለሁ
“ጥብቅ ትእዛዛትህን ሁሉ እታዘዛለሁ”

ጥልቅ ትእዛዝ
ሌሎች ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች “ምስክርነቶች” ወይም “ሕጎች” ናቸው። ይህንን በመዝሙር 119:2 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

ትእዛዛትህን እጠብቃለሁ
“ትእዛዛትህን እታዘዛለሁ”

Psalms 119:169

ታው
ይህ የዕብራይስጥ ፊደላት ሃያ ሁለተኛ የፊደል ስም ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ ከቁጥር 169 እስከ 176 ያሉት እያንዳንዱ መስመር በዚህ ፊደል ይጀምራል።

በቃልህ ውስጥ ማስተዋልን ስጠኝ
መዝሙረኛው የመረዳት ችሎታን እንደ አንድ ጠንካራ ነገር ገልጾታል። “ቃልህን ለመረዳት እንድችል እርዳኝ”

ልመናዬ በፊትህ ይሁን
መዝሙረኛው በጸሎቱ የሚናገራቸውን ቃላት ለንጉሥ መናገር እንደሚፈለጉ ሰዎች አድርጎ ያቀርባል። “ጸሎቴን ስማ”

Psalms 119:171

ከንፈሮቼ ምስጋናን ያፍልቁ
መዝሙረኛው ከንፈሮቹን እንደ መያዣ ምስጋናውንም ከውስጡ እንደሚወጣ ፈሳሽ አድርጎ ይናገራል። እዚህ ላይ ላይ “ከንፈሮች” የሚለው ቃል መላ ማንነቱን የሚወክል ማዕከል ሆኖ ቀርቧል። “በጣም ላመሰግንህ እፈልጋለሁ”

ምላሴ ይዘምራል
መዝሙረኛው ስለ ምላስ ሲናገር 1) ልክ ሰው እንደ ሆነ አድርጎ ወይም 2) ለመላ ማንነቱ ማዕከል አድርጎ ነው። “እኔ እዘምራለሁ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 119:173

እጅህ ይርዳኝ
እጅ የመላ ሰውነት ማዕከል ነው። “እባክህን እርዳኝ”

መርጠዋል
“ለመታዘዝ መርጠዋል”

ለማዳንህ
“አንተ ልታድነኝ”

ሕግህ ደስታዬ ነው
“ደስታዬ” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊገለፅ ይችላል። “እኔ ሕግህን መታዘዜ በጣም ያስደስተኛል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 120

1 በጨነቀኝ ጊዜ ወደ ያህዌ ተጣራሁ እርሱም መለሰልኝ። **2** ከሐሰተኛ ከንፈር፣ ከአታላይ ምላስም አድነኝ። **3** እናንት አታላዮች እግዚአብሔር እንዴት ይቅጣችሁ፣ ምንስ ቢከፍላችሁ ይሻላል? **4** በተሳለ የጦረኛ ቀስት በግራር ከሰል ፍም ይቀጣችኃል። **5** የምኖረው በሜሼክ ስለ ሆነ የነበርኩትም በቄዳር ድንኳኖች መካከል ስለ ነበር ወየልኝ። **6** ሰላምን ከሚጠሉ ጋር በጣም ረጅም ጊዜ ኖርሁ። **7** እኔ ሰላም ፈላጊ ነኝ። በተናገርሁ ጊዜ ግን እነርሱ ጠብ ይፈልጋሉ።

Psalms 120:1

አጠቃላይ ሃሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው

መዝሙረ መዐርግ
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) “ለማክበር ሕዝቡ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ የዘመሩት መዝሙር ነው።” ወይም 2) “ወደ መቅደሱ ለመግባት ሕዝቡ የዘመሩት መዝሙር ነው” ወይም 3) “ቃላቶቹ እንደ እርምጃ የሆኑ መዝሙሮች ናቸው”።

በተጨነኩ ጊዜ
“በተቸገርኩ ጊዜ” ወይም “ተቸግሬ በነበረበት ጊዜ”

ነፍሴን አድናት
“ነፍሴን” የሚለው ቃል ሙሉ ሰውን ያመለክታል። “አድነኝ”

ከዓመፀኛ ከንፈር ከሸንጋይም አንደበት
“ከንፈር” እና “አንደበት” የሚሉት ቃላት ውሸት የሚናገሩ እና ሸንጋይ ሰዎችን ያመለክታል። “እኔ ላይ ከሚያምፁ እና እኔን ከሚሸነግሉኝ ሰዎች”

Psalms 120:3

ሐሰተኛ አንደበት ሆይ ምን ይከፈልህ ከዚህስ የባሰ ምን ይደረግብህ
ጸሐፊው ይህንን ጥያቄ ለሐሰተኛ አንደበት ላላቸው ሰዎች እግዚአብሔር ምን እንደ ሚያደርግ ያስረዳል። “ሐሰተኛ አንደበት ያላቸችሁ እግዚአብሔር እንዲህ ይቀጣችኋል እና ይህን ደግሞ በእናንተ ላይ ያመጣል።”

ሐሰተኛ አንደበት
“ሐሰተኛ አንደበት” የሚለው ቃል ውሸትን የሚናገርን ሰውን ነው። “ውሸትን የምትናገሩ ሰዎች”

በተሳለ የጦረኛ ቀስት...ይቀጣችኋል
ጸሐፊው እግዚአብሔር ሐሰተኛ ተናጋሪዎችን ልክ በቀስት እንደሚቀጣቸው መስሎ ይናገራል። “እርሱ ልክ እንደ ተሳለ የጦረኛ ቀስት በተደጋጋሚ ይቀጣችኋል”

በግራር ከሰል ፍም ይቀጣሃል
ይህ የሚያመለክተው ሰዎች የቀስት ጫፉን በእሳት ያደርጋሉ። “በግራር ከሰል ፍም አድርጎ”

Psalms 120:5

በሜሼክ እኖራለሁና በቄዳር ድንኳኖች መካከል እቀመጣለሁና
እነዚህ ሁለት ቦታዎች የተራራቁ ቦታዎች ናቸው። ጸሐፊው እነዚህን ስሞች በሰዎች መካከል ክፉ እና ጨካኝ ሰዎች እንዳሉ ለማሳየት ነው። “በሜሼክ እንደምኖር ወይም በቄዳር ድንኳኖች መካከል”

በቄዳር ድንኳኖች
ይህ ሐረግ በድንኳን ውስጥ የሚኖሩትን የቄዳርን ሕዝብን ያመለክታል። “በቄዳር የሚኖሩ ሰዎች”

እኔ ሰላማዊ ነኝ
“እኔ ሰላምን እፈልጋለሁ”

እነርሱ ግን በተናገርሁ ጊዜ ጠብ ይሻሉ
x

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 121

1 ዐይኖቼን ወደ ተራሮች አነሣሁ ረዳቴ ከወዴት ይመጣል? **2** ረዳቴ ሰማይና ምድርን ከሠራ ከያህዌ ዘንድ ይመጣል። **3** እግርህ እንዲንሸራተት አይፈቅድም አንተን የሚጠብቅህም አይተኛም። **4** እነሆ እስራኤልን የሚጠብቅ አይተኛም አያንቀላፉምም። **5** ያህዌ ይጠብቅሃል፤ ያህዌ በቀኝህ በኩል ይከልልሃል። **6** ፀሐይ በቀን አያቃጥልህም ጨረቃም በሌሊት አይጐዳህም። **7** ያህዌ ከክፉ ሁሉ ይጠብቅሃል እርሱ ሕይወትህንም ይጠብቃል። **8** ከአሁን ጀምሮ እስከ ዘላለም ያህዌ በምታደርገው ሁሉ ይጠብቅሃል።

Psalms 121:1

አጠቃላይ ሃሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው

መዝሙረ መዐርግ
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) “ለማክበር ሕዝቡ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ የዘመሩት መዝሙር ነው።” ወይም 2) “ወደ መቅደሱ ለመግባት ሕዝቡ የዘመሩት መዝሙር ነው” ወይም 3) “ቃላቶቹ እንደ እርምጃ የሆኑ መዝሙሮች ናቸው”። በመዝሙረ ዳዊት 120፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

አይኖቼን ወደተራሮች አነሳሁ
ይህ አረፍተ ነገር “መመልከት” ወይም “ትኩረት ማድረግ” እንደሆነ ይናገራል።

ረዳቴ ከወዴት ይምጣ
ጸሐፊው ይህን ጥያቄ ረዳቱ ላይ ትኩረት ማድረግ እንዳለበት ለማሳየት ነው። “ረዳቴ ከወዴት እንደሚመጣ እነግራችኋለሁ”

ረዳቴ ሰማይና ምድርን ከሰራ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።
ይህ የበፊቱን ጥያቄ ይመልሳል።

Psalms 121:3

አጠቃላይ ሃሳብ
እዚህ ጋር ወደ ሌላ ሰው ሲዞር ይመለከታል። ይህም ማለት 1) ጸሐፊው የእሥራኤል ሕዝብ ማናገር ጀመረ ወይም 2) ጸሐፊው ሌላ ሰው ጸሐፊውን እያናገረ እንደ ሆነ ይናገራል።

እግርህን ለመናወጥ
ይህ ከመውደቅ ጋር ያያይዘዋል። “እንድትወድቅ”

የሚጠብቅህም... የሚጠብቅ
እነዚህ ሐረጎች አንድ አይነት ሃሳብ ሲኖራቸው ሁለቱም የእግዚአብሔርን ጠባቂነት አግንኖ ያሳያል።

የሚጠብቅህም አይተኛም
“አይተኛም” ማለት ጥበቃውን ያቆማል። “እግዚአብሔር አይተኛም እና መጠበቁንም አያቆምም” ወይም “እግዚአብሔር ሁልጊዜ ይጠብቅሃል።”

አይተኛም... አይተኛም አያንቀላፋም
እነዚህ ሁለት ሐረጎች አንድ አይነት ሀሳብ አላቸው። ሁለተኛው የመጀመሪያውን ያጠናክረዋል።

እነሆ
ተመልከት ወይም ልብ በል

አይተኛም አያንቀላፋም
x

Psalms 121:5

እግዚአብሔርም በቀኝ እጅህ በኩል ይጋርድሃል።
“ይጋርድሃል” የሚለው ቃል ጥበቃን ያመለክታል። “እግዚአብሔር አንተን ከሚጎዱ ነገሮች ሊጠብቅህ ከአጠገብህ ነው”

በቀኝ እጅህ በኩል
ይህ ሐረግ ከጸሐፊው አጠገብ መሆኑን ያመለክታል።

ፀሐይ በቀን አያቃጥልህም ጨረቃም በሌሊት
“ቀን” እና “ሌሊት” የሚሉት ቃላት በመካከላቸው ያለውን ያመለክታል። “እግዚአብሔር ከሁሉም ነገሮች በማንኛውም ጊዜ ይጠብቅሃል።”

ጨረቃም በሌሊት
ይህ የሚያመለክተው “አንተን አይጎዳህም”። “ጨረቃም በሌሊት አይጎዳህም”

Psalms 121:7

ይጠብቅሃል...ነፍስህንም ይጠብቃታል...እግዚአብሔር መውጣትና መግባትህን ይጠብቃል።
እነዚህ ሦስት ሐረጎች አንድ አይነት ትርጉም አላቸው። ድግምጋሞሹ ሃሳቡን ያጠነክረዋል።

ነፍስህን
ይህ ጸሐፊውን ያመለክታል። “አንተን”

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 122

1 «ወደ ያህዌ ቤት እንሂድ» ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ። **2** ኢየሩሳሌም ሆይ፣ እግሮቻችን በደጆችሽ ውስጥ ቆመዋል። **3** ኢየሩሳሌም በጥንቃቄ የተገነባች ከተማ ናት! **4** ለእስራኤል ምስክር ይሆን ዘንድ ነገዶች፣ የያህዌ ነገዶች ወደዚያ ይወጣሉ። **5** በዚያም የፍርድ ዙፋኖች የዳዊት ቤት ዙፋኖች ተዘርግተዋል። **6** ለኢየሩሳሌም ሰላም ጸልዩ። «የሚወዱሽ ሰላም ይሁንላቸው። **7** በቅጥሮችሽ ውስጥ ሰላም ይሁን በምሽጐችሽም ውስጥ መረጋጋት ይስፈን።» **8** ስለ ወንድሞቼና ስለ ወዳጆቼ ኢየሩሳሌምን፣ «ሰላም ከአንቺ ጋር ይሁን» እላታለሁ። **9** ስለ አምላካችን ያህዌ ቤት መልካም እንዲሆንልሽ እሻለሁ።

Psalms 122:1

አጠቃላይ ሃሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው

መዝሙረ መዐርግ
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) “ለማክበር ሕዝቡ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ የዘመሩት መዝሙር ነው።” ወይም 2) “ወደ መቅደሱ ለመግባት ሕዝቡ የዘመሩት መዝሙር ነው” ወይም 3) “ቃላቶቹ እንደ እርምጃ የሆኑ መዝሙሮች ናቸው”። በመዝሙረ ዳዊት 120፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ኢየሩሳሌም ሆይ እግሮቻችን በአደባባይ ቆሙ
ጸሐፊው ለአድማጮች መናገር አቁሞ ወዲያው ለኢሩሳሌም ከተማ መናገር ጀመረ። ኢየሩሳሌም ጸሐፊውን እንደሚሰማ መስሎ ይናገራል።

እግሮቻችን ከደጆሽ ውስጥ ቆመዋል።
“እግሮቻችን” የሚለው ቃል ሙሉ ሰውን ያመለክታል። “እኛ ቆመናል።”

እንደ ተገጠገጠች ከተማ
ይህ ሙሉ ከተማዋን ያመለክታል። “በኢየሩሳሌም ውስጥ”

Psalms 122:4

የእግዚአብሔርን ስም
“ስም” እግዚአብሔርን ራሱን ያመለክታል። “እግዚአብሔር”

የዳዊት ቤት
“ቤት” የሚለው የዳዊት ልጆችን ያመለክታል። “የዳዊት ልጆች”

Psalms 122:6

አንተን ለሚወድዱ ልማት ...በቅጥርሽም ልማት ይሁን
ይህ ክፍል ጸሐፊው ለአንባቢዎች እንዲፀልዩ የሚፈልገውን የፀሎት ይዘት ነው። የኢየሩሳሌም ከተማን ቀጥታ በመናገር ልክ እንደ ሚሰማው ሰው መስሎ ይናገራል።

ሰለም ይሁን... መረጋጋትም ይስፈን
እነዚህ ሁለት ሐረጎች አንድ አይነት ሀሳብ ሲኖራቸው እርስ በእርስ ለማጠናከር ነው። “በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሕዝቦች ሰላም ይሁንላቸው።”

በቅጥርሽ ላይ....በምሽግሽም
ኢየሩሳሌም በዙሪያዋ ያለውን ቅጥር መስሎ ይናገራል። “ቅጥር” ወይም “ምሽግ” የሚሉት ቃላት አንድ አይነት ሀሳብ አለው። “በኢየሩሳሌም ውስጥ”

Psalms 122:8

አጠቃላይ ሀሳብ
በዚህ ክፍል ጸሐፊው ኢየሩሳሌምን ቀጥታ ሲያናግራት ከተማዋ ልክ እንደ ሰው እንደሚሰማው መስሎ ይናገራል።

ስለ
“ለእነርሱ ስል”

በውስጥሽ ሰላም ይሁን
“በአንቺ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች በውስጠቸው ሰላም ይሁን”

ላንቺ መልከምነትሽን ፈለግሁ
“ሰዎች በመልካም እንዲያዩሽ እፀልያለሁ”

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 123

1 በሰማያት የምትኖር ሆይ፣ ዐይኖቼን ወደ አንተ አነሣለሁ። **2** የባርያዎች ዐይን ወደ ጌታቸው እጅ እንደሚመለከት የባርያዬቱም ዐይን ወደ እመቤቷ እጅ እንደሚመለከት ምሕረት እስኪያደርግልን ድረስ የእኛም ዐይን ወደ አምላካችን ወደ ያህዌ ይመለከታሉ። **3** ያህዌ ሆይ፣ እጅግ ተዋርደናልና ማረን፣ አቤቱ ማረን። **4** በትዕቢተኞች ብዙ ተዋርደናል፣ በትምክሕተኞችም እጅግ ተንቀናል።

Psalms 123:1

አጠቃላይ ሃሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው

መዝሙረ መዐርግ
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) “ለማክበር ሕዝቡ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ የዘመሩት መዝሙር ነው።” ወይም 2) “ወደ መቅደሱ ለመግባት ሕዝቡ የዘመሩት መዝሙር ነው” ወይም 3) “ቃላቶቹ እንደ እርምጃ የሆኑ መዝሙሮች ናቸው”። በመዝሙረ ዳዊት 120፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ዓይኖቼን ወደ አንተ አነሣሁ።
ጸሐፊው አይኖቹን የሚያመለክተው የሚመለከትበት አካሉ ስለሆነ ነው። “ወደ አንተ ተመለከትኩ”

በሰማይ የምትኖር
በዙፋንህ ላይ የተቀመጥህ እና የምትገዛን ንጉሥ

የባሪያዎች አይኖች...የባሪያይቱም አይን...አይናችን ወደ
እነዚህ ሦስት ነገሮች አንድ አይነት ትርጉም ሲኖራቸው ሶስተኛው ሐረግ ስለ እሥራኤላውያን ልክ እንደ ባሪያዎች እነ ባሪያይቱ አለቆቻቸውን እንደሚመለከቱት ጋር ያነፃፅራል። አይኖች የሚለው በሁሉም ሁኔታ ሙሉ ሰውን ያመለክታል።

ጌታቸው እጅ...እመቤትዋ እጅ
x

Psalms 123:3

ማረን
በመዝሙረ ዳዊት 123፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት። “ለኛ ምሕረት እስኪያደርግ”

ጠግበናልና...እጅግ ጠገበች
እነዚህ ሁለት ሐረጎች አንድ አይነት ትርጉም ሲኖረቸው ሁለተኛው የመጀመሪያውን አግንኖ ያሳያል።

ንቀትን እጅግ ጠግበናልና
x

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 124

1 «ያህዌ ከእኛ ጋር ባይሆን ኖሮ» ይበል እስራኤል። **2** ሰዎች በእኛ ላይ በተነሡ ጊዜ ያህዌ ከእኛ ጋር ባይሆን ኖሮ **3** ቁጣቸው በእኛ ላይ በነደደ ጊዜ በሕይወት እያለን በዋጡን ነበር። **4** ጐርፍ በወሰደን፣ ውሃም በሸፈነን ነበር። **5** ብርቱ ማዕበልም ባሰጠመን ነበር **6** በጥርሳቸው እንዲቦጫጭቁን ያልፈቀደ ያህዌ ይባረክ **7** ነፍሳችን እንደ ወፍ ከአዳኝ ወጥመድ አመለጠች ወጥመዱ ተሰበረ እኛም አመለጥን። **8** ሰማይና ምድርን የሠራ ያህዌ ረዳታችን ነው።

Psalms 124:1

አጠቃላይ ሃሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው

መዝሙረ መዐርግ
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) “ለማክበር ሕዝቡ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ የዘመሩት መዝሙር ነው።” ወይም 2) “ወደ መቅደሱ ለመግባት ሕዝቡ የዘመሩት መዝሙር ነው” ወይም 3) “ቃላቶቹ እንደ እርምጃ የሆኑ መዝሙሮች ናቸው”። በመዝሙረ ዳዊት 120፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ባይሆን...ሕያዋን ሳለን በዋጡን ነበር
ይህ የሚያሳየው እግዚአብሔር ከነርሱ ጋር ስለሆነ ያልተፈጠረ ነገርን ነው። “እግዚአብሔር ከኛ ጋር ነበር...ህያዋን ሆነን አይውጡንም”

እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ባይሆን...እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ባይሆን
እነዚህ ሁለት አረፍተ ነገሮች አንድ አይነት ሀሳብ ኣላቸው። “ያለ እግዚአብሔር እርዳታ...ያለ እግዚአብሔር እርዳታ”

ሕያዋን ሳለን በዋጡን ነበር
ይህ ልክ ትልቅ እንስሳ ትንሽን እንስሳ እንደሚውጥ እሥራኤላውያን እንደዚህ ነበር ይሞቱ የነበረው። “ይገድሉን ነበር”

ቁጣቸው በላያችን በነደደ ጊዜ
“ቁጣቸው” የሚለው ቃል የተቆጡትን ጠላቶቻቸውን ያመለክታል። “በእኛ እጅግ በጣም ተቆጥተው ነበር”

Psalms 124:4

አጠቃላይ ሃሳብ
በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች ጸሐፊው የእሥራኤልን ጠላቶች ከ የጎርፍ ውሃ ጋር ያወዳድረዋል።

ጎርፍ ባጥለቀለቀን...በሰጠመን
ከበፊቱ ቁጥር ጋር የቀጠለ ነው። ይህ እግዚአብሔር አብሮአቸው ስለነበረ ያልተፈጠረን ነገር ያስረዳል። “ጎርፉ አላጥለቀለቀንም...አላሰጠመንም”

ጎርፍ...ፈረሰኛው...ደራሽ ውሃም
እነዚህ ሐረጎች አንድ አይነት ትርጉም አለቸው

ባጥለቀለቀን...ባሰጠመን...በወሰደን
እነዚህ ሐረጎች አንድ አይነት ትርጉም አላቸው

ደራሽ ውሃም ጠራርጎ በወሰደን
የጸሐፊው ጠላቶቻቸው ልክ እንደ ደራሽ ውሃ መስሎ ይናገራል። “ጠላቶቻችን በቀላሉ ያሸንፉን ነበር”

ጎርፍ ባጥለቀለቀን
የጸሐፊው ጠላቶቻቸው ልክ እሥራኤላውያንን እንደሚያጥለቀልቅ ጎርፍ መስሎ ይናገራል። “ጠላቶቻችን እኛን ያጥለቀልቁን ነበር።”

ፈረሰኛው ውሃ ባሰመጠን
የጸሐፊው ጠላቶቻቸው ልክ እሥራኤላውያንን እንደ ፈረሰኛ ውሃ መስሎ ይናገራል። “ጠላቶቻችን እኛን ያጠፉን ነበር።”

Psalms 124:6

ለጥርሳቸው ንክሻ ያላደረገ
ጠላቶቻቸው ልክ እሥራኤላውያንን በልቶ እንደ ሚጨርሳቸው የዱር እንስሳ መስሎ ይናገራል። “በዱር እንስሳ እንደ ተበላ ያህል ያጠፉን ነበር”

እንደ ወፍ ከአዳኞች ወጥመድ አመለጠች
ጸሐፊው ከጠላቶቹ ማምለጥን ልክ እሱን ከአዳኞች ወጥመድ እንዳመለጠች ወፍ መስሎ ይናገራል። “ወፍ ከአዳኞች ወጥመድ እንዳመለጠች እኔም ከጠላቶቼ አመለጥኩኝ”

ወጥመድ
ትናንሽ እንስሳትን ወይም ወፎችን ለመያዝ ከገመድ የሚሰራ ነው።

ወጥመድ ተሰበረ
ጸሐፊውን ለመያዝ የጠላት ሴራን መክሸፍ ልክ እንደ ተሰበረ ወጥመድ መስሎ ይናገራል።

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 125

1 በያህዌ የሚተማመኑ ሳትናወጥ ለዘላለም እንደምትኖር የጽዮን ተራራ ናቸው። **2** ተራሮች ኢየሩሳሌምን እንደ ከበቧት ከአሁን ጀምሮ ለዘላለም ያህዌም በሕዝቡ ዙሪያ ነው። **3** ጻድቁ ክፉ እንዳያደርግ የዐመፃ በትረ መንግሥት የጻድቃንን ምድር አይግዛ። **4** ያህዌ ሆይ፣ መልካም ለሆኑ፣ ልባቸውም ቀና ለሆኑት መልካም አድርግ። **5** ወደ ጠማማ መንገዳቸው የሚመለሱትን ግን ያህዌ ከክፉ አድራጊዎች ጋር ያጠፋቸዋል። ሰላም በእስራኤል ላይ ይሁን።

Psalms 125:1

አጠቃላይ ሃሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው

መዝሙረ መዐርግ
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) “ለማክበር ሕዝቡ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ የዘመሩት መዝሙር ነው።” ወይም 2) “ወደ መቅደሱ ለመግባት ሕዝቡ የዘመሩት መዝሙር ነው” ወይም 3) “ቃላቶቹ እንደ እርምጃ የሆኑ መዝሙሮች ናቸው”። በመዝሙረ ዳዊት 120፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

በእግዚአብሔር የታመኑ እንደማይታወክ ለዘላለም እንደሚኖር እንደ ጽዮን ተራራ ናቸው።
በእግዚአብሔር የታመኑ ሰዎች ልክ እነርሱ እንደ ማይነቀሳቀስ የፅዮን ተራራ እንደሆኑ መስሎ ይናገራል።

ተራሮች በኢየሩሳሌም ዙሪያ እንደ ሆኑ፣ ከዛሬ ጀምሮ ለዘላለም እግዚአብሔር በሕዝቡ ዙሪያ ነው።
የእግዚአብሔር ጥበቃ ልክ እንደ እየሩሳሌምን እንደ ከበበ ተራራ መስሎ ይናገራል። ኢየሩሳሌም በብዙ ተራራዎች ተከበው ነበር ይህም ከጥቃት ጠብቋቸው ነበር። “ልክ ተራራ ኢየሩሳሌምን እንደከበባት እና እንደጠበቃት ሁሉ እግዚአብሔር ሕዝቡን ይጠብቃል።”

ከዛሬ ጀምሮ ለዘላለም
ይህ ሐረግ ሁልጊዜ እንደ ሆነ ያለክታል

የክፉዎች በትር
የክፉዎች በትር የመለው ሐረግ የሚያመለክተው የክፉ ሰዎችን ግዛትን ነው። “ክፉ ሰዎች” ወይም “ክፉ መሪዎች”

Psalms 125:4

እግዚአብሔር ሆይ ... መልካም አድርግ።
x

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 126

1 ያህዌ የጽዮንን ምርኮ በመለሰ ጊዜ ሕልም እንጂ፣ እውን አልመሰለንም። **2** በዚያ ጊዜ አፋችን በሣቅ፣ አንደበታችንም በዝማሬ ተሞላ። በዚያ ጊዜ በሕዝቦች መካከል፣ «ያህዌ ታላቅ ነገር አደረገላቸው» ተባለ። **3** ያህዌ ታላቅ ነገር አደረገልን እኛም እጅግ ደስ አለን። **4** ያህዌ ሆይ፣ በኔጌብ እንዳሉ ምንጮች ምርኮአችን መልስ። **5** በእንባ የሚዘሩ በእልልታ ይዘራሉ **6** ዘሩን ተሸክመው እያለቀሱ የተሰማሩ ነዶአቸውን ተሸክመው እልል እያሉ ይመለሳሉ።

Psalms 126:1

አጠቃላይ ሃሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው

መዝሙረ መዐርግ
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) “ለማክበር ሕዝቡ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ የዘመሩት መዝሙር ነው።” ወይም 2) “ወደ መቅደሱ ለመግባት ሕዝቡ የዘመሩት መዝሙር ነው” ወይም 3) “ቃላቶቹ እንደ እርምጃ የሆኑ መዝሙሮች ናቸው”። በመዝሙረ ዳዊት 120፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

የፅዮንን ምርኮ በመለሰ ጊዜ
“ፅዮንን መልሶ በለፀገች”

Psalms 126:2

አፋችንን በሳቅ
ሳቅ የሚለው ቃል ልክ አፋቸው እንደ መያዣ እቃ መስሎ ሳቅ ደግሞ በውስጡ እንዳለ መስሎ ይናገራል። ሳቅ የሚለው የደስታቸው መልስ እንደሆነ ግልፅ አድርጎ ይናገራል። “በደስታ ሳቅን”

አንደበታችን በእልልታ ተሞላ
እልልታ የሚለው ቃል ልክ አንደበታቸው እንደ መያዣ እቃ መስሎ እልልታ ደግሞ በውስጡ እንዳለ መስሎ ይናገራል። “አንደበታችን በእልልታ ተሞላ”

በሕዝቦች መካከል
“በራሳቸው በከተማዋ ሕዝቦች መካከል”።

እግዚአብሔር ታላቅ ነገር አደረገልን እኛም ደስ አለን
“እግዚአብሔር ታላቅ ነገር ስላደረገልን በጣም ደስተኛ ሆንን”

Psalms 126:4

በእንባ የሚዘሩ...እያለቀሱ የተሰማሩ...ነዶአቸውን ተሸክመው ደስ እያላቸው ይመጣሉ
እነዚህ ሁለት ቁጥሮች ተነፃፃሪ ናቸው። ሁለተኛው አረፍተ ነገር ከመጀመሪያው አረፍተ ነገር ጋር ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖረው ብዙ መረጃ ይይዛል።

በእንባ የሚዘሩ
በእንባ የሚዘሩ

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 127

1 ያህዌ ቤትን ካልሠራ ሠራተኞች በከንቱ ይደክማሉ ያህዌ ከተማን ካልጠበቀ ጠባቂ በከንቱ ይተጋል። **2** የዕለት ጉርስ ለማግኘት በመጣር ማለዳ መነሣት፣ አምሽቶም መግባት ከንቱ ነው። ያህዌ ለወዳጆቹ ተኝተው እያለ የሚያስፈልጋቸውን ይሰጣቸዋል። **3** እነሆ ልጆች የያህዌ ስጦታ ናቸው የማሕፀንም ፍሬ የእርሱ ችሮታ ነው። **4** በወጣትነት የተገኙ ልጆች በጦረኛ እጅ እንዳሉ ፍላጾች ናቸው **5** ኮረጆዎቹን በእነዚህ የሞላ ሰው የተባረከ ነው። ከጠላቶቹ ጋር በሚሟገትበት ጊዜ አፍሮ አይገባም።

Psalms 127:1

አጠቃላይ ሃሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው

መዝሙረ መዐርግ
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) “ለማክበር ሕዝቡ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ የዘመሩት መዝሙር ነው።” ወይም 2) “ወደ መቅደሱ ለመግባት ሕዝቡ የዘመሩት መዝሙር ነው” ወይም 3) “ቃላቶቹ እንደ እርምጃ የሆኑ መዝሙሮች ናቸው”። በመዝሙረ ዳዊት 120፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ማልዳችሁ መነሳታችሁ አምሽታችሁም መተኛታችሁ
ታታሪ ሰራተኛ ሰው በብዛት በማለዳ ተነስቶ ማታ አምሽቶ ነው ቤት ሚመለሰው።

የእለት ጉርስ
የእለት ጉርስ የሚለው አንድ ሰው ሁልጊዜ ለመኖር የሚያስፈልገውን ምግብ ያመለክታል። “ተግታችሁ ስሩ የእለት እንጀራ ለማግኘት”

Psalms 127:3

ስጦታ
አንድ ሰው ከቤተሰቡ የሚወርሰው እቃን ያመለክታል። ልጆች ከወላጆቻቸው ውርስን ይቀበላሉ። ውርስ ከወላጅ ወደ ልጅ ይሄዳል። ይህ አረፍተ ነገር ወላጆች ከእግዚአብሔር ልጆችን እንደወረሱ መስሎ ሲናገር እግዚአብሔር ደግሞ ልጆችን የሚሰጠው እርሱ እንደሆነ ይናገራል።

በኃያል እጅ እንዳሉ ፍላጾች፣ የጐልማስነት ልጆች እንዲሁ ናቸው
ፍላፃ ለአንድ ጦረኛ አስፈላጊ ነገር ነው ምክንያቱም እርሱን ይጠብቀዋልና። ልጆች ልክ እንደ ፍላፃ መስሎ ይናገራል። “ብዙ ልጆች መኖራቸው ይጠብቅሃል።”

ኮሮጆዎቹ በእነዚህ የተሞሉ
ኮሮጆ ማለት ፍላፃ መያዣ እቃ ነው። የብዙ ልጆች መኖር ልክ ልጆች እንደ ፍላፃ በኮሮጆ እንዳለ መስሎ ይናገራል። “በልጆች የሞላ ቤት” ወይም “ብዙ ልጆች”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 128

1 ያህዌን የሚፈሩ ሁሉ በመንገዶቹም የሚሄዱ የተባረኩ ናቸው። **2** በእጆችህ ሥራ ደስ ይልሃል ትባረካለህ፤ ይሳካልሃልም። **3** በቤትህ ውስጥ ሚስትህ እንደሚያፈራ ወይን ትሆናለች ልጆችህም በማእድህ ዙሪያ እንደ ወይራ ተክል ይሆናሉ፡ **4** አዎን፣ ያህዌን የሚፈራ እንዲህ ይባረካል። **5** ያህዌ ከጽዮን ይባርክህ በሕይወትህ ዘመን ሁሉ የኢየሩሳሌምን ብልጽግና ያሳይህ። **6** የልጅ ልጆችን ለማየት ያብቃህ እስራኤል ላይ ሰላም ይሁን።

Psalms 128:1

አጠቃላይ ሃሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው

መዝሙረ መዐርግ
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) “ለማክበር ሕዝቡ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ የዘመሩት መዝሙር ነው።” ወይም 2) “ወደ መቅደሱ ለመግባት ሕዝቡ የዘመሩት መዝሙር ነው” ወይም 3) “ቃላቶቹ እንደ እርምጃ የሆኑ መዝሙሮች ናቸው”። በመዝሙረ ዳዊት 120፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

እግዚአብሔርን የሚፈሩት ሁሉ፣ በመንገዶቹም የሚሄዱ ምስጉኖች ናቸው።
ይህ ሐረግ እግዚአብሔር የሚፈሩትን እና የሚያከብሩትን ሁሉ እንደሚባርክ ይናገራል። “እግዚአብሔር የሚፈርቱን ሁሉ ይባርካል።”

የድካምህን ፍሬ
የሰው ልጅ ሥራን ሰርቶ፣ ደክሞ ፍሬውን ያገኛል፣ ‹‹ የሥራህን ውጤት ››

መልካምም ይሆንልሃል።
መልካምም የሚለው ቃል የእግዚአብሄርን ፈቃድ እና ፍላጎት ያሳያል። “እግዚአብሔር ይባርክሃል ደግሞም መልካም ይሆንልሃል።” ወይም “እግዚአብሔር መልካም ያደርግልሃል በረከትንም ያደርግልሃል።”

Psalms 128:3

እንደሚያፈራ ወይን ናት
ሚስት ልክ እንደ ብዙ እንደ ምታፈራ ወይን መስሎ ይናገራል። ይህ ልጆች ፍሬ እንደሆኑ ሲናገር ሚስት ብዙ ልጆች ይኖሯታል። “ፍሬአማ እና ብዙ ልጆች ይሰጣችሁአል”

ልጆችህ በማዕድህ ዙሪያ እንደ ወይራ ቡቃያ ናቸው
ልጆች ከወይራ ቡቃያ ጋር ያወዳድራል ምክንያቱም በሚያድጉበት ቦታ ስለሚከቡት ነው። ልጆች ጠረጴዛውን ይከቡታል ደግሞም ይሞላሙ። “የሚያድጉ እና መልካም የሆኑ ብዙ ልጆች ይኖሯቹኀል”

በማዕድህ ዙሪያ
ይህ ቤተሰብ ተሰብስቦ የሚመገብበትን ቦታ ያመለክታል። በብዛት በአንድ ሰው ማዕድ ተሰብስበው የሚመገቡ በዛ ሰው ሥልጣን ስር ናቸው።

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 129

1 «ከልጅነቴ ጀምሮ ብዙ ጊዜ አስጨነቁኝ» ይበል እስራኤል። **2** በእርግጥ፣ ከልጅነቴ ጀምሮ ብዙ ጊዜ አስጨነቁኝ ይሁን እንጂ አላሸነፉኝም። **3** አራሾች ጀርባዬን አረሱት ትልማቸውንም አስረዘሙት። **4** እግዚአብሔር ጻድቅ ነው የክፉዎችን ገመድ በጣጥሶ ጣለ። **5** ጽዮንን የሚጠሉ ሁሉ ይፈሩ ወደ ኃላቸውም ይመለሱ። **6** ገና ከመብቀሉ እንደሚደርቅ ቤት ጣር ላይ እንዳለ ሣር ይሁኑ። **7** ደግሞ ለዐጫጁ እጁን ለነዶ ሰብሳቢ እቅፉን እንደማይሞላ ነዶ ይሁኑ። **8** መንገድ ዐላፊዎችም፣ «የያህዌ በረከት እናንተ ላይ ይሁን፤ በያህዌ ስም ባረክናችሁ አይበሉ።»

Psalms 129:1

አጠቃላይ ሃሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው

መዝሙረ መዐርግ
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) “ለማክበር ሕዝቡ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ የዘመሩት መዝሙር ነው።” ወይም 2) “ወደ መቅደሱ ለመግባት ሕዝቡ የዘመሩት መዝሙር ነው” ወይም 3) “ቃላቶቹ እንደ እርምጃ የሆኑ መዝሙሮች ናቸው”። በመዝሙረ ዳዊት 120፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ጎጢአተኞች በጀርባዬ ላይ መቱኝ
በግርፋት የሚመጣ ጠባሳ እንደ ሚተረስ መስሎ ይነገረል። ገበሬ በመስመር ሜዳላይ በጥልቁ ያርሳል። “ጠላቶቼ ጀርባዬን ቆራርጠውኛል።”

ጎጢአታቸውን አስረዘሙብኝ
ይህ ከለይ የቀጠለ ሀሳብ ነው። “ጎጢአታቸውን” የሚለው ቃል ገበሬ የሚያርሰው መስመር ነው። “በረጃጅሙ ጀርባዬን ቆራረጡኝ”

Psalms 129:4

የጎጢአተኞችን አንገት ቆረጠ
እሥራኤል በጎጢአተኞች እንደተየ መስሎ ይናገራል። “ከጠላቶቻችን ነፃ አውጥቶናል።”

ወደኋላቸውም ይመለሱ
እግዚአብሔር ይህን ለሚያደርግ አስጠንቅቆ እየተናገረ አደለም። “እግዚአብሔር ያሳፍራቸው ደግሞም ይሸነፉም”

Psalms 129:6

በሰገነት ለይ እንደበቀለ...ነዶዎቹን ለሚሰበስብ
መዝሙረኛው ጠላቶቹ እየሞቱ እንዳሉ እና በቁጥር ማነሳቸውን ይናገራል። እነዚህን ቤት ጠራ ላይ ከሚበቅሉ ለመቁረጥ የሚያስቸግሩ ሳር ጋር ያወዳድራቸዋል። “ይሙቱ ደግሞም ቁጥራቸው ይቀንስ ልክ እንደ ሳር... ነዶዎቹን ለሚሰበስብ”

የእግዚአብሔር በረከት በእናንተ ላይ ይሁን
እግዚአብሔር ይባርካችሁ

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 130

1 ያህዌ ሆይ፣ ከጥልቅ ወደ አንተ እጮኻለሁ። **2** ጌታ ሆይ፣ ምሕረትን ፈልጌ ስጮኽ ድምፄን ስማ ጆሮህንም ወደ እኔ አዘንብል። **3** ያህዌ ሆይ፣ አንተ ኃጢአትን ብትከታተል ኖሮ ማን መቆም ይችል ነበር። **4** ነገር ግን በአንተ ዘንድ ይቅርታ አለ ስለዚህ ልትፈራ ይገባሃል። **5** ያህዌን በትዕግሥት እጠብቃለሁ በቃሉም ተስፋ አደርጋለሁ። **6** ዘብ አዳሪ ንጋትን እንደሚጠብቅ እኔም ጌታን በትዕግሥት እጠብቃለሁ። **7** ያህዌ መሓሪ ነው፤ ይቅር ለማለትም ፈቃደኛ ነው እስራኤል ሆይ፣ ያህዌን ተስፋ አድርግ። **8** እርሱ እስራኤልን ከኃጢአቱ ሁሉ ያድነዋል።

Psalms 130:1

አጠቃላይ ሃሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው

መዝሙረ መዐርግ
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) “ለማክበር ሕዝቡ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ የዘመሩት መዝሙር ነው።” ወይም 2) “ወደ መቅደሱ ለመግባት ሕዝቡ የዘመሩት መዝሙር ነው” ወይም 3) “ቃላቶቹ እንደ እርምጃ የሆኑ መዝሙሮች ናቸው”። በመዝሙረ ዳዊት 120፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

አንተን ከጥልቅ
የጸሐፊውን ሀዘን ልክ እንደ መያዣ እቃ መስሎ ይናገራል። ሀዘኑን ከማጠራቀሚያ እቃው ከታችኛው ክፍል ይመነጫል። ሀዘን አንዳንዴ ልክ አቃውን ከላይ እስከ ታች ድረስ መሙላትን ያሳያል። “በጣም ስላዘንኩ”

ጆሮህ የልመናዬን ቃል
ጆሮ የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ሲያመለክት ጸሐፊው እግዚአብሔር ሁሉንም እንደሚሰማ ስለሚያውቅ እግዚአብሔር እንዲመልስለት እየጠየቀ ነው። “እባክህ ስማኝ” ወይም “እባክህ መልስልኝ”

Psalms 130:3

አቤቱ ማን ይቆማል
ተናጋሪው ይህንን ጥያቄ ማን በዚህ ሁኔታ ላይ እንደሚቆም ለመግለፅ ነው። “ማንም መቆም አይችልም”

አቤቱ ማን ይቆማል
“ይቆማል” የሚለው በብዛት ከአንድ ጥቃት ማምለጥ ወይም መትረፍን ያመለክታል። በዚህ ሁኔታ ከቅጣት ማምለጥ ወይም መትረፍን ያመለክታል። “ማንም ቅጣትህን አያመልጥም”

Psalms 130:5

ነፍሴ
“ነፍሴ” የሚለው ቃል መዝሙረኛውን ያመለክታል።

ነፍሴ በሕግህ ታገሰች
መዝሙረኛው ልክ እንደ አንድ ነገር በተስፋ እንደመጠበቅ ያመለክታል። “እታመንብሃለሁ” ወይም “አንድን ነገር እሻለሁ”

ነፍሴ በሕግህ ታገሰችህ...ከማለዳው ሰዓት ጀምሮ እስከ ሌሊት ነፍሴ በእግዚአብሔር ታመነች
መዝሙረኛው እግዚአብሔር እንዲረዳው ያለውን መሻቱ ልክ ከማለዳ እስከ ሌሊት ድረስ ለመሥራት ከሚሹት በላይ ታላቅ እንደሆነ ለማሳየት ነው።

Psalms 130:7

እሥራኤል...ከኀጢአቱ
የእሥራኤል ሕዝብ ልክ እንደ ወንድ ሰው መስሎ ይናገራል። “የእሥራኤል ሕዝብ...የእነርሱን” ወይም “እኛ የእሥራኤል ሕዝብ...የእኛ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 131

1 ያህዌ ሆይ፣ ልቤ አልታበየም ዐይኔም ከፍ ከፍ አላለም። ለራሴም ታላላቅ ነገሮችን ተስፋ አላደረግሁም ከእኔ በላይ በሆነ ነገርም አልተጨነቅሁም። **2** ነገር ግን ነፍሴን ጸጥ፣ ዝም አሰኘኃት ነፍሴ ጡት እንዳስተውት ሕፃን በውስጤ ጸጥ አለች። **3** እስራኤል ሆይ አሁንና ለዘላለም ያህዌ ተስፋ አድርግ።

Psalms 131:1

አጠቃላይ ሃሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው

መዝሙረ መዐርግ
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) “ለማክበር ሕዝቡ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ የዘመሩት መዝሙር ነው።” ወይም 2) “ወደ መቅደሱ ለመግባት ሕዝቡ የዘመሩት መዝሙር ነው” ወይም 3) “ቃላቶቹ እንደ እርምጃ የሆኑ መዝሙሮች ናቸው”። በመዝሙረ ዳዊት 120፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ልቤ አይታበይብኝ አይኖቼም ከፍ ከፍ አይበሉብኝ
ልብ እና አይን ሙሉ ሰውን ያመለክታል። “አልኮራሁም ”

ለእኔ ትልቅነት አልተነሳሳም
ሊሆን የሚችል ትርጉም “እራሴን ትልልቅ ነገርን አደርጋለሁ ብዬ አልጠብቅም” ወይም “እራሴን ትልቅ ነኝ ብዬ አላስብም”

ከአቅሜ በላይ
ሰው ከሚረዳበት አቅም በላይ ከባድ የሆነ ልክ እንደ ከሰው በላይ ወይም ለመያዝ በጣም እሩቅ የሆነን ነገር መስሎ ይናገራል። “ለመረዳት ከባድ የሆነ ነገር”

Psalms 131:2

ነፍሴን አሳረፍኩአት
ነፍስ የሚለው የአንድን ሰው ስሜትን ያመለክታል። መረጋጋት የሚለውን ቃል የአንድን ነፍስ ረጋ ማድረግን ያመለክታል። “እኔ ተረጋጋሁ”

ነፍሴ
“ነፍሴ” የሚለው ቃል የአንድን ሰው ስሜት ወይም ሰውየውን ራሱን ያመለክታል።

የጣለ ልጅ እርፎ እኔቴ ላይ እደሚቀመጥ
መዝሙረኛው ራሱን እንደ ተረጋጋ አድርጎ ሲናገር ልክ ልጅ የእናቱን ጡት እንዳቆመ መስሎ ይናገራል። “ለጡት ማልቀስ እንዳቆመ ህፃን ልጅ ነገር ግን በእናቱ እቅፍ ያለ”

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 132

1 ያህዌ ሆይ፣ ዳዊትን፣ የተቀበለውንም መከራ ሁሉ አስብ። **2** እርሱ ለያህዌ ማለ፣ ለያዕቆብም ኃያል አምላክ ቃል ገባ፤ **3** እንዲህም አለ፣ «ወደ ቤቴ አልገባም፤ አልጋዬ ላይ አልወጣም **4** ለዐይኖቼ እንቅልፍን ለሽፋሽፍቶቼም ዕረፍትን አልሰጥም፤ **5** ለያህዌ ስፍራን፣ ለያዕቆብ ኃያል ማደሪያን እስካገኝ ድረስ። **6** እነሆ፣ በኤፍራታ ሰማነው፣ በይዓሪም አገኘነው። **7** ወደ ማደሪያው እንግባ እግሮቹ በሚቆሙበት ስፍራ እንስገድ። **8** ያህዌ ሆይ ተነሥ አንተና የኃይልህ ታቦታ ወደ ማደሪያህ ስፍራ ሂዱ። **9** ካህናትህ ጽድቅን ይልበሱ ታማኞችህ እልል ይበሉ። **10** ስለ ባርያህ ስለ ዳዊት ስትል የተቀባኸውን ንጉሥ አትተወው። **11** ያህዌ ለዳዊት በእውነት ማለ በማይታጠፍ መሐላ እንዲህ አለ «ከልጆችህ አንዱን ዙፋንህ ላይ አስቀምጣለሁ **12** ልጆችህ ኪዳኔን፣ የማስተምራቸውንም ሕጌን ቢጠብቁ፣ ልጆቻቸው ለዘላለም በዙፋንህ ላይ ይቀመጣሉ።» **13** ያህዌ ጽዮንን መርጧልና ማደሪያው እንድትሆን ወዶአልና። **14** «ይህች ለዘላለም ማረፊያዬ ናት ፈልጌአታለሁና በእርሷ እኖራለሁ። **15** እጅግ አትረፍርፌ እባርካታለሁ ድኾቿን እንጀራ አጠግባለሁ። **16** ካህናቶቿን ማዳንን አለብሳቸዋለሁ ታማኞቿም እልል ይላሉ። **17** በዚያ ለዳዊት ቀንድ አበቅላለሁ ለቀባሁትም ሰው መብራት አዘጋጃለሁ። **18** ጠላቶቹን እፍረት አከናንባቸዋለሁ እርሱ ላይ ግን አክሊሉ ያበራል።

Psalms 132:1

አጠቃላይ ሃሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው

መዝሙረ መዐርግ
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) “ለማክበር ሕዝቡ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ የዘመሩት መዝሙር ነው።” ወይም 2) “ወደ መቅደሱ ለመግባት ሕዝቡ የዘመሩት መዝሙር ነው” ወይም 3) “ቃላቶቹ እንደ እርምጃ የሆኑ መዝሙሮች ናቸው”። በመዝሙረ ዳዊት 120፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ዳዊትን ገርነቱንም
ዳዊት ስላለፈበት መንገድ እንዲሁም የዳዊትን ባህሪ አስብ

አስብ
“አስታውስ” ወይም “ስለሱ አስብ”

ለያዕቆብ አምላክ
ይህ እግዚአብሔርን ያመለክታል።

ለያዕቆብ አምላክ
ይህ እግዚአብሔርን ያመለክታል።

Psalms 132:3

ለዓይኖቼም መኝታ ለሽፋሽፍቶቼም እንቅልፍ
“መኝታ እና እንቅልፍ” ልክ እንደሚሰጥ ነገር መስሎ ይናገራል። አይን እና ሽፋሽፍት ሙሉ ሰውን ያመለክታል። “አይኔ እንዲተኛ ወይም ለሽፋሽፍቶቼ እረፍት አልሰጣቸውም” ወይም “አልተኛም ወይም ደግሞ ለማረፍ አይኖቼን አልከድንም”

ለእግዚአብሔር ስፍራ...እስካገኝ ድረስ
ለእግዚአብሔር ቦታ ላይ መገንባትን ልክ ለእርሱ ቦታን እንደ መፈለግ መስሎ ይናገራል። “ለእግዚአብሔር ስፍራ አገኝቼ እስክገነባ ድረስ”

ለያዕቆብ አምላክ
ይህ እግዚአብሔርን ያመለክታል።

Psalms 132:6

በኤፍራታ ሰማነው
“በኤፍራታ” የሚለው ቃል ከየት ሆነው የሰሙበትን ቦታ ያመለክታል። “እኛ በኤፍራታ ያለን ሰዎች የቃል ኪዳኑ ታቦት የት እንዳለ ሰማን”

በጁአሪም ውስጥ
ይህ ከተማዋን የከበባት ሜዳ ነው።

እግሮቹ በሚቆሙበት ስፍራ እንሰግዳለን
እግዚአብሔርን በቃል ኪዳኑ ታቦት ማምለክ ልክ እንደ በዙፋኑ ላይ የተቀመጠ ንጉሥ እግር ስር እንደመስገድ መስሎ ይናገራል። ይህ ለእግዚአብሔር መሰጠት እና ታማኝነትን ያመለክታል። “ወደ እግዚአብሔር ቅዱሱ የቃል ኪዳን ታቦት ጋር ሄደን እርሱን እንደ ንጉሥ እናመልከዋለን”

ወደ እረፍትህ ተነስ
“አቤቱ ወደ እረፍትህ ተነሳ እና ና”

ወደ እረፍትህ
እግዚአብሔር ሰዎች እንዲያመለኩት የመረጠው ስፍራ ልክ እንደ ለዘለአለም የሚኖርበት ወይም የሚያርፍበት መስሎ ይናገራል። “የሚታረፍበት ቦታ”

የሃይልህን ምልክት ከሆነችው ከቃልኪዳን ታቦት ጋር
ሊሆን የሚችል ትርጉም 1) “የሃይልህን ምልክት ከሆነችው ከቃልኪዳን ታቦት ጋር” ወይም 2) “ና እና የቃልኪዳንህ ታቦት ጋር”

የኀይልህ ምልክት ከሆነችው
“ታላቁን ሀይልህን የሚያሳይ”

Psalms 132:9

ካህናቶችህ ፅድቅህን ይልበሱ
ፅድቅ ልክ እንደ ልብስ መስሎ ይናገራል። “በካህናቶችህ ላይ ፅድቅን ሰዎች ይዩት” ወይም “ሰዎች ያንተ ካህናቶች ትክክለኛውን ነገር እንደሚያደርጉ እንዲያዩ እፈልጋለሁ”

ስለ ዳዊት
ባሪያህ ዳዊት ስላለፈበት መንገድ ስትል። መዝሙር 132፡1 የተተረጎመበትን መንገድ ተመልከት

ስለ ባሪያህ የቀባኸውን ሰው ፊት አትመልስ
“አትመልስ” የሚለው አትተወው ሚለውን ያመለክታል። “አንተ የቀባኸውን ባሪያህን አትተወው”

Psalms 132:11

ከሆድህ ፍሬ በዙፋንህ ላይ አስቀምጣለሁ።
የንጉሥን ልጅ ባለበት ንጉሥ ማድረግ ልክ እንደ በንጉሱ ዙፋን ላይ እንደማስቀመጥ መስሎ ይናገራል። “እሥራኤልን እንዲመራ ልጅህን አነግሳለሁ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በዙፋንህ ላይ ለዘላለም ይቀመጣሉ
ንጉሥ ሆኖ መምራት ልክ እንደ ዙፋን ላይ እንደመቀመጥ መስሎ ይናገራል። “ንጉሥ ሆኖ ይመራል።”

ልጆችህ
“ልጆችህ” የሚለው ቃል ንጉሥ የሚሆነውን የዳዊትን ልጅን ነው። “ልጅህን”

Psalms 132:13

አጠቃላይ ሀሳብ
“እርሱ” “የእኔ” እና “እኔ” የሚሉት ቃላት እግዚአብሔርን ሲያመለክት “እርሱዋ” የሚለው ደግሞ ፅዮንን ነው።

ፅዮንን...መርጦአታልና...ወድዶአታል
ጸሐፊው የፅዮን ከተማን በሴት መስሎ ነው የፃፈው።

ማደሪያውም ትሆነው ዘንድ ወድዶአታልና
“ማደሪያው” የሚለው የሚያመለክተው 1) የሚመራበት ዙፋኑን ነው። ወይም 2) የሚያርፍበት ቦታን ነው

ማደሪያውም ትሆነው ዘንድ ወድዶአታልና
“እግዚአብሔር የፅዮን ከተማ ለማረፊያ ፈልጎአታል።”

ማረፊያዬ ናት
እግዚአብሔር ሕዝቡ እንዲያመልኩት የመረጠው ቦታ ልክ እርሱ የሚያርፍበት ቦታ ወይም ደግሞ ለዘለአለም የሚኖርበት ስፍራ መስሎ ይናገራል። “እኔ በምቆይበት ስፍራ”

Psalms 132:15

አያያዥ ሀሳብ
እግዚአብሔር ስለ ፅዮን ከተማ እንደ ሴት መስሎ መናገሩን ቀጠለ።

አሮጊቶችዋን እጅግ እባርካለሁ
“ፅዮንን እጅግ አበዝቼ እባርካታለሁ”

ድሆችዋንም እንጀራ አጠግባለሁ
“ድሆች” የሚለው በፅዮን የሚገኙ ድሆችን ሲሆን “እንጀራ” ደግሞ አጠቃላይ ምግብን ያመለክታል። “በፅዮን ያሉ ድሃዎችን በምግብ አጠግባቸዋለሁ”

ካህናቶችዋንም ደህንነትን አለብሳቸዋለሁ
x

Psalms 132:17

በዚያ ለዳዊት ቀንድን አበቅላለሁ
እግዚአብሔር የዳዊትን ልጅ እንደ ሀይለኛ የእንስሳ ቀንድ መስሎ ይናገራል። “የዳዊትን ልጅ ከሱ ቀጥሎ ንጉሥ አደርገዋለሁ” ወይም “የዳዊት ልጅ ንጉሥ እንዲሆን አደርጋለሁ”

ለቀባሁትም ሰው መብራትን አዘጋጃለሁ
እግዚአብሔር የዳዊት ልጅ በንግስና እንደመሚመራ ልክ እንደ መብራት እንደሚያበራ መስሎ ይናገራል። “የቀባሁትን የዳዊት ልጅ በንግስና መምራቱን ይቀጥላል”

ለቀባሁት
“የመረጥኩት ንጉሥ”

ጠላቶችንም እፍረትን አለብሳቸዋለሁ
እፍረት ልክ እንደ ልብስ መስሎ ይናገራል። ይህ እፍረት በጦርነት ሽንፈትን ያመለክታል። “ጠላቶቹን አሳፍራቸዋለሁ” ወይም “ጠላቶቹ እንዲሸነፉ እና እንዲያፍሩ አደርጋለሁ”

እርሱ ግን በራሱ ላይ የደፋው ዘውድ ያበራል።
ዘውድ የሚለው ግዛቱን ሲሆን ታላቅነቱ ደግሞ በብርሃን መስሎ ይናገራል። “ታላቅ ንጉሥ ይሆናል” ወይም “የእሱ ታላቅነት ያበራል።”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 133

1 ወንድሞች ተስማምተው በአንድነት ቢኖሩ እንዴት መልካም ነው! ምንኛስ አስደሳች ነው። **2** በአሮን ራስና ጢም ላይ እንደሚፈስስ እስከ ልብሱን ዐንገት ጌጥ ድረስ እንደሚወርድ ውድ ሽቱ ነው። **3** ደግሞም በጽዮን ተራራ ላይ እንደሚወርድ እንደ አርሞንዔም ጠል ነው። ያህዌ በዚያ በረከቱን አዞአልና ሕይወትንም እስከ ዘላለም አዞአል።

Psalms 133:1

አጠቃላይ ሃሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው

መዝሙረ መዐርግ
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) “ለማክበር ሕዝቡ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ የዘመሩት መዝሙር ነው።” ወይም 2) “ወደ መቅደሱ ለመግባት ሕዝቡ የዘመሩት መዝሙር ነው” ወይም 3) “ቃላቶቹ እንደ እርምጃ የሆኑ መዝሙሮች ናቸው”። በመዝሙረ ዳዊት 120፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

እነሆ
ይህ ቃል ቀጣይ የሚናገረውን አስፈላጊነት አጉልቶ ያሳያል

ወንድሞች በህብረት ቢቀመጡ
ከእግዚአብሔር ሰዎች ጋር ያለውን ህብረት ልክ እንደ ወንድም መስሎ ይናገራል። “የእግዚአብሔር ሰዎች በአንድነት ልክ እንደ ወንድማማቾች ቢቀመጡ”

Psalms 133:2

ከራስ እስከ ጢም እንደሚፈስስ፣ እስከ አሮን ጢም፣ በልብሱ መደረቢያ እንደሚወርድ ሽቱ ነው።
የእግዚአብሔር ሰዎች አንድነት መልካምነት ልክ በአሮን ጢም እንደሚፈስ ሽቱ መስሎ ይናገራል። “አንድነት ልክ በአሮን ጢም እንደሚፈስ ሽቱ መልካም ነው”

እንደሚወርድ እንደ አርሞንኤም ጠል ነው
የእግዚአብሔር ሰዎች አንድነት መልካምነት ልክ እንደ ሚፈስ ጠል መስሎ ይናገራል። “እንደሚወርድ እንደ አርሞንኤም ጠል ነው”

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 134

1 እናንት በሌሊት ቆማችሁ በያህዌ ቤት የምታገለግሉ የያህዌ ባርያዎች ሁላችሁ፣ ያህዌን አመስግኑ። **2** ወደ መቅደሱ እጆችሁን አንሡና ያህዌን ባርኩ። **3** ሰማይና ምድርን የሠራ ያህዌ ከጽዮን ይባርካችሁ።

Psalms 134:1

አጠቃላይ ሃሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው

መዝሙረ መዐርግ
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) “ለማክበር ሕዝቡ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ የዘመሩት መዝሙር ነው።” ወይም 2) “ወደ መቅደሱ ለመግባት ሕዝቡ የዘመሩት መዝሙር ነው” ወይም 3) “ቃላቶቹ እንደ እርምጃ የሆኑ መዝሙሮች ናቸው”። በመዝሙረ ዳዊት 120፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

የእግዚአብሔር ባሪያዎች ሁላችሁ
“እግዚአብሔርን የምታገለግሉ ሁላችሁ”

እጆቻችሁን አንሱ
እንደዚህ ሰዎች እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑት እና የሚፀልዩት።

በቤተ መቅደስ
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) “በመቅደሱ” 2) “በመቅደስ ውስጥ ወደ ቅዱሱ ቦታ”

Psalms 134:3

ሰማይና ምድርን
“ሰማይና ምድር” የሚለው ሐረግ ሁሉንም ነገር ያመለክታል። “በሰማይ እና በምድር ውስጥ ያሉ ሁሉም ነገር”

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 135

1 ያህዌን አመስግኑ የያህዌን ስም ወድሱ፤ እናንት የያህዌ አገልጋዮች አመስግኑት። **2** በያህዌ ቤት በአምላካችንም ቤት አደባባይ የምትቆሙ አመስግኑት። **3** መልካም ነውና ያህዌን አመስግኑ ደስ የሚያሰኝ ነውና ለስሙ ዘምሩ። **4** ያህዌ ያዕቆብን ለራሱ፣ እስራኤልም ርስቱ እንዲሆን መርጦአልና። **5** ያህዌ ታላቅ መሆኑን፣ ጌታችንም ከአማልክት በላይ መሆን ዐውቃለሁ። **6** በሰማይም ሆነ በምድር በባሕርና በጥልቅ ውቅያኖስ ያህዌ የወደደውን ያደርጋል። **7** እርሱ ደመናትን ከሩቅ ቦታ ያመጣል ከዝናብ ጋር መብረቅ እንዲኖር ያደርጋል። ነፋሳትንም ከማከማቻው ያወጣል። **8** ከሰው ጀምሮ እስከ እንስሳ የግብፃውያንን በኩር ገደለ። **9** ግብፅ ሆይ፣ በፈርዖንና በአገልጋዮቹ ሁሉ ላይ፣ በመካከልሽም ምልክቶችንና ድንቆችን አደረገ። **10** ብዙ ሕዝቦች መታ ኃያላን ነገሥታት ገደለ። **11** የአሞራውያን ንጉሥ ሴዎንን የባሰን ንጉሥ ዐግን የከነዓንን ነገሥታት ሁሉ ገደለ። **12** ምድራቸውንም ለሕዝቡ ለእስራኤል ርስት አድርጎ ሰጠ። **13** ያህዌ ሆይ፣ ስምህ ዘላለማዊ ነው መታሰቢያህም ከትውልድ እስከ ትውልድ ይኖራል። **14** ያህዌ ለሕዝቡ ይፈርዳልና ለአገልጋዮቹም ይራራልና። **15** የአሕዛብ ጣዖቶች ከብርና ከወርቅ በሰው እጅ የተሠሩ ናቸው **16** አፍ አላቸው አይናገሩም ዐይን አላቸው አያዩም። **17** ጆሮ አላቸው አይሰሙም፤ በአፋቸውም እስትንፋስ የለም። **18** የሚሠሩዋቸውና የሚታመኑባቸው ሁሉ እንደ እነርሱ ይሁኑ። **19** የእስራኤል ልጆች ሆይ፣ ያህዌን ባርኩ የአሮን ልጆች ሆይ፣ ያህዌን ባርኩ። **20** የሌዊ ልጆች ሆይ፣ ያህዌን ባርኩ ያህዌን የምትፈሩ ሆይ፣ ያህዌን ባርኩ። **21** በኢየሩሳሌም የሚኖር ያህዌ ከጽዮን ይባረክ ያህዌን አመስግኑ።

Psalms 135:1

አጠቃላይ ሃሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው

የእግዚአብሔርን ስም አመስግኑ
የእግዚአብሔር ስም ራሱን ያመለክታል። “እግዚአብሔርን አመስግኑት” ወይም “አመስግኑት እሱን”

በእግዚአብሔር ቤት
ይህ እግዚአብሔርን በመቅደሱ ማገልገልን ያመለክታል

እግዚአብሔር...በአምላካችን
አምላካችን የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ያመለክታል።

Psalms 135:3

መልካም ነውና
ስሙን ስናመሰግን መልካም ነው

እግዚአብሔር ያዕቆብን ለራሱ...መርጦአልና
“ያዕቆብ” የሚለው የሚያመለክተው የእርሱን ልጆች የእሥራኤል ሕዝብን ነው። “እግዚአብሔር የያዕቆብን ልጆች መረጠ”

እሥራኤልን ለመዝገቡ
“እሥራኤልን ለራሱ መርጦአቸዋል።”

Psalms 135:5

ጌታችንም ከአማልክት ሁሉ እንዲበልጥ
“የኛ ጌታ ከሌሎች አማልክት በላይ እንደሆነ አውቃለሁ”። ከሁሉ በላይ መብለጥ ልክ በምንም በላይ እንደ መሆን መስሎ ይናገራል። “የኛ አምላክ ከማንም አማልክት በላይ ነው።”

Psalms 135:7

ነፋሳትንም ከመዛግብቱ ያወጣል
መዛግብቱ ማለት ለወደፊት የሚጠቅሙ እቃዎች የሚቀመጡበት ቤት ነው። ይህ የሚያሳየው እግዚአብሔር ንፋስን ሁሉ የመቆጣጠር ሀይል እንዳለው ነው። “በሃይሉ ንፋሳትን እንዲነፍሱ ያደርጋል።”

Psalms 135:8

ተአምራትንና ድንቅን
እነዚህ ሁለት ቃላት አንድ አይነት ትርጉም ሲኖራቸው ይህም እግዚአብሔር በግብፅ ላይ የላከውን ተአምራታዊ ችግሮችን ያሳያል።

ግብፅ ሆይ
መዝሙረኛው የግብፅ ሕዝብ ልክ እንደሚሰማው መስሎ ይናገራል። “ከግብፅ ሕዝብ መሃከል” ወይም “ከግብፃውያን ሕዝብ መካከል።”

በፈርኦንና በባሪያዎቹ ላይ
“ፈርኦንን ለመቅጣት”

Psalms 135:10

ሴዎን...ዐግን
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው።

Psalms 135:12

ምድራቸውን ርስት አድርጎ...ሰጠ
የእግዚአብሔር ለእሥራኤላውያን ምድሪቱን ስጦታ ልክ ከአባት ወደ ልጅ ውርስ እንደሚሄድ መስሎ ይናገራል። “ምድሪቱን ለዘለአለም እርሱ ሰጠን” ወይም “የነርሱን ምድር ለኛ ለዘላለም ሰጠን”

ስምህ
ይህ የሚያመለክተው የሱን ዝና እና ማዕረጉን ነው። “ዝናህን” ወይም “ማዕረግህን”

Psalms 135:14

የሚሰሩአቸው ሁሉ የሚታመኑባውም ሁሉ እንደ እነርሱ ይሁን
ሀይል የሌላቸው እና ችላ ማለት ልክ እንደ ጣኦት ሲመስለው ይህም አያይም አይናገርም አይሰማም ወይም አይተነፍስም። “እነሱን የሚሰሩኣቸው ልክ እንደ ጣኦታቸው ሀይል የሌላቸው እና የማይገባቸው ይሆናሉ።”

የሚታመኑባቸውም ሁሉ
“እነዛ በጣኦቶቻቸው የሚተማመኑ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 135:19

በኢየሩሳሌም የሚያድር
እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም እንደሚኖር መስሎ ሲናገር ምክንያቱም ደግሞ
እሥራኤላውያን የሚያመለኩበት መቅደስ በእዛ ስለሚገኝ ነው። “እርሱ
በእየሩሳሌም መቅደስ ያለው።”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 136

1 ቸር ነውና ያህዌን አመስግኑ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። **2** የአማልክትን አምላክ አመስግኑ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። **3** የጌቶችን ጌታ አመስግኑ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። **4** ብቻውን ታላላቅ ተአምራት ያደረገውን አመስግኑ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። **5** በጥበብ ሰማያትን የሠራ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። **6** ምድርን ውሃ ላይ የዘረጋ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። **7** ታላላቅ ብርሃናትን የሠራ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። **8** ፀሐይ በቀን እንዲገዛ ያደረገ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። **9** ጨረቃና ከዋክብት ሌሊት እንዲገዙ ያደረገ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። **10** የግብፅን በኩር የገደለ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። **11** እስራኤልን ከመካከላቸው ያወጣ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። **12** በብርቱ እጅ፣ በተዘረጋችም ክንድ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። **13** ቀይ ባሕርን የከፈለውን አመስግኑ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። **14** እስራኤልን በመካከሉ ያሳለፈ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። **15** ፈርዖንና ሰራዊቱን ቀይ ባሕር ውስጥ ያሰጠመ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። **16** ሕዝቡን በምድረ በዳ የመራውን አመስግኑ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። **17** ታላላቅ ነገሥታትን የገደለውን ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። **18** ኃያላን ነገሥታትን የገደለ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። **19** የአሞራውያን ንጉሥ ሴዎንን ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። **20** የባሳንን ንጉሥ ዐግን የገደለ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። **21** ምድራቸውን ርስት አድርጎ የሰጠ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። **22** ለባርያው ለእስራኤል ርስት አድርጎ የሰጠ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። **23** በውርደታች ያሰበን፣ የረዳንም ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። **24** በጠላቶቻችን ላይ ድል የሰጠን ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። **25** ለፍጡር ሁሉ ምግብ የሚሰጥ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። **26** የሰማይን አምላክ አመስግኑ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና።

Psalms 136:4

ምሕረቱ ለዘላለም ነውና
“ምሕረቱ ለዘላለም ነው” በመዝሙረ ዳዊት 136፡1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎመው ተመልከት

በብልሃት
ይህ ጠቢብ ስለነበር ነው

Psalms 136:6

ምድርን በጥልቅ ውሃዎች ላይ
በድሮ ግዜ እሥራኤላውያን የምድር ደረቅ ክፍል በውሃዎች ላይ ነው ብለው ያስቡ ነበር። “በውሃዎች ላይ ምድርን አስቀመጠ”

ምሕረቱ ለዘላለም ነውና
“ምሕረቱ ለዘላለም ነው” በመዝሙረ ዳዊት 136፡1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎመው ተመልከት

ታላላቅ ብርሃናትን
ይህ የምድርን የብርሃን ምንጭን ሲያመለክት በተለይ ፀሀይና ጨረቃን ያመለክታል። “ፀሃይ ጨረቃና ከዋክብትን”

Psalms 136:8

ቀንን ያስገዛው...ሌሊትን ያስገዛቸው
ፀሀይ ጨረቃ እና ከዋክብት እንደ ንጉሥ መስሎ ይናገራል። “በቀን እንድትሆን...በለሊት እንድትሆን”

ምሕረቱ ለዘላለም ነውና
“ምሕረቱ ለዘላለም ነው” በመዝሙረ ዳዊት 136፡1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎመው ተመልከት

Psalms 136:10

ምሕረቱ ለዘላለም ነውና
“ምሕረቱ ለዘላለም ነው” በመዝሙረ ዳዊት 136፡1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎመው ተመልከት።

ከመካከላቸው
“ከግብፃውያን መካከል”

በፀናች እጅ በተዘረጋችም ክንድ
“እጅ” እና “ክንድ” የሚሉት ቃላት ሃይልን ያመለክታል። “በታላቅ ሀይል”

Psalms 136:13

የኤርትራን ባህር
የፈርኦን ሰራዊት በኤርትራ ባህር ሰጥመዋል።

ምሕረቱ ለዘላለም ነውና
“ምሕረቱ ለዘላለም ነው” በመዝሙረ ዳዊት 136፡1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎመው ተመልከት

ፈርኦንንና ሰራዊቱን በኤርትራ ባህር የጣለ
እዚህ ጋር መሸነፍ ልክ እንደ ተደናቅፎ እንደወደቀ መስሎ ይናገራል። “ፈርኦንንና ሰራዊቱን አሸነፋቸው” ወይም “የግብፅን ንጉሥ አሸነፈው”

ፈርኦን
ይህ የፈርኦንን ሰራዊት ያመለክታል።

Psalms 136:18

ምሕረቱ ለዘላለም ነውና
“ምሕረቱ ለዘላለም ነው” በመዝሙረ ዳዊት 136፡1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎመው ተመልከት

ሴዎንን...አግን
እነዚህ ሁለት ንጉሶች እግዚአብሔር እሥራኤላውያንን እንዲያሸንፉ ያደረጋቸው ናቸው።

Psalms 136:21

ምሕረቱ ለዘላለም ነውና
“ምሕረቱ ለዘላለም ነው” በመዝሙረ ዳዊት 136፡1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎመው ተመልከት

አስቦናልና
“ስለኛ አስቦአል”

እኛን በመዋረዳችን
የመዋረድ ስሜት ልክ እንደ እሥራኤላውያን የነበሩበት ቦታ አድርጎ ይናገራል። ይህ የእሥራኤላውያን ጠላት ብዙ ጊዜ እንዳሸነፉአቸው እና እንዳዋረዱአቸው ያመለክታል። “ስንዋረድ አስቦልናል።”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 136:24

ከጠላቶቻችንም እጅ አድኖናልና
ሕዝቡ ጠላቶቻቸውን እንዲያሸንፉ ማድረጉን ልክ እንደ ማሸነፍ እንደሚታደል እቃ መስሎ ይናገራል። “በጠላቶቻችን አሸናፊዎች አደረገን” ወይም “ጠላቶቻችንን እንድናሸንፍ አደረገን”

ምሕረቱ ለዘላለም ነውና
“ምሕረቱ ለዘላለም ነው” በመዝሙረ ዳዊት 136፡1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎመው ተመልከት

የሰማይን አምላክ
“በሰማይ ያለውን አምላክ” ወይም “በሰማይ የሚመለከው አምላክ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 137

1 በባቢሎን ወንዞች አጠገብ ተቀምጠን ጽዮንን ባሰብናት ጊዜ አለቀስን። **2** እዚያ በገናዎቻችንን በአኻያ ዛፎች ላይ ሰቀልን። **3** የማረኩን ሰዎች እንድንዘምርላቸው ጠየቁን ሲያፌዙብን የነበሩት የደስታ ዜማ ፈለጉብን፣ «እስቲ ከጽዮን መዝሙሮች አንዱን ዘምሩልን» አሉን። **4** የያህዌን መዝሙር እንዴት ብለን በባዕድ ምድር እንዘምራለን? **5** ኢየሩሳሌም ሆይ፣ ብረሳሽ ቀኝ እኔ ይክዳኝ። **6** አንቺን ሳላስታውስ፣ ደስ ከሚያሰኘኝ ነገር ሁሉ በላይ ሳላደርግሽ ብቀር ምላሴ ከትናጋዬ ትጣበቅ። **7** ያህዌ ሆይ፣ ኢየሩሳሌም በወደቀችበት ቀን ኤዶማውያን ያደረጉትን አስብ። እነርሱ፣ «አፍርሷት፣ ጨርሳችሁ አፍርሷት!» አሉ። **8** የባቢሎን ልጅ ሆይ፣ እኛ ላይ ስላደረግሺው ድርጊት ብዙም ሳይቆይ፣ የእጅሽን የሚሰጥሽ የተባረከ ነው **9** ሕፃናቶችሽን ዐለት ላይ የሚፈጠፍጥ እርሱ የተመሰገነ ነው።

Psalms 137:1

አጠቃላይ ሃሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው

በባቢሎን ወንዞች አጠገብ
ከባቢሎን ወንዝ አጠገብ የሚገኝ

ተቀመጥን...አለቀስን...ባሰብናት...ሰቀልን
ጸሐፊው አንባቢውን አያካትትም

በአኻያ ዛፎችዋ
ይህ ዛፍ በእሥራኤል አይበቅልም። “በአኻያ ዛፎች” በባቢሎን የሚገኙ ሁሉንም ዛፎች ያመለክታል። “በባቢሎን በሚገኙ ዛፎች ላይ”

Psalms 137:3

የማረኩን በዚያ የዝማሬን ቃል ፈለጉብን
“እኛን የማረኩን እንድንዘምር ፈለጉ”

በመዘመር እንድናስደስታቸው
“እንደተደሰትን እንድናስመስል አደረጉን”

ከፅዮን መዝሙሮች አንዱን
ይህ በኢሩሳሌም በመቅደስ ውስጥ ለማምለክ የሚጠቀሙት የእሥራኤላውያን መዝሙር ነው

Psalms 137:5

ኢየሩሳሌም ሆይ ብረሳሽ
ጸሐፊው ኢየሩሳሌም እሱን እንደመሚሰማው መስሎ ይናገራል።
“ኢየሩሳሌምን ለመርሳት ብሞክር”

ቀኜ እጄ
ብዙ ሰው የሚቀመው እጅ

Psalms 137:7

አስብ
“አስታውስ” ወይም “አስብ”

በኢየሩሳሌም ቀን የኤዶምን ልጆች አስብ
ኤዶምያውያንን አስብ ሲል ላደረጉት ነገር ሁሉ ቅጣቸው ማለቱ ነው።
“ኤዶምያውያንን ላደረጉት ነገር ቅጣቸው”

ኢየሩሳሌም በተያዘችበት ቀን
ኢየሩሳሌም በጠላት መያዝ እንደ ውድቀት መስሎ ይናገራል። “ኢየሩሳሌም በተያዘችበት ቀን” ወይም “የባቢሎን ሰራዊት ኢየሩሳሌም የገቡ ቀን”

Psalms 137:8

አጠቃላይ ሃሳብ
መዝሙረኛው የባቢሎን ሕዝብን እሱን እንደሚሰሙት ያህል መስሎ ሲናገር ያሳያል።

የባቢሎን ልጅ ሆይ
ይህ የባቢሎን ከታማንና ህዝቦቿን ያመለክታል።

የተመሰገነ ነው
“እግዚአብሔር ይባርከው”

ስለተበቀልሽን የሚበቀልሽ
ጸሐፊው የሆነሰው እነሱላይ ስለተደረገባቸው ነገር ሌሎቹ ላይ የሚያደርግ ልክ እንደ ክፍያ። “በኛ ላይ ያደረጋችሁብን እናንተ ላይ ይሁን”

በአለት ላይ የሚፈጠፍጣቸው
“የሕፃናቶቻችሁን ጭንቅላት ከድንጋይ ላይ አፈረሰው”

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 138

1 በፍጹም ልቤ አመሰግንሃለሁ በአማልክትም ፊት በመዝሙር እወድስሃለሁ። **2** ወደ ቅዱስ መቅደስህ እሰግዳለሁ ስለ ምሕረትህና ስለ ታማኝነትህ ለስምህ
ምስጋና አቀርባለሁ። ቃልህንና ስምህን ከሁሉ በላይ ከፍ አደረግህ። **3** በጠራሁህ ቀን መለስህልኝ ነፍሴን በማጽናናት አደፋፈርሃት። **4** ያህዌ ሆይ፣ የአፍህን ቃል
ሲሰሙ የምድር ነገሥታት ሁሉ ያመሰግኑሃል። **5** የያህዌ ክብር ታላቅ ነውና ስለ ያህዌ ሥራ ይዘምራሉ። **6** ያህዌ እጅግ ከፍ ያለ ቢሆንም፣ ዝቅ ያሉትንም
ይመለከታል ትዕቢተኞችን ግን ገና ከሩቅ ያውቃቸዋል። **7** በአደጋ መካከል ብሄድ እንኳ አንተ ሕይወቴን ትጠብቃለህ። እጅህን ዘርግተህ ከጠላቶቼ ቁጣ
ታወጣኛለህ በቀኝ እጅህም ታድነኛለህ። **8** ያህዌ እስከ መጨረሻ ከእኔ ጋር ነህ ያህዌ ሆይ፣ ምሕረትህ ለዘላለም ነው። የእጅህን ሥራ ቸል አትበል።

Psalms 138:1

አጠቃላይ ሃሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው

የዳዊት መዝሙር
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) ዳዊት መዝሙሩን ነው የፃፈው 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው የሚናገረው 3) መዝሙሩ የዳዊት መዝሙር አይነት ነው።

በፍፁም ልቤ አመሰግንሃለሁ
ልብ የሚለው ስሜትን ያመለክታል። አንድን ነገር ሙሉ በሙሉ እና በታማኝነት ማድረግ ከልብ እንደተደረገ መስሎ ይናገራል።

በመላእክት ፊት እዘምርልሃለሁ
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) “ምንም ሐሰተኛ አማልክት ቢኖሩም” ወይም 2) “በሰማይ ያሉት መልአክት ፊት”

እሰግዳለሁ
ስግደት የማምለክ እና ክብርን መስጠትን ያመለክታል። “አመልክሃለሁ”

ስምህንም አመሰግናለሁ
“ስምህ” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ራሱን ያመለክታል። “አንተን አመሰግንሃለሁ”

ስለ ምሕረትህና ስለ እውነትህ
“ስለ ምሕረትህ እና አንተ ሰዎች የሚያምኑብህ ነህና”

የትእዛዛትህን
“የተናገርከውን” ወይም “ትእዛዛትህን እና ቃልኪዳንህ”

ስምህን
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) “አንተን” ወይም 2) “ዝናህን”

Psalms 138:3

የአፍህን
ይህ እግዚአብሔርን ራሱን ያመለክታል። “አንተን”

Psalms 138:5

እግዚአብሔር ከፍ ያለ ነውና ወደ ችግረኞችም ይመለከታልና
እግዚአብሔር ከፍጥረታት ሁሉ በሃይል እና በሥልጣን ከፍ ያለ ነው። የእርሱ ፍላጎትም ለመንፈሱ ታማኝ እና የሚታዘዙ ላይ ነው።

Psalms 138:7

ብሄድ
መኖር

በመከራ መካከል
በመከራ መሆን እንደ አለ ቦታ መስሎ ይናገራል።

በጠላቶቼ ቁጣ ላይ እጆቼን ትዘረጋለህ
እግዚአብሔር ጠላቶችን በእጁ እንዳሚቀጣ መስሎ ይናገራል።

በጠላቶቼ ቁጣ
“ቁጣ” የሚለው ቃል “መቆጣት” ማለት ይቻላል። “በተቆጡት ጠላቶቼ ላይ”

የገባኸውን ቃል ኪዳን ትፈፅምልኛለህ እግዚአብሔር ሆይ ፍቅርህ ዘላለማዊ ነው።
“አንተ እግዚአብሔር ለዘለአለም ታማኝ ነህ”

የእጅህን ሥራ
ይህ የሚያመለክተው የእሥራኤልን ከተማ ነው።

የእጅህን ሥራ
እግዚአብሔር ልክ እጁን ተጠቅሞ እንደሰራ መስሎ ይናገራል። “አንተ ሰርተሃል”

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 139

1 ያህዌ ሆይ፣ መረመርኸኝ፤ ደግሞም ዐወቅኸኝ። **2** አንተ መቀመጤንና መነሣቴን ታውቃለህ የልቤንም ሐሳብ ገና ከሩቅ ትረዳለህ። **3** መሄድ መተኛቴን
በሚገባ ታውቃለህ መንገዶቼንም ሁሉ ዐውቀሃቸዋል **4** ገና ቃል ከአንደበቴ ሳይወጣ ያህዌ ሆይ፣ ፈጽመህ ታውቃለህ። **5** አንተ ከኋላም ከፊትም ዙሪያዬን
ከለልኸኝ እጅህንም በላዬ አደረግህ። **6** እንዲህ ያለው ዕውቀት እጅግ ጥልቅ ነው ከእኔም ማስተዋል በላይ ነው። **7** ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ ከፊትህስ
ወዴት እሸሻለሁ። **8** ወደ ሰማይ ብወጣ አንተ በዚያ አለህ መኝታዬን በሲኦል ባደርግ በዚያ ትገኛለህ። **9** በንጋት ክንፍ ተነሥቼ ብበር እስከ ባሕሩ መጨረሻ
ብሄድ **10** በዚያም ቢሆን እጅህ ትመራኛለች ቀኝ እጅህም ትይዘኛለች። **11** ደግሞም፣ «ጨለማው በእርግጥ ይሸፍነኛል በዙሪያዬ ያለውም ብርሃን ሌሊት
ይሆናል» ብል **12** ጨለማ እንኳ ለአንተ አይጨልምም ሌሊቱም እንደ ቀን ያበራል በአንተ ጨለማም ሆነ ብርሃን አንድ ናቸው። **13** አንተ የውስጥ ሰውነቴን
ፈጥረሃል በእናቴ ማሕፀን ውስጥ አበጃጅተህ ሠራኸኝ። **14** ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና አመሰግንሃለሁ ሥራህ እጅግ ድንቅ ነው ነፍሴም ይህን በሚገባ
ታውቃለች። **15** እኔ በስውር በተሠራሁ ጊዜ ዐጥንቶቼ ከአንተ አልተደበቁም። በምድር ጥልቅ ውስጥ በጥበብ በተሠራሁ ጊዜ **16** በእናቴ ማሕፀን እያለሁ
አየኸኝ። ገና አንዳቸውም ወደ መኖር ሳይመጡ ለእኔ የተወሰኑልኝ ዘመኖች በመጽሐፍህ ተጻፉ። **17** አምላኬ ሆይ፣ ለእኔ ያለህ ሐሳብ እንዴት ግሩም ነው!
ቁጥሩስ ምንኛ የበዛ ነው! **18** ልቁጠራቸው ብል ከአሸዋ ቁጥር ይበልጣሉ ተኛሁ ነቃሁም፤ ያም ሆኖ ግን አሁንም ከአንተው ጋር ነኝ። **19** አምላክ ሆይ፣
ክፉዎችን ብትገድላቸው ምናለበት! ደም የጠማችሁ ዐመፀኞች ከእኔ ራቁ። **20** እነርሱ በአንተም ላይ ክፉ ይናገራሉ በጠላትነትም ስምህን በክፉ ያጠፋሉ። **21**
ያህዌ ሆይ፣ የሚጠሉህን አልጠላሁምን? በአንተ ላይ የሚነሡትንስ አልተጸየፍሁምን? **22** በፍጹም ጥላቻ ጠልቻቸዋለሁ እነርሱም ባላጋራዎቼ ሆነዋል። **23**
እግዚአብሔር ሆይ፣ መርምረኝ ልቤንም ዕወቅ ፈትነኝ ሐሳቤንም ዕወቅ። **24** በእኔ ውስጥ የዐመፅ መንገድ ቢኖር እይ በዘላለምም መንገድ ምራኝ።

Psalms 139:1

አጠቃላይ ሃሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው

ለመዘምራን አለቃ
ይህ ቃል ለዝማሬ/አምልኮ መሪ የተጠቀመው ነው

የዳዊት መዝሙር
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) ዳዊት መዝሙሩን ነው የፃፈው 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው የሚናገረው 3) መዝሙሩ የዳዊት መዝሙር አይነት ነው።

መረመርኸኝ
መረመርኸኝ

መቀመጤንና መነሳቴን
መዝሙረኛው እነዚህን ሁለት ቃላቶች ሲጠቀም ሁል ጊዜ የሚያደርገውን ለማሳየት ነው። “የማረገውን ሁሉ” ወይም “ስለ እኔ ያለ ሁሉ”

Psalms 139:3

እረፍቴን አንተ መረመርህ መንገዶቼን ሁሉ
“መንገዶቼን” የአንድን ባህሪ ያመለክታል። በአንድላይ ይህ የሚያመለክተው ስለ መዝሙረኛው ያለውን የሚያመለክት ነው።

ገና ከመናገሬ በፊት
“ገና ከመናገሬ በፊት” የሚለው ቃል ንግግርን ያመለክታል። “ምንም ነገር ከመናገሬ በፊት”

Psalms 139:7

ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ
እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች ተመሳሳይነት አላቸው። መዝሙረኛው ከእግዚአብሔር መገኘት ወዴትም መሄድ እንደማይችል ይናገራል። “መንፈስህን ልሸሽ አልችልም”

ወደ ሲኦል ብወርድ
ይህ የሚያሳየው የሆነ ቦታ መቆየትን ነው። “በሲኦል እንኳን ብቆይ”

Psalms 139:9

እንደ ንስር የንጋትን ክንፍ ብወስድ፣ እስከ ባሕር መጨረሻም ብበርር
ጸሐፊው ይህን አግንኖ የሚናገረው የትም ቢሆን የት እግዚአብሔር በዚያ እንደሚገኝ ለማሳየት ነው።

እንደ ንስር የንጋት ክንፍ ብወስድ
በድሮ ጊዜ በስተምሥራቅ በኩል ፀሀይ ስትወጣ ሰማይ ላይ እንድትበር ክንፍ አላት ተብሎ ይቆጠራል። “ፀሃይዋ ራሷ ተሸክማኝ በሰማይ ላይ ብትሄድ ራሱ”

እስከ ባህር መጨረሻ ብበርር
“ወደ እሩቅ ምዕራብ በኩል”

ትይዘኛለች
ትረዳኛለህ

Psalms 139:11

በውኑ ጨለማ ትሸፍነኛለች ብል
መዝሙረኛው ጨለማን ልክ እንደ ሚሸፍነው ጨርቅ መስሎ ይናገራል።

ሌሊት በዙሪያዬ ብርሃን ትሆናለች
ሌሊት ማለትም ጨለማው ልክ እንደ ብርሃን መስሎ ይናገራል።

Psalms 139:15

እኔ በስውር በተሰራሁጊዜ
ውስብስብ በሆነ መንገድ ብሰራም

በምድር ታች
ይህ የእናትን ማሕፀንን ያመለክታል።

ቀኖቼ ሁሉ አንድ ስንኳ ሳይኖር በመጽሐፍህ ተጻፉ
የድሮ እሥራኤላውያን እግዚአብሄ እቅዱን የሚፅፍበት መጽሐፍ እንዳለው ያስባሉ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Psalms 139:17

አሳቦችህ በእኔ ዘንድ እንደምን እጅግ የተከበሩ ናቸው
“ያንተ ሃሳብ እጅግ የተከበረ ነው” ወይም “ሃሳብህ ለኔ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው”

ቁራቸው እንደምን በዛ
“ሃሳብ እጅግ በጣም ብዙ ናቸው”

ብቆጥራቸው ከአሸዋ ይልቅ ይበዛሉ
ይህ ግነት የእግዚአብሔርን ሃሳብ መቁጠር እንደሚከብድ ጸሐፊው ለማሳየት ነው። “ልቆጥረው ከምችለው በላይ ነው ”

Psalms 139:19

የምትገድል ከሆንህስ፣ የደም ሰዎች ሆይ፣ ከእኔ ፈቀቅ በሉ
መዝሙረኛው በአእምሮ ላይ የሳለውን ገዳይ ሰው እንደሚናገር መስሎ ያሳያል።

በከንቱ ያምፁብሃል
“በአንተ በእግዚአብሔር ሥልጣን ላይ ያምፃሉ”

በክፋት ይናገሩብሃል
ስላንተ ክፉ ነገር ያወራሉ

Psalms 139:21

የሚጠሉህን እኔ የጠላሁ አይደለሁምን? ስለ ጠላቶችህም አልተሰቀቅሁምን?
እነዚህ ሁለት አረፍተነገሮች አንድ አይነት ትርጉም አላቸው። ሁለተኛው የመጀመሪያውን አጠናክሮ ያግዘዋል። “እግዚአብሔር ሆይ አንተን የሚጠሉህን ጠላሁ በአንተ ላይ የተነሱትንም ተሰቀቅሁ”

በአንተ ላይ የሚያምፁትንም
ማመፅ

Psalms 139:23

መርምረኝ
መዝሙረኛው ለእግዚአብሔር ማንኛውንም አይነት ሊኖረው የሚችለውን ሀጥያታዊ ሀሳብ የቀረበ ጥያቄ ነው። “እባክህ ፈልገኝ” ወይም “እንድትፈልግብኝ እለምንሃለሁ”

መርምረኝ ልቤንም እወቅ ፍተነኝ መንገዴንም እወቅ
እነዚህ ሁለቱ አረፍተ ነገሮች አንድ አይነት ተመሳሳይ ሃሳብ አላቸው። የሁለተኛው አረፍተ ነገር የመጀመሪያውን አረፍተነገር ያጠነክራል።

በደልንም በእኔ
ይህ ባህሪን ይገልፃል

የዘላለም መንገድ ምራኝ
“መንገድ” የሚለው ቃል በእግዚአብሔር እምነትና ታዛዥነትን ነው። ማንም በዘላለማዊ መንገድ ቢሄድ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 140

1 ያህዌ ሆይ፣ ከክፉ ሰዎች አድነኝ ከዐመፀኞችም ጠብቀኝ። **2** እነርሱ በልባቸው ክፉ ነገር ያውጠነጥናሉ በየዕለቱም ጦርነት ይጭራሉ። **3** ምላሳቸው እንደ እባብ ይነድፋል የእፉኝትም መርዝ በከንፈራቸው አለ። ሴላ **4** ያህዌ ሆይ፣ ከክፉዎች እጅ ጠብቀኝ መትተው ሊጥሉኝ ከሚፈልጉ ዐመፀኛ ሰዎች አድነኝ። **5** ትዕቢተኞች በስውር ወጥመድ ዘርግተውብኛል የመረባቸውን ገመድ ዘረጉብኝ በመንገዴም አሽክላ አኖሩ። ሴላ **6** እኔም ያህዌን፣ «አንተ አምላኬ ነህ እንድትምረኝ የማቀርበውን ጩኸት ስማ» እለዋለሁ። **7** ያህዌ ሆይ፣ እኔን ለማዳን ብርቱ ነህ በጦርነት ቀን ራሴን ከለልህ። **8** ያህዌ ሆይ፣ የክፉዎች ምኞት አይሳካ ሤራቸውም አይከናወን። **9** ዙሪያዬን የከበቡኝ ራሳቸውን ቀና ቀና አደረጉ የገዛ ከንፈራቸው ሸፍጥ ይዋጣቸው። **10** የእሳት ፍም በላያቸው ይውረድ እሳት ውስጥ ጣላቸው ዳግመኛም እንዳይነሡ ማጥ ወዳለበት ጉድጓድ ይውደቁ። **11** ምላሰኛ በምድሪቱ ጸንቶ አይኑር ዐመፀኛውን ክፋት አሳድዶ ያጥፋውቭ **12** ያህዌ ለተበደሉ እንደሚፈርድ ለችግረኛውም ፍትሕ እንደሚሰጥ ዐውቃለሁ። **13** ጻድቃን በእውነት ስምህን ያመሰግናሉ ቅኖችም በፊትህ ይኖራሉ።

Psalms 140:1

አጠቃላይ ሃሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው

ለመዘምራን አለቃ
ይህ ቃል ለዝማሬ/አምልኮ መሪ የተጠቀመው ነው

የዳዊት መዝሙር
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) ዳዊት መዝሙሩን ነው የፃፈው 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው የሚናገረው 3) መዝሙሩ የዳዊት መዝሙር አይነት ነው።

ለሰልፍ ያከማቻሉ
“ለሰልፍ” የሚለው ጦርነት እና ግጭቶችን ያመለክታል

ምላሳቸው እንደ እባብ
ግጭትን የሚፈጥሩ ሰዎችን ልክ እንደ እባብ ምላስ መስሎ ይናገራል። እባብ በምላሱ ምንም አይነት ጉዳት አያደርስም ነገር ግን ሲናደፍ እና በውስጡ ያለው መርዝ ነው። ሰውም ምላሱ እንደ እባብ ነው ሳይሆን የሚያስረዳው ችግርን ከመፍጠር አንፃር ስለሆነ ሲሆን አንዳንድ እባቦች በምላሳቸው መርዝ ስላላቸውም ነው።

Psalms 140:4

ከኀጢአተኞች እጅ ጠብቀኝ
ይህ የሚያሳየው የኀጢአተኞችን ሃይልን ነው።

ወጥመድን ሰወሩብኝ...ገመድን ዘረጉ....እንቅፋትን አኖሩ
ዋናው ሀሳብ ትዕቢተኞችና ክፉ ሰዎች የዘማሪውን ሕይወት ለማክበድ እቅድ እንደነበራቸው ነው። አንባቢዎች ይህንን የክፋት እቅድ ለመተግበር የተጠቀሙት ምን አይነት ወጥመድ እንደሆነ ማወቅ ብዙ አይጠበቅባቸውም። በአጭር አረፍተነገር ‹‹ እኔን ለመያዝ ወጥመድ አዘጋጁ ››

Psalms 140:6

የልመናዬን ቃል አቤቱ አድምጥ
ይህ እርዳታን መጠየቅን ያሳያል። “እባክህ እንድትረዳኝ ስጠራህ ስማኝ”

በሰልፍ ቀን ራሴን ሸፈንህ
የአንድ ሰው ራስ በሰልፍ ጊዜ የሚጎዳ ቦታ ነው። ራሱን መሸፈን ሙሉ ሰውን ስለ መጠበቅን ያመለክታል። “ወደ ጦርነት ስወጣ እኔን ጠበቅከኝ”

ሰልፍ
x

Psalms 140:9

የሚከቡኝን ራስ
‹‹ራስ›› የሚለው የሚያመለክተው የሚንቁትን ሰዎች (ንቀትን) ነው። (ምልክታዊ ትርጉም የሚለውን ተመልከት)

የከንፈራቸው ክፋት ይክደናቸው
ይህ ክፉ ነገሮችን የሚያደርጉ ሰዎችን ራሳቸው በተናገሩት ነገሮች የፈጠሩት ችግሮች እንዲሰቃዩ የሚናገር ፀሎት ነው።

የከንፈራቸው ክፋት
በተናገሩት ነገር ያመጡት ክፉ ነገሮች

ይክደናቸው
ተጨማሪ ሌላ ችግሮችን ሳያመጡ አስቆማቸው

የእሳት ፍም በላያቸው ይውደቅ እንዳይነሡም ወደ እሳትና ወደ ማዕበል ይጣሉ
“እሳት” የሚለው ክፉ ነገሮችን ለሚያደርጉት የመጣ ቅጣትን ያመለክታል።

ወደ ማዕበል ይጣሉ
ይህ ሲኦልን ያመለክታል፡ የሙት አለም

ተናጋሪ ሰው
ስለ ሰዎች ክፉ ነገር የሚናገሩ ሰዎች

አመፀኛን ሰው ክፋት ለጥፋት ይፈልገዋል
እዚህ ላይ ክፋት አንድ ሰው ሌላ ሰውን ፈልጎ እንደሚበቀለው መስሎ ይናገራል።

Psalms 140:12

ለችግረኛ ፍርድን እንዲያደርግ
“ችግረኛውን ለመርዳት በስርአት ያደርጋል”

ስምህን
ይህ እግዚአብሔርን ያመለክታል። “አንተን”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 141

1 ያህዌ ሆይ፣ ወደ አንተ እጣራለሁ ፈጥነህ ድረስልኝ ወደ አንተ ስጣራ ድምፄን ስማ **2** ጸሎቴ በፊትህ እንደ ዕጣን ይሁንልኝ ወደ አንተ ያነሣሁት እጄም እንደ
ሠርክ መሥዋዕት ይቆጠርልኝ። **3** ያህዌ ሆይ፣ ለአፌ ጠባቂ አኑር የከንፈሮቼንም መዝጊያ ጠብቅ **4** ክፉ ለማድረግ ከመመኘትና ከክፉ አድራጊዎች ጋር
ከመተባበር፣ የድግሳቸውም ተካፋይ ከመሆን ጠብቀኝ። **5** ጻድቅ ሰው ቢቀጣኝ ለእኔ በጐነት ነው፤ እርሱ ቢገሥጸኝ ራሴን እንደሚቀባ ዘይት ነው እኔ ራሴም
ይህን እንቢ አልልም። ጸሎቴ ግን ሁሌም በክፉዎች ተግባር ላይ ነው። **6** መሪዎቻቸው ከገደል ጫፍ ቁልቁል ይወርወሩ ቃሌ እውነት መሆኗንም ይሰማሉ። **7**
ደግሞም፣ «ሰው ምድርን እንደሚያርስና ዐፈሩን እንደሚፈረካክስ፣ እንዲሁ ዐጥንታችን በሲኦል አፋፍ ላይ ተበታተነ» ይላሉ። **8** ጌታ፣ ያህዌ ሆይ፣ ዐይኖቼ ወደ
አንተ ይመለከታሉ መጠጊያዬ አንተ ነህ፤ ከእንግዲህ ነፍሴን አትተዋት። **9** ከዘረጉብኝ ወጥመድ ከክፉ አድራጊዎችም አሽክላ ጠብቀኝ። **10** እኔ በደኅና
ሳመልጥ ክፉዎች በገዛ ወጥመዳቸው ይውደቁ።

Psalms 141:1

አጠቃላይ ሃሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው

የዳዊት መዝሙር
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) ዳዊት መዝሙሩን ነው የፃፈው 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው የሚናገረው 3) መዝሙሩ የዳዊት መዝሙር አይነት ነው። በመዝሙረ ዳዊት 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ተመልከት

ጮኽሁ
“እርዳታ ጠየኩኝ”

የልመናዬን ቃል አድምጥ
“ስጠራህ እባክህ ስማኝ” ወይም “እለምንሃለሁ ስጠራህ ስማኝ”

ፀሎቴ በፊትህ እደ ዕጣን ተቀበልልኝ
መዝሙረኛው እግዚአብሔርን ፀሎቱን እና ልመናውን ልክ እንደ እጣን እንዲቀበለው ይጠይቃል። “የእጣን ሽታ ሰዎችን እንደሚማርክ የእኔ ልመና አንተን ይማርክ”

ፀሎቴ
መዝሙረኛው እግዚአብሔር በፀሎቱ እንዲማረክ ይፈልጋል።

እጅ መንሳቴ
እጅ መንሳት ፀሎትን ያመለክታል። ሰዎች ሲፀልዩ እና እግዚአብሔርን ሲያመልኩ እጃቸውን ወደላይ ያነሳሉ። መዝሙረ ዳዊት 134:2 ላይ “እጃችሁን አንሱ” የሚለው እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት።

እንደ ሰርክ መስዋእት ትሁን
ይህ ማለት በሰርክ ላይ በመሰዊያው የሚቀጣጠል እንስሳ ማለት ነው። መዝሙረኛው እግዚአብሔር በሚያደርገው የእንስሳ መስዋዕት ደስ እንዲሰኝ ይፈልጋል። እግዚአብሔር በሚፀልየው ፀሎት ደስ እንዲለው ይፈልጋል።

Psalms 141:3

ለአፌ ጠባቂ አኑር
መዝሙረኛው በአፉ ውስጥ ሊያመልተጥ እንደሚታገል ክፉ ነገር መስሎ ይናገራል። “እባክህ መጥፎን ነገርን እንዳልናገር እርዳኝ”

ጠባቂ አኑር
“እንዲጠብቅ መናገር”

የከንፈሮቼን መዝጊያ ጠብቅ
መዝሙረኛው በአፉ ውስጥ ሊያመልተጥ እንደሚታገል ክፉ ነገር መስሎ ይናገራል። “እባክህ መጥፎን ነገርን እንዳልናገር እርዳኝ”

ዓመፃን ከሚያደርጉ ሰዎች ጋር
“ኀጢአትን ማድረግ”

ከምርጦቻቸውም ጋር
“ለየት ያለ ምግብ”

Psalms 141:5

ይገስፀኝ
መዝሙረኛው መገሰፅን እንደ መምታት መስሎ ይናገራል። “ይገስፅሰኝ” ወይም “ሲያርመኝ እንደሰማ ምታኝ”

በቅንነት መንፈስ
“እርሱ ለኔ ቅን በሆነ መንፈስ”

የኀጢአተኛ ዘይት ግን ራሴን አይቀባ
ዘይት በራስ ላይ የሚቀባው ለሹመት/ማክበር ወይም ራስን ለማሻል ነው። ኀጢአተኛ ሰው በራሱ ላይ ዘይት እንዳያፈስ ያለው የእርሱ ራስ ሊቀበለው ይችላል ነገር ግን ጸሎቱ ገና ስለሀጥያታቸው ስለሆነ ነው።

ፀሎቴ ገና በክፋታቸው ላይ ነውና
“በክፋታቸው” የሚለው ቃል ክፋትን የሚያደርጉ ሰዎችን ያመለክታል። “እግዚአብሔር ክፉ ሰዎች ክፋትን ማድረግ እንዲያቆሙ ሁል ጊዜ እፀልያለሁ”

ሀያላኖቻቸው በአለት አጠገብ ተጣሉ
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) “አለቆችን ወደ አለት ይጥላቸዋል” ወይም 2) “አለቆቻቸው ይጥሉአቸዋል”

በገደል አለት
ወደታች ረጅም ርቀት ያለው ገደል

አጥንቶቻቸው በሲኦል ተበተኑ
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) “ሰዎች አጥንቶቻችንን በተለያየ አቅጣጫ አጥንቶቻችንን ጣሉአቸው” ወይም 2) ከገደል ላይ የመውደቅ ውጤት (141:6) “ሰውነታችን ተሰባብሮአል አጥንቶቻችን ተበታትነዋል።”

Psalms 141:8

አይኖቼ ወደ አንተ ናቸውና
“አይኖቼ” የሚለው ቃል ሙሉ ሰውን ያመለክታል። “ልታደርጋቸው ያልካቸውን ነገሮች አያለሁ” ወይም “እንድትረዳኝ እጠብቃለሁ”

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 142

1 ድምፄን ከፍ አድርጌ እንዲረዳኝ ወደ ያህዌ እጮኻለሁ ድምፄን ከፍ አድርጌ እንዲምረኝ ልመናየን ወደ ያህዌ አቀርባለሁ። **2** ብሶቴን በፊቱ አፈስሳለሁ
ችግሬንም እነግረዋለሁ። **3** መንፈሴ በውስጤ ሲዝል አንተ መንገዴን ታውቃለህ፤ መተላለፊያ መንገዴ ላይ በስውር ወጥመድ ዘረጉብኝ። **4** ወደ ቀኜ ብመለከት
የሚያስብልኝ ሰው አጣሁ ማምለጫም የለኝም ለሕይወቴም ደንታ ያለው የለም። **5** ያህዌ ሆይ፣ ወደ አንተ እጮኻለሁ «አንተ መጠጊያዬ ነህ በሕያዋን ምድር
ዕድል ፈንታዬ ነህ» እላለሁ። **6** እጅግ ተስፋ ቆርጫለሁና ጩኸቴን ስማ ከእኔ ይበልጥ ብርቱ ስለሆኑ ከአሳዶጆቼ አድነኝ። **7** ስምህን እንዳመሰግን ነፍሴን
ከእስር ቤት አውጣት። ለእኔ ያደረግኸውን መልካም ነገር ሲመለከቱ ጻድቃን በዙሪያዬ ይሰበሰባሉ።

Psalms 142:1

አጠቃላይ ሃሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው

ዋሻ
ከመሬት ስር ሰፊ ክፍት ቦታ ሲሆን ብዙ ሰዎች እንዲንቀሳቀሱ ያስችላል።

ወደ እግዚአብሔር ጮኽሁ...ወደ እግዚአብሔር ለመንሁ
እነዚህ ዐረፍተነገሮች ተመሳሳይነት ያላቸው በመሆናቸው አንባቢውን ግራ የሚያጋቡ ወይም ሌላ ትርጉም የሚሰጡ ከሆነ ወደአንድ አረፍተነገር ይተርጎሙ።

በቃሌ
“ቃሌን ተጠቅሜ”

ልመናዬን በፊቱ አፈስሳለሁ መከራዬንም በፊቱ እናገራለሁ
እነዚህ ዐረፍተነገሮች ተመሳሳይነት ያላቸው በመሆናቸው አንባቢውን ግራ የሚያጋቡ ወይም ሌላ ትርጉም የሚሰጡ ከሆነ ወደአንድ አረፍተነገር ይተርጎሙ።

ልመናዬን በፊቱ አፈሳለሁ
መዝሙረኛው ለእግዚአብሔር ለምን እንዳዘነ ልክ እንደ ፈሳሽ እንደሚፈስ መስሎ ይናገራል። “ለምን እንዳዘንኩ እነግረዋለሁ”

መከራዬንም በፊቴ እናገራለሁ
“የሚያሳስበኝን ሁሉ ለርሱ እነግረዋለሁ”

Psalms 142:3

ነፍሴ በውስጤ ባለቀች ጊዜ
x

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 143

1 ያህዌ ሆይ፣ ጸሎቴን ስማ ልመናዬንም አድምጥ። በታማኝነትህና በጽድቅህ ሰምተህ መልስልኝ። **2** በአንተ ፊት ማንም ጻድቅ አይደለምና ከባርያህ ጋር ወደ ፍርድ አትግባ። **3** ጠላት ነፍሴን አሳደዳት ገፍትሮም ወደ መሬት ጣለኝ። ቀደም ብለው እንደ ሞቱ ሰዎች በጨለማ ውስጥ አኑሮኛል። **4** ስለዚህ መንፈሴ በውስጤ ልቤም ተስፋ ቆረጠ። **5** የቀድሞውን ዘመን አስታወስሁ ሥራህንም ሁሉ አሰላሰልሁ አንተ ያደረግኸውንም አውጠነጠንሁ። **6** በጸሎት እጆቼን ወደ አንተ ዘረጋሁ እንደ ደረቀች ምድር ነፍሴ አንተን ተጠማች። ሴላ **7** ያህዌ ሆይ፣ መንፈሴ ዝሎአልና ፈጥነህ ስማኝ። ወደ ጉድጓድ እንደሚወርዱ እንዳልሆን ፊትህንም ከእኔ አትሰውር። **8** በአንተ ታምኛለሁና በማለዳ ምሕረትህን አሰማኝ። ነፍሴን ወደ አንተ አንሥቻለሁና የምሄድበትን መንገድ አሳየኝ። **9** ያህዌ ሆይ፣ አንተን መሸሸጊያ አድርጌአለሁና ከጠላቶቼ አድነኝ። **10** አንተ አምላኬ ነህና ፈቃድህን ማድረግ አስተምረኝ። ቅዱስ መንፈስህም በጽድቅ ምድር ይምራኝ። **11** ያህዌ ሆይ፣ ስለ ስምህ በሕይወት ጠብቀኝ በጽድቅህም ነፍሴን ከመከራዋ አውጣት። **12** ከታማኝነትህ የተነሣ ጠላቶቼን አጥፋቸው እኔ ባርያህ ነንና የሕይወቴን ጠላቶች ደምስሳቸው።

Psalms 143:1

አጠቃላይ ሃሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው

የዳዊት መዝሙር
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) ዳዊት መዝሙሩን ነው የፃፈው 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው የሚናገረው 3) መዝሙሩ የዳዊት መዝሙር አይነት ነው።

ፀሎቴን ስማ
“ፀሎቴን” የሚለው እየፀለየ ያለ ሰውን ያመለክታል። በመዝሙረ ዳዊት 39፡12 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት። “ወደአንተ ስፀልይ ስማኝ” ወይም “የምጠይቅህን ታደርግልኛለህ”

ወደ ፍርድ አትግባ
“አትፍረድ” ወይም “እንዳትፈርድ እለምንሃለው”

ከባሪያህ ጋር
መዝሙረኛው ራሱን ልክ ሌላ ሰው እንደሚያናግር መስሎ ያወራል። “እኔ ጋር”

በፊትህ ፃድቅ አይደለምና
“በፊትህ” የሚለው ፍድን ያመለክታል። “በፍርድህ ማንም ፃድቅ አደለም”

Psalms 143:3

ነፍሴን አሳድዶአታል
ነፍሴ የሚለው ሰውን ያመለክታል። “እኔን አሳድዶኛል”

በምድር ውስጥ አጎስቆሎአታል
ጠላትን ማሸነፍ ልክ እንደ ከባድ እቃ ቀለል ያለ እቃ ላይ ወድቆ እንደሚያበላሽ አድርጎ ይናገራል። “አሸንፎኛል”

ነፍሴ በውስጤ አለቀችብኝ
“እኔ ደከምኩ” ወይም “እኔ ተስፋ ቆረጥኩ”

ልቤም በውስጤ ደነገጠብኝ
“ተስፋ አጣሁ”

Psalms 143:5

አሰብሁ
“አሰብኩ”

ሥራህንም ሁሉ አሰላሰልሁ
“የሰራሃቸውን ሥራዎች ሁሉ” ወይም “ያደረካቸውን ትልቅ ነገሮች”

እጆቼን ወደአንተ ዘረጋሁ
እሥራኤላውያን በብዛት ቆመው እጃቸውን አንስተው እና ዘርግተው ይፀልያሉ። “እጄን አንስቼ ወደ አንተ ዘርግቼ እፀልያለሁ”

ነፍሴ እንደ ምድረበዳ አንተን ተጠማች
መዝሙረኛው ከእግዚአብሔር መሆንን ልክ እንደ ምድረበዳ ላይ እንዳለ ሆኖ በጥም ሊሞት እንዳለ አድርጎ ይናገራል። “ሰው በምድረበዳ በጥም ሆኖ ውሃ እንደሚፈልግ እኔም ከአንተ ጋር መሆን እፈልጋለሁ ”

ነፍሴ... አንተን ተጠማች
መዝሙረኛው እግዚአብሔርን ለማወቅ ያለውን ፍላጎት ያሳያል። እግዚአብሔርን የሚፈልግበት ልክ ደግሞ ልክ እንደ ተጠማ ሰው መስሎ ይናገራል። “አንተን እፈልግሀለሁ”

ነፍሴ
ነፍሴ የሚለው ሙሉ ሰውን ያመለክታል

ምድረበዳ
በውሃ እጦት ሁሉም የሚሞትበት ምድር ነው።

Psalms 143:7

ነፍሴ አልቃለች
“ነፍሴ” የሚለው ቃል ሙሉ ሰውን ያመለክታል። “እኔ ደክሜአለሁ” ወይም “እኔ ተስፋ ቆርጬአለሁ”

ፊትህን ከእኔ አትመልስ
ይህ ልመና ነው። “ከእኔ እትሸሽ” ወይም “ከእኔ እንዳትሸሽ አለምንህለሁ”

ፊትህን ከእኔ አትመልስ
መዝሙረኛው እግዚአብሔርን የጠየቀውን ነገር አለመመለሱን ልክ እንደ እግዚአብሔር መዝሙረኛውን መመልከት እስኪያቆም ድረስ መስሎ ይናገራል። “እኔን ከመስማት አትቆጠብ” ወይም “እባክህ ስማኝ”

ወደ ጉድጓድ እንደሚወርዱ አልሁን
ጉድጓድ የሚለው የሚያመለክተው የሙታን ቦታን ነው። ይህ ሐረግ የሞት ተመሳሳይ ነው። “እኔም ሌላ የሞተ ሰው እሆናለሁ።”

ምሕረትህን አሰማኝ
“ምሕረትህ እሰማ ዘንድ አድርግ” ወይም “ምሕረትህን ንገረኝ”። “ምንያህል ምሕረት እንደምታደርግ አሰማኝ”

በማለዳ
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) በማለዳ ብዙ ሰዎች ለፀሎት አመቺ ጊዜ ነው። 2) ማለደ በማለዳ ሁል ጊዜ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አስታውቀኝ
“ንገረኝ”

የምሄድበትን መንገድ
መዝሙረኛው የሰዎች አኗኗር ልክ አንደ የሚሄዱበት መንገድ መስሎ ይናገራል። “እንዴት እንድኖር የምትፈልግበትን”

ነፍሴን ወደ አንተ አንስቼአለሁና
ሊሆን የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ወደ አንተ እፀልያለሁ” ወይም 2) “አንተ እንደ ምትጠብቀኝ እና እንደ ምትመራኝ አምናለሁ”

Psalms 143:9

ወደ አንተ ተማፅኛለሁና
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) “ወደ አንተ መጣሁ አንተም ትሸፍነኛል” 2) “ወደአንተ ሸሸሁ አንተም ሸሸገኝ ጠብቀኝም”

ፈቃድህን ለማድረግ
“አንተ ምትፈልገውን እንዳደርግ”

በፅድቅ ምድር ይምራኝ
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) “በፅድቅ እንድኖር እርዳኝ” 2) “ህይወቴ ከችግር የራቀ ይሁን”

በፅድቅ ምድር
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) “የፅድቅ ኑሮን ያመለክታል” 2) “ከችግር የራቀ ሕይወትን ያመለክታል”

Psalms 143:11

ስለ ስምህ
የእግዚአብሔር ስም የሱን ማንነት ያመለክታል። “አንተ ስለሆንክ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 144

1 እጆቼን ለጦርነት ጣቶቼንም ለውጊያ የሚያሠለጥን ዐለቴ ያህዌ ይባረክ። **2** አንተ መታመኛዬና መጠጊያዬ ነህ ጽኑ ዐምባዬና ታዳጊዬ የምከለልበት ጋሻዬም ነህ ሕዝቦችን ከእግሬ በታች የምታስገዛልኝም አንተ ነህ። **3** ያህዌ ሆይ፣ ይህን ያህል የምትንከባከበው ሰው ምን ስለሆነ ነው? ይህን ያህል የምታስብለት የሰው ልጅስ ምንድነው? **4** ሰው እንደ እስትንፋስ ነው ዘመኑም እንደ ጥላ ያልፋል። **5** ያህዌ ሆይ፣ ሰማያትን ሰንጥቀህ ውረድ ይጤሱም ዘንድ ተራሮችን ዳስሳቸው። **6** የመብረቅ ብልጭታ ልከህ ጠላቶቼን በትናቸው ፍላጻህን ሰድደህ ግራ አጋባቸው። **7** ከላይ እጅህን ሰደህ ከብዙ ውሆች፣ ከባዕድ ሰዎችም እጅ ታደገኝ። **8** አንደበታቸው ሐሰት ይናገራል ቀኝ እጃቸውም የቅጥፈት ቀኝ እጅ ናት። **9** አምላክ ሆይ፣ አዲስ መዝሙር እዘምርልሃለሁ ዐሥር አውታር ባለው በገና ምስጋና አቀርብልሃለሁ። **10** አንተ ነገሥታትን ድልን ታጐናጽፋቸዋለህ አገልጋይህ ዳዊትንም ከስለታም ሰይፍ ትታደገዋለህ። **11** አንደበታቸው ሐሰት ከሚናገር ቀኝ እጃቸው የቅጥፈት ቀኝ እጅ ከሆነችው ከባዕዳን እጅ ታደገኝ። **12** ወንዶች ልጆቻችን በወጣትነታቸው የተሟላ ዕድገት እንዳገኘ ተክል ሴቶች ልጆቻችንም ቤተ መንግሥት ለማስጌጥ እንደ ተቀረጹ የማእዘን ዐምዶች ይሁኑ። **13** ጐተራዎቻችን በተለያዩ የእህል ዐይነቶች የተሞሉ ይሁኑ። በመስኮቻችን የተሰማሩ በጐች እስከ ሺህ ይወለዱ፣ እስከ ዐሥር ሺህ ይባዙ። **14** ከብቶቻችን ወላድ ይሁኑ። አይጨንግፉ አይጥፉ ቅሮቻችን በማንም አይደፈሩ እኛም በምርኮ አንወሰድ። በአደባባዮቻችን ጩኸት አይሰማ። **15** እንዲህ የሚሆንለት ሕዝብ የተባረከ ነው ያህዌ አምላኩ የሆነለት ሕዝብ የተባረከ ነው።

Psalms 144:1

አጠቃላይ ሃሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው

የዳዊት መዝሙር
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) ዳዊት መዝሙሩን ነው የፃፈው 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው የሚናገረው 3) መዝሙሩ የዳዊት መዝሙር አይነት ነው።

አለቴ
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) “የሚጠብቀኝ” ወይም 2) “ሀይልን የሚሰጠኝ”

ለእጆቼ ሰልፍን፣ ለጣቶቼም ዘመቻን የሚያስተምር
“ለእጆቼ” እና “ለጣቶቼም” የሚሉት ቃላት “እኔ” ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይነት አላቸው። “ለሰልፍ እና ለጦርነት የሚያዘጋጀኝ” ወይም “ለጦርነት የሚያለማምደኝ”

መሀሪዬ
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) የሚወደኝ 2) የሚጠብቀኝ

መሸሸጊያዬ...መጠጊያዬ
መዝሙረኛው የተለያዩ ቃላትን በመጠቀም የእግዚአብሔርን ጥበቃ ይናገራል።

ምሽጌ
ዳዊት እግዚአብሔርን ከውጊያ እንደሚጠብቀው ምሽግ መስሎ ይናገራል። ዳዊትን ከክፉ ነገር የሚጠብቀው እግዚአብሔር ነው።

መከታዬ
ዳዊት እግዚአብሔር ልክ አንደ መከታ የሚጠብቀው መስሎ ይናገራል። እግዚአብሔር ዳዊትን ከክፉ ነገሮች የሚጠብቀው ነው። በመዝሙረ ዳዊት 18፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

መጠጊያዬና
ወደ እግዚአብሔር ለከለላ መሄድ ልክ እርሱ እንደ መጠጊያ መስሎ ይናገራል። “እንዲጠብቀኝ ወደሱ የምሄድበት”

ሕዝቤንም ከእኔ በታች የሚያስገዛልኝ
“ሕዝቦችን እንዲሸነፉ ሊያደርግ የሚችል”

Psalms 144:3

እርሱን ታውቀው ዘንድ ሰው ምንድር ነው?
“ከፈጠርካቸው ነገሮች ሁሉ ሰው ትንሽ ሲሆን አንተ የሰውን ልጅ ማወቅህ ይገርመኛል”

ሰው... የሰው ልጅ
እነዚህ ሁለት ቃላቶች ሙሉ ሰውን ያመለክታል።

ከንቱን ነገር ይመስላል ዘመኑ እንደ ጥላ ያልፋል
ጸሐፊው ሰውን ከነዚህ ትናንሽ ነገሮች ጋር በማነፃፀር ህይወቱ ምን ያህል አጭር እንደሆነ ያሳያል።

Psalms 144:5

ዝቅ ዝቅ...ውረድም...አድርጋቸው...ዳስሳቸው...ላካቸው...በትናቸው...ላካቸው
መዝሙረኛው ከእርሱ በላይ እግዚአብሔር ትልቅነቱን ስለተረዳ እያዘዘ ሳይሆን እያቀረበ ነው።

ሰማዮችህን ዝቅ ዝቅ አድርጋቸው
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) ሰማዩን ክፈተው 2) የአንድ ዛፍን ቅርንጫፍ የሆነ ነገር ሲሄድበት እንደሚወርድ ወይም ቀስት ከመተኮሱ በፊት እንደሚጣመመው ሁሉ ሰማይን አውርድ።

አስደንግጣቸው
“አንተ ምታስበውን አያቁምና ወይም የምታደርገውን አያቁም”

Psalms 144:7

እጅህን ከአርያም ላክ አድነኝም ከብዙ ውኖች
ዳዊት እግዚአብሔር በምድር ላይ ከውሃ በላይ ሆኖ ዳዊትን ከውሃው በእጅ እንደሚጎትተው እና አእንደሚያወጣው መስሎ ይናገራል። ውሃዎች የሚለው ቃል በሌሎች የሚፈጠር ችግሮችን ያመለክታል። “አንተ ሁሉን የምትችል ችግሮችን እንዳልፍ እባክህ እርዳኝ”

ከባዕድ ልጆች እጅ
“እጅ” የሚለው ቃል ሃይል ወይም ጉልበትን ያመለክታል። “ከባዕድ ልጆች ጉልበት”

አፋቸው ምናምንን ከሚናገር
“አፋቸው” የሚለው ቃል የሚናገረውን ሰው ያመለክታል። “ምናምንን ይናገራሉ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እየማሉ እንኳን ይክዳሉ
x

Psalms 144:9

አዲስ ቅኔ
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) ከዚህ ቀደም ተቀኝተኸው ማታቀውን ቅኔ 2) ከዚህ ቀደም ማንም ተቀኝቶት ማያውቀውን ቅኔ

የሚሰጥ...ለነገስታት መድሃኒት
“አንተ የምትሰጥ” ...ለነገስታት አንተ መድሃኒት የምትሰጥ

ባሪያውን ዳዊትን
ዳዊት እራሱን እንደ ሌላ ሰው አድርጎ ይናገራል። “እኔ ዳዊት ያንተ ባሪያ”

ከክፉ ሰይፍ
ዳዊት ክፉ ሰዎችን እንደ ሰይፍ መሳሪያ መስሎ ይናገራል። “እኔን ለመግደል ከሚፈልጉ ከክፉ ሰዎች”

አድነኝ
እባክህ አድነኝ ነፃ አውጣኝ

ከባእድ ልጆች እጅ
“እጅ” የሚለው ቃል ሃይልን ያመለክታል። በመዝሙረ ዳዊት 144፡7-8 ላይ እንዴት እንደ ተረጎመው ተመልከት። “ከባዕድ ልጆች ሃይል”

አፋቸው ምናምንን ከሚናገር
“አፋቸው” የሚለው ቃል የሚናገረውን ሰው ያመለክታል። በመዝሙረ ዳዊት 144፡7-8 ላይ እንዴት እንደ ተረጎመው ተመልከት። “ምናምንን ይናገራሉ”

እየማሉ እንኳን ይክዳሉ
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) ዳዊት የሚናገረው በፍርድቤት ቀኝ እጃቸውን አንስተው የሚምሉ ከሆነ የሚናገሩት ነገር ሁሉ እውነት መሆን አለበት። “ምለው እንኳን እውነት አይናገሩም ይክዳሉ” 2) ቀኝ እጅ የሚያመለክተው ሀይል እና ጉልበትን ሲሆን “የሚያገኙት ነገር ሁሉ በውሸት ነው።” መዝሙረ ዳዊት 144፡7-8 እንዴት እንደ ተረጎመው ተመልከት።

Psalms 144:12

እንደ አዲስ አትክልት
ጤነኛ እና ጠንካራ

በጎልማሳነታቸው
ሰዎች የሚያድጉበት ጊዜ

ሴቶች ልጆቻቸውም እንደ እልፍኝ ያማሩና ያጌጡ
“ሴት ልጆቻችንም እንደ እልፍኝ ያማሩና ያጌጡ ይሁኑ”

እልፍኝ ያማሩና ያጌጡ
ትላልቅ ቤቶችን ደግፈው የሚይዙ የሚያምሩ የሚሰቀሉ

ተቀርፀው ቀጥ እንዳሉ ምሶሶዎች ናቸው
ቤተመቅደስን እንዲያምር ተቀርፀው ቀጥብለው የተሰሩ ናቸው

በመስካችን የተሰማሩት በጎች በሺህ የሚቆጠሩ
በሺህ የሚቆጠሩ ከመሆናቸው መስካችንን ይሞሉታል።

Psalms 144:14

ቅጥራቸውም መፍረሻና መውጫ የለውም
x

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 145

1 አምላኬና ንጉሤ ሆይ ከፍ ከፍ አደርግሃለሁ ስምህንም ከዘላለም እስከ ዘላለም እባርካለሁ። **2** በየቀኑ እባርክሃለሁ ስምህንም ከዘላለም እስከ ዘላለም
እባርካለሁ። **3** ያህዌ ምስጋናው ታላቅ ነው ታላቅነቱም አይመረመርም። **4** አንዱ ትውልድ ለቀጣዩ ትውልድ ሥራህን ያስተላልፋል ድቅ ሥራህንም ያውጃል። **5**
የክብርህን ግርማ፣ የሥራህንም አስደናቂነት አሰላስላለሁ። **6** ስለ ድንቅ ሥራህ ኃይል ይናገራሉ እኔም ታላቅነትህን ዐውጃለሁ። **7** የበጐነትህን ብዛት ያወሳሉ ስለ
ጽድቅህም ይዘምራሉ። **8** ያህዌ ቸር ነው፤ ርኅሩኅም ነው ለቁጣ የዘገየ ምሕረቱም የበዛ ነው። **9** ያህዌ ለሁሉም ቸር ነው ምሕረቱም በፍጥረቱ ሁሉ ላይ ነው። **10**
ያህዌ ሆይ፣ ፍጥረቶችህ ሁሉ ያመሰግኑሃል ቅዱሳንህም ይባርኩሃል። **11** ቅዱሳንህ የመንግሥትህን ክብር ይናገራሉ ስለ ኃይልህምይነጋገራሉ። **12**
የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ ለሰው ልጆች ያሳውቃሉ የመንግሥቱንም ክብር ይናገራሉ። **13** መንግሥትህ የዘላለም መግሥት ነው ግዛትህም ለትውልድ ሁሉ
ጸንቶ ይኖራል። **14** ያህዌ የሚንገዳገዱትን ሁሉ ይደግፋል የወደቁትንም ሁሉ ያነሣል። **15** የሁሉም ዐይን አንተን በተስፋ ይጠብቃል በተገቢ ጊዜ ምግባቸውን
ትሰጣቸዋለህ። **16** እጅህን ትዘረጋለህ የሕያዋንን ሁሉ ፍላጐት ታረካለህ። **17** ያህዌ በመንገዱ ሁሉ ጻድቅ ነው በሥራውም ሁሉ ቸር ነው። **18** ያህዌ ለሚጠሩት
ሁሉ በእምነት ለሚጠሩት ሁሉ ቅርብ ነው። **19** የሚፈሩትን ፍላጐት ይፈጽማል ጩኸታቸውንም ሰምቶ ያድናቸዋል። **20** ያህዌ የሚወዱትን ይጠብቃል
ዐመፀኞችን ሁሉ ግን ያጠፋል። **21** አፌ የያህዌን ምስጋና ይናገራል የሰው ልጅ ሁሉ ከዘላለም እስከ ዘላለም ቅዱስ ስሙን ይባርክ።

Psalms 145:1

አጠቃላይ ሀሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው

የዳዊት የምስጋና መዝሙር
ይህ ዳዊት የፃፈው የምስጋና መዝሙር ነው።

ከፍ ከፍ አደርግሃለሁ
“ለሕዝቦች አስገራሚነትህን እነግራለሁ”

ስምህን ለዘላለም እባርካለሁ
“ስም” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ራሱን ያመለክታል። በመዝሙረ ዳዊት 72:19 “ታላቁን ስም እባርካለሁ” የሚለው እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት። “እባርክሃለሁ” ወይም “አንተን ደስ የሚያሰኘውን አደርጋለሁ”

ስምህን ለዘላለም አመሰግናለሁ
“ስም” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ራሱን ያመለክታል። “አመሰግንሃለሁ” ወይም “ትልቅነትህል ለሕዝቦች እናገራለሁ”

Psalms 145:4

ኃይልህንም ያወራሉ
“ኃያል ስለሆን የምታደርገውን ነገሮች ሁሉ”

Psalms 145:6

የቸርነትህን ብዛት መታሰብ ያወጣሉ
“መልካምነትህን ለሌሎች ተናገር”

Psalms 145:8

x
ምሕረቱም በሥራው ሁሉ ላይ ነው

x
“በሚሰራው ሥራ ሁሉ ሰዎች እርሱ ምሕረትን ሲያደርግ ያያሉ”

Psalms 145:10

አቤቱ ሥራህ ሁሉ ያመሰግኑሃል
“የፈጠርካቸው ሰዎች ሁሉ ያመሰግኑሃል” ወይም “የፈጠርካቸው ሁሉ አንተን ያመሰግኑሃል”

Psalms 145:13

ግዛትህም ለልጅ ልጅ ነው
“ለዘለአለም ይቆያል”

Psalms 145:14

የተፍገመገሙትን ሁሉ ይደግፋቸዋል፣ የወደቁትንም ያነሣቸዋል
መዝሙረኛው እግዚአብሔር ሕዝቡን ሲያበረታታ ልክ ህዘቡ ደክመው አጠገቡ ሆነው እንደሚረዳ መስሎ ይናገራል። “ተስፋ የቆረጡትን ያበረታታቸዋል።”

የሁሉ አይን አንተን ተስፋ ያደርጋል
“አይን” የሚለው ቃል እግዚአብሔር ሥራውን እስኪሰራ ተስፋ የሚያደርጉ እና የሚያዩ ናቸው። “ሁሉም ያያል ተስፋንም ያደርጋሉ”

አንተ እጅህን ትከፍታለህ
በመልካምነት አንተ ትሰጣለህ

ሕይወት ላለውም ሁሉ መልምን ታጠግባለህ
“አንተ ለሁሉም ከሚያስፈልገው በላይ እና እስከፈለጉት መጠን ትሰጣለህ”

Psalms 145:17

እግዚአብሔር በመንገዱ ሁሉ ፃድቅ ነው
“ሕዝቡ እግዚአብሔር በሚያደርገው ነገር ሁሉ ፃድቅ እንደሆነ ያያሉ”

በሥራው ሁሉ ቸር ነው
“በሁሉ ነገር እርሱ ቸር ነው” ወይም ““ሕዝቡ እግዚአብሔር በሚያደርገው ነገር ሁሉ ፃድቅ እንደሆነ ያያሉ”

ለሚጠሩት ሁሉ ቅርብ ነው።
“ቅርብ ” የሚለው ቃል “ለመርዳት መዘጋጀቱን ነው”። “ለሚጠሩት ሁሉ ለመርዳት እርሱ ተዘጋጅቶአል”

ለሚፈሩት ምኞታቸውን ያደርጋል፣ ልመናቸውንም ይሰማል ያድናቸዋልም
“ለሚፈሩት እና በእውነት ለሚፀልዩት” ወይም “በሚፀልዩት ፀሎት ለሚያምናቸው”

Psalms 145:20

አፌ ... ይናገራል
“አፌ” የሚለው ቃል የሚናገረውን ያመለክታል። “የእግዚአብሔርን ምስጋና እናገራለሁ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የእግዚአብሔርን ምስጋና ይናገራል
“ለሁሉም የእግዚአብሔርን መልካምነት ተናገር”

ስጋም ሁሉ ለዘላለም ዓለም የተቀደሰውን ስሙን ይባርክ
“ስሙን” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ራሱን ያመለክታል። በመዝሙረ ዳዊት 72፡19 “ታላቁን ስም እባርካለሁ” የሚለው እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት። “ሁሉም ሕዝብ ይባርክ” ወይም “ሁሉም ሕዝብ እርሱን ደስ የሚያሰኘውን ነገር ያድርግ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 146

1 ያህዌን አመስግኑ ነፍሴ ሆይ፣ ያህዌን ባርኪ። **2** በሕይወት በምኖርበት ዘመን ሁሉ ለያህዌ እዘምራለሁ። **3** በገዦች አትተማመኑ ማዳን በማይችል የሰው ልጅም አትመኩ። **4** የሰው እስትንፋስ ሲያቆም ወደ መሬት ይመለሳል። ያን ጊዜ ዕቅዱ እንዳልነበረ ይሆናል። **5** ረዳቱ የያዕቆብ አምላክ ተስፋውም ያህዌ የሆነለት ሰው የተባረከ ነው። **6** ሰማይና ምድርን፣ ባሕርንና በውስጡ ያሉትንም የፈጠረ ያህዌ **7** ለተጨቆኑት የሚፈርድ፣ ለተራቡ ምግብን የሚሰጥ እርሱ ነው። ያህዌ እስረኞችን ነጻ ያወጣል። **8** ያህዌ የዕውራን ዐይን ይከፍታል። ያህዌ የተዋረዱን ከፍ ያደርጋል። ያህዌ ጻድቃንን ይወዳል። **9** ያህዌ መጻተኞን በምድር ይጠብቃል ደኸ አደጐችንና መበለቶችን ይደግፋል። የክፉዎችን መንገድ ግን ያጠፋል። **10** ያህዌ ለዘላለም ይነግሣል ጽዮን ሆይ፣ አምላክሽ ለትውልድ ሁሉ ንጉሥ ነው። ያህዌ ይመስገን።

Psalms 146:1

አጠቃላይ ሃሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው

ነፍሴ ሆይ እግአብሄርን አመስግኚ
“ነፍሴ” የሚለው ቃል የጸሐፊውን የውስጣዊ ማንነትን ያመለክታል። ጸሐፊው የውስጥ ማንነቱን እግዚአብሔርን እንዲያመሰግን ያዘዋል። “እግዚአብሔርን ከነፍሴ አመሰግነዋለሁ” ወይም “እግዚአብሔርን በሙሉ ህይወቴ አመሰግነዋለሁ”

በሕይወቴ
“እስክሞት ድረስ” ወይም “በሕይወት እስካለሁ ድረስ”

Psalms 146:3

በአለቆች
“በአለቆች” የሚለው ቃል የሁሉም ሰው መሪዎችን ያመለክታል።

ማዳን በማይችሉ በሰው ልጆች
“በማንም ሰው ምክንያቱም እነርሱ አያድናችሁም”

በሰው ልጆች
“በሰው ዘር” ወይም “በሰዎች”

ነፍሱ ትወጣለች
ይህ አነጋገር አንድ ሰው መሞቱን ያሳያል። “ሲሞት”

ወደ መሬቱም ይመለሳል
እግዚአብሔር በመጀመሪያ አዳምን ከአፈር እንደፈጠረው ሁሉ ሰው ሲሞት የሰው ስጋ ተመልሶ አፈር ይሆናል ይበሰብሳል።

Psalms 146:5

እርሱም ሰማይንና ምድርን ... ሁሉ የፈጠረ
“ሰማይና” እና “ምድርን” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት አጠቃላይ በአለም ላይ እና ጠፈር ላይ የተፈጠሩትን ነው።

እውነትን ለዘላለም የሚጠብቅ
“እውነትን ይጠብቃታል” ወይም “ታማኝነቱ ይኖራል”

Psalms 146:7

ለተበደሉት የሚፈርድ
“ሳያዳላ በነገሮች ይፈርዳል”

ለተበደሉት
“ለተበደሉት ሰዎች” ወይም “ሌሎች ሰዎች ለበደሉአቸው”

ለተራቡት
“ለተራቡ ሰዎች” ወይም “ለነዛ ለተራቡት ሰዎች”

እውሮችን ጥበበኞች ያደርጋቸዋል
እውሮችን ጥበበኛ መሆናቸውን ልክ እንደ እግዚአብሔር ራሱ ሰውን ጥበበኛ እንዳረገ መስሎ ይናገራል። “እውሮችን ጥበበኛ ያደርጋል”

እውሮች
“እውር ሰዎች” ወይም “ማየት የተሳናቸው ሰዎች”

እግዚአብሔር የወደቁትን ያነሳል
እግዚአብሔር ሰውን መርዳት እንደ አጠገቡ ሆኖ ከወደቀበት እንደ ሚያነሳ ሰው መስሎ ይናገራል። “እግዚአብሔር ተስፋ የቆረጡትን ይረዳል”

የወደቁትን
ይህ ድርጊት የሀዘን ምልክት ነው

Psalms 146:9

ይደግፋል
እግዚአብሔር አንድን ሰው ሲረዳ ልክ እንደ ሚያነሳቸው መስሎ ይናገራል።

ፅዮን ሆይ አምላክሽ
“ፅዮን” የሚለው ቃል የእሥራኤል ሕዝብን ያመለክታል። ጸሐፊው ለእሥራኤል ሕዝብ እንደሚሰሙት አርጎ እንደሚናገር ያሳያል። “የእሥራኤል ሕዝብ አምላካችሁ”

ለልጅ ልጅ
“ይነሳል” የሚለውን ቃል ከዚህ ላይ እናያለን። “ለልጀ ልጅ ይነሳል” ወይም “ለዘለአለም ይነሳል”

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 147

1 ያህዌ ይመስገን አምላካችንን በመዝሙር ማመስገን እንዴት መልካም ነው እርሱን ማመስገን ደስ ያሰኛል፤ ተገቢም ነው። **2** ያህዌ ኢየሩሳሌምን መልሶ ይሠራታል የተበተነውን የእስራኤል ሕዝብ ይሰበስባል። **3** ልባቸው የተሰበረውን ይፈውሳል ቁስላቸውንም ይጠግናል። **4** ከዋክብቱን ይቆጥራል ለእያንዳንዳቸውም ስም ይሰጣቸዋል። **5** ጌታችን ታላቅ፣ ኃይሉን የሚያስፈራ ነው ማስተዋሉም አይመረመርም። **6** ያህዌ የተጨቆኑትን ያነሣል ክፉዎችን ግን ወደ ምድር ይጥላል። **7** ለያህዌ በምስጋና ዘምሩ ለአምላካችን በበገና ዘምሩ። **8** ሰማያትን በደመና ይሸፍናል በተራሮች ሣር እንዲበቅል ለምድር ዝናብ ያዘጋጃል። **9** ለእንስሳት ምግባቸውን፣ የቁራ ጫጩቶች ሲንጫጩ ምግባቸውን ይሰጣቸዋል። **10** በፈረስ ኃይል አይደሰትም ደስታውን በሰው ጉልበት ጥንካሬ አያደርግም። **11** ያህዌ በሚፈሩት፣ በምሕረቱም በሚታመኑ ይደሰታል። **12** ኢየሩሳሌም ሆይ፣ ያህዌን አመስግኚ ጽዮንም አምላክሽን አወድሺ **13** እርሱ የበሮችሽን መወርወሪያ አጽንቶአልና በመካከልሽ ያሉ ልጆችሽንም ባርኮአል። **14** በድንበርሽ ውስጥ ብልጽግና አድርጐአል ማለፊያ ስንዴም ያጠግብሻል። **15** ትእዛዙን ወደ ምድር ይልካል ቃሉም በፍጥነት ይሮጣል። **16** በረዶውን እንደ ባዘቶ ያነጥፈዋል ጭጋጉንም እንደ ደመና ይበትነዋል። **17** የበረዶውን ድንጋይ ቁልቁል ይለቃል በውሽንፍሩስ ቅዝቃዜ ፊት ማን መቆም ይችላል? **18** ቃሉን ልኮ ያቀልጠዋል ነፋሱን ያነፍሳል ውሃንም ያፈስሳል። **19** ቃሉን ለያዕቆብ፣ ሥርዐት ጽድቁንም ለእስራኤል ያውጃል። **20** ለማንኛውም ሌላ ሕዝብ ይህን አላደረገም እነርሱም ፍርዱን አላወቁም። ያህዌ ይመስገን።

Psalms 147:1

አጠቃላይ ሀሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው

Psalms 147:2

ልባቸውን የቈሰሉትን ይፈውሳል፣ ሕማማቸውንም ይጠግናል።
ጸሐፊው የሕዝቡን ሀዘን እና ተስፋ መቁረጥ ልክ እንደ የሰውነት ቁስል መስሎ ሲናገር እግዚአብሔር ደግሞ ከቁላቸው እንደሚድኑ ተስፋ እየሰጣቸው እንደሆነ ይናገራል። “ላዘኑት እና አምሮአዊ ጉዳታቸው እነደ ሚድኑ ተስፋ ይሰጣቸዋል።”

Psalms 147:4

ለጥበቡም ቁጥር የለውም
“ማንም የእግዚአብሔርን ጥበብ የሚለካ የለም” ወይም “ጥበቡ ጥግ የለውም”

Psalms 147:6

እግዚአብሔር የዋሃንን ያነሳል
ጸሐፊው እግዚአብሔር የዋሃዎችን እምደሚያከብር ሲናገር ልክ ከመሬት ወደ ሰማይ ከፍ እንደአደረጋቸው መስሎ ይናገራል። “እግዚአብሔር የዋሃንን ያከብራል”

ኃጢአተኞችን ግን እስከ ምድር ድረስ ያዋርዳል
ጸሐፊው እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን እንደሚያዋርድ ልክ እግዚአብሔር መሬት ድረስ እንደሚያወርድ አድርጎ ይናገራል። “ኀጢአተኞችን ያዋርዳል”

በመሰንቆ ዘምሩ
መሰንቆ በመጫወት ዘምሩ

Psalms 147:10

የፈረስን ኃይል አይወድድም
ኃያል ፈረሶችን አይወድም

በሰውም ጭን
የሚሆነው ትርጉም 1) “የሰው ጭን” የሚለው ቃል አንድ ሰው በምንያህል ፍጥነት እንደሚሮጥ የሚያመለክት ነው። “በፍጥነት የሚሮጡ ሰዎች” 2) “የሰው ጭን” የአንድ ሰው ሙሉ አካል ጥንካሬን ያመለክታል። “እንዴት ሰዎች ጠንካሮች እንደሆኑ”

Psalms 147:15

ቃሉም እጅግ ፈጥኖ ይሮጣል
ጸሐፊው የእግዚአብሔር ቃልን ልክ እንደ ተላላኪ በፍጥነት የእግዚአብሔርን መልዕክት ለማድረስ እንደሚሄድ መስሎ ይናገራል።

አመዳዩን እንደ ባዘቶ ይሰጣል ጉሙን እንደ አመድ ይበትነዋል
x

Psalms 147:17

በረዶውን እንደ ፍርፋሪ ያወርዳል
እግዚአብሔር በረዶውን እንደሚያወርድ ልክ እንደ ሰው በቀላሉ ዳቦ እንደሚፈረፍር ይመስለዋል። “በረዶውን በቀላሉ ያወርዳል ልክ እንደ ፍርፋሪ”

ያወርዳል
ይልካል

በረዶ
ትናንሽ በረዶ ከሰማይ የሚዘንብ

በበረዶውስ ፊት ማን ይቆማል
ጸሐፊው ይህንን ጥያቄ ምንያህል እግዚአብሔር የላከው በረዶ ከባድ እንደሆነ እግንኖ ያሳያል። “ማንም ቢሆን በላከው በረዶ ሚኖር አይኖርም”

ቃሉን ልኮ ያቀልጠዋል።
ጸሐፊው የእግዚአብሔር ቃል እንደ መልእክተኛ መስሎ ይናገራዋል። “በረዶ እንዲቀልጥ በቃሉ ያዛል”

Psalms 147:19

ቃሉን ለያዕቆብ፣ ሥርዓቱንና ፍርዱን ለእሥራኤል ይናገራል
እነዚህ ሁለት አረፍተ ነገሮች አንድ አይነት ሀሳብ ሲኖራቸው ይህም እግዚአብሔር ህጎቹን ለእሥራኤል ብቻ እንደሰጠ ይናገራል።

ሥርዓቱንና ፍርዱን ለእሥራኤል ይናገራል
“ሥርዓቱንና ፍርዱን ለእሥራኤል ይናገራል”

ሥርዓቱንና ፍርዱን ለእሥራኤል ይናገራል
“ስርአቱንና ፍርዱን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሙሴ ህጎችን ነው።

ፍርዱንም አልገለጠላቸውም
ሌሎች ከተሞች የእግዚአብሔርን ስርአት እና ፍርዱን አያቁትም።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 148

1 ያህዌን አመስግኑ በሰማያት ያላችሁ ያህዌን አመስግኑ በከፍታዎች ያላችሁ ያህዌን አመስግኑ። **2** መላእክቱ ሁሉ አመስግኑ የመላእክቱ ሰራዊት ሁሉ አመስግኑት። **3** ፀሐይና ጨረቃ አመስግኑት የምታበሩ ከዋክብት ሁሉ አመስግኑት። **4** ሰማየ ሰማያት አመስግኑት ከሰማይ በላይ ያላችሁ ውሆች አመስግኑት። **5** እርሱ ስላዘዘ ተፈጥረዋልና የያህዌን ስም ያመስግኑ። **6** ከዘላለም እስከ ዘላለም አጸናቸው የማይሻር ሕግም ደነገገላቸው። **7** የባሕር ውስጥ ፍጥረትና ጥልቁ ውሃ ሁሉ ያህዌን ከምድር አመስግኑት። **8** እሳትና በረዶ ዐመዳይና ጭጋግ ትእዛዙንም የሚፈጽም ዐውሎ ነፋስ **9** ተራሮችና ኮረብቶች፣ የፍሬ ዛፎችና ዝግቦች ሁሉ አመስግኑ። **10** የዱር አራዊት፣ የቤት እንስሳት በምድር የሚርመሰመሱ ፍጥረቶችና ወፎችም ሁሉ **11** የምድር ነገሥታትና ሕዝቦች ሁሉ መሳፍንቶችና የምድር ገዦች ሁሉ ያህዌን አመስግኑ። **12** ወጣት ወንዶችና ወጣት ሴቶች አረጋውያንና ሕፃናት ያመስግኑት። **13** የእርሱ ስም ብቻውን ከፍ ከፍ ብሎአልና ክብሩም ከምድርና ከሰማያት በላይ ነውና የያህዌን ስም ያመስግኑ። **14** እርሱ ለሕዝቡ ቀንድን አስነሥቶአል ለቅዱሳኑ ሁሉ ምስጋና፣ እጅግ ቅርቡ ለሆነው ሕዝቡ ለእስራኤል ልጆች። ያህዌን አመስግኑ።

Psalms 148:1

አጠቃላይ ሀሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው

እግዚአብሔርን ከሰማያት አመስግኑት በአርያም አመስግኑት
“እግዚአብሔርን ከሰማያት አመስግኑት በአርያም አመስግኑት” እነዚህ ሁለቱ “አርያም” እና “ከሰማያት” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ከበፊቱ መስመር ጋር አንድ አይነት ሃሳብ አላቸው።

Psalms 148:3

ፀሀይና ጨረቃ አመስግኑት
ጸሐፊው ፀሃይና ጨረቃ ልክ እንደ ሰው መስሎ እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑት ያዛል። “እግዚአብሔርን ሰዎች እንደሚያመሰግኑት ፀሃይና ጨረቃ አመስግኑት”

ከዋክብት እና ብርሃን ሁሉ አመስግኑት
ጸሐፊው ከዋክብት እና ብርሃን ልክ እንደ ሰው መስሎ እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑት ያዛል። “እግዚአብሔርን ሰዎች እንደሚያመሰግኑት ከዋክብት እና ብርሃን አመስግኑት”

Psalms 148:5

የእግዚአብሔርን ስም ያመስግኑት
“ስም” የሚለው ቃል ራሱን እግዚአብሔርን ያመለክታል። “እግዚአብሔርን ያመስግኑት”

ተፈጠሩም
“እርሱ ፈጠራቸው”

ለዘላለም ዓለም አቆማቸው ትእዛዝን ሰጠ፣ አያልፉምም
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) “የማይለዋወጥ ትዛዝን ሰጠ” 2) “መታዘዝ ያለባቸውን ትዕዛዛትን ሰጣቸው”

ሰጠ
“ሰጠ”

Psalms 148:7

ጥልቆችም ሁሉ
ይህ ሃረግ ጥልቀት ካላቸው ባህሮች ውስጥ የሚኖሩ ፍጥረታትን ያመለክታል። “በጥልቁ ባህር ውስጥ ያሉ ፍጥረታት ሁሉ”

እሳትና በረዶ አመዳይና ውርጭ
ጸሐፊው እነዚህን የተፈጥሮ ተአምራቶችን እንደ ሰው መስሎ እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ ያዛቸዋል።

ቃሉን የሚያደርግ ዓውሎ ነፋስም
ቃሉን የሚያዘውን የሚያደርግ ዓውሎ ነፋስ

Psalms 148:9

አያያዥ ሀሳብ
ጸሐፊው ሰው ያልሆኑ ነገሮችን ሰዎች እንደሆኑ ያህል እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ ማዘዙን ይቀጥላል።

አራዎት እንስሳትም ሁሉ ተንቀሳቃሾች
እነዚህ ቃላቶች የተለያዩ ሲሆኑ በአንድ ላይ ሁሉንም እንስሳቶችን ይወክላሉ። “እንስሳት ሁሉ”

Psalms 148:11

አያያዥ ሀሳብ
ጸሐፊው ሁሉም ሰው እግዚአብሔርን እንዲያመሰግን ያዛል።

የምድር ነገሥታት
ይህ ቃል የሚያመለክተው በውስጡ የሚኖሩትን ሕዝቦችን ነው። “በምድር ላይ ሕዝቦች ሁሉ”

ጎልማሶችና ቆነጃጅቶች ሽማግሌዎችና ልጆች
ጎልማሶችና ቆነጃጅቶች ሽማግሌዎችና ልጆች ጸሐፊው ሁለት ማነፀፀሪያ ሲጠቀም አንደኛው በፆታ ሲሆን አንደኛው ደግሞ በእድሜ ነው ይህም ሁሉንም ሰው ለማመልከት ነው።

Psalms 148:13

የእግዚአብሔርን ስም ያመስግኑ ስሙ ብቻውን
እዚህ ጋር “ስም” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ራሱን ነው። “እግዚአብሔር ራሱ ብቻውን”

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 149

1 ያህዌን አመስግኑ ለያህዌ አዲስ መዝሙር ዘምሩ **2** በቅዱሳን ጉባኤ ምስጋናውን አቅርቡ። እስራኤል በፈጣሪው ደስ ይበለው የጽዮንም ልጆች በንጉሣቸው ሐሤት ያድርጉ። **3** ስሙን በሽብሸባ ያመስግኑ በከበሮና በመሰንቆ ይዘምሩለት። **4** ያህዌ በሕዝቡ ደስ ይለዋል በማዳኑ ትሑታንን ያከብራቸዋል። **5** ቅዱሳን በድል ደስ ይበላቸው በመኝታቸውም ላይ እልል ይበሉ። **6** የእግዚአብሔር ምስጋና በአንደበታቸው በሁለት ወገን የተሳለ ሰይፍም በእጃቸው ይሁን። **7** ይህም በአሕዛብ ላይ በቀልን፣ በሕዝቦችም ላይ ፍርድን ያደርጉ ዘንድ **8** ንጉሦቻቸውን በሰንሰለት መሳፍንቶቻቸውንም በእግር ብረት ያስራሉ። **9** ይህም በእነርሱ ላይ የተጻፈውን ፍርድ ለመፈጸም ነው። ይህ ለቅዱሳኑ ሁሉ ክብር ይሆናል። ያህዌን አመስግኑ።

Psalms 149:1

አጠቃላይ ሀሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው

አጠቃላይ ሃሳብ
መዝሙረኛው የእግዚአብሔርን ሕዝቦች እየተናገረ ነው

አዲሱን ቅኔ
የሚሆነው ትርጉም 1) ከዚህ ቀደም ተቀኝተኸው ማታቀውን ቅኔ 2) ከዚህ ቀደም ማንም ተቀኝቶት ማያውቀውን ቅኔ

ተቀኙለት ምስጋናው...
“በምስጋና ዘምሩለት”

Psalms 149:2

በፈጣሪው ደስ ይበለው
የሚሆነው ትርጉም 1) ስለፈጠራቸው ደስ ይበላችሁ 2) የፈጠራቸው መልካም ስለሆነ ደስ ይበላችሁ

በንጉሣቸው ሐሤትን ያድርጉ
“በንጉሳቸው” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ያመለክታል። የሚሆነው ትርጉም 1) እርሱ ንጉሳቸው ስለሆነ ደስ ይበላቸው 2) ንጉሳቸው መልካም ስለሆነ ሀሴት ያድርጉ

ስሙን በዘፈን ያመስግኑ
“ስሙን” የሚለው ቃል ራሱን እግዚአብሔርን ያመለክታል። “እሱን አመስግኑ” ወይም “ታላቅነቱን ለሕዝቦች ተናገሩ”

በከበሮ
የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን ከላይ በኩል የሚመታ እንደ ከበሮ ሲመስል በጎኖቹ ደግሞ ብረት ዙሪያውን ሲኖረው ሲነቃነቅ የሚያሰማው ድምፅ ነው።

Psalms 149:4

የዋሃንንም በማዳኑ ከፍ ከፍ ያደርጋልና
“የዋሆችን በማዳን ከፍ ከፍ ያደርጋቸዋል”

የዋሆች
“የዋህ የሆኑትን”

በምንጣፋቸውም ላይ
ይህ የሚያመለክተው በማታ ወደ መኝታው አልጋ የሚተኛውን ሰው ነው።
“በምሽት ወደ አልጋቸው የሚተኙትን”

Psalms 149:6

የእግዚአብሔር ምስጋና በጉሮሮአቸው ነው
“ጉሮሮአቸው” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሙሉ ሰውን ነው።
“እግዚአብሔርን ለማመስገን ሁልጊዜ የተዘጋጁ ይሁኑ”

ሁለት አፍ ያለውም ሰይፍ በእጃቸው ነው
“ሰይፍ” የሚለው ቃል ለጦርነት እና ለውጊያ መዘጋጀትን ያመለክታል።
“ለእርሱ ጦርነት ለመዋጋት ሁልጊዜ ዝግጁ ይሁኑ”

አሕዛብ ላይ
“አሕዛብ ላይ” የሚለው ቃል በዛች ከተማ የሚኖሩትን ሕዝብ ያመለክታል።
“የከተማዋ ሕዝቦች”

Psalms 149:8

በሰንሰለት
እስረኛዎች እንዳይንቀሳቀሱ ተብሎ ከከባድ ብረታብረት የሚሰራ ነው።

በእግር ብረት
በእግር ወይም በእጅ ላይ የሚደረጉ ሰንሰለት ሲሆን እንቅስቃሴን ይቀንሳል።

የተጻፈውን ፍርድ ያደርጉባቸው ዘንድ
“ፍርድ” የሚለው ቃል “መፍረድ” ወደሚለው መቀየር ይቻላል።
“እግዚአብሔር እንዲሆን እንደፃፈው ሕዝቡ ላይ ይፈርዳሉ እናም ይቀጧቸዋል”

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 150

1 ያህዌን አመስግኑ እግዚአብሔርን በመቅደሱ አመስግኑት **2** ስለ ብርቱ ሥራው አመስግኑት ከአእምሮ በላይ ስለሆነው ታላቅነቱ አመስግኑት። **3** በመለከት ድምፅ አመስግኑት በበገናና በመሰንቆ አመስግኑት። **4** በከበሮና በሽብሸባ አመስግኑ በባለ አውታርና የእስትንፋስ መሣሪያ አመስግኑት። **5** ከፍ ያለ ድምፅ ባለው ጸናጽል አመስግኑት ድምፁ መልካም በሆነ ጸናጽል ወድሱት። **6** እስትንፋስ ለው ሁሉ ያህዌን ያመስግን። ያህዌን አመስግኑ።

Psalms 150:1

አጠቃላይ ሀሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው

አጠቃላይ ሀሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው

አጠቃላይ ሀሳብ
በመቅደሱ የሚሆኑትን አምልኮ እና ምስጋና ላይ ያተኩራል

እግዚአብሔርን በመቅደሱ አመስግኑት
ይህ ቦታ ለአምልኮ የሚኬድበት ቦታ ነው።

በሀይሉ ጠፈር
x

Psalms 150:3

አጠቃላይ ሀሳብ
ይህ የሚያተኩረው በሙዚቃ መሳሪያ እና በጭፈራ ማመስገን እና ማምለክ ላይ ነው።

በከበሮ
የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን ከላይ በኩል የሚመታ እንደ ከበሮ ሲመስል በጎኖቹ ደግሞ ብረት ዙሪያውን ሲኖረው ሲነቃነቅ የሚያሰማው ድምፅ ነው።

ፅናፅል
ሁለት ቀጫጭን ብረቶች አብረው በመሆን አንድላይ ሲመቱ ከፍተኛ ድምፅ ያሰማሉ።

Psalms 150:6

አጠቃላይ ሀሳብ
ይህ ቁጥር የመዝሙረ ዳዊት መጽሐፍ መጨረሻ ከመሆን ያለፈ ለሁሉም 5 የመዝሙር መጽሐፎች የመደምደሚያ ሀሳብ ነው። በመዝሙር 107 ጀምሮ በመዝሙር 150 ይጨርሳል።

እስትንፋስ ያለው ሁሉ
ይህ አግንኖ የሚናገረው በሕይወት ሆነው እግዚአብሔር እንዲያመልኩ የሚጠራ መልእክት ነው።

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Proverbs

Proverbs

Chapter 1

1 የእስራኤል ንጉስ፣ የዳዊት ልጅ የሰለሞን ምሳሌዎች። 2 እነዚህ ምሳሌዎች የተጻፉት ጥበብንና ተግሳጽን፣ አርቆ ለማስተዋል የሚያስችሉ ቃላትን፣ 3 እርማትን በመቀበል ጽድቅ፣ ፍትሕና ሚዛናዊ የሆነ ብያኔን በማድረግ እንድትኖር ለማስተማር ነው። 4 ከዚህ በተጨማሪ እነዚህ ምሳሌዎች የተጻፉት ላልተማሩ ጥበብን፣ ለወጣቶች ደግሞ እውቀትንና ልባምነትን ለመስጠት ነው። 5 ጥበበኞች ያድምጡና ትምህርታቸውን ያዳብሩ፣ አስተዋዮች ደግሞ ምሪትን ያግኙበት፣ 6 ይህ ደግሞ የጠቢባንን ምሳሌዎች፣ አባባሎችና ቃላቶች እንደዚሁም እንቆቅልሾቻቸውን እንዲረዱ ነው። 7 እግዚአብሔርን መፍራት የጥበብ መጀመርያ ነው፣ ሞኞች ግን ጥበብንና ተግሳጽን ይንቃሉ። 8 ልጄ ሆይ፣ የአባትህን ምክር ስማ፣ የእናትህንም ሕግ አትተው፤ 9 ለራስህ የሞገስ አክሊል፣ ለአንገትህ ደግሞ ውበት የሚሰጥ ጌጥ ይሆኑልሃል። 10 ልጄ ሆይ፣ ኃጢአተኞች በኃጢአታቸው እንድትሳተፍ ሊያባብሉህ ቢሞክሩ፣ እሺ አትበላቸው። 11 “ከእኛ ጋር ና፣ ነፍስ ለመግደል ተደብቀን እንጠብቅ፣ ንጹሐን ሰዎችን ያለ ምንም ምክንያት ለማትፋት እንሸምቅበት። 12 ሲኦል ጤናማ ሰዎችን እንደሚውጣቸው፣ ወደ ጉድጓድ እንደሚወርዱ፣ እንዲሁ በሕይወት እያሉ እንዋጣቸው። 13 ሁሉም አይነት ውድ የሆኑ ነገሮች እናገኛለን፤ ከሌሎች ሰዎች በሰረቅናቸው ነገሮች ቤቶቻችንን እንሞላለን። 14 ከእኛ ጋር ዕጣህን ጣል፤ ሁላችንም አንድ የጋራ ቦርሳ ይኖረናል።” ቢሉህ፣ 15 ልጄ ሆይ፣ ከእነርሱ ጋር በዚያ መንገድ አትሂድ፤ እነርሱ በሚሄዱበት መንገድ እግርህ አይርገጥ፤ 16 እግሮቻቸው ወደ ክፋት ይሮጣሉ፣ ደም ለማፍሰስም ይቸኩላሉ። 17 ወፍ ፊት ለፊት እያየች ወፍን ለመያዝ ወጥመድ መዘርጋት ጥቅም የለውም። 18 እነዚህ ሰዎች ራሳቸውን ለመግደል ተደብቀው ይጠብቃሉ፣ በራሳቸው ላይ ወጥመድን ይዘረጋሉ። 19 ፍትሃዊ ባልሆነ መንገድ ሀብትን ያከማቹ ሰዎች መንገዳቸው እንደዚህ ነው፣ ፍትሃዊ ባልሆነ መንገድ የተከማቸ ሃብት የባለቤቱን ሕይወት ያጠፋል። 20 ጥበብ በጎዳና ላይ ጮኻ ትጣራለች፣ በአደባባይም ድምጿን ከፍ ታደርጋለች፤ 21 ጩኸት በበዛባቸው ጎዳናዎች ላይ ትጣራለች፣ በከተማ መግቢያ በሮች ላይ እንዲህ በማለት ትናገራለች፣ 22 እናንተ ጥበብ የሌላችሁ አላዋቂነትን የምትወዱት እስከ መቼ ነው? እናንተ ፌዘኞች በፌዝ የምትደሰቱት እስከ መቼ ነው? እናንተ ሞኞች እውቀትን የምትጠሉት እስከ መቼ ነው? 23 ለዘለፋየ ትኩረት ስጡ፤ ሃሳቤን ሁሉ ለእናንተ አፈስሳለሁ፤ ቃሎቼን አሳውቃችኋለሁ። 24 ጠራኋችሁ፣ እናንተ ግን ለመስማት እምቢ አላችሁ፤ እጄን ለእናንተ ዘረጋሁ፣ ነገር ግን አንድም ሰው ትኩረት አልሰጠውም። 25 ነገር ግን እናንተ ተግሳጼን በሙሉ ችላ አላችሁ፣ ለዘለፋየ ደግሞ ትኩረት አልሰጣችሁም። 26 እኔ ደግሞ በመከራችሁ እስቃለሁ፣ ሽብር በመጣባችሁ ጊዜ አላግጥባችኋለሁ፣ 27 አስፈሪ ድንጋጤ እንደ ማዕበል በእናንተ ላይ ሲመጣባችሁ፣ ጥፋት እንደ አውሎ ነፋስ እናንተን ሲጠራርጋችሁ፣ ጭንቅና ችግር በእናንተ ላይ በመጣ ጊዜ። 28 በዚያን ጊዜ ይጠሩኛል፣ እኔም አልመልስላቸውም፤ አጥብቀው ይፈልጉኛል፣ ነገር ግን አያገኙኝም። 29 እውቀትን ስለ ጠሉ፣ እግዚአብሔርን መፍራት ስላልመረጡ፣ 30 ምክሬን አልተከተሉምና፣ ዘለፋየንም ሁሉ ናቁ። 31 የመንገዳቸውን ፍሬ ይበላሉ፣ በእቅዳቸው ፍሬ ይጠግባሉ። 32 እነዚህ ያልተማሩ ሰዎች ከእውቀት መራቃቸው ይገድላቸዋል፣ ሞኞችንም ቸልተኝነታቸው ያጠፋቸዋል። 33 ነገር ግን የሚያደምጠኝ ሁሉ በሰላም ይኖራል፣ ከመከራም ስጋት ያርፋል።

Proverbs 1:1

አጠቃላይ መረጃ፦
ቁጥር 2-33 ግጥም ነው። (ግጥም የሚለውን ይመልከቱ)

ጥበብን እና ተግሳፅን ለማስተማር
ይህን ለውጦ “ጥበብ” እና “ተግሳፅ” የተባሉት ረቂቅ ስሞችን እንደ ገላጭ ወይም ግስ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ እንዴት ጥበበኛ መሆን እንደሚቻል እናንተን ለማስተማር እና እንዴት ግብረገባዊ ህይወት መኖር እንደሚቻል አቅጣጫ ለማሳየት ነው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

አርቆ ለማስተዋል የሚያስችሉ ቃላትን ለማስተማር
“ጥበበኛ አስተምህሮዎችን እንድትረዱ ለማገዝ”

ስለዚህ እናንተ እንድትቀበሉ
እዚህ ላይ “እናንተ” የሚመለከተው አንባቢዎችን ነው። በእናንተ ቋንቋ የተለመደ ከሆነ “እኛ” በሚለው አካታች ቃል መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ስለዚህ እኛ እንድንቀበል” (የሁለተኛ መደብ ቅርጾችን እና አካታች “እኛ” ይመልከቱ)

ለመኖር የሚያስችል መመሪያ ለመቀበል
ይህን ለውጦ “መመሪያ” የሚለው ረቂቅ ስምን እንደ ግስ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እንዴት መኖር እንደሚገባህ ታውቅ ዘንድ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 1:4

በተጨማሪ ለአላዋቂዎች ጥበብ ለመስጠት ነው
ይህን ለውጦ “ጥበብ” የሚለውን ረቂቅ ስም እንደ ቅፅል “ጠቢብ” ብሎ ማቅረብ ይቻላል። ይህ ደግሞ እንደ ገቢር/አድራጊ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ደግሞ ለአላዋቂዎች እንዴት ጠቢብ መሆን እንደሚቻል ለማስተማር ነው” (ረቂቅ ስሞች እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገቢሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

አላዋቂ
ልምድ የሌለው ወይም የአእምሮ ብስለት የሌለው

እውቀት እና ጥንቃቄን ለወጣቶች ለመስጠት
“እውቀት” እና “ጥንቃቄ” የሚሉት ረቂቅ ስሞች እንደ ግስ መቅረብ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ ወጣቶች ማወቅ የሚገባቸውን እና ማድረግ የሚገባቸውን ትክክለኛውን ነገር እንዴት መወሰን እንዳለባቸው ለማስተማር ነው (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ጥንቃቄ
በእያንዳንዱ ሁኔታ ምን መደረግ እንዳለበት ለማወቅ

ጥበበኛ ሰዎች ያድምጡ፣ እውቀትንም ይጨምሩ
“ጠቢቦች ያስተውሉ፣ ተጨማሪ እውቀትን ያግኙ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አስተዋዮች ምሪት ያግኙ
“አስተዋይ ሰዎች ከእነኚህ ምሳሌዎች እንዴት ጥሩ ውሳኔ መወሰን እንዳለባቸው ይማሩ”

እንቆቅልሾች
አንድ ሰው ስለ እነርሱ ካሰላሰለ በኋላ ብቻ ሊረዳቸው የሚችላቸው አባባሎች

Proverbs 1:7

አጠቃላይ መረጃ፦
አባት ልጁን ያስተምራል።

የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው
“ፍርሀት”፣ “መጀመሪያ” እና “ጥበብ” የሚሉት ረቂቅ ስሞች እንደ ግስ መቅረብ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ጥበብ ምን እንደሆነ ማወቅ ከመጀመርህ በፊት እግዚአብሔርን መፍራት አለብህ” ወይም “ጥበብ ምን እንደሆነ ለመማር መጀመሪያ እግዚአብሔርን ማክበር እና መታዘዝ አለብህ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ
ይህ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ውስጥ ለህዝቡ የገለጠላቸው ስሙ ነው። ይህንን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ ለመረዳት ስለ ያህዌ የሚናገረውን የትርጉም ቃል ገፅ ላይ ይመልከቱ።

ሞኞች ጥበብን እና ተግሳፅን ይንቃሉ
ለጥበብ እና ለምክር ዋጋ የማይሰጡ ሞኞች ናቸው።

አትተወው
ይህ ፈሊጥ “ችላ አትበለው” ወይም “አትናቀው” ማለት ነው (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ለራስህም የሞገስ ዘውድ ለአንገትህም ውበት የሚሰጥ ጌጥ ይሆንሃልና
ወላጆች ለልጆቻቸው የሚያስተምሩት መመሪያ እና ተግሳፅ በጣም ጠቃሚ እና ትልቅ ዋጋ ያለው ስለሆነ እንደ ቆንጆ አንገት ላይ የሚደረግ ጌጥ ወይም የአበባ ጉንጉን ተደርገው ተገልፀዋል። አማራጭ ትርጉም፦ የአበባ ጉንጉን በራስ ላይ ወይም ድሪ በአንገት ላይ ማድረግ ውበትን እንደሚሰጥ እንደዚሁ እነርሱ ጠቢብ ያደርጉሀል (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አክሊል
ከአበባ ወይም ከቅጠል ተሰካክቶ የተሰራ ክብ ቅርፅ ያለው ዘውድ

ድሪ
በአንገት ዙሪያ የሚደረግ ጌጥ

Proverbs 1:10

በሀጢያታቸው እንድትሳተፍ ሊያባብሉህ ሞከሩ
“እነርሱ እንደሚያደርጉት ሀጢያትን እንድትሰራ ሊያሳምኑህ ሞከሩ”

አትከተላቸው
“እሺ አትበላቸው” ወይም “አትስማቸው”

ቢያባብሉህ
እዚህ ላይ ተናጋሪው ሀጢያተኞች አንድን ሰው ምን ማድረግ እንዳለበት ለማባበል ለሞክሩ የሚችሉትን ምሳሌ ይሰጣል። (ግምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

እናድባ
“ተሸሸጎ ትክክለኛውን ጊዜ መጠበቅ”

Proverbs 1:12

አጠቃላይ መረጃ፦
ቁጥር 12-14 ሌሎች ሰዎች ሀጢያት እንዲሰሩ ለማባበል የሚሞክሩ የሀጢያተኞችን የሀሳብ ቃል ይጠቀልለዋል።

ሲኦል ጤናማ ሰዎችን እንደሚውጣቸው እንዲሁ በህይወታቸው ሳሉ እንዋጣቸው
ሀጢያተኞች ልክ እንደ ሲኦል ንፁሀንን ስለ መግደል ያወራሉ፣ ህያው እና ጤነኛ ሰዎችን የሞቱ ሰዎች ወደሚሄዱበት ቦታ ይወስዳሉ። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንዋጣቸው. . . . ሲኦል እንደሚውጥ
እዚህ ላይ መቃብር ሰዎችን እንደሚውጥና ወደ ሙታን ቦታ እንደሚወስድ ሰው ተመስሎ ይነገራል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሲኦል ጤናማ ሰዎችን እንደሚውጣቸው
የሙታን መኖሪያ የሆነው ሲኦል ጤናማ ሰዎችን እንኳን እንደሚውጥ እንዲሁ ክፉዎች ሰለባዎቻቸውን ለማጥፋት ተስፋ ያደርጋሉ።

ወደ ጉድጓድ እንደሚወርዱ እናርጋቸው
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች እነዚህ ናቸው፦ 1) ማንም ሊያገኘው የማይችል፣ ጥልቅ ጉድጓድ ውስጥ የገቡ መንገደኞችን ያመለክታል ወይም 2) እዚህ ላይ “ጉድጓድ” የሚለው ቃል ሲኦል ወይም የሞቱ ሰዎች የሚገቡበት ቦታ ማለት ነው።

ከእኛ ጋር ዕጣህን ጣል
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ተቀላቀለን” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ሁላችንም አንድ የጋራ ቦርሳ ይኖረናል
እዚህ ላይ “ቦርሳ” የሚወክለው የሰረቁትን ነገር በሙሉ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የሰረቅነውን በሙሉ እኩል እንካፈላለን” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ቦርሳ
ገንዘብ ለመያዝ የሚሆን ከረጢት

Proverbs 1:15

ከእነርሱ ጋር በዚያ መንገድ አትሂድ፤ እነርሱ በሚሄዱበት መንገድ እግርህ አይርገጥ
የሀጢያተኞችን ድርጊት እና ባህርይ አለመከተል ልጁ ሀጢያተኞች በሚሄዱበት መንገድ አለመሄዱ እና ፈፅሞም አለመንካቱ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “ከሀጢያተኞች ጋር አትሂድ ወይም የሚያድርጉትን አታድርግ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እግሮቻቸው ወደ ክፋት ይሮጣሉ
ሀጥያተኞች ክፉ ነገሮችን ለማድረግ ያላቸው ጉጉት ወደ ክፋት እየሮጡ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “ክፉ ነገሮችን ለማድረግ የተጠመ ናቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እግሮቻቸው ይሮጣሉ
እዚህ ላይ “እግር” የሚለው የሚወክለው ሙሉ ግለሰቡን ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ይሮጣሉ” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ደም ለማፍሰስ
እዚህ ላይ “ደም” የሚወክለው የሰውን ህይወት ነው። “ደም ለማፍሰስ” ማለት አንድ ሰውን መግደል ማለት ነው። (ምትክ ስም የሚለውን የመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወፍ ፊት ለፊት እያየች እርስዋን ለመያዝ ወጥመድ መዘርጋት ጥቅም የለውም
ይሄ ተለዋጭ ዘይቤ ፊት ለፊት እያየች ያለውን ወጥመድ ያመለጠች ወፍን ጥበብ እና ለራሳቸው በሰሩት ወጥመድ ስር የወደቁ ሀጥያተኞችን ሞኝነት ያወዳድራል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 1:18

እነዚህ ሰዎች የራሳቸውን ደም ለማፍሰስ ተደብቀው ይጠብቃሉ - በራሳቸው ላይ ወጥመድን ይዘረጋሉ
ይህ በምሳሌ 1:17 የጀመረውን ንፅፅር ያጠናቅቀዋል። ኃጢአትን በመለማመድ ራሳቸውን እያጠፉ ያሉት ሰዎች ለራሳቸው ወጥመድ አጥምደው ራሳቸውን እንደ ገደሉ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነኚህ ሰዎች ግን ከወፎቹም የበለጠ ሞኝ ናቸው። ራሳቸውን በገዛ ወጥመዳቸው ገደሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ ሰዎች የራሳቸውን ደም ለማፍሰስ ተደብቀው ይጠብቃሉ
ተደብቆ መጠበቅ መሸሸግ ነው፣ ጭካኔን ለማድረግ መዘጋጀት። አማራጭ ትርጉም፡- “ራሳቸውን ለመግደል ምቹ ጊዜ እንደ መጠባበቅ ነው” ወይም “ሌሎችን ለመግደል እየሞከሩ ስለሆነ እነርሱ ራሳቸው ይገደላሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የራሳቸውን ደም
እዚህ ላይ ደም ለአስከፊ ሞት ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- ራሳቸውን በአስከፊ ሁኔታ ለመግደል (ምትክ ስም የሚለውን የመልከቱ)

በራሳቸው ህይወት ላይ ወጥመድን ይዘረጋሉ
እዚህ ላይ “የራሳቸው ህይወት” የሚለው ራሳቸው ለሚለው ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- ራሳቸው የገዛ ራሳቸውን በድንገት አጥቅቶ ለመግደል በመጠባበቅ ላይ እንዳሉ የሚቆጠር ነው (ምትክ ስም የሚለውን የመልከቱ)

የሁሉም መንገዳቸው እንደዚህ ነው
የአንድ ሰው መድረሻ ወይም እጣ ፋንታ ልክ አንድ ሰው እንደሚራመድበት መንገድ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይህ ነው ሁሉም ሰው ላይ የሚደርሰው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ፍትሀዊ ባልሆነ መንገድ የተከማቸ ሀብት የባለቤቱን ህይወት ያጠፋል
ሀብትን በሀይል፣ በስርቆት እና በማታለል ለማግኘት በመሞከር ራሳቸውን እያጠፉ ያሉ ሰዎች ፍትሃዊ ባልሆነ መንገድ የተገኘው ሀብት ራሳቸውን እንደሚገላቸው ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- ፍትሀዊ ባልሆነ መንገድ የተገኘው ሀብት የባለቤቶቹን ህይወት እንደሚያጠፋ እንደዚያ ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 1:20

አጠቃላይ መረጃ፡-
በ 1:20-1:33 ላይ ጥበብ ለህዝቡ እንደምትናገር ሴት ተደርጎ ተነግሯል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥበብ ትጮሀለች
ቋንቋህ ጥበብን በከተማው ውስጥ ለህዝቡ እንደምትጮህ ሴት ለመጠቀም ካልፈቀደልህ እንደዚህ ብለህ መሞከር ትችላለህ፡- “እምዬ ጥበብ ትጮሀለች” ወይም “ክብርት ጥበብ ትጮሀለች” ወይም “ጥበብ እንደምትጮህ ሴት ናት” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን የመልከቱ)

ድምፅዋን ከፍ ታደርጋለች
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጉም፡- በጉልህ ደምፅ ትናገራለች (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

በአደባባይ
ይህ ቡዙ ሰዎች የሚገኙበት ቦታ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በገበያ ቦታዎች” ወይም “በከተማዋ ዋና አደባባዮች” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ጩኸት በበዛባቸው ዋና ጎዳናዎች ላይ
እነዚህ አማጭ ትርጉሞች ናቸው፡- 1) “ዋና” የሚለው የተጨናነቁ ጎዳናዎች የሚገናኙበት ቦታ ያመለክታል ወይም 2) “ዋና” ጩኸት በበዛበት ጎዳና ላይ ያሉ ሰዎች ጥበብን ሊመለከቱ እና ሊሰሙ የሚችሉበት የግንብ ጫፍን ያመለክታል።

እናንት አላዋቂዎች እስከመቼ አላዋቂነትን ትወዳላችሁ?
ጥበብ ይህንን ጥያቄ ጠቢብ ያልሆኑትን ለመገሰፅ ትጠቀምበታለች። አማራጭ ትርጉም፡- “እናንተ አላዋቂዎች አላዋቂ መሆንን መውደድ ማቆም አለባችሁ።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

አላዋቂ
ልምድ የሌለው ወይም የአእምሮ ብስለት የሌለው

እናንተ ፌዘኞች እስከመቼ በፌዝ ትደሰታላችሁ፣ እናንተ ሰነፎች እስከመቼ እውቀትን ትጠላላችሁ?
ጥበብ ፌዘኞችን እና ሰነፎችን ለመገሰፅ ይህንን ጥያቄ ትጠቀማለች። አማራጭ ትርጉም፡- “እናንተ የምታፌዙ በፌዝ መደሰታችሁን ማቆም አለባችሁ፣ እና እናንተ ሰነፎች እውቀትን መጥላት ማቆም አለባችሁ።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 1:23

አጠቃላይ መረጃ፡-
ጥበብ መናገሯን ቀጥላለች። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ትኩረት ስጡ
“በጥንቃቄ አዳምጡ”

ሀሳቤን ለእናንተ አፈስሳለሁ
ጥበብ ስለ ህዝቡ የምታስበውን በሙሉ ለእነርሱ መንገሯ ሀሳቧ እንደ ፈሳሽ የምታፈሰው እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን የመልከቱ)

ቃሎቼን አሳውቃችኋለሁ
“የማስበውን እነግራችኋለሁ”

እጄን ዘረጋሁ
x

Proverbs 1:26

አጠቃላይ መረጃ፡-
ጥበብ በናቋት ላይ ምን እንደሚደርስ በማብራራት መናገሯን ቀጥላለች።

እስቃለሁ
ጥበብ የምትባለው ሴት እርስዋን በማቃለላቸው ምክንያት በናቋት ላይ የምትስቅባቸው እንደሆነ ለማሳየት “ስለዚህ” የሚለውን ቃል በመጠቀም መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለዚህ እስቃለሁ” (አያያዥ ቃላት የሚለውን ይመልከቱ)

በመከራችሁ ላይ
“መጥፎ ነገር ሲደርስባችሁ”

ሽብር በመጣ ጊዜ
“ሽብር” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ቅፅል መገለፅ ይችላል። “በተሸበራችሁ ጊዜ” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

አስፈሪ ድንጋጤ እንደ ማዕበል በመጣባችሁ ጊዜ ..... እንደ ዐውሎ ነፋስ ..... በመጣባችሁ ጊዜ
(ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ) በሕዝቡ ላይ የደረሰው አስከፊ ነገር እነርሱን እንደመታቸው ማዕበል፣ ፍርሃትና መከራ ጋር ተነጻጽሯል።

ዐውሎ ነፋስ
በጣም ሀይለኛ ጉዳትን የሚያስከትል የነፋስ ማዕበል

Proverbs 1:28

አያያዥ ሀሳብ፡-
ጥበብ መናገሯን ቀጥላለች። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የዚያን ጊዜ ይጠሩኛል
“የዚያን ጊዜ የናቁኝ ለእርዳታ ወደ እኔ ይጮሀሉ”

እውቀትን ስለ ጠሉ
“እውቀት” የሚለውን ረቂቅ ስም “ተማረ” እንደሚለው ግስ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- ጠቢብ ለመሆን መማርን ስላልፈቀዱ (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን መፍራት አልመረጡም
“ፍርሀት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔርን አልፈሩም” ወይም “እግዚአብሔርን አላከበሩትም ደግሞም አልታዘዙትም” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ምክሬን አልተከተሉም
“ትዕዛዜን አልተቀበሉም” ወይም “ምክሬን አልተቀበሉም”

Proverbs 1:31

አጠቃላይ መረጃ፡-
ቀጥር 33 በምሳሌ 1:22 ላይ የጀመረውን የጥበብ መግለጫ ይደመድማል።

የመንገዳቸውን ፍሬ ይበላሉ
እዚህ ላይ የአንድ ግለሰብ ባህርይ መንገድ ወይም አቅጣጫ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። በተጨማሪም አንድ ሰው የባህሪውን ውጤት መቀበሉ ግለሰቡ የባህሪውን ፍሬ እየበላ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- ድርጊታቸው የሚያመጣውን መዘዝ መለማመድ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በእቅዳቸውም ፍሬ ይጠግባሉ
“የእቅዳቸውን ፍሬ እስከሚጠግቡ ድረስ ይመገባሉ።” የተንኮለኛ ሴራውን ውጤት የሚቀበል ግለሰብ የእቅዱን ፍሬ እንደሚበላ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “በተንኮለኛ ሴራቸው መዘዝ ይሰቃያሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አላዋቂ
ልምድ የሌለው ወይም የአእምሮ ብስለት የሌለው

መራቃቸው ይገድላቸዋል
ጥበብን የማይቀበል ግለሰብ በአካል ከጥበብ እንደ ራቀ ተደርጎ ተነግሯል። ይህ በገቢር/አድራጊ መልኩ ሊነገር ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለመማር ስላልፈቀዱ ሞቱ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰነፎችን ቸልተኛነታቸው ያጠፋቸዋል
“ቸልተኛ” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሞኞች ምን መደረግ እንደሚገባ ግድ ስለማይሰጣቸው ይሞታሉ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ቸልተኛነት
ስለ አንድ ነገር ፍላጎት ማጣት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 ልጄ ሆይ፣ ቃሎቼን ብትቀበልና ትእዛዛቴን በአንተ ዘንድ ብታኖር፣ **2** ጥበብን ብታደምጥና ልብህን ወደ እውቀት ብትመልስ። **3** እውቀትን ለማግኘት ብትጣራና ድምጽህን ከፍ አድርገህ ለማስተዋል ብትጮህ፣ **4** ብርን አጥብቀህ እንደምትፈልግ እርስዋንም ብትፈልጋት፣ የተሰወረ ሃብትን እንደምትፈልግ እንደዚሁ ማስተዋልን ብትሻት፣ **5** በዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን መፍራት ታውቃለህ፣ የአምላክንም እውቀት ታገኛለህ። **6** እግዚአብሔር ጥበብን ይሰጣልና፣ እውቀትና ማስተዋል ከአንደበቱ ይወጣሉ። **7** እርሱ ደስ ለሚያሰኙት ጥልቅ ጥበብን ያከማቻል፣ ያለ ነቀፋ ለሚሄዱ ጋሻ ነው፣ **8** የፍትህን መንገድ ይጠብቃል፣ ለእርሱ ታማኞች ለሆኑት ደግሞ መንገዳቸውን ያጸናል። **9** በዚያን ጊዜ ጽድቅን፣ ፍትህንና ሚዛናዊነትን እንደዚሁም ማንኛውንም መልካም መንገድ ትገነዘባለህ። **10** ጥበብ ወደ ልብህ ትመጣለችና፣ እውቀትም ነፍስህን ደስ ታሰኛለች። **11** የመለየት ችሎታ ይጠብቅሃል፣ ማስተዋል ይጋርድሃል። **12** እነዚህ ከክፋት መንገድ፣ ጠማማ ንግግር ከሚናገሩ ሰዎች፣ **13** ትክክለኛውን መንገድ ከተዉና በጨለማ መንገድ ከሚሄዱ ይጠብቁሃል። **14** እነዚህ ክፋትን ሲያደርጉ ደስ ይላቸዋል፣ በጠማማነት ሃሴት ያደርጋሉ። **15** ጠማማ መንገድን ይከተላሉ፣ አካሄዳቸውን ደግሞ በአታላይነታቸው ይደብቃሉ። **16** ጥበብና ልባምነት ከአመንዝራ፣ ከጀብደኛና በንግግሯ ከምታታልል ሴት ያድኑሃል። **17** ይህች ሴት የወጣትነት በልዋን የተወችና የአምላክዋን ቃል ኪዳን የረሳች ናት። **18** ቤቷ ወደ ሞት ያዘነበለ ስለሆነ አካሄዷ በመቃብር ወዳሉት ሙታን ይመራሃል። **19** ወደ እርስዋ የሚገቡ ሁሉ እንደገና አይመለሱም፣ የሕይወትንም መንገድ አያገኙም። **20** ስለዚህ አንተም በመልካም ሰዎች መንገድ ትሄዳለህ፣ የጻድቃንን መንገድ ትከተላለህ። **21** ጻድቃን ቤታቸውን በምድሪቱ ይሰራሉና፣ እነዚህ ነቀፋ የሌለባቸው ደግሞ በእርሷ ጸንተው ይኖራሉና። **22** ክፉዎች ግን ከምድሪቱ ይቆረጣሉ፣ ታማኝነት የሌላቸውም ከእርሷ ይወገዳሉ።

Proverbs 2:1

አጠቃላይ መረጃ:-
አባት ልጁን ግጥም በመጠቀም ያስተምራል። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ቃሎቼን ብትቀበል
“የማስተምርህን ብትሰማ”

ትዕዛዛቴን በአንተ ዘንድ ብታኖር
ለታዘዙት ነገር ዋጋ መስጠት ትዕዛዛቶቹ ሀብት እንደሆኑ እና ግለሰቡ ሀብቱን ለማስቀመጥ አስተማማኝ ቦታ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም:- “ትዕዛዞቼ እንደ ሀብት ዋጋ እንዳላቸው አስብ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጆሮዎችህ እንዲያተኩሩ አድርግ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጉም:- “በጥንቃቄ ለማዳመጥ ራስህን አስገድድ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥበብን
ይህ ረቂቅ ስም እንደ ቅፅል ሊቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “እያስተማርኋችሁ ወዳለሁት ወደ ጥበብ ነገሮች” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ልብህን ወደ ማስተዋል አዘንብል
እዚህ ላይ “ልብ” የሰውን አእምሮ ይወክላል። “ልብህን አዘንብል” የሚለው ሀረግ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን አእምሮን ለአንድ ተግባር ሙሉ ለሙሉ መስጠት ወይም ማዘጋጀት ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ጥበብ የሆነውን ለመረዳት ጠንክረህ ሞክር” ወይም “ጠቢብ አስተምሮዎችን ለመረዳት ራስህን ሙሉ በሙሉ ስጥ” (ምትክ ስም እና ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 2:3

ማስተዋልን ለማግኘት ብትጣራ እና ድምፅህን ከፍ አድርገህ ብትጮህ
እነኚህ ሁለት ሀረጎች አንድ አይነት ትርጉም አላቸው። ግለሰቡ እግዚአብሔርን አጥብቆ ማስተዋልን እየለመነ እንደሆነ ያመላክታል። አማራጭ ትርጉም:- “በአስቸኳይ እግዚአብሔርን ከጠየቅህ እና ማስተዋልን ከለመንክ” (ትይዩነት እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ድምፅህን ከፍ አድርገህ ብትጮህ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ጮክ ብሎ መናገር ወይም መጮህ ማለት ነው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

እርስዋን ብር እንደምትፈልግ ብትሻት እና ማስተዋልን የተቀበረ ገንዘብን እንደምትፈልግ ብትፈልጋት
ሁለቱም ሀረጎች አንድ አይነት ትርጉም አላቸው። እነዚህ ተነፃፃሪ ዘይቤዎች አንድ ሰው ጠቢብ የሆነውን ለመረዳት ማድረግ የሚገባውን ፅኑ ጥረት ያሳስባሉ። አማራጭ ትርጉም:- “ዋጋ ያለው ነገርን ለማግኘት ጥረት በምታደርጉበት መጠን ማስተዋልን ብትፈልጉ” (ትይዩነት እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ብትሻት..... ማስተዋልን ብትፈልጋት
ጥበብ የሆነውን ለመረዳት በጣም በፀና መሞከር አንድ ሰው መፈለግ ያለበት እቃ በሚገባ እንደመረዳት ተደርጎ ተነግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔርን እውቀት ታገኛለህ
እግዚአብሔርን በማወቅ ስኬታማ መሆን የእግዚአብሔር እውቀት አንድ ሰው ከፍለጋ በኋላ የሚያገኘው ነገር እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 2:6

ከአንደበቱም እውቀት እና ማስተዋል ይወጣሉ
እዚህ ላይ “አንደበት” እግዚአብሔር ራሱን ወይም የሚናገረውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “ከእግዚአብሔር እውቀት እና ማስተዋል ይወጣሉ” ወይም “እግዚአብሔር ማወቅ እና ማስተዋል ያለብንን ይነግረናል” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ደስ ለሚያሰኙት ጥልቅ ጥበብን ያከማቻል
እግዚአብሔር ለሰዎች ጥበብ ማስተማሩ ጥበብ እግዚአብሔር የሚያከማቸው እና ለሰዎች የሚሰጠው ነገር እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም:- “ለሚያስደስቱት ለእነርሱ በእውነት ጠቢብ የሆነውን ያስተምራል።” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መልካም
“የሚያስተማምን”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለእነርሱ ጋሻ ነው
እግዚአብሔር ህዝቡን መከላከል መቻሉ እርሱ ጋሻ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር እነርሱን ይከላከላል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ያለነቀፋ ለሚሄዱ
ያለነቀፋ የሚሄድ ሰው ያለነቀፋ እንደሚራመድ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነቀፋ የሌለበት ሕይወት የሚኖር” ወይም “መኖር የሚገባቸውን ሕይወት የሚኖሩ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የፍትህን መንገድ ይጠብቃል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ፍትህ ራሱ መንገድ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ሰዎች በፍትህ መመላለሳቸውን ያረጋግጣል” ወይም 2) የሰው ህይወት መንገድ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “በፍትህ የሚመላለሱትን እግዚአብሔር ይጠብቃል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የእነርሱን መንገድ ያፀናል
የአንድ ሰው ህይወት መንገድ ወይም አቅጣጫ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚያን ይከላከላል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 2:9

ፍትሃዊነት
ትክክለኛነት

መልካም መንገድን ሁሉ
x

Proverbs 2:11

ጥንቃቄ ይጠብቅሀል፣ ማስተዋልም ይጋርድሀል
“ጥንቃቄ” እና “ማስተዋል” አንድ ሌላ ሰውን መጠበቅ የሚችሉ ሰዎች እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። እነዚህ ሁለት ሀሳቦች በመሰረቱ አንድ አይነት ትርጉም አላቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ በጥንቃቄ ስለምታስብ እና ትክክል እና ስህተት የሆነውን ስለምትረዳ የተጠበቅህ ትሆናለህ” (ሰውኛ ዘይቤ እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ጥንቃቄ
በድርጊት እና ንግግር ጥንቁቅ የመሆን ችሎታ

ይጠብቅሀል
አንድን ሰው ወይም እንድን ነገር ለመጠበቅ፣ ለመከላከል ወይም ለመንከባከብ

እነርሱ ከክፋት መንገድ ያድኑሃል
“እነርሱ” የሚለው አንድን ሰው መጠበቅ የሚችሉ ሰዎች እንደሆኑ ተደርጎ የተነገረላቸው ጥንቃቄ እና ማስተዋልን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ከሆነው መራቅን ታውቃለህ” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከክፋት መንገድ
ክፉ ባህሪ ክፋት አንድ ሰው የሚራመድበት መንገድ ወይም አቅጣጫ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ትክክለኛውን መንገድ የተወ እና በጨለማ መንገድ የሚጓዝ
ትክክለኛ የሆነውን የማያደርግ ነገር ግን ክፉ የሆነውን ለማድረግ የወሰነ ግለሰብ በትክክለኛው መንገድ መጓዝ እንዳቆመ እና በጨለማው መንገድ መጓዝ እንደመረጠ ሰው ተደርጎ ተነግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የተወ
“እርሱ” የሚለው ጠማማውን ነገር የሚናገሩትን ሰዎች ይወክላል።

መተው
ወደ አንድ ሰው ወይም አንድ ነገር ፈጽሞ ላይመለሱ ትቶ መሄድ

Proverbs 2:14

ደስ ይሰኛሉ
እነርሱ የሚለው ምሳሌ 2:12 ላይ ያሉትን ሰዎች ይወክላል

በክፉ ጠማማነት ሀሴት ማድረግ
ይህ ከመጀመሪያው የዐረፍተ ነገር ክፍል ጋር በመሰረቱ አንድ አይነት ትርጉም አለው። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ እንደሆነ የሚያውቁትን በማድረግ ሀሴት ያደርጋሉ” (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ጠማማ መንገድን ይከተላሉ
ሌሎችን የሚዋሹ ሰዎች የተጣመመ ወይም የተጠመዘዘ መንገድ ላይ እንደሚጓዙ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሌላ ሰዎችን ያታልላሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አካሄዳቸውን በአታላይነታቸው ይደብቃሉ
ሌሎች ሰዎች ምን እንዳደረጉ እንዳያውቁባቸው የሚዋሹ ሰዎች ማንም ሰው መንገድ ላይ እንዳያይከተላቸው አካሄዳቸውን እንደሸፈኑ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ማንም ሰው ያደረጉትን እንዳያውቅ ይዋሻሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 2:16

አጠቃላይ መረጃ፡-
አባት ልጁን ጥበብ እንዴት እንደምትጠብቀው ማስተማር ቀጥሏል።

ጥበብ እና ጥንቃቄ ያድኑሀል
ፀሀፊው ጥበብ እና ጥንቃቄን የተቆጣጠራቸውን ግለሰብ የሚያድኑ ሰዎች እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበብ እና ጥንቃቄ ካለህ ራስህን ታድናለህ” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የወጣትነት ወዳጅዋን
ይህ ልጅ እያለች ያገባችውን ባለቤትዋን የሚያመለክት ነው።

የአምላክዋን ቃል ኪዳን
ይህ ሊወክል የሚችለው በእግዚአብሔር መገኘት ውስጥ ከባለቤትዋ ጋር ስለፈፀመችው የጋብቻ ቃል ኪዳን ነው።

Proverbs 2:18

ቤትዋ ወደ ሞት ይመራል
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች 1) “ወደ ቤትዋ መሄድ ወደ ሞት ይወስዳል” ወይም 2) “ወደ ቤትዋ የሚወስደው መንገድ ወደ ሞት የሚወስድ መንገድ ነው።”

አካሄዷ ይመራሀል
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች 1) “ወደ ቤትዋ ያለው መንገድ ይመራሀል” ይህ ወደ ቤትዋ የሚያመራውን መንገድ ወይም ዱካ ይወክላል 2) ይህ ተለዋጭ ዘይቤ አኗኗርዋን እንደምትጓዝበት መንገድ አድርጎ የሚናገር ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የአኗኗር መንገዷ ይመራሀል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በመቃብር ወዳሉት
ይህ የሙታንን መንፈስ ይወክላል ደግሞም ለሙታን መኖሪያም ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ወደ መቃብር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እርስዋ መግባት
ይህ አንድ ሰው ከሴተኛ አዳሪ ጋር እንደሚያደርገው ከእርስዋ ጋር ለመተኛት ወደ ቤትዋ መሄድ ማለት ነው። (ለስላሴ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የህይወትን መንገድ አያገኙም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ወደ ህያዋን ምድር አይመለሱም” ወይም 2) “መቼም ቢሆን እንደገና ደስተኛ ህይወትን አይኖሩም።”

Proverbs 2:20

ታዲያ
ፀሀፊው ማስተዋል እና ጥንቃቄን የማግኘት ውጤትን ይናገራል።

በመንገድ ትሄዳለህ ..... ጎዳና ትከተላለህ
የአንድ ሰው ጠባይ በመንገድ ላይ እየተጓዘ እንዳለ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “በመንገዱ ትኖራለህ.....ምሳሌውን ተከተል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉዎች ከምድሪቱ ይቆረጣሉ
ፀሀፊው እግዚአብሔር ሰዎችን ከምድሪቱ ማስወገዱን አንድ ሰው ቅርንጫፍን ከዛፍ ላይ እንደሚቆርጥ እግዚአብሔር ሰዎቹን እየቆረጠ እንደሆነ አድርጎ ተናግሯል። ይህ በገቢር/አድራጊ መልኩ መገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ክፉዎችን ከምድሪቱ ያስወግዳል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉዎች ..... ታማኝነት የጎደላቸው
እነኚህ የስም ቅፅሎች እንደ ቅፅል ሊገለፁ የሚችሉ ናቸው። አማራጭ ትርጉም፡- እነዚያ ክፉ የሆኑት..... እነዚያ ታማኝነት የጎደላቸው ወይም ክፉ ሰዎች..... ታማኝነት የጎደላቸው ሰዎች (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ታማኝነት የሌላቸው ከእርስዋ ይቆረጣሉ
ፀሀፊው እግዚአብሔር ሰዎችን ከምድሪቱ ማስወገዱን አንድ ሰው ቅርንጫፍን ከዛፍ ላይ እንደሚቆርጥ እግዚአብሔር ሰዎቹን እየቆረጠ እንደሆነ አድርጎ ተናግሯል። ይህ በገቢር/አድራጊ መልኩ መገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ታማኝነት የሌላቸውን ከእርስዋ ያስወግዳል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 ልጄ ሆይ፣ ትእዛዛቴን አትርሳ፣ ትምህርቴንም በልብህ ጠብቅ፣ **2** በሕይወትህ ብዙ ቀኖችንና ዓመቶችን እንደዚሁም ሰላምን ይጨምሩልሃል። **3** በኪዳን የተመሰረተ ታማኝነትና እውነተኛነት አይለዩህ፣ በአንገትህ ዙርያ በአንድ ላይ እሰራቸው፣ በልብህም ጽላት ላይ ጻፋቸው። **4** በዚያን ጊዜ ሞገስና መልካም ስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ታገኛለህ። **5** በሙሉ ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፣ በራስህም ማስተዋል ላይ አትደገፍ፤ **6** በመንገድህ ሁሉ እርሱን እወቅ፣ እርሱም መንገድህን ቀና ያደርገዋል። **7** በራስህ አስተያየት ጥበበኛ አትሁን፤ እግዚብሔርን ፍራ፣ ከክፉም ራቅ። **8** ይህም ለስጋህ ፈውስ፣ ለሰውነትህም መታደስ ይሆንልሃል። **9** እግዚአብሔርን በሀብትህና በምርትህ ሁሉ በኩራት አክብረው፣ **10** ጎተራህ ሙሉ ይሆናል፣ ገንዳህ ደግሞ በአዲስ ወይን ጠጅ ተትረፍርፎ ይሞላል። **11** ልጄ ሆይ፣ የእግዚአብሔርን ቅጣት አትናቅ፣ ተግሳጹንም አትጥላ፣ **12** አባት ደስ የሚሰኝበትን ልጁን እንደሚቀጣ እንደዚሁ እግዚአብሔርም የሚወዳቸውን ይቀጣልና። **13** ጥበብን የሚያገኛት ሰው ደስተኛ ነው፣ እውቀትንም ያገኛል። **14** ከጥበብ የምታገኘው ጥቅም ብር ከሚሰጥህ ትርፍ ይልቅ እጅግ ይበልጣል፣ የጥበብ ትርፍ ከወርቅም ይበልጣል። **15** ጥበብ ከከበረ ዕንቁ ይልቅ እጅግ ውድ ናት፣ አንተ ከምትመኘው ነገር ሁሉ እርሷን የሚተካከላት ምንም ነገር የለም። **16** በቀኝ እጇ ረጅም ዕድሜ አለ፤ በግራ እጇ ደግሞ ባለጠግነትንና ክብርን ይዛለች። **17** መንገዷ የደግነት መንገድ ነው፣ ጎዳናዋም ሰላም ነው። **18** እርሷ አጥብቀው ለሚይዟት የሕይወት ዛፍ ናት፣ የሚደገፉባትም ደስተኞች ናቸው። **19** እግዚአብሔር በጥበብ ምድርን መሰረተ፣ ሰማያትን ደግሞ በማስተዋል አጸና። **20** በእወቀቱ ጥልቆች ተሰንጥቀው ተከፈቱ፣ ደመናትም ጠልን አንጠበጠቡ። **21** ልጄ ሆይ፣ ትክክለኛ ፍርድንና ነገሮችን በሚገባ መለየትን ጠብቅ፣ እነዚህ ከእይታህ አይራቁ። **22** እነዚህ ለነፍስህ ሕይወት፣ በአንገትህ ዙርያ የምታስራቸው የሞገስ ጌጥ ይሆናሉ። **23** በዚያን ጊዜ በመንገድህ ተማምነህ በሰላም ትራመዳለህ፣ እግርህም አይሰናከልም፤ **24** በምትተኛበት ጊዜ አትፈራም፤ ስትተኛ እንቅልፍህ ጣፋጭ ይሆናል። **25** በድንገተኛ ሽብርና በክፉዎች አማካይነት በሚደርስ ጥፋት አትፍራ፣ **26** እግዚአብሔር በአጠገብህ ይሆናልና፣ እግርህም በወጥመድ እንዳያያዝ ይጠብቅሃልና። **27** ልታደርግ የሚቻልህ ሲሆን፣ ለሚገባቸው ሰዎች መልካምን ነገር ከማድረግ አትከልክል። **28** አሁን በእጅህ ገንዘብ እያለ ለጎረቤትህ “አሁን ሂድ፣ እንደገና ተመልሰህ ና፣ ነገ እሰጥሃለሁ” አትበለው። **29** በአጠገብህ የሚኖረውንና በአንተ የሚተማመነውን ጎረቤትህን ለመጉዳት አትምከርበት። **30** አንድ ሰው አንተን ለመጉዳት ክፉ ካልሰራብህ ያለ በቂ ምክንያት ከዚህ ሰው ጋር አትከራከር። **31** በክፉ ሰው አትቅና፣ የትኛውንም መንገዱን አትምረጥ። **32** ጠማማ ሰው በእግዚብሔር ፊት የተጠላ ነውና፣ ቅን ሰውን ግን ወዳጁ ያደርገዋል። **33** የእግዚአብሔር እርግማን በክፉ ሰዎች ቤት ላይ ነው፣ የጻድቃንን ቤት ግን ይባርካል። **34** እርሱ በፌዘኞች ላይ ያፌዛል፣ ለትሁታን ግን ሞገሱን ይሰጣቸዋል። **35** ጥበበኞች ክብርን ይወርሳሉ፣ የሞኞች ከፍታ ግን ውርደታቸው ነው።

Proverbs 3:1

አጠቃላይ መረጃ:-
ፀሀፊው ግጥምን በመጠቀም ልጁን እንደሚያስተምር አባት ይናገራል። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ትእዛዛቴን አትርሳ
“ትእዛዛት” የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ያዘዝኩህን እንዳትረሳ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ትምህርቴንም በልብህ ጠብቅ
የፊተኛው ሀረግ በአሉታዊ አነጋገር ያለውን ይሄ ሀረግ በአዎንታዊ አነጋገር ይናገረዋል። እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል አእምሮን ይወክላል። “ትምህርቴን” የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ሁልጊዜ ያስተማርኳችሁን አስታውሱ” (ትይዩነት እና ምትክ ስም እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ረጅም ቀኖችን እና የሕይወት ዘመናትን
እነዚህ ሁለት ሀረጎች አንድ አይነት ትርጉምን ይጋራሉ ደግሞ ረጅም ህይወት መኖርንም ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጉም:- ረጅም እድሜ (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 3:3

በኪዳን የተመሰረተ ታማኝነት እና እውነተኛነት አይለዩህ
ፀሀፊው ስለ “የኪዳን ታማኝነት” እና “እውነተኛነት” አንድን ሰው ትተው መሄድ የሚችሉ ሰዎች እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። “ታማኝነት” እና “እውነተኛነት” የተባሉት ረቂቅ ስሞች “ታማኝ” እና “እውነተኛ” ተብለው ሊገለፁ ይችላሉ። እናም አሉታዊው ትእዛዝ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ሁልጊዜ እውነተኛ እና ለኪዳኑ ታማኝ ሁን” (ሰውኛ ዘይቤ እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በአንገትህ ዙሪያ እሰራቸው
ፀሃፊው ስለ ታማኝነት እና እውነተኛነት አንድ ሰው እንደ አንገት ጌጥ በአንገቱ ዙሪያ የሚያስራቸው ነገሮች እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። አምሳያው እነዚህ አንድ ሰው ወደ ውጪ የሚያሳያቸው ዋጋቸው የከበረ ነገሮች እንደሆኑ ይጠቁማል። አማራጭ ትርጉም:- “አንድ ሰው የአንገት ጌጥ እንደሚያስረው እነርሱን በኩራት አሳያቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በልብህ ፅላት ላይ ፃፋቸው
እዚህ ላይ ልብ የአንድ ሰውን አእምሮ ይወክላል። አእምሮ አንድ ሰው መልእክት እና ትእዛዛትን መፃፍ የሚችልበት ፅላት እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም:- በፅላት ላይ በቋሚነት እንደፃፍሃቸው እንደዚሁ ሁልጊዜ አስታውሳቸው (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በእግዚአብሔረ እና በሰው ፊት
እዚህ ላይ ፊት ፍርድን ወይም ምዘናን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- በእግዚአብሔር እና በሰው ዳኝነት (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 3:5

ፍፁም ልብህ
“ልብ” የሚለው ቃል ውስጣዊ ማንነትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “ሙሉ ማንነትህ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በራስህ ማስተዋል አትደገፍ
ፀሀፊው በራስ ማስተዋል መደገፍን “ማስተዋል” አንድ ሰው ሊደገፍበት የሚችል ነገር እንደሆነ አድርጎ

በመንገድህ ሁሉ
ፀሀፊው የአንድ ሰው ድርጊትን ግለሰቡ የሚጓዝበት መንገድ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም:- “በምታደርገው ሁሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መንገድህን ቀና ያደርገዋል
እግዚአብሔር የአንድ ሰው ተግባርን ማበልፀጉ የዚያ ሰው ተግባር እርሱ የሚጓዝበት እና እግዚአብሔር ከእንቅፋት ነፃ የሚያደርገው መንገድ አንደሆነ አድርጎ ፀሀፊው ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ መሳካትን ይሰጥሀል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 3:7

በራስህ አስተያየት ጥበበኛ አትሁን
ፀሀፊው የአንድ ሰውን አስተሳሰብ ያ ሰው በአይኑ አንድ ነገር እያየ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- በራስህ አስተሳሰብ ጥበበኛ አትሁን (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከክፉ ራቅ
ፀሃፊው ክፉ ተግባር አለመፈፀምን ከክፋት እየራቀ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፋትን አትፈፅም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ለስጋህ ፈውስ ይሆንልሀል
“እርሱ” የሚለው ቃል በቀደመው ቁጥር ላይ ፀሀፊው የሰጠውን ትእዛዛት ያመለክታል። የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልፅ መደረግ ይችላል። “ስጋ” የሚለው ቃል ሙሉ አካልን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይህንን ካደረግህ ለአካልህ ፈውስ ይሆንልሀል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 3:9

በምርትህ ሁሉ
“በሰበሰብከው ምግብ ሁሉ”

ጎተራህ ሙሉ ይሆናል
ይህ በገቢር/አድራጊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጎተራህ ሙሉ ይሆናል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ጎተራ
ምግብ የሚከማችበት ህንፃ ወይም ክፍል

ገንዳህም ይትረፈረፋል
ማከማቻህም መክደን እስከማይቻል ድረስ እጅግ በጣም ይሞላል።

Proverbs 3:11

አጠቃላይ መረጃ፡-
ፀሀፊው ልጁን እንደሚያስተምር አባት ይፅፋል።

ደስታን የሚፈጥርለት ልጅ
“እርሱ ሀሴት የሚያደርግበት ወንድ ልጅ። ይህ አባትየውን ለወንድ ልጁ ያለውን ፍቅር ያመለክታል እንጂ የወንድ ልጁ ባህርይ በአባትየው ዘንድ ያለውን ቅቡልነት አይደለም። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ የሚወደው ወንድ ልጅ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 3:13

ጥበብን የሚያገኝ ሰው
ፀሀፊው “ጥበብ” አንድ ሰው የሚያገኘው ነገር እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበብን ያገኘ ሰው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ብር በምላሹ የሚሰጠው
ይህ ሰው ብርን ስራ ላይ በማዋል ወይም በመሸጥ የሚያገኘውን ትርፍ ያመለክታል።

Proverbs 3:15

አጠቃላይ መረጃ፡-
ፀሀፊው ጥበብ ሴት እንደሆነች አድርጎ ይናገራል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይበልጥ የከበረ
“የላቀ ዋጋ ያለው”

በቀኝ እጅዋ ረጅም እድሜ ይዛለች፤ በግራ እጅዋ ባለጠግነት እና ክብር
x

Proverbs 3:17

መንገድዋ የደግነት መንገድ ነው፣ ጎዳናዋም ሁሉ ሰላም ነው
ፀሀፊው ጥበብ ሴት እንደሆነች እና ጥበብ ለሰው የምትሰጠው ጥቅም ያንን ሰው ጥበብ በመንገድ ላይ እየመራችው እንዳለች አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበብ ሁልጊዜ በደግነት ትይዝሀለች እና ሰላም ትሰጥሀለች” (ሰውኛ ዘይቤ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርስዋ አጥብቀው ለሚይዟት የህይወት ዛፍ ናት
ፀሀፊው ጥበብን ህይወት የሚሰጥ ፍሬ እንደሚያፈራ ዛፍ እና ከጥበብ የሚጠቀም ሰውን ያም ሰው ከፍሬዋ እንደበላ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበብ ከፍሬዋ የበሉትን ሰዎች በህይወት እንደምታቆይ ዛፍ ናት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የህይወት ዛፍ
“ህይወትን የሚሰጥ ዛፍ” ወይም “ፍሬው ህይወትን የሚያቆይ ዛፍ”

አጥብቀው ለሚይዟት
“ፍሬውን አጥብቀው ለሚይዙ”

Proverbs 3:19

እግዚአብሔር ምድርን መሰረተ..... ሰማያትንም አፀና
ፀሀፊው እግዚአብሔር ምድርና ሰማያት መፍጠሩን የህንፃ መሰረትን እንደጣለ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ምድርን ፈጠረ..... ሰማያትን ሰራ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥልቆች ተሰንጥቀው ተከፈቱ
በጥንት አስተሳሰብ ውሀ ከመሬት በታች ይገኛል። ይህ ሀረግ እግዚአብሔር ይህንን ውሀ ከመሬት እንዲወጣ እንዳደረገና ውቅያኖሶችና ወንዞች እንዲገኙ እንዳደረገ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ወንዞቹ እንዲፈሱ አደረገ” ወይም “ውቅያኖሶች እንዲፈጠሩ አደረገ” (ግምታው እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ጠል
ሌሊት በመሬት ላይ የሚሰበሰብ ውሀ

Proverbs 3:21

እነርሱ ከእይታህ አይራቁ
ፀሀፊው አንድ ነገር አለመርሳትን ሁልጊዜ እርሱን ማየት እንደመቻል አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱን አትርሳ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለነፍስህ ህይወት ይሆናሉ
እዚህ ላይ “ነፍስ” ግለሰቡን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለአንተ ህይወት ይሆናሉ” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በአንገትህ ዙሪያ የምታስረው የሞገስ ጌጥ
ፀሀፊው “ትክክለኛ ፍርድ” እና “ማስተዋል” አንድ ሰው በአንገቱ ዙሪያ እንደ አንገት ጌጥ የሚያስራቸው ነገሮች እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። ይህ ምስል እነዚህ አንድ ሰው ወደ ውጪ የሚያሳያቸው ዋጋ ያላቸው እንደሆኑ ይጠቁማል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ሰው ራሱን በአንገት ጌጥ እንደሚያስጌጥ እንደዚያ የሞገስ ማሳያ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሞገስ ጌጥ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “የሚስማማ ጌጥ” ወይም 2) “የእግዚአብሔርን ሞገስ የሚያሳይ ጌጥ።”

Proverbs 3:23

በመንገድህ ላይ በደህንነት ትራመዳለህ
ፀሀፊው የአንድ ሰው ህይወትን መኖር ያ ሰው በመንገድ ላይ እየተራመደ እንዳለ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ህይወትህን በደህንነት ትኖራለህ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እግርህ አይሰናከልም
“እግር” የሚለው ቃል የሰውን ሁለንተና ይወክላል። ፀሀፊው ስህተት ማድረግን ሰው በመንገድ ላይ በአንድ ነገር እንደተደናቀፈ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስህተት የሆኑ ነገሮችን አታደርግም” (ተዛምዶአዊ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በተጋደምህ ጊዜ
ሰው የሚጋደመው ለመተኛት እንደሆነ ያመለክታል። የዚህ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለመተኛት ስትጋደም” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እንቅልፍህ ጣፋጭ ይሆናል
ፀሀፊው ስለ ሰላማዊ እና አስደሳች እንቅልፍ ለሚተኛው ሰው ጣፋጭ ጣእም እንደሚያስገኝለት አድርጎ ይናገራል። “እንቅልፍ” የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እንቅልፍህ አስደሳች ይሆናል” ወይም “በሰላም ትተኛለህ” (ተለዋጭ ዘይቤ ወይም ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 3:25

በክፉዎች አማካኝነት የሚደርስ ጥፋት፣ ሲመጣ
ይህ በገቢር/አድራጊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉዎች ጥፋትን ሲያመጡ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ከጎንህ ይሆናል
“እግዚአብሔር ከአጠገብህ ይሆናል።” አንድ ሰው ከሌላ ሰው ጎን መቆም የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር አንዱ ሰው ሌላኛውን ሰው ይረዳዋል እና ይደግፈዋል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ይደግፍሀል እና ይከራከርልሀል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

እግርህ በወጥመድ እንዳይያዝ ይጠብቃል
ፀሀፊው “በሸብር” እና “በጥፋት” የተጎዳውን ሰው በወጥመድ እንደተያዘ አድርጎ ይናገራል። “እግር” የሚለው ቃል የሰውን ሁለንተና ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተን ሊጎዱ ከሚፈልጉህ ሰዎች ይጠብቅሀል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 3:27

መልካሙን አትከልክል
“መልካም ነገርን አትከልክል” ወይም “መልካም ተግባርን አትከልክል”

ልታደርግ የሚቻልህ ሲሆን
“መርዳት የምትችል ሲሆን”

በእጅህ ላይ ገንዘብ ሲኖር
በእጅህ ላይ ገንዘብ ሲኖርህ። የዚህ ትርጉም ግለሰቡ ለመርዳት የሚሆን ገንዘብ በአሁኑ ጊዜ እያለው ነገር ግን ጎረቤቱን ነገ ተመልሶ እንዲመጣ ይነግረዋል የሚል ነው።

Proverbs 3:31

መንገዱን ሁሉ አትምረጥ
የሁከተኛ ግለሰብ ተግባርን ማድረግ መምረጥ እንደሌለበት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡ “መንገዱን ሁሉ ለማድረግ አትምረጥ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ጠማማ ሰው በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ነው
“እግዚአብሔር ጠማማን ሰው ይጠላል”

ጠማማ ሰው
የማይታመን ወይም አታላይ የሆነ ሰው

ለቅን ሰው ሚስጥሩን ይገልፅለታል
እግዚአብሔር ትክክለኛውን ነገር የሚያደርጉትን እንደ ቅርብ እና ታማኝ ጓደኛ ሀሳቡን ያካፍላቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ለቅኖች ቅርብ ጓደኛ ነው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 3:33

የእግዚአብሔር እርግማን በክፉዎች ቤት ላይ ነው
ፀሀፊው የእግዚአብሔርን እርግማን በክፉ ሰው ቤት ጫፍ ላይ እግዚአብሔር እንዳስቀመጠው ነገር እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። “ቤት” የሚለው ቃል የቤተሰብ ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የክፉ ሰውን ቤተሰብ ረግሟል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የፃድቃን ሰዎችን ቤት ይባርካል
“ቤት” የሚለው ቃል ቤተሰብን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የፃድቅ ሰዎችን ቤተሰብ ይባርካል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ለትሁታን ሞገሱን ይሰጣል
ፀሀፊው የእግዚአብሔርን ሞገስ እርሱ ለሰዎች የሚሰጠው ነገር እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትረጉም፡- “ሞገሱን ለትሁት ሰዎት ያሳያል” ወይም “ለትሁት ሰዎች ጸጋውን ይሰጣል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 3:35

ጠቢብ ሰዎች ክብርን ይወርሳሉ
ፀሀፊው ጠቢብ ሰዎች የክብር ስም ማግኘታቸውን ክብርን በቋሚ ባለቤትነት እንደወረሱ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠቢብ ሰዎች ክብርን ያገኛሉ” ወይም “ጠቢብ ሰዎች የተከበረ ስም ያገኛሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሞኞች ከፍታ ውርደታቸው ይሆናል
ፀሀፊው እግዚአብሔር የሞኞች ውርደትን ለሁሉም ሰው ግልፅ ማድረጉን እግዚአብሔር ሞኞችን ሁሉም ሰው እንዲያያቸው ወደላይ ከፍ እንዳደረጋቸው አድርጎ ይናገራል። ይህ በገቢር/አድራጊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የሞኞችን ውርደት ሁሉም ሰው እንዲያይ ያደርጋል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 ልጆች ሆይ፣ የአባትን ተግሳጽ አድምጡ፣ ማስተዋል ምን እንደሆነ እንድታውቁ ልብ በሉ። **2** እኔ መልካም ትምህርት አሰጣችኋለሁ፣ ትምህርቴን አትተዉ። **3** የአባቴ ልጅ ሳለሁ፣ ለእናቴም ተወዳጅና ብቸኛ ልጅ ሳለሁ፣ **4** አባቴ አስተማረኝ፣ እንዲህም አለኝ፦ “ቃሎቼን ሁሉ በልብህ ያዝ፤ ሕግጋቴን ጠብቅ በሕይወትም ኑር።” **5** ጥበብንና ማስተዋልን አግኝ፤ የአፌን ቃላቶች አትርሳ፣ እነርሱንም አትተው፤ **6** ጥበብን አትተዋት፣ እርሷ ከለላ ትሆንሃለች፤ ውደዳት፣ ትጠብቅሃለች። **7** ጥበብ እጅግ በጣም ጠቃሚ ናት፣ ስለዚህ ጥበብን አግኛት፣ ያለህን ሀብት ሁሉ ከፍለህ ማስተዋልን የራስህ አድርጋት። **8** ለጥበብ ከፍተኛ ስፍራ ስጣት፣ እርሷም ከፍ ከፍ ታደርግሃለች፤ እርሷን አጥብቀህ ስትይዛት ታከብርሃለች። **9** በራስህ ላይ የክብር አክሊል ታስቀምጥልሃለች፤ ውብ የሆነ ዘውድም ትሰጥሃለች። **10** ልጄ ሆይ፣ አድምጠኝ፣ ለቃሎቼም ትኩረት ስጥ፣ በሕይወት ዘመንህም ብዙ አመታት ይጨመሩልሃል። **11** በጥበብ ጎዳና አስተምርሃለሁ፤ በቀጥተኛ መንገዶችም እመራሃለሁ። **12** በምትራመድበት ጊዜ ማንም በመንገድህ ላይ አይቆምም፣ በሮጥህ ጊዜ አትሰናከልም። **13** ምክርን ያዝ፣ አትልቀቀው፤ ጠብቀው፣ እርሱ ሕይወትህ ነውና። **14** የክፉዎችን መንገድ አትከተል፣ ክፋትን በሚያደርጉ ሰዎች መንገድ አትሂድ። **15** ከእርሷ ራቅ፣ በዚያ አትሂድ፤ ከዚያ ተመለስ፣ በሌላ መንገድ ሂድ። **16** ክፋትን እስኪፈጽሙ ድረስ መተኛት አይችሉምና፣ አንድ ሰው እስኪያሰናክሉ ድረስ እንቅልፋቸው አይመጣምና። **17** የክፋትን እንጀራ ይበላሉና፣ የአመጽንም ወይን ጠጅ ይጠጣሉና። **18** ጽድቅን የሚያደርግ ሰው መንገድ ግን እየፈካ እንደሚሔድ የንጋት ብርሃን ነው፤ ሙሉ ቀን እስከሚሆን ድረስ ብርሃኑ የበለጠ እየጨመረ ይሄዳል። **19** የክፉዎች መንገድ ግን እንደ ጨለማ ነው፣ምን እንደሚያሰናክላቸው በፍጹም አያውቁም። **20** ልጄ ሆይ፣ ቃሎቼን ልብ በል፣ ንግግሮቼን አድምጥ። **21** ከአይኖችህ አይራቁ፣ በልብህ ውስጥ ጠብቃቸው። **22** ቃሎቼ ለሚያገኘኟቸው ሰዎች ሕይወት፣ ለመላው ሰውነታቸውም ፈውስ ናቸውና። **23** ልብህን በጥንቃቄ ጠብቅ፣ በትጋትም ከልለው፣ የሕይወት ምንጭ የሚፈልቀው ከእርሱ ነውና። **24** ጠማማ ንግግርን ከአንተ አስወግድ፣ ብልሹ ወሬ ከአንተ አርቅ። **25** ዓይኖችህ ወደ ፊት በቀጥታ ይመልከቱ፣ በቀጥታ ፊት ለፊት አተኩረህ እይ። **26** ለእግርህ ደልዳላ ጎዳና አበጅለት፤ ከዚያ በኋላ መንገድህ በሙሉ አስተማማኝ ይሆናል። **27** ወደ ቀኝ ወይም ወደ ግራ አትበል፤ እግርህን ከክፉ መልስ።

Proverbs 4:1

አጠቃላይ መረጃ፦
ፀሀፊው ልጁን እንደሚያስተምር አባት ይናገራል።

ትኩረት ስጥ
“በጥንቃቄ አዳምጥ”

ማስተዋል ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ
“እንዴት ማስተዋል እንዳለባችሁ ታውቃላችሁ” ወይም “ማስተዋልን ታገኛላችሁ”

እኔ መልካም ትምህርትን እሰጣችኋለሁ
“እኔ የማስተምራችሁ መልካም ነው”

Proverbs 4:3

የአባቴ ልጅ ሳለሁ
ይህ ፀሀፊው ገና በአባቱ እንክብካቤ ስር ያለ ልጅ የነበረበትን ጊዜ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “ገና ከአባቴ የምማር ወንድ ልጅ ሳለሁ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ተወዳጅ ራሱን ያልቻል እና ብቸኛ ልጅ
እዚህ ላይ ተወዳጅ “ራሱን ያልቻለ” የሚለው ቃል አካላዊ ብቃት ገና የሌለው የታዳጊነት እድሜውን ያመለክታል። “ብቸኛ” ከሚለው ቃል ጋር ጥምር ቃልን ይፈጥራል። አማራጭ ትርጉም፦ “ተወዳጅ ራሱን ያልቻለ ብቸኛ ልጅ” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ልብህ ቃሎቼን ይያዝ
እዚህ ላይ “ልብ” የሰውን አእምሮ ይወክላል። ፀሀፊው ቃሎች ማስታወስን ልብ እነርሱን አጥብቃ እንደያዘች አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትጉርም፦ “የማስተምርህን ሁልጊዜ አስታውስ” (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 4:5

Possible
አባትየው የራሱ አባት ያስተማረውን ለልጆቹ ማስተማር ቀጥሏል።

ጥበብ ማግኘት
“ጥበብን ለራስህ ለማግኘት ጠንክረህ ስራ” ወይም “ጥበብ አግኝ”

አትርሳ
“አስታውስ”

አትተው
“ተቀበል”

የአፌን ቃላቶች
እዚህ ላይ “አፍ” የሚለው ቃል የሚናገረውን ግለሰብ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የምናገረውን” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥበብን አትተዋት እርስዋም ከለላ ትሆንህለች፤ ውደዳት እርስዋም ትጠብቅሃለች
ፀሀፊው ጥበብ ታማኝ የሆነላትን ሰው የምትጠብቅ ሴት እንደሆነች አድርጎ ይናገራል። (ሰውኛ ዘይቤ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥበብን አትተዋት
ይህ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ጥበብን አጥብቀህ ያዝ” ወይም “ለጥበብ ታማኝ ሁን”

ውደዳት
“ጥበብን ውደድ”

Proverbs 4:7

አጠቃላይ መረጃ፦
አባትየው የራሱ አባት ያስተማረውን ለልጆቹ ማስተማሩን አበቃ።

ማስተዋልን ማግኘት እንድትችል ያለህን ሁሉ ክፈል
“ካለህ ነገር ሁሉ በላይ ለማስተዋል ዋጋ ስጥ”

ለጥበብ ከፍተኛ ስፍራ ስጥ እርስዋም ከፍ ከፍ ታደርግሀለች
ፀሀፊው ጥበብ ሴት እንደሆነችና ለሰው ትልቅ ክብር መስጠቷን ያንንም ሰው ጥበብ ወደ ታላቅ ስፍራ እንዳወጣች አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “ለጥበብ ከፍተኛ ስፍራን ከሰጠህ ትልቅ ክብርን ትሰጥሀለች” (ሰውኛ ዘይቤ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከፍተኛ ስፍራን መስጠት
ለአንድ ነገር ወይም ለአንድ ሰው ታላቅ ፍቅር መሰማት ወይም ማሳየት

እርስዋን አጥብቀህ ስትይዛት ታከብርሀለች
ፀሀፊው ጥበብ ሴት እንደሆነች እና ለጥበብ ዋጋ የሚሰጥ ሰው ክንዱን በእርስዋ ዙሪያ እንዳሰቀመጠ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበብን በጣም ከወደድህ ጥበብ ሰዎች እንዲያከብሩህ ታደርጋለች” (ሰውኛ ዘይቤ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በራስህ ላይ የክብር አክሊልን ታስቀምጣለች
ፀሀፊው ሰው ጥበብን ከማግኘቱ የተነሳ የሚኖረውን ክብር ጥበብ በግለሰቡ ራስ ላይ አክሊልን እንዳስቀመጠችለት አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበብ የአንተን ታላቅ ክብር የምታሳይ በራስህ ላይ እንደተቀመጠ አክሊል ትሆንልሃለች” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አክሊል
ከአበባ ወይም ከቅጠል ተሰካክቶ የተሰራ ክብ ቅርፅ ያለው ዘውድ

የተዋበ ዘውድን ትሰጥሀለች
ፀሀፊው ሰው ጥበብን ከማግኘቱ የተነሳ የሚኖረውን ክብር ጥበብ በግለሰቡ ራስ ላይ ዘውድን እንዳስቀመጠችለት አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- ጥበብ በራስህ ላይ እንደሚሆን የተዋበ ዘውድ ይሆናል (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመላከቱ)

Proverbs 4:10

ለቃሎቼ ትኩረት ስጥ
“የማስተምርህን በጥንቃቄ አዳምጥ”

በህይወትህ ዘመን ቡዙ አመታት ይኖሩሀል
“ቡዙ አመታትን ትኖራለህ”

በጥበብ ጎዳና አስተማርሁህ፤ በቀጥተኛ መንገዶች መራሁህ
ፀሀፊው ወንድ ልጁ በጥበብ እንዲኖር ማስተማሩ ወንድ ልጁን ሰው ጥበብ ሊያገኝ በሚችልበት መንገዶች እየመራው እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “በጥበብ መኖር እንዴት መኖ እንዳለብህ እያስተማርሁህ ነው፤ ለመኖር ትክክለኛውን መንገድ እያብራራሁ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በምትራመድ ጊዜ ማንም በመንገድህ ላይ አይቆምም፣ በሮጥህ ጊዜም አትሰናከልም
እነዚህ ሁለት መስመሮች ተመሳሳይ ትርጉም ይጋራሉ። ፀሀፊው ሰው የሚያደርገውን ውሳኔ እና ተግባር ያ ሰው በመንገድ ላይ እየተራመደ ወይም እየሮጠ እንደሆነ እና ስኬታማ ስለሆነ ሰው ደግሞ መንገዱ ሰው እንዲሰናከል ከሚያደርግ መሰናክል ነፃ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ነገር ስታቅድ፣ እርሱን በማድረግ ስኬታማ ትሆናለህ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 4:13

ተግሳፅን ያዝ፣ አትተወውም
ፀሀፊው የተማረውን የሚያስታውስ ሰውን “ተግሳፅ” ያ ሰው አጥብቆ ሊይዘው የሚችለው ነገር እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ያስተማርሁህን መታዘዝ ቀጥል እና መቼም ቢሆን አትርሳው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ህይወትህ ነውና
ፀሀፊው ምክር የሰውን ህይወት መጠበቁ የዚያ ሰው ህይወት እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ ህይወትህን ይጠብቃልና” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የክፉዎችን መንገድ አትከተል ደግሞም ክፋትን በሚያደርጉ ሰዎች መንገድም አትሂድ
ፀሀፊው የሰውን ተግባር ያ ሰው በመንገድ ላይ እየሄደ እንዳለ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ሰዎች የሚያደርጉትን አታድርግ፣ ክፉ በሚያደርጉ ሰዎች ድርጊትም አትተባር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሽሽው
“የክፉዎችን መንገድ ሽሽ”

Proverbs 4:16

ክፋትን እስኪፈፅሙ ድረስ መተኛት አይችሉም
ምናልባት ቃል በቃል ሊተኙ ይችላሉ፣ ፀሀፊው ግን እንዴት ክፉ ተግባርን ለመፈጸም በብርቱ እንደሚፈልጉ ለመግለፅ ግነትን ተጠቅሟል። (ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እንቅልፋቸው አይመጣም
ፀሀፊው እንቅልፍ መተኛት ያልቻሉ ሰዎችን እንቅልፍ አንድ ሰው ከእነርሱ እንደሰረቀባቸው እቃ አድርጎ ይናገራል። አነርሱ ምናልባትም ቃል በቃል እንቅልፍ ሊተኙ ይችላሉ ነገር ግን ፀሀፊው ክፉ ተግባርን ለመፈጸም ምን ያህል አጥብቀው እንደሚሹ ለማስረዳት ግነትን ተጠቅሟል። አማራጭ ትርጉም፡- “መተኛት አይችሉም” (ግነት እና ጅምላ ፍረጃ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ሰው እስኪያሰናክሉ ድረስ
ፀሀፊው ሌላ ሰው ላይ ጉዳት ማድረስን ያን ሰው እንዲሰናከል ማድረግ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- አንድ ሰው እስኪጎዱ ድረስ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የክፋትን እንጀራ ይበላሉና የአመፃንም ወይን ጠጅ ይጠጣሉና
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ይህ ፀሀፊው እነዚህ ሰዎች ሳያቋርጡ ክፋትን እና አመፃን የሚያደርጉ ሰዎች አንድሰው እንጀራ እና ወይንጠጅ እንደሚጠጣ እንደዚያ እንደበሏቸው እና እንደጠጧቸው አድርጎ የሚናገርበት ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- ክፋት እንደሚመገቡት እንጀራ አመፅ ደግሞ እንደሚጠጡት ወይንጠጅ ነው። ወይም 2) እነዚህ ሰዎች ምግባቸውን እና መጠጣቸውን የሚያገኙት ክፋትን እና አመፃን በማድረግ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- ክፉ ነገሮችን በማድረግ የሚያገኙትን እንጀራ ይበላሉ፣ በአመፅ ያገኙትንም ወይን ጠጅ ይጠጣሉ። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 4:18

የፃድቅ ሰዎች መንገድ..... የክፉዎች መንገድ
ፀሀፊው የፃድቅ እና የክፉ ሰዎች ተግባር እና የአኗኗር ዘይቤ እነርሱ የሚራመዱበት “መንገድ” ወይም “አቅጣጫ” እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- የፃድቅ ሰዎች የአኗኗር ዘይቤ..... የክፉዎች የአኗኗር ዘይቤ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የፃድቅ ሰዎቸ መንገድ እየፈካ እንደሚሄድ የንጋት ብርሀን ነው
ፀሀፊው የፃድቅ ሰዎችን መንገድ ከፀሀይ መውጣት ጋር ያወዳድረዋል፤ ትርጉሙም እነርሱ የተጠበቁ ናቸው ምክንያቱም በሚራመዱበት ጊዜ የሚሄዱበትን ቦታ ለማየት የሚሆን ብርሀን አላቸው ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- ፃድቅ ሰዎች በመንገዳቸውን በአስተማማኝ ሁኔታ ይራመዳሉ ምክንያቱም የጠዋት ፀሀይ በመንገዳቸው ላይ ይበራል፣ እየፈካም ይሄዳል (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የንጋት ብርሀን
ይህ ንጋትን ወይም የፀሀይ መውጣትን ያመለክታል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሙሉ ቀን እስኪመጣም ድረስ
ይህ ፀሀይ ይበልጥ ደማቅ ሆና የምትወጣበት የቀኑን ጊዜ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ፀሀይ እጅግ ደምቃ እስክትወጣ ድረስ” ወይም “እስከ ሙሉ የቀን ብርሀን ድረስ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

የክፉዎች መንገድ እንደ ጨለማ ነው
ፀሀፊው የክፉዎች መንገድን ከጨለማ ጋር ያወዳድራል፣ ትርጉሙም እነርሱ ሁልጊዜ ለአደጋ የተጋለጡ ናቸው ማለት ነው ምክንያቱም ወዴት እንደሚራመዱ ለማየት ብርሀን የላቸውም። አማራጭ ትርጉም፡- ክፉ ሰዎች በመንገዳቸው ላይ በአደገኛ ሁኔታ ይራመዳሉ ምክንያቱም ለማየት የሚያስችል ብርሀን የላቸውም (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ በምን እንደሚሰናከሉ አያውቁም
ፀሀፊው መጎዳትን ሰው በሚጓዝበት መንገድ ላይ በሆነ ነገር መደናቀፍ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለምን እንደሚጎዱ እና መጥፎ አጋጣሚ እንደሚገጥማቸው አያውቁም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 4:20

ትኩረት ስጥ
“በጥንቃቄ አዳምጥ”

ወደ ንግግሮቼ ጆሮህን አዘንብል
እዚህ “ጆሮ” የሚለው ቃል የሚያደምጠውን ሰው ይወክላል። ፀሀፊው አንድ ሰውን በትኩረት ማዳመጥን ጆሮ ለተናጋሪው ቅርብ እንዲሆን ወደሚናገረው ሰው አንገትን ማዝመም እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። “ንግግሮች” የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለምናገራቸው ነገሮች ትኩረት በመስጠት አዳምጥ” (ተዛምዶአዊ እና ተለዋጭ ዘይቤ እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ከአይኖችህ እንዲርቁ አታድርግ
ፀሀፊው ስለ አንድ ነገር ሁልጊዜ ማሰብን አንድ ሰው ሊያይ በሚችልበት ቦታ መጠበቅ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። “ስለ እነርሱ ማሰብ አታቁም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በልብህ ውስጥ ጠብቃቸው
ፀሀፊው አንድን ነገር ማስታወስ በልብ ውስጥ ማስቀመጥ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሁልጊዜ አስታውሳቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 4:22

ቃሎቼ ህይወት ናቸው
ፀሀፊው የእርሱ ቃሎች የሰውን ህይወት መታደጋቸው እነዚያ ቃች የሰውየው ህይወት እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእኔ ቃሎች ህይወት ይሰጣሉ” ወይም “የተናገረኋቸው ነገሮች ህይወት ይሰጣሉ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ለሚያገኟቸው ለእነዚያ
ፀሀፊው ሙሉ በሙሉ የእርሱን ቃል መረዳት ሰው እነርሱን ፈልጎ እንደደሚያገኛቸው አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለሚረዱአቸው እና ለሚተገብሯቸው ለእነርሱ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለመላው የእነርሱ ሰውነት ፈውስ ነው
“የእነርሱ” የሚለው ቃል “ለሚያገኟቸው ለእነዚያ” የሚለውን ይወክላል። የዚህ ሀረግ ባለቤት ከፊተኛው ሀረግ ሊቀርብ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ቃሎቼ ለሚያገኟቸው ለሰውነታቸው በሙሉ ፈውስን ይሰጣሉ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ልብህን በጥንቃቄ ጠብቅ ከልለውም
እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል የሰውን አእምሮ እና ሀሳብ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አእምሮህን በጥንቃቄ ጠብቅ ሀሳብህንም ከልል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በመላው ትጋት
በማያቋርጥ እና በቅን ጥረት

የህይወት ምንጭ ከእርሱ ይፈልቃል
“እርሱ” የሚለው ቃል ለአእምሮ እና ለሀሳብ ምትክ ስም የሆነው ልብን ይወክላል። ፀሀፊው የሰውን ህይወት ከልብ የሚመነጭ ፈሳሽ ምንጭ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡ “የምትናገረው እና የምታደርገው ሁሉ ከሀሳብህ ይመጣል” ወይም “ሀሳቦችህ የህይወትህን መንገድ ይወስናሉ” (ምትክ ስም እና ተለዋጩ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 4:24

ጠማማ ንግግርን ከአንተ አስወግድ ብልሹ ወሬንም ከአንተ አርቅ
ፀሀፊው መዋሸት ወይም አታላይ ንግግርን ጠማማ እንደሆነ እና እንደዚህ አይነቱን ቋንቋ የማይጠቀም ሰውን ደግሞ ውሸትና አታላይነትን ከራሱ አርቆ ማስወገድ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “አትዋሽ በማታለልም አትናገር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አይኖችህ ወደ ፊት በቀጥታ ይመልከቱ ደግሞም በቀጥታ ፊት ለፊት አትኩረህ ተመልከት
እዚህ ላይ “አይኖች” የሚለው ቃል የሚመለከተውን ሰው ይወክላሉ። ፀሀፊው ትክክለኛውን ነገር ለማድረግ የቆረጠ ሰውን ያ ሰው ወደ ሌላ አቅጣጫ ለማየት ጭንቅላቱን ሳያዞር ያለማቋረጥ ወደፊት የሚያይ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሁልጊዜ ወደፊት በቀጥታ ተመልከት በቀጥታ ፊትለፊትም አተኩረህ እይ” (ተዛምዶአዊ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 4:26

ለእግርህን ደልዳላ መንገድ አዘጋጅ
እዚህ ላይ “እግር” የሚለው ቃል የሚራመደውን ሰው ይወክላል። ፀሀፊው የሰውን ተግባር ያ ሰው በመንገድ እየተጓዘ እንደሆነ እና ያንን ተግባር በጥንቃቄ ማቀድን ደግሞ ያንን መንገድ ደልዳላ ማድረግ እንደሆነ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለመራመድ ደልዳላ መንገድን አዘጋጅ” ወይም “ማድረግ የምትፈልገውን ደህና አድርገህ አዘጋጅ” (ተዛምዶአዊ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ደልዳላ መንገድ
“ለስላሳ መንገድ” ወይም “የተስተካከለ መንገድ”

መንገድህ በሙሉ አስተማማኝ ይሆናል
ፀሀፊው የሰውን ተግባር ያ ሰው በመንገድ ላይ እየተጓዘ እንደሆነ እና እነዚያ ተግባሮች ስኬታማ መሆናቸውን መንገዱ አስተማማኝ እና ደህንነቱ የተጠበቀ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከዚያ የምታደርገው ሁሉ ትክክል ይሆናል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ቀኝ ወይም ወደ ግራ አትበል
“ቀኝ” እና “ግራ” የሚሉት አቅጣጫዎች ወካይ ይመሰርታሉ፣ ትርጉሙም ሰው ደልዳላውን መንገድ በየትኛውም አቅጣጫ ሊተው አይገባውም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በቀጥታ ወደፊት ተራመድ ደልዳላውን መንገድንም አትተው” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

እግርህን ከክፉ መልስ
እዚህ ላይ “እግር” የሚለው ቃል የሚራመደውን ሰው ይወክላል። ፀሀፊው ክፉ ድርጊት አለማድረግን ሰው ከክፉ ርቆ እየሄደ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከክፉ ሸሽ” ወይም “ከክፉ ራቅ” (ተዛምዶአዊ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 5

1 ልጄ ሆይ፣ ለጥበቤ ትኩረት ስጥ፤ የማስተዋል ቃሌንም በጥንቃቄ አድምጥ። **2** ይህም ልባምነትን ትማር ዘንድ፣ ከንፈሮችህም እውቀትን ይጠብቁ ዘንድ ነው። **3** የአመንዝራ ሴት ከንፈር ማርን ያንጠባጥባልና፣ አንደበቷም ከዘይት ይልቅ የለሰለሰ ነውና፣ **4** ነገር ግን ፍጻሜዋ እንደ እሬት መራራ ናት፣ እንደ ስለታም ሰይፍ የምትቆርጥ ናት። **5** እግሮቿ ወደ ሞት ይወርዳሉ፣ እርምጃዎቿም ወደ ሲኦል መንገድ ይሄዳሉ። **6** ስለ ሕይወት መንገድ ምንም አታስብም። አረማመዷ የተቅበዘበዘ ነው፣ ወዴት እንደምትሄድም አታውቅም። **7** አሁንም ልጆቼ ሆይ፣ አድምጡኝ፣ የአፌን ቃል ከማድመጥ ፈቀቅ አትበሉ። **8** መንገድህን ከእርሷ አርቅ፣ ወደ ቤቷም በር አትቅረብ። **9** እንዲህ ካደረግህ ክብርህን ለሌሎች ሰዎች፣ የሕይወት ዘመንህንም ለጨካኝ ሰው አሳልፈህ አትሰጥም፤ **10** ባዕዳን በሀብትህ አይፈነጥዙም፣ የደከምክበት ነገር ወደ ባዕዳን ቤት አይገባም። **11** በሕይወትህ መጨረሻ ስጋህና ሰውነትህ ሲጠፋ ታቃስታለህ። **12** እንዲህም ትላለህ፦ “ተግሳጽን እንዴት ጠላሁ፣ መታረምን ልቤ ናቀ! **13** አስተማሪዎቼን አልታዘዝሁም፣ አሰልጣኞቼንም አላደመጥሁም። **14** በጉባኤና ሰዎች በተሰበሰቡበት መካከል ሙሉ በሙሉ ወደ ጥፋት ተቃርቤ ነበር።” **15** ከማጠራቀሚያህ ውሃ ጠጣ፣ ከጉድጓድህም የሚፈልቀውን ውሃ ጠጣ። **16** ምንጮችህ በሁሉም ቦታ ያለገደብ ሊፈስሱ፣ ወንዞችህስ በአደባባዩ ሁሉ ሊጎርፉ ይገባልን? **17** እነርሱ ለአንተ ብቻ ይሁኑ፣ ከአንተ ጋር ላሉ ባዕዳን አይሁኑ። **18** ምንጭህ የተባረከ ይሁን፣ በወጣትነት ሚስትህም ደስ ይበልህ። **19** ምክንያቱም እርሷ በፍቅር እንደተሞላች ዋላ፣ ግርማ ሞገስ እንዳላትም ሚዳቋ ናት። ጡቷም ሁልጊዜ ያስደስትህ፣ ሁልጊዜም በፍቅሯ ተማረክ። **20** ልጄ ሆይ፣ ስለምን በጋለሞታ ሴት ትማረካለህ፤ የሌላይቱንስ ሴት ሰውነት ለምን ታቅፋለህ? **21** እግዚአብሔር ሰው የሚሰራውን በሙሉ ያያል፣ የሚሄድበትንም መንገድ ሁሉ ይመለከታል። **22** ክፉ ሰው በራሱ ኃጢአት ይጠመዳል፤ የኃጢአቱም ገመድ አጥብቆ ይይዘዋል። **23** አልተቀጣምና ይሞታል፤ ከሞኝነቱም ብዛት የተነሳ መንገድ ይስታል።

Proverbs 5:1

አጠቃላይ መረጃ፦
ፀሀፊው ልጆቹን እንደሚያስተምር አባት ይናገራል።

ጆሮህን አዘንብል
እዚህ ላይ “ጆሮ” የሚለው ቃል የሚያዳምጠውን ሰው ይወክላል። ፀሀፊው አንድ ሰውን በትኩረት ማዳመጥን ጆሮ ለተናጋሪው ቅርብ እንዲሆን ወደሚናገረው ሰው አንገትን ማዝመም እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። ይህንን በምሳሌ 4፡20 ላይ እንዴት እነደተረጎምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “በትኩረት አዳምጥ” (ተዛምዶአዊ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥንቃቄ
ጥንቃቄ ድርጊት እና ንግግርን በተመለከተ ጥንቁቅ የመሆን ችሎታ ነው። ይህንን በምሳሌ 1፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ከንፈሮችህ እውቀትን ይጠብቁ
እዚህ ላይ “ከንፈሮች” የሚለው ቃል የሚናገረውን ሰው ይወክላል። ፀሀፊው እውነተኛ የሆነውን ነገር ብቻ ለመናገር ጥንቁቅ የሆነ ሰውን የዚያ ሰው ከንፈሮች እውቀትን እየጠበቁ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “እውነት የሆነውን ብቻ ትናገራለህ” (ተዛምዶአዊ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 5:3

የአመንዝራ ሴት ከንፈሮች ማርን ያንጠባጥባል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ከንፈሮች” የሚለው ቃል የአመንዝራ ሴት ቃሎችን ይወክላል እናም ፀሀፊው ቃላቶችዋ የሚስቡ መሆናቸው ከንፈሯ ማር የሚያንጠባጥቡ እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “የአመንዝራ ሴት ቃሎች ማር እንደሚያንጠባጥቡ ጣፋጭ ናቸው” ወይም 2) ፀሀፊው አመንዝራ ሴትን መሳም ስሜት መሳቡን የእርስዋ ከንፈሮች ማር እንደሚያንጠባጥቡ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “አመንዝራ ሴት መሳም ከንፈሮቿ ማር እንደሚያንጠባጥቡ ጣፋጭ ነው” (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አፏ ከዘይት ይበልጥ የለሰለሰ ነው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “አፍ” የሚለው ቃል የአመንዝራ ሴት ንግግርን ይወክላል ፀሀፊውም የንግግርዋን አሳማኝነት አፏ ከወይራ ዘይት የለሰለሰ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “ንግግሯ አሳማኝ እና ከወይራ ዘይት የለሰለሰ ነው” ወይም 2) ፀሀፊው አመንዝራ ሴትን የመሳም ደስታ አፏ ከዘይት የለሰለሰ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “የእርስዋ መሳም ከወይራ ዘይት ይለሰልሳል” (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በመጨረሻ ግን እንደ እሬት መራራ ናት
ፀሀፊው ከአመንዝራ ሴት ጋር ትስስር መጀመር የሚያመጣው ጉዳት እርስዋ እንደ እሬት የምትመር እንደሆነች አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “በመጨረሻ ግን እርስዋ እንደሚመር እሬት ናት

እሬት
መራራ ጣእም ያለው ተክል

እንደ ስለታም ሰይፍ የሚቆርጥ
ፀሀፊው አመንዝራ ሴት ከእርስዋ ጋር ትስስር ያለው ሰው ላይ የምታስከትለውን ስቃይ እርስዋ ሰውየውን የሚቆርጥ ስለታም መሳሪያ እንደሆነች አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “ስለታም መሳሪያ እንደሆነች ሰውን ታቆስላለች” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 5:5

እግሮቿ ወደ ሞት ይወርዳሉ
አዚህ ላይ “እግሮቿ” አመንዝራ ሴት ስትራመድ ይወክላል። ፀሀፊው ተግባሯን በመንገድ ላይ እየተራመደች እንዳለች አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “ወደ ሞት የሚያመራ መንገድ ላይ እየተራመደች ነው” ወይም “የአኗኗር ዘይቤዋ ወደ ሞት ያመራል” (ተዛምዶአዊ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርምጃዎችዋ ወደ ሲኦል ይሄዳሉ
ፀሀፊው ተግባሯን በመንገድ ላይ እየተራመደች እንዳለች አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “ወደ ሲኦል ትራመዳለች” ወይም “ተግባሯ ወደ ሲኦል ይወስዳታል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ ህይወት መንገድ አታስብም
ፀሀፊው ለሰው ረጅም ህይወት የሚሰጥ ባህርይ ወደ ህይወት የሚመራ መንገድ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “ወደ ህይወት በሚመራው መንገድ ላይ መራመድን አታስብም” ወይም “ወደ ህይወት ስለሚመራ ተግባር አትጨነቅም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አረማመዷ የተቅበዘበዘ ነው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “አንደጠፋ ወዲህ እና ወዲያ ትቅበዘበዛለች” ወይም 2) “በተሳሳተ መንገድ ላይ ትጓዛለች”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Proverbs 5:7

አሁን
እዚህ ላይ አስተማሪው ስለ አመንዝራ ሴት ከማስጠንቀቅ ምክር ወደ መስጠት ተሸጋግሯል።

አድምጠኝ..... ከማዳመጥ ፈቀቅ አትበል
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተማሪው ትኩረት እንዲሰጥ ተመሳሳይ ሀሳብን ይገልፃሉ። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ከማዳመጥ ፈቀቅ አትበል
ፀሀፊው አንድ ድርጊት ማቆምን ያ ሰው በአካላዊ አቋም ከእርሱ ፈቀቅ ያለ እንደሆነ አስመስሎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ማዳመጥ አታቁም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የአፌን ቃል
እዚህ ላይ “አፍ” የሚለው ቃል የሚናገረውን ሰው ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእኔ ቃሎች” ወይም “የምናገረውን” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ምንገድህን ከእርስዋ አርቅ
እዚህ ላይ “መንገድ” የሚለው ቃል የሰውን የእለት ከእለት ተግባርንና ሁኔታን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ራስህን ከእርስዋ አርቀህ ጠብቅ” ወይም” ከእርስዋ ራቅ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ቤትዋ በር አቅራቢያ አትምጣ
እዚህ ላይ “የቤትዋ በር” ቤቱን ራሱን ይወክላል። “አትምጣ” በሚለው ቃል ፈንታ “አትሂድ” የሚለውን ቃል መጠቀም በይበልጥ ተስማሚ ሊሆን ይችላል ምክንያቱም የመጀመሪያው ተናጋሪው የእርስዋ በር ላይ እንደሆነ ሊያመለክት ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ወደ ቤትዋ በር አቅራቢያ አትሂድ” ወይም “ወደ ቤትዋ አቅራቢያ እንኳን ሳይቀር አትሂድ” (ተዛምዶአዊ እና የአትምጣ እና አትሂድ አጠቃቀም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 5:9

በዚያ መንገድ
“እንዲህ ካደረግህ።” ይህ ሀረግ በቀደመው ቁጥር ላይ የተናገረውን ያመለክታል።

ክብርህን ለሌሎች አሳልፈህ አትሰጥም
“ክብር” ለሚለው ቃል ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉ፡- 1) ይህ የአንድን ሰው ዝና ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በሌሎች ሰዎች መካከል ያለህን መልካም ዝና አታጣም” ወይም 2) ይህ የሰውን ሀብት እና ንብረት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሀብትህን ለሌሎች ሰዎች አሳልፈህ አትሰጥም” ወይም 3) ይህ ብርታትን ያመለክታል፣ የአንድን ሰው የሕይወት ግንባር ቀደም ዘመናት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የህይወትህን ምርጥ ጊዜያት ለሌሎች ሰዎች አሳልፈህ አትሰጥም”

ወይም የህይወት ዘመንህን ለጨካኝ ሰው
ፀሀፊው ያለጊዜው ምናልባትም በግድያ የሞተን ሰው የህይወቱን ዘመን ለሌላ ሰው አሳልፎ እንደሰጠው እቃ እንደሆነ ይናገራል። ግሱ በፊተኛው ሀረግ የቀረበ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ወይም የህይወት ዘመንህን ለጨካኝ ሰው ስጥ” ወይም “ወይም ጨካኝ ሰው እንዲገድልህ አድርግ” (አስጨምሬ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጨካኝ ሰው
ይህ ከአመንዝራዋ ሴት ጋር የተኛውን ሰው በጭካኔ የሚቋቋመውን የአመንዝራዋን ሴት ባል ሊያመለክት ይችላል።

ባእድ ሰው በሀብትህ አይጠግቡም
ፀሀፊው የሌላ ሰውን ሀብት የወሰዱና የተጠቀሙበትን ሰዎች በሃብቱ እንደጨፈሩ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ባእድ ሰዎች ሀብትህን በሙሉ አይወስዱም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የደከምክበት ነገር ወደ ባእዳን ቤት አይሄድም
እዚህ ላይ “ቤት” የሚለው ቃል የዚያን ሰው ቤተሰብ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ያገኘህው ነገሮች መጨረሻቸው የባእድ ቤተሰብ ንብረት አይሆኑም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 5:11

ስጋህ እና ሰውነትህ መነመነ
“ስጋ” እና “ሰውነት” የሚሉት ቃሎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው እናም የሰውን ሁለንተና ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰውነትህ መነመነ” ወይም “አንተ መነመንህ” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

መነመነ
“በሰውነት አካል መድከም” ወይም “ደካማ እና ጤና የጎደለው መሆን”

ተግሳፅን ጠላሁ..... ልቤ እርማትን ናቀ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ሀሳብን ይገልፃሉ እናም ምን ያህል ይህ ሰው አስተማሪው የነገረውን ነገር እንደጠላ ያስገነዝባል። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ተግሳፅን እንዴት ጠላሁ
“እንዴት” የሚለው ቃል የጥላቻውን ብርታት የሚያጎላ ቃለ አጋኖ ነው። ተግሳፅ የሚለው ቃል በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ሰው ሲገስፀኝ በጣም እጠላለሁ” (ቃለ አጋኖ እና ረቂቂ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ልቤ ተግሳጽን ጠላ
እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ሰውየውንና ስሜቶቹን ይወክላል።: “ተግሳጽ” የሚለው ቃል በግስ ሐረግ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ተርጉም፡- “ሰዎች ሲገስጹኝ ጠላኋቸው” (ተዛምዶአዊ እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 5:13

ጆሮየን ወደ አስተማሪዎቼ አዘነበልሁ
እዚህ “ጆሮ” የሚለው ቃል የሚያደምጠውን ሰው ይወክላል። ፀሀፊው አንድ ሰውን በትኩረት ማዳመጥን ጆሮ ለተናጋሪው ቅርብ እንዲሆን ወደሚናገረው ሰው አንገትን ማዝመም እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። በምሳሌ 4፡20 ላይ ይህን ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመለክት። (ተዛምዶአዊ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በጉባኤው መካከል፣ በሕዝቡ ስብሰባ መካከል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው ደግሞም 1) እግዚአብሔርን ለማምለክ ወይም 2) ለፈጸመው ክፉ ድርጊት ፍርድ ሊሰጡት በአንድ ላይ የተሰበሰቡትን የሰውየውን የማሕበረሰብ አካላት ያመለክታል። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 5:15

ውኃ ከጕድጓድህ ... የሚፈልቅ ውኃ ከምንጭህ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሰረታዊነት ትርጉማቸው አንድ ነው። ፀሐፊው ከሚስቱ ጋር ብቻ የሚተኛ ሰውን ከራሱ ጉድጓድና ምንጭ ብቻ ውኃ እንደሚጠጣ አድርጎ ተናግሯል። (ትይዩነት እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የሚፈልቅ ውኃ
ፀሐፊው አዲስ ወይም የሚፈልቅ ውኃን ውኃው እንደሚፈስ አድርጎ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “አዲስ ውኃ” ወይም “የሚፈስ ውኃ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ምንጮችህ ... ወንዞችህ ወደ ሕዝብ አደባባይ ሊፈሱ ይገባልን?
ፀሐፊው እነዚህን መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የጠየቀው ልጁ እነዚህን ነገሮች ማድረግ እነደሌለበት አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ምንጮችህ ... ወንዞችህ ወደ ሕዝብ አደባባይ ሊፈሱ አይገባም።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ምንጮችህ ... ወንዞችህ ወደ ሕዝብ አደባባይ ሊፈሱ ይገባልን?
እነዚህ “ምንጮችህ” እና “ወንዞችህ” የሚሉት ቃላት የወንድ የዘር ፈሳሽን የሚወክሉ ለስላሴ ዘይቤ ይመስላሉ። ለእነዚህ ተለዋጭ ሐረጎች ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት የሚከተሉት ናቸው፡- 1) ሰው ከሚስቱ ውጭ ከሌሎች ሴቶች ጋር መተኛት የአንድን ሰው ውኃ በሕዝብ አደባባዮች እንዲፈስስ መፍቀድ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። ወይም 2) ሰው ከሚስቱ ውጭ ከሌሎች ሴቶች ልጆች መውለድ የአንድን ሰው ውኃ በሕዝብ አደባባዮች እንዲፈስስ መፍቀድ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። (ለስላሴ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሕዝብ አደባባዮች
እነዚህ በትልልቅ ወይም በትንንሽ ከተማዎች ሁለትና ከዚያም በላይ መንገዶች የሚገናኙበት ባዶ ቦታ ናቸው። ሰዎች እርስ በርሳቸው የሚገናኙበትና የሚነጋገሩበት የተለመዱ ቦታዎች ናቸው።

እነርሱ ይሁኑ
“እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው “ምንጮችን” እና “ወንዞችን” እንደዚም ለቆሙለት ዓላማ ነው።

ከአንተ ጋር ለሚገኙ እንግዶች አይሁኑ
“እነርሱን ከእንግዶች ጋር አትጋራ”

Proverbs 5:18

ምንጭህ ቡሩክ ይሁን
ፀሐፊው የወንዱ ልጅ ሚስት ምንጭ እንደሆነች አድርጎ ተናግሯል። በዚህ ስፍራ “ብሩክ” የሚለው ቃል አንድ ሰው በሚስቱ ያለውን የደስታ ስሜት የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሁልጊዜም ቢሆን ከሚስትህ ጋር ደስ ይበልህ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የጉብዝናህም ሚስት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ወጣት እያለህ ያገባሃት ሚስትህ” ወይም 2) “ወጣት ሚስትህ”

እንደ ተወደደች አጋዘን እንደ ተዋበችም ሚዳቋ
ፀሐፊው የወንድ ልጁን ሚስት “የተወደደች አጋዘን እና የተዋበች ሚዳቋ” እነደሆነች አድርጎ ይናገራል። በዚህ ክፍል “አጋዘን” እና “ሚዳቋ” ትርጉሙ ሴት አጋዘን ነው። እነዚህ በመልካቸውም ሆነ በእንቅስቃሴአቸው የውበት ምልከት ናቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “እርስዋ እንደ አጋዘን እና እንደ ሚዳቋ ውብና ሞገስ የተሞላች ናት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሞገስ የተሞላች
ይህ ቃል “ጸጋን የተሞላች” ማለት ኤደለም፣ “ስትንቀሳቀስ ውበት አላት” ለማለት ነው።

ጡቶችዋ ሁልጊዜ ያርኩህ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) የሚስት ጡቶች የባልን የወሲብ ፍላጎት ይቀሰቅሳል ይህም የሚስትን ሁለንተና አካልዋን የሚወክል ይሆናል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጡቶችዋ ፍላጎትህን ያርኩ” ወይም “ ሰውነቷ ፍላጎትህን ያርካ” ወይም 2) ይህ ፀሐፊው የእናት ጡቶች የተራበ ልጅዋን እንደሚያረካ እንደዚሁ የሚስት ጡቶች የባልን ፍላጎት እንደሚያረኩ የተናገረበት ተለዋጭ ዘይቤ ነው። (ተዛምዶአዊ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በፍቅርዋም ሁልጊዜ ጥገብ
ከሚስት ጋር የሚደረግ ወሲባዊ ፍቅር ጥልቅ ስሜትና ደስታባል ከፍቅር እንደጠጣ ተደርጎ ተነግሯል። ይህ በገቢር ግስ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አልኮል የሰከረን ሰው እንደሚቆጣጠር እንደዚሁ የሚስትህ ፍቅር ይቆጣጠርህ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በፍቅርዋ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) “አንተ ለእርስዋ ባለህ ፍቅር” ወይም “እርስዋ ለአንተ ባላት ፍቅር”

Proverbs 5:20

ልጄ ሆይ፣ ስለምን በጋለሞታ ሴት ትማረካለህ፤ ስርአት የሌላትንስ ሴት ጡቶች ለምን ታቅፋለህ?
ፀሐፊው እነዚህን መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የጠየቀው ወንድ ልጁ እነዚህን ነገሮች ማድረግ እንደሌለበት አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ልጄ ሆይ፣ በጋለሞታ ሴት አትማረክ! ስርአት የሌላትንስ ሴት ጡቶች አትቀፍ” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በጋለሞታ ሴት ትማረካለህ
ለሴት በሚኖር ፍላጎት የሚመጣ ጥልቅ መነሳሳት ልጁ በዚያች ሴት እንደመማረክ ተደርጎ ተነግሯል። ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጋለሞታ ሴት እንድትማርክህ ፍቀድ” ወይም “ጋለሞታ ሴት እንድታፈዝዝህ ፍቀድ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ስርአት የሌላትን ሴት ጡቶች ለምን ታቅፋለህ?
“እዚህ ላይ “ጡቶች” የሚለው ቃል ስርአት የሌላትን ሴትና ወሲባዊ ማራኪነትዋን የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ስርአት የሌላትን ሴት ለምን ታቅፋለህ”

ስርአት የሌላትን ሴት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) “ሚስትህ ያልሆነች ሴት” ወይም “የሌላ ሰው ሚስት የሆነች ሴት”

ሁሉንም ነገር ያያል ... የሚሄድበትንም መንገድ ሁሉ ይመለከታል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ትርጉማቸው ተመሳሳይ ነው፣ እግዚአብሔር ማንኛውም ሰው የሚሰራውን ማኛውንም ነገር እንሚያውቅ አጽንዖት ይሰጣል። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

የሚሄድበትንም መንገድ ሁሉ
ፀሐፊው የሰውን ድርጊት ወይም የሕይወት ዘይቤ አንድ ሰው የሚሄድበት መንገድ እንደሆነ አድርጎ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሚሄድበት ቦታ ሁሉ” ወይም “የሚያደርገውን ነገር ሁሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 5:22

ክፉ ሰው ኃጢአቱ ታጠምደዋለች፥ በኃጢአቱም ገመድ ይታሰራልA
ፀሐፊው እነዚህ ኃጢአቶች ክፉውን ሰው የሚያጠምዱት ሰዎች እንደሆኑ አድርጎ በመናገር “ክፉ ሰው” የኃጢአቱን መዘዝ ፈጽሞ ሊያመልጠው እንደማይችል ይናገራል። ይህ በገቢር ግስ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ሰው የራሱ ኃጢአት ታጠምደዋለች” ወይም “ክፉ ሰው የኃጢአቱን መዘዝ ፈጽሞ ሊያመልጠው አይችልም” (ሰውኛ ዘይቤ እና ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የኃጢአቱ ገመድ አጥብቆ ያስረዋል
ፀሐፊው ኃጢአቱ ሰውየው የተጠመደበት በገመድ የተሰራ ወጥመድ እንደሆነ አድርጎ በመናገር ክፉ ሰው የኃጢአቱን መዘዝ ፈጽሞ ሊያመልጥ እንደማይችል

ይናራል። አማራጭ ትርጉም፡- “በኃጢአቱ ምክንያት በወጥመድ እንሚጠመድ እንስሳ ይሆናል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከሞኝነቱም ብዛት የተነሳ መንገድ ይስታል።
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይህ ታላቅ ሞኝነት ከትክክለኛው መንገድ ያስተዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ከሞኝነቱም ብዛት
“በጣም ሞኝ ስለሆነ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 6

1 ልጄ ሆይ፣ ጎረቤትህ ለወሰደው ብድር ዋስ ብትሆንና ገንዘብህን ለዋስትና ብታስይዝ፣ የማታውቀው ሰው ለወሰደው ብድር መተማመኛ ሰጥተህ ከሆነ፣ **2** የዚያን ጊዜ በቃልህ ምክንያት በራስህ ላይ ወጥመድ ዘርግተሃል፣ በአፍህም ቃል ተጠምደህ ተይዘሃል። **3** ልጄ ሆይ፣ ይህን አድርግ፣ ራስህንም አድን፣ አንተ በጎረቤትህ ምህረት ስር ነህና። ሂድ፣ ጎረቤትህም እንዲተውህ ሄደህ በትህትና ለምነው። **4** ለአይንህ እንቅልፍን ለሽፋሽፍቶችህም እንጉልቻን አትስጥ። **5** የሜዳ ፍየል ከአዳኝ እጅ፣ ወፍም ከአጥማጅ እጅ እንደምታመልጥ እንዲሁ ራስህን አድን። **6** አንተ ሰነፍ ሰው፣ ወደ ጉንዳን ተመልከት፣ መንገዷን አስተውል፣ ጥበበኛም ሁን። **7** አዛዥ፣ አለቃ ወይም ገዥ የላትም፣ **8** ይሁን እንጂ ምግቧን በበጋ ታዘጋጃለች፣ በመኸር ደግሞ የምትበላውን ታከማቻለች። **9** አንተ ሰነፍ፣ የምትተኛው እስከ መቼ ነው? ከእንቅልፍህስ የምትነሣው መቼ ነው? **10** “ጥቂት ማንቀላፋት፣ ጥቂት ማንጎላቸት፣ ጥቂት እጅን አጣጥፎ ማረፍ” **11** ድህነትህ እንደ ወንበዴ፣ ችግርህም መሳርያ እንደ ታጠቀ ወታደር ይመጣብሃል። **12** የማይረባ፣ ክፉ ሰው፣ በጠማማ ንግግሩ ይኖራል፣ **13** በዓይኑ ይጠቅሳል፣ በእግሩም ምልክት ያስቀምጣል፣ በጣቶቹም ይጠቁማል። **14** በልቡ ውስጥ ባለው አጭበርባሪነት ክፋትን ይዶልታል፣ ግጭትንም ሁልጊዜ ይጭራል። **15** ስለዚህ ጥፋቱ ሳይታሰብ በቅጽበት ይደርስበታል፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደማይድን ሆኖ ይሰበራል። **16** እግዚአብሔር የሚጠላቸው ስድስት ነገሮች አሉ፣ የሚጸየፋቸውም ሰባት ናቸው፦ **17** የትዕቢተኛ ሰው አይን፣ ሐሰትን የሚናገር ምላስ፣ የንጹሃን ሰዎችን ደም የሚያፈስስ እጅ፣ **18** ክፋትን የሚፈጥር ልብ፣ ክፋት ለማድረግ በፍጥነት የሚሮጥ እግር፣ **19** ውሸትን የሚለፈልፍ ምስክር፣ በወንድማማቾች መካከል ብጥብጥ የሚዘራ ሰው። **20** ልጄ ሆይ፣ የአባትህን ትዕዛዝ ፈጽም፣ የእናትህንም ትምህርት አትተው። **21** ሁልጊዜ በልብህ አኑራቸው፣ በአንገትህም ዙርያ እሰራቸው። **22** ስትሄድ፣ ይመሩሃል፤ በተኛህ ጊዜ ይጠብቁሃል፤ በነቃህም ጊዜ ያስተምሩሃል። **23** ትዕዛዛቱ መብራት ናቸው፣ ትምህርቱም ብርሃን ነው፤ የተግሳጽም ዘለፋዎች የሕይወት መንገድ ናቸውና። **24** ከምግባረ ብልሹ ሴት፣ ከአመንዝራ ሴትም ጣፋጭ ቃላት ይጠብቅሃል። **25** በልብህ ውበቷን አትመኝ፣ በሽፋሽፍትዋም አትጠመድ። **26** ከጋለሞታ ሴት ጋር መተኛት የአንድ ቁራሽ ዳቦ ዋጋ ያሳጣሃል፤ ከሌላ ሰው ሚስት ጋር መተኛት ግን ሕይወትህን ያሳጣሃል። **27** አንድ ሰው ልብሱ ሳይቃጠል በደረቱ እሳት መያዝ ይችላልን? **28** አንድ ሰው እግሩ ሳይቃጠል በፍም ላይ መራመድ ይችላልን? **29** ከጎረቤቱ ሚስት ጋር የሚተኛም ሰው እንዲሁ ነው፤ ከእርሷ ጋር የሚተኛም ሳይቀጣ አይቀርም። **30** ሌባ በተራበ ጊዜ ፍላጎቱን ለማሟላት ቢሰርቅ ሰዎች አይንቁትም። **31** ሆኖም ሌባው ሲሰርቅ ከተያዘ፣ የሰረቀውን ሰባት እጥፍ ይመልሳል፤ በቤቱም ያለውን ንብረት ሁሉ መስጠት አለበት። **32** የሚያመነዝር ሰው አእምሮው አያመዛዝንም፤ እንዲህ የሚያደርግ ራሱን ያጠፋል። **33** ቁስልና ውርደት ይገባዋል፣ ውርደቱም አይደመሰስለትም። **34** ቅናት ሰውን ቁጡ ያደርገዋልና፤ በሚበቀልበት ጊዜ ምህረትን አያደርግም። **35** እርሱ ምንም ዓይነት ካሳ አይቀበልም፣ ብዙ ስጦታዎችን ብታቀርብለትም እሺ አይልም።

Proverbs 6:1

ገንዘብህን ዋስ ሆነህ ብታስይዝ
እዚህ ላይ ቃል ኪዳንህና ሁኔታዎች ገንዘብህን እንድትቆጥብ አስገድደውሃል የሚል ሃሳብ አለው። አማራጭ ትርጉም፦ “የተወሰነ ገንዘብህን እንድትቆጥብ አድርጎሃል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለጎረቤትህ ብድር ዋስ ብትሆን
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) ጎረቤትህ ብድር ሊጠይቅህ ወደ አንተ መጥቶ ይሆናል” ወይም 2) ጎረቤትህ ከሌላ ሰው ብድር ለመውሰድ ፈልጎ ነገር ግን ጎረቤትህ ብድሩን መመለስ ባይችል በድሩን ለመክፈል ቃል ገብተህ ይሆናል”

ጎረቤት
ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለበት የዕብራይስጡ ቃል “ጓደኛ” የሚል ትርጉም አለው።

በአፍህም ቃል ተጠምደህ ተይዘሃል
ይህ ዘይቤአዊ ንግግር አንተ ራስህን ልታስጠምድ ነው ይላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አንተ ራስህ የምጥጠመድበትን ወጥመድ ሰርተሃል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

በአፍህ ቃል
“በተናገርከው” ወይም “ቃል በገባኸው”

Proverbs 6:3

ራስህን አድን
“ራስህነ ጠብቅ” ወይም “ከእነዚህ ችግሮች ለመውጣት ራስህን እርዳ”

በጎረቤትህ እጅ ወድቀሃልና
ይህ የንግግር ዘይቤ “እጅ” የሚለውን ቃል በመጠቀም “ጉዳት” የሚለውን ትርጉም ያስተላልፋል። አማራጭ ትርጉም፦ “ጎረቤትህ ከፈለገ ወደ አንተ ጉዳት ሊያመጣብህ ይችላል” ወይም “ጎረቤትህ በአንተ ላይ የሚፈልገውን ለማድረግ ሐይል አለው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ጎረቤት
“ጓደኛ”

Proverbs 6:4

ለአይንህ እንቅልፍን ለሽፋሽፍቶችህም እንጉልቻን አትስጥ።
“አይኖችህ አያንቀላፉ፤ ሽፋሽፍቶችህ አያንጎላጁ።” እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው እናም የተደጋገሙት ሰነፍ መሆን እንደማይገባ አጽንዖት ለመስጠት ነው። የበለጠ አጽንዖት ለመስጠት በአሉታዊ መንገድ ተገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ “ነቅተህ ጠብቅ፣ የምትችለውን ሁሉ አድርግ” (ትይዩነት እና ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

አይንህ ... ሽፋሽፍቶችህ
ይህ የፊትን አካላት በመጠቀም የሰውን ሙሉ ሰውነት የሚያሳይ ዘይቤአዊ ንግግር ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “አንተ ራስህ ... የአንተ ሰውነት” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

የሜዳ ፍየል ከአዳኝ እጅ እንደምታመልጥ እንዲሁ ራስህን አድን።
“ከአዳኝ እንደምታመልጥ የሜዳ ፍየል ከጎረቤትህ አምልጥ”

የሜዳ ፍየል
ይህ ሳር የሚበላና ብዙ ጊዜ ሰዎች ለምግብነት የሚያድኑት በጣም ትልቅና ቀጭን እንስሳ ነው። ይህ እንስሳ በፍጥነት በመሮጥ ችሎታው የታወቀ ነው።

ከአዳኝ እጅ
የአዳኝ እጅ የአዳኙን በቁጥጥር ስር ማድረግ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ከአዳኝ ቁጥጥር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ከአጥማጅ እጅ እንደምታመልጥ ወፍ
“ከወፍ ወጥመድ በርራ እንደምታመልጥ ወፍ አምልጥ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Proverbs 6:6

ተመልከት ... አስተውል
“አጥና ... አስብ” ወይም “በጥንቃቄ አስተውል ... አሰላስል”

ጉንዳን
ጉንዳን ከምድር በታች ወይም ራሳቸው በሰሩት የአፈር ክምር የሚኖሩ ትንሽ ነፍሳት ናቸው። ብዙ ጊዜ በሺዎች የሚቆጠሩ በቡድን ተሰባስበው የሚኖሩና ከራሳቸው እጅግ የበለጡ ነገሮችን መሸከምና ማንሳት የሚሉ ናቸው።

መንገዷን አስተውል
ይህ የጉንዳንን “መንገድ” በመጠቀም የጉንዳንን ባህርይ የሚያሳይ ዘይቤአዊ ንግግር ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ጉንዳን እንዴት እንደምትሰራ አስተውል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አለቃ፣ አዛዥ ወይም ገዢ
እነዚህ ሶስት ቃላቶች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ በአንድ ጉንዳን ላይ በመደበኛነት ስልጣን ያለው ማንም እንደሌለ አጽንዖት ለመስጠት ጥቅም ላይ የዋሉ ናቸው። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ምግቧን በበጋ ታዘጋጃለች ... የምትበላውን በመከር ትሰበስባለች
እነዚህ ሁለት ቃላቶች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ የተደጋሙት ጉንዳን ምን ያህል ኃላፊነት የምትሸከም መሆኗን ለማሳየት ነው።

በጋ
በጋ አንዳንድ ዛፎች ፍሬ የሚያፈሩበት የዓመቱ ወቅት ነው።

Proverbs 6:9

እስከ መቼ ትተኛለህ ... ከእንቅልፍህስ መቼ ትነሣለህ?
አስተማሪው እነዚህን ጥያቄዎች የሚጠቀመው ብዙ እንቅልፍ የሚተኛውን ሰነፍ ሰው ለመገሰጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “አንተ ሰነፍ ሰው ንቃ! ከአልጋህ ውጣ!” (ትይዩነት እና መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ጥቂት ትተኛለህ ... ጥቂት እጅህን ታጥፋለህ
እነዚህ ነገሮች ሰነፍ ሰው የሚናገራቸው ዓይነት ናቸው።

ጥቂት ትተኛለህ፣ ጥቂት ታንቀላፋለህ
እነዚህ ሃሳቦች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። እንደ ሙሉ ዓረፍተ ነገር ሊገለጹ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ትንሽ ረዘም ላለ ጊዜ እተኛለሁ። ረዘም ላለ ጊዜ ዘና ብየ ልተኛ።” (ትይዩነት እና አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ለማረፍ እጅህን ታጥፋለህ
ሰዎች ብዙ ጊዜ የበለጠ ተመቻችተው ለማረፍ ጋደም ሲሉ እጆቻቸውን ያጥፋሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ተመቻችቼ እጆቼን አጥጥፋለሁ ከዚያም ለትንሽ ጊዜ አርፋለሁ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ድህነትህ ይመጣብሃል
ይህ የስንፍና ውጤት እንደሆነ ግልጽ ለማድረግ እንደ አዲስ አረፍተ ነገር መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰነፍ መሆንህን ከቀጠልህ ድህነትህ ይመጣብሃል” ወይም “በተኛህበት ድህነት ይመጣብሃል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ድህነትህ እንደ ወንበዴ ትመጣብሃለች
ሰነፍ ሰው በድንገት ድሃ የሚሆንበት መንገድ ልክ ወንበዴ በድንገት መጥቶ ሀብትን ሰርቆ የሚሄድበት ዓይነት መንገድ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ወንበዴ በድንገት መጥቶ ያለህን በሙሉ እንደሚሰርቅ እንደዚሁ በድንገት ድሃ ትሆናለህ” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ችጋርህም ሰይፍ እንደ ታጠቀ ወታደር
ሰነፍ ሰው በድንገተኛ መንገድ ችጋሩ የሚመጣበት አንድ የታጠቀ ወታደር ከአንድ ሰው ያለውን ሁሉ በድንገተኛ መንገድ እንደሚወስድበት ነው። ይህ እንደ ሙሉ ዓረፍተ ነገር ለገለጽ ይችላ። አማራጭ ትርጉም፦ “ችጋርህ እንደ ታጠቀ ወታደር ወደ አንተ ይመጣብሃል” ወይም “የታጠቀ ወታደር ወደ አንተ መጥቶ ያለህን ሁሉ እንደሚሰርቅብህ እንደዚሁ ችጋርህ ይመጣብሃል” (ተነፃፃሪ ዘይቤ እና አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

የታጠቀ ወታደር
“የጦር መሳርያ የያዘ ወታደር” ወይም “ የጦር መሳርያ የያዘ ሰው”

Proverbs 6:12

የማይረባ ሰው - ክፉ ሰው
እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው እናም ይህ ሰው ምን ያህል ክፉ እንደሆነ አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ምንም ዓይነት ጥቅም የሌለው ሰው - ክፉ ሰው” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

በጠማማ ንግግሩ ይኖራል
በዚህ ስፍራ ውሸት እንደ ጠማማ ንግግር ተገልጿል። አማራጭ ትርጉም፦ ያለማቋረጥ ውሸት ይናገራል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በዓይኑ ይጠቅሳል፣ በእግሩም ምልክት ያስቀምጣል እና በጣቶቹም ይጠቁማል
እነዚህ ሶስት ሐረጎች ክፉ ሰው ሌሎች ሰዎችን ለማታለል መልእክት በምስጢር የሚያስተላልፍበትን መንገድ ያብራራሉ።

በዓይኑ ይጠቅሳል
አንድ ሰው በዓይኑ ከጠቀሰ፣ አንድ ዓይኑን በቅጽበት ጨፍኖ በመግለጥ ለሌላ ሰው ምስጢራዊ ምልክት ይሰጣል። ይህ እምነት የመጣል፣ የማረጋጋጫ ወይም የሌላ ነገር ምልክት ሊሆን ይችላል።

Proverbs 6:14

ክፋትን ያስባል
“ክፋትን ያቅዳል” ወይም “ክፉ ድርጊቶችን ለመፈጸም ይዘጋጃል”

ሁልጊዜ ጠብን ያነሳሳል
“ሁልጊዜ የጠብ ምክንያት ነው” ወይም “ያለማቋረጥ ግጭትን ይፈልጋል ደግሞም ያባብሳል”

ስለዚህ
“በዚህ ምክንያት”

ጥፋቱ ድንገት ይደርስበታል
ይህ ጥፋቱ እንደ ሰው ወይም እንደ እንስሳ እንደሚያሳድደውና ወዲያውኑ እንደሚደርስበት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ጥፋቱ ያገኘዋል” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥፋቱ
ይህ በእርሱ ላይ የሚደርስበትን ጥፋት ያሳያል ነገር ግን እርሱ ራሱ የሚያደርሰውንም ጥፋት ያመለክታል።

ድንገት፣ በቅጽበት
ሁለቱም ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ አንዱ ወይም ሁለቱ “ሳይታሰብ” ወይም “በፍጥነት” በሚለው ሊተኩ ይችላሉ።

Proverbs 6:16

እግዚአብሔር የሚጠላቸው ስድስት ነገሮች፣ ሰባትንም
ይህ ሙሉ ጥቅስ እግዚአብሔር አንድ ነገር ብቻ ሳይሆን ብዙ ነገሮችን እንደሚጠላ አጽንዖት የሚሰጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የሚጠላቸው ስድስት ነገሮች፤ ሰባት ነገሮች” (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

የሚጠላቸው
x

Proverbs 6:17

አያያዥ ሃሳቦች፡-
ይህ በምሳሌ 6፡16 ላይ የተመለከቱ እግዚአብሔር የሚጠላቸው የተለያዩ ነገሮች ዝርዝር ነው።

ዓይኖች ... ምላስ ... እጅ ... ልብ ... እግር
እነዚህ የሰውነት አካላት በሙሉ የሰውን ሁለንተና ያመለክታሉ። እያንዳንዳቸውን “ሰዎች” ብለህ ልትተረጉማቸው ትችላለህ። (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ደም የምታፈስስ
“መግደል” ወይም “ነፍስ ማጥፋት”

ክፉ ሃሳብ
“ክፉ እቅድ”

ውሸትን ወደ ውጭ ይተነፍሳል
ይህ ዘይቤአዊ ንግግር የማያቋርጥ ውሸትን ለማመልከት “ይተነፍሳል” የሚለውን ቃል ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፡- “ያለማቋረት ይዋሻል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ጠብ
ይህንን በምሳሌ 6፡16 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልት።

ጠብን የሚዘራ
ይህ ዘይቤአዊ ንግግር “የሚዘራ” የሚለውን ቃል በመጠቀም የጠብ ምክንያት መሆንንና ጠብ ማምጣትን ያመለክታል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 6:20

የአባትህን ትዕዛዝ ጠብቅ ... የእናትህንም ትምህርት አትተው
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በአንድ በኩል ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። በሌላ በኩል ደግሞ “አባት” እና “እናት” በሚሉት ድግግሞሽ አጽንዖት ሴቶችን በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ በግልጽ ያካትታል። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

የእናትህንም ትምህርት አትተው
ይህ የንግግር ዘይቤ አዎንታዊውን “ጠብቅ” ለማለት አሉታዊውን “አትተው” የሚለውን ተጠቅሟል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእናትህን ትምህርት ጠብቅ” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

ሁልጊዜ በልብህ አኑራቸው፣ በአንገትህም ዙርያ አሰራቸው
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። እነዚህ ሐረጎች አንተን ለማስታወስ በሰውነትህ ውስጥ ወይም በሰውነትህ ላይ ልታስቀምጣቸው እንድትችል ትእዛዘቱና ትምህርቶቹ እንደተጻፉ አድርገው ይገልጿቸዋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በልብህ አኑራቸው
“ውደዳቸው” “ስለእነርሱ አስብ”

Proverbs 6:22

ስትሄድም ... ስትተኛ ... ስትነሣ
እነዚህ ሶስት ሐረጎች በአንድ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት ትምህርቶቹ በየትኛውም ጊዜ ጠቃሚ እንደሆኑ አጽንዖት ለመስጠት ነው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ይመሩሃል ... ይጠብቁሃል ... ያስተምሩሃል
የእነዚህ ሐረጎች መደጋገም ትምህርቶቹ ለሁሉም ዓይነት ጉዳዮች ጠቃሚዎች መሆናቸውን ለማሳየት ነው። በተጨማሪ እነዚህ ትምህርቶች ሰዎች እንደሆኑ አድርጎ ይናራል። (ትይዩነት እና ሰውኛ የሚለውን ይመልከቱ)

በምክር የሚገኙት ትዕዛዛቱ ... ትምህርቶቹ ... ተግሳጾቹ
እነዚህ ሶስት ሐረጎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ በአንድ ላይ አባትና እናት የሚያስተምሩትን የተለያዩ ትምህርቶች ያሳያሉ። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

መብራት ... ብርሃን ... የሕይወት መንገድ
እነዚህ ሶስት ሐረጎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ የተደጋገሙት ትምህርቶቹ ሕይወትን የተሻለና ቀላል የሚያደርጉ የመሆናቸውን እውነታ አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እንደ መብራት ጠቃሚ ናቸው ... በጨለማ ውስጥ እንዳለ ብርሃን አጋዥ ናቸው ... እንደ ሕይወት መንገድ ልንከተላቸው የሚያስፈልጉ ናቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

የሕይወት መንገድ
“ወደ ሕይወት የሚመራ መንገድ” ወይም “እግዚአብሔር የተቀበለው የሕይወት መንገድ”

Proverbs 6:24

እርሱ ይጠብቅሃል
እዚህ ላይ “እርሱ” የሚለው ቃል በምሳሌ 6፡20 ላይ በአባትና በእናት የተማራቸውን ትምህሮች ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ያድንሃል” ወይም “ይጠብቅሃል” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ምግባረ ብልሹ ሴት ... አመንዝራ ሴት
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። “አመንዝራ ሴት” የሚለውን በምሳሌ 5፡3 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

በሸፋሸፍትዎቿ እንድታጠምድህ አትፍቀድላት
ፀሐፊው የሴትን ሸፋሸፍቶች ወጣት ወንድ ልጅ ሊሳስት የሚችልበት ወጥመድ እንደሆነ አድርጎ ተናግሯል። እነዚህ ለውበቷ ተዛምዶአዊ ንግግር ዘይቤ ናቸው፣ በእርስዋ እንዲሳብና እርስዋን እንዲፈልጋት ለማድረግ ሴቷ ወጣት ወንድ ልጅን ለምታይበት መንገድ ደግሞ ምትክ ስም ናቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “በቁንጅናዋና አንተን በዓይኖቿ በምታይበት ሁኔታ በቁጥጥር ስር እንድታደርግህ አትፍቀድላት” (ተለዋጭ፣ ተዛምዷዊ እና ምትክ ስም የሚለውን ተመልከት)

ምግባረ ብልሹ
“ክፉ ምግባር”

በልብህ
“ልቧ” አእምሮዋን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡ “በሃሳብህ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ውበቷ
“ስለ እርስዋ ያላት ውበት” ይህ ለሴቷ ምትክ ስም ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእርስዋ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አያጥምድህ
“በቁጥጥር ስር አታድርግህ”

ሸፋሸፍትዎቿ
“ሸፋሸፍቶች” የወንድ ልጅ ቀልብ ለመሳብ የምትጠቀምበት በሰውነቷ ስለሚታዩ ማንኛውም ውበት የሚቆም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “መልከ መልካም ዓይኖቿ” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 6:26

የአንድ ቁራሽ ዳቦ ዋጋ
ይህ የሚናገረው ስለ ቁስ ዋጋ እንጂ ስለ መንፈሳዊ ዋጋ ወይም ስለ ስነ ምግባር ዋጋ አይደለም። አማራጭ ትርጉም፦ “ትንሽ ነው”

ሕይወትህን ሊያስከፍልህ ይችላል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) የሌላ ወንድ ሚስት ሕይወትህን ታጠፋዋለች ምክንያቱም እርስዋ ሁልጊዜ የምትፈልገው የላቀ ነገር ነው ወይም 2) የሌላ ሴት ባል አድኖ ይገድልሃል

አንድ ሰው ልብሶቹ ሳይቃጠል በደረቱ እሳት መያዝ ይችላልን?
ይህ ድርጊት በጣም አደገኛ ስለሚሆን ጉዳት ያስከትላል። ለዚህ ጥያቄ የሚቀርበው መልስ “አይችልም” የሚል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በደረቱ ላይ እሳት የሚይዝ ወንድ ልብሱን ያቃጥላል” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ሳይቃጠል
“ጥፋት ሳይደርስ” ወይም “ሳይወድም”

ልብሶቹ
ልብሶቹ የሚለው ቃል ለሰውየው ሙሉ ሁለንተና የሚቆም ነው። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 6:28

ሰው እግሩ ሳይቃጠል በፍም ላይ መራመድ ይችላልን?
በፍም ላይ መራመድ የሰውየውን እግር ያቃጥላል፤ ለዚህ ጥያቄ ስለዚህ ተገቢው መልስ “አይችልም” ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በፍም ላይ የሚራመድ ማንኛውም ሰው እግሩ ይቃጠላል።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በፍም ላይ መራመድ
ይህ ለአመንዝራነት የቆመ ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መራመድ
ይህ ያለ ማታለል እና ያለ አስማት ሩቅ ርቀት ቀስ ብሎ መጓዝ ነው።

መቃጠል
“መንደድ”

Proverbs 6:30

ሌባን አይንቁትም
“ሌባን በንቀት አትመልከት” ወይም “ሌባ ክፉ እንደሆነ አታስብ”

ቢያዝ
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አንድ ሰው እርሱን ቢይዘው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በቤቱ
ይህ የንግግር ዘይቤ በቤቱ ያለው ማንኛውም ነገር እርሱ በባለቤትነት የያዘው ነው ይላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የእርሱ የሆነው ሁሉ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 6:32

ሰው
“ሰውየው” ወይም “ያ ሰው”

የሚገባው
“ሌባ ለሰራው ድርጊት ተገቢው ቅጣት”

ውርደቱ
ይህ ዘይቤአዊ ንግግር “ውርደት” የሚለውን ቃል የተጠቀመው ስላደረገው አሳፋሪ ተግባር የሚሰማውን ስሜት ለማመልከት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የአሳፋሪ ተግባሩ ትዝታ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

አይደመሰስም
ይህ ዘይቤአዊ ንግግር “አይደመሰስም” የሚለውን አሉታዊ አገላለጽ የተጠቀመው ስድቡ ሁልጌዜ በዚያ እንደሚኖር ለማመልከት ነው። (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 6:34

ቁጡ
በጣም መናደድ

እርሱ ምህረት አያደርግም
“እርሱ” የሚለው የሚያመለክተው ሚስቱ ከሌላ ወንድ ጋር ያመነዘረችው የአመንዝራይቱ ባል ወይም ጎረቤት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በአንተ ላይ የሚያመጣው ጉስቁልና ገደብ አይኖረውም” ወይም “የተቻለውን ያህል ይጎዳሃል” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

በሚበቀልበት ጊዜ
“በቀል በሚያደርስበት ጊዜ” ወይም “የበቀል እርምጃ ለመውሰድ ጊዜው በሚቀርብበት ጊዜ”

ይበቀላል
ሰውየው ሲበቀል፣ ቀድሞ የጎዳውን ሰው ለመጉዳት ነው

ካሳ
ይህ በደል ያደረሰው ሰው ለተበዳዩ የሚከፍለው ክፍያ ነው

እሺ አይልም
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የእርሱን አእምሮ ለመለወጥ የሚችል በቂ ገንዘብ ልትከፍለው አትችልም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እሺ አይልም፣ ብታቀርብለትም
“እሺ አይልም። ብታቀርብለትም ይህ እውነት ነው”

Chapter 7

1 ልጄ ሆይ፣ ቃሎቼን ጠብቅ፣ ትእዛዜንም በአንተ ውስጥ አኑር። **2** ትእዛዜን ጠብቅ በሕይወትም ኑር፣ ሕጌንም እንደ ዓይንህ ብሌን ጠብቅ። **3** በጣቶችህም ላይ እሰራቸው፤ በልብህም ጽላት ጻፋቸው። **4** ጥበብ “አንቺ እህቴ ነሽ” በላት፣ ማስተዋልን ደግሞ ዘመዴ ብለህ ጥራው፣ **5** ከአመንዝራ ሴት፣ ቃሏንም ከምታለዝብ ከዘማዊም ሴት ትጠብቅህ ዘንድ። **6** በቤቴ መስኮት ላይ ሆኜ ወደ ውጭ ተመለከትሁ፣ **7** ብዙ እውቀት አልባ ወጣቶች ተመለከትሁ። ከመካከላቸው አንድ የማያስተውል ወጣት ተመለከትሁ። **8** ያ ወጣት በቤቷ ማዕዘን አጠገብ ባለው መንገድ አለፈ፣ ከዚያም ወደ ቤቷ አቅጣጫ ሄደ **9** ብርሃን ደንገዝገዝ፣ ቀኑ መሸትሸት ብሎ ነበር፣ በምሽትና በሌሌት ጨለማ። **10** በዚያ አንዲት ሴት አገኘችው፣ እንደ ሴተኛ አዳሪ የለበሰች፣ እዚያ ለምን እንደ መጣች በሚገባ ታውቃለች። **11** ጫኺና እምቢተኛ ናት፣ እግሮቿ በቤት አይቀመጡም **12** አንዴ በመንገድ፣ አንዴ በገበያ፣ በየማዕዘኑም ተጋድማ ታደባለች። **13** ስለዚህም ትይዘዋለች፣ ትስመውማለች፣ ፊቷም እፍረት ሳይታይበት እንዲህ አለችው፣ **14** ዛሬ የሰላም መስዋዕቴን አቅርቤአለሁ፣ ስእለቴንም ፈጽሜአለሁ፣ **15** ስለዚህ አንተን ለማግኘት፣ ፊትህን ለመፈለግ ወጣሁ፣ አግኝቼሃለሁም። **16** በአልጋየ ላይ መሸፈኛ ዘርግቼበታለሁ፣ ከግብጽ የመጣ ባለቀለም የአልጋ ልብስ አንጥፌበታለሁ። **17** አልጋየን ከርቤ፣ አልሙንና ቀረፋ ረጭቼበታለሁ። **18** ና፣ እስኪነጋ ድረስ በፍቅር እንርካ፤ ፍቅራችንን በምንገልጥባቸው የተለያዩ መንገዶች በታላቅ ደስታ እንፈንድቅ። **19** ባሌ በቤት የለም፤ ወደ ሩቅ መንገድ ሄዷል። **20** በገንዘብ የተሞላ ቦርሳ ወስዷል፤ ሙሉ ጨረቃ በወጣበት ቀን ይመለሳል።” **21** በሚያባብል ንግግሯ ታሳስተዋለች፣ በለሰለሰ ንግግሯም ታታልለዋለች። **22** ለመታረድ እንደሚነዳ በሬ፣ ፍላጻ ጉበቱን እስኪወጋው ድረስ በወጥመድ እንደተያዘ አጋዘን፣ **23** ወደ ወጥመድ በርራ እንደምትገባ ወፍ፣ ሕይወቱን እንደሚያሳጣው ሳያውቅ እርሷን ይከተላታል። **24** አሁን፣ ልጆቼ ሆይ፣ አድምጡኝ፤ የምናገረውንም ልብ ብላችሁ ስሙኝ። **25** ልባችሁ ወደ መንገዷ እንዲያዘነብል አትፍቀዱ፤ በጎዳናዋም አትሳቱ። **26** ብዙ ተጎጂዎችን አጥምዳ ጥላለች፤ ቁጥራቸውም እጅግ ብዙ ነው። **27** ቤቷ ወደ ሲኦል በሚወስደው መንገድ ነው፤ ወደ ሞት ማደርያም የሚያወርድ ነው።

Proverbs 7:1

ቃሎቼን ጠብቅ
እዚህ መጠበቅ መታዘዝን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ቃሎቼን ታዘዝ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ትእዛዜንም በአንተ ውስጥ አስቀምጥ
እዚህ የእግዚአብሔር ትእዛዛት አንድ ሰው በመጋዘን ውስጥ እንደሚያሰስቀምጣቸው ዕቃዎች ተደርገው ተነግረዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ትእዛዛቴን በቃልህ አጥና/ሸምድድ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ትእዛዜን ጠብቅ
እዚህ መጠበቅ መታዘዝን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ቃሎቼን ታዘዝ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ዓይንህ ብሌን
የዓይን ብሌን ሰዎች ብዙ ጊዜ በፊታቸው የተለያየ ነገር ሲመጣባቸው በተለምዶ በደመነፍስ ጥበቃ የሚያደርጉለትና የሚከላከሉለት በዓይን ውስጥ ያለው ጥቁሩ የዓይን ክፍል ነው። እዚህ “የዓይን ብሌን” አንድ ሰው እጅግ ዋጋ የሚሰጠውና በሚገባ ጥበቃ የሚያደርግለት ማንኛውንም ነገር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እጅግ ውድ እንደሆነው ንብረትህ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

በጣቶችህ እሰራቸው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ፀሐፊው ወንድ ልጁ አንዳንድ የእግዚአብሔር ትእዛዛት በቀለበቱ ላይ ቀርፆ በጣቱ ላይ እንዲያደርገው ይፈልጋል ወይም 2) ፀሐፊው ወንድ ልጁ ቀለበቱን ሳይረሳ ሁልጊዜ እንደሚያደርገው እንደዚሁ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ሁልጊዜ እንዲያስታውስ ይፈልጋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በልብህ ጽላት ጻፋቸው
እዚህ ልብ የሰውን አእምሮ ይወክላል፣ አንድን ነገር በሚገባ ማስታወስ ደግሞ ያ ሰው በድንጋይ ጽላት ላይ እንደጻፈው ተደርጎ ተነግሯል። ይህንን በምሳሌ 3፡3 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “በድንጋይ ላይ እንደጻፍካቸው እያሰብህ ትእዛዛቴን በሚገባ አስታውሳቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 7:4

ጥበብን አንቺ እኅቴ ነሽ በላት
እዚህ ላይ ጥበብ ሰው እንደሆነች ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “እህትህን እንደምትወድ እንደዚሁ ለጥበብ ተገቢ ዋጋ ስጣት” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ማስተማውልንም ወዳጄ ብለህ ጥራት
እዚህ ላይ የማስተዋልን ባሕርይ እንደ ወዳጅ ወይም ዘመድ ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም፡- “ወዳጅህን እንደምትንከባከብ እንደዚሁ ማስተዋልን ተንከባከባት” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወዳጅ
“ዘመድ” ወይም “የቤተሰብ አባል”

ጋለሞታ ሴት
ይህ አንድ ወንድ ጋብቻ ያልፈጸመላትን ማንኛዋንም ሴት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከእርስዋ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት ሊኖርህ የማትገባ ሴት”

ብልሹ ስነምግባር ያላት ሴት
ይህ አንድ ወንድ የማያውቃትን ማንኛዋም ሴት ያመለክታል።

በለዘበ ቃሏ
ለማታለል የሚነገሩ ቃላት ለስላሳ እቃዎች እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ደስ የሚያሰኙ ነገሮችን የምትናገር፣ ነገር ግን ልታታልልህ የምትፈልግ”

Proverbs 7:6

ርብራብ
እርስ በርሳቸው በተጠላለፉ ቀጭን እንጨቶች የተሰራ ያዘነበሉ አራት ማዕዘን ንድፍ ያላቸው ቀዳዳዎች ያሉት የመስኮት ክዳን።

አላዋቂ
ልምድ የሌለው ወይም የአእምሮ ብስለት የሌለው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Proverbs 7:8

የእርስዋ ማዕዘን
እዚህ ላይ “የእርስዋ” የሚለው ቃል በምሳሌ 7:5 ላይ እንደተጠቀሰው ማንኛዋንም እንግዳ ሴት የሚያመለክት ነው። እርስዋ በተወሰኑ ማዕዘኖች በአጠገቧ የሚያልፍ የሚስማማትን ወንድ እየጠበቀች ቆማ ነበር። አማራጭ ትርጉም፡- “እንግዳ ሴት ቆማበት የነበረው ማዕዘን”

ማዕዘን
ይህ ሁለት መንገዶች የሚገናኙበትነ ስፍራ ያመለክታል።

ማታ ሲመሸ
የሚጨልምበትና ሌሊቱ የሚመጣበት የቀኑ ጊዜ ነው

Proverbs 7:10

በሐሰተኛ ልብ
እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ሃሳብን ወይም እቅድን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርስዋ አንድን ሰው ለማታለል አቅዳለች” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጫኺና እምቢተኛ ናት
“የምትናገረው በጩኸት ነው፣ የምታደርገው ደግሞ እሷ በምትፈልገው መንገድ ነው”

እግሮችዋም በቤትዋ አይቀመጡም
“እግሮቿ” የሚለው ሐረግ የሚወክለው ሴቷን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በቤት ፈጽሞ አትቀመጥም” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

አድፍጣ ትጠብቃለች
እዚህ ላይ ሴቷ በአካል አንድን ሰው ወይም እንስሳ ለመያዝ እንደተዘጋጀች አድርጎ ገልጧታል። በተጨማሪ እዚህ ላይ አንድን ሰው የማጥመዷ ሃሳብ ኃጢአት እንዲፈጽም አንድን ሰው መገፋፋትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰው ለማጥመድ ትጠብቃለች” ወይም “ኃጢአት እንዲሰራ ልትገፋፋው የምትችለውን ሰው ለማጥመድ ትጠብቃለች” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 7:13

እርስዋ
ይህች በምሳሌ 7:10 ላይ የተጠቀሰችው ሴት ናት።

ያዘችው
“አጥብቃ አፈፍ አደረገችው”

ፊትዋም ያለ እፍረት ሆኖ
እዚህ “ያለ እፍረት” የሚለው “ግትርነትን” ይወክላል። “ፊትዋ እፍረት ሳይታይበት” የሚለው በአንድ ሰው የሚታይ መንቻካ የፊት ገጽታ ማለት ነው። ይህ ሴትየዋ በከባድ መንገድ ስራዋን እንደምትሰራ፣ ትክክል እንዳልሆነ እያወቀች ሆን ብላ እንደምታደርገው የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በፊትዋ ምንም ዓይነት የሀፍረት ገጽታ ሳይታይባት” (ፈሊጥ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ስእለቴንም ፈጽሜአለሁ
እዚህ ላይ “ስእለት” የሚለው ሰውየው ለእግዚአብሔር ለመሰዋት የገባውን ቃል ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለእግዚአብሔር ቃል የገባሁትን መስዋዕት አቅርቤአለሁ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ፊትህን እሻለሁ
እዚህ ላይ “ፊት” ሰውየውን በተለይም ደግሞ የሰውየውን ሕልውና የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እፈልግሃለሁ” ወይም “ባለህበት እፈልግሃለሁ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 7:16

በአልጋየ ላይ መሸፈኛ ዘርግቼበታለሁ
“በአልጋየ ላይ አንጥፌአለሁ”

አልሙን
በጣም ቆንጆ ሽታ ካለው ዛፍ የሚገኝ የግንድ ዓይነት ነው።

በጥልቅ ፍቅር እንርካ
እዚህ ላይ የወሲባዊ ፍቅር ደስታ እንደሚጠጣ መልካም ነገር ተደርጎ ተነግሮአል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርስ በርሳችን የፈለግነውን ያህል ፍቅርን እናድርግ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 7:19

በቤቱ የለም
“በቤት ውስጥ የለም”

ሙሉ ጨረቃ
ጨረቃ ሙሉ የምትባለው ሙሉ በሙሉ ክብ ቅርጽ ስትይዝና ከፍተኛ ብርሃንዋን ስታንጸባርቅ ነው።

እንዲስት ታደርገዋለች
አንድ ሰው በሆነ መንገድ አንድ ነገር እንዲያደርግ ማነሳሳት በመንገድ ይሄድ የነበረ ሰው አቅጣጫውን እንደቀየረ ተደርጎ ተነግሮአል። አማራጭ ትርጉም፡- “ገፋፋችው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርስዋ ... እርስዋ ... የእርሱ
ሴትዮዋ በትዳር ያለች ስትሆን ነገር ግን “ከእርሱ” ማለትም ከወጣት ወንድ ጋር መተኛት የምትፈልግ ሴት ናት።

ለስላሳ ከንፈር
እዚህ ላይ “ከንፈር” የሚወክለው የሰውን ንግግር ነው። አንድ ሰው እውነተኛ ያልሆነ ነገር በመናገር ሌላውን ሰው ከፍ ከፍ ሲደርገው እነዚህ በልዝብነት የተነገሩ ቃላቶች እንደ ለስላሳ እቃዎች ተደርገው ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሸንገላ፣ የማታለያ ቃላት” (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲስት አደረገችው
“ክፉ ነገር እንዲሰራ አሳመነችው” አማራጭ ትርጉም፡- “ከእርስዋ ጋር ኃጢአት እንዲሰራ አሳመነችው”

Proverbs 7:22

በድንገት ተከትሏት ሄደ
ወጣት ወንድ ምን ማድረግ እንዳለበት ለማሰብ የሚወስደው ጊዜ በጣም አጭር እንደሆነ ይህ ሃሳብ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርስዋን ተከትሎ ለመሄድ በፍጥነት ወሰነ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለመታረድ እንደሚነዳ በሬ
ይህ ወጣት ወንድ በአላዋቂነትና ሳይጠረጥር አመንዝራይቱን ተከትሎ የሄደበት መንገድ ሶስቱ እንስሳት የገቡበትን አደጋ ባለማወቅ ከሄዱበት መንገድ ጋር ተነጻጽሯል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መታረድ
ይህ ስጋውን ለመብላት እንስሳን ማረድ ያመለክታል።

አጋዘን
ይህን ቃል በምሳሌ 5፡19 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

ፍላጻ ጉበቱን እስኪወጋው ድረስ
ይህ ክፍል አዳኙ አጋዘኑን በወጥመድ የያዘው በፍላጻ ለመውጋት እንደሆነ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “አዳኝ በጣም ዋነኛ የሆነውን የሰውነቱን ክፍል እስኪወጋው ድረስ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ጉበት
እዚህ ላይ ይህ ብልት የአጋዘኑን በጣም ዋነኛ የሰውነት ክፍል ይወክላል።

ሕይወቱን ያሳጣዋል
ይህ ሰው ከዚህ የተነሳ ይሞታል ለማለት የአባባል ዜይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ይገድለዋል” ወይም “ወዲያውኑ ይሞታል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 7:24

አሁን
ይህ በዚህ ትምህርት ማጠቃለያ ላይ የተናጋሪው ወንድ ልጆች ትኩረት ላይ ለማነጣጠር የተነገረ ነው።

ልብህ ወደ መንገዶቿ አያዘንብል በጎዳናዋ አትሳት።
እዚህ ላይ “መንገዶች” ማለት ሰው ሊሄድበት የሚመርጠው መንገዶች ናቸው። ይህ የሰውን ባሕርይ ማለትም በሕይወቱ ሊፈጽማቸው የወሰናቸውን ነገሮች ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ልብህ ከአመንዝራይቱ ሴት መንገዶች በጣም ርቆ እንዲቆይ አድርግ” ወይም “አመንዝራይቱ ሴት የምታደርጋቸውን ነገሮች እንዲያደርግ ልብህ እንዲሻ አትፍቀድለት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ልብህ
እዚህ ላይ “ልብ” ሰውን ይወክላል፣ ለፍላጎቱም አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ”(ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

በመንገዶቿ አትሳት
ይህ ከቀደመው ዓረፍተ ነገር ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው። የመጀመርያውን ማስጠንቀቂያ የሚያጠናክር ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በእርስዋ መንገድ ለመሄድ ስትል ትክክለኛውን መንገድ አትተው” (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 7:26

ወግታ የጣለቻቸው ብዙ ናቸው
በፍላጻ ወይም በጦር መወጋት መገደልን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ብዙ ሰዎች ተወግተው እንዲሞቱ አድርጋለች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ቤቷ ወደ ሲኦል በሚወስደው መንገድ ነው ... ይወርዳሉ
እዚህ ላይ “መንገድ” ሞኞች ሰዎች የሚሳተፉበትን የባህርይ ዓይነት የሚወክል ነው። ሲኦል ሙታን ለሚኖሩበት ስፍራ የተሰጠ ስም ነበር።

ወደ ሲኦል በሚወስደው መንገድ ... ጨለማ ወደሆነው ወደ ሞት ማደርያም የሚያወርድ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ የተደጋገሙት የሴትየዋ ተጠቂዎች እንደሚተፉ አጽንዖት ለመስጠት ነው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ቸለማ የሆነው የሞት ማደርያ
ይህ መግለጫ ሙታን በሲኦል ውስጥ በብዙ የተለያዩ ክፍሎች እንደሚተኙ የሚያሳይ ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 8

1 ጥበብ እየጮኸች አይደለምን? ማስተዋልስ ድምጿን ከፍ አላደረገችምን? **2** ከመንገድ አጠገብ ባሉት ኮረብታዎች ጫፍ ላይ፣ መንገዶች በሚገናኙበት ቦታ፣
ጥበብ ትቆማለች። **3** ወደ ከተማይቱ በሚያስገቡት በሮች አጠገብ፣ በከተማይቱ መግቢያ አጠገብ፣ ትጣራለች። **4** እናተ ሰዎች፣ ወደ እናንተ እጣራለሁ፣
ድምጼንም ከፍ አድርጌ ወደ ሰው ልጆች እጮኻለሁ። **5** እናንተ ትምህርት ያላገኛችሁ፣ ጠንቃቃነትን ተማሩ፣ እናንተ እውቀትን የምትጠሉ፣ የሚያስተውል ልብ
ይኑራችሁ። **6** የከበሩ ነገሮችን እናገራለሁና አድምጡኝ፣ ከንፈሮቼ ሲከፈቱ ቀና የሆነውን ነገር እናገራለሁ **7** አንደበቴ እውነትን ይናገራልና፣ ከንፈሮቼም ክፋትን
ይጠላሉና። **8** ከአንደበቴ የሚወጡ ቃሎች ሁሉ ጽድቅ ናቸው፤ በእነርሱ ውስጥ ጠማማ ወይም አሳሳች ነገር የለውም። **9** ለሚያስተውል ሰው ቃሎቼ በሙሉ ቀና
ናቸው፤ እውቀትን ለሚያገኙ ቃሎቼ ትክክለኛ ናቸው። **10** ከብር ይልቅ ተግሳጼን ምረጡ፣ ከንጹህ ወርቅም ይልቅ እውቀትን ምረጡ። **11** እኔ ጥበብ፣ ከከበረ
ዕንቁ እበልጣለሁና፤ ከምትመኙት ነገር በሙሉ ከእኔ ጋር የሚስተካከል የለም። **12** እኔ ጥበብ፣ ከጥንቃቄ ጋር እኖራለሁ፣ እውቀትና ነገሮችን ለይቶ ውሳኔ
የመስጠት ኃይልም አለኝ። **13** እግዚአብሔርን መፍራት ክፋትን ይጠላል፤ ትዕቢት፣ እብሪት፣ ክፉ መንገድና ጠማማ ንግግር እጠላለሁ፣ ፈጽሞም
እጠላቸዋለሁ። **14** እኔ መልካም ምክርና እውነተኛ ጥበብ አለኝ፤ ማስተዋል አለኝ፣ ብርታትም የእኔ ነው። **15** ነገስታት፣ የከበሩ ሰዎችና በፍትሃዊነት ሕዝብን
የሚመሩ ሁሉ በእኔ ያስተዳድራሉ። **16** መሳፍንቶች፣ የከበሩ ሰዎችና በፍትህ ሕዝብን የሚመሩ ሁሉ በእኔ ያስተዳድራሉ። **17** የሚወዱኝን እወዳቸዋለሁ፣
ተግተው የሚፈልጉኝም ያገኙኛል። **18** ባለጠግነትና ክብር፣ ዘላቂነት ያለው ሃብትና ጽድቅም በእኔ ዘንድ አሉ። **19** ፍሬየ ከወርቅ ይበልጣል፣ ከነጠረ ወርቅም
ይበልጣል፤ ስጦታየም ከንጹህ ብር ይበልጣል። **20** እኔ በጽድቅ መንገድ እሄዳለሁ፣ ወደ ፍትህ በሚወስድ ጎዳና እጓዛለሁ፣ **21** ስለዚህ ለሚወዱኝ ሀብትን
እሰጣቸዋለሁ፣ ግምጃ ቤታቸውንም እሞላለሁ። **22** እግዚአብሄር ከመጀመርያ ፈጠረኝ፣ በቀድሞ ዘመን የስራው መጀመርያ ነኝ። **23** ከመጀመርያ፣ ምድር
ከመፈጠሯ በፊት፣ ከረጅም ዘመናት ጀምሮ ተሾምሁ። **24** ውቅያኖሶች ሳይኖሩ፣ የውኃ ምንጮች ሳይፈልቁ በፊት፣ እኔ ተወልጄ ነበር፣ **25** ተራሮች ገና
ሳይመሰረቱ፣ ከኮረብቶችም በፊት፣ እኔ ተወለድሁ። **26** እግዚአብሔር ምድርንና ሜዳዎቿን፣ የመጀመርያውን የዓለም አፈር እንኳ ከመፍጠሩ በፊት እኔ
ተወለድሁ። **27** እርሱ ሰማያትን ሲመሰርት፣ በውቅያኖስ ገጽ የአድማስን ምልክት ባደረገ ጊዜ እኔ እዚያ ነበርሁ። **28** እርሱ በላይ ያሉትን ደመናት ባጸና ጊዜ፣
የውቅያኖስን ምንጮች በመሰረተ ጊዜ እኔ እዚያ ነበርሁ። **29** ውሆች የእርሱን ትዕዛዝ አልፈው እንዳያጥለቀልቁ እርሱ ለባህር ድንበርን ባበጀለት ጊዜ፣ የምድርም
መሰረት የት መሆን እንዳለበት በወሰነበት ጊዜ እኔ እዚያ ነበርሁ። **30** እኔ ዋና ሰራተኛ ሆኜ በአጠገቡ ነበርሁ፣ እኔ ዕለት በዕለት እርሱን ደስ አሰኘው ነበርሁ፣
ሁልጊዜ በፊቱ ደስ ይለኝ ነበር። **31** የእርሱ በሆነው በመላው ዓለም ደስ ይለኝ ነበር፣ ደስታየም በሰው ልጅ ነበር። **32** አሁንም፣ ልጆቼ ሆይ፣ አድምጡኝ፣
መንገዴን የሚጠብቁ ሁሉ ደስተኞች ይሆናሉና። **33** ምክሬን አድምጡ፣ ጥበበኞችም ሁኑ፤ ቸልም አትበሉት። **34** እኔን የሚያደምጠኝ ደስተኛ ይሆናል፣ ዕለት
በዕለት በመግቢያየ የሚተጋ፣ በቤቴም በሮች አጠገብ የሚጠብቀኝ። **35** እኔን ያገኘ ሕይወትን ያገኛልና፣ የእግዚአብሔርንም ሞገስ ያገኛል። **36** እኔን ያጣ ግን
ራሱን ይጎዳል፤ እኔን የሚጠሉኝ በሙሉ ሞትን ይወድዳሉ።

Proverbs 8:1

አጠቃላይ መረጃ፡-
በምዕራፍ 8 ጥበብ ሰዎች እንዴት ጥበበኛ መሆን እንዳለባቸው እንደምታስተምር ሴት ተደርጋ ተነግራለች። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ፡-
በምዕራፍ 8 ውስጥ ብዙ ጥቅሶች ትይዩነት አላቸው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

በውኑ ጥበብ አትጮኽምን?
ይህ ጥያቄ ጥቅም ላይ የዋለው አንባቢዎች ቀድመው የሚያውቁትን ነገር ለማስታወስ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበብ ትጣራለች” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በውኑ ጥበብ አትጮኽምን?
እዚህ ላይ ጥበብ እንደ ሴት ቀርባለች። አንድ ቋንቋ እንዲህ ዓይነት ተለዋጭ ዘይቤ መጠቀም የማይፈቅድ ከሆነ የሚከተሉት ሌሎች አማራጮች ናቸው፡- 1) “ጥበብ እንደ ሴት የምትጮኽ አይደለችምን?” 2) “ጥበብ የምትባል ሴት እየጮኸች አይደለምን?” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ማስተዋልስ ድምፅዋን ከፍ አታደርግምን? **Does not Understanding raise her voice?**
እዚህ ላይ “ማስተዋል” ትርጉሙ ከ“ጥበብ” ጋር ተመሳሳይ ነው። (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ድምፅዋን ከፍ አደረገች
“ተናገረች”

ወደ ከተማይቱ በሚያስገቡት በሮች አጠገብ
በጥንት ጊዜ ከተሞች ብዙ ጊዜ በር የተገጠመላቸው የውጭ የግንብ አጥር ነበራቸው።

ትጣራለች
ይህ እንደ ሴት የተመሰለችውን ጥበብን ያመለክታል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 8:4

አጠቃላይ መረጃ፡-
በቁጥር 4-36 ጥበብ ለሕዝቡ ትናገራለች።

ድምፄም ወደ ሰዎች ልጆች ነው
እዚህ ላይ “ድምጽ” የሚወክለው የተነገሩትን ቃላት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ቃላቶቼ ወደ ሰዎች ልጆች ናቸው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የሰዎች ልጆች
ይህ ሁሉንም የሰው ልጆች የሚወክል ምትክ ስም ነው። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

አላዋቂነት
ልምድ የሌለው ወይም የአእምሮ ብስለት የሌለው

ጥበብን ተማር
“ጥበብ” የሚለው ረቂቅ ቃል የሚያመለክተው ጥበበኛ ሰው የሚያምንበትንና ድርጊቱን የሚፈጽምበት መንገድ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበበኛ ሰው እንዴት እንደሚያደርግ ተማር” ወይም “ጥበበኛ መሆን ምን ማለት እንደሆነ ተማር” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የሚያስተውል ልብ ይኑራችሁ
“ነገሮችን በአእምሮአችሁ መረዳት መጀመር አለባችሁ”

Proverbs 8:6

ከንፈሮቼ ሲከፈቱ
እዚህ ላይ “ከንፈሮች “ የሚወክለው የሚናገርበትን የሰውን አንደበት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ለመናገር አንደበቴን ስከፍት” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ቅን
ተገቢ የሆነ ወይም ፍትሃዊ

አፌ ይናገራል
እዚህ ላይ “አፍ” የሚወክለው የሚናገረውን ሰው ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እናገራለሁ” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

እውነትን
“ሰዎች ሊያምኑት የሚችሉት”

ከንፈሮቼም ክፋትን ይጠላሉ
እዚህ ላይ “ከንፈሮች” የሚወክሉት የሚናገረውን ሰው ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፋትን እጠላለሁ” ወይም “ክፉ ነገሮችን መናገር በእኔ ዘንድ የተጠላ ነው” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ክፋት
እዚህ ላይ “ክፋት” የሚለው ረቂቅ ስም የሚወክለው ክፉ ንግግርን ነው። (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 8:8

ከአፌ የሚወጡ ቃሎች
“አፍ” የሚወክለው የሚናገረውን ሰው ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ የማስተምራቸው ነገሮች” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ጠማማ አይደሉም
መልእክትን ማጣመም እውነተኛውን መልእክት ወደ ውሸት ለመለወጥ እንደ ተለዋጭ የተነገረ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ውሸት አይደለም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀጥታ
እውነተኛ እና ግልጽ

ቃሎቼ እውቀትን ለሚያገኙ ጽድቅ ናቸው
ይህ አረፍተ ነገር እውቀትን የሚያገኙ ሰዎች የተናጋሪው ቃሎች ጽድቅ እንደሆኑ በቀላሉ ይረዳሉ የሚል ትርጉም አለው። እዚህ ላይ “ቃላቶች” የሚወክለው መልእክትን ወይም ትምህርትን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ጽድቅ ምን እንደሆነ እና ስህተት ምን እንደሆነ የሚያውቁ እኔ የማስተምረው ጽድቅ እንደሆነ ይረዳሉ።” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ቅን
እውነተኛ እና የሚታመን

Proverbs 8:10

ከብር ይልቅ ተግሳጼን ምረጡ
“ብርን ለማግኘት ከመድከም ይልቅ ተግሳጼን ለመረዳት በብዙ ልትደክሙ ይገባችኋል”

ጥበብ ከቀይ ዕንቊ ትበልጣለች፤ የከበረ ነገር ሁሉ አይተካከላትም
እዚህ ላይ የምትናገረው በሴት የተመሰለችው ጥበብ አይደለችም። ይሁን እንጂ በዚህ ስፍራ ጥበብ ተናጋሪዋ እንደሆነች ለማሰብም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ ጥበብ ከቀይ እንቁ እሻላለሁ፤ ምንም ዓይነት ሃብት ከእኔ ጋር አይስተካከልም” (ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ጥቅሶች የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 8:12

እኔ ጥበብ በብልሃት ተቀምጫለሁ
ብልሃት በዚህ ክፍል እንደ ሰው ተወክላለች። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ብልሃት
ጥንቃቄ ወይም መልካም ውሳኔ

እውቀትንም ጥንቃቄንም አግኝቻለሁ
“እውቀት” እና “ጥንቃቄ” የሚሉት ረቂቅ ስሞች በሌላ መንገድ ሊገለጹ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ እውቀት እና ጥንቃቄ ነኝ” ወይም “እኔ ብዙ ነገር አውቃለሁ፣ እኔ ጠንቃቃ ነኝ” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ጥንቃቄ
ለምንናገረውና ለምንሰራው ነገር ጥንቁቅ መሆን፤ ጉዳትን ላለመፍጠርና ሌሎችን ላለመጉዳት ጥንቁቅ መሆን

ጠማማ ንግግር
“ክፉ ንግግር”

ጠማማ
ትክክለኛ ያልሆነ

Proverbs 8:14

መልካም ምክር
“ጥበብ የተሞላ ሃሳብ”

ምክር
አንድን ሰው ለመርዳት የሚሰጥ ሃሳብ

መልካም
ጥሩ፣ ተዓማኒነት ያለው

እኔ ማስተዋል ነኝ
እዚህ ላይ ጥበብ ማስተዋል እንደሆነች ተደርጋ ቀርባለች። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ ማስተዋል አለኝ” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሹማምንቶች
የከበሩ ሰዎች፣ በአንድ አገር ውስጥ ወሳኝ የሆኑ ቤተሰቦችን የሚመሩ አባላት

Proverbs 8:17

ፍቅር
ይህ የሚያመለክተው ወንድማዊ ፍቅር ወይም ለጓደኛ ወይም ለቤተሰብ ያለንን ፍቅር ነው። ይህ በጓደኞችና በቤተዘመዶች መካከል ያለው ተፈጥሮአዊ ፍቅር ነው።

በትጋት
ጥንቃቄ የተሞላበትና የማያቋርጥ ጥረት

ብልጥግናና ክብር በእኔ ዘንድ ናቸው
“ብልጥግናና ክብር አለኝ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ዘላቂነት ያለው ሃብትና ጽድቅ
ይህ “ሃብትና ክብር” ምን እንደሆነ ያብራራል። ይህ “ስለዚህ” በሚለው አያያዥ አረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለዚህ እኔ ለሚፈልጉኝ ዘላቂነት ያለው ሃብትና ጽድቅ እሰጣለሁ” (አያያዥ ቃላቶች የሚለውን ይመልከቱ)

ጽድቅ
“በትክክለኛው መንገድ የመኖር ችሎታ”

Proverbs 8:19

ፍሬየ
ጥበብ የምታፈራውና የምታመጣው ነገር

ቡቃያየ
ጥበብ ካመጣችው ነገር የሚገኘው ትርፍ ወይም ጥቅም

እኔ በጽድቅ መንገድ እሄዳለሁ
በትክክለኛው መንገድ መኖር በትክክለኛው መንገድ እንደመራመድ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ በትክክል እኖራለሁ” ወይም “ትክክል የሆነውን ነገር አደርጋለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ፍትህ በሚወስዱ ጎዳናዎች
ይህ “የጽድቅ መንገድ” የሚለውን ትርጉሙ ምን እንደሆነ የበለጠ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ ፍጹም ፍትህ የሆነውን አደርጋለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መዛግብት
በታም ውድ የሆኑ ነገሮች የሚቀመጡበት። ጥበብ የተከታዮቿን መዛግብት በውድ ነገሮች የምትሞላ ሴት ተደርጋ ተገልጻለች። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 8:22

በቀድሞ ዘመን የስራው መጀመርያ
“እኔ እርሱ በቀድሞ ዘመን ከፈጠራቸው ነገሮች የመጀመርያው ነበርሁ

በቀድሞ ዘመን
“በጣም ከረጅም ጊዜ በፊት”

ዘመናት
“ዘመን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በጥቅሉ በጣም ረጅም ጊዜን ነው።

ተሰራሁ
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ሰራኝ”

ምድር ከመፈጠርዋ አስቀድሞ
“አስቀድሞ” የሚለው ቃል በጥቂቱ ረቂቅ በሆነ መንገድ ሊተረጎም ይችላ። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ምድርን ከፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 8:24

አጠቃላይ መረጃ፡-
ጥበብ መናገር ቀጥላለች። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ተራሮች ገና ሳይመሠረቱ
“የተራሮች መሰረት በቦታው ላይ ገና ሣይቀመጥ” ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል።: አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተራሮችን መሰረት ገና ሳይሰራና በተገቢው ቦታቸው ሳያስቀምጣቸው በፊት” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 8:26

ተወለድሁ ... ነበርሁ
ኢዚህ ላይ ጥበብ ስለራስዋ ትናገራለች። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ተወለድሁ
“እኖር ነበር”

ተመሰረተ
አንድን ነገር መመስረት ማለት በማይናወጥ መሰረት ላይ ወደ ሕልውና ማምጣት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ፈጠረ” ወይም “ሰራ”

በቀላያት ፊት ክበብን በደነገገ ጊዜ
ይህ የሚያመለክተው በባህር ላይ በመርከብ ውስጥ ያለ አንድ ሰው በሁሉም አቅጣጫ እንዴት ማየት እንደሚችል መነሻ ቦታ ማስቀመጥን ነው። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀላይ
“ውቅያኖስ”

Proverbs 8:28

አጠቃላይ መረጃ፡-
ጥበብ መናገርዋን ቀጥላለች። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ተመሰረተ
ወደ ቋሚ ማንነት ማምጣት

የቀላይን ምንጮች ባጸና ጊዜ
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ምንጮችን በቀላይ ውስጥ ባጸና ጊዜ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የቀላይ ምንጮች
የጥንት ዕብራውያን ውቅያኖስ ውኃውን የሚያገኘው ከባህር ጣጭኛው ክፍል ውስጥ ካሉት ምንጮች ነው ብለው ያስተምሩ ነበር።

ለባሕርም ዳርቻን በወሰነ ጊዜ
ለውቅያኖሶች ዳርቻ በፈጠረላቸው ጊዜ። “የባህር ዳርቻ” ውቅያኖሶችን ከደረቅ መሬት ይለያቸዋል።

የምድርም መሰረት የት መሆን እንዳለበት በወሰነበት ጊዜ
“ምድር” የሚለው የዕብራይስጡ ቃል ብዙ ጊዜ “መሬት” የሚል ትርጉም አለው።

የምድርም መሰረት የት መሆን እንዳለበት በወሰነበት ጊዜ
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ለምድር መሰረት ዳርቻ ባስቀመጠለት ጊዜ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 8:30

በአጠገቡ ነበርሁ
አሁንም ጥበብ እየተናገረች ነው። ጥበብ ከእግዚአብሔር አጠገብ እንደነበረች እየተናገረች ነው፣ ይህን ያለችው እግዚአብሔር ዓለምን ሲፈጥር የእርሱ ረዳት እንደነበረች ለማመልከት ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዋና ሰራተኛ
ይህ ጠቃሚ ነገሮችን ማለትም የቤት እቃዎችንና ቤቶችን በሚገባ ለመስራት ለአመታት የሰለጠነ ሰው ነው።

ደስ አሰኘው ነበር
“እርሱ እንዲደሰት የማደርገው እኔ ነበርሁ።” “ደስ” የሚለው ቃል እንደ ግስ መገለጽ የሚችል ረቂቅ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በእኔ ምክንያት ደስተኛ ነበር” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ዕለት በዕለትዕለት በዕለት
ይህ የልማዳዊ ድርጊት ሃሳብን ወይም ቀጣይነት ያለው ሁኔታን ለመግለጽ የምንጠቀምበት መንገድ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ያለማቋረጥ” ወይም “ሁልጊዜ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ በሆነው በመላው ዓለም
“እርሱ የፈጠረው መላው ዓለም” ወይም “እርሱ የፈጠረው በሙሉ”

የሰው ልጆች
ይህ የሚያመለክተው በአጠቃላይ የሰው ልጆችን በሙሉ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ወደ ሕልውና ያመጣቸው ሕዝብ በሙሉ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 8:32

አሁን
ይህ የልጆቹን ትኩረት ወደ ትምህርቱ መደምደሚያ እንዲያደርጉ ለማገዝ ነው።

አድምጡኝ
አሁንም ጥበብ ስለራስዋ እየተናገረች ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መንገዴን የሚጠብቁ
እዚህ ላይ “መንገዴን” የሚወክለው የጥበብን ባሕርይ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ የማስተምረውን የሚያደርጉ” ወይም “የእኔን ምሳሌ የሚከተሉ ሰዎች” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቸል አትበል
“ግድየለሽ አትሁን” አማራጭ ትርጉም፡- “ትኩረት ለመስጠትህ እርግጠኛ ሁን” ወይም “ለመከተል እርግጠኛ ሁን” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

ዕለት ዕለት በቤቴ መግቢያ የሚተጋ፣ የደጄንም መድረክ የሚጠብቅ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ጥበብ ቤት እንዳላት ተገል ጧል፤ “መትጋት” ለሚለው ቃል ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉ፡- 1) ጥበበኛ ሰው እርስዋን ለማገልገል በማለዳ በጥበብ ቤት መግቢያ ሆኖ ይጠብቃል፣ ወይም 2) ጥበበኛ ሰው እርስዋ እንድትመጣና እንድታስተምረው በጥበብ ቤት መግቢያ ሆኖ ይጠብቃል። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 8:35

ያገኘኛል ... ይጠላኛል
አሁንም ጥበብ ሰለራስዋ ትናገራለች። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔን ያጣ
ሙሉ ሃሳቡ እንዲህ የሚል ነው፡- “እኔን ሊያገኘኝ ያልቻለ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሕይወቱን
እዚህ ላይ “ሕይወት” የሚወክለው ሰውየውን ነው። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 9

1 ጥበብ ቤቷን ሰራች፤ ሰባት ምሰሶዎችን ከድንጋይ ጠርባ አቆመች። **2** ለእራት እንስሳዎቿን አረደች፤ የወይን ጠጇንም ደባለቀች፤ ማዕዷንም አዘጋጀች። **3** በሴት ሰራተኞቿ በኩል የጥሪ ወረቀት ላከች፣ ከከተማይቱ ከፍተኛ ቦታ ተጣራች። **4** እርሷም አእምሮ ለጎደላቸው “እውቀትን ያላገኙ ሁሉ ወደዚህ ይምጡ!” አለች። **5** “ኑ፣ ምግቤን ተመገቡ፣ የደባለቅሁትንም የወይን ጠጄን ጠጡ። **6** የአላዋቂነት መንገዳችሁን ወደኋላ በመተው በሕይወት ኑሩ፤ በማስተዋል መንገድ ተመላለሱ። **7** ፌዘኛን የሚገስጽ ሰው በራሱ ላይ ስድብን ያመጣል፣ ክፉን ሰው የሚገስጽ ደግሞ ይጎዳል። **8** ፌዘኛን ሰው አትገስጽ፣ ይጠላሃል፤ ጥበበኛን ሰው ገስጽ፣ ይወድድሃል። **9** ለጥበበኛ ሰው ትምህርትን ስጠው፣ ይበልጥ ጥበበኛ ይሆናል፤ ጻድቅን ሰው አስተምረው፣ እርሱም ይበልጥ እውቀትን ይጨምራል። **10** የጥበብ መጀመርያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፣ ቅዱሱንም ማወቅ ማስተዋል ነው። **11** በእኔ ዘመንህ ይበዛልና፣ በሕይወትህም ዓመታት ይጨመሩልሃል። **12** ጥበበኛ ከሆንህ፣ ጥበበኛ የምትሆነው ለራስህ ነው፣ ነገር ግን የምታፌዝ ከሆንህ፣ ፌዘኛነትህን ለብቻህ ትሸከመዋለህ።” **13** ሞኝ ሴት ለፍላፊ ናት፣ ትምህርት የሌላትና ምንም የማታውቅ ናት። **14** በከተማዋ ከፍተኛ ስፍራ በቤቷ በር በመቀመጫ ላይ ትቀመጣለች። **15** እርሷ በመንገድ የሚያልፉትን፣ በመንገዳቸውም ቀጥ ብለው የሚሄዱትን ሰዎች ትጣራለች። **16** እርሷም አእምሮ ለጎደላቸው “እነዚህ ትምህርት የሌላቸው ሰዎች ወደዚህ ይምጡ!” አለች። **17** “የተሰረቀ ውኃ ጣፋጭ ነው፣ በምስጢር የበሉት እንጀራም አስደሳች ነው።” **18** ነገር ግን እርሱ ሙታን በዚያ እንዳሉ አያወቅም፣ ተጋባዦቿ በሲዖል ጥልቀት ውስጥ እንዳሉ አያውቅም።

Proverbs 9:1

አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች ጥበብ ለሰዎች መልካም ምክር የምትሰጥ ሴት ተደርጋ የተገለጸችበት ተምሳሌት ይጀምራሉ።(ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥበብ ሠራች
ፀሐፊው ስለ ጥበብ የራስዋን ቤት እንደሰራች ሴት አድርጎ ያቀርባታል። ቤትዋን ሠራች

ፍሪዳዎቿን አረደች
ይህ ጥበብ እራት በምታቀርብበት ጊዜ ስጋቸው የሚበላውን እንስሳት የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ለእራት የሚቀርበውን ስጋ ለማዘጋጀት ፍሪዳዎችን አረደች” (ምትክ ስም እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የወይን ጠጅዋን ደባለቀች
በጥንቷ እስራኤል ሰዎች ብዙ ጊዜ የወይን ጠጅን ከውኃ ጋር ይደባልቁ ነበር። አማራጭ ትርጉም፡- “የወይን ጠጇን ከውኃ ጋር በመደባለቅ አዘጋጀች” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ማዕድዋን አዘጋጀች
“እርስዋ ማዕድዋን አዘጋጀች”

Proverbs 9:3

አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ቁጥሮች እንደ ሴት የቀረበችውን የጥበብን መልእክት ማቅረብ ይጀምራሉ። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰራተኞችዋን ላከች
እነዚህ ሰራተኞች ወደ ውጭ ሄደው ጥበብ ወዳዘጋጀችው ድግስ እንዲመጡ ሰዎችን ጋበዙአቸው።

ሰራተኞችዋ
ጥበብን የመሰሉ የተከበሩ ሴቶችን የሚያገለግሉ ወጣት ሴቶች ወይም ልጃገረዶች።

ጠራች
“እርስዋ አወጀች” ወይም “እርስዋ ጥሪ አደረገች” አማራጭ ትርጉም፡- “እርስዋ ደጋግማ በመጮህ ጥሪዋን አስተላፈች”

በከተማይቱ ከፍተኛ ስፍራ ላይ
ግብዣው በሁሉም ሰዎች ዘንድ በሚገባ መደመጥ እንዲችል ከፍ ባለ ድምጽ የተላለፈው በከፍተኛ ስፍራ ላይ ነው።

አላዋቂ የሆነ ማን ነው? ... አእምሮ የጎደለውም ይምጣ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች የሚገልጹት በሕይወታቸው የበለጠ ጥበብ የሚያስፈልጋቸው ተመሳሳይ ዓይነት ሰዎችን ነው። በዚህ ስፍራ ጥያቄው የቀረበው እንዲህ ለመሰሉ ለሁሉም ሰዎች ነው። አማራጭ ትርጉም፡- አላዋቂ የሆነ ማንኛውም ሰው፣ አእምሮ የጎደለውም ሁሉ ይምጣ”

አላዋቂ
“ልምድ የሌለው ወይም የአእምሮ ብስለት የሌለው”

ወደዚህ ፈቀቅ ይበል
“መንገዱን ይተውና ወደ ቤቴ ይምጣ”

Proverbs 9:5

አጠቃላይ መረጃዎች፡-
እነዚህ ቁጥሮች የጥበብን መልእክት ማስተላለፍ ቀጥለዋል።

ኑ ... ብሉ ... ጠጡ .... ተዉ ... ኑሩ ... ሂዱ
እነዚህ ትእዛዛት በሙሉ በብዙ ቁጥር የተገለጡ ናቸው፤ ጥበብ በአንድ ጊዜ ለብዙ ሰዎች ጥሪ እያደረገች ነው።

የደባለቅሁትንም የወይን ጠጅ
በጥንትዋ እስራኤል ሰዎች ብዙ ጊዜ የወይን ጠጅን ከውኃ ጋር ይደባልቁ ነበር። አማራጭ ትርጉም፡- የወይን ጠጅዋን ከውኃ ጋር በመደባለቅ አዘጋጀች” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አላዋቂ ድርጊቶቻችሁን ተዉ
እዚህ ላይ የአላዋቂ ድርጊቶች አንድ ሰው ትቶት ሊሄድ እንደሚገባ ስፍራ ተደርጎ ተገልጿል። አማራጭ ትርጉም፡- “አላዋቂነት የተሞላ ባህርይህን ተው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የአላዋቂ ድርጊቶች
“ልምድ የሌለው ወይም የአእምሮ ብስለት የሌለው ሰው ድርጊቶች”

የማስተዋልም መንገድ
እዚህ ላይ ጥበብን የመረዳት ሂደት አነድ ሰው ሊከተለው የሚችለው መንገድ እንደሆነ ተደርጎ ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበበኛ ሰው ያለው የሕይወት ዘይቤ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Proverbs 9:7

አጠቃላይ መረጃ፦
እነዚህ ቁጥሮች የጥበብን መልእክት ማስተላለፍ ቀጥለዋል።

የሚገስጽ ... የሚዘልፍ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረታዊነት የሚናገሩት ተመሳሳይ ነገር ነው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ፌዘኛ
በልምድ ሰዎች ላይ የሚያፌዝ ሰው። አማራጭ ትርጉም፦ “ስለ ሌሎች ሰዎች የስድብ ነገሮችን የሚናገር ሰው” ወይም “የሌሎች ሰዎችን ስም ማጥፋት የሚወድ ሰው”

ስድብን ይቀበላል
“መጥፎ ምላሽ ይቀበላል”

የሚዘልፍ
“የሚያስተካክል”

አትገስጽ
“አታርመው”

ለጠቢብ ሰው ... ስጠው፥ እርሱም ... ጻድቅን ሰው አስተምረው፣ እርሱም
እነዚህ ሁለት ትእዛዛት በእርግጥ የሚወክሉት ቅድመ ሁኔታ ያለበት ሃሳብ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ለጠቢብ ሰው ብትሰጠው፣ እርሱም ... ለጻድቅ ሰው ብታስተምረው፣ እርሱም”

ለጠቢብ ሰው ስጠው ... ጻድቅን ሰው አስተምረው
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረታዊነት የሚናገሩት ተመሳሳይ ነገር ነው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ለጠቢብ ሰው ስጠው
ይህ የሚያመለክተው ለጠቢብ ሰው ምክርን መስጠት ነው። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 9:10

አጠቃላይ መረጃ፦
እነዚህ ቁጥሮች የጥበብን መልእክት ይፈጽማሉ።

የእግዚአብሔር ፍርሃት
ይህንን በምሳሌ 1:7 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

ዘመንህ በእኔ ይበዛል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ዘመንህን እኔ አበዛዋለሁ” ወይም “እኔ ብዙ ዘመን እንድትኖር አደርግሃለሁ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በእኔ
ጥበብ እንደ ሴት ተመስላ እዚህ መናገር ቀጥላች። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዘመንህ በእኔ ይበዛልና፥ የሕይወትህም ዕድሜ ይጨመርልሃል
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ጥቅም ላይ የዋሉትም ጥበብ ያላትን ታላቅ ጥቅም አጽንዖት ለመስጠት ነው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

የሕይወትህም ዕድሜ ይጨመርልሃል
ጥበብ ስለ ሕይወት ዕድሜ ቁሳዊ ነገሮች እነደሆኑ አድርጋ ትናገራለች።ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔ ለአንተ የሕይወት ዕድሜ እጨምርልሃለሁ” ወይም “ረጅም ዕድሜ እንድትኖር አደርግሃለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ጠቢብ ብትሆን ... ፌዘኛም ብትሆን
እነዚህ ሁለት ሃሳቦች ሰዎች ከጥበባቸው የተነሳ ለራሳቸው ጥቅም እንደሚያገኙ ፌዘኞች ደግሞ ከባህርያቸው የተነሳ እንደሚሰቃዩ የሚናገሩ ይመስላሉ።

ለብቻህ ትሸከመዋለህ
ይህ ከመጥፎ ባሕርዩ የተነሳ ሰው የሚመጣበትን መዘዝ አንድ ሰው በጀርባው ሊሸከመው የሚገባው ከባድ ሸክም እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 9:13

ሞኝ ሴት
የሚቻል ከሆነ “ሞኝነት” የሚለውን “ሞኝ ሴት” እና በተመሳሳይ መግለጫዎች ተርጉመው። ይሁን እንጂ በዚህ ምዕራፍ የቀደሙ ክፍሎች ላይ እንደነበረው ቋንቋው ለጥበብ የሰው ባህርይ እንዲሰጣት የሚፈቅድ ከሆነ ለሞኝነትም የሰው ባህርይ እንዲሰጣት ሊፈቅድ ይችላል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አልተማረችም፣ አንዳችም አታውቅም
እነዚህ ሁለት መግለጫዎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ የተደጋገሙት ሞኝ ሴት ምን ያህል የማትጠቅም እንደሆነች ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እርስዋ አንዳች ነገር እንኳ በጭራሽ አታውቅም” (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ያልተማረች ናት
“ከልምድ አልተማረችም” ወይም “ወጣትና አላዋቂ ናት”

በመንገድ የሚያልፉትን
ይህ ፈሊጥ ሲሆን “የራሳቸውን ጉዳይ ብቻ የሚያስቡትን” ወይም “የራሳቸውን ስራ ብቻ የሚያስቡትን” ለማሳየት ይመስላል። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 9:16

አላዋቂ ነው
“ልምድ የሌለው ወይም የአእምሮ ብስለት የሌለው ነው”

ወደዚህ ፈቀቅ ይበል
“ይህንን መንገድ ይተውና ወደዚህ ይምጣ”

እንዲህ አለች
ይህች በምሳሌ 9:13 ላይ የተዋወቀችው ሞኝ ሴት ናት።

እነዚህ አእምሮ የጎደላቸው
“እነዚህ ጥበብ የሌላቸው” ወይም “እነዚህ ጠቢባን ያልሆኑ”

የተሰረቀ ውኃ ጣፋጭ ነው፣ በምስጢር የበሉት እንጀራም ደስ ያሰኛል
ይህች ሞኝ ሴት ከእርስዋ ጋር ከተኙ ደስተኛ እንደሚሆኑ ለወንዶች ለመናገር ስለ ተሰረቀ ውኃ እና በምስጢር ስለተበላ እንጀራ አስደሳችነት ትናገራለች። ይህ በተነጻጻሪ ዘይቤ በግልጽ ሊብራራ ይችላል፦ “የሰረቅኸው ውኃ እና በምስጢር የበላኸው ደስ እንደሚያሰኝህ ሁሉ ከእኔ ጋር ብትተኛ በእኔ ደስ ትሰኛለህ። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሙታን ከዚያ እንዳሉ
“ወደ እርስዋ የሄዱ ወንዶች አሁን ሞተዋል”

በሲኦል ጥልቀት
“ሲኦል” የሚያመለክተው የሙታን ዓለምን ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 10

1 የሰሎሞን ምሳሌዎች። ጥበበኛ ልጅ አባቱን ደስ ያሰኛል፣ ሞኝ ልጅ ግን ለእናቱ ሃዘንን ያመጣል። **2** በክፋት የተከማቸ ሃብት ምንም ጥቅም የለውም፣ ጽድቅ ግን ከሞት ያድናል። **3** እግዚአብሔር በጽድቅ የሚሄዱትን እንዲራቡ አያደርግም፣ የክፉዎችን ምኞት ግን ያከሽፋል። **4** የሰነፍ እጅ ድሃ ታደርጋለች፣ የትጉ እጅ ግን ብልጽግናን ታመጣለች። **5** ጥበበኛ ልጅ በበጋ ምርትን ይሰበስባል፣ በመከር መተኛት ግን ለእርሱ ውርደት ነው። **6** የእግዚአብሔር ስጦታ በጻድቃን ራስ ላይ ነው፣ የክፉ ሰው አፍ ግን ጥፋት ይከድነዋል። **7** ጻድቅ ሰው ስለ እርሱ ስናስብ ደስ እንድንሰኝ ያደርገናል፣ የክፉ ሰው ስም ግን ይጠፋል። **8** አዋቂዎች ትእዛዛትን ይቀበላሉ፣ ለፍላፊ ሞኝ ግን ወደ ጥፋት ይሄዳል። **9** በሀቀኝነት የሚሄድ ሰው ተማምኖ ይሄዳል፣ መንገዱን የሚያጣምም ግን ይጋለጣል። **10** በዓይኑ የሚጠቅስ መከራን ያመጣል፣ ለፍላፊ ሞኝ ግን ወደ ይጠፋል። **11** ጽድቅን የሚያደርግ ሰው አፍ የሕይወት ምንጭ ነው፣ የክፉ ሰው አፍ ግን ጥፋትን ይደብቃል። **12** ጥላቻ ጠብን ያነሳሳል፣ ፍቅር ግን ስህተትን ሁሉ ይሸፍናል። **13** በአስተዋይ ሰው ከንፈር ጥበብ ትገኛለች፣ በትር ግን አእምሮ ለጎደለው ሰው ጀርባ ነው። **14** ጥበበኛ ሰዎች እውቀትን ይሰበስባሉ፣ የሞኝ አፍ ግን ጥፋትን ያመጣል። **15** የባለጠጋ ሰው ሀብት የተመሸገ ከተማው ነው፤ የድሆች ድህነት ግን መጥፊያቸው ነው። **16** የጻድቅ ሰው ደመወዝ ወደ ሕይወት ይመራል፤ የክፉዎች ትርፍ ግን ወደ ኃጢአት ይመራቸዋል። **17** እርምትን ለሚከተል ሰው ወደ ሕይወት የምትመራ ጎዳና አለች፣ ተግሳጽን የማይቀበል ሰው ግን ይስታል። **18** ጥላቻን የሚደብቅ ሰው ሐሰተኛ ከንፈሮች አሉት፣ ሐሜትን የሚያስፋፋ ሞኝ ነው። **19** በብዙ ቃላቶች ውስጥ ኃጢአት ሳይኖር አይቀርም፣ ለሚናገረው ነገር ጥንቃቄ የሚደርግ ሰው ግን ጥበበኛ ነው። **20** የጻድቅ ሰው ምላስ የነጠረ ብር ነው፤ የክፉ ሰው ልብ ግን ዋጋ የለውም። **21** የጻድቅ ሰው ከንፈሮች ብዙ ሰዎችን ያንጻሉ፣ ሞኞች ግን ባለማማዛዘናቸው ምክንያት ይሞታሉ። **22** የእግዚአብሔር መልካም ስጦታዎች ሃብትን ያመጣሉ፣ መከራንም አያክልበትም። **23** ክፋት የሞኞች ጨዋታ ነው፣ ጥበብ ግን ለአስተዋይ ሰው ደስታ ነው። **24** የክፉ ሰው ፍርሃት ድንገት ይደርስበታል፣ የጻድቅ ሰው ምኞት ግን ይፈጸማል። **25** ክፉ ሰዎች እንደሚያልፍ አውሎ ነፋስ ናቸው፣ ከዚያም በኋላ አይገኙም፣ ጽድቅን የሚያደርጉ ግን ለዘላለም የሚኖሩ መሰረት ናቸው። **26** በጥርስ ላይ ያለ ሆምጣጤ፣ በዓይንም ውስጥ ያለ ጢስ እንደሚጎዳ፣ ሰነፍ ሰው ለሚልኩት እንዲሁ ነው። **27** እግዚአብሔርን መፍራት ዕድሜን ያረዝማል፣ የክፉዎች ዕድሜ ግን አጭር ይሆናል። **28** ጽድቅን የሚያደርጉ ሰዎች ተስፋ ደስታቸው ነው፣ የክፉዎች ዕድሜ ግን አጭር ይሆናል። **29** የእግዚአብሔር መንገድ ሃቀኞችን ይጠብቃቸዋል፣ ለክፉዎች ግን መጥፊያቸው ነው። **30** ጽድቅን የሚያደርጉ ፈጽሞ አይወድቁም፣ ክፉዎች ግን በምድሪቱ አይቀሩም። **31** ከጻድቃን አፍ የጥበብ ፍሬ ይወጣል፣ ጠማማ ምላስ ግን ይቆረጣል። **32** የጻድቃን ከንፈሮች ተገቢ የሆነውን ነገር ያውቃሉ፣ የክፉዎች አፍ ግን የሚያውቀው ጠማማ የሆነውን ነገር ብቻ ነው።

Proverbs 10:1

አጠቃላይ መረጃ፦
በምዕራፍ 10 የሚገኙ ብዙ ቁጥሮች ትይዩነትን ያነጻጽራሉ። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

የሰሎሞን ምሳሌዎች
ከምዕራፍ 1-9 ካለው መግቢያ በኋላ ምዕራፍ 10 የምሳሌዎችን ማለትም ጥበብን የሚያስተምሩ አጫጭር ትምህሮችን ስብስብ ማቅረብ ይጀምራል።

መዝገብ
በጊዜ ሂደት የተከማቸ

እግዚአብሔር የጻድቁን ነፍስ አያስርብም
እዚህ ላይ “ነፍስ” የሚለው ሰውየውን የሚያመለክት ነው። ይህ በአዎንታዊ ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ጽድቅ የሚያደርጉትን ሰዎች የሚበሉት እንጀራ እንዲኖራቸው ማረጋጋጫ ይሰጣቸዋል” (ተዛምዶአዊ እና ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 10:4

የታካች እጅ
“እጅ” የሰውን ብርታትና ችሎታ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ለመስራ ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የትጉ እጅ
“እጅ” የሰውን ብርታትና ችሎታ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በትጋት የሚሰራ ሰው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 10:6

ራስ ላይ ነው
“ራስ” የሰውን ሁለንተና ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ለእነርሱ ይሰጣል” (ፈሊጥ እና ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

የጎጥኣንን አፍ
“አፍ” ሰውየው የተናገረውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ኃጢአተኛ የሚናገራቸው ቃላቶች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ይከድነዋል
እውነትን ይደብቃል

ስም
“ስም” የሚለው ቃል የሰውየውን ዝና ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም “ትውስታ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 10:8

ይወድቃል
“ይጠፋል” ወይም “ከጥቅም ውጭ ይሆናል”

ጠማማ
ቀጥተኛ ያልሆነ፤ የተንሻፈፈ፤ የማይታመን፤ አታላይ

Proverbs 10:10

በዓይኑ የሚጠቅስ
“በዓይን መጥቀስ” በሌላ ሰው ላይ ጭካኔ ለመፈጸም ምስጢራዊ ምልክትን የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በሰውነት እንቅስቃሴ ምልክት የሚሰጥ” (ምሳሌያዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወደ ታች ይጣላል
የወደቀ ሰው ወደ ታች እንደ ተጣለ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- ሌሎች ይጥሉታል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የጻድቅ አፍ
እዚህ ላይ “አፍ” ሰውየው የተናገረውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የጻድቅ ሰው ንግግር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ጻድቅ
ይህ በአጠቃላይ ጻድቅ ሰዎችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጻድቅ ሰዎች” (ብዙ ገላጭ ስም ሐረጎች የሚለውን ይመልቱ)

የሕይወት ውኃ ምንጭ ነው
የዚህ ሰው ንግግር የውኃ ምንጭ በደረቅ መሬት እንደሚያደርገው እንዲሁ ሕያዋን እንስሳትን ወይም ሰዎችን በሕይወት የሚያኖር ተደርጎ ተነግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የኃጥኣንን አፍ ግን ግፍ ይከድነዋል
ክፉ ሰው ጉዳት የማያደርሱ ነገሮችን ይናገራል ነገር ግን በሌሎች ሰዎች ላይ ግፍ ለማድረግ ያቅዳል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የኃጥእ አፍ
እዚህ ላይ “አፍ” የሰውየውን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የክፉ ሰው ንግግር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉ ሰው
ይክ በአጠቃላይ ክፉ ሰዎችን በሙሉ ይወክላል። (ብዙ ገላጭ ስም ሐረጎች የሚለውን ይመልቱ)

Proverbs 10:12

ፍቅር ትከድናለች
ፍቅር ጠብን ከማባባስ ይልቅ በሰዎች መካከል ያለውን ችግር እንደሚያስታግስ ሰው እንዲሁ ታደርጋለች። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልቱ)

በብልሃተኛ ሰው ከንፈር
“ከንፈርየሰውየውን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሚያስተውል ሰው በሚናገረው ውስጥ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በትር ለጀርባ ነው
“በትር” ጠንካራ የሆነ አካላዊ ቅጣት ይወክላል፣ “ጀርባ” ደግሞ ቅጣቱን የሚቀበለውን ሰው ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አእምሮ የጎደለው ሰው ጠንካራ ቅጣት ያስፈልገዋል” (ተዛምዶአዊ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 10:14

የሰነፍ አፍ
“አፍ” ሰውየው የሚናገረውን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከሞኝ ሰው የሚወጣ ንግግር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ የጸናች ከተማ
ይህ ሃብት እንደ አስተማማኝ ስፍራ የተወከለበት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የእርሱ ደህንነት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 10:16

ደሞዝ ... ትርፍ
እነዚህ ቃላቶች ብዙውን ጊዜ የሚያመለክቱት ሰራተኛ የሚከፈለውን ገንዘብ ነው። እዚህ ላይ ትክክለኛውን ነገር የመስራት ወይም ደግሞ ትክክለኛ ያልሆነውን ነገር የመስራት ውጤት ይወክላሉ። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ተግሣጽን የሚጠብቅ በሕይወት መንገድ
“ጥበብ ያለበትን ምክር የሚታዘዝ ሰው ረጅምና ደስተኛ ሕይወት ይኖረዋል”

ተግሳጽን የማይቀበል ሰው ግን ይስታል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበብ የተሞላበት ምክር የማይቀበል ሰው ግን ጥሩ ሕይወት አይኖረውም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 10:18

ሐሰተኛ ከንፈር አለው
“ከንፈር” ሰውየው የሚናገረውን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ውሸትን ይናገራል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ኃጢአት ሳይኖር አይቀርም
ይህ ሀረግ አዎንታዊ ሃሳብን አጽንዖት ለመስጠት አሉታዊ ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፡- “ብዙ ኃጢአት አለበት” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 10:20

የጻድቅ ምላስ
“ምላስ” ሰውየው የተናገረውን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጻድቅ ሰው የተናገረው ማንኛውም ነገር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ንጹህ ብር ነው
“ብር” ውድ ዋጋ ያላቸውን ነገሮች ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እጅግ በጣም የከበረ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የጻድቅ መምላስ
“ምላስ” ሰውየው የሚናገረውን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የጻድቅ ሰው ንግግር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ይመግባሉ
እንዲጎለብቱ ወይም ጠንክረው እንዲያድጉ

Proverbs 10:22

ክፉ ነገር ማድረግ ለሰነፍ ሰው ጨዋታ ነው
ጨዋታ ሰዎች ለመዝናናት የሚፈጽሙት ተግባር ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሞኞች ክፉ ነገር በማድረግ ይደሰታሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 10:24

በላዩ ይመጣበታል
አንድን ሰው ያሸንፋል

ክፉ ሰዎች እንደ ዐውሎ ነፋስ ናቸው
ዐውሎ ነፋስ እንደሚመጣና ማንኛውንም ነገር እንደሚያጠፋ ክፉ ሰዎችም እንዲሁ ይጠፋሉ (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የዘላለም መሠረት ነው
“መሠረት” አርማታን ወይም ሰዎች የሚገነቡት የአንድ ነገር መጀመርያን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለረጅም ጊዜ ለሚቆይ ነገር መጀመርያው ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Proverbs 10:26

በጥርስ ላይ ያለ ሆምጣጤ፣ በዓይንም ውስጥ ያለ ጢስ እንደሚጎዳ፣ ሰነፍ ሰው ለሚልኩት እንዲሁ ነው።
“ሆምጣጤ” እና “ጢስ” የሰውን ጥርስ እና ዓይን የሚጎዱ ነገሮችን የሚወክሉ ናቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰነፍን ሰው አንድ ነገር እንዲያከናውን መላክ የሚቆጠቁጥና የሚያሳዝን ነው” (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሆምጣጤ
ምግብ ለማጣፈጥና ሳይበላሽ ለመጠበቅ የሚረዳ የሚኮመጥጥ ፈሳሽ ነው

የክፉ እድሜ
“እድሜ” አንድ ሰው የሚኖርበትን ጊዜ የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የክፉ ሰው የሕይወት ዘመን” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 10:28

የክፉ ሰዎች እድሜ
እዚህ ላይ “እድሜ” የሚወክለው ሰው የሚኖርበት ዘመን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የክፉ ሰው የሕይወት ዘመን” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አይናወጥም
ይህ በገቢር ግስና በአዎንታዊ መንገድ ሊገለጽ ይችላ። አማራጭ ትርጉም፡- “ዋስትና አለው” (ምፀት እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 10:31

ከጻድቅ ሰው አፍ
“አፍ” የሰውየውን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከጻድቅ ሰው ንግግር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ጠማማ ምላስ ግን ትቈረጣለች
“ምላስ” የሰውየውን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ውሸት የሚናገሩትን ሰዎች አንደበት ይዘጋል” (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የጻድቅ ከንፈሮች ደስ የሚያሰኝ ነገርን ያውቃሉ
“ከንፈሮች” የሰውየውን ንግግር ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ጻድቅ ሰው ደስ የሚያሰኝ ነገር እንዴት እንደሚናገር የውቃል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የኀጥኣን አፍ
“አፍ” የሰውየውን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- የክፉ ሰው ንግግር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 11

1 እግዚአብሔር ትክክለኛ ያልሆነ ሚዛን ይጠላል፣ በትክክለኛ ሚዝን ግን ሚዛን ደስ ይለዋል። **2** ትዕቢት ከመጣች ውርደት ትመጣለች፣ ከትህትና ጋር ግን ጥበብ ትመጣለች። **3** የቅኖች ሀቀኝነታቸው ይመራቸዋል፣ የከዳተኞች ጠማማ መንገድ ግን ራሳቸውን ያጠፋቸዋል። **4** በቁጣ ቀን ሀብት ዋጋ ቢስ ነው፣ ጽድቅ ግን ከሞት ታድንሃለች። **5** ነቀፋ የሌለበት ሰው ጽድቅ መንገዱን ያቀናለተል፣ ክፉዎች ግን በክፋታቸው ይወድቃሉ። **6** እግዚብሔርን ደስ የሚያሰኙ ሰዎች ጽድቃቸው ትታደጋቸዋለች፣ ከዳተኞች ግን በክፉ ምኞታቸው ይጠመዳሉ። **7** ክፉ ሰው ሲሞት ተስፋው ይጠፋል፣ በብርታቱ የተመካበት ተስፋም ከንቱ ይሆናል። **8** ጽድቅን የሚያደርግ ከመከራ ይድናል፣ ይልቁንም መከራው በክፉው ይመጣበታል። **9** አምላክ የለሽ ሰው በአንደበቱ ጎረቤቱን ያጠፋል፣ ጽድቅን የሚያደርጉ ግን በእወቀት ይድናሉ። **10** ጽድቅን የሚያደርጉ ሰዎች ሲበለጽጉ ከተማ ትደሰታለች፤ ክፉዎች ሲጠፉ የደስታ ጩኸት ይሆናል። **11** እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኙ ሰዎች መልካም ስጦታ ከተማ ታላቅ ትሆናለች፤ በክፉዎች አንደበት ግን ከተማ ትፈርሳለች። **12** ጓደኛውን የሚንቅ ሰው አእምሮ የጎደለው ነው፣ አስተዋይ ሰው ግን ዝም ይላል። **13** ለሐሜት የሚሄድ ሰው ምስጢርን ይገልጣል፣ ታማኝ ሰው ግን ምስጢርን ይሰውራል። **14** በጥበብ አልባ አመራር ሕዝብ ይወድቃል፣ የመካሮች ብዛት ባለበት ግን ድል ይመጣል። **15** ለማይታወቅ ሰው ዋስ የሚሆን መከራን ይቀበላል፣ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ዋስ ለመሆን የሚጠላ ሰው ግን ይድናል። **16** ሞገስ ያላት ሴት ክብር ታገኛለች፣ ጨካኝ ሰዎች ግን ሀብትን ብቻ ያገኛሉ። **17** ደግ ሰው ራሱን ይጠቅማል፣ ጨካኝ ሰው ግን ራሱን ይጎዳል። **18** ክፉ ሰው ደመወዙን ለማግኘት ይዋሻል፣ ጽድቅን የሚዘራ ግን የእውነትን ደመወዝ ይሰበስባል። **19** ጽድቅን የሚያደርግ ታማኝ ሰው በሕይወት ይኖራል፣ ክፋትን የሚያደርግ ግን ይሞታል። **20** እግዚአብሔር ጠማማ ልብ ያላቸውን ይጠላል፣ በመንገዳቸው ነቀፋ በሌለባቸው ሰዎች ግን ደስ ይሰኛል። **21** ክፉ ሰዎች ሳይቀጡ እንደማይቀሩ ይህን እርግጠኛ ሁን፣ ጽድቅን የሚያደርጉ ሰዎች ዘሮች ግን ይድናሉ። **22** በአሳማ አፍንጫ እንደተሰካ የወርቅ ቀለበት፣ ማስተዋል የሌላትም ቆንጆ ሴት እንዲሁ ናት። **23** ጽድቅን የሚያደርጉ ሰዎች ምኞት መልካም ውጤት ያመጣል፣ ክፉ ሰዎች ግን ተስፋ ሊያደርጉት የሚችሉት መቅሰፍት ብቻ ነው። **24** ዘርን የሚዘራ አንድ ሰው አለ፣ እርሱ ይበልጥ ይሰበስባል፤ ሌላ ደግሞ የማይዘራ አለ፣ እርሱ ይደኸያል። **25** ለጋስ ሰው ይበለጽጋል፣ ለሌሎች ውኃ የሚሰጥ ደግሞ ለራሱም ውኃ ያገኛል። **26** እህል ለመሸጥ ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው ሕዝብ ይረግመዋል፣ በሚሸጠው ግን መልካም ስጦታዎችን በራሱ ላይ እንደ አክሊል ይጎናጸፋል። **27** መልካምን ነገር ተግቶ የሚፈልግ ሞገስን ይፈልጋል፣ ክፉን የሚፈልግ ግን ክፉ በራሱ ላይ ይመጣበታል። **28** በባለጠግነታቸው ላይ የሚታመኑ ሰዎች ይወድቃሉ፣ ጽድቅን የሚያደርጉ ግን እንደ ቅጠል ይለመልማሉ። **29** በቤተሰቡ ላይ ሁከትን የሚያመጣ ሰው ነፋስን ይወርሳል፣ ሞኝም ሰው በልቡ ጥበበኛ ለሆነው ሰው አገልጋይ ይሆናል። **30** ጽድቅን የሚያደርጉ ሰዎች እንደ ሕይወት ዛፍ ይሆናሉ፣ ሁከት ግን ሕይወትን ያጠፋል። **31** ጽድቅን የሚደርጉ ሰዎች ለሰሩት ስራ የሚገባቸውን የሚቀበሉ ከሆነ፣ ይልቁንስ ክፉዎችና ኃጢአተኞች እንዴት አይቀበሉ!

Proverbs 11:1

አጠቃላይ መረጃ:-
በምዕራፍ 11 ውስጥ ያሉ ብዙ ቁጥሮች ትይዩነትን ያነጻጽራሉ። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ትክክለኛ ያልሆነ ሚዛን ይጠላል
“ሚዛን” በስምምነት የሚደረግ ትክክለኛ መለኪያን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔር አታላይነት ያለበትን መለኪያ ይጠላል” ወይም “እግዚአብሔር ሰዎች አታላዮች ሲሆኑ ይጠላል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ትክክለኛ ሚዛን ግን ደስ ያሰኘዋል
“ትክክለኛ ሚዛን” በስምምነት የሚሆን ልክነትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “ነገር ግን እርሱ በሀቀኛ መንገድ ይደሰታል” ወይም “ነገር ግን እርሱ ሰዎች ሀቀኛ ሲሆኑ ይደሰታል”

Proverbs 11:3

ወስላቶች
የስም ቅጽል እንደ መደበኛው ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ወስላቶች ሰዎች” ወይም “እነዚያ ወስላቶች የሆኑ ሰዎች” (የስም ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)

በቀጣ ቀን ሀብት አትረባም
“የቁጣ ቀን” እንደ “የእግዚአብሔር ቀን” ወይም “የፍርድ ቀን” ወይም “የመጨረሻው ቀኖች” የመሳሰሉት ወሳኝ ጊዜያትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔር ለፍርድ ሲመጣ ሰው ሀብቱ ምንም ሊያደርግለት አይችልም” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 11:5

መንገዱን ያቀናለታል
“ግልጽ አቅጣጫ አለው”

ክፉው ... ወስላታው
እነዚህ የስም ቅጽሎች እንደ መደበኛው ቅጽል ሊገለጹ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም:- “እነዚህ ክፉዎች .... እነዚህ ወስላቶች” (የስም ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)

ወስላቶች ግን በምኞታቸው ይጠመዳሉ
“እነዚህ ክፉ ስራ የሚሰሩ ሰዎች በምኞታቸው ይጠመዳሉ”

ወስላቶች
እምነት ለማጥፋት ዝግጁ የሆኑ፤ ከሃዲዎች፤ አታላዮች

Proverbs 11:7

በብርታቱ የተመካበት ተስፋ
“በራሱ ኃይል የነበረው ትምክህት”

ከንቱ ይሆናል
“ይጠፋል”

ጻድቅ ሰው ከመከራ ይድናል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ጽድቅን የሚያደርግ ሰው እግዚአብሔር ከመከራ ይጠብቀዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ይመጣል
“መከራ ይመጣበታል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Proverbs 11:9

አምላክ የለሽ ሰው በአንደበቱ
“አንደበት” የሰውየውን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የአምላክ የለሽ ሰው ቃሎች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ከተማዋ ታላቅ ትሆናለች
“ከተማ” ማህበረሰቡን ወይም ሕዝቡን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሕዝቡ ይበለጽጋል ዌም “ሕብረተሰቡ ባለጠጋ ይሆናል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በክፉዎች አንደበት
“አንደበት” የሰውየውን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የክፉ ሰዎች ንግግር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 11:12

ነገሩን ይሰውራል
“ይሰውራል” በተቻለ መጠን ነገሮች እንዳይገለጡ መጠበቅን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አይናገርም” ወይም “ስለ ጉዳዩ አያወራም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 11:14

አማካሪዎች
ድርጊትን በምሪት ለማከናወን ሃሳብ የሚሰጡ ሰዎች፤ አማካሪዎች

Proverbs 11:15

መስጠት የሚጠላ ሰው
“መስጠት የማይፈልግ ሰው”

ጨካኝ ሰዎች
ሃዘኔታ ወይም ርህራሄ የሌላቸው ሰዎች፤ አረመኔ ሰዎች

ሀብትን የሚጨብጥ
“እነዚህ ለሃብት የሚሳሱ ናቸው”

Proverbs 11:17

እርሱ
“ያ ሰው”

ትክክለኛውን ነገር ይዘራል
“መዝራት” የበለጠ ለማግኘት መበተንን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ትክክል የሆነውን ነገር ይበትናል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የእውነትን ደመወዝ ይሰበስባል
“መሰብሰብ” ማግኘት ወይም መሸከፍን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በእርግጠኝነት ወሮታን ይቀበላል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 11:19

እርሱ
“ያ ሰው”

ክፋትን የሚከተል
“ከክፋት በኃላ የሚከተል” ወይም “ክፋትን ለማድረግ የሚፈልግ”

ጠማማ ልብ ያላቸው
“ልብ” የሰውን ስሜት፣ አመለካት እና ተነሳስቶት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ክፉ ሃሳብ ያላቸው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 11:21

ሳይቀጣ አይቀርም
ይህ ሀረግ አዎንታዊውን አጽንዖት ለመስጠት አሉታዊውን ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፦ “በእርግጠኝነት ይቀጣል” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ወርቅ ቀለበት ... ማስተዋል የሌላትም
Like a gold ring ... without discretion ማስተዋል የሌላት ቆንጆ ሴት ከማይጠቅምና ከማይስማማ በዓሳማ አፍንጫ ካለ የወርቅ ቀለበት ጋር ተነጻጽሯል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ማስተዋል የሌላት
x

Proverbs 11:23

ያለውን የሚበትን ሰው አለ፥ እርሱ የበለጠ ይሰበስባል
ይህ በቸርነት በመስጠት የበለጠ ባለጠጋ ለሆነ ሰው ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “አንዳንድ ሰዎች ለሌሎች በነጻ ይሰጣሉ፣ እንዲህም ሆኖ ግን የበለጠ ባለጠጋ ይሆናሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሚበትን
ይህ ሰው እህል እንዲበቅል ዘርን እንደሚበትን ግልጽ ማድረግ ያስፈልግሃል። አማራጭ ትርጉም፦ “ብዙ ዘር የሚበትን ሰው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ እና ተተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የበለጠ ይሰበስባል
“የበለጠ ያገኛል”

መስጠት የሚገባውን ያለ ቅጥ የሚይዝ
ይህ ባለመስጠት ባለጠጋ መሆን እንደሚችል የሚያስብን ሰው ይወክላል።

Proverbs 11:25

ይበለጽጋል
“የበለጠ ያገኛል”

እርሱ
“ያ ቸር ሰው” ወይም “ማንኛውም ሰው”

ለመሸጥ ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው
ይህ ድሆችን ከመርዳት ይልቅ ሀብትን የሚያከማች ሰውን ይገልጻል።

መልካም ስጦታዎች ግን በሚሸጠው ራስ ላይ እንደ አክሊል ይጎናጸፋል
“አክሊል” እህል ለመሸጥ ፈቃደኛ ለሆነው ሰው የሚሰጠውን ወሮታ ወይም ሽልማት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “መልካም ስጦታዎች እንደ ክብር አክሊል ለሚሸጥ ሰው ይሰጠዋል” ወይም “የሚሸጥ ሰው በብዙ በረከቶች ይከበራል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 11:27

ተግቶ የሚፈልግ ሰው
በጥንቃቄና በማያቋርጥ ጥረት የሚፈልግ ሰው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይወድቃል
ይህ ፈሊጥ ነው። “ይወድቃል” ጥፋትን እና ውድቀትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይጠፋል” ወይም “ለወደፊት ክፉ ነገር ይጠብቀዋል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ጽድቅን የሚያደርጉ ግን እንደ ቅጠል ይለመልማሉ
“ቅጠል” እድገትንና ባለጠግነትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጽድቅን የሚያደርጉ ሰዎች ጤነኛ ቅጠል እንደሚያድግ እንደዚሁ ይበለጽጋሉ” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጽድቅን የሚያደርጉ ይለመልማሉ
ይህ ጽድቅን የሚያደርጉ ሰዎች ያድጋሉ ወይም ይበለጽጋሉ ማለት ነው።

Proverbs 11:29

ነፋስን ይወርሳሉ
“ነፋስ” ለማይጨበጥ ነገር ወይም ዋጋ ለሌለው ነገር የቆመ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ምንም አይወርስም” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 11:30

ጽድቅን የሚያደርግ ሰው እንደ ሕይወት ዛፍ ይሆናል
ጽድቅን የሚያደርግ ሰው የሕይወት ፍሬን ከሚያፈራ ዛፍ ጋር ተነጻጽሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጽድቅን የሚያደርጉ ሰዎች ለራሳቸውና ለሌሎች ሰዎች ሕይወትን ያመጣሉ” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሕይወት ዛፍ
ይህን በምሳሌ 3፡18 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልት።

ምን ያህል የላቀ
“ከዚያም የበለጠ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 12

1 ተግሳጽን የሚወድ እውቀትን ይወዳል፣ እርምትን የሚጠላ ግን ደነዝ ነው። **2** እግዚአብሔር ለመልካም ሰው ሞገስን ይሰጠዋል፣ ክፉ እቅድ ለሚያወጣ ሰው ግን ይፈርድበታል። **3** ሰው በክፋት ላይ ተመስርቶ ጸንቶ ሊቆም አይችልም፣ ጽድቅን የሚያደርጉ ግን ከመሰረታቸው አይነቀሉም። **4** መልካም ሴት ለበሏ ዘውድ ናት፣ አሳፋሪ ሴት ግን አጥንቱን እንደሚያበሰብስ በሽታ ናት። **5** ጽድቅን የሚያደርጉ ሰዎች እቅድ ጽድቅ ነው፣ የክፉዎች ምክር ግን ተንኮል ነው። **6** የክፉ ሰዎች ቃል ድንገት ለመግደል አድፍጦ ያደባል፣ የቅኖች ቃል ግን ይታደጋቸዋል። **7** ክፉ ሰዎች ይገለበጣሉ፣ አይገኙምም፣ ጽድቅን የሚያደርጉ ሰዎች ቤት ግን ጸንቶ ይቆማል። **8** ሰው በጥበቡ ብዛት ይመሰገናል፣ ጠማማ ምርጫዎች የሚያደርግ ግን ይናቃል። **9** የሚበላው ምግብ ሳይኖረው ከሚኩራራ ሰው ይልቅ ራሱን ዝቅ አድርጎ አገልጋይ መሆን ይሻላል። **10** ጽድቅን የሚያደርግ ሰው እንስሳቱ ስለሚያስፈልጋቸው ነገር ግድ ይለዋል፣ ክፉ ሰው ግን ርህራሄ አደረገ ቢባል እንኳ ስራው ጭካኔ የተሞላ ነው። **11** መሬቱን በሚገባ የሚያርስ የተትረፈረፈ ምግብ ያገኛል፣ ዋጋ ቢስ ስራዎችን የሚያሳድድ ሰው ግን አእምሮ አልባ ነው። **12** ኃጢአተኞች ክፉ ሰዎች ከሌሎች የሰረቁትን ይመኛሉ፣ ጽድቅን የሚያደርጉ ሰዎች ፍሬ ግን ከገዛ ራሳቸው ይመጣል። **13** ክፉ ሰው በክፉ ንግግሩ ይጠመዳል፣ ጽድቅን የሚያደርጉ ሰዎች ግን ከመከራ ያመልጣሉ። **14** ሰው ከቃሉቹ ፍሬ የተነሳ መልካም ነገርን ይጠግባል፣ እንደ እጁ ስራም ዋጋውን ይቀበላል። **15** የሞኝ መንገድ ለራሱ ትክክል መስሎ ይታየዋል፣ ጥበበኛ ሰው ግን ምክርን ይሰማል። **16** ሞኝ ቁጣውን በቶሎ ይገልጣል፣ ስድብን ንቆ የሚተው ግን አስተዋይ ነው። **17** እወነትን የሚናገር ትክክለኛውን ነገር ይናራል፣ ሐሰተኛ ምስክር ግን ውሸትን ይናገራል። **18** የለፍላፊ ሰው ቃሎች እንደሚዋጋ ሰይፍ ነው፣ የጥበበኛ አንደበት ግን ፈውስን ያመጣል። **19** እውነተኛ ከንፈሮች ለዘላለም ይኖራሉ፣ ሀሰተኛ ከንፈር ግን ለቅጽበት ብቻ ነው። **20** ክፋትን ለማድረግ በሚያቅዱ ሰዎች ልብ ውስጥ ተንኮል አለ፣ ሰላምን ለሚመክሩ ሰዎች ግን ደስታ ይመጣል። **21** ጽድቅን የሚያደርጉ ሰዎች በሽታ አያገኛቸውም፣ ክፉ ሰዎች ግን በመከራ የተሞሉ ናቸው። **22** እግዚአብሔር ሀሰተኛ ከንፈሮችን ይጠላል፣ በእውነተኛነት በሚኖሩ ሰዎች ግን ደስ ይለዋል። **23** አስተዋይ ሰው እወቀቱን ይሰውራል፣ የሞኞች ልብ ግን ከንቱነትን ያወራል። **24** የትጉ ሰዎች እጅ ይገዛል፣ ሰነፍ ሰዎች ግን ለጉልበት ስራተኝነት ታልፈው ይሰጣሉ። **25** በሰው ልብ ውስጥ የሚገኝ ጭንቀት ያዋርደዋል፣ መልካም ቃል ግን ደስ ያሰኘዋል። **26** ጽድቅን የሚያደርግ ሰው ለጓደኛው መንገድን ያሳያል፣ የክፉ መንገድ ግን ታስታቸዋለች። **27** ሰነፍ ሰዎች አድነው ያመጡትን እንስሳ እንኳ አይጠብሱም፣ ትጉ ሰው ግን የከበረ ሀብት ያገኛል። **28** በጽድቅ መንገድ የሚሄዱ ሰዎች ሕይወትን ያገኛሉ፣ በጎዳናዋም ሞት የለም።

Proverbs 12:1

አጠቃላይ መረጃዎች፡-
ጸሐፊው በዚህ ምዕራፍ በሙሉ ትይነትን ይጠቀማል።

አጠቃላይ መረጃዎች፡-
ከቁጥር 5-15 ያለው ጥበብንና ሞኝነትን ያወዳድራል።

ማንም
“ማንም ሰው”

እርምትን የሚጠላ ግን ደነዝ ነው።
“ሊያደርግ የሚገባውን ነገር ሊነገረው የማይወድ ሰው”

ደንቆሮ ነው
“ሞኝ ነው” ወይም “ጥበብ የሌለው ነው”

Proverbs 12:3

ሰው በክፋት ላይ ተመስርቶ ጸንቶ ሊቆም አይችልም
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ነገር በማድረግ ማንም ሰው ዋስትናና ጥበቃ ሊኖረው አይችልም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

አይነቀልም
“አይነቀልም” እንደ ተክል ወይም ዛፍ ከምድር መነቀልን ይወክላል። ጽድቅ የሚያደርጉ ሰዎች ላይ ይህ አይሆንም። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥልቅ ስር እዳላቸው ተክሎች ጽኑ ናቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

መልካም ሴት ለባሏ ዘውድ ናት
ዘውድ አንድ ሰው ሊቀበለው የሚችለውን ታላቅ ክብር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “መልካም ሴት ለባሏ የታላቅ ክብር ምልክት ናት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አሳፋሪ ሴት ግን አጥንቱን እንደሚያበሰብስ በሽታ ናት
አጥንትን የሚያበሰብስ በሽታ የሰው ሕይወት መበለላሸትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሚስት አሳፋሪ ተግባር የባሏን መልካም ተጽዕኖና ደስታ ያጠፋል” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 12:5

የክፉ ሰዎች ቃል ድንገት ለመግደል አድፍጦ ያደባል
ሌሎችን ሰዎች ለመጉዳት ክፉ ሰዎች የሚናገሩት አታላይ ነገር ቃሎቻቸው አንድን ሰው በድንገት ለመግደል እንደሚጠብቁ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ሰዎች የሚናገሩት ቃል አንድን ሰው በድንገት ለመግደል እንደሚጠብቅ ሰው ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የቅኖች አፍ ግን ይታደጋቸዋል።
“ከቅን ሰው የሚገኝ ምክር ሰዎችን በደህንነት ይጠብቃቸዋል”

ቅን
“ጻድቅ ሰው” ወይም “ታማኝ ሰው” ወይም “ፍትህ የተሞላ ሰው”

Proverbs 12:7

ኀጥኣን ይገለበጣሉ
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች ክፉ ሰዎችን ይገለብጣሉ” ወይም “ሰዎች ክፉ ሰዎችን ከስልጣናቸው ያስወግዱአቸዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ጊዜ በዘይቤአዊ አነጋር ቅድመ አያቶችን፤ የትውል ሀረግን ወይም ሌሎች ዘመዶችን ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል። አማራጭ ትርጉም፡- “ቤተሰብ” ወይም “የትውልድ ሀረግ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ሰው በጥበቡ ብዛት ይመሰገናል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች ጥበብ ያላቸውነ ሰዎች ያወድሳሉ (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጠማማ ምርጫዎች የሚያደርግ ግን ይናቃል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች ክፉ ሃሳብ ሁልጊዜ የሚያስብን ሰው ይጠላሉ” ወይም “ሰዎች መልካምን ነገር አጣምሞ በመጥፎ የሚለውጥን ሰው ይጠላሉ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 12:9

ራሱን ዝቅ አድርጎ አገልጋይ መሆን ይሻላል።
“ስልጣንና ዝና የሌው ሰው መሆን ይሻላል”

ጨካኝ ነው
“ለሌሎች መከራን ያስከትላል”

Proverbs 12:11

ዋጋ ቢስ ስራዎችን
“ዋጋ የሌለው እቅድ” ወይም “ዋጋ የሌላቸው ስራዎች”

ፍሬው
ይህ የሰውን ድርጊትና ሃሳብ ያመለክታል። በዛፍ ላይ ያለ ፍሬ ዛፉ ምን እንደሆነ እንደሚያሳይ ሁሉ እንደዚሁ በተመሳሳይ መንገድ የሰው ቃላቶችና ድርጊቶች የሰውየው ባሕርይ ምን እንደሚመስል ያሳያል።

Proverbs 12:13

ክፉ ሰው በክፉ ንግግሩ ይጠመዳል
“ይጠመዳል” በወጥመድ መያዝን ወይም ደግሞ መታለልን ይወክላል። ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ሰው የሚናገራቸው ነገሮች ራሱን ያጠምዱታል” (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ እጁ ስራም ዋጋውን ይቀበላል
“የእጁ ስራ” የሚለው ሀረግ የጉልበት ስራን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “መልካም ስራው ዋጋ እንዲቀበል እንደሚያደርገው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 12:15

ይመስለዋል
ይህ ሀረግ በራሱ ግንዛቤ፣ አስተሳሰብ ወይም ትውስታ የሚለውን ሃሳብ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በራሱ አመለካከት” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ምክር
ጥበብ ያለባቸው ሃሳቦች

ጠንቃቃ ነው
“ጥበበኛ ነው” ወይም “ጥሩ ግንዛቤ አለው”

Proverbs 12:17

የለፍላፊ ሰው ቃሎች እንደሚዋጋ ሰይፍ ነው።
“እንደሚዋጋ ሰይፍ” የሚለው ሀረግ ሌላ ሰው የሚጎዳ ጭካኔ የተሞሉ ቃላቶችን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ሰው እንደሚገባ ሳያስብ የሚናገረው ንግግር እንደ ስለታም ሰይፍ ሰውን ሊጎዱ ይችላሉ። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የጠቢባን ምላስ
“ምላስ” ሰውየው የሚናገረውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበበኛ ሰዎች የሚናገሩት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ፈውስን ያመጣል
“ያጽናናል እና ይፈውሳል”

Proverbs 12:21

መከራ አያገኘውም
“አያገኘውም” የሚለው አሉታዊ ቅርጽ የመከራን (ሊመጡ የሚችሉ ክፉ ነገሮችን) ሃሳብ ይሰርዘዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “መልካም ነገሮች ይመጣሉ (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

ውሸተኛ ከንፈርን እግዚአብሔር ይጠላል
“ከንፈር” የሰውየውን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “Yahweh detests those who tell lies” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 12:23

እውቀትን ይሸሸጋል
“የሚያውቀውን ሁሉ አይናገርም”

የትጉ እጅ
“እጅ” ሰውየው የሚሰራውን ስራ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ትጉ ሰዎች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ለጉልበት ስራተኝነት ታልፈው ይሰጣሉ
“የጉልበት ስራ” ሰውየው ሊሰራው የሚፈልገውን ነገር ለመስራት ነጻነት የሌለው መሆኑና በግዴታ ሊሰራው የሚገባውን የሚገልጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ባርያ ይሆናል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 12:25

ጭንቀት
በጣም ከባድ የፍርሃት ወይም ስጋት፣ ትካዜ ስሜት

ያዋርደዋል
“ማዋረድ” አንድ ሰው በነጻነት እንደሚገባ እንዳይንቀሳቀስ ለማድረግ በጣም ከባድ ሸክም በሰውየው ላይ የመጫን ሃሳብን ይወክላል። ይህ ሀረግ አንድን ሰው እንዲያዝን ወይም እንዲጨነቅ ማድረግ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እንዲያዝን ወይም እንዲጨነቅ ማድረግ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መልካም ቃል ግን ደስ ያሰኘዋል
“ቃል” የሚለው ረቂቅ ስም “ተናገረ” በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን ሌሎች ለእርሱ በደግነት ሲናገሩ እንደገና ደስተኛ ይሆናል” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 12:27

ሰነፍ ሰዎች አድነው ያመጡትን እንስሳ እንኳ አይጠብሱም
“እንስሳ” በአደን ጊዜ የተያዘና የታረደ እንስሳ ማለት ነው። “መጥበስ” የሚለው ደግሞ ምግብን የማዘጋጀት መንገድ ነው።

የከበረ ሀብት
“ዋጋው የከበረ መዝገብ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 13

1 ጥበበኛ ልጅ የአባቱን ምክር ይሰማል፣ ፌዘኛ ግን ተግሳጽን አያዳምጥም። **2** ሰው ከአፉ ፍሬ መልካምን ነገር ይጠግባል፣ ጠማማ ሰው ግን ዓመጽን ይመኛል። **3** አፉን የሚጠብቅ ሕይወቱን ይጠብቃል፣ ከንፈሮቹን ያለ ልክ የሚከፍት ግን ይጠፋል። **4** ሰነፍ ሰው ይመኛል ነገር ግን አንዳችም አያገኝም፣ የትጉ ሰው ምኞት ግን በሙላት ይረካል። **5** ጽድቅን የሚያደርግ ሰው ውሸትን ይጠላል፣ ክፉ ሰው ግን ራሱ ጥላቻን ይፈጥራል፣ አሳፋሪ ተግባርንም ይፈጽማል። **6** በመንገዳቸው ያለ ነቀፋ የሚሄዱትን ጽድቅ ትጠብቃቸዋለች፣ ክፋት ግን ኃጢአተኞችን ትጥላቸዋለች። **7** ራሱን ባለጠጋ የሚያስመስል ሰው አለ፣ ነገር ግን አንዳች የለውም፣ ምንም እንደሌለው መስሎ የሚታይ ሰው ደግሞ አለ፣ ይሁን እንጂ እጅግ ባለጠጋ ነው። **8** ባለጠጋ ሰው ሀብቱን ለሕይወቱ ቤዛ አድርጎ ያቀርብ ይሆናል፣ ድሀ ግን እንዲህ ዓይነት ሥጋት በፍጹም የለበትም። **9** ጽድቅን የሚያደርግ ሰው ብርሃን ደምቆ ይበራል፣ የክፉዎች መብራት ግን ይጠፋል። **10** ትዕቢት ጠብን ብቻ ያስፋፋል፣ መልካም ምክርን ለሚያደምጡ ግን ጥበብ አለ። **11** ብዙ ከንቱነት ሲኖር ሀብት እየመነመነ ያልቃል፣ በእጁ እየሰራ ገንዘብ የሚያከማች ሰው ግን ገንዘቡ እየጨመረ እንዲሄድ ያደርጋል። **12** ተስፋ ሲዘገይ ልብን ይሰብራል፣ የተሳካ ምኞት ግን የሕይወት ዛፍ ነው። **13** ትእዛዝን የሚንቅ በትእዛዝ ይቀጣል፣ ትእዛዝን የሚያከብር ግን ወሮታን ያገኛል። **14** የጥበበኛ ሰው ትምህርት የሕይወት ምንጭ ነው፣ ከሞት ወጥመድ እንድታመልጥ ያደርግሃል። **15** መልካም እውቀት ሞገስ ያስገኛል፣ የከዳተኛ ሰው መንገድ ግን አያልቅም። **16** ጥንቃቄ የተሞሉ ሰዎች ማንኛውንም ውሳኔ የሚያደርጉት በጥበብ ነው፣ ሞኝ ግን ከንቱነቱን ይገልጣል። **17** ክፉ መልእክተኛ መከራ ውስጥ ይገባል፣ ታማኝ መልእክተኛ ግን እርቅን ያመጣል። **18** ተግሳጽን የሚንቅ ድህነትና ኃፍረት ይመጣበታል፣ ከእርምት የሚማር ግን ክብር ወደ እርሱ ይመጣል። **19** ምኞት ሲፈጸም የውስጥ ፍላጎትን ደስ ያሰኛል፣ ሞኞች ግን ከክፋት መመለስን ይጠላሉ። **20** ከጥበበኞች ጋር ሂድ አንተም ጥበበኛ ትሆናለህ፣ የሞኞች ባልንጀራ ግን እጅግ ይጎዳል። **21** መቅሰፍት ኃጢአተኞችን ይከታተላቸዋል፣ ጽድቅን የሚያደርጉ ግን መልካምን ነገር ይቀበላሉ። **22** መልካም ሰው ለልጅ ልጆቹ የሚያወርሰውን ይተዋል፣ የኃጢአተኛ ሀብት ግን ጽድቅን ለሚያደርጉ ይከማቻል። **23** የድሆች እርሻ ያልታረሰም ቢሆን ብዙ ምግብ ሊያመርት ይችላል፣ ነገር ግን በፍትህ መጓደል ምክንያት ተጠራርጎ ይወሰዳል። **24** ልጁን የማይቀጣ ይጠላዋል፣ ልጁን የሚወድ ግን በጥንቃቄ ይቀጣዋል። **25** ጽድቅን የሚያደርግ ሰው ፍላጎቱን እስከሚያረካ ድረስ ጠግቦ ይበላል፣ የክፉዎች ሆድ ግን ሁልጊዜ እንደተራበ ነው።

Proverbs 13:1

ጥበበኛ ልጅ ይሰማል
እዚህ ላይ “ይሰማል” የሚለው በተግባር ለመፈጸም ማድመጥን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበበኛ ልጅ ይታዘዛል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ተግሣጽን አይሰማም
እዚህ ላይ “መስማት” የተነገረውን በተግባር ለመፈጸም ትኩረት መስጠትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከተግሳጽ አይማርም” ወይም “ቢገሰጽም እንኳአይታዘዝም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ከአፉ ፍሬ
እዚህ ላይ “ፍሬ” ሰውየው የተናገረውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከአንደበቱ ቃላቶች” ወይም “ከተናገረው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ምኞት
የአንድ ነገር አምሮት ወይም ፍላጎት

ጠማማው
ይህ የስም ቅጽል እንደ መደበኛ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠማማ ሰው” (የስም ቅጽል የሚለውን ይመለከቱ)

Proverbs 13:3

አፉ
አዚህ ላይ “አፍ” ሰውየው የሚናገረውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የተናገረው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ከንፈሮቹን ያለ ልክ የሚከፍት
ከንፈሮችን መክፈት መናገርን ይወክላል፣ ከንፈሮችን ያለ ልክ መክፈት ደግሞ በተደጋጋሚ መናገር ወይም ብዙ መናገርን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ብዙ ይናገራል” ወይመ “በተደጋጋሚ ይናገራል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ምኞት ... ምኞት
ይህን በምሳሌ 13:2 ላይ እንዴት እንደተረጎም'ኸው ተመልከት።

ትመኛለች አንዳችም አታገኝም
“በብርቱ ይፈልጋል ነገር ግን ምንም አያገኝም”

የትጉ ሰው ምኞት ግን በሙላት ይረካል
እዚህ ላይ ምኞት” ፍላጎትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ትጉ ሰዎች በሙላት የሚረካ ሕይወት ይኖራቸዋል” ወይም “ትጉ መሆን ሰወች በሙላት እንዲረኩ ያደርጋል” (ገቢር/አድርጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ትጉ ሰዎች
በጥንቃቄ እና በማያቋርጥ ጥረት የሚሰሩ ሰዎች

Proverbs 13:5

ጥላቻ የሚፈጥር ሰው
ብርቱ የሆነ የጥላቻ ስሜት የሚፈጥር

ጽድቅ ይጠብቀዋል
“ጽድቅ” በእግዚአብሔር ተቀባይነት ያለው የሕይወት ዘይቤን ይወክላል። ይህ የሕይወት ጥራት እንደሚጠብቅ ሰው ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “በእግዚአብሔር ተቀባይነት ያለው የሕይወት ዘይቤ ይጠብቃል” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በመንገዱ ያለ ነውር የሚሄደውን
እዚህ ላይ “መንገድ” አንድ ሰው ሕይወቱን እንዴት እንደሚመራ የሃሚያሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በአናነኗር ዘይቤአቸው ያለ ነውር የሚሄዱ” ወይም “ሀቀኝነት የተሞላ ሕይወት የሚኖሩ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ክፋት ግን ኃጢአተኞችን ትጥላቸዋለች
እዚህ ላይ “ኃጢአተኝነት” ክፋት የተሞላ የሕይወት ዘይቤን ይወክላል። ይህ የሕይወት ዘይቤ ኃጢአት የሚሰሩትን ሰዎች እንደሚጥል ሰው ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፋት ኃጢአተኞችን ከስኬታማ መንገድ ያርቃቸዋል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወይም “ክፋት የኃጢአተኞችን ሕይወት ያከስራል” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 13:7

ራሱን ባለጠጋ የሚያስመስል
“ራሱን ባለጠጋ የሚያስመስል ሰው”

ተግሣጽን አይሰማም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) ከእርሱ ለመስረቅ ማንም ሰው አያስፈራራውም ምክንያቱም ማንም ሰው ሊሰርቀው የሚችለው አንዳች ነገር የለውም 2) ሰዎች ሲያስተካክሉት ፈጽሞ አይሰማም ምክንያቱም ቢቀጡትም አንዳች የሚያጣው ነገር የለም። አማራጭ ትርጉም፦ “ተግሳጽ ፈጽሞ አይሰማም”

Proverbs 13:9

ጽድቅን የሚያደርግ ሰው ብርሃን ደምቆ ይበራል
እዚህ ላይ ብርሃን የጻድቅ ሰውን ሕይወት ወይም መልካ ባህርይ ይወክላል፤ “ደምቆ መብራት” ደግሞ ሰዎች ደስ እንዲሰኙ ማድረግን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የጻድቅ ሰው ሕይወት ሰዎችን እንደሚያስደስት በብርሃን ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የኀጥኣን መብራት ይጠፋል
እዚህ ላይ መብራት የክፉ ሰው ሕይወት ወይም ባህርይ ይወክላል፣ “ይጠፋል” ደግሞ እሳቱ ይቆማል ለማለት ጥቅም ላይ የዋለ ፈሊጥ ነው። የሚጠፋው መብራት የሰውየውን መሞት ወይም የሰውየው ሕይወት ደስታ አልባ መሆኑን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የክፉ ሰዎች ሕይወት እሳቱ መንደድ እንደሚያቆም መብራት ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ትዕቢት ጠብን ብቻ ያስፋፋል
“ትዕቢት ሁልጊዜ ጠብን ያመጣል”

ምክርን የሚቀበሉ
“ይሰውራሉ” ወይም “ይከተላሉ”

መልካም ምክር
የሚጠቅሙና የሚያግዙ ሃሳቦች

Proverbs 13:11

ሀብት ትጐድላለች
“ሀብት ይቀንሳል” ወይም “ሀብት ቀስ በቀስ እየጠፋ ይሄዳል”

በእጁ እየሰራ
“በእጁ እየሰራ” የሚለው ሀረግ ከአእምሮ ወይም ከሌሎች የስራ ዓይነቶች ይልቅ በጉልበት የሚሰራ ስራን ይወክላል። ብዙ ሰዎች የጉልበት ስራን አነስተኛ ዋጋ ይሰጡታል። አማራጭ ትርጉም፦ “በአካላዊ ብርታት መስራት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ገንዘቡ እየጨመረ እንዲሄድ ያደርጋል
ገንዘብ ከሚያድግ ዛፍ ጋር ተነጻጽሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “ገንዘቡ እንዲጨምር ያደርጋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ተስፋ ሲዘገይ
እዚህ ላይ “ተስፋ” አንድ ሰው ለወደፊት የሚጠብቀውን ነገር ይወክላል። ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አንድ ሰው አንድ ነገር ተስፋ እያደረገ ነገር ግን ያን ተስፋውን ለረጅም ጊዜ ሳይቀበል ሲቀር” (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ልብን ይሰብራል
የሰውን ልብ መስበር ያንን ሰው በሀዘን ስሜቱን መጉዳት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ጥልቅ ሃዘን ያስከትላል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

የተሳካ ምኞት ግን የሕይወት ዛፍ ነው
ሰዎች ተስፋ ያደረጉትን ነገር ሲቀበሉና በጣም ደስተኛ ሲሆኑ የተስፋቸው መሳካት ሕይወት እንደሚሰጥ ዛፍ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “የተሳካ ተስፋ እንደ ሕይወት ዛፍ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሕይወት ዛፍ
“ሕይወት የሚሰጥ ዛፍ” ወይም “ፍሬው ሕይወትን የሚያቆይ ዛፍ።” ይህንን በምሳሌ 3:18 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

Proverbs 13:13

ትእዛዝን የሚያከብር ግን ወሮታን ያገኛል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ትእዛዝ የሚያከብርን ሰው ወሮታ ይከፍሉታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የሕይወት ምንጭ
ምንጭ የተትረፈረፈ የውኃ ምንጭ ነው እናም በዚህ የሚወክለው የሕይወት ምንጭን ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የሕወይት የተትረፈረፈ ምንጭ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሞት ወጥመድ
እዚህ ላይ “ወጥመድ” የሚገድል አደጋን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ወደ ሞት የሚመራ ወጥመድ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 13:15

የከዳተኛ መንገድ ግን አያልቅም
እዚህ ላይ የሰው ባህርይ ወይም ጠባይ አንድ ሰው የሚጓዝበት መንገድ ወይም አቅጣጫ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። በራሳቸው ክፋት ውድቀት የሚደርስባቸው ሰዎች ዘመናቸውን ሁሉ ቢጓዙ የማያልቅ መንገድ ወይም ጉዞ ላይ እንደሆኑ ተደርጎ ተንግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “ነገር ግን የከዳተኞች ባህርይ በራሳቸው ላይ ጥፋት ያመጣባቸዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዳተኞች
ይህ የስም ቅጽል በመደበኛው ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ከዳተኛ ሰው” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ሞኝ ሞኝነቱን ይገልጣል
“መግለጥ” በማንኛውም ሰው ፊት ማሳየት ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ሞኝ ሞኝነቱን ለሁሉም ሰው ያሳያል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 13:17

በመከራ ውስጥ ይወድቃል
“አይታመንም” ወይም “ክፉ ነገር ያደርጋል”

የታመነ መልእክተኛ
“ታማኝ መልእክተኛ” ወይም “ታማኝ ወኪል”

ከእርምት ይማራል
ይህ “እርምት” የሚለው ረቂቅ ስም በድርጊት ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አንድ ሰው ሲያርመው በሚገባ ይማራል” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Proverbs 13:19

ጣፋጭ ነው
“ደስ ያሰኛል” ወይም “ደስታን ያመጣል”

ምኞት
የአንድ ነገር ፍላጎት ወይም አምሮት

መከራን ይቀበላል
“መከራ ይገጥመዋል” ወይም “ጥፋት ይመጣበታል”

Proverbs 13:21

ክፉ ነገር ኃጢአተኞችን ይከታተላቸዋል
“ክፉ ነገር” እንደ ሩጫ ችሎታ የሰው ልጅ የሚከታተል መጥፎ ባህርይ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ኃጢአተኞች የትም ቢሄዱ መከራ ይገጥማቸዋል” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጽድቅን የሚያደርጉ ሰዎች መልካምን ነገር ይቀበላሉ
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ጻድቅ ሰዎችን በመልካም ነገር ይባርካቸዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የልጅ ልጆቹ
“የወንድ ልጆቹ ወንድ ልጆች” ወይም “የልጆቹ ልጆች” ወይም “ዘሮቹ”

የኃጢአተኛ ሀብት ጽድቅን ለሚያደርጉ ይከማቻል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጽድቅን የሚያደርግ ሰው ኃጢአተኛ ያከማቸውን ሀብት ይቀበላል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 13:23

ያልታረሰ እርሻ
“ምግብ ለማምረት ያልተዘጋጀ እርሻ” ወይም “ዘር ለመዝራት ያልተዘጋጀ ባዶ እርሻ”

ነገር ግን በፍትህ መጓደል ምክንያት ተጠራርጎ ይወሰዳል
“ተጠራርጎ ይወሰዳል” የሚለው አንድን ነገር ሙሉ በሙሉ ማስወገድን ያመለክታል። ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን የፍትህ መጓደል ያንን ምግብ ይወስደዋል” ወይም “ነገር ግን ፍትህ የማያደርጉ ሰዎች ምግቡን ይወስዱታል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በጥንቃቄ ይቀጣዋል
“እርሱን ለመገሰጽ ይተጋል”

Proverbs 13:25

ፍላጎቱን ያረካል
“ራሱን አጠገበ” ወይም “ፍላጎቱን አረካ”

የጎጥኣን ሆድ ሁልጊዜ እንደተራበ ነው
እዚህ ላይ “ሆድ” የሚለው የሰውየውን ፍላጎት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ሰው ሁልገዜ በጣም እንደተራበ ነው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 14

1 ጥበበኛ ሴት ቤቷን ትሰራለች፣ ሞኝ ሴት ግን በገዛ እጇ ታፈርሰዋለች። 2 በጽድቅ የሚሄድ ሰው እግዚአብሔርን ይፈራል፣ በመንገዱ ታማኝ ያልሆነ ግን
ይንቀዋል። 3 ከሞኝ አፍ የትዕቢት በትር ይወጣል፣ የጥበበኛ ከንፈሮች ግን ይጠብቋቸዋል። 4 ከብቶች በሌሉበት የመመገቢያ ገንዳ ባዶ ይሆናል፣ በበሬ
ጉልበት ግን ብዙ ምርት ይገኛል። 5 እውነተኛ ምስክር አይዋሽም፣ ሐሰተኛ ምስክር ግን ውሸትን ይለፈልፋል። 6 ፌዘኛ ጥበብን ይፈልጋል ሆኖም አያገኛትም፣
እውቀት ግን ወደ አስተዋይ ሰው በቀላሉ ትመጣለች። 7 ከሞኝ ሰው ራቅ፣ ከከንፈሮቹ እውቀትን አታገኝምና። 8 የጠንቃቃ ሰው ጥበብ መንገዱን ማስተዋል
ነው፣ የሞኞች ከንቱነት ግን ማታለል ነው። 9 ሞኞች የኃጢአት መስዋዕት በሚቀርብበት ጊዜ ያፌዛሉ፣ በጻድቃን መካከል ግን ቸርነት ይገኛል። 10 ልብ የራሱን
ምሬት ያውቃል፣ ደስታውንም ሌላ ሰው አይጋራውም። 11 የክፉ ሰዎች ቤት ይጠፋል፣ የጻድቃን ድንኳን ግን ይስፋፋል። 12 ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ
አለች፣ ፍጻሜዋ ግን ወደ ሞት ይመራል። 13 ልብ በሐዘን ውስጥ ሆኖ ሊስቅ ይችላል፣ የደስታም ፍጻሜ ሐዘን ሊሆን ይችላል። 14 ታማኝ ያልሆነ ሰው
ለመንገዱ የሚገባውን ዋጋ ያገኛል፣ መልካም ሰው ግን የራሱ የሆነውን ያገኛል። 15 እውቀት አልባ ሰው ሁሉንም ነገር ያምናል፣ አስተዋይ ሰው ግን አካሄዱን
ያስተውላል። 16 ጥበበኛ ሰው ይፈራል ከክፉም ይርቃል፣ ሞኝ ግን ራሱን ታምኖ ማስጠንቀቂያን ችላ ይላል። 17 ለቁጣ የሚቸኩል ሰው ከንቱ ነገሮችን
ይፈጽማል፣ ክፋትን የሚያሴር ሰው ደግሞ ይጠላል። 18 እውቀት አልባ ሰዎች ሞኝነትን ይወርሳሉ፣ አስተዋይ ሰዎች ግን በእውቀት ይከበባሉ። 19 ክፉዎች
በመልካም ሰዎች ፊት ይሰግዳሉ፣ ኃጢአተኞች ደግሞ በጻድቃን ደጅ ይሰግዳሉ። 20 ድሃ ሰው በራሱ ባልንጀሮችም ጭምር ይጠላል፣ ባለጠጋ ሰዎች ግን ብዙ
ወዳጆች አሏቸው። 21 ለጎረቤቱ ንቀትን የሚያሳይ ኃጢአትን ያደርጋል፣ ለድሃ በጎነትን የሚያሳይ ግን ደስተኛ ነው። 22 ክፋትን የሚያሴሩ አይስቱምን?
መልካምን ለማድረግ የሚያቅዱ ግን በኪዳን የተመሰረተ ታማኝነትና እውነተኛነት ይቀበላሉ። 23 በብዙ ድካም ትርፍ ይገኛል፣ ወሬ ግን ወደ ድህነት ይመራል።
24 የጥበበኞች ዘውድ ባለጠግነታቸው ነው፣ የሞኞች ሞኝነት ግን ተጨማሪ ከንቱነትን ያመጣባቸዋል። 25 እውነተኛ ምስክር ሕይወት ያድናል፣ ሐሰተኛ ምስክር
ግን ውሸትን ይለፈልፋል። 26 ሰው እግዚአብሔርን ሲፈራ፣ በእርሱ ይታመናል፤ እነዚህ ነገሮች ደግሞ ለልጆቹ እንደ ብርቱ መጠጊያ ስፍራ ይሆኗቸዋል። 27
እግዚአብሔርን መፍራት የሕይወት ምንጭ ነው፣ ሰውን ከሞት ወጥመድ እንዲያመልጥ ያደርገዋል። 28 የንጉስ ክብር የሚገኘው ከሕዝቡ ብዛት ነው፣ ሕዝብ
በሌለበት ግን ልዑል ይጠፋል። 29 ትዕግስተኛ ሰው ታላቅ ማስተዋል አለው፣ ለቁጣ የሚቸኩል ሰው ግን ሞኝነትን ከፍ ከፍ ያደርጋል። 30 በሰላም የተሞላ ልብ
ለሰውነት ሕይወት ነው፣ ቅናት ግን አጥንትን ያበሰብሳል። 31 ድሀን የሚያስጨንቅ ሰው ፈጣሪውን ይሰድባል፣ ለድሀ ቸርነትን የሚያሳይ ግን ፈጣሪውን
ያከብራል። 32 ክፉ ሰው በክፉ ስራው ይወድቃል፣ ጻድቅ ግን በሞት ጊዜ እንኳ መጠጊያ አለው። 33 ጥበብ በአስተዋይ ሰው ዘንድ ትኖራለች፣ በሞኞች
መካከል እንኳ ራሷን ታሳውቃለች። 34 ጽድቅን ማድረግ ህዝብን ከፍ ከፍ ያደርጋል፣ ኃጢአት ግን ለማንኛውም ሕዝብ ውርደት ነው። 35 የንጉስ ሞገስ ተግተው
በሚሰሩ አገልጋዮቹ ላይ ነው፣ ቁጣው ግን በአሳፋሪ አገልጋይ ላይ ነው።

Proverbs 14:1

ቤቷን ትሰራለች
“ቤቷን ትገነባለች” ወይም “ቤቷን የተሻለ አድርጋ ትሰራለች”

ቤት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ይህ ቃል በቃል ቤቷን ማለትም የምትኖርበትን ሕንጻ ሊያመለክት ይችላል” ወይም 2) ቤተሰቧን ሊያመለክት ይችላል።

በራሷ እጅ
ይህች ሴት “በእጇ” ተወክላለች። አማራጭ ትርጉም፡- “በራሷ” ወይም “በባህርይዋ” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ሴት ... ሴት
“ብልሃተኛ ሴት ... ሞኝ ሴት”

በጽድቅ ይሄዳል
“ይሄዳል” የሚለው የሰውየውን የአኗኗር ዘይቤ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሕይወቱን በትክክለኛነት እና በታማኝነት ይመራል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይንቀዋል
“አያከብረውም” ወይም “እንደሚጠላው ያመለክታል”

በመንገዱ ሁሉ ይንቀዋል
“በመንገዱ” የሚለው ታማኝ ያልሆነውን ሰው ያመለክታል፣ “ይንቀዋል” የሚለው ደግሞ እግዚአብሔርን ያመለክታል።

Proverbs 14:3

አፍ ... ከንፈር
አፍና ከንፈር ሁለቱም ሰውየው የተናገረውን ነገር ያመለክታል። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የትዕቢት ቅርንጫፍ
ቅርንጫፍ ከሌላ ነገር የሚወጣ ነገር ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ትዕቢቱ የሚያመጣው ነገር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጠቢባን
ይህ ቃል በእርግጥ ብዙ ቁጥር ነው። “ጥበበኛ ሰዎች” ወይም “ጥበበኛ ሕዝብ”

ትጠብቃቸዋለች
“ከጉዳት ትጠብቃቸዋለች” ወይም “በደህንነት ትጠብቃቸዋለች”

የመመገቢያ ገንዳ
“ገንዳ” ለእንስሳት መኖ የሚቀርብበት ትልቅ እቃ ነው

ብዙ ምርት
“ጥሩ ምርት”

በበሬ ጉልበት
“ጉልበት” በሬ ሊሰራ የሚችለውን ጠንካራ ስራ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በሬ በሚሰራው ስራ ምክንያት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Proverbs 14:5

ውሸት ይለፈልፋል
ይህ የንግግር ዘይቤ ያለማቋረጥ እንደሚዋሽ ለማሳየት “ይለፈልፋል” የሚለውን ቃል ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሁልጊዜ ይዋሻል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ) ይህንን በምሳሌ 6:19 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

ምንም የለም
“ጥበብ በዚያ አትገኝም” ወይም “ነገር ግን ጥበብን አያገኝም”

በቀላሉ ትመጣለች
“በቀላሉ ትገኛለች” ወይም “ያለ ምንም ችግር ያገኛታል”

አስተዋይ ሰው
“ጥበበኛ የሆነ ሰው” ወይም “ግንዛቤ ያለው ሰው”

Proverbs 14:7

በከንፈሩ
“ከንፈር” የሚለው ቃል ሰውየው የተናገረውን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከንግግሩ” ወይም “ከሃሳቡ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ጠንቃቃ ሰው
ጥሩ ግንዛቤና አመለካከት ያለው

በመንገዱ
“መንገድ” የሚለው ቃል የሰውየውን የሕይወት ዘይቤ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ባህርዩ” ወይም “እንዴት እንደሚኖር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የሞኞች ሞኝነት ማታለል
የሞኞች ሞኝነት እነርሱ ሞኞች ሆነው ሳለ ጥበበኞች እንደሆኑ ያስባሉ።

Proverbs 14:9

የኃጢአት መስዋዕት በሚቀርብበት ጊዜ
“በኃጢአት” ወይም “የኃጢአት መስዋዕት” በእነዚህ ሀረጎች በስተጀርባ ያለው ትርጉም እንዲህ የሚል ነው፡- ሞኞች ለበደሉት በደል እግዚአብሔርን ወይም ሰዎችን ይቅርታ አይጠይቁም።

በጻድቃን መካከል ግን ቸርነት ይገኛል።
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን ጻድቃን ሁሉ ቸርነትን ይለማመዳሉ” ወይም “ነገር ግን የእግዚአብሔር ሞገስ በጻድቃን ሁሉ መካከል ይገለጣል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የራሱን ምሬት
“የራሱን ሃዘን” ወይም “የራሱን ጉስቁልና”

ሌላ ሰው
“እርሱን የማያውቁት”

Proverbs 14:11

ድንኳን
“ድንኳን” የሚለው ቃል በቤት ውስጥ የሚከናወነውን ማንኛውንም ነገር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ቤት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ያብባል
“ያብባል” የሚለው ቃል ኃይለኛ የሆነ የአበቦች መፍካት ማለት ነው፣ ስለዚህ በኃይል የሚያድጉትን ማንኛውንም ነገር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በሚገባ የተሰራና ዘለቄታዊነት ያለው” ወይም “በጣም ስኬታማ መሆን” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለሰው ትክክል የምትመስል መንገድ አለች
“መንገድ” የሚለው ቃል ሰው የሚከተለውን የሕይወት ዘይቤ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች የሚኖሩት የሕይወት ዘይቤ ትክክለኛው መንገድ እንደሆነ ያስባሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 14:13

ልብ ሊስቅ ይችላል
“ልብ” የሚለው ቃል የሰውን ስሜት፣ አመለካከትና ተነሳስቶት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሰው ስሜት ሳቅን ሊያሳይ ይችላል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በሐዘን ውስጥ መሆን
“ማዘን” ወይም “መጎዳት”

ሰው
“ያ ሰው”

ለመንገዱ የሚገባውን ዋጋ ያገኛል
“መንገድ” የሚለው ቃል የሰውን የሕይወት ዘይቤ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እንዴት እንደኖረ መሰረት በማድረግ የሚገባውን ያገኛል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የራሱ
“የእርሱ የሆነው” ወይም “ሊያዝዝበት የሚችለው ያለው ነገር”

Proverbs 14:15

አላዋቂ
ልምድ የሌለው ወይም ያልበሰለ አእምሮ ያለው

አካሄድ
እዚህ ላይ አካሄድ የሚለው ሃሳብ የሰውን ባህርይ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ድርጊቱ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከክፉም ይሸሻል
እዚህ ላይ ክፉ ቦታ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ አያደርግም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ራሱን ታምኖ ማስጠንቀቂያን ችላ ይላል
“በድፍረት ይንቃል”

Proverbs 14:17

ለቁጣ የሚቸኩል ነው
“በቶሎ ይቆጣል”

አላዋቂ
ልምድ የሌለው ወይም ያልበሰለ አእምሮ ያለው

ሞኝነትን ይወርሳል
እዚህ ላይ “ይወርሳል” የሚለው የአንድ ነገር ቋሚ ባለቤት መሆን ይወክላል። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሞኝነት
“ሞኝነት” የሚለው ቃል ሞኝ አስተሳሰብና ሞኝ ድርጊትን የሚወክል ረቂቅ ስም ነው።

ጠንቃቃ ሰዎች
“ጥበበኛ ሰዎች”

እውቀትን እንደ ዘውድ ይጭናሉ
እዚህ ላይ እውቀት እንቁ እንዳለበት ጥምጥም በአንድ ሰው ጸጉር ላይ የሚደረግ ውብ ጌጥ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “እንደ ጥምጥም እውቀትን ልበስ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 14:19

ይሰግዳል
ይህ በትህትና አክብሮትን ለመግለጽ መጎንበስ እና ለሌላ ሰው ራስን ማስገዛት ማለት ነው። (ምሳሌያዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

በጻድቃን በር
“በር” የሚለው ቃል ከሌላ ሰው ጋር ለመገናኘት መግቢያን ይወክላል። ይህ ማለት ክፉ ሰው ጻድቅ ወዳለበት ለመግባት እርሱን መጠበቅ እና መለመን እንዳለበት ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፦ “ከጻድቅ ሰው ጋር ለመገናኘት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ድሃ ሰው በራሱ ባልንጀሮችም ጭምር የተጠላ ነው
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ድሃ ሰው ጎረቤቶቹን ጨምሮ ሁሉም ሰው ይጠላዋል” (ገቢር/አድርጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 14:21

ሰው ... ሰው
“ያ ሰው ... ያ ሰው”

ድሃ
“ድሃ ሰው”

ክፋትን የሚያሴሩ አይስቱምን?
ለዚህ ጥያቄ የሚጠበቀው መልስ “አዎ” የሚል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ክፋትን የሚያሴሩ ሰዎች ይስታሉ” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ክፋትን የሚያሴሩ
“ክፉ እቅድ የሚያቅዱ ሰዎች” ወይም “ክፋትን ለማድረግ የሚያቅዱ ሰዎች”

መልካምን ለማድረግ የሚያቅዱ ግን በኪዳን የተመሰረተ ታማኝነትና እውነተኛነት ይቀበላሉ
“ታማኝነት” እና “እውነተኛነት” የሚሉት ረቂቅ ስሞች “ታማኝ” እና “እውነተኛ” ተብለው ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር መልካምን ለማድረግ ለሚያቅዱ ሰዎች ለከኪዳኑ ታማኝ እና እውነተኛ ለመሆኑ ራሱን ያሳያል። (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 14:23

ነገር ግን ወሬ ብቻ ሲኖር
“ነገር ግን የምታወራ ብቻ ከሆንህ” ወይም “ነገር ግን ሰው የሚሰራው ወሬ ብቻ ከሆነ”

የጠቢባን ዘውድ
“ዘውድ” የሚለው ቃል ሰው ሊደርስበት የሚችለው ከፍተኛውና ለሁሉም ሰው የሚታይ ስኬትን የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የጠቢባን ሰዎች ወሮታ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሞኞች ሞኝነት
ይህንን እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። ምሳሌ 14:8.

Proverbs 14:25

ውሸት ይለፈልፋል
ይህ የንግግር ዘይቤ ያለማቋረጥ እንደሚዋሸ ለማሳየት “ይለፈልፋል” የሚለውን ቃል ይጠቀማል። ይህንን በምሳሌ 6:19 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “ሁልጊዜ ይዋሻል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 14:26

የሕይወት ምንጭ
ምንጭ የተትረፈረፈ የውኃ ምንጭ ነው እናም በዚህ የሚወክለው የሕይወት ምንጭን ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የሕወይት ምንጭ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከሞት ወጥመድ
“ወጥመድ” እንስሳትን ለማደን የሚጠቅም ነገር ሲሆን የሚገድል አታላይና አደገኛ የሆነ ነገርን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ከሚገድል ወጥመድ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 14:28

ከሕዝቡ ብዛት
“የሚመራው ብዙ ሕዝብ”

ልዑል ይጠፋል
“ልዑል ምንም የለውም መንግስቱም ይወድቃል”

ለቁጣ የሚቸኩል
ለመቆጣት የሚፈጥን ሰው

Proverbs 14:30

ሰላም የተሞላ ልብ
“ሰላማዊ የሆነ አእምሮ” ወይም “ሰላም የሰፈነበት አመለካከት”

አጥንትን ያነቅዛል
“ያነቅዛል” የሚለው ቃል የሰውየውን መበስበስ ይወክላል “አጥንት” ደግሞ የሰውየውን ሁለንተና ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰውየውን በአካልና በመንፈስ በሽተኛ እንዲሆን ያደርገዋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰው ... ሰው
“ያ ሰው ... ያ ሰው”

መርገም
ይህ ክፉ ነገር በአንድ ሰው ላይ እንዲመጣበት ምኞትን መግለጽ ማለት ነው።

ድሃ ... ምንም የሌለው
“ድሃ ሰው ... ምንም የሌለው ሰው”

ምህረትን የሚያደርግ
“ደግ ነው” ወይም “ይረዳል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Proverbs 14:32

በክፉ ስራው ይወድቃል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ስራው ይጥለዋል” ወይም “ክፉ ስራው ያጠፋዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥበብ በልብ ትቀመጣለች
“ልብ” የሚለው ቃል የሰውን ስሜት፣ አመለካከትና ተነሳስቶት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበብ በአመለካከት ውስጥ አለች” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አስተዋይ
“አስተዋይ ሰው”

ራሷን ታሳውቃለች
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች እንደሚያውቋት እርግጠኛ ትሆናለች” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እርስዋ
“እርስዋ” የሚለው ቃል ጥበብን ያመለክታል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 14:34

ውርደት ነው
“በማንኛውም ሰው እፍረትን ያመጣል” ወይም “ሰው ሁሉ እንዲዋረድ ታደርጋለች”

በማስተዋል የሚያደርግ
“በጥበብ የሚያደርግ” ወይም “ክፉ ነገር እንዳይመጣ እርግጠኛ የሚሆን”

ያ ሰው
“ያ አገልጋይ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 15

1 የለዘበ መልስ ቁጣን ይመልሳል፣ መጥፎ ቃል ግን ቁጣን ያስነሳል። **2** የጥበበኛ ሰዎች ምላስ እውቀትን የተላበሰ ነው፣ የሞኞች አፍ ግን ሞኝነትን ያንቆረቁራል። **3** የእግዚአብሔር ዓይኖች በሁሉም ስፍራ ናቸው፣ ክፉውንና መልካሙን ሁሉ ነቅተው ይመለከታሉ። **4** ፈዋሽ ምላስ የሕይወት ዛፍ ነው፣ አታላይ ምላስ ግን መንፈስን ይሰብራል። **5** ሞኝ የአባቱን ተግሳጽ ይንቃል፣ ከእርምት የሚማር ግን አስተዋይ ነው። **6** ጽድቅን በሚያደርጉ ሰዎች ቤት ብዙ ሀብት አለ፣ ክፉ ሰዎች የሚያገኙት ገቢ ግን መከራ ያመጣባቸዋል። **7** የጥበበኛ ሰዎች ከንፈሮች እውቀትን ያስፋፋሉ፣ የሞኞች ልብ ግን እንዲህ አይደለም። **8** እግዚአብሔር የክፉዎችን መስዋዕት ይጠላል፣ የቅኖች ጸሎት ግን ደስ ያሰኘዋል። **9** እግዚአብሔር የክፉዎችን መንገድ ይጠላል፣ ጽድቅን የሚከታተለውን ግን ይወደዋል። **10** ከመንገድ የሚወጣ ሰው ከባድ ቅጣት ይጠብቀዋል፣ እርምትን የሚጠላም ይሞታል። **11** ሲኦልና ጥፋት በእግዚአብሔር ፊት የተገለጡ ናቸው፤ የሰው ልጆች ልብማ ምንኛ የተገለጠ ይሆን? **12** ፌዘኛ እርምትን ይንቃል፤ ወደ ጥበበኞም አይሄድም። **13** ደስተኛ ልብ ፊትን ያፈካል፣ የልብ ሐዘን ግን መንፈስን ይሰብራል። **14** የአስተዋይ ልብ እውቀትን ይፈልጋል፣ የሞኞች አፍ ግን ከንቱነትን ይመገባል። **15** የተጨቆኑ ሰዎች ቀናት በሙሉ አሰቃቂ ናቸው፣ ደስተኛ ልብ ግን የማይቋረጥ ግብዣ አለው። **16** እግዚአብሔርን ከመፍራት ጋር ያለ ጥቂት ነገር ከሁከት ጋር ካለ ትልቅ ሃብት ይሻላል። **17** ፍቅር ባለበት የአትክልት ምግብ መብላት ጥላቻ ባለበት የሰባ ጥጃ ከመብላት ይሻላል፡ **18** ቁጡ ሰው ጭቅጭቅን ያነሳሳል፣ ለቁጣ የዘገየ ሰው ግን ጠብን ጸጥ ያሰኛል። **19** የታካች ሰው መንገድ በእሾህ እንደ ታጠረ ስፍራ ነው፣ የቅን መንገድ ግን በሚገባ የተገነባ አውራ ጎዳና ነው። **20** ጥበበኛ ልጅ ለአባቱ ደስታን ያመጣለታል፣ ሞኝ ሰው ግን እናቱን ይንቃል። **21** ከንቱ ነገር አእምሮ ለጎደለው ሰው ደስ ያሰኛል፣ አስተዋይ ሰው ግን በቅን መንገድ ይሄዳል። **22** ምክር በሌለበት እቅድ ይበላሻል፣ በአማካሪዎች ብዛት ግን ይከናወናል። **23** ሰው ተገቢ የሆነ መልስ ሲሰጥ ደስታን ያገኛል፤ የጊዜው ቃል ምንኛ መልካም ነው! **24** የሕይወት መንገድ አስተዋይ ሰዎችን ወደ ላይ ይመራቸዋል፣ በታች ካለው ከሲኦል ያመልጥ ዘንድ። **25** እግዚአብሔር የትዕቢተኛውን ውርስ ያፈራርሳል፣ የመበለቲቱን ንብረት ግን ይጠብቃል። **26** እግዚአብሔር የክፉ ሰዎችን ሐሳብ ይጠላል፣ የርኅራኄ ቃሎች ግን ንጹሐን ናቸው። **27** ዘራፊ ለቤተሰቡ መከራን ያመጣል፣ ጉቦን የሚጠላ ግን በሕይወት ይኖራል። **28** ጽድቅን የሚያደርግ ሰው ልብ መልስ ከመስጠቱ በፊት አጥብቆ ያስባል፣ የክፉ ሰዎች አፍ ግን ክፋትን ሁሉ ያጎርፋል። **29** እግዚአብሔር ከክፉ ሰዎች እጅግ ሩቅ ነው፣ ጽድቅን የሚያደርጉ ሰዎችን ጸሎት ግን ይሰማል። **30** የዓይን ብርሃን ለልብ ደስታን ያመጣል፣ መልካም ወሬ ደግሞ ለሰውነት ጤና ነው። **31** አንድ ሰው እንዴት መኖር እንዳለብህ እርምትን ሲሰጥህ ትኩረት ሰጥተህ የምትሰማ ከሆንህ፣ በጥበበኛ ሰዎች መካከል ትቆያለህ። **32** ተግሳጽን የማይቀበል ራሱን ይንቃል፣ እርምትን የሚያደምጥ ግን ማስተዋልን ያገኛል። **33** የእግዚአብሔር ፍርሃት ጥበብን ያስተምራል፣ ትህትናም ከክብር በፊት ትመጣለች።

Proverbs 15:1

የለዘበ መልስ ቁጣን ይመልሳል

አንድ ሰው ቁጣውን እንዲያቆም ማድረግ የዚያን ሰው ቁጣ መመለስ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለአንድ ሰው በጨዋነት መልስ መስጠት የዚያን ሰው ቁጣ ያበርዳል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መጥፎ ቃል ግን ቁጣን ያስነሳል

አንድ ሰው የበለጠ እንዲቆጣ ማድረግ ቁጣን ማነሳሳት ወይም ማቀጣጠል ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን መጥፎ ቃል መናገር ያንን ሰው የበለጠ እንዲቆጣ ያደርገዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የጥበበኛ ሰዎች ምላስ እውቀትን ያሳምራል

እዚህ ላይ “ምላስ” የሚለው ቃል የሚናገረውን ሰው የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበበኛ ሰዎች ሲናገሩ በእውቀት ላይ የተመሰረተ ነው።” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

እውቀትን ያሳምራል

“እውቀትን ማራኪ ያደርጉታል” ወይም “እውቀትን በትክክል ይጠቀማሉ”

የሞኞች አፍ ግን ሞኝነትን ያፈልቃል

ጸሐፊው የሞኞችን አፍ የፈሳሽ መያዣ ዕቃ እንደሆነ፣ ሞኝነት ደግሞ እነርሱን የሞላቸው ፈሳሽ እንደሆነ አድርጎ ተናግሮታል። ሞኞች ሲናገሩ አፋቸው ፈሳሹን ያፈሳል። “አፍ” የሚለው ቃል የሚናገሩትን ሰዎች የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሞኞች ሁልጊዜ ሞኝነትን ይናገራሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 15:3

የእግዚአብሔር ዓይኖች በሁሉ ስፍራ ናቸው

እዚህ ላይ “ዓይኖች” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ይወክላል ደግሞም የእርሱን ሁሉን ነገር የማየት ችሎታውን አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ይመለከታል” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉዎችንና ደጎችን

“ክፉ” እና “ደግ” የሚሉት ቃላት ሰዎችን ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ሰዎችና መልካም ሰዎች” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ፈዋሽ ምላስ የሕይወት ዛፍ ነው

“ምላስ” የሚለው ቃል ንግግርን ያመለክታል። ጸሐፊው ሌሎችን የሚያግዝና የሚያበረታታ ንግግር ስለተናገረው ሰው ሲናገር ንግግሮቹ ሕይወት የሚሰጥ ምግብ እንሚያቀርብ ዛፍ እንደሆኑ አድርጎ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “መልካም ቃላቶች ሕይወት እንደሚሰጥ ዛፍ ናቸው (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጠማማ ምላስ ግን መንፈስን ይሰብራል

“ጠማማ ምላስ” የሚለው አታላይነት የተሞላና ጉዳት የሚያስከትል ንግግርን ያመለክታል። ጸሀፊው የተጎዳውን ወይም ተስፋ የቆረጠውን ሰው መንፈስ ቃላት እንደሰበሩት ዕቃ አድርጎ አቅርቦታል። አማራጭ ትርጉም፡- “አታላይነት የተሞላ ንግግር ሰውን ተስፋ እንዲቆርጥ ያደርገዋል” (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 15:5

ከእርምት የሚማር

“እርምት” የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰው ሲያስተካክለው የሚማር” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አስተዋይ ነው
“ጥበበኛ ነው”

ክፉ ሰዎች የሚያገኙት ገቢ
“ገቢ” የሚለው ቃል እንደ ግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ሰው የሚያካብተው ሀብት” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 15:7

የጠቢባን ከንፈር እውቀትን ትዘራለች
“ከንፈር” የሚለው ጠቢባን የሚናገሩትን ይወክላል። ጸሐፊው ስለ እውቀት ጠቢባን ሲናገሩ በየአካባቢው የሚዘሩት ዘር እንደሆነ አድርጎ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “የጠቢባን ንግግር እውቀትን ያሰራጫል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የሞኞች ልብ ግን እንዲህ አይደለም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) “ልብ” የሚለው ቃል ለሞኞች ተዛምዶአዊ ዘይቤ ሲሆን ትርጉሙም እንደ ጠቢባን እውቀትን አይዘሩም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሞኞች እውቀትን አይዘሩም” ወይም 2) ሞኞች በልባቸው ውስጥ እውቀት የላቸውም፣ እዚህ ላይ “ልብ” ለሃሳብ ተዛምዶአዊ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሞኞች እውቀትን አይረዱም” (ተዛምዶአዊ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ቅን ሰዎች
“በጽድቅ የሚኖሩ ሰዎች”

በእርሱ ዘንድ የተወደደ ነው
“ያስደስተዋል”

Proverbs 15:9

እግዚአብሔር የኃጢአተኞችን መንገድ ይጠላል
የኃጢአተኞች የሕይወት ዘይቤ እነዚህ ሰዎች እንደሚሄዱባቸው መንገዶች እንደሆኑ ተደርገው ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ኃጢአተኞች የሚኖሩትን የሕይወት ዘይቤ ይጠላል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጽድቅን የሚከታተለውን
ጽድቅን ለመኖር መትጋ ትክክለኛ ነገሮችን እንደመከታተል ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- በጽድቅ ለመኖር ጥረት የሚያደርግ ሰው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መንገድን የሚተው ሰው
እዚህ ላይ “መንገድን” የሚለው የጽድቅ መንገድን ያመለክታል። ጽድቅን ማድረግ የተወ ሰው በትክክለኛው መንገድ መሄድን እንዳቆመ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጽድቅን መኖር የተወ ሰው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርምትን የሚጠላ
“እርምት” የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሌሎች ሲያርሙት የሚጠላ ሰው” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 15:11

ሲኦልና ጥፋት በእግዚአብሔር ፊት የታወቁ ናቸው
“ሲኦልና ጥፋት” የሚሉት ቃላቶች ሁሉም የሚያመለክቱት የሙታንን መኖርያ ነው። እግዚአብሔር ስለ ሙታን መኖርያ ሁሉን ነገር ማወቁ በእግዚአብሔር ፊት የተገለጠ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ሙታን ስለሚኖሩበት ስፍራ ሁሉን ነገር ያውቃል” (ጥምር ቃል እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይልቁንም የሰው ልጆች ልብማ ምንኛ የተገለጠ ይሆን?
ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ እግዚአብሔር ስለ ሙታን መኖርያ ሁሉን ነገር ስለሚያውቅ፣ ስለ ሰዎች ልብ ሁሉን ነገር እንደሚያውቅ የበለጠ ግልጽ እንደሆነ አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለዚህ የሰው ልጆችን ልብ በእርግጠኝነት ያውቃል!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጆች ልብ
እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል ሃሳብንና ተነሳስቶትን ይወክላል። “የሰው ልጆች” የሚለው ሀረግ ለሰው ዘር ሁሉ የቆመ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የሰዎች ሃሳብ” (ምትክ ስም እና ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ፌዘኛ ሰው እርምትን አይወድድም
“እርምት” የሚለው ቃል በግስ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ፌዘኛ ሰው ሌሎች ሲያርሙት ይጠላል” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ጠቢባንም አይሄድም።
የእነርሱን ምሪትና ምክር ለመፈለግ ወደ ጠቢባን እንደማይሄድ የሚያመላክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ምክራቸውን ለመፈለግ ወደ ጠቢባን አይሄድም” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 15:13

ደስተኛ ልብ ፊትን ያፈካል
እዚህ ላይ “ልብ” የሚወክለው ሰውየውን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ሰው ደስተኛ ሲሆን ፊቱ ይፈካል” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

መንፈስን ይሰብራል
ጸሐፊው ልቡ ስለተሰበረ ሰው ሲናገር የዚያ ሰው መንፈስ እንደተሰበረ ዕቃ አድርጎ ገልጾታል። ይህንን በምሳሌ 15:4 እንዴት እንደተረጎም'ኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰውን ልቡ እንዲሰበር ያደርጋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የአስተዋይ ልብ
እዚህ ላይ “ልብ” የሚወክለው አእምሮንና ሃሳብን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የአስተዋይ ሰው አእምሮ” ወይም “አስተዋይ ሰው” (ምትክ ስም እና ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

የሞኞች አፍ ግን ሞኝነትን ይመገባል
እዚህ ላይ “አፍ” የሚወክለው ሰውየውን ነው። ጸሐፊው ሞኝ ነገሮች ስለሚፈልጉ ሞኞች ሲናገር ሞኝነትን እንደተመገቡ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሞኞች ሰዎች የሚመገቡት ምግብ እንደሆነ ዓይነት ሞኝነትን ይፈልጋሉ” (ተዛምዶአዊ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 15:15

የተጨቆኑ ሰዎች ቀናት በሙሉ አሰቃቂ ናቸው
“የተጨቆኑ ሰዎች ቀኖቻቸው ሁሉ አሰቃቂ ናቸው”

ደስተኛ ልብ ግን የማያልቅ ድግስ አለው
እዚህ ላይ “ልብ” የሚወክለው ሰውየውን ነው። ጸሐፊው ሕይወቱን በደስታ እየኖረ ሀሴት ስለሚያደርግ ሰው ሲናገር ሰውየው የማያቋርጥ ድግስ እያከበረ እንደሆነ እድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ደስተኛ ሰው የማያልቅ ድግስ እንደደገሰ ያህል ሕይወትን በሚገባ ይኖራል” (ተዛምዶአዊ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የማያልቅ ድግስ
“የማያቋርጥ ድግስ”

ከሁከት ጋር
“ከጭንቀት ጋር”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Proverbs 15:17

የአትክልት ምግብ
አትክልት በጣም ትንሽ ምግብ ያለበትን ትንሽ ማዕድ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ትንሽ ማዕድ” ወይም “በጣም ትንሽ ምግብ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ፍቅር ባለበት
“ፍቅር” የሚለው ቃል በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች እርስ በርሳቸው በሚዋደዱበት” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ጥላቻ ባለበት የሰባ ጥጃ ከመብላት
ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ሰው በጥላቻ ከሚያቀርበው የሰባ ጥጃ ይልቅ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰባ ጥጃ
ይህ የሚያመለክተው በሚገባ እንዲወፍር በጣም ብዙ ምግብ የተመገበ ጥጃን ይወክላል። ይ የሚወክለው በጣም ጣፋጭ ምግብ ወይም ድግስ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “መንደላቀቅ ያለበት መዐድ” ወይም “ድግስ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ከጥላቻ ጋር
“ጥላቻ” የሚለው ቃል በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች እርስ በርሳቸው በሚጣሉበት” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ጭቅጭቅን ያነሳሳል
ሰዎች የበለጠ እንዲጨቃጨቁ ማድረግ ጭቅጭቅን ማባባስ ወይም መቀስቀስ ተደርጎ ተነግሮአል። “ጭቅጭቅ” የሚለው ረቂቅ ስም “ተጨቃጨቀ” ተብሎ ሊገለጽ ይችላ። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች የበለጠ እንዲጨቃጨቁ ማድረግ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 15:19

የታካች ሰው መንገድ ... የቅን ሰው መንገድ
ጸሐፊው ስለ ሰው ሕይወት ሲናገር ሰውየው የሚጓዝበት መንገድ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “የታካች ሰው ሕይወት ... የቅን ሰው ሕይወት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የታካች ሰው መንገድ በእሾህ እንደ ታጠረ ስፍራ ነው
ጸሐፊው የታካች ሰው የሕይወት ዘይቤን በእሾህ በታጠረ ስፍራ ለመራመድ ከመሞከር ጋር ያነጻጽረዋል። ሁሉም ቢሆኑ ሰውየው እንዲሰቃይ ያደርጋሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “የታካች ሰው ሕይወት በእሾህ በታጠረ ስፍራ ለመራመድ እንደሚሞክር ሰው ነው” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የቅን መንገድ ግን በሚገባ የተገነባ አውራ ጎዳና ነው
ጸሐፊው ቅን ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው የሚለማመዱትን በረከት በተደላደለ መንገድ እንደሚራመዱ አድርጎ ገልጾታል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በሚገባ የተገነባ አውራ ጎዳና
ይህ በጣም ሰፊ፣ ለጥ ያለ እና ምንም እንቅፋት ወይም የተቦረቦረ ነገር የሌለው መንገድ ነው።

Proverbs 15:21

አስተዋይ ሰው ቀጥ ባለ መንገድ ይሄዳል
ጸሐፊው ትክክለኛውን ነገር ስለሚያደርግ ሰው ሲናገር በመንገድ ላይ ቀጥ ብሎ እንደሚሄድ ሰው አድርጎ ይገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “አስተዋይ ሰው ትክክለኛውን ነገር ያደርጋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እቅድ ይበላሻል
“እቅድ አይከናወንም”

ምክር በሌለበት
“ምክር ለመስጠት አንድም ሰው በሌለበት”

አማካሪዎች
ድርጊትን በምሪት ለማከናወን ሃሳብ የሚሰጡ ሰዎች

ይከናወናል
“እቅድ ይከናወናል”

Proverbs 15:23

ተገቢ የሆነ መልስ
“የሚስማማ መልስ” ወይም “ተገቢ መልስ”

የጊዜው ቃል ምንኛ መልካም ነው
ይህ ቃለ አጋኖ በጊዜው የተነገረ ቃል በጣም መልካም እንደሆነ አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰው በትክክለኛው ጊዜ የሚናገረው ቃል በጣም መልካም ነው”

የሕይወት መንገድ ወደ ላይ ይመራቸዋል ... በታች ካለው ከሲኦል
ጸሐፊው ወደ ሕይወት ስለሚወስደው የሕይወት ዘይቤን ወደላይ ወደ ሕይወት የሚሄድ መንገድ እንደሆነ፤ ወደ ሞት ስለሚወስደው የሕይወት ዘይቤን ደግሞ ወደታች ወደ ሙታን መኖርያ የሚመራ መንገድ እንደሆነ አድርጎ ተናግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 15:25

ቤት
ይህ የሰውን ቤተሰብ፣ ንብረት እና ሀብት የሚወክል ተዛምዶአዊ ዘይቤ ነው። (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

የደግነት ቃሎች ንጹህ ናቸው
“ደግ ቃሎች ንጹህ ናቸው” ወይም “ደስ የሚያሰኙ ቃሎች ንጹህ ናቸው”

Proverbs 15:27

ጽድቅን የሚያደርግ ሰው ልብ መልስ ከመስጠቱ በፊት አጥብቆ ያስባል
እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል ለአእምሮ እና ለሃሳብ ምትክ ስም ነው። ይህ የሚያስብን ሰው ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጽድቅን የሚያደርግ ሰው መልስ ከመስጠቱ በፊት ምን መናገር እንዳለበት አጥብቆ ያስባል” (ምትክ ስም እና ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

የክፉ ሰዎች አፍ ክፋትን ሁሉ ያጎርፋል
ጸሐፊው ስለ ክፉ ሰዎች አፍ ሲናገር አፋቸው የፈሳሽ መያዣ ዕቃ እንደሆነና፣ ስለ ክፋት ሲናገር ደግሞ እነርሱን የሞላቸው ፈሳሽ እንደሆነ አድርጎ ተናግሮታል። “አፍ” የሚለው ቃል የሚናገሩትን ሰዎች የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ሰዎች ሁልጊዜ ክፉ ነገሮችን ይናገራሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የክፉ ሰዎች አፍ ክፋትን ሁሉ ያጎርፋል
በአንተ ቋንቋ እነዚህን ቃላቶች ሁሉ በነጠላ ቁጥር ወይም በብዙ ቁጥር መተርጎም የበለጠ የተለመደ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የክፉ ሰው አፍ ክፋቱን ሁሉ ያጎርፋል” ወይም “የክፉ ሰዎች አፎች ክፋታቸውን ሁሉ ያጎርፋሉ”

Proverbs 15:29

እግዚአብሔር ከክፉ ሰዎች እጅግ ሩቅ ነው
ጸሀፊው ክፉ ሰዎች በአካል እግዚአብሔር ከእነርሱ እጅግ በጣም ሩቅ እንደሆነ ያህል እነርሱን እንደማይሰማቸው አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ክፉ ሰዎችን አይሰማም” ወይም “እግዚአብሔር ለክፉ ሰዎች መልስ አይሰጥም“ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የዓይን ብርሃን
ጸሀፊው በአንድ ሰው ፊት የሚታየውን ደስታ ሲገልጽ የሰውየው ዓይኖች ብርሃን እንደሚፈነጥቁ አድርጎ ተናግሮታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ደስ የሚያሰኝ መግለጫ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለልብ ደስታን ያመጣል
“ልብ” የሚለው ቃል ሰውየውን ይወክላል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ፍልቅልቅ ፊት ያለው ሰው ደስተኛ ይሆናል ወይም 2) ፍልቅልቅ ፊት ያለው ሰው ሲመለከቱ ሌሎች ሰዎች ደስተኛ ይሆናሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰውን ደስተኛ እንዲሆን ያደርጋል” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

መልካም ወሬ ለሰውነት ጤና ነው
እዚህ ላይ “ሰውነት” የሚለው ቃል ሰውየውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “መልካም ወሬ መስማት ሰውን ጥሩ ስሜት እንዲሰማው ያደርጋል” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 15:31

በጥበበኛ ሰዎች መካከል ትቆያለህ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ሰዎች አንተ ጥበበኛ ሰው እንደሆንህ ያስቡሃል ወይም 2) ከጥበበኛ ሰዎች ጋር በመሆንህ ምክንያት ደስተኛ ትሆናለህ።

እርምትን ያደምጣል
“እርምት” የሚለው ቃል በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሌሎች ሲያርሙት ያደምጣል” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 15:33

የእግዚአብሔር ፍርሃት ጥበብን ያስተምራል
“ፍርሃት” እና “ጥበብ” የሚሉት ቃላቶች በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ሰው እግዚአብሔርን ሲፈራ ጥበበኛ መሆንን ይማራል” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን መፍራት
ይህንን በምሳሌ 1:7 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

ትህትና ከክብር በፊት ትመጣለች
አንድ ሰው እግዚአብሔር እርሱን ከማክበሩ በፊት ያ ሰው በመጀመርያ ትህትናን መማር አለበት ማለት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 16

1 የልብ እቅድ የሰው ነው፣ መልስ ግን ከእግዚአብሔር አንደበት ይመጣል። 2 የአንድ ሰው መንገዶች ሁሉ ለእርሱ ንጹህ ሆኖ ይታየዋል፣ እግዚአብሔር ግን መንፈስን ይመዝናል። 3 ስራህን ለእግዚአብሔር አስረክብ፣ እቅድህም ይሳካልሃል። 4 እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ለራሱ ዓላማ ፈጠረ፣ ሃጢአተኛውንም እንኳ ለክፉ ቀን። 5 እግዚአብሔር እምቢተኛ ልብ ያለውን ሁሉ ይጠላል፣ ተባብረው ቢቆሙም ከቅጣት አያመልጡም። 6 በኪዳን በተመሰረተ ታማኝነትና እውነተኛነት ኃጢአት ስርየት ያገኛል፣ እግዚአብሔርን በመፍራትም ሰዎች ከክፋት ይርቃሉ። 7 የሰው መንገዶቹ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙ ሲሆኑ፣ እግዚአብሔር የዚያን ሰው ጠላቶች እንኳ ከእርሱ ጋር በሰላም እንዲኖሩ ያደርጋል። 8 ፍትህ በጎደለው መንገድ ከተገኘ በርካታ ገቢ ይልቅ፣ በጽድቅ የተገኘ ጥቂት ገቢ ይሻላል። 9 ሰው በልቡ መንገዱን ያቅዳል፣ እግዚአብሔር ግን እርምጃውን ያቀናለታል። 10 ውሳኔ በንጉስ ከንፈሮች ላይ አለ፣ በፍርድም ጊዜ አፉ በማታለል አይናገርም። 11 እውነተኛ ሚዛን ከእግዚአብሔር ይመጣል፤ በከረጢትም ውስጥ ያሉት መመዘኛዎች ሁሉ የእርሱ ስራዎች ናቸው። 12 ነገስታት ክፋትን ሲሰሩ፣ እርሱ አጸያፊ ነገር ነው፣ ዙፋን የሚጸናው ጽድቅን በማድረግ ነውና። 13 ንጉስ እውነትን በሚናገሩ ከንፈሮች ደስ ይለዋል፣ በግልጽነት የሚናገረውንም ሰው ይወደዋል። 14 የንጉስ ቁጣ የሞት መልእክተኛ ነው፣ ጥበበኛ ሰው ግን የንጉሱን ቁጣ ያበርዳል። 15 የንጉስ ፊት ሲያበራ ሕይወት አለ፣ መልካም ፈቃዱም የጸደይን ዝናብ እንደሚያመጣ ደመና ነው። 16 ከወርቅ ይልቅ ጥበብን ማግኘት ምንኛ ይበልጣል። ከብርም ይልቅ ማስተዋል ይመረጣል። 17 የጻድቃን መንገድ ከክፋት ትርቃለች፤ ሕይወቱን የሚጠብቅም መንገዱን ይጠብቃል። 18 ትዕቢት ከጥፋት በፊት ትመጣለች፣ ኩሩ መንፈስም ከውድቀት በፊት። 19 ከትዕቢተኞች ጋር ዝርፊያን ከመካፈል ይልቅ ከድሆች ጋር ራስን ዝቅ ማድረግ ይሻላል። 20 የተማሩትን የሚያሰላስሉ ሰዎች መልካምን ነገር ያገኛሉ፣ በእግዚአብሔር የሚታመኑም ደስተኛ ይሆናሉ። 21 በልቡ ጥበበኛ የሆነ ሰው አስተዋይ ይባላል፣ ጣፋጭ ንግግርም የማስተማር ችሎታን ያዳብራል። 22 ገንዘብ ላደረገው ማስተዋል የሕይወት ምንጭ ነው፣ የሞኞች ቅጣት ግን ሞኝነታቸው ነው። 23 የጥበበኛ ሰው ልብ ለአፉ ትምህርትን ይሰጠዋል፣ ለከንፈሮቹም ትምህርትን ይጨምራል። 24 ደስ የሚያሰኙ ቃላት የማር ወለላ ናቸው፣ ለነፍስ የሚጣፍጡ አጥንትንም የሚፈውሱ ናቸው። 25 ለሰው ትክክል የሚመስል መንገድ አለ፣ ፍጻሜው ግን ወደ ሞት የሚወስድ ነው። 26 የሰራተኛ ረሃብ ለእርሱ ይሰራል፤ ረሃቡም ያነሳሳዋል። 27 የማይረባ ሰው ክፋትን ይቆፍራል፣ ንግግሩም እንደሚያቃጥል እሳት ነው። 28 ጠማማ ሰው ጥልን ያነሳሳል፣ ሐሜትም የቅርብ ወዳጆችን ያለያያል። 29 በጥባጭ ሰው ጎረቤቱን ይዋሻል፣ መልካም ወዳልሆነ መንገድም ይመራዋል። 30 በዓይኑ የሚጠቅስ ሰው ጠማማ ነገሮችን ያስባል፤ ከንፈሮቻቸውን የሚነክሱም ክፋትን ይጎትታሉ። 31 ሽበት የክብር ዘውድ ነው፤ በጽድቅ መንገድ በመኖር ይገኛል። 32 ጦረኛ ከመሆን ይልቅ ትዕግስተኛ መሆን ይሻላል፣ መንፈሱን የሚገዛም ከተማን ከሚቆጣጠር ይልቅ ይበረታል። 33 እጣ በጉያ ይጣላል፣ ውሳኔው ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።

Proverbs 16:1

የልብ እቅድ የሰው ነው

እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል የሰውን አእምሮና ሃሳብ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰው እቅዱን የሚያቅደው በአእምሮው ውስጥ ነው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

መልስ ከእግዚአብሔር አንደበት ይመጣል

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) እግዚአብሔር ለሰው እቅድ መልስ ይናገራል፤ ይህ ተለዋጭ ዜይቤ ሲሆን የሰውን የእቅዱ ውጤት የሚወስነው እግዚአብሔር ነው የሚል ትርጉም አለው ወይም 2) ሰው ስላቀደው እቅድ ቃሎች እንዲናገር እግዚአብሔር ያስችለዋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መልስ ከእግዚአብሔር አንደበት

ለንግግሩ አጽንዖት ለመስጠት ሰውየው በራሱ “አንደበት” ተወክሏል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ የሚናገረው መልስ” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

የአንድ ሰው መንገዶች በሙሉ በራሱ ዓይኖች ንጹህ ናቸው

ዓይኖች መመልከትን ይወክላሉ፤ መመልከት ደግሞ ሃሳብን ወይም ውሳኔን ይወክላል። ጸሐፊው ሰው ስለሚሰራው ስራ ሲናገር ያ ሰው በመንገድ ወደታች እየተጓዘ እደነበር አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰው የሚሰራው ስራ ሁሉ ንጹህ እንደሆነ ያስባል” ወይም “ሰው የሚሰራው ስራ ሁሉ ንጹህ እንደሆነ ይገምታል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር መንፈስን ይመዝናል

እዚህ ላይ “መንፈስ” የሚለው ቃል የሰዎችን ምኞትና ተነሳስቶት ይወክላል። ጸሐፊው እግዚአብሔር የሰውን ምኞትና ተነሳስቶት እንደሚለይና እንደሚያውቅ ሲናገር እርሱ የዚያን ሰው መንፈስ እንደሚመዝን አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የሰውን ተነሳስቶት ይመዝናል” (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 16:3

ሃጢአተኛውንም እንኳ ለክፉ ቀን

ይህ በሀረግ የተገለጸ የቃላት አገባብ የመጣው ምናልባት ከቀደመው ሀረግ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ ኃጢአተኛውን እንኳ ለመከራ ቀን አዘጋጅቶታል” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 16:5

እምቢተኛ ልብ ያለውን ሁሉ

እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል ሰውየውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እምቢተኛ የሆነ ማንኛውም ሰው” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ሳይቀጡ አይቀሩም

በዚህ ሀረግ ውስጥ ያሉት ሁለት አሉታዊ አገላለጾች አዎንታዊውን አጥብቀው አጽንዖት ይሰጣሉ። ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር በእርግጠኝነት ይቀጣቸዋል” (ምፀት እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በኪዳን በተመሰረተ ታማኝነትና እውነተኛነት ኃጢአት ስርየት ያገኛል

“ታማኝነት” እና “እውነተኛነት” የሚሉት ረቂቅ ስሞች “ታማኝ” እና “እውነተኛ” ተብለው ሊገለጹ ይችላሉ። ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ለኪዳኑ ታማኝና እውነተኛ ስለሆነ የሰዎችን ኃጢአት ይቅር ይላል” ወይም 2) አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ለኪዳኑ ታማኝና እውነተኛ ለሆኑ ሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ይላል” (ረቂቅ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰዎች ከክፋት ይርቃሉ

ጸሐፊው ክፉ ነገሮችን መስራት ስላቆሙ ሰዎች ሲናገር ከክፋት እንደራቁ አድርጎ ገልጾቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች ክፋትን መስራት አቁመዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Proverbs 16:7

ያደርጋል
“እግዚአብሔር ያደርጋል”

ትልቅ ገቢ
“ብዙ ገንዘብ ማግኘት”

ፍትህ በጎደለው
“ክፉ ስራ በመስራት”

Proverbs 16:9

ሰው በልቡ መንገዱን ያቅዳል
እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል የሰውን አእምሮ እና ሀሳብ ይወክላል። ጸሐፊው ሰውየው ስለሚሰራው ስራ ሲናገር ያ ሰው በመንገድ እየተጓዘ እደነበር አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰው የሚሰራውን ስራ በአእምሮው ውስጥ ያቅዳል” (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር እርምጃውን ያቀናለታል
ጸሐፊው የሰውን የእቅዱ ውጤት የሚወስነው እግዚአብሔር እንደሆነ ሲገልጽ እግዚአብሔር ለዚያ ሰው ወዴት መሄድ እንዳለበት እየነገረው እንደነበር አድርጎ ገልጾታል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ማስተዋል የተሞሉ ውሳኔዎች በንጉስ ከንፈሮች ላይ አሉ
እዚህ ላይ “ከንፈሮች” የሚለው ቃል ንጉስ ለተናገረው ንግግር ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ንጉስ የሚናገረው ንግግር ማስተዋል የተሞላበት ነው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በፍርድም ጊዜ አፉ በማታለል አይናገርም።
“አፍ” የሚለው ቃል ንጉሱን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ ሲፈርድ በማታለል ሊናገር አይገባውም” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 16:11

እውነተኛ ሚዛን ከእግዚአብሔር ይመጣል
የንግድ ስራ ስንሰራ እግዚአብሔር ፍትህና ትክክለኛነት እንድናደርግ ይጠብቅብናል። አታላይ ሰዎች ከሚገባው በላይ ለማትረፍ ሲሉ ሲገዙና ሲሸጡ በሚዛናቸው ከባድ ወይም ቀላል ክብደት ይጠቀማሉ። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በቦርሳ ውስጥ ያሉት መመዘኛዎች ሁሉ የእርሱ ስራዎች ናቸው
ነጋዴዎች መመዘኛዎቻቸውን በቦርሳ ውስጥ ይይዛሉ። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) እግዚአብሔር እያንዳንዱ ክብደት ምን ያህል ሊመዝን እንደሚገባ ወስኗል ወይም 2) እግዚአብሔር ነጋዴ በሚጠቀምበት እያንዳንዱ ክብደት ግድ ይለዋል።

ጸያፍ ነገር ነው
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይህ ሰዎች የሚጸየፉት ነገር ነው” ወይም “ይህ እግዚአብሔር የሚጸየፈው ነገር ነው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ዙፋን የሚጸናው ጽድቅን በማድረግ ነውና
እዚህ ላይ “ዙፋን” የሚለው ቃል የንጉሱን አመራር የሚወክል ነው። ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ንጉስ አመራሩን የሚመሰርተው ጽድቅን በማድረግ ነው” (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 16:13

እውነትን የሚናገሩ ከንፈሮች
እዚህ ላይ “ከንፈሮች” የሚወክሉት የሚናገረውን ሰው ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እውነትን የሚናገር ሰው” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

የንጉስ ቁጣ የሞት መልእክተኛ ነው
ጸሐፊው አንድን ሰው እንዲገደል ያደረገ ንጉስን ሲገልጽ የንጉሱ ቁጣ አንድን ሰው ለመግደል የላከው መልእክተኛ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “የተቆጣ ንጉስ ሰዎች እንዲገደሉ ማድረግ ይችላል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 16:15

አጠቃላይ መረጃ፡-
ቁጥር 15 ከቁጥር 14 ጋር ያነጻጽራል።

የንጉስ ፊት ሲያበራ ሕይወት አለ
ጸሐፊው በንጉሱ ፊት የሚገለጠውን የደስተኝት ስሜት ፊቱ ብርሃን እንደሚፈነጥቅ አድርጎ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ንጉሱ ደስተኛ ሲሆን ሰዎች በሕይወት ይኖራሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መልካም ፈቃዱም የጸደይን ዝናብ እንደሚያመጣ ደመና ነው
ጸሐፊው ንጉሱ ለአንድ ሰው ሞገሱን ማሳየቱ የተዘራ እህል ማደግ እንዲችል ዝናብ እንዲመጣ ከሚያደርግ ደመና ጋር አነጻጽሮታል። ሁለቱም ለሚቀበላቸው በረከት ያስገኙላቸዋል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከወርቅ ይልቅ ጥበብን ማግኘት ምንኛ ይበልጣል
ይህ ቃለ አጋኖ ጥበብ ማግኘት ወርቅ ከማግኘት እጅግ በጣም እንደሚበልጥ አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበብን ማግኘት ወርቅ ከማግኘት እጅግ በጣም ይበልጣል” (ቃለ አጋኖ የሚለውን ይመልከቱ)

ማስተዋል ማግኘት ከብር ይልቅ ሊመረጥ ይገባዋል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰው ማስተዋልን ማግኘት ብርን ከማግኘት ይልቅ እጅግ አብልጦ ሊመርጥ ይገባዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 16:17

የጻድቃን መንገድ
ጸሐፊው የጻድቃንን የሕይወት ዘይቤ እንቅፋት የሌለበት በሚገባ የተገነባ መንገድ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጻድቃን የሚኖሩት የጽድቅ መንገድ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከክፋት ትርቃለች
ጸሐፊው ክፋትን መተው ወይም ክፉ ነገሮችን አለማድረግን ከክፋት መራቅ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፋትን ከማድረግ ይጠብቃቸዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ኩሩ መንፈስም
እዚህ ላይ “መንፈስ” የሚለው ቃል የሰውየውን መለካትና ባህርይ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ግትር አመለካከት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ውድቀት
“ጥፋት” ወይም “አለመሳካት”

Proverbs 16:19

ምርኮ
በጦርነት ጊዜ የተወሰዱ እቃዎች

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የተማሩት ነገር
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አንድ ሰው ያስተማራቸው ነገር” ወይም “የተማሩት ነገር” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 16:21

በልቡ ጥበበኛ የሆነ ሰው አስተዋይ ይባላል
ይህ ሰው አስተዋይ ሰው የሚል መልካም ስም ይኖረዋል። ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰዎች በልቡ ጥበበኛ የሆነውን ሰው አስተዋይ ይሉታል” ወይም “በልቡ ጥበበኛ የሆነ ሰው አስተዋይ ሰው የሚል መልካም ስም ይኖረዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በልቡ ጥበበኛ የሆነው ሰው
እዚህ ላይ ልብ አእምሮንና ሃሳብን የይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ጥበበኛ የሆነ ሰው” ወይም “በአስተሳሰቡ ጥበበኛ የሆነ ሰው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ጣፋጭ ንግግር
ጸሐፊው ስለ መልካም ወይም ደስ የሚያሰኝ ንግግር ሲናገር ጣፋጭ ጣዕም እንዳለው ነገር አድርጎ አቅርቦታል። አማራጭ ትርጉም፦ “መልካም ንግግር” ወይም “ደስ የሚያሰኝ ንግግር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ማስተዋል የሕይወት ምንጭ ነው
ጸሐፊው ስለ “ማስተዋል” ሲናር ያለማቋረጥ የሚፈስ ውኃ እንዳለውና ከእርሱ ለሚጠጡ ሰዎች በሕይወት እንዲኖሩ እንደሚያደርግ ምንጭ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ማስተዋል እንደሚፈስ የሕይወት ውኃ ምንጭ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 16:23

የጥበበኛ ሰው ልብ ... ይሰጣል
እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል አእምሮንና ሃሳብን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የጥበበኛ ሰው ሃሳብ ... ይሰጣል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ለአፉ ትምህርትን ይሰጠዋል
እዚህ ላይ “አፍ” የሚለው ቃል ለንግግር ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ንግግሩን ጥበብ የተሞላ ያደርገዋል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ለከንፈሮች
እዚህ ላይ “ከንፈሮች” የሚለው ቃል ለንግግር ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ለሚናገረው ነገር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ደስ የሚያሰኙ ቃላት የማር ወለላ ናቸው
ጸሐፊው ደስ የሚያሰኙ ቃላት ለሰሚዎች ደስታን ማምጣት የሚችሉ እንደሆኑ ሲናገር እነዚህ ቃላት አዲስ ማር የሚያንጠባጥቡ የማር እሸት እነደሆኑ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ደስ የሚያሰኙ ቃላት እንደ ማር እሸት ናቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለነፍስ የሚጣፍጡ
“ነፍስ” ለሚለው ቃል ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች፦ 1) ይህ የሰውን ውስጣዊ ምኞትና ደስታ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰውን ደስ ለማሰኘት በጣም ጣፋጭ ናቸው” ወይም 2) “ጉሮሮ” ማለት ሊሆን ይችላል፣ ይህ ደግሞ የሰውን ምላስና ጣዕም የመለየት ችሎታውን የሚያሳይ ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ለሰው ጣፋጭ ነው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ለአጥንቶችም ፈውስ ናቸው
እዚህ ላይ “አጥንቶች” የሚለው ቃል የሰውን አካል የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ለሰውነትም ፈውስ ናቸው” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 16:25

ለሰው ትክክል የሚመስል መንገድ አለ
ጸሐፊው ስለ ሰው ጠባይ ወይም ባህርይ ሲናገር ሰውየው የሚጓዝበት መንገድ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰው የሚኖርበት መንገድ ትክክል እንደሆነ ያስባል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ፍጻሜው ግን ወደ ሞት የሚወስድ ነው
“ፍጻሜው” የሚለው ቃል የሚያያዘው በቀደመው መስመር ላይ ከተጠቀሰው “መንገድ” ከሚለው ጋር ነው።

የሰራተኛ ረሃብ ለእርሱ ይሰራል
ጸሐፊው ስለ ረሃብ ሲናገር የቀን ሰራተኛውን ወክሎ የሚሰራ ሰው እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። ይህም የሚሰራ ሰው ለመብላት ባለው ፍላጎት ይነሳሳል ለማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰራተኛ የምግብ ፍላጎቱን ለማርካት ይሰራል” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ረሃቡም ያነሳሳዋል
ጸሐፊው ስለ “ረሃብ” ሲናገር ስራውን በሚገባ እንዲሰራ ሰራተኛውን የሚያነሳሳ ሰው እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፦ “እርሱ ስራውን ሳያቋርጥ ይሰራል ምክንያቱም ርቦታል” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 16:27

የማይረባ ሰው ክፋትን ይቆፍራል
ጸሐፊው ሌሎች ሰዎችን ለመጉዳት መንገድ ለመፈለግ ስለሚሞክር ሰው ሲናገር ያ ሰው አንድ የተቀበረ ነገር ለመፈለግ መሬት እየቆፈረ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፦ “የማይረባ ሰው አንድ ነገር ለማግኘት መሬት እንደሚቆፍር እንደዚሁ ክፋትን ይፈልጋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የማይረባ
“የማይጠቅም” ወይም “ክፉ”

ክፋት
መከራ

ንግግሩ እንደሚያቃጥል እሳት ነው
ጸሐፊው የዚህ ሰው ቃላት ሌሎች ሰዎችን የሚጎዳበት መንገድ እሳት ቁሳቁሶችን ከሚያቃጥልበት መንገድ ጋር አነጻጽሮታል። አማራጭ ትርጉም፦ “እሳት የሚነካውን ማንኛውንም ነገር እንደሚያቃጥል ሁሉ እንደዚሁ ይህ ሰው በቃሎቹ ሰዎችን ይጎዳል” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አሉባልተኛ
ሀሜት የሚናገር ወይም ወሬ የሚያሰራጭ ሰው

Proverbs 16:29

በጥባጭ ሰው ጎረቤቱን ይዋሻል
ይህ ሰው ብጥብጥ በመፍጠር ስራው ጎረቤቱ ከእርሱ ጋር እንዲተባበር ለማድረግ ጎረቤቱን ይዋሸዋል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በጥባጭ ሰው ጎረቤቱን ያባብላል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የብጥብጥ ሰው
“በጥባጭ ሰው” ወይም “የሚረብሽ ሰው”

መልካም ወዳልሆነ መንገድ ይመራዋል
ጸሐፊው የሰውየውን ድርጊት ሰውየው የሚጓዝበት መንገድ እንደሆኑ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፦ “መልካም ያልሆኑ ነገሮችን በማድረግ ያገኘዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መልካም ያልሆነ መንገድ
ጸሐፊው ይህ መንገድ ምን ያህል መጥፎ እንደሆነ አጽንዖት ለመስጠት ዝቅ አድርጎ የሚያሳይ መግለጫ ተጠቅሟል። አማራጭ ትርጉም፦ “በጣም መጥፎ መንገድ” ወይም “አስከፊ መንገድ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በዓይኑ የሚጠቅስ ሰው ... ከንፈሮቻቸውን የሚነክሱ
እነዚህ ሁለቱም ሰዎች ዕቅዳቸውን ለሌች በስውር ለማስተላለፍ ሊጠቀሙባቸው የሚችሉአቸው የፊት እንቅስቃሴዎች ናቸው።

ክፋትን ይጎትታሉ
“ክፉ ነገሮችን ያደርጋሉ”

Proverbs 16:31

ሽበት የክብር ዘውድ ነው
ጸሐፊው ስለ ሽበት ሲናገር ዘውድ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። “ሽበት” ለእርጅና ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ሽበት ለማውጣት የደረሰና ለረጅም ዘመን የኖረ ሰው በራሱ ላይ የክብር ዘውድ እንደጫነ ሰው ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ይገኛል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰው ያገኘዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

መንፈሱን የሚገዛ ሰው
ጸሐፊው ግልፍተኝነቱንና ስሜቱን ስሚቆጣጠር ሰው ሲናገር ንጉስ ሕዝቡን እንደሚመራ እንደዚሁ መንፈሱን እንደሚመራ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ግልፍተኝነቱን የሚቆጣጠር ሰው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 16:33

እጣ በጉያ ይጣላል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰው እጣውን በጉያው ይጥላል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ውሳኔው ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) እጣ እንዴት እንደሚወድቅ የሚወስነው እግዚአብሔር ነው ወይም 2) ምን እንደሚሆን የሚወስነው እጣው ሳይሆን እግዚአብሔር ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 17

1 ጥል ባለበት ግብዛ ከሞላበት ቤት ይልቅ ሰላም ባለበት ደረቅ ቁራሽ ዳቦ ይሻላል። **2** ጥበበኛ ባርያ አስነዋሪ ስራ የሚሰራውን ልጅ ይገዛል፣ ከወንድማማቾችም መካከል እንደ አንዱ ውርስን ይካፈላል። **3** ማቅለጫ ለብር ነው እቶንም ለወርቅ ነው፣ እግዚአብሔር ግን ልብን ያነጥራል። **4** ክፋትን የሚያደርግ ሰው ክፋትን የሚናገሩ ሰዎች ምክር ይሰማል፤ ውሸታምም ክፉ ነገሮች የሚያወሩ ሰዎችን ያዳምጣል። **5** በድሃ የሚቀልድ ሰው ፈጣሪውን ይሰድባል፣ በጥፋትም የሚደሰት ከቅጣት አያመልጥም። **6** የልጅ ልጆች ለሽማግሌዎች ዘውድ ናቸው፣ ወላጆችም ለልጆቻቸው ክብር ናቸው። **7** መልካም ንግግር ለሞኝ ሰው አይስማማውም፤ ውሸታም ከንፈሮችም ለንጉሳውያን አይመቹም። **8** ጉቦ ለሰጪው እንደ አስማት ድንጋይ ነው፤ በሄደበት ስፍራ ሁሉ ስኬትን ያገኛል። **9** በደልን የሚሸፍን ፍቅርን ይፈልጋል፣ ነገርን የሚደጋግም ግን የቅርብ ወዳጆችን ይለያያል። **10** መቶ ግርፋት ወደ ሞኝ ጠልቆ ከሚገባ ይልቅ ተግሳጽ ወደ አስተዋይ ሰው ጠልቆ ይገባል። **11** ክፉ ሰው አመጽን ይፈልጋል፣ ጨካኝ መልዕክተኛም ወደ እርሱ ይላክበታል። **12** ሞኝን በሞኝነቱ ከመገናኘት ይልቅ ግልገሎቿ የተነጠቀችን ድብ መገናኘት ይሻላል። **13** አንድ ሰው በበጎ ፈንታ ክፋትን ሲመልስ፣ ክፋት ከቤቱ ፈጽሞ አይርቅም። **14** የጠብ መጀመርያ በሁሉም ስፍራ ውኃ እንደሚለቅ ሰው ነው፣ ስለዚህ ከመበርታቱ በፊት ከግጭት ራቅ። **15** ክፉ ሰዎችን ነጻ የሚለቅም ሆነ ጽድቅን የሚያደርጉትን ደግሞ የሚኮንን ማንኛውም ሰው፣ ሁለቱም በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠሉ ናቸው። **16** ሞኝ ጥበብን ለመማር የማይችል ሆኖ ሳለ፣ ጥበብን ለመማር ለምን ገንዘብ ይከፍላል? **17** ጓደኛ በዘመኑ ሁሉ ወዳጅ ነው፣ ወንድምም ለክፉ ቀን ይወለዳል። **18** አእምሮ የጎደለው ሰው ቃል በመግባት ግዴታ ውስጥ ይገባል፣ ለጎረቤቱም ብድር ዋስ ይሆናል። **19** ጠብ የሚወድ ኃጢአትን ይወዳል፤ መግቢያ በሩን እጅግ ከፍ አድርጎ የሚሰራ አጥንቶች እንዲሰበሩ ያደርጋል። **20** ጠማማ ልብ ያለው ሰው አንዳችም መልካም ነገር አያገኝም፤ ጠማማ ምላስ ያለውም ወደ መከራ ይወድቃል። **21** ሞኝን የወለደ ሐዘንን ወደራሱ ያመጣል፣ የሞኝም አባት ደስታን አያገኝም። **22** ደስተኛ ልብ ጥሩ መድሃኒት ነው፣ የተሰበረ መንፈስ ግን አጥንትን ያደርቃል። **23** ክፉ ሰው የፍትህን መንገድ ለማጣመም በሚስጥር ጉቦን ይቀበላል። **24** አስተዋይ ሰው ፊቱን ወደ ጥበብ ያዘነብላል፣ የሞኝ አይኖች ግን ወደ ምድር ዳርቻ ያዘነብላሉ። **25** ሞኝ ልጅ ለአባቱ ሐዘን ነው፣ ለወለደችውም እናቱ ምሬትን ያመጣል። **26** ጽድቅ የሚያደርግን ሰው መቅጣት በፍጹም መልካም አይደለም፤ በሐቀኝነት የሚሄዱትን የተከበሩ ሰዎችን መግረፍም መልካም አይደለም። **27** እውቀት ያለው ሰው ጥቂት ቃላትን ይናገራል፣ አስተዋይ ሰውም ለቁጣ የዘገየ ነው። **28** ሞኝ እንኳ ዝም ሲል ጥበበኛ እንደሆነ ይታሰባል፤ አፉንም ዘግቶ ዝም ሲል፣ እንደ ምሁር ይቆጠራል።

Proverbs 17:1

ጸጥታ ያለበት
እዚህ ላይ ”ጸጥታ” የሚወክለው “ሰላም” ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰላም ያለበት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ጥል ባለበት ግብዣ ከሞላበት ቤት ይልቅ
“ከሞላበት” የሚለው ቃል ከፊተኛው ሀረግ መረዳት ይቻላል። ሊደጋገሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥል ባለበት ትልቅ ድግስ ከሞላበት ቤት ይልቅ” ወይም “ጥል ባለበት ትልቅ ድግስ በሞላበት ቤት ከመገኘት ይልቅ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 17:3

ማቅለጫ ለብር ነው እቶንም ለወርቅ ነው
ይህ ወርቅና ብር እንዴት እንደሚነጥሩ የሚያሳይ ነው። ብረት መቅለጥ እንዲችልና በውስጡ ያለው ቆሻሻ እንዲወገድ የሚነጥረው እጅግ በጣም ሀይለኛ በሆነ የሙቀት ሃይል በማሞቅ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ማቅለጫ ብር ለማንጠር ይጠቅማል፣ እቶን ደግሞ ወርቅ ለማንጠር ይጠቅማል” ። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ማቅለጫ
በጣም ከፍተኛ በሆነ ሙቀት ብረት የሚቀልጥበት ማሰሮ ነው።

እግዚአብሔር ልብን ያነጥራል
ይህ የሰዎች ልብ ብረት እንደሆነ ያህል እነርሱ ክፉ እና ሞኝ መሆንን እንዲያቆሙ በሕይወታቸው ያለውን ማንኛውንም ቆሻሻ ለማስወገድ ሲል እግዚአብሔር ሰዎችን በማንጠር እንደሚፈትናቸው አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የሰዎችን ልብ ይፈትናል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉ ከንፈሮች
እዚህ ላይ “ከንፈሮች” የሚለው ቃል በሚከተሉት መንገድ ሊተረጎም ይችላል፡- 1) ለሰው ተዛምዶአዊ ነው ወይም 2) ከእነዚህ ከንፈሮች ለሚወጡት ቃላት ደግሞ ምትክ ስም ነው አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ሰው” ወይም “ክፉ ንግግር” (ተዛምዶአዊ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ጆሮውን ይሰጣል
ይህ ፈሊጥ ሲሆን “ማዳመጥ” የሚል ትርጉም አለው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥፋት የሚያደርስ ምላስ
“ምላስ” የሚለው ቃል እንደሚከተለው ሊተረጎም ይችላል፡- 1) ለሰውየው ተዛምዶአዊ ዘይቤ ነው ወይም 2) ምላሱ ለሚፈጥረው ቃላት ደግሞ ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አጥፊ ሰው” ወይም “አጥፊ ንግግር” (ተዛምዶአዊ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 17:5

ድሃr
ይህ ድሃ ሰዎችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ድሃ የሆኑ ሰዎች” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ፈጣሪውን
ይህ እግዚአብሔርን የሚያመለክት ስም ነው። ይህ እንደ ግስ ሊጻፍ የሚችል ረቂቅ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የፈጠረው” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በጥፋት
ይህ የሌሎችን ጥፋት የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በሌሎች ጥፋት” ወይም “በሌሎች ሰዎች መከራ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ዘውድ ናቸው
ይህ የትልልቅ ሰዎች የልጅ ልጆች ለእነርሱ የክብር ምልክት ስለመሆናቸው ሲናገር የልጅ ልጆቻቸው ዘውድ እንደሆኑ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ኩራትና ክብር ያመጡላቸዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሽማግሌዎች
ይህ ትልልቅ ሰዎችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ትልልቅ የሆኑ ሰዎች” ወይም “ትልልቅ ሰዎች” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 17:7

ልብ የሚነካ ንግግር
“መልካም ንግግር” ወይም “እጅግ በጣም ጥሩ ንግግር”

ውሸታም ከንፈሮች ለንጉሳውያን አይመቹም
ይህ የሚዋሹ ሰዎች ውሸትን የሚናገሩት የእነርሱ “ከንፈሮች” እንደሆኑ አድርጎ ይገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለንጉሳውያን ቤተሰብ መዋሸት ይልቁንም ደግሞ መልካም ኤደለም” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ጉቦ ለሰጪው እንደ አስማት ድንጋይ ነው
ይህ ጉቦ መስጠትን ከአስማት ድንጋይ ወይም ከክታብ ጋር በማነጻጸር ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጉቦ ለሰጪው እንደ አስማት ድንጋይ ይሰራል” ወይም “ጉቦ ለሰጪው እንደ አስማት ይሰራል” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በሄደበት ስፍራ ሁሉ
እዚህ ላይ “በሄደበት” የሚለው ሰው የሚሰራውን የተለያዩ ነገሮች ያመለክታል። በተለይ ደግሞ ይህ አንድ ሰው በጉቦ ምክንያት የሚሰራቸውን የተለያዩ ነገሮችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በሚሰራው ስራ ሁሉ” ወይም “ጉቦ በመስጠት ለመስራት የሚሞክረውን ማንኛውንም ነገር“ (ፈሊጥ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 17:9

ጥቃት
እርሱን የሚጎዳው ድርጊት ወይም ቃል

ነገርን የሚደጋግም
ይህ አንድ ጓደኛ የተጎዳበትን ወይም የተናደደበትን ያለፈ ሁኔታን አሁን ጎትቶ ማምጣትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ያለፈ ጉዳትን የሚደግም ሰው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የቅርብ ወዳጆችን ይለያያል
“ሰዎች የቅርብ ጓደኞች መሆናቸውን እንዲያቆሙ” ወይም “የቅርብ ጓደኞች እርስ በርስ መዋደዳቸውን እንዲያቆሙ”

መቶ ግርፋት በሞኝ ጠልቆ ከሚገባ ይልቅ ተግሣጽ በአስተዋይ ሰው ጠልቆ ወደ ልቡ ይገባል።
ይህ ተግሳጽ በአስተዋይ ሰው ውስጥ እንዴት ውጤት እንደሚያመጣ እና ግርፋት ደግሞ በሞኝ ሰው ውስጥ እንዴት ውጤት እንደሚያመጣ ያነጻጽራል። ይህ በእነዚህ ሰዎች ውስጥ የሚመጣው ውጤት ወደ እነርሱ ውስጥ ጠልቆ በሚገባበት መጠን ሊለካ እንደሚችል አደርጎ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “መቶ ግርፋት በሞኝ ውስጥ ከሚያመጣው ውጤት ይልቅ ተግሣጽ በአስተዋይ ሰው ውስጥ የበለጠ ውጤት አለው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አስተዋይ ሰው
“ጥሩ ግንዛቤ ያለው ሰው። “ማስተዋል” የሚለው ቃል በግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሚያስተውል ሰው” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

መቶ ግርፋት ይገባል
“መቶ የግርፋት ምት ይገባል”

Proverbs 17:11

አመጽን ይፈልጋል
“አመጽ” የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለማመጽ ይፈልጋል” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ጨካኝ መልዕክተኛም ወደ እርሱ ይላክበታል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጨካኝ መልዕክተኛም ወደ እርሱ ይመጣበታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እርሱ ይላክበታል
ወደ አንድ ሰው “ይላክበታል” የሚለው እርሱን ለመጉዳት ይላካል ለማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱን ለመጉዳት ይላካል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ግልገሎቿ የተነጠቀች ድብ
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ግልገሎቿ የጠፉባት ድብ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በሞኝነቱ
“ሞኝነት” የሚለው ቃል በቅጽል ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሞኝ ተግባር የሚፈጽም” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 17:13

ክፋት ከቤቱ ፈጽሞ አይርቅም
እዚህ ላይ “ክፉ” የሰውየውን ቤት የማይለቅ ሰው እንደሆነ ተደርጎ ተገልፏል። “ቤት” የሚለው ቃል በቁሙ መኖርያ በሚለው ሊተረጎም ይችላል ነገር ግን ለቤተሰቡም ምትክ ስም ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በእርሱና በቤተሰቡ ላይ መጥፎ ነገሮች መፈጸም ይቀጥላል” ወይም “መጥፎ ነገሮች በእርሱና በቤተሰቡ ላይ ከመፈጸም በፍጹም አይከለከልም” (ሰውኛ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የጠብ መጀመርያ በሁሉም ስፍራ ውኃ እንደሚለቅ ሰው ነው
ይህ ጠብ በቀላሉ እንዴት እንደሚሰራጭ እና የፈሰሰ ውኃ በሁሉም ስፍራ እንዴት እንደሚፈስ ያነጻጽራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠብ መጀመር ውኃን እንደ መልቀቅና በሁሉም ስፍራ እንዲፈስ እንደማድረግ ነው” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይበረታል
“ይጀምራል” ወይም “ይነሳል”

Proverbs 17:15

ክፉ ሰዎችን ነጻ የሚለቅም ሆነ ጽድቅን የሚያደርጉትን ደግሞ የሚኮንን ማንኛውም ሰው
“ክፉ ሰዎችን ነጻ የሚለቅ ሰው እና ጽድቅን የሚያደርጉትን የሚኮንን ሰው”

በነጻ የለቀቀ
ተገቢ የሚያስመስል፣ ወንጀለኛ እንዳልሆነ የሚያውጅ

ሞኝ ጥበብን ለመማር የማይችል ሆኖ ሳለ፣ ጥበብን ለመማር ለምን ገንዘብ ይከፍላል?
ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ ሞኝ ይህን ማድረግ እንደሌለበት አጽንዖት ይሰጣል። ይህ ጥያቄ እንደ አረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሞኝ ስለ ጥበብ ለመማር ገንዘብ ሊከፍል አይገባውም ምክንያቱም ጥበብን ለመማር ችሎታ የለውም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Proverbs 17:17

ወንድምም ለመከራ ቀን ይወለዳል
የወንድም አንዱ ዓላማ ወንድሙን ወይም እህቱን በመከራ ጊዜ ለመርዳት አብሮ ለመሆን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ወንድም ለመከራ ጊዜ በዚያ ይገኛል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አእምሮ የጎደለው
“ጥሩ ግንዛቤ የሌለው”

ግዴታ የሚያስገባ ቃልኪዳን
ይህ መጠበቅ ያለባቸውና ቃል ለገባው ሰው ደግሞ ብዙ ጊዜ ሸክም የሚሆኑ ቃል ኪዳኖችን የሚያመለክት ነው።

Proverbs 17:19

አጥንቶች እንዲሰበሩ ያደርጋል
ይህ አንድ ሰው ወደ መግቢያ በር ይሄድና አጥንት ምናልባትም የእግር አጥንት ይሰብራል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- ““አንድ ሰው እንዲሄድና የእግራቸውን አጥንት እንዲሰብር በእርግጠኝት ያደርጋል” ወይም “አንድ ሰው እንዲሄድና ራሱን እንዲጎዳ በእርግጠኝነት ያደርጋል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ጠማማ ልብ ያለው ሰው
“ልብ” የሰውን ስሜት፣ አመለካከትና ተነሳስቶት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አታላይ ሰው” ወይም “የማይታመን ሰው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ጠማማ ምላስ አለው
“ምላስ” የሰውየውን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በጠማማነት ይናገራል” ወይም “በክፋት ይናገራል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

አደጋ ውስጥ ይወድቃል
“መከራ ውስጥ ይወድቃል” ወደ አንድ ነገር “መውደቅ” ማለት ወደዚያ ሁኔታ ውስጥ መግባት ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አደጋ ያገኘዋል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 17:21

ደስተኛ ልብ ጥሩ መድሃኒት ነው
ይህ ስለ ደስተኛ ልብ ሲናገር እንደ ጥሩ መድኃኒት እንደሆነ ገልጾታል ምክንያቱም እድትፈወስ ያደርግሃል። አማራጭ ትርጉም፡- “ደስተኛ ልብ እድትፈወስ እንደሚያደርግ እንደ ጥሩ መድኃኒት ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ደስተኛ ልብ
“ልብ” የሰውን ስሜት፣ አመለካከትና ተነሳስቶት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ደስተኛ መሆን” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የተሰበረ መንፈስ
እዚህ ላይ “መንፈስ” የሰውን ጥልቅ ስሜትና ስሜታዊ ሁኔታ ይወክላል። የተሰበረ መንፈስ ደካማ ስሜታዊ ሁኔታን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ድብርት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

አጥንትን ያደርቃል
የሰው አጥንት የሰውየውን አካላዊ ጤንነትና ጥንካሬ ይወክላል። የሰው አጥንት ከደረቀ በጣም የታመሙና ጤንነት የሌላቸው ናቸው ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰውን በሽተኛና ደካማ ያደርጋሉ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 17:23

የፍትህን መንገድ ለማጣመም
“ፍትህ እንዳይተገበር ማጣመም” ወይም “ፍትህን ማጣመም”

ፊቱን ወደ ጥበብ ያዘነብላል
ይህ የሚናገረው ጥበብን ከማድረግ አቅጣጫ ስለ ሰውየው ትኩረት ሲሆን ያ ሰው ጥበብን ይመለከት እንደነበር አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በጥበብ ማከናወን ላይ ትኩረት ያደርጋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሞኝ አይኖች ... ናቸው
ይህ ሞኝን በዓይኖቹ አማካይነት የሚያመለክት ሲሆን በምን ላይ ትኩረት እንደሚያደርግ አጽንዖት ለመስጠት የቀረበ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሞኝ ... ነው” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

የምድር መጨረሻ
ይህ ተግባራዊነት ስለሌላቸው የሞኝ ሕልሞች የሚናገር ሲሆን ተጨባጭነት እንደሌላቸው አጽንዖት ለመስጠት የምድር መጨረሻ ላይ እንደሆኑ አድርጎ ገልጾአቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከእርሱ ዘንድ የምድር መጨረሻ ያህል የራቁትን ነገሮች ለማግኘት ጥረት ያደርጋል” ወይም “በማይሆንና በማይቻል ነገር ላይ ትኩረት ያደርጋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 17:25

ሞኝ ልጅ ለአባቱ ሐዘን ነው
ይህ ለአባቱ የሐዘን ምክንያት ስለሆነ ልጅ የሚናገር ሲሆን ልጁ ራሱ “ሐዘን” እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሞኝ ልጅ ለአባቱ ሐዘን ያመጣል”

ሞኝ ልጅ ... ለወለደችውም እናቱ ምሬትን ያመጣል
ይህ ለእናቱ የምሬት ምክንያት ስለሆነ ልጅ የሚናገር ሲሆን ልጁ ራሱ “ምሬት” እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሞኝ ልጅ ... ለእናቱ ምሬትን ያመጣል”

ለወለደችው
“እርሱን ለወለደችው”

ምሬት
ስሜታዊ ጉዳት፣ ሐዘን

በፍጹም መልካም አይደለም ... መልካምም አይደለም
እነዚህ ሃሳቦች በአዎንታዊ መንገድ ሊገለጹ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ይህ ሁልጊዜ ስህተት ነው .... ይህ ሁልጊዜም ክፉ ነው” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

ጻድቅ ሰው
የዚህ ሌላኛው ተቀበይነት ያለው ትርጉም የሚከተለው ነው፡- “ንጹህ ሰው” ባልሰራው ወንጀል ሌሎች እንደፈጸመ አድርገው የሚወነጅሉት ማንኛውም ሰው ነው።

መግረፍ
በአሰቃቂ ሁኔታ መምታት

በሐቀኝት የሚሄድ
“ሐቀኝነት” የሚለው ቃል “ታማኝ” በሚለው ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ታማኝ የሆኑ” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Proverbs 17:27

ጥቂት ቃላትን ይናገራል
ይህ የሚናገርበትን መንገድ የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በጥቂት ቃላት ይናገራል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሞኝ እንኳ እንደ ጥበበኛ ይቆጠራል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች ሞኝ እንኳ ጥበበኛ እንደሆነ ያስባሉ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

አፉንም ዘግቶ ዝም ሲል
ይህ አይናገርም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አይናገርም” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ምሁር እንደሆነ ይታሰባል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች ምሁር እንደሆነ ያስቡታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 18

1 ራሱን ከሰው የሚለይ የራሱን ምኞት ይፈልጋል፣ ትክክለኛውንም ፍርድ ሁሉ ይቃወማል። **2** ሞኝ ሰው በማስተዋል ደስታን አያገኝም፣ በራሱ ልብ ውስጥ ያለውን ነገር በመግለጥ እንጂ። **3** ክፉ ሰው ሲመጣ፣ ንቀት ከእፍረትና ከስድብ ጋር አብረውት ይመጣሉ። **4** ከሰው አፍ የሚወጡ ቃላት ጥልቅ ውሃ ናቸው፤ የጥበብ ምንጭም የሚፈስ ወንዝ ነው። **5** ለክፉው ማድላት፣ ጽድቅን ለሚያደርጉም ፍትህን ማጉደል መልካም አይደለም። **6** የሞኝ ከንፈሮች ጥልን ያመጡበታል፣ አፉም በትርን ትጠራለች። **7** የሞኝ አፍ መጥፊያው ነው፣ በከንፈሮቹም ራሱን ወጥመድ ውስጥ ይጥላል። **8** የሐሜት ቃላት እንደ ጣፋጭ ጉርሻ ናቸው፣ ወደ ሰውነት ውስጣዊ ክፍሎች ጠልቀው ይገባሉ። **9** በስራው ችላ የሚልም ብዙውን የአጥፊ ሰው ወንድም ነው። **10** የእግዚአብሔር ስም ጽኑ ግንብ ነው፤ ጽድቅን የሚያደርግ ሰው ወደ እርሱ ሮጦ ይድናል። **11** የባለጸጋ ሐብት የእርሱ የተመሸገ ከተማ ነው፣ ሃሳቡም እንደ ረዥም ግንብ ነው። **12** ከውድቀቱ በፊት የሰው ልብ ትዕቢተኛ ይሆናል፣ ትህትና ግን ክብርን ቀድሞ ይመጣል። **13** ከማድመጡ በፊት የሚመልስ ሰው ሞኝነትና ዕፍረት ይሆንበታል። **14** የሰው መንፈስ ሕመምን ትታገሳለች፣ የተሰበረን መንፈስ ግን ማን ሊሸከም ይችላል? **15** የአስተዋይ ሰው ልብ እውቀትን ያገኛል፣ የጠቢብም ጆሮ ይፈልገዋል። **16** የሰው ስጦታ መንገዱን ትከፍትለታለች በተከበሩም ሰዎች ፊት ታቆመዋለች። **17** ወደ ፍርድ ቀድሞ በመምጣት ጉዳዩን የሚያሰማ ጻድቅ ይመስላል፣ ይህ ግን የሚሆነው ተቀናቃኙ መጥቶ እስከሚጠይቀው ድረስ ነው። **18** እጣ ማውጣት ክርክርን ያቆማል፣ ሃይለኛ ጠላቶችንም ትለያለች። **19** የተበደለ ወንድምን መርታት ጠንካራ ከተማን ከማሸነፍ ይልቅ በጣም የከበደ ነው፣ ጠብም እንደ ግንብ ብረት ነው። **20** የሰው ሆድ ከአፉ ፍሬ ይሞላል፤ በንፈሮቹም ምርት ይረካል። **21** ሞትና ሕይወት በምላስ ላይ ናቸው፣ የሚወዱትም ፍሬዋን ይበላሉ። **22** ሚስትን ያገኘ መልካምን ነገር አግኝቷል፣ ከእግዚአብሔርም ዘንድ ሞገስን አግኝቷል። **23** ድሃ ሰው ምህረትን ይለምናል፣ ሃብታም ግን በማመናጨቅ ይመልሳል። **24** ብዙ ጓደኞች ያለው ሰው በእነርሱ አማካኝነት ወደ ጥፋት ይመጣል፣ ከወንድም የቀረበ ጓደኛ ግን አለ።

Proverbs 18:1

ራሱን ይለያል
“ከሌሎች ሰዎች ራሱን ይለያል”

ትክክለኛውንም ፍርድ ሁሉ ይቃወማል
ይህ ትክክለኛውን ፍርድ ስለሚቃወም ሰው የሚናገር ሲሆን “ትክክለኛ ፍርድ” ከእርሱ ጋር እንደሚዋጋ ሰው ተደርጎ ተገልጿል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ ከትክክለኛ ፍርድ ሁሉ ጋር አይስማማም” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ትክክለኛውን ፍርድ
“መልካም ፍርድ” ወይም “ጥበብ የተሞላበት ምርጫ”

ሞኝ ሰው በማስተዋል ደስታን አያገኝም፣ ... እንጂ
“ሞኝ ሰው ስለ ማስተዋል ፈጽሞ አይገደውም፣ ነገር ግን ስለ ... እንጂ” ይህ ሞኝ “ማስተዋልን” የደስታ ተቃራኒ እንደሆነ ያስባል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሞኝ ማስተዋል ይጠላል እናም ደስታን ብቻ ይፈልጋል” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

በራሱ ልብ ውስጥ ያለውን ነገር በመግለጥ እንጂ
ይህ ማለት ሞኝ ሰው ደስታ የሚያገኘው ለሌሎች ሰዎች በልቡ ምን እንደሚሰማውና ምን እንደሚመኝ በመንገር ብቻ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን ለሌሎች በልቡ ውስጥ ያለውን በመናገር ብቻ ነው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በልቡ ውሰጥ ያለውን
በሰው ልብ ውስጥ ያለው ነገር የሰውየውን ሃሳብና ስሜት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሚያስበውን” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 18:3

ንቀት ከእፍረትና ከስድብ ጋር አብረውት ይመጣሉ
እዚህ ላይ “ንቀት፣” “እፍረት፣” እና “ስድብ” ክፉ ሰውን የሚያጅቡት ሰዎች እንደሆኑ ተደርገው ተገልጸዋል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ሰዎች ለክፉ ሰው ንቀት ያሳያሉ ከዚህ የተነሳ እፍረትና ስድብ እንዲሰማው ያደርጋሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች ስለ እርሱ ከእፍረትና ከስድብ ጋር ንቀት ይሰማቸዋል” ወይም 2) ክፉ ሰው ለሌሎች ንቀት ያሳያል ከዚህ የተነሳ እፍረትና ስድብ እንዲሰማቸው ያደርጋል” አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ ለሌሎች ሰዎች ያለውን ንቀቱን ያሳያል ከዚህ የተነሳ እፍረትና ስድብ እንዲሰማቸው ያደርጋል” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እፍረትና ስድብ
እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ሁለቱም በአንድ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት ክፉው ሰው ወይም ደግሞ ሌሎች ሰዎች የተሰማቸውን “እፍረት” አጽንዖት ለመስጠት ነው። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ከሰው አፍ የሚወጡ ቃላት ጥልቅ ውሃ ናቸው፤ የጥበብ ምንጭም የሚፈስ ወንዝ ነው
እነዚህ ሁለት መስመሮች ተመሳሳይ ናቸው፣ በመጀመርያው መስመር ላይ ያለው ሰው ጥበበኛ እንደሆነ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከጥበበኛ ሰው የሚወጡ ቃላት ጥልቅ ውኃ ናቸው፤ የጥበብ ምንጭም የሚፈስ ወንዝ ነው” (ትይዩነት እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከሰው አፍ የሚወጡ ቃላት ጥልቅ ውሃ ናቸው
ይህ የሚናገረው የጥበበኛ ሰው ቃላት ጥልቅ እውቀት የሚገለጥባቸው እንደሆኑ ሲሆን በጣም ጥልቅና እንደ ጥልቅ ውኃ የጠለቁ እንደሆኑ ተደርገው ተገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከሰው አፍ የሚወጡ ቃላት እንደ ጥልቅ ውኃ የጠለቁ ናቸው” ወይም “ከሰው አፍ የሚወጡ ቃላት ጥልቅና እውቀት ያለባቸው ናቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው አፍ
እዚህ ላይ ለተናገረው ነገር አጽንዖት ለመስጠት ሲባል ሰውየው በአፉ ተወክሏል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሰው” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

የጥበብ ምንጭም የሚፈስ ወንዝ ነው
ይህ የሚናገረው የጥበብ ምንጭ እንደሚፈልቅ ምንጭ የተትረፈረፈ እንደሆነ ነው። የምንጭ መፍለቅ እንደሚፈስ ወንዝ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “የጥበብ ምንጭ ከሚፈልቅ ምንጭ እንደሚፈስ ውኃ የተትረፈረፈ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 18:5

ጽድቅን ለሚያደርጉ ... መልካም አይደለም
እነዚህ ሀረጎች በአዎንታዊ ቅርጽ ሊጻፉ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ለክፉ ሰው የሚገባውን ዋጋ መክፈል፣ ለጻድቃን ደግሞ ፍትሃዊ መሆን መልካም ነው (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የሞኝ ከንፈሮች ያመጣሉ
እዚህ ላይ ንግግሩ ላይ አጽንዖት ለመስጠት ሲባል ሞኝ “በከንፈሮቹ” ተወክሏል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሞኝ የተናገረው ያመጣል” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ያመጣል
“ምክንያት ይሆናል”

አፉም በትርን ትጠራለች
ይህ የሚናገረው ስለ ሞኝ ሲሆን ሰዎች እንዲመቱት የሚያደርግ ነገሮችን መናገሩ እርሱ ራሱ ሰዎቹ እንዲመቱት እንደጋበዛቸው ተደርጎ ተገልጿል። አማራጭ ትርጉም፦ “አፉ ሰዎች እንዲመቱት ያደርጋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አፉ
እዚህ ላይ “አፍ” የሞኝ ሰው ንግግርን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የተናገረው ንግግር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 18:7

የሞኝ አፍ ... ከከንፈሮቹ ጋር
እነዚህ ሁለቱም ሞኝ የሚናገረውን ነገር ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ሞኝ የተናገረው .... በተናገረው ነገር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

መጥፊያው ነው
“ያጠፋዋል”

ራሱን ወጥመድ ውስጥ ይጥላል
በራሱ ላይ ችግርና መከራ ስለሚያመጣ ሰው ሲናገር ሰው እንስሳን እንደሚያጠምድ እንዲሁ ይህ ሰው ራሱን እንዳጠመደ አድርጎ አቅርቦታል። አማራጭ ትርጉም፦ “በራሱ ላይ ችግር ያመጣል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሐሜት ቃላት እንደ ጣፋጭ ጉርሻ ናቸው
ይህ የሐሜት ቃላት ለማድመጥ በጣም ደስ የሚያሰኙ ስለመሆናቸው ሲናገር ለመብል የሚመች በጣም ጣፋጭ ምግብ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፦ “የሀሜት ቃላት ለመስማት ደስ የሚሉ ናቸው” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሐሜት ቃላት
ይህ የሐሜተኛ ሰው ንግግርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሐሜተኛ ሰው የተናገራቸው ቃላት” (ባለቤትነት የሚለውን ይመልከቱ)

ጉርሻ
ትንሽ የምግብ ጥቅልል

ወደ ሰውነት ውስጣዊ ክፍሎች ጠልቀው ይገባሉ
ይህ ወደ ሰው ውስጣዊ ክፍል ገብተው አስተሳሰቡን ስለሚያበላሹ የሐሜት ቃላት የሚናገር ሲሆን ወደ ሰውየው ሆድ ውስጥ እንደሚገባ ምግብ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ወደ ሰው አእምሮ ገብተው አስተሳሰቡን ያበላሻሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 18:9

በስራው ችላ የሚል የአጥፊ ሰው ወንድም ነው
በስራው ችላ የሚል ሰው ከአጥፊ ጋር ተመሳሳይ እንደሆኑና በእርግጠኝነት ሁለቱም የሚመሳሰሉ እንደሆኑ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “በጣም ይገናኛሉ” ወይም “በጣም ተመሳሳይ ናቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ችላ ባይ ነው
“ሰነፍ ነው” ወይም “ፍላጎት የለውም”

በጣም አጥፊ የሆነ
“ሁሉንም ነገር የሚያጠፋ” ወይም “ሁልጊዜ አጥፊ የሆነ”

የእግዚአብሔር ስም ጽኑ ግንብ ነው
ይህ ሃሳብ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚጠብቅ የሚናገር ሲሆን የእርሱ ሕዝብ የሚጠለሉበት ጠንካራ ግንብ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር እንደ ጠንካራ ግንብ ይጠብቃል” ወይም “እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደ ጠንካራ ግንብ ይጠብቃቸዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ስም
እዚህ ላይ እግዚአብሔር በስሙ ተወክሏል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ጻድቅ
ይህ ጽድቅ የሚያደርጉ ሰዎችን ይወክላል።፡ አማራጭ ትርጉም፦ “ጻድቃን የሆኑ ሰዎች” ወይም “ጻድቅ ሰዎች” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ጻድቅ ወደ እርሱ ሮጦ ይድናል
ይህ ከእግዚአብሔር ደህንነትን ስለሚፈልጉና እግዚአብሔር ስለሚጠብቃቸው ሰዎች የሚናገር ሲሆን እግዚአብሔርን እነዚህ ሰዎች ደህንነትን ለማግኘት ወደ እርሱ የሚሮጡበት ጠንካራ ግንብ እንደሆነ አድርጎ ገለጾታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ወደ እርሱ ይሮጣሉ ደግሞም ደህንነትን ያገኛሉ” ወይም “እርሱን ይፈልጉታል ደግሞም ደህንነትን ያገኛሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 18:11

የባለጸጋ ሐብት የእርሱ የተመሸገ ከተማ ነው
ይህ በብልጽግናው ስለሚታመን ሀብታም ሰው የሚናገር ሲሆን ሀብቱ እርሱን የሚጠብቀው የተመሸገ ግንብ እንደሆነ ተደርጎ ተገልጿል። አማራጭ ትርጉም፦ “ከተማ በተመሸገ ግንብ ላይ እንደሚደገፍ ሁሉ ባለጸጋ ሰው ደግሞ በሀብቱ ላይ ይደገፋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ባለጸጋ
ይህህ ሀብታም ሰዎችን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሀብታም ሰው” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

የተመሸገ ከተማ
በግድግዳና በግንብ የተከበበች ጠንካራ ከለላ ያላት ከተማ

ሃሳቡም እንደ ረዥም ግንብ ነው
ይህ የሚናገረው ከፍ ያለ ግንብ በከተማ ውስጥ ያሉትን በደህንነት እንዲጠበቁ እንደሚያደርግ ሁሉ ሀብቱ በደህንነት ይጠብቀኛል ብሎ ስለሚያምን ባለጸጋ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ከፍ እንዳለ ግንብ ሀብቱ ይጠብቀኛል ብሎ ያስባል” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከውድቀቱ በፊት የሰው ልብ ትዕቢተኛ ይሆናል
“በመጀመርያ የሰው ልብ በትዕቢት ይሞላል፣ ነገር ግን ወዲያውኑ ውድቀቱ ይመጣል”

ውድቀት
ይህ በሰው መልካም ስምና ጤንነት ላይ የሚመጣውን ውድቀት የሚያመለክት ነው።

የሰው ልብ
እዚህ ላይ ለሃሳቡና ለስሜቱ አጽንዖት ለመስጠት ሰው በልቡ ተተወክሏል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰው” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ትህትና ግን ክብርን ቀድሞ ይመጣል
“ትህትና” የሚለው ቃል እንደ ቅጽል ሊገለጽ ይችላል፣ “ክብር” የሚለው ደግሞ እንደ ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰው ከመከበሩ በፊት ትሁት ሊሆን ይገባዋል” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 18:13

ሞኝነትና ዕፍረት ይሆንበታል
“ሞኝነት” እና “እፍረት” የሚሉት ረቂቅ ቃላት እንደ ቅጽል ሊገለጹ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ሞኝነቱ ነው፣ ሊያፍር ይገባዋል” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው መንፈስ ሕመምን ትታገሳለች
እዚህ ላይ ሰው ለአስተሳሰቡ አጽንዖት ለመስጠት በመንፈሱ ተወክሏል። አማራጭ ትርጉም፡- “ተስፋ ያለው ሰው ሕመም ይታገሳል” ወይም “ሰው በውስጣዊ ማንነቱ ተስፋ የተሞላ ከሆነ ከመታመም ይድናል” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

የተሰበረን መንፈስ ግን ማን ሊሸከም ይችላል?
ጥቂቶች ብቻ ሊሸከሙት ይችላ የሚል መልስ እንደሚሰጥ በማሰብ ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን የተሰበረ መንፈስ መሸከም በጣም ከባድ ነው” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የተሰበረ መንፈስ
ይህ በድብርት መውደቅን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በድብርት ውስጥ መሆን” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 18:15

የአስተዋይ ሰው ልብ ያገኛል
እዚህ ላይ ለፍላጎቱ አጽንዖት ለመስጠት አስተዋይ ሰው በልቡ ተወክሏል። አማራጭ ትርጉም፡- “አስተዋይ ሰው ለማግኘት ይፈልጋል” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

አስተዋይ ሰው
ይህ አስተዋይ የሆኑ ሰዎችን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አስተዋይ የሆኑ ሰዎች” ወይም “አስተዋይ ሰዎች” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ያገኛል
“ያተርፋል” ወይም “ይጨምራል”

የጠቢብም ጆሮ ይፈልገዋል
እዚህ ላይ ጥበበኛ ሰው ለመስማት የሚፈልገውን ነገር አጽንዖት ለመስጠት ሲባል ጆሮ በሚለው ተወክሏል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠቢብ ስለዚያ ነገር ለመማር ይፈልጋል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ጠቢብ
ይህ ጠቢብ የሆኑ ሰዎችን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠቢብ የሆኑ ሰዎች” ወይም “ጠቢብ ሰዎች” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ይፈልገዋል
እዚህ ላይ “ይፈልገዋል” የሚለው ቃል የሚወክለው “እውቀትን” ነው።

መንገዱን ትከፍትለታለች
እዚህ ላይ “መንገዱን ትከፍትለታለች” እድል ይፈጥርለታል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ለእርሱ እድል ይፈጥርለታል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ፊት ታቆመዋለች
ይህ አንድን ሰው ለማየት ይፈቀድለታል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ያግኘው” ወይም “ከእርሱ ጋር ይተዋወቅ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 18:17

ጉዳዩን ለማሰማት የመጀመርያ ነው
ይህ ተቀናቃኙ ቀርቦ ጉዳዩን ከማሰማቱ በፊት ቀድሞ ጉዳዩን የሚያሰማውን ሰው የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ጉዳዩን ለማሰማት የመጀመርያው ሰው” ወይም “ጉዳዩን ያሰማ የመጀመርያው ሰው” (ደረጃ የሚያሳይ እና የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

እጣውን ማውጣት
“እጣ ማውጣት”

ሃይለኛ ጠላቶችንም ትለያለች
ይህ በክርክር ምክንያት ክፉኛ የሚጣሉ ሰዎችን ያመለክታል። ሲለያዩ በክርክራቸው ምክንያት መጣላታቸውን ያቆማሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ተቀናቃኞች በክርክራቸው ምክንያት መጣላታቸውን እንዲያቆሙ ያደርጋል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 18:19

የተበደለ ወንድምን መርታት ጠንካራ ከተማን ከማሸነፍ ይልቅ በጣም የከበደ ነው
ይህ ጠንካራ ከተማን በጦርነት ማሸነፍ በጣም አስቸጋሪ ከመሆኑ ጋር በማነጻጸር ከበደልከው ወንድምህ ጋር ሰላም መፍጠር በጣም አስቸጋሪ እንደሆነ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ወንድምህን ከበደልከው እንደገና ከእርሱ ጋር ሰላምን ለመፍጠር መንገድ መፈለግ ከተማን ለማሸነፍ ጦርነት ከመግጠም በላይ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጠብ እንደ ግንብ ብረት ነው
ይህ የሚናገረው የግንብ ብረት መስበር በጣም አስቸጋሪ ከመሆኑ ጋር በማነጻጸር ለጠብ መፍትሔ መስጠትም አስቸጋሪ መሆኑን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠብን ማስቆም የግንብ ብረትን እንደመስበር በጣም አስቸጋሪ ነው” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ግንብ
የተመሸገ ስፍራ

የሰው ሆድ ከአፉ ፍሬ ይሞላል፤ ከንፈሩም ከሚያፈራው ይጠግባል
ሁለቱ መስመሮች አንድ ዓይነት ትርጉም አላቸው፤ ጥቅም ላይ የዋሉት ደግሞ ለተነገረው ነገር አጽንዖት ለመስጠት ነው። ሁለቱን በአንድ ላይ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰው የሚናገረው መልካም ነገር ባመጣው ውጤት ይረካል” (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

የአፉ ፍሬ
ይህ ሰው ስለሚናገረው መልካም ነገሮች የሚናገር ሲሆን ከአፉ የሚወጣ ፍሬ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበብ የተሞላ ንግግሩ” ወይም “መልካም ቃላቶቹ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሆዱ ይሞላል
ይህ በተናገሩት ነገር ምክንያት በመጣው ውጤት ስለጠገቡ ወይም ስለረኩ ሰዎች የሚናገር ሲሆን እንደበሉና እንደጠገቡ አድርጉ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ረክቷል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የከንፈሮቹ ምርት
ይህ ሰው ስለሚናገረው መልካም ነገር የሚናገር ሲሆን ከዛፉ ላይ እንደሚሰበሰብ ፍሬ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእርሱ ጥበብ የተሞላ ንግግር” ወይም “የእርሱ መልካም ቃላት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ይረካል
“እርሱ ይደሰታል”

Proverbs 18:21

ሞትና ሕይወት በምላስ ላይ ናቸው
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ምላስ ወደ ሕይወት ወይም ወደ ሞት ሊመራ ይችላል” ወይም “ሰዎች የሚናገሩት ንግግር ወደ ሕይወት ወይም ወደ ሞት ሊመራ ይችላል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በምላስ ... ምላስ ይወዳሉ
እዚህ ላይ “ምላስ” ንግግርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰዎች በሚናገሩት ... መናገር ይወዳሉ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ፍሬዋን ይበላሉ
ይህ የሚናገረው በተናገረው ንግግር ምክንያት ያስከተለውን ውጤት ስለተቀበለ ሰው ሲሆን ውጤቱን እንደሚቀበለው ፍሬ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ውጤቱን ይቀበላል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 18:23

ብዙ ጓደኞች ያለው ሰው በእነርሱ አማካኝነት ወደ ጥፋት ይመጣል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ብዙ ጓደኞች ያሉት ሰው እነርሱ ጥፋት ያመጡበታል” ወይም “ብዙ ጓደኞች ያሉት ጓደኞቹ ያጠፉታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የሚጠጋጋ
“የበለጠ ታማኝ ነው” ወይም “ታማኝ ሆኖ ይቆያል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 19

1 በንግግሩ ጠማማ ከሆነና ከሞኝ ሰው ይልቅ በሃቀኝነት የሚራመድ ድሃ ሰው ይሻላል። **2** ደግሞም ያለ እውቀት አንድን ነገር መመኘት መልካም አይደለም፣ በችኮላ የሚሮጥም መንገዱን ይስታል። **3** የሰው ጅልነት ሕይወቱን ያበላሸዋል፣ ልቡም በእግዚአብሔር ላይ ይቆጣል። **4** ሐብት ብዙ ጓደኞችን ይጨምራል፣ ድሃ ሰው ግን ከወዳጆቹ የተለየ ነው። **5** ሐሰተኛ ምስክር ሳይቀጣ አይታለፍም፣ ውሸትንም የሚያሰራጭ አያመልጥም። **6** ብዙዎች ከቸር ሰው ውለታን ይጠይቃሉ፣ ስጦታን ለሚሰጥም ሁሉ ጓደኛ ይሆነዋል። **7** ድሃ ሰው ወንድሞቹ ሁሉ ይጠሉታል፤ ከእርሱ ብዙ ርቀው የሚገኙ ጓደኞቹማ ምንኛ ይጠሉት! ወደ እነርሱ ይጣራል፣ እነርሱ ግን አይገኙም። **8** ጥበብን የሚያገኝ ሕይወቱን ይወዳል፤ ማስተዋልንም ገንዘቡ ያደረገ መልካም ነገር ያገኛል። **9** ሐሰተኛ ምስክር ሳይቀጣ አይቀርም፣ ውሸትን የሚያሰራጭ ግን ይጠፋል። **10** ለሞኝ በቅንጦት መኖር አይገባውም፣ ባርያ መሳፍንትን ሲገዛ ደግሞ ምንኛ የከፋ ይሆን። **11** ጠቢብ አእምሮ ሰውን ታጋሽ ያደርገዋል፣ በደልንም መተው ክብር ይሆንለታል። **12** የንጉስ ቁጣ እንደ ጎረምሳ አንበሳ ግሳት ነው፣ በፊቱ ሞገስ ማግኘት ግን ሳር ላይ እንዳለ ጤዛ ነው። **13** ሞኝ ልጅ ለአባቱ መጥፊያ ነው፣ ጨቅጫቃ ሚስትም እንደማያቋርጥ የውኃ ነጠብጣብ ናት። **14** ቤትና ሐብት ከወላጆች ይወረሳል፣ ጠንቃቃ ሚስት ግን ከእግዚአብሔር ናት። **15** ስንፍና ሰውን ወደ እንቅልፍ ይጥለዋል፣ ለመስራት የማይፈቅድ ግን ይራባል። **16** ትእዛዛትን የሚያከብር ሕይወቱን ይጠብቃል፣ ስለ መንገዶቹ የማያስብ ሰው ግን ይሞታል። **17** ለድሃ ቸር የሆነ ሰው ለእግዚአብሔር ያበድራል፣ ለሰራውም ቸርነት መልሶ ይከፍለዋል። **18** ተስፋ ሳለ ልጅህን ስርዓት አስይዘው፣ ሞቱንም እየተመኘህ ዝም ብለህ አትየው። **19** ንዴቱን መቆጣጠር የማይችል ሰው ቅጣቱን ማግኘት አለበት፤ ብታድነውም ለሁለተኛ ጊዜ ማድረግህ አይቀርም። **20** ምክርን ስማ ተግሳጽንም ተቀበል፣ በሕይወትህ መጨረሻ ጥበበኛ እንድትሆን። **21** በሰው ልብ ብዙ እቅዶች አሉ፣ የሚፈጸመው ግን የእግዚአብሔር ሃሳብ ነው። **22** ሰው የሚመኘው ታማኝ ሆኖ መገኘት ነው፣ ድሃም ሰው ከውሸታም ይሻላል። **23** እግዚአብሔርን ማክበር ሰዎችን ወደ ሕይወት ይመራል፤ እንዲህ ያለውም ሰው ይረካል በመከራም አይጎዳም። **24** ሰነፍ ሰው እጁን በሳህን ውስጥ ያጠልቃል፤ ወደ አፉም እንኳ እንደገና መልሶ አያመጣውም። **25** ፌዘኛን ብትመታው፣ ያልተማረው ጠንቃቃ ይሆናል፤ አስተዋዩን ብታርመው እውቀትን ያገኛል። **26** ከአባቱ የሚሰርቅ እናቱንም የሚያሳድድ ዕፍረትና ውርደት የሚያመጣ ልጅ ነው። **27** ልጄ ሆይ፣ ተግሳጽን አልሰማ ብትል፣ ከእውቀት ቃሎች ትስታለህ። **28** ምግባረ ብልሹ ምስክር በፍትህ ላይ ያፌዛል፣ የክፉ ሰው አፍም በደልን ይውጣል። **29** ለፌዘኞች ፍርድ፣ ለሞኞች ጀርባም ጅራፍ ተዘጋጅቶላቸዋል።

Proverbs 19:1

ድሃ ሰው ይሻላል
“ድሃ ሰው መሆን ይሻላል”

በሃቀኝነት የሚራመድ ሰው
ይህ ፈሊጥ ነው። እዚህ ላይ መራመድ መኖርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በሐቀኝነቱ የሚኖር ሰው” ወይም “እውነተኛ ሕይወት የሚኖር ሰው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

በንግግሩ ጠማማ ነው
“ንግግር” የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በጠማማነት ይናገራል” ወይም “በክፉ መንገድ ይናገራል” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ያለ እውቀት አንድን ነገር መመኘት
ይህ የሚያመለክተው አንድን ነገር በትክክለኛ መንገድ እንዴት መስራት እንዳለባቸው እውቀት ሳይኖራቸው ለመስራት የሚሞክሩ ሰዎችን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የምትሰራው ነገር ምን እንደሆነ ሳታውቅ በትጋት መስራት” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ

በችኮላ የሚሮጥም መንገዱን ይስታል
ይህ የሚናገረው ነገሮችን በጣም በችኮላ ስለሚሰራና ስህተትን ስለሚፈጽም ሰው ሲሆን ይህን ሰው በችኮላ እንደሚሮጥና መንገዱን እንደሚስት ሰው አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በጣም በችኮላ የሚሰራ ሰው ስህተት ይፈጽማል” ወይም “በጣም በችኮላ የሚሰራ ሰው የተሳሳተ ምርጫ ያደርጋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 19:3

ልቡም ይቆጣል
እዚህ ላይ ስሜቱን አጽንዖት ለመስጠት ሲባል ሰው “በልቡ” ተወክሏል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይቆጣል” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ሐብት ብዙ ጓደኞችን ይጨምራል
ይህ ሀብታም ሰው ብዙ ጓደኞች ይኖረዋል ምክንያቱም ሀብት ሰውን ይስባል ማለት ነው። የዚህ ሃሳብ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሀብታም ሰዎች በቀላሉ ብዙ ጓደኞች ያገኛሉ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ

ድሃ ሰው ግን ከወዳጆቹ የተለየ ነው
ድሃ ሰው በድህነቱ ምክንያት ከብዙ ጓደኞቹ ይለያል። የዚህ ሃሳብ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ድህነት ሰው ጓደኞቹን እንዲያጣ ያደርጋል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 19:5

ሐሰተኛ ምስክር ሳይቀጣ አይታለፍም
ይህ በአዎንታዊና በገቢር ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ ሐሰተኛ ምስክርን በእርግጠኝነት ይቀጡታል” (ጥምር አሉታ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ውሸትንም የሚያሰራጭ ሰው አያመልጥም
እርሱ ይያዛል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ ውሸት የሚያሰራጨውን ሰው ይይዙታል” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

ውሸት ያሰራጫል
ይህ ፈሊጥ ነው። እዚህ ላይ “ያሰራጫል” የሚለው ቃል የማያቋርጥ ውሸትን ያመለክታል። ይህንን በምሳሌ 6:19 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “ያለማቋረጥ ይዋሻል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ቸር ሰው
ብዙ ጊዜ አንዳንድ ነገሮችን ለሰው የሚሰጥ

ሁሉ ጓደኛ ይሆነዋል
“ሁሉ” የሚለው ቃል ግነት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሁሉ ጓደኛው የሆነ ይመስላል” ወይም “ሁሉም ሰው ጓደኛው ነው ማለት እንችላለን” (ግነትና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Proverbs 19:7

ከእርሱ ብዙ ርቀው የሚገኙ ጓደኞቹማ ምንኛ ይጠሉት!
ከበፊቱ ሀረግ ይልቅ ይህ ሀረግ ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችል ለማሳየት ቃለ አጋኖ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለዚህ ጓደኞቹ በእርግጠኝት ይጠሉታል ደግሞም ከእርሱ ርቀው ይሄዳሉ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሕይወቱን ይወዳል
እዚህ ላይ ሰውየው በሕይወት እየኖረ እንደሆነ አጽንዖት ለመስጠት “ሕይወት” በሚለው ተወክሏል። አማራጭ ትርጉም፡- “ራሱን ይወዳል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ማስተዋልን ገንዘቡ ያደርጋል
“ማስተዋል አለው”

Proverbs 19:9

ሐሰተኛ ምስክር ሳይቀጣ አይቀርም
ይህ በአዎንታዊና በገቢር ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። ይህንን በምሳሌ 19:5 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ ሐሰተኛ ምስክርን በእርግጠኝነት ይቀጡታል” (ጥምር አሉታ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ውሸት ያሰራጫል
ይህ ዘይቤአዊ ንግግር “ያሰራጫል” የሚለውን ቃል ሳያቋርጡ መዋሸትን ለማመልከት ተጠቅሞበታል። ይህንን በምሳሌ 6:19 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “ያለማቋረጥ ይዋሻል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

አይገባውም
“ትክክል አይደለም”

ቅንጦት
የባለጠግነትና የደስታ ሁኔታ

ለባርያ ደግሞ የከፋ ነው
“ይህ” እና “አይገባውም” የሚሉት ቃላት ከቀደመው ሀረግ ግልጽ ተደርገዋል። ሊደገሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ለባርያ ፈጽሞ አይገባውም” ወይም “ለባርያ ከዚህም የከፋ ነው” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 19:11

ጠቢብ አእምሮ ሰውን ታጋሽ ያደርገዋል
“ጠቢብ አእምሮ ያለው ሰው ቁጡ ከመሆን ይታገሳል”

ማስተዋል
ይህ በአንድ ወሳኝ ሁኔታ ላይ ምን መደረግ እንዳለበት ማወቅ ማለት ነው። ይህንን በምሳሌ 1:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

መተው ክብር ይሆንለታል
“መተው ክብር ያመጣለታል” ወይም “እርሱ ከተወ ሌሎች ክብር እንደሆነ ያስባሉ”

መተው
በዓላማ መርሳት

የንጉስ ቁጣ እንደ ጎረምሳ አንበሳ ግሳት ነው
እዚህ ላይ የጎረምሳ አንበሳ ግሳት ማጥቃትን ያመለክታል። የንጉስ ቁጣ ካልተጠበቀና አደገኛ ከሆነ የአንበሳ ደቦል ጥቃት ጋር ተነጻጽሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “የንጉስ ቁጣ እንደ አንበሳ ደቦል ጥቃት አደገኛ ነው” (ተነፃፃሪ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በፊቱ ሞገስ ማግኘት ግን ሳር ላይ እንዳለ ጤዛ ነው
በንጉስ ፊት ሞገስ ማግኘት በማለዳ በሳር ላይ ከሚታየው የሚያድስ ውኃ ጋር ተነጻጽሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን በፊቱ ሞገስ ማግኘት በሳር እንዳለ ጤዛ ያድሳል” ወይም “ነገር ግን በፊቱ ሞገስ ማግኘት በማለዳ በመሬት ላይ እንደሚታየው ጤዛ የሚያድስ ነው” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 19:13

ለአባቱ መጥፊያ ነው
“አባቱን ያጠፋዋል”

ጨቅጫቃ ሚስትም እንደማያቋርጥ የውኃ ነጠብጣብ ናት
ይህ የሚናገረው ስለ ጨቅጫቃ ሚስት ሲሆን እርሷ የማታቋርጥ የውኃ ነጠብጣብ እንደሆነች አድርጎ ገልጿታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጨቅጫቃ ሚስት እንደማያቋርጥ የውኃ ነጠብጣብ ነዝናዛና በጥባጭ ናት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጨቅጫቃ ሚስት
“ተከራካሪ ሚስት” ወይም “ስምምነት የሌላት ሚስት”

ቤትና ሐብት ከወላጆች ይወረሳል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ልጆች ቤትና ሐብት ከወላጆች ይወርሳሉ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

አስተዋይ
ይህን ቃል በምሳሌ 12:23 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

አስተዋይ ሚስት ከእግዚአብሔር ናት
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር አስተዋይ ሚስት ይሰጣል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 19:15

ስንፍና ሰውን ወደ እንቅልፍ ይጥለዋል
ይህ ስንፍና ሰውን ብዙ እንዲተኛ እንደሚያደርገው የሚናገር ሲሆን ስንፍና ሰውን በጉልበት ወደ እንቅልፍ እንደሚጥለው ተደርጎ ተገልጿል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስንፍና ሰው ብዙ እንዲተኛ ያደርገዋል” ወይም “ሰነፍ ሰው ብዙ ይተኛል” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይራባል
ይህ አይበላም የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አይበላም” ወይም “ይራባል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ትእዛዛት
“እርሱ የተማረው ትእዛዛት”

ሕይወቱን ይጠብቃል
“ሕይወቱን ይጋርዳል”

መንገዱ
ይህ ሰውየው እንዴት እንደሚኖር የሚያመለክት ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ የሚኖርበት መንገድ” ወይም “እንዴት እንደሚኖር” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Proverbs 19:17

ለድሃ ቸር የሆነ ሰው ለእግዚአብሔር ያበድራል
እግዚአብሔር ለድሃ የተደረገውን ቸርነት ለእርሱ እንደተደረገ ይቆጥራል። ሰዎች ለድሃ ደግነትን የሚገልጡበት አንዱ መንገድ በመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ለድሃ የሚሰጥ ሰው ለእግዚአብሔር ይሰጣል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ድሃ
ይህ ድሃ ሰዎችን የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ድሃ የሆኑ ሰዎች” ወይም “ድሃ ሰዎች” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ተስፋ ሳለ
ይህ የሚያመለክተው ልጅ ገና በሕጻንነቱ ሳለና ቅጣትና ተግሳጽ ሊቀበል የሚችልበትን ጊዜ ነው። የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ገና ልጅ ሳለ” ወይም “ሊማር በሚችልበት ጊዜ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሞቱንም እየተመኘህ ዝም ብለህ አትየው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ይህ ሀረግ የሚገልጸው ልጅህን መቅጣት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን ልጅህ እንዳይሞት አስከፊ በሆነ ሁኔታ አትቅጣው” ወይም 2) ይህ ሀረግ የሚገልጸው ልጅህን ባትቀጣው ምን ሊሆን እንሚችል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ካልቀጣኸው ራሱን እንዲያጠፋ እያገዘኸው ነው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እየተመኘህ ዝም ብለህ አትየው
ይህ ፈሊጥ ሲሆን ትርጉሙም አንድ ነገር እንዲከናወን መጨከን ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱን ዝም ብሎ ማየት” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 19:19

ንዴቱን መቆጣጠር የማይችል ሰው
ይህ ፈሊጥ ሲሆን በቀላሉ የሚበሳጭ ሰውን የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ስሜቱን መቆጣጠር የማይችል ሰው” ወይም “በቶሎ የሚቆጣ ሰው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ቅጣቱን ማግኘት አለበት
ይህ የሚያመለክተው እርሱ ሲቆጣ የሚከተለውን አሉታዊ ውጤት የተሸከመውን ሰው ነው። የዚህ ዓረፍተ-ሃሳብ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የቁጣውን አሉታዊ ውጤት መሸከም አለበት” ወይም “በቁጣው የፈጸመው ድርጊት አሉታዊ ውጤት መሸከም አለበት” (ፈሊጥ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ብታድነው
“ብትታደገው።” ይህ የሚያመለክተው ከቁጣው የተነሳ ከሚወስደው እርምጃ እርሱ ማዳን ነው። የዚህ ዓረፍተ-ሃሳብ ትርጉም በቀላሉ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በቁጣ ከተሞላ በኋላ ብታድነው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለሁለተኛ ጊዜ
“ሌላ ጊዜ” ወይም “እንደገና” (ደረጃ የሚያሳይ ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

ምክርን ስማ ተግሳጽንም ተቀበል
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ናቸው፣ የተደጋገሙት ነገሩ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ አጽንዖት ለመስጠት ነው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ምክርን ስማ
ይህ ፈሊጥ ነው። እዚህ ላይ “ስማ” የሚለው እንዲያው ዝም ብሎ በጆሮ መስማት ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ከተሰጠህ ምክር መማርና ምክሩን መከተል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ለምክር ትኩረት ስጥ” ወይም “ምክርን ተከተል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 19:21

በሰው ልብ ውስጥ
እዚህ ላይ “ልብ” ጥቅም ላይ የዋለው አእምሮን ለማመልከት ሲሆን ለሰው ምኞት አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በሰው አእምሮ ውስጥ” ወይም “ሰው የሚመኘው ነገር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ዓላማ
“የእግዚአብሔር ዓላማ” ወይም “የእግዚአብሔር እቅድ”

የሚጸናው
ይህ ፈሊጥ ሲሆን “መፈጸም” ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ ይፈጸማል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 19:23

እግዚአብሔርን ማክበር ሰዎችን ወደ ሕይወት ይመራል፤ እንዲህ ያለውም ሰው ይረካል
ይህ ሰዎች እግዚአብሔርን ቢያከብሩ ረጅም እድሜ ይኖራሉ ማለት ነው። የዚህ ዓረፍተ-ሃሳብ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔርን የሚያከብሩ ሰዎች ረጅም እድሜ ይኖራሉ፤ እግዚአብሔርን የሚያከብር ማንኛውም ሰው ይረካል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ያለው ሰው
እዚህ ላይ “ያለው” የሚለው ቃል የሚያመለክተው “እግዚአብሔርን ማክበር” ነው።

ይረካል በመከራም አይጎዳም
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይረካል፤ ምንም ነገር አይጎዳውም” ወይም “ይረካል፤ በደህንነት ይጠበቃል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰነፍ
ይህንን በምሳሌ 10:26 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

እጁን በሳህን ውስጥ ያጠልቃል
“እጁን በሳህን ውስጥ ያስገባል” ወይም “እጁን በራሱ ሳህን ውስጥ ያስቀምጣል።” በዘመናችን በብዙ ባህሎች ውስጥ እንደሚሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ባህል ሰዎች ብዙ ጊዜ የሚበሉት በእጃቸው ነበር።

ወደ አፉም እንኳ እንደገና መልሶ አያመጣውም
እጁን እንደገና ወደ አፉ መልሶ አያመጣውም ምክንያቱም እጅግ በጣም ሰነፍ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን በጣም ሰነፍ ከመሆኑ የተነሳ ራሱን ለመመገብ እጁን መልሶ ወደ አፉ ማምጣት አይችልም። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 19:25

ፌዘኛን ብትመታው፣ አላዋቂው
“ቀልደኛውን ብትመታው፣ አላዋቂው”

ቀልደኛውን ብትመታው
“ቀልደኛውን ቅጣው”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አላዋቂ ሰው
“ልምድ የሌለው” ወይም “ብስለት የሌለው ሰው”

አስተዋይ
ይህንን በምሳሌ 12:23 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

አስተዋዩን አርመው
“አስተዋይ የሆነውን ሰው ብታርመው”

እውቀትን ያገኛል
ይህ “እውቀት” የሚለው ረቂቅ ስም “አወቀ” በሚለው ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የበለጠ ያውቃል” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 19:26

ዕፍረትና ውርደት ያመጣል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) ለራሱ ዕፍረትና ውርደት ያመጣል። አማራጭ ትርጉም፦ “ለራሱ ዕፍረትና ውርደት ያመጣል” ወይም 2) ለቤተሰቡ ያመጣል። አማራጭ ትርጉም፦ “ለቤተሰቡ ዕፍረትና ውርደት ያመጣል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ

ተግሳጽን መስማት እምቢ ብትል
እዚህ ላይ “ማድመጥና መታዘዝ” እንደ “መስማት” ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “ለተግሳጽ ትኩረት መስጠት ካቆምህ” ወይም “ተግሳጽን መታዘዝ እምቢ ብትል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ትስታለህ
“ትተዋለህ” ወይም “ጀርባህን ትሰጣለህ”

የእውቀት ቃላት
“እውቀት”

Proverbs 19:28

የክፉ ሰው አፍ በደልን ይውጣል
ይህ የሚናገረው ክፉ ሰዎች እንዴት ክፋትን በማድረግ እንደሚደሰቱ ሲሆን ምግብ በቀላሉ እንደሚውጡ እንደዚሁ በደልን በቀላሉ እንደሚውጡ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ክፉዎች ምግብን ሲበሉ እንደሚደሰቱ እንደዚሁ ክፋትን በማድረግ ይደሰታሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የክፉ ሰው አፍ ይውጣል
“የክፉ ሰው አፍ” የሚለው ሀረግ ክፉ ሰዎችን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ክፉ ሰዎች ይውጣሉ” ወይም “ክፉ ይውጣል” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉ
ይህ ክፉ ሰዎችን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ክፉ ሰው” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ለፌዘኞች ፍርድ ተዘጋጅቶላቸዋል፣ ግርፋት ደግሞ
“ፍርድ” እና “ግርፋት” የሚሉት ቃላት እንደ ግስ ሊገለጹ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር በፌዘኞች ላይ ለመፍረድና ለመግረፍ ዝግጁ ነው” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ለሞኞች ጀርባ ግርፋት
“ዝግጁ ነው” የሚሉት ቃላት ከቀደመው ሀረግ በግልጽ መረዳት ይቻላል፤ ሊደገሙም ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ግርፋት ለሞኞች ጀርባ ተዘጋጅቷል” ወይም “እርሱ ጀርባቸውን ለመግረፍ ዝግጁ ነው” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

መግረፍ
በጅራፍ ወይም በበትር መምታት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 20

1 ወይን ጠጅ ፌዘኛ፣ ብርቱ መጠጥም ጠበኛ ያደርጋል፤ በመጠጥ የሳተ ሁሉ ጠቢብ አይደለም። **2** የንጉስ ቁጣ እንደሚያገሳ ደቦል አንበሳ ቁጣ ነው፤ የሚያስቆጣውም ሰው ሕይወቱን ይከፍላል። **3** ጥልን መራቅ ለማንም ሰው ቢሆን ክብር ነው፣ ሞኝ ሰው ግን ወደ ጭቅጭቅ ይገባል። **4** ሰነፍ ሰው በመከር ወቅት አያርስም፤ በምርት ጊዜ እህል ይለምናል ነገር ግን ምንም አያገኝም። **5** በሰው ልብ ውስጥ ያለ አሳብ እንደ ጥልቅ ውሃ ነው፣ አስተዋይ ሰው ግን ከዚያ ቀድቶ ያወጣዋል። **6** ብዙ ሰው ታማኝ እንደሆነ ይናገራል፣ ታማኝ የሆነውን ግን ማን ሊያገኘው ይችላል? **7** ጽድቅን የሚያደርግ ሰው በሐቀኝነቱ ይራመዳል፣ ፍለጋውን የሚከተሉ ልጆቹም ደስተኞች ናቸው። **8** የዳኛን ተግባር በማከናወን በዙፋኑ ላይ የተቀመጠ ንጉስ በፊቱ ያለውን ክፋት ሁሉ በዓይኖቹ አበጥሮ ይለያል። **9** “ልቤን በንጽህና ጠብቄያለሁ፤ ከኃጢአቴ ንጹህ ነኝ” ብሎ መናገር የሚችል ማን ነው? **10** 1የተለያዩ ሚዛኖችና እኩል ያልሆኑ መስፈሪያዎች፣ ሁለቱንም እግዚአብሔር ይጠላቸዋል። **11** ወጣት እንኳ ባህርዩ ንጹህና ቅን መሆኑ በስራው ይታወቃል። **12** የሚሰሙ ጆሮዎችና የሚያዩ ዓይኖች፣ ሁለቱንም እግዚአብሔር ሰራቸው። **13** እንቅልፍን አትውደድ ወደ ድህነት ትመጣለህና፤ ዓይኖችህን ክፈት፣ የተትረፈረፈ መብል ይኖርሃል። **14** ዕቃ የሚገዛ ሰው “መጥፎ ነው! መጥፎ ነው!” ይላል፣ በሄደ ጊዜ ግን ይኩራራል። **15** ወርቅና ብዙ ውድ ድንጋዮች አሉ፣ የእውቀት ከንፈሮች ግን የከበረ ጌጥ ናቸው። **16** ለማይታወቅ ሰው ብድር በዋስትና ገንዘብ ያስያዘውን ሰው ልብስ ውሰድበት፣ ዝሙት ለምትፈጽም ሴት ዋስትና አስይዞ ከሆነ ውሰድበት። **17** በማጭበርበር የተገኘ ዳቦ ይጣፍጣል፣ ከዚያ በኋላ ግን አፉ ጠጠር ይሞላል። **18** እቅዶች በምክር ይጸናሉ፣ በጠቢብ ምክርም ብቻ ጦርነት አድርግ። **19** ሐሜት ሚስጥርን ያባክናል፣ ስለዚህ ወሬን ከሚያበዙ ሰዎች ጋር አንድነት አትፍጠር። **20** አንድ ሰው አባቱን ወይም እናቱን ከሰደበ፣ መብራቱ በድቅድቅ ጨለማ መካከል ይጠፋል። **21** በመጀመርያ በጥድፊያ የተገኘ ሀብት በመጨረሻ ላይ በረከት አይኖረውም። **22** “ለፈጸምክብኝ በደል ብድራትህን እመልስልሃለሁ” አትበል! እግዚአብሔርን ጠብቅ እርሱም ያድንሃል። **23** እኩል ያልሆኑ ሚዛኖችን እግዚአብሔር ይጠላል፣ ሐሰተኛ መስፈሪያም መልካም አይደለም። **24** የሰው አካሄድ በእግዚአብሔር ይመራል፤ ታዲያ ሰው የራሱን መንገድ እንዴት ሊያስተውል ይችላል? **25** ሰው በችኮላ “ይህ ነገር የተቀደሰ ነው” ቢሎ ስእለት ቢሳል፣ ከተሳለም በኋላ ስለ ነገሩ ምንነት ማሰላሰል ቢጀምርና ቢጸጸት ወጥመድ ይሆንበታል። **26** ጥበበኛ ንጉስ ክፉውን አበጥሮ ያወጣል፣ ከዚያም የመውቂያ ጋሪውን በላያቸው ላይ ይነዳል። **27** የሰው መንፈስ የእግዚአብሔር መብራት ነው፣ ውስጣዊ ማንነቱንም ይመረምራል። **28** በኪዳን የተመሰረተ ታማኝነትና እውነተኛነት ንጉስን ይጠብቁታል፤ ዙፋኑም በፍቅር ይጸናል። **29** የወጣት ወንዶች ክብር ጥንካሬያቸው ነው፣ የሽማግሌዎችም ውበት ሽበታቸው ነው። **30** የሚያቆስል ምት ክፋትን ያስወግዳል፣ ግርፋትም ውስጣዊ የሰውነት ክፍሎችን ያነጻል።

Proverbs 20:1

ወይን ጠጅ ፌዘኛ፣ ብርቱ መጠጥም ጠበኛ ያደርጋል

እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ በአንድ ላይ የተጣመሩት ብዙ አልኮል የመጠጣት አደገኛትን አጽንዖት ለመስጠት ነው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ወይን ጠጅ ፌዘኛ

እዚህ ላይ “ወይን” የሚያመለክተው በወይን የሰከረን ሰው ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በወይን የሰከረ ሰው ፌዘኛ ነው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ብርቱ መጠጥም ጠበኛ ያደርጋል

እዚህ ላይ “ብርቱ መጠጥ” የሚያመለክተው በጠንካራ ወይን የሰከረ ሰውን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በብርቱ መጠጥ የሰከረ ሰው ጠብ ይጀምራል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ጠበኛ

ብዙ ጊዜ ሕዝብ በሚሰበሰብበት ቦታ በጩኸት የሚጣላ ሰው

በመጠጥ የሳተ ሁሉ ጠቢብ አይደለም

ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በግልጽ ማሰብ እስከማይችሉ ድረስ የሚጠጡ ሰዎች ሁሉ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በመጠጥ

እዚህ ላይ “መጠጥ” የሚያመለክተው አልኮል መጠጦችን ነው።

ጠቢብ አይደለም

ይህ የጥበበኛ ተቃራኒ ነው፣ “ሞኝ” ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሞን ነው” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

የንጉስ ቁጣ እንደሚያገሳ ደቦል አንበሳ ቁጣ ነው

እዚህ ላይ የንጉስ ቁጣ ሰዎች እንዴት እንደሚፈሩት እና የደቦል አንበሳ ቁጣ እንዴት እንደሚፈሩት ተነጻጽሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች የአንበሳ ደቦል ሲመጣባቸው እንደሚፈሩ እንደዚሁ የንጉስ ቁጣ ያስፈራቸዋል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ያስቆጣዋል

“ንጉሱን ያስቆጣዋል”

ሕይወቱን ይከፍላል

ይህ የሚያመለክተው መሞትን ነው። እዚህ ላይ “ሕይወት” የሚያመለክተው ስጋዊ ሕይወትን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ይሞታል” (ለስላሴ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 20:3

ክብር ነው

“የሚያስከብር ነው።” ይህ ሰውየው ይከበራል ማለት ነው።

ሞኝ ሰው ሁሉ ወደ ጭቅጭቅ ይገባል

ይህ ወደ ጭቅጭቅ ፈጥኖ ስለመግባት የሚናገር ሲሆን ጭቅጭቅ ሞኝ ሰው በአካል ዘልሎ የሚገባበት እንደሆነ ተደርጎ ተገልጿል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሞኝ ሁሉ ወደ ጭቅጭቅ ፈጥኖ ይገባል” ወይም “ሞኝ ሁሉ ወደ ጭቅጭቅ ለመግባት ፈጣን ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ማረስ

ለመዝራት መሬትን ማዘጋጀት

በመኸር

“እህል የሚዘራበት ወቅት”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምንም አያገኝም
ይህ ሊሰበስበው የሚችለው በእርሻው ላይ የበቀለ ምንም ነገር አይኖርም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን የሚሰበስበው ምንም ነገር አይኖረውም” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 20:5

በሰው ልብ ውስጥ ያለ አሳብ እንደ ጥልቅ ውሃ ነው
ይህ የሰውን ድርጊት መነሻ ምክንያት መረዳት እንዴት አስቸጋሪ እንደሆነ በጥልቅ ጉድጓድ ያለውን ውኃ ለማግኘት አስቸጋሪ ከመሆኑ ጋር በማነጻጸር ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “በጥልቅ ጉድጓድ ያለውን ውኃ ለማግኘት አስቸጋሪ እንደሆነ እንደዚሁ በሰው ልብ ውስጥ ያለውን ሃሳብ መረዳት አስቸጋሪ ነው። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አስተዋይ ሰው
“ማስተዋል ያለው ሰው”

ቀድቶ ያወጣዋል
ይህ በሰው ልብ ውስጥ ያለውን ሃሳብ ስለመለየት የሚናገር ሲሆን ከጥልቅ ጉድጓድ ተቀድቶ እንደሚወጣ ውኃ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሃሳቡ እንዲታወቅ ያደርጋል” ወይም “ሃሳቡን ይለየዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጣማኝ
“ታማኝ ነው” ወይም “አመኔታ የሚጣልበት ነው”

ታማኝ የሆነውን ግን ማን ሊያገኘው ይችላል?
ግልጽ የሆነው መልስ “እንደዚያ ያለ ሰው ማግኘት የሚችሉት ጥቂቶች ናቸው” የሚል ነው። ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ እንደ ዓረፍተ-ሃሳብ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን ጥቂት ሰዎች ታማኝ ሰው ሊያገኙ ይችላሉ” ወይም “ነገር ግን ታማኝ የሆነ ሰው ማግኘት በጣም አስቸጋሪ ነው!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 20:7

በሐቀኝነቱ ይራመዳል
እዚህ ላይ መራመድ መኖርን ያመለክታል። ይህንን በምሳሌ 19:1 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “በሐቀኝነቱ ይኖራል” ወይም “ታማኝ ሕይወት ይኖራል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ፍለጋውን የሚከተሉ ልጆቹም
ከእርሱ ይልቅ በእድሜ ለጋ ስለሆኑና ልጆቹም ስለሆኑ እርሱን “እርሱን ይከተሉታል” ለማለት ነው። ይህ ሀረግ በአንተ ቋንቋ ያልተለመደ ከሆነ እንዳለ መተው ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ልጆቹ ይከተሉታል “ ወይም “ልጆቹ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በፊቱ ያለውን ክፋት ሁሉ በዓይኖቹ አበጥሮ ይለያል
ይህ ንጉስ በተለያዩ የክፋት ዓይነቶች መካከል የሚለይ ስለመሆኑ የሚናገር ሲሆን ይህ የመለየቱን ተግባር ሰው እህል አበጥሮ እንደሚለይ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በእርሱ ፊት የሚመጡትን የተለያዩ የክፋት ዓይነቶች ይመለከታል ደግሞም ይለያል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 20:9

“ልቤን በንጽህና ጠብቄያለሁ፤ ከኃጢአቴ ንጹህ ነኝ” ብሎ መናገር የሚችል ማን ነው?
ለዚህ ጥያቄ ጠቋሚ መልስ ሊሆን የሚችለው፡- “ማንም ሰው ይህን ሊናገር አይችልም” የሚል ነው። ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ እንደ ዓረፍተ-ሃሳብ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- ““ልቡ ንጹህ እንደሆነና ኃጢአት የለብኝ ብሎ መናገር የሚችል አንድም ሰው የለም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ልቤ
እዚህ ላይ የሰው “ልብ” ሃሳቡንና ምኖቱን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሃሳቤ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ንጹህ
በመንፈሳዊነቱ እግዚአብሔር ተቀባይነት እንዳለው የቆጠረው ሰው በአካል ንጹህ እንደሆነ ተደርጎ ተገልጿል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ከኃጢአቴ ንጹህ ነኝ
“ኃጢአት የለብኝም” ወይም “ኃጢአት አልሰራሁም”

Proverbs 20:11

ወጣት እንኳ በስራው ይታወቃል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች ወጣትን በስራው ያውቁታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ባህርዩ ንጹህና ቅን መሆኑ
“ባህርዩ ንጹህና ቅን መሆኑና አለመሆኑ”

ባህርዩ
“ተግባሩ” ወይም “የሚሰራው ስራ”

ንጹህና ቅን
እነዚህ ሁለት ቃላት በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ናቸው፤ ይህ ወጣት ምን ያህል መልካም እንደሆነ አጽንዖት ይሰጣል። አስፈላጊ ከሆነ ወደ አንድ ቃል መጣመር ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ንጹህ” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

የሚሰሙ ጆሮዎችና የሚያዩ ዓይኖች
እግዚአብሔር ስሜቶቻችንን በሙሉ እርሱ እንደፈጠራቸው አጽንዖት ለመስጠት ተመሳሳይ ሃሳቦች ተደጋግመዋል። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 20:13

ወደ ድህነት ትመጣለህ
እዚህ ላይ “ትመጣለህ” የሚለው ቃል ወደ አዲስ ሁኔታ ትገባለህ፤ ትመጣለህ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ድሃ ትሆናለህ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ዓይንህን ክፈት
እዚህ ላይ “የአንድ ሰው ዓይን መከፈት” “መንቃት” እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ንቁ ሁን” ወይም “ጥንቁቅ ሁን” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ዕቃ የሚገዛ ሰው “መጥፎ ነው! መጥፎ ነው!” ይላል፣ በሄደ ጊዜ ግን ይኩራራል
እዚህ ላይ ገዢ ለራሱ የሚገዛውን በዝቅተኛ ዋጋ እንዲያገኝ አንድ ሰው የሚሸጠውን ነገር ያቃልላል። ከገዛ በኋላ ግን ሻጩ እንዲሸጥለት በማሳመን ስለገዛበት ጥሩ ዋጋ ይኩራራል። የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ገዢ የሻጩን እቃ እያቃለለ ‘መጥፎ ነው! መጥፎ ነው!’ ይላል ነገር ግን እቃውን ከገዛ በኋላ ይሄዳል ከዚያም ስለከፈለው ዝቅተኛ ዋጋ ይኩራራል (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Proverbs 20:15

የእውቀት ከንፈሮች የከበረ ጌጥ ናቸው
ይህ የሚናገረው ከከበረ ጌጥ ጋር በማወዳደር ስለ እውቀት ከንፈሮች ዋጋ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የእውቀት ከንፈሮች እንደ ውድ ጌጥ በጣም የከበሩ ናቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የእውቀት ከንፈሮች
እዚህ ላይ “ቃላት” የሚሉት “ከንፈሮች” በሚሉት ተገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “የጥበብ ቃላት” ወይም “የእውቀት ቃላት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ለማይታወቅ ሰው ብድር በዋስትና ገንዘብ ያስያዘውን ሰው ልብስ ውሰድበት
ገንዘብ ስትበደር አበዳሪው ከተበዳሪው እንደገና ለመከፈሉ ዋስትና ይሆን ዘንድ አንድ ነገር እንደ ልብስ የመሳሰሉ ይወስዳል። አበዳሪውም መያዣውን ገንዘቡ ከተከፈለው ቧላ ይመልሳል። ተበዳሪው በጣም ድሃ ከሆነ ደግሞ ለአበዳሪው ሌላ ሰው እንደ ዋስትና አንድ ነገር ሊሰጠው ይችላል። የዚህ ዓረፍተ-ሃሳብ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላ። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ እንግዳ ሰው የተበደረውን ብድር መክፈል ለመቻሉ ማረጋገጫ ይሆን ዘንድ እንደ ዋስትና ዋስ ከሆነው ሰው ልብሱን ውሰድ። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ማስያዣ አስይዝ
ይህ ፈሊጥ ነው። አንድ ሰው ብድር ከተበደረ በኋላ ዋስ የሆነው ሰው ብድሩ የሚከፈል መሆኑን ለማረጋገጥ ለአበዳሪው አንድ ነገር ይሰጠዋል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ብድሩ ተመልሶ የሚከፈል መሆኑን ለማረጋገጥ ዋስትና ስጠው” ወየም “ብድር ለመክፈል ቃል ግባ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

በዋስትና ያዘው
ይህ ፈሊጥ ነው። “አንድን ነገር ማስያዣ መያዝ” አንድ ሰው የወሰደውን ዕዳ እንደሚከፍል ለማረጋገጥ አንድ ሰው እንደ ማስያዣ የሰጠውን ነገር ወይም ቃል ኪዳን መያዝ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ዕዳው የሚከፈል ለመሆኑ ዋስትና እንዲሆን ኮቱን እንደ ማስያዣ ያዝ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 20:17

በማጭበርበር የተገኘ ዳቦ
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ሰው በማጭበርበር ያገኘው ዳቦ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በማጭበርበር
“ማጭበርበር” የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሌሎችን በማጭበርበር” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ዳቦ
እዚህ ላይ “ዳቦ” በአጠቃላይ ምግብን ሁሉ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ምግብ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ይጣፍጣል
“ጥሩ ጣዕም አለው”

ነገር ግን ከዚያ በኋላ አፉ ጠጠር ይሞላል
ይህ ምግቡ የማይጣፍጥ ስለመሆኑ የሚናገር ሲሆን አፉ በእርግጥም ከምግብ ይልቅ በጠጠር እንደተሞላ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን ከዚያ በኋላ በአፉ ውስጠ እንደ ጠጠር ጣዕም ይሆንበታል” ወይም “ነገር ግን ወዲያውኑ በአፉ ውስጥ እንደ አፈር ጣዕም ይሆንበታል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጠጠር
ትንሽ ድንጋዮች

እቅዶች በምክር ይጸናሉ
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች እቅዳቸውን በምክር ላይ ተመስርተው ያቅዳ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 20:19

ሐሜት
ይህ በስተጀርባ ብዙ መናገር ነው።

ከእርሱ ጋር አንድነት አትፍጠር
“አንተ ከእርሱ ጋር ጓደኛ አትሁን”

አንድ ሰው ከሰደበ
አንድ ሰው ክፉ ነገር በሌላ ሰው ላይ እንዲሆን ምኞቱን ከገለጸ ማለት ነው።

መብራቱ በድቅድቅ ጨለማ መካከል ይጠፋል
ይህ የሚናገረው በድንገትና ባልተጠበቀ ሁኔታ ስለሚሞት ሰው ሲሆን የዚህን ሰው ሕይወት በድቅድቅ ጨለማ እንደጠፋ መብራት አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በድቅድቅ ጨለማ እንደጠፋ መብራት ሕይወቱ በድንገት ይቆማል” ወይም “በድንገት ይሞታል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መብራቱ በድንገት ይጠፋል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “መብራቱ ይጠፋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

መብራቱ
ይህ የሚንበለበል ነበልባል ያለው መብራት ያመለክታል። እዚህ ላይ የመብራቱ ነበልባል እንደ መብራት ተተጠቅሷል። አማራጭ ትርጉም፡- “የመብራቱ ነበልባል” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ይጠፋል
ነበልባል እንዲጠፋ ማድረግ

Proverbs 20:21

በመጀመርያ
ይህ የሚያመለክተው ውርሱን ሊቀበል ከሚገባበት ጊዜ በፊት ቀድሞ የተቀበለን ሰው ነው። የዚህ ዓረፍተ-ሃሳብ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከትክክለኛው ጊዜ በፊት” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እመልስልሃለሁ
ይህ አንተ በሌሎች ሰዎች ላይ መጥፎ ነገር ስላደረግህ እነርሱም በአንተ ላይ የሚወስዱት በቀል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እቀጣሃለሁ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን ጠብቅ
ይህ እግዚአብሔር የአንተን ጉዳይ እርሱ ይይዘዋል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በእግዚአብሔር ታመን” ወይም “በእግዚአብሔር ተስፋ አድርግ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 20:23

እኩል ያልሆኑ ሚዛኖችን እግዚአብሔር ይጠላል፣ ሐሰተኛ መስፈሪያም መልካም አይደለም
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ናቸው፣ በአንድ ላይ የተጣመሩት ይህ ምን ያህል መጥፎ እንደሆነ አጽንዖት ለመስጠት ነው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው አካሄድ በእግዚአብሔር ይመራል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሰውን አካሄድ እግዚአብሔር (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው አካሄድ
ይህ ሰው የሚያደርገውን የተለያዩ ነገሮች ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሰው ድርጊቶች” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ታዲያ ሰው የራሱን መንገድ እንዴት ሊያስተውል ይችላል?
የዚህ አመልካች መልስ ሊያስተውለው አይችልም የሚል ነው። ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለዚህ ሰው የራሱን መንገድ ሊያስተውለው አይችልም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

መንገዱን አያስተውልም
ይህ ፈሊ ነው። “መንገዱን” የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው የሰውየውን ሕይወት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በሕይወቱ ለምን አንድ ነገር እንደሚሆን አያስተውልም” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 20:25

ወጥመድ ነው
ይህ የሚናገረው አደገኛ ስለሆነ ነገር ሲሆን እንደ ወጥመድ ወይም መንጠቆ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “አደገኛ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በችኮላ ቢናገር
ምን ትርጉም ሊኖረው እንደሚችል በጥንቃቄ ሳያስተውሉ በችኮላ አንድ ነገር መናገር

ስእለት ቢሳል
ይህ ሰው አንድ ነገር ለእግዚአብሔር የተቀደሰና የተለየ ነው ብሎ ስእለት ገባ። አማራጭ ትርጉም፡- “ለእግዚአብሔር የተለየ አደረገ” ወይም “የተቀደሰ ነው አለ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉውን ያበጥራል
ይህ የሚናገረው ንጉስ እህልን እንደሚያበጥር እንደዚሁ ክፉ ሰዎችን እንደሚለይ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉዎችን ይለያል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉ
ይህ የሚያመለክተው ክፉ ሰዎችን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ የሆኑ ሰዎች” ወይም “ክፉ ሰዎች” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያም የመውቂያ ጋሪውን በላያቸው ላይ ይነዳል
ይህ ንጉስ የመውቂያ ጋሪውን በእነርሱ ላይ እንደሚነዳ አድርጎ በመግለጽ ክፉዎችን እንደሚቀጣ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ በአሰቃቂ ሁኔታ ይቀጣቸዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የመውቂያ ጋሪ
“የመውቂያ ጋሪ።” ይህ እህል ለመውቃትና ከገለባው ለመለየት የሚረዳ መሳርያ ነው።

Proverbs 20:27

የሰው መንፈስ የእግዚአብሔር መብራት ነው፣ ውስጣዊ ማንነቱንም ይመረምራል
ይህ የሚናገረው ስለ ሰው መንፈስ ሲሆን እንደ መብራት ገልጾታል። የሰው መንፈስ ውስጣዊ ማንነቱን እንደሚገባ እንዲረዳ ያግዘዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “መብራት በጨለማ እንድናይ እንደሚያግዘን እንደዚሁ ጥልቅ ማንነታችንን በሚገባ እንድንረዳ እግዚአብሔር መንፈስ ሰጥቶናል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በኪዳን የተመሰረተ ታማኝነትና እውነተኛነት ንጉስን ይጠብቁታል
“ታማኝነት” እና “እውነተኛነት” የተባሉት ረቂቅ ስሞች “ታማኝ” እና “እውነተኛ” ተብለው ሊገለፁ ይችላሉ። ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- ንጉስ ለኪዳኑ “ታማኝ” እና “እውነተኛ” በመሆን ራሱን ሊጠብቅ ይችላል። (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉስን ይጠብቁታል
ንጉሱን በደህንንት ከጉዳት ይጠብቁታል

ዙፋኑም በፍቅር ይጸናል
እዚህ ላይ “ዙፋን” የንጉሱን የአገዛዝ ኃይል ይወክላል። “ፍቅር” የሚለው ረቂቅ ስም በግስ ሊገለጽ ይችላል። በተጨማሪ ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ንጉስ ለረጅም ጊዜ መምራቱን ሌሎችን በመውደድ ያረጋግጣል” (ምትክ ስም እና ረቂቅ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 20:29

የሚያቆስል ምት ክፋትን ያስወግዳል፣ ግርፋትም ውስጣዊ የሰውነት ክፍሎችን ያነጻል
ሁሉም ዓረፍተ ሃሳቦች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ የተደጋገሙት አጽንዖት ለመስጠት ነው። አንድን ሰው ለማረም አካላዊ ቅጣት ስለ መጠቀም ሲናገር ክፉ ነገር ቆሻሻ እንደሆነና ቅጣት ደግሞ እንደሚያነጻው ተደርጎ ተገልጿል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥፋት የሰራን ሰው መግረፍ ከጥፋቱ እንዲታረም ያደርገዋል ደግሞም የተሻለ ሰው እንዲሆን ያደርገዋል። (ትይዩነት እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 21

1 የንጉስ ልብ በእግዚአብሔር እጅ እንዳለ የውኃ ፈሳሽ ነው፤ እርሱ ደስ ወዳሰኘው ይመራዋል። 2 ለሰው መንገዱ በራሱ ዓይን ፊት ቀና ሊመስለው ይችላል፣ ልብን የሚመዝን ግን እግዚአብሔር ነው። 3 ከመስዋዕት ይልቅ ጽድቅንና ፍትሕን ማድረግ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት አለው። 4 ትቢተኛ ዓይንና ኩሩ ልብ፣ የክፉ ሰውም መብራት፣ ኃጢአት ናቸው። 5 የትጉ ሰው እቅዶች ወደ ብልጽግና ይመራሉ፣ በችኮላ የሚያደርግ ሰው ሁሉ ግን ወደ ድህነት ይመጣል። 6 በሐሰተኛ ምላስ ሀብትን ማግኘት በኖ የሚጠፋ ተን፣ የሚገድልም ወጥመድ ነው። 7 የክፉዎች አመጽ ራሳቸውን ይጠራርጋቸዋል፣ ፍትሕን ማድረግ አይፈቅዱምና። 8 የበደለኛ ሰው መንገድ ጠማማ ነው፣ ንጹሕ ሰው ግን ጽድቅን ያደርጋል። 9 ከጠበኛ ሚስት ጋር በአንድ ቤት ከመኖር በጣራ ማእዘን ላይ ተጠግቶ መኖር ይሻላል። 10 የክፉ ሰው ምኞት ክፋትን አጥብቆ ይመኛል፤ ጎረቤቱም በዓይኖቹ ውስጥ ምንም ደግነት አያይም። 11 ፌዘኛ ሲቀጣ ፣ እውቀት አልባ ሰው ጥበበኛ ይሆናል፣ ጥበበኛ ሰው ሲገሰጽ፣ እውቀትን ይጨምራል። 12 ጽድቅን የሚያደርግ ሰው የክፉውን ቤት ልብ ብሎ ይመለከታል፤ እርሱ ክፉውን ወደ ጥፋት ያወርደዋል። 13 የድሆችን ጩኸት የማይሰማ ሰው፣ እርሱም ሲጮህ ማንም አይሰማውም። 14 በምስጢር የተደረገ ስጦታ ቁጣን ያበርዳል፣ የተሸሸገ ስጦታም ታላቅ ቁጣን ያጠፋል። 15 ፍትሕ በተደረገ ጊዜ ጽድቅን ላደረገው ሰው ደስታን ያመጣለታል፣ ለክፉ አድራጊዎች ግን ሽብር ያመጣባቸዋል። 16 ከማስተዋል መንገድ የሳተ ሰው፣ በሙታን ጉባኤ ውስጥ ያርፋል። 17 ቅንጦት የሚወድ ሰው ድሃ ይሆናል፤ የወይን ጠጅና ዘይት የሚወድ ደግሞ ባለጠጋ አይሆንም። 18 ክፉ ሰው ጽድቅን ለሚያደርግ ሰው ቤዛ ይሆናል፣ ከዳተኛ ሰው ደግሞ ለጻድቅ ቤዛ ነው። 19 ጠብ ከምታነሳሳና ያለማቋረጥ ከምታማርር ሴት ጋር ከመኖር በምድረ በዳ መኖር ይሻላል። 20 የከበረ ሀብትና ዘይት በጥበበኛ ቤት ይገኛሉ፣ ሞኝ ሰው ግን ያባክናቸዋል። 21 ጽድቅን የሚያደርግና ደግ ሰው፣ ይህ ሰው ሕይወትን፣ ጽድቅንና ክብርን ያገኛል። 22 ጥበበኛ ሰው ወደ ኃያላን ከተማ ይገባል፣ የምትታመንበት ምሽጓንም ያፈርሳል። 23 አፉንና ምላሱን የሚጠብቅ ሰው ራሱን ከመከራ ይጠብቃል። 24 ኩሩና ትዕቢተኛ ሰው ስሙ “ሞኝ” ይባላል፣ እርሱም በእብሪትና በትዕቢት ያደርጋል። 25 የሰነፍ ምኞት ራሱን ይገድለዋል፣ እጆቹ ለመስራት አይፈቅዱምና። 26 እርሱ ቀኑን በሙሉ ይመኛል፣ ተጨማሪ ይመኛል፣ ጽድቅን የሚያደርግ ግን ይሰጣል፣ አይሰስትምም። 27 የክፉዎች መስዋዕት አስጸያፊ ነው፤ በክፉ ሃሳብ ሲያቀርበው ደግሞ የበለጠ አስጸያፊ ነው። 28 ሐሰተኛ ምስክር ይጠፋል፣ የሚያዳምጥ ሰው ግን ለሁልጊዜ የሚሆን ይናገራል። 29 ክፉ ሰው ራሱን ጠንካራ አስመስሎ ያቀርባል፣ ጻድቅ ሰው ግን ስለ ድርጊቶቹ ይጠነቀቃል። 30 እግዚአብሔርን ሊቋቋም የሚችል ጥበብ፣ ማስተዋል ወይም ምክር የለም። 31 ፈረስ ለጦርነት ቀን ይዘጋጃል፣ ድል ግን የእግዚአብሔር ነው።

Proverbs 21:1

የንጉስ ልብ በእግዚአብሔር እጅ እንዳለ የውኃ ፈሳሽ ነው

ጸሐፊው ስለ ንጉስ ልብ ሲናገር ሰዎች እርሻቸውን በአስፈላጊ ጊዜ ለማጠጣት ውኃውን እንደሚፈልጉ እንደሚመሩት እንደ መስኖ ቦይ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰው የመስኖ ውኃን እንደሚመራው ሁሉ እንደዚሁ እግዚአብሔር የንጉስን ልብ ይቆጣጠራል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የንጉስ ልብ

ልብ ሰው ለሚያስበውና ሊሰራ ለሚፈልገው ነገር ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የንጉስ ሃሳብና ተግባር” ወይም “ንጉስ የሚያስበውና ሊያደርገው የሚፈልገው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ለሰው መንገዱ በራሱ ዓይን ፊት ቀና ሊመስለው ይችላል

ዓይን ማየትን ይወክላል፣ ማየት ደግሞ ሃሳብን ወይም ፍርድን ይወክላል። ጸሐፊው ሰው ስለሚያደርገው ነገር ሲናገር ያ ሰው በመንገድ እንደሚጓዝ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እያንዳንዱ ሰው የሚሰራው ስራ ሁሉ መልካም እንደሆነ ያስባል” ወይም “እያንዳንዱ ሰው የሚሰራው ስራ ሁሉ መልካም እንደሆነ ይደመድማል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ልብን የሚመዝን

ጸሐፊው ሰው ትክክለኛውን ነገር ለማድረግ ይፈልግ እንደሆነና እንዳልሆነ እግዚአብሔር ስለሚያደርገው ውሳኔ ሲናገር እግዚአብሔር ወደ እቃ እንደሚመለከትና መልካም ጥራት ያለው እንደሆነ መዝኖ ድምዳሜ እንደሚደርስ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሰውን የውስጥ ሃሳብ የሚመዝን ማን ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 21:3

ቅን የሆነውን ነገር ማድረግ

“እግዚአብሔር ትክክል እንደሆነ የሚያስበውን ነገር ማድረግ”

ፍትህን ... ማድረግ

“እግዚአብሔር ሰዎች ሌሎች ሰዎችን ሊይዙ የሚፈልገውን ዓይነት አያያዝ ለሰዎች ማድረግ”

ለእግዚአብሔር ፍትህ የበለጠ ተቀባይነት አለው

“ፍትህ - እግዚአብሔር ይህን የበለጠ ይፈልገዋል”

ትቢተኛ ዓይንና ኩሩ ልብ

“ዓይን” እና “ልብ” የሚሉት ቃላት ራሱን ከሌሎች ሰዎች ይልቅ እንደሚሻል ለሚቆጥርና ሌሎች ሰዎች ይህን ሃሳቡን እንዲያወቁለት ለሚፈልግ ሰው ተዛምዶአዊ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ከሌሎች ሰዎች ይልቅ እንደሚሻሉ ሰዎች እንዲያስቡ የሚፈልጉ ሰዎች” (ተዛምዶአዊ እና ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ትዕቢተኛ ዓይን

ይህ እርሱ ከእነርሱ ይልቅ እንደሚሻል እንደሚያስብ ሌሎች ሰዎች እንዲያውቁለት ለሚፈልግ ሰው ተዛምዶአዊ ዘይቤ ነው። (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ኩሩ ልብ

ይህ እርሱ ከሌሎች ሰዎች ይልቅ የተሸለ እንደሆነ ለሚያስብ ሰው ተዛምዶአዊ ዘይቤ ነው። (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

የክፉ ሰውም መብራት

ክፉ ሰውን የሚያግዙ ነገሮች በሙሉ እንደ መብራት እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ሰውን እንደ መብራት የሚያግዙ ነገሮች በጨለማ እንዲያይ ይረዱታል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 21:5

ትጉ ሰው

ይህ የስም ቅጽል እንደ ስም ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ትጉ ሰው” ወይም “ጠንክሮ የሚሰራ ሰው” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወደ ድህነት ይመጣል
“ድህነት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ድሃ ይሆናል” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ሃብትን ማግኘት
“ሃብትን ማከማቸት”

ውሸታም ምላስ
ምላስ አንደበቱ ይናገር ዘንድ ሰው ለሚጠቀምባቸው ቃላቶች ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ውሸት መናገር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የሚጠፋ ተን
ጸሐፊው ሰው በውሸት የሚያገኘውን ሃብት በማለዳ በፍጥነት ከሚጠፋ ተን ጋር አመሳስሎታል። አማራጭ ትርጉም፦ “የሚጠፋ ተን” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሚገድል ወጥመድ
ጸሐፊው ሰው በውሸት የሚያገኘውን ሃብት በአዳኝ ወጥመድ ላይ እንደሚደረገው የማታለያ ምግብ እንደሆነ አድርጎ ተናግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 21:7

የክፉዎች አመጽ ራሳቸውን ይጠራርጋቸዋል፣
ጸሐፊው ስለ ክፉዎች አመጽ ሲናገር ሌሎችን እንደሚጠራርግ ሰው አድርጎ ገልጾታል። እግዚአብሔር ቅን የሆኑ ጎረበቶቻቸውን የሚጎዱትን ክፉ ሰዎች ይቀጣል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የክፉዎች አመጽ
“አመጽ” የሚለው ረቂቅ ስም የሚያመለክተው ሰዎች ቅን ጎረቤቶቻቸውን ለመጉዳት የሚሰሯቸውን ድርጊቶችን ወይም ሌሎች ነገሮችን ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የክፉ ሰዎች አመጸኛ ድርጊት” (ረቂቅ ስም እና የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ራሳቸውን ይጠራርጋቸዋል
ይህ ሀረግ የሚያመለክተው በውኃ ውስጥ ዓሳ ለመያዝ መረብ መጎተትን ነው። በራሳቸው ድርጊት ስለሚጠፉ ክፉ ሰዎች ሲናገር አንድ ሰው ዓሳ እንደሚይዝ እንደዚሁ ድርጊታቸው በመረብ አጥምዶ እንደሚይዛቸው አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡ “እንደ ዓሳ አጥምዳቸው” ወይም “አንድ ሰው ዓሳ በመረብ እንደሚይዝ እንደዚሁ በቀላሉ አጥፋቸው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የበደለኛ ሰው መንገድ ጠማማ ነው
ይህ አንድ ሰው የሚኖርበትን መንገድ አንድ ሰው ከሚጓዝበት ጠማማ መንገድ ጋር ያነጻጽረዋል። ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በደለኛ ሰው የሚኖርበት መንገድ ጠማማ ነው” (ፈሊጥ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጠማማ
እዚህ ላይ “ጠማማ” የሚለው የታጠፈ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ማለት ነው። ይህ በስነ ምግባር ለተሳሳተ ሰው ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ስህተት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 21:9

በጣራ ማእዘን
በዚያን ጊዜ የነበሩ ቤቶች ለጥ ያለ ጣራ ነበራቸው። የጥንት እስራኤላውያን ጣራቸውን ለመስራት ብዙ ጊዜ ይወስድባቸው ነበር። ጣራው ከቤቱ ውስጠኛው ክፍል ይልቅ ቀዝቃዛ ነበር። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ለመኝታ የሚሆን ትልቅ መጠለያ በጣራው በአንዱ ማእዘን ላይ ይሰሩ ነበር። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ጠበኛ ሚስት
“ብዙ ጊዜ የምትጨቃጨቅና የምታማርር ሚስት”

የክፉ ሰው ምኞት ክፋትን አጥብቆ ይመኛል
ጸሐፊው ስለ ሰው ምኞት ማለትም ለሚበላና ለሚጠጣ ነገር ስላለው ፍላጎት ሲናገር አንድን ነገር እንደሚፈልግ ሰው አድርጎ ገልጾታል። “ክፉ” የሚለው ቃል ክፉ ሰዎችን የሚያመለክት የስም ቅጽል ሲሆን “ክፋት” የሚለው ቃል ደግሞ ክፉ ድርጊቶችን የሚወክል የስም ቅጽል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ክፉ ሰዎች ለመብላትና ለመጠጣት እንደሚመኙ እንደዚሁ ክፉ ድርጊቶችን ለመፈጸም ይመኛሉ” (ሰውኛ ዘይቤ እና የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

መመኘት
አጥብቆ መፈለግ

ጎረቤቱም በዓይኖቹ ውስጥ ምንም ደግነት አያይም
“ደግነት መፈለግ” የሚለው ፈሊጥ አንድ ሰው ደግነት ለሚፈልገው ሰው ማረጋገጫ ሲሰጠውና በደግነት ሲያደርግለት ማለት ነው። በተጨማሪ ዓይኖች ማየትን ይወክላል፣ ማየት ደበደግነት ግሞ ሰውየው ለሌሎች ሰዎች ያለውን ሃሳብና አመለካከት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ጎረቤቱ ከእርሱ ምንም ዓይነት ደግነት አላገኘም” ወይም “ለጎረቤቱ ደግነትን አላሳየም” (ፈሊጥ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 21:11

ፌዘኛ ሲቀጣ
ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አንድ ሰው ፌዘኛውን ሲቀጣ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

አላዋቂ
“ልምድ የሌላቸው” ወይም “ብስለት የሌላቸው”

ፈዘኛ
“በሌሎች ላይ የሚያፌዝ”

ጥበበኛ ሰው ሲገሰጽ
ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አንድ ሰው ጥበበኛውን ሰው ሲገስጸው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እውቀትን ይጨምራል
እዚህ ላይ እውቀት አንድ ሰው ሊጨብጠውና ለራሱ ሊወስደው የሚችለው እቃ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጽድቅን የሚያደርግ ሰው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) ማንኛውም ጻድቅ ሰው ወይም 2) “ጻድቅ የሆነው እግዚአብሔር”

ቤት ልብ ብሎ ይመለከታል
“ለቤት ጥንቃቄ የተሞላበት ትኩረት ያደርጋል” “ቤቱ ላይ ምን ሊሆን እንደሚችል ለማየት ይጠብቃል”

እርሱ ክፉውን ወደ ጥፋት ያወርደዋል
እዚህ ላይ ጥፋት አንድ ሰው የሚወሰድበት ቦታ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “እርሱ ያጠፋቸዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Proverbs 21:13

የድሆችን ለቅሶ የማይሰማ ሰው
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ድሆች ለእርዳታ ሲጮሁ የማይሰማ ሰው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱም ሲጮህ ማንም አይመልስለትም
“አይመልስለትም” የሚለው ቃል ሌላ ሰው ለእርዳታና ተግባራዊ እርምጃ ሲጠይቀው ለሚሰማ ሰው ምትክ ስም ነው። ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አንድም ሰው እርሱን ለመርዳት አንዳች አያደርግም” (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ቁጣን ያበርዳል
“የተቆጣን ሰው በቁጣው እንዳይቀጥል ስሜቱን ያረጋጋል”

Proverbs 21:15

ፍትሕ በተደረገ ጊዜ
“ፍትሕ” የሚለው ረቂቅ ስም በስም ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። እነዚህ ቃላት በገቢር ቅርጽ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “መሪዎች ፍትሕ ሲያደርጉ” (ረቂቅ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ከማስተዋል መንገድ ይስታል
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ለወደፊት በጥበብ መኖር ፈጽሞ ኤችልም” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

በሙታን ጉባኤ ውስጥ ያርፋል
“የሙታን መናፍስት ባሉበት ጉባኤ ይኖራል”

Proverbs 21:17

ቤዛ ይሆናል
“ቤዛ” የሚለው ቃል የሌላውን ሰው ስፍራ ለሚወስድ ሰው ተለዋጭ ዘይቤ ነው። እዚህ ላይ ጽድቅ ካደረገው ሰው ይልቅ ስህተት የፈጸመው ሰው ቅጣት ይቀበላል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዳተኛ ሰው
በመዋሸትና ሌሎች ውሸት የተሞሉ ነገሮችን በማድረግ የሚያምኑትን ሰዎች የሚጎዳ ሰው

Proverbs 21:19

ጠቢብ
ይህ የስም ቅጽል በስም ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ጠቢብ ሰው” (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ያባክናቸዋል
x

Proverbs 21:21

ከተማ ይገባባታል
“በከተማዋ ዙርያ ያለውን የግንብ አጥር ዘልሎ ይገባል”

የኃያላን ከተማ
“ኃያላን ሰዎች የሚኖሩባት ከተማ” ወይም “ኃያላን ተዋጊዎች ያሉባት ከተማ”

ያፈርሳል
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ያጠፋዋል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

የታመኑበትን ምሽግ
“ማንም ሰው ወደ ከተማው አልፎ ሊገባ ይችላል ብለው ያላሰቡትንና ከዚህም የተነሳ ደህንነት እንዲሰማቸው የሚያደርጉትን በከተማዋ ዙርያ ያሉትን ግንቦቹንና ማማዎችን”

Proverbs 21:23

አፉንና ምላሱን የሚጠብቅ ሰው
“አፍ” እና “ምላስ” ሰውየው የተናገረውን ነገር ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ለሚናገረው ነገር ጥንቃቄ የሚያደርግ ማንኛውም ሰው” (ጥምር ቃል እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ))

ኩሩና ትዕቢተኛ ሰው ... በእብሪትና በትዕቢት ያደርጋል
“ኩሩና ትዕቢተኛ ሰዎች በእብሪትና በትዕቢት እንሚያደርጉ መጠበቅ ትችላለህ”

ኩሩና ትዕቢተኛ ሰው
እነዚህ ሁለተ ቃላት በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ነገር ናቸው፣ ሰውየው ምን ያህል ትዕቢተኛ እንደሆነ አጽንዖት ይሰጣሉ። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ስሙ “ፌዘኛ” ይባላል
“ስም” የሚለው ቃል ሰዎች ለሚጠሩት መጠሪያው ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ልትጠራው የሚገባህ ፌዘኛ ብለህ ነው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 21:25

የሰነፍ ምኞት ራሱን ይገድለዋል
ጸሐፊው ሰውየው ስለሚፈልገው ነገር ሲናገር ምኞቱ ሰነፍ ሰው ሊገድል የሚችል ሰው አድርጎ ገልጾታል። እዚህ ላይ ሰነፍ ሰው ስራ ፈት እና የማይሰራ መሆን ይፈልጋል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰነፍ ሰው ስራ መፍታት ይወዳል ከዚህ የተነሳ ይሞታል” ወይም “ሰነፍ ሰው ሊሰራ ካለመፈለጉ የተነሳ ይሞታል” (ሰውኛ ዘይቤ እና የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ))

እጆቹ አይፈቅዱም
እጅ ለሰውየው ተዛምዶአዊ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “አይፈቅድም” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ይመኛል
በብርቱ ይፈልገዋል

ይሰጣል፤ አይሰስትም
“አይሰስትም” የሚለው ቃል በአዎንታዊ መንገድ ሊገለጽ ይችላል፤ የሚሰጠው ነገር ደግሞ በግልጽ ሊቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሊሰጥ የሚገባውን ሁሉ ይሰጣል” ወይም “በቸርነት ይሰጣል “ (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 21:27

የክፉዎች መስዋዕት አስጸያፊ ነው
ጸሐፊው በምሳሌ 15:8 ላይ እንዳደረገው እዚህ ላይ እግዚአብሔርን አልጠቀሰም፣ ነገር ግን አንባቢው የክፉዎችን መስዋዕት የሚጸየፈው እግዚአብሔር እንደሆነ ሊያስተውል ይገባል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ክፉ
“ክፉ” የሚለው የስም ቅጽል በስም ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ሰው” ወይም “ክፉ ሰዎች” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ደግሞ የበለጠ አስጸያፊ ነው
“እግዚአብሔር መስዋዕቱን የበለጠ ይጸየፈዋል”

ለሁልጊዜ የሚሆን ይናገራል
እንዲህ የሚሆነው ሰዎች እርሱ የሚናገረውን ስለማይረሱት ነው።

Proverbs 21:29

ፊቱን ያጠነክራል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) “ጀግና እንደሆነ ያስመስላል” ወይም 2) “ተግሳጽን አይሰማም” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ መንገዶቹ እርግጠኛ ነው
የሰው ድርጊት ሰው የሚሄድበት መንገድ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለሚሰራው ነገር እርግጠኛ ነው” ወይም “ስለሚሰራው ነገር ልበ ሙሉ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 21:30

ጥበብ የለም፣ ማስተዋል የለም እና ምክር የለም
“የለም” የሚለው ቃል የተደጋገመው ረቂቅ ስም ለሆኑት “ጥበብ፣” “ማስተዋል” እና “ምክር” አጽንዖት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ማንኛውም ሰው ሊያውቅ ወይም ሊያስብ ወይም ሊናገር ከሚችለው ማንኛውም ነገር ይበልጣል። በአንተ ቋንቋ “የለም” የሚለው ቃል እንዲደጋገም አያስፈልገውም ይሆናል። ይህ ረቂቅ ስም እንደ ቅጽል ወይም ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበበኛ ሰው የለም፣ ነገሮችን የሚያስተውል አንድም ሰው የለም እና ለሌሎች ምን መስራት እንዳለባቸውና ማን መስራት እንደሚገባው የሚነግራቸው አንድም ሰው የለም” ወይም “ጥበብ፣ ማስተዋል ወይም ምክር የለም” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን ሊቋቋም የሚችል
“እግዚአብሔርን የሚያሸንፍ” ወይም “እግዚአብሔር ሊሰራ ከሚፈልገው በተቃራኒ የሚሰራ” ወይም “እርሱ ትክክል እግዚአብሔር ግን ስህተት እንደሆነ ሊያሳይ የሚችል”

ፈረስ ለጦርነት ቀን ይዘጋጃል
እነዚህ ቃላት በገቢር ቅርጽ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ወታደሮች ለጦርነት ቀን ያዘጋጃሉ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የጦርነት ቀን
“ቀን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከቀን ለሚያጥር ወይም ለሚረዝም ጊዜ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ጦርነት በሚኖርበት ጊዜ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 22

1 ከብዙ ሐብት ይልቅ ጥሩ ስም ይመረጣል፣ ሞገስም ከብርና ከወርቅ ይበልጣል። **2** ሃብታምና ድሃ ሰዎች የሚጋሩት አንድ ነገር አለ፤ ይህም እግዚአብሔር የሁሉም ፈጣሪ መሆኑ ነው። **3** ጠንቃቃ ሰው ችግር ሲያይ ራሱን ይሸሽጋል፣ አላዋቂዎች ግን በዚያው ገፍተው ይሄዳሉ በሱም ምክንያት ይጎዳሉ። **4** የትህትናና እግዚአብሔርን የመፍራት ሽልማት ባለጠግነት፣ ክብርና ሕይወት ነው። **5** እሾህና አሜኬላ በጠማማ ሰው መንገድ ላይ ይገኛሉ፤ ሕይወቱን የሚጠብቅም ከእነርሱ ይርቃል። **6** ልጅን የሚሄድበትን መንገድ አስተምረው፣ በሸመገለም ጊዜ ከነገርከው መንገድ ፈቀቅ አይልም። **7** ባለጠጎች ድሆችን ይገዛሉ፣ ተበዳሪም ለአበዳሪው ባርያ ነው። **8** ክፋትን የሚዘራ መከራን ያጭዳል፣ የቁጣውም በትር አይጠቅመውም። **9** ቸር አይኖች ያሉት ሰው ይባረካል፣ እንጀራውን ከድሆች ጋር ይካፈላልና። **10** ፌዘኛን ከአንተ አርቀው፣ ጠብም ከአንተ ይርቃል፤ ግጭትና ስድብም ይቆማሉ። **11** ንጹህ ልብ የሚወድድና ንግግሩም ሞገስ ያለው ሰው፣ ንጉስ ጓደኛው ይሆናል። **12** የእግዚአብሔር ዓይኖች እውቀትን ይከታተላሉ፣ የከዳተኞችን ቃሎች ግን ይገለብጣል። **13** ሰነፍ ሰው “አንበሳ በመንገድ ላይ አለ! በውጪ ላይ እገደላለሁ” ይላል። **14** የአመንዝራ ሴት አፍ ጥልቅ ጉድጓድ ነው፤ ወደ እርሱም በሚወድቅ ሰው ሁሉ የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይሆናል። **15** ሞኝነት በሕጻን ልብ ላይ ታስሯል፣ የስርዓት በትር ግን ከእርሱ ያርቀዋል። **16** ሀብቱን ለማካበት ወይም ለሀብታሞች ለመስጠት ሲል ድሆችን የሚያስጨንቅ፣ ወደ ድህነት ይመጣል። **17** የጠቢብን ቃላት ልብ በል አስተውለህም ስማ፣ ልብህንም ወደ ከእውቀቴ አዘንብል፣ **18** በውስጥህ ብትጠብቃቸውና ሁሉም በከንፈሮችህ ላይ ዝግጁ ቢሆኑ ለአንተ ደስ ያሰኙሃልና። **19** እምነትህ በእግዚአብሔር ላይ ይሆን ዘንድ፣ እነዚህን ለአንተ ዛሬ አስተምርሃለሁ፣ ለአንተም ቢሆን አስተምርሃለሁ። **20** ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎችን ለአንተ አልጻፍኩልህምን፣ **21** በእነዚህ ታማኝ ቃሎች እውነትን አስተምርህ ዘንድ፣ አንተም ለላኩህ ታማኝ መልስ ትሰጥ ዘንድ? **22** ድሃ በመሆኑ ምክንያት ድሃ ሰው አትዝረፍ፣ ችግረኛውንም በበር ላይ አትግፋው፣ **23** እግዚአብሔር ለእነርሱ ይፈርድላቸዋልና፣ የዘረፏቸውንም ሰዎች ሕይወት እርሱ ይነጥቃል። **24** ግልፍተኛ ሰውን ጓደኛ አታድርግ፣ ቁጣም ካለበት ሰው ጋር አብረህ አትሂድ፣ **25** አለበለዚያ መንገዱን ትማራለህ፣ ራስህንም በወጥመድ ታጠላልፋለህ። **26** ገንዘብን በተመለከተ ግዴታ የሚያስገባ ውል የምትሰጥ አትሁን፣ ለሌሎችም ብድር ዋስ አትሁን። **27** መክፈል ካልቻልህ፣ ያንን ሰው አልጋህን ከስርህ ከመውሰድ ሊያቆመው የሚችል ምን ነገር አለ? **28** አባቶችህ ያስቀመጡትን የጥንቱን የድንበር የምልክት ድንጋይ አታንሳ። **29** በስራው ስልጡን የሆነውን ሰው አይተሃልን? በነገስታት ፊት ይቆማል፤ በተራ ሰዎች ፊትም አይቆምም።

Proverbs 22:1

ከብዙ ሐብት ይልቅ ጥሩ ስም ይመረጣል

እነዚህ ቃላት በገቢር ቅርጽ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰው ከብዙ ሀብት ይልቅ ጥሩ ስም ሊመርጥ ይገባዋል። (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥሩ ስም

“ሌሎች ሰዎች አንድ ሰው መልካም እንደሆነ እንዲያስቡ የሚያደርግ”

ሰዎች የሚጋሩት አንድ ነገር

“በአንድ መንገድ ተመሳሳይነት አላቸው” ወይም “በዚህ መልክ ተመሳሳይ ናቸው”

Proverbs 22:3

ጠንቃቃ ሰው

“ጥበበኛ የሆነ ሰው” ወይም “ጥሩ የማመዛዘን ችሎታ ያለው ሰው” ይህንን በምሳሌ 12:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

አላዋቂ ሰው

“ልምድ የሌለው ወይም ብስለት የሌለው ሰው”

Proverbs 22:7

ይበደራል ... ያበድራል

ይህንን መበደር ወይም ማበደር ምን ማለት እንደሆነ ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። አማራጭ ትርጉም፡- “ገንዘብ ይበደራል ... ገንዘብ ያበድራል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ኢፍትሐዊነትን የሚዘራ መከራን ያጭዳል፣

ጸሐፊው ሀይል የሌላቸውን ሰዎች በኢፍትሐዊነት ስለሚያሰቃዩ መሪዎች ወይም ሌሎች ሃያላን ሰዎች ሲናገር እነርሱ መከራ የሚያመጡ ዛፎችን የሚያበቅሉ ዘሮችን እንደዘሩ አድርጎ ገልጿቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰው ከእርሱ ይልቅ ሃይል የሌላቸውን ሰዎች በኢፍትሐዊነት ያሰቃያቸው እንደሆነ በኋላ መከራ ያመጡበታል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የቁጣውም በትር ይጠፋል

“በትር” የሚለው ቃል በሌሎች ሰዎች ላይ ላለን ሃይል ምትክ ስም ነው። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ኢፍትሐዊ መሪ ሌሎች ሰዎችን እንዲያሰቃይ የፈቀደለትን ስልጣን ያጣዋል ወይም 2) እርሱ ለፈጸመው ኢፍትሐዊነት ሰዎች እርሱን በመጉዳት ምላሽ ሲሰጡ እነርሱን ለማስቆም የሚችልበት ምንም ዓይነት ሃይል አይኖረውም። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎችን ለመጉዳት የተጠቀመበት ሃይል ከእንግዲህ ወዲህ ፈጽሞ አይኖረውም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የቁጣው በትር

“በትር” የሚለው ቃል በሌሎች ሰዎች ላይ ላለን ስልጣን ምትክ ስም ነው። ኢፍትሐዊ ሰው በንጹሃን ሰዎች ላይ በጣም እንደተቆጣ ያህል እነርሱን ሲጎዳቸው ነበር። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎችን እንደሚቀጣ ይጠቀምበት የነበረ በትር” ወይም “ሌሎችን ለመጉዳት የተጠቀመበት ሃይል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ይጠፋል

“ይጠፋል” ተብሎ የተተረጎመው ቃል እጽዋት ሲደርቁም ጥቅም ላይ ይውላል።

Proverbs 22:9

ቸር አይኖች ያሉት ሰው ይባረካል

እነዚህ ቃላት በገቢር ቅርጽ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ቸር ዓይን ያለውን ሰው እግዚአብሔር ይባርከዋል። (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ቸር አይኖች ያሉት ሰው

ዓይን ሌሎች ሰዎች የሚያስፈልጋቸውን ለማየት ምትክ ስም ነው፣ “ቸር ዓይን” ደግሞ ማየት ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ሌሎች ሰዎች የሚያስፈልጋቸውን ይሰጣል። ዓይን ለሰው ሁለንተና ተዛምዶአዊ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ቸር ሰው” ወይም “ለሌሎች ሰዎች የተለያዩ ነገሮችን ለመስጠት ፈቃደኛ የሆነ ሰው” (ምትክ ስም እና ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ዳቦ
በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ዳቦ ለብዙ ሰዎች ምግብ ስለነበር በአጠቃላይ ምግብን ለማመልከት ጥቅም ላይ ይውላል። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ግጭትና ስድብም ይቆማሉ
“ግጭት” እና “ስድብ” የሚሉት ረቂቅ ስሞች እንደ ግስ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰዎች እርስ በርሳቸው ለወደፊት አይጨቃጨቁም ወይም እርስ በርሳቸው ለመጎዳዳት ምክንያት የሚሆኑ ነገሮችን አይናገሩም” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 22:11

ንጹህ ልብ ይወዳል
ሰው ንጹህ እንዲሆን የሚፈልገው ልቡ ነው። ልብ ለሰውየው ተዛምዶአዊ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ንጹህ ልብ ሲኖረው ይወዳል” ወይም “ንፁህ እንዲሆን ይፈልጋል” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ቸር ነው
“ደግ ነው”

የእግዚአብሔር ዓይኖች ይከታተላሉ
ዓይን ለሰውየው ተዛምዶአዊ ዘይቤ ነው። ጸሐፊው እግዚአብሔር እንደ ሰው ስጋዊ ዓይን እንዳለው አድርጎ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ይከታተላል” ወይም “እግዚአብሔር እውቀትን ይጠብቃል” (ተዛምዶአዊ እና ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እውቀትን ይከታተላሉ
መከታተል ለጥበቃ ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እውቀት ይይብቃል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ይገለብጣል
“ያጠፋል”

ከዳተኞች
ከዳተኞች የሚለው የስም ቅጽል እንደ ስም ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። “ከዳተኞች” የሚለውን በምሳሌ 11:3 ላይ እንዳለው ተርጉመው። አማራጭ ትርጉም፦ “ከደተኛ ሰው” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 22:13

ሰነፍ ሰው ይላል
ከዚህ የሚቀጥለው አባባል ውሸትና ለላመስራት ምክንያት መስጠት ነው። የአንተ ቋንቋ በተለየ መንገድ ሀሰተኛ አረፍተ ሃሳብ የሚያስተዋውቅ ከሆነ እዚህ ላይ እሱን መጠቀም ትችላለህ።

የአመንዝራ ሴት አፍ ጥልቅ ጉድጓድ ነው
“አፍ” የሚለው ከአፍ ለሚወጡ ቃላት ምትክ ስም ነው። ጸሐፊው ለሰራው ክፉ ስራ ሰዎች ሲቀጡት ሊያመልጥ ስላልቻለ ሰው ሲናገር አንድ ሰው በመሬት ላይ ከቆፈረው ሊያመልጠው ከማይችለው ጉድጓድ እንደወደቀ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፦ “በአመንዝራ ሴት የተነገሩ ቃላቶች ወደታች ያዘቅጥሃል፣ አንተ ወደ ጥልቅና አደገኛ ጉድጓድ እንደወደቅህ ያህል ነው” (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አመንዝራ
ይህንን በምሳሌ 5:3 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

የእግዚአብሔር ቁጣ ይነሳሳል
እዚህ ላይ “ይነሳሳል” የሚለው ቁጣው ይጨምራል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ተቆጥቷል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚያ ይወድቃል
አመንዝራነት ሰው ወደዚያ ሊወድቅበት የሚችልበት ነገር እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “በአመንዝራ ምክንያት ኃጢአት ይሰራል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 22:15

ሞኝነት በሕጻን ልብ ላይ ታስሯል
“የሕጻን ልብ በሞኝነት የተሞላ ነው”

የስርዓት በትር
ጸሐፊው የቅጣት አማራጮችን ስለሚጠቀም ወላጅ ሲናገር ያ ወላጅ ልጁን በእንጨት በትር እንደሚመታ አድርጎ ገልጾታል። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ከእርሱ ያርቀዋል
ጸሐፊው ሞኝነት ሰው እንደሆነና ሌላ ሰው እርሱን ለማራቅ በትር ሊጠቀም እንደሚችልና አድርጎ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “ልጅን ጥበበኛ ያደርገዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሃብቱን ለመጨመር
“የበለጠ ሀብታም ለመሆን” ወይም “የበለጠ ገንዘብ ለማግኘት”

ለሃብታሞች ይሰጣል
“ገንዘብ ለሃብታሞች ይሰጣል”

ወደ ድህነት ይመጣል
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ድሃ ይሆነል። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 22:17

አጠቃላይ መረጃ፦
ቁጥር 17 ለመጽሐፈ ምሳሌ አዲስ ክፍል መግቢያ ሆኖ ይጀምራል።

ጆሮህን አዘንብልና አድምጥ
እዚህ ላይ “ጆሮ” የሚለው ቃል የሚያደምጠውን ሰው ይወክላል። ጸሐፊው አንድን ሰው በጥሞና ስለማድመጥ ሲናገር ጆሮ ወደተናጋሪው መጠጋት እንዲችል በሚናገረው ሰው ላይ እንደመደገፍ አድርጎ ገልጾታል። “ጆሮን ማዘንበል” የሚለውን በምሳሌ 4:20 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “ትኩረት በመስጠት አድምጥ” ወይም “በትኩረት አድምጥ” (ተዛምዶአዊ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የጥበበኛ ቃላት
“ጥበበኛ ሰዎች የሚናገሩት”

ልብ በል
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በሚገባ ለመረዳትና ለማስታወስ የምትችለውን ሁሉ አድርግ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

እውቀቴ
የሚናገረው ሰው ምናልባት በምሳሌ 1:8 ላይ ካለው አባት ጋር ተመሳሳይ ሊሆን ይችላሉ። “እውቀቴ” በማለት የሚናገረው ስለ “ጥበበኛ ቃላት” ሊሆን ይችላል። “እውቀት” የሚለው ረቂቅ ስም “እወቅ” በሚለው ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ከአንተ ጋር የምካፈለው እኔ ያለኝ እውቀት” ወይም “የማውቀውን” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉም በከንፈሮችህ ላይ ዝግጁ ናቸው
ለመናገር ዝግጁ የሆነው ሰው ለመነገር ዝግጁ እንደሆኑት ቃላት ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “አንተ በማንኛውም ጊዜ ቃላቶቹን ለመናገር ትችላለህ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ዛሬ ለአንተ
“ዛሬ። አዎ፣ እኔ እያስተማርኩህ ነው፣” ተናጋሪው የሚያስተምረው አድማጩን እንጂ ሌላ ሰውን እያስተማረ እንዳልሆነ አጽንዖት ይሰጣል፣ አድማጩን የሚያስተምረው ደግሞ አድማጩ መማር ስለሚያስፈልገው ነው። በዚህ መንገድ አጽንዖት መስጠት በቋንቋህ ተስማሚ ካልሆነ በሌላ መንገድ አጽንዖት ልትሰጠው ትችላህ ወይም “ለአንተ” የሚለውን ቃል ሳትተረጉመው ልታልፈው ትችላለህ።

Proverbs 22:20

አጠቃላይ መረጃ፦
እነዚህ ቁጥሮች የሚቀጥሉ ሲሆን በምሳሌ 22፡17 ላይ የተጀመረውን መግቢያ ይጨርሳሉ።

ለአንተ አልጻፍኩልህምን
ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ እንደ ዓረፍተ-ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ለአንተ የጻፍኩልህን ልትረዳው ይገባሃል” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች
አንዳንድ ትርጉሞች “እጅግ በጣም ጥሩ አባባሎች” ብለው ተርጉመውታል። (የጽሑፍ መልክ የሚለውን ይመልከቱ)

ለላኩህ
ይህ የሚያመለክተው አድማጩ መረጃ እንዲያገኝና ይዞ እንዲመለስ የተላከ ነው ወይም ደግሞ ከተላኩት ብዙዎች ውስጥ አንዱ ነው።

Proverbs 22:22

አጠቃላይ መረጃ፦
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይጀምራሉ (ምሳሌ 22:20)።

አትዝረፍ ... አታድቅቀው
የአንተ ቋንቋ አንድ ሰው ለሌላ ሰው ጠንከር ባለ መልኩ የሚናገርበት መንገድ ይህ እንደሆነ የሚያሳዩበትና ሰዎች ሊያከብሩት የሚገባቸው ከአጠቃላይ መመርያ የተለየ መንገድ ካለ እዚህ ላይ ልትጠቀምበት ትችላለህ።

ድኃ
ይህ እንደ ስም ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ማንኘውም ድኃ ሰው” ወይም “ድኃ ሰዎች” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ማድቀቅ
ዱቄት እንዲሆን መፍጨት። ይህ “ኢፍትኀዊነት” ለሚለው ተለዋጭ ዘይቤ ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ችግረኛ
ይህ የስም ቅጽል እንደ ስም ሀረግ ሊተረጎም ይችላ። አማራጭ ትርጉም፦ “ማንኛውም ችግረኛ ሰው” ወይም “ለመኖር የሚያስችለው ነገር የሌለው ማንኛውም ሰው” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

በደጅ ላይ
ይህ ስፍራ ሰዎች የተለያዩ ነገሮች የሚገዙበትና የሚሸጡበት ስፍራና ሕጋዊ ጉዳዮችና ክርክሮች የሚፈቱበት ሲሆን ለንግድና ሕጋዊ ጉዳዮች ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ፍርድ ቤት ውስጥ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ለእነርሱ ይፈርድላቸዋልና
ይህ ተለዋጭ ዘይቤ በዳኛው ፊት ለፊት ችግረኛውን ሰው የሚሟገትለት ዳኛ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ለችግረኞች በጨቋኞቻቸው ፊት ይሟገትላቸዋል” ወይም “እግዚአብሔር ችግረኞች ፍትህ ሲያገኙ ይመለከታል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የዘረፏቸውንም ሰዎች ሕይወት እርሱ ይነጥቃል
እግዚአብሔር ሌባ አይደለም፣ ነገር ግን ቸርነት ለማድረግና ለመስጠት ከማይፈልጉ ሰዎች እንደ ሌባ ሕይወታቸውን ይወስዳል። አማራጭ ትርጉም፦ “ድኃ ሰዎችን የሚጨቁኑ ሰዎች ያጠፋቸዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 22:24

አጠቃላይ መረጃ፦
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።

በቁጣ የሚነዳ ሰው
ቁጣውን መቆጣጠር የማይችል ሰው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ግልፍተኝነት
በጣም ኃይለኛ የሆነ ቁጣ

ለነፍስህም ወጥመድ እንዳታገኝህ
እንደ ቁጡ ሰው መምሰል የሚፈልግ ሰው በወጥመድ ላይ የተቀመጠ ምግብን እንደሚወስድ እንስሳ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ወጥመድ እንዲስፈነጠር ለማድረግ ወጥመድ ላይ የተቀመጠ ምግብን እንደሚበላ እንስሳ ትሆናለህ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለነፍስህ ወጥመድ
ነፍስ ለሰውየው ሕይወት ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ይገድልህ ዘንድ አንድ ሰው የሚያስቀምጠው መሳቢያ ነገር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 22:26

አጠቃላይ መረጃ፦
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።

እጅ ይመታል
አንድ ሰው ሊያደርግ የተስማማውን ነገር የሚያደርግ መሆኑን ቃል ለመግባት በእጁ የሌላውን ሰው እጅ ይመታል። እዚህ ላይ ተናጋሪው የሌላ ሰው ዕዳ እንዲከፍል ቃል በመግባት እጅ እንዳይመታ አድማጩን ያስጠነቅቀዋል።

ውል መስስት
“አንድ ሰው ለሌላ ሰው ያለበትን ዕዳ እንዲከፍል መስማማት”

Proverbs 22:28

አጠቃላይ መረጃ፦
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።

ጥንት
በጣም ያረጀ

የድንበር ድንጋይ
የአንድ ሰው የመሬት ድንበር የት እንደሚያልቅና የሌላው ሰው መሬት የት እንደሚጀምር የሚያሳይ ትልቅ ድንጋይ ነው።

አባቶች
ቅድመ አያቶች

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በስራው ስልጡን የሆነውን ሰው አይተሃልን?
ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ በእርግጥ ትእዛዝ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በስራው ጥበበኛ የሆነ የሆነ የምታውቀውን ሰው አስብ” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በፊቱ ይቆማል
ይህ የወሳኝ ሰው አገልጋይ መሆንን ይወክላል። ነገስታትና ሌሎች ትልልቅ ሰዎች አገልግሎቱን በመመልከት ስለ እርሱ ከፍ አድርገው ያስባሉ። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 23

1 ከገዢ ጋር ለመብላት ስትቀመጥ፣ በፊት ያለውን በጥንቃቄ አስተውል፣ **2** ከመጠን ያለፈ ምግብ መብላት የምትወድ ዓይነት ሰው ከሆንህ በጉሮሮህ ላይ ካራ አድርግ። **3** የእርሱ ጣፋጭ ምግቦች አያስጎምጁህ፣ በውሸት የመጣ ምግብ ነውና። **4** ባለጠጋ ትሆን ዘንድ ከመጠን በላይ አትልፋ፤ መቼ ማቆም እንዳለብህም ታውቅ ዘንድ ብልህ ሁን። **5** አይንህን በገንዘብ ላይ በጣልክ ጊዜ፣ እርሱ ይጠፋል፣ በድንገት ክንፍ ያወጣል እንደ ንስርም ወደ ሰማይ እየበረረ ይሄዳል።፤ **6** የክፉ ሰውን፣ እጅግ በጣም ከርቀት በምግብህ ላይ በቅናት የሚመለከተውን ሰው ምግብ አትብላ፣ ጣፋጭ መብሎቹንም አትጎምጅ፣ **7** እርሱ የምግቡን ዋጋ የሚቆጥር ሰው ነውና። “ብላ፣ ጠጣ!” ይልሃል፣ ልቡ ግን ከአንተ ጋር አይደለም። **8** ትንሽ የበላኸው ያስታውክሃል፣ የምስጋና ቃልህንም ከንቱ ታደርጋለህ። **9** ሞኝ ሰው ባለበት ንግግር አታድርግ፣ እርሱ የቃሎችህን ጥበብ ያንኳስሳልና። **10** የጥንቱን የድንበር የምልክት ድንጋይ አታንሳ፣ ወላጅ የሌላቸውን ልጆች እርሻ አትግፋ፣ **11** ታዳጊያቸው ብርቱ ነውና፣ እርሱ ጉዳያቸውን ከአንተ ጋር ይፋረዳል። **12** ልብህን ለተግሳጽ ጆሮህንም ለእውቀት ቃሎች ስጥ። **13** ልጅን ከመቅጣት ወደ ኋላ አትበል፣ በበትር ብትመታው አይሞትምና። **14** በበትር ብትመታው ነፍሱን ከሲኦል ታድናታለህ። **15** ልጄ ሆይ፣ ልብህ ጥበበኛ ቢሆን፣ ያኔ ልቤ ደግሞ ደስተኛ ይሆናል፤ **16** ከንፈሮችህ ትክክለኛ የሆነውን በሚናገሩበት ጊዜ ውስጣዊ ሰውነቴ ሁሉ ደስ ይለዋል። **17** ልብህ በኃጢአተኞች እንዲቀና አትፍቀድ፣ ነገር ግን ቀኑን ሙሉ እግዚአብሔርን በመፍራት ተመላለስ። **18** ለወደፊት እርግጠኛ አለኝታ አለህ፣ ተስፋህም አይጠፋም። **19** ልጄ ሆይ፣ ስማኝ፣ ጥበበኛ ሁን ልብህንም በትክክለኛው መንገድ ላይ አዘንብል። **20** ከሰካራሞች ወይም በሆዳምነት ስጋ ከሚበሉ ጋር አትተባበር፣ **21** ሰካራሞችና ሆዳሞች ድሃ ይሆናሉ፣ እንቅልፋምነትም ቁራጭ ጨርቅ ያስለብሳቸዋል። **22** የወለደህን አባትህን ስማ እናትህም ባረጀች ጊዜ አትናቃት። **23** እውነትን የራስህ አድርጋት፣ አትሸጣትም፤ ጥበብን፣ ስርዓትንና ማስተዋልንም ገንዘብህ አድርግ። **24** የጻድቅ አባት በደስታ ይሞላል፣ ጥበበኛ ልጅንም የወለደ በልጁ ይደሰታል። **25** አባትህና እናትህን ደስ አሰኛቸው፣ የወለደችህ እናትህም ሐሴት ታድርግ። **26** ልጄ ሆይ፣ ልብህን ስጠኝ፣ አይኖችህም የእኔን መንገድ ያስተውሉ። **27** ዝሙት አዳሪ ሴት ጥልቅ ጉድጓድ፣ የሌላ ሰውም ሚስት ጠባብ ጉድጓድ ናትና። **28** እንደ ሌባ አድፍጣ ጥጠብቃለች፣ በሰዎችም መካከል የከዳተኞችን ቁጥር ታበዛለች። **29** ዋይታ የማን ነው? ሃዘን የማን ነው? ጠብስ የማን ነው? ማጉረምረም የማን ነው? ያለ ምክንያት መቁሰል የማን ነው? የዓይን መቅላት የማን ነው? **30** ወይን ጠጅ በመጠጣት የሚቆዩ፣ ድብልቅ ወይን ጠጅ የሚቀምሱ ሰዎች ነው። **31** በቀላ ጊዜ ወደ ወይን ጠጅ አትመልከት፣ በብርጭቆ ውስጥ መልኩ ባንጸባረቀ ጊዜ የሚያንጸባርቅ በሆነ ጊዜ፣ ስትጠጣውም ያለ ምንም ችግር በገባ ጊዜ። **32** በመጨረሻ እንደ እባብ ይናከሳል፣ እንደ እፉኝትም ይናደፋል። **33** አይኖችህ አዲስ ነገሮችን ያያሉ፣ ልብህም ጠማማ ነገሮችን ይናገራል። **34** በባህር ከፍታ ላይ እንደተኛ፣ በመርከብ ምሰሶ ጫፍ ላይ እንደተጋደመ ሰው ትሆናለህ። **35** “መቱኝ!” “ነገር ግን አልተጎዳሁም። ደበደቡኝ፣ ነገር ግን አልተሰማኝም። መቼ ይሆን የምነቃው? ሌላ መጠጥ እፈልጋለሁ።” ትላለህ።

Proverbs 23:1

አጠቃላይ መረጃ፦
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።

በጉሮሮህ ላይ ካራ አድርግ
ለዚህ ግነት ፤ሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፦ 1) “ብዙ እንዳትበላ ጠጠንቀቅ” ወይም 2) “ምንም ነገር እትብላ” (ግነትና ጅምላ ፍረጃ እና ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

አትመኝ
“ክፉኛ አትጎምጅ።” ይህንን በምሳሌ 21፡19 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

ጣፋጭ ምግቡ
“ልዩና ውድ ምግቦቹ”

ይህ በውሸት የተገኘ ምግብ ነው
ይህ ፈሊጥ ነው። “ያታልልህ ዘንድ ይሰጥሃል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 23:4

አጠቃላይ መረጃ፦
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።

ከመጠን በላይ አትልፋ
“ሁልጊዜ እንዳትደክም ከመጠን በላይ አትስራ”

በ ... ላይ አትጣል
በሐብት ላይ እንደ ወፍ አትረፍ (ቁጥር 4)። ይህ በሐብት ላይ ለአጭር ጊዜ ዓይንን መጣል ለሚለው ተለዋጭ ዘይቤ ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በድንገት ክንፍ ያወጣል እንደ ንስርም ወደ ሰማይ እየበረረ ይሄዳል
ሐብቱን ስላጣ ሰው ሲናገር ሐብቱ ወፍ እንደሆነ ተደርጎ ተገልጿል። አማራጭ ትርጉም፦ “ንስር በፍጥነት እንደሚበርር እነደዚሁ ሐብት በፍጥነት ይጠፋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ንስር ክንፍ
እንደ ንስር ክንፍ የመሰለ ክንፍ

Proverbs 23:6

አጠቃላይ መረጃ፦
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።

ክፉ ዓይን ያለው ሰው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) ተናዳፊ ሰው፣ ለሌሎች ሰዎች ያለውን ነገር ለመስጠት የማይወድ ሰው ወይም 2) ክፉ ሰው።

አትመኝ
“አጥብቀህ አትጎምጅ።” ይህንን በምሳሌ 21:9 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

ጣፋጭ መብሎቹ
“ልዩና ውድ የሆኑ ምግቦቹ” ይህንን በምሳሌ 23:3 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ልቡ ከአንተ ጋር አይደለም
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ምግቡን እንድትበላና እንድትደሰት በእርግጥም አይፈልግም” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ትንሽ የበላኸው ያስታውክሃል
ይህ አንድ ሰው ምንም ነገር ባልበላሁ ብሎ ለተመኘው ግነት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ምንም ነገር ባትበላ ትመኝ ነበር” (ግነትና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የምስጋና ቃልህንም ከንቱ ታደርጋለህ
ምስጋና እጅግ ውድና የከበሩ ነገሮች እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። “ምስጋና” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለ እርሱና ስላቀረበልህ ምግብ መልካም ነገር ብትነናገር እንኳ ደስተኛ አይሆንም” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 23:9

አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።

ሞኝ ሰው በሚሰማበት
ይህ “በሚሰማበት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሞኝ ሊሰማህ በሚችልበት ስፍራ” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ጥንት
በጣም ያረጀ። ይህንን በምሳሌ 22:28 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

የድንበር ድንጋይ
የአንድ ሰው የመሬት ድንበር የት እንደሚያልቅና የሌላው ሰው መሬት የት እንደሚጀምር የሚያሳይ ትልቅ ድንጋይ ነው። ይህንን በምሳሌ 22:28 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

ጥሶ ገባ
ይህ የሌላ ሰውን መሬት (ወይም ሌላ ነገር) ቀስ በቀስ መውሰደድ ወይም ለመጠቀም መጀመር ማለት ነው።

መላጅ አልባ
መወላጆቻቸው የሞቱባቸው ልጆች

ታዳጊያቸው
እግዚአብሔር

እርሱ ጉዳያቸውን ከአንተ ጋር ይፋረዳል
ይህ ተለዋጭ ዘይቤ ጠበቃ በዳኛ ፊት ችግረኞችን ሲከላከልላቸው የሚያሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ወላጅ አልባዎችን ከአንተ ይከላከልላቸዋል” ወይም “ወላጅ አልባዎች ፍትህ ሲቀበሉና አንተ ስትቀጣ ያያል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 23:12

አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።

ልብህን ስጥ
ይህ ፈሊጥ ነው። ይህንን በምሳሌ 22:17 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “ለመረዳትና ለማስታወስ የምትችለውን ሁሉ አድርግ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ቅጣት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) “ትክክል እና ስህተት የሆነውን ነገር ምን እንደሆነ የሚያውቁ ሰዎች የሚነግሩህ” ወይም 2) “አንተን ሲያስተካክሉህ ሰዎች የሚናገሩትና የሚያደርጉት ነገር”

ጆሮችህ
ይህ አስጨምሬ ሊሞላ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጆጥንቃቄ አድምጥ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

የእውቀት ቃላት
“ለእኔ የማውቀውን ነገር ለአንተ ስነግርህ”

Proverbs 23:13

አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።

ልጅን ከመቅጣት ወደ ኋላ አትበል
ይህ “ቅጣት” የሚለው እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ልጅን ከመቅጣት ቸል አትበል” ወይም “ልጅን ለመቅጣት እምቢይ አትበል” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ያዘ
ሌላ ሰው እንደሚያስፈልገው እያወቀ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን

በትር
ከእንጨት የተሰራ ዱላ

በበትር ልትመታው የሚገባህ አንተ ነህ ... እና ነፍሱን ታድናለህ
“ልትመታው የሚገባህ አንተ ነህ ... እና ነፍሱን ታድናለህ” ከአንተ ሌላ ማንም ይህን አያደርገውም። አድማጩ የልጁን ነፍስ ከሲኦል ለማዳን ኃላፊነት አለው፣ ልጁን ለማዳን መንገዱ ደግሞ መምታት ነው።

ነፍሱን ከሲኦል ታድናለህ
አድማጩ ልጆቹን በበትር ቢመታቸው በሰሩት ሞኝነት ወይም ክፉ ነገር በልጅነታቸው አይሞቱም። “ነፍስ”` የሚለው ቃል ለሰውየው ምትክ ስም ነው። ሲኦል የሙታን ዓለም ነው፤ ወደ ሙታን ዓለም መሄድ የሚለው ሀረግ ለመሞት ለስላሴ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ወደ ሙታን ዓለም ከመሄድ ትጠብቀዋለህ” ወይም “ከመሞት ትጠብቀዋለህ” (ምትክ ስም እና ለስላሴ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 23:15

አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።

አፎችህ ሲናገሩ
“አፈች” ማት የሰው ሁለንተና ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ስትናገር” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 23:17

አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።

ልብህ በኃጢአተኞች እንዲቀና አትፍቀድ
“ልብ” የሚለው ቃል ለሰው ሁለንተና ተዛምዶአዊ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በሀጢአተኞች ላይ እድትቀና አትፍቀድ” ወይም “በሀጢአጠኞች ላይ አለመቅናትህ እርግጠኛ ሁን” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ተስፋህ አይጠፋም
ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ተስፋህን ማንም ሰው እንዲያጠፋው እግዚአብሔር አይፈቅድም” ወይም “እግዚአብሔር ለአንተ የገባልህን ቃል ኪዳን ይጠብቃል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 23:19

አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።

ልጄ ሆይ፣ ስማኝ
“ልጄ ሆይ በጠንቃቄ ስማኝ።” ተናጋሪው አድማጩ በአግባቡ ትኩረት ሰጥቶ እንደሆነ እርግጠኛ ለመሆን ተጨማሪ ቃላት ይናራል።

ልብህንም በትክክለኛው መንገድ ላይ አዘንብል
ትክክለኛውን ነገር ለማድረግ መወሰን አንድ ሰው ለሌላ ሰው ትክክለኛውን መንገድ እንዲከተለው እንደማሳየት ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበብ ያለበትን ነገር ለማድረግህ እርግጠTኛ ሁን” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በሆዳምነት ስጋ የሚበሉ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) “መብላት ከሚያስፈለጋቸው በላይ ብዙ ስጋ የሚበሉ ሰዎች” ወይም 2) “ስጋ” በአጠቃላይ ምግብን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “መብላት ከሚያስፈልጋቸው በላይ ብዙ ምግብ የሚበሉ ሰዎች (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

እንቅልፋምነት ቁራጭ ጨርቅ ያስለብሳቸዋል
“እንቅልፋምነት” የሚለው ቃል አስፈላጊ ስራ ሳይሰራ ምግብ በመብላትና መጠጥ በመጠጣት ብዙ ጊዜውን ለሚያሳልፍ ሰው በግነት የተጻፈ ነው። ይህ ድርጊት ወላጅ ለልጁ ልብስ እንደሚያለብሰው ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ በመብላትና በመጠጣት ብዙ ጊዜአቸውን ስለሚያጠፉ ምንም ስራ አይሰሩም፣ ከዚህ የተነሳ ድኃ ይሆናሉ” (ሰውኛ ዘይቤ እና ግነትና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 23:22

አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።

አትናቃት
ይህ በአዎንታዊ መንገድ ሊጸፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለእርስዋ አክብሮት አሳይ” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

እውነትን የራስህ አድርጋት፣ አትሸጣትም፤ ጥበብን፣ ስርዓትንና ማስተዋልንም ገንዘብህ አድርግ።
ሌሎች አማራጭ ትርጉሞች፡- “እውነትን የራስህ አድርጋት፣ ጥበብን፣ ስርዓትንና ማስተዋልንም ገንዘብህ አድርግ።” “እውነት፣” “ጥበብ፣” “ስርዓትና” “ማስተዋል” የሚሉት ቃላት ረቂቅ ስሞች ሲሆኑ ቁሳዊ ነገሮች እንደሆኑና አንድ ሰው ወደ ገበያ ሄዶ የሚገዛውና የሚሸጠው እንደሆነ ተደርገው ተገልጸዋል። እነዚህ በገቢር ግስ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “እውነት የሆነውን ማወቅ እንድትችል፣ ጥበበኛ እንድትሆን፣ አንድን ነገር እንዴት መስራት እንዳለብህ መማር እንድትችል እና ከመጥፎ ይልቅ መልካም ነገር መናገር እንድትችል ማድረግ የሚገባህን አድርግ፤ ከእነዚህ ነገሮች በላይ የበለጠ ጠቃሚ ነገር እንዳለ ፈጽሞ አታስብ” (ረቂቅ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 23:24

አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።

የጻድቅ ሰው አባት በደስታ ይሞላል፣ ጥበበኛ ልጅንም የወለደ በልጁ ይደሰታል።
ሌሎች አማራጭ ትርጉሞች፡- “የወለደ” የሚለው “የጻድቅ ሰው አባት” ማን እንደሆነ ያብራራል። አማራጭ ትርጉም፡- “የጻድቅ ሰው አባት፣ ጥበበኛ ልጅንም የወለደ፣ በደስታ ይሞላል ደግሞም በልጁ ይደሰታል።”

በእርሱ ደስ ይሰኛል
“ከእርሱ የተነሳ ደስ ይለዋል”

Proverbs 23:26

አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።

ልብህን ስጠኝ
“ልብ” የሚሚው ቃል ሰው ለሚያስበውና ለማድረግ ለሚወስነው ምትክ ስም ነው። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) “ጥንቃቄ የተሞላበትe ትኩረት አድርግ” ወይም 2) “ሙሉ በሙሉ እኔን ታመን” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ዓይኖችህ ያስተውሉ
“ዓይን” ለሰው ሁለንተና ተዛምዶአዊ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አስተውል” ወይም “በጥንቀቄ ተመልት” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ዝሙት አዳሪ ሴት ... ምግባረ ብልሹ ሴት
በወሲብ ሕይወታቸው ምግባረ ብልሹ የሆኑ ሁለት ዓይነት ሴቶች አሉ። “ዝሙት አዳሪ” ያላገባች ናት፣ “የሌላ ሰው ሚስት” ያገባች ናት። ሁለቱ በአንድ ላይ ለማንኛውም በወሲብ ምግባረ ብልሹ ለሆኑት ሴቶች ጥምረ ቃል ይፈጥራሉ። (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዝመት አዳሪ ሴት ጥልቅ ጉድጓድ ናት
“ጉድጓድ” የሚለው ቃል ከዝሙት አዳሪ ሴት ጋር የሚተኙ ወንዶች ላይ ምን እንሚሆባቸው የሚያሳይ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ከዝሙት አዳሪ ሴት ጋር መተኛት በጥልቅ ጉድጓድ እንደመውደቅ ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዝሙት አዳሪ ሴት
እዚህ ላይ ቃሉ የሚያመለክተው ይህንን ስራ ገንዘብ ለማግኘት ብለው ለሚሰሩ ብቻ ሳይሆን ወሲብ ለምትፈጽም ማንኛዋንም ያላገባችን ሴት ነው።

ጥልቅ ጉድጓድ ... የጠለቀች አዘቅት
“ጉድጓድ” በጣም “ጥልቅ” ስለሆነ “አዘቅት” ደግሞ “ጠባብ” ስለሆነ እነዚህ ወደ ውስጥ ለመውደቅ በጣም ቀላልና ለመውጣት ግን በጣም ከባድ የሆኑ ስፍራዎች ናቸው።

ምግባረ ብልሹ ሴት ጠባብ አዘቅት ናት
አንድ ሰው የሚቀጣበትን ክፉ ስራ መስራት ፈጽሞ ሊያመልጠው በማይችለው በጠባብ ስፍራ እንደ መውደቅ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከሌላ ሰው ሚስት ጋር መተኛት በጠባብ አዘቅት እንደ መውደቅ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የውኃ ጉድጓድ
ሰዎች ውኃ ለማግኘት ሲሉ በመሬት ላይ የቆፈሩት ጉድጓድ

አድፍጣ ትጠብቃለች
ተጠቂ ሲመጣ ለማጥቃት በስውር ትጠብቃለች

ከዳተኛ ሰው
ይህ የስም ቅጽል እንደ ቅጽል ወይም እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከዳተኛ ሰዎች”` ወይም “ሌሎች ሰዎችን በማታለል የሚጎዱ ሰዎች” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 23:29

አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።

ዋይታ የማን ነው? ሃዘን የማን ነው? ጠብስ የማን ነው? ማጉረምረም የማን ነው? ያለ ምክንያት መቁሰል የማን ነው? የዓይን መቅላት የማን ነው?
ጸሐፊው እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመው ስለ አንድ ሰው መናገር የፈለገውን ነጥብ አንባቢው መጨበጥ እንዲችል ለማዘጋጀት ነው። ለእያንዳንዱ ጥያቄ መልስ እንዲመለስለት አይጠብቅም። የአንተ ቋንቋ አንድን ትምህርት ለማስተዋወቅ የተለየ መንገድ ይኖረው ይሆናል። አማራጭ ትርጉም፡- “ምን ዓይነት ሰው ዋይታ፣ ኃዘን፣ ትግል፣ ማጉረምረም፣ ያለ ምንም ምክንያት ቁስልና የዓይን ቅላት እንዳለበት ስነግርህ አድምጠኝ። (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የዓይን ቅላት
“እንደ ደም ቀለም ዓይን መቅላት”

ወይን ጠጅ በመጠጣት የሚቆዩ፣ ድብልቅ ወይን ጠጅ የሚቀምሱ ሰዎች ነው
እነዚህ ቃላቶች በቁጥር 29 ለተጠየቁት ጥያቄዎች መልስ የሚሰጡና ብዙ ወይን የሚጠጡ ሰዎችን የሚገልጹ ናቸው።

ወይን ጠጅ በመጠጣት የሚቆዩ
ወይን በመጠጣት ብዙ ጊዜ የሚያሳልፉና ከዚህ የተነሳ ብዙ ወይን የሚጠጡ (ለስላሴ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ድብልቅ ወይን
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) የተለያዩ ወይኖች በአንድ ላይ ተደባልቀው ወይም 2) ከወይን ይልቅ በጣም ጠንካራ የሆኑ መጠጦች

Proverbs 23:31

አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።

በመጨረሻ
“ወይኑን ከጠጣህ በኋላ”

እንደ እባብ ይናከሳል ... እንደ እፉኝትም ይናደፋል
“ይናከሳል” እና “ይናደፋል” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት “ወይኑ ቀይ ሲሆን” ነው። “ንክሻ” እና “ንድፊያ” ብዙ ወይን ሰዎች እንዲሰማቸው ለሚያደርግበት መንገድ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እባብ እንደነከሰህና እፉኝት እንደነደፈህ እንደነደፈህ መጥፎ ስሜት እንዲሰማህ ያደርጋል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እፉኝት
መርዘኛ የእባብ ዓይነት

ልብህ ጠማማ ነገሮችን ይናገራል
“ልብ” የሚለው ቃል የሚወክለው ሰውየውን ሲሆን ለሚያስበውና ለማድረግ ለሚወስነው ነገር አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ነገር ታስባለህ ደግሞም ጠማማ ነገሮችን ለማድረግ ትወስናለህ” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ጠማማ ነገሮች
እግዚአብሔር በስነ ምግባር የተበላሹና መጥፎ እንደሆኑ የተናገራቸው፤ ክፉ የሆኑ ነገሮች

Proverbs 23:34

አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)። የሰካራም ሰው ገለጻ ቀጣይ ክፍሎች ናቸው።

ምሰሶ ጫፍ ላይ ይጋደማል
ሰውየው የተጋደመበት ምሰሶ ጫፍ ላይ ያለው ስፍራ በሚገባ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በምሰሶ ጫፍ አጠገብ በቅርጫት ውስጥ ተጋድሟል” (ፈሊጥ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ምሰሶ ጫፍ
ቀዛፊ መርከብ ላይ ያሉ የመርከብ ሸራዎችን የሚያያይዙ በጣም ረጅም የእንጨት ምሰሶዎች።

“መቱኝ!” “ነገር ግን አልተጎዳሁም። ደበደቡኝ፣ ነገር ግን አልተሰማኝም።
የሰከረ ሰው በሚገባ ማሰብ ስለማይችል ሰዎች እንደሚመቱትና እንደሚደበድቡት ያስባል፣ ነገር ግን ምንም ዓይነት ሕመም አይሰማውም ደግሞም ምንም ዓይነት ነገር አያስታውስም።

መጩ እነቃለሁ?
የሰከረ ሰው እንደገና የሚነቃበትን ጊዜ መቼ እንደሆነ ይጠይቃል፤ የወይን ስራ በውስጡ መስራት ባቆመ ጊዜ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 24

1 ክፉ በሆኑ ሰዎች አትቅና፣ ከእነርሱም ጋር ለመተባበር አትፈልግ፣ **2** ምክንያቱም ልባቸው ግጭትን ያሴራል፣ ከንፈራቸውም ችግርን ያወራል። **3** ቤት በጥበብ ይሰራል፣ በማስተዋልም ይጸናል። **4** በእውቀትም ውድና ባማሩ እቃዎች ክፍሎቹ ይሞላሉ። **5** ጥበበኛ ሰው ብርቱ መሆኑን ያረጋግጣል፣ እውቀት ያለውም ሰው ከጠንካራ ሰው ይልቅ ይሻላል፣ **6** በጥበበኛ ምክር ጦርነትህን መዋጋት ትችላለህ፣ በብዙ አማካሪዎችም ድል ይገኛልና። **7** ለሞኝ ሰው ጥበብ እጅግ ትርቃለች፤ በበርም አፉን አይከፍትም። **8** ክፋትን ለማድረግ የሚያስብ አንድ ሰው አለ፣ ሰዎችም የተንኮል አለቃ ብለው ይጠሩታል። **9** የስንፍና እቅድ ኃጢአት ነው፣ ሰዎችም ፌዘኛን ይንቁታል። **10** በችግር ጊዜ ፍርሃትህን ካሳየህ፣ እንግዲያው አቅምህ ትንሽ ነው። **11** ወደ ሞት የሚወሰዱትን አድናቸው፣ እየተጎተቱ ለመታረድ የሚነዱትንም ይዘህ መልሳቸው። **12** አንተም “እዚያ! ስለዚህ ነገር ምንም አናውቅም” ብትል ልብን የሚመረምረው እርሱ ንግግርህን አያስተውለውምን? ሕይወትህን የሚጠብቀው እርሱ አያውቅምን? ለእያንዳንዱ እንደ ስራው መጠን እግዚአብሔር አይሰጠውምን? **13** ልጄ ሆይ፣ መልካም ነውና ማር ብላ፣ የማር ወለላ ጠብታዎች ለጣዕምህ ጣፋጭ ናቸው። **14** ጥበብም ለነፍስህ እንዲህ ነው፣ ካገኘኸውም፣ ወደፊት ዋስትና ይኖርሃል፣ ተስፋህም አይጠፋም። **15** ጽድቅን የሚያደርጉ ሰዎችን ቤት እንደሚዘርፉ ክፉ ሰዎች አድፍጠህ አትጠብቅ። የጻድቁንም ቤት አታፍርስ። **16** ጽድቅን የሚያደርግ ሰው ሰባት ጊዜ ቢወድቅ፣ እንደገና ከወደቀበት ይነሳልና፣ ክፉዎች ግን ይቀሰፋሉ። **17** ጠላትህ በወደቀ ጊዜ ደስ አይበልህ፣ በተሰናከለም ጊዜ ልብህ ደስ አይበለው፣ **18** እግዚአብሔር ያያል፣ ተመልሶም ቁጣውን ከእርሱ ይመልሳልና። **19** ክፋትን በሚያደርጉ ሰዎች አትጨነቅ፣ በክፉዎችም አትቅና፣ **20** ክፉ ሰው ተስፋ የለውምና፣ የክፉ ሰውም መብራት ይጠፋልና። **21** እግዚአብሔርን ፍራ፣ ንጉስንም ፍራ፣ ልጄ ሆይ፤ በእነርሱ ላይ ከሚያምጹ ሰዎችም ጋር አትተባበር፣ **22** ጥፋታቸው በድንገት ይመጣልና፣ ከሁለቱም የሚመጣባቸውን ጥፋት ምን ያህል እንደሆነ ማን ያውቃል? **23** እነዚህ ደግሞ የጥበበኛ ሰው ንግግር ናቸው። በዳኝነት አድልዎ ማድረግ መልካም አይደለም። **24** ወንጀለኛውን “ጻድቅ ነህ” የሚለው በሕዝብ ዘንድ ይረገማል፣ በመንግስታትም ዘንድ ይጠላል። **25** ነገር ግን በደለኛውን የሚገስጹ ደስታ ይሆንላቸዋል፣ የደግነት ስጦታዎችም ወደ እነርሱ ይመጣሉ። **26** እውነተኛ መልስ የሚሰጥ ሰው ከንፈሮችን ይስማል። **27** የውጪ ስራህን አዘጋጅ፣ በመስክም ሁሉንም ነገር ለራስህ ዝግጁ አድርግ፣ ከዚያም በኋላ ቤትህን ስራ። **28** ያለ ምክንያት በጎረቤትህ ላይ አትመስክር፣ በከንፈሮችህም አታታልል። **29** “እርሱ በእኔ ላይ ያደረገውን እኔም በእርሱ ላይ አደርግበታለሁ፤ በእኔ ላይ ላደረገው ነገር ዋጋውን እከፍለዋለሁ” አትበል። **30** በሰነፍ ሰው እርሻ በኩል ሄድሁ፣ አእምሮ በሌለውም ሰው የወይን እርሻ አለፍሁ። **31** እሾህም በየቦታው በቅሎ ነበር፣ መሬቱም በሳማ ተሸፍኖ ነበር፣ የድንጋይ ካቡም ፈርሶ ነበር። **32** ከዚያም አየሁና አሰብኩኝ፤ ተመለከትሁና ተግሳጽን ተቀበልሁ። **33** ጥቂት መተኛት፣ ጥቂት እንቅልፍ፣ ጥቂት ለማረፍ እጅን ማጣጠፍ፣ **34** ድህነት እንደ ሌባ በአንተ ላይ ይመጣል፣ ችግርህም መሳርያ እንደታጠቀ ወታደር ይመጣብሃል።

Proverbs 24:1

አጠቃላይ መረጃ፦
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።

ልባቸው
“ልባቸው” የሚለው ቃል የሰው ሁለንተና የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እነርሱ” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ከንፈሮቻቸው
“ከንፈሮቻቸው” የሚለው ቃል የሰው ሁለንተና የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እነርሱ” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 24:3

አጠቃላይ መረጃ፦
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።

ቤት በጥበብ ይሰራል፣
“ጥበብ” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። እነዚህ ቃላቶች በገቢር ግስ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰዎች ጥሩ ቤት መስራት የሚፈልጉ ከሆነ ጥበበኛ መሆን አለባቸው” (ረቂቅ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በማስተዋልም ይጸናል
ይህ “ማስተዋል” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰዎች ቤት ለመስራት የሚፈልጉ ከሆነ መልካም ባህርይና መጥፎ ባህርይ ምን እንደሆነ መረዳት አለባቸው” (ረቂቅ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ይጸናል
“ይጸናል” የሚለው ቃል ጽኑ እና ጠንካራ መሆን ማለት ነው። “ቤት” የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩት ቤተሰቦች ምትክ ስም ነው፣ ጽኑ እና ጠንካራ ሆኖ የተሰራው ቤት ደግሞ በቤት ውስጥ ለሚኖሩት ቤተሰቦች ተለዋጭ ዘይቤ ነው። (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በእውቀትም ክፍሎቹ ይሞላሉ
“እውቀት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰዎች መኖርያ ክፍሎቻቸው እንዲሞሉ የሚፈልጉ ከሆነ ውድና አስደሳች የሆነውን ነገር ማወቅ ያስፈልጋቸዋል” (ረቂቅ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 24:5

አጠቃላይ መረጃ፦
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።

ተዋጊና ጥበበኛ
ይህ “ጥበብ” የሚለው ረቂቅ ስም “ጥበበኛ” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ጥበበኛ ተዋጊ” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እውቀት ያለው ሰው ጥንካሬውን ይጨምራል
ይህ “እውቀት” እና “ጥንካሬ” የሚሉት ረቂቅ ስሞች “እወቅ” በሚለው ግስ እና “ጠንካራ” በሚለው ቅጽል ሊተረጎም ይችላል” አማራጭ ትርጉም፦ “ብዙ ነገሮች የሚያውቅ ሰው ጠንካራ ነው ምክንያቱም እነዚህን ነገሮች ያውቃል” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በጥበበኛ ምክር
ይህ “ምክር” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊተረገም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ምን ማድረግ እንዳለብህ የሚነግሩህ ጥበበኛ ሰዎች” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ጦርነትህን መዋጋት ትችላለህ፣
“ጦርነት ተዋጋ”

አማካሪዎች
ለመንግስት አካላት ምን ማድረግ እንዳለባቸው የሚነግሩአቸው ሰዎች

Proverbs 24:7

አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።

ለሞኝ ሰው እጅግ ትርቃለች
ይህ “ለሞኝ ሰው እጅግ ትርቃለች” የሚለው ፈሊጥ ነው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

አፉን አይከፍትም
አፍ የሚለው ቃል ከአፍ ለሚወጡ ቃላት ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “መናገር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 24:8

አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።

የተንኮል አለቃ
ክፉ እቅድ የሚያቅድ ክህሎት ያለው ሰው። አማራጭ ትርጉም፡- “አታላይ ሰው” ወይም “ችግር ፈጣሪ”

Proverbs 24:10

አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።

አቅምህ ትንሽ
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በጣም ትንሽ ኃይል አለህ” ወይም “በእርግጥም ደካማ ነው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 24:11

አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።

የሚነዱትን
እነዚህ ቃላት “እነርሱ” በሚለውና ማንኛውም ሰው የሚል ትርጉም ባለው ቃል በመጠቀም በገቢር ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል፣ ነገር ግን እነዚህ የመንግስት ባለስልጣኖች ሊሆኑ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱን የወሰዱአቸው ሰዎች” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የተወሰዱ
ሌላ አማራጭ ትርጉም “የተጎተቱ” የሚል ነው።

የሚንገዳገዱትን
እየተንቀጠቀጡ መራመድና ለመውደቅ መድረስ። ይህ ቃል አንድ ሰው ሲጎተት እንዴት እንደሚራመድ የሚገልጽ ነው።

ለመታረድ
“መታረድ” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። ጸሐፊው ሲናገር የሚወስዱአቸው ሰዎች ከእንስሳሳ ያልተሸሉ እንደሆኑ ያስባል። የአንተ ቋንቋ እንስሳትን ለማረድ የሚገልጽበት ቃል ካለው እርሱ ተገቢ ሊሆን ይችላሉ፣ ይህንን መጠቀም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፡- “እንስሳ እንደሚገድሉ ሰዎችን ወደሚገድሉበት ሰፍራ” (ረቂቅ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተም “እዚያ! ስለዚህ ነገር ... ” ብትል
ጸሐፊው አንባቢው ምናልባት በስህተት ስላሰበው አንድ ነገር መልስ እየሰጠው ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እንዲህ ትላህ ‘እነሆ፣ ... ይህ፣’ ነገር ግን ሰራ”

እነሆ፣ እኛ
“እኛን አዳምጡ! እኛ” ወይም “ነገር ግን እኛ” ወይም “እኛ ምንም ሰህተት ነገር አልሰራንም፣ ምክንያቱም እኛ ... ”

ልብን የሚመረምረው እርሱ ንግግርህን አያስተውለውምን?
ጸሐፊው አንባቢዎቹ መልሱን ያውቃሉ ብሎ ያስባል፣ ከዚህ የተነሳ አጽንዖት ለመስጠት ሲል ይህን ጥያቄ ይጠይቃል። አማራጭ ትርጉም፡- “ልብን የሚመረምረው እርሱ ንግግርህን በሚገባ ይረዳል” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ
ጸሐፊው “እርሱ” የሚለው እግዚአብሔር እንደሆነ አንባቢው ያውቃል ብሎ ያስባል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር፣ እርሱ” (ለስላሴ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ልብን ይመረምራል
“ልብ” ሰው ለሚያስበውና ለሚመኘው ነገር ምትክ ስም ነው። ጸሐፊው ሰው የሚያስበውና የሚመኘው ነገር ቁስ የሆነ ያህል ሰው የሚመዝነው አድርጎ ተናግሮታል፤ አንድን ነገር መመዘን ምን ያህል ጥሩ እንደሆነ ለማወቅ አንድ ነገር ላይ አስተውሎ ለማየት ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች የሚያስቡትና የሚመኙት ነገር ምን ያህል ጥሩ እንደሆነ ያውቃል” (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሕይወትህን የሚጠብቀው እርሱ አያውቅምን?
ጸሐፊው አንባቢዎቹ መልሱን እንደሚያውቁት ያስባል ከዚህ የተነሳ ይህንን አጽንዖት ለመስጠት ሲል ይጠይቃል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሕይወትህን የሚጠብቀው እርሱ ያውቀዋል” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ለእያንዳንዱ እንደ ስራው መጠን እግዚአብሔር አይሰጠውምን?
ጸሐፊው አንባቢዎቹ መልሱን እንደሚያውቁት ያስባል ከዚህ የተነሳ ይህንን አጽንዖት ለመስጠት ሲል ይጠይቃል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ እንደ ስራው መጠን ይሰጠዋል” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 24:13

አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።

ተስፋህም አይጠፋም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ይህ ተሳቢ ቅርጽ ሲሆን እንደ ገቢር ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ተስፋህን ማንም ሰው

አይወስድብህም” ወይም 2) ይህ በአዎንታዊ ቅርጽ ሊተረጎም የሚችል ምፀት ነው። (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 24:15

አጠቃላይ መረጃ፦
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።

አድፍጠህ አትጠብቅ
“አድፍጠህ አትጠብቅ” የሚሉት ቃላት ፈሊጥ ነው። “አድፍጠህ አትጠብቅ” የሚለውን በምሳሌ 1:11 ላይ እንደተረጎምኸው ተርጉመው። አማራጭ ትርጉም፦ “አጋጣሚውን ለመጠቀም አድፍጠህ አትጠብቅ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ቤቱ
የጻድቅ ሰው ቤት

እንደገና ይነሳል
“በእግሩ እንደገና ይነሳል” ወይም “እንደገና ይቆማል”

ክፉ ሰዎች ግን በመቅሰፍት ላይ ይወድቃሉ
ጸሐፊው “መቅሰፍት” በሌሎች ሰዎች ላይ መጥፎ ነገሮችን የሚያደርግ ሰው እንደሆነ አድርጎ ተናግሯል። እነዚህ ቃላት እንደ ገቢር ቅርጽ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ክፉ ሰዎችን ለመጣል መቅሰፍት ይጠቀማል” (ሰውኛ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ይወድቃሉ
ይህ ተለዋጭ ዘይቤ ሲሆን የሚወክለው ቆሞ የነበረ ሰው ነገር ግን ሌላ ሰው ወደ መሬት ወደታች ጎትቶ ያመጣው ወይም እንዲወድቅ ያደረገው ሰው ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መቅሰፍት
በሰዎችና በንብረታቸው ላይ መጥፎ ነገር የተከናወነበት ጊዜ

Proverbs 24:17

አጠቃላይ መረጃ፦
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።

ጠላትህ ይወድቃል
“መጥፎ ነገር በጠላትህ ላይ ይሆናል”

ደስ አይበልህ
ይህ ጠንካራ ትእዛዝ ነው። “ልብ” የሚለው ቃል ሰውየውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ደስተኛ ለመሆን ለራስህ አትፍቀድለት” ወይም “ደስተኛ ከመሆን ራስህን ከልክል” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ተመልሶም ቁጣውን ከእርሱ ይመልሳል
“ቁጣውን ከእርሱ ይመልሳል” የሚሉት ቃላቶች ለወደፊት ቁጡ ላለመሆን ፈሊጥ ናቸው። ከዚህ ይልቅ እግዚአብሔር ለወደፊት የሚሰራው ነገር ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በእርሱ ላይ መቆጣትህን አቁምና ይልቁንም በራስህ ላይ ተቆጣ” (ፈሊጥ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 24:19

አጠቃላይ መረጃ፦
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።

የክፉ ሰውም መብራት ይጠፋልና
መብራት ለሕይወት እንደ ተለዋጭ ዘይቤ ጥቅም ላይ ውሏል። መብራት ወዲያው እንደሚጠፋ እንደዚሁ የክፉ ሰዎች ሕይወት ይጠፋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 24:21

አጠቃላይ መረጃ፦
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።

ፍርሃት
ጥልቅ አክብሮት እና በስልጣን ላይ ለሚገኝ ሰው የሚደረግ አክብሮታዊ ፍርሃት።

ከሁለቱም የሚመጣውን ጥፋት ምን ያህል እንደሆነ ማን ያውቃል?
ጸሐፊው የጥፋቱን ከፍተኛነት አጽንዖት ለመስጠት ይህን ጥያቄ ይጠይቃል። አማራጭ ትርጉም፦ “ከሁለቱም የሚመጣውን ጥፋት ምን ያህል እንደሆነ ማንም ሰው አያውቅም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ከሁለቱም
እነዚህ ቃላቶች እግዚአብሔርን እና ንጉሱን ይወክላሉ

Proverbs 24:23

እነዚህ ደግሞ የጥበበኛ ሰው ንግግር ናቸው
ይህ ዓረፍተ ነገር የምሳሌ አዳዲስ ስብስቦችን ይጀምራል።

በዳኝነት
አንድ ሰው ሕግ በመተላለፉ ምክንያት ተከስሶ በዳኛ ፊት የቀረበ አንድ ሁኔታ

Proverbs 24:24

ወንጀለኛውን ... የሚለው በሕዝብ ዘንድ ይረገማል፣ በመንግስታትም ዘንድ ይጠላል።
“መንግስታት” የሚለው ቃል በአገሮቹ ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች ምትክ ስም ነው። እነዚህ ቃላት በገቢር ቅርጽ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ክፉውን ሰው ... ለሚለው ሰዎች ይረግሙታል፣ የሌሎች አገሮች ሕዝቦች ደግሞ ይጠሉታል”

ክፉ ሰው ... ጻድቅ ሰው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) ሰዎች ለክፉ ሰው ጻድቅ ሰው ብለው ሊጠሩት በፍጹም አይገባም ወይም 2) ሕግ በመተላለፉ ምክንያት ወንጀለኛ ለሆነ ሰው ማም ሰው ንጹሕ ነው ሊለው አይገባም። አማራጭ ትርጉም፦ “ሕግ በመተላለፉ ምክንያት ወንጀለኛ የሆነ ሰው ... ንጹሕ ሰው”

ደስ ይለዋል
“በጣም ደስተኛ ይሆናል”

የደግነት ስጦታዎችም ወደ እነርሱ ይመጣሉ
ስጦታዎች በራሳቸው መንቀሳቀስ የሚችሉ ሰዎች እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሯል። “ደግነት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰዎች ጥሩ ስጦታዎች ይሰጧቸዋል” (ሰውኛ ዘይቤ እና ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የደግነት ስጦዎች
“ጥሩ ነገሮች” ወይም “በረከቶች”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Proverbs 24:28

በከንፈሮችህ
ከንፈሮች ሰውየው ለተናገራቸው ቃላቶች ምትክ ስም ናቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “በተናገርኸው ቃል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ዋጋውን እከፍለዋለሁ
ይህ ፈሊጥ ነው። “እርሱን እበቀለዋለሁ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 24:30

እሾህ
ጥቅቅ የሌላቸው ሹል እሾህ ያለባቸው ተክሎች

ሳማ
በሚያቃጥል ቅጠሎችና ጸጉሮች የተሸፈነ ተክል

ፈርሶ ነበር
“ወድቆ ነበር”

Proverbs 24:32

ተግሳጽን ተቀበልሁ
“ትምህርት ተማርሁ”

ጥቂት እንቅልፍ ... ጥቂት ለማረፍ ... ድህነት ይመጣል
የተዘለሉትን ቃላት መሙላት ያስፈልግህ ይሆናል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለራስህ እንዲህ ትለው ይሆናል፣ ‘ጥቂት እንቅልፍ ... ጥቂት ማረፍ’ - ነገር ግን ወዲያውኑ ድህነት ይመጣል” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ድህነት በአንተ ላይ ይመጣል
አንዳንድ ትርጉሞች እንዲህ ብለው ተርጉመውታል፣ “ድህነት እንደ ሌባ በአንተ ላይ ይመጣል።” ድህነት ሰነፍ ሰውን ሊያጠቃ የሚችል ሰው ወይም እንስሳ ተደርጎ ተነግሯል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ችግርህም መሳርያ እንደታጠቀ ወታደር ይመጣብሃል
ችግር ሰነፍ ሰው ሊያጠቃ የሚችል ሰው እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ችግርህም መሳርያ እንደታጠቀ ወታደር ሆኖ ወደ አንተ ይመጣብሃል” (ተነፃፃሪ ዘይቤ እና ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 25

1 እነዚህ የይሁዳ ንጉስ፣ የሕዝቅያስ ሰዎች የቀዷቸው ተጨማሪ የሰለሞን ምሳሌዎች ናቸው። **2** ነገርን መሰወር የእግዚአብሔር ክብር ነው፣ የነገስታት ክብር ግን ነገርን መርምሮ ማውጣት ነው። **3** ሰማያት ከፍ ያሉ እንደሆኑ፣ ምድርም ጥልቅ እንደሆነች ሁሉ፣ የነገስታት ልብም አይመረመርም። **4** ቆሻሻውን ከብር አስወግድ፣ የብረት ሰራተኛውም ብሩን ለእጅ ሙያው ሊጠቀምበት ይችላል። **5** እንደዚሁ ክፉ ሰዎችን ከንጉስ ፊት አርቃቸው፣ ዙፋኑ ጽድቅን በማድረግ ይጸናል። **6** በንጉስ ፊት ራስህን ከፍ ከፍ አታድርግ፣ ለታላቅ ሰዎች መቆሚያ በተዘጋጀም ስፍራ ላይ አትቁም። **7** በተከበሩ ሰዎች ፊት ከምትዋረድ ይልቅ፣ እርሱ “ወደዚህ ና” ቢልህ ይሻላል። ያየኸውን ነገርም፣ **8** ወደ ፍርድ ፈጥነህ አታምጣው። ጎረቤትህ ባሳፈረህ ጊዜ በመጨረሻ ምን ታርጋለህ? **9** ጉዳይህን በአንተና በጎረቤትህ መካከል ተከራከር፣ የሌላ ሰው ምስጢር ግን አታውጣ፣ **10** አለበለዚያ ግን አንተን የሰማ ሰው በአንተ ላይ ሃፍረትን ያመጣብሃል፣ ስለ አንተም ልትመልሰው የማትችለው መጥፎ ወሬ ይወራብሃል። **11** በጥንቃቄ የተመረጠ ቃል መናገር፣ በብር ላይ እንደተቀረጸ የወርቅ ንድፍ ነው። **12** ለሚሰማ ጆሮ የጥበበኛ ተግሳጽ እንደ ወርቅ ቀለበት፣ ከንጹህ ወርቅም እንደተሰራ ጌጥ ነው። **13** በምርት መሰብሰቢያ ወቅት እንዳለ የበረዶ ቅዝቃዜ ታማኝ መልዕክተኛ ለላኩት ሰዎች እንዲሁ ነው፤ የጌቶቹን ሕይወት ይመልሳል። **14** የማይሰጠውን ስጦታ እሰጣለሁ ብሎ የሚመካ ሰው ዝናብ እንደሌለው ደመናና ንፋስ ነው። **15** በትዕግስት ገዢን እንዲለዝብ ማድረግ ይቻላል፣ መልካም ምላስም አጥንትን ትሰብራለች። **16** ማር ካገኘህ፣ ለአንተ በቂ የሆነውን ብላ፣ አለበለዚያ ግን ከመጠን በላይ ከበላህ ትተፋዋለህ። **17** ወደ ጎረቤትህ ቤት እግር አታብዛ፣ ሊሰለችህና ሊጠላህ ይችላልና። **18** በጎረቤቱ ላይ በሐሰት የሚመሰክር ሰው በጦርነት ላይ ጥቅም ላይ እንደሚውል ዱላ፣ ሰይፍ ወይም የተሳለ ቀስት ነው። **19** በችግር ጊዜ የታመንከው ወስላታ ሰው እንደ ተበላሸ ጥርስ ወይም እንደሚያነክስ እግር ነው። **20** ለዘነ ልብ መዝሙር የሚዘምር፣ በብርድ ጊዜ ልብሱን እንደሚያወልቅ ወይም በሶዳ ላይ ኮምጣጤ እንደሚጨምር ነው። **21** ጠላትህ ቢራብ እንዲበላ ምግብ ስጠው፣ ቢጠማም እንዲጠጣ ውኃ ስጠው፣ **22** በራሱ ላይ ፍም ትከምራለህና፣ እግዚአብሔርም ዋጋህን ይከፍልሃልና። **23** የሰሜን ንፋስ በእርግጠኝነት ዝናብን ይዞ እንደሚመጣ፣ ሚስጥርን የሚያባክን ሰው ሰዎችን ያስቆጣል። **24** ከጠበኛ ሴት ጋር በአንድ ቤት ከመኖር በጣራ ማእዘን ላይ ተጠግቶ መኖር ይሻላል። **25** ለተጠማ ሰው ቀዝቃዛ ውሃ እንደሚያረካው ሁሉ፣ ከሩቅ አገር የመጣ የምስራችም እንዲሁ ነው። **26** በክፉ ሰዎች ፊት የሚንበረከክ መልካም ሰው፣ እንደ ተበከለ ፈሳሽና እንደተበላሸ ምንጭ ነው። **27** እጅግ በጣም ብዙ ማር መብላት ጥሩ አይደለም፤ በክብር ላይ ክብር እንደመፈለግ ነው። **28** ራሱን መግዛት የማይችል ሰው እንደፈረሰችና ቅጥር እንደሌላት ከተማ ነው።

Proverbs 25:1

ነገርን መሰወር
“አንዳንድ ነገሮችን በምስጢር መያዝ”

ነገር ግን ክብር
አስጨምሬ ሊሞላ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን ክብር ነው” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

መርምረህ አውጣት
“ይህንን ጉዳይ መርምረህ አውጣው” ወይም “እግዚአብሔር የሰወረውን ነገር መርምር”

ሰማያት ከፍ ያሉ እንደሆኑ፣ ምድርም ጥልቅ እንደሆነች ሁሉ፣ የነገስታት ልብም አይመረመርም
የንጉስ ልቦች ከሰማያትና ከምድር ግዝፈት ጋር ተነጻጽረዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሰማያትን ከፍታና የምድርንም ጥልቀት አንድም ሰው ሊለካው እንደማይችል ሁሉ የነገስታትን ልብ አንድም ሰው ሊመረምረው አይችልም” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰማያት
ይህ ጸሐይን፣ ጨረቃንና ከዋክብትን ጨምሮ ከምድር በላይ የምናየውን ማኛውንም ነገር የሚያመለክት ነው።

Proverbs 25:4

ቆሻሻ
ሰዎች የማይፈልጉት በብረት ላይ ያለ ነገርና ብረቱን በማሞቅ የሚያሰስወግዱት

ዙፋኑ ጽድቅን በማድረግ ይጸናል
ዙፋን ለመምራት ለሚያስፈልገው ስልጣን ምትክ ስም ነው። እነዚህ ቃላት በገቢር ቅርጽ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ንጉስ በማድረግ ዙፋኑን ያጸናል” ወይም “ለመምራት ስልጣን ይኖረዋል ምክንያቱም ይሰራል” (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 25:7

ይልቅ፣ እርሱ “ወደዚህ ና” ቢልህ ይሻላል።
እዚህ ላይ “ና” የሚለው ለንጉሱ ቅርብ የሆነው ጠረጴዛ ወዳለበት ስፍራ ተነስቶ መጠጋት ማለት ነው። ከንጉሱ አጠገብ መቀመጥ ለአንድ ሰው ትልቅ ክብር ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ከ … ይልቅ አንድ ሰው ከንጉሱ አጠገብ እንድትቀመጥ ቢጋብዝህ ይሻላል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በተከበሩ ሰዎች ፊት
“በተከበሩ ሰዎች ፊት ለፊት”

ጎረቤትህ ባሳፈረህ ጊዜ በመጨረሻ ምን ታርጋለህ?
ይህ ጥያቄ የተጠየቀው አንባቢው ሁኔታውን በተሳሳተ መንገድ የመረዳት እድል ሊገጥመው እንደሚችል ግንዛቤ እንዲኖረው ለማድረግ ነው። ጎረቤቱ አንባቢውን ለሃፍረት ሊዳርገው የሚችልበት መንገድ በግልጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በመጨረሻ ጎረቤትህ ለሃፍረት ከዳረገህ በኋላ ምን ማድረግ እንዳለብህ አታውቅም” ወይም “ጎረቤትህ ማብራሪያ ካለው፣ አንተን ለሃፍረት ይዳርግሃል፣ ከዚያ በኋላ ራስህን ለመከላከል ምንም የምትናገረው ነገር የለህም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 25:9

ጉዳይህ
“አለመስማማትህ”

የሌላ ሰው ምስጢር ግን አታውጣ
“የጎረቤትህን ምስጢር ለሌሎች ሰዎች አታውራ”

ስለ አንተም ልትመልሰው የማትችለው መጥፎ ወሬ ይወራብሃል
እዚህ ላይ “መጥፎ ወሬ” አንድ ሰው ለሌሎች ሰዎች የሚናገረው ጉዳት የሚያደርሱ ነገሮችን ይወክላል። “ልትመልሰው የማትችለው” የሚለው ሀረግ በግስ ቅርጽ ሊገለጽ ይችላ። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለ አንተ ጉዳት የሚያደርሱ ነገሮችን ከመናገር ልታስቆመው አትችልም” ወይም “ስለ አንተ ክፉ ነገሮችን

ለሌሎች ሰዎች ይናገራል ከዚህ የተነሳ ጥሩ ስም አይኖርህም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 25:11

በብር ላይ እንደተቀረጸ የወርቅ ንድፍ፣ በትክክለኛ ሁኔታ የተነገረ ቃል እንዲሁ ነው
“በትክክለኛ ሁኔታ የተነገረ ቃል” መልካምነት በአካል እንደሚታይ “በብር ላይ እንደተቀረጸ የወርቅ ንድፍ” ውበት ተደርጎ ተነግሯል። ብዙ ትርጉሞች ይህንን ተለዋጭ ዘይቤ እንደ ተነፃፃሪ ዘይቤ በመተርጎም የሀረጎቹን ቅደም ተከተል ለውጠዋቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “በትክክለኛ ሁኔታ የተነገረ ቃል፣ በብር ላይ እንደተቀረጸ የወርቅ ንድፍ ውብ ናቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በብር ላይ እንደተቀረጸ የወርቅ ንድፍ
የጥንት እስራኤላውያን ዛሬ ብዙ ሰዎች የሚያውቁትን ንድፍ አያውቁም። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) “ንድፎች” የሚለው “ዲዛይን” ተብሎ ሊተረጎም ይገባል።” አማራጭ ትርጉም፡- “የወርቅ ዲዛይን በብር ሳህን ላይ የተቀረጸ” ወይም 2) “ፖም” አንድ ሰው በዝርግ ወይም በጎድጓዳ ሳህን ላይ ያስቀመጠው ወርቃማ ቀለም ያለው ሌላ ዓይነት ፍሬ የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በብር ሳሳን ላይ የተቀመጠ ወርቃማ ቀለም ያለው ፍሬ”

የተነገረ ቃል ነው
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ሰው የተናገረው መልእክት ነው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ለሚሰማ ጆሮ የጥበበኛ ተግሳጽ እንደ ወርቅ ቀለበት፣ ከንጹህ ወርቅም እንደተሰራ ጌጥ ነው
“የጥበበኛ ተግሳጽ” ዋጋና አስፈላጊነት የወርቅ ውበትና ዋጋ እንዳለው ተደርጎ ተነግሯል። ብዙ ትርጉሞች ይህንን ተለዋጭ ዘይቤእንደ ተነፃፃሪ ዘይቤ ተርጉመውታል እና የሀረጎቹ ቅደም ተከተል ቀይረውታል። አማራጭ ትርጉም፡- “የጥበበኛ ተግሳጽ ለሚሰማ ጆሮ እንደ ወርቅ ቀለበት ወይም የወርቅ ጌጥ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለሚሰማ ጆሮ
ጆሮ ለሰው ሁለንተና ተዛምዶአዊ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ለመስማት ፈቃደኛ የሆነ ሰው” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 25:13

በምርት መሰብሰቢያ ወቅት እንዳለ የበረዶ ቅዝቃዜ ታማኝ መልዕክተኛ
እዚህ ላይ ታማኝ መልእክተኛ ከበረዶ ቅዝቃዜ ጋር ተነጻጽሯል ምክንያቱም ሁለቱም ደስ የሚያሰኙ ናቸው። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የበረዶ ቅዝቃዜ
በረዶ የሚወርደው መተራራ ጫፎች ላይ ብቻ ነው፣ ምርት የሚሰበሰበው ደግሞ በሞቃት ወቅት የአየር ሁኔታ ነው፣ ስለዚህ ይህ ምናልባት ከንጹህ ምንጭ ለሚወጣ ቀዝቃዛ ውኃ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በረዶ
እንደ ዝናብ ከሰማይ የሚወርድ ነጭ የደቀቀ በረዶ

የጌቶቹን ሕይወት ይመልሳል
ደካማና አቅመ ቢስ የሆኑትን ጌቶቹን ጠንካራና በእረፍት የተሞሉ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል።

የማይሰጠውን ስጦታ እሰጣለሁ ብሎ የሚመካ ሰው ዝናብ እንደሌለው ደመናና ንፋስ ነው
ብዙ ትርጉሞች ይህን ተለዋጭ ዘይቤ እንደ ተነፃፃሪ ዘይቤ ተርጉመውታል፣ የሀረጎቹንም ቅደም ተከተል ለውጠዋቸዋል። ዝናብ ለእስራኤላውያን በጣም አስፈላጊ ነው ምክንያቱም የሚዘንበው በጣም ትንሽ ዝናብ ነው፣ ስለዚህ ዝናብ የሌለው ደመና ጥቅም የሌለውና እስራኤላውያንን የሚያሳዝን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የሚመካ ነገር ግን የማይሰጥ ሰው ዝናብ እንደሌለው ደመናና ነፋስ ነው” ወይም “የማይሰጥ ነገር ግን የሚመካ ሰው ዝናብ እንደሌለው ደመናና ነፋስ ጥቅም የሌለውና ጎዘን የሚያመጣ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 25:15

በትዕግስት ገዢን እንዲለዝብ ማድረግ ይቻላል
እነዚህ ቃላት በገቢር ቅርጽ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ትእግስተኛ የሆነ ሰው ንጉስን እንዲለዝብ ማድረግ ይችላል” ወይም “ትእግስተኛ ሰው ከንጉስ ጋር መነጋገርና ሃሳቡን ማስለወጥ ይችላል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

መልካም ምላስ አጥንትን መስበር ትችላለች
“ምላስ” ሰው ምላሱን በመጠቀም ለሚናገረው ንግግር ምትክ ስም ነው። “አጥንት” የሚለው ቃል ለጠንካራ ተቃውሞ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “መልካም ንግግር ጠንካራ ተቃውሞን ማሸነፍ ይችላል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 25:16

አጠቃላይ መረጃ፡-
ቁጥር 16 አጠቃላይ መርህ የሚናገር ሲሆን ቁጥር 17 ደግሞ አንድ የተወሰነ ምሳሌ ይሰጣል። ብዙ ማር የመብላትና የመትፋት ሃሳብ ብዙ መልካም ነገር ለመውሰድና በኋላ ለመጸጸት ተለዋጭ ዘይቤ ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 25:18

በጎረቤቱ ላይ በሐሰት የሚመሰክር ሰው በጦርነት ላይ ጥቅም ላይ እንደሚውል ዱላ፣ ሰይፍ ወይም የተሳለ ቀስት ነው
ሐሰተኛ ምስክር ሰዎችን ከሚጎዱ ወይም ከሚገድሉ ከሶስት መሳርያዎች ጋር ተነጻጽሯል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በችግር ጊዜ የታመንከው ወስላታ ሰው እንደ ተበላሸ ጥርስ ወይም እንደሚያነክስ እግር ነው
ሞኝ ሰው ለሰው ችግር ከሚፈጥር የሰውነት ክፍል ጋር ተነጻጽሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “በችግር ጊዜ ወስላታ ሰውን መታመን እንደ ተበላሸ ጥርስ ወይም እንደሚያነክስ እግር ችግር ያመጣብሃል” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 25:20

በሶዳ ላይ ኮምጣጤ
ይህ እንደ ኮምጣጤ ያሉ የአሲድ ፈሳሽ ጋር ሲገናኝ በኃይል የሚፍለቀለቅና ተሸ የሚል ድምጽ የሚያሰማ የማዕድን ዓይነት ነው። ብዙ ትርጉሞች ይህንን ሀረግ “ቁስል” ብለው ይተረጉምታል።

መዝሙር የሚዘምር
ዘማሪዎቹ የሚዘምሩት ምን ዓይነት መዝሙር እንደሆነ በግልጽ ማስቀመጥ ያስፈልግ ይሆናል። አማራጭ ትርጉም፡- “ደስ የሚሉ መዝሙሮች ይዘምራሉ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ያዘነ ልብ
x

Proverbs 25:21

በራሱ ላይ ፍም ትከምራለህና
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የበደለኝነት አእምሮ እንዲፈጠርበትና የሰራው ስራ እንዲያሳፍረው ያደርጋል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Proverbs 25:23

የሰሜን ነፋስ
በእስራኤል አገር ከሰሜን የሚመጣ ነፋስ ብዙ ጊዜ ዝናብ ይዞ ይመጣል። ተርጓሚዎች ተመሳሳይ ውጤት ለሚያሳይ ሀኔታ የተለያዩ ዓይነት ነፋሳትን ለመጠቀም ነጻነት አላቸው፣ ለምሳሌ፦ “ቀዝቃዛ ነፋስ።”

ምስጢር የሚያባክን ምላስ
አንዳንድ ትርጉሞቸ ይህን “ምስጢር የሚያባክን አንድ ሰው” ብለው ተርጉመውታል።

የሰዎችን ፊት ያስቆጣል
ፊት ለሰውየው ተዛምዶአዊ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ሌሎች ሰዎችን በጣም ያስቀጣል፣ ይህንን ደግሞ በፊታቸው ማየት ትችላለህ” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

በጣራ ማእዘን
በዚያን ጊዜ የነበሩ ቤቶች ለጥ ያለ ጣራ ነበራቸው። የጥንት እስራኤላውያን ጣራቸውን ለመስራት ብዙ ጊዜ ይወስድባቸው ነበር። ጣራው ከቤቱ ውስጠኛው ክፍል ይልቅ ቀዝቃዛ ነበር። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ለመኝታ የሚሆን ትልቅ መጠለያ በጣራው በአንዱ ማእዘን ላይ ይሰሩ ነበር። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ጠበኛ ሚስት
“ብዙ ጊዜ የምትጨቃጨቅና የምታማርር ሚስት”

Proverbs 25:25

ለተጠማ ሰው ቀዝቃዛ ውሃ እንደሚያረካው ሁሉ፣ ከሩቅ አገር የመጣ የምስራችም እንዲሁ ነው
ቀዝቃዛ ውሃ ከሚያድስና ከሚያስደስት መልካም የምስራች ጋር ተነጻጽሯል።። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በክፉ ሰዎች ፊት የሚንበረከክ ጻድቅ ሰው፣ እንደ ተበከለ ወንዝና እንደተበላሸ ምንጭ ነው
አንድ ሰው ጻድቅ ለሚያምነት ነገር በጽናት እንዲቆም እንደሚጠብቅ ሁሉ እንዲሁ፣ አንድ ሰው ወንዝና ምንጭ ንጹህ ውኃ እንዲኖረው ይጠብቃል። የተበከለ ወንዝና የተበላሸ ምንጭ በአቋሙ ከወደቀ ጻድቅ ሰው ጋር ተነጻጽሯል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በክፉ ሰዎች ፊት የሚንበረከክ
መንበርከክ ለሚከተሉት ተለዋጭ ዘይቤ ነው፦ 1) ክፉ ሰዎችን ለመጋፈጥ አለመፈለግ ወይም 2) በክፋታቸው መሳተፍ። አማራጭ ትርጉም፦ “ክፉ ሰዎች ክፋት እንዲያደርጉ መፍቀድ” ወይም “ክፉ ሰዎች የሚሰሩትን ስራ መስራት የሚጀምር ሰው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መንበርከክ
መንበርከክ መልካም ስራ መስራት መቀጠል ለአለመቻል ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ለመቆም አለመቻል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በክፉ ሰዎች ፊት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) “ክፉ ሰዎች ሲያጠቁት” ወይም 2) “ክፉ ሰዎች ክፉ ነገር እንዲሰሩ ሲገፉት።” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 25:27

እጅግ በጣም ብዙ ማር መብላት ጥሩ አይደለም፤ በክብር ላይ ክብር እንደመፈለግ ነው
ሁሉም አንተን ሊያከብሩህ ሲፈለጉና ማር መብላት መልካም ነው፣ ነገር ግን ብዙ ማር መብላት ትችላለህ፣ ሰዎች አንተን ሊያከብሩህ መሞከር አስቸጋሪ ይሆንብሃል” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መልካም አይደለም
ይህ በአዎንታዊ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የይህ መጥፎ ነገር ነው” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

በክብር ላይ ክብር እንደመፈለግ ነው
“ይህ ሌሎች አንተን እንዴት እንደሚያከብሩህ ሁልጊዜ እንደ ማሰብ ነው።” የመጀመርያው ቋንቋ ትርጉም ግልጽ አይደለም። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ይህንን “ለሰዎች በጣም ብዙ አስተያየቶችን እንደ መናገር ነው” ብለው ተርጉመውታል።

ራሱን መግዛት የማይችል ሰው እንደፈረሰችና ቅጥር እንደሌላት ከተማ ነው
ራሱን መግዛት የማይችል ሰውና ቅጥር የሌላት ከተማ ደካማና ተጋላጭ ናቸው። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የፈረሰና ቅጥር የሌላት
“የግንብ አጥሮቹን ወታደር ያጠቃውና ያፈረሰው”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 26

1 በበጋ ጊዜ እንደሚወርድ በረዶና በመከር ጊዜ እንደሚዘንብ ዝናብ፣ ክብርም ለሞኝ ሰው አይገባውም። **2** ድንቢጥ ከቦታ ቦታ እንደምትበርር፣ ጨረባም እንደምትሸመጥጥ፣ ያልተገባ እርግማን ማንም ላይ አይደርስም። **3** ጅራፍ ለፈረስ፣ ልጓምም ለአህያ እንደሆነ፣ በትርም ለሞኞች ጀርባ ነው። **4** ለሞኝ መልስ አትስጠው፣ በሞኝነቱም አትተባበር፣ አለዚያ እንደ እርሱ ትሆናለህ። **5** ሞኝን እንደ ሞኝነቱ መልስለት፣ በሞኝነቱም ተባበረው፣ አለዚያ በዓይኖቹ ጥበበኛ የሆነ ይመስለዋል። **6** በሞኝ ሰው እጅ መልዕክትን የሚልክ ሁሉ የራሱን እግር ይቆርጣል ሁከትንም ይጠጣል። **7** የሰለሉ የሸባ እግሮች በሞኝ አፍ እንዳለ ምሳሌ ናቸው። **8** ለሞኝ ክብር መስጠት ድንጋይን በወንጭፍ እንደ ማሰር ነው። **9** በሰካራም እጅ ላይ ያለ እሾህ በሞኞች አፍ እንዳለ ምሳሌ ነው። **10** ሁሉንም ሰው የሚያቆስል ቀስተኛ፣ ሞኝን ወይም አላፊ አግዳሚውን እንደሚቀጥር ሰው ነው። **11** ውሻ ወደ ትውከቱ እንደሚመለስ፣ ሞኝነቱን የሚደጋግም ሞኝም እንዲሁ ነው። **12** በራሱ ዓይን ጥበበኛ እንደሆነ የሚያስብን ሰው አይተሃልን? ከእርሱ ይልቅ ለሞኝ የተሻለ ተስፋ አለው። **13** ሰነፍ ሰው እንዲህ ይላል፣ “አንበሳ በመንገድ አለ! በውጭ በአውራ ጎዳና አንበሳ አለ።” **14** በር በማጠፊያው ላይ እንደሚዞር፣ ሰነፍም በአልጋው ላይ ይዟዟራል። **15** ሰነፍ ሰው እጁን ወደ ሳህኑ ያስገባል፣ ነገር ግን እጁን ወደ አፉ ለመመለስ ጉልበት የለውም። **16** ሰነፍ ሰው ማስተዋል ካላቸው ከሰባት ሰዎች የበለጠ ጥበበኛ እንደሆነ በራሱ ዓይን ያስባል። **17** የውሻን ጆሮ እንደሚይዝ ሰው፣ የራሱ ባልሆነ ጥል ላይ የሚገባ መንገድ አላፊ ሰውም እንዲሁ ነው። **18** ተቀጣጣይ ቀስት እንደሚወራወር እብድ ሰው፣ **19** “የተናገርሁት እኮ ቀልዴን ነበር?” በማለት ጎረቤቱን የሚያታልል ሰው እንዲሁ ነው። **20** በእንጨት እጦት እሳት ይጠፋል፣ ሐሜት በሌለበትም ጥል ያቆማል። **21** ከሰል ፍምን እንጨትም እሳትን እንደሚያቀጣጥል፣ ጠበኛ ሰውም ሁከትን ያቀጣጥላል። **22** የሐሜት ቃላቶች እንደ ጣፋጭ ጉርሻ ናቸው፤ ወደ ውስጣዊ የሰውነት ክፍሎችም ይወርዳሉ። **23** እንሚያቃጥሉ ከንፈሮችና እንደ ክፉ ልብ በብር ፈሳሽ የተለበጠ የሸክላ ድስት እንዲሁ ነው። **24** ሌሎችን የሚጠላ ሰው ስሜቱን በከንፈሮቹ ይሸነግላል፣ ተንኮሉን ግን በውስጡ ያኖራል። **25** ማራኪ የሆነ ንግግር ይናገራል፣ ነገር ግን አትመነው፣ በልቡ ውስጥ ሰባት ርኩሰቶች አሉና። **26** ምንም እንኳ ጥላቻው በሸንገላ የተሸፈነ ቢሆንም፣ ክፋቱ ግን በጉባኤ ይገለጣል። **27** ጉድጓድን የሚቆፍር ሰው እርሱ ይገባበታል፣ ድንጋይንም የሚያንከባልል ተመልሶ በላዩ ላይ ይገለበጥበታል። **28** ውሸታም ምላስ የጎዳቸውን ሰዎች ይጠላል፣ ሸንጋይ አፍም ጥፋትን ያመጣል።

Proverbs 26:1

በበጋ ጊዜ እንደሚወርድ በረዶና በመከር ጊዜ እንደሚዘንብ ዝናብ
ብዙውን ጊዜ በረዶ በበጋ ጊዜ አይወርድም፣ ዝናብ ደግሞ በመከር ጊዜ አይዘንብም። ይህ በግልጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በረዶ በበጋ ጊዜ መውረድና ዝናብ ደግሞ በመከር ጊዜ መዝነብ እንግዳ ነገር እንደሆነ ሁሉ” (ተነፃፃሪ ዘይቤ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ያልተገባ እርግማን ማንም ላይ አይደርስም
ሰውን የማይጎዳ እርግማን መሬት ላይ እንደማታርፍ ወፍ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለዚህ ያልተገባ እርግማን በታሰበው ሰው ላይ አይደርስም” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ያልተገባ እርግማን
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በማይገባው ሰው ላይ የሚደረግ እርግማን” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

አረፈ
በአንድ ሰው ወይም ነገር ላይ ማረፍ

Proverbs 26:3

ጅራፍ ለፈረስ፣ ልጓምም ለአህያ እንደሆነ፣ በትርም ለሞኞች ጀርባ ነው።
ጅራፍ፣ ልጓምና በትር ሰዎ ፈረስ፣ አህያና ሞኝ ሰው የፈለጉትን እንዲያደርጉ የሚጠቀሙባቸው ነገሮች ናቸው።

ልጓም ለአህያ ነው
ልጓም ከጠፍር የተሰራ ነው። ሰዎች ልጓሙን በአህያው ራስ ላይ ያስገቡትና አህያውን ወደሚፈልጉት ቦታ እንዲሔድ ለማድረግ ከጠፍሩ አንዱን ይይዙታል።

ጅራፍ ለሞኞች ጀርባ ነው
በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰዎች ልጆቻቸውን ወይም ባሪያዎቻቸውን ስርዓት ለማስያዝ በእንጨት በትር ይመቷቸው ነበር።

Proverbs 26:5

ሞኝን እንደ ሞኝነቱ መልስለት፣ በሞኝነቱም ተባበረው፣
ለሞኝ ስትመልስለት በሞኝነቱ መተባበር በሞኝነት መንገድ ለእርሱ መመለስን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለሞኝ እንደሞኝነቱ መልስለት” ወይም “ለሞኝ በሞኝነት መልስለት”

ስለዚህ በዓይኖቹ ጥበበኛ የሆነ እንዳይመስለው
ዓይን መመልከትን ይወክላል፣ መመልከት ደግሞ ሃሳብንና ግንዛቤን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለዚህ በእርሱ ግንዛቤ ጥበበኛ የሆነ እንዳይመስለው” ወይም “ስለዚህ ራሱን ጥበበኛ እንደሆነ እንደያስብ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በሞኝ ሰው እጅ መልዕክትን የሚልክ ሁሉ
እዚህ ላይ እጅ መልእክትን ለማድረስ ሞኝ ያለውን ኃላፊነት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “መልእክት እንዲያደርስለት ሞኝን የሚልክ ሀሉ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የራሱን እግር ይቆርጣል
የራስን እግር መቁረጥ ራስን ለመጉዳት የግነት መግለጫ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የራሱን እግር እንሚቆርጥና ሁከትን እንደሚጠጣ ሰው ራሱን ይጎዳል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሁከትንም ይጠጣል
ሁከት አንድ ሰው ሊጠጣው የሚችል መርዛም ፈሳሽ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “በሁከት ፈጣሪነት ራሱን ይጎዳል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 26:7

እንደ እግሮች ... በሞኝ አፍ ያለ ምሳሌ እንዲሁ ነው
የእነዚህ ሀረጎች አቀማመጥ ቅደም ተከተሉ ሊለወጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በሞኝ አፍ ያለ ምሳሌ እንደ ተንጠለጠሉ የሰለሉ የሸባ እግሮች ናቸው” ወይም “በሞኝ አፍ ያለ ምሳሌ እንደ ተንጠለጠሉ የሰለሉ የሸባ እግሮች የማይጠቅሙ ናቸው” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሸባ
መንቀሳቀስ የማይችል ሰው ወይም ሁሉም ወይም ከፊል ሰውነቱ እንዲህ የሚሰማው

በሞኞች አፍ
“አፍ” ለመናገር ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በሞኞች ንግግር” ወይም “ሞኞች የሚናገሩት ነገር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ድንጋይን በወንጭፍ ማሰር
ወደ ረጅም ርቀት ድንጋይ ለመወርወር ሰዎች ድንጋይ በወንጭፍ ያስቀምጣሉ ከዚያም ግንጋዩ በጣም በፍጥነት ወደቦታው እንዲስፈነጠር ወንጭፉን ያዞሩታል። ድንጋይን በወንጭፍ የማሰር ውጤት በግልጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እንዳይወረወር ድንጋይን በወንጭፍ ማሰር” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለሞኝ ክብር መስጠት
“ሞኝን ማክበር”

Proverbs 26:9

እንደ እሾህ ... በሞኝ አፍ ውስጥ ያለ ምሳሌ እንዲሁ ነው
ሁለቱ እንዴት ተመሳሳይነት እንዳላቸው በግልጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በሰካራም እጅ እንደገባ እሾህ በሞኝ አፍ ውስጥ ያለ ምሳሌ አደገኛ ነው” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰካራም እጅ እንደገባ እሾህ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ሰካራም እሾህ ያለው ቁጠቋጦ በእጁ ከያዘ፣ እሾሁ እጁን ይወጋዋል፣ ወይም 2) ሰካራም ሰው ከተቆጣ፣ እሾህ ያለው ቁጠቋጦ ይዞ በሰዎች ላይ ይጥለዋል። ለሁለተኛው ትርጉም “እሾህ” የሚለው ቃል የእሾህ ቁጥቋጦን ይወክላል። (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

በሞኞች አፍ
እዚህ ላይ “አፍ” ለመናገር ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በሞኞች ንግግር” ወይም “ሞኞች የተናገሩት ነገር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ሞኝ ይቀጥራል
“ለሞኝ ስራ ይሰጣል”

Proverbs 26:11

ውሻ ወደ ትፋቱ እንደሚመለስ
“ውሻ የራሱን ትፋት እንደሚበላ”

በራሱ ዓይኖች ጥበበኛ እንደሆነ የሚያስብ ሰው አይተሃል?
ይህ ጥያቄ በራሱ ዓይኖች ጥበበኛ እንደሆነ ስለሚቆጥር አንድ ሰው እንዲያስብ አንባቢውን ለመምራት የሚጠቅም ነው። “በራሱ ዓይኖች ጥበበኛ የሆነ” የሚለው ሀረግ “ጥበበኛ አንደሆነ የሚያስብ” ማለት ነው፣ እዚህ ላይ ሰውየው በግልጽ ጠቢብ እንዳልሆነ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበበኛ እንደሆነ የሚስያብን ነገር ግን ጥበበኛ ያልሆነውን ሰው ተመልከት” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእርሱ ይልቅ ለሞኝ የተሻለ ተስፋ አለው
“ከእርሱ ይልቅ ሞኝ በቀላሉ ጥበበኛ መሆን ይችላል።”

Proverbs 26:13

ሰነፍ ሰው እንዲህ ይላል፣ “አንበሳ በመንገድ አለ! በውጭ በአውራ ጎዳና አንበሳ አለ።”
ሰነፍ ሰው በውሸት በመንገድ ላይ ወይም በባዶ ሜዳዎቹ መካከል አንበሳ አለ ብሎ ምክንያት በመስጠት ወደ ውጭ መሄድና መስራት እንደማይችል ይናገራል።

በመንገድ ላይ አንበሳ አለ
ይህንን በምሳሌ 22:13 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

በባዶ ሜዳዎቹ
ይህ በከተማ መካካል ሰዎች የሚዘዋወሩበት ወይም የሚሰበሰቡበት ብዙ ስፍራዎችን የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የከተማ የገበያ ማዕከል” ወይም “መንገዶች”

ማጠፊያዎች
በርን ከሌላ ነገር ጋር የሚያያይዘዙና በሮቹ እንዲዘጉና እንዲከፈቱ የሚያደርጉ የብረት ቁራጮች

በር በማጠፊያው ላይ እንደሚዞር፣ ሰነፍም በአልጋው ላይ ይዟዟራል
ሰነፍ ሰውና በር ሁለቱም ይንቀሳቀሳሉ ነገር ግን ሁለቱም የትም አይሄዱም (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 26:15

ሰነፍ ሰው እጁን ወደ ሳህኑ ያስገባል
“ምግብ ለማግኘት እጁን ወደ ሳህኑ ያስገባል” ወይም “ለምግብ ይዘረጋል”

እጁን ወደ አፉ ለመመለስ ጉልበት የለውም
ይህ ሰውየው በግልጽ መልካም የሚያደርገውን አስፈላጊ ስራ ስለመስራት የሚያመለክት ግነት ነው። (ግነትና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰነፍ ሰው ማስተዋል ካላቸው ከሰባት ሰዎች የበለጠ ጥበበኛ እንደሆነ በራሱ ዓይን ያስባል
“በራሱ ዓይን” የሚለው ሀረግ የሰውየውን ሃሳብ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰነፍ ሰው ከሰባት ሰዎች የበለጠ ጥበበኛ እንደሆነ ያስባል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 26:17

የውሻን ጆሮ እንደሚይዝ ሰው፣ የራሱ ባልሆነ ጥል የሚበሳጭ መንገድ አላፊ ሰውም እንዲሁ ነው
ይህ ቅደም ተከተሉ መለወጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የራሱ ባልሆነ ጥል ላይ የሚገባ መንገድ አላፊ ሰው የውሻን ጆሮ እንደሚይዝ ሰው ነው” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የውሻን ጆሮ እንደሚይዝ ሰው
ይህ የሚያሰተላልፈው መረጃ ውሻ ይቆጣና ሰውየውን ይነክሰዋል” የሚል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ጆሮውን በመጎተት ውሻን እንደሚያስቆጣ ሰው” ወይም “የውሻን ጆሮ እንደሚጎትትና በውሻ እንደሚነከስ ሰው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ

የራሱ ባልሆነ ጥል የሚበሳጭ መንገድ አላፊ ሰውም እንዲሁ ነው
ይህ የሚያስተላልፈው መረጃ መንገድ አላፊው መጨቃጨቅ ይጀምራል ከዚያም ሲጣሉ የነበሩት ሰዎች ከእርሱ ላይ ይቆጣሉ ደግሞም ይጎዱታል የሚል ነው። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Proverbs 26:18

እንደ እብድ ሰው ... የተናገርሁት እኮ ቀልዴን ነበር? ... በማለት የሚያታልል ሰው እንዲሁ ነው
እብድ ሰውና አታላዩ ሁለቱም ሰዎችን ይጎዳሉ ነገር ግን ለሰሩት ስራ ኃላፊነት አይወስዱም።

“የተናገርሁት እኮ ቀልዴን ነበር?”
አታላዩ የእርሱ ቀልድ ለማዝናናት ስለሆነ እርሱ ለፈጠረው ለማንኛውም ጉዳት ሊወቀስ እንደማይገባ ለማሳየት ይህንን ጥያቄ ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ እኮ እንዲሁ እየቀለድሁ ነበር” ወይም “እኔን አትውቀሱኝ። እኔ የተናገርሁት ቀልዴን ነበር።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 26:20

ሐሜተኛ
ብዙ ሐሜት የሚናገር ሰው

ከሰል ፍምን እንጨትም እሳትን እንደሚያቀጣጥል
ከሰል በፍም ላይ እንጨት ደግሞ በእሳት ላይ የሚያመጣው ውጤት በግልጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከሰል ፍም እንዲቀጣጠል እንደሚያግዝና እንጨት እሳትን እንዲነድ እንደሚያግዝ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሁከትን ያቀጣጥላል
አንድን ነገር ማቀጣጠል በእሳት ማያያዝ ማለት ነው። ሁከትን በእሳት ማቀጣጠል ሰዎች እንዲጣሉ ወይም እንዲከራከሩ ለማድረግ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች እንዲጣሉ ማድረግ” ወይም “ሰዎች እንዲከራከሩ ማድረግ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 26:22

የሐሜት ቃላቶች እንደ ጣፋጭ ጉርሻ ናቸው
ለመብላት ጣፋጭ እንደሆነ ምግብ ሐሜትም ለመስማት ደስ የሚያሰኝ ሰለመሆኑ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሐሜት ቃላቶች ለመስማት ደስ የሚያሰኙ ናቸው” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ውስጣዊ የሰውነት ክፍሎችም ይወርዳሉ
ይህ ሐሜት የሚናገራቸው ቃላቶች ወደ ሰው አእምሮ ገብተው ሃሳቡን እንደሚያበላሹ የሚናገር ሲሆን ወደ ሆዱ እንደሚገባ ምግብ ተደርገው ተገልጸዋል። ይህ ዓረፍተ-ሃሳብ በምሳሌ 18:8 ካለው ጋር ተመሳሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ወደ ሰው አእምሮ ይገቡና ሃሳቡን ያበላሻሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንሚያቃጥሉ ከንፈሮችና እንደ ክፉ ልብ በብር ፈሳሽ የተለበጠ የሸክላ ድስት እንዲሁ ነው
ይህ ተነፃፃሪ ዘይቤ ክፋትን በልባቸው ለመደበቅ የተለያዩ ነገሮችን የሚናገሩ ሰዎች ጥሩ እንዲመስል ለማድረግ በብር ፈሳሽ እንደተለበጠ የሸክላ ድስት ነው። እነዚህ ሀረጎች ቅደም ተከተላቸው ሊለዋወጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሚያቃጥሉ ከንፈሮች ያላቸው ሰዎችና ክፉ ልብ በብር ፈሳሽ እንደተለበጠ የሸክላ ድስት ነው። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በብር ፈሳሽ የተለበጠ የሸክላ ድስት
“የሸክላ ድስትን የሚሸፍን የሚያብረቀርቅ ቅብ።” የሸክላ ድስት ርካሽና በሁሉም ስፍራ የሚገኝ ነው። ስለዚህ የሚያብረቀርቅ እንዲሆንና በጣም ውድ እንደሆነ ለማስመሰል ሰዎች በሚያብረቀርቅ ቅብ ይሸፍኑታል።

የሚያቃጥሉ ከንፈሮችና ክፉ ልብ እንደዚሁ ናቸው
ይህ የሚወክለው የሚያቃጥሉ ከንፈሮችና ክፉ ልብ ያለውን ሰው ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የሚያቃጥሉ ከንፈሮችና ክፉ ልብ ያለው ሰው እንደዚሁ ነው” ወይም “መልካም ንግግር የሚናገር ነገር ግን ልቡ ክፉ የሆነ ሰው እንደዚሁ ነው” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

የሚያቃጥሉ ከንፈሮች
“የሚያቃጥሉ” የሚለው ቃል “ከመጠን ያለፈ ስሜታዊ መሆን” ለማመልከት ተለዋጭ ዘይቤ ሲሆን “ከንፈሮች” የሚለው ቃል ደግሞ “ንግግር” ለማመልከት ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ስሜታዊ ንግግር” ወይም “ጥሩ ነገሮች መናገር” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉ ልብ
ልብ የሰውን ሃሳብ፣ ዝንባሌ፣ ፍላጎት ወይም ስሜት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ሃሳብ” ወይም “ክፉ ምኞት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 26:24

ስሜቱን በከንፈሮቹ ይሸነግላል
ስሜትን መሸንገል ስሜቱን ሰዎች እንዳያውቁ መደበቅን ይወክላል። “ከንፈሮቹ” የሚለው ቃል ለተናገረው ንግግር ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በሚናገረው ንግግር ስሜቱን ይደብቃል” ወይም “እውነተኛ ስሜቱን ሰዎች ሊያውቁ በማይችሉበት ሁኔታ ይናገራል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ተንኮሉን ግን በውስጡ ያኖራል
ተንኮለኛ መሆን ሰውየው ተንኮል በውስጡ ያጠራቅም እንደነበር ተደርጎ ተነግሯል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- “ተንኮል” ውሸትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ብዙ ውሸቱን ይወድደዋል” 2) ተንኮል ሰዎችን ለመጉዳት ምስጢራዊ እቅዶችን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎችን ለመጉዳት በምስጢር አቅዷል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን አትመነው
“ነገር ግን የሚናገረውን አትመነው”

በልቡ ውስጥ ሰባት ርኩሰቶች አሉ
ሰባት ቁጥር ፍጹምነትን ይወክላል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) “ርኩሰት” እግዚአብሔር የሚጠላውን አመለካከት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ልቡ ሙሉ በሙሉ በጥላቻ ነገሮች የተሞላ ነው” ወይም 2) “ርኩሰት” ለሰዎች ያለውን ጥላቻ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- ““ልቡ ሙሉ በሙሉ በጥላቻ የተሞላ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ምንም እንኳ ጥላቻው በሸንገላ የተሸፈነ ቢሆንም
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ምንም እንኳ ሸንገላው ጥላቻውን ቢሸፍነውም” ወይም “ምንም እንኳ ጥላቻውን በሸንገላው ቢሸፍነውም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ምንም እንኳ ጥላቻው በሸንገላ የተሸፈነ ቢሆንም
ሰዎች እነርሱን እንደሚጠላቸው እንዳያውቁ መደበቁ ጥላቻውን እንደሸፈነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ምንም እንኳ ሰዎች እነርሱን እንደሚጠላቸው እንዳያውቁ ለመደበቅ ቢዋሽም” ወይም “ምንም እንኳ ሰዎች እነርሱን እንደሚጠላቸው እንዳያውቁ ቢዋሽም” “Though he lies so that people will not know that he hates them” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ክፋቱ ግን በጉባኤ ይገለጣል
መገለጥ መለየት ወይም መታወቅ የሚለውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፋቱ በጉባኤ ይታወቅበታል” ወይም “ጉባኤው ክፋቱን ይደርስበታል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጉባኤው
“የእስራኤል ማህበረሰብ”

Proverbs 26:27

ጉድጓድን የሚቆፍር ሰው እርሱ ይገባበታል
ይህ ሰው ጉድጓድ የሚቆፍረው ሌላ ሰው በዚያ ጉድጓድ ላይ እንዲወድቅበት እንደ ወጥመድ እንደሆነ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም:- “ሌላ ሰው ለማጥመድ ጉድጓድን የሚቆፍር ማንኛውም ሰው እርሱ ይገባበታል” ወይም ““ሌላ ሰው ለማጥመድ በማሰብ አንድ ሰው ጉድጓድ ከቆፈረ፣ የቆፈረው ሰው ራሱ ይገባበታል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ድንጋይንም የሚያንከባልል ተመልሶ በላዩ ላይ ይገለበጥበታል
ይህ ሰው በኮረብታ ላይ ሆኖ ወደታች ትልቅ ድንጋይን የሚያንከባልለው ከታች ያለውን ሌላ ሰው ለመጨፍለቅ እንደሆነ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም:- “አንድ ሰው ከታች ያለውን ሌላ ሰው ለመጨፍለቅ በኮረብታ ላይ ሆኖ ወደታች ትልቅ ድንጋይ የሚያንከባልል ከሆነ፣ ድንጋዩ በራሱ ላይ ተመልሶ ይንከባለልበታል” ወይም “አንድ ሰው ሌላ ሰው ለመጉዳት ድንጋይ የሚያንከባልል ከሆነ ድንጋዩ ተመልሶ ራሱን ይጨፈልቀዋል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ውሸታም ምላስ የጎዳቸውን ሰዎች ይጠላል
“ውሸታም ምላስ” የሚለው ሀረግ ውሸት የሚናገረውን ሰው ይወክላል። ሰዎችን መጉዳት በሰዎች ላይ ችግር መፍጠርን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “ውሸታም ሰው በውሸቱ የጎዳቸውን ሰዎች ይጠላል” (ተዛምዶአዊ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሸንጋይ አፍም ጥፋትን ያመጣል
“ሸንጋይ አፍ” የሚለው ሀረግ ሰዎችን የሚሸነግለውን ሰው ይወክላል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች:- ሌሎችን የሚሸነግል ሰው ችግር ይፈጥራል። ወይም 2) ሌሎችን የሚሸነግል ሰው ያጠፋቸዋል (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

መሸንገል
አንድን ሰው እውነተኛነት በሌለው ሁኔታ ማመስገን፣ ወይም አንድን ሰው እውነተኛ ላልሆኑ ነገሮች ማመስገን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 27

1 ነገ በሚሆነው አትመካ፣ ቀኑ የሚያመጣው ምን እንደሆነ አታውቅምና። **2** ሌላ ያመስግንህ እንጂ በራስህ አፍ ራስህን አታመስግን፤ የማያውቅህ ሰው እንጂ የራስህ ከንፈሮች አያመስግኑህ። **3** የድንጋይን ክብደትና የአሸዋንም ክብደት አስብ፣ የሞኝ ሰው ትንኮሳ ግን ከሁለቱም እጅግ የከበደ ነው። **4** የንዴት ጨካኝነትና የቁጣ ጎርፍ አለ፣ በቅናት ፊት መቆም የሚችል ግን ማን ነው? **5** ከተሰወረ ፍቅር ይልቅ የተገለጠ ተግሳጽ ይሻላል። **6** የጓደኛ ማቁሰል የታመኑ ናቸው፣ ጠላት ግን ከመጠን በላይ ይስማል። **7** በጣም ጠግቦ የበላ ሰው የማር ወለላንም አይቀበልም፣ ለራበው ሰው ግን ማንኛውም መራራ ነገር እንኳ ጣፋጭ ነው። **8** ከጎጆዋ ወጥታ የምትንከራተት ወፍ ከመኖሪያው አካባቢ ወጥቶ እንደሚባዝን ሰው ናት። **9** ሽቶና እጣን ልብን ደስ ያሰኛሉ፣ የጓደኛ ጣፋጭነት ግን ከምክሩ ይበልጣል። **10** በችግርህ ጊዜ ጓደኛህንና የጓደኛህን አባት ትተህ ወደ ወንድምህ ቤት አትሂድ። በቅርብ ያለ ወዳጅ በሩቅ ካለ ወንድም ይሻላልና። **11** ልጄ ሆይ፣ ጥበበኛ ሁን፣ ልቤንም ደስ አሰኛት፤ በዚያን ጊዜ ለሚያፌዝብኝ ሰው እኔ መልስ እሰጣለሁ። **12** ጥንቁቅ ሰው ችግር ሲያይ ራሱን ይሸሸጋል፣ አላዋቂዎች ግን ቀድመው ሄደው በችግሩ ምክንያት ይጎዳሉ። **13** ለማይታወቅ ሰው ብድር በዋስትና ገንዘብ ያስያዘውን ሰው ልብስ ውሰድበት፤ ዝሙት ለምትፈጽም ሴት ዋስትና አስይዞ ከሆነ ውሰድበት። **14** ጎረቤቱን በማለዳ ድምጹን በጣም ከፍ አድርጎ የሚባርክ ሰው፣ ባርኮቱ እንደ እርግማን ይቆጠራል! **15** ጠበኛ ሚስት በዝናብ ቀን እንደማያቋርጥ ነጠብጣብ ናት፤ **16** እሷን ማቆም ንፋስን እንደማቆም ወይም ዘይትን በቀኝ እጅህ ለመጨበጥ እንደ መሞከር ነው። **17** ብረት ብረትን ይስለዋል፤ በተመሳሳይ መንገድ ሰው ጓደኛውን ይስለዋል። **18** የበለስ ዛፍ የሚጠብቅ ፍሬውን ይበላል፣ ጌታውንም የሚጠብቅ ይከብራል። **19** ውኃ የሰውን ፊት እንደሚያሳይ፣ የሰው ልብ ሰውየውን ያሳያል። **20** ሲኦልና የሙታን ዓለም መቼም እንደማይጠግቡ፣ የሰውም ዓይኖች መቼም አይጠግቡም። **21** ማቅለጫ ለብር ከውርም ለወርቅ ነው፣ ሰውም በሚመሰገንበት ጊዜ ይፈተናል። **22** ሰነፍን ከእህል ጋር በዘነዘና ብትወቅጠውም፣ ሞኝነቱ ግን እርሱን አይለቀውም። **23** የመንጋህን ሁኔታ በእርግጠኝነት እወቅ፣ ስለ ከብቶችህም ግድ ይበልህ፣ **24** ሐብት ለዘላለም አይኖርምና። ዘውድ ለትውልድ ሁሉ ይጸናልን? **25** የነበረው ሳር ጠፍቶ፣ አዲሱ ቡቃያ አድጎ ሲታይ፣ በተራሮች ደግሞ ለከብቶች የሚሆን መብል ተሰብስቦ ይገባል። **26** ለልብስህ የሚሆን ከበጎች ታገኛለህ፣ ለእርሻህ ዋጋ የሚሆን ደግሞ ከፍየሎችህ ታገኛለህ። **27** ለአንተና ለቤተሰብህ መብል፣ ሴት አገልጋዮችህንም ለመመገብ የሚበቃ የፍየሎች ወተት ይኖራል።

Proverbs 27:1

ነገ በሚሆነው አትመካ
ይህ ነገ ይሆናል ብለህ ስለምትጠብቀው ነገር ጉራ እንደትነዛ ማስጠንቀቂያ ነው። ይህ በግልጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለነገ ስላለህ እቅድ በኩራት አትናገር” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀኑ የሚያመጣውን
በተወሰነ ቀን የሚከናወነው ነገር ያንን ክስተት ቀኑ እንደሚያመጣው ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “በዚያ ቀን የሚሆነውን” ወይም “ነገ የሚሆነውን” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በራስህ አፍ ሳይሆን ... የራስህ ከንፈሮች ሳይሆኑ
“ያመስግኑህ” የሚለውን ቃል ከመጀመርያው ሀረግ በግልጽ መረዳት ይቻላል። ቃላቶቹ ሊደጋገሙ ይችላሉ። እዚህ ለላይ ሰውየው በ “አፉ” እና በ “ከንፈሮቹ” ተወክሏል ምክንያቱም እነዚህ ለመናገር የሚጠቅሙ የሰውነት አካላት ናቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “የራስህ አፍ አያመስግንህ ... የራስህ ከንፈሮች አያመስግኑህ” ወይም “ራስህን አታመስግን ... ራስህን አታመስግን” (አስጨምሬ እና ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

የማያውቅህ ሰው
“ያመስግኑህ” የሚለውን ቃል ከመጀመርያው ሀረግ በግልጽ መረዳት ይቻላል። እዚህ ላየ ቃላቶቹ ሊደጋገሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “የማያውቅህ ሰው ያመስግንህ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 27:3

የሞኝ ሰው ትንኮሳ ግን ከሁለቱም እጅግ የከበደ ነው
ሞኝ ሰው ሲተነኩሰህ የሚገጥምህ ትዕግስተኛ የመሆን ችግር ያ ችግር እጅግ የከበደ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሞኝ ትንኮሳ መታገስ ከሁለቱም ይከብዳል” ወይም “ሞኝ ሲተነኩስህ መታገስ እነርሱን ለመሸከም ከመታገስ የበለጠ ይከብዳል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሞኝ ትንኮሳ
“በሞኝ አማካኝነት የሚመጣ ችግር።” “ትንኮሳ” ቁጣ ወይም መራራነት የሚፈጥሩ ድርጊቶች ወይም ቃላት ናቸው።

የንዴት ጭካኔና የቁጣ ጎርፍ አለ፣ በቅናት ፊት መቆም የሚችል ግን ማን ነው?
“ንዴት፣” “ጭካኔ” እና “ቁጣ” እንደ ቅጽል ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ተናዳጅ ሰው ጨካኝ ነው፣ ቁጡ ሰው ይጎዳል፣ ነገር ግን በቀናተኛ ሰው ፊት ማን መቆም ይችላል? (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ጭካኔ
“ሀይለኛነት”

የቁጣ ጎርፍ
“የቁጣ አጥፊነት።” እዚህ ላይ ቁጣ ሀይለኛ ጎርፍ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በቅናት ፊት መቆም የሚችል ግን ማን ነው?
ይህ ጥያቄ ማንም ሰው በቅናት ፊት መቆም እንደማይችል የሚያመለክት ነው። እንደ ዓረፈተ-ሃሳብ ሊቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን በቅናት ፊት መቆም የሚችል ማንም ሰው የለም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በቅናት ፊት መቆም
እዚህ ላይ መቆም የሚለው ቃል ጥቃት በሚፈጽም ቀናተኛ ሰው ላለመጎዳት ጠንካራ እና ጽኑ መሆንን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ቀናተኛ ሰውን መከላከል” ወይም “ቀናተኛ ሰው ጥቃት ሲፈጽምበት በጥንካሬ መጽናት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 27:5

የተገለጠ ተግሳጽ ይሻላል
ይህ “ተግሳጽ” የሚለው ረቂቅ ስም “መገሰጽ” በሚለው ግስ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በገልጽ መገሰጽ ይሻላል” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከተሰወረ ፍቅር
“በግልጽ ከማይታይ ፍቅር ይልቅ።” ይህ ““ፍቅር” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ የግስ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በምስጢር ከመወደድ ይልቅ” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የጓደኛ ማቁሰል የታመኑ ናቸው
“ጓደኛ የሚያመጣው ጉዳቶች የታመኑ ናቸው።” እዚህ ላይ “ቁስል” የሚለው ቃል ጓደኛ ሲገስጸውና ሲያስተካክለው ሰውየው የሚሰማው ሕመምና ሀዘንን ይወክላል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የጓደኛ ማቁሰል የታመኑ ናቸው
የጓደኛ ተግሳጽ ታማኝነት ተግሳጹ የሚያመጣው ሀዘን ታማኝ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “ምንም እንኳ ሀዘን ቢያስከትልም፣ የጓደኛ ተግሳጽ የታመነ ነው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ጠላት ግን ከመጠን በላይ ይስማል
የጠላት መሳም ታማኝ እንዳልሆነ በግልጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ነገር ግን የጠላት ብዙ መሳም ታማኝ አይደሉም” ወይም “ነገር ግን ጠላት ከመጠን በላይ በመሳም ሊያታልልህ ይሞክር ይሆናል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ

ከመጠን በላይ
“በብዛት” ወይም “ብዙ ጊዜ”

Proverbs 27:7

በጣም ጠግቦ የበላ ሰው
“የጠገበ ሰው” ወይም “በጣም ጠግቦ የበላ ሰው”

የማር ወለላንም አይቀበልም
የማር ወለላ ብዙ ጊዜ አስፈላጊ ነው፣ ነገር ግን በጣም ጠግቦ ለበላ ሰው ግን አይሆንም።

ማንኛውም መራራ ነገር እንኳ ጣፋጭ ነው
“ማንኛውም መራራ ነገር ይጣፍጣል”

ከጎጆዋ ወጥታ እንደምትንከራተት ወፍ ከመኖሪያው አካባቢ ወጥቶ እንደሚባዝን ሰው እንደዚሁ ነው
በዚህ ጥቅስ “መንከራተት” እና መባዘን” የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 27:9

ሽቶ
እዚህ ላይ “ሽቶ” የሚለው ቃል ደስ የሚል ዘይት ወይም ቅባት ማለት ነው።

ልብን ደስ ያሰኛል
እዚህ ላይ “ልብ” የሰውን ስሜት ወይም መንፈስ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰውን የደስተኝነት ስሜት እንዲሰማው ማድረግ” ወይም “ሰውን ደስ እንዲለው ማድረግ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የጓደኛ ጣፋጭነት ግን ከምክሩ ይበልጣል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) “ጣፋጭነት” ደግነትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እኛ የጓደኛችንን ደግነት በምክሩ አውቀናል” ወይም 2) “ጣፋጭነት” ስለ ሰው የምናደንቀውን ነገር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ስለጓደኛ የምናደንቀውን ነገር ምክሩን ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የወንድምህ ቤት
እዚህ ላይ “ወንድም” የሚለው ቃል ለዘመዶች ማለትም ተመሳሳይ ጎሳ፣ ዘር ወይም ሕዝብ አባላት አጠቃላይ መግለጫ ነው።

ችግር
ጽኑ የሆነ መከራና አጋጣሚ

Proverbs 27:11

ልቤንም ደስ አሰኛት
እዚህ ላይ “ልብ” የሰውን ስሜት ወይም መንፈስ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ደስተኛ አድርገኝ” ወይም “ደስ አሰኘኝ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በዚያን ጊዜ ለሚያፌዝብኝ ሰው እኔ መልስ እሰጣለሁ
እዚህ ላይ “መልስ” ለጥያቄ መልስ መስጠት ማለት አይደለም። ለሚያፌዝ ሰው ምላሽ መስጠት ወይም ተገቢውን መልስ መስጠት ማለት ነው። ይህ በፊቱ ካው ሀረግ ጋር እንዴት እንደሚገናኝ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔ በእኔ ላይ ለሚያፌዝብኝ ሰው ለእርሱ ስለ አንተ በመንገር ምላሽ አሰጠዋለሁ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ማፌዝ
ለየተ ባለ መልኩ ጭካኔ በተሞላበት መንገድ በአንድ ሰው ላይ መቀለድ

ጥንቁቅ ሰው ችግር ሲያይ ራሱን ይሸሸጋል፣ አላዋቂዎች ግን ቀድመው ሄደው በችግሩ ምክንያት ይጎዳሉ
ይህንን በምሳሌ 22:3 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

ጥንቁቅ ሰው
“ጥበበኛ የሆነ ሰው” ወይም “ጥሩ የማገናዘብ ችሎታ ያለው ሰው”

አላዋቂዎች
“ልምድና የሕይወት ብስለት የሌላቸው ሰዎች”

ይጎዳሉ
የሚያሳዝኑ ነገሮች ማለትም እንደ በሽታ፣ ሕመም ወይም ሌሎች መከራዎች በሕይወታቸው ይገጥማቸዋል

Proverbs 27:13

ለማይታወቅ ሰው ብድር በዋስትና ገንዘብ ያስያዘውን ሰው ልብስ ውሰድበት
ገንዘብ በማበደር ጊዜ አበዳሪ ከተበዳሪው ብድሩን መልሶ ለመክፈሉ እንደ ዋስትና የሚሆን ልብስ ወይም ሌላ ነገር ይወስዳል። ገንዘቡ ከተመለሰለት በኋላ የያዘውን መያዣ ይመልሳል። ተበዳሪው በጣም ድኃ ከሆነ ሌላ ሰው ስለ እርሱ እንደ ዋስትና ለአበዳሪው የሆነ ነገር ይሰጣል። ይህንን በምሳሌ 20:16 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “የማይታወቅ ሰው የተበደረው ብድር ተመልሶ እንዲከፈል ተያዥ ከሆነው ሰው እንደ ዋስትና እንዲሆን ልብስ ውሰድበት” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በዋስትና ገንዘብ ያስያዘውን ሰው
የተበደረው ብድር እንደገና ለመከፈሉ እንደ ዋስትና እንዲሆን አንድ ሰው አንድ ነገር ለአበዳሪው ይሰጣል ማለት ነው። ይህንን በምሳሌ 20:16 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “የተበደረው ብድር ተመልሶ እንዲከፈል ተያዥ የሆነው ሰው” ወይም “ብድርን ለመክፈል ቃል የገባው ሰው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

መያዣ ውሰድበት
“አነድን ነገር በመያዣነት መውሰድ” ዕዳውን እንዲከፍል አንድ ሰው እንደ መያዣ ወይም ቃል ኪዳን የሰጠውን ነገር መያዝ ማለት ነው። ይህንን በምሳሌ 20:16 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “ብድሩ ለመከፈሉ እንደ ዋስትና ልብሱን ውሰድበት” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጎረቤቱን የሚባርክ ሰው
“አንድ ሰው ለጎረቤቱ በረከት ቢሰጠው”

ባርኮቱ እንደ እርግማን ይቆጠራል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጎረቤቱ በረከቱን እንደ እርግማን ይቆጥረዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 27:15

ጠበኛ
ይህ ሰዎች እርስ በርሳቸው እንዲበሳጩ ማድረግ ወይም በሰዎች መካከል ጠንካራ ጠብ እንዲፈጠር ማድረግ ማለት ነው።

እንደማያቋርጥ ነጠብጣብ
ይህ የሚያስተላልፈው መልእክት በማያቋርጥ ሁኔታ የሚንጠባጠብ ዝናብ ነው የሚል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የማቋርጥ የዝናብ ነጠብጣብ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የዝናብ ቀን
“የማያቋርጥ ዝናብ የሚዘንብበት ቀን”

እሷን ማቆም ንፋስን እንደማቆም ወይም ዘይትን በቀኝ እጅህ ለመጨበጥ እንደ መሞከር ነው፡
የዚህ መልእክት እርስዋን ለማስቆም መሞከር ነፋስን እንደ ማቆም ወይም በእጅህ ዘይትን እንደ መጨበጥ በጣም አስቸጋሪና ጥቅም አልባ ነው። (ተነፃፃሪ ዘይቤ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እርስዋን ማስቆም
“እርስዋን ወደኋላ መመለስ” ወይም “እርስዋን መቆጣጠር።” የዚህ መልእክት እርስዋን ከመጣላት ለማስቆም መሞከር የሚል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እርስዋን ከመጣላት ማስቆም” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ንፋስን ማስቆም
“ነፋስን መመለስ” ወይም “ነፈስን በቁጥጥር ስር ማዋል”

Proverbs 27:17

ብረት ብረትን ይስለዋል፤ በተመሳሳይ መንገድ ሰው ጓደኛውን ይስለዋል
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ብረት እና ሰው እንዴት ሊለወጡ እንደሚችለ ያነጻጽራሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ብረት ሌላ ቁራጭ ብረትን እንደሚስል በተመሳሳይ መንገድ የሰው ባህርይ ከጓደኛው ጋር ባለው ግንኙነት ይለወጣል” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሚጠብቅ
“የሚንከባከብ”

ጌታውንም የሚጠብቅ ይከብራል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሚጠብቀውን ጌታው የከብረዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 27:19

የሰው ልብ
እዚህ ላይ የሰው ሃሳብ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰው የሚያስበው ነገር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የሙታን ዓለም
ይህ ስም “አጥፊ” ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አጥፊው” (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

አይጠግቡም
“አይሞሉም”

የሰው ዓይን
እዚህ ላይ “ዓይን” የሰውን ምኞት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሰው ምኞት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 27:21

ማቅለጫ ለብር ከውርም ለወርቅ ነው
ይህ ወርቅና ብር እንዴት እንደሚነጥሩ የሚያሳይ ነው። ብረት መቅለጥ እንዲችልና በውስጡ ያለው ቆሻሻ እንዲወገድ የሚነጥረው እጅግ በጣም ሀይለኛ በሆነ የሙቀት ሃይል በማሞቅ ነው። ይህን በጣም ተመሳሳይ ሀረግ በምሳሌ 17:3 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- አማራጭ ትርጉም፡- “ማቅለጫ ብር ለማንጠር ይጠቅማል፣ ከውር ደግሞ ወርቅ ለማንጠር ይጠቅማል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ማቅለጫ
በጣም ከፍተኛ በሆነ ሙቀት ብረት የሚቀልጥበት ማሰሮ ነው። (የማይታወቁ ነገሮችን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

ከውር
ከመጠን በላይ ማሞቅ የሚቻል ምድጃ (የማይታወቁ ነገሮችን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

ሰውም በሚመሰገንበት ጊዜ ይፈተናል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ሰው ሌላ ሰው ሲያመሰግን ያንን ሰው እየፈተኑት ነው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ሞኝን ብትወቅጠውም ... ሞኝነቱ ግን እርሱን አይለቀውም
ምንም እንኳ ሞኝ በብዙ መከራ ወይም ውጣ ውረድ ቢያልፍም (መወቀጥ በዕብራይስጥ ብዙ ጊዜ ለመከራ ተለዋጭ ዘይቤ ነው) ሞኝ እንደሆነ ይቀራል ማለት ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዘነዘና
የተለያዩ ነገሮችን በሙቀጫ ለማድቀቅ የሚረዳ ክብ ጫፍ ያለው ጠንካራ መሳርያ ነው (የማይታወቁ ነገሮችን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 27:23

የመንጋህን ሁኔታ በእርግጠኝነት እወቅ፣ ስለ እንስሳዎችህም ግድ ይበልህ፣
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ በአንድ ላይ የተቀመጡት አጽንዖት ለመስጠት ነው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

መንጋህ
“የበግ መንጋ”

እንስሳዎችህ
“የፍየል መንጋ”

ዘውድ ለትውልድ ሁሉ ይጸናልን?
ይህ ጥያቄ የምድር ገዢዎች የአገዛዝ ዘመን ለዘላለም እንደማይኖር ግንዛቤ ለማስጨበጥ አሉታዊ መልስ የሚሰጥበት እንደሆነ ግልጽ ነው። ይህ እንደ ዓረፍተ-ሃሳብ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ዘውድ ለትውልድ ሁሉ አይጸናም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ዘውድ
እዚዚ ላይ “ዘውድ” የንጉሱን በመንግስቱ ላይ ያለውን አገዛዝ የሚያሳይ ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የንጉስ አገዛዝ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

አዲሱ ቡቃያ አድጎ ይታያል
“አዲስ ቡቃያ ይታያል” ወይም “አዲስ ሳር ማደግ ጀምሯል”

Proverbs 27:26

አያያዥ ዓረፍተ-ሃሳቦች
ቁጥር 26 እና 27 ከቁጥር 23 እና 25 ጋር እንደ አንድ ምሳሌ አብረው ይሄዳሉ።

እነዚህ በጎች ለልብስህ የሚሆን ይሰጡሃል
ከዚህ የምናገኘው አመልካች መረጃ ከበጎች የሚገኘው ሱፍ (ጸጉር) ልብስ ለመስራት ጥቅም ላይ ይውላል የሚል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የበጎች ሱፍ ለልብስህ የሚሆን ይሰጥሃል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእርሻህ ዋጋ የሚሆን ደግሞ ከፍየሎችህ ታገኛለህ
ከዚህ የምናገኘው አመልካች መረጃ ፍየሎችን በመሸጥ የሚገኘው ገንዘብ እርሻ ለመግዛት በቂ ነው የሚል ነው። ከበጎች የሚገኘው ሱፍ (ጸጉር) ልብስ ለመስራት ጥቅም ላይ ይውላል የሚል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ፍየሎችህን መሸጥ የእርሻህን ዋጋ ይሰጥሃል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለቤተሰብህ
“ለቤተሰብህ በሙሉ”

ሴት አገልጋዮችህንም ለመመገብ የሚበቃ
ከዚህ የምናገኘው አመልካች መረጃ ከዚህ በተጨማሪ ሴት አገልጋዮችንም ለመመገብ የሚበቃ በቂ የፍየሎች ወተት ይኖራል የሚል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሴት አገልጋዮችህን ለመመገብ የሚበቃ በቂ የፍየሎች ወተት ይኖራል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መመገብ
“ምግብ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 28

1 ኃጢአተኛ ማንም ሳያባርረው ይሸሻል፣ ጽድቅን የሚያደርጉ ግን እንደ አንበሳ ደፋር ናቸው። **2** በአገር አመጽ ምክንያት ብዙ ገዢዎች አሏት፣ ማስተዋልና እውቀት ባለው ሰው ግን፣ አገር ለረዥም ዘመን ትቆያለች። **3** ድሃ ሆኖ ሌሎች ድሆችን የሚያስጨንቅ ሰው፣ ሰብልን እንሚያጠፋ ዶፍ ዝናብ ነው። **4** ሕግን የሚተዉ ሰዎች ክፉዎችን ያመሰግናሉ፣ ሕግን የሚጠብቁ ግን ከእነርሱ ጋር ይዋጋሉ። **5** ክፉ ሰዎች ፍትህን አያውቁም፣ እግዚአብሔርን የሚፈልጉ ግን ሁሉን ነገር ያውቃሉ። **6** በመንገዱ ጠማማ ከሆነ ባለጠጋ ይልቅ፣ በሐቀኝነቱ የሚራመድ ድሃ ሰው ይሻላል። **7** ሕግን የሚጠብቅ ማስተዋል ያለው ልጅ ነው፣ የሆዳሞች ጓደኛ ግን አባቱን ያሳፍራል። **8** ከፍተኛ ወለድ በመሰብሰብ ሀብቱን የሚያከማች ለድሀዎች ለሚራራ ለሌላ ሰው ሀብቱን ይሰበሰብለታል። **9** አንድ ሰው ሕግን ከማድመጥ ጆሮውን የሚያዞር ከሆነ፣ ጸሎቱ እንኳ የተጠላ ነው። **10** ቅኑን ሰው ወደ ክፋት መንገድ የሚመራ ሁሉ ራሱ በቆፈረው ጉድጓድ ይገባል፣ ንጹሐን ግን መልካምን ነገር ይወርሳሉ። **11** ባለጠጋ ሰው በራሱ ዓይኖች ጥበበኛ ሊሆን ይችላል፣ አስተዋይ የሆነ ድሃ ሰው ግን እርሱን ይመረምረዋል። **12** ጽድቅን የሚያደርጉ ድል በሚያገኙበት ጊዜ፣ ታላቅ ክብር አለ፣ ክፉዎች በሚነሱበት ጊዜ ግን ሰዎች ራሳቸውን ይሸሸጋሉ። **13** ኃጢአቱን የሚሸሸግ አይሳካለትም፣ የሚናዘዝና የሚተወው ግን ምህረትን ያገኛል። **14** ዘወትር እግዚአብሔርን እየፈራ የሚኖር ሰው ደስተኛ ነው፣ ልቡን የሚያደነድን ግን ወደ መከራ ይወድቃል። **15** እንደሚያገሳ አንበሳ ወይም እንደ ተቆጣ ድብ በድሆች ላይ የሚገዛ ክፉ ገዥም እንዲሁ ነው። **16** ማስተዋል የሌለው ገዥ በጭካኔ የሚያስጨንቅ ነው፣ ማታለልን የሚጠላ ግን እድሜውን ያረዝማል። **17** አንድ ሰው የሌላውን ደም በማፍሰሱ ምክንያት በደለኛ ከሆነ፣ እስከ ሞቱ ቀን ድረስ ኮብላይ ይሆናል፣ ማንም ሰው አይረዳውም። **18** በሐቀኝነት የሚራመድ ሰው በደህና ይጠበቃል፣ መንገዱ በጠማማነት የተሞላ ግን በድንገት ይወድቃል። **19** መሬቱን የሚያርስ ሰው ብዙ መብል ይኖረዋል፣ የማይጠቅም ሞያ የሚከተል ግን እጅግ በጣም ይደኸያል። **20** ታማኝ ሰው ታላቅ በረከት ያገኛል፣ በጥድፊያ ሃብታም የሆነ ግን ሳይቀጣ አይቀርም። **21** አድልዎን ማሳየት መልካም አይደለም፣ ነገር ግን ለቁራጭ ዳቦ ሲል ሰው ስህተትን ይሰራል። **22** ስስታም ሰው ሐብትን ያሳድዳል፣ ድህነት በላዩ ላይ እንደሚመጣ ግን አያውቅም። **23** ሰውን በምላሱ ከሚያሞግስ ይልቅ የሚገስጽ ሰው በኋላ ውሎ አድሮ ከገሰጸው ሰው ብዙ ሞገስ ያገኛል። **24** አባቱንና እናቱን ሰርቆ “ኃጢአት አይደለም” የሚል ሰው የአጥፊ ተባባሪ ነው። **25** ስግብግብ ሰው ግጭትን ያነሳሳል፣ በእግዚአብሔር የሚታመን ግን ይባረካል። **26** በራሱ ልብ የሚታመን ሰው ሞኝ ነው፣ በጥበብ የሚራመድ ግን ከአደጋ ይርቃል። **27** ለድሃ የሚሰጥ ምንም ነገር አይጎድልበትም፣ በድሆች ላይ ዓይኖቹን የሚከድን ሰው ግን ብዙ እርግማን ይቀበላል። **28** ክፉ ሰዎች ሲነሱ፣ ሰዎች ራሳቸውን ይሸሸጋሉ፣ ክፉ ሰዎች ሲጠፉ ግን፣ ጽድቅን የሚያደርጉ ይበዛሉ።

Proverbs 28:1

በምድሪቱ በደል ምክንያት
“በደል” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ምድሪቱ በበደለችው በደል ምክንያት” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የምድሪቱ በደል
ይህ በምድሪቱ የሚኖረው ሕዝብ ኃጢአት ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የምድሪቱ ሕዝብ በደል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ማስተዋልና እውቀት ባለው ሰው
ከዚህ የምናገኘው አመልካች መረጃ ይህ ሰው መሪ ወይም ገዢ መሆነኑ ነው። “ማስተዋል” እና “እውቀት” የሚሉት ረቂቅ ስሞች እንደ ግስ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “በሚያስተውልና እንዴት መምራት እንዳለበት በሚያውቅ ሰው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ እና ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 28:3

የሚጨቁን
“በጭካኔ የሚያስጨንቅ”

ሰብልን እንሚያጠፋ ዶፍ ዝናብ ነው
ድሆችን የሚጨቁን ድሃ ሰው በከባድ ሁኔታ ከሚወርድና ሰብልን ከሚያጠፋ ዶፍ ዝናብ ጋር ተነጻጽሯል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዶፍ ዝናብ
ይህ በከባድ ሁኔታ ለሚወርድና ሰብልንለሚያጠፋ ዝናብ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አጥፊ ዝናብ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሕግን የሚተዉ
“የእግዚአብሔርን ሕግ መተው”

ሕግን የሚጠብቁ
“ሕግን መጠበቅ” የእግዚአብሔር ሕግ የሚፈልገውን መፈጸም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የእግዚአብሔርን ሕግ የሚታዘዙ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእነርሱ ጋር ይዋጋሉ
“ከእነርሱ ጋር ይታገላሉ።” ይህ እነርሱን አጥብቀው ይቃወሟቸዋል ወይም ይቋቋሟቸዋል ማለት ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 28:5

ክፉ ሰዎች
እዚህ ላይ “ሰዎች” የሚለው በአጠቃላይ ሕዝብ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ነገሮችን የሚሰሩ ሕዝብ” (ለወንዶች የምንጠቀምባቸው ቃላቶች ሴቶችንም ሲያካትቱ የሚለውን ይመልከቱ)

ፍትህን አያውቁም
“ፍትህ” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ፍትህ ምን እንደሆነ አታውቅም” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚብሔርን የሚፈልጉ ሰዎች
እግዚአብሔርን ለማወቅ የሚፈልጉና እርሱን የሚያስደስቱ ሰዎች እግዚአብሔርን በአካል ለማግኘት እንደሚፈልጉ ተደርገው ተነግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉን ነገር ያውቃሉ
ከዚህ የምናገኘው አመልካች መረጃ እግዚአብሔርን የሚፈልጉ ሰዎች ስለ ፍትህ ሁሉን ነገር ያውቃሉ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ፍትህ ምን እንደሆነ ሙሉ በሙሉ ያውቃሉ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከባለጠጋ ይልቅ ... ድሃ ሰው ይሻላል
“ባለጠጋ ሰው ከመሆን ይልቅ … ድሃ ሰው መሆን ይሻላል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በሐቀኝነት የሚራመድ
ይህ የሐቀኝነትን ሕይወት የሚኖር ሰውን ይወክላል። ይህ “ሐቀኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ተውሳከ ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በታማኝነት ይራመዳል” walks honestly” or “lives honestly” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በመንገዱ ጠማማ የሆነ
ታማኝ ያልሆኑ ባለጠጋ ሰዎች በጠማማ መንገድ ወይም በጠመዝማዛ መንገድ እንደሚሄዱ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “በሚያደርገው ነገር ታማኝ ያልሆነ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 28:7

ሕግን የሚጠብቅ
“ሕግን መጠበቅ” የእግዚአብሔር ሕግ የሚጠይቀውን ነገር ማድረግ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የእግዚአብሔርን ሕግ የሚታዘዝ ሰው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ማስተዋል ያለው ልጅ
“ማስተዋል” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የሚያስተውል ልጅ” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ሆዳሞች
“ከመጠን በላይ የሚበሉ ሰዎች።” “ሆዳም” ሰው ብዙ ጊዜ ከመጠን በላይ የሚበላና የሚጠጣ ሰው ነው።

አባቱን ያሳፍራል
“አባቱ እንዲያፍር ያደርጋል” ወይም “አባቱን ያዋርዳል”

ሀብት የሚያከማች
“ሀብቱን ይጨምራል”

ከፍተኛ ወለድ መሰብሰብ
“ለማበደር ተጨማሪ ገንዘብ መሰብሰብ”

ወለድ
የሌላ ሰው ገንዘብ በመጠቀሙ በተበዳሪው የሚከፈል ገንዘብ

ሀብቱን ይሰበስባል
“ገንዘቡን በአንድ ላይ ያመጣል”

ሌላ ሰው
“ለሌላ ሰው”

ማዘን
ለአንድ ሰው የማዘን ወይም የመራራት ጠንካራ ስሜት

Proverbs 28:9

አንድ ... ከሆነ
“አንድ ሰው … ከሆነ”

ሕግን ከማድመጥ ጆሮውን የሚያዞር ከሆነ
ይህ ሰው በሁለንተናው የእግዚአብሔርን ሕግ ከማድመጥ ጆሮውን ማዞርና አለመቀበልን የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የእግዚአብሔርን ሕግ ከማድመጥና ከመታዘዝ ይዞራል” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ጸሎቱ እንኳ የተጠላ ነው
“ጸሎቱ እንኳ በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ነው።” ይህ በገቢር ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ጸሎቱን እንኳ ይጠላዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የጠጠላ
ይህንን በምሳሌ 3:32 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

ቅኑን ሰው ወደ ክፋት መንገድ የሚመራ ሁሉ
ይህ ቅን ሰዎችን ወደ ክፋት መንገድ ለመምራት ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ቅኑን ሰው ወደ ክፋት መንገድ እንዲሔድ የሚያደርግ ሁሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ክፋት መንገድ የሚመራ ሁሉ ... ይወድቃል
“አንድ ሰው ወደ ክፋት መንገድ ከመራ … ይወድቃል”

ቅን
ይህ በአጠቃላይ ቅን ሰዎችን የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ቅን ሰዎች” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

በቆፈረው ጉድጓድ ይገባል
“ራሱ በቆፈረው ወጥመድ ውስጥ ይገባል።” ፍጻሜው ሌሎችን ወደመራበት ተመሳሳይ መጥፎ ቦታ ስለመሆኑ የሚያመለክት ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እርሱ ሌሎች ሰዎቸን ወደመራበት ክፉ ስፍራ የእርሱም ፈጻሜ እንደዚያው ይሆናል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ንጹሐን ሰዎች
ይህ በአጠቃላይ ነቀፌታ የለለባቸውን ሰዎች የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ነቀፌታ የሌለባቸው ሰዎች” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

መልካምን ነገር ይወርሳሉ
“መልካም የሆነውን ነገር ይወርሳሉ”

Proverbs 28:11

በራሱ ዓይኖች ጥበበኛ ሊሆን ይችላል
ዓይኖች መመልከትን ይወክላል፣ መመልከት ደግሞ ሃሳብንና ግንዛቤን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በራሱ አስተሳሰብ ጥበበኛ ነው” ወይም “ጥበበኛ እንደሆነ ያስባል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ማስተዋል ያለው
“ማስተዋል” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የሚያስተውል” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱን ይመረምረዋል
ይህ ፈሊጥ ሲሆን ድሃው ሰው ሀብታምን ሰው በእርግጥ ጥበበኛ እንደሆነና እንዳልሆነ መወሰን ይችላል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እውነተኛ ተፈጥሮውን ይመለከታል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ጽድቅን የሚያደርግ ድል በሚያገኙበት ጊዜ
“ጽድቅን የሚያደርግ በሚሳካለት ጊዜ”

ክፉዎች በሚነሱበት ጊዜ
ይህ ፈሊጥ ሲሆን ክፉ ሰዎች ስልጣን በሚይዙበት ጊዜ ወይም መምራት በሚጀምሩበት ጊዜ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ክፉ ሰዎች ወደ ስልጣን በሚመጡበት ጊዜ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉ ሰው
ይህ በአጠቃላይ ክፉ ሰዎችን የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ክፉ ሰዎች” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰዎች ራሳቸውን ይሸሸጋሉ
እነዚህ “ራሳቸውን የሸሸጉ” ሰዎች ከክፉ ሰዎች ለማምለጥ ሲሉ ራሳቸውን መደበቃቸውን ግልጽ ማድረግ ያስፈልግ ይሆናል። ይህ በገቢር ግስ ለገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰዎችን ያገኙአቸዋል” ወይም “ከእነርሱ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የተደበቁትን ሰዎች ያገኙአቸዋል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ እና ገቢር/አድርጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 28:13

ኃጢአቱን ይደብቃል
“ኃጢአቱን ይሰውራል።” ይህ ንስሃ የመግባትና ኃጢአትን የመተው ተቃራኒ ሲሆን ኃጢአትን ወደ ብርሃን ከማምጣት ይልቅ ኃጢአትን መሰወር ተደርጎ ተነግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አይበለጽግም
“አይሳካለትም” ወይም “አያድግም”

ኃጢአቱን የሚሰውር አይሳካለትም፣ የሚናዘዝና የሚተወው ግን ምህረትን ያገኛል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን ለሚናዘዙና የሚተወው ምህረትን ይሰጣቸዋል” (ገቢር/አድርጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ዘወትር እግዚአብሔርን እየፈራ የሚኖር ሰው ደስተኛ ነው
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ዘወትር እየፈራ የሚኖርን ሰው ይባርካል” (ገቢር/አድርጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እየፈራ የሚኖር ሰው
“መፍራት” የሚለው ረቂቅ ስም አንደ ቅጽል ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በፍርሃት የተሞላ ሕይወት ይኖራል” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

መፍራት
ይህ እግዚአብሔርን በጥልቀት ማክበርና ይህንን አክብሮት እርሱን በመታዘዝ ማሳየትን ያመለክታል።

ልቡን የሚያጠነክር ሰው
“ልቡን የሚያደነድን ሰው”

ልቡን አጠነከረ
ይህ ፈሊጥ ሲሆን ግትርና እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ፈቃደኛ ያልሆነ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ፈቃደኛ አይደለም” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

መከራ ውስጥ ይወድቃል
ይህ በስቃይና በጉስቁልና ውስጥ መግባትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በችግር ውስጥ ይገባል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 28:15

እንደሚያገሳ አንበሳ ወይም እንደ ተቆጣ ድብ በድሆች ላይ የሚገዛ ክፉ ገዥም እንዲሁ ነው
ከክፉ ገዥ ሊያድናቸው የሚችል ማንም የሌላቸው ድሃ ሰዎች አንበሳ በላያቸው ላይ ከሚያገሳባቸው ሰዎች ወይም ድብ ከሚያጠቃቸው ሰዎች ጋር ተነጻጽረዋል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የተቆጣ ድብ
ድብ በአራት እግር የሚራመድ ስለታም ጥፍርና ጥርስ ያለው ትልቅ፣ አስፈሪና አደገኛ እንስሳ ነው። (የማይታወቁ ነገሮችን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

ማስተዋል የሌለው ገዥ
“ማስተዋል” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የማያስተውል ገዥ” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ጨቋኝ
ሰዎችን በማስጨነቅ የሚይዝና የሰዎችን ሕይወት አሰቃቂ የያደርግ

ማታለልን የሚጠላ ሰው
“ማታለል” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ታማኝ አለመሆንን የሚጠላ ሰው” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እድሜውን ያረዝማል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ይህ ፈሊጥ ሲሆን ለበለጠ ጊዜ ይኖራል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ረጅም ጊዜ መኖር” ወይም 2) ይህ ፈሊጥ ሲሆን የመሪነት ጊዜውን ማስረዘም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ለረጅም ጊዜ ይመራል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 28:17

የሌላ ሰው ደም አፍስሷል
እዚህ ላይ “ደም” የሚለው የሰውን ሕይወት ይወክላል። “ደምን ማፍሰስ” አንድን ሰው መግደል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የሆነ ሰው ገድሏል” ወይም “የሆነ ሰውን ነፍስ አጥፍቷል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ኮብላይ
እንዳይያዝ ለማምለጥ የሚሸሸ ሰው

እስከ ሞት ድረስ
“እስከሚሞት ድረስ።” ለቀጣይ የሕይወቱ ዘመን ሁሉ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሕይወቱን በሙሉ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

በሐቀኝነት የሚራመድ ሰው በደህና ይጠበቃል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአበሔር በሐቀኝነት የሚሄድን ማንኛውንም ሰው በደህንነት ይጠብቀዋል” (ገቢር/አድርጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ማንም
“ማንኛውም ሰው”

በሐቀኝት የሚራመድ
ይህ የሐቀኝነት ሕይወት የሚኖር ሰው የሚወክል ነው። “ሐቀኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ተውሳከ ግስ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በታማኝነት ይራመዳል” ወይም “በታማኝነት ይኖራል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

መንገዱ በጠማማነት የተሞላ
ታማኝ ያልሆኑ ባለጠጋ ሰዎች በጠማማ መንገድ ወይም በጠመዝማዛ መንገድ እንደሚሄዱ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “በታማኝነት የማይኖር ሰው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በድንገት ይወድቃል
ታማኝ ባልሆነ ሰው የሚደርሰው ነገር በድንገት እንደሚወድቅ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “በድንገት ይጠፋል” ወይም “በድንገት ይከስራል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 28:19

መሬቱን የሚያርስ
ይህ መሬቱን የሚያርስ፣ የሚዘራ እና ሰበሉን የሚንከባከብ ማለት ነው።

የሚከተል
“የሚከተል ማንኛውም ሰው”

የማይጠቅም ሞያ የሚከተል
“የማይጠቅም ሞያ ያሳድዳል።” ምንም ትርፍ የሌላቸውን ነገሮች በመስራት የሚደክምና ጊዜ አልባ የሚሆን ሰው የማይጠቅሙ ነገሮችን እንደሚያሳድድ ተደርጎ ተነግሯል። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

በድህነት ይሞላል
የማይጠቅሙ ሞያዎችን የሚከተል ሰው የተትረፈረፈ ምግብ እንደማያገኝ ተደርጎ ተነግሯል። “ድህነት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “will be very poor” (ምፀት እና ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ))

በጥድፊያ ሃብታም የሆነ ግን ሳይቀጣ አይቀርም
“ሳይቀጣ አይቀርም” የሚለው ሁለት አሉታዊ አገላለጽ ጥቅም ላይ የዋለው አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በጥድፊያ ሃብታም የሚሆኑትን ሰዎች እግዚአብሔር በእርግጠኝት ይቀጣል” (ምፀት እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በጥድፊያ ሃብታም የሆነ
እዚህ ላይ ያለው አመልካች መረጃ ይህ ሰው ሀብት ያገኘው ታማኝነት በጎደለውና አታላይነት በተሞላበት መንገድ መሆኑን የሚያሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በጠድፊያ ሀብታም ለመሆን የሚሞክር ሰው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 28:21

ለቁራጭ ዳቦ ሲል ሰው ስህተትን ይሰራል
እዚህ ላይ “ቁራጭ ዳቦ” የሚለው በጣም ትንሽ ጉቦ ወይም ስጦታ ለማሳየት ጥቅም ላይ የዋለ ግነት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰው ለትንሽ ጥቅም ሲል ኃጢአትን ይሰራል” (ግነትና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ስህተት ይሰራል
“ኃጢአት”

ስስታም ሰው
“ራስ ወዳድ ሰው።” ይህ ያለውን ሀብት ለሌሎች ለማካፈልና ገንዘብ ለማውጣት የማይወድ ሰው ነው።

ሀብት ያሳድዳል
ስስታም ሰው ሀብት እንደሚያሳድድ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለሀብት በጣም ስስታም ነው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ድህነት በእርሱ ላይ ይመጣል
የስስታምነት ውጤት ድህነት በስስታም ላይ በድንገት እንደሚደርስበት ተደርጎ ተነግሯል። “ድህነት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በድንገት ድሃ ይሆናል” (ፈሊጥ እና ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 28:23

ሰውን በምላሱ ከሚያሞግስ ይልቅ የሚገስጽ ሰው በኋላ ውሎ አድሮ ከገሰጸው ሰው ብዙ ሞገስ ያገኛል
ይህ “ሞገስ” የሚለው ረቂቅ ስም በገቢር ቅርጽ በመግለጽ፣ እንደ ግስ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ሰው በምላሱ የሚያሞግሰው ሰው በፊቱ ሞገስ ከሚያገኝ ይልቅ ይልቅ የሚገስጸው በፊቱ ሞገሰ (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የሚገስጽ ሰው
“ሰው የሚገስጽ ከሆነ”

መገሰጽ
ሰዎች ለሞራላዊ ባህርይ የተለያዩ መመርያዎችን እንዲታዘዙ ማሰልጠን

በምላሱ ያሞግሰዋል
እዚህ ላይ ምላስ መናገርን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በቃላት ይክበዋል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ይክበዋል
አንድን ሰው እውነተኛ ባልሆነ መንገድ ማመስገን፣ ወይም እውነተኛ ስላልሆኑ ነገሮች አንድን ሰው ማመስገን

የሚሰርቅ
“የሚሰርቅ ሰው”

“ኃጢአት አይደለም” የሚል፣ እርሱ
ይህ ቀጥተኛ ባልሆነ ትመህርተ ጥቅስ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይህ ኃጢአት አይደለም” የሚል፣ እርሱ” (ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ጥቅሶች የሚለውን ይመልከቱ)

ተባባሪ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡-: 1) “የእርሱ ጓደኛ” ወይም 2) ይህ ፈሊጥ አንድ ዓይነት ባህሪይ ያላቸው ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እንደ እርሱ ተመሳሳይ የሆነ ሰው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 28:25

ስግብግብ ሰው
ከሚያስፈልገው በላይ በራስ ወዳድነት ተጨማሪ ነገሮችን፣ ገንዘብ ወይም ምግብ የሚፈልግ ሰው።

ግጭትን ያነሳሳል
የስግብግቡ ሰው ድርጊት ግጭትን እንደሚያስነሳ ወይም እንደሚቀሰቅስ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ግጭትን ያመጣል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በራሱ ልብ የሚደገፍ ሰው
በራስ ልብ መደገፍ በራስ ልብ እንደ መታመን ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “በራሱ የሚታመን ሰው” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

የሚራመድ
“የሚራመድ ማንኛውም ሰው”

በጥበብ ይመላለሳል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ይህ ፈሊጥ ሲሆን በጥበብ መኖር ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በጥበብ ይኖረል” ወይም 2) ይህ ፈሊጥ ሲሆን የጥበበኛ ሰዎች ትምህርትን መከተል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የጥበብ ትምህርቶችን ይከተላል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 28:27

ሰው
“ያ ሰው”

ድሀ
ይህ በአጠቃላይ ድሆችን የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ድሀ ሰዎች” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ምንም አያጡም
ይህ ድርብ አሉታዊ ቃላት ጥቅም ላይ የዋለው አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የሚያስፈልጋቸው ማንኛውም ነገር አላቸው” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

በእነርሱ ላይ ዓይኖቹን የሚከድን ሰው ብዙ እርግማን ይቀበላል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ከድሀው ብዙ እርግማ ይቀበላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ድሆች በእነርሱ ላይ ዓይናቸውን ለሚከድኑ ለማንኛውም ሰው ብዙ እርግማ ይሰጣሉ” ወይም 2) በአጠቃላይ ብዙ እርግማን ከሰዎች ይቀበላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች በድሆች ላይ ዓይናቸውን ለሚከድኑ ለማንኛውም ሰው ብዙ እርግማን ይሰጣሉ” ወይም 3)

ከእግዚአብሔር ብዙ እርግማን ይቀበላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር በድሆች ላይ ዓይናቸውን ለሚከድኑ ለማንኛውም ሰው ብዙ እርግማን ይሰጣቸዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ዓይኖቹን የሚከድን
“ዓይኑን የሚገድን ማንኛውም ሰው”

ለ ... ዓይኖቹን የሚከድን
ዓይንን መክደን ለድሆች ፍላጎት ምላሽ አለመስጠትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ቸል የሚል” ወይም “ላለመርዳት መምረጥ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉ ሰዎች ሲነሱ
ይህ ፈሊጥ ሲሆን ክፉ ሰዎች ስልጣን ሲይዙ ወይም መግዛት ሲጀምሩ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ሰዎች ወደ ስልጣን ሲወጡ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰዎች ራሳቸውን ይሸሸጋሉ
ክፉ ሰዎች እነርሱን እንዳይጎዱአቸው ሊያደርጉ የሚችሉትን ሁሉ ለማድረጋቸው በግነት የቀረበ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች ወደ መሸሸጊያ ይሄዳሉ” (ግነትና ጅምላ ፍረጃ እና ከባለቤቱ ጋር የሚጣቀስ አመልካች ተውላጠ ስም የሚለውን ይመልከቱ))

ይጠፋሉ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) “ይሄዳሉ” ወይም 2) “ከስልጣን ይወርዳሉ” ወይም 3) “ይወድማሉ።”

ይጨምራሉ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) “ይበዛሉ” ወይም 2) “ወደ ስልጣን ይወጣሉ።”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 29

1 ብዙ ተግሳጽን ተቀብሎ አንገቱን ያደነደነ ሰው እንደማይድን ሆኖ በቅጽበት ይሰበራል። **2** ጽድቅን የሚያደርጉ ሰዎች ሲበዙ፣ ሕዝብ ደስ ይለዋል፣ ክፉ ሰው ገዢ ሲሆን ግን ሕዝብ ያቃስታል። **3** ጥበብን የሚወድ ሁሉ አባቱን ደስ ያሰኛል፣ አመንዝራዎች ወዳጅ ግን ሀብቱን ያጠፋል። **4** ንጉስ አገሩን በፍትህ ያጸናል፣ ጉቦን የሚፈልግ ግን ያፈራርሳታል። **5** ጎረቤቱን የሚሸነግል ሰው ለገዛ እግሩ መረብ እየዘረጋ ነው። **6** ክፉ ሰው በራሱ ኃጢአት በወጥመድ ይያዛል፣ ጽድቅን የሚያደርግ ግን ይዘምራል፣ ይደሰታልም። **7** ጽድቅን የሚያደርግ ሰው ለድሆች ፍትሕ ይጨነቃል፤ ክፉ ሰው ግን እንዲህ ዓይነት እውቀት የለውም። **8** ፌዘኞች ከተማን ያቃጥላሉ፣ ጥበበኞች ግን ቁጣን ይመልሳሉ። **9** ጥበበኛ ሰው ከሞኝ ጋር በሚከራከርበት ጊዜ፣ ሞኝ ይቆጣል ይስቃልም፣ እረፍትም አይኖርም። **10** ደም የተጠማ ሰው ንጹሐንን ይጠላሉ፣ ቅን የሆነውንም ሕይወት ለማጥፋት ይፈልጋሉ። **11** ሞኝ ቁጣውን ሁሉ ይገልጣል፣ ጥበበኛ ሰው ግን ቁጣውን ይቆጣጠራል፣ ራሱንም ያረጋጋል። **12** ገዢ ለሐሰተኛ ወሬ ትኩረት የሚሰጥ ከሆነ፣ ሹማምንቶቹ ሁሉ ክፉ ይሆናሉ። **13** ድሃና ጨቋኝን አንድ የሚያደርጋቸው አለ፣ እግዚአብሔር ለሁለቱም የዓይን ብርሃንን ሰጥቷቸዋልና። **14** ንጉስ ለድሃ በእውነት ከፈረደ፣ ዙፋኑ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል። **15** በትርና ተግሳጽ ጥበብን ይሰጣሉ፣ ያልተቀጣ ልጅ ግን እናቱን ያሳፍራል። **16** ክፉ ሰዎች ስልጣን ሲይዙ፣ አመጸኝነት ይጨምራል፣ ጽድቅን የሚያደርጉ ግን የክፉዎችን ውድቀት ያያሉ። **17** ልጅህን ቅጣው እረፍትም ይሰጥሃል፤ ለሕይወትህም ደስታን ያመጣል። **18** ትንቢታዊ ራዕይ በሌለበት ሕዝብ መረን ይሆናል፣ ሕግን የሚጠብቅ ግን የተባረከ ነው። **19** አገልጋይ በቃል አይታረምም፣ ቢገባውም ምላሽ አይሰጥም። **20** በቃሎቹ የሚቸኩለውን ሰው ተመልክተሃል? ከእርሱ ይልቅ ለሞኝ የበለጠ ተስፋ አለው። **21** አገልጋዩን ከወጣትነቱ ጀምሮ የሚያሞላቅቅ፣ በመጨረሻ ችግር ይገጥመዋል። **22** ቁጡ ሰው ሁከትን ያነሳሳል፣ ቁጣ የሞላበትም ሰው ብዙ ኃጢአቶችን ይሰራል። **23** የሰው ትዕቢት ያዋርደዋል፣ ትሁት መንፈስ ያለው ግን ይከበራል። **24** ከሌባ ጋር የሚካፈል ሰው ሕይወቱን ይጠላል፤ እርግማንን ይሰማል መልስ ግን አይሰጥም። **25** ሰውን መፍራት ወጥመድ ውስጥ ይከትታል፣ በእግዚአብሔር የሚታመን ግን ይጠበቃል። **26** ብዙዎች የገዢን ፊት ይሻሉ፣ ፍትህ ለሰው የሚመጣው ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው። **27** ፍትህን የሚያጓድል ሰው ጽድቅን በሚያደርጉ ሰዎች ፊት የተጠላ ነው፣ መንገዱ ቅን የሆነ ሰው ግን በክፉዎች የተጠላ ነው።

Proverbs 29:1

አንገቱን ያደነደነ ሰው
ግትር ሰው አንገቱን እንዳደነደነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ግትር የሆነ ሰው” ወይም “ለመስማት እምቢተኛ የሆነ ሰው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በቅጽበት ይሰበራል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር በቅጽበት ይሰብረዋል፡ (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደማይድን ሆኖ
“እንዲፈወስ ሊረዳው የሚችል አንድም ሰው የለም።” በሽታ ለማንኛውም ዓይነት መጥፎ ሁኔታ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሊረዳው የሚችል ማም የለም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰዎች በኃይል ይተነፍፍሉ
ሰዎች በጥልቀት በረጅሙ ይተነፍሳሉ፣ መድከማቸውንና ማዘናቸውን የሚያሳይ ጩኾ መተንፈስ። አማራጭ ትርጉም፡- “ሕዝቡ ይደክማሉ፣ ያዝናሉ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 29:3

በፍትህ
“ፍትህ” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ስም ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ፍትህ ያለበትን ነገር በማድረግ” ወይም “ፍትሃዊ ሕግጋትን በማዘጋጀት” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 29:5

ጎረቤቱን የሚሸነግል ሰው
ተናጋሪው የሚፈልገውን ነገር እንዲያደርግለት በማወቅ ሆን ብሎ ለጎረቤቱ እውነት ያልሆነውን ነገር መንገር።

ለገዛ እግሩ መረብ ይዘረጋል
ተናጋሪው የሰውን ጉራ ሰውየው እንዲያዝ ወጥመድ ከማዘጋጀት ጋር አነጻጽሮታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ያንን ሰው በወጥመድ ለመያዝ ወጥመድ ማዘጋጀት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉ ሰው በራሱ ኃጢአት በወጥመድ ይያዛል
ክፉ ሰው ኃጢአትን ሲሰራ ወደ ወጥመድ እየሄደ እንደሆነ ያህል ነው። በሌሎች ሰዎች ላይ ክፋትን ለማድረግ ይመኛል፤ ነገር ግን እርሱ የሰራውን ነገር ራሱን ለመቅጣት እግዚአብሔር ይጠቀምበታል። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 29:7

ከተማን ያቃጥላሉ
እዚህ ላይ “ከተማ” የሚለው ቃል በከተማይቱ ውስጥ የሚኖሩትን ሰዎች የሚወክል ነው። ምናልባትም ጎይላቸውን ለማሳየት ሕዝብ በብጥብጥ ውስጥ እንዲገባ የሚያደርጉ ሰዎች ከተማይቱን በእሳት እንዳቃጠሉ ተደርገው ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለከተማይቱ ሕዝብ ብጥብጠጥ ይፈጥራሉ” (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቁጣን ይመልሳሉ
ይህ ፈሊጥ ቁጡ ሰዎችን ለወደፊት ተቆጭ እንዳይሆኑ ማድረግ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የቁጡ ሰዎችን ቁጣ ያበርዳሉ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 29:9

ከ ... ጋር ክርክር አለው
ሌላ አማራጭ ትርጉም እንዲህ የሚል ነው፡- “ሊከስሰው ወደ ፍርድ ቤት ይሄዳል።”

ይቆጣል ይስቃልም
ሞኝ በጣም ይናደዳል ከዚያም ጥበበኛውን ሰው እንዳይናገር ወይም ዳኛው ፍርድ እንዳይሰጥ ሊከለክለው ይሞክራል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይቆጣል
ይህ እንደ ጠንካራ አውሎ ነፋስ በጣም መጮህና መደናገጥ ከዚያም ኃይል በተሞላበት ሁኔታ ንቅስቃሴ ማድረግ ማለት ነው። ይህ አሉታዊ ቃል ነው።

እረፍትም አይኖርም
“ችግሩን መፍታት ፈጽሞ አይችሉም”

ሕይወት ይፈልጋሉ
ይህ ፈሊጥ ሲሆን “ሊገድሉ ይፈልጋሉ” ማለት ነው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 29:11

ትኩረት ይሰጣል
“ያደምጣል።” ይህንን በምሳሌ 17:4 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

ሹማምንቶቹ ሁሉ ክፉ ይሆናሉ
የገዢው ተግባር የፈጸሙት ነገር የሚያመጣውን ውጤት በመዘርዘር ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሹማምንቶቹ ሁሉ ክፉ እንዲሆኑ እንደሚያስተምር ያህል ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 29:13

ጨቋኝ
ሰዎችን በማስጨነቅ የሚይዝና የሰዎችን ሕይወት አሰቃቂ የያደርግ

እግዚአብሔር ለሁለቱም የዓይን ብርሃንን ሰጥቷቸዋል
ይህ ፈሊጥ ሲሆን “እግዚአብሔር ሁለቱም በሕይወት እንዲኖሩ አድርጓቸዋል” ማለት ነው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

በዙፋኑ
ዙፋን በዙፋኑ ላይ ሆኖ ለሚመራው መንግስት ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በመንግስቱ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 29:15

በትርና ተግሳጽ ጥበብን ይሰጣሉ
ጸሐፊው በትርና ተግሳጽ እንደ ቁሳዊ እቃ ጥበብን የሚሰጡ ሰዎች አንደሆኑ አድርጎ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “ወላጅ ልጁን ለመቅጣት በትር ቢጠቀምና ቢገስጸው፣ ልጁ ጥበበኛ ይሆናል” ወይም “ወላጆች ልጃቸውን ቢቀጡና ጥፋት ሲሰራ ቢነግሩት ልጁ በጥበብ መኖርን ይማራል” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በትር
በእስራኤል የነበሩ ወላጆች ልጆቻቸውን በመምታት ስነ ስርዓት ለማስያዝ የእንጨት በትር እንደ መሳርያ ይጠቀሙ ነበር። አማራጭ ትርጉም፦ “ስነ ስርዓት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ተግሳጽ
አንድ ሰው ለሌላ ሰው ተግሳጽ ሲሰጥ ወይም ያንን ሰው ሰገስጽ እርሱ የሚሰራውን ስራ እንደማይቀበለው ለዚያ ሰው እየነገረው ነው።

አመጸኝነት ይጨምራል
ይህ “አመጸኝነት” የሚለው ረቂቅ ቃል እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ተጨማሪ ሰዎች አመጽን ያደርጋሉ ከዚያም ኃጢአታቸው እየበዛ ይመጣል” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የክፉ ሰዎች ውድቀት
“ውድቀት” የሚለው ረቂቅ ስም “ወደቀ” በሚለውና የመምራት ስልጣንን ለማጣት ተለዋጭ ዘይቤ በሆነው ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እነዚህ ክፉ ሰዎች ይወድቃሉ” ወይም “እነዚህ ክፉ ሰዎች የመሪነት ስልጣናቸውን ያጣሉ” (ረቂቅ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 29:17

ሕግን የሚጠብቅ ግን የተባረከ ነው
ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ሕግን የሚጠብቁትን ሰዎች ይባርካል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 29:19

ባርያ በቃል አይታረምም
ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። “ባሪያን ከእርሱ ጋር በመነጋገር ብቻ ልታስተካክለው አትችልም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በቃሎቹ የሚቸኩለውን ሰው ተመልክተሃል?
ጸሐፊው የአንባቢውን ትኩረት ለማግኘት ሲል ጥያቄ ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፦ “በቃሎቹ የሚቸኩል ሰው ላይ ምን እንደሚመጣ ልብ ብለህ ልታስተውል ይገባሃል። (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 29:21

ባርያውን የሚያሞላቅቅ
“ባርያውን ስራ እንዳይሰራ የሚያደርግና ባርያውን ከሌሎቹ ባርያዎቹ የበለጠ የሚንከባከበው”

በመጨረሻ
“በባርያው የወጣትነት እድሜ መጨረሻ” ወይም “ባርያው ሲያድግ”

ችግር ይኖራል
እነዚህ ቃላት ማንም ፈጽሞ አያውቅም የሚል ትርጉም ካለው የዕብራይስጥ ቃል የተተረጎሙ ናቸው። አንዳንድ ሰዎች ባርያው ደካማ ይሆናል የሚል መረዳት አላቸው፣ ሌሎች ደግሞ ባርያው ቤተሰቡን ይመራል የሚል መረዳት አላቸው።

ሁከትን ያነሳሳል
ሰዎች የበለጠ እንዲከራከሩ ማድረግ ሁከትን እንደ መቀስቀስ ወይም እንደ ማነሳሳት ተደርጎ ተነግሯል። “ሁከት” የሚለው ረቂቅ ቃል “ክርክር” በሚል ሊብራራ ይችላል። ይህንን በምሳሌ 15:18 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰዎች የበለጠ እንዲከራከሩ ያደርጋል” ወይም “ሰዎች የበለጠ እንዲከራከሩና እንዲጣሉ ያደርጋል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ቁጣ የሞላበትም ሰው
ይህ ፈሊጥ ሲሆን “በቀላሉ የሚቆጣ ሰው” ማለት ነው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 29:23

ትሁት መንፈስ ያለው ሰው ክብር ይሰጠዋል
ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ትሁት መንፈስ ላለው ሰው ሰዎች ክብር ይሰጡታል” ወይም “ትሁት መንፈስ ያለው ሰው ከሰዎች ክብር ይቀበላል” ወይም “ትሁት መንፈስ ላለው ሰው እግዚአብሔር ሰዎች እንዲያከብሩት ያደርጋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የራሱን ሕይወተት ይጠላል
“የራሱ ጠላት ይሆናል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እርግማንን ይሰማል መልስ ግን አይሰጥም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) “ከሌባ ጋር የሚካፈል ሰው” ስለሚያውቀው ነገር ማለትም ሌባው ስለሰረቀው ነገር እውነቱን እንዲናገር ሰዎች በመኃላ ስር ይይዙታል፣ እርሱም እውነቱን ቢናገር እንደሚቀጣ ያውቃል። አማራጭ ትርጉም፡- “በመኃላ ለመመስከር ፈቃደኛ አይሆንም” ወይም 2) ሰዎች ሌባው ማን እንደሆነ አያውቁም ነገር ግን ሌባው እንዲረገም ወደ እግዚአብሔር ይጮሃሉ፣ ከዚያም “ከሌባው ጋር የተካፈለው” ሰው ለመናዘዝ ይፈራል ስለዚህ ከእርግማኑ ይወጣል ምክንያቱም ሌባውን ስለሚፈራ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች ከረገሙት በኋላ እንኳ መልስ አይሰጥም” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 29:25

ሰውን መፍራት ወጥመድ ውስጥ ይከትታል
ሌሎች ሰዎች የሚያደርጉትን በማሰብ መፍራት በወጥመድ ውስጥ እንደመግባት ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሌሎች ሰዎች የሚያደርጉትን በማሰብ የሚፈራ ሰው በወጥመድ ውስጥ እንደተየያዘ ሰው ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወጥመድ
እንስሳትን በገመድ አፍኖ የሚይዝ

በእግዚአብሔር የሚታመን ይጠበቃል
ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር በእርሱ የሚታመነውን ይጠብቀዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ብዙዎች የገዢን ፊት ይፈልጋሉ
“ፊት” የሚለው ቃል ሕዝቡ እርሱ ሊያደርግላቸው የሚፈልጉት ነገር ምን እንደሆነ ሲነግሩት የሚሰማና ሰምቶም የሚፈጽም መሪን የሚወክል ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ብዙ ሕዝብ መሪያቸው ለእነርሱ ትኩረት እንዲሰጣቸው ይፈልጋሉ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ፍትህ ለሰው የሚመጣው ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው
ሰዎች አንድን ሰው በፍትህ ይዘው እንደሆነና እንዳልሆነ የሚመለከት እግዚአብሔር እንጂ የሰው መሪዎች አይደሉም። “ፍትህ” የሚለው ረቂቅ ስም “ፍትሀዊ” ተብሎ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለሰዎች እውነተኛ ፍትሀዊ የሆነ እግዚአብሔር ነው” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 29:27

የተጠላ
ሊጠላ የሚገባው ሰው። ይህንን በምሳሌ 3:32 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 30

1 የያቄ ልጅ የአጉር ቃል፡- ይህ ሰው ለኢቲኤል፣ ለኢቲኤልና ለኡካል ተናገረ፡- 2 በእርግጠኝነት እኔ ከሰው ሁሉ ይልቅ እንደ እንስሳ ሞኝ ነኝ፣ የሰው ልጅ
ማስተዋልም የለኝም። 3 ጥበብን አልተማርሁም፣ ስለ ቅዱሱም እውቀት የለኝም። 4 ወደ ሰማይ ከፍ ብሎ የሄደና ወደታች የተመለሰ ማን ነው? ነፋሳትን በእጁ
መዳፍ ሰብስቦ የያዘ ማን ነው? ውሆችንስ በካባው ላይ የሰበሰበ ማን ነው? የምድርን ዳርቻ ሁሉ ያጸና ማን ነው? ስሙ ማን ነው፣ የልጁስ ስም ማን ነው?
አንተ በእርግጠኝነት ታውቃለህ! 5 የእግዚአብሔር ቃል ሁሉ ተፈትኗል፣ በእርሱ ለሚታመኑ ጋሻ ነው። 6 በቃሉ ላይ ምንም አትጨምር፣ አለዚያ ይገስጽሃልና፣
ሐሰተኛም ትሆናለህ። 7 ሁለት ነገር እጠይቅሃለሁ፣ ከመሞቴም በፊት እነዚህን ነገሮች አትከልክለኝ፡ 8 ከንቱነትንና ውሸትን ከእኔ አርቅ። ድህነትንም
ብልጽግናንም አትስጠኝ፣ የሚያስፈልገኝን መብል ብቻ ስጠኝ። 9 ብዙ ሃብት ካለኝ፣ አንተን ከድቼ “እግዚአብሔርን ማን ነው?” እላለሁና፣ ድሃ ከሆንኩኝ ደግሞ
እሰርቃለሁ፣ የአምላኬንም ስም አሰድባለሁና። 10 አገልጋዩን በጌታው ፊት ስሙን አታጥፋ፣ ይረግምሃል አንተም በደለኛ ሆነህ ትገኛለህና። 11 አባቱን
የሚረግም፣ እናቱንም የማይባርክ ትውልድ፣ 12 ይህ ትውልድ ራሱን ንጹህ አድርጎ የሚያይ፣ ነገር ግን ከእድፉ ያልጸዳ ትውልድ ነው። 13 ይህ ትውልድ ዓይናቸው
ምንኛ ትዕቢተኛ ነው፣ ሽፋሽፍቶቻቸውም ምንኛ ወደ ላይ ከፍ ያሉ ናቸው! 14 ጥርሳቸው ሰይፍ የሆነ፣ መንጋጋቸውም ካራ የሆነ ትውልድ ናቸው፣ ድሆችን
ከምድር፣ ችግረኞችንም ከሰው ልጆች መካከል ያጠፉ ዘንድ። 15 አልቅት “ስጡን፣ ስጡን” እያሉ የሚጮሁ ሁለት ሴቶች ልጆች አሉት። ፈጽሞ የማይጠግቡ
ሦስት ነገሮች አሉ፣ ፈጽሞ “በቃኝ” የማይሉ አራት፤ 16 እነርሱም ሲኦል፣ የማትወልድ ማህጸን፣ ውሃ የተጠማች መሬትና፣ “በቃኝ” የማትል እሳት ናቸው። 17
በአባት ላይ የሚያፌዝ ለእናት መታዘዝን የሚንቅ ዓይን፣ ዓይኑ በሸለቆ አሞራዎች ይጎጠጉጡአታል፣ በአሞራዎችም ይበላል። 18 እጅግ የሚያስደንቁኝ ሦስት
ነገሮች አሉ፣ አራት ደግሞ ፈጽሞ የማላስተውለው፡- 19 የንስር መንገድ በሰማይ ውስጥ፤ የእባብ መንገድ በቋጥኝ ላይ፤ የመርከብ መንገድ በባህር ልብ
ውስጥ፤ የሰውም መንገድ ከወጣት ሴት ጋር ናቸው። 20 ይህም የአመንዝራ ሴት መንገድ ነው፣ ትበላለች አፏንም ትጠርጋለች፣ “ምንም ስህተት አልሰራሁም”
ትላለች። 21 በሶስት ነገሮች ምድር ትናወጣለች፣ አራተኛውንም መቋቋም አትችልም፡- 22 ባርያ ንጉስ ሲሆን፤ ሞኝ በመብል በጠገበ ጊዜ፤ 23 የተጠላች ሴት
ትዳር ስትይዝና፤ የቤት ሰራተኛ የእመቤቷን ቦታ ስትወስድ። 24 በምድር ላይ አራት ነገሮች ትንሽ ናቸው፣ ሆኖም እጅግ ጥበበኞች ናቸው፡- 25 ጉንዳኖች
ጠንካራ ያልሆኑ ፍጡራን ናቸው፣ ነገር ግን ምግባቸውን በበጋ ያዘጋጃሉ፤ 26 ሽኮኮዎች ብርቱ ያልሆኑ ፍጡሮች ናቸው፣ ነገር ግን ቤታቸውን በአለት ውስጥ
ይሰራሉ። 27 አንበጣዎች ንጉስ የላቸውም፣ ነገር ግን ሁሉም በሰልፍ ይሄዳሉ። 28 እንሽላሊቶችም በሁለት እጅህ ልትይዛቸው ትችላለህ፣ ይሁን እንጂ
በነገስታት ቤተ መንግስታት ውስጥ ይገኛሉ። 29 ግርማ ሞገስ ያለው አረማመድ ያላቸው ሶስት ነገሮች አሉ፣ በአካሄዳቸው ግርማ ሞገስ ያላቸው አራት አሉ፡- 30
አንበሳ፣ ከዱር እንስሳት ሁሉ ብርቱ የሆነና ከምንም ነገር ወደኋላ የማይመለስ ነው፤ 31 እየተንጎራደደ የሚሄድ አውራ ዶሮ፤ ፍየል፤ እና በወታደሮቹ የታጀበ ንጉስ
ናቸው። 32 ሞኝ ከሆንህ፣ ራስህንም ከፍ ከፍ የምታደርግ ከሆነ ወይም ክፉ ሃሳብን እያሰብክ ከሆነ፣ እጅህን በአፍህ ላይ አድርግ። 33 የተናጠ ወተት ቅቤ
እንደሚወጣው፣ በጣም የታሸ አፍንጫም ደም እንደሚወጣው፣ በቁጣ የሚፈጸሙ ድርጊቶችም ጠብን ያመጣሉ።

Proverbs 30:1

አጉር ... ያቄ ... ኢቲኤል ... ኡካል
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

አጉር የያቄ ልጅ
ይህ የያቄ ልጅ ነው፣ የልጅ ልጅ አይደለም።

ንግግር
“መልእክት”

ለኢቲኤል፣ ለኢቲኤልና ኡካል
“ለኢቲኤል - ኢቲኤል የተባለውና ኡካል”

በእርግጥ
“በእውነት” ወይም “ምንም ጥርጥር የለውም”

የሰው ልጅ ማስተዋልም የለኝም
“ማስተዋል” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ማንኛውንም ነገር ሰዎች ሊያስተውሉ በሚገባቸው መንገድ እኔ አላስተውልም” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ ቅዱሱም እውቀት የለኝም
“እውቀት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለ ቅዱሱ በእርግጥም ምንም ነገር አላውቅም” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 30:4

ማን ነው ... የተመለሰ? ማን ነው ... በእጁ የያዘ? ማን ነው ... በካባው የሰበሰበ? ማን ነው ... የምድር ዳርቻ የጸና?
ጸሐፊው እነዚህን ጥያቄዎች የጠየቀው አንባቢው እግዚአብሔር ከሰዎች ይልቅ ምን ያህል ትልቅ እንደሆነ እንዲያስብ ለማድረግ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ማንም ሰው ወደላይ ደርሶ የተመለሰ የለም። ማንም ሰው በእጁ የያዘ የለም። ማንም ሰው በካባው የሰበሰበ የለም። ማንም ሰው ምድርን ያጸና የለም።” ወይም “ማን ነው ... የተመለሰ? ማን ነው ... በእጁ የያዘ? ማን ነው ... በካባው የሰበሰበ? ማን ነው ... የምድር ዳርቻ የጸና? እነዚህን ነገሮች የሰራ አንድም ሰው የለም።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰማይ
እግዚአብሔር የሚኖርበት

ነፋሳትን በእጁ መዳፍ ሰብስቦ ያዘ
ጸሐፊው ስለ ነፋስ ሲናገር ሰው በእጁ ሊይዘውና ሊጨብጠው የሚችለው ነገር እንደሆነ አድርጎ አቅርቦታል። ማራጭ ትርጉም፡- “ነፋስን በእጁ ውስጥ ይዟል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በእጁ መዳፍ
የተለያዩ ነገሮችን ለምሳሌ ውኃ እና አሸዋ የመሳሰሉትን ሲሰፍር እጁ የተቀረጸበት ሁኔታ። “ጎድጓዳ መሰል እጁ”

ሰብስቦ ያዘ
የተበታተኑ ትንንሽ ነገሮችን መያዝ እንዲቻል ሰብስቦ ከምሮ አስቀመጣቸው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የምድርን ዳርቻ ሁሉ አጸና
“የምድርን መጨረሻ የት እንደሆነ ወሰነ” ወይም “የምድርን መጨረሻ ዳርቻውን ምልክት አደረገበት”

ስሙ ማን ነው፣ የልጁስ ስም ማን ነው?
አንባቢው መልስ እንዲሰጥ ለማስገደድ ጸሐፊው እነዚህን ጥያቄዎች ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱን የምታውቃቸው ከሆነ የእርሱንና የልጁን ስም ንገረኝ” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ በእርግጠኝነት ታውቃለህ!
ጸሐፊው እርሱ ራሱም ሆነ አንባቢው “ማን” ተብሎ በጥያቄዎቹ የተጠቀሰው ማድረግ የሚችለውን የሚያደርግ አንድም ሰው እንደማያውቁ ለማሳየት ምፀት ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህን ነገሮች ማድረግ የሚችል አንድም ሰው ታውቃለህ ብየ በእርግጥ አላስብም” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 30:5

ተፈትኗል
ቃላት አንድ ሰው ቆሻሻቸውን ከውስጣቸው ሊያጸዳቸው የሚያስፈልጋቸው ብረታ ብረት እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ሰው የማይጠቅሙ ቆሻሻ ነገሮቹን ሊያሰወግድልት እንደሚገባ እንደ ውድና የከበረ ብረት ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መሸሸጊያቸውን በእርሱ ውስጥ ለሚያደርጉ ጋሻ ነው
“ጋሻ” የሚለው ቃል ሰውን ለሚከላከል ነገር ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ወደ እርሱ ለሚመጡና ሊጠብቃቸው ለሚለምኑት ይጠብቃቸዋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በቃሉ ላይ መጨመር
እርሱ ከተናገረው በላይ መናር

ትመዘናለህ
ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ አንተ … እንደሆንህ ይመዝንሃል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 30:7

ከንቱነትንና ውሸትን ከእኔ አርቅ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) “ሰዎች ለእኔ ከንቱነትንና ውሸትን እንዲነግሩኝ አትፍቀድላቸው” ወይም 2) “ከንቱነትንና ውሸትን እንድናገር አትፍቀድልኝ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከንቱነት
ውሸት፣ የማይጠቅሙ ቃላት

ድህነትንም ብልጽግናንም አትስጠኝ
ጸሐፊው “ድህነት” እና “ብልጽግና” አንድ ሰው ለሌላ ሰው ሊሰጣቸው የሚችለው ግዑዝ ነገሮች እንደሆኑ አድርጎ ተናግሯል። ከዚህ በተጨማሪ እነዚህ ቃላት ረቂቅ ስም ናቸው፣ “ድሀ” እና “ባለጸጋ” ተብለው ሊብራሩ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “በጣም ድሃ ወይም በጣም ባለጸጋ እንድሆን አትፍቀድልኝ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ብዙ ሃብት ካለኝ፣ አንተን ከድቼ … እላለሁና
ይህ ያልሆነ ሃሳባዊ ሁኔታ የሚገልጽ ሲሆን ጸሐፊው ባለጠጋ ከሆነ ግን እውን ሊሆን የሚችል ነው። (ግምታዊ ሁኔታ የሚለውን ይመልከቱ)

ድሃ ከሆንኩኝ ደግሞ እሰርቅ ይሆናል … አሰድባለሁ
ይህ የሚገልጸው ያልተፈጸመ ሃሳባዊ ሁኔታ ሲሆን ጸሐፊው ድሀ ከሆነ ግን እውን ሊሆን የሚችል ነው። (ግምታዊ ሁኔታ የሚለውን ይመልከቱ)

ድሃ ከሆንኩኝ ደግሞ እሰርቃለሁ፣ የአምላኬንም ስም አሰድባለሁና
“የተለያዩ ነገሮች እንደሰረቅሁ የሚያውቁ ሰዎች እግዚአብሔር የለም ብለው እንዲያስቡ ላደርግ እችላለሁ” ወይም “በመስረቄ የእግዚአብሔርን መልካም ስም አሰድብ ይሆናል”

Proverbs 30:10

ስም ማጥፋት
እርሱን ለመጉዳት በመፈለግ ስለ ሌላ ሰው በውሸት መናገር

ይረግምሃል
“ባርያው ይረግመዋል”

አንተም በደለኛ ትሆናለህ
ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች በደለኛ ያደርጉሃል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 30:11

የሚረግም ትውልድ … የማይባርክ … ትውልድ
“የሚረግም የሕዝብ ትውልድ … የማይባርክ … ትውልድ ናቸው”

ትውልድ
የክፍል ወይም የቡድን ዓይነት

በራሳቸው ዓይን ንጹሐን ናቸው
ዓይን መመልከትን ይወክላል፣ መመልከት ደግሞ ሃሳብና ግንዛቤን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ራሳቸውን ንጹህ እንደሆኑ ይቆጥራሉ” ወይም “ንጹህ እንደሆኑ ያምናሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእድፋቸው ያልታጠቡ ናቸው
“ታጠቡ” እና “እድፍ” የሚሉት ቃላት የሚናገሩት እግዚአብሔር ኃጢአትን የሰሩ ሰዎችን ይቅርታ እንደሚያደርግላቸው ሲሆን እርሱ አካላዊ እድፈትን ከሰዎች እንደሚያጥብና እንደሚያነጻ ዓይነት አድርጎ አቅርቦታል። ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን ይቅር አላላቸውም” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እድፍ
ይህ የሰዎችንና የእንስሳትን ትውከትና ሰገራ ሚጨምር ትህትና በተሞላበት ቃል ሊተረጎም ይገባል።

Proverbs 30:13

ዓይናቸው ትዕቢተኛ ነው … ሽፋሽፍቶቻቸውም ወደ ላይ ከፍ ያሉ ናቸው
ይህ የሚገልጸው ከሌሎች ሰዎች ይልቅ እነርሱ እንደሚሻሉ ስለሚያስቡ ሰዎች ነው። ዓይኖቻቸው ትዕቢተኞች እንደሆኑ ያሳያሉ፣ ሌሎችን የሚያዩበት መንገድ ደግሞ ከሌሎች ሰዎች ይልቅ እነርሱ የተሻሉ እንደሆኑ እንደሚያስቡ ያሳያል። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ጥርሳቸው ሰይፍ የሆነ፣ መንጋጋቸውም ቢላዋ የሆነ ትውልድ ናቸው፣ ድሆችን ከምድር፣ ችግረኞችንም ከሰው ልጆች መካከል ያጠፉ ዘንድ
በጣም የሚጎዳ ንግግር የሚናሩ የእነዚህ ትውልድ ሕዝብ ጥርሳቸውና መንጋጋቸው ሰይፍና ቢላዋ ሆኖ የተሰራ እና ድሀ እና ችግረኛን የሚበሉ የዱር እንስሳት እንደሆኑ ተደርገው ተገልጸዋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መንጋጋ
ጥርስ የሚበቅልበት የፊት አጥንቶች

Proverbs 30:15

አልቅት ሁለት ሴቶች ልጆች አሉት
ይህ ሁልጊዜ ስጠኝ ለሚል ለማይጠግብ ነገር ምሳሌ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ስስት ሁለት ልጆች አሏት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አልቅት
በቆዳ ላይ በመጣበቅ ደም የሚመጥጥ የትል ዓይነት

“ስጡን፣ ስጡን” እያሉ የሚጮሁ
ለዚህ ሌላ ተቀባይነት ያለው ትርጉም አንዲህ የሚል ነው፡- “ሁሉም ስጡን የሚል ስም ተሰጥቷቸዋል።”

ፈጽሞ የማይጠግቡ ሦስት ነገሮች አሉ፣ ፈጽሞ “በቃኝ” የማይሉ አራት፤
እዚህ ላይ “ሶስት” እና “አራት” የሚሉት ቁጥሮች በአንድ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት እንደ ግጥም ዘዴ ሳይሆን አይቀርም። አማራጭ ትርጉም፡- “ፈጽሞ ጠገብሁ የማይሉ አራት ነገሮች አሉ፣ ፈጽሞ ‘በቃኝ’ የማይሉ” (ግጥም የሚለውን ይመልከቱ)

በቃኝ አይሉም
ይህ በአዎንታዊ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሁልጊዜ የበለጠ ይፈልጋሉ” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

ውኃ ፈጽሞ የማትጠግብ ምድር
ዝናብ ስላልነበረ ምግብ የማታመርት ምድር ለመጠጣት በቂ ውኃ እንደሌለው ሰው እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእናት መታዘዝን የሚንቅ
“መታዘዝ” የሚለው ቃል ለራሷ ለእናት ምትክ ስም ነው። በተጨማሪ “ታዘዝ” ተብሎ ሊብራራ የሚችል ረቂቅ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እናቱ ምንም የማትጠቅም እንደሆነች የሚቆጥርና የማይታዘዛት” (ረቂቅ ስም እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ዓይኑ ... አሞራዎች
ጸሐፊው በሕዝብ መካከል ከሚኖሩበት ስፍራ ተለይተው በሚሞቱ ሰዎች ላይ ምን እንደሚሆን ሁለት መግለጫዎችን በመስጠት ሰውየው ይሞታል ይላል።

ዓይኑ የሸለቆ ቁራዎች ይጎጠጉጡታል
ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሸለቆ ቁራዎች ዓይኑን ይጎጠጉጡታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ቁራ
እጽዋትንና የሞቱ እንስሳትን የሚበላ ትልቅ፣ የሚያብረቀርቅ፣ ጥቁር ወፍ

በአሞራዎችም ይበላል
ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አሞራዎች ይበሉታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

አሞራዎች
የሞቱ እንስሳትን የሚበሉና ትንንሽ ላባ የሌለው ራስ ካላቸው ከብዙ ትልልቅ ወፎች መካከል አንዱ ነው

Proverbs 30:18

ሦስት ነገሮች አሉ ... አራት ደግሞ ፈጽሞ የማላስተውለው፡-
እዚህ ላይ “ሶስት” እና “አራት” የሚሉት ቁጥሮች በአንድ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት እንደ ግጥም ዘዴ ሳይሆን አይቀርም። አማራጭ ትርጉም፡- “ለእኔ ፈጽሞ የማለስተውላቸው በጣም አስደናቂ የሆኑ አንዳንድ ነገሮች አሉ - አራቱ የሚከተሉት ናቸው፡-“

በባህር ልብ ውስጥ
“ልብ” የመሐል ክፍሉን የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በባህር መሐል” ወይም “በክፍት ባህር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 30:20

ትበላለች አፏንም ትጠርጋለች
ይህ ለማመንዘር ከዚያም ለመታጠብ ለስላሴና ተለዋጭ ዘይቤ ሊሆን ይችላል። (ለስላሴ ዘይቤ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 30:21

በሶስት ነገሮች ምድር ትናወጣለች፣ አራተኛውንም መቋቋም አትችልም
እዚህ ላይ “ሶስት” እና “አራት” የሚሉት ቁጥሮች በአንድ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት እንደ ግጥም ዘዴ ሳይሆን አይቀርም። “ምድር እንድትናወጥ የሚያደርጉ መቋቋም የማትችለው አንዳንድ ነገሮች አሉ። አራቱ የሚከተሉት ናቸው፡-“

ሞኝ በመብል በጠገበ ጊዜ
ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሚበላው በጣም በቂ ምግብ ያለው ሞኝ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የተጠላች ሴት ትዳር ስትይዝ
ይህች ሴት ከማግባቷ በፊት ሰዎች በትክክል ይጠሏት ነበር፤ አንድ ጊዜ ካገባች በኋላ ከማግባቷ በፊት ከነበራት የበለጠ ተቀባይነት ይኖራታል። ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥሩ ሰዎች የጠሏት ሴት ስታገባ” ወይም “የተጠላች ሴት ስታገባ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የእመቤቷን ቦታ ስትወስድ
ቤቱን ስታስተዳድር

Proverbs 30:24

ሽኮኮዎች
ትንሽ፣ ክብ ጆሮ፣ አጭር እግርና ጭራ ያላቸው እንስሳት

Proverbs 30:27

እንሽላሊት
አራት እግር፣ ረጅም፣ ቀጭን ሰውነትና ጭራ ያለው በደረቱ የየሚሳብ ትንሽ እንስሳ

Proverbs 30:29

ስት ነገሮች አሉ ... በአካሄዳቸው ግርማ ሞገስ ያላቸው አራት አሉ
እዚህ ላይ “ሶስት” እና “አራት” የሚሉት ቁጥሮች በአንድ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት እንደ ግጥም ዘዴ ሳይሆን አይቀርም። አማራጭ ትርጉም፡- “በግርማ ሞገስ የሚራመዱ አንዳንድ ነገሮች አሉ። አራቱ የሚከተሉት ናቸው።”

ግርማ ሞገስ
በግርማ ወይም በክብር፣ እንደ ንጉስ

አውራ ዶሮ
በኩራት የሚራመድ ያደገ ትልቅ ወንድ ዶሮ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Proverbs 30:32

ቅቤ
ከእንስሳት ወተት በሰው ተንጦ የሚወጣው ወፍራም ነገር

እየተንጎራደደ
በኃይል እየተናጠ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 31

1 እናቱ ያስተማረችው የንጉስ ልሙኤል ቃሎች፣ **2** ልጄ ሆይ፣ ምንድን ነው? የማሕጸኔ ልጅ ሆይ ምንድን ነው? የስእለቴ ልጅ ሆይ ምንድን ነው? **3** ብርታትህን ለሴቶች አትስጥ፣ ነገስታትን ለሚያጠፉም መንገድህን። **4** ለነገስታት አይደለም፣ ልሙኤል ሆይ፣ የወይን ጠጅ መጠጣት ለነገስታት አይደለም፣ “ብርቱ መጠጥ የት ነው” ብለው ይጠይቁ ዘንድ ለገዢዎችም አይደለም። **5** ምክንያቱም እነርሱ መጠጥ ከጠጡ የተደነገገውን ሕጉን ይረሳሉ፣ የተጨቆኑ ሰዎችንም መብት ያጣምማሉ። **6** እየጠፉ ላሉ ሰዎች ብርቱ መጠጥ ስጧቸው፣ መራራ ችግር ውስጥ ላሉትም ወይን ስጧቸው። **7** ይጠጣል ድህነቱንም ይረሳል፣ ችግሩንም አያስታውስም። **8** መናገር ለማይችሉ ተናገርላቸው፣ እየጠፉም ላሉት ሁሉ ስለ ጉዳያቸው ተናገር። **9** ትክክል ስለሆነው ነገር ጮህ ብለህ ተናገር፣ ፍርድም ስጥ፣ ስለ ድሆችና ስለ ተቸገሩም ሰዎች ጉዳይ መልስ ስጥ። **10** ችሎታ ያላትን ሴት ማን ሊያገኛት ይችላል? የእርሷ ዋጋ ከእንቁ የበለጠ ነው። **11** የባሏ ልብ በእርሷ ይተማመናል፣ ድሃም አይሆንም። **12** በሕይወት ዘመኗ ሁሉ ለእርሱ መልካም ነገር ታደርግለታለች፣ ክፋትንም አታደርግበትም። **13** የበግ ጠጉርና የተልባ ትመርጣለች፣ በእጆቿም ደስ ብሏት ትሰራለች። **14** እርሷ እንደ ነጋዴ መርከብ ናት፤ መብሏን ከሩቅ ታመጣለች። **15** በሌሊት ተነስታ ለቤተሰቧ መብልን ታቀርባለች፣ ስራዋንም ለሴት አገልጋዮቿ ታከፋፍላለች። **16** እርሻን ተመልክታ ትገዛለች፣ በእጆቿም ፍሬ የወይን ተክል ትተክላለች። **17** ራሷን በብርታት ታለብሳለች፣ ክንዶቿንም ታጠነክራለች። **18** ለእርሷ ጥሩ ትርፍ የሚያመጣላትን ታውቃለች፤ ሌሊቱንም ሙሉ መብራቷ አይጠፋም። **19** እጆቿን በእንዝርቱ ላይ ታስቀምጣለች፣ የሚሽከረከረውንም ክር ትይዛለች። **20** እጇን ለድሆች ትዘረጋለች፤ ለተቸገሩትም እጆቿን ትዘረጋለች። **21** በረዶም ቢዘንብ ስለ ቤተሰቧ አትፈራም፣ ቤተሰቧ ሁሉ ቀይ ልብስ ለብሰዋልና። **22** ለመኝታዋ የአልጋ ልብስ ትሰራለች፣ ቀጭን ሐምራዊ ልብስም ትለብሳለች። **23** ባለቤቷም ከአገሩ ሽማግሌዎች ጋር ሲቀመጥ በበሮቹ የታወቀ ይሆናል፣ ። **24** የሊኖ ልብሶችን ትሰራለች፣ ትሸጣለችም፣ ለነጋዴዎችም መቀነቶችን ታስረክባለች። **25** ጥንካሬንና ክብርን ተላብሳለች፣ ወደፊት የሚመጣውን ጊዜ እያሰበች ትስቃለች። **26** አፏን በጥበብ ትከፍታለች፣ የደግነት ሕግም በምላሷ ላይ አለ። **27** የቤተሰቦቿን መንገዶች ትመለከታለች፣ የስንፍናንም እንጀራ አትበላም። **28** ልጆቿም አድገው የተባረክሽ ነሽ ይሏታል፤ ባለቤቷም እንዲህ ብሎ ያመሰግናታል፣ **29** “ብዙ ሴቶች መልካምን አድርገዋል፣ አንቺ ግን ከሁሉ ትበልጫለሽ።” **30** ቁንጅና አሳሳች ነው፣ ውበትም ጠፊ ነው፣ እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት ግን እርሷ ትመሰገናለች። **31** የእጆቿን ፍሬ ስጧት፣ ስራዋቿም በአደባባዮች ያስመሰግኗት።

Proverbs 31:1

ንጉስ ልሙኤል
ይህ የንጉስ ስም ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ልጄ ሆይ፣ ምንድን ነው? የማሕጸኔ ልጅ ሆይ ምንድን ነው? የስእለቴ ልጅ ሆይ ምን ፈለግህ?
የዚህ “ምን” የሚለው መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች:- 1) “ምን ትሰራለህ?” ወይም “የምትሰራውን ልትሰራው አይገባም” ወይም 2) “ምን ልንገርህ?” ወይም “የምነግርህን ስማኝ” ወይም 3) “እንዳታደርግ የማስጠነቅቅህን ነገሮች አትስራ” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ልጄ ... የማሕጸኔ ልጅ ... የስእለቴ ልጅ
ጸሐፊው አድማጩ በጥንቃቄ እንዲያስተውልና ለሚናገረው ሰው አክብሮት እንዲሰጥ ይፈልጋል።

የማሕጸኔ ልጅ
ማህጸን ለሰውየው ተዛምዶአዊ ዘይቤ ነው። ልጆች ከመወለዳቸው በፊት ለሚያድጉበት ለሰውነት ክፍል የበለጠ ትህትና ያለው ቃል መጠቀም ተመራጭ ነው።

የስእለቴ ልጅ
“ስእለት” የሚከተሉትን ሊሆን ይችላል:- 1) የእናት የጋብቻ ቃል ኪዳን ወይም 2) ካገባች በኋላ እግዚአብሔር ልጅ እንዳተገኝ የፈቀደላት ከሆነ ልጇን ለእግዚአብሔር ለመስጠት ቃል የገባችው።

ብርታትህን ለሴቶች አትስጥ
ከትዳር ውጭም ሆነ ከቁባቶች ጋር “ከሴቶች ጋር ወሲብ ለመፈጸም ብዙ አትድከም።

ነገስታትን ለሚያጠፉም መንገድህን
“ወይም ነገስታትን የሚያጠፉ ሰዎች እንዲመክሩህ ፍቀድላለቸው”

መንገድህ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች:- 1) “ሕይወትህን የምትኖርበት መንገድ” ወይም 2) “የምትሰራው ስራ”

ነገስታትን ለሚያጠፉም
ምናልባት ብርታቱን ሊሰጣቸው የማይገቡ ስነ-ምግባር የሌላቸው “ሴቶች”

Proverbs 31:4

ልሙኤል
ይህ የወንድ ሰው ስም ነው። ይህንን በምሳሌ 31:1 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

የተደነገገው
ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች:- 1) “እግዚአብሔር የደነገገው” ወይም 2) “ነገስታቱ ራሳቸው የደነገጉት” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የተጨቆኑ ሰዎችንም መብት ያጣምማሉ
“ለተጨቆኑ ሰዎች ሕጋዊ መብታቸውን ይነፍጋሉ”

ያጣምማሉ
መልካምን በክፉ ይለውጣሉ

የተጨቆኑ ሰዎችንም በሙሉ
“ሌሎች ሰዎች ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ የጎዷቸው ሰዎች በሙሉ

Proverbs 31:6

ወይን
x

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Proverbs 31:8

መናገር ለማይችሉ ተናገርላቸው
መናገር ንጹሐን ሰዎችን ለመከላከል ለምንጠቀምባቸው ቃላት ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ራሳቸውን መከላከል ለማይችሉ አንተ ተከላከልላቸው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

እየጠፉም ላሉት ሁሉ ስለ ጉዳያቸው ተናገር
ስለ ጉዳያቸው የሚለው ጉዳይ ያለበትን ሰው የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለዚህ ሰዎች በፍትህ ምክንያት እየጠፉ ያሉትን በአግባቡ እንዲይዙአቸው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ ጉዳያቸው
ይህ አስጨምሬ ሊሞላ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለ ጉዳያቸው ተናገር” ወይም “ስለ እነርሱ ተናገር” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ድሆችና የተቸገሩ ሰዎች
እነዚህ ሁለት ቃላት በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ በአንድ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት ደግሞ አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ድሃ የሆኑና የሚያስፈልጋቸውን ነገር ማግኘት የማይችሉ ሰወች” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 31:10

ችሎታ ያላትን ሴት ማን ሊያገኛት ይችላል?
ጸሐፊው አዲስ ክፍል እየጀመረ እንደሆነ ለማሳየት ጥያቄ ይጠይቃል። አማራጭ ትርጉም፡- “ብዙ ወንዶች ችሎታ ያላትን ሴት ማግኘት አይችሉም” ወይም “ብዙ ወንዶች ብዙ ስራን በጥራት የመስራት ችሎታ ያላትን ሚስት ማግኘት አይችሉም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሷ ዋጋ ከእንቁ የበለጠ ነው
“እርሷ ከእንቁ ይልቅ ዋጋዋ የከበረ ነው”

ድሃም በፍጹም አይሆንም
ይህ ምፀት በአዎንታዊ መልኩ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ ሁልጊዜ የሚያስፈልገው ነገር ሁሉ ይኖረዋል” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 31:16

የእጆቿ ፍሬ
ከሱፍና ከተልባ እግር ከሰራችው ያገኘችው ገንዘብ (ምሳሌ 31:13) ከዛፍ የሚገኝ ፍሬ እንደሆነ ተደርጎ ተንሯል። እጆች ለዚያ ሰው ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ያገኘችው ገንዘብ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ራሷን በብርታት ታለብሳለች
ልብስ መልበስ ለስራ ለመዘጋጀት ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ራስዋን ለከባድ አካላዊ ስራ ታዘጋጃለች” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ክንዶቿንም ታጠነክራለች
“ስራዋን በመስራት ክንዶቿን ታበረታለች”

Proverbs 31:18

ታውቃለች
በጥንቃቄ በማየት ትገነዘባለች

ሌሊቱንም ሙሉ መብራቷ አይጠፋም
ይህ ምናልባት ግነት ሊሆን ይችላል፡- ሌሊቱን ሁሉ ቆይታ ትሰራለች፣ ነገር ግን ጸሐይ ጠልቃ እስከምትወጣ ድረስ አይደለም” አማራጭ ትርጉም፡- “ስራዋን ስትሰራ ሌሊቱን ሁሉ መብራቷን ታበራለች” (ግነትና ጅምላ ፍረጃ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እንዝርት
ሹል ጫፍ ያለው ክር ለመፍተል የሚጠቅም በጣም ቀጭን እንጨት

Proverbs 31:20

እጆቿን ለድሆች ትዘረጋለች
እጅ ሴትዮዋ በእጇ ተጠቅማ በመስጠት ለምታደርገው እርዳታ ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ድሀ ትረዳለች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እጆቿን ትዘረጋለች
እነዚህ ቃላቶች በምሳሌ 31:19 ላይ “እጆቿን ለድሆች ትዘረጋለች” በሚለው እንደተተረጎመው በተመሳሳይ ቃላት ይተረጎማሉ።

ቀይ ልብስ ለብሰዋልና
እዚህ ላይ “ቀይ ልብስ” የልብሱን ቀለም አያመለክትም፣ ነገር ግን የሚያሳየው ልብሱ በጣም ውድና የሚሞቅ መሆኑን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ውድና የሚሞቅ ልብስ አላቸው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ቀይ
ቀይ ቀለም፣ ነገር ግን ብርቱካናማ የተቀላቀለበት።

Proverbs 31:22

ላይነን
በተልባ እግር ክር የተሰራ ልብስ

ባለቤቷ ይታወቃል
ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። “ማወቅ” የሚለው ግስ ለአክብሮት ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች ባለቤቷን ያከብሩታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ባለቤቷም ከአገሩ ሽማግሌዎች ጋር ሲቀመጥ
ሕግ ለመስጠትና ክርክሮችን ለመፍታት

Proverbs 31:24

ላይነን
x

Proverbs 31:26

አፏን በጥበብ ትከፍታለች
አፋችንን የመክፈት ተግባር ለመናገር ምትክ ስም ነው። ”ጥበብ” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ተውሳከ ግስ ወይም ቅጽልሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በጥበብ ትናገራለች” ወይም “የጥበብ ቃላት ትናገራለች” (ምትክ ስም እና ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የደግነት ሕግም በምላሷ ላይ አለ
“በምላሷ ላይ” የሚለው ሀረግ ንግግሯን የሚያመለክት ነው፣ ምክንያቱም ምላስ የአፍ አንዱ አካል ነው። “የደግነት ሕግ” የሚለው ሀረግ ሰዎችን ደግ እንዲሆኑ ማስተማርን የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች ደግ እንዲሆኑ ታስተምራለች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የቤተሰቦቿን መንገዶች ትመለከታለች
“መንገዶች” የሚለው ቃል ሰዎች የሚኖሩበትን መንገድ የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ቤተሰቦቿ በሙሉ እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ መንገድ እየኖሩ እንደሆነ ታረጋግጣለች” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የስንፍናንም እንጀራ አትበላም
የአንድ ነገር “እንጀራ መብላት” አንድ ነገር መስራት ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰነፍ አይደለችም” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ስንፍና
ምንም አለመስራት እና ሰነፍ መሆን

Proverbs 31:28

አድገው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ቃል በቃል “ተነስተው” ወይም 2) እንደ ምትክ ስም፣ “በቅልጥፍና።” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የተባረክሽ ነሽ ይሏታል
መልካም ነገሮች በሕይወቷ እንደተከናወኑ መናገር ምክንያቱም መልካም ነገሮችን ሰርታለች። ይህ በቀጥታ እንደ ተጠቀሰ ሆኖ ሊቀርብ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እንኳን ደስ አለሽ ማለት” ወይም ‘“እናቴ እንኳን ደስ አለሽ!’ ብሎ መናገር” (ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ጥቅሶች የሚለውን ይመልከቱ)

ትበልጫለሽ
“ከሁሉም የተሸለ ስራ ሰርተሸል”

Proverbs 31:30

ቁንጅና አሳሳች ነው
“ቁንጅና” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ቆንጆ ሴት ሰዎችን ልታታልል ትችላለች” ወይም “መልካም ውበት ያላት ሴት በእርግጠኝነት ክፉ ልትሆን ትችላለች።” ይህንን በምሳሌ 11:16 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ውበትም ጠፊ ነው
“ውበት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አሁን ውብ የሆነች ሴት ሁልጊዜ ውብ ልትሆን አትችልም” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እርሷ ትመሰገናለች
ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች ያመሰግኗታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የእጆቿን ፍሬ
ከሱፍ እና ከተልባ እግር (ምሳሌ 31:13) ስራ ያገኘችው ገንዘብ ፍሬ ከሚሰጥ ዛፍ እነንደሚገኝ ፍሬ ተደርጎ ተነግሯል። እጆች ለሰውየው ተዛምዶአዊ ዘይቤ ነው። ይህንን በምሳሌ 31:16 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “ያገኘችው ገንዘብ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ስራዋቿም በአደባባዮች ያስመሰግኗት
ስለ ሰራችው ስራዎቿ ትመሰገናለች፣ በስራዎቿ አይደለም። “በአደባባይ” ያሉት ሰዎች ንግድና የሕግ ጉዳዮች በከተማይቱ መግቢያ አካባቢ የሚሰሩ የከተማይቱ ዋነኛ ሰዎች ናቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “በሰራችው ስራዎቿ ምክንያት የከተማይቱ ዋነኛ ሰዎች ያመስግኗት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Ecclesiastes

Ecclesiastes

Chapter 1

1 ይህ በኢየሩሳሌም የነገሠውና የዳዊት ልጅ የሆነው የአስተማሪው ቃል ነው። 2 አስተማሪው እንዲህ ይላል፥ "እንደ እንፋሎት ትነት፥ በደመናም ውስጥ እንዳለ እስትንፋስ፥ ሁሉም ነገር ይጠፋል፥ በርካታ ጥያቄዎችን ትቶ። 3 ከፀሐይ በታች በሚደክሙበት ሥራ ሁሉ የሰው ልጆች ምን ትርፍ ያገኙበት ይሆን? 4 አንደኛው ትውልድ ይሄዳል፥ ሌላኛው ትውልድ ይመጣል፥ ምድር ግን ለዘላለም ትኖራለች። 5 ፀሐይ ትወጣለች፥ ትጠልቃለችም፥ ዳግም ወደምትወጣበት ሥፍራ ለመመለስም ትቸኩላለች። 6 ነፋስ ወደ ደቡብ ይነፍሳል፥ ወደ ሰሜንም ያከብባል፥ ሁሌም በመንገዱ ይሄዳል፥ እንደገናም ይመለሳል። 7 ወንዞች ሁሉ ወደ ባህር ይፈስሳሉ፥ ባህሩ ግን መቼም ቢሆን አይሞላም። ወንዞቹ ወደሚሄዱበት ሥፍራ፥ ወደዚያው ሥፍራ እንደገና ይሄዳሉ። 8 ሁሉም ነገር አድካሚ ነው፥ ሊያስረዳ የሚችልም የለም። ዓይን በሚያየው አይረካም፥ ጆሮም በሚሰማው አይሞላም። 9 የሆነው ሁሉ ወደፊትም የሚሆን ነው፥ የተደረገውም ሁሉ ወደፊት የሚደረግ ነው። ከፀሐይ በታች አንድም አዲስ ነገር የለም። 10 'ተመልከት፥ ይህ አዲስ ነው' ሊባልለት የሚችል አንዳች ነገር አለ? አሁን ያለው ሁሉ ለብዙ ዘመናት አስቀድሞ የነበረ ነው፥ ወደ እኛ ከመምጣቱ በፊት በዘመናት መካከል። 11 በቀድሞ ዘመን የሆኑትን ነገሮች የሚያስታውስ ያለ አይመስልም። እጅግ ዘግይተው የሆኑትን ነገሮችና ወደፊት ሊሆኑ ያሉት ሁለቱም የሚታወሱ አይመስሉም። 12 እኔ አስተማሪ ነኝ፥ በእስራኤልም ላይ በኢየሩሳሌም ንጉሥ ነበርኩ። 13 ከሰማይ በታች የተደረገውን ነገር ሁሉ በጥበብ ለማጥናትና ለመመርመር አዕምሮዬን አሠራሁት። ይህ ምርምር እግዚአብሔር የሰው ልጆች በሥራ እንዲጠመዱ የሰጣቸው አድካሚ ተግባር ነው። 14 ከሰማይ በታች የተሠሩትን ሥራዎች ሁሉ አየሁ፥ ተመልከቱ፥ ሁሉም የሚተንና ነፋስን ለማገድ መሞከር ነው። 15 የተጣመመ መቃናት አይችልም! የጠፋው መቆጠር አይችልም! 16 ለልቤ እንዲህ ስል ተናገርኩ፥ "ተመልከት፥ ከእኔ በፊት በኢየሩሳሌም ከነበሩት ሁሉ ይልቅ ጥበብን አከማችቻለሁ። አዕምሮዬ ትልቅ ጥበብንና እውቀትን አይቷል።" 17 ስለዚህ ጥበብን ለማወቅ ልቤን አሠራሁት፥ ደግሞም ዕብደትንና ሞኝነትን። ይህም ደግሞ ነፋስን ለማገድ እንደ መሞከር መሆኑን አስተዋልኩኝ። 18 ጥበብን በማብዛት ውስጥ ብዙ ተስፋ መቁረጥ አለ፥ እውቀትንም የሚያበዛ ሐዘንን ያበዛል።

Ecclesiastes 1:1

እንደ ተን (ከንቱ) እንፋሎት እንደ ንፋስ ሽዉታ ሁሉም ነገር ጠፊ ነው
ይህ የሚናገረው እንዴት በሕይወት ወስጥ ሁሉም ነገር እንደ ተን ወይም ንፋስ ሽዉታ ጠፊ እንደሆነና ዘላቂ እሴት ወይም ጥቅም እንደሌለው ነው። ተርጓሚ "እንደ ተን (ከንቱ) እንፋሎት አላፊ እንደ ንፋስ ሽዉታ ጠፊ ሁሉም አላፊና ዘላዊ እሴት ወይም ጥቅም የለውም"

ከፀሐይ በታች ..... የሰው ትርፍ ምንድር ነው?
ፀሐፊው ይህን የግነት ጥያቄ የተጠቀመው የሰው ድካሙ ከንቱና ዘላቂ ትርፍ እንደሌለው አፅንኦት ለመስጠት ነው። ጥያቄው በአረፍተ-ነገር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "ከፀሐይ በታች የሰው ልጅ ትርፍ የለውምን "(የግባት ጥያቄ ተመልከት)

ከፀሐይ በታች ..... የሰው ትርፍ ምንድነው ?
ፀሐፊው በተጋነነ መልኩ የጠየቀበት ምክንያት የሠው ሥራ እርባና ቢስና ዘለቄታዊ ፍፃሜ እንደሌለው አፅንኦት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ አንድ በአረፍተ ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "ከፀሐይ በታች የሰው ልጅ ትርፍ የለውም" (የተጋነነ ጥያቄ ተመልከት)

ከፀሐይ በታች
ይህ በምድር ላይ የተደረጉትን ነገሮች ሁሉ የሚገልፅ ሐሳብ ነው።

Ecclesiastes 1:4

አጠቃላይ መረጃ
ፀሐፊው በተረዳው መልኩ ተፈጥሮአዊ የሕይወት ሥረዓትን እያቀረበ (እየገለፀ) ነው።

ወደምትወጣበትም ስፍራ ትቸኩላለች
ይህ ፀሐይን በሠው አስመስሎ ከገባችበት ወደምትጠልቅበት በፍጥነት ወጥታ እንድትሄድ እንዴት በቀኑ መጨረሻ እንደምትጠልቅና በፍጥነት ዳግም መልሳ እንደምትወጣ የሚናገር ሃሳብ ነው።(በሰው ማስመሰል ተመልከት)

Ecclesiastes 1:7

አጠቃላይ መረጃ
ፀሐፊው ስለተፈጥሮ ስርዓት ግንዛቤውን (ማስተዋልን) ቀጥሏል። ነገር ሁሉ ያደክማል

"ሁሉም ነገር አድካሚ ይሆናል
የሰው ልጅ እነዚህን ነገሮች ለመግለፅ ስለማይችል መሞከሩ ዋጋ የለውም።"

ዓይን ከማየት አይጠግብም
እዚህ ጋር ዓይን የሚወክለው ሙሉ ሰውን ነው። ተርጓሚ የሰው ልጅ በዓይን በሚያየው ነገር አይረካም

ጆሮም ከመስማት አይሞላም
እዚህ ጋር "ጆሮ" የሚወክለው ሙሉ ሰው ነው። ተርጓሚ የሰው ልጅ በጆሮ በሚሰማውም አይደሰትም

Ecclesiastes 1:9

አጠቃላይ መረጃ
በጆሮ በሚሰማው ነገር ሁሉ እርሱ የሚሆን ነው ሰውና ድርጊቶቹን ተመልከት ምንም አዲስ ነገር የለውም ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ " ከዚህ በፊት የሆነው ነገር ሁሉ ተመልሶ ወደፊት ይሆናል "

ከፀሐይ በታች
ይህ ምድር ላይ የተደረጉትን ነገሮች ሁሉ ይገልፃል። የመክብብ 1:3 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ "በምድር ላይ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ማንም እነሆ ይህ ነገር አዲስ ነው ይል ዘንድ ይችላልን?
ይህ የግነት ጥያቄ የተጠየቀው የሰው ልጅ አዲስ ነገር አለ ማለት እንደማይችል አፅንኦት ለመስጠት ነው። ይህ በአረፍተ ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "ይህ ነገር አዲስ ነው የሚባል ነገር የለም " (የግነት ጥያቄ ተመልከት)

ይል ዘንድ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "የሆነ ሰው ሊናገር ያለው ነገር "

እርሱ የሚደረግ ነው
ጥገኛ ሊቀርብ ይችላል ተርጓሚ "ሰዎችም አያስተውሉአቸውም "

Ecclesiastes 1:12

ልቤን አተጋሁ
እዚህ ጋር ፀሐፊው "ልብ"ን የተጠቀመው ለስሜቱ አፅንኦት ለመስጠት ነው። ተርጓሚ "ቆራጥ ሆንኩ" ወይም እራሴን አፀናሁ።"

እመረምርና እፈልግ ዘንድ
እነዚህ ሁለቱ ቃላት ተመሳሳይ ሲሆኑ ተግቶ እንዳጣ አፅንኦት ለመስጠት ነው ።

ከሰማይ በታች
ይህ ምድር ላይ የተደረጉትን ነገሮች ሁሉ ይገልፃል። ተርጓሚ "ምድር ላይ"

ለሰው ልጅ
"የሰው ዘር" (የሰው ልጅ)

የተወራውን ሥራ ሁሉ
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል ። ተርጓሚ "ሰዎች የሚያደርጉት ሁሉ "

ከፀሐይ በታች
ይህ ምድር ላይ የተደረጉትን ነገሮች ሁሉ ይገልፃል። የመክብብ 1:3 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ "በምድር ላይ" (ፈሊጣዊ ተመልከት)

እነሆ
ፀሐፊው ይህን ቃል የተጠቀመው ቀጥሎ ለሚናገረው ንግግር ትኩረት ለመሳብ ነው። ተርጓሚ "በእርግጥ " "በእውነት " (ፈሊጣዊ ተመልከት)

ሁሉ ከንቱ ነፋስንም እንደመከተል ነው
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ዘይቤኣዊ ሲሆኑ ነገሮች ሁሉ ከንቱና የማይረቡ መሆናቸውን አፅንኦት ለመስጠት ነው።

ሁሉ ከንቱ ነው
"እንደተን ብቻ " ተርጓሚው ስለማይጠቅሙና ትርጉም ስለሌላቸው ነገሮች ንፋስን ለመቆጣጠር ሊሞክሩ እንደፈለጉ ይናገራል። ተርጓሚ "ጥቅም የሌላቸው ነገሮች ንፋስን ለመቆጣጠር ሲሞክሩ" (ዘይቤአዊ ተመልከት)

ጠማማ ይቀና ዘንድ አይችልም ጎዶሎም ይቆጠር ዘንድ አይችልም
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "የተጣመመን ነገር ሰዎች ሊያቀኑ አይችሉም የሌለን ነገር መቁጠር አይችሉም።"

Ecclesiastes 1:16

እኔ በልቤ ..... ተናገርሁ
እዚህ ጋር ተርጓሚው እራሱን በልቡ ይገልፃል። ይህም ለስሜቱ አፅንኦት ለመስጠት ነው ተርጓሚ "እኔ ለራሴ ተናገርኩ"

ልቤን ሰጠሁ
እዚህ ጋር እራሱን በ"ልብ" ይገልፃል። ሲገልፅ ለተማረው ነገር አፅንኦት ለመስጠት ነው። ተርጓሚ "አገኘሁ ወይም ተማርኩ"

ልቤን ሰጠሁ
እዚህ ጋር ፀሐፊው ለስሜቱ አፅንኦት ለመስጠት እራሱን በልቡ ይገልፃል። ተርጓሚ "ቆረጥኩ" ወይም "እራሴን ሰጠው"

እብደትን ሞኝነትንም
"እብደትና " ሞኝነት " ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው ሁለቱም ቃላት ስለሞኝነት አስተሳሰብና ባህሪይ ይናገራል ።

ነፋስንም እንደመከተል ነው።
ፀሐፊው፡ጥበብን፡ መማርና እብደትና ሞኝነት፡ ልክ ነፋስን ለመቆጣጣር የመሞከር ያክል፡ እርባና ቢስ ነው። ተርጓሚ ይህን በመክብብ፡ 1:14 ላይ ተተርጉሟል። ተርጓሚ "ልክ ነፋስን የመቆጣጣር ያክል እርባና ቢስ ነው።"(ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 እኔም በልቤ፥ "ና እንግዲህ፥ በደስታ እፈትንሃለሁ። ስለዚህ እንዳሻህ ተደሰት" አልኩ። ግን ተመልከት፥ ይህም ደግሞ ልክ የአፍታ እስትንፋስ ነበር። 2 ስለ ሣቅ "እርሱ ዕብደት ነው"፥ ስለ ደስታም "ምን ይጠቅማል?" አልኩ። 3 በወይን ጠጅ ራሴን እንዴት እንደማስደስተው በልቤ መረመርሁ። እስካሁን ሞኝነትን ብይዛትም አዕምሮዬ በጥበብ እንዲመራ ተውኩት። ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው ከሰማይ በታች ሊያደርጉት የሚገባቸውን መልካም ነገር ለማግኘት ፈለግሁ። 4 ታላላቅ ነገሮችን አከናወንኩ። ለራሴ ቤቶችን ሠራሁ፥ ወይንንም ተከልሁ። 5 የአትክልትና የመዝናኛ ቦታዎችን ለራሴ ሠራሁ፤ በእነርሱም ላይ ሁሉንም ዓይነት የፍሬ ዛፎች ተከልሁባቸው። 6 ዛፎች የሚያድጉበትን ዱር የሚያጠጡ የውሃ ገንዳዎችን አበጀሁ። 7 ወንድና ሴት ባሪያዎችን ገዛሁ፤ በቤተ መንግሥቴ የተወለዱ ባሪያዎችም ነበሩኝ። ከእኔ በፊት በኢየሩሳሌም ከነገሡት ሁሉ እጅግ የሚበልጥ የከብት መንጋና የቤት እንስሶች ነበሩኝ። 8 ብርና ወርቅን፥ የነገሥታቱንና የአውራጃዎቹንም ሃብት ለራሴ አከማቸሁ። ለእኔ ለራሴ ወንድና ሴት አዝማሪዎች ነበሩኝ፤ እጅግ በበዙት ሚስቶቼና ቁባቶቼም በምድር ማንኛውንም ሰው ሊያስደስተው የሚችለውን ነገር አደረግሁ። 9 ከእኔ በፊት በኢየሩሳሌም ከነበሩት ሁሉ ይልቅ ታላቅና ባለጸጋ ሆንኩ፥ ጥበቤም ከእኔው ጋር ቆየች። 10 ዓይኖቼ የፈለጉትን ማናቸውንም ነገር አልከለከልኳቸውም። በምሠራው ሁሉ ልቤ ስለ ተደሰተና ደስታ የሠራሁት ሥራ ሁሉ ብድራት ስለ ነበረ ከየትኛውም ደስታ ልቤን አልከለከልኩትም። 11 ከዚያም እጆቼ ያከናወኗቸውን ተግባራት ሁሉ፥ እኔም የሠራኋቸውን ሥራዎች ተመለከትኩ፥ ነገር ግን ሁሉም እንፋሎትና ነፋስን ለማገድ መሞከር ነበር። በእርሱ ውስጥ ከፀሐይ በታች አንድም ትርፍ አልነበረበትም። 12 ከዚያም ጥበብን፥ ደግሞም ዕብደትንና ሞኝነትን ለመመርመር ራሴን መለስኩ። አስቀድሞ ከተደረገው በቀር ከዚህኛው ንጉሥ በኋላ የሚመጣው ንጉሥ ምን ለማድረግ ይችላል? 13 ከዚያም ልክ ብርሃን ከጨለማ እንደሚሻል ጥበብም ከሞኝነት የሚሻል መሆኑን መረዳት ጀመርሁ። 14 ጥበበኛ ሰው የሚሄድበትን እንዲያውቅ ዓይኖቹን በራሱ ላይ አድርጎ ይጠቀምባቸዋል፥ ሞኙ ግን በጨለማ ይሄዳል፥ ቢሆንም ለእያንዳንዱ የተዘጋጀለት ፍጻሜ ተመሳሳይ መሆኑን አውቃለሁ። 15 እኔም በልቤ፥ "በሞኙ ላይ የሚደርሰው በእኔም ላይ ይደርሳል። ስለዚህ በጣም ጥበበኛ ብሆን ምን ልዩነት ያመጣል?" አልኩ። "ይህም ደግሞ እንፋሎት ብቻ ነው" ብዬ በልቤ ደመደምኩኝ። 16 ምክንያቱም ጠቢቡም እንደ ሞኙ ለዘላለም አይታሰብም። በሚመጣው ዘመን ሁሉም ነገር የተረሳ ይሆናል። ልክ ሞኙ እንደሚሞት ጠቢቡም ሰው ይሞታል። 17 ከፀሐይ በታች የሚሠራው ሥራ ሁሉ ክፉ ስለሆነብኝ ሕይወትን ጠላሁ። ይህም የሆነው ሁሉም ነገር እንፋሎትና ነፋስን ለማገድ መሞከር ስለሆነ ነው። 18 ከፀሐይ በታች በሥራ የደከምኩበትን ሁሉ ጠላሁ፥ ከእኔ በኋላ ለሚመጣው ሰው ልተውለት የግድ ነውና። 19 እርሱ ጥበበኛ ወይም ሞኝ ይሆን እንደሆነ ማን ያውቃል? ሆኖም ከሰማይ በታች በጥበቤ በሠራሁት ሁሉ ላይ አዛዥ ይሆናል። ይህም ደግሞ እንፋሎት ነው። 20 ከዚህ የተነሣ ከፀሐይ በታች በሠራሁት ሥራ ሁሉ ላይ ልቤ ተስፋ መቁረጥ ጀመረ። 21 ምክንያቱም አንዱ በጥበብ፥ በእውቀትና በብልሃት ይሠራ ይሆናል፥ ነገር ግን የነበረውን ነገር ሁሉ አንድም ላልለፋበት ሰው ይተውለታል። 22 ይህም ደግሞ እንፋሎትና እጅግ የሚያሳዝን ነው። ከፀሐይ በታች ሰው ተግቶ በመሥራቱና ሥራውን ሁሉ ለማጠናቀቅ በልቡ በመሞከሩ ምን ያተርፋል? 23 የየዕለት ሥራው በስቃይና በውጥረት የተሞላ ነው፥ ስለዚህ ነፍሱ በሌሊት እረፍት አታገኝም። ይህም ደግሞ እንፋሎት ነው። 24 ለማንኛውም ሰው ከመብላት፥ መጠጣትና ከሥራው መልካም በሆነው ከመርካት የሚበልጥበት ምንም ነገር የለም። ይህ እውነት የሚመጣው ከእግዚአብሔር እጅ እንደሆነም አየሁ። 25 ከእግዚአብሔር ካልሆነ በስተቀር ማን ሊበላ ይችላል? ወይም የትኛውንም ዓይነት ደስታ ማን ሊደሰት ይችላል? 26 እርሱን ደስ ለሚያሰኝ እግዚአብሔር ጥበብን፥ እውቀትንና ደስታን ይሰጠዋል። እንዲሁም ለኃጢአተኛው የመሰብሰብንና የማከማቸትን ሥራ ይሰጠዋል፥ እግዚአብሔርን ደስ ለሚያሰኘው ሰው ይሰጠው ዘንድ። ይህም ደግሞ እንፋሎትን ማብዛትና ነፋስን ለማገድ መሞከር ነው።

Ecclesiastes 2:1

እኔ በልቤ አልሁ
እዚህ ጋር ፀሐፊው ለስሜቱ አፅንኦት ለመስጠት እራሱን በልቡ ይገልፃል። ተርጓሚ"ለራሴ አልኩ "

በደስታም እፈትንሃለሁ
እዚህ ጋር እራሱን በሦስተኛ ወገን ይናገራል ። መልካም ደስታ የሚለው ቃልም እንደ ቅፅል ሊገለፅ ይችለል ። ተርጓሚ" እራሴን ደስታ በሚሰጡኝ ነገሮች እፈትናለሁ "(ረቀቅ ስሞች ተመልከት) መልካም የሚለው ቃል በግስ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። ተርጓሚ "በሚያስደስቱም ነገሮች ሐሴት አደርጋለሁ።"(ረቂቂ ስም ተመልከት)

ይህም ደግሞ እነሆ ከንቱ ነበር
ይህ ደስታ ልክ እንደ ተን ጊዜአዊ አንደሆነና ለተወሰነ ጊዜ ብቻ እንደሆነ ይናገራል። ተርጓሚ ይህም ልክ እንደ ተን ጊዜአዊና ለአጭር ጊዜ ብቻ ነው። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

ሳቅን "ዕብድ ነህ" አልሁት
በትምህረተ ጥቅስ ውስጥ ያለው ሐሳብ ቀጥተኛ ባልሆነ መልኩ ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ "በነገሮች ላይ መሣቅ እብደት ነው አልሁ"(ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅስ ተመልከት)

ምን ታደርጋለህ?
ፀሐፊው መልካም (እርካታ) እርባና ቢስ እንዲሆንና አፅንኦት ለመስጠት የግነት ጥያቄን ይጠቀማል ። የግነት ጥያቄን ተመልከት)

Ecclesiastes 2:3

እስካይ ድረስ ልቤ
ይህ ሐሳብ (ንግግር) የሚናገረው ላይታዬ ነገር በጣም ማሰብን ያሳያል። ስሜቱና ሐሳቡ ልቡ የሆኑ ያክልም ፀሐፊው ይናገራል።

ሰውነቴን በወይን ጠጅ ደስ ለማሰኘት
"ሰውነቴን" የሚለው ቃል በቀላል ሐረግ ሊገለፅ ይችለል። ተርጓሚ "እራሴን ደስ ለማሰኘት ወይን ጠጅ መውሰድ (መጠቀም) (ረቂቂ ስም ተመልከት)

ልቤ በጥበብ እየመራኝ
ፀሐፊው የተማረን ጥበብ በሰው አስመስሎ ልክ የሆነ ሰው እንደመራው እንዴት ሊመራው እንደነበረ ይናገራል። ተርጓሚ "ጥበበኞች ስላስተማሩኝ ነገሮች አሰብኩ" (ሕይወት ክል ነገሮቸን በሰው ማስመሰል ተመልከት)

ከፀሐይ በታች
ይህ በምድር ላይ ስለሆኑት ነገሮች ሁሉ ይገልፃል ። ተርጓሚ "በምድር ላይ"

በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ
"በሕይወት እያሉ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ecclesiastes 2:4

ቤቶችንም አደረግሁ ወይንም ተከልሁ አትክልትንና ገነትን አደረግሁ
ምናልባት ፀሐፊው ሌሎች ሥራውን እንዲሠሩ ተናግሮአል። ተርጓሚ ቤትን የሠሩልኝና ወይንም የተከሉ ሰዎች ነበሩኝ ። አስተከልኩአቸው አስደረኩአቸው ። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

አትክልትንና ገነትን
እነዚህ ሁለት ተመሣሣይ ትርጉም ሲኖራቸው የሚገልፁትም የሚያምር የፍራፍሬ እርሻ ተክል (ዛፍን)ነው።

ዘፎችን አጠጣበት ዘንድ
"ለዛፎች ውሃ አቀርብ ዘንድ"

በድር የተተከሉትንም ዛፎች
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል ። ተርጓሚ "ዛፎች ያሉበት (የሚያድጉበት) ዱር"

Ecclesiastes 2:7

የቤት ውልድ ባሪያዎችም ነበሩኝ
"በቤት ውስጥ የተወለዱ ባሪያዎች ነበሩኝ " ወይም "ባሪያዎች ልጆች ወልደው እነርሱም ባሪያዎች ነበሩ"

ከነበሩት ሁሉ ይልቅ
ግልፅ የሆነ ግሥ ሊቀርብ ይችላል ። ተርጓሚ "ማንም ከነበረው በላይ "ወይም ማንም የትኛውም ንጉሥ ከነበረው በላይ"

የከበረውንም የነገሥታትና የአውራጃዎችን መዝገብ
ይህ የሚገልፀው የጎረቤት ሀገሮች ለእሥራኤል ንጉሥ ተገደው ይከፍሉት የነበረውን ወርቅና ሀብት ነው። ተርጓሚ ከነገሥታትና ከአውራጃ ገዥዎች መዝገብ አገኘው።

አውራጃዎች
እዚህ ጋር "አውራጃዎች"የክፍለ-ሀገር ገዥዎችን ይወክላሉ ።ተርጓሚ "የክፍለ-ሀገር ገዥዎች"

የሰዎች ልጆችንም ተድላ ..... የብዙ ሴቶችም
ይህ ማለት አንድ ሰው ልክ ከሴቶች ጋር ሲተኛ የሚያገኘውን እርካታ ያክል ከብዙ ሴቶች ጋር በመተኛት ደስ ይሰኝ ነበር። ተርጓሚ "ሰው ከሴት ጋር በመተኛት እንደሚደሰተው እንዲህ ከብዙ ሴቶች ጋር በመተኛት እጅግ እደሰት ነበር ።

Ecclesiastes 2:9

ከእኔ አስቀድመው በኢየሩሳሌም ከነበሩት ሁሉ ይልቅ
ይህ የቀደሙትን የኢየሩሳሌም ገዥዎች ይገልፃል። ተርጓሚ "ከእኔ በፊት በኢየሩሳሌም ውስጥ ገዥ ከነበሩት ይልቅ"

ጥበቤ ከእኔ ጋር ፀንታ ቀረች
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። "በጥበብ መመለስ ቀጠልኩ " (ፈሊጣዊ ተመልከት)

ዓይኖቼን ከፈለጉት ሁሉ
እዚህ ጋር ፀሐፊው ለተመለከተው ነገር አፅንኦት ለመስጠት እራሱን በዓይኖቹ ይገልፃል።ተርጓሚ ያየሁትንና የተመኘሁትን ሁሉ .... ከራሴ "

... ሁሉ አላራቅሁትም
"ሁሉንም አገኘሁ"

ልቤን ከደስታ ሁሉ አላራቅሁትም
እዚህ ጋር ፀሐፊው ለምኞቱ አፅንኦት ለመስጠት እራሱን በልቡ ይገልፃል ይህ በመልካም መልኩ ሊቀመጥ /ሊፃፍ የሚችል ሲሆን ደስታ የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊገልፅ ይችላል። ተርጓሚ "እራሴን ከየትኛውም ደስታ አልከለከልኩም" ወይም "በሚያስደስተኝ ነገር ሁሉ ለመደሰት ለራሴ ፈቀድኩ"

ልቤም ..... ደስ ይለው ዘንድ
እዚህ ጋር ፀሐፊው ለምኞቱ አፅንኦት ለመስጠት እራሱን በልቡ ይገልፃል። ተርጓሚ "ደስ ተሰኘሁ"

Ecclesiastes 2:11

እጄ የሠራቻት ሥራዬን ሁሉ
እዚህ ጋር ፀሐፊው እራሱን በእጁ ይገልፃል። ተርጓሚ "ያከናወንኳቸውን ሁሉ"

ከንቱ ነፋስንም እንደመከተል ነበር
እነዚህ ሁለት ቃላት ዘይቤአዊ ሲሆን እርባና ቢስ ስለሆኑት ነገሮች የሚገልፅ ሀሳብ ነው።

ከንቱ
ፀሐፊው እርባና ቢስና ትርጉም ስለሌላቸው ነገሮች ተን የሆኑ ያክል ይናገራል። መክብብ 1:14 እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት። ተርጓሚ "ልክ እንደ ተን እርባና ቢስ " ወይም "ትርጉም የለሽ (ዘይቤአዊ ተመልከት)

ንፋስን እንደመከተል
ፀሐፊው የሚለው ሰዎች የሚያደርጉት ሁሉ ንፋስን ለመቆጣጠር እንደ መሞከር እርባና ቢስ ነው ። የመክብብ 1:14 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ "ንፋስን እንደመቆጣጠር ያክል እርባና ቢስ ነው።" (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

ከፀሐይ በታችም ትርፍ አልነበረም
"ነገር ግን ከፀሐይ በታች ትርፍ አልነበረም"

ከፀሐይ በታች
ይህ የሚገልፀው በምድር ላይ የተደረጉትን ሁሉ ነው። የመክብብ 1:3 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ "በምድር ላይ "(ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

እብደትንና ስንፍናን
ሁለቱ ቃላት ተመሣሣይ ትርጉም ሲኖራቸው የሞኝነት አስተሳሰብንና ባህሪይን በቅደም ተከተሉ ይገልፃል። የመክብብ 1:17 ትርጉምን ተመልከት።

በፊት ከተደረገው በቀር ከንጉሥ በኋላ የሚመጣው ሰው ምን ያደርጋል
ፀሐፊው የግነት ጥያቄን ንጉሡ በፊት ከሠራው የተሻለ ነገር የሚቀጥለው ንጉሥ ምንም ሊያደርግ እንደማይችል አፅንኦት ለመስጠት ነው ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "ከንጉሡ ቀጥሎ የሚመጣው ንጉሥ የቀደመው ንጉሥ ያልሠራውን ሊሠራ እንደማይችል" (የግነት ጥያቄ ተመልከት)

ከንጉሥ በኋላ የሚመጣው ሰው (ንጉሥ)
አሁን ያለውን ንጉሥ የሚተካ ንጉሥ ወይም "ከእኔ ቀጥሎ የሚመጣው ንጉሥ"

Ecclesiastes 2:13

ብርሃን ከጨለማ እንደሚበልጥ እንዲሁ ጥበብ ከሥንፍና
ይህ ንግግር ብርሃን ከጨለማ እንደሚሻል በማነፃፀር ጥበብ ከሥንፍና እንደሚሻል ያሳያል። (ንግግር ተመልከት)

የጠቢብ ዓይኖች በራሱ ላይ ናቸው
ይህ ጠቢብ ሰው ለመንገዱ ወዴት እንደሚሄድ አትኩሮት በመስጠት በጥበብ እንዴት እንደሚሄድ የሚናገር ነው። ተርጓሚ ጠቢብ ሰው ወዴት እንደሚሄድ አይኖቹን እንደሚጠቀም አይነት ሰው ነው። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ዓይኖቹ በራሱ ላይ ናቸው
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው ተርጓሚ ለማየትና ለመመልከት ትኩረት ይሰጣል

ሰነፉ ግን በጨለማ ይሄዳል
ይህ ሰነፉ የሚወስነውን ያልተገባ ውሳኔ በጨለማ ውስጥ ከሚሄድ ሰው ጋር ያነፃፅራል (ያወዳድራል) ተርጓሚ "ሰነፉ በጨለማ ወስጥ እንደሚሄድ አይነት ሰው ነው"(ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

ተመሳሳይ ክስተት
ሞት

Ecclesiastes 2:15

በልቤ .....አለው
እዚህ ጋር ፀሐፊው ለስሜቱ አፅንኦት ለመስጠት እራሱን "በልቡ" ይገልፃል። ተርጓሚ "ለራሴ ተናገርኩ (አልኩ)

ለምን እጅግ ጠቢብ ሆንሁ?
ይህ ፀሐፊው የግነት ጥያቄን የሚጠቀመው ጠቢብ መሆን ትርፍ እንደሌለው አፅንኦት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "በጣም ጠቢብ ቢሆን ምንም ለወጥ አያመጣም" (የግነት ጥያቄን ተመልከት)

በልቤ ..... አልሁ
እዚህ ጋር ፀሐፊው ለስሜቱ አፅንኦት ለመስጠት እራሱን "በልቡ" ይገልፃል። ተርጓሚ "ደመደምኩ"

ይህ ደግሞ ከንቱ ነው
ይህ ደግሞ "ተን" ነው ፀሐፊው ተን (ከንቱ) እንደሆኑ ያክል ስለማይረቡና ትርጉም ስለሌላቸው ነገሮች ያወራል። የመክብብ 1:14 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ "እንደ ከንቱ እርባና ቢስ ወይም ትርጉም የለሽ" (ዘይቤአዊ ተመልከት)

ለዘላለም የሚሆን የጠቢብና የሰነፍ መታሰቢያ አያገኝም
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "ሰነፍን ለዘላለም እንደማያሰተውሉ ሁሉ ጠቢብንም እንደዚሁ ለዘላለም አያስታውሱም"

ነገር ሁሉ የተረሳ ይሆናልና
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "ሁሉም ነገር በሰዎች ዘንድ የተረሳ ይሆናል።"

Ecclesiastes 2:17

የተሠራው ሥራ ሁሉ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል ። ተርጓሚ "ሠዎች የሚሰሩት ሥራ ሁሉ"

ከብዶኛልና
"አስቸግሮኛልና "

ከንቱ ነፋስንም እንደመከተል ነው።
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች ዘይቤአዊ ሲሆኑ እርባና እና ከንቱ ስለሆኑ ነገሮች አፅንኦት የሚሰጥ ሀሳብ ነው።

ከንቱ
"ተን "ፀሐፊው እርባና ቢስን ትርጉም የሌላቸው ነገሮች ተን (ከንቱ) እንደሆኑ ይናገራል። የመክብብ 1:14፡ ትርጉምን የለሽ"(ዘይቤአዊ ተመልከት)

ነፋስን እንደመከተል
ፀሐፊው የሚናገረው ሰዎቸ የሚያደርጉት ሁሉ ነፋስን ለመቆጣጠር እንደመሞከር እርባና ቢስ ነው ። የመክብብ ፡1:14፡ ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ "ነፋስን እንደመቆጣጠር ያክል እርባና ቢስ ነው" (ዘይቤአዊ ተመልከት)

ከፀሐይ በታች
ይህ በምድር ላይ የተደረጉ ነገሮችን ሁሉ ይገልፃል። የመክብብ ፡1:3፡ ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ "በምድር ላይ" (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ከእኔ በኋላ ለሚመጣው ሰው
"ከእኔ በኋላ ለሚወርሰው ሰው"

Ecclesiastes 2:19

ጠቢብ ወይም ሰነፍ እንዲሆን የሚያውቅ ሰው ማን ነው?
ፀሐፊ ይህን የግነት ጥያቄ ሀብቱን ስለሚወርሰው ሰው ባህርይ ማንም እንደማያወቅ አፅንኦት ለመስጠት ነው ። ተርጓሚ "ጠቢብ ወይም ሰነፍ ስለመሆኑ ማንም ስለማያውቅ" (የግነት ጥያቄን ተመልከት)

እንዲሆን
የፀሐፊውን ወራሽ ማንነት ይገልፃል።

ከፀሐይ በታች
ይህ በምድር ላይ የተደረጉ ነገሮችን ሁሉ ይገልፃል የመክብብ ፡1:3፡ትርጉምን ተመልከት ። ተርጓሚ "በምድር ላይ "(ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

በድካም ሀብትና ጠቢብ ብሆን ሀብት በድካሜ
እዚህ ጋር የፀሐፊው "ድካም "እና ጥበብ እራሱንና በጥበብ የሠራቸውን ነገሮች ይወክላሉ። ምናልባት በትክክል ለሠራቸው ሕንፃዎች ገነ ይኖረው ይሆናል ተርጓሚ "ለመገንባት፤በጥበብና በጣም እንደደከምኩበት"

ከንቱ
ፀሐፊው እርባና ቢስና ትርጉም የሌላቸው ነገሮች ተን (ከንቱ) እንደሆኑ ይናገራል። የመክብብ ፡1:14፡ ትርጉም የለሽ (ዘይቤአዊ ተመልከት)

ልቤን ---- ድካም ሁሉ
እዚህ ጋር ፀሐፊው ለሥሜቱ አፅንኦት ለመስጠት እራሱን በልቡ ይወክለል። ተርጓሚ "መድከም ጀመርኩ " ወይም "ተስፋ መቁረጥ ጀመረኩ"

Ecclesiastes 2:21

በጥበብና በእውቀት በብልኃትም ከደከመ
"የተማረውን በመጠቀም በጥበብና በብለሃት የሚሠራ"

ለሌላ ላልደከመበት
"ለሌላ ለልሠራበት "

ከንቱ
ፀሐፊው እርባና ቢስና ትርጉም የሌላቸው ነገሮች ከንቱ (ተን) እንደሆኑ ይናገራል የመክብብ ፡1:14፡ ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ እንደ ከንቱ (ተን) እርባና ቢስ ወይም ትርጉም የለሽ (ዘይቤአዊ ተመልከት)

ትልቅም መከራ
"ትልቅም ጥፋት"

ከፀሐይ በታች በደከመበት ድካም ሁሉና በልቡ ሃሳብ የሰው ጥቅም ምንድር ነው?
ፀሐፊው የግነት ጥያቄን ጠንክሮ የሚሠራ ሠው ምንም እንደማያገኝ አፅንኦት ለመስጠት ነው ። በመክብብ ፡1:3፡ ላይ ያለውን ትርጉም ተመልከት ተርጓሚ "ከፀሐይ በታች ጠንክሮ የሚሠራና በልቡ ሥራውን ለመፈፀም እንደሚሞክር ሠው ምንም አያገኝም" (የግነት ጥያቄን ተመልከት)

በደከመበት ድካም ሁሉና በልቡ ሀሳብ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሠረቱ ተመሣሣይ ትርጉም ሲኖራቸው ሰወየው እንዴት በርትቶ እንደሚሰራ አፅንኦት ይሠጣሉ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በልቡ ..... ጥረትም
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። ተርጓሚ "ተጨንቆ መሞከር"

ከፀሐይ በታች
ይህ በምድር ላይ የተደረጉትን ነገሮች ይገልፃል። የመክብብ ፡1፡3 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ "በምድር ላይ"

ሀዘን ..... ትካዜ ነው
ሁለቱ ዋይታ ተመሣሣይ ትርጉም ያላቸውና የሠውየው ሥራ ምን ያህል አድካሚ እንደሆነ አፅንኦት ለመስጠት ነው።

ልቡም በሌሊት አይተኛም
እዚህ ጋር የሰው አዕምሮ በልቡ ሲገለፅ ጥልቅ ሀሳቡን አፅንኦት ለመስጠት ነው። ተርጓሚ "አዕምሮው አያርፍም " ወይም "መጨነቁን ይቀጥላል" (ፈሊጣዊና ዘይቤአዊ ተመልከት)

Ecclesiastes 2:24

የእግዚአብሔር እጅ
እዚህ ጋር እግዚአብሔር እንዴት ለህዝቡ እንደሚያዘጋጅ አፅንኦት ለመስጠት በእጅ ይገለፃል። ተርጓሚ ከእግዚአብሔር

ያለ እርሱ ፈቃድ የበላ ደስ ብሎትም ተድላን የቀመሠ ማን ነው?
ፀሐፊው ይህን የግነት ጥያቄ ከእግዚአብሔር አቅርቦት በስተቀር ተድላ ሊኖር እንደማይችል አፅንኦት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ ከእግዚአብሔር ካልሆነ በስተቀር ማንም ሊበላ ወይም የትኛውንም አይነት ተድላ ማግኘት አይችልም።

Ecclesiastes 2:26

እግዚአብሔርን ደስ ለሚያሰኘው ሰው ይሰጥ ዘንድ
ይህ ኃጢያተኛው የሚያከማቸውን ሰጪው ማን እንደሆነ በግልፅ ሳይናገር መተርጎም ይቻላል። ተርጓሚ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው ሰው ይሰጠው ዘንድ (ይኖረው ዘንድ)

ከንቱ ነፋስንም እንደመከተል ነው
ይህ ዘይቤአዊ ንግግር ሀሳቡ ነገሮች እርባና ቢስና ከንቱ እንደሆኑ አፅንኦት ለመስጠት ነው።

ከንቱ
"ተን" ፀሐፊው የሚናገረው እርባና ቢስና ትርጉም የሌላቸው ነገሮች ከንቱ እንደሆኑ አድርጎ ነው። የመክብብ ፡1፡14፡ ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ "እንደ ከንቱ እርባና ቢስ" ወይም "ትርጉም የለሽ" (ዘይቤአዊ ንግገር ተመልከት) ነፋስን እንደመከተል ፀሐፊው ሰዎች ነፋስን ለመቆጣጠር እንደሚሞክሩ እንዲሁ የሚሰሩት ነገር ሁሉ እርባና ቢስ መሆኑን ይነገራል ። የመክብብ ፡1፡14፡ ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ "ነፋስን እንደመቆጣጠር ያክል እርባና ቢስ ናቸው።" (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 ለሁሉም ነገር የተቀጠረለት ጊዜ አለው፥ ከምድር በታች ለሚሆነውም ወቅት አለው። **2** ለመወለድ ጊዜ አለው፥ ለመሞት ጊዜ አለው፥ ለመትከል ጊዜ አለው፥ ለመንቀል ጊዜ አለው፥ **3** ለመግደል ጊዜ አለው፥ ለመፈወስ ጊዜ አለው፥ ለማፍረስ ጊዜ አለው፥ ለመገንባት ጊዜ አለው፥ **4** ለማልቀስ ጊዜ አለው፥ ለመሣቅ ጊዜ አለው፥ ለማዘን ጊዜ አለው፥ ለመጨፈር ጊዜ አለው፥ **5** ድንጋይ ለመወርወር ጊዜ አለው፥ ድንጋይ ለመሰብሰብ ጊዜ አለው፥ ለመተቃቀፍ ጊዜ አለው፥ ከመተቃቀፍ ለመራቅ ጊዜ አለው፥ **6** ለመፈለግ ጊዜ አለው፥ ፍለጋን ለማቆም ጊዜ አለው፥ ነገሮችን ለመጠበቅ ጊዜ አለው፥ ነገሮችን ወርውሮ ለመጣል ጊዜ አለው፥ **7** ልብስ ለመቅደድ ጊዜ አለው፥ ለመስፋት ጊዜ አለው፥ ዝም ለማለት ጊዜ አለው፥ ለመናገር ጊዜ አለው፥ **8** ለመውደድ ጊዜ አለው፥ ለመጥላት ጊዜ አለው፥ ለጦርነት ጊዜ አለው፥ ለሰላም ጊዜ አለው። **9** ሠራተኛው ከጥረቱ የሚያተርፈው ምንድነው? **10** እግዚአብሔር እንዲፈጽሙት ለሰው ልጆች የሰጣቸውን ሥራ አይቻለሁ። **11** እግዚአብሔር ሁሉን ነገር በጊዜው ተስማሚ አድርጎ ሠራው። ደግሞም በልባቸው ውስጥ ዘላለማዊነትን አስቀመጠ። ነገር ግን የሰው ልጆች ከጅማሬአቸው እስከ ፍጻሜአቸው ድረስ እግዚአብሔር የሠራውን ሥራ ሊያስተውሉት አይችሉም። **12** ለሰው በሕይወት ዘመኑ ከመደሰትና መልካም ከማድረግ በቀር የሚሻል ምንም ነገር እንደሌለ አውቃለሁ። **13** ደግሞም ሰው ሁሉ ሊበላና ሊጠጣ፥ ከሥራውም ሁሉ በሚመጣ መልካም እንዴት መደሰት እንዳለበት ሊያውቅ። ይህ የእግዚአብሔር ሥጦታ ነው። **14** እግዚአብሔር የሠራው ሁሉ ለዘላለም እንደሚኖር አውቃለሁ። በዚህ ላይ መጨመርም ሆነ መቀነስ አይቻልም። ምክንያቱም ሰዎች በአክብሮት እንዲቀርቡት ይህንን ያደረገው እግዚአብሔር ነው። **15** አሁን ያለው ሁሉ ቀደም ሲል የነበረ ነው፤ ወደ ፊት የሚኖረውም ሁሉ ቀደም ሲል የነበረ ነው። እግዚአብሔር ሰዎችን የተደበቁ ነገሮችን እንዲፈልጉ ያደርጋቸዋል። **16** ከፀሐይ በታች ፍትሕ ሊኖር በሚገባበት ግፍ መኖሩን አየሁ፥ ጽድቅ ሊኖር በሚገባበትም ሥፍራ ብዙ ጊዜ የሚገኘው ግፍ ነው። **17** እኔም በልቤ፥ "ስለ እያንዳንዱ ጉዳይና ስለ እያንዳንዱ ሥራ በጻድቁና በአመጸኛው ላይ በትክክለኛው ጊዜ እግዚአብሔር ይፈርዳል" አልሁ። **18** እኔም በልቤ፥ "የሰው ልጆች እንደ እንስሳ መሆናቸውን ለማሳየት እግዚአብሔር ይፈትናቸዋል" አልሁ። **19** በእንስሳት ላይ የሚደርሰው ያው ዕድል ፈንታ በሰው ልጆች ላይ ይደርሳልና። እንደ እንስሳቱ፥ ሰዎች ሁሉ ይሞታሉ። ያንኑ አየር ሁሉም ይተነፍሱታል፥ ስለዚህ በዚህ መንገድ ሰው ከእንስሳ ብልጫ የለውም። ሁሉም ነገር ፈጥኖ የሚጠፋ እስትንፋስ አይደለም? **20** ሁሉም ወደ አንድ ሥፍራ ይሄዳሉ። ሁሉም ነገር ከአፈር ይመጣል፥ ሁሉም ነገር ደግሞ ወደ አፈር ይመለሳል። **21** የሰው መንፈስ ወደ ላይ፥ የእንስሳ መንፈስም ወደ ታች ወደ ምድር ውስጥ ይሄድ እንደሆነ የሚያውቅ ማን ነው? **22** ስለዚህ ማንም ሰው በሥራው ከመደሰት የሚበልጥ የተሻለ ነገር እንደሌለ እንደገና አስተዋልሁ፥ ያ ዕድል ፈንታው ነውና። ከእርሱ በኋላ የሚሆነውን እንዲያይ ማን መልሶ ሊያመጣው ይችላል?

Ecclesiastes 3:1

አጠቃላይ መረጃ
ፀሐፊው ከአንድ ጥግ እስከ ሌላኛው ያሉትን የተለያዩ የሕይወት ጉዳዮችን ለመግለፅ የተወሰነ የአፃፃፍ ለውጥ ይጠቀማል።

ለሁሉ ዘመን ..... ለሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ አለው
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ ትርጉም ሲኖራቸው የተጣመሩትም አፅንኦት ለመስጠት ነው ። (ተመሳሳይነት ተመልከት)

ከሰማይ በታች
ይህ በምድር ላይ የተደረጉትን ይገልፃል። የመክብብ ፡1:3 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ "በምድር ላይ" (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

የተተከለውንም ለመንቀል ጊዜ
ትርጉም ሊሆን የሚችለው 1. "የመከር ጊዜ" ወይም 2. "የመንቀል ጊዜ"

Ecclesiastes 3:4

አጠቃላይ መረጃ
ፀሐፊው ከአንድ ጥግ እስከ ሌላኛው ያሉትን የተለያዩ የሕይወት ጉዳዮችን ለመግለፅ የተወሰነ የአፃፃፍ ለውጥ መጠቀሙን ቀጥሏል።

ማቀፍ (መተቃቀፍ)
አንድን ሰው ለፍቅር ወይም ወዳጅነትን ማሳያ በክንዳችህ ውስጥ መያዝ

Ecclesiastes 3:6

አጠቃላይ መረጃ
አሁንም ፀሐፊ ከአንድ ጥግ እስከ ሌላኛው ጥግ ያሉትን የተለያዩ የሕይወት ጉዳዮች ለመግለፅ የተወሳነ የአፃፃፍ ለውጥ መጠቀሙን ቀጥሏል።

Ecclesiastes 3:8

አጠቃላይ መረጃ
ፀሐፊው ከአንድ ጥግ እስከ ሌለኛው ያሉትን የተለያዩ የሕይወት ጉዳዮች ለመግለፅና ለመደምደም የተወሰነ የአፃፃፍ ለውጥ መጠቀሙን ቀጥሏል ።

ለሠራተኛ የድካሙ ትርፍ ምንድር ነው?
ይህ ሐሳብ ቀስቃሽ ጥያቄ ሲሆን አንባቢው በቀጣዩ የውይይት ርዕስ ላይ ትኩረት እንዲሠጥ ነው። ፀሐፊው ይህን የግነት ጥያቄ የተጠቀመው የሰው ድካሙ ከንቱና ዘለቂ ትርፍ እንደሌለው አፅንኦት ለመስጠት ነው። ጥያቄው በአረፍተ ነገር መልኩ ሲቀመጥ ተርጓሚ "ሠራተኛ ለደከመበት ትርፍ የለውም (የግነት ጥያቄ ተመልከት)

Ecclesiastes 3:11

እግዚአብሔር ..... ነገርን ሁሉ በጊዜው ውብ አድርጎ ሰራው
እግዚአብሔር ሁሉም ነገር በጊዜው እንዲከወን የተወሰነ ጊዜ ስጥቷል። ወይም እግዚአብሔር እያንዳንዱ ነገር እንደሆነ ትክክለኛ ጊዜ አስቀምጧል።

ዘላለምነትን በልቡ ሰጠው
እዚህ ጋር በልቡ የሚለው ቃል የሰው ልጅን ይወክላል። እዚህ ጋር "ልብ" የሰው ልጅን ሀሳብና ምኞት ይወክላል። ተርጓሚ "በሰው ልጆች ልብ ውስጥ ዘላለማዊነትን አስቀመጠ"

ከጥንት ጀምሮ እስከ ፍፃሜ ድረስ
ይህ ጅማሬንና ፍፃሜን እንዲሁም በመካከል ያሉትን ሁሉ ይወክላል።

Ecclesiastes 3:12

ሰው ደስ ከሚለውና ..... በቀር
"እንዴት ሐሴት ማድረግ እንዳለበት ማወቅ አለበት" ወይም "ሐሴት ማድረግ አለበት"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ecclesiastes 3:14

ሊጨመርበት ወይም ከእርሱ ሊጎድል አይቻልም
ይህ ገቢር መልኩ ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ "ማንም ማንንም ሊጨምር ወይም ሊያጎድል አይችልም "

Ecclesiastes 3:16

በፍርድ ሥፍራ ኃጢአት በፅድቅም ሥፍራ ኃጢአት አየሁ
እነዚህ ሀረጎች ተመሳሳይነት ሲኖራቸው ተመሳሳይ የኃጢአት (ክፋት) ባህሪይ እንዳለ አፅንኦት ለመስጠት ነው።

ፅድቅ ሥፍራ
"ፅድቅ መኖር ባለበት ቦታ"

ከፀሐይ በታች
ይህ በምድር ላይ የሚደረጉትን ለመግለፅ ነው። የመክብብ 1:3 ትርጉም ተመልከት። ተርጓሚ "በምድር ላይ" (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

እኔም በልቤ ..... አልሁ
እዚህ ጋር ፀሐፊው ለሥሜቱ አፅንኦት ለመስጠት እራሱን "በልቡ" ይገልፃል። ተርጓሚ "ለራሴ አልኩ (ተናገርኩ)"

በፃድቅና በኃጢአተኛ
ይህ ስለ ፃድቅና ኃጢአተኛ ሰዎች ነው። ተርጓሚ "ፃድቅ የሆኑና ኃጢአተኛ የሆኑ" ወይም ፃድቃንና ኃጢአተኞች"

ለነገር ሁሉና ለሥራ ሁሉ
ሁለቱ ሐረጎች ተመሳሳይነት ሲኖራቸው የሰው ልጅ ድርጊትን ሁሉ ይገልፃል።

Ecclesiastes 3:18

በልቤ ..... አልሁ
እዚህ ጋር ፀሐፊው ለሥሜቱ አፅንኦት ለመስጠት እራሱን በ"ልቡ" ይገልፃል። ተርጓሚ "ለራሴ ተናገርኩ"

እንደ እንስሳ መሆናቸውን
እዚህ ጋር ፀሐፊው ሰዎች እንደ እንስሳ ናቸው እያለ ነው። በቀጣዩ ቁጥር ፀሐፊው በእርግጥ ሰዎች እንዴት እንደ እንስሳ እንደሆኑ በግልፅ ያስረዳል። (ተመሳሳይ ተመልከት

Ecclesiastes 3:19

እድል ፈንታ አንድ ነው
"ለሁለቱም አንድ አይነት ነው" ወይም "አንድ አይነት ነው"

የሁሉም እስትንፋስ አንድ ነው
"ሁሉም ተመሳሳይ ይተነፍሳሉ"

ሰው ከእንስሳ ብልጫ የለውም
የሰው ልጅ ከእንስሳ ምንም አይሻልም"

ሁሉም እንደ እስትንፋስ አይደለምን?
እዚህ ጋር ፀሐፊው ሁሉም ነገር እንደ እስትንፋስ ጊዜአዊ እንደሆነ ይናገራል። ፀሐፊው የግነት ጥያቄን ሁሉም ነገር ጊዜአዊ እንደሆነ አፅንኦት ለመስጠት ይጠቀማል። ጥያቄው በዐፍተ-ነገር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "ሁሉም ነገር እስትንፋስ ነው" ወይም ሁሉም ነገር እንደ ተን ጊዜአዊ ነው" (ዘይቤአዊና ግነት ተመልከት)

ሁሉ ወደ አንድ ቦታ ይሄዳል
ይህ ማለት ሁሉም ሰውና ሁሉም እንስሳት ይሞታል ይበሰብሳልም አፈርም ይሆናል። ተርጓሚ "ሁሉም ነገር ይሞታል ወደ አንድ ቦታም ይሄዳል" አፈር

Ecclesiastes 3:21

ነፍስ ..... ወደ ምድር እንደምትወርድ የሚያውቅ ማነው?
ፀሐፊው የግነት ጥያቄን ሰዎችም እንስሳትም ከሞቱ በኋላ በእርግጥ ምን እንደሚሆን የሚያውቅ ማንም እንደሌለ አፅንኦት ለመስጠት ነው። ጥያቄው በዐረፍተ-ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "ነፍስ ወደ ምድር..... ማንም የሚያውቅ የለም" (የግነት ጥያቄ ተመልከት)

ደስ ከሚለው በቀር ሌላ
የመክብብ 3:12 ትርጉም ተመልከት

ከእርሱ በኋላስ የሚሆነውን ያይ ዘንድ የሚያወጣው ማን ነው?
ፀሐፊው ይህን የግነት ጥያቄ የሚሆነው ነገር ከሞት በኋላ የሚያይ ማንም የለም ለሚለው አፅንኦት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ-ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "ከእኛ መካከል ከሞት በኋላ ምን እንደሚያጋጥመን ማንም የሚያውቅ የለም" (የግነት ጥያቄ ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 እንደገና ከፀሐይ በታች ስለሚደረገው ግፍ ሁሉ አሰብሁ። የሚጨቆኑትን ሰዎች ዕንባ ተመልከቱ። የሚያጽናናቸውም የለም። በጨቋኞቻቸው እጅ ኃይል አለ፥ ነገር ግን የተጨቆኑት ሰዎች አጽናኝ የላቸውም። **2** ስለዚህ ካሉት የሞቱት፥ እስካሁን በሕይወት ካሉት ቀደም ሲል የሞቱት ይሻላሉ አልሁ። **3** ሆኖም ከሁለቱ የሚሻለው ያልኖረው፥ ከፀሐይ በታች የሚደረገውን ክፉ ድርጊት ያላየው ነው። **4** ከዚያም የትኛውም ጥረትና የጥበብ ሥራ ባልንጀራውን ለቅንዓት እንደሚያነሣሣው አየሁ። ይህም ደግሞ እንፋሎትና ንፋስን ለማገድ መሞከር ነው። **5** ሞኝ ሰው እጁን አጣምሮ ይቀመጣል፥ አይሠራምም፥ ስለዚህ የራሱ ሥጋ ምግቡ ነው። **6** ንፋስን ለማገድ በመሞከር ከሚገኝ ሁለት እፍኝ ይልቅ በጥሞና የተሠራ አንድ እፍኝ ይሻላል። **7** ከዚያም እንደገና ስለሚበልጠው ከንቱነት፥ ከፀሐይ በታች በይበልጥ ተንኖ ስለሚጠፋው እንፋሎት አሰብሁ። **8** ብቻውን የሆነ አንድ ሰው አለ። ወንድ ልጅም ሆነ አባት አንድም የለውም። ለሚሠራው ሁሉ ማለቂያ የለውም፥ ዓይኖቹም ባገኘው ብልጽግና አይረኩም። እርሱም፥ "የምለፋው ለማን ነው? ራሴንስ ከደስታ የማርቀው ለምንድነው?" ብሎ ይደነቃል። ይህ የከፋ ሁኔታ ደግሞም እንፋሎት ነው። **9** ከአንድ ሰው ይልቅ ሁለቱ የተሻለ ሥራ ይሠራሉ፤ በጋራ ለሥራቸው የተሻለ ገቢ ማግኘት ይችላሉ። **10** አንደኛው ቢወድቅ ሌላኛው ጓደኛውን ሊያነሣው ይችላልና። በመሆኑም በወደቀ ጊዜ የሚያነሣው ካልኖረ ብቸኛውን ሰው ሀዘን ይከተለዋል። **11** ሁለቱ አብረው ቢተኙ ለሞቃቸው ይችላል፥ ብቻውን ቢሆን ግን እንዴት ለሞቀው ይችላል? **12** አንድ ሰው ብቻውን ሊሸነፍ ይችላል፥ ሁለቱ ግን ጥቃቱን መመከት ይችላሉ። በሦስት የተገመደ ገመድ ቶሎ አይበጠስም። **13** ማስጠንቀቂያዎችን እንዴት መስማት እንዳለበት ከማያውቅ ሞኝ ሽማግሌ ንጉሥ ይልቅ ድሃ፥ ነገር ግን ጥበበኛ የሆነ ወጣት ይሻላል። **14** ወጣቱ ከወህኒ ወጥቶ ቢነግሥ ወይም በሀገሩ በድህነት ተወልዶ ቢያድግም ይህ አውነት ነው። **15** ይሁንና ከፀሐይ በታች ሕያው የሆነና የሚንቀሳቀሰው ሁሉ ራሳቸውን ንጉሥ ሆኖ ለተነሣው ለሌላው ወጣት ሲያስገዙ አየሁ። **16** አዲሱን ንጉሥ መታዘዝ ለሚፈልገው ሕዝብ ሁሉ መጨረሻ የለውም፥ በኋላ ላይ ግን ብዙዎቹ አያመሰግኑትም። በርግጥ ይህ ሁኔታ እንፋሎት፥ ንፋስንም ለማገድ መሞከር ነው።

Ecclesiastes 4:1

ከፀሐይ በታች
ይህ በምድር ላይ ስለተደረጉት ነው። የመክብብ 1:3 ትርጉም ተመልከት ተርጓሚ "ከፀሐይ በታች"

እነሆም.....እንባ
“ተመለከትኩ አየሁም”

የተገፉ ሰዎች እንባ
እዚህ ጋር እንባ ማልቀስን ይገልፃል። ተርጓሚ “የተገፉ ሰዎች ያለቅሱ ነበር”

በሚገፉአቸው እጅ ኃይል ነበረ
ይህ ማለት ገፊዎቻቸው ኃያል ነበሩ ማለት ነው። እዚህ ጋር “እጅ” የያዘውን ይወክላል። ተርጓሚ “ገፊዎቻቸው ኃያል (ኃይለኛ) ነበሩ”

Ecclesiastes 4:2

እስከ ዛሬ በሕይወት ካሉት
በሕይወት የሚለው ቃል በሕይወት ያሉትን ይወክላል። እስከ ዛሬ የሚለው ሐረግ ደግሞ አሁንም በሕይወት ያሉትን ይወክላል። ተርጓሚ “እስከ ዛሬ በሕይወት ያሉትን ሰዎች”

ከሁለቱ ይልቅ ገና ያልተወለደው.....ይሻላል “ገና ያልተወለደው ከሁለቱ ይሻላል” ከእነዚህም ከሁለቱ
ይህ ሐረግ የሞቱትንና በሕይወት ያሉትን ይገልፃል። ተርጓሚ “ሁለቱም እነዚህ የሞቱትም እነዚህ በሕይወት ያሉት”

ከፀሃይ በታች
ይህ በምድር የተደረጉትን ይገልጻል (ይወክላል) የመክብብ 1:3 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ “በምድር ላይ” (ፈሊጣዊ ተመልከት)

Ecclesiastes 4:4

በባልንጀራውም ዘንድ ቅንዓት .....አየሁ
ቅንአት የሚለው ቃል እንደ ቅፅል ተገልጾ ይሆናል። ተርጓሚ “ባልንጀራውን ቀናተኛ አደረገ” (ረቂቅ ስም ተመልከት)

በባልንጀራውም ዘንድ ቅንዓት

1. የጎረቤት ባልንጀራ፡ በጎረቤት ባልንጀራውን ንብረት ይሆናል
2. የጎረቤት ባልንጀራ ፡በጎረቤቱ የእኛ ጥበብ ይሆናል

ከንቱ ንፋስንም እንደመከተል ነው
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች ሲሆኑ እርባና ቢስ ስለሆኑ ነገሮች አጽንኦት የሚሰጥ ሀሳብ ነው። (ተመሳሳይ ተመልት)

ከንቱ
“ተን” ፀሃፊው እርባና ቢስና ትርጉም የሌላቸው ነገሮች ተን (ከንቱ) እንደሆኑ ይናገራል የመክብብ 1:14 ትርጉምን ተመልከት :: ተርጓሚ እንደ ከንቱ እርባና ቢስ ወይም ትርጉም የለሽ (ዘይቤአው ተመልከት)

ነፋስን እንደመከተል
ፀሃፊው ሰዎች የሚያደርጉት ሁሉ ነፋስን ለመቆጣጠር እንደ መሞከር እርናባ ቢስ መሆኑን ይናገራል የመክብብ 1:14 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ “ነፋስን ለመቆጣጠር እንደመሞከር እርባና ቢስ ነው” (ዘይቤአዊ ተመልከት)

Ecclesiastes 4:5

ሰነፍ እጆቹን ኮርትሞ ይቀመጣል
“እጅን ማኮራተም” የስንፍና ምልክትና በሌላ አባባል ይህ ሰው ስራ ለመስራት ፈቃደኛ አይደለም ማለት ነው። ተርጓሚ “ሰነፍ ለመስራት ፈቃደኛ አይደለም” (ተምሳሌታዊ ድርጊትና ተመሳሳይ ተመልከት)

የገዛ ሥጋውንም ይበላል
ይህ ሰውን የራሱን ስጋ እንደሚበላ ያክል እራሱን ያጠፋል ማለት ነው። ተርጓሚ “በውጤቱም ለራሱ ጥፋት ምክኒያት ይሆናል።” ወይም “በውጤቱም እራሱን ያጠፋል” (ዘይቤአዊ ተመልከት)

እጅ ሙሉ
“ትንሽ መጠን”

ሁለት እጅ ሙሉ
“በጣም ብዙ” የተገኘ ትርፍን ያስረዳል። ተርጓሚ “ሁለት እጅ ትርፍ” ወይም “በጣም ብዙ ትርፍ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ነፋስን በመከተል
ፀሓፊው የሚናገረው ሰዎች የሚያደርጉት ሁሉ ነፋስን ለመቆጣጠር እንደ መሞከር እርባና ቢስ ነው። የመክብብ 1:14 ትርጉምን ተመልከት ። ተርጓሚ “እሱም ነፋስን ለመቆጣጠር እንደመሞከር እርባና ቢስ ነው።” (ዘይቤአዊ ተመልከት)

Ecclesiastes 4:7

ከንቱን ነገር(ከንቱነት)
“ያለ ትርፍ እርባና ቢስ መሆን”

ደግሞ ከንቱ
“አሁንም ደግሞ የሚጠፋ ተን” ፀሓፊው እርባና ቢስና ትርጉም የሌላቸው ነገሮች ከንቱ እንደሆኑ ይናገራል። የመክብብ 1:14 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ“ አሁንም እንደ ከንቱ እርባና ቢስ የሆኑ ነገሮች” ወይም “አሁንም ትርጉም የለሽ ነገሮች።” (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

ከፀሃይ በታች
ይህ በምድር ላይ የተደረጉ ነገሮችን ይገልፃል። የመክብብ 1:3 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ “በምድር ላይ” (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ልጅም ሆነ ወንድም የለውም
ይህ ሰው ቤተሰብ የለውም ተርጓሚ “እሱ ቤተሰብ የለውም”

ዓይኖቹ.....አይጠግቡም
ይህ አንድ ሙሉ ሰው ለምኞቱ አፅንኦት ለመስጠት በዓይኖቹ ይወከላል። ተርጓሚ “እሱ አልረካም/ አልጠገበም”

ለማን እደክማለሁ ሰውነቴንስ መልካሙን ነገር ለምን እነፍጋታለሁ?
እኔ በጣም ተግቼ ሰውነቴን ካላስደሰትኩ ትርፍ የሚያገኘው ማን ነው?

ከንቱ
ፀሓፊው እርባና ቢስና ትርጉም የሌላቸው ነገሮች ከንቱ እንደሆኑ ይናገራል። የመክብብ 1:14 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ “እንደ ከንቱ እርባና ቢስ” ወይም “ትርጉም የለሽ” (ዘይቤአዊ ተመልከት)

Ecclesiastes 4:9

አንዱ ብቻውን ሆኖ በወደቀ ጊዜ.....ወዮለት
ወዮለት የሚለው ቃል መከራ እንደሚከተለው ለማሳየት ነው። ተርጓሚ “አንዱ ብቻውን ሆኖ በወደቀ ጊዜ ሀዘንተኛ ነው(ይሆናል)”

ሁለቱ በአንድነት ቢተኙ ይሞቃቸዋል
ፀሓፊው የሚናገረው ሁለት ሰዎች በቀዝቃዛ ሌሊት አንዱ ሌላኛውን ያሞቃል ተርጓሚ “ሁለት ሰዎች በሌሊት አብረው ቢተኙ ሊሞቁ ይችላሉ”

አንድ ብቻውን ግን እንዴት ይሞቃል?
ይህ ስለተኛ ሠው ይገልፃል። ፀሃፊው ይህን የግነት ጥያቄ የተጠቀመው አንድ ሰው ብቻውን ቢተኛ እንደማይሞቀውና ሁለት ሲሆኑ ግን አንዱ ሌላኛውን ሊያሞቀው እንደሚችል አፅንኦት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ በ ዓረፍተ ነገር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ሰው ብቻውን ሲሆን አይሞቀውም” ወይም “ብቻውን የሚተኛ ሰው አይሞቀውም” (የግነት ጥያቄ ተመልከት)

Ecclesiastes 4:12

አንዱም አንዱን ቢያሸንፍ
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ “አንድ ሰው ብቻውን የሆነውን ሰው ሊያሸንፍ ይችላል።”

ሁለቱ(ሁለቱ ግን)
“ግን ሁለት ሰዎች”

ይቆማሉ
“እራሳቸው ከጥቃት ይከላከላሉ”

በሦስት የተገመደ ገመድ
ይህ ልክ በሦስት ድርብ እንደተገመደ ገመድ ሦስት ሰዎች በአንድነት ሲሆኑ ጠንካራ እንደሆኑ ይናገራል። ተርጓሚ “ልክ በሦስት ድርብ እንደተገመደ ገመድ ሶስት ሠዎች ጠንካራ ናቸው ።” (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

በሦስት የተገመደ ገመድ ፈጥኖ አይበጠስም
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “በሦስት ድርብ የተገመደ ገመድ ሠዎች በቀላሉ አይበጥሱትም”

Ecclesiastes 4:13

ጠቢብ ብላቴና
“ጢብ ወጣት”

ከእንግዲህ ወዲህ ከማያውቅ
እዚህ ጋር ማወቅ ፈቃኝነትን ይወክላል። ተርጓሚ “ከእንግዲህ ወዲያ ፈቃደኛ ያልሆነ”

ተግሳፅን
“በተግሳጽ ስር ከሆነ በኋላ”

በመንግስቱ አገር ዳግም ችግረኛ ሆኖ ቢወለድ
ይህ ማለት ችግረኛ ወላጆች ነበሩት ማለት ነው። ተርጓሚ አንድ ቀን ከሚመራው ችግረኛ ወላጆቹ ከሚኖሩበት ምድር ተወለደ።

Ecclesiastes 4:15

x
ከጠቢቡን ብላቴና ይልቅ ጠቢብ ላይሆን ከሚችል የንጉስ ልጅ መረጡ

የሚሄዱትን ሕያዋን
ሕያዋን የሚለው ቃልና የሚሄዱትን የሚለው ቃል በመሰረቱ ተመሳሳይ ነገር ሲሆኑ ተጣምረው በሕይወት ያሉትን ሰዎች አፅንኦት ለመስጠት ነው።

ከፀሃይ በታች
ይህ በምድር ላይ የተደረጉትን ይገልፃል። የመክብብ 1:3 ትርጉምን ተመልከት ። ተርጓሚ “በምርድ ላይ” (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ሕዝብ ሁሉ አይቆጠሩም
ይህ የተጋነነ ንግግር ብዙ ቁጥር ያለውን ህዝብ እንደሆነ አፅንኦት ለመስጠት ነው። ተርጓሚ “እጅግ በጣም ብዙ ህዝብ አሉ”

ከንቱ ንፋስንም እንደመከተል
እነዚህ ሐረጎች ዘይቤአዊ ሲሆኑ እርባና ቢስና ከንቱ ስለሆኑ ነገሮች አፅንኦት የሚሰጥ ሀሳብ ነው ። (ዘይቤአዊ ተመልከት)

ከንቱ
“ተን” ፀሃፊው እርባና ቢስና ትርጉም የሌላቸው ነገሮች ከንቱ ከንቱ እንደሆኑ ይናገራል። የመክብብ 1:14 ትርጉም ተመልከት። ተርጓሚ እንደ ከንቱ እርባና ቢስ ወይም ትርጉም የለሽ (ዘይቢአዊ ንግግር ተመልከት)

ነፋስን እንደመከተል
ፀሃፊው ሰዎች የሚያደርጉት ሁሉ ነፋስን ለመቆጣጠር እንደመሞከር እርባና ቢስ መሆኑን ይናገራል። የመክብብ 1:14 ትርጉም ተመልከት ተርጓሚ “ነፋስን ለመቆጣጠር እንደመሞከር እርባና ቢስ ነው።” (ዘይቤአዊ ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 5

1 ወደ እግዚአብሔር ቤት በምትሄድበት ጊዜ ጠባይህን ተቆጣጠር። ለመስማት ወደዚያ ሂድ። ሞኞች ክፉ መሥራታቸውን ሳያውቁ ከሚያቀርቡት መሥዋዕት ይልቅ መስማት ይበልጣል። **2** ለመናገር እጅግ አትፍጠን፥ በእግዚአብሔር ፊት የትኛውንም ጉዳይ ለማቅረብ ልብህ እጅግ አይፍጠን። እግዚአብሔር በሰማይ ነው፥ አንተ ግን በምድር፤ ስለዚህ ቃልህ ጥቂት ይሁን። **3** የምትሠራው ከበዛና ሃሳብ ከሆነብህ፥ ክፉ ህልም ሊገጥምህ ይችላል። ቃልህ ብዙ ሲሆን ብዙ የሞኝነት ነገርም ትናገራለህ። **4** ለእግዚአብሔር በምትሳልበት ጊዜ ከመፈጸም አትዘግይ፥ እግዚአብሔር በሞኞች ደስ አይለውምና። **5** የተሳልከውን ፈጽመው። የተሳሉትን ካለመፈጸም ያለመሳል ይሻላል። **6** አንደበትህ ሰውነትህን ለኃጢአት እንዲያነሣሣው አትፍቀድለት። ለካህኑ መልዕክተኛ፥ "ያ ስዕለት ስሕተት ነበረ" አትበል። በሐሰት በመሳል እግዚአብሔርን ለምን ታስቆጣዋለህ፥ የእጅህንስ ሥራ እንዲያጠፋ እግዚአብሔርን ለምን ታነሣሣዋለህ? **7** በብዙ ሕልም ውስጥ፥ በብዙም ቃል ውስጥ እንፋሎት የሆነ ከንቱነት አለ። ስለዚህ እግዚአብሔርን ፍራ። **8** በግዛትህ ውስጥ ድሃው ሲበደል፥ ፍትህንና መብቱን ሲነጠቅ በምታይበት ጊዜ፥ ማንም አላወቀም ብለህ አትደነቅ፥ ምክንያቱም ከሥራቸው ያሉትን የሚቆጣጠሩ አለቆች አሉ፥ በእነርሱም ላይ እንኳን የበላይ አለቆች አሉ። **9** በአጠቃላይ የምድሪቱ ምርት ለሁሉም ነው፥ ንጉሡ ራሱም ምርቱን ከእርሻ ይወስዳል። **10** ማንም ብርን የሚወድ በብር አይረካም፥ ማንም ብልጽግናን የሚወድ ሁልጊዜ ተጨማሪውን ይፈልጋል። ይህም ደግሞ እንፋሎት ነው። **11** ሀብት ሲበዛ በእርሱ የሚጠቀሙ ደግሞ ይበዛሉ። ባለቤቱ በዓይኖቹ ከማየቱ በስተቀር ሀብቱ ምን ይጠቅመዋል? **12** ብዙም ሆነ ጥቂት ቢበላ፥ የሚሠራ ሰው እንቅልፉ ጣፋጭ ናት፥ የባለጸጋው ሀብት ግን እንቅልፉን ይነሳዋል። **13** ከፀሐይ በታች ያየሁት እጅግ የከፋ ነገር አለ፡ ይኸውም በባለሌቱ የተከማቸው ሀብት መጥፊያው ሲሆን ነው። **14** ባለጸጋው በክፉ አጋጣሚ ሀብቱን በሚያጣበት ጊዜ ለልጁ፥ እርሱ ላሳደገው፥ በእጁ የሚተውለት አይኖረውም። **15** ሰው ከእናቱ ማኅፀን ራቁቱን እንደ ተወለደ፥ ራቁቱን ደግሞ የምድሩን ሕይወት ይሰናበታል። ከሥራው አንዱን በእጁ መውሰድ አይችልም። **16** ሌላው እጅግ ክፉ ነገር፥ ሰው እንደ መጣ እንዲሁ ደግሞ መሄዱ ነው። ስለዚህ ለንፋስ በመሥራት ሰው የሚያገኘው ትርፍ ምንድነው? **17** በዘመኑ ሁሉ በጨለማ ይበላል፥ በህመምና በቁጣ በብዙ ይበሳጫል። **18** ተመልከቱ! እኔ እግዚአብሔር በሰጠን በምድር ሕይወታችን ከፀሐይ በታች በምንደክምበት፥ መልካምና ተስማሚ ሆኖ ያገኘሁት፥ መብላት፥ መጠጣትና ባገኘነው በሥራችን ውጤት ሁሉ መደሰትን ነው። ይህ የሰው ዕድል ፈንታው ነው። **19** እግዚአብሔር ለማንኛውም ሰው ሀብትንና ባለጸግነትን፥ ድርሻውን የሚያገኝበትን ችሎታና በሥራው መደሰትን መስጠቱ ይህ የእግዚአብሔር ሥጦታ ነው። **20** ለመሥራት በሚያስደስተው ነገር እግዚአብሔር ባተሌ ስለሚያደርገው፥ የሕይወት ዘመኑን እምብዛም አያስባቸውም።

Ecclesiastes 5:1

እግርህን ጠብቅ
እዚህ ጋር “እግርህን” የሚለው የአንድ ሠው ባህሪን ሲገልጽ ዘይቤአዊ ንግግር ነው። ተርጓሚ “እንዴት እራስህን እንደምትመራ ተጠንቀቅ”

Ecclesiastes 5:2

አትፍጠን.....ልብህ አይቸኩል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ሲሆኑ እግዚአብሄርን ስለሆነ ጉዳይ ከማናገርህ በፊት ማሰብ እንዳለብህ አፅንኦት ለመስጠት ነው። (ከመናገርህ በፊት ማሰብ እንዳለብህ አፅንኦት ለመስጠት)

አፍህ.....ይናገር ዘንድ
እዚህ ጋር በአፍህ የሚለው ቃል ስለሚናገር ሰው አፅንኦት እና ገለፃ ለመስጠት ነው ። ተርጓሚ “ለመናገር”

ልብህ አይቸኩል
እዚህ ጋር ግለሰብ በስሜቱና ምኞቱ አፅንኦት ለመስጠት “በልቡ” ተወክሏል። ተርጓሚ “አታድርግ” ወይም “ተው”

ቃልህ ጥቂት ትሁን
“ብዙ አትናገር(አትበል)”

Ecclesiastes 5:4

ሰነፎች ደስ አይሰኙምና ለእግዚአብሔር.....ትፈፅመው ዘንድ አትዘግይ
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ጋር ያደረግነውን ቃል አለመፈፀም ሞኝነት መሆኑን ነው ተርጓሚ እግዚአብሔር በሰነፎች ደስ ስለማይሰኝ የገባኸውን ቃል ከማድረግ አትስነፍ

Ecclesiastes 5:6

ሥጋህን በኃጢአት እንዲያስተው ለአፍህ አርነት አትስጥ
እዚህ ጋር "አፍህ" የሚለው ቃል ግለሰብን ሲወክል ሰውየው ደግሞ በሥጋው ተወክሏል። ተርጓሚ "የተናገርከው ኃጢአት እንዲሆን አታድርግ"

እግዚአብሔር በቃል ይቆጣ ዘንድ የእጅህንም ሥራ ያጠፋ ዘንድ ስለምን ትሻለህ?
ፀሐፊው ይህን የግነት ጥያቄ የማትፈፅመውን ቃል መስጠት ሞኝነት መሆኑን አፅንኦት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ-ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ በሐሰት ቃል እግዚአብሔርን ማስቆጣትና የእጅህን ሥራ እንዲያጠፋ ማድረግ ሞኝነት ይሆናል። (የግነት ጥያቄ ተመልከት)

የእጅህን ሥራ ያጠፋ ዘንድ
እዚህ ጋር ግለሠቡ በ"እጅ" ተወክሏል ተርጓሚ "የሠራኸውን ሁሉ ያጠፋል" ብዙ ህልም ባለበት ዘንድ እንዲሁም ደግሞ ብዙ ቃል ባለበት ስፍራ ብዙ ከንቱ ነገር አለ። ፀሐፊው ነገሮት ከንቱ እንደሆኑ እርባና ቢስና ትርጉም የሌላቸው መሆኑን ይናገራል። የመክብብ 1:14 ትርጉም ተመልከት። ተርጓሚ "ብዙ ህልምና ብዙ ቃል እንደ ከንቱ እርባና ቢስ ናቸው።"

Ecclesiastes 5:8

ድሆች ሲገፉ .....ሲነጠቁ
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "ሰዎች ድሆችን ሲገፉና ሲነጥቁ"

ድሆች
ይህ ችግረኛ ሠዎችን ይወክላል ተርጓሚ "ድሆች የሆኑ" ወይም "ችግረኛ"

ፍርድና ፅድቅ
ሁለቱ ቃላት በመሠረቱ ተመሣሣይ ሲሆኑ ሠዎች ስለባቸው ሁኔታ ይናገራል። ተርጓሚ "ፍትሐዊ ፍርድ"

በዚህ ነገር አትደነቅ
ሰዎች ስላሉ አትደነቅ (አትገረም)"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሌሎች ክፉ ይላሉና
በሰዎች ላይ ሥልጣን ያላቸው ሌሎች ሰዎች አሉ። ተርጓሚ "ምድሩ የሚያመርተው መብል ... ከምድሩ ምርት (እህል)" (ረቂቅ ሥራ ተመልከት)

Ecclesiastes 5:10

ከንቱ
ፀሐፊው እርባና ቢስና ትርጉም የሌላቸው ነገሮች ከንቱ እንደሆኑ ይናገራል። የመክብብ 1:14 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ" እንደ ከንቱ እርባና ቢስ ወይም ትርጉም የለሽ" (ዘይቤአዊ ተመልከት)

ሀብት ሲበዛ
ሀብት የሚለው ቃል እንደ ቅፅል ሊገለፅ ይችላል ተርጓሚ "ሰው በጣም ሀብታም በሆነ መጠን"

የሚበሉት ይበዛሉ
አማራጭ ትርጉሞች 1) "እንዲሁ ሰው ብዙ ገንዘብ ያጠፋል (ያወጣል) 2) "እንዲሁ ሀብቱን የሚበሉት ሰዎች ይበዛሉ።"

የሚበሉት
ይህ የሚበሉት ያክል ሰዎች ሀብት ሊያጠፉ (ሊያወድሙ) ተርጓሚ "የሚጠቀሙት" (ዘይቤአዊ ተመልከት)

ሀብቱን በዓይኑ ብቻ ከማየት በቀር ለባለቤቱ ምን ይጠቅመዋል?
ፀሐፊው ይህን የግነት ጥያቄ ባለሀብቱ ከሀብታቸው ምንም እንደ ማያተርፉ አፅንኦት ለመስጠት ይጠቀማል። ጥያቄው በዐረፍተ-ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "ባለሀብቱ አንድ የሚያገኘው ጥቅም ሀብቱን በዓይኑ መመልከት ብቻ ነው።"

Ecclesiastes 5:12

የሠራተኛ እንቅልፉ ጣፋጭ ነው
ይህ የግለሰብ እንቅልፉ የሚበላው ጣፋጭ እንደሆነ ያክል እንቅልፉም የሞላና ሰላማዊ መሆኑን የናገራል። ተርጓሚ "የሠራተኛ እንቅልፍ ሰላማዊ ነው።" (ዘይቤአዊ ተመልከት)

እጅግ ወይም ጥቂት ቢበላ
"እጅግ ብዙ ምግብ ወይም ጥቂት ምግብ ቢበላም"

የባለጠጋ ጥጋብ ግን እንቅልፉን ይከለክለዋል።
የባለጠጋ ጥጋብ ግን እንቅልፉን ይከለክለዋል። ይህ ባለጠግነት እንቅልፍ እንደሚከለክለው ሰው ሊከለክለውና መተኛት አለመቻሉንና ስለገንዘቡም መጨነቁን ይናገራል። ተርጓሚ "ባለጠጋ ግን ሥለ ገንዘቡ ስለሚጨነቅ እንቅልፍ አይተኛም"

Ecclesiastes 5:13

ከፀሐይ በታች
ይህ በምድር ላይ የተደረጉትን ይገልፃል። የመክብብ 1:3 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ በምድር ላይ

በባለቤቱ ዘንድ የተቆጠበች ባለጠግነት
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ባለቤቱ ባለጠግነት ቆጠበ (አከማቸ)

በክፉ ነገር
አማራጭ ትርጉሞች 1) በመጥፎ ዕድል 2) በመጥፎ ውል

ልጅንም ቢወልድ በእጁ ምንም የለውም
እዚህ ጋር በእጁ የሚለው ቃል ባለቤትነት ይወክላል (ያሳያል) ። ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "ለልጅ ምንም ይዞታ አልተወም (አላስቀመጠም) "

Ecclesiastes 5:15

ከእናቱ ሆድ ራቁቱን እንደወጣ እንዲሁ እንደ መጣሁ ይመስላል
ይህ ሰው ሲወለድ ራቁቱን እንደሆነ ያሳያል። "ራቁቱን የሚለው ቃል ያለልብስ መሆንን ብቻ ሳይሆን ሰዎች ሲወለዱ ምን ነገር (ይዞታ) እንደሌላቸው አፅንኦት ለመስጠት ነው። ተርጓሚ "ሰው ሲወለድ ራቁቱንና ምንም ነገር እንደሌለው ይህን ሕይወት እንዲሁ ይተዋል (ይሰናበታል)። "(ዘይቤአዊ ተመልከት)

ከእናቱ ሆድ .....እንደ ወጣ
"እንደ ተወለደ

ይመለሳል
"ይህ መሞትን ይገልፃል" ተርጓሚ "ይሞታል"

ከጥረቱም በእጁ ሊወስድ የሚችለውን ምንም አያገኝም
እዚህ ጋር የሰው ሀብት (ይዞታው) በጥረት ተወክሏል። ተርጓሚ "ከሀብት አንድም ነገር ከእርሱ ጋር አይሄድም"

እንደ መጣ እንዲሁ ይሄዳል
ይህ ሰው እንደሚወለድና እንደሚሞት የሚገልፅ ሲሆን ከቀድሞው ቁጥር ጋር ተመሣሣይ ሀሳብን ይገልፃል። ይህ ወንድንም ሴትንም ይወክላል። ተርጓሚ ሰዎች ወደ ዚህ ምድር ምንም ይዘው እንዳልመጡ ሁሉ እንዲሁ ሲሞቱና ይህን አለም ሲሰናበቱ ምንም ነገር ይዘው አይሄዱም።"

ድካሙም ለነፍስ ከሆነ ጥቅሙ ምንድን ነው
ፀሐፊው ለነፍስ ከመድከም ምንም ትርፍ እንደማይገኝ አፅንኦት ለመስጠት የግነት ጥያቄን ይጠቀማል። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ-ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "ለነፍስ ከመስራት ማንም ትርፍ የሚያገኝ የለም" (የግነት ጥያቄን ተመልከት)

ድካሙ ለነፋስ ከሆነ
ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉ 1) ይህ ነፋስን ለመቆጣጠር እንደሚሞክር ሰው ዘላቂ ያልሆነ ትርፍ በቀላል ይገልፃል ተርጓሚ "ነፋስን መከተል መሞከር" ወይም "ነፋስን እንደመከተል እርባና ቢስ ድካም (ሥራ) "2) ይህ የሚያመለክተው ሰው ለትርፍ የሚተነፍሰውን አየር ብቻ ይቀበላል።"

ዘመኑን ሁሉ በጨለማ ..... ነው።
ይህ በጨለማ ስላለና በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ስለሚያዝን ሰው ይናገራል። እዚህ ጋር "ጨለማ" ኃዘንና ብስጭትን ይወክላል። "ተርጓሚ እርሱ ሕይወቱን በኃዘንና በብስጭት ያሳልፋል። " (ዘይቤአዊ ተመልከት)

ዘመኑን
እዚህ ጋር "ዘመን" የሰውን ሕይወት ይወክላል። ተርጓሚ "ሕይወቱን"

በብስጭት በደዌና በቁጣ ነው
"ብስጭት" ና "ደዌ" በቅፅል ሊገለፁ ይችላሉ። ተርጓሚ እጅግ በጣም መንከራተት ትልቅ ህመምና ብስጭት"

Ecclesiastes 5:18

እነሆ
ፀሐፊው በቀጣይ ስለሚናገረው የአንባቢውን ቀልብ ለመሳብ ይህን ቃል ይጠቀማል። ተርጓሚ "ትኩረት ስጥ" ወይም "አዳምጥ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እኔ ያየሁት መልካምና የተዋበ
እዚህ ጋር "መልካምና" "የተዋበ" የሚሉት ቃላት በመሰረቱ አንድ ናቸው። ሁለተኛው የመጀመርያውን ትርጉም ያሰፋዋል። ተርጓሚ "እኔ ያየሁት ከሁሉ የተሻለ ነገር ነው።"

ከፀሐይ በታች
ይህ በምድር ላይ የተደረጉትን ይገልፃል የመክብብ 1:3 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ "በምድር ላይ"

ሰው እግዚአብሔር በሰጠው በሕይወቱ ዘመን ሁሉ
ይህ ፈሊጣዊ ነው። ተርጓሚ "እግዚአብሔር መኖር እስከፈቀደልን ድረስ"

ሰው ..... ይህ እድል ፈንታው ነውና
አማራጭ ትርጉሞች 1) ሰው .... ይህ ብድራቱ ነውና። 2) ሰው ሊከውናቸው (ሊያደርጋቸው) የተፈቀደለት ነውና።

Ecclesiastes 5:19

ባለጠግነትና ሀብትን
እነዚህ ሁለት ቃላት በመሰረቱ ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው ገንዘብና ሠው ገንዘብ የሚገዛቸውን ነገሮች ሁሉ ይወክላሉ።

እድል ፈንታውን ይወስድ ዘንድ
"የተሰጠውን ሊቀበል።"

እርሱ የሕይወቱን ዘመን እጅግ አያስብም
እዚህ ጋር "እርሱ" የሚለው ቃል እግዚአብሔር ስጦታ የሰጠውን ሰው ይወክላል። "አያስብም" የሚለው ቃል ፈሊጣዊ ነው። ተርጓሚ "እርሱ አያስታውስም" ወይም "እርሱ አያስብም"

የሕይወቱን ዘመን
ይህ በሕይወቱ ዘመን የተከሰቱትን ነገሮች ይወክላል። ይህ በግልፅ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "በሕይወቱ ዘመን የተከሰቱትን ነገሮች ሁሉ" (ፈሊጣዊ ተመልከት)

ማሰልጠኑ
"ማጨናነቁ (ሥራ ማብዛቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 6

1 ከፀሐይ በታች ያየሁት ክፉ ነገር አለ፥ እርሱም ለሰዎች ከባድ ነው። **2** ለራሱ የሚመኘውን አንዳች ላያጣ እግዚአብሔር ሀብትን፥ ባለጠግነትንና ክብርን ይሰጠዋል፥ የሚደሰትበትን ችሎታ ግን አይሰጠውም። ይልቁንም እነዚህን ነገሮች ሌላው ሰው ይጠቀምባቸዋል። ይህ እንፋሎት፥ ክፉ ስቃይም ነው። **3** ሰው አንድ መቶ ልጆች ቢወልድና ብዙ ዘመን ቢኖር፥ የዕድሜው ዘመን ቢረዝም፥፥ ልቡ ግን በመልካም ነገር ባይረካ፥ በክብርም ባይቀበር፥ ከዚህ ሰው ይልቅ ሞቶ የተወለደ ሕጻን ይሻላል አልሁ። **4** እንዲህ ያለው ሕጻን እንኳን በከንቱ ይወለዳል በጨለማም ይሄዳል፥ ስሙም አይታሰብም። **5** ይህ ሕጻን ፀሐይን ባያይ ወይም ምንም ባያውቅ፥ ያኛው ባይኖረውም ለዚህኛው ዕረፍት አለው። **6** ሰው ሁለት ሺህ ዓመት ያህል እንኳን ቢኖር በመልካም ነገሮች ግን መደሰትን ባያውቅ፥ እንደ ሌላው ሁሉ ወደዚያው ስፍራ ይሄዳል። **7** የሰው ሁሉ ሥራ አፉን ለመሙላት ነው፥ ፍላጎቱ ግን አይሞላም። **8** በርግጥ ከሞኙ ይልቅ የጠቢብ ሰው ብልጫው ምንድነው? ድሃ በሌሎች ሰዎች ፊት እንዴት መመላለስ እንዳለበት ቢያውቅ ምን ብልጫ አለው? **9** በምኞት ከመቅበዝበዝ በዓይን አይቶ መርካት ይሻላል፥ ይህም ደግሞ እንፋሎትና ንፋስን ለማገድ መሞከር ነው። **10** ለነበረው ሁሉ ቀደም ሲል ስያሜ ተሰጥቶታል፥ ሰው ምን እንደሚመስልም አስቀድሞ ታውቋል። ስለዚህ በሁሉ ላይ ብርቱ ፈራጅ ከሆነው ጋር መከራከር አይረባም። **11** የሚነገር ቃል ሲበዛ ከንቱነትም ይበዛል፥ ታዲያ ይህ ለሰው ምን ይጠቅመዋል? **12** እንደ ጥላ በሚያልፍበት ከንቱና የተቆጠረ የሕይወት ዘመኑ ለሰው በሕይወቱ መልካም የሆነውን የሚያውቅ ማን ነው? እርሱ ካለፈ በኋላ ከፀሐይ በታች ምን ሊሆን እንዳለ ማን ሊነግረው ይችላል?

Ecclesiastes 6:1

በሰው ልጅ ላይ እጅግ የከበደ ነው ።
እዚህ ጋር ክፍት እንደሆነ ነገር ለመሸከም የከበደ ጭነት ያሳያል። ተርጓሚ "ለሰዎች መከራ ይሆናል።" (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

አልጎደለውም
ተርጓሚ "ሁሉ ነገር አለው"

እግዚአብሔር አላሠለጠነውም
"ችሎታ አልሠጠውም"

ከንቱ
ፀሐፊው እርባና ቢስና ትርጉም ስለሌላቸው ነገሮች ከንቱ (ተን) የሆኑ ያክል ይናገራል። የመክብብ 1:14 ትርጉም ተመልከት ። ተርጓሚ"ልክ እንደ ተን እርባና ቢስ" ወይም ትርጉም የለሽ" (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

Ecclesiastes 6:3

መቶ ልጆች ቢወልድ
"መቶ ልጅ ወለደ" ይህ መላምታዊ ሁኔታ ነው። ይህ የገነነም ሲሆን ከመቶ ልጆች በታች ላላቸውም ይሠራል። ተርጓሚ "ብዙ ልጆች ቢወልድ"

እጅግ ዘመንም በሕይወት ቢኖር ዕድሜውም እጅግ ዓመት ቢሆን
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሰረቱ በትርጉም አንድ ሲሆን አንድ ላይ የሆኑትም አፅንኦት ለመስጠት ነው። ተርጓሚ "ብዙ ዘመን/አመት/ ኖረ"

ነፍሱም መልካምን ባትጠግብ
ይህ ለስሜቱ አፅንኦት ለመስጠት ሲሆን በ"ነፍሱ" ይገልፃል። ተርጓሚ "በመልካም አይረካም (አይደሠትም)

መቃብርንም ባያገኝ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉሞች 1) በጭራሽ ማንም አልቀበረውም" 2) "ክብርን አላገኘውም ማንም በሥርዓት አልቀበረውም።"

ከእርሱ ይልቅ ጭንጋፍ
"ምንም ላይጠቅም የተወለደ ሕፃን (ልጅ)"

በጨለማ ይሸፈናል
x

Ecclesiastes 6:5

ሺህ አመት ሁለት ጊዜ በሕይወት ቢኖር
ይህ መላምታዊ ሁኔታ ነው። "ይህ ሰው ደስ ከተሰኘ በስተቀር ምንም ያህል ዓመት በሕይወት ቢኖር ምንም እንደማይጠቅም ለማጋነን ነው።

ሺህ ዓመት ሁለት ጊዜ
"2000" ዓመት"

ሁሉ ወደ አንድ ሥፍራ የሚሄድ .....
ይህ ማለት ማንም ሰው እንደሚሞተው ይሞታል። "ይሞታልም ሁሉም ሰው ወደ ሚሄደው ይሄዳል። "ወይም" ሁሉም ሰው ወደ መቃብር እንደሚሄድ እርሱም ይሄዳል።

Ecclesiastes 6:7

ለአፍ ነው
እዚህ ጋር በሰው አፍ ውስጥ ምግብን መጨመር መመገብን ይወክላል። ተርጓሚ "ምግብን በአፍ ለማድረግ ነው። ወይም እርሱን ለመመገብ ነው።"

ነፍሱ ግን አትጠግብም
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "ነፍሱን አያጠግብም "

ከሰነፍ ይልቅ ለጥበበኛ ጥቅም ምድር ነው ?
ፀሐፊው ጥበበኛ ከሰነፍ ይልቅ ዘላቂ ትርፍ እንደሌለው አፅንኦት ለመስጠት ነው። ይህን የግነት ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ-ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ ጠቢብ ከሰነፍ የተሻለ ጥቅም እንደሌለው ይመስላል።" (የግነት ጥያቄ ተመልከት)

በሕያዋን ፊትስ መሄድ ለሚያውቅ ለድሀ ጥቅሙ ምንድር ነው ?
ፀሐፊው ድሃ ከማንም የተሻለ ዘላቂ ትርፍ እንደሌለው አፅንኦት ለመስጠት የግነት ጥያቄን ይጠቀማል። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ-ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "በሕያዋን ፊት መሄድ ቢያውቅም ድሃ ጥቅም የለውም" (የግነት ጥያቄ ተመልከት)

መሄድ ለሚያውቅ
"እራሱን እንዴት እንደሚገዛ"

Ecclesiastes 6:9

በዓይን ማየት
ሰው እነዚህን ነገሮች ስላሉት በዓይኑ ማየት ይችላል። ተርጓሚ "ሰው ያለውን ነገር"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በነፍስ ከሚቅበዘበዝ
ይህ ሰው ስለሚፈልገው ነገር ግን የሚያገኘውን ይገልፃል። ተርጓሚ "የማያገኘውን መፈለግ"

ከንቱ ነፋስንም እንደመከተል
እነዚህ ሁለቱ ሀረጎች ዘይቤአዊ ሲሆኑ እርባና ቢስና ከንቱ ስለሆኑ ነገሮች አፅንኦት የሚሠጥ ሀሳብ ነው።(ተመሣሣይ ተመልከት) ከንቱ "ተን" ፀሐፈው እርባና ቢስና ትርጉም የሌላቸው ነገሮች ከንቱ እንደሆኑ ይናገራል። የመክብብ : 1:14፡ ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ "እንደ ከንቱ እርባና ቢስ ወይም ትርጉም የለሽ" (ዘይቤአዊ ተመልከት)

ነፋስን እንደመከተል
ፀሐፊው የሚናገረው ሰዎች የሚያደርጉት ሁሉ ነፋስን ለመቆጣጠር እንደመሞከር እርባና ቢስ ነው። የመክብብ 1:14 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ "ነፋስን ለመቆጣጠር እንደመሞከር እርባና ቢስ ነው ።"(ዘይቤአዊ ተመልክት)

የሆነው ሰው አስቀድም ተጠራ
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "ያለውን ነገር ሁሉ ሰዎች ስም ስጥተውታል (ሰይመውታል)።"

ሰውም እንደሆና ታወቀ
ይህ በገቢር መልክ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "ሰውም እንዲሆን ሰዎች አስቀድመው ያውቃሉ።"

ከሚበረታው ጋር ይፋረድ ዘንድ
"እግዚአብሔር የበረታ (የበላይ) ፈራጅ"

የሚያበዛ ብዙ ነገር
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "ሰዎች ብዙ ነገር በተናገሩ ልክ"

ከንቱን የሚያበዛ ነገር
ሰው ብዙ ባወራ ልክ የማይረባ ነገር ይናገራል። ተርጓሚ "ባወራ ልክ ቃላቱ እርባና ቢስ ይሆናሉ።" ከንቱ "ያለትርፍ ጥቅም አልባ መሆን"

ለሰው ጥቅም ምንድ ነው?
ፀሐፊው ለሠው ብዙ ማውራት ትርፍ እንደሌለው አፅንኦት ለመስጠት የግነት ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "ያ ለሠው ትርፍ የለውም"

እንደ ጥላ በሚያሳልፈው ..... ለሰው የሚሻለውን የሚያውቅ ማነው?
ፀሐፊው በእርግጥ ለሰው የሚሻለውን የሚያውቅ እንደሌለ አፅንኦት ለመስጠት የግነት ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ እንደ ጥላ በሚያልፈው ለሠው የሚሻለውን የሚያወቅ ማንም የለም። (የግነት ጥያቄ ተመልከት)

ሰው በከንቱ ወራት ቁጥርና እንደ ጥላ በሚያልፈው ዘመኑ በሕይወቱ ሳለ
ይህ ጥላ በፍጥነት እንደሚያልፍ ሁሉ ሕይወት በፍጥነት እንደምታልፍ ይናገራል። "ወራት ቁጥር" የሚለው ሀረግ የሰው ሕይወት አጭር መሆኑን አፅንኦት ለመስጠት ነው። ተርጓሚ በከንቱነቱ ዘመን እንደ ጥላ አጭር ዕድሜ ውስጥ ያልፋል።

ከእርሱ በኋላ የሚሆነውን ማን ይነግረዋል?
ፀሐፊው ሰው ከሞተ በኋላ ምን እንደሚሆን እንደማይታወቅ አፅንኦት ለመስጠት የግነት ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "ሰው ካለፈ (ከሞተ) በኋላ ማንም የሚነግረው የለም።"(የግነት ጥያቄ ተመልከት)

ከፀሐይ በታች ..... የሚሆነውን
ይህ በምድር ላይ የሆኑትን ነገሮች ይገልፃል። በመክብብ፡1፡3፡ላይ "ከፀሐይ በታች" የሚለው እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት። ተርጓሚ "በምድር ላይ የሚሆነውን"

ከእርሱ በኋላ
ይህ ለሞት የትህትና አገላለፅ ነው። ተርጓሚ "በምድር ላይ የሚሆነውን"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 7

1 ከውድ ሽቶ መልካም ስም ይሻላል፥ ከልደት ቀንም የሞት ቀን ይሻላል። **2** ወደ ግብዣ ቤት ከመሄድ ወደ ሀዘን ቤት መሄድ ይሻላል፥ በሕይወቱ መጨረሻ ሰው ሁሉ ሀዘን ይገጥመዋልና፥ ስለዚህ ሕያዋን የሆኑ ሰዎች ይህንን ልብ ማለት አለባቸው። **3** ከሣቅ ጥልቅ ሐዘን ይሻላል፥ ከፊት ሐዘን በኋላ የልብ ደስታ ይመጣልና። **4** የጠቢብ ልቡ ሐዘን ቤት ውስጥ ነው፥ የሞኞች ልብ ግን በግብዣ ቤት ውስጥ ነው። **5** የሞኞችን መዝሙር ከመስማት የጠቢብን ተግሳጽ መስማት ይሻላል። **6** ከድስጥ ሥር የሚነድ እሾህ እንደሚንጣጣ የሞኞች ሣቅ ደግሞ እንደዚሁ ነው። ይህም ደግሞ እንፋሎት ነው። **7** ቀማኛነት ጠቢቡን ሰው ያለጥርጥር ሞኝ ያደርገዋል፥ ጉቦም ልቡን ያበላሸዋል። **8** የአንድ ነገር መጨረሻ ከጅማሬው ይሻላል፤ በመንፈሳቸው ትዕግስተኞች የሆኑ ሰዎች በመንፈሳቸው ከሚታበዩት ይሻላሉ። **9** በመንፈስህ ለመቆጣት አትቸኩል፥ ቁጣ በሞኞች ልብ ያድራልና። **10** "ከእነዚህ ይልቅ ያለፉት ዘመናት ለምን ተሻሉ?" አትበል፥ ይህንን የምትጠይቀው ጥበበኛ ስለሆንክ አይደለምና። **11** ጥበብ ከአባቶቻችን የምንወርሳቸውን ጠቃሚ ነገሮች ያህል መልካም ነው። እርሱ ፀሐይን ለሚያዩ ለእነዚያ ትርፍ ያስገኝላቸዋል። **12** ገንዘብ ጥበቃ ሊሰጥ እንደሚችል ጥበብም ጥበቃን ይሰጣል፥ የዕውቀት ብልጫው ግን ጥበብ ላገኟት ሕይወት መስጠቷ ነው። **13** የእግዚአብሔርን ሥራ ተመልከት፡ እርሱ ያጣመመውን የትኛውንም ነገር ማን ሊያቃናው ይችላል? **14** ጊዜው መልካም ሲሆን በደስታ ኑርበት፥ ቀኑ ሲከፋ ግን ይህን አስብ፡ ሁለቱም አጠገብ ለአጠገብ እንዲኖሩ እግዚአብሔር ፈቅዶላቸዋል። በዚህ ምክንያት ማንም ሰው ከእርሱ በኋላ የሚሆነውን የትኛውንም ነገር አያውቅም። **15** ከንቱ በሆነው የሕይወት ዘመኔ ብዙ ነገሮችን ተመልክቻለሁ። ጻድቃን ቢሆኑም የሚጠፉ ጻድቅ ሰዎች አሉ፥ ክፋትን ቢያደርጉም ረጅም ዘመን የሚኖሩ አመጸኞችም አሉ። **16** ራስህን አታጽድቅ፥ በራስህም ግምት ጠቢብ አትሁን። ለምን ራስህን ታጠፋለህ? **17** እጅግ አመጸኛ ወይም ሞኝ አትሁን። ለምን ከቀንህ በፊት ትሞታለህ? **18** ይህንን ጥበብ ብትይዝ መልካም ነው፥ ጽድቅንም ከማድረግ እጅህን ባትመልስ። እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ኃላፊነቱን ሁሉ ይወጣልና። **19** በአንድ ከተማ ውስጥ ካሉ አሥር አስተዳዳሪዎች ይልቅ በጥበበኛ ሰው ውስጥ ያለች ጥበብ ተጽዕኖዋ ትልቅ ነው። **20** መልካምን የሚያደርግና ፈጽሞ ኃጢአትን የማይሠራ አንድም ጻድቅ በምድር ላይ የለም። **21** የሚነገረውን ቃል ሁሉ አታድምጥ፥ ምናልባት አገልጋይህ ሲረግምህ ትሰማው ይሆናልና። **22** በተመሳሳይ፥ ሌሎችን በልብህ ብዙ ጊዜ እንደረገምካቸው አንተ ራስህ ታውቃለህ። **23** ይህንን ሁሉ በጥበብ አረጋገጥሁ። እኔም፥ "ጠቢብ እሆናለሁ" አልሁ፥ እርሱ ግን መሆን ከምችለው በላይ ነው። **24** ጥበብ ሩቅና ጥልቅ ናት። ማን ሊያገኛት ይችላል? **25** ለመማርና ለመፈተን፥ ጥበብንና የእውነታን ማብራሪያ ለመፈለግና ክፋት የማይረባ፥ ሞኝነትም ዕብደት መሆኑን ለመረዳት ልቤን መለስሁ። **26** ልቧ በወጥመድና በመረብ የተሞላ፥ እጆቿም የእግር ብረት የሆኑ የትኛዋም ሴት ከሞት ይልቅ መራራ ናት። እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ማንም ቢሆን ከእርሷ ያመልጣል፥ ኃጢአተኛው ግን በእርሷ ይወሰዳል። **27** "መርምሬ ያገኘሁትን ተመልከቱ" ይላል አስተማሪው። የእውነታን ፍቺ ለማግኘት በአንደኛው ምርምር ላይ ሌላውን እጨምር ነበር። **28** እስካሁን የምፈልገው ይህንን ነው፥ ነገር ግን አላገኘሁትም። በሺህ ሰዎች መካከል አንድ ጻድቅ አገኘሁ፥ በእነዚያ ሁሉ መካከል ግን አንዲት ሴት አላገኘሁም። **29** እግዚአብሔር ሰዎችን ቅን አድርጎ እንደ ፈጠራቸው፥ እነርሱ ግን ብዙ ችግሮችን እየፈለጉ ርቀው እንደ ሄዱ ይህንን ብቻ አገኘሁ።

Ecclesiastes 7:1

መልካም ስም
እዚህ ጋር የሰው ስም የሰውን ማንነት (ዝና) ለመግለፅ ይጠቅማል። ተርጓሚ "መልካም ማንነት (ዝና) ወይም " መልካም ስም

በልቡ ያኖረዋል
ይህ ፈሊጣዊ ነው ። ተርጓሚ"ስለዚህ ጉዳይ በጥንቃቄ መታሰብ አለበት

Ecclesiastes 7:3

ከፊት ኅዘን
ይህ ማዘንን ይገልፃል። ተርጓሚ "ሰውን ሀዘንተኛ የሚያዳርግ ልምምድ

ልብ ደስ ይሰኛል ልብ .... በደስታ
እዚህ ጋር "ልብ" የሰውን ሐሳብ ይገልፃል። "ደስታ" 1) የስሜትን ደስታና ሰላማዊ መሆንን ወይም 2) እውነትን የመረዳት ችሎታ ያስረዳል። ተርጓሚ "ትክክለኛ አስተሳሰብ"

የጠቢብን ልብ በለቅሶ ቤት ነው።
እዚህጋር ጠቢብን "በልባቸው" ተወክለዋል። ይህ የጠቢብ ሰው ለቅሶ በልቅሶ ቤት መሆንን ይናገራል። ተርጓሚ "ጠቢባን ስለሞት በጥልቀት ያስባሉ።"

የሰነፎች ልብ ግን በደስታ ቤትነው።
እዚህ ጋር ሰነፎች "በልባቸው" ተወክለዋል። ይህ ሰነፎችን በደስታ ቤት እንደመሆን የሚያስደስታቸው ነገር ብቻ ማሰባቸውን ይናገራል። ተርጓሚ "ሰነፎች ግን ስለሚያስደስታቸው ነገር ብቻ ያስባሉ።"

በለቅሶ ቤት ..... በደስታ ቤት
እነዚህ ሐረጎች በዚህ ቦታ የሆኑትን ነገር ይገለፃል።

Ecclesiastes 7:5

የጠቢባንን ተግሣፅ
ተግሣፅ የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊገለፅ ይችላል። ተርጓሚ "ጠቢባን ሲገሥፁህ"

የሰነፎችን ዜማ ከሚሰማ
"የሰነፎችን መዝሙር ከመስማት"

ከድስት በታች እንደሚቃጠል እሾህ ድምፅ የሰነፍ ሳቅ እንዲሁ ነው።
ይህ ከድስት በታች እንደሚቃጠል እሾህ ድምፅ የሰነፍ ወሬና ሳቅ ምንም ትምህርት እንደሌለው ይናገራል። ተርጓሚ የሰነፍን ሳቅ ማዳመጥ ከድስት በታች የሚቃጠልን የእሾህ ድምጽ ከማዳመጥ ምንም የተሻለ ነገር ሰውን አያስተምርም።

ከንቱ
ፀሐፊው እርባና ቢስና ትርጉም የሌላቸው ነገሮች ከንቱ እንደሆኑ ይናገራል። የመክብብ ፡1፡14፡ ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ "እንደ ከንቱ እርባና ቢስ" ወይም "ትርጉም የለሽ" (ዘይቤአዊ ተመልከት)

Ecclesiastes 7:7

በግፍ
ይህ አንድን ሰው ገንዘብ ወይም ሌላ ሰው እንዳያጠቃው በግድ እንዲሠጥ ማድረግ። ትክክል አይደለም

ጠቢቡን ያሳብዳዋል
አማራጭ ትርጉሞች 1) "ጠቢብን ወደ ሞኝ ይለውጣል። ወይም2)የጠቢብን ምክር የሞኝ ምክር ያደርጋል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ልብን ያሳብደዋል
እዚህ ጋር ልብ አእምሮን ይወክላል (ይገልፃል) ተርጓሚ "ሰው በትክክል እንዳያሳብና እንዳይፈርድ ችሎታውን ያጠፋል።"

Ecclesiastes 7:8

ታጋሽም ከትዕቢተኛ ይሻላል
ተርጓሚ"ታጋሽ ሰዎች ከትዕቢተኛ ሰዎች ይሻላሉ" ወይም ያታጋሽ አመለካከት ከትዕቢተኛ አመለካከት ይሻላል።"

በነፍስህ ለቁጣ ችኩል አትሁን
እዚህ ጋር“ነፍስ” የሚለው ቃል የሰውን አመለካከት ይገልጻል። ተርጓሚ “ቶሎ አትቆጣ(አትናደድ)” “መጥፎ ንዴት (ብስጭት) አይኑርህ”

ቁጣ በሰነፍ ብብት ያርፋልና
ይህ ቁጣ በውስጡ እንደሚኖር በቁጣ ስለተሞላ ሰው ይናገራል። ይህ በሰው ልብ ውስጥ ስላለው ቁጣ ይናገራል። ምክኒያቱም ልብ የሰው ልጅ ስሜት ምንጭ ተደርጎ ስለሚታሰብ ነው። ተርጓሚ ሞኝ የሞላው ቁጣ ነው።

Ecclesiastes 7:10

ከዚህ ዘመን ይልቅ ያለፈው ዘመን በምን ተሻለ
ሰውየው ይህን ዘመን ለማማረር ይህን ግነት ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ ጥያቄ በዓረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። ተርጓሚ “ከአሁን ዘመን ይልቅ ነገሮች ባለፈው ዘመን ይሻላሉ።”

የዚህን ነገር ጥበብ አትጠይቅም
እዚህ ጋር ፀሀፊው የሰውየውን ጥያቄ ለመመገሰጽ ምጸት ይጠቀማል። (ምፀት ተመልከት)

Ecclesiastes 7:11

ፀሃይንም ለሚያዩ
ይህ ፈሊጣዊ ነው። ተርጓሚ “በሕይወት ያሉት” (ፈሊጣዊ ተመልከት)

ይህ ፈሊጣዊ ነው። ተርጓሚ “በሕይወት ያሉት” **(**ፈሊጣዊ ተመልከት**)**
አማራጭ ትርጉሞች 1) ፀሓፊው “እውቀት” ና “ጥበብ” የሚሉት ቃላትን የተጠቀመው አንድ አይነት ነገር ለማለት ነው። ወይም 2) ጥበብን የማወቅ ትርፍ ሕይወትን ስለምትሰጥ ነው።

ገንዘብ ላደረጉት ሕይወትን እንዲሰጥ ነው።
ይህ የሚናገረው ጥበብ ለዛ ሰው ሕይወት እንደምትሰጥ የሰው ሕይወትን እንደምትጠብቅ ነው። ሰው ጠቢብ ሲሆን በተሻለ ብልጽግናና ረጅም እድሜ እንዲኖር መልካም ውሳኔን ይወስናል። ተርጓሚ “ሰውን ሕይወት ይጠብቃል” ወይም “መልካም ውሳኔን እንዲወስንና ረጅም እድሜን እንዲኖር ያደርገዋል።”

Ecclesiastes 7:13

እርሱ ጠማማ ያደረገውን ማን ሊያቃና ይችላል**?**
ፀሓፊው እግዚአብሄር ስራውን ማንም ሊቀይር እንደማይችል አፅንኦት ለመስጠት የግነት ጥያቄን ይጠቀማል። ይህ በ ዓረፍተ ነገር መልክ ሊፃፍ ይችላል።ተርጓሚ “እርሱ ጠማማ ያደረገውን ማንም ሊያቀና አይችልም።”

Ecclesiastes 7:14

በመልካም ቀን**.....**በክፉም ቀን
“ቀን” የሚለው ቃል ለሚከሰቱ ነገሮች ፈሊጣዊ ነው። ተርጓሚ “መልካም ነገሮች ሲከሰቱ.....ክፉ ነገሮችም ሲከሰቱ” (ፈሊጣዊ ተመልከት)

በመልካም**.....**ደስ ይበልህ
“በእነዚያ መልካም ነገሮች ደስ ይበልህ”

ይህንም ያንም እንደዚያ ሰርቷል
“ይህንም ያንም” የሚለው ሐረግ ፈሊጣዊ ሲሆን “ይህኛውም” ማለት ነው ተርጓሚ “ አንድ ላይ እንዲሆኑ”ወይም “መልካምም ክፉም ይኖር ዘንድ”

ከእርሱ በኋላ**.....**ምንም
አማራጭ ትርጉሞች 1) “ወደፊት የሚሆን ምንም ነገር” ወይም “ከሞተ በኋላ በእርሱ ላይ የሚሆን የትኛውም ነገር”

Ecclesiastes 7:15

ከንቱ በሆነ ዘመኔ
“ከንቱ በሆነ ህይወቴ”

ፃድቅ በፅድቁ
“ምንም እንኳ ጻድቅ ቢሆኑ”

ኃጥእም በክፋቱ
“ምንም እንኳ ኃጥእ ቢሆኑ”

እጅግ ፃዲቅ**.....**እጅግ ጠቢብም
ሁለቱ ሐረጎች በመሰረቱ ስለ አንድ ነገር ነው የሚያወሩት የተጣመሩትም ለአጽንኦት ነው።

እጅግም ፃዲቅ አትሁን
“ከሆንከው በላይ ፃድቅ ነኝ ብለህ እንዳታስብ”

እጅግ ጠቢብም አትሁን
ተርጓሚ “በራስህ አመለካከት ጠቢብ አትሁን” “በራስህ ፍርድ ጠቢብ መሆን”

እንዳትጠፋ - እራስህን ማፅደቅ ሰውን እንደሚያጠፋ ያመለክታል። ተርጓሚ “እራስህን የምታጠፋበት ምንም
ምክኒያት የለም ወይም በዚህ መንገድ ካሰብክ እራስህን ታጠፋለህ”

Ecclesiastes 7:17

ጊዜ ሳይደርስ እንዳትሞት
ፀሐፊው ሰዎች ያለ ጊዜአቸው እንዲሞቱ የሚያደርጋቸውን ነገር የሚያደርጉበት ምንም ምክኒያት የለም። ተርጓሚ “መሞት ካለብህ ቀን በፊት አስቀድመህ የምትሞትበት ምንም ምክኒያት የለም”

ይህን ብትይዝ**....**መልካም ነው
“ይህ የሚናገረው ሰው እንደ ዕቃ ጥበብን ለመያዝና ጠቢብ ለመሆን ስለመታገል ነው።” ተርጓሚ “ለዚህ ጥበብ እራስህን አስገዛ”

ከዚያም ዳግም እጅህን ባታርቅ መልካም ነው።
ይህ የሚናገረው ፅድቅ እቃ እንደሆነ ያክል ሰው ፅድቅን ለመያዝ ስለመታገል ነው። ተርጓሚ “ፃድቅ መሆንህን ማቆም የለብህም” ወይም “ፃድቅ መሆን መምከርህን መቀጠል አለብህ”

ከሁሉ ይወጣልና
“እግዚአብሄር ከእርሱ ጋር የሚጠብቀውን ሁሉ ያደርጋል”

Ecclesiastes 7:19

በከተማ ከሚኖሩ ከአስር ገዢዎች ይልቅ ጥበብ ጠቢብን ታበረታለች።
“ጥበብ ሰውን ብርቱ ታደርጋለች ፤ በከተማ ከሚኖሩ ከአስር ገዢዎች ይልቅ የበለጠ ብርቱ ታደርገዋለች”

መልካምንም የሚሰራ ኃጢአትንም የማያደርግ
“መልካምን የሚሰራና ኃጢአትን የማይሰራ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ecclesiastes 7:21

በሚጫወቱበት ቃል ሁሉ
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ “ሰዎች የሚሉትን ሁሉ”

ልብህ ያውቃልና
“አንተ ራስህ ታውቃለህ - ልብህ የሚለው ቃል ያውቃልና” ለሚለው ቃል አጽንኦት ለመስጠት ነው።

“ልብህ”
እዚህ ጋር የሰው ሐሳብ በልብህ ተገልጾአል። ተርጓሚ “በሃሳብህ”

Ecclesiastes 7:23

ይህን ሁሉ በጥበብ ፈተንሁ
አዚህ ጋር ይህን የሚለው ቃል ፀሐፊው የፃፈውን ነገሮች ሁሉ ይገልፃል። ተርጓሚ ስለፃፍኩአቸው ነገሮች ሁሉ ፈትኜ አወቅኩ።

ግን ከእኔ ራቀች
ለመረዳት ከችሎታዬ በላይ ነበረች ወይም “ነገር ግን ለማድረግ አልቻልኩም”

ራቀ እጅግም ጠለቀ
ይህ የሚናገረው በርቀት በጥልቅ ቦታ እንደተቀመጠ ነገር ጥበብን ለመረዳት ከባድ ስለመሆንን ነው። ተርጓሚ “ለመረዳት ከባድ”

የሚያገኘውስ ማን ነው?
ፀሀፊው ጥበብን መፈለግ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ አጽንኦት ለመስጠት የግነት ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ “ማንም ሊረዳ አይችልም”

በልቤ ዞርሁ
እዚህ ጋር ልብ ሃሳብን ይገልፃል። ዞርሁ የሚለው ቃል ፈሊጣዊ ነው። ተርጓሚ “ሐሳቤን መራሁት” “ቆረጥኩ”

የነገሩን ሁሉ መደምደሚያ
“ለነገሮች ምክኒያት” መደምደሚያ የሚለው ቃል በግስ ሊገለፅ ይችላል። ተርጓሚ“በህይወት ውስጥ የተለያዩ ነገሮች እንዴት እንደሚደመደም(መደምደም)”

Ecclesiastes 7:26

ልብዋ ወጥመድና መርባብ የሆነ እጆችዋም እግር ብረት የሆኑ ሴት
ፀሃፊው የምታማልል ሴት በእጆቹ እንስሳትን ለማጥመድ እንደያዘ ሰው ነች ይላል፡ ፀሃፊው አማላይ ሴት አጥማጅ የሆኑ ሰዎች ወጥመድ ይዘው እንደሚዞሩ አጥማጅ ስለመሆኑዋ ነው። “ልብዋ ሐሳቡዋና ስሜቱዋን ይወክላል።” ተርጓሚ “ማንኛዋም ሴት ወንዶችን በማማለል ታጠምዳለች”

ወጥመድና መርበብ
እነዚህ ሁለቱ ቃላት ሰዎች እንስሳትን በሚያጠምዱበት መንገድ እንዴት ሴት ወንዶችን እንደምታጠምድ አፅንኦት ለመስጠት ነው።

እጆቹዋ እግር ብረት የሆኑ
እዚህ ጋር “እጆቹዋ” ኃይሏንና ቁጥጥሯን ይገልፃል። ይህ የሚናገረው አማላይ ስለመሆኗና ሰዎችን የምታስርበት ሰንሰለት በእጆቿ እንዳለነው። ተርጓሚ “ማንም ከእሷማምለጥ አይችልም”

ኃጢአተኛ ግን ይጠመድባታል
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ኃጢአንን ታጠምዳለች”

Ecclesiastes 7:27

አንዱን በአንዱ ላይ ጨምሬ
“ጨምሬ” የሚለው ቃል እንደ ፈሊጣዊ ይጠቅማል። ተርጓሚ “ከአንዱ በኋላ አንዱን መጨመር”

ወደ ነገር ሁሉ መደምደሚያ እደርስ ዘንድ
መደምደሚያ የሚለው ቃል በግስ ሊገለፅ ይችላል ። በመክብብ 7:25 ፤ላይ መደምደሚያ እንዴትእንደተተረጎመ ተመልከት። ተርጓሚ በህይወት ውስጥ ነገርን ሁሉ ለመደምደም ይቻል ዘንድ።

ከሺህ ወንዶች አንድ አገኘሁ
ከአንድ ሺ ሰው አንድ ፃድቅ ከአንድ ሺህ ሰው ስብስብ አንድ ፃድቅ ብቻ ተገኘ

ከእነዚያ ሁሉ.....አንዲት ሴት
ከአንድ ሺህ ሰው ስብስብ አንድ ጻድቅ ሴት አልተገኘም

Ecclesiastes 7:29

እነርሱ ግን ብዙ ብልሃት ፈለጉ
አማራጭ ትርጉሞች 1) “ብዙ ኃጢአተኛ እቅድ ሠሩ (አደረጉ)” 2) “የራሳቸውን ሕይወት ከባድ አደረጉ”

ብዙ ብልሃትን ፈለጉ
ይህ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በሄዱ ጊዜ ሰብአዊነት ትክክል ወደ አለመሆን ስለመቀየር ያወራል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 8

1 ጥበበኛ የሆነ ሰው ማን ነው? በሕይወት ውስጥ የሚያጋጥሙ ሁነቶችን ትርጉም የሚያውቅ ማን ነው? በሰው ውስጥ ያለች ጥበብ ፊቱን ታበራለች፥ የፊቱም
ክባዴ ይለወጣል። **2** እግዚአብሔር ሊጠብቀው ምሎለታልና የንጉሡን ትዕዛዝ እንድትፈጽም እመክርሃለሁ። **3** ንጉሡ ደስ ያለውን ያደርጋልና ከፊቱ በችኮላ
አትውጣ፥ ትክክል ላልሆነውም ነገር ድጋፍህን አትስጥ። **4** የንጉሥ ቃል ይገዛል፥ ስለዚህ፥ "ምን እያደረግህ ነው?" ማን ይለዋል? **5** የንጉሡን ትዕዛዝ
የሚጠብቅ ጉዳትን ያርቃል። የጠቢብ ልብ የመተግበሪያ ጊዜንና ተገቢ አካሄድን ያስተውላል። **6** የሰው መከራው ብዙ ነውና ለእያንዳንዱ ጉዳይ ትክክለኛ
ምላሽና ምላሹን የሚሰጥበት ጊዜ አለ። **7** ቀጥሎ የሚሆነውን ማንም አያውቅም። ሊመጣ ያለውን ማን ሊነግረው ይችላል? **8** መተንፈስን ለማቆም በሕይወት
እስትንፋስ ላይ ሥልጣን ያለው ማንም የለም፥ **9** ደግሞም በሞቱ ቀን ላይ ሥልጣን ያለው ማንም የለም። በጦርነት ጊዜ ከሠራዊቱ የሚሰናበት ማንም የለም፥
አመጸም ባሪያ የሆኑለትን አይታደጋቸውም። ይህንን ሁሉ አስተዋልሁ፤ ከፀሐይ በታች ለሚሠራው ለሁሉም ዓይነት ሥራ ልቤን ሰጠሁ። አንድ ሰው በሌሎች ላይ
ክፉ ለማድረግ አቅም የሚያገኝበት ጊዜ አለ። **10** ስለዚህ አመጸኞች በይፋ ሲቀበሩ አየሁ። ከተቀደሰው አካባቢ ተወስደው ተቀበሩ፥ የአመጽ ሥራቸውን ይሠሩበት
የነበረ ከተማ ሰዎችም አመሰገኗቸው። ይህ ደግሞ ከንቱነት ነው። **11** በክፉ ወንጀል ላይ ፍርድ ፈጥኖ በማይሰጥበት ጊዜ፥ ክፋትን እንዲያደርጉ የሰው ልጆችን
ልብ ያነሣሣል። **12** አንድ ኃጢአተኛ መቶ ጊዜ ክፋትን ቢያደርግና ረጅም ዘመን ቢኖር እንኳን እግዚአብሔርን ለሚያከብሩት፥ አብሯቸው መሆኑን ለሚያከብሩ
በጎነት እንደሚሆንላቸው አውቃለሁ። **13** ለክፉ ሰው ግን በጎነት አይሆንለትም፤ ሕይወቱም አይረዝምም። እግዚአብሔርን አያከብርምና ዘመኑ ፈጥኖ
እንደሚያልፍ ጥላ ነው። **14** በምድር ላይ የተደረገ ሌላ ከንቱ እንቆሎት አለ። በክፉ ሰዎች ላይ የሚደርሰው በጻድቃኑም ላይ ይደርሳል፥ ለጻድቃኑ የሚደርሰውም
ለክፉዎች ሰዎችም ይደርሳል። እኔም፥ ይህ ደግሞ ክፉ እንቆሎት ነው አልሁ። **15** ለሰው ከፀሐይ በታች ከመብላት፥ መጠጣትና መደሰት የሚሻል ነገር
ስለሌለው ደስታ ይሻላል እላለሁ። ከፀሐይ በታች እግዚአብሔር በሰጠው የሕይወት ዘመኑ ሁሉ በሚደክምበት ነገር ደስታ አብሮት ይሆናል። **16** ጥበብን
ለማወቅና በምድር ላይ የሚሠራውን ሥራ ለማስተዋል ልቤን በሰጠሁ ጊዜ ብዙ ጊዜ በቀንም ሆነ በሌሊት ያለ እንቅልፍ በሚሠራው ሥራ **17** ከዚያም
የእግዚአብሔርን ሥራ ሁሉ ተመለከትሁ ከፀሐይ በታች የሚሠራውን ሥራ ሰው ሊያስተውለው አይችልም። አንድ ሰው መልሶቹን ለማግኘት ምንም ያህል ቢጥር
አያገኛቸውም። ጠቢብ ሰው እንድሚያውቅ ቢያምንም እንኳን በርግጥ አያውቅም።

Ecclesiastes 8:1

እንደ ጠቢብ የሆነ ሰው ማን ነው ነገርንስ መተርጎም የሚያውቅ ማን ነው
ፀሐፊው ይህን መሪ ጥያቄ የሚጠይቀው ቀጥሎ ለሚናገረው ነገር መልስ ለመስጠት ነው።

ፊቱን ታበራለች
ይህ ማለት የሰው ፊት ጠቢብ መሆኑን ያሳያል። ተርጓሚ “በፊቱ ላይ ያሳያል” የፊቱንም ድፍረት ይህ ፈሊጣዊ ነው። ተርጓሚ “ጨካኝ ገፅታው(ፊቱ)”

ትለውጣለች
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ይለወጣል”

Ecclesiastes 8:2

“በእግዚአብሄር መሐላ ምክኒያት”
“ትጠብቀው ዘንድ ለእግዚአብሄር ያደረግኸው መሐላ”

ከፊቱ ትወገድ ዘንድ አትቸኩል
አማራጭ ትርጉሞች 1) ከንጉሱ ፊት ትሄድ ዘንድ አትቸኩል 2) ይህ በንጉስ ፊት ትሆን ዘንድ ዘይቤአዊ ንግግር ነው። ተርጓሚ “ንጉሱን አትተወው”

የንጉስ ቃል ኃይለኛ ነውና
“ንጉስ ያለው ያ ሕግ ነው”

ማን ይለዋል ?
ይህ የሚቀጥለውን ጥያቄ ማንም አይጠይቀውም ለሚለው አፅንኦት ለመስጠት የግነት ጥያቄ ነው። ይህ ጥያቄ በዓረፍተ ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ “ማንም ሊለው አይችልም”

ይህንስ ለምን ታደርጋለህ?
ይህ የግነት ጥያቄ ተግሳፅ ነው። ይህ ጥያቄ በአረፍተ ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ “አደረክ ያለውን ማድረግ የለብህም”

Ecclesiastes 8:5

የጠቢብም ልብ.....ያውቃል።
እዚህ ጋር ለጠቢብ ሃሳብ(አስተሳሰብ) አጽንኦት ለመስጠት በልቡ ይገልፃል። ተርጓሚ “ጠቢብ ያውቃል”

ለነገር ሁሉ ጊዜና ፍርድ
“ነገሮችን የማድረግ ትክክለኛ ጊዜና በትክክል ማድረግ”

እንዴትስ እንደሚሆን የሚናገረው ማነው?
ይህ የግነት ጥያቄ ወደፊት ስለሚከሰት ነገር ማንም ሊያውቅ እንደማይችል አፅንኦት ይሰጣል። ጥያቄው ሲፃፍ በዓረፍተ ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። “ምን እንደሚመጣ ማንም ሊነግረው የሚችል የለም “ (የግነት ጥያቄ ተመልከት)

Ecclesiastes 8:8

መንፈስን ለማስቀረት በመንፈስ ላይ ስልጣን ያለው የለም በሞቱም ቀን ስልጣን የለውም
ከመተንፈስ ማንም እራሱን ሊያግድ የሚችል እንደሌለ እንዲሁ የመሞት ጊዜ ሲደርስ ለመኖር የሚችል ማንም የለም

ሥልጣን ያለው.....የለም
ቁጥጥር ያለው የለም

በሞቱም ቀን
ይህ ፈሊጣዊ ነው። ተርጓሚ “እርሱ ሲሞት” ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "የትኛውም ሰልፍ ማንንም ማሠናበት አይችልም"

ሰልፉም ቀን ስንብቻ የለም
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ"የትኛውም ሰልፍ ማንንም አያሰናብትም" ወይም "ወታደርን የሚያሰናብት ሰልፍ የለም"

ኃጢአትም ሠሪውን አያድነውም
ይህ ኃጢአት ሠራተኛ እንዳለው አለቃ መሆኑን ይናገራል። ተርጓሚ"ክፉ ሰዎች ክፋትን በመስራት አይድኑም "

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ልቤን ሰጠው
እዚህ ጋር ፀሐፊው ለስሜቱ አፅንኦት ለመስጠት እራሱን በልቡ ይገልፃል። የመክብብ 1፡17 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ"እራሴን ሰጠሁ"

ወደ ተደረገው ሥራ ሁሉ
ይህ በገቢር መልኩ ሊጠቀም ይችላል። "ሠዎች የሚሰሩት የትኛውም ሥራ"

ከፀሐይ በታች
ይህ በምድር ላይ የተደረጉ ነገሮችን ይገልፃል። የመክብብ 1:3 ትርጉም ተመልከት። ተርጓሚ"በምድር ላይ"

ሰው ሰውን ለመጉዳት ገዢ የሚሆንበት ጊዜ አለ።
"አንዳድ ጊዜ ጉዳት ለማድረስ አንዱ ሌላኛው ላይ ገዢ ይሆናል።"

Ecclesiastes 8:10

ኃጥኣን ተቀብረው አየሁ
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። የሞቱ ክፉ ሰዎች የተከበረ የቀብር ሥነ-ሥርዓት ተደረገላቸው ። ተርጓሚ"ሰዎች ክፍዎችን በክብር ቀበሩ"

ከቅድስት ስፍራ ወጡ ተቀበሩም በሰዎችም ተሞገሱ
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ"ሰዎች ከቅድስት ሥፍራ ወሰዱአቸው ቀበሩአቸውም አመሰገኑአቸውም"

በክፉ ስራ ላይ ፈጥኖ ፍርድ አይፈርድምና
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "በሥልጣን ላይ ያሉ ሠዎች ፈጥነው በክፉ ወንጀል ፍርድ አይፈርዱምና"

ልባቸው ክፉን ለመስራት ጠነከረ
እዚህ ጋር ለፍቃዳቸውና ለምኞቶቻቸው አፅንኦት ለመስጠት ሰዎችን በልባቸው ይወክላል (ይገልፃል) ተርጓሚ"የሰው ልጅ ጠነከረ" ወይም ሠው ክፉን ለመስራት ተሳበ"

Ecclesiastes 8:12

መቶ ጊዜ
"100 ጊዜ" (ቁጥር ተመልከት)

እግዚአብሔርን ለሚፈሩት..... ደኅንነት እንዲሆን
"እንዲሆን " የሚለው ቃል ፈሊጣዊ ነው። "እግዚአብሔርን ለሚፈሩት ሕይወት መልካም ይሆናል።

እግዚአብሔርን ለሚፈሩት በፊቱም ለሚፈሩት ... በፊቱም ለሚፈሩት
እነዚህሁለቱ ሐረጎች ሰዎች እግዚአብሄርን መፍራታቸውን አፅንኦት ለመስጠት አንድ ላይ የተጠመሩ ሲሆን ትርጉማቸው በመሰረቱ አንድ ነው።

ዘመኑ....አትረዝምም
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፉ ይችላል። ተርጓሚ “እግዚአብሄር ዘመኑን አያረዝምም”

ዘመኑ እንደ ጥላ ነው
ይህ የሚናገረው የክፉ ሰው እድሜ ጥላ በፍጥነት እንደሚያልፍ ዘመኑም ፈጥኖ እንደሚያልፍ ነው ። ተርጓሚ ዘመኑ እንደ ጥላ ፈጥኖ ያልፋል

ዘመኑ
“ሕይወቱ”

Ecclesiastes 8:14

ከንቱ ነገር አለ
“ተን ነገር አለ” ፀሃፊው እርባና ቢስና ትርጉም የሌላቸው ነገሮች ተን የሆኑ ያክል ይናገራል። የመክብብ 1:14 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ እንደ ከንቱ እርባና ቢስ የሆነ ነገር አለ ወይም “እርባና ቢስ የሆነ ነገር አለ” (ዘይቤአዊ ትርጉም ተመልከት) በምድር .....የሚደረግ ስራ ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ “ሰዎች በምድር ላይ የሚሰሩት ነገር”

ይህም ደግሞ ከንቱ ነው
“ይህም ደግሞ ከንቱ ነው” ፀሐፊው እርባና ቢስና ትርጉም የሌላቸው ነገሮች ተን የሆነ ያክል ይናገራል። የመክብብ 1:14 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ ይህም ደግሞ እንደ ከንቱ እርባና ቢስ ነው።

ከፀሐይ በታች
ይህ በምድር ላይ የተደረጉትን ይገልፃል ። የመክብብ 1:3 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ “በምድር ላይ” ከፀሐይ በታች....እግዚአብሄር በሰጠው በሕወቱ ዘመን ይህ ፈሊጣዊ ነው። ተረጓሚ “እግዚአብሄር እንዲኖር እስከፈቀደለት ድረስ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 9

1 ስለ ጻድቃንና ስለ ጥበበኛ ሰዎች፥ ስለ ሥራቸውም፥ ስለ እነዚህ ሁሉ ለመገንዘብ በልቤ አሰብሁ። ሁሉም በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ ናቸው። አንድ ሰው ፍቅር ወይም ጥላቻ ይገጥመው እንደሆነ ማንም አያውቅም። **2** ሁሉም ሰው ተመሳሳይ ዕጣ ፈንታ አለው። ጻድቃንን እና አመጸኞችን፥ መልካምና ክፉ ሰዎችን፥ ንጹሕ የሆኑትንና ያልሆኑትን፥ መሥዋዕት የሚያቀርበውንና የማያቀርበውን ተመሳሳይ ዕጣ ፈንታ ይጠብቃቸዋል። መልካም ሰዎች እንደሚሞቱ ኃጢአተኞችም ደግሞ እንዲሁ ናቸው። የሚምለው ሰው እንደሚሞተው ሁሉ ለመማል የሚፈራው ሰውም ይሞታል። **3** ከፀሐይ በታች ለተደረገው ሁሉ ክፉ ዕጣ ፈንታ አለው፥ ለሁሉም አንድ መጨረሻ። የሰዎች ልብ በክፋት የተሞላ ነው፥ በሕይወት እያሉም ዕብደት በልባቸው አለ። ከዚያ በኋላ ወደ ሙታን ይሄዳሉ። **4** ከሞተ አንበሳ በሕይወት ያለ ውሻ እንደሚሻል በሕይወት ላለ ሰውም አሁንም ተስፋ አለው። **5** ሕያዋን ሰዎች እንደሚሞቱ ያውቃሉ፥ ሙታን ግን ምንም አያውቁም። መታሰቢያቸው ተረስቷልና ምንም ብድራት አይኖራቸውም። **6** ፍቅራቸው፥ ጥላቻቸውና ቅናታቸው ከብዙ ጊዜ በፊት ጠፍቷል። ከፀሐይ በታች በተደረገ በማንኛውም ነገር ዳግም ስፍራ አይኖራቸውም። **7** መንገድህን ሂድ፥ ምግብህን በደስታ ተመገብ፥ በደስተኛ ልብ ወይንህን ጠጣ፥ መልካሙን ሥራህን እግዚአብሔር ተቀብሎታልና። **8** ልብሶችህ ሁልጊዜ ነጭ ይሁኑ፥ ራስህንም በዘይት ተቀባ። **9** ከፀሐይ በታች እግዚአብሔር በሰጠህ በከንቱ ዘመንህ፥ ከንቱ በሆነው የሕይወት ዘመንህ ሁሉ ከምትወዳት ሚስትህ ጋር በደስታ ኑር። ከፀሐይ በታች ለሆነው ሥራህ ይህ ብድራት ነው። እጅህ ለመሥራት የሚያገኘውን ሁሉ በሙሉ ኃይልህ ሥራ፥ **10** በምትሄድበት በመቃብር ስፍራ ሥራ ወይም ገለጻ ወይም እውቀት ወይም ጥበብ በዚያ የለምና። **11** ከፀሐይ በታች አንዳንድ የሚያስደስቱ ነገሮችን አየሁ፡ ሩጫ ለፈጣኖች አይሆንም። ውጊያ ለብርቱ ሰዎች አይሆንም። እንጀራ ለጥበበኞች ሰዎች አይሆንም። ሀብት ለአስተዋይ ሰዎች አይሆንም። ሞገስ እውቀት ላላቸው ሰዎች አይሆንም። ከዚህ ይልቅ ጊዜና ዕድል በሁሉ ላይ ተጽዕኖ ያደርጋል። **12** ዓሳ በሚሞትበት መረብ እንደሚጠመድ ወይም ወፎች በወጥመድ እንደሚያዙ ማንም ሰው የሚሞትበትን ጊዜ አያውቅም። የሰው ልጆችም ልክ እንደ እንስሳ ድንገት በሚወድቅባቸው ክፉ ጊዜ ይታሰራሉ። **13** ደግሞም ከፀሐይ በታች ያስገረመኝን ጥበብ አየሁ። **14** ጥቂት ሰዎች ብቻ የሚኖሩባት አንዲት ከተማ ነበረች፥ አንድ ታላቅ ንጉሥ መጣባት፥ ከበባት፥ በዙሪያዋም ታላቅ ምሽግ ገነባባት። **15** በከተማው ውስጥ አንድ ድሃ ጠቢብ ሰው ተገኘ፥ በጥበቡም ከተማይቱን አዳነ። በኋላ ላይ ያንን ድሃ ሰው ማንም አላሰበውም። **16** እኔም፥ "ጥበብ ከኃይል ይሻላል፥ ነገር ግን የድሃው ጥበብ ተንቋል፥ ቃሎቹም አልተሰሙም" ብዬ ደመደምኩ። **17** በሞኞች መካከል ከሚጮህ ማንኛውም ገዥ ይልቅ በዝግታ የሚነገሩ የጥበበኞች ሰዎች ቃል ይደመጣል። **18** ከጦር መሣሪያዎች ጥበብ ትሻላለች፥ ነገር ግን አንድ ኃጢአተኛ ብዙ መልካም ነገሮችን ሊያበላሽ ይችላል።

Ecclesiastes 9:1

ይህን ሁሉ መረምር ዘንድ በልቤ አኖርሁ
“ስለዚሁ ሁሉ በጣም በጥልቀት መረመርኩ”

በእግዚአብሄር እጅ እንዲሆኑ ይህን ሁሉ
እዚህ ጋር “እንዲሆኑ የሚለው ቃል ፃድቃንን ጠቢብን ይገልፃል ድርጊታቸውንም

በእግዚአብሄር እጅ”
እዚህ ጋር “እጅ” እግዚአብሄር ኃይልና ስልጣን ይገልፃል። ተርጓሚ "በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር"

ፍቅር ወይም ጥል .... ወደ ፊታቸው ነው።
ይህ "ፍቅር" ጥል ሰውን ለመጎብኘት ወደ ቤት እንደሚመጡ አድርጎ ይናገራል። ተርጓሚ"ፍቅር ወይም ጥልን መገናኘታቸው ነው

Ecclesiastes 9:2

የፃድቁና የበደለኛው
ይህ ሁሉንም ይገልፃል። ሁለቱ ፃድቁንም በደለኛውንም አፅንኦት ይሰጣል።

በደለኛ መልካሙና የክፉው የንፁሀኑ
እነዚህ ሁሉ ቃላት ሰዎች ሁሉ ይገልፃሉ። ተርጓሚ “በደለኞች፣መልካም ሰዎች፣ክፉ ሰዎችና ንፁሃን ሰዎች”

ንፁሃን ሰዎች
ይህ ሁሉንም ሰው ሲገልፅ ለሁለቱ ተቃራኒ፣ንፁህና ርኩስ ሰው አፅንኦት ለመስጠት ነው።(ዘይቤአዊ ተመልከት)

ንፁህ
በአካሉ ንፁህ የሆነ ያክል ለ እግዚአብሄር ዓላማ ተቀባይነት ያለው ሰው ነው

ርኩስ
በአካሉ ርኩስ (ንፁህ ያልሆነ) ያክል ለእግዚአብሄር ዓላማ ተቀባይነት የሌለው ሰው (ዘይቤአዊ ተመልከት)

መስዋዕትን የሚሰዋውና የማይሰዋው
ይህ ሰውን ይወክላል።ሁለቱ ተቃራኒ፣መስዋዕትን ለሚሰውና ለማይሰው ሰው አጽንኦት ለመስጠት።

እንደ መልካም ሰው እንዲሁ ሀጢአተኛው ሰው
ይህ ሁሉንም ሰው ይገልጻል። ለመልካሙም ለሃጢአተኛውም ለሁለቱም አጽንዕት ይሰጣል።

ሃጢአተኛው እንደ መሃለኛው ሰው እንዲሁ መሃላን የሚፈራ ነው።
ይህ ሁሉንም ሰው ይገልጻል። መሃላን የሚምል መሃላ የሚፈራውን ሁለቱንም አጽንኦት ይሰጣል።

Ecclesiastes 9:3

በተደረገው ሁሉ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “የሆነው ነገር ሁሉ”

ከጸሃይ በታች
ይህ በምድር ላይ የተደረጉትን ይገልጻል የመክብብ 1:3 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ“በምድር ላይ”

አንድ ድርሻ
ሞት

የሰው ልጆች ልብ ክፋትን ትሞላለች በሕይወታቸውም ሳሉ እብደት በልባቸው ነው።
እዚህ ጋር ልብ የሚለው ቃል ሃሳብንና ስሜትን ይገልጻል። ተርጓሚ “የሰው ልጅ በክፋት የተሞላ ነው። ሃሳባቸውም የእብደት ነው።”

እብደት
“ስህተት” ወይንም “ከንቱነት”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወደ ሙታን ይወርዳሉ
“”ሙታን የሚለው ቃል የሞቱ ሰዎችን ይገልጻል። እዚህ ጋር ሙታን ሰዎች ከሞቱ በኋላ የሚሄዱበትን ቦታ ይገልጻል። ተርጓሚ “ሙታን ወዳሉበት ቦታ ይሄዳሉ” ወይንም “ይሞቱና ወደ መቃብር ይሄዳሉ”

Ecclesiastes 9:4

ሕያዋን ---- ሙታን
ይህ በሕይወት ያሉትንና የሞቱትን ይገልጻል። ተርጓሚ “ በሕይወት ያሉ -- የሞቱት”

ያልሞተ ውሻ ከሞተ አንበሳ ይሻላል
ውሻ አነስተኛ እንስሳ ተደርጎ ቢገለጽም አንበሳ ደግሞ የተከበረ እንስሳ ተደርጎ ተገልጸአል። ይህ የተከበረ ሆነ ከሞተው አነስተኛ ሆኖ በሕይወት ስላለው ይናገራል። ተርጓሚእንደ አንበሳ የተከበረ ሆኖ ከመሞት እንደ ውሻ አነስተኛ ሆኖ መኖር ይሻላል።

መታሰቢያቸው ተረስቷልና
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ “ሰዎች ይረሱአቸዋል”

Ecclesiastes 9:6

ፍቅራቸውና ጥላቸው ቅንዓታቸውም
ይህ ሙታን በሕይወት እያሉ ለሌሎች ያሳዩት ፍቅር፣ጥላቻንና ቅንዓትን ይገልፃል።

በሚሰራው ነገር
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል።ተርጓሚ“ሰዎች የሰሩት ማናኛውም ነገር”

ከፀሃይ በታች
ይህ በምድር ላይ የተደረጉትን ይገልፃል። የመክብብ 1:3 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ “በምድር ላይ”

እንጀራህን በደስታ ብላ ! የወይን ጠጅህንም በተድላ ጠጣ
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው በሕይወት መሠረታዊ ድርጊቶች (እንቅስቃሴዎች) መርካትን አፅንኦት ይሰጣል።

እንጀራህን
ይህ መብልን ሁሉ ይገልጻል። ተርጓሚ “መብልህን”

የወይን ጠጅህን በተድላ ጠጣ
እዚህ ጋር “በተድላ” የሚለው ቃል ስሜትን ይገልጻል። ተርጓሚ የወይን ጠጅህን በደስታ ጠጣ

ሁልጊዜ ልብስህ ነጭ ይሁን ቅባትም ከራስህ ላይ አይታጣ
ነጭ ልብስን መልበስና ቅባትን በራስ ላይ መቀባት ሁለቱም የደስታና የበአል ምልክቶች ነበሩ።

ቅባትም ከራስህ ላይ አይታጣ
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ “ራስህን ቅባት ተቀባ”

Ecclesiastes 9:9

ከምትወዳት ሚስህ ጋር ደስ ይበልህ
አንድ ሰው ሚስቱን ሊወድ ይገባል። ተርጓሚ “የምትወዳት ሚስት ስላለችህ በደስታ ከእርሷ ጋር ኑር”

ከፀሃይ በታች
ይህ በምድር ላይ የተደረጉትን ይገልጻል የመክብብ 1:3 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ “በምድር ላይ”

ዘመንህ
“የህይወት ዘመንህ”

ይህ እድል ፈንታህ ነውና
“ይህ” የሚለው ቃል ከሚስትህ ጋር በደስታ መኖርን ይገልፃል።

እጅህ ለማድረግ የምታገኘውን ሁሉ
እዚህ ጋር በእጁ ተወክሎአል። ምክኒያቱም ሰው ብዙ ጊዜ ለመስራት እጁን ስለሚጠቀም ነው። ተርጓሚ “መስራት የምትችለውን ነገር ሁሉ”

ስራና አሳብ እውቀትና ጥበብ አይገኙምና
“ሥራ” “አሳብ” ና “እውቀት” የሆኑት ሰዎች በግስ ሊገለፅ ይችላሉ። ተርጓሚ “ሙታን ሥራን አይሰሩም ወይም አያስቡም ወይም አያውቁም ወይም ጥበብ የላቸውም።”

Ecclesiastes 9:11

ከፀሃይ በታች
ይህ በምድር ላይ የተደረጉትን ይገልፃል የመክብብ 1:3 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ-በምድር ላይ

ሩጫ.....እንዳልሆነ....ሰልፍም....እንዳልሆነ
“ሩጫ ሁልጊዜ ለሯጭ እንዳልሆነ.....ሰልፍም ሁልጊዜ ለኃያላን እንዳልሆነ”

እንጀራ
እዚህ ጋር መብልን ሀሉ ይገልጻል። ተርጓሚ“ መብል”

ጊዜና እድል ሁሉ ይገናኛቸዋል
“እነዚህ ሁሉ ይገናኛቸዋል” እዚህ ጋር “ሁሉ” የሚለው ቃል ሩጫ ፣ ሰልፍ ፣እንጀራን፣ ባለጠግነትንና ሞገስን ይገልፃል፤፤

በክፉ ጊዜ ....ሲወድቅባቸው
ይህ ሰው ሲሞትን ይገልፃል። ተርጓሚ “እርሱ ሲሞት” ወይም “የሞት ጊዜ ሲመጣ”

ዓሣዎች.....እንደተያዙ ወፎችም እንዲሁ የሰው ልጆች በክፉ...ይጠመዳሉ
ይህ ሰዎች ሳይጠብቁ ስለመሞታቸው ይናገራል። ልክ እንደዚያው ሳይጠብቁ ድንገት ሰዎች እንስሳትን ይይዛሉ።

የሰው ልጆች በክፉ ጊዜ ይጠመዳሉ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ይህም እንደተሰሩና በወጥመድ እንደተያዙ ሰዎች አደጋና ጥሩ ጊዜ ያልሆነ እንደሚያጋጥማቸው ይናገራል። ተርጓሚ"በሰው ልጆች ላይ ክፉ ጊዜ እየመጣ ነው"

በድንገት ሲወድቅባቸው
ይህ ፈሊጣዊ ነው ተርጓሚ"ይከሰታል ድንገት ሳይጠብቁ በአንድ ጊዜ" ወይም "ድንገት ሲመጣባቸው"

Ecclesiastes 9:13

ከፀሐይ በታች
ይህ በምድር ላይ የተደረጉትን ይገልፃል። የመክብብ 1:3 ትርጉም ተመልከት ተርጓሚበምድር ላይ (ፈሊጣዊ ተመልከት)

ታላቅ ንጉሥም መጣበት
እዚህ ጋር "ንጉሥ" የሚለው ቃል እራሱን ሠራዊቱን በሙሉ ይወክላል። ተርጓሚ "ታላቅ ንጉሥና ሠራዊቱ"

ታላቅ ግንብም ሠራባት
ይህ መውጣት እንዲችሉና ከተማዋን እንዲያጠቁ ሠራዊቱ በከተማ ዙሪያ በጭቃ የሠሩትን ግንብ ይገልፃል።

ጠቢብ ድሀ ሰውም ተገኘባት
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ"በከተማው ወስጥ ሰዎች፤ ደሀ፤ ጠቢብ ሠው አገኙ" ወይም "ደሀ ጠቢብ ሠው በከተማው ውስጥ ኖረ"

Ecclesiastes 9:16

የድሀው ጥበብ ግን ተናቀች
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ"ሰዎች የድሀን ሰው ጥበብ ይንቃሉ"

ቃሉም አልተሰማችም
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። "የሚለውን አይሰሙትም" ወይም "ምክሩን አይቀበሉም"

Ecclesiastes 9:17

ይልቅ የጠቢባን ቃል በፀጥታ ትሰማለች
እዚህ ጋር "ትሰማለች" የሚለው ቃል መረዳትን ይወክላል። ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። የጠቢባን በፀጥታ የሚናገሩት ቃል መረዳት የተሻለ ቀላል ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 10

1 የሞቱ ዝንቦች ሽቶን ያገሙታል፥ ትንሽ ሞኝነትም ጥበብና ክብርን ለጎዳ ይችላል። **2** የጠቢብ ልብ ወደ ቀኝ ያዘነብላል፥ የሞኝ ልብ ግን ወደ ግራው። **3** ሞኝ መንገድ ላይ በሚሄድበት ጊዜ ማስተዋሉ ያነሰ ነው፥ ሞኝነቱን ለሁሉ ያሳውቃል። **4** አለቃ በቁጣ ቢነሣብህ ሥራህን አትልቀቅ። ትዕግስት ታላቁን ቁጣ ጸጥ ማድረግ ይችላል። **5** ከፀሐይ በታች ያየሁት ክፉ አለ፥ ያም ከገዢ የሚመጣ ስህተት ነው፡ **6** ውጤታማ ሰዎች ዝቅተኛ የሥራ መደብ ሲሰጣቸው ሞኞች የመሪነት ሥራ ተሰጣቸው። **7** ባሪያዎች በፈረስ ተቀምጠው፥ ስኬታማ ሰዎች አንደ ባሪያ በእግራቸው ሲሄዱ አየሁ። **8** ጉድጓድ የሚቆፍር በዚያ ውስጥ ሊወድቅ ይችላል፥ ካብ የሚያፈርሰውንም እባብ ሊነድፈው ይችላል። **9** ድንጋዮችን የሚፈነቅል በእነርሱ ሊጎዳ ይችላል፥ ግንድ የሚጠርብም አደጋ ይደርስበታል። **10** የብረቱ መቁረጫ ጫፉ ቢደንዝና ሰው ባይስለው ብዙ ኃይል ሊያወጣበት የግድ ነው፥ ጥበብ ግን ውጤታማ የሚሆንበትን መንገድ ያዘጋጅለታል። **11** ድግምቱ ከመደገሙ በፊት እባብ ቢነድፍ ደጋሚው ምንም አይጠቀምም። **12** ከጠቢብ ሰው አፍ የሚወጣ ቃል ሞገስ አለው፥ የሞኝ ከንፈር ግን ራሱን ያጠፋዋል። **13** ከሞኝ አፍ ቃል መውጣት ሲጀምር ሞኝነት አብሮ ይወጣል፥ በመጨረሻም ከአፉ ክፉ ዕብደት ይወጣል። **14** ሞኝ ቃሉን ያበዛል፥ የሚመጣው ምን እንደሆነ ግን ማንም አያውቅም። ከእርሱ በኋላ የሚሆነውን ማን ያውቃል? **15** ወደ ከተማ የሚወስደውን መንገድ እንኳን እስከማያውቁ ድረስ ሞኞችን ሥራቸው ያደክማቸዋል። **16** ንጉሣችሁ ወጣት ከሆነና መሪዎቻችሁም ግብዣቸውን በማለዳ የሚጀምሩ ከሆኑ በዚያች ምድር መከራ ይሆናል። **17** ነገር ግን ንጉሣችሁ ከተከበረው ቤተሰብ የተወለደ፥ መሪዎቻችሁ ለመስከር ሳይሆን ለመበርታት በተገቢው ጊዜ ሲመገቡ ምድሪቱ ደስ ይላታል። **18** በስንፍና ምክንያት ጣሪያ ይዘብጣል፥ በእጅ ሥራ መፍታትም ቤት ያንጠባጥባል። **19** ሰዎች ምግብን ለሣቅ ያዘጋጃሉ፥ ወይን ሕይወትን ደስ ያሰኛል፥ ገንዘብም ፍላጎትን ሁሉ ያሟላል። **20** በልብህም ቢሆን ንጉሡን አትርገመው፥ በመኝታህም ላይ ባለጸጎችን አትርገም። በሰማይ የሚበር ወፍ ቃልህን ይወስድ ይሆናልና ክንፍ ያለውም ሁሉ ጉዳዩን ሊያሰራጨው ይችላል።

Ecclesiastes 10:1

የሞቱ ዝንቦች እንዲሁም ትንሽ ስንፍና
ዝንቦች ሽቶን እንደሚያበላሹት ሁሉ ሰነፍም እንዲሁ የሰውን መልካም ስም ጥበብና ክብር ያጠፋል። ዝንቦች ሽቶን ያበላሻሉ

ትንሽ ስንፍና ጥበብና ክብርን ያጠፋል።
ይህ የሰው ስንፍና ጥበቡ ሰው የሆኑ ያክል ሞኝነቱ የራሱን መልካም ስም ጥበብና ክብርን እንደ ሚያበላሽና ጥበብና ክብርን ይናገራል።

የጠቢብ ልብ ..... የሰነፍ ልብ
እዚህ ጋር "ልብ" "አእምሮ" ወይም "ፈቃድን ይገልፃል። ተርጓሚ"ጠቢብ እንዴት እንደሚያስብ ..... ሰነፍ እንዴት እንደሚያስብ"

በስተቀኙ ነው ..... በስተግራው ነው
እዚህ ጋር "ቀኝና ግራ" ትክክል የሆነና ስህተት የሆነ ነገርን ይገልፃሉ። ተርጓሚ"ትክክል ነገርን ለማድረግ ..... ስህተትን ለመስራት

የሚያስበውም ሁሉ ስንፍና ነው
ይህ እንዴት እንደሚያደርግ ይገልፃል። "የማይረባ" ወይም "ደደብ ነው።"

Ecclesiastes 10:4

የገዢ ቁጣ የተነሳብህ እንደሆነ
እዚህ ጋር "ገዢ" "በስሜቱ" ይወክላል። "ገዢ በአንተ ላይ ሲቆጣ"

ትዕግሥት ታላቁን ኃጢአት ፀጥ ያደርጋል
"ፀጥ በማለት የሚቆጣን ሰው ፀጥ ማድረግ ትችላለህ"

Ecclesiastes 10:5

ከፀሐይ በታች
ይህ በምድር ላይ የተደረጉትን ይገልፃል። የመክብብ 1:3 ትርጉም ተመልከት ተርጓሚ "በምድር ላይ" ሰነፍ በታላቅ ማዕረግ ተሾመ ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ -"ገዢዎች የመሪነት ማዕረግ ለሰነፎች ይሰጣሉ"

ባለጠጎች ግን በተዋረደ ስፍራ ተቀመጡ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "ለባለጠጎች የተዋረደ ስፍራ ይሰጣሉ"

በተዋረደ ስፍራ
ይህ ፈሊጣዊ ነው። ተርጓሚ"ጥቅም የሌለው ስፍራ (ማዕረግ)"

መሳፍንትም እንደ ባሪያዎች በምድር ላይ ሲሄዱ
ይህ መሳፍንት እንደ ባሪያዎች እንደሚሄዱ ይናገራል። ምክንያቱም ባሪያዎች ተገደው ይሄዱ ነበር።ፈረስ ላይ ለመውጣትም ፈቃድ አልነበራቸውም።

Ecclesiastes 10:8

እባብ ትነድፈዋለች
ይህ በግንብ ውስጥ ይደበቅ ስለነበረው እባብ ይገልፃል።

ድንጋይን የሚፈነቅል
ይህ በድንጋይ ካብ ውስጥ መስራትንና ትልልቅ ድንጋዮች መፈንቀል ይገልፃል።

ይታመምበታል
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ"እነዚያ ድንጋዮች ልያሳምሙት ይችላሉ። ይጎዳበታል ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። "እንጨት ሊጎዳው ይችላል።

Ecclesiastes 10:12

የጠቢብ ሰው የአፍ ቃል ሞገስ ናት
እዚህ ጋር የጠቢብ ቃል በ"አፍ"ተወክሏል። ተርጓሚ"ጠቢብ የሚናገረው ነገር የተከበረ ነው።"

የሰነፍ ከንፈሮች ግን ራሱን ይውጡታል
እዚህ ጋር የሰነፍ ቃል(ንግግር) በ"አፍ" ተወክሏል። ይህ ንግግሮች የሚባሉት ያክል ሰነፉን በንግግር እንደሚያጠፉት ይናገራል።

Ecclesiastes 10:13

የአፍ ቃል መጀመሪያ ስንፍና ነው
የሰነፍ ንግግሩ በ"አፉ" ተወክሏል። ተርጓሚ "ሰነፍ መናገር ሲጀምር"

የንግግሩ ፍፃሜም ክፉ እብደት ነው
የሰነፍ ንግግሩ በ "አፍ" ተወክሏል። ተርጓሚ "ተናግሮ ሲጨርስ ክፉ እብደትን ይናገራል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ቃሉን ያበዛል
ይህ ፈሊጣዊ ነው። ተርጓሚ"መናገሩን ይቀጥላል።" (ፈሊጣዊ ተመልከት)

በኃላ የሚሆነውን
"ወደ ፊት የሚከሰተውን ነገር"

ከእርሱ በኃላ የሚሆነውን ማን ይነግረዋል?
ፀሐፊው ይህን ጥያቄ የሚጠይቀው ማንም ሰው ከሞቱ በኃላ ወደፊት የሚሆነውን የሚያውቅ እንደሌለ አፅንኦት ለመስጠት ነው። ይህ በዐረፍተ-ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ"ከእርሱ በኃላ የሚመጣውን የሚያውቅ ማንም የለም" የሚያውቅ የለም" ወይም "ከሞተ በኃል ምን እንደሚከሰት የሚያውቅ ማንም የለም"

Ecclesiastes 10:15

ያደክመዋል
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "ሰነፍ በልፋቱ ደካማ ይሆናል።" ወይም "ሰነፍ በሚሰራው ስራ ይደክመዋል።"

ወደ ከተማ መሄድ አያውቅምና
አማራጭ ትርጉም 1) "ብዙ ጊዜ ወደ ከተማ የሚወስደውን መንገድ ስያገኝም" ሰነፍ በጣም ከመስራቱ የተነሳ ስለሚደክመው መንገዱን የትም ማግኘት አይችልም 2) " ወደ ከተማ የሚወስደው መንገድ ባለማወቁ" ሰነፍ በጣም ከመስራቱ የተነሳ ስለ ሚደክመው ወደ ቤት መሄድን በደንብ አያውቅም

Ecclesiastes 10:16

አንቺ አገር ሄይ ወዮልሽ
በዝህ ቁጥር ፀሐፊው ለህዝቡ እንደ ግለሰብ(እንደ አንድ ሰው) ይናገራል።

ንጉሥሽ ሕፃን የሆነ
"ይህ ማለት ንጉሡ ልምድ የሌለው ወይም ያልበሰለ"

ማልደው የሚበሉ
ይህ የሚያሳየው ገዢዎች ሀገር ከመምራት ይልቅ መዥናናት ላይ ማተኮራቸውን ነው።

ንጉሥሽ የከበረ ልጅ የሆነ
ይህ ልጅ ጥሩ ንጉሥ እንደሚሆን ታስቦ በተላላቆቹ መሠላጠኑን ያሳያል። ተርጓሚ "ንጉሥ" በከበሩ ሰዎች ሠልጥኖአል።"

ለብርታት..... ለስካር ያልሆነ
ይህ የተከበሩ ገዢዎች ለምን እንደሚበሉ ይገልፃል።

Ecclesiastes 10:18

በእጅ መታከት ቤት ያፈስባል
ሰነፍ ሰው ቤቱን በየጊዜው አያድስም/አይጠግብም። ተርጓሚ "ሰነፍ ሰው ቤቱን ስለ ማያድስ ጣሪያው ያፈሳል።"

በእጅ መታከት
እዚህ ጋር ሰው በእጅ ይወከላል። ተርጓሚ "በታካች ሰው ምክንያት" ወይም "ሰውየው ታካች በመሆኑ"

ቤት ያፈሳሳል
እዚህ ጋር ጣሪያው በሙሉ ቤቱ ተወክሏል። ተርጓሚ "ጣሪያው ያፈሳሳል"

እንጀራን ለሳቅ..... ያደርጉታል
"ሳቅ" የሚለው ቃል በ ግስ ሊገለፅ ይችላል። ተርጓሚ "ሰዎች ለመሳቅ እንጀራን ያዘጋጃሉ"

የወይን ጠጅንም ለሕይወት ደስታ ያደርጉታል
ተርጓሚ "የወይን ጠጅ ሰዎች በሕይወት እንዲደሰቱ ይረዳቸዋል።"

ሁሉም ለገንዘብ ይገዛል
አማራጭ ትርጉም 1)"ገንዘብ ፍላጎትን ሁሉ ያሟላል። 2)ገንዘብ ምግብንም ወይን ጠጅንም ያሟላል"

Ecclesiastes 10:20

በልብህ ሃሳብ እንኳን ቢሆን
የሰው ሃሳብ በሰው አእምሮ ተወክሏል። ተርጓሚ "በሃሳብህም እንኳን ቢሆን"

በመኝታ ቤትህም ባለጠጋን
"ባለጠጋን በመኝታ ክፍልህ ሳለህ" ይህ ማንም ሊሠማህ በማይችል በግል ሥፍራ እንኳን ሆነህ ባለጠጎችን መርገም የለብህም ማለት ነው።

ባለ ክንፎችም ነገሩን ይናገራሉና
እነዚህ ሁለት ሀረጎች አፅንኦት ለመስጠት ሲባል የተጣመሩ ሲሆን በመሰረቱም አንድ አይነት ነገር ይናገራሉ። ይህ የተናገርከውን የሚፈልጉና ሰዎችትንሽ ወፍ ያልከውን እንደሚሠሙ ያክል ሰምተው ለሌሎች ስለሚናገሩ ሠዎች ይናገራል። ተርጓሚ "ወፎች የተናገርከውን ሰምተው ነገሩን ለሌሎች ሠዎች ስለሚናገሩ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 11

1 እንጀራህን በውሃ ላይ ጣል፥ ከብዙ ቀናት በኋላ መልሰህ ታገኘዋለህ። **2** ከሰባት እንዲያውም ከስምንት ሰዎች ጋር ተካፈለው፥ በምድር ላይ የሚመጣውን ጥፋት አታውቅምና። **3** ደመና ዝናብን ከተሞላ በምድር ላይ ይለቀዋል፥ አንድ ዛፍ ወደ ደቡብ አቅጣጫ ወይም ወደ ሰሜን ቢወድቅ፥ ዛፉ በወደቀበት በዚያው ይኖራል። **4** ማንም ንፋስን የሚጠባበቅ አይተክልም፥ ደመናንም የሚጠብቅ መከሩን አይሰበስብም። **5** ንፋስ ከየት አቅጣጫ እንደሚመጣ፥ እንዲሁም የሕጻኑ አጥንቶች በእናቱ ማኅፀን ውስጥ እንዴት እንደሚያድግ እንደማታውቅ ሁሉን የፈጠረውን የእግዚአብሔር አሠራር ደግሞ ለማወቅ አትችልም። **6** በጠዋት ዘርህን ዝራ፤ እስከ ምሽትም ድረስ፥ የሚያስፈልገውን ያህል በእጆችህ ሥራ፤ የትኛው እንደሚበቅል፥ የጠዋቱ ወይም የምሽቱ፥ ይህ ወይም ያኛው፥ ወይም ሁለቱም መልካም ይሆኑ እንደኾነ አታውቅምና። **7** በእውነት ብርሃን ጣፋጭ ነው፥ ፀሐይን ማየትም ለዓይን የሚያስደስት ነገር ነው። **8** ሰው ረጅም ዘመን ቢኖር በእነዚያ ሁሉ ደስ ይበለው፥ ነገር ግን ብዙዎች ናቸውና ሊመጡ ያሉትን ጨለማ ቀናት ያስብ። የሚመጣውም ሁሉ እንደ እንፋሎት ጠፊ ነው። **9** አንተ ወጣት፥ በወጣትነትህ ደስ ይበልህ፥ በወጣትነትህም ዘመን ልብህን ደስታ ይሙላው። የልብህን መልካም ምኞትና ዓይንህ የሚያየውን ሁሉ ተከተል። ይሁን እንጂ ስለ እነዚህ ነገሮች ሁሉ እግዚአብሔር ወደ ፍርድ እንደሚያመጣህ እወቅ። **10** ከልብህ ቁጣን አስወግድ፥ የትኛውንም በሰውነትህ ያለውን ሕመም ቸል በለው፥ ወጣትነትና ብርታቱ እንፋሎት ነውና።

Ecclesiastes 11:1

እንጀራህን በውኃ ፊት ላይ ጣለው ከብዙ ቀን በኋላ ታገኘዋለህና

አማራጭ ትርጉሞች 1)ይህ ዘይቤአዊ ነው። ሰው ባለው ንብረት ላይ ለጋሽ መሆን አለበት ከዚያም ከሌሎች በቸርነት ይቀበላል። ማለት ነው 2) ሰው ሀብቱን ከባህር ማዶ ሥራ ማዋል አለበት ከዚያም ትርፉን ያገኛል። (ዘይቤአዊ ተመልከት)

ለሰባት ደግሞም ለስምንት እድል ፈንታን ክፍል

አማራጭ ትርጉሞች 1) ሀብትህን ለብዙ ሠዎች ማካፈል። 2) ሀብትን ብዙ ቦታ ላይ ሥራ ላይ ማዋል።

ሰባት ደግሞም ስምንት

"7" ደግሞም "8" ሰዎች። ይህ ፈሊጣዊ ሲሆን በርከት ያሉ ሰዎች ማለት ነው። ተርጓሚ"በርከት ያሉ ሰዎች ወይም "ብዙ ሰዎች"

በምድር ላይ የሚሆነውን ክፉ ነገር ምን እንደሆነ

"ክፉ ነገሮች" የሚለው ቃል ክፉ ነገሮች ወደ ሆነ ቦታ እንደሚመጡ ነገር አድርጎ ይናገራል። እዚህ ጋር ምናልባት "በምድር ላይ" የሚለው ሐረግ እንዲያካፍል በታዘዘው ላይ የመጣ ክፉ ነገር ሊሆን ይችላል። ተርጓሚ "በአለም ላይ የሚሆነውን ክፉ ነገር።"

ደመናት ዝናብ ቢሞሉ

"ደመናት በዝናብ ጠቁረዋል"

በምድር ላይ ያፈስሱታል

"በመሬት ላይ ያፈስሱታል"

ወደ ደቡብ ወይም ወደ ሰሜን

እዚህ ጋር ደቡብና ሰሜን ሁለቱም አቅጣጫ ይወክላሉ። ተርጓሚ "በየትኛውም አቅጣጫ"

Ecclesiastes 11:4

ነፋስን የሚጠባበቅ አይዘራም

አማራጭ ትርጉሞች 1) "ለነፋስ ትኩረት የሚሰጥ የትኛውም ገበሬ ነፍስ በተሳሳተ አቅጣጫ ሲነፍስ አይዘራም" 2) "ለነፋስ በጣም ትኩረት የሚሰጥ የትኛውም ገበሬ መቼም አይዘራም"

ደመናትንም የሚመለከት አያጭድም

አማራጭ ትርጉሞች 1) ለደመናት ትኩረት የሚሰጥ የትኛውም ገበሬ ሊዘንብ ባለ ጊዜ መቼም አያጭድም" 2) ለደመናት በጣም ትኩረት የሚሰጥ የትኛውም ገበሬ መቼም አያጭድም"

የነፋስን መንገድ..... እንደማታውቅ

ይህ ነፋስ በመንገድ ላይ እንደሚራመድ አድርጎ ያናገራል። ተርጓሚ "ነፋስ ከወዴት እንደሚመጣ ወይም ወዴት እንደሚሄድ እንደማታውቅ" (ዘይቤአዊ ተመልከት)

አጥንትም በእርጉዝ ሆድ

አማራጭ ትርጉሞች 1) "አጥንት" የሚለው ቃል ሙሉ ሕፃንን ይወክላል። ተርጓሚ"ሕፃን እንዴት እንደሚያድግ ወይም 2) ቀስ በቀስ የሕፃን አጥንት እንዴት እንደሚያድግ"

Ecclesiastes 11:6

እጅህን አትተው

እዚህ ጋር እጅ ሙሉ ሰውን ይወክላል። ተርጓሚ "መስራትህን ቀጥል"

ወይም ይህ ወይም ያ ..... በማለዳ ..... በማታም

እዚህ ጋር ሁለት ሐረጎች በመሰረቱ አንድ ሲሆኑ የሰው ሥራ መቼም ቢሠራው እንደሚሣካ አፅንኦት ለመስጠት ነው። ተርጓሚ "በማለዳ የዘራኸውን ዘር ወይም በማታ የዘራኸው ዘር"

ብርሃን ጣፋጭ ነው

እዚህ ጋር ብርሃን የሚለው ቃል ፀሐይን ማየት መቻልንና በሕይወት መኖርን ይወክላል። እና ይህ የሚናገረው ስለ በሕይወት መኖር ሐሴት ማድረግን ልክ ብርሃን ጣፋጭ ነገር የሆነ ያክል። ተርጓሚ "ፀሐይን ማየት ሐሴት ነው ወይም በሕይወት መኖር ያስደስታል።"

ፀሐይም ማየት ለዓይን

"ዓይን" ሙሉ ሰውን ይወክላል። ይህ ሐሳብ ከበፊቱ ሀሳብ ጋር ተመሣሣይ ነው። ተርጓሚ "ፀሐይን እንዲያይ" ወይም "በሕይወት መኖር"

በሁለቱም ደስ ይበለው

እዚህ ጋር "በሁሉም" የሚለው ቃል ሰው በእድሜው ዘመን የሚኖረውንዘመን ይገልፃል።

የጨለማውን ዘመን ..... የሚመጣው

ቀናት እንደሚመጡ ያክል ስለ ወደፊት ይናገራል። እዚህ ጋር "ጨለማ "ሞትን" ይገልፃል። ተርጓሚ "ምን ያህል ቀናት ሟች እንደሚሆን"

ብዙ ቀን ይሆናልና

እዚህ ጋር "ብዙ" የሚለው ቃል የጨለማውን ቀናት ይገልፃል። ተርጓሚ "በሕይወት ከኖረው ዘመን የበለጠ ሟች ስለሚሆን" ወይም "ዘላለም ሟች ስለሚሆን"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የሚመጣው ነገር ሁሉ ከንቱ ነው
እዚህ ጋር "ከንቱ" የሚለው ቃል ዘይቤአዊ ነው። አማራጭ ትርጉሞች 1)"ከሞተ በኋላ ምን እንደሚከሰት ማንም የሚያውቅ የለም" 2) ሊመጣያለው ነገር ሁሉ ትርጉም የለውም"

የሚመጣው ነገር ሁሉ
አማራጭ ትርጉሞች 1) "ከሞት በኋላ የሚከሰቱ ነገሮች ሁሉ" 2) ወደ ፊት የሚከሰቱ ነገሮች ሁሉ"

Ecclesiastes 11:9

አንተ ጎበዝ በጉብዝናህ ደስ ይበልህ በጉብዝናህም ወራት ልብህን ደስ ይበለው
እነዚህ ሐረጎች አንድ አይነት ነገር ሲናገሩ አንድ ላይ የተጣመሩትም ሠው በዝናው ሊደሰት ይገባል ለሚለው ሐሳብ አፅንኦት ለመስጠት ነው።

ልብህን ደስ ይበለው
እዚህ ጋር ልብህ የሚለው ቃል ስሜትን ይወክላል። ተርጓሚ "ሐሴትን አድርግ"

በልብህም መንገድ ሂድ
እዚህ ጋር "ልብ የሚለው ቃል አእምሮን ወይም ስሜትን ሊወክል ይችላል። ተርጓሚ "የምትመኘውን መልካም ነገር ተከተል" ወይም ልትከተል የወሰድከውን መልካም ነገሮች ተከተል"

ዓይኖችህም በሚያዩት
እዚህ ጋር "አይን" ሙሉ ሠውን ይወክላል። ተርጓሚ "አይተህ የተመኘኸውን" ወይም "አይተህ በጣም የተሻለውን"

ስለዚህ ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ወደ ፍርድ እንዲያወጣህ
ፍርድ የሚለው ቃል "ተጠያቂ ያደርግሃል" በሚለው ሊተካ ይችላል። ተርጓሚ "በነዚህ ነገሮች ሁሉ ምክንያት እግዚአብሔር ይፈርድብሃል" ወይም "ላደረግኽው ነገር በሙሉ ተጠያቂ ያደርግ ሃል"

ከልብህ ሃዘንን አርቅ
ለማዘን አለመፈለግ፤ ሐዘንን ማስወገድ እንደሚቻል አድርጎ ይናገራል "ልብም የሰውን ስሜት ይወክላል። ተርጓሚ "ለማዘን ፈቃደኛ አትሁን"

ሕፃንነትና ጉብዝና ከንቱዎች ናቸውና
ፀሐፊው ከንቱ እንደሚጠፉና ዘላቂ የሆነውን ያክል እርባና ቢስና ትርጉም ስለሌላቸው ነገሮች ይናገራል። ፀሐፊው ዘላቂ ጥቅም ስለሌላቸው ነገሮች ይናገራል። የመክብብ 1:14 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ "ምክንያቱም ሕፃንነትና ጉብዝና ለዘላለም አይደሉም ወይም ምክንያቱም ለዘላለም (ሁሉ ጊዜ) ሕፃንና ጎበዝ አትሆንም።"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 12

1 አስቸጋሪዎቹ ቀናት ሳይመጡ፥ "ደስ አያሰኙኝም" የምትላቸው ዓመታትም ሳይደርሱ፥ **2** የፀሐይ፥ የጨረቃና የከዋክብት ብርሃን ሳይጨልም፥ የጠቆረው ደመና ከዝናብ ኋላ ሳይመለስ፥ በወጣትነት ዘመንህ ፈጣሪህን አስብ። **3** ያ ጊዜ የቤተ መንግሥት ጠባቂዎች የሚርበደበዱበት፥ ብርቱዎች የሚጎብጡበት፥ ጥቂቶች በመሆናቸው የሚፈጩት ሥራቸውን የሚያቆሙበት፥ በመስኮት ወደ ውጪ የሚመለከቱ አጥርተው የማያዩበት፥ ይሆናል። **4** ያ ጊዜ በጎዳናው ላይ በሮች የሚዘጉበትና የወፍጮ ድምጽ የሚቆምበት፥ ከወፍ ድምጽ የተነሣ ሰዎች የሚደነግጡበትና የሚዘምሩ ልጃገረዶች ድምጻቸው ዝግ የሚልበት ይሆናል። **5** ያ ጊዜ ሰዎች ከፍታዎችንና በመንገድ ላይ የሚገጥማቸውን አደጋ በማሰብ የሚፈሩበት፥ የለውዝ ዛፍ ሲያብብ፥ አንበጣዎች ተከታትለው ሲሳቡ፥ ተፈጥሯዊ ፍላጎት የሚጠፋበት ጊዜ ነው። ሰው ወደ ዘላለም ቤቱ ይሄዳል፥ አልቃሾችም በጎዳናዎቹ ላይ ይወርዳሉ። **6** የብር ሰንሰለት ሳይበጠስ ወይም ጎድጓዳው የወርቅ ሳሕን ሳይሰበር ወይም እንስራው በምንጩ አጠገብ ብትንትኑ ሳይወጣ ወይም የውሃ ማውጫው ጉድጓዱ ውስጥ ሳይበጠስ፥ **7** አፈር ወደ መጣበት መሬት ሳይመለስና መንፈስም ወደ ሰጪው ወደ እግዚአብሔር ሳይመለስ ፈጣሪህን አስብ። **8** አስተማሪው፥ "የሚተን እንፋሎት፥ ሁሉም ነገር የሚጠፋ እንፋሎት ነው" ይላል። **9** አስተማሪው ጠቢብ ነበር፥ ለሕዝቡም እውቀትን አስተማረ። ብዙ ምሳሌዎችን መረመረና አጠና፥ በስርዓትም አስቀመጣቸው። **10** አስተማሪው ግልጽና ቅን የእውነት ቃላትን በመጠቀም ለመጻፍ ፈለገ። **11** የጠቢባን ቃል አንደ ከብት መንጃ አርጩሜ ነው። ጠልቀው እንደ ገቡ ሚስማሮች አንድ እረኛ ያስተማራቸውና አስተማሪዎች የሰበሰቧቸው ምሳሌዎችም እንዲሁ ናቸው። **12** ልጄ ሆይ፥ በይበልጥ አንድ ነገር ተጠንቀቅ፡ ብዙ መጻሕፍት መጻፍ ማለቂያ የለውም። ብዙ ማጥናትም ሰውነትን ያደክማል። **13** ሁሉም ነገር ከተሰማ በኋላ የጉዳዩ መጨረሻ እግዚአብሔርን እንድትፈራውና ትዕዛዙን እንድትጠብቅ ነው፥ ይህ የሰው ሙሉ ተግባሩ ነውና። **14** መልካምም ይሁን ክፉ፥ የተደረገውን ሁሉ፥ ከተሰወረው ነገር ሁሉ ጋር፥ እግዚአብሔር ወደ ፍርድ ያመጣዋልና።

Ecclesiastes 12:1

አስብ
ይህ ፈሊጣዊ ነው። ተርጓሚ "አስታውስ"

የጭንቀት ቀን ሳይመጣ
ቀናት እንደሚመጡ ያክል ስለወደፊት ይናገራል። ተርጓሚ "የጭንቀት ቀን ሳይመጣብህ" ወይም "ክፉ ነገር ሳይደርስብህ በፊት" (ዘይቤአዊ ተመልከት)

ደስ አያሰኙትም የምትላቸው ዓመታት ሳይደርሱ
ዓመታት እንደሚመጡ ያክል ስለወደፊት ይናገራል። ተርጓሚ "ሳታረጅና በመኖር ከዚህ በኃላ ደስ አልሰኝም ከማለትህ በፊት"

ሳይደርሱ ፀሐይና ብርሃን .....ከዝናብ በኋላ
ፀሐይና ጨረቃ እንደሚጠቁሩና ጥቁር ዳመናም እንዳሚመስል ያክል ስለ ማርጀትና ሞት ይናገራል። ተርጓሚ"ፀሐይና ብርሃን ሳይደርሱ ከዝናብ በኋላም ሳይመስልህ ይህንን አድርግ" (ዘጥቤዘዊ ተመልከት)

Ecclesiastes 12:3

x
ፀሐይ ምንም ተግባር መከናወን ስለቆመበት ቤት ይናገራል። ይህ ሰው ሰውነቱ እያረጀ ሲመጣ ፈሊጣዊ ይሆናል። (ዘይቤአዊ ተመልከት)

ኃያላን ሰዎችም በሚጎብጡበት
"ኃያላን ደካማ ይሆናሉ"

ጥቂቶች ሆነዋልና ፈጭታዎች ሥራ በሚፈቱበት
"ሚፈጨው ነገር ጥቂት ከመሆኑ ፈጭታዎቸ ሥራ ያቆማሉ"

Ecclesiastes 12:4

x
ፀሐፊው ዘይቤአዊ ንግግሩን ቀጥሏል።

ደጆች በሚዘጉበት ቀን
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ"ሰዎች ወደ መንገድ የሚያሳየውን መንገድ ይዘጋሉ"

ከወፍ ድምፅ የተነሣ ሰው ሲነሣ
ይህ የወፍ ድምፅ ሰዎችን ሲቀሰቅስ ይገልፃል። ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "የወፍ ድምፅ ሰዎችን ለማስነሣት ሲቀሰቅስ"

የሚጮኹ ሴቶች ልጆች ሁሉ ዝግ ሊሉ
እዚህ ጋር ሴቶች ልጆች "ለወፎቹ ፈሊጣዊ ነው። ተርጓሚ "የወፎቹ ዜማ ዝግ ይላል"

Ecclesiastes 12:5

x
ፀሐፊው ዘይቤውን ቀጥሏል።

ለውዝም ሲያብብ
የለውዝ ተክል በበጋ ነጭ አበባን የሚያብብ ተክል ነው።

አንበጣም እንደ ሸክም ሲከብድ
አንበጣ ትልቅ ነው። ቀጥ ያለ ክንፍ ረጅም ርቀት እንዘል ወዳ ኋላ ከተጋጠሙ ረጅም እግሮች ጋር ስላረጀና ደካማ ስለሆነ እራሱን ብቻ ነው መሸከም የሚችለው።

ፈቃድም ሲጠፋ
ፈቃድ የሚለው ስውር ቃል እና ግስ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "ሰዎች ከዚህ በፊት ያደረጉትን ሴይመች ሊቀሩ"

ሰው ወደ ዘላለም ቤት ሲሄድ
ይህ ሞትን ይገልፃል። ተርጓሚ "ሰው ወደ መሞቻ ስፍራው ይሄዳል። ወይም "ሰው ይሞታል ዳግም ወደ ሕይወት አይመለሥም"

አልቃሾችም በአዳባባይ ሲዞሩ
አመራጭ ትርጉሞች 1)ቀብሩን ለመመልከት አልቃሾች ወደ አዳባባይ ሲሄዱ 2) አልቃሾች ለሞት ወደ ተቃረበው ሰው ቤት ለመሄድ ወደ አዳባባይ ሲሄዱ"

Ecclesiastes 12:6

አስብ
ይህ ፊሊጣዊ ነው። ተርጓሚ"አስታውስ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የብር ድሪ ሳይበጠስ የወርቅም ኩስኩስት ሳይሰበር ማድጋውም በምንጭ አጠገብ ሳይከሰከስ
ይህ ሞት ከእነዚህ ተሰባሪ ነገሮች አንዱ የሆነ ያክል ስለመሞት ይናገራል። ሰዎቸ እነዚህን ነገሮች ሊጠቀሙበት ድንገት እንደሚሠብሩ ሁሉ ሞትም ሰውነትን ይሰብራል።

የብር ድሪ ሳይበጠስ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "የሆነ ሰው የብር ድሪ ይበጥሳል"

የወርቅ ኩስኩስት ሳይሰበር
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "የሆነ ሰው ማድጋ ይሰብራል"

መንኮራኩርም ሳይሰበር
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍይችላል። ተርጓሚ "የሆነሰው መንኮራኩሩን ይሰብራል"

አፈርም ወደ ነበረበት ምድር ሳይመለስ
እዚህ ጋር አፈር የሚለው ቃል የሚበስብስውን ሰውን አካል ይገልፃል።

Ecclesiastes 12:8

ከንቱ ፤ ከንቱ ፤ ሁሉ ከንቱ ነው
ሰባኪው ከንቱ እንዲሚጠፋና ዘለቄታ እንደ ሌላቸው ሁሉ እርባና ቢስና ትርጉም ስለሌላቸው ነገሮች ይናገራል። ፀሐፊው ዘላቂ ጥቅም ስለሌላቸው ነገሮች ይናገራል። የመክብብ፡1:14፡ ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ "ጊዜያዊና እርባና ቢስ ..... ሁሉም ነገር ትርጉም የለሽ ነው (ዘይቤአዊ ተመልከት)

ሰባኪው
የመክብብ ፡1:1፡ትርጉምን ተመልከት

መረመረና ፈለለገ አስማማም
"በጣም አሰበም አስማማም " ወይም "በጣም አሰበበትና ፃፈ"

Ecclesiastes 12:10

በቅንም ..... ቃል ፈለገ
ሲባልም ቃለቱ ለአድማጭአስደሳች እንዲሆኑ ፈለገ ሰለሚመቹ ሳይሆን በደንብ ስለተፃፈያስደስታሉ።

የጠቢባን ቃል .....ከአንድ እረኛ የተሰጡት
ፀሐፊው ሰባኪው እረኛ በትሩን መንጋውን ለመምራት እንደ ሚጠቀም ሁሉ ሰበኪው ሰዎችን ለማስተማር የራሱን ቃለት ይጠቀማል። (ዘይቤአዊ ተመልከት)

የጠቢባን ቃል እንደ በሬ መውጊያ ነው
ይህ ተነፃፃሪ ነው። ተርጓሚ "ከብት እንዲንቀሳቀስ የበሬ መውጊያ እንደ ሚጠቅም ጠቢባንም ሰዎች እንዲንቀሳቀሱ ያበረታታሉ።

የተሰበሰቡትም ቃላት እንደተቸነከሩ ችንካሮች ናቸው
ይህ ተነፃፃሪ ነው። በደንብ በተቸነከሩ ችንካሮች እንደምትተማመን ሁሉ እንዲሁ በምሳሌ በተሰበሰቡ የጠቢባን ቃል ላይም መተማመን ትችላለህ"

የጠቢብን ቃል .....የተሰበሰቡትም
ጠቢብ ቃለት በምሳሌ የተሰበሰቡ ናቸው። ወይም "የጠቢባን አባባል"

በአንድ እረኛ የተሰጡት
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "አንድ እረኛ የሚያሰተምረው"

Ecclesiastes 12:12

ብዙ መፃሕፍትን ማድረግ ፍፃሜ የለውም
ማድረግ የሚለው ቃል ። በግስ መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "ሰዎች ብዙ መፅፍትን ማድረግ መቼም አያቆሙም ።"

ሰውነትን ያደክማል
እዚህ ጋር "ሰውነት" የሚለው ቃል ሙሉ ሰውን ይወክላል። ተርጓሚ "ሰውን ያደክማል"

Ecclesiastes 12:13

የነገር ሁሉ ፍፃሜ
"በነገር ላይ የመጨረሻው መደምደሚያ"

ፍፃሜ እንስማ ይህ .....ነውና
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "ከሁሉንም ነገር ከሰማህ በኋላ"

የተሰወረውንም ነገር ሁሉ
ይህ የተሰወረው ነገር እቃ እንደተደበቀ ነገር ይናገራል።ተርጓሚ "ሰዎች በድብቅ ከሚሠሩትነገር ሁሉ ጋር " (ዘይቤአዊ ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Song of Solomon

Song of Solomon

Chapter 1

1 ከመዝሙሮች የሚበልጥ የሰለሞን መዝሙር። ልጃገረዲቱ ፍቅረኛዋን እንዲህ ትለዋለች፥ **2** ኦ በአፍህ መሳም በሳምከኝ፥ ፍቅርህ ከወይን ጠጅ ይሻላልና። **3** ሽቶህ አስደሳች መዓዛ አለው፤ ስምህ እንደሚፈስ ሽቶ ነው፥ ስለዚህ ልጃገረዶች ወደዱህ። **4** ካንተ ጋር ውሰደኝ፥ አብረንም እንሮጣለን። ሴቲቱ ለራሷ ትናገራለች፥ ንጉሡ ወደ ቤቱ ውስጥ አስገባኝ። ሴቲቱ ፍቅረኛዋን እንዲህ ስትል ትናገረዋለች፥ ደስ ብሎኛል፤ ስለ አንተ ደስ ይለኛል፤ በፍቅርህ ሐሴት ላድርግ፤ እርሱ ከወይን ጠጅ ይሻላል። ሌሎቹ ሴቶች ቢያደንቁህ ተፈጥሮአዊ ነው **5** አንደኛዋ ሴት ለሌላይቱ ስትናገር፥ እኔ ጥቁር ነኝ፥ ቢሆንም ውብ ነኝ፥ እናንተ ከኢየሩሳሌም ወንዶች የተወለዳችሁ ሴቶች ልጆች፥ እንደ ቄዳር ድንኳኖች ጥቁር፥ እንደ ሰለሞንም መጋረጃዎች ውብ ነኝ። **6** ጥቁር ስለ ሆንኩ ትኩር ብላችሁ አትመልከቱኝ፥ ምክንያቱም ፀሐይ አጥቁሮኛል። የእናቴ ልጆች ወንድሞቼ ተቆጡኝ፥ የወይን አትክልት ጠባቂም አደረጉኝ፥ የራሴን የወይን ቦታ ግን አልጠበቅሁም። ሴቲቱ ለፍቅረኛዋ ስትናገር፥ **7** ንገረኝ የምወድህ፥ መንጋህን የምታሰማራው የት ነው? በቀትር ጊዜስ መንጋህን የምታሳርፈው የት ነው? ከባልንጀሮችህ መንጋ ኋላ እንደሚቅበዘበዝ ሰው ለምን እሆናለሁ? ፍቅረኛዋ ሲመልስላት፥ **8** ከሴቶች ሁሉ እጅግ የተዋብሽው ሆይ፥ አታውቂ እንደሆነ፥ የመንጋዬን ኮቴ ተከተይ፥ የፍየል ግልገሎችሽንም በእረኞቹ ድንኳን አጠገብ አሰማሪ። **9** የኔ ፍቅር፥ በፈርዖን የሰረገላ ፈረሶች መካከል ካለችው ባዝራ ጋር አመሳሰልሁሽ። **10** ጉንጮችሽ በማስዋቢያ ተውበዋል፥ አንገትሽም በዕንቁ ሐብል። **11** የብር ፈርጥ ያለበት የወርቅ ማጌጫ እሠራልሻለሁ። ሴቲቱ ለራስዋ ስትናገር፥ **12** ንጉሥ ማዕዱ ላይ እያለ፥ የናርዶስ ሽቶዬ መዓዛውን ናኘው። **13** ውዴ ለእኔ ልክ ሌሊቱን ሙሉ በጡቶቼ መካከል እንደሚያርፍ እንደ ተቋጠረ ከርቤ ነው። **14** ውዴ ለእኔ በዓይንጋዲ የወይን ቦታ ውስጥ እንደ ሂና የአበባ ዕቅፍ ነው። ፍቅረኛዋ ሲናገራት፥ **15** ወዳጄ ሆይ፥ እነሆ አንቺ ውብ ነሽ፤ እነሆ ያማርሽ ነሽ፤ ዓይኖችሽ እርግቦችን ይመስላሉ። ሴቲቱ ለፍቅረኛዋ ስትናገር፥ **16** ውዴ ሆይ፥ እነሆ አንተ መልከ መልካም ነህ፥ ያማርክም ነህ። የለመለመው ሣር እንደ አልጋ ያገለግለናል። **17** የቤታችን የማዕዘን ተሸካሚ የዝግባ እንጨት፥ የጣሪያችን ማዋቀሪያም የጥድ እንጨት ነው።

Song of Solomon 1:1

አጠቃላይ መረጃ
የመጽሐፉ ክፍል አንድ ከመኃልየ መኃልይ 1:2 ይጀምራል።

የመዝሙራት መዝሙር
“ምርጥ መዝሙር” ወይም “እጅግ በጣም ምርጥ የሆነ መዝሙር”

የሰለሞን የሆነው
“ስለ ሰለሞን የሆነው” ወይም “ሰለሞን ያቀናበረው” አማራጭ የሚሆኑ ትርጉሞች ናቸው።

ፍቅርህ ከወይን ጠጅ ይልቅ
“ወይን በመጠጣት ከምደሰተው ይልቅ በአጠገቤ መሆንህ ያስደስተኛል”

ሽቱህ
“የተቀባኸው ሽቱ”

አስደሳች መዓዛ አለው
“አስደናቂ ሽታ አለው”

ስምህ እንደሚፈስ ሽቱ ነው
ሽቱ አየሩ በሚነፍስበት ጊዜ አካባቢውን የሚያዳርስ ጥሩ ሽታ አለው። ስሙ 1) ሰውየው ላለው ምስክርነት፣ ሌሎች ስለ እርሱ ስለሚያስቡት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። እዚህ ጋ፣ ተናጋሪው፣ ሰዎች አድማጮቹ ጥሩ ሰው እንደሆነ ሁልጊዜ ያስባሉ ይላል፣ ወይም 2) ሰውየውን ራሱን አመልካች ይሆናል።

ከአንተ ጋር
“አንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰውየውን ስለሆነ ነጠላ ቁጥር ነው።

ውሰድ
“ሳብ” ወይም “ጎትት”፣ እዚህ ጋ ሴቲቱ ማራኪዋን ለመከተል ፈቃደኛ እንደሆነች ምርኮኛ ሆና ተገልጻለች።

እንሮጣለን
በውስጠ ታዋቂ ያለው “እኛ” የሚለው ቃል ከሰውየው ጋር ያለችውን ወጣት ሴት ያመለክታል።

ደስ ይለናል ... ሐሴት እናደርጋለን ... በዓል እናድርግ
ሴቲቱ ከአንድ ሰው በላይ አድርጋ ስለ ራሷ ትናገራለች። የተከፈተው ተለዋጭ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም እንደሚያደርገው ሁሉ በርካታ ትርጉሞች ተውላጠ ስሙን ወደ “እኔ” ይለውጡታል። ሌሎች ትርጉሞች እነዚህን የሴቲቱ ባልንጀሮች ስለ ሴቲቱ ወይም ስለ ሰውየው ንግግር እንደሚያደርጉ አድርገው ያቀርባሉ።

ስለ አንተ
“በአንተ ምክንያት”

በዓል እናድርግ
“እናመስግን”

ሌሎች ሴቶች አንተን ማድነቃቸው ተፈጥሮአዊ ነው
“የሚያደንቁህ ሴቶች ያደረጉት ማድረግ የሚገባቸውን ነው”

Song of Solomon 1:5

እኔ ጥቁር ነኝ፣ ነገር ግን ውብ ነኝ
“ቆዳዬ ጥቁር ነው፣ ነገር ግን ቆንጆ ነኝ” ወይም “ቆዳዬ ቢጠቁርም ቆንጆ ነኝ”

የኢየሩሳሌም ሴቶች ልጆች
“የኢየሩሳሌም ወጣት ሴቶች”፣ እነዚህ ወጣት ሴቶች በዚያ ስላልነበሩ ሊሰሟት አይችሉም፣ ነገር ግን ሴቲቱ እንዳሉና ሊሰሟት እንደሚችሉ ቆጥራ ትናገራለች።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንደ ቄዳር ድንኳኖች ጥቁር
የቄዳር ዘላን ጎሳዎች ቤቶቻቸውን ለመሥራት የጥቁር ፍየሎችን ቆዳ ይጠቀሙ ነበር። ሴቲቱ የራሷን የቆዳ ቀለም ከእነዚህ ድንኳኖች ጋር ታነጻጽራለች።

እንደ ሰለሞን መጋረጃ ውብ
ሰለሞን ለራሱ ቤተ መንግሥት ወይም ለቤተ መቅደሱ የተዋቡ መጋረጃዎችን ሠርቶ ነበር። እርሷ የቆዳ ቀለሟ ቆንጆ መሆኑን ትናገራለች።

በእሳት የተለበለበ
ይህ “የተቃጠለ” ወይም “የጠቆረ” ለሚለው የሚውለው ግነት የሚያመለክተው ፀሐይ ቆዳዋን ከብሩኅነት ወደ ጥቁረት መለወጡን ነው።

የእናቴ ወንዶች ልጆች
“በእናቴ በኩል ወንድሞቼ የሆኑ”፣ እነዚህ ወንድሞች ከአንድ አባት ባይሆንም እንደ ሴቲቱ ሁሉ ከአንድ እናት የተወለዱ ይሆኑ ይሆናል።

የወይን ቦታ ጠባቂ አደረጉኝ
“የወይኑን ቦታ እንድንከባከብ አደረጉኝ”

የራሴን የወይን ቦታ ግን አልጠበቅሁም
ሴቲቱ ራሷን ከወይን ቦታ ጋር ታነጻጽራለች። አ.ት፡ “የራሴን የወይን ቦታ ግን መንከባከብ አልቻልኩም”

Song of Solomon 1:7

ነፍሴ የምትወድህ
ነፍስ ሰውን ገላጭ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “የምወድህ”

መንጋህን የምታሰማራው
“መንጋህ ሣር እንዲግጡ የምታደርግበት”

መንጋህን የምታሳርፍበት
“መንጋህ እንዲጋደሙ የምታደርግበት”

ከጓደኞችህ መንጋ አጠገብ እንደሚቅበዘበዝ ሰው የምሆነው ለምንድነው?
ሴቲቱ ከሌሎች ሴቶች ይልቅ ከሰውየው ጋር የቅርብ ግንኙነት እንዳላት አጽንዖት ለመስጠት ይህንን ጥያቄ ትጠይቃለች። ጥያቄው እንደ መግለጫ ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “አንተን በምፈልግበት ጊዜ በጓደኞችህ መንጋ መካከል እንዳልቅበዘበዝ ንገረኝ”።

የምትቅበዘበዝ
“የምትዞር”፣ ሰውየውን የምትፈልግ መስላ መታየት አትፈልግም። ምናልባት ሌሎች ሰዎች የዝሙት ሥራ የምትፈልግ ሴት አዳሪ አድርገው እንዳያስቧት ሳትፈራ አትቀርም።

ጓደኞችህ
“ባልንጀሮችህ” ወይም “የሥራ ባልደረቦችህ”

Song of Solomon 1:8

በሴቶች መካከል እጅግ የተዋብሽ
“አንቺ ከሴቶቹ ሁሉ እጅግ የተዋብሽ ሆይ”

የመንጋዬን ፍለጋ ተከተዪ
“ከመንጋዎቹ ኋላ ተከተዪ”

ፍለጋ
በመሬት ላይ የሚቀር የመንጋው የኮቴ ምልክት

የፍየል መንጋዎችሽን አሰማሪ
“የፍየል ግልገሎችሽ ሣር እንዲግጡ አድርጊ” ወይም “የፍየል ግልገሎችሽ እንዲመገቡ አድርጊ”

Song of Solomon 1:9

አጠቃላይ መረጃ
ሰውየው ለሴቲቱ መናገሩን ይቀጥላል።

የኔ ፍቅር፣ በፈርዖን የሰረገላ ፈረሶች መካከል ባለች ባዝራ እመስልሻለሁ
የዚያ ዘመን አይሁድ የፈረሶችን ውበት ያደንቁ ነበር፣ እርሱ የፈርዖንን ፈረሶች እጅግ የተዋቡ ሆነው አግኝቷቸዋል። ሰውየው ወጣቷ ሴት ውብ እንደሆነች ያስባል። አ.ት፡ “የኔ ፍቅር፣ ከፈርዖን የሰረገላ ፈረሶች እንደ አንዱ ውብ ነሽ”

የኔ ፍቅር
“የምወድሽ”

የፈርዖን የሰረገላ ፈረሶች
“የፈርዖንን ሰረገላዎች የሚጎትቱ ፈረሶች”

ጉንጮችሽ ከጌጣጌጦቹ ጋር ውቦች ናቸው
እነዚህ ጌጣጌጦች 1) በጭንቅላት ዙሪያ በክር የሚታሰሩ ፈርጦች ወይም 2) የጆሮ ጉትቻዎች ወይም 3) ረጅም ጸጉሯን የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ሊሆን ይችላል።

እንሠራልሻለን
ሰውየው ራሱን እንደ ብዙ ሰው አድርጎ ይናገራል። አንዳንድ ትርጉሞች ይህንን “እኔ” ወደሚል ነጠላ ቁጥር ይቀይሩታል። ሌሎች ትርጉሞች እነዚህን ቃላት የሴቲቱ ጓደኞች ንግግር እንደሆነ አድርገው ይወስዱታል።

የብር ፈርጥ
“የብር ጠቃጠቆ”

Song of Solomon 1:12

መከዳው ላይ ተጋድሞ
“ልዩ ማዕዱን ለመብላት ተቀምጧል”፣ ይህ ምናልባት በግብዣ ጠረጴዛ ዙሪያ ሰዎች ከሚጋደሙባቸው መከዳዎች አንዱን ያመለክት ይሆናል። ሰዎች ልዩ ማዕድ በሚበሉበት ጊዜ አካላቸውን የሚያሳርፉበትን የተለመደ ቃል በመጠቀም መተርጎም ትችላለህ።

ናርዶስ
ሰዎች ውድ ከሆነው ከናርዶስ ወይም የናርዶስ ተክል የሚያገኙት ዘይት (ትናንሽ ሮዝ ወይም ነጭ አበባ ያለው ተክል” ሲሆን ሰውነታቸውን ለማለስለስና አስደሳች መዓዛ እንዲኖራቸው ለማድረግ ይጠቀሙበታል።

መዓዛውን ናኘ
“መልካም ሽታውን ለቀቀው”

የእኔ ተወዳጅ በጡቶቼ ... እንደ ከርቤ መቋጠሪያ ነው
ሴቶች በአንገት ጌጣቸው ላይ አነስተኛ የከርቤ መቋጠሪያ ወይም መከዳ በጡቶቻቸው መካከል እንዲያርፍ በማድረግ በጣፋጭ መዓዛው ይደሰቱ ነበር። ይህቺ ሴት በቅርቧ ባለው ፍቅረኛዋ ትደሰታለች። እንዲህ ባለው መንገድ፣ ሌላ ማንም፣ ከፍቅረኛዋ ጋር ግንኙነት እንዲኖረው እንደማትጠብቅ ለማሳየት “ለእኔ” የሚለውን ቃል ትጨምራለች። አ.ት፤ “በጡቶቼ ... በከርቤ መቋጠሪያ ደስ እንደሚለኝ በፍቅረኛዬ ደስ ይለኛል”።

ፍቅረኛዬ
ይህ ቃል ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች “የእኔ አፍቃሪ” ብትለው የተለመደ ሊሆን ይችላል። አ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ አፍቃሪ”።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በጡቶቼ መካከል እንዳረፈ
ይህ ሐረግ አንባቢዎችህን የሚያሳዝን ከሆነ ሻል ባለ ቃል መጠቀም ትችላለህ። አ.ት፡ “ለእኔ ቅርብ ሆኖ”

ፍቅረኛዬ ለእኔ እንደ ሄና የአበባ ዕቅፍ ነው
የሄና አበቦች ሰዎች ደስ የሚሰኙበት መዓዛ አላቸው። ሴቲቱ በፍቅረኛዋ ትደሰታለች። እንዲህ ባለው መንገድ ሌላ ማንም ከፍቅረኛዋ ጋር ግንኙነት እንዲኖረው እንደማትጠብቅ ለማሳየት “ለእኔ” የሚለውን ቃል ትጨምራለች። አ.ት፡ “በሄና ዕቅፍ አበባ ሽታ ደስ እንደሚለኝ በፍቅረኛዬ እደሰታለሁ”።

የሄና አበቦች
ሰዎች ለሽቱነት የሚጠቀሙበት በአነስተኛ ሸለቆ የሚገኝ የአበባ ዓይነት

Song of Solomon 1:15

አንቺ፣ ስሚ
“አንቺ፣ ልናገረው ያለው እውነትና አስፈላጊ ስለሆነ ልብ በይ”

የእኔ ፍቅር
“የምወድህ አንተ”፣ መኃልይ 1:9ን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

ዓይኖችሽ እርግቦች ናቸው
1) እስራኤላውያን፣ እርግቦች ገርና ለስላሳ ወፎች እንደሆኑ ያስቡ ነበር፤ ሰውየው የሴቲቱ ዓይኖች ውቦች እንደሆኑ ያስባል፤ ምክንያቱም ሴቲቱ ወደ እርሱ የምትመለከትበት አኳኋን ገር ናት ብሎ እንዲያስብ ያደርገዋል። አ.ት፡ “አንቺ በጣም ገር ነሽ” ወይም 2) ሰውየው የሚናገረው ስለ ሴቲቱ ነጭ የዓይኗ ክፍል ወይም የዓይኖቿ ቅርፅ የእርግቦቹን ቅርፅ ስለመምሰላቸው ነው የሚሉት አማራጭ ትርጉሞች ናቸው።

Song of Solomon 1:16

አንተ፣ ስማ
“አንተ፣ ልናገረው ያለው እውነትና አስፈላጊ ስለሆነ ልብ በል”

ውብ
በአንተ ቋንቋ፣ መልከ መልካም የሆነ ወንድ የሚገለጽበትን ቃል ተጠቀም።

የእኔ ፍቅር
ይህ ሐረግ ሴቲቱ የምትወደውን ሰው ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች እርሷ “የእኔ አፍቃሪ” ብላ ብትጠራው ይበልጥ የተለመደ ሊሆን ይችላል። ይህንን በመኃልየ መኃልይ 1:13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ አፍቃሪ”።

ለምለሞቹ ሣሮች መኝታዎቻችን ናቸው
መኝታ የሚሆኑ ይመስል ይህ የሚናገረው ስለ ለምለሞቹ ሣር ነው። አ.ት፡ “ለማንቀላፋት የምንተኛው በለመለሙት ሣሮች ላይ ነው”።

የለመለሙ ሣሮች
ሣሮቹ አረንጓዴ፣ እርጥብ እና በብዛት የሚያድጉ ናቸው

የቤታችን ተሸካሚዎች ዝግባዎች ናቸው፤ ወራጆቹ ጥዶች ናቸው
ሴቲቱ የሚተኙበት ቤት በሚመስል መልኩ ስለ ጫካው ታብራራለች

ተሸካሚዎች ... ወራጆች
1) “ተሸካሚዎች” ከግድግዳዎቹ በላይ ያለውን ሁሉ ለመሸከም የሚያገለግሉ ትላልቅ ግንዶችን ሲያመለክት “ወራጆች” የሚያመለክቱት ጣሪያውን የሚያያይዙ ረጃጅም አጠናዎችን ነው ወይም 2) “ተሸካሚዎች” የሚያመለክቱት ወራጆቹን ሆኖ “ወራጆች” አናጺዎቹ ከጣሪያ መስሪያዎች እንዲሁም ከተሸካሚዎቹ ጋር የሚያያይዙባቸውን ፍልጦች ያመለክታሉ የሚሉት ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች ናቸው።

ዝግባዎች ... ጥዶች
ዝግባዎች ረጃጅምና ጠንካራ ዛፎች ናቸው። “ጥዶች” ተብሎ የተተረጎመው ቃል እንደ ዝግባ ሁሉ ለዛፎቹ የተሰጠ ጥቅል ስም ነው፣ ይሁን እንጂ እነዚህ ትንንሾች ናቸው። ዝግባና ጥድ በአንተ አካባቢ የማይታወቁ ከሆኑ ለረጅሞቹና ለጠንካራዎቹ ዛፎች ጥቅል የሆኑ ቃሎችን መጠቀም ትችላለህ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 እኔ በሜዳ የሚገኝ አበባ፥ በሸለቆም የሚገኝ አበባ ብቻ ነኝ። ሰውየው ሲናገራት፥ **2** ውዴ ሆይ፥ አበባ በእሾህ መካከል እንደሆነ አንቺም በሀገሬ ሴቶች ልጆች መካከል ነሽ። ሴቲቱ ለራስዋ ስትናገር፥ **3** በዱር ዛፍ መካከል እንዳለ የእንኮይ ዛፍ የእኔም ውድ በጎልማሶች መካከል ነው። በታላቅ ደስታ ከጥላው ሥር ተቀመጥኩ፥ የፍሬውም ጣዕም ጣፋጭ ነው። **4** ወደ ግብዣው አዳራሽ አመጣኝ፥ በእኔ ላይ ያለው ሰንደቁ ፍቅር ነው። ሴቲቱ ለፍቅረኛዋ ስትናገር፥ **5** በዘቢብ ጥፍጥፍ ነፍስ ዝሩብኝ፥ በእንኮይ ጭማቂም አበርቱኝ፥ በፍቅር ተይዤ ደክሜአለሁና። ሴቲቱ ለራስዋ ስትናገር፥ **6** ግራ እጁ ከአንገቴ ሥር ነው፥ ቀኝ እጁም ያቅፈኛል። ሴቲቱ ለሌላዋ ሴት ስትናገር፥ **7** የኢየሩሳሌም ሴቶች ልጆች፥ በፍቅር ግንኙነታችን ወቅት እስክንረካ ድረስ ላታቋርጡን በሜዳ ፍየሎችና በአጋዘኖች ቃል እንድትገቡልኝ እፈልጋለሁ። ሴቲቱ ለራሷ ትናገራለች፥ **8** የውዴ ድምጽ ነው! ኦ፥ በተራራዎች ላይ እየዘለለ፥ በኮረብታዎች ላይ እየተስፈነጠረ ሲመጣ ይታወቀኛል። **9** ውዴ የሜዳን ፍየል ወይም ግልገል አጋዘንን ይመስላል፤ እነሆ እርሱ ከቤታችን ግድግዳ በስተኋላ ቆሟል፥ በመስኮቱ በኩል አተኩሮ፥ በፍርግርጉም አጮልቆ ይመለከታል። **10** ውዴ እንዲህ ሲል ተናገረኝ፥ "ውዴ ሆይ ተነሽ፤ የኔዋ ቆንጆ ከእኔ ጋር ነይ። **11** ተመልከች፥ ክረምቱ አልፏል፥ ዝናቡም ቆሟል፥ ሄዷልም። **12** አበቦች በምድር ላይ ታይተዋል፤ ወይን የሚገረዝበትና የወፎች ዝማሬ ጊዜ ደርሶአል፥ የእርግቦችም ድምጽ በምድራችን ተሰምቷል። **13** የበለስ ዛፍ አረንጓዴ ፍሬዎቿ በስለዋል፥ ወይኖቹም አብበዋል፥ መዓዛቸውንም ሰጥተዋል። ውዴ ሆይ ተነሽ፥ የኔዋ ቆንጆ ነይ። **14** በዐለት ሥንጣቂ ውስጥ፥ በድብቁ የተራራማው ቋጢኝ ስንጣቂ ውስጥ ያለሽ እርግቤ ሆይ፥ ፊትሽን ልየው። ድምጽሽን ልስማው፥ ድምጽሽ ጣፋጭ ነውና ፊትሽም ውብ ነው።" ሴቲቱ ለራሷ ስትናገር፥ **15** የወይናችን ቦታ አብቦአልና የወይን ቦታዎችን የሚያበላሹትን ትናንሽ ቀበሮዎች ያዙልን። **16** ውዴ የእኔ ነው፥ እኔም የእርሱ ነኝ፤ እርሱ መንጋውን በአበቦቹ መካከል በደስታ ያሰማራል። **17** ሴቲቱ ለፍቅረኛዋ ስትናገር፥ ውዴ ሆይ፥ ተመለስ፣ የንጋቱ ቀዝቃዛ ንፋስ ሳይነፍስ፥ ጥላውም ሳይሸሽ። ተመለስ፤ በጎርበጥባጣዎቹ ኮረብቶች ላይ የሜዳ ፍየልን ወይም ግልገል አጋዘንን ምሰል።

Song of Solomon 2:1

እኔ በአረንጓዴ መስክ እንደሚገኝ የሳሮን አበባ ነኝ

ሴቲቱ ራሷን በውብ አበቦች በሚታወቅ ቦታ ካሉ አበቦች እንደ አንዱ አድርጋ ትናገራለች

ሳሮን

ለጥ ያለ፣ዛፎች የሌሉበት፣የተለያዩ አይነት አበቦች እና ሳሮች የሚበቅሉበት ምድር ስም

በሸለቆ ያለ አበባ

ሴቲቱ ራሷን በውብ አበቦች በሚታወቅ ቦታ ካሉ አበቦች እንደ አንዱ አድርጋ ትናገራለች

የተዋበ አበባ

ብዙ ውሃ ባለበት ስፍራ የሚበቅል መልካም መዓዛ ያለው አበባ። ይህንን በመኃልይ 2፡1-2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሸለቆዎች

በተራሮች መካከል እና በውሃ አቅራቢያ የሚገኝ ለጥ ያለ ስፍራ

ወጣት ሴቶች... በእሾህ መሀከል እንዳለ ውብ አበባ

አበባ እሾህ ካለው ቁጥቋጦ የበለጠ ያማረ ነው። ሰውየው ሴቲቱ ከሌሎች ሴቶች ሁሉ ያማረች እንደሆነች ያስባል።

የኔ ፍቅር

“የምወድሽ አንቺ”። ይህንን በመኃልይ 1:9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ወጣት ሴቶች

“ሌሎች ወጣት ሴቶች”

Song of Solomon 2:3

ወጣት ወንዶች ... እንደ እንኮይ ዛፍ

ሰዎች የእንኮይ ዛፍ ፍሬን ይወዳሉ፣ ነገር ግን ሌሎች የዱር ዛፎች ፍሬ አያፈሩም። ሴቲቱ ከሌሎች ወንዶች ይልቅ ከሰውየው ጋር መሆን ያስደስታታል።

የእንኮይ ዛፍ

ቢጫ እና በጣም ጣፋጭ ፍሬ የሚያፈራ ዛፍ ነው። አንባቢዎችህ ይህ ምን እንደሆነ የማያውቁ ከሆኑ በሌላ የፍራፍሬ ዛፍ ስም ወይም “የፍራፍሬ ዛፍ” በሚል ጥቅል ቃል ልትተካው ትችላለህ።

ጫካው

እዚህ ጋ፣ የዕብራይስጡ ቃል ሰዎች የማይጠቀሙበት ፣ ዛፎች የሚበቅሉበት ስፍራ ይለዋል።

ወዳጄ

ይህ ሀረግ ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች ሴቲቱ “የኔ አፍቃሪ” ብትለው በይበልጥ የተለመደ ይሆን ይሆናል። ይህንን በመኃልይ 1:13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የኔ አፍቃሪ”

ከጥላው በታች በታላቅ ደስታ እቀመጣለሁ

ሴቲቱ ከሰውየው አጠገብ በመሆኗ ሀሴት እና መፅናናትን አግኝታለች።

ፍሬው ለምርጫዬ ጣፋጭ ነው

ሴቲቱ ጣፋጭ ፍሬ በመመገብና በሰውየው አጠገብ በመሆን ትደሰታች።

የወይን ቤት

ትርጉሞቹ 1) ንጉሱ ለብዙ ሰዎች ወይንና ብዙ ምግብ የሚያቀርብበትን ሰፊ ክፍል ወይም 2) ሴቲቱ እና ሰውየው ብቻቸውን ሊሆኑ የሚችሉበት በወይን ተክል ውስጥ ያለ ትንሽ ዳስ

በኔ ላይ ያለው አላማው ፍቅር ነበር

በኔ ላይ ያለው አላማው ፍቅር ነበር ትርጉሞቹ 1) ሰንደቅ አላማ ለወታደራዊ አጀብ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ወታደራዊ አጀቡ፣ ንጉሱ ብዙ ሰዎችን ወደሚመግብበት ትልቅ ክፍል ውስጥ ለመግባት የፈራችውን ሴት የሚያበረታ የሰውየውን ፍቅር የሚወክል ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ነገር ግን የፍቅር ጥበቃው መራኝ፣ ብርታትንም ሰጠኝ” ወይም 2) ሰውየው ክእርሷ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም መፈለጉን ሴቲቱ ከአስተያየቱ ተረዳች። አ.ት፡ “በፍቅር ዐይን አየኝ” ወይም “ባየኝ ጊዜ ከእኔ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም መፈለጉን አውቄአለሁ” ወይም 3) የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጸሙ። አ.ት፡ “በፍቅር ሸፈነኝ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Song of Solomon 2:5

አበረታቱኝ
“ብርታቴን መልሱልኝ” ወይም “ኃይል ስጡኝ”

በዘቢብ ጥፍጥፍ
“የዘቢብ ጥፍጥፍ እንድበላ በመስጠት” የዘቢብ ጥፍጥፍ ከደረቁ የወይን ፍሬዎች ተጠፍጥፈው የሚሰሩ ናቸው።

በእንኮይ አድሱኝ
“እንኮይ በመስጠት ደግፉኝ” ወይም “እንኮይ በመስጠት እርዱኝ”

በፍቅር ደክሜአለሁና
ፍቅር የህመም አይነት የሆነ ያህል ከፍቅሯ ብርታት የተነሳ ድካም እንደተሰማት ሴቲቱ ትናገራለች። አ.ት፡ “ፍቅሬ ብርቱ በመሆኑ ምክንያት ከስቻለሁ”

ግራ እጅ ... ቀኝ እጅ
“ግራ ክንድ ... ቀኝ ክንድ”

እቀፈኝ
“ይይዘኛል”

Song of Solomon 2:7

የኢየሩሳሌም ሴት ልጆች
“የኢየሩሳሌም ወጣት ሴቶች”። እነዚህ ወጣት ሴቶች አብረዋት ስላልነበሩ ሊሰሟት አይችሉም፣ እርሷ ግን አብረዋት እንዳሉና እንደሚሰሟት አድርጋ ትናገራለች።

በሚዳቆዎቹና በሜዳ ባሉ አጋዘኖች
የኢየሩሳሌም ሴቶች ሊሰሟት ባይችሉም፥ ሴቲቱ እንደሚሰሟት አድርጋ ቃላቸውን ቢያፈርሱ ሚዳቋዎቹ እና አጋዘኖቹ እንደሚቀጧቸው ትናገራለች።

ሚዳቆዎቹ
እነዚህ አጋዘን የሚመስሉና በፍጥነት የሚንቀሳቀሱ እንስሶች ናቸው።

ሴት አጋዘን
ሴት አጋዘን

የሜዳ
“በገጠር የሚኖሩ”። ይህ ታርሶ የማያውቅ ምድር ነው።

እርሷ እስክትፈልግ ድረስ ፍቅርን አትቀስቅሱ ወይም አታነሣሡ
እዚህ ጋ “ፍቅር” መቀስቀስ እንደማይፈልግ የተኛ ሰው ተደርጎ ተነግሮለታል። ሰውየው እና ሴቲቱ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጽመው እስኪጨርሱ ድረስ መታወክ እንደማይፈልጉ የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው።

አትቀስቅሱት ወይም አታነሣሡት
ቋንቋህ ሰዎችን ክእንቅልፍ ለማስነሣት አንድ ቃል ብቻ ካለው ሁለቱን ቃላት ማዋሀድ ትችላለህ። አ.ት፡ “አታንቁት”

Song of Solomon 2:8

አጠቃላይ መረጃ፡
የመጽሐፉ ሁለተኛው ክፍል እዚህ ይጀምራል።

አጠቃላይ መረጃ
ሴቲቱ የምታወራው ለራሷ ወይም ለኢየሩሳሌም ሴቶች ልጆች መሆኑ ግልፅ አይደለም።

አድምጡ
ትርጓሜዎች ሊሆኑ የሚችሉት 1) “ልናገር ያለሁትን በጥንቃቄ አድምጡ”። በራስህ ቋንቋ አድማጮች በጥሞና እንዲያደምጡ የሚናገር ቃል ልትጠቀም ትችላለህ፣ ወይም 2) “ሲመጣ መሰማት እንድትችሉ አድምጡ”

ወዳጄ
ወዳጄ ይህ ሐረግ ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች ሴቲቱ አገላፅ “የኔ አፍቃሪ” ብትለው በይበልጥ የተለመደ ይሆናል። ይህንን በመኃልይ 1:13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ አፍቃሪ”።

እየተወረወረ ... እየዘለለ ... እያየ... አተኩሮ እየተመለከተ
ሴቲቱ ሰውየው መምጣቱን ስታይ በመደነቅ የሚያደርገውን በተቻላት መጠን በጥቂት ቃላት ትገልፃለች። የአንተ ቋንቋ፣ ተናጋሪው ሊሆን ስላለ ነገር የሚደነቅበትን ስሜት የሚያሳይበት የተለየ አገላለፅ ይኖረው ይሆናል።

በተራሮች ላይ እየተወረወረ፣ በኮረብታዎች ላይ እየዘለለ
“በተራሮች ላይ እየተወረወረ፣ በኮረብቶች ላይ በፍጥነት እየሮጠ”። ሰውየው እንጆ “ሚዳቋ ወይም ወንድ አጋዘን” በአስቸጋሪ መሬት ላይ በፍጥነት ወደ እርሷ እንደሚመጣ ሴቲቱ ትናገራለች (ቁ. 9)።

እንደ ሚዳቋ ወይም የአጋዘን ግልገል
ሚዳቋ እና የአጋዘን ግልገል አስቸጋሪ መሬት ላይ በፍጥነት መንቀሳቀስ ይችላሉ። ሰውየው ከእርሷ ጋር ለመሆን በተቻለው ፍጥነት እንደሚመጣ ሴቲቱ ታስባለች። በቋንቋህ ሰዎች ፈጣን ነው ብለው የሚያስቡትን እንስሳ ተጠቅመህ መተርጎም ትችላለህ።

ሚዳቋ
ይህ አጋዘን የሚመስልና በፍጥነት የሚንቀሳቀስ እንስሳ ነው። ”አጋዘኖች” የሚለውን በመኃልይ 2:7 እንዳለው በነጠላ ተርጉመው።

የአጋዘን ግልገል
“ተባእት የአጋዘን ግልገል”

ተመልከቺ
“በጥንቃቄ አድምጪ” ወይም “ልናገር ያለሁት ጠቃሚ ነገር ነው”። አድማጭ በጥሞና እንዲያዳምጥ የሚያሳስብ ቃል በራስህ ቋንቋ መጠቀም ትችላለህ።

ከግምባችን በስተጀርባ
“በግንባችን በሌላኛው ጎን”። ሴቲቱ ቤት ውስጥ ስትሆን ሰውየው ከቤት ውጪ ነው።

የኛ ግንብ
“የኛ” የሚለው ቃል ሴቲቱንና አብረዋት በቤት ያሉ ሌሎች ሰዎችን ያመለክታል። ሴቲቱ ከራሷ ጋር የምታወራ ከሆነ አካታች ነው፣ ነገር ግን ለኢየሩሳሌም ሴት ልጆች የምትናገር ከሆነ፣ ራሷንና ጓደኞቿን ወይም ራሷን በብዙ ቁጥር የምታመለክት ከሆነ ፥ እንደ “ደስ ተሰኝተናል” ... “ሐሴት እናደርጋለን” ... “እንደሰት” የማያካትት ይሆናል።

በመስኮት አሻግሮ እየተመለከተ
“በመስኮቱ በኩል አተኩሮ ይመለከታል”

በርብራቡ መካከል አጮልቆ እየተመለከተ
“በርብራቡ መካከል ሰረቅ አድርጎ ያያል ”

ርብራብ
ረዘም ረዘም ያሉ እንጨቶችን አንድ ላይ በመሰካካት የተሰራ የመስኮት ወይም ሌላ በር መከለያ ነው። ርብራብ ሰዎች አጮልቀው ማየት የሚችሉበት ክፍተት አለው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Song of Solomon 2:10

ወዳጄ
ይህ ሐረግ ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች ሴቲቱ “የኔ ፍቅር” ብትለው በይበልጥ የተለመደው አገላለፅ ይሆናል። ይህንን በመኃልይ 1፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ አፍቃሪ”።

የኔ ፍቅር፣ ተነሺ
“የኔ ፍቅር ከአልጋሽ ተነሺ”

የኔ ፍቅር
“አንቺ፣ የምወድሽ”። ይህንን በመኃልይ 1፡9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ተመልከቺ
“በጥሞና አድምጪ” ወይም “ልናገር ያለሁት ጠቃሚ ነገር ነው”። በቋንቋህ አድማጭ በጥሞና እንዲያዳምጥ የሚያሳስበውን ቃል መጠቀም ትችላለህ።

ክረምቱ አልፏል፣ ዝናቡም አልፎ ሄዷል
በክረምት ከቤት ውጪ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም እጅግ ቀዝቃዛና እርጥበታማ ነው፣ ነገር ግን የቅዝቃዜውና የእርጥበቱ ጊዜ አልፏል።

ክረምቱ አልፏል
ክረምት እፅዋት የማያድጉበትና ሰዎች ቤታቸው ውስጥ ለመቆየት የሚመርጡበት የአመቱ ቀዝቃዛ ወቅት ነው። በዓመቱ ውስጥ ስላለው ስለዚያ ወቅት በቋንቋህ መጠቀም ትችላለህ።

ዝናቡ አልፎ ሄዷል
በእስራኤል ዝናብ የሚዘንበው በክረምት ብቻ ነው። እዚህ ጋ የተገለፀው የሚያረሰርስ የሙቀት ወቅት ዝናብ ሳይሆን ደስ የማይልና ቀዝቃዛ ዝናብ ነው።

Song of Solomon 2:12

አበቦቹ ብቅ ብለዋል
“ሰዎች አበቦቹን ማየት ይችላሉ”

በምድሪቱ ላይ
“በዚህ ምድር ሁሉ ላይ”

ለመከርከም
ለውበት ወይም ብዙ ፍሬ እንዲያፈራ የተክል ቅርንጫፎችን መግረዝ

የወፎች ዝማሬ
“ወፎች እንዲዘምሩ”

የእርግቦቹ ድምፅ ይሰማል
ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ሰዎች የእርግቦቹን ድምፅ መስማት ይችላሉ” ወይም “እርግቦቹ ድምፃቸውን እያሰሙ ነው”

የበለስ ዛፊቱ አረንጓዴ በለሶቿን ታበስላለች
ዛፊቱ ፍሬዋን በራሷ እንዲበስሉ እንዳደረገቻቸው ተነግሮላታል። ይህ የጋራ ነጠላ ሲሆን በብዙ ቁጥር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “በዛፉ ላይ ያሉት በለሶች በስለዋል”

ወይኖቹ እያበቡ ናቸው
“ወይኖቹ እያበቡ ነው” ወይም “ወይኖቹ አበባ አላቸው”

ይሰጣሉ
“እነርሱ” የሚለው ቃል በወይኑ ላይ ሆነው ያበቡትን ያመለክታል።

መአዛቸው
“ጣፋጭ ሽታቸው”

የኔ ፍቅር
“አንቺ የምወድሽ”፤ ይህንን በመኃልይ 1፡9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Song of Solomon 2:14

አጠቃላይ መረጃ፡
ሰውየው እየተናገረ ነው።

እርግቤ
እስራኤላውያን እርግቦችን አስደሳች ድምፅ ያላቸው ውብ ወፎች እንደሆኑ ያስቡ ነበር። ሰውየው የሴቲቱ ፊት እና ድምፅ ያማረ እንደሆነ ያስባል። አንዲትን ሴት “እርግብ” ብሎ መጥራት ቅር የሚያሰኛት ከሆነ ዘይቤአዊውን አነጋገር ልትተወው ትችላለህ። አ.ት፡ “የእኔ ውብ ሴት”

ንቃቃቶቹ
ሰዎችን ለመሸሸግ የሚያስችል ስፋት ያለው በተራራ አለቶች ጎን ያለ ስንጥቅ

የተራራው ቋጥኞች
“በተራሮች ጎን ያሉ ቀጥ ያሉ አለቶች”

ፊትሽ
አንዳንድ ትርጉሞች ይህንን “ገፅታሽ” ወይም “ቅርፅሽ” ወይም “አንቺ የምትመስይው” ብለው ይተረጉሙታል።

Song of Solomon 2:15

ያዙ
ይህ ሴቲቱ ከአንድ በላይ ለሆኑ ወንዶች የምትናገር ይመስል ብዙ ቁጥር ነው፤ ነገር ግን አብዛኛዎቹ ትርጉሞች ለሰውየው እንደምትናገር አድርገው ይተረጉሙታል፣ ስለዚህ በነጠላ ልትተረጉመው ትችላለህ።

ቀበሮዎቹ
እነዚህ እንስሶች ትናንሽ ውሾችን የሚመስሉ ሲሆኑ በፍቅር ስነ-ግጥም ውስጥ ብዙ ጊዜ ወጣት ሴትን ሊያባልጉ የሚችሉ ጉጉ ወጣት ወንዶችን እንዲወክል ጥቅም ላይ ውለዋል።

የኛ የወይን ቦታ ... ለኛ
“እኛ” እና “ለኛ” የሚሉት ቃላት ሊሆኑ የሚችሉት 1) በመኃልይ 1፡4 እንዳለው ሌላውን ሳይሆን ሴቲቱን ራሷን የሚያመለክት ወይም 2) ሴቲቱንና ሰውየውን የሚያካትት ወይም 3) ሌሎችን ሳያካትት ሴቲቱንና የተቀሩትን ቤተሰቦቿን የሚያመለክት ይሆናል።

ቀበሮዎች
ሌላው ትርጉም ሊሆን የሚችለው “የጫካ ውሻ” ነው። የጫካ ውሻ ረጃጅም እግሮች ያሉት ቀጭን የውሻ አይነት ነው።

የሚያበላሹ ትናንሽ ቀበሮዎች
ቀበሮዎች ጉድጓድ በመቆፈርና የወይን ፍሮዎችን በመብላት የወይን ተክሎችን ያበላሻሉ። ይህ ወጣት ሴቶችን የሚያባልጉ ወጣት ወንዶችን የሚገልፅ ዘይቤአዊ አነጋገር ሊሆን ይችላል።

በማበብ ላይ
ይህ የሚያመለክተው የወይኑ ቦታ ጤናማ እንደሆነና ወይኑም ማፍራቱን ነገር ግን ለመበላት ዝግጁ አለመሆናቸውን ያመለክታል። ይህ ለማግባትና ልጆችን ለመውለድ የደረሰችን ወጣት ሴት የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ሊሆን ይችላል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Song of Solomon 2:16

ወዳጄ የእኔ ነው
“ውዴ የኔ ነው”

ወዳጄ
ይህ ሐረግ ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች ሴቲቱ “የኔ አፍቃሪ” ብትለው በይበልጥ የተለመደ ይሆን ይሆናል። ይህንን በመኃልይ 1፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ አፍቃሪ”።

እኔ የእርሱ ነኝ
“እኔ የእርሱ ነኝ”

ያሰማራል
“ይመግባል” ወይም “ሳር ይበላል”። ሴቲቱ ሰውየውን በአበቦች መሐከል እፅዋትን እንደሚመገብ “ሚዳቋ ወይም የአጋዘን ግልገል” አድርጋ ትናገራለች። መሰማራት ምናልባት የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸምን የሚገልፅ ዘይቤአዊ አነጋገር ሊሆን ይችላል።

የተዋቡ አበቦች
ብዙ ውሃ ባለበት ቦታ የሚበቅሉ ባለጣፋጭ ሽታ አበቦች። በመኃልይ 2፡1 እንዳለው “ውብ አበቦች” ብለህ በብዙ ቁጥር ተርጉመው።

ንጋት
ፀሐይ የምትወጣበት የቀኑ ክፍል

ጥላዎቹ ሸሽተዋል
ሴቲቱ ጥላዎቹ ከፀሐይ ብርሐን እየሸሹ እንዳሉ አድርጋ ትገልፃቸዋለች። አ.ት፡ “ጥላዎቹ ጠፍተዋል”

እንደ ሚዳቋ ወይም የአጋዘን ግልገል
ይህንን በመኃልይ 2፡9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሚዳቋ
እነዚህ እንስሶች አጋዘን የሚመስልና በፍጥነት የሚንቀሳቀስ እንስሳ ነው። በመኃልይ 2፡7 ላይ እንዳለው “ሚዳቋዎች” በነጠላ ቁጥር ተርጉመው።

ወንድ አጋዘን
ጎልማሳ ወንድ አጋዘን

ወጣ ገባ ያለባቸው ተራሮች
“አለታማ ተራሮች” ወይም “ አስቸጋሪ ተራሮች”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 ሌሊት በመኝታዬ የምወደውን ናፈቅሁት፤ ፈለግሁት፥ ነገር ግን ላገኘው አልቻልኩም። **2** እኔም ለራሴ፥ "እነሣለሁ፥ ወደ ከተማው ውስጥ፥ ወደ ጎዳናዎቹና ወደ አደባባዮቹ እሄዳለሁ፤ ውዴንም እፈልገዋለሁ" አልኩ። ፈለግሁት፥ ላገኘው ግን አልቻልኩም። **3** ጠባቂዎች በከተማው ውስጥ ለጥበቃ ሲዘዋወሩ አገኙኝ። እኔም፥ "ውዴን አይታችሁታል?" ብዬ ጠየቅኋቸው። **4** ከእነርሱ ጥቂት እልፍ እንዳልኩኝ ነፍሴ የወደደችውን አገኘሁት። ያዝኩት፥ ወደ እናቴ ቤት፥ ወደ ፀነሰችኝም መኝታ ቤት እስካመጣው ድረስ አልለቀውም። ሴቲቱ ለሌላይቱ ሴት ስትናገር፥ **5** እናንተ የኢየሩሳሌም ሰዎች ሴቶች ልጆች፥ በፍቅር ግንኙነታችን እስክንረካ ድረስ ላታቋርጡን በሜዳ ፍየሎችና አጋዘኖች እንድትምሉልኝ እፈልጋለሁ። ወጣቷ ሴት ለራሷ ስትናገር፥ **6** ይህቺ በዕጣንና ከርቤ፥ ነጋዴዎችም በሚሸጡት ልዩ ልዩ ቅመም በተቀመመ ሽቶ ተቀብታ እንደ ጢስ ምሶሶ ከምድረ በዳ የምትወጣ ማናት? **7** እነሆ እርሱ የሰለሞን ተንቀሳቃሽ አልጋ ነው፤ ስልሳ የእስራኤል ወታደሮች፥ ስልሳ ጦረኞች ከብበውታል። **8** እነርሱ በሰይፍ የላቁ ናቸው፥ በጦርነትም የታወቁ። እያንዳንዱ በወገቡ ሰይፍ አለው፥ በሌሊት የሚያሸብሩትን ለመከላከል ታጥቀዋል። **9** ንጉሥ ሰለሞን ከሊባኖስ በመጣ እንጨት ሰው ተቀምጦበት የሚሸከሙትን [ለአንድ ሰው መቀመጫ የሚሆን ወንበር የሚይዝ] ሳጥን ለራሱ ሠራ። **10** ምሶሶዎቹን ከብር፥ ጀርባው ከወርቅ፥ መቀመጫው ከሐምራዊ ጨርቅ ተደርጎ ተሠራ። ውስጡ የተዋበው በኢየሩሳሌም ሰዎች ሴቶች ልጆች ነበር። ወጣቷ ለኢየሩሳሌም ሴቶች ስትናገር፥ **11** የጽዮን ሴቶች ልጆች ሆይ፥ ሂዱ ውጡ፥ ንጉሥ ሰለሞንን ትኩር ብላችሁ እዩት፥ በሕይወቱ በተደሰተባት በዚያች ቀን፥ በሠርጉ ቀን እናቱ የደፋችለትን አክሊል ጭኖ።

Song of Solomon 3:1

ስናፍቀው ነበር ... ላገኘው አልቻልኩም
“ከእርሱ ጋር ለመሆን ታላቅ ምኞት ነበረኝ ... የምወደው፣ ነገር ግን እርሱ በዚያ አልነበረም”

ነፍሴ የምትወደው እርሱ
ነፍስ የሰውን ሁለንተና የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። እዚህ ጋ “የእኔ ፍቅር” ከሚለው ይልቅ ሴቲቱ ለሰውየው ስላላት ፍቅር ጠንከር ባለ አገላለጽ ያመለክታል።

በከተማው መሐል እሄዳለሁ
“በከተማው መሐል እዘዋወራለሁ”

በጎዳናዎቹና በአደባባዮቹ
“አደባባዮች” የሚለው ቃል ጎዳናዎች ወይም መንገዶች የሚገናኙበትን መሐል ከተማ ያመለክታል። አብዛኛውን ጊዜ ሰዎች ዕቃዎቻቸውን የሚሸጡበት አካባቢና ሰዎች ለመነጋገር የሚገናኙበት ስፍራ ነው።

እፈልገዋለሁ
“ላገኘው”

Song of Solomon 3:3

ጠባቂዎች
በምሽት የሕዝቡን ደኅንነት ለመጠበቅ በከተማይቱ የጥበቃ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች

ከተማይቱን ለመጠበቅ በሚዞሩበት ጊዜ
“በከተማይቱ ዙሪያ በቅጥሩ ላይ ይመላለሱ የነበሩ”

ነፍሴ የምትወደውን እርሱን
ነፍስ የሰውን ሁለንተና የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። እዚህ ጋ “የእኔ ፍቅር” ከሚለው ይልቅ ሴቲቱ ለሰውየው ስላላት ፍቅር ጠንከር ባለ አገላለጽ ያመለክታል። መኃልይ 3:1ን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የአልጋ ክፍል
“የመኝታ ክፍል”

የፀነሰችኝ
ይህ ስለ እናቷ የምትናገረው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው።

Song of Solomon 3:5

x
ይህንን ቁጥር በመኃልይ 2:7 ባለው መልክ ተርጉመው

የኢየሩሳሌም ሴት ልጆች
“የኢየሩሳሌም ወጣት ሴቶች”፣ እነዚህ ወጣት ሴቶች በዚያ ስላልነበሩ ሊሰሟት አይችሉም፣ ነገር ግን ሴቲቱ እንዳሉና ሊሰሟት እንደሚችሉ ቆጥራ ትናገራለች።

በሜዳ ባሉ ሚዳቋዎችና በሴት አጋዘኖች
ምንም እንኳን የኢየሩሳሌም ሴቶች ልጆች በዚያ ኖረው የሚሰሟት ባይሆኑም ቃል ኪዳናቸውን ስለማፍረሳቸው ሚዳቋዎችና ሴት አጋዘኖች እንደሚቀጧቸው ሴቲቱ ትነግራቸዋለች።

ሚዳቋዎች
አጋዘን የሚመስሉና በፍጥነት የሚንቀሳቀሱ እንስሳት

ሴት አጋዘን
ሴት አጋዘን

በሜዳ ያሉ
“በገጠራማ አካባቢ የሚኖሩ”፣ ይህ ያልታረሰውን መሬት ያመለክታል።

ደስ እስክታሰኝ ድረስ ፍቅርን አትቀስቅሱ ወይም አታነሣሡ
እዚህ ጋ “ፍቅር” በተኛና ሊቀሰቅሱት በማይፈልግ ሰው ተመስሎ ተነግሮለታል። ይህ የአነጋገር ዘይቤ በግብረ ሥጋ ግንኙነታቸው እስኪረኩ ድረስ መታወክ የማይፈልጉትን ወንዱንና ሴቲቱን ይወክላል። አ.ት፡ “በግብረ ሥጋ ግንኙነታችን እስክንረካ ድረስ አያውኩንም”።

አትቀስቅሱት ወይም አታነሣሡት
በቋንቋህ ሰዎችን ከእንቅልፋቸው ለመቀስቀስ የምትጠቀመው አንድ ቃል ብቻ ከሆነ የእንግሊዝኛ ቃላቱን ልታጣምራቸው ትችላለህ። አ.ት፡ “አትቀስቅሱት”።

Song of Solomon 3:6

አጠቃላይ መረጃ
የመጽሐፉ ሦስተኛው ክፍል እዚህ ጋ ይጀምራል። ክፍሉ የሰለሞንን አልጋ ከምድረ በዳው ወደ ኢየሩሳሌም ተሸክመው በሚሄዱ ስልሳ ሰዎች ገለጻ ይጀምራል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ያ ከምድረ በዳው ወጥቶ የሚመጣው ምንድነው?
በቡድን የሆኑ ሰዎች ከምድረ በዳው ወደ ኢየሩሳሌም ይጓዛሉ። በዮርዳኖስ ሸለቆ ያለው ምድረ በዳ ዝቅ ያለ ስለሆነና ኢየሩሳሌም በተራሮች ላይ ስለምትገኝ ወደ እርሷ ለመድረስ ወደ ላይ መውጣት አለባቸው።

ያ ምንድነው?
በርካታ ትርጉሞች ይህንን “ያ ማነው” ብለው ይተረጉሙታል

እንደ ጢስ ዐምድ
ሕዝቡ በሚጓዙበት ጊዜ ብዙ አቧራ ወደ አየር ያስነሡ ስለነበር ከሩቅ ጢስ መስሎ ይታይ ነበር።

በከርቤና በዕጣን ሸቱ
“በከርቤና በዕጣን ጣፋጭ ሽታ”

ነጋዴዎች ከሚሸጧቸው ቅባቶች ሁሉ ጋር
“ለሽቱነት ተቀምመዋል” የሚሉትን ቃላት ቀደም ካለው ሐረግ ይገነዘቧቸዋል። እዚህ ጋ ሊደገሙ ይችላሉ። አ.ት፡ “ነጋዴዎች በሚሸጧቸው ቅባቶች ሁሉ ለሽቱነት ተቀምመዋል” ወይም “ነጋዴዎች ከሚሸጧቸው ጣፋጭ ሽታ ካላቸው ቅባቶች ሁሉ ጋር”።

ቅባቶች
ጠጣር የሆነውን አንዳች ነገር በመፍጨት የሚሠራ ደቃቅ ብናኝ

ተመልከቱ
“በጥንቃቄ አድምጡ” ወይም “የምነግራችሁ ጠቃሚ የሆነ ጉዳይ ነው”። በቋንቋህ አድማጭህ በጥንቃቄ ሊሰማህ የሚያስችለውን ቃል መጠቀም ትችላለህ። አሁን ተናጋሪው በቁጥር 6 ላይ ላለው ጥያቄ መልስ ያገኛል።

አልጋ ነው
ይህ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ተሸክመው ሊወስዱት የሚችሉትን አልጋ ከነአልጋ ልብሱ ያመለክታል።

ስልሳ ጦረኞች ከብበውታል፣ ስልሳ የእስራኤል ወታደሮች
እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚያመለክቱት እነዚያኑ ስልሳ ሰዎች ነው። ሁለተኛው ሐረግ “ጦረኞች” የተባሉት “የእስራኤል ወታደሮች” መሆናቸውን ያብራራል።

ጦረኞች
የሚዋጉ ሰዎች

Song of Solomon 3:8

አጠቃላይ መረጃ
በመኃልይ 3፡6 የሰለሞንን አልጋ ከምድረ በዳው ወደ ኢየሩሳሌም ስለተሸከሙት ስልሳ ሰዎች የተጀመረው ገለጻ ይቀጥላል።

አገናኝ መግለጫ
የአልጋው ገለጻ ራሱ ቁጥር 9 ላይ ይጀምራል። በቋንቋህ ዳራዊ መረጃን የሚያሳይ ቃላት ልትጠቀም ትችላለህ።

ጦርነትን ተለማምደዋል
“ጦርነቶችን በሚገባ መዋጋት ይችላሉ”

በእነርሱ ላይ ታጥቋል “እነርሱን መዋጋት ይችል ዘንድ”

የሌሊት ሽብር
የነገር ስም የሆነው “ሽብር” ሌሎችን በማጥቃት የሚያስፈራሩ ክፉ ሰዎችን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “በሌሊት ሌሎችን የሚያጠቁ ክፉ ሰዎች”።

ከነተቀማጩ ሊሸከሙት የሚያስችል ወንበር
ይህ ታላላቅ ሰዎች የሚቀመጡበት ወንበር ወይም የሚጋደሙበት መከዳ ነው። ሰዎች ሊሸከሙት በሚያስችላቸው ረጃጅም መሸከሚያዎች ላይ ያንጠለጥሉታል።

Song of Solomon 3:10

አገናኝ መግለጫ
ስለ አልጋው በመኃልይ 3፡9 የጀመረው ገለጻ ይቀጥላል።

የማዕዘን ቋሚ
“የ” የሚያመለክተው የንጉሥ ሰለሞንን ከነተቀማጩ ሊሸከሙት የሚያስችለውን ወንበር ነው።

መደገፊያዎች
“መደገፊያዎች” የሚለው ቃል በወንበሩ ዙሪያ ያለውን የጨርቁን ድንኳን በመደገፍ የሚቆሙትን ከብር ወይም ከእንጨት ተሠርተው በብር የሚለበጡትን ቋሚዎች ያመለክታል።

ውስጣዊ ገጽታው
“ውስጠኛው ክፍሉ”

በፍቅር
ተስማሚ ትርጉሞቹ 1) “በፍቅር” የሚለው ቃል ሴቶቹ ለሰለሞን ያላቸውን ፍቅር ለማሳየት ከነተቀማጩ የሚሸከሙበትን ወንበር በልዩ ሁኔታ ማስዋባቸውን ያመለክታል ወይም 2) “በለፋ ቆዳ” የሚሉት ናቸው።

የጽዮን ሴቶች ልጆች
“እናንተ በጽዮን የምትኖሩ ወጣት ሴቶች”

ንጉሥ ሰለሞንን አተኩራችሁ ተመልከቱ
“ንጉሥ ሰለሞንን እዩት”፣ “አተኩሮ መመልከት” የሚለው ሐረግ አንድን ሰው ወይም አንድን ነገር በብርቱ ስሜት ለረጅም ጊዜ ማየትን ያመለክታል።

አክሊሉን ደፍቶ
“አክሊሉን ለብሶ”

በልቡ የደስታ ቀን
“ልብ” የሚለው ቃል የሰውን ሁለንተና የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “የእውነት ደስ በተሰኘበት ቀን” ወይም “በሕይወቱ ደስ የተሰኘበት ቀን”።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 ኦ፥ ወዳጄ ሆይ፥ አንቺ ውብ ነሽ፥ እነሆም ቆንጆ ነሽ። በመሸፈኛሽ ውስጥ ዓይኖችሽ እርግቦች ናቸው። ጸጉርሽ ከገለዓድ ተራራ ቁልቁል የሚወርደውን የፍየል መንጋ ይመስላል። **2** ጥርስሽ በቅርቡ ተሸልቶ ከመታጠቢያው ሥፍራ የሚወጣውን የበግ መንጋ ይመስላል። እያንዳንዱ መንታ ወልዷል፥ በመካከላቸውም መካን የለም። **3** ከንፈሮችሽ ቀይ የሐር ፈትል ይመስላሉ፤ አፍሽ ውብ ነው። ጉንጮችሽ በመሸፈኛሽ ውስጥ ለሁለት የተከፈለ ሮማን ይመስላል። **4** አንገትሽ በረድፍ በተደረደሩ ድንጋዮች ላይ የተገነባውን የዳዊትን የጥበቃ ማማ ይመስላል፥ አንድ ሺህ ጋሻ፥ የወታደሮቹ ሁሉ ጋሻ በእርሱ ላይ ተሰቅሏል። **5** ሁለቱ ጡቶችሽ በአበቦች መካከል የተሰማሩ ሁለት የአጋዘን ግልገሎችን፥ መንታም የተወለዱ የሜዳ ፍየሎችን ይመስላሉ። **6** ጎሕ እስኪቀድና ጥላው እስኪሸሽ ድረስ፥ ወደ ከርቤው ተራራ፥ ወደ ዕጣኑም ኮረብታ እሄዳለሁ። **7** ውዴ ሆይ፥ ሁለመናሽ ውብ ነው፥ እንከንም የለብሽም። **8** ሙሽራዬ ሆይ፥ ከሊባኖስ ከእኔ ጋር ነይ። አዎን፥ ከሊባኖስ ከእኔ ጋር ነይ፥ ከአማና ጫፍ፥ ከሳኔርና ከኤርሞን ጫፍ፥ ከአንበሶች ዋሻ፥ የነብሮች ዋሻ ከሆነውም ተራራ ነይ። **9** እህቴ ሙሽራዬ ሆይ፥ ልቤን ሰርቀሽዋል፤ በአንድ አፍታ ዕይታሽ ብቻ፥ በአንድ ሐብልሽ ብቻ ልቤን ሰርቀሽዋል። **10** እህቴ ሙሽራዬ ሆይ፥ ፍቅርሽ እንዴት ያማረ ነው! ፍቅርሽ ከወይን ጠጅ ይልቅ ምንኛ ይሻላል፥ የሽቶሽ መዓዛም ከቅመሞች ሁሉ። **11** ሙሽራዬ ሆይ፥ ከንፈሮችሽ ማር ያንጠባጥባሉ፥ ማርና ወተት ምላስሽ ሥር ናቸው። የልብሶችሽ መዓዛ የሊባኖስን መዓዛ ይመስላል። **12** እህቴ ሙሽራዬ የተቆለፈበት የመናፈሻ ቦታ ናት፥ የተቆለፈበት የመናፈሻ ቦታ፥ የታተመበትም ምንጭ። **13** ቅርንጫፎችሽ የሮማን ዛፍ ከተመረጠ ፍሬ ጋር፥ ሂናና የናርዶስ ተክል፥ **14** ናርዶስና ቀጋ፥ ጠጅ ሣርና ቀረፋ ከልዩ ልዩ ቅመሞች ጋር፥ ከርቤና እሬት ምርጥ ከሆኑት ቅመሞች ሁሉ ጋር አሉባቸው። **15** አንቺ የአትክልት ሥፍራ ምንጭ፥ የንጹህ ውሃ ጉድጓድ፥ ከሊባኖስ ወደ ታች የሚወርድ ምንጭ ነሽ። ወጣቷ ለፍቅረኛዋ ስትናገር፥ **16** የሰሜን ንፋስ ሆይ ንቃ፤ የደቡቡም ንፋስ ና፤ ቅመሞቹ መዓዛቸውን እንዲሰጡ በአትክልት ሥፍራዬ ላይ ንፈስ። ውዴ ወደ አትክልቱ ሥፍራ ይምጣ፥ ከምርጡም ፍሬ ጥቂት ይብላ።

Song of Solomon 4:1

አይኖችሽ እርግቦች ናቸው
ሊሆኑ ከሚችሉት አንዱ፣ ሰውየው የሴቲቱ ነጭ የአይን ኳሶች ወይም የአይኗ ቅርፅ እንደ እርግብ ቅርፅ መሆናቸውን እየተናገረ ይሆናል። ሌላው ሊሆን የሚችለው፣ እስራኤላውያን እርግቦች ገሮችና ለስላሳ ወፎች እንደሆኑ ያስቡ ነበር፣ ሰውየውም የሴቲቱ አይኖች ውብ እንደሆኑ ያስባል ምክንያቱም ሴቲቱ እርሱን የምታይበት አስተያየት ገር እንደሆነች እንዲያስብ አድርጎታል።

የኔ ፍቅር
“አንቺ የምወድሽ”፤ ይህንን በመኃልይ 1:9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ፀጉርሽ ከገለዓድ ተራራ የሚወርድ የፍየል መንጋ ይመስላል
በእስራኤል ያሉ ፍየሎች ብዙ ጊዜ ቀለማቸው ጥቁር ነበር። የሴቲቱም ፀጉር ጥቁር ሳይሆን አይቀርም። ፍየሎቹ ጥቁር እንደነበሩ መግለፅ ያስፈልግህ ይሆናል ወይም አንባቢው ሊረዳው የሚችል ጥቁረት እና ውበትን የሚያመለክት ሌላ የንፅፅር ቃል መጠቀም ትችላለህ። ሰዎች የገለዓድ ተራራ ለምና ውብ እንደሆነ ያስቡ ነበር። ተናጋሪው ሴቲቱ ውብ እንደሆነችና የልጆቹ እናት ለመሆን ዝግጁ እንደሆነች ቆጥሯል። ከፍየሎቹ ጋር ያለውን ንፅፅር ካስወገድከው የተራራውንም ንፅፅር ማስወገድ ይኖርብሃል። አ.ት፡ “ጸጉርሽ ከለም መሬት በላይ እንዳለው የጥቁር ደመና ማዕበል ነው”።

Song of Solomon 4:2

ጥርሶችሽ በቅርቡ የተሸለቱ የሴት በጎች መንጋን ይመስላሉ
በጎች ከተሸለቱ በኋላ ይታጠባሉ፤ ቆዳቸውም በጣም ነጭ ሆኖ ይታያል። የሴቲቱም ጥርሶች ነጫጭ ናቸው።

በቅርቡ የተሸለቱ የሴት በጎች መንጋ
ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ሰዎች ሱፋቸውን የሸለቷቸውን የሴት በግ መንጋ”

ከመታጠቢያ ስፍራ የሚመጡ
ሴቶቹ በጎች ከውሃው ውስጥ ወጥተው እየመጡ ነው። አ.ት፡ “ሰዎች ካጠቧቸው በኋላ ከውሃው ወጥተው እየመጡ ነው”

እያንዳንዱ መንታ አለው
በጎች አብዛኛውን ጊዜ በአንዴ ሁለት ግልገሎችን ይወልዳሉ። እነዚህ መንታዎች ብዙውን ጊዜ ይመሳሰላሉ። እያንዳንዱ የሴቲቱ ጥርስ በሌላ ጎን ካለው ጋር እኩል ነው።

ከመካከላቸው አንዱም አልጎደለም
እያንዳንዱ የሴቲቱ ጥርስ በሌላ ጎን ካለው ጋር እኩል ነው። ከጥርሶቿ አንድም የወለቀ የለም።

ሐዘንተኛ
የቅርብ ሰው የሞተበት

Song of Solomon 4:3

አጠቃላይ መረጃ፡
ሰውየው ሴቲቱን ማድነቁን ይቀጥላል

እንደ ደማቅ ቀይ ክር
ደማቅ ቀይ ውብ ቀለም ነው፤ ደማቅ ቀይ ክር ደግሞ በጣም ውድ ነበር። የሴቲቱ ከንፈሮች ቀይ ነበሩ። አ.ት፡ “እንደ ደማቅ ቀይ ክር ብስል ቀይ ናቸው” ወይም “ቀይና በጣም ውቦች ናቸው”።

ደማቅ ቀይ
ከደም ቀለም ጋር የሚመሳሰል ደማቅ ቀይ ቀለም

አስደሳች ነው
“ያማረ ነው”

እንደ ሮማን ክፋይ ናቸው
ሮማኖች ደማቅ ቀይ፣ ክብ እና ለስላሳ ናቸው። ሰውየው የሴቲቱ ጉንጮች ውቦችና እርሷም ጤነኛ መሆኗን እንደሚያሳዩ ያስባል። አ.ት፡ “እንደ ሁለት የሮማን ክፋዮች ቀይና ክብ ናቸው” ወይም “ቀይ፣ ሙሉና ጤናማ ናቸው”

ከአይነርግብሽ በስተጀርባ
ይህንን በመኃልይ 4:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Song of Solomon 4:4

አጠቃላይ መረጃ:
ሰውየው ሴቲቱን ማድነቁን ቀጥሏል።

አንገትሽ እንደ ዳዊት ግምብ ነው
ይህ እውነተኛ ግምብ ስለመሆኑ የሚያውቅ የለም። ግምብ ማለት ረጅምና ቀጭን ሕንጻ ሲሆን ዳዊት የገነባው መባሉ ውብ መሆኑን ያሳያል። ሰውየው የሴቲቱ አንገት ረጅም፤ ቀጭንና ውብ እንደሆነ ያስባል። አ.ት: “አንገትሽ እንደ ዳዊት ግምብ ረጅምና ያማረ ነው”

የዳዊት
“ዳዊት የገነባው”

በድንጋይ ድርድር የተገነቡ
ሴቶች ሙሉ አንገታቸውን የሚሸፍን የአንገት ሀብል ከጌጣጌጥ ድርድር ጋር ነበራቸው። ሰውየው እነዚህን የጌጣጌጥ ድርድሮች በግምቡ ላይ ካሉት የድንጋይ ድርድሮች ጋር ያነጻጽራቸዋል።

ከሺህ ጋሻ ጋር
ሰውየው በሴቲቱ የአንገት ሀብል ላይ ያሉትን ጌጣጌጦች በግምቡ ላይ ከተንጠለጠሉት ጋሻዎች ጋር ያነጻጽራቸዋል። የአንገት ሀብሏ አንገቷ ላይ ብዙ ዙር ዞሮ ይሆናል።

ሺህ ጋሻ
“1,000” ጋሻዎች

ሁሉም የወታደር ጋሻዎች
“የብርቱ ጦረኞች የሆኑ ጋሻዎች ሁሉ”

ሁለት ጡቶች
“ሁለት” የሚለው ቃል አላስፈላጊና ያለቦታው የገባ መስሎ ከታየህ ልታስወግደው ትችላለህ።

እንደ ሁለት የአጋዘን ግልገሎች፤ የአጋዘን መንታዎች
ሰውየው የሴቲቱ ጡቶች ተመሳሳይ፤ ለስላሳና ምናልባትም ትንንሽ እንደሆኑ ያመለክታል።

መንታዎች
ሁለት ልጆችን በአንድ ጊዜ የወለደች እናት፤ ልጆቹ መንታ ይባላሉ።

ሚዳቋ
አጋዘን የሚመስልና በፍጥነት የሚንቀሳቀስ እንስሳ ነው። ”አጋዘኖች” በመኃልይ 2:7 እንዳለው በነጠላ ቁጥር ተርጉመው።

በተዋቡ አበቦች መካከል እየጋጠ
“በተዋቡ አበቦች መካከል እየተመገበ”፤ ሰውየው “በተዋቡ አበቦች መካከል እየጋጠ” የሚለው የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸምን የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር መሆኑ የሚታወቅ ቢሆንም፤ እነዚህ ቃላት ምንን እንደሚያመለክቱ ግልፅ አይደለም። ቃል በቃል ቢተረጎሙ የተሻለ ይሆናል።

የተዋቡ አበቦች
ብዙ ውሃ ባለበት ስፍራ የሚበቅሉ መልካም መዓዛ ያላቸው አበቦች። በመኃልይ 2:1 ላይ እንዳለው “አበባ” የሚለውን በብዙ ቁጥር ተርጉመው።

Song of Solomon 4:6

አጠቃላይ መረጃ:
ሰውየው ሴቲቱን ማድነቁን ይቀጥላል።

ንጋት እስኪሆንና ጥላዎቹ እስኪሸሹ ድረስ
በመኃልይ 2:17 ያለውን ስንኝ እንደተረጎምከው በተመሳሳይ ቃላት ተርጉማቸው።

ወደ ከርቤ ተራራና ወደ ዕጣን ኮረብታ እሄዳለው
የ”ከርቤ ተራራ” እና “የዕጣን ኮረብታ” የሴቲቱን ጡቶች የሚገልፁ ዘይቤአዊ አነጋገሮች ናቸው። አ.ት: “የከርቤና የዕጣን ሽታ ያለባቸውን ተራሮች ወደሚመስሉት ጡቶችሽ ተጠግቼ እተኛለሁ” ወይም “ጣፋጭ ሽታ ወዳላቸው ጡቶችሽ ተጠግቼ እተኛለሁ” ወይም “ጣፋጭ ሽታ ወደሚሸቱት ተራሮች እሄዳለሁ”

የከርቤ ተራራ
“ከከርቤ የተሠራ ተራራ” ወይም “ከርቤ የሚበቅልበት ተራራ”

የእጣን ኮረብታ
“ከሚጨሰው የእጣን ጭስ የተነሳ በአየሩ ውስጥ የጭስ ደመና ያለበት ኮረብታ”

በሁሉም መልኩ ውብ ነሽ
“ሁሉም ክፍልሽ ውብ ነው” ወይም “ሁለመናሽ ውብ ነው”

የኔ ፍቅር
“አንቺ የምወድሽ”፣ ይህንን በመኃልይ 1:9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ምንም እንከን የለብሽም
“ምንም የሚነቀፍ ነገር የለብሽም”

Song of Solomon 4:8

አጠቃላይ መረጃ:
ሰውየው ለሴቲቱ መናገሩን ይቀጥላል። እርሱ ሰው በማይኖርበት፣ አደገኛና እንግዳ በሆነ ቦታ ያሉ ይመስል የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም ነጻ ያለመሆናቸውን ይናገራል።

ከሊባኖስ
“ከሊባኖስ ወዲያ”

ሙሽራዬ
ይህ የዕብራይስጡ ቃል ያገባችን ሴት ወይም አንድ ሰው ወንድ ልጁን ለመዳር ያዘጋጃትን ሴት ይወክላል። በቋንቋህ ውስጥ ባል ለሚስቱ ሊጠቀም የሚችለው ጨዋነት ያለው ቃል ካለና እስካሁን በዚህ መጽሐፍ ካልተጠቀምክበት እዚህ ጋ ልትጠቀምበት ትችላለህ። ካልሆነም ባል ለሚስቱ ሊጠቀምበት የሚችለውን ሌላ የጨዋነት ቃል መጠቀም ትችላለህ።

አማና
በሰሜን እስራኤል የሚገኝ የተራራ ስም

ሳኔር
በአማና እና አርሞንዔም አቅራቢያ ያለ ተራራ ስም ነው። አንዳንድ ሰዎች ይህ ራሱን አርሞንዔም ተራራን እንደሚያመለክት ያስባሉ።

ዋሻ
እንደ ጎሬ ያለ ቦታ ወይም የተቦረበረ መሬት ሆኖ አንበሶችና ነብሮች የሚኖሩበት

Song of Solomon 4:9

አጠቃላይ መረጃ:
ሰውየው ለሴቲቱ መናገሩን ይቀጥላል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ልቤን ሰርቀሽዋል
የዚህ ፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት 1) “አሁን ልቤ ሙሉ በሙሉ ያንቺ ነው” ወይም 2) “ካንቺ ጋር የግብረ ሥጋ ለመፈጸም አጥብቄ እፈልጋለው” ናቸው።

የኔ እህት
ይህ የፍቅር አነጋገር ነው። በመሠረቱ እነርሱ ወንድምና እህት አይደሉም። አ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ ፍቅር”

ሙሽራዬ
ይህ የዕብራይስጡ ቃል ያገባችን ሴት ወይም አንድ ሰው ወንድ ልጁን ለመዳር ያዘጋጃትን ሴት ይወክላል። በቋንቋህ ውስጥ ባል ለሚስቱ ሊጠቀም የሚችለው ጨዋነት ያለው ቃል ካለና እስካሁን በዚህ መጽሐፍ ካልተጠቀምክበት እዚህ ጋ ልትጠቀምበት ትችላለህ። ካልሆነም ባል ለሚስቱ ሊጠቀምበት የሚችለውን ሌላ የጨዋነት ቃል መጠቀም ትችላለህ። ይህንን በመኃልይ 4፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

አማና
x

ልቤን፤ በአንድ እይታ ብቻ፤ በአንድ ጌጥ ብቻ
“ልቤ፤ ማድረግ የሚኖርብሽ አንዴ ብቻ እኔን መመልከት ወይም አንድ ጌጥ ማሳየት ነው።” የሴቲቱ ዐይንና ጌጣጌጧ ሰውየውን ወደርሷ ስቧል።

የአንገት ሀብል
ይህ የአንገት ሀብል በአንገቷ ላይ ደጋግሞ ተጠምጥሞ ይሆናል።

Song of Solomon 4:10

አጠቃላይ መረጃ፡
ሰውየው ለሴቲቱ መናገሩን ይቀጥላል።

ፍቅርሽ እንዴት ያማረ ነው
“ፍቅርሽ ግሩም ነው”

እህቴ
ይህ የፍቅር አነጋገር ነው። በመሠረቱ እነርሱ ወንድምና እህት አይደሉም። ይህንን በመኃልይ 4፡9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ ፍቅር”

ሙሽራዬ
ይህ የዕብራይስጡ ቃል ያገባችን ሴት ወይም አንድ ሰው ወንድ ልጁን ለመዳር ያዘጋጃትን ሴት ይወክላል። በቋንቋህ ውስጥ ባል ለሚስቱ ሊጠቀም የሚችለው ጨዋነት ያለው ቃል ካለና እስካሁን በዚህ መጽሐፍ ካልተጠቀምክበት እዚህ ጋ ልትጠቀምበት ትችላለህ። ካልሆነም ባል ለሚስቱ ሊጠቀምበት የሚችለውን ሌላ የጨዋነት ቃል መጠቀም ትችላለህ። ይህንን በመኃልይ 4፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ፍቅርሽ ከወይን ጠጅ ይልቅ እጅጉን ይሻላል
“ፍቅርሽ ከወይን ጠጅ ይልቅ እጅግ የተሻለ ነው”። ተመሳሳዩን ሐረግ በመኃልይ 1፡2 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የሽቶሽ መዓዛ ከየትኛውም ቅመም
ግሱ ምናልባት ቀደም ብሎ ካለው ሐረግ ወስዶ ይሆናል። አ.ት፡ “ከየትኛውም ቅመም ይልቅ የሽቱሽ መዓዛ እጅግ የተሻለ ነው”

መዓዛ ...ሽቱ
እነዚህን ቃላት በመኃልይ 1፡3 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

ቅመም
መልካም ሽታ ወይም ጣዕም ያላቸው የደረቁ እፅዋት ወይም ዘሮች

ከንፈሮችሽ ... ማር ያንጠባጥባሉ
ማር ትርጓሜዎች ሊሆኑ ለሚችሉ ለሚከተሉት 1) የሴቲቱን የአሳሳም ጣፋጭ ጣዕም ወይም 2) የሴቲቱን ቃላት ለማመልከት የዋለ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው።

ከምላስሽ በታች ወተትና ማር አለ
“ወተትና ማር” በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተለመደ ሐረግ ስለሆነ ቃል በቃል መተርጎም አለብህ። ትርጉሞች ሊሆኑ የሚችሉት ማር የሚለው ዘይቤአዊ አነጋገር 1) የሴቲቱን የአሳሳም ጣፋጭ ጣዕም 2) የሴቲቱን ቃላት ሊሆን ይችላል። ወተት የምቾት፤ ሰዎች ሕይወትን ለማጣጣም የሚኖሯቸውን በርካታ ነገሮች የሚገልፅ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ሴቲቱ ሰውየውን ስትስመው፣ እርሱ ሕይወትን ያጣጥማል።

የልብስሽ መዓዛ እንደ ሊባኖስ ሽታ ነው
“የልብስሽ ሽታ እንደ ሊባኖስ ሽታ ነው”። በሊባኖስ ብዙ የጥድ ዛፎች ይበቅሉ ነበር። የጥድ ዛፎች በጣም ጥሩ ሽታ አላቸው፤ በመሆኑም፣ሊባኖስ ንጹሕና ጣፋጭ ሽታ ሳይኖራት አልቀረችም።

Song of Solomon 4:12

አጠቃላይ መረጃ፡
ሰውየው ሴቲቱን ማድነቁን ቀጥሏል።

የኔ እህት
ይህ የፍቅር አነጋገር ነው። በመሠረቱ እነርሱ ወንድምና እህት አይደሉም። ይህንን በመኃልይ 4፡9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ ፍቅር”

ሙሽራዬ
ይህ የዕብራይስጡ ቃል ያገባችን ሴት ወይም አንድ ሰው ወንድ ልጁን ለመዳር ያዘጋጃትን ሴት ይወክላል። በቋንቋህ ውስጥ ባል ለሚስቱ ሊጠቀም የሚችለው ጨዋነት ያለው ቃል ካለና እስካሁን በዚህ መጽሐፍ ካልተጠቀምክበት እዚህ ጋ ልትጠቀምበት ትችላለህ። ካልሆነም ባል ለሚስቱ ሊጠቀምበት የሚችለውን ሌላ የጨዋነት ቃል መጠቀም ትችላለህ። ይህንን በመኃልይ 4፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የተቆለፈበት የአትክልት ስፍራ ነው
“ማንም ሊገባበት የማይችል የአትክልት ስፍራ”። የአትክልት ስፍራው ለሴቲቱ፤ ቁልፉ ደግሞ ለድንግልናዋ ዘይቤአዊ አነጋገሮች ናቸው።

የታተመ ምንጭ
“መክደኛ ያለው ምንጭ”። ምንጩ ወይም የውሃው ጉድጓድ ሴቲቱን፤ ሽፋኑ ደግሞ ድንግልናዋን የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው።

ቅርንጫፎችሽ
ቅርንጫፎች ወይም የወንዝ መውረጃዎች የሴቲቱን የሰውነት ክፍል በጨዋ አነጋገር የሚገልጹ ናቸው። የእነዚህ ቃላት አጠቃቀም ቅር የሚያሰኝ ከሆነ የሰውን ሁለንተና መግለጽ በሚችል የተሻለ ምሳሌአዊ አነጋገር ተርጉመው።

ጫካ
ብዙ ዛፎች በአንድ ላይ የሚበቅሉበት ስፍራ

ከምርጥ ፍራፍሬዎች ጋር
“ምርጥ ከሆኑ የፍራፍሬ አይነቶች ጋር”

የናርዶስ ተክሎች
ሰዎች ቆዳቸውን ለማለስለስና መልካም መዓዛ እንዲኖራችው የሚጠቀሙበትን ዘይት የሚሰጥ ተክል። ይህንን በመኃልይ 1፡14 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሄና
ሰዎች እንደ ሽቱ የሚጠቀሟቸው ትናንሽ የበረሃ ዛፎች። ይህንን በመኃልይ 1፡14 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

እርድ
ከአንድ ዓይነት አበባ መሐሉ ላይ ከሚገኝ ቢጫ የደረቀ ክፍል የሚገኝ ቅመም

ቀጋ
ሰዎች የቅባት ዘይት ለመስራት የሚጠቀሙበት መልካም መዓዛ ያለው ተክል

ቀረፋ
ሰዎች ለማብሰል ከሚጠቀሙበት ዛፍ ቅርፊት የሚገኝ ቅመም

ከርቤ
እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሬት
ጣፋጭ ሽታ ያለው፣ ሰፊ ቅጠል ያለው የተክል ዓይነት

ምርጥ ቅመማ ቅመሞች ሁሉ
“ምርጥ የሆኑ ቅመሞች ሁሉ”

Song of Solomon 4:15

አጠቃላይ መረጃ
ሰውየው ሴቲቱን ማድነቁን ይቀጥላል።

አንቺ የአትክልት ቦታ ምንጭ ነሽ
“በአትክልት ቦታ ያለ ምንጭ ነሽ”። በአትክልት ቦታ የሚገኝ ምንጭ ሰዎች ለመጠጣት የሚወዱትን ጣፋጭና ንፁህ ውሃ ይሰጣል። ሰውየው በሴቲቱ አጠገብ በመሆኑ ይደሰታል።

ንፁህ ውሃ
ለመጠጥ ጥሩ የሆነ ውሃ

ከሊባኖስ የሚወርዱ ምንጮች
ሊባኖስ በዛፍ የተሸፈኑ ተራሮች ስላነበሯት ከሊባኖስ የሚወርዱት ምንጮች ንጹሕና ቀዝቃዛ ነበሩ።

የሰሜኑ ንፋስ ተነሥ፤ የደቡቡ ንፋስ ና ንፈስ
ሴቲቱ የሰሜኑ እና የደቡቡ ንፋስ ሰዎች እንደሆኑ አድርጋ ትናገራለች። አ.ት፡ “የሰሜኑ ንፋስና የደቡቡ ንፋስ መጥተው ቢነፍሱ እወዳለሁ”

የሰሜኑ ንፋስ ተነሥ
“የሰሜን ንፋስ መንፈስ ጀምር”

በአትክልት ቦታዬ ላይ ንፈስ
የአትክልት ስፍራው መልካም ሽታ ባላቸው ቅባቶች የተቀባውን የሴቲቱን ገላ የሚገልጽ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው (መኃልይ 4፡14) ።

መዓዛቸውን ይስጡ
“መልካም ሽታቸውን ይልቀቁ”

ወዳጄ ... ምርጥ ፍራፍሬ
ሴቲቱ ሰውየው አብሯት እንዲተኛ እየጋበዘችው ነው።

ወዳጄ
ይህ ሐረግ ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች ሴቲቱ “የኔ አፍቃሪ” ብትለው በይበልጥ የተለመደ ይሆን ይሆናል። ይህንን በመኃልይ 1፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ አፍቃሪ”።

ምርጥ ፍሬ
“ግሩም ፍሬ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 5

1 እህቴ፥ ሙሽራዬ፥ ወደ አትክልቴ ቦታ መጣሁ፤ ከርቤዬን ከቅመሜ ጋር ሰብስቤአለሁ። የማር እንጀራዬን ከወለላው ጋር በልቻለሁ፤ ወይኔን ከወተቴ ጋር ጠጥቻለሁ። ጓደኞች ለአፍቃሪዎች ሲናገሩ፥ ጓደኞቻችን ሆይ ብሉ፤ ጠጡ፥ በፍቅርም ስከሩ። ወጣቷ ለራሷ ስትናገር፥ **2** እኔ ተኝቻለሁ፥ ልቤ ግን በሕልም ነቅቷል። የውዴ ድምጽ ነው፥ በሩን ያንኳኳል፥ "እህቴ፥ ውዴ፥ እርግቤ፥ እንከን የሌለብሽ ሆይ፥ ራሴ በጤዛ ርሷል ፀጉሬም በሌሊቱ እርጥበት፥ ስለዚህ ክፈችልኝ" እያለ። **3** "ልብሴን አውልቄአለሁ፤ እንደገና መልበስ አለብኝ? እግሬን ታጥቤአለሁ፤ ማቆሸሽ አለብኝ?" **4** ውዴ በበሩ መካፈቻ ቀዳዳ በኩል እጁን አስገባ፥ ልቤም ስለ እርሱ ታወከ። **5** ለውዴ በሩን ልከፍትለት ተነሣሁ፥ እጆቼ ከርቤን አንጠባጠቡ፥ ጣቶቼ በበሩ እጀታ ላይ በከርቤ ረጠቡ። **6** ለውዴ በሩን ከፈትኩለት፥ ውዴ ግን ተመልሶ ሄዶ ነበር። ልቤ ደነገጠ፤ እኔም ተከፋሁ። ፈለግሁት፥ ነገር ግን አላገኘሁትም፤ ጠራሁት፥ ነገር ግን አልመለሰልኝም። **7** ጠባቂዎቹ በከተማ ሲዘዋወሩ አገኙኝ፤ መቱኝ፥ አቆሰሉኝም፤ በቅጥሩ ላይ ያሉት ጠባቂዎችም ካባዬን ወሰዱብኝ። ወጣቷ ለከተማው ሴቶች ስትናገር፥ **8** እናንተ የኢየሩሳሌም ሴቶች ልጆች፥ ውዴን ካገኛችሁት ለእርሱ ካለኝ ፍቅር የተነሣ መታመሜን ልትነግሩት ቃል እንድትገቡልኝ እፈልጋለሁ። የከተማው ሴቶች ለወጣቷ ሲናገሩ፥ **9** አንቺ በሴቶች መካከል የተዋብሽዋ ሆይ፥ ውድሽ ከሌላው አፍቃሪ ወንድ የተሻለው እንዴት ነው? እንዲህ ያለውን መሐላ እንድናደርግ የጠየቅሽን ውድሽ ከሌላው አፍቃሪ የተሻለው ለምንድነው? ወጣቷ ለከተማው ሴቶች ስትናገር፥ **10** ውዴ ደስተኛና ቀይ ነው፥ ከአሥር ሺዎችም የላቀ ነው። **11** ራሱ ንጹህ ወርቅ ነው፤ ፀጉሩም ዘማና እንደ ቁራ የጠቆረ ነው። **12** ዓይኖቹ በጅረት አጠገብ እንዳሉ እርግቦች፥ በወተት እንደ ታጠቡ፥ በማስቀመጫቸው ያሉ ዕንቁዎችን ይመስላሉ። **13** ጉንጮቹ የሽቶ መዓዛ የሚሰጡ የልዩ ልዩ ቅመማ ቅመም መደብ ይመስላሉ። ከንፈሮቹ ከርቤን የሚያንጠባጥቡ አበቦች ናቸው። **14** ክንዶቹ የዕንቁ ፈርጥ ባለበት ወርቅ ተሸፍኗል፤ ሆዱ በሰንፔር ያጌጠ የዝሆን ጥርስ ነው። **15** እግሮቹ በንጹህ የወርቅ መሠረት ላይ የቆሙ፥ የእምነ በረድ ምሶሶዎች ናቸው፤ መልኩ እንደ ሊባኖስ፥ እንደ ተመረጠም ዝግባ ነው። **16** አፉ እጅግ ጣፋጭ ነው፤ እርሱ ፍጹም ውብ ነው። የኢየሩሳሌም ሴቶች ልጆች ሆይ፥ ውዴ ይህ ነው፥ ጓደኛዬም እርሱው ነው።

Song of Solomon 5:1

አጠቃላይ መረጃ
x

መጥቻለሁ
ተናጋሪው የሴቲቱ አፍቃሪ መሆኑ ግልጽ ነው።

ወደ አትክልት ቦታዬ መጥቻለሁ
“የአትክልት ቦታ” የሚለው ቃል ሴቲቱን የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። በመጨረሻም ሰውየው ከሴቲቱ ጋር ባደረጉት የግብረ ሥጋ ግንኙነት በሚገባ መርካት ችሎአል።

እህቴ
ይህ ማፍቀርን የሚያመለክት የአነጋገር ዘይቤ ነው። በእርግጥ እነርሱ ወንድምና እህት አይደሉም። መኃልይ 4:9ን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልክት። አ.ት፡ “የእኔ ተወዳጅ” ወይም “የእኔ ተፈቃሪ”።

ሙሽራዬ
ይህ የዕብራይስጡ ቃል የተዳረችን ሴት ወይም ለልጁ ሚስት ያጨለትን ሰው ያመለክታል። በቋንቋህ በዚህ መጽሐፍ ጥቅም ላይ ያልዋለ፣ ባል ለሚስቱ የሚጠቀምበት ትህትናን የተላበሰ ቃል ካለ እዚህ ጋ ልትጠቀምበት ትችላለህ። ካልሆነም አንድ ሰው ከሚስቱ ጋር ሊጠቀም የሚችልበትን ሌላ የትኛውንም ትህትና የተላበሰ ቃል መጠቀም ትችላለህ። መኃልይ 4:9ን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ከርቤ ... ቅመም ... የማር እንጀራ ... ማር ... ወይን ... ወተት
እነዚህ ሁሉ ሰውየው በሴቲቱ አካል የሚደሰትባቸው ዘይቤአዊ አነጋገሮች ናቸው (መኃልይ 1:13፣ 2:4፣ 4:11 እና 4:14)።

ቅመም
ጠንካራ ሽታ ወይም ጣዕም ያላቸው ተክሎች

ብሉ ... ጠጡ ... በፍቅር ስከሩ
መብላትና መጠጣት የግብረ ሥጋ ግንኙነት የመፈጸም ዘይቤአዊ አነጋገሮች ናቸው። አ.ት፡ “በሚገባ እስክትረኩ ድረስ የግብረ ሥጋ ግንtttttኙነት ፈጽሙ ... የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጽሙ”

Song of Solomon 5:2

አጠቃላይ ማስታወሻ
የመጽሐፉ አራተኛው ክፍል እዚህ ጋ ይጀምራል።

አጠቃላይ መረጃ
ወጣቷ ሴት ሕልሟ በሁለት የተለያዩ መንገዶች እንዲተረጎሙ ጨዋነት ያለበትን ቃል በመጠቀም ትገልጻለች፤ 1) ሴቲቱ፣ ሰውየው በምሽት ሊጎበኛት ወደ ቤቷ ስለመጣበት ሕልም ትገልጻለች፤ ደግሞም 2) ሴቲቱ ከሰውየው ጋር መተኛት ስለመጀመሯ ያየችውን ሕልም ትገልጻለች።

ልቤ ግን ነቅቷል
ልብ የአሳብና የስሜት ማዕከል ነው። አ.ት፡ “ነገር ግን በሚገባ ማሰብ እችል ነበር” ወይም “ነገር ግን ይሰማኝ የነበረውን ስሜት ዐውቅ ነበር”

የእኔ ተወዳጅ
ሐረጉ ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች “የእኔ አፍቃሪ” ማለቷ በይበልጥ የተለመደ ሊሆን ይችላል። መኃልይ 1:13ን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ አፍቃሪ”።

ክፈቺልኝ
1) ቃል በቃል “በሩን ክፈቺልኝ”፣ ወይም 2) በዘይቤአዊ አነጋገር “ከአንቺ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንድፈጽም ፍቀጅሊኝ” ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች ናቸው።

እህቴ
ይህ ማፍቀርን የሚያመለክት የአነጋገር ዘይቤ ነው። በእርግጥ እነርሱ ወንድምና እህት አይደሉም። መኃልይ 4:9ን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልክት። አ.ት፡ “የእኔ ተወዳጅ” ወይም “የእኔ ተፈቃሪ”።

የእኔ ፍቅር
“እኔ የምወድህ”፣ መኃልይ 1:9ን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

እርግቤ
ይህንን በመኃልይ 2:14 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

እንከን የሌለብሽ
“የእኔ ፍጹም” ወይም “የእኔ ታማኝ” ወይም “የእኔ ንጹሕ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጤዛ
የውሃ ጠብታዎች ወይም ሌሊቱ በሚቀዘቅዝበት ጊዜ የሚፈጠር እርጥበት

ጸጉሬ በሌሊቱ እርጥበት
“ረጥቧል” የሚለውን ቃል ቀደም ብሎ ካለው ሐረግ መረዳት ይቻላል። እዚህ ጋ መደገም ይችላል። አ.ት፡ “ጸጉሬ በሌሊቱ እርጥበት ረጥቧል”

Song of Solomon 5:3

“ልቤሴን አውልቄአለሁ ... አቆሽሻለሁ?”
ሰውየው ሲናገር በሰማች ጊዜ ሴቲቱ በልቧ ያሰበችው ይህንን ነው። ሴቲቱ እንዲህ ብላ ታስብ ነበር ተብሎ ሊተረጎም ይችላል ወይም በተከፈተው ተለዋዋጭ ትርጉም (ዩ ዲ ቢ) እንዳለው ሴቲቱ ሁኔታውንና አሳቧን ብቻ መግለጽ ትችላለች። አ.ት፡ “ ‘ልብሴን አውልቄአለሁ ... አቆሽሻለሁ? ብዬ አሰብኩ” ወይም “ልብሴን አውልቄአለሁ፣ እንደገና ልለብሰው አልፈልግም፤ እግሬን ታጥቤአለሁ፣ እንዲቆሽሽብኝ አልፈልግም”

ልብስ
ከላይነን ጨርቅ የሚሠራ፣ ሰዎች ከውስጥ የሚለብሱት ስስ ልብስ

እንደገና መልበስ አለብኝ?
ይህ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እንደገና መልበስ አልፈልግም”

እግሬን ታጥቤአለሁ
“እግር” ድብቅ የአካል ክፍሎችን እንዲያመለክት በጨዋነት የሚነገር ቃል ሆኖ ሳለ ይህኛው ቃል በቃል እግርን ሳያመለክት አይቀርም። ሴቲቱ በመታጠቧ ምክንያት ከግብረ ሥጋ ግንኙነት ከመራቅ ይልቅ ልታደርገው የፈለገች ትመስላለች።

ላቆሽሸው?
ይህ በመግለጫነት ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እንዲቆሽሽብኝ አልፈልግም”።

ወዳጄ እጁን በበሩ መወርወሪያ መክፈቻ በኩል እጁን ሰደደ
1) ቃል በቃል፣ አፍቃሪዋ በሩን ለመክፈት በበሩ ቀዳዳ በኩል እጁን ማስገባት ችሎአል ወይም 2) የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ መጀመራቸው በጨዋ አነጋገር ተገልጿል የሚሉት ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች ናቸው።

ወዳጄ
ይህ ሐረግ ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች “የእኔ አፍቃሪ” ማለቷ በይበልጥ የተለመደ ሊሆን ይችላል። መኃልይ 1፡13ን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ አፍቃሪ”።

የበር መወርወሪያ
“የበር ቁልፍ”

Song of Solomon 5:5

ለወዳጄ በሩን ልከፍትለት ተነሣሁ
1) ቃል በቃል፣ ሰውየውን ወደ ቤት ለማስገባት ወጣቷ ሴት ከአልጋዋ ተነሥታለች፣ ወይም 2) ዘይቤአዊ አነጋገር ሊሆን ይችላል። አ.ት፡ “ከወዳጄ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም ራሴን አዘጋጀሁ” የሚሉት ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች ናቸው።

እጆቼ ... ጣቶቼ ... የበሩን እጀታ
እነዚህ የሴቲቱንና የሰውየውን አካላት የሚያመለክቱ ጨዋ አገላለጾች ቢሆኑም ቃል በቃል መተርጎማቸው የተሻለ ነው።

ከእርጥብ ከርቤ ጋር
“ከፈሳሽ ከርቤ ጋር”

Song of Solomon 5:6

አጠቃላይ ማስታወሻ
ሴቲቱ ሕልሟን መግለጿን ትቀጥላለች።

ወዳጄ
ይህንን በመኃልይ 1፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ልቤ ፈሰሰ
ልብ የሰውን ሁለንተና የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ሲሆን መስመጥ፣ መጥለቅ የመድከም ወይም የማዘን ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “በጣም አዝኜ ነበር”

Song of Solomon 5:7

ጠባቂዎች
በምሽት የሕዝቡን ደኅንነት ለመጠበቅ በከተማይቱ የጥበቃ ሥራ ላይ የተሠማሩ ሰዎች ናቸው። ይህንን በምዕራፍ 3፡3 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

በከተማይቱ ውስጥ እየተዟዟሩ በሚጠብቁበት ጊዜ
“በከተማይቱ ቅጥሮች ላይ ይመላለሱ የነበሩት”። ይህንን በመኃልይ 3፡3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

አገኙኝ
ሴቲቱን አገኟት

መቱኝ
“ደበደቡኝ” ወይም “ጎሰመኝ”

አቆሰሉኝ
“እንድቆስል አደረጉኝ”

በቅጥሩ ላይ ያሉ ጠባቂዎች
“ቅጥሩን የሚጠብቁ ሰዎች”

መደረቢያ ልብስ
ሰዎች ወደ ውጭ ሲወጡ በለበሱት ልብስ ላይ ደርበው የሚለብሱት ልብስ

Song of Solomon 5:8

እንድትምሉልኝ እፈልጋለሁ
ይህንን በምዕራፍ 2፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የኢየሩሳሌም ሴቶች ልጆች
“የኢየሩሳሌም ወጣት ሴቶች”፣ እነዚህ ወጣት ሴቶች በዚያ የሉም፣ ሊሰሟትም አይችሉም፤ ነገር ግን ሴቲቱ እነርሱ እንዳሉና እንደሚሰሟት ቆጥራ ትናገራለች። ይህንን በመኃልይ 2፡7 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ወዳጄ
ይህ ሐረግ ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች “የእኔ አፍቃሪ” ማለቷ በይበልጥ የተለመደ ሊሆን ይችላል። ይህንን በመኃልይ 1፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ አፍቃሪ”።

ለወዳጄ ምን እንደሆንኩ የምትነግሩት መሰላችሁ?
ሴቲቱ የኢየሩሳሌም ሴቶች ልጆች ለወዳጇ እንዲነግሩት የምትፈልገውን በጥያቄ መልክ ታቀርብላቸዋለች። አ.ት፡ “ለወዳጄ እንዲህ ብላችሁ እንድትነግሩት እፈልጋለሁ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከፍቅሩ የተነሣ መታመሜን
ሰውየውን ሕመም እስኪሰማት ድረስ እጅግ ትወደዋለች።

Song of Solomon 5:9

ወዳጅሽ
ይህ ቃል ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች ሌሎች ሴቶች እርሱን በሚመለከት “አፍቃሪሽ” ማለታቸው በይበልጥ የተለመደ ሊሆን ይችላል። በመኃልይ 1:13 “ወዳጄ” የሚለውን ቃል እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ከሴቶች መካከል እጅግ የተዋብሽ
“አንቺ ከሴቶች ሁሉ እጅግ የተዋብሽ ነሽ”። ይህንን በመኃልይ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ወዳጅሽ የተሻለ የሆነው ለምንድነው?
“ወዳጅሽን የተሻለ የሚያደርገው ምንድነው”

እንዲህ ያለ መሓላ እንድናደርግ የምትጠይቂን
“ይህንን መሓላ እንድናደርግ ያስደረገሽ”

እንዲህ ያለ መሓላ
መሓላ በመኃልይ 5:8

Song of Solomon 5:10

ወዳጄ
ይህ ሐረግ ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች “የእኔ አፍቃሪ” ማለቷ በይበልጥ የተለመደ ሊሆን ይችላል። ይህንን በመኃልይ 1:13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ አፍቃሪ”።

ብሩህና ደመ ግቡ ነው
ሐረጉ የፊት ቆዳውን ያመለክታል። አ.ት፡ “ብሩህና ማራኪ የቆዳ ቀለም አለው”

ብሩህ
“ፍጹም ጤነኛ” ወይም “ንጹሕ ነው”። ሰውየው ምንም እንከን የሌለበት የፊት ቆዳ አለው።

ደመ ግቡ
ጤናማ የሆነ የቀይ ዳማ

በአሥር ሺዎች መካከል በላጭ ነው
“ከ10,000ዎች የተመረጠው”። አ.ት፡ “ከማንም ይልቅ የተሻለ” ወይም “እንደ እርሱ ያለ ማንም የለም”።

ራሱ ንጹሕ ወርቅ ነው
የሰውየው ራስ ለሴቲቱ ከንጹሕ ወርቅ ይልቅ የከበረ ነው።

ቁራ
በጣም የጠቆረ ላባ ያለው ወፍ

Song of Solomon 5:12

አጠቃላይ መረጃ
ወጣቷ ሴት ሰውየውን መግለጿን ትቀጥላለች።

ዓይኖቹ እንደ እርግቦች ናቸው
“ዓይኖቹ እንደ እርግቦች ናቸው” የሚለውን በመኃልይ 1:15 እንዳለው አድርገህ ተርጉመው። 1) እስራኤላውያን እርግቦች ረጋ ያሉና ለስላሳ ወፎች እንደሆኑ ያስባሉ፣ ሴቲቱም ሰውየው ወደ እርሷ የሚያይበት አስተያየት ረጋ ያለ፣ ዓይኖቹም የተዋቡ እንደሆኑ ታስባለች። አ.ት፡ “ዓይኖቹ እንደ እርግብ ረጋ ያሉ ናቸው” ወይም 2) ሴቲቱ ስለ ሰውየው ነጩ የዓይን ኳስ ወይም ዓይኖቹ የእርግብ ቅርፅ እንዳላቸው እየተናገረች ነው የሚሉት ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች ናቸው።

በውሃ ምንጮች ዳር ያሉ እርግቦች
እስራኤላውያን ረጋ ያለን ሰው በእርጋታ በሚወርድ ምንጭ አጠገብ እንደሚቀመጡ ረጋ ያሉ ወፎች የሚቆጥሩበት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው።

የውሃ ምንጮች
“በዝግታ የሚወርድ ውሃ”

በወተት የታጠቡ
ወተት የእርግቦቹን ነጭነት የሚገልጽ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “እንደ ወተት የነጡ እርግቦች” ወይም 2) ወተት የሰውየውን ነጭ የዐይን ክፍል የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “የዐይን ብሌኖቹ በነጭ ወተት እንደ ታጠቡ እርግቦች ናቸው”

ፈርጥ የገባበት የከበሩ ድንጋዮች
ዐይኖቹ ውቦች ናቸው። አንጥረኛ በጥንቃቄ ያስቀመጣቸው ባለ ፈርጥ የከበሩ ድንጋዮች የተዋቡ ናቸው።

Song of Solomon 5:13

አጠቃላይ መረጃ
ወጣቷ ሴት ሰውየውን መግለጿን ትቀጥላለች።

ጉንጮቹ ... የጠረኑ መዓዛ
ይህ ጉንጮቹ የቅመማ ቅመም መደቦችን እንደሚመስሉ ያብራራል፣ ምክንያቱም ሁለቱም ጣፋጭ መዓዛቸውን ይለቃሉ።

የቅመማ ቅመም መደቦች
ሰዎች ቅመማ ቅመሞችን የሚያበቅሉበት የአትክልት ስፍራ ወይም ከፊል የአትክልት ስፍራ። ቅመማ ቅመሞች ለሰዎች ደስታን ይሰጣሉ። የሰውየው አካል ለሴቲቱ ደስታን ይሰጣታል።

የሸቱ መዓዛ የሚያመጡ
“ግሩም ሽታቸውን የሚሰጡ”

ከንፈሮቹ ውብ አበቦች ናቸው
ሴቲቱ ምናልባት ከንፈሩ ውቦችና መልካም ሽታ ያላቸው በመሆናቸው ምክንያት ከተዋቡ አበቦች ጋር ታነጻጽራቸዋለች።

ውብ አበቦች
ይህንን በመኃልይ 2:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ፈሳሹን ከርቤ የሚያንጠባጥቡ
“ምርጥ ከርቤ የሚያንጠባጥብ”፣ ከንፈሮቹ የረጠቡና እንደ ግሩም ከርቤ የሚሸቱ ናቸው።

Song of Solomon 5:14

አጠቃላይ መረጃ
ሴቲቱ ስለ ሰውየው መግለጫ መሰጠቷን ቀጥላለች።

ክንዶቹ ፈርጦች በገቡበት ወርቅ የተለበጡ ናቸው
“ክንዶቹ ሁለመናቸው ፈርጥ ያለባቸው የወርቅ ዘንግ ናቸው”። ሴቲቱ ይህንን ሥዕል የምትጠቀመው ክንዶቹ ያማሩና የከበሩ ናቸው ለማለት ነው። የመጀመሪያዎቹ አንባቢዎች ይህንን በዘይቤአዊ አነጋገር የወንድ አካል ክፍል አድርገው ሳይረዱ አልቀሩም (መኃልይ 5:3ን ተመልከት)፣ ነገር ግን ይህንን በትርጉም ማሳየት አስቸጋሪ ይሆናል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሆዱ በዕንቁ የተለበጠ የዝሆን ጥርስ ነው
“ሆዱ ዕንቁ የሞላበት ልሙጥ የዝሆን ጥርስ ነው”። ሴቲቱ ሆዱ ያማረና የከበረ ነው ለማለት ይህንን ሥዕል ትጠቀማለች።

የዝሆን ጥርስ
አጥንት የሚመስል፣ የእንስሳው ነጭ ጥርስ። ሰዎች የለሰለሱና የሚያብረቀርቁ የጥበብ ሥራዎችን ለመሥራት በዝሆን ጥርስ ይጠቀማሉ።

ዕንቁዎች
የከበሩ ድንጋዮች ሲሆኑ 1) ሰማያዊ ወይም 2) ንጹሕ ሰማያዊ ወይም ወርቃማ ናቸው።

Song of Solomon 5:15

አጠቃላይ መረጃ
ሴቲቱ ስለ ሰውየው መግለጫ መሰጠቷን ቀጥላለች።

እግሮቹ በወርቅ መሠረት ላይ የቆሙ የዕብነ በረድ ዐምድ ናቸው
ዕብነ በረድና ወርቅ ጠንካራና የተዋቡ ናቸው።

ዕብነ በረድ
የተለያየ ቀለም ያለው ጠንካራ ድንጋይ ሲሆን ሰዎች በጣም ልሙጥ እንዲሆን ይወለውሉታል

መልኩ እንደ ሊባኖስ ነው
“ሊባኖስን ይመስላል”። ሊባኖስ በርካታ ተራሮችና ጥዶች ያሉበት በጣም ውብ አካባቢ ነበር።

Song of Solomon 5:16

አጠቃላይ መረጃ
ሴቲቱ ስለ ሰውየው መግለጫ መስጠቷን ቀጥላለች።

አፉ እጅግ ጣፋጭ ነው
አፍ 1) የሰውየውን ጣፋጭ አሳሳም ወይም 2) እርሱ የሚናገራቸውን ጣፋጭ ቃላት የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው።

እርሱ ሁለንተናው ያማረ ነው
“የእርሱ ሁለንተናው ያማረ ነው” ወይም “ሁለመናው ያማረ ነው”

ወዳጄ ይህ ነው፣ ጓደኛዬም ይህ ነው
“ይህ” የሚለው ቃል ሴቲቱ ገለጻዋን የጨረሰችለትን ሰውዬ ያመለክታል። አ.ት፡ “የምወደው የሚመስለው ይህንን ነው፣ ጓደኛዬ የሚመስለውም ይህንን ነው”

ወዳጄ
ይህ ሐረግ ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች “የእኔ አፍቃሪ” ማለቷ በይበልጥ የተለመደ ሊሆን ይችላል። ይህንን በመኃልይ 1፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ አፍቃሪ”።

የኢየሩሳሌም ሴቶች ልጆች
“የኢየሩሳሌም ወጣት ሴቶች”፣ እነዚህ ወጣት ሴቶች በዚያ ስላልነበሩ ሊሰሟት አይችሉም፣ ነገር ግን ሴቲቱ እንዳሉና ሊሰሟት እንደሚችሉ ቆጥራ ትናገራለች። ይህንን በመኃልይ 2፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 6

[1] በሴቶች መካከል እጅግ የተዋብሽዋ ሆይ፥ ውድሽ ወዴት ሄደ? ካንቺ ጋር እንድንፈልገው ውድሽ የሄደው በየትኛው አቅጣጫ ነው? ወጣቷ ለራሷ ስትናገር፥ [2] በአትክልቱ ሥፍራ መንጋውን ሊያሠማራ፥ አበቦችንም ሊሰበስብ፥ ውዴ ወደ አትክልቱ ሥፍራ፥ ወደ ቅመማ ቅመሞቹ መደቦች ወርዷል። [3] እኔ የውዴ ነኝ፥ ውዴም የእኔ ነው፤ በአበቦቹ መካከል መንጋውን በደስታ ያሰማራል። የሴቲቱ አፍቃሪ እንዲህ ይላታል፥ [4] ውዴ ሆይ፥ እንደ ቴርሳ ቆንጆ ነሽ፥ እንደ ኢየሩሳሌም ውብ ነሽ፥ ሰንደቁን እንደያዘ ሠራዊት ታስፈሪያለሽ። [5] አድክመውኛልና ዓይኖችሽን ከእኔ መልሺ። ፀጉርሽ ከገለዓድ ተራራ ቁልቁል የሚወርደውን የፍየል መንጋ ይመስላል። [6] ጥርሶችሽ ከመታጠቢያ ሥፍራቸው የሚመጡትን የሴት በግ መንጋ ይመስላሉ። እያንዳንዱ መንታ ወልዷል፥ በመካከላቸውም መካን የለም። [7] በመሸፈኛሽ ውስጥ ጉንጮችሽ ለሁለት የተከፈለ ሮማን ይመስላሉ። የሴቲቱ አፍቃሪ ለራሱ ሲናገር፥ [8] ስልሳ ንግሥቶች፥ ሰማንያ ቁባቶች፥ ሥፍር ቁጥር የሌላቸው ልጃገረዶች አሉ። [9] እርግቤ፥ እንከን የሌለባት፥ ብቸኛዋ ናት፤ ለእናቷ ልዩ ልጅ፥ ለወለደቻት ሴትም የተመረጠች ነች። የሀገሬ ሴቶች ልጆች አይተው የተባረክሽ ነሽ አሏት፤ ንግሥቶችና ቁባቶችም ደግሞ አይተው አመሰገኗት፤ ንግሥቶቹና ቁባቶቹ እንዲህ አሏት፦ [10] የንጋት ብርሃን መስላ የምትወጣ፥ እንደ ጨረቃ ያማረች፥ እንደ ፀሐይ ያበራች፥ ሰንደቅ እንደ ያዘ ሠራዊት የምታስፈራ ይህቺ ማን ናት? የሴቲቱ አፍቃሪ ለራሱ ሲናገር፥ [11] በሸለቆው ውስጥ አዲስ የበቀለውን ለማየት፥ ወይኑ አፍርቶ እንደሆነ፥ ሮማኑም አብቦ እንደሆነ ለማየት፥ የለውዝ ተክል ወዳለበት ጥሻ ወረድሁ። [12] በልዑሉ ሠረገላ እንደ ተቀመጥኩ ስለ ተሰማኝ፥ በጣም ደስ አለኝ። የሴቲቱ አፍቃሪ እንዲህ ይላል፥ [13] አንቺ ፍጹሟ ሴት፥ ተመለሽ፥ ተመለሽ፤ አተኩሬ እንዳይሽ ተመለሽ፥ እባክሽ ተመለሽ። ወጣቷ ሴት ፍቅረኛዋን እንዲህ ትለዋለች፥ በሁለት ረድፍ ጨፋሪዎች መካከል የምጨፍር ይመስል፥ ፍጹሟን ሴት ለምን ትክ ብለህ ታየኛለህ?

Song of Solomon 6:1

ወዳጅሽ የሄደው በየትኛው አቅጣጫ ነው
“ወዳጅሽ በየት በኩል ነው የሄደው ”

ወዳጅሽ ያንቺ ውድ
ይህ ሐረግ ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች ሌሎች ሴቶች “አፍቃሪሽ” ብለው ቢጠሩት በይበልጥ የተለመደ ይሆን ይሆናል። ይህንን በመኃልይ 1:13 ላይ “ወዳጄ” የሚለውን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ ውድሽ” ወይም “አፍቃሪሽ” ወይም “የምትወጂው ሰውዬ”

በሴቶች መካከል እጅግ የተዋብሽ
“አንቺ ከሴቶች ሁሉ የተዋብሽው”። ይህንን በመኃልይ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሄዷል፤ ካንቺ ጋር እንድንፈልገው?
“ንገሪን” የሚለውን ቃል ከ0ውዱ መረዳት ይቻላል። ቃሉን በግልጽ ማስቀመጥ ይቻላል። አ.ት፡ “ሄዷል? ከአንቺ ጋር ልንፈልገው እንድንችል ንገሪን”

Song of Solomon 6:2

ወዳጄ ወደ አትክልት ቦታው ሄዷል
“የአትክልት ቦታ” የሚለው ቃል ሴቲቱን የሚገልፅ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። በመጨረሻም ሰውየው ከሴቲቱ ጋር በፍቅር ግንኙነት ሙሉ ደስታ ማግኘት ችሏል። የዚህን ዘይቤአዊ አነጋገር ማብራሪያ በመኃልይ 5:1 ውስጥ ተመልከት።

ወዳጄ
ይህ ሐረግ ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች ሴቲቱ ሰውየውን “የኔ አፍቃሪ” ብትለው በይበልጥ የተለመደ ይሆን ይሆናል። ይህንን በመኃልይ 1:13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ አፍቃሪ”።

የቅመማ ቅመም መደብ
ሰዎች ቅመማ ቅመም የሚያበቅሉባቸው የአትክልት ስፍራዎች ወይም የአትክልት ስፍራ ክፍል። ይህንን በመኃልይ 1:13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

በአትክልት ስፍራ ለመሰማራትና የተዋቡ አበቦችን ለመሰብሰብ
እነዚህ ቃላት ሰውየው በሴቲቱ ገላ መደሰቱን የሚያሳዩ ዘይቤአዊ አነጋገሮች ናቸው።

መሰማራት
“ይመግባል” ወይም “ሳር ይበላል”። ሴቲቱ ሰውየውን በተዋቡት አበቦች መሐከል እፅዋትን እንደሚመገብ “ሚዳቋ ወይም የአጋዘን ግልገል” ቆጥራ ትናገራለች (መኃልይ 2:17)። መሰማራት ምናልባት የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸምን የሚገልፅ ዘይቤአዊ አነጋገር ሊሆን ይችላል (መኃልይ 2:1-2)። “ይመግባል”ን በመኃልይ 2:16 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የተዋቡትን አበቦች ለመሰብሰብ
“የተዋቡ አበቦችን ለመልቀም”

የተዋቡ አበቦች
ብዙ ውሃ ባለበት ቦታ የሚበቅሉ ባለጣፋጭ ሽታ አበቦች። በመኃልይ 2:1 እንዳለው “የተዋበ አበባ” የሚለውን በብዙ ቁጥር ተርጉመው።

እኔ የወዳጄ ነኝ፣ ወዳጄም የእኔ ነው
“ወዳጄ የእኔ ነው፣ እኔም የእርሱ ነኝ” የሚለውን ተመሳሳይ ሐረግ በመኃልይ 2:16 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

በተዋቡት አበቦች መሐከል በደስታ ይግጣል
ይህንን በመኃልይ 2:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Song of Solomon 6:4

አጠቃላይ መረጃ፡
የመጽሐፉ ክፍል አምስት እዚህ ጋ ይጀምራል

የኔ ፍቅር እንደ ቴርሳ ውብ፣ እንደ ኢየሩሳሌም ተወዳጅ
እነዚህ ከተሞች በውበታቸው የታወቁና በውስጣቸው ለመኖር የሚያስደስቱ ነበሩ። ሰውየው ሴቲቱ ውብ እንደሆነችና ከእርሷ ጋር መሆን እንደሚያስደስተው ያስባል።

የኔ ፍቅር
“አንቺ የምወድሽ”፣ ይህንን በመኃልይ 1:9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ተወዳጅ
ይህንን በመኃልይ 1:5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ዐርማቸውን ይዘው እንደሚያስፈሩ ወታደሮች
የሴቲቱ ውበት ኃያል ከመሆኑ የተነሣ ሰውየው ወታደሮች የመጡበት ያህል አቅመ ቢስነት እንዲሰማው አድርጎታል።

Song of Solomon 6:5

አጠቃላይ መረጃ:
ሰውየው ሴቲቱን ማድነቁን ይቀጥላል።

አድክመውኛል
“ያስፈሩኛል”። የሴቲቱ አይኖች በጣም ከማመራቸው የተነሳ ሰውየው ኃይላቸውን መቋቋም ባለመቻሉ ፍርሐትና ድካም እንዲሰማው አድርገውታል።

ፀጉርሽ ...ከገለአድ ቁልቁለት
በመኃልይ 4፡1 እንዳለው “ጸጉርሽ ... ከገለዓድ ተራራ” ብለህ ተርጉመው።

Song of Solomon 6:6

ጥርሶችሽ በቅርቡ የተሸለቱ የሴት በጎች መንጋ ይመስላሉ
በጎች ጸጉራቸው ከተሸለተ በኋላ ይታጠቡና ቆዳቸው በጣም ነጭ ሆኖ ይታያል። የሴቲቱ ጥርሶች ነጭ ናቸው። በመኃልይ 4፡2 ላይ “ጥርሶችሽ በቅርቡ የተሸለቱ የሴት በግ መንጋ ይመስላሉ” የሚለው እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።

ከመታጠቢያው ስፍራ የሚመጡ
ሴቶቹ በጎች ከውሃው ውስጥ ወጥተው እየመጡ ነው። ይህንን በመኃልይ 4፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት: “ሰዎች ካጠቡዋቸው በኋላ ከውሃው ውስጥ ወጥተው የሚመጡትን”

እያንዳንዱ መንታ አለው
በጎች አብዛኛውን ጊዜ በአንዴ ሁለት ግልገሎችን ይወልዳሉ። እነዚህ መንታዎች ብዙውን ጊዜ ይመሳሰላሉ። እያንዳንዱ የሴቲቱ ጥርስ ከአፏ በሌላኛው ጎን ካለው ጋር እኩል ነው። ይህንን በመኃልይ 4፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ከእነርሱ አንዱም አልጎደለም
እያንዳንዱ የሴቲቱ ጥርስ ከአፏ በሌላኛው ጎን ካለው ጋር እኩል ነው። ከጥርሶቿ አንድም የወለቀ የለም።

ሐዘንተኛ
የቅርብ ሰው የሞተበት። ይህንን በመኃልይ 4፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

እንደ ሮማን ክፋይ ናቸው
ሮማኖች ደማቅ ቀይ፣ ክብ እና ለስላሳ ናቸው። ሰውየው የሴቲቱ ጉንጮች ያማሩና እርሷም ጤነኛ መሆኗን እንደሚያሳዩ ያስባል። ይህንን በመኃልይ 4፡3ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ከአይነርግብሽ በስተጀርባ
ይህንን በመኃልይ 4፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Song of Solomon 6:8

60 ንግስቶች እና **80** ቁባቶች አሉ ... ከቁጥር ያለፉ ወጣት ሴቶች
እነዚህ ቁጥሮች በጣም ብዙ፤ እጅግ ብዙ፤ ከመቆጠርም ያለፉ ናቸው። አ.ት: “60 ንግስቶች፣ 80 ቁባቶች ... ማንም ሊቆጥራቸው የማይቻለው በርካታ ወጣት ሴቶች አሉ” ወይም “ ብዙ ንግስቶች፣ ከዚያም የሚበልጡ ቁባቶችና ማንም ሊቆጥራቸው የማይችል ብዙ ወጣት ሴቶች”

እርግቤ
እስራኤላውያን እርግቦችን አስደሳች ድምፅ ያላቸው ውብ ወፎች እንደሆኑ ያስቡ ነበር። ሰውየው የሴቲቱ ፊትና ድምፅ ያማረ እንደሆነ ያስባል። አንዲትን ሴት “እርግብ” ብሎ መጥራት ቅር የሚያሰኛት ከሆነ ዘይቤአዊውን አነጋገር ልትተወው ትችላለህ። ይህንን በመኃልይ 2፡14 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የእኔ እንከን ዐልባ
“የኔ ፍፁም”ወይም “የኔ ታማኝ” ወይም “የኔ የዋህ”። ይህንን በመኃልይ 5፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ለእናቷ ብቸኛ ሴት ልጅ የሆነች
ይህ ግነት ነው። አ.ት: “ለእናቷ ልዩ የሆነች ልጅ” ወይም “ከእናቷ ከተወለዱት ከሌሎች እህቶቿ የተለየች”

የወለደቻት ሴት
“እርሷን የወለደቻት ሴት”። ይህ ሐረግ እናቷን ያመለክታል።

ወጣት ሴቶች ... ንግስቶች ... ቁባቶች
በቁጥር 8 የተነገረላት ሴት ናት

የተባረክሽ ብለው ጠሯት
“ነገሮች ለርሷ በጣም የተሻሉ እንደሆኑላት ተናገሩ”

Song of Solomon 6:10

አጠቃላይ መረጃ:
የተከፈተው የቃል በቃል የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ይህንን የሚረዳው ንግስቶቹና ቁባቶቹ ስለ ሴቲቱ እንደተናገሩት ይገነዘባል። ይሁን እንጂ፣ አንዳንድ ትርጉሞች የሚገነዘቡት እነዚህን የሰውየው ቃላት እንደሆኑ ነው።

አርማ ... እንደ ንጋት የምትታይ ይህቺ ማን ናት?
ይህንን ጥያቄ የሚጠቀሙት ወጣቷ ሴት አስደናቂ መሆኗን እንደሚያስቡ ለመናገር ነው። አ.ት: “ይህች አስደናቂ ሴት ናት! ዓርማ ... እንደ ንጋት ትታያለች!”

እንደ ንጋት የምትታይ
ንጋት ውብ ነው። ሴቲቱ ውብ ናት። አ.ት: “እንደ ንጋት ወጥታ የምትታይ”

ዐርማቸውን ይዘው እንደሚያስፈሩ ወታደሮች
የሴቲቱ ውበት ኃያል ከመሆኑ የተነሣ ሌሎች ሴቶች ወታደሮች የመጡባቸው ያህል አቅመ ቢስነት እንዲሰማቸው አድርጓቸዋል። ይህንን በመኃልይ 6፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Song of Solomon 6:11

አጠቃላይ መረጃ:
ሰውየው ለራሱ መናገሩን ያበቃል። እጽዋት በቅለው እንደሆነ ማየቱ ምናልባት የሴቲቱን ገላ በማየት ለመደሰት መፈለጉን የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ይሆናል።

ጫካ
ይህንን በመኃልይ 4፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ቡቃያ
“አዳጊ ተክሎች” ወይም “አዲስ ቦቆልቶች”

እንቡጥ አውጥቷል
እንቡጣቸው ማደግ ጀምሯል። እንቡጦች ወደፊት ተከፍተው አበቦች የሚሆኑ ትናንሽ፤ ክብ የተክል ክፍሎች ናቸው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በመፍካት ላይ ነበሩ
“አበቦቻቸው እየተከፈቱ ነበር”

በንጉስ ሰረገላ ላይ እየጋለብኩ እንዳለሁ ያህል በጣም ደስተኛ ነበርኩ
ሰውየው ምን ያህል ደስተኛ እንደሆነ ለመግለፅ ይህን ምስል ይጠቀማል።

Song of Solomon 6:13

አጠቃላይ መረጃ
በአንዳንድ ትርጉሞች ይህ 7፡1፣ የሰባተኛው ምዕራፍ የመጀመሪያ ቁጥር ነው። የተከፈተ የቃል በቃል የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ይህንን የሚገነዘበው ሴቲቱና ጓደኞቿ እርስ በእርሳቸው እንደሚነጋገሩ ነው። አንዳንድ ትርጉሞች ደግሞ ሰውየው ለሴቲቱ የሚናገረው እንደሆነ ይገነዘባሉ።

ተመለሽ ... እንድናይሽ
ትርጓሜዎች ሊሆኑ የሚችሉት 1) ጓደኞቿ ሴቲቱን እያናገሯት ነው ወይም 2) ሰውየው ራሱን በብዙ ቁጥር እያመለከተ ነው።

ተመለሽ፣ ተመለሽ
“ወደ ኋላሽ ተመለሽ፣ ወደ ኋላሽ ተመለሽ”። ይህ የተደገመው አጽንዖት ለመስጠት ነው።

እንድናይሽ
አንዳንድ ትርጉሞች ብዙውን ቁጥር ሰውየው ስለ ራሱ የሚናገረውን እንደሚያመለክት ይረዳሉ። አ.ት፡ “እንዳይሽ”

አተኩሮ መመልከት
ለረጅም ጊዜ በጥሞና መመልከት

እንከን ዐልባዋን ሴት አተኩራችሁ የምትመለከቷት ለምንድነው ... ሰራዊቶች
ትርጓሜዎች ሊሆኑ የሚችሉት 1) ሴቲቱ ራሷን እንደ ሌላ ሰው አድርጋ ለጓደኞቿ ትናገራለች ወይም 2) ሴቲቱ ለብዙ ወንዶች እንደምትናገር አድርጋ ለሰውየው ትናገራለች።

በሁለት ሰራዊት መሐል እንደምትጨፍር
“በሁለት ሰራዊት መሐል ስትጨፍር እንደነበረች”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 7

1 አንቺ የልዑል ልጅ! እግሮችሽ በነጠላ ጫማ ውስጥ ሲታዩ እንዴት ያምራሉ? የዳሌዎችሽ ቅርጽ በእውቅ አንጥረኛ እጅ የተሠሩ ዕንቁዎችን ይመስላሉ። **2** እንብርትሽ ክብ ጽዋ ይመስላል፤ ድብልቅ ወይን በፍጹም አይጉደለው። ሆድሽ በአበቦች የተከበበ የስንዴ ክምር ይመስላል። **3** ሁለቱ ጡቶችሽ መንታ የሜዳ ፍየሎችን፥ ሁለት የአጋዘን ግልገሎችን ይመስላሉ። **4** አንገትሽ በዝሆን ጥርስ የተሠራ የጥበቃ ማማ ይመስላል፤ ዓይኖችሽ በባትረቢ በር አጠገብ በሐሴቦን ያሉትን ኩሬዎች ይመስላሉ። አፍንጫሽ ወደ ደማስቆ አቅጣጫ የሚመለከተውን በሊባኖስ ያለውን የመጠበቂያ ማማ ይመስላል። **5** ራስሽ በአንቺ ላይ የቀርሜሎስን ተራራ ይመስላል፤ በራስሽ ላይ ያለው ጸጉር ጥቁር ሐምራዊ ነው። ንጉሡ በረጅሙ ጸጉርሽ ተይዞ ታስሮአል። **6** ተወዳጂ ሆይ፥ እንዴት የምታስደስቺ፥ ውብና ያማርሽ ነሽ! **7** ቁመትሽ የቴምር ዘንባባ ዛፍ ይመስላል፥ ጡቶችሽም እንደ ተከማቹ ፍሬዎች ናቸው። **8** እኔም፥ "በዚያ የዘንባባ ዛፍ ላይ እወጣለሁ፤ ቅርንጫፎቹንም እይዛለሁ" ብዬ አሰብኩ። ጡቶችሽ የወይን ክምችቶች ይሁኑ፥ የአፍንጫሽ እስትንፋስ መዓዛውም እንደ እንኮይ ይሁኑ። **9** አፍሽ እንደ ምርጥ የወይን ጠጅ ይሁን፥ በዝግታም በውዴ ከንፈርና ጥርስ እየፈሰሱ ይንቆርቆሩ። ወጣቷ ፍቅረኛዋን እንዲህ ትለዋለች፥ **10** እኔ የውዴ ነኝ፥ እርሱም ይመኘኛል። **11** ውዴ ሆይ ና፥ ወደ ገጠር እንሂድ፥ በመንደሮቹም እንደር። **12** ወደ ወይኑ ቦታ ለመሄድ ማልደን እንነሣ፤ ወይናቸው አፍርቶ፥ አበባቸውም ፈክቶ፥ ሮማኑም አብቦ እንደሆነ እንይ። በዚያም ፍቅሬን እሰጥሃለሁ። **13** ትርንጉዎች መዓዛቸውን ሰጡ፤ በምንቆይበት ቤት ደጃፍ ሁሉም ዓይነት የተመረጡ ፍሬዎች አሉ፥ አዲስና የቆዩ፥ ውዴ ሆይ፥ ለአንተ አስቀምጫቸዋለሁ።

Song of Solomon 7:1

አጠቃላይ መረጃ:
በአንዳንድ ትርጉሞች ይህ 7፡2 ነው፣ የሰባተኛው ምዕራፍ ሁለተኛ ቁጥር

በነጠላ ጫማዎችሽ ውስጥ ሲታዩ እግሮችሽ ምንኛ ያምራሉ
ምናልባት ሴቲቱ እየደነሰች ነው (መኃልይ 6፡13) ። አ.ት፡ “በምትደንሽበት ጊዜ በነጠላ ጫማዎቹ ውስጥ እግሮችሽ እጅግ በጣም ያማሩ ናቸው”

የልዑል ሴት ልጅ
ሌላው አማራጭ ትርጉም ሊሆን የሚችለው “አንቺ ምስጉን ጠባይ ያለሽ” የሚለው ነው።

የዳሌዎችሽ መታጠፊያዎች ዕንቁዎችን ይመስላሉ
የሴቲቱ ዳሌዎች ቅርፃቸው ለተናጋሪው ብልህ ቅርፃ ቅርፅ ሠሪ የሠራውን ውብ የከበረ ድንጋይ ያስታውሰዋል። አ.ት፡ “የዳሌዎችሽ መታጠፊያዎች ብልህ ቀራጺ እንደሚሠራቸው የተዋቡ የዕንቁ መታጠፊያዎች የተዋቡ ናቸው”።

ዳሌዎችሽ
“ዳሌዎችሽ” የሚለው ቃል የሴቲቱን ሽንጥና ከጉልበትዋ በላይ ያለውን የዳሌዋን ክፍል ያመለክታል።

የብልህ ቀራጺ እጆች የሠሩት
እጆች የሰው ምሳሌዎች ናቸው። አ.ት፡ “የብልህ ቀራጺ ሥራ” ወይም “ብልህ ቀራጺ የሠራው አንዳች ነገር”

Song of Solomon 7:2

አጠቃላይ መረጃ:
የወጣት ሴቷ አፍቃሪ የሚወዳትን እርሷን መግለጹን ይቀጥላል።

እምብርትሽ እንደ ክብ ጎድጓዳ ሳህን ነው
ጎድጓዳ ሳህን ክብ ነው። የሴቲቱ እምብርት ክብ ነው።

እምብርት
ልጅ ከእናቱ ጋር የሚያያዝበት እትብት የነበረበት፣ በሆድ ላይ የሚገኝ ምልክት

የተደባለቀ ወይን እንደማይጎድልበት
ሰዎች በግብዣ ላይ ወይንን በውሃ ወይም በቅመም ለማዋሃድ ትላልቅ ጎድጓዳ ሳህኖችን ይጠቀማሉ። ወይን መጠጣት በውበት የመደሰት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። የተጋነነው አባባል በአዎንታዊነት ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ሁሌም የተደባለቀ ወይን እንደ ያዘ” ወይም “ሁሌም በውበቱ ልደሰት ይሆን”።

ሆድሽ በውብ አበቦች እንደ ተከበበ የስንዴ ክምር ነው
እስራኤላውያን የስንዴ ክምርና ውብ አበቦች ሲያዩአቸው የሚያስደስቱ እንደሆኑ ያስቡ ነበር። ብዙ ስንዴ፣ ለመብላት የሚሆን ብዙ ምግብ የመኖሩ ምልክት ነበር። ስንዴን የሚወቁት ከፍ ባለና በደረቅ ስፍራ ሲሆን የተዋቡት አበቦች የሚያድጉት በዝቅተኛና እርጥበት ባለባቸው አካባቢዎች ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ምልክታዊ ድርጊት ሰዎች በአብዛኛው በአንድ ጊዜ ሊያዩት የማይችሉትን አስደሳች ዕይታ አጣምሮ ያቀርባል።

ሆድሽ እንደ ስንዴ ክምር ነው
ሰዎች ስንዴ የሚመስለውን የሰውነት የቆዳ ቀለም እጅግ የተዋበ ቀለም እንደሆነ ያስቡ ነበር፣ በክብ የተከመሩ የስንዴ ክምሮችም ያምሩ ነበር። አ.ት፡ “የሆድሽ ቀለም ያማረ ነው፣ እንደ ስንዴ ክምርም ክብ ነው”

የስንዴ ክምር
ይህ ሰዎች የማይጠቀሙበትን ገለባውን ካስወገዱለት በኋላ የስንዴ ምርት ክምር ነው።

በተዋቡ አበቦች የተከበበ
ዙሪያው በተዋቡ አበቦች”

የተዋቡ አበቦች
ብዙ ውሃ በሚገኝበት አካባቢ የሚያድጉ ጣፋጭ ሽታ ያላቸው አበቦች ናቸው። በመኃልይ 2፡1 እንዳለው በብዙ ቁጥር አድርገህ ተርጉመው።

Song of Solomon 7:3

x
የወጣት ሴቷ አፍቃሪ የሚወዳትን እርሷን መግለጹን ይቀጥላል።

ሁለት ጡቶች
“ሁለት” የሚለው ቃል የማያስፈልግና ያለ ቦታው የተቀመጠ መስሎ ከታየህ ልትሰርዘው ትችላለህ። ይህንን በመኃልይ 4፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

እንደ ሁለት የአጋዘን ግልገሎች፣ መንታ የሜዳ ፍየል
ሰውየው ምናልባት የሴቲቱ ጡቶች እኩል፣ ለስላሳና ትንሽ መሆናቸውን ያመለክታል። ይህንን በመኃልይ 4፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

መንትዮች
ከአንዲት እናት በአንድ ጊዜ የተወለዱ ልጆች። ይህንን በመኃልይ 4፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የሜዳ ፍየል
አጋዘን የሚመስልና በፍጥነት የሚንቀሳቀስ እንስሳ። በመኃልይ 2:7 እንዳለው “የሜዳ ፍየሎች” የሚለውን በነጠላ ቁጥር ተርጉመው።

አንገትሽ እንደ ዝሆን ጥርስ ግምብ ነው
ግምብ ረጅምና ቀጥ ያለ ነው። የዝሆን ጥርስ ነጭ ነው። የሴቲቱ አንገት ረጅምና ቀጥ ያለ ነው፣ ቆዳዋም ብሩህ ቀለም አለው።

የዝሆን ጥርስ ግምብ
“ሰዎች በዝሆን ጥርስ ያስጌጡት ግምብ”

የዝሆን ጥርስ
አጥንት የሚመስል የእንስሳው ነጭ ጥርስ ነው። ሰዎች የጥበብ ሥራዎችን ለመሥራትና አንዳንድ ነገሮችን ለማሳመር በዝሆን ጥርስ ይጠቀማሉ።

ዓይኖችሽ እንደ ሐሴቦን ኩሬዎች ናቸው
የሴቲቱ ዓይኖች የጠራ የኩሬ ውሃ እንደሚመስሉ ተነግሮላቸዋል። የኩሬ ውሃ የጠራና የፀሐይ ብርሃን ሲያርፍበት ስለሚያንጸባርቅ ሲመለከቱት ያስደስታል። የሴቲቱም ዓይኖች የጠሩና አብረቅራቂዎች ናቸው፣ ስለዚህ ሲታዩ ያስደስታሉ። ይህ በምስስሎሽነት ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ዓይኖችሽ በሐሴቦን እንዳሉት ኩሬዎች የጠሩ ናቸው”

ሐሴቦን
ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምሥራቅ ያለች ከተማ ስም ነው

ባት ረቢ
የከተማ ስም

አፍንጫሽ በሊባኖስ እንዳለ ግምብ ነው ግምብ ረጅምና ቀጥ ያለ ነው፣ የእርሷም አፍንጫ ረጅምና ቀጥ ያለ ነው።

Song of Solomon 7:5

አጠቃላይ መረጃ፡
ሰውየው ሴቲቱን መግለጹን ይቀጥላል።

የራስሽ ቅርፅ እንደ ቀርሜሎስ ነው
የቀርሜሎስ ተራራ በአካባቢው ካሉት ሁሉ ረጅም ነው። ሰውየው ከምንም ነገር በላይ የሴቲቱን ራስ ማየት ይፈልጋል። አ.ት፡ “ራስሽ በአንቺ ላይ ከምንም ነገር በላይ ከፍ ያለ ዘውድ ይመስላል”

ያልደመቀ ሐምራዊ
ሊሆን የሚችለው ሌላው ትርጉም 1) “ያልደመቀ ጥቁር” ወይም 2) “ያልደመቀ ቀይ”

ንጉሡ በረጅሙ ጸጉር ተይዞ ታስሯል
ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “በጀርባሽ ላይ የወረደው ጸጉርሽ እጅግ የተዋበ ነው፣ ንጉሡ አለማድነቅ አልቻለም።

ረጅም የሴት ጸጉር
ከአንዲት ሴት ራስ ወደ ታች የሚወርድ ሽሩባ

የኔ ፍቅር፣ ታስደስቻለሽ!
“የእኔ ፍቅር። ታስደስችኛለሽ!”

Song of Solomon 7:7

አጠቃላይ መረጃ፡
ሰውየው ከሴቲቱ ጋር ማድረግ የሚፈልገውን ይገልጻል።

ቁመናሽ እንደ የቴምር ዘንባባ ዛፍ ዘለግ ያለ ነው
“አቋቋምሽ እንደ ዘንባባ ዛፍ ነው”። የቴምር የዘንባባ ዛፎች ረጃጅምና ቀጥ ያሉ፣ ቅርንጫፎቻቸው አናቱ ላይ ብቻ የሚገኙና ፍሬአቸውን ከሥራቸው የሚያደርጉ ናቸው።

የቴምር ዘንባባ ዛፍ
እጅብ ብለው የሚያድጉ ጣፋጭ፣ ቡናማና ሙጫነት ያላቸውን ፍሬዎች የሚሰጥ ረጅምና ቀጥ ያለ ዛፍ

ጡቶችሽ የፍሬውን ዘለላ ይመስላሉ
ቴምር ለስላሳና ክብ ሆኖ በዘንባባ ዛፍ አናት ላይ ከቅርንጫፎቹ ሥር በሚንጠለጠሉ ረጃጅም ዘለላዎች ይገኛል። የሴቲቱ ጡቶችም ለስላሳ፣ ክብና ከክንዶቿ ዝቅ ያሉ ናቸው።

አልኩኝ
“አሰብኩኝ” ወይም “ለራሴ ተናገርኩ”። ሰውየው ይህንን የተናገረው በዝምታ ውስጥ ነው።

በቅርንጫፎቹ ... ለመውጣት እፈልጋለሁ
ሰውየው ሴቲቱን ለማቀፍ ይፈልጋል።

ጡቶችሽ እንደ ወይን ዘለላ ይሁኑ
ሰውየው ጡቶቿን ለመንካት ይፈልጋል። የወይን ዘለላዎች ክብና ለስላሳዎች ናቸው።

የአፍንጫሽ መዓዛ እንደ እንኮይ ይሁን
“አፍንጫ” የሚለው ቃል ከአፍንጫ ለሚወጣው ትንፋሽ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ከአፍንጫሽ የሚወጣው ትንፋሽ ሽታው እንደ እንኮይ ይጣፍጥ”

እንኮይ
የሚጣፍጥ ቢጫ ፍሬ

Song of Solomon 7:9

አጠቃላይ መረጃ፡
ሰውየው ከሴቲቱ ጋር ለማድረግ የሚፈልገውን መግለጹን ቀጥሏል።

ላንቃሽ እንደ ምርጥ ወይን ይሁን
ላንቃ የከንፈር ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ወይን ጣፋጭ ጣዕም አለው። ሰውየው የሴቲቱን ከንፈር ለመሳም ይፈልጋል።

ለወዳጄ በዝግታ ይንቆረቆርለት
“ለምወደው በዝግታ የሚንቆረቆርለት”። ሰውየው ሴቲቱን በዝግታ በመሳም ይደሰታል።

በተኙት ከንፈሮች ላይ ተንሸራቶ
“ስንተኛ በከንፈሮቻችን ላይ ይፍሰስ”

Song of Solomon 7:10

እኔ የወዳጄ ነኝ
ተመሳሳዩን ሐረግ በመኃልይ 6:3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የወዳጄ
ይህ ሐረግ ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች ሴቲቱ፣ “የእኔ አፍቃሪ” ብትለው በይበልጥ የተለመደ ሊሆን ይችላል። ይህንን በመኃልይ 1:13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ አፍቃሪ”።

እኔን ይመኘኛል
“ከእኔ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለማድረግ ይፈልጋል” ወይም “ይፈልገኛል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሌሊቱን በመንደሮቹ ውስጥ እናሳልፍ
እዚህ ጋ ያሉት ቃላት “መንደሮች” እና “ሌሊቱን ያሳልፋል” ተብለው ቢተረጎሙም እንኳን በመኃልይ 1:13-14 በአንድነት እንደ “ሌሊቱን ያሳልፋል” እና “የሄና አበቦች” ተብለዋል፣ እንዲሁም በዚህና በዚያ ያለው ዐውድ የሚያመለክተው የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸምን ነው። የተከፈተው የቃል በቃል የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም፣ ተከታዩ ዘይቤአዊ አነጋገር ሰውየውና ሴቲቱ በመንደር ውስጥ ማደራቸውን፣ ማልደው መነሣታቸውንና ወደ ወይኑ ቦታ መሄዳቸውን ስለሚያመለክት እንዲህ ያለውን ንባብ ይመርጣል። “የሄና ተክሎች” እና “መንደሮች” የሚሉት ቃላት ድምፃቸው ተመሳሳይ ነው።

Song of Solomon 7:12

አጠቃላይ መረጃ:
ሴቲቱ ለሰውዬው መናገሯን ትቀጥላለች።

ማልዶ መነሣት
“ማልዶ መነሣት” ወይም “ማልዶ መንቃት”

እምቡጥ ይዟል
“ማበብ ጀምሯል”

ያብባል
እምቡጡ በሚከፈትበት ጊዜ ያብባል

አብቧል
“በእጽዋቱ ላይ አበቦቹ ፈክተዋል”

ፍቅሬን እሰጥሃለሁ
“ካንተ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት እፈጽማለሁ”

Song of Solomon 7:13

አጠቃላይ መረጃ:
ሴቲቱ ለሰውዬው መናገሯን ትቀጥላለች።

ለመድኃኒት ቅመማ የሚያገለግሉ እፅዋት
ይህ ጠንካራ ነገር ግን አስደሳች ሽታ የሚለቁ እፅዋት ስም ነው። ሽታው በመጠኑ አስካሪና አነቃቂ ስለሆነ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፍላጎትን ያነሣሣል።

መዓዛቸውን ሰጡ
“ሽታቸውን ለቀቁ” ወይም “በጣም ጥሩ ሽታ አላቸው”

በበሩ ላይ
በሮቹ የቤታቸው ነው። አ.ት፡ “ከቤታችን መግቢያ በላይ” ወይም “በቤታችን በሮች”

አዲስና የበሰሉ፣ ከሁሉም ዓይነት የተመረጡ ፍሬዎች
“ምርጥ የሆኑ የተለያየ ዓይነት ፍሬ፣ ከበሰለውና ከአዲሱ ፍሬ”

ለአንተ ተቀምጦልሃል
“ልሰጥህ እንድችል ተቀምጦልሃል”

ወዳጄ
ይህ ሐረግ ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች ሴቲቱ፣ “የእኔ አፍቃሪ” ብትለው በይበልጥ የተለመደ ሊሆን ይችላል። ይህንን በመኃልይ 1:13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ አፍቃሪ”።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 8

1 ምነው የእናቴን ጡቶች እንደጠባ እንደ ወንድሜ በሆንክ። ከዚያም በውጭ ባገኘሁህ ጊዜ ሁሉ በሳምኩህና፥ ማንም ባልናቀኝ ነበር። **2** በመራሁህና ወደ እናቴ ቤት ባመጣሁህ፥ አንተም ባስተማርከኝ ነበር። የምትጠጣውን ጣፋጭ ወይን ጠጅ በሰጠሁህ፥ ከሮማኖቼም ጭማቂ ጥቂቱን። **3** ወጣቷ ለራሷ ስትናገር፥ ግራ እጁ ይዞኛል፤ ቀኝ እጁም አቅፎኛል። ሴቲቱ ለሌሎች ሴቶች ስትናገር፥ **4** የኢየሩሳሌም ሴቶች ልጆች ሆይ፥ በፍቅር ግንኙነታችን ጊዜ እስክንረካ ድረስ ላታቋርጡን እንድትምሉልኝ እፈልጋለሁ። የኢየሩሳሌም ሴቶች ሲናገሩ፥ **5** በውዷ ላይ ተደግፋ ከምድረ በዳ የምትመጣ ይህቺ ማን ናት? ሴቲቱ ለፍቅረኛዋ ስትናገር፥ ከእንኮዩ ዛፍ ጥላ ሥር አነቃሁህ፤ በዚያ እናትህ ፀነሰችህ፤ በዚያም አንተን ወለደችህ፤ ተገላገለችህ። **6** በልብህ ላይ እንደ ማኅተም አስቀምጠኝ፥ እንደ ማኅተም በክንድህ ላይ፥ ፍቅር እንደ ሞት ብርቱ ነውና። የታማኝነቷም ጠንካራ ስሜት እንደ ሲዖል ጨካኝ ነው፤ ነበልባሏ ይነዳል፤ የምትንጦገቦግ ነበልባል ናት፥ ነበልባሏ ከሌላ ከየትኛውም እሳት ይልቅ የጋለ ነው። **7** የማዕበል ውሃ ፍቅርን ለማጥፋት አይችልም፥ ጎርፍም ሊያሰጥመው አይችልም። ሰው በቤቱ ያለውን ሀብት ሁሉ ስለ ፍቅር ብሎ ቢሰጥ ስጦታው ፈጽሞ ይናቃል። የወጣቷ ወንድሞች እርስ በርሳቸው ሲነጋገሩ፥ **8** ታናሽ እህት አለችን፥ ጡቶቿም ገና አላደጉም። ለጋብቻ በምትሰጥበት በዚያን ቀን ለእህታችን ምን ልናደርግላት እንችላለን? **9** እርሷ ቅጥር ብትሆን፥ በላይዋ ላይ የጥበቃ ማማ እንሠራባታለን። በር ብትሆን በዝግባ ሳንቃ እናስውባታለን። ወጣቷ ለራሷ ስትናገር፥ **10** እኔ ቅጥር ነኝ፥ አሁን ግን ጡቶቼ እንደ ተመሸጉ ግንቦች ናቸው፤ ስለዚህ በዓይኖቹ ፊት በሚገባ አድጌአለሁ። ወጣቷ ለራሷ ስትናገር፥ **11** ሰለሞን በብኤላሞን የወይን ቦታ ነበረው፤ እርሱም የወይኑን ቦታ ለሚንከባከቡት አከራየው። እያንዳንዱ ስለ ፍሬው አንድ አንድ ሺህ ሰቅል ብር ያመጣለት ነበር። **12** የእኔ የወይን ቦታ የእኔው የግሌ ነው፤ ወዳጄ ሰለሞን ሆይ፥ አንድ ሺህ ሰቅሉ ያንተ ይሆናል፥ ሁለት መቶ ሰቅሉ ፍሬውን ለሚንከባከቡት ነው። የሴቲቱ አፍቃሪ ሲናገራት፥ **13** በአትክልቱ ቦታ የምትኖሪ ሆይ፥ ጓደኞቼ ድምጽሽን እየሰሙት ነው፤ እኔም ከሚሰሙት አንዱ ልሁን። ሴቲቱ ለፍቅረኛዋ ስትናገር፥ **14** ውዴ ሆይ፥ ፍጠን፤ በቅመማ ቅመም ተራራዎች ላይ የአጋዘንን ወይም የሜዳ ፍየል ግልገልን ምሰል።

Song of Solomon 8:1

እንደ ወንድሜ በሆንክ
አንዲት ሴት ለወንድሟ በአደባባይ ፍቅሯን መግለፅ ትችል ነበር። ይህቺ ሴት ለሰውየው ያላትን ፍቅር በይፋ ማሳየት ትፈልግ ነበር።

አንተን በውጪ
“አንተን በይፋ”

እስምህ ነበር
አንዲት ሴት ምናልባት ለሰላምታ የወንድሟን ጉንጭ ትስም ይሆናል።

ይንቁኝ ይሆናል
“መጥፎ ሰው እንደሆንኩ ያስቡ ይሆናል”

Song of Solomon 8:2

አጠቃላይ መረጃ:
ወጣቷ ሴት ለሰውየው መናገሯን ትቀጥላለች።

እየመራሁህ ወደ እናቴ ቤት ባመጣሁህ
ሰውየው ወንድሟ ቢሆን ኖሮ ወደ ቤተሰቧ ቤት ማምጣት ትችል ነበር። ይህ በዚያ ባህል የተለመደና አሁንም በአንዳንዶች ዘንድ ልማድ የሆነ ነው።

ያስተማረችኝ እርሷ
የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዴት እንደሚፈጸም ያስተማረቻት

እንድትጠጣው ልዩ ከሆነው ወይን፣ ከሮማኔም ጭማቂ ጥቂት በሰጠሁህ
ሴቲቱ ራሷን እንደምትሰጠውና ከእርሱ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደምትፈጽም ለመናገር እነዚህን ምስሎች ትጠቀማለች።

የተቀመመ ወይን
“ወይን ከቅመማ ቅመም ጋር” ወይም “ቅመማ ቅመም ያለበት ወይን”። ይህ በግብረ ሥጋ ግንኙነት መስከርን ይወክላል።

ቀኝ እጁ ... ያቅፈኛል
ይህንን በመኃልይ 2:6 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ግራ እጅ ...ቀኝ እጅ
“ግራ ክንድ” ... ቀኝ ክንድ”

ያቅፈኛል
“ይይዘኛል”

Song of Solomon 8:4

እንድትምሉልኝ እፈልጋለው
ይህንን በመኃልይ 2:7 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የኢየሩሳሌም ሴት ልጆች
“የኢየሩሳሌም ወጣት ሴቶች”። እነዚህ ወጣት ሴቶች አብረዋት አልነበሩም፤ ሊሰሟትም አይችሉም፣ ነገር ግን ሴቲቱ አብረዋት እንዳሉና እንደሚሰሟት ቆጥራ ትናገራለች። ይህንን በመኃልይ 2:7 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

እስከመጨረሻው ... እንደምታደርጉት
ይህንን በመኃልይ 2:7 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Song of Solomon 8:5

አጠቃላይ መረጃ:
የመጨረሻ የሆነው የመጽሐፉ ስድስተኛ ክፍል እዚህ ጋ ይጀምራል።

የምትወጣው ይህቺ ማናት
ሴቲቱ አስደናቂ እንደሆነች እንደሚያስቡ ለመናገር ይህንን ጥያቄ ተጠቅመዋል። ተመሳሳይ ሐረግ በመኃልይ 6:10 ላይ ተተርጉሞአል። አ.ት: “በምትወጣበት ጊዜ ይህቺን አስደናቂ ሴት ተመልከቷት”

አስነሣሁህ
“ቀሰቀስኩህ” ወይም “አነሣሁህ”

የእንኮይ ዛፍ
በጣም ጣፋጭ የሆነ አነስተኛ ቢጫ ፍሬ የሚያፈራ ተክል ነው። አንባቢዎችህ ይህ ምን እንደሆነ ካላወቁ በሌላ የፍራፍሬ ዛፍ ስም ወይም “የፍራፍሬ ዛፍ” በሚል ጥቅል ቃል ልትተካው ትችላለህ። ይህንን በመኃልይ 2:3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በዚያ
ከእንኮዩ ዛፍ በታች

አማጠችህ
“ወለደችህ”

Song of Solomon 8:6

አጠቃላይ መረጃ:
ወጣቷ ሴት ለሰውየው መናገሯን ትቀጥላለች።

እንደ ማህተም በክንድህ፤ እንደ ማህተም በልብህ ላይ አስቀምጠኝ
ትርጓሜዎች ሊሆኑ የሚችሉት 1) ማህተሞች በጣም ጠቃሚ ከመሆናቸው የተነሳ ሰዎች ሁል ጊዜም በአንገታቸው ወይም በእጃቸው ዙርያ ያስቀምጡት ነበር። ሴቲቱ እንደ ማህተም ዘወትር ከሰውየው ጋር መሆን ትፈልጋለች ወይም 2) ማህተም ያለበት ነገር የባለቤቱን ማንነት ያሳያል፤ ሴቲቱም ራሷን በሰውየው እጅና ልብ ላይ እንደ ማህተም በማኖር ሀሳቦቹ ሁሉ፣ ስሜቶቹና ድርጊቶቹ የእርሷ እንደሆኑ ለማሳየት ትፈልጋለች።

ፍቅር እንደ ሞት የበረታ ነውና
ሞት በምድር ላይ እጅግ እጅግ ኃይለኛ የተባሉትን ሰዎች እንኳን ስለሚያሸንፍ በጣም ብርቱ ነው።

ይቅር እንደማትል እንደ ሲዖል
“እንደ ሲዖል ጨካኝ”። ሲዖል ሰዎች ከሞቱ በኋላ ድጋሚ ወደ ሕይወት እንዲመለሱ ፈፅሞ አትፈቅድም። ፍቅር መቼም ስለማይለወጥ እንደ ሲዖል ያለማቋረጥ የሚቀጥል ነው።

ነበልባሎቹ ይንጦቦጋሉ ...ሌላ የትኛውም አይነት እሳት
ፍቅር እንደ እሳት በጣም ኃይለኛ ነው።

ይንጦቦጋል
“በድንገት ይነዳል”

Song of Solomon 8:7

አጠቃላይ መረጃ:
ወጣቷ ሴት ለሰውየው መናገሯን ትቀጥላለች።

የማዕበል ውኃ ፍቅርን ሊያጠፋ አይችልም
እጅግ እንደሚነድ፣ ውቅያኖስ ሙሉ ውሃ እንኳን ቢደፋበት እንደማይጠፋ እሳት፣ ፍቅር ኃይለኛ ነው።

የማእበል ውሃ
“የውቅያኖስ ውሃ” ወይም “ብዙ ውሃ”

ሊያጠፋው አይችልም
“ማጥፋት አይችልም” ወይም ”ሊያስወግደው አይችልም”

ጎርፍ ሊጠርገውም አይችልም
ኃይለኛ ጎርፍም እንኳን እስከማያንቀሳቅሰው ድረስ ፍቅር መቼም አይቀየርም፤ ሁሌም ጸንቶ ይኖራል።

ጎርፍ
በእስራኤል የዝናብ ውሃ ወደ ጠባብና ጥልቅ ሸለቆዎች ይወርዳል። ይህም ግዙፍ ቋጥኞችንና ዛፎችን ማንቀሳቀስ የሚያስችለውን ጎርፍ ይፈጥራል።

ጠርጎ ይወስደዋል
“ይዞት ይሄዳል” ወይም “ያጥበዋል”

ሰው ቢሰጥ ... ያቀረበው ፈፅሞ ይናቃል
ይህ ሊያጋጥም የሚችል ነገር ነው። አ.ት: “ሰው ቢ ... እንኳን ፈጽሞ ይናቃል”

ሰጠ
ለመስጠት አቀረበ

በቤቱ ያለውን ንብረት ሁሉ
“የእርሱ የሆነውን ነገር ሁሉ”

ስለ ፍቅር
“ፍቅርን ለማግኘት” ወይም “ፍቅርን ለመግዛት”

ያቀረበው ፈፅሞ ይናቃል
ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። አ.ት: “ሰዎች ፈጽመው ይንቁታል” ወይም “ሰዎች በማፌዝ ይስቁበታል”

Song of Solomon 8:8

ትንሽ እህት
“ታናሽ እህት”

በትዳር ውስጥ ... ምን ማድረግ እንችላለን?
ተናጋሪው ለመናገር የፈለገውን ለማስተዋወቅ ይህንን ጥያቄ ይጠቀማል። አ.ት: “የምናደርገው ይህንን ነው ... በጋብቻ”

ለትዳር ቃል ይገባላታል
ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። አ.ት: “አንድ ሰው ይመጣና ሊያገባት ይፈልጋል”

Song of Solomon 8:9

አጠቃላይ መረጃ:
የወጣቷ ሴት ወንድሞች እርስ በእርሳቸው መነጋገራቸውን ይቀጥላሉ።

እርሷ ግድግዳ ከሆነች ... እርሷ በር ከሆነች
ትንሿ እህት ያላደጉ ወይም በጣም ትንንሽ የሆኑ ጡቶች አሏት (መኃልይ 8:8) ።

በርሷ ላይ የብር ግምብ እንገነባለን ... በዝግባ ሳንቃ እናስጌጣታለን
x

እናስጌጣታለን
“እናስውባታለን” ወንድማማቾቹ እህታቸው ጥሩ ባል የመማረክ ዕድል እንዲኖራት በብርና በዝግባ ሊያስዉቧት ይወስናሉ፤ ይህም የሀብት ምልክት ነው።

Song of Solomon 8:10

ግንብ ነበርኩ
ግንቡ ትናንሽ ጡቶች ያሏትን ሴት የሚገልፅ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው።

አሁን ጡቶቼ እንደ ትልቅ መመሸጊያ ማማ ናቸው
የመመሸጊያ ማማዎች ረጃጅሞች ናቸው።

እኔ በአይኖቹ ፊት እንደ አንዱ ሆንኩ
አይኖቿ የዋጋ ወይም የፍርድ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት: “በእርሱ ፍርድ እንደ አንዱ ነኝ” ወይም “እንደ አንዱ ያስበኛል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሰላምን ያመጣል
ሴቲቱ ሰላምን የምታመጣው ለማን እንደሆነ መግለጽ ይኖርብህ ይሆናል። አ.ት፡ “ሰላምን ታመጣለታለች”

ሰላም
“ደህንነት”

Song of Solomon 8:11

አጠቃላይ መረጃ፡
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡ 1) ሴቲቱ ፍቅሩን ለሚሰጣት ለሰውየው ራሷን የምትሰጥበትን መንገድ ሰለሞን የወይን ቦታውን ገንዘብ ለሚከፍሉት ሰዎች ከሚያከራይበት መንገድ ጋር ታነጻጽራለች። 2) ሰውየው ለሌላ ሰው የማይሰጣትን ሴቲቱን ሰለሞን ለሌሎች ሰዎች ከሚሰጣቸው የወይን ቦታ ጋር ያነጻጽራታል።

ብኤልላሞን
ይህ በእስራኤል ሰሜኑ ክፍል የሚገኝ ከተማ ስም ነው።

የወይን ቦታውን ሰጠ
ኮንትራት፤ ሌሎች ሰዎች እየከፈሉት ወይኖችን በወይን ቦታው እንዲያበቅሉ ተስማምቶ በኮንትራት አከራየው

ማስተዳደር ለሚችሉ
“ሊንከባከቡ ለሚችሉ ሰዎች”

እያንዳንዱ ለፍሬው አንድ ሺህ የብር ሰቅል ማምጣት ነበረበት
ይህ ክፍያ ለወይን ቦታው ፍሬ እንደሆነ መግለጽ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። አ.ት፡ “እያንዳንዱ ሰው ለወይኑ ቦታ ፍሬ አንዳንድ ሺህ ሰቅል ብር ለሰለሞን መስጠት ይጠበቅበታል”

አንድ ሺህ ሰቅል ብር ለማምጣት
“1000 ሰቅል የብር ለማምጣት”

የወይን ቦታዬ፣ የእኔ የራሴ
ሴቲቱ በመኃልይ 1:6 እንዳለው ራሷን የወይን ቦታ አድርጋ ታመለክታለች። እዚህ ጋ ማንም ከእርሷ ውጪ ስለ ወይን ቦታው መወሰን እንደማይችል አጽንዖት ትሰጣለች።

በፊቴ ነው
ይህ አንድ ሰው ማድረግ ስለሚፈልገው ነገር የማድረግ መብት እንዳለው የሚገልፅ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “በእኔ ኃላፊነት ስር ነው” ወይም “እንደ ፈለግሁ ማድረጉ የእኔ ፈንታ ነው”

ሺህ ሰቅሎች ላንተ ናቸው፣ ሰለሞን
ሴቲቱ ሰለሞን የወይን ቦታውን በኮንትራት በማከራየት ገንዘብ ማግኘት እንደቻለ ታውቃለች፤ ነገር ግን እርሷ ገንዘብ አትፈልግም።

ሰቅሎች
“ሳንቲሞች”

ሰለሞን
አንዳንድ ትርጉሞች ሴቲቱ የምትናገረው በቀጥታ ለሰለሞን እንደሆነ ይረዳሉ። ሌሎች የሚረዷት በምናቧ ለጓደኞቿ፣ ለሰውየው ወይም ለራሷ እንደምትናገር አድርገው ነው።

ሁለት መቶ ሰቅሎቹ
ተናጋሪው ካሁን በፊት ይህንን አልጠቀሰም ነበር ፤ አድማጭ ግን ሴቲቱ ሰዎቹ በወይን ቦታው ሠርተው ለሰለሞን ከከፈሉት በኋላ ለራሳቸው የሚቀራቸውን ገንዘብ እንደምታወራ ይረዳል።

Song of Solomon 8:13

አንቺ የምትኖሪ
ሰውየው የሚናገረው ለሴቲቱ ነው፤ ስለዚህ፣ “አንቺ” እና “የምትኖሪ” ነጠላ እንስት ናቸው።

ድምፅሽን እየሰማሁ
ድምፁ ሰውየው ለሚናገረው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ቋንቋህ አንድ ሰው እየሰማው ያለውን ነገር ብቻ የሚያስብ መሆኑን የሚገልፅ ቃል ካለው መጠቀም ትችላለህ። አ.ት፡ “መናገር ስትጀምሪ ለመስማት እየጠበቅሁ ነው” ወይም “የምትለውን ለመስማት እየጠበቅሁ ነው”

እንድሰማው ፍቀጂልኝ
“ድምፅሽን እንድሰማው ፍቀጂልኝ”

Song of Solomon 8:14

የእኔ ተወዳጅ
ሐረጉ ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች “የእኔ አፍቃሪ” ማለቷ በይበልጥ የተለመደ ሊሆን ይችላል። መኃልይ 1:13ን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ አፍቃሪ”።

ሚዳቋ
ቀጭን፣ አጋዘን መሳይ ባለ ረጅም ጠምዛዛ ቀንድ እንስሳ

ወንድ አጋዘን
ጎልማሳ ወንድ አጋዘን

የቅመማ ቅመም ተራሮች
“ቅመማ ቅመም የሞላባቸው ተራሮች”። ሴቲቱ ይህንን ዘይቤአዊ አነጋገር ሰውየው ከእርሷ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዲፈጽም ለመጋበዝ ትጠቀምበታለች። ሰውየው በመኃልይ 4:8 የከርቤ ተራሮችንና የዕጣን ኮረብቶችን እንዴት በዘይቤአዊ አነጋገር እንደገለጻቸው ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Isaiah

Isaiah

Chapter 1

1 የይሁዳ ነገሥታት በሆኑት በዖዝያንና በኢዮአታም በአካዝና በሕዝቅያስ ዘመን ስለ ይሁዳና ስለ ኢየሩሳሌም ያየው የአሞጽ ልጅ የኢሳይያስ ራእይ። 2 ሰሙ፣
ምድርም አድምጪ፤ "ልጆችን ወለድሁ አሳደግሁም፣ እነርሱም አመጹብኝ።" ሲል እግዚአብሔር ተናግሮአልና። 3 በሬ የገዢውን፣ አህያም የጌታውን ጋጣ አወቀ፤
እስራኤል ግን አላወቀም፥ እስራኤል አልተገነዘበም" 4 ወዮላችሁ! ኃጢአተኛ ወገንና በደል የተሞላበት ሕዝብ፣ የክፉ አድራጊዎች ልጆች፣ ርኵሰትን የምታደርጉ
ልጆች ሆይ! እግዚአብሔርን ትተዋል፣ የእስራኤልንም ቅዱስ አቃልለዋል ወደ ኋላቸውም እየሄዱ ተለይተዋል። 5 አሁን ድረስ ለምን ትቀሰፋላችሁ? አሁንም
አሁንም ዓመፃ ለምን ትጨምራላችሁ? ራስ ሁሉ ለሕመም፣ ልብም ሁሉ ለድካም ሆኗል። 6 ከእግር መርገጫ አንስቶ እስከ ራስ ድረስ ያልታመመ የለውም፤
ቍስልና እበጥ፣ የሚደማ ቍስል ነው፤ አልፈረጠም፣ አልተጠገነም፣ በዘይትም አልለዘበም። 7 ምድራችሁ ባድማ ናት፤ ከተሞቻችሁ በእሳት ተቃጠሉ፤
እርሻችሁንም በፊታችሁ እንግዶች ይበሉታል፤ ባዕድ እንዳፈረሳት ምድር ባድማ ሆነች። 8 የጽዮንም ሴት ልጅ በወይን ቦታ እንዳለ ዳስ፣ በዱባ አትክልትም
እንዳለ ጎጆ፣ እንደተከበበችም ከተማ ሆና ቀረች። 9 የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ጥቂት ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ፣ እንደ ሰዶም በሆንን፣ እንደ ገሞራም በመሰልን
ነበር። 10 የሰዶም አለቆች ሆይ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ፤ እናንተ የገሞራ ሕዝብ ሆይ፣ የአምላካችንን ሕግ አድምጡ። 11 "የመሥዋዕታችሁ ብዙ ጋጋታ ለእኔ
ምን ይጠቅመኛል?" ይላል እግዚአብሔር። "የሚቃጠለውን የአውራ በግ መሥዋዕትንና የፍሪዳን ስብ ጠግቤያለሁ፤ የበሬና የበግ ጠቦት የአውራ ፍየልም ደም
ደስ አያሰኘኝም። 12 በእኔ ፊት ልትታዩ ብትመጡ፣ ይህን የመቅደሴን አደባባይ መርገጣችሁን ከእጃችሁ የሚሻ ማን ነው? 13 ምናምንቴውን ቍርባን
ጨምራችሁ አታምጡ፤ ዕጣን በእኔ ዘንድ አጸያፊ ነው፤ መባቻችሁንና ሰንበታችሁን በጉባኤ መሰብሰባችሁን አልወድድም - እነዚህን የረከሱ ጉባዔዎች
አልታገሥም። 14 መባቻችሁንና በዓላቶቻችሁን ነፍሴ ጠልታለች፤ ሸክም ሆነውብኛል፥ ልታገሣቸውም ደክሜያለሁ። 15 ስለዚህም እጃችሁን በጸሎት ወደ እኔ
ብትዘረጉ ዓይኔን ከእናንተ እሰውራለሁ፣ ልመናንም ብታበዙ አልሰማችሁም፤ እጆቻችሁ ደም ተሞልተዋል። 16 ታጠቡ፣ ሰውነታችሁንም አንጹ፤ የሥራችሁን ክፋት
ከዓይኔ ፊት አስወግዱ፤ ክፉ መሆንን ተዉ፤ 17 መልካም ማድረግን ተማሩ፣ ፍርድን ፈልጉ፣ የተጨቆነውን እርዱ፣ አባት ለሌለው ፍረዱለት፣ ስለ መበለቲቱም
ተሟገቱ።" 18 "አሁን ኑና በአንድ ላይ እንዋቀስ" ይላል እግዚአብሔር፤ "ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን፣ እንደ በረዶ ትነጻለች፤ እንደ ደምም ብትቀላ፣ እንደ
ባዘቶ ትጠራለች። 19 እሺ ብትሉ ብትታዘዙ፣ የምድርን በረከት ትበላላችሁ። 20 ነገር ግን እምቢ ብትሉ፣ ብታምፁም፣ ሰይፍ ይበላችኋል፣" የእግዚአብሔር አፍ
ይህን ተናግሮአልና። 21 ፍርድ ሞልቶባት የነበረችው የታመነችይቱ ከተማ እንዴት ጋለሞታ ሆነች! ጽድቅ ሞልቶባት ነበር፣ አሁን ግን ገዳዮች ሞልተውባታል። 22
ብርሽ ወደ ዝገት ተለወጠ፣ የወይን ጠጅሽ ከውሃ ጋር ተደባለቀ። 23 አለቆችሽ አመጸኞችና የሌቦች ባልንጀሮች ሆኑ፤ ሁሉ ጉቦ ይወድዳሉ፣ ዋጋም ለማግኘትም
ይሮጣሉ። ለድሀ አደጉ አይፈርዱም፣ የመበለቲቱም ሙግት ወደ እነርሱ አይደርስም። 24 ስለዚህ የእስራኤል ኃያል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣
"ወዮላቸው! የሚቋቋሙኝ ላይ ቍጣዬን እፈጽማለሁ፣ በጠላቶቼ ላይ እበቀላለሁ። 25 እጄንም በአንቺ ላይ አመጣለሁ፣ ዝገትሽንም በጣም አነጻለሁ፣
አለመንጻትሽንም ሁሉ አወጣለሁ፤ 26 ፈራጆችሽንም እንደ ቀድሞ፣ አማካሪዎችሽንም እንደ መጀመሪያው ጊዜ መልሼ አስነሣለሁ፤ ከዚያም በኋላ የጽድቅ
ከተማ፣ የታመነችም ከተማ ተብለሽ ትጠሪያለሽ።" 27 ጽዮን በፍርድ፣ ከእርሷም በንስሃ የሚመለሱ በጽድቅ ይድናሉ። 28 በደለኞችና ኃጢአተኞች ግን
በአንድነት ይሰበራሉ፣ እግዚአብሔርንም የሚተዉ ይጠፋሉ። 29 "በተመኛችኋት የተቀደሰች የአድባር ዛፍ ታፍራላችሁና፣ በመረጣችኋትም አትክልት ስፍራ ላይ
እፍረት ይይዛችኋልና፤ 30 ቅጠልዋ እንደ ረገፈ ዛፍ፣ ውሃም እንደሌለባት አትክልት ትሆናላችሁና። 31 ኃይለኛውም እንደ ተልባ ጭረት፣ ሥራውም እንደ ጠለሸት
ይሆናል፤ አብረውም ይቃጠላሉ፣ እነርሱንም የሚያጠፋ የለም።"

Isaiah 1:1

ኢሳይያስ ያየው ራእይ
‹‹ይህ ያህዌ ያሳየው የኢሳይያስ ራእይ ነው›› ወይም፣ ‹‹ይህ ያህዌ ለኢሳይያስ ያሳየው ነው››

አሞጽ
አሞጽ የኢሳይያስ አባት ነው።

ይሁዳና ኢየሩሳሌም
‹‹ይሁዳ›› ደቡባዊው የእስራኤል መንግሥት ነው። ‹‹ኢየሩሳሌም›› በጣም አስፈላጊ ከተማ ናት። የቦታዎች ስም በውስጣቸው የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በይሁዳና በኢየሩሳሌም የሚኖሩ›› ወይም፣ ‹‹የይሁዳና የኢየሩሳሌም ሰዎች››

በይሁዳ ነገሥታት በዖዝያን፣ በኢዮአታም፣ በአካዝና በሕዝቅያስ ዘመን
ይህ እያንዳንዱ ንጉሥ የገዛበትን ዘመን ያመለክታል። የገዙት ተራ በተራ እንጂ፣ ሁሉም በአንድ ጊዜ አልነበረም። አማረጭ ትርጒም፣ ‹‹ዖዝያን፣ ኢዮአታም፣ አካዝና ሕዝቅያስ የይሁዳ ነገሥታት በነበሩ ጊዜ››

Isaiah 1:2

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።

ሰማያት ሆይ ስሙ፤ ምድርም አድምጪ
ምንም እንኳ እነዚህ ትንቢቶች የኢየሩሳሌምና የይሁዳ ሕዝብ እንዲሰሙ የተነገሩ ቢሆኑም፣ ኢሳይያስ እንደማይሰሙ ያውቃል። ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ሰማያት›› እና ‹‹ምድር›› ያህዌ የተናገረውን መስማት እንደሚችሉ በሚያመለክት ሁኔታ መናገሩ ነበር፤ ወይም 2) ‹‹ሰማያት›› እና ‹‹ምድር›› በየአገሩ ሁሉ ያሉ ሰብዓዊ ፍጡራን ናቸው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በሰማያት የምትኖሩ... በምድርም የምትኖሩ››

ያህዌ
ይህ በብሉይ ኪዳን ዘመን ለነበሩ ሕዝብ የተገለጠ የእግዚአብሔር ስም ነው። ይህን እንዴት እንደምትተረጒም በትርጒም ገጽ ስለ ያህዌ የተነገረውን ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መገብኃቸው እነርሱ ግን አላወቁም
ያህዌ ለሕዝቡ የተናገረውና ኢሳይያስ በያህዌ ምትክ ለእስራኤል የተናገረው ቃል

ልጆች ወለድሁ አሳደግኃቸውም
የእርሱ ቃል ምግብ፣ እስራኤላውያን ደግሞ ልጆቹ እንደ ሆኑ ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በይሁዳ ለሚኖሩ ሰዎች እንደ ልጆቼ ተጠነቀቅሁ››

አህያ የባለቤቱን ጋጥ
በውስጠ ታዋቂነት የተቀመጠውን መረጃ ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አህያ የሚመገብበትን የጌታውን ጋጥ አወቀ›› ወይም፣ ‹‹አህያ ጌታው ለእርሱ ምግብ የሚሰጥበትን አወቀ››

እስራኤል ግን አላወቀም፤ እስራኤል አልተረዳም
ይህም ማለት፣ ‹‹የእስራኤል ሕዝብ ግን አላወቁኝም፤ ለእነርሱ የምጠነቀቅ መሆኔን አልተረዱም››

እስራኤል
ይህ የእስራኤል ሕዝብ መጠሪያ ነው። ይሁዳም የእስራኤል ሕዝብ አካል ነበረ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የእስራኤል ሕዝብ››

Isaiah 1:4

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።

ሕዝብ፣ ኀጢአተኛ
በሌላ መልኩ፣ 1) ኢሳይያስ ስለ እነርሱ ሁለት የተለያዩ ነገሮች እየተናገረ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የእስራኤል ሕዝብ፣ እናንት ኀጢአተኞች›› ወይም፣ 2) ስለ እነርሱ አንድ ነገር ብቻ ይናገራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ኀጢአተኛ ሕዝብ››

ርኩሰት የተጫነው ሕዝብ
ሰው የሚሸከመው ከባድ ሸክም፣ የብዙ ኀጢአታቸው ምሳሌ ሆኗል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ኀጢአታቸው ጀርባቸው ላይ እንደ ተሸከሙት ከባድ ሸክም ነው፤ መራመድም ተስኖአቸዋል››

የክፉ አድራጊ ዘር
‹‹ዘር›› የሚለው ቃል ሌሎች ያደረጉትን የሚያደርጉ ሰዎች መጠሪያ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሌሎች ያደረጉን ክፉ ነገር የሚያደርጉ ሰዎች››

በደል ፈጸሙ
ክፉ አደረጉ

ያህዌን ተዉ
‹‹ከያህዌ ራቁ››

እርሱን ናቁ
‹‹መታዘዝ አልፈለጉም›› ወይም፣ ‹‹እርሱን አላከበሩም››

እስራኤል
ይሁዳም የእስራኤል ሕዝብ አካል ነበር።

ጀርባቸውን በእርሱ ላይ አዞሩ
ምንም እንኳ በአንድ ወቅት ወዳጆቹ የነበሩ ቢሆንም፣ አሁን ግን ጨርሰ እንደማያውቁት ሆኑበት።

Isaiah 1:5

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።

ለምን ዳግመኛ ትመታላችሁ? ለምንስ በዐመፅ ትጸናላችሁ?
ኢሳይያስ እንዲህ በማለት የጠየቀው፣ የይሁዳን ሕዝብ ለመገሠጽ ነው። ጥያቄዎቹን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ እናንተን የቀጣበትን ነገሮች ማድረግ ቀጥላችኃል፤ በእርሱ ላይ በማመፅ ጸንታችኃል››

እናንተ
‹‹እናንተ›› የሚለው በይሁዳ የሚኖረውን ሕዝብ ሲሆን፣ ብዙ ቁጥር ነው።

ራሳችሁ በሙሉ ታውኮአል፤ ልባችሁ ሁሉ ታውኮአል
የእስራኤልን ሕዝበ ከተመታ ሰው ጋር ያነጻጽራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እናንተ ራሱ እንደ ቆሰለ፣ ልቡ እንደ ታወከ ሰው ናችሁ›› ወይም ‹‹እናንተ መላው አእምሮውና ልቡ እንደ ታመመ ሰው ናችሁ››

ያልተጐዳ አካል የለም
ይህን ይበልጥ በተብራራ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አካላችሁ ሁሉ ተጐድቷል›› ወይም፣ ‹‹አንዳች ነገር አካላችሁን ሁሉ ጐድቶታል››

አልታጠበም፤ አልታሰረም፤ በዘይትም አልለዘበም
ምሳሌው እግዚአብሔር እስራኤልን መቅጣቱን ከአካላዊ ቁስል ገር ያነጻጽራል። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ማንም አላጠበውም፤ አላሰረውም፤ በዘይትም አላለዘበውም››

Isaiah 1:7

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።

አገራችሁ ጠፍቷል
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አገራችሁን አጥፍተዋል›› ወይም፣ ‹‹ጠላቶቻችሁ አገራችሁን አጥፍተዋል››

ከተሞቻችሁ ተቃጥለዋል
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከተሞቻችሁን አጥፍተዋል››

እርሻዎቻችሁን በፊታችሁ እንግዶች ያጠፏቸዋል።
‹‹የአገራችሁ ያልሆኑ ሰዎች ዐይናችሁ እያየ እህላችሁን ከእርሻዎቻችሁ ይወስዳሉ››

ጠፍ ሆኖ ይቀራል
‹‹ባዶና የፈረሰ›› ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ምድሩን አጥፍተዋል፤ ማንም አይኖርበትም››

በባዕድ ይነጠቃል
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ባዕዳን አገራችሁን ይነጥቃሉ›› ወይም፣ ‹‹የሌላ አገር ሰራዊት ጨርሶ ድል አድርጐታል››

የጽዮን ሴት ልጅ ተተወች
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የጽዮንን ሴት ልጅ ትቻታለሁ››

የጽዮን ሴት ልጅ
የከተማ፣ ‹‹ልጅ›› የዚያ ከተማ ሕዝብ ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የጽዮን ሕዝብ›› ወይም፣ በጽዮን የሚኖር ሕዝብ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በወይን አትክልት ውስጥ እንዳለ ዳስ፣ በዱባ ተክል ውስጥ እንደሚገኝ ጐጆ ተተወች
ይህም ማለት 1) ‹‹የወይን ተክል ውስጥ እንዳለ ዳስ፣ የዱባ ተክል ውስጥ እንደሚገኝ ጐጆ አነሰች›› ወይም፣ 2) ‹‹ገበሬ ጉዳዩን ስጨርስ እንደሚተወው ወይን ተክል ውስጥ እንዳለ ዳስ የዱባ እርሻ ውስጥ እንዳለ ጐጆ ተተወች››

እንደ... ዱባ፤ እንደ ተከበበ ከተማ
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። ‹‹እንደ... ዱባ እንደ ተከበበ ከተማ ሆነች››

Isaiah 1:9

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።

ያህዌ... ኖሮ
ይህ የሚያመለክተው ባለፈው ጊዜ መሆን የነበረበትን፣ ግን ያልሆነ ነገርን ነው።

ትንሽ ትሩፍ
‹‹የተረፉ ጥቂቶች››

የእኛ... እኛ
እነዚህ ቃሎች የሚያመለክቱት ኢሳይያስን ሲሆን፣ የይሁዳና የኢየሩሌምንም ሕዝብ ይጨምራል።

እንደ ሰዶም በሆንን፣ ገሞራንም በመሰልን
ይሁዳ እንደ ሶዶምና እንደ ገሞራ ሊሆን ይችል የነበረበትን ምክንያት ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰዶምና ገሞራን እንዳጠፋ እግዚአብሔር ያጠፋን ነበር››

Isaiah 1:10

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።

እናንተ የሰዶም ገዦች... እናንተ የገሞራ ሰዎች
ምን ያህል ጎጢአተኞች እንደ ሆኑ ለማሳየት ኢሳይያስ የይሁዳን ሕዝብ ከሰዶምና ከገሞራ ሕዝብ ጋር ያነጻጽራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እናንተ እንደ ሰዶም ሕዝብ ጎጢአተኞች የሆናችሁ ገዦች... እናንተ በገሞራ እንደሚኖሩ ዐመፀኛ የሆናችሁ ሰዎች››

የመሥዋዕታችሁ ብዛት ለእኔ ምኔ ነው?
የእስራኤልን ሕዝብ ለመገሠጽ እግዚአብሔር በጥያቄ ተጠቅሟል። ይህን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ብዙ መሥዋዕት ማቅረባችሁ ለእኔ ምንም ማለት አይደለም››

Isaiah 1:12

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ የያህዌን ቃል ይናገራል።

ይህን ሁሉ እንድታመጡ፣ የመቅደሴን ደጅ እንድትረግጡ የጠየቃችሁ ማን ነው?
‹‹መርገጥ›› አንድ ነገር ላይ ቆሞ በእግሮች መጨፍለቅ ማለት ነው። በይሁዳ የሚኖሩ ሰዎችን ለመገሠጽ እግዚአብሔር በጥያቄ ይጠቀማል። ይህን ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የመቅደሴን ደጅ እንድትረግጡ የጠየቃችሁ የለም።››

ከንቱ መባ አታምጡ
‹‹ከንቱ ስጦታዎቻችሁን አታምጡልኝ››

ዕጣናችሁን እጸየፋለሁ
‹‹እጸየፋለሁ›› የሚለውን ቃል፣ ‹‹እጠላለሁ›› በማለት መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ካህናት የሚያጨሱትን ዕጣን እጠላለሁ››

እነዚህ ክፋት የሞላባቸው ጉባኤዎቻችሁን መታገሥ አልችልም
ይህም ማለት፤ 1) ‹‹ከምታደርጓቸው ክፉ ነገሮች የተነሣ እንድትሰበሰቡ አልፈቅድላችሁም›› ወይም 2) ‹‹ከምታደርጓቸው ክፉ ነገሮች የተነሣ ስብሰባችሁን ማየት አልፈልግም››

Isaiah 1:14

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ የያህዌን ቃል ይናገራል።

አዲስ ጨረቃና የተደነገጉ በዓሎቻችሁ
‹‹አዲስ ጨረቃ›› የሚለው የአዲስ ጨረቃ በዓል የሚከበርት ነው። የተቀሩትም መደበኛ በዓሎች መጠሪያ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የአዲስ ጨረቃና ሌሎች መደበኛ በዓሎቻችሁን››

አዲስ ጨረቃ
አዲስ ጨረቃ ከጨለመች በኃላ ጨረቃዋ መጀመሪያ የምትታይበት ቀን ነው።

ሸክም ሆነውብኛል፤ መታገሥም አልቻልሁም
ይህ የሕዝቡን በዓል ማክበር እግዚአብሔር እንደ ከባድ ሸክም እንደሚያየው ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለእኔ እንደ ከባድ ሸክም ስለሆኑ መታገሥ ሰልችቶኛል››

ዐይኖቼን ከእናንተ ሰወርሁ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር፣ ‹‹ወደ እናንተ አላይም›› ወይም፣ ‹‹እናንተ የምትሉትን አልሰማም›› ማለት ነው።

እጆቻችሁ በደም ተበክለዋል
እግዚአብሔር ጸሎታቸውን የማይሰማው በዚህ ምክንያት ነው። ደም የሚያመለክተው ሌሎች ላይ የፈጸሙትን ግፍ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እጆቻችሁ እናንተ ግፍ ባደረጋችሁባቸው ሰዎች ደም ተበክለዋል›› ወይም፣ ‹‹ግፍ በማድረግ በድላችኃል››

Isaiah 1:16

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ የያህዌን ቃል ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።

ታጠቡ፤ ራሳችሁነ አንጹ
እዚህ ላይ ጎጢአት ማድረግ የተወ ሰው፣ አካሉን እንደ ታጠበ ሰው፣ እንደ ሆነ እግዚአብሔር ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ንስሐ ግቡ፤ ከአካሉ ቆሻሻ እንደሚያጥብ ሰው ልባችሁን ከጎጢአት አንጹ››

ክፉ ሥራችሁን ከፊቴ አርቁ
እግዚአብሔር ክፉ ማድረጋቸውን እንዲተዉ እንጂ፣ ሌላ ቦታ ክፉ እንዲያደርጉ እየነገራቸው አይደለም። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ስታደርጉ የማየውን ጎጢአት ማድረጋችሁን ተዉ››

ፍትሕን እሹ
ሌሎችን የሚጨቁኑ ሰዎች መቃናት ያለበት ጠማማ ነገር እያደረጉ እንደ ሆነ እግዚአብሔር ይናገራል፤ ያንን እንዲያቃኑም ይጣራል። ‹‹ጭቆና›› የሚለውን ቃል በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እናንተ የጐዳችኃቸው ምስኪን ሰዎች ካደረሳችሁባቸው ክፉ ነገር የተነሣ ከእንግዲህ እንዳይሰቃዩ አድርጉ››

አባት ለሌለቸው ቁሙላቸው
‹‹አባት ለሌላቸው መልካም አድርጉላቸው››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለመበለቲቱ ተማገቱ
‹‹ባሏ የሞተባትን ሴት ተከላከሉላት››

Isaiah 1:18

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ አሁንም ለይሁዳ ሕዝብ እየተናገረ ነው።

ኑና...
ቃሉን እንዲሰሙ ያህዌ በቸርነትና በፍቅር ሰዎችን ይጣራል። ‹‹እኔን ስሙ፤ ኑና›› ወይም፣ ‹‹ልብ በሉ፤ ልረዳችሁ እፈልጋለሁ፤ ኑና››

ኑና እንዋቀስ
‹‹በአንድነት ስለዚህ ጉዳይ እናስብ›› ወይም፣ ‹‹እዚህ ላይ እንወያይ›› ወይም፣ ‹‹ታዲያ፣ ምን ማድረግ አለብን?›› ስለ ወደ ፊቱ እንዲወያዩ ያህዌ ሕዝቡ ይጠራል። እዚህ ላይ፣ ‹‹እኛ›› የሚለው ያህዌንና የይሁዳን ሕዝብ ይወክላል።

ኃጢአታችሁ እንደ ዐለላ ቢቀላ እንደ በረዶ ይነጣል፤ እንደ ደም ቢቀላም እንደ ባዘቶ ነጭ ይሆናል
ሕዝቡ እንደ ባዘቶ መንጻት የነበረበትን ልብስ እንደ ለበሱና ኀጢአታቸውም ልብስ ላይ እንዳረፈ ቀይ ጠብታ እንደ ሆነ ኢሳይያስ ይናገራል። ያህዌ ኀጢአታቸውን ይቅር ካለ ልብሳቸው እንደ ገና ይነጣል።

እንደ ዐለላ
ዐለላ ደማቅ ቀይ ቀለም ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ደማቅ ቀይ››

እንደ በረዶ ይነጣል
ብዙውን ጊዜ ነጭ የቅድስናና የንጽሕና ምልክት ነው። ‹‹በረዶ›› ወደ ጠጣርነት የተለወጠ በጣም ነጭ ነገርን ያመለክታል። ይህ የሚያሳየው በጣም ነጭ የሆነ ነገርን በመሆኑ ነጭ በሆነ ሌላ ነገር መተካት ትችላላችሁ፤ ‹‹እንደ ኖራ ነጭ›› ወይም፣ ‹‹እንደ ርግብ ነጭ›› ይህም ማለት ኀጢአታቸው ይቅር ይባላል ማለት ነው።

እንደ ዐለላ ቢቀላ
ዐለላ ደብዛዛ ቀይ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ደብዛዛ ቀይ››

እንደ ባዘቶ
ባዘቶ የበግ ወይም የፍየል ጠጉር ነው። እንደ ባዘቶ መንጻትን በተመለከተ የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንደ ባዘቶ ነጭ››

Isaiah 1:19

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር አሁንም ለይሁዳ ሕዝብ እየተናገረ ነው።

እሺ ብትሉ ብትታዘዙም
‹‹እሺ›› ማለት እና፣ ‹‹መታዘዝ›› ጥቅም ላይ የዋሉት አንድን ሐሳብ ለመግለጽ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በፈቃደኝነት ብትታዘዙ››

የምድርን በረከት ትበላላችሁ
‹‹ምድሪቱ የምትበሉት በረከት ትሰጣችኃላችሁ››

እንቢ ብላችሁ ብታምፁ ግን
‹‹አልሰማም ብላችሁ እኔ ላይ ብታምፁ››

ሰይፍ ይበላችኃል
‹‹ሰይፍ›› የሚያመለክተው የይሁዳን ጠላቶች ነው። ‹‹ይበላችኃል›› የሚለውም ቃል የይሁዳን ጠላቶች ሌላውን እንስሳ ከሚያጠቁና ከሚበሉ አራዊት ጋር ያመሳስላቸዋል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጠላቶቻችሁ ይገድሏችኃል››

የያህዌ አፍ ይህን ተናግሮአል
‹‹አፍ›› የሚለው ቃል ያህዌ መናገሩንና የተናገረውም በእርግጥ የሚፈጸም መሆኑን አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ ተናግሮአል›› ወይም፣ ‹‹ይህ እንደሚፈጸም ያህዌ ተናግሮአል››

Isaiah 1:21

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።

ታማኝ የነበረችው ከተማ እንዴት...
ይህ ቃለ አጋኖ የኢየሩሳሌምን ሕዝብ በተመለከተ ኢሳይያስ ያደረበትን ቁጣና ሐዘን ያሳያል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ለእግዚአብሔር ታማኝ የነበሩት የኢየሩሳሌም ሕዝብ ላይ የሆነውን ተመልከቱ››

አመንዝራ ሆነች
ኢሳይያስ ሕዝቡን ለባልዋ ታማኝ ካልሆነች፣ ነገር ግን ገንዘብ ለማግኘት ከሌሎች ወንዶች ጋር ከምትተኛ ሴት ጋር ያመሳስላቸዋል። ሕዝቡ ሐሰተኛ አማልክት አመለኩ እንጂ፣ ለእግዚአብሔር ታማኝ አልሆኑም። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንደ አመንዝራ ሆኑ››

ቀድሞ ፍትሕ የሞላባት ከተማ
‹‹እርሷ›› የሚለው ኢየሩሳሌምና ሕዝቧን ያመለክታል። መጽሐፍ ቅዱስን የጻፉ ሰዎች ብዙውን ጊዜ ከተሞችን ከሴቶች ጋር ያመሳስላሉ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የኢየሩሳሌም ሕዝብ መልካም ነበሩ፤ መልካም ነገርንም ያደርጉ ነበር››

አሁን ግን ነፍሰ ገዳዮች የሞሉባት ሆነች
‹‹እርሷ›› የሚለው ኢየሩሳሌምንና ሕዝቧን ያመለክታል። መጽሐፍ ቅዱስን የጻፉ ሰዎች ብዙውን ጊዜ ከተሞችን ከሴቶች ጋር ያመሳስላሉ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አሁን ግን የኢየሩሳሌም ሰዎች ነፍሰ ገዳዮች ሆኑ››

ብርሽ ዝጐአል፤ የወይን ጠጅሽ ከውሃ ጋር ተቀላቀለ
እዚህ ላይ ኢሳይያስ ብርና ወይን ጠጅን - ከሚከተሉት ጋር ያመሳስላል 1) ከኢየሩሳሌም ሕዝብ ጋር። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ንጹሕ እንዳልሆነ ብር፣ ከውሃ ጋር እንደ ተቀላቀለ ወይን ጠጅ ሆናችኃል›› ወይም 2) ሕዝቡ ቀድሞ ያደረግ ከነበረው መልካም ነገር ጋር። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ቀድሞ መልካም ነገር ታደርጉ ነበር አሁን ግን መልካም ሥራችሁን ከንቱ የሚያደርግ ነገር እያደረጋችሁ ነው››

የዛገ... ብር
ብር በየጊዜው መንጻት አለበት፤ አለበለዚያ ደምቆ አይታይም።

ወይን ጠጅ... ውሃ
ውሃ የበዛበት ወይን ጠጅ በጣም አይጣፍጥም፤ እንዲያውም ከውሃ አይሻልም።

Isaiah 1:23

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ የያህዌን ቃል ለሕዝቡ እየተናገረ ነው።

ገዢዎቻችሁ ዐመፀኞች ሆነዋል
‹‹መሪዎቻችሁ በእግዚአብሔር ላይ ዐምፀዋል።››

የሌቦች ግብረ አበር
‹‹ከሌሎች የሚሰርቁ ሰዎች ጓደኞች ሆነዋል››

ጉቦ... እጅ መንሻ
መሪዎቹ ፍርድ እንዲያጣምሙላቸው ሕዝቡ ለክፉ መሪዎች፣ ‹‹ጉቦ›› ይሰጣሉ። ሕጉን በመተላለፍ ጥቅም እንዲያገኙ መሪዎች፣ ‹‹እጅ መንሻ ይቀበላሉ።››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እጅ መንሻን በብርቱ ይፈልጋሉ
ጉቦ እንዲሰጠው በብርቱ የሚፈልግ ሰው እጅ መንሻ ከእርሱ ከሚሸሸና ያንን ለመያዝ ከሚሮጥ ሰው ጋር ተመሳስሎአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እውነተኛ ያልሆነ ፍርድ ለማድረግ ሰው ሁሉ አጥብቆ ገንዘብ እንዲከፈለው ይፈልጋል››

አባት ለሌላቸው አይቆሙም
‹‹አባት ለሌላቸው አይሟገቱም››

የመበለቶችንም አቤቱታ አይሰሙም
‹‹በሕግ ተላላፊዎች ላይ እንዲፈርዱላቸው መበለቶች ወደ እነርሱ ሲመጡ አይሰሟቸውም›› ወይም፣ ‹‹ከሕግ ተላላፊዎች እንዲያስጥሏቸው መበለቶች ወደ እነርሱ ሲመጡ አይረዷቸውም››

Isaiah 1:24

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ የያህዌን ቃል ለይሁዳ ሕዝብ መናገር ይጀምራል።

ስለዚህ
‹‹በዚህ ምክንያት››

የሰራዊት ጌታ የእስራኤል ኀያል ያህዌ እንዲህ ይላል
የሚናገረውን ቃል እርግጠኝነት ለማመልከት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሰራዊት ጌታ የእስራኤል ኀያል ያህዌ እንዲህ በማለት ይናገራል።›› ወይም፣ ‹‹የሰራዊት ጌታ የእስራኤል ኀያል እኔ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ››

በባላንጣዎቼ ላይ ቁጣዬን እገልጣለሁ፤ ጠላቶቼንም እበቀላለሁ
ሁለቱም ሐረጐች የሚናገሩት ስለ ተመሳሳይ ነገር ነው። ‹‹ባላንጣዎቼ ላይ ቁጣዬን እገልጣለሁ›› የሚለው ይበልጥ የሚያመለክተው እርሱን ደስ እንዲለው ተቃዋሚዎቹ ላይ ያህዌ የፈቀደውን ማድረግ እንደሚችል ነው። ‹‹ጠላቶቼንም እበቀላለሁ›› የሚለው ይበልጥ የሚያመለክተው ያህዌ ጠላቶቹን በጽድቅ እንደሚቀጣ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሚቃወመኝን እቀጣለሁ›› ወይም፣ ‹‹እኔ ላይ በሚነሱት ደስ ያለኝን አደርግባቸዋለሁ፤ ጠላቶቼንም በጽድቅ እቀጣለሁ››

እጄን በአንቺ ላይ አነሣለሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› ሕዝቡን ለመቅጣት የሚጠቀምበትን የእግዚአብሔር ኀይል ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እናንተ ለመቅጣት ኀይሌን ሁሉ እጠቀማለሁ››

ዝገትሽን ፈጽሜ አጠራለሁ
እግዚአብሔር የሕዝቡን ኀጢአት ለማስወገድ የሚያደርገው የእርሷን ኀጢአት ብርን ከተቀላቀለበት ቆሻሻ ነገር ከማንጻት ጋር ተመሳስሎአል። እዚህ ላይ የተጠቀመበት ቃል ብርን ከሚያነጻ ነገር ጋር ሳይሆን ሳሙና ውስጥ የሚደባለቅ ነገርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ብርን ከቆሻሻ ነገር እንደሚያጠራ እሳት፣ ክፉንም ሁሉ ከመካከልሽ አስወግዳለሁ››

ዝገት
ይህ ዕቃው ንጹሕ እንዲሆን ሰዎች የሚያስወግዱት ቆሻሻና ሌላ መጥፎ ነገር ነው።

Isaiah 1:26

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።

እንደ ቀድሞው... እንደ መጀመሪያው
ይህ እስራኤል በመጀመሪያ መንግሥት ስትሆን የእስራኤል ታሪክ ጅማሬ ላይ ስለ ተፈጸመው የመጀመሪያ ክፍል ለመናገር የተጠቀመባቸው ሁለት የአነጋገር መንገድ ነው።

...ተብለሽ ትጠሪያለሽ
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች... በማለት ይጠሩሻል››

የጽድቅ መዲና፤ የታመነች ከተማ
‹‹መዲና›› እና ‹‹ከተማ›› የሚያመለክተው በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎችን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ለእግዚአብሔር ጻድቃንና ታማኞች የሚሆነባቸው ከተሞች››

Isaiah 1:27

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ የያህዌን ቃል ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።

ጽዮን በፍትሕ፣ በንስሐ የሚመለሱ ነዋሪዎቿም በጽድቅ ይዋጃሉ
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። የበለጠ ግልጽ ማድረግም ይቻላል። እንዲህ ማለት ሊሆን ይችላል፤ 1) ‹‹እዚያ ያሉ ሰዎች ትክክለኛ ነገር በማድረጋቸው ያህዌ ጽዮንን ይዋጃል፤ ያህዌ ትክክል የሚለውን በማድረጋቸው በንስሐ የሚመለሱትን ያህዌ ያድናል›› ወይም 2) ‹‹እርሱ ጻድቅ ስለሆነ ያህዌ ጽዮንን ይዋጃል፤ ጻድቅ ስለሆነም በንስሐ የሚመለሱትን ያድናል››

ጽዮን
ይህ በጽዮን ተራራ የሚኖሩ ሰዎች መጠሪያ ነው።

ዐመፀኞችና ኀጢአተኞች በአንድነት ይደቅቃሉ
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በእርሱ ላይ የሚያምፁትንና ኀጢአት የሚያደርጉትን ያህዌ ያጠፋቸዋል››

ያህዌንም የሚተዉ ይጠፋሉ
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእርሱ የሚመለሱትን ያህዌ ፈጽሞ ያጠፋቸዋል›› ወይም፣ ‹‹እርሱን ችላ የሚሉትን ያህዌ ይገድላቸዋል››

Isaiah 1:29

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ የያህዌን ቃል ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።

የተቀደሱ ወርካ ዛፎች... አትክልት ቦታዎች
እነዚህ ሐረጐች የይሁዳ ሕዝብ ጣዖት ያመለኩባቸውን ቦታዎች ያመለክታሉ።

በ... ታፍራላችሁ
አንዳንድ ቅጂዎች፣ ‹‹ከዚህ የተነሣ ትደነግጣላችሁ›› ይላሉ። አንድ ሰው መጥፎ ነገር እንዳደረገ ሲሰማው ይደነግጣል ፊቱ ይቀላል።

ቅጠሉ እንደ ጠወለገ ወርካ፣ ውሃም እንደሌለው የአትክልት ቦታ ትሆናላችሁ
ውሃ ለዛፎችና ለአትክልት ቦታዎች ሕይወት ይሰጣል። ሕዝቡ ሕይወት ከሚሰጣቸው ከያህዌ ራሳቸውን ለይተዋል።

Isaiah 1:31

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ የያህዌን ቃል ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።

ብርቱ ሰው
‹‹ብርቱ ሰው›› ወይም፣ ‹‹ብርቱ የሆነ ሰው›› - ይህ የሚመለከተው ታዋቂና ሌሎች ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ሰዎችን ሊሆን ይችላል።

ገለባ
ገለባ በቀላሉ የሚቃጠል ደረቅ ሣር ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሥራውም እንደ ብልጭታ
ይህ የሰውን ሥራ ወይም ክፉ ሥራን ገለባ ላይ ወድቆ ከሚነድ ነገር ጋር
ያመሳስላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሥራው እሳት እንደሚያስነሣ ብልጭታ
ይሆናል››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 የአሞጽ ልጅ ኢሳይያስ ስለ ይሁዳና ስለ ኢየሩሳሌም በራእይ ያያቸው ነገሮች። **2** በኋለኞቹ የፍጻሜ ቀናት፣ የእግዚአብሔር ቤት ተራራ በተራሮች ከፍታ ላይ ጸንቶ ይቆማል፣ ከኮረብቶችም በላይ ከፍ ከፍ ይላል፤ አሕዛብም ሁሉ ወደ እርሱ ይጎርፋሉ። **3** ሕግ ከጽዮን የእግዚአብሔርም ቃል ከኢየሩሳሌም ይወጣልና ብዙዎች አሕዛብ መጥተው፣ "ኑ፣ ወደ እግዚአብሔር ተራራ፣ ወደ ያዕቆብ አምላክ ቤት እንውጣ፤ እርሱም መንገዱን ያስተምረናል፥ በጎዳናውም እንሄዳለን ይላሉ።" **4** በአሕዛብም መካከል ይፈርዳል፣ በብዙ አሕዛብም ላይ ይበይናል፤ ሰይፋቸውንም ማረሻ ጦራቸውንም ማጭድ ለማድረግ ይቀጠቅጣሉ፤ ሕዝብም በሕዝብ ላይ ሰይፍ አያነሣም፣ ጦርነትንም ከእንግዲህ ወዲህ አይማሩም። **5** እናንተ የያዕቆብ ቤት ሆይ፣ ኑ፣ በእግዚአብሔር ብርሃን እንሂድ። **6** የምሥራቅን ሰዎች አመል ስለ ተሞሉ፣ እንደ ፍልስጥኤማውያንም ምዋርተኞች ስለ ሆኑ፣ ከባዕድ ልጆችም ጋር ስለ ተባበሩ፣ የሕዝብህን የያዕቆብን ቤት ትተሃል። **7** ምድራቸው በብርና በወርቅ ተሞልታለች፣ ለመዛግብቶቻቸውም ፍጻሜ የለውም፤ ምድራቸውም ደግሞ በፈረሶች ተሞልታለች፣ ለሠረገሎቻቸውም ፍጻሜ የለውም። **8** ምድራቸው ደግሞ በጣዖታት ተሞልታለች፤ ጣቶቻቸውም ላደረጉት ለእጃቸው ሥራ ይሰግዳሉ። **9** ታናሹም ሰው ዝቅ ብሎአል፣ ግለሰቦችም ይዋረዳሉ፤ ስለዚህ አትቀበላቸው። **10** ከእግዚአብሔር ማሸበርና ከግርማው ክብር የተነሣ ወደ ድንጋይ ዋሻ ግቡ፣ በመሬትም ውስጥ ተሸሸጉ። **11** ከፍ ያለችውም የሰው ዓይን ትዋረዳለች፣ የሰዎችም ኩራት ተጎትታ ትወድቃለች፣ በዚያም ቀን እግዚአብሔር ብቻውን ከፍ ይላል። **12** የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር ቀን በትዕቢተኛውና በኩራተኛው ሁሉ ላይ፣ ከፍ ባለውም ላይ ይሆናል፣ እርሱም ይዋረዳል፤ **13** ደግሞም በረጅሙ ከፍ ባለው በሊባኖስ ዝግባ ሁሉ ላይ፣ በባሳንም ዛፍ ሁሉ ላይ ይሆናል፣ **14** በረጅሞቹም ተራራዎች ሁሉ ላይ፣ ከፍ ባለውም ኮረብቶች ሁሉ ላይ፣ **15** በረጅሙም ግንብ ሁሉ ላይ፣ በተመሸገውም ቅጥር ሁሉ ላይ፣ **16** በተርሴስም መርከቦች ሁሉ ላይ፣ በሚያማምሩ ጣዖታትም ሁሉ ላይ ይሆናል። **17** የሰው ሁሉ ክብር ይዋረዳል፣ የሰውም ኩራት ይወድቃል፤ በዚያም ቀን እግዚአብሔር ብቻ ከፍ ከፍ ይላል። **18** ጣዖቶቻቸውም ሁሉ ፈጽመው ይጠፋሉ። **19** እግዚአብሔርም ምድርን ያናውጥ ዘንድ በተነሣ ጊዜ፣ ሰዎችን ከማስደንገጡና ከግርማው ክብሩ የተነሣ፣ ወደ ድንጋይ ዋሻና ወደ ምድር ንቃቃት ውስጥ ይገባሉ። **20** በዚያን ቀን ሰው ይሰግድላቸው ዘንድ ያበጁአቸውን የብሩንና የወርቁን ጣዖቶቻቸውን ለፍልፈልና ለሌሊት ወፍ ይጥላሉ። **21** እግዚአብሔርም ምድርን ያናውጥ ዘንድ በተነሣ ጊዜ ከማስደንገጡና ከግርማው ክብር የተነሣ ወደ ድንጋይ ዋሻና ወደ ተሰነጠቁ ዓለቶች ውስጥ ይገባሉ። **22** እስትንፋሱ በአፍንጫው ውስጥ ያለበትን ሰው ተዉት፣ እርሱ ስለ ምን ይቈጠራል?

Isaiah 2:1

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ የያህዌ ቃል ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።

ይሁዳና ኢየሩሳሌም
‹‹ይሁዳ›› እና፣ ‹‹ኢየሩሳሌም›› እዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በይሁዳና በኢየሩሳሌም የሚኖሩ››

በመጨረሻዎቹ ቀኖች
‹‹ወደ ፊት››

የያህዌ ቤት ተራራ ይመሠረታል
ይህም ማለት 1) ገለጻ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የያህዌ ቤት ተራራ ጸንቶ ይቆማል›› ወይም 2) በሌላ መልኩ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቤተ መቅደሱ የሚሠራበትን ተራራ ያህዌ ይመሠርታል››

በተራሮችም ከፍታ ላይ
ያህዌ ግዙፍ ከፍታን በመሰለ ሁኔታ ስለ አስፈላጊነቱ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጣም አስፈላጊ የሆኑ ተራሮች›› ወይም፣ ‹‹በዓለም ላይ በጣም አስፈላጊ የሆነ ቦታ››

ከኮረብቶችም በላይ ከፍ ይላል
ኢሳይያስ ከፍታን በመጠቀም በምሳሌያዊ መንገድ ስለ ክብር ይናገራል። ይህንን በሚከተለው ሁኔታ ማስቀመጥ ይቻላል። 1) አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ከሌላው ኮረብታ የበለጠ ያከብረዋል›› ወይም፣ እዚያ የሚያመልኩ ሰዎችን ለማመልከት፣ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሌሎች ሰዎችን ካከበረው የበለጠ ያህዌ እዚያ የሚያመልኩትን ሰዎች ያከብራል››

ሕዝቦች ሁሉ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ሕዝቦች›› በእነዚህ አገሮች የሚኖሩ ሰዎች ናቸው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከአገሮች ሁሉ የመጡ ሕዝቦች››

ይጐርፋሉ
ወደ ያህዌ ተራራ የሚሄዱ ሰዎች ከጐርፍ ጋር ተመሳስለዋል። ይህም ጥቂት ሳይሆኑ ብዙ ሰዎች እንደሚመጡ አጽንዖት ለመስጠት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ወንዝ ወደ እርሱ ይጐርፋሉ›› ወይም፣ ‹‹ወደ እርሱ ይሄዳሉ››

Isaiah 2:3

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።

እንዲያስተምረን ያዕቆብ... እንሄዳለን
ሌላው ትርጉም፣ ‹‹ያዕቆብ ያስተምረናል... እኛም እንሄዳለን››

እርሱ መንገዱን ያስተምረናል፤ በጎዳናውም እንሄዳለን
‹‹መንገድ›› እና፣ ‹‹ጐዳና›› የሰውን አኗኗር የሚያመለክቱ ምሳሌዎች ናቸው። በቋንቋህ ሰዎች ስለሚሄዱበት መንገድ ያላችሁ ቃል አንድ ብቻ ከሆነ ሁለቱን እንደ አንድ ቃል ልትጠቀምባቸው ትችላለህ።

ሕግ ከጽዮን፣ የያህዌም ቃል ከኢየሩሳሌም ይወጣል
ሁለቱም ሐረጐች የሚያመለክቱት ተመሳሳይ ነገርን ነው። እውነት በኢየሩሳሌም መገኘቱን ሰዎች ሁሉ እንደሚረዱ ኢሳይያስ አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጽዮን ያሉ የእግዚአብሔርን ሕግ፣ በኢየሩሳሌም የሚኖሩም የያህዌን ቃል ያስተምራሉ››

ከጽዮን ሕግ ይወጣልና
‹‹ሕግ ከጽዮን ይወጣልና›› ሕጉ ሰዎች ምንም ሳያደርጉ እንደ ወንዝ የሚወጣ ነገር መሆኑን ኢሳይያስ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለሚያስተምሯቸው ሰዎች ሕጉ ከጽዮን ይወጣላቸዋል›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ከጽዮን ሕጉን ይናገራል››

የያህዌ ቃል ከኢየሩሳሌም
‹‹የያህዌ ቃል ከኢየሩሳሌም ወጥቶ ይሄዳል›› የያህዌ ቃል ሰዎች ምንም ሳያደርጉ እንደ ወንዝ የሚሄድ ነገር እንደ ሆነ ኢሳይያስ ይናገራል። በውስጠ ታዋቂነት ያለውን መረጃ የበለጠ ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለሚያስተምሯቸው ሰዎች ከኢየሩሳሌም የያህዌ ቃል ይወጣላቸዋል›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ቃሉን ከኢየሩሳሌም ይናገራል››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Isaiah 2:4

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።

ይፈርዳል
‹‹ያህዌ ይፈርዳል››

ውሳኔ ያሳልፋል
‹‹አለመግባባትን ያስወግዳል››

ሰይፋቸውን ቀጥቅጠው ማረሻ፣ ጦራቸውንም ማጭድ ያደርጋሉ
እነዚህ ቃሎች ማንኛውንም የጦር መሣሪያ ይወክላሉ።

ማረሻ... ማጭድ
እነዚህ ቃሎች ሰዎች ለሰላማዊ ጉዳይ የሚጠቀሙባቸውን መሣሪያዎች ሁሉ ይወክላሉ።

ሰይፋቸውን ቀጥቅጠው ማረሻ ያደርጋሉ
‹‹ሰይፋቸውን ዘር ለማብቀል የሚጠቅም መሣሪያ ያደርጉታል››፤ ማረሻ ዘር ለመዝራት ሲፈልጉ ሰዎች መሬቱን የሚቆፍሩበት ስለታም መሣሪያ ነው።

ጦራቸውንም ማጭድ ያደርጋሉ
‹‹ጦራቸውን ቀጥቅጠው ማጭድ ያደርጉታል›› ወይም፣ ‹‹ጦራቸውን ለተክሎች አገልግሎት የሚውል መሣሪያ ያደርጋሉ›› ማጭድ ሰዎች የማያስፈልግ ቅርንጫፍ ከአትክልቶች የሚቆርጡበት ጠማማ ቢላ ነው።

ሕዝብ በሕዝብ ላይ ሰይፍ አያነሣም
‹‹አንዱ ሕዝብ ሌላው ሕዝብ ላይ ሰይፉን አያነሣም›› ሰይፍ ጦርነትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንዱን ሕዝብ ሌላው ሕዝብ ላይ ጦርነት አያውጅም››

የጦርነት ልምምድም አያደርጉም
‹‹ሌላው ቀርቶ የጦርነት ዝግጅት እንኳ አያደርጉም›› ሰዎች ጦርነት ከማድረጋቸው በፊት ልምምድ እንደሚያደርጉ፣ ልምምድ ካደረጉት አንዳንዶቹም እንደማይዋጉ አንባቢዎቹ ይረዳሉ ብሎ ጸሐፊው ይጠብቃል።

Isaiah 2:5

አጠቃላይ መረጃ
2፥5 ላይ ኢሳይያስ ለይሁዳ ሕዝብ፣ 2፥6 ላይ ለያህዌ ይናገራል። ሁለቱንም ጊዜ የተናገረው በግጥም መልክ ነው።

የያዕቆብ ቤት
x

Isaiah 2:7

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለያህዌ ይናገራል።

ምድራቸው በብር ተሞልቷል... ምድራቸው በፈረሶች ተሞልቷል... ምድራቸው በጣዖቶች ተሞልቷል
ምድሪቱ ሰዎች በብር፣ በፈረሶችና በጣዖቶች የሚሞሏት አንዳች ነገር እንደሆነች ኢሳይያስ ይናገራል። ‹‹ምድሪቱ›› የሚለው ሰዎች ራሳቸውን ያመለክታል፤ ‹‹ተሞልተዋል›› የሚለው ሰዎቹ የእነዚህ ነገሮች ባለቤቶች መሆናቸውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ብዙ ብር... ብዙ ፈረሶች... ብዙ ጣዖቶች አሏቸው››

የእጆቻቸው ሥራ፣ የገዛ ጣቶቻቸው ያበጇቸውን
እነዚህ ሁለት ሐረጐች የሚናገሩት ስለ አንድ ነገር ነው፤ በእውነት አማልክት እንዳይደሉም አጽንዖት ይሰጣሉ። በቋንቋህ ሰው ለሠራው ነገር ቃል ከሌለ ሁለቱን ሐረጐች በአንድ ማጣመር ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነርሱ ራሳቸው የሠሯቸውን ነገሮች››

የእጆቻቸው ሥራ
‹‹እጆች›› ሰዎቹ ራሳቸውን ይወክላሉ፤ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እጃቸው የሠራውን ነገር›› ወይም፣ ‹‹የራሳቸውን ሥራ›› ወይም፣ ‹‹በእጆቻቸው የሠሩትን ነገር››

ጣቶቻቸው ያበጇቸውን
‹‹ጣቶች›› ሰዎቹ ራሳቸውን ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጣቶቻቸው ያበጇቸውን ነገሮች››

Isaiah 2:9

አጠቃላይ መረጃ
2፥9 ላይ ኢሳይያስ ለያህዌ መናገሩን ያበቃል። 2፥10-11 ላይ ኢሳይያስ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል። ሁለቱንም ጊዜ የሚናገረው በቅኔ መልክ ነው።

ሰዎች ዝቅ ብለዋል፤ ግለ ሰቦችም ወድቀዋል
እዚህ ላይ ሰዎች ወደ መሬት ዝቅ ማለታቸው የሚያመለክተው የታመኑበት ሁሉ ከንቱ መሆኑንና ራሳቸውንም ለመርዳት ምንም ማድረግ አለመቻላቸውን በመረዳታቸው በጣም መዋረዳቸውን ነው። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔር ሰዎችን ያዋርዳል፤ የታመኑበት ሁሉ ከንቱ መሆኑንም ይረዳሉ››

ሕዝቡ
ከእንስሳት የተለዩ ሰብዓዊ ፍጡራን

ግለ ሰቦች
‹‹እያንዳንዱ ሰው››

ከእንግዲህ አታንሣቸው
‹‹አታንሣቸው›› የሚለው ያህዌ ሕዝቡን ይቅር የማለቱ ምሳሌ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይቅር አትበላቸው››

ወደ ዐለቶች ሂድ
ይህ የሚከተሉትን ማለት ሊሆን ይችላል። 1) ሰዎች ኮረብቶች ላይ ወዳሉ ዐለቶች መሄድ አለባቸው ወይም 2) መደበቅ የሚችሉበት ብዙ ዐለቶች ያሉበት ቦታ።

በመሬት ውስጥ ተሸሸግ
ይህ የሚከተሉትን ማለት ሊሆን ይችላል፤ 1) መሬት ውስጥ ባሉ ጉድጓዶች መደበቅ ወይም 2) መሬት ውስጥ በቆፈሩት ጉድጓድ።

ከያህዌ አስፈሪነት
እዚህ ላይ ‹‹አስፈሪ›› የሚለውን፣ ‹‹አስደንጋጭ›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከአስደንጋጭ የያህዌ ፊት ለመሸሸ›› ወይም፣ ‹‹በጣም ከምትፈሩት ከያህዌ››

የግርማው ክብር
‹‹እንደ ንጉሥ እርሱ ያለው ውበትና ኀይል›› ወይም፣ ‹‹ንጉሣዊ ክብሩ›› ኢሳይያስ 2፥10 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐመኸው ተመልከት።

የዕብሪተኛ ዐይን ይሰበራል
‹‹ያህዌ የሰዎችን እብሪት ያዋርዳል›› ‹‹የሰዎች እብሪት ዐይን›› ከሰዎች ሁሉ በላይ ሆኖ መታየት ከእነርሱ የተሻለ እንደሆነ ማሰብ ማለት ነው። እዚህ ላይ ከያህዌ የተሻሉ እንደሆኑ በማሰብ ሰዎች ሁሉ በደል ፈጽመዋል፤ ያህዌን የሚያመልኩትን የሚያዩበት ሁኔታ የትዕቢታቸው መገለጫ ነው። አማራጭ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ትርጉም፣ ‹‹ከእርሱ የተሻሉ እንዲሆኑ በማሰባቸው ያህዌ ሰዎችን ሁሉ ያሳፍራል››

የሰዎችም ትዕቢት ይዋረዳል
‹‹የሰዎች ትዕቢት›› ትዕቢተኞችን ይወክላል፤ ‹‹ይሰበራል›› ዝቅ ይላል ወይም ያፍራል ማለት ነው። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ትዕቢተኞችን ያዋርዳል›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ትዕቢተኞች በራሳቸው እንዲያፍሩ ያደርጋል››

ያህዌ ብቻውን ከፍ ይላል
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ያህዌን ብቻ ያመሰግናሉ››

በዚያን ቀን
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በዚያ ቀን ያህዌ በሁሉም ላይ ይፈርዳል››

Isaiah 2:12

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።

ረጅምና ከፍ ከፍ ያሉትን
‹‹ከፍ ያለ ሰው›› ትዕቢተኛና ከሌሎች የበለጠ እንደ ሆነ የሚያስብ ሰው ነው። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ትዕቢተኛና ራሱን ከሌሎች በላይ ከፍ የሚያደርግ ሰው›› ወይም፣ ‹‹ትዕቢተኛና ከሌሎች የበለጠ እንደ ሆነ የሚያስብ ሰው››

ትዕቢተኛና እብሪተኛ
እብሪተኛ የሆነ ሰው ከሌሎች የበለጠ መሆኑን ይናገራል። እነዚህ ሁለት ሐረጐች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ በአንድነት የቀረቡት ያህዌ እንደሚቀጣቸው አጽንዖት ለመስጠት ነው።

ይዋረዳል
‹‹ማንኛውም ትዕቢተኛ ይዋረዳል›› ይህን በተሻለ ሁኔታ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ያዋርደዋል››

የሊባኖስ ዝግባዎች ሁሉ... የባሳንን የወርካ ዛፍ ሁሉ
‹‹የሰራዊት ጌታ የያህዌ ቀን›› በዝግባዎችና በወርካዎች ላይ ይሆናል። ይህም ማለት የሚከተሉትን ማለት ሊሆን ይችላል። 1) እነዚህ ዛፎች ያህዌ የሚፈርድባቸው ትዕቢተኞች ምሳሌ ናቸው። ወይም 2) እግዚአብሔር እነዚህ ግዙፍ ዛፎችን ያጠፋል።

Isaiah 2:14

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል። በሰራዊት ጌታ በያህዌ ቀን የሚሆነውን በተመለከተ ገለጻውን ቀጥሏል።

በ... ላይ
2፥14-16 እግዚአብሔር የሚያጠፋቸውን ነገሮች ይዘረዝራል። ይህም የሚከተሉትን ማለት ሊሆን ይችላል። 1) እግዚአብሔር የሚያዋርዳቸውን ክፉ ሰዎች ያመለክታል። ወይም 2) እግዚአብሔር ዝርዝሩ ውስጥ የተጠቀሱ ነገሮች ሁሉ ያጠፋል።

ተራሮች... ኮረብቶች
እነዚህ ቃሎች ትዕቢተኛ እስራኤላውያንን ያመለክታሉ። ኢሳይያስ 2፥2 ላይም ይገኛሉ።

ከፍ ያለው ሁሉ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጣም ከፍ ያለው››

ረጅሙ ግንብ... የተመሸገው ቅጥር
ይህ የሚያመለክተው ራሳቸውን ከጠላቶቻቸው ለመከላከል ሰዎች ከተሞቻቸው ዙሪያ የሚሠሩዋቸውን ግንቦች ነው። የእስራኤላውያን ትዕቢትና ያህዌን አታስፈልገንም ማለታቸው ለኀጢአታቸው ያህዌ የሚያመጣባቸውን ቅጣት ሁሉ መቋቋም እንደሚችሉ የማሰባቸው ምሳሌ ነው።

የተመሸገው ቅጥር
‹‹ምንም የማያፈርሰው ወይም የማይሻገረው››

የተርሴስ መርኮቦች... ያማሩ ጀልባዎች
እነዚህ የሚያመለክቱት ሰዎች በባሕር ላይ ርቀው በመሄድ የተለያዩ ነገሮችን ወደ ከተሞቻቸው ለማምጣት የሚጠቀሙባቸውን መጓጓዣዎች ነው።

የተርሴስ መርከቦች
‹‹ወደ ተርሴስ የሚሄዱባቸው መርከቦች››

Isaiah 2:17

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል። በሰራዊት ጌታ በያህዌ ቀን የሚሆነውን መግለጽ ቀጥሏል። (ኢሳይያስ 2፥12)

የሰው እብሪት ይዋረዳል
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ማንኛውንም እብሪተኛ ሰው ይጥላል›› ወይም፣ ‹‹ማንኛውንም እብሪተኛ ዝቅ ያደርጋል››

የሰውም ኩራት ይወድቃል
‹‹ኩራት›› የሚለውን ቃል በሌላ መተካት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሰዎች ኩራት እንዳልነበረ ይሆናል››

ያህዌ ብቻ ከፍ ከፍ ይላል
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። 2፥11 ላይ ይህን እንዴት እንደተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ያህዌን ብቻ ያመሰግናሉ››

ጣዖቶች ሁሉ ፈጽሞ ይወድማሉ
‹‹ጣዖቶች ሁሉ ይጠፋሉ›› ወይም፣ ‹‹ከእንግዲህ ጣዖቶች አይኖሩም››

ሰዎች ከአስፈሪነቱ... ሮጠው ይገባሉ
ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከአስፈሪነቱ ሰዎች... ሮጠው ይደበቃሉ››

የዐለት ዋሻዎች
‹‹ዐለት ውስጥ ያሉ ዋሻዎች›› እነዚህ በእጅ የሚያዙ ትንንሽ ድንጋዮች ሳይሆኑ፣ በጣም ትልልቅ ዐለቶች ናቸው።

ከያህዌ አስፈሪነት ከግርማው ክብር የተነሣ
ኢሳይያስ 2፥10 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

ከያህዌ አስፈሪነት
ያህዌን በጣም ከመፍራታቸው

ከግርማው ክብር የተነሣ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ክብር›› የሚለው፣ ‹‹ግርማ›› የሚለውን ቃል ይገልጻል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የንጉሥነት ክብሩ››

ምድርን ለማስፈራት ሲነሣ
‹‹ያህዌ ለተግባር ሲነሣና የምድር ሰዎች እንዲፈሩት ሲያደርግ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Isaiah 2:20

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል። በሰራዊት ጌታ በያህዌ ቀን የሚሆነውን በተመለከተ ገለጻ መስጠቱን ቀጥሏል። (ኢሳይያስ 2፥12)

ለፍልፈልና ለሌሊት ወፍ
ፍልፈል መሬት ቆፍሮ ውስጥ የሚኖር ትንሽ እንሰሳ ነው። የሌሊት ወፍ አንዳንዴ ዋሻ ውስጥ የሚኖር ትንሽ በራሪ ፍጥረት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለእንስሳት››

ወደ ድንጋይ ዋሻ... ወደ ዐለት ስንጣቂ
ቋንቋህ፣ ‹‹ዋሻ›› እና፣ ‹‹ስንጣቂ›› የሚሉ ቃሎች ከሌሉት ሁለቱን ሐረጎች እንደ አንድ ቃል ልትጠቀምባቸው ትችላለህ።

ከያህዌ አስፈሪነት
ያህዌን በጣም በመፍራታቸው። ኢሳይያስ 2፥19 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

የግርማው ክብር
‹‹የንጉሥነት ታላቅ ውበትና ኀይሉ›› ወይም፣ ‹‹የንጉሥነት ግርማው›› ኢሳይያስ 2፥10 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

ምድርን ለማስፈራት ሲነሣ
‹‹ያህዌ ለተግባር ሲነሣና የምድር ሰዎች እንዲፈሩት ሲያደርግ›› ኢሳይያስ 2፥19 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

እስትንፋሱ በአፍንጫው ላይ ባለች
ለመኖር መተንፈስ እንዳለበት በማሳየት የሰው ልጅ ምን ያህል ዐቅመቢስና ደካማ መሆኑን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ደካማና ሟች የሆነውን›› ወይም፣ ‹‹ለመኖር በአፍንጫው መተንፈስ የሚያስፈልገውን››

አፍንጫ
ሰዎች የሚተነፍሱባቸው አፍንጫ ላይ ያሉ ቀዳዶች

ከቶ ምን የሚበጅ ነገር አለው?
ኢሳይያስ ጥያቄውን የሚያቀርበው ቀድሞውኑ የሚያውቁትን ለሰዎች ለማሳሰብ ነው። ጥያቄውን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰው ምንም ማለት አይደለም›› ወይም፣ ‹‹ሰው ምንም ዋጋ የለውም››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 ተመልከቱ፣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ከኢየሩሳሌምና ከይሁዳ ድጋፍንና ብርታትን፡ የእንጀራን ድጋፍ ሁሉ የውኃውንም ድጋፍ ሁሉ ይወስዳል፤ 2 ኃያሉንም፣
ተዋጊውንም፣ ፈራጁንም፣ ነቢዩንም፣ ምዋርተኛውንም፣ ሽማግሌውንም፤ 3 የአምሳ አለቃውንም፣ ከበርቴ የሆነውን ዜጋ፣ አማካሪውንም፣ የብልኃት ሠራተኛውንም፣
አስማት አዋቂውንም ይነቅላል። 4 "አለቆቻቸው እንዲሆኑ ተራ ወጣቶችን አስነሣባቸዋለሁ፣ ብላቴናውም ይገዛቸዋል። 5 ሕዝቡም ይጨቆናሉ፣ ሰው በሰው ላይ፣
ሰውም በባልንጀራው ላይ ይገፋፋል፤ ብላቴናውም በሽማግሌው ላይ የተጠቃውም በከበርቴው ላይ ይኰራል። 6 ሰውም በአባቱ ቤት ውስጥ ወንድሙን ይዞ፣
'አንተ ልብስ አለህ፤ አለቃም ሁንልን፣ ይህችም ባድማ ከኃላፊነትህ በታች ትሁን' ይለዋል። 7 በዚያ ቀን ድምፁን ከፍ አድርጎ እንዲህ ይላል፣ 'እኔ በቤቴ ውስጥ
እንጀራ ወይም ልብስ የለኝምና ባለ መድኃኒት አልሆንም። በሕዝቡም ላይ አለቃ አታደርጉኝም" ይላል። 8 ንጉሣዊ ሥልጣኑን ያረክሱ ዘንድ ንግግራቸውና
ሥራቸው በእግዚአብሔር ላይ ነውና ኢየሩሳሌም ተፈታች ይሁዳም ወደቀ። 9 የፊታቸውም እፍረት ይመሰክርባቸዋል፤ እንደ ሰዶምም ኃጢአታቸውን ያወራሉ፤
አይሠውሩአትም። በራሳቸው ላይ ጥፋትን ሠርተዋልና ለነፍሳቸው ወዮ! 10 የሥራውን ፍሬ ይበላልና፣ ጻድቁን መልካም ይሆንልሃል በሉት። 11 እንደ እጁ ሥራ
ፍዳው ይደረግበታልና ለበደለኛ ወዮ! ክፉም ደርሶበታል። 12 ሕዝቤን አስገባሪዎቻቸው ይገፉአቸዋል፣ ሴቶችም ይሠለጥኑባቸዋል። ሕዝቤ ሆይ፣ መሪዎቻችሁ
ያስቱአችኋል የምትሄዱበትንም መንገድ አቅጣጫ ያጠፋሉ። 13 እግዚአብሔር በፍርድ ቤት ሊፈርድ ተነሥቶአል፣ በሕዝቡም ላይ ሊፈርድ ቆሞአል። 14
እግዚአብሔር ከሕዝቡ ሽማግሌዎችና ከአለቆቻቸው ጋር ይፋረዳል፡ "የወይኑን ቦታ የበላችሁ እናንተ ናችሁ፤ ከድሆች የበዘበዛችሁት በቤታችሁ አለ፤ 15
ሕዝቤንስ ለምን ታደቅቁአቸዋላችሁ? የድሆችንስ ፊት ለምን ትፈጫላችሁ?" ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር። 16 ደግሞም እግዚአብሔር እንዲህ አለ፣
የጽዮን ቈነጃጅት ኰርተዋልና፣ አንገታቸውንም እያሰገጉ በዓይናቸውም እያጣቀሱ፣ ፈንጠርም እያሉ፣ በእግራቸውም እያቃጨሉ ይሄዳሉ። 17 ስለዚህ ጌታ
የጽዮንን ቈነጃጅት አናት በበሽታ ቡሀነት ይመታል፣ እግዚአብሔርም መላጣ ያደርጋቸዋል። 18 በዚያም ቀን ጌታ የእግር አልቦውን ክብር፣ መርበብንም፣ ጨረቃ
የሚመስለውንም ጌጥ፣ 19 የጆሮ እንጥልጥሉንም፣ አንባሩንም፣ መሸፈኛውንም፣ 20 ቀጸላውንም፣ የቁርጭምጭሚት ሰንሰለቱንም፣ መቀነቱንም፣ የሽቱውንም
ዕቃ። 21 አሸንክታቡንም፣ የእጅና የአፍንጫ ቀለበቱንም ያስወግዳል፤ 22 የዓመት በዓል ልብሶችን፣ መጐናጸፊያውንም፣ መሸፈኛውንም፣ ከረጢቱንም፤ 23 የእጅ
መስተዋቱንም፣ ከጥሩ በፍታ የተሰራውንም ልብስ፣ ራስ ማሰሪያውንም፣ ዓይነ ርግቡንም ያስወግዳል። 24 በሽቱ ፋንታ ግማት፣ በመታጠቂያውም ፋንታ ገመድ፣
ጠጕርንም በመንቀስ ፋንታ ቡሀነት፣ በመጐናጸፊያ ፋንታ ማቅ፣ በውበትም ፋንታ ጠባሳ ይሆናል። 25 ጕልማሶችሽ በሰይፍ፣ ኃያላንሽም በውጊያ ይወድቃሉ። 26
በሮችዋ ያዝናሉ ያለቅሱማል፤ እርስዋም ብቻዋን በምድር ላይ ትቀመጣለች።

Isaiah 3:1

እነሆ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እነሆ›› ለሚከተለው አጽንዖት ይሰጣል። ‹‹ተመልከቱ›› ወይም፣ ‹‹በእርግጥ›› ተብሎ ሊተረጐምም ይችላል።

ድጋፍና ርዳታ
ሁለቱም የሚያመለክቱት ሰዎች የሚደገፉበትን ምርኩዝ ነው። እዚህ ላይ የሚያመለክተው በሕይወት ለመኖር ሰዎች በጣም የሚፈልጉትን ነገር እህልና ውሃን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ድጋፍ የሚሆናችሁን ነገር ሁሉ›› ወይም፣ ‹‹የምትተማመኑበትን ነገር ሁሉ››

ጀግናው... ብልኑልና አስማተኛውን
ይህ አንዳንድ ሰዎች የሚደገፉባቸው ነገሮች ዝርዝር ነው። ስለ የትኛውም ዐይነት ግለሰብ እንደ ተነገረ ስለሚያመለክቱ UDB ላይ እንዳለው በብዙ ቁጥር መተርጐም አለበት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ተዋጊ ሰዎች... ብልኅ አስማተኞች››

ጥንቆላ የሚለማመድ
ይህ የእንስሳትን አካል ክፍሎች ወይም ቅጠሎችን የመሳሰሉ ነገሮች በማየት የወደ ፊቱን መናገር እችላለሁ የሚል ሰው ነው። ኢሳይያስ 2፥6 ላይ ያለውን ተመሳሳይ ቃል እንዴት እንደ ተረጐመኸው ተመልከት።

የአምሳ አለቃው
ይህ የሚከተለውን ማለት ሊሆን ይችላል። 1) ‹‹አምሳ›› የሚለው ቃል ሰውየው የሚመራቸውን ሰዎች ቁጥር ያመለክት ይሆናል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የ50 ወታደሮች አለቃ›› ወይም 2) ‹‹አምሳ›› ተብሎ የተተረጐመው ቃል የአነስተኛ ወታደራዊ ምድብ ስም እንጂ፣ ትክክለኛ ቁጥርን አይወክልም። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የአነስተኛ ወታደራዊ ምድብ ጎላፊ››

አምሳ
50

Isaiah 3:4

ልጆችን መሪዎች አደርጋለሁ፤ ያልበሰሉ ሕፃናትም ይገዟቸዋል
እነዚህ ሐረጐች በመሠረታዊ ደረጃ ተመሳሳይ ትርጒም አላቸው። የሚከተለው ትርጒም ሊኖራቸውም ይችላል፤ 1) ‹‹ልጆችን መሪዎቻቸው አደርጋለሁ፤ ለጋ ወጣቶችም ይገዟቸዋል›› ወይም 2) ‹‹ለጋ ወጣቶች›› ተራና አላዋቂ ሰዎች ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያልበሰሉ መሪዎች በላያቸው እሾማለሁ፤ ለጋ ወጣቶችና መጥፎ መሪዎች ይገዟቸዋል››

አደርጋለሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እኔ›› የሚለው ቃል ያህዌን ያመለክታል። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ›› እንዲህ ይላል፣ ‹‹እኔ አደርጋለሁ››

ሕዝቡ እርስ በርሱ ይጨቋቈናል፤ ሰውም በባልንጀራው ላይ ይነሣል
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰዎች እርስ በርስ ይጨካከናሉ፤ በባልንጀራቸውም ላይ ግፍ ይፈጽማሉ››

ተራው ሰው
‹‹ክብር የሌለው›› ወይም፣ ‹‹ሰዎች የማያከብሩት››

የተከበረ ሰው
‹‹ክብር ያለው›› ወይም፣ ‹‹ሰዎች የሚያከብሩት››

Isaiah 3:6

ይህን ፍርስራሽ በእጅህ አድርግ
‹‹እጅ›› ሥልጣንን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በዚህ ፍርስራሽ ላይ ኀላፊ ሁን›› ወይም፣ ‹‹በዚህ ፍርስራሽ ላይ ግዛ››

ይህን ፍርስራሽ
ይህ ማለት የሚከተሉትን ማለት ሊሆን ይችላል፤ 1) ብዙዎቹ የኢየሩሳሌም ሕንፃዎች ፈራርሰው ነበር። ወይም 2) የኢየሩሳሌም ሰዎች ሀብት ወይም መሪ አልነበራቸውም። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አሁን የፈረሰው ይህ ከተማ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ፈዋሽ አልሆንም
የሰዎችን ችግር መፍታት እነርሱን መፈወስ እንደ ሆነ ተነግሮአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በፍጹም፤ እኔ ይህን ችግር መፍታት አልችልም›› ወይም፣ ‹‹የለም፤ እኔ ልረዳችሁ አልችልም››

Isaiah 3:8

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ነቢዩ በዚህ ሁኔታ ላይ ሐሳብ መስጠት ቀጥሏል።

ኢየሩሳሌም ተሰናከለች፤ ይሁዳም ወደቀች
ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ ተሰናክሎ መውደቅ እንደሆነ ተነግሯል።

የክብሩ ዐይን
‹‹ዐይን›› ክቡር የሆነውን ራሱ እግዚአብሔርን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ክቡር የሆነው እርሱ›› ወይም፣ ‹‹ክቡር የሆነው ያህዌ››

የፊታቸው ገጽታ ይመሰክርባቸዋል
ሰዎች ፊት ላይ የሚታየው እብሪት፣ የሰዎቹን ኩራት እንደሚመሰክርባቸው ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ፊታቸው ላይ የሚታየው እብሪት ያህዌን እንደሚቃወሙ ያሳያል››

ኀጢአታቸውን እንደ ሰዶም በይፋ ይናገራሉ፤ አይደብቁትምም
በኀጢአታቸው ስለሚኩራሩ እዚህ ላይ የይሁዳ ሰዎች እንደ ሰዶም ሰዎች መሆናቸው ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ሰዶም ሰዎች ሰው ሁሉ እንዲያውቅላቸው ስለ ኀጢአታቸው ያወራሉ››

ጥፋትን በራሳቸው ላይ ያመጣሉ
አሁንም ቢሆን ጥፋት እየመጣ ነው፤ ሕዝቡ ግን እንዲመጣ ጥፋት የሚያደርገውን ሁሉ አድርገው ጨርሰዋል። የጥፋቱ መምጣት ምክንያት ራሱ ጥፋቱ እንደ ሆነ እዚህ ላይ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጥፋት እንዲመጣ ምክንያት የሆነውን ሁሉ አድርገው ጨርሰዋል››

Isaiah 3:10

ጻድቃን መልካም ነገር እንደሚያገኙ ንገራቸው
‹‹ተገቢ የሆነውን ለሚያደርጉ እኔ መልካም ነገር እንደማደርግላቸው ንገራቸው››

ጻድቃን ሰዎች
ይህ በአጠቃላይ ጻድቃን ሰዎችን ይመለከታል፤ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጻድቃን የሆኑ ሰዎች››

የሥራቸውን ፍሬ ይበላሉና
ሥራ ሰዎች የሚበሉት ፍሬ የሚያፈሩ ዛፎች መሆናቸው ተነግሯል። ፍሬ የመልካም ሥራ ሽልማትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የመልካም ሥራቸውን ሽልማት ይቀበላሉና›› ወይም፣ ‹‹ስላደረጉት መልካም ሥራ ሽልማት ይቀበላሉ››

የሥራቸውን ፍሬ ይበላሉና
የዕብራይስጡ ምንባብ እዚህ ላይ በብዙ ቁጥር በሚያመለክት ተውላጠ ስም ይናገራል፤ ይሁን እንጂ ማንኛውንም ጻድቅ ሰው ይመለከታል። ተርጓሚዎች በነጠላ ቁጥር መተርጐም ይችላሉ፦ ‹‹የሥራውን ፍሬ ይበላል››

የእጁን ያገኛል
እዚህ ላይ ‹‹እጅ›› ሰው የሚያደርገውን ሥራ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ክፉ ሰው ሌሎች ላይ እንደሚያደርገው ይደረግበታል።››

ሕዝቤ... ሕዝቤ
ይህም ማለት 1) ኢሳይያስ እየተናገረ ነው፤ ‹‹የእኔ›› የሚለው የሚያመለክተው ኢሳይያስን ነው፤ ወይም 2) ያህዌ እየተናገረ ነው፤ ‹‹የእኔ›› የሚለው የሚያመለክተው ያህዌን ነው።

ልጆች ጨቋኞቻቸው ናቸው
ይህም ማለት 1) ‹‹ወጣቶች መሪዎቻቸው ሆኑ፤ እነርሱም ሕዝቡን ይጨቁናሉ›› ወይም 2) ‹‹መሪዎቻቸው እንደ ልጆች ያልበሰሉ ናቸው። ሕዝቡንም ይጨቁናሉ››

ሴቶችም ይገዟቸዋል
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ሴቶች ሕዝቡን ይገዛሉ›› ወይም 2) ‹‹መሪዎቻቸው እንደ ሴቶች ደካሞች ናቸው››

መሪዎችህ አሳስተውሃል፤ ከመንገድም መልሰውሃል
በጥንታዊው መካከለኛው ምሥራቅ የሕዝብ መሪዎች እረኞች እንደ ሆኑ መናገር የተለመደ ነበር። እረኞች በጐቹን ለመመገብ በመልካም መንገድ ወደ ደህና ቦታ እንደሚመሩ፤ መሪዎችም ሕዝቡን እውነቱን ማስተማርና መልካም እንዲያደርጉ ማስተማር ይኖባቸዋል። የይሁዳ መሪዎች ይህን እያደረጉ አልነበረም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መሪዎችህ ከመልካም መንገድ የሚመልሱህ መጥፎ እረኞች ናቸው፤ ወዴት መሄድ እንዳለብህም አላሳዩህም››

Isaiah 3:13

ያህዌ ለክስ ተነሥቶአል፤ ሕዝቡን ለመክሰስ ተነሥቶአል
ያህዌ እስራኤልን ላይ ክስ ለማቅረብ ወደ ፍርድ ቤት የሄደ ይመስል፣ ኢሳይያስ ያህዌ ሕዝቡን ለመጉዳት ያሳለፈውን ውሳኔ ያመለክታል። የዚህ መስመር ሁለተኛው ክፍል ከመጀመሪያው ጋር ተመሳሳይ ነው፤ የተደገመው አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ፍርድ ቤት ውስጥ ያህዌ ቦታውን ይዞአል፤ ሕዝቡን ለመክሰስም ተዘጋጅቶአል››

ከፍርድ ጋር ይመጣል
ፍርድ ሰው ይዞት የሚመጣ አንዳች ነገር እንደሆነ ተመልክቷል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ፍርድን ያውጃል›› ወይም፣ ‹‹ፍርድን ይናገራል››

የወይኑን እርሻ አጥፍታችኃል
‹‹እናንተ›› የሚያመለክተው ሽማግሌዎቹንና መሪዎቹን ነው። ሕዝቡ የወይን እርሻ እንደሆኑ ያህዌ ይናገራል። የወይን እርሻው ፍሬ እንዳይሰጥ እርሻውን እንደማይንከባከብ ሰው ሽማግሌዎቹና መሪዎቹም እስራኤላውያን እግዚአብሔርን እንዳያገለግሉ አድርገዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕዝቤ የወይን እርሻ ነው፤ እናንተ ግን አጠፋችሁት››

ከድኾች የዘረፋችሁ በቤታችሁ አለ
‹‹ከድኾች የወሰዳችሁት ንብረት ቤታችሁ ውስጥ አለ››

ድኾች
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ድኾች የሆኑ ሰዎች››

ሕዝቤን ለምን ትረግጣላችሁ፤ የድኾችንም ፊት ለምን ታደቅቃላችሁ?
ያህዌ ይህን የሚጠይቀው የሕዝቡን መሪዎች ለመክሰስ ነው። ይህን ክስ በዐረፍተ ነገር መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕዝቤን ስለምትረግጡ፣ የድኾችንም ፊት ስለምታደቅቁ ክፉዎች ሆይ፣ በእናንተ ላይ ተቆጥቻለሁ››

ሕዝቤን የምትረግጡ
ሰዎችን ማሰቃየት ከባድ ሸክም እነርሱ ላይ መጣል እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጭካኔ ሕዝቤን የጐዳችሁ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የድኾችን ፊት የምታደቅቁ
ሰዎችን ማሰቃየት ፊታቸውን መሬት ላይ መፈግፈግ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ድኾችን የምትጐዱና የምታሰቃዩ››

የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
የሚናገረውን እርግጠኝነት ለማሳየት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሰራዊት ጌታ ያህዌ የሚለው ይህን ነው›› ወይም፣ ‹‹እኔ የሰራዊት ጌታ ያህዌ ይህን ብያለሁ››

Isaiah 3:16

የጽዮን ሴት ልጆች
እዚህ ላይ፣ ጽዮን የኢየሩሳሌም ከተማ ስትሆን፣ የራሷ ሴት ልጆች እንዳላት ሴት ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የጽዮን ሴት ልጆች››

ዐንገታቸውን እያሰገጉ
‹‹እብሪት በሚያሳይ መንገድ››

በዐይናቸውም እየጠቀሱ
ሴቶቹ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ እንደ ፈለጉ እንዲያስቡ ለማድረግ ወንዶችን ማየት።

እየተቄነኑ በመራመድ
ወንዶችን ለመማረክ በዚህ ሁኔታ ይራመዳሉ፤ ምናልባትም ቁርጭምጭሚታቸው ላይ ያለው የእግር አልቦ ከቃጭል ጋር በጌጠኛ ሰንሰለት የተያያዘ በመሆኑ በተለመደው ሁኔታ እንዳይራመዱ አድርጓቸው ይሆናሉ።

Isaiah 3:18

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ክፍል ያህዌ በእንዴት ያለ ሁኔታ የኢየሩሳሌምን ሴቶች እንደሚቀጣ መናገሩን ይቀጥላል።

ጌታ ይነጥቃቸዋል
ጌታ ሌሎች እንዲያደርጉ የሚያነሣሣው እርሱ የሚያደርገው እንደ ሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጌታ ሌሎች እንዲነጥቋቸው ያደርጋል››

የእግር ዐልቦ
ከእግር ከፍ ብሎ ቁርጭምጭሚታቸው ላይ ሴቶች የሚያደርጉት ጌጥ።

የራስ መሸፈኛ
ሴቶች ራሳቸውና ጠጉራቸው ላይ የሚያደርጉት ጌጥ

የጨረቃ ቅርጽ ያለው የዐንገት ጌጥ
ሰዎችን ከክፉ ነገር ያድናል ብሎ በማሰብ ዐንገት ላይ የሚጠለቅ ባለ ጨረቃ ቅርጽ ጌጥ

የጆሮ ጉትቻ
ጆሮ ላይ የሚንጠለጠል ጌጥ

የእጅ አንባር
ሴቶች እጆቻቸው ላይ የሚያደርጉት ጌጥ

የፊት መሸፈኛ
የሴት ልጅን ፊትና ራስ የሚሸፍን በጣም ስስ ልብስ

የራስ መሸፈኛ
ሴቶች ራሳቸው ወይም ጠጉራቸው ላይ የሚያስሩት ረጅም ስስ ጨርቅ

ዐልቦ
ይህ ሴቶች ቁርጭምጭሚታቸው ላይ የሚያደርጉት ጌጥ ነው። ብዙውን ጊዜ ደስ የሚል ድምፅ እንዲኖረው ሰንሰለት ይንጠለጠልበታል።

ሻሽ
ሰዎች ወገባቸው ላይ የሚያደርጉት ጨርቅ

የሽቶ ብልቃጥ
መልካም ሽታ እንዲኖራቸው ሴቶች የሚቀቡት፣ በሰንሰለት ወይም በክር አንገታቸው ላይ የሚያንጠለጥሉት ብልቃጥ ወይም መያዣ

አሸንክታቡን
መልካም ዕድል እንዲያመጣ በማመን ሰዎች የሚያንጠለጥሉት ጌጥ

Isaiah 3:21

ቀለበቶች
ጣት ላይ የሚደረጉ ጌጣ ጌጦች

የአፍንጫ ቀለበቶች
አፍንጫ ላይ የሚደረጉ ጌጣ ጌጦች

ያማረውን ቀሚስ
ሰው ሁሉ እንዲያየው ከሌሎች ልብሶች በላይ የሚለበስ ረጅምና ሰፊ ባለ ጌጥ ቀሚስ

ካባውን
ከሌሎች ልብሶች በላይ ትከሻ ላይ የሚደረግ ልብስ

መሸፈኛውን
ኢሳይያስ 3፥19 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

የእጅ ቦርሳውን
ትንንሽ ነገሮች የሚይዙበት ቦርሳ

የእጅ መስታወት
በእጅ የሚያዝና ራስን ለማየት የሚያገለግል ትንሽ መስታወት

ጥሩ በፍታ
ሀብታዎች የሚለብሱት ስስ ልብስ

የራስ ጌጥ
ጠጉር ላይ የሚደረግ ልብስ ወይም ትንሽ ባርኔጣ

መጠምጠሚያውን
ውበት እንዲሰጣት ሴት ልጅ ላዩዋ ላይ የምትጠመጥመው ልብስ

Isaiah 3:24

ሻሽ
ሰዎች ወገባቸው ወይም ደረታቸው ላይ የሚለብሱት ልብስ። ኢሳይያስ 3፥20 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

ገመድ
ይህ የሚያመለክተው እነርሱን ሲይዟቸው ጠላቶቻቸው የይሁዳን ሰዎች የሚያስሩበትን ገመድ ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ የኢየሩሳሌም ሴቶች በገመድ የሚታሰር ተራ ልብስ እንጂ፣ ሌላ ምንም የሚለብሱት እንደማይኖራቸው የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።

አምሮ በተሠራ ጠጉር ፈንታ ቡሀነት
‹‹ያመረ ጠጉር ቢኖራቸውም መላጣ ይሆናሉ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወንዶቻችሁ በሰይፍ፣ ይወድቃሉ ተዋጊዎቻችሁም በጦርነት ይወድቃሉ
መውደቅ መገደልን፣ ሰይፍ ጦርነትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ወንዶቻችሁ በጦርነት ይገደላሉ፤ ተዋጊዎቻችሁ በውጊያ ይገደላሉ›› ወይም፣ ‹‹ጠላቶች ወታደሮቻችሁን በጦርነት ይገድሏቸዋል››

የኢየሩሳሌም ደጆች ያዝናሉ ያለቅሳሉ
እዚህ ላይ የከተማው ደጆች ከተማው ደጃፍ ላይ አደባባይ የሚቀመጡ ሰዎችን ይወክላሉ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የኢየሩሳሌም ሰዎች ከተማው በሮች ላይ ተቀምጠው ያዝናሉ ያለቅሳሉ››

ብቻዋን ትሆናለች መሬት ላይ ትቀመጣለች
ኢሳይያስ የኢየሩሳሌም ሕዝብ ከጠላቶቿ የሚያድናት ሰው እንደሌላትና ወዳጆቿ ሁሉ ስለ ተውአት መሬት ላይ ተቀምጣ እንደምታለቅስ ሴት መሆናቸውን ይናገራል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 በዚያም ቀን ሰባት ሴቶች "የገዛ እንጀራችንን እንበላለን የገዛ ልብሳችንንም እንለብሳለን፤ ስምህ ብቻ በእኛ ላይ ይጠራ፥ ውርደታችንንም አርቅ" ብለው አንዱን ወንድ ይይዙታል። **2** በዚያም ቀን የእግዚአብሔር ቍጥቋጥ ውብና የከበረ ይሆናል፣ ከእስራኤልም ወገን ላመለጡ ሰዎች የምድሪቱን ፍሬ ለትምክሕትና ለውበት ይሆናል። **3** ከዚያም፣ ጌታ የጽዮንን ቈነጃጅት እድፍ ባጠበ ጊዜ፣ የኢየሩሳሌምንም ደም በፍርድ መንፈስና በሚያቃጥል መንፈስ ከመካከልዋ ባነጻ ጊዜ፣ **4** በጽዮን የቀረ በኢየሩሳሌምም የተረፈ፣ በኢየሩሳሌም ለሕይወት የተጻፈ ሁሉ፣ ቅዱስ ይባላል። **5** እግዚአብሔርም በጽዮን ተራራ ላይ ባለ ማደሪያ ሁሉ በጉባኤያቸውም ላይ፣ በቀን ዳመናንና ጢስን፣ በሌሊትም የሚቃጠለውን የእሳት ብርሃን ይፈጥራል፤ በክብርም ሁሉ ላይ መጋረጃ ይሆናል። **6** በቀን ከሙቀት ለጥላ፣ ከዐውሎ ነፋስና ከዝናብም ለመጠጊያና ለመሸሸጊያ ጎጆ ይሆናል።

Isaiah 4:1

በስምህ ብቻ እንጠራ
ይህ ሐረግ፣ ‹‹እናግባህ›› ማለት ነው።

የያህዌ ዛፍ ቅርንጫፍ ያማረ ይሆናል
ይህም ማለት 1) ‹‹ቅርንጫፍ›› ያህዌ በእስራኤል ምድር የሚያበቅለው እህል የሚወክል ቃል ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ የእስራኤልን እህል ያማረ ያደርጋል›› ወይም 2) ‹‹ቅርንጫፍ›› መሲሑን የሚመለከት ሊሆን ይችላል።

ያማረና የከበረ ይሆናል
‹‹ውበትና ክብር ይኖረዋል››

የምድሪቱ ፍሬ ከጥፋት ለተረፈው የእስራኤል ሕዝብ ጣፋጭና ደስ የሚያሰኝ ይሆናል
አንዳንዴ፣ ‹‹ፍሬ›› በምድሪቱ የሚገኝ ምግብን ይወክላል፤ አንዳንዴ መንፈሳዊ ባርኮትን ይወክላል። እዚህ ላይ የሚከተሉን ማለት ሊሆን ይችላል። 1) እግዚአብሔር ምድሪቱ እንደ ገና መልካም ምግብ እንድታበቅል ያደርጋል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በእስራኤል ያሉ ሰዎች የምድሪቱን መልካም ነገር ይበላሉ›› ወይም 2) ወደ ፊት የሚመጣው መሲሕ በምድሪቱ ላሉ ሰዎች መንፈሳዊ በረከት ይዞላቸው ይመጣል።

Isaiah 4:3

በጽዮን የቀሩት፤ በኢየሩሳሌም የተረፉት
ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች አንድ ትርጒም ነው ያላቸው። እዚህ ላይ፣ ‹‹የተረፉት›› ሲል ግለ ሰብን ሳይሆን በኢየሩሳሌም በሕይወት ያሉትን ሁሉ ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በኢየሩሳሌም የሚቀር ሁሉ››

ቅዱሳን ተብለው ይጠራሉ
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጌታ ቅዱሳን በማለት ይጠራቸዋል›› ወይም፣ ‹‹የጌታ ይሆናሉ››

በኢየሩሳሌም በሕይወት ከተመዘገቡት ሁሉ
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ስሙ በኢየሩሳሌም ነዋሪዎች መዝገብ ያለ ሰው ሁሉ››

ጌታ የጽዮንን ሴቶች እድፍ ሲያጥብ
ይህ አባባል ጎጢአት እንደሚታጠብ እድፍ እንደ ሆነ ይናገራል፤ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጌታ እድፍ እንደሚያጠራ፣ የጽዮንን ሴቶች ጎጢአት ካጠበ በኋላ››

የጽዮን ሴቶች
ይህ ማለት፣ 1) የኢየሩሳሌም ሴቶች፤ ወይም 2) የኢየሩሳሌም ሕዝብ ማለት ሊሆን ይችላል።

ኢየሩሳሌምን ከተነከረችበት ደም ያነጻታል
‹‹የተነከረችበት ደም›› የሚያመለክተው ግፍንና ግድያን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ንጹሐንን የሚጐዱ የኢየሩሳሌምን ሰዎች ያስወግዳል››

በፍርድና መንፈስና በሚያቃጥል መንፈስ
እግዚአብሔር የኢየሩሳሌምን ጎጢአት የሚያስወግደው በዚህ መንገድ ነው። እዚህ ላይ፣ ‹‹መንፈስ›› የፍርድና የማቃጠልን እንቅስቃሴ የሚወክል ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በፍርድና በእሳት ነበልባል››

የፍርድ መንፈስ
ይህም ማለት 1) ያህዌ ሕዝቡን ይቀጣል፤ ወይም 2) ያህዌ ሕዝቡን በደለኛ ያደርጋል ማለት ሊሆን ይችላል።

በሚያቃጥል መንፈስ
ይህም ማለት 1) አንዳች ርኩስ ነገርን እንደሚስወግድ ያህዌ ጎጢአተኞችን ከጽዮን ያስወግዳል ማለት ሊሆን ይችላል፤ ወይም 2) ‹‹የሚያቃጥል እሳት›› የጎጢአተኞችን ሁሉ መደምሰስ ሊያመለክት ይችላል።

Isaiah 4:5

በክብሩ ሁሉ ላይ መጋረጃ
ይህም ማለት 1) የከበረችውን ከተማ የሚጋርድ መጋረጃ፤ ወይም 2) ከተማዋን የሚጋርድ መጋረጃን የያዘ የእግዚአብሔር ክብር ማለት ሊሆን ይችላል። የመጀመሪያውን ትርጒም ከያዝን ያህዌ በውስጧ ስለሚኖር ከተማዋ የከበረች ትሆናለች ማለት ነው።

መጋረጃ
ለመከለያ እንዲሆን አንዳች ነገር ላይ የተሰቀለ ጨርቅ ነው።

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 5

1 አሁን ስለ ወዳጄና ስለ ወይን ቦታው ለወዳጄ ቅኔ እቀኛለሁ። ለወዳጄ በለመለመው ኮረብታ ላይ የወይን ቦታ ነበረው። **2** በዙሪያው ቈፈረ፣ ድንጋዮችንም ለቅሞ አወጣ፣ ምርጥ የሆነውንም ወይን ተከለበት። በመካከሉም ግንብ ሠራ፣ ደግሞም የመጥመቂያ ጕድጓድ ማሰበት። ወይንንም ያፈራ ዘንድ ጠበቀ፣ ዳሩ ግን ሆምጣጣ ፍሬ አፈራ። **3** ስለዚህ አሁን፣ እናንተ በኢየሩሳሌም የምትኖሩ የይሁዳ ሰዎች ሆይ፤ በእኔና በወይኑ ቦታዬ መካከል ፍረዱ። **4** ለወይኔ ያላደረግሁለት፥ ከዚህ በተጨማሪ አደርግለት ዘንድ የሚገባኝ ምንድር ነው? መልካም ወይንን ያፈራል ብዬ ስትማመን፣ ስለ ምን ሆምጣጣ ፍሬ አፈራ? **5** አሁንም በወይኔ ላይ የማደርገውን አስታውቃችኋለሁ፤ አጥሩን እነቅላለሁ፤ ለማሰማርያም ይሆናል፤ ቅጥሩንም አፈርሳለሁ፣ ለመራገጫም ይሆናል። **6** ባድማ አደርገዋለሁ፤ አይቈረጥም፣ አይኰተኰትም፤ ኵርንችትና እሾህ ይበቅልበታል፤ ዝናብንም እንዳያዘንቡበት ዳመናዎችን አዝዛለሁ። **7** የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር ወይን ቦታ እርሱ የእስራኤል ቤት ነው፣ የደስታውም አትክልት የይሁዳ ሰዎች ናቸው፤ ፍርድን ይጠብቅ ነበር፣ እነሆም ግድያ ሆነ፤ ጽድቅንም ይተማመን ነበር፣ ይልቅ እርዳታ የሚለምን ጩኸት ሆነ። **8** ስፍራ እስከማይቀር ድረስ እናንተም በምድር ላይ ብቻችሁን እስክትቀመጡ ድረስ፣ ቤትን ከቤት ጋር ለሚያያይዙ እርሻንም ከእርሻ ጋር ለሚያቀራርቡ ወዮላቸው! **9** የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ፣ ታላላቆቹና መልካም የሆኑት ቤቶች ሳይቀሩ ባድማ ይሆናሉ፣ የሚኖርባቸውም አይገኝም። **10** ከወይኑ ቦታ ዐሥር ጥማድ በሬ ካረሰው አንድ የባዶስ መስፈሪያ ብቻ ይወጣል፤ አንድ የቆሮስ መስፈሪያ ዘር አንድ የኢፍ መስፈሪያ ብቻ ይሰጣል። **11** ጠንካራ መጠጥን ለማፈላለግ በጠዋት ለሚነቍ፣ የወይን ጠጅም እስኪያቃጥላቸው እስከ ሌሊት ድረስ ለሚዘገዩ ወዮላቸው! **12** መሰንቆና በገና፣ ከበሮና እምቢልታም፣ የወይን ጠጅም በግብዣቸው አለ፤ የእግዚአብሔርን ሥራ ግን አልተመለከቱም፣ እንዲሁም እጁ ያደረገችውን አላስተዋሉም። **13** ስለዚህ ሕዝቤ ባለማወቃቸው ወደ ምርኮ ሄዱ፣ መሪዎቻቸውም ተራቡ፣ ሕዝባቸውም የሚጠጡት የላቸውም። **14** ስለዚህም ሲኦል የመዋጥ ፍላጎትዋን አስፍታለች፣ አፍዋንም ያለ ልክ ከፍታለች፤ ከበርቴዎቻቸውና አዛውንቶቻቸው፣ ባለጠጎቻቸውም ደስተኞቻቸውም ወደ ሲዖል ይወርዳሉ። **15** ሰውም ይጐሰቍላል፣ ሰውም ይዋረዳል፣ የትዕቢተኞችም ዓይን ትዋረዳለች። **16** የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ግን በፍርድ ከፍ ከፍ ብሎአል፣ ቅዱሱም አምላክ በጽድቅ ተቀድሶአል። **17** የበግ ጠቦቶች በገዛ መሰማርያቸው ውስጥ፣ እንዲሁም በባለጠጋ ሰዎች ጥፋት ውስጥ ይሰማራሉ፣ ጠቦቶችም ይግጣሉ። **18** በደልን በምናምንቴ ገመድ፣ ኃጢአትንም በሰረገላ ማሰሪያ ወደ ራሳቸው ለሚስቡ፣ እናይ ዘንድ ይቸኵል፣ **19** "ሥራውንም ያፋጥን፤ እናውቃትም ዘንድ የእስራኤል ቅዱስ ምክር ትቅረብ፣ ትምጣ ለሚሉ ወዮላቸው!" **20** ክፉውን መልካም፣ መልካሙን ክፉ ለሚሉ፤ ጨለማውን ብርሃን፣ ብርሃኑንም ጨለማ ለሚያደርጉ፤ ጣፋጩን መራራ፣ መራራውንም ጣፋጭ ለሚያደርጉ ወዮላቸው! **21** በገዛ ዓይናቸው ዘንድ ጥበበኞች፣ በነፍሳቸውም አስተዋዮች ለሆኑ ወዮላቸው! **22** የወይን ጠጅ ለመጠጣት ኃያላን፣ የሚያሰክረውንም ብርቱ መጠጥ ለማደባለቅ ጨካኞች ለሆኑ፤ **23** በደለኛውን ስለ ጕቦ ጻድቅ ለሚያደርጉ፣ የጻድቁንም ጽድቅ ለሚያስወግዱበት ወዮላቸው! **24** ስለዚህ የእሳት ወላፈን ቃርሚያን እንደሚበላ፣ እብቅም በነበልባል ውስጥ እንደሚጠፋ፣ እንዲሁ የእነርሱ ሥር የበሰበሰ ይሆናል፣ ቡቃያቸውም እንደ ትቢያ ይበንናል፣ የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔርን ሕግ ገፍተዋልና፣ የእስራኤልም ቅዱስ የተናገረውን ቃል አቃልለዋልና። **25** ስለዚህ የእግዚአብሔር ቍጣ በሕዝቡ ላይ ነድዶአል፣ እጁንም በላያቸው ዘርግቶ ቀጥቷቸዋል፤ ተራሮችም ተንቀጠቀጡ፣ ሬሳቸውም በአደባባይ ላይ እንደ ጕድፍ ሆኖአል። በዚህም ሁሉ እንኳ ቍጣው አልተመለሰችም፣ ነገር ግን እጁ በድጋሚ ለመምታት ገና ተዘርግታለች። **26** ለአሕዛብም በሩቅ ምልክትን ያቆማል፣ ከምድርም ዳርቻ በፉጨት ይጠራቸዋል። ተመልከቱ፣ እየተጣደፉ ፈጥነው ይመጣሉ። **27** በመካከላቸው ደካማና ስንኩል የለባቸውም፣ የሚያንቀላፋና የሚተኛም የለም፤ የወገባቸውም መቀነት አይፈታም፣ የጫማቸውም ማሰሪያ አይበጠስም፤ **28** ፍላጻቻቸው ተስለዋል፣ ቀስቶቻቸውም ሁሉ ተለጥጠዋል፤ የፈረሶቻቸውም ኮቴ እንደ ቡላድ፣ የሰረገሎቻቸውም መንኰራኵር እንደ ዐውሎ ነፋስ ነው። **29** ጩኸታቸው እንደ አንበሳ ነው፣ እንደ አንበሳ ደቦሎችም ያገሣሉ። ንጥቂያንም ይዘው ያገሣሉ፣ ይወስዱትማል፣ የሚታደግም የለም። **30** በዚያም ቀን እንደ ባሕር መትመም ይተምሙባቸዋል፤ ወደ ምድርም ቢመለከቱ፣ ጨለማና መከራ ይመለከታል፤ ብርሃንም በደመናዎችዋ ውስጥ ጨልሞአል።

Isaiah 5:1

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ስለ ገበሬውና ስለ ወይን እርሻው ምሳሌ ይናገራል። ገበሬው ያህዌን፣ የወይን እርሻው ደቡባዊውን የእስራኤል መንግሥት የይሁዳን ሕዝብ ይወክላል።

ወዳጄ
‹‹በጣም የምወደው››

በለመለመ ኮረብታ
‹‹መልካም ፍሬ በሚገኝበት ኮረብታ ላይ››

መሬቱን ቈፈረ
‹‹አፈሩን አዘጋጀ›› ይህ ለተክል ምቹ ለማድረግ መሬቱን በመቆፈሪያ መቆፈርን ያመለክታል።

በመካከሉ ማማ ሠራ
‹‹ላዩ ላይ ሆኖ ለመጠበቅ በመካከሉ ረጅም ግንብ ሠራ›› የወይን እርሻውን ለመጠበቅ አንድ ሰው ማማው ጫፍ ላይ ሆኖ ሰዎች ወይም እንስሳት ወደዚያ እንዳይገቡ ይከላከላል። ይህን ዐረፍተ ነገር የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል።

የወይን መጭመቂያ ጉድጓድም አበጀ
‹‹ወይኑን ለመጭመቅ ጉድጓድ ቆፈረ›› የወይን መጭመቂያ ሰዎች ወይን ፍሬውን እየረገጡ ጭማቂውን የሚያወጡበት መሬት ላይ ባለ ትልቅ ድንጋይ የተሠራ ነገር ነው።

ኮምጣጣ ፍሬ
‹‹የማይጠቅም ፍሬ›› ወይም፣ ‹‹የማይጣፍጥ ፍሬ››

Isaiah 5:3

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ስለ ወይኑ እርሻ በተናገረው ምሳሌ እግዚአብሔርን የሚወክለው ባለቤት፣ የወይን እርሻውን በተመለከተ ለኢየሩሳሌምና ለይሁዳ ሰዎች ይናገራል።

በኢየሩሳሌም የምትኖሩ የይሁዳ ሰዎች
ይህ የሚናገረው በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ለሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ነው፤ ስለዚህ በብዙ ቁጥር መናገር ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በኢየሩሳሌምና በይሁዳ የምትኖሩ ሁሉ››

ኢየሩሳሌም... ይሁዳ
‹‹ይሁዳ›› የደቡባዊው እስራኤል መንግሥት ስም ነበር፤ ዋና ከተማውም ኢየሩሳሌም ነበር።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በእኔና በወይን ቦታዬ መካከል እስቲ ፍረዱ
በሁለት ነገሮች መካከል ያለ ክፍት ቦታ ብዙውን ጊዜ ከሁለት አንዱን የመምረጥን ሐሳብ ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ማን ትክክል እንደ ነበር ፍረዱ፤ እኔ ወይስ የወይን ቦታዬ››

ከዚህ ካደረግሁለት በላይ ለወይኔ ቦታ ምን ሊደረግለት ይገባ ነበር?
ባለቤቱ ይህን ጥያቄ ያቀረበው ስለ ወይን ቦታው ጠንከር አድርጐ ለመናገር ነው። ጥያቄውን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለወይን ቦታዬ ማድረግ የምችለውን ሁሉ አድርጌአለሁ››

መልካም የወይን ፍሬ ያፈራል ብዬ ስጠብቅ ለምን ኮምጣጣ ፍሬ አፈራ?
ባለቤቱ ጥያቄውን ያቀረበው የወይን ቦታው መልካም ፍሬ ማፍራት እንደ ነበረበት ለመናገር ነው። ጥያቄውን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የፈለግሁት ጥሩ ፍሬ እንዲያፈራ ነበር፣ ግን ኮምጣጣ ፍሬ አፈራ››

Isaiah 5:5

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ባቀረበው ምሳሌ የወይኑ ቦታ ባለቤት ስለ ወይን ቦታው መናገር ቀጥሏል።

ሐረጉን እነቅላለሁ
‹‹የቁጥቋጠውን ሐረግ እነቅላለሁ›› ሐረግ መደዳውን ያለ ቁጥቋጦ ወይም የአትክልት ቦታን ወይም ሌላ ክልልን ለመጠበቅ መደዳውን የሚተከል ዛፍ ነው። እዚህ ላይ፣ ‹‹ሐረግ›› ምናልባት ወይን ቦታው ዙሪያ ባለው ግንብ ላይ የሚተከል እሾኻማ ቁጥቋጦ ሊሆን ይችላል።

የግጦሽ ቦታ እንዲሆን አደርጋለሁ
‹‹ከብቶች ገብተው የሚመገቡበት ቦታ አደርገዋለሁ›› ይህ ከብቶች የሚመገቡት ሣር የበዛበት ቦታ ነው።

መረጋገጫም ይሆናል
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከብቶች ይረጋግጡታል››

ጠፍ መሬት አደርገዋለሁ
‹‹አጠፋዋለሁ››

ከእንግዲህ አይኮተኮትም አይታረምም
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ማንም አይኮተኩተውም፤ አያርመውም›› ወይም፣ ‹‹ማንም የማያስፈልጉትን ቅርንጫፎች አይቆርጥም፤ ለአፈሩም ጥንቃቄ አያደርግም››

ኩርንችትና እሾኽም ይበቅልበታል
ብዙውን ጊዜ ኩርንችትና እሾኽ ጠፍ የሆኑ ከተሞችንና አገሮችን ለማመልከት ጥቅም ላይ ይውላሉ።

Isaiah 5:7

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ስለ ወይኑ ቦታ ገለጻ ይሰጣል

የሰራዊት ጌታ የያህዌ የወይን ቦታው የእስራኤል ቤት ነው።
ምሳሌው ውስጥ ያለው ወይን ቦታ የእስራኤልን ሕዝብ እንደሚወክል ኢሳይያስ ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሰራዊት ጌታ የያህዌ ወይን ቦታ የእስራኤልን ቤት ይወክላል›› ወይም፣ ‹‹የእስራኤል ሕዝብ የሰራዊት ጌታ የያህዌ ወይን ቦታ ናቸው››

የእስራኤል ቤት
‹‹ቤት›› — ቤቱ ውስጥ የሚኖረውን ቤተ ሰብ ያመለክታል። እዚህ ላይ የሚያመለክተው የእስራኤልን መንግሥት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እስራኤል›› ወይም፣ ‹‹የእስራኤል መንግሥት›› ወይም፣ ‹‹የእስራኤል ሕዝብ››

የይሁዳ ሰዎች የደስታው አትክልት ናቸው
የይሁዳ ሰዎች ያህዌ የተከለው ወይን ዛፍ መሆናቸው ተነግሯል። ይህን በምስስል ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የይሁዳ ሰዎች ለያህዌ ደስታ ያህዌ እንደ ተከለው ወይን ዛፍ ናቸው››

የይሁዳ ሰዎች
‹‹ሰዎች›› የሚወክለው የይሁዳን ሕዝብ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የይሁዳ ሕዝብ››

ፍትሕን ፈለገ፤ ግን ግድያ ነበረ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ፍትሕ›› የሚለውን፣ ‹‹መልካሙን ማድረግ›› ብሎ መለወጥ ይችላል። ‹‹ግድያ›› የሚለውን፣ ‹‹እርስ በርስ መገዳደል›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ ሕዝቡ መልካም ነገር እንዲያደርግ ፈለገ፤ ግን እርስ በርስ ተገዳደሉ››

ጽድቅን ፈለገ
‹‹ፈለገ›› የሚለውን በዚህ ቁጥር ከተመለከትነው መረዳት ይቻላል። ትርጒሙን የበለጠ ግልጽ ለማድረግ መደጋገም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጽድቅን ፈለገ›› ወይም፣ ‹‹መልካም የሆነውን እንዲያደርጉ ፈለገ››

ይልቁን የጭንቅ ጩኸት ነበረ
‹‹ነበረ›› የሚለውን ቀደም ሲል ከነበረው ቁጥር መረዳት ይቻላል። ትርጒሙን የበለጠ ግልጽ ለማድረግ መደጋገም ይቻላል። ሰዎች ርዳታ ለመፈለግ የጮኹበትን ምክንያት የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይችላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ይልቁን የርዳታ ጩኸት ነበረ›› ወይም፣ ‹‹ይልቁን ሌሎች ስላጠቋቸው የሚረዳቸው ሰው ፍለጋ ጩኸት ነበረ››

ጩኸት
ምናልባት ብዙ ጩኸቶችን የሚያመለክት ገለጻ ሊሆን ይችላል።

Isaiah 5:8

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ የእግዚአብሔርን ፍርድ ይናገራል

ቤትን ቤት ላይ መሬትን ከመሬት ጋር ለማያያዝ
‹‹በጣም ብዙ ቤቶችን፣ በጣም ብዙ መሬቶችን የሚወስዱ›› ለዘለቄታው ከቤተ ሰብ መሬት መውሰድን ሕጉ እንደሚከለክል ሰሚዎቹ እንደሚረዱ ኢሳይያስ ይገነዘባል። ይህን ዐረፍተ ነገር የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል።

የሰራዊት ጌታ ያህዌ
ኢሳይያስ 1፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

ወና ይቀራሉ
‹‹ማንም አይኖርባቸውም››

የዐሥር ጥማድ ወይን እርሻ
የወይን እርሻው ስፋት ያንን ለማረስ በቀን ውስጥ በሚያውላቸው ጥማድ በሬዎች ብዛት ይገመታል። እያንዳንዱ ጥማድ በሬ በቀንበር ይያያዛል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ዐሥር ጥማድ በሬዎች የሚያውል እርሻ››

አንድ መስፈሪያ የወይን ጭማቂ
‹‹አንድ መስፈሪያ ወይን ጭማቂ›› ወይም፣ ‹‹22 ሊትር ወይን ጭማቂ›› አንድ ጐሜር ከዐሥር ኢፍ ጋር እኩል ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አንድ የጐሜር መስፈሪያ አንድ ኢፉ ብቻ ይሰጣል።
‹‹220 ሊትር ዘር 22 ሊትር እህል ብቻ ይሰጣል።›› አንድ ጐሜር ከአሥር ኢፉ ጋር እኩል ነው።

Isaiah 5:11

ማልደው ለሚነሡ... ሌሊቱን ለሚያነጉ
ይህ የሚያመለክተው አልኮል ከመጠጣት ውጪ ቀኑን ሙሉ ምንም ስለማይሠሩ ሰዎች ነው።

እስኪያነጻቸው ወይን በመጠጣት
ጠጪዎቹን የሚያሰክር ወይን ጠጅ የሚያቃጥል ወይም የሚያነድ እሳት እንደ ሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በወይን ጠጅ እስኪሰክሩ ድረስ››

በገና፣ መሰንቆ፣ ከበሮ፣ ዋሽንትና ወይን ጠጅ
እነዚህ የሙዚቃ መሣሪያዎችና ወይን ጠጅ ሰዎቹ በፈንጠዝያ ጊዜያቸውን እንደሚያሳልፉ ያመለክታሉ።

ከበሮ
በእጅ የሚመታ፣ እንደ ታንቡር የሚመታ ራስ ያለው የሙዚቃ መሣሪያ። ምናልባትም ተጫዋቹ ሲንጣቸው ድምፅ የሚሰጡ የብረት ቁርጥራጮች ዙሪያውን ሊኖሩት ይችላሉ። ከበሮው ተጫዋቹ በአንድ እጁ ይዞ እስኪንጠው ድረስ በጣም ትንሽ ሊሆን ይችላል።

አልሰጡም
አጥብቀው አላሰቡም

የእጆቹን ሥራ
‹‹ሥራ›› የሚለውን፣ ‹‹ያደረገውን›› ወይም፣ ‹‹የፈጠረውን›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እርሱ ያደረገውን›› ወይም፣ ‹‹እርሱ የፈጠረውን››

የእጆቹን ሥራ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጆች›› አንዳች ነገር ያደረገ ሰውን ይወክላሉ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ ያደረገውን››

Isaiah 5:13

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ቁጥሮች ለእግዚአብሔር ባለመታዘዛቸው ሰዎች ላይ የሚደርሰውን ያመለክታሉ።

ሕዝቤ በምርኮ ተወስደዋል
በትንቢት ወደ ፊት የሚፈጸሙ ነገሮች ብዙውን ጊዜ አሁንእንደ ተፈጸሙ ተደርጐ ይነገራል። ይህ አጽንዖት የሚሰጠው ትንቢቱ በእርግጥ የሚፈጸም መሆኑን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከሌላ አገር የመጣ ጠላት ሕዝቤ እስራኤልን በባርነት ይወስዳል››

ዕውቀት በማጣት
ያላወቁት ምን እንደ ነበር ይበልጥ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌን ወይም ሕጉን አላወቁም››

ሲኦል ሆዷን አሰፋች፤ አፏንም ያለ ልክ ከፈተች
ይህ ሐረግ የሚናገረው በመቃብር ወይም ሌሎች እንስሳትን በሚበላ አውሬ ስለ ተመሰለው ስለ ሲኦል ነው። በጣም ብዙ ሰዎች እንደሚሞቱ ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሞት ብዙ ሰዎችን ለመብላት እንደ ተራበ አውሬ አፉን በሰፊው ከፍቷል››

መኳንንቱ፣ ሕዝቡ፣ መሪዎቻቸውና ረብሸኞቻቸውና ጨፋሪዎቻቸው ወደ ሲኦል ይወርዳሉ
ነቢዩ አሁን የተፈጸመ ይመሳል ስለ የወደ ፊቱ ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ብዙ የእስራኤል ሰዎች፣ ታላላቅና ታናናሾቻቸው፣ መሪዎቻቸውና ጭፈራን የሚወዱ ወደ ሲኦል ይወርዳሉ››

Isaiah 5:15

ሰው ይዋረዳል፤ የሰው ልጅም ዝቅ ይላል
ሁለቱም ሐረጐች የሚናገሩት ስለ ተመሳሳይ ነገር ሲሆን፣ በአንድነት የተነገሩት አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህን በሌላ መልኩ ማቅረብ ይቻላል። ኢሳይያስ 2፥9 ላይ ተመሳሳይ ነገርን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እግዚአብሔር ሰውን ሁሉ ዝቅ በማድረግ ያዋርዳል››

ሰው ይዋረዳል፤ የሰው ልጅም ዝቅ ይላል
ወደ ፊት የሚሆኑ ነገሮች አሁን እንደ ተፈጸሙ ተደርጐ ተነግሮአል።

ሰው ይዋረዳል
ብዙውን ጊዜ እንዲህ ሲባል የሚያመለክተው እጅግ ዝቅ ማለትን ነው።

የእብሪተኛው ዐይን ይሰበራል
ብዙውን ጊዜ መሰበር የእፍረት ምልክት ነው። ኢሳይያስ 2፥11 ተመሳሳዩን ቃል እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የትዕቢተኛው ዐይን በእፍረት መሬት ያያል›› ወይም፣ ‹‹ትዕቢተኞች የነበሩ አሁን አፍረዋል››

ከፍ ከፍ ያለ
ትዕቢተኛና እብሪተኛ ሰዎች ከሌሎች ይልቅ በጣም ከፍ ከፍ ያሉ መሆናቸው ተነግሮአል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ኩሩዎች››

የሰራዊት ጌታ ያህዌ በፍትሕ ከፍ ከፍ ይላል
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እርሱ ትክክል በመሆኑ ሰዎች የሰራዊት ጌታ ያህዌን ያመሰግናሉ››

የሰራዊት ጌታ ያህዌ
ኢሳይያስ 1፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት

ከፍ ከፍ ይላል
መከበር ከፍ ከፍ ማለት እንደ ሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እጅግ ይከበራል››

በጐች በገዛ መሰማሪያቸው ይግጣሉ
ያህዌ ኢሳይያስ 5፥1 ላይ፣ ‹‹የወይን ቦታ›› ተብሎ የተጠራውን የኢየሩሳሌም ከተማ ያጠፋል። የበጐች መሰማሪያ ከመሆን ውጪ ለምንም አይጠቅምም።

ይግጣሉ
ሣር ይበላሉ

የበግ ጠቦቶችም በፍርስራሽ ላይ ሣር ይበላሉ
ይህ ጠቦቶቹ እዚያ ሣር ይበላሉ ማለት ነው። ቦታው ለሌላ ነገር አይጠቅምም።

Isaiah 5:18

ኀጢአትን በከንቱነት ገመድ ለሚስቡ፤ በደልንም በሰረገላ ማሰሪያ ለሚጐትቱ ወዮላቸው።
እነዚህ ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ነው ያላቸው። በሙሉ ኀይላቸው በገመድ ሰረገላ የሚጐትቱ ይመስል ሆን ብለው ኀጢአት በመሥራት ይጸናሉ። እግዚአብሔር ለኀጢአታቸው ይቀጣቸዋል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰረገላን በገመድ እንደሚጐትት ሰው ኀጢአት ለማድረግ በርትቶ ለሚሠራ ሰው ወዮለት››

እንዲህ ለሚሉ
ይህ የሚያመለክተው በኀጢአት የጸኑትንና (ቁ.18) እንዲያስቆማቸው በፌዝ እግዚአብሔርን የሚገዳደሩትን ሰዎች ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እያፌዙ እንዲህ ለሚሉ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የእስራኤል ቅዱስ ዕቅድ ትምጣ
የእግዚአብሔር ዕቅድ በራሳቸው ጊዜ ማምጣት የሚችሉት ነገር ተደርጐ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤል ቅዱስ ዕቅዱን ይፈጽም››

የእስራኤል ቅዱስ
ይህን ኢሳይያስ 5፥16 ላይ እንደ ተረጐምህ ተርጕመው።

Isaiah 5:20

ጨለማውን ብርሃን፣ ብርሃኑን ጨለማ ለሚሉ፣ መራራውን ጣፋጭ ጣፋጩን መራራ ለሚሉ
እነዚህን ነገሮች የሚያደርጉ፣ ‹‹ክፉውን መልካም፣ መልካሙን ክፉ›› እንደሚሉ ሰዎች ናቸው። እነዚህ ነገሮች ተቃራኒዎች ናቸው፤ ሰዎች በመካከላቸው ያለውን ልዩነት ያውቃሉ፤ አንዳንዶች ግን በሐሰት መጥፎ ነገሮች መልካም እንደሆኑ ይናገራሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጨለማውን ብርሃን፣ ብርሃኑን ጨለማ እንደሚሉ ሰዎች ናቸው፤ መራራውን ጣፋጭ ጣፋጩን መራራ እንደሚሉ ሰዎች ናቸው።››

በራሳቸው ዐይን አስተዋዮች የሆኑ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ዐይን›› የሚወክለው አስተሳሰብን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ራሳቸውን እንደ አስተዋይ የሚመለከቱ››

በራሳቸውም አመለካከት ጥበበኞች ለሆኑ
‹‹ሁሉንም ነገር መረዳት የሚችሉ የሚመስላቸው››

Isaiah 5:22

ጉቦን በመቀበል በደለኛን ንጹሕ ለሚያደርጉ
ይህ ምንባብ የሚያመለክተው ፍርድ ቤት ውስጥ ስላሉ ብልሹ ዳኞች ነው።

በደለኛውን ንጹሕ ለሚያደርጉ
‹‹በደል ያለባቸውን ሰዎች ንጹሕ ናችሁ ለሚሉ››

ለበደል አልባ ፍትሕ ለሚነፍጉ
‹‹ንጹሕ ሰዎችን በአግባቡ ለማያስተናግዱ››

Isaiah 5:24

የእሳት ልሳኖች
‹‹የእሳት ነበልባል›› ወይም፣ ‹‹ነበልባል››

የእሳት ነበልባል ገለባን እንደሚበላ፣ ድርቆሽም በእሳት ጋይቶ እንደሚጠፋ
የእነዚህ ሐረጐች ትርጉም በመሠረቱ ተመሳሳይ ነው። ኢሳይያስ 5፥18-23 ላይ የተጠቀሱትን ሰዎች እግዚአብሔር ይቀጣቸዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእሳት ነበልባል ገለባን እንደሚያቃጥል››

ገለባ
እህል ከታጨደ በኃላ እርሻው ላይ የሚቀር ደረቅ የተክሎች አካል።

ሥራቸው ይበሰብሳል፤ አበባቸውም እንደ ትቢያ ይሆናል
እነዚህ ሰዎች እንደ ሞቱ ተክሎች እንደ ሆነ ኢሳይያስ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሥሩ እንደበሰበሰ ተክል ይሞታሉ፤ ደርቆ በነፋስ እንደሚወሰድ አበባ ይበንናሉ››

Isaiah 5:25

የያህዌ ቁጣ ነደደ
ኢሳይያስ የያህዌ ቁጣ እንደ እሳት እንደሆነ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ በጣም ተቆጥቷል››

እነርሱ ላይ እጁን በመዘርጋት ቀጣቸው
ነቢዩ የወደ ፊቱን አሁን እንደ ተፈጸመ ይናገራል። እንዲህ ያደረገው ትንቢቱ በትክክል እንደሚፈጸም አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ብርቱ በሆነው እጁ ይቀጣቸዋል››

እጁን በእነርሱ ላይ ዘረጋ
እዚህ ላይ ‹‹እጅ›› የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ኀይልና ቁጥጥር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነርሱ ላይ ኀይሉን ገለጠ››

ሬሳዎች
የሞቱ ሰዎች

ሬሳዎቻቸው በመንገድ ላይ እንደ ተጣለ ጥራጊ ናቸው
ጥራጊ ይመስል የሞቱ ሰዎች ሬሳ መንገድ ላይ እንዲጣል ይደረጋል። ይህም ብዙዎች እንደሚሞቱና የሚቀብራቸው እንደማይኖር ያመለክታል። ‹‹ጥራጊ›› የሚለው ቃል፣ ‹‹ቆሻሻ›› ወይም፣ ‹እበት›› ተብሎ መተርጐም ይቻላል።

ይህ ሁሉ ሆኖ ግን ቁጣው ገና አልተመለሰም እጁም ገና እንደ ተዘረጋ ነው።
‹‹ይህ ሁሉ ሆኖ እንኳ፣ አሁንም እንደ ተቆጣ ነው፤ እጁም››

እጁ ገና እንደ ተዘረጋ ነው
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› የእግዚአብሔርን ኀይልና የበላይነት ይመለከታል። ኢሳይያስ ያህዌ እንደ ሰው የሚማታ እንደ ሆነ ይናገራል። ይህ ያህዌ እስራኤልን የመቅጣቱ ምሳሌ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አሁንም ሊቀጣቸው ዝግጁ ነው››

Isaiah 5:26

ከሩቅ ያሉትን ሕዝቦች የሚጠራበትን ምልክት ያቆማል፤ ከምድር ዳርቻም በፉጨት ይጠራቸዋል።
ኢሳይያስ በሁለት የተለያዩ መንገዶች የሚናገረው ስለ አንድ ጉዳይ ነው። ከይሁዳ በጣም ርቀው ያሉት ሕዝቦች መጥተው እንዲያጠቁ ማድረጉ፣ እነርሱን ወደ ይሁዳ ለመጥራት ምልክት ማቆምና ማፏጨት ተደርጐ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከይሁዳ በጣም ርቀው ያሉትን የአሕዛብ ሰራዊት ይጠራና እንዲመጡ ይነግራቸዋል››

ማፏጨት
ሰውን ወይም እንስሳን ለመጥራት አንድ ሰው ከአፉ የሚያወጣው ከፍ ያለ ቃና ያለው ድምፅ

ይመጣሉ
‹‹የጠላት ሰራዊት ይመጣሉ››

እየተጣደፉ በፍጥነት
እነዚህ ቃሎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ሲሆኑ፣ ምን ያህል ቶሎ እንደሚመጡ አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጣም ፈጥነው››

Isaiah 5:27

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ይሁዳን ስለሚያጠቃው ሰራዊት መናገሩን ቀጥሏል። አሁን እንኳ እንደ መጣ አድርጐ ይናገራል። (ኢሳይያስ 5፥26 ይመ.)

ደካማ፣ ስንኩል፣ የሚያንቀላፉ፣ የሚተኛ
እነዚህ አራት ቃሎች በሥራ ከመድከም እስከ መራመድ አለመቻል፣ ንቁ ለመሆን ካለመቻል እስከ ሙሉ በሙሉ ንቁ አለ መሆን እያደጉ ይሄዳሉ፤ ስለዚህ ትርጉሙ ውስጥ አራቱም መኖር አለባቸው።

ቀበቶአቸውንም አይፈቱም
በቀላሉ ተነሥተው መዋጋት እንዲያስችላቸው ወታደሮች ሁሌም ትጥቃቸው እንደ ተጠበቀ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የጫማቸውም ማሰሪያ አይበጠስም
‹‹የጫማቸው ክር››

የፈረሶቻቸው ሸኾና እንደ ባልጩት ናቸው
‹‹ሸኾናቸው እንደ ጠንካራ ድንጋይ ነው›› ኢሳይያስ የፈረሶችን እግር ጠንካራ ክፍል ከተነካ የእሳት ብልጭታ ከሚወጣው ከጠንካራው ድንጋይ ከባልጩት ጋር ያመሳስለዋል። ይህም ማለት 1) ኢሳይያስ ሸኾናቸውን ከባልጩት ጋር ያመሳስለው በሚሮጡበት ጊዜ የሚወጣውን ብልጭታ አስፈሪነት ለማሳየት ሊሆን ይችላል። ወይም 2) ኢሳይያስን ሸኾናቸውን ከባልጩት ጋር ያመሳሰለው ፈረሶቹ ጌቶቻቸው የሚፈልጉትን ሁሉ ለማድረግ እንዲያስችላቸው ሸኾናቸው ምን ያህል ጠንካራ እንደ ሆነ ለማሳየት ሊሆን ይችላል።

የሠረገሎቻቸው መንኩራኩሮች እንደ ዐውሎ ነፋስ ናቸው
በመንገዳቸው የሚገኙትን ሁሉ እንደሚያጠፉ ለማሳየት ኢሳይያስ የሠረገሎቹን መንኮራኩር ከዐውሎ ነፋስ ጋር አመሳስሎታል።

የሠረገሎች መንኮራኩሮች
ከእነዚህ መንኮራኩሮች ጋር የተያያዙ ስለታም ነገሮች አሉ፤ በአጠገቡ የሚያልፈውን ነገር ደቅቁታል።

Isaiah 5:29

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ይሁዳን ስለሚያጠቃው ሰራዊት መግለጹን ቀጥሏል።

ሠረገሎቹ እንደ አንበሳ ያገሳሉ፤ እንደ አንበሳ ደቦል ያገሣሉ።
እነዚህ ሐረጎች በመሠረቱ የሚናገሩት ስለ አንድ ነገር ነው። ድምፃቸው የይሁዳን ሕዝብ በጣም እንደሚያስፈራ ለማመልከት ኢሳይያስ የጠላትን ሰራዊት ከአንበሳ ጋር ያመሳስላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጦርነት ጊዜ ሰራዊቱ ሲጮኹ የሚያገሣ አንበሳ ይመስላሉ››

የአንበሳ ደቦል
ወጣትነት የብርታት መገለጫ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ብርቱ አንበሳ››

ያደነቱንም ይዘው ይጮኻሉ
ጠላት የይሁዳን ሕዝብ መግደሉን አንበሳ ደካማውን እንስሳ ከመግደሉ ጋር ኢሳይያስ ያመሳስላል። ይህም ማለት 1) አንበሶች ጥቃት ከማድረሳቸው በፊት ከፍ ያለ ጩኸት አያሰሙም። ወይም 2) ጸሐፊው በሁለት ቃላት የተጠቀመው አንድ ትርጉም ስላለው ነገር ለመናገር ነው።

ንጥቂያ
አራዊት አድነው የሚዙት እንስሳ

የሚያስጥልም የለም
‹‹ማንም ሊያድናቸው አይችልም››

ያገሣሉ... እንደ ባሕር ሞገድ
እነዚህ ቃሎች ቁጥር 29 ላይ፣ ‹‹ይጮኻሉ›› በሚል የተተረጐሙት ናቸው። የባሕር ሞገድን ወይም ከባድ ዝናብን ወይም ሌላ አስፈሪ ተፈጥሮአዊ ድምፅን የሚመለክት ቃል በቋንቋህ ካለ ተጠቀምበት።

ብርሃን እንኳ በደመናዎች ይጨልማል
እዚህ ላይ፣ ጨለማ መከራና ጥፋትን ይወክላል። ምሳሌያዊ ቋንቋውን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጨለማው ደመና የፀሐይ ብርሃንን ፈጽሞ ይጋርዳል››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 6

1 ንጉሡ ዖዝያን በሞተበት ዓመት፣ እግዚአብሔርን በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት፣ የልብሱም ዘርፍ መቅደሱን ሞልቶት ነበር። **2** ሱራፌልም ከእርሱ በላይ ቆመው ነበር፤ ለእያንዳንዱም ስድስት ክንፍ ነበረው፤ በሁለት ክንፍ ፊቱን ይሸፍን ነበር፣ በሁለቱም ክንፍ እግሮቹን ይሸፍን ነበር፣ በሁለቱም ክንፍ ይበር ነበር። **3** አንዱም አንደኛውን በመጥራት፣ "ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር! ምድር ሁሉ በክብሩ ተሞልታለች" እያለ ይጮኽ ነበር። **4** የመድረኩም መሠረት ከሚጮኹት ድምፅ የተነሣ ተናወጠ፣ ቤቱም ጢስ ሞላበት። **5** ከዚያ እኔ፣ "ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው በመሆኔ፣ ከንፈሮቻቸውም በረከሱባቸው ሕዝብ መካከል በመቀመጤ ዓይኖቼ የሠራዊትን ጌታ ንጉሡን እግዚአብሔርን ስለ አዩ፣ ጠፍቻለሁና ወዮልኝ!" አልሁ። **6** ከዚያም ከሱራፌል አንዱ እየበረረ ወደ እኔ መጣ፤ በእጁም ከመሠዊያው በጒጠት የወሰደው ፍም ነበረ። **7** በዚያም አፌን ዳሰሰበትና። "ተመልከት፣ ይህ ከንፈሮችህን ነክቶአል፤ በደልህም ከአንተ ተወገደ፣ ኃጢአትህም ተሰረየልህ።" አለኝ። **8** የጌታንም ድምፅ፣ "ማንን እልካለሁ? ማንስ ይሄድልናል?" ሲል ሰማሁ። እኔም፣ "እኔ አለሁ፤ እኔን ላከኝ።" አልሁ። **9** እርሱም፣ "ሂድና ይህን ሕዝብ፣ ትሰማላችሁ፣ አታስተውሉምም፤ ታያላችሁ፣ አትመለከቱምም" በላቸው። **10** በዓይናቸው እንዳያዩ፣ በጆሮአቸውም እንዳይሰሙ፣ በልባቸውም እንዳያስተውሉ፣ ተመልሰውም እንዳይፈወሱ፣ የዚህን ሕዝብ ልብ አደንድን፣ ጆሮአቸውንም አደንቊር፣ ዓይናቸውንም አሳውር" አለኝ። **11** ከዚያም እኔ፣ "ጌታ ሆይ፣ እስከ መቼ ድረስ ነው?" አልሁ። እርሱም ሲመልስ፣ "ከተሞች የሚኖርባቸውን አጥተው እስኪፈርሱ ድረስ፣ ቤቶችም ሰው የሌለባቸው እስኪሆኑ፣ ምድርም ፈጽሞ ባድማ ሆና እስክትቀር ድረስ፣ **12** እግዚአብሔርም ሰዎችን እስኪያርቅ፣ በምድርም መካከል ውድማው መሬት እስኪበዛ ድረስ ነው።" አለ። **13** በእርስዋም ዘንድ አንድ ዐሥረኛ ሰው ቀርቶ እንደ ሆነ እነርሱ ደግሞ በድጋሚ ይቃጠላሉ፤ በተቈረጡ ጊዜ ጉቶቻቸው እንደ ቀሩ እንደ ግራርና እንደ ኮምበል ዛፍ ሆኖ፣ ጉቶው የተቀደሰ ዘር ይሆናል።"

Isaiah 6:1

ከፍ ባለና በከበረ
‹‹ከፍ ያለ››እና፣ ‹‹የከበረ›› የተሰኙት ቃሎች ዙፋኑ በጣም ከፍ ያለና በዙሪያው ካሉት ሁሉ በላይ መሆኑን አጽንዖት ይሰጣሉ። የዙፋኑ ከፍታ ጌታ ምን ያህል ታላቅና ኀያል መሆኑን ያመለክታል።

ቤተ መቅደሱን ሞላው
‹‹ቦታውን ሞላው››እዚህ ላይ ቤተ መቅደስ ለማለት ጥቅም ላይ የዋለው ቃል ብዙውን ጊዜ ቤተ መንግሥትን ነው የሚያመለክተው።

ከበላዩም ሱራፌል ነበሩ
‹‹ሱራፌል›› የሚለው ቃል፣ ሱራፍ የሚለው ብዙ ቁጥር ነው። ይህም ማለት ጌታ ዙፋን ላይ ተቀምጦ ነበር፤ ሱራፌልም ለማገልገል ዝግጁ ሆነው ጌታ አጠገብ ቆመው ነበር ወይም እየበረሩ ነበር ማለት ነው።

ሱራፌል
ይህ ቃል እነዚህ ፍጡራን የእሳት ነበልባል ወይም እባብ የሚመስል ሁኔታ ሳይኖራቸው እንዳልቀረ ያመለክታል። ‹‹ሱራፌል›› ምን ማለት እንደ ሆነ በትክክል ስለማይታወቅ ‹‹ባለ ክንፍ ፍጥረቶች›› ወይም፣ ‹‹ክንፋም ሕያው ፍጥረቶች›› በማለት መተርጐም ትችላለህ። ወይም ቃሉን ወስደህ በቋንቋህ ልትጠቀምበት ትችላለህ።

እያንዳንዱ ስድስት ክንፎች ነበሩት
‹‹እያንዳንዱ ሱራፍ ስድስት ክንፎች ነበሩት›› ወይም፣ ‹‹እያንዳንዱ ፍጡር ስድስት ክንፎች ነበሩት››

በሁለቱ ፊታቸውን ይሸፍኑ ነበር፤ በሁለቱ እግራቸውን ይሸፍኑ ነበር፤ በሁለቱም ይበሩ ነበር
‹‹ክንፍ›› እና፣ ‹‹ሱራፍ›› የተሰኙት ቃሎች ውስጠ ታዋቂ ናቸው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እያንዳንዱ ሱራፍ በሁለት ክንፍ ፊቱን ይሸፍን ነበር፤ በሁለቱ ክንፍ እግሮቹን ይሸፍን ነበር፤ በሁለቱም ክንፍ ይበር ነበር››

Isaiah 6:3

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ስለ ራእዩ መናገሩን ቀጥሏል

እርስ በርሳቸውም በመቀባበል እንዲህ ይሉ ነበር
‹‹ሱራፌል በመቀባበል እንዲህ ይሉ ነበር›› ወይም፣ ‹‹ባለ ክንፍ ፍጥረቶቹ አንዱ ለሌላው እንዲህ ይል ነበር››

ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ጌታ እግዚአብሔር
‹‹ቅዱስ›› የሚለው ቃል ሦስት ጊዜ መደጋገሙ እግዚአብሔር ፍጹም ቅዱስ እንደሆኑ ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጌታ ያህዌ ከሁሉም በላይ ቅዱስ ነው። ወይም፣ ‹‹ጌታ ያህዌ ፍጹም ቅዱስ ነው››

ምድር ሁሉ በክብሩ ተሞልታለች
ይህ ምድር መያዣ እንደሆነች፣ ክብር ደግሞ መያዝውን የሚሞላ ነገር እንደ ሆነ ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በምድር ያለ ማንኛውም ነገር የእግዚአብሔር ክብር ማስረጃ ነው››

Isaiah 6:4

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ስለ ራእዩ መናገሩን ቀጥሏል።

ከድምፃቸው ጩኸት የተነሣ የመድረኩ መሠረት ተናወጠ
‹‹ሱራፌል ሲጮኹ ድምፃቸው መድረኩንና መሠረቱን አናወጠው››

ቤቱ በጢስ ተሞላ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ቤተ መቅደሱን ጢስ ሞላው›› ወይም፣ ‹‹ቤተ መንግሥቱን ጢስ ሞላው››

ጠፍቻለሁ ወዮልኝ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ታላቅ ችግር ውስጥ ነኝ! አስቸጋሪ ነገር ይደርስብኛል››

ከንፈሮቼ የረከሱብኝ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ከንፈሮች›› ሰው የሚናገረውን ያመለክታሉ። ሰዎች እግዚአብሔርን ደስ የማያሰኝ ነገር መናገራቸው የከንፈሮቻቸው መርከስ ማለት እንደ ሆነ ተነግሯል።

ያህዌ፣ የሰራዊት ጌታ ያህዌ
‹‹የመላእክት ሰራዊት ገዢ ያህዌ››

ዐይኖቼ ዐይተዋል
‹‹ዐይኖች›› መላውን ሰው ይወክላሉ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አይቻለሁ››

Isaiah 6:6

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ስለ ራእዩ መናገሩን ቀጥሏል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሱራፌል
እነዚህ ፍጥረታት እሳት፣ የእሳት ነበልባልና እባብ መሰል ሁኔታ ሳይኖራቸው አልቀረም። ‹‹ሱራፌል›› ምን ማለት እንደ ሆነ በትክክል ስለማይታወቅ፣ ‹‹ፍጡሮች›› ወይም፣ ‹‹ሕያው ነገሮች›› ወይም፣ ‹‹ኅላዌ›› በማለት መተርጐም ትችላለህ። ወይም ይህን ቃል ወስደህ ቋንቋህ ውስጥ ልትጠቀምበት ትችላለህ። ኢሳይያስ 6፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

ጉጠት
ነገሮችን ለመያዝ የሚረዳ መሣሪያ

በደልህ ተወግዶልሃል፤ ኀጢአትህም ተሰርዮልሃል
እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ የሚናገሩት ስለ ተመሳሳይ ነገር ነው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ በደልህን አስወግዷል፤ ኀጢአትህንም ይቅር ብሎልሃል››

በደልህ ተወግዶአል
ያህዌ አንድን ሰው ከእንግዲህ እንደ በደለኛ እንደማይቆጥረው ለማሳየት፣ ‹‹በደል›› አንድ ሰው ከሌላው የሚወስደው ነገር እንደ ሆነ ተነግሯል።

Isaiah 6:8

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ስለ ራእዩ መግለጹን ቀጥሏል

የጌታም ድምፅ እንዲህ አለ
‹‹ድምፁ›› ጌታ ራሱን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጌታ እንዲህ አለ››

ማንን እልካለሁ?
ይህ የሚያመለክተው የእርሱን መልእክት ለእስራኤል ሕዝብ እንዲናገር ያህዌ አንድ ሰው እንደሚልክ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ለሕዝቤ መልእክተኛ እንዲሆን ማንን እልካለሁ››

ማንስ ይሄድልናል?
‹‹እኛ›› የሚለው የሚያመለክተው ያህዌንና እርሱ እየተናገራቸው ያለውን የሰማይ መማክርት ነው።

ይህ ሕዝብ
‹‹የእስራኤል ሕዝብ››

ይሰማሉ፤ ግን አያስተውሉም፤ ያያሉ ግን ልብ አይሉም
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹አያስተውሉም›› እና፣ ‹‹ልብ አይሉም›› የሚሉት ያህዌ የሚያደርገውን ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ትሰማላችሁ ግን ያህዌ እንድታስተውሉ አያደርጋችሁም፤ በጥንቃቄ ታያላችሁ ግን ያህዌ ልብ እንድትሉ አያደርጋችሁም›› ወይም 2) ‹‹መስማት›› እና፣ ‹‹ማየት›› የተሰኙት ሐረጐች ‹‹እንዲህ ቢሆን›› የሚል ሐሳብ ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ብትሰሙ እንኳ አታስተውሉም፤ በጥንቃቄ ብታዩ እንኳ ልብ አትሉም››

ይሰማሉ ግን አያስተውሉም፤ ያያሉ ግን ልብ አይሉም
በውስጠ ታዋቂነት ያለውን መረጃ መግለጽ ይቻላል። ‹‹የያህዌን መልእክት ይሰማሉ፣ ግን ምን ማለት እንደ ሆነ አያስተውሉም፤ ያህዌ እያደረገ ያለውን ያያሉ፤ ግን ምን እንደሆነ አይገነዘቡም››

Isaiah 6:10

አጠቃላይ መረጃ
ለሕዝቡ እንዲሰብክ ሲልከው ምን ማለት እንዳለበት ያህዌ ለኢሳይያስ መናገሩን ቀጥሏል።

የዚህን ሕዝብ ልብ አደንድን
‹‹ልብ›› የሚወክለው የሰውን አእምሮ ነው። በደንብ የማይሰማና መረዳት የማይችል ሰው ልቡ የደነደነ እንደሆነ ተናግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ይህ ሕዝብ መረዳት እንዳይችል አድርግ›› ወይም፣ ‹‹የዚህን ሕዝብ አእምሮ ደነዝ አድርግ››

የዚህን ሕዝብ ልብ
‹‹ልብ›› እና፣ ‹‹የዚህ›› የሚሉትን ቃሎች በብዙ ቁጥር መተርጐም የበለጠ አግባብነት ይኖረዋል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የእነዚህን ሰዎች ልቦች››

ልብ... አደንድን
የተሰጠው ትእዛዝ የኢሳይያስን መልእክት እንዳያስተውሉ ለማድረግ፣ ያህዌ እያደረገ ላለው የበለጠ ደንዳኖች እንዲሆኑ ያህዌ የሚጠቀምበት መሆኑ ነው።

ጆሮአቸውን ድፈን፤ ዐይኖቻቸውንም አሳውር
‹‹እንዳይሰሙ አድርገው፤ እንዳያዩ አድርገው›› ኢሳይያስ ሰዎች የያህዌን መልእክት እንዳያስተውሉ ማድረጉ ወይም እያደረገ ያለው ደንቆሮና ዕውሮች እያደረጋቸው እንደሆነ ተነግሯል።

በዐይናቸው ዐይተው፤ በጆሮአቸውም ሰምተው
x

Isaiah 6:11

ከተሞች እስኪፈራርሱ፣ ቤቶችም የሚኖርባቸው እስኪያጡ
‹‹ማንም እንዳኖርባቸው ከተሞችና ቤቶች እስኪወድሙ ድረስ››

ምድርም ፈጽሞ ባድማ እስክትሆን ድረስ
‹‹ባድማ›› መሆን አስከፊ ደረጃ ላይ መድረስ ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ምድሪቱ ጠፍ ምድረ በዳ እስክትሆን››

ያህዌ ሕዝቡን ወደ ሩቅ እስከሚሰድና የምድሪቱ ባዶነት ከባድ እስኪሆን
እዚህ ላይ ያህዌ ስለ ራሱ በሦስተኛ ሰው ደረጃ ይናገራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እኔ ያህዌ ሕዝቡን ከምድራቸው ወደ ሩቅ አገር እስከምሰድና እዚያ ማንም እስከማይቀር ድረስ››

Isaiah 6:13

እንደገና ይጠፋል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሰራዊት እንደ ገና የእስራኤልን ምድር ያጠፋሉ››

የኮምባል ወይም የባሉጥ ዛፍ በተቆረጠ ጊዜ ጉቶ እንደሚቀር ቅዱሱም ጉቶ ሆኖ ይቀራል
ይህ ምስስል ያህዌ እስራኤልን ቢያጠፋ እንኳ፣ ከእነርሱ መካከል እርሱን የሚያገለግሉትን ለይቶ እንደሚያስቀር ያመለክታል።

ኮምበል
ወርካ የሚመስል ዛፍ

ግንድ... ጉቶ
ግንድ ጠንካራው የዛፍ አካል ነው፤ ጉቶ ዛፍ ከተቆረጠ በኃላ ምድር ውስጥ የሚቀረው ነው።

ቅዱሱም ዘር
ሰራዊቱ እስራኤልን ካጠፋ በኃላ ያህዌን የሚያገለግሉ ሰዎች እንደ ቅዱስ ዘር የተለዩ እንደሚሆኑ ተነግሯል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 7

[1] በይሁዳ ንጉሥ በዖዝያን ልጅ በኢዮአታም ልጅ በአካዝ ዘመን የሶርያ ንጉሥ ረአሶን፣ የእስራኤልም ንጉሥ የሮሜልዩ ልጅ ፋቁሔ፣ ኢየሩሳሌምን ሊወጉ ወጡ፣ ሊያሸንፉአትም አልቻሉም። [2] ለዳዊትም ቤት፣ ሶርያ ከኤፍሬም ጋር እንደተባበሩ ወሬ ተነገረ። የእርሱም ልብ፣ እንዲሁም የሕዝቡም ልብ፣ የዱር ዛፍ በነፋስ እንድትናወጥ ተናወጠ። [3] ከዚያም እግዚአብሔር ኢሳይያስን፣ "አንተና ልጅህ ያሱብ አካዝን ትገናኙት ዘንድ በልብስ አጣቢው እርሻ መንገድ ወዳለው ወደ ላይኛው የኩሬ መስኖ ጫፍ ውጡ። [4] እንዲህም በለው፣ 'ተጠንቀቅ፣ ዝምም በል፣ ስለ እነዚህ ስለሚጤሱ ስለ ሁለት የእንጨት ጠለሸቶች፣ ስለ ሶርያና ስለ ረአሶን፣ ስለ ሮሜልዩም ልጅ ቍጣ አትፍራ፣ ልብህም አይድከም። [5] ሶርያና ኤፍሬም የሮሜልዩም ልጅ፣ [6] "ወደ ይሁዳ እንውጣ እናስጨንቃትም፣ እንስበራትም፣ የጣብኤልንም ልጅ እናንግሥባት" ብለው ክፋት ስለ መከሩብህ፤ [7] ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "ይህ ምክር አይጸናምና አይሆንም፣ [8] የሶርያ ራስ ደማስቆ ስለሆነ፣ የደማስቆም ራስ ረአሶን ስለሆነ አይከናወንም። በስድሳ አምስት ዓመት ውስጥ ኤፍሬም ይሰባበራልና ከእንግዲህ ወዲህ ሕዝብ አይሆንም፤ [9] የኤፍሬምም ራስ ሰማርያ ነው፣ የሰማርያም ራስ የሮሜልዩ ልጅ ነው። በእምነት ባትጸኑ፣ በእርግጥም በዋስትና አትጸኑም።" [10] እግዚአብሔርም ደግሞ አካዝን እንዲህ ብሎ ተናገረው፣ [11] "ከጥልቁ ወይም ከከፍታው ቢሆን ከአምላክህ ከእግዚአብሔር ምልክትን ለምን።" [12] አካዝ ግን፣ "አልለምንም፣ እግዚአብሔርንም አልፈታተንም" አለ። [13] ስለዚህ ኢሳይያስ ሲመልስ፣ "እናንተ የዳዊት ቤት ሆይ፣ ስሙ። በውኑ የሰውን ትእግሥት መፈታተናችሁ ቀላል ነውን? ዩአምላኬን ትእግሥት ደግሞ ልትፈታተኑ ይገባችኋልን? [14] ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤ ተመልከቱ፣ ድንግል ትፀንሳለች፣ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፣ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች። [15] ክፉን ለመጥላት መልካሙንም ለመምረጥ ሲያውቅ ቅቤና ማር ይበላል። [16] ሕፃኑ ክፉን ለመጥላት መልካሙን ለመምረጥ ከማወቁ በፊት፣ የፈራሃቸው የሁለቱ ነገሥታት አገር ባድማ ትሆናለች። [17] እግዚአብሔርም ኤፍሬም ከይሁዳ ከተለየበት ቀን ጀምሮ ያልመጣውን ዘመን በአንተና በሕዝብህ በአባትህም ቤት ላይ ያመጣል፤ እርሱም የአሦር ንጉሥ መምጣት ነው።" [18] በዚያም ጊዜ እግዚአብሔር በግብጽ ወንዝ ርቀት ያለውን ዝምብ፣ በአሦርም አገር ያለውን ንብ በፉጨት ይጠራል። [19] ሁሉም ይመጡና በበረሃ ሸለቆ፣ በድንጋይም ዋሻ ውስጥ በእሾህ ቍጥቋጦ ሁሉ ላይ፣ በማሰማርያውም ሁሉ ላይ ይሰፍራሉ። [20] በዚያም ቀን እግዚአብሔር ከወንዙ ማዶ በተከራየው ምላጭ በአሦር ንጉሥ የራሱንና የእግሩን ጠጕር ይላጨዋል፤ ምላጩም ጢሙን ደግሞ ይላጫል። [21] በዚያም ቀን፣ ሰው አንዲት ጊደርንና ሁለት በጎችንም በሕይወት ያቆያል፣ [22] ደግሞም ከሚሰጡት ወተት ብዛት የተነሣ ቅቤ ይበላል፤ በአገሪቱም መካከል የቀረ ሁሉ ቅቤና ማር ይበላል። [23] በዚያም ቀን፣ ሺህ ብር የተገመተ ሺህ የወይን ግንድ በነበረበት ስፍራ ሁሉ ለኩርንችትና ለእሾህ ብቻ ይሆናል። [24] ኩርንችትና እሾህ በምድር ሁሉ ላይ ነውና በፍላጻና በቀስት ወደዚያ ይገባሉ። [25] በመቄፈርያም ወደ ተቈፈሩ ኮረብቶች ሁሉ ከኩርንችትና እሾህ ፍርሃት የተነሣ ወደዚያ አትሄድም፤ ነገር ግን የበሬ ማሰማርያና የበግ መራገጫ ይሆናል።

Isaiah 7:1

በይሁዳ ንጉሥ በአካዝ ዘመን
‹‹አካዝ የይሁዳ ንጉሥ በነበረ ዘመን›› — ይህ ታሪኩ የተፈጸመበት ነው።

ረአሶን… ፋቁሔ… ሮሜልዩ
የሰዎች ስም

ረአሶንና… ፋቁሔ… ወጡ
ነገሥታቱ የሚመሩት ሰራዊት እንደሆኑ ጸሐፊው ይናገራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ረአሶንና… ፋቁሔ ከሰራዊታቸው ጋር ወጡ››

ሊወጉ ወጡ
ጸሐፊው፣ ከተማው ራሱ ውስጡ የሚኖሩ ሰዎች እንደሆነ ይናገራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ኢየሩሳሌምን ሊወጉ ወጡ››

ለዳዊት ቤት ወሬ በደረሰ ጊዜ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የዳዊት ቤት ወሬውን ሰሙ››

የዳዊት ቤት
‹‹ቤት›› የሚለው ቤቱ ውስጥ የሚኖሩ ቤተ ሰብን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ንጉሥ አካዝና አማካሪዎቹ››

ሶርያና ኤፍሬም ተባብረዋል
‹‹ሶርያ›› እና፣ ‹‹ኤፍሬም›› ነገሥታቶቻቸውን ያመለክታል። እዚህ ላይ፣ ‹‹ኤፍሬም›› መላው ሰሜናዊ የእስራኤልን መንግሥት ነው የሚያመለክተው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የሶርያ ንጉሥ ረአሶን የእስራኤል ንጉሥ ፋቁሔን እየረዳ ነበር››

የዱር ዛፍ በነፋስ እንደሚናወጥ የእርሱና የሕዝቡ ልብ ተናወጠ
በዚህ ወሬ ልባቸው መናወጡ ነፋስ ሲያናውጠው ከሚናወጥ ዛፍ ጋር ተመሳስሎአል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አካዝና ሕዝቡ በጣም ፈሩ››

Isaiah 7:3

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ሌሎች ላይ የደረሰው እርሱ ላይ እንደ ደረሰ ይናገራል።

ሸአር ያሹብ
ተርጓሚዎቹ፣ ‹‹ሸአር፣ ያሹብ፣ ‹ትሩፋኑ ይመለሳሉ› ማለት ነው የሚል የግርጌ ማስታወሻ መጨመር ይችላሉ። ትርጕሙ ለአካዝ ተስፋ ይሰጠዋል።

የላይኛው የኩሬ መስኖ ጫፍ
‹‹ውሃው በቦይ አልፎ ወደ ላይኛው ኩሬ የሚገባበት››

መስኖ
ውሃ የሚያልፍበት ሰው ሠራሽ መተላለፊያ

መንገድ
ቋንቋህ ዝቅ ያለውን ቦታ በመሙላት፣ ከፍ ያለውን በመደልደል የተመቸ እንዲሆን ሰዎች የሚሠሩትን መንገድ ወይም ጐዳና የሚያመለክት ቃል ካለው እዚህ ላይ መጠቀም ትችላለህ።

የልብስ አጣቢው መስክ
ይህ ማለት፣ 1) ሰዎች ያንን መስክ የሚጠሩበት የተለመደ ስም ሊሆን ይችላል። ወይም 2) ሰዎች ያንን መስክ፣ ‹‹የልብስ አጣቢው መስክ›› የሚል ስም ስለ ሰጡት ሊሆን ይችላል። ወይም ‹‹ሰዎች ልብስ የሚያጥቡበት ቦታ›› ወይም፣ ‹‹ሴቶች ልብስ የሚያጥቡበት ቦታ›› ማለት ሊሆን ይችላል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የልብስ አጣቢው መስክ
ልብስ አጣቢው፣ 1) ከበጎች የተሸለተውን ጠጉር የሚያጥብ ሰው፤ ‹‹የበግ ጠጉር አጣቢው›› ወይም 2) የቆሸሸ ልብስ የምታጥብ ሴት›› ‹‹የልብስ አጣቢዋ መስክ››

ንገሩት
‹‹ለአካዝ ንገሩት››

አትፍራ፤ በእነዚህ ከእሳት ተርፈው በሚጤሱት በሁለቱ የእንጨት ጉማጆች በሶርያና በንጉሥዋ በረአሶን እንዲሁም በሮሜልዩ ልጅ ቁጣ አትሸበር
እግዚአብሔር ረኦሶንና ፋቁሔን ነድዶ እሳቱ ከወጣለት፣ አሁን ግን ጭስ ብቻ ከተረፈው የእንጨት ጉማጅ ጋር ያመሳስለቸዋል። ለይሁዳ ይህን ያህል የሚያሰጉ እንዳይደሉ እግዚአብሔር አስረግጦ ይናገራል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ረአሶንና ፋቁሔን አትፍራ፤ የእነርሱ ቁጣ እሳቱ ወጥቶ ጭስ ብቻ እንደ ቀረው የእንጨት ጉማጆች ናቸው።

አትፍራ ወይም አትሸበር
‹‹አትፍራ›› እና፣ ‹‹አትሸበር›› የተሰኙት ቃሎች ትርጉም ተመሳሳይ ስለሆነ በአንድ ቃል መተርጐም ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አትፍራቸው››

Isaiah 7:5

አጠቃላይ መረጃ
ለአካዝ መናገር ያለበትን ያህዌ ለኢሳይያስ መናገሩን ቀጥሏል

ሶርያ፣ ኤፍሬምና የሮሜልዩ ልጅ
‹‹ሶርያ›› እና፣ ‹‹ኤፍሬም›› የእነዚህ አገሮችን ነገሥታት ያመለክታሉ። እንዲሁም፣ ‹‹ኤፍሬም›› ሰሜናዊውን የእስራኤል መንግሥት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሶርያ ንጉሥ ረአሶንና የእስራኤል ንጉሥ የሮሜልዩ ልጅ ፋቁሔ››

ሮሜልዩ
ይህ የሰው ስም ነው። ኢሳይያስ 7፥1 ላይ እንደ ተረጐምኸው ተርጉመው።

በአንተ ላይ ክፉ መክረዋል
እዚህ ላይ፣ ‹‹አንተ›› ነጠላ ቁጥር ሲሆን፣ የሚያመለክተው አካዝን ነው።

የጣብኤል ልጅ
ይህ ሰው ማን እንደሆነ አይታወቅም

Isaiah 7:7

አጠቃላይ መረጃ
ለአካዝ መናገር ያለበትን ያህዌ ለኢሳይያስ መናገሩን ቀጥሏል።

የሶርያ ራስ ረአሶን ነው
እዚህ ላይ፣ ‹‹ራስ›› በጣም አስፈላጊ አካል ነው። ረአሶን ሰው እንጂ፣ ሌላ ነገር ባለ መሆኑ የያህዌን ዕቅድ ማስቆም እንደማይችል ያመለክታል። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሶርያ ንጉሥ ረአሶን ነው፤ እርሱ ሰው ብቻ ነው››

ሥልሳ አምስት ዓመት
‹‹65 ዓመት››

ኤፍሬም ይበታተናል፤ ሕዝብ መሆኑም ይቀራል
እዚህ ላይ፣ ‹‹ኤፍሬም›› ሰሜናዊው የእስራኤልን መንግሥት ሁሉ ያመለክታል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰራዊት ኤፍሬምን ይደመስሰዋል፤ በእስራኤልም ሕዝብ አይኖርም››

የሰማርያም ራስ የሮሜልዩ ልጅ ነው
ይህ ማለት ፋቁሔ የሰማርያና የመላው እስራኤል ንጉሥ ነው ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሰማርያ ንጉሥ ደካማው ፋቁሔ ነው››

በእምነታችሁ ካልጸናችሁ ፈጽሞ መቆም አትችሉም
ይህን በአዎንታዊ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በእኔ በማመን ከጸናችሁ አትናወጡም››

ካልጸናችሁ
‹‹ጽኑ ካልሆናችሁ››

Isaiah 7:10

ከጥልቁ ጥልቅ ከከፍታው ከፍታ... ጠይቅ
ያህዌ፣ ‹‹ጥልቅ›› እና፣ ‹‹ከፍታ›› በተሰኙ ቃሎች የተጠቀመው አካዝ ማንኛውንም ነገር መጠየቅ እንደሚችል ለማመልከት ነው።

ጥልቅ... ከፍታ
‹‹ጥልቅ›› እና፣ ‹‹ከፍታ›› የተሰኙትን ቃሎች በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። ‹‹በጣም ጥልቅ ከሆነብህ ቦታ... በጣም ከፍ ካለብህ ቦታ››

አልለምንም
‹‹ከያህዌ ምልክት አልጠይቅም››

Isaiah 7:13

የዳዊት ቤት
‹‹ቤት›› ማለት፣ ቤት ውስጥ የሚኖር ቤተ ሰብ ማለት ነው። ኢሳይያስ 7፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተ ንጉሥ አካዝና አማካሪዎችህ››

የሰውን ትዕግሥት መፈታተናችሁ አንሶ የአምላኬን ትዕግሥት ትፈታተናላችሁን?
ይህ አጽንዖት የሚሰጠው ሕዝቡ ታላቅ ኀጢአት ማድረጋቸውን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሰውን ትዕግሥት ትፈታተናላችሁ! አሁን ደግሞ የአምላኬን ትዕግሥት ትፈታተናላችሁ!››

ወጣት ሴት ትፀንሳለች
አንዳንድ የጥንት ቅጂዎችና፣ አንዳንድ የዘመኑ ቅጂዎች፣ ‹‹ድንግል ትፀንሳለች›› በማለት ተርጕመዋል፤ ሌሎች፣ ‹‹ወጣት ሴት ትፀንሳለች›› የሚል ትርጉም ይዘዋል።

ስሙንም አማኑኤል
ተርጓሚዎች፣ ‹‹አማኑኤል እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ማለት ነው›› የሚል የግርጌ ማስታወሻ መጨመር ይችላሉ።

ክፉውን መተውና መልካሙን መምረጥ ሲችል ቅቤና ማር ይበላል
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ሕፃኑ አድጐ ቅቤና ማር ለመብላት ሲደርስ፣ ክፉውን መተውና መልካሙን መምረጥ ይችላል›› ማለት ሊሆን ይችላል። ሕፃኑ ክፉ ከሆነው ይልቅ፣ መልካሙን የሚያውቀው ገና በሕፃንነቱ እንደሆነ ይህ አጽንዖት ይሰጣል። ወይም 2) ሕፃኑ አድጐ ክፉውን ትቶ፣ መልካሙን ሲመርጥ ቅቤና ማር ይበላል›› አይሁድ አንድ ሕፃን መልካሙን ለማድረግ ኀላፊነት የሚኖረው 12 ዓመት ሲሞላው እንደሆነ ያምናሉ። አብዛኞቹ እስራኤላውያን ስለሚገደሉ ወይም በምርኮ ስለሚወሰዱ በዐሥራ ሁለት ዓመት ውስጥ ሕዝቡ ብዙ ቅቤና ማር እንደሚበሉ ይህ አጽንዖት ይሰጣል።

ቅቤ
ሰዎች ከወተት የሚያወጡት ጠጣሩ ክፍል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ክፉውን መተው መልካመን መምረጥ
እዘህ ላይ፣ ‹‹ክፉው›› እና፣ ‹‹መልካሙ›› በአጠቃላይ ክፉና መልካም ነገሮችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ክፉ ነገሮችን በመተው መልካም ነገሮችን ለማድረግ መምረጥ››

Isaiah 7:16

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ እግዚአብሔር ለዳዊት ቤት ስለሚሰጠው ምልክት መግለጹን ቀጥሏል።

ክፉውን መተውና መልካሙ መምረጥ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ክፉው›› እና፣ ‹‹መልካሙ›› በአጠቃላይ ክፉና መልካም ነገሮችን ያመለክታል። ኢሳይያስ 7፥15 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ክፉ ነገሮችን በመተው መልካም ነገሮች ለማድረግ መምረጥ››

የሚያስደነግጡህ
‹‹የፈራሃቸው›› እዚህ ላይ፣ ‹‹አንተ›› ነጠላ ቁጥር ሲሆን፣ አካዝን ያመለክታል።

ሕዝብህ
ይህ የሚያመለክተው የይሁዳን ሕዝብ ነው።

ኤፍሬም ከይሁዳ ከተለየበት ቀን
እዚህ ላይ፣ ‹‹ኤፍሬም›› እና፣ ‹‹ይሁዳ›› በዚያ አካባቢ የሚኖረውን ሕዝብ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከይሁዳ ሕዝብ የተለየው የኤፍሬም ሕዝብ››

Isaiah 7:18

በዚያን ቀን
ሕፃኑ ክፉውን በመተው መልካሙን መምረጥ ከመቻሉ በፊት

ያህዌ በፉጨት
‹‹ያህዌ ይጣራል›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ኑ ይላል››

ከግብፅ ወንዞች ዝንቦችን፣ ከአሦርም ምድር ንቦችን
እዚህ ላይ የግብፅና የአሦር ሰራዊት የእስራኤልን ምድር በሚወርሩ ነፍሳት ተመስለዋል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የግብፅና የአሦር ሰራዊት ከወታደሮቻቸው ጋር እንደ ዝንብና ንብ በየቦታው ይገኛሉ››

Isaiah 7:20

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ የአሦር ሰራዊት እስራኤልን የሚወርረው መቼ እንደሆነ መግለጹን ቀጥሏል።

እግዚአብሔር ከወንዝ ማዶ በተከራየው ምላጭ ማለትም በአሦር ንጉሥ ይላጫል
‹‹ምላጭ›› የአሦር ንጉሥና ሰራዊቱን ያመለክታል፤ ንጉሡ የያህዌን ሥራ የሚሠራና ለዚያም ከያህዌ ገንዘብ እንደሚቀበል ሰው እንደሆነ ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እናንተን እንዲላጭ የአሦርን ንጉሥ ከኤፍራጥስ ወንዝ ማዶ ይጠራዋል››

በተከራየው
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በገዛው››

የራስና የእግር ጠጉራችሁን... ጢማችሁን
የአንድን ሰው አናት መላጨት መጥፎ ነው፤ ‹‹የእግርን ጠጉር›› መላጨት የባሰ መጥፎ ነው፤ ጢምን መላጨት ደግሞ ከሁሉ የባሰ መጥፎ ነው።

የራስና የእግር ጠጉራችሁን... ጢማችሁን
እግዚአብሔር የሚላጨው የማንን ራስ ጠጉርና ጢም እንደሆነ ኢሳይያስ አይናገርም፤ አካዝና አንባቢዎቹ ግን ይህ የሚያመለክተው ስለ ሰው መሆኑንና ያ ደግሞ በይሁዳ ምድር የሚኖረውን ሕዝብ ሊያመለክት እንደሚችል ይረዳሉ።

ራስ
‹‹ራስ›› እዚያ ላይ የሚበቅል ጠጉርን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የራስ ጠጉር››

የእግር ጠጉር
ይህም ማለት 1) የሰውነት ታችኛው አካል ላይ የሚበቅል ጠጉርን በጨዋነት ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለ ሐረግ ሊሆን ይችላል፤ ወይም 2) እግር ላይ የሚበቀለውን ጠጉር የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።

እንዲሁም... ይላጫል
‹‹እንዲሁም ምላጩ... ይላጫል›› ቋንቋህ፣ ‹‹የሚላጭ ሰው›› እንዲኖር የሚጠይቅ ከሆነ፣ ‹‹እግዚአብሔር ይላጨዋል›› ማለት ትችላለህ።

ከሚሰጡት የተትረፈረፈ ወተት የተነሣ
‹‹የተትረፈረፈ›› የሚለውን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጣም ብዙ ወተት ከመስጠታቸው የተነሣ››

Isaiah 7:23

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ የአሦር ሰራዊት የእስራኤልን ምድር የሚያጠቃው መቼ እንደሆነ መግለጹን ቀጥሏል።

አንድ ሺህ የወይን ተክል... ኩርንችትና እሾኽ ብቻ ይሆናል
‹‹1,000 የወይን ተክል›› ያም ማለት ኢሳይያስ በጻፈበት ጊዜ አንዳንዶቹ 1000 የወይን ተክል የያዙ የወይን እርሻ ቦታዎች ነበሩ። እነዚህ የወይን እርሻዎች ግን፣ ኩርንችትና እሾኽ እንደሚሞላባቸው ይናገራል።

ሺህ ሰቅል ብር
‹‹1,000 ሰቅል ብር›› ሰቅል የ4 ቀን ደመወዝ የሚሆን የብር ሳንቲም ነው አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹1,000 የብር ሰቅል››

ኩርንችትና እሾህ
‹‹ኩርንችት›› እና፣ ‹‹እሾኽ›› ሁለቱም የሚያመለክቱት ጥቅም የሌላቸው ተክሎችን ነው። ሁለቱንም ቃሎች መተርጐም አስፈላጊ አይደለም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእሾህ ቁጥቋጦ›› ወይም፣ ‹‹የኩርንችት ቁጥቋጦ››

ምድሩ ሁሉ ኩርንችትና እሾኽ ስለሚሆን
አዳኞቹ ወደዚህ ቦታ የሚመጡበትን ምክንያት ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በዚያ ቦታ ኩርንችትና እሾኽ እንዲሁም የዱር አራዊት እንጂ፣ ሌላ ምንም ስለማይኖር››

ከዚያ በፊት በመቆፈሪያ ተቆፍረው ወደ ነበሩት ኮረብታዎች አይሄዱም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ከዚያ በፊት እህል ለመዝራት ዝግጁ ወደ ነበሩት ቦታዎች አይሄዱም››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 8

1 እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ፣ "ታላቅ ሰሌዳ ወስደህ፣ 'ምርኮ ፈጠነ፣ ብዝበዛ ቸኰለ' ብለህ ጻፍበት። 2 የታመኑትን ሰዎች፣ ካህኑን ኦርዮንና የበራክዩን ልጅ
ዘካርያስን ምስክሮች አድርግልኝ" አለኝ። 3 ወደ ነቢይቱም ቀረብሁ፣ እርስዋም ፀነሰች ወንድ ልጅንም ወለደች። 4 ከዚያም እግዚአብሔር፣ "ሕፃኑ 'አባባ' እና
'እማማ' በማለት መጣራት ከማወቁ በፊት የደማስቆን ሀብትና የሰማርያን ምርኮ በአሦር ንጉሥ ፊት ይወስዳልና ስሙን ምርኮ ፈጠነ፣ ብዝበዛ ቸኰለ ብለህ
ጥራው፤" አለኝ። 5 እግዚአብሔር በድጋሚ ተናገረኝ፣ እንዲህም አለኝ፣ 6 "ይህ ሕዝብ በቀስታ የሚሄደውን የሰሊሆምን ውኃ ጠልቶአልና፣ ረአሶንንና
የሮሜልዩንም ልጅ ወዶአልና፣ 7 ስለዚህ እግዚአብሔር ብርቱና ብዙ የሆነውን የወንዝ ውኃ፣ የአሦርን ንጉሥና ክብሩን ሁሉ፣ ያመጣባቸዋል። መስኖውንም ሁሉ
ሞልቶ ይወጣል፣ በዳሩም ሁሉ ላይ ይፈስሳል፤ 8 እስከ አንገት እስኪደርስ ድረስ እየጐረፈ ወደ ይሁዳ ይገባል፣ እያጥለቀለቀም ያልፋል። አማኑኤል ሆይ፣ የክንፉ
መዘርጋት የአገርህን ስፋት ትሞላለች።" 9 አሕዛብ ሆ፣ እወቁና ደንግጡ፣ እናንተም አገራችሁ የራቀ ሁሉ፣ አድምጡ፤ ታጠቁም፣ ደንግጡ፤ ታጠቁ፤ ደንግጡ።
10 ዕቅድን አብጁ፣ ነገር ግን አይከናወንም፤ ትእዛዙን ተናገሩ፣ ነገር ግን አይከናወንም፣ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነውና። 11 እግዚአብሔር በጽኑ እጁ ጭምር
እንዲህ ተናገረኝ፣ በዚህም ሕዝብ መንገድ አንዳልሄድ አስጠነቀቀኝ፣ እንዲህም አለኝ። 12 ይህ ሕዝብ፣ አድማ ነው የሚሉትን ሁሉ፣ አድማ ነው አትበሉ፤
ማስፈራታቸውንም አትፍሩ፣ አትደንግጡ። 13 ነገር ግን የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርን ቀድሱት፤ የሚያስፈራችሁና የሚያስደነግጣችሁም እርሱ ይሁን። 14
እርሱም ለመቅደስ ይሆናል፤ ነገር ግን ለሁለቱ ለእስራኤል ቤቶች ለዕንቅፋት ድንጋይና ለማሰናከያ ዓለት ይሆናል። በኢየሩሳሌምም ለሚኖሩ ለወጥመድና
ለአሽክላ ይሆናል። 15 ብዙዎችም በእርሱ ይሰናከላሉ፣ ይወድቁማል፣ ይሰበሩማል፣ ይጠመዱማል፣ ይያዙማል። 16 ምስክሬን እሰር፣ በደቀ መዛሙርቶቼም
መካከል ሕጉን አትም። 17 ከያዕቆብም ቤት ፊቱን የሰወረውን እግዚአብሔርን እጠብቃለሁ፣ እጠብቀዋለሁም። 18 ተመልከቱ፣ እኔና እግዚአብሔር የሰጠኝ
ልጆች ለእስራኤል በጽዮን ተራራ ከሚኖረው ከሠራዊት ጌታ ከእግዚአብሔር ዘንድ ምልክትና ተአምራት ነን። 19 እነርሱ፣ "የሚጮኹትንና ድምፃቸውን ዝቅ
አድርገው የሚናገሩትን መናፍስት ጠሪዎችንና ጠንቋዮችን ጠይቁ" ባሉአችሁ ጊዜ፣ ሕዝቡ ከአምላኩ መጠየቅ አይገባውምን? ወይስ ለሕያዋን ሲሉ ሙታንን
ይጠይቃሉን? 20 ስለዚህ ለሕግና ለምስክር ትኩረት ልትሰጡ ይገባል! እንዲህም ያለውን ቃል ባይናገሩ፣ የንጋት ብርሃን ስለሌላቸው ነው። 21 እነርሱም
ተጨንቀውና ተርበው ያልፋሉ። በተራቡም ጊዜ፣ ተቈጥተው ንጉሣቸውንና አምላካቸውን ይረግማሉ፣ ፊታቸውን ወደ ላይያቀናሉ። 22 ወደ ምድርም ይመለከታሉ፣
ተመልከቱ፣ መከራና ጨለማ፣ የሚያስጨንቅም ጭጋግ አለ። ወደ ድቅድቅም ጨለማ ይሰደዳሉ።

Isaiah 8:1

ያህዌ እንዲህ አለኝ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እኔ›› ኢሳይያስን ይመለከታል።

ታማኝ ምስክሮች እንዲሆኑ እጠራቸዋለሁ
ይህም ማለት፣ 1) ያህዌ፣ ‹‹ምስክሮች እንዲሆኑ ታማኝ ሰዎችን እየጠራሁ ነኝ›› እያለ ነው ወይም 2) ኢሳይያስ፣ ‹‹ምስክሮች እንዲሆኑ ታማኝ ሰዎችን
እየጠራሁ ነኝ›› እያለ ነው። ወይም 3) ያህዌ ኢሳይያስን፣ ‹‹ምስክሮች እንዲሆኑ ታማኝ ሰዎችን ጥራ›› በማለት እያዘዘው ነው።

Isaiah 8:3

ወደ ነቢዩቱ ሄድሁ
ኢሳይያስ ነቢዩቱን ማግባቱ በግልጽ መነገር አለበት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከነቢዩቱ ሚስቴ ጋር ተኛሁ››

የደማስቆ ሀብትና የሰማርያ ምርኮ በአሦር ንጉሥ ይወሰዳል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የአሦር ንጉሥ የደማስቆንና የሰማርያን ሀብት ሁሉ ይወስደዋል››

Isaiah 8:5

ይህ ሕዝብ በጸጥታ የሚፈሰስውን የሰሊሆምን ውሆች ስለ ተወ
‹‹በጸጥታ የሚሄደው›› የተባለው የሚያመለክተው የጌታን ሕግ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ይህ ሕዝብ እንደ ሰሊሆም ውሆች በጸጥታ የሚሄደውን የያህዌን ሕግ ስለ ተወ››

ይህ ሕዝብ
‹‹ይህ ሕዝብ ሁሉ›› እዚህ ላይ ቋንቋህ ብዙ ቁጥር የሚፈልግ ከሆነ፣ ‹‹እነዚህ ሕዝቦች ስለ ተው… ደስተኛ ናቸው›› በማለት ይህን ሐረግና
የሚከተለውን ግሥ መተርጐም ይቻላል።

በረአሶንና በሮሜልዩ ልጅ ተደስቶአልና
ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። ኢሳይያስ 7፥1 ላይ የእነዚህን ሰዎች ስም እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የአሦር ሰራዊት የሶርያን ንጉሥ ረአሶንንና የሮሜልዮን ልጅ የእስራኤል ንጉሥ ፋቁሔን ድል ስላደረገ ተደስቶአል››

ስለዚህ ጌታ
ስለ ማንነቱ ለሕዝቡ ለማሳሰብ ያህዌ እርሱ ሌላ ሰው ይመስል ስለ ራሱ እየተናገረ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ስለዚህ እኔ ያህዌ…››

ያመጣባቸዋል
ግሡ፣ ‹‹ያመጣባቸዋል››፤ ተውሳከ ግሡ፣ ‹‹እነርሱ ላይ››

እነርሱ ላይ
‹‹የይሁዳ ሕዝብ ላይ››

ታላቁንና ብርቱውን የጐርፍ ውሃ፤ የአሦር ንጉሥ ከነግርማ ሞገሱ
ወንዙ የሚወክለው የአሦርን ሰራዊት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንደ ታላቅና ብርቱ ጐርፍ የሆነው ከአሦር የሚመጣው ሰራዊት››

ወንዙ
በአሦር ያለው የኤፍራጥስ ወንዝ

Isaiah 8:8

አጠቃላይ መረጃ
ጌታ የአሦር ሰራዊት እንደ ወንዝ እየጐረፈ ወደ ይሁዳ እንደሚመጣ መናገሩን ቀጥሏል።

ወንዙ እየጠራረገ ወደ ይሁዳ ይወርዳል፤ እያጥለቀለቀ ያልፋል፤ እስከ ዐንገትም ይደርሳል
የአሦር ሰራዊት እንደ ውሃ ጐርፍ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከፍ እያለ ሄዶ እስከ ዐንገታችሁ እንደሚደርስ ወንዝ እጅግ ብዙ ወታደሮች ይመጣሉ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወንዙ
ይህ የሚያመለክተው በአሦር ያለውን የኤፍራጥስ ወንዝ ነው። ከቤታቸው ተነሥተው በኤፍራጥስ ወንዝ በኩል የሚመጡት የአሦር ወታደሮችም ምሳሌ ነው። (ኢሳይያስ 8፥7)

የተዘረጉ ክንፎቹ ይሞላሉ
ይህም ማለት፣ 1) በምሳሌው እንዳየነው፣ ‹‹ወንዝ›› ወደ ደረቁ ምድር ‹‹ይወርዳል፣ ‹‹በክንፎቹም›› ይሸፍናል። ወይም 2) አሁን ኢሳይያስ ምሳሌውን በመለወጥ ያህዌ ምድሩን እንደሚጋርድ ወፍ እንደሆነ ይናገራል፤ ‹‹የተዘረጉ ክንፎቹ ይሸፍናሉ››

አማኑኤል
ተርጓሚዎቹ፣ ‹‹አማኑኤል›› የሚለው ስም፣ ‹እግዚአብሔር ከእኛ ጋር› ማለት ነው የሚል የግርጌ ማስታወሻ መጨመር ያስፈልጋቸው ይሆናል። 7፥14 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

Isaiah 8:9

እናንተ ሰዎች እስክትደቅቁ ትሰባበራላችሁ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሰራዊታችሁን እስኪደቅ እሰባብራለሁ››

በሩቅ አገር ያላችሁ አድምጡ
ኢሳይያስ በሌላ አገር ያሉ ሰዎች እንደሚሰሙት አድርጐ ይናገራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በሩቅ ቦታዎች ያላችሁ ሰዎች ሁሉ አድምጡ››

ለጦርነት ተዘጋጁ፤ እስክትደቅቁ ተሰባበሩ፤ ተዘጋጁ እስክትደቅቁ ተሰባበሩ
ይህ በመሠረቱ ተመሳሳይ ቢሆንም፣ የተደጋገመው አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ራሳችሁን ለጦርነት ማዘጋጀት ትችላላችሁ፤ እኔ ግን አሸንፋችኃለሁ።››

ዕቅዱ አውጡ፤ ሆኖም አይጸናም፤ ተመካከሩ ግን አይሳካም
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ይሁዳን ለማጥቃት መዘጋጀት ትችላላችሁ፤ ግን አይሳካላችሁም››

አይጸናም... አይሳካም
ዕቅዱን ወይም ትእዛዝን መፈጸም ዕቅዱን ወይም ትእዛዙን ያወጣው ሰው መስማት የሚፈልገውን ማድረግ ማለት ነው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ማድረግ ያቀዳችሁትን ማድረግ አትችሉም... ወታደሮቻችሁም አዛዦቻቸው ያዘዟቸውን ማድረግ አይችሉም››

Isaiah 8:11

ብርቱ እጁን በላዬ አድርጐ ያህዌ ተናገረኝ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ብርቱ እጁን በላዬ አድርጐ›› የሚለው የያህዌን ኀይል የሚያመለክት ምሳሌ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ በጣም ብርቱ በሆነ መንገድ ተናገረኝ››

በዚህ ሕዝብ መንገድ እንዳልሄድ አስጠነቀቀኝ
ይህ 8፥17 የሚደመደምበት ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅስ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንዲህ ሲል አስጠነቀቀኝ፤ ‹ይህ ሕዝብ የሚያደርገውን አታድርግ››

እነዚህ ሰዎች አድማ ነው የሚሉትን ማንኛውንምነገር አድማ አትበል
ሰዎች አድማ መኖሩን ስለሚያስቡ ስጋት አድሮባቸዋል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሁሌም እነርሱ መጉዳት የሚፈልግ ሰው እንዳለ እንደሚገምቱት እንደ እነዚህ ሰዎች አትጨነቅ››

ልትቀድሱ የሚገባው የሰራዊት ጌታ ያህዌን ብቻ ነው፤ ልትፈሩት የሚገባው እርሱን ነው፤ ልትንቀጠቀጡለት የሚገባውም እርሱ ነው።
ይህን በቀጥተኛ ጥቅስ የምትተረጉም ከሆነ፣ ያህዌ በመጀመሪያ ሰው ደረጃ እየተናገረ መሆኑንም መተርጐም ይኖርብሃል፤ ‹‹ነገር ግን እኔን የሰራዊት ጌታ ያህዌን ልትቀድሱኝ ይገባል፣ እኔን መፍራትና በፊቴም መደንገጥ አለባችሁ››

Isaiah 8:14

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ 8፥11-13 ላይ የጀመረውን ያህዌን ቀጥተኛ ባልሆነ ሁኔታ መጥቀሱን ኢሳይያስ ቀጥሏል። ያህዌ በመጀመሪያ ሰው ደረጃ እየተናገረ እንደሆነ በሚያመለክት ሁኔታ በቀጥታ ሊጠቀስ ይችላል።

እርሱ መቅደስ ይሆናል
‹‹መቅደስ›› የሚለው ቃል ያህዌ ሕዝቡን እንደሚጠብቅና ለእነርሱ እንደሚከላከል የሚያመለክት ምሳሌ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ወደ እርሱ ሲሄዱ፣ እርሱ ይጠብቃቸዋል››

የሚያደናቅፍ ድንጋይ፣ የሚያሰናክልም ዐለት ይሆናል
‹‹የሚያደናቅፍ ድንጋይ›› እና፣ ‹‹የሚያሰናክል ዐለት›› የተሰኙት ያህዌ ሕዝቡን እንደሚጐዳ የሚመለክቱ ምሳሌዎች ናቸው። አንዳንዶች፣ ‹‹የሚያደናቅፍ›› እና፣ ‹‹የሚያሰናክል›› የሚለውን፣ ‹‹የሚያሰናክል››እና፣ ‹‹የሚጥል›› በማለት ይተረጉሙታል። ሌሎች ደግሞ፣ ‹‹በደል›› እና፣ ‹‹መሰናከያ›› በማለት ይተረጉማሉ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የሰዎችን እግር እንደሚመታና እንደሚያሰናክል ድንጋይ፣ ሰዎችን አደናቅፎ እንደሚጥል ዐለት ያህዌ ሕዝቡን ይጐዳል››

ለኢየሩሳሌም ሕዝብም ወጥመድና አሽክላ ይሆናል
‹‹ወጥመድ›› እና፣ ‹‹አሽክላ›› የተሰኙት ቃሎች በአመዛኙ ተመሳሳይ ናቸው፤ ያህዌ የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ለመቅጣት ሲወስን ማምለጥ እንደማይችሉ አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከእርሱ ማምለጥ እንዳይችሉ የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ያጠምዳል››

ወጥመድ
ወፍን በመረብ ወይም በቅርጫት የሚይዝ ነገር

አሽክላ
የእንስሳን እግር ወይም አፍንጫ የሚይዝ ወጥመድ

ብዙዎች ይሰናከላሉ፤ ይወድቃሉ፤ ይሰበራሉ፤ ወጥመድ ውስጥ ይገባሉ፤ ይያዛሉም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ብዙ ሰዎች በድንጋዩ ይሰናከላሉ፤ ከወደቁም አይነሡም፤ ብዙዎች አሽክላው ላይ ይቆማሉ፤ ከዚያ መውጣትም አይችሉም››

ይጠመዳሉ ይያዛሉም
እነዚህ ቃሎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው፤ በወጥመድ እንደሚያዙ አጽንዖት ይሰጣሉ።

Isaiah 8:16

ምስክርነቴን አሸገው፤ ሕጉንም አትመው
እነዚህ ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው፤ አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በላዩ ይህን መልእክት ጽፈህ፣ ጥቅልል ጽሑፉን አጥብቀህ አሸገው››

ምስክርነቴ... ደቀ መዛሙርቴ
‹‹የእኔ›› የሚለው ቃል የሚያመለክተው ማንን እንደሆነ ግልጽ አይደለም። ኢሳይያስ ወይም ያህዌ ሊሆኑ ይችላሉ። ቋንቋህ የሚፈቅድ ከሆነ ተውላጠ ስሙን አሻሚ እንደሆነ መተው ይመረጣል።

ያህዌን እጠብቃለሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እኔ›› የሚያመለክተው ኢሳይያስን ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ፊቱን ከያዕቆብ ቤት የሰወረውን
የያህዌ፣ ‹‹ፊት›› በረከቱንና ሞገሱን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከያዕቆብ ቤት በረከቱን የወሰደውን›› ወይም፣ ‹‹የያዕቆብን ቤት በሞገስ ማየት የተወውን››

የያዕቆብ ቤት
የእስራኤል ሕዝብ

እኔና ያህዌ የሰጠኝ ልጆቼ ለእስራኤል ምልክትና ድንቅ ነን
‹‹እኔና ያህዌ የሰጠን ልጆቼ የእስራኤልን ሕዝብ የምናስጠነቅቅ ምልክቶች ነን›› ልጆቹ ስሞቻቸው ለእስራኤል ሕዝበ መልእክት የሆኑት ሸአብ ያሹብ እና ማኽር-ሻላል-ሃሽ-ባዝ ናቸው።

Isaiah 8:19

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ እየተናገረ ነው።

የሚያነበንቡትንና የሚያሸኮሸኩትን ሟርተኞችና መናፍስት ጠሪዎችን ጠይቁ ቢሏችሁ፤ ሕዝቡ አምላኩን መጠየቅ አይገባውምን? በሕያዋን ምትክ ሙታንን መጠየቅ ለምን አስፈለገ? ወደ ሕጉና ወደ ምስክር ቃሉ ሂዱ
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹መናፍስት ጠሪዎችንና ሟርተኞን፣ የሚያነበንቡትንና የሚያሾከሹኩትን ጠይቁ ይላችኃል፤ ግን ሕዝቡ አምላኩን መጠየቅ የለበትምን›› ትምህርትና ምስክርነት ለማግኘት ለሕያዋን ሙታን መጠየቅ አለባቸውን?›› ወይም 2) ‹‹እነዚያን የሚያነበንቡትንና የሚያሾካሽኩትን መናፍስት ጠሪዎችን ሟርተኞች ጠይቁ ይሏችኃል፤ ሕዝቡ አምላኩን መጠየቅ የለበትምን? ሕጉንና ምስክርነቱን በተመለከተ ለሕያዋን ሙታን መጠየቅ አለባቸውን?››

እንዲህ ይሉሃል
‹‹እነርሱ›› የሚለው የሚያመለክተው በያህዌ የማይታመኑን ነው። ‹‹አንተ›› የሚለው በብዙ ቁጥር ነው፤ በያህዌ የሚታመኑትን ያመለክታል።

መናፍስት ጠሪዎችንና ሟርተኞችን ጠይቁ
‹‹ምን ማድረግ እንዳለባችሁ መናፍስት ጠሪዎችንና ሟርተኞችን ጠይቁ››

መናፍስት ጠሪዎችና ሟርተኞች
ከሙታን ጋር እንነጋገራለን የሚሉ ሰዎች

የሚያነበንቡ
እንደ ወፍ ያለ ድምፅ የሚያወጡ

ሕዝቡ አምላኩን መጠየቅ አይገባውምን? በሕይወት ስላሉትስ ሙታንን መጠየቅ አለባቸውን?
ባለ ማስተዋል ከሙታን ጋር ለመነጋገር ከመሞከር ይልቅ፣ ሕዝቡ እግዚአብሔርን መጠየቅ እንዳለበት እነዚህ ጥያቄዎች ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እንዲመራቸው ሕዝቡ ያህዌን መጠየቅ አለባቸው፤ ከሞቱ ሰዎች መልስ መፈለግ የለባቸውም››

ሕጉና ምስክሩ
ይህም ማለት 1) ‹‹የእግዚአብሔርን መመሪያና ትምህርት ልብ ብላችሁ አድምጡ›› ወይም 2) ‹‹ያኔ እኔ የሰጠሁትን ትምህርትና ምስክር ማስታወስ አለባችሁ›› (ኢሳይያስ 8፥16)

ሕጉ
ይህ ኢሳይያስ 8፥16 ላይ፣ ‹‹ሕጉ›› ተብሎ ከተተረጐመው ጋር አንድ ነው።

ምስክሩ
ኢሳይያስ 8፥16 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት

እነርሱም እንዲህ ያለውን ቃል ባይናገሩ
‹‹ሕጉንና ምስክሩን ባይናገሩ››

የንጋት ብርሃን ስለሌላቸው ነው
እግዚአብሔርን የማያውቁ ምንም ብርሃን በሌለበት ጨለማ እንደሚመላለሱ ሰዎች እንደሆኑ ኢሳይያስ ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጨለማ እንደዋጠው ሰው ስለሆኑ ነው››

Isaiah 8:21

ተጨንቀውና ጨፍግገው
‹‹በጣም አዝነው››

ወደ ድቅድቅ ጨለማ ይገባሉ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ ወደ ድቅድቅ ጨለማ ያገባቸዋል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 9

1 ነገር ግን ተጨንቃ ለነበረች ጨለማ አይሆንም። በመጀመሪያው ዘመን የዛብሎንንና የንፍታሌምን ምድር አቃለለ፣ በኋለኛው ዘመን ግን በዮርዳኖስ ማዶ በባሕር መንገድ ያለውን የአሕዛብን ገሊላ ያከብራል። **2** በጨለማ የሄደ ሕዝብ ታላቅ ብርሃን አየ፤ በሞት ጥላ አገርም ለኖሩ ብርሃን በራላቸው። **3** ሕዝቡን አብዝተሃል፣ ደስታንም ጨምረህላቸዋል፤ በመከር ደስ እንደሚላቸው፣ ሰዎችም ምርኮን ሲካፈሉ ደስ እንደሚላቸው በፊትህ ደስ ይላቸዋል። **4** በምድያም ጊዜ እንደ ሆነ የሸክሙን ቀንበር የጫንቃውንም በትር የአስጨናቂውንም ዘንግ ሰብረሃል። **5** የሚረግጡ የሰልፈኞች ጫማ ሁሉ፣ በደምም የተለወሰ ልብስ ለቃጠሎ ይሆናል፣ እንደ እሳት ማቃጠያም ሆኖ ይቃጠላል። **6** ሕፃን ተወልዶልናልና፣ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፣ ኃያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል። **7** ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ በፍርድና በጽድቅ ያጸናውና ይደግፈው ዘንድ በዳዊት ዙፋንና በመንግሥቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል፣ ለሰላሙም ፍፃሜ የለውም። የእግዚአብሔር ቅንዓት ይህን ያደርጋል። **8** ጌታ በያዕቆብ ላይ ቃልን ሰደደ፣ በእስራኤልም ላይ ወደቀ። **9** በትዕቢትና በልብ ኵራት የሚናገሩ በኤፍሬምና በሳርያ የሚኖሩ ሕዝብ ሁሉ። **10** "ጡቡ ወድቆአል፣ ነገር ግን በተወቀረ ድንጋይ እንሠራለን፤ የሾላ ዛፎች ተቈርጠዋል፣ ነገር ግን ዝግባን እንተካባቸዋለን" የሚሉት ሁሉ ያውቃሉ። **11** ስለዚህ እግዚአብሔር በረአሶን ላይ በጽዮን ተራራ ተቋቋሚ ያስነሣበታል፣ **12** ጠላቶቹን ሶርያውያንንም ከምሥራቅ፣ ፍልስጥኤማውያንንም ከምዕራብ ያንቀሳቅስበታል፤ እስራኤልንም በተከፈተ አፍ ይበሉታል። በዚህም ሁሉ እንኳ ቍጣው አልተመለሰችም፣ ነገር ግን እጁ ገና ተዘርግታ ትኖራለች። **13** ሕዝቡ ግን ወደ ቀሠፋቸው አልተመለሱም፣ የሠራዊትንም ጌታ እግዚአብሔርን አልፈለጉም። **14** ስለዚህ እግዚአብሔር ራስና ጅራትን፣ የሰሌኑን ቅርንጫፍና እንግጫውን በአንድ ቀን ከእስራኤል ይቆርጣል። **15** ሽማግሌውና ከበርቴው እርሱ ራስ ነው፤ በሐሰትም የሚያስተምር ነቢይ እርሱ ጅራት ነው። **16** ይህን ሕዝብ የሚመሩ ያስቱአቸዋል፤ በእነርሱ የሚመሩትም ይዋጣሉ። **17** ስለዚህም ሰው ሁሉ ዝንጉና ክፉ ሠሪ ነውና፣ አፍም ሁሉ ስንፍናን ይናገራልና ስለዚህ ጌታ በጕልማሶቻቸው ደስ አይለውም፥ ለድሀ አደጎቻቸውና ለመበለቶቻቸውም አይራራም። በዚህም ሁሉ እንኳ ቍጣው አልተመለሰችም፣ ነገር ግን እጁ ገና ተዘርግታ ትኖራለች። **18** ክፋት እንደ እሳት ይቃጠላል፤ ኵርንችቱንና እሾሁን ይበላል፤ ጭፍቅ የሆነውንም ዱር ያቃጥላል፥ ጢሱም ተትጐልጕሎ እንደ ዓምድ ይወጣል። **19** በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ቍጣ ምድር ተቃጥላለች፤ ሕዝቡም እሳት እንደሚበላው እንጨት ሆኖአል፤ ሰውም ለወንድሙ ራርቶ አያድንም። **20** ሰው ከቀኙ በኩል ሥጋ ቆርጦም ይራባል፤ ሥጋውን በግራ በኩል ይበላል አይጠግብምም። እያንዳንዱም የገዛ ራሱን ክንድ ሥጋ ይበላል፤ **21** ምናሴ ኤፍሬምን፣ ኤፍሬምም ምናሴን ይበላል፤ እነርሱም በአንድነት የይሁዳ ጠላቶች ይሆናሉ። በዚህም ሁሉ እንኳ ቍጣው አልተመለሰችም፣ ነገር ግን እጁ ገና ልትመታ ትዘረጋለች።

Isaiah 9:1

በጨለማ የሚኖር ሕዝብ ብርሃን ወጣለት
መንፈሳዊ ጉስቁልና ውስጥ ያሉ ሰዎች በድቅድቅ ጨለማ እየተመላለሱ እንደሆነ ኢሳይያስ ይናገራል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጭንቀት ውስጥ ለነበረች ያህዌ ጨለማን ያስወግዳል››

ድንግዝግዝ
ይህ፣ ‹‹ከፊል ወይም ሙሉ ጨለማ›› ማለት ነው። ኢሳይያስ 8፥22 ላይ ‹‹ድንግዝግዝ›› የሚለውን በተረጐምህበት መንገድ ተርጕመው።

ተጨንቃ ለነበረች
‹‹ከባድ ስቃይና ሀዘን ውስጥ ለነበረች›› ምናልባትም ይህ የይሁዳን ሕዝብ የሚመለከት ሊሆን ይችላል።

በቀደመው ዘመን የዛብሎንንና የንፍታሌምን ምድር አዋረደ
‹‹ምድር›› በዚያ አካባቢ የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ባለፈው ጊዜ ጌታ በዛብሎንና በንፍታሌም የሚኖሩትን ዝቅ አደረገ››

በኋለኛው ዘመን ግን ከዮርዳኖስ ወንዝ ማዶ በባሕር መንገድ አጠገብ ያለውን የአሕዛብ ገሊላ ያከብራል
ይህ የሚናገረው በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ስለሚወክለው ገለላ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ወደ ፊት ጌታ በሜዲትራንያንና በዮርዳኖስ ወንዝ መካከል ባለው መንገድ ላይ ያለውን የአሕዛብ ገሊላን ያከብራል››

የአሕዛብ ገሊላ
‹‹አሕዛብ›› በገሊላ የሚኖሩ የሌላ አገር ሰዎች ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ብዙ ባዕዳን የሚኖሩበት ገሊላ››

በጨለማ የሚኖር... በሞት ጥላ ምድር ለኖሩት
ኢሳይያስ በጨለማ ወይም በሞት ጥላ ምድር ውስጥ ከመኖራቸው የተነሣ የኅጢአትና የመከራ ሕይወት ስለሚኖሩ ሰዎች ይናገራል።

ታላቅ ብርሃን... ብርሃን ወጣላቸው
እዚህ ላይ ‹‹ብርሃን›› ተስፋና መዳንን ይወክላል።

የሞት ጥላ ምድር
‹‹የሞት ጥላ›› የሚለው ድቅድቅ ጨለማ ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ድቅድቅ ጨለማ ያለበት ምድር››

Isaiah 9:3

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ የሚያድነው መቼ እንደሆነ መናገር ቀጥሏል። እነዚህ ነገሮች የሚሆኑት ወደ ፊት ቢሆንም (ኢሳይያስ 9፥1) ኢሳይያስ አሁን እንደ ተፈጸሙ አድርጐ ይናገራል። ይህም በትክክል እንደሚፈጸሙ አጽንዖት ይሰጣል።

ሕዝብን አበዛህ፤ ደስታቸውንም ጨመርህ
‹‹አንተ›› የሚለው የሚያመለክተው ያህዌን ነው። ‹‹እነርሱ›› የሚለው የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው፤ እንደ እስራኤል አካል ኢሳይያስ ራሱንም ይጨምራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጌታ ሆይ፣ አንተ ሕዝባችንና ደስታችንን እጅግ ታበዛለህ››

ሰዎች ምርት ሲሰበስቡ፣ ምርኮንም ሲካፈሉ ደስ እንደሚላቸው ሁሉ እነርሱም በፊትህ ደስ ይላቸዋል።
ያህዌ ለእስራኤል የሚሰጠው ደስታ ምርት ሲሰበስቡና ምርኮን ሲካፈሉ ደስ እንደሚላቸው ሰዎች ዐይነት ደስታ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሰዎች ምርት ሲሰበስቡ፣ ጦርነት ካበቃ በኋላ ወታደሮቹ የወሰዱትን ሲከፋፈሉ ደስ እንደሚላቸው እነርሱም በፊትህ ደስ ይላቸዋል››

Isaiah 9:4

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ስለሚያድንበት ጊዜ መናገሩን ቀጥሏል። ምንም እንኳ እነዚህ ነገሮች የሚሆኑት ወደ ፊት ቢሆንም፣

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

(ኢሳይያስ 9፥1-2) ኢሳይያስ አሁን እንደ ተፈጸሙ አድርጐ ይናገራል። ይህም በእርግጥ እንደሚፈጸም አጽንዖት ይሰጣል።

ምድያም ድል በተመታ ጊዜ እንደሆነው የከበዳቸውን ቀንበር ሰብረህላቸዋል
የአሦራውያን ባርያዎች የነበሩ እስራኤላውያን ቀንበር እንደ ተሸከመ በሬ መሆናቸውን ኢሳይያስ ይናገራል። ይህ የሚሆነው ወደ ፊት ነው፤ እርሱ ግን አሁን እንደ ተፈጸመ አድርጐ ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በምድያም ቀን እንደሆነው ሰው ቀንበርን ከበሬ ላይ እንደሚያነሣ አንተም የጨቋኞቻቸው ባርያዎች የሆኑበን የእስራኤል ሕዝብ ነጻ ታወጣለህ››

የከበደውን ቀንበር... ትከሻው... የተጨቆነበት
ኢሳይያስ የእስራኤል ሕዝብ አንድ ሰው እንዲሆኑ አድርጐ ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የከበዳቸው ቀንበር... ትከሻቸው... የተጨቆኑበትን››

ትከሻው ላይ የነበረው ሞፈር
በሬ ትከሻ ላይ የሚውለው ቀንበር አካል ነው

ሞፈር
ሌላው አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በትር›› በሬዎቹ እንዲሠሩ የሚመቱበትንና ሌሎች ላይ ለመግዛት አንድ ሰው ስላለው ኀይል ምሳሌ የሆነ የእንጨት አካል ማለት ነው።

የጨቋኙ በትር
ጨቋኙ የይሁዳ ሕዝብ ላይ የነበረው ኀይል በርትተው እንዲሠሩ በሬዎቹን ለመምታት እንደሚጠቀምበት እንጨት እንደ ነበር ኢሳይያስ ይናገራል።

በምድያም ቀን እንደሆነው
‹‹ቀን›› የሚለው ቃል ከአንድ ቀን በላይ የወሰዱ ድርጊቶችን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አንተ ምድያምን እንዳሸነፍህበት ጊዜ››

የጦረኞች ጫማ ሁሉ፣ በደም የተለወሰ ልብስም ሁሉ ይቃጠላል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ በደም የተለወሰውን የወታደሮቹን ጫማና ልብሳቸውን ታቃጥላለህ።››

ለእሳቱ ማገዶ ይሆናል
ይህን በአዲስ ዐረፍተ ነገር በመተርጐም የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ይቃጠላል። ልብሳቸውንና ጫማቸውን ማገዶ ታደርገዋለህ››

Isaiah 9:6

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ስለሚያድንበት ጊዜ መናገሩን ቀጥሏል (ኢሳይያስ 9፥1-2) እነዚህ ነገሮች የሚፈጸሙት ወደ ፊት ቢሆንም ኢሳይያስ አሁን እንደ ተፈጸሙ አድርጐ ይናገራል። ይህም በእርግጥ እንደሚፈጸሙ አጽንዖት ይሰጣል።

ሕፃን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅ ተወልዶልናል
እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው። ‹‹ለእኛ›› የሚለው ቃል ተናጋሪውንና ሰሚዎቹን ያጠቃልላል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጌታ ሕፃን ልጅ ይሰጠናል››

አለቅነት በጫንቃው ላይ ይሆናል
የአለቅነት ሥልጣኑ የገዢነቱ ሥልጣኑ ምልክት የሆነው ልብስ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የገዢነት ሥልጣኑን ጫንቃው ላይ ይለብሳል›› ወይም፣ ‹‹እንደ ንጉሥ የሚገዛበት ሥልጣን ይኖረዋል››

መካር
‹‹ነገሥታትን የሚያማክር››

ለመንግሥቱ ስፋት፣ ለሰላሙም ብዛት ፍጻሜ የለውም
‹‹ጊዜ እያለፈ ሲሄድ፣ በጣም ብዛት ባላቸው ሰዎች ላይ ይገዛል፤ እጅግ በበዛ ሰላም ውስጥ ይኖራሉ››

በዳዊት ዙፋን ይገዛል
‹‹በዳዊት ዙፋን›› ላይ መቀመጥ የመግዛት መብትን ያመለክታል፤ የእስራኤል ንጉሥ የሚሆኑት የዳዊት ዘሮች ብቻ ናቸው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እንደ ዳዊት ዘር የመግዛት መብት ይኖረዋል››

መንግሥቱን በፍትሕና በጽድቅ ይመሠርታል፤ ደግፎ በመያዝም ያጸናዋል።
ይህን በአዲስ ዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹መንግሥቱ፤ መንግሥቱን ያጸናል፤ ይጠብቃል፤ መልካምና ትክክል የሆነውን ያደርጋል››።

የሰራዊት ጌታ ያህዌ
ኢሳይያስ 1፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት፡

Isaiah 9:8

ጌታ በያዕቆብ ላይ ቃል ላከ፤ በእስራኤልም ላይ ይወድቃል
‹‹ቃል መላክ›› መናገር ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጌታ በእስራኤል ሕዝብ ላይ ተናገረ››

ያዕቆብ... እስራኤል... ኤፍሬም... ሰማርያ
እነዚህ ስሞች ሁሉ የሚያመለክቱት የሰሜናዊውን የእስራኤል መንግሥት ሰዎች ነው።

ሕዝቡ በሙሉ፣ ኤፍሬምና የሰማርያ ነዋሪዎች ይህን ያውቃሉ
የሚያውቁት ምንን እንደሆነ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጌታ እንደ ፈረደባቸው ሰዎች ሁሉ፣ ኤፍሬምና በሰማርያ የሚኖሩት እንኳ ያውቃሉ››

ጡቦቹ ወድቀዋል፤ እኛ ግን በጥርብ ድንጋይ መልሰን እንገነባለን፤ የሾላ ዛፎች ተቈርጠዋል፤ እኛ ግን በዝግባ እንተካለን
ምን ማለት እንደሆነ የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የፈረሱት ከተሞቻችንን ተራ ጡብ በጥርብ ድንጋይ መልሰን እንተካዋለን፤ ተራ የሾላ ዛፍ በነበረበትም ቦታ ዝግባ እንተክላለን››

Isaiah 9:11

ስለዚህ ያህዌ ጠላቱ የሆነውን ረአሶንን ያስነሣል
እዚህ ላይ፣ ‹‹ረአሶን›› የሚወክለው ራሱንና ሰራዊቱን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ስለዚህ ያህዌ በእስራኤል ሕዝብ ላይ ረአሶንና ሰራዊቱን ያስነሣል››

ረአሶን
የሰው ስም። ኢሳይያስ 7፥1 ላይ ረአሶንን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት

ባለጋራዎቻቸውን ያነሣሣቸዋል
‹‹ያነሣሣል›› ለጥቃት ያነሣሣል ማለትን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ የእስራኤልን ጠላቶች ያነሣሣባቸዋል››

አፋቸውን ከፍተው እስራኤልን ይቦጫጭቋቸዋል።
‹‹ይቦጫጭቋቸዋል›› የሚለው የዱር አራዊት የያዙትን እንስሳ እንዴት የሚበሉበትን ሁኔታ ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የዱር አውሬ ሌሎች እንስሳትን እንደሚበላ፣ የጠላት ሰራዊት የእስራኤልን ሕዝብ ያወድማል››

በዚህ ሁሉ ቁጣው ገና አልበረደም፤ ይልቁን እጁም
‹‹ይህ ሁሉ ቢሆን እንኳ አሁንም እንደ ተቆጣ ነው፤ እጁም›› ኢሳይያስ 5፥25 ላይ ይህን እንዴ እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እጁ እንደ ተዘረጋ ነው።
ኢሳይያስ ያህዌን ሌላውን ሰው ለመምታት ካሰበ ሰው ጋር ያመሳስለዋል። ይህ ያህዌ እስራኤልን እንደሚቀጣ ምሳሌ ነው። ኢሳይያስ 5፥25 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አሁንም እነርሱን ለመቅጣት እንደ ተዘጋጀ ነው››

Isaiah 9:13

የሰራዊት ጌታ ያህዌ
ኢሳይያስ 1፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

ራስንና ጅራትን
ቁጥር 15 ላይ ኢሳይያስ ይህን ምሳሌ ይገልጸዋል። ‹‹በራስ›› የተመሰሉት፣ ‹‹ሽማግሌዎችና የተከበሩ ሰዎች›› ሲሆኑ፣ ‹‹ጭራ›› ደግሞ፣ ‹‹ሐሰትን የሚያስተምሩ ነቢያት›› ምሳሌ ነው።

የዘንባባ ቅርንጫፍና ሸንበቆውን
‹‹የዘንባባ ቅርንጫፍ›› ከፍ ብሎ ዛፉ ላይ የሚያድግ ሲሆን፣ በጣም አስፈላጊና ሌሎችን የሚገዙ ሰዎች ምሳሌ ነው። ‹‹ሸንበቆ›› ጥልቅ ያልሆነ ውሃ ውስጥ የሚያድግ ሲሆን፣ በሌሎች የሚገዙ በጣም አስፈላጊ ያልሆኑ ድኾች ምሳሌ ነው።

Isaiah 9:16

ይህን ሕዝብ የሚመሩት ያስቱታል
ሕዝቡ እንዲያምፅ የሚያደርጉ መሪዎች በተሳሳተ መንገድ የሚመሩ መሪዎች እንደሆኑ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የእስራኤል መሪዎች ሕዝቡ ለእግዚአብሔር እንዳይታዘዝ አደረጉ››

በእነርሱ የሚመሩ ይዋጣሉ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፤ የዚህ ትርጕም፣ 1) አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እነርሱ የሚመሩዋቸው ግራ ይጋባሉ›› ማለት ሊሆን ይችላል፤ ወይም 2) አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የሚመሩትን ያህዌ ያጠፋል›› ማለት ሊሆን ይችላል።

አፍ ሁሉ ከንቱ ነገር ይናገራል
‹‹አፍ›› የሚለው ሰውየውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሰው ሁሉ ከንቱ ነገር ይናገራል››

በዚህ ሁሉ ቁጣው ገና አልበረደም፤ ይልቁን እጁ
‹‹ይህ ሁሉ ሆኖ እንኳ፣ አሁንም እንደ ተቆጣ ነው፤ እጁም›› ኢሳይያስ 5፥25 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

እጁ እንደ ተዘረጋ ነው
ኢሳይያስ ያህዌን ሌላውን ሰው ለመምታት እጁን ካነሣ ሰው ጋር ያመሳስለዋል። ይህ ያህዌ እስራኤልን የመቅጣቱ ምሳሌ ነው። ኢሳይያስ 5፥25 ላይ ይህን እንዴ እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አሁንም እነርሱን ለመቅጣት እንደ ተዘጋጀ ነው››

Isaiah 9:18

ርኩሰት እንደ እሳት ይቀጣጠላል፤ ኩርንችቱንና እሾኹን ይበላል፤ ጥቅጥቅ ያለውን ደን ያነዳል
የሕዝቡ ክፉ ሥራ በአውዳሚ እሳት ተመስሎአል። እሳቱ ከእንግዲህ ሰዎች በማይኖሩባቸው ቦታዎች የሚበቅሉትን፣ ‹‹ኩርንችትና እሾኽ›› ያቃጥላል፤ ሰዎች የሚኖሩባቸውን ቦታዎች ስላጠፋ፣ ከዚያ በፊት ሰው ያልነበረበትን ‹‹ጥቅጥቅ ያለውን ደን›› ያወድማል።

ኩርንችት... እሾኽ
‹‹ኩርንችትና›› እና፣ ‹‹እሾኽ›› ጥቅም የለሽ እሾኻማ ተክሎችን ያመለክታሉ፤ ይህን በአንድ ቃል መተርጐም ይቻላል። ኢሳይያስ 7፥23 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እሾኻማ ቁጥቋጦ››

በሰራዊት ጌታ በያህዌ ቁጣ ምድር ትጋያለች
‹‹የሰራዊት ጌታ ያህዌ›› የሚለውን ኢሳይያስ 1፥9 ላይ ያለውን እንደ ተረጐምህ ተርጕመው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ምድርን እንደሚያጋይ እሳት የእግዚአብሔር ጽኑ ቁጣ የእስራኤልንም ሕዝብ ያነዳል››

ማንም ወንድሙን አያድንም
‹‹አያድንም›› ከጥፋት አያወጣም ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ማንም የገዛ ወንድሙ እንዲያመልጥ መርዳት አይችልም››

Isaiah 9:20

በቀኝ እጃቸው ይነጥቃሉ፤... በግራ እጃቸው
ይህ ማለት ምግብ ካገኙ ይነጥቃሉ ማለት ነው።

እያንዳንዱ የገዛ ክንዱን እንኳ ይበላል
ይህም ማለት 1) ሰዎች የገዛ ክንዳቸውን እንኳ እስኪበሉ ድረስ በጣም ይራባሉ ማለት ሊሆን ይችላል ወይም 2) ‹‹ክንድ›› የሰውየው ወገን ማለት ሊሆን ይችላል።

በዚህ ሁሉ ቁጣው ገና አልበረደም፤ ይልቁን እጁ
‹‹ይህ ሁሉ ሆኖ እንኳ አሁንም እንደ ተቆጣ ነው፤ እጁም›› ኢሳይያስ 5፥25 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

አሁንም እጁ እንደ ተዘረጋ ነው
ኢሳይያስ ያህዌን ሌላውን ሰው ለመምታት እጁን ከዘረጋ ሰው ጋር ያመሳስለዋል። ይህ ያህዌ እስራኤልን የመቅጣቱ ምሳሌ ነው። ኢሳይያስ 5፥25 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አሁንም እነርሱን ለመቅጣት እንደ ተዘጋጀ ነው››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 10

1 መበለቶችም ቅሚያቸው እንዲሆኑ፣ ድሀ አደጎችንም ብዝበዛቸው እንዲያደርጉ፣ የድሀውን ፍርድ ያጣምሙ ዘንድ፣ 2 የችግረኛውንም ሕዝቤን ፍርድ ያጐድሉ
ዘንድ የግፍን ትእዛዛት ለሚያዝዙ፣ ክፉንም ጽሕፈት ለሚጽፉ ወዮላቸው! 3 በፍርድ ቀን፣ መከራም ከሩቅ በሚመጣበት ዘመን ምን ታደርጉ ይሆን? ለእርዳታስ
ወደ ማን ትሸሻላችሁ? ብልጥግናችሁንስ ወዴት ትተዉታላችሁ? 4 ከእስረኞች በታች ይጐነበሳሉ፣ ከተገደሉትም በታች ይወድቃሉ። በዚህም ሁሉ እንኳ ቍጣው
አልተመለሰችም፣ ነገር ግን እጁ ገና ልትመታ ተዘርግታለች። 5 ለቍጣዬ በትር ለሆነ፣ የመዓቴም ጨንገር በእጁ ላለ ለአሦር ወዮለት! 6 እርሱንም በዝንጉ ሕዝብ
ላይ እልካለሁ፣ ምርኮውንና ብዝበዛውንም ይወስድ ዘንድ እንደ አደባባይም ጭቃ የተረገጡ ያደርጋቸው ዘንድ በምቈጣቸው ሰዎች ላይ አዝዘዋለሁ። 7 እርሱ
እንዲሁ አያስብም፣ በዚህ ሁኔታ አይወጥንም። ነገር ግን በልቡ በርካታ አሕዛብን ለማጥፋትና ለመቍረጥ በልቡ አለ። 8 እንዲህ ብላልና፣ "መሳፍንቴ ሁሉ
ነገሥታት አይደሉምን? 9 ካልኖ እንደ ከርከሚሽ አይደለችምን? ሐማትስ እንደ አርፋድ አይደለችምን? ሰማርያስ እንደ ደማስቆ አይደለችምን? 10 የተቀረጹ
ምስሎቻቸው ከኢየሩሳሌምና ከሰማርያ ምስሎች የበለጡትን የጣዖቶችን መንግሥታት እጄ እንደረታች፣ 11 በሰማርያና በጣዖቶችዋም እንዳደረግሁ፣ እንዲሁስ
በኢየሩሳሌምና በጣዖቶችዋ አላደርግምን?" 12 ስለዚህ እንዲህ ይሆናል፤ ጌታ ሥራውን ሁሉ በጽዮን ተራራና በኢየሩሳሌም ላይ በፈጸመ ጊዜ፣ "የአሦርን ንጉሥ
የኩሩ ልብ ፍሬን የዓይኑንም ከፍታ ትምክሕት እቀጣለሁ።" 13 እርሱ እንዲህ ብሎአልና፣ "አስተዋይ ነኝና በእጄ ኃይልና በጥበቤ አደረግሁት፤ የአሕዛብን
ድንበሮች አራቅሁ፣ ሀብታቸውንም ዘረፍሁ፣ እንደ ጀግናም ሆኜ በምድር የተቀመጡትን አዋረድሁ፤ 14 እጄም የአሕዛብን ባለጠግነት እንደ ወፍ ቤት አገኘች፤
የተተወም እንቍላል እንደሚሰበሰብ፣ እንዲሁ እኔ ምድርን ሁሉ ሰበሰብሁ። ክንፉን የሚያሪግብ አፉንም የሚከፍት የሚጮኽም የለም።" 15 በውኑ መጥረቢያ
በሚቈርጥበት ሰው ላይ ስለ ራሱ ይመካልን? ወይስ መጋዝ በሚስበው ላይ ራሱን ይክባልን? ይህስ፣ በትር የሚያነሣውን እንደ መነቅነቅ ዘንግም እንጨት
ያይደለውን እንደ ማንሣት ያህል ነው። 16 ስለዚህም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር በወፍራሞች ጦረኞቹ ላይ ክሳትን ይልካል፤ ከክብሩም በታች ቃጠሎው እንደ
እሳት መቃጠል ይነድዳል። 17 የእስራኤልም ብርሃን እንደ እሳት፣ ቅዱሷም እንደ ነበልባል ይሆናል፤ እሾሁንና ኵርንችቱን በአንድ ቀን ያቃጥላል ይበላውማል።
18 ከነፍስም እስከ ሥጋ ድረስ የዱሩንና የሚያፈራውን እርሻ ክብር ይበላል፣ ይህም የታመመ ሰው እንደሚሰለስል ይሆናል። 19 ታናሽ ብላቴናም ይጽፋቸው ዘንድ
እስኪችል ድረስ የቀሩት የዱር ዛፎች በቍጥር ጥቂት ይሆናሉ። 20 በዚያም ቀን፣ የእስራኤል ቅሬታ ከያዕቆብም ቤት ያመለጡት ከእንግዲህ ወዲህ በመቱአቸው
ላይ አይደገፉም፣ ነገር ግን በእስራኤል ቅዱስ በእግዚአብሔር ላይ በእውነት ይደገፋሉ። 21 የያዕቆብም ቅሬታ ወደ ኃያል አምላክ ይመለሳሉ። 22 እስራኤል
ሆይ፣ የሕዝብህ ቍጥር እንደ ባሕር አሸዋ ቢሆን ቅሬታው ይመለሳል። ጽድቅ የተትረፈረፈበትም ጥፋት ተወስኖአል። 23 የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርም ያለቀ
የተቈረጠ ጥፋትን በምድር ሁሉ መካከል ይፈጽማል። 24 ስለዚህ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "በጽዮን የምትኖር ሕዝቤ ሆይ አሦርን አትፍራ።
አሦር በበትር ይመታሃል፣ ግብጽም እንዳደረገ ዘንጉን ያነሣብሃል። 25 ቍጣዬ እስኪፈጸም መዓቴም እስኪያጠፋቸው ድረስ በጣም ጥቂት ጊዜ ቀርቶአልና
አትፍራው።" 26 የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርም ምድያምን በሔሬብ ዓለት በኩል እንደ መታው ጅራፍ ያነሣበታል፤ በትሩንም በባሕር ላይ ያነሣል፣ በግብጽም
እንዳደረገ ያነሣዋል። 27 በዚያም ቀን፣ ሸክሙ ከጫንቃህ ቀንበሩም ከአንገትህ ላይ ይወርዳል፤ ቀንበሩም ከአንገትህ ከፍተኛ ውፍረት የተነሣ ይሰበራል። 28
ጠላት ወደ አንጋይ መጥቶአል፤ በመጌዶን በኩል አልፎአል፤ በማክማስ ውስጥ ዕቃውን አኑሮአል፤ 29 በመተላለፊያ አልፎአል፤ በጌባ ማደሪያው ነው፤ ራማ
ደንግጣለች፤ የሳኦል ጊብዓ ኰብልላለች። 30 አንቺ የጋሊም ልጅ ሆይ፥ በታላቅ ድምፅሽ ጩኺ፤ ላይሳ ሆይ፥ አድምጪ! አንቺ ምስኪን ዓናቶት ሆይ፣ መልሽላት!
31 መደቤና እየሸሸች ናት፣ በግቤርም የሚኖሩ ቤተሰቦቻቸውን አሸሽተዋል። 32 ዛሬ በኖብ ይቆማል፤ በጽዮን ሴት ልጅ ተራራ በኢየሩሳሌም ኮረብታ ላይ
ቡጢውን ይንጣል። 33 ተመልከቱ፣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ቅርንጫፎቹን በሚያስፈራ ኃይል ይቈርጣል፤ በቁመት የረዘሙትም ይቈረጣሉ፣ ከፍ ያሉትም
ይዋረዳሉ። 34 ጭፍቅ የሆነውንም ዱር በመጥረቢያ ይቈርጣል፣ ሊባኖስም በኃያሉ እጅ ይወድቃል።

Isaiah 10:1

ፍትሕ የጐደለውን ሕግ ለሚያወጡ፣ ጭቆና የሞላበትን ሥርዐት ለሚደነግጉ
እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለሰው ሁሉ መልካም ያልሆኑ ሕጐችንና ሥርዐቶችን ለሚያወጡ››

የድኾችን መብት ይጋፋሉ፤ የተጨቆነውን ሕዝቤን ፍትሕ ያዛባሉ
እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በሕዝቤ መካከል ላሉ ድኾችና ችግረኞች ፍትሕ አያደርጉም››

ችግረኛ
‹‹ድኻ››

መበለቶችን ይበዘብዛሉ
‹‹ባሎቻቸው ከሞቱባቸው ሴቶች ማንኛውንም ነገር ይወስዳሉ››

ወላጅ የሌላቸውን ያጠቃሉ
ኢሳይያስ ወላጅ የሌላቸውን አራዊት አድነው ከሚበሏቸው እንስሳት ጋር አመሳስሎአቸዋል፡፡ ይህም ወላጅ የሌላቸው ዐቅመ ቢስ መሆናቸውንና ዳኞች በቀላሉ ሊጐዱዋቸው እንደሚችሉ አጽንዖት ይሰጣል፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሚያድነውን እንደሚያጠቃ አውሬ ወላጆች የሌላቸውን ልጆች ያጠቃሉ››

ታዳኝ
ኢሳይያስ 5፥29 ላይ እንዳለው፣ ‹‹ታዳኝ›› ተብሎ ተተርጒሞአል፡፡

Isaiah 10:3

በፍርድ ቀን ምን ታደርጋላችሁ... ምን ይውጣችኃል?
ኢሳይያስ ጥያቄውን ያቀረበው ድኻውንና ደካማውን የሚጐዱ በይሁዳ ያሉ ሰዎችን ለመገሠጽ ነው፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በፍርድ ቀን ምንም ማድረግ አትችሉም... ምን ይሻላችኃል!››

የፍርድ ቀን
‹‹ያህዌ ለፍርድ ሲመጣ›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ እናንተን በሚቀጣበት ቀን››

ርዳታ ለማግኘት ወደ ማን ትሸሻላችሁ? ሀብታችሁንስ የት ታደርጉታላችሁ?
ኢሳይያስ ጥያቄውን ያቀረበው ደኻውንና ደካማውን የሚጐዱ በይሁዳ ያሉ ሰዎችን ለመገሠጽ ነው፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ርዳታ ለማግኘት የምትሄዱበት የለም፤ ሀብታችሁን የምትደብቁባትም ቦታ የላችሁም!

ምን አይተርፋችሁም፣ ትሸማቀቃላችሁ
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ከሀብታችሁ ምንም አይተርፍም፤ ትሸማቀቃላችሁ›› ወይም 2) ‹‹ከመሸማቀቅ ሌላ የምታደርጉት ነገር የለም››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በታሰሩ ወይም በሞቱት መካከል ትሸማቀቃላችሁ
‹‹ጠላቶቻችሁ አሥረው ይወስዳችኃል ወይም ትገደላላችሁ››

በዚህ ሁሉ ቁጣው ገና አልበረደም፤
‹‹ይህ ሁሉ ሆኖ እንኳ፣ አሁንም እንደ ተቆጣ ነው›› ኢሳይያስ 5፥25 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

አሁንም እጁ እንደ ተዘረጋ ነው
ኢሳይያስ ያህዌን ሌላውን ሰው ለመምታት እጁን ከዘረጋ ሰው ጋር ያመሳስለዋል። ይህ ያህዌ እስራኤልን የመቅጣቱ ምሳሌ ነው። ኢሳይያስ 5፥25 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አሁንም እነርሱን ለመቅጣት እንደ ተዘጋጀ ነው››

Isaiah 10:5

ወዮ
ይህ ቃል አሦር ላይ እግዚአብሔር የሚያመጣው ቅጣት መጀመሩን ያመለክታል።

አሦራውያን
ይህ የሚያመለክተው የአሦርን ነገሥታት ነው።

የቁጣዬ በትር የመቅሠፍቴም ዱላ በእጁ ላለው
ሁለቱም በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። ያህዌ የአሦር ንጉሥን እጁ ላይ መሣሪያ ከያዘና በዚያም ሌሎችን ከሚመታ ሰው ጋር ያመሳስለዋል። ይህም የአሦር ንጉሥና ሰራዊቱ ያህዌ እስራኤልን የሚቀጣበት መሣሪያዎች መሆናቸውን አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ቁጣዬን ለማሳየት የምጠቀምበት እጄ ላይ እንዳለ መሣሪያ ለሆነ››

እልከዋለሁ... አዝዘዋለሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እርሱ›› የሚለው ቃል የሚያመለክተው የአሦርን ንጉሥ ነው። እግዚአብሔር ንጉሡን ብቻ ሳይሆን፣ ከእርሱ ጋር የአሦርን ሰራዊም የላከ ይመስላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የአሦርን ሰራዊት እልካለሁ... አዝዛቸዋለሁ››

እብሪተኛ ሕዝብ ላይ፣ የሚፈስሰው ቁጣየን የሚሸከም ሕዝብ ላይ
‹‹ትዕቢት የሚላበትን እኔንም በጣም ያስቆጣኝን ሕዝብ እንዲቀጣ››

የሚፈስሰውን ቁጣዬን የሚሸከም
የእርሱ ቁጣ መያዣው ከሚችለው በላይ ሞልቶ እንደሚፈስስ ነገር እንደሆነ ያህዌ ይናገራል፣ ‹‹ሕዝቡ›› ይህን መያዣ ለመሸከም ቢሞክሩም በጣም ከባድ ነበር፤ ሞልቶ መፍሰስ ከጀመረ በኃላ እንኳ ይህዌ መጨመሩን ቀጥሏል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከቀጣኃቸው በኃላ እንኳ አሁንም የተቆጣሁት ሕዝብ››

ምርኮ እንዲያግበሰብስ
‹‹ያላቸውን ሁሉ እንዲወስድ››

የሚታደነውን እንዲወስድ
እንደ ታዳኝ ነገር ሕዝቡን እንዲወስድ። ‹‹ታዳኝ›› የሚለውን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ኢሳይያስ 5፥29 ተመልከት።

እንደ ጭቃ እንዲረግጣቸው
ይህ ማለት፣ 1) የአሦር ሰራዊት እስራኤልን ማጥቃቱን ጭቃው ምን እንደሚሆን ደንታ ሳይኖረው ጭቃው ላይ ከሚረማመድ ሰው ጋር ያመሳስለዋል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንደ ጭቃ እስኪሆኑ ድረስ ይረግጣቸዋል›› ወይም 2) እንደ ጭቃ እስኪሆኑና መነሣት እስከማይችሉ ድረስ ሕዝቡ ሌሎች ሰዎችን ይረግጣሉ። ይህ የሚያመለክተው ሙሉ በሙሉ እንደሚያሸንፏቸው ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ፈጽሞ ያሸንፏቸዋል››

Isaiah 10:7

እርሱ ግን እንዲህ አላሰበም፤ በልቡም ይህ አልነበረም
‹‹እንዲህ›› እና፣ ‹‹ይህ›› የተሰኙትን ቃሎች የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የአሦር ንጉሥ እኔ የነገርሁትን ለማድረግ አላሰበም፤ እንደ መሣሪያ እየተጠቀምሁበት እንደ ነበረም አላስተዋለም ነበር››

ዕቅዱ ለማጥፋት፣ ብዙ ሕዝቦችንም ለመደምሰስ ነበር
‹‹ማጥፋት›› እና፣ ‹‹መደምሰስ›› በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። ጥቅም ላይ የዋሉት አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ብዙ ሕዝቦችን ፈጽሞ ለመደምሰስ ይፈልጋል››

የጦር አዛዦቼ በሙሉ ነገሥታት አይደሉምን?
የአሦር ንጉሥ ይህን ጥያቄ ያቀረበው ሁሉም ማወቅ አለበት ብሎ ለሚያስበው አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ድል ባደረግሁት አገር ሁሉ ላይ ነገሥታቴን የጦር አዛዦች አድርጌአለሁ››

ካልኖ እንደ ከርከሚሽ አይደለችምን? ሐማት እንደ አርፋድ አይደለችምን? ሰማርያ እንደ ደማስቆ አይደለችምን?
የአሦር ንጉሥ እነዚህን ጥያቄዎች ያቀረበው አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ካልኖ ከኩርኩማሽ የተለየች አይደለችም፤ ሐማት ከአርፋድ የተለየች አይደለችም፤ ሰማርያም ከደማስቆ የተለየች አይደለችም፤ እኔ ሁሉንም ድል አድርጌአለሁ››

ካልኖ... ከርከሚሽ... ሐማት... አርፋድ
እነዚህ ሁሉ የከተሞች ስም ናቸው።

Isaiah 10:10

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ የአሦር ንጉሥ የተናገረውን መናገር ቀጥሏል።

እጄ፣ እንዳሸነፈች ሁሉ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› ወታደራዊ ብርታትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ብርቱ የሆነው ሰራዊት ድል እንዳደረገ ሁሉ›› ወይም፣ ‹‹እኔ ድል እንዳደረግሁ››

የእኔ
ይህ የሚያመለክተው የአሦርን ንጉሥ ነው።

ምስሎቻቸው የበለጡትን
በዚያ ዘመን የጣዖቱ ትልቅነት ያንን የሠራውን መንግሥት ትልቅነት ያመለክታል በማለት ሰዎች ያምኑ ነበር። የአሦር ንጉሥ የኢየሩሳሌም ጣዖቶች ድል ያደረጋቸው አገሮች ጣዖቶችን ያህል ትልልቅ አልነበሩም፤ ስለዚህም እርሱን ለመቋቋም ኢየሩሳሌም ያላት ጉልበት በጣም ታናሽ እንደሆነ መናገሩ ነበር።

በሰማርያና ከንቱ በሆኑት ጣዖቶቿ እንዳደረግሁ
‹‹ሰማርያ›› የሚለው ቃል እዚያ የነበሩ ሰዎችን፣ ‹‹የእርሷ›› የሚለው የሰማርያ ከተማን ያመለክታል። ከተሞችና አገሮች ብዙውን ጊዜ በእንስታዊ ጾታ ይጠሩ ነበር። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በሰማርያ ሕዝብና ከንቱ በሆኑ ጣዖቶቿ እንዳደረግሁ››

በኢየሩሳሌምና በጣዖቶቿስ እንዲሁ አላደርግምን?
የአሦር ንጉሥ ይህን ጥያቄ ያቀረበው የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ድል እንደሚያደርግ አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በኢየሩሳሌምና በጣዖቶቿም በእርግጥ ይህንኑ አደርጋለሁ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Isaiah 10:12

ጌታ በጽዮን ተራራና በኢየሩሳሌም ላይ የሚያደርገውን ከፈጸመ በኃላ እቀጣዋለሁ።
ያህዌ ስለ ራሱ እንደሌላ ሰው ይናገራል። ‹‹እኔ ጌታ በጽዮን ተራራና በኢየሩሳሌም የምሠራውን ከፈጸምሁ በኃላ እቀጣዋለሁ››

የሚያደርገው... ላይ
የመቅጣቱ ሥራ። ‹‹እቀጣለሁ... እቀጣዋለሁ››

የአሦርን ንጉሥ ልብ እብሪትና የንቀት አመለካከት እቀጣለሁ
‹‹ስለ ተናገረው እብሪትና የትዕቢት አመለካከቱ የአሦርን ንጉሥ እቀጣለሁ››

እንዲህ ብሏልና
‹‹የአሦር ንጉሥ እንዲህ ብሏልና››

አፈረስሁ... ዘረፍሁ
‹‹እኔ›› የሚለው የሚያመለክተው የአሦርን ንጉሥ ነው። እርሱ የአሦር ሰራዊት መሪ ስለ ነበር በእርሱ ትእዛዝ ሰራዊቱ ስላደረገው ሁሉ ክብሩን ይወስድ ነበር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰራዊቴ አፈረሰ... ዘረፈ››

እንደ ወይፈን
‹‹እንደ ወይፈን የበረታ›› አንዳንድ የጥንት ቅጂዎች፣ ‹‹እንደ ጎያል ሰው›› ይላሉ።

ነዋሪዎቹን አዋረድሁ
ይህም ማለት፣ 1) የአሦር ንጉሥ ድል ያደረጋቸው አገሮችን ሕዝቦች አዋርዶ ነበር፤ ወይም 2) ከእንግዲህ መግዛት እንዳይችሉ የአሕዛብ ነገሥታትን አስወግዶ ነበር ማለት ሊሆን ይችላል።

ሰበሰብሁ
‹‹እኔ›› የሚያመለክተው የአሦርን ንጉሥ ነው። የአሦር ሰራዊት መሪ ስለ ነበር በእርሱ ትእዛዝ ሰራዊቱ ላደረገው ሁሉ ክብር ይወስድ ነበር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔና ሰራዊቴ ሰበሰብን›› ወይም፣ ‹‹እኛ ሰበሰብን››

Isaiah 10:14

አጠቃላይ መረጃ
አሁንም ያህዌ የአሦር ንጉሥ የተናገረውን እየተናገረ ነው። (ኢሳይያስ 10፥13 ይመ.)

በእጄ ያዝሁ
እጅ የንጉሡን ወይም የሰራዊቱን ኀይል ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በኅይሌ ያዝሁ›› ወይም ‹‹ሰራዊቴ ያዘ››

ከወፍ ጐጆ እንደሚይዝ የሕዝቦችን ሀብት ያዝሁ
የአሦር ንጉሥ የሕዝቦችን ሀብት መውሰዱን ወፍ ጐጆ ውስጥ ያለውን ዕንቁላል ከሚወስድ ሰው ጋር ያመሳስለዋል። ይህም እነዚያን ሕዝቦች ድል ማድረግ ለእርሱና ለሰራዊቱ ምን ያህል ቀላል እንደ ነበር ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዕንቁላል ከወፍ ጐጆ እንደሚሰበሰብ፣ ሰራዊቴ የሕዝቦችን ሀብት በቀላሉ ዘረፈ››

የተተወ ዕንቁላል እንደሚሰበሰብ እኔም ምድርን ሁሉ ሰበሰብሁ
የአሦር ንጉሥ መንግሥታትን መውሰዱን ዕንቁላል ከመውሰድ ጋር ያመሳስለዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱን ለመከላከል ወፏ በሌለችበት ጊዜ ከጐጆዋ ዕንቁላሎች እንደሚሰበስብ ሰው፣ ሰራዊቴም ከአገር ሁሉ ሀብት ሰበሰበ››

ክንፉን ያራገበ አልነበረም፤ አፉን ከፍቶ የጮኸ አልነበረም
ይህ ሕዝቦችን ዕንቁላሎቿ ሲወሰዱ ዝም ብላ ከምታይ ወፍ ጋር ያመሳስላቸዋል። ይህም የአሦር ንጉሥ ሰራዊት ሀብታቸውን ሁሉ ሲወስድ ሕዝቦች ምንም አለማድረጋቸውን አጽንዖት ይሰጣል›› አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዕንቁላሎቿ ሲሰረቁ ድምፅ እንደማታሰማ ወይም ክንፏን እንደማታራግፍ ወፍ፣ እኛ ሀብታቸውን ስንዘርፍ ሕዝቦች ምንም አላደረጉም››

Isaiah 10:15

መጥረቢያ በሚቆርጥበት ሰው ላይ ይኩራራልን፤ መጋዝስ ከሚጠቀምበት ሰው ይበልጥ ራሱን ያመሰግናልን?
ተናጋሪው እነዚህን ጥያቄዎች የሚያቀርበው በአሦር ንጉሥ ለመሳለቅ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መጥረቢያ ከሚጠቀምበት ሰው የበለጠ እንደሆነ አይኩራም፤ መጋዝም ከሚቆርጥበት ሰው የበለጠ ክብር አያገኝም››

መጋዝ
እንጨት ለመቁረጥ የሚያገለግል ስለታም መሣሪያ

በትር በሚያነሣው ሰው ላይ ራሱን እንደሚነቀንቅ ወይም የእንጨት ዱላ ሰውን እንደሚያነሣ አድርጐ እንደሚኩራራ ነው
እነዚህ ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው፤ ጥቅም ላይ የዋሉት የሁለቱን ጥያቄዎች ትርጉም ለማጠናከር ነው። ይህን በአዲስ ዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በትርም ሆነ ዱላ በሚያነሣው ሰው ላይ አይኩራራም››

ስለዚህ የሰራዊት ጌታ ያህዌ በምርጥ ጦረኞቹ ላይ የሚያከሳ በሽታ ይልካል
እየተናገረ ያለው ያህዌ ወይም ኢሳይያስ መሆኑ ግልጽ አይደለም። ‹‹የሚያከሳ›› የሚለውን፣ ‹‹የሚያደክም›› በማለት መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለዚህ የሰራዊት ጌታ ያህዌ፣ ብርቱዎቹን የንጉሡን ወታደሮች ያደክማል››

ከክብሩም በታች እንደ ነበልባል የሚንቦገቦግ እሳት ይለኮሳል
ያህዌ የእርሱን ቅጣት ከእሳት ጋር ያመሳስለዋል። ይህም የሚያመለክተው የእርሱ ቅጣት የአሦርን መንግሥት ውበትና ታላቅነት ሁሉ ጨርሶ የሚያወድም መሆኑን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱ የታበየበትን ማንኛውንም ነገር የሚያጠፋ እሳት በመሆን ታላቅነቱን ሁሉ አወድማለሁ››

Isaiah 10:17

የእስራኤል ብርሃን እሳት ይሆናል
‹‹የእስራኤል ብርሃን›› የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ያህዌን ነው። እየተናገረ ያለው ያህዌ ወይም ኢሳይያስ መሆኑ ግልጽ አይደለም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤል ብርሃን አኔ ያህዌ፣ የማያከብረኝን ሁሉ ማጥፋት እንደሚችል እሳት እሆናለሁ››

ቅዱሱም ነበልባል ይሆናል
‹‹የእስራኤል ቅዱስ እኔ ያህዌ እንደ ነበልባል እሆናለሁ›› ኢሳይያስ 1፥4 ላይ፣ ‹‹ቅዱስ›› የሚለውን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

እሾኹንና ኩርንችቱን ሁሉ እሳት ይበላዋል
‹‹እሳቱ የአሦር ንጉሥ እሾኽና ኩርንችት ይበላዋል›› ተናጋሪው የአሦርን ንጉሥ ሰራዊት ከእሾኽና ከኩርንችት ጋር ያመሳስለዋል። ይህም እግዚአብሔር ምን ያህል በቀላሉ እንደሚያጠፋው አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እሾኹንና ኩርንችቱን እንደሚበላ እሳት አሦራውያንን አጠፋለሁ››

Isaiah 10:20

በዚያን ቀን
ይህ የሚያመለክተው ኢሳይያስ 10፥16-19 ላይ ያለውን ያህዌ የሚፈጽምበትን ጊዜ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በዚያ ጊዜ››

ያመለጠ
ይህ ምን ማለት እንደሆነ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከአሦር ሰራዊት ያመለጠ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ድል ባደረጋቸው ላይ አይታመኑም
‹‹ጉዳት ባደረሰባቸው በአሦር ንጉሥ ከእንግዲህ አይታመኑም››

ቅዱሱ
ኢሳይያስ 1፥4 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

Isaiah 10:22

እስራኤል ሕዝብህ
እዚህ ላይ ‹‹የአንተ›› ነጠላ ቁጥር ነው። ይህም ማለት፣ 1) እግዚአብሔር ለኢሳይያስ እየተናገረ ነው፤ ‹‹አንተ›› የሚለው ኢሳይያስን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የአንተ ሕዝብ እስራኤል›› ወይም 2) ለእስራኤል ሕዝብ ኢሳይያስ ወይም እግዚአብሔር እየተናገሩ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ‹‹የአንተ›› የእስራኤልን መንግሥት ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እስራኤል ሆይ፣ ሕዝብህ››

በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ ናቸው
ይህ አጽንዖት የሚሰጠው የእስራኤል ሕዝብ ቁጥር በጣም ብዙ እንደሚሆን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ መቆጠር አይችሉም››

ጥፋት ታውጅአል
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በእስራኤል የሚኖሩ ብዙዎችን ለማጥፋት ያህዌ ወስኖአል››

እንደ ወንዝ እየፈሰሰ ያለው ጽድቅ፣ ይህ እንዲሆን ግድ ይላል።
ይህን እንደ አዲስ ዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ይህ መሆን ያለበት ፍጹም ከሆነው ጽድቅ የተነሣ ነው›› ወይም፣ ‹‹እርሱ ፍጹም ጻድቅ ስለሆነ ያህዌ ይህን ማድረግ ይኖርበታል።››

የወሰነውን ጥፋት በምድር ሁሉ ላይ ያመጣል
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። ይህም ማለት፣ 1) አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እርሱ እንደ ወሰነው በምድሪቱ ያለውን ማንኛውንም ነገር ያጠፋል›› ወይም 2) አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እርሱ እንደ ወሰነው በምድሪቱ ያለውን ሕዝብ ያጠፋል››

እንደ ወሰነ
‹‹እንዳቀደው››

Isaiah 10:24

አሦራውያን
ኢሳይያስ እንደ አንድ ሰው አድርጐ ስለ አሦር ንጉሥና ስለ ሰራዊቱ ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የአሦር ንጉሥና ሰራዊቱ››

በበትር ይመታሃል፤ ሸመል ያነሣብሃል
‹‹በትር›› እና፣ ‹‹ሸመል›› የተሰኙት ቃሎች ሰዎች እንስሳትን ወይም ሌሎች ሰዎችን ለመምታት የሚጠቀሙባቸው እንጨቶች ናቸው። አሦራውያን እስራኤላውያንን ስለሚገዙበት መንገድ ነው ኢሳይያስ እየተናገረ ያለው፤ አሦራውያን እስራኤላውያንን በበትር ይመቷቸዋል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እናንተን ይገዛል፤ ባርያዎቹም ያደርጋችኃል››

ይመታል
‹‹እርሱ›› የሚለው የአሦር ንጉሥና ሰራዊቱን የሚወክለው ‹‹አሦርን›› ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እርሱና ሰራዊቱ ይመታሉ››

ግብፃውያን እንዳደረጉት
ይህ ምን ማለት እንደሆነ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ግብፃውያን አባቶችህን እንደ ገዙና ባርያዎች እንዳደረጓቸው››

በቁጣዬ ይጠፋል
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በእርሱ ላይ ስለ ተቆጣሁ አጠፋዋለሁ››

Isaiah 10:26

የሰራዊት ጌታ ያህዌ
ኢሳይያስ 1፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

በጅራፍ ይገርፋቸዋል
‹‹አሦራውያንን በአለንጋ ይገርፋቸዋል›› እግዚአብሔር በእርግጥ ጅራፍ አይጠቀምም። ይህ የሚያመላክተው አሦራውያንን በጽኑ ለመቅጣት እግዚአብሔር ያለውን ኀይል ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በጅራፍ እንደሚገረፍ አሦራውያንን በጣም ይቀጣል››

በሔሬብ ዐለት አካባቢ ምድያምን እንደ መታ
ይህ የሚያመለክተው የምድያምን ጦር ድል እንዲያደርግ ጌዴዎን የሚባለውን ሰው እግዚአብሔር መርዳቱን ነው።

በግብፅ እንዳደረገው ሁሉ በትሩን በባሕር ላይ ያነሣል
ይህ የሚያመለክተው እነርሱ የግብፃውያን ሠራዊት የነበሩ ይመስል፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከአሦራውያን ማዳኑን ነው። ይህ የሚያመለክተው እስራኤላውያን ከግብፃውያን ሰራዊት እንዲያመልጡና የግብፃውያን ሰራዊት ግን ሰጥሞ እንዲቀር እግዚአብሔር ቀይ ባሕር እንዲከፈል ማድረጉን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አባቶቻችሁ ከግብፅ ሰራዊት እንዲያመልጡ እንደ ረዳቸው ሁሉ እናንተም ከአሦር ሰራዊት እንድታመልጡ ይረዳችኃል።››

ሸክሙ ከትከሻህ ቀንበሩም ከዐንገትህ ላይ ይነሣል
‹‹አሦር ትከሻህ ላይ ያደረገውን ሸክም ያህዌ ያነሣል፤ ዐንገትህ ላይ ያስቀመጡትንም ቀንበር ያህዌ ያስወግዳል ሁለቱ ሐረጐች የሚሉት በመሠረቱ ተመሳሳይ ነው። ‹‹ሸክም›› እና፣፣ ‹‹ቀንበር›› የሚያመለክቱት ባርነትን ነው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ የጨቆኑህን አሦራውያን ያስወግዳል፤ አንተን ባርያቸው እንዳያደርጉም ያስቆማቸዋል››

ቀንበሩ ከውፍረት የተነሣ ይሰበራል
አገላለጹ ቀንበሩን የሚሸከመው እንስሳ ዐንገት በጣም እንደሚወፍርና ከዚያ በኃላ ለቀንበሩ ተስማሚ እንደማይሆን ያመለክታል። ይህ የሚያመለክተው እስራኤል በጣም ብርቱ እንደሚሆንና ከእንግዲህ አሦራውያን እርሱን መግዛት የማይችሉ መሆናቸውን ነው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ዐንገትህ በጣም ከመወፈሩ የተነሣ ቀንበር ይሰበራል›› ወይም፣ ‹‹በጣም ብርቱ ስለምትሆን ከእንግዲህ የአሦራውያን ባርያ አትሆንም››

Isaiah 10:28

ይገባሉ... ያልፋሉ... ያከማቻሉ... ይሻገራሉ... ያድራሉ... ይደነግጣሉ... ሸሸች
እነዚህ ወደ ፊት የሚፈጸሙ ሁኔዎች አሁን እንኳ እንደ ተፈጸሙ አድርጐ ኢሳይያስ ይናገራል።

ዐያት... ግሮን... ሚክማስ... ጌባ... ራማ... ጊብዓ
እነዚህ ሁሉ የአሦር ሰራዊት ያለፈባቸውና ብዙ ችግር ያደረሰባቸው ኢየሩሳሌም አጠገብ ያሉ ከተሞችና መንደሮች ናቸው።

ራማ ደነገጠች የሳኦል ጊብዓ ሸሸች
‹‹ራማ›› እና፣ ‹‹የሳኦል ጊብዓ›› የሚያመለክቱት በእነዚህ ከተሞች የነበሩትን ሕዝብ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የራማ ሕዝብ ደነገጡ የሳኦል ጊብዓ ሰዎችም ሸሹ››

Isaiah 10:30

የጋሊም ሴት ልጅ
‹‹ሴት ልጅ›› በእነዚያ ከተሞች ሚኖሩትን ሰዎች ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጋሊም›› ወይም፣ ‹‹የጋሊም ሰዎች››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጋለም... ላይሻ... ዓናቶት... ማድሜናህ... ጌቢም... ኖብ
እነዚህ የአሦር ሰራዊት ያለፈባቸውና ብዙ ችግር ያደረሰባቸው ኢየሩሳሌም አጠገብ የነበሩ የተጨማሪ ከተሞችና መንደሮች ስም ናቸው። እነዚህ ሁሉ በእነዚህ ከተሞች የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታሉ።

ኖብ ላይ ይቆማል፤ እጁን ይነቀንቃል
እዚህ ላይ፣ ‹‹እርሱ›› እና፣ ‹‹የእርሱ›› የአሦር ንጉሥና ወታደሮቹን ያመለክታሉ። ሰዎች በሚዝቱባቸው ላይ እጃቸውን ይነቀንቃሉ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የአሦር ንጉሥ ኖብ ላይ ይቆምና ያስፈራራል››

የጽዮን ሴት ልጅ ተራራ፤ የኢየሩሳሌም ኮረብታ
‹‹ተራራ›› እና፣ ‹‹ኮረብታ›› እነርሱ ላይ የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታሉ። ‹‹የጽዮን ሴት ልጅ ተራራ›› እና ‹‹የኢየሩሳሌም ኮረብታ›› የተሰኙት ቃሎች በአመዛኙ አንድ ዐይነት ነገር ማለት ናቸው። ኢሳይያስ 2፥14 ላይ እንዴት እንደ ተረጐምሃቸው ተመልከት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የጽዮን ተራራ ሰዎችና በኢየሩሳሌም ኮረብታ የሚኖሩ ሰዎች››

Isaiah 10:33

እነሆ
ይህን፣ ‹‹ተመልከቱ›› ወይም፣ ‹‹አድምጡ›› ወይም፣ ‹‹የምናገረውን ልብ ብላችሁ ስሙ›› በማለት መተርጐም ይቻላል።

የሰራዊት ጌታ ያህዌ
ኢሳይያስ 1፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐመኸው ተመልከት።

ረጃጅም ዛፎች ይገነደሳሉ... ለባኖስም በግርማው ፊት ይወድቃል
ኢሳይያስ የአሦር ሰራዊት በለባኖስ እንዳሉ ረጃጅም ዛፎች እንደሆነ ይናገራል። ሰዎች የለባኖስን ታላላቅ ዛፎች እንደሚገነድሱ እግዚአብሔር ሰራዊቱን ይደመሰሳል። ይህ አጽንዖት የሚሰጠው ሰራዊቱ በጣም ብርቱ ቢሆንም፣ እግዚአብሔር እርሱን ለማጥፋት ያለውን ጎይል ነው።

ረጃጅም ዛፎች ይገነደሳሉ
‹‹የዛፉ ትልልቅ ቅርንጫፎች ይቆረጣሉ›› እየተናገረ ያለው የአሦር ሰራዊትን እንደሆነ ግልጽ ለማድረግ በተመሳሳይ መንገድ መተርጐም ይቻላል፤ አንድ ብርቱ ሰው ትልልቆቹን የዛፎች ቅርንጫፎች እንደሚቆርጥ የአሦርን ሰራዊት ያጠፋል።

በአስፈሪ ድምፅ
‹‹ድምፅ›› የሚለውን የነገር ስም፣ ‹‹ድምፅ ያወጣል›› በሚል ግስ ለመተርጐም እንዲቻል ዐረፍተ ነገሩን እንደ ገና ማቀናጀት ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ቅርንጫፎቹ መሬት ላይ ሲወድቁ አስፈሪ ድምፅ ይሰጣሉ›› ወይም፣ ‹‹ቅርንጫፎቹ በታላቅ ድምፅ መሬት ላይ ይወድቃሉ››

ረጃጅሞቹ ዛፎች ይቆረጣሉ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ረጃጅሞቹን ዛፎች ይቆርጣል››

ረጃጅም ዛፎች
ይህ፣ ‹‹ብርቱዎች ወታደሮች›› ማለት ነው።

ከፍ ከፍ ያሉትም ይወድቃሉ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ታላላቅ ሰዎችን ይጥላል።

ከፍ ከፍ ያሉ
‹‹የታበዩ››

ጥቅጥቅ ያለው ደን
‹‹በተክሎች ጥቅጥቅ ያለ ጫካ›› ይህ በሚገባ ያልታወቁ ሰዎችን የሚያመላክት ምሳሌ ነው።

ሊባኖስም በግርማው ፊት ይወድቃል
‹‹የሊባኖስ ጫካዎች ከእንግዲህ ታላቅ አይሆኑም›› ይህ የአሦር ሰራዊትን የሚያመለክት ምሳሌ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እርሱ እጅግ ብርቱ ስለሆነ ያህዌ የአሦርን ሰራዊት ያሸንፋል››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 11

1 ከእሴይ ግንድ በትር ይወጣል፣ የሥሩም ቊጥቋጥ ፍሬን ያፈራል። **2** የእግዚአብሔር መንፈስ፣ የጥበብና የማስተዋል መንፈስ፣ የምክርና የኃይል መንፈስ፣ የእውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ ያርፍበታል። **3** እግዚአብሔርን በመፍራት ደስታውን ያያል፤ ዐይኑም እንደምታይ አይፈርድም፣ ጆሮውም እንደምትሰማ አይበይንም፤ **4** ነገር ግን ለድሆች በጽድቅ ይፈርዳል፣ ለምድርም የዋሆች በቅንነት ይበይናል። በአፉም በትር ምድርን ይመታል፣ በከንፈሩም እስትንፋስ ክፉዎችን ይገድላል። **5** የወገቡ መታጠቂያ ጽድቅ፣ የጎኑም መቀነት ታማኝነት ይሆናል። **6** ተኵላ ከበግ ጠቦት ጋር ይኖራል፣ ነብርም ከፍየል ጠቦት ጋር ይተኛል፤ ጥጃና የአንበሳ ደቦል፣ ፍሪዳም በአንድነት ያርፋሉ፤ ትንሽም ልጅ ይመራቸዋል። **7** ላምና ድብ አብረው ግጦሽ ይውላሉ፣ ግልገሎቻቸውም በአንድነት ያርፋሉ። አንበሳም እንደ በሬ ገለባ ይበላል። **8** ሕፃን በእባብ ጕድጓድ ላይ ይጫወታል፣ ጡት የጣለውም ሕፃን በእፉኝት ቤት ላይ እጁን ይጭናል። **9** በተቀደሰው ተራራዬ ሁሉ ላይ አይጐዱም አያጠፉምም፤ ውኃ ባሕርን እንደሚከድን ምድር እግዚአብሔርን በማወቅ ትሞላለችና። **10** በዚያም ቀን፣ ለአሕዛብ ምልክት ሆኖ ይቆማል። የእሴይን ሥር አሕዛብ ይፈልጉታል፣ ማረፊያውም የተከበረ ይሆናል። **11** በዚያም ቀን፣ የቀረውን የሕዝቡን ቅሬታ ከአሦርና ከግብጽ፣ ከጳትሮስና ከኢትዮጵያ፣ ከኤላምና ከሰናዖር ከሐማትም፣ ከባሕርም ደሴቶች ይመልስ ዘንድ ጌታ እንደ ገና እጁን ይገልጣል። **12** ለአሕዛብም ምልክትን ያቆማል፣ ከእስራኤልም የተጣሉትን ይሰበስባል፣ ከይሁዳም የተበተኑትን ከአራቱ የምድር ማዕዘኖች ያከማቻል። **13** የኤፍሬምንም ምቀኝነት ያቆማል፣ ይሁዳንም የሚጠሉ ይቆረጣሉ። ኤፍሬምም በይሁዳ አይቀናም፣ ይሁዳም ኤፍሬምን አይጠላም። **14** በምዕራብም በኩል በፍልስጥኤማውያን ጫንቃ ላይ እየበረሩ ይወርዳሉ፣ የምሥራቅንም ልጆች በአንድነት ይበዘብዛሉ። በኤዶምያስና በሞዓብም ላይ እጃቸውን ይዘረጋሉ፣ የአሞንም ልጆች ለእነርሱ ይታዘዛሉ። **15** እግዚአብሔርም የግብጽን ባሕር ያጠፋል፤ በትኩሱም ነፋስ እጁን በኤፍራጥስ ወንዝ ላይ ያነሣል፣ ሰባት ፈሳሾች አድርጎም ይከፋፍለዋል፣ ስለዚህም በጫማ ሊሻገሩት የሚችሉት ይሆናል። **16** ከግብጽም በወጣ ጊዜ ለእስራኤል እንደ ነበረው ሁሉ ለቀረውም ሕዝብ ቅሬታ ከአሦር የሚወጣበት ጐዳና እንዲሁ ይሆናል።

Isaiah 11:1

ከእሴይ ግንድ ቁጥቋጥ ይወጣል... ከሥሮቹም አንዱ ቅርንጫፍ ፍሬ ይሰጣል
ኢሳይያስ እሴይና ዘሮቹ ተቆርጦ እንደ ነበረ ዛፍ እንደሆነ ይናገራል። ሁለቱም ሐረጐች የሚናገሩት ንጉሥ ስለሚሆነው የእሴይ ዘር ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከዛፉ ግንድ ቅርንጫፎች እንደሚወጡ የእሴይም ዘር በእስራኤል በተረፈት ላይ ንጉሥ ይሆናል››

የእሴይ ግንድ
ግንዱ ዛፉ ከተመለመለ በኋላ የሚቀረው ክፍል ነው። ‹‹የእሴይ ግንድ›› የእሴይ ልጅ ዳዊት በአንድ ወቅት ንጉሥ ከነበረበት መንግሥት የቀረውን ያመለክታል።

የያህዌ መንፈስ ያርፍበታል
እርሱ ላይ ማረፉ ከእርሱ ጋር እንደሚሆንና እንደሚረዳው ያመለክታል። ‹‹እርሱ›› የሚለው ቃል ንጉሥ የሚሆነውን ሰው ያመለክታል።

የጥበብ መንፈስ.. የምክር መንፈስ... የዕውቀት መንፈስ... ያህዌን የመፍራት መንፈስ
እዚህ ላይ፣ ‹‹መንፈስ›› የሚለው ቃል የያህዌ መንፈስ የሚሰጠውን ችሎታ ወይም ባሕርይ ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጥበብና ማስተዋል፤ ምክርና ኀይል፣ ዕውቀትና ያህዌን መፍራት እንዲኖረው ያደርገዋል።››

Isaiah 11:3

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ኢሳይያስ ስለ ንጉሡ መናገሩን ቀጥሏል

ዐይኑ እንዳዬ አይፈርድም
‹‹ዐይኑ እንዳዬ›› የሚለው ሐረግ ሰውየው ላይ ለመፍረድ የሚያስችሉ አስፈላጊ ያልሆኑ ነገሮችን ማየትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ውጫዊ ሁኔታውን በማየት ብቻ ሰውየው ላይ አይፈርድም››

ጆሮውም እንደ ሰማ አይበይንም
‹‹ጆሮው በሚሰማው አይወስንም›› - ‹‹ጆሮው እንደ ሰማ›› የሚለው ሐረግ ሰዎች ስለ ሌላው ሰው የሚናገሩን መስማት ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሌሎች ስለ እርሱ የሚናገሩትን በመስማት ብቻ ማንም ላይ አይፈርድም››

ለድኾች... ለምስኪኖች... ለክፉዎች
እነዚህ ቃሎች እነዚህ ባሕርያት ያሏቸውን ሰዎች ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ድኾች ሰዎች... ምስኪን ሰዎች... ክፉዎች ሰዎች››

በአፉ በትር ምድርን ይመታል፤ በከንፈሩም እስትንፋስ ክፉዎችን ይገድላል
ሁለቱም ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው

በአፉ በትር ምድርን ይመታል
‹‹ምድር›› በምድር የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታል። በአፉ እስትንፋስ መምታት እነርሱ ላ መፍረድንና ፍርዱም ወደ ቅጣት ማድረሱን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በምድር ሕዝብ ላይ ይፈርዳል፤ እነርሱም ይቀጣሉ››

በከንፈሩም እስትንፋስ ክፉዎችን ይገድላል
‹‹የከንፈሩ እስትንፋስ›› እነርሱ ላይ መፍረድን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ክፉዎች ላይ ይፈርዳል፤ እነርሱም ይገደላሉ››

የወገቡ መታጠቂያ... የጐኑ መቀነት
ይህም ማለት፣ 1) መታጠቂያ መሥራት እንዲችል የሰውን ልብስ ለመያዝ ይጠቅማል። ወይም 2) መታጠቂያ በውስጥ የሚለበስ ነው ወይም 3) መታጠቂያ ሥልጣኑን ለማሳየት ንጉሡ የሚለብሰው መጐናጸፊያ ነው።

ጽድቅ የወገቡ መታጠቂያ ይሆናል
እንደ ቀበቶ ጽድቅን ወገብ ላይ መታጠቅ ጻድቅ መሆንን ይወክላል። ይህም ማለት፣ 1) የንጉሡ ጽድቅ ለመግዛት ያስችለዋል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በጽድቅ ይገዛል››

ታማኝነትም የጐኑ መቀነት
እዚህ ሐረግ ላይ፣ ‹‹ይሆናል›› የሚለው ውስጠ ታዋቂ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ታማኝነት ጐኑ ላይ መቀነት ይሆናል››

ታማኝነት የጐኑ መቀነት
እንደ መቀነት ታማኝነትን መታጠቅ ታማኝ መሆንን ያመለክታል። ይህም ማለት፣ 1) የንጉሡ ታማኝነት ለመግዛት ያስችለዋል ማለት ነው፣ ወይም 2) የንጉሡ ታማኝነት ለመግዛት ያለውን ሥልጣን ያሳያል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ታማኝነት እንደ መቀነት ጐኑ ላይ ይሆናል›› ወይም፣ ‹‹በታማኝነት ይገዛል››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Isaiah 11:8

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ንጉሡ በሚገዛበት ጊዜ በዓለም የሚኖረውን የተሟላ ሰላም መግለጹን ቀጥሏል

ሕፃን ልጅ በእባብ ጉድጓድ ይጫወታል
እባቡ ስለማይነድፈው ልጁ ደህና እንደሚሆን በግልጽ መነገር አለበት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሕፃናት ምንም ሳይጐዳቸው በእባብ ጉድጓድ ላይ ይጫወታሉ››

እባብ... የእባብ ጉድጓድ
ይህ የሚያመለክተው በጠቅላላ መርዛማ እባቦችን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እባቦች... የእባቦች ጉድጓድ››

ጡት የጣለ ሕፃን
የእናቱን ጡት ወተት መጠጣት ያቆመ

በተቀደሰው ተራራዬ ሁሉ ላይ
‹‹የተቀደሰ ተራራ›› በኢየሩሳሌም ያለው የጽዮን ተራራ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በያህዌ ቅዱስ ተራራ ሁሉ››

ምድር ያህዌን በማወቅ ትሞላለች
‹‹ያህዌን በማወቅ›› የሚለው ሐረግ ያህዌን የሚያውቁ ሰዎችን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ምድር ያህዌን በሚያውቁ ሰዎች ትሞላለች›› ወይም፣ ‹‹ያህዌን የሚያውቁ ምድርን ይሸፍናሉ››

ውሃ ባሕርን እንደሚሸፍን
ይህ ሐረግ ጥቅም ላይ የዋለው ምድር ምን ያህል ያህዌን በሚያውቁ ሰዎች እንደምትሞላ ለማሳየት ነው። ቃሎቹ ከቀደመው ሐረግ ጋር ተመሳሳይ ከሆኑ ይህ እንደሚሆን የበለጠ ግልጽ ይሆናል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ውሃ ባሕሮችን እንደሚሞላ››

Isaiah 11:10

የእሴይ ሥር
ይህ የሚያመለክተው ንጉሥ እንደሚሆን ኢሳይያስ 1፥1 የተነገረለትን የእሴይንና የንጉሥ ዳዊትን ልጅ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ንጉሡ የእሴይ ልጅ›› ወይም፣ ‹‹ንጉሥ የሚሆነው የእሴይ ልጅ››

ለሕዝቦች ምልክት ሆኖ ይቆማል
‹‹ምልክት›› ሰዎች ዐይተው ወደ እርሱ እንዲመጡ ንጉሡ ከፍ የሚያደርገው ባንዲራ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለሕዝቡ እንደ ምልክት ይሆናል›› ወይም፣ ‹‹ወደ እርሱ እንዲመጡ ሕዝቡን ይስባል››

ሕዝቦች
‹‹የአገሩ ሰዎች››

ጌታ እጁን ዘርግቶ የተረፈውን የሕዝቡን ቅሬታ ይሰበስባል
እጅ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ኀይል ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሕዝቡን ቅሬታ መልሶ ለማምጣት እንደ ገና ጌታ ኀይሉን ይጠቀማል››

ጳጥሮስ... ኤላም... ሐማት
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው

Isaiah 11:12

ለመንግሥታት ምልክትን ያቆማል
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ጌታ ለመንግሥታት ንጉሡን እንደ ምልክት ያቆማል›› ወይም፣ ‹‹ንጉሡ ለመንግሥታት ምልክት ያቆማል››

ለመንግሥታት ምልክት
‹‹ሰዎች የሚያዩት ባንዲራ›› ወይም፣ ‹‹መንግሥታትን ወደ ራሱ ለመጥራት ባንዲራ››

የተበተኑትን የይሁዳ ሕዝብ
‹‹በዓለም ዙሪያ የተበተኑ የአይሁድ ሕዝብ››

ከአራቱም የምድር ማእዘን
ምድር አራት ማእዘኖች እንዳሏት ተስሏል፤ እነዚህ ማእዘኖች በጣም ተራርቀው ነው ያሉት። ይህም እነዚህ ሰዎች የሚገኙባቸው መላውን ምድር ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በምድር ካሉ በጣም ሩቅ ቦታዎች እንኳ ሳይቀር›› ወይም፣ ‹‹ከምድር ሁሉ››

የኤፍሬም ምቀኝነት ያከትማል
እዚህ ላይ፣ ኤፍሬም የሰሜናዊው የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል። ‹‹ምቀኝነት›› የሚለውን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የኤፍሬም ሕዝብ ምቀኝነት እንዳይኖራቸው ያደርጋል››

ይሁዳም የኤፍሬም ጠላት አይሆንም
እዚህ ላይ ይሁዳ የሚያመለክተው የደቡባዊውን መንግሥት ሰዎች ነው። ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የይሁዳ ሕዝብ ጠላት እንዳይሆኑ ያደርጋል›› ወይም፣ ‹‹የይሁዳን ሕዝብ ጥላቻ ያስቆማል››

Isaiah 11:14

በፍልስጥኤም ተራሮች ላይ ቁልቁል ይበርራሉ
የእስራኤልና የይሁዳ ሕዝብ ሰውን ወይም እንስሳን ለማጥቃት በድንገት ቁልቁል በሚበሩ ወፎች ተመስለዋል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እዚያ ያሉትን ሰዎች ለማጥቃት ወደ ፍልስጥኤም ተራሮች በፍጥነት ይሄዳሉ››

የግብፅ ባሕረ ሰላጤ
‹‹ባሕረ ሰላጤ›› በከፊል በመሬት የተከበበ ትልቅ የውሃ አካል ነው።

በሚጋረፍ ነፋስ እጁን በኤፍራጥስ ወንዝ ላይ ያንቀሳቅሳል
እጁን በአንዳች ነገር ላይ ማንቀሳቀሱ የመለወጥ ኀይሉን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በታላቅ ኀይሉ በኤፍራጥስ ወንዝ ላይ የሚጋረፍ ነፋስ ያነፍሳል››

የሚጋረፍ ነፋስ
ይህ ጥቂቱን የወንዞች ውሃ የሚያደርቅ ሞቃት ነፋስ ነው።

ከነጫማቸው መሻገር ይችላሉ
‹‹ሰዎች ጫማቸውን እንዳደረጉ እንዲሻገሩት››

Isaiah 11:16

አውራ መንገድ ይሆናል
አውራ መንገድ ብዙ ሰዎች መጓዝ የሚችሉበት ሰፊ መንገድ ነው። ‹‹ያህዌ መንገድ ያደርጋል››

ከግብፅ ምድር ሲመጡ
‹‹ከግብፅ ምድር ወጥተው ሲመጡ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 12

1 በዚያም ቀን፣ "እግዚአብሔር ሆይ፣ አመሰግንሃለሁ። ተቈጥተኸኛልና፣ ቍጣህንም ከእኔ መልሰሃልና፣ አጽናንተኸኛልምና። **2** ተመልከቱ፣ እግዚአብሔር መድኃኒቴ ነው፤ ጌታ እግዚአብሔር ኃይሌና ዝማሬዬ ነውና፣ አዎን፣ በእርሱ ታምኜ አልፈራም። መድኃኒቴም ሆኖአልና" ትላለህ። **3** ውኃውንም ከመድኃኒት ምንጮች በደስታ ትቀዳላችሁ። **4** በዚያም ቀን እንዲህ ትላላችሁ፣ "እግዚአብሔርን አመስግኑ፣ ስሙንም ጥሩ፤ በአሕዛብ መካከል ሥራውን አስታውቁ፤ ስሙ ከፍ ያለ እንደ ሆነ ተናገሩ። **5** ታላቅ ሥራ ሠርቶአልና ለእግዚአብሔር ተቀኙ፤ ይህንም በምድር ሁሉ ላይ የታወቀ እንዲሆን አድርጉ። **6** አንቺ በጽዮን የምትኖሪ ሆይ፣ የእስራኤል ቅዱስ በመካከልሽ ከፍ ከፍ ብሎአልና ደስ ይበልሽ እልልም በዪ።"

Isaiah 12:1

አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ላይ ኢሳይያስ እግዚአብሔር የመረጠው ንጉሥ በሚገዛበት ጊዜ የሚሆነውን መግለጽ ቀጥሏል።

Isaiah 12:3

ከድነት ምንጮች ውሃ በደስታ ትቀዳላችሁ
የዳኑት ሰዎች ከምንጭ ውሃ እንዳገኙ ሰዎች እንደሆኑ ኢሳይያስ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ከምንጭ ውሃ ሲቀዱ ደስ እንደሚላቸው እርሱ ሲያድናችሁ እናንተም ደስ ይላችኃል››

ስሙንም ጥሩ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ስሙ›› የተባለው ያህዌ ነው። ስሙን ጥሩት ማለት እርሱን ማመስገንን ወይም የእርሱን ርዳታ መለመንን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ አመስግኑት›› ወይም፣ ‹‹እንዲረዳችሁ ጥሩት››

ያደረገውን በአሕዛብ መካከል አስታወቁ
‹‹ያደረገውን›› የሚለውን፣ ‹‹እርሱ አድርጐ የነበረውን›› በሚል ሐረግ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱ ያደረገውን ታላላቅ ነገሮች ለሕዝብ ተናገሩ››

ስሙ ከፍ ከፍ ማለቱን ዐውጁ
‹‹ስሙ›› የሚያመለክተው፣ ያህዌን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱ ከፍ ከፍ ያለ መሆኑን ዐውጁ›› ወይም፣ ‹‹እርሱ ታላቅ መሆኑን ዐውጁ››

Isaiah 12:5

አጠቃላይ መረጃ
ንጉሡ በሚገዛበት ጊዜ ሕዝቡ ምን እንደሚሉ ኢሳይያስ መናገር ቀጥሏል

በመካከላችሁ ያለው የእስራኤል ቅዱስ ታላቅ ነውና
‹‹ምክንያቱም በመካከላችሁ ያለው የእስራኤል ቅዱስ ብርቱ ነው›› ወይም፣ ‹‹የእስራኤል ቅዱስ ብርቱ ስለሆነ በመካከላችሁም ስለሚኖር››

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 13

1 የአሞጽ ልጅ ኢሳይያስ ያየው ስለ ባቢሎን የተነገረ ሸክም። **2** ምድረ በዳ በሆነ ተራራ ላይ ምልክትን አቁሙ፣ ድምፅንም ከፍ አድርጉባቸው፤ በአለቆችም ደጆች እንዲገቡ እጃችሁን አንስታችሁ አሳዩ። **3** ቍጣዬን ይፈጽሙ ዘንድ ቅዱሳኔን አዝዣለሁ፣ እኔ ኃያላኔንና በታላቅነቴ ደስ የሚላቸውን ጠርቻለሁ። **4** በተራሮች ላይ እንደ ታላቅ ሕዝብ ድምፅ የሆነ የብዙ ሰው ድምፅ አለ! የተከተማቹት የአህዛብ መንግሥታት የውካታ ጫጫታ አለ! የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ሠራዊትን ለሰልፍ አሰልፎአል። **5** እግዚአብሔርና የቍጣው የጦር ዕቃ ምድርን ሁሉ ያጠፉአት ዘንድ ከሩቅ አገር፣ ከሰማይ ዳርቻ ይመጣሉ። **6** የእግዚአብሔር ቀን ቀርቦአልና፣ አልቅሱ፤ ሁሉን ከሚችል አምላክ ዘንድ እንደሚመጣ ጥፋት ይመጣል። **7** ስለዚህ፣ እጅ ሁሉ ትዝላለች፣ የሰውም ሁሉ ልብ ይቀልጣል፤ **8** ይደነግጣሉ፤ ምጥና ሕማም ይይዛቸዋል፣ እንደምትወልድ ሴትም ያምጣሉ። አንዱም በሌላው ይደነቃል፣ ፊታቸውም የነበልባል ፊት ነው። **9** ተመልከቱ፣ ምድሪቱን ባድማ ሊያደርግ፣ ኃጢአተኞችዋንም ከእርስዋ ዘንድ ሊያጠፋ ጨካኝ ሆኖ በመዓትና በጽኑ ቍጣ ተሞልቶ የእግዚአብሔር ቀን ይመጣል። **10** የሰማይም ከዋክብትና ሠራዊቱ ብርሃናቸውን አይሰጡም፣ ፀሐይም በወጣች ጊዜ ትጨልማለች፣ ጨረቃም በብርሃኑ አያበራም። **11** ዓለሙን ስለ ክፋታቸው ክፉዎቹንም ስለ በደላቸው እቀጣለሁ። የእብሪተኞችንም ኵራት፣ የጨካኞቹንም ትዕቢት አዋርዳለሁ። **12** የቀሩትም ከጥሩ ወርቅ ይልቅ የከበሩ ይሆናሉ፣ ሰውም ከኦፊር ወርቅ ይልቅ የከበረ ይሆናል። **13** ስለዚህ በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር መዓት፣ በጽኑ ቍጣ ቀንም ሰማያትን አነቃንቃለሁ፣ ምድርም ከስፍራዋ ትናወጣለች። **14** እንደ ተባረረም ሚዳቋ፣ ማንም እንደማይሰበስበው እንደ በግ መንጋ፣ ሰው ሁሉ ወደ ወገኑ ይመለሳል፣ ሁሉም ወደ አገሩ ይሸሻል። **15** የተገኘ ሁሉ ይገደላል፣ የተያዘም ሁሉ በሰይፍ ይሞታል። **16** ሕፃናቶቻቸውም በዐይናቸው ፊት እስኪቆራረጡ ድረስ ይጨፈጨፋሉ። ቤቶቻቸውም ይበዘበዛሉ፣ ሚስቶቻቸውም ተይዘው ይነወራሉ። **17** ተመልከቱ፣ ብር የማይሹትን፣ ወርቅም የማያምራቸውን ሜዶናውያንን በላያቸው አናውጣለሁ። **18** ፍላጾቻቸውም ጎበዞችን ይወጋሉ። ጨቅላዎችን አይምሩም፣ ዓይኖቻቸውም ለሕፃናት አይራሩም። **19** እግዚአብሔርም ሰዶምንና ገሞራን ባፈረሰ ጊዜ እንደ ነበረው፣ የመንግሥታት ክብር፣ የከለዳውያንም ትዕቢት ጌጥ ባቢሎን እንዲሁ ትሆናለች። **20** ከትውልድ እስከ ትውልድ ድረስ ማንም ሰው አይኖርባትም፤ ዓረቦቹ ድንኳንን በዚያ አይተክሉም፣ እረኞችም መንጎቻቸውን በዚያ አያሳርፉም። **21** በዚያም የምድረ በዳ አራዊት ያርፋሉ። ጕጕቶችም በቤቶቻቸው ይሞላሉ፤ ሰጎኖችና የበረሃ ፍየሎች በዚያ ይኖራሉ። **22** ጅቦችም በግንቦቻቸው፣ ቀበሮችም በሚያማምሩ አዳራሾቻቸው ይጮኻሉ። ጊዜዋም ለመምጣት ቀርቦአል ቀንዋም አይዘገይም።

Isaiah 13:1

ስለ ባቢሎን
የከተማዋ ስም የባቢሎንን ሕዝብ ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ስለ ባቢሎን ሕዝብ››

አሞጽ
አሞጽ የኢሳይያስ አባት ነው። ኢሳይያስ 1፥1 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ ወደ እነርሱ ጩኹ
‹‹እነርሱ›› የሚለው የሌላ አገር ወታደሮች ያመለክታል።

በመሳፍንቱ በር
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹መሳፍንቱ የሚኖሩበት የባቢሎን በሮች›› ወይም 2) ‹‹የመሳፍንቱ ትልልቅ ቤቶች በሮች››

መሳፍንቱ
‹‹የተከበሩ ሰዎች›› ወይም፣ ‹‹ገዦች››

ቅዱሳኔ
‹‹እኔ ለራሴ የለየሁቸው›› ወይም፣ ‹‹ለራሴ የለየሁዋቸው ሰራዊት››

ቁጣየን እንዲፈጽሙ ተዋጊዎቼን ጠርቻለሁ
የእግዚአብሔርን ቁጣ መፈጸም እርሱ ስለ ተቆጣ ሰዎችን መቅጣትን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እንድቆጣ ስላደረጉን የባቢሎንን ሕዝብ እንዲቀጡ ብርቱ ተዋጊዎቼን ጠርቻለሁ››

በድል አድራጊነቴ ደስ የሚላቸውን
‹‹በተገኘው ድል ደስ የሚላቸው›› ደስ የሚላቸው ለምን እንደሆነ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ካደረግሁት ታላቅ ነገር የተነሣ እጅግ ደስ የሚላቸው ሕዝቤ››

Isaiah 13:4

በተራሮች ላይ እንደ ብዙ ሕዝብ ድምፅ
‹‹አለ›› የሚለው ውስጠ ታዋቂ ነው። ‹‹ብዙ›› እና፣ ‹‹ብዙ ሕዝብ›› የሚሉት ሐረጐች ተመሳሳይ ናቸው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ተራሮች ላይ የብዙ ሕዝብ ድምፅ አለ›› ወይም፣ ‹‹የብዙ ሕዝብ ድምፅ ተራሮች ላይ አለ››

በመንግሥታትም መካከል እንደ ተጨናነቁ ሕዝብ ድምፅ የሆነውን ውካታ
‹‹አለ›› የሚለው ውስጠ ታዋቂ ነው። እዚህ ላይ፣ ‹‹መንግሥታት›› እና፣ ‹‹ሕዝብ›› የሚያመለክቱት ተመሳሳይ ነገርን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በአንድነት የተከማቹ የብዙ መንግሥታት ታላቅ ጩኸት አለ››

ተከማችተዋል
‹‹ተሰብስበዋል››

ከአድማሱ ባሻገር
‹‹ከአድማስ ማዶ ርቆ ካለ ቦታ›› ወይም፣ ‹‹በጣም ሩቅ ከሆነ ቦታ››

የፍርዱ ጦር መሣሪያ
ባቢሎንን እንዲያጠቁ እግዚአብሔር የሚልካቸው ወታደሮች የጦር መሣሪያዎች እንዲሆኑ ተነግሯል። ‹‹ፍርድ›› እግዚአብሔር ባቢሎን ላይ ስለ ፈረደ ቅጣትን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ባቢሎንን ለመቅጣት የሚጠቀምበት ሰራዊት››

Isaiah 13:6

ጩኹ
ድምፃችሁን አሰምታችሁ ጩኹ፤ ብዙውን ጊዜ ቃሉ የሚያመለክተው ጉዳት ስለ ደረሰበት እየጮኸ ያለውን እንስሳ ድምፅ ነው።

የያህዌ ቀን ቀርቦአል
የሚሆነው ነገር በጣም እየቀረበ እንዳለ ነገር መሆኑ ተነግሮአል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የያህዌ ቀን በቅርቡ ይሆናል››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሁሉን ከሚችል አምላክ ዘንድ ጥፋት ይመጣል
‹‹ይመጣል›› የተባለው የያህዌ ቀን ነው። ‹‹ከጥፋት ጋር ይመጣል›› ማለት በዚያ ቀን ጥፋት ይሆናል ማለት ነው። ‹‹ሁሉን ከሚችል አምላክ ዘንድ ጥፋት›› ማለት ሁሉን ቻዩ ያጠፋቸዋል ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በዚያን ቃል ሁሉን ቻዩ አምላክ ያጠፋቸዋል››

እጆች ሁሉ ሽባ ይሆናሉ
ይህ የሚያሳየው ሰዎች ሁሉ በጣም ደካማና ምንም ማድረግ አለመቻላቸውን ነው።

የሰውም ሁሉ ልብ ይቀልጣል
ሰዎች በጣም መፍራታቸው ከልባቸው መቅለጥ ጋር ተመሳስሎአል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰው ሁሉ በጣም ይፈራል››

ሥቃይና ጭንቀት ይይዛቸዋል
ሰዎች ላይ ከባድ ሥቃይና ጭንቀት በድንገት መድረሱ ሥቃይና ጭንቀት ጨምድዶ እንደሚይዝ ሰው ተመስሎአል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በድንገት ከባድ ሥቃይና ጭንቀት ይደርስባቸዋል››

ምጥ እንደ ያዛት ሴት
ምጥ ልጅ መውለድን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ልጅ እንደምትወልድ ሴት ወይም፣ ‹‹ልጅ የምትወልድ ሴት እንደሚሰማት ሥቃይ››

ፊታቸው እንደ እሳት ነበልባል ይሆናል
ቀይና ፍም መሆኑ በእሳት ተመስሎአል። ፊታቸው ቀይ የሚሆንበት ምክንያት ሊሆን የሚችለው፣ 1) ሰዎቹ በጣም በመፍራታቸው ወይም 2) ሰዎቹ በጣም በማፈራቸው፤ ወይም 3) በማልቀሳቸው ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ፊታቸው ቀይና ፍም ይሆናል››

Isaiah 13:9

የያህዌ ቁጣ ከጨካኝ መዓትና ከብርቱ ቁጣ ጋር ተሞልቶ ይመጣል።
ቀኑ የሚመጣው ከመዓትና ከቁጣ ጋር መሆኑ በዚያ ቀን መዓትና ቁጣ ይኖራል ማለት ነው። ‹‹መዓት›› እና፣ ‹‹ቁጣ›› የተሰኙትን ቃሎች፣ ‹‹አስፈሪ›› እና፣ ‹‹ቁጡ›› ብሎ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በዚያ የያህዌ ቀን እርሱ አስፈሪና ቁጡ ይሆናል››

ቁጣ ተሞልቶ
እዚህ ላይ ቁጣ የሚቆጣውን ሰው መያዣ የሚሞላ ነገር መሆኑ ተነግሯል። ቁጣ ተሞልቶ በጣም ተቆጥቶ ማለት ነው።

ምድሪቱን ባድማ ለማድረግ
‹‹ባድማ›› የሚለውን ቃል፣ ‹‹የፍርስራሽ ክምር›› በሚል ቃል መለወጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ምድሪቱን የፍርስራሽ ክምር ለማድረግ››

የሰማይ ከዋክብትና ሰራዊታቸው
‹‹ሰማይ ላይ ያሉ ከዋክብት››

ብርሃናቸውን አይሰጡም
ብርሃን መስጠት፣ ‹‹ማብራት›› የሚለውን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አያበሩም››

ፀሐይ ትጨልማለች
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ ፀሐይን ያጨልማል›› ወይም፣ ‹‹ፀሐይ ጨለማ ትሆናለች››

Isaiah 13:11

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
በያህዌ ቀን ምን እንደሚያደርግ ያህዌ እየተናገረ ነው።

ዓለም
ይህ ሕዝብ ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የዓለም ሕዝብ››

ክፉዎች... ትዕቢተኞች... ጨካኞች
እነዚህ ሐረጐች የሚያመለክቱት እነዚህ ባሕርያት ያሏቸውን ሰዎች ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ክፉ ሰዎች... ትዕቢተኛ ሰዎች... ጨካኝ ሰዎች››

ጨካኝ
‹‹ምሕረት የለሽ››

የጨካኞችን እብሪት ዝቅ ይላል
ብዙውን ጊዜ ዝቅ ማለት የሚያመለክተው መዋረድን ነው። የሰዎችን እብሪት ዝቅ ማድረግ እነርሱን ማዋረድን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጨካኞችን ያዋርዳል››

ከነጠረ ወርቅ ይልቅ ሰዎች ጥቂት ይሆናሉ
ጥቂት ሰዎች ብቻ የሚኖሩበትን ምክንያት ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ብዙ ሰዎች እንዲገደሉ ስለማደርግ፣ በሕይወት ያሉት ከነጠረ ወርቅ ይልቅ ያነሱ ይሆናሉ››

ሰዎች ከነጠረ ወርቅ ይልቅ ጥቂት... ከንጹሕ የአፈር ወርቅ ይልቅ ለማግኘት የሚያስቸግር ይሆናሉ
እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው።

ንጹህ የኦፊር ወርቅ
ኦፊር ንጹሕ ወርቅ የነበረበት ቦታ ነው።

Isaiah 13:13

አጠቃላይ መረጃ
አሁንም ያህዌ እየተናገረ ነው።

እንደሚታደን ሚዳቋ፣ እረኛም እንደሌለው በግ
ምንም መከላከያ የሌላቸው የእስራኤል ሕዝብ አዳኝ ወይም የዱር አውሬ እንደሚያሳድደው ሚዳቋ ወይም በግ እንደሆኑ ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰዎች ሲያድኑት በፍጥነት እንደሚሮጥ ሚዳቋ፣ ከአራዊት እንደሚሸሽ እረኛ እንደሌለው በግ››

ሚዳቋ
አጋዛን የሚመስል እንስሳ። ሰዎች ያድኗቸዋል፤ አንዳንዴም የዱር አራዊት ያጠፏቸዋል፤ ይበሏቸዋል።

እረኛ እንደ ሌለው በግ
እረኛ የሌለው በግ ከሚያጠቁትና ከሚገድሉት የዱር አራዊት የሚከላከልበት የለውም።

Isaiah 13:15

የተገኘ ሁሉ ይገደላል... የተያዘም ሁሉ በሰይፍ ይሞታል
እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጠላት ያገኘውን ሰው ሁሉ በሰይፍ ይገድላል››

ሕፃናቶቻቸው ይጨፈጨፋሉ
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጠላት ሕፃናቶቻቸውንም ይቆራርጣል›› ወይም፣ ‹‹ጠላት ሕፃናቶቻቸው እስኪሞቱ ድረስ ይደበደባል››

በዐይናቸው ፊት
እዚህ ላይ ለሚያዩት ነገር አጽንዖት ለመስጠት ሰዎች፣ ‹‹በዐይናቸው›› ተወክለዋል። ወላጆች ልጆቻቸውን ለመርዳት ምንም ማድረግ እንደማይችሉ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ፊት ለፊታቸው›› ወይም፣ ‹‹ዐቅም ያጡ ወላጆቻቸው እያዩ››

ቤታቸው ይዘረፋል
ይህም ማለት ዋጋ ያለው ማንኛውም ነገር ከቤታቸው ይወሰዳል ማለት ነው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጠላት የሕዝቡን ቤት ይዘርፋል›› ወይም፣ ‹‹ጠላት ማንኛውንም ጠቃሚ ነገር ከቤታቸው ይወስዳል››

ሚስቶቻቸው ይደፈራሉ
ይህም ማለት ሚስቶቻቸው ጥቃት ይደርስባቸዋል፤ ከእነርሱ ጋር እንዲተኙ ይገደዳሉ ማለት ነው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ የሰዎች ሚስቶች ይደፈራሉ›› ወይም፣ ‹‹ጠላቶቻቸው ሚስቶቻቸውን ይደፍራሉ››

Isaiah 13:17

አያያዝ ዐረፍተ ነገር
አሁንም ያህዌ እየተናገረ ነው።

ሜዶናውያንን አስነሣባቸዋለሁ
ሰዎች አንድ ነገር ማድረግ እንዲፈልጉ ማድረግ እነርሱን ማነሣሣት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሜዶናውያን እነርሱን ማጥቃት እንዲፈልጉ አደርጋለሁ››

ቀስታቸው ይናደፋል
‹‹ቀስታቸው›› ቀስቶች የሚጠቀሙ ወታደሮች ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ወታደሮቻቸው ለመግደል ቀስትና ፍላጻ ይጠቀማሉ››

Isaiah 13:19

አያያዝ ዐረፍተ ነገሮች
አሁንም ያህዌ እየተናገረ ነው

በጣም የተደነቁ መንግሥታት
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። ‹‹አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰዎች በጣም የሚያደንቁት መንግሥት››

ከዚያም ባቢሎንን... እግዚአብሔር ይገለብጣታል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። ‹‹አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከዚያም ሶዶምና ገሞራን እንዲያጠፋ ከመንግሥታት በጣም የተደነቀችውን፣ የከለዳውያን ትምክህት የሆነችውን ባቢሎንን እግዚአብሔር ያጠፋል።››

የከለዳውያን ውበት ትምክህት
‹‹ውበት›› እና፣ ‹‹ትምክህት›› የተሰኙትን ቃሎች በሌላ መተርጐም ይቻላል። ‹‹ውበት›› የባቢሎንን ማማር ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከለዳውያን የሚመኩባት ውብ ከተማ››

የሚቀመጥባት ወይም የሚኖርባት አይኖርም
ሁለቱ ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ማንም አይኖርባትም››

ከትውልድ እስከ ትውልድ
‹‹ከትውልድ እስከ ትውልድ›› የተሰኘው ሐረግ በሚመጣው ዘመን ትውልዶች ሁሉ ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለዘላለም›› ወይም፣ ‹‹ለሁልጊዜ››

ዐረብ
የሚያመለክተው ጠቅላላ ዐረቦችን እንጂ፣ ግለሰብን አይደለም። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ዐረቦች›› ወይም፣ ‹‹የዐረብ ሕዝብ››

Isaiah 13:21

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ያህዌ ባቢሎን ላይ የሚደርሰውን እየተናገረ ነው።

በዚያ ይተኛሉ
‹‹በባቢሎን ይተኛሉ››

ቤቶቻቸው
‹‹የሕዝቡ ቤት››

ጉጉቶች
ጉጉቶች ሌሊት የሚያድኑ የዱር ወፎች ናቸው

ሰጐኖች
ሰጐኖች በፍጥነት መሮጥ እንጂ፣ መብረር የማይችሉ የዱር ወፎች ናቸው።

ጅቦች
ጅቦች ውሾች የሚመስሉ የሞቱ እንስሳዎች የሚበሉ ትልልቅ የዱር አራዊት ናቸው። ጩኸታቸው የሚስቅ ሰው ይመስላል።

ባማሩ ቤቶች ያሉ ቀበሮዎች
‹‹ይጮኻሉ›› የሚለው ውስጠ ታዋቂ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በማሩ ቤቶች ቀበሮዎች ይጮኻሉ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 14

1 እግዚአብሔርም ያዕቆብን ይምረዋል፣ እስራኤልንም ደግሞ ይመርጠዋል፣ በገዛ አገራቸውም ያኖራቸዋል። መጻተኛም ከእርሱ ጋር ይተባበራል፣ ከያዕቆብም
ቤት ጋር ይጣበቃል። 2 አሕዛብም ይዘው ወደ ስፍራቸው ያመጡአቸዋል። የእስራኤልም ቤት በእግዚአብሔር ምድር እንደ ወንዶችና ሴቶች ባሪያዎች አድርገው
ይገዙአቸዋል። የማረኩአቸውን ይማርካሉ፣ አስጨናቂዎችንም ይገዛሉ። 3 በዚያም ቀን፣ እግዚአብሔር ከጎዘንህና ከመከራህ ከተገዛህለትም ከጽኑ ባርነት
ያሳርፍሃል። 4 ይህንም ምሳሌ በባቢሎን ንጉሥ ላይ ታነሣለህ፣ "አስጨናቂ እንዴት በፍጻሜው ዐረፈ፣ ኩሩውስ እንዴት ጸጥ አለ!" ይላሉ። 5 እግዚአብሔር
የአሕዛብ ገዢዎችን በትር በመዓትና በማያቋርጥ መምታት መታ፣ 6 አሕዛብንም ባልተከለከለ መከራ፣ በቍጣው የገዛውን የጎጥኣንን በትር የአለቆችንም ዘንግ
እግዚአብሔር ሰብሮአል። 7 ምድርም ሁሉ ዐርፋ በጸጥታ ተቀምጣለች፤ በዝማሬ ክብረ-በዓላቸውን ማድረግ ጀምረዋል። 8 ጥድና የሊባኖስ ዝግባ፣ 'አንተ
ከተዋረድህ ጀምሮ ማንም ይቈርጠን ዘንድ አልወጣብንም' ብለው በአንተ ደስ አላቸው። 9 ሲኦል በመምጣትህ ልትገናኝህ በታች ታወከች፤ የሞቱትንም፣
የምድርን ታላላቆች ሁሉ፣ ለአንተ አንቀሳቀሰች፣ የአሕዛብንም ነገሥታት ሁሉ ከዙፋኖቻቸው አስነሣች። 10 እነዚህ ሁሉ ተናግረው፣ 'አንተ ደግሞ እንደ እኛ
ደክመሃል። እኛን መስለሃል። ጌጥህና የበገናህ ድምፅ ወደ ሲኦል ወረደ፤ 11 በበታችህም ብል ተነጥፎአል። ትልም ይሸፍንሃል' ብለው ይመልሱልሃል። 12
አንተ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ ሆይ፣ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ! አሕዛብንም ያዋረድህ አንተ ሆይ፣ እንዴት እስከ ምድር ድረስ ተቈረጥህ! 13 አንተ በልብህ፣
'ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ፣ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ፣ በሰሜንም ዳርቻ በመሰብሰቢያ ተራራ ላይ እቀመጣለሁ፤ 14
ከዳመናዎች ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ፣ በልዑልም እመሰላለሁ' አልህ። 15 ነገር ግን ወደ ሲኦል፣ ወደ ጕድጓዱም ጥልቅ ትወርዳለህ። 16 የሚያዩህ አፍጥጠው
ይመለከቱሃልና። በውኑ ምድርን ያንቀጠቀጠ፣ መንግሥታትንም ያናወጠ፥ 17 ዓለሙን ሁሉ ባድማ ያደረገ፣ ከተሞችንም ያፈረሰ ምርከኞቹንም ወደ ቤታቸው
ያልሰደደ ሰው ይህ ነውን? ብለው ያስተውሉሃል። 18 የአሕዛብ ነገሥታት ሁሉ፣ በየመቃብራቸው በክብር አንቀላፍተዋል። 19 አንተ ግን እንደ ተጠላ ቅርንጫፍ
ከመቃብርህ ተጥለሃል፤ በሰይፍም የተወጉት፣ ተገድለውም ወደ ጕድጓዱ ድንጋዮች የወረዱት ከድነውሃል፤ እንደ ተረገጠም ሬሳ ሆነሃል። 20 ምድርህን
አጥፍተሃልና፣ ሕዝብህንም ገድለሃልና ከእነርሱ ጋር በመቃብር በአንድነት አትሆንም፤ የክፉዎች ዘር ለዘላለም የተጠራ አይሆንም።" 21 እንዳይነሡም፣
ምድርንም እንዳይወርሱ፣ የዓለሙንም ፊት በከተሞች እንዳይሞሉ ስለ አባቶቻቸው በደል ለልጆቹ ሞትን አዘጋጁለቸው። 22 "በእነርሱ ላይ እነሣለሁ" ይላል
የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፤ ከባቢሎን ስምንና ቅሬታን፣ ዘርንና ትውልድንም እቈርጣለሁ ይላል እግዚአብሔር። 23 "የጃርት መኖርያ የውኃም መቋሚያ
አደርጋታለሁ፤ በጥፋትም መጥረጊያ እጠርጋታለሁ" ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር። 24 የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ምሎአል፣ "እንደ
ተናገርሁ በእርግጥ ይሆናል፣ እንደ አሰብሁም እንዲሁ ይቆማል። 25 አሦርን በምድሬ ላይ እሰብረዋለሁ፣ በተራራዬም ላይ እረግጠዋለሁ። ከዚያም ቀንበሩ
ከእነርሱ ላይ ይነሣል፣ ሸክሙም ከጫንቃቸው ላይ ይወገዳል።" 26 በምድር ሁሉ ላይ እግዚአብሔር ያሰበው አሳብ ይህ ነው፣ በአሕዛብም ሁሉ ላይ የተዘረጋች
እጅ ይህች ናት። 27 የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ይህን አስቦአል፤ የሚያስጥለውስ ማን ነው? እጁም ተዘርግታለች፤ የሚመልሳትስ ማን ነው? 28 ንጉሡ አካዝ
በሞተበት ዓመት ይህ ዐዋጅ ወጣ። 29 ፍልስጥኤም ሆይ፣ ከእባቡ ሥር እፉኝት ይወጣልና፣ ፍሬውም የሚበርርና እሳት የሚመስል እባብ ይሆናልና የመታሸ
በትር ስለ ተሰበረ ሁላችሁም ደስ አይበላችሁ። 30 የድሆችም የበኩር ልጆች ይሰማራሉ፣ ችግረኞችም ተዘልለው ይተኛሉ፤ ሥርህንም በራብ እገድላለሁ፣
ቅሬታህም ይገደላል። 31 አንተ በር ሆይ፣ ወዮ በል አንቺም ከተማ ሆይ፣ ጩኺ፤ ፍልስጥኤም ሆይ፣ ሁላችሁም ቀልጣችኋል፤ ጢስ ከሰሜን ይመጣል
ከጭፍራውም ተለይቶ የሚቀር የለም። 32 ለሕዝቡም መልእክተኞች ምን ብሎ መመለስ ይገባል? እግዚአብሔር ጽዮንን እንደ መሠረተ፣ የሕዝቡም ችግረኞች
በእርስዋ ውስጥ እንደሚጠጉ ነው።

Isaiah 14:1

ያህዌ ለያዕቆብ ይራራለታል
‹‹ያዕቆብ›› የሚያመለክተው የያዕቆብን ዘር ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ የያዕቆብን ዘሮች ይምራቸዋል››

ከያዕቆብ ቤት ጋር ይተባበራሉ
የያዕቆብ ቤት የሚያመለክተው የያዕቆብን ዘር እስራኤላውያንን ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከያዕቆብ ዘሮች ጋር ይተባበራሉ››

ሕዝቦች ወደ ገዛ ቦታቸው ያመጧቸዋል
‹‹ሕዝቦች የያዕቆብን ዘሮች ወደ እስራኤል ምድር መልሰው ያመጧቸዋል››

የእስራኤል ቤት
ይህ የሚያመለክተው እስራኤላውያንን፣ የእስራኤል ዘሮችን ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የእስራኤል ዘሮች››

የማረኳቸውን ይማርካሉ
‹‹የእስራኤል ወታደሮች እስራኤላውያንን ማርከው የነበሩትን ይማርካሉ››

Isaiah 14:3

ከሥቃይህና ከመከራህ
‹‹የአንተ›› የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር ቢሆንም፣ የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። እንዲሁም፣ ‹‹ሥቃይ›› እና፣ ‹‹መከራ›› በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ቢሆኑም፣ በአንድነት ጥቅም ላይ የዋሉት አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በጣም እንድትሠቃይ ካደረጉህ ነገሮች››

ጨቋኙ እንዴት አበቃለት
‹‹ጨቋኙ አበቃለት›› ይህ ቃለ አጋኖ ነው።

የትዕቢተኛም ቁጣ አበቃለት
‹‹የትዕቢተኛ ቁጣ›› የሚለው የሚያመለክተው ሌሎች ሕዝቦችን በጭካኔ ያሠቃይ የነበረውን የባቢሎንን ንጉሥ ትዕቢት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጭካኔው አበቃለት›› ወይም፣ ‹‹ከእንግዲህ ሕዝብን አይጨቁንም››

Isaiah 14:5

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ይህ እስራኤላውያን የባቢሎን ንጉሥ ላይ የሚያዜሙት የፌዝ ዜማ ክፍል ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ያህዌ የክፉዎችን ዘንግ ሰብሮአል
የክፉዎች ዘንግ ክፉዎች ሌሎች ሰዎችን የሚመቱበትን ዘንግ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። ዘንጋቸውን መስበር ሌሎች ላይ የሚያደርሱትን ጭካኔ ጎይል መስበር ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ የክፉዎችን ጎይል ደምስሶአል።››

የገዦች በትረ መንግሥት
በትረ መንግሥት የሚያመለክተው የመግዛትን ሥልጣን ነው። በትረ መንግሥቱን መስበር የገዢውን ሥልጣን መደምሰስ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ የክፉ ገዦችን ሥልጣን ደምስሶአል።››

ሕዝቦችን የመታውን
‹‹ሕዝቦችን ሲመታ የነበረውን›› ክፉዎች በበትራቸው ሰዎችን ይመታሉ።

በማያቋርጥ ምት
‹‹ማቆሚያ የሌለው›› ወይም፣ ‹‹ደግሞ ደጋግሞ››

ሕዝቦችን ያስገበረውን
‹‹ሌሎች አገሮችን ድል ያደረገውን››

ያለ መከልከል የመታውን
‹‹ማቆሚያ የሌለው ጥቃት››

Isaiah 14:7

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ይህ እስራኤላውያን የባቢሎን ንጉሥ ላይ የሚያዜሙት የፌዝ ዜማ ክፍል ነው።

ምድር ሁሉ
ይህ በምድር የሚኖረውን ሁሉ ይመለከታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በምድር የሚኖር ማንኛውም››

ጥድና የሊባኖስ ዝግባ እንኳ በአንተ ላይ ደስ አላቸው
ኢሳይያስ ዛፎች ደስ እንደሚላቸው ሰዎች እንደሆኑ ይናገራል። ይህም እግዚአብሔር የባቢሎንን ንጉሥ ማስቆሙ ታላቅ ነገር ስለሆነ፣ ቢችል ኖሮ ሌላው ቀርቶ ተፈጥሮ እንኳ ደስ እንደሚለው አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የጥድ ዛፍና የሊባኖስ ዝግባ እንኳ ሳይቀር፣ በአንተ ላይ በደረሰው ደስ ይላቸዋል››

በአንተ ላይ ደስ ይላቸዋል
ደስ የሚላቸው ለምን እንደሆነ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔር ዐቅም ስላሳጣህ ደስ ይላቸዋል››

ዝቅ ዝቅ ብለሃልና
ዝቅ ዝቅ ማለት ዐቅመ ቢስና ዋጋ የሌለው መሆን ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዐቅመ ቢስ ሆነሃልና››

ከበታችህ ሲኦል ልትቀበልህ ጓጉታለች
ሲኦል እንግዶችን የሚቀበል ሰው ተደርጐ ተነግሯል። ይህ የሚመለክተው ንጉሡ እንደሚሞት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሲኦል አንተን ለማስተናገድ ዝግጁ ናት››

እንዲቀበሉህ ሙታንን፣ የምድር ነገሥታትን ሁሉ ያስነሣል
‹‹ሙታንን፣ የምድር ነገሥታትን ሁሉ ያነቃል።›› ሲኦል ውስጡ ላሉት የሚነቃ ሰው ተደርጐ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሲኦል ውስጥ ያሉ የሞቱ የምድር ነገሥታት ሁሉ እንኳን መጣህ ሊሉህ ይነቃሉ››

Isaiah 14:10

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ይህ እስራኤላውን የባቢሎን ንጉሥ ላይ የሚያዜሙት የፌዝ ዜማ ክፍል ነው። እዚህ ላይ የሚያዜሙት ሲኦል ውስጥ ያሉ የሞቱ ነገሥታት ምን እንደሚሉት ነው።

ሁሉም ይናገሩሃል፤ እንዲህም ይሉሃል
‹‹እነርሱ›› የሚለው ሲኦል ውስጥ ያሉትን የሞቱ ነገሥታት ሲሆን፣ ‹‹አንተ›› የሚለው የባቢሎንን ንጉሥ ነው።

ክብርህ ወደ ሲኦል ወረደ
ክብሩ ወደ ታች ወደ ሲኦል የወረደ ይመስል፣ ከእንግዲህ ምንም ክብር እንደሌለው የሞቱ የምድር ነገሥታት ስለ ባቢሎን ንጉሥ ይናገራሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔር ወዲህ ወደ ሲኦል ከላከህ ወዲህ ክብርህ አብቅቷል››

ከባለ አውታር የሙዚቃ መሣሪያዎችህ ጋር
ንጉሡን ለማክበር ሰዎች ባለ አውታር የሙዚቃ መሣሪያዎች ይሠራሉ። ሙዚቃው ወደ ሲኦል ስለ ወረደ ከእንግዲህ ሰዎች በሙዚቃ የባቢሎንን ንጉሥ እንደማያከብሩ የሞቱት ነገሥታት ይናገራሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተን ለማክበር ሙዚቃ ከሚጫወቱ ሰዎች ድምፅ ጋር››

Isaiah 14:12

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ይህ እስራኤላውያን የባቢሎን ንጉሥ ላይ የሚያዜሙት የፌዝ ዜማ ክፍል ነው።

አንተ የንጋት ልጅ የአጥቢያ ኮከብ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ
የንጋት ኮከብ ከመንጋቱ በፊት የሚወጣ ደማቅ ኮከብ ነው። በአንድ ወቅት ታላቅ እንደ ነበር፣ አሁን ግን ምንም ማለት እንዳልሆነ ለማመልከት የእስራኤል ሕዝብ ስለ ባቢሎን ንጉሥ ይናገራሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ንጋት ኮከብ ደማቅ ነበርህ፤ አሁን ግን ከሰማይ ወድቀሃል››

እንዴት ተቆርጠህ ወደ ምድር ተጣልህ
የእስራኤል ሕዝብ የባቢሎን ንጉሥ ተቆርጦ የተጣለ ዛፍ እንደሆነ ይናገራሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ተቆርጦ ወደ መሬት እንደ ተጣለ ዛፍ ተሸንፈሃል››

በመሰብሰቢያ ተራራ እቀመጣለሁ
ይህ የሚያመለክተው በቅርብ ምሥራቅ የነበሩ አብዛኞቹ ሰዎች የከነዓናውያን አማልክት ከሶርያ በስተ ሰሜን ባለው ቦታ ተራራ ጫፍ ላይ እንደሚሰበሰቡ እንደሚያውቁ ነው። ተራራ ላይ መቀመጥ ከአማልክት ጋር መግዛትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አማልክት በሚሰበሰቡበት ተራራ ላይ እገዛለሁ››

በሰሜን በኩል ጫፍ ላይ
‹‹በሰሜን በኩል ርቆ›› በሰሜን ያለው ተራራ ዛፎን ተብሎ ነበር የሚጠራው። አንዳንድ ዘመናዊ ቅጂዎች፣ ‹‹በዛፎን በኩል ሩቅ ቦታ›› ይላሉ።

Isaiah 14:15

አያያዥ ዐረፍተ ነገሮች
ይህ እስራኤላውን የባቢሎን ንጉሥ ላይ የሚያዜሙት የፌዝ ዜማ ክፍል ነው።

አሁን ወደ ሲኦል ወርደሃል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አሁን ግን እግዚአብሔር ወደ ሲኦል ጥሎሃል››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሰውየው ይኽ ነው?
ሰዎች እንዲህ በማለት የሚጠይቁት በባቢሎን ንጉሥ ላይ ለማፌዝ ወይም በእርሱ ላይ በደረሰው የተሰማቸውን ድንጋጤ ለመግለጽ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹መቼም ሰውየው ይኼ ሊሆን አይችልም››

ምድርን ያናወጠ
ይህም ማለት 1) የንጉሡ ሰራዊት ሕዝብን ድል ለማድረግ ሲገሠግሥ ምድር ተናወጠች ማለት ሊሆን ይችላል፤ ወይም 2) የምድር ሕዝብ እርሱን በመፍራት ተንቀጠቀጡ ማለት ሊሆን ይችላል።

መንግሥታትን ያንቀጠቀጠ
ይህም ማለት 1) መንግሥታትን ድል ማድረግን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል ወይም 2) ‹‹መንግሥታትን ማሸበርን›› የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።

ዓለምን ምድረ በዳ ያደረገ
‹‹ሰዎች የሚኖሩባቸውን ቦታዎች ምድረ በዳ ያደረገ››

Isaiah 14:18

አያያዥ ዐረፍተ ነገሮች
ይህ እስራኤላውያን የባቢሎን ንጉሥ ላይ ሲያዜሙ ከነበረው የፌዝ ዜማ የመጨረሻ ክፍል ነው።

ሁሉም በክብር ተጋድመዋል
ይህ ማለት ሥጋቸው በክብር ተቀብሯል ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ክብር ባለው ሁኔታ የተቀበሩ ነገሥታት ሁሉ››

ነገር ግን ከመቃብር ወጥተህ ተጥለሃል
ከመቃብር ወጥቶ መጣል መጀመሪያውኑ አለመቀበርን ነው የሚያመለክተው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አንተ ግን አልተቀበርህም፤ ሥጋህ መሬት ላይ ቀርቷል››

እንደሚጣል ቅርንጫፍ
የተጣለ ቅርንጫፍ ዋጋ የሌለው ነገርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ወዲያ እንደሚጣል የማይረባ ቅርንጫፍ››

ሙታን እንደ መጐናጸፊያ ይሸፍኑሃል
ይህ ማለት ብዙ ሙታን እርሱ ላይ ይሆናሉ ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የሙታን አካል ጨርሶ ይሸፍንሃል›› ወይም፣ ‹‹የሞቱ ወታደሮች ሬሳ ይከመርብሃል››

በሰይፍ የተወጉት
ይህ የሚገልጸው በዚህ ዐረፍተ ነገር መጀመሪያ ላይ ተነሥተው የነበሩትን፣ ‹‹ሙታን›› ነው። በሰይፍ መወጋት በጦርነት መገደል ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በጦርነት የተገደሉ››

ወደ ጥልቁ ድንጋዮች በወረዱት
ጥልቁ የሚለው የሚያመለክተው ገሃነምን ወይም ብዙ የሞቱ ሰዎች የሚጣሉበት ምድር ላይ ያለ ሰፊ ጉድጓድን ነው።

ከእነርሱ ጋር በመቃብር አትሆንም
‹‹እነርሱ›› የተባሉት ሞተው በሚገባ የተቀበሩት ሌሎች ነገሥታት ናቸው። ከእነርሱ ጋር በመቃብር መሆን እነርሱ እንደ ተቀበሩ መቀበር ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሌሎች ነገሥታት እንደ ተቀበሩ አትቀበርም››

የክፉ አድራጊዎች ዘር ጨርሶ አይታወስም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከእንግዲህ ስለ ክፉ አድራጊዎች ዘር የሚናገር አይኖርም››

Isaiah 14:21

ልጆቹ የሚታረዱበትን ቦታ አዘጋጅ
‹‹የሚታረዱበት›› የሚለውን፣ ‹‹የሚገደሉበት›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የባቢሎንን ንጉሥ ልጆች ለመግደል ተዘጋጁ››

ለአባቶቻቸው ርኩሰት
‹‹ርኩሰት›› የሚለውን፣ ‹‹ታላቅ ኀጢአት›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አባቶቻቸው ለመፈጸሙት ታላቅ ኀጢአት››

ከእንግዲህ አይነሡም
‹‹መነሣት›› ኀያል መሆንን ወይም ማጥቃትን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከእንግዲህ ኀያል እንዳይሆኑ›› ወይም፣ ‹‹ከእንግዲህ እንዳያጠቁ››

ምድርን እንዲወርሱ
ይህ የሚያመለክተው የምድር ሰዎችን መቆጣጠርን ሲሆን፣ እዚህ ላይ ግን እነርሱን ድል ማድረግ ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የምድር ሰዎችን መቆጣጠር›› ወይም፣ ‹‹የምድርን ሕዝብ ድል ማድረግ››

ዓለምን በከተሞች በሙላት
ይህ ዓለም ብዙ ከተሞች እንዲኖሩዋት ማድረግ ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በመላው ዓለም ከተሞች መሥራት››

በእነርሱ ላይ እነሣለሁ
ይህ ማለት እግዚአብሔር እነርሱ ላይ አንዳች ነገር ያደርጋል ማለት ነው። ‹‹እነርሱ›› የሚያመለክተው የባቢሎንን ሕዝብ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አጠቃቸዋለሁ›› ወይም፣ ‹‹የሚያጠቋቸው ሰዎች እልካለሁ››

የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
ያህዌ ስሙን በመጥራት የተናገረው እርግጥ መሆኑን ይገልጻል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የሰራዊት ጌታ ያህዌ የሚለው እንዲህ ነው›› ወይም፣ ‹‹እኔ የሰራዊት ጌታ ያህዌ ያልሁት እንዲህ ነው››

የሰራዊት ጌታ ያህዌ
ኢሳይያስ 1፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደተረጐምኸው ተመልከት።

የባቢሎንን ስም፣ ትውልድና ትሩፋኖችዋን እቆርጣለሁ
‹‹እቆርጣለሁ›› አጠፋለሁ ማለት ነው። ‹‹ባቢሎን›› የባቢሎንን ሕዝብ ይወክላል። እንዲሁም፣ ‹‹ስም›› የባቢሎንን ዝና ወይም፣ እንደ መንግሥት ባቢሎን ራሷን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከሕዝቡ ልጆችና የልጅ ልጆች ጋር ባቢሎንን አጠፋለሁ››

አደርጋታለሁ
‹‹እርሷ›› የባቢሎንን ከተማ ያመለክታል። ብዙውን ጊዜ ከተሞች በሴቶች ስም ይጠራሉ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንዲህም… አደርጋታለሁ››

የጃርት መኖሪያ
ይህ የሚያመለክተው የሚኖርባቸው ስለማይኖር አራዊት በከተማው ውስጥ እንደሚኖሩ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጃርቶች የሚኖሩበት ቦታ›› ወይም፣ ‹‹የዱር አራዊት የሚኖሩበት ቦታ››

ረግረግ ቦታ
የታቆረና የተከማቸ ውሃ እንዳኖርበት ማድረግ ከተማው የእነዚህ ነገሮች መኖሪያ እንዲሆን ማድረግ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የታቆረ ውሃ መኖሪያ ቦታ››

በጥፋት መጥረጊያ እጠርጋታለሁ
ይህ የሚያመለክተው የባቢሎንን ጨርሶ መውደምና ሰዎች ጠርገው የሚጥሉት ቆሻሻ ይመስል፣ ከእንግዲህ እንደማትኖር ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በመጥረጊያ እንደሚጠረግ ነገር ጨርሶ አጠፋታለሁ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Isaiah 14:24

የሰራዊት ጌታ ያህዌ
ኢሳይያስ 1፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

እንደ ዐቀድሁት እንዲሁ ይሆናል፤ እንደ አሰብሁት ይከናወናል
እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እኔ ያቀድሁት ነገር በእርግጥ ይሆናል››

አሦራውያንን በእጄ ላይ እሰብራለሁ
መስበር የሚወክለው ማሸነፍን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አሦራውያንን በምድሬ ላይ አሸንፋቸዋለሁ›› ወይም፣ ‹‹በምድሬ ያሉትን አሦራውያን አሸንፋቸዋለሁ››

አሦራውያን
ይህ የሚወክለው የአሦራውያንን ንጉሥና ሰራዊቱን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የአሦራውያን ንጉሥና ሰራዊቱ›› ወይም፣ ‹‹የአሦራውያን ሰራዊት››

በእግሬ እረግጠዋለሁ
ይህ የሚያመለክተው ጨርሶ ማሸነፍን ነው።

በዚያ ጊዜ ቀንበሩ ከላያቸው፣ ሸክሙም ከትከሻቸው ይነሣል
ይህ በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በዚያ ጊዜ ቀንበሩን ከላያቸው ሸክሙንም ከትከሻው አነሣለሁ።

በዚያ ጊዜ ቀንበሩ ከላያቸው፣ ሸክሙም ከትከሻቸው ይነሣል
እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። ቀንበርንና ሸክምን ማንሣት ሰዎችን ከባርነት ነጻ ማድረግ ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በዚያ ጊዜ ከባዱን ሸክም ከትከሻቸው በማስወገድ እስራኤላውያንን ከአሦራውያን ባርነት ነጻ አደርጋለሁ››

ቀንበሩ... ሸክሙ
‹‹የእርሱ›› የሚለው የሚያመለክተው አሦርን ነው።

ከላያቸው... ከትከሻቸው ላይ
x

Isaiah 14:26

አጠቃላይ መረጃ
እየተናገረ ያለው ኢሳይያስ ይሆናል ወይም ያህዌ ይሆናል

ለምድር ሁሉ የታቀደው ይህ ነው
‹‹የታቀደው›› የሚለውን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለምድር ሁሉ እግዚአብሔር ያለው ዕቅድ ይህ ነው››

በአሕዛብ ሁሉ ላይ የተዘረጋው እጅ ይህ ነው
እግዚአብሔር አሕዛብን ለመቅጣት መዘጋጀቱ እነርሱን ለመምታት እጁን ከመዘርጋት ጋር ተመሳስሎአል። ‹‹እጅ›› የሚለው ቃል ኀይሉን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ይህ አሕዛብን ሁሉ የሚቀጣ የያህዌ ኀይል ነው›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ አሕዛብን የሚቀጣው እንዲህ ነው››

ማን ያስቆመዋል?
ጥያቄው ያህዌን ማንም እንደማያስቆመው አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሚያስቆመው የለም››

የሰራዊት ጌታ ያህዌ
ኢሳይያስ 1፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

እጁም ተዘርግቷል
ይህ ያህዌ አሕዛብን ለመቅጣት መዘጋጀቱን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እነርሱን›› ለመቅጣት ተዘጋጅቶአል››

ማንስ ይመልሰዋል?
ጥያቄው የቀረበው የእግዚአብሔርን እጅ የሚመልሰው እንደሌለ ለመናገር ነው። የእርሱን እጅ መመለስ አሕዛብን እንዳይቀጣ እርሱን ማስቆም ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ማንም›› አይመልሰውም›› ወይም፣ ‹‹እነርሱን እንዳይቀጣ ማንም አይመልሰውም››

Isaiah 14:28

የመታህ በትር ተሰብሮአል
ፍልስጥኤምን የመታ በትር እነርሱን እንዲያጠቃ ሰራዊቱን የላከውን ንጉሥ ይወክላል። መሰበር መሞት ወይም መሸነፍን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰራዊቱን ወደ አንተ የላከው ንጉሥ ሞቶአል›› ወይም፣ ‹‹አንተን ያጠቃ ሰራዊት ተሸንፎአል››

ከእባቡ ሥር እፉኝት ይወጣል... ዘሩም በራሪ እሳት ይሆናል
እነዚህ ሁሉ ሐረጐች የሚያመለክቱት የእባቡ ዘር ከራሱ ከእባቡ የባሰ ጐጂ መሆኑን ነው። የንጉሡ ወራሽ ከመጀመሪያው ንጉሥ የበለጠ ኀይለኛና ጨካኝ እንደሚሆን ያመለክታሉ።

እፉኝት
የአደገኛ እባብ ዐይነት

እሳታማ በራሪ እባብ
‹‹እሳታማ›› የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእባቡን መርዘኛነት ሲሆን፣ ‹‹በራሪ›› የሚለው ፈጣን እንቅስቃሴውን ሊያመለክት ይችላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ፈጣን መርዘኛ እባብ››

የድኻ በኩር
ይህ የሚያመለክተው በጣም ድኻ የሆኑ ሰዎችን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከድኻም ድኻ›› ወይም፣ ‹‹የሕዝቤ የባሰባቸው ድኾች››

ሥርህን በራብ እገድላለሁ፤ ትሩፍህንም እፈጃለሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ሥርህ›› የፍልስጥኤምን ሕዝብ ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሕዝብህን በራብ እገድላለሁ፤ ትሩፍህንም እጨርሳለሁ››

Isaiah 14:31

ዋይ በል፣ በር፣ ጩኽ፣ ከተማ
‹‹በር›› እና፣ ‹‹ከተማ›› በከተሞች በር የሚቀመጡ ሰዎችን ይወክላል። ‹‹በከተማው በሮች ያላችሁ ሰዎች ዋይ በሉ፤ በከተሞቹም ያላችሁ ጩኹ››

ትቀልጣላችሁ
መቅለጥ ከፍርሃት የተነሣ ደካማ መሆንን ነው የሚያመለክተው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከፍርሃት የተነሣ በጣም ትደክማላችሁ››

የጢስ ደመና ከሰሜን መጥቶብሃል
ይህ የሚያመለክተው ግዙፍ ሰራዊት ከሰሜን እየመጣ መሆኑን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከጢስ ደመና ጋር ከሰሜን ብዙ ሰራዊት መጥቶብሃል››

የጢስ ደመና
ይህም ማለት፣ 1) በደረቁ ዐፈር ላይ ሲጓዝ ሰራዊቱ የሚያስነሣውን የአቧራ ደመና ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የአቧራ ደመና›› ወይም 2) ሰራዊቱ ከሚያጠፋውና ከሚያቃጥለው ነገር የተነሣ ብዙ ጢስ ሊኖር ይችላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ብዙ ጢስ››

ከሰልፉ ተነጥሎ የሚቀር የለም
‹‹ከሰልፉ ከሌሎች ኃላ በዝግታ የሚራመድ አይኖርም››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለዚያ ሕዝብ መልእክተኞች ምን መልስ ይሰጣሉ?
ጸሐፊው ይህን ጥያቄ ያነሣው እስራኤላውያን ለመልእክተኞቹ እንዴት መናገር እንዳለባቸው የሚያቀርበውን መመሪያ ለማስተዋወቅ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለፍልስጥኤም መልእክተኞች እንዲህ በሏቸው››

ያህዌ ጽዮንን መሥርቶአታል
‹‹ያህዌ ጽዮንን ሠርቷል››

በእርሷ
‹‹በኢየሩሳሌም›› ወይም፣ ‹‹በዚያ››

ከሕዝቡ በጣም የተጐዱት
‹‹ከሕዝቡ በጣም የተጐዱ ሰዎች››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 15

1 ስለ ሞዓብ የተነገረ ሸክም፣ በእርግጥ፣ የሞዓብ ዔር በሌሊት ፈርሶ ጠፋ፤ ቂር የሚባልም የሞዓብ ምሽግ በሌሊት ፈርሶ ጠፋ። **2** ወደ ባይት ወደ ዲቦንም ወደ
ኮረብታ መስገጃዎችም ለልቅሶ ወጥተዋል፤ ሞዓብ በናባው በሜድባ ላይ ታለቅሳለች፤ ራሳቸው ሁሉ ተነጭቶአል፥ ጢማቸውም ሁሉ ተላጭቶአል። **3**
በየመንገዳቸውም በማቅ ታጥቀዋል፤ በየሰገነቶቻቸውና በየአደባባዮቻቸው እንባ እጅግ እያፈሰሱ ሁሉም አልቅሰዋል። **4** ሐሴቦንና ኤልያሊ ለእርዳታ ጮኹ፤
ድምፃቸው እስከ ያሀጽ ድረስ ይሰማል። ስለዚህ የሞዓብ ሰልፈኞች ጮኹ፤ ነፍስዋ በውስጥዋ ተንቀጠቀጠች። **5** ልቤ ስለ ሞዓብ ጮኸ፤ ከእርስዋም የሚሸሹ
ወደ ዞዓር ወደ ዔግላት ሺሊሺያ ኰበለሉ፤ በሉሒት ዓቀበት ላይ እያለቀሱ ይወጣሉ፣ በሖሮናይምም መንገድ የዋይታ ጩኸት ያነሣሉ። **6** የኔምሬም ውኆች
ይደርቃሉ፤ ሣሩም ደርቋል፣ ለጋውም ጠውልጓል፥ ልምላሜውም ሁሉ የለም። **7** ስለዚህ የሰበሰቡትን ሀብትና መዝገባቸውን ወደ አኻያ ዛፍ ወንዝ ማዶ
ይወስዱታል። **8** ጩኸት የሞዓብን ዳርቻ ሁሉ ዞረ፤ ልቅሶዋም ወደ ኤግላይምና ወደ ብኤርኢሊም ደረሰ። **9** የዲሞንም ውኃ ደም ተሞልታለች፤ በዲሞንም ላይ
ሥቃይን እጨምራለሁ፣ ከሞዓባውያንም በሚያመልጡ፣ ከምድርም በሚቀሩ ላይ አንበሳን አመጣለሁ።

Isaiah 15:1

አጠቃላይ መረጃ
ብዙውን ጊዜ ትንቢት ውስጥ ወደ ፊት የሚፈጸሙ ጉዳዮች አሁን ወይም ባለፈው ጊዜ እንደ ተፈጸሙ ተደርገው ይነገራሉ። ይህ አጽንዖት የሚሰጠው በእርግጥ የሚፈጸም መሆኑን ነው።

የንግር ቃል
‹‹ያህዌ እንዲህ ይላል›› ወይም፣ ‹‹ይህ የያህዌ መልእክት ነው››

ዔር... ቂር... ዲቦን... ናባው... ሜድባ
እነዚህ ሞዓብ ውስጥ የነበሩ ከተሞችና መንደሮች ናቸው።

የሞዓብ ዔር ፈራረሰች ተደመሰሰች
‹‹ፈራረሰች›› እና፣ ‹‹ተደመሰሰች›› የተሰኙት ቃሎች ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው፤ ከተማዋ ሙሉ በሙሉ እንደምትደመሰስ አጽንዖት ይሰጣሉ። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የጠላት ሰራዊት የሞዓብን ዔር ሙሉ በሙሉ ይደመስሳታል››

ሊያለቅስም ወደ ከፍታዎች ሄደ
እነዚህ ላይ፣ ‹‹ወደ ከፍታዎች›› ሲል ቤተ መቅደስ ወይም መሠዊያ የተሠራበት ኮረብታ ወይም ተራራ የመሳሰሉ ከፍታ ቦታዎችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለማልቀስ ኮረብታው ጫፍ ላይ ወዳለው ቤተ መቅደስ ሄደ››

ሞዓብ ስለ ናባው እና ስለ ሜድባ አለቀሰ
እነዚህ ቦታዎች እዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ናባው እና ሜድባ ከተማ ላይ ከደረሰው የተነሣ የሞዓብ ሕዝብ ያለቅሳል››

ራሳቸውን ሁሉ ተላጭተዋል፤ ጢማቸውን ሁሉ ተላጭተዋል
እንዲህ ያደረጉት በጣም ማዘናቸውን ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ራሳቸውንና ጢማቸውን ሁሉ ተላጭተው በጣም ያዝናሉ››

Isaiah 15:3

አጠቃላይ መረጃ
እዚህም ላይ ስለ ሞዓብ ሕዝብ የተነገረው ትንቢት ቀጥሏል። ወደ ፊት የሚሆኑ ነገሮችን እግዚአብሔር አሁን እንደ ተፈጸሙ አድርጐ ይናገራል። (ኢሳይያስ 15፥1-2 ይመ.)

ማቅ ይለብሳሉ
እንዲህ የሚያደርጉት በጣም ማዘናቸውን ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ማቅ ለብሰው ያለቅሳሉ››

ሐሴቦን... ኤልያሉ... ያሁድ
እነዚህ የከተሞችና የመንደሮች ስም ናቸው

ሐሴቦንና ኤልያሊ ይጣራሉ
የከተሞቹ ስሞች በውስጣቸው ያለውን ሕዝብ ይወክላሉ። ‹‹የሐሴቦንና የኤልያሊ ሕዝብ ይጣራሉ››

ይርዳሉ፤ ይንቀጠቀጣሉ
መንቀጥቀጥ የፍርሃት ምልክት ሲሆን፣ ፍርሃትን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከባድ ፍርሃት ይሞላባቸዋል›› ወይም፣ ‹‹በፍርሃት ይንቀጠቀጣሉ››

Isaiah 15:5

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ስለ ሞዓብ የተነገረው ትንቢት እየቀጠለ መሆኑን ያሳያል። ወደ ፊት የሚሆኑ ነገሮችን እግዚአብሔር አሁን እንደ ተደረጉ አድርጐ ይናገራል። (ኢሳይያስ 15፥1-2 ይመ.)

ልቤ ለሞዓብ ያለቅሳል
እዚህ ላይ፣ ‹‹ልብ›› የሚወክለው እግዚአብሔርን ሲሆን፣ ስሜቱን ያመለክታል። ልቡ ያለቀሰ ይመስል እግዚአብሔር የተሰማውን ታላቅ ሐዘን እየተናገረ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሞዓብ ላይ በሆነው እጅግ አዝኛለሁ››

ስደተኞቿም ሸሹ
‹‹ስደተኞቹ ከሞዓብ ሸሹ›› ስደተኛ ጠላት እንዳይዘው የሚሸሽ ሰው ነው።

ዞዓር... ዔግላት ሺሊሺያ... ሉሒት... ሖሮናይም... ኒምሪም
እነዚህ የከተሞችና የመንደሮች ስም ናቸው

ስለ ውድመታቸው
‹‹ውድመት›› የሚለውን ቃል፣ ‹‹መደምሰስ›› በሚለው ቃል ለመተካት ቃላቱን መለወጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከተማቸው ስለ ተደመሰሰች››

ያከማቹት
‹‹ማንኛውም ነገራቸው››

የዲሞን ወንዞች
ይህ የሚያመለክተው ደቡባዊ የሞዓብ ድንበር ላይ ያለውን ወንዝ ሊሆን ይችላል።

Isaiah 15:8

አጠቃላይ መረጃ
ስለ ሞዓብ ሕዝብ የተነገረው ትንቢት ቀጥሏል። ወደ ፊት የሚሆኑ ነገሮችን እግዚአብሔር አሁን እንደ ተነገሩ አድርጐ ይናገራል። (ኢሳይያስ 15፥1-2 ይመ.)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጩኸታቸው ወደ ሞዓብ ዳርቻ ወጣ
ሰዎቹ ሲጮኹ ሌሎች ያንን መስማታቸው የጩኸታቸው መውጣት እንደሆነ ተነግሮአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሞዓብ ምድር ያሉ ሰዎች ሁሉ ጮኹ››

ዋይታቸው እስከ ዔግሌምና ብኤር ኢላም
‹‹ወጣ›› ውስጠ ታዋቂ ነው። ሰዎች ዋይ ሲሉ ሌሎች ያንን መስማታቸው ዋይታቸው ወደ እነዚህ ሁለት ቦታዎች ወጣ ማለት እንደሆነ ተነግሮአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዋይታቸው እስከ ዔግላምና ብኤርኢላም ወጣ›› ወይም፣ ‹‹እስከ ዔግራምና ብኤርኤላም እንኳ ወጣ››

ዔግላም... ብኤርኤላም.. ዲሞን
እነዚህ የከተማና የመንደር ስሞች ናቸው። ዲሞን የሞዓብ አገር ዋና ከተማ ነበረች። አንዳንድ ቅጂዎች ከዲሞን ይልቅ፣ ‹‹ዶቦን›› ይላሉ።

በዲሞን ላይ ግን ከዚያ የበለጠ ነገር አደርጋለሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እኔ›› ያህዌን፣ ‹‹ዲሞን›› ደግሞ እዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ነው የሚያመለክተው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የዲሞን ሕዝብ ላይ የባሰ መከራ አመጣለሁ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 16

1 በምድርም ላይ ለሠለጠነው አለቃ የበግ ጠቦቶችን በምድረ በዳ ካለችው ከሴላ ወደ ጽዮን ሴት ልጅ ተራራ ስደዱ። **2** እንደሚበርር ወፍ፣ እንደ ተበተኑም ጫጩቶች፣ እንዲሁ የሞዓብ ሴቶች ልጆች በአርኖን መሻገሪያዎች ይሆናሉ። **3** "መመሪያን ስጪ፣ ፍርድን አድርጊ፣ በቀትር ጊዜ ጥላሽን እንደ ሌሊት አድርጊ፤ የተሰደዱትን ሸሽጊ፣ የሸሹትን አትግለጪ። **4** ከሞዓብ የተሰደዱት ከአንቺ ጋር ይኑሩ፤ ከሚያጠፋቸው ፊት መጋረጃ ሁኛቸው።" ጭቆናው ይቆማልና፣ ጥፋትም ይቆማልና፣ ይጨቍኑ የነበሩ ከምድር ይጠፋሉና። **5** ዙፋንም በኪዳን ታማኝነት ይመሠረታል፤ ከዳዊት ድንኳን የሆነው በታማኝነት በዚያ ይቀመጣል። ፍርድን የሚሻ ጽድቅንም የሚያደርግ እንደመሆኑ ይፈርዳል። **6** ስለ ሞዓብ ትዕቢት፣ ስለ እብሪተኝነቱ፣ ስለ ኩራቱና፣ ስለ ቁጣው ሰምተናል። ትምክህቱ ባዶ ቃላት ናቸው። **7** ስለዚህ ሞዓብ ስለ ሞዓብ ያለቅሳል፤ ሁሉም ያለቅሳል። ፈጽሞ ስለሚጠፋው ስለ ቂርሐራሴት የዘቢብ ጥፍጥፍ ታለቅሳላችሁ። **8** የሐሴቦን እርሻዎችና የሴባማ ወይን ግንዶች ደርቀዋል። የአሕዛብ አለቆች የሰባበሩአቸው ቅርንጫፎች እስከ ኢያዜር ደርሰው ወደ ምድረ በዳ ተበትነዋል። ቍጥቋጦቹም ተንሰራፍተው ወደ ባሕር ሄደው ነበር። **9** በእርግጥ በኢያዜር ልቅሶ ስለ ሴባማ ወይን ግንድ አለቅሳለሁ። ሐሴቦንና ኤልያሊ ሆይ፣ በእምባዬ አረሰርሳችኋለሁ። በበጋሽ ፍሬና በመከር ላይ የደስታን ጩኸት ትቻለሁና። **10** ደስታና ሐሤትም ከፍሬያማው የእርሻ ደን ተወስዶአል፤ በወይኑም ቦታዎች ዝማሬና የደስታ እልልታ የለም። በመጥመቂያም ወይን የሚረግጥ የለም፤ የረጋጮቹን እልልታ አጥፍቻለሁ። **11** ስለዚህ ልቤ ስለ ሞዓብ አንጀቴም ስለ ቂርሔሬስ እንደ መሰንቆ ትጮኻለች። **12** ሞዓብም መጥቶ በኮረብታ መስገጃ ላይ ራሱን በደከመና ለጸሎት ወደ መቅደሱ በገባ ጊዜ፣ ጸሎቱ ምንም ነገር አያሳካም። **13** እግዚአብሔር በሞዓብ ላይ አስቀድሞ የተናገረው ነገር ይህ ነው። **14** አሁን ግን እግዚአብሔር፣ "በሦስት ዓመት ውስጥ እንደ ምንደኛ ዓመት የሞዓብ ክብርና የሕዝቡ ሁሉ ብዛት ይዋረዳል፣ ቅሬታውም እጅግ ያነሰና የተጠቃ ይሆናል" ይላል።

Isaiah 16:1

አጠቃላይ መረጃ
ስለ ሞዓብ ሕዝብ የተነገረው ትንቢት እየቀጠለ ነው። ወደ ፊት የሚሆኑ ነገሮችን እግዚአብሔር አሁን እንደ ተደረጉ አድርጐ ይናገራል። ቁጥር አንድ የሞዓብ ገዦች እርስ በርስ የሚነጋገሩትን በተመለከተ እግዚአብሔር የተናገረው ሊሆን ይችላል። (ኢሳይያስ 15፥1-2 ይመ.)

ለምድሪቱ ገዥ የበግ ጠቦት ላኩ
ከጠላት ሰራዊት እንዲከላከልላቸው ሞዓባውያን ለይሁዳ ንጉሥ የበግ ጠቦት ይልካሉ።

ሴላ
ይህ የከተማ ስም ነው።

የጽዮን ሴት ልጅ
የከተማው፣ ‹‹ሴት ልጅ›› ማለት የከተማው ሕዝብ ማለት ነው። ኢሳይያስ 1፥8 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። ‹‹የጽዮን ሕዝብ›› ወይም፣ ‹‹በጽዮን የሚኖር ሕዝብ››

እንደ ተቅበዝባዥ ወፎች፣ እንደ ተበተኑ ጐጆዎች የሞዓብ ሴቶችም በአርኖን ወንዝ መሻገሪያ እንዲሁ ይሆናሉ
ሴቶቹን ጨምሮ የሞዓብ ሕዝብ ሁሉ ከቤታቸው ይሸሻሉ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የሞዓብ ሴቶች ጐጆ እንደሌላቸው በጐች ከአንዱ ወንዝ ወደ ሌላው ወንዝ ይቅበዘበዛሉ››

እንደ ተቅበዝባዥ ወፎች፣ እንደ ተበተኑ ጐጆዎች
እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ አንድ ነገር ማለት ናቸው።

Isaiah 16:3

አጠቃላይ መረጃ
ስለ ሞዓብ የተነገረው ትንቢት ቀጥሏል። ወደ ፊት የሚሆኑ ነገሮችን እግዚአብሔር አሁን እንደ ተደረጉ አድርጐ ይናገራል። ከቁጥር 3-4 ያለው የሞዓብ ገዦች ለይሁዳ ንጉሥ የላኩት መልእክት ሊሆን ይችላል። (ኢሳይያስ 15፥1-2 ይመ.)።

በቀትር ጥላችሁን እንደ ሌሊት አጥሉብን
እኩለ ቀን ላይ ያለው ሙቀት ሞዓባውያን በጠላቶቻቸው የሚደርስባቸውን መከራ ያመለክታል፤ ጥላ ከጠላቶቻቸው መከለያን ያመለክታል። ጥላውን ከሌሊት ጋር ማመሳሰሉ ጠንካራ መከለያ እንደሚያስፈልጋቸው ያመለክታል።

አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ታላቅ ጥላ ሕዝቡን ከፀሐይ ሙቀት እንደሚከላከል እናንተም ከጠላቶቻችን ከለሉን››

የሞዓብ ስደተኞች በመካከላችሁ ይኑሩ
‹‹የሞዓብ ስደተኞች ከእናንተ ጋር ይኑሩ›› እዚህ ላይ፣ ‹‹እናንተ›› የሚያመለክተው የይሁዳን ሕዝብ ነው።

ከአጥፊው መደበቂያ ቦታ ሁኑላቸው
መደበቂያ ቦታ ማዘጋጀት መደበቂያ ቦታ መሆን ተደርጐ ተነግሮአል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሊያጠፏቸው ከሚፈልጉ የሚደበቁበት ቦታ ስጧቸው›› ወይም፣ ‹‹ሊያጠፏቸው ከሚፈልጉ ደብቋቸው››

Isaiah 16:5

በኪዳን ታማኝነት ዙፋን ይመሠረታል
‹‹ዙፋን›› እንደ ንጉሥ የመግዛትን ሥልጣን ያመለክታል። ‹‹ታማኝነት›› የሚለውን ‹‹ታማኝ›› ማለት ይቻላል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ ለኪዳኑ ታማኝ ይሆናል፤ እርሱም ንጉሥ ይሾማል››

ከዳዊት ድንኳን የሆነውም በዚያ ላይ በታማኝነት ይቀመጣል
‹‹የዳዊት ድንኳን›› ዘሮቹን ጨምሮ የዳዊትን ቤተ ሰብ ይወክላል። ዙፋን ላይ መቀመጥ መግዛትን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የዳዊት ዘር በታማኝነት ይገዛል››

ፍትሕን ይፈልጋል
ፍትሕ መፈለግ ትክክል የሆነውን ማድረግን ያመለክታል።

Isaiah 16:6

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ስለ ሞዓብ የተነገረው ትንቢት ቀጣይ ነው። ወደ ፊት የሚደረጉ ነገሮችን እግዚአብሔር አሁን እንደ ተደረጉ ይናገራል። (ኢሳይያስ 15፥1-2 ይመ.)

የሞዓብን ትዕቢት፣ እብሪቱን፣ የእርሱን ፉከራና ቁጣውን ሰምተናል።
‹‹ሞዓብ›› እና፣ ‹‹የእርሱ›› የሚሉት ቃሎች፣ የሞዓብን ሕዝብ ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጕም፣ የሞዓብ ሕዝብ ትዕቢተኞች፣ እብሪተኞች፣ ፎካሪችና ቁጣዎች መሆናቸውን ሰምተናል››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሰምተናል
ይህም ማለት፣ 1) ኢሳይያስ እየተናገረ ነው፤ ‹‹እኛ›› እርሱንና የይሁዳን ሕዝብ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። ወይም፣ 2) እየተናገረ ያለው እግዚአብሔር ነው፤ ‹‹እኛ›› የሚለው እግዚአብሔርን ያመለክታል።

ትዕቢቶቹ ግን ከንቱ ቃላት ናቸው
‹‹አንዳች ነገርን አስመልክቶ የሚናገሩት ከንቱ ነው›› ወይም፣ ‹‹የሚታበዩበት ነገር እውነት አይደለም››

ስለዚህ ሞዓብ ለሞዓብ ዋይ ይላል - ሁሉም ዋይ ይላሉ
‹‹ሞዓብ›› የሚወክለው የሞዓብን ሕዝብ ነው። ‹‹የሞዓብ ሕዝብ ሁሉ ከተሞቻቸው ላይ ከሆነው የተነሣ ዋይ ይላሉ››

ስለ ቂርሐራሴት የዘቢብ ቂጣ
‹‹በቂርሐራሴት የዘቢብ ቂጣ ስለሌለ››

የዘቢብ ቂጣ
እዚህ ጥቅም ላይ የዋለው የዕብራይስጥ ቃል፣ ‹‹የዘቢብ ቂጣ›› ወይም፣ ‹‹ሰዎች›› ማለት ሊሆን ይችላል።

ቂርሐራሴት
ቂርሐራሴት የከተማ ስም ነው።

Isaiah 16:8

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ስለ ሞዓብ ሕዝብ የተነገረው ትንቢት ቀጣይ ነው። ወደ ፊት የሚሆኑ ነገሮችን እግዚአብሔር አሁን እንደ ተደረጉ አድርጐ ይናገራል። (ኢሳይያስ 15፥1-2 ይመ.)

ሐሴቦን
የዚህን ከተማ ስም ኢሳይያስ 15፥4 ላይ እንደ ተረጐምህ ተርጉመው

ሴላማ... ኢያዜር
እነዚህ የከተሞች ስም ናቸው

የአሕዛብ ገዦች የተመረጡ የወይን ተክሎችን ረግጠዋል
የሞዓብ ምድር በወይን ዕርሻው የታወቀ ነበር። እዚህ ላይ እግዚአብሔር ስለ ሞዓብ እንደ አንድ ትልቅ የወይን እርሻ ይናገራል። ይህም ሰራዊትን የሚያመለክቱት ገዦች በሞዓብ ያለውን ማንኛውንም ነገር እንደሚያወድሙ አጽንዖት ይሰጣል

Isaiah 16:9

አጠቃላይ መረጃ
ይህ የሞዓብ ምድር እንደ አንድ ትልቅ የወይን እርሻ እንደሆነ የተነገረው ቀጣይ ነው። (ኢሳይያስ 16፥8 ይመ.)። ወደ ፊት የሚሆኑ ነገሮችን እግዚአብሔር አሁን እንደ ተፈጸሙ አድርጐ ይናገራል።

በእርግጥ አለቅሳለሁ
16፥9-10 ላይ፣ ‹‹እኔ›› የሚለው ያህዌን ያመለክታል።

እንባዬን አጠጣሃለሁ
ብዙ እንደሚያለቅስና የሰራዊቱም እንባ እነርሱ ላይ እንደሚወርድ ያህል እግዚአብሔር ለእነዚህ ቦታዎች ያለውን ጥልቅ ሐዘን ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለአንተ ብዙ አለቅሳለሁ››

ኢያዜር... ሴባማ
የእነዚህን ከተሞች ስም ኢሳይያስ 16፥8 ላይ እንደ ተረጐምህ ተርጉመው።

ሐሴቦን... አልያሊ
የእነዚህን ከተሞች ስም ኢሳይያስ 15፥4 ላይ እንደ ተረጐምህ ተርጉመው።

ፍሬ ባፈራሽበት ወቅት የነበረው ሆታ፣ መከርሽም ሲደርስ የነበረውን የደስታ ጩኸት አስወግጃለሁ
‹‹የደስታ ጩኸት›› በፍሬ ዛፎቻቸው መከር ደስ የተሰኙ ሰዎችን ደስታ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ ከማደርገው የተነሣ ፍሬ ባፈራሽበት ወቅት የሚኖረው ደስታ አይኖርሽም››

የረጋጮችን ሆታ አጥፍቻለሁና
እዚህ ላይ ‹‹ሆታ›› ወይን ጠጅ እንዲገኝ የወይን ፍሬዎችን የሚረግጡ ሰዎችን ደስታ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለዚህ የወይን ፍሬ የሚረግጡ ሰዎች የደስታ ሆታ አይኖርም››

Isaiah 16:11

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ስለ ሞዓብ ሕዝብ የተነገረው ትንቢት ቀጣይ ነው። ወደ ፊት የሚሆን ነገሮችን እግዚአብሔር አሁን እንደ ተፈጸሙ አድርጐ ይናገራል። (ኢሳይያስ 15፥1-2 ይመ.)።

ስለዚህ ልቤ ለሞዓብ እንደ በገና የሐዘን እንጉርጉሮ ታሰማለች
‹‹ልቤ›› የሚለው ያህዌንና ያዘነ ስሜቱን ይወክላል። የእርሱን እንጉርጉሮ ከአሳዛኝ የበገና ዜማ ጋር ያመሳስለዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለዚህ በበገና እንደሚሰማው የሐዘን ዜማ አንጐራጉራለሁ››

ሞዓብ... እርሱ ራሱ... የእርሱ
እነዚህ ቃላት ሁሉ የሞዓብን ሕዝብ ያመለክታሉ።

ውስጤ ስለ ቂርሐራሴት
‹‹ውስጤ›› የሚለው ቃል ያህዌን ያመለክታል። ‹‹እንጉርጉሮ›› የሚለው ካለፈው ሐረግ ውስጠ ታዋቂ ነው። ኢሳይያስ 16፥7 ላይ ቂርሐራሴትን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ውስጤ ስለ ቂርሐራሴት ታንጐራጉራለች›› ወይም፣ ‹‹ለቂርሐራሴት ሰዎች በጣም አዝኛለሁ››

ጸሎቱ ምንም አያደርግም
‹‹ጸሎቱ መልስ አያገኝም››

Isaiah 16:13

ቃሉ ይኸው ነው
‹‹መልእክቱ ይኸው ነው›› ይህ የሚያመለክተው 15፥1-16፥12 ላይ የተናነገረውን ሁሉ ነው።

ስለ ሞዓብ
‹‹ሞዓብ›› የሚያመለክተው የሞዓብን ሕዝብ ነው።

የሞዓብ ክብር ይጠፋል
‹‹የሞዓብ ምድር ከእንግዲህ የተከበረች አትሆንም››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 17

1 ስለ ደማስቆ የተነገረ ሸክም። እነሆ፣ ደማስቆ ከእንግዲህ ከተማ አትሆንም፤ የፍርስራሽ ክምር ትሆናለች። **2** የአሮኤር ከተሞች ይጣላሉ። ለመንጋ ማሰማሪያ ሆናሉ፣ የሚያስፈራቸውም የለም። **3** የተመሸጉ ከተሞች ከኤፍሬም ይጠፋሉ፣ መንግሥትም ከደማስቆ፤ የሶርያም ቅሬታ እንደ እስራኤል ልጆች ክብር ይሆናል ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር። **4** በዚያም ቀን የያዕቆብ ክብር ይከሳል፣ የሥጋውም ውፍረት ይሸበሸባል። **5** አጫጅ የቆመውን እህል በእጁ ሰብስቦ ዛላውን እንደሚያጭድ ይሆናል። በራፋይም ሸለቆ ቃርሚያ እንደሚለቅም እንዲሁ ይሆናል። **6** ወይራ በተመታ ጊዜ ሁለት ወይም ሦስት ፍሬ በራሱ ላይ እንደሚቀር፥ አራት ወይም አምስት በዛፊቱ ጫፍ እንደሚገኝ፣ በእርሱ ዘንድ ቃርሚያ ይቀራል ይላል የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር። **7** በዚያ ቀን ሰው ወደ ፈጣሪው ይመለከታል፣ ዐይኖቹም ወደ እስራኤል ቅዱስ ያያሉ። **8** እጆም የሠራችውን መሠዊያ አይመለከትም፣ ጣቶቹም ወደ አበጁአቸው፣ ወደ አሼራ ዐምዶች ወይም ወደ ፀሐይ ምስሎች አያይም። **9** በዚያም ቀን በእስራኤል ልጆች ፊት የአሞራውያንና የኤውያውያን ከተሞች እንደ ተፈቱ እንዲሁ ከተሞችህ ይፈታሉ ባድማም ይሆናሉ። **10** የደኅንነትህን አምላክ ረስተሃልና፣ የብርቱነትህንም ዐለት አላሰብክምና። ስለዚህ ያማረውን ተክል ተክለሃል፣ እንግዳንም ዘር ዘርተሃል **11** በዚያ ቀን ተክለህ ታጥርለትና ታበቅለዋለህ። ብዙም ሳይቆይ ዘርህ ያብባል፣ ነገር ግን መከሩ የሚሆነው በኀዘንና በጥልቅ ኃዘን ነው። **12** ወዮላችሁ! እንደ ባሕር ሞገድ ድምፅ ለሚጮኹ፣ እንደ ኃይለኛም ውኃ ጩኸት ለሚጮኹ አሕዛብ! **13** አሕዛብ እንደ ብዙ ውኃ ጩኸት ይጮኻሉ፣ እግዚአብሔር ግን ይገሥጻቸዋል። እነርሱም ወደ ሩቅ ይሸሻሉ፣ በተራራም ላይ እንዳለ እብቅ፣ በነፋስ ፊት ዐውሎ ነፋስ እንደሚያዘረው ትቢያ ይበተናሉ። **14** በመሸ ጊዜ፣ ተመልከቱ፣ ድንጋጤ አለ፤ ከማለዳም በፊት አይገኙም። የዘረፉን ሰዎች እድል ፈንታ፣ የበዘበዙን ዕጣ ይህ ነው።

Isaiah 17:1

ስለ ደማስቆ
ደማስቆ የከተማ ስም ነው። ኢሳይያስ 7፥8 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

የአሮኤር ከተሞች ባድማ ይሆናሉ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። ‹‹ሰዎች ሁሉ የአሮኤርን ከተማ ትተው ይሄዳሉ››

ማንም አያስፈራቸውም
‹‹እነርሱ›› የሚለው የሚያመለክተው በጐቹን ነው።

የተመሸጉ ከተሞች ከኤፍሬም ይጠፋሉ
ኤፍሬም በእስራኤል ትልቁ ነገድ ነበር። እዚህ ላይ መላው የእስራኤልን ሰሜናዊ መንግሥት ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከእስራኤል ጠንካራ ከተሞች ይጠፋሉ››

ይጠፋሉ
ይህ ማለት ብን ብለው ይጠፋሉ ሳይሆን፣ ይደመሰሳሉ ማለት ነው።

ከደማስቆ መንግሥት
‹‹ይጠፋሉ›› ቀደም ሲል ከነበረው ቁጥር ውስጠ ታዋቂ ነው። ደማስቆ የሶርያ ንጉሥ የሚገዛበት ቦታ ነበረች። መንግሥቱ መጥፋቱ ከእንግዲህ እንደ ንጉሥ የመግዛት ሥልጣን እንደማይኖረው ነው የሚያመለክተው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከደማስቆ መንግሥት ይጠፋል›› ወይም፣ ‹‹በደማስቆ የንጉሥ ሥልጣን አይኖርም››

ሶርያ
ሶርያ የአገር ስም ነው። ኢሳይያስ 7፥1 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

እንደ እስራኤል ሕዝብ ክብር ይሆናሉ
የእስራኤል ሕዝብ ምንም ክብር እንዳልነበራቸው ሁሉ፣ ከሶርያ የተረፉትም ምንም ክብር አይኖራቸውም ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከእንግዲህ እንደ እስራኤል ሕዝብ እነርሱም ምንም ክብር አይኖራቸውም›› ወይም፣ ‹‹በእስራኤል ሕዝብ እንዳደረግሁ እነርሱም ላይ እፍረት አመጣለሁ››

የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
የሚናገረውን ነገር እርግጠኝነት ለማመልከት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። ኢሳይያስ 14፥22 ላይ እንደ ተረጐምህ ተርጕመው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የሰራዊት ጌታ ያህዌ የሚለው ይህን ነው›› ወይም፣ ‹‹እኔ የሰራዊት ጌታ ያህዌ ይህን ብያለሁ››

Isaiah 17:4

እንዲህም ይሆናል
ይህ ሐረግ እዚህ ጥቅም ላይ የዋለው አንድ በጣም አስፈላጊ ነገር እንደሚሆን ለማመልከት ነው። ቋንቋህ ይህን የምታደርግበት መንገድ ካለው፣ እዚህ ላይ ልትጠቀምበት ትችላለህ።

የያዕቆብ ክብር ይከሳል፤ የሥጋውም ውፍረት ይመነምናል
‹‹ያዕቆብ›› የሚያመለክተው የእስራኤልን መንግሥት ነው። ከእንግዲህ እስራኤል ክብር ያላት አትሆንም። ይልቁን ደካማና ድኻ ትሆናለች።

ገበሬ ሰብሉን ከሰበሰበ በኃላ እንዳለው ይሆናል፤ ...በራፋይም ሸለቆ
እግዚአብሔር የእስራኤል ሕዝብ ከቀጣ በኃላ፣ በምድሩ ምንም የሚቀር ነገር አይኖርም።

በራፋይም ሸለቆ
ይህ ሰዎች ብዙ እህል የሚያመርቱበትና የሚሰበስቡበት ሸለቆ ነው።

Isaiah 17:6

አጠቃላይ መረጃ
የእስራኤልን ሕዝብ መከር ከታጨደ በኃላ ካለው እርሻ ጋር ማመሳሰሉን ቀጥሏል። (ኢሳይያስ 17፥4-5 ይመ.)

ቃርሚያ ይተርፋል
እዚያ ላይ፣ ‹‹ቃርሚያ›› በእስራኤል የቀረውን ሕዝብ ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በእስራኤል ጥቂት ሰዎች ይቀራሉ››

የወይራ ዛፍ በተናወጠ ጊዜ
ሰዎች የወይራ ፍሬ የሚሰበሰቡት ፍሬው እንዲረግፍ ዛፉን በመነቅነቅ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሰዎች ከሰበሰቡ በኃላ ዛፉ ላይ እንደሚቀር ጥቂት የወይራ ፍሬ››

አራት ወይም አምስት
ከዚህ በፊት ከነበረው ቁጥር ‹‹የወይራ ፍሬ›› የሚለው ቃል ውስጠ ታዋቂ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አራት ወይም አምስት ፍሬ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይላል የእስራኤል አምላክ ያህዌ
እየተናገረ ያለውን እርግጠኝነት ለማመልከት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህ የእስራኤል አምላክ ያህዌ የተናገረው ነው›› ወይም፣ ‹‹ይህ እኔ የእስራኤል አምላክ ያህዌ የተናገርሁት ነው››

ሰዎች ወደ ፈጣሪያቸው ይመለከታሉ... ወደ እስራኤል ቅዱስ ያያሉ
እዚህ ላይ ወደ እግዚአብሔር መመልከት እንደሚረዳቸው በእርሱ ተስፋ ማድረግን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች የፈጠራቸው የእስራኤል ቅዱስ እንደሚረዳቸው ተስፋ ያደርጋሉ››

ሰዎች ይመለከታሉ
‹‹ሰዎች›› በጠቅላላው የእስራኤል ሕዝብ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ያያሉ››

ዐይኖቻቸው ያያሉ
‹‹ዐይኖች›› የሚመለከቱ ሰዎችን ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያያሉ›› ወይም፣ ‹‹ሕዝቡ ያያሉ››

የእስራኤል ቅዱስ
ኢሳይያስ 1፥4 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

Isaiah 17:8

ወደ መሠዊያቸው አይመለከቱም
ወደ መሠዊያ መመልከት ጣዖቶቹ ይረዱናል በሚል ተስፋ ጣዖቶችን ማምለክን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መሠዊያቸው ላይ ጣዖቶችን አያመልኩም›› ወይም፣ ‹‹የእስራኤል ሕዝብ ወደ መሠዊያቸው ሄደው እንዲረዷቸው አማልክቶቻችውን አይለምኑም››

በእጆቻው ወደ ሠሯቸው
መሠዊያዎቹን ወይም ጣዖቶቹን የሠሯቸው እነርሱ መሆናቸውን አጽንዖት ለመስጠት እዚህ ላይ ሰዎች ‹‹በእጆቻው›› ተወክለዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በእጆቻቸው የሠሯቸው›› ወይም፣ ‹‹ራሳቸው የሠሩትን››

በጣቶቻቸው ላበጇቸው... የአሼራ ዐምዶች ወይም የፀሐይ ምስሎች
ሁለተኛው ሐረግ ሰዎቹ የሠሩትን ያመለክታል። ስለ ጣቶች የተነገረው ሰዎች እንዳበጇቸውና ስለዚህ እነዚህ እውነተኛ አማልክት አለመሆናቸውን አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነርሱ ራሳቸው ላበጇቸው የአሼራ ዐምዶች ወይም የፀሐይ ምስሎች››

በእስራኤል ልጆች ምክንያት የተተውት
እነዚህን ምድሮች የተውት እነማን እንደ ነበሩ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤል ሕዝብ ከመጡ በኃላ ኬጢያውያንና አሞራውያን ትተው ሄዱ››

Isaiah 17:10

አንተ ረስተሃልና
‹‹አንተ›› የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። ‹‹ረስተሃል›› የሚለው ቃል እግዚአብሔርን አያስታውሱም ማለት አይደለም። እየታዘዙለት አይደለም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አልታዘዝህምና››

አዳኝ አምላክህን
‹‹የሚያድንህን አምላክ››

የብርታትህን ዐለት ችላ ብለሃል
እዚህ ላይ እግዚአብሔርን ከጠላቶቻቸው ለማምለጥ ወይም ከጀርባው ለመደበቅ ሰዎች ከሚወጡበት ትልቅ ዐለት ጋር አመሳስሎታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ መከታ ዐለት የሆነልህን ችላ ብለሃል›› ወይም፣ ‹‹የከለለህን ችላ ብለሃል።

መከር ይበላሻል
‹‹የምትሰበሰቡት ብዙ ፍሬ አይኖራችሁም››

Isaiah 17:12

የብዙ ሕዝብ ጩኸት፤ እንደ ባሕር ሞገድ ያለ ጩኸት
ጩኸት በጣም ከፍ ያለ ድምፅ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ባሕር ሞገድ በጣም ከፍ ያለ የብዙ ሰዎች ድምፅ››

እንደ ውሃ ሙላት የተጣደፈ የሕዝቦች ሩጫ
የጠላት ሰራዊት ማንም የማያስቆመው ታላቅ ኀይል ይመስላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕዝቡ እንደ ውሃ ሙላት እየተጣደፉ ይመጣሉ››

የሕዝቦች ጥድፊያ
‹‹ሕዝቦች›› የሚለው ቃል የእነዚህ አገሮችን ሰራዊት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የጠላት ሰራዊት ጥድፊያ››

በዐውሎ ነፋስ ፊት ተራራ ላይ እንዳለ ገለባ... በማዕበል ፊት እንደሚበተን አረም
እነዚህ ሁለት ሐረጐች ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። የጠላት ሰራዊት በጣም ኀይለኛ ይመስላል፤ እግዚአብሔር ግን በቀላሉ ያስቆማቸዋል ያባርራቸዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ነፋስ እንደሚያበንነው ተራራ ላይ እንዳለ ገለባ... ማዕበል ሲመጣ በንኖ እንደሚጠፋ አረም››

የ... ዕድል ፈንታ
እነርሱ ላይ የደረሰው በውርስ እንዳገኙት ዕድል ፈንታ ተመስሎአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በ... የሚደርሰው ይኸው ነው››

የዘረፉን... የበዘበዙን
‹‹እኛን›› የሚለው ኢሳይያስንና የይሁዳን ሕዝብ ያመለክታል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 18

1 ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ የክንፎች ድምፅ ለሚሰማባት አገር ወዮላት፤ 2 መልእክተኞችን ከደንገል በተሠራ ጀልባ በአባይ ወንዝ ላይ ለምትልከው አገር፤
ሕዝብዋ ረጃጅሞችና ቆዳቸው ለስላሳ፣ አገራቸው በወንዞች የተከፋፈለች፣ ጠንካሮችና ኃያላን በመሆናቸው በዓለም ሁሉ ወደሚፈሩት ሕዝቦች እናንት ፈጣን
መልእክተኞች ሂዱ! 3 በዓለም የምትኖሩ ሁሉ እና በምድር የምትኖሩ፣ በተራሮች ጫፍ ላይ የተተከለ የሰንደቅ ዓላማ ምልክት ሲውለበለብ አስተውሉ፤ መለከት
ሲነፋ ስሙ። 4 እግዚአብሔር ያለኝ ነገር እንዲህ ነው፣ "በቀትር ጊዜ በጸጥታ እንደምታበራ ፀሐይ፣ በመከርም ወራት በሞቃት ሌሊት እንደሚታይ ጤዛ ከሰማያዊ
መኖሪያዬ ጸጥ ባለ መንፈስ ቊሌቊል እመለከታለሁ።" 5 የወይን መከር ከመሰብሰቡ በፊት አበቦች ረግፈው የወይን ፍሬ በሚበስልበት ጊዜ የወይን ሐረግ
ቅርንጫፎች በስለት ተቈርጠው እንደሚጣሉ እርሱ የዚያችን አገር ሕዝብ ያጠፋል። 6 በአንድነት ለተራራ ወፎችና ለምድረ በዳ አራዊት ይተዋሉ። በበጋ ወፎች፣
በክረምትም አራዊት ይቀራመቷቸዋል። 7 የሠራዊት አምላክ በዓለም ሁሉ የመፈራት ግርማ ካላቸው፣ ቆዳቸው ለስላሳ፣ ቁመታቸው ረጅም ኀያላንና ብርቱዎች
ከሆኑት፣ በወንዞች የተከፋፈለች ምድር ካላቸው ከእነዚያ ሕዝብ መባ የሚቀበልበት ጊዜ ይመጣል፤ እነርሱም የሠራዊት አምላክ ወደሚመለክባት ወደ ጽዮን
ኰረብታ ይመጣሉ።

Isaiah 18:1

በኩሽ ወንዞች ማዶ ለምትገኝ ፉር ፉር የሚሉ ክንፎች ላሉበት ምድር ወዮላት
‹‹ፉር ፉር የሚሉ ክንፎች›› ማለት ሊሆን የሚችለው፣ 1) መቅዘፊያዎች ያሉባቸው ጀልባዎች ክንፎች እንዳሏቸው መነገሩ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ውሃ ላይ እንዳሉ ክንፉም ብዙ ጀልባዎች ላሏት ከኩሽ ወንዞች ማዶ ላለች ምድር ወዮላት›› ወይም 2) ፉር ፉር የሚሉ ክንፎች የሚለው የክንፋም ፍጥረቶችን ምናልባትም የአንበጣዎችን ድምፅ ሊሆን ይችላል።

ባሕሩ ላይ
የዐባይ ወንዝ በጣም ሰፊ በመሆኑ በግብፅና በኩሽ ያሉ ሕዝብ፣ ‹‹ባሕሩ›› በማለት ይጠሩት ነበር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በታላቁ ባሕር›› ወይም፣ ‹‹በዐባይ ወንዝ ዳር››

የደንገል ዕቃ
ደንገል ዐባይ ወንዝ ዳር የሚበቅል ረጅም ተክል ነው። የደንገል ክምሮችን በአንድነት በማያያዝ ሰዎች ጀልባዎች ይሠሩ ነበር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የደንገል ጀልባ›› ወይም፣ ‹‹ከቀጤማ የተሠሩ ጀልባዎች››

ረጅምና ለሰላሳ ቆዳ... ከቅርቡም ከሩቅም ወደሚፈራ ሕዝብ... ኀያልና ረጋጭ ወንዝ በሚከፍለው ምድር የሚኖር ሕዝብ
እነዚህ ሐረጎች ሁሉ የአንድ አገር ሕዝብን ነው የሚገልጹት።

ረጅምና ቆዳው የለሰለሰ ሕዝብ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ሕዝብ›› የዚያን አገር ሕዝብ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ረጅምና ቆዳው የለሰለሰ ሕዝብ ያሉት አገር››

በቅርብም በሩቅም ወደሚፈራ
‹‹ቅርብ›› እና፣ ‹‹ሩቅ›› የተሰኙት ቃሎች በአንድነት የቀረቡት፣ ‹‹የትም አገር›› ለማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የትም አገር የሚፈራ ሕዝብ›› ወይም፣ ‹‹በየትኛውም ምድር ያሉ የሚፈሩት ሕዝብ››

ኀያልና ረጋጭ ሕዝብ
መርገጥ መንግሥታትን ድል ማድረግን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኀያልና ሌሎች መንግሥታን ድል የሚያደርግ ሕዝብ››

ወንዝ የሚከፍለው ምድር
የተለያዩ ክፍሎች ያሉት ምድር እንዲሆን ምናልባት ይህ በዚያ አገር የሚያልፉ ብዙ ወንዞችን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።

Isaiah 18:3

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ቁጥር 3 ኢሳይያስ 18፥2 ላይ የተጠቀሱት መልእክተኞች ለዓለም ሕዝብ መንገር ያለባቸውን ያመለክታል።

እናንት የዓለም ሕዝቦች... በምድርም የምትኖሩ ሁሉ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በምድር ያላችሁ ሕዝቦች ሁሉ››

ተራሮች ላይ ምልክት ሲሰቀል ተመልከቱ፤ መለከት ሲነፋም አድምጡ
ምልክትና የመለከት ድምፅ ሰዎችን ወደ ጦርነት ለመጥራት ያገለግላሉ። እንዲመለከቱና እንዲያደምጡ የተሰጠውን ትእዛዝ ልብ እንዲሉና ለጦርነት እንዲዘጋጁ የሚያሳስብ ትእዛዝ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምልክት ተራሮች ላይ ሲሰቀልና መለከት ሲነፋ ልብ በሉ››

ምልክት ተራሮች ላይ ሲሰቀል ተመልከቱ
ምልክት ሰዎችን ለጦርነት ለመጥራት የሚያገለግል ባንዲራ ነበር። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የጦርነቱን ባንዲራ ተራሮች ላይ ስትመለከቱ ልብ በሉ››

መለከት ሲነፋ አድምጡ
መለከት ሰዎችን ለጦርነት ለመጥራት ጥቅም ላይ ይውላል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የጦርነቱን መለከት ድምፅ ስትሰሙ ልብ በሉ››

Isaiah 18:4

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ስለ ወይን እርሻ ገበሬ በተነገረ ምሳሌ የተጠቀመው አንድን ሕዝብ እንደሚቀጣ ለማመልከት ነው። ያ ሕዝብ ኢትዮጵያ ወይም የኢትዮጵያ ጠላት ሊሆን ይችላል።

ያህዌ ያለኝ ይህን ነው
‹‹ያህዌ እንዲህ አለኝ›› እዚህ ላይ፣ ‹‹እኔ›› ኢሳይያስን ይመለከታል።

እቤቴ ሆኜ በእርጋታ እመለከታለሁ
እግዚአብሔር የሚመለከተው ምን እንደሆነ በግልጽ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እቤቴ ሆኜ ያንን ሕዝብ በእርጋታ እመለከታለሁ›› ወይም፣ ‹‹እቤቴ ሆኜ የዚያ አገር ሕዝብ የሚያደርገውን በእርጋታ እመለከታለሁ››

በፀሐይ ሐሩር እንደሚያብረቀርቅ ትኩሳት፣ በመከርም ሙቀት እንደ ደመና ጠል
እነዚህ ሐረጎች እግዚአብሔር ሕዝቡን በእርጋታ እንደሚመለከት ያሳያሉ።

ከመከር በፊት
ይህ የወይን ፍሬ መከር ነው። ይህን ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የወይን ፍሬ ከመሰብሰቡ በፊት››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የአበባው ወቅት ሲያልፍ
ይህ የሚያመለክተው የወይን ፍሬ ሲጐመራ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የወይን ዛፉ ላይ አበቦች ታይተው ሲያበቁ››

የወይን ሐረጉን ተቀጥላ በመግረዝ ይቆርጠዋል
የወይኑ ፍሬ ከመብሰሉ በፊት ያህዌ ቅርንጫፎቹን ይቆርጣል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ፍሬ ከማፍራቱ በፊት ያህዌ በመቁረጫ ቅርንጫፎቹን ይቆርጣል››

መግረዝ መንጠቆ
መግረዝ መንጠቆ ሰዎች ከወይን ዛፍና ከሌሎች ተክሎች ቅርንጫፎችን ለመቁረጥ የሚጠቀሙበት ነው።

የተንሰራፋውንም ቅርንጫፍ ቆራርጦ ያስወግደዋል
ያህዌ ቅርንጫፎቹን ለፍርድ ይጥላል

Isaiah 18:6

በአንድነት ይተዋሉ
እግዚአብሔር ምሳሌውን መናገሩን ትቶ በቀጥታ ስለ ሕዝቡ ወደ መናገር የሄደ ይመስላል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የተገደሉት ሁሉ በአንድነት ይተዋሉ›› ወይም፣ ‹‹ተቆርጠው እንደ ተጣሉ ቅርንጫፎች የተገደሉት ሰዎችም ሬሳዎች መሬት ላይ በአንድነት ይተዋሉ››

ወፎች በበጋ ወቅት ይበሉታል
‹‹በጋ በሚሆንበት ጊዜ ወፎች ይበሉታል›› እዚህ ላይ፣ ‹‹ወፎች›› የሚለው በድን የሚበሉ ወፎችን ነው።

የምድር አራዊት ሁሉ
‹‹ማንኛውም ዐይነት የዱር አውሬ››

ክረምቱን ሁሉ ይበሉታል
‹‹ክረምት በሚሆንበት ጊዜ ይበሉታል››

ረጅምና ቆዳው የለሰለሰ ሕዝብ... ከቅርብም ከሩቅም የሚፈራ ሕዝበ... ጎያልና ረጋጭ ምድሩን ወንዞች የሚከፍሉት ሕዝብ
እነዚህ ሐረጐች የሚናገሩት ስለ አንድ አገር ሕዝብ ነው። ኢሳይያስ 18፥2 ላይ ይህን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

ረጅምና ቆዳው የለሰለሰ ሕዝብ
‹‹ረጅም የሆነና ለስላሳ ቆዳ ያለው ሕዝብ››

ከሩቅም ከቅርቡም የሚፈራ ሕዝብ
‹‹ሩቅ›› እና፣ ‹‹ቅርብ›› የተሰኙት ቃሎች በአንድነት ጥቅም ላይ የዋሉት፣ ‹‹የትም ቦታ›› ለማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በየትም ቦታ የሚፈራ ሕዝብ›› ወይም ‹‹በምድር ያለ ሁሉ የሚፈራው ሕዝብ››

ጎይልና ረጋጭ ሕዝብ
መርገጥ ሌሎች መንግሥታትን ድል ማድረግን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ብርቱ የሆነና ሌሎች መንግሥታትን ድል የሚያደርግ ሕዝብ››

የሰራዊት ጌታ ያህዌ ስም የሚጠራበት ቦታ የጽዮን ተራራ
‹‹ስም›› የሚለው የሚያመለክተው ያህዌን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሰራዊት ጌታ ያህዌ የሚኖርበት የጽዮን ተራራ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 19

1 ስለ ግብጽ የተነገረ የእግዚአብሔር ቃል የሚከተለው ነው። ተመልከቱ፣ እግዚአብሔር በፈጣን ደመና ሆኖ ወደ ግብጽ ይመጣል፤ የግብጻውያን ጣዖቶች
በእርሱ ፊት ይናወጣሉ፤ የግብጽ ሕዝብም በፍርሃት ይቀልጣሉ። 2 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ "ግብጻዊያንን በግብጻዊያን ላይ አስነሣለሁ፤ ወንድም
በወንድሙ ላይ፣ ጐረቤትም በጐረቤቱ ላይ በጠላትነት እንዲነሣ አደርጋለሁ፤ ከተሞች በከተሞች ላይ፣ ነገሥታት በነገሥታት ላይ በጠላትነት ተነሥተው
ይዋጋሉ። 3 የግብጻውያን መንፈስ በውስጡ ይዳከማል። የጣዖቶቻቸውን የጠንቋዮቻቸውን የሙታን መናፍስት ጠሪዎችን ምክር ቢፈልጉም ምክሩን
እደመስሳለሁ። 4 እነርሱን በጭካኔ ለሚገዛቸው ጌታ አሳልፌ እሰጣቸዋለሁ፤ እኔ ጌታ የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር ይህን ተናግሬአለሁ።" 5 በዓባይ ውስጥ
ያለው ውሃ ይደርቃል፣ ወንዙም እየደረቀ ሄዶ ባዶ ይሆናል 6 ወንዞቹ ይገማሉ፤ የግብጽ ምንጭ እየጐደለ ይደርቃል፤ ደንገሎቹና ቄጤማዎቹ ይጠወልጋሉ። 7
በዓባይ ወንዝ ዳርቻ ያለው ቄጤማ ሁሉ ይደርቃል፤ በወንዙ አጠገብ የተዘራውም ሰብል ሁሉ ደርቆ ወደ አፈርነት በመለወጥ ነፋስ ይወስደዋል። 8 ዓሣ
አጥማጆችና መንጠቆአቸውን ወደ አባይ ወንዝ የሚጥሉ ሁሉ ያዝናሉ፤ ያለቅሳሉም፤ መረቦቻቸውንም በውሃ ላይ የሚዘረጉ ተስፋ ይቈርጣሉ፤ 9 የተበጠረውን
የተልባ እግር የሚሠሩ እና ቀጭን ሐር የሚሠሩ ያፍራሉ። 10 የግብጽ ሸማኔዎች ግራ ይጋባሉ፤ ደመወዝተኞችም በውስጣቸው ያዝናሉ። 11 በጾዓን ያሉ ልዑላን
ፍጹም ሞኞች ናቸው። ጠቢባን የሆኑት የፈርዖን አማካሪዎች ምክር ትርጉም የለሽ ይሆናል። ለፈርዖን "እኔ የብልኅ ሰው ልጅ ነኝ የጥንት ነገሥታት ልጅ ነኝ እንዴት
ይላሉ?" 12 እንግዲያው እነዚያ ጠቢባን ወዴት ናቸው? የሠራዊት አምላክ በግብጽ ላይ ያቀደውን ይንገሩህ፣ ደግሞም ያሳውቁህ። 13 የጾዓን ልዑላን ሞኞች
ሆኑ፤ የሜምፊስ ልዑሎችም ተታለሉ፤ የነገዶችዋ ማእዘናት የሆኑት ግብጽን አሳትዋት። 14 የተቀያየጠ ምክር እንዲሰጡ ያደረጋቸውም እግዚአብሔር ነው፤
በመጨረሻም ግብጽ በሁሉ ነገር በመሳሳት የገዛ ትውከቱ አዳልጦት እንደሚጥለው ሰካራም ትንገዳገዳለች። 15 በግብጽ ራስም ሆነ ጭራ፣ የዘንባባ ዝንጣፊ
ቢሆን ወይም ቄጤማ የሆነ ምንም ነገር ማድረግ አይችልም። 16 በዚያ ቀን፣ ግብጻዊያን እንደ ሴቶች ይሆናሉ። በእነርሱ ላይ ከሚነሣው የሠራዊት አምላክ
እግዚአብሔር የቅጣት እጅ አንጻር ይሸበራሉ፣ ደግሞም ይፈራሉ። 17 ይሁዳ ለግብጽ ሕዝብ የምታንገዳግድ ትሆናለች። ማንኛውም ሰው ስለ እርሷ
ሲያስታውሳቸው፣ ከእግዚአብሔር የመቅጣት እቅድ የተነሣ ይሸበራሉ። 18 በዚያን ቀን በግብጽ ምድር ውስጥ የሚገኙ አምስት የዕብራውያን ቋንቋ የሚናገሩ
ከተሞች ይኖራሉ፤ በዚያም የሚኖሩ ሕዝቦች በሠራዊት አምላክ ስም ይምላሉ፤ ከእነዚህ ከተሞች አንዲቱ የፀሐይ ከተማ ተብላ ትጠራለች። 19 በዚያን ቀን
በግብጽ ምድር መካከል ላይ ለእግዚአብሔር መሠዊያ ይሠራል፤ እንዲሁም በግብጽ ጠረፍ ላይ ለእግዚአብሔር የተለየ የድንጋይ ዐምድ ይተከላል። 20 እነርሱም
የሠራዊት አምላክ በግብጽ ምድር ለመኖሩ ምልክትና ምስክር ይሆናሉ። ከጭቆና የተነሣ እግዚአብሔር እንዲረዳቸው በሚጠይቁበት ጊዜ፣ የሚታደጋቸውን አዳኝ
ይልክላቸዋል፣ እርሱም ከጠላቶቻቸው ያድናቸዋል። 21 እግዚአብሔር ለግብጽ ሕዝብ የታወቀ ይሆናል፤ ደግሞም በዚያን ጊዜ እነርሱ ያውቁታል። መሥዋዕትና
መባም ያቀርቡለታል፣ ለእግዚአብሔርም ስእለት ይሳላሉ፤ ስእለታቸውንም ሁሉ ይፈጽማሉ። 22 እግዚአብሔር ግብጻውያንን ይቀጣል፤ ነገር ግን መልሶ
ይፈውሳቸዋል፤ ወደ እርሱ ይመለሳሉ፤ እርሱም ጸሎታቸውን ሰምቶ ይፈውሳቸዋል። 23 በዚያን ጊዜ በግብጽና በአሦር መካከል አውራ ጎዳና ይከፈታል፤
አሦራዊያን ወደ ግብጽ፣ ግብጻዊያንም ወደ አሦር ይመጣሉ፤ ደግሞም ግብጻዊያን ከአሦራዊያን ጋር ያመልካሉ። 24 በዚያን ቀን፣ እስራኤል ከግብጽና ከአሦር ጋር
ሦስተኛ አገር ትሆናለች፤ እነዚህም ሕዝቦች በዓለም መካከል በረከት ይሆናሉ። 25 የሠራዊት አምላክም፣ "እናንተ በግብጽ የምትኖሩ ሕዝቤ፣ የፈጠርኳችሁ
አሦራውያንና የመረጥኳችሁ የእስራኤል ሕዝብ የተባረካችሁ ሁኑ" ይላቸዋል።

Isaiah 19:1

እነሆ
‹‹ተመልከቱ›› ወይም፣ ‹‹አድምጡ›› ወይም፣ ‹‹የምናገረውን ልብ በሉ››

ያህዌ በፈጣን ደመና ይመጣል
በሰረገላ እየመጣ ያለ ይመስል ያህዌ በደመና እየሄደ እንደሆነ ተመስሎአል።

የግብፅ ጣዖቶች በፊቱ ይርዳሉ
ያህዌ ሲመጣ ጣዖቶቹ ፍርሃት እንደሚያድርባቸው ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የግብፅ ጣዖቶች ያህዌ ፊት በፍርሃት ይንቀጠቀጣሉ››

የግብፃውያን ልብ በውስጣቸው ይቀልጣል
የልብ መቅለጥ የሚያመለክተው ወኔ ማጣትን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ግብፃውያን ምንም ወኔ አልቀራቸውም››

ሰው በጐረቤቱ ላይ
‹‹ይነሣል›› የሚለው ካለፈው ሐረግ ውስጠ ታዋቂ ነው። ‹‹ሰው በጐረቤቱ ላይ ይነሣል››

ከተማ በከተማ ላይ
‹‹ከተማ›› የከተማውን ሰዎች ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአንድ ከተማ ሕዝብ፣ በሌላ ከተማ ሕዝብ ላይ ይነሣል›› ወይም፣ ‹‹በተለያዩ ከተሞች ያሉ ሰዎች እርስ በርስ ይዋጋሉ››

መንግሥት በመንግሥት ላይ
‹‹ይነሣል›› ወይም፣ ‹‹ይዋጋል›› የተሰኙ ቃላት ካለፉ ሐረጐች ውስጠ ታዋቂ ናቸው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መንግሥት በመንግሥት ላይ ይነሣል›› ወይም፣ ‹‹አንድ መንግሥት ከሌላ መንግሥት ጋር ይዋጋል››

መንግሥት በመንግሥት ላይ
‹‹መንግሥት›› የሚለው ቃል ግብፅ ውስጥ ያለ ታናሽ መንግሥት ያመለክታል። ክፍለ ሀገርም ሊባል ይችላል። የዚያን መንግሥት ወይም ክፍለ ሀገር ሰዎች ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአንድ ክፍል ሀገር ሰዎች በሌላ ክፍለ ሀገር ሰዎች ላይ ይነሣሉ›› ወይም፣ ‹‹በተለያዩ ክፍለ ሀገሮች ያሉ ሰዎች እርስ በርስ ይዋጋሉ››

Isaiah 19:3

የግብፅ መንፈስ በውስጡ ይደክማል፤ ምክሩን አጠፋለሁ
እዚህ ላይ የግብፅ መንግሥት አንድ ሰው እንደሆነ ተነግሯል።

የግብፅ መንፈስ በውስጡ ይደክማል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የግብፅን መንፈስ በውስጡ አደክማለሁ››

የመናፍስት ጠሪዎችን ምክር ቢፈልግ እንኳ... ምክሩን አጠፋለሁ
‹‹የመናፍስት ጠሪዎችን ምክር ፈልገው ነበር፤ ግን ምንም አይጠቅማቸውም፤ ምክሩን ከማጥፋትም አያግደኝም››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምክሩን አጠፋለሁ
ይህም ማለት፣ 1) የሚሰጠውን ምክር ያህዌ ውጤት የለሽ ያደርገዋል፤ ወይም 2) ያህዌ ምንም ምክር እንዳይሰጥ ያደርገዋል። ይህን ዐረፍተ ነገር በሌላ ዐረፍተ ነገር መተካት ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ንጉሡን የሚመክሩትን ግራ አጋባለሁ››

መናፍስት ጠሪዎች... ጠንቋዮች
እነዚህ ከሞቱ ሰዎች ጋር እንነጋገራለን የሚሉ ናቸው።

ግብፃውያንን ለጨካኝ ጌታ እጅ አሳልፌ እሰጣለሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› ሥልጣንን ወይም ቁጥጥርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ግብፃውያንን በጨካኝ ጌታ ቁጥጥር ሥር እንዲሆኑ አሳልፌ እሰጣለሁ››

ይህ የሰራዊት ጌታ የያህዌ ቃል ነው
የሚናገረው እርግጥ እንደሆነ ለማሳየት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። ኢሳይያስ 3፥15 ላይ እንደ ተረጐምህ ተርጉመው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ይህ የሰራዊት ጌታ ያህዌ የተናገረው ነው›› ወይም፣ ‹‹ይህ እኔ የሰራዊት ጌታ ያህዌ የተናገርሁት ነው›› ወይም፣ ‹‹ይህ እኔ የሰራዊት ጌታ ያህዌ የተናገርሁት ነው››

Isaiah 19:5

የባሕሩ ውሃ ይደርቃል፤ ወንዝም ባዶ እስኪሆን ይደርቃል
ግብፃውያን የዐባይ ወንዝን፣ ‹‹ባሕሩ›› በማለት ይጠሩታል። እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የዐባይ ወንዝ ጨርሶ ይደርቃል››

ይከረፋሉ
‹‹መጥፎ ሽታ ይኖራቸዋል›› ወይም፣ ‹‹ይገማሉ››

እየጐደለ
‹‹እያነሰ፤ እያነሰ ይሄዳል››

ደንገሉና ቀጤማውም ይጠወልጋል
‹‹ደንገል›› እና፣ ‹‹ቀጤማ›› የተለያዩ የውሃ ውስጥ ተክል ናቸው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ወንዙ ዳርቻ ያሉት ተክሎች ጠውልገው ይደርቃሉ››

Isaiah 19:7

እንዲሁም በዐባይ ዳር የተዘራው እርሻ
‹‹ሰዎች እህል የዘሩበት ዐባይ ወንዝ አጠገብ ያለው እርሻ››

ዓሣ አጥማጆች ዋይ ይላሉ ያለቅሳሉ፤ በዐባይ ወንዝ ላይ መንጠቆአቸውን የሚጥሉ ሁሉ ያለቅሳሉ፤ በውሃው ላይ መረባቸውን የሚዘረጉ ሁሉ ያዝናሉ
እነዚህ ሦስት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። አስፈላጊ ከሆነ የሚያዝኑበትን ምክንያት መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ዐባይ ውስጥ ያሉ ዐሣዎች በመሞታቸው በመረብ ወይም በመንጠቆ ዓሣ የሚያጠምዱ ሰዎች ተስፋ በመቁረጥ ያለቅሳሉ››

ዐባይ ላይ መንጠቆ የሚጥሉ
ዓሣ ለመያዝ አንዳንድ ሰዎች መንጠቆው ላይ ጥቂት ምግብ ያስቀምጣሉ፤ መንጠቆውን በክር ያሰሩና ባሕር ውስጥ ይወረውሩታል። ዓሣው ምግቡን ለመብላት ሲሞክር፣ አፉ በመንጠቆው ይያዛል፤ ሰውየውም በመጐተት ዓሣውን ከውሃው ያወጣዋል።

መጣል
መወርወር

ውሃ ላይ መረብ መዘርጋት
ዓሣ ለመያዝ አንዳንድ ሰዎች ውሃው ላይ መረብ ይወረውራሉ። ዓሣው ሲጠመድ መረቡን ከዓሣው ጋር ከውሃው ስበው ያወጡታል።

Isaiah 19:9

የተበጠረውን ነጭ የተልባ እግር የሚሠሩ ሸማኔዎች ይገረጣሉ፤ የግብፅ ልብስ ሠሪዎችም ያዝናሉ
እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው፤ አስፈላጊ ከሆነ የሚያዝኑበትን ምክንያት መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ፈትል ስለማይኖር የግብፅ ተልባ እግር ልብስ ሠሪዎች ይዋረዳሉ››

ሸመና የሚሠሩ
‹‹የሸማና መሣሪያ በመጠቀም ልብስ የሚሠሩ››

ጥጥ
ጥጥ ዐባይ ወንዝ ዳር የሚያድግ ተክል ነው። መልካምና ያማረ ልብስ ለመሥራት ሰዎች ያበጥሩት ነበር።

ይገረጣሉ
‹‹ያፍራሉ››

የግብፅ ልብስ ሠሪዎች
x

Isaiah 19:11

የጣኔዎስ አለቆች ጨርሶ ሞኞች ይሆናሉ፤ የፈርዖን ጠቢባን ምክርም ከንቱ ይሆናል
ሁለቱ ሐረጐች ተመሳሳይ ትርጒም አላቸው። የፈርዖን ጠቢባን የተባሉት የጣኔዎስ አለቆች ሊሆኑ ይችላሉ፤ ወይም ደግሞ እነርሱ ራሳቸውም ሞኞች የሚሆኑ ሌሎች ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

ጣኔዎስ
ይህ በሰሜናዊ ግብፅ ያለ ከተማ ነው።

ፈርዖን እንዴት ትሉታላችሁ... ነገሥታት?
ኢሳይያስ በጥያቄ የተጠቀመው ጥበበኞች ነን በሚሉ ሰዎች ላይ ለማፌዝ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በሞኝነት ፈርዖንን... ነገሥታት››

ታዲያ፣ የአንተ ጥበበኞች ወዴት ናቸው?
ኢሳይያስ ጥያቄውን ያቀረበው በጥበበኞች ላይ ለማፌዝ ነው። ‹‹የአንተ›› የሚለው ፈርዖንን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጥበበኞች የሉህም›› ወይም፣ ‹‹ጥበበኞችህ ሞኞች ናቸው››

የሰራዊት ጌታ ያህዌ ግብፅ ላይ ያሰበውን ይንገሩህ ያሳውቁህ
ኢሳይያስ ጥበበኞቹ የእግዚአብሔርን ሐሳብ መረዳት እንዳለባቸው ቢያመለክትም፣ በእርግጥ መረዳት ይችላሉ ብሎ አያምንም። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በእውነት ጥበበኞች ከሆኑ፣ የሰራዊት ጌታ ያህዌ ግብፅ ላይ ያሰበውን ይንገሩህ››

Isaiah 19:13

የነገዶቿ የማእዘን ራስ የሆኑት ግብፅን አስተዋታል
የጣኔዎስና የሜምፊስ አለቆች ማኅበረ ሰቡ ውስጥ አስፈላጊ ሰዎች በመሆናቸው የሕንፃዎች ማእዘን ራሶች እንደሆኑ ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹መሪዎቹ ግብፅን አሳስተዋል››

የጣኔዎስ አለቆች
ጣኔዎስ ሰሜናዊ ግብፅ ላይ ያለች ከተማ ናት። ኢሳይያስ 19፥11 ላይ እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሜምፊስ
ይህ ሰሜናዊ ግብፅ ላይ ያለ ከተማ ነው።

ግብፅን አስተዋታል
‹‹ግብፅ›› የግብፅን ሕዝብ ያመለክታል። መሳት ትክክል ያልሆነ ነገር ማድረግን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የግብፅን ሕዝብ አሳስተዋል›› ወይም፣ ‹‹የግብፅ ሕዝብ ትክክል ያልሆነ ነገር እንዲያደርግ አድርገዋል››

ያህዌ በመካከልዋ የድንዛዜ መንፈስ ቀላቅሏል
ኢሳይያስ የያህዌ ፍርድ ግብፅን የወይን ጠጅ ጽዋ እንደሚያደርጋት ይናገራል። የመሪዎቹ አስተሳሰብ ግራ መጋባት ያህዌ ከወይን ጠጅ ጋር የሚቀላቅለው ፈሳሽ እንደሆነ ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሐሳባቸውን ግራ በማጋባት ያህዌ ፈርዶባቸዋል›› ወይም፣ ‹‹የሚያሰክር መጠጥ የሰዎችን አስተሳሰብ ግራ እንደሚያጋባ የመሪዎቿን ሐሳብ ግራ በማጋባት ያህዌ ግብፅ ላይ ፈርዷል››

ግራ መጋባት
‹‹መጣመም›› ወይም፣ ‹‹መታወክ››

በመካከልዋ
‹‹እርሷ›› ግብፅን ያመለክታል። ብዙ ጊዜ ሕዝቦች በሴቶች ይመሰላሉ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በግብፅ ውስጥ››

እነርሱ ግብፅን አስተዋታል
እዚህ ላይ፣ ‹‹እነርሱ›› ቀደም ባለው ቁጥር የተጠቀሱት መሪዎች ናቸው። ‹‹ግብፅ›› የሚለው ቃል የግብፅን ሕዝብ ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አለቆቹ የግብፅን ሕዝብ አስተዋል››

ግብፅን አስተዋል
ሕዝብን ማሳት ትክክል ያልሆነ ነገርን እንዲያደርጉ ማድረግን ይወክላል።

ሰካራም በትውከቱ እንደሚንገዳገድ
የሰከረ ሰው እንደሚንገዳገድ የግብፅ ሕዝብ ትክክል ያልሆነ ነገር እንደሚደርግ ኢሳይያስ ይናገራል።

ራስም ይሁን ጅራት
የሰውም ሆነ የእንስሳ፣ ‹‹ራስ›› መሪን ይወክላል። ‹‹ጅራት›› ተቃራኒ ሲሆን፣ ተከታዮችን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹መሪም ሆነ ተከታይ››

የዘንባባ ዝንጣፊም ይሁን ደንገል
‹‹የዘንባባ ዝንጣፊ›› ዛፍ ላይ ከፍ ብሎ የሚያድግ ስለሆነ ሀብታሞችና ታላላቆችን ይወክላል። ‹‹ደንገል›› ረግረግ ውሃ ውስጥ የሚያድግ ስለሆነ ድኾችና ታናናሾችን ይወክላል። ኢሳይያስ 9፥14 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ታላላቆችም ሆኑ ታናናሾች›› ወይም፣ ‹‹ሀብታሞችም ሆኑ ድኾች››

Isaiah 19:16

ግብፃውያን እንደ ሴቶች ይሆናሉ
ይህ የሚመለክተው እግዚአብሔር ሲቀጣቸው የግብፅ ሕዝብ እንደሚፈሩና ዐቅመ ቢስ እንደሚሆኑ ነው።

የሰራዊት ጌታ ያህዌ እነርሱ ላይ ካነሣው እጁ የተነሣ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› የሚወክለው የእግዚአብሔርን ኀይል ሲሆን፣ እነርሱ ላይ እጅ ማንሣት እነርሱን መቅጣትን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እነርሱን ለመቅጣት የሰራዊት ጌታ ያህዌ ካነሣው ኀይል እጁ የተነሣ››

የይሁዳ ምድር ለግብፅ መንገዳገድ ምክንያት ትሆናለች
‹‹የይሁዳ ምድር›› እና፣ ‹‹ግብፅ›› በእነዚያ አገሮች የሚኖረውን ሕዝብ ያመለክታሉ። ግብፃውያን ከመፍራታቸው የተነሣ ይንገዳገዳሉ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የይሁዳ ሕዝብ የግብፅ ሕዝብ እንዲንገዳገድ ያደርጋሉ›› ወይም፣ ‹‹የይሁዳ ሕዝብ ግብፃውያን እጅግ እንዲፈሩ ያደርጋሉ››

ስለ እርሷ ሲነገራቸው ይሸበራሉ
‹‹የእነርሱ›› እና፣ ‹‹እነርሱ›› የሚያመለክተው ግብፃውያንን ሲሆን፣ ‹‹እርሷ›› የሚያመለክተው የይሁዳን ሕዝብ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለግብፃውያን ስለ ይሁዳ ሕዝብ ሲነገራቸው ግብፃውያን ይሸበራሉ››

Isaiah 19:18

በግብፅ ምድር የሚናገሩ አምስት ከተሞች ይሆናሉ
ይህ የሚያመለክተው የዚያ ከተማ ሰዎችን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በአምስት የግብፅ ከተሞች የሚኖሩ ሰዎች ይናገራሉ››

በከነዓን ቋንቋዎች
ይህ የሚያመለክተው በከነዓን ምድር የሚኖሩ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ቋንቋ ዕብራይስጥን ነው። እዚህ ላይ፣ ከነዓን እዚያ የሚኖር ሕዝብን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የከነዓን ሕዝብ ቋንቋ››

ይምላሉ
‹‹ታማኝ ለመሆን ቃል ይገባሉ››

ከእነዚህ አንዷ ትጠራለች
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። ‹‹ሰዎች ከእነዚህ ከተሞች አንዷን ይጠሯታል››

የፀሐይ ከተማ ትባላለች
እዚህ ላይ፣ ‹‹ፀሐይ›› ተብሎ የተተረጐመው የዕብራይስጥ ቃል፣ ‹‹ፀሐይ›› ወይም ‹‹ጥፋት›› ማለት መሆኑ ግልጽ አይደለም። ስሙ ስለ ከተማዋ የሚነግረን ምን እንደሆነም ግልፅ አይደለም። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የፀሐይ ከተማ የተባለች ከተማ›› ወይም፣ ‹‹የጥፋት ከተማ የተባለች ከተማ››

Isaiah 19:19

ለያህዌ ድንበር ላይ ያለ የድንጋይ ዐምድ
‹‹ድንበር›› የሚያመለክተው የግብፅን ድንበር ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ግብፅ ድንበር ላይ ለያህዌ የድንጋይ ዐምድ››

በግብፅ ምድር ለሰራዊት ጌታ ለያህዌ ምልክትና ምስክር ይሆናል
‹‹ምልክት›› እና፣ ‹‹ምስክር›› የተሰኙትን ቃሎች፣ ‹‹ማሳያ›› እና፣ ‹‹ማረጋገጫ›› በማለት መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ዐምዱ የሰራዊት ጌታ ያህዌ በግብፅ ምድር መሆኑን ያሳያል፤ ያረጋግጣል››

በግብፅ ምድር ለሰራዊት ጌታ ለያህዌ
ያህዌ በግብፅ ምድር መሆኑ የግብፅ ሕዝብ እርሱን እንደሚያመልኩ ያሳያል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በግብፅ ምድር ያሉ ሰዎች የሰራዊት ጌታ ያህዌን ያመልካሉ››

ሲጮኹ
‹‹ግብፃውያን ሲጮኹ››

ከሚያስጨንቋቸው የተነሣ
‹‹ሰዎች ከሚፈጽሙባቸው ግፍ የተነሣ›› ወይም፣ ‹‹ሌሎች ከሚያደርሱባቸው መከራ የተነሣ››

አዳኝና ታዳጊ ይልክላቸዋል
‹‹ያህዌ የሚያድናቸውና የሚታደጋቸው ሰው ይልክላቸዋል››

ያህዌ ያድናቸዋል
ያህዌ የሚያድናቸው ከማን እንደሆነ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ ግብፃውያንን ከሚያስጨንቋቸው ያድናቸዋል››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Isaiah 19:21

ያህዌ በግብፅ የታወቀ ይሆናል
‹‹ግብፅ›› የሚያመለክተው የግብፅን ሕዝብ ነው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ የግብፅ ሕዝብ እንዲያውቀው ያደርጋል››

ይቀበሉታል
‹‹ስለ ያህዌ እውነቱን ይቀበላሉ›› ወይም፣ ‹‹ስለ ያህዌ እውነት ጋር ይስማማሉ››

ያመልካሉ
የሚያመልኩት ማንን እንደሆነ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌን ያመልካሉ››

ለያህዌ ይሳላሉ፤ ይፈጽማሉ
‹‹ለያህዌ ቃል ይገባሉ፤ ቃላቸውን ይጠብቃሉ›› ወይም፣ ‹‹ለያህዌ ቃል ይገባሉ፤ እናደርጋለን ያሉትንም ያደርጋሉ››

ያህዌ ግብፅን ይመታል
‹‹ግብፅ›› የሚያመለክተው የግብፅን ሕዝብ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ የግብፅን ሕዝብ ይመታል››

ይመታል
‹‹ይቀጣል›› ወይም፣ ‹‹ይፈርዳል››

ይመታል፤ ይፈውሳል
በዚህ ሐረግ ‹‹እነርሱ›› የሚለው ውስጠ ታዋቂ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ይመታቸዋል ደግሞም ይፈውሳቸዋል››

ይመታል፤ ይፈውሳል
ይህን ሐረግ ቀድሞ ከነበረው ሐረግ ጋር ለማያያዝ፣ ‹‹በኋላ›› ወይም፣ ‹‹ደግሞም›› በተሰኙ ቃሎች ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከመታቸው በኋላ ይፈውሳቸዋል››

Isaiah 19:23

አውራ መንገድ ይኖራል
አውራ መንገድ ብዙ ሰዎች መጓዝ የሚችሉበት ትልቅ መንገድ ነው።

አሦራዊ ይመጣል
‹‹አሦራዊ›› ከአሦር የሆነ ሰው ሲሆን፣ ግን ከአሦር ወደ ግብፅ የመጣ ማንኛውንም ሰው ይመለከታል። ‹‹አሦራውያን ይመጣሉ››

ግብፃዊ ወደ አሦር
‹‹ይመጣል›› የሚለው ውስጠ ታዋቂ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ግብፃውያን ወደ አሦር ይመጣሉ››

ግብፃዊ
ይህ የሚያመለክተው ከግብፅ የሆነ ሰውን ሲሆን፣ ነገር ግን ወደ አሦር የመጣ ማንኛውንም ግብፃዊ ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ግብፃውያን››

ግብፃውያን ከአሦራውያን ጋር ያመልካሉ
የሚያመልኩት ማንን እንደሆነ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ግብፃውያንና አሦራውያን ያህዌን ያመልካሉ››

Isaiah 19:24

እስራኤል ከግብፅና ከአሦር ጋር ሦስተኛ ይሆናል
የሦስቱ አገሮች ስም በእነዚያ አገሮች የሚኖሩ ሰዎችን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እስራኤላውያን ከግብፃውያንና ከአሦራውያን ጋር ሦስተኛ ይሆናሉ››

ሦስተኛ ይሆናል
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹አብረው ይሆናሉ›› ወይም 2) ‹‹ከእነርሱ ጋር ሦስተኛ በረከት›› ወይም 3) ‹‹እኩል ይሆናል›› ማለት ሊሆን ይችላል።

ሕዝቤ ግብፅ፣ የእጆቼ ሥራ አሦር፣ ርስቴ እስራኤል የተባረኩ ይሁኑ
የሦስቱ አገሮች ስም በእነዚያ አገሮች የሚኖሩ ሰዎችን ይወክላል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የግብፅ ሕዝብ ሆይ፣ ሕዝቤ ስለሆናችሁ ባርኬአችኃለሁ፤ የአሦር ሕዝብ ሆይ፣ ስለ ፈጠርኃችሁ ባርኬአችኃለሁ፤ የእስራኤል ሕዝብ ሆይ፣ ርስቴ ስለሆናች ባርኬአችኃለሁ››

የእጆቼ ሥራ
‹‹እጆች›› የእግዚአብሔርን ኀይልና ተግባር ያመለክታሉ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 20

1 የአሦር ንጉሥ ሳርጎን ተርታንን በሰደደ ጊዜና ወደ አዛጦን በመጣ ጊዜ አዛጦንም ወግቶ በያዛት ጊዜ፥ 2 በዚያ ጊዜ እግዚአብሔር የአሞጽን ልጅ ኢሳይያስን፣ "ሂድና ማቅህን ከወገብህ አውጣ፣ ጫማህንም ከእግርህ አውልቅ" ብሎ ተናገረው። እንዲህም አደረገ፣ ራቁቱንም ባዶ እግሩንም ሄደ። 3 እግዚአብሔርም አለ፣ "ባሪያዬ ኢሳይያስ በግብጽና በኢትዮጵያ ላይ ሦስት ዓመት ለምልክትና ለተአምራት ሊሆን ራቁቱንና ባዶ እግሩን እንደ ሄደ፣ 4 በዚህ መንገድ የአሦር ንጉሥ የግብጽንና የኢትዮጵያን ምርኮ፣ ጐበዛዝቱንና ሽማግሌዎቹን፣ ራቁታቸውንና ባዶ እግራቸውን አድርጎ ገላቸውንም ገልጦ፣ ለግብጽ ጕስቍልና ይነዳቸዋል። 5 እነርሱም ከተስፋቸው ከኢትዮጵያ ከትምክሕታቸውም ከግብጽ የተነሣ ይፈራሉ ያፍሩማል፤ 6 በዚያም ቀን በዚች ባሕር ዳርቻ የሚኖሩ፣ "በእርግጥ፣ ከአሦር ንጉሥ እንድን ዘንድ ለእርዳታ ወደ እነርሱ የሸሸንበት ተስፋችን ይህ ነበረ፤ እኛስ እንዴት እናመልጣለን?" ይላሉ።

Isaiah 20:1

ታርታን
የአሦር ሰራዊት ዋና አዛዥ ስም

ሳርጐን
የአሦር ንጉሥ ስም

አሽዶድን ወግቶ ያዛት
አሽዶድ የአስዶድን ሰራዊት ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከአሽዶድ ሰራዊት ጋር ተዋግቶ ድል አደረገ››

ዕርቃኑንና ባዶ እግሩን ሄደ
‹‹ያለ ልብስና ያለ ጫማ ሄደ›› እዚህ ላይ፣ ‹‹ዕርቃኑን›› ሲል ምናልባት በውስጥ የሚለበስ ልብስ ብቻ ለብሶ ማለቱ ሊሆን ይችላል።

Isaiah 20:3

ለምልክት
‹‹ለማስጠንቀቂያ››

ለግብፅ ለኩሽ
የቦታዎቹ ስም ሕዝቡን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ለግብፅ ሕዝብና ለኩሽ ሕዝብ››

የአሦር ንጉሥ ምርኮኞቹን ይወስዳቸዋል
ንጉሡ እንዲህ እንዲያደርጉ ሰራዊቱን ያዝዛል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የአሦር ንጉሥ ሰራዊቱ ምርኮኞቹን እንዲወስዱ ያደርጋል››

የግብፅ ምርኮኞችን፣ የኩሽ ስደተኞችን
በመጀመሪያ እንደሚዋጉ ከዚያም ምርኮኞችን እንደሚወስዱ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ግብፅና ኩሽን ወግቶ ሕዝባቸውን ይይዛል፤ ከዚያም ይወስዳቸዋል››

ወደ ግብፅ ውርደት
ግብፅ የግብፅን ሕዝብ ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የግብፅ ሕዝብ ላይ ውርደት ወደሚያመጣ››

Isaiah 20:5

ይደነግጣሉ ይዋረዳሉ
‹‹ይፈራሉ፤ እፍረት ይይዛቸዋል››

ተስፋቸው ከሆነው ኩሽ፣ ክብራቸው ከሆነው ግብፅ የተነሣ
ተስፋና ክብር በእነዚህ አገሮች ወታደራዊ ኀይል መተማመናቸውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በኩሽና በግብፅ ሰራዊት ኀይል ከመተማመናቸው የተነሣ››

በእነዚህ ባሕር ዳርቻዎች የሚኖሩ
ሜዲትራንያን ባሕር ዳርቻ የሚኖሩ ሕዝቦች

እንዲድኑን የሸሸንባቸው
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያድኑናል በማለት ሸሽተን የነበርንባቸው አገሮች››

ታዲያ፣ አሁን እንዴት እናመልጣለን?
ጸሐፊው ይህን ጥያቄ ያነሣው ሁኔታው ምን ያህል ተስፋ የሌለው መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አሁን ምንም ማምለጫ የለንም››

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 21

1 በባሕር አጠገብ ስላለው ስለ ምድረ በዳ የተነገረ ዐዋጅ። ዐውሎ ነፋስ ከኔጌቭ እንደሚወጣ፣ እንዲሁ ከሚያስፈራ አገር በምድረ በዳ አልፎ ይወጣል። **2** የሚረብሽ ራእይ ተነገረኝ፤ ወንጀለኛው በወንጀል ይሠራል፣ አጥፊውም ያጠፋል። ኤላም ሆይ፣ ወደ ላይ ውጪ፣ ሜዶን ሆይ ክበቢ፤ ትካዜውን ሁሉ አስቀርቻለሁ። **3** ስለዚህ ወገቤ በሕመም ተሞላ፤ እንደምትወልድ ሴት ምጥ ያዘኝ፤ ከሰማሁት የተነሣ ጎበጥኩ፤ ካየሁት ነገር የተነሣ ተረበሽኩ። **4** ልቤ ተርበደበደ፣ መንቀጥቀጥ አስፈራኝ፤ የተመኘሁት ሌሊት የሚያንቀጠቅጠኝ ሆነብኝ። **5** ማዕዱን ያዘጋጃሉ፣ ምንጣፉንም ይዘረጋሉ፣ ይበሉማል፣ ይጠጡማል፤ እናንተ ልዑላን ሆይ፣ ተነሡ፣ ጋሻውን በዘይት ቀቡ። **6** ጌታ ያለኝ እንዲህ ነው፣ "ሂድ፣ ጕበኛም አቁም፣ የሚያየውንም ይናገር። **7** በከብት የሚቀመጡትን፣ ሁለት ሁለት እየሆኑ የሚሄዱት ሠረገሎች፥ በአህዮች የሚጋልቡትንና በግመሎች የሚጋልቡትን ባየ ጊዜ፣ በጽኑ ትጋት አስተውሎ ተግቶም ያድምጥ።" **8** ያየውም። ጌታ ሆይ፥ ቀኑን ሁሉ ዘወትር በማማ ላይ ቆሜአለሁ፥ ሌሊቱንም ሁሉ በመጠበቂያዬ ላይ ተተክያለሁ፣" **9** እነሆም፣ በፈረሶች የሚቀመጡ፣ ሁለት ሁለት ሆነው የሚሄዱ ፈረሰኞች ይመጣሉ ብሎ ጮኸ፤ እርሱም መልሶ፣ "ባቢሎን ወደቀች፣ ወደቀች፣ የተቀረጹም የአማልክቶችዋ ምስሎች ሁሉ በምድር ላይ ተጥለው ደቀቁ" አለ። **10** እናንተ በአውድማዬ ላይ የተወቃችሁ የአውድማዬ ልጆች ሆይ! ከእስራኤል አምላክ፣ ከሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የሰማሁትን ነገርኋችሁ። **11** ስለ ኤዶምያስ የተነገረ ዐዋጅ። አንዱ ከሴይር ይጣራል፣ "ጕበኛ ሆይ፣ ከሌሊቱ ምን ያክል ሰዓት ቀረ? ጕበኛ ሆይ፣ ከሌሊቱ ምን ያክል ሰዓት ቀረ?" ብሎ ጠራኝ። **12** ጕበኛውም እንዲህ አለ፣ "ማለዳው ይመጣል፣ ድግሞም ምሽቱ፤ ብትጠይቁ፣ ጠይቁ፤ ተመልሳችሁም ኑ" አለ። **13** ስለ ዓረብ የተነገረ ዐዋጅ። የዴዳናውያን ነጋዴዎች ሆይ፣ በዓረብ ዱር ውስጥ ታድራላችሁ። **14** በቴማን የምትኖሩ ሆይ፣ ወደ ተጠሙት ሰዎች ውኃ አምጡ፣ እንጀራ ይዛችሁ የሸሹትን ሰዎች ተቀበሉአቸው። **15** ከሰይፍ፣ ከተመዘዘው ሰይፍ፣ ከተለጠጠውም ቀስት ከጽኑም ሰልፍ ሸሽተዋልና። **16** ጌታ ያለኝ እንዲህ ነውና፣ "ምንደኛ ለአንድ ዓመት እንደሚቀጠር፣ በአንድ ዓመት ውስጥ የቄዳር ክብር ሁሉ ይጠፋል፤ **17** ከቀስተኞች ቍጥር ጥቂቶቹ ብቻ፣ የቄዳር ልጆች ኃያላን፣ ያንሳሉ፤" የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ተናግሮአልና።

Isaiah 21:1

ንግር
‹‹ይህ ያህዌ የተናገረው ነው›› ወይም፣ ‹‹ይህ የያህዌ መልእክት ነው››

ባሕሩ ዳር ስላለው ምድረ በዳ
ይህ እንደ ምድረ በዳ አድርጐ የተነገረ ቃል የሚያመለክተው የባቢሎንን ሕዝብ ነው፤ ምንም እንኳ እግዚአብሔር ገና ምድረ በዳ ባያደርጋትም አሁን እንደሆነች አድርጐ ይናገራል፤ ይህም የሚያመለክተው በእርግጥ ምድረ በዳ እንደምትሆን ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በቅርቡ ምድረ በዳ በምትሆን ምድር ለሚኖር ሕዝብ››

እየጠራረገ ከኔጌቭ እንደሚመጣ ዐውሎ ነፋስ
ሕዝቡን ለማጥቃት የሚመጣውን ሰራዊት እግዚአብሔር ከብርቱ ነፋስ ጋር አመሳስሎታል። ፈጣንና ኀይለኛ ሰራዊት ነው።

ከምድረ በዳ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ምድረ በዳ›› የይሁዳን ምድረ በዳ ነው የሚያመለክተው።

ከአሸባሪ ምድር
ሰራዊቱ የሚመጣው ታላቅ ፍርሃት ከሚያደርስ ሕዝብ ነው።

የሚያስጨንቅ ራእይ አየሁ
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ የሚያስጨንቅ ራእይ አሳየኝ››

ከሐዲ ክሕደቱን ያደርጋል
‹‹የሚያሳስቱ ያሳስታሉ››

አጥፊም ያጠፋል
‹‹የሚያጠፉ ይጠፋሉ››

ወደ ላይ ወጥታችሁ አጥቁ፣ ኤላም፣ መክበብ፣ ሜዶን
ለኢሳይያስ በተሰጠው ራእይ እግዚአብሔር እርሱን እንደሚሰሙ አድርጐ ለኤላምና ለሜዶን ሰራዊት ይናገራል።

ወደ ላይ ወጥታችሁ አጥቁ፤ ኤላም፣ መክበብ፣ ሜዶን
የሚያጠቁት ባቢሎናውያንን መሆኑ ግልጽ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ወደ ላይ ወጥታችሁ ባቢሎናውያንን አጥቁ፤ እናንት የኤላም ሰራዊት ሄዳችሁ›› ባቢሎናውያንን ክበቡ፤ እናንት የሜዶን ሰራዊት››

ኤላም... ሜዶን
እዚህ ላይ፣ ‹‹ኤላም›› እና፣ ‹‹ሜዶን›› ከእነዚህ አገሮች የመጡ ሰራዊት ያመለክታል።

እርሷ ያደረሰችውን ስቃይ ሁሉ አስቀራለሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እርሷ›› በባቢሎናውያን ምክንያት መከራ የደረሰባቸውን ሕዝብ ሁሉ ይወክላል። የኤላምና የሜዶንን ሰራዊት ልኮ ባቢሎናውያንን ሲደመሰስ ያህዌ ስቃያቸውን ሁሉ ያስቀራል።

Isaiah 21:3

ወገቤ በስቃይ ተሞላ
ኢሳይያስ ያየው ራእይ በጣም አስጨናቂ ስለ ነበር አካላዊ ሕመም አሳድሮበት ነበር። እዚህ ላይ ስቃዩና ሕመሙ ምኑ ላይ እንደነበር ይናገራል።

በምጥ ላይ እንዳለች ሴት ጭንቅ ያዘኝ
ኢሳይያስ ሕመሙን ምጥ ከያዛት ሴት ሕመም ጋር ያመሳስለዋል። ይህም ሕመሙ ምን ያህል ከባድ እንደ ነበር ያመለክታል።

የሰማሁትን ነገር አጐበጠኝ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የሰማሁት ነገር በሕመም አጐበጠኝ››

ባየሁት ነገር ተሸበርሁ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያየሁት ነገር በጣም አሸበረኝ››

ልቤ መታ፤ ፍርሃት አንቀጠቀጠኝ
‹‹ልቤ በፍጥነት መታ፤ እኔም ተንቀጠቀጥሁ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Isaiah 21:5

እነርሱ ተዘጋጁ
‹‹እነርሱ›› የተባሉ የባቢሎን መሪዎች ናቸው።

ማእዱን አዘጋጁ
‹‹ማእድ›› የተባለው ግብዣው ላይ ሰዎች የሚበሉት ምግብ ነው።

ሹማምንት፣ ተነሡ
እዚህ ላይ ‹‹ሹማምንቱ›› የተባሉት ሥልጣን ያላቸው ሰዎች በጠቅላላ እንጂ፣ የግድ የነገሥታት ልጆች ብቻ አይደለም።

ጋሻውን በዘይት ወልውሉ
በጦርነት ጊዜ እንዳይሰነጠቁና ሁሌም ለስላሳ እንዲሆኑ ወታደሮች ጋሻዎቻቸውን በዘይት ይወለውሉ ነበር።

Isaiah 21:6

ጠባቂ አቁም
‹‹ጠባቂው በኢየሩሳሌም ቅጥር ላይ እንዲቆም ንገር››

ሰረገላ፣ ጥንድ ፈረሰኞች
‹‹በሁለት ፈረሶች የሚሳብ ሰረገላ የሚነዳ ወታደር››

Isaiah 21:8

ጌታ ሆይ፣ በመጠበቂያው ማማ ቆሜአለሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ጌታ ሆይ›› የተባለው ቅጥር ጠባቂው በኢየሩሳሌም ቅጥር እንዲቆም የሚያዝዘው ባለ ሥልጣን ነው።

ባቢሎን ወደቀች፤ ወደቀች
ባቢሎን ጨርሶ በጠላቶችዋ መሸነፍዋ የባቢሎን መውደቅ እንደሆነ ተነግሯል። ‹‹ባቢሎን›› የባቢሎንን ሕዝብ ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የባቢሎን ሕዝብ ጨርሶ ድል ሆነ››

ወደቀች፤ ወደቀች
‹‹ወደቀች›› የሚለው ቃል የተደገመው የባቢሎን ሕዝብ በጠላቶቻቸው ጨርሶ ድል መሆናቸውን አጽንዖት ለመስጠት ነው።

Isaiah 21:10

የተወቃችሁና የተበራያችሁ የዐውድማዬ ልጆች
የእስራኤል ሕዝብ በባቢሎናውያን መሰቃየት ሕዝቡ ዐውድማ ላይ የሚወቃ እህልና የሚበራይ ወይን ፍሬ እንደሆነ ተነግሯል።

ዐውድማዬ
‹‹የእኔ›› የሚለው ቃል ኢሳይያስን ያመለክታል።

የሰራዊት ጌታ ያህዌ
ኢሳይያስ 1፥9 ላይ እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት

Isaiah 21:11

ንግር
‹‹ይህ ያህዌ የተናገረው ነው›› ወይም፣ ‹‹ይህ የያህዌ መልእክት ነው››

ስለ ዱማ
ይህ የኤዶም ሌላ ስም ነው። እዚህ ላይ፣ ‹‹ዱማ›› እዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ስለ ዱማ ሕዝብ›› ወይም፣ ‹‹ስለ ኤዶም ሕዝብ››

እንዲህ ሲል ጠራኝ
‹‹እኔን›› የሚለው ኢሳይያስን ነው።

ሴይር
ይህ ከኤዶም በስተ ምዕራብ ያለ ተራራ ስም ነው።

ጠባቂ ሆይ፣ ሊነጋ ምን ያህል ቀረው? ጠባቂ ሆይ፣ ሊነጋ ምን ያህል ቀረው?
ይህ የተደጋገመው ጥያቄውን ያቀረበው ሰው ምን ያህል እንደ ተጨነቀና ግራ እንደ ተጋባ አጽንዖት ለመስጠት ነው።

መጠየቅ ከፈለግህ ጠይቅ፣ ደግሞም ተመልሰህ ና
‹‹ማወቅ የፈለግኸውን አሁን ጠይቀኝ፤ ደግሞም በኋላ ተመልሰህ ናና ጠይቀኝ››

Isaiah 21:13

ንግር
‹‹ይህ ያህዌ የተናገረው ነው›› ወይም፣ ‹‹ይህ የያህዌ መልእክት ነው››

ስለ ዐረቢያ
ዐረቢያ የዐረቢያ ሕዝብን ይመለከታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ስለ ዐረቢያ ሕዝብ››

በዐረቢያ ምድረ በዳ
ዐረቢያ ደን የላትም። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከዐረቢያ መንገድ በጣም ርቆ›› ወይም፣ ‹‹ከዐረቢያ ቆጥቋጦዎች ውጪ››

ሲራራ ነጋዴዎች
በአንድነት የሚጓዙ ሰዎች

የድዳን ሰዎች
እነዚህ በዐረቢያ የሚኖሩ ሰዎች ናቸው።

የቴማ ምድር
ይህ አረቢያ ውስጥ ያለ ከተማ ስም ነው።

ስደተኞች
ስደተኛ ጠላት እንዳይይዘው የሸሸ ሰው ነው። ኢሳይያስ 15፥5 ላይ እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

ከእንጀራ ጋር
‹‹እንጀራ›› በአጠቃላይ ምግብን ያመለክታል።

ከሰይፍ፣ ከተመዘዘ ሰይፍ፣ ከተደገነ ቀስት
እዚህ ላይ፣ ‹‹ሰይፍ›› እና፣ ‹‹ቀስት›› የቴማን ነዋሪዎችን የሚያጠቁ ወታደሮችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በሰይፍና በቀስት ከሚያጠቋቸው ጠላቶቻቸው››

ከጦርነት ሸክም
በጦርነቱ ጊዜ የሚደርስባቸው ሸብርና መከራ ሕዝቡ ላይ እንደ ተጫነ ከባድ ሸክም ተመስሎአል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከጦርነት ሸብር››

Isaiah 21:16

በውል የተቀጠረ ሠራተኛ ቀን እንደሚቆጥር
‹‹በውል የተቀጠረ ሠራተኛ ዓመቱን እንደሚቆጥር›› አንድ የቅጥር ሠራተኛ በሥራ ባሳለፈው ጊዜ መሠረት እንዲከፈለው ተጠንቅቆ ጊዜ ይቆጥራል። ይህም ማለት በአንድ ዓመት ውስጥ ቁዳር ድል ትሆናለች ማለት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የቄዳር
ይህ ዐረቢያ ውስጥ ያለ አካባቢ ነው። ቄዳር የቄዳርን ሕዝብ ያመለክታል።
አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የቄዳር ሕዝብ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 22

1 ስለ ራእይ ሸለቆ የተነገረ ዐዋጅ፤ እናንተ ሁላችሁ ወደ ቤት ሰገነት መውጣታቸሁ ምን ሆናችኋል? **2** ጩኸትና ፍጅት የተሞላብሽ ከተማ፣ ደስታ ያለሽ ከተማ ሆይ፣ በአንቺ ውስጥ የተገደሉት በሰይፍ የተገደሉ አይደሉም፣ በሰልፍም የሞቱ አይደሉም። **3** ገዢዎችሽ ሁሉ በአንድነት ሸሹ፣ ያለ ቀስትም ተማረኩ፤ ከሩቅ ሸሽተው ከአንቺ ዘንድ የተገኙት ሁሉ በአንድነት ታሰሩ። **4** ስለዚህም፣ "ወደ እኔ አትመልከቱ፣ መራራ ልቅሶ አለቅሳለሁ፤ ስለ ሕዝቤ ሴት ልጅ ጥፋት ታጽናኑኝ ዘንድ አትድከሙ" አልሁ። **5** ከሠራዊት ጌታ ከእግዚአብሔር ዘንድ የድንጋጤና የመረገጥ የድብልቅልቅም ቀን፣ የቅጥርም መፍረስ ወደ ተራራም መጮኽ በራእይ ሸለቆ ውስጥ ሆኖአል። **6** ኤላምም ከሰዎች ሠረገለኞችና ከፈረሰኞች ጋር ሆኖ አፎቱን ተሸከመ፣ ቂርም ጋሻውን ገለጠ። **7** መልካሞቹንም ሸለቆችሽን ሠረገሎች ሞሉባቸው፣ ፈረሰኞችም መቆሚያቸውን በበር ላይ አደረጉ። **8** የይሁዳንም መጋረጃ ገለጠ፤ በዚያም ቀን በዱር ቤት የነበረውን የጦር ዕቃ ተመለከትህ። **9** የዳዊትም ከተማ ፍራሾች እንደ በዙ አይታችኋል፣ የታችኛውንም ኩሬ ውኃ አከማችታችኋል። **10** የኢየሩሳሌምን ቤቶች ቈጥራችሁ ቅጥሩንም ለማጥናት ቤቶችን አፈረሳችሁ። **11** በአሮጌው ኩሬ ላለው ውኃ በሁለቱ ቅጥር መካከል መጠባበቂያ ማከማቻ ሠራችሁ፤ ይህን ያደረገውን ግን አልተመለከታችሁም፣ ቀድሞ የሠራውንም አላሰባችሁም። **12** በዚያም ቀን የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ወደ ልቅሶና ወደ ዋይታ ራስን ወደ መንጨትና ማቅንም ወደ መልበስ ጠራ። **13** ነገር ግን ተመልከቱ፣ ሐሜትና ደስታ በሬውንና በጉንም ማረድ፣ ሥጋንም መብላት፣ የወይን ጠጅንም መጠጣት ሆነዋል። እናንተ፣ ነገ እንሞታለንና እንብላ እንጠጣ ብላችኋል። **14** ይህም ነገር በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ጆሮ ተገለጠ፦ "እስክትሞቱ ድረስ ይህ በደል በእውነት አይሰረይላችሁም" ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር። **15** የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "በቤቱ ውስጥ ወደ ተሾመው ወደዚህ አዛዥ ወደ ሳምናስ ሂድ እንዲህም በለው፣ **16** "መቃብር በዚህ ያስወቀርህ ከፍ ባለው ስፍራ መቃብር ያሠራህ በድንጋይም ውስጥ ለራስህ መኖርያ ያሳነጽህ በዚህ ምን አለህ? በዚህስ በአንተ ዘንድ ማን አለ?" **17** እነሆ፣ እግዚአብሔር ወርውሮ ይጥልሃል፣ ኃያል ሰውም አጠንክሮ ይወረውርሃል፤ በኃይል ይጎትትሃል። **18** ጠቅልሎም ያንከባልልሃል ወደ ሰፊይቱም ምድር እንደ ኳስ ይጥልሃል። በዚያ ትሞታለህ በዚያም የክብርህ ሰረገላዎች ይሆናሉ። አንተ የጌታህ ቤት እፍረት ትሆናለህ! **19** ከአዛዥነትህና ከጣቢያ ሥራህ አሳድድሃለሁ። ከሹመትህም ትወርዳለህ። **20** በዚያም ቀን ባሪያዬን የኬልቅያስን ልጅ ኤልያቄምን እጠራለሁ፥ **21** መጐናጸፊያህንም አለብሰዋለሁ፣ በመታጠቂያህም አስታጥቀዋለሁ፣ ሹመትህንም በእጁ አሳልፌ እሰጠዋለሁ። በኢየሩሳሌምም ለሚኖሩ ለይሁዳም ቤት አባት ይሆናል። **22** የዳዊትንም ቤት መክፈቻ በጫንቃው ላይ አኖራለሁ፤ እርሱም ይከፍታል የሚዘጋም የለም እርሱም ይዘጋል የሚከፍትም የለም። **23** በአስተማማኝ ስፍራ እንደ ችንካር እተክለዋለሁ፣ ለአባቱም ቤት የክብር ዙፋን ይሆናል። **24** የአባቱንም ቤት ክብር ሁሉ ልጆቹንም የልጅ ልጆቹንም፣ ከጽዋ ዕቃ ጀምሮ እስከ ማድጋ ዕቃ ድረስ፣ ታናናሹን ዕቃ ሁሉ ይሰቅሉበታል። **25** በዚያ ቀን፣ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፣ በታመነው ስፍራ የተከለው ችንካር ይወልቃል፤ ተሰብሮም ይወድቃል፣ በእርሱም ላይ የተሰቀለው ሸክም ይጠፋል እግዚአብሔር ተናግሮአልና።

Isaiah 22:1

ንግር
‹‹ይህ ያህዌ የተናገረው ነው›› ወይም፣ ‹‹ይህ የያህዌ መልእክት ነው››

ስለ ራእይ ሸለቆ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ሸለቆ›› በሸለቆ ውስጥ የሚኖር ሕዝብን ማለት ኢየሩሌምን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በራእይ ሸለቆ ውስጥ ስለሚኖሩ ሰዎች›› ወይም፣ ‹‹በኢየሩሳሌም ስለሚኖሩ ሰዎች››

ሁላችሁም ወደ ቤቱ ሰገነት የወጣችሁበት ምክንያት ምንድነው?
ኢሳይያስ ጥያቄውን ያቀረበው በይሁዳ ሕዝብ ላይ ለማፌዝ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ወደ ቤታችሁ ሰገነት ወጥታችሁ እዚያ መቆም የለባችሁም››

ጫጫታ የሞላባት ከተማ
‹‹ግብዣ ላይ ያሉ ሰዎች ሁካታ››

የተገደሉብህ ሁሉም በሰይፍ አልተገደሉም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሕዝብህን የገደሉ የጠላት ወታደሮች አይደሉም››

በሰይፍ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ሰይፍ›› ጦርነት ላይ ያሉ ወታደሮችን ይወክላል።

Isaiah 22:3

ቀስት እንኳ ሳያነሡ ተይዘዋል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሌላው ቀርቶ ቀስት እንኳ ያልያዙ መሪዎችህን ጠላት ማርኮአቸዋል››

ሁሉም በአንድነት ተያዙ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጠላት ሁሉንም በአንድነት ያዛቸው››

ስለዚህ እንዲህ አልሁ
‹‹እኔ›› የሚለው የሚያመለክተው ኢሳይያስን ነው።

ስለ ሕዝቤ ሴት ልጅ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ሴት ልጅ›› የሚወክለው ሕዝቡን ሲሆን፣ ምናልባትም ኢሳይያስ ለእነርሱ ያለውን ፍቅር የሚያሳይ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ስለምወዳቸው ሕዝቤ›› ወይም፣ ‹‹ስለ ሕዝቤ››

Isaiah 22:5

ቀን አለው
‹‹ጊዜ ይኖረዋል››

የመጯጯህ፣ የመረገጥ፣ ከሰራዊት ጌታ ያህዌ ዘንድ የሆነ ግራ የመጋባት
‹‹የሰራዊት ጌታ ያህዌ ሽብር፣ መረገጥና ግራ መጋባት ሲያደርግ››

መረገጥ
ይህም ማለት፣ 1) የሚገሠግሡ ወታደሮችን ሊያመለክት ይችላል ወይም 2) ከሽብር የተነሣ ወዴት እንደሚሄዱ እንኳ ሳያውቁ የሚሮጡ ሰዎችን ሊያመለክት ይችላል።

በራእይ ሸለቆ ውስጥ
ይህ የሚያመለክተው ኢየሩሳሌምን ነው። ኢሳይያስ 22፥1 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

ወደ ተራሮች የሚጮኹ ሰዎች
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ተራሮች ላይ ያሉ ሰዎች ጩኸታቸውን ይሰማሉ›› ወይም 2) ‹‹የሕዝቡ ጩኸት ከተራሮች ያስተጋባል››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ኤላም የፍላጻ ሰገባ ወሰደች
ሰገባ ፍላጻዎች የሚያዙበት ኮሮጆ ሲሆን፣ የቀስተኛውን መሣሪያ ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የኤላም ሰዎች ቀስትና ፍላጻዎቻቸውን ወሰዱ››

ቂር ጋሻዋን አነገበች
እዚህ ላይ፣ ‹‹ቂር›› ወታደሮቹን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የቂር ወታደሮች ጋሻዎቻቸውን ከመያዣዎቻቸው ያወጣሉ››

ቂር
ቂር ሜዶን ውስጥ ያለች ከተማ ናት።

መልካሞቹ ሸለቆዎቻችሁ
እዚያ ላይ፣ ‹‹የእናንተ›› የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ይወክላል። ኢሳይያስ ከኢየሩሳሌም ነዋሪዎች አንዱ ስለሆነ ራሱንም ይጨምራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹መልካም ሸለቆዎቻችን››

Isaiah 22:8

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ሰራዊት የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ስለሚያጠቃበት ወደ ፊት ስላለው ጊዜ መናገሩን ቀጥሏል። የጎላፊ ጊዜ የወደ ፊት ጊዜ ተደርጐ መተርጐም ይችላል።

የይሁዳን መከላከያ ወሰደ
‹‹መከላከያ›› የሚለውን የነገር ስም ግሥ አድርጐ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ የይሁዳን ሕዝብ የከለለውን ማንኛውንም ነገር ወስዷል››

በዚያ ቀን የጦር መሣሪያ ተመለከትህ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ተመለከትህ›› የሚለው በአንዳች ነገር መተማመን ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለራስህ ለመከላከል መሣሪያ ታገኛለህ››

የዱር ቤተ መንግሥት
ይህ የጦር መሣሪያ የሚያከማቹበት በኢየሩሳሌም የነበረው ቤተ መቅደስ አካል የነበረ ቤት ነው።

በታችኛው ኩሬ ውሃ አጠራቀምህ
ጠላቶች ከተማቸውን ሲከቡ የሚጠጡት በቂ ውሃ እንዲያገኙ ሕዝቡ ውሃ ያጠራቅማሉ።

Isaiah 22:10

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ሰራዊት የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ስለሚያጠቃበት ወደ ፊት ስላለው ጊዜ መናገሩን ቀጥሏል።

ቤቶችን ቆጠርህ
እዚህ ላይ ‹‹ቆጠርህ›› ማለት የከተማዋን ቅጥር ለመሥሪያ የሚሆን ነገር ለማግኘት ቤቶችን ማሰስን ያመለክታል።

የውሃ ማከማቻ ሠራችሁ
‹‹ማጠራቀሚያ ቦታ ሠራችሁ››

በሁለቱ ቅጥሮች መካከል
ኢሳይያስ ስለ የትኞቹ ሁለት ቅጥሮች እየተናገረ እንደሆነ ግልጽ አይደለም። ዋናው በከተማዋ ቅጥር ማከማቻ መሥራታቸው ነው።

የከተማዋ ሠሪ
ይህ የሚያመለክተው ያህዌን ነው።

Isaiah 22:12

የሰራዊት ጌታ ያህዌ
ኢሳይያስ 1፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

ጠጉራችሁን እንድትላጩ
ይህ የልቅሶና የንስሐ ምልክት ነው።

እንብላ እንጠጣ፤ ነገ እንሞታለንና
እዚህ ላይ፣ ‹‹እንብላ እንጠጣ›› ድግስ ማድረግን፣ አለቅጥ መብላትንና ወይን ጠጅ መጠጣትን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እኛም የምንፈልገውን ያህል እየበላንና እየጠጣን አሁን ደስ ይበለን፤ ምክንያቱም በቅርቡ እንሞታለንና››

ይህን በጆሮዬ የገለጠ የሰራዊት ጌታ ያህዌ ነው
‹‹ጆሮ›› የኢሳይያስን ሁለንተና ይወክላል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ይህን የገለጠልኝ የሰራዊት ጌታ ያህዌ ነው››

ይህ ኀጢአት እስክትሞቱ ድረስ አይሰረይላችሁም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሌላው ቀርቶ በምትሞቱበት ቀን እንኳ ቢሆን፣ ያደረጋችሁትን ኀጢአት ይቅር አልላችሁም››

ስትሞቱ እንኳ
ይህም ማለት፣ 1) ከሞቱ በኃላ እንኳ ያህዌ ይቅር አይላቸውም ወይም 2) እስኪሞቱ ድረስ ያህዌ ይቅር አይላቸውም።

Isaiah 22:15

ሳምናስ
ይህ በኢየሩሳሌም ያለው የንጉሡ ቤተ መንግሥት መልእክተኛ ነው።

የቤቱን ጎላፊ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ቤቱ›› በንጉሡ ቤተ መንግሥት ያሉትን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በንጉሡ ቤተ መንግሥት ለሚሠሩት ሁሉ ጎላፊ የሆነው››

እዚህ ምን ታደርጋለህ የፈቀደልህስ ማን ነው... ዐለት ውስጥ?
ያህዌ ይህን የሚጠይቀው ሳምናስ ላይ ለማፌዝ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ዐለቱ ውስጥ... ምንም መብት የለህም!››

መቀበሪያ እንድትወቅር... መቃብር እንድትጠርብ... ማረፊያ ቦታ እንድትጠርብ
ሦስቱም ሐረጐች የሚያመለክቱት መቃብር መሥራትን ነው።

ከፍታዎች ላይ
እስራኤል ውስጥ ታላላቅ ሰዎች ከፍታ ቦታ ላይ መቃብር ይሠሩ ነበር።

Isaiah 22:17

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለሳምናስ የእግዚአብሔርን መልእክት መናገር ቀጥሏል።

አዙሮ አዙሮ እንደ ኳስ አጡዞ ወደ ሰፊ አገር ይወነጭፍሃል
የጠላት ወታደሮች መጥተው ሳምናስን በምርኮ ወደ ሌላ አገር መውሰዳቸው ያህዌ እንደ ኳስ ወደ ሌላ አገር እርሱን መወርወር ተደርጐ ተነግሯል።

ለጌታህ ቤት ማፈሪያ ትሆናለህ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ቤት›› ንጉሡ ቤተ መንግሥት ውስጥ የሚሠሩ ሰዎችን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጌታህ ቤተ መንግሥት ውስጥ ላሉት ሁሉ እፍረት ታመጣለህ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከማእረግህ አወርድሃለሁ፤ ከኀላፊነትህም ትባረራለህ ወደ ታች ትጐተታለህ
ያህዌ ሳምናስን ቤተ መንግሥት ውስጥ እንዳይሠራ ማድረጉ ያህዌ እርሱን ወደ መሬት መወርወሩ እንደሆነ ተነግሯል።

ወደ ታች ትጐተታለህ
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከክብር ቦታህ ወደ ታች አወርድሃለሁ››

Isaiah 22:20

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለሳምናስ የእግዚአብሔርን መልእክት መናገሩን ቀጥሏል።

በዚያ ቀን ይመጣል
‹‹ይህ በዚያ ቀን ይሆናል››

አልያቂም... ኬልቅያስ
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው

መጐናጸፊያህን አለብሰዋለሁ፤ መታጠቂያህንም አስታጥቀዋለሁ
ያህዌ ኤልያቂም ቤተ መንግሥት ውስጥ የሳምናስን ቦታ እንዲወስድ ማድረጉ ቤተ መንግሥት ውስጥ ሥልጣኑን የሚወክለውን የሳምናስን ልብስ ለአልያቂም ማልበስ እንደሆነ ተናግሯል።

መጐናጸፊያህን... መታጠቂያህን
እዚህ ላይ፣ መጐናጸፊያና መታጠቂያ ቤተ መንግሥት ውስጥ ሥልጣንን ያመለክታሉ።

መታጠቂያ
ይህ ሰዎች ወገባቸው ላይ ወይም ደረታቸው ላይ የሚያደርጉት የልብስ ዐይነት ነው። ኢሳይያስ 3፥20 ላይ እንዴት እንደ ተረጐመኸው ተመልከት።

በእጁ
‹‹እጅ›› ኀይልና ቁጥጥርን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለእርሱ››

እርሱ አባት ይሆናል
አልያቂም ለይሁዳ ሕዝብ ማሰቡና መጠንቀቁ እርሱ አባታቸው እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እርሱ እንደ አባት ይሆናል››

ለይሁዳ ቤት
እዚህ ላይ፣ ‹‹ቤት›› ሕዝብን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለይሁዳ ሕዝብ››

የዳዊትን ቤት መክፈቻ በትከሻው ላይ አደርጋለሁ... ማንም አይከፍትም
እዚህ ላይ ‹‹ቁልፍ›› የሚወክለው ሥልጣንን ነው። ማንም የማይከፍተው ወይም ማንም የማይዘጋው የቤተ መንግሥቱ መክፈቻ እንዳለው ሁሉ ይህም ኤልያቂም ማንም የማይቃወመው ሥልጣን እንዳለው ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ቤተ መንግሥቱ ውስጥ በሚሠሩት ላይ ኀላፊነት እሰጠዋለሁ፤ የሚያደርገውን ውሳኔ ማንም መቃወም አይችልም።››

Isaiah 22:23

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ቤተ መንግሥቱ ውስጥ ሳምናስን ስለሚተካው ኤልያቂም መናገሩን ቀጥሏል።

በአስተማማኝ ስፍራ እንደ ካስማ እተክለዋለሁ
ያህዌ ቤተ መንግሥቱ ውስጥ የኤልያቂምን ሥልጣን ጠንካራና አስተማማኝ ማድረጉ አልያቂም ካስማ እንደሆነ፣ ያህዌ ደግሞ ቤተ መንግሥቱ ቅጥር ውስጥ ጠንካራ ቦታ ላይ እንደሚተክለው ተነግሯል።

ለአባቱም ቤት የክብር ማኅተም ይሆናል
‹‹የክብር ማኅተም›› የክብርን ቦታ ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አልያቂም ለቤተ ሰቡ ክብር ያመጣል››

የአባቱ ቤት
‹‹ቤት›› የሚወክለው ቤተ ሰብን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የአባቱ ቤተ ሰብ›› ወይም፣ ‹‹የእርሱ ቤተ ሰብ››

የአባቱን ቤት ክብር ሁሉ እርሱ ላይ ይሰቅላሉ
ከአልያቂም የተነሣ ያህዌ መላው የአልያቂም ቤተ ሰብ እንዲከበር ማድረጉ አልያቂም ካስማ ቤተ ሰቡ ደግሞ እዚያ ካስማ ላይ የሚሰቀሉ ነገሮች እንደሆኑ ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከእርሱ የተነሣ ለቤተ ሰቡ ክብር ይሰጣሉ››

ከማሰሮ ጀምሮ እስከ ጋን ድረስ ያለ የቤት ዕቃ ሁሉ
ይህ እየተናገረ ያለው ስለ ኤልያቂም ካስማ ነው። ቤተ ሰቡ ካስማ ላይ እንደሚሰቀሉ ማስሮና ጋኖች ይሆናሉ። ይህም ከእርሱ የተነሣ ዘሮቹ ይከበራሉ ማለት ነው።

ከማሰሮ እስከ ጋን
ማሰሮ ውሃ የሚይዝ ትንሽ ዕቃ ነው፤ ጋን ውሃ የሚይዝ ትልቅ ዕቃ ነው።

Isaiah 22:25

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ያለፈው ቁጥር ቀጣይ ምስላዊ ገለጻ ነው። (ኢሳይያስ 22፥23-24 ይመ.)

በዚያ ቀን
‹‹በዚያ ጊዜ››

ይህ የሰራዊት ጌታ ያህዌ ቃል ነው
የተናገረውን እርግጠኝነት ለማመልከት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። ኢሳይያስ 14፥22 ላይ እንደ ተረጐምህ ተርጉመው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ይህ የሰራዊት ጌታ ያህዌ የተናገረው ነው›› ወይም፣ ‹‹ይህ የሰራዊት ጌታ የያህዌ ዐዋጅ ነው››

በአስተማማኝ ስፍራ የተተከለ ካስማ... ተሰብሮ ይወድቃል
ያህዌ ሳምናስ ቤተ መንግሥት ውስጥ የነበረውን ሥልጣን እንዲያጣ ማድረጉ ሳምናስ ግድግዳ ላይ እንዳለና ተሰብሮ እንደሚወድቅ ካስማ እንደሆነ ተነግሯል። ይህ አጽንዖት የሚሰጠው ሳምናስ ሥልጣኑ አስተማማኝ እንደ ሆነ ማሰቡንና እግዚአብሔር ግን ያንን የሚያስወግድ መሆኑን ነው።

የተሸከመውም ሸክም ወድቆ ይከሰከሳል
እዚህ ላይ፣ ‹‹ሸክም›› የሳምናስን ኀይልና ሥልጣን ይወክላል። ሳምናስን የሚወክለው ካስማ ላይ በተሰቀለ ነገር ተመስሎአል። ያህዌ ሳምናስ ኀይልና ሥልጣኑን እንዲያጣ ማድረጉ፣ ካስማው ላይ ተንጠልጥሎ የነበረው ዕቃ ወድቆ መስበር ማለት እንደሆነ ተነግሯል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 23

1 ስለ ጢሮስ የተነገረ ሸክም። የተርሴስ መርከቦች ሆይ፣ አልቅሱ፤ ፈርሶአልና ቤት የለም፣ መግቢያም የለም፤ ከኪቲም አገር ጀምሮ ተገልጦላቸዋል። **2** እናንተ በደሴት የምትኖሩ፣ በባሕርም የምትሻገሩ የሲዶና ነጋዴዎች፣ ወኪሎቻችሁ የሚያቀርቡላችሁ፣ ጸጥ በሉ። **3** የሺሖር ዘርና የዓባይ ወንዝ መከር በብዙ ውኖች ላይ ገቢዋ ነበረ፤ እርስዋም የአሕዛብ መናገጃ ነበረች። **4** እፈሪ፣ ሲዶና ሆይ፣ ባሕር ተናግሯልና፣ የባሕሩ ኃያል ተናግሯል። እንዲህ አለ፣ "አላማጥሁም፣ አልወለድሁምም፤ ጐበዛዝትንም አላሳደግሁም፤ ወጣት ሴቶችንም አላሳደግሁም" ብሎ ተናግሮአልና እፈሪ። **5** ወሬዋ ወደ ግብጽ በደረሰ ጊዜ፣ በጢሮስ ወሬ ስለ እርሷ ምጥ ይይዛቸዋል። **6** ወደ ተርሴስ ተሻገሩ፤ እናንተ በደሴት የምትኖሩ አልቅሱ። **7** ደስተኛዋ ከተማ፣ ከቀድሞ ዘመን ጀምሮ የነበርሽ፣ ይህ ደርሶብሻልን፣ እንግዳ በሆነ ስፍራዎች ለመኖር እግሮችዋ ወደ ሩቅ ያፈለሱአት የደስታችሁ ከተማ ይህች ናትን? **8** አክሊል ባስጫነች ከተማ ነጋዴዎችዋ ልዑላን በሆኑ፣ በእርስዋም የሚሸጡና የሚለውጡ የምድር ክቡራን የሆኑባት ጢሮስ ላይ ይህን የወጠነ ማን ነው? **9** የክብርን ሁሉ ትዕቢት ይሸር ዘንድ የምድርንም ክቡራን ሁሉ ያስንቅ ዘንድ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ወስኖታል። **10** የተርሴስ ልጅ ሆይ፣ የሚከለክልሽ የለምና እንደ ዓባይ ወንዝ በአገርሽ ላይ እረሺ። **11** እግዚአብሔር በባሕር ላይ እጁን ዘረጋ፣ መንግሥታትንም አናወጠ፤ ምሽጎችዋንም ያጠፉ ዘንድ እግዚአብሔር ስለ ከነዓን አገር አዘዘ። **12** እርሱም፣ "አንቺ የተበደልሽ የሲዶና ድንግል ልጅ ሆይ፣ ተነሺ፣ ከእንግዲህ ወዲህ በድጋሚ ደስ አይልሽም፤ ወደ ኪቲም ተሻገሪ፣ በዚያም ደግሞ አታርፊም አለ። **13** ተመልከቱ የከለዳውያን ሰዎች። ይህ ሕዝብ መኖሩ ይቆማል፤ አሦራውያን ለምድረ በዳ አራዊት ሰጥተውታል። የወረራ ግንቦቻቸውን ሠሩ፥ አዳራሾችዋንም አፈረሱ፣ የጥፋት ባድማም አደረጓት። **14** እናንተ የተርሴስ መርከቦች ሆይ፣ ምሽጋችሁ ፈርሶአልና ዋይ በሉ። **15** በዚያም ቀን፣ ጢሮስ እንደ ንጉሥ ቀናት ሁሉ ሰባ ዓመት ያህል የተረሳች ትሆናለች። ከሰባ ዓመት በኋላ ግን ለጢሮስ በጋለሞታ ዘፈን እንደሚሆን እንዲሁ ይሆናል። **16** አንቺ የተረሳሽ ጋለሞታ ሆይ፣ መሰንቆ ያዢ፣ በከተማ ላይም ዙሪ፤ መታሰቢያም ይሆንልሽ ዘንድ ዜማን አሳምሪ ዘፈንሽንም አብዢ። **17** ከሰባ ዓመትም በኋላ እግዚአብሔር ጢሮስን ይረዳታል፣ ወደ ተቀጠረችበት ትመለሳለች። ደግሞም በምድር ፊት ላይ ከሆኑ ከዓለም መንግሥታት ሁሉ ጋር ትገለሙታለች። **18** ንግድዋና ዋጋዋ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ይሆናል። ንግድዋም በልተው ይጠግቡ ዘንድ ማለፊያም ልብስ ይለብሱ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት ለሚኖሩ ይሆናል እንጂ በዕቃ ቤትና በግምጃ ቤት ውስጥ አይከተትም።

Isaiah 23:1

አጠቃላይ መረጃ
በ13፡1-23፡18 ኢሳይያስ እግዚአብሔር በሕዝቦች ላይ እንዴት እንደሚፈርድ መናገሩን ይቀጥላል።

ስለ ጢሮስ የተነገረ መግለጫ
"እግዚአብሔር ስለ ጢሮስ የተናገረው ይህ ነው'

የተርሴስ መርከቦች ሆይ አልቅሱ
በዚህ ስፍራ መርከቦች የሚለው በመርከቦች ላይ ያሉትን ሰዎች ይወክላል። ኢሳይያስ ሊሰሙት የሚችሉ ይመስል በተርሴስ መርከቦች ላይ ላሉ ሰዎች ይናገራል። አት፡- "እናንተ በተርሴስ መርከቦች ላይ ያላችሁ ሰዎች ተስፋ በመቁረጥ አልቅሱ' (ምትክ ስምና የ "የ' ምልክት ተመልከት)

ወደብ (ደሴት)
ቅርብ መሬትና ለመርከቦች ምቹ የሆነ የባሕር አካባቢ ነው።

ከኪቲም አገር ጀምሮ ተገልጦላቸዋል
ይህ ሀረግ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊተረጎም ይችላል። አት፡- "ሰዎቹ በኪቲም ምድር እያሉ ስለ ጢሮስ ሰሙ' (የስሞች አተረጓጎም መንገድ እና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

እናንተ በባሕር ዳር የምትኖሩ ጸጥ በሉ
ኢሳይያስ ሊሰሙት የሚችሉ ይመስል በባሕር ዳር ላይ ለሚኖሩ ሰዎች ይናገራል። (የ "የ' ምልክት ተመልከት)

ጸጥ በሉ
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። በዚህ ስፍራ ጸጥታ ማለት ድንጋጤንና መደነቅን ማመልከት ነው። አት፡- "ደንግጡ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ባሕር ዳር
"ባሕር ዳር' በባሕር ወይም በውቅያኖስ አቅራቢያ ወይም ዙሪያ የሚገኝ መሬት ነው። በዚህ ስፍራ ከሜዲትራኒያን ባሕር ጋር በሚዋሰነው በፊንቂያ የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታል።

በባሕር ላይ የሚጓዝ፣ የሲዶና ነጋዴ የሞላባችሁ
በዚህ ስፍራ "ነጋዴ' ማለት ብዙ "ነጋዴዎች' ማለት ነው። አት፡- "በባሕር ላይ የሚጓዙ፣ የሲዶና ነጋዴዎች ባለጸጋ አደረጓችሁ' (አጠቃላይ ስማዊ ሐረጎች)

የሺሖር ጥራጥሬ በብዙ ውኖች ላይ ነበር
ሺሖር በጥራጥሬ ምርቱ የሚታወቅ በግብጽ በዓባይ ወንዝ አቅራቢያ የሚገኝ ሸለቆ ስም ነው። አት፡- "በግብጽ ከሺሖር ጥራጥሬ ለማጓጓዝ በታላቅ ባሕር የሚጓዙ ሰዎች' (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)

የዓባይ መከር ምርቷ ነበር
"የዓባይ መከር' በዓባይ ወንዝ አቅራቢያ የሚመረትንና በወንዝ ላይ ወደ ፊንቄ የሚጓጓዝን ጥራጥሬ ያመለክታል። (ንብረት ተመልከት)

ምርቷ
"የእርሱ ምርት።' ወንዙ የእርሷ እንደሆነ ማመልከት የተለመደ ነበር።

የአሕዛብ መናገጃ ነበረች
ንግድ ነገሮችን የመግዛትና የመሸጥ እንቅስቃሴ ነው። በዚህ ስፍራ "አሕዛብ' የሚለው ሰዎቹን ይወክላል። አት፡- "አንተ ከሌሎች ሕዝቦች የሆኑ ሰዎች ነገሮችን ለመግዛትና ለመሸጥ በሚመጡበት ስፍራ ነበርክ።' (ምትክ ስም ተመልከት)

Isaiah 23:4

ወጣት ሴቶችን አላሳደግሁም... ሲል ባሕር፣ የባሕሩ ኃያል ተናግሮአል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) እግዚአብሔር የጢሮስን ከተማ፣ በከተማይቱ የሚኖሩ ሰዎችን በሚመለከት ልጆቿ እንደሆኑ አድርጋ እንደምትናገር እናት ይገልጻታል ወይም 2) እግዚአብሔር የሜዲትራንያን ባሕር እየተናገረ እንዳለ እየገለጸ ነው። የጢሮስ ሰዎች ባሕሩን አምላካቸውና አባታቸው አድርገው ይመለከቱ ነበር። በሁለቱም ትርጉሞች ተናጋሪው ልጆቹ ስለ ጠፉ ያለቅሳል። (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየትን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Isaiah 23:6

ወደ ተርሴስ ተሻገሩ
"ጉዞአችሁን ወደ ተርሴስ አድርጉ።' ተርሴስ፣ የጢሮስ ሰዎች ለንግድ ጉዞ የሚያደርጉባት ሩቅ ቦታ ነች። ከጢሮስ ላመለጡ ብቸኛ የድኅንነት ቦታ ነች።

በቀድሞ ዘመን ተመሥርታ የነበረችው፣ ... ደስተኛይቱ ከተማ፣ ይህ ደረሰባትን
እግዚአብሔር በጢሮስ ላይ ለመሳለቅ ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ አሳብ ገላጭ ጥያቄ በአሳብ ገላጭ አረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። አት፦ "ለመደለደል ... በጥንታዊቷ የጢሮስ ከተማ በሙሉ ደስታ የምትኖሩ በእርግጥ ይህ ይደርስባችኋል' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ደስተኛይቱ ከተማ
በዚህ ስፍራ "ከተማ' የሚለው ሕዝቡን ይወክላል። አት፦ "በጢሮስ ከተማ የሚኖር ደስተኛ ሕዝብ' (ምትክ ስም ተመልከት)

ለመደላደል እግሮችዋ ወደ ሩቅ ወደ እንግዳ ሥፍራዎች የወሰዷት
በዚህ ስፍራ "እግር' መላውን የሰው ማንነት ይወክላል። አት፦ "ለመኖርና ገንዘብ ለማትረፍ ወደ ሩቅ ስፍራዎች የሄዱ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

ወደ ሩቅ ... የወሰዷት
በዚህ ስፍራ "የወሰዷት' የሚለው የጢሮስን ሕዝብ የምትወክለውን የጢሮስን ከተማ ያመለክታል። (ምትክ ስም ተመልከት)

Isaiah 23:8

በጢሮስ ላይ ይህን ያቀደ ማነው? ... የምድር
ኢሳይያስ በጢሮስ ላይ ለመሳለቅ ይህን ጥያቄ ይጠቀማል። "ይህን' የሚለው ቃል ኢሳይያስ በ23፡1-7 የገለጸውን ጢሮስን ለማጥፋት የተዘጋጀውን የእግዚአብሔር እቅድ ያመለክታል። እንዲሁም ጢሮስ የሚለው በጢሮስ የሚነሩትን ሰዎች ያመለክታል። ይህ አሳብ ገላጭ ጥያቄ በአሳብ ገላጭ አረፍተ ነገርነት ሊተረጎም ይችላል። አት፦ "የጢሮስን ሰዎች ለማጥፋት ያቀደው እግዚአብሔር ነበር ... የምድር' (አሳብ ገላጭ ጥያቄና ምትክ ስም ተመልከት)

ዘውዶችን ሰጪ
በዚህ ስፍራ "ዘውድ' የሚለው አንድ ሰው እንደ ገዢ በሕዝብ ላይ ያለውን ሥልጣን ያመለክታል። አት፦ "በሌሎች ላይ እንዲገዙ ለሰዎች ሥልጣንን የሚሰጥ' (ምትክ ስም ተመልከት)

ነጋዴዎቿ ልዑላን ናቸው
ወደ ሌሎች አገሮች ሲሄዱ ምን ያህል ሥልጣን እንዳላቸው በአጽንዖት ለመናገር ነጋዴዎቹ ከልዑላን ጋር ተነጻጽረዋል። አት፦ "ነጋዴዎቿ እንደ ልዑላን ናቸው' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ነጋዴዎቿ ... የምድር ክቡራን ናቸው
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊተረጎም ይችላል። አት፦ "የምድር ሕዝቦች እጅግ ከፍተኛ ክብር የሚሰጡአቸው ነጋዴዎቿ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ክብሯን ሁሉና ትዕቢቷን ለማዋረድ
"በገዛ ራሳቸው ክብር ስለሚመኩ እነርሱን ለማዋረድ'

ትዕቢቷ ... ክብሯ ... ክቡራኖቿ
በዚህ ስፍራ እርሷ የሚለው በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች የምትወክለውን የጢሮስን ከተማ ያመለክታል። አት፦ "ትዕቢታቸው ... ክብራቸው ... ክቡራኖቻቸው' (ምትክ ስም ተመልከት)

Isaiah 23:10

የተርሴስ ሴት ልጅ፣ ሰው አባይን እንደሚያርስ፣ መሬትሽን አረሺ። ከእንዲህ ወዲያ በጢሮስ የገበያ ስፍራ አይኖርም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) ከእንግዲህ ወዲያ ከጢሮስ ጋር መነገድ ስለማይችሉ የተርሴስ ሰዎች እህል መዝራት እንዲጀምሩ ኢሳይያስ እየነገራቸው ነው ወይም 2) የተርሴስ ሰዎች ከጢሮስ ቁጥጥር ነፃ መሆናቸውን ኢሳይያስ እየነገራቸው ነው። አት፦ የተርሴስ ልጅ ሆይ፣ እንደ ወንዝ በአገርሽ ያልፋል። የጢሮስ ሰዎች ከእንግዲህ ወዲያ ምንም ሥልጣን አይኖራቸውም። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

የተርሴስ ሴት ልጅ
የከተማይቱ ሴት ልጅ የከተማይቱን ሰዎች ትወክላለች። አት፦ "የተርሴስ ሕዝብ' ወይም "በተርሴስ የሚኖሩ ሰዎች' (ምትክ ስም ተመልከት)

እግዚአብሔር በባሕር ላይ እጁን ዘረጋ፣ መንግሥታትን አናወጠ
ባሕርንና የኃያል መንግሥታን ሕዝቦች ለመቆጣጠር እግዚአብሔር ኃይሉን መጠቀሙ እግዚአብሔር እጅን እንደሚዘረጋና መንግሥታትን እንደሚያናውጥ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በባሕር ላይ እጁን ዘረጋ
በዚህ ስፍራ እጅ የእግዚአብሔርን ኃይልና ቁጥጥር ያመለክታል። አት፦ "በባሕር ላይ ኃይሉን አሳየ' (ምትክ ስም ተመልከት)

የተጨቆንሽ የሲዶና ድንግል ሴት ልጅ ሆይ
በዚህ ስፍራ ድንግል ሴት ልጅ የሲዶናን ሕዝብ ያመለክታል። አት፦ "የሲዶና ሕዝብ ሆይ፣ ሌላ ሕዝብ ስለሚጨቆናችሁ' (ምትክ ስም ተመልከት)

Isaiah 23:13

የከለዳውያንን አገር ተመልከቱ
ከለዳውያን በዚህ ስፍራ የባቢሎናውያን ሌላ ስም ነው። አት፦ "በባሎናውያን አገር ምን እንደሆነ ተመልከቱ' ወይም "በባቢሎን ምን እንደሆነ ተመልከቱ'

ከባቢ ግንቦች
በከተማ ግንቦች ላይ በመሆን ለማጥቃት ወታደሮች ግንቦችን ወይም የጭቃ መወጣጫዎችን ይገነባሉ።

እናንተ የተርሴስ መርከቦች አልቅሱ
በዚህ ስፍራ መርከቦች የሚለው በመርከብ ላይ ያሉትን ሰዎች ይወክላል። ይህንን በኢሳይያስ 23፡1 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። (ምትክ ስም ተመልከት)

ምሽጋችሁ ፈርሷልና
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "ጠላቶች ምሽጋችሁን አፍርሰዋልና' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

Isaiah 23:15

በዚያ ቀን
"በዚያ ጊዜ' ወይም "በመቀጠል'

ጢሮስ ለሰባ ዓመት የተረሳች ትሆናለች
ከእንግዲህ ወዲያ ለመግዛትና ለመሸጥ ሕዝቡ ወደ ጢሮስ የማይሄድ እስከሆነ ድረስ፣ ከተማይቱን የመርሳት ያህል ነው። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "ለሰባ ዓመታት ሕዝቡ ጢሮስን የመርሳት ያህል ይዘነጋታል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልክት)

ለሰባ ዓመታት
"ለ70 ዓመታት' (ቁጥሮች ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንደ አንድ ንጉሥ ዘመን
"እንደ አንድ ንጉሥ ዓመታት' ወይም "አንድ ንጉሥ የሚኖርበትን ያህል'

በጋለሞታ ዘፈን እንደሚሆን እንዲሁ ይሆናል
ይህ የጢሮስ ሰዎች ጋለሞታ እንደነበሩ አይነት መስሎ ይናገራል። ታዋቂነቷን ያጣች ጋለሞታ የቀድሞ ፍቅረኞቿን እንደገና ለማግኘት በየመንገዱ እንደምተዘፍን፣ የጢሮስ ሰዎች እንደገና ባላጸጎችና ኃያላን ይሆኑ ዘንድ ንግዱን ለማስቀጠል ከሌሎች ሕዝቦች ወደ እነርሱ የሚመለሱ ሰዎችን ለማግኘት የጢሮስ ሰዎች ጥረት ያደርጋሉ። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ትታወሺ ዘንድ
ይህ በአደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ሰዎች ያስታውሱሽ ዘንድ' ወይም "ሰዎች ወደ አንቺ ይመለሱ ዘንድ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

Isaiah 23:17

በኋላም እንዲህ ይሆናል
አንድ አስፈላጊ ሁኔታ ሊሆን እንዳለ ለማመልከት ይህ ሐረግ በዚህ ስፍራ ጥቅም ላይ ውሏል። ቋንቋህ ይህን የሚያደርገበት መንገድ ካለው በዚህ ስፍራ ልትጠቀምበት ትችላለህ።

ሰባ ዓመታት
"70 ዓመታት' (ቁጥሮች ተመልከት)

እግዚአብሔር ጢሮስን ይጎበኛታል
በዚህ ስፍራ ጢሮስ የሚለው በጢሮስ የሚኖረውን ሕዝብ ይወክላል። አት፡- "እግዚአብሔር በጢሮስ የሚኖረውን ሕዝብ ይጎበኛል' (ምትክ ቃል ተመልከት)

ከምድር ... የግልሙትናን ሥራ በመሥራት እንደገና ገንዘብ ማትረፍ ትጀምራለች
ኢሳይያስ የጢሮስን ሕዝብ ከጋለሞታ ጋር ያመሳስላል። ጋለሞታ ለገንዘብ ስትል ለማንኛውም ወንድ ራሷን እንደምትሸጥ እንደዚያው የጢሮስም ሕዝብ ከ(ለ)ሁሉም መንግሥታት ይገዛሉ ይሸጣሉ። አት፡- እንደጋለሞታም ከምድር መንግሥታት ሁሉ ጋር ይገዛሉ ይሸጣሉም። (ምትክ ቃል ተመልከት)

በግምጃ ቤት አይከማችም ወይም አይጠበቅም
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ነጋዴዎቹ ገንዘባቸውን ሰውረው አያከማቹም' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

በእግዚአብሔር ፊት ለሚኖሩ
"እግዚአብሔርን ለሚታዘዙና ለሚያገለግሉ'

የተትረፈረፈ ምግብ ለእነርሱ ለማቅረብ
"የሚመገቡት በቂ ምግብ ይኖራቸው ዘንድ'

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 24

1 ተመልከቱ፣ እግዚአብሔር ምድርን ባዶ ያደርጋታል፣ ባድማም ያደርጋታል፣ ይገለብጣትማል፣ በእርስዋም የሚኖሩትን ይበትናል። **2** እንደ ሕዝቡም እንዲሁ ካህኑ፣ እንደ ባሪያውም እንዲሁ ጌታው፣ እንደ ባሪያይቱም እንዲሁ እመቤትዋ፣ እንደሚገዛም እንዲሁ የሚሸጠው፣ እንደ አበዳሪውም እንዲሁ ተበዳሪው፣ እንደ ዕዳ አስከፋዩም እንዲሁ ዕዳ ከፋዩ ይሆናል። **3** ምድር ፈጽሞ ትጠፋለች፣ ፈጽማም ትበላሻለች፤ እግዚአብሔር ይህን ቃል ተናግሮአልና። **4** ምድር ደረቀች ረገፈችም፤ ዓለም ተናወጠች ረገፈችም፤ የምድርም ስመ-ጥር ሕዝብ ደከሙ። **5** ሕጉን ተላልፈዋልና፣ ሥርዓቱንም ለውጠዋልና፣ የዘላለሙንም ቃል ኪዳን አፍርሰዋልና፣ ምድርም ከሚቀመጡባት በታች ረክሳለች። **6** ስለዚህ መርገም ምድርን ትበላለች፣ የሚኖሩባትም ጥፋተኞች ይሆናሉ። ስለዚህ የምድር ነዋሪዎች ይቃጠላሉ፣ ጥቂት ሰዎችም ይቀራሉ። **7** አዲስ የወይን ጠጅ ይደርቃል፣ የወይን ንግድ ደከመች፣ ልባቸው ደስ ያለው ሁሉ ተከዙ። **8** የከበሮው ደስታ ቆሟል፣ የደስተኞች ድምፅ ዝም ብሎአል፣ የመሰንቆ ደስታ ቀርቶአል። **9** እየዘፈኑም የወይን ጠጅን አይጠጡትም፣ የሚያሰክርም መጠጥ ለሚጠጡት መራራ ይሆናል። **10** የተቃወሰችው ከተማ ፈረሰች፤ ቤት ሁሉ ተዘግቶ ባዶ ሆነ። **11** ስለ ወይኑም ጠጅ በአደባባይ ለቅሶ ይሆናል፤ ደስታ ሁሉ ጨልሞአል፥ የምድርም ደስታ ጠፍቷል። **12** ከተማይቱም ባድማ ሆናለች፣ በርዋም በጥፋት ተመትቶአል። **13** የወይራን ዛፍ እንደ መምታት፣ ከወይንም መከር በኋላ ቃርሚያውን እንደ መልቀም፣ እንዲሁ በምድር መካከል በአሕዛብም መካከል ይሆናል። **14** እነዚህ ድምፃቸውን አሰምተው እልል ይላሉ፣ ስለ እግዚአብሔር ክብርም ከባሕር በደስታ ይጮኻሉ። **15** ስለዚህ እግዚአብሔርን በምሥራቅ፣ የእስራኤልንም አምላክ የእግዚአብሔርንም ስም በባሕር ደሴቶች አክብሩ። **16** "ለጻድቁ ክብር ይሁን!" የሚለውን ዝማሬ ከምድር ዳርቻ ሰምተናል። እኔ ግን፣ "ባከንሁ፣ ባከንሁ፣ ወዮልኝ! ወንጀለኞች ወንጀለዋል፤ አዎን፣ ወንጀለኞች እጅግ ወንጀለዋል" አልሁ። **17** በምድር ላይ የምትኖር ሆይ፣ ፍርሃትና ገደል ወጥመድም በአንተ ላይ አሉ። **18** ከፍርሃት ድምፅ የሸሸ፣ በገደል ይወድቃል፤ ከገደልም የወጣ በወጥመድ ይያዛል። የሰማይ መስኮቶች ተከፍተዋል፣ የምድርም መሠረት ተናውጣለች። **19** ምድር ፈጽሞ ትሰባበራለች፣ ምድር ፈጽማ ደቀቀች፤ ምድር በኃይል ትነዋወጣለች። **20** ምድር እንደ ሰካራም ሰው ትንገዳገዳለች፣ እንደ ዳስም ትወዛወዛለች። መተላለፍዋ ይከብድባታል፣ ትወድቃለች ደግማም አትነሣም። **21** በዚያም ቀን እንደዚህ ይሆናል፤ እግዚአብሔር በከፍታ ያለውን ሠራዊት በከፍታ ላይ፣ በምድርም ያሉትን ነገሥታት በምድር ላይ ይቀጣቸዋል። **22** ግዞተኞች በጕድጓድ እንደሚከማቹ በአንድነት ይከማቻሉ፣ በግዞት ቤትም ውስጥ ተዘግተው ይኖራሉ፣ ከብዙ ቀንም በኋላ ይፈረድባቸዋል። **23** ከዚያም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርም በጽዮን ተራራና በኢየሩሳሌም ላይ ይነግሣልና፣ በሽማግሌዎቹም ፊት ክብር ይሆናልና ጨረቃ ያፍራል፣ ፀሐይም ይዋረዳል።

Isaiah 24:1

ምድርን ባዶ ለማድረግ
"ምድርን ባድማ ለማድረግ' ወይም "በምድር ያለውን ነገር ሁሉ ለማጥፋት'

እነሆ
ይህ ቃል አስፈላጊ ሁናቴን ያመላክታል። ቋንቋህ ይህን የሚያደርግበት መንገድ ካለው፣ በዚህ ስፍራ ለመጠቀም ልታጤነው ትችላለህ።

እንደ ... እንዲሁ
እግዚአብሔር ሊያደርገው ያለው ነገር አልተገለጸም፣ ነገር ግን ይታወቃል። ይህ እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ በተመሳሳይ መንገድ እንደሚመለከት ያሳያል። አት፡- "እግዚአብሔር እንደሚበትን ... እንዲሁ ይበትናል' (መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉ)

ካህኑ ... አራጣ ተቀባዩ
ኢሳይያስ በ24፡2 የተወሰኑ የሕዝቡን የመደብ ክፍሎች ይዘረዝራል። በዩዲቢ እንደሚገኘው በብዙ ቁጥር ስሞች ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ካህናቱ ... አራጣ ተቀባዮቹ' (አጠቃላይ ስማዊ ሐረጎች)

አራጣ ተቀባዩ
"ገንዘብ ያበድረው።' አራጣ ማለት አንድ ሰው ገንዘብ ስለተበደረ ሊከፍለው የሚገባ ተጨማሪ ገንዘብ ማለት ነው።

አራጣ ከፋዩ
"ገንዘብ የተበደረው'

Isaiah 24:3

ምድር ፈጽማ ትጠፋለች፣ ትገፈፋለችም
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር ምድርን ፈጽሞ ያጠፋታል፣ የከበረውንም ነገር ሁሉ ያስወግዳል።' (አጓዳኝነት ተመልከት)

እግዚአብሔር ይህን ቃል ተናግሮአል
"እግዚአብሔር ይህን አደርጋለሁ አለ'

ምድር ደረቀች ጠወለገችም፣ ዓለም ደረቀች ከሰመችም
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሃረጎች ተመሣሣይ ነገር ይናገራሉ። አት፡- በምድር ያለ ነገር ሁሉ ይደርቃል ይሞታልም (አጓዳኝነት ተመልከት)

ምድር ... ዓለም
ሁለቱም በምድር ላይ ያለውን ነገር ሁሉ ይወክላሉ። (ምትክ ስም ተመልከት)

ምድር በነዋሪዎቿ ረክሳለች
ሕዝቡ ኃጢአት መሥራታቸውና ምድር በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዳይኖራት ማድረጋቸው ሕዝቡ ምድርን በተጨባጭ እንድትቆሽሽ እንዳደረጓት ተደርጎ ተነግሮአል። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ሕዝቡ ምድርን አረከሷት' (ስዕላዊ ንግግር፣ አደራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ሕግጋቱን ጥሰዋል፣ ሥርዓቱን ተላልፈዋል፣ የዘላለሙንም ኪዳን አፍርሰዋል
የእግዚአብሔርን ሕግጋትና ሥርዓት አልታዘዙም፣ የእግዚአብሔርንም ዘላለማዊ ኪዳን አፍርሰዋል

Isaiah 24:6

አጠቃላይ መረጃዎች
ኢሳይያስ እግዚአብሔር በምድር ላይ በሚፈርደበት ጊዜ የሚሆነውን የወደፊቱን ጊዜ መግለጹን ቀጠለ። አንዳንድ ጊዜ ነቢያት የወደፊቱን ጊዜ ሁኔታ ባላፊ ወይም በአሁን ጊዜ እንደሆነ ነገር አድርገው ይገልጻሉ። ይህ ሁኔታው በእርግጥ እንደሚፈጸም አጽንዖት ይሰጣል። (ትንቢታዊ አላፊ ጊዜ ተመልከት)

እርግማን ምድርን ትበላለች
የእግዚአብሔር ምድርን መርገምና ማጥፋት ምድርን ፈጽሞ እንደሚበላ የዱር አውሬ ወይም ምድርን ፈጽሞ እንደሚያቃጥል እሳት ዓይነት እንደሆነ እንደ መርገም ተደርጎ ተነግሮአል። (ሥዕላዊ ንግግር ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ነዋሪዎቿ በደለኞች ሆነው ተገኝተዋል
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እግዘአብሔር ሕዘቡ በደለኛ መሆኑን ያስታውቃል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

Isaiah 24:8

አጠቃላይ መረጃዎች፡-
ኢሳይያስ እግዚአብሔር በምድር ላይ በሚፈርደበት ጊዜ የሚሆነውን የወደፊቱን ጊዜ መግለጹን ቀጠለ። አንዳንድ ጊዜ ነቢያት የወደፊቱን ጊዜ ሁኔታ ባላፊ ወይም በአሁን ጊዜ እንደሆነ ነገር አድርገው ይገልጻሉ። ይህ ሁኔታው በእርግጥ እንደሚፈጸም አጽንዖት ይሰጣል። (ትንቢታዊ አላፊ ጊዜ ተመልከት)

ከበሮ ... መሰንቆ
እንዚህ የሙዚቃ መሣሪያዎች ናቸው። እነዘህን በኢሳይያስ 5፡12 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

Isaiah 24:10

አጠቃላይ መረጃዎች፡-
ኢሳይያስ እግዚአብሔር በምድር ላይ በሚፈርደበት ጊዜ የሚሆነውን የወደፊቱን ጊዜ መግለጹን ቀጠለ። አንዳንድ ጊዜ ነቢያት የወደፊቱን ጊዜ ሁኔታ ባላፊ ወይም በአሁን ጊዜ እንደሆነ ነገር አድርገው ይገልጻሉ። ይህ ሁኔታው በእርግጥ እንደሚፈጸም አጽንዖት ይሰጣል። (ትንቢታዊ አላፊ ጊዜ ተመልከት)

የትርምስዋ ከተማ ፈረሰች
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊተረጎም ይችላል። አት፡- "የትርምስዋን ከተማ እግዚአብሔር ያፈርሳታል።' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

የትርምስዋ ከተማ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ጌታ እርሷን ከማፈርሱ በፊት ከተማይቱ በትርምስ ውስጥ ነበረች፤ ሕዝቡ እግዚአብሔርን አይታዘዙም ነበር፣ መንግሥቱ ምግባረ ብልሹ ነበር፣ ከተማይቱም በመጠጣትና በጭፈራ ተሞልታ ነበር ወይም 2) እግዚአብሔር ካፈረሳት በኋላ ከተማይቱ ትርምስ ውስጥ ገብታለች። በአንድ ወቅት ጠንካራና ረጃጅም ሆነው የተገነቡት ቅጥሮችና ሕንፃዎች አሁን መሬት ላይ ፍርስራሽ ሆነዋል። በሁለቱም ትርጉሞች አንዲት ከተማ ማለት አይደለም። በአጠቃላይ ከተሞችን ያመለክታል።

ቤት ሁሉ ዝግና ባዶ ነው
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊተረጎም ይችላል። አት፡- "ሕዝቡ ቤቶቻቸውን ይዘጋሉ ባዷቸውንም ይተውአቸዋል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ስለ ወይን ጠጁ
"ወይን ጠጅ ስለሌለ'

ደስታ ሁሉ ጨልሞአል፣ የምድሪቱም ሐሴት ጠፍቶአል
የእነዚህ ሁለት ሃረጎች ትርጉም በመሠረቱ አንድ ነው። አት፡- "ደስታ ሁሉ ከምድር ይጠፋል' (አጓዳኝነት ተመልከት)

የምድረቱ ሐሴት
በዚህ ስፍራ "ምድር' የምድርን ሕዝብ ይወክላል። (ምትክ ቃል ተመልከት)

Isaiah 24:12

አጠቃላይ መረጃዎች፡-
ኢሳይያስ እግዚአብሔር በምድር ላይ በሚፈርደበት ጊዜ የሚሆነውን የወደፊቱን ጊዜ መግለጹን ቀጠለ። አንዳንድ ጊዜ ነቢያት የወደፊቱን ጊዜ ሁኔታ ባላፊ ወይም በአሁን ጊዜ እንደሆነ ነገር አድርገው ይገልጻሉ። ይህ ሁኔታው በእርግጥ እንደሚፈጸም አጽንዖት ይሰጣል። (ትንቢታዊ አላፊ ጊዜ ተመልከት)

ከተማይቱም ባድማ ሆናለች
ባድማ የሚለው የነገር ስም ሰው የማይኖርበት ወይም ባዶ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ከተማይቱ ሰው የማይኖርባት ሆነች' ወይም "ከተማይቱ ባዶዋን ቀረች' (የነገር ስም ተመልከት)

ከተማይቱ
ይህ የተወሰነ አንድ ከተማን ሳይሆን ከተሞችን በአጠቃላይ ነው። (አጠቃላይ ስማዊ ሐረጎች ተመልከት)

የወይራን ዛፍ እንደ መምታት፣ ከወይንም መከር በኋላ ቃርሚያውን እንደ መልቀም
ይህ እግዚአብሔር ምድሪቱን ካጠፋት በኋላ፣ ሕዝቡን ፍሬያቸው ከተለቀመ ዛፎችና የወይን ተክሎች ጋር ያስተያያል። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 24:14

ድምፃቸውን ያነሣሉ፣ ስለ እግዚአብሔርም ክብር ይጮኻሉ
ድምፃቸውን ያነሣሉ የሚለው ሃረግ ድምፅን ከፍ አድርጎ መናገር የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፡- "ለእግዚአብሔር ክብር ይዘምራሉ ይጮኻሉም' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

... ያነሣሉ ... ይጮኻሉ
በዚህ ስፍራ ... ያነሣሉ ... ይጮኻሉ የሚለው እግዚአብሔር ምድርን ካጠፋት በኋላ ገና በሕይወት ያሉትን ያመለክታል።

በደስታ ከባሕር ይጮኻሉ
በዚህ ስፍራ "ባሕር' የሚለው ከእስራኤል በምዕራብ የሚገኘውን የሜዲትራንየንን ባሕር ያመለክታል። አት፡- "በምዕራብም ወደ ባሕሩ ሲል የሚኖሩ በደስታ ይጮኻሉ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ስለዚህ በምሥራቅ እግዚአብሔርን አክብሩ
በምሥራቅ የሚለው ሃረግ ከእስራኤል በስተ—ምሥራቅ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላል። ኢሳይያስ እነዚህ ሕዝቦች ከእርሱ ጋር እንዳሉ አድርጎ ያዝዛቸዋል። ነገር ግን የሚናገረው እግዚአብሔር ምድሪቱን ካጠፋ በኋላ ወደፊት ለሚኖሩት ሰዎች ነው። አት፡- "ስለዚህ በስተ ምሥራቅ በሩቅ ምድር የሚኖሩ ሁሉ እግዚአብሔርን ያክብሩ' (ምትክ ቃል፣በስፍራው ለሌለ ወይም እንደ ሰው ለተወሰደ ግዑዝ ነገር መናገርና ትንቢታዊ አላፊ ጊዜ ተመልከት)

በባሕር ደሴቶች ክብር ስጡ
ኢሳይያስ በሜዲትራንየን ደሴቶች ላይ የሚኖሩትን ሰዎች ከእርሱ ጋር እንዳሉ አድርጎ ያዝዛቸዋል። ነገር ግን የሚናገረው እግዚአብሔር ምድሪቱን ካጠፋ በኋላ ለሚኖሩት ሰዎች ነው። አት፡- "በደሴቶች የምትኖሩ ሁሉ ክብር ስጡ' (ምትክ ቃል፣በስፍራው ለሌለ ወይም እንደ ሰው ለተወሰደ ግዑዝ ነገር መናገርና ትንቢታዊ አላፊ ጊዜ ተመልከት)

ለእግዚአብሔር ስም
በዚህ ስፍራ ስም እግዚአብሔርን ይወክላል። አት፡- "ለእግዚአብሔር' (ምትክ ቃል ተመልከት)

Isaiah 24:16

ሰምተናል
በዚህ ስፍራ ሰምተናል የሚለው ኢሳይያስንና የእስራኤል ሕዝብን ያመለክታል። ኢሳይያስ ወደ ፊት ሊሆን ያለን ነገር ገና ቀድሞ እንደ ተፈጸመ አድርጉ ይገልጻል። አት፡- "እንሰማለን' (አካታች "እኛ' ና ትንቢታዊ አላፊ ጊዜ ተመልከት)

እኔ ግን ከሳሁ፣ ከሳሁ
ኢሳይያስ ለሐዘኑ አጽንዖት ለመስጠት ይህን ሃረግ ይደጋግማል። አት፡- "በእርግጥ፣ ያታለሉ አሁንም ሌሎችን እያታለሉ ናቸው' ወይም "በእርግጥ አታላዮች እያታለሉ ናቸው' (አጓዳኝነት ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Isaiah 24:17

በምድር ላይ የምትኖሩ ሆይ፣ ፍርሃት፣ ገደልና ወጥመድም በእናንተ ላይ ነው
"በምድር ላይ የምትኖሩ ሰዎች ፍርሃት፣ ገደልና ወጥመድ ይገጥማችኋል'

ከገደል .. በወጥመድ ይያዛል
በዚህ ስፍራ ገደልና ወጥመድ የሚሉት ሕዝቡ ላይ ሊሆኑ ያሉትን የተለያዩ ክፉ ነገሮች ይወክላሉ። ሰዎች አንድን ክፉ ነገር ለማምለጥ ይሸሻሉ ነገር ግን ሌላ ክፉ ነገር ይገጥማቸዋል። (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

የሸብር ድምጽ
"አስፈሪ ድምጽ'

በወጥመድ ይያዛል
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ወጥመዱ ይይዘዋል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

የሰማይ መስኮቶች ይከፈታሉ
ይህ እግዚአብሔር የሰማይ መስኮትን እንደሚከፍትና በእርሱ አማካይነት ውኃ እንዲፈስስ እንደሚያደርግ ዓይነት ብዙ መጠን ያለው ዝንብ ከሰማይ እንደሚወርድ ይናገራል። አት፡- "ሰማይ ይከፈታል የዝናብም ዶፍ ይወርዳል' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የምድር መሠረቶችም ይናወጣሉ
በተለምዶ "መሠረት' የሚለው ቃል ከሥር ሆኖ ለአንድ ሕንፃ ድጋፍ የሚሰጥን የድንጋይ ክፍል (መዋቅር) ያመለክታል። በዚህም ስፍራ ምድርን በቦታዋ ደግፎ ወይም ይዞ እንዳቆመ ይታሰብ የነበረን ተመሣሣይ መዋቅር ይገልፃል። ኢሳይያስ ምድርን ደግፎ የያዛት መዋቅር እንኳን ይናወጣል ይላል። አት፡- "በጣም በሚያስፈራ ሁኔታ ምድር ትናወጣለች' ወይም "በጣም የሚያስፈራ የምድር መንቀጥቀጥ ይሆናል'

Isaiah 24:19

ምድር ፈጽሞ ተሰባበረች፣ምድር ፈራረሰች፤ ምድር በኃይል ተነዋወጠች
እነዚህ የተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሃረጎች በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጹ ይችላሉ። አት፡- "ምድር ትሰበባረለች ትለያያለችም፤ ምድር በኃይል ትናወጣለች' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ምድር እንደ ሰካር ሰው ትንገደገዳለች፣ እንደ ዳስም ትወዘወዛለች
ይህ ዘይቤአዊ ንግግር ምድር እንዴት ወደ ፊት ወደ ኋላ እንደ ምትናወጥ አጽንዖት ይሰጣል። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

መተላለፍዋ ይከብድባታል፣ ትወድቅማለች ደግሞም አትነሣም
ይህ ምድር ሰው እንደሆነች መተላለፍዋም ከባድ እቃ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። ሰውዬው ከባድ ሸክም ለመሸከም ይጥራል ነገር ግን ክብደቱ ሰውዬው እንዲወድቅና ዳግመኛ መነሣት እንዳይችል ያደርገዋል። በዚህ ስፍራ ምድር ከኃጢአታቸው የተነሣ እግዚአብሔር ምድርን እንዲያጠፋት ያደረጉትን የምድርን ሕዝብ ትወክላለች። አት፡- "የሕዝቡ ኃጢአት ብዙ ነው ስለዚህም እግዚአብሔር ምድርን ያጠፋታል፣ ምድርም የወደቀና ዳግመኛ መነሣት ያልቻለን ሰው ትመስላለች።' (ስዕላዊ ንግግርና ምትክ ስም ተመልከት)

Isaiah 24:21

በዚያም ቀን
"በዚያን ጊዜ'

የሰማይ ሠራዊት
ሠራዊት ሲል የጦር ሠራዊት ነው። በዚህ ስፍራ "የሰማይ ሠራዊት' የሚለው በሰማይ የሚገኙትን ብዙዎች ኃያላን መናፍስት ያመለክታል። ክፉዎች እንደሆኑ በግልጽ ሊቀመጥ ይችላል። አት፡- "ኃያላን አካላት' ወይም "ክፉ መንፈሳዊያን አካላት' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

በሰማያት
"በሰማይ

ግዞተኞች በጉድጓድ እንደሚከማቹ በአንድነት ይከማቻሉ
በዚህ ስፍራ "ጉድጓድ' የሚለው በወህኒ ቤት የሚገኝን ጨለማ ክፍል ወይም ጉድጓድ ያሳያል። አት፡- እግዚአብሔር እንደ እስረኞቹ በአንድ ላይ ይሰበስባቸዋል በወህኒውም አንደኛው ክፍል ይቆልፍባቸዋል። (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ይቀጣሉ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር ይቀጣቸዋል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ጨረቃ ያፍራል፣ ፀሐይም ይዋረዳል
ጨረቃና ፀሐይ ታላቅ ኃይል ካለው ሰው ፊት ከመሆኑ የተነሳ እንዳፈረ ሰው ተደርገው ተገልጸዋል። እግዚአብሔር ባለበት የጨረቃና የፀሐይ ብርሃን ይደበዝዛል። (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየት ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 25

1 እግዚአብሔር፣ አንተ አምላኬ ነህ፤ ድንቅን ነገር፣ ከጥንት የታቀዱትን በፍጹም ታማኝነት አድርገሃልና ከፍ ከፍ አደርግሃለሁ፤ ስምህንም አመሰግናለሁ። **2** ከተማይቱን የድንጋይ ክምር፣ የተመሸገችውን ከተማ ውድማ እንድትሆን፣ የጎጥአንንም አዳራሽ ከተማ እንዳትሆን አድርገሃል፤ ከቶ አትሠራም። **3** ስለዚህ ኃያላኑ ወገኖች ያከብሩሃል፤ የጨካኞች አሕዛብ ከተማም ትፈራሃለች። **4** የጨካኞችም ቍጣ እስትንፋስ ቅጥርን እንደሚመታ ዐውሎ ነፋስ በሆነ ጊዜ፣ ለድሀው መጠጊያ፣ ለችግረኛው በጭንቁ ጊዜ መጠጊያ፣ ከውሽንፍር መሸሸጊያ ከሙቀትም ጥላ ሆነሃል። **5** እንደ በረሃ ሙቀት፣ የጎጥአንን ጩኸት ዝም ታሰኛለህ፤ ሙቀትም በደመና ጥላ እንዲበርድ እንዲሁ የጨካኞች ዝማሬ ይዋረዳል። **6** የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ለሕዝብ ሁሉ በዚህ ተራራ ላይ ታላቅ የሰባ ግብዣ፣ የተመረጠ የወይን ጠጅ፣ ቅልጥም የሞላባቸው የሰቡ ነገሮች፣ የጥሩና ያረጀ የወይን ጠጅ ግብዣ ያደርጋል። **7** በዚህም ተራራ ላይ በወገኖች ሁሉ ላይ የተጣለውን መጋረጃ፣ በአሕዛብም ሁሉ ላይ የተዘረጋውን መሸፈኛ ያጠፋል። **8** ሞትን ለዘላለም ይውጣል፣ ጌታ እግዚአብሔርም ከፊት ሁሉ እንባን ያብሳል፣ የሕዝቡን ስድብ ከምድር ሁሉ ላይ ያስወግዳል፤ እግዚአብሔር ተናግሮአልና። **9** በዚያም ቀን፣ "ተመልከቱ፣ አምላካችን ይህ ነው፤ ጠብቀነዋል፣ ያድነንማል። እግዚአብሔር ይህ ነው፤ ጠብቀነዋል፤ በማዳኑ ደስ ይለናል ሐሤትም እናደርጋለን" ይባላል። **10** የእግዚአብሔርም እጅ በዚህ ተራራ ላይ ታርፋለች፣ ጭድም በጭቃ ውስጥ እንደሚረገጥ እንዲሁ ሞዓብ በስፍራው ይረገጣል። **11** ዋናተኛ ለመዋኘት እጁን እንደሚዘረጋ፣ እንዲሁ በመካከሉ እጁን ይዘረጋል፤ ነገር ግን ምንም ያክል እጆቹ ቢወራጩም እግዚአብሔር ትዕቢቱን ያዋርዳል። **12** ከፍ ያሉት የተመሸገው ቅጥርህን እስከ ትቢያ ድረስ ዝቅ ያደርገዋል።

Isaiah 25:1

ስምህን አመሰግናለሁ
በዚህ ስፍራ "ስም' እግዚአብሔርን ይወክላል። አት፡- "አንተን አመሰግናለሁ' (ምትክ ስም ተመልከት)

ከጥንት የታቀዱ ነገሮች
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ከጥንት ያቀድካቸው ነገሮች' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

በፍጹም ታማኝነት
"ታማኝነት' የሚለው የነገር ስም "ታማኝ' ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "አንተ ፍጹም ታማኝ ስለሆንክ' (የነገር ስም ተመልከት)

ከተማይቱ
ይህ አንድ የተወሰነ ከተማን የሚያመለክት አይደለም። ይህ ከተሞች በአጠቃላይ ማለት ነው። (አጠቃላይ ስማዊ ሃረጎች ተመልከት)

የባዕዳን ምሽጎች
"የውጪዎች የሆኑ ምሽጎች'

የጨካኝ ሕዝቦች ከተማ
በዚህ ስፍራ "ከተማ' እና "ሕዝቦች' የሚለው በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላሉ። (ምትክ ስም ተመልከት)

Isaiah 25:4

መጠጊያ ... መጠጊያ ... ከውሽንፍር መሸሸጊያ፣ ከሙቀትም ጥላ ሆነሃል
እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚያደርገው ጥበቃ ሕዝቡ ወደ እርሱ ለመጠበቅና ለመጽናናት እንደሚሸሹበት ስፍራ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የጨካኞችም ቁጣ እስትንፋስ ቅጥርን እንደሚመታ ዐውሎ ነፋስ በሆነ ጊዜ
ጨካኝ ሕዝቦች በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የሚያደርሱትን ጭቆና ግንብን እንደሚመታ ዐውሎ ነፋስ ተደርጎ ተነግሮአል:: (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

እስትንፋሱ
"ንፋሱ' ወይም "ጩኸቱ'

የጨካኞች
ይህ ስማዊ አንቀጽ ነው። አት፡- "ጨካኝ ሕዝብ' ወይም "ጨካኞች የሆኑ' (ስማዊ ቅጽል ተመልከት)

በደረቅ መሬት እንደ ሙቀት
ይህ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ጠላቶች ምድሪቱን ከሚያደርቅ ሙቀት ጋር ያመሳስላል። ይህ ጠላቶቹ ምን ያህል የእግዚአብሔርን ሕዝብ መከራ እንዲቀበል እንዳደረጉ አጽንዖት ይሰጣል። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

ሙቀትም በደመና ጥላ እንዲበርድ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ልክ ደመና ከላይ ሲያልፍ ሙቀትን እንደ ሚያቀዘቅዝ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

የጨካኞች ዝማሬ ይዋረዳል
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ጨካኝ ሰዎችን ከመዘመር ታስቆማለህ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

Isaiah 25:6

በዚህ ተራራ ላይ
ይህ ኢየሩሳሌምን ወይም የጽንን ተራራ ያመለክታል።

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርም
ይህንን በኢሳይያስ 1፡9 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

የሰቡ ነገሮች ... ግብዣ
በዚህ ስፍራ "የሰቡ ነገሮች' ማለት እጅግ የተመረጠ ምግብ ማለት ነው።

የአተላ የወይን ጠጅ ግብዣ
"ያረጀ ወይን ጠጅ።' ይህ ማለት እጅግ የተመረጠ ወይን ጠጅ ማለት ነው።

በሕዝቦች ሁሉ ላይ የተጣለውን መጋረጃ፣ በአሕዛብም ሁሉ ላይ የተዘረጋውን መሸፈኛ
ሞት፣ መከራና ሐዘን በምድር ያለውን ሁሉ እንደሚሸፍን ጥቁር ደመና ወይም መረብ ተደርጎ ተነገሮአል። (ስዕላዊ ንግግርና አጓዳኝነት ተመልከት)

ሞትን ለዘላለም ይውጣል
እግዚአብሔር ሰዎችን ለዘላለም እንዲኖሩ ማድረጉ ሞትን እንደሚውጥ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የሕዝቡንም ስድብ ከምድር ሁሉ ያሰወግዳል
እግዚአብሔር ሕዝቡን ዳግመኛ እንዳያፈር ማድረጉ ውርደት እግዚአብሔር እንደሚያስወግደው ግዑዝ ነገር ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Isaiah 25:9

ይባላል
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- ሰዎች ይላሉ (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

በዚያም ቀን
"በዚያን ጊዜ'

የእግዚአብሔር እጅ በዚህ ተራራ ላይ ታርፋለች
"እጅ' የእግዚአብሔርን ኃይል ይወክላል። የእግዚአብሔር እጅ በዚህ ተራራ ላይ ታርፋለች ማለት ሕዝቡን ይጠብቃል ማለት ነው። አት፡- "የእግዚአብሔር ኃይል በዚህ ተራራ ላይ ይሆናል' ወይም "በጽዮን ተራራ ላይ እግዚአብሔር ሕዝቡን ይጠብቃል' (ምትክ ስም እና ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ጭድም በጭቃ ውስጥ እንደሚረገጥ እንዲሁ ሞዓብ በስፍራው ይረገጣል
የእግዚአብሔር የሞዓብን ሕዝብ ማጥፋት እንደሚረግጣቸውና እንደሚያድቅቃቸው ተደርጎ ተነግሮአል። ይህ ሰዎች ገለባን ከጭቃ ጋር ለመደባለቅ ከሚረግጡበት መንገድ ጋር ተመሳስሎአል። (ስዕላዊ ንግግርና ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

ሞአብ በስፍራው ይረገጣል
በዚህ ስፍራ ሞዓብ የሞዓብን ሕዝብ ይወክላል። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር ሕዝቡን በሞዓብ ምድር ይረግጣል' (ምትክ ስምና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

Isaiah 25:11

ሲዋኝ እጁን እንደሚዘረጋ ... እንዲሁ ... እጁን ይዘረጋል
ይህ ዘይቤአዊ ንግግር እግዚአብሔር እንዴት ክፉኛ የሞዓብን ሕዝብ እንደሚያዋርድ አጽንዖት ይሰጣል። ዋናተኛ እጆቹን በውኃ ውስጥ እንደሚዘረጋ እጆቻቸውን በጭቃ ውስጥ ይዘረጋሉ። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

በመካከሉ እጁን ይዘረጋል
"የሞዓብ ሕዝብ በጭቃ ሁሉ ወስጥ እጁን ይዘረጋል'

ዋናተኛ ሲዋኝ እጁን እንደሚዘረጋ
"እየዋኙ እንዳሉ'

ትዕቢቱን ... ያዋርዳል
የእግዚአብሔር ትዕቢተኛን ሰው ማዋረድ በሚመለከት ትዕቢት እግዚአብሔር ዝቅ እንደሚያደርገው ከፍ ብሎ እንዳለ ነገር ተደርጎ ተነግርአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ከእጆቻቸው ችሎታ ጋር
በዚህ ስፍራ "እጆች' የሚለው አንድን ነገር ለማድረግ ወይም ለመሥራት የሚሆንን ኃይል ይወክላል። አት፡- "ከገነቧቸው ታላላቅ ነገሮች ጋር' ወይም "ከሠሯቸው ታላላቅ ነገሮች ጋር' (ምትክ ስም ተመልከት)

የተመሸገውንም ከፍ ከፍ ያለውንም ቅጥርህን ... ወደ መሬት እስከ አፈር ድረስ ይጥለዋል
ይህ እግዚአብሔር የጦር ሠራዊቶች ቅጥሮቹን እንዲያፈርሱ ማድረጉ እርሱ ራሱ እንደሚያፈርሳቸው አድርጎ ይናገራል። አት፡- "ከፍ ከፍ ያሉትን የተመሸጉ ቅጥሮችህን ወደ መሬት ወደ አፈር ለመጣል ሠራዊት ይልካል' (ምትክ ስም ተመልከት)

ከፍ ከፍ ያሉ ምሸጎችህ
በዚህ ስፍራ ምሸጎችህ የሚለው የሚመለከትው የሞዓብ ሕዝብ ነው። ከቀደመው ጥቅስ ጋር የአሳብ ወጥነት እንዲኖረው ለማድረግ በሦሥተኛ መደብ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ከፍ ከፍ ያለ ምሸጋቸው' (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦሥተኛ መደብ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 26

1 በዚያም ቀን ይህ ቅኔ በይሁዳ ምድር ላይ ይዘመራል። የጸናች ከተማ አለችን፤ ለቅጥርና ለምሽግ መድኃኒትን አድርጎባታል። **2** እውነትን የሚጠብቅ ጻድቅ ሕዝብ ይገባ ዘንድ በሮችን ክፈቱ። **3** በአንተ ታምናለችና በአንተ ለምትጸና አእምሮ ፈጽመህ በሰላም ትጠብቃታለህ። **4** ጌታ እግዚአብሔር የዘላለም ዐለት ነውና ለዘላለም በእግዚአብሔር ታመኑ። **5** በኩራት የሚኖሩትን ሰዎች ዝቅ ያደርጋል፤ የተመሸገችውን ከተማ ወደ ምድር ያዋርዳል፤ እስከ መሬት ድረስ ያወርዳታል፤ እስከ አፈርም ድረስ ያርዳታል። **6** በድሆች እንዲሁም በችግረኞች ረገጣ የምትረገጥ ትሆናለች። **7** የጻድቃን መንገድ ደልዳላ ናት፣ አንተ ጻድቅ የሆንህ የጻድቃንን መንገድ ታቃናለህ። **8** አዎን፣ በፍርድህ መንገድ ጠብቀንሃል፤ ስምህም መታሰቢያህም ምኞታችን ነው። **9** ነፍሴ በሌሊት ትናፍቅሃለች፥ መንፈሴም በውስጤ ወደ አንተ ትገሠግሣለች። ፍርድህ ወደምድር በመጣ ጊዜ በዓለም የሚኖሩት ጽድቅን ይማራሉና። **10** ለኃጢአተኛ ሞገስ ይደረግለት፣ ነገር ግን ጽድቅን አይማርም። በቅኖች ምድር ክፉን ነገር ያደርጋል፤ የእግዚአብሔርንም ግርማ አያይም። **11** እግዚአብሔር ሆይ፣ እጅህ ከፍ ብላ ተነሣች፣ ነገር ግን አላስተዋሉም። ነገር ግን በሕዝብህ ላይ ያለህን ቅንዓት አይተው ያፍራሉ፤ ምክንያቱም እሳትም ጠላቶችህን ትበላቸዋለች። **12** እግዚአብሔር ሆይ፣ ሥራችንን ሁሉ ሠርተህልናልና ሰላምን ትሰጠናለህ። **13** አቤቱ አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ፣ ከአንተ በተጨማሪ ሌሎች ጌቶች ገዝተውናል፤ ነገር ግን የአንተን ስም ብቻ እናስባለን። **14** እነርሱ ሞተዋል፣ በሕይወት አይኖሩም፤ ሞተዋል፣ አይነሡም፤ በእርግጥ፣ አንተ በፍርድ መጥተህ አጥፍተሃቸዋል፣ መታሰቢያቸውን ሁሉ እንዲጠፋ አድርገሃል። **15** እግዚአብሔር ሆይ፣ ሕዝብን አበዛህ፣ ሕዝብን አበዛህ፤ አንተም ተከበርህ፣ የአገሪቱን ዳርቻ ሁሉ አሰፋህ። **16** እግዚአብሔር ሆይ፣ በመከራ ጊዜ ተመለከቱህ፤ ቅጣትህ በእነርሱ ላይ በሆነ ጊዜ ድግምታቸውን ሳይቀር በክፉው ላይ ተናገሩ። **17** የፀነሰች ሴት ለመውለድ ስትቀርብ እንደምትታመምና በምጥ እንደምትጮኽ፣ አቤቱ፣ እንዲሁ በፊትህ ሆነናል። **18** እኛ ፀንሰናል፣ ምጥም ይዞናል፣ ነገር ግን ነፋስን እንደምንወልድ ሆነናል፤ ድነትን ወደምድር አላመጣንም፣ በዓለምም የሚኖሩ አልወደቁም። **19** ሙታንህ ሕያዋን ይሆናሉ፤ ሬሳዎችም ይነሣሉ። በምድር የምትኖሩ ሆይ፣ ጠልህ የመድሃኒት ጠል ነውና፣ ምድርም ሙታንን ታወጣለችና ንቁ ዘምሩም። **20** ሂድ ሕዝቤ ሆይ፣ ወደ ክፍሎችህ ግባና ደጅህን በኋላህ ዝጋ፤ ቍጣ እስኪያልፍ ድረስ ጥቂት ጊዜ ተሸሸግ። **21** ተመልከት፣ በምድር በሚኖሩት ላይ በበደላቸው ምክንያት ቍጣውን ያመጣባቸው ዘንድ፣ እነሆ፣ እግዚአብሔር ከስፍራው ይወጣል፤ ምድርም ደምዋን ትገልጣለች፣ ሙታኖችዋንም ከእንግዲህ ወዲህ አትከድንም።

Isaiah 26:1

በዚያም ቀን
"በዚያን ጊዜ'

ይህ ቅኔ በይሁዳ ምድር ይዘመራል
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "በይሁዳ ምድር የሚኖሩ ሰዎች ይህን ቅኔ ይዘምራሉ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

የጸናች ከተማ አለችን
ይህ የኢየሩሳሌምን ከተማ ያመለክታል።

እግዚአብሔር ማዳኑን ቅጥሮቿና ምሽጎቿ ያደርጋል
ሕዝቡን ለመጠበቅና ለማዳን የሆነው የእግዚአብሔር ኃይል፣ ማዳኑ በከተማይቱ ዙሪያ እንዳለ ቅጥር ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

እምነትን የሚጠብቅ ጻድቅ አገር
በዚህ ስፍራ አገር የሚለው ሕዝቡን ይወክላል። አት፦ "ጻድቅና ታማኝ ሕዝብ' (ምትክ ስም ተመልከት)

Isaiah 26:3

በአንተ ለሚጸና አእምሮ
በዚህ ስፍራ አእምሮ የግለሰቡን አሳቦች ይወክላል። እንዲሁም በአንተ የሚለው እግዚአብሔርን ያመልክታል። በአንት የሚጸና የሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፦ ባለማቋረጥ ስለአንተ የሚያስብ ሰው (ምትክ ስምና ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ጌታ እግዚአብሔር
ጌታ፣ የእግዚአብሔር ሌላኛው ስም ነው።

እግዚብሔር የዘላለም ዓለት ነው
እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመጠበቅ ያለው ኃይል ከጠላቶቻቸው ለማምለጥ ሕዝቡ የሚሹሸበት ትልቅ ዓለት እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 26:5

በትዕቢት የሚኖሩትን ዝቅ ያደርጋል
እግዚአብሔር የሚታበዩትን ማዋረዱ ትዕቢተኞች ሰዎች በከፍታ እንደሚኖሩ እርሱም ዝቅ እንደሚያደርጋቸው ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የተመሸገቸው ከተማ
ይህ የተወሰነችን አንዲትን ከተማ ሳይሆን የተመሸገቱን ከተሞች በአጠቃላይ ማለት ነው። (አጠቃላይ ስማዊ ሐረጎች ተመልከት)

ያዋርዳል፣ ... ድረስ ያወርዳታል
እግዚአብሔር የተመሸጉትን ከተሞች የጦር ሠራዊት እንዲያጠፋቸው ማድረጉ እግዚአብሔር ራሱ እንዳደረገው ተደርጎ ተነግሮአል። (ምትክ ስም ተመልከት)

በድሀ እግርም በችግረኛም አረጋገጥ ትረገጣለች
ሁለቱም ንግግሮች ተመሳሳይ አሳብ ይናገራሉ። ይሕ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "ድሆችና የተጨቆኑ ሰዎች በከተማይቱ ፍርስራሽ ላይ ይረማመዳሉ።' (አጓዳኝነትና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

Isaiah 26:7

የጻድቃን መንገድ የቀናች ናት ... አንተ ... የጻድቃንን መንገድ ታቀናለህ
እንዚህ ሁለት ሃረጎች በመሠረቱ የሚናገሩት ተመሣሣይ አሳብ ነው። እግዚአብሔርን የሚታዘዙ ሰዎች በመንገዱ እንደሚሄዱ ተደርጎ ተነግሮአል። የሚያደርጉት ትክክል መሆኑን እግዚአብሔር ለሕዝቡ ማረጋገጡ መንገዳቸውን ቀናና የተስተካከለ እንደሚያደርግላቸው ተደርጎ ተነግሮአል። (አጓዳኝነትና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በፍርድህ መንገድ፣ እግዚአብሔር ሆይ፣ ተስፋ አድርገንሃል
ትክክል እንደሆነ እግዚአብሔር የበየነውን ማድረግ በመንገዱ እንደመሄድ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፦ "አንተ ትክክል ነው ብለህ የበየንከውን በማድረግ ስለጸናን፣ እግዚአብሔር ሆይ፣ ተስፋ አድርገንሃል' (ስዕላዊ ንግግር ተመለከት)

በፍርድህ
"በሕግጋትህ' ወይም "በትምህርቶችህ'

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ተስፋ አድርገንሃል
በዚህ ስፍራ "እኛ' የሚለው ለእግዚአብሔር እየተናገሩ ያሉትን ኢሳይያስንና ጻድቃን የሆኑ ሰዎችን ሁሉ ያመለክታል። (አግላይና አካታች "እኛ' ተመልከት)

ስምህና ክብርህ የነፍሳችን ምኞት ነው
በዚህ ስፍራ "ስም' እና "ክብር' እግዚአብሔርን ራሱን የሚወክሉትን የእግዘኢብሔር ባሕርያት ይወክላሉ። አት፡- "አንተን ማክበር ብቸኛ ምኞታችን ነው' (ምትክ ስም ተመልከት)

መንፈሴ በውስጤ አጥብቆ ይፈልግሃል
እግዚአብሔርንና ሕግጋቱን ከፊቱ በተሻለ ለማወቅ መፈለግ ሰውዬው እግዚአብሔርን ለማግኘት እንደሚፈልግ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "የተሻለ እንዳውቅህ አጥብቄ እፈልጋለሁ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

መንፈሴ በውስጤ አጥብቆ ይፈልግሃል
በዚህ ስፍራ "መንፈስ' የተናጋሪውን ሁለንተና ይወክላል። (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

Isaiah 26:10

ለኃጢአተኛ ሞገስ ቢደረግለት ጽድቅን አይማርም
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር ለክፉ ሰዎች መልካም ቢሆንላቸውም እንኳን በጎ ማድረግን አይማሩም' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ኃጢአተኛ
ይህ ክፉ ሰዎች በአጠቃላይ ማለት ነው። (አጠቃላይ ስማዊ ሃረጎች ተመልከት)

በቅኖች ምድር
"ምድር' የሚለው በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላል። አት፡- "ሰዎች ትክክል የሆነውን የሚያደርጉበት ምድር' (ምትክ ቃል ተመልከት)

የእግዚአብሔርን ግርማ አያይም
"ማየት' በዚህ ስፍራ አንድን ነገር መገንዘብን ይወክላል። አት፡- "እግዚአብሔር ታላቅ እንደሆነ አይገነዘቡም' (ምትክ ስም ተመልከት)

Isaiah 26:11

እጅህ ከፍ ከፍ አለች
እግዚአብሔር ክፉ ሰዎችን ለመቅጣት መዘጋጀቱ ክፉ ሰዎችን ለመምታት እጆቹ እንደተነሱ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

አላስተዋሉም
"ክፉ ሰዎች ግን አላስተዋሉም'

ለሕዝብህ ያለህን ቅንዓት አይተው
"ማየት' በዚህ ስፍራ አንድን ነገር መገንዘብን ይወክላል። አት፡- "ሕዝብህን ለመባረክ አጥብቀህ እንደምትፈልግ ይገነዘባሉ' (ምትክ ቃል ተመልከት)

በሃፍረት ይከደናሉ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ያፍራሉ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

የጠላቶችህ እሳት ትበላቸዋለች
የእግዚአብሔር ጠላቶቹን መቅጣትና ፈጽሞ ማጥፋት ፈጽሞ የሚያቃጥላቸውን እሳት እንደሚልክ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የጠላቶችህ እሳት
በዚህ ስፍራ "የ' የሚለው እሳቱ የጠላቶቹ ንብረት የሆነ ነው ማለት አይደለም ነገር ግን እሳቱ ጠላትን ለማጥቃት ጥቅም ላይ ለማዋል የታቀደ ነው። አት፡- "እሳትህ ፈጽሞ ያቃጥላቸዋል'

ለእኛ
በዚህ ስፍራ "እኛ' የሚለው ጻድቃን ሰዎችን ሁሉ ጨምሮ ኢሳይያስን ያመለክታል። (አግላይና አካታች "እኛ' ተመለከት)

Isaiah 26:13

ነገር ግን ስምህን ብቻ እናመሰግናለን
በዚህ ስፍራ ስም የሚለው የእግዚአብሔርን ማንነት ይወክላል። አት፡- "ነገር ግን አንተን ብቻ እናመሰግናለን' (ምትክ ቃል ተመልከት)

አይነሱም
"ወደ ሕይወት ተመልሰው አይመጡም'

መታሰቢያቸውንም ሁሉ አጥፍተሃል
እግዚአብሔር ያጠፋቸውን ሌሎች ሰዎች እንዳያስቧቸው ማድረጉ እግዚአብሔር መታሰቢያቸው እንዲጠፋ ወይም እንዲሞት እንዳደረገ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 26:15

ሕዝብን አበዛህ፣ እግዚአብሔር ሆይ፣ ሕዝብን አበዛህ
አጽንዖት ለመስጠት ሀረጉ ተደግሞአል። በዚህ ስፍራ ሕዝብ የሚለው ሰዎችን ይወክላል። አት፡- "በሕዝባችን ዘንድ ሰዎች በከፍተኛ ቁጥር እንዲጨምሩ አድርገሃል' (አጓዳኝነትና ምትክ ቃል ተመልከት)

Isaiah 26:16

ፈለጉህ
በዚህ ስፍራ እነርሱ የሚለው የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል። ይህ ኢሳይያስን ያካትታል። አት፡- "እንፈልግሃለን' (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሦሥተኛ መደብ ተመልከት)

ፈለጉህ
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር እግዚአብሔርን እርዳታ ይጠይቁ ነበር ማለት ነው። (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

የአንተ ተግሣጽ በእነርሱ ላይ በሆነ ጊዜ
ተግሣጽ የሚለው የነገር ስም በማሰሪያ አንቀጽነት ሊቀመጥ ይችላል። አት፡- "በገሠጽሃቸው ጊዜ' (የነገር ስሞች ተመልከት)

የፀነሰች ሴት ... በምጥ እንደምትጮኽ
ይህ ሕዝቡን ከምትወልድ ሴት ጋር ያነጻጽራል። ይህ እግዚአብሔር በሚገሥጻቸው ጊዜ ስለሚሆነው መከራቸውና ጩኸታቸው አጽንዖት ይሰጣል። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 26:18

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ የይሁዳን ሕዝብ መከራ ከምትወለድ ሴት ጋር ማነጻጸሩን ይቀጥላል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ነፋስን ብቻ እንደምንወልድ ሆነናል
"አየር ብቻ እንደምንወልድ ሆነናል' ወይም "ምንም የሌለው እንደምንወልድ ሆነናል።' ይህ የሕዝቡ መከራ የሚያስከትለው ውጤር ምንም እንደሆነ አጽንዖት የሚሰጥ ዘይቤአዊ ንግግር ነው። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በምድርም ደኅንነት አላደረግንም፤ በዓለምም የሚኖሩ አልወደቁም
በዚህ ስፍራ "ምድር' የሚለው በምድር የሚኖሩትን ትወክላለች። ትርጉሙ ግልጽ አይደለም፣ የእስራኤል ሕዝብ በጦርነት ጠላቶቻቸውን በማሸነፍ ራሳቸውንና ሌሎች ሕዝቦችን ማዳን አልቻሉም የሚል ይመስላል። (ምትክ ስምና እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

በምድርም ደኅንነት አላደረግንም
ይህ "ደኅንነት' የሚለው የነገር ስም "ማዳን' በሚል ማሰሪያ አንቀጽ እንዲገለጽ እንደገና ሊጻፍ ይችላል። አት፡- "የምድር ነዋሪዎችን አላዳናቸውም' (የነገር ስም ተመልከት)

በዓለም የሚኖሩ አልወደቁም
የዓለም ክፉ ሰዎች በጦርነት እንዲወድቁ አላደረግንም

Isaiah 26:19

ሙታንህ ሕያዋን ይሆናሉ
"ሙታን' የሚለው ስማዊ ቅጽል "የሞቱ' በሚል ማሰሪያ አንቀጽ እንዲገለጽ እንደገና ሊጻፍ ይችላል። አት፡- "የሞቱ ሕዝብህ ሕያዋን ይሆናሉ' (ስማዊ ቅጽል ተመልከት)

ሙታንህ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) "ሙታንህ' የሚለው እግዚአብሔርን ያመለክታል ወይም 2) "ሙታንህ' የሚለው የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል። ሁለተኛውን አማራጭ ከወሰድህ "ሙታኖቻችን' ብለህ መተርጎም ትችላለህ።

ንቁ
ይህ የሞቱ ሰዎች ሕያው መሆንን ከእንቅልፍ እንደሚነቁ አድርጎ ይናገራል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በምድር የምትኖሩ ሆይ
ይህ የሞቱት የተገለጹበት ትህትና የተሞላ መንገድ ነው። አት፡- የሞቱና የተቀበሩ (የማያስደስት ቃልን በሌላ ቃል መተካት ተመልከት)

ጠልህ የብርሃን ጠል ነውና
እግዚአብሔር ለሕዝቡ በበጎነት የሚሠራውና እነርሱን መልሶ ሕያዋን ማድረጉ ተክሎችን ሕያዋን እንደሚያደርግ ጠል ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ጠልህ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) "ጠልህ' የሚለው እግዚአብሔርን ያመለክታል ይኼውም እግዚአብሔር የሚሰጠውን ጠል ነው ወይም 2) "ጠልህ' የሚለው የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል ይኼውም ከእግዚአብሔር የተቀበሉትን ጠል ነው።

የብርሃን ጠል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ብርሃን ሙታንን ሕያዋን የሚያደርግበትን የእግዚአብሔርን ኃይል ያመለክታል። አት፡- "ከእግዚአብሔር የሆነ ጠል' ወይም 2) ብርሃን በተክሎች ላይ ጠል የሚሆንበትን የማለዳ ጊዜን ያመለክታል። አት፡- "የማለዳ ጠል'

ምድር ሙታኖቿን ታወጣለች
"ምድር የሞቱትን ትወልዳለች።' የእግዚአብሔር የሞቱ ሰዎችን ሕያው ማድረግ ምድር የሞቱትን እንደምትወልድ ተድርጎ ተነግሮአል። አት፡- "እግዚአብሔር የሞቱትን ከምድር እንዲነሱ ያደርጋል' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 26:20

ሕዝቤ ሆይ
በዚህ ስፍራ "ሕዝቤ (የኔ ሕዝብ)' የሚለው ኢሳይያስን ያመልክታል። እንዲሁም "ሕዝቤ' የሚለው የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል።

ቁጣ እስኪያልፍ ድረስ
"ቁጣ' የሚለውን የነገር ስም "ቁጡ' በሚል ቅጽል ተርጉም። አት፡- "ከእንግዲህ ወዲያ እግዚአብሔር በእኛ ላይ ቁጡ እስከማይሆን ድረስ' (የነገር ስም ተመልከት)

ምድርም ደምዋን ትገልጣለች፣ ሙታኖችዋንም ከእንግዲህ ወዲህ አትከድንም
ነፍስ ገዳዮችን መቅጣት ይችል ዘንድ በምድር የተፈጸሙትን ግድያዎች ሁሉ እግዚአብሔር መግለጡ ምድር ራሷ ነፍስ የገደሉትን ሁሉ እንደምትገልጥ ተደርጎ ተነግሮአል። (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየትን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 27

1 በዚያም ቀን እግዚአብሔር ፈጣኑን እባብ ሌዋታንን ጠማማውንም እባብ ሌዋታንን በጠንካራ፣ በታላቅ፣ በብርቱም ሰይፍ ይቀጣል፥ በባሕርም ውስጥ ያለውን አውሬ ይገድላል። **2** በዚያም ቀን፣ ለተወደደው የወይን ቦታ ተቀኙለት። **3** "እኔ፣ እግዚአብሔር ጠባቂው ነኝ፤ ሁልጊዜ አጠጣዋለሁ፤ ማንም እንዳይጐዳው በሌሊትና በቀን እጠብቀዋለሁ። **4** እሾህና ኩርንችት ለሰልፍ በመኖራቸው አልተቈጣሁም! በውጊያ በእነርሱ ላይ ተራምጄ፣ በአንድነት ባቃጠልኋቸው ነበር። **5** ከለላነቴን ካልያዙና ከእኔ ጋር ሰላም ካላደረጉ፣ ከእኔ ጋር ሰላም ያድርጉ። **6** በሚመጣው ዘመን ያዕቆብ ሥር ይሰድዳል፣ እስራኤልም ያብባል ይጨበጭብማል፤ በፍሬያቸውም የዓለሙን ፊት ይሞላሉ።" **7** በውኑ የመቱትን እንደ መታ እንዲሁ እርሱን መታውን? ወይስ እነርሱ እንደ ተገደሉበት መገደል ያዕቆብና እስራኤል ተገድሎአልን? **8** ያዕቆብና እስራኤልን ለማባረር በታገልክበት መጠን፣ እርሱ ነዳቸው ሰደዳቸው ቀሠፋቸው፤ የምሥራቅ ነፋስ በሚነፍስበት ቀን በጠንካራ ዐውሎ ነፋስ አስወገዳቸው። **9** ስለዚህም በዚህ መንገድ፣ የማምለኪያ ዐፀዶችና የፀሐይ ምስሎች ዳግመኛ እንዳይነሡ የመሠዊያውን ድንጋይ ሁሉ እንደ ደቀቀ እንደ ኖራ ድንጋይ ባደረገ ጊዜ፣ እንዲሁ የያዕቆብ በደል ይሰረያል፣ ይህም ከኀጢአት የመመለስ ፍሬ ሁሉ ነው። **10** የተመሸገችው ከተማ ጠፋች፣ እንደ ምድረ በዳ የተፈታችና የተተወች መኖሪያ ናት። በዚያም ጥጃ ይሰማራል፣ በዚያም ይተኛል ቅርንጫፍዋንም ይበላል። **11** ጫፎችዋ በደረቁ ጊዜ ይሰበራሉ። ሴቶችም መጥተው ያቃጥሉአቸዋል፤ የማያስተውል ሕዝብ ነውና ስለዚህ ፈጣሪው አይራራለትም ሠሪውም ምሕረት አያደርግለትም። **12** በዚያም ቀን እንዲህ ይሆናል፤ እግዚአብሔር ከኤፍራጥስ ወንዝ ምንጭ ጀምሮ እስከ ግብጽ ወንዝ ድረስ እህሉን ይወቃል፥ እናንተም የእስራኤል ሕዝቦች ሆይ፣ አንድ በአንድ ትሰበሰባላችሁ። **13** በዚያም ቀን እንዲህ ይሆናል፤ ታላቅ መለከት ይነፋል፣ በአሦርም የጠፉ፣ በግብጽ ምድርም የተሰደዱ ይመጣሉ፣ በተቀደሰውም ተራራ በኢየሩሳሌም ለእግዚአብሔር ይሰግዳሉ።

Isaiah 27:1

በዚያም ቀን
"በዚያን ጊዜ'

እግዚአብሔር በጠንካራ፣ በታላቅና በብርቱ ሰይፉ ይቀጣዋል
እግዚአብሔር ጠላቶቹን ለማጥፋት ያለው ኃይል ጠንካራና ትልቅ ሰይፍ እንዳለው ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በባሕር ውስጥ ያለውን አስፈሪ ፍጡር
ይህ ሌዋታንን ያመለክታል።

ለወይን ቦታው ተቀኙለት
"ስለ ወይን ቦታው ተቀኙ።' ይህ የእስራኤልን ሕዝብ ፍሬ በሚሰጥ የወይን ቦታ መስሎ ይናገራል። አት፦ "ለወይን ጠጅ የሚሆን የወይን ፍሬ እንደሚያፈራ የወይን ቦታ እንደሆኑ አድርጋችሁ ስለ እስራኤል ሕዝብ ዘምሩ።' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

እኔ እግዚአብሔር ጠባቂው ነኝ
"እኔ እግዚአብሔር የወይን ቦታው ጠባቂ ነኝ'

በሌሊትና በቀን
"ሌሊት' እና "ቀን' የሚሉት ቃላት "ሁልጊዜ' ለማለት ተጣምረዋል። አት፦ "ሁልጊዜ' ወይም "ያለማቋረጥ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 27:4

አያያዥ አሳብ፦
የእስራኤልን ሕዝብ በወይን ቦታ መስሎ መናገሩን ቀጥሏል።

አልቆጣም፣ ኦ፣ እሾህና ኩርንችት በነበሩ! በጦርነት በወጣሁባቸው ነበር
አልቆጣም። እሾህና ኩርንችት ቢኖሩ ኖሩ በጦርነት ባሰለፍኩባቸው ነበር

አልቆጣም
እግዚአብሔር ከእንግዲህ ወዲያ በሕዝቡ ላይ እንዳማይቆጣ የሚታወቅ ነው። አት፦ "ከአንግዲህ ወዲያ በሕዝቤ ላይ አልቆጣም' (መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉ)

እሾህና ኩርንችት በነበሩ
የእስራኤል ጠላቶች በወይን ቦታ እንደሚበቅሉ እሾህና ኩርንችት ተደርገው ተገልጸዋል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

እሾህና ኩርንችት
ይህንን ሃረግ በኢሳይያስ 5፡6 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

በጦርነት በወጣሁባቸው ነበር
እግዚአብሔር ጠላቶቹን መውጋቱ ስለ እርሱ በጦሩ መካከል እንደሚገኝ ተዋጊ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በወጣሁባቸው ነበር፣ በአንድነትም ባቃጠልኋቸው ነበር
በዚህ ስፍራ ኢሳይያስ ስለ እግዚአብሔር ጠላቶች ለመናገር የተለያዩ ምስሎችን ያጣምራል። እሾህና ኩርንችት እንደሆኑ ደግሞም በጦሩ ውስጥ እንዳሉ ወታደሮች አድርጎ ስለ እነርሱ ይናገራል። (ስላዊ ንግግር ተመልከት)

የእኔን ጥበቃ ካለገኙ
ይህ "ጥበቃ' የሚለው የነገር ስም "ጠበቀ' በሚለው ማሰሪያ አንቀጽ እንዲገለጽ እንደገና ሊጻፍ ይችላል። አት፦ "እንድጠብቃቸው እስካልጠየቁኝ ድረስ' (የነገር ስም ተመልከት)

ከእኔ ጋር ሰላም ያድርጉ፣ ከእኔ ጋር ሰላም ያደርጉ
"ከእኔ ጋር በሰላም ለመኖር ጠይቀዋል፣ከእ ጋር በሰላም እንዲኖሩ እፈልጋለሁ'

Isaiah 27:6

አጠቃላይ መረጃ፦
ኢሳይያስ እየተናገረ ነው። የእስራኤልን ሕዝብ በወይን ቦታ መስሎ መገልጹን ይቀጥላል። (ኢሳይያስ 27፡2 ተመልከት)

በሚመጣው ዘመን
ይህ ዘመንን እንደሚጓዝና አንድ ቦታ እንደሚደርስ አድርጎ ይናገራል። አት፦ "ወደፊት' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ያዕቆብ ሥር ይሰድዳል፣ እስራኤልም ያብባል
እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ መባረኩና እንዲበለጽግ ማድረጉ ሥሩ እንደሚያድግና እንደሚያብብ ወይን ተደርጎ ተነገሮአል። አት፦ "የእስራኤል ልጆች ሥሩን እንደሚሰድድና እንደሚያብብ ወይን ይበለጽጋሉ' (ስዕላ ንግግር ተመልከት)

ያዕቆብ ... እስራኤል
በዚህ ስፍራ "ያዕቆብ' እና "እስራኤል' የያዕቆብን ልጆች የሚወክሉ ምትክ ስሞች ናቸው። (ምትክ ስም ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የምድርን ፊት በፍሬ ይሞላሉ
ሌላውን ሕዝብ ይረዱ ዘንድ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ እንዲበለጽጉ ማድረጉ ፍሬው እጅግ እንደበዛና ምድርን እንደሸፈነ ወይን ተደርገው ተገልጸዋል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 27:7

የመቱትን ሕዝቦች እንደመታ እግዚአብሔር ያዕቆብን መትቶታልን
ጥያቄው የእግዚብሔርን ቅጣት ክብደት ለማነጻጸር ጥቅም ላይ ውሏል። አት፦ "በእርግጥ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ከቀጣው በላይ ጠላት ሕዝቦችን በእጅጉ ቀጥቷል።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ)

ያዕቆብ ... እስራኤል
የያዕቆብን ልጆች ይወክላል። (ምትክ ስም ተመልከት)

ሌሎች ሕዝቦች በእነርሱ በተገደሉበት መገደል ያዕቆብና እስራኤል ተገድለዋልን?
ይህም ጥያቄ የእግዚአብሔርን ቅጣት ክብደት ለማነጻጸር ጥቅም ላይ ውሏል። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "እነርሱ ጠላቶቻቸውን ከሌሎች ሕዝቦች እንደገደሉ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ አልገደለም።' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽና አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

በልኬቱ ተገዳደርካቸው
በዚህ ስፍራ "አንተ' የሚለው እግዚአብሔርን ያመልክታል። የሚገባቸውን ያህል እግዚአብሔር ሕዝቡን መቅጣቱ፣ የእግዚአብሔር ቅጣት ሊለካ የሚችል ነገር እንደሆነ ተደርጎ ተገልጸአል። አት፦ "ነገር ግን አንተ የሚገባቸውን ያህል ቀጣሃቸው።' (የ "አንተ' ልዩ ልዩ አጠቃቀሞችና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ያዕቆብን ሰደደው እስራኤልን አስወገደው
ይህ የያዕቆብን ልጆች ይወክላል። አት፦ "እስራኤላውያንን ወዲያ ሰደዳቸው' (ምትክ ስም ተመልከት)

የምሥራቅ ነፋስ እንደሚነፍስበት ቀን በጠንካራ ዐውሎ አስወገዳቸው
እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ ባዕድ አገር ወዲያ የሚሰድበት ኃይሉ እነርሱን ወደ ባዕድ አገር ለመውሰድ የአፉን እስትንፋስ እንደሚጠቀም ተደርጎ ተነግሮአል። አት፦ "የእግዚአብሔር ኃይል እንደ ምሥራቅ ጠንካራ ዐውሎ ጠርጎ አስወገዳቸው' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 27:9

ስለዚህ እንዲሁ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) እንዲሁ የሚለው ኢሳይያስ በቀደመው ጥቅስ እንደገለጸው እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ ምርኮ መሰደዱን ያመለክታል ወይም 2) እንዲሁ የሚለው ኢሳይያስ በቁጥር 9 ቀጥይ ክፍል የሚገልጻቸውን ድርጊቶች ያመለክታል።

የያዕቆብ በደል ይሰረያልና
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "እግዚአብሔር ከእስራኤል ኃጢአትን ያስወግዳል' ወይም "እግዚአብሔር የእስራኤላውያንን ኃጢአት ይቅር ይላል።' (አድጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

የያዕቆብ በደል ... የእርሱን ኃጢአት የማስወገድ
በዚህ ስፍራ "ያዕቆብ' የያዕቆብን ልጆች ይወክላል። አት፦ "የእስራኤላውያን በደል... የእነርሱን ኃጢአት የማስወገድ' (ምትክ ስም ተመልከት)

ይህም
በዚህ ስፍራ "ይህ' በቁጥር 9 ቀጥይ ክፍል ኢሳይያስ የሚገልጻቸውን ድርጊቶች ያመለክታል።

ሙሉ ፍሬው
ፍሬ በዛፍ ላይ ወይም በወይን ተክል ላይ እንደሚያድግ ይህ የድርጊቱን ውጤቶች ይናገራል። አት፦ "ውጤቱ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የመሠዊያ ድንጋዮችን እንደ ኖራ ድንጋይ ያደርጋቸዋል ያደቅቃቸዋልም፣ የአሼራህ ዐፀዶች ወይም የማጠኛ መሠዊያዎች ጸንተው አይቆሙም
በዚህ ስፍራ እርሱ የሚለው ልጆቹን የሚወክለውን ያዕቆብን ያመለክታል። አት፦ "ለሐሰተኛ አማልክት የሚሠውባቸውን መሠዊያዎች ፈጽመው ያፈርሳሉ፣ የአሼራህን ጣዖታትና ለሐሰተኛ አማልክት እጣን የሚያቃጥሉባቸውን መሠዊያዎች ሁሉ ያስወግዳሉ።' (ምትክ ስም ተመልከት)

Isaiah 27:10

የተመሸገችው ከተማ ... ቅርንጫፍዋንም ይበላል
በዚህ ስፍራ ኢሳይያስ ወደፊት ሊሆን ያለውን ነገር ገና አስቀድሞ እንደተፈጸመ አድርጎ ይናገራል። ይህ በእርግጥ የሚፈጸም ለመሆኑ አጽንዖት ይሰጣል። (ትንቢታዊ ሃላፊ ጊዜ ተመልከት)

የተመሸገችው ከተማ ብቻዋን ሆነች፣ እንደ ምድረ በዳ ሆና የተፈታችና የተተወች መኖሪያ ናት
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል።አት፦ "ጠንካሮችና ብዙ ሰዎች ይኖሩባቸው የነበሩ ከተሞች እንደ ምድረ በዳ ባዶ ሆኑ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

የተመሸገችው ከተማ ... መኖሪያ
ይህ አንድ የተወሰነ ከተማን ወይም መኖሪያ ስፍራን ሳይሆን ከተሞችን ወይም መኖሪያ ስፍራዎችን የሚያመለክት ነው። (አጠቃላይ ስማዊ ሐረጎች ተመልከት)

ጥጃ ይሰማራል፣ በዚያም ይተኛል፣ ቅርንጫፍዋንም ይበላል
በዚህ ስፍራ ጥጃ፣ ጥጃዎችን ወይም ከብቶችን በአጠቃላይ ያመለክታል። አት፦ "ጥጃዎች ይሰማራሉ፣ በዚያም ይተኛሉ፣ ቅርንጫፍዋንም ይበላሉ' (አጠቃላይ ስማዊ ሐረጎች ተመልከት)

ጫፎችዋ ... የማያስተውል ሕዝብ
ሕዝቡ ሴቶች እንደሚሰብሩአቸው ደረቅ ቅርንጫፎች ተደርገው እስኪገለጹ ድረስ እግዚአብሔርን ካለመታዘዛቸው የተነሳ ጠላቶች በቀላሉ የሚያጠፏቸው ደካሞች ሆነው ነበር። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ጫፎችዋ በደረቁ ጊዜ ይሰበራሉ፣ሴቶችም መጥተው ያቃጥሉአቸዋል
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "ቅርንጫፎቹ በደረቁ ጊዜ፣ ሴቶች ይመጡና ይሰብሩአቸዋል፣ለእሳት ማገዶም ያደርጓቸዋል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

የማያስተውልም ሕዝብ ነውና
ይህ በይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አት፦ "ይህ እግዚአብሔርን ወይም ሕጉን የሚረዳ ሕዝብ አይደለም' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ሕዝብ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) "ሕዝብ' የሚለው የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል ወይም 2) "ሕዝብ' የሚለው የእስራኤልን ሕዝብ የሚጨቁኑትን የባዕድ ሕዝቦች ያመለክታል።

ስለዚህ ፈጣሪያቸው አይራራላቸውም፣ ሠሪያቸውም ምሕረት አያደርግላቸውም
ሁለቱም ሐረጎች አንድ ዓይነት ነገር ይናገራሉ። አት፦ "ስለማያስተውሉ፣እግዚአብሔር፣ የፈጠራቸው፣ ምሕረት አያደርግላቸውም' (አጓዳኝነት ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Isaiah 27:12

እንዲህ ይሆናል
ይህ ሃረግ አንድ አስፈላጊ ሁኔታ እንደሚፈጸም ያመለክታል።

በዚያም ቀን
"በዚያን ጊዜ'

እግዚአብሔር ይወቃል
ከባዕዳን አገር ወደ እስራኤል ምድር መልሶ ለማምጣት እግዚአብሔር ሕዝቡን መሰብሰቡ ፍሬውን ከገለባው ለመለየት ስንዴን እንደመውቃት ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ከኤፍራጥስ ወንዝ እስከ ግብጽ ወንዝ ድረስ
ኢሳይያስ የኤፍራጥስን ወንዝና የግብጽን ወንዝ የሚጠቅሰው ወደ እነዚህ ወንዞች አቅራቢያ ወደሚገኙ አገሮች ማለትም ወደ አሦርና ግብጽ የተጋዙትን የእስራኤልን ሕዝብ መልሶ ያመጣቸዋል ለማለት ነው። የኤፍራጥስ ወንዝ ከእስራኤል በስተ ሰሜን ምሥራቅ የሚገኝ ሲሆን የግብጽ ወንዝ ደግሞ ከእስራኤል በስተ ደቡብ ምዕራብ የሚገኝ ነው።

የግብጽ ወንዝ
"የግብጽ ጅረት'

አንድ በአንድ ትሰበሰባላችሁ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "እግዚአብሔር አንድ በአንድ ይሰበስባችኋል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ታላቅ መለከት ይነፋል
ይህ በአድራጊ ማሰሪየ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "አንድ ሰው ከፍ ባለ ድምጽ መለከት ይነፋል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

በአሦር አገር የጠፉ፣ በግብጽም ምድር የተሰደዱ ይመጣሉ
መረዳት የሚቻለው መረጃ በግልጽ ሊቀመጥ ይችላል። አት፦ "በአሦር ምድርና በግብጽ ምድር በስደት ያሉና የሞቱ ወደ እስራኤል ምድር ይመለሳሉ' (መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉ ተመልከት)

በተቀደሰው ተራራ
"የተቀደሰው ተራራ' በኢየሩሳሌም የሚገኘው የጽዮን ተራራ ነው። ይህንን በኢሳይያስ 11:9 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 28

1 ለኤፍሬም ሰካሮች ትዕቢት አክሊል፣ በወይን ጠጅ ለተሸነፉ በወፍራም ሸለቆአቸው ራስ ላይ ላለችም ለረገፈች ለክብሩ ጌጥ አበባ ወዮ! 2 እነሆ፣ በጌታ ዘንድ ኃያል ብርቱ የሆነ አለ። እንደ በረዶ ወጨፎ፣ እንደሚያጠፋም ወጀብ፣ እንደሚያጥለቀልቅም እንደ ታላቅ ውኃ ፈሳሽ በጠነከረ እጅ ምድርን ያጠቃል። 3 የኤፍሬም ሰካሮች ትዕቢት አክሊል በእግር ይረገጣል፤ 4 በወፍራሙ ሸለቆ ራስ ላይ ያለች የረገፈች የክብሩ ጌጥ አበባ፣ ከመከር በፊት አስቀድማ እንደምትበስል በለስ ትሆናለች፤ ሰው ባያት ጊዜ በእጁ እንዳለች ይበላታል። 5 በዚያ ቀን የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ለቀሩት ሕዝቡ የክብር ዘውድና የጌጥ አክሊል ይሆናል፤ 6 በፍርድ ወንበር ላይ ለሚቀመጥም የፍርድ መንፈስ፣ ሰልፉን ወደ በር ለሚመልሱም ኃይል ይሆናል። 7 እነዚህም ደግሞ ከወይን ጠጅ የተነሣ ይስታሉ፤ ከሚያሰክርም መጠጥ የተነሣ ይፋንናሉ። ካህኑና ነቢዩ ከሚያሰክር መጠጥ የተነሣ ይስታሉ፣ በወይን ጠጅም ይዋጣሉ። ከሚያሰክርም መጠጥ የተነሣ ይፋንናሉ፤ በራእይ ይስታሉ፣ በፍርድም ይሰናከላሉ። 8 በእውነት፣ ገበታው ሁሉ ትውከትን ተሞልቷል፤ ንጹሕ ስፍራ እንኳ የለም። 9 እውቀትን ለማን ያስተምረዋል፣ ወይስ መልእክቱን ለማን ያስረዳል? ወተትን ለተዉ ወይስ ጡትን ለጣሉ ነውን? 10 ትእዛዝ በትእዛዝ ላይ፣ ትእዛዝ በትእዛዝ ላይ፣ ሥርዓት በሥርዓት ላይ፣ ደንብ በደንብ ላይ፣ እዚህ ጥቂት፣ ጥቂት በዚያ ነው። 11 በእርግጥ፣ በፌዘኛ አፍ በሌሎችም ልሳን ለዚህ ሕዝብ ይናገራል፤ 12 "ይህች እረፍት ናት፣ የደከመውን አሳርፉ፤ ይህችም የምታድስ ማረፊያ ናት" አላቸው፤ እነርሱ ግን አልሰሙም። 13 ስለዚህ ሄደው ወደ ኋላ እንዲወድቁ እንዲሰበሩም ተጠምደውም እንዲያዙ የእግዚአብሔር ቃል ትእዛዝ በትእዛዝ ላይ፣ ትእዛዝ በትእዛዝ ላይ፣ ሥርዓት በሥርዓት ላይ፣ ሥርዓት በሥርዓት ላይ፣ ጥቂት በዚህ ጥቂት በዚያ ይሆንላቸዋል። 14 ስለዚህ በኢየሩሳሌም ያለውን ይህንን ሕዝብ የምትገዙ ፌዘኞች ሆይ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ። 15 እናንተም፣ "ከሞት ጋር ቃል ኪዳን አድርገናል፣ ከሲኦልም ጋር ተማምለናል፤ ስለዚህ ሐሰትን መሸሸጊያችን አድርገናልና፣ በሐሰትም ተሰውረናልና የሚትረፈረፍ መቅሠፍት ባለፈ ጊዜ አይደርስብንም" አላችሁ። 16 ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። "ተመልከቱ፡ በጽዮን የመሠረት ድንጋይን አስቀምጣለሁ፤ የተፈተነውን ድንጋይ፣ የከበረውን፣ መሠረቱ የጸናውን የማዕዘን ድንጋይ። የሚያምን እርሱ አያፍርም። 17 ለገመድ ፍርድን፣ ለቱንቢም ጽድቅን አደርጋለሁ። በረዶውም የሐሰትን መሸሸጊያ ይጠርጋል፣ ውኆችም መሰወሪያውን ያሰጥማሉ። 18 ከሞትም ጋር ያደረጋችሁት ቃል ኪዳን ይፈርሳል፣ ከሲኦልም ጋር የተማማላችሁት መሐላ አይጸናም። የሚትረፈረፍ መቅሠፍት ባለፈ ጊዜ ትረገጡበታላችሁ። 19 ባለፈም ጊዜ ይወስዳችኋል፤ ማለዳ ማለዳ ቀንና ሌሊት ያልፋል፤ መልእክቱ በገባቸው ጊዜ ድንጋጤ ይሆናል። 20 ሰው በእርሱ ላይ ተዘርግቶ ቢተኛ አልጋው አጭር ነው፤ ሰውም ሰውነቱን መሸፈን ቢወድድ ብርድልብሱ እጅግ ጠባብ ነው።" 21 እግዚአብሔርም ሥራውን፣ ማለትም እንግዳ የሆነ ሥራውን ይሠራ ዘንድ፣ አድራጎቱንም ማለት ያልታወቀውን አድራጎቱን ያደርግ ዘንድ በፐራሲም ተራራ እንደ ነበረ ይነሣል፣ በገባዖንም ሸለቆ እንደ ነበረ ይቈጣል። 22 አሁንም እስራት እንዳይጸንባችሁ አታፊዙ። በምድር ሁሉ ላይ የሚጸናውን የጥፋት ትእዛዝ ከሠራዊት ጌታ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሰምቻለሁና። 23 በትኩረት አድምጡና ድምፄን ስሙ፤ ልብ አድርጉ ንግግሬንም ስሙ። 24 በውኑ ገበሬ ሊዘራ ሁልጊዜ ያርሳልን? ወይስ ሁልጊዜ እርሻውን ይጎለጉላልን? 25 እርሻውን ባስተካከለ ጊዜ ጥቁሩን አዝሙድ፣ ከሙኑንም፣ ስንዴውንም፣ በተርታ፣ ገብሱንም በስፍራው፣ አጃንም በደረጃው የሚዘራ አይደለምን? 26 አምላኩ ያስታውቀዋል፣ በብልሃት ያስተምረውማል። 27 በተጨማሪም፣ ጥቁሩ አዝሙድ በተሳለች መሄጃ አያስኬድም፣ የሰረገላም መንኰራኵር በከሙን ላይ አይዞርም፤ ነገር ግን ጥቁሩ አዝሙድ በሸመል ከሙኑም በበትር ይወቃል። 28 የእንጀራ እህል ይደቅቃል፣ ነገር ግን ለዘላለም አያኬደውም፤ የሰረገላውን መንኰራኵርና ፈረሶቹን ምንም ቢያስኬድበት አያደቅቀውም። 29 ይህም ደግሞ ድንቅ ምክር ከሚመክር በግብሩም ማለፊያ ከሆነው ከሠራዊት ጌታ ከእግዚአብሔር ወጥቶአል።

Isaiah 28:1

በወይን ጠጅ በተሸነፉ በወፍራም ሸለቆአቸው ራስ ላይ ... ወዮ ለትዕቢት አክሊል
"አክሊል' የሚለው ከአበባ የሚሠራን ዘውድ ነው። በዚህ ስፍራ ከለምለም ሸለቆ በላይ የተቀመጠችውን የእስራኤልን ዋና ከተማ የሰማሪያ ከተማን ይወክላል። የአክሊል አበባዎች እንደሚያረጁና ውበታቸው እንደሚጠፋ የሰማሪያና የሕዝቧ መጥፋት ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

እነሆ
"ስሙ' ወይም "ልብ በሉ'

በወይን ጠጅ ለተሸነፉ
"በወይን ጠጅ ለሰከሩ'

ጌታ ኃያልና ብርቱ የሆነውን አንድ ሰው ይልካል
በዚህ ስፍራ አንድ ሰው የሚለው ኃያል ሠራዊቱን የሚወክለውን ኃያል ንጉሥ ያመለክታል። አት:- "ጌታ አንድን ንጉሥ ከኃያል ሠራዊቱ ጋር ይልከዋል' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

የበረዶ ዝናብ
"የበረዶ ዝናብ' ወይም የበረዶ ወጨፎ ጠንካራ የበረዶ ክፋዮች ከሰማይ ሲወርዱ ይከሰታል። ይህ የሰማሪያን ሕዝብ ለማጥፋት እግዚአብሔር የሚልከውን የጠላት ጦር የሚያመለክት ዘይቤአዊ ንግግር ነው። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

እያንዳንዱን አክሊል ወደ መሬት ይጥለዋል
ንጉሡና ኃያል ሠራዊቱ የሰማሪያና ሕዝብና ከተማቸውን ማጥፋቱ የሕዝቡን አክሊል ምድር ላይ እንደመጣል ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 28:3

አጠቃላይ መረጃ፡-
ኢሳይያስ የሰማሪያ ሕዝበና ከተማ አክሊል እንደሆኑ አድርጎ መናገሩን ይቀጥላል። (ኢሳይያስ 28:1-2 ተመልከት)

የኤፍሬም ሰካራሞች ትዕቢት አክሊል በእግር ይረገጣል
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት:- "የጠላት ሠራዊት አበባን በእግራቸው እንደሚያደቅቁ የሰማሪያን ትዕቢተኛ ሰካራሞች ያደቅቋቸዋል።' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

የኤፍሬም ... ትዕቢት አክሊል ... በወፍራሙ ሸለቆ ራስ ላይ ያለች
"አክሊል' ከአበባ የተሠራ ዘውድ ነው። በዚህ ስፍራ ከለምለሙ ሸለቆ በላይ የተቀመጠችውን፣ የእስራኤልን ዋና ከተማ፣ የሰማሪያ ከተማን ይወክላል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የረገፈች ... ከመከር በፊት አስቀድማ እንደምትበስል በለስ ትሆናለች
ይህ ከመከር በፊት የበሰለች በለስን እንዳየና ፈጥኖ እንደሚበላ ሰው የጠላት ወታደሮች የሰማሪያን ውበት እንደሚያዩና ፈጥነው እንደሚበዘብዟት ይናገራል። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Isaiah 28:5

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር
ይህንን በኢሳይያስ 1:9 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ውብ ዘውድና የውበት አክሊል ይሆናል
እንደ እውነተኛ ንጉሣቸው ለብሰውት ለሚያከብሩት ሕዝብ እግዚአብሔር ውብ ዘውድ እንደሚሆን ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ውብ ዘውድና የውበት አክሊል
የሁለቱም ትርጉም አንድ ነው። አት፦ "ውብ ዘውድ' (የሁለት ነገሮች ተመሳሳይነት ተመልከት)

ሕዝብ፣ በፍርድ ወንበር ላይ ለሚቀመጥም የፍትህ መንፈስ፣ ... ብርታትም
እንደ "ፍትህ' እና "ብርታት' ያሉ የነገር ስሞች በቅጽልነት እንዲገለጹ ይህ እንደገና ሊጻፍ ይችላል። አት፦ "ሕዝብ፣ እግዚአብሔር ዳኞችን ጻድቃን እንዲሆኑ ያደርጋል እንዲሁም ብርቱዎች ያደርጋቸዋል' (የነገር ስም ተመልከት)

የፍትህ መንፈስ
የፍትህ መንፈስ ያለው ሰው የፍትሃዊነት ባሕርይ ያለውና ጻድቅ ሰው ነው። (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

በፍርድ ወንበር ላይ ለሚቀመጥ
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር የዳኝነት ሥልጣን ያለው ሰው ማለት ነው። (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

በበራቸው ጠላቶቻቸውን ወደ ኋላ ለሚመልሱ ብርታትን
በዚህ ስፍራ "ወደ ኋላ ለሚመልሱ' የሚለው በጦርነት ለሚያሸነፉ የሚል ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፦ "ጠላቶች ከተማቸውን ሲያጠቁ ጠላቶቻቸውን ያሸንፉ ዘንድ እግዚአብሔር ወታደሮቹን ብርቱዎች ያደርጋቸዋል' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 28:7

ነገር ግን እነዚህም እንኳን
"ነገር ግን መሪዎቹ እንኳን'

ካህኑና ነቢዩ
ይህ አንድ የተወሰነ ካህን ወይም ነቢይ ማለት አይደለም። ካህናትንና ነቢያትን በአጠቃላይ ያመለክታል። አት፦ "ካህናትና ነቢያት' (አጠቃላይ ስማዊ ሐረጎች ተመልከት)

ከወይን ጠጅ የተነሣ ይንገዳገዳሉ፣ ከሚያሰክርም መጠጥ የተነሣ ይንደፋደፋሉ
እነዚህ ሁለት ሃረጎች በመሠረቱ የሚናገሩት ስለ አንድ ነገር ሲሆን ሰካራሞች ከመሆናቸው የተነሣ ካህናቱና ነቢያቱ ሥራቸውን መሥራት እንዳልቻሉ አጽንዖት ይሰጣሉ። አት፦ "ሰካራሞች ስለሆኑ በየአካባቢው ይንገዳገዳሉ' (አጓዳኝነት ተመልከት)

በወይን ጠጅም ይዋጣሉ
በተገቢው ሁኔታ ማሰብ እስከማይችሉ ድረስ ይጠጡ ስለነበር የወይን ጠጅ እንደዋጣቸው ተደርጎ ተነግሮአል። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "የወይን ጠጅ እንዲደነጋገርባቸው አደርጓል' (ሰስዕላዊ ንግግርና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

በራእይ ይንገዳገዳሉ በፍርድም ይደነቃቀፋሉ
በትክክል ለመራመድ አብዝተው እንደሚጠጡ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ራእይ ለመረዳት ወይም መልካም ፍርድ ለማድረግ አብዝተው ይጠጣሉ።

Isaiah 28:9

እውቀትን ለማን ያስተምራል ወይስ መልእክቱን ለማን ያብራራል
ሰካራሞቹ ነቢያትና ካህናት ሊያርማቸው የሚፈልገውን ኢሳይያስን ለመተችት ጥያቄ ይጠቀማሉ። አት፦ "ሰካራሞቹ ነቢያትና ካህናት፣ 'ኢሳይያስ ስለ እግዚአብሔር መልእክት ሊያስተምረን እየሞከረ አይደለምን!' ይላሉ' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ወተትን ለተዉ ወይስ ጡትን ለጣሉ ነውን
እንደ ሕፃናት እንደተመለከታቸው ስለተሰማቸው ሰካራሞቹ ነቢያትና ካህናት ኢሳይያስን ለመተቸት ጥያቄ ይጠቀማሉ። አት፦ "እንደ ሕፃናት ሊመለከተን አይገባም' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ እና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ትእዛዝ በትእዛዝ፣ ትእዛዝ በትእዛዝ፣ ሥርዓት በሥርዓት፣ ሥርዓት በሥርዓት፣ ጥቂት በዚህ ጥቂት በዚያ
ለሕፃን እንደሚናገር ኢሳይያስ ቀላል ትእዛዛትን እንደሚደጋግም ስለተሰማቸው ሰካራሞቹ ነቢያትና ካህናት ኢሳይያስን ይተቻሉ።

Isaiah 28:11

ለዚህ ሕዝብ በሚያላግጡ ከንፈሮችና በባዕድ ልሳን ይናገራል
በዚህ ስፍራ "ከንፈሮች' እና "ልሳን' የሚለው እስራኤላውያን ከሚናገሩት የተለየ ቋንቋ የሚናገሩትን ባዕዳን ይወክላል። ይህ እስራኤላውያንን የሚወጋውን የአሦራውያንን ሠራዊት እንደሚያመልክት ይጦቅማል። አት፦ "እግዚአብሔር ለዚህ ሕዝብ የባዕድ ቋንቋ በሚናገሩ የጠላት ወታደሮች አማካይነት ይናገራል።' (ተለዋጭ ስም እና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

የሚያላግጡ ከንፈሮች
"የሚንተባተቡ ከንፈሮች'

ዕረፍት ይህች ናት
"ዕረፍት' የሚለው የነገር ስም በማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "ይህ ማረፊያ ቦታ ነው።' (የነገር ስም ተመልከት)

ለደከመው ዕረፍት ስጡ
"ዕረፍት' የሚለው የነገር ስም በማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "የደከመው ማንም ይምጣና ይረፍ' (የነገር ስም ተመልከት)

ይህችም ማረፊያ ናት
ማረፊያ የሚለው የነገር ስም በማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "ይህ ልትታደስ የምትችልበት ቦታ ነው' (የነገር ስም ተመልከት)

Isaiah 28:13

ስለዚህ ... የእግዚአብሔር ቃል
ስለዚህ ... የእግዚአብሔር መልእክት

ትእዛዝ በትእዛዝ፣ ትእዛዝ በትእዛዝ፣ ሥርዓት በሥርዓት፣ ሥርዓት በሥርዓት፣ ጥቂት በዚህ ጥቂት በዚያ
እነዚህ ኢሳይያስ እንዴት እያስተማራቸው እንዳለ ለመተቸት ሰካራሞቹ ነቢያትና ካህናት የሚጠቀሙባቸው ቃላት ናቸው። ይህንን በኢሳይያስ 28:10 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ስለዚህ ሄደው ወደ ኋላ እንዲወድቁ፣ እንዲሰበሩም፣ እንዲጠመዱ፣ እንዲማረኩም
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "የአሦር ሠራዊት ይመጣና ያሸንፋቸው፣ ምርኮኞችም አድርጎ ይወስዳቸው ዘንድ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሄደው ወደ ኋላ እንዲወድቁ፣ እንዲሰበሩም
ሕዝቡ በጦርነት በጠላት ሠራዊት መሸነፉ ሕዝቡ እንደሚወደቅና እንደሚሰበር ተደርጎ ተነገሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

እንዲጠመዱ
የእስራኤልን ሕዝብ የሚማርኩ የጠላት ወታደሮች እንሰሳን በወጥመድ እንደሚያጠምዱ አዳኞች ተደርገው ተገልጸዋል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 28:14

ስለዚህ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ
"ስለዚህ የእግዚአብሔርን መልእክት ስሙ'

ከሞት ጋር ቃል ኪዳን አድርገናል፣ ከሲኦልም ጋር ተስማምተናል
በመሠረቱ ሁለቱም አረፍተ ነገሮች የሚናሩት አንድ ነገር ነው። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) የኢየሩሳሌም መሪዎች የሙታን መኖሪያ አማልክት ከመሞት እንዲጠብቋቸው ከእነርሱ ጋር ስምምነት ለማድረግ በመጣር አስማትና ጥንቆላ ተጠቅመዋል ወይም 2) ይህ መሪዎቹ ከግብጽ መሪዎች ጋር ስምምነት ማድረጋቸውን የሚገልጽ ስዕላዊ ንግግር ነው። የኢየሩሳሌም መሪዎች ከሙታን መኖሪያ አማልክት ጋር ስምምነት እንዳደረጉ ሁሉ ግብጻውያንም ጥበቃ ማድረግ እንደሚችሉ ተማምነዋል። (አጓዳኝነትና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የሚያጥለቀልቅ መቅሠፍት ባለፈ ጊዜ አይደርስብንም
ይህ የእግዚአብሔር ፍርድና ቅጣት ሕዝቡን እንደሚመታ ጅራፍ ተደርጎ ተነግሮአል። ጅራፉም በኢየሩሳሌም እንደሚያልፍ ጎርፍ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፦ "ስለዚህም ሰው ሁሉ ሲሰቃይና ሲሞት፣ የሚጎዳን ምንም ነገር የለም።' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ውሸትን መሸሸጊያችን አድርገናልና፣ በሐሰትም ተሰውረናልና
በመሠረቱ ሁለቱም ሐረጎች የሚናገሩት አንድ ነገር ነው። ወሸት እና ሐሰት ሰው ሄዶ እንደሚሸሸግባቸው ቦታ ተደርገው ተነግረዋል። በኢየሩሳሌም የሚገኙ መሪዎች በውሸት እንደሚታመኑ አልተናገሩም። በእርግጥ ደኅንነታቸው አስተማማኝ እንደሆነ አምነዋል። ነገር ግን በውሸት ስለታመኑ ደኅንነታቸው አስተማማኝ እንዳልሆነ ኢሳይያስ ያውቃል። አት፦ "ውሸትና ሐሰት ከአደጋ ልንሸሸግባቸው እንደምንችልባቸው ቦታ ሆነዋልና' (አጓዳኝነትና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ውሸትን መሸሸጊያችን ... በሐሰትም ተሰውረናልና
ሊሆኑየሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) መሪዎቹ ራሳቸውን ለመጠበቅ በዋሹአቸው በገዛ ራሳቸው ውሸቶች ይታመናሉ ወይም 2) መሪዎቹ ከሙታን መኖሪያ ሐሰተኛ አማልክት ጋር ያደረጉት ኪዳን በሰላም እንደሚጠብቃቸው ይታመናሉ ወይም 3) መሪዎቹ ከግባጻውያን ጋር ያደረጉት ስምምነት በሰላም እንደሚጠብቃቸው ይታመናሉ

Isaiah 28:16

እይ
"ተመልከት' ወይም "ስማ' ወይም "ለምነግርህ ትኩረት ስጥ'

በጽዮን የመሠረት ድንጋይ አስቀምጣለሁ ... የጸናውን መሠረት
እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ለመርዳት ጠንካራ ሰው መላኩ እግዚአብሔር ለአንድ ሕንፃ ጠንካራ መሠረት እንደሚገነባ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የተፈተነውን ድንጋይ
"ጠንካራ የሆነውን ድንጋይ'

አስተማማኝ መሠረት
"ጽኑ ደጋፊ'

የሚያምንም አያፍርም
"ማንም በዚህ የመሠረት ድንጋይ የሚታመን አይጸጸትም'

Isaiah 28:17

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለሕዝቡ በኢየሩሳሌም የሚያደርገውን ሕንፃን ከሚመሠርት ገንቢ ጋር ማነጻጸሩን ይቀጥላል። (ኢሳይያስ 28፡16)

ለመለኪያ ገመድ ፍትህን ለቱምቢም ጽድቅን አደርጋለሁ
ሕዝቡ ፍትሐዊና ጻድቅ መሆኑን ለመወሰን እግዚአብሔር በፍርዱና በጽድቁ መሠረት መፈተኑ አንድ ነገር ተገቢ ቁመት ያለውና ፍጽም የተስተካከለ መሆኑን ለመወሰን መለኪያ መሣሪያዎች እንደሚጠቀም ግንበኛ ተደርጎ ተገልጾአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

መለኪያ ገመድ
ግንበኛ የአንድ ነገር ቁመት ትክክል እንደሆነ ለመወሰን መለኪያ ገመድ ይጠቀማል።

ቱምቢ
ግንበኛ አንድ ነገር ቀጥ ያለና የተስተካከለ መሆኑን ለመወሰን ቱምቢ ይጠቀማል።

በረዶ ጠርጎ ይወስደዋል
እግዚአብሔር ከፍተኛ መጠን ያለው በረዶ እንዲወርድ ማድረጉ የሚያጠለቀልቅ ጎርፍ እንደሚሆን ተደርጎ ተነግሮአል። አት፦ "የበረዶ ዶፍ ያጠፋል' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በረዶ ... የውኃ ሙላት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) ጥፋትን የሚያስከትል የትኛውንም ነገር በአጠቃለይ የሚወክሉ ተለዋጭ ስሞች ናቸው ወይም 2) የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ለማጥፋት እግዚአብሔር የሚልከውን የጠላት ሠራዊት የሚያመለክት ስዕላዊ ንግግር ነው (ተለዋጭ ስምና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የውሸቶች መሸሸጊያ ... መሰወሪያ
ይህ ውሸቶች ሰው ሄዶ እንደሚሸሸግባቸው ቦታ አድርጎ ይናገራል። የኢየሩሳሌም መሪዎች ከእግዚአብሔር ቁጣ ይጠብቀናል ብለው የታመኑበትን ይወክላሉ። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) መሪዎቹ ራሳቸውን ለመጠበቅ በተናገሩት በገዛ ራሳቸው ውሸቶች ይታመናሉ ወይም 2) መሪዎቹ በሰላም እንዲጠብቃቸው ከሙታን መኖሪያ የሐሰት አማልክት ጋር ባደረጉት ቃል ኪዳን ይታመናሉ ወይም 3) መሪዎቹ በሰላም እንዲጠብቃቸው ከግብፃውያን ጋር ባደረጉት ስምምነት የታመናሉ። ተመሳሳይ ሐረግ በኢሳይያስ 28፡15 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። (ስዕላዊ ንግግር እና እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

Isaiah 28:18

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል።

ከሞትም ጋር ያደረጋችሁት ቃል ኪዳን ይፈርሳል፣ ከሲኦልም ጋር የተማማላችሁት መሐላ አይቆምም
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "ከሞት ጋር ያላችሁን ቃል ኪዳን ከሲኦልም ጋር ያላችሁን ስምምነት እሰርዘዋለሁ።' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ከሞት ጋር ... ቃልኪዳን ... ከሲኦልም ጋር ስምምነት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) የኢየሩሳሌም መሪዎች የሙታን መኖሪያ አማልክት ከመሞት እንዲጠብቋቸው ከእነርሱ ጋር ስምምነት ለማድረግ በመጣር አስማትና ጥንቆላ ተጠቅመዋል ወይም 2) ይህ መሪዎቹ ከግብጽ መሪዎች ጋር ስምምነት ማድረጋቸውን የሚገልጽ ስዕላዊ ንግግር ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የኢየሩሳሌም መሪዎች ከሙታን መኖሪያ አማልክት ጋር ስምምነት እንዳደረጉ ሁሉ ግብጻውያንም ጥበቃ ማድረግ እንደሚችሉ ተማምነዋል። ይህንን በኢሳይያስ 28:15 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት (አጓዳኝነትና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

አይቆምም
"አይጸናም'

የሚጠራርግ ጎርፍ ባለፈ ጊዜ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች:- 1) ጎርፍ ጥፋት ሊያደርስ የሚችል የትኛውንም ነገር በአጠቃላይ የሚወክል ተለዋጭ ስም ነው ወይም 2) ጎርፍ የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ለማጥፋት እግዚአብሔር የሚልከውን የጠላት ሠራዊት የሚያመለክት ስዕላዊ ንግግር ነው (ተለዋጭ ስምና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በእርሱ ትጥለቀለቃላችሁ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት:- "ያጥለቀልቃችኋል' ወይም "ያጠፋችኋል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ማለዳ ማለዳ
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት:- "በየቀኑ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ቀንና ሌሊት
"ሙሉ ቀኑን' ማለት ነው። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 28:20

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል።

ሰው በእርሱ ላይ ተዘርግቶ ቢተኛ አልጋው አጭር ነው፤ ሰውም ሰውነቱን መሸፈን ቢወድድ መጎናጸፊያ ጠባብ ነው
ይህ ምናልባት ሕዝቡ በዚያ ዘመን የሚያውቀው ምሳሌ ነው። በጣም አጭር እንደሆነ አልጋ ወይም በጣም ጠባብ እንደሆነ መጎናጸፊያ ከእግዚአብሔር ቅጣት በሳለም ይጠብቀናል ብለው የተማመኑበት ያሳዝናቸዋል። (ምሳሌዎች ተመልከት)

እግዚአብሔር ይነሣል
እግዚአብሔር ለሥራ መዘጋጀቱ ተቀምጦ እንደነበረና እንደሚነሣ ተደርጎ ተነግሮአል።

በፐራሲም ተራራ ... በገባዖንም ሸለቆ
እነዚህ እግዚአብሔር የጠላትን ሠራዊት በተዓምራት ያሸነፈባቸውን ቦታዎች ያመለክታሉ። (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ እና የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

ራሱን ይቀሰቅሳል
"ይቆጣል

እንግዳ ሥራውን ... ያልታወቀ አደራጎቱን
እነዚህ ሁለት ሐረጎች አንድ ነገር ይናገራሉ። የኢየሩሳሌም ሕዝብ ጠላቶቻቸውን እንዲያሸንፉ ከመርዳት ይልቅ የኢየሩሳለምን ሕዝብ ለማሸነፍ እግዚአብሔር የጠላትን ሠራዊት መጠቀሙ እንግዳ ሥራ ነው።

Isaiah 28:22

አሁን
ይህ "በዚቺ ቅጽበት' ማለት ሳይሆን ወደ የሚከተለው አስፈላጊ ነጥብ ትኩረትን ለመሳብ ጥቅም ላይ የዋለ ነው።

እስራታችሁ ይጠብቃል
የእግዚአብሔር ሕዝቡን መቅጣት እጅግ በከፋ ሁኔታ እስራታቸውን እንደሚያጠብቅ ተደርጎ ተነግሮአል። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት:- "እግዚአብሔር እስራታችሁን ያጠብቃል' ወይም "እግዘአብሔር በጣም በከፋ ሁኔታ ይቀጣችኋል' (ስዕላዊ ንግግርና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር
ይህንን በኢሳይያስ 1:9 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

በምድር ላይ የተወሰነውን ጥፋት
ጥፋት የሚለው የነገር ስም አጠፋ በሚለው ማሰሪያ አንቀጽ እንዲገለጽ ይህ እንደገና ሊጻፍ ይችላል። አት:- "በመላ ምድሪቱ ሕዝቡን ያጠፋል' (የነገር ስም ተመልከት)

Isaiah 28:23

አጠቃላይ መረጃ
ይህ በ28:29 የሚያልቀውን ምሳሌ ይጀምራል። (ምሳሌዎች ተመልከት)

አድምጡ ድምፄንም ስሙ፣ልብ አድርጉ ንግግሬንም ስሙ
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚናገሩት አንድ ነገር ነው። ሁለተኛው ሐረግ የመጀመሪያውን ለማጠናከር ጥቅም ላይ የዋለ ነው። (አጓዳኝነት ተመልከት)

ድምፄንም
በዚህ ስፍራ ድምፅ የሚለው ኢሳይያስ የተናገረውን ይወክላል። አት:- "ለተናገርኩት' (ምትክ ቃል ተመልከት)

ንግግሬንም
መልእክቴንም

ለመዝራት ቀኑን ሙሉ የሚያርስ ገበሬ ሁልጊዜ ያርሳልን? ወይስ ሁልጊዜ እርሻውን ይገለግላልን? ጓሉንስ ይከሰክሳልን?
ሕዝቡ በጥልቀት እንዲያስብ ኢሳይያስ አሳብ ገላጭ ጥያቄ ይጠቀማል። አት:- "ገበሬ ዘርን ሳይዘራ መሬትን ደግሞ ደጋግሞ አያርስም ያለማቋረጥም አፈሩ ላይ አይሰራም' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

Isaiah 28:25

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ ምሳሌውን መንገሩን ይቀጥላል። (ምሳሌዎች ተመልከት)

እርሻውን ባስተካከለ ጊዜ
ገበሬው መሬቱን ባረሰ ጊዜ

ጥቁሩን አዝሙድ፣ ከሙኑንም፣ ስንዴውንም በተርታ፣ ገብሱንም በስፍራው፣ አጃንም በዳርቻው የሚዘራ አይደለምን
ኢሳይያስ የኢየሩሳሌም ሰዎች በጥልቀት እንዲያስቡ ጥያቄ ይጠቀማል። ቋንቋህ ለእያንዳንዱ የዘር ዓይነት ቃል ከሌለው ጠቅለል ተደርገው ሊገለጹ ይችላሉ። አት:- "በእርግጥ እያንዳንዱን የዘር ዓይነት በትክክለኛው መንገድና በተገቢው ቦታ ይተክላል።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

አዝሙድ ... ከሙን
እነዚህ የቅመማ ቅመም ተክሎች ስሞች ናቸው። (የማይታወቁትን ስለመተርጎም ተመልከት)

ስንዴ ... ገብስ ... አጃ
እነዚህ የእህል ተክሎች ስሞች ናቸው። ተርጓሚዎች በአጠቃላይ የእህል የዘር ዓይነቶች በሚል ሊወክሏቸው ይችላሉ። (የማይታወቁትን ስለመተርጎም ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይህንም ብልሃት አምላኩ ያስታውቀዋል ያስተምረዋልም
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች አንድ ነገር ይናገራሉ። አት፡- "ገበሬው እያንዳንዱን የተክል ዓይነት እንዴት መንከባከብ እንዳለበት እንዲያውቅ እግዚአብሔር ይረዳዋል' (አጓዳኝነት ተመልከት)

Isaiah 28:27

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለኢየሩሳሌም ምሳሌ መንገሩን ይቀጥላል። (ምሳሌዎች ተመልከት)

ጥቁር አዝሙድ በተሳለች ማሄጃ አያኬድም
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ገበሬው የጥቁር አዝሙድን ፍሬ ከተክሉ በከባድ ማሄጃ አይለይም' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ጥቁር አዝሙድ
ይህንን በኢሳይያስ 28፡25 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ወይም የሰረገላ መንኮራኩር በከሙን ላይ አያዞርም
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ወይም ከባድ መንኮራኩር በከሙን ዘር ላይ አያሽከረክርም' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ከሙን
ይህንን በኢሳይያስ 28፡25 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ነገር ግን ጥቁር አዝሙድ በሸመል ከሙኑንም በበትር ይወቃል
ፍሬውን ከተክሉ ለመለየት ለገበሬው ትክክለኛ የሆነውን መንገድ ኢሳይያስ ይገልጻል። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ነገር ግን ጥቁር አዝሙዱን በሸመል ይወቃዋል፣ ከሙንም በዱላ ይወቃዋል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

እህል ለእንጀራ ይወቃል እንጂ ፈጽሞ አይደቅም
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ገበሬ እህልን ለእንጀራ ይወቃዋል እንጂ በጣም ትንንሽ እንዲሆን አይወቃውም' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

Isaiah 28:29

ይህም በጥበብ ግሩም ከሆነው መጥቶአል
ይህ በኢሳይያስ 28፡23 የተጀመረውን ምሳሌ ይቋጫል። ስለ መዝራትና መውቃት የእግዚአብሔርን መመሪያ ለመስማት ገበሬዎቹ አስተዋዮቹ መሆናቸው ምሳሌው የሚያመልክተው ትምህርት ነው። ነገር ግን የኢየሩሳሌም መሪዎች በኢሳይያስ በኩል የሚናገረውን የእግዚአብሔር መመሪያ የማይሰሙ ሞኞች ናቸው። (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ)

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር
ይህንን በኢሳይያስ 1፡9 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 29

1 ዳዊት ሰፍሮባት ለነበረችው ከተማ ለአርኤል፣ ወዮላት! ዓመት በዓመት ላይ ጨምሩ፣ በዓላትም ተመልሰው ይምጡ። 2 ነገር ግን አርኤልንም እከብባለሁ፣
ለቅሶና ዋይታም ይሆንባታል፤ ለእኔም እንደ አርኤልም ትሆንልኛለች። 3 በዙሪያሽም እሰፍራለሁ፣ በቅጥርም ከብቤ አስጨንቅሻለሁ፣ አምባም በላይሽ
አቆማለሁ። 4 ትዋረጂማለሽ፣ በመሬትም ላይ ሆነሽ ትናገሪያለሽ፣ ቃልሽም ዝቅ ብሎ ከአፈር ይወጣል፤ ድምፅሽም ከመሬት እንደሚወጣ እንደ መናፍስት ጠሪ
ድምፅ ይሆናል፣ ቃልሽም ከአፈር ወጥቶ በደካማነት ይጮኻል። 5 ነገር ግን የጠላቶችሽ ብዛት እንደ ደቀቀ ትቢያ፣ የጨካኞችም ብዛት እንደሚያልፍ ገለባ
ይሆናል። በድንገት፣ በፍጥነትም ይሆናል። 6 የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር በነጐድጓድ፣ በምድርም መናወጥ፣ በታላቅም ድምፅ፣ በዐውሎ ነፋስም፣
በወጨፎም፣ በምትባላም በእሳት ነበልባል ይጐበኛታል። 7 በአርኤልም ላይ የሚዋጉ፣ እርስዋንና ምሽግዋንም የሚወጉ የሚያስጨንቋትም፣ የአሕዛብ ሁሉ
ብዛት እንደ ሕልምና እንደ ሌሊት ራእይ ይሆናል። ሊያስጨንቋት እርሷንና ምሽጎቿን ያጠቃሉ። 8 የተራበ ሰው በሕልሙ ሲበላ እንደሚያይ፣ ነገር ግን ሲነቃ ሆዱ
ባዶ እንደሆነው ያክል ነው። የተጠማም ሰው በሕልሙ እየጠጣ እንደሚያይ፣ ነገር ግን ሲነቃ ጥሙ ሳይቆርጥለት ይዘላል። እንዲሁ የጽዮንን ተራራ የሚወጉ
የአሕዛብ ሁሉ ብዛት ይሆናል። 9 ለራሳችሁ ተደነቁ፣ ተገረሙም፤ ራሳችሁን አሳውሩ፣ የታወራችሁ ሁኑ! በወይን ጠጅ አይሁን እንጂ ሰከሩ፤ በሚያሰክር መጠጥ
አይሁን እንጂ ተንገደገዱ። 10 እግዚአብሔር የጥልቅ እንቅልፍ መንፈስ አፍስሶባችኋል። ዐይኖቻችሁን አጨፍኗል፣ ራሶቻችሁን ደግሞ ነቢያት
አጨፍነውባችኋል። 11 ራእይ ሁሉ እንደ ታተመ መጽሐፍ ቃል ሆኖባችኋል፤ ማንበብንም ለሚያውቅ። ይህን አንብብ ብለው በሰጡት ጊዜ እርሱ። ታትሞአልና
አልችልም ይላቸዋል፤ 12 ደግሞም መጽሐፉን ማንበብን ለማያውቅ "ይህን አንብብ" ብለው በሰጡት ጊዜ እርሱ፣ "ማንበብ አልችልም" ይላቸዋል። 13 ጌታም
አለ፣ "ይህ ሕዝብ በአፉ ወደ እኔ ይቀርባልና፣ በከንፈሮቹም ያከብረኛልና፣ ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነው። የሚያከብሩኝ ሰዎች ባስተማሩት ትእዛዝ ነው። 14 ስለዚህ፣
ተመልከቱ፣ ድንቅ ነገርን በዚህ ሕዝብ መካከል ለማድረግ እቀጥላለሁ፤ ድንቅ ነገርን በድንቅ ነገር ላይ አደርጋለሁ። የጥበበኞቻቸውም ጥበብ ትጠፋለች፣
የአስተዋዮችም ማስተዋል ትሰወራለች።" 15 ምክራቸውን ጥልቅ አድርገው ከእግዚአብሔር ለሚሰውሩ፣ ሥራቸውንም በጨለማ ውስጥ አድርገው፣ "ማን
ያየናል፣ ወይስ ማን ያውቀናል?" ለሚሉ ወዮላቸው! 16 ነገሮችን ገለባብጣችኋል! የተሠራው ነገር የሠራውን "አልሠራኝም፣" ይለው ዘንድ ሸክላ ሠሪው እንደ
ጭቃው ሊቆጠር ይገባልን? ወይስ የተበጀው ነገር ያበጀውን "አታስተውልም" ይለዋልን? 17 ሊባኖስ እንደ ፍሬያማ እርሻ ሊለወጥ ፍሬያማውም እርሻ እንደ ዱር
ሊቈጠር ጥቂት የቀረው አይደለምን? 18 በዚያም ቀን ደንቆሮች የመጽሐፍን ቃል ይሰማሉ፣ የዕውሮችም ዓይኖች ከጭጋግና ከጨለማ ተለይተው ያያሉ። 19
የተጨቆኑ ደስታቸውን በእግዚአብሔር ያበዛሉ፣ በሰዎች መካከል ያሉ ድሆችም ሐሤትን በእስራኤል ቅዱስ ያደርጋሉ። 20 ጨካኙ ይቋረጣልና፣ ፌዘኛውም
ይጠፋልና። ክፋትን ማድረግ የሚወድዱ ይወገዳሉ። 21 እነዚህም ሰውን በነገር በደለኛ የሚያደርጉ። በበርም ለሚገሥጸው ወጥመድ የሚያኖሩ፣ ጻድቁንም
በከንቱ ውሸት የሚያስቱ ናቸው። 22 ስለዚህ አብርሃምን የተቤዠ እግዚአብሔር ስለ ያዕቆብ ቤት እንዲህ ይላል፣ "ያዕቆብ ከእንግዲህ አያፍርም፣ ፊቱም
አይገረጣም። 23 ነገር ግን የእጄ ሥራ የሆኑትን ልጆቹን ባያቸው ጊዜ ስሜን ይቀድሳሉ። የያዕቆብንም ቅዱስ ይቀድሳሉ፣ የእስራኤልንም አምላክ ይፈራሉ። 24
በመንፈስም የሳቱ ማስተዋልን ያገኛሉ፣ የሚያጕረመርሙም ትምህርትን ይቀበላሉ።"

Isaiah 29:1

ወዮ ለአርኤል
በዚህ ስፍራ አርኤል የሚለው በአርኤል ከተማ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላል። አት፡- ለአርኤል ሰዎች እጅግ አስፈሪ ጊዜ ይሆናል (ምትክ ቃል ተመልከት)

አርኤል
የኢየሩሳሌም ሌላኛው ስም ሲሆን "መሠዊያ' ማለት ነው። "አርኤል' የሚለው ትርጉም በ29፡2 ላይ አስፈላጊ ስለሆነ ከተቻለ "ኢየሩሳሌም' በማለት ፈንታ ይህንን "አርኤል' ብለህ ተርጉም።

ዳዊት ለሰፈረባት
"ዳዊት ላደረባት' ወይም "ዳዊት ለኖረባት'

ዓመት በዓመት ላይ ጨምሩ፣ በዓላትም እየዞሩ ይምጡ
"ዓመት በዓመት በዓላቶቻችሁን ማክበር ቀጥሉ።' ይህ የምፀት ንግግር ነው። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ለእርሱ በሚሠውቡት ስፍራ በዓላቶቻቸውን ማክበር እንዲቀጥሉ ይነግራቸዋል ነገር ግን እነርሱን ከማጥፋት እንደማይከለክለው ያውቃል። (ምፀት ተመልከት)

እከብባታለሁ
በዚህ ውስጥ "እኔ' የሚለው እግዚአብሔርን ያመለክታል። ይህ እግዚአብሔር የጠላትን ሠራዊት ኢየሩሳሌምን አንዲከብብ ማደረጉን ይወክላል። (ምትክ ቃል ተመልከት)

እርሷም
በዚህ ስፍራ "እርሷ' የሚለው የአርኤልን ሕዝብ የምትወክለውን አርኤልን ያመለክታል። አት፡- "የአርኤልም ሕዝብ' (ምትክ ቃል ተመልከት)

ልቅሶና ዋይታ
በመሠረቱ ልቅሶና ዋይታ የሚሉት ቃላት ትርጉማቸው አንድ ሲሆን ለለቅሶው ክብደት አጽንዖት የሚሰጥ ነው። (የሁለት ነገሮች ተመሳሳይነት ተመልከት)

እንደ አርኤል
ተርጓሚዎች "አርኤል የሚለው ስም ‘መሠዊያ’ ማለት ነው' የሚል የግርጌ ማስታወሻ መጨመር ይችላሉ።

Isaiah 29:3

በዙሪያሽም እሰፍራለሁ
በዚህ ውስጥ "እኔ' የሚለው እግዚአብሔርን ያመለክታል፡ ይህ እግዚአብሔር የጠላትን ሠራዊት ኢየሩሳሌምን እንዲከቡ ማደረጉን ይወክላል። አት፡- "የጠላቶችሽን ሠራዊት እንዲከቡሽ አዝዛለሁ' (ምትክ ቃል ተመልከት)

ቅጥር ... የከበባ ሥራ
"ቅጥር' ከረጃጅም ግንቦች ከተሞችን ለማጥቃት ሠራዊቶች የሚገነቡት ማማ ነው። "የከበባ ሥራዎች' ከተሞችን ለማጥቃት ሠራዊቶች የሚገነቧቸውን የተለያዩ የጦር መሳሪያዎችን ያመለክታል። (የማይታወቁትን ስለመተርጎም ተመልከት)

ትዋረጂማለሽ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ጠላትሽ ወደ ታች ያወርድሻል ወይም ጠላትሽ ዝቅ ያደርግሻል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በመሬትም ላይ ሆነሽ ትናገሪያለሽ፣ ቃልሽም ዝቅ ብሎ ከአፈር ይወጣል፣ ድምጽሽም ከመሬት እንደሚወጣ እንደ መናፍስት ጠሪ ድምጽ ይሆናል፣ ቃልሽም ከአፈር ወጥቶ ይጮኻል
በመሠረቱ እነዚህ ሁሉ ዐረፍት ነገሮች የሚናገሩት ስለ አንድ ነገር ነው። አንድ ወቅት በትዕቢት ቃላት ይናገሩ የነበሩ ሰዎች ጠላታቸው ካሸነፋቸው በኋላ ደካሞችና ሐዘንተኞች እንደሚሆኑ አጽንዖት ይሰጣል። አት፡- "ሙታን ከሚያድሩበት ስፍራ መንፈስ እንደሚናገረ እንዲሁ በደካማና የሸክሹክታ ድምፅ ብቻ ትናገራላችሁ' (ዘይቤአዊ ንግግርና አጓዳኝነት ተመልከት)

Isaiah 29:5

የወራሪዎችሽ ብዛት እንደ ደቀቀ ትቢያ፣ የጨካኞችም ብዛት እንደሚያልፍ ገለባ ይሆናል
ወራሪው ሠራዊት በእግዚአብሔር ምን ያህል ደካማና እዚህ ግባ የማይባል መሆኑን አጽንዖት ይሰጣል። አት፡- "እግዚአብሔር የወራሪዎችሽን ብዛትና የጨካኞቹን ብዛት በቀላሉ ያስወግዳል።' (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

የወራሪዎችሽ ብዛት
ጥቃት የሚያደርሱብህ ብዙ ወታደሮች

ጨካኞቹ ... እንደ ገለባ
ተርጓሚው "ይሆናሉ' የሚለውን ማሰሪያ አንቀጽ መጠቀም ይችላል። አት፡- "ምሕረት የማያሳዩሽ ወታደሮች እንደ ገለባ ይሆናሉ' (መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉ ተመልከት)

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ወደ አንቺ ይመጣል
አንቺ የሚለው ቃል የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ያመልክታል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ሊረዳሽ ይመጣል' ወይም 2) "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ሊቀጣሽ ይመጣል' (የ "አንተ' ልዩ ልዩ አጠቃቀሞች)

Isaiah 29:7

እንደ ሕልምና እንደ ሌሊት ራእይ ይሆናል
"የሌሊት ራእይ' የሚለው ሐረግ "ሕልም' ከሚለው ጋር ተመሣሣይ ነው። ሁለቱ ሐረጎች በዚያ እንዳልነበረ እንደ ወራሪው ሠራዊት ፈጥኖ እንደሚሆን አጽንዖት ይሰጣሉ። (የሁለት ነገሮች ተመሳሳይነት እና ዘይቤአዊ አነጋገር ተመልከት)

የሕዝቦች ሁሉ ብዛት
"ከሕዝቦች ሁሉ የሆነ ታላቅ ሠራዊት'

አርኤልን የሚዋጉ
"አርኤል' የሚለው ስም የኢየሩሳሌም ሌላ ስም ሲሆን፣ በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላል። "አርኤልን' በኢሳይያስ 29:1 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። አት፡- "የአርኤልን ሰዎች የሚዋጉ' (ምትክ ስም ተመልከት)

ምሽጎችዋ። እርስዋን ለመጫን እርሷንና ምሽጎችዋን ይወጋሉ
"እርስዋ' የሚለው ቃል በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች የምትወክለውን አርኤልን ያመለክታል። አት፡- "ምሽጎቻቸው። የአርኤልን ከተማና መከላከያዎቿን ይወጋሉ ሕዝቡንም በታለቅ በመከራ ውስጥ እንዲገባ ያደርጋሉ።' (ምትክ ስም ተመልከት)

የተራበ ሰው በሕልሙ እንደሚበላ ይሆናል ... ጥሙ እንደማይረካ
እነዚህ ዘይቤአዊ ንግግሮች ጠላቶች ድል ቢጠብቁም እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን እንዲያሸንፉ ስላልፈቀደላቸው አልተሳካላቸውም ማለት ነው። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

እንዲሁ የጽዮንን ተራራ የሚወጉ የአሕዛብ ሁሉ ብዛት ይሆናል
በዚህ ስፍራ የጽዮን ተራረ የሚለው በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላል። አት፡- "አዎን፣ በጽዮን ተራራ የሚኖሩትን ሰዎች በሚወጉ የሕዝቦች ሠራዊት ላይ ይህ ይሆናል' (ምትክ ስም ተመልከት)

Isaiah 29:9

ራሳችሁ ተደነቁ፣ ተደነቁም
"ራሳችሁ' የሚለው ቃል በኢየሩሳልም የሚኖሩትን ሰዎች ያመልከታል። ለምን እንደሚደነቁ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አት፡- "እየነገርኳችሁ ባለው ነገር ተደነቁ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ እና የሁለት ነገሮች ተመሳሳይነት ተመልከት)

ራሳችሁን አሳውሩ እውሮችም ሁኑ
ሕዝቡ እግዚአብሔር የሚለውን ችላ ማለታቸው ራሳቸውን እንዳሳወሩ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "ለማሳያችሁ ነገር ቸልተኛና በመንፈስ እውር በመሆን ቀጥሉ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በወይን ጠጅ አይሁን እንጂ ስከሩ፤ በሚያሰክር መጠጥ አይሁን እንጂ ተንገድገዱ
ሕዝቡ ማስተዋል የጎደላቸውና እግዚአብሔር እያደረገ ያለው ነገር የማይረዱ መሆናቸው ሰካራሞች እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "እንደ ሰካራም ሰው ማስተዋል የጎደላችሁ ሁኑ ነገር ግን ብዙ ወይንና የሚያሰክር መጠጥ ስለጠጣችሁ አይሁን።' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

እግዚአብሔር የጥልቅ እንቅልፍ መንፈስ አፍስሶባችኋል
በዚህ ስፍራ "የ... መንፈስ' ማለት የእንቅልፋምነት ባሕርይ ያለው መሆን ማለት ነው። እግዚአብሔር ሕዝቡ እንዲተኛ ማድረጉ "መንፈሱ' በሕዝቡ ላይ የሚያፈስሰው ፈሳሽ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮል። "ጥልቅ እንቅልፍ' ማለት ሕዝቡ ማስተዋል የጎደለውና እግዚአብሔር እያደረገ ያለውን የማይረዳ ነው የሚል ትርጉም ያለው ስዕላዊ ንግግር ነው። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ዓይኖቻችሁን ከድኖታል፣ ነቢያቱን፣ ራሶቻችሁንም ሸፍኖታል፣ ባለራእዮችን
እግዚአብሔር ሕዝቡን ማስተዋል የጎደላቸውና እርሱ እየፈጸመው ያለውን የማይረዱ ማድረጉ ማየት እንዳይችሉ ዓይኖቻቸውን እንደከደነውና ራሶቻቸውን እንደሸፈነው ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "እንዲሁም እግዚአብሔር የነቢያቱን ዓይኖች ከድኖአል የባለራእዮቹንም ራሶች ሸፍኖአል' ((ስዕላዊ ንግግርተመልከት))

Isaiah 29:11

ራእዩም ሁሉ እንደ ታተመ መጽሐፍ ቃላት ሆኖባችኋል
በኢየሩሳሌም የሚገኙ ሌሎቹ ነቢያት የእግዚአብሔርን መልእክት መስማትና መረዳት አልቻሉም። አት፡- "እግዚአብሔር ለእናንተ የገለጠው ሁሉ የታተመ መጽሐፍ ይመስላል።' (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

ታተሞአል፣ ለተማረውም ሰጡት
ይህ በአዲስ አረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ታትሞአል። አንድ ሰው የታተመውን መጽሐፍ ማንበብ ለሚችል ለአንድ ሰው ሰጠው።'

መጽሐፉ ማንበብ ለማይችል ለአንዱ ከተሰጠው
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "አንድ ሰው መጽሐፉን ማንበብ ለማይችል ከሰጠው' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

Isaiah 29:13

ይህ ሕዝብ በአፉ ወደ እኔ ይቀርባል፣ በከንፈሮቹም ያከብረኛል
"አፍ' እና "ከንፈር' የሚሉት ቃላት ሕዝቡ የሚናገረውን ይወክላሉ። በዚህም ስፍራ አንድ ነገር መናገርን ነገር ግን በእውነታው የተባለውን የማይል ንግግርን ይወክላል። አት፡- "የኢየሩሳሌም ሰዎች በንግግር እኔን የሚያመልኩና የሚያከብሩ ያስመስላሉ' (ምትክ ስም ተመልከት)

ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነው
በዚህ ስፍራ "ልብ' የሚለው የሰውን አሳብና ስሜት የሚወክል ምትክ ስም ነው። ለእግዚአብሔር በእውነት ያልተሰጠ ሕዝብ ልቡ ከእርሱ ርቆ እንደ ሄደ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "ነገር ግን በአሳቡ አያከብረኝም' ወይም "ነገር ግን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በእውነት ለእኔ የተሰጠ አይደለም' (ምትክ ስም እና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በሰዎች ሥርዓትና ትምህርት ብቻ ያከብሩኛል
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ሰዎች እንዲያደርጉ የነገሯቸው ያ ስለሆነ ብቻ ያከብሩኛል' (አድረጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ስለዚህ፣ እይ፣ በዚህ ሕዝብ መካከል ድንቅ ነገር እንደገና አደርጋለሁ፣ በተዓምራት ላይ ተዓምራት
"ስለዚህ ተመልከትና እይ! ልታብራራቸው የማትችላቸውን አስደናቂና አስገራሚ ነገሮች በመካከልህ አደርጋለሁ'

የጥበበኞቻቸው ጥበብ ትጠፋለች፣ የአስተዋዮቻቸውም ማስተዋል ትሰወራለች
ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች አንድ ነገር ይናገራሉ። እግዚአብሔር ያደረገውን ጠቢባን ሰዎች ሊረዱና ሊያብራሩ አለመቻላቸውን እግዚአብሔር መግለጡ ጥበባቸውና ማስተዋላቸው እንደጠፋ ተደርጎ ተነግሮአል። (አጓዳኝነትና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 29:15

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ እየተናገረ ነው ወይም የ29፡13-14 የእግዚአብሔር ንግግር ቀጥሏል

እቅዳቸውን ጥልቅ አድርገው ከእግዚአብሔር ለሚሰውሩ
ሕዝቡ እግዚአብሔር ስለ እቅዱ ሳያውቅ ለማቀድ መሞከራቸው እግዚአብሔር ሊያይ በማይችልበት በጥልቅ ስፍራ እቅዳቸውን ለመሰውር እንደፈለጉ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "እቅዳቸውን ከእግዚአብሔር ለመሰወር የሚጥሩ' ወይም "ለማድረግ ያቀዱትን እግዚአብሔር እንዳይደርስበት ለመከልከል የሚጥሩ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ሥራቸው በጨለማ የሆነ
በምስጢር ክፉ ነገሮችን እንደሚያደርጉ ተመላክቷል። አት፡- "ማንም ሊያያቸው እንዳይችል ክፉ ነገሮችን በጨለማ ውስጥ የሚያደርጉ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ማን ያየናል? ማንስ ያውቀናል የሚሉ?
የሚያደርጉትን ማንም እንደማያውቅ ማመናቸውን አጽንዖት ለመስጠት ጥያቄ ይጠቀማሉ። አት፡- "የምናደርገውን ማንም እግዚአብሔርም እንኳን አያየንም ወይም አያውቅም!' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

Isaiah 29:17

ሊባኖስ ወደ እርሻነት ይለወጣል፣ እርሻውም ዱር ይሆናል
ሊሁኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ይህ ቃል በቃል የሚተረጎም፣ እግዚአብሔር በሊባኖስ የዱር ዛፍ የሚያድግባቸውን ስፍራዎች ፍሬ የሚሰጡ እርሻዎች እንዲሆኑ እንደሚያደርጋቸው የሚናገር ነው ወይም 2) ይህ በስዕላ ንግግርነት የሚተረጎም ሲሆን የሊባኖስ ትላልቅ ደኖች ኃያላን ጨቋኝ ገዢዎችን፣ ወደ ደንነት የሚለወጠው የእርሻው ሰብል ደግሞ መከራ እያየ ያለውን ተራውን ሕዝብ የሚወክሉ ናቸው። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ሊባኖስ ወደ እርሻነት ይለወጣል
በዚህ ስፍራ "ሊባኖስ' የሚለው በሊባኖስ የሚገኘውን ትልቁን የጥድ ደን ይወክላል። ይህ በአድረጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊተረጎም ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር ታላላቅ የሊባኖስ ደኖችን ወደ እርሻነት ይለውጣቸዋል' (ምትክ ስምና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ደንቆሮች የመጽሐፍ ቃል ይሰማሉ፣የዕውሮችም ዓይኖች ከጥልቅ ጨለማ ውስጥ ያያሉ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ይህ ቃል በቃል እግዚአብሔር ደንቆሮች እንዲሰሙ እውሮችም እንዲያዩ ያደርጋል ማለት ነው ወይም 2) እግዚአብሔር ሕዝቡን መልእክቱን እንዲሰሙና እንዲረዱ ያስችላቸዋል የሚል ትርጉም ያለው ስዕላዊ ንግግር ነው ወይም 3) ሁለቱንም አማራጮች 1 እና 2 ማለት ሊሆን ይችላል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የዕውሮች ዓይኖች
በዚህ ስፍራ ዓይኖች የሰውን ሁለንተና ይወክላሉ። አት፡- "ዕውራን የሆኑቱ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

የተጨቆኑ እንደገና በእግዚአብሔር ደስ ይላቸዋል፣ በሰዎች መካከል ያሉ ድሆችም በእስራኤል ቅዱስ ደስ ይላቸዋል
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች ትርጉማቸው አንድ ነው። አት፡- "ድሆችና የተጨቆኑ ሰዎች እግዚአብሔር፣ የእስራኤል ቅዱሱ ካደረገው ነገር የተነሳ እንደገና ደስ ይላቸዋል።' (አጓዳኝነት ተመልከት)

Isaiah 29:20

ጨካኞች ይጠፋሉና
"ጨካኞች' የሚለው ስማዊ ቅጽል፣ በቅጽልነት ሊቀመጥ ይችላል። አት፡- "ጨካኞች ሰዎች ይጠፋሉና' (ስማዊ ቅጽል ተመልከት)

ፌዘኞቹ ይጠፋሉና
"ፌዘኞች' የሚለው ስማዊ ቅጽል በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊተርጎም ይችላል። አት፡- "የሚያፌዙ ይጠፋሉና' ወይም "የሚያሾፉ ሰዎች ይጠፋሉና' (ስማዊ ቅጽል ተመልከት)

ክፉ ለማድረግ የሚወዱ ሁሉ ይጠፋሉ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ክፉ ማድረግ የሚወዱትን ሁሉ እግዚአብሔር ያጠፋቸዋል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

በቃል ሰውን በደለኛ የሚያደርጉ
ይህ በችሎት አንድን ሰው በመቃወም ምስክርነትን መስጠትን ያመለክታል። አት፡- "አንድን ሰው በመቃወም የሚመሰክርና በደለኛም የሚያደርገው' ወይም "አንዳች ስሕተት ፈጽሟል በሚል ችሎት ላይ ንጽሑን ሰው በደለኛ የሚያደርግ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

በበርም ላይ ፍትሕ ለሚፈልግ ወጥመድ የሚያኖሩ ጻድቁንም በባዶ ሐሰት እንዲሸማቀቅ የሚያደርጉ
መልካሙን ሰው ለማስቆም ክፉ ሰዎች የሚያደርጉት የትኛውም ነገር አዳኝ የሚያድነውን አጥምዶ እንደሚይዝ እንደዚያው ክፉ ሰዎች ወጥመድ እንደሚያጠምዱ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "ተገቢና ትክክል የሆነውን የሚያደርጉትን ለማስቆም ይጥራሉ ይዋሻሉም።' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በበር ላይ ፍትሕ ለሚፈልግ
የከተማይቱ በር ብዙውን ጊዜ የከተማይቱ መሪዎች ሕጋዊ ውሳኔዎችን የሚያስተላልፉበት ቦታ ነው።

Isaiah 29:22

የያዕቆብ ቤት
በዚህ ስፍራ "ቤት' የሚለው ቤተሰብን ይወክላል። አት፡- "የያዕቆብ ትውልዶች' (ምትክ ስም ተመልከት)

አብርሃምን የተቤዠ
ይህ ምናልባት የሚያመለክተው እግዚአብሔር አብርሃምን ከትውልድ አገሩ የጠራበትንና ወደ ተስፋይቱ ምድር የላከበትን ጊዜ ነው። (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ያዕቆብ ከእንግዲህ ወዲያ ... ፊቱ ... ልጆቹን ያያል
በዚህ ስፍራ "ያዕቆብ' የሚለው ትውልዶቹን ይወክላል። አት፡- "የያዕቆብ ትውልዶች ከእንግዲህ ወዲያ ... ፊታቸው ... ልጆቻቸውን ያያሉ' (ምትክ ስም ተመልከት)

ወይም ፊቱ አይለወጥም
ከእንግዲህ ወዲያ አይፈራም የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፡- "ወይም አይፈሩም' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ነገር ግን የእጆቼን ሥራ ልጆቹን ባየ ጊዜ
በዚህ ስፍር እጅ የሚለው የእግዚአብሔርን ኃይልና ሥራ ይወክላል። አት፡- "የሰጠኋቸውን ልጆችና ያደረግሁላቸውን ሁሉ ባየ ጊዜ' (ምትክ ቃል ተመልከት)

ስሜን ይቀድሳሉ
በዚህ ስፍራ "ስም' እግዚአብሔርን ይወክላል። አት፡- "ያከብሩኛል' (ምትክ ስም ተመልከት)

የያዕቆብን ቅዱስ ስም ይቀድሳሉ
በዚህ ስፍራ "ስም' እግዚአብሔርን ይወክላል። እግዚአብሔር ራሱን "የያዕቆብ ቅዱስ' ብሎ ይጠራል። አት፡- "የያዕቆብን ቅዱስ፣ እኔን ያከብሩኛል።' (ምትክ ስምና አንደኛ፣ሁለተኛና ሦሥተኛ መደብ ተመልከት)

የእስራኤልንም አምላክ
እግዚአብሔር ራሱን "የእስራኤል አምላክ' ብሎ ይጠራል። አት፡- "እኔን፣ የእስራኤልን አምላክ' (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሦሥተኛ መደብ ተመልከት)

በመንፈስ የሳቱ
በዚህ ስፍራ "መንፈስ' የሚለው የሰውን ውስጣዊ ማንነት ይወክላል። አት፡- "በሚያስቡት የተሳሳቱ' ወይም "በዝንባሌአቸው የተሳሳቱ' (ምትክ ስም ተመልከት)

መረዳትን ያገኛሉ
የሚረዱት ምን እንደሆነ በማብራራት ይህ በይበልጥ ገልጽ ሊሆን ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔርንና ሕግጋቱን መረዳት ይጀምራሉ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

የሚያጉረመርሙ እውቀትን ይማራሉ
የሚማሩት እውቀት ምን እንደሆነ በማብራራት ይህ በይበልጥ ግልጽ ሊሆን ይችላል። አት፡ "የሚያጉረመርሙ እግዚአብሔር የሚያስተምራቸው እውነት እንደሆነ ማወቅ ይጀምራሉ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 30

1 "ለዓመፀኞች ልጆች ወዮላቸው፣" ይላል እግዚአብሔር። "ከእኔ ዘንድ ያልሆነን ዕቅድ ይመክራሉ፣ ኃጢአትንም በኃጢአት ላይ ይጨምሩ ዘንድ በመንፈሴ
ያልተመራውን የትብብር ኪዳን ያደርጋሉ። 2 ከእኔም ምሪትን ሳይጠይቁ ወደ ግብጽ ይሄዱ ዘንድ ይወጣሉ። በፈርዖን ኃይል ይጸኑ ዘንድ በግብጽም ጥላ ይታመኑ
ዘንድ ይፈልጋሉ። 3 ስለዚህ የፈርዖን ከለላ እፍረት፣ በግብጽም ጥላ መታመን ውርደት ይሆንባችኋል። 4 አለቆቻቸው በጣኔዎስ ቢሆኑ እንኳን፣
መልክተኞቻቸውም ወደ ሓኔስ ቢደርሱ እንኳን። 5 ሁላቸው ይጠቅሙአቸው ዘንድ ስለማይችሉ፣ እፍረትና ስድብ እንጂ ረድኤትና ረብ ስለማይሆኑ ሕዝብ ያፍራሉ።
6 በኔጌቭ ስላሉ አውሬዎች የተነገረ ሸክም፦ ተባትና እንስት አንበሳ እፉኝትም ነዘር እባብም በሚወጡባት በመከራና በጭንቀት ምድር በኩል ብልጥግናቸውን
በአህዮች ጫንቃ ላይ መዛግብቶቻቸውንም በግመሎች ሻኛ ላይ እየጫኑ ወደማይጠቅሙአቸው ሕዝብ ይሄዳሉ። 7 የግብጽ እርዳታ ከንቱና ምናምን ነው፤
ስለዚህ ስሙን፣ ተረጋግጦ የሚቀመጥ ረዓብ ብዬ ጠርቼዋለሁ። 8 አሁንም ሂድ፣ ለሚመጣውም ዘመን ለምስክርነት እንዲሆን በሰሌዳ ላይ በመጽሐፍም
ውስጥ ጻፍላቸው። 9 እነዚህ ዓመፀኛ ሕዝብ ናቸውና፣ የእግዚአብሔርን ሕግ ለመስማት የማይወድዱ የሐሰት ልጆች ናቸውና። 10 ለባለ ራእዮች፣
"አትመልከቱ፤" ይላሉ፣ ለነቢያትም፣ "የለዘበውን ነገር፣ አታላዩን ነገር እንጂ፣ ቀጥተኛውን እውነት አትንገሩን፤ 11 ከመንገድ ፈቀቅ በሉ፤ ከጐዳናውም ዘወር በሉ፤
የእስራኤልንም ቅዱስ ከእኛ ዘንድ አስወግዱ" ይሉአቸዋል። 12 ስለዚህ የእስራኤል ቅዱስ እንዲህ ይላል፣ "ይህችን ቃል አቃልላችሁ፣ በግፍና በጠማምነት
ታምናችኋልና፣ በእርሱም ተደግፋችኋልና፣ 13 ስለዚህ ይህ በደል አዘብዝቦ ለመፍረስ እንደ ቀረበ፣ አፈራረሱም ፈጥኖ ድንገት እንደሚመጣ እንደ ረጅም ቅጥር
ይሆንባችኋል።" 14 የሸክላ ሠሪ ማድጋ እንደሚሰበር ይሰብረዋል፤ ሳይራራም ያደቅቀዋል፤ ከስባሪውም እሳት ከማንደጃ የሚወስዱበት ወይም ውኃ ከጕድጓድ
የሚቀዱበት ገል አይገኝም። 15 የእስራኤል ቅዱስ፣ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፣ "በመመለስና በማረፍ ትድናላችሁ፤ በጸጥታና በመታመን ኃይል
ይሆንላችኋል። እናንተም እንቢ አላችሁ። 16 ነገር ግን፣ 'አይሆንም፣ በፈረስ ላይ ተቀምጠን እንሸሻለን እንጂ እንዲህ አይሆንም' አላችሁ፣ ስለዚህም
ትሸሻላችሁ፤ ደግሞም፣ 'በፈጣን ፈረስ ላይ እንቀመጣለን' አላችሁ፣ ስለዚህም የሚያሳድዱአችሁ ፈጣኖች ይሆናሉ። 17 ከአንድ ሰው ዛቻ የተነሣ ሺህ ሰዎች
ይሸሻሉ፤ እናንተም በተራራ ራስ ላይ እንዳለ ምሰሶ፣ በኮረብታም ላይ እንዳለ ምልክት ሆናችሁ እስክትቀሩ ድረስ፣ ከአምስት ሰዎች ዛቻ የተነሣ ትሸሻላችሁ።"
18 ይሁን እንጂ እግዚአብሔርም የፍርድ አምላክ ነውና ስለዚህ እግዚአብሔር ይራራላችሁ ዘንድ ይታገሣል፣ ይምራችሁም ዘንድ ከፍ ከፍ ይላል፤ እርሱን
በመተማመን የሚጠባበቁ ሁሉ ብሩካን ናቸው። 19 በኢየሩሳሌም ውስጥ በጽዮን የምትኖሩ ሕዝብ ሆይ፣ ከእንግዲህ ወዲህ አታለቅሱም፤ በጩኸትም ድምፅ
ይራራላችኋል፣ በሰማችሁም ጊዜ ይመልስላችኋል። 20 ጌታም የጭንቀትን እንጀራና የመከራን ውኃ ቢሰጥህም፣ አስተማሪህ ከእንግዲህ ከአንተ አይሰወርም፣
ነገር ግን አስተማሪህን በገዛ ራስህ ዐይኖች ታያለህ። 21 ወደ ቀኝም ወደ ግራም ብትዞር ከበስተኋላህ ጆሮችህ "መንገዱ ይህች ናት፣ በእርስዋም ሂድ"
የሚለውን ቃል ይሰማሉ። 22 በብርም የተለበጡትን የተቀረጹትን ምስሎችህን በወርቅም የተለበጡትን ቀልጠው የተሠሩትን ምስሎችህን ታረክሳለህ፤ እንደ
ርኩስ ጨርቅ ትጥላቸዋለህ። "ከዚህ ውጡ" ትላቸውማለህ። 23 በምድርም ለተዘራው ዘርህ ዝናብ ይሰጣል፣ ከምድርም ፍሬ የሚወጣ እንጀራ ወፍራምና ብዙ
ይሆናል። እህሉም ብዙ ይሆናል። በዚያም ቀን ከብቶችህ በሰፊ መስክ ይግጣሉ። 24 መሬትንም የሚያርሱ በሬዎችና አህዮች በመንሽና በወንፊት የነጻውን ጨው
ጨው የሚለውን ገፈራ ይበላሉ። 25 በታላቅም እልቂት ቀን ግንቦች በወደቁ ጊዜ በረጅሙ ተራራ ሁሉ ከፍ ባለውም ኮረብታ ሁሉ ላይ ወንዞችና የውኃ ፈሳሾች
ይሆናሉ። 26 እግዚአብሔርም የሕዝቡን ስብራት በጠገነ ዕለት፣ መቅሰፍቱ ያቈሰለውንም በፈወሰ ዕለት፣ የጨረቃ ብርሃን እንደ ፀሐይ ብርሃን፣ የፀሐይም ብርሃን
እንደ ሰባት ቀን ብርሃን ሰባት እጥፍ ይሆናል። 27 ተመልከቱ፣ የእግዚአብሔር ስም ከሚነድድ ቍጣ ከሚትጐለጐልም ጢስ ጋር ከሩቅ ይመጣል፤ ከንፈሮቹም
ቍጣን የተሞሉ ናቸው፣ ምላሱም እንደምትበላ እሳት ናት። 28 እስትንፋሱም አሕዛብን በአጥፊ ወንፊት ሊነፋቸው እንደሚያጥለቀልቅ እስከ አንገትም
እንደሚደርስ ወንዝ ነው፣ በሕዝብም መንጋጋ የሚያስት ልጓም ይሆናል። 29 ዝማሬ በተቀደሰች የዐውደ ዓመት ሌሊት እንደሚሆን ዝማሬ ይሆንላችኋል፤ ወደ
እግዚአብሔርም ተራራ ወደ እስራኤል አምባ ይመጣ ዘንድ እንቢልታ ይዞ እንደሚሄድ ሰው የልብ ደስታ ይሆንላችኋል። 30 እግዚአብሔርም ክቡር ድምፁን
ያሰማል፣ የክንዱንም መውረድ በሚነድድ ቍጣውና በምትባላ እሳት ነበልባል፣ በዐውሎ ነፋስም በወጨፎም፣ በበረዶ ጠጠርም ይገልጣል። 31 አሦርም
በበትር ከመታው ከእግዚአብሔር ድምፅ የተነሣ ይደነግጣል። 32 እግዚአብሔር በላዩ በሚያወርድበት የታዘዘበቱ የበትር ድብደባ ሁሉ በከበሮና በመሰንቆ
ይሆናል፤ በጦርነትም ክንዱን አንሥቶ ይዋጋቸዋል። 33 ከጥንት ጀምሮ የማቃጠያ ስፍራ ተዘጋጅታለች። በእርግጥ፣ ለንጉሡም ተበጅታለች፣ እግዚአብሔርም
ጥልቅና ሰፊ አድርጎአታል። እሳትና ብዙ ማገዶ ተከምሮአል፤ የእግዚአብሔርም እስትንፋስ እንደ ዲን ፈሳሽ ያቃጥለዋል።

Isaiah 30:1

ዓመፀኞቹ ልጆች
እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ልጆቹ እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኝነት ለመግለጽ እግዚአብሔር በራሱ ስም ይናገራል። አት፦ "እግዚአብሔር ያወጀው ይህ ነው' ወይም "እኔ፣ እግዚአብሔር ያወጅኩት ይህ ነው' (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሦሥተኛ መደብ ተመልከት)

እቅዶችን ያወጣሉ፣ ነገር ግን ከእኔ አይደለም
እቅዶች የሚለው የነገር ስም አቀደ በሚል ማሰሪያ አንቀጽ እንዲገለጽ ይህ እንደገና ሊጻፍ ይችላል። አት፦ "ነገሮችን ለማድረግ አቀዱ፣ ነገር ግን እንዲያደርጉ የምፈልገውን አልጠየቁኝም' (የነገር ስሞች ተመልከት)

ነገር ግን በመንፈሴ አይመሩም
ይህ በአደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "ነገር ግን መንፈሴ አይመራቸውም' (አድራጊ ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

በኃጢአት ላይ ኃጢአት ይጨምራሉ
ኃጢአት በማድረግ መጽናት ኃጢአቶች አንዳቸው በአንዳቸው ላይ እንደሚከመሩ ቁሳ ቁሶች ተደርገው ተነግረዋል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ከፈርዖን ዘንድ ጥበቃ ፈለጉ
"ጥበቃ' የሚለው የነገር ስም "ጠበቀ' በሚለው ማሰሪያ አንቀጽ እንዲገለጽ ይህ እንደገና ሊጻፍ ይችላል። አት፦ "እንዲጠብቃቸው ፈርዖንን ጠየቁት' (የነገሮች ስም ተመልከት)

በግብጽ ጥላ ይሸሸጋሉ
ከጠላት ሠራዊት የሚደረገው የግብጻውያን ጥበቃ ጥላ አንድን ሰው ከሚያቃጥል የፀሐይ ሙቀት እንደሚጠብቅ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፦ "በሰላም እንዲጠብቋቸው በግብጻውያን ይታመናሉ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Isaiah 30:3

አጠቃልይ መረጃ
እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል።

ስለዚህ የፈርዖን ጥበቃ እፍረት በግብጽም ጥላ መሸሸግ ውርደት ይሆንባችኋል
"ጥበቃ'፣ "እፍረት' እና "ውርደት' የተሰኙት የነገር ስሞች እንደ ቅጽሎች ወይም ማሰሪያ አንቀጾች እንዲገለጹ ይህ እንደገና ሊጻፍ ይችላል። አት፦ "ፈርዖን ይጠብቀናል ስትሉ ስለታመናችሁ ታፍራላችሁ፣ በሰላም እንዲጠብቋችሁ በግብጻውያን ስለታመናችሁ ትዋረዳላችሁ' (የነገር ስሞች ተመልከት)

በግብጽ ጥላ መሸሸግ
ከጠላት ሠራዊት የሚደረገው የግብጻውያን ጥበቃ ጥላ አንድን ሰው ከሚያቃጥል የፀሐይ ሙቀት እንደሚጠብቅ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ልዑላኖቻቸው
በዚህ ስፍራ ልዑላን ማለት ሕጋዊ ባለሥልጣን ወይም አምባሰደር ማለት ነው፣ የግድ የንጉሥ ልጆች ማለት አይደለም።

የእነርሱ ... እነርሱ ... እነሱ
እነዚህ ቃላት የይሁዳን ሕዝብ ያመለክታሉ።

ዞአን ... ሓኔስ
እነዚህ በግብጽ ሰሜናዊ ክፍል የሚገኙ ከተሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

ወደ ሓኔስ ቢመጡ
በዚህ ስፍራ "መጣ' የሚለው "ሄደ' ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። (ሄደና መጣ ተመልከት)

ከሕዝቡ የተነሳ
"ከግብጽ ሕዝብ የተነሳ'

Isaiah 30:6

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ክፍል የይሁዳን ሕዝብ በሚመለከት የእግዚአብሔርን አዋጅ ማቅረቡን ይቀጥላል

አዋጅ
"እግዚአብሔር ይህን ያውጃል'

እንስትና ተባት አንበሳ፣ እፉኝትም የሚበርር ቁጡ እባብ
ይህ እንደ እነዚህ ዓይነት እንስሳትን በአጠቃላይ ያመለክታል። አት፦ "እንስትና ተባት አንበሳ በሚያድሩበት ስፍራ፣ እንዲሁም እፉኝትና እባብ ባለበት' (አጠቃላይ ስማዊ ሐረጎች ተመልከት)

ቁጡ በራሪ እባብ
በዚህ ስፍራ "ቁጡ' የሚለው ቃል ምናልባት የእባቡን መርዛማ መናደፍ ያመለክታል፣ "በራሪ' የሚለው ቃልም ፈጣን እንቅስቃሴውን ያመለክታል። ይህንን በኢሳይያስ 14:29 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ኃብታቸውን ያግዛሉ
"የይሁዳ ሰዎች ኃብታቸውን ያግዛሉ'

እስካሁን የሚቀመጥ ረዓብ ብዬ ጠርቼዋለሁ
ስሙ ረዓብ ስለተባለ አስፈሪ የባሕር ፍጡር ታዋቂ የሆነ ታሪኮች አሉ። ረዓብ የሚለው ስም "ጥንካሬ' ወይም "እብሪት' ማለት ነው። አት፦ "ግብጽን ምንም የማያደርግ የሚጮኽ ጉረኛ ብዬ ጠርቼዋለሁ' (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

Isaiah 30:8

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለኢሳይያስ መናገሩን ቀጥሏል

አሁንም
ቃሉ በዚህ ስፍራ ይሁዳን በሚመለከት የእግዚአብሔር አዋጅ ለጊዜው መቋረጡን ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል።

ባሉበት
"የይሁዳ ሰዎች ባሉበት'

ለሚመጣው ዘመን
ይህ ጊዜን በሚመለከት እንደሚጓዝና አንድ ቦታ እንደሚደርስ አድርጎ ይናገራል። አት፦ "ለወደፊቱ ጊዜ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ሐሰተኞች ልጆች፣ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መስማት የማይወዱ ልጆች
ይህ ክፍል የእግዚአብሔር ሕዝብ ልጆቹ እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። ይህ እንደ አዲስ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። አት፦ "አኗኗራቸው እንደሚዋሹና እግዚአብሔር ያዘዛቸውን እንደማይሰሙ ልጆች ነው።' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 30:10

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ስለ ይሁዳ ሰዎች መናገሩን ቀጥሏል።

ከመንገድ ፈቀቅ በሉ፣ ከጎዳናውም ዘወር በሉ
ሕዝቡ እንዴት መኖር እንዳለባቸው እግዚአብሔር ያለው ፍላጎት በላዩ እንደሚከድበት መንገድ ወይም ጎዳና ተደርጎ ተነገሮአል። ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ ሰውዬው ከእግዚአብሔር መንገድ ስቶ እንደሄደ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የእስራኤል ቅዱስ
ይህን ስም በኢሳይያስ 1:4 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

Isaiah 30:12

የእስራኤል ቅዱስ
ይህን ስም በኢሳይያስ 1:4 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ይህን ቃል አቃልላችኋል
ይህን መልእክት አቃልላችኋል

በግፍና በማታለል ታምናችኋል በእርሱም ተደግፋችኋል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፤- 1) የይሁዳ መሪዎች ሌሎችን በመጨቆንና በማታለል በሚገዙ በግብጻውያን መሪዎች ታምነዋል ወይም 2) የይሁዳ መሪዎች ገንዘባቸውን ለመውሰድና ለሚደረግላቸው ጥበቃ ለግብጻውያን መሪዎች ክፍያ ለመላክ የገዛ ሕዝባቸውን ይጮቁኑና ያታልሉ ነበር። (ስዕላዊ ንግግር ተመለከት)

በእርሱም ተደግፋችኋል
በዚህ ስፍራ "በእርሱ' የሚለው ግፍንና ማታለልን ያመለክታል። አት፦ "በእነርሱ ተደግፋችኋል' (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሦሥተኛ መደብ ተመልከት)

በእርሱም ላይ
በአንድ ነገር ላይ መታመን ወይም መደገፍ የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ ንግግር ነው። (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ስለዚህ ይህ በደል እንደ ፈረሰ ጎን ይሆንባችኋል ... በድንገት
ይህ ዘይቤአዊ ንግግር ከበደላቸው የተነሣ እግዚአብሔር የይሁዳን ሕዝብ በድንገት ያጠፋቸዋል የሚል ነው። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

ለመውድቅ እንደ ቀረበ እንደ ፈረሰ ጎን
ይህ የተሰበረ የቅጥር ጎን እንደሆነ የሚታወቅ ነው። አት፦ "ለመውደቅ እንደቀረበ የፈረሰ የቅጥር ጎን' (መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉ ተመልከት)

አወዳደቁም በድንገት እንደሚሆን
አወዳደቅ የሚለው የነገር ስም ወደቀ በሚል ማሰሪያ አንቀጽ እንዲገለጽ ይህ እንደገና ሊጻፍ ይችላል። አት፦ "በድንገት ይወድቃል' (የነገር ስም ተመልከት)

በድንገት፣ ፈጥኖ
እነዚህ አንድ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ቅጥሩ እንዴት ፈጥኖ እንደሚወድቅ አጽንዖት ይሰጣሉ። (የሁለት ነገሮች ተመሳሳይነት)

Isaiah 30:14

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ እግዚአብሔር የይሁዳን ሕዝብ እንዴት እንደሚያጠፋ ይገልጻል። (ኢሳይያስ 30፡ 12-13 ተመልከት)

እርሱን ይሰብረዋል
በዚህ ስፍራ እርሱን የሚለው ሊወድቅ ያለውን የቅጥሩን ጎን ያመለክታል። የቅጥሩ ጎን የይሁዳን ሕዝብና በኢሳይያስ 30፡ 12-13 የተጠቀሰውን ኃጢአታቸውን የሚወክል ስዕላዊ ንግግር ነው። (ስዕላ ንግግር ተመልከትሰ)

የሸክላ እቃ እንደሚሰበር
ይህ ዘይቤአዊ ንግግር ወደ መሬት እንደ ወደቀ የሸክላ ማሰሮ የቅጥሩ ጎን ፈጥኖ እና ሙሉ ለሙሉ ይሰበራል ማለት ነው። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

ሸክላ ሠሪ
ሸክላ ሠሪ ከሸክላ አፈር ገንቦና ማሰሮ የሚሠራ ሰው ነው።

አይገኝም
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "ማንም ሊያገኘው አይችልም' ወይም "አይኖርም' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

የሚዛቅበት ስባሪ
"ለመዛቅ በቂ የሆነ ስባሪ'

እሳት ከምድጃ
"እሳት' የሚለው ቃል በዚህ ስፍራ አመድን ያመልክታል። አት፦ "አመድን ከእሳት ማንደጃ' (ምትክ ስም ተመልከት)

Isaiah 30:15

የእስራኤል ቅዱስ
ይህን ስም በኢሳይያስ 1:4 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

በመመለስና በማረፍ ትድናላችሁ
ንስሐ መግባት በአካል ወደ እግዚአብሔር እንደ መመለስ ተደርጎ ተነግሮአል። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "ንስሐ ከገባችሁና እንደምጠነቀቅላቸሁ በማወቅ ካረፋችሁ ከጠላቶቻችሁ አድናችኋለሁ።' (ስዕላዊ ንግግር እና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

በማረፍ
እግዚአብሔር እንደሚጠነቀቅላቸው ከማመን የተነሳ ሕዝቡ ማረፉን ያመለክታል። (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

በጸጥታና በመታመን ኃይል ይሆንላችኋል
ጸጥታ በዚህ ስፍራ ተጨናቂና ስጉ አለመሆንን ያመለክታል። በእግዚአብሔር ከመታመናቸው የተነሣ የማይጨነቁ መሆናቸውን ያመለክታል። አት፦ ጸጥ ካላችሁና በእኔ ከታመናችሁ ትበረታላችሁ (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

በፈረስ ላይ ተቀምጠን እንሸሻለን
በግልጽ እነዚህ የይሁዳ ሰዎች ከግብጻውያን የወሰዱአቸው ፈረሶች ናቸው። (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

Isaiah 30:17

ከአንድ ሰው ዛቻ የተነሳ ሺህ ሰዎች ይሸሻሉ ... ከአምስት ሰዎች ዛቻ የተነሳ ትሸሻላችሁ
"ወታደር' የሚለው ቃል ታሳቢ ሊደረግ ይቻላል። አት፦ "ከአንድ የጠላት ወታደር ዛቻ የተነሳ አንድ ሺህ ወታደሮች ይሸሻሉ ... ከአምስት የጠላት ወታደሮች ዛቻ የተነሳ ወታደሮቻችሁ ሁሉ ይሸሻሉ' (መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉ ተመልከት)

አንድ ሺህ
"1000' (ቁጥሮች ተመልከት)

እናንተምበ በተራራ ራስ ላይ እንዳለ ሰንደቅ፣ በኮረብታም ላይ እንዳለ ሰንደቅ ዓላማ ሆናችሁ
እስክትቀሩ ድረስ
ይህ ዘይቤአዊ ንግግር በተራራ አናት ላይ እንዳለ አንድ ነጠላ ሰንደቅ ዓላማ ጥቂት ሰዎች ይቀራሉ ማለት ነው። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 30:18

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለይሁዳ ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል።

እናንተም ... ለእናንተ ... ይመልስላችኋል
በዚህ ስፍራ እናንተ የሚለው በጽዮን የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታል።

ይመልስላችኋል
"ይረዳችኋል

Isaiah 30:20

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለይሁዳ ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል።

የጭንቀትን እንጀራና የመከራን ውኃ
በዚህ ስፍራ "እንጀራ' እና "ውኃ' በጣም ድሀ የሆነ ሰው ምግብ ነው። ሐረጉ እንዳለ የመከራን ጊዜና የሕዝቡን ድህነት ይወክላል። (ምትክ ስም ተመልከት)

አስተማሪህን
ይህ እግዚአብሔርን ያመለክታል።

አስተማሪህን በገዛ ዓይኖችህ ታያለህ
በዚህ ስፍራ "ዓይኖች' የሰወን ሁለንተና ይወክላሉ። አት፦ "አንተ ራስህ አስተማሪህን ታያለህ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

ጆሮችህ ይሰማሉ
በዚህ ስፍራ "ጆሮች' የሚለው የሰውን ሁለንተና ይወክላሉ። አት፦ "ትሰማለህ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በኋላህ የሚለውን ቃል
ከኋላህ እንዲህ በማለት የሚናገረውን

መንገዱ ይህች ናት በእርስዋም ሂድ
ሕዝቡ እንዴት መኖር እንዳለባቸው እግዚአብሔር ያለው ፍላጎት በላዩ እንደሚከድበት መንገድ ወይም ጎዳና ተደርጎ ተነገሮአል። ለእግዚአብሔር መታዘዝ አንድ ሰው በእግዚአብሔር መንገድ እንደሄደ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ወደ ቀኝ ፈቀቅ ስትል ወይም ወደ ግራ ፈቀቅ ስትል
ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ ከእግዚአብሔር መንገድ ወደ ግራ ወይም ወደ ቀኝ ፈቀቅ እንደ ማለት ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 30:22

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለይሁዳ ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል።

እንደ አደፍ ጨርቅ ወዲያ ትወረውራቸዋለህ
ይህ ጣዖቶቻቸውን እንደ ቆሻሻ ወደዚያ ይጥሉአቸዋል የሚል ትርጉም ያለው ዘይቤአዊ ንግግር ነው። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

ከዚህ ሂዱ ትላቸዋልህ
ይህ ጣዖታት መስማት፣ መነሣትና አንድን ስፍራ ለቅቆ መሄድ እንደሚችሉ አድርጎ ይናገራል። ይህ ሕዝቡ ከእንግዲህ ወዲያ ጣዖታትን አይፈልጓቸውም ማለት ነው። (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየት ተመልከት)

Isaiah 30:23

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለይሁዳ ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል።

ይሰጣል
"እግዚአብሔር ይሰጣል'

ከምድር የተትረፈረፈ እንጀራ
በዚህ ስፍራ "እንጀራ' የሚለው ምግብን በአጠቃለይ ይወክላል። አት፦ "የምትመገበውን የተትረፈረፈ ፍሬ ምድር እንደትሰጥ ያደርጋታል' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

በዚያም ቀን
"በዚያን ጊዜ'

በመንሽና በመንሽ ሹካ የተለየውን
መንሽ እና መንሽ ሹካ ነፋሱ ሊበላ የሚችለውን ብቻ በመተው ገለባውን እንዲወስደው እህልን ወደ አየር ለመወርወር የሚያገለግሉ ናቸው። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "በመንሽና በመንሽ ሹካ ትለያለህ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

Isaiah 30:25

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለይሁዳ ሰዎች መናገሩን ቀጥሏል።

በረጅሙ ተራራ ሁሉ ... ሰባት ቀን የፀሐይ ብርሃን
ኢሳይያስ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከታደገ በኋላ የሚኖረውን ምናባዊ ሁኔታ ይገልጻል። የቋንቋ አጠቃቀሙ ግነታዊ ነው፤ ይህንን ኢሳያያስ እንደ ገለጸው እንደዚያው መተርጎም ይኖርብሃል።

በታላቅም እልቂት ቀን ግንቦች በወደቁ ጊዜ
"እግዚአብሔር ጠላቶቻችሁን በጨረሰና ትላልቅ ግንቦቻቸው እንዲወድቁ ባደረገ ጊዜ'

በዚያን ቀን
"በዚያን ጊዜ'

የፀሐይም ብርሃን እንደ ሰባት ቀን የፀሐይ ብርሃን ሰባት እጥፍ ይሆናል
"ሰባት ፀሐዮች እንደሚያበሩት ፀሐይ ታበራለች' ወይም "ፀሐይ በተለምዶ በሰባት ቀን የምትሰጠውን ያህል ብዙ ብርሃን በአንድ ቀን ትሰጣለች'

እግዚአብሔር የሕዝቡን ስብራት በጠገነ ዕለት፣ የቆሰለውንም በፈወሰ ዕለት
የእግዚአብሔር ሕዝቡን ማጽናናትና መከራቸው እንዲያበቃ ማድረጉ ቁስላቸውን በፋሻ እንዳሰረላቸው ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 30:27

የእግዚአብሔር ስም ... እንደምትባላ እሳት
እግዚአብሔር እጅግ መቆጣቱ ታላቅ እሳት እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የእግዚአብሔር ስም ይመጣል
በዚህ ስፍራ "ስም' የሚለው እግዚአብሔርን ይወክላል። አት፦ "እግዚአብሔር ይመጣል' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ከንፈሮቹ ቁጣን የሞሉ ናቸው፣ ምላሱም እንደምትባላ እሳት ናት
በዚህ ስፍራ "ከንፈር' እና "ምላስ' የእግዚአብሔርን ንግግር የሚወክሉ ምትክ ስሞች ናቸው። እንዲሁም እግዚአብሔር በታላቅ ቁጣና ኃይል መናገሩ ምላሱ እሳት እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፦ "እርሱ ሲናገር ቁጣው ሁሉን እንደሚያጠፋ እሳት ነው' (ተለዋጭ ስምና ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

እስትንፋሱ እንደሚያጥለቀልቅ ወንዝ ነው
ለማጥፋት ያለውን ኃይል በሚመለከት አጽንዖት ለመስጠት ከእግዚአብሔር አፍ የሚወጣውን አየር ከጎርፍ ጋር ያመሳስለዋል። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

አሕዛብን በአጥፊ ወንፊት ሊነፋቸው
እግዚአብሔር በአሕዛብን መካከል ሰዎችን መለየቱና ክፉ ሰዎችን ማጥፋቱ እግዚአብሔር አሕዛብን በወንፊት ላይ እንዳስቀመጣቸው ተደርጎ ተነግሮአል። ይህ በአዲስ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። አት፦ "እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል የሚገኙ ክፉ ሰዎችን ይለያል ያጠፋልም።' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

እስትንፋሱ በሕዝብም መንጋጋ የሚሰያስት ልጓም ይሆናል
እግዚብሐር የሰዎች እቅድ እንዲጨናገፍ ወይም እንዲጠፉ ለማድረግ ያለው ኃይል እስትንፋሱ ሰዎችን ከትክክለኛው መንገድ አወጥቶ እንደሚነዳ ልጓም ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በሕዝብ መንጋጋ እንዳለ ልጓም
ልጓም ሰዎች አንድን ፈረስ ለመቆጣጠርና ለመምራት በራሱ ላይ የሚያስገቡት ነገር ነው። ልጓም በፈረሱ አፍ ውስጥ የሚገባ ትንሽ ብረት ይኖረዋል። አት፦ "ልጓም በሰዎች ራስ ላይ' ወይም "ልጓም በሰዎች መንጋጋ ውስጥ' (የማይታወቅ ነገርን ስለ መተርጎም ተመልከት)

Isaiah 30:29

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለይሁዳ ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ዝማሬ ይኖራችኋል
ዝማሬ የሚለው ስም በማሰሪያ አንቀጽ እንዲገለጽ ይህ ክፍል እንደገና ሊጻፍ ይችላል። አት፡- "ትዘምራላችሁ'

የተቀደሰው በዓል በሚከበርበት ሌሊት እንደሚሆን
ይህ ዘይቤአዊ ንግግር ምን ያህል ሕዝቡ ደስተኛ እንደሚሆን አጽንዖት ይሰጣል። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

የተቀደሰው በዓል በሚከበርበት
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "የተቀደሰውን በዓል በምታከብሩበት ጊዜ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

የልብ ደስታ
በዚህ ስፍራ ልብ የሰውን ውስጣዊ ማንነት ይወክላል። አት፡- "ደስ ይልሃል' (ምትክ ሰም ተመልከት)

ወደ እስራኤል ዓለት ... አንድ ሰው እንደሚሄድ
ይህ ዘይቤአዊ ንግግር ሕዝቡ ምን ያህል ደስተኛ እንደሚሆን አጽንዖት ይሰጣል። (ዘይቤአዊ ንግግረ ተመልከት)

ወደ እስራኤል ዓለት
እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመጠበቅ የሚችል መሆኑ ሕዝቡ የሚወጣበትና ከጠላቶች የሚያመልጥበት ዓለት እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "ወደ እስራኤል የመከላከያ ዓለት' ወይም "ለእስራኤል እንደ መከላከያ ዓለት ወደሆነው' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 30:30

የክንዱን ሥራ ያሳያል
በዚህ ስፍራ "ክንድ' የሚለው የእግዚአብሔርን ኃይል ይወክላል። እግዚአብሔር የሕዝቡን ጠላቶች በማጥፋት ኃይሉን እንደሚያሳይ ያመለክታል። አት፡- "ጠላቶቻችሁን በማጥፋት ኃያል መሆኑን ያሳይል' (ምትክ ስምና እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

በሚነደድ ቁጣና በእሳት ነበልባል
የእግዚአብሔር ቁጣ እንደ ኃይለኛ ዝናብ ወይም እሳት ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- " ኃይለኛ ዝናብና የእሳት ነበልባል በሚመስል ቁጣ' ወይም "በታላቅ ቁጣ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በውሽንፍር፣ በዶፍ ዝናብ፣ እና በከባድ በረዶ ዶፍ
"ነፋስ፣ ዝናብ፣ እና በረዶ በተሞላ ኃይለኛ ዝናብ'

ከባድ የበረዶ ዶፍ
እንደ ዝናብ ከሰማይ የሚወርዱ ከበደ ከበደ ያሉ በረዶዎች

Isaiah 30:31

ከእግዚአብሔር ደምጽ የተነሳ አሦር ይሰባበራል
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር በመናገር የአሦርን ወታደሮች ይሰባብራቸዋል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

አሦር ይሰባበራል
አሦር የእግዚአብሔር ድምጽ የሚሰባብረው እቃ እንደሆነ አድርጎ ኢሳይያስ ስለ አሦር ፍርሃት ይናገራል። አት፡- "አሦር ይደነግጣል' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

አሦር
በዚህ ስፍራ የአሦርን ወታደሮች ይወክላል።

እግዚአብሔር በላዩ የሚያወርድበት የተመደበበት በትር ሁሉ
እግዚአብሔር ሠራዊቱ አሦራውያንን እንዲያሸነፉ ማድረጉ እግዚአብሔር አሦራውያንን በበትር እንደሚመታ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ይታጀባል
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "የይሁዳ ሰዎች አብረውት ይሆናሉ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ከበሮ
ሊመታ የሚችል ታምቡር የሚመስል ከላዩ ያለውና ሲነቃነቅ ድምጽ የሚሰጡ የብረት ቁርጥራጮች ዙሪያውን ያሉት የሙዚቃ መሣሪያ ነው። ይህንን በኢሳይያስ 5:12 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ከእነርሱ ጋር ይዋጋል
እግዚአብሔር ሠራዊቱ አሦራውያንን እንዲያሸነፉ ማድረጉ እግዚአብሔር ከጠላት ሠራዊት ጋር የሚዋጋ ተዋጊ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 30:33

ከቀድሞም ጀምሮ የማቃጠያ ቦታ ተዘገጅታለች
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ከቀድሞም ጀምሮ እግዚአብሔር የማቃጠያ ቦታ አዘጋጅቷል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ማቃጠያ ቦታ
ይህ ሐረግ "ቶፌዝ' የሚለው ቃል ትርጉም ነው። "ቶፌዝ' በአንድ ወቅት ሰዎች ልጆቻቸውን ለሐሰተኛ አማልክት መስዋዕት አድርገው ልጆቻቸውን የሚያቃጥሉበት በሂኖም ሸለቆ፣ ከኢየሩሳሌም በሰተ ደቡብ የሚገኝ ቦታ ነው። (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ለንጉሥም ተዘጋጅታለች
ይህ የአሦርን ንጉሥ ያመለክታል። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር ለአሦር ንጉሥ አዘጋጅት' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ እና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ክምር ከእሳት ጋር ተዘጋጅቷል ብዙም እንጨት
እሳት ለማንደድ ክምር ከብዙ እንጨት ጋር ተዘጋጅቷል

የእግዚአብሔር እስትንፋስ እንደ ድኝ ፈሳሽ ያቃጥለዋል
ይህ ክፍል የእግዚአብሔርን እስትንፋስ ክምሩን የሚያቃጥል የእሳት ወንዝ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 31

1 ስለ እርዳታ ወደ ግብጽ ለሚወርዱ በፈረሶችም ለሚደገፉ፣ ስለ ብዛታቸውም በሰረገሎች፣ (እጅግ ብርቱዎችም) ስለ ሆኑ፣ በፈረሰኞች ለሚታመኑ (የማይቆጠሩ ስለሆኑ) ፣ ወደ እስራኤልም ቅዱስ ለማይመለከቱ፣ እግዚአብሔርንም ለማይፈልጉ ወዮላቸው! **2** እርሱ ደግሞ ጠቢብ ነው፣ ክፉንም ነገር ያመጣል፣ ቃሉንም አይመልስም። በክፉም አድራጊዎች ቤት ላይ በደልንም በሚሠሩ ረዳት ላይ ይነሣል። **3** ግብጻውያን ሰዎች እንጂ አምላክ አይደሉም፣ ፈረሶቻቸውም ሥጋ እንጂ መንፈስ አይደሉም። እግዚአብሔርም እጁን በዘረጋ ጊዜ፣ ረጂው ይሰናከላል ተረጂውም ይወድቃል፣ ሁለቱም በአንድ ላይ ይጠፋሉ። **4** እግዚአብሔር የሚለኝ እንዲህ ነውና፣ "አንበሳ ወይም የአንበሳ ደቦል በንጥቂያው ላይ ሲያገሳ፣ ብዙ እረኞች ቢከማቹበት ከቃላቸው እንደማይፈራ፣ ከድምፃቸውም እንደማይዋረድ፣ እንዲሁ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር በጽዮን ተራራና በኮረብታዋ ላይ ይዋጋ ዘንድ ይወርዳል። **5** እንደሚበርር ወፍ፣ እንዲሁ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ኢያሩሳሌምን ይጋርዳታል፤ ይከልላታል፥ በላይዋ ሲያልፍ ይታደጋታል ያድናታልም። **6** እናንተ የእስራኤል ልጆች ሆይ፣ አጥብቃችሁ ወደ ዐመፃችሁበት ተመለሱ። **7** በዚያም ቀን እያንዳንዳቸው እጆቻቸው ለኃጢአት የሠሩላቸውን የብሩንና የወርቁን ጣዖቶቻቸውን ይጥላሉና። **8** አሦርም በሰይፍ፣ የሰው ባልሆነ ሰይፍ ይወድቃል፣ የሰውም ያልሆነ ሰይፍ ይበላዋል፤ ከሰይፍም ይሸሻሉ ጐበዛዝቱም ገባሮች ይሆናሉ። **9** አምባው ከፍርሃት የተነሣ ያልፋል፣ መሳፍንቱም ከዓላማው የተነሣ ይደነግጣሉ፤" ይላል እሳቱ በጽዮን፣ እቶኑም በኢየሩሳሌም የሆነ እግዚአብሔር።

Isaiah 31:1

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለይሁዳ ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል።

ወደ ግብጽ ለሚወርዱ
በዚህ ስፍራ ለሚወርዱ የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው ከቦታ ከፍታ አንጻር ግብጽ ከኢየሩሳሌም በዝቅተኛ ስፍራ ላይ ስለምትገኝ ነው።

ለሚወርዱ
"ለሚወርዱት ለይሁዳ ሰዎች'

በፈረሶችም ለሚደገፉ
ይህ ክፍል እንደሚረዷቸው ፈረሶቻቸውን ተስፋ ስለሚያደርጉ ሰዎች በፈረሶቻቸው እንደሚደገፉ አድርጎ ይናገራል። አት፡- በፈረሶቻቸው ለሚደገፉ (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የእስራኤል ቅዱስ
ይህንን ስም በኢሳይያስ 1:4 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

እግዚአብሔርንም ለማይፈልጉ
"እንዲረዳቸው እግዚአብሔርን ለማይጠይቁ'

ክፉ ነገርንም ያመጣል
በዚህ ስፍራ "ያመጣል' የሚለው ቃል "እንዲሆን ያደርጋል' ማለት ነው። አት፡- "ክፉ ነገር እንዲሆን ያደርጋል' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ቃሉንም አይመልስም
"ቃልን መመለስ' የሚለው ይህ ሐረግ እንደሚያደርግ የተናገረውን የማይፈጽም ሰው የተናገራቸው ቃላት ወደ እርሱ መመለስ እንደሚችሉ ነገሮች እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር ይህን አያደርግም ይላል፣ ማለትም የተናገረውን ይፈጽማል። አት፡- "አደርገዋለሁ ብሎ የተናገረውን ያደርጋል' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ይነሣል
"ይቀጣል

ክፉ ቤት
ይህ በዚያ የሚኖሩ ክፉ የሚያደርጉ ሰዎችን ያመለክታል። አት፡- ክፉ የሚያደርጉ ሁሉ (ምትክ ስም ተመልከት)

Isaiah 31:3

ግብጽ ሰው ነው
በዚህ ስፍራ ግብጽ የሚለው የግብጽን ወታደሮች ያመለክታል። አት፡- "የግብጽ ወታደሮች ሰዎች ናቸው' (ምትክ ስም ተመልከት)

ፈረሶቻቸውም ሥጋ እንጂ መንፈስ አይደሉም
ይህ ፈረሶቻቸው ፈረሶች ብቻ እንጂ መንፈሳዊ ፍጥረት አይደሉም። አት፡- "ፈረሶቻቸው ፈረሶች ብቻ ናቸው፣ ኃያላን መናፍስት አይደሉም' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

እግዚአብሔር እጁን በዘረጋ ጊዜ
እጅ የሚለው ቃል በአብዛኛው የእግዚአብሔርን ኃይልና ሥራ በሚመለከት ጥቅም ላይ ውሏል። አት፡- "እግዚአብሔር ኃይሉን እነርሱን በመቃወም በተጠቀመ ጊዜ' (ምትክ ስም ተመልከት)

ረጂው ይሰናከላል፣ተረጂውም ይወድቃል
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሣሣይ ነገር ይናገራሉ። መሰናከልና መውደቅ የመውደቅ ስዕላዊ ንግግሮች ናቸው። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- እነዚህ ሁለት ነገሮች ይሆናሉ፡- "የምትረዳችሁን ግብጽን አጠፋለሁ ግብጽም የምትረዳችሁን እናንተን አጠፋለሁ።' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ፣ ስዕላዊ ንግግርና አጓዳኝነት ተመልከት)

ተረጂውም
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እርዳታ የሚፈልገውም' (አድጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

Isaiah 31:4

አጠቃላይ መረጃ
እግዚብሔር ለኢሳይያስ ይናገራል።

እንደ አንበሳ ... የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲሁ
"አንበሳ ... በተመሣሣይ መንገድ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።'
እግዚአብሔር በዚህ ስፍራ የሚያድነውን ከሚጠብቅ አንበሳ ጋር ራሱን እያመሣሰለ እንዴት የእርሱ ለሆኑት ሕዝብ እንደሚከላከልና እንደማይሰጋ ይናገራል። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ... በኮረብታ ላይ ይወርዳል
የመጨረሻው መስመር ከመጀመሪያው መስመር በፊት እንዲሆን ካደረግህ በይበልጥ ግልጽ ይሆናል። አት፡- "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንደ አንበሳ፣ እንደ ደቦል አንበሳ በጽዮን ተራራ፣ በዚያኮረብታ ላይ ሊዋጋ ይወርዳል።'

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Isaiah 31:5

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ቀጥሏል።

እንደ ሚበርር ወፍ እንዲሁ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ይጋርዳታል
በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር እስራኤልን የሚጠብቅበት መንገድ እናት ወፍ ልጆቿን በጎጆአቸው ከምትጠብቅበት መንገድ ጋር ተስተያይቷል። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

ይጋርዳታል ይጠብቃታልም፤ ይጠብቃታል ያድናታልም
በከተማይ ላይ እንደሚበርር ወፍ እርሱን በመግለጥ፣ እግዚአብሔር እንዴት ኢየሩሳሌምን እንሚጠብቃትና እንደሚያድናት ይናገራል። አት፦ "ከተማይቱን ከጠላቶቿ ይጠብቃታል ይድናታልም' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር
ይህን ሐረግ በኢሳይያስ 1:9 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ኢየሩሳሌም
ይህ በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታል። አት፦ "የኢሩሳሌም ሕዝብ' (ምትክ ስም ተመልከት)

አጥብቃችሁ ወደ ዓመፃችሁበት ተመለሱ
"ወደ ዓመፃችሁበት ወደ እርሱ ተመለሱ'

የገዛ እጆቻችሁ በኃጢአት የሰሯቸውን
በእጆቻቸው ለሠሩት ነገር አጽንዖት ለመስጠት ሕዝቡ "በእጆቻቸው' ተወክለዋል። አት፦ "በገዛ እጆቻችሁ በመሥራት ኃጢአት አድርጋችኋል' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

አጠቃላይ መረጃ
እግዘአብሔር አሦራውያንን እንደ አንድ ሰው አድርጎ በመጥቀስ ለይሁዳ ሰዎች መናገሩን ይቀጥላል።

አሦር በሰይፍ ይወድቃል፣ በሰው ያልተሠራ ሰይፍ ይበላዋል
ሰይፍ ወታደረዊ ኃይልን ይህ በአደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "የእግዚአብሔር ሰይፍ፣ የሰውም ሰይፍ አይደለም፣ የአሦርን ሠራዊት ያጠፋል' (ምትክ ስምና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ይሸሻል
"አሦራውያን ይሸሻሉ'

ከፍርሃት የተነሣ ድፍረታቸውን ሁሉ ያጣሉ
"ድፍረት' የሚለው ቃል "ደፋር' በሚለው ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። "ፍርሃት' የሚለው ቃል "የፈራ' በሚል ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "እጅግም ስለፈሩ ከእንግዲህ ወደያ ደፋሮች አይሆኑም' (የነገር ስም ተመልከት)

መሣፍንቱ
"መሪዎቻቸው

በእግዚአብሔር የጦርነት ሰንደቅ ዓላማ መታየት
"መታየት' የሚለው ቃል "አየ' በሚል ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "የእግዚአብሔርን ሠራዊት ሰንደቅ ዓላማ ባዩ ጊዜ' (የነገር ስም ተመልከት)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኝነት ለመግለጽ እግዚአብሔር በራሱ ስም ይናገራል። አት፦ "እግዚአብሔር ያወጀው ይህ ነው' ወይም "እኔ፣ እግዚአብሔር ያወጅኩት ይህ ነው' (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሦሥተኛ መደብ ተመልከት)

እሳቱ በጽዮን እቶኑም በኢየሩሳሌም የሆነ
እነዚህ ሐረጎች ተመሣሣይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን አጽንዖት ለመስጠት በአንድነት ጥቅም ላይ ይውላሉ። በዚህ ስፍራ የእግዚአብሔር መገኘትና ለመፍረድና ለማጥፋት ያለው ኃይሉ እሳት እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፦ "አስፈሪ መገኘቱ በጽዮን የሆነው' (አጓዳኝነትና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 32

1 ተመልከቱ፣ ንጉሥ በጽድቅ ይነግሣል፣ መሳፍንትም በፍርድ ይገዛሉ። **2** ሰውም ከነፋስ እንደ መሸሸጊያ፣ ከዐውሎ ነፋስም እንደ መጠጊያ፣ በጥም ቦታም እንደ ወንዝ ፈሳሽ፣ በበረሃም አገር እንደ ትልቅ ድንጋይ ጥላ ይሆናል። **3** ከዚያም፣ የሚያዩትም ሰዎች ዓይኖች አይደበዝዙም፣ የሚሰሙትም ጆሮች በትኩረት ያደምጣሉ። **4** ጥንቃቄ የሌላቸው ሰዎች ልብ እውቀትን ታስተውላለች፣ የተብታቦችም ምላስ በቀላሉ አድርጋ ትናገራለች። **5** ከእንግዲህ ወዲህ ሰነፍ ከበርቴ ተብሎ አይጠራም፣ አታላዩም የተገራ አይባልም። **6** ሰነፍ ግን ስንፍናን ይናገራል፣ ልቡም ዝንጉነትን ይፈጽም ዘንድ በእግዚአብሔርም ላይ ስሕተትን ይናገር ዘንድ፣ የተራበችውንም ሰውነት ባዶ ያደርግ ዘንድ፣ ከተጠማም ሰው መጠጥን ይቈርጥ ዘንድ በደልን ይሠራል። **7** የንፉግም ዕቃ ክፉ ናት። ችግረኛ ትክክል ነገርን በተናገረ ጊዜ እንኳ እርሱ በሐሰት ቃል ድሀውን ያጠፋ ዘንድ ክፉን አሳብ ያስባል። **8** ነገር ግን፣ ከበርቴው ሰው ለመከበር ያስባል፤ በመከበርም ጸንቶ ይኖራል። **9** እናንተ ዓለመኞች ሴቶች ሆይ፣ ተነሡ፣ ድምፄንም ስሙ፤ እናንተ ተማምናችሁ የምትቀመጡ ሴቶች ልጆች ሆይ፣ ንግግሬን አድምጡ። **10** እናንተ ተማምናችሁ የምትቀመጡ ሴቶች ሆይ፣ ወይንን መሰብሰብ ይቀራልና፣ ፍሬም ማከማቸት አይመጣምና ከዓመትና ከጥቂት ቀን በኋላ ትንቀጠቀጣላችሁ። **11** እናንተ ዓለመኞች ሴቶች ሆይ፣ ተጠንቀቁ፤ ተማምናችሁም የምትቀመጡ ሆይ፣ ተንቀጥቀጡ፤ የቅምጥል ልብሳችሁን አውልቁ፣ ዕራቁታችሁን ሁኑ፣ ወገባችሁንም በማቅ ታጠቁ። **12** ስለ ተወደደችውም እርሻ፣ ስለሚያፈራውም ወይን ደረታችሁን ድቁ። **13** በሕዝቤ ምድር ላይ፣ በደስታ ከተማ ባሉት በደስታ ቤቶች ሁሉ ላይ እሾህና ኩርንችት ይወጣባቸዋል፤ **14** አዳራሹ ወና ትሆናለችና፣ የብዙ ሰውም ከተማ ትለቅቃለችና፣ አምባውና ግንቡም ለዘላለም ዋሻ፣ የምድረ በዳም አህያ ደስታ፣ የመንጎችም ማሰማርያ ይሆናልና፤ **15** ይህም፣ መንፈስ ከላይ እስኪፈስስልን፣ ምድረ በዳውም ፍሬያማ እርሻ እስኪሆን፣ ፍሬያማውም እርሻ ጫካ ተብሎ እስኪቈጠር ድረስ ይሆናል። **16** ከዚያ በኋላ ፍርድ በምድረ በዳ ይኖራል፤ ጽድቅም በፍሬያማው እርሻ ያድራል። **17** የጽድቅም ሥራ ሰላም፣ የጽድቅም ፍሬ ለዘላለም ጸጥታና መታመን ይሆናል። **18** ሕዝቤም በሰላም ማደሪያ፣ በታመነም ቤት በጸጥተኛ ማረፊያ ይቀመጣል። **19** በረዶ ግን በዱር ላይ ይወርዳል፣ ከተማም ፈጽማ ትዋረዳለች፣ **20** እናንተ የበሬና የአህያ እግር እየነዳችሁ በውኃ ሁሉ አጠገብ የምትዘሩ ትባረካላችሁ።

Isaiah 32:4

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ጻድቃን ገዢዎችን በይሁዳ ከመለሰ ወዲህ የሕዝቡን ሁኔታ ኢሳይያስ ይገልጻል።

ችኩሎች ... ተብታቦች
x

Isaiah 32:7

አታላዩ
ይህ ሌሎችን የሚያታልል ሰውን ያመለክታል። አት፦ "አታላይ ሰው' (ስማዊ ቅጽል ተመልከት)

በሐሰት ደሀውን ያጠፋ ዘንድ
"ደሀ' የሚለው ድሀውን ሕዝብ ያመለክታል። እንዲሁም፣ ያጠፋ ዘንድ የሚለው ሐረግ እነርሱን መግደል ማለት አይደለም ነገር ግን ስለ እነርሱ ውሸት በመናገር እነርሱን መጉዳት ማለት ነው። አት፦ ውሸት በመናገር ድሆች ሰዎችን መጉዳት' (ስማዊ ቅጽል ተመልከት)

ጸንቶ ይኖራል
ይህ የተሳካለት ይሆናል ማለት ነው። አት፦ "የተሳካለት ይሆናል' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 32:9

ተነሡ
"ቁሙ' ወይም "ልብ በሉ'

በምኞት
"ተማምኖ' ወይም "በደስታ'

ድምፄን
ለተናገረው አጽንዖት ለመስጠት ኢሳይያስ ራሱን በድምጹ ይወክላል። አት፦ "እኔ ስናገር' (ምትክ ስም ተመልከት)

መተማመናችሁ ይሰበራል
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። ኢሳይያስ መተማመናቸው የሚሰበር ቁስ ነገር እንደሆነ አድርጎ ከእንግዲህ ወዲያ የሚተማመኑ እንደማይሆኑ ይናገራል። አት፦ "ከእንግዲህ ወዲያ የምትተማመኑ አትሆኑም' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

የወይን መኸር አይኖርም
ይህ ለመልቀም የሚሆን መልካም ወይን አይኖርም ማለት ነው። አት፦ "የምትሰበስቡት ወይን አይኖራችሁም' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ማከማቸት አይመጣም
"እህል ማከማቺያ ጊዜ አይመጣም'

Isaiah 32:11

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ መናገሩን ይቀጥላል።

ተንቀጥቀጡ
ከፍርሃት የተነሳ ተንቀጥቀጡ

በምኞት
"ተማምኖ' ወይም "በደስታ'

ልብሳችሁን አውልቁ ዕራቁታችሁንም ሁኑ
ዕራቁት ማለት ዕርቃንን መሆን ላይሆን ይችላል ነገር ግን ዝቅተኛዎቹን እንደ ውስጥ ልብስ ያሉትን መልበስ ነው። አት፦ "የክት ልብሳችሁን አውልቁና ዕረቁታችሁን ሁኑ ወይም ቄንጠኛ ልብሳችሁን አውልቁ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ወገባችሁን በማቅ ታጠቁ
ይህ የሐዘን ወይም የለቅሶ ተግባር ነው። አት፦ "ስላዘናችሁ ወገባችሁን በማቅ ታጠቁ' (ምሳሌያዊ ተግባር ተመልከት)

ስለተወደደችው እርሻ፣ ስለሚያፈራውም ወይን ታለቅሳላችሁ
በሚያፈራው እርሻቸውና ወይናቸው ከሚሆነው ነገር የተነሣ በማዘናቸው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ያለቅሳሉ ማለት ነው። አት፦ "በተወደደችው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እርሻችሁና በሚያፈራው ወይናችሁ ከሚሆነው ነገር የተነሣ ታለቅሳላችሁ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

እሾህና ኩርንችት
ይህንነ ሐረግ በኢሳይያስ 5:6 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ደስተኞች ቤቶች በነበሩት
ደስተኛ ሰዎች በውስጣቸው ስለነበሩ በዚህ ስፍራ ቤቶች ደስተኞች ተደርገው ተገልጸዋል። አት፦ "በነበራችሁባቸው ጊዜ ቤቶቻችሁ ደስተኞች ነበሩ' (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየት ተመልከት)

የፈንጠዚያ ከተማ
"ደስተኛ ከተማችሁ' ፈንጠዚያ የሚለው ቃል ግብዣና ጭፈራ ማለት ነው።

Isaiah 32:14

ቤተ መንግሥቱ ይተዋልና የብዙ ሰዎችም ከተማ ትለቀቃለችና
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "ሕዝቡ ቤተ መንግሥቱን ይተዋልና ብዙውም ሰው ከተማይቱን ይለቅቃልና' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ኮረብታው
ይህ በኮረብታው አናት ላይ የተገነባውን ምሽግ ያመለክታል። አት፦ "በኮረብታው ላይ ያለ ምሽግ' (ምትክ ስም ተመልከት)

ኮረብታውና ማማው ዋሻ ይሆናሉ
ይህ ምሽጉና ማማው ዋሻ እንደሆኑ አድርጎ መተዋቸውን ይናገራል። አት፦ "ኮረብታውና ማማው የተተውና ባዶ ይሆናሉ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

የሜዳ አህዮች ደስታ፣ የመንጎችም መሰማሪያ
ይህ እነዚህ እንስሳት በተተውት ምሽጋና ማማ መካከል የበቀለውን ሣር በደስታ ይመገባሉ ማለት ነው። አት፦ "የሜዳ አህዮችና የበግ መንጎች በዚያ የሚገኘውን ሣር ይበላሉ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ለዘላለም
ይህ ረጅም ጊዜ ለማለት ጥቅም ላይ የዋለ ግነት ነው። አት፦ "እጅግ በጣም ረጅም ጊዜ' (ግነትና ማጠቃለይ ተመልከት)

መንፈሱ እስኪፈስስብን
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "እግዚአብሔር መንፈሱን እስኪያፈስስ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

መንፈሱ እስኪፈስስብን
እግዚአብሔር መንፈሱን ለሕዝቡ መስጠቱ መንፈሱ በእነርሱ ላይ የሚያፈስሰው ፈሳሽ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፦ "መንፈሱ እስኪሰጠን' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ከላይ
በዚህ ስፍራ ሰማይ "በላይ' እንዳለ ተመላክቷል። አት፦ "ከሰማይ' (ምትክ ስም ተመልከት)

ፍሬያማው እርሻ እንደ ዱር ይቆጠራል
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። ፍሬያማውን እርሻ ከጥቅጥቅ ደን ጋር በማነጻጸር ከመጠን በላይ የተትረፈረፈ መሆኑን ያስተያያል። አት፦ ሰዎች ፍሬያማው እርሻ እንደ ደን ጥቅጥቅ ብሎ አደገ ይላሉ ወይም ፍሬያማው እርሻ ከመጠን በላይ የተትረፈረፈ ይሆናል (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽና ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 32:16

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ መናገሩን ይቀጥላል።

ፍትህ ያደራል ... ጽድቅ ይኖራል
ኢሳይያስ "ፍትህ' እና "ጽድቅ' በእነዚህ ቦታዎች እንደሚኖር ሰው አድርጎ ይገልጻል። ይህ በእነዚህ ቦታዎች የሚኖሩ ሰዎች ፍትሃዊና ትክክለኛ የሆነውን ነገር ያደርጋሉ ማለት ነው። አት፦ "ሰዎች በምድረ በዳ በፍትህ ያደርጋሉ በፍሬያማ እርሻዎችም በጽድቅ ያከናውናሉ።' (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየት ተመልከት)

የጽድቅ ሥራ ሰላም ይሆናል፣ የጽቅም ፍሬ ለዘላለም ጸጥታና መታመን ይሆናል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተጓዳኞች ናቸው፣ ሁለቱም የጽድቅን ውጤቶች ያቀርባሉ። እነዚህ ሊጣመሩ ይችላሉ። አት፦ "በጽድቅ የሚኖሩ ሰዎች ፍሬ ለዘላለም ሰለም፣ጸጥታና መታመን ይሆናል።' (አጓዳኝነት ተመልከት)

መኖሪያ
ሰዎች የሚኖሩበት ቦታ

Isaiah 32:19

በረዶ
ይህንን በኢሳይያስ 28:2 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ደኑ ጠፋ፣ ከተማይቱም ፈጽማ ወደመች
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "ደኑን ያጠፋል ከተማይቱን ፈጽሞ ያወድማል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

እንዲግጡ በሬዎቻችሁንና አህዮቻችሁን የምትልኩ፣ በውኃ ፈሳሽ አጠገብ የምትዘሩ የተባረካችሁ ናችሁ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። ይህ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆነውን የእግዚአብሔርን በረከት ያመለክታል እንዲሁም ሕዝቡ ሊያደርጋቸው ስላሉ የተለመዱ ነገሮች ይናገራል። አት፦ "በውኃ ፈሳሽ ዳርቻ በሚገኝ እርሻ እህላችሁን በተከላችሁ ጊዜ በሬዎቻችሁንና አህዮቻችሁን በማሰማሪያው እንዲግጡ በሰደዳችሁ ጊዜ እግዚአብሔር ይባርካችኋል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ እና እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 33

1 አንተ ሳትጠፋ የምታጠፋ፣ በአንተም ላይ ወንጀል ሳይደረግ ወንጀል የምታደርግ ወዮልህ! ማጥፋትን በተውህ ጊዜ ትጠፋለህ፣ አሳልፎ መስጠትንም በተውህ ጊዜ አሳልፈው ይሰጡሃል። **2** እግዚአብሔር፣ ማረን፤ አንተን ተማምነናል፤ በየጠዋቱ ክንድ፣ በመከራም ጊዜ ማዳን ሁነን። **3** ከታላቅ ጫጫታ ወገኖች ሸሹ፣ ስትነሣም አሕዛብ ተበትነዋል። **4** አንበጣ እንደሚሰበስብ፣ ምርኮአችሁ ትሰበሰባለች፣ ኩብኩባም እንደሚዘልል፣ ሰዎች ይዘልሉበታል። **5** እግዚአብሔር ገነነ። እርሱ በአርያም ይኖራል። ጽዮንን በፍትህና በጽድቅ ሞላት። **6** የዘመንህም ጸጥታ፣ የመድኃኒት ብዛት፣ ጥበብና እውቀት ይሆናል፤ እግዚአብሔርን መፍራት መዝገቡ ነው። **7** ተመልከቱ፣ ባለሥልጣናቶቻቸው በጎዳና ይጮኻሉ፤ የሰላም መልእክተኞች መራራ ለቅሶ ያለቅሳሉ። **8** መንገዶች ተራቆቱ፣ ተላላፊም ቀረ፤ እርሱም ቃል ኪዳንን አፈረሰ፣ ከተሞችንም ናቀ ሰውንም አልተመለከተም። **9** ምድሪቱ አለቀሰች ከሳችም፤ ሊባኖስ አፈረ ጠወለገም፤ ሳሮን እንደ ምድረ በዳ ሆነ፤ ባሳንና ቀርሜሎስ ቅጠላቸውን አረገፉ። **10** "አሁን እነሣለሁ" ይላል እግዚአብሔር፤ "አሁን እከበራለሁ፤ አሁን ከፍ ከፍ እላለሁ።" **11** ገለባን ትፀንሳላችሁ፣ እብቅንም ትወልዳላችሁ፤ እስትንፋሳችሁ የምትበላችሁ እሳት ናት። **12** አሕዛብም እንደ ተቃጠለ ኖራ፣ ተቈርጦም በእሳት እንደ ተቃጠለ እሾህ ይሆናሉ። **13** እናንተ በሩቅ ያላችሁ፣ የሠራሁትን ስሙ፣ እናንተም በቅርብ ያላችሁ ኃይሌን እወቁ።" **14** በጽዮን ያሉ ኃጢአተኞች ፈሩ፣ መንቀጥቀጥ ዝንጉዎቹን ያዘ፤ ከምትበላ እሳት ጋር መኖርን የሚችል ከእኛ ማን አለ? ለዘላለምም ከምትነድድ እሳት ጋር መኖርን የሚችል ከእኛ ማን አለ? **15** በጽድቅ የሚሄድ ቅን ነገርንም የሚናገር፤ በሸንገላ የሚገኝ ትርፍን የሚንቅ፥ መማለጃ ጉቦን ከመጨበጥ እጁን የሚያርቅ፣ ደም የማፍሰስ ወንጀልን ከመስማት ጆሮቹን የሚያደነቍር፣ ክፋትንም ከማየት ዓይኖቹን የሚጨፍን ነው። **16** እርሱ ከፍ ባለ ስፍራ ይቀመጣል፣ ጠንካራ አምባ መጠጊያው ይሆናል፣ እንጀራም ይሰጠዋል፣ ውኃውም የታመነች ትሆናለች። **17** ዓይኖችህ ንጉሥን በውበቱ ያዩታል፤ እነርሱም በሩቅ ያለች ሰፊ ምድርን ያዩአታል። **18** ልብህም፣ ጸሐፊ ወዴት አለ? ገንዘቡንስ መዛኝ ወዴት አለ? ግንቦቹንስ የቈጠረ ወዴት አለ? ብሎ የሚያስፈራ ነገር ያስባል። **19** ጨካኝን ሕዝብ፣ ቋንቋው ለማስተዋል ጥልቅ የሆነውንና አንደበቱ ለማስተዋል ጸያፍ የሆነውን ሕዝብ፣ አታይም። **20** የበዓላችንን ከተማ ጽዮንን ተመልከት፣ ዓይኖችህ የሰላም ማደሪያ፣ ካስማውም ለዘላለም የማይነቀል፣ አውታሩም ሁሉ የማይበጠስ፣ የማይወገድ ድንኳን የሆነውን ኢየሩሳሌምን ያያሉ። **21** ይልቅ፣ እግዚአብሔር በዚያ የሰፉ ወንዞችና የመስኖች ስፍራ ሆኖ ከእኛ ጋር በግርማ ይሆናል። የሚቀዘፉ መርከቦች አይጓዙባትም፣ ታላላቆችም መርከቦች አያልፉባትም። **22** እግዚአብሔር ፈራጃችን ነውና፣ እግዚአብሔር ሕግን የሰጠን ነውና፣ እግዚአብሔር ንጉሣችን ነው፤ እርሱ ያድነናል። **23** ገመዶችህ ላልተዋል፣ ደቀላቸውንም አላጸኑም፣ ሸራውንም መዘርጋት አልቻሉም፤ በዚያም ጊዜ የብዙ ምርኮ ብዝበዛ ተከፈለ፤ አንካሶች እንኳ ብዝበዛውን በዘበዙ። **24** በዚያም የሚኖር፣ "ታምሜአለሁ፣" አይልም፤ በእርስዋም ለሚቀመጡ ሰዎች በደላቸው ይቅር ይባልላቸዋል።

Isaiah 33:1

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ስለ እግዚአብሔር ለአሦራውያን በግጥም ይናገራል።

የማይጠፋ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ሌሎች የማያጠፉት' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ትጠፋለህ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ሌሎች ያጠፉሃል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

አሳልፈው ይሰጡሃል
"ሌሎች አሳልፈው ይሰጡሃል'

Isaiah 33:2

ክንድ ሁነን
ቢዚህ ስፍራ የእግዚአብሔር ክንድ ብርታቱን ያመለክታል። ይህ እገዚአብሔር እነርሱን ማበርታቱን ስለ እነርሱ ብርታቱን እንደሚጠቅም አድርጎ ይናገራል። አት፡- "ብርታት ስጠን' (ምትክ ስምና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በየማለዳው
ይህ ማለዳን ብቻ ሳይሆን ሙሉውን ቀን ያመለክታል። አት፡- "በየቀኑ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

መዳናችን
የ"መሆን' ማሰሪያ አንቀጽ ሊታክልልት ይችላል። እንዲሁም "መዳን' የሚለው ቃል "አዳነ' በሚል ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "መዳናችን ሁን' ወይም "አድነን' (መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉ እና የነገር ስም ተመልከት)

በመከራ ጊዜ
ይህ መከራ የገጠማቸውን ጊዜ ያመለክታል። አት፡- "መከራ ሲኖረን' (ባለቤትነት ተመልከት)

Isaiah 33:3

ከከፍተኛ ድምጽ የተነሣ ሰዎች ሸሹ
ከፍተኛ ድምጽ የሚለውን በሚመለከት ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) የእግዚአብሔርን ድምጽ ያመለክታል። አት፡- "ከአንተ ከፍተኛ ድምጽ የተነሣ ሰዎች ሸሹ' ወይም 2) የእግዚአብሔርን ሠራዊት ከፍተኛ ድምጽ ያመለክታል። አት፡- "ከሠራዊትህ ድምጽ የተነሣ ሰዎች ሸሹ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ተነሥ
ይህ አንድ ነገር ለማድረግ መጀመር ማለት ነው። አት፡- "መሥራት ጀምር' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

አሕዛብ ተበተኑ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "አሕዛብን በተንክ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

አንበጦች እንደሚሰበሰቡ ምርኮህ ይሰበሰባል፣ አንበጦች እንደሚዘልሉ ሰዎች ይዘልሉበታል
ይህ የእግዚአብሔር ሕዝብ ከጠላቶቻቸው ምርኮ በማረኩ ጊዜ የሚያሳዩትን ከፍተኛ ፍጥነትና ጉጉት ምግብ በሰበሰቡ ጊዜ ከሚታየው የአንበጦች መጓጓት ጋር ያስተያያል። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "አንበጦች አረንጓዴ ተክልን እንደሚበሉ በተመሣሣይ መስገብገብ ሕዝብህ ከጠላቶችህ ምርኮ ይሰበስባሉ' (ዘይቤአዊ ንግግርና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

Isaiah 33:5

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እግዚአብሔር ከፍ ከፍ አለ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር ከማንም ይልቅ ታላቅ ነው' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ጽዮንን በፍርድ በጽድቅ ይሞላታል
እግዚአብሔር በፍርዱና በጽድቁ ጽዮንን መግዛቱ ጸዮንን በፍርድና በጽድቅ እንደሞላ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "ጽዮንን በፍርድና በጽድቅ ይገዛል' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የዘመንህም መረጋጋት ይሆናል
እግዚአብሔር ሕዝቡን ደህንነቱ የተጠበቀ ማድረጉ እርሱ ራሱ መረጋጋት እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮአል። በዘመንህም የሚለው ቃል ሕይወታቸውን ያመለክታል። አት፡- "በሕይወት ዘመንህ ሁሉ ደህንነትህን የተጠበቀ ያደርጋል' (ስዕላዊ ንግግርና ምትክ ስም ተመልከት)

የደህንነት፣ የጥበብና የዕውቀት ብዛት
ይህ እግዚአብሔር የሚሰጣቸውን ነገሮች ያመለክታል። "ደህንነት' የሚለው የነገር ስም "አዳነ' በሚለው ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። "ጥበብ' እና "ዕውቀት' የተሰኙት የነገር ስሞች በቅጽሎች ሊገለጹ ይችላሉ። አት፡- "የተትረፈረፈ ደህንነት፣ ጥበብና ዕውቀት ይሰጣችኋል' ወይም "ያድናችኋል እጅግም ጠቢብና አዋቂም ያደርጋችኋል' (መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉና የነገር ስም ተመልከት)

የእግዚአብሔር ፍርሃት ሀብቱ ነው
ይህ እግዚአብሔርን መፍራት እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚሰጠው ሀብት እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "እግዚአብሔርን ማክበር እግዚአብሔር የሚሰጥህ ውድ ሀብት ይመስላል' ወይም "እግዚአብሔርን መፍራት እንደ ሀብት ለአንተ ውድ ነው' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 33:7

ተመልከቱ
ይህ ቃል በዚህ ስፍራ በመቀጠል ሊነገር ወደ አለው የሕዝቡን ትኩረት ለመሳብ ጥቅም ላይ ውሏል። በተጨማሪም በዚህ ስፍራ የመጽሐፉን አዲስ ክፍል ለማስተዋወቅ ጥቅም ላይ ውሏል። አት፡- "ስሙ'

በውክልና የተላኩ
መልእክተኞች

ለሰላም የሚሠሩ መልእክተኞች መራራ ለቅሶ ያለቅሳሉ
ይህ ሰላም በማምጣት ስላልተሳካላቸው ያለቅሳሉ ማለት ነው። አት፡- "መልእክተኞቹ ሰላም እንደሚሆን ተስፋ አድርገው ነበር ነገር ግን አልተሳካላቸውም ስለዚህም መራራ ለቅሶ አለቀሱ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

መንገዶች ባድማ ሆኑ፣ ተጓዦችም የሉም
ሁለተም ሐረጎች በመንገዶች ላይ ተጓዦች ባለመኖራቸው ላይ አጽንዖት ያደርጋሉ። እነዚህ ሊጣመሩና በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጹ ይችላል። አት፡- "ከእንግዲህ ወዲያ ሰዎች በመንገዶች ላይ አይጓዙም።' (አጓዳኝነትና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ቃል ኪዳን ፈረሰ፣ ምስክሮች ተዋረዱ፣ የሰው ልጆችም አልተከበሩም
ይህ ምንባብ በእስራኤል የነበረውን የሥነ ምግባር ውድቀት አጠቃላይ ሁኔታ ያመለክታል ወይም አገሪቱ ከአሦር ጋር አሰተማማኝ የሰላም ስምምነት ማደረግ አለመቻሏን ያመለክታል። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ሕዝቡ የፈጸመውን ቃል ኪዳን ሰበረ፣ ሕዝቡ የምስክሮችን ምስክርነት ችላ አለ፣ እንዲሁም ሕዝቡ እርስ በእርሱ አልተከባበረም' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

Isaiah 33:9

ምድሪቱ አለቀሰች ጠወለገችም
ይህ ያለቅስ እንደ ነበረ ሰው ምድሪቱ ደረቅ እንደምትሆን ይናገራል። አት፡- "ምድሪቱ ትደርቃለች ተክሎችዋም ይጠወልጋሉ' (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየት ተመልከት)

ሊባኖስ አፈረ ጠወለገም
በዚህ ስፍራ "ሊባኖስ' የሊባኖስን ዛፎች ይወክላል። ይህ የዛፎችን መጠውለገንና መበስበስን የሚያፍር ሰው እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። አት፡- "የሊባኖስ ዛፎች ጠወለጉ በሰበሱም' (ምትክ ስምና ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየት ተመልከት)

ሳሮን ... ባሳን ... ቀርሜሎስ
አንድ ወቅት ብዙ ዛፎችና አበባዎች በእነዚህ ቦታዎች ያድጉ ነበር።

ሳሮን እንደ ምድረ በዳ ሆነ
ይህ ሳሮን ምን ያህል ደረቅ እንደሆነ ከምድረ በዳ ጋር ያስተያያል።

ባሳንና ቀርሜሎስ ቅጠላቸውን አረገፉ
በዚህ ስፍራ ባሳንና ቀርሜሎስ በዛፎቻቸው ተወክለዋል። አት፡- "ከእንግዲህ በባሳንና በቀርሜሎስ በሚገኙ ዛፎች ላይ ቅጠል አይኖርም' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

Isaiah 33:10

እነሣለሁ
መነሣት ወይም መቆም ከእንግዲህ ወዲያ ማየትና ማሰብ እንደማይኖርና በዚያ ፈንታ የሥራ መጀመሪያ እንደሆነ የሚያሳይ ስዕላዊ ንግግር ነው። አት፡- "መሥራት እጀምራለሁ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

አሁን ወደ ላይ ከፍ እላለሁ፣ አሁን ከፍ ከፍ እላለሁ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። እነዘህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ ተመሣሣይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን በእግዚአብሔር መክበር ላይ አጽንዖት ያደርጋሉ። አት፡- "አሁን እኔ ራሴን አከብራለሁ፣ ሁሉ ሊያከብረኝ የሚገባኝ እንደሆነም አሳያለሁ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ እና አጓዳኝነት ተመልከት)

ገለባን ትፀንሳላቸሁ፣ እብቅንም ትወልዳላችሁ
ይህ የአሦራውያን ማቀድ እናት ልጅን እንደምትወልድ እቅዶቻቸውን እንደሚፀንሱና እንደሚወልዱ አድርጎ ይናገራል። ይህ እቅዶቻቸውን ከገላባ ጋር እያስተያየ ከንቱ እንደሆኑ ይናገራል። አት፡- "እንደ ገለባና ሳር ከንቱ የሆኑ እቅዶችን ታቅዳላችሁ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ተቆርጦ እንደ ቀረ ደረቅ የእህል ግንድ
ፍሬ የሚሸከመው ክፍል ከተቆረጠ በኋላ በምድር ላይ የተተው ደረቅ የተክል ክፍል።

እስትንፋሳችሁ የምትበላችሁ እሳት ናት
በዚህ ስፍራ የአሦራውያን እቅዶች እንደ እስትንፋሳቸው ተጥቀስዋል። ይህ እቅዶቻቸው በተጨባጭ ሰውነታቸውን እንደሚያቃጥል አድርጎ እቅዶቻቸው ለሞት እንደሚዳርጓቸው ይናገራል። አት፡- "እቅዶቻችሁ ይገድሉአችኋል' (ምትክ ስምና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

አሕዛብም እንደ ተቃጠለ ኖራ፣ ተቆርጦም በእሳት እንደ ተቃጠለ እሾህ ይሆናሉ
ይህ የአሕዛብ አስከሬን የሚቃጠልበትን መንገድ እሾህ ከሚቃጠልበት መንገድ ጋር ያስተያያል። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽም ሊገለጽም ይችላል። አት፡- "ገበሬ እሾህን እንደሚቆርጥና እንደሚያቃጥል እሳት የአሕዛብን አስከሬን ለኖራ ያቃጥላል።' (ዘይቤአዊ ንግግርና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ኖራ
የተቃጠሉ አጥንቶች አመድ

Isaiah 33:13

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል።

እናንተ በሩቅ ያላችሁ የሠራሁትን ስሙ፣ እናንተም በቅርብ ያላችሁ የእኔን ኃይል እወቁ
እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ለማለት በሩቅ እና በቅርብ የሚሉትን ቃላት ይጠቀማል። ኃይል የሚለው ቃል ኃያል በሚል ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "ሕዝቦች ሁሉ በሁሉ ስፍራ ያደረግሁትን ስሙ ኃያል መሆኔንም እውቁ' (ስዕላዊ ንግግርና የነገር ስም ተመልከት)

አምላክ የለሾቹን መንቀጥቀጥ ያዛቸው
ይህ የአምላክ የለሾቹ መንቀጥቀጥን በሚመለከት መንቀጥቀጣቸው የያዛቸው ጠላት እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አት፦ "አምላክ የለሾቹ በመንቀጥቀጥ ተዋጡ' (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየት ተመልከት)

ከእኛ መካከል ... ከምትነድድ?
በጽዮን የሚገኙ ኃጢአተኞች እነዚህን ጥያቄዎች እንደጠየቁ ተመላክቷል። አት "እንዲህ አሉ፣ ‘ከእኛ መካከል ... ከምትነድድ?’ ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ከምትባላ እሳት ጋር መኖርን የሚችል ከእኛ ማን አለ? ለዘላለም ከምትነድድ እሳት ጋር መኖርን የሚችል ከእኛ ማን አለ?
እነዚህ አሳብ ገላጭ ጥያቄዎች በመሠረቱ አንድ ትገሩም ያላቸው ሲሆን ማንም ከእሳት ጋር መኖር እንደማይችል አጽንዖት ይሰጣሉ። አት፦ "ማንማ ከሚበላ እሳት ጋር መኖር አይችልም! ለዘላለም ከምትነድድ ጋር ማንም መኖር አይችልም!' ወይም "ማንም የእግዚአብሔርን ፍርድ ታግሦ መኖር አይችልም፣ እንደ ዘላለማዊ እሳት ነውና' (አሳብ ገላጭ ጥያቄና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በጊዜያዊነት መቀመጥ
ቤቱ ባልሆነ አንድ ቦታ መኖር

Isaiah 33:15

የሚሄድ
በዚህ ስፍራ መሄድ የሚለው አኗኗርን ያመለክታል። አት፦ "የሚኖር' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

የጭቆናን ትርፍ የሚንቅ
"የጭቆና ትርፍ' የሚለው ስማዊ ሐረግ፣ በግሳዊ ሐረግ መገለጽ ይችላል። አት፦ "ሌሎች ሰዎችን በመጉዳት የሚገኝ ሀብትን የሚጠላ' (የነገር ስም ተመልከት)

ክፋትንም ከማየት ዓይኖቹን የሚከለክል
በዚህ ስፍራ ማየት አንድን ነገር ማጽደቅን ወይም ማረጋገጥን ያመልክታል። አት፦ "ክፉ ማድረግን የማያጸድቅ' (ፈሊጣዊ ንግግርን ተመልከት)

በከፍታዎች የሚያደር፣ መከለያ ስፍራው በአምባዎች መካከል የሚገኝ ምሽግ የሆነለት ሰው ይህ ነው
ይህ በኮረብታ ላይ በሚገኝ ቤቱ እንደሚኖር ደኅንነቱ ስለተጠበቀው ሰው ይናገራል። እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተጓዳኝ ናቸው እንዲሁም ሁለተኛው ሐረግ ሰውዬው የሚኖርበትን ቦታ ይገልጻል። አት፦ "ለመከላከል ምቹ በሆነ ዓለታማ ቦታ፣ በኮረብታ ላይ ቤቱን እንደሠራ ሰው ደኅንነቱ የተጠበቀ ይሆናል' (ስዕላዊ ንግግርና አጓዳኝነት ተመልከት)

ከፍታዎች
ይህ ከፍ ያለ ኮረብታ ወይም በተራራ ላይ የሚገኝ ቦታ። አት፦ "ከፍ ያለ ኮረብታ' ወይም "በተራራ ላይ የሚገኝ ቦታ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በአምባዎች መካከል የሚገኝ ምሽግ
ይህ በተጨባጭ ምሽግ እንደሆኑ አድርጎ ለመከላከል ምቹ ስለሆኑ ድንጋያማ አካባቢዎች ይናገራል። አት፦ "ታላቅ የደንጋዮች ክምር' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የማይቋረጥ አቅርቦት ይኖረዋል
"ሁልጊዜ ይገኛል'

Isaiah 33:17

ዓይኖቻችሁ ያያሉ ... ያያሉ
ይህ አድማጮቹን "በዓይኖቻቸው' ይወክላቸዋል። አት፦ "ታያላችሁ ... ታያላችሁ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

ንጉሡን በውበቱ
የንጉሡ ንጉሣዊ መጎናጸፊያው "እንደ ውበቱ' ተመላክቷል። አት፦ "ንጉሡ በውብ መጎናጸፊያው' (ምትክ ስም ተመልከት)

ልብህ የሚያስፈራ ነገር ያስባል
ይህ አድማጮቹን በልባቸው ይወክላቸዋል። "የሚያስፈራ' የሚለው ከአሦራውያን ጋር ያላቸውን ጦርነት ያመለክታል። ይህ በግልጽ ሊቀመጥ ይችላል። አት፦ "በጦርነት በወጓችሁ ጊዜ አሦራውያን ያሳደሩባችሁን ፍርሃት ታስታውሳላችሁ' (ተለዋጭ ስምና እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ጸሐፊ ወዴት አለ? ገንዘቡንስ የመዘነ ወዴት አለ? ግንቦቹንስ የቆጠረ ወዴት አለ?
እነዚህ አሳብ ገላጭ ጥያቄዎች የተጠየቁት የአሦራውያን አለቆች መሄዳቸውን በሚመለከት አጽንዖት ለመሰጠት ነው። እነዚህ ጥያቄዎች በአሳብ ገላጭ ዐረፍተ ነገርነት ሊጸፉ ይችላል። አት፦ "ለእነርሱ እንድንከፍል እንገደድ የነበረበትን የግብር ገንዘብ ይቆጥሩ የነበሩ የአሦር አለቆች ጠፍተዋል! ግንቦችን ይቆጥሩ የነበሩ ሰዎች ሄደዋል!' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ገንዘቡንስ የመዘነ
ገንዘብ ዋጋ ያለው ብረት ነበር፤ ዋጋው በክብደቱ ይወሰን ነበር።

ዓመጸኛን ሕዝብ፣ የማትረዳው የእንግዳ ቋንቋ ሕዝብ
"የማትረዳውን ቋንቋ የሚናገር ጨካኝ ሕዝብ'

Isaiah 33:20

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለይሁዳ ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል።

የበዓላቶቻችን ከተማ
ይህ በዚች ከተማ የራሳቸው በዓላትና ግብዣዎች ያደርጉ ነበር ማለት ነው። አት፦ "የራሳችንን ግባዣዎች እናደርግባት የነበረች ከተማ' ወይም "የራሳችንን በዓላት እናከብርባት የነበረች ከተማ' (ባለቤትነት ተመልከት)

ዓይኖቻችሁ ያያሉ
እያዩ ላሉት አጽንዖት ለመስጠት ሕዝቡ በዓይኖቻቸው ተወክለዋል። አት፤- "ታያላችሁ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

Isaiah 33:22

የእኛ ... ለእኛ
ይህ የይሁዳን ሕዝብ ጨምሮ ኢሳይያስን ያመለክታል። (አካታች "እኛ' ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Isaiah 33:23

ገመዶችህ ላልተዋል፤ ደቀላቸውንም አላጸኑም፤ ሸራውንም መዘርጋት አልቻሉም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) የአሦር ሠረዊት በውኃ ላይ መሄድ እንዳልቻለ ጀልባ ነው፤ ደቀላውንና ሸራውን የሚደግፉት ገመዶች ላልተዋል ደቀላውንም የሚደግፍ ከእንግዲህ የለም ስለዚህ ሸራው ምንም አይጠቅምም (ኢሳይያስ 33፡1) ወይም 2) የይሁዳ ሰዎች ከእንግዲህ ጦርነት ላይ አይሆኑም፡ "የሰንደቅ ዓላማህን ምሰሶ የሚደግፈውን ገመድ አላልተሃል፣ ሰንደቅ ዓላመው ከእንገዲህ አይሰቀልም' (ኢሳ33፡17-ኢሳ 22)። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ደቀላ
ሸራውን የሚደግፍ ረጅም ምሰሶ

ሸራ
በነፋስ የሚወጠርና ጀልባውን በውኃ ላይ እንዲንቀሳቀስ የሚያደርግ ትልቅ ጨርቅ

ታላቅ ምርኮ በሚከፋፈልበት ጊዜ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- ሀብቱን በሚከፋፈሉበት ጊዜ (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

አንካሶች
ይህ መሄድ የማይችሉ ሰዎችን ያመለክታል። አት፡- "አንካሶች የሆኑ' (ስማዊ ቅጽል)

በዚያ የሚኖሩ ሰዎች በደል ይቅር ይባልላቸዋል
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር በዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ኃጢአት ይቅር ይላል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 34

1 እናንተ አሕዛብ ሆይ፣ ቅረቡ፣ ስሙ፤ እናንተ ሕዝቦች ሆይ፣ አድምጡ! ምድርና ሞላዋ፣ ዓለምና ከእርስዋ የሚወጣ ሁሉ ይስሙ። 2 የእግዚአብሔር ቍጣ በአሕዛብ ሁሉ ላይ፣ መዓቱም በሠራዊታቸው ሁሉ ላይ ነው፤ ፈጽሞ አጠፋቸው፣ ለመታረድም አሳልፎ ሰጣቸው። 3 ከእነርሱም የተገደሉት ይጣላሉ፣ የሬሳቸውም ግማት በሁሉ ቦታ ይሸታል፣ ተራሮችም በደማቸው ይርሳሉ። 4 የሰማይም ሠራዊት ሁሉ ይበሰብሳሉ፣ ሰማያትም እንደ መጽሐፍ ጥቅልል ይጠቀለላሉ፣ ከወይንና ከበለስም ቅጠል እንደሚረግፍ፣ ሠራዊታቸው ሁሉ ይረግፋል። 5 ሰይፌ በሰማይ ሆና እስክትረካ ድረስ ጠጥታለች፤ ተመልከቱ፣ በኤዶምያስና በረገምሁት ሕዝብ ላይ አሁን ለፍርድ ትወርዳለች። 6 የእግዚአብሔር ሰይፍ በደም ተሞልታለች፣ በስብም፣ በበግ ጠቦትና በፍየል ደምም፣ በአውራም በግ ኵላሊት ስብ ወፍራለች። እግዚአብሔር መሥዋዕት በባሶራ፣ ታላቅም እርድ በኤዶምያስ ምድር አለውና። 7 ጎሽ ከእነርሱ ጋር፣ ወይፈኖችም ከኮርማዎች ጋር ይወድቃሉ፤ ምድራቸውም በደም ትረካለች፣ አፈራቸውም በስብ ትወፍራለች። 8 የእግዚአብሔር የበቀሉ ቀን፣ ስለ ጽዮንም ክርክር የብድራት ዓመት ነው። 9 የኤዶምያስም ምንጮች ዝፍት ሆነው ይለወጣሉ፣ አፈርዋም ዲን ይሆናል፣ መሬትዋም የሚቀጠል ዝፍት ትሆናለች። 10 በሌሊትና በቀንም ይቃጠላል፣ ጢስዋም ለዘላለም ይወጣል፤ ከትውልድ እስከ ትውልድም ድረስ ባድማ ሆና ትኖራለች፤ ለዘላለም ዓለም ማንም አያልፍባትም። 11 ነገር ግን፣ ጭልፊትና ጃርት ግን ይኖሩባታል፤ ጕጕትና ቊራም መረባቸውን ይሠሩባታል። በላይዋም የመፍረስ ገመድና የባዶነት ቱንቢ ይዘረጋባታል። 12 መሳፍንቶችዋን ወደ መንግሥት ይጠራሉ፣ ነገር ግን ማንም አይገኝባትም፤ አለቆችዋም ሁሉ ምናምኖች ይሆናሉ። 13 በቤተ መንግሥቶቿ እሾህ፣ በቅጥሮችዋም ሳማን፣ አሜከላ ይበቅሉባታል፤ የቀበሮም ማደሪያና የሰጐን ስፍራ ትሆናለች። 14 የምድረ በዳም አራዊት ከተኵሎች ጋር ይገናኛሉ፣ አጋንንትም እርስ በርሳቸው በጩኸት ይጠራራሉ፤ ጅንም በዚያ ትኖራለች ለእርስዋም ማረፊያ ታገኛለች። 15 በዚያም ዋሊያ ቤትዋን ትሠራለች፣ እንቍላልም ትጥላለች ትቀፈቅፈውማለች ልጆችዋንም በጥላዋ ትሰበስባለች፤ በዚያም ደግሞ አሞራዎች እያንዳንዳቸው ከባልንጀሮቻቸው ጋር ይሰበሰባሉ። 16 በእግዚአብሔር የመጽሐፍ ጥቅልል ውስጥ ፈልጉ፣ አንዳቸውም አይጠፉም። አፌ አዝዞአልና፣ መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፣ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም። 17 እርሱም ዕጣ ጣለባቸው፣ እጁም በገመድ ከፈለችላቸው፤ ለዘላለም ይገዙአታል፣ ከትውልድም እስከ ትውልድ ድረስ ይቀመጡባታል።

Isaiah 34:1

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር በግጥም ይናገራል። (አጓዳኝነት ተመልከት)

ምድርና መላዋ፣ዓለምና ከእርስዋ የሚወጣ ሁሉ ይስሙ
በዚህ ስፍራ በእግዚአብሔር ሥልጣን ሥር እንዳለች አጽንዖት ለመስጠት ምድር እግዚአብሔርን መስማት እንደምትጠየቅ ተደርጎ ተነግሮአል። እነዚህ ሁለት ተጓዳኝ ሐረጎች በዓለም ለሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ምትክ ስሞች ናቸው። አት፦ "በሁሉ ስፍራ በዓለም በየትኛውም ቦታ፣ እያንዳንዱ ሰው እኔ የምለውን መስማት አለበት።' (ግዑዝ ነገረን እንደ ሰው ማየትና ምትክ ስም ተመልከት)

ዓለምና ከእርስዋ የሚወጣ ሁሉ
ይህ ከተጓዳኞቹ ሁለቱ ሐረጎች ሁለተኛው ነው። ባይባሉም የሚታወቁ ቃላት በዚህ ሐረግ ሊጨመሩ ይችላሉ። አት፦ "ዓለም፣ ከእርስዋ የሚወጡ ነገሮች ሁሉ መስማት አለባቸው' (መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉ ተመልከት)

ፈጽሞ አጠፋቸው፣ ለመታረድም አሳልፎ ሰጣቸው
ብዙ ጊዜ ነቢያት ገና ወደፊት ሊሆኑ ያሉ ነገሮችን አስቀድሞውኑ እንደተፈጸሙ አድርገው ይናገራሉ። ይህም ሁኔታው በእርግጥ እንደሚፈጸም አጽንዖት ለመስጠት ነው። አት፦ "ፈጽሞ ያጠፋቸዋል፣ ለመታረድም አሳልፎ ይሰጣቸዋል' (ትንቢታዊ አላፊ ጊዜ ተመልከት)

Isaiah 34:3

የሟቾቻው ሰውነት ወደ ውጪ ይጣላል
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "ማናቸውም የሞቱባቸውን አይቀብሩም' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ሟቾቻቸው
ይህ የሞቱ ሰዎችን ያመለክታል። አት፦ "የሞቱት' (ስማዊ ቅጽል ተመልከት)

ተራሮች ደማቸውን ይጠጣሉ
"ተራሮች በደማቸው ይሸፈናሉ'

ሰማያት እንደ መጽሐፍ ጥቅልል ይጠቀለላሉ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። ይህ እግዚአብሔር በሰማይ ላይ የሚያደርገው የመጽሐፍን ጥቅልል ከሚጠቀልል ሰው ጋር ተስተያይቶአል። አት፦ "አንድ ሰው የመጽሐፍን ጥቅልል እንደሚጠቀልል እግዚአብሔር ሰማይን ይጠቀልላል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ እና ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

ፍሬም ከበለስ ቅጠልም ከወይን እንደሚጠውልግና እንደሚረግፍ፣ ከዋክብቶቻቸው ይከስማሉ
ይህ ሰዎች ለዘላለም በዚያ እንደሚኖሩ የሚያስቧቸው በሰማይ ያሉ ነገሮች እንኳን እንደ ቅጠል በቀላሉ እንደሚወድቁ አጽንዖት ይሰጣል። አት፦ "ቅጠል ከወይን እንደሚረግፍ ወይም የበለስ ፍሬ ከዛፍ እንደሚረግፍ እንዲሁ ከዋክብት ሁሉ ከሰማይ ይወድቃሉ' (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 34:5

ሰይፌ በሰማይ ሆና ጠጥታ እስክትረካ ድረስ
እግዚአብሔር ራሱን ሰይፍ እንደታጠቀ ተዋጊ ይገልጻል። ጠጥታ እስክትረካ የሚለው ሐረግ የእግዚአብሔርን ሰይፍ እንደሚበላና እንደሚረካ ሰው አድርጎ ይናገራል። በሰማይ ብዙ ጥፋት እንደሚሆንና የእርሱን ፍጻሜ ለመግለጽ እግዚአብሔር ይህን ስዕላዊ መግለጫ ይጠቀማል። አት፦ "በሰማይ ያሉትን ነገሮች ማጥፋቴን ስፈጽም' (ስዕላዊ ንግግርና ግዑዝን እንደ ሰው ማየትን ተመልከት)

ተመልከቱ
የአድማጮቹን ትኩረት ለመሳብና የተነገሩትን ነገሮች እንዲያስቡ ለማድረግ ይህ ቃል በዚህ ስፍራ ጥቅም ላይ ውሏል። አት፦ "ስሙ' ወይም "በመቀጠል'

ለጥፋት በለየኋቸው ሕዝብ ላይ፣ በኤዶምያስ ላይ ትወርዳለች
በዚህ ስፍራ ትወርዳለች የሚለው የእግዚአብሔርን ሰይፍ ያመለክታል። ይህ እግዚአብሔር ነገሮችን በሰይፍ የማጥፋቱን ስዕላዊ ንግግር ይቀጠላል። አት፦ "ላጠፋቸው ለራሴ የለየኋቸውን ሰዎች፣ የኤዶምን ሕዝብ ለመቅጣት እመጣለሁ' (ስዕላ ንግግር ተመልከት)

በኤዶም ላይ
ኤዶም የሚለው በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታል። አት፦ "በኤዶም ሕዝብ ላይ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የእግዚአብሔር ሰይፍ በደም ተሞልታለች በበግም ... ስብ ተሸፍናለች
ይህ እንስሳትን እንደሚሠዋ ካህን እግዚአብሔር ሕዝቡን ስለ መግደሉ ይናገራል። የካህንን ሰይፍ በመግለጽ ይህን ያደርጋል። አት፡- "ካህን እንስሳትን እንደሚሠዋ እግዚአብሔር ይሠዋቸዋል፤ ሰይፉ በበግ ጠቦት፣ በፍየልና በአውራ በግ ደምና ስብ ተሞልታለች' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

እግዚአብሔር መሥዋዕት በባሶራ ታላቅም እርድ በኤዶምያስ ምድር አለውና
"መሥዋዕት' እና "እርድ' የሚሉት ቃላት በማሰሪያ አንቀጽነት ሊገለጹ ይችላሉ። አት፡- "እግዚአብሔር ብዙ ሰዎችን በባሶራ ይሠዋልና፣ ብዙ ሰዎችን በኤዶምያስ ያርዳልና' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ባሶራ
ይቺ በኤዶምያስ ቁልፍ ከተማ ነበረች። (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)

Isaiah 34:7

ይወድቃሉ
"ይሞታሉ

ምድራቸው በደም ትሰክራለች
ይህ ምድሪቱን ከሰከረ ሰው ጋር በማስተያያት በመሬት ላይ የሚፈስሰውን የደም ብዛት ይገልጻል። አት፡- "ምድራቸው በደም ትሞላለች' (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየት ተመልከት)

አፈራቸውም በስብ ትወፍራለች
በዚህ ስፍራ አፈር ማለት የመሬት ትቢያ ማለት ነው። እጅግ ብዙ እንስሳትን በመብላት ከወፈረ ሰው ጋር በማስተያየት በመሬት ትቢያ ላይ የሚፈስሰውን የስብ ብዛት ይገልጻል። (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየት ተመልከት)

Isaiah 34:8

ለእግዚአብሔር የበቀል ቀን ይሆናል
በዚህ ስፍራ "ቀን' የሚለው በቀጥታ "ቀን' ማለት ሳይሆን አንድ የተወሰነ ጊዜን የሚያመለክት ፈሊጣዊ ንግግር ነው። (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

በጽዮን ጉዳይ ብድራታቸውን መልሶ ይከፍላቸዋል
ይህ ማለት አስቀድሞ በኢያሩሳሌም ላይ ላካሄዱት ጦርነት እግዚአብሔር ይበቀላቸዋል ማለት ነው። አት፡- "በጽዮን ሰዎች ላይ ስላደረጉት እግዚአብሔር የሚገባቸውን ቅጣት ይሰጣቸዋል' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

የኤዶምያስ ፈሳሾች ዝፍት ሆነው ይለወጣሉ፣ አፈርዋም ድኝ ይሆናል
ስለ ተቃጠሉና በዝፍትና በድኝ ስለተሸፈኑ ውኃውና መሬቱ ለመጠጥና ምግብ ለማሳደግ የማይጠቅሙ መሆናቸው ፈሳሾቻቸውና ምድራቸው በተጨባጭ ዝፍትና ድኝ እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "የኤዶምያስ ፈሳሾች በዝፍት የተሞሉ ይሆናሉ ምድራቸውም በሚነድድ ድኝና ዝፍት ይሸፈናል' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

መሬትዋ ... አፈርዋ
"የኤዶምያስ መሬት... የኤዶምያስ አፈር'

ዝፍት
ለረጅም ጊዜ የሚነድድ ወፍራም፣ ጥቁር ነገር።

በሌሊትም በቀንም ይነድዳል
ይህ ሁልጊዜ ማለት ነው። አት፡- "ሌሊቱንና ቀኑን ሙሉ ይነድዳል' ወይም "ሌሊቱንና ቀኑን ሁሉ ሳያቋርጥ ይነድዳል' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ከትውልድ እስከ ትውልድ
"ከትውልድ እስከ ትውልድ' የሚለው ሐረግ ወደፊት የሚኖሩትን የሰዎች ትውልዶች ሁሉ ያመለክታል። ይህንን ሐረግ በኢሳይያስ 13:20 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። አት፡- "ለዘላለም' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 34:11

በዚያ ይኖራሉ
"በኤዶም ምድር ይኖራሉ'

ጉጉት
ይህንን በኢሳይያስ 13:21 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ቁራ
ይህ ትልቅ ጥቁር አሞራ ነው። በዚህ ምንባብ የተጠቀሱትን አንዳንድ የወፍ ዓይነቶች በትክክል መለየት አስቸጋሪ ነው። ነገር ግን፣ ወፎች ሁሉ ሰዎች በሌሉበት ቦታ መኖር ይመርጣሉ፣ ስለዚህ ሰው የሌለበት ቦታ ወይም ምድረ በዳን ይወክላሉ።

በውስጥዋ
"በዚያ።' ይህ ኤዶምያስን ያመልክታል።

በላያዋም የመፍረስ ገመድና የባዶነት ቱንቢ ይዘረጋባታል
ይህ የኤዶምያስን ጥፋት የሚያስከትል ጠንቃቃ ግንበኛ እንደሆነ አድርጎ ስለ እግዚአብሔር ይናገራል። አት፡- "እግዚአብሔር ምድሪቱን በጥንቃቄ ይለካል፣ ከየት ማፍረስና ማጥፋት እንዳለበት ለመወሰን ይለካታል።' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

መለኪያ ገመድ ... ቱንቢ
እነዚህ የግንበኛ መሣሪያዎች ናቸው። ተመሣሣይ የሆኑ ቃላትን በኢሳይያስ 28:17 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

መሳፍንቶችዋን ... ልዑላንዋን
"የኤዶምያስ መሳፍንቶች ... የኤዶምያስ ልዑላን'

ልዑላንዋ ሁሉ ምናምን ይሆናሉ
ይህ ልዑላኑ ንጉሣዊ የሆነ ማኅበራዊ ደረጃቸውን ማጣታቸውን ምናምን ይሆናሉ በማለት አጋኖ ያቀርበዋል። አት፡- "ልዑላኗ ሁሉ ከእንግዲህ ወዲህ አይገዙም' (ግነትን ማጠቃለያ ተመልከት)

Isaiah 34:13

እሾህ ... ሳማ ...አሜክላ
እነዚህ ሁሉ እሾህ ያላቸው አረሞች ናቸው። የሳማ እሾህ የሚያሳክክ መርዝ አለው።

ቀበሮዎች ... ሰጎኖች ... የዱር እንስሳት ... ጅቦች ... ጉጉቶች
የእነዚህን እንስሳት ስም በኢሳይያስ 13:21-22 እንዳደረግኸው ተርጉም።

የሌሊት እንስሳት
በሌሊት የሚነቁና ንቁ የሆኑ እንስሳት።

ጭልፊት
ትናንሽ እንስሳትን ለምግብነት የሚገድል አሞራ።

Isaiah 34:16

በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ
የእግዚአብሔር መጽሐፍ ማለት እግዚአብሔር የተናገረውን መልእክት የያዘ ማለት ነው። አት፡- "የእግዚአብሔርን መልእክት በያዘው መጽሐፍ ውስጥ የተጻፈውን በጥንቃቄ አንብብ' (ባለቤትነት ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከእነዚህ አንዱ
"ከእንስሳቱ አንዱ'

ጓደኛውን የሚያጣ የለም
ይህ በአዎንታዊ አረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እያንዳንዱ እንስሳ ጓደኛ ይኖረዋል' (ድርብ አሉታዊ ተመልከት)

አፉ አዝዞአልና
ለተናገረው አጽንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር በአፉ ተወክሏል። አት፡- "እግዚአብሔር አዝዞልና' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

ለስፍራቸውም ዕጣ ጣለላቸው
ይህ እግዚአብሔር እንስሳት የት መኖር እንዳለባቸው መወሰኑ ለስፍራቸው በተጨባጭ ዕጣ እንደጣለላቸው ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "የት እንደሚኖሩ ወሰነ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

እጁም በገመድ ለካችላቸው
ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ሰዎች ነገሮችን የሚለኩበትን መንገድ ያመለክታል። አት፡- "ለእንስሳት መኖሪያቸውን ሰጣቸው'

ከትውልድ እስከ ትውልድ ድረስ
ከትውልድ እስከ ትውልድ የሚለው ሐረግ ወደፊት የሚኖሩትን የሰዎች ትውልዶች ሁሉ ያመለክታል። ከትውልድ እስከ ትውልድ የሚለውን ሐረግ በኢሳይያስ 13:20 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። አት፡- "ለዘላለም' ወይም "ሁልጊዜ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 35

1 ምድረ በዳውና ደረቁ ምድር ደስ ይላቸዋል፣ በረሀውም ሐሤት ያደርጋል እንደ ጽጌ ረዳም ያብባል። **2** እጅግ ተትረፍርፎ ያብባል፣ በደስታና በዝማሬ ሐሤትን ያደርጋል፤ የሊባኖስ ክብር፥ የቀርሜሎስና የሳሮን ግርማ ይሰጠዋል፤ የእግዚአብሔርንም ክብር የአምላካችንንም ግርማ ያያሉ። **3** የደከሙትን እጆች አበርቱ፣ የላሉትንም ጕልበቶች አጽኑ። **4** ፈሪ ልብ ላላቸው፣ "ተመልከቱ፣ አምላካችሁ በበቀል በእግዚአብሔርም ብድራት ይመጣልና፣ መጥቶም ያድናችኋልና በርቱ፣ አትፍሩ" በሉአቸው። **5** በዚያን ጊዜም የዕውሮች ዓይን ያያል፣ የደንቆሮችም ጆሮ ይሰማል። **6** በዚያን ጊዜ አንካሳ እንደ ሚዳቋ ይዘልላል፣ የድዳም ምላስ ይዘምራል፤ በምድረ በዳ ውኃ፣ በበረሀም ፈሳሽ ይፈልቃልና። **7** ደረቂቱ ምድር ኩሬ፣ የጥማት መሬት የውኃ ምንጭ ትሆናለች፤ ቀበሮ የተኛበት መኖሪያ ልምላሜና ሸምበቆ ደንገልም ይሆንበታል። **8** በዚያም ጐዳናና መንገድ ይሆናል እርሱም የተቀደሰ መንገድ ይባላል። ንጹሐንም ያልሆኑ አይጓዙበትም። ነገር ግን ለሚጓዙበት ይሆናል፤ ተላላፊዎችና ሰነፎች አይጓዙበትም። **9** አንበሳም አይኖርበትም፣ ነጣቂ አውሬም አይወጣበትም፣ ከዚያም አይገኙም፤ የዳኑት ግን በዚያ ይሄዳሉ፤ **10** እግዚአብሔርም የተቤዣቸው ይመለሳሉ እየዘመሩም ወደ ጽዮን ይመጣሉ፤ የዘላለም ደስታ በራሳቸው ላይ ይሆናል፤ ሐሤትንና ደስታን ያገኛሉ፣ ኀዘንና ትካዜም ይሸሻሉ።

Isaiah 35:1

ምድረ በዳውና ደረቁ ምድር ደስ ይላቸዋል፣ በረሃውም ሐሴት ያደርጋል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ አንድ ትርጉም አላቸው። እነዚህ ቦታዎች ውኃን ማበብንም ስለገኙ ሰው ደስ እንደሚለው ደስ እንዳላቸው ተገልጸአል። አት፡- "እንደ ምድረ በዳው ደረቁ ምድር ደስ ይለዋል በረሃውም ሐሴት ያደርጋል' (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየትና አጓዳኝነት ተመልከት)

አበባ
በምድረ በዳ የሚገኙ ተክሎች ማበብ እንደ ራሱ እንደ ምድረ በዳው ማበብ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "ተክሎቹ ያብባሉ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

እንደ ጽጌ ረዳም እጅግ ያብባል
ይህ የምድረ በዳ ተክሎች የሚያብቡበትን መንገድ ብዙ አበባዎች ያሉት ጽጌ ረዳ ከሚያብበት መንገድ ጋር ያስተያያል። አት፡- "ምድረ በዳው ብዙ አዳዲስ ተክሎችንና ዛፎችን ያበቅላል' (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

በደስታና በዝማሬ ሐሤትን ያደርጋል
ይህ እንደ ሰው ደስተኛ እንደሚሆንና እንደሚዘምር አድርጎ ስለ ምድረ በዳ ይናገራል። አት፡- "ቢሆንም ይሆናል ሁሉም ነገር ደስ ይለዋል ይዘምራልም' (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየት)

የሊባኖስ ክብር ይሰጠዋል
ይህ በአደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። ይህ እግዚአብሔር ምድረ በዳውን እንደ ሊባኖስ ታላቅ ማድረጉ ለምድረ በዳው የሊባኖስን ክብር እንደሰጠው ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "እግዚአብሔር የሊባኖስን ክብር ይሰጠዋል' ወይም "እግዚአብሔር እንደ ሊባኖስ ታላቅ ያደርገዋል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የቀርሜሎስና የሳሮን ግርማ
ይህ እግዚአብሔር ምድረ በዳውን እንደ ቀርሜሎስና ሳሮን ውብ እንዲሆን ማድረጉ ለምድረ በዳው የእነርሱን ውበት እንደሰጠ ተደርጎ ተነግሮአል። ይታወቃል በሚል ያልተነገረው መረጃ ሊታከል ይችላል። አት፡- "የቀርሜሎስና የሳሮን ውበት ይሰጠዋል' ወይም "እግዚአብሔር እንደ ቀርሜሎስና ሳሮን ውብ ያደርገዋል' (ስዕላዊ ንግግርና መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉ ተመልከት)

የእግዚአብሔርንም ክብር የአምላካችንንም ግርማ
እነዚህ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች በመሠረቱ የሚናገሩት አንድ ነገር ሲሆን ለእግዚአብሔር መገለጥ ላይ አጸንዖት ይሰጣሉ። (የሁለት ነገሮች ተመሳሳይነት ተመልከት)

Isaiah 35:3

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።

የደከሙትን እጆች አበርቱ፣ የላሉትንም ጕልበቶች አጽኑ
"የደከሙ እጆች' እና "የላሉ ጕልበቶች' የሚሉት ቃላት የፈራን ሰው ይወክላሉ። አት፡- "ከፍርሃት የተነሳ እጆቻቸው የደከሙባቸውን አበርቱ፣ ጕልበቶቻቸውም የላሉባቸውን አጽኑ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

ፈሪ ልብ ላላቸው
በዚህ ስፍራ ሰዎች የውስጥ ስሜቶቻቸውን በሚያጎሉ በልቦቻቸው ተወክልዋል። አት፡- "የፈሩ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

ተመልከቱ
ይህ የአድማጮችን ትኩረት ቀጥሎ ወደ ሚነገረው ለመሳብ ጥቅም ላይ ውሏል። አት፡- "ስሙ'

አምላካችሁ በበቀል፣ በእግዚአብሔርም ብድራት ይመጣልና
ይህ "በቀል' እና "ብድራት' የሚሉት የነገር ስሞች "ቀጣ' በሚል ማሰሪያ አንቀጽ እንዲገለጹ እንደገና ሊጻፍ ይችላል። "በቀል' እና "ብድራት' የሚሉት ቃላት ትርጉማቸው ተመሣሣይ ሲሆን እግዚአብሔር የይሁዳን ጠላቶች የሚቀጣ መሆኑን ያጎላሉ። አት፡- "ስላደረጉት ነገር አምላካችሁ ጠላቶቻችሁን ይቀጣል' (የነገር ስምና የሁለት ነገሮች ተመሳሳይነት ተመልከት)

Isaiah 35:5

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ቁጥሮች የእግዚአብሔርን ሕዝብ መፃኢ ክብር መግለጽ ይጀምራሉ።

የዕውሮች ዓይኖች ያያሉ
"ዕውሮች' የሚለው ዕውሮች ሰዎችን ያመለክታል። ፈውሳቸውን ለማጉላት በዓይኖቻቸው ተወክለዋል። (ስማዊ ቅጽልና ተለዋጭ ስም ተመልከት)

የደንቆሮች ጆሮች ይሰማሉ
"ደንቆሮ' የሚለው መስማት የማይችሉትን ሰዎች ይወክላል። ፈውሳቸውን ለማጉላት በጆሮቻቸው ተወክለዋል። አት፡- "ደንቆሮች ሰዎች ይሰማሉ' (ስማዊ ቅጽልና ተለዋጭ ስም ተመልከት)

አንካሳ እንደ ሚዳቋ ይዘላል
ሚዳቋ በርቀትና በከፍታ ይዘላል። አንደ ሚዳቋ መዝለል በፍጥነትና በቀላሉ መንቀሳቀስ ለመቻል ጥቅም ላይ የሚውል ግነት ነው። አት፡- "አንካሳ ሰው ከፍ ብሎ ይዘላል' (ዘይቤአዊ ንግግር እና ግነትና ማጠቃለያ ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የድዳም ምላስ ይዘምራል
ይህ መናገር የማይችሉትን ሰዎች ያመለክታል። ፈውሳቸውን ለማጉላት በምላሳቸው ተወክለዋል። አት፡- "ድዳ ሰዎች ይዘምራሉ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

ውኃ በምድረ በዳ
ባይባልም እንደተባለ የሚታወቀውን ማሰሪያ አንቀጽ መጠቀም ይቻላል። አት፡- "ውኃ በምድረ በዳ ይፈስሳል' (መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉ ተመልከት)

የሚፋጅ አሸዋ ኩሬ ይሆናል
ይህ የውኃ ኩሬ በጋለ አሸዋ ውስጥ ይታያል ማለት ነው። የዚህ ዐረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ መሆን ይችላል። አት፡- "በሚፋጅ አሸዋ ውስጥ ኩሬ ይታያል' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

የጥማት መሬት
በዚህ ስፍራ ደረቅ መሬት እንደ ተጠማ ሰው ተደርጎ ተገልጾአል። አት፡- "ደረቅ መሬት' (ግዑዙን እንደ ሰው ማየት ተመልከት)

የጥማት መሬት የውኃ ምንጭ ትሆናለች
ይህ በደረቅ መሬት ምንጭ ይታያል ማለት ነው። የዚህ አረፍተ ነገር መሉ ትርጉም ግልጽ መሆን ይችላል። አት፡- "በጥማት መሬት የውኃ ምንጭ ይታያል' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ቀበሮዎች
ይህንን በኢሳይያስ 13:22 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ቁጤማና ሸምበቆ
በደረቅ አካባቢ የሚበቅሉ ተክሎች ናቸው።

Isaiah 35:8

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ቁጥሮች የእግዚአብሔርን ሕዝብ መፃኢ ክብር ገለጻ ይቀጥላሉ።

ቅዱስ መንገድ የሚባል አውራ ጎዳና በዚያ ይሆናል
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ቅዱስ መንገድ የሚል ስም ያለው አውራ ጎዳና በዚያ ይሆናል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

አውራ ጎዳና
ይህንን ቃል በኢሳይያስ 11:16 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ንጹሐንም ያልሆኑ
ይህ ንጹሐን ያልሆኑ ሰዎችን ያመለክታል። እግዚአብሔር በመንፈሱ ተቀባይነት የሌለውና የረከሰ አድርጎ የሚቆጥረው ሰው በአካሉ ንጹሕ እንዳልሆነ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "ንጹሕ ያልሆኑ ሰዎች' ወይም "በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸው ሰዎች' (ስማዊ ቅጽልና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በእርሷ የሚሄድባት
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። በዚህ ስፍራ መሄድ መኖርን ያመልክታል። ይህ የተቀደሰ ሕይወት የሚኖርን ሰው ያመለክታል። የዚህ አረፍተ ነገር መሉ ትርጉም ግልጽ መሆን ይችላል። አት፡- "በተቀደሰ መንገድ የሚኖር' ወይም "የተቀደስ ሕይወት የሚኖር' (ፈሊጣዊ ንግግርና እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

በዚያ አይገኙም
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊተረጎም ይችላል። አት፡- "ማንም በዚያ አያገኛቸውም' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

የዳኑ
ይህ እግዚአብሔር ያዳናቸውን ሰዎች ያመለክታል። አት፡- "የዳኑቱ' ወይም "እግዚአብሔር ያዳናቸው' (ስማዊ ቅጽል ተመልከት)

Isaiah 35:10

እግዚአብሔር የተቤዣቸው
"መቤዠት' ማለት "ማዳን' ማለት ነው። ይህ እግዚአብሔር ያዳናቸውን ሰዎች ያመለክታል። አት፡- "እግዚአብሔር ያዳናቸው እነርሱ' (ስማዊ ቅጽል ተመልከት)

የዘላለም ደስታ በራሳቸው ላይ ይሆናል
ይህ የሰውን ራስ የሰው ሁለንተና ለማለት ይጠቀማል። አት፡- "ዘላለማዊ ደስታ ይኖራቸዋል' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

ሐሤትና ደስታ ... ጎዘንና ትካዜ
"ጎዘን' እና "ትካዜ' እንደሆኑት ሁሉ "ሐሤት' እና "ደስታ' የሚሉት ቃላት በመሠረቱ ትርጉማቸው አንድ ነው። በአንድነት የእንዚህን ስሜቶች ከፍተኛ ደረጃ መድረስ ያጎላሉ። (የሁለት ነገሮች ተመሣሣይነት ተመልከት)

ሐሤትና ደስታ ይቆጣጠራቸዋል
ይህ አንድን ሰው በኃይል ለመቆጣጠር የመቻልን ሰብዓዊ ችሎታ ለእነዚህ ስሜቶች በመስጠት ሕዝቡ በሐሤትና በደስታ እንደሚጥለቀለቁ ይናገራል። አት፡- "በሐሤትና በደስታ ይጥለቀለቃሉ' (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየት ተመልከት)

ጎዘንና ትካዜ ይሸሻሉ
የሰውን የመሮጥ ችሎታ ለእነዚህ ስሜቶች በመስጠት ሕዝቡ ከእንግዲህ ወዲያ ሐዘንተኞችና የሚተክዙ እንደማይሆኑ ይናገራል። አት፡- "ከእንግዲህ ወዲያ ሐዘንተኞችና የሚተክዙ አይሆኑም' (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየት ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 36

1 እንዲህም ሆነ፣ በንጉሡ ሕዝቅያስ በዐሥራ አራተኛው ዓመት፣ የአሦር ንጉሥ ሰናክሬም ወደ ይሁዳ ወደ ተመሸጉት ከተሞች ሁሉ ወጥቶ ያዛቸው። 2 ከዚያም፣ የአሦርም ንጉሥ ራፋስቂስን ከብዙ ሠራዊት ጋር ከለኪሶ ወደ ንጉሡ ወደ ሕዝቅያስ ወደ ኢየሩሳሌም ላከ፣ እርሱም በአጣቢው እርሻ መንገድ ባለችው በላይኛይቱ ኵሬ መስኖ አጠገብ ቆመ። 3 የቤቱም አዛዥ የኬልቅያስ ልጅ ኤልያቄም ጸሐፊውም ሳምናስ ታሪክ ጸሐፊም የአሳፍ ልጅ ዮአስ ወደ እርሱ ወጡ። 4 ራፋስቂስም እንዲህ አላቸው፣ "ለሕዝቅያስ እንዲህ ብላችሁ ንገሩት፣ ታላቁ የአሦር ንጉሥ እንዲህ ይላል፣ "ይህ የምትታመንበት መተማመኛ ምንድር ነው? 5 እኔ፣ ለሰልፍ የሆነው ምክርህና ኃያልህ ከንቱ ነገር ነው አልሁ፤ አሁንም በእኔ ላይ ያመፅኸው በማን ተማምነህ ነው? 6 ተመልከት፣ እየታመንክ ያለኸው በዚህ በተቀጠቀጠ በሸምበቆ በትር በግብጽ ነው። ሰው ቢመረኰዘው ተሰብሮ በእጁ ይገባል ያቈስለውማል። የግብጽ ንጉሥ ፈርዖን ለሚታመኑበት ሁሉ አንዲሁ ነው። 7 አንተም፣ "በአምላካችን በእግዚአብሔር እንታመናለን ብትለኝ፣ ሕዝቅያስ ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን፣ "በዚህ መሠዊያ ፊት ስገዱ" ብሎ የኮረብታ መስገጃዎቹንና መሠዊያዎቹን ይስፈረሰ ይህ አይደለምን? 8 አሁን እንግዲህ፣ ከጌታዬ ከአሦር ንጉሥ ጋር በመልካም ተደራደር። የሚጋልቡባቸውንም ሰዎች ማግኘት ቢቻልህ እኔ ሁለት ሺህ ፈረሶች እሰጥሃለሁ። 9 ስለ ሰረገሎችና ስለ ፈረሶኞች በግብጽ ስትታመን፣ ከጌታዬ ባሪያዎች የሚያንሰውን የአንዱን አለቃ ፊት ትቃወም ዘንድ እንዴት ይቻልሃል? 10 አሁንም በውኑ ያለ እግዚአብሔር ትእዛዝ ይህን አገር አጠፋ ዘንድ ወጥቻለሁን? እግዚአብሔር፣ "ወደዚህ አገር ወጥተህ አጥፋው" አለኝ። 11 ከዚያም ኤልያቄምና ሳምናስ፣ ዮአስም ራፋስቂስን፣ "እኛ እንሰማለንና እባክህ፣ በሶርያ ቋንቋ ለባሪያዎችህ ተናገር፤ በቅጥርም ላይ ባለው ሕዝብ ጆሮ በአይሁድ ቋንቋ አትናገረን" አሉት። 12 ራፋስቂስ ግን፣ "ጌታዬ ይህን ቃል እናገር ዘንድ ወደ አንተና ወደ ጌታህ ልኮኛልን? ከእናንተ ጋር ዐይነምድራቸውን ይበሉ ዘንድ ሽንታቸውንም ይጠጡ ዘንድ በቅጥር ላይ ወደ ተቀመጡት ሰዎች አይደለምን?" አላቸው። 13 ራፋስቂስም ቆሞ በታላቅ ድምፅ በአይሁድ ቋንቋ እንዲህ ብሎ ጮኸ፣ "የታላቁን የአሦርን ንጉሥ ቃል ስሙ፤ 14 ንጉሡ እንዲህ ይላል፣ 'ያድናችሁ ዘንድ አይችልምና ሕዝቅያስ አያታልላችሁ። 15 ሕዝቅያስም፣ "እግዚአብሔር በእርግጥ ያድነናል ይህችም ከተማ በአሦር ንጉሥ እጅ አትሰጥም" ብሎ በእግዚአብሔር እንድትታመኑ አያድርጋችሁ። 16 ሕዝቅያስንም አትስሙ፣ የአሦር ንጉሥ እንዲህ ይላልና፦ 'ከእኔ ጋር ታረቁ ወደ እኔም ውጡ። እያንዳንዳችሁም ከወይናችሁና ከበለሳችሁ ብሉ፣ ከጕድጓዳችሁም ውኃ ጠጡ። 17 ይህም መጥቼ ምድራችሁን ወደምትመስለው ምድር፣ እህልና የወይን ጠጅ፣ እንጀራና ወይን ወዳለበት ምድር እስካፈልሳችሁ ድረስ ነው።' 18 ሕዝቅያስም፣ 'እግዚአብሔር ያድነናል' ብሎ እንዳያታልላችሁ ተጠንቀቁ። በውኑ የአሕዛብ አማልክት አገሮቻቸውን ከአሦር ንጉሥ እጅ አድነዋቸዋልን? 19 የሐማትና የአርፋድ አማልክት ወዴት አሉ? የሴፈርዋይም አማልክት ወዴት አሉ? ሰማርያን ከእጄ አድነዋታልን? 20 እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ከእጄ ያድን ዘንድ ከእነዚህ አገሮች አማልክት ሁሉ አገሩን ከእጄ ያዳነ ማን ነው?" 21 ነገር ግን ንጉሡ አንዳይመልሱለት አዝዞ ነበርና ሕዝቡ ዝም አሉ፣ አንዳችም አልመለሱለትም። 22 ከዚያም የቤቱ አዛዥ የኬልቅያስ ልጅ ኤልያቄም ጸሐፊውም ሳምናስ ታሪክ ጸሐፊም የአሳፍ ልጅ ዮአስ ልብሳቸውን ቀድደው ወደ ሕዝቅያስ መጡ፣ የራፋስቂስንም ቃል ነገሩት።

Isaiah 36:1

አሥራ አራተኛ ዓመት
"14 ዓመት' (የደረጃ ቁጥር ተመልከት)

ንጉሥ ሕዝቅያስ
የዚህን ንጉሥ ስም በኢሳይያስ 1:1 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ሰናክሬም
ይህ የአሦር ንጉሥ ስም ነው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

ሰናክሬም ... የተመሸጉ ከተሞችን ሁሉ ወጋቸው
በዚህ ስፍራ ሰናክሬም ራሱንና ሠራዊቱን ይወክላል። አት፦ "ሰናክሬምና ሠራዊቱ ... የተመሸጉ ከተሞችን ሁሉ ወጉ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

ዋናው አዛዥ
አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ እትሞች ይህንን "ራፋስቂስ' ብለው ይተረጉሙታል። በአሦር የሠራዊት አመራሮች ከፍተኛ ማዕረግ ላለው ጥቅም ላይ የሚውል የአሦራውያን ቃል ነው።

ለኪሶ
ከኢየሩሳሌም ደቡብ ምዕራብ የምትገኝ ከተማ ነች። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

ቱቦ
የውኃ መተላለፊያ ሰው ሰራሽ ቦይ ወይም ዋሻ። ይህንን በኢሳይያስ 7:3 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

የአጣቢው እርሻ
አጣቢዎች፦ 1) ከበግ የተሸለተ የበግ ጸጉር የሚያጥብ ሰው፤ "የበግ ጸጉር አጣቢ' እርሻ ወይም 2) የቆሸሹ ልብሶችን የምታጥብ ሴት፤ "የልብስ አጣቢ እርሻ።' ይህንን በኢሳይያስ 7:3 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

ኬልቂያስ ... ኤልያቄም
የእነዚህን ሰዎች ስም በኢሳይያስ 22:20 እንዴት እንደረጎምህ ተመልከት። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

ሳምናስ
የዚህን ሰው ስም በኢሳይያስ 22:15 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

አሳፍ ... ዮአስ
እነዚህ ሰዎች ስሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

Isaiah 36:4

አላቸው
"ለኤልያቄም፣ ሳምናስ እና ዮአስ'

የመተማመኛችሁ ምክንያት ምንድር ነው?
ለመተማመኛ በቂ ምክንያት የለውም በማለት ንጉሥ ሕዝቅያስን ለመገዳደር የአሦር ንጉሥ ይህን ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ ጥያቄ በአሳብ ገላጭ አረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። አት፦ "ለመተማመኛ አስተማማኝ ምክንያት የለህም።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ለሰልፍ የሆነ ምክርና ኃይልህ
"ለሰልፍ የሆነ ምክርና ኃይል አለህ።' "ለሰልፍ የሆነ ... ኃይል' የሚለው ሐረግ በብዛቱ በቂ በኃይሉም በቂ የሆነ ሠራዊትንና የጦር መሣሪያ ያለው መሆንን ያመልክታል። አት፦ "ሰልፍ ለማድረግ በቂ ወታደራዊ ምክር፣ ኃያላን ሰዎችና የጦር መሣሪያ አለህ' (ምትክ ስም ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አሁን የተማመንከው በማን ነው? በእኔ ላይ እንድታምጽ ድፍረት የሰጠህ ማን ነው?
ለማመጽ ኃይል እንዳለው በማመኑ በሕዝቅያስ ላይ ለመሳለቅ የአሦር ንጉሥ እነዚህን ጥያቄዎች ይጠቀማል። ይህ ጥያቄ በአሳብ ገላጭ ዐረፍተ ነገርነት ሊጻፍ ይችላል። አት፦ "በማንም ተማመንክ ምንም ለውጥ አያስከትልም፣ በእኔ ላይ ለማመጽ ድፍረት አይኖርህም።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

Isaiah 36:6

አጠቃላይ መረጃ
ከአሦር ንጉሥ ለሕዝቅያስ የተላከው መልእክት ይቀጥላል። ዋናው አዛዥ ለሕዝቅያስ ሰዎች መልእክቱን ይናገራል። (ኢሳይያስ 36፡4-5 ተመልከት)

ተመልከት
በመቀጠል ወደ ሚናገረው የሕዝቅያስን ትኩረት ለመሳብ ሰናክሬም ይህን ቃል ይጠቀማል። አት፦ "ስማ'

በግብጽ መታመን
በዚህ ስፍራ ግብጽ የሚለው የግብጽን ሠራዊት ያመለክታል። አት፦ "በግብጻውያን ሠራዊት መታመን' (ምትክ ስም ተመልከት)

እንደ ምርኩዝ የምትጠቀምበት የተቀጠቀጠ ሸምበቆ፣ ነገር ግን ሰው ቢመረኮዘው ተሰብሮ በእጁ ይገባል ያቆስለውማል
ይህ በእነርሱ መታመኑ እንደማይረዳቸው ነገር ግን እንደሚጎዳቸው ለማጉላት የተቀጠቀጡ ሸምበቆ እንደሆኑ አድርጎ ስለ ግብጽ በተለይ ስለ ሠራዊቱና ስለ ፈርዖን ይናገራል። አት፦ "የተቀጠቀጠን ሸምበቆ ምርኩዝ አድርጎ እንደመሄድ ነው። ሰው ከተመረኮዘው ተሰብሮ በእጁ ይገባል ያቆስለውማል።' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የተቀጠቀጠ ሸምበቆ
ሸምበቆ ሣር የሚመስል ረጅም፣ ቀጭን ግንድ ያለው ተክል ነው። ከተቀጠቀጠ ወይም ከተጎዳ ምንም ክብደት መሸከም አይችልም።

ምርኩዝ
ከየትኛውም ዓይነት የዛፍ ቅርንጫፍ የሚሠራ አንድ ሰው በሚሄድበት ጊዜ ለመደገፊያነት የሚጠቀምበት በትር ነው።

ሕዝቅያስ የኮረብታ መስገጃዎቹንና መሠዊያዎቹን ያፈረሰበት አይደለምን ... ኢየሩሳሌም
ሕዝቡን ለማሞኘትና ሕዝቅያስ ባደረገው እግዚአብሔር ስለተቆጣ አይጠብቃችሁም ለማለት የአሦር ንጉሥ እነዚህ ጥያቄዎች ይጠቀማል። ይህ አሳብ ገላጭ ጥያቄ በአሳብ ገላጭ አረፍተ ነገርነት ሊተረጎም ይችላል። አት፦ "እርሱ፣ ሕዝቅያስ የኮረብታ መስገጃዎቹንና መሠዊያዎቹን ያፈረሰበት ነው ... ኢየሩሳሌም' ወይም "እርሱ፣ ሕዝቅያስ የኮረብታ መስገጃዎቹንና መሠዊያዎቹን በማፍረስ ያቃለለው ነው ... ኢየሩሳሌም' (አሳብ ገላጭ ጥያቄና እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን፣ "በኢየሩሳሌም በዚህ መሠዊያ ፊት መስገድ' አለባችሁ ያለ?
ይህ በቀጥታ እንዳልተወሰደ ሊጻፍ ይችላል። "ይሁዳ' እና ኢየሩሳሌም በውስጣቸው የሚኖረውን ሕዝብ ያመለክታሉ። አት፦ "ለይሁዳና ለኢየሩሳሌም ሕዝብ በኢየሩሳሌም በዚህ መሠዊያ ብቻ መስገድ እንዳለባቸው ነገራቸው' (በቀጥታ የተወሰደና በቀጥታ ያልተወሰደ ጥቅስ እና ምትክ ስም ተመልከት)

Isaiah 36:8

አጠቃላይ መረጃ
ለሕዝቅያስ ሰዎች በመናገር የአሦር ንጉሥ ለሕዝቅያስ የላከው መልእክት ይቀጥላል። (ኢሳይያስ 36፡4-5 ተመልከት)

ሁለት ሺህ ፈረሶች
"2000 ፈረሶች' (ቁጥሮች ተመልከት)

የሚጋልቡባቸውን ሰዎች ማግኘት ቢቻልህ
ዋናው አዛዥ ብዙ ወታደሮች እንደሌለው በማመልከት በሕዝቅያስና በሠራዊቱ ላይ መሳለቁን ይቀጥላል። (ምጸት ተመልከት)

Isaiah 36:9

አጠቃላይ መረጃ
ለሕዝቅያስ ሰዎች በመናገር የአሦር ንጉሥ ለሕዝቅያስ የላከው መልእክት ይቀጥላል። (ኢሳይያስ 36፡4-5 ተመልከት)

ከባሪያዎቹ ... አንዱን አለቃ እንኳን እንዴት መቋቋም ይቻልሃል?
ዋናው አዛዥ በሕስቅያስና ሠራዊቱ ላይ መሳለቁን ይቀጥላል። በዚህ ወስጥ "አንተ' እያለ ሲናገር የሚያመለክው ሕስቅያስን ነው፣ በእውነቱ ግን የሚያመለክተው የሕዝቅያስን ሠራዊት ነው። ይህ ጥያቄ በአረፍት ነገርነት ሊጻፍ ይችላል። አት፦ "ሠራዊትህ አንዱን አለቃ እንኳን ማሸነፍ አይችልም ... ከባሪያዎቹ' (አሳብ ገላጭ ጥያቄና ምትክ ስም ተመልከት)

አሁንም በውኑ ያለ እግዚአብሔር ትእዛዝ ይህን አገር አጠፋ ዘንድ ወጥቻለሁን?
ዋናው አዛዥ በሕዝቅያስና በይሁዳ ሕዝብ ላይ ለመሳለቅ ሌላ ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ ጥያቄ በአረፍተ ነገርነት ሊጻፍ ይቻላል። አት፦ "በእግዚአብሔር ትእዛዝ ኢየሩሳሌምን ለማጥፋት ወደዚህ መጥቼአለሁ።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ)

ያለ እግዚአብሔር
በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር የሚለው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ያመለክታል። አት፦ "ያለ እግዚአብሔር ትእዛዝ' (ምትክ ስም ተመልከት)

ይህን አገር አጠፋ ዘንድ ... ወደዚህ አገር ወጥተህ አጥፋው
ይህ ሕዝቡን መውጋትና በሚኖሩበት ቦታ ላይ ጥፋት ማድረስ ማለት ነው። አገር የሚለው በዚህ ሰፍራ ኢየሩሳሌምን ያመለክታል። አት፦ "በዚህ ሕዝብ ላይ ውጣ ምድራቸውን አጥፋ ... ይህንን ሕዝብ ውጋ ምድራቸውን አጥፋ' (ምትክ ስም ተመልከት)

Isaiah 36:11

ኤልያቄም ... ኬልቂያስ ... ሳምናስ
የእነዚህን ሰዎች ስም በኢሳይያስ 22፡20 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ሳምናስ
የዚህን ሰው ስም በኢሳይያስ 22፡15 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ዮአስ ... ዋናው አዛዥ
የዚህን ሰው ስምና ዋና አዛዥ የሚለውን ሐረግ በኢሳይያስ 36፡2-3 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

እባክህ ለባሪያዎችህ ተናገር
አልያቄም፣ ሳምናስና ዮአስ ራሳቸውን የዋናው አዛዥ አገልጋዮች እንደሆኑ አድርገው ይጠራሉ። ይህ አንድ ትልቅ ሥልጣን ያለውን ሰው በትህትና ማናገሪያ መንገድ ነው።

የአረሚን ቋንቋ፣ አረማይክ
አረሚን የተወሰነ የሰዎች ቡድን ስም ነው። አረማይክ የቋንቋቸው ስም ነው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

በቅጥርም ላይ ባሉት ሰዎች ጆሮ
በአንድ ሰው ጆሮ መናገር የሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ሊሰሙህ በሚችሉበት ቦታ ላይ መናገር ማለት ነው። አት፦ "በቅጥር ላይ ያሉ ሰዎች ሊሰሙን በሚችሉበት ቦታ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በቅጥርም ላይ ባለት
ይህ በቅጥሩ ላይ ቆመዋል ማለት ነው። የቅጥር ላይኛው ጫፍ ሰፊና ሰዎች ሊቀመጡና ሊቆሙ የሚችሉበት ቦታ ነው። የዚህ አረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም በይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አት፦ "በቅጥሩ ላይ በቆሙት' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ጌታዬ ይህን ቃል እናገር ዘንድ ወደ አንተና ወደ ወደ ጌታህ ልኮኛልን?
ዋናው አዛዥ መልእክቱ ለይሁዳ ሕዝብ ሁሉ አንደሆነ ለማጉላት ይህንን ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ ጥያቄ በአረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። አት፦ "በእርግጥ አለቃዬ ይህን መልእክት ለአንተና መስማት ለሚችሉ ሁሉ እናገር ዘንድ ልኮኛል።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ከእናንተ ጋር ... ዘንድ በቅጥር ላይ ወደ ተቀመጡት ሰዎች አይደለምን?
ዋናው አዛዥ ስላቁን ለማጉላት ይህን ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ በአረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። አት፦ "ከአናንተ ጋር ... ዘንድ ይህን ለሚሰሙ ሁሉ እናገር ዘንድ ጌታዬ ልኮኛል።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ከእናንተ ጋር ኩሳቸውን ይበሉ ዘንድ ሸንታቸውንም ይጠጡ ዘንድ
ይህ በጣም የሚያበሳጭ አሳብ ነው። ከተማይቱ በውጊያ ውስጥ ስለሆነች እና የሚበሉት ምንም ስለሌላቸው እነዚህን ነገሮች ለመብላት ይፈልጋሉ ማለቱ ነው። የዚህ አረፍተ ነገር ሙሉ አሳብ በይበልጥ ግልጽ ሊሆን ይችላል። አት፦ "ምንም የምተበሉት ስለሌላችሁ፣ እንደ እናንተ፣ በቅርቡ ኩሳቸውን ለመብላት ሸንታቸውንም ለመጠጣት ይፈልጋሉ።' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ)

Isaiah 36:13

ዋናው አዛዥ
ይህን በኢሳይያስ 36:2 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ይህችም ከተማ በአሦር ንጉሥ እጅ አትሰጥም
ይህ በአደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን በአሦር ንጉሥ እጅ አሳልፎ አይሰጣትም' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

የንጉሥ እጅ
"የንጉሥ እጅ' የሚለው ንጉሡ በሌሎች ላይ ያለውን ሥልጣን ያመለክታል። አት፦ "ንጉሥ በሌሎች ላይ ያለው ሥልጣን' (ምትክ ስም ተመልከት)

Isaiah 36:16

አጠቃላይ መረጃ
ዋናው አዛዥ ለይሁዳ ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል።

ከእኔ ጋር ሰላም አድርጉ
ይህ ፈሊጣዊ ንግገር እርስ በእርስ በሰላም ለመገናኘት ሕጋዊ ስምምነት ማድረግ ማለት ነው። አት፦ "ሰላም እንዲኖረን እንስማማ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ወደ እኔ ወጡ
ይህ ፈሊጣዊ ንግግረ እጅ መስጠት ማለት ነው። አት፦ "ለእኔ እጃችሁን ስጡ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

እስክመጣና እስክወስድ
በዚህ ስፍራ የአሦር ንጉሥ ሠራዊቱን እንደራሱ አድርጎ ይናገራል። አት፦ "ሠራዊቴ እስኪመጣና እስኪወስድ' (ምትክ ስም ተመልከት)

የእህልና የወይን ጠጅ ምድር፣ የእንጀራና የወይን ምድር
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው፣ ሁለቱም ምድሪቱ ምን ያህል የበለጸገች እንደምትሆን ለማጉላት ጥቅም ላይ ውለዋል። (አጓዳኝነት ተመልከት)

የእህል ምድር ... የእንጀራ ምድር
ይህ ምድራቸው እንደ እህል ባሉ የተፈጠሮ ሀብቶች የተሞላች ነች ማለት ነው። አት፦ "የተትረፈረፈ እህል ያለባት ምድር ... የተትረፈረፈ እንጀራ ያለባት ምድር' (ባለቤትነት ተመልከት)

Isaiah 36:18

አጠቃላይ መረጃ
ዋናው አዛዥ የአሦርን ንጉሥ መልእክት ለይሁዳ ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል። (ኢሳይያስ 36:16 ተመልከት)

ከአሦር ... ከአሕዛብ አማልክት መካከል ያዳኗቸው
ዋናው አዛዥ በይሁዳ ሕዝብ ላይ ለመሳለቅ ይህን ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ ጥያቄ በአረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። አት፦ "ከአሦር ... ከሕዝቦች አማልክት መካካል ማንም አላዳኗቸውም' (አሳብ ገለጭ ጥያቄ ተመልከት)

የንጉሥ እጅ
ንጉሥ በሌሎች ላይ ያለው ሥልጣን እንደ እጁ ተገልጾአል። አት፦ "ንጉሡ በሌሎች ላይ ያለው ሥልጣን' (ምትክ ስም ተመልከት)

የሐማትና የአርፋድ አማልክት ወዴት አሉ የሴፈርዋይም አማልክት ወዴት አሉ? ሰማርያን ከኃይሌ አድነዋታልን?
ዋናው አዛዥ በይሁዳ ሕዝብ ላይ ለመሳለቅ ይህን ጥያቄ ይጠቀማል። እነዚህ ጥያቄዎች ሊጣመሩና በአረፍተ ነገር መልክ ሊጻፉ ይችላል። አት፦ "የሐማት፣ የአርፋድ፣ የሴፈርዋይ እና የሰማርያ አማልክት ሕዝባቸውን ከኃይሌ አላዳኗቸውም።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ሐማት ... አርፋድ
የእነዚህን ከተሞች ስም በኢሳይያስ 10:09 ባደረኸው መሠረት ተርጉም። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

ሴፈርዋይ
ይህ የከተማ ስም ነው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ከእጁ ያድን ዘንድ ... ሌላ ያዳነ አምላክ አለን?
ዋናው አዛዥ በይሁዳ ሕዝብ ላይ ለመሳለቅ ይህን ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ ጥያቄ በአረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። አት፦ "ያዳነ አምላክ የለም ... እግዚአብሔርም በኢየሩሳሌም ከእኔ ኃይል አያድናችሁም።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ምድሩን
x

Isaiah 36:21

ኤልያቄም ... ኬልቅያስ ... ሳምናስ ... ዮአስ ... አሳፍ
የእነዚህን ሰዎች ስም በኢሳይያስ 36:03 ባደረግኸው መሠረት ተርጉም። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

የቤቱ አዛዥ
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር በቤተ መንግሥት ቤተሰብ ጉዳዮች ሥልጣን ያለው ማለት ነው። አት፦ "በቤተ መንግሥቱ ላይ የተሾመ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 37

1 እንዲህም ሆነ፣ ንጉሡ ሕዝቅያስ ይህን በሰማ ጊዜ ልብሱን ቀደደ፣ ማቅም ለበሰ፣ ወደ እግዚአብሔርም ቤት ገባ። 2 የቤቱንም አዛዥ ኤልያቄምን፣
ጸሐፊውንም ሳምናስን የካህናቱንም ሽማግሌዎች ማቅ ለብሰው ወደ ነቢዩ ወደ አሞጽ ልጅ ወደ ኢሳይያስ ይሄዱ ዘንድ ላካቸው። 3 እነርሱም፣ "ሕዝቅያስ እንዲህ
ይላል፣ 'ይህ ቀን የመከራና የተግሣጽ የዘለፋም ቀን ነው፤ ልጆች የሚወለዱበት ጊዜ ደርሶአል፣ እናታቸው ግን ለመውለድ ኃይል የላትም። 4 ምናልባት በሕያው
አምላክ ላይ ይገዳደር ዘንድ ጌታው የአሦር ንጉሥ የላከውን የራፋስቂስን ቃል አምላክህ እግዚአብሔር ይሰማ እንደ ሆነ፣ አምላክህ እግዚአብሔር ስለ ሰማው ቃል
ይገሥጸው እንደ ሆነ፣ ስለዚህ አሁን ድረስ እዚህ ላለው ቅሬታ ጸልይ" አሉት። 5 ስለዚህ የንጉሡ የሕዝቅያስ ባሪያዎች ወደ ኢሳይያስ መጡ፣ 6 ኢሳይያስም
እንዲህ አላቸው፣ ለጌታችሁ እንዲህ በሉት፦ 'እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ የአሦር ንጉሥ ባሪያዎች ስለ ሰደቡኝ፣ ስለ ሰማኸው ቃል አትፍራ። 7 ተመልከት፣
በላዩ መንፈስን እሰድዳለሁ፣ ወሬንም ይሰማል፣ ወደ ምድሩም ይመለሳል። በምድሩም በሰይፍ እንዲወድቅ አደርጋለሁ" በሉት" አላቸው። 8 ከዚያም የአሦርም
ንጉሥ ከለኪሶ እንደ ራቀ ሰምቶ ነበርና ራፋስቂስ ተመልሶ በልብና ሲዋጋ አገኘው። 9 እርሱም፣ የኢትዮጵያ ንጉሥ ቲርሐቅ እና ግብጽ ሊወጉህ መጥቶአል የሚል
ወሬ ሰማ። በሰማም ጊዜ ወደ ሕዝቅያስ መልእክተኞችን ላከ፦ 10 እንዲህ ሲል፣ "ለይሁዳ ንጉሠ ለሕዝቅያስ እንዲህ ብላችሁ ንገሩት፣ 'ኢየሩሳሌም በአሦር
ንጉሥ እጅ አትሰጥም ብሎ የምትታመንበት አምላክህ አያታልልህ።' 11 ተመልከት፣ የአሦር ነገሥታት በምድር ሁሉ ላይ ያደረጉትን፣ እንዴትስ ፈጽመው
እንዳጠፉአቸው ሰምተሃል። አንተስ ትድናለህን? 12 አባቶቼ ያጠፉአቸውን ጎዛንን፣ ካራንን፣ ራፊስን፣ በተላሳር የነበሩትንም የዔድንን ልጆች የአሕዛብ አማልክት
አዳኑአቸውን? 13 የሐማት ንጉሥ፣ የአርፋድ ንጉሥ፣ የሴፈርዋይም ከተማ ንጉሥ፣ የሄናና የዒዋ ንጉሥ ወዴት አሉ?" 14 ሕዝቅያስም ደብዳቤውን
ከመልእክተኞች እጅ ተቀብሎ አነበበው። ሕዝቅያስም ወደ እግዚአብሔር ቤት ወጥቶ በእግዚአብሔር ፊት ዘረጋው። 15 ሕዝቅያስም ወደ እግዚአብሔር እንዲህ
ብሎ ጸለየ፣ 16 "አቤቱ፣ በኪሩቤል ላይ የምትቀመጥ የእስራኤል አምላክ የሠራዊት ጌታ ሆይ፣ አንተ ብቻህን የምድር መንግሥታት ሁሉ አምላክ ነህ፤ ሰማይንና
ምድርን ፈጥረሃል። 17 አቤቱ፣ ጆሮህን አዘንብልና ስማ። አቤቱ፣ ዐይኖችህን ክፈትና እይ፤ በሕያው አምላክ ላይ ይገዳደር ዘንድ የላከውን የሰናክሬም ቃል ስማ።
18 አቤቱ፣ በእውነት የአሦር ነገሥታት ዓለሙን ሁሉ አገሮቻቸውንም አፍርሰዋል፣ 19 አማልክቶቻቸውንም በእሳት ላይ ጥለዋል፣ የእንጨትና የድንጋይ የሰው እጅ
ሥራ ነበሩ እንጂ አማልክት አልነበሩምና ስለዚህ አጥፍተዋቸዋል። 20 እንግዲህም አምላካችን አቤቱ፣ የምድር መንግሥታት ሁሉ አንተ ብቻ እግዚአብሔር እንደ
ሆንህ ያውቁ ዘንድ ከእጁ አድነን።" 21 ከዚያም የአሞጽ ልጅ ኢሳይያስ እንዲህ ብሎ ወደ ሕዝቅያስ መልእክት ላከ፣ "የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል፣ 'ስለ አሦር ንጉሥ ስለ ሰናክሬም ወደ እኔ ለምነሃልና 22 እግዚአብሔር ስለ እርሱ የተናገረው ቃል ይህ ነው፣ ድንግሊቱ የጽዮን ልጅ ቀላል ንቃሃለች፣
በንቀትም ስቃብሃለች፤ የኢየሩሳሌም ልጅ ራስዋን ነቅንቃብሃለች። 23 የተገዳደርኸው የሰደብኸውስ ማን ነው? ቃልህንስ ከፍ ከፍ ያደረግህበት ዓይንህንስ ወደ
ላይ ያነሣህበት ማን ነው? በእስራኤል ቅዱስ ላይ ነው። 24 አንተም፣ በሰረገላዬ ብዛት ወደ ተራሮች ከፍታ፣ ወደ ሊባኖስ ጥግ ላይ ወጥቻለሁ፤ ረጃጅሞቹንም
ዝግባዎች የተመረጡትንም ጥዶች እቈርጣለሁ፣ ወደ ከፍታውም ዳርቻ ወደ ቀርሜሎስ ዱር እገባለሁ። 25 ቈፈርሁም ውኃም ጠጣሁ የግብጽንም ወንዞች ሁሉ
በእግሬ ጫማ አደርቃለሁ ብለህ በባሪያዎችህ እጅ በጌታ ላይ ተገዳደርህ።' 26 እኔ ጥንቱን እንደ ሠራሁት፣ ቀድሞውንም እንዳደረግሁት አልሰማህምን?
አሁንም የተመሸጉትን ከተሞች የፍርስራሽ ክምር እስኪሆኑ ድረስ እንድታፈርስ አደረግሁህ። 27 ስለዚህ የሚኖሩባቸው ሰዎች እጃቸው ዝሎአል፣ ደንግጠውም
ታውከዋል። እንደ ምድረ በዳ ሣር፣ እንደ ለመለመም ቡቃያ፣ በሰገነትም ላይ እንዳለ ሣር፣ ሳይሸት ዋግ እንደ መታው እህል ሆነዋል። 28 ነገር ግን እኔ
መቀመጫህንና መውጫህን፣ መግቢያህንም በእኔም ላይ የተቈጣኸውን ቍጣ አውቄአለሁ። 29 ቍጣህና ትዕቢትህ ወደጆሮዬ ደርሶአልና ስለዚህ ስናጋዬን
በአፍንጫህ ልጓሜንም በከንፈርህ አደርጋለሁ፣ በመጣህበትም መንገድ እመልስሃለሁ።" 30 ይህም ምልክት ይሆንሃል፦ በዚህ ዓመት የገቦውን፣ በሁለተኛውም
ዓመት ከገቦው የበቀለውን ትበላላችሁ። በሦስተኛውም ዓመት ትዘራላችሁ ታጭዳማላችሁ፣ ወይንም ትተክላላችሁ ፍሬውንም ትበላላችሁ። 31 ያመለጠው
የይሁዳ ቤት ቅሬታ ሥሩን ወደ ታች ይሰድዳል፣ ወደ ላይም ያፈራል። 32 ከኢየሩሳሌም ቅሬታ፣ ከጽዮንም ተራራ ያመለጡት ይወጣሉና።' የሠራዊት ጌታ
የእግዚአብሔር ቅንዓት ይህን ያደርጋል።" 33 ስለዚህም እግዚአብሔር ስለ አሦር ንጉሥ እንዲህ ይላል፣ "ወደዚህች ከተማ አይመጣም፣ ፍላጻንም
አይወረውርባትም። በጋሻም አይመጣባትም፣ የአፈርንም ምሽግ አይደለድልባትም። 34 በመጣበት መንገድ በዚያው ይመለሳል፤ ወደዚችም ከተማ
አይመጣም፤ ይላል እግዚአብሔር። 35 ስለ እኔም፣ ስለ ባሪያዬም ስለ ዳዊት፣ ይህችን ከተማ አድናት ዘንድ እጋርዳታለሁ።" 36 የእግዚአብሔርም መልአክ
ወጣ፣ ከአሦራውያንም ሰፈር መቶ ሰማንያ አምስት ሺህ ገደለ። ማለዳም በተነሡ ጊዜ፣ እነሆ፣ ሁሉ በየሥፍራው በድኖች ተረፍርፈው ነበሩ። 37 የአሦርም ንጉሥ
ሰናክሬም ተነሥቶ ሄደ፣ ተመልሶም በነነዌ ተቀመጠ። 38 ኋላ ላይ፣ በአምላኩም በናሳራክ ቤት ሲሰግድ፣ ልጆቹ አድራሜሌክና ሳራሳር በሰይፍ ገደሉት። ወደ
አራራትም አገር አመለጡ። ልጁም አስራዶን በእርሱ ፋንታ ነገሠ።

Isaiah 37:1

እንዲህም ሆነ
በዚህ ስፍራ ይህ ሐረግ በታሪኩ ወስጥ አስፈላጊ የሆነን ሁኔታ ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል። ቋንቋህ ይህን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ ልትጠቀምበት ትችላለህ። (አዲስ ሁኔታን ማስተዋወቅ ተመልከት)

ልብሱን ቀደደ፣ ማቅም ለበሰ
ይህ የልቅሶና የጭንቀት ምልክት ነው። አት፦ "በጣም ተጨንቆ ስለነበር ልብሱን ቀደደ በማቅም ተሸፈነ' (የምልክት ተግባር ተመልከት)

ኤልያቄም ... ሳምናስ
የእነዚህን ሰዎች ስም በኢሳይያስ 36፡03 ባደረግኸው መሠረት ተርጉም። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

የቤቱ አዛዥ
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር በቤተ መንግሥት ቤተሰብ ጉዳዮች ሥልጣን ያለው ማለት ነው። አት፦ "በቤተ መንግሥቱ ላይ የተሾመ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ሁሉም ማቅ ለበሱ
ይህ የልቅሶና የጭነቀት ምልክት ነው። (የምልክት ተግባር ተመልከት)

Isaiah 37:3

እንዲህ አሉት
በሕዝቅያስ የተላኩ ሰዎች ኢሳይያስን እንዲህ አሉት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ልጅ ለመወለድ ጊዜው እንድ ደረሰ ነገር ግን እናቲቱ ለመውለድ አቅም እንዳጣች ዓይነት ነው
እጅግ አስቸጋሪ በሆነ ጊዜ ውስጥ እንዳሉ ለማጉላት ይህ ማስተያየት ጥቅም ላይ ውሏል። አት፡- "ልጅ ለመወለድ ጊዜው እንድ ደረሰ ነገር ግን እናቲቱ ለመውለድ አቅም እንዳጣችበት አስፈሪ የሆነ ቀን ነው' (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

... ቃል አምላክህ እግዚአብሔር ይሰማ እንደ ሆነ
ሕዝቅያስ በተዘዋዋሪ ሕዝቡ ከጸለየ ዋናው አዛዥ የተናገረውን እግዚአብሔር ሊሰማና ተግባራዊ ምላሽ ሊሰጥ ይችላል። የዚህ አሳብ ሙሉ ትርጉም በይበለጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አት፡- "ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ከጸለይህ መልእክቱን ይሰማ ይሆናል' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ዋናው አዛዥ
ይህንን ሐረግ በኢሳይያስ 36:2 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ጌታው
ሐረጉ ንጉሡ የዋናው አዛዥ ጌታ ነው ማለት ነው።

አምላክህ እግዚአብሔርም ስለ ሰማው ቃል ይገሥጸው እንደሆነ
በዚህ ስፍራ አምላክህ እግዚአብሔርም ስለ ሰማው ቃል የሚለው ሐረግ የአሦር ንጉሥ የተናገረውን ያመለክታል። የዚህ አሳብ ሙሉ ትርጉም በይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር አምላክህ የአሦርን ንጉሥ ስለ ተናገረው ነገር ይገሥጸዋል' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ጸሎትህን ወደ ላይ አንሳ
እግዚአብሔር በሰማይ እንዳለ ለማጉላት ወደ እግዚአብሔር መጸለይ በዚህ መንገድ ተገልጾአል። ጸሎት ወደ ሰማይ ከፍ ሊደረግ እንደሚችል ቁስ ነገሮች ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "ጸልይ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

እስካሁን ቢዚህ ላሉት ለቅሬታው ጸልይ
ይህ በኢየሩሳሌም የቀሩትን ሰዎች ያመለክታል። አት፡- "እስከ አሁን በዚህ ላለን ለጥቂቶች' (ምትክ ስም ተመልከት)

Isaiah 37:5

በላዩ መንፈስን እሰድዳለሁ፣ ወሬንም ይሰማል፣ ወደ ምድሩም ይመለሳል
"በላዩ መንፈስን አሰድዳለሁ' የሚለው ሐረግ አንድ የተወሰነ ውሳኔ እንዲወስን እግዚአብሔር ተጽእኖ ያደርግበታል ማለት ነው። በዚህ ስፍራ መንፈስ የሚለው ቃል ጠንካራ ዝንባሌ ወይም ስሜት ማለት ነው። አት፡- "የተወሰነ ዘገባ ሲሰማ ወደ ምድሩ እንዲመለስ ተጽእኖ አደርግበታለሁ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ተመልከት
በዚህ ስፍራ ይህ ቃል በመቀጠል ወደ ሚነገረው የሕዝቡን ትኩረት ለመሳብ ጥቅም ላይ ውሏል። አት፡- "ስሙ'

በምድሩም በሰይፍ እንዲወድቅ አደርጋለሁ
"በሰይፍ እንዲወድቅ' የሚለው ሐረግ ጠላቱ በሰይፍ ይገድለዋል የሚል ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፡- "በገዛ ምድሩም፣ ጠላቶቹ በሰይፎቻቸው እንዲገድሉት አደርጋለሁ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 37:8

ለኪሶ
የዚህን ከተማ ስም በኢሳይያስ 36:2 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

ሰናክሬም
የዚህን ሰው ስም በኢሳያየስ 36:1 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

ልብና
ይህ በደቡብ ይሁዳ የምትገኝ ከተማ ነች። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

የኢትዮጵያ ንጉሥ ቲርሐቅ ሊዋጋው አንቀሳቅሷል
ቲርሐቅ የሰው ስም ነው። ለመዋጋት ዝግጁ እንዲሆኑ ሠራዊቱን አንቀሳቅሷል። የዚህ አሳብ ሙሉ ትርጉም በይበልጥ ግልጽ ሊሆን ይችላል። አት፡- "የኢትዮጵያ ንጉሥ ቲርሐቅ ሠራዊቱን አንቀሳቅሷል' (የስሞች አተረጓገም መንገድ እና እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ሊዋጋው
በዚህ ወስጥ "እርሱን' የሚለው ሰናክሬምን ይወክላል። በዚህ ስፍራ ሰናክሬም ሠራዊቱን ይወክላል። አት፡- "የሰናክሬምን ሠራዊት ሊዋጋ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ኢየሩሳሌም በአሦር ንጉሥ እጅ አትሰጥም
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። "እጅ' የሚለው ቃል የንጉሡን ወታደራዊ ኃይል ያመለክታል። አት፡- "የአሦር ንጉሥና ሠራዊቱ በኢየሩሳሌም አያሸንፉህም' (ምትክ ስምና አድራጊና ተደራጊ አንቀጽ ተመልከት)

Isaiah 37:11

አጠቃላይ መረጃ
ለሕዝቅያስ የተላከውን የአሦርን ንጉሥ መልእክት ይቀጥላል።

ተመልከት ሰምተሃል
በዚህ ስፍራ "ተመልከት' የሚለው ቃል በመቀጥል ለሚነገረው ተጨማሪ አጽንዖት ለመስጠት ጥቅም ላይ የዋለ ነው። አት፡- "በእርግጥ ሰምተሃል'

አንተስ ትድናለህን?
በሕዝቅያስና በሠራዊቱ ላይ ለመሳለቅ የአሦር ንጉሥ ይህን ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ በአረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። አት፡- "ስለዚህ አንተም አትድንም' ወይም "በእርግጥ አንተንም ማንም አያድንህም' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

የአሕዛብ አማልክት አዳኑአቸውን ... ተላሳር
x

Isaiah 37:14

ከመልእክተኞች እጅ
በዚህ ስፍራ ራሳቸው እንደሰጡት ለማጉላት መልአክተኞቹ በእጃቸው ተወክለዋል። አት፡- "መልእክተኞቹ ሰጡት' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

ወደ እግዚአብሔር ቤት ወጣ
የእግዚአብሔር ቤት በኢየሩሳሌም በከፍታ ስፍራ ላይ ስለነበረ፣ "ወደ ላይ' እንደሆነ ተነግሮአል።

በእግዚአብሔር ፊት ዘረጋው
ደብዳቤውን በእግዚአብሔር ፊት ዘረጋው። በእግዚአብሔር ቤት መገኘት እግዚአብሔር ባለበት ከመሆን ጋር አንድ እንደሆነ ይታሰብ ነበር። ደብዳቤው ጥቅልል ስለሆነ መተርተርና መዘርጋት ነበረበት።

በኪሩቤል ላይ የምትቀመጥ
ኪሩቤል በቃል ኪዳኑ ታቦት የስርየት መክደኛ ላይ የሚገኙ መሆናቸውን ግልጽ ማድረግ ይጠበቅብሃል። ብዙ ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች እግዚአብሔር በላይ በሰማይ ዙፋኑ ላይ እንደሚቀመጥ ሁሉ የቃል ኪዳኑ ታቦት እግዚአብሔር እግሩን የሚያሳርፍበት የእግሩ መረገጫ እንደሆነ አደርገው ይናገራሉ። አት፡- "በቃል ኪዳኑ ታቦት ከኪሩቤል በላይ በዙፋንህ ላይ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የምትቀመጥ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

አንተ ብቻህን አምላክ ነህ
"አንተ ብቻ አምላክ ነህ'

በመንግሥታት ሁሉ ላይ
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር በመንግሥታት ሁሉ ላይ ሥልጣን ያለው መሆንና መግዛት ማለት ነው። አት፦ "በመንግሥታት ሁሉ ላይ ሥልጣን አለህ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ሰማይንና ምድርን ፈጥረሃል
ይህ ሁሉን ነገር ፈጥሮአል ማለት ነው። አት፦ "ሁሉን ፈጥረሃል' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 37:17

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቅያስ ወደ እግዚአብሔር መጸለዩን ይቀጥላል።

የላከውን
ሕዝቅያስ ሰናክሬም የላከውን ደብዳቤ እያመለከተ ነው። ይህ ምን ማለት እንደሆነ ግልጽ መሆን አለበት። አት፦ "በላከው መልእክት' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ጆሮህን መልስ
ጆሮህን አዘንብል ወይም ራስህን መልስ። ይህ አንድን ነገር በተሻለ ሁኔታ ለመስማት ራስን መመለስ ማለት ነው።

ሰናክሬም
የዚህን ሰው ስም በኢሳይያስ 36:1 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

አሕዛብን ሁሉና አገሮቻቸውን
ይህ አጠቃላይነት ነው። ነገሥታቱ በቅርብ ያሉትን በዙ አገራትን አጥፍተዋል፣ ነገር ግን አገራትን ሁሉ ማለት አይደለም። አት፦ "ብዙ ሕዝቦችንና አገራቸውን' (ግነትና ማጠቃለያ ተመልከት)

Isaiah 37:19

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቅያስ ወደ እግዚአብሔር መጸለዩን ይቀጥላል።

የእንጨትና የድንጋይ የሰው እጅ ሥራ ነበሩ እንጂ አማልክት አልነበሩምና
ሰዎች እነዚህን ጣዖታት በገዛ እጆቻቸው ሠሯቸው ስለዚህም ከንቱ ናቸው የሚለውን ያጎላል። አት፦ "ሰዎች ከእንጨትና ከድንጋይ የሠሯቸው ሐሰተኛ አማልክት ስለሆኑ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

ከኃይሉ
"ከአሦር ንጉሥ ኃይል'

መንግሥታት ሁሉ
ይህ በመንግሥታት ውስጥ ያሉትን ሰዎች ያመለክታል። አት፦ "በመንግሥታት ውስጥ ያሉ ሕዝቦች ሁሉ' (ምትክ ስም ተመልከት)

አንተ ብቻ እግዚአብሔር ነህ
"አንተ ብቻ እግዚአብሔር አምላክ ነህ'

Isaiah 37:21

መልእክት ላከ
ይህ መልእክቱን ለንጉሡ ለመስጠት መልእክተኛ ላከ ማለት ነው። አት፦ "መልእክቱን ለመስጠት አንድ ሰው ላከ' (ምትክ ስም ተመልከት)

እግዚአብሔር የተናገረው ቃል ይህ ነው
"እግዚአብሔር ያለው'

በንቀት ስቃብሃለች
"ስቃብሃለች' ወይም "ተሳልቃብሃለች'

የጽዮን ድንግል ሴት ልጅ ... የኢየሩሳሌም ሴት ልጅ
እነዚህ ፈሊጣዊ ንግግር ናቸው። ሁለተም ሐረጎች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው። የከተማይቱ ሴት ልጅ ማለት በከተማይቱ የሚኖሩ ሰዎች ማለት ነው። ተመሣሣይ ሐረግ በኢሳይያስ 1:8 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። አት፦ "የጽዮን ሰዎች ... የኢየሩሳሌም ሰዎች' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

የተገዳደርኸው የሰድብኸውስ ማን ነው ... በእስራኤል ቅዱስ ላይ ነው
በአሦር ንጉሥ ላይ ለመሳለቅ እግዚአብሔር እነዚህን አሳብ ገላጭ ጥያቄዎቸች ይጠይቃል። ይህ በአረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። አት፦ "አንተ እግዚአብሔርን ተገዳደርሃል ተሳድበሃልም፤ በእስራኤልም ቅዱስ ላይ ጮኸኻል፣ በትዕቢትም አድርገሃል።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ድምህን ከፍ አድርገሃል
ይህ የሰው ድምጽ ወደ ላይ ከፍ የሚድረግ ቁስ ነገር እንደሆነ አድርጎ ጮኾ መናገረን ያመልከትል። አት፦ "ጮኸሀል' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ዓይኖችህን በትዕቢት ወደ ላይ አንስተሃል
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ከሆንከው በላይ ራስህን አስፈላጊ እንደሆነ በመቁጠር ወደ አንድ ነገር በትዕቢት መመልክት ማለት ነው። አት፦ "በትዕቢት መመልከት ወይም በትዕቢት ማድረግ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 37:24

አጠቃላይ መረጃ
ለአሦር ንጉሥ የሚተላለፈው የእግዚአብሔር መልእክት ይቀጥላል።

በባሪያዎችህ
ይህ መልእክት አስይዞ ወደ ሕዝቅያስ የላካቸውን አገልጋዮቹን ያመለክታል። ይህ በይበልጥ ግልጽ ሆኖ ሊቀመጥ ይችላል። አት፦ "በአገልጋዮችህ በላከው መልእክት' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ሄጃለሁ ... እቆርጣለሁ ... እገባለሁ ... ቆፈርሁ ... አደርቅሁ ... በእግሬ
በዚህ ስፍራ ሰናክሬም ብዙ ነገሮችን እንዳሸነፈ ስለራሱ ይናገራል። በእውነቱ ያሸነፋቸው በሚያዘው ሠራዊትና ሠረገሎች ነው። አት፦ "ሄደናል ... እንቆርጣለን ... እንገባለን ... ቆፈርን ... አደረቅን ... በእግራችን' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

ረጃጅሞቹን ዝግባዎቹን
"የሊባኖስን ረጃጅም ዝግባዎች'

እጅግ ፍሬያማ ወደ ሆነው ደኑ
በዚህ ስፍራ "ፍሬያማ' የሚለው ቃል ደኑ ጥቅጥቅ ያለና ጤነኛ ዛፎች የሞሉበት መሆኑን ያመለክታል። አት፦ "እጅግ ፍሬያማ ወደ ሆነው ደኑ ውስጥም' (መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉ ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የግብጽንም ወንዞች ሁሉ በእግሬ ጫማ አደረቅሁ
በዚህ ስፍራ ሰናክሬም በግብጽ ወንዞች በኩል ሠራዊቱን ሲመራ እንዳደረቃቸው በመናገር ድሉንና የግብጽ ወንዞችን በማቋረጥ ያደረገውን ጉዞ አጋኖ ያቀርባል። አት፡- "ከእግሬ በታች ደረቅ እንደሆኑ አድርጌ በግብጽ ወንዞች ሁሉ በኩል ሠራዊቴን መራሁ' (ግነትና ማጠቃለያ ተመልከት)

Isaiah 37:26

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለአሦር ንጉሥ የላከው መልእክት ይቀጥላል።

በጥነት ጊዜ ... አልሰማህምን
ሰናክሬም አስቀድሞ የሚያውቃቸውን መረጃዎች ሊያሳስበው እግዚአብሔር ይህን አሳብ ገላጭ ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ በአረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይቻላል። አት፡- "በእርግጥ በጥንት ጊዜ ... ሰምተሃል' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

የተመሸገቱን ከተሞች የፍርስራሽ ክምር እስኪሆኑ ድረስ እንድታፈርስ
የሰናክሬም ሠራዊት ያጠፏቸውን ከተሞች እንዲያጠፉ እግዚአብሔር አቅዶ ነበር። ይህ በይበልጥ ግልጽ ሆኖ ሊቀመጥ ይችላል። አት፡- "ሠራዊትህ ከተሞችን እንዲያጠፋና የፍርስራሽ ክምር እንዲያደርጋቸው አቅጄአለሁ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

የተመሸጉትን
ጠንካራና በጽኑ የሚጠበቁ

ጥቂት ጉልበት
ደካሞች

ተሰባበሩ
ትናንሽ ቁርጥራጮች ሆኖ መሰባበር። በእጅጉ ተስፋ ለመቁረጥ ጥቅም ላይ የሚውል ስዕላዊ ንግግር ነው። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

እንዲሆን አደረግሁ
እንዲሆን ማድረግ የሚለው ፈሊጣዊ ንግግር አንድ የተወሰነ ነገር እንዲፈጸም ማድረግ ማለት ነው። አት፡- "እንዲሆን አደረግሁት ወይም እነዚህ ነገሮች እንዲሆኑ አደረግሁ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

በምሥራቅ ነፋስ ፊት፣ በእርሻ ያለ ተክል፣ የለመለመ ቡቃያ፣ በእርሻ ወይም በሰገነት ላይ ያለ ሣር ናቸው
ይህ ከተሞቹን ከሣር ጋር በማስተያየት ከተሞቹ በአሦር ሠራዊት ፊት ምን ያህል ደካማና ለጉዳት የተጋለጡ እንደሆኑ ይናገራል። አት፡- "ከተሞቹ በሠራዊትህ ፊት በእርሻ እንዳለ ሣር ደካሞች ናቸው። በሰገነት ላይ እንደ በቀለና በምሥራቅ ሞቃት ነፋስ እንደተለበለበ ሣር ደካሞች ናቸው።' (ስዕለዊ ንግግር ተመልከት)

በምሥራቅ ነፋስ ፊት
የምሥራቅ ነፋስ ከምድረ በዳ የሚነፈስ ሞቃትና ደረቅ ነፋስ ሲሆን በነፈሰም ጊዜ ተክሎች ይሞታሉ።

Isaiah 37:28

አጠቃላይ መረጃ
ለአሦር ንጉሥ የተላከው የእግዚአብሔር መልእክት ይቀጥላል።

እኔ ግን መቀመጥህን፣ መውጣትህን፣ መግባትህን አውቃለሁ
ይህ የሕይወት እንቅስቃሴዎችን በሙሉ ያመለክታል። አት፡- "የምታደርገውን ሁሉ አውቃለሁ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በእኔ ላይ መቆጣትህን
"መቆጣት' የሚለው ቃል በማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እንዴት በእኔ ላይ ትቆጣለህ' (የነገር ስም ተመልከት)

ትዕቢትህ
በዚህ ስፍራ የንጉሡ ትዕቢት የንጉሡን የትዕቢት ንግግር ያመለክታል። አት፡- "የትዕቢት ንግግርህ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ትዕቢትህ ወደ ጆሮዬ ደርሶአል
ይህ የንጉሡ ንግግር ወደ ጆሮው ጉዞ እንዳደረገ አንድ ነገር እግዚአብሔር የንጉሡን ንግግር እንደሰማ ይናገራል። አት፡- "በትዕቢት ስትናገር ሰምቼአለሁ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ስናንዬን በአፍንጫህ፣ ልጓሜንም በከንፈርህ አደርጋለሁ
ሰው እንስሳትን ለመምራት ስናጋና ልጓም ይጠቀማል። ይህ እግዚአብሔር ንጉሡን እንደ እንሰሳ በስናጋና በልጓም እንደሚቆጣጠረው አድርጎ እግዚአብሔር ንጉሡን እንደሚቆጣጠረው ይናገራል። አት፡- "ሰው እንሰሳውን ስናጋን በአፍንጫው፣ ልጓምን በአፉ በማድረግ እንደሚቆጣጠረው እቆጣጠርሃለሁ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በመጣህበት መንገድ እመለስሃለሁ
ይህ ንጉሡ ወደ ገዛ ትውልድ አገሩ እንዲመለስ እንደሚደረግ ያመለክታል። ይህ ምን ማለት እንደሆነ በይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አት፡- "ወደ ገዛ አገርህ እንድትመለስ አስገድድሃለሁ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

Isaiah 37:30

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ወደ ሕዝቅያስ የላከው መልእክት ይቀጥላል። (ኢሳይያስ 37፡ 21 ተመልከት)

ለአንተ ምልክት
"ሕዝቅያስ፣ ለአንተ ምልክት' በዚህ ስፍራ "አንተ' ነጠላ ቁጥር ሲሆን ሕዝቅያስን ያመልክታል። (የ"አንተ' ልዩ ልዩ አጠቃቀሞች ተመልከት)

መትከል አለባችሁ ... ትበላላችሁ
በዚህ ስፍራ "አንተ' ብዙ ቁጥር ሲሆን የይሁዳን ሕዝብ ያመለክታል። (የአንተ ልዩ ልዩ አጠቃቀሞችን ተመልከት)

በሁለተኛው ዓመት የበቀለውን
ይህ ሕዝቡ የሚበላውን ያመለክታል። ትበላላችሁ የሚለው ቃል ከቀደመው ሐረግ ጋር ተያያዘ ሊታይ ይገባል። አት፡- "በሁለተኛው ዓመት የበቀለውን ትበላላችሁ ወይም በሚቀጥለው ዓመት የበቀለውን ትበላላችሁ' (መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉ እና የደረጃ ቁጥር ተመልከት)

ከገቦው የበቀለውን
"ከዚያ በወፍ ዘራሽ የበቀለውን' ወይም "በወፍ ዘራሽ የበቀለውን'

Isaiah 37:31

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለሕዝቅያስ የላከው መልእክት ይቀጥላል።

ቅሬታ
ቅሬታ የተቀረው ከሄደ በኋላ የተረፈው የአንድ ነገር ክፍል ነው። በዚህ ስፍራ በይሁዳ የቀሩትን ሰዎች ያመለክታል።

የይሁዳ ቤት
በዚህ ስፍራ "የይሁዳ ቤት' የሚለው ትውልዱን ያመለክታል። አት፡- "የይሁዳ ትውልድ' (ምትክ ስም ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንደገና ሥር ይሰድዳል ፍሬም ያፈራል
ይህ ሥር እንደሚሰድዱና ፍሬ እንደሚያፈሩ ተክሎች የይሁዳ ሰዎች ባለጸጎች እንደሚሆኑ ይናገራል። አት፡- "ሥር እንደሚሰድድና ፍሬ እንደሚያፈራ ተክል ባለጸጎች ይሆናሉ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ከኢየሩሳሌም ቅሬታ፣ ከጽዮንም ተራራ ያመለጡት ይመጣሉና
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሣሣይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን የዳኑትን የሕዝቡን ቅሬታዎች ለማጉላት በአንድነት ጥቅም ላይ የዋሉ ናቸው። (አጓዳኝነት ተመልከት)

የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር ቅንዓት ይህን ያደርጋል
ይህ እግዚአብሔር ከቅንዓቱ የተነሣ አንድ ነገር ማድረጉን ቅንዓቱ ራሱ በእውነቱ ያን ድርጊት እንደፈጸመ አድርጎ ይናገራል። አት፡- "ከቅንዓቱ የተነሣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ይህን ያደርጋል' ወይም "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ከቅንዓቱ የተነሣ ይህን ያደርጋል' (ምትክ ስም ተመልከት)

Isaiah 37:33

አይመጣም ... አይመጣም
በዚህ ስፍራ የአሦር ንጉሥ ራሱንና ሠራዊቱን ሁለቱንም ያመለክታል። አት፡- "ሠራዊቱ አይመጣም ... አይመጡም' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

በጋሻም
"በጋሻዎችም'

መክበቢያ ድልድል
ከተማን በተሻለ ለማጥቃት አንድን ሰራዊት የሚረዳ በአንድ ከተማ ቅጥር ትይዩ የሚገነባ ትልቅ የአፈር ድልድል

ይመጣል ... አይገባም
በዚህ ስፍራ የአሦር ንጉሥ ራሱንና ሠራዊቱን ሁለቱንም ያመለክታል። አት፡- "ይመጣሉ ... አይገቡም' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
ያወጅውን እርግጥኝነት ለመግለጽ እግዚአብሔር በስሙ ስለ ራሱ ይናገራል። እንደ ኢሳይያስ 30፡1 ተርጉም። አት፡- "እግዚአብሔር ያወጀው ይህ ነው' ወይም "ይህ እኔ፣ እግዚአብሔር ያወጅኩት ነው' (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሦሥተኛ መደብ ተመልከት)

Isaiah 37:35

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል። ስለ እኔም ስለ ባሪያዬም ስለ ዳዊት ለእኔና ለባሪያዬ ለዳዊት ነገሮች የተሻሉ ይሆኑ ዘንድ

Isaiah 37:36

እንዲሞቱ አደረገ
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር መግደል ማለት ነው። አት፡- "ገድያ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

185000 ወታደሮች
"አንድ መቶ ሰማንያ አምስት ሺህ ወታደሮች' (ቁጥሮች ተመልከት)

የአሦር ንጉሥ ሰናክሬም እስራኤልን ለቀቀ ወደ ቤትም ሄደ በነነዌም ተቀመጠ
በዚህ ስፍራ ሰናክሬም ራሱንና ሠራዊቱን ሁለቱንም ያመለክታል። ሁሉም እስራኤልን ለቀቁ ወደ አሦር ወደ ቤት ተመለሱ። ሰናክሬም ወደ ነነዌ ከተማ ተመለሰ። አት፡- "ሰናክሬምና ሠረዊቱ እስራኤልን ለቀቁ ወደ ቤትም ሄዱ፤ ሰናክሬምም በነነዌ ቆየ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

ሰናክሬም
የዚህን ሰው ስም በኢሳያያስ 36፡1 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

Isaiah 37:38

እየሰገደ እያለ
"ሰናክሬም እየሰገደ እያለ'

ናሳራክ
ይህ የሐሰተኛ አምላክ ስም ነው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

አድራሜሌክ ... ሳራሳር ... አሰስራዶን
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 38

1 በዚያም ወራት ሕዝቅያስ ለሞት እስኪደርስ ድረስ ታመመ። ስለዚህ፣ ነቢዩ የአሞጽ ልጅ ኢሳይያስ ወደ እርሱ መጥቶ፣ "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ 'ትሞታለህ እንጂ በሕይወት አትኖርምና ቤትህን አስተካክል' አለው። **2** ከዚያም፣ ሕዝቅያስም ፊቱን ወደ ግድግዳው መልሶ እንዲህ ሲል ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፣ **3** "አቤቱ፣ በፊትህ በእውነትና በፍጹም ልብ እንደ ሄድሁ ደስ የሚያሰኝህንም እንዳደረግሁ ታስብ ዘንድ እለምንሃለሁ።" ሕዝቅያስም እየጮኸ አለቀሰ። **4** ከዚያም የእግዚአብሔርም ቃል ወደ ኢሳይያስ እንዲህ ሲል መጣ፣ **5** "ሂድ፣ ሕዝቅያስን እንዲህ በለው፣ 'የአባትህ የዳዊት አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ጸሎትህን ሰምቻለሁ፣ እንባህንም አይቻለሁ። ተመልከት፣ በዕድሜህ ላይ ዐሥራ አምስት ዓመት አጨምራለሁ። **6** አንተንና ይህችንም ከተማ ከአሦር ንጉሥ እጅ እታደጋለሁ፣ ይህችንም ከተማ እጋርዳታለሁ። **7** እግዚአብሔርም የተገረውን ነገር እንዲፈጽመው ከእግዚአብሔር ዘንድ ምልክቱ ይህ ይሆንልሃል፦ **8** ተመልከት፣ በአካዝ የጥላ ስፍረ-ሰዓት ላይ ከፀሐይ ጋር የወረደውን በደረጃዎች ያለውን ጥላ ዐሥር ደረጃ ወደ ኋላ እንዲመለስ አደርጋለሁ።" ስለዚህ ፀሐይም በጥላ ስፍረ-ሰዓት ላይ የወረደበት ዐሥር ደረጃ ወደ ኋላ ተመለሰ። **9** የይሁዳ ንጉሥ ሕዝቅያስ ታምሞ ከደዌው በተፈወሰ ጊዜ የጻፈው ጽሕፈት ይህ ነው፦ **10** "እኔ፣ በሕይወት ዘመኔ መካከል ወደ ሲኦል በሮች እገባለሁ፤ የቀረው ዘመኔ ጐደለብኝ አልሁ። **11** ደግሞም፣ በሕያዋን ምድር እግዚአብሔርን አላይም፤ በዓለምም ከሚኖሩ ጋር ሰውን እንግዲህ አልመለከትም አልሁ። **12** ማደሪያዬ ተነቀለች፣ እንደ እረኛ ድንኳንም ከእኔ ዘንድ ተወገደች፤ ሕይወቴንም እንደ ሸማኔ ጠቀለልሁ፤ እርሱም ከመጠቅለያው ይቈርጠኛል፤ ከማለዳም ጀምሮ እስከ ማታ ድረስ ታጠፋኛለህ። **13** እስኪነጋ ድረስ ቈይቼ ነበር፤ እርሱ እንደ አንበሳ አጥንቴን ሁሉ ሰበረ፤ ከማለዳ ጀምሮ እስከ ማታ ድረስ ታጠፋኛለህ። **14** እንደ ጨረባና እንደ ሸመላ ተንጫጫሁ፣ እንደ ርግብም አጒረመረምሁ፤ ዓይኖቼ ወደ ላይ ከማየት ደከሙ። ጌታ ሆይ፣ ተጨንቄአለሁና መከታ ሁነኝ። **15** ምን እላለሁ? እርሱ ተናግሮኛል፣ እርሱ ራሱም ይህን አድርጎአል፤ በዘመኔ ሁሉ ስለ ነፍሴ ምሬት ቀስ ብዬ እሄዳለሁ። **16** ጌታ ሆይ፣ የላክኸው መከራ ለእኔ መልካም ነው፤ ሕይወቴ ተመልሶ ይሰጠኝ፤ አንተም ፈወስኸኝ ወደ ሕይወትም መለስኸኝ። **17** ታላቅ ምሬት ለጥቅሜ ሆነ። አንተም ነፍሴን ከጥፋት ጕድጓድ አዳንሃት፤ ኃጢአቴንም ሁሉ ወደ ኋላህ ጥለሃልና። **18** ሲኦል አያመሰግንህምና፤ ሞትም አያከብርህምና፤ ወደ ጕድጓዱ የሚወርዱ እውነትህን ተስፋ አያደርጉም። **19** እኔ ዛሬ አንደማደርግ ሕያዋን እነርሱ ያመሰግኑሃል፤ አባት ለልጆች እውነትህን ያስታውቃል። **20** እግዚአብሔር ያድነኛል፣ ስለዚህ በዕድሜያችን ዘመን ሁሉ በእግዚአብሔር ቤት ቅኔዎችን አውታር ባለው ዕቃ እንዘምራለን።" **21** አሁን ኢሳይያስም፣ "የበለስ ጥፍጥፍ አምጥተው በእባጩ ላይ ይለብጡት፣ እርሱም ይፈወሳል" ብሎ ነበር። **22** ሕዝቅያስም፣ "ወደ እግዚአብሔር ቤት እወጣ ዘንድ ምልክቱ ምንድር ነው?" ብሎ ነበር።

Isaiah 38:1

ቤትህን አስተካክል
ይህ አንተ ከሞትክ በኋላ ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንዲያውቁ ቤተ ሰብህንና በጉዳዮችህ ላይ ኃላፊነት የተሰጣቸውን ሰዎች አዘጋጅ ማለት ነው። ይህ በይበልጥ ግልጽ ሆኖ ሊጻፍ ይችላል። አት፦ "ከሞትህ በኋላ እንዲያደርጉት የምትፈልገውን ነገር በቤተ መንግሥትህ ላሉ ሰዎች መንገር አለብህ።' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

አስብ
ፈሊጣዊ ንግግሩ ማስታወስ ማለት ነው። አት፦ "አስታውስ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

በታማኝነት በፊትህ እንደ ሄድሁ
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። በዚህ ስፍራ መሄድ ማለት መኖር ማለት ነው። ሐረጉ እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ መንገድ መኖር ማለት ነው። አት፦ "በፊትህ በታማኝነት ኖሬአለሁ' ወይም "በታማኝነት አገልግዬሃለሁ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

በፍጽም ልቤ
በዚህ ስፍራ ልብ የአንድን ሰው ፈጽሞ መሰጠትን የሚወክለውን የውስጥ ማንነትን ያመለክታል። አት፦ "በውስጥ ማንነቴ ሁሉ' ወይም "ፍጹም በሆነ መሰጠቴ' (ምትክ ስም ተመልከት)

በዓይንህ ፊት መልካም የሆነውን
የእግዚአብሔር እይታ የእግዚአብሔርን ፍርድ ወይም ምዘና ይወክላል። አት፦ "ደስ የሚያሰኝህን' ወይም "አንተ መልካም ነው ያልከውን' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 38:4

የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ የተናገረውን ነገር ለማስተዋወቅ ጥቅም ላይ የሚውል ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፦ "እግዚአብሔር ይህን መልእክት ተናገረ' ወይም "እግዚአብሔር እነዚህን ቃላት ተናገረ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ተመልከት
ይህ አድማጩን በመቀጠል ለሚነገረው ነገር ትኩረት እንዲሰጥ ለመጠየቅ ጥቅም ላይ የዋለ ነው። አት፦ "ስማ'

አስራ አምስት ዓመት
"15 ዓመት' (ቀጥሮች ተመልከት)

የአሦር ንጉሥ እጅ
በዚህ ስፍራ የንጉሥ "እጅ' የሚለው ኃይሉን ያመለክታል። አት፦ "የአሦር ንጉሥ ኃይል' (ምትክ ስም ተመልከት)

Isaiah 38:7

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለሕዝቅያስ መናገሩን ይቀጥላል።

ተመልከት
እግዚአብሔር በመቀጠል ወደ ሚነገረው ነገር የአድማጩን ትኩረት ለመሳብ ይህንን ቃል ይጠቀማል። "ስማ'

የአካዝ ደረጃዎች
እነዚህ ደረጃዎች በዚህ መንገድ የተጠቀሱት አካዝ ንጉሥ በነበረ ጊዜ ስለተገነቡ ነው። ይህን መረጃ በይበልጥ ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

Isaiah 38:9

በሕይወት ዘመኔ መካከል
"ከማርጀቴ አስቀድሞ።' ይህ ከማርጀት በፊት በመካከለኛ እድሜ ላይ መሞትን ያመለክታል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በሲኦል በሮች እገባለሁ
ይህ ሲኦል መንግሥት እንደሆነና አንድ ሰው የሚገባባበት በሮች እንዳሉት አድርጎ ስለመሞት ይናገራል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ለቀረው ዘመኔ ወደዚያ እላካለሁ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ዘመኔን ሁሉ ከመኖሬ በፊት ወደ መቃብር እሄዳለሁ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

በሕያዋን ምድር
ሕያዋን የሚለው አሁን በሕይውት ያሉትን ሰዎች ያመለክታል። አት፡- "ሰዎች በሕይወት በሚኖሩበት ምድር' ወይም "ሰዎች በሕይወት በሚኖሩበት በዚህ ዓለም' (ስማዊ ቅጽ ተመልከት)

Isaiah 38:12

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቅያስ የተጻፈ ጸሎቱን ይቀጥላል።

ሕይወቴ እንደ እረኛ ድንኳን ከእኔ ተወገደች ተወሰደችም
ይህ እረኛ ድንኳኑን ከመሬት ከሚያስወግድበት መንገድ ጋር በማስተያየት እግዚአብሔር የሕዝቅያስን ሕይወት በፍጥነት እንደሚፈጽመው ይናገራል። አት፡- "እረኛ ድንኳኑን እንደሚሸክፍና ተሸክሞ እንደሚሄድ እግዚአብሔር ሕይወቴን ከእኔ ፈጥኖ ይወስዳታል።' (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

ሕይወቴ ተወገደች
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር ሕይወቴን ወሰዳት' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ሕይወቴን እንደ ሸማኔ ጠቀለልሁ፣ አንተ ከመጠቅለያው ትቆርጠኛለህ
ይህ ሸማኔ ልብሱን ከመጠቅለያው ከሚቆርጥበትና ከሚጠቀልልበት መንገድ ጋር በማስተያየት እግዚአብሔር የሕዝቅያስን ሕይወት በፍጥነት እንደሚፈጽመው ይናገራል። አት፡- "ሲጨረስ ሸማኔ ልብሱን ከመጠቅለያው እንደሚቆርጥ፣ ሕይወቴን በፍጥነት ትፈጽማታለህ' (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

ትቆርጠኛለህ
በዚህ ውስጥ "አንተ' የሚለው ነጠላ ቁጥር ነው እግዚአብሔርንም ያመልክታል። (የ "አንተ' ልዩ ልዩ አጠቃቀሞች ተመልከት)

መጠቅለያ
ልብስ ለመሥራት ክሮችን ለማጠላለፍ የሚያገለግል መሣሪያ ነው።

እንደ አንበሳ አጥንቶቼን ሁሉ ሰበረ
በአንበሶች ከተበጫጨቀ ሰውነት ጋር እያስተያየ ሕዝቅያስ በከፍተኛ ስቃይ ውስጥ መሆኑን ይናገራል። አት፡- "ስቃዬ በአንበሶች እንደተበጫጨቅሁ ዓይነት ነበር' (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 38:14

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቅያስ የተጻፈ ጸሎቱን ይቀጥላል።

እንደ ጨረባ ተንጫጫሁ፣ እንደ ርግብም አጉተመተምኩ
ሁለቱም ሐረጎች ተመሣሣይ ነገር ይናገራሉ፣ የሕዝቅያስ ጩኸቶች ምን ያህል አሳዛኝ አንደሆነም ያጎላሉ። ጨረባና ርግብ የወፍ ዓይነት ናቸው። አት፡- "ጩኸቶቼ አሳዛኝ ናቸው–የጨረባ ጫጫታና የርግብ ማጉተምተም ዓይነት ድምጽ ያሰማሉ' (አጓዳኝነትና ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

ዓይኖቼ
በዚህ ስፍራ ወደ አንድ ነገር መመልከቱን ለማጉላት "ዓይኖቼ' በማለት ወደ ራሱ ያመለክታል። አት፡- "እኔ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

ወደ ላይ ከማየት
ይህ እግዚአብሔር እንዲረዳው ሕዝቅያስ ወደ ሰማይ መመልከቱን ያመለክታል። የዚህ አሳብ ሙሉ ትርጉም በይበልጥ ግልጽ መሆን ይችላል። አት፡- "ከሰማይ የሚመጣ እርዳታ እጠብቃለሁ' ወይም "እንድትረዳኝ እጠብቅሃለሁ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ)

ተጨንቄአለሁ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "በሽታዬ አስጨንቆኛል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ምን እላለሁ?
ሕዝቅያስ ምንም የሚለው እንዳልቀረው ለማጉላት ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ በአረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። አት፡- "የምናገረው የቀረኝ ምንም ነገር የለኝም' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ቀስ ብዬ ሄዳለሁ
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። በዚህ ስፍራ እሄዳለሁ የሚለው አኗኗሩን ያመለክታል። አት፡- "በትህትና እኖራለሁ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ምክንያቱም በሐዘን ተሸንፌአለሁና
"ምክንያቱም ሐዘንን ጠግቤአለሁና' ወይም "ምክንያቱም በጣም አዝኜአለሁና'

Isaiah 38:16

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቅያስ የተጻፈ ጸሎቱን ይቀጥላል።

ሕይወቴ ተመልሶ ይሰጠኝ እንደሆነ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ሕይወቴን መልስህ ትሰጠኝ እንደሆነ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ከጥፋት ጉድጓድ
ሕዝቅያስ አልሞተም ነገር ግን እያጣጣረ ነበር። ይህ እግዚአብሔር ከጣር እንዳዳነው ያመልክታል። የዚህ አሳብ ሙሉ ትርጉም በይበልጥ ግልጽ መሆን ይችላል። አት፡- "ከጣርና ወደ ጥፋት ጉድጓድ ከመውረድ' ወይም "ስለዚህ አልሞትኩም' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልሆነ መረጃ)

ኃጢአቴንም ሁሉ ወደ ኋላህ ጥለሃልና
ሕዝቅያስ፣ እግዚአብሔር ኃጢአቱን ይቅር ማለቱን እግዚአብሔር ወደ ኋላው እንደወረወረውና እንደረሳው ቁስ ነገር አድርጎ ይናገራል። አት፡- "ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር ብለሃልና ከእንግዲህም ወዲያ አታስበውምና' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 38:18

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቅያስ የተጻፈ ጸሎቱን ይቀጥላል።

ሲኦል አያመሰግንህምና፣ ሞትም አያከብርህምና
በዚህ ስፍራ "ሲኦል' እና "ሞት' የሚሉት የሞቱ ሰዎችን ያመለክታሉ። አት፡- "በሲኦል ያሉ አያመሰግኑህምና፣ የሞቱ ሰዎችም አያከበሩህም' (ምትክ ስም ተመልከት)

ወደ ጉድጓድ የሚወርዱ
"ወደ መቃብር የሚወርዱ'

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በተዓማኒነትህ ተስፋ አያደርጉም
"በታማኝነትህ ተስፋ አይኖራቸውም::' በዚህ ውስጥ "አንተ' የሚለው ነጠላ ቁጥር ሲሆን እግዚአብሔርን ያመለክታል:: (የ "አንተ' ልዩ ልዩ አጠቃቀሞች ተመልከት)

ሕያው ሰው ... ሕያው ሰው
የሞተ ሰው ሳይሆን ሕያው ሰው ብቻ፣ ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረብ ይችላል የሚለውን ለማጉላት ሕዝቅያስ ይህን ሐረግ ይደግማል:: (አጓዳኝነት ተመልከት)

Isaiah 38:20

አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቅያስ የተጻፈ ጸሎቱን ይቀጥላል::

ያድነኛል
ይህ ከሞት ጣር መዳኑን ያመለክታል:: በይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት:- "ከሞት ጣር ያድነኛል' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ)

እናከብራለን
በዚህ ውስጥ እኛ የሚለው ሕዝቅያስንና የይሁዳን ሕዝብ ያመለክታል:: (አካታች "እኛ' ተመልከት)

Isaiah 38:21

አሁን
ይህ ቃል በዋናው ታሪክ አቅጣጫ ውስጥ መቋረጥን ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል:: ይህ ስለ ሕዝቅያስና ኢሳይያስ ታሪካዊ ዳራ መረጃ ይሰጣል (ታሪካዊ ዳራ መረጃ ተመልከት)

ይለብጡት
የሕዝቅያስ ባሮች ይለብጡት

የበለስ ጥፍጥፍ
ይህ ለቅባትነት ጥቅም ላይ ይውል ነበር:: ይህ ምን ማለት እንደሆነ በይበልጥ ግልጽ መሆን ይችላል:: አት:- "የተፈጨ የበለስ ቅባት ተጠቀሙ' (እንደሚታወቅ ታሳበ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልሆነ መረጃ ተመልከት)

እባጭ
ያመረቀዘ ቆዳ ላይ የሚገኝ ሕመም የሚሰማበት አካባቢ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 39

1 በዚያ ጊዜ የባቢሎን ንጉሥ የባልዳን ልጅ መሮዳክ ባልዳን፣ ሕዝቅያስ ታምሞ እንደ ተፈወሰ ሰምቶ ነበርና ደብዳቤና እጅ መንሻ ላከለት። **2** ሕዝቅያስም በእነዚህ ነገሮች ደስ አለው፣ ግምጃ ቤቱንም፣ ብሩንና ወርቁንም፣ ቅመሙንና የከበረውንም ዘይት፣ መሣርያም ያለበትን ቤት ሁሉ፣ በቤተ መዛግብቱም የተገኘውን ሁሉ አሳያቸው፤ በቤቱና በግዛቱ ሁሉ ካለው ሕዝቅያስ ያላሳያቸው የለም። **3** ከዚያም ነቢዩ ኢሳይያስ ወደ ንጉሡ ወደ ሕዝቅያስ መጥቶ፣ "እነዚህ ሰዎች ምን አሉህ? ከወዴትስ መጡ?" አለው። ሕዝቅያስም፣ "ከሩቅ አገር ከባቢሎን መጡልኝ" አለው። **4** እርሱም፣ "በቤትህ ያዩት ምንድር ነው?" አለው። ሕዝቅያስም፣ "በቤቴ ያለውን ሁሉ አይተዋል፤ በቤተ መዛግብቴ ካለው ያላሳየኋቸው የለም" አለው። **5** ኢሳይያስም ሕዝቅያስን፣ "የሠራዊትን ጌታ የእግዚአብሔርን ቃል ስማ። **6** 'ተመልከት፣ በቤትህ ያለው ሁሉ፣ አባቶችህም እስከ ዛሬ ድረስ ያከማቹት ሁሉ፣ ወደ ባቢሎን የሚፈልስበት ወራት ይመጣል። ምንም አይቀርም፥ ይላል እግዚአብሔር። **7** ከአንተም ከሚወለዱት ልጆችህ ማርከው ይወስዳሉ፤ በባቢሎንም ንጉሥ ቤት ውስጥ ጃንደረቦች ይሆናሉ" አለው። **8** ሕዝቅያስም ኢሳይያስን፣ "የተናገርኸው የእግዚአብሔር ቃል መልካም ነው" አለው። ደግሞም፣ "በዘመኔ ሰላምና እውነት ይሁን" አለ።

Isaiah 39:1

ማርዱክ—በልዳን ... በልዳን
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

ሕዝቅያስም በእነዚህ ነገሮች ደስ ተሰኘ
ይህ በይበልጥ ግልጽ መሆን ይችላል። አት፡- "የንጉሡ መልእክተኞች በደረሱ ጊዜ፣ ሕዝቅያስ ባመጡት ነገር ደስ ተሰኘ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የሚደረግ እውቀትና ግልጽ ያልሆነ መረጃ ተመልከት)

የከበሩ ነገሮች ግምጃ ቤቱን ለመልእክተኞቹ አሳያቸው
"ያሉትን ውድ ነገሮች ሁሉ ለመልእክተኞቹ አሳያቸው'

ግምጃ ቤት
ነገሮች የሚጠበቁበት ሕንፃ

በግምጃ ቤቱ የተገኘውን ሁሉ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "በግምጃ ቤቱ የነበረውን ነገር ሁሉ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

በቤቱና በግዛቱ ሁሉ ካለው ሕዝቅያስ ያላሳያቸው ምንም የለም
ሁሉን ነገር አላሳየም፣ ነገር ግን ሕዝቅያስ ብዙ ነገር ለማሳየቱ ትንሽ ግነት ነው። ደግሞም ይህ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ሕዝቅያስ በቤቱና በቤተ መንግሥቱ የሚገኙትን ነገሮች ሁሉንም ማለት በሚቻል ደረጃ አሳያቸው' (ድርብ አሉታዊና ግነትና ማጠቃለያ ተመልከት)

Isaiah 39:3

በቤቴ ያለውን ሁሉ አይተዋል። ከከበሩት ነገሮቼ ያላሳየኋቸው ምንም የለም
እነዚህ ሁለት ዐረፍት ነገሮች የሚናገሩት አንድ ነገር ሲሆን ሕዝቅያስ ለሰዎቹ ምን ያህል እንዳሳያቸው ለማጉላት ተያይዘው ጥቅም ላይ ውለዋል። (አጓዳኝነት ተመልከት)

በቤቴ ያለውን ሁሉ
ሕዝቅያስ ብዙ ነገር አሳይቶአቸዋል፣ ነገር ግን ይህ ማለት በግድ በቤተ መንግሥቱ ያለውን ሁሉ ማለት ባለመሆኑ የጅምላ ንግግር ነው። (ግነትና ማጠቃለያ ተመልከት)

ከከበሩት ነገሮቼ ያላሳየኋቸው ምንም የለም
ይህ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "በቤተ መንግሥቴ የሚገኙትን ውድ ነገሮች ሁሉ አሳየኋቸው' (ድርብ አሉታዊ ተመልከት)

Isaiah 39:5

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር
ይህን ሐረግ በኢሳይያስ 1:9 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ቃል
"መልእክት'

ተመልከት
በመቀጠል ወደ ሚነገረው ነገር የሕዝቅያስን ትኩረት ለመሳብ ይህ ቃል በዚህ ስፍራ ጥቅም ላይ ውሏል። "ስማ'

በቤተ መንግሥትህ የሚገኝ ነገር ሁሉ ... ወደ ባቢሎን በሚጋዝበት ጊዜ
ይህ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- የጠላት ሠራዊት በቤተ መንግሥትህ የሚገኘውን ነገር ሁሉ ... ወደ ባቢሎን በወሰደ ጊዜ (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

Isaiah 39:7

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ የእግዚአብሔርን መልእክት ለሕዝቅያስ መናገሩን ይቀጥላል።

ከአንተ የሚወለዱ ልጆች
"ልጆችህ

ይወስዷቸዋል
"ባቢሎናውያን ይወስዷቸዋል'

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 40

1 "አጽናኑ፣ ሕዝቤን አጽናኑ" ይላል አምላካችሁ። **2** ለኢየሩሳሌም ልብ ተናገሩ የተቀጠረችበት ወራት እንደ ተፈጸመ፣ ኃጢአትዋም እንደ ተሰረየ፣ ከእግዚአብሔርም እጅ ስለ ኃጢአትዋ ሁሉ ሁለት እጥፍ እንደ ተቀበለች ወደ እርስዋ ጩኹ። **3** የሚጮኽ የአዋጅ ነጋሪ ቃል፣ "የእግዚአብሔርን መንገድ በምድረ በዳ አዘጋጁ፤ ለአምላካችንም ጐዳና በበረሀ አስተካክሉ።" **4** ሸለቆው ሁሉ ከፍ ይላል፣ ተራራውና ኮረብታውም ሁሉ ዝቅ ይላል፤ ጠማማውም ይቃናል፣ ስርጓጕጡም ሜዳ ይሆናል፤ **5** የእግዚአብሔርም ክብር ይገለጣል፣ ሥጋ ለባሹም ሁሉ በአንድነት ያየዋል፣ የእግዚአብሔር አፍ ይህን ተናግሮአልና። **6** አንድ ድምጽ፣ "ጩኽ" ይላል፣ "ምን ብዬ ልጩኽ?" አልሁ። "ሥጋ ለባሽ ሁሉ ሣር ነው፣ ክብሩም ሁሉ እንደ ምድረ በዳ አበባ ነው። **7** የእግዚአብሔር እስትንፋስ ይነፍስበታልና ሣሩ ይደርቃል አበባውም ይረግፋል፤ በእውነት ሕዝቡ ሣር ነው። **8** ሣሩ ይደርቃል፣ አበባውም ይረግፋል፣ የአምላካችን ቃል ግን ለዘላለም ጸንታ ትኖራለች።" **9** የምስራች የምትነግሪ ጽዮን ሆይ፣ ከፍ ወዳለው ተራራ ውጪ፣ የምስራች የምትነግሪ ኢየሩሳሌም ሆይ፣ ድምፅሽን በኃይል አንሺ፣ አንሺ፣ አትፍሪ፤ ለይሁዳም ከተሞች፣ "እነሆ፣ አምላካችሁ!" ብለሽ ንገሪ። **10** ተመልከቱ፣ ጌታ እግዚአብሔር እንደ ኃያል ይመጣል። ክንዱም ስለ እርሱ ይገዛል፤ እነሆ፣ ዋጋው ከእርሱ ጋር ደመወዙም በፊቱ ነው። **11** መንጋውን እንደ እረኛ ያሰማራል፣ ጠቦቶቹን በክንዱ ሰብስቦ በብብቱ ይሸከማል፣ የሚያጠቡትንም በቀስታ ይመራል። **12** ውኖችን በእፍኙ የሰፈረ፣ ሰማይንም በስንዝር የለካ፣ የምድርንም አፈር በመስፈሪያ ሰብስቦ የያዘ፣ ተራሮችን በሚዛን ኮረብቶችንም በሚዛኖች የመዘነ ማን ነው? **13** የእግዚአብሔርን መንፈስ ያዘዘ፣ ወይስ አማካሪ ሆኖ ያስተማረው ማን ነው? **14** ወይስ ከማን ጋር ተመካከረ? ወይስ ማን መከረው? የፍርድንም መንገድ ማን አስተማረው? እውቀትንስ ማን አስተማረው? የማስተዋልንስ መንገድ ማን አሳየው? **15** ተመልከቱ፣ አሕዛብ በገንቦ እንዳለች ጠብታ ናቸው፣ በሚዛንም እንዳለ ትንሽ ትቢያ ተቈጥረዋል፤ ተመልከቱ፣ ደሴቶችን እንደ ቀላል ነገር ያነሣል። **16** ሊባኖስ ለማንደጃ፣ እንስሶችዋም ለሚቃጠል መሥዋዕት አይበቁም። **17** አሕዛብ ሁሉ በፊቱ እንዳልነበሩ ናቸው፤ ከምናምን እንደሚያንሱ፣ እንደ ከንቱ ነገርም ይቈጥራቸዋል። **18** እንግዲህ እግዚአብሔርን በማን ትመስሉታላችሁ? ወይስ በምን ምሳሌ ታስተያዩታላችሁ? **19** የተቀረጸውንስ ምስል! ሠራተኛ ሠርቶታል፤ አንጥረኛም በወርቅ ለብጦታል፣ የብሩንም ሰንሠለት አፍስሶለታል። **20** ለዚህ መባዕ ገንዘቡ ያልበቃው ድሀ የማይነቅዘውን እንጨት ይመርጣል፤ ምስሉም እንዳይናወጥ ያቆመው ዘንድ ብልህ ሠራተኛን ይፈልጋል። **21** አላወቃችሁምን? ወይስ አልሰማችሁምን? ከጥንትስ አልተወራላችሁምን? ወይስ ምድር ከተመሠረተች ጀምሮ አላስተዋላችሁምን? **22** እርሱ በምድር ክበብ ላይ ይቀምጣል፣ በእርስዋም የሚኖሩት እንደ አንበጣ ናቸው፤ ሰማያትን እንደ መጋረጃ የሚዘረጋቸው እንደ ድንኳንም ለመኖርያ የሚዘረጋቸው፥ **23** አለቆችንም እንዳልነበሩ፣ የምድርንም ፈራጆች እንደ ከንቱ ነገር የሚያሳንሳቸው እርሱ ነው። **24** ተመልከቱ፣ ገና እንደ ተተከሉና እንደ ተዘሩ፣ በምድርም ሥር ገና እንደ ሰደዱ ወዲያውኑ ነፈሰባቸው፣ እነርሱም ደረቁ፣ ዐውሎ ነፋስም እንደ እብቅ ጠረጋቸው። **25** "እንግዲህ እተካከለው ዘንድ በማን መሰላችሁኝ?" ይላል ቅዱሱ። **26** ዓይናችሁን ወደ ላይ አንሥታችሁ ተመልከቱ፤ እነዚህን የፈጠረ ማን ነው? ሠራዊታቸውን በቍጥር የሚያወጣ እርሱ ነው፣ ሁሉንም በየስማቸው ይጠራቸዋል፤ በኃይሉ ብዛትና በችሎቱ ብርታት አንድስ እንኳ አይታጣውም። **27** ያዕቆብ ሆይ፣ እስራኤልም ሆይ፣ "መንገዴ ከእግዚአብሔር ተሰውራለች፣ ፍርዴም ከአምላኬ አልፋለች" ለምን ትላለህ? ለምንስ እንዲህ ትናገራለህ? **28** አላወቅህምን? አልሰማህምን? እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ፣ የምድርም ዳርቻ ፈጣሪ ነው፤ አይደክምም፣ አይታክትም፣ ማስተዋሉም ወሰን የለውም። **29** ለደካማ ኃይልን ይሰጣል፤ ጕልበት ለሌለውም ብርታትን ይጨምራል። **30** ብላቴኖች ይደክማሉ፣ ይታክቱማል፣ ጐበዛዝቱም ፈጽሞ ይወድቃሉ፤ **31** እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ፤ እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ፤ ይሮጣሉ፣ አይታክቱም፤ ይሄዳሉ፣ አይደክሙም።

Isaiah 40:1

አጽናኑ፣ አጽናኑ
አጽናኑ የሚለው ቃል አጽንዖት ለመስጠት ተደግሞአል።

ይላል አምላካችሁ
በዚህ ውስጥ "አናንተ' የሚለው የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንዲያጽናኑ ነቢዩ የሚነግራቸውን ሰዎች ያመለክታል። (የ "አንተ' ልዩ ልዩ አጠቃቀሞች ተመልከት)

ለኢየሩሳሌም በፍቅር ልብ ተናገሩ
ነቢዩ ስለ ኢየሩሳሌም እግዚአብሔር ይቅር እንዳላት ሴት አድርጎ ይናገራል። ኢየሩሳሌምም በከተማይቱ ውስጥ የሚኖሩትን ሰዎች ትወክላለች። አት፡- "ለኢየሩሳሌም ሕዝብ በፍቅር ልብ ተናገሩ' (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየትና ምትክ ስም ተመልከት)

አውጁለት ... ጦርነትዋ ... ኃጢአትዋ ... ተቀብላለች ... ኃጢአትዋ
በዚህ ውስጥ የሚገኘው ተውላጠ ስም ኢየሩሳሌምን ያመልክታል፣ ነገር ግን "የኢየሩሳሌም ሕዝብ' እንደ አማራጭ ትርጉም ከተወሰደ ሊቀየር ይችላል። አት፡- "አውጁለቸው ... ጦርነታቸው ... ኃጢአታቸው ... ተቀብለዋል ... ኃጢአታቸው' (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሦሥተኛ መደብ ተመልከት)

ጦርነትዋ
"ጦርነት' የሚለው ቃል ሊያመለክታቸው የሚችሉ ትርጉሞች 1) ወታደራዊ ውጊያ ወይም 2) የግዳጅ የጉልበት ሥራ።

ኃጢአትዋ ተሰረየ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር ኃጢአትዋን ይቅር አለት' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ከእግዚአብሔር እጅ
በዚህ ስፍራ "እጅ' የሚለው እግዚአብሔርን ራሱን ይወክላል። አት፡- "ከእግዚአብሔር' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

Isaiah 40:3

የሚጮኽ ድምጽ
ድምጽ የሚለው "ቃል' የሚጮኸውን ሰው ይወክላል። አት፡- "የሚጮኽ ሰው' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

የእግዚአብሔርን መንገድ በምድረ በዳ ጥረጉ፣ለአምላካችንም ጎዳና በበረሃ አስተካክሉ
እነዚህ ሁለት መስመሮች ተጓዳኝ ሲሆኑ በመሠረቱ የሚናገሩትም አንድ ዓይነት ነገር ነው። ለእግዚአብሔር እርዳታ የሕዝቡ ራሱን ማዘጋጀት እንዲሄድበት ለእግዚአብሔር መንገድ ማዘጋጀት እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮአል። (አጓዳኝነትና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በረሃ
ይህንን ቃል በኢሳይያስ 35፡1 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ሸለቆው ሁሉ ከፍ ይላል፣ ተራራውና ኮረብታውም ሁሉ ዝቅ ይላል
እነዚህ ሐረጎች ሕዝቡ እንዴት ለእግዚአብሔር ጎዳና ማዘጋጀት እንዳለባቸው ያብራራሉ። በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጹ ይችላል። አት፡- "ሸለቆውን ሁሉ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከፍ አድርጉ፣ ተራራውንና ኮረብታውን ሁሉ ዝቅ አድርጉ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ሸለቆው ሁሉ ከፍ ይላል
ሸለቆውን ከተቀረው መሬት ጋር የተስተካከለ ማድረግ ሸለቆውን ከፍ ማድረግ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፦ "ሸለቆው ሁሉ ይሞላል' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ጠማማውም መሬት ይቃናል፣ ስርጓጉጡም ቦታ ሜዳ ይሆናል
እነዚህ ሐረጎች ሕዝቡ እንዴት ለእግዚአብሔር ጎዳና ማዘጋጀት እንዳለባቸው ያብራራሉ። በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጹ ይችላሉ። አት፦ "ጠማማውን መሬት አቃኑ፣ ስርጓጉጡንም ቦታ ሜዳ አድርጉ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ እና መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉ ተመልከት)

የእግዚአብሔርም ክብር ይገለጣል
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "እግዚአብሔር ክብሩን ይገልጻል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

የእግዚአብሔር አፍ ይህን ተናግሮአልና
"አፍ' የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ራሱን ይወክላል። አት፦ "እግዚአብሔር ተናግሮአልና' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

Isaiah 40:6

ሥጋ ለባሽ ሁሉ ሣር ነው
"ሣር' የሚለው ቃል ሕዝቡን ያመለክታል። ሁለቱም ፈጥነው ስለሚሞቱ ተናጋሪው ሰዎች እንደ ሣር እንደሆኑ ይናገራል። አት፦ "ሰው ሁሉ እንደ ሣር ነው' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የኪዳናቸው ታማኝነት እንደ ሜዳ አበባ ነው
ተናጋሪው ሕዝቡ ለኪዳናቸው ያላቸውን ታማኝነት ከአበቦች ማበብና ፈጥኖ መሞት ጋር ያስተያያል። "ታማኝነት' የሚለው የነገር ስም "ታማኝ' በሚል ሊገልጽ ይችላል። "የኪዳን ታማኝነት' የሚለውን በኢሳይያስ 16፡5 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። አት፦ "የሜዳ አበባ ፈጥኖ እንደሚሞት ለኪዳን ታማኝ መሆንን ፈጥነው ያቆማሉ' (ዘይቤአዊ ንግግርና የነገር ስም ተመልከት)

የኪዳን ታማኝነት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) የኪዳን ታማኝነት ወይም 2) ውበት

የእግዚአብሔር እስትንፋስ ሲነፍስበት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) "እግዚአብሔር እስትንፋሱን ሲያነፍስበት' ወይም 2) "እንዲነፍስበት እግዚአብሔር ነፋስ ሲልክ።'

ሰው ሣር ነው
ሁለቱም ፈጥነው ስለሚሞቱ ተናጋሪው ሰዎች ሣር እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የአምላካችን ቃል ግን ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል
ቃሉ ለዘላለም ጸንቶ እንደሚኖር አድርጎ እግዚአብሔር የተናገረው ለዘላለም እንደሚኖር ተናጋሪው ይናገራል። (ሰስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 40:9

የምስራች የምትነግሪ ጽዮን ሆይ ከፍ ወዳለው ተራራ ውጪ
ከተራራ ጫፍ የምሥራች የምታወጅ መልእክተኛ እንደሆነች አድርጎ ጸሐፊው ስለ ጽዮን ይናገራል። (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየት ተመልከት)

ከፍ ወደ አለ ተራራ ውጪ
የሚያውጁትን ብዙ ሰዎች መስማት እንዲችሉ መልእክተኞች እንደ ተራራ ባለ ከፍ ባለ መሬት ላይ ብዙ ጊዜ ይቆማሉ። (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ጽዮን
ይህ በጽዮን የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታል። አት፦ "እናንተ የጽዮን ሰዎች' (ምትክ ስም ተመልከት)

የምስራች የምታመጪ ኢየሩሳሌም ሆይ
ጸሐፊው ኢየሩሳሌም የምስራች የምታውጅ መልእክተኛ እንደሆነች አድርጎ ይናገራል። (ግዑዝ ነገር እንደ ሰው ማየትን ተመልከት)

ክንዱ ስለ እርሱ ይገዛል
በዚህ ስፍራ ክንድ የእግዚአብሔርን ኃይል ይወክላል። አት፦ "በታላቅ ኃይል ይገዛል' (ምትክ ስም ተመልከት)

ዋጋው ከእርሱ ጋር ነው ... ያዳናቸው በፊቱ ይሄዳሉ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ ተመሣሣይ ነገር ይናገራሉ። ያዳናቸው እነርሱ ዋጋው ናቸው። አት፦ "ያዳናቸውን እንደ ዋጋው ከራሱ ጋር ያመጣቸዋል' (አጓዳኝነት ተመልከት)

Isaiah 40:11

መንጋውን እንደ እረኛ ያሰማራል
ጸሐፊው የእግዚአብሔር ሕዝብ በጎች እግዚአብሔር ደግሞ እረኞቸው እንደሆነ ይናገራል። አት፦ "እረኛ መንጋውን እንደሚመግብ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ይጠነቀቃል' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 40:12

ተራሮችን በሚዛን ... የመዘነ
ይህ አሳብ ገላጭ ጥያቄ አሉታዊ ምላሽ ይጠብቃል እንዲሁም እግዚአብሔር ብቻ እነዚህን ነገሮች ማድረግ በመቻሉ ላይ አጽንዖት ያደርጋል። አት፦ "እንዲሁም ተራሮችን በሚዛን ... ማንም የለም ነገር ግን እግዚአብሔር መዘናቸው' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ውኆችን በእፍኙ የሰፈረ
እግዚአብሔር በውቂያኖሶች ውስጥ ምን ያህል ውኃ እንዳለ ማወቁ እግዚአብሔር ውኃን በእጁ እንደያዘ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ሰማይንም በስንዝር የለካ
"ስንዝር' እጅ እስከ መጨረሻ ሲዘረጋ በአውራ ጣትና በትንሹ ጣት መካከል ያለ የርዝመት መለኪያ ነው። እግዚአብሔር የሰማይን ርዝመት ማወቁ በእጁ እንደለካ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የምድርን አፈር በቅርጫት ውስጥ የያዘ
እግዚአብሔር በመሬት ላይ ምን ያህል አፈር እንዳለ ማወቁ በቅርጫት ውስጥ እንደያዘው ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ተራሮችን በሚዛን፣ ኮረብቶችንም በሚዛን የመዘነ ... ?
እግዚአብሔር የተራሮች ክብደታቸው ምን ያህል እንደሆነ ማወቁ በሚዛን እንደ መዘናቸው ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 40:13

አጠቃላይ መረጃ
የእግዚአብሔርን ልዩ መሆን ለማጉላት ኢሳይያስ ጥያቄዎችን መጠቀሙን ይቀጥላል። (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

የእግዚአብሔርን አእምሮ ያወቀ ማን ነው? ወይም አማካሪው ሆኖ ያስተማረው ማን ነው?
ይህ አሳብ ገላጭ ጥያቄ አሉታዊ ምላሽ ይጠብቃል፣ ማንም እነዚህን ነገሮች ማድረግ እንደማይችል አጽንዖት ይሰጣል። አት፦ "ማንም የእግዚአብሔርን አእምሮ አላወቀም፣ ወይም አማካሪው ሆኖ አላስተማረውም።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የእግዚአብሔርን አእምሮ ያወቀ
በዚህ ስፍራ "አእምሮ' የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን አሳብ ብቻ ሳይሆን ፍላጎቱንና ገፊ ምክንያቶቹን ጭምር ያመለክታል።

መመሪያን ከማን ተቀበለ?
ይህ አሳብ ገላጭ ጥያቄ አሉታዊ ምላሽ ይጠብቃል፣ ማንም መቼም ይህን ማድረግ እንደማይችል አጽንዖት ይሰጣል። አት፡- "ነገሮችን በትክክለኛ መንገድ እንዲያደርግ ማንም አላስተማረውም። ማንም እውቀትን አላስተማረውም። የማስተዋልን መንገድ ማንም አላስተማረውም።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

Isaiah 40:15

ተመልከት ... እይ
እነዚህ ቃላት በሚከተለው ላይ አጽንዖት ይጨምራሉ።

አሕዛን በገንቦ እንዳለች ጠብታ ናቸው፣ በሚዛንም ላይ እንዳለ ትቢያ ተቆጥረዋል
ነቢዩ፣ አሕዛብ ለእግዚአብሔር ምን ያህል ትንሽና እዚህ ግቡ የማይባሉ መሆናቸውን ለማጉላት ከውኃ ጠብታና ከትቢያ ጋር ያስተያያቸዋል። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

በገንቦ እንዳለች ጠብታ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ገንቦ ውስጥ ጠብ ያለ የውኃ ጠብታ ወይም 2) ከገንቦው ወደ ወጪ ጠብ ያለ የውኃ ጠብታ

በሚዛን ላይ እንዳለ ትቢያ ተቆጥረዋል
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር በሚዛን ላይ እንዳለ ትቢያ ይቆጥራቸዋል።' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

በእርሱ ዘንድ እንደሌለ ነገር ተቆጥረዋል
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እርሱ እንደሌለ ነገር ይቆጥራቸዋል' (አድጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

Isaiah 40:18

እንግዲህ እግዚአብሔርን ከማን ጋር ታስተያዩታላችሁ? ከምን ጣዖትስ ጋር ታመሳስሉታላችሁ?
ከእግዚአብሔር ጋር የሚስተያይ ጣዖት እንደሌለ ለማጉላት ኢሳይያስ ሁለት ተመሣሣይ ጥያቄዎችን ይጠቀማል። አት፡- "እግዚአብሔርን የምታስተያዩበት ማንም የለም። እርሱን የምታመሳስሉበት ጣዖት የለም።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄና አጓዳኝነት ተመልከት)

አንተ
ይህ ብዙ ቁጥር ሲሆን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ሁሉ ያመለክታል። (የ "አንተ' ልዩ ልዩ አጠቃቀሞች ተመልከት)

የእጅ ባለ ሙያ ቀርጾታል፡- የወርቅ አንጥረኛ በወርቅ ለብጦታል፣ የብሩንም ሰንሰለት አድርጎለታል
"ባለ ሙያ ቀርጾታል፣ ሌላኛው በወርቅ ለብጦታል የብሩንም ሰንሰለት አድርጎለታል'

Isaiah 40:21

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለእግዚአብሔር ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል።

አላወቃችሁምን? አልሰማችሁምን? ከመጀመሪያው አንስቶ አልተወራላችሁምን? ምድር ከተመሠረተች ጀምሮ አላስተዋላችሁምን?
እንደ ፈጣሪነቱ የእግዚአብሔርን ታላቅነት ሕዝቡ ማወቅ እንደሚገባቸው አጽንዖት ለመስጠት ኢሳይያስ እነዚህን ጥያቄዎች ይጠቀማል። አት፡- "እናንተ በእርግጥ አውቃችኋል ሰምታችኋልም! ከመጀመሪያው አንስቶ ተነግሮአችኋል፤ ምድር ከተመሠረተች ጀምሮ አስተውላችኋል!' (አሳብ ገላጭ ጥያቄና አጓዳኝነት ተመልከት)

ከመጀመሪያ አንስቶ አልተወራላችሁምን?
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ከመጀመሪያው አንስቶ ሰዎች አላወሩላችሁምን?' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ምድር ከተመሠረተች ጀምሮ
ምድር እግዚአብሔር መሠረት የጣለላት ሕንፃ እንደሆነች አድርጎ እግዚአብሔር ምድርን እንደፈጠራት ነቢዩ ይናገራል። አት፡- "እግዚአብሔር ምድርን ከፈጠረበት ጊዜ አንስቶ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በምድር ክበብ ላይ የሚቀመጠው
እግዚአብሔር ምድርን መግዛቱን፣ እግዚአብሔር ከምድር ከፍ ብሎ ዙፋን ላይ እንደተቀመጠ አድርጎ ነቢዩ ይናገራል።

በእርስዋም የሚኖሩት በፊቱ እንደ አንበጣ ናቸው
ነቢዩ እግዘአብሔር ሰዎችን የሚያይበትን መንገድ ሰዎች አንብጣን ከሚያዩበት መንገድ ጋር ያስተያያል። አንበጦች ለሰዎች ትንሽ እንደሆኑ እንዲሁ ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት ትንሽና ደካማ ናቸው። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

ሰማያትን እንደ መጋረጃ የሚዘረጋቸው እንደ ድንኳንም ለመኖሪያ የሚዘረጋቸው
እነዚህ ሁለት መስመሮች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው። እግዚአብሔር ሰማያትን የፈጠረው በውሰጡ ለመኖር ድንኳን እንደሚተክል እንደሆነ አድርጎ ነቢዩ ይናገራል። አት፡- "ሰው በቀላሉ መጋረጃ እንደሚዘረጋ ወይም በውስጡ ለመኖር ድንኳን እንደሚተክል ሰማያትን ዘረጋ' (አጓዳኝነትና ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 40:23

ዝቅ ያደርጋል
"እግዚብሔር ዝቅ ያደርጋል'

ገና እንደ ተተከሉ ... እነርሱም ደረቁ
አዳዲስ ተክሎች ሞቃታማ ነፋስ ሲነፍስባቸው እንደሚደርቁ አለቆች በእግዚአብሔር ፊት ተስፋ የሌላቸው እንደሆኑ ነቢዩ ይናገራል ። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

እነርሱ ገና እንደተተከሉ፣ ገና እንደተዘሩ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ የሚናገሩት አንድ ነገር ሲሆን ተክሉ ወይም ዘሩ መሬት ውስጥ የተተከለበትን ነጥብ ያመለክታሉ። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "አንድ ሰው ወዲያው እንደተከላቸው ... አንድ ሰው ወዲያው እንደዘራቸው' (አጓዳኝነትና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ነፋስ እንደ እብቅ ጠርጎ ወሰዳቸው
አለቆችን እንደ ተክል እግዚአብሔርን ደግሞ እንዲጠወልጉ በሚያደርግ ነፋስ የገለጻቸው ስዕላዊ ንግግር በዚህ ዘይቤአዊ ንግግር ቀጥሏል። ነፋስ እብቅን ጠርጎ እንደሚወስድ የእግዚአብሔር የፍርድ ነፋስ የደረቁትን ተክሎች በቀላሉ ያስወግዳቸዋል። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 40:25

እመሳሰለው ዘንድ ከማን ጋር አስተያያችሁኝ?
የሚመስለው ማንም እንደሌለ ለማጉላት እግዚአብሔር ሁለት ተመሣሣይ አሳብ ገላጭ ጥያቄዎችን ይጠቀማል። አት፡- "እኔን ልታስተያዩ የምትችሉበት ማንም የለም። የምመስለው ማንም የለም።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄና አጓዳኝነት ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እነዚህን ከዋክብት ሁሉ የፈጠረ ማን ነው?
ይህ እግዚአብሔር ነው የሚል ምላሽ የሚጠብቅ መሪ ጥያቄ ነው። አት፡- "እነዚህን ሁሉ ከዋክበት እግዚአብሔር ፈጠራቸው!' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ሰልፋቸውን ይመራል
በዚህ ስፍራ "ሰልፍ' የሚለው ቃል ወታደራዊ ሰልፍን ያመለክታል። ከዋክበቱ እግዚአብሔር እንዲገለጡ የሚያዝዛቸው ወታደሮች እንደሆኑ አድርጎ ነቢዩ ይናገራል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በኃይሉ ታላቅነትና በኃይሉ ብርታት
"የኃይሉ ታላቅነት' እና "የኃይሉ ብርታት' የሚሉት ሐረጎች የእግዘአብሔርን ኃይል የሚያጎሉ ሁለት ተመሣሣይ ነገሮችን ይመሠርታሉ። አት፡- "በታላቅ ኃይሉና በብርቱ ኃይሉ' (የሁለት ነገሮች ተመሳሳይነት ተመልከት)

አንዱም አይጠፋም
አሉታዊው አሳብ አዎንታዊዉን ያጎላል። አት፡- "እያንዳንዱ ይኖራል' (ሁኔታን በማንበብ ላይ የተመሠረተ ትንቢት ተመልከት)

Isaiah 40:27

ያዕቆብ ሆይ፣ እስራኤልም ሆይ ... ፍርዴ ... ለምን ትላለህ? ... ትናገራለህ'?
ጥያቄው እየተናገሩ ያሉትን መናገር እንደሌለባቸው ያጎላል። አት፡- "የእስራኤል ሕዝብ ሆይ ... ፍርዴ ... አትበል' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ያዕቆብ ሆይ፣ እስራኤልም ሆይ ... ለምን ትላለህ? ትናገራለህ?
እነዚህ ሁለቱም ሐረጎች የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታሉ። አት፡- "የእስራኤል ሕዝብ ሆይ ለምን ትላለህ' (የሁለት ነገሮች ተመሣሣይነት ተመልከት)

መንገዴ ከእግዚአብሔር ተሰውራለች
የእግዚአብሔር የሚሆንባቸውን አለማወቅ እግዚአብሔር የሚጓዙበትን መንገድ እንደማያይ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "የሚሆንብንን እግዚአብሔር አያውቅም' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

አምላኬ ስለ ፍርዴ ግድ የለውም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ሌሎች በእኔ ላይ ስለሚያደርጉት ኢፍትሐዊ ነገር አምላኬ ግድ የለውም' ወይም 2) "አምላኬ ለእኔ ፍትሕን ለማድረግ ግድ የለውም'

አላወቅህምን? አልሰማህምን?
ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ታላቅነት ማወቅ እንዳለበት ለማጉላት ኢሳይያስ እነዚህን ጥያቄዎች ይጠቀማል። እነዚህን በኢሳይያስ 40:21 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት፡ አት፡- "በእርግጥ ታውቃላችሁ ሰምታችኋልም' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

የምድር ዳርቻ
በምድር በጣም ሩቅ የሆኑ ቦታዎች ምድር የምታልቀበት ቦታዎች እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሮአል። እነዚህ ሐረጎች ስዕላዊ ንግግር ይፈጥራሉ በዳርቻዎችም መካከል ያሉትን ቦታዎች ሁሉ ያመለክታል። አት፡- "በጣም ሩቅ የሆኑ የምድር ቦታዎች' ወይም "መላው ምድር' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 40:29

ለደካማ ኃይልን ይሰጣል፣ ጉልበት ለሌለውም ብርታትን ይጨምራል
እነዚህ ሁለት መስመሮች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው እግዚአብሔርም ብርታት የሌላቸውን እንደሚያበረታ ያጎላሉ። (አጓዳኝነት ተመልከት)

ኃይልን ይሰጣል
"እግዚአብሔር ኃይል ይሰጣል'

እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ
የሕዝቡ ከእግዚአብሔር ኃይል መቀበል ሕዝቡ ንስር እንደሚበርር መብረር እንደቻለ ተደርጎ ተነግሮአል። ንስር ብዙ ጊዜ ለብርታትና ለኃይል ምልክት ሆኖ ጥቅም ላይ የሚውል ወፍ ነው። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ይሮጣሉ አይታክቱም፣ ይሄዳሉ አይደክሙም
እነዚህ ሁለት መስመሮች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው። ከእግዚአብሔር ኃይል የተቀበሉ ሰዎች ሳይደክማቸው መሮጥና መሄድ እንደቻሉ ተደርጎ ተነግሮአል። (አጓዳኝነትና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 41

1 "ደሴቶች ሆይ በፊቴ ዝም ብላችሁ አድምጡ፣ አሕዛብም ኃይላቸውን ያድሱ፤ ይቅረቡም በዚያን ጊዜም ይናገሩ፤ ለፍርድ ለአንድነት እንቅረብ። 2 ከምሥራቅ
አንዱን ያስነሣ፣ በጽድቅም ወደ አገልግሎቱ የተጠራው ማን ነው? አሕዛብንም አሳልፎ በፊቱ ሰጠው፣ ነገሥታትንም አስገዛለት፤ ለሰይፉ እንደ ትቢያ ለቀስቱም
እንደ ተጠረገ እብቅ አድርጎ ሰጣቸው። 3 አሳደዳቸው፣ እግሮቹም አስቀድመው ባልሄዱባት ፈጣን መንገድ በደኅነት አለፈ። 4 ይህን የሠራና ያደረገ፣
ትውልድንም ከጥንት የጠራ ማን ነው? እኔ፣ እግዚአብሔር፣ ፊተኛው በኋላኞችም ዘንድ የምኖር እኔ ነኝ። 5 ደሴቶች አይተው ፈሩ፣ የምድርም ዳርቻች
ተንቀጠቀጡ፤ ቀረቡም ደረሱም። 6 ሁሉም እያንዳንዱ ባልንጀራውን ይረዳው ነበር፣ ወንድሙንም፣ 'አይዞህ' ይለው ነበር። 7 አናጢውም አንጥረኛውን፣
በመዶሻም የሚያሳሳውን መስፍ መችውን አጽናና፣ ስለ ብየዳ ሥራውም፣ 'መልካም ነው' አለ፤ እንዳይንቀሳቀስም በችንካር አጋጠመው። 8 አንተ ግን፣ ባሪያዬ
እስራኤል፣ የመረጥሁህ ያዕቆብ፣ የወዳጄ የአብርሃም ዘር ሆይ፣ 9 አንተ ከምድር ዳርቻ የያዝሁህ፣ ከማዕዘንዋም የጠራሁህና፣ 'አንተ ባሪያዬ ነህ፤' መርጬሃለሁ
አልጥልህም ያልሁህ ሆይ። 10 እኔ ከአንተ ጋር ነኝና፣ አትፍራ፤ እኔ አምላክህ ነኝና አትደንግጥ፤ አበረታሃለሁ፣ እረዳህማለሁ፣ በጽድቄም ቀኝ ደግፌ እይዝሃለሁ።
11 ተመልከት፣ እነሆ የሚቆጡህ ሁሉ ያፍራሉ፣ ይዋረዱማል፤ የሚከራከሩህም እንዳልነበሩ ይሆናሉ፣ ይጠፉማል። 12 የሚያጣሉህንም ትሻቸዋለህ
አታገኛቸውምም፣ የሚዋጉህም እንዳልነበሩና እንደ ምናምን ይሆናሉ። 13 እኔ አምላክህ እግዚአብሔር፣ 'አትፍራ፣ እረዳሃለሁ' ብዬ ቀኝህን እይዛለሁና። 14
አንተ፣ ትል ያዕቆብ፣ የእስራኤልም ሰዎች ሆይ፣ አትፍሩ፤ እረዳሃለሁ፤" ይላል እግዚአብሔር፣ የሚቤዥህም የእስራኤል ቅዱስ ነው። 15 "ተመልከቱ፣ እንደ
ተሳለች እንደ አዲስ ባለ ሁለት ጎን ጥርስ ማሄጃ አድርጌሃለሁ፤ ተራሮችንም ታሄዳለህ ታደቅቃቸውማለህ፣ ኮረብቶችንም እንደ ገለባ ታደርጋቸዋለህ። 16
ታበጥራቸዋለህ፣ ነፋስም ይጠርጋቸዋል፣ ዐውሎ ነፋስም ይበትናቸዋል። አንተም በእግዚአብሔር ደስ ይልሃል፣ በእስራኤልም ቅዱስ ትመካለህ። 17 ድሆችና
ምስኪኖችም ውኃ ይሻሉ አያገኙምም፣ ምላሳቸውም በጥማት ደርቋል፤ እኔ እግዚአብሔር እሰማቸዋለሁ፣ የእስራኤል አምላክ እኔ አልተዋቸውም። 18 በወናዎቹ
ኮረብቶች ላይ ወንዞችን፣ በሸለቆችም መካከል ምንጮችን እከፍታለሁ፤ ምድረ በዳውን ለውኃ መቆሚያ፣ የጥማትንም ምድር ለውኃ መፍለቂያ አደርጋለሁ። 19
የእግዚአብሔር እጅ ይህን እንደ ሠራች፣ የእስራኤልም ቅዱስ እንደ ፈጠረው ያዩ ዘንድ ያውቁም ዘንድ ያስቡም ዘንድ በአንድነትም ያስተውሉ ዘንድ፣ 20 በምድረ
በዳ ዝግባውንና ግራሩን ባርሰነቱንና የዘይቱን ዛፍ አበቅላለሁ፣ በበረሀውም ጥዱንና አስታውን ወይራውንም በአንድነት አኖራለሁ። 21 ክርክራችሁን አቅርቡ፣"
ይላል እግዚአብሔር፤ "ማስረጃችሁን አምጡ፣" ይላል የያዕቆብ ንጉሥ። 22 የገዛ ራሳቸውን ሙግት ያምጡ፣ የሚሆነውንም ይንገሩን፤ ልብም እናደርግ ዘንድ
ፍጻሜአቸውንም እናውቅ ዘንድ፣ የቀደሙት ነገሮች ምን እንደ ሆኑ ተናገሩ፣ የሚመጡትንም አሳዩን። 23 አማልክትም መሆናችሁን እናውቅ ዘንድ፣ በኋላ
የሚመጡትን ተናገሩ፤ እንደነግጥም ዘንድ በአንድነትም እናይ ዘንድ መልካሙን ወይም ክፉውን አድርጉ። 24 ተመልከቱ፣ እንዳልነበረ ናችሁ፣ ሥራችሁም ከንቱ
ነው፤ የሚመርጣችሁም አስጸያፊ ነው። 25 አንዱን ከሰሜን አነሣሁ፣ እርሱም መጥቶአል፤ አንዱም ከፀሐይ መውጫ ስሜን የሚጠራ ይመጣል፤ በጭቃ ላይ
እንደሚመጣ ሰው አፈርም እንደሚረግጥ ሸክለኛ በአለቆች ላይ ይመጣል። 26 እናውቅ ዘንድ ከጥንት የተናገረው። "እውነት ነው" እንልም ዘንድ ቀድሞ
የተናገረው ማን ነው? የሚናገር የለም፣ የሚገልጥም የለም፣ ቃላችሁንም የሚሰማ የለም። 27 በመጀመሪያ ለጽዮን፣ "ተመልከቱ እዚህ ናቸው፤" እላለሁ፤
ለኢየሩሳሌምም የምስራች ነጋሪን እሰጣለሁ። 28 ብመለከት፣ ማንም አልነበረም፤ ብጠይቃቸውም የሚመልስልኝ አማካሪ በመካከላቸው የለም። 29 ተመልከቱ፣
እነርሱ ሁሉ ከንቱዎች ናቸው፣ ሥራቸውም ምንምን ናት፤ ቀልጠው የተሠሩት ምስሎቻቸውም ነፋስና ኢምንት ናቸው።

Isaiah 41:1

በፊቴ በጸጥታ አድምጡ
በዚህ ወስጥ "እኔ' የሚለው እግዚአብሔርን ያመለክታል።

እናንተ ደሴቶች
ይህ በደሴቶችና አዋሳኝ መሬቶች ወይም ከሜዲትራኒያን ባሕር ማዶ የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታል። (ምትክ ስምና በስፍራው ለሌለ ወይም እንደ ሰው ለተወሰደ ግዑዝ ነገር መናገር ተመልከት)

ኃይላቸውን ያድሱ
ይህንን ሐረግ በኢሳይያስ 40:31 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ይቅረቡ በዚያን ጊዜም ይናገሩ፣ ለክርክርም በአንድነት እንቅረብ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው። ሁለተኛው ለመጀመሪያው ምክንያትን ያቀርባል። አት፡- "ይናገሩና ከእኔ ጋር ይከራከሩ ዘንድ ይቅረቡ' (አጓዳኝነት ተመልከት)

አንዱን ከምሥራቅ ያስነሳው በጽድቅም ለአገልገሎቱ የጠራው ማን ነው?
ይህንን ገዢ ከምሥራቅ ድል አድራጊ አድርጎ ያስነሣው እርሱ እንደሆነ ለማጉላት እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ ይጠቀማል። አት፡- "ይህን ኃያል ገዢ ከምሥራቅ የጠራሁት በመልካሙ አገልግሎቴም ላይ የሾምኩት እኔ ነኝ' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

አሕዛብንም አሳልፎ ሰጠው
"አሕዛብን አሳልፌ ሰጠሁት' ወይም "እነዚህን ነገሮች ያደረገ እርሱ አሕዛብን አሳልፎ ሰጠው'

ለሰይፉ እንደ ትቢያ ለቀስቱም እንደ ተጠረገ እብቅ አደረጋቸው
እነርሱን ትቢያና የተጠረገ እብቅ እንዳደረገ መነገሩ የእነዚህ ሕዝቦች ሰዎች የሠሩትን ሁሉ ፈጽሞ ለማጥፋቱ ስዕላዊ ንግግርና ግነት ነው። ከምሥራቅ የሆነው የእርሱ ሠራዊት አሕዛብን ድል ይነሣሉ በቀለሉም ይበትኑአቸዋል። (ስዕላዊ ንግግር፣ ዘይቤአዊ ንግግርና ግነትና ማጠቃለያ ተመልከት)

Isaiah 41:3

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለደሴቶችና ለአሕዛብ መናገሩን ይቀጥላል።

አሳደዳቸው በሰላምም አለፈ
"ከምሥራቅ የሆነው ገዢ አሕዛብን አሳደዳቸው'

እግሮቹ ላመል በሚረግጡበት በፈጣን መንገድ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርገሞች 1) ይህ እግሮቹ ላመል መሬቱን እንደሚነኩ ተደርጎ እርሱና ሠራዊቱ በጣም በፍጥነት መሄዳቸው የተነገረበት ስዕላዊ ንግግር ነው። አት፡- "በታላቅ ፍጥነት በሚሄድበት መንገድ' ወይም 2) "እግር' የሰውን ሁለንተና ይወክላል፣ ሐረጉም መንገዱ ከዚህ በፊት ያልሄዱበት መንገድ እንደሆነ ያመልክታል። አት፡- "አስቀድሞ ባልሄደበት መንገድ' (ስዕላዊ ንግግርና ተለዋጭ ስም ተመልከት)

እነዚህን የሠራና ያደረገ ማን ነው?
እነዚህን ነገሮች ያደረገ እርሱ እንደሆነ ለማጉላት እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ ይጠቀማል። አት፡- "እኔ እነዚህን ተግባራት ሁሉ ሠራሁ አደረግሁም።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄዎች ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ትውልድንም ከጥንት የጠራ ማን ነው?
በዚህ ስፍራ "ትውልድ' የሚለው ቃል በታሪክ ሁሉ ውስጥ እግዚአብሔር የፈጠራቸውንና የመራቸውን የሰው ታሪክ ሁሉ ይወክላል። ይህ አሳብ ገላጭ ጥያቄ፣ እግዚአብሔር የሚል ምላሽ ይጠብቃል። አት፡- "እኔ የሰዎችን ትውልድ ሁሉ ከመጀመሪያው ጠራሁ' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

የሠራና ያደረገ
እነዚህ ሁለት ቃላት በመሠረቱ የሚናገሩት አንድ ነገር ሲሆን እነዚህን ነገሮች ሁሉ ያደረገ እግዚአብሔር መሆኑን ያጎላሉ። (የሁለት ነገሮች ተመሣሣይነት ተመልከት)

ፊተኛው፣ በኋለኞችም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እግዚአብሔር ከፍጥረት በፊት ነበረ ደግሞም ከፍጥረት ፍጻሜም በኋላ ይኖራል ወይም 2) እግዚአብሔር ከመጀመሪያው የሰው ትውልድ በፊት ነበረ ደግሞም በመጨረሻው የሰው ትውልድ ጊዜም ይኖራል።

Isaiah 41:5

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል።

ደሴቶች ... የምድር ዳርቻች
እነዚህ ሐረጎች በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላሉ። አት፡- "በደሴቶች የሚኖሩ ሰዎች ... በምድር ዳርቻች የሚኖሩ ሰዎች' (ምትክ ስም ተመልከት)

ደሴቶች
በኢሳይያስ 41:1 በተረጎምኸው መሠረት መተርጎም ትችላለህ።

የምድር ዳርቻች
በምድር በጣም ሩቅ የሆኑ ቦታዎች ምድር የምታበቃባቸው ቦታዎች እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "የምድር በጣም ሩቅ ቦታዎች' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ቀረቡ መጡም
እነዚህ ሁለቱ ተመሣሣዮች ሕዝቡ በአንድነት ተሰበሰቡ የሚል ትርጉም አላቸው። አት፡- "በአንድነት መጡ' (የሁለት ነገሮች ተመሣሣይነት ተመልከት)

የብረት ቅርጽ ማውጫ
ሰው በመዶሻ ብረትን ቅርጽ የሚያስዝበት የብረት ማስቀመጫ

አንጥረኛውን ... አለ
በዚህ ስፍራ ማንጠር የሚለው ቃል ሠራተኞቹ ጣዖቱን መሥራት እንደጨረሱ ወርቁን ከእንጨቱ ጋር የማጠበቅን ሂደት ያመለክታል።

እንዳይንቀሳቀስም በምስማር ቸነከሩት
በዚህ ውስጥ እርሱ የሚለው የሠሩትን ጣዖት ያመለክታል።

Isaiah 41:8

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል

አንተ ከምድር ዳርቻዎች ያመጣሁህ፣ ከሩቅ ስፍራዎችም የጠራሁህ
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት መስመሮች አንድ ዓይነት ነገር የሚናገሩ ሲሆን እግዚአብሔር እስራኤልን ሕዝብ በሩቅ ከሚገኙ አገራት ወደ ምድራቸው እንዳመጣቸው ያጎላሉ። (አጓዳኝነት ተመልከት)

የምድር ዳርቻዎች
በምድር በጣም ሩቅ የሆኑ ቦታዎች ምድር የምታበቃባቸው ቦታዎች እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሮአል። ይህንን በኢሳይያስ 45:1 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። አት፡- "የምድር በጣም ሩቅ ቦታዎች' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 41:10

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል።

በጽድቄም ቀኝ እጅ ደግፌ እይዝሃለሁ
የእግዚአብሔር ሕዝቡን ማበረታታት በእጁ እንደያዛቸው ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በጽድቄ ቀኝ እጅ
በዚህ ስፍራ ቀኝ እጅ የእግዚአብሔርን ኃይል ይወክላል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የእግዚአብሔር ቀኝ እጅ ጻድቅ ነው በዚያም ሁልጊዜ ትክክለኛውን ነገር ያደርጋል 2) የእግዚአብሔር ቀኝ እጅ ድል ነሺ ነው በዚያም ሁልጊዜ የሚያደርገው ይከናወንለታል። አት፡- "ድል አድራጊ ኃይሌ' (ምትክ ስም ተመልከት)

Isaiah 41:11

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል

ያፍራሉ ይዋረዳሉም፣ ከአንተ ጋር የሚጣሉ ሁሉ
"ከአንተ ጋር የሚጣሉ ሁሉ ያፍራሉ ይዋረዳሉም'

ያፍራሉ ይዋረዳሉም
በመሠረቱ ሁለቱም ቃላት ተመሣሣይ ነገር ይናገራሉ የጎፍረታቸውንም ታላቅነት ያጎላሉ። (የሁለት ነገሮች ተመሣሣይነት ተመልከት)

እንዳልነበሩ ይሆናሉ ይጠፉማል፣ የሚቃወሙህ
"የሚቃወሙህ እንዳልነበሩ ይሆናሉ ይጠፉማል'

Isaiah 41:12

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል።

ቀኝ እጅህን እይዛለሁና
የእግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ መርዳት ቀኝ እጁቸውን እንደያዘ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 41:14

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል።

አንተ ትል ያዕቆብ፣ የእስራኤልም ሰዎች ሆይ
በዚህ ስፍራ ያዕቆብ እና የእስራኤል ሰዎች ማለት ተመሣሣይ ነገር ነው። አት፡- "ትል የምትመስሉ የእስራኤል ሰዎች ሆይ' (የሁለት ነገሮች ተመሣሣይነት ተመልከት)

አንተ ትል ያዕቆብ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ ሌሎች ሕዝቦች የእስራኤልን ሕዝብ በሚመለከት ያላቸውን አስተያየት ያመለክታል ወይም 2) ይህ ራሳቸው እስራኤላውያን ስለ ራሳቸው ያላቸውን አስተያየት ያመለክታል። ትል እንደሆኑ አድርጎ እግዚአብሔር ስለ ትንሽነታቸው ይናገራል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኝነት ለመግለጽ እግዚአብሔር በራሱ ስም ይናገራል። በኢሳይያስ 30:1 እንዳለው ተርጉም። አት፦ "እግዚአብሔር ያወጀው ይህ ነው' ወይም "እኔ፣ እግዚአብሔር ያወጅኩት ይህ ነው' (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሦሥተኛ መደብ ተመልከት)

የእስራኤል ቅዱስ
ይህንን ሐረግ በኢሳይያስ 1:4 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

እኔ እንደተሳለች እንደ አዲስ ባለ ጥርስ ማሄጃ አድርጌሃለሁ ... ኮረብቶችን እንደ ገለባ ታደርጋቸዋለህ
ሕዝቡን ተራራሮችን ደልዳላ የሚያደርግ ስለታም ማሄጃ እንደሚያደርግ ዓይነት እስራኤል ጠላቶቹን እንዲያሸነፍ እንደሚያስችለው እግዚአብሔር ይናገራል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የተሳለ ስለታም ማሄጃ
ፍሬውን ከገለባው ለመለየት እንድ ሰው ስንዴ ላይ የሚጎትተው የሾሉ ብረቶች ያሉት ነገር ነው።

በሁለት ወገን የተሳለ
ይህ ከስለታም ማሄጃ ጋር የሚያያዙትን የሾሉ ብረቶች ጠርዝ ያመለክታል። በሁለት ወገን የተሳሉ ናቸው ማለት በጣም ስለታም ናቸው ማለት ነው።

ተራሮችን ታሄዳለህ ታደቅቃቸውማለህ
ይህ ድርብ ስዕላዊ ንግግር ነው። ተራራሮች እህልን ለማመልከት ጥቅም ላይ የዋለ ስዕላዊ ንግግር ነው፤ እህልን ማሄድ ደግሞ በአቅራቢያዋ የሚገኙ ኃያላን የሆኑ ጠላት ሕዝቦችን እስራኤል እንደምታሸነፍ ለማመልከት ጥቅም ላይ የዋለ ስዕላዊ ንግግር ነው። አት፦ "እንደ ተራሮች ጠንካሮች መስለው ቢታዩም ጠላቶቻችሁን እንደ እህል ታሄዷቸዋለችሁ፣ ታደቅቋቸውማላችሁ።' (ስዕላዊ ንግግር እና ገነትና ማጠቃለይ ተመልከት።)

ኮረብቶችንም እንደ ገለባ ታደርጋቸውማለህ
ኮረብቶች በእስራኤል አቅራቢያ የሚገኙ ኃያላን የሆኑ ጠላት ሕዝቦችን የሚያመልከት ስዕላዊ ንግግር ነው። ሕዝቡ እህሉን ካሄዱት በኋላ ነፋሱ ገላባውን ጠርጎ እንዲወስደው ማድረግ የሚገባቸው መሆኑ እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን እንዲያጠፋ ሊፈቅዱለት የሚገባ ለመሆኑ ስዕላዊ ንግግር ነው። (ስዕላዊ ንግግርና ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 41:16

አያያዥ አሳብ
እስራኤል እንዴት ጠላቶቿን እንደምታሸንፍ ለመግለጽ እግዚአብሔር እህልን ከገለባው የመለየትን ስዕላዊ ንግግር መጠቀሙን ይቀጥላል።

ታበጥራቸዋለህ ... ነፋስም ይበትናቸዋል
በዚህ ውስጥ እነርሱ የሚለው በኢሳይያስ 41:15 የተጠቀሱትን ተራሮችና ኮረብታዎች ያመለክታል። ይህ ገለባውን ለማስወገድ እህሉ የሚበጠርበትን፣ እህልን በማሄድ ሂደት ውስጥ ቀጣዩን ደረጃ ይወክላል። ገለባ በነፋስ ተጠርጎ እንደሚሄድ የእስራኤል ጠላቶች ይጠፋሉ። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ነፋስ ይጠርጋቸዋል፤ ነፋስም ይበትናቸዋል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች አንድ ዓይነት ነገር ይናገራሉ። አት፦ "ነፋስ ጠርጎ ይወስዳቸዋል' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 41:17

አጠቃላይ መረጃ
እጅግ የሚያስፈልጋቸው ነገር ያላቸውን ሰዎች በሚመለከት እጅግ እንደ ተጠሙ አድርጎ፤ የእርሱንም አቅርቦት በተለምዶ ውኃ በማይታይባቸው ቦታዎች ውኃ እንደሚሰጣቸው እግዚአብሔር ይናገራል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 41:19

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል።

ዝግባውንና ግራሩን ... ባርሰነቱንና የዘይቱን ዛፍ
እነዚህ የዛፍ ስሞች ናቸው። (የማይታወቁትን መተርጎም ተመልከት)

የእግዚአብሔር እጅ ይህን ሠርታለች
በዚህ ስፍራ እጅ የሚለው እግዚአብሔርን ራሱን ይወክላል። አት፦ "እግዚአብሔር ይህን አደረገ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

Isaiah 41:21

አጠቃላይ መረጃ
በእነዚህ ቁጥሮች እግዚአብሔር በሕዝቡና በጣዖቶቻቸው ላይ ይሳለቃል። ወደፊት የሚሆነውን እንዲናገሩ በመጠየቅ ጣዖታትን ይገዳደራል፣ ነገር ግን እነርሱ የማያውቁትን እርሱ ያውቃል። (ምጸት ተመልከት)

Isaiah 41:23

አያያዥ አሳቦች
እግዚአብሔር በጣዖታትና በሚያመልኳቸው ሰዎች ላይ መሳለቁን ይቀጥላል። (ኢሳ 41:21-22)

መልካሙን ወይም ክፉውን አድርጉ
"መልካም' ወይም "ክፉ' የሚሉት ቃላት ስዕላዊ ንግግር ሲሆኑ ማንኛውንም ነገር ይወክላሉ። አት፦ "ማንኛውንም ነገር አድርጉ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የሚመርጣችሁም
በዚህ ውስጥ "እናንተ' የሚለው ጣዖታትን የሚያመልከት ነው። አት፦ "እናንተን ጣዖታትን የመረጠ ሰው' (የ "አንተ' ልዩ ልዩ አጠቃቀሞች ተመልከት)

Isaiah 41:25

አጠቃላይ መረጃ፦
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል

አንዱን አነሣሁ
እግዚአብሔር አንድን ሰው መሾሙን ያንን ሰው ወደ ላይ እንዳነሣ አድርጎ ይናገራል። አት፦ "አንዱን ሾምሁ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ከፀሐይ መውጫ
ይህ ፀሐይ ወደ ምትወጣበት አቅጣጫ ወደ ምሥራቅ ያመለክታል። አት፦ "ከምሥራቅ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ስሜን የሚጠራ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እንዲሰካለት እግዚአብሔርን የሚለምን ሰው 2) እግዚአብሔርን የሚያመልክ ሰው

ገዢዎችን ይረጋግጣል
የሌሎች ሕዝቦች ገዢዎችን ማሸነፍ ከእግር በታች እነርሱን መርገጥ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፦ "ገዢዎችን ድል ያደርጋል' (ሰስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ጭቃ እንደሚረግጥ ሸክላ ሠሪ
እግዚአብሔር ይኼ ሰው ሌሎች ገዢዎችን የሚረግጥበትን መንገድ ከውኃ ጋር ለማደባለቅ ሸክላ ሠሪ ጭቃን ከሚረግጥበት መንግድ ጋር ያስተያያል። (ዘይቤአዊ አነጋገር ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እናውቅ ዘንድ ከጥንት የተናገረው ማን ነው? "እውነት ነው' እንልም ዘንድ ቀድሞ የተናገረው ማን ነው?
እግዚአብሔር ሕዝቡ በሚያመልካቸው ጠያታት ላይ ለመሳለቅ እነዚህን አሳብ ገላጭ ጥያቄዎች ይጠቀማል። የተጠቆሙ መልሶች 1) ጣያታት እነዚህን ነገሮች አላደረጉም 2) እነዚህን ያደረገ እግዚአብሔር ብቻ ነው። አት፡- "እናውቅ ዘንድ ከጣያታት መካከል ማንም ይህንን ከጥንት አላስታወቀም። ‘እውነት ነው’ እንል ዘንድ ከመካከላቸው ማንም አስቀድሞ አልተናገረም።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄና መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉ ተመልከት)

በእውነቱ ከመካከላቸው ማንም አልተናገረም፣ አዎ፣ ምንም ስትሉ የሰማ የለም
"በእውነቱ ከጣያታት መካከል ማንም አልተናገረም። በእውነቱ ጣያታት ምንም ስትሉ የሰማ የለም'

Isaiah 41:27

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል

ከመካከላቸው አንድም
"አንድም ጣያት'

ቀልጠው የተሠሩት ምስሎቻቸው ነፋስና ባዶ ናቸው
ጣያታት ነፋስና ባዶ ናቸው በማለት እግዚአብሔር የጣያታትን ከንቱነት ይናገራል። አት፡- "ጣያቶቻቸው ከንቱዎች ናቸው' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 42

1 እነሆ፣ ደግፌ የያዝሁት ባሪያዬ፤ ነፍሴ ደስ የተሰኘችበት ምርጤ፤ በእርሱ ላይ መንፈሴን አድርጌአለሁ። እርሱም ለአሕዛብ ፍርድን ያወጣል። **2** አይጮኽም
ቃሉንም አያነሣም፣ ድምፁንም በጎዳናዎች አያሰማም። **3** የተቀጠቀጠን ሸምበቆ አይሰብርም፣ የሚጤስንም ክር አያጠፋም፤ በእውነት ፍርድን ያወጣል። **4**
በምድርም ፍትሕን እስኪያደርግ ድረስ ይበራል እንጂ አይጠፋም፤ አሕዛብም ሕጉን ይጠብቃሉ። **5** ሰማያትን የፈጠረ የዘረጋቸውም፣ ምድርንና በውስጥዋ
ያለውን ያጸና፣ በእርስዋ ላይ ለሚኖሩ ሕዝብ እስትንፋስን፣ ለሚሄዱባትም መንፈስን የሚሰጥ አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ **6** "እኔ፣ እግዚአብሔር
በጽድቅ ጠርቼሃለሁ፣ እጅህንም እይዛለሁ እጠብቅህማለሁ። እጠብቅሃለሁ፣ ለአሕዛብ ብርሃን እንደሆንክ ሁሉ፣ ለሕዝቡም እንደ ኪዳን አደርግሃለሁ። **7**
የዕውሩንም ዓይን ትከፍት ዘንድ፣ የተጋዘውንም ከግዞት ቤት በጨለማም የተቀመጡትን ከወህኒ ቤት ታወጣ ዘንድ ለሕዝብ ቃል ኪዳን ለአሕዛብም ብርሃን
አድርጌ እሰጥሃለሁ። **8** እኔ እግዚአብሔር ነኝ፣ ስሜ ይህ ነው፤ ክብሬን ለሌላ፣ ምስጋናዬንም ለተቀረጹ ምስሎች አልሰጥም። **9** ተመልከቱ፣ የቀድሞው ነገር
ተፈጸመ፣ አዲስ ክስተቶችንም እናገራለሁ። አስቀድሞም ሳይከሰት ስለ እነርሱ አስታውቃችኋለሁ።" **10** ወደ ባሕር የምትወርዱ በእርስዋም ውስጥ ያላችሁ
ሁሉ፣ ደሴቶችና በእነርሱም ላይ የምትኖሩ ሆይ፣ ለእግዚአብሔር አዲስ መዝሙር፣ ከምድርም ዳርቻ ምስጋናውን ዘምሩ። **11** ምድረ በዳውና ከተሞቹ የቄዳርም
ሰዎች የሚቀመጡባቸው መንደሮች ድምፃቸውን በደስታ ያንሡ! በሴላ የሚኖሩ እልል ይበሉ፤ በተራሮችም ራስ ላይ ሆነው ይጩኹ። **12** ለእግዚአብሔር ክብርን
ይስጡ፣ ምስጋናውንም በደሴቶች ይናገሩ። **13** እግዚአብሔር እንደ ኃያል ይወጣል፤ እንደ ሰልፈኛም ቅንዓትን ያስነሣል፤ ይጮኻል ድምፁንም ያሰማል፣
በጠላቶቹም ላይ ኃይሉን ያሳያል። **14** ከድሮ ዘመን ጀምሮ ዝም ብያለሁ፤ ዝም ብዬም ታግሻለሁ፤ አሁን ምጥ እንደ ያዛት ሴት እጮኻለሁ፤ አጠፋለሁ
በአንድነትም እጨርሳለሁ። **15** ተራሮችንና ኮረብቶችን አፈርሳለሁ፣ ቡቃያዎቻቸውንም ሁሉ አደርቃለሁ፤ ወንዞችንም ደሴቶች አደርጋለሁ፣ ኩሬዎችንም
አደርቃለሁ። **16** ዕውሮችንም በማያውቁት መንገድ አመጣቸዋለሁ፤ በማያውቋትም ጎዳና እመራቸዋለሁ፤ በፊታቸውም ጨለማውን ብርሃን አደርጋለሁ፣
ጠማማውንም አቀናለሁ። ይህን አደርግላቸዋለሁ፣ አልተዋቸውምም። **17** በተቀረጹትም ምስሎች የሚታመኑ፣ ቀልጠው የተሠሩትንም ምስሎች፣ "አምላኮቻችን
ናችሁ" የሚሉ ወደ ኋላቸው ይመለሳሉ ፈጽመውም ያፍራሉ። **18** እናንተ ደንቆሮች፣ ስሙ፤ እናንተም ዕውሮች፣ ታዩ ዘንድ ተመልከቱ። **19** ከባሪያዬ በቀር ዕውር
ማን ነው? እንደምልከው መልእክተኛዬስ በቀር ደንቆሮ የሆነ ማን ነው? እንደ ፍጹሙ ወይስ እንደ እግዚአብሔር ባሪያ ዕውር የሆነ ማን ነው? **20** ብዙ ነገርን
ታያላችሁ ነገር ግን አትገነዘቡትም፤ ጆሮአችሁም ተከፍተዋል፣ ነገር ግን አትሰሙም። **21** እግዚአብሔር ስለ ጽድቁ ሕጉን ታላቅ ያደርግና ያከብር ዘንድ ወደደ። **22**
ይህ ግን የተበዘበዘና የተዘረፈ ሕዝብ ነው፤ ሁላቸው በዋሻ ውስጥ ተጠምደዋል፣ በግዞት ቤትም ተሸሽገዋል፤ ብዝበዛ ሆነዋል የሚያድንም የለም፣ ምርኮም
ሆነዋል፣ ማንም፣ "መልሷቸው!" የሚል የለም። **23** ከመካከላችሁ ይህን የሚያደምጥ፣ ለሚመጣውም ጊዜ የሚያደምጥና የሚሰማ ማን ነው? **24** ያዕቆብን
ለማረኩ እስራኤልንም ለበዘበዙ ሰዎች የሰጠ ማን ነው? እኛ የበደልነው፥ እነርሱም በመንገዱ ይሄዱ ዘንድ ያልወደዱት ለሕጉም ያልታዘዙለት እግዚአብሔር
እርሱ አይደለምን? **25** ስለዚህ፣ የቍጣውን መዓትና የሰልፉን ጽናት አፈሰሰበት። በዙሪያም አነደደው እርሱ ግን አላወቀም፣ አቃጠለውም እርሱ ግን ልብ
አላደረገም።

Isaiah 42:1

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል

እነሆ ባሪያዬ
"ባሪያዬን ተመልከቱ' ወይም "ባሪያዬ ይኼው'

በእርሱ ደስ ይለኛል
"እጅግ ደስ የተሰኘሁበት'

Isaiah 42:3

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል።

የተቀጠቀጠን ሸምበቆ አይሰብርም፣ የሚጠስንም ክር አያጠፋም
እንደ ተቀጠቀጠ ሸምበቆና እንደ ሚጤስ ክር ደካና ተስፋ የሌላቸው ሰዎች እንደሆኑ እግዚአብሔር ይናገራል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የተቀጠቀጠ ሸምበቆ
ሸምበቆ ረጅም ሣር የሚመሥል፣ ረጅም፣ ቀጭን ግንድ ያለው ተክል ነው። ከተቀጠቀጠ ወይም ከተጎዳ ምንም ክብደት መሸከም አይችልም። ይህንን በኢሳይያስ 36:6 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

አይሰብርም
ባሪያዬ አይሰብርም

ደሴቶች
ይህ በደሴቶችና አዋሳኝ መሬቶች ወይም ከሜዲትራኒያን ባሕር ማዶ የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታል። ይህንን በኢሳይያስ 41:1 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። አት፦ "በደሴቶች የሚኖሩ ሰዎች' (ምተክ ስም ተመልከት)

Isaiah 42:5

ሰማያትን የፈጠረ፣ የዘረጋቸውም፣ ምድርን የፈጠረ
ሰማያትና ምድር እንደ ጨረቅ የዘረጋቸው እንደሆነ አድርጎ ነቢዩ ስለ እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን መፍጠር ይናገራል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በእርስዋ ላይ ላሉ ሰዎች እስትንፋስን፣ በእርስዋም ለሚኖሩ ሕይወትን የሚሰጥ
በመሠረቱ እነዚህ ሐረጎች የሚናገሩት አንድ ነገር ሲሆን እግዚአብሔር ለሁሉም ሰው ሕይወት እንደሚሰጥ አጉልተው ይናገራሉ። እስትንፋስ የሚለው ቃል ለሕይወት ምትክ ቃል ነው። አት፦ "በምድር ለሚኖሩ ሰዎች ሕይወትን ይሰጣል' (አጓዳኝነትና ምትክ ስም ተመልከት)

ጠርቼሃለሁ
በዚህ ውስጥ "አንተ' የሚለው የእግዚአብሔርን ባሪያ ያመልክታል። (የ"አንተ' ልዩ ልዩ አጠቃቀሞ ተመልከት)

ለሕዝብ ኪዳን አድርጌህ ...
በዚህ ስፍራ "ኪዳን' የሚለው ቃል ኪዳኑን ለመሠረተው ወይም ተፈጻሚ ላደረገው ምትክ ስም ነው። አት፦ በሕዝቡ ዘንድ የኪዳኑን አስፈጻሚ አደርግሃለሁ ... (ምትክ ስም ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለአሕዛብ ብርሃን
ለአሕዛብ በጨለማ ስፍራ የሚያበራ ብርሃን እንደሚያደርገው በሚመስል መልኩ እግዚአብሔር ባሪያውን ሕዝቦችን ከእስራት የሚፈታ እንደሚያደርገው ይናገራል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 42:7

አጠቃላይ መረጃ
ባሪያው የሚያደርገውን እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል

የዕውሩን ዓይን ትከፍት ዘንድ
ዕውራን ሰዎችን እንዲያዩ ማድረግ ዓይኖቻቸውን እንደ መክፈት ተደርጎ ተነግሮአል። እንዲሁም፣ ባሪያው ለዕውራን ሰዎች ማየትን የሚመለስ በሚመስል መልኩ እግዚአብሔር ያለአግባብ ያታሰሩትን አገልጋዩ ነጻ እንደሚያወጣ ይናገራል። አት፡- "ዕውሩ እንዲያይ ይደርጋል' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

እስረኛውን ከጨለማ ቤት ታወጣ ዘንድ፣ በጨለማም የተቀመጡትን ከግዞት ቤት
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚናገሩት አንድ ዓይነት ነገር ነው። ማሰሪያ አንቀጹ በሁለተኛው ሐረግ ላይ ሊታከል ይችላል። አት፡- "እስረኛውን ከጨለማ ቤት ታወጣ ዘንድ፣ በጨለማም የተቀመጡትን ከግዞት ቤት ታወጣ ዘንድ' (አጓዳኝነትና መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉ ተመልከት)

Isaiah 42:8

ምስጋናዬን ለተቀረጹ ምስሎች
ማሰሪያ አንቀጽ ከቀደመው ግስ ሊወሰድ ይችላል። አት፡- "ምስጋናዬን ለተቀረጹ ምስሎች አልሰጥም' (መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉ ተመልከት)

ምስጋናዬን
ይህ እግዚአብሔር ከሕዝቡ የሚቀበለውን ምስጋናውን ያመለክታል።

እነግራችኋለሁ
በዚህ ውስጥ "አናንተ' የሚለው የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል። (የ"አንተ' ልዩ ልዩ አጠቃቀሞ ተመልከት)

Isaiah 42:10

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል።

ባሕርና በውስጥዋም ያላችሁ ሁሉ፣ ደሴቶችና በእነርሱም የምትኖሩ ሁሉ
"በባሕር ውስጥ የምትኖሩ ፍጥረታት ሁሉና በደሴቶች የምትኖሩ ሁሉ'

ምድረ በዳና ከተሞች ይጩኹ
ይህ በምድረ በዳና በከተሞች የሚኖሩ ሰዎቸን ያመልክታል (ምትክ ስም ተመልከት)

ቄዳር
ይህ የሰሜን አረብ ከተማ ነች። ይህ በኢሳይያስ 21:16 እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።

ሴላ
በኤዶምያስ የምትገኝ ከተማ ነች። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

Isaiah 42:12

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል።

ክብርን ይስጡ
በዚህ ውስጥ "እነርሱ' የሚለው በደሴቶች ዳርቻ የሚገኙትን ሰዎች ያመለክታል።

እግዚአብሔር እንደ ተዋጊ ይወጣል፣ እንደ ተዋጊ ሰው
እግዚአብሔር የሕዝቡን ጠላቶች ሊያሸንፍ ዝግጁ ከሆነ ተዋጊ ጋር ተነጻጽሮአል። (ዘይቤአዊ ንግግር እና አጓዳኝነት ተመልከት)

ቅንዓቱን ያነሳሳል
በዚህ ስፍራ ቅንዓት ወደ ጦርነት ሊገባ ሲል ተዋጊ የሚሰማውን ስሜት ያመለክታል። እግዚአብሔር ቅንዓቱን ማነሳሳቱ፣ ነፋስ የወኃን ሞገድ እንደሚያስነሳ እርሱም እንዲሁ ቅንዓቱን እንደሚያስነሳ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 42:14

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል።

ከድሮ ዘመን ጀምሮ ጸጥ ብያለሁ፣ ዝም ብያለሁ ራሴንም ገድቤአለሁ
እነዚህ ሁለት መሥመሮች አንድ ዓይነት ትርጉም አላቸው። የእግዚአብሔር አለመንቀሳቀስ እንደ ጸጥታና ዝምታ ተገልጾአል። (አጓዳኝነት ተመልከት)

ዝም ብያለሁ ራሴንም ገድቤአለሁ
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች ትርጉማቸው አንድ ሲሆን እግዚአብሔር ራሱን ከእንቅስቃሴ እንደ ገታ ያመለክታሉ። አት፡- "ምንም ከማድረግ ራሴን ገትቼአለሁ' (የሁለት ነገሮች ተመሳሳይነት ተመልከት)

ምጥ እንደያዛት ሴት እጮኻለሁ ... አቃስታለሁ ትንፋሼም ቁርጥ ቁርጥ ይላል
እንደሚጮህ ተዋጊ የእግዚአብሔር እንቅስቃሴ ከምጥ ህመም የተነሣ ከምትጮህ እርጉዝ ሴት ጋር ተነጻጽሮአል። ከተወሰነ የዝምታ ጊዜ በኋላ በድነገት የሚሆንን አይቀሬ እንቅስቃሴ ያጎላል። (ዘይአዊ ንግግር ተመልከት)

ተራሮችን አፈርሳለሁ ... ረግረጉን አደርቃለሁ
ጠላቶቹን ለማጥፋት ያለውን ታላቅ ኃይል ለመግለጽ እግዚአብሔር ይህን ስዕላዊ ቋንቋ ይጠቀማል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ረግረግ
ረግረግ ለስላሳ መሬት፣ ውኃ ያቆረበት እርጥብ መሬት ነው።

Isaiah 42:16

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል

ዕውሮችን በማያውቋት መንገድ አመጣቸዋለሁ፣ በማያውቋትም መንገድ እመራቸዋለሁ
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚናገሩት ተመሣሣይ ነገር ነው። አት፡- "ዕውሮችን በማያውቋት መንገድ እመራቸዋለሁ' (አጓዳኝነት ተመልከት)

ዕውሮች
ዕውሮች ስለሆኑ ማየት እንደማይችሉ አድርጎ እግዚአብሔር ሕዝቡ ተስፋ ቢስ እንደሆኑ ይናገራል። (ስዕለዊ ንግግር ተመልከት)

በማያውቋት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ከቶም ባልሄዱበት' 2) "ባለመዱት'

በፊታቸው ጨለማውን ብርሃን አደርጋለሁ
በጨለማ ከመሄዳቸው የተነሣ ማየት አንደማይችሉ ሕዝቡ ተስፋ ቢስ መሆናቸውን ፣ እንዲሁም የሚያደርግላቸውን እርዳት በጨለማ የሚያበራ ብርሃን እንደ ማድረግ መሆኑን እግዚአብሔር ይናገራል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Isaiah 42:17

አጠቃላይ መግቢያ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል

ወደ ኋላቸው ይመለሳሉ ፈጽመውም ያፍራሉ
ጣዖታትን የሚያመልኩትን መቃወም ወደ ኋላቸው እንዲመለሱና በተቃራኒ አቅጣጫ እንዲሄዱ ማስገደድ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮአል። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ለገለጽ ይችላል። አት፡- "እቃወማቸዋለሁ አሳፍራቸውማለሁ' (ስዕላዊ ንግግርና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

Isaiah 42:18

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል

እናንተ ደንቆሮች ... እናንተ ዕውሮች
በዚህ ስፍራ "እናንተ' የሚለው የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል። እርሱን ከመስማትና ከመታዘዝ መውደቃቸውን እውሮችና ደንቆሮች እንደሆኑ አድርጎ እግዚአብሔር ይናገራል። (የ "አንተ' ልዩ ልዩ አጠቃቀሞች እና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ከባሪያዬ በቀር ዕውር ማን ነው? እንደምልከው እንደ መልእክተኛዬስ ደንቆሮ የሆነ ማን ነው?
በሕዝቡ ላይ ለመሳለቅና እንደ እነርሱም ዕውርና ደንቆሮ የሆነ ማንም እንደሌለ ለማጉላት እግዚአብሔር ይህን አሳብ ገላጭ ጥያቄ ይጠይቃል። አት፡- "እንደ ኪዳን አጋሬ ዕውር የሆነ ማንም የለም። እንደ እግዚአብሔር ባሪያም ዕውር የሆነ ማንም የለም።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

Isaiah 42:20

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል።

ብዙ ነገርን ታያላችሁ ነገር ግን አትገነዘቡም
"ብዙ ነገር ታያላችሁ ነገር ግን ምን ማለት እንደሆነ አትረዱም'

ጆሮአችሁም ተከፍቷል፣ ነገር ግን አትሰሙም
የመስማት ችሎት የጆሮ መከት ተደርጎ ተነግሮአል። በዚህ ስፍራ መስማት የሚለው ቃል አንድ ሰው የሚሰማውን መረዳትን ያመልክታል። አት፡- "ሕዝቡ ይሰማል፣ ነገር ግን ማንም የሰሙትን አይረዳም።' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ጽድቁን ያከብር ሕጉንም ታላቅ ያደርግ ዘንድ እግዚአብሔር ወደደ
"ሕጉን ታላቅ በማድረግ ጽድቁን ያከብር ዘንድ እግዚአብሔር ወደደ።' የሐረጉ ሁለተኛ ክፍል እግዚአብሔር ሁለተኛውን ክፍል እንዴት እንደሚፈጽም ያብራራል።

Isaiah 42:22

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል።

ይህ ግን የተበዘበዘና የተዘረፈ ሕዝብ ነው
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ነገር ግን ጠላት ይህን ሕዝብ በዝብዞታል ዘርፎታልም' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

የተበዘበዘና የተዘረፈ
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ቃላት የሚናገሩት አንድ ዓይነት ነገር ሲሆን እንዴት ክፉኛ ጠላት እንደ በዘበዛቸው አጽንዖት ይሰጣሉ። (የሁለት ነገሮች ተመሳሳይነት ተመልከት)

ሁሉም በጉድጓድ ውስጥ ተጠምደዋል፣ በወህኒም በምርኮ ተይዘዋል
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚናገሩት አንድ ዓይነት ነገር ነው። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ጠላት ሁሉንም በጉድጓድ አጠመዳቸው በወህኒም ምርኮ አድርጎ ያዛቸው' (አጓዳኝነትና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

Isaiah 42:23

አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ጋ ኢሳይያስ መናገር ይጀምራል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 43

1 አሁንም ያዕቆብ ሆይ፣ የፈጠረህ፣ እስራኤልም ሆይ፣ የሠራህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "ተቤዥቼሃለሁና አትፍራ፤ በስምህም ጠርቼሃለሁ፣ አንተ የእኔ
ነህ። **2** በውኃ ውስጥ ባለፍህ ጊዜ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፣ በወንዞችም ውስጥ ባለፍህ ጊዜ አያሰጥሙህም፤ በእሳትም ውስጥ በሄድህ ጊዜ አትቃጠልም፥
ነበልባሉም አይፈጅህም። **3** እኔ የእስራኤል ቅዱስ አምላክህ እግዚአብሔር መድኃኒትህ ነኝ፤ ግብጽን ለአንተ ቤዛ አድርጌ፣ ኢትዮጵያንና ሳባንም ለአንተ ፋንታ
ሰጥቻለሁ። **4** በዓይኔ ፊት የከበርህና የተመሰገንህ ነህና፣ እኔም ወድጄሃለሁና ስለዚህ ሰዎችን ለአንተ አሕዛብንም ለነፍስህ እሰጣለሁ። **5** እኔ ከአንተ ጋር ነኝና፣
አትፍራ፤ ዘርህንም ከምሥራቅ አመጣዋለሁ፣ ከምዕራብም እሰበስብሃለሁ። **6** ሰሜንን፣ 'መልሰህ አምጣ፣' ደቡብንም፣ 'ማናቸውንም አትከልክል፤' ወንዶች
ልጆቼን ከሩቅ፣ ሴቶች ልጆቼንም ከምድር ዳርቻ፣ **7** በስሜ የተጠራውን ለክብሬም የፈጠርሁትን፣ የሠራሁትንና ያደረግሁትን ሁሉ አምጣ እለዋለሁ። **8** ዓይኖች
ያሉአቸውን ዕውሮችን ሕዝብ፣ ጆሮችም ያሉአቸውን ደንቆሮቹን አውጣ። **9** አሕዛብ ሁሉ በአንድነት ይሰብሰቡ፣ ወገኖችም ይከማቹ። ከመካከላቸው፤ ይህን
የሚናገር፣ የቀድሞዎቹንስ ክስተቶች የሚያሳየን ማን ነው? ይጸድቁ ዘንድ ምስክሮቻቸውን ያምጡ፣ ሰምተውም 'እውነት ነው' ይበሉ። **10** "ታውቁና ታምኑብኝ
ዘንድ፣ እኔም እንደሆንሁ ታስተውሉ ዘንድ፣ እናንተ የመረጥሁትም ባሪያዬ ምስክሮቼ ናችሁ" ይላል እግዚአብሔር። ከእኔ በፊት አምላክ አልተሠራም ከእኔም
በኋላ አይሆንም። **11** እኔ፣ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፣ ከእኔ ሌላም የሚያድን የለም። **12** ተናግሬአለሁ፣ አድኜማለሁ፣ አውጄማለሁ፥ በእናንተም ዘንድ ባዕድ አምላክ
አልነበረም። ስለዚህ እናንተ ምስክሮቼ ናችሁ፣" ይላል እግዚአብሔር። "እኔም አምላክ ነኝ።" **13** ከጥንት ጀምሮ እኔ ነኝ፣ ከእጄም የሚያመልጥ የለም፤
እሠራለሁ፣ የሚከለክልስ ማን ነው?" **14** የእስራኤል ቅዱስ፣ የሚቤዣችሁ፣ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ "ስለ እናንተ ወደ ባቢሎን ሰድጃለሁ፣
ከለዳውያንንም ሁሉ ስደተኞች አድርጌ በሚመኩባቸው መርከቦች አዋርዳቸዋለሁ። **15** ቅዱሳችሁ፣ የእስራኤል ፈጣሪ፣ ንጉሣችሁ፣ እግዚአብሔር እኔ ነኝ።" **16**
እግዚአብሔር የሚለው ይህንን ነው (በባሕር ውስጥ መንገድን በኃይለኛም ውኃ ውስጥ መተላለፊያን ያደርጋል፤ **17** እግዚአብሔር ሠረገላውንና ፈረሱን፣
ሠራዊቱንና አርበኛውን ያወጣል። እነርሱ ግን በአንድነት ተኝተዋል፤ መቼም አይነሡም፤ ቀርተዋል፣ እንደ ጥዋፍ ኩስታሪም ጠፍተዋል።) **18** "የፊተኛውን ነገር
አታስተውሉ፣ የጥንቱንም ነገር አታስቡ። **19** ተመልከቱ፣ አዲስ ነገርን አደርጋለሁ፤ እርሱም አሁን ይበቅላል፣ አታዩትምን? በምድረ በዳም መንገድን በበረሀም
ወንዞችን አደርጋለሁ። **20** የምድረ በዳ አራዊት፥ ቀበሮችና ሰጎኖች፥ ያከብሩኛል። **21** ምስጋናዬን እንዲናገሩ ለእኔ የፈጠርሁት ሕዝብ፣ የመረጥሁትን ሕዝቤን
አጠጣ ዘንድ በምድረ በዳ ውኃን በበረሀም ወንዞችን ሰጥቻለሁና። **22** ያዕቆብ ሆይ፣ አንተ ግን አልጠራኸኝም፣ አንተም እስራኤል ሆይ፣ በእኔ ዘንድ ደክመሃል።
23 ለሚቃጠል መሥዋዕት በጎችህን አላቀረብህልኝም፣ በሌላም መሥዋዕትህ አላከበርኸኝም፤ በእህልም ቍርባን አላስቸገርሁህም፣ በዕጣንም
አላደከምሁህም። **24** ጣፋጭ መዐዛ ያለው ዕጣን በገንዘብ አልገዛህልኝም፣ በመሥዋዕትህም ስብ አላጠገብኸኝም፤ ነገር ግን በኃጢአትህ አስቸገርኸኝ፣
በበደልህም አደከምኸኝ። **25** አዎን፣ መተላለፍህን፣ ስለ እኔ ስል የምደመስስ እኔ ነኝ፤ ኃጢአትህንም ከእንግዲህ አላስብም። **26** የተከሰተውን አሳስበኝ።
በአንድነትም ሆነን እንከራከር፤ ስለ ንጹህነትህ እንድትጸድቅ ነገርህን ተናገር። **27** የመጀመሪያው አባትህ ኃጢአት ሠርቶአል፣ መምህሮችህም በድለውኛል። **28**
ስለዚህ የመቅደሱን ቅዱሳን አለቆች አረከስሁ፣ ያዕቆብንም እርግማን፣ እስራኤልንም ስድብ አደረግሁ።"

Isaiah 43:1

ያዕቆብ ሆይ የፈጠረህ እስራኤል ሆይ የሠራህ
ሁለቱም አነጋገሮች ተመሳሳይ ናቸው፤ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የእስራኤል ሕዝብ ሆይ፣ የፈጠራችሁ››

Isaiah 43:2

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል።

በውሃ ውስጥ ስታልፍ አያሰጥምህም... በእሳት ውስጥ ስትሄድ አያቃጥልህም።
ሰዎች ላይ የሚደርስ መከራና ችግር የሚያልፉበት ጥልቅ ውሃና እሳት እንደሆነ ያህዌ ይናገራል። ‹‹ውሃ›› እና፣ ‹‹እሳት›› ምሳሌያዊ ሲሆኑ ማንኛውንም አስቸጋሪ ሁኔታ ያመለክታሉ።

በውሃ ውስጥ በምታልፍበት ጊዜ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፤ ወንዙን ስትሻገረው አያሰጥምህም።
እነዚህ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው፤ ያህዌ ከእነርሱ ጋር ከሆነ ምንም ጉዳት እንደማይደርስባቸው አጽንዖት ይሰጣሉ።

አያቃጥልህም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በፍጹም አይፈጅህም››

ግብፅ ለአንተ ቤዛ እንድትሆን፣ ኩሽና ሳባንም በአንተ ፈንታ ሰጥቻለሁ።
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጒም አላቸው፤ እስራኤልን ሳይሆን የእስራኤል ጠላቶች እነዚህን መንግሥታት ድል እንዲያደርጉ ያህዌ እንደ ፈቀደ አጽንዖት ይሰጣል።

ሳባ
ይህ የአገር ስም ነው።

Isaiah 43:4

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል።

በዐይኔ ፊት ብርቅና ክቡር ስለሆንህ
‹‹ብርቅ›› እና፣ ‹‹ክቡር›› የተሰኙት ቃሎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ሲሆኑ፣ ያህዌ ሕዝቡን ምን ያህል እንደሚወድ አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በእኔ ዘንድ በጣም የተወደድህ ስለሆነ››

ስለዚህ ሰዎችን በአንተ ምትክ፣ ሕዝቦችንም በሕይወትህ ፈንታ እሰጣለሁ
ሁለቱም ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጒም አላቸው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ስለዚህ በአንተ ፈንታ ጠላት ሌሎች መንግሥታትን ድል እንዲያደርግ አደርጋለሁ››

ልጆችህን ከምሥራቅ አመጣለሁ፤ አንተንም ከምዕራብ እሰበስባለሁ
‹‹ምሥራቅ›› እና ‹‹ምዕራብ›› የተሰኙት አቅጣጫዎች ከሁሉም ቦታ ማለት ናቸው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አንተንና ልጆችህን ከሁሉም ቦታ አመጣለሁ››

Isaiah 43:6

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለሕዝቡ መናገር ቀጥሏል።

ለሰሜን... በል፤ ለደቡብ... በል
በእነዚህ ቦታዎች ያሉትን ሕዝቦች እያዘዘ ያለ ይመስል ያህዌ ለ‹‹ሰሜን›› እና፣ ለ‹‹ደቡብ›› ይናገራል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወንዶች ልጆቼ... ሴቶች ልጆቼ
የእርሱ የሆኑት የእርሱ ልጆች እንደሆኑ ያህዌ ይናገራል።

በስሜ የተጠራው ሁሉ
በአንድ ሰው ስም መጠራት የዚያ ሰው መሆንን ያመለክታል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በስሜ የተጠራ ማንኛውም ሰው›› ወይም፣ ‹‹የእኔ የሆነ ሁሉ››

የሠራሁት፣ አዎን ያበጀሁት
ሁለቱም ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው፤ የእስራኤልን ሕዝብ የሠራ እግዚአብሔር መሆኑን አጽንዖት ይሰጣሉ።

Isaiah 43:8

ዕውር... ደንቆሮ የሆነ ሕዝብ
እርሱን የማይሰሙ ወይም የማይታዘዙ ዕውርና ደንቆሮ እንደሆኑ ያህዌ ይናገራል።

ከእነርሱ አስቀድሞ ይህን የነገረን፣ የቀድሞን ነገር ያወጀልን ማን ነው?
ይህ ጥያቄ ሰዎች የሚያመልኳቸውን አማልክት ይመለከታል። መልሱ ማንም ይህን ማድረግ አይችልም የሚል ነው። ጥያቄውን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከአማልክቶቻቸው አንዱ እንኳ ይህን መናገርና የቀድሞን ነገር ማወጅ አይችልም››

የቀድሞን ነገር ያወጀልን
ይህ ሐረግ የሚያመለክተው ነገሮች ከመሆናቸው በፊት ለሰዎች የመነገርን ችሎታ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የቀደሙት ነገሮች ከመሆናቸው በፊት አወጀልን››

ትክክለኛነታቸው እንዲረጋገጥ ምስክሮቻቸውን ያቅርቡ፤ ሰምተውም ያረጋግጡላቸው ‹እውነት ነው›
ምንም እንኳ ያንን ማድረግ እንደማይችሉ ቢያውቅም፣ አሕዛብ የሚያመልኳቸው አማልክት እነዚህን ነገሮች ማድረግ እንደሚችሉ የሚያረጋግጡ ምስክሮች እንዲያቀርቡ ያህዌ ይጠይቃል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነዚህ አማልክት ትክክል መሆናቸውን የሚመሰክሩ ምስክሮች አድምጠውም፣ ‹እውነት ነው› የሚሉ ምስክሮች የሏቸውም››

Isaiah 43:10

እናንተ... የእኔ አገልጋይ
‹‹እናንተ›› ብዙ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። ‹‹የእኔ አገልጋይ›› ጠቅላላ መንግሥቱን ያመለክታል።

ከእኔ በፊት... ከእኔ በኋላ
በዚህ መልኩ መናገሩ ከእርሱ በፊት የነበረና ከእርሱ በኋላም እንደሚኖር ያህዌ እየተናገረ አይደለም። እርሱ ዘላለማዊ ሲሆን፣ ሕዝቡ የሚያመልኳቸው አማልክት ግን አለመሆናቸውን እያረጋገጠ ነው።

ከእኔ በፊት አምላክ አልተሠራም
እዚህ ላይ፣ ‹‹አልተሠራም›› ሲል ያህዌ ሕዝቡ ስለሠሩዋቸው ጣዖቶች እየተናገረ ነው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አሕዛብ ካሠሩዋቸው ጣዖቶች አንዱ እንኳ ከእኔ በፊት አልተሠሩም››

ከእኔም በኋላ አይኖርም
‹‹ከእነዚህ አማልክት አንዱም ከእኔ በኋላ አይኖርም››

እኔ፣ እኔ ያህዌ ነኝ
‹‹እኔ›› የሚለው ቃል የተደገመው አጽንዖቱ ያህዌ ላይ እንዲያተኩር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ ብቻ ያህዌ ነኝ›› ወይም፣ ‹‹እኔ ራሴ ያህዌ ነኝ››

ከእኔ ሌላ አዳኝ የለም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አዳኝ እኔ ብቻ ነኝ›› ወይም፣ ‹‹እናንተን ማዳን የምችል እኔ ብቻ ነኝ››

Isaiah 43:12

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

ከእጄም ማዳን የሚችል የለም
‹‹እጅ›› የሚለው የያህዌን ኀይል ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ማንም ከእኔ ኀይል ማዳን አይችልም።››

ማን ማጠፍ ይችላል?
ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው ማንም እጁን ማጠፋ እንደማይችል ለመናገር ነው። በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። እጁን ማጠፍ አንድ ነገር እንዳያደረግ እርሱን ማገድን ይወክላል። ኢሳይያስ 14፥27 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ማንም ሊያጥፈው አይችልም›› ወይም፣ ‹‹ማንም አያስቆመኝም››

Isaiah 43:14

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

የእስራኤል ቅዱስ
ኢሳይያስ 1፥4 ላይ ይህን ሐረግ እንዴ እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

ባቢሎን ላይ እሰድዳለሁ፤ ሁሉንም እመራለሁ
ትርጉሙ ውስጥ፣ ‹‹እሰዳለሁ›› የሚለው ማንን እንደሆነ ማመልከት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ባቢሎን ላይ ሰራዊት እሰድዳለሁ››

እንደ ኮብላይ ሁሉንም እመራለሁ
‹‹ባቢሎናውያንን ሁሉ ኮብላይ ይሆናሉ››

ኮብላይ
ኮብላይ ጠላት እንዳይዘው የሚሸሽ ሰው ነው።

Isaiah 43:16

መንገድ የከፈተ... እንደ ጧፍ ኩስታሪ
በእነዚህ ጥቅሶች ኢሳይያስ እስራኤላውያን በደረቅ ምድር እንዲሻገሩ፣ ግብፃውያን ግን እንዲሰጥሙ ያህዌ ባሕሩን የከፈተበትን ከግብፅ መውጣት በኋላ የነበረውን ሁኔታ እያመለከተ ነው። የዐረፍተ ነገሩን ትርጉም የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል።

በአንድነት ወደቁ፤ ከእንግዲህ አይነሡም
መሞት መሬት ከመውደቅ ጋር ተመሳስሎአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሁሉም በአንድነት ሞቱ፤ ከእንግዲህ በሕይወት አይኖሩም››

ጠፉ፤ እንደ ጧፍ ኩስታሪ ረገፉ
የሕዝቡ መሞት ከሚጠፋ ጧፍ ጋር ተመሳስሎአል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰው የሚነድደውን ሻማ እንደሚያጠፋ ሕይወታቸው አብቅቷል››

Isaiah 43:18

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የቀደመውን ነገር አታስቡ፤ ያለፈውንም አታስታውሱ
እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው፤ ባለፈው ጊዜ ስለሆነው መጨነቅ እንደሌለባቸው አጽንዖት ይሰጣሉ።

እነሆ
ቃሉ ጥቅም ላይ የዋለው ለሚከተለው ጠቃሚ መረጃ ትኩረት ለመሳብ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አድምጡ›› ወይም፣ ‹‹ልብ በሉ››

አታስተውሉትምን?
ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው የእስራኤልን ሕዝብ ለማስተማር ነው። ጥያቄውን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በእርግጥ አስተውላችሁታል››

Isaiah 43:20

የዱር አራዊት፣ ቀበሮና ሰጐን ያከብሩኛል
እንደ ሰዎች ሁሉ እንስሳትም ያህዌን ያከብሩታል።

ቀበሮዎችና ሰጐኖች
እነዚህ ያህዌን የሚያከብሩ እንስሳት ምሳሌዎች ናቸው። ኢሳይያስ 13፥21-22 ላይ የእነዚህን እንስሳት ስም እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። ትርጕሙን ግልጽ ለማድረግ ውስጠ ታዋቂ የሆነውን መረጃ ማቅረብ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ቀበሮዎችና ሰጐኖች ያከብሩኛል››

Isaiah 43:22

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

Isaiah 43:24

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

መልካም መዐዛ ያለው ነገር
ይህ የቅባት ዘይት ለመሥራት ጥቅም ላይ የሚውል ጣፋጭ ሽታ ያለው ተክል ነው። በእስራኤል ምድር ስለማይበቅል ከሌሎች አገሮች ይገዙት ነበር።

የኀጢአት ሸክም ጫናችሁብኝ፤ በክፉ ሥራህ አደከምኸኝ
እነዚህ ሁለቱም ተመሳሳይ ናቸው፤ ያህዌ በሕዝቡ ማዘኑን አጽንዖት ይሰጣሉ።

የኀጢአት ሸክም ጫናችሁብኝ
‹‹በኀጢአታችሁ አስቸገራችሁኝ››

Isaiah 43:25

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

እኔ፣ እኔው ነኝ
‹‹እኔ›› የሚለው ቃል የተደገመው አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እኔ ብቻ ነኝ››

በደልህን የምደመስስ
ኀጢአትን ይቅር ማለት፣ 1) መደምሰስና መጥረግ እንደሆነ፣ ወይም 2) የተጻፈውን ኀጢአት መሰረዝ እንደሆነ ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አንዳች ነገር እንደሚደመስስ ሰው ኀጢአትህን ይቅር የምል›› ወይም፣ ‹‹የተጻፈውን ኀጢአት እንደሚሰርዝ ሰው ኀጢአትህን ይቅር የምል››

ስለ ራሴ ስል
‹‹ስለ ክብሬ›› ወይም፣ ‹‹ስለ ማንነቴ››

አላስብም
‹‹አላስታውስም››

ንጹሕ መሆንህን አስረዳ
ምንም እንኳ ያንን ማድረግ እንደማይችሉ ቢያውቅም፣ እነርሱ ላይ ከቀረበው ክስ ነጻ መሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ያህዌ ሕዝቡን ይጠይቃል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ንጹሕ መሆናችሁን ማረጋገጥ ከቻላችሁ ማስረጃ አቅርቡ››

ንጹሕ እንድትሆኑ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ንጹሕ መሆናችሁን ማስረዳት እንድትችሉ››

Isaiah 43:27

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል። የመጀመሪያው አባትህ ኀጢአት ሠርቷል ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን መሥራች ሲሆን፣ አብርሃምን ወይም ይስሐቅን ነው።

ያዕቆብን ለጥፋት አሳልፌ እሰጣለሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹አሳልፌ›› የሚለው በሌላው ኀይል ሥር ያለ ሰውን ነው። ‹‹ጥፋት›› የሚለውን በሌላ ቃል መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጠላት ያዕቆብን ጨርሶ እንዲደመሰስ አደርጋለሁ››

እስራኤልን ለስድብና ለውርደት
ግሡን የዚህ ሐረግ ተጓዳኝ ከሆነው ቀደም ሲል ከነበረ ሐረግ ጋር ማያያዝ ይቻላል። ‹‹ውርደት›› የሚለውን በሌላ ቃል መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጠላት እስራኤልን እንዲሰድብና እንዲያዋርድ አደርጋለሁ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 44

1 አሁንም ባሪያዬ ያዕቆብ፣ የመረጥሁህም እስራኤል ሆይ፣ ስማ። 2 የፈጠረህ፣ ከማኅፀንም የሠራህ፣ የሚረዳህም እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "ባሪያዬ
ያዕቆብ የመረጥሁህም ይሹሩን ሆይ፣ አትፍራ። 3 በተጠማ ላይ ውኃን፣ በደረቅም መሬት ላይ ፈሳሾችን አፈስሳለሁና፤ መንፈሴን በዘርህ ላይ፣ በረከቴንም
በልጆችህ ላይ አፈስሳለሁ፥ 4 በፈሳሾችም አጠገብ እንደሚበቅሉ እንደ አኻያ ዛፎች በሣር መካከል ይበቅላሉ። 5 ይህ፣ 'እኔ የእግዚአብሔር ነኝ' ይላል፤
ሌላኛውም በያዕቆብ ስም ይጠራል፤ ይህም፣ 'እኔ የእግዚአብሔር ነኝ' ብሎ በእጁ ይጽፋል፣ በእስራኤልም ስም ይጠራል።" 6 የእስራኤል ንጉሥ እግዚአብሔር
የሚለው እንዲህ ነው - የሚቤዥም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "እኔ ፊተኛ ነኝ፣ እኔም ኋለኛ ነኝ፣ ከእኔ ሌላም አምላክ የለም። 7 እንደ እኔ ያለ
ማን ነው? ይነሣና ይጥራ ይናገርም፤ ከጥንት የፈጠርሁትን ሕዝብ ያዘጋጅልኝ፣ የሚመጣውም ነገር ሳይደርስ ይንገሩኝ። 8 አትፍሩ አትደንግጡም። ከጥንቱ
ጀምሬ አልነገርኋችሁምን? ወይስ አላሳየኋችሁምን? እናንተ ምስክሮቼ ናችሁ፦ ከእኔ ሌላ አምላክ አለን? ሌላ ዐለት የለም፤ ማንንም አላውቅም።" 9 የተቀረጸውን
ምስል የሚሠሩ ሁሉ ከንቱዎች ናቸው፤ የወደዱትም ነገር አይረባቸውም፤ ምስክሮቻቸውም አያዩምና አያውቁም፤ ስለዚህ እንዲያፍሩ ይደረጋሉ። 10 አምላክን
የሠራ ወይስ ለምንም የማይረባ ምስልን የቀረጸ ማን ነው? 11 ተመልከቱ፣ ባልንጀሮቹ ሁሉ ያፍራሉ፤ ሠራተኞቹም ከሰዎች ወገን ብቻ ናቸው። ሁላቸው
ተሰብስበው ይቁሙ፤ ይፈራሉ በአንድነትም ያፍራሉ። 12 ብረት ሠሪ መጥረቢያውን ይሠራል፣ በፍምም ውስጥ ያደርገዋል፣ በመዶሻም መትቶ ቅርጽ
ይሰጠዋል። በክንዱም ኃይል ይሠራዋል፣ እርሱም ይራባል፣ ይደክምማል፣ ውኃም አይጠጣም ይታክትማል። 13 አናጢውም ገመድ ዘርግቶ በበረቅ ይለካዋል፣
በመቅረጫም ይቀርጸዋል። በመለኪያም ይለካዋል። በቤትም ውስጥ ይቀመጥ ዘንድ በሰው አምሳልና በሚስብ የሰው ውበት ያስመስለዋል። 14 የዝግባን
ዛፎች ይቈርጣል፣ የዞጲንና የኮምቦልን ዛፍ ይመርጣል። ከዱር ዛፎችም መካከል ይጠነክር ዘንድ ይተወዋል፤ የጥድንም ዛፍ ይተክላል ዝናብም ያበቅለዋል። 15
ለሰውም ማገዶ ይሆናል፤ ከእርሱም ወስዶ ይሞቃል፣ አዎን፣ አንድዶ እንጀራ ይጋገርበታል። ከእርሱም አምላክ አበጅቶ ይሰግድለታል፣ የተቀረጸውንም ምስል ሠርቶ
በእርሱ ፊት ይንበረከካል። 16 ግማሹን በእሳት ያቃጥላል፣ በዚያ በግማሹ ሥጋ ይበላል። ሥጋም ይጠብስበትና ይጠግባል። ራሱን ያሞቅና፣ "እሰይ ሞቅሁ፣
እሳቱን አይቻለሁ" ይላል። 17 የቀረውንም እንጨት አምላክ አድርጎ ምስል ይቀርጽበታል፤ በፊቱም ተጐንብሶ ይሰግዳል ወደ እርሱም እየጸለየ፣ "አምላኬ ነህና፣
አድነኝ" ይላል። 18 አያውቁም፣ አያስቡም፣ እንዳያዩ ዓይኖቻቸውን፣ እንዳያስተውሉ ልቦቻቸውን ታውረዋል። 19 በልቡም ማንም አያስብም፣ "ግማሽዋን በእሳት
አቃጥያለሁ፣ በፍምዋም ላይ እንጀራን ጋግሬአለሁ፣ ሥጋም ጠብሼ በልቻለሁ። የቀረውንም አስጸያፊ ነገር አደርጋለሁን? ለዛፍስ ግንድ እሰግዳለሁን? እንዲልም
እውቀትና ማስተዋል የለውም።" 20 አመድ ይበላል፤ የተታለለ ልብ አስቶታል። ነፍሱን ለማዳን አይችልም፣ ወይም፣ በቀኝ እጄ ሐሰት አለ" አይልም። 21 ስለ
እነዚህ ነገሮች አስብ፣ ያዕቆብ ሆይ፣ አንተም እስራኤል፣ ባሪያዬ ነህና ይህን አስብ፤ እኔ ሠርቼሃለሁ፤ አንተም ባሪያዬ ነህ፤ እስራኤል ሆይ፣ በእኔ ዘንድ ያልተረሳ
ትሆናለህ። 22 መተላለፍህን እንደ ደመና፣ ኃጢአትህንም እንደ ጭጋግ ደምስሼአለሁ፤ ተቤዥቼሃለሁና ወደ እኔ ተመለስ። 23 ሰማያት ሆይ፣ እግዚአብሔር
አድርጎታልና ዘምሩ፤ እግዚአብሔር ያዕቆብን ተቤዥቶአልና፣ በእስራኤልም ዘንድ ይከበራልና አንተ የምድር ጥልቅ ሆይ፣ ጩኽ፤ እናንተም ተራሮች፣ አንተም ዱር
በአንተም ያለ ዛፍ ሁሉ፣ እልል በሉ። 24 ከማኅፀን የሠራህ፣ የሚቤዥህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "ሁሉን የፈጠርሁ፣ ሰማያትን ለብቻዬ የዘረጋሁ ምድርንም
ያጸናሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ፤ ከእኔ ጋር ማን ነበረ? 25 የሐሰተኞችን ምልክት ከንቱ አደርጋለሁ፣ ምዋርተኞችንም አሳብዳለሁ፣ ጥበበኞቹንም ወደ ኋላ
እመልሳለሁ፣ እውቀታቸውንም ስንፍና አደርጋለሁ፤ 26 እኔ፣ እግዚአብሔር! የባሪያዬን ቃል አጸናለሁ፣ የመልእክተኞቼንም ምክር እፈጽማለሁ፤ ኢየሩሳሌምን፣
'የሰው መኖሪያ ትሆኛለሽ፣' የይሁዳንም ከተሞች፣ 'ድጋሚ ትታነጻላችሁ፣ ፍራሾቻችሁንም አቆማለሁ' እላለሁ፤ 27 ቀላዩንም፣ 'ደረቅ ሁን፣ ፈሳሾችህንም
አደርቃለሁ' እላለሁ፤ 28 ቂሮስንም፣ 'እርሱ እረኛዬ ነው፤ እርሱም ኢየሩሳሌምን፣ - 'ትታነጺያለሽ፣ ቤተ መቅደስም ይመሠረታል' ብሎ ፈቃዴን ሁሉ ይፈጽማል"
እላለሁ።

Isaiah 44:1

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል

ባርያዬ ያዕቆብ
ይህ የሚያመለክተው የያዕቆብን ዘሮች ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ባርያዎቼ የያዕቆብ ዘሮች››

በማሕፀን የሠራህና ያበጀህ
የእስራኤልን ሕዝብ መፍጠሩ በእናት ማሕፀን እንዳለ ሕፃን መሥራትና ማበጀት ማለት እንደሆነ ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕፃን ልጁን ማሕፀን ውስጥ እንደሚያበጅ አንተን የሠራህ››

የመረጥሁህ ይሹሩን ሆይ
ግሡ ያለፈውን ሐረግ የሚመለከት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ የመረጥሁህ ይሹሩን ሆይ፣ አትፍራ››

ይሹሩን
ይህም የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው።

Isaiah 44:3

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል

በተጠማ ምድር ላይ ውሃ፣ በደረቅ መሬት ላይ ምንጮች አፈስሳለሁ
ለእስራኤል ሕዝብ መንፈሱን መስጠቱ በተጠማ ምድር ላይ ዝናብ ማዝነብና በደረቅ መሬት ላይ ምንጮች ማፍሰስ እንደ ሆነ ያህዌ ይናገራል።

የተጠማ ምድር
ደረቅ መሬት የተጠማ ሰው ማለት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ደረቅ መሬት››

መንፈሴን በዘርህ ላይ አፈስሳለሁ
መንፈሱን ለሕዝቡ መስጠቱ መንፈሱ እነርሱ ላይ የሚፈስስ ፈሳሽ ነገር መሆኑን ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መንፈሴን ለዘርህ እሰጣለሁ››

በረከቴንም በልጆችህ ላይ
ግሡ ባለፈው ሐረግ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በረከቴን በልጆችህ ላይ አፈስሳለሁ›› ወይም ‹‹በረከቴን ለልጆችህ እሰጣለሁ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በለመለመ መስክ ላይ እንደ ሣር፣ በምንጭ ዳር እንደ አኻያ ይበቅላሉ
የእስራኤል ሕዝብ መበልጸግና መብዛት ብዙ ውሃ በማግኘቱ እንዳደገ ተክል መሆናቸው ተነግሯል።

አኻያ
አኻያ ቀጫጭን ቅርንጫፎች ያሉት ውሃ አጠገብ የሚያድግ ዛፍ ነው።

Isaiah 44:5

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል።

ሌላው ራሱን በያዕቆብ ስም ይጠራል
‹‹ሌላው ሰው የያዕቆብ ዘር መሆኑን ይናገራል››

ራሱን በእስራኤል ስም ይጠራል
‹‹ራሱን የእስራኤል ዘር በማለት ይጠራል››

Isaiah 44:6

የእርሱ ቤዛ
‹‹የእስራኤል ቤዛ››

የሰራዊት ጌታ ያህዌ
ኢሳይያስ 1፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት

እኔ የመጀመሪያው ነኝ፤ እኔ የመጨረሻው ነኝ
ይህ ሐረግ ለያህዌ ዘላለማዊ ባሕርይ አጽንዖት ይሰጣል። እንዲህ ማለት፣ 1) ‹‹ነገሮችን ሁሉ የጀመርሁ እኔ ነኝ፤ ነገሮችን ሁሉ የምጨረስ እኔ ነኝ›› ማለት ሊሆን ይችላል ወይም 2) ‹‹እኔ ሁሌም የነበርሁ፤ እኔ ሁሌም የምኖር ነኝ›› ማለት ሊሆን ይችላል።

Isaiah 44:7

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል

እንደ እኔ ማን ነው? ይናገር
ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው እንደ እርሱ ማንም እንደሌለ አጽንዖት ለመስጠት ነው። ጥያቄውን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እንደ እኔ እንደሆነ የሚያስብ ካለ ይናገር››

Isaiah 44:8

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

አትፍራ አትደንግጥ
የእርሱን ማበረታቻ ለማጠናከር ያህዌ በሁለት ተመሳሳይ ገለጻዎች ይጠቀማል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አትፍራ››

አልነገርኃችሁምን፤ ቀድሞንስ አላስታወቅኃችሁምን?
ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው አሁን የሆነውን አስቀድሞ መናገር የሚችል እርሱ መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። ‹‹ማስታወቅ›› የሚለው ቃል፣ ‹‹መናገር›› ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከረጅም ጊዜ በፊት ነገርኃችሁ››

ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ አለን?
ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው ከእርሱ በቀር አምላክ እንደሌለ አጽንዖት ለመስጠት ነው። ጥያቄውን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከእኔ በቀር አምላክ የለም››

ሌላ ዐለት የለም
ያህዌ እርሱ ሰዎች የሚጠለሉበት ትልቅ ዐለት እንደሆነ ይናገራል። ይህም ማለት ሕዝቡን ለመጠበቅ ኀይል አለው ማለት ነው።

Isaiah 44:9

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ እየተናገረ ነው።

የሚደሰቱባቸው ነገሮች ከንቱ ናቸው
‹‹ደስ የሚሰኙባቸው ጣዖቶች ከንቱ ናቸው››

ምስክሮቻቸው አያዩም ወይም አያውቁም
ይህ ሐረግ የሚያመለክተው ስለ ጣዖቶቹ ኀይል ምስክር እንደሆኑ የሚናገሩ እነዚህን ጣዖቶች የሚያመልኩ ሰዎችን ነው። እውነቱን መረዳት አለመቻላቸውን ያህዌ ዕውራን ናቸው ብሏል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለእነዚህ ጣዖቶች ምስክር በመሆን የሚያገለግሉ ምንም እንደማያውቁ ዕውሮች ናቸው››

ያፍራሉ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ይዋረዳሉ›› ወይም፣ ‹‹ጣዖቶቻቸው ያሳፍሩዋቸዋል››

አምላክን የሚያበጅ ወይም ጥቅም የሌለውን ጣዖት የሚቀርጽ ማን ነው?
ያህዌ ይህን ጥያቄ ያቀረበው ጣዖት የሚሠሩትን ለመገሠጽ ነው። ጥያቄውን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አምላክ የሚሠራ ጥቅም የሌለውን ጣዖት የሚቀርጽ ሞኝ ብቻ ነው››

ጥቅም የሌለውን ጣዖት የሚቀርጽ
‹‹ጥቅም የሌለው›› የሚለው ቃል ጥቅም ካለው ጣዖት ጋር ለማነጻጸር የተነገረ አይደለም፤ ምክንያቱም ጣዖቶች ሁሉ ከንቱ ናቸው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጥቅም የለሽ ጣዖት የሚቀርጽ››

Isaiah 44:11

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል

ተባባሪቹ ሁሉ
ይህም ማለት፤ 1) ጣዖት ከሚሠራው ጋር የሚተባበሩ ማለት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የጣዖት ሠሪው ተባባሪዎች ሁሉ›› ወይም 2) ጣዖቱን በማምለክ ከእርሱ ጋር የሚተባበሩትን ማለት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጣዖት የሚያመልኩ ሁሉ››

ያፍራሉ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ይዋረዳሉ››

በአንድ ላይ ይቁሙ
‹‹ሁሉም መጥተው ፊቴ ይቅረቡ››

ይደነግጣሉ
‹‹ይሸበራሉ›› ቃሉ በፍርሃት መጉበጥ ማለት ነው።

Isaiah 44:12

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል።

ያበጀው
‹‹ጣዖቱን ያበጀው›› ወይም፣ ‹‹ጣዖቱን የፈጠረው››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Isaiah 44:13

በገመድ የለካው
በእንጨት የሚሠራውን ጣዖት ቅርጽ ለማስያዝ በገመድ ይለካ ነበር

ድርካል
ይህ የሚሠራው ሰው የት ላይ መቁረጥ እንዳለበት ለማመልከት እንጨቱ ላይ ጭረት የሚደረግበት ሹል መሣሪያ ነው።

ንድፍ ማውጫ
ይህ ሁለት ጫፎች ያሉት መሣሪያ ሲሆን፣ ጣዖቱን ቅርጽ ለማስያዝ ጥቅም ላይ ይውላል።

Isaiah 44:14

ይቆርጠዋል
‹‹አናጢው ይቆርጠዋል›› ወይም፣ ‹‹ባለ ሙያው ይቆርጠዋል››

የቆፕሮስ ዛፍ
ሁሌ ለምልሞ የሚገኝ ዛፍ

Isaiah 44:15

ከዚያም ሰው ይጠቀምበታል
‹‹ሰውየው በእንጨቱ ይጠቀማል››

ጣዖት ሠርቶ ወድቆ ይሰግድለታል
ይህ የዐረፍተ ነገሩ አካል ከመጀመሪያው ጋር በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ሲሆን፣ አጽንዖት ይሰጣል።

Isaiah 44:18

ዐይኖቻቸው ስለ ታወሩ አያዩም
ጣዖትን የማምለክን ከንቱነት መረዳት ያቃታቸው ሰዎች ዕውሮች እንደሆኑ ያህዌ ይናገራል።

ዐይኖቻቸው አያዩም
እዚህ ላይ ‹‹ዐይኖቻቸው›› ሁለንተናቸው ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ታውረዋልና››

ልባቸው ማስተዋል አይችልም
እዚህ ላይ ሰዎች፣ ‹‹በልቦቻቸው›› ተወክለዋል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹መረዳት አይችልም››

Isaiah 44:19

በቀረው እንዴት ጸያፍ ነገር እሠራለሁ? ... ለግንድ መስገድ ይገባኛልን?
እነዚህ ሰዎች እነዚህን ጥያቄዎች መጠየቅ እንዳለባቸው ያህዌ ይናገራል። መልሱ አሉታዊ ሲሆን፣ እነዚህን ነገሮች ማድረግ ምን ያህል ሞኝነት እንደሆነ አጽንዖት ይሰጣል። ጥያቄዎቹን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ለማምለክ የሚያስጸይፈውን ይህን አላደርግም... ለግንድ እንጨት ወድቄ አልሰግድም››

Isaiah 44:20

ዐመድ እንደሚበላ ነው
ጣዖት የሚያመልክ ሰው ጣዖቱን ከሠራበት እንጨት የተረፈው ተቃጥሎ ሲነድ ዐመዱን እንደሚበላ ሰው እንደሆነ ያህዌ ይናገራል። ዐመድ መብላት እንደማይጠቅም ሁሉ፣ ጣዖት ማምለክም አይጠቅምም።

የተታለለ ልቡ አስሳቶታል
ልብ ውስጣዊ ሁኔታን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በመታለሉ ራሱን አስቶአል››

ራሱን ማዳን አይችልም
‹‹ጣዖት የሚያመልክ ራሱን አያድንም››

Isaiah 44:21

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል።

ያዕቆብና እስራኤል
ይህ ከያዕቆብና ከእስራኤል የተገኘውን ሕዝብ ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እናንተ የእስራኤል ዘሮች››

እኔ አልረሳችሁም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እኔ አልረሳችሁም››

ዐመፃህን እንደ ድቅድቅ ደመና፣ ኀጢአትህንም እንደ ጭጋግ አስወግጃለሁ
ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። ነፋስ ደመናን በቀላሉና በፍጥነት እንደሚያስወግደው እግዚአብሔር ኀጢአታቸውን ይቀር ብሏል።

ኀጢአትህን እንደ ጭጋግ
ግሡ ባለፈው ሐረግ ተገልጿል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንደ ጭጋግ ኀጢአትህን አስወግጃለሁ››

Isaiah 44:23

ሰማያት ሆይ ዘምሩ... ክብር በእስራኤል
እዚህ ላይ ኢሳይያስ ያህዌን እንዲያመሰግኑ የሚያዝዛቸው ሰዎች የሆኑ ይመስል ለተለያዩ የፍጥረት ክፍሎች ይናገራል።

የምድር ጥልቆች ሆይ
‹‹ዝቅ ያላችሁ የምድር ክፍሎች›› ይህም ማለት፣ 1) ባለፈው ሐረግ ከተጠቀሱ፣ ‹‹ሰማያት›› ጋር በንጽጽር የሚቀርቡ ዋሻዎችን፣ ወይም ጉድጓዶችን ለመሳሰሉ ዝቅ ያሉ የመሬት ክፍሎችን ያመለክት ይሆናል። ወይም 2) የሞቱ ሰዎችን የሚያመለክት ሊሆን ይቸላል።

Isaiah 44:24

የተቤዠህ
ኢሳይያስ 41፥14 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት

ከማሕፀን የሠራህ
በእናቱ ማሕፀን ያለ ሕፃንን በሠራበት ሁኔታ ያህዌ የእስራኤልን ሕዝብ መፍጠሩን ይናገራል። ኢሳይያስ 44፥2 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ማሕፀን ውስጥ ሕፃን እንደምሠራ የፈጠረህህ››

ብቻውን ሰማያትን የዘረጋ
ሰማያትን መፍጠሩ እንደሚዘረጋ ነገር የሆኑ ይመስል ያህዌ ይናገራል። ኢሳይያስ 42፥5 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

ምልክቶች
እነዚህ የወደ ፊቱን ለማወቅ በመሞከር ሰዎች የሚጠቀሙባቸው ምልክቶች ናቸው።

ከንቱ ተናጋሪዎች
ይህ ትርጉም የለሽ ነገሮችን የሚናገሩ ሰዎችን ያመለክታል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Isaiah 44:26

የባርያውን ቃል ያጸና፣ የመልእክቶቹን ትንቢት የፈጸመ
ትንቢቶች እንዲፈጸሙ ማድረግ የሚችል እርሱ ብቻ መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት ያህዌ አንድን ነገር ደጋግሞ ይናገራል።

የባርያው ቃል... የመልእክተኞቹ ትንቢት ‹‹ቃል› እና፣ ‹‹ትንቢት›› የሚሉትን ቃሎች በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ
ትርጒም፣ ‹‹ባርያው የተናገረውን... መልእክተኞቹ ያወጁትን››

መኖሪያ ትሆናለች
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በዚያ ሰዎች እንደ ገና ይኖራሉ››

እንደ ገና ይሠራሉ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰዎች እንደ ገና ይሠሯቸዋል››

ፍርስራሻቸውን አነሣለሁ
‹‹ፍርስራሽ›› የሚለው ሐረግ የፈረሰ ቦታ ያመለክታል። እርሱ የሚያነሳቸው ይመስል ያህዌ እንደ ገና እንደሚሠሩ ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሌሎች ያወደሙትን እንደ ገና እሠራለሁ››

Isaiah 44:28

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል።

እርሱ እረኛዬ ነው
ቂሮስ እረኛቸው የሆነ ይመስል የእስራኤልን ሕዝብ እየገዛና እየጠበቀ ስላለው ቂሮስ ያህዌ ይናገራል።

እንደ ገና ትሠራለች
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሕዝቡ ከተማዋን ይሥሩ››

መሠረቷ ይጣል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰዎች መሠረቷን ይጣሉ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 45

1 እግዚአብሔር ለቀባሁት፣ አሕዛብንም በፊቱ አስገዛ ዘንድ የነገሥታትንም ወገብ እፈታ ዘንድ፣ በሮቹም እንዳይዘጉ መዝጊያዎቹን በፊቱ እከፍት ዘንድ፣ ቀኝ እጁን ለያዝሁት ለቂሮስ እንዲህ ይላል፦ **2** "በፊትህ እሄዳለሁ ተራሮችንም ትክክል አደርጋለሁ፤ የናሱንም ደጆች እሰብራለሁ የብረቱንም መወርወሪያዎች እቈርጣለሁ፤ **3** በስምህም የምጠራህ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እኔ እንደ ሆንሁ ታውቅ ዘንድ፣ በጨለማ የነበረችውን መዝገብ በስውርም የተደበቀችውን ሀብት እሰጥሃለሁ። **4** ስለ ባሪያዬ ስለ ያዕቆብ፣ ስለ መረጥሁትም ስለ እስራኤል ብዬ በስምህ ጠርቼሃለሁ፤ በቀ፟ልምጫ ስምህ ጠራሁህ፤ አንተ ግን አላወቅኸኝም። **5** እኔ እግዚአብሔር ነኝ፣ ከእኔም ሌላ ማንም የለም፤ ከእኔም በቀር አምላክ የለም፤ **6** በፀሐይ መውጫና በምዕራብ ያሉ ከእኔ በቀር ማንም ሌላ እንደሌለ ያውቁ ዘንድ አስታጠቅሁህ፥ አንተ ግን አላወቅኸኝም፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፣ ከእኔም ሌላ ማንም የለም። **7** ብርሃንን ሠራሁ፣ ጨለማውንም ፈጠርሁ፤ ደኅንነትን እሠራለሁ፣ ክፋትንም እፈጥራለሁ፤ እነዚህን ሁሉ ያደረግሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ። **8** እናንተ ሰማያት ከላይ አንጠባጥቡ፣ ደመናትም ጽድቅን ያዝንቡ! ምድርም ትከፈት መድኃኒትንም ታብቅል፣ ጽድቅም በአንድነት ይብቀል። እኔ እግዚአብሔር ፈጥሬዋለሁ። **9** ከሠሪው ጋር ለሚከራከር ወዮለት! በምድር ሸክላዎች መካከል ያለ ሸክላ ነው! ጭቃ የሚሠራውን፣ 'ምን ትሠራለህ?' ወይስ 'ሥራህ - እጅ የለውም' ይላልን? **10** አባቱን፣ 'ምን ወልደሃል?' ወይም ሴትን፣ 'ምን አማጥሽ?' ለሚል ወዮ! **11** የእስራኤል ቅዱስ፣ ሠሪውም እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ 'ስለሚመጣው ነገር ጠይቁኝ፣ ስለ ልጆቼና ስለ እጄ ሥራም እዘዙኝ።' **12** 'እኔ ምድርን ሠርቻለሁ ሰውንም በእርስዋ ላይ ፈጥሬአለሁ። እኔ በእጄ ሰማያትን ዘርግቼአለሁ፣ ሠራዊታቸውንም ሁሉ አዝዣለሁ። **13** እኔ ቂሮስን በጽድቅ አስነሥቼዋለሁ፣ መንገዱንም ሁሉ አቀናለሁ። እርሱ ከተማዬን ይገነባል፣ በዋጋም ወይም በደመወዝ ሳይሆን ምርኮኞቼን ያወጣል፣" ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር። **14** እግዚአብሔርም እንዲህ ይላል፣ "የግብጽ ድካምና የኢትዮጵያ ንግድ ቁመተ ረጅሞችም የሳባ ሰዎች ወደ አንተ ያልፋሉ፤ ለአንተም ይሆናሉ። እጆቻቸውም ታስረው ይከተሉሃል፤ በፊትህም ያልፋሉ፣ ለአንተም እየሰገዱ። 'በእውነት እግዚአብሔር በአንተ አለ፣ ከእርሱም ሌላ አምላክ የለም' ብለው ይለምኑሃል።" **15** የእስራኤል አምላክ መድኃኒት ሆይ፣ በእውነት አንተ ራስህን የምትሰውር አምላክ ነህ። **16** ሁሉም ያፍራሉ ይዋረዱማል፤ ጣዖታትንም የሚሠሩ በአንድነት ወደ ውርደት ይሄዳሉ። **17** እግዚአብሔር ግን እስራኤልን በዘላለማዊ መድኃኒት ያድነዋል፤ እናንተም ለዘላለም አታፍሩምና አትዋረዱም። **18** ሰማያትን የፈጠረ እግዚአብሔር፣ እርሱም ምድርን የሠራና ያደረገ ያጸናትም፣ መኖሪያም ልትሆን እንጂ ለከንቱ እንድትሆን ያልፈጠራት አምላክ፣ እንዲህ ይላል፣ "እኔ እግዚአብሔር ነኝ፣ ከእኔም በቀር ሌላ የለም። **19** በስውር ወይም በጨለማ ምድር ስፍራ አልተናገርሁም፤ ለያዕቆብ ዘር፣ 'በከንቱ ፈልጉኝ አላልሁም!' እኔ እግዚአብሔር ጽድቅን እናገራለሁ፣ ቅንንም አወራለሁ። **20** እናንተ ከአሕዛብ ወገን ሆናችሁ ያመለጣችሁ ኑ! ተሰብስባችሁ ኑ፣ በአንድነትም ቅረቡ! የተቀረጸውን የምስላቸውን እንጨት የሚሸከሙና ያድን ዘንድ ወደማይችል አምላክ የሚጸልዩ እውቀት የላቸውም። **21** ይናገሩ ይቅረቡም በአንድነትም ይማከሩ! ከጥንቱ ይህን ያሳየ ከቀድሞስ የተናገረ ማን ነው? ያሳየሁም የተናገርሁም እኔ እግዚአብሔር አይደለሁምን? ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ የለም፤ እኔ ጻድቅ አምላክና መድኃኒት ነኝ፣ ከእኔም በቀር ማንም የለም። **22** እናንተ የምድር ዳርቻ ሁሉ፣ እኔ አምላክ ነኝና፤ ከእኔም በቀር ሌላ የለምና ወደ እኔ ዘወር በሉ ትድኑማላችሁ። **23** 'ቃሌ ከአፌ በጽድቅ ወጥታለች፣ አትመለስም። ጕልበት ሁሉ ለእኔ ይንበረከካል፣ ምላስም ሁሉ በእኔ ይምላል ብዬ በራሴ ምያለሁ። **24** ስለ እኔም፣ "በእግዚአብሔር ዘንድ ብቻ ጽድቅና ኃይል አለ፣ ወደ እርሱም ሰዎች ይመጣሉ።" በእርሱም ላይ የተቈጡ ሁሉ ያፍራሉ። **25** የእስራኤልም ዘር ሁሉ በእግዚአብሔር ይጸድቃሉ፤ ይመካሉም ይባላል።

Isaiah 45:1

ቀኝ እጁን ለያዝሁት
ያህዌ ቂሮስን መርዳቱና እንዲሳካለት ማድረጉ ቀኝ እጁን መያዝ እንደሆነ ይናገራል።

Isaiah 45:2

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለቂሮስ መናገር ቀጥሏል።

ተራሮችን እደለድላለሁ
የያህዌን ስኬት የሚያሰናክል እንቅፋትን ሁሉ ማስወገዱ በፊቱ ተራሮችን ደልዳላ ማድረግ እንደ ሆነ ያህዌ ይናገራል።

ተራሮች
በዐውዱ የተጠቀሰው የዕብራይስጥ ቃል ብዙም ጥቅም ላይ የማይውል ሲሆን፣ ትርጕሙም ግልጽ አይደለም። አንዳንድ ዘመናዊ ትርጕሞች፣ ‹‹አስቸጋሪ ቦታዎች›› ወይም፣ ‹‹ጐርበጥባጣ ስፍራዎች›› ብለዋል።

የብረት መወርወሪያዎች
ይህ የሚያመለክተው የናሱ ደጆች ላይ ያሉትን የብረት ዘንጐች ነው።

በጨለማ ያለውን ንብረት
‹‹በጨለማ›› በምስጢር ቦታ ማለት ነው። ‹‹ጨለማ ቦታ ያለ ንብረት›› ወይም፣ ‹‹በምስጢር ቦታዎች ያለ ንብረት››

Isaiah 45:4

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለቂሮስ መናገር ቀጥሏል።

ያዕቆብ... እስራኤል
ሁለቱም የሚናገረው ስለ እስራኤል ዘር ነው።

ለጦርነት አስታጥቅሃለሁ
ይህ ማለት፣ 1) ‹‹ለጦርነት አበረታሃለሁ›› ወይም 2) ‹‹ለጦርነት አዘጋጅሃለሁ›› ማለት ሊሆን ይችላል።

ከፀሐይ መውጫ እስከ ምዕራብ
ፀሐይ የምትወጣው በምሥራቅ በመሆኑ፣ ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር በየትኛውም ምድር ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በምድር ካለ ማንኛውም ቦታ››

Isaiah 45:7

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል

ብርሃንን ሠራሁ ጨለማን ፈጠርሁ፤ ሰላም አመጣለሁ፤ ጥፋትንም እፈጥራለሁ
ዐረፍተ ነገሮቹ ተመሳሳይ ነገር ማለት ሲሆኑ፣ ያህዌ የማንኛውም ነገር ሉዐላዊ ፈጣሪ መሆኑን አጽንዖት ይሰጣሉ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሰማያት ከላይ አዝንቡ... ጽድቅም አብሮ ይብቀል
የእርሱ ጽድቅ ምድር ላይ እንደሚወርድ ዝናብ እንደሆነና ጽድቁና ማዳኑም ምድር ላይ የሚበቅሉ ተክሎች እንደሆኑ ያህዌ ይናገራል።

እናንት ሰማያት
ለጊዜውም ቢሆን ያህዌ ትኩረቱን ከሕዝቡ አንሥቶ ለሰማያት መናገር ይጀምራል።

Isaiah 45:9

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል

በምድር ካሉ የሸክላ ማሰሮዎች መካከል
ያህዌ ስለ ራሱ ሲናገር እርሱ ሸክላ ሠሪ እንደሆነ፣ ከእርሱ ጋር የሚከራከረውና የተቀረው የሰው ዘር በሙሉ ሸክላዎች እንደሆኑ ይናገራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከብዙ ሸክላዎች መካከል አንዱ››

የሸክላ ማሰሮ
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ከሸክላ የተሠራ ማሰሮ›› ወይም 2) ‹‹የተሰበረ የሸክላ ማሰሮ›› ማለት ሊሆን ይችላል።

ጭቃ ሸክላ ሠሪውን... ምን እየሠራህ ነው? ይለዋልን
ያህዌ ይህን የሚጠይቀው እርሱ የሚያደርገውን የሚከራከሩትን ለመገሠጽ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጭቃ ሸክላ ሠሪውን... ምን እየሠራህ ነው? ማለት የለበትም››

Isaiah 45:10

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ የሚያደርገውን የሚከራከሩትን መገሠጽ ቀጥሏል።

አባቱን... ለምን ትወልደኛለህ? ለሚል ወየለት
ከእርሱ ጋር የሚከራከሩ ከወላጆቻቸው ጋር የሚከራከሩ ገና ያልተወለዱ ልጆች እንደሆኑ ያህዌ ይናገራል።

የወለድኸው ምንድነው?... ምን ወለድህ?
ያልተወለደው ልጅ ይህን የሚጠይቀው እርሱን በመወለዳቸው ወላጆቹ ላይ ለማፌዝ ነው። ይህን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አባቴ መሆን አልነበረብህም... ለምን ወለድኸኝ?›› ወይም፣ ‹‹ለእኔ ጥሩ አባት አይደለህም... እኔን በትክክል አልወለድኸኝም››

Isaiah 45:11

የእስራኤል ቅዱስ
ኢሳይያስ 1፥4 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

ልጆቼ ላይ የማደርገውን ለምን ትጠይቁኛላችሁ? የእጆቼን ሥራ በተመለከተ ማድረግ ያለብኝን ትነግሩኛላችሁን?
ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው የሚያደርገውን የሚከራከሩትን ለመገሠጽ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ልጆቼ ላይ የማደርገውን አትጠይቁኝ፤ በእጆቼ ሥራ... አትጠይቁኝ››

ልጆቼ
ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው።

የእጆቼ ሥራ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጆች›› የሚወክሉት ያህዌን ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እኔ ያደረግሁትን››

Isaiah 45:12

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል።

የእጆቼ ሥራ ነው
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጆች›› ያህዌን ይወክላሉ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያን ያደረግሁ እኔ ነኝ››

ሰማያትን የዘረጋሁ
ያህዌ ሰማያትን መፍጠሩን እንደሚዘረጋ ነገር መዘርጋት እንደ ሆነ ይናገራል። ኢሳይያስ 42፥5 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

Isaiah 45:13

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል።

ቂሮስን በጽድቅ አስነሥቻለሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ጽድቅ›› የሚያመለክተው ተገቢ የሆነ ሥራ ነው። ይህም ማለት፣ 1) ተገቢ የሆነውን ነገር እንዲያደርግ ያህዌ ቂሮስን አስነሣው፤ ወይም 2) ቂሮስን በማስነሣቱ ያህዌ ትክክል ነበር ማለት ሊሆን ይችላል።

ቂሮስን አስነሥቻለሁ
ቂሮስን ማስነሣቱ እርሱን ከእንቅልፍ መቀስቀሥ እንደሆነ ያህዌ ይናገራል።

መንገዱን ሁሉ አስተካክልለታለሁ
ዕንቅፋትን ማስወገዱና ቂሮስ እንዲሳካለት ማድረግ መንገዱን ማስተካከል እንደሆነ ያህዌ ይናገራል።

ከተማዬን እንደ ገና ይሠራታል
ይህ የሚያመለክተው ኢየሩሳሌምን ነው።

ያለ ክፍያ ወይም ያለ ጉቦ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ክፍያ›› እና፣ ‹‹ጉቦ›› ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። ቂሮስ ይህን ሁሉ የሚያደረገው ለገንዘብ አይደለም። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ይህንንም የሚያደርገው ለሚያገኘው ገንዘብ ሲል አይደለም››

የሰራዊት ጌታ ያህዌ
ኢሳይያስ 1፥9 ላይ ይህን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

Isaiah 45:14

የግብፅ ሀብትና የኩሽ ንግድ፣ ቁመተ ረጃጅሞቹ የሰባ ሰዎች ወደ አንተ ይመጣሉ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የግብፅ ሕዝብ፣ ኩሽና ቁመተ ረጃጅሞቹ የሳባ ሰዎች ሀብታቸውንና ንግዳቸውን ወደ አንተ ያመጣሉ››

የግብፅ ሀብት
‹‹የግብፅ ጥቅም››

ሳባውያን
እነዚህ የሳባ አገር ሰዎች ናቸው።

ወደ አንተ
እዚህ ላይ፣ ‹‹አንተ›› የሚያመለክተው የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Isaiah 45:16

ሁሉም ያፍራሉ፤ በአንድነት ይዋረዳሉ፤ ጣዖትን የሚሠሩ በውርደት ይመላለሳሉ
ሁለቱም መስመሮች የሚናገሩት ተመሳሳይ ነው፤ ሁለተኛው የመጀመሪያውን ርዕሰ ጉዳይ ግልጽ ያደርጋል።

ያፍራሉ፤ በአንድነት ይዋረዳሉ
‹‹ያፍራሉ›› እና፣ ‹‹ይዋረዳሉ›› የሚሉት በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ሲሆኑ፣ አጽንዖት የሚሰጡት የእፍረቱን መጠን ነው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጣዖቶቻቸው ሁሉንም ለእፍረት ይዳርጓቸዋል

በውርደት ይመላለሳሉ
ዘወትር ውርደት ውስጥ መኖር በውርደት መመላለስ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዘወትር ይዋረዳሉ››

እስራኤልን ያህዌ ያድነዋል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ የእስራኤልን ሕዝብ ያድናል››

ከእንግዲህ አታፍርም፤ አትዋረድም
‹‹አንተ›› የሚለው የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል። ‹‹ማፈር›› እና፣ ‹‹መዋረድ›› በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእንግዲህ ማንም አያዋርድህም››

Isaiah 45:18

እንድትባክን
‹‹ባዶ እንድትሆን›› እዚህ ላይ መባከን›› ባዶ፣ ጠፍ ቦታ መሆን ማለት ነው።

መኖሪያ እንጂ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ነገር ግን የሰዎች መኖሪያ እንድትሆን ወሰነ››

Isaiah 45:19

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል

Isaiah 45:20

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል

የኮበለላችሁ
ጠላት እንዳይዛቸው ወይም እንዳይገድላቸው ከቤታቸው የሸሹ ሰዎች

Isaiah 45:21

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለኮብላዮቹ መናገር ቀጥሏል (ኢሳይያስ 45፥20 ይመ.)

በአንድነት ይምከሩ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እነርሱ›› የተባሉት ከአሕዛብ መካከል የኮበለሉት ጣዖቶች የሚያመልኩ ሰዎች ናቸው።

ከጥንት ጀምሮ ይህን ያሳየ ማን ነው? ያወጀውስ ማን ነው? እኔ ያህዌ አይደለሁም?
ያህዌ ጥያቄዎቹን ያቀረበው እነዚህ እንደሚሆኑ የተናገረ እርሱ መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከጥንት ጀምሮ ይህን ያሳየ ማን እንደሆነ እነግራችኃለሁ። እኔ ያህዌ ነኝ››

Isaiah 45:22

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል

ትድኑ ዘንድ ወደ እኔ ተመለሱ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወደ እኔ ተመለሱ፤ እኔም አድናችኃለሁ››

የምድር ዳርቻዎች ሁሉ
ሩቅ ቦታ የሚኖሩ ሰዎች የምድር ዳርቻዎች ላይ እንደሚኖሩ ተነግሯል። ይህ ማለት በዳርቻዎቹ መካከል ያለ ማንኛውም ቦታ ማለትም ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በምድር ሩቅ ቦታ ያላችሁ ሁሉ›› ወይም፣ ‹‹በምድር ሁሉ››

የምድር ዳርቻዎች ሁሉ
ይህ ሐረግ፣ ‹‹በምድር ዳርቻዎች ሁሉ›› የሚኖሩ ሰዎችን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በምድር ሩቅ ቦታ የምትኖሩ ሁሉ›› ወይም ‹‹በምድር ሁሉ የምትኖሩ››

ጉልበት ሁሉ ለእኔ ይንብረከካል፤ አንደበትም ሁሉ በእኔ ይምላል
‹‹ጉልበት›› እና፣ ‹‹አንደበት›› የሚወክሉት ሰዎችን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰው ሁሉ በፊቴ ይንበረከካል፤ ማንኛውም ሰው በእኔ ይምላል››

Isaiah 45:24

ይላሉ
የምድር ሕዝብ ሁሉ ይናገራሉ

በያህዌ የእስራኤል ዘር ሁሉ ይጸድቃል
እዚህ ላይ፣ ‹‹ይጸድቃል›› ማለት እርሱን በማምለክ እስራኤል መልካም ማድረጓን ለአሕዛብ ማሳየት እንጂ፣ ያህዌ ኀጢአታቸውን ይቅር ይላቸዋል ማለት አይደለም። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ የእስራኤልን ዘር ሁሉ ያጸድቃል›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ የእስራኤልን ዘር ጽድቅ ይገልጣል››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 46

1 ቤል ተዋረደ፣ ናባው ተሰባበረ፤ ጣዖቶቻቸው በእንስሳና በከብት ላይ ተጭነዋል። ሸክሞቻችሁ ለደካማ እንስሳ ከባድ ጭነት ሆነዋል። **2** ተጐነበሱ
በአንድነትም ተዋረዱ፤ ሸክሙን ለማዳን አልቻሉም፣ ራሳቸው ግን ተማረኩ። **3** እናንተ የያዕቆብ ቤት ሆይ፣ የእስራኤልም ቤት ቅሬታ ሁሉ፣ ከሆድ ያነሣኋችሁ
ከማኅፀንም የተሸከምኋችሁ፣ ስሙኝ። **4** እስከ ሸምግልና ድረስ እኔ ነኝ፣ እስከ ሸበትም ድረስ እሸከማችኋለሁ፤ እኔ ሠርቻለሁ እኔም አነሣለሁ፤ እኔ እሸከማለሁ
እኔም አድናለሁ። **5** በማን ትመስሉኛላችሁ? ከማንስ ጋር ታስተካክሉኛላችሁ? እንመሳሰል ዘንድ ከማን ጋር ታስተያዩኛላችሁ? **6** ወርቁን ከኮረጆ የሚያፈስሱ
ብሩንም በሚዛን የሚመዝኑ እነርሱ አንጥረኛውን ይቀጥራሉ፣ እርሱም አምላክ አድርጎ ይሠራ ዋል፤ ለዚያም ይጐነበሱለታል ይሰግዱለትማል። **7** በጫንቃቸው
ላይ አንሥተው ይሸከሙታል፤ በስፍራውም ያደርጉታል፣ በዚያም ይቆማል፣ ከስፍራውም ፈቀቅ አይልም፤ ሰውም ወደ እርሱ ቢጮኽ አይሰማውም ከመከራውም
አያድነውም። **8** ስለእነዚህ ነገሮች አስቡና አልቅሱ፤ ተላላፊዎች ሆይ፣ ንስሐ ግቡ! ልባችሁንም መልሱ። **9** እኔ አምላክ ነኝና፣ ሌላም የለምና የቀድሞውን
የጥንቱን ነገር አስቡ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ እንደ እኔም ያለ ማንም የለም። **10** በመጀመሪያ መጨረሻውን፣ ከጥንትም ያልተደረገውን ሳይሆን በፊት እነግራለሁ፤
"ምክሬ ትጸናለች፣ ፈቃዴንም ሁሉ እፈጽማለሁ፤" እላለሁ። **11** ከምሥራቅ ነጣቂ ወፍን፣ ከሩቅም አገር ምክሬን የሚያደርገውን ሰው እጠራዋለሁ፤ ተናግሬአለሁ፤
እፈጽማለሁ፤ አስቤአለሁ አደርግማለሁ። **12** እናንተ ጽድቅን ከማድረግ የራቃችሁ፣ እልከኞች፣ ስሙኝ። **13** ጽድቄን አቀርባለሁ፤ አይርቅም መድኃኒቴም
አይዘገይም፤ ከጽዮን ለክብር እንዲሆን መድኃኒትን ለእስራኤል ሰጥቻለሁ።

Isaiah 46:1

ቤል ዝቅ አለ፤ ኔቦ አጐነበሰ፤ ጣዖቶቻቸው... ለደከሙ እንስሳት
ሰዎች ቤል እና ኔቦን በእንሳስት በሚሳብ ሰረገላ ላይ ማስቀመጣቸውን ኢሳይያስ የእነዚህ ጣዖቶች ዝቅ ማለትና ማጐንበስ ማለት እንደሆነ ይናገራል። ሁለቱም የሚያመለክቱት መዋረድን ነው።

ቤል... ኔቦ
እነዚህ ባቢሎናውያን የሚያመልካቸው ሁለቱ ዋና አማልክት ናቸው።

ጣዖቶቻቸው
ጣዖቶቹ ቤልና ኔቦን ይወክላሉ

ምስሎቹን አያድኑም
‹‹ቤልና ኔቦ ምስላቸውን ማዳን አይችሉም››

እነርሱ ራሳቸው በምርኮ ተወስደዋል
እነዚህ ሰዎች የሚሸከሙዋቸው ሐሰተኛ አማልክትን የሚወክሉ ጣዖቶች ወደ ምርኮ እንደ ተወሰዱ ኢሳይያስ ይናገራል።

Isaiah 46:3

እኔን ስሙ
‹‹እኔ›› ያህዌን ያመለክታል።

ከመወለዳችሁ በፊት የተሸከምኋችሁ ከማሕፀን ጀምሮ የተሸከምኋችሁ
የእስራኤል መንግሥት ሰው እንደሆነና የመንግሥቱም ጅማሬ ልጅ መወለድ እንደ ሆነ ያህዌ ይናገራል።

የተሸከምኋችሁ
የእስራኤልን ሕዝብ መርዳቱና ማዳኑ እነርሱን መሸከም እንደሆነ ያህዌ ይናገራል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እኔ የተሸከምኋችሁ››

እስከ ሸምግልና እኔ ነኝ፤ እስከ ሸበትም እሸከማችኋለሁ
የእስራኤልን ሸምግልና ጠጉሩ ከሸበተ ሸማግሌ ሰው ጋር በማመሳሰል ያህዌ ይናገራል።

Isaiah 46:5

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

ከማን ጋር ታወዳድሩኛላችሁ? ከማንስ ጋር እኩል ታደርጉኛላችሁ?
ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው እንደ እርሱ ማንም እንደሌለ አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከማንም ጋር ልታወዳድሩኝ አትችሉም፤ ከእኔ ጋር የምታስተካክሉት እኔን የመሰለ የለም››

ከማንስ ጋር እኩል ታደርጉኛላችሁ?
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከእኔ ጋር የምታመሳስሉት››

Isaiah 46:7

ያነሡታል
‹‹እነርሱ›› ጣዖቱን የሠሩ ሰዎችን ያመለክታል፤ ‹‹እርሱ›› የሠሩትን ጣዖት ያመለክታል።

Isaiah 46:8

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለሕዝቡ መናገር ቀጥሏል

Isaiah 46:10

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለሕዝቡ መናገር ቀጥሏል

የመጨረሻውን ከመጀመሪያው፣ ገና የሚሆነውን አስቀድሜ ተናግሬአለሁ።
አጽንዖት ለመስጠት እየደገመ ያለው በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገርን ነው። የመጀመሪያው ሐረግ ግሥ ለሁለተኛውም ይሆናል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የመጨረሻውን ከመጀመሪያው ተናግሬአለሁ፤ ገና ያልተደረገውን አስቀድሜ ተናግሬአለሁ››

ከምሥራቅ ነጣቂ ወፍ ጠርቻለሁ
ቂሮስ፣ ‹‹ነጣቂ ወፍ›› እንደሆነ ያህዌ ይናገራል። ወፍ በድንገት የምታድነውን እንደምትይዝ፣ ቂሮስም በፍጥነት መንግሥታትን ድል ለማድረግ የያህዌን ዓላማ በፍጥነት ይፈጽማል።

የተናገርሁትን አደርጋለሁ፤ ያቀድሁትን እፈጽማለሁ
አጽንዖት ለመስጠት ተመሳሳዩን ነገር ደጋግሞአል።

Isaiah 46:12

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መልካም ከማድረግ የራቃችሁ
በመደጋገም ክፉ የሚያደርጉ ሰዎች መልካም ከማድረግ የራቁ እንደሆኑ ያህዌ ይናገራል።

ማዳኔ አይዘገይም
ሕዝቡን ቶሎ ማዳኑ ለተግባር የማይዘገይ ሰው እንደሆነ ያህዌ ይናገራል። ማዳን የሚለውን በሌላ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እናንተን ከማዳን አልዘገይም››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 47

1 አንቺ ድንግል የባቢሎን ልጅ ሆይ፣ ውረጂ በመሬት ትቢያም ላይ ያለ ዙፋን ተቀመጪ፤ የከለዳውያን ሴት ልጅ ሆይ፤ ከዚህ በኋላ ቅልጣናምና ቅምጥል
አትባይምና። 2 ወፍጮ ወስደሽ ዱቄትን ፍጪ፤ መሸፈኛሽን አውጪ፣ ረጅሙንም ልብስሽን አውልቀሽ ጣዪው፤ ባትሽን ግለጪ፣ ወንዙን ተሻገሪ። 3 ኀፍረተ
ሥጋሽ ይገለጣል እፍረትሽም ይታያል፤ አዎን፣ እኔ እበቀላለሁ፥ ለማንም አልራራም። 4 ታዳጊያችን፣ ስሙ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፣ የእስራኤል ቅዱስ ነው።
5 የከለዳውያን ሴት ልጅ ሆይ፣ ከዚህ በኋላ፣ የመንግሥታት እመቤት አትባይምና ዝም ብለሽ ተቀመጪ ወደ ጨለማም ውስጥ ግቢ። 6 በሕዝቤ ላይ ተቈጥቼ
ነበር፤ ርስቴንም አረከስሁ፣ በእጅሽም አሳልፌ ሰጠኋቸው፤ ለእነርሱ ምንም ምሕረት አላደረግሽም፣ በሸማግሌዎቻቸው ላይ ቀንበርሽን እጅግ አክብደሻል። 7
አንቺም፣ "እኔ ለዘላለም እመቤት እሆናለሁ" ብለሻል፤ ይህንም በልብሽ አላደረግሽም ፍጻሜውንም አላሰብሽም። 8 አሁንም አንቺ ቅምጥል ተዘልለሽ
የምትቀመጪ፣ በልብሽም፣ "እኔ እኖራለሁ፣ ከእኔም በቀር ሌላ የለም፤ መበለትም ሆኜ አልኖርም የወላድ መካንነትንም አላውቅም" የምትዪ ይህን ስሚ፤ 9 አሁን
ግን በአንድ ቀን እነዚህ ሁለት ነገሮች፦ የወላድ መካንነትና መበለትነት፣ በድንገት ይመጡብሻል፤ ስለ መተቶችሽ ብዛትና ስለ አስማቶችሽ ጽናት ፈጽመው
ይመጡብሻል። 10 በክፋትሽ ታምነሻል፤ "የሚያየኝ የለም" ብለሻል፤ ጥበብሽና እውቀትሽ አታልለውሻል፣ ነገር ግን በልብሽ፣ "እኔ እኖራለሁ፣ ከእኔም በቀር ሌላ
የለም።" ብለሻል። 11 ስለዚህ ምክንያት ክፉ ነገር ይመጣብሻል፤ በምዋርትሽም እንዴት እንደምታርቂው አታውቂም። ጉዳት ይውድቅብሻል ታስወግጅውም
ዘንድ አይቻልሽም፤ የማትውቂያትም ጕስቍልና ድንገት ትመጣብሻለች። 12 ምናልባትም መጠቀም ትችዪ ወይም ታስደነግጪ እንደ ሆነ፣ ከአስማቶችሽና
ከሕፃንነትሽ ጀምረሽ ከደከምሽበት ከመተቶችሽ ብዛት ጋር ቁሚ። 13 በምክርሽ ብዛት ደክመሻል፤ አሁንም የሰማይን ከዋክብት የሚቈጥሩ፣ ከዋክብትንም
የሚመለከቱ፣ በየመባቻውም የሚመጣውን ነገር የሚናገሩ ተነሥተው ከሚመጣብሽ ነገር ያድኑሽ። 14 ተመልከቱ፣ እንደ እብቅ ይሆናሉ። እሳትም
ያቃጥላቸዋል። ሰውነታቸውንም ከነበልባል ኃይል አያድኑም። እርሱም ሰው እንደሚሞቀው ፍም፣ ወይም በፊቱ ሰው እንደሚቀመጥበት እሳት ያለ አይደለም! 15
የደከምሽባቸው ነገሮች እንዲህ ይሆኑብሻል፤ ከሕፃንነትሽ ጀምረው ከአንቺ ጋር ይነግዱ የነበሩ እያንዳንዳቸው ወደ ስፍራቸው ይሄዳሉ፣ የሚያድንሽም የለም።

Isaiah 47:1

አጠቃላይ መረጃ
በዚህ ምዕራፍ የተዋረደች ንግሥት ይመስል፣ ያህዌ ስለ ባቢሎን መውደቅ ይናገራል።

ትቢያ ላይ ተቀመጪ፤ የባቢሎን ድንግል ልጅ ሆይ፣ መሬት ላይ ተቀመጪ...የከለዳውያን ልጅ ሆይ
እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። ትቢያ ላይ መቀመጥ የውርደት ምልክት ነው።

የባቢሎን ድንግል ልጅ... የከለዳውያን ልጅ
ሁለቱም ሐረጐች የሚያመለክቱት እንደ ሴት ልጅ የተነገረላት የባቢሎንን ከተማ ነው። ከተማዋ፣ ‹‹ሴት ልጅ›› መሆንዋ ሕዝቡ ለእርሷ ያለውን ፍቅር ያመለክታል።

ያለ ዙፋን
እዚህ ላይ፣ ‹‹ዙፋን›› የመግዛት ሥልጣንን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያለ የመግዛት ሥልጣን››

ከእንግዲህ ውብ ወይም ለግላጋ ተብለሽ አትጠሪም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከእንግዲህ ሰዎች ውብና ለግላጋ በማለት አይጠሩሽም››

ውብና ለግላጋ
እነዚህ ሁለት ቃሎች ተመሳሳይ ትርጕም አላቸው። ያማረና በምኞት መኖርን ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በጣም ያማርሽ›› ወይም፣ ‹‹በጣም የተመቸሽ››

ወፍጮ
እህል ለመፍጨት የሚያገለግል ትልቅ ድንጋይ

Isaiah 47:3

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ያህዌ የተዋረደች ንግሥት የሆነችው የባቢሎንን ውድቀት መናገር ቀጥሏል።

ዕርቃንሽ ይገለጣል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ዕርቃንሽን ትሆኛለሽ››

ኀፍረትሽ ይታይ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ኀፍረት›› የሚለው የሰውን ድብቅ አካል ነው። ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሰዎች ኀፍረትሽን ያያሉ›› ወይም፣ ‹‹ሰዎች ድብቅ አካልሽን ያያሉ››

የሚቤዠን
‹‹የእኛ›› የሚለው ኢሳይያስንና የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል። ኢሳይያስ 41፥14 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

የሰራዊት ጌታ ያህዌ
ኢሳይያስ 1፥24 ላይ ይህን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

የእስራኤል ቅዱስ
ኢሳይያስ 5፥16 ላይ ይህን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

የከለዳውያን ሴት ልጅ
ይህ ሐረግ እንደ ሴት ልጅ የተመሰለችው የባቢሎንን ከተማ ያመለክታል። ከተማዋ፣ ‹‹በሴት ልጅ›› መመሰልዋ ከለዳውያን እርሷን በጣም መወደዳቸውን ያመለክታል። ኢሳይያስ 47፥1 ላይ ይህን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

ከእንግዲህ አትጠሪም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከእንግዲህ ሰዎች አንቺን አይጠሩሽም።

የመንግሥታት ልዕልት
የባቢሎን መንግሥት ዋና ከተማ የሆነችው ባቢሎን ብዙ መንግሥታትን ትገዛ የነበረች ልዕልት እንደሆነች ያህዌ ይናገራል።

Isaiah 47:6

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ያህዌ የተዋረደች ልዕልት ስለሆነችው ስለ ባቢሎን ውድቀት መናገር ቀጥሏል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እኔ ተቆጥቼ ነበር
‹‹እኔ›› ያህዌን ያመለክታል።

ርስቴን አርክሼው ነበር
የእስራኤል ሕዝብ የእርሱ የተለየ ርስት እንደሆነ ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የእኔ የተለየ ርስት የሆነውን ሕዝቤን አርክሼ ነበር››

አሳልፌ በእጅሽ ሰጠኃቸው
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› የባቢሎንን ኀይል ወይም ቁጥጥር ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በሥልጣንሽ ሥር አደረግኃቸው››

በዕድሜ በገፉት ላይ ከባድ ቀንበር ጫንሽባቸው።
ባቢሎን በዕድሜ የገፉትን መጨቆንዋ እንደ እንስሳት አንገታቸው ላይ ቀንበር ማድረግ እንደሆነ ያህዌ ይናገራል።

ለዘላለም ንግሥት እሆናለሁ
እርሷ ለዘላለም የምትገዛ ይመስል ብዙ መንግሥታትን እንደ ልዕልት እንደምትገዛ ትናገራለች።

እነዚህን ነገሮች አላስተዋልሽም
እነዚህን ነገሮች ልብ ውስጥ እንደማኖር ያህዌ ስለ ነገሮች በጥንቃቄ ማሰብ እንደሚገባ ይናገራል።

Isaiah 47:8

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
እንደ ተዋረደች ንግሥት ባቢሎን እንደምትወድቅ ያህዌ መናገር ቀጥሏል።

እናንት ደስታ የምትወዱ
‹‹እናንት ቅምጥሎች›› ይህ የባቢሎንን ቅጥ ያጣ ፈንጠዝያ ያመለክታል።

ተማምነሽ የምትቀመጪ
ይህ ሀብቷንና ክብሯን በፍጹም እንደማታጣ በማሰብ ባቢሎን የነበራትን አጉል በራስ መተማመን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሁሉም ደህና እንደሆነ የምታስቢ››

መበለት አልሆንም... የወላድ መካን አልሆንም
ሌሎች መንግሥታት በፍጹም ድል እንደማያደርጓት ባቢሎን የነበራት እምነት መበለት አልሆንም፤ የወላድ መካን አልሆንም በማለት የማሰብ ያህል እንደሆነ ተነግሯል።

መበለት አልሆንም
‹‹ባል የሌላት ሴት አልሆንም››

በአንድ ቀን ውስጥ
‹‹ድንገት በአንድ ጊዜ››

Isaiah 47:10

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ያህዌ የተዋረደች ልዕልት ስለሆነችው ባቢሎን መውደቅ መናገር ቀጥሏል።

አንቺም በልብሽ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ልብ›› ውስጣዊውን ሰው ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ለራስሽ እንዲህ አልሽ››

ጥፋት ያሸንፍሻል
ጥፋት ባቢሎንን የሚያሸንፍ ሰው እንደሆነ ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጥፋት ይደርስብሻል››

ውድመት ይወድቅብሻል
የባቢሎን መውደም ከተማዋ ላይ የሚወድቅ አንዳች ነገር እንደሆነ ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ውድመት ይመጣብሻል››

አደጋ ይመታሻል
ባቢሎን ላይ የሚደርሰው አደጋ እርሷን የሚመታ ሰው እንደሆነ ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አደጋ ይደርስብሻል››

Isaiah 47:12

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
እንደ ተዋረደች ንግሥት ባቢሎን እንደምትወድቅ ያህዌ መናገር ቀጥሏል።

መተት ማድረግሽን ቀጥዪ፤ ምናልባት አደጋን ማራቅ ትችዪ ይሆናል
መጥፎ ነገሮች እንዳይደርስባት መተት ማድረግን እንድትቀጥል በመንገር ያህዌ ባቢሎን ላይ ያፌዛል፤ ያ እንደማይረዳት ግን ያውቃል።

Isaiah 47:14

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
እንደ ተዋረደች ንግሥት ባቢሎን ላይ ስለሚደርሰው ውድቀት መናገሩን ያህዌ ቀጥሏል።

እንደ ገለባ ይሆናሉ፤ እሳትም ያቃጥላቸዋል
አስማተኞችና መተተኞች እሳት በቀላሉ እንደሚያቃጥለው ገለባ እንደ ሆኑ ያህዌ ይናገራል። ይህም ማለት እሳት ገለባ እንደሚያቃጥል፣ ያህዌ በፍጥነት ያጠፋቸዋል ማለት ነው፤ ባቢሎንን ለማዳን ዐቅም የላቸውም።

የነበልባሉ እጅ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› ብርታትን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የነበልባሉ ኀይል››

የሚሞቁት ፍም፤ ተቀምጠው የሚሞቁት እሳት አይኖርም
ይህ ሰዎች የሚሞቁት ሳይሆን፣ የሚያጠፋ እሳት መሆኑን ያህዌ ይናገራል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 48

1 እናንተ በእስራኤል ስም የተጠራችሁ፣ ከይሁዳም ዘር የወጣችሁ፣ በእግዚአብሔር ስም የምትምሉ፣ በእውነት ሳይሆን በጽድቅም ሳይሆን የእስራኤልን አምላክ
የምትጠሩ። **2** በቅድስት ከተማ ስም የተጠራችሁ፣ ስሙም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር በሚባል በእስራኤል አምላክ የምትደገፉ፤ የያዕቆብ ቤት ሆይ፣ ይህን
ስሙ። **3** የቀድሞውን ነገር ከጥንት ተናግሬአለሁ፣ ከአፌም ወጥቶአል፣ አሳይቼውማለሁ፤ ድንገት አድርጌዋለሁ ተፈጽሞማል። **4** አንተ እልከኛ፣ አንገትህም
የብረት ጅማት፣ ግምባርህም ናስ እንደሆነ አውቄአለሁ፤ **5** ስለዚህ፣ አንተ፣ 'ጣዖቴ ይህን አድርጎአል፣ የተቀረጸው ምስሌና ቀልጦ የተሠራው ምስሌ ይህን አዘዙኝ'
እንዳትል፣ አስቀድሜ ነግሬህ ነበር ሳይሆንም አሳይቼህ ነበር። **6** ስለ እነዚህ ነገሮች ሰምተሃል፤ ይህን ሁሉ ማረጋገጫ ተመልከት፤ እናንተም የምትናገሩት
አይደላችሁምን? የተሰወሩትን ያላወቅሃቸውንም አዲሶች ነገሮችን ከዚህ ጀምሬ አሳይቼሃለሁ። **7** እነርሱም አሁን እንጂ ከጥንት አልተፈጠሩም፤ አንተም፣ እነሆ፣
'አውቄአቸዋለሁ' እንዳትል ከዛሬ በፊት አልሰማሃቸውም። **8** አልሰማህም፣ አላወቅህም፣ ጆሮህ ከጥንት አልተከፈተችም። አንተ ፈጽሞ ወንጀለኛ እንደ ሆንህ
ከማኅፀንም ጀምረህ ተላላፊ ተብለህ እንደተጠራህ አውቄአለሁና። **9** ስለ ስሜ ቍጣዬን አዘገያለሁ፣ እንዳላጠፋህም ስለ ምስጋናዬ እታገሣለሁ። **10**
ተመልከት፣ አንጥሬሃለሁ፣ ነገር ግን እንደ ብር አይደለም፤ በመከራም እቶን ፈትኜሃለሁ። **11** ስለ እኔ፣ ስለ ራሴ አደርገዋለሁ፣ ስሜ እንዲነቀፍ የምፈቅደው
እንዴት ነው? ክብሬንም ለሌላ አልሰጥም። **12** ያዕቆብ ሆይ፣ የጠራሁህም እስራኤል ሆይ፣ ስማኝ፤ እኔ ነኝ፤ እኔ ፊተኛው ነኝ፣ እኔም ኋለኛው ነኝ። **13** አዎን፣
እጄ ምድርን መሥርታለች፣ ቀኜም ሰማያትን ዘርግታለች፤ በጠራኋቸው ጊዜ በአንድነት ይቆማሉ። **14** እናንተ ሁሉ፣ በአንድነት ተሰብስባችሁ ስሙ፤ ከእነርሱ ይህን
የተናገረ ማን ነው? እግዚአብሔር የወደደው ፈቃዱን በባቢሎን ላይ ያደርጋል፣ ክንዱም በከለዳውያን ላይ ይሆናል። **15** እኔ፣ እኔ ራሴ ተናግሬአለሁ፤ እኔ
ጠርቼዋለሁ፤ አምጥቼዋለሁ፥ መንገዱም ትሳካለታለች። **16** ወደ እኔ ቅረቡ፣ ይህንም ስሙ፤ እኔ ከጥንት ጀምሬ በስውር አልተናገርሁም፤ ከሆነበት ዘመን ጀምሮ
እኔ በዚያ ነበርሁ፣ አሁንም ጌታ እግዚአብሔርና መንፈሱ" ልከውኛል። **17** ታዳጊህ፣ የእስራኤል ቅዱስ፣ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። "እኔ የሚረባህን ነገር
የማስተምርህ፣ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ፣ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ።" **18** ትእዛዜን ብትፈጽም ኖሮ፣ ሰላምህ እንደ ወንዝ ጽድቅህም እንደ ባሕር
ሞገድ በሆነ ነበር፤ **19** ዘርህም እንደ አሸዋ፣ የሆድህም ትውልድ እንደ ምድር ትቢያ በሆነ ነበር፣ ስሙም ከፊቴ ባልጠፋና ባልፈረሰ ነበር። **20** ከባቢሎን ውጡ!
ከከለዳውያንም ኰብልሉ! በእልልታ ድምፅ ተናገሩ፣ ይህንም ንገሩ፣ እስከ ምድርም ዳርቻ ድረስ አውሩና፣ 'እግዚአብሔር ባሪያውን ያዕቆብን ታድጎታል' በሉ። **21**
በምድረ በዳ በኩል በመራቸው ጊዜ አልተጠሙም፤ ውኃንም ከዓለቱ ውስጥ አፈለቀላቸው፣ ዓለቱንም ሰነጠቀ ውኃውም ፈሰሰ። **22** ለክፉዎች ሰላም የላቸውም"
ይላል እግዚአብሔር።

Isaiah 48:1

ይህን ስሙ
‹‹መልእክቴን ስሙ›› ያህዌ እየተናገረ ነው።

የያዕቆብ ቤት
እዚህ ላይ፣ ‹‹ቤት›› የያዕቆብን ዘር ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የያዕቆብ ዘሮች››

በእስራኤል ስም የተጠራችሁ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰው ሁሉ የእስራኤል ሕዝብ እያለ የሚጠራችሁ››

ከይሁዳ ፍሬ የመጣችሁ
ይህ ሐረግ አጽንዖት የሚሰጠው እነርሱ በአካል የይሁዳ ዘር መሆናቸውን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የይሁዳ ዘር ናችሁ››

በእስራኤል አምላክ የምትታመኑ
‹‹የእስራኤልን አምላክ የምትጠሩ››

ራሳቸውን ይጠራሉ
ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ራሳችሁን ትጠራላችሁ››

የተቀደሰች ከተማ
ይህ የሚያመለክተው ኢየሩሳሌምን ነው።

የሰራዊት ጌታ ያህዌ
ኢሳይያስ 1፥9 ላይ ይህን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

Isaiah 48:3

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

ከአፌ ወጥተዋል
‹‹አፍ›› የሚናገር ሰውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እነዚህን ነገሮች ተናግሬአለሁ››

አንገትህ እንደ ብረት ጠንክሮአል ግንባርህ እንደ ናስ ሆኖአል።
የዐንገታቸውንና የግንባራቸውን ጥንካሬ ያህዌ ከብረትና ከናስ ጥንካሬ ጋር ያመሳስለዋል። የዐንገትና የግንባር ጥንካሬ የግትርነት ምሳሌ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ዐንገትህ ብረት፣ ግንባርህም ናስ የሆነ ያህል ነው››

ስለ እነዚህ ነገሮች ገና ድሮ ነገርሁህ፤ ከመፈጸማቸው በፊት አስታወቅሁህ
ይህ አጽንዖት ለመስጠት ተመሳሳይ ነገር ሁለቴ መናገር ነው።

Isaiah 48:6

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

የተናገርሁት እውነት መሆኑን አትቀበልምን?
ያህዌ እነዚህን ጥያቄዎች ያቀረበው እውነት መሆኑን የሚያውቁትን ነገር ባለ መቀበላቸው፣ የእስኤልን ሕዝብ ለመገሠጽ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ግትር ናችሁ፤ የተናገርሁት እውነት መሆኑን አትቀበሉም››

Isaiah 48:8

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

እነዚህ ነገሮች ለጆሮዋችሁ የተገለጡት አሁን እንጂ፣ ዱሮ አይደለም
ያህዌ አንዳች ነገር መናገሩ ያንን መግለጥ እንደሆነ ያመለክታል። ‹‹ጆሮ›› የሚሰሙ ሰዎችን ይወክላል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እነዚህ ነገሮች ለእናንተ አስቀድሜ አልገለጥሁም››

ከልደት
የሕዝቡ ጅማሬ ልደቱ እንደሆነ ያህዌ ይናገራል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Isaiah 48:9

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

ስለ ስሜ ስል ቁጣዬን አዘገያለሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ስም›› የያህዌን ማንነት ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ስለ ማንነቴ ስል ቁጣዬን አዘገያለሁ››

ስለ ክብሬ ስል እናንተን ከማጥፋት እታቀባለሁ
ይህ የዐረፍተ ነገሩ ክፍል ከመጀመሪያው ክፍል ጋር በመሠረቱ ተመሳሳይ ነው።

እነሆ፣ እንደ ብር ባይሆንም፣ አንጥሬሃለሁ፤ በመከራ እቶን አንጽቼሃለሁ
እነርሱ የከበሩ ማዕድኖች የሆኑ ይመስል እቶን ደግሞ እነርሱን የሚያነጻ እሳት ይመስል ያህዌ ሕዝቡን በመከራ ውስጥ እንደሚያነጻ ይናገራል።

ስሜን ለውርደት እንዴት አሳልፌ እሰጣለሁ?
ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው ስሙን ለውርደት አሳልፎ እንደማይሰጥ አጠንክሮ ለማመልከት ነው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ማንም ስሜን እንዲያዋርድ አልፈቅድም››

Isaiah 48:12

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

ያዕቆብና እስራኤል
ሁለቱም የሚያመለክቱት የእስራኤልን ሕዝብ ነው።

እኔ የመጀመሪያው፣ የመጨረሻውም ነኝ
ይህ ሐረግ ለያህዌ ዘላለማዊ ባሕርይ አጽንዖት ይሰጣል። ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ሁሉንም የጀመርሁ እኔ ነኝ፤ ሁሉንም የምጨርስ እኔ ነኝ›› ወይም 2) ‹‹እኔ ሁሌም የነበርሁ፣ ሁሌም የምኖር ነኝ›› ኢሳይያስ 46፥6 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

እጄ፣ ምድርን መሠረተ፤ ቀኝ እጄ ሰማያትን ዘረጋ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› የሚያመለክተው ያህዌን ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የምድርን መሠረት አኖርሁ፤ ሰማያትንም ዘረጋሁ››

የምድር መሠረት
መሠረት ከሥር ሆኖ ሕንፃውን ደግፎ የሚይዝ የድንጋይ መዋቅር ነው። እዚህም ላይ በተመሳሳይ መልኩ ምድርን የሚይዝ መዋቅር እንደሆነ ተነግሯል። ኢሳይያስ 24፥18 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

ሰማያትን ዘረጋሁ
ያህዌ ሰማያትን መፍጠሩን አንዳች የሚዘረጋ ነገር መዘርጋት ማለት እንደሆነ አድርጐ ይናገራል። ኢሳይያስ 42፥5 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

ስጠራቸው በአንድነት ይቆማሉ
ያህዌ ሲጠራቸው መቆም ለእርሱ ለመታዘዝ ዝግጁ መሆን ማለት ነው። ምድርና ሰማያት እንደሚሰሙትና እንደሚታዘዙት ያህዌ ይናገራል።

ስጠራቸው
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ምድርና ሰማያትን ስጠራቸው›› ወይም 2) ‹‹በሰማይ ያሉ ከዋክብትን ስጠራቸው›› ማለት ሊሆን ይችላል።

Isaiah 48:14

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

ከእናንተ መካከል እነዚህን ነገሮች ያስታወቀ ማን ነው?
ያህዌ ጥያቄውን ያነሣው ጣዖቶች እነዚህን ነገሮች እንዳልነገሯቸው አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከጣዖቶቻችሁ አንዱም ይህን አልነገራችሁም››

የያህዌ አጋር ባቢሎን ላይ ዓላማውን ይፈጽማል፤ ከለዳውያንም ላይ ፈቃዱን ያደርጋል
የያህዌ፣ ‹‹አጋር›› የተባለው ቂሮስ ነው። ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ቢሆኑም ጥቅም ላይ የዋሉት አጽንዖት ለመስጠት ነው።

ዓላማው
‹‹የያህዌ ዓላማ››

እኔ፣ እኔ
‹‹እኔ›› የሚለው የተደገመው አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እኔ ራሴ››

Isaiah 48:16

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

በድብቅ አልተናገርሁም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የተናገርሁት በግልጽና በአደባባይ ነው››

ልከውኛል
እዚህ ላይ፣ ‹‹እኔ›› የተባለው በግልጽ ያልታወቀ የያህዌ ባርያ ነው፤ ምናልባት ኢሳይያስ ወይም ቂሮስ ወይም ተስፋ የተሰጠለት መሲሕ ሊሆን ይችላል።

Isaiah 48:17

የተቤዠህ... አምላክህ
እዚህ ላይ፣ ‹‹የአንተ›› የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል።

የተቤዠህ
ኢሳይያስ 41፥14 ላይ ይህን ቃል እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

የእስራኤል ቅዱስ
ኢሳይያስ 1፥4 ላይ ይህን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

መሄድ በሚገባህ መንገድ የሚመራህ
እንዴት መኖር እንዳለባቸው ያህዌ ሕዝቡን ማስተማሩ እነርሱን በትክክለኛው መንገድ መምራት ማለት እንደሆነ ተነግሯል።

ትእዛዜን ሰምተህ ብቻ ቢሆን ኖሮ
ያህዌ መሆን ስለ ነበረበት ግን ስላልሆነ ነገር ይናገራል።

ሰላምህና ብልጽግናህ እንደ ወንዝ፣ መዳንህም እንደ ባሕር ሞገድ በሆነ ነበር
እነዚህ ሁለት ሐረጐች የሚናገሩት ስለ ተመሳሳይ ጉዳይ ነው። በሁለቱም እነዚህ በረከቶች እንደ ውሃ የሚፈሰሱ ይመስል እስራኤል በረከትን እንደምትለማመድ ያህዌ ይናገራል።

መዳንህም እንደ ባሕር ሞገድ
ግሡን ካለፈው ሐረግ መውሰድ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹መዳንህ እንደ ባሕር ሞገድ በፈሰሰ ነበር››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Isaiah 48:19

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ስለ ወደ ፊቱ የእስራኤል ሁኔታ መናገር ቀጥሏል።

ዘርህ እንደ አሸዋ፣ የማሕፀንህም ልጆች ስፋር እንደሌለው ትቢያ ይሆኑ ነበር
ሁለቱም ሕዝቡ መቁጠር ከሚችሉት በላይ ዘሮቻቸው ይበዙ እንደ ነበር ያመለክታሉ።

የማሕፀንህም ልጆች
የእስራኤል ሕዝብ ዘሮች እንደሚወለዱ ልጆች እንደሚሆኑ ያህዌ ይናገራል።

ስማቸው አይቆረጥም ወይም አይደመሰሰም ነበር
የእስራኤል ሕዝብ መጥፋት እንደ ልብስ ወይም እንደ ዛፍ ቅርንጫፍ መቆረጥ ወይም መደምሰስ እንደሚሆን ያህዌ ይናገራል። ይህን በሌላ መልኩ መተርጎም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስማቸውን አልቆርጥም ወይም አልደመስስም ነበር››

ስማቸውን
‹‹ስም›› የሚለው ቃል የእስራኤልን ስም የሚያስጠሩ ዘሮችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነርሱ››

አይቆረጥም ወይም አይደመሰስም
በዚህ ዐውድ ሁለቱም አገላለጾች የሕዝቡን መጥፋት ነው የሚያመለክቱት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አይጠፋም››

Isaiah 48:20

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

እስከ ምድር ዳርቻ
ምድር ላይ ያሉ ሩቅ ቦታዎች ስም፣ የምድር ዳርቻዎች እንደሆኑ ተነግሯል። በምሳሌያዊ አነጋገር በዳርቻዎቹ መካከል ያሉትን ቦታዎች ሁሉ ይጨምራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምድር ላይ ያሉ ሩቅ ቦታዎች ሁሉ›› ወይም፣ ‹‹በምድር ሁሉ››

ባርያውን ያዕቆብን
ይህ የሚያመለክተው የያዕቆብን ዘር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ባርያዎቹ የእስራኤል ሕዝቦች››

Isaiah 48:21

አልተጠሙም... ውሃው ፈልቆ ወጣ
ይህ የሚያመለክተው ከግብፅ ከወጡ በኃላ በምድረ በዳ እየኖሩ ሳለ፣ ለእነርሱ ለመጠንቀቅ በእስራኤል ሕዝብ ታሪክ ውስጥ ያህዌ ያደረገውን ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 49

1 ደሴቶች ሆይ፣ ስሙኝ! እናንተም በሩቅ ያላችሁ አሕዛብ፣ አድምጡ፤ እግዚአብሔር ከማኅፀን በስም ጠርቶኛል፣ ከእናቴም ሆድ ጀምሮ ። 2 አፌንም እንደ ተሳለ
ሰይፍ አድርጎአል፣ በእጁ ጥላ ሰውሮኛል፤ እንደ ተሳለ ፍላጻም አድርጎኛል፣ በሰገባውም ውስጥ ሸጎኛል። 3 እርሱም፣ "እስራኤል ሆይ፣ አንተ ባሪያዬ ነህ፣
በአንተም እከበራለሁ" አለኝ። 4 እኔ ግን፣ በከንቱ ደከምሁ፣ ምንም ጥቅም ለሌለውና ለከንቱ ጕልበቴን ፈጀሁ፤ ፍርዴ ግን በእግዚአብሔር ዘንድ፣ ዋጋዬም
በአምላኬ ዘንድ ነው አልሁ። 5 አሁንም በእግዚአብሔር ዓይን ከብሬአለሁና፣ አምላኬም ጕልበት ሆኖኛልና ያዕቆብን ወደ እርሱ እንድመልስ እስራኤልንም ወደ
እርሱ እንድሰበስብ፣ ባሪያ እሆነው ዘንድ ከማኅፀን ጀምሮ የሠራኝ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። 6 እርሱ እንዲህ ይላል፣ "የያዕቆብን ነገዶች እንድታስነሣ፣
ከእስራኤልም የዳኑትን እንድትመስል፣ ባሪያዬ ትሆን ዘንድ እጅግ ቀላል ነገር ነውና እስከ ምድር ዳር ድረስ መድኃኒት ትሆን ዘንድ ለአሕዛብ ብርሃን አድርጌ
ሰጥቼሃለሁ" ይላል። 7 የእስራኤል ታዳጊ ቅዱሱም፣ እግዚአብሔር፣ ሰዎች ለሚንቁት ሕዝብም ለሚጠላው ለገዥዎች ባሪያ እንዲህ ይላል፣ "ስለ ታማኙ ስለ
እግዚአብሔር፣ ስለ መረጠህም ስለ እስራኤል ቅዱስ ነገሥታት አይተው ይነሣሉ፣ መሳፍንትም አይተው ይሰግዳሉ።" 8 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣
"በተወደደ ጊዜ ሰምቼሃለሁ፣ በመዳንም ቀን እረዳሃለሁ፤ እጠብቅህማለሁ፣ ምድርንም ታቀና ዘንድ፣ ውድማ የሆኑትንም ርስቶች ታወርስ ዘንድ፥ 9 የተጋዙትንም፣
'ውጡ፤' በጨለማም የተቀመጡትን፣ 'ራሳችሁን ግለጡ' ትል ዘንድ ቃል ኪዳን አድርጌ ለሕዝቡ ሰጥቼሃለሁ። በመንገድም ላይ ይሰማራሉ፣ ማሰማርያቸውም
በወና ኮረብታ ሁሉ ላይ ይሆናል። 10 የሚራራላቸውም ይመራቸዋልና፣ በውኃም ምንጮች በኩል ይነዳቸዋልና አይራቡም፣ አይጠሙም፣ ትኩሳት ወይም ፀሐይ
አይጐዳቸውም። 11 ተራሮቼንም ሁሉ መንገድ አደርጋለሁ፣ ጎዳኖቼም ከፍ ከፍ ይላሉ።" 12 ተመልከቱ፣ እነዚህ ከሩቅ፣ አንዳንዶቹም፣ ከሰሜንንና ከምዕራብ፣
እነዚህም፣ ከሲኒም አገር ይመጣሉ። 13 እግዚአብሔር ሕዝቡን አጽናንቶአልና፣ ለችግረኞቹም ራርቶአልና ሰማያት ሆይ፣ ዘምሩ፣ ምድር ሆይ፣ ደስ ይበልሽ
ተራሮችም ሆይ፣ እልል በሉ። 14 ጽዮን ግን፣ "እግዚአብሔር ትቶኛል፣ ጌታም ረስቶኛል" አለች። 15 "በውኑ ሴት ከማኅፀንዋ ለተወለደው ልጅ እስከማትራራ
ድረስ ሕፃንዋን ትረሳ ዘንድ ትችላለችን? አዎን፣ እርስዋ ትረሳ ይሆናል፣ እኔ ግን አልረሳሽም። 16 ተመልከቱ፣ እኔ በእጄ መጻፍ ቀርጬሻለሁ፤ ቅጥሮችሽም
ሁልጊዜ በፊቴ አሉ። 17 ልጆችሽ ተመልሰው ይፈጥናሉ፤ ያፈረሱሽና ያወደሙሽ ከአንቺ ዘንድ ይወጣሉ። 18 ዓይንሽን አንሥተሽ ዙሪያሽን ተመልከቺ፤ እነዚህ ሁሉ
ተሰብስበው ወደ አንቺ ይመጣሉ። እኔ ሕያው ነኝና እነዚህን ሁሉ እንደ ጌጥ ትለብሻቸዋለሽ፣ እንደ ሙሽራም ትጐናጸፊአቸዋለሽ፣ ይላል እግዚአብሔር። 19
ባድማሽና ውድማሽ ወናም የሆነው ምድርሽ ከሚኖሩብሽ የተሣ ዛሬ ጠባብ ትሆናለችና፣ የዋጡሽም ይርቃሉና። 20 የወላድ መካን ከሆንሽ በኋላ የተወለዱልሽ
ልጆችሽ በጆሮሽ፣ 'ስፍራ ጠብቦናልና፣ እንቀመጥ ዘንድ ቦታ አስፊልን' ይላሉ። 21 አንቺም በልብሽ፣ 'የወላድ መካን ሆኛለሁና፣ እኔም ብቻዬን ተሰድጄአለሁና
ተቅበዝብዤ አለሁምና እነዚህን ልጆች ማን ወለደልኝ? እነዚህንስ ማን አሳደጋቸው? እነሆ፣ ብቻዬን ቀርቼ ነበር፤ እነዚህስ ከወዴት መጡ?" ትያለሽ። 22 ጌታ
እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "ተመልከቺ፣ እጄን ወደ አሕዛብ አነሣለሁ፣ ዓላማዬንም ወደ ወገኖች አቆማለሁ፤ ወንዶች ልጆችሽንም በብብታቸው
ያመጡአቸዋል። ሴቶች ልጆችሽንም በጫንቃቸው ላይ ይሸከሙአቸዋል። 23 ነገሥታትም አሳዳጊ አባቶችሽ ይሆናሉ፣ እቴጌዎቻቸውም ሞግዚቶችሽ ይሆናሉ፤
ግምባራቸውንም ወደ ምድር ዝቅ አድርገው ይሰግዱልሻል፥ የእግርሽንም ትቢያ ይልሳሉ፤ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቂያለሽ፤ እኔንም በመተማመን
የሚጠባበቁ አያፍሩም።" 24 በውኑ ብዝበዛ ከኃያል እጅ ይወሰዳልን? ወይስ የጨካኙ ምርኮኞች ያመልጣሉን? 25 እግዚአብሔር ግን እንዲህ ይላል፣ "አዎን፣
በኃያላን የተማረኩ ይወሰዳሉ፣ የጨካኞችም ብዝበዛ ያመልጣል፤ ከአንቺ ጋር የሚጣሉትን እጣላቸዋለሁ፣ ልጆችሽንም አድናለሁ። 26 አስጨናቂዎችሽንም
ሥጋቸውን አስበላቸዋለሁ፣ እንደ ጣፋጭም ወይን ጠጅ ደማቸውን ጠጥተው ይሰክራሉ፤ ሥጋ ለባሹም ሁሉ እኔ እግዚአብሔር መድኃኒትሽና ታዳጊሽ፣ የያዕቆብ
ኃያል እንደ ሆንሁ ያውቃል።"

Isaiah 49:1

እኔን ስሙ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እኔ›› የሚያመለክተው የያህዌን ባርያ ነው።

ደሴቶች
ይህ የሚያመለክተው ደሴቶች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በደሴቶች የምትኖሩ››

አፌን እንደ ተሳለ ሰይፍ አደረገው
እዚህ ላይ፣ ‹‹አፍ›› እርሱ የሚናገረውን ቃል ይወክላል። የሚሠራ መሆኑን ለማሳየት ቃሉ ከሰይፍ ጋር ተመሳስሎአል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ቃሌን እንደሚሠራ የተሳለ ሰይፍ አድርጐታል››

በእጁ ጥላ ሰውሮኛል፤
ያህዌ ባርያውን መጠበቁና ዓላማውን በምስጢር መያዙ የያህዌ እጅ ጥላ እርሱ ላይ ማረፍ እንደሆነ ተነግሯል።

የተወለወለ ፍላጻ አደረገኝ፤ በሰገባውም ውስጥ ሸሸገኝ
ያህዌ ባርያውን መጠበቁና ዓላማውን በምስጢር መያዙ፣ በሰገባው ውስጥ መሆን ማለት እንደሆነ ተነግሯል።

ሰገባ
ፍላጻዎች የሚያዙበት ቦርሳ

Isaiah 49:3

አጠቃላይ መረጃ
የያህዌ ባርያ መናገር ቀጥሏል

እንዲህም አለኝ
‹‹ያህዌ እንዲህ አለኝ››

እስራኤል፣ አንተ ባርያዬ ነህ
‹‹አንተ፣ እስራኤል ብዬ የጠራሁህ ባርያየ ነህ››

Isaiah 49:5

አጠቃላይ መረጃ
የያህዌ ባርያ መናገር ቀጥሏል።

እስራኤልን ወደ እርሱ እንድሰበስብ
ይህ የዐረፍተ ነገሩ ክፍል ቀደም ሲል ከነበረው ጋር ተመሳሳይ ነው። በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የእስራኤልን ሕዝብ መልሼ ወደ እርሱ እንዳመጣ››

በያህዌ ዐይን ከብሬአለሁ
ዐይን ማየትን፣ ማየት ደግሞ ሐሳብን ወይም ፍርድን ይወክላል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ አክብሮኛል››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አምላኬ ብርታት ሆኖኛል
እግዚአብሔር ለባርያው ብርታት መስጠቱ፣ እግዚአብሔር ራሱ ብርታት ሆነለት ማለት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አምላኬ ብርታት ሰጥቶኛል›› ወይም ‹‹አምላኬ አበርትቶኛል››

ለአሕዛብ ብርሃን አደርግሃለሁ
አገልጋዩ የያህዌን መልእክት ለአሕዛብ ማምጣቱና እንዲያስተውሉም መርዳቱ ያህዌ አገልጋዩን በአሕዛብ መካከል ብርሃን አደረገው ማለት እንደሆነ ተነግሯል። ኢሳይያስ 42፥6 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

የምድር ዳርቻዎች
በምድር ላይ በጣም ሩቅ ያሉ ቦታዎች የምድር ዳርቻዎች ላይ ያሉ ቦታዎች እንደሆኑ ተነግሯል። ምሳሌያዊ አነጋገሩ በዳርቻዎቹ መካከል ያሉትን ቦታዎችም ይጨምራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በምድር በሩቅ ያሉ ቦታዎች ሁሉ›› ወይም፣ ‹‹በምድር ሁሉ››

Isaiah 49:7

ታዳጊ
ኢሳይያስ 41፥14 ላይ ይህን ቃል እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

ሕይወቱ ለተናቀ፣ በአሕዛብ ለተጣለውና የገዢዎች ባርያ ለሆነው
እዚህ ላይ፣ ‹‹ሕይወት›› ሰውየውን ይወክላል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰዎች ለናቁት፣ አሕዛብ ለጠሉትና የገዦች ባርያ ለሆነው››

የእስራኤል ቅዱስ
ኢሳይያስ 1፥4 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

Isaiah 49:8

ሞገሴን በማሳይበት ጊዜ እመልስልሃለሁ፤ በማዳን ቀን እረዳሃለሁ
እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው።

እመልስልሃለሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹አንተ›› የተባለው የያህዌ አገልጋይ ነው።

በመዳን ቀን
‹‹መዳን›› የሚለውን ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አንተን የማድንበት ቀን ሲመጣ››

ለአሕዛብ ኪዳን አድርጌ እሰጥሃለሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ኪዳን›› ኪዳኑን የሚመሠርተውን ወይም መካከለኛ የሆነውን የሚያመለክት ምሳሌ ነው። ኢሳይስ 42፥6 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከሕዝቡ ጋር ለሚደረገው ኪዳን መካከለኛ አደርግሃለሁ››

ምድሪቱን እንደ ገና እንድትሠራ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ምድሪቱ›› በዚያ ምድር የነበሩና የተደመሰሱ ከተሞች ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በምድሪቱ ያሉ የፈረሱ ቦታዎችን እንድትሠራ››

ጠፍ የሆኑ ርስቶችን እንድትመልስ
ምድሪቱ ለዘላለም ርስታቸው እንድትሆን የእስራኤል ሕዝብ የተቀበሏት ንብረት እንደሆነች ያህዌ ይናገራል። ባርያው ርስቱን የሚመልሰው ለእስራኤል ሕዝብ መሆኑ ግልጽ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጠፍ የሆነው ምድር ርስታቸው እንዲሆን ለእስራኤል ሕዝብ እንድትመልስ››

Isaiah 49:9

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለባርያው መናገር ቀጥሏል።

በመንገዱ ዳር ይመገባሉ፤ የተራቆተውም ኮረብታ ሁሉ መሰማሪያቸው ይሆናል
በነጻነትና በብልጽግና የሚኖር ሕዝቡ የሚመገቡት ብዙ ሣር እንዳላቸው በጐች እንደሆኑ ያህዌ ይናገራል።

Isaiah 49:10

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል

አይራቡም
‹‹እነርሱ›› የሚለው የእግዚአብሔርን ሕዝብ ነው።

ትኩሳት ወይም የፀሐይ ቃጠሎ አይመታቸውም
እዚህ ላይ፣ ‹‹ትኩሳት›› የሚለው ቃል፣ ‹‹ፀሐይ›› የሚለውን ቃል ይገልጻል። የፀሐይ ሙቀት የጐዳቸው ሰዎች በትኩሳቱ የተመቱ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የፀሐይ ትኩሳት አይመታቸውም››

የሚራራላቸው ይመራቸዋል
ያህዌ ስለ ራሱ በሦስተኛ ሰው ደረጃ ይናገራል። ሕዝቡን መጠበቁና ለእርሱንም መንከባከቡ እረኛቸው እንደሆነ ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የምራራላቸው እኔ፣ እመራቸዋለሁ››

ተራሮቼን ሁሉ መንገድ አደርጋለሁ፤ ጐዳናዎቼንም አስተካክላለሁ
ሕዝቡን በሰላም መምራቱና ከመንገዳቸውም እንቅፋቶችን ማስወገዱ፣ ተራሮቹን መንገድ ጐዳናዎቹንም ማስተካከል ማለት እንደሆነ ያህዌ ይናገራል።

Isaiah 49:12

የሲኒም ምድር
ይህ ቦታ የት እንደሆነ አይታወቅም፤ ግን ከግብፅ ደቡብ ያለውን አካባቢ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።

ሰማያት ሆይ፣ እልል በሉ፤ ምድር ሆይ ደስ ይበልሽ!
ኢሳይያስ ትኩረቱን ከእስራኤል ሕዝብ ላይ አንሥቶ ሰዎች የሆኑ ይመስል ለሰማያትና ለምድር እንዲሁም ለተራሮች ይናገራል።

Isaiah 49:14

ጽዮን ግን... አለች
ጽዮን የኢየሩሳሌም ሌላ ስም ነው። ከተማዋ እግዚአብሔር ትቶኛል በማለት እንደምታማርር ሴት እንደሆነች ኢሳይያስ ይናገራል።

እናት የምታጠባውን ልጇን መርሳት ትችላለችን? ለወለደችውስ አትራራለትምን?
እርሱ በፍጹም እንደማይረሳቸውና ለእነርሱ ማሰቡንም እንደማያቆም መረዳት እንዲችሉ ለመርዳት ያህል እነዚህ ጥያቄዎች አቅርቧል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እናት የምታጠባውን ልጇን መርሳት አትችልም፤ ለወለደችው መራራትዋንም አትተውም››

Isaiah 49:16

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለጽዮን መናገር ቀጥሏል።

በእጄ መዳፍ ላይ ቀርጬሻለሁ
ለጽዮን ያለውን የማይለወጥ ፍቅር ለማሳየት ያህዌ እርሷን በእጁ መዳፍ ላይ መቅረጹን ይናገራል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ቅጥሮችሽ ሁሌም በፊቴ ናቸው
ቅጥሮቿ ሁሌም በፊቱ ያሉ ያህል እርሱ ሁሌም ለጽዮን እንደሚያስብ ያህዌ ይናገራል። ‹‹ቅጥሮች›› የከተማዋ ምሳሌ ናቸው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ምንጊዜም ስለ ቅጥሮችሽ አስባለሁ›› ወይም፣ ‹‹ምንጊዜም ስለ አንቺ አስባለሁ››

ልጆችሽ ፈጥነው ይመለሳሉ
በኢየሩሳሌም ለመኖር ስለሚመለሰው ሕዝብ ያህዌ ሲናገር፣ እነርሱ የከተማዋ ልጆች እንደሆኑ ይናገራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ኗሪዎችሽ ፈጥነው ይመለሳሉ››

እኔ ሕያው እንደሆንሁ
የሚናገረው እውነት እንደሆነ ለማስረገጥ ያህዌ የሚጠቀምበት መሐላ ነው።

ይህ የያህዌ ዐዋጅ ነው
የሚናገረው እውነት መሆኑን ለማስረገጥ ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን ኢሳይያስ 30፥1 ላይ እንዳለው ተርጕመው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ ያወጀው ይህን ነው›› ወይም፣ ‹‹እኔ ያህዌ ይህን ዐውጃለሁ››

እንደ ጌጥ ትለብሻቸዋለሽ፤ እንደ ሙሽራ ትጐናጸፊያቸዋለሽ
የጽዮን ነዋሪዎች ውበትና ደስታዋን ለማሳየት ከተማዋ የምትለብሳቸው ጌጥ እንደሆኑ ያህዌ ይናገራል።

እንደ ሙሽራ ትጐናጸፊያቸዋለሽ
ቀደም ሲል ከነበረው መስመር የሐረጉን መጨረሻ ክፍል መረዳት ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሙሽራ ጌጥ እንደምትለብስ አንቺም ትለበሻቸዋለሽ››

Isaiah 49:19

አጠቃላይ መረጃ
ሴት የሆነች ይመስል ያህዌ ለጽዮን መናገር ቀጥሏል።

ባድማና ጠፍ ብትሆኚም
‹‹ባድማ›› እና፣ ‹‹ጠፍ›› የተሰኙት ቃሎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው፤ ጠላት ጽዮንን እንደደመሰሰና ባዶዋን እንደ ተዋት አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ምንም እንኳ ጨርሶ ጠፍ የነበርሽ ቢሆንም››

የዋጡሽ
ጽዮንን የደመሰሰ ጠላት እርሷን ውጦ እንደ ነበር ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አንቺን የዋጡ ሰዎች››

በሐዘንሽ ዘመን የወለድሻቸው ልጆች
የኢየሩሳሌም ሕዝብ በምርኮ በነበሩ ዘመን ከተማዋ ለልጆቿ ሐዘን ላይ እንደ ነበረች ሴት መሆንዋን ያህዌ ይናገራል። ሕዝቡ በምርኮ በነበረ ጊዜ የተወለዱ የከተማዋ ልጆች እንደሆኑ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሕዝቡ በምርኮ በነበሩ ጊዜ የተወለዱ ልጆች የሚኖሩብሽ››

ቦታው ጠብቦናል
ይህም ማለት ሕዝቡ በጣም ብዙ ከመሆኑ የተነሣ መኖሪያ ለመሆን ከተማዋ ታንሣለች ማለት ነው።

Isaiah 49:21

አጠቃላይ መረጃ
ሴት የሆነች ይመስል ያህዌ ለጽዮን መናገር ቀጥሏል።

እነዚህን የወለደልኝ ማን ነው?
እዚያ ለመኖር ስለሚመለሱ ሰዎች ስትናገር ሕዝቡ ልጆቿ እንደሆኑ ጽዮን ትናገራላችሁ። ጥያቄው ብዙ ልጆች ስላላት ጽዮን መደነቋን ያሳያል።

ሐዘንተኛና መካን፣ የተሰደድሁና የተፈታሁ ነበርሁ
ስለ ራሷ ስትናገር ጽዮን ብዙ ልጆች መወለድ እንደማትችል ሴት እንደ ነበረች ትናገራለች። በጣም የተደነቀችውም ለዚህ እንደ ነበር ትገልጻለች።

ሐዘንተኛና መካን ነበርሁ
‹‹በሞቱት ልጆቼና ከእንግዲህም መወለድ ባለ መቻሌ እያዘንሁ ነበር››

የተሰደድሁና የተፈታሁ
‹‹ተሰድጄ ነበር፤ ባል አልነበረኝም››

እነዚህን ልጆች ማን አሳደገልኝ፤ ብቸኛ ነበርሁ፤ እነዚህ ከየት መጡ?
መደነቋን ለማሳየት እንደ ገና ጽዮን ጥያቄዎች ታነሣለች። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እነሆ፣ ብቸኛ ነበርሁ፤ አሁን ግን እኔ ያላሳደግሁቸው እነዚህ ልጆች ሁሉ ወደ እኔ መጡ››

Isaiah 49:22

አጠቃላይ መረጃ
ሴት የነበረች ይመስል ያህዌ ለጽዮን መናገር ቀጥሏል። ብዙ ልጆች ሊኖሩዋት እንደ ቻለ ይናገራል።

እጆቼን ለአሕዛብ አነሣለሁ፤ ለሰዎችም የምልክት ባንዲራ ከፍ አደርጋለሁ
እነዚህ ሁለት አነጋገሮች በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በየአገሩ ያሉ ሰዎች እንዲመጡ እጆቼንና የምልክት ባንዲራን አነሣለሁ››

ወንዶች ልጆችሽን በእቅፋቸው፣ ሴቶች ልጆችሽን በትከሻቸው ያመጣቸዋል
በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎች የከተማዋ ልጆች እንደሆኑ ያህዌ ይናገራል። እስራኤላውያንን ታቅፈው የሌላ አገር ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚያመጡዋቸውም ይናገራል።

Isaiah 49:23

አጠቃላይ መረጃ
ሴት የሆነች ይመስል ያህዌ ለጽዮን መናገር ቀጥሏል።

ነገሥታት አሳዳጊ አባቶችሽ፣ እቴጌዎቻቸው ሞግዚቶችሽ ይሆናሉ
በጽዮን የሚኖሩ ሰዎች የከተማ ልጆች እንደሆኑ ያህዌ ይናገራል። ‹‹አሳዳጊ አባቶች›› እና፣ ‹‹ሞግዚቶች›› የተሰኙት ቃሎች ለልጆቹ የመንከባከብን ኃላፊነት የሚወስዱ ወንዶችና ሴቶችን ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የሌላ አገር ነገሥታትና እቴጌዎች ለነዋሪዎችሽ የሚያስፈልገውን ያቀርባሉ››

በግንባራቸው ተደፍተው ይሰግዱልሻል፤ የእግርሽንም ትቢያ ይልሳሉ
እነዚህ ሐረጐች ሰዎች ለበላያቸው ፍጹም ተገዢ መሆናቸውን የሚያሳዩባቸው ሁኔታዎች ናቸው።

የእግርሽንም ትቢያ ይልሳሉ
ይህም ማለት፣ 1) ቃል በቃል አንድ ሰው የበላዩ እግር ላይ ያለ ትቢያን እንደሚልስ ያመለክታል ወይም 2) አንድ ሰው የበላዩ ፊት በአክብሮት እጅ መንሣቱን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው።

አያፍሩም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እፍረት አያድርባቸውም›› ወይም፣ ‹‹ተስፋ አይቆርጡም››

Isaiah 49:24

አጠቃላይ መረጃ
በሴት ጾታ ያህዌ ለጽዮን መናገር ቀጥሏል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከተዋጊ ብዝበዛ ማስጣል፣ ከጨካኝስ ምርኮኞችን ማዳን ይቻላልን?
ኢሳይያስ ጥያቄዎቹን ያቀረበው ከብርቱ ወታደር ወይም ጦረኛ አንድን ነገር መውሰድ አስቸጋሪ መሆኑን ለማመልከት ነው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንድ ሰው ከተዋጊ ብዝበዛ ማስጣል ወይም ከብርቱ ተዋጊ ምርኮኞችን ማዳን አይችልም››

ብዝበዛ
በጦርነት ከተሸነፉ የሚወሰዱ ጠቃሚ ነገሮች

ከተዋጊች ምርኮኞችን ይወስዳሉ፤ ከጨካኞችም ምርኮ ይበዘበዛል
ይህዌ ያልተለመዱ ነገሮችን ሕዝቡ እንደሚያደርግ ይናገራል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከተዋጊው ምርኮኞችን እወስዳለሁ፤ ብዝበዛዎችንም እነጥቃለሁ››

ልጆችሽን አድናለሁ
በጽዮን የሚኖሩ ሰዎች የከተማዋ ልጆች እንደሆኑ ያህዌ ይናገራል።

Isaiah 49:26

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ እንደ ሰው ለጽዮን መናገር ቀጥሏል።

አስጨናቂዎችሽን የራሳቸውን ሥጋ አስበላቸዋለሁ
ይህም ማለት፣ 1) አስጨናቂዎቹ በጣም ስለሚርባቸው የሞቱ ወዳጆቻቸውን ሥጋ ይበላሉ ማለት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አስጨናቂዎችሽ የራሳቸውን ሥጋ እንዲበሉ አደርጋለሁ›› ወይም 2) ጨቋኞቹ እርስ በርስ እንደሚጠፋፉ ያህዌ እየተናገረ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የገዛ ሥጋቸውን የሚበሉ ይመስል አስጨናቂዎች እርስ በርስ ይጠፋፋሉ››

እንደ ወይን ጠጅ በገዛ ራሳቸው ደም ይሰክራሉ
ይህም ማለት፣ 1) አስጨናቂዎቹ በጣም ስለሚጠሙ የሞቱ ወዳጆቻቸውን ደም ይጠጣሉ ማለት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የወዳጆቻቸውን ደም ይጠጣሉ። በወይን ጠጅ እንደ ሰከረ ሰው ይደክማሉ›› ወይም 2) አስጨናቂዎቹ የራሳቸውን ደም የሚጠጡ ይመስል እርስ በርስ ይጠፋፋሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በወይን ጠጅ የሰከሩ ይመስል የብዙ ወጆጆቻቸውን ደም ያፈስሳሉ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 50

1 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "እናታችሁን የፈታሁበት የፍችዋ ጽሕፈት የት አለ? ወይስ እናንተን የሸጥሁ ከአበዳሪዎች ለየትኛው ነው? እነሆ፣ ስለ ኃጢአታችሁ ተሸጣችኋል፥ ስለ በደላችሁም እናታችሁ ተፈትታለች። **2** እኔ በመጣሁ ጊዜ ሰው ስለ ምን አልነበረም? በጠራሁስ ጊዜ የሚመልስ ስለ ምን አልነበረም? መታደግ እንዳትችል እጄ አጭር ሆናለችን? ወይስ ለማዳን ኃይል የለኝምን? እነሆ፣ በገሠጽሁ ጊዜ ባሕርን አደርቃለሁ፤ ወንዞችንም ምድረ በዳ አደርጋቸዋለሁ፤ ውኃም በማጣት ዓሦቻቸው ይገማሉ በጥማትም ይሞታሉ። **3** ሰማያትን ጥቊረት አለብሳቸዋለሁ፣ መጋረጃቸውንም ማቅ አደርጋለሁ።" **4** የደከመውን በቃል እንዴት እንደምደግፍ አውቅ ዘንድ ጌታ እግዚአብሔር የተማሩትን ምላስ ሰጥቶኛል ማለዳ ማለዳ ያነቃኛል፣ እንደ ተማሪዎችም ትሰማ ዘንድ ጆሮዬን ያነቃቃል። **5** ጌታ እግዚአብሔር ጆሮዬን ከፍቶአል፣ እኔም ዓመፀኛ አልነበርሁም ወደ ኋላዬም አልተመለስሁም። **6** ጀርባዬን ለገራፊዎች፣ ጕንጩንም ለጠጕር ነጪዎች ሰጠሁ፣ ፊቴንም ከውርደትና ከትፋት አልመለስሁም። **7** ጌታ እግዚአብሔር ይረዳኛልና፣ ስለዚህ አልተዋረድሁም፤ ስለዚህም ፊቴን እንደ ባልጩት ድንጋይ አድርጌዋለሁ፣ እንዳላፍርም አውቃለሁ። **8** የሚያጸድቀኝ ቅርብ ነው። ከእኔስ ጋር የሚከራከር ማን ነው? በአንድነት እንቁም፤ የሚከስሰኝ ማን ነው? ወደ እኔ ይቅረብ። **9** ተመልከቱ፣ ጌታ እግዚአብሔር ይረዳኛል። ማን ይፈርድብኛል? ተመልከቱ፣ ሁሉ እንደ ልብስ ያረጃሉ ብልም ይበላቸዋል። **10** ከእናንተ እግዚአብሔርን የሚፈራ፣ የባሪያውንም ቃል የሚሰማ፣ በጨለማም የሚሄድ፣ ብርሃንም የሌለው፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ስም የሚታመን፣ በአምላኩም የሚደገፍ ማን ነው? **11** ተመልከቱ፣ እሳት የምታነድዱ የእሳትንም ወላፈን የምትታጠቁ ሁላችሁ፥ በእሳታችሁ ነበልባል ባነደዳችሁትም ወላፈን ሂዱ፤ ይህ ከእጄ ይሆንባችኋል፦ በኀዘን ትተኛላችሁ።

Isaiah 50:1

እናታችሁን የፈታሁበት የፍቺ ወረቀት የታለ?
ከተማዋ እዚያ የነበሩ ሰዎች እናት እንደ ነበረችና ወደ ምርኮ የሰደደቻቸው ከባልዋ የተፋታች ሴት እንደሆነች ያህዌ ስለ ጽዮን ይናገራል።

እናታችሁን የፈታሁበት የፍቺ ወረቀት የታለ?
ያህዌ ይህን ጥያቄ ያቀረበው እነርሱን ወደ ምርኮ የሰደደበት ምክንያት እንዲሆን ሕዝቡ ‹‹የፍቺውን ወረቀት›› እንዲያቀርቡ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እናታችሁን የፈታሁበትን የፍቺ ወረቀት አሳዩኝ››

እናንተን የሸጥኋችሁ ለየትኛው አበዳሪ ነው?
የተሸጡ ይመስል ሕዝቡን ወደ ምርኮ እንደ ሰደደ ያህዌ ይናገራል።

እናንተን የሸጥኋችሁ ለየትኛው አበዳሪ ነው?
ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው የማንም ዕዳ ስለሌለበት እነርሱን አለመሸጡን አጽንዖት ለመስጠት ነው። ሰዎቹ ግን እንደዚያ አስበው የነበሩ ይመስላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የማንም ዕዳ ስለሌለብኝ እናንተን አልሸጥሁም››

ስለ ኀጢአታችሁ ተሸጣችኋል፤ ስለ መተላለፋችሁም እናታችሁ ተፈትታለች
ያህዌ ሕዝቡን ወደ ምርኮ የሰደደበትን ምክንያት ይናገራል፤ እነርሱ የተሸጡትና እናታቸውም የተፈታችው በዚህ ምክንያት ነበር። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ስለ ኀጢአታችሁ ሸጥኋችሁ፤ ስለ መተላለፋችሁም እናታችሁን ፈታሁ››

Isaiah 50:2

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

እኔ ስመጣ ማንም ያልነበረው ለምንድነው? ስጣራ መልስ የሚሰጥ ያልነበረው ለምንድነው?
እነዚህ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው። ሕዝቡ በምርኮ የተወሰዱት እርሱ እነርሱን ለማዳን ፈቃደኛ ባለ መሆኑ ሳይሆን፣ መልስ ስላልሰጡት መሆኑን ያህዌ አጽንዖት ሰጥቶ ይናገራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እኔ ስመጣ እዚያ መኖር ሲገባችሁ አልነበራችሁም፤ ስጣራ መመለስ ነበረባችሁ ግን አልመለሳችሁም›› ወይም፣ ‹‹ልናገራችሁ ስመጣ ምላሽ አልሰጣችሁኝም››

እናንተን ለማዳን እጄ አጭር ናትን? ልታደጋችሁ ኀይል የለኝምን?
እነርሱን ለማዳን ዐቅም እንደሌለው በማሰባቸው ሕዝቡን ለመገሠጽ ያህዌ ሁለት ጥያቄዎች አቅርቧል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እናንተን ለማዳን እጄ በእርግጥ አጭር አይደለችም፤ እናንተን ለመታደግ ኀይል አለኝ›› ወይም፣ ‹‹እናንተን ከጠላቶቻችሁ ለማዳን በእርግጥ ኀይል አለኝ››

እጄ አጭር ናትን?
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጄ›› የያህዌን ኀይል ይወክላል። ያህዌ ዐቅም ከሌለው እጁ አጥራለች ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እኔ በቂ ኀይል የለኝምን?››

ልታደጋችሁስ ኀይል የለኝምን
‹‹እኔ ኀይል የለኝምን?››

ወንዞቹን ምድረ በዳ አደርጋለሁ
ያህዌ ወንዞቹን ማድረቁ እነርሱን ምድረ በዳ ማድረጉ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ወንዞቹን እንደ ምድረ በዳ ደረቅ አደርጋለሁ››

ዓሣዎቹም ውሃ በማጣት ሞተው ይገማሉ
‹‹ውሃ ከማጣታቸው የተነሣ ዓሣዎቹ ይሞታሉ፣ ይገማሉ›› - ‹‹የእነርሱ›› የሚለው ቃል የሚያመለክተው ባሕሮችና ወንዞችን ነው።

ሰማዩን ጨለማ አለብሰዋለሁ፤ በማቅ እሸፍነዋለሁ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። ማቅ የሚያለብሰው ይመስል ሰማዩን ጨለማ እንደሚያደርገው ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጥቁር ጨርቅ የለበሰ ይመስል ሰማዩን ጨለማ አደርገዋለሁ።››

Isaiah 50:4

አጠቃላይ መረጃ
የያህዌ ባርያ መናገር ጀምሯል

ጌታ ያህዌ የተማሩትን አንደበት ሰጥቶኛል
‹‹አንደበት›› መናገርን ይወክላል። ይህም ማለት፣ 1) በማስተዋል መናገርን እንደ ተማረ ሰው መናገርን ያህዌ አስችሎኛል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጌታ ያህዌ አስተዋይ ተናጋሪ አደረገኝ›› ወይም፣ 2) ያህዌ መናገር ያለብኝን አስተማረኝ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጌታ ያህዌ ያስተማረኝን መናገር አስቻለኝ››

ጆሮዬ እንድትሰማ ያነቃል
‹‹ጆሮዬ›› የሚለው የሚያመለክተው የያህዌን አገልጋይ ነው። ያህዌ እንዲሰማና እንዲያስተውል እርሱን ማስቻሉ ጆሮውን ከእንቅልፍ ማንቃት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እርሱ የሚናገረውን መረዳት አስቻለኝ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በመማር ላይ እንዳለ ተማሪ
አገልጋዩን ራሱን ከአስተማሪ መናገርን ከሚማር ተማሪ ጋር ያመሳስላል። ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ከአስተማሪው እንደሚማር›› ወይም 2) ‹‹እርሱ እንዳስተማረው››

Isaiah 50:5

አጠቃላይ መረጃ
የያህዌ ባርያ መናገር ቀጥሏል።

ጌታ ያህዌ ጆሮዬን ከፍቷል
ያህዌ አገልጋዩን እንዲሰማና እንዲያስተውል መርዳቱ ጆሮውን መክፈት ማለት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጌታ ያህዌ እንድሰማና እንዳስተውል ረዳኝ››

ዐመፀኛ አልነበርሁም፤ ጀርባዬንም አላዞርሁም
እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። ያህዌ ለሚናገረው አለመታዘዝ እርሱ ላይ ጀርባ ማዞር እንደሆነ ተነግሯል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱ ለሚናገረው ታዘዝሁ››

ጀርባዬን ለሚገርፉኝ፣ ጢሜን ለሚነጩ ጉንጬን ሰጠሁ
ሰዎች እንዲገርፉትና ጢሙን እንዲነጩ መፍቀድ ጀርባውንና ጉንጩን ለእነርሱ መስጠት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ጀርባዬን እንዲገርፉኝ፣ ከጉንጩ ላይ ጢሜን እንዲነጩ ፈቀድሁ››

ፊቴን ከውርደትና ከትፋት አልሰወርሁም
ፊትን መሰወር ለራስ መከላከል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሲያፌዙብኝና ሲተፉብኝ ለራሴ አልተከላከልሁም››

Isaiah 50:7

አጠቃላይ መረጃ
የያህዌ ባርያ መናገር ቀጥሏል።

ስለዚህ አልዋረድም
ምንም እንኳ በደል ቢፈጸምበትም ለያህዌ በመታዘዙ አይዋረድም። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለዚህም አላፍርም››

ፊቴን እንደ ባልጩት ድንጋይ አድርጌአለሁ
‹‹ፊቴን›› የሚለው የሚያመለክተው ባርያውን ነው። ባርያው ለያህዌ ለመታዘዝ መቁረጡ ፊቱን እንደ ባልጩት ድንጋይ ማድረግ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በፍጹም ቆርጫለሁ››

እንደማላፍር አውቃለሁ
የያህዌ ባርያ የወደ ፊቱን በተስፋ ይመለከታል፤ በያህዌ ጥሪ ይተማመናል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጠላቶቼ እንዳፍር ማድረግ እንደማይችሉ አውቃለሁ››

Isaiah 50:8

አጠቃላይ መረጃ
የያህዌ ባርያ መናገር ቀጥሏል

የሚቃወመኝ ማን ነው? እንጋጠም?... ከሳሼስ ማን ነው? እስቲ ይምጣ
የያህዌ ባርያ እነዚህን ጥያቄዎች የሚያቀርበው በጎጢአት ሊከሰሰው የሚችል እንደሌለ አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሚቃወመኝ ካለ ይግጠመኝ፤ ...የሚከስሰኝ ካለ፣ ይምጣ››

የሚፈርድብኝስ ማን አለ?
የያህዌ ባርያ ይህን የሚጠይቀው የሚፈርድበት እንደሌላ ለማስረገጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔን በደለኛ ነህ የሚለኝ የለም››

እንደ ልብስ ያረጃሉ፤ ብልም ይበላቸዋል
የያህዌን ባርያ የሚከሰስ ሰው አለመቅረቱ ከሳሾቹ እንደ ልብስ እንዳረጁና ብልም እንደ በላቸው መሆኑ ተነግሯል።

Isaiah 50:10

አጠቃላይ መረጃ
የያህዌ ባርያ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል

ከእናንተ መካከል ያህዌን የሚፈራ ማን ነው? ለባርያው ድምፅ የሚታዘዝ ማነው? ብርሃን በሌለበት ድቅድቅ ጨለማ የሚመላለስ ማን ነው ከሆነ... በአምላኩ
የያህዌ ባርያ ጥያቄዎቹን ያቀረበው ከሚናገራቸው ጋር ለመተባበር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእናንተ መካከል ያህዌን የሚፈራ፣ ለባርያው ድምፅ የሚታዘዝ፣ ግን ብርሃን በሌለበት ድቅድቅ ጨለማ የሚመላለስ ሰው ካለ... በአምላኩ››

ለባርያው ድምፅ የሚታዘዝ
‹‹ድምፅ›› የሚወክለው የያህዌ ባርያ የሚናገረውን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለባርያው የሚታዘዝ››

ብርሃን በሌለበት ድቅድቅ ጨለማ የሚመላለስ
መከራ ውስጥ ያሉና ዐቅመ ቢስ የሆኑ ሰዎች በጣም ጨለማ በሆነ ቦታ እንደሚመላለስ ሰው እንደሆኑ የያህዌ ባርያ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መከራ ውስጥ ያለ ዐቅመ ቢስ››

በያህዌ ስም ይታመን በአምላኩም ይደገፍ
እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። ‹‹ስም›› የሚያመለክተው ያህዌ ራሱን ነው። በእግዚአብሔር መታመን በእርሱ መደገፍ ማለት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በአምላኩ በያህዌ ይታመን››

Isaiah 50:11

እሳት አንድዳችሁ... የሚንቦገቦግ ችቦ የያዛችሁ ሁሉ
ይህ በጨለማ እየተመላለሱ እንደሆነ ባለፈው ቁጥር የተነገረው ምሳሌ ቀጣይ ነው። በያህዌ ከመታመን ይልቅ በራሳቸው ጥበብ ለመታመን የሚሞክሩ ሰዎች በጨለማው ውስጥ ማየት እንዲያስችላቸው የራሳቸውን እሳት አንድደው ችቦ እንደያዙ ሰዎች እንደሆኑ ተነግሯል።

በሥቃይ ትጋደማላችሁ
‹‹መጋደም›› የሚያመለክተው መሞትን ነው። በዚህ ዓይነት ሁኔታ መሞት በሥቃይ መጋደም ማለት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በታላቅ ሥቃይ ትሞታላችሁ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 51

1 እናንተ ጽድቅን የምትከተሉ እግዚአብሔርንም የምትሹ፣ ስሙኝ፤ ከእርሱ የተቈረጣችሁበትን ድንጋይ ከእርሱም የተቈፈራችሁበትን ጕድጓድ ተመልከቱ። 2 ወደ አባታችሁ ወደ አብርሃም፣ ወደ ወለደቻችሁም ወደ ሳራ ተመልከቱ፤ አንድ ብቻውን በሆነ ጊዜ ጠራሁት፣ ባረክሁትም አበዛሁትም። 3 አዎን፣ እግዚአብሔር ጽዮንን ያጽናናል፤ በእርስዋም ባድማ የሆነውን ሁሉ ያጽናናል፤ ምድረ በዳዋንም እንደ ዔደን፣ በረሀዋንም እንደ እግዚአብሔር ገነት ያደርጋል፤ ደስታና ተድላ ምስጋናና የዝማሬ ድምፅ ይገኝበታል። 4 ወገኔ ሆይ፣ አድምጠኝ፤ ሕዝቤ ሆይ፣ ስማኝ! ሕግ ከእኔ ይወጣልና፣ ፍርዴም ለአሕዛብ ብርሃን ይሆናልና። 5 ጽድቄ ፈጥኖ ቀርቦአል፣ ማዳኔም ወጥቶአል፣ ክንዴም በአሕዛብ ላይ ይፈርዳል፤ ደሴቶች እኔን በመተማመን ይጠባበቃሉ፣ በክንዴም ይታመናሉ። 6 ዓይናችሁን ወደ ሰማይ አንሡ፣ ወደ ታችም ወደ ምድር ተመልከቱ፤ ሰማያት እንደ ጢስ በንነው ይጠፋሉ፣ ምድርም እንደ ልብስ ታረጃለች፣ የሚኖሩባትም እንዲሁ ይሞታሉ። ማዳኔ ግን ለዘላለም ይሆናል፣ ጽድቄም አይፈርስም። 7 ጽድቅን የምታውቁ ሕጌም በልባችሁ ያለ ሕዝብ ሆይ፣ ስሙኝ፤ የሰውን ተግዳሮት አትፍሩ፣ በስድባቸውም አትደንግጡ። 8 እንደ ልብስም ብል ይበላቸዋል፣ እንደ በግ ጠጕርም ትል ይበላቸዋል፤ ጽድቄ ግን ለዘላለም ማዳኔም ለትውልድ ሁሉ ይሆናል።" 9 የእግዚአብሔር ክንድ ሆይ፣ ተነሥ፣ ተነሥ፣ ኀይልንም ልበስ። በቀድሞው ወራትና በጥንቱ ዘመን በነበረው ትውልድ እንደ ሆነው ተነሥ። ረዓብን የቈራረጥህ ዘንዶውንም የወጋህ አንተ አይደለህምን? 10 ባሕሩንና የታላቁን ጥልቅ ውኃ ያደረቅኽው፣ የዳኑትም ይሻገሩ ዘንድ ጠሊቁን ባሕር መንገድ ያደረግህ አንተ አይደለህምን? 11 እግዚአብሔርም የተቤዣቸው ይመለሳሉ ወደ ጽዮንም ይመጣሉ፤ የዘላለምም ደስታ በራሳቸው ላይ ይሆናል፤ ደስታንና ተድላን ያገኛሉ፣ ኀዘንና ልቅሶም ይሸሻል። 12 "እኔ፣ የማጽናናችሁ እኔ ነኝ፣ እኔ ነኝ፤ የሚሞተውን ሰው እንደ ሣርም የሚጠወልገውን የሰው ልጅ ትፈራ ዘንድ አንተ ማን ነህ? 13 ሰማያትንም የዘረጋው ምድርንም የመሠረተውን ፈጣሪህን እግዚአብሔርን ረስተሃል፤ ያጠፋ ዘንድ ባዘጋጀ ጊዜ ከአስጨናቂው ቊጣ የተነሣ ሁልጊዜ ቀኑን ሁሉ ፈርተሃል፤ የጨቋኙ ቊጣ የት አለ? 14 ምርኮኛ ፈጥኖ ይፈታል፣ አይሞትም ወደ ጕድጓድም አይወርድም፣ እንጀራም አይጐድልበትም። 15 ሞገዱም እንዲተምም ባሕርን የማናውጥ አምላክህ እግዚአብሔር እኔ ነኝ፣ ስሜም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው። 16 ሰማያትን እዘረጋ ዘንድ ምድርንም እመሠርት ዘንድ፣ ጽዮንንም፣ 'አንቺ ሕዝቤ ነሽ' እል ዘንድ ቃሌን በአፍህ አድርጌአለሁ፣ በእጄም ጥላ ጋርጄሃለሁ።" 17 ከእግዚአብሔር እጅ የቊጣውን ጽዋ የጠጣሽ ኢየሩሳሌም ሆይ፣ ንቂ፣ ንቂ፣ ቁሚ፤ የሚያንገደግድን ዋንጫ ጠጥተሻል፣ ጨልጠሽውማል። 18 ከወለደቻቸው ልጆች ሁሉ የሚመራት የለም፣ ካሳደገቻቸውም ልጆች ሁሉ እጅዋን የሚይዝ የለም። 19 እነዚህ ሁለት ነገሮች ሆነውብሻል፣ ማንስ ያስተዛዝንሻል? መፈታትና ጥፋት ራብና ሰይፍ ናቸው፤ እንዴትስ አድርጌ አጽናናሻለሁ? 20 ልጆችሽ ዝለዋል፤ በወጥመድ እንደተያዘ ሚዳቋ በአደባባይ ሁሉ ራስ ላይ ተኝተዋል፤ በእግዚአብሔር ቊጣና በአምላክሽ ተግሣጽ ተሞልተዋል። 21 አሁን ግን ይህንን ስሚ፣ ያለ ወይን ጠጅ የሰከርሽ አንቺ የተጨቈንሽ። 22 ስለ ወገኑ የሚምዋገት አምላክሽ ጌታሽ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "ተመልከቺ፣ የሚያንገደግድን ጽዋ የቊጣዬንም ዋንጫ ከእጅሽ ወስጃለሁ፤ ደግመሽም ከእንግዲህ ወዲህ አትጠጪውም። 23 ነፍስሽንም፣ 'እንሻገር ዘንድ ዝቅ በዪ፣ በሚሉአት በአስጨናቂዎችሽ እጅ አኖረዋለሁ፤' ጀርባሽንም ለሚሻገሩት እንደ መሬትና እንደ መንገድ አደረግሽላቸው።"

Isaiah 51:1

እኔን ስሙ
‹‹እኔን›› የሚለው ያህዌን ያመለክታል።

ወደ ዐለቱ... የወጣችሁበትንም ጕድጓድ ተመልከቱ
አንድን ነገር መመልከት ስለዚያ ነገር ማሰብን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ስለ ዐለቱ.. ስለ ወጣችሁበት ጕድጓድ አስቡ››

ተቆርጣችሁ የወጣችሁበትን ዐለት፣ ተቆፍራችሁ የወጣችሁበትንም ጕድጓድ ተመልከቱ
እግዚአብሔር ስለ እስራኤል ሕዝብ ሲናገር፣ ከድንጋይ የተሠራ ሕንፃ እንደሆኑና የጥንት አባቶቻቸውም እግዚአብሔር እነርሱን የቆረጠበት ዐለት ወይም ጕድጓድ እንደሆኑ ይናገራል። ይህን ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የጥንት አባቶቻችሁ ተቆርጣችሁ እንደ ወጣችሁበት ዐለት፣ ተቆፍራችሁም እንደወጣችሁበት ጕድጓድ ናቸው››

ተቆርጣችሁ የወጣችሁበት ዓለት
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እኔ ቆርጬ ያወጣኃችሁ ዐለት››

መሮ
‹‹በመሮ መቁረጥ›› ወይም፣ ‹‹መቆፈር››

የተቆፈራችሁበት ጕድጓድ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እኔ እናንተን የቆፈርሁበት ጕድጓድ››

Isaiah 51:2

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

አባታችሁ፣ አብርሃም
እግዚአብሔር የጥንት ዝርያዎቻቸው አባት እንደሆነ ይናገራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የጥንት አባታችሁ አብርሃም›› ወይም፣ ‹‹የዘር ግንዳችሁ አብርሃም››

የወለደቻችሁ ሣራ
የአብርሃም ሚስት ሣራ እነርሱን የወለደች እናት እንደሆነች እግዚአብሔር ይናገራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የዘር ግንዳችሁ የሆነች የአብርሃም ሚስት ሣራ››

ብቻውን በነበረ ጊዜ
ይህ ማለት ምንም ልጅ ሳይኖረው ማለት ነው። ይህን ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ምንም ልጅ በሌለው ጊዜ››

አበዛሁት
የአብርሃም ዘሮች መብዛት የአብርሃም መብዛት እንደሆነ እግዚአብሔር ይናገራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ዘሮቹን አበዛሁ›› ወይም፣ ‹‹ብዙ ዘሮች እንዲኖሩት አደረግሁ››

Isaiah 51:3

ያህዌ ጽዮንን ያጽናናታል
ኢየሩሳሌም ተብላ የምትጠራው የጽዮን ከተማ እዚህ ላይ የጽዮንን ሕዝብ ትወክላለች። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ የጽዮንን ሕዝብ ያጽናናል››

የፈራረሱ ቦታዎቿን ያጽናናል
‹‹የፈራረሱ ቦታዎች›› በእነዚያ ጠፍ ቦታዎች የሚኖረውን ሕዝብ ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በፈራረሱ ቦታዎቿ የሚኖረውን ሕዝብ ያጽናናል››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የፈራረሱ ቦታዎቿ... ምድረ በዳዎቿ... በረሓ መስኮቿ
‹‹እርሷ›› የሚለው ጽዮንን ያመላክታል። ብዙውን ጊዜ ከተሞች በሴት ጾታ ያጠራሉ።

የፈራረሱ ቦታዎች
የወደሙ ቦታዎች ማለት ነው

ምድ በዳዋን፣ በረሓ መስኮቿን እንደ ዔደን፣... እንደ እግዚአብሔር ተክል ቦታ ያደርጋል
እነዚህ ሐረጐች በእስራኤል ያሉ ባዶ ቦታዎችን እግዚአብሔር ውብ እንደሚያደርግ ይናገራሉ። ትንቢቶቹ ወደ ፊት የሚሆኑት ነገሮች ባለፈው ጊዜ እንደ ተደረጉ ተነግሯል። ይህ አጽንዖት የሚሰጠው በእርግጥ እንደሚፈጸም ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ምድረ በዳውን በረሓ፣ መስኮቿን እንደ ዔደን... እንደ እግዚአብሔር ተክል ቦታ ያደርጋል።››

ተድላና ደስታ በውስጧ ይገኛል
ተድላና ደስታ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። እዚያ ይገኛል ማለት እዚያ ይሆናል ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ተድላና ደስታ እንደ ገና በጽዮን ይሆናል››

Isaiah 51:4

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ ይናገራል።

ስሙኝ... አድምጡኝ
እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። በአንድነት ሲሆኑ እንዲሰሙ የተሰጠውን ትእዛዝ ያጠናክራሉ።

ፍርዴም ለሕዝቦች ብርሃን ይሆናል
ፍርድ የእግዚአብሔርን ሕግ ይወክላል፤ ብርሃን ደግሞ እውነት የሆነውን ማወቅን ይወክላል። ይህም ማለት ሕዝቦች የእግዚአብሔርን ሕግ ያውቃሉ፤ ይታዘዛሉ ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እውነት የሆነውን ለሕዝቦች አስተምራለሁ›› ወይም፣ ‹‹ሕዝቦች ሕጌን ያውቃሉ››

ጽድቄ ቀርቦአል
‹‹ቀርቦአል›› የሚለው ሐሳብ፣ ‹‹ደርሶአል›› ማለት ነው። የእግዚአብሔር ጽድቅ ቀርቦአል ማለት በቅርቡ ጽድቁን ይገልጣል ማለት ነው። ይህንንም የሚያደርገው ተስፋውን በመፈጸምና ሰዎችን በማዳን ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በቅርቡ ጽድቄን አሳያለሁ››

ማዳኔም እየወጣ ነው
የእርሱ ማዳን ወደ እነርሱ እየወጣ ያለ ነገር እንደሆነ እግዚአብሔር ይናገራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሕዝብን አድናለሁ››

ክንዴ በሕዝቦች ላይ ይፈርዳል
የእግዚአብሔር ክንድ ኀይሉን ይወክላል፤ ፍርዱ መግዛትን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በኀይሌ ሕዝቦችን እገዛለሁ››

ደሴቶች
ይህ የሚያመለክተው ከባሕር ማዶ ሩቅ አገር ደሴቶች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በደሴቶች የሚኖሩ ሰዎች›› ወይም፣ ‹‹ከባሕሩ ማዶ ባለው ምድር የሚኖሩ ሰዎች››

ክንዴንም በተስፋ ይጠብቃሉ
የእግዚአብሔር ክንድ እርሱ የሚያደርገውን ይወክላል። እዚህ ላይ ሰዎችን ማዳኑን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አንዳች ነገር እንዳደርግ በተስፋ ይጠብቃሉ›› ወይም፣ ‹‹እንዳድናቸው በተስፋ ይጠባበቃሉ››

Isaiah 51:6

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

ዐይኖቻችሁን ወደ ሰማይ አንሡ
ዐይኖችን ማንሣት ከላይ ያለ ነገር ማየትን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ወደ ሰማይ እዩ››

እንደ ጢስ... እንደ ልብስ... እንደ አሸን
እነዚህ ሁሉ ቶሎ የሚጠፉ ጥቅም የለሽ ነገሮችን ያመለክታሉ።

ማዳኔ ግን ለዘላለም ይኖራል
እዚህ ላይ፣ የእግዚአብሔር፣ ‹‹ማዳን›› የማዳኑን ውጤት ነጻነትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አድናችኃለሁ እናንተም ለዘላለም ነጻ ትሆናላችሁ››

ጽድቄም መጨረሻ የለውም
የእግዚአብሔር ጽድቅ በጽድቅ መግዛቱን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ የጽድቅ አገዛዜ መጨረሻ የለውም›› ወይም፣ ‹‹በጽድቅ ለዘላለም እገዛለሁ››

Isaiah 51:7

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል

ሕጌን በልባችሁ ያኖራችሁ
የእግዚአብሔርን ሕግ በልብ ማኖር የእግዚአብሔርን ሕግ ማወቅንና ለመታዘዝ መፈለግን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሕጌን የምታውቁና የምታከብሩ››

ሰዎች ሲበድሏችሁ ተስፋ አትቁረጡ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሲበድሏችሁ ልባችሁ አይዛል››

ብል እንደ ልብስ ይበላቸዋል፤ ትል እንደ በግ ጠጕር ያነክታቸዋል
ጻድቃንን የሚበድሉ ሰዎች እንደ ልብስ ብል እንደሚበላቸው፤ እንደ በግ ጠጕር ትል እንደሚያነክታቸው እግዚአብሔር ይናገራል።

ጽድቄ ለዘላለም ይኖራል
የእግዚአብሔር ጽድቅ በጽድቅ መግዛቱን፣ ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የጽድቅ ግዛቴ ለዘላለም ነው›› ወይም፣ ‹‹ለዘላለም በጽድቅ እገዛለሁ››

ማዳኔም ከትውልድ እስከ ትውልድ ነው
የእግዚአብሔር ማዳን የማዳኑን ውጤት ነጻነትን ይወክላል። ‹‹ከትውልድ እስከ ትውልድ›› ለዘላለም መኖርን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አድናችኃለሁ፣ እናንተም ለዘላለም ነጻ ትሆናላችሁ››

Isaiah 51:9

የያህዌ ክንድ ሆይ ተነሥ፣ ተነሥ ኀይልህንም ልበስ
የእርሱ ክንድ ሰው የሆነ ይመስል ሰዎች የያህዌ ክንድ በፍጥነት እንዲረዳቸው ይጠይቃሉ። ለክንድ መናገር ያልተለመደ ከሆነ በቀጥታ ለያህዌ እንዲናገር ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ ሆይ፣ ተነሥ፣ ተነሥ ኀይልህንም ልበስ››

የያህዌ ክንድ ሆይ... ተነሥ
እየረዳቸው ስላልነበረ ሰዎች የያህዌ ክንድ ከእንቅልፍ እንዲነሣ ይጠይቃሉ። ‹‹የያህዌ ክንድ›› ያህዌን በተለይም ሰዎችን መርዳቱን ይወክላል። ‹‹ተነሥ›› የሚለው ቃል የተደገመው ሰዎቹ ያህዌ ቶሎ እንዲረዳቸው አጥብቀው መፈለጋቸውን ለማሳየት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጎይልህንም ልበስ
ጎይል በጦርነት ጊዜ ብርታት እንዲሆናቸው የሚለበስ ልብስ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ራስህን አበርታ››

ረዓብን የቆራረጥህ፣ ታላቁን ዘንዶ የወጋህ አንተ አይደለህምን?
ተናጋሪው የያህዌ ጎይል ታላቅ ነገር እንዲያደርግ አጽንዖት ለመስጠት በጥያቄዎች ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተ ረዓብን የቆራረጥህ፣ ታላቁን ዘንዶ የወጋህ›› ረዓብ ባሕር ውስጥ የሚኖር እባብ ነው። ረዓብ የግብፅን መንግሥት ወይም ክፋትና ሁከት ይወክላል።

የዳኑት እንዲሻገሩ... ባሕሩን ያደረቅህ አንተ አይደለህምን?
የያህዌ ጎይል ታላቅ ነገር እንዲያደርግ አጽንዖት ለመስጠት ተናጋሪው እንደ ገና በጥያቄዎች ይጠቀማል። ይህ የሚያመለክተው እስራኤላውያን በዚያ ውስጥ ተሻግረው ከግብፃውያን ሰራዊት እንዲያመልጡ ያህዌ ቀይ ባሕርን መክፈሉን ነው።

Isaiah 51:11

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ከኢሳይያስ 38፥10 ጋር በጣም ይመሳሰላል።

ያህዌ የተቤዣቸው
‹‹መቤዠት›› ማለት፣ ‹‹መታደግ›› ማለት ነው። ይህ የሚያመለክተው ያህዌ የታደጋቸውን ሰዎች ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ የታደጋቸው››

ደስታ ለዘላለም ራሳቸው ላይ ይሆናል
የሰው ራስ የሰው ሁለንተና ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለዘላለም ደስ ይሰኛሉ››

ተድላና ደስታ... ሐዘንና ልቅሶ
እንደ፣ ‹‹ሐዘን›› እና ‹‹ልቅሶ›› ሁሉ፣ ‹‹ተድላ›› እና ‹‹ደስታ›› በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው። በአንድነት ሲሆኑ እነዚህ ስሜቶች ምን ያህል ብርቱ እንደሆኑ አጽንዖት ይሰጣሉ።

ተድላና ደስታ ያጥለቀልቃቸዋል
ይህ የሚያመለክተው እንደ ብርቱ ወንዝ ተድላና ደስታ ሕዝቡን እንደሚያጥለቀልቁ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በተድላና በደስታ ይዋጣሉ›› ወይም፣ እጅግ ደስ ይላቸዋል ሐሤትም ያደርጋሉ››

ሐዘንና ልቅሶም ከእነርሱ ይሸሻሉ
እነዚህ ስሜቶች ሸሽተው የሚያመልጡ ይመስል ሕዝቡ ከእንግዲህ ሐዘንና ልቅሶ እንደማይገጥመው ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእንግዲህ ወዲህ አያዝኑም አያለቅሱም››

Isaiah 51:12

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል

እኔ፣ እኔ፣ እርሱ ነኝ
‹‹እኔ›› የሚለው የተደገመው አጽንዖት ለመስጠት ነው። በቋንቋህ ይህ ያልተለመደ ከሆነ ድግግሙን መተው ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ እርሱ ነኝ››

እንደ ሣር የሆኑ ሰዎችን... ለምን ትፈራለህ?
ጥያቄው የቀረበው የጌታ ጥበቃ ያላቸው ሰዎችን መፍራት እንደሌለባቸው አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህን ዐረፍተ ነገር ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ሣር የሆኑትን ሰዎች... አትፍራ››

እንደ ሣር የሆነውን
የሰው ሕይወት አጭር መሆኑንና ቶሎ እንደሚሞት አጽንዖት ለመስጠት ሰዎችን ከሣር ጋር ይመሳስላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ሣር ኖረው በፍጥነት የሚሞቱትን›› ወይም ‹‹እንደ ሣር ጠውልገው ቶሎ የሚጠፉትን››

እንደ... የሆኑትን
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ... የሆኑ››

Isaiah 51:13

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

ያህዌን ለምን ረሳህ... ምድርን?
ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው እርሱን መርሳት እንደሌለባቸው አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህን ዐረፍተ ነገር ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌን መርሳት አልነበረብህም... ምድር››

የፈጠረህን
ኢሳይያስ 17፥7 ላይ ይህን የያህዌን ስም እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

ሰማያትን የዘረጋውን
‹‹ሰማያትን መዘርጋት›› አንድ ሰው ትልቅ ልብስ በሚዘረጋበት ሁኔታ እርሱም ሰማያትን የዘረጋ ይመስል ያህዌ ሰማያትን እንደ ፈጠረ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰማያትን እንደ ልብስ የዘረጋውን››

የምድር መሠረቶች
በተለምዶ መሠረት ከታች ሆኖ ሕንፃውን የሚደግፍ የድንጋይ ሥራ ነው። እዚህም ላይ ምድርን በቦታዋ የያዘና የቆመ መሠረት ነው ተብሎ ይታሰብ እንደ ነበር ያመለክታል። ኢሳይያስ 24፥18 ላይ ይህን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

ለማጥፋት የወሰነ የጨቋኙ
‹‹ለማጥፋት የተዘጋጀ፤ የጨቋኙ ጽኑ ቁጣ››

ጽኑ ቁጣ
‹‹ጽኑ›› ማለት ‹‹ብርቱ›› ወይም ‹‹ታላቅ›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ታላቅ ቁጣ››

የጨቋኙ ቁጣ የት አለ?
ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው ሕዝቡ ጨቋኞችን መፍራት እንደሌለባቸው አጽንዖት ለመስጠት ነው። ጨቋኞቹ ይህን ያህል አስፈሪዎች አይደሉም። ይህን በዐረፍተ ነገር መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የጨቋኙ ቁጣ ያን ያህል አስፈሪ አይደለም››

Isaiah 51:14

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

ዐንገታቸውን የደፉ
ይህ የሚያመለክተው የባቢሎናውያን ባርያዎች የነበሩትን እስራኤላውያን ነው። ይህ ሐረግ እንዴት ይሠሩ እንደ ነበር ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ባርያዎቹ››

ጥልቁ
ይህ የሚያመለክተው ሲኦልን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሲኦል ጥልቅ›› ወይም ‹‹መቃብር››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንጀራም አይጐድልበትም
‹‹እንጀራ›› ጠቅላላ ምግብን ይወክላል። ይህን በሌላ መልኩ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ምግብ አያጣም››

ባሕሩን የማማሰል
ይህ የሚያመለክተው አንድ ትልቅ ጐድጓዳ ሳህን ውስጥ ያለውን በማማሰያ እንደማማሰል ያህዌ ማዕበሉን ወደ ፊትና ወደ ኃላ፣ ወደ ላይና ወደ ታች የሚያደርገው መሆኑን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ባሕሩን የሚያማስለው›› ወይም፣ ‹‹ባሕሩን ወደ ላይ ወደ ታች የሚያደርገው››

ማዕበሉ እንዲያገሣ
ማዓራት ድብን ወይም አንበሳን ከመሳሰሉ በሕይወት ካሉ ነገሮች የሚወጣ ጎይለኛ፣ ጯኺ ድምፅ ነው። እዚህ ላይ ማዕበሉ ተመሳሳይ ድምፅ እንደሚያወጣ ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ማዕበሉ በጩኸት ይላተማል››

የሰራዊት ጌታ ያህዌ
ኢሳይያስ 1፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

Isaiah 51:16

ቃሌን በአፍህ አኖርሁ
ይህ የሚናገረው ቃሉ አንዳች ቁሳዊ ነገር ይመስል፣ ኢሳይያስ አፍ ውስጥ በማኖር ያህዌ ለኢሳይያስ ምን ማለት እንዳለበት የነገረው መሆኑን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ምን እንደምትል ነግሬሃለሁ››

በእጄ ጥላ ጋረድሁህ
የያህዌ፣ ‹‹እጅ›› ጎይሉን ያመለክታል። እርሱን ለመጠበቅ እጁ የሸፈነው ይመስል ያህዌ ኢሳይያስን እንደሚጠብቀው ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጎይሌ ጠብቆሃል›› ወይም፣ ‹‹ጋረድሁህ፤ በሰላምም ጠበቅሁህ››

ሰማያትን የተከልሁ
‹‹መትከል›› አንድን ነገር መሬት ውስጥ ማኖር ማለት ነው። እዚህ ያህዌ ሰማያትን ማጽናቱ፣ ሰማያት እርሱ የሚዘረጋው ድንኳን እንደሆኑና በካስማ አጥብቆ የተከላቸው መሆኑን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰማያትን አጸናሁ››

ምድርን መሠረትሁ
በተለምዶ፣ ‹‹መሠረት›› ማለት ሕንፃውን ደግፎ የሚይዝ ከበታቹ ያለ የድንጋይ ሥራ ነው። እዚህም ላይ ምድርን በቦታዋ የሚይዝ ተመሳሳይ ዐይነት ነገር እንደሆነ ተነግሯል። ኢሳይያስ 24፥18 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

Isaiah 51:17

ተነሺ ተነሺ ኢየሩሳሌም ሆይ ቁሚ
ኢየሩሳሌም እዚያ የሚኖረውን ሕዝብ ትወክላለች። ያህዌ የኢየሩሳሌም ሕዝብ እዚያ ሆነው እንደሚሰሙ አድርጐ ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ተነሡ፣ ተነሡ፣ የኢየሩሳሌም ሕዝብ ንቁ››

ተነሺ፣ ተነሺ፣ ቁሚ
‹‹ንቂ፣ ተነሺ›› ተነሺ የሚለው ቃል መደገሙ የእስራኤል ሕዝብ እንዲነሣ የቀረበው ጥሪ አስቸኳይ መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት ነው። ቃል በቃል እነርሱን ከእንቅልፍ የሚቀሰቅስ ጥሪ አይደለም።

ከያህዌ እጅ የጠጣሽ... የሚያንገደግደውን ዋንጫ ጭላጭ የጨለጥሽ።
ያህዌ ሕዝቡን መቅጣቱ፤ በቁጣው ከሞላውን ዋንጫ ለመጠጣት መገደድ መሆኑ ተነግሯል። ከቁጣው ዋንጫ ከጠጡ በኃላ ብዙ ወይን ጠጅ ጠጥቶ እንደ ሰከረ ሰው ይንገዳገዳሉ።

ዝቃጭ
ዝቃጭ የሚባለው ፈሳሽ ሥር የሚቀር ጠጣሩ ነገር ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ዝቃጩ እንኳ ሳይቀር››

ከያህዌ እጅ
ዋንጫውን ለሕዝቡ የሚሰጠው እርሱ መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት እዚህ ላይ የያህዌ እጅ የሚያመለክተው ያህዌ ራሱን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እርሱ የሰጣችሁን››

ከሚያንገዳግድ ዋንጫ
‹‹በወይን ጠጅ እንደ ሰከረ ሰው እንድትንገዳገዱ ከሚያደርግ ዋንጫ››

መንገዳገድ
ቀጥ ብሎ አለመሄድ፣ ሲራመዱ መሰናከል

የመራት አልነበረም... እጇን ይዞ የወሰዳት... አልነበረም
ሁለቱ ሐረጐች ተመሳሳይ ነገር ማለት በመሆናቸው መዋሐድ ይችላሉ። ይህ የሚያመለክተው ከተማዋ እንደ ሰከረች፣ እጇንም ይዞ የሚመራ እንደሌላት ሴት ኢየሩሳሌምም ዐቅመ ቢስ መሆንዋን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሚረዳሽ የለም! እጇን ይዞ የሚመራት ልጅ እንደሌላት ሰካራም ሴት ነሽ››

Isaiah 51:19

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

የሚያዝንልሽ ማነው? የሚያጽናናሽ ማነው?
ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው የሚያዝንላቸው ወይም የሚያጽናናቸው አለመኖሩን አጽንዖት ለመስጠት ነው። ጥያቄዎቹን ዐረፍተ ነገር ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሚያዝልሽ የለም... የሚያጽናናሽ የለም››

እነዚህ ሁለት መዓቶች
ሁለቱ ‹‹መዓቶች›› የተባሉት፣ ‹‹መፈራረስና ጥፋት››፣ ‹‹ራብና ሰይፍ›› ናቸው።

መፈራረስና ጥፋት
እነዚህ ሁለት ቃሎች ተመሳሳይ ትርጒም አላቸው፤ የጠላት ሰራዊት ምድሪቱን እንደሚያጠፋ አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጠላቶቻችሁ ምድራችሁን ባዶና ጠፍ አድርገዋል››

ራብና ሰይፍ
‹‹ራብ›› እና፣ ‹‹ሰይፍ›› በሕዝቡ ላይ የሚመጣውን መዓት ያመለክታሉ። ‹‹ሰይፍ›› ጦርነትን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ብዙዎቻችሁ›› በራብና በጦርነት ትሞታላችሁ››

በየጐዳናው ጥግ ተጋድመዋል
ይህ አጠቃላይ አነጋገር ነው። ብዙዎች በየጐዳናው ጥግ ይጋደማሉ ሲባል ሁሉም ማለት አይደለም። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹መንገዱ ላይ ይጋደማሉ››

በወጥመድ እንደ ተያዘ ሚዳቋ
ይህ የሚያመለክተው በወጥመድ እንደ ተያዘ ሚዳቋ ሕፃናት በጣም መድከማቸውንና ዐቅመ ቢስ መሆናቸውን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በወጥመድ እንደ ተያዘ ሚዳቋ ዐቅመ ቢስ ሆነዋል›› ወይም፣ ‹‹ወጥመድ እንደ ያዘው ሚዳቋ ዐቅመ ቢስ››

ሚዳቋ
ይህ አጋዘን የሚመስል፣ ቀንድ ያለውና በፍጥነት የሚሮጥ እንስሳ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አጋዘን››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በያህዌ ቁጣ በአምላካችሁ ተግሣጽ ተሞልተዋል።
የያህዌ፣ ‹‹ቁጣ›› እነርሱን ስለ ተቆጣ ያህዌ ሕዝቡን መቅጣቱን ያመለክታል። ይህ የሚያመለክተው በያህዌ ቁጣ የተሞሉ ያህል ሕዝቡ ክፉኛ መቀጣታቸውን ነው። ‹‹ተግሣጽ›› የሚለውን ቃል ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እርሱ ስለ ተቆጣቸውና ስለ ገሠጻቸው ያህዌ ክፉኛ ቀጣቸው››

Isaiah 51:21

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

አንቺ የተጐዳሽ፣ የሰከርሽ
ያህዌ፣ ‹‹አንቺ›› የሚለው የተጐዳውን ሕዝብ ለማመልከት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እናንት የተጐዳችሁና የሰከራችሁ ሕዝብ››

ያለ ወይን ጠጅ የሰከርሽ
ከያህዌ ቁጣ ዋንጫ እንዲጠጡ በመገደድ እንደ ሰከሩ ሁሉ፣ ከመከራቸው ብዛት የተነሣ እንደ ሰካራም ስለሆኑ ሰዎች ይናገራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የያህዌን ቁጣ ዋንጫ ጠጥታችሁ የሰከራችሁ›› ወይም፣ ‹‹በደረሰባችሁ ከባድ መከራ እንደ ሰካራም የሆናችሁ››

እነሆ፣ የሚያንገደግደውን ዋንጫ፣ የቁጣዬ ዋንጫ የሆነውን ጽዋ ከእጅሽ ወስጃለሁ፤ ከእንግዲህ
ቁጣው ከእነርሱ ያራቀው ዋንጫ ይመስል፣ ከእንዲህ ያህዌ በሕዝቡ እንደማይቆጣ ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከእንግዲህ በአንቺ ላይ አልቆጣም፤ ያንገዳገደሽን ጽዋ፣ ቁጣዬ የሞላበትን ዋንጫ ከአንቺ ወስጃለሁ››

እነሆ
ይህ ጥቅም ላይ የዋለው ቀጥሎ ለሚናገረው የአድማጮችን ትኩረት ለመሳብ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አድምጡ››

የሚያንገደግድ ዋንጫ
‹‹ዋንጫ›› የሚለው ዋንጫው ውስጥ ያለውን ለማመልከት ነው። ኢሳይያስ 51፥17 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሕዝብን የሚያንገደግድ የወይን ጠጅ ዋንጫ››

የቁጣዬ ዋንጫ የሆነው ጽዋ
ያህዌ በቁጣው ከተሞላው ጽዋ እንዲጠጡ ያስገደደ ያህል ሕዝቡን እንደቀጣ ይናገራል። ኢሳይያስ 51፥17 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በቁጣዬ የተሞላ ጽዋ›› ወይም፣ ‹‹ቁጣዬ የሞላበት ዋንጫ››

Isaiah 51:23

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

በአስጨነቁሽ እጅ አደርጋዋለሁ
በቁጣው የሞላውን ዋንጫ እንዲጠጡ ያስገደዳቸው ያህል ያህዌ ጠላቶቻቸውን እንደሚቀጣ ይናገራል።

በአስጨነቁሽ እጅ አደርጋዋለሁ
ዋንጫው እጃቸው ላይ እንዲሆን በማድረግ ዋንጫው ውስጥ ካለው እንዲጠጡ ያህዌ ያስገድዳቸዋል ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጠላቶችህን ከቁጣዬ ጽዋ ወይን ጠጅ እንዲጠጡ አስገድዳለሁ››

አስጨናቂዎችሽ
አስጨናቂዎች የሚለውን ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አንቺን ያስጨነቁ›› ወይም፣ ‹‹መከራ ያደረሱብሽ››

እንድንራመድበት ጀርባሽን እንደ መሬት፣ እንደ መንገድ አድርጊልን
ጠላቶቻቸው በጀርባቸው መረማመዳቸውን መንገድ ላይ ከመራመድ ጋር ያመሳስለዋል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጠላቶችሽ በጀርባሽ እንዲረማመዱ መንገድ ላይ ተጋደሚ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 52

1 ጽዮን ሆይ፣ ተነሺ፣ ተነሺ፣ ኃይልሽን ልበሺ፤ ቅድስቲቱ ከተማ ኢየሩሳሌም ሆይ፣ ያልተገረዘና ርኩስ ከእንግዲህ ወዲህ አይገባብሽምና ጌጠኛ ልብስሽን
ልበሺ። 2 ኢየሩሳሌም ሆይ፣ ትቢያን አራግፊ፤ ተነሺና ተቀመጪ፤ ምርኮኛይቱ የጽዮን ልጅ ሆይ፣ የአንገትሽን እስራት ፍቺ። 3 እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፣
"በከንቱ ተሸጣችሁ ነበር፣ ያለ ገንዘብም ትቤዣላችሁ።" 4 ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "ወገኔ በዚያ እንግዳ ሆኖ ይቀመጥ ዘንድ አስቀድሞ ወደ ግብጽ
ወረደ፣ አሦርም ቅርብ ጊዜ ላይ ያለ ምክንያት በደለው። 5 ወገኔ በከንቱ ተወስዶአልና አሁን ከዚህ ምን አለኝ? ይላል እግዚአብሔር፤ የሚገዙአቸው ይጮኻሉ፣
ይላል እግዚአብሔር፣ ስሜም ሁልጊዜ ቀኑን ሁሉ ይሰደባል። 6 ስለዚህ ወገኔ ስሜን ያውቃል፤ ስለዚህም የምናገር እኔ እንደ ሆንሁ በዚያ ቀን ያውቃሉ፤ አዎን፣ እኔ
ነኝ!" 7 የምስራች የሚናገር፣ ሰላምንም የሚያወራ፣ የመልካምንም ወሬ የምስራች የሚናገር፣ መድኃኒትንም የሚያወራ፣ ጽዮንንም፣ "አምላክሽ ነግሦአል!"
የሚል ሰው እግሩ በተራሮች ላይ እጅግ ያማረ ነው። 8 አድምጪ፣ ጕበኞችሽ ጮኸዋል፤ እግዚአብሔር ወደ ጽዮን በተመለሰ ጊዜ ዓይን በዓይን ይተያያሉና
ድምፃቸውን ያነሣሉ፣ በአንድነትም ይዘምራሉ። 9 እናንተ የኢየሩሳሌም ፍርስራሾች ሆይ፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን አጽናንቶአልና፤ ኢየሩሳሌምንም ታድጎአልና ደስ
ይበላችሁ፣ በአንድነትም ዘምሩ። 10 እግዚአብሔር የተቀደሰውን ክንዱን በአሕዛብ ሁሉ ፊት ገልጦአል፤ በምድር ዳርቻ የሚኖሩትም ሁሉ የአምላካችንን መድኃኒት
ያያሉ። 11 እናንተ የእግዚአብሔር ዕቃ የምትሸከሙ ሆይ፣ ትታችሁ ውጡ፣ ትታችሁ ውጡ፤ ከዚያ ውጡ፣ ርኩስን ነገር አትንኩ፣ ከመካከልዋ ውጡ፣ ንጽሑን
ሁኑ። 12 እግዚአብሔር ይቀድማችኋልና፣ የእስራኤልም አምላክ ይከተላችኋልና በችኰላ አትወጡም በመኰብለልም አትሄዱም። 13 ተመልከቱ፣ ባሪያዬ
በማስተዋል ያደርጋል፤ ይከብራል ከፍ ከፍም ይላል፣ እጅግ ታላቅም ይሆናል። 14 ፊቱ ከሰዎች ሁሉ ይልቅ፣ መልኩም ከሰዎች ልጆች ይልቅ ተጐሳቍሎአልና
ብዙ ሰዎች ስለ አንተ እንደ ተደነቁ፣ እንዲሁ ብዙ አሕዛብን ያስደንቃል፤ 15 ያልተነገረላቸውንም ያያሉና፣ ያልሰሙትንም ያስተውላሉና ነገሥታት ስለ እርሱ አፋቸውን
ይዘጋሉ።

Isaiah 52:1

ተነሺ ተነሺ
x

Isaiah 52:2

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል

ትቢያሽን አራግፊ፣ ኢየሩሳሌም ሆይ፣ ተነሺ፣ ተቀመጪ
‹‹ኢየሩሳሌም›› የምትወክለው እዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የኢየሩሳሌም ሰዎች፣ ትቢያችሁን አራግፉ፣ ተነሡ፣ ተቀመጡ››

ምርኮኛዪቱ፣ የዐንገትሽን እስራት አውልቀሽ ጣዪ
በባቢሎን ምርኮኞች በነበሩ ዘመን የኢየሩሳሌም ሰዎች አንገታቸው ላይ ሰንሰለት አድርገው እንደ ነበር ተመልክቶአል። ዐረፍተ ነገሩን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል።

የጽዮን ሴት ልጅ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። የከተማዋ፣ ‹‹ሴት ልጅ›› የከተማዋ ሕዝብ ማለት ነው። ኢሳይያስ 1፥8 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የጽዮን ሕዝብ›› ወይም፣ ‹‹በጽዮን የምትኖሩ ሰዎች››

ያለ ዋጋ ተሸጣችሁ ነበር፤ ያለ ገንዘብ ትቤዣላችሁ
ይህ የሚያመለክተው የእስራኤል ሕዝብ ባለቤት ያህዌ መሆኑን ነው። እውነተኛ ባለቤት እንደ መሆኑ እርሱ በወደደ ጊዜ ሊሸጣቸው ወይም መልሶ ሊወስዳቸው መብት አለው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያለ ዋጋ ሸጥኃችሁ፤ ያለ ገንዘብ እቤዣችኃለሁ››

Isaiah 52:4

በመጀመሪያ
እዚህ ላይ፣ ‹‹በመጀመሪያ›› የእስራኤል ታሪክ የተጀመረበትንና ሕዝብ የሆኑበትን ጊዜ ያመለክታል።

ወደ ግብፅ... ወረደ
‹‹ወደ ግብፅ... ሄደ›› ከከነዓን ወደ ግብፅ ሲጓዙ፣ ‹‹ወረደ›› ማለት የተለመደ ነበር።

አሦር አስጨነቀው
‹‹አሦር›› የሚያመለክተው የአሦርን ሕዝብ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የአሦር ሕዝብ ግፍ አደረገበት››

Isaiah 52:5

አሁን እዚህ ምን አለኝ... ሕዝቤ ያለ ምክንያት ተወስዷል?
ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው ሕዝቡ የሚናገረውን ልብ እንዲሉ ነው። ጥያቄውን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አሁን የሆነውን ተመልከቱ... ሕዝቤ ያለ ምክንያት ተወስዷል››

ያህዌ እንዲህ ይላል
የሚናገረውን እርግጠኝነት ለማሳየት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። ኢሳይያስ 30፥1 ላይ እንዳለው ተርጉመው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ይህ ያህዌ የተናገረው ነው›› ወይም፣ ‹‹እኔ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ››

ሕዝቤ ያለ ዋጋ መወሰዱን ሳይ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጠላት ሕዝቤን ያለ ዋጋ ሲወስደው አየሁ››

ያለ ዋጋ
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ያለ ዋጋ›› ማለት ባቢሎናውያን ሕዝቡን የወሰዱት በግፍ ወይም ያለ ምክንያት ነበር ማለት ነው፤ ወይም 2) ያህዌ የእስራኤል ሕዝብ ባለቤት መሆኑና ያለ ዋጋ ሊሸጣቸው ወይም ለገዛቸው መብት እንዳለው የሚናገረው የኢሳይያስ 52፥3 ላይ ያለው ቀጣይ ሊሆን ይችላል።

የገዟቸው ተላልቀውባቸዋል
ይህ የሚያመለክተው ሕዝቡን ድል ያደረጉትን ባቢሎናውያንን ነው። ይሁን እንጂ፣ አንዳንድ ቅጂዎች፣ ‹‹የገዟቸው ያለቅሳሉ›› ይላሉ። በእነዚህ ቅጂዎች መሠረት ይህ ጥቅስ የሚያመለክተው በምርኮ የነበሩ እስራኤላውያንን ይመሩ የነበሩ ሰዎች ነው።

ስሜ ቀኑን ሙሉ ያለ ማቋረጥ ይሰደባል
እዚህ ላይ፣ ‹‹ስም›› የያህዌን ማንነት ይወክላል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጠላት ሕዝቡን ሲወስድ የሚመለከቱ ስለ እኔ ያለ ማቋረጥ ክፉ ይናገራሉ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ስለዚህ ሕዝቤ ስሜን ያውቃል
እዚህ ላይ፣ ‹‹ስም›› የያህዌን ማንነት ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ስለዚህ ሕዝቤ በእውነት እኔ ማን መሆኔን ያውቃሉ››

Isaiah 52:7

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለእስራኤል ሕዝብ ይናገራል።

መልካም ዜና ይዘው የሚመጡ መልእክተኛ እግሮች በተራሮች ላይ ምንኛ ያማሩ ናቸው
እዚህ ላይ፣ ‹‹እግሮች›› እየተራመደ ያለውን መልእክተኛ ይወክላሉ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹መልካሙን ዜና ለመናገር በተራሮች ላይ የሚመጣውን መልእክተኛ ማየት በጣም ያማረ ነው››

ለጽዮን
እዚህ ላይ ‹‹ጽዮን፣›› የጽዮንን ሕዝብ ትወክላለች። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የጽዮን ሕዝብ››

ድምፃቸውን ያነሣሉ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ይጮኻሉ››

ዐይን ሁሉ
‹‹ዐይን›› መላውን ሰው ይወክላሉ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እያንዳንዳቸው››

Isaiah 52:9

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል

የኢየሩሳሌም ፍርስራሾች
ኢሳይያስ የኢየሩሳሌም ፍርስራሾች ደስ የሚሰኙ ሰዎች እንደሆኑ አድርጐ ይናገራል። ይህ ተሸንፈው የነበሩ የኢየሩሳሌምን ሰዎች ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በኢየሩሳሌም ፍርስራሽ መካከል የምትኖሩ ሰዎች››

ኢየሩሳሌምን ተቤዥቶአልና
‹‹ኢየሩሳሌም›› ሕዝቡን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ተቤዥቶአል››

የተቀደሰ ክንዱን ይገልጣል
‹‹ክንድ›› የያህዌን ኀይል ይወክላል። ያህዌ ቅዱስና ኀያል መሆኑን ለሕዝቡ ማሳየቱ እንደ አንድ ጦረኛ ካባውን አውልቆ ክንዱን በመግለጥ ለጦርነት መዘጋጀት መሆኑ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ቅድስናውንና ብርቱ ኀይሉን አሳየ››

ሕዝቦች ሁሉ፣ ምድር ሁሉ
‹‹ሕዝቦች›› እና፣ ‹‹ምድር›› በምድር ሁሉ ያሉ አገሮች ሕዝቦችን ይወክላሉ።

Isaiah 52:11

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

ተለዩ፣ ተለዩ
ይህ ቃል የተደገመው ምንም እንኳ ወዲያው ባይሆንም ሕዝቡ በእርግጥ መለየት እንዳለባቸው አጽንዖት ለመስጠት ነው።

ከዚያ ውጡ
የእስራኤል ሕዝብ በባቢሎን ባርያዎች እንደ ነበሩ ይታወቃል። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ባርያዎች ከሆናችሁበት ምድር ውጡ።

ርኩሱንም አትንኩ
መነካት ወይም መበላት እንደሌለበት ያህዌ የተናገረለት ነገር ንጹሕ እንዳልሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ የማይወደውን አትንኩ››

ከመካከልዋ ውጡ
‹‹እርሷ›› ባቢሎንን ይወክላል።

ያህዌ ፊት ፊታችሁ ይሄዳል፤ የእስራኤል አምላክ ደጀን ይሆንላችኋል
ያህዌ ሕዝቡን ከጠላቶቻችው መጠበቁ እርሱ ፊት ፊታቸው የሚሄድ፣ እነርሱን ለመጠበቅ ከሕዝቡ ኋላ እንዳለ ጦረኛ እንደሆነ ተነግሯል።

Isaiah 52:13

ገናና ይሆናል፤ ከፍ ከፍ ይላል፤ እጅግ ይከብራል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። ‹‹ገናና ይሆናል›› — ‹‹ከፍ ከፍ ይላል›› — ‹‹ይከብራል›› የተሰኙት ቃሎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ቢሆኑም፣ ያህዌ ባርያውን እንደሚያከብር አጽንዖት ይሰጣሉ። ኢሳይያስ 33፥10 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ለባርያዬ ከፍ ያለውን ክብር እሰጠዋለሁ››

በአንተ ደንግጠዋል
‹‹አንተ›› የሚለው የሚያመለክተው የያህዌን ባርያ ነው። ይሁን እንጂ፣ ተርጓሚዎች ‹‹አንተ›› የሚለውን፣ ‹‹እርሱ›› ማለት ይችላሉ።

መልኩ ከማንም ሰው የተለየ ጐሰቆለ
የያህዌ ባርያ መልክ የጐሰቆለው ጠላቶቹ ክፉኛ ስለ ደበደቡት ነው። የዚህን የተሟላ ትርጕም የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጠላቶቹ ክፉኛ ስለ ደበደቡት የሰው ልጅ እንኳ አይመስልም››

Isaiah 52:15

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ስለ ባርያው መናገር ቀጥሏል

ባርያዬ ብዙ ሕዝቦችን ይረጫል
ሰዎች በያህዌ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖራቸው ማድረግ፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖራቸው ሰዎችን በመሥዋዕቱ ደም የሚረጭ ካህን እንደሆነ ተደርጐ ተነግሯል።

ይረጫል
እዚህ ላይ ‹‹ይረጫል›› ተብሎ የተተረጐመው የዕብራይስጥ ቃል፣ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች እንዳደረጉት፣ ‹‹ያስደንቃል›› ወይም፣ ‹‹ያስገርማል›› ተብሎ ሊተረጐም ይችላል።

ብዙ ሕዝቦች
‹‹ሕዝቦች›› የየአገሩን ሰዎች ይወክላሉ።

ነገሥታት አፋቸውን ይዘጋሉ
‹‹አፋቸውን ይዘጋሉ›› ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ነገሥታት ማውራታቸውን ያቆማሉ›› ወይም፣ ‹‹ነገሥታት ዝም ይላሉ››

ያልተነገራቸው
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ማንም ያልነገራቸው›› ወይም፣ ‹‹ማንም ያልነገራቸውን ነገር››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 53

1 የሰማነውን ነገር ማን አምኖአል? የእግዚአብሔርስ ክንድ ለማን ተገልጦአል? **2** በፊቱ እንደ ቡቃያ፣ ከደረቅም መሬት እንደ ሥር አድጎአል። መልክና ውበት የለውም፣ ባየነውም ጊዜ እንወድደው ዘንድ ደም ግባት የለውም። **3** የተናቀ ከሰውም የተጠላ፣ የሕማም ሰው ደዌንም የሚያውቅ ነው። ሰውም ፊቱን እንደሚሰውርበት የተናቀ ነው፣ እኛም አላከበርነውም። **4** በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸክሞአል፤ እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ እንደ ተቸገረም ቈጠርነው። **5** እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፣ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፣ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን። **6** እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ፤ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ። **7** ተጨቆነ፣ ተሣቀየም አፉንም አልከፈተም፤ ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት፣ በሸላቶቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ፣ እንዲሁ አፉን አልከፈተም። **8** በማስጨነቅና በፍርድ ተወሰደ፤ ስለ ሕዝቤ ኃጢአት ተመትቶ ከሕያዋን ምድር እንደ ተወገደ ከትውልዱ ማን አስተዋለ? **9** ከክፉዎችም ጋር መቃብሩን አደረጉ፣ ከባለጠጎችም ጋር በሞቱ ሆኖም ግፍን አላደረገም ነበር፣ በአፉም ተንኮል አልተገኘበትም ነበር። **10** እግዚአብሔርም በደዌ ያደቅቀው ዘንድ ፈቀደ፤ ነፍሱን ስለ ኃጢአት መሥዋዕት ካደረገ በኋላ ዘሩን ያያል፣ ዕድሜውም ይረዝማል፣ የእግዚአብሔርም ፈቃድ በእጁ ይከናወናል። **11** ከነፍሱ መከራ በኋላ፣ ብርሃን ያያል ደስም ይለዋል፤ ጻድቅ ባሪያዬም በእውቀቱ ብዙ ሰዎችን ያጸድቃል፣ ኃጢአታቸውን ይሸከማል። **12** ስለዚህም እርሱ ብዙዎችን ይወርሳል፣ ከብዙ ኃያላንም ጋር ምርኮን ይከፋፈላል፤ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶአልና፣ ከዓመፀኞችም ጋር ተቈጥሮአልና፤ እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ተሸከመ፣ ስለ ዓመፀኞችም ማለደ።

Isaiah 53:1

አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ላይ ኢሳይያስ ወደ ፊት የሚሆኑ ነገሮችን ባለፈው ጊዜ እንደ ተፈጸሙ አድርጐ ይናገራል። ይህ በእርግጥ እንደሚሆን አጽንዖት ይሰጣል።

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ስለ ያህዌ ባርያ መናገር ቀጥሏል።

ከእኛ የሰሙትን ያመነ ማን ነው?
ኢሳይያስ የተረዳው በጣም አስገራሚ በመሆኑ ምርኮኞቹ ያምኑ እንደሆነ ይጠይቃል። ‹‹እኛ›› የሚለው እርሱንና በምርኮ ያሉትን ይጨምራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እኛ የሰማነውን ማመን በጣም ከባድ ነው››

የያህዌስ ክንድ ለማን ተገለጠ?
ክንድ የእግዚአብሔርን ኀይል ያመለክታል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ ኀይሉን ለሕዝቡ ገለጠ››

እርሱ በያህዌ ፊት እንደ ቡቃያ አደገ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እርሱ›› ኢሳይያስ ከቡቃያ ጋር የሚያመሳስለው የእግዚአብሔርን ባርያ ያመለክታል። ይህም እንደ ደካማ መገለጡ ያመለክታል።

ከደረቅም መሬት
‹‹ደረቅ መሬት›› ተክል የማያድግበት ጠንካራ መሬት ሲሆን፣ የያህዌ ባርያ የሚመጣበትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በፍጹም ከማይታሰብ ሁኔታ››

Isaiah 53:3

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ስለ ያህዌ ባርያ መናገር ቀጥሏል። (ኢሳይያስ 53፥1-2 ይመ.)

በሰዎች የተናቀና የተጠላ ነበር
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሰዎች እንደ ከንቱ ነገር ቆጥረው ናቁት››

የሐዘን ሰው
‹‹ማንኛውንም ሐዘን የሚያውቅ ሰው››

ሰዎች ፊታቸውን የሚሰወሩበት
‹‹ፊት›› የሰውን ትኩረትና ኀብረት ይወክላል። ፊትን መሰወር ፊትን ማዞር ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሰዎች ፊታቸውን የሚያዞሩበት››

የተናቀ ነበር
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ምንም ጥቅም እንደሌለው ቆጠሩት››

Isaiah 53:4

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ስለ ያህዌ ባርያ መናገር ቀጥሏል (ኢሳይያስ 53፥1-2 ይመ.)

ደዌያችንን ወስዶ፤ ሕመማችንንም ተሸከመ
‹‹መሸከም›› እንደ ሕመምና ሐዘን ሁሉ የነገር ስም ሲሆን፣ መውሰድን ይወክላል። ‹‹አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሕመማችንና ደዌያችንን በራሱ ወሰዶ››

እኛ ግን በእግዚአብሔር እንደ ተቀጣ፣ እንደ ተመታ፣ እንደ ተሠቃየም ቆጠርነው
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እግዚአብሔር እየቀጣውና እያሠቃየው እንደሆነ ቆጠርን››

Isaiah 53:5

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ስለ ያህዌ ባርያ መናገር ቀጥሏል (ኢሳይያስ 53፥1-2 ይመ.)

እርሱ ግን ስለ ክፉ ተግባራችን ተወጋ፣ ስለ ኀጢአታችንም ደቀቀ
እነዚህ ሁለት ሐረጐች ተመሳሳይ ትርጕም አላቸው፤ አጽንዖት የሚሰጡት የያህዌ ባርያ ያን ሁሉ መከራ የተቀበለው ስለ ሰዎች ኀጢአት መሆኑን ነው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከእኛ ኀጢአት የተነሣ ጠላት እንዲወጋውና እንዲገድለው እግዚአብሔር ፈቀደ››

የሰላማችን ቅጣት እርሱ ላይ ነበረ
ይህ የሚያመለክተው ከእግዚአብሔር ጋር ሰላምን ነው። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እኛ በሰምምነት እንድንኖር እርሱ ይህን ቅጣት ተቀበለ››

በእርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በእርሱ ስቃይና ቁስል ፈወሰን››

Isaiah 53:6

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ስለ ያህዌ ባርያ መናገር ቀጥሏል (ኢሳይያስ 53፥1-2 ይመ.)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እኛ ሁላችን እንደ በግ ተቅበዘበዝን
በጐች ብዙ ጊዜ እረኛው እነርሱን ከሚመራበት መንገድ ይወጣሉ። ኢሳይያስ ይህን ሲል እግዚአብሔር ካዘዘው ይልቅ፣ እኛ የወደድነውን እናደርጋለን ማለቱ ነው።

የሁላችንም ርኩሰት
እዚህ ላይ፣ ‹‹ርኩሰት› የኀጢአታችንን በደል ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የሁላችንም ኀጢአት በደል››

Isaiah 53:7

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ስለ ያህዌ ባርያ መናገር ቀጥሏል (ኢሳይያስ 53፥1-2 ይመ.)

ተጨነቀ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ግፍ አደረጉበት››

አፉን አልከፈቱም
‹‹አፍ›› ሰው የሚናገረውን ይወክላል። አፍን መክፈት መናገር ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አልተቃወመም››

ለዕርድ እንደሚነዳ ጠቦት፣ በሸላቾቹ ፊት ዝም እንደሚል በግ
ሰዎች ሲጐዱትና ሲያዋርዱት ዝም ማለቱን አጽንዖት ለመስጠት ኢሳይያስ የያህዌን ባርያ ከጠቦትና ከበግ ጋር ያመሳስለዋል።

ለዕርድ እንደሚነዳ በግ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሰው ሲያርደው ዝም እንደሚል ጠቦት››

Isaiah 53:8

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ስለ ያህዌ ባርያ መናገር ቀጥሏል (ኢሳይያስ 53፥1-2 ይመ.)

በማስጨነቅና በፍርድ ተወገዘ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። ‹‹ማስጨነቅ›› የሚለውን አንዳንድ ቅጂዎች ‹‹በእስራት›› ብለውታል። እንደ እነዚህ ቅጂዎች ከሆነ፣ የያህዌ ባርያ ይታሠራል፣ ከዚያም ይፈረድበታል፣ ይወገዛል ማለት ነው።

ከዚያ ትውልድ ስለ እርሱ የሚያስብ ማን ነው?
ጥያቄው አጽንዖት የሚሰጠው ስለ እርሱ የሚያስብ አለመኖሩን ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከእርሱ ትውልድ እርሱ ላይ ለሆነው የሚያስብ የለም›› ወይም፣ ‹‹በዘመኑ ከነበሩ ሰዎች መካከል እርሱ ላይ ስለ ሆነው የሚያስብ የለም።››

ከዚያ ትውልድ ስለ እርሱ የሚያስብ ማን ነው?
ይህን የዕብራይስጥ ምንባብ ብዙ ቅጂዎች በተለያየ መንገድ ተርጕመውታል። ‹‹ስለ ዘሮች የሚናገር ማን ነው?›› ወይም፣ ‹‹ስለ ዕጣ ፈንታው የሚናገር ማን ነው?››

እርሱ ግን ከሕያዋን ምድር ተቆረጠ
‹‹መቆረጥ›› መሞት ማለት ነው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እርሱ ግን ሞተ›› ወይም፣ ‹‹ግን ሞት ወሰደው››

ስለ ሕዝቤ
‹‹ስለ እስራኤል ሕዝብ››

በአፉ ምንም ተንኰል አልተገኘም
‹‹አፍ›› ሰው የሚናገረውን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በንግግሩ ማንንም አላታለለም››

Isaiah 53:10

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ስለ ያህዌ ባርያ መናገር ቀጥሏል (ኢሳይያስ 53፥1-2 ይመ.)

ዘሩን ያያል
እዚህ ላይ፣ ‹‹ዘሩ›› ማለት ከባርያው መሥዋዕት የተነሣ ያህዌ ይቅር ያላቸውን ሰዎች ነው።

ዕድሜውም ይረዝማል
ይህ የሚናገረው ብዙ ዘመን እንደሚኖር ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ ባርያውን እንደ ገና እንዲኖር ያደርጋል››

የያህዌ ዓላማ በእርሱ ይከናውናል
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ በባርያው በኩል ዓላማውን ያከናውናል››

ከሕይወቱ ስቃይ በኃላ
‹‹ሕይወቱ›› የሚለው የሚያመለክተው የያህዌን ባርያ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የያህዌ ባርያ መከራ ከተቀበለ በኃላ››

ብርሃን ያያል
እዚህ ላይ፣ ‹‹ብርሃን›› የሚለው ሕይወትን እንደሆነ ብዙ ቅጂዎች ይገነዘባሉ። ይህም ባርያው እንደ ገና ይኖራል ማለት ነው።

ጻድቅ ባርያዬ
እዚህ ላይ፣ ‹‹የእኔ›› የሚለው ያህዌ ነው።

ርኩሰታቸውን ይሸከማል
‹‹ይሸከማል›› ማለት፣ ይወስዳል ማለት ነው። ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ርኩሰታቸው›› የኀጢአታቸውን ቅጣት ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ቅጣታቸውን ይወሰድዳል›› ወይም፣ ‹‹ለኀጢአታቸው ይቀጣል›› ወይም 2) ‹‹ርኩሰታቸው›› በደልን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በደላቸውን በራሱ ይወስዳል›› ወይም፣ ‹‹ለኀጢአታቸው በደለኛ ይሆናል።››

Isaiah 53:12

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ስለ ባርያው መናገር ቀጥሏል።

ስለዚህ ድርሻውን ከታላላቆች ጋር እሰጠዋለሁ፤ ምርኮውንም ከብዙዎች ጋር ይከፋፈላል
ሁለቱም ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። ‹‹ድርሻ›› እና ‹‹ምርኮ›› ጦርነት በድል ከተጠናቀቀ በኃላ አንድ ንጉሥ የተዘረፈውን መካፈል ወይም ለወታደሮች መሸለምን ያመለክታሉ። ይህም ማለት ከመሥዋዕቱ የተነሣ ያህዌ ባርያውን እጅግ ያከብረዋል ማለት ነው።

ብዙዎች
ብዙ ቅጂዎች ይህን፣ ‹‹አያሌ›› ወይም፣ ‹‹ብርቱዎች›› በማለት ተርጕመዋል።

ራሱን ለሞት ስላጋለጠ
‹‹መጋለጥ›› ምቹ መሆን ወይም ያለ ምንም ከለላ ማለት ነው። የያህዌ ባርያ ራሱን የሚሞትበት ሁኔታ ውስጥ አኖረ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በፈቃደኝነት ለሞት መጋለጥን ተቀበለ››

ከሕግ ተላላፊዎች ጋር ተቆጠረ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሰዎች እንደ ወንጀለኛ እንዲቆጥሩት ፈቀደ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 54

1 "አንቺ ያልወለድሽ መካን ሆይ፣ ዘምሪ፤ አንቺ ያላማጥሽ ሆይ፣ እልል በዪ፣ ጩኺም፤ ባል ካላት ይልቅ ፈት የሆነቺቱ ልጆች በዝተዋልና፣" ይላል
እግዚአብሔር። 2 የድንኳንሽን ስፍራ አስፊ፣ መጋረጃዎችሽንም ይዘርጉ፤ አትቈጥቢ፤ አውታሮችሽን አስረዝሚ ካስሞችሽንም አጽኚ። 3 በቀኝና በግራ
ትሰፋፊያለሽና፣ ዘርሽም አሕዛብን ይወርሳልና፣ የፈረሱትንም ከተሞች መኖሪያ ያደርጋልና። 4 አታፍሪምና አትፍሪ፤ አተዋረጂምና አትደንግጪ፤ የሕፃንነትሽንም
እፍረት ትረሺዋለሽ፣ የመበለትነትሽንም ስድብ ከእንግዲህ ወዲህ አታስቢም። 5 ፈጣሪሽ ባልሽ ነው፣ ስሙም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው፤ የእስራኤልም
ቅዱስ ታዳጊሽ ነው፣ እርሱም የምድር ሁሉ አምላክ ይባላል። 6 እግዚአብሔር እንደ ተተወችና እንደ ተበሳጨች በልጅነትዋም እንደ ተጣለች ሚስት ጠርቶሻል፣
ይላል አምላክሽ። 7 "ለጥቂት ጊዜ ተውሁሽ፣ በታላቅም ምሕረት እሰበስብሻለሁ። 8 በጥቂት ቍጣ ለቅጽበት ዓይን ፊቴን ከአንቺ ሰወርሁ፣ በዘላለምም ቸርነት
እምርሻለሁ፣ ይላል ታዳጊሽ እግዚአብሔር። 9 ይህ ለእኔ እንደ ኖኅ ውኃ ነው፤ የኖኅ ውኃ ደግሞ በምድር ላይ እንዳያልፍ እንደ ማልሁ፣ እንዲሁ አንቺን እንዳልቈጣ
እንዳልገሥጽሽም ምያለሁ። 10 ተራሮች ይፈልሳሉ፣ ኮረብቶችም ይወገዳሉ፤ ቸርነቴ ግን ከአንቺ ዘንድ አይፈልስም የሰላሜም ቃል ኪዳን አይወገድም፣ ይላል
መሐሪሽ እግዚአብሔር። 11 አንቺ የተቸገርሽ በዐውሎ ነፋስም የተናወጥሽ ያልተጽናናሽም፣ ተመልከቺ፣ ድንጋዮችሽን ሸላልሜ እነሳባለሁ፣ በሰንፔርም
እመሠርትሻለሁ። 12 የግንብሽንም ጕልላት በቀይ ዕንቊ፣ በሮችሽንም በሚያብረቀርቅ ዕንቊ፣ ዳርቻሽንም ሁሉ በከበሩ ድንጋዮች እሠራለሁ። 13 ልጆችሽም
ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ፣ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል። 14 በጽድቅ ትታነጺያለሽ፤ ከግፍ ራቂ፣ አትፈሪምም፣ ድንጋጤም ወደ አንቺ
አትቀርብም። 15 ተመልከቺ፣ ይሰበሰባሉ፣ ነገር ግን ከእኔ ዘንድ አይሆንም፤ በአንቺም ላይ ችግር የሚፈጥሩ ሁሉ ይሸነፋሉ። 16 ተመልከቺ፣ ፍሙን በወናፍ
የሚያናፋ ለሥራውም መሣሪያ የሚያወጣ ብረት ሠሪን እኔ ፈጥሬአለሁ፤ የሚያፈርሰውንም እንዲያጠፋ ፈጥሬአለሁ። 17 በአንቺ ላይ የተሠራ መሣሪያ ሁሉ
አይከናወንም፤ በፍርድም በሚነሣብሽ ምላስ ሁሉ ትፈርጂበታለሽ። የእግዚአብሔር ባሪያዎች ርስት ይህ ነው፣ ጽድቃቸውም ከእኔ ዘንድ ነው፣" ይላል
እግዚአብሔር።

Isaiah 54:1

አንቺ መካን ሴት... ያላገባች ሴት ልጆች
እንደ ገና በኢየሩሳሌም ብዙ ሰዎች ስለሚኖሩ ደስ እንዲላቸው ያህዌ ለሕዝቡ ይናገራል። ይህንን በተመለከተ ያላገባች ሴት ብዙ ልጆች ይኖሩዋታል ማለት መሆኑን ያህዌ ይናገራል።

አንቺ ልጅ ወልደሽ የማታውቂ ዘምሪ፣ እልል በዪ፤ በደስታ ጩኺ
ይህ ከመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ጋር ተመሳሳይ ነው።

የተተወችው ሴት ልጆች በዝተዋልና
ወደ ፊት የሚሆነው ነገር ባለፈው ጊዜ እንደ ተፈጸመ ተደርጐ ተነግሯል። ይህም ነገሩ በእርግጥ እንደሚሆን አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የተተወችው ሴት ልጆች እጅግ ብዙ ይሆናሉ››

የተተወችው
እዚህ ላይ፣ ‹‹የተተወችው›› ማለት ባልዋ የናቃትና የተዋት ሴት ማለት ነው።

Isaiah 54:2

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

ድንኳንሽን አስፊ... ካስማሽንም አጠንክሪ
ይህ ኢሳይያስ 54፥1 ላይ የጀመረው ምሳሌ ቀጣይ ነው። ሕዝባቸው እጅግ ስለሚበዛ እንዲዘጋጁ ያህዌ ለኢየሩሳሌም ሰዎች ይናገራል፤ የሕዝባቸው መብዛት ለብዙ ልጆች የሚበቃ ክፍል እንዲኖር ድንኳንዋን እንድታሰፋ ይናገራል።

ትስፋፊያለሽ
እዚህ ላይ፣ ‹‹አንቺ›› ነጠላ ቁጥር ሲሆን፣ መካን ስለሆነች ሴት ያመለክታል። እርሷ የሚለው ራስዋንና ዘሮችዋን ሁሉ ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አንቺና ዘሮችሽ ትስፋፋላችሁ››

ሕዝቦችን ያሸንፉሉ
‹‹ሕዝቦች›› ሰዎችን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የሌላ አገር ሕዝቦችን ያሸንፋሉ››

Isaiah 54:4

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

የወጣትነት ሐፍረትና የመተውሽንም ውርደት ትረሺዋለሽ
ጠላቶቻቸው ሲያሸንፏቸው የተሰማቸው ሐፍረት ከእንግዲህ እንደማይሰማቸው ያህዌ ለሕዝቡ ይናገራል፤ ይህም ልጅ ባለመውለድዋና ባልዋ ስለ ተዋት እፍረት ከተሰማት ሴት ጋር ተመሳስሎአል።

Isaiah 54:5

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገር ቀጥሏል

ፈጣሪሽ ባልሽ ነው
ያህዌ ሕዝቡን መወደዱና መጠንቀቁ እርሱ ባላቸው እንደሆነ ተነግሯል።

ፈጣሪሽ
ይህን ኢሳይያስ 17፥7 እንደ ተረጐምህ ተርጕመው።

የሰራዊት ጌታ ያህዌ
ይህን ኢሳይያስ 1፥24 እንደ ተረጐምህ ተርጕመው

የእስራኤል ቅዱስ
ይህን ኢሳይያስ 5፥16 እንደ ተረጐምህ ተርጕመው

የሚቤዥሽ
ይህን ኢሳይያስ 41፥14 እንደ ተረጐምህ ተርጕመው።

የምድር ሁሉ አምላክ ይባላል
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እርሱ የምድር ሁሉ አምላክ ነው።››

ያህዌ እንደ ሚስት... በወጣትነትዋ እንዳገባችና እንደ ተተወች ሴት ጠርቶሻል
ያህዌ ሕዝቡ ወደ ምርኮ እንዲሄድና ተመልሶ እንዲመጣ ማድረጉ፣ እርሱ ሚስቱን ትቶ እንደ ነበር፣ አሁን ግን መልሶ እንደ ተቀበላት ባል እንደሆነ ተነግሯል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በመንፈስ ማዘን
እዚህ ላይ፣ ‹‹መንፈስ›› የሰውን ውስጣዊ ማንነት ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አዘነ›› ወይም፣ ‹‹ተከዘ››

Isaiah 54:7

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገር ቀጥሏል

በቁጣ ጐርፍ
የያህዌ በጣም መቆጣት ሕዝብን በሚያጥለቀልቅ ጐርፍ ተመስሎአል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በጣም በተቆጣሁ ጊዜ››

ፊቴን ከአንቺ ሰወርሁ
‹‹ፊትን መሰወር›› ያህዌ ሕዝቡን መተዉንና እንዲሠቃዩ መፍቀዱን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ተውሁሽ››

ነገር ግን በዘላለም ኪዳንና ታማኝነት
‹‹ታማኝነት›› የሚለውን ‹‹ታማኝ›› በማለት መተርጐም ይቻላል። ኢሳይያስ 16፥5 ላይ፣ ‹‹ኪዳናዊ ታማኝነት›› የሚለውን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ነገር ግን እኔ ከአንቺ ጋር ላደረግሁት ኪዳን ሁሌም ታማኝ ነኝ›› ወይም፣ ‹‹ቃል የገባቡልሽን ለመፈጸም እኔ ሁሌም ታማኝ ነኝ››

ይላል፣ ያህዌ ታዳጊሽ
እዚህ ላይ ያህዌ ስለ ራሱ በሦስተኛ ሰው ደረጃ ይናገራል። በመጀመሪያ ሰው መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እኔ ታዳጊሽ ያህዌ ለአንቺ የተናገርሁት ይህን ነው››

Isaiah 54:9

የኖኅ ውሆች
ይህ በኖኅ ዘመን ያህዌ ያደረገውን ጐርፍ ያመለክታል።

ተራሮች ቢወድቁና ኮረብቶችም ቢናወጡ እኔ ለአንቺ ያለኝ ፍቅር
እነዚህ መስፈርቶች ቢሟሉ ኖሮ ምን ይሆን እንደ ነበር ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ተራሮች ቢወድቁ፣ ኮረብቶችም ቢናወጡ ለአንቺ ያለኝ ፍቅር››

ኮረብቶችም ቢናወጡ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ኮረብቶች ይናወጡ ይሆናል››

ለአንቺ ያለኝ ፍቅር ግን ከአንቺ አይመለስም
ያህዌ ለሕዝቡ ያለው ቀጣይ ፍቅር፣ ከሕዝቡ በማይመለስ ነገር ተመስሎአል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አንቺን መውደዴን አልተውም››

የሰላሜም ኪዳን አይናወጥም
ያህዌ ከሕዝቡ ጋር ያለውን ኪዳን አለመሻሩ፣ ኪዳኑ የማይናወጥ ነገር እንደሆነ ተነግሯል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የሰላም ኪዳኔን አልሽርም›› ወይም፣ ‹‹በኪዳኔ በሰጠሁሽ ተስፋ መሠረት ሰላሜን በእርግጥ እሰጥሻለሁ››

የሚራራልሽ ያህዌ እንዲህ ይላል
እዚህ ላይ ያህዌ ስለ ራሱ በሦስተኛ ሰው ደረጃ ይናገራል። በመጀመሪያ ሰው መግለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የምራራልሽ እኔ ያህዌ የምለው ይህን ነው››

Isaiah 54:11

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

የተጨነቅሽ
እዚህ ላይ ያህዌ የምትሰማው ይመስል ለኢየሩሳሌም ይናገራል። ኢየሩሳሌም እዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ትወክላለች። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እናንት የተጨነቃችሁ የኢየሩሳሌም ሰዎች››

በዐውሎ ነፋስ የተወሰድሽ
ሕዝቡ በዐውሎ ነፋስና በማዕበል ተወስደውና ተጐድተው እንደ ነበር ያህዌ ይናገራል። ይህም በጣም የተጐዱና መረጋጋትም እንዳልነበራቸው ያመለክታል።

ያልተጽናናሽ
‹‹አጽናኝ የሌለሽ››

በሰንፔር ድንጋይ እመሠርትሻለሁ... በከበሩ ድንጋዮች አስጌጥሻለሁ
ያህዌ ኢየሩሳሌምን እንደሚመሠርትና ውብ እንደሚያደርጋት ባማሩ ቃላት ይናገራል። ምንም እንኳ የተጋነነ ቢመስልም ያህዌ በተናገረው መሠረት መተርጐም አለበት።

የሚያብረቀርቅ ዕንቁ... ሰንፔር... ቀይ ዕንቁ
እነዚህ ሁሉ የከበሩ ድንጋዮች ናቸው። የሚያብረቀርቅ ዕንቁ ነጣ ያለ ሰማያዊና አረንጓዴ ነው፤ ሰንፔር ጥቁር ሰማያዊ ነው፤ ቀይ ዕንቁ ቀይ ሐምራዊ ነው።

Isaiah 54:13

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገር ቀጥሏል

ልጆችሽ ከያህዌ የተማሩ ይሆናሉ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ ልጆችሽን ሁሉ ያስተምራል››

ከያህዌ
ያህዌ በሦስተኛ ሰው ደረጃ ስለ ራሱ ይናገራል። በመጀመሪያ ሰው ደረጃ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በእኔ በያህዌ››

በጽድቅ ትመሠረቻለሽ
‹‹ጽድቅ›› የሚለውን የነገር ስም፣ ‹‹ትክክል›› በሚለው መተርጐም ይቻላል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ትክክል የሆነውን ስለምታደርጊ እኔ አበረታሻለሁ››

አጠገብሽ አይደርሱም
በከተማው ወይም በውጪ ያለ ማንም ከእንግዲህ የኢየሩሳሌምን ነዋሪዎች አያስፈራቸውም።

Isaiah 54:15

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገር ቀጥሏል

መከራን የሚያሪግብ
‹‹የሚያሪግብ›› የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን፣ ‹‹ችግር የሚፈጥር›› ወይም፣ ‹‹የሚያውክሽ›› ማለት ነው።

ይሸነፋል
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን፣ ‹‹ድል ታደርጊያቸዋለሽ›› ማለት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Isaiah 54:17

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

በአንቺ ላይ የተሠራ መሣሪያ ይከሸፋል
የጠላት ሐሳብ በያህዌ ሕዝብ ላይ አለመሳካቱ፣ እነርሱ ላይ የተሠራ መሣሪያ መክሸፍ ማለት እንደሆነ ተነግሯል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጠላቶች አንቺ ላይ መሣሪያ ያበጁ ይሆናል፤ ግን አያሸንፉሽም››

የያህዌ ባርያዎች ርስት ይህ ነው
ለሚያገለግሉት ሰዎች ያህዌ የሚሰጠው ሽልማት ርስታቸው እንደሆነ ተነግሯል።

ይላል ያህዌ
የተናገረው እርግጥ መሆኑን ለማሳየት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። ኢሳይያስ 30፥1 ላይ ያለውን እንደ ተረጐምህ ተርጉመው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ የተናገረው ይህን ነው›› ወይም፣ ‹‹እኔ ያህዌ የተናገርሁት ይህን ነው››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 55

1 "እናንተ የተጠማችሁ ሁሉ፣ ወደ ውኃ ኑ፣ ገንዘብም የሌላችሁ ኑና ግዙ ብሉም፤ ኑ ያለ ገንዘብም ያለ ዋጋም የወይን ጠጅና ወተት ግዙ። **2** ገንዘብን እንጀራ ላይደለ፣ የድካማችሁንም ዋጋ ለማያጠግብ ነገር ለምን ትመዝናላችሁ? በጥንቃቄ አድምጡኝ በረከትንም ብሉ፣ ሰውነታችሁም በጮማ ደስ ይበለው። **3** ጆሮአችሁን አዘንብሉ ወደ እኔም ቅረቡ! ስሙ፣ ሰውነታችሁም በሕይወት ትኖራለች! የታመነችይቱን የዳዊትን ምሕረት፣ የዘላለምን ቃል ኪዳን ከእናንተ ጋር አደርጋለሁ። **4** ተመልከቱ፣ ለአሕዛብ ምስክር፣ ለወገኖችም አለቃና አዛዥ እንዲሆን ሰጥቼዋለሁ። **5** ተመልከቱ፣ የማታውቀውን ሕዝብ ትጠራለህ፤ የእስራኤልም ቅዱስ አክብሮሃልና ስለ አምላክህ ስለ እግዚአብሔር የማያውቁህ ሕዝብ ወደ አንተ ይሮጣሉ።" **6** እግዚአብሔር በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት፣ ቀርቦም ሳለ ጥሩት፤ **7** ክፉ ሰው መንገዱን በደለኛም አሳቡን ይተው፤ ወደ እግዚአብሔርም ይመለስ እርሱም ይምረዋል፣ ይቅርታውም ብዙ ነውና ወደ አምላካችን ይመለስ። **8** አሳቤ እንደ አሳባችሁ፣ መንገዳችሁም እንደ መንገዴ፣ አይደለምና ይላል እግዚአብሔር። **9** ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል፣ እንዲሁ መንገዴ ከመንገዳችሁ አሳቤም ከአሳባችሁ ከፍ ያለ ነው። **10** ዝናብና በረዶ ከሰማይ እንደሚወርድ፣ ምድርን እንደሚያረካት፣ ታበቅልና ታፈራም ዘንድ እንደሚያደርጋት፣ ዘርንም ለሚዘራ እንጀራንም ለሚበላ እንደሚሰጥ እንጂ ወደ ሰማይ እንደማይመለስ፣ **11** ከአፌ የሚወጣ ቃሌ እንዲሁ ይሆናል፤ የምሻውን ያደርጋል የላክሁትንም ይፈጽማል እንጂ ወደ እኔ በከንቱ አይመለስም። **12** እናንተም በደስታ ትወጣላችሁ በሰላምም ትሸኛላችሁ፤ ተራሮችና ኮረብቶች በፊታችሁ እልልታ ያደርጋሉ፣ የሜዳም ዛፎች ሁሉ ያጨበጭባሉ። **13** በእሾህም ፋንታ ጥድ፣ በኩርንችትም ፋንታ ባርሰነት፣ ይበቅላል፤ ለእግዚአብሔርም መታሰቢያን ለዘላለምም የማይጠፋ፣ ምልክት ይሆናል።"

Isaiah 55:1

በኢሳይያስ በኩል ያህዌ በምርኮ ላሉ የኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገር ቀጥሏል። አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ የሚበላና የሚጠጣ ነገር በነጻ እንደሚሰጥ፣ እርሱም ሕዝቡን በነጻ እንደሚባርክ ይናገራል።

ኑ... ኑ
ይህ ቃል መደገሙ የግብዣውን አጣዳፊነት ያመለክታል።

ወይን ጠጅና ወተት ያለ ገንዘብ፣ ያለ ዋጋ ግዙ
ብዙውን ጊዜ አንዳች ነገር ለመግዛት ማንም ገንዘብ መክፈል ያለበት እንደ መሆኑ መጠን፣ ይህ ዐረፍተ ነገር ስላቅ ይመስላል። ይህ አጽንዖት የሚሰጠው እነዚህን ነገሮች በነጻ ለመስጠት የያህዌን አስደናቂ ጸጋ ነው።

Isaiah 55:2

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

እንጀራ ባልሆነ ነገር ላይ ለምን ትመዝንላችሁ... በማያጠግብስ... ለምን ጉልበታችሁን ትጨርሳላችሁ?
ያህዌ ጥያቄዎቹን ያቀረበው ሕዝቡን ለመገሠጽ ነው። ከያህዌ ውጪ ደስታ ማግኘት የሚፈልጉ ሰዎች መብል ላልሆነ ነገር ገንዘብ ከማውጣትና ለማያጠግብ ነገር ጉልበትን ከመጨረስ ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንጀራ ላልሆነ ነገር ገንዘብ ማውጣት የለባችሁም... ለማያጠግብ ነገር መሥራት የለባችሁም››

ብራችሁን ለምን ትመዝናላችሁ
ይህ የሚያመለክተው ለአንዳች ነገር ለመክፈል የብር ሳንቲሞችን መቁጠርን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ገንዘብ መክፈል››

እንጀራ ላልሆነ ነገር
እዚህ ላይ፣ ‹‹እንጀራ›› በአጠቃላይ ምግብን ይወክላል። ሰዎቹ ገንዘብ ያወጡ የነበረው ምግብ ላልሆነ ነገር ነበር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምግብ ላልሆኑ ነገሮች››

መልካም የሆነውን ብሉ፣ በጮማ ደስ ይበላችሁ
በያህዌ በረከትና ደስታ የሚተማመኑ ሰዎች ደስ የሚያሰኛቸውን መልካም ምግብ እንደሚበሉ ሰዎች መሆናቸው ተነግሯል።

በጮማ
‹‹ጮማ›› ውስጡ ብዙ ስብ ያለው ሥጋ ሲሆን፣ መልካም ምግብን የሚወክል ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምርጥ በሆነ ምግብ››

Isaiah 55:3

ጆሮዋችሁን መልሱ
ልብ ብሎ መስማት ጆሮን መመለስ ማለት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ልብ በሉ››

አድርጌዋለሁ
ይህም ማለት፣ 1) ባለፈው ጊዜ ያህዌ ለንጉሥ ዳዊት ያደረገውን ያመለክታል። ወይም 2) ያህዌ ከዳዊት ዘሮች በአንዱ የሚያደርገውን ያመለክታል።

Isaiah 55:5

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

የእስራኤል ቅዱስ
ኢሳይያስ 1፥4 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

Isaiah 55:6

ያህዌ በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱን ማግኘት በሚቻልበት ጊዜ ያህዌን ፈልጉት››

ክፉ መንገዱን ይተው
‹‹ክፉ›› የሚያመለክተው ክፉ ሰውን ነው። ከዚህ በፊት ይራመዱበት በነበረው መንገድ መራመድ እንደ ተወ ሰው፣ ክፉ ሰዎችም ከእንግዲህ ኀጢአት እንደማያደርጉ ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ክፉዎች አኗኗራቸውን ይለውጡ››

በደለኛም ሐሳቡን
ግሡ ካለፈው ሐረግ ጋር የተያያዘ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኀጢአተኛ ሰው ሐሳቡን ይተው››

ሐሳቡን
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹አስተሳሰቡን›› ወይም 2) ‹‹ዕቅዱን››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ያዝንለታል
‹‹ያህዌ ያዝንለታል››

ወደ አምላካችን
ግሡ በዚህ ዐረፍተ ነገር የመጀመሪያ ሐረግ ውስጥ ይገኛል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ወደ አምላካችን ይመለስ››

Isaiah 55:8

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

ይላል ያህዌ
የሚናገረው እርግጥ መሆኑን ለማሳየት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። ኢሳይያስ 30፥1 ላይ እንዳለው ተርጕመው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ የተናገረው ይህን ነው›› ወይም፣ ‹‹እኔ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ››

ሰማያት ከምድር ከፍ እንደሚሉ መንገዴ ከመንገዳችሁ፣ ሐሳቤም ከሐሳባችሁ ከፍ ያለ ነው።
እርሱ የሚያስበውና የሚያደርገው ሰዎች ከሚያስቡትና ከሚያደርጉት ሰማይ ከምድር ከፍ የሚለውን ያህል ከፍ ያለ ወይም የላቀ መሆኑን ያህዌ ይናገራል።

Isaiah 55:10

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

ዝናብና በረዶ... እንደማይመለስ
ይህ የሚያመለክተው ዝናብና በረዶ እንደሚተንን ነው።

እንዲሁ ቃሌ... እኔ የላክሁትን ዓላማ ይፈጽማል
ቃሉ አንድ ነገር እንዲያደርግ እንደ ተላከ መልእክተኛ እንደሆነ ያህዌ ይናገራል።

ከአፌ የወጣ ቃሌ
እዚህ ላይ፣ ‹‹አፍ›› ያህዌ ራሱን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እኔ የምናገረው ቃል››

ወደ እኔ ባዶውን አይመለስም
እዚህ ላይ ቃሉ ወደ ያህዌ መመለሱ እርሱ የላከውን ሥራ ማከናወኑን ያመለክታል። ‹‹ባዶውን›› አይመለስም ማለት ሥራውን ሳይፈጽም አይቀርም ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሥራውን መፈጸሙ አይቀርም››

Isaiah 55:12

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

በሰላም ትመራላችሁ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በሰላም እመራችኃለሁ››

ተራሮችና ኮረብቶች በፊታችሁ በእልልታ ይዘምራሉ፤ የሜዳ ዛፎች ሁሉ ያጨበጭባሉ
ተራሮችና ኮረብቶች ድምፅና እጆች እንዳሉዋቸው ሰዎች ያህዌ ሕዝቡን ሲታደግ ደስ እንደሚላቸው ያህዌ ይናገራል።

በእሾኽ ፈንታ የጥድ ዛፍ፣ በኩርንችት ፈንታ ባርሰነት ይበቅላል
‹‹እሾኽ›› እና ‹‹ኩርንችት›› የሚዋጋ እሾኽ ያላቸው ተክሎችን ያመለክታሉ። ‹‹የጥድ ዛፍ›› እና፣ ‹‹ባርሰነት›› ሁሌም ለምለም የሆኑ ዛፎችን ያመለክታሉ። እሾኻማ ተክሎች ጥፋትን ሲወክሉ፣ ለምለም ዛፎች ግን ሕይወትንና ብልጽግናን ይወክላሉ።

ለስሙ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ስም›› የያህዌን ዝና ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ለእርሱ ዝና›› ወይም፣ ‹‹ለእርሱ ክብር››

አይቆረጥም
መኖሩን የሚያቋርጥ ነገር ከዛፍ እንደ ተቆረጠ ቅርንጫፍ ወይም ከልብሱ እንደ ተቀደደ ቅዳጅ እንደሆነ ተነግሯል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አያልቅም›› ወይም፣ ‹‹ለዘላለም ይኖራል››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 56

1 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "ማዳኔ ሊመጣ፣ ጽድቄም ሊገለጥ ቀርቦአልና ፍርድን ጠብቁ ጽድቅንም አድርጉ። **2** ይህን የሚያደርግ ሰው ይህንንም የሚይዝ
የሰው ልጅ፣ እንዳያረክሰው ሰንበትንም የሚጠብቅ እጁንም ክፋት ከማድረግ የሚጠብቅ ብፁዕ ነው።" **3** ወደ እግዚአብሔርም የተጠጋ መጻተኛ፣ "በእውነት
እግዚአብሔር ከሕዝቡ ይለየኛል" አይበል፤ ጃንደረባም፣ "ተመልከቱ፣ እኔ ደረቅ ዛፍ ነኝ አይበል።" **4** እግዚአብሔር ሰንበቴን ስለሚጠብቁ ደስ የሚያሰኘኝንም
ነገር ስለሚመርጡ ቃል ኪዳኔንም ስለሚይዙ ጃንደረቦች እንዲህ ይላልና፣ **5** "በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ
መታሰቢያና ስም እሰጣቸዋለሁ፤ የማይጠፋም የዘላለም ስም እሰጣቸዋለሁ።" **6** ያገለግሉት ዘንድ የእግዚአብሔርንም ስም ይወድዱ ዘንድ ባሪያዎቹም ይሆኑ
ዘንድ ወደ እግዚአብሔር የሚጠጉትንም መጻተኞች፣ እንዳያረክሱት ሰንበትን የሚጠብቁትን ቃል ኪዳኔንም የሚይዙትን ሁሉ፣ **7** "ወደ ተቀደሰ ተራራዬ
አመጣቸዋለሁ፣ በጸሎቴም ቤት ደስ አሰኛቸዋለሁ፤ ቤቴ ለአሕዛብ ሁሉ የሚሆን የጸሎት ቤት ይባላልና የሚቃጠለውን መሥዋዕታቸውንና ሌላ መሥዋዕታቸውን
በመሠዊያዬ ላይ እቀበላለሁ። **8** ከእስራኤል የተበተኑትን የሚሰበስብ ጌታ እግዚአብሔር፣ ወደ ተሰበሰቡት ዘንድ ሌሎችን እሰበስብለታለሁ" ይላል። **9** እናንተ
የምድረ በዳ አራዊት ሁሉ፣ እናንተም የዱር አራዊት ሁሉ፣ ትበሉ ዘንድ ቅረቡ! **10** ጕበኞቹ ዕውሮች ናቸው፣ ሁሉ ያለ እውቀት ናቸው፤ ሁሉም ዲዳ የሆኑ ውሾች
ናቸው ይጮኹም ዘንድ አይችሉም፤ ሕልምን ያልማሉ፤ ይተኛሉ፤ ማንቀላፋትንም ይወድዳሉ። **11** መብል ወዳጆች ከቶ የማይጠግቡ ውሾች ናቸው፤ እነርሱም
ያስተውሉ ዘንድ የማይችሉ እረኞች ናቸው፤ ሁሉ ወደ መንገዳቸው፣ ከፊተኛው እስከ ኋለኛው ድረስ ሁሉ፣ እያንዳንዳቸው ወደ ጥቅማቸው ዘወር ብለዋል። **12** "ኑ፣
የወይን ጠጅ እንውሰድ፣ በሚያሰክርም መጠጥ እንርካ፤ ዛሬም እንደ ሆነ እንዲሁ ነገ ይሆናል፣ ከዛሬም ይልቅ እጅግ ይበልጣል" ይላሉ።

Isaiah 56:1

ማዳኔ ቅርብ ነው፤ ጽድቄም ሊገለጥ ነው
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በቅርቡ አድናችኃለሁ፤ ጻድቅ መሆኔንም አሳያችኃለሁ››

አጥብቆ የያዘ
እዚህ ላይ፣ ‹‹አጥብቆ የያዘ›› ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን፣ አንድን ነገር ማክበር ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሁሌም ያን ለማድረግ ጠንቃቃ የሆነ››

ክፉ ከማድረግ እጁን የሚሰበሰብ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› የሚወክለው መላውን ሰው ሲሆን፣ የሰውን ድርጊትና ጸባይ ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ክፉ ነገር የማያደርግ››

Isaiah 56:3

እኔ ደረቅ ዛፍ ነኝ
ይህም ማለት ጃንደረቦች በመኮላሸታቸው ከደረሰባቸው አካለ ጐዶሎነት የተነሣ የያህዌ ሕዝብ አካል እንዳይደሉ ሊያስቡ እንደሚችሉ ያመለክታል (ልጆች መውለድ ስለማይችሉ)። እስራኤላውያን ማኮላሸት አይፈጽሙም፤ ያን የሚያደርጉ ለቅጣት ሲባል የሌላ አገር ሰዎች ናቸው። የዕብራውያንን እምነት የተቀበሉ ጃንደረቦች መቅደስ ውስጥ እንዲያመልኩ እንደማይፈቀድላቸው ያውቃሉ። (ዘዳግም 23፥1)። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል።

Isaiah 56:4

በቤቴና በቅጥሮቼ
እነዚህ ሁለት ሐረጐች ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በቤተ መቅደሴ ቅጥር ውስጥ››

ያ አይቆረጥም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አያልቅም›› ወይም፣ ‹‹አይረሳም››

Isaiah 56:6

ራሳቸውን ከያህዌ ጋር ያቆራኙ
ይህ የሚያመለክተው ከያህዌ ሕዝብ ጋር የተባበሩ የሌላ አገር ሰዎችን ነው።

የያህዌን ስም የሚወዱ
‹‹የያህዌ ስም›› እርሱ ራሱን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌን የሚወዱ››

የተቀደሰ ተራራ
ኢሳይያስ 11፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

በመሠዊያየ ተቀባይነት ያገኛል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹መሠዊያየ ላይ እቀበለዋለሁ››

ቤቴ የጸሎት ቤት ይባላል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ቤቴ የጸሎት ቤት ይሆናል››

Isaiah 56:8

ይህ ከእስራኤል የተጣሉትን የሚሰበሰብ የያህዌ ቃል ነው።
የተናገረው እርግጥ መሆኑን ለማሳየት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከእስራኤል የተጣሉትን የሚሰበሰብ ያህዌ እንዲህ ይላል›› ወይም፣ ‹‹ይህ ከእስራኤል የተጣሉትን የምሰበስብ እኔ ያህዌ የተናገርሁት ነው››

Isaiah 56:9

እናንት የምድር አራዊት ሁሉ እናንት የዱር አራዊት ሁሉ መጥታችሁ በጫጭቁ
በዱር አራዊት የሚመስላቸውን የሌላ አገር ሰራዊት መጥተው የእስራኤልን ሕዝብ እንዲያጠቁ እግዚአብሔር ይጠራል።

ጠባቂዎቻቸው ሁሉ ዕውሮች ናቸው
ይህ ማለት የእስራኤል መሪዎች ማኅበረ ሰቡ ውስጥ እየሆነ ያለውን ማየት አልቻሉም ምናልባትም አልፈለጉም ማለት ነው።

ሁሌም ዝም ያሉ ውሾች ናቸው
መሪዎቹ ሕዝቡን ማስጠንቀቅ ነበረባቸው፣ ግን ያን አላደረጉም። ማኅበረ ሰቡ ውስጥ አንድን ሰው በውሻ መመሰል ትልቅ ስድብ ነው።

ተጋድመው ያልማሉ፤ መተኛት ይወዳሉ
ይህ ማለት መሪዎቹ የእግዚአብሔርን ማስጠንቀቂያ ለሕዝቡ አያመጡም፤ ግን የራሳቸውን ምኞት ብቻ ይፈልጋሉ ማለት ነው።

Isaiah 56:11

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ የሕዝቡን ክፉ መሪዎች መግለጽ ቀጥሏል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ውሾቹ ሆዳሞች ናቸው
ያህዌ የእስራኤልን ክፉ መሪዎች ከውሾች ጋር አመሳስሎአቸዋል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 57

1 ጻድቅ ይጠፋል፣ በልቡም ነገሩን የሚያኖር የለም፤ ምሕረተኞችም ይወገዳሉ፣ ጽድቅም ከክፋት ፊት እንደ ተወገደ ማንም አያስተውልም። **2** ወደ ሰላም ይገባል፤ በቅንነት የሄደ በአልጋው ላይ ያርፋል። **3** እናንተ የአስማተኛይቱ ልጆች፣ የአመንዝራውና የጋለሞታይቱ ዘር፣ ወደዚህ ቅረቡ። **4** በማን ታላግጣላችሁ? በማንስ ላይ አፋችሁን ታላቅቃላችሁ? ምላሳችሁንስ በማን ላይ ታስረዝማላችሁ? **5** እናንተ በአድባር ዛፎች መካከል በለመለመም ዛፍ ሁሉ በታች በፍትወት የምትቃጠሉ፣ እናንተም በሸለቆች ውስጥ በዓለትም ስንጣቂዎች በታች ሕፃናትን የምታርዱ፣ የዓመፅ ልጆችና የሐሰት ዘር አይደላችሁምን? **6** በሸለቆው ውስጥ ያሉ የለዘቡ ድንጋዮች እድል ፈንታሽ ናቸው፣ እነርሱም ዕጣሽ ናቸው፤ ለእነርሱም የመጠጥ ቍርባን አፍስሰሻል፣ የእህልንም ቍርባን አቅርበሻል። እንግዲህ በዚህ ነገር አልቈጣምን? **7** ከፍ ባለውም በረዘመውም ተራራ ላይ መኝታሽን አደረግሽ፣ መሥዋዕትንም ትሠዊ ዘንድ ወደዚያ ወጣሽ። **8** ከመዝጊያውና ከመቃኑ በኋላ መታሰቢያሽን አደረግሽ፤ እኔን ትተሽ ለሌላ ተገልጠሻል፣ ወጥተሽ መኝታሽን አስፍተሻል፤ ቃል ኪዳንም ተጋባኻቸው፣ ባየሽበትም ስፍራ ሁሉ መኝታቸውን ወደድሽ። **9** ዘይትም ይዘሽ ወደ ንጉሡ ሄድሽ፣ ሽቱሽንም አበዛሽ፣ መልእክተኞችሽንም ወደ ሩቅ ላክሽ፣ እስከ ሲኦልም ድረስ ተዋረድሽ። **10** በመንገድሽም ብዛት ደከምሽ፣ ነገር ግን፣ "ተስፋ የለም" አላልሽም፤ የጕልበትን መታደስ አገኘሽ፣ ስለዚህም አልዛልሽም። **11** "ሐሰትን የተናገርሺው እኔንም ያላሰብሺው በልብሽም ነገሩን ያላኖርሺው ማንን ሰግተሽ ነው? ማንንስ ፈርተሽ ነው? እኔ ብዙ ጊዜ ዝም አልሁ፣ አንቺም አልፈራሽም። **12** እኔ ጽድቅሽን እናገራለሁ፣ ሥራሽም አይረባሽም። **13** ወደ አንቺ የሰበሰብሻቸው በጮኽሽ ጊዜ ይታደጉሽ፤ ንፋስ ግን ይወስዳቸዋል ሽውሽውታም ሁሉን ያስወግዳቸዋል። በእኔ የታመነ ግን ምድሪቱን ይገዛል፣ የተቀደሰውንም ተራራዬን ይወርሳል። **14** እርሱም፣ 'ጥረጉ፣ መንገድን አዘጋጁ! ከሕዝቤም መንገድ ዕንቅፋትን አውጡ!" ይላል። **15** ለዘላለም የሚኖር ስሙም ቅዱስ የሆነ፣ ከፍ ያለው ልዑል እንዲህ ይላል፣ "የተዋረዱትን ሰዎች መንፈስ ሕያው አደርግ ዘንድ፣ የተቀጠቀጠውንም ልብ ሕያው አደርግ ዘንድ፣ የተቀጠቀጠና የተዋረደ መንፈስ ካለው ጋር በከፍታና በተቀደሰ ስፍራ እቀመጣለሁ። **16** መንፈስም የፈጠርሁትም ነፍስ ከፊቴ እንዳይዝል ለዘላለም አልጣላም፣ ሁልጊዜም አልቈጣም። **17** ስለ ኃጢአቱ ጥቂት ጊዜ ተቈጥቼ ቀሠፍሁት፣ ፊቴን ሰውሬ ተቈጣሁ፤ እርሱም በልቡ መንገድ እያፈገፈገ ሄደ። **18** መንገዱን አይቻለሁ እፈውሰውማለሁ፣ እመራውማለሁ፣ ለእርሱና ስለ እርሱም ለሚያለቅሱ መጽናናትን እመልሳለሁ። **19** የከንፈሮችን ፍሬ እፈጥራለሁ። በሩቅም በቅርብም ላለው ሰላም ሰላም ይሁን፣ እፈውሰውማለሁ፣ ይላል እግዚአብሔር። **20** ክፉዎች ግን እንደሚንቀሳቀስ ባሕር ናቸው፤ ጸጥ ይል ዘንድ አይችልምና፣ ውኖቹም ጭቃና ጕድፍ ያወጣሉና። **21** ለክፉዎች ሰላም የላቸውም" ይላል አምላኬ።

Isaiah 57:1

የኪዳን ታማኝነት ሕዝብ
‹‹ታማኝነት›› የሚለውን፣ ‹‹ታማኝ›› ማለት ይቻላል። ኢሳይያስ 16፥5 ላይ፣ ‹‹ኪዳናዊ ታማኝነት›› የሚለውን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ለኪዳኑ ታማኝ የሆኑ ሰዎች›› ወይም፣ ‹‹ታማኝ ሰዎች››

ተሰብስበዋል... አልጋቸው ላይ አርፈዋል
ሁለቱም የሚያመለክቱት መሞትን ነው።

ጻድቅ ከክፉ ይሰበሰባል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጻድቃን ይሞታሉ፤ እግዚአብሔርም ክፉ ከሆነው ሁሉ ይወስዳቸዋል››

ወደ ሰላም ይገባል
‹‹ጻድቅ ወደ ሰላም ይገባል››

በቅንነት የሚመላለሱ
‹‹መልካም የሆነውን የሚያደርጉ››

Isaiah 57:3

ግን ወዲህ ኑ
እግዚአብሔር ታማኝ ያልሆኑ ሰዎች የእርሱን ፍርድ እንዲቀበሉ ወደ ፊቱ እንዲመጡ ይጣራል፤ ይህ ቀደም ሲል ከተነገረው ለጻድቃን ከተሰጠው ተስፋ በጣም የተለየ ነው።

የአስማተኛዪቱ ልጆች
ይህ አስማተኝነትን ለሚለማመዱ ትልቅ ስድብ ነው፤ ምክንያቱም አስማትንም ሆነ ጥንቆላ ባዕድ አምልኮን የሚጨምር በመሆኑ ነው።

እናንት የአመንዝውና የጋለሞታዪቱ ልጆች
ይህ የሚያመለክተው በተግባር የተገለጠ መንፈሳዊ አመንዝራነትን ነው። እግዚአብሔርን ማምለክ ትተው በአረማውያኑ ከነዓናውያን መንገድ አማልክትንና ጣዖቶችን እያመለኩ ነበር።

የምትሳለቁት በማን ላይ ነው? ምላሳችሁን አውጥታችሁ የምታሾፉት በማን ላይ ነው?
በሐሰተኛ አምልኮ እርሱ ላይ የሚሳለቁትን ለመገሠጽ ያህዌ ጥያቄዎችን ያነሣል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አፋችሁን አስፍታችሁ በመክፈትና ምላሳችሁንም በማውጣት እኔ ላይ እየተሳለቃችሁ ነው››

እናንተ የዐመፃ ልጆች፣ የሐሰት ልጆች አይደላችሁምን?
ሕዝቡን ለመገሠጽ ያህዌ ሌላ ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ የሚያመለክተው በሥጋ የተወለዱበትን ሳይሆን መንፈሳዊ ይዞታቸውን ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እናንተ የዐመፃ ልጆ፣ የሐሰትም ልጆች ናችሁ››

Isaiah 57:5

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእምነተ ቢሶቹ የእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

በዐለት ሰንጣቂዎች ውስጥ... ራሳችሁን ታቃጥላላችሁ
እነዚህ ድርጊቶች ሁሉ ከጣዖት አምልኮ ጋር የተያያዙ ናቸው። ዋርካ ዛፎች ለከነዓናውያን የተቀደሱ ናቸው። እንዲህ ያለው ተግባር የሕዝቡንና የምድሩን ለም መሆን ይጨምራል በማለት ሰዎች ያስቡ ነበር።

Isaiah 57:6

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእምነተ ቢሶቹ የእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

ያ ለአንቺ ተመድቦአል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። የዕብራይስጡ ትክክለኛ ትርጕም ግልጽ አይደለም። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያ ዕጣ ፈንታሽ ነው›› ወይም፣ ‹‹ያ የአንቺ ድርሻ ነው››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በእነዚህ ነገሮች ደስ መሰኘት አለብኝን?
ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው ሕዝቡን ለመገሠጽ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እነዚህ ነገሮች እኔን ደስ አያሰኙኝም››

Isaiah 57:7

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእምነተ ቢሶቹ የእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል

ዐልጋሽን አነጠፍሽ
ይህ ሐሰተኛ አማልክትን ለማምለክ ሲባል ከአመንዝራዎች ጋር መተኛትን ያመለክታል።

ከፍ ባለው ተራራ
ብዙውን ጊዜ ሰዎች ሐሰተኛ አማልክትን ለማምለክ ወደ ኮረብቶችና ተራሮች ጫፍ ይሄዱ ነበር። እነዚህ ቦታዎች ለአምልኮ የተሻሉ ቦታዎች እንደሆኑ ያስቡ ነበር። ምናልባትም ይህ ኢየሩሳሌምንም የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።

ከእነርሱ ጋር ኪዳን አደረግሽ
‹‹ከእነርሱ ጋር ውል አደረግሽ››

Isaiah 57:9

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእምነተ ቢሶቹ የእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

ወደ ሲኦል ወረድሽ
ሰዎች በአካል የሙታን ዓለም ወደሆነው ሲኦል አልወረዱም። ከዚያ ይልቅ ሕዝቡ አዳዲስ አማልክት ለመፈለግ የትም ቦታ ለመሄድ ፈቃደኛ መሆናቸውን ያህዌ ግነታዊ በሆነ ቋንቋ መናገሩ ነው።

በእጅሽ ሕይወት አገኘሽ
ከባድ ሙከራ ካደረጉ በኃላ እንኳ ጣዖት አምላኪዎቹ አሁንም ገና ዐቅም እንዳላቸው ተረዱ። እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› — ‹‹ብርታትን›› — ‹‹ብቃትን›› ይወክላል።

Isaiah 57:11

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእምነተ ቢሶቹ የእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

እኔን የዋሸሽኝ ማንን ፈርተሽ፣ ማንንስ ሠግተሽ ነው?
ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው ሕዝቡን ለመገሠጽ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እኔን ለመዋሸት እነዚህን ጣዖቶች በእርግጥ መፍራት አለብሽ››

እኔን አላስታወስሽም፤ ስለ እኔ አላሰብሽም
እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ሲሆኑ፣ ሕዝቡ ያህዌን ማስታወስ ቢኖርባቸውም እነርሱ እንደዚያ እንዳላደረጉ አጽንዖት ይሰጣል።

ጽድቅሽንና ሥራሽንም ሁሉ እገልጣለሁ
እዚህ ላይ ክፉ ሥራቸውን ጽድቅ ብሎ በመጥራት ያህዌ በስላቅ እየተናገረ ነው።

Isaiah 57:13

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእምነተ ቢሶቹ የእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

የጣዖቶችሽ ብዛት ያድኑሽ
ያህዌ በሕዝቡና በጣዖቶቻቸው እያፌዘ ነው። ምንም እንኳ እንደማያድኑዋቸው ቢያውቅም ያህዌ ጣዖቶቹ ሕዝቡን እንዲያድኑ ይናገራል።

ሁሉንም ነፋስ ይወስዳቸዋል፤ እስትንፋስ ሁሉንም ይጠራርጋቸዋል።
ጣዖቶቹ ዐቅመ ቢስና ከንቱ መሆቸውን አጽንዖት ለመስጠት በሁለት መንገዶች ተመሳሳይ ነገር ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ነፋስ ወይም እስትንፋስ እንኳ ጠራርጎ ይወስዳቸዋል››

የተቀደሰ ተራራ
‹‹የተቀደሰ ተራራ›› በኢየሩሳሌም ያለው የጽዮን ተራራ ነው። ኢሳይያስ 11፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

Isaiah 57:14

አብጁ አብጁ! ከሕዝቤ መንገድ እንቅፋት አስወግዱ
ሕዝቡ ወደ እርሱ እንዲመለሱና እርሱን ለማምለክ እንቅፋቶች እንዳይኖሩ ያህዌ አጽንዖት በመስጠት መንገዱ በአስቸኳይ እንዲስተካከል ይናገራል። ይህ ኢሳይያስ 40፥3 ላይ ያለውን ያስተጋባል።

ከፍ ያለውና ልዕልና ያለው ይህን ይናገራል
‹‹ከፍ ያለ›› እና፣ ‹‹ልዕልና›› በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ያላቸው ቢሆኑም፣ ያህዌ ከፍ ያለ መሆኑን አጽንዖት ይሰጣል። ኢሳይያስ 6፥1 እና 33፥10 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። ኢሳይያስ 52፥13 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

የትሑንን መንፈስ ለማነሣሣት፣ የልበ ሰባራዎችን ልብ ለማነሣሣት
እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ቢሆኑም፣ በፊቱ ትሑት የሆኑትን እንደሚያበረታና እንደሚያጽናና አጽንዖት ይሰጣል።

መንፈስ... ልብ
እነዚህ የሰውን ሐሳብና ስሜት ያመለክታሉ፤ ቃል በቃል መንፈስና ልብ ማለት አይደለም።

Isaiah 57:16

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

ፊቴን ሰወርሁ
ይህ ማለት ሕዝቡን ትቶአል፤ ከእንግዲህ አይረዳቸውም አይባርካቸውም ማለት ነው።

በልቡ መንገድ ወደ ኃላ ተመለሰ
ይህ ማለት እስራኤላውያን ለሐሰተኞቹ ሲሉ እውነተኛውን አምላክ ተዉ ማለት ነው። እዚህ ላይ፣ ‹‹ወደ ኃላ›› እና፣ ‹‹መንገድ›› የሚሉት ቦታን የሚያመለክቱ ቃላት ቢሆኑም፣ ዝንባሌንና ስሜትን ይወክላሉ።

Isaiah 57:18

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል።

መንገዱ
‹‹መንገዳቸው›› እዚህ ላይ፣ ‹‹የእርሱ›› የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል።

ለእርሱ የሚያለቅሱትን አጽናኑ፣ አበርቱ
‹‹በክፉ መንገዳቸው ምክንያት ለሕዝቡ መከራ የሚያዝኑትን አጽናናቸዋለሁ››

የከንፈሮችን ፍሬ እፈጥራለሁ
‹‹የከንፈሮች ፍሬ›› ሰው የሚናገረውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እንዲመሰግኑኝና እንዲያከብሩኝ አደርጋለሁ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በሩቅ ላሉት ሰላም፣ ሰላም
‹‹በሩቅ ካሉት ጋር ሰላም አደርጋለሁ›› — ‹‹ሰላም›› የሚለው ቃል የተደገመው አጽንዖት ለመስጠት ነው።

Isaiah 57:20

ክፉዎች ግን እንደሚናወጥ ባሕር ናቸው... ጭቃና ጉድፍ
ይህ ክፉዎችን ውሃውን ከሚያቆሽሽ ባሕሩ ዳርቻ ካለው ውሃ ጋር ያመሳስላቸዋል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 58

1 "በኃይልህ ጩኽ፣ አትቈጥብ፣ ድምፅህን እንደ መለከት አንሣ፣ ለሕዝቤ መተላለፋቸውን ለያዕቆብ ቤትም ኃጢአታቸውን ንገር። 2 ነገር ግን ዕለት ዕለት ይሹኛል መንገዴንም ያውቁ ዘንድ ይወድዳሉ፤ ጽድቅን እንዳደረጉ የአምላካቸውንም ፍርድ እንዳልተዉ ሕዝብ እውነተኛውን ፍርድ ይለምኑኛል። ወደ እግዚአብሔርም ለመቅረብ ይወድዳሉ። 3 'ስለ ምን ጾምን፣' አንተም 'አልተመለከትኸንም? ሰውነታችንንስ ስለ ምን አዋረድን፣ አንተም አላወቅህም?' ይላሉ። ተመልከቱ፣ በጾማችሁ ቀን ፈቃዳችሁን ታደርጋላችሁ፣ ሠራተኞቻችሁንም ሁሉ ታስጨንቃላችሁ። 4 ተመልከቱ፣ ለጥልና ለክርክር ትጾማላችሁ በግፍ ጡጫም ትማታላችሁ፤ ድምፃችሁንም ወደ ላይ ታሰሙ ዘንድ ዛሬ እንደምትጾሙት አትጾሙም። 5 እኔ የመረጥሁት ጾም ይህ ነውን? ሰውስ ነፍሱን የሚያዋርደው እንደዚህ ባለ ቀን ነውን? በውኑ ራሱን እንደ እንግጫ ዝቅ ያደርግ ዘንድ ማቅንና አመድንም በበታቹ ያነጥፍ ዘንድ ነውን? በውኑ ይህን ጾም፣ በእግዚአብሔርም ዘንድ የተወደደ ቀን ትለዋለህን? 6 እኔስ የመረጥሁት ጾም ይህ አይደለምን? የክፋት በደልን እስራት ትፈቱ ዘንድ፣ የቀንበርንስ ጠፍር ትለቅቁ ዘንድ፣ የተገፉትንስ አርነት ትሰድዱ ዘንድ፣ ቀንበሩንስ ሁሉ ትሰብሩ ዘንድ አይደለምን? 7 እንጀራህንስ ለተራበ ትቈርስ ዘንድ፣ ስደተኞቹን ድሆች ወደ ቤትህ ታገባ ዘንድ፣ የተራቈተውንስ ብታይ ታለብሰው ዘንድ፣ ከሥጋ ዘምድህ እንዳትሸሸግ አይደለምን? 8 የዚያን ጊዜ ብርሃንህ እንደ ንጋት ይበራል፣ ፈውስህም ፈጥኖ ይበቅላል፣ ጽድቅህም በፊትህ ይሄዳል፣ የእግዚአብሔርም ክብር በኋላህ ሆኖ ይጠብቅሃል። 9 የዚያን ጊዜ ትጠራለህ፣ እግዚአብሔርም ይሰማሃል፤ ትጮኻለህ እርሱም፣ "እነሆኝ" ይላል። ከመካከልህ ቀንበርን ብታርቅ፣ ጣትህንም መጥቀስ ብትተው፣ 10 ባታንጐራጕርም፣ ነፍስህንም ለተራበ ብታፈስስ፣ የተጨነቀውንም ነፍስ ብታጠግብ፣ ብርሃንህ በጨለማ ይወጣል ጨለማህም እንደ ቀትር ይሆናል። 11 እግዚአብሔርም ሁልጊዜ ይመራሃል፤ ነፍስህንም በመልካም ነገር ያጠግባል አጥንትህንም ያጠናል። አንተም እንደሚጠጣ ገነት፣ ውኃውም እንደማያቋርጥ ምንጭ ትሆናለህ። 12 ከዱሮ ዘመን የፈረሱት ስፍራዎች ይሠራሉ፣ የብዙ ትውልድም መሠረት ይታነጻል፤ አንተም፣ "ቅጥሩን ጠጋኝ፣" "የመኖሪያ መንገድን አዳሽ" ትባላለህ። 13 ፈቃድህን በተቀደሰው ቀኔ ከማድረግ እግርህን ከሰንበት ብትመልስ፣ ሰንበትንም ደስታ፣ እግዚአብሔርም የቀደሰውን ክቡር ብትለው፣ የገዛ መንገድህንም ከማድረግ ፈቃድህንም ከማግኘት ከንቱ ነገርንም ከመናገር ተከልክለህ ብታከብረው። 14 "በዚያን ጊዜ በእግዚአብሔር ደስ ይልሃል፤ በምድርም ከፍታዎች ላይ አወጣሃለሁ፤ የአባትህንም የያዕቆብን ርስት አበላሃለሁ፤ የእግዚአብሔር አፍ ተናግሮአልና።"

Isaiah 58:1

ድምፅህን እንደ መለከት አንሣ
ይህ በጎይል ጩኽ ማለት ነው። እዚህ ላይ፣ ‹‹የአንተ›› የሚያመለክተው ኢሳይያስን ነው።

ለሕዝቤ ዐመፃቸውን፣ ለያዕቆብም ቤት ኀጢአታቸውን ተናገሩ
እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። ሁለቱ በአንድነት ለያህዌ ሕዝብ በአስቸኳይ መናገርን ያጠናክራሉ።

Isaiah 58:3

‹‹ስለምን ብለን ጾምን›› ይላሉ፤ ‹‹አንተ ግን አላየህም? ራሳችንን ስለምን አዋረድን አንተ ልብ አላልህም?
እርሱ ችላ ያላቸው ስለ መሰላቸው የእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔር ላይ ለማማረር ጥያቄ አንሥተዋል።

Isaiah 58:4

አጠቃላይ መረጃ
ለጥያቄያቸው መልስ በመስጠት ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

እነሆ
‹‹ተመልከቱ›› ወይም፣ ‹‹ልብ በሉ›› ልብ እንዲሉ በመናገር ያህዌ ለጥያቄያቸው መልስ ይሰጣል።

የግፍ ጡጫ
‹‹የግፍ ጡጫ›› — ይህ የምር መደባደባቸውን ያመለክታል። ‹‹ጡጫ›› በግልጽ የሚታይ ቁጣን ያመለክታል።

እኔ የምፈልገው ጾም ይህን ነውን... ራሱን የሚያዋርደው?
ሕዝቡን ለመገሠጽ ያህዌ ጥያቄ ያነሣል። በእግዚአብሔር ፊት ራሳቸውን እንዳዋረዱ ያስመስላሉ፤ ግን ሰዎችን ይጐዳሉ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እኔ የመረጥሁት ጾም ይህ አይደለም... ራሱን እንዲያዋርድ››

ሰው ራሱን የሚያዋርደው እንደ ደንገል ራሱን ዝቅ የሚያደርገው
ይህ ሰውየው ዝቅ ብሏል፤ ግን በእውነት ትሑት አይደለም ማለት ነው። ‹‹ደንገል›› በቀላሉ የሚታጠፍ ደካማ ተክል ይወክላል።

ይህን ጾም ትለዋለህ፤ ያህዌን ደስ የሚያሰኝ ቀን ትለዋለህ?
ያህዌ ጥያቄ ያቀረበው ሕዝቡን ለመገሠጽ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹መቼም እንዲህ ያለውን ጾም እኔን ያስደስታል ብለህ አታስብም!››

Isaiah 58:6

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል

እኔ የመረጥሁት ጾም ይህ አይደለምን... ቀንበርን ሁሉ እንድትሰብሩ?
ያህዌ ጥያቄውን ያነሣው እርሱን ደስ ስለሚያሰኘው ጾም ሕዝቡን ለማስተማር ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እኔ የመረጥሁት ጾም ይህ ነው... ቀንበርን ሁሉ እንድትሰብሩ››

የጭቆናን ሰንሰለት እንድትበጥሱ፣ የቀንበርን ገመድ እንድትፈቱ፣ የተጨቆኑትን ነጻ እንድታወጡ፣ ማንኛውንም ቀንበር እንድትሰብሩ
እነዚህ ሐረጐች ሁሉ ክፉዎች የበደሉዋቸውንና ያጠቁዋቸውን ሰዎች መርዳት እንዳለባቸው ያመለክታሉ።

ወደ ቤትህ እንድታስገባው... አይደለምን?
ያህዌ ሕዝቡን ለማስተማር ሌላ ጥያቄ ያነሣል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ወደ ቤትህ እንድታስገባው... ነው?››

እንጀራህን እንድትቆርስ
ይህ ሐረግ ባለቤቱ እንጀራውን በመቁረስ ምግቡን መጀመር እንዳለባት ያመለክታል።

Isaiah 58:8

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ያኔ ብርሃንህ እንደ ንጋት ጮራ ይፈነጥቃል
‹‹ይፈነጥቃል›› ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን፣ ደምቆ ያበራል ማለት ነው። ይህ ማለት ችግረኞችን ቢረዱ ከጨለማው ሌሊት በኃላ እንደሚመጣ ፀሐይ ተግባራቸው ሌሎች ሰዎች የሚያዩት ብርሃን ይሆናል ማለት ነው። ወይም ብርሃን እነርሱ ላይ የሚያበራውንና የሚባርካቸውን የጌታ ብርሃን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።

ፈውስህ ፈጥኖ ይበቅላል
ይህ ማለት ቶሎ እንደሚድን ቁስል እግዚአብሔር ቶሎ ይባርካቸዋል ይመልሳቸዋል ማለት ነው።

ጽድቅህ በፊትህ ይሄዳል፤ የያህዌ ክብር ደጀን ይሆንልሃል
ይህ ከግብፅ በወጡ ጊዜ እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ ያደረገውን ጥበቃ ያመለክታል። ይህ መልካም የሆነውን ቢያደርጉ እግዚአብሔር እንደ ገና ከጠላቶቻቸው ይጠብቃቸዋል ማለት ነው።

ጽድቅህ
ይህ አገላለጽ በዕብራይስጥ ጽድቅን እንዲያውም ድልን የሚሰጥ ተብሎ ሊተረጐም ይችላል። በዚህ ዐውድ የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው። ጥቂት የዘመኑ ቅጂዎች ይህን ትርጉም ይዘዋል።

Isaiah 58:9

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

ያኔ ብርሃንህ በጨለማ ይወጣል፤ ጨለማህም እንደ ቀትር ይሆናል
‹‹ብርሃንህ›› ለሰው ሁሉ ምሳሌ የሚሆን መልካም ሥራን ይወክላል፤ ‹‹ጨለማ›› ማለት ክፉ ሥራ በመልካም ሥራቸው ይሸነፋል።

Isaiah 58:11

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል

በውሃ እንደ ረካ ቦታ ትሆናለህ
‹‹ውሃ›› አካባቢያቸው በቂ ባይኖረው እንኳ የሞላ ሕይወት ለመኖር የሚያስፈልገውን ሁሉ ይወክላል።

ውሃ እንደ ጠጣ አትክልት ቦታ ትሆናለህ
‹‹ውሃ የጠጣ አትክልት ቦታ›› ሙላትና መትረፍረፍን ይወክላል፤ ስለዚህ የሚያስፈልጋቸው ሁሉ ይኖራቸዋል።

ውሃው እንደማይደርቅ ምንጭ
‹‹የውሃ ምንጭ›› ውሃ ውድ በሆነበት ምድር ሙላትና መትረፍረፍን ያመለክታል።

Isaiah 58:12

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

ተብለህ ትጠራለህ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ይጠሩሃል››

Isaiah 58:13

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

እግርህን ከሰንበት መንገድ ብትመልስ፣ በተቀደሰውም ቀን ደስ የሚያሰኝህን ባታደርግ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እግር›› ሰዎቹን ይወክላል። እግዚአብሔር በዕረፍት ቀን ረጅም ጉዞን ወይም ሥራ አይፈቅድም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በተቀደሰው ቀኔ በሰንበት ጉዞ አታድርግ የምትፈልገውንም አታድርግ››

Isaiah 58:14

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

በምድር ከፍታዎች ላይ እንድትጋልብ አደርግሃለሁ
ይህ የሚያመለክተው በጽድቅ የመኖር ምላሽ እንዲሆን እግዚአብሔር የሕዝቡን ጎይልና ዝና ከፍ የሚያደርግ መሆኑን ነው።

የያህዌ አፍ ተናግሮአልና
‹‹አፍ›› ያህዌ የተናገረውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ተናግሮታልና››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 59

1 ተመልከቱ፣ የእግዚአብሔር እጅ ከማዳን አላጠረችም፣ ጆሮውም ከመስማት አልደነቈረችም፤ 2 ነገር ግን፣ በደላችሁ በእናንተና በአምላካችሁ መካከል
ለይታለች፣ እንዳይሰማም ኃጢአታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል። 3 እጃችሁ በደም ጣታችሁም በበደል ረክሳለች፣ ከንፈራችሁም ሐሰትን ተናግሮአል፣
ምላሳችሁም ኃጢአትን አሰምቶአል። 4 በጽድቅ የሚጠራ በእውነትም የሚፈርድ የለም፤ በምናምንቴ ነገር ታምነዋል ሐሰትንም ተናግረዋል፤ ጕዳትን ፀንሰዋል
በደልንም ወልደዋል። 5 የእባብን እንቍላል ቀፈቀፉ፣ የሸረሪትንም ድር አደሩ። እንቍላላቸውንም የሚበላ ሰው ይሞታል፣ እንቍላሉም ሲሰበር እፉኝት ይወጣል።
6 ድሮቻቸውም ልብስ አይሆኑላቸውም፣ በሥራቸውም አይሸፈኑም፤ ሥራቸውም የበደል ሥራ ነው፣ የግፍም ሥራ በእጃቸው ነው። 7 እግሮቻቸው ወደ ክፋት
ይሮጣሉ፣ ንጹሑን ደም ለማፍሰስ ይፈጥናሉ፤ አሳባቸው የኃጢአት አሳብ ነው። ጕስቍልናና ቅጥቃጤ በመንገዳቸው አለ። 8 የሰላምን መንገድ አያውቁም፣
በአካሄዳቸውም ፍርድ የለም፤ መንገዳቸውን አጣምመዋል፣ የሚሄድባትም ሁሉ ሰላምን አያውቅም። 9 ስለዚህ ፍርድ ከእኛ ዘንድ ርቆአል፣ ጽድቅም አላገኘንም፤
ብርሃንን በተስፋ እንጠባበቅ ነበር። እነሆም፣ ጨለማ ሆነ፤ ጸዳልን በተስፋ እንጠባበቅ ነበር፣ ነገር ግን በጨለማ ሄድን። 10 እንደ ዕውሮች ወደ ቅጥሩ
ተርመሰመስን፣ ዓይን እንደሌላቸው ተርመሰመስን፤ በቀትር ጊዜ በድግዝግዝታ እንዳለ ሰው ተሰናከልን፣ እንደ ሙታን በጨለማ ስፍራ ነን። 11 ሁላችን እንደ
ድቦች እንጮኻለን፤ እንደ ርግብ እንለቃቀሳለን፤ ፍርድን በተስፋ እንጠባበቅ ነበር። እርሱም የለም፤ መዳንም ከእኛ ዘንድ ርቆአል። 12 ዓመፃችን በአንተ ፊት
በዝቶአልና፣ ኃጢአታችን መስክሮብናልና፣ ዓመፃችን ከእኛ ጋር ነውና፣ በደላችንን እናውቃለንና። 13 ዐምፀናል፣ ሐሰትን ተናግረናል፣ አምላካችንንም ከመከተል
ተመልሰናል፤ ግፍንና ዓመፅንም ተናግረናል፣ የኃጢአት ቃልንም ፀንሰን ከልብ አውጥተናል። 14 ፍርድም ወደ ኋላ ተመልሶአል፣ ጽድቅም በሩቅ ቆሞአል፤
እውነትም በአደባባይ ላይ ወድቆአልና፣ ቅንነትም ሊገባ አልቻለምና። 15 እውነትም ታጥቶአል፣ ከክፋትም የራቀ ሰው ለብዝበዛ ሆኖአል። እግዚአብሔርም አየ፣
ፍርድም ስለሌለ ተከፋ። 16 ሰውም እንደሌለ አየ፣ ወደ እርሱ የሚማልድ እንደሌለ ተረዳ ተደነቀም፤ ስለዚህ የገዛ ክንዱ መድኃኒት አመጣለት፣ ጽድቁም
አገዘው። 17 ጽድቅንም እንደ ጥሩር ለበሰ፣ በራሱም ላይ የማዳንን ራስ ቍር አደረገ፤ የበቀልንም ልብስ ለበሰ፣ በቅንዓትም መጐናጸፊያ ተጐናጸፈ። 18 እንደ
ሥራቸው መጠን እንዲሁ ቍጣን ለባላጋራዎቹ፣ ፍዳንም ለጠላቶቹ ይከፍላል፤ ለደሴቶችም ፍዳቸውን ይከፍላል። 19 እርሱ የእግዚአብሔር ነፋስ እንደሚነዳው
እንደ ጐርፍ ፈሳሽ ይመጣልና በምዕራብ ያሉት የእግዚአብሔርን ስም፣ በፀሐይ መውጫም ያሉት ክብሩን ይፈራሉ። 20 "ለጽዮን ታዳጊ ይመጣል፣ በያዕቆብም
ዘንድ ከኃጢአት ለሚርቁ፣ ይላል እግዚአብሔር። 21 ከእርሱ ጋር ያለው ቃል ኪዳኔ ይህ ነው ይላል እግዚአብሔር፣ በአንተ ላይ ያለው መንፈሴ በአፍህም ውስጥ
ያደረግሁት ቃሌ ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ ከአፍህ ከዘርህም አፍ ከዘር ዘርህም አፍ አያልፍም፣" ይላል እግዚአብሔር።

Isaiah 59:1

እነሆ
‹‹ተመልከቱ›› ወይም ‹‹ማወቅ አለባችሁ!›› ያህዌ ልብ እንዲሉ ለሕዝቡ ይናገራል።

የያህዌ እጅ አላጠረም
‹‹እጅ›› ኀይልና ችሎታን ይወክላል። ‹‹አጭር›› እጅ ኀይልና ችሎታ የለውም። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ በቂ ችሎታ አለው››

የእናንተ... እናንተ
እነዚህ የብዙ ቁጥር ተውላጠ ስሞች እንደ አንድ ነጠላ ወገን የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታሉ።

ኀጢአታችሁ ፊቱን ከእናንተ እንዲሰውር አድርጓል።
‹‹ፊት›› መገኘትንና ማየትን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ኀጢአታችሁ ከእናንተ ዘወር እንዲል አድርጐአል››

Isaiah 59:3

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

እጃችሁ በደም፣ ጣቶቻችሁም በኀጢአት ቆሽሸዋል
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› እና፣ ‹‹ጣቶች›› ድርጊታቸውን ያመለክታሉ። ይህም ማለት ግፍና ኀጢአት በመፈጸም በድለዋል ማለት ነው። ‹‹የእናንተ›› ብዙ ቁጥር ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከባድ ኀጢአቶች ፈጽማችኃል››

ከንፈሮቻችሁ ሐሰት ተናገሩ፣ ምላሶቻችሁ ሐሜት ተናገሩ
ሰዎች እንዲናገሩ የሚረዱ የአካል ክፍሎች ንግግርን ይወክላሉ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሐሰትና ሐሜት ትናገራላችሁ››

ችግር ፀነሱ፤ ኀጢአትን ወለዱ
‹‹መፀነስ›› እና ‹‹መውለድ›› ምን ያህል ተዘጋጅተው ኀጢአት እንደሚያደርጉ ያመለክታል። ‹‹እነርሱ›› የሚለው የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ኀጢአት ለማድረግ በርትተው ይሠራሉ››

Isaiah 59:5

አጠቃላይ መረጃ
መርዛማ እባብንና የሸረሪትን ድር ምሳሌ በማድረግ ኢሳይያስ የእስራኤል ሕዝብ ስለሚሠሩት ኀጢአት መናገር ቀጥሏል።

የመርዛማ እባብ ዕንቁላሎች ቀፈቀፉ
የመርዛማ እባብ ዕንቁላሎች፣ ብዛት ያላቸው መርዛማ እባቦች ያስገኛሉ። ‹‹መርዛማ እባብ›› የሚለው የበለጠና የበለጠ ሌሎችን የሚጐዳ ሰዎቹ የሚያደርጉት ክፉ ነገር ነው።

የሸረሪት ድር አደሩ
ይህ የሚወክለው እርባና ቢስ የሰዎቹን ተግባር ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጥቅም የሌለው ነገርንና እንቅስቃሴን አስገኙ››

ዕንቁላላቸውን የሚበላ ይሞታል፤ ዕንቁላሉ ከተሰበረ መርዛማ እባብ ይወጣል
መርዛማ ዕንቁላል በልቶ መሞት ራስን ማጥፋትን ይወክላል። ዕንቁላሉ ሲሰበር የሚወጣው መርዛማ እባብ ጥፋትን ማስፋፋትን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የሚሠሩት ነገር ያጠፋቸዋል፤ ጥፋቱም ወደ ሌሎች እንዲስፋፋ ያደርጋል።››

Isaiah 59:7

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እግሮቻቸው ወደ ክፉ ይሮጣሉ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እግሮች›› ሰዎችን ይወክላሉ። ይህ የሚያመለክተው እግሮቻቸው እንደሚሮጡ ሁሉ እነርሱም ክፉ ለማድረግ ፈጣኖች መሆናቸውን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ክፉ ለማድረግ ፈጣኖች ናቸው››

የመንገዶቻቸው ናቸው
‹‹መንገዶች›› አኗኗራቸውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሁሉም እንዲህ ያደርጋሉ››

በጐዳናዎቻቸው ፍትሕ የለም
‹‹ጐዳናዎቻቸው›› አኗኗራቸውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በፍጹም ትክክል የሆነውን አያደርጉም›› ወይም፣ ‹‹የሚያደርጉት ሁሉ ክፉ ነው››

መንገዳቸውን ጠማማ አድርገውታል
‹‹ጠማማ መንገድ›› አኗኗራቸው ብልሹ መሆኑን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሐሰት ይናገራሉ ያደርጋሉ፤ አታላዮች ናቸው››

Isaiah 59:9

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

ፍትሕ ከእኛ ርቆአል
እዚህ ላይ፣ ‹‹እኛ›› የሚወክለው ኢሳይያስንና የእስራኤልን ሕዝብ ነው። ‹‹ርቆአል›› ፍትሕ መጥፋቱንና ለማግኘትም አስቸጋሪ መሆኑን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ፍትሕ ጠፍቷል፤ ለማግኘትም ያስቸግራል››

ብርሃንን ጠበቅን ግን፣ ጨለማ አየን፤ የብርሃን ጸዳል ጠበቅን ግን በጨለማ እንሄዳለን።
እያንዳንዱ ሐረግ ሕዝቡ የእግዚአብሔርን መልካምነት ጠብቀው እንደ ነበርና እርሱ ግን የተዋቸው እንደሚመስል ያመለክታል።

እንደ ዕውር ቅጥሩ ላይ ተደናበርን... እንደ ሙታን
ይህ ማለት እግዚአብሔር ወደ እነርሱ ስለማይመጣ ትክክለኛውን መንገድ ለማግኘት ዐቅም እንደሌላቸው በወደ ፊቱም ተስፋ መቁረጣቸውንና በሕይወት ለመኖር ተስፋ እንደሌላቸው ያመለክታል።

Isaiah 59:11

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ መናገር ቀጥሏል።

በደላችን በዝቶአል
እዚህ ላይ ‹‹እኛ›› ኢሳይያስንና የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል።

በፊትህ
እዚህ ላይ፣ ‹‹አንተ›› የሚያመለክተው ያህዌን ነው።

ኃጢአታችን ይመሰክርብናል
ኢሳይያስ ኀጢአትን ሰዎቹ በደለኛ መሆናቸውን ለመናገር በእግዚአብሔር ፊት እንደሚሄድ ሰው ይገልጻል።

በደላችን ከእኛ ጋር ነውና
‹‹ከእኛ ጋር›› መገንዘብን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በደላችንን እንገነዘባለንና››

Isaiah 59:14

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ መናገር ቀጥሏል

ፍትሕ ርቆአል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎቹ ፍትሕ እንዲጠፋ አድርገዋል››

ፍትሕ... ጽድቅ... እውነት... መልካም... ታማኝ
ኢሳይያስ እነዚህ ነገሮች እንደ ሰው እየሠሩ እንደሆነ ያመለክታል።

Isaiah 59:16

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ መናገር ቀጥሏል።

ሰው እንደሌለ አየ፤ ጣልቃ የሚገባ ባለ መኖሩ ተገረመ
‹‹መከራ ውስጥ ያሉትን ለመርዳት ማንም ባለ መምጣቱ ያህዌ ተገረመ›› ወይም፣ ‹‹መከራ ውስጥ ያሉትን ለመርዳት የመጣ ሰው ባለመኖሩ ያህዌ ተደነቀ››

ስለዚህ የገዛ ራሱ ክንድ ማዳን አመጣለት
የያህዌ፣ ‹‹ክንድ›› ችሎታውንና ኀይሉን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕዝቡን ለማዳን ያህዌ የራሱን ኀይል ተጠቀመ››

ጻድቁ ደግፎ ያዘው
እዚህ ላይ፣ ‹‹ጽድቅ›› የሰው ባሕርይ እንዳለው ተነግሯል። ይህን ቃል ቅጽል ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሁሌም እንደሚያደርገው መልካም አደረገ››

Isaiah 59:17

ጽድቅን እንደ ጥሩር አጠለቀ፤ የድነትን ቁር ራሱ ላይ ደፋ። በቀልን ለበሰ፤ ቅናትን እንደ መጐናጸፊያ ደረበ
‹‹ጥሩር››፣ ‹‹ቁር››፣ ‹‹ልብስ›› እና፣ ‹‹መጐናጸፊያ›› በጦርነትና በውጊያ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው። ሕዝቡን ለመቅጣት ያህዌ እነዚህን እንደ ለበሰ ኢሳይያስ ይናገራል።

መጐናጸፊያ
ከላይ እስከ ታች የሚዘልቅ ሰፊ ልብስ

ከፈላቸው
ኢሳይያስ ወደ ፊት የሚሆኑ ነገሮች ባለፈው ጊዜ እንደሆኑ አድርጐ ይናገራል። ይህም በእርግጥ ይፈጸማል ማለት ነው።

Isaiah 59:19

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ መናገር ቀጥሏል።

የያህዌን ስም ፍሩ
‹‹ስም›› የሚያመለክተው የያህዌን ዝናና ባሕርይ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌን ፍሩ››

ከምዕራብ... ከፀሐይ መውጫ
ኢሳይያስ በእነዚህ ቃሎች የተጠቀመው በዓለም ሁሉም ቦታ ያሉ ሰዎችን ለማመልከት ነው።

እንደሚፍለቀለቅ ምንጭ ይመጣል
ድንገተኛና ከባድ ዝናብ እንደ ፈጣን ጐርፍ እስኪያደርጋቸው ድረስ ይሁዳ ውስጥ ያሉ ጠባብ ሸለቆዎች ደረቆች ናቸው። ያ በሚሆንበት ጊዜ ታላቅ ድምፅና ነፋስ ይኖራል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በያህዌ እስትንፋስ ተወገዱ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የያህዌ እሳት ንፋስ የሚያስወግዳቸው››

ይህ የያህዌ ቃል ነው
የሚናገረውን እርግጠኝነት ለማሳየት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። ኢሳይያስ 30፥1 ላይ እንዳለው ተርጉመው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ የተናገረው ይህን ነው›› ወይም፣ ‹‹እኔ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ››

Isaiah 59:21

አፍህ ውስጥ ያኖርሁት ቃሌ
‹‹እንድትናገር የሰጠሁህ መልእክት››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 60

1 ብርሃንሽ መጥቶአልና፣ የእግዚአብሔርም ክብር ወጥቶልሻልና ተነሺ፣ አብሪ። 2 እነሆ፣ ጨለማ ምድርን ድቅድቅ ጨለማም አሕዛብን ይሸፍናል፤ ነገር ግን
በአንቺ ላይ እግዚአብሔር ይወጣል፣ ክብሩም በአንቺ ላይ ይታያል፤ 3 አሕዛብም ወደ ብርሃንሽ ነገሥታትም ወደ መውጫሽ ጸዳል ይመጣሉ። 4 ዓይኖችሽን
አንሥተሽ በዙሪያሽ ተመልከቺ። እነዚህ ሁሉ ተሰብስበው ወደ አንቺ ይመጣሉ። ወንዶች ልጆችሽ ከሩቅ ይመጣሉ፣ ሴቶች ልጆችሽንም በጫንቃ ላይ
ይሸከሙአቸዋል። 5 በዚያን ጊዜ የባሕሩ በረከት ወደ አንቺ ስለሚመለስ፣ የአሕዛብም ብልጥግና ወደ አንቺ ስለሚመጣ፣ አይተሽ ደስ ይልሻል፣ ልብሽም
ይደነቃል ይሰፋማል። 6 የግመሎች ብዛት፣ የምድያምና የጌፌር ግመሎች፣ ይሸፍኑሻል፤ ሁሉ ከሳባ ይመጣሉ፣ ወርቅንና ዕጣንን ያመጣሉ የእግዚአብሔርንም
ምስጋና ያወራሉ። 7 የቄዳር መንጎች ሁሉ ወደ አንቺ ይሰበሰባሉ፣ የነባዮትም አውራ በጎች ያገለግሉሻል፤ እኔን ደስ ሊያሰኙ በመሠዊያዬ ላይ ይወጣሉ፣
የክብሬንም ቤት አከብራለሁ። 8 ርግቦች ወደ ቤታቸው እንደሚበርሩ፣ እነዚህ እንደ ደመና የሚበርሩ እነማን ናቸው? 9 እርሱ አክብሮሻልና ለአምላክሽ
ለእግዚአብሔር ስምና ለእስራኤል ቅዱስ ልጆችሽን ከሩቅ ከእነርሱ ጋርም ብራቸውንና ወርቃቸውን ያመጡ ዘንድ ደሴቶች የተርሴስ መርከቦችም አስቀድመው
ይጠባበቁኛል። 10 በቍጣዬ ቀሥፌ በፍቅሬ ምሬሻለሁና መጻተኞች ቅጥርሽን ይሠራሉ፣ ነገሥታቶቻቸውም ያገለግሉሻል። 11 በሮችሽም ሁልጊዜ ይከፈታሉ፤
ሰዎች የአሕዛብን ብልጥግና የተማረኩትንም ነገሥታቶቻቸውን ወደ አንቺ ያመጡ ዘንድ ሌሊትና ቀን አይዘጉም። 12 ለአንቺም የማይገዛ ሕዝብና መንግሥት
ይጠፋል፣ እነዚያ አሕዛብም ፈጽመው ይጠፋሉ። 13 የመቅደሴንም ስፍራ ያስጌጡ ዘንድ የሊባኖስ ክብር፣ ጥዱና አስታው ባርሰነቱም፣ ወደ አንቺ ይመጣሉ፣
የእግሬንም ስፍራ አከብራለሁ። 14 የአስጨናቂዎችሽም ልጆች አንገታቸውን ደፍተው ወደ አንቺ ይመጣሉ፣ የናቁሽም ሁሉ ወደ እግርሽ ጫማ ይሰግዳሉ፤
የእግዚአብሔርም ከተማ፣ የእስራኤል ቅዱስ የሆንሽ ጽዮን ይሉሻል። 15 ከሰውም ማንም እስከማያልፍብሽ ድረስ የተተውሽና የተጠላሽ ነበርሽ፤ ነገር ግን
የዘላለም ትምክሕትና የልጅ ልጅ ደስታ አደርግሻለሁ። 16 የአሕዛብንም ወተት ትጠጫለሽ፣ የነገሥታትንም ጡት ትጠቢያለሽ፤ እኔም እግዚአብሔር የያዕቆብ
ኃይል፣ መድኃኒትሽና ታዳጊሽ እንደ ሆንሁ ታውቂያለሽ። 17 በናስ ፋንታ ወርቅን፣ በብረትም ፋንታ ብርን፣ በእንጨትም ፋንታ ናስን፣ በድንጋይም ፋንታ ብረትን
አመጣለሁ። አለቆችሽንም ሰላም፣ የበላይ ገዢዎችሽንም ጽድቅ አደርጋለሁ፤ 18 ከዚያ በኋላ በምድርሽ ውስጥ ግፍ፣ በዳርቻሽም ውስጥ ጕስቍልናና
ቅጥቃጤ አይሰማም፤ ቅጥርሽን መዳን በሮችሽንም ምስጋና ብለሽ ትጠሪያለሽ 19 ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር የዘላለም ብርሃንሽ፣ አምላክሽም ክብርሽ
ይሆናልና ፀሐይ በቀን ብርሃን አይሆንልሽም፣ የጨረቃም ብርሃን በሌሊት አይበራልሽም። 20 እግዚአብሔር የዘላለም ብርሃንሽ ይሆናልና፣ የልቅሶሽም ወራት
ታልቃለችና ፀሐይሽ ከዚያ በኋላ አትጠልቅም ጨረቃሽም አይቋረጥም። 21 ሕዝብሽም ሁሉ ጻድቃን ይሆናሉ፤ እኔም እከብር ዘንድ የአታክልቴን ቡቃያ፣ የእጄ
ሥራ የምትሆን ምድሪቱንም ለዘላለም ይወርሳሉ። 22 ታናሹ ለሺህ የሁሉም ታናሹ ለብርቱ ሕዝብ ይሆናል፤ እኔ እግዚአብሔር በዘመኑ ይህን አፋጥነዋለሁ።

Isaiah 60:1

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል

ብርሃንሽ መጥቶአልና ተነሺ አብሪ፤ የያህዌ ክብር ወጥቶልሻል
ይህ የሚያመለክተው ለኢየሩሳሌም ሰዎች ያህዌ ያደረገውን የከበሩ ነገሮች ነው። በሚያደርጉትና በሚናገሩት ያንን ክብር ማሳየትና ለወደ ፊቱም ያላቸውን ተስፋ አሁን ማሳየት አለባቸው።

Isaiah 60:2

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በእስራኤል ሕዝብ ይናገራል። ‹‹ብርሃን››ን ምሳሌ ማድረጉን ቀጥሏል። (ኢሳይያስ 60፥1 ይመ.)

ጨለማ ምድርን፣ ድቅድቅ ጨለማ ሕዝቦችን ቢሸፍንም
እነዚህ ሐረጐች ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው፤ ተያይዘው ጥቅም ላይ የዋሉት አጽንኦት ለመስጠት ነው። ‹‹መንፈሳዊ ጨለማ››ን ያመለክታሉ። ይህም ማለት የተቀሩት ሰዎች ያህዌን ወይም እርሱን ደስ እንደሚያሰኙ አያውቁም ማለት ነው። ይህ የመለኮታዊ ፍርድ ምሳሌ ነው።

በአንቺ ላይ ያህዌ ይወጣል
ይህም ማለት የእግዚአብሔር መገኘት ክብር ለእስራኤል ሕዝብ ይገለጻል፣ መሄድ ያለባቸውንም መንገድ ያሳያቸዋል ማለት ነው።

ክብሩም በአንቺ ላይ ይታያል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሕዝቦች ክብሩን በአንቺ ላይ ያያሉ።››

Isaiah 60:4

አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ላይ ያህዌ መናገር ጀምሯል

ሁሉም ይሰበሰባሉ
‹‹እነርሱ›› የሚያመለክተው ወደ ኢየሩሳሌም ለመመለስ የሚሰበሰቡትን የተቀሩትን የእስራኤል ሕዝብ ነው።

ሴቶች ልጆችሽን በዕቅፋቸው ይሸከሟቸዋል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሴቶች ልጆችሽን ዐቅፈው ይሸከሟቸዋል›› ወይም፣ ‹‹ሴቶች ልጆችሽን ያዝሏቸዋል››

ከዚያም ታያለሽ ታብረቀርቂያለሽ፣ ልብሽ በደስታ ይሞላል
የሐረጐቹ ትርጕም ተመሳሳይ ሲሆን፣ በኢየሩሳሌም ከሚሆነው የተነሣ በጣም ደስ እንደሚላቸው አጽንዖት ይሰጣሉ።

የባሕር ብዛት
ይህ የሚያመለክተው በመርከብ ምናልባትም ከሜዲትራኒያን ባሕር ማዶ ወደ ኢየሩሳሌም የሚመጣውን ሀብትና ብልጥግና ነው።

አንቺ ላይ ይፈስሳል
ይህ የሚያመለክተው የሀብቱ ብዛት እንደ ውሃ ሙላት እንደሚሆን ነው።

Isaiah 60:6

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

ግልግል ግመሎች
‹‹የግመል መንጋ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጌፌር... ቄዳር... ነባዮት
እነዚህ አረቢያ አካባቢ ያሉ ቦታዎች ስሞች ናቸው።

የቄዳር የበግ መንጋ ሁሉ ወደ አንቺ ይሰበሰባል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የቄዳር ሕዝብ የበግ መንጋዎቻቸውን ወደ አንቺ ይሰበስባሉ››

የነባዮት አውራ በጎች ለሚያስፈልግሽ ይውላሉ
ይህ የሚያመለክተው ለመሥዋዕት የሚያስፈልጋቸውን ነው።

መሠዊያሽ ላይ ተቀባይነት ያለው መሥዋዕት ይሆናሉ
‹‹እኔ ያህዌ፣ መሠዊያየ ላይ እቀበላቸዋለሁ››

Isaiah 60:8

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል

እነዚህ እንደ ደመና የሚጓዙ፣ እንደ ርግቦች ወደ ጐጆአቸው የሚበርሩ እነማን ናቸው?
እዚህ ላይ ያህዌ ትኩረት ለመሳብ ጥያቄዎችና ቅኔያዊ ምስሎች ይጠቀማል። የመርከቦቹን መቅዘፍ ከደመናና ከርግቦች ጋር ያመሳስለዋል። ይህ እስራኤላውያን ወደ አገራቸው መመለሳቸውንም ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ተመልከቱ፣ እንደ ደመና በፍጥነት፣ የሚጓዝ እንደ ርግቦችም ወደ ጐጆአቸው የሚመለሱ አያለሁ››

ደሴቶች
ይህ የሚያመለክተው በደሴቶች የሚኖሩ ሰዎችን ነው፤ የደሴቶች አካባቢ ማየት እንደሚችሉ ሰዎች እንደሆኑ አድርጐ ያቀርባል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በደሴቶቹ ያሉ ሰዎች››

የተርሴስ መርከቦች
ብዙውን ጊዜ ይህ ለረጅም ጉዞ የሚስማሙ ብዙ የንግድ መርከቦች ነው የሚያመለክተው

የእስራኤል ቅዱስ
ኢሳይያስ 1፥4 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

እርሱ አክብሮሻል
‹‹ያህዌ እናንተ የእስራኤል ሰዎችን አክብሮአል››

Isaiah 60:10

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል

ቀንም ሆነ ሌሊት አይዘጉም
‹‹ቀን›› እና፣ ‹‹ሌሊት›› በአንድነት፣ ‹‹ሁልጊዜ›› ማለት ናቸው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ማንም አይዘጋቸውም››

የመንግሥታት ብልጥግና ከንጉሦቻቸው ጋር
ይህን በሌለ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከነገሥቶቻቸው ጋር ሰዎች የመንግሥታትን ብልጥግና ወደ አንቺ እንዲያመጡ››

Isaiah 60:12

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

እነዚያ ሕዝቦች ጨርሶ ይጠፋሉ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የእነዚያን አገሮች ሰዎች ጨርሶ አጠፋቸዋለሁ››

የሊባኖስ ክብር
ይህ የሚያመለክተው ሊባኖስ ውብ በሆነ ዛፎቿ በተለይም፣ በዝግባና በጥድ ዝነኛ መሆንዋን ነው። የዛፎቹ ሁሉ ትክክለኛ ምንነት አይታወቅም።

የእግሬ ማረፊያ
ይህ የሚያመለክተው የያህዌን ቤተ መቅደስ ነው።

Isaiah 60:14

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

የእስራኤል ቅዱስ
ኢሳይያስ 1፥4 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

Isaiah 60:15

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

ማንም የማያልፍብሽ
‹‹ማንም ምድርሽን ቢንቅም፣›› ወይም፣ ‹‹ባዕዳን ምድርሽን ቢንቁም››

የሕዝቦችን ወተት ትጠጪያለሽ፣ የነገሥታትን ጡት ትጠቢያለሽ
ይህ የሚናገረው ከሌሎች መንግሥታት ስለሚገኘው ሀብትና ብልጥግና ነው። አጽንኦት ለመስጠት ሁለቱም ሐረጐች የደጋገሙት ተመሳሳይ ነገርን ነው።

ቤዛ
ኢሳይያስ 41፥14 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

የያዕቆብ ኀያል
ኢሳይያስ 49፥26 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

Isaiah 60:17

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

በእንጨት ፈንታ ናስ፣ በድንጋይ ፈንታ ብረት
ያህዌ የበለጠ ዋጋ ያለው የሕንፃ መሥሪያ ነገሮች ይሰጣቸዋል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በእንጨት ፈንታ ናስ አመጣለሁ፤ በድንጋይ ፈንታ ብረት አመጣለሁ››

ሰላም አለቃሽ፣ ፍትሕ ገዥሽ ይሆናል
‹‹ሰላም›› እና፣ ‹‹ፍትሕ›› ሰብዓዊ ገዦች እንደሆኑ ያህዌ ይናገራል። ይህም ማለት በእስራኤል ምድር የተሟላ ሰላምና ፍትሕ ይኖራል ማለት ነው።

ከእንግዲህ በምድርሽ ሁከት አይሰማም
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በምድርሽ የሁከት ወሬ አይኖርም››

ቅጥሮችሽን መዳን፣ ደጆችሽን ምስጋና ብለሽ ትጠሪያቸዋለሽ
ቁሳዊ ነገሮች መንፈሳዊ ባሕርያት ያላቸው ስሞች ተሰጥቷቸዋል። የኢየሩሳሌም ከተማ የሰላም ከተማ ትሆናለች፤ እዚያ የሚኖሩትም ያህዌን ያመሰግኑታል።

Isaiah 60:19

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ያህዌ የዘላለም ብርሃንሽ ይሆናልና
አጽንዖት ለመስጠት ሁለቱም ሐረጎች ተመሳሳይ ነገር ይደግማሉ

ከእንግዲህ ፀሐይሽ አትጠልቅም፣ ጨረቃሽም አትጠፋም
በመሠረቱ ጨረቃ አትጠፋም። ይህ ግነታዊ አባባል የፀሐይና የጨረቃ ብርሃን ከያህዌ ብርሃን ያነሰ ይሆናል ማለት ነው።

Isaiah 60:21

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል

የተከልሁት ቅርንጫፍ፣ የእጆቼ ሥራ
እነዚህ ሐረጎች ተመሳሳይ ነገር ማለት ቢሆኑም፣ አጽንዖት ለመስጠት ተደግመዋል።

የተከልሁት ቅርንጫፍ
ያህዌ እንደ አንድ አትክልተኛ ሕዝቡን እየበቀሉ ካሉ ተክሎች ጋር ያመሳስላል። ያህዌ ሕዝቡን በእስራኤል ምድር አኑሮአል። ይህ ለሕዝቡ ተስፋ ይሰጣል።

የእጆቼ ሥራ
የእስራኤልን ሕዝብ ያህዌ በብልሃት ከሠራው የእጅ ሥራ ጋር ያመሳስላል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 61

1 የጌታ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው፣ ለድሆች የምሥራችን እሰብክ ዘንድ እግዚአብሔር ቀብቶኛልና፤ ልባቸው የተሰበረውን እጠግን ዘንድ፣
ለተማረኩትም ነጻነትን ለታሰሩትም መፈታትን እናገር ዘንድ ልኮኛል። **2** የተወደደችውን የእግዚአብሔርን ዓመት አምላካችንም የሚበቀልበትን ቀን እናገር ዘንድ፣
የሚያለቅሱትንም ሁሉ አጽናና ዘንድ፤ **3** እግዚአብሔር ለክብሩ የተከላቸው የጽድቅ ዛፎች እንዲባሉ ለጽዮን አልቃሾች አደርግላቸው ዘንድ፣ በአመድ ፋንታ
አክሊልን፣ በልቅሶም ፋንታ የደስታን ዘይት፣ በኀዘንም መንፈስ ፋንታ የምስጋናን መጐናጸፊያ እሰጣቸው ዘንድ ልኮኛል። **4** ከጥንትም ጀምሮ ባድማ የነበሩትን
ይሠራሉ፤ ከቀድሞ የፈረሱትንም ያቆማሉ። ባድማ የነበሩትንና ከብዙ ትውልድ በፊት የፈረሱትን ከተሞች እንደ ገና ይሠራሉ። **5** መጻተኞችም ቆመው በጎቻችሁን
ያሰማራሉ፣ ሌሎች ወገኖችም አራሾችና ወይም ጠባቂዎች ይሆኑላችኋል። **6** እናንተ ግን የእግዚአብሔር ካህናት ትባላላችሁ፣ ሰዎቹም የአምላካችን አገልጋዮች
ብለው ይጠሩአችኋል፤ የአሕዛብን ሀብት ትበላላችሁ፣ በክብራቸውም ትመካላችሁ። **7** በእፍረታችሁ ፋንታ ሁለት እጥፍ ይሆንላችኋል፣ በውርደታችሁም ፋንታ
ዕድል ፈንታችሁ ደስ ይላቸዋል፤ ስለዚህ በምድራቸው ሁሉ እጥፍ ይገዛሉ፣ የዘላለምም ደስታ ይሆንላቸዋል። **8** እኔ እግዚአብሔር ፍርድን የምወድድ፣ ስርቆትንና
በደልን የምጠላ ነኝ፤ ፍዳቸውንም በእውነት እሰጣቸዋለሁ፣ ከእነርሱም ጋር የዘላለም ቃል ኪዳን አደርጋለሁ። **9** ዘራቸውም በአሕዛብ መካከል፣ ልጆቻቸውም
በወገኖች መካከል የታወቁ ይሆናሉ፤ ያያቸው ሁሉ እግዚአብሔር የባረካቸው ዘር እንደ ሆኑ ይገነዘባል። **10** አክሊልን እንደ ለበሰ ሙሽራ፣ በጌጥ ሽልማትዋም
እንዳጌጠች ሙሽራ፣ የማዳንን ልብስ አልብሶኛልና፣ የጽድቅንም መጐናጸፊያ ደርቦልኛልና በእግዚአብሔር እጅግ ደስ ይለኛል፣ ነፍሴም በአምላኬ ሐሤት
ታደርጋለች። **11** ምድርም ቡቃያዋን እንደምታወጣ፣ ገነትም ዘሩን እንደሚያበቅል፣ እንዲሁ ጌታ እግዚአብሔር ጽድቅንና ምስጋናን በአሕዛብ ሁሉ ፊት ያበቅላል።

Isaiah 61:1

የያህዌ መንፈስ እኔ ላይ ነው
እዚህ ላይ፣ ‹‹መንፈስ›› ሰዎችን የሚያነሣሣና የሚያንቀሳቅስ መንፈስ ቅዱስ ነው። ኢሳይያስ 11፥2 ወይም ኢሳይያስ 42፥1 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

ለተጐዱ
ይህ ታላቅ መከራ ውስጥ ያሉ ድኾችን ወይም፣ በራሳቸው ማስወገድ የማይችሉት ችግር ውስጥ ያሉ ጭቁኖችን ያመለክታል።

ለምርኮኞች ነጻነት፣ ለእስረኞች መፈታት
ሁለቱም ሐረጐች ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። እግዚአብሔር ለምርኮኞች ነጻነትን በእርግጥ እንደሚሰጥ ያመለክታሉ።

Isaiah 61:2

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ መናገር ቀጥሏል።

የያህዌን የሞገስ ዓመት፣ የበቀሉን ቀን
ሁለቱም ሐረጐች የሚናገሩት ስለ ተመሳሳይ ወቅት ነው። ‹‹ዓመት›› እና፣ ‹‹ቀን›› አንድ የተሟላ ነገርን የሚወክሉ ምሳሌዎች ናቸው።

የያህዌን የሞገስ ዓመት
‹‹ያህዌ ለሕዝቡ መልካም ነገር የሚያደርግበት ጊዜ››

Isaiah 61:3

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ መናገር ቀጥሏል።

ለመስጠት... ለመስጠት
ኢሳይያስ ይህን የደገመው አጽንዖት ለመስጠት ነው

ጥምጥም
‹‹የራስ ጥምጥም›› ወይም፣ ‹‹የተዋበ የራስ መሸፈኛ›› ይህ ራስ ላይ የሚጠመጠም ረጅም የጨርቅ አካል ነው።

የደስታ ዘይት... የምስጋና መጐናጸፊያ
ሰዎች ራሳቸውን ዘይት ይቀባሉ፤ በከበረ በዓልና በደስታ ጊዜ ሰዎች ያማረ ልብስ ይለብሳሉ።

በትካዜ መንፈስ ፈንታ
‹‹በሐዘን ፈንታ›› ወይም፣ ‹‹በለቅሶ ፈንታ››

ያህዌ የተከላቸው የጽድቅ ዋርካ ዛፎች
ይህ ማለት ያህዌ ሕዝቡን፣ ጠንካራና ብርቱ አድርጓል ማለት ነው።

ለእርሱ ክብር
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሕዝቡ ኑሮ እርሱን እንዲያከብር››

Isaiah 61:4

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በእያንዳንዱ መስመር ተጓዳኝ ሐሳብን በመጠቀም መናገር ቀጥሏል።

Isaiah 61:6

አጠቃላይ መረጃ
የያህዌ ባርያ በእያንዳንዱ መስመር ተጓዳኝ ሐሳብን በመጠቀም ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

ትጠራላችሁ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰዎች ይጠሯችኃል››

ዕጥፍ ይኖራችኃል
ምናልባት፣ ዕጥፍ የርስት ድርሻ ሊሆን ይችላል።

በድርሻቸው ደስ ይላቸዋል... እነርሱ... ምድራቸው የእነርሱ ይሆናል
ይህም የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። ይህን በሁለተኛ ሰው ደረጃ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በድርሻችሁ ደስ ይላችኃል... እናንተ... ምድራችሁ... የእናንተ ይሆናል››

Isaiah 61:8

ዘሮቻቸው በሕዝቦች ዘንድ፣ ልጆቻቸውም በሰዎች ዘንድ የታወቁ ይሆናሉ
ሁለቱም ሐረጐች ተመሳሳይ ናቸው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሌላ አገር ሰዎች ዘሮቻቸውን ያውቋቸዋል››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ልጆቻቸውም በሰዎች ዘንድ
የዚህ ሐረግ ግሥ ቀደም ሲል እንደ ነበረው ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ልጆቻቸው በሰዎች ዘንድ የታወቁ ይሆናሉ››

Isaiah 61:10

እኔ በያህዌ እጅግ ደስ ይለኛል
‹‹እኔ›› የሚለው ያህዌ እንደ ገና የመለሳቸው የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደ አንድ ሰው መናገራቸውን ያመለክታል።

የመዳን ልብስ አልብሶኛል፤ የጽድቅ መጐናጸፊያ ደርቦልኛል
እንደ አንድ ሰው ሆነው ለያህዌ ሲናገሩ የነበሩ ሕዝብ አሁን ሰው ሁሉ የሚያየው የመዳንና የጽድቅ ልብስ ለብሰዋል። ‹‹ልብስ›› እና፣ ‹‹መጐናጸፊያ›› ሰው ሁሉ የሚያየው ነገሮች ናቸው።

ሙሽራ ራሱን በጥምጥም እንደሚያሳምር፣ ሙሽራዪቱም ራሷን እንደምታስጌጥ
ይህ ንጽጽር ተናጋሪው እጅግ ደስ እንዳለው ያንንም ደስታ እያጣጣመ መሆኑን አጽንዖት ይሰጣል።

ጥምጥም
ኢሳይያስ 61፥3 ላይ ያለውን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

ምድር ቡቃያ እንደምታበቅል፣ የተክል ቦታ ችግኝ እንደሚያፈለ
ይህ በሁለት መንገድ ተመሳሳይ ነገር መናገር ነው። እግዚአብሔር የተናገረው በእርግጥ የሚፈጸም መሆኑ ከተተከለ በኃላ ከሚበቅል ተክል ጋር ተመሳስሎአል አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አትክልት ቦታ የተተከለ ዘር እንደሚበቅልና እንደሚያድግ››

ጽድቅና ምስጋናም ይበቅላል
እነዚህ ምግባሮች እንደ አትክልት ከዘር እንደሚያድጉ ተነግሯል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 62

1 ስለ ጽዮን ዝም አልልም፣ ስለ ኢየሩሳሌምም ጸጥ አልልም፣ ጽድቅዋ እንደ ጸዳል መዳንዋም እንደሚበራ ፋና እስኪወጣ ድረስ። **2** አሕዛብም ጽድቅሽን
ነገሥታትም ሁሉ ክብርሽን ያያሉ፤ የእግዚአብሔርም አፍ በሚጠራበት በአዲሱ ስም ትጠሪያለሽ። **3** በእግዚአብሔር እጅ የክብር አክሊል፣ በአምላክሽም እጅ
የመንግሥት ዘውድ ትሆኛለሽ። **4** ከእንግዲህ ወዲህ፣ "የተተወች" አትባዪም፤ ምድርሽም ከእንግዲህ ወዲህ፣ "ውድማ" አትባልም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር
በአንቺ ደስ ብሎታልና፣ ምድርሽም ባል ታገባለችና አንቺ፣ "ደስታዬ የሚኖርባት" ትባያለሽ ምድርሽም፣ "ባል ያገባች" ትባላለች። **5** ጕልማሳም ድንግሊቱን
እንደሚያገባ፣ እንዲሁ ልጆችሽ ያገቡሻል። ሙሽራም በሙሽራይቱ ደስ እንደሚለው፣ እንዲሁ አምላክሽ በአንቺ ደስ ይለዋል። **6** ኢየሩሳሌም ሆይ፣ ጕበኞችን
በቅጥርሽ ላይ አቁሜአለሁ፤ ቀንና ሌሊት ከቶ ዝም አይሉም፤ እናንተ እግዚአብሔርን የምታሳስቡ፣ **7** ኢየሩሳሌምን እስኪያጸና በምድርም ላይ ምስጋና
እስኪያደርጋት ድረስ አትረፉ ለእርሱም ዕረፍት አትስጡ። **8** እግዚአብሔር፣ "ከእንግዲህ ወዲህ በእርግጥ ለጠላቶችሽ መብል ይሆን ዘንድ እህልሽን
አልሰጥም፣ መጻተኞችም የደከምሽበትን ወይንሽን አይጠጡም። **9** ነገር ግን የሰበሰቡት ይበሉታል፣ እግዚአብሔርንም ያመሰግናሉ፣ ያከማቹትም በመቅደሴ
አደባባይ ላይ ይጠጡታል" ብሎ በቀኙና በኃይሉ ክንድ ምሎአል። **10** እለፉ፣ በበሮች በኩል እለፉ! የሕዝቡንም መንገድ ጥረጉ፤ አዘጋጁ፣ ጐዳናውን አዘጋጁ፣
ድንጋዮቹንም አስወግዱ፤ ለአሕዛብም ዓለማ አንሡ! **11** ተመልከቱ፣ እግዚአብሔር ለምድር ዳርቻ አዋጅ እንዲህ ብሎ ነግሮአል፣ "ለጽዮን ልጅ፣ እነሆ፣
መድኀኒትሽ ይመጣል፤ እነሆ፣ ዋጋው ከእርሱ ጋር ሥራውም በፊቱ አለ" በሉአት። **12** እግዚአብሔር፣ "የተቤዣቸው፣ የተቀደሰ ሕዝብ" ብለው ይጠሩአቸዋል፤
አንቺም፣ "የተፈለገች ያልተተወችም" ከተማ ትባያለሽ።

Isaiah 62:1

ስለ ጽዮን ዝም አልልም፤ ስለ ኢየሩሳሌም ጸጥ አልልም
ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። እዚህ ላይ፣ ‹‹ጽዮን›› እና፣ ‹‹ኢየሩሳሌም›› በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎችን ይወክላሉ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ስለ ኢየሩሳሌም ሕዝብ ዝም አልልም››

ዝም አልልም
‹‹እኔ›› የሚያመለክተው ያህዌን ነው።

ጽድቋ ደምቆ እስኪወጣ፣ ድነቷ እንደ ፋና እስኪሆን ድረስ
ሁለቱም ሐረጐች የሚያመለክቱት የኃላ ኀላ እግዚአብሔር መጥቶ የእስራኤልን ሕዝብ እንደሚያድን ያም የብርሃን ያህል በግልጽ እንደሚታይ ነው።

Isaiah 62:3

በያህዌ እጅ የውበት አክሊል በአምላክሽ እጅ እንደ ነገሥታት ዘውድ ትሆኛለሽ
ሁለቱም ተመሳሳይ ነገር ማለት ሲሆኑ፣ ተያይዘው የቀረቡት አጽንዖት ለመስጠት ነው። በእግዚአብሔር ኀይልና ሥልጣን ሥር ኢየሩሳሌም የንጉሥ ከተማ እንደምትሆን ይናገራሉ። የያህዌ እጅ የእርሱን ኀይልና ሥልጣን ይወክላል።

ከእንግዲህ... ‹‹የተተወች››... አትባዪም
ሁለቱም ተመሳሳይ ነገር ማለት ሲሆኑ፣ ተያይዘው ያቀረቡት አጽንዖት ለመስጠት ነው።

ከእንግዲህ ስለ አንቺ አይባልም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሰዎች አንቺን አይሉሽም››

ከእንግዲህ ስለ ምድርሽ አይባልም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከእንግዲህ ሰዎች ስለ ምድርሽ አይሉም››

ምድርሽ ታገባለች
ይህ ማለት ያህዌ የእስራኤልን ሕዝብ ይወዳል፤ እንደ ባል ሁሌም ከእነርሱ ጋር ይሆናል ማለት ነው።

Isaiah 62:5

ጐልማሳ ድንግሊቱን እንደሚያገባ ልጆችሽ ያገቡሻል
‹‹ልጆችሽ›› የእስራኤልን ሕዝብ ሲሆን፣ ‹‹አንቺ›› ይሁዳንና የእስራኤልን ምድር ያመለክታል። ሰው የሚስቱ ባለቤት እንደሚሆን ሕዝቡም የምድሪቱ ባለቤት ይሆናል ማለት ነው።

ሙሽራ በሙሽራዋ ደስ እንደሚለው አምላክሽ በአንቺ ደስ ይለዋል
ይህ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ባለው ግንኙነት ደስ እንደሚሰኝ ይናገራል።

Isaiah 62:6

አድርጌአለሁ
‹‹እኔ›› የሚያመለክተው ኢሳይያስን ወይም ያህዌን ነው።

ጠባቂዎች በቅጥሮችሽ ላይ
ይህ የሚያመለክተው ነቢያትን፣ ባለ ሥልጣኖችን ወይም ምናልባትም ያለ ማቋረጥ ከተማዋን የኢየሩሳሌምን ሕዝብ የሚጠብቁ መላእክትን ይሆናል። ኢሳይያስ 52፥8 እና ኢሳይያስ 56፥10 ላይ፣ ‹‹ጠባቂዎች›› የሚለውን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

ቀንና ሌሊት ዝም አይሉም
ይህም ማለት ያለ ማቋረጥ ያህዌን ይለምናሉ ወይም እርስ በርስ ይጠራራሉ ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ቀኑን በሙሉ አጥብቀው ወደ ያህዌ ይጸልያሉ››

ዕረፍት አትሰጡት
‹‹እርሱ›› የሚያመለክተው ያህዌን ነው።

Isaiah 62:8

በቀኝ እጁና በብርታቱ ክንድ
የቀኝ እጅና ክንድ ኀይልና ሥልጣንን ይወክላሉ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በኀይልና በሥልጣኑ››

ከእንግዲህ መብል እንዲሆናቸው እህልሽን ለጠላቶችሽ በእርግጥ አልሰጥም
ይህ ማለት ጠላቶቻቸው የእስራኤልን ሕዝብ አያሸንፉም፣ ከእንግዲህ እህላቸውን አይወስዱም ማለት ነው። ምናልባትም ጠላቶች በግብር መልክ ወይም ሰራዊታቸውን ለመመገብ ባለፈው ጊዜ እህላቸውን ወስደው ሊሆን ይችላል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከእንግዲህ መብል እንዲሆናቸው እህልሽን ለጠላቶችሽ በእርግጥ አልሰጥም… ባዕዳንም አዲሱን ወይን ጠጅሽን አይጠጡም።
እነዚህ ዐረፍተ ነገሮች በአንድነት የተቀመጡት አጽንዖትና ለመስጠትና መጠናቀቅን ለማመልከት ነው።

Isaiah 62:10

ወዲህ ኑ፤ በበሩ በኩል ኑ
‹‹ኑ›› የሚለው የተደጋገመው አስቸኳይ መሆኑን ለማሳየት ነው።

ሥሩ፣ አውራ መንገዱን ሥሩ
‹‹ሥሩ›› የሚለው ቃል የተደገመው ያህዌ ባስቸኳይ መንገዱ እንዲስተካከል መፈለጉን አጽንዖት ለመስጠት ነው። ‹‹አውራ መንገድ›› ሕዝቡ የሚመለስበትን መንገድ ይወክላል። ይህ ከኢሳይያስ 40፥3 እና ኢሳይያስ 57፥14 ጋር ይመሳሰላል።

ድንጋዮች ሰብስቡ
‹‹መንገዱን ለስላሳ ለማድረግ ድንጋዮቹን አውጡ›› ድንጋይ በፍጥነት ለመራመድ እንቅፋት የሆኑ ነገሮችን ሁሉ ይወክላል።

ለሕዝቦች የምልክት ባንዲራ አንሡ
የምልክት ባንዲራ የሌሎችን ትኩረት መሳብ ያመለክታል። ይህም ማለት የሌሎች አገሮች ሰዎች የእስራኤልን ምድርና አድርግላቸዋለሁ እንዳለው ያህዌ የፈጸመውን ልብ እንዲሉ ያህዌ ሕዝቡን እየጠራ ነው ማለት ነው።

Isaiah 62:11

እነሆ
‹‹ልብ በሉ››

የምድር ዳርቻዎች
ሩቅ ቦታ ያለ ስፍራ የምድር ዳርቻዎች ተብሎአል። ይህም ማለት በዳርቻዎቹ መካከል ያለውንም ቦታ ያመለክታል። ኢሳይያስ 40፥28 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሩቅ ቦታ ያሉ ስፍራዎች›› ወይም፣ ‹‹በምድር ሁሉ››

የጽዮን ሴት ልጅ
‹‹ሴት ልጅ›› የኢየሩሳሌምን (ጽዮን) ሕዝብ ይወክላል። ኢሳይያስ 1፥8 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

ዋጋው ከእርሱ ጋር ብድራቱም ፊት ፊቱ ይሄዳል
እነዚህ ሐረጐች አጽንዖት ለመስጠት ተመሳሳይ ሐሳብ ይወክላሉ። ኢሳይያስ 40፥10 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

ትጠሪያለሽ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። ‹‹ይጠሩሻል››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 63

1 ይህ ከኤዶምያስ፣ ልብሱም የቀላ ከባሶራ የሚመጣ፣ አለባበሱ ያማረ፣ በጕልበቱ ጽናት በራስ መተማመን የሚራመድ ማን ነው? በጽድቅ የምናገር ለማዳንም
የምበረታ እኔ ነኝ። **2** ቀሚስህ ስለ ምን ቀላ፣ ልብስህስ በወይን መጥመቂያ እንደሚረግጥ ሰው ልብስ ስለ ምን መሰለ? **3** መጥመቂያውን ብቻዬን ረግጫለሁ፣
ከአሕዛብም አንድ ሰው ከእኔ ጋር አልነበረም፤ በቍጣዬ ረገጥኋቸው በመዓቴም ቀጠቀጥኋቸው፤ ደማቸውም በልብሴ ላይ ተረጭቶአል፣ ልብሴንም ሁሉ
አስደፈአለሁ። **4** የምበቀልበት ቀን በልቤ ነውና፣ የምቤዥበትም ዓመት ደርሶአልና። **5** ተመለከትሁ፣ የሚረዳም አልተገኘም፤ የሚያግዝም አልነበረምና
ተደነቅሁ፤ ስለዚህ የገዛ ክንዴ መድኃኒት አመጣልኝ፣ ቍጣዬም እርሱ አገዘኝ። **6** በቍጣዬም አሕዛብን ረገጥሁ በመዓቴም ቀጠቀጥኋቸው፣ ደማቸውንም ወደ
ምድር አፈሰስሁት። **7** እግዚአብሔር እንደ ሰጠን ሁሉ፣ የእግዚአብሔርን ቸርነትና የእግዚአብሔርን ምስጋና፣ እንደ ምሕረቱና እንደ ቸርነቱም ብዛት ለእስራኤል
ቤት የሰጠውን ትልቅ በጎነት አሳስባለሁ። **8** እርሱም፣ "በእውነት ሕዝቤ፣ ሐሰትን የማያደርጉ ልጆች ናቸው" አለ፤ መድኃኒትም ሆነላቸው። **9** በጭንቃቸው ሁሉ
እርሱ ተጨነቀ፣ የፊቱም መልአክ አዳናቸው፤ በፍቅሩና በርኅራኄውም ተቤዣቸው፣ በቀደመውም ዘመን ሁሉ አንሥቶ ተሸከማቸው። **10** እነርሱ ግን ዐመፁ ቅዱስ
መንፈሱንም አስመረሩ። ስለዚህ ተመልሶ ጠላት ሆነባቸው፣ እርሱም ተዋጋቸው። **11** እርሱም እንዲህ ብሎ የቀደመውን ዘመን አሰበ። "የበጎቹን እረኛ ከባሕሩ
ያወጣው ወዴት ነው ያለ? ቅዱስ መንፈሱንም በመካከላቸው ያኖረ ወዴት ነው ያለ? **12** የከበረውንም ክንድ በሙሴ ቀኝ ያስሄደ፣ ለራሱም የዘላለምን ስም
ያደርግ ዘንድ ውኃውን በፊታቸው የከፈለ፣ **13** በምድረ በዳም እንደሚያልፍ ፈረስ፣ በቀላይ ውስጥ ያለ ዕንቅፋት ያሳለፋቸው ወዴት ነው ያለ? **14** ወደ ሸለቆ
እንደሚወርዱ ከብቶች፣ እንዲሁ የእግዚአብሔር መንፈስ ወደ ዕረፍት አመጣቸው። እንዲሁም ለራስህ የከበረ ስም ታደርግ ዘንድ ሕዝብን መራህ። **15** ከሰማይ
ቁልቊል ተመልከት፣ ከቅዱስነትህና ከክብርህም ማደሪያ ጐብኝ፤ ቅንዓትህና ኃይልህስ ወዴት ነው? ለእኔም የሆነው የልብህ ናፍቆትና ርኅራኄህ ተከለከለ። **16**
አብርሃም ባያውቀን እስራኤልም ባይገነዘበን፣ አንተ አባታችን ነህ፤ 'አቤቱ፣ አንተ አባታችን ነህ፣' ስምህም ከዘላለም ታዳጊያችን ነው። **17** አቤቱ፣ ከመንገድህ
ለምን አሳትኸን? እንዳንፈራህም ልባችንን ለምን አጸናህብን? ስለ ባሪያዎችህ ስለ ርስትህ ነገዶች ተመለስ። **18** የተቀደሰው ሕዝብህ መቅደስህን ጥቂት ጊዜ
ወረሱት፤ ጠላቶቻችንም ረግጠውታል። **19** ከዘላለም እንዳልገዛኸን በስምህም እንዳልተጠራን ሆነናል።

Isaiah 63:1

ይህ ከኤዶም... ከባሶራ የሚመጣ ማን ነው?
ኢሳይያስ የእስራኤል ጠላት ኤዶም ላይ የሚመጣውን የያህዌን ፍርድ ለማመልከት እንደ ጠባቂ በጥያቄና መልስ መልክ ይጠቀማል። ጥያቄውን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እኔ ያህዌ ከኤዶም ቀይ ለብሼ ከባሶራ እመጣለሁ››

ባሶራ
ይህ የኤዶም ዋና ከተማ ነው።

እኔ ነኝ
‹‹እኔ›› ያህዌን ይወክላል።

ልብስህ ለምን ቀይ ሆነ... በወይን መጥመቂያ
ይህን ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ልብስህ ላይ ያለው ቀይ በወይን መጥመቂያ የነበርህ ሰው አስመስሎሃል››

ወይን መርገጫ
የወይን መርገጫ ዐለት ውስጥ የተፈለፈለ ጐድጓዳ ነገር ሲሆን፣ የወይን ጠጅ እንዲወጣ ሰዎች የወይን ፍሬዎቹን የሚረግጡበት ነው።

Isaiah 63:3

ወይኑን ረገጥሁ
‹‹እኔ›› የሚለው ያህዌ ነው። ይህ ምስል የሚያመለክተው ያህዌ ጠላቶቹን መደምሰሱን ነው።

የበቀል ቀን
‹‹የበቀል ጊዜ›› ወይም፣ ‹‹በቀል የሚፈጸምበት ቀን››

በቀል
ፍትሕ ለማምጣት ያህዌ በተገቢ መንገድ ይቀጣል። የእርሱ በቀል ከሰው በቀል ይለያል።

የምቤዥበት ዓመት
‹‹ዓመት›› የሚለው እስራኤልን ለመመለስ ያህዌ የወሰነውን ጊዜ ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እኔ የምቤዥበት ጊዜ››

Isaiah 63:5

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል

የገዛ ክንዴ ግን
‹‹ክንድ›› ኀይልን ይወክላል።

በመዓቴ አሰከርኃቸው
ይህም ማለት በመዓቱና በቁጣው ብዛት ያህዌ ግራ እንዲጋቡና ዐቅል እንዲያጡ አደረጋቸው ማለት ነው።

ደማቸውን አፈሰስሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ደም›› የሚገደሉትን የያህዌን ጠላቶች ሕይወት ይወክላል።

Isaiah 63:7

የያህዌን የኪዳን ታማኝነት እናገራለሁ
‹‹ታማኝነት›› የሚለውን ቃል፣ ‹‹ታማኝ›› ወይም፣ ‹‹በታማኝነት›› በማለት መግለጽ ይቻላል። ኢሳይያስ 16፥5 ላይ ‹‹የኪዳን ታማኝነት›› የሚለውን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እግዚአብሔር ለኪዳኑ እንዴት ታማኝ እንደሆነ እናገራለሁ›› ወይም፣ ‹‹እግዚአብሔር በታማኝነቱ ለሕዝቡ ያደረጋቸውን ነገሮች እናገራለሁ››

እናገራለሁ
‹‹እኔ›› የሚለው የሚያመለክተው ኢሳይያስን ነው።

ለእኛ ያደረገውን
‹‹እኛ›› ኢሳይያስንና የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Isaiah 63:9

በመከራቸው ሁሉ
‹‹በመከራችን ሁሉ›› እዚህ ላይ፣ ‹‹እነርሱ›› የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል። የሕዝቡ አካል እንደ መሆኑ ኢሳይያስ ራሱን ጨምሯል።

እርሱ ተጨነቀ
‹‹እርሱ›› የሚያመለክው ያህዌን ነው።

የፊቱ መልአክ
ይህ የሚያመለክተው ከእግዚአብሔር ፊት የተላከውን ነው።

አንሥቶ ተሸከማቸው
ይህ ከብዙ ዓመታት በፊት እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ከግብፃውያን መጠበቁንና ማዳኑን ያመለክታል። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል።

Isaiah 63:10

እነርሱ ግን ዐመፁ
‹‹እኛ ግን ዐመፅን›› እዚህ ላይ፣ ‹‹እነርሱ›› የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። ኢሳይያስ እንደ ሕዝቡ አካል ራሱንም ጨምሯል።

መንፈስ ቅዱሱ
‹‹የያህዌ መንፈስ ቅዱስ››

Isaiah 63:11

እንዲህ አሉ
‹‹እንዲህ አልን›› እዚህ ላይ፣ ‹‹እነርሱ›› የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል። የሕዝቡ አካል እንደ መሆኑ ኢሳይያስ ራሱንም ጨምሯል።

ከባሕር ያወጣቸውን
እስራኤላውያን ተሻግረው ከግብፃውያን እንዲያመልጡ ያህዌ በተአምር ቀይ ባሕርን መክፈሉ በውስጠ ታዋቂነት ግልጽ ነው።

የመንጋው እረኞች
አንዳንዴ መሪዎች ‹‹እረኞች›› ይባላሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሕዝቡ መሪዎች››

Isaiah 63:12

አጠቃላይ መረጃ
የእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥለዋል

ታላቅ ኀይሉ ከሙሴ ቀኝ እጅ ጋር እንዲሄድ ያደረገ
‹‹ቀኝ እጅ›› በሙሴ በኩል የያህዌን ኀይል ይወክላል። ይህም ማለት ሙሴ ቀይ ባሕርን እንዲከፍል ያስቻለው የእግዚአብሔር ኀይል ነበር ማለት ነው።

ሜዳ ላይ እንደሚሮጥ ፈረስ አልተሰናከሉም
ይህ ማለት ፈረስ ሜዳ ላይ እንደሚራመድ ከግብፅ ወደ እስራኤል ሲጓዙ እስራኤላውያንም ለአረማመዳቸው እርግጠኞች ነበሩ ማለት ነው።

Isaiah 63:14

አጠቃላይ መረጃ
የእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥለዋል

ወደ ሸለቆ እንደሚወርድ የከብት መንጋ... ዕረፍት
ይህ የከብት መንጋ ሣሩ ወደ ለመለመበትና ውሃ ወዳለበት ሸለቆ የመሄዱ ምስል የእስራኤልን ሕዝብ እግዚአብሔር መምራቱንና መጠበቁን አጽንዖት ይሰጣል።

ለራስህ የምስጋና ስም እንዲሆን
‹‹የምስጋና ስም›› የሰውን ዝና ክብር ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለራስህ የከበረ ዝና እንዲኖርህ››

Isaiah 63:15

አጠቃላይ መረጃ
የእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሎዋል

ቅንዓትህና ታላቅ ሥራህ የት አለ?
እግዚአብሔር እየረዳቸው ስለማይመስል ጥልቅ ስሜቱን ለመግለጽ ጸሐፊው ጥያቄ ያነሣል። ጥያቄውን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቅንዓትህንና ታላቅ ሥራህን አላየንም››

ቸርነትህና ርኅራኄህ ከእኛ ርቀዋል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቸርነትህንና ርኅራኄኅን ከእኛ አርቀሃል››

አብርሃም ባያውቀን፣ እስራኤልንም ባይገነዘበን
በጣም ተለውጠው ስለ ነበር እነዚህ የእስራኤል ሕዝብ አባቶች ዘሮቻቸውን ማወቅ አልቻለም። ‹‹አብርሃም›› እና፣ ‹‹ያዕቆብ›› ከረጅም ጊዜ በፊት የነበረውን ሕዝብ ይወክላሉ።

እስራኤል
ይህ እግዚአብሔር ለ፣ ‹‹ያዕቆብ›› የሰጠውን ስም ያመለክታል።

Isaiah 63:17

አጠቃላይ መረጃ
የእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥለዋል።

ያህዌ ለአንተ ከመታዘዝ ከመንገድህ እንድንወጣ፣ ልባችንንም እንድናደነድን ለምን አደረግህኸን?
ጸሐፊው ጥያቄውን ያቀረበው የእግዚአብሔርን ሕዝብ ማጉረምረም ለማመልከት ነው። ይህን ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ለአንተ እንዳንታዘዝ ከመንገድህ እንድንወጣና እልኸኞች እንድንሆን አደረግኸን››

ለምን ከመንገድህ እንድንወጣ አደረግኸን?
የያህዌን ትእዛዝ አለመፈጸም ከትክክለኛው መንገድ መውጣት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለምን ትክክል ያልሆነ ነገር እንድናደርግ አደረግኸን››

ልባችንን አደነደንህ
ይህ ማለት ለመስማትና ለመታዘዝ ባለ መፈለግ የያህዌን ትምህርት መቃወም ማለት ነው። እዚህ ላይ፣ ‹‹ልብ›› ዝንባሌን፣ ፍላጐትንና ስሜትን ይወክላል።

Isaiah 63:18

አጠቃላይ መረጃ
የእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥለዋል።

በስምህ አልተጠሩም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። ‹‹ስም›› የሚለው ቃል የቤተ ሰብ ግንኙነትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቤተ ሰብህ አልነበሩም››

እኛ ሆነናል... በስምህ ተጠርተናል
አንዳንድ የዘመኑ ቅጂዎች ይህን ምንባብ በተለየ መንገድ ተርጉመዋል። ‹‹በስምህ እንደ ተጠሩ ሰዎች እኛም አንተ ገዢያችን እንዳልነበርህ ሆነናል››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 64

1 "ሰማዮችን ቀድደህ ምነው ብትወርድ! ተራሮችም ምነው ቢናወጡ! 2 እሳት ጭራሮውን እንደሚያቃጥል፥ እሳትም ውኃውን እንደሚያፈላ፥ ስምህ ለጠላቶችህ ይገለጥ ዘንድ፥ አሕዛብም በፊትህ ይንቀጠቀጡ ዘንድ! 3 ያልተጠባበቅነውን የክብርህን ሥራ ባደረግህ ጊዜ፣ ወረድህ ተራሮችም በፊትህ ተንቀጠቀጡ። 4 ሰዎች ከጥንት ጀምሮ ለሚጠብቁህ ከምትሠራላቸው ከአንተ በቀር ሌላ አምላክን አልሰሙም በጆሮአቸውም አልተቀበሉም ዓይንም አላየችም። 5 ጽድቅን የሚያደርገውን በመንገዶችህም የሚያስቡህን ትገናኛቸዋለህ። እነሆ፣ አንተ ተቈጣህ እኛም ኃጢአት ሠራን፤ ስለዚህም ተሳሳትን። 6 ሁላችን እንደ ርኩስ ሰው ሆነናል፣ ጽድቃችንም ሁሉ እንደ መርገም ጨርቅ ነው፤ ሁላችንም እንደ ቅጠል ረግፈናል፣ በደላችንም እንደ ነፋስ ወስዶናል። 7 ስምህንም የሚጠራ፣ አንተንም ሊይዝ የሚያስብ የለም፤ ፊትህንም ከእኛ ሰውረሃል፣ በኃጢአታችንም አጥፍተኸናል። 8 አሁን ግን፣ አቤቱ፣ አንተ አባታችን ነህ፤ እኛ ጭቃ ነን አንተም ሠሪያችን ነህ፣ እኛም ሁላችን የእጅህ ሥራ ነን። 9 አቤቱ፣ እጅግ አትቈጣ፣ ለዘላለምም ኃጢአትን አታስብ፤ እነሆ፣ እባክህ፣ ተመልከት፣ እኛ ሁላችን ሕዝብህ ነን። 10 የተቀደሱ ከተሞችህ ምድረ በዳ ሆነዋል፤ ጽዮን ምድረ በዳ ኢየሩሳሌምም ውድማ ሆናለች። 11 አባቶቻችን አንተን ያመሰገኑበት የተቀደሰና የተዋበ ቤታችን በእሳት ተቃጥሎአል፣ ያማረውም ስፍራችን ሁሉ ፈርሶአል። 12 አቤቱ፣ በውኑ በዚህ ነገር ትታገሣለህን? ዝምስ ትላለህን? አጥብቀህስ ታስጨንቀናለህን?

Isaiah 64:1

አጠቃላይ መረጃ
የእስራኤል ሕዝብ ለያህዌ መናገር ቀጥለዋል

እንዲህ አድርገህ ቢሆን
ይህ ባለፈ ታሪካቸው የሆነውን የያህዌ መገኘት መፈለጉን ኢሳይያስ ጠንከር ባለ ቃለ አጋኖ ያስተዋውቃል።

ሰማያትን በቀደድህ ኖሮ
ሰማያትን በአስደናቂ ሁኔታ በመቅደድ ያህዌ ራሱን ቢገልጥ ኖሮ። ‹‹መቅደድ›› የሚለው ልብስን ግራና ቀኝ መሰንጠቅን ያመለክታል።

ተራሮች ቢናወጡ ኖሮ
ምድር በምትንቀጠቀጥበት ጊዜ እንደሚሆነው ተራሮች ቢንቀጠቀጡ ኖሮ።

እሳት ጭራሮውን እንደሚያቃጥል ወይም እሳት ውሃ እንደሚያፈላ
ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር መገኘት ተራሮችንና ሕዝቡን ማንቀጥቀጥ እንደሚችል ነው።

Isaiah 64:3

አጠቃላይ መረጃ
የእስራኤል ሕዝብ ለያህዌ መናገር ቀጥለዋል።

ዐይን አላየም
‹‹ዐይን›› መላውን ሰው ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ማንም አላየም››

Isaiah 64:5

አጠቃላይ መረጃ
የእስራኤል ሕዝብ ለያህዌ መናገር ቀጥለዋል

አስቡ
ይህ ‹‹አስታውሱ›› ለማለት ፈሊጣዊ ንግግር ነው።

Isaiah 64:6

አጠቃላይ መረጃ
የእስራኤል ሕዝብ ለያህዌ መናገር ቀጥለዋል

የጽድቅ ሥራችን እንደ መርገም ጨርቅ ነው
‹‹የመርገም ጨርቅ›› አንዲት ሴት ከማሕፀንዋ በምትደማበት ጊዜ የምትጠቀምበት ጨርቅ ነው። ይህ ማለት እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ያደረጉት ሙከራ ሁሉ አልተሳካም ማለት ነው። ይህ ዐረፍተ ነገር አስደንጋጭ መሆን አለበት።

ሁላችንም እንደ ቅጠል ጠውልገናል
ኢሳይያስ የእስራኤልን ሕዝብ ከጠወለገ ቅጠል ጋር ያመሳስላል።

በደላችን እንደ ነፋስ ጠራርጐናል
ይህም ማለት የውድቀታቸው ምክንያት እንደ ማኅበረ ሰብ የፈጸሙት ኀጢአት ነበር ማለት ነው። የሕዝቡን በደል ኢሳይያስ የያህዌን ቅጣት ካመጣባቸው ነፋስ ጋር ያመሳስለዋል።

ፊትህን ከእኛ ሰወርህ
ይህ ማለት እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመከራ ተወ ማለት ነው።

Isaiah 64:8

አጠቃላይ መረጃ
የእስራኤል ሕዝብ ለያህዌ መናገር ቀጥለዋል።

እኛ ሸክላዎች ነን፤ አንተ ሸክላ ሠሪ ነህ፤ ሁላችንም የእጅህ ሥራዎች ነን።
ይህ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ፈጠረ ማለት ነው።

አስቡ
ይህ ማለት ያለፈውን አስታውሱ ማለት ነው።

ሁላችንንም ተመልከተን
ኢሳይያስ ያህዌ ያሉበትን ሁኔታ እንዲያይ ይጠይቃል።

Isaiah 64:10

አጠቃላይ መረጃ
የእስራኤል ሕዝብ ለያህዌ መናገር ቀጥለዋል።

የተቀደሱ ከተሞችህ ምድር በዳ ሆኑ
ይህ አጽንዖት የሚሰጠው ከተሞቹ መደምሰሳቸውንና የሚኖርባቸውም እንደሌለ ነው።

አባቶቻችን አንተን ያመሰገኑበት የተቀደሰውና ያማረው ቤተ መቅደሳችን በእሳት ተደምስሶአል።
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አባቶቻችን አንተን ያመሰገኑበትን የተቀደሰውንና ያማረውን ቤተ መቅደሳችንን ጠላት በእሳት አውድሞታል››

ያህዌ ለምን ዝም ትላለህ፤ ለምን ዝም ትላለህ እኛን በማዋረድም ትጸናለህ?
እግዚአብሔር እነርሱን ለመርዳት ባለ መምጣቱ ተስፋ መቁረጣቸውን ለመግለጽ በጥያቄዎች ተጠቅመዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ እባክህ ዝም አትበል፤ እባክህ ዝም አትበለን እኛንም አታዋርደን!››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 65

1 ላልጠየቁኝ ተገለጥሁ፣ ላልፈለጉኝም ተገኘሁ፤ በስሜም ያልተጠራውን ሕዝብ፣ 'እነሆኝ! እነሆኝ!' አልሁት። **2** መልካም ባልሆነው መንገድ፣ አሳባቸውን እየተከተሉ፣ ወደሚሄዱ ወደ ዓመፀኛ ሕዝብ ቀኑን ሁሉ እጆቼን ዘረጋሁ! **3** ይህ ሕዝብ ዘወትር የሚያስቈጡኝ ናቸው፤ እነርሱ በአትክልት ውስጥ የሚሠዉ በጡብም ላይ የሚያጥኑ፣ **4** በመቃብርም መካከል የሚቀመጡ፣ በስውርም ስፍራ የሚያድሩ፣ የእሪያ ሥጋም የሚበሉ ናቸው። የረከሰው መረቅ በዕቃቸው ውስጥ አለ። **5** እነርሱም፣ 'ርቀህ ቁም፣ እኔ ከአንተ ይልቅ ቅዱስ ነኝና ወደ እኔ አትቅረብ' ይላሉ፤ እነዚህ በአፍንጫዬ ዘንድ ጢስ ቀኑንም ሁሉ የምትነድድ እሳት ናቸው። **6** እነሆ፣ በፊቴ ተጽፎአል። ኃጢአታችሁና የአባቶቻችሁን ኃጢአት በአንድ ላይ ወደ ብብታቸው ፍዳ አድርጌ አመልሳለሁ እንጂ ዝም አልልም፣" ይላል እግዚአብሔር፤ **7** "በተራሮችም ላይ ስላጠኑ፣ በኮረብቶችም ላይ ስለ ሰደቡኝ፣ ስለዚህ አስቀድመው የሠሩትን ሥራቸውን በብብታቸው እሰፍራለሁ።" **8** እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "ወይን በዘለላው በተገኘች ጊዜ፣ በረከት በእርስዋ ላይ አለና አታጥፉት" እንደሚባለው፣ ሁሉን እንዳላጠፉ ስለባሪያዎቼ እንዲሁ አደርጋለሁ።' **9** ከያዕቆብ ዘርን ከይሁዳም ተራሮቼን የሚወርሰውን አወጣለሁ፤ እኔም የመረጥኋቸው ይወርሱአታል፣ ባሪያዎቼም በዚያ ይኖራሉ። **10** ሳሮንም የበጎች ማሰማርያ፣ የአኮርም ሸለቆ የላሞች መመሰግያ ለፈልጉኝ ሕዝቤ ይሆናል። **11** እናንተን ግን እግዚአብሔርን የተዋችሁትን፣ ቅዱሱንም ተራራዬን የረሳችሁትን፣ ጉድ ለተባለ ጣዖትም ማዕድ ያዘጋጃችሁትን፣ እድል ለተባለ ጣዖትም የወይን ጠጅ ለመጠጥ ቍርባን የቀዳችሁትን - **12** እድላችሁን ለሰይፍ አደርገዋለሁ፣ ሁላችሁም ለመታረድ ትጐነበሳላችሁ፤ በፊቴም ክፉ ነገርን አደረጋችሁ፣ ያልወደድሁትንም መረጣችሁ እንጂ በጠራሁ ጊዜ አልመለሳችሁልኝምና፣ በተናገርሁም ጊዜ አልሰማችሁኝምና።" **13** ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "ተመልከቱ፣ ባሪያዎቼ ይበላሉ እናንተ ግን ትራባላችሁ፤ ተመልከቱ፣ ባሪያዎቼ ይጠጣሉ እናንተ ግን ትጠማላችሁ፤ ተመልከቱ፣ ባሪያዎቼ ደስ ይላቸዋል እናንተ ግን ታፍራላችሁ፤ **14** ተመልከቱ፣ ባሪያዎቼ ከልባቸው ደስታ የተነሣ ይዘምራሉ፣ እናንተ ግን ከልባችሁ ጎዝን የተነሣ ትጮኻላችሁ፣ መንፈሳችሁም ስለ ተሰበረ ወዮ ትላላችሁ። **15** ስማችሁንም ለተመረጡት ሕዝቤ እርግማን አድርጋችሁ ትተዋላችሁ፣ ጌታ እግዚአብሔርም ይገድላችኋል፣ ባሪያዎቹንም በሌላ ስም ይጠራቸዋል። **16** እንዲሁም በምድር ላይ የተባረከ በእውነት አምላክ ይባረካል፣ በምድርም ላይ የማለ በእውነት አምላክ ይምላል፤ የቀድሞው ጭንቀት ተረስቶአልና፣ ከዓይኔም ተሰውሮአልና። **17** ተመልከቱ፣ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እፈጥራለሁና፤ የቀደሙትም አይታሰቡም፣ ወደ ልብም አይገቡም። **18** ነገር ግን በፈጠርሁት ደስ ይበላችሁ፣ ለዘላለምም ሐሤት አድርጉ፤ ተመልከቱ፣ ኢየሩሳሌምን ለሐሤት፣ ሕዝብዋንም ለደስታ እፈጥራለሁና። **19** እኔም በኢየሩሳሌም ሐሤት አደርጋለሁ በሕዝቤም ደስ ይለኛል፤ ከዚያም ወዲያ የልቅሶ ድምፅና የዋይታ ድምፅ አይሰማባትም። **20** ከዚያም ወዲያ ጥቂት ዘመን ብቻ የሚኖር ሕፃን, ወይም ዕድሜውን ያልፈጸመ ሸማግሌ አይገኝም፤ ጕልማሳው የመቶ ዓመት ሆኖት ይሞታልና, ኃጢአተኛውም የመቶ ዓመት ሆኖት የተረገመ ይሆናልና። **21** ቤቶችንም ይሠራሉ ይቀመጡባቸውማል፤ ወይኑንም ይተክላሉ ፍሬውንም ይበላሉ። **22** ሌላ እንዲቀመጥበት አይሠሩም፣ ሌላም እንዲበላው አይተክሉም፤ የሕዝቤ ዕድሜ እንደ ዛፍ ዕድሜ ይሆናልና፣ እኔም የመረጥኋቸው በእጃቸው ሥራ ረጅም ዘመን ደስ ይላቸዋልና። **23** እነርሱ ከነልጆቻቸው የእግዚአብሔር ቡሩካን ዘር ናቸውና በከንቱ አይደክሙም ለጥፋትም አይወልዱም። **24** እንዲህም ይሆናል፤ ሳይጠሩ አመልስላቸዋለሁ፣ ገናም ሲናገሩ እሰማለሁ። **25** ተኵላና ጠቦት በአንድነት ይሰማራሉ፣ አንበሳም እንደ በሬ ገለባ ይበላል፣ የእባብም መብል ትቢያ ይሆናል። በተቀደሰው ተራራዬ ሁሉ አይጐዱም፣ አያጠፉምም፣" ይላል እግዚአብሔር።

Isaiah 65:1

ዝግጁ ነበርሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እኔ›› ያህዌን ያመለክታል።

ለማይታዘዝ ሕዝብ ቀኑን ሙሉ እጆቼን ዘረጋሁ
‹‹እጆችን መዘርጋት›› ልመናን ወይም ጥያቄ ለማቅረብ አንድ ሰው የሚያደርገውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እርዳታየን እንዲቀበሉ ያለ መታከት ለማይታዘዙ ሰዎች እጆቼን ዘረጋሁ››

Isaiah 65:3

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

በአትክልት ቦታዎች... በሸክላ ወለሎች
ይህ የሚያመለክተው ከነዓናውያን ጣዖት የሚያመልኩባቸውን ቦታዎች ነው። የተቀደሱ መሠዊያዎቻቸው ያህዌ ለመሠዊያ እንዳይውል በከለከለው በሸክላ የተሠሩ ነበሩ። የያህዌ መሠዊያዎች የተሠሩት ከድንጋይ ነበር።

በመቃብር መካከል ለሚቀመጡ ሌሊቱን ሁሉ ለሚጠብቁ
ይህ ሙታንን መጠየቅን ያመለክታል፤ ያህዌ ይህን ከለክሎአል።

የዐሣማ ሥጋ የሚበሉ
ያህዌ የእስራኤል ሕዝብ ዐሣማ እንዲበሉ አልፈቀደም።

Isaiah 65:5

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤልና ስለ እስራኤል መናገር ቀጥሏል።

እነዚህ ነገሮች በአፍንጫዬ እንደ ጢስ ናቸው
እነዚህ ዘወትር የሚያውኩትን ሰዎች ያህዌ የሰውን እስትንፋስ ከሚያውክ ጢስ ጋር ያመሳስላቸዋል።

ቀኑን ሙሉ የሚቃጠል እሳት
ያህዌ የእስራኤልን ሕዝብ ቀኑን በሙሉ ዝግ ብሎ ከሚነድና ጢሱም ያለ ማቋረጥ ከሚወጣ እሳት ጋር ያመሳስላቸዋል።

Isaiah 65:6

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤልና ስለ እስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

እነሆ፣ ተጽፎአል
‹‹ልብ በሉ፤ አስተውሉ››

በጭናቸው
ይህ ማለት እግዚአብሔር በሚገባ ይቀጣቸዋል ማለት ነው። ያህዌ ሕዝቡን መቅጣቱን እግሮቻቸው መካከል ከሚቀመጥ ነገር ጋር ያመሳስለዋል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Isaiah 65:8

በወይኑ ዘለላ ውስጥ እንዳለ ጭማቂ
ያህዌ የእስራኤልን ሕዝብ ውስጡ መልካም ጭማቂ ከያዘ የወይን ዘለላ ጋር ያመሳስላቸዋል።

ዘለላ ውስጥ እንዳለ ጭማቂ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ዘለላው ውስጥ ጭማቂ ስታገኙ››

ሙሉ በሙሉ አላጠፋቸውም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጻድቃን የሆኑትን አንዳንዶቹን እኖራቸዋለሁ››

Isaiah 65:9

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል

ተራራዬ
ይህ ኢየሩሳሌምና መላው ይሁዳ ውስጥ ያሉ ከፍታ ቦታዎች ያመለክታል።

ሣሮን
ይህ ለም የግጦሽ ቦታ ነው።

የአኮር ሸለቆ
ይህ ምናልባት ከኢየሩሳሌም አንሥቶ እስከ ደቡባዊ ኢያሪኮ የሚዘረጋ ሸለቆ ስም ሊሆን ይችላል። ይህም ለም የግጦሽ ቦታ ነው።

Isaiah 65:11

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል

የተቀደሰ ተራራ
ኢሳይያስ 11፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

ገበታ ላዘጋጁ... የድብልቅ ወይም ጠጅ ዋንጫዎችን የሞሉ
ሰዎች መብልና መጠጥ አምጥተው እንደ አምልኮ ጣዖት ፊት ያደርጋሉ

የተደባለቀ ወይን ጠጅ
ቅመማ ቅመሞች የተጨመሩበት ወይን ጠጅ

ዕድል... ዕጣ ፈንታ
እነዚህ የሐሰተኛ አማልክት ስሞች ናቸው ‹‹ጋድ›› እና፣ ‹‹ሜኒ›› በመባልም ይጠራሉ።

Isaiah 65:12

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ በእስራኤል ጣዖት ለሚያመልኩ ሰዎች መናገር ቀጥሏል።

ለሰይፍ እዳርጋችኃለሁ
‹‹ሰይፍ›› የእርሱን ጥሪ የማይሰሙትን ለመቅጣት ያህዌ የሚጠቀምበትን ማንኛውንም የጦር መሣሪያ ይወክላል።

በተጣራሁ ጊዜ አልመለሳችሁም፤ በተናገርሁ ጊዜ አልሰማችሁም
ሁለቱም ሐረጐች ተመሳሳይ ቢሆኑም የተደገሙት አጽንዖት ለመስጠት ነው።

Isaiah 65:13

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ በእስራኤል ጣዖት ለሚያመልኩ ሰዎች መናገር ቀጥሏል።

እነሆ፣ ባርያዎቼ
‹‹አስተውሉ፤ ልብ በሉ›› ያህዌ የደገመው አጽንዖት ለመስጠት ነው።

ልባችሁ በማዘኑ ትጮኻላችሁ፤ መንፈሳችሁ በመሰበሩም ወዮ ትላለችሁ
ሁለቱም ሐረጐች ተመሳሳይ ነገር ማለት ቢሆኑም፣ የተደገሙት አጽንዖት ለመስጠት ነው።

መንፈሳችሁ በመሰበሩ
ይህ አገላለጽ አስከፊ ተስፋ መቁረጥና ሐዘንን፣ ከከባድ ጫና የተነሣ መሰበር ጋር ያመሳስላል።

Isaiah 65:15

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ በእስራኤል ጣዖት ለሚያመልኩ መናገር ቀጥሏል።

በእውነት አምላክ በእኔ ይባረካል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሁልጊዜ እውነት የምናገር እኔ እባርከዋለሁ››

ያለፈው ዘመን መከራ ይረሳል... ይሰውራል
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከእንግዲህ እነዚህን መከራዎች ስለማላስብ ያለፈውን ዘመን መከራ ይረሱታል››

ከዐይኖቼ ይሰወራሉ
‹‹ከዐይኖች መሰወር›› ከያህዌ ትኩረትና ትውስታ መወገድን ያመለክታል። አማራጭ ትረጉም፣ ‹‹ከእንግዲህ ስለ እነርሱ አላስብም››

Isaiah 65:17

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል

እዩ
‹‹ልብ በሉ፤ አስተውሉ››

አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር
ሁለቱም በመካከል ያለውን ማንኛውንም ነገር የሚጨምሩ ጽንፎች ናቸው።

ያለፉት ነገሮች አይታሰቡም፤ አይታወሱም
ሁለቱም ሐረጐች ተመሳሳይ ነገር ማለት ሲሆኑ፣ በአንድነት የሆኑት አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ባለፈው ጊዜ የሆነውን አታስቡትም››

እናንተ ደስ ይላችኃል
‹‹እናንተ›› የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ባርያዎችን ሁሉ ነው።

የልቅሶና የጩኸት ድምፅ ከእንግዲህ እርሷ ውስጥ አይሰማም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ትችላለህ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከእንግዲህ በእርሷ ውስጥ የጭንቀት ለቅሶና ጩኸት አይሰማም››

Isaiah 65:20

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለታማኝ ሕዝቡ መናገር ቀጥሏል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አንድ መቶ ዓመት
‹‹100 ዓመት››

እንደ ወጣት ይቆጠራል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። ‹‹ሰዎች እንደ ወጣት ይቆጥሩታል››

የተረገመ ይባላል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰዎች ይህን ሰው የተረገመ ይሉታል››

Isaiah 65:22

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለታማኝ ሕዝቡ መናገር ቀጥሏል

የሕዝቤ ዕድሜ እንደ ዛፍ ዕድሜ ይሆናል
‹‹ሕዝቤ እንደ ዛፍ ረጅም ዘመን ይኖራሉ››

ያህዌ የባረካቸው ሰዎች ልጆች ናቸው
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እነርሱ ያህዌ የባረካቸው ሰዎች ልጆች ናቸው››

Isaiah 65:24

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለታማኝ ሕዝቡ መናገር ቀጥሏል።

የተቀደሰ ተራራ
ኢሳይያስ 11፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 66

1 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "ሰማይ ዙፋኔ ነው፣ ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት፤ የምትሠሩልኝ ቤት ምን ዓይነት ነው? የማርፍበትስ ስፍራ ምንድር ነው? **2** እነዚህን ሁሉ እጄ ሠርታለችና እነዚህ ሁሉ የእኔ ናቸው ይላል እግዚአብሔር፤ ነገር ግን ወደዚህ ወደ ትሑት፣ መንፈሱም ወደ ተሰበረ፣ በቃሌም ወደሚንቀጠቀጥ ሰው እመለከታለሁ። **3** በሬን የሚያርድልኝ ሰውን እንደሚገድል ነው፤ ጠቦትንም የሚሠዋ የውሻውን አንገት እንደሚሰብር ነው፤ የእህልን ቍርባን የሚያቀርብ የእርያን ደም እንደሚያቀርብ ነው፤ ዕጣንን የሚያጥን ጣዖትን እንደሚባርክ ነው። እነዚህ የገዛ መንገዳቸውን መረጡ፤ ነፍሳቸውም በርኵሰታቸው ደስ ይላታል፤ **4** እኔ ደግሞ የተሳለቀባቸውን እመርጣለሁ፣ የፈሩትንም ነገር አመጣባቸዋለሁ፤ በፊቴ ክፉ ነገርን አደረጉ፣ ያልወደድሁትንም መረጡ እንጂ በጠራሁ ጊዜ አልመለሱልኝምና፣ በተናገርሁም ጊዜ አልሰሙኝምና።" **5** በቃሉ የምትንቀጠቀጡ ሆይ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ፣ "የጠሉአችሁ ስለ ስሜም ያባረሩአችሁ ወንድሞቻችሁ፣ ደስታችሁን እናይ ዘንድ እግዚአብሔር ይክበር' ብለዋል፤ ነገር ግን ያፍራሉ። **6** የጩኸት ድምፅ ከከተማ፣ ድምፅም ከመቅደስ፣ በጠላቶቹ ላይ ፍዳን የሚያመጣ የእግዚአብሔር ድምፅ ተሰምቶአል። **7** ሳታምጥ ወለደች፤ ምጥም ሳያገኛት ወንድ ልጅን ወለደች። **8** ከቶ እንዲህ ያለ ነገር ማን ሰምቶአል? እንዲህስ ያለ ነገር ማን አይቶአል? በውኑ አገር በአንድ ቀን ታምጣለችን? ወይስ በአንድ ጊዜ ሕዝብ ይወለዳልን? ጽዮን እንዳማጠች ወዲያው ልጆችዋን ወልዳለችና። **9** በውኑ ወደ መውለድ የማደርስ እኔ አላስወልድምን? ይላል እግዚአብሔር፤ የማስወልድስ ማኅፀንን እኔ እዘጋለሁን?" ይላል አምላክሽ። **10** እናንተ የምትወድዱአት ሁሉ፣ ከኢየሩሳሌም ጋር ሐሤትን አድርጉ፣ ስለ እርስዋም ደስ ይበላችሁ፤ እናንተም የምታለቅሱላት ሁሉ፣ ከእርስዋ ጋር በደስታ ሐሤትን አድርጉ፣ **11** ትጠቡ ዘንድ ከማጽናናትዋም ጡት ትጠግቡ ዘንድ፤ እጅግ ጠጥታችሁ በክብርዋ ሙላት ደስ ይላችሁ ዘንድ። **12** እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፣ "እነሆ፣ ሰላምን እንደ ወንዝ፣ የአሕዛብንም ክብር እንደሚጐርፍ ፈሳሽ እመልስላታለሁ፤ ከዚያም ትጠባላችሁ፣ በጫንቃ ላይ ይሸከሙአችኋል በጕልበትም ላይ እያስቀመጡ ያቀማጥሉአችኋል። **13** እናት ልጅዋን እንደምታጽናና እንዲሁ አጽናናችኋለሁ፣ በኢየሩሳሌምም ውስጥ ትጽናናላችሁ።" **14** ታያላችሁ፣ ልባችሁም ሐሤት ታደርጋለች፣ አጥንታችሁም እንደ ለምለም ሣር ትበቅላለች፤ የእግዚአብሔርም እጅ ለሚፈሩት ትታወቃለች፣ በጠላቶቹም ላይ ይቈጣል። **15** ተመልከቱ፣ እግዚአብሔር መዓቱን በቍጣ፣ ዘለፋውንም በእሳት ነበልባል ይመልስ ዘንድ ከእሳት ጋር ይመጣል፣ ሰረገሎቹም እንደ ዐውሎ ነፋስ ይሆናሉ። **16** እግዚአብሔርም በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ በእሳትና በሰይፉ ይፈርዳልና፤ በእግዚአብሔርም ተወግተው የሞቱት ይበዛሉ። **17** በመካከላቸው ያለውን አንዱን ተከትለው ወደ ገነቱ ይገቡ ዘንድ ሰውነታቸውን የሚቀድሱና የሚያነጹ፣ የእሪያንም ሥጋ አስጸያፊ ነገርንም አይጥንም የሚበሉ በአንድነት ይጠፋሉ፣ ይላል እግዚአብሔር። **18** ሥራቸውንና አሳባቸውን አውቄአለሁና፤ አሕዛብንና ልሳናትን ሁሉ የምሰበስብበት ጊዜ ይደርሳል፣ እነርሱም ይመጣሉ ክብሬንም ያያሉ። **19** በመካከላቸውም ምልክት አደርጋለሁ፣ ከእነርሱም የዳኑትን ዝናዬን ወዳልሰሙ፣ ክብሬንም ወዳላዩ ወደ አሕዛብ ወደ ተርሴስ ወደ ፉጥ ወደ ሉድ ወደ ሞሳሕ ወደ ቶቤል ወደ ያዋን በሩቅ ወዳሉ ደሴቶች እልካቸዋለሁ፣ በአሕዛብም መካከል ክብሬንም ይናገራሉ። **20** የእስራኤል ልጆች ቍርባናቸውን በጥሩ ዕቃ አድርገው ወደ እግዚአብሔር ቤት እንደሚያመጡ፣ እንዲሁ ለእግዚአብሔር ቍርባን ይሆን ዘንድ ወንድሞቻችሁን ሁሉ፣ በፈረሶችና በሰረገሎች፣ በአልጋዎችና በበቅሎች በጠያር ግመሎችም ላይ አድርገው፣ ከአሕዛብ ሁሉ ወደ ተቀደሰው ተራራዬ ወደ ኢየሩሳሌም ያመጡአቸዋል፣ ይላል እግዚአብሔር። **21** ካህናትና ሌዋውያን እንዲሆኑ ከእነርሱ እወስዳለሁ፣ ይላል እግዚአብሔር። **22** እኔ የምሠራቸው አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ከፊቴ ጸንተው እንደሚኖሩ፣ እንዲሁ ዘራችሁና ስማችሁ ጸንተው ይኖራሉ፣ ይላል እግዚአብሔር። **23** እንዲህ ይሆናል፤ በየመባቻውና በየሰንበቱ ሥጋ ለባሽ ሁሉ በፊቴ ይሰግድ ዘንድ ዘወትር ይመጣል፣ ይላል እግዚአብሔር። **24** ወጥተውም በእኔ ያመፁብኝን ሰዎች ሬሳቸውን ያያሉ፤ ትላቸው አይሞትምና፣ እሳታቸውም አይጠፋምና፤ ለሥጋ ለባሽም ሁሉ አስጸያፊ ነገር ይሆናሉ።"

Isaiah 66:1

ሰማይ ዙፋኔ ነው፤ ምድርም የእግሬ ማረፊያ ናት
ያህዌ ሰማይን ከዙፋን፣ ምድርን ከእግሩ ማረፊያ ጋር የሚያመሳስለው ምን ያህል ታላቅ መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት ነው።

ታዲያ፣ የምትሠሩልኝ ቤት የት አለ? የማርፍበትስ ቦታ የታለ?
የሰው ልጅ ለእርሱ መኖሪያ መሥራት እንደማይችል አጽንዖት ለመስጠት ያህዌ ጥያቄዎች ያቀርባል።

Isaiah 66:2

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል

እነዚህን ነገሮች ሁሉ እጄ ሠርታለች
ያህዌ ለእርሱ ጎይልና ሥልጣን አጽንዖት በሚሰጠው በእጁ ተወክሏል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ሠርቻለሁ››

ያህዌ እንዲህ ይላል
የሚናገረውን ነገር እርግጠኝነት ለማመልከት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። ኢሳይያስ 30፥1 ላይ እንዳለው ተርጉመው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ እንዲህ ብሏል›› ወይም፣ ‹‹እኔ ያህዌ እንዲህ ብያለሁ››

ትሑት የሆነ መንፈሱ የተሰበረ
እዚህ ‹‹የተሰበረ›› እና፣ ‹‹ትሑት›› በእውነት ትሑት የሆነና ለእምነቱ መከራ የሚቀበል ሰውን ያመለክታል።

Isaiah 66:4

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ስለ ክፉ ሰዎች መናገር ቀጥሏል

በፊቴ ክፉ የሆነውን
እዚህ ላይ ፊት ፍርድን ወይም ውሳኔን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ክፉ ነው ያልሁትን›› ወይም፣ ‹‹በእኔ ፍርድ ክፉ የሆነውን››

Isaiah 66:5

ያህዌ ይክበር
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌን አክብሩ›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ራሱን ያክብር››

እነርሱ ግን ያፍራሉ
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ አስፍራቸዋለሁ››

Isaiah 66:6

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ የአምላኪዎቹን ግብዝነት ቅጣት ይገልጻል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Isaiah 66:7

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል።

ከማማጢ በፊት ትወልዳለች፤ በምጥ ጣር ከመያዟ በፊት ወንድ ልጅ ትገላገላለች
ያህዌ እንደምትወልድ ሴት ስለ ጽዮን ይናገራል። ምንም እንኳ ጽዮን ብትወድምም፣ ሕዝቡም እዚያ ባይኖሩም፣ በጥቂት ጥረት በፍጥነት መላው ሕዝብ ከእርሷ ይመጣል።

እንደዚያ ያለ ነገር ማን ሰምቷል? እንደዚህ ያለ ማን ዐይቷል? በአንድ ቀን አገር ይወለዳልን? ሕዝብስ በቅጽበት ይገኛልን?
ይህ ሁኔታ ምን ያህል ያልተለመደ እንደሚሆን አጽንዖት ለመስጠት ያህዌ ጥያቄዎች ያነሣል። መጨረሻ ላይ ጽዮን እስከምትጠቀስ ድረስ ተከታታይ ጥያቄዎቹ ውጥረት ይፈጥራሉ።

Isaiah 66:9

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ እንደ እናት ስለ ኢየሩሳሌም መናገር ቀጥሏል (ኢሳይያስ 66፥7-8 ይመ)

ሊወለድ የተቃረበውን እንዳይወለድ አደርጋለሁን... መውለድ?
ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው ለኢየሩሳሌም ሕዝብ የሰጠውን ተስፋ እንደሚፈጽም አጽንዖት ለመስጠት ነው።

Isaiah 66:10

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ኢየሩሳሌም እናት እንደሆነች፣ የኢየሩሳሌም ሰዎችም የተወለዱ ልጆች እንደሆኑ ይናገራል። (ኢሳይያስ 66፥7-8 ይመ.)

ከሚያጽናኑ ጡቶቿ ትጠባላችሁ ትረካላችሁም
ይህ ማለት ኢየሩሳሌም ለእግዚአብሔር ሕዝብ የሰላምና የመጽናናት ቦታ ትሆናለች ማለት ነው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በወተቷ ታረካችኃለች፤ በጡቶቿ ታጽናናችኃለች››

Isaiah 66:12

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ እንደ እናት ስለ ኢየሩሳሌም መናገር ቀጥሏል። (ኢሳይያስ 66፥7-8 ይመ.)

እንደ ወንዝ... ሞልቶ እንደ ተረፈ ወንዝ
ይህ ማለት እንደ ወንዝ ዘላቂና ብዙ የሆነ የተትረፈረፈ ብልጥግና እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያመጣል ማለት ነው።

ትጠባላችሁ በዕቅፏም ትያዛላችሁ፤ በጭኖቿ ላይ ትፈነድቃላችሁ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በክንዶቿ ታቅፋችኃለች፤ በደስታ በጭኖቿ ትይዛችኃለች!››

እኔ አጽናናችኃለሁ፤ እናንተም በኢየሩሳሌም ትጽናናላችሁ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እኔ በኢየሩሳሌም አጽናናችኃለሁ››

Isaiah 66:14

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

ዐጥንታችሁ ይለመልማል
‹‹ዐጥንት›› መላውን አካል ያመለክታል።

እንደ ሣር ቡቃያ ይለመልማል
‹‹የሣር ቡቃይ›› ቶሎ እና ጠንክሮ ማደጉ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጤናና ጥንካሬ ጋር ተመሳስሎአል።

የያህዌ እጅ ለባርያዎቹ ይታወቃል።
‹‹እጅ›› ኀይልን ያመለክታል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ ኀይሉን ለባርያዎቹ ይገልጣል››

Isaiah 66:15

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

ከእሳት ጋር ይመጣል
ብዙውን ጊዜ ያህዌ በብሉይ ኪዳን የሚገለጠው ቁጣውንና ፍርዱን በሚያመለክት እሳት ታጅቦ ነበር።

እንደ ዐውሎ ነፋስ
ዐውሎ ነፋስ ፍርዱን እውን ለማድረግ የያህዌን ብርቱ ሥራ ይወክላል።

ከሰይፉ ጋር
‹‹ሰይፍ›› ጦርነትንና ግድያን የሚወክል አንድ የጦር መሣሪያ ነው።

በያህዌ የተገደሉ ብዙ ይሆናሉ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ ብዙዎችን ይገድላል።

Isaiah 66:17

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ መናገር ቀጥሏል

ራሳቸውን ይቀድሳሉ
‹‹እነርሱ›› ያህዌን የሚያመልኩ ሆኖም ከመንገዱ በተቃራኒ የሚሄዱ ናቸው።

ወደ አትክልት ቦታው ይገባሉ
ይህ ጣዖቶች ለማምለክ ሰዎች የሚሄዱበት ቦታ ነው።

በመካከል ያለው
ይህ የሚያመለክተው ጣዖቶቹን ለማምለክ የሚሄዱትን ሰዎች መሪ ነው።

ያህዌ እንዲህ ይላል
የሚናገረውን ነገር እርግጠኝነት ለማሳየት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። ኢሳይያስ 30፥1 ላይ እንዳለው ተርጉመው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ይህ ያህዌ የተናገረው ነው›› ወይም፣ ‹‹እኔ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ››

Isaiah 66:18

እኔ ዐውቃለሁ
‹‹እኔ›› የሚያመለክተው ያህዌን ነው።

ሥራቸው... ሐሳባቸው
‹‹እነርሱ›› የሚያመለክተው ቀደም ሲል ያህዌ የተናገረላቸውን ግብዝ የሆኑ አምላኪዎችን ነው።

ፉጥ... ሉድ... ቶባል... ያዋን
እነዚህ ከእስራኤል ምድር ርቀው ያሉ ቦታዎች ናቸው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Isaiah 66:20

ያመጣሉ
‹‹እነርሱ›› የሚያመለክተው የተረፉትንና ለሕዝቡ የመሰከሩ ባዕዳን ሰዎች ነው። በምርኮ ከተወሰዱ እስራኤላውያን ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ይመለሳሉ።

የተቀደሰ ተራራ
ኢሳይያስ 11፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

Isaiah 66:22

አዲሱ ሰማይና አዲሱ ምድር
ኢሳይያስ 65፥17 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

ያህዌ እንዲህ ይላል
የሚናገረውን ነገር እርግጠኝነት ለማሳየት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። ኢሳይያስ 30፥1 ላይ እንዳለው ተርጉመው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ይህን ተናግሮአል›› ወይም፣ ‹‹እኔ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ››

Isaiah 66:24

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር አቁሞአል

ይሄዳሉ
‹‹እነርሱ›› የሚያመለክተው ያህዌን ለማምለክ የመጡ ታማኝ እስራኤላውያንና ባዕዳንን ጨምሮ ሰዎችን ሁሉ ነው።

ትሎቹ... እሳቱ
ለያህዌ ቅጣት አጽንዖት ለመስጠት ሁለቱም ሐረጐች የሚናገሩት ስለ ተመሳሳይ ነገር ነው።

የሚበሏቸው ትሎች
ትሎች የሚያመለክቱት ያህዌ ዐመፀኞች ላይ የሚያመጣውን የመበስበስና የመበላሸትን አስፈሪነት ነው።

የሚበላቸው እሳት
እሳት የያህዌን ቅጣት ይወክላል።

አይጠፋም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለዘላለም ይነዳል››

ሥጋ ሁሉ
ይህ የሚያመለክተው ከሞት የተረፉ ሕያው ፍጥረትን ሁሉ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Jeremiah

Jeremiah

Chapter 1

1 ይህ የኬልቅያስ ልጅ የሆነው የኤርምያስ ቃል ነው፤ እርሱ በብንያም ምድር ከነበሩት ካህናት አንደኛው ነበር። 2 የአሞጽ ልጅ በሆነው በይሁዳ ንጉሥ ዐሥራ
ሦስተኛ ዓመት አገዛዝ ዘመን ላይ የእግዚአብሔር ቃል ወደ እርሱ መጣ። 3 ቃሉ የመጣው በይሁዳ ንጉሥ የኢዮስያስ ልጅ በሆነው ኢዮአቄም ዘመን፣ የኢዮስያስ
ልጅ በሆነው የይሁዳ ንጉሥ ሴዴቅያስ የዐሥራ አንደኛው አመት አገዛዝ አምስተኛ ወር ድረስ፣ የኢየሩሳሌም ሕዝቦች ምርኮኛ ሆነው ሲወሰዱ ነበር። 4
የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፣ 5 "በማኅፀን ሳልሠራህ አውቄሃለሁ፥ ከማኅፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ፥ ለአሕዛብ ነቢይ አድርጌሃለሁ።" 6
እኔም፣ "ወዮ ጌታ እግዚአብሔር፥ ገና ብላቴና በመሆኔ እንዴት እንደምናገር አላውቅም" አልሁ። 7 ነገር ግን እግዚአብሔር "'ገና ብላቴና ነኝ' አትበል።
ወደምልክህ ሁሉ ልትሄድ ይገባል፣ የማዝዝህንም ሁሉ ልትናገር ይገባል! 8 ላድንህ ከአንተ ጋር ስለሆንኩ አትፍራ - ይህ የእግዚአብሔር ንግግር ነው።" አለኝ። 9
እግዚአብሔርም እጁን ዘርግቶ አፌን ዳሰሰ፣ እንዲህም አለኝ "ቃሌን በአፍህ ውስጥ አኑሬአለሁ፤ 10 ትነቅልና ታፈርስ ዘንድ፥ ታጠፋና ትገለብጥ ዘንድ፥ ትሠራና
ትተክል ዘንድ በአሕዛብና በመንግሥታት ላይ ዛሬ ሾሜሃለሁ" አለኝ። 11 የእግዚአብሔር ቃል "ኤርምያስ ሆይ፥ ምን ታያለህ?" እያለ ወደ እኔ መጣ። እኔም
"የለውዝ በትር አያለሁ" አልሁት። 12 እግዚአብሔርም "መልካም አይተሃል፣ እፈጽመው ዘንድ በቃሌ እተጋለሁና" አለኝ። 13 የእግዚአብሔር ቃል ለሁለተኛ ጊዜ
"ምን ታያለህ?" እያለ ወደ እኔ መጣ። እኔም "ፊቱ ከሰሜን አቅጣጫ የሆነ የሚፈላ ማሰሮ አያለሁ" አልሁ። 14 እግዚአብሔርም "በዚህች ምድር በሚኖሩት
ሁሉ ላይ ከሰሜን አቅጣጫ ክፉ ነገር ይገለጣል" አለኝ። 15 በሰሜን ያሉትን የመንግሥታትን ወገኖች ሁሉ እጠራለሁና ይላል እግዚአብሔር። እነርሱም
ይመጣሉ፣ እያንዳንዳቸውም በኢየሩሳሌም መግቢያ በራፍ ላይ፣ በዙሪያዋ ባሉት በአጥሮቿ ሁሉ ላይ፣ በይሁዳም ከተሞች ሁሉ ላይ ዙፋናቸውን ያኖራሉ። 16
እኔን ስለተዉበት ክፋታቸው ሁሉ፣ ለሌሎችም አማልክት ስላጠኑ፣ በገዛ እጃቸው ለሠሯቸውም ስለሰገዱላቸው፣ ፍርዴን በእነርሱ ላይ እናገራለሁ። 17 አንተ
ራስህን አዘጋጅ! ተነሥና ያዘዝሁህን ሁሉ ንገራቸው። በእነርሱ ፊት አትፍራ፣ አሊያ እኔ በእነርሱ ፊት አስፈራሃለሁ! 18 ተመልከት! ዛሬ በምድሪቱ ሁሉ ላይ
በይሁዳም ነገሥታት -በአለቆችዋና በካህናትዋ ላይ በምድሪቱም ሕዝብ ላይ እንደ ተመሸገ ከተማ እንደ ብረትም ዓምድ እንደ ናስም ቅጥር አድርጌሃለሁ። 19
ይዋጉሃል፣ ነገር ግን አድንህ ዘንድ እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አያሸንፉህም" ይላል እግዚአብሔር።

Jeremiah 1:1

ከካህናቱ አንዱ የሆነ የኬልቅያስ ልጅ ኤርምያስ
“ኤርምያስ፣ የኬልቅያስ ልጅ። ኤርምያስ ከካህናቱ አንዱ ነበር”

ኬልቅያስ
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ዓናቶት
ይህ የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የብንያም አገር
“ለብንያም ጎሳ የተሰጠች ምድር”

የእግዚአብሔር ቃል ወደ እርሱ መጣ
ይህ ፈሊጥ ጥቅም ላይ የዋለው እግዚአብሔር ለእርሱ መልእክት እንደሰጠው ለማወጅ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር መልእክት ለእርሱ ሰጠው” ወይም “እግዚአብሔር ለኤርምያስ ተናገረው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ
ይህ በብሉይ ኪዳን ራሱን ለሕዝቡ የገለጠበት የእግዚአብሔር ስም ነው። ይህንን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ ለመረዳት የትርጉም ቃል ገጽ ላይ ሄደው ይመልከቱ።

በይሁዳ ንጉሥ በአሞጽ ልጅ በኢዮስያስ ዘመን
እዚህ ላይ “ዘመን” የሚለው ንጉሱ የገዛበትን ጊዜ የሚያመለክት ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የአሞጽ ልጅ ኢዮስያስ የይሁዳ ንጉሥ በነበረበት ጊዜ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

አሥራ ሦስተኛው ... አሥራ አንደኛው
(ደረጃ የሚያሳይ ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

አሞጽ
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በመንግስቱ
“የአሞጽ መንግስት”

እንዲህ ሲል መጣ
“የእግዚአብሔር ቃል ደግሞ መጣ”

በይሁዳም ንጉሥ በኢዮስያስ ልጅ በኢዮአቄም ዘመን
እዚህ ላይ “ዘመን” የሚለው ንጉሱ የገዛበትን ጊዜ የሚያመለክት ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የኢዮስያስ ልጅ ኢዮአቄም የይሁዳ ንጉሥ በነበረበት ጊዜ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

አምስተኛው ወር
ይህ በዕብራይስጥ የቀን መቁጠርያ አምስተኛው ወር ነው። ይህ በምዕራባውያን የቀን መቁጠርያ የሐምሌ የመጨረሻው ክፍልና የነሐሴ የመጀመርያው ክፍል ወቅት ነው። (የዕብራይስጥ ወራቶች እና ደረጃ የሚያሳይ ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

የሴዴቅያስ
ይህ የሴዴቅያስን አመራር የሚያመለክት ነው። ይህ በግልጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የሴዴቅያስ የመንግስቱ ዘመን” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የኢየሩሳሌም ሕዝብ እንደ እስረኞች በተወሰዱበት ጊዜ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። ወደ ባቢሎን እንደተወሰዱ በግልጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የባቢሎን ሰራዊት የኢየሩሳሌምን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሕዝብ እንደ እስረኞች በወሰዳቸው ጊዜ” ወይም “የባቢሎን ሰራዊት የኢየሩሳሌምን ሕዝብ እንደ እስረኞች ወደ ባቢሎን በወሰዳቸው ጊዜ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 1:4

የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ
ይህ ፈሊጥ ጥቅም ላይ የዋለው ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ልዩ መልእክት ለማስተዋወቅ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር መልእክት ሰጠኝ። እንዲህ አለ” ወይም “እግዚአብሔር ይህን መልእክት ለእኔ ተናገረኝ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰርቼሃለሁ
“ቅርጽ ሰጥቼሃለሁ”

ከማኅፀን ከመውጣትህ በፊት
ይህ ማኅፀንን ሳንጠቅስ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከመወለድህ በፊት”

ወዮ ጌታ እግዚአብሔር
እዚህ ላይ “ወዮ” የሚለው ቃል ኤርምያስ እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር ለማድረግ መፍራቱን ያሳያል።

እንዴት መናገር እንዳለብኝ አላውቅም
ኤርምያስ በጉባኤ ለመናገር እንደሚፈራ ለማሳየት ምናልባት እያጋነነ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በጉባኤ እንዴት መናገር እንዳለብኝ አላውቅም” ወይም” ለሰዎች አዋጅ መናገር እንዴት እንዳለብኝ አላውቅም” (ግነት/ግነታዊ ቋንቋ እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 1:7

እነርሱን አትፍራቸው
“ሕዝቡን አትፍራ፣ እኔ ለእነርሱ እንድትናገር እልክሃለሁ”

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
“ይህ” የሚለው ቃል እግዚአብሔር በቁጥር 7 እና 8 ላይ የተናገረውን የሚያመለክት ነው።

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተነገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 1:9

ከዚያም እግዚአብሔር እጁን ዘርግቶ አፌን ዳሰሰ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ይህ እግዚአብሔርን የሚወክል ተለዋጭ ዘይቤ ሲሆን ለኤርምያስ የመናገር ልዩ ስልጣን መስጠቱን የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ከዚያም እግዚአብሔር አፌን እንደ ዳሰሰኝ ሆኖ ተሰማኝ” ወይም 2) ኤርምያስ ራዕይ እያየ ነበርና እግዚአብሔር ይህን ያደረገው ለኤርምያስ የመናገር ልዩ ስልጣን እንደሰጠው ለማሳየት ምሳሌአዊ ድርጊት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ከዚያም እግዚአብሔር እጁን ዘርግቶ አፌን ዳሰሰኝ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምሳሌያዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ቃሌን በአፍህ ውስጥ አኑሬአለሁ
ይህ ሀረግ እግዚአብሔር ለኤርምያስ መልእክቱን መስጠቱን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለሕዝቡ ትናገር ዘንድ እኔ መልእክቴን ለአንተ ሰጥቼሃለሁ” ወይም “ለሕዝቡ መልእክቴን እንድትናገር አስችየሃለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ትነቅልና ታፈርስ ዘንድ፣ ታጠፋና ትገለብጥ ዘንድ፣ ትሠራና ትተክል ዘንድ ... ሾሜሃለሁ
ኤርምያስ የእግዚአብሔር መልእክቶች እንደሚፈጸሙ ለተለያዩ መንግስታት በመናገር እነዚህን ነገሮች ይሰራል።

ትነቅልና ታፈርስ ዘንድ፣ ታጠፋና ትገለብጥ ዘንድ፣ ትሠራና ትተክል ዘንድ
አንዳንድ መንግስታትን ይነቅላል፣ ያፈርሳል፣ ያጠፋል ደግሞም ይገለብጣል፣ ሌሎች መንግስታትን ደግሞ ይሰራል እንዲሁም ይተክላል።

መንቀል
እግዚአብሔር ስለ ኤርምያስ ሲናገር መንግስታቱ ተክሎች እንደሆኑና እርሱ ከመሬት ነቅሎ እንደሚጥላቸው አድርጎ በመግለጽ በሚናገረው ቃል መንግስታትን እንደሚያፈርስ ይናራል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ማጥፋት እና መገልበጥ
እነዚህ ቃላት በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ኤርምያስ እነዚህን ቃላት የተጠቀመው ይህ ቃል በእርግጠኝነት እንደሚፈጸም ለማሳየት ነው። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

መስራት እና መትከል
እግዚአብሔር ስለ ኤርምያስ ሲናገር መንግስታት እንደ ሕንጻ እንደሆኑና እርሱ እንደሚገነባቸው፣ እንደ ተክሎች እንደሆኑና እርሱ እንደሚተክላቸው በዚህም ጠንካራ እንዲሆኑ እንደሚያደርጋቸው ይናገራል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 1:11

የእግዚአብሔር ቃል ምን ታያለህ? እያለ ወደ እኔ መጣ
ይህ ፈሊጥ ከእግዚአብሔር የመጣውን ልዩ መልእክት ለማስተዋወቅ ጥቅም ላይ ውሏል። በ ኤርምያስ 1:4 ላይ ተመሳሳይ ቃላት እንዴት እንደተረጎምኻቸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር መልእክት ሰጠኝ። እንዲህ አለ፡- ‘ምን’” ወይም “እግዚአብሔር ይህንን መልእክት ለእኔ ተናገረኝ፡- ‘ምን’” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

የለውዝ ቅርንጫፍ አያለሁ አልሁ
እግዚአብሔር ለኤርምያስ መንፈሳዊ ራዕይ አሳየው።

የለውዝ ቅርንጫፍ
የለውዝ ዛፍ የለውዝ ፍሬ የሚሰጥ ዛፍ ነው። (የማይታወቁ ነገሮችን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

እፈጽመው ዘንድ በቃሌ እተጋለሁ
ይህ የሚወክለው እግዚአብሔር የተናገረውን እንደሚፈጽመው ዋስትና መስጠቱን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ እፈጽመው ዘንድ ቃሌን አስባለሁ” ወይም “እኔ የተናገርሁትን እንደምፈጽመው ዋስትና እሰጣለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በቃሌ እተጋለሁ
“ለውዝ” እና “እተጋለሁ” የሚሉት የዕብራይስጡ ቃላት በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። እግዚአብሔር ቃሉን በእርግጠኝነት እንደሚፈጽም ኤርምያስ እንዲያስብ እግዚአብሔር ይፈልጋል።

Jeremiah 1:13

ሁለተኛም ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል ... እያለ ወደ እኔ መጣ
ይህ “የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ መጣ” የሚለው ፈሊጥ ጥቅም ላይ የዋለው ከእግዚአብሔር የመጣውን መልእክት ለማስተዋወቅ ነው። በ ኤርምያስ 1:4 ላይ ተመሳሳይ ሀረግ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት፣ ለውጥ የሚያስፈልግ ከሆነ ለውጥ አድርግ። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ለሁለተኛ ጊዜ መልእክት ሰጠኝ። እንዲህም አለኝ” ወይም “እግዚአብሔር ይህንን ሁለተኛ መልእክት ለእኔ ተናገረኝ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ላይ ላዩን የሚፈለ
ላይ ላዩን የሚለው የሚያመለክተው በማሰሮ ውስጥ ያለውን የውኃው የላይኛውን ክፍል ነው። ኤርምያስ ውኃው ሲፈለ ማየት ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ውኃው የሚፈለ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

አፉ ከሰሜን ወደዚህ ያዘነበለ
ይህ ማሰሮው ወደ ሰሜን ማለትም ኤርምያስ ወደ ነበረበት ወደ ይሁዳ ያዘነበለ ነው ማለት ነው።

ከሰሜን ወገን ክፉ ነገር ይገለጣል
“ክፉ ነገር ከሰሜን በኩል ይወርድባቸዋል።” ይህ የሚወክለው እግዚአብሔር ከሰሜን ወደ ደቡብ ክፉ ነገር እንደሚያመጣ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ነገር ከሰሜን ይመጣል” ወይም “እኔ ከሰሜን ክፉ ነገር እልካለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 1:15

አያያዥ ሀሳብ፡-
እግዚአብሔር ከሰሜን ስለሚመጣው ክፉ ነገር ለኤርምያስ መናገሩን ቀጥሏል።

ሁሉ
ይህ ጅምላ ፍረጃ በሰሜናዊ ክፍል ያሉትን መንግስታት ነገስታትን ሁሉ የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እያንዳንዱ ንጉስ” ወይም “የሰሜናዊው ክፍል ነገስታት በሙሉ” (ግነት/ግነታዊ ቋንቋ እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በኢየሩሳሌም በር መግቢያ ዙፋኑን ያስቀምጣል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ይህ የሚወክለው በኢየሩሳሌም ላይ መግዛትን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በኢየሩሳሌም በር መግቢያ ላይ ይገዛል” ወይም 2) ይህ የሚወክለው በኢየሩሳሌም ላይ መፍረድ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በኢየሩሳሌም ላይ ይፈርዳል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በዙሪያዋ በቅጥርዋ ሁሉ ላይ
“በዙሪያዋ በቅጥርዋ ሁሉ ላይ” ዙፋናቸውን ያስቀምጣሉ የሚለው በኢየሩሳሌም ዙርያ ያለውን ቅጥርዋን ለማፍረስ ለጦር ሰራዊቶቻቸው ትዕዛዝ መስጠታቸውን የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በይሁዳ ዙርያ ያለውን ቅጥር ለማፍረስ ለጦር ሰራዊቶቻቸው ትዕዛዝ ይሰጣሉ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በይሁዳም ከተሞች ሁሉ ላይ
“በይሁዳም ከተሞች ሁሉ ላይ” ዙፋናቸውን ያስቀምጣሉ የሚለው የይሁዳ ከተሞችን ሁሉ ለማፍረስ ለጦር ሰራዊቶቻቸው ትዕዛዝ መስጠታቸውን የሚወክል ነው። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ፍርዴን በእነርሱ ላይ እናገራለሁ
“እነርሱን እንዴት እንደምቀጣ እናገራለሁ”

ፍርዴን በእነርሱ ላይ እናገራለሁ
“በይሁዳ ሕዝብ ላይ ፍርድን እናገራለሁ”

በእጃቸው ለሰሩአቸው ስለ ሰገዱ
ሕዝቡ ጣዖታቱን በራሳቸው እጆች ስለሰሩአቸው፣ ጣዖታቱ ሊሰገድላቸው የሚገቡ እንዳልሆኑ ሊያውቁ ይገባቸው ነበር

Jeremiah 1:17

አያያዥ ሀሳብ፡-
እግዚአብሔር ለኤርምያስ መናገሩን ቀጥሏል።

አትፍራቸው ... በፊታቸው አስፈራሃለሁ
እዚህ ላይ “አትፍራቸው” የሚለው ከመጠን በላይ መፍራትን ይወክላል፣ “አስፈራሃለሁ” የሚለው ደግሞ ኤርምያስን በጣም እንዲፈራ ማድረግን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አትፍራ ... አስፈራሃለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ
“ትኩረት ስጥ!”

በምድሪቱ ሁሉ ላይ እንደ ተመሸገ ከተማ፣ እንደ ብረትም ዓምድ፣ እንደ ናስም ቅጥር ዛሬ አድርጌሃለሁ
እንደ እነዚህ ነገሮች ጠንካራ መሆን እግዚአብሔር እንዲናገር የነገረውን ነገር ለመናገር ልበ ሙሉ መሆንና የማይለወጥ አቋም መያዝን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በምድሪቱ ሁሉ ላይ እንደ ተመሸገ ከተማ፣ እንደ ብረትም ዓምድ እና እንደ ናስ ቅጥር ጠንካራ አድርጌሃለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ብረት ... ናስ
እነዚህ በዚያን ጊዜ እጅግ በጣም ጠንካራ በመሆናቸው የሚታወቁ ነገሮች ነበሩ። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሪቱ ሁሉ
ይህ የምድሪቱን ሕዝብ ሁሉ የሚወክል ነው። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ከአንተ ጋር ይዋጋሉ
ይህ የሚያመለክተው የይሁዳ ሕዝብን ነው።

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር እርሱ የተናገረው ቃል እንደሚፈጸም እርግጠኝነቱን ለመግለጽ ስለ ራሱ በስሙ ተናግሯል። በ ኤርምያስ 1:8 ላይ ይህን እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ መጣ፣ እንዲህም አለኝ፣ 2 "ሂድና በኢየሩሳሌም ጆሮ ጩኽ። እንዲህም በል 'እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በወጣትነትሽ የነበረሽን የኪዳን ታማኝነት፣ በታጨሽበት ጊዜ የነበረሽን ፍቅር፣ ዘር ባልተዘራበት ምድረ በዳ እንደ ተከተልሽኝ ስለአንቺ አስታውሳለሁ። 3 እስራኤል ለእግዚአብሔር ቅዱስ ነበረ፣ የእርሻው መከር በኩራትም ነበረ! ከበኩራቱ የበሉት ሁሉ ኃጢአት አድርገዋል! ክፉም ነገር ይመጣባቸዋል ይላል እግዚአብሔር።'" 4 የያዕቆብ ቤትና የእስራኤልም ቤት ቤተሰቦች ሁሉ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ። 5 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "አባቶቻችሁ ምን ክፋት አግኝተውብኝ ነው እኔን ከመከተል የራቁት፣ ከንቱ ጣዖታትንም የተከተሉት፣ እና ራሳቸውም ከንቱ የሆኑት? 6 እነርሱም 'ከግብጽ ምድር ያወጣን እግዚአብሔር፣ በምድረ በዳ ጉድጓድ ወዳለበት የአረባህ ምድር፣ በውኃ ጥምና በሞት ጥላ ምድር፥ ማንም በማያልፍበትና ማንም በማይቀመጥበት ምድር የመራን እግዚአብሔር ወዴት አለ?' አላሉም። 7 ነገር ግን ፍሬዋንና ሌሎች መልካም ነገሮቿን እንድትበሉ ወደ ቀርሜሎስ ምድር አገባኋችሁ! ይሁን እንጂ በመጣችሁ ጊዜ፣ ምድሬን አረከሳችሁ፣ ርስቴንም አጐሳቈላችሁ! 8 ካህናቱም 'እግዚአብሔር ወዴት አለ? አላሉም፥ ባለ የኦሪቶች ሊቅ የሆኑትም ስለ እኔ ግድ አላላቸውም! እረኞችም በደሉኝ፥ ነቢያትም ለበኣል ትንቢት ተናገሩ፣ ትርፍ የሌለውንም ነገር ተከተሉ። 9 ስለዚህ እከስሳችኋለሁ - የልጆቻችሁንም ልጆች እከስሳለሁ። 10 ወደ ኪቲም ደሴቶች እለፉና ተመልከቱ። ወደ ቄዳርም መልእክተኞችን ላኩና እንደዚህ ያለ ነገር ህኖ እንደ ሆነ መርምራችሁ እዩ። 11 አማልክት ባይሆኑ እንኳን አማልክት ያልሆኑትን አማልክቱን የለወጣቸው አንድ ሕዝብ አለን? ነገር ግን ሕዝቤ ሊረዳቸው ለማይችለው ነገር ክብሩን ለወጠ። 12 ሰማያት ከዚህ የተነሣ ተደነቁ! ተንቀጥቀጡ እና ደንግጡ ይላል እግዚአብሔር። 13 ሕዝቤ ሁለቱን ክፉ ነገሮች በእኔ ላይ አድርገዋልና፦ ውሃ ለመያዝ የማይችሉትን የተቀደዱ ጉድጓዶች ለራሳቸው በመቆፈር እኔን የሕያውን ውኃ ምንጭ ትተውኛል! 14 እስራኤል ባርያ ነውን? ወይስ በቤት የተወለደ አይደለምን? እናስ ብዝበዛ የሆነው ለምንድነው? 15 የአንበሳ ደቦሎች በእርሱ ላይ አገሡ። ብዙ ድምጽ በማሰማት ምድሩን አስፈሪ አደረጉት! ከተሞቹም የሚኖርባቸው እንዳይኖር ሆኖ ተደመሰሰ። 16 የሜምፎስና የጣፍናስ ልጆች የራስ ቅልሽን ላጭተው ባርያዎችን ከአንቺ ወሰዱ! 17 ይህን ሁሉ በራስሽ ላይ ያደረግሽው በመንገድ ላይ ሲመራሽ አምላክሽን እግዚአብሔርን ስለተውሽ አይደለምን? ይላል እግዚአብሔር አምላክሽ። 18 አሁንስ በግብጽ መንገድ ሄደሽ የሺሖርን ውኃ የምትጠጪው ለምንድነው? በአሦርስ መንገድ ሄደሽ የኤፍራጥስንም ውኃ የምትጠጪው ለምንድነው? 19 ክፋትሽ ይገሥጽሻል፣ ክዳትሽም ይቀጣሻል፤ አምላክሽንም እግዚአብሔርን መተውሽ እኔንም መፍራት ማቆምሽ ክፉና መራራ ነገር እንደ ሆነ እወቂ፥ ተመልከቺ፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር። 20 ከጥንት ጀምሮ የነበረብሽን ቀንበር ሰብሬአለሁና፣ እስራትሽንም ቈርጫለሁ። እንዲህም ሆኖ አንቺ 'አላገለግልም!' አልሽ፥ ነገር ግን ከፍ ባለው ኮረብታ ሁሉ ላይ ከለምለምም ዛፍ ሁሉ በታች ተጋደምሽ፣ አንቺ አመንዝራ። 21 እኔ ራሴ ግን የተመረጠች ወይን፣ ፈጽሞ እውነተኛ የሆነ ዘር አድርጌ ተክዬሽ ነበር። አንቺ ግን ክፉ የእንግዳ ወይን ግንድ ሆነሽ እንዴት ተለወጥሽብኝ? 22 በወንዝ ብትታጠቢ ወይም በብርቱ ሳሙና ብትታጠቢ፣ በእኔ ፊት በኃጢአትሽ ረክሰሻል ይላል ጌታ እግዚአብሔር። 23 'አልረከስሁም! በአሊምንም አልተከተልሁም' እንዴት ትያለሽ? በሸለቆዎች ያለውን ባህርይሽን ተመልከቺ! ያደረግሽውንም ተገንዘቢ፣ በመንገዷ ላይ እንደ ተለቀቀች ፈጣን ግመል ሆነሻል፤ 24 በምኞትዋ ከንቱ ነፋስን እንደምታሸትት፣ ምድረ በዳ እንደ ለመደች እንደ ሜዳ አህያ ነሽ! ከምኞትዋ የሚመልሳት ማን ነው? የሚፈልጋት ሁሉ ራሱን አያደክምም። ወደ እርሷ ሄደው በትኩሳቷ ወራት ያገኟታል። 25 እግርሽን ባዶ ከመሆን፣ ጉሮሮሽንም ከውኃ ጥም ከልክዪ! አንቺ ግን 'ተስፋ-ቢስ ነው! አይሆንም፣ እንግዶችን ወድጄአለሁና እከተላቸዋለሁ!' አልሽ። 26 ሌባ ሲያዝ እንደሚያፍረው ሁሉ፣ እንዲሁ የእስራኤል ቤት፣ እነርሱ፣ ንጉሦቻቸው፣ አለቆቻቸው፣ ካህናቶቻቸውና ነብያቶቻቸውም ያፍራሉ። 27 ለዛፉ፣ 'አንተ አባቴ ነህ፣' ድንጋዮንም 'አንተ ወለድከኝ' ይላሉ። ፊታቸውንም ሳይሆን ጀርባቸውን ሰጡኝ። በመከራቸው ጊዜ ግን 'ተነሥና አድነን!' ይላሉ። 28 ለአንተ የሠራሃቸው አማልክትህ ወዴት ናቸው? ይሁዳ ሆይ፥ አማልክትህ እንደ ከተሞችህ ቍጥር እንዲሁ ናቸውና ይነሡ በመከራህም ጊዜ ያድኑህ! 29 ስለዚህ እኔ እንዳጠፋሁ አድርጋችሁ የምትከስሱኝ ለምንድር ነው? ሁላችሁ በእኔ ላይ ኃጢአት ሠርታችሁብኛል ይላል እግዚአብሔር። 30 ሕዝባችሁን በከንቱ ቀጥቼአቸዋለሁ፤ ተግሣጽን አልተቀበሉም፤ እንደሚሰብር አንበሳ ሰይፋችሁ ነቢያቶቻችሁን በልቶአል! 31 ከዚህ ትውልድ የሆናችሁ እናንተ! የእግዚአብሔር ቃል ለሆነው ለቃሌ ትኩረት ስጡ! በውኑ ለእስራኤል ምድረ በዳ፣ ወይስ የጥልቅ ጨለማ ምድር ሆንሁባትን? ሕዝቤስ ስለ ምን 'እኛ እንቅበዝበዝ፣ ከእንግዲህ ወዲህ ወደ አንተ አንመለስም' ይላል? 32 ደናግሏ ጌጥዋን፣ ወይስ ሙሽራ ዝርግፍ ጌጥዋን ትረሳለችን? ሕዝቤ ግን ለማይቈጠሩ ቀናት ረስቶኛል። 33 ፍቅርን ለመሻት መንገድሽን እንዴት በደህና ታቀኛለሽ። እንደውም መንገድሽን ለክፉዎች ሴቶች እንኳ አስተምረሻል። 34 የንፁሐን ሕይወት የሆነው ደም፣ የድሆችም ደም በልብሶችሽ ላይ ተገኝቷል። እነዚህ ሰዎች በስርቆሽ ተግባር የተያዙ አልነበሩም። 35 ይልቁን፣ ይህ ሁሉ ሆኖ ሳለ፣ 'ወቀሳ የለብኝም፤ በእውነት የእግዚአብሔር ቍጣ ከእኔ ተመልሶአል' አልሽ። ነገር ግን ተመልከቺ! 'ኃጢአት አልሠራሁም' ብለሻልና ይፈረድብሻል። 36 መንገድሽን ትለዋውጪ ዘንድ ነገሩን ለምን ታቀልያለሽ? አሦር እንዳሳፈረሽ ግብጽ ያሳፍርሻል። 37 እግዚአብሔር የታመንሽባቸውን ጥሎአልና፥ በእነርሱም አይከናወንልሽምና እጅሽን በራስሽ ላይ አድርገሽ ከዚያ ደግሞ ትወጫለሽ።

Jeremiah 2:1

የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፣ ሂድ
ይህ ፈሊጥ ጥቅም ላይ የዋለው ከእግዚአብሔር የመጣውን ልዩ መልእክት ለማስተዋወቅ ነው። በ ኤርምያስ 1:4 ላይ ተመሳሳይ ቃላት እንዴት እንደተረጎምኻቸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር መልእክት ሰጠኝ። እንዲህ አለኝ፦ ‘ሂድ’” ወይም “እግዚአብሔር ይህን መልእክት ለእኔ ተናገረኝ፦ ‘ሂድ’” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ሂድና በኢየሩሳሌም ጆሮ ተናገር
“ሂድና በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎች ሊሰሙህ በሚችሉበት ስፍራ ተናገር”

ስለ አንቺ አስባለሁ
“ስለ አንቺ አስታውሳለሁ”

በወጣትነትሽ ጊዜ የነበረሽን የቃል ኪዳን ታማኝነት፣ ፍቅርሽንም
“ታማኝነት፣” ወጣትነት፣” እና “ፍቅር” የሚሉት ረቂቅ ስሞች “ታማኝ” እና “ወጣት፣” በሚሉት ቅጽሎች እና “መውደድ” በሚለው ግስ ሊገለጹ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ወጣት በነበርሽ ጊዜ፣ ለቃል ኪዳናችን እንዴት ታማኝ እንደነበርሽ፣ እና እንዴት እንደወደድሽኝ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በእጮኝነት ጊዜአችን
እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ስለነበረው ግንኙነት ሲገልጽ ሁለቱ ለመጋባት ተጫጭተው እንደነበር አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሁለታችን እንድንጋባ በመጀርያ በተስማማንበት ጊዜ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ዘር ባልተዘራበት ምድር
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ማንም ሰው ዘር ባልዘራበት ምድር” ወይም “ምንም ዓይነት የምግብ ዘር ባልበቀለበት ምድር” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የመከሩ በኩራት ነበረች
እግዚአብሔር ስለ እስራኤል ሲገልጽ ለእግዚአብሔር የተበረከተች ስጦታ እንደሆነች አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “እንደ እርሱ መከር በኩራት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከመከሩ በኩራት የበሉት ሁሉ እንደ በደለኞች ይቈጠራሉ
እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ጥቃት ስለፈጸሙት ሲናገር ለእግዚአብሔር ብቻ የተለየውን መስዋዕት እንደበሉ አድርጎ ገልጾአቸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ “በእስራኤል ላይ ጥቃት የፈጸሙ በሙሉ ከመከሩ በኩራት እንደበሉ ሕዝብ በበደላቸው ተጠይቀዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉ ነገር በእነርሱ ላይ መጣባቸው
“በእነርሱ ላይ መጣባቸው” የሚለው ሀረግ በእነርሱ ላይ ሆነ ለሚለው ሃሳብ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ክፉ ነገር በእነርሱ ላይ ሆነ” ወይም “እኔ በእነርሱ ላይ አሰቃቂ ነገር እንዲሆንባቸው አደረግሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ቃል በእርግጠኝነት እንደሚፈጸም ለመግለጽ ስለ ራሱ በስሙ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ያወጀው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ))

Jeremiah 2:4

የያዕቆብ ቤት የእስራኤልም ቤት ወገኖች ሁሉ
ያዕቆብና እስራኤል ለአንድ ሰው የተሰጡ ሁለት ስሞች ነበሩ፣ ስለዚህ እነዚህ ሁለት ሀረጎች የሚያመለክቱት ለአንድ የሕዝብ ወገን ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እናንተ የያዕቆብ ወገኖች ሁሉ” (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

የያዕቆብ ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ምትክ ስም ነው። በዚህ ሁኔታ ይህ የሚያመለክተው የያዕቆብን ወገኖች ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የያዕቆብ ወገኖች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ምትክ ስም ነው። በዚህ ሁኔታ ይህ የሚያመለክተው የእስራኤል ኦገርና ሕዝብ የሆኑትን የእስራኤልን ወገኖች ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እስራኤላውያን” ወይም “የእስራኤላውያን ሕዝብ ወገኖች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

አባቶቻችሁ እኔን ከመከተል የራቁት፣ የማይጠቅሙ ጣዖቶችን የተከተሉና ለራሳቸውም ከንቱም የሆኑ ምን ክፋት አግኝተውብኝ ነው?
እርሱ በሕዝቡ ላይ ምንም ዓይነት ክፋት ስላላደረገ ሕዝቡ እርሱን በመተው ጣዖቶችን መከተል አልነበረባቸውም ብሎ ለመናገር እግዚአብሔር እነዚህን ጥያቄዎች ተጠቅሟል። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔ ለአባቶቻችሁ ምንም ዓይነት ክፋት አላደረግሁም፣ ስለዚህ እኔን ከመከተል ርቀው መሄድ አልነበረባቸውም፣ የማይጠቅሙ ጣዖቶችን ተከትለው መሄድ አልነበረባቸውም። ይህንን በማድረጋቸው እነርሱ ራሳቸው የማይጠቅሙ ሆኑ!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

እኔን ከመከተል ርቀው ሄዱ
ይህ የሚወክለው እግዚአብሔርን መተውና ለእርሱ ታማኝ ለመሆን እምቢተኛ መሆንን ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እነርሱ እኔን ትተውኛል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የማይጠቅሙ ጣዖቶችን ተከትለው ሄዱ
ይ የሚወክለው ለጣዖቶች ታማኝ መሆንንና እነርሱን ማምለክ መምረጥን ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የማይጠቅሙ ጣዖቶችን አመለኩ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የማይጠቅሙ ጣዖቶች
ሰዎች ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ ነገር ግን ምንም ዓይነት መልካም ነገር የማያመጡላቸው ጣዖቶች። ትርጉሙ ጠቃሚ የሆኑ አንዳንድ ጣዖቶች እንዳሉ ሰዎች እንዲያስቡ የሚያደርግ መሆን የለበትም።

አላሉም
ይህ በክፍሉ የተገለጸውን መናገር ይኖርባቸው እንደነበር የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እንዲህ ማለት ነበረባቸው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከግብጽ ምድር ያወጣን እግዚአብሔር ... ወዴት አለ?
ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ እግዚአብሔር ለሕዝቡ አስፈላጊ መሆኑን ለማሳየት ጥቅም ላይ መዋል ነበረበት። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ያስፈልገናል። ከግብጽ ምድር ያወጣን እርሱ ነው።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በማይኖርበት ... የመራን እግዚአብሔር ወዴት አለ?
ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ እግዚአብሔር ለሕዝቡ አስፈላጊ መሆኑን ለማሳየት ጥቅም ላይ መዋል ነበረበት። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ያስፈልገናል። በማይኖርበት ... የመራን እግዚአብሔር እርሱ ነው።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ድርቅና ጥልቅ ጨለማ ያለበት ምድር
“ድርቅ ያለበት ምድር” በቂ ውኃ የሌለበት ምድር ነው። እዚህ ላይ “ጥልቅ ጨለማ” ለአደጋ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በቂ ውኃ የሌለበት አደገኛ ምድር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 2:7

ምድሬን አረከሳችሁ፣ ርስቴንም ጸያፍ አደረጋችሁ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። አማራጭ ትርጉም፦ “ኃጢአትን አደረጋችሁ የሰጠኋችሁን ምድር ደግሞ በእኔ የተጠላ እንዲሆን አደረጋችሁት!” (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሬን አረከሳችሁ
እዚህ ላይ “አረከሳችሁ” የሚወክለው ምድሪቱ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እንዳይኖራት ማድረግን ነው። ይህንን ያደረጉት በዚያች ምድር ሆነው ጣዖቶችን በሚያመልኩበት ጊዜ በእርሱ ላይ ኃጢአት በማድረጋቸው ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ምድሬን ኃጢአት በማድረጋችሁ አረከሳችኋት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ርስቴንም ጸያፍ አደረጋችሁ
“በኃጢአታችሁ ምክንያት ርስቴን የተጠላ አደረጋችሁት” ወይም “ኃጢአት በማድረጋችሁ ርስቴን ገፊ አደረጋችሁት”

ርስቴ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦

1. እግዚአብሔር ስለ ምድሩ ሲናገር እርሱ እንደወረሰው አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “የእኔ ምድር” ወይም

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2. እግዚአብሔር ለእስራኤል ስለ ሰጣት ምድር ሲናገር እርሱ ለእነርሱ እንደ ርስት እንደሰጣቸው አድርጎ ይናገራል” አማራጭ ትርጉም፡- “ለእናንተ የሰጠኋችሁ ምድር” ወይም “እንደ ርስት ለእናንተ የሰጠኋችሁ ምድር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ

እግዚአብሔር ወዴት አለ?
ይህ ጥያቄ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ መፈለጋቸውን ማሳየት ነበረበት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔርን መታዘዝ እንፈልጋለን!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ እኔ ግድ የላቸውም
“ለእኔ የተሰጡ አልነበሩም” ወይም “እኔን ተዉኝ”

እረኞቹ በእኔ ላይ አመጹብኝ
መሪዎቹ እን እረኞች እነርሱን የሚከተሏቸው ሕዝብ ደግሞ እንደ በጎች ተደርገው ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “መሪዎቻቸው በእኔ ላይ ኃጢአትን አደረጉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከንቱ ነገሮችን ተከትለው ሄዱ
እዚህ ላይ “ተከትለው ሄዱ” የሚወክለው መታዘዝ ወይም ማምለክ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ከንቱ ነገሮችን ታዘዙ” ወይም “ከንቱ ነገሮችን አመለኩ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከንቱ ነገሮች
ከንቱ ነገሮች ሰውን መርዳት የማይችሉ ነገሮች ናቸው። እዚህ ላይ ጣዖቶችን ያመለክታል።

Jeremiah 2:9

ስለዚህ ከእናንተ ጋር እከራከራለሁ
እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ እየተናገረ ነው።

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተነገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

የልጆቻችሁ ልጆች
“የወደፊቱ ትውልዳችሁ”

ወደ ኪቲም ጠረፍ ተሻገሩ
ኪቲም በምዕራብ እስራኤል ትገኝ የነበረች ደሴት ናት። አሁን ቆጵሮስ ተብላ ትጠራለች። በምዕራብ እስራኤል ሩቅ ያሉትን ምድር በሙሉ የሚወከል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ወደ ኪቲም ውቅያኖስ በምዕራብ በኩል ሂዱና ተሻገሩ” (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ቄዳርም መልእክተኞች ላኩ
ቄዳር ከምስራቅ እስራኤል በኩል በርቀት ለሚገኝ ምድር የተሰጠ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ወደ ቄዳር ምድር በምስራቅ በኩል በርቀት ወዳሉት መልእክተኞች ላኩ” (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በውኑ አማልክት ... አማልክቱን የለወጣቸው አንድ ሕዝብ አለን?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ሌሎች ሕዝቦች የራሳቸውን አማልክት ማምለክ መቀጠላቸውን ለእስራኤል ሕዝብ ለመንገር ነው። እነርሱ አማልክቶቻቸውን ለውጠው ሌሎች አማልክትን አላመለኩም። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድም ሕዝብ አማልክቱን ... አማልክቱን የለወጠ ፈጽሞ እንደሌለ ታያላችሁ።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን ሕዝቤ ክብራቸውን ሊረዳቸው ለማይችል ነገር ለወጡ
እዚህ ላይ እግዚአብሔር ለሕዝቡ በቀጥታ እንደማይናገር አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን፣ እናንተ፣ ሕዝቤ እኔን የክብራችሁን አምላክ ሊረዳችሁ ለማይችል ነገር ለወጣችሁኝ” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ክብራቸው
ይህ መግለጫ የሚያመለክተው ክቡር የሆነውን ራሱን እግዚአብሔርን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የከበረ አምላካቸውን” ወይም “እኔ፣ የእናንተ የከበርሁ አምላካችሁ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ሊረዳቸው ለማይችል ነገር
እዚህ ላይ ሐሰተኛ አማልክት ሊሰሩት በማይችሉት ነገር ተገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሊረዱ የማይችሉ፣ ሐሰተኛ አማልክት” ወይም “ሊረዱ የማይችሉ አማልክት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 2:12

ሰማያት ሆይ፥ በዚህ ተደነቁ! እጅግም ደንግጡና ተንቀጥቀጡ
እግዚአብሔር መለስ ብሎ እዚያ ሆነው እርሱን እንደሚሰሙት አድርጎ ለሰማያት ይናገራል። እግዚአብሔር ይህን የሚናገረው እስራኤል የሰራችው ነገር እጅግ በጣም አስደንጋጭ እንደሆነ ለመግለጽ ነው። (እንቶኔ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰማያት ሆይ፥ በዚህ ተደነቁ! እጅግም ደንግጡና ተንቀጥቀጡ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) እግዚአብሔር በሰማይ ላይ ለሚገኙ ፍጡራን ይናገራል ወይም 2) እግዚአብሔር ሕዝብ እንደሆኑ አድርጎ ለራሳቸው ለሰማያት ይናገራል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

የሕያውን ውኃ ምንጭ ትተውኛል
እግዚአብሔር ስለ ራሱ የሕያው ውኃ ምንጭ እንደሆነ አድርጎ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእነርሱ ሕያው ውኃ ምንጭ የሆንሁትን እኔን ትተውኛል” ወይም “እንደ ሕያው ውኃ ምንጭ የሆንሁትን እኔን ትተውኛል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጉድጓዶች ለራሳቸው ቆፍረዋል
እግዚአብሔር ስለ ሐሰተኛ አማልክት ሲናገር ሰዎች ውኃ ለማግኘት ሲሉ የቆፈሯቸው ጉድጓዶች እንደሆኑ አድርጎ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለራሳቸው እንደቆፈሯቸው ጉድጓዶች ወደ ሐሰተኛ አማልክት ሄደዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጉድጓዶች
ውኃ ለማከማቸት የሚረዱ ጥልቅ ጉድጓዶች

Jeremiah 2:14

በውኑ እስራኤል ባሪያ ነውን? የተወለደው በጌታው ቤት ነውን? ታዲያ ስለምን ለብዝበዛ ተዳረገ?
ምንም እንኳ እግዚአብሔር የሚናገረው ለሕዝቡ ቢሆንም ስለ እስራኤል ለሌላ ሰው እንደሚናገር አድርጎ ሶስተኛ ሰው ተጠቅሟል። አማራጭ ትርጉም፡- “እስራኤል፣ አንተ ባሪያ ነህ እንዴ? የተወለድከው በቤት ነው? ታዲያ ለምን ለብዝበዛ ተዳረግህ? (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እስራኤል ባሪያ ነውን? የተወለደው በጌታው ቤት ነውን?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው እስራኤል ለብዝበዛ መዳረግ እንዳልነበረባት ምክንያቱን ለመናገር ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እስራኤል ባርያ አይደለም። እስራኤል በቤት አልተወለደም ነበር።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የተወለደው በጌታው ቤት ነውን?
እዚህ ላይ “በጌታው ቤት ተወለደ” የሚለው ሀረግ ለባርነት መወለድን የሚያሳይ ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የተወለደው ባርያ ሆኖ ነው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ታዲያ ስለምን ለብዝበዛ ተዳረገ?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው እስራኤል ለብዝበዛ መዳረግ እንዳልነበረባት ለማመልከት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለዚህ ለብዝበዛ መዳረግ አልነበረበትም።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ታዲያ ስለምን ለብዝበዛ ተዳረገ?
እዚህ ላይ “ለብዝበዛ ተዳረገ” የሚለው ሀረግ ተጠቂ መሆንና ወደሌላ አገር ምርኮኛ ሆኖ መወሰድን የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ታዲያ እስራኤል እንደ ምርኮኛ ወደሌላ የተወሰደው ለምንድን ነው” ወይም “ታዲያ የእስራኤል ጠላቶች እስራኤልን እንደ ምርኮኛ ለምን ወሰዱት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚእስለውን ይመልከቱ)

የአንበሳ ደቦሎች በእርሱ ላይ አገሡ፥ ብዙ ድምጽም አሰሙ
እግዚአብሔር እስራኤልን ስላጠቋት የእስራኤል ጠላቶች ሲናገር ጠላቶቿ የሚያገሱና እስራኤልን የሚያጠቁ አንበሶች እንደሆኑ አድርጎ ገልጿቸዋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሩንም ባድማ አድርገውታል
ይህ ሕዝቡ ምድሩን ሲያዩ የሚያስፈራ እንደሆነ እስኪሰማቸው ድረስ ምድሩን ለማጥፋታቸው የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የእስራኤልን ምድር አፈራራሱ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የአንበሳ ደቦሎች አገሱ
ማግሳት የዱር እንስሳት ሲያጠቁ የሚያሰሙት እጅግ በጣም ከፍ ያለ ጩኸት ነው።

ከተሞቹ ተቃጠሉ፣ የሚቀመጥባቸው ማንም የለም
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእስራኤልን ከተሞች አቃጠሉአቸው፣ አሁን በእነርሱ ውስጥ የሚኖር ማንም ሰው የለም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የሚቀመጥባቸው
በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች

ሜምፎስና ጣፍናስ
እነዚህ በግብጽ ምድር የሚገኙ የሁለት ከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አናትሸን ይላጩሻል
ግብጻውያን የባርያዎቻቸውን ራስ ይላጩ ነበር፣ ይህን የሚያደርጉት የባርያ ምልክት ለመስጠት ነው።

አናትሸን ይላጩሻል
አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ጥቅስ “አናትሸን ሰንጥቀውሻል።”

በመንገድ የሚመራሽን፣ እግዚአብሔር አምላክሽን በመተውሽ፣ ይህን በራስሽ ላይ አላመጣሽምን?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ጠላቶቻቸው ያጠቋቸው በራሳቸው ጥፋት እንደሆነ እስራኤልን ለማስታወስ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አምላካችሁ እግዚአብሔር በመንገድ ሁሉ እየመራችሁ ሳለ እናንተ ግን እርሱን በመተዋችሁ ይህን በራሳችሁ ላይ አመጣችሁ።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 2:18

ስለዚህ አሁን፣ የሺሖርን ውኃ ትጠጪ ዘንድ በግብጽ መንገድ ለምን ሄድሽ? የኤፍራጥስን ወንዝ ውኃ ትጠጪ ዘንድ በአሦር መንገድ ለምን ሄድሽ?
እግዚአብሔር እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመው ግብጽንና አሦርን አነርሱን እንዲረዱአቸው መጠየቃቸው ምንም ዓይነት መልካም ነገር እንደማያመጣላቸው ለሕዝቡ ለማስታወስ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ወደ ግብጽ በመሄድ ከሺሖር ወንዝ ውኃ መጠጣት ወይም ወደ አሦር በመሄድ ከኤፍራጥስ ወንዝ ውኃ መጠጣት ለእናንተ ምንም አይጠቅማችሁም።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የሺሖርን ውኃ ትጠጪ ዘንድ በግብጽ መንገድ ለምን ሄድሽ? የኤፍራጥስን ወንዝ ውኃ ትጠጪ ዘንድ በአሦር መንገድ ለምን ሄድሽ?
እነዚህ የግብጽንና የአሦርን ሰራዊት እነርሱን እንዲረዱአቸው ለመጠየቃቸው ተለዋጭ ዘይቤ ናቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “ግብጻውያን እንዲረዱአችሁ ለምን ጠየቃችሁ … አሦራውያን እንዲረዱአችሁ ለምን ጠየቃችሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሺሖር
ይህ ከግብጽጋር የተያያዘ የአንድ ምንጭ ስም ነው። ምናልባት የአባይ ወንዝ ገባር ሳይሆን አይቀርም። አንዳንድ ትርጉሞች አባይ ብለው ይጠሩታል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሺሖር ምንጭ” ወይም “የሺሖር ወንዝ” ወይም “የአባይ ወንዝ” (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ክፋትሽ ይገስጽሻል፣ ክህደትሽ ይቀጣሻል
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው ቅጣታቸው የክፉ ስራቸው ውጤት እንደሆነ የሚያሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉና ከዳተኛ ስለሆንሽ እቀጣሻለሁ” (ሰውኛ ዘይቤ እና ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉና መራራ ነው
እዚህ ላይ “መራራ” የሚለው ቃል “ክፉ” የሚለውን ይገልጻል። አማራጭ ትርጉም፡- “እጅግ በጣም መራራ የሆነ ክፋት ነው” ወይም “እጅግ በጣም ክፉ ነው” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 2:20

ከጥንት ጀምሮ ቀንበርሽን ሰብሬአለሁ፤ እስራትሽንም ቈርጫለሁ አንቺም። አንቺ ግን “አላገለግልም አልሽ”
እዚህ ላይ “ቀንበርሽን ሰብሬአለሁ” እና “እስራትሽንም ቆርጫለሁ” ከባርነት አርነት እንዳወጣቸው የሚገልጹ ተለዋጭ ዘይቤ ናቸው። የእስራኤል ሕዝብ በግብጽ ምድር ባሮች ነበሩ። አማራጭ ትርጉም፡- “ከረጅም ጊዜ በፊት እኔ ከባርነት ነፃ አወጣኋችሁ፣ ነገር ግን አሁንም እኔን ለማምለክ እንቢ አላችሁ!” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እስራት
አንድን ሰው ወይም እንስሳ ለማሰር የሚጠቅም ሰንሰለት

ነገር ግን ከፍ ባለው ኮረብታ ሁሉ ላይ እና ከለምለምም ዛፍ ሁሉ በታች ለማመንዘር ተጋደምሽ
ለምን እንደተጋደሙ በግልጽ ሊብራራ ይችላል። እዚህ ላይ “ማመንዘር” ለእግዚአብሔር ታማኝ ያልሆነ ሰውን የሚወክል ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ለባሏ ታማኝ እንዳልሆነች አመንዝራ ሚስት አንቺም ከእኔ ይልቅ ለጣዖቶች በመስገድ እነርሱን አመለክሽ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በታች
ከስር

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እኔ እንደ ተመረጠች ወይን፣ ፍጹምም ንጹሕ ዘር አድርጌ ተክዬሽ ነበር
እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ሲናገር ሕዝቡን እርሱ እንደተከለው እንደ ተመረጠ ወይን በከነዓን ታላቅ ሕዝብ አድርጎ እንደሰራው ይገልጻል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከሁሉ የተሻለውን የወይን ዓይነት ለመትከል እጅግ በጣም ጥሩ የሆነውን ዘር እንደሚጠቀም ገበሬ፣ እኔ እግዚአብሔር በመልካም አጀማመር እንድትጀምሩ አድርጌ ነበር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የተመረጠ ወይን
“በጣም ጥሩ ጥራት ያለው ወይን”

ፍጹም ንጹህ ዘር
እዚህ ላይ “ንጹህ ዘር” ጥሩ ካልሆነ ዘር ጋር ያልተዳቀለ በጣም ጥሩ ዘር ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እጅግ በጣም ጥሩ ከሆነ ዘር የበቀለ”

ታዲያ አንቺ ብልሹ፣ የማይጠቅም ወይን ግንድ ሆነሽ እንዴት ተለወጥሽብኝ?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ለመለወጡና እንደ ብልሹና የማይጠቅም ወይን ግንድ ለመሆኑ ሕዝቡን ለመገሰጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን አንቺ ብልሹና የማይጠቅም ወይን ግንድ ሆነሽ ተለወጥሽ!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በእኔ ፊት በኃጢአትሽ ረክሰሻል
በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት የሌለው ነገር እንደረከሰ ተደርጎ ይነገራል። እዚህ ላይ “ረክሰሻል” የሚለው ለእስራኤል ኃጢአት የማያቋርጥ ማሳሰቢያ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ኃጢአትሽን እንደ ርኩሰት አይቼዋለሁ” ወይም “ኃጢአትሽ እንደ ርኩሰት ነው፤ በደልሽ ጸንቶ ይኖራል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የጌታ እግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን ተመሳሳይ ሀረግ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “ጌታ እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ ጌታ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 2:23

በአለምንም አልተከተልሁም እንዴት ትያለሽ?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ሕዝቡ በአሊምን አላመለክሁም ብሎ ለተናገረው ለመገሰጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “You lie when you say, ‘በአሊምንም አልተከተልሁም’ ብለሽ መናገርሽ ዋሽተሻል” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

መከተል
ይህ ለማገልገልና ለማምለክ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አንቺ እዚህና እዚያ የምትሮጥ ፈጣን ሴት ግመል ነሽ
እግዚአብሔር እስራኤል ሌሎች አማልክትን ስለማምለካቸው ሲናገር ወንድ ግመል ለመፈለግና ከእርሱ ጋር ወሲብ ለማድረግ በሌላ አቅጣጫ እንደምትሮጥ ሴት ግመል አድርጎ ገልጿቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንቺ ወንድ ግመል ለመፈለግና ከእርሱ ጋር ወሲብ ለማድረግ ወደፊትና ወደኋላ እንደምትሮጥ ፈጣን ሴት ግመል ነሽ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ፈጣን
በፍጥነት መሮጥ የምትችል

በምኞትዋ ነፋስን እንደምታሸትት፣ በምድረ በዳ እንደ ለመደች እንደ ሜዳ አህያ ነሽ
እግዚአብሔር እስራኤል ሌሎች አማልክትን ስለማምለካቸው ሲናገር ወንድ የሜዳ አህዮች ለመፈለግ እንደምትሮጥ ሴት የሜዳ አህያ አድርጎ ገልጿቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንቺ በምድረ በዳ እንደምትኖር ወጣት ሴት የሜዳ አህያ ነሽ። ወሲብ መፈጸም ስትፈልግ ከቁጥጥር ውጭ ትሆናለች፣ ወንድ የሜዳ አህያ ለመፈለግ ነፋስን ታሸትታለች” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በምኞትዋ
ይህ ሀረግ ፈሊጥ ሲሆን የሚያመለክተው ሴት የሜዳ አህያ ከወንድ የሜዳ አህዮች ጋር ወሲብ ለመፈጸም የምትፈልግበትን ጊዜ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ወሲብ ለመፈጸም ስትፈልግ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ከምኞትዋ የሚመልሳት ማን ነው?
ይህ ጥያቄ ጥቅም ላይ የዋለው ሴት የሜዳ አህያ ከወንድ የሜዳ አህያ ጋር ወሲብ ለመፈጸም ስትፈልግ ሊቆጣጠራት የሚችል ማንም እንደሌለ አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ወሲብ መፈጸም ስትፈልግ ማንም ወደኋላ ሊመልሳት አይችልም።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

እግርሽን ባዶ ከመሆን ጉሮሮሽንም ከውኃ ጥም ከልክዪ!
እግዚአብሔር እስራኤል ሌሎች አማልክትን ለማምለክ ስለመፈለጋቸው ሲናገር እነዚህን አማልክት ለመፈለግ በምድረ በዳ ይሮጡ እንደነበር አድርጎ ገልጿቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህን ሐሰተኛ አማልክት ለመፈለግ እዚህና እዚያ መሮጥሽን እንድታቆሚ ነግሬሻለሁ፣ ምክንያቱም ይህ ሁሉ ድርጊትሽ ውጤቱ ጫማሽ እንዲያልቅና በጣም እንድትጠሚ የሚያደርግ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ተስፋ የለውም
“ራሳችንን በመከልከል ምንም ዓይነት ተስፋ የለም።” ይህ ሌሎች አማልክትን ከመከተል ራሳቸውን ማስቆም እንደማይችሉ የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ራሳችንን ፈጽሞ ማስቆም አንችልም” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አይሆንም፣ እንግዶችን ወድጃለሁና፣ እከተላቸዋለሁም
እዚህ ላይ “እንግዶች” የሚለው ባዕዳን አማልክትን የሚወክል ነው፣ እና “እከተላቸዋለሁ” የሚለው እነርሱን ማምለክ የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ባዕዳን አማልክትን መከተልና እነርሱን ማምለክ አለብን!” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 2:26

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰብ ምትክ ስም ነው። በዚህ ጥቅስ የሚያመለክተው የእስራኤልን ልጆች ነው። ይህን በኤርምያስ 2:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እስራኤላውያን” ወይም “የእስራኤላውያን ሕዝብ ወገን” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በተያዘ ጊዜ
ይህ ፈሊጥ አንድ ሰው የሌላውን ሰው ድርጊት ለይቶ ማወቁን የሚያሳይ ነው። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ሰው ሲያገኘው” ወይም “አንዳንድ ነገሮች መስረቁን ሰዎች ባወቁ ጊዜ” (ፈሊጥ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ፣ ንጉሦቻቸው፣ አለቆቻቸው፣ ካህናቶቻቸውና ነቢያቶቻቸው
ይህ ዝርዝር የእስራኤል አካል የሆነ ማንኛውም ሰው እንደሚያፍር ያሳያል።

ግንዱን፡- ‘አንተ አባቴ ነህ’ ድንጋዮንም፡- ‘አንተ ወለድኸኝ’ የሚሉ እነዚህ ናቸው
እዚህ ላይ “ግንድ” እና “ድንጋይ” የሚሉት ከእንጨትና ከድንጋይ ተቀርታ የተሰሩ ጣዖቶችን የሚወክሉ ናቸው። እነዚህ ቀላት ጣዖቱ የተሰራው በተራ ነገሮች ስለሆነ ሊመለኩ የተገባቸው እንዳልሆኑ አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ከእንጨት ተቀርጾ ለተሰራው ጣዖት ‘አንተ አባቴ ነህ’ ለተቀረጸው ድንጋይ ደግሞ ‘አንተ ወለድኸኝ’ የሚሉ እነዚህ ሕዝቦች ናቸው። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ፊታቸውንም ሳይሆን ጀርባቸውን ሰጡኝ
“ጀርባቸው ወደ እኔ ነው፤ ፊታቸው ግን ወደ እኔ ዘወር አላለም።” ይህ እግዚአብሔርን መተዋቸውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ፊታቸውን ከእኔ መለሱ” ወይም “ፊታቸውን ሳይሆን ጀርባቸውን ወደ እኔ መለሱ” ወይም “አነርሱ ፈጽመው ተዉኝ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ተነስተህ አድነን
ይህንን የተናገሩት ለእግዚአብሔር እንደሆነ ግልጽ መደረግ አለበት። “እግዚአብሔር ሆይ፣ ተነስተህ አድነን” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ታዲያ ለአንተ የሠራሃቸው አማልክትህ ወዴት ናቸው?
እግዚአብሔር በዚህ ጥያቄ አማካይነት ሕዝቡ የሚያመልኩአቸው ጣዖታቱን እንዲረዷቸው ሊጠይቁአቸው እንደሚገባ ያመለክታል። እርሱ ይህንን ምፀት የተጠቀመው ሕዝቡ ሌሎች ጣዖቶችን በማምለካቸው እርሱ እንዳዘነ ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሊረዷችሁ ለራሳችሁ የሰራችኋቸውን አማልክት ልትጠይቋቸው ይገባል።” ወይም “ሊረዷችሁ ለራሳችሁ የሰራችኋቸውን አማልክት አልጠየቃችኋቸውም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች እና ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

በመከራህ ጊዜ ለያድኑህ የሚችሉ ከሆነ፣ እስቲ ተነስተው ይምጡና ያድኑህ
እግዚአብሔር ሊያመለክት የፈለገው ሐሰተኛ አማልክት የሚያልኩአቸውን ሰዎች ሊረዷቸው ይገባል የሚል ነው። ሐሰተኛ አማልክት ሰዎችን ሊረዱ እንደማይችሉ ያውቃል። እርሱ ይህን ሲናገር የእርሱ ሕዝብ ሐሰተኛ አማልክትን በማምለካቸው እንዳዘነ ለማሳየት ምፀት ተጠቅሟል። አማራጭ ትርጉም፡- “በመከራችሁ ጊዜ እነርሱ ሊያድኑአችሁ እንደማይችሉ ስለምታውቁ እነርሱን አልጠየቃችሁም” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 2:29

ታዲያ ለምን እኔን ክፋት እንዳደረግሁባችሁ ትከስሱኛላችሁ? በእኔ ላይ ኃጢአት ያደረጋችሁ እናንተ ሁላችሁ ናችሁ።
እግዚአብሔር ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው የእስራኤል ሕዝብ ክፉ እንዳደረገባቸው በማሰብ እርሱን መውቀሳቸውን ለመገሰጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እስራኤል፣ ምንም እንኳ በእኔ ላይ ኃጢአት ማድረግን ብትቀጥሉም፣ እኔን በጠራችሁ ጊዜ ሳላድናችሁ በመቅረቴ እኔ ትክክል እንዳልሆንሁ አሰባችሁ” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ተግሣጽን አልተቀበሉም
እዚህ ላይ “ተግሳጽ መቀበል” ከቅጣት መማርን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከተግሳጽ መማርን አልተቀበሉም” ወይም “እኔ እነርሱን በገሰጽሁ ጊዜ እኔን መታዘዝን ለመማር ፈቃደኞች አልሆኑም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰይፋችሁ እንደሚያጠፋ አንበሳ ነቢያቶቻችሁን በልቶአል
እግዚአብሔር የእስራኤል ሕዝብ ነቢያቶቻቸውን ስለመግደላቸው ሲናገር ሰይፋቸው ነቢያቶቻቸውን የበላ አንበሳ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እናንተ ነቢያቶቻችሁን እንደሚያጠፋ አንበሳ በጭካኔ በሰይፋችሁ ገደላችኋቸው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አጥፊ
መጠኑ በጣም ሰፊ የሆነ አደጋ የማምጣት ችሎታ ያለው

የዚህ ትውልድ ሰዎች ሆይ! ቃሌን አስተውሉ፣ የእግዚአብሔር ቃል
“ይህ ትውልድ” የሚለው ሀረግ ኤርምያስ ይኖር በነበረበት ዘመን ይኖሩ የነበሩ ሰዎችን የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እናንተ ዛሬ የምትኖሩ ሰዎች፣ እኔ እግዚአብሔር ለእናንተ የምናገረውን ቃል አስተውሉ”

በውኑ ለእስራኤል ምድረ በዳ ወይስ ድቅድቅ ጨለማ ያለበት ምድር ሆንሁባትን?
እዚህ ላይ “ምድረ በዳ” እና “ድቅድቅ ጨለማ ያለበት ምድር” ለአደጋ ተለዋጭ ዘይቤ ናቸው። እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው እርሱ አደገኛ እንደሆነ በማሰባቸው እስራኤልን ለመውቀስ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ ለእናንተ እንደ ምድረ በዳ ወይም ድቅድቅ ጨለማ ያለበት ምድር እንደሆንሁባችሁ አሰባችሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ሕዝቤስ ስለ ምን “እኛ ተንከራትተናል ከእንግዲህ ወዲህ ወደ አንተ አንመለስም ይላል”?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ሕዝቡ ይህን በመናገሩ ሊገስጸው ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እናንተ ሕዝቤ ‘መሄድ ወደምንፈልገው መሄድ እንችላለን፣ ከእንግዲህ ወዲህ እግዚአብሔርን አናመልክም’ ብላችኋል።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

መንከራተት
ወደ ተለያዩ አካባቢዎች ወይም ስፍራዎች ያለ ምንም ግልጽ ዓላማ ወይም አቅጣጫ መንቀሳቀስ

Jeremiah 2:32

በውኑ ቆንጆ ጌጥዋን ወይስ ሙሽራ የሰርግ ልብሷን ትረሳለችን?
“ትረሳለች” የመሚለው ቃል የሁለተኛው ሀረግ አካል ጭምር እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል። አማራጭ ትርጉም፡- “በውኑ ቆንጆ ጌጥዋን ትረሳለችን፣ ወይስ ሙሽራ የሰርግ ልብሷን ትረሳለችን?” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

በውኑ ቆንጆ ጌጥዋን ወይስ ሙሽራ የሰርግ ልብሷን ትረሳለችን?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ለአንድ ሰው በጣም ጠቃሚ የሆኑትን ነገሮች የማስታወስን ሃሳብ ለማስተዋወቅ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ቆንጆ ጌጥዋን ማድረግ ፈጽሞ እንደማትረሳ፣ ሙሽራ ደግሞ የሰርግ ልብሷን መልበስ እንደማትረሳ ታውቃላችሁ።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የማይቆጠሩ ቀናቶች
“በጣም ረጅም ጊዜ”

ፍቅርን ለመፈለግ መንገድሽን እንዴት ታቀኛለሽ
እግዚአብሔር ፍቅርን በመፈለጋቸው ሕዝቡን እያመሰገናቸው ይታያል፣ ነገር ግን ይህ ምፀት ነው። እርሱ ለእርሱ ታማኞች ባለመሆናቸው በእነርሱ ላይ እንዳዘነ እያሳያቸው ነበር። (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

ፍቅርን ለመፈለግ
እግዚአብሔር ሌሎች አማልክትን ስለሚያመልከው ሕዝቡ ሲናገር ለባሏ ታማኝ እንደልሆነችና እንዲወዳት ሌላ ወንድ እነደምትፈልግ ሴት አድርጎ ገልጿቸዋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለክፉዎች ሴቶች እንኳ መንገድሽን አስተምረሻል
እግዚአብሔር ሕዝቡ ምን ያህል ለእርሱ ታማኝነት የጎደላቸው ስለመሆናቸው ሲናገር ለሴተኛ አዳሪዎች እንኳ እንዴት ለባሎቻቸው ታማኝ መሆን እንደሌለባቸውና ሌሎች ወንዶች የእነርሱ ወዳጆች እንዲሆኑ እንዴት መፈለግ እንዳለባቸው የሚያስተምሩ እንደሆኑ አድርጎ ገልጿቸዋል። (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

የንጹሐን ድሆች ሕይወት የሆነው ደም በልብስሽ ላይ ተገኝቶአል
በልብሳቸው የተገኘው ደም ሰዎችን እንደገደሉ ማስረጃ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በልብስሽ ላይ የተገኘው የንጹሐን ድሆች ደም እነርሱን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በመግደልሽ ወንጀለኛ እንደሆንሽ ያሳያል” ወይም “የንጹሐን ድሆች ደም በመግደልሽ ወንጀለኛ ነሽ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሕይወት የሆነው ደም
“ሕይወትን የሚወክለው ደም”

እነዚህ ሰዎች በስርቆት ተግባር የተያዙ አልነበሩም
እነርሱ ሰዎችን በስርቆት ተግባር ተሰማርተው ይዘዋቸው ቢሆን ኖሮ ሰዎቹን ለመግደል ምክንያት ይሆንላቸው ነበር። ነገር ግን እነርሱ የገደሏቸው ሰዎች ንጹሐን ነበሩ። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህን ሰዎች የተለያዩ ነገሮች ሲሰርቁ አላገኛችኋቸውም” ወይም “ነገር ግን እነዚህ ሰዎች ምንም እንኳ አንድም ነገር ባይሰርቁም እነርሱን ገድላችኋቸዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 2:35

በእርግጥ ቁጣው ከእኔ ርቋል
እዚህ ላይ ቁጣ ከእስራኤል እንደሚርቅ ሰው ተደርጎ ተነግሯል። ርቋል የሚለው እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር የነበረውን ቁጣ ማቆሙን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በእርግጥ እግዚአብሔር ከእኔ ጋር የነበረውን ቁጣ አቁሟል” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ግን በአንቺ ላይ ፍርድን አመጣብሻለሁ
እዚህ ላይ “ፍርድ” ቅጣትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ እቀጣሻለሁ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

መንገድሽን እንደ ቀላል ነገር እየለዋወጥሽ ለምን ትሮጫለሽ?
እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ይገስጻቸዋል ምክንያቱም እነርሱ ለእርዳታ ሲሉ ከአንድ መንግስት ወደ ሌላ መንግስት እየለዋወጡ ሲሄዱ ነበር ነገር ግን ለእርዳታ በእግዚአብሔር ላይ አልተደገፉም። (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ቀላል ነገር
ያለ ጥንቃቄ ወይም ተገቢ ግንዛቤ

አንቺ ደግሞ በግብጽ ትዋረጃለሽ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ግብጽ ታዋርድሻለች”

አንቺ ደግሞ በግብጽ ትዋረጃለሽ
የእስራኤል ሕዝብ ያዝናል ምክንያቱም የግብጽ ጦር ሰራዊት እነርሱን ሊታደጋቸው አይችልም። አማራጭ ትርጉም፡- “ግብጽ ሊታደግሽ ባልቻለ ጊዜ አንቺ ትዋረጃለሽ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አሦር እንዳዋረደሽ
“እንዳዋረደሽ” የሚለው ቃል ከበፊቱ ሀረግ ልንረዳው የምንችለው ነው። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንቺ በአሦር እንደተዋረድሽ” ወይም “አሦር አንቺን እንዳዋረደችሽ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያም ትወጫለሽ
“አንቺ ከግብጽ ትወጫለሽ”

እጆችሽን በራስሽ ላይ አድርገሽ
ይህ የኃፍረት ምልክት ነው። (ምሳሌያዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

አንቺም በእነርሱ አይከናወንልሽም
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰለዚህ እነርሱ አይረዱሽም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 በሰው ዘንድ፣ 'ሰው ሚስቱን በፍቺ ቢያባርራት፣ ከእርሱም ሄዳ የሌላ ሰው ሚስት ትሆናለች። በድጋሚ ወደ እርሷ ሊመለስ ይገባዋልን? እርሷ ፈጽሞ የረከሰች አይደለችምን?' ይባላል። ያቺ ሴት ማለት ይህች ምድር ናት! አንቺ እንደ ሴተኛ አዳሪ ከብዙ ውሽሞች ጋር አመንዝረሻል፣ ወደ እኔም ትመለሻለሽን? ይላል እግዚአብሔር። 2 ዓይንሽን ወደ ተራቆቱት ኮረብቶች አንሺና ተመልከቺ! ያልተነወርሽበት ስፍራ ወዴት አለ? ዘላን በምድረ በዳ እንደሚቀመጠው፣ አንቺ በመንገድ ላይ ተቀምጠሽ አፍቃሪዎችሽን ትጠብቂያቸው ነበር። በዘማዊነትሽና በኃጢአትሽ ምድሪቱን አረከስሽ። 3 ስለዚህ የጸደይ ዝናብ ተከለከለ፣ የኋለኛውም ዝናብ አልመጣም። ነገር ግን እንደ ዘማዊት ሴት ፊት፣ ፊትሽ የእብሪተኛ ነበር። ልታፍሪም እንቢ ብለሻል። 4 ከእንግዲህ ወዲህ 'አባቴ! የወጣትነቴ የቅርብ ወዳጅ ነህ።' ብለሽ ወደ እኔ አልጮኽሽልኝምን? 5 እስከ ለዘላለም ትቆጣለህን? ቊጣህንስ እስከ ፍጻሜ ድረስ ትጠብቀዋለህን?' ብለሽ ተናገርሽ። ተመልከቺ! ክፋትን እንደምትፈጽሚ ተናገርሽ፣ አደረግሽውም። ስለዚህ ማድረግሽን ቀጥይ!" 6 እግዚአብሔርም በንጉሡ በኢዮስያስ ዘመን እንዲህ አለኝ "እስራኤል እኔን መክዳቷን ታያለህ? ከፍ ወዳለው ተራራ ሁሉ፣ ወደለመለመ ዛፍም ሁሉ በታች ሄደች፣ በዚያም እንደ ዘማዊት ሴት ሆነች። 7 'ይህንም ሁሉ ካደረገች በኋላ፣ ወደ እኔ ትመለሳለች' ብዬ ነበር፤ ነገር ግን አልተመለሰችም። ከዚያም እምነት የለሿ እኅቷ ይሁዳ እርሷ ያደረገችውን አየች። 8 ስለዚህ፣ ለእነዚህ ምክንያቶች ሁሉ ማመንዘሯን አየሁ። ከዳተኛይቱ እስራኤል! ፈትቼያት አባርሬያታለሁ፣ ደግሞም የፍችዋንም ወረቀት ሰጥቻታለሁ። አታላይ እኅትዋ ይሁዳ ግን አልፈራችም፣ እርስዋም ደግሞ ሄዳ ዝሙትን ፈጸመች። 9 በዝሙትዋ ምድሪቱ መርከሷ ምንም አልመሰላትም፣ ስለዚህ ከድንጋይና ከግንድ ጣዖታትን አደረጉ። 10 ከዚያም ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ፣ እምነት-የለሿ ይሁዳ በውሸት እንጂ በፍጹም ልብዋ ወደ እኔ አልተመለሰችም!"-ይላል እግዚአብሔር። 11 ከዚያም እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ፣ "ከእምነት-የለሿ ይሁዳ ይልቅ እምነት-የለሿ እስራኤል ጸደቀች! 12 ሂድና ይህን ቃል ለሰሜን ተናገር። 'እምነት የለሿ እስራኤል ሆይ፥ ተመለሽ! ይላል እግዚአብሔር፤ ለሁልጊዜ አልቈጣብሽምና። እኔ ታማኝ ስለሆንኩ - ለዘላለም እንደተቆጣሁ አልቆይም ይላል እግዚአብሔር። 13 በአምላክሽ በእግዚአብሔር ላይ እንዳመፅሽ፥ መንገድሽንም ከለመለመ ዛፍ ሁሉ በታች ለእንግዶች እንደ ዘረጋሽ፥ ቃሌንም እንዳልሰማሽ ኃጢአትሽን ዕወቂ ይላል እግዚአብሔር። 14 አግብቻችኋለሁና እምነት-የለሽ የሆናችሁት ሕዝቦች፣ ተመለሱ! ይላል እግዚአብሔር፤ አንዱንም ከአንዲት ከተማ ሁለቱንም ከአንድ ወገን እወስዳችኋለሁ! ወደ ጽዮንም አመጣችኋለሁ! 15 እንደ ልቤም የሆኑ እረኞችን እሰጣችኋለሁ፣ እነርሱም በዕውቀትና በማስተዋልም ይጠብቁአችኋል። 16 በእነዚያ ቀናት ትበዛላችሁ፣ በምድሪቱም ላይ ታፈራላችሁ ይላል እግዚአብሔር። "የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታቦት!" ብለው ከእንግዲህ ወዲህ አይናገሩም። ከእንግዲህ አያስቡትምና፣ ወይም አያስተውሉትምና ይህ ጉዳይ ከእንግዲህ በልባቸው አይመጣም። ከእንግዲህ ወዲህም ይህ ንግግር አይኖርም።' 17 በዚያም ዘመን ስለ ኢየሩሳሌም 'ይህች የእግዚአብሔር ዙፋን ናት' ብለው ይናገራሉ፣ ደግሞም ሌሎች አሕዛብ ሁሉ በእግዚአብሔር ስም ኢየሩሳሌም ላይ ይሰበሰባሉ። ከእንግዲህም ወዲህ በእልከኛ ልባቸው አይሄዱም። 18 በእነዚያም ቀናት፣ የይሁዳ ቤት ከእስራኤል ቤት ጋር ይሄዳል። በአንድም ሆነው ከሰሜን ምድር ርስት አድርጌ ለአባቶቻቸው ወደ ሰጠኋት ምድር ይመጣሉ። 19 እኔ ግን 'እንደ ወንድ ልጄ ላከብርሽና በሌሎች አሕዛብ ካለው ይልቅ የበለጠ ውብ የሆነውን አስደሳቹን ምድር ልሰጥሽ እንዴት ፈለግሁ!' ብዬ ነበር። "አባቴ" ብለሽ ትጠሪኛለሽ። እኔንም ከመከተል አትመለሽም' ብዬ ነበር። 20 ነገር ግን ለባሏ ታማኝ እንዳልሆነች ሴት፣ እንዲሁ የእስራኤል ቤት የሆናችሁት ከዳችሁኝ ይላል እግዚአብሔር። 21 "የእስራኤል ልጆች መንገዳቸውን ቀይረዋልና፣ አምላካቸውንም እግዚአብሔርን ረስተውኛልና በወና ኮረብቶች ላይ የልመናቸውና ልቅሶአቸው ድምፅ ተሰማ። 22 ከዳተኞች ሕዝቦች ሆይ ተመለሱ! ከዳተኛነታችሁንም እፈውሳለሁ!" እነሆ! አንተ አምላካችን እግዚአብሔር ነህና ወደ አንተ እንመጣለን። 23 የኮረብቶችና የብዙ ተራሮች ሐሰት ብቻ መጥቷል። በእርግጥም የእስራኤል መዳን በአምላካችን በእግዚአብሔር ነው። 24 ይሁን እንጂ አሳፋሪ ጣዖታት ለበጎቻቸውና ላሞቻቸው፣ ለወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸው አባቶቻችን የሠሩትን በልተውባቸዋል። 25 በእፍረት እንጋደም። በአምላካችን እግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ሠርተናልና እፍረታችን ይሸፍነን። ከትንሽነታችን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ እኛና አባቶቻችን በአምላካችን በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ሠርተናልና፣ የአምላካችንንም የእግዚአብሔርን ቃል አልሰማንምና!"

Jeremiah 3:1

አጠቃላይ መረጃ፦

እግዚአብሔር መናገሩን ቀጥሏል። ይህ በኤርምያስ 2:1 ላይ ለኤርምያስ ሊገልጥለት የጀመረው የትንቢቱ አካል ነው።

እርሱ እንደገና ወደ እርሷ ይመለሳልን?

እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው አንድ ወንድ ሚስቱን ሌላ ወንድ ካገባት በኋላ እንደገና ወደ እርሷ ፈጽሞ እንደማይመለስ ሕዝቡን ለማሳሰብ ነው። ይህ ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ሐሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እንደገና ወደ እርሷ አይመለስም።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሪቱ ፈጽማ አትረክስምን

እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ያገባ ወንድ ሚስቱ ሌላ ወንድ ካገባች በኋላ እንደገና ወደ ሚስቱ እንደማይመለስ ሕዝቡን ለማሳሰብ ነው ምክንያቱም ምድሪቱ በስርዓት እንደምትረክስ ስለሚያውቅ ነው። ይህ ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ሐሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ምድሪቱ ፈጽማ እንደረከሰች እርሱ ያውቃል።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ፈጽማ ረክሳለች

ይህ በእግዚአብሔር ዘንድ ፈጽሞ ተቀባይነት ለማጣት ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በእግዚአብሔር ዘንድ ፈጽሞ ተቀባይነት ማጣት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አንቺ ግን ከብዙ ወዳጆችሽ ጋር እንደ አመንዝራ ኖረሻል

እግዚአብሔር ብዙ ባዕድ አማልክትን የምታመልከውን እስራኤልን ከብዙ ወንዶች ጋር ወሲብ እንደፈጸመች ሴት አድርጎ ገልጿታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሴተኛ አዳሪ ሰውነቷን ባልዋ ላልሆኑ ለብዙ ወንዶች እንደምትሰጥ እንዲሁ ፍቅርሽን እና ታማኝነትሽን ለጣዖቶች ሰጥተሻል” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አሁን ወደ እኔ መመለስ ትፈልጊያለሽ?

እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው እስራኤላውያን ጣዖቶችን ስላመለኩ እግዚአብሔር እነርሱን እንደገና ወደ እርሱ እንዲመለሱ እንደማይፈቅድላቸው ለማሳየት ነው። ይህ ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ሐሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እንዲህም አድርጋችሁ ወደ እኔ ለመመለስ ትፈልጋላችሁ” ወይም “እንዲህም አድርጋችሁ እንደገና ወደ እኔ እንድትመለሱ እንደማፈቅድላችሁ ታስባላችሁ!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው

እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እስቲ ዓይኖችሽን አንሺ
እዚህ ላይ “ዓይኖች” የሚወክለው አንድ ነገር ማየትን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ወደላይ ተመልከቺ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

አስጸያፊ ወሲብ ያልፈጸምሽበት ስፍራ ወዴት አለ?
እግዚአብሔር እስራኤል ጣዖቶችን ስለማምለኳ ሲናገር ከብዙ የተለያዩ ወንዶች ጋር ወሲብ የፈጸመች ሴት እንደሆኑ አድርጎ አቅርቦአቸዋል። ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ለእስራኤላውያን በየትኛውም ስፍራ ጣዖቶችን እንዳመለኩ እንደሚያውቅ ለእነርሱ ለመንገር ነው። ይህ ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ሐሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አስጸያፊ ወሲብ ያልፈጸምሽበት ስፍራ ምንም የለም!” ወይም “ሴተኛ አዳሪ ከብዙ ወንዶች ጋር እንደምትተኛ፣ አንቺም በሁሉም ስፍራ ጣዖታቶችሽን አምልከሻል!” (ተለዋጭ ዘይቤ እና መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

አንቺ በመንገድ ላይ ተቀምጠሽ ወዳጆችሽን ትጠብቂያቸው ነበር
እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ሲናገር ሴተኛ አዳሪ በመንገድ ላይ ተቀምጣ በመንገድ የሚያልፈውን ወንድ ሁሉ እንደምትጠብቅ እንደዚሁ እነርሱም ጣዖትን ለማምለክ በጉጉት ይጠብቁ ነበር። አማራጭ ትርጉም፡- “ሴተኛ አዳሪ በመንገድ ላይ ተቀምጣ በመንገድ የሚያልፉትን ወዳጆችዋን እንደምትጠብቅ አንቺም ያወቅሻቸውን ማንኛውንም ጣዖት ለማምለክ በጉጉት ትጠብቂ ነበር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በምድረ በዳ እንደተቀመጠ ዘላን አረብ
እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ሲናገር ሴተኛ አዳሪ በምድረ በዳ ተቀምጦ የሚያልፈውን ማንኛውንም ሰው መዝረፍ እንዲችል እንደሚጠብቅ እንደዚሁ እነርሱም ጣዖትን ለማምለክ በጉጉት ይጠብቁ ነበር። አማራጭ ትርጉም፡- “ሊዘርፋቸው የሚችላቸውን ሰዎች ለመጠበቅ በምድረ በዳ እንደተቀመጠ ዘላን አረብ” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በምድረ በዳ እንደተቀመጠ ዘላን አረብ
አረብ ከአረብ አገር የሆነ ሰው ነው። አንዳንድ አረቦች በምድረ በደ እንደ ዘላን ስለሚኖሩ በአጠገባቸው የሚመጡትን ሰዎች ይዘርፋሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “በምድረ በዳ የሚኖር ዘላን” ወይም “በምድረ በዳ የሚኖር ዘራፊ” (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ እና የማይታወቁ ነገሮችን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 3:3

ስለዚህ ካፊያ ተከለከለ፥ የኋለኛውም ዝናብ ጠፋ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለዚህ ካፊያውን ከእናንተ ከለከልሁ” ወይም “ስለዚህ ዝናብ እንዳይዘንብ ከለከልሁ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 3:6

ከዳተኛይቱ እስራኤል ያደረገችውን አየህን?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው የኤርምያስን ትኩረት ወደ እስራኤል ከዳተኝነት ለመሳብ ነው። ይህ እንደ ትዕዛዝ ወይም እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከዳተኛይቱ እስራኤል ለእኔ እንዴት እንደሆነች ተመልከት።” ወይም “ከዳተኛይቱ እስራኤል ለእኔ እንዴት እንደሆነች አይተሃል።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ከፍ ወዳለው ኮረብታ ወጣች
ስለ እስራኤል ሕዝብ ሲነገር እስራኤል ሴት እንደሆነች ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእስራኤል ሕዝብ ወደ ኮረብታ ወጡ” ወይም “እነርሱ ወደ ኮረብታ ወጡ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ረዘመው ተራራ ሁሉ ከለመለመ ዛፍም ሁሉ በታች
የተራራ ጫፎች እና የለመለመ ዛፍ በታች ሰዎች ጣዖቶች የሚያመልኩባቸው የተለመዱ ስፍራዎች ናቸው። “ሁሉ” የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው ሕዝቡ በብዙ የተለያዩ ስፍራዎች ጣዖቶችን ያመልኩ እንደነበር ለማሳየት እንደ ጅምላ መግለጫ ነው። (ግነት/ግነታዊ ቋንቋ እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ሴተኛ አዳሪ አደረገች
እግዚአብሔር እስራኤል ጣዖቶችን ስለማምለኳ ሲናገር ከብዙ ወንዶች ጋር ወሲብ እንደምታደርግ ሴት አድርጎ ገልጾአታል። አማራጭ ትርጉም፡- (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከኃዲቷ እኅትዋም ይሁዳ አየች
እግዚአብሔር ስለ እስራአልና ይሁዳ እህቶች እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔን ያልታዘዙት የይሁዳ ሕዝብም አይተዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 3:8

አጠቃላይ መረጃ፡-
እግዚአብሔር ስለ እስራኤልና ይሁዳ ሲናገር ለእርሱ ያልታመኑ ሁለት እህትማማች ከዳተኛ ሚስቶች እንደነበሩ አድርጎ ገልጾአቸዋል።

የፍች ወረቀት
ይህ አንድ ወንድ ሚስቱን ለመፍታቱ ማረጋገጫ ለመስጠት የሚጽፈው ነገር ነው።

አመንዝራነቷ ለእርሷ ምንም አልመሰላትም
እዚህ ላይ አመንዝራነቷ “ምንም አልመሰላትም” የሚለው ሃሳብ የሚወክለው ይሁዳ ስለዚህ ጉዳይ ስሜት እንዳልሰጣት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለ አመንዝራነቷ ምንም አልመሰላትም” ወይም “ስለ አመንዝራነቷ ፈጽሞ አላፈረችም”

ምድሪቱን አረከሰች
እዚህ ላይ “አረከሰች” የሚለው የሚወክለው ምድሪቱን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዳይኖራት ማድረጓን ነው። ይህን ያደረጉት ጣዖቶችን ባመለኩበት ጊዜ በእግዚብሔር ላይ ኃጢአት በማድረጋቸው ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሷ ምድሬን አበላሸቻት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርስዋም ከድንጋይና ከግንድ ጋር አመነዘረች
እዚህ ላይ “ድንጋይ” እና “እንጨት” ጣዖቶችን ለመስራት የተጠቀሙበትን የድንጋይና የእንጨት ቁሳቁሶችን ይወክላል። የሕዝቡ ጣዖት አምልኮ ዝሙት እንደፈጸሙ ተደርጎ ተነግሯል። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ and ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ) ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 3:11

ከከሓዲዋ ይሁዳ ይልቅ ከዳተኛይቱ እስራኤል ጻድቅ ሆና ተገኘች
እስራኤልን ከይሁዳ ይልቅ “የበለጠ ጻድቅ” ሆና ተገኘች ብሎ በመጥራት ይሁዳ በጣም ኃጢአተኛ እንደሆነች እግዚአብሔር አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፡- “እስራኤል ለእኔ ታማኝ አልነበረችም ነገር ግን ከእስራኤልም የበለጠ ይሁዳ ኃጢአተኛ ሆናለች”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ሂድና እነዚህን ቃላት ለሰሜን ተናገር
እዚህ ላይ ሰሜን የሚለው ወደ ሰሜን ማለትም አሦር የተወሰዱትን የእስራኤልን ሕዝብ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሂድና እነዚህን ቃላት ለእስራኤል ሕዝብ ተናገር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 3:13

ኃጢአትሽን እወቂ
“ኃጢአት እንደሰራሽ እመኚ።” እግዚአብሔር ለእስራኤል ይናገር ነበር።

መንገድሽንም ከለመለመ ዛፍ ሁሉ በታች ለእንግዶች ዘረጋሽ!
“እንግዶች” የሚለው ቃል ባዕድ አማልክትን ያመለክታል። ባዕድ አማልክት ስለምታመልከው ስለ እስራኤል እግዚአብሔር ሲናገር እስራኤል ከእንግዶች ጋር ወሲብ እንደምትፈጽም ሴት አድርጎ ገልጾአታል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከለመለመ ዛፍ ሁሉ በታች
ሰዎች ጣዖቶችን በዛፍ ስር ያመልኩ ነበር። “ሁሉ” የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው የእስራኤል ሕዝብ በብዙ የተለያዩ ዛፎች ስር ብዙ አማልክትን እንዳመለኩ በጅምላ ለማሳየት ነው። (ግነት/ግነታዊ ቋንቋ እና ጅምላ ፍረጃ)

ድምጼንም አልሰማሽም
እዚህ ላይ “መስማት” የሚለው መታዘዝን ይወክላል፣ “ድምጼን” የሚለው ደግሞ እግዚአብሔር የተናገረውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔ የተናገርሁትን አልታዘዝሽም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ባላችሁ ነኝ
እስራኤል የእርሱ እንደሆነች እግዚአብሔር ሲናገር እርሱ የእስራኤል ባል እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሚስት የባልዋ እንደሆነች ሁሉ እንዲሁ እናንተ ደግሞ የእኔ ናችሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ እረኞችን እሰጣችኋለሁ ... ይጠብቁአችኋል
እዚህ ላይ እግዚአብሔር ስለ መሪዎች ሲናገር እነርሱ እረኞች እንደነበሩና የሚመሩት ሕዝብ ደግሞ በጎች እንደነበሩ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔ መሪዎችን እሰጣችኋለሁ ... ይመሯችኋል”` (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 3:16

እናንተ ትበዛላችሁ ፍሬም ታፈራላችሁ
“እናንተ” የሚለው ቃል የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል። “ፍሬ ታፈራላችሁ” የሚለው ሀረግ ብዙ ልጆች እንደሚኖራቸው የሚያሳይ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በቁጥር እጅግ በጣም ትበዛላችሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ነገር ከእንግዲህ ወዲህ ወደ ልባቸው አይመጣም
እዚህ ላይ “ወደ ልባቸው መምጣት” የሚለው ስለ ነገሩ ማሰብን ይወክለል። አማራጭ ትርጉም፦ “ለወደፊት ይህን ነገር አያስቡትም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 3:17

ይህ የእግዚአብሔር ዙፋን ነው
እዚህ ላይ “የእግዚአብሔር ዙፋን” እግዚአብሔር ተቀምጦ የሚመራበትን ስፍራ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ይህ እግዚአብሔር ከሚመራበት ስፍራ ነው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህም ወዲህ ክፉውን እልከኛ ልባቸውን ተከትለው አይሄዱም
እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ድርጊት ሲናገር ሕዝቡ በመንገድ እንደሚጓዙ አድርጎ ገልጾታል። እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል አእምሮአቸውን ወይም ፈቃዳቸውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ከእንግዲህም ወዲህ ሊያደርጉ የሚፈልጉትን ክፉ ነገር በእልከኝነት አያደርጉትም” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳ ቤት ከእስራኤል ቤት ጋር አብረው ይሄዳሉ
እዚህ ላይ “አብረው ይሄዳሉ” የሚለው አንድ እንደሚሆነ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “የይሁዳ ቤት ከእስራኤል ቤት ጋር አንድ ይሆናሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳ ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩት ቤተሰቦች ምትክ ስም ነው። እዚህ ላይ የይሁዳንና የቢንያምን ልጆች የሚያካትተውን የይሁዳን መንግስት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ይሁዳ” ወይም “የይሁዳ መንግስት” ወይም “የይሁዳ ሕዝብ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩት ቤተሰቦች ምትክ ስም ነው። እዚህ ላይ የእስራኤልን መንግስት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “እስራኤል” ወይም “የእስራኤል መንግስት” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ርስት አድርጌ ለአባቶቻችሁ የሰጠኋት ምድር
እግዚአብሔር ለዘላለም ይወርሷት ዘንድ ምድሪቱን ለእነርሱ ስለመስጠቱ ሲናገር የሚወርሱት ርስት እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ለዘላለም ለልጆቻቸው ይሆን ዘንድ ርስት አድርጌ ለአባቶቻችሁ የሰጠኋት ምድር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 3:19

እንደ እኔ
“እኔ” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ያመለክታል።

እንደ ወንዶች ልጆቼ ምንኛ በደስታ ልቁጠርሽ አልሁ ... ሕዝቤ
ይህ የእግዚአብሔርን ፍላጎት የሚገልጽ ድምፀተ-አንክሮ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እንደ ወንድ ልጄ ልንከባከባችሁ እጅግ በጣም ፈለግሁ ... ሕዝቤ” (ቃለ አጋኖ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንደ ወንድ ልጄ ልንከባከባችሁ ፈለግሁ
እግዚአብሔር እስራኤል ወንድ ልጁ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን ለባልዋ ታማኝ እንዳልሆነች ሚስት እንዲሁ አታለላችሁኝ
እግዚአብሔር እስራኤል ለእርሱ ታማኝ ስላለመሆኗ ሲናገር ታማኝ እንዳልሆነች ሚስት አድርጎ ገልጾአታል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ያማረቸው ርስት
እግዚአብሔር ለእስራኤል ሊሰጣት ስለሚፈልጋት ምድር ሲናር ርስት እንደሆነች አድርጎ ገልጾአታል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩት ቤተሰቦች ምትክ ስም ነው። እዚህ ላይ የእስራኤልን መንግስት ያመለክታል። ይህን በኤርምያስ 3:18 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “እስራኤል” ወይም “የእስራኤል መንግስት” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 3:21

ድምፅ ተሰማ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሕዝብ ጩኸት ሰሙ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ሕዝብ ልቅሶና ልመና
“የእስራኤል ሕዝብ በታላቅ ጩኸት ያለቅሱና ይለምኑ ነበር”

እግዚአብሔረር አምላካቸውን ረሱ
እዚህ ላይ “ረሱ” የሚለው መተውና ችላ ማለትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አምላካቸውን እግዚአብሔርን ችላ አሉት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ከዳተኛነታችሁን እፈውሳለሁ!
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) “ከዳተኝነታችሁን እፈውሳለሁ” እግዚአብሔር ለእግዚአብሔር አለመታመኗን እንድታቆም ማድረጉን የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ለእኔ አለመታመንሽን እንድታቆሚ አደርጋለሁ” ወይም 2) “ከዳተኝነታችሁን እፈውሳለሁ” ስለ አለመታመኗ ይቅር እንደሚላት የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ለእኔ አለመታመንሽን ይቅር እላለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አለመታመንሽን እፈውሳለሁ
“ለእኔ አለመታመንሽን እንድታቆሚ እፈውስሻለሁ”

እነሆ! ወደ አንተ እንመጣለን
ይህ የእስራኤል ሕዝብ የሚናገረው ነገር እንደሆነ የሚታሰብ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ሕዝቡ እንዲህ ብለው ይመልሳሉ፣ ‘እነሆ! ወደ አንተ እንመጣለን’ ወይም “ እንዲህ ትላላችሁ፣ ‘እነሆ! ወደ አንተ እንመጣለን’” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ
x

Jeremiah 3:23

በእርግጥ መታለል ከኮረብቶች ይመጣል
እዚህ ላይ “ኮረብቶች” የሚለው ሕዝቡ በኮረብቶች ላይ የሚያደርጉትን የሐሰተኛ አማልክት አምልኮ ይወክላል። አሁን ሕዝቡ እነዚህ ሐሰተኛ አማልክት እነርሱን ሊመሩአቸውና ሊረዱአቸው እንደማይችሉ አውቀዋል። አማራጭ ትርጉም፦ “እኛ በኮረብቶች ላይ የምናመልካቸው ሐሰተኛ አማልክት ሊመሩን አይችሉም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ከተራሮች የሚመጣ ግራ የሚያጋባ ጩኸት
ሰዎች ሐሰተኛ አማልክትን በኮረብቶችና በተራሮች ላይ ሲያመልኩ ብዙ ጩኸት ያሰማሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “እኛ ሐሰተኛ አማልክትን ስናመልክ በተራሮች ላይ ግራ የሚያጋባ ጩኸት እናሰማለን ነገር ግን እነርሱ እኛን አይረዱንም” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመለክቱ)

በእውነት የእስራኤል መዳን በአምላካችን በእግዚአብሔር ዘንድ ነው
“በእውነት የእስራኤል አዳኝ አምላካችን እግዚአብሔር ነው” ወይም “በእውነት እስራኤልን ሊያድን የሚችል ብቸኛው አምላካችን እግዚአብሔር ነው”

ነውረኛ ጣዖቶች አባቶቻችን የሰሩትን ሁሉ በሉት
ይህ የእስራኤል ሕዝብ ያላቸውን ንብረት ሁሉ ለጣዖቶች መስዋዕት አድርገው ከማቅረባቸው የተነሳ ብዙ ሀብታቸውን ማጣታቸውን የሚወክል ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በጎቻቸውንና ከብቶቻቸውን፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን
ይህ የእስራኤል ሕዝብ ለጣዖቶች እያረዱ መስዋዕት አድርገው ያቀረቡት የእንስሳትና የሰዎች ዝርዝር ነው።

እንግዲህ እፍረታችንን ተከናበን እንተኛ፤ ውርደታችንም ይሸፍነን
እነዚህ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ይጋራሉ፣ ደግሞም ሕዝቡ ነውረኛ ባህርያቸውን ሙሉ በሙሉ እንደተገነዘቡ አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ሙሉ በሙሉ ራሳችንን እናዋርድ” (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

ውርደታችንም ይሸፍነን
ውርደታቸውን ሙሉ በሙሉ መገንዘባቸው ውርደት እንደ ብርድ ልብስ ወይም ጨርቅ እነርሱን እንደሸፈናቸው ተደርጎ ተነግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከልጅነታችን ጊዜ ጀምሮ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) “ከልጅነታችን ጊዜ ጀምሮ” የሚለው እያንዳንዱ ሰው ወጣት የነበረበትን ጊዜ ያመለክታል። ወይም 2) “ከልጅነታችን ጊዜ ጀምሮ” እስራኤል መጀመርያ ሕዝብ የሆነችበትን ጊዜ የሚያመለክት ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “መጀመርያ ሕዝብ ከሆንንበት ጊዜ ጀምሮ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የአምላካችንንም የእግዚአብሔርን ድምፅ አልሰማንም
እዚህ ላይ “መስማት” መታዘዝን ይወክላል፣ “የእግዚአብሔር ድምፅ” ደግሞ እግዚአብሔር የተናገረውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አምላካችን እግዚአብሔር የተናገረውን አልታዘዝንም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 እስራኤል ሆይ፣ ብትመለሺ፣ የምትመለሺው ወደ እኔ ይሁን፣ ይላል እግዚአብሔር፤ ከፊቴ ርኩሰትሽን ብታስወግጂ፣ በድጋሚም ከእኔ ባትርቂ **2** 'ሕያው እግዚአብሔርን!' ብለሽ በእውነትና በፍትሕ፣ በጽድቅም ብትምይ፥ አሕዛብ በረከቴን ይጠይቃሉ፣ እኔንም ያመሰግኑኛል። **3** ለይሁዳና ለኢየሩሳሌም ሰዎች እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ 'ጥጋቱን እርሻ እረሱ፣ በእሾህም ላይ አትዝሩ። **4** እናንተም የይሁዳ ሰዎች፣ የኢየሩሳሌምም ነዋሪዎች፣ ስለ ሥራችሁ ክፋት ቊጣዬ እንደ እሳት እንዳይወጣ የሚያጠፋውም ሳይኖር እንዳያቃጥል፥ ለእግዚአብሔር ተገረዙ፥ የልባችሁንም ሸለፈት አስወግዱ። **5** ይሁዳ ውስጥ ተናገሩ፣ በኢየሩሳሌምም ላይ አውሩ። "በአገሪቱ ላይ መለከት ንፉ" በሉ፤ ጮኻችሁም "ሁላችሁ ተሰብሰቡ። ወደ ተመሸጉትም ከተሞች እንግባ" በሉ። **6** ከሰሜን ክፉ ነገርንና ጽኑ ጥፋትን አመጣለሁና ወደ ጽዮን ሰንደቅ ዓላማን አንሡ፤ ሸሹ፥ አትዘግዩ። **7** አንበሳ ከጥቅጥቅ ዱር እየወጣ ነው፣ አሕዛብንም የሚያጠፋ እየወጣ ነው። ምድርሽን ለማሸበር፣ ከተሞችሽም ሰው የሌለባቸው ፍርስራሾች ለማድረግ ከስፍራው ወጥቶአል። **8** ከዚህ የተነሣ፣ ራስሽን በማቅ ልብስ ሸፍኚ፣ ሙሾ አውጪ፣ አልቅሺም። የእግዚአብሔር ጽኑ ቊጣ ከእኛ ዘንድ አልተመለሰምና። **9** በዚያም ቀን፥ ይላል እግዚአብሔር፥ የንጉሡና የመኳንንቱ ልብ ይሞታል። ካህናቱም ይደነቃሉ ነቢያቱም ይደነግጣሉ። **10** እኔም "ጌታ እግዚአብሔር ሆይ! ወዮ፥ 'ሰላም ይሆንላችኋል' በማለት ይህን ሕዝብና ኢየሩሳሌምን በእርግጥም ፈጽመህ አታልለሃል። ሆኖም 'ሰይፉ እስከ ነፍስ ድረስ ያጠቃል።" **11** በዚያ ጊዜ ለዚህ ሕዝብና ለኢየሩሳሌም፣"የሚያቃጥል ነፈሳስ በምድረበዳ ካሉት ወና ኮረብቶች ወደ ሕዝቤ ሴት ልጅ ይመጣል። እነርሱን አያበጥርም ወይም አያጠራም። **12** ከዚያም ይልቅ እጅግ ብርቱ የሆነ ነፋስ በትእዛዜ ይመጣል፣ ደግሞም እኔ ፍርዴን በእነርሱ ላይ እናገራለሁ። **13** ተመልከቱ እንደ ደመና ያጠቃል፣ ሠረገሎቹም እንደ ዐውሎ ነፋስ ናቸው። ፈረሶቹም ከንስር ይልቅ ፈጣኖች ናቸው። ጠፍተናልና ወየልን! **14** ኢየሩሳሌም ሆይ፣ ትድኚ ዘንድ ልብሽን ከክፉ ነገር እጠቢ። እንዴት ኃጢአት እንደምትሠሪ ክፉ አሳብ የሚኖርብሽ እስከ መቼ ድረስ ነው? **15** የተናጋሪ ድምፅ ከዳን ይናገራል። የሚመጣውም ጥፋት ከኤፍሬምም ተራሮች ይሰማል። **16** አሕዛብ ይህንን እንዲያስቡ አድርጉ፦ ተመልከቱ፣ ወራሪዎች በይሁዳ ከተሞች ላይ የጦርነት ጩኸት ለመጮኽ ከሩቅ ምድር እየመጡ ነው ብላችሁ አውሩ። **17** በእኔ ላይ ዓመፀኛ ሆናለችና የለማ እርሻን ከብበው እንደሚጠብቁ ይሆናሉ ይላል እግዚአብሔር። **18** ባሕርይሽና ሥራሽ ይህን አድርጎብሻል። ይህ ቅጣትሽ ይሆናል። እንዴት አስጨናቂ ይሆናል! የገዛ ልብሽም ይመታል። **19** ልቤ! ልቤ! በልቤ ተጨንቄያለሁ። ልቤ በውስጤ ታውኮብኛል። የመለከትን ድምፅና የጦርነት ማንቂያን ሰምቻለሁና ዝም ልል አልችልም። **20** በጥፋት ላይ ጥፋት ተጠርቶአል፣ መላዋ ምድርም ተበዝብዛለች። በድንገትም ድንኳኔንና መጋረጃዬን አጠፉ። **21** መስፈርቱን የምመለከተው እስከመቼ ነው? የመለከቱንስ ድምፅ እሰማ ይሆን? **22** ሕዝቤ ተሞኝተዋልና አላወቁኝም። ሰነፍ ሕዝብ ናቸው፣ ማስተዋልም የላቸውም። ክፉ ነገርን ለማድረግ ብልሃተኞች ናቸው፣ በጎ ነገርን ማድረግ ግን አያውቁም። **23** ምድሪቱን አየሁ፣ እነሆም፥ ባዶ ነበረች አንዳችም አልነበረባትም፤ ለሰማያትም ብርሃንም አልነበረባቸውም። **24** ተራሮችን አየሁ። እነሆም፣ ይንቀጠቀጡ ነበር፣ ኮረብቶችም ሁሉ ተናወጡ። **25** አየሁ። እነሆ፣ ሰው አልነበረም፣ የሰማይም ወፎች ሁሉ ሸሽተው ነበር። **26** ተመለከትሁ። እነሆ፣ ፍሬያማ እርሻ ምድረ በዳ ሆነች፣ ከተሞችም ሁሉ ከእግዚአብሔር ፊት ከጽኑ ቊጣው የተነሣ ፈርሰው ነበር። **27** እግዚአብሔርም እንዲህ ይላል "ምድር ሁሉ ትጠፋለች፣ ነገር ግን ፈጽሜ አላጠፋቸውም። **28** ስለዚህ ምድር ታለቅሳለች፣ ከላይ ያለው ሰማይ ይጠጨልማል። ተናግሬአለሁና፥ አስቤአለሁም፤ አልጸጸትም ከመፈጸምም አልመለስም። **29** ከፈረሰኞችና ከቀስተኞች ጫጫታ የተነሣ እያንዳንዱ ከተማ ሁሉ ይሸሻሉ፤ ወደ ጫካም ይገባሉ። እያንዳንዱ ከተማ በቋጥኝ ላይም ይወጣሉ። ከተሞቹ ይተዋሉ፣ የሚኖርባቸው ሰው አይኖርምና። **30** አንቺም ባድማ ሆንሽ፥ ምን ታደርጊአለሽ? ቀይ በለበስሽ ጊዜ፥ በወርቅ አንባርም አጌጥሽ፣ ዓይንሽንም ተኳልሽ፣ የሚመኙሽ ወንዶች ገፉሽ። ይልቊን፣ ነፍስሽን ይሹአታል። **31** ስለዚህ የምጥ፣ የበኩር ልጅ እንደሚወለድበት ያለ የጭንቅ ድምጽ፣ የጽዮን ሴት ልጅን ድምጽ ሰምቻለሁ። ለመተንፈስ ትታገላለች። እጆቿንም ትዘረጋለች፣ ከገዳዮቹ የተነሣ ነፍሴ ዝላለችና 'ወዮልኝ!' አለች።

Jeremiah 4:1

እስራኤል ሆይ፣ ብትመለስ
እዚህ ላይ “መመለስ” የሚያመልኩትን ለመለወጥ ተለዋጭ ዜቤ ነው፣ እስራኤል ደግሞ የእስራኤልን ሕዝም የሚወክል ምትክ ስም ነው። ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ይልቅ ጣዖቶችን ያመልክ ነበር። አማራጭ ትርጉም፦ “የእስራኤል ሕዝብ ሆይ፣ የምትመለስ ከሆነ” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ ሆይ፣ የምታመልከውን የምትለውጥ ከሆነ” (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

በመመለስህ ለእኔ ትሆናለህ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) ይህ ወደ ማን መመለስ እንዳለባቸው አጽንዖት የሚሰጥ ትዕዛዝ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ወደ እኔ ተመለስ” ወይም “እኔን አምልክ” 2) ይህ ሁኔታዎችን የሚያብራራው የመጀመርያው ሀረግ ድጋሚ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ወደ እኔ የምትመለስ ከሆነ” ወይም “እንደገና እኔን ማምለክ የምትጀምር ከሆነ” (ምትክ ስም እና ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

አስጸያፊ ነገሮችህን ከፊቴ ብታስወግድ
እዚህ ላይ “አስጸያፊ ነገሮች” የሚለው እግዚአብሔር የሚጠላቸው ጣዖቶችን የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “አስጸያፊ ጣዖቶችህን ከእኔ ፊት ብታስወግድ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ከእኔ ርቀህ መቅበዝበዝ ብትተው
እዚህ ላይ “መቅበዝበዝ” የሚለው ታማኝ ላለመሆን ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ለእኔ ታማኝ ሆነህ ብትቀጥል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሕያው እግዚአብሔር
“እግዚአብሔር በእርግጠኝነት ሕያው እንደሆነ ሁሉ።” ሕዝቡ ይህን መግለጫ የሚጠቀሙት ቀጥለው የሚናገሩት ነገር በእርግጠኝነት እውነት እንደሆነ ለማሳየት ነው። ይህ የማይናወጥ ቃል ኪዳን የማድረግ መንገድ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔ በማይናወጥ መልኩ እምላለሁ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

አሕዛብ በእርሱ ይባረካሉ
እዚህ ላይ “አሕዛብ” ለሌሎች መንግስታት ሕዝቦች ምትክ ስም ነው። “እርሱ” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ያመለክታል። የሚናገረው እግዚአብሔር ስለሆነ “እኔ” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የሌሎች

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መንግስታት ሕዝቦች በእኔ ይባረካሉ” (ምትክ ስም እና አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

አሕዛብ በእርሱ ይባረካሉ
እዚህ ላይ “በእርሱ ይባረካሉ” የሚለው እንዲባርካቸው እግዚአብሔርን ለመጠየቃቸው ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የሌሎች መንግስታት ሕዝቦች እንዲባርካቸው ይጠይቁታል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ ይከበራሉ
“እርሱ” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ያመለክታል። የሚናገረው እግዚአብሔር ስለሆነ “እርሱ” የሚለው “እኔ” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በእኔ ይመካሉ” ወይም “እኔን ያመሰግኑኛል” (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ዕዳሪውን መሬታችሁን እረሱ በእሾህም ላይ አትዝሩ
እግዚአብሔር ዘር ለመዝራት መሬቱን እንደሚያዘጋጅ ገበሬ አእንደዚሁ ሕይወታቸውን እንዲያዘጋጁ ለሕዝቡ ይነግራቸዋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 4:4

ለእግዚአብሔር ራሳችሁን ግረዙ፥ የልባችሁንም ሸለፈት አስወግዱ
እግዚአብሔር ሕዝቡ ለእርሱ ያለውን ታማኝነት በአካል በሚገለጥ የቃል ኪዳን ምልክት መግለጫ ቋንቋ ይገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ “ራሳችሁን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር አቅርቡ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ራሳችሁን ግረዙ ... የልባችሁንም ሸለፈት አስወግዱ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ሁለተቱም አንድ ላይ ትዕዛዙን አጽንዖት ይሰጡታል። (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

ቍጣዬ እንደ እሳት እንዳይወጣ የሚያጠፋውም ሳይኖር እንዳያቃጥል
እግዚአብሔር ከመጠን በላይ ስለመቆጣቱ ሲናገር ቁጣው እሳት እንደሆነ አድርጎ ይገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ “ቍጣዬ እንደ እሳት ይነድዳል ማንም ሊያጠፋው አይችልም” ወይም “እኔ ከመጠን በላይ እቆጣለሁ እኔን ማቆም የሚችል ማንም የለም” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቁጣ
“ታላቅ ንዴት”

በይሁዳ ዘንድ ተናገሩ በኢየሩሳሌምም ላይ አውሩ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ሁለቱም በአንድ ላይ ትዕዘዙን አጽንዖት ይሰጡታል። (ትይዩነት/ተመሳሳይነትየሚለውን ይመልከቱ)

በኢየሩሳሌምም ላይ አውሩ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎች እንዲሰሙት አድርጉ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በአገሪቱ ላይ መለከት ንፉ
መለከት ሰዎችን ጠላቶቻቸው ሊያጠቁአቸው እየመጡ እንደሆነ ያስጠነቅቃል።

ወደ ተመሸጉት ከተሞች እንሂድ
እነርሱ ከጠላቶቻቸው ለመዳን ወደ ተመሸጉት ከተሞች ይሄዳሉ።

ክፉ ነገር ... ታላቅ ጥፋት
እነዚህ ሁለት ቃላት በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። “ታላቅ ጥፋት” የሚለው ሀረግ “ክፉው ነገር” ምን እንደሚሆን ያብራራዋል። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ከሰሜን ክፉ ነገርንና ጽኑ ጥፋትን አመጣለሁና
ይህ እግዚአብሔር በይሁዳ ላይ ክፉ ነገርንና ጽኑ ጥፋትን ለማምጣት ከሰሜን ጦር ሰራዊት እንደሚልክ የሚያሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔ እናንተን እንዲያጠፋ ከሰሜን ጦር ሰራዊት እንዲመጣ አደርጋለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከሰሜን
ይህ ከሰሜን የሚመጣውን የጠላት ጦር ሰራዊት የሚወክል ነው። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 4:7

አንበሳ እየመጣ ነው
እግዚአብሔር በጣም ኃያል ስለሆነ ጦር ሰራዊት ሲናገር በጣም ኃይለኛ ተናካሽ አንበሳ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ኃይለኛና ምህረት አልባ ጦር ሰራዊት እየቀረበ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጭፍቅ ዱር
ተጠጋግተው አብረው ያደጉ የቁጥቋጦ ክምችት

ሕዝብን የሚያጠፋ አንድ ሰው
እዚህ ላይ “አንድ ሰው” የሚለው ንጉስና ሰራዊቱን የሚወክል ነው። (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወጥቶአል
ይህ ፈሊጥ መንቀሳቀስ መጀመሩን የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “መዝመት እየጀመረ ነው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ምድርሽን ባድማ የሚያደርግ
ይህ ሰዎች ምድሪቱን ሲመለከቱ ድንጋጤ የሚፈጥርባቸው ዓይነት ጥፋት የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ምድርሽን ለማጥፋት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ማቅ ልበሱ
ሰዎች በጣም ኃዘንተኞች እንደሆኑ ለመግለጽ ማቅ ይለብሳሉ። በዚህ ዓውድ ሕዝቡ ስለሰሩአቸው ክፉ ስራዎች በጣም ማዘናቸውን ለማሳየት ሊሆን ይችላ። አማራጭ ትርጉም፦ “ማዘናችሁን የሚያሳዩ ልብሶችን ልበሱ” (ምሳሌያዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ዋይ በሉ
በከፍተኛ ጩኸት ማልቀስ

የእግዚአብሔር ጽኑ ቍጣ ከእኛ ዘንድ አልተመለሰምና
“ቁጣ” ከሰዎች ሊመለስ የሚችል ሕይወት ያለው ነገር እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። እዚህ ላይ “የእግዚአብሔር ቍጣ ከእኛ ዘንድ አልተመለሰም” የሚለው እግዚአብሔር አሁንም በሕዝቡ ላይ ተቆጥቷል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር አሁንም በሕዝቡ ላይ በጣም ተቆጥቷልና” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 4:9

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የንጉሡና የመኳንንቱ ልብ ይሞታል
እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ወኔን ይወክላል። በተጨማሪ “ልብ ይሞታል” የሚለው ወኔ ማጣትንና መፍራትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ንጉሡና መኳንንቱ ወኔአቸው ይጠፋል” ወይም “ንጉሡና መኳንንቱ ይፈራሉ” (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰይፍ በሕይወታቸው ላይ ተቃጥቷል
እዚህ ላይ ሕዝቡን ለመግደል ስለተዘጋጁት ጠላቶች ሲናገር ሰይፉ በሰዎች ላይ እንደሚሰነዝር ሰው ተደርጎ ተገልጾአል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላቶቻችን በሰይፋቸው እኛን ለማረድ ተዘጋጅተዋል” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 4:11

እንዲህ ተብሎ ይነገራል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ይናራል” (ገቢር/አድርጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የሚያቃጥል ነፋስ በምድረ በዳ ካሉ ከወናዎች ኮረብቶች ... ጽኑ የሆነ ነፋስ
እዚህ ላይ “የሚያቃጥል ነፋስ” የሚለው በጣም አጥፊና ምህረት አልባ ጠላትን ይወክላል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይመጣል
“ይጓዛል” ወይም “ይፈጥናል”

የሕዝቤ ሴት ልጅ
እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንደ ሴት ልጅ አድርጎ በመናገር ፍቅሩን ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሕዝቤ፣ ለእኔ እንደ ሴት ልጅ የሆኑት” ወይም “ውድ ሕዝቤ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አያበጥራቸውም ወይም አያጠራቸውም
“ማበጠር” እና “ማጥራት” የሚሉት ቃላት ጠቃሚ ያልሆነውን ሸፋን ከእህል ማራገፍን ያመለክታል። ለዚህ የሚያስፈልገው ቀላል ነፋስ ብቻ ነበር። አማራጭ ትርጉም፡- “ገለባውን ከእህል ለመለየት የሚያስፈልገው ቀላል ነፋስ አይሆንም” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ and ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በእኔ ትዕዛዝ ይመጣል
“እኔ እንዲመጣ ባዘዝሁት ጊዜ ይመጣል”

በእኔ ትዕዛዝ
ይህ አገላለጽ በዕብራይስጡ በአንዳንድ የቅርብ ጊዜ ትርጉሞች “ለእኔ” ወይም “በእኔ” ተብሎ ተተርጉሟል።

ፍርዴን በእነርሱ ላይ እናገራለሁ
“ቅጣታቸውን አውጃለሁ”

Jeremiah 4:13

ተመልከቱ፣ እርሱ እንደ ደመና ያጠቃቸዋል
“እርሱ” የሚለው ቃል ጠላት የሆነውን ንጉስና ጦር ሰራዊቱን ያመለክታል። የጦር ሰራዊቱ በቁጥር ብዙ መሆን እጅግ በጣም ከባድ የደመና አውሎ ነፋስ እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ተመልከቱ፣ እንደ ታላቅ ደመና የሆኑ ብዙ ጦር ሰራዊቶች ለማጥቃት እየተሰባሰቡ ነው” ወይም “ብዙ ጦር ሰራዊቶች ለማጥቃት እየተሰባሰቡ ነው” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰረገሎቹም እንደ ዐውሎ ነፋስ ናቸው
የጠላት ሰረገሎች እንደ ዐውሎ ነፋስ እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል። ዐውሎ ነፋስ ታላቅ ድምጽ ያላቸው፣ አጥፊና ፈጣን እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ሊሆኑ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “የሚመጡት የሰረገሎቻቸው ጩኸት እንደ አጥፊ ዐውሎ ነፋስ ነው” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእኛ ወየልን
“ይህ አሰደንጋጭ ነው”

መጥፋታችን ነውና
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ ያጠፉናልና” ወይም “እነርሱ ያወድሙናልና” (ገቢር/አድርጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ኢየሩሳሌም ሆይ፥ ልብሽን ከክፉ ነገር እጠቢ
ይህ በኢየሩሳሌም ለሚኖሩ ሰዎች ንስሃ እንዲገቡ ማስጠንቀቂያ ነው። “ልብሽን እጠቢ” የሚለው ክፋትን ከሕይወታቸው ለማስወገድ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የእስራኤል ሕዝብ ሆይ፣ ክፉ መሆን አቁሙ” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ ሆይ፣ በክፋት መኖር አቁሙ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ኃጢአት እንዴት እንደምትሰሪ ጥልቅ አሳብ የሚኖርብሽ እስከ መቼ ድረስ ነው?
ይህ ጥያቄ ጥቅም ላይ የዋለው ሁልጊዜ እንዴት ኃጢአት መስራት እንዳለባቸው ስለማቀዳቸው ሕዝቡን ለመገሰጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የእናንተ ጥልቅ ሃሳብ እንዴት ኃጢአት መስራት እንዳለባችሁ ነው” ወይም “ሁልጊዜ ኃጢአት እንዴት መስራት እንዳለባችሁ ታስባላችሁ!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የተናጋሪ ድምፅ ከዳን ዘንድ ዜና ያመጣል
እዚህ ላይ “ድምፅ” መልእክተኛን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “መልእክተኛ ይመጣና በዳን ምን እየሆነ እንዳለ ይነግራችኋል” (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዳን
ይህ የሚያመለክተው ምናልባት ምዕራባዊ ኢየሩሳሌም የሆነውን የዳን አካባቢ ነው።

ከኤፍሬም ተራሮች የሚመጣው ጥፋት ይሰማል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በኤፍሬም ላይ ስለሚመጣው ጥፋት ሰዎች ይሰማሉ” (ገቢር/አድርጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዳን ... የኤፍሬም ተራሮች
ጠላቶች ወደ ዳንና ኤፍሬም እንደደረሱ በመስማት በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎች ጠላቶች ወደ እነርሱ እየቀረቡ እንደሆነ ይገነዘባሉ።

Jeremiah 4:16

ጠባቂዎች ይመጣሉ
“ጠባቂዎች” በከተማው የሚኖሩ ሰዎች የምግብና የውኃ አቅርቦት እንዳያገኙ ለመጠበቅ ከተማይቱን የሚከብቡ ወታደሮች ናቸው።

እነርሱ በዙሪያዋ ከብበው እንደ እርሻ ጠባቂዎች ይሆኑባታል
ሰዎች ወደ ውስጥ እንዳይገቡና ወደ ውጭ እንዳይወጡ ከተማን በጥንቃቄ መጠበቅ ሰዎች ከእርሻ እንዳይሰርቁ እርሻን በጥንቃቄ እንደሚጠብቁ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “የተመቻቸ እርሻን በጥንቃቄ እንደሚጠብቁ ጠባቂዎኢየሩሳሌምን በጥንቃቄ ይጠብቁአታል” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሷን ዙርያዋን ሁሉ ከብበው
“እርሷ” የሚለው ቃል ኤሩሳሌምን ያመለክታል። ኢየሩሳሌም ብዙ ጊዜ እንደ ሴት እንደሆነች ተደርጋ ትነገራለች። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እርሷ በእኔ ላይ ዓመፀኛ ነበረች
“እርሷ” የሚለው ቃል ኢየሩሳሌምን ያመለክታል፣ የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ደግሞ ይወክላል። “እኔ” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “የኢየሩሳሌም ሕዝብ በእኔ ላይ አመፀኞች ነበሩ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

የገዛ ጠባይሽና ሥራሽ እነዚህን ነገሮች አድርጎብሻል
እዚህ ላይ “ጠባይ” እና “ስራ” ነገሮችን ማድረግ የሚችሉ ሰዎች እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል። እነዚህ ረቂቅ ስሞች “የሰራችሁት ስራ” በሚለው ሀረግ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህ ነገሮች በእናንተ ላይ የደረሱት በሰራችሁት ስራ ምክንያት ነው” (ሰውኛ ዘይቤ እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ልብሽን ይሰብራል
እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል ምናልባት ስሜትን ያመለክታል፣ “ልብሽን የይብራል” የሚለው ሀረግ ደግሞ ምናልባት በከፋ መልኩ እንዲሰቃዩ ማድረጉን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ልብሽን በጥልቀት እንደሚሰብር ይሆንብሻል” ወይም “በጣም አስደንጋጭ በሆነ ጭንቀት እንድትሰቃዪ ያደርግሻል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 4:19

ልቤ! ልቤ!
እዚህ ላይ “ልብ” እንደ ሀዘንና ፍርሃት የመሳሰሉ የሚያሰቃዩ ስሜቶች ይወክላል። ሀረጎቹ የተደጋገሙት የስቃዩ ጥልቀትን ለመግለጽ ነው። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ በልቤ ጭንቀት አለብኝ
ተናጋሪው ከባድ አካላዊ ሕመም የሚያመጣ ከባድ ስሜታዊ ሕመም ተሰምቶታል።

በውስጤ ልቤ ታውኮብኛል
“በውስጤ ልቤ ከመጠን በላይ ይመታል።” እዚህ ላይ “ልብ” የሰውነት ክፍልን ያመለክታል። ልቤ የሚታወከው ከመደበኛው በላይ በጣም ጠንካራና ፈጣን በሆነ መልኩ ስለሚመታ ነው።

ሁከት
ግራ መጋባት፣ አመጽ፣ ወይም ምስቅልቅል የሆነ ነገር የተሞላበት፤ ያልተረጋጋ ወይም ያልሰከነ

በድንገትም ድንኳኔ ጠፉ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላቶች በድንገት ድንኳኔን አፈረሱት” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በቅጽበት ዓይን መጋረጃዎቼ ጠፉ
“ጠፉ” የሚለው ቃል ከበፊቱ ሀረግ በሚገባ መረዳት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “መጋረጃዎቼ በቅጽበት ዓይን ጠፉ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

መጋረጃዎች
መጋረጃዎች በድንኳን ውስጥ የተለያዩ ክፍሎችን ለመከፋፈል የሚሰቀሉ ጨርቆች ናቸው።

Jeremiah 4:21

እስከ መቼ የጦርነት ዓርማ እመለከታለሁ? እስከ መቼስ የመለከቱን ድምፅ እሰማለሁ?
ኤርምያስ እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመው ለዚህ ያህል ረጅም ጊዜ የጦርነት ዓርማ ስለመመልከቱና የመለከቱን ድምፅ ስለመስማቱ ያለውን ጭንቀት ለማሳየት ነው። ጦርነቱ በፍጥነት ቢያልቅ ይመኛል። ይህ በግነት መልክ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጦርነቱ ቢያልቅና የጦርነት ዓርማው ቢወርድ እና የጦር ሰራዊቱ የመለከት ድምጽ ቢቆም እንዴት እመኝ ነበር” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የጦርነት ዓርማ
“የጦጦነት ሰንደቅ ዓላማ”

የመለከት ድምፅ
አንድ ሰው ለጦርነት ጥሪ ለማድረግ እንደ ምልክት መለከት ይነፋል።

ሕዝቤ ሰንፈዋልና ... በጎ ነገርን ማድረግ አያውቁም
እግዚአብሔር እንዲህ እንደተናገረ በግልጽ ሊብራራ ይችላል። ይህ ምናልባት እግዚአብሔር ጦርነቱ አሁንም ለምን እየተካሄደ እንደሆነ ለኤርምያስ የሰጠው ምላሽ ሳይሆን አይቀርም። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር እንዲህ ሲል መለሰ፣ ‘በሕዝቤ ሞኝነት ምክንያት ነው ... በጎ ነገርን ማድረግ አያውቁም።’” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሞኝ ሕዝብ
“ደደብ ሕዝብ”

Jeremiah 4:23

አጠቃላይ መረጃ፡-
ኤርምያስ በኋላ ስለሚሆኑት ነገሮች እግዚአብሔር የሰጠውን ራዕይ ያብራራል።

እነሆ
እዚህ ላይ “እነሆ” የሚለው ቃል ተከታዩን አስደናቂ መረጃ ልብ እንድንል ያነቃናል።

ቅርጽ የለሽና ባዶ
ራእዩ ሕዝቡ በሙሉ ምርኮኛ ሆነው ከተወሰዱ በኋላ የእስራኤል ምድር ምን እንደምትመስል የሚያሳይ ትንቢት ነው።

ለሰማያት ብርሃን አልነበራቸውም
“በሰማይ ላይ ብርሃን አልነበረም”

ከተሞች በሙሉ ፈራርሰዋል
“ከተሞች በሙሉ ጠፍተዋል” ወይም “ከተሞች በሙሉ የፍርስራሽ ክምር ሆነዋል”

በእግዚአብሔር ፊት፣ በእርሱ ብርቱ ቁጣ ፊት
ይህ እነዚህ ነገሮች በሙሉ የተፈጸሙት እግዚአብሔር በይሁዳ ሕዝብ ላይ በመቆጣቱ ምክንያት እንደሆነ ያመለክታል።

Jeremiah 4:27

ምድር ሁሉ ባድማ ትሆናለች
“የይሁዳ ምድር ሁሉ ባድማ ትሆናለች” ወይም “የይሁዳ ምድር ሁሉ ትፈራርሳለች”

ምድሪቱ ታለቅሳለች፥ በላይም ሰማይ ይጨልማል
ምድሪቱ ራሷ ታላቅ ሃዘን እየገለጸች ነው ብሎ በመናገር ኤርምያስ የእግዚአብሔርን ፍርድ አጽንዖት ይሰጣል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወደ ኋላ አልልም
“ሃሳቤን አልለውጥም”

እነዚህን ከማድረግ አልመለስም
እዚህ ላይ “አልመለስም” የሚለው እሰራለሁ ብሎ የተናገረውን ነገር ላለመስራት መወሰኑን የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እሰራለሁ ብየ የተናገርሁትን ነገር ስለመስራቴ ሀሳቤን አልለውጥም” ወይም “እኔ ለመስራት ያቀድሁትን ነገር መስራቴን አልተውም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከተማ ሁሉ
እዚህ ላይ “ከተማ” የሚለው በከተማ የሚኖረውን ሕዝብ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የከተማው ሁሉ ሕዝብ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ፈረሰኞች
ፈረሶች የሚጋልቡ የወታደሮች በቡድን

ወደ ችፍግ ደን ይገባሉ
ለደህንነታቸው ሲሉ ወደ ችፍግ ጫካዎች ይሮጣሉ።

ከተሞች ሁሉ ባዶ ቀርተዋል፣ የሚኖርባቸው አንድም ሰው የለም
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፡፡ ሁለተኛው ሀረግ በመጀመርያው ሀረግ ውስጥ ያለውን ሃሳብ ያጠናክረዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከተሞች ሰው አልባ ይሆናሉ። በእነርሱ ለመኖር የቀረ አንድም ሰው የለም። (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 4:30

አያያዥ ሀሳብ፡-
እግዚአብሔር ለይሁዳ መናገሩን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡-
እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ ሴተኛ አዳሪ እንደነበሩ አድርጎ ይናገራቸዋል ምክንያቱም እነርሱ ሌሎች አማልክትን በማምለክ ለእርሱ ታማኞች ስላልነበሩ ነው።

አንቺ ለጥፋት የተዳረግሽ ሆይ፣ አሁን ምን ትሰሪያለሽ?
ይህ ጥያቄ ጥቅም ላይ የዋለው ራሳቸውን ለመርዳት ሊያደርጉት የሚችሉት ምንም ነገር እንደሌለ ለእስራኤል ሕዝብ ለመንገር ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አሁን ጠላቶቻችሁ ለጥፋት ዳርገዋችኋል፣ እርዳታ ለማግኘት ልታደርጉ የምትችሉት ምንም ነገር የለም።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ቀይ ለበስሽ ... በወርቅ አጌጥሽ ... ዓይኖችሽን ... በኩል ተኳልሽ
እግዚአብሔር ስለ ይሁዳ ሕዝብ ሲናር ወንዶችን ወደራሷ ለመማረክ ራስዋን እንደምታስውብ ሴተኛ አዳሪ እንደነደበሩ አድርጎ ይናገራል። ይህ በግልጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እንደ ሴተኛ አዳሪ ቀይ ለበስሽ ... በወርቅ አጌጥሽ ... ዓይኖችሽን ... በኩል ተኳልሽ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀይ ልብስ ለበስሽ
እዚህ ላይ “ቀይ” የሚለው ውድ የሆነ ቀይ ልብስን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ውድ የሆነ ቀይ ልብስ ለበስሽ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ራስሽን በወርቅ ጌጣጌጥ አጌጥሽ
“የወርቅ ጌጣጌጥ አደረግሽ”

የተወዳጀሻቸው ወንዶች አሁን ትተውሻል
እግዚአብሔር ይሁዳ ለባለጠግነትና ለንግድ ስለተማመነችባቸው መንግስታት ሲናገር ይሁዳን እንደተወዳጁ ወንዶች አድርጎ ገልጾአቸዋል። እነዚህ መንግስታት የእግዚአብሔርን ፍርድ ሲመለከቱ ይሁዳን ይተዉአታል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ሕይወትሽን ለማጥፋት እየሞከሩ ነው
እዚህ ላይ “ሕይወትሽን ለማጥፋት እየሞከሩ ነው” የሚለው የይሁዳን ሕዝብ ለመግደል እየሞከሩ መሆናቸውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ አንቺን ለመግደል እየሞከሩ ነው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በወሊድ እንደምትጨነቅ
ይህ ተነጻጻሪ ዘይቤ ጥቅም ላይ የዋለው ይሁዳ ምን ያህል ክፉኛ እንደምትጨነቅ ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሴት ልጅ በምትወልድበት ጊዜ የሚሰማት ዓይነት ሕመምና ስቃይ ከባድ ጭንቀት” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የጽዮን ሴት ልጅ
እግዚአብሔር ስለ እነርሱ እንደ ሴት ልጁ አድርጎ በመናገር ለኢየሩሳሌም ሕዝብ ፍቅሩን ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፡- “ውድ ሴት ልጄ፣ ጽዮን” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወየልኝ
“እኔ ትልቅ አደጋ ውስጥ ነኝ”

ተዝለፈለፍሁ
“እኔ እየደከምሁ ነው”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 5

1 በኢየሩሳሌም መንገድ እየተመላለሳችሁ ሩጡ፤ በአደባባዮችዋም ፈልጉ። ከዚያም ተመልከቱ፣ ስለዚህም አስቡ፦ ፍትሕን የሚያደርገውን በታማኝነትም
ለማድረግ የሚሞክረውንም ሰው ታገኙ እንደሆነ፣ ይቅር እላታለሁ። **2** እነርሱም 'ሕያው እግዚአብሔርን!' ቢሉ የሚምሉት በሐሰት ነው። **3** እግዚአብሔር ሆይ፣
ዓይንህ ታማኝነትን የምትመለከት አይደለችምን? አንተ ቀሥፈሃቸዋል፣ ነገር ግን አላመማቸውም። ሙሉ ለሙሉ አሸንፈሃቸዋል፣ ነገር ግን ተግሣጽን እንቢ አሉ።
ፊታቸውን ከድንጋይ ይልቅ አጠንክረዋል፤ ይመለሱ ዘንድ እንቢ አሉ። **4** ስለዚህ እኔም "እነዚህ ድሆች ብቻ የሆኑ ሕዝቦች ናቸው። የእግዚአብሔርን መንገድና
የአምላካቸውን ሕግ አላወቁምና እነዚህ ሰነፎች ናቸው፤ **5** ወደ ጠቃሚዎቹ ሕዝቦች እሄዳለሁ የእግዚአብሔርን መልእክት እናገራቸዋለሁ፤ የእግዚአብሔርን
መንገንድና የአምላካቸውን ሕግ ያውቃሉና። ነገር ግን እነርሱ በሙሉ ቀንበሩን በአንድነት ሰብረዋል፣ ለእግዚአብሔር ያሰራቸውንም ሰንሰለቶች ቄርጠዋል። **6**
ስለዚህ ኃጢአታቸው በዝቶአልና፣ የክዳታቸውም ብዛት አይቆጠርምና አንበሳ ከዱር ወጥቶ ይሰብራቸዋል፣ የበረሀም ተኵላ ያጠፋቸዋል፣ ነብርም
በከተሞቻቸው ላይ ይተጋል፣ ከዚያም የሚወጣ ሁሉ ይነጠቃል። **7** እነዚህን ሰዎች ይቅር የምላቸው ለምንድነው? ልጆችሽ ትተውኛል አማልክትም ባልሆኑትም
ምለዋል። ሞልቼ መገብኳቸው፣ እነርሱ ግን አመነዘሩ የምንዝርና ቤትን ምልክቶችንም ወሰዱ። **8** በትኩሳት እንዳሉ ፈረሶች ሆኑ፤ ወዳጅነት ፈልገው ተንከላወሱ።
እያንዳንዱ ሰው ወደባልንጀሮቻቸው ሚስቶች አሸካኩ። **9** ስለዚህ ልቀጣ አይገባኝምን? ይላል እግዚአብሔር፤ ነፍሴስ እንደዚህ ባለ ሕዝብ ላይ አትበቀልምን?
10 ወደ ወይን ከፍታዋ ወጥታችሁ አፍርሱ። ነገር ግን ፈጽማችሁ አታጥፏቸው። ወይኖቻቸውን ቊረጡ፣ እነዚህ ወይኖች ከእግዚአብሔር አልመጡምና። **11**
የእስራኤል ቤትና የይሁዳ ቤት በእኔ ላይ ፈጽሞ ከድተውኛልና ይላል እግዚአብሔር። **12** እነርሱም ከድተውኛል። 'እርሱ እውነተኛ አይደለም። ክፉ ነገርም
አይመጣብንም፣ ሰይፍንና ራብንም አናይም' አሉ። **13** ነብያትም የነፋስን ያህል ጥቅም የለሽ ሆነዋል የእግዚአብሔርንም ቃል ለእኛ የሚነግረን የለም። ዛቻቸው
በራሳቸው ላይ ይምጣባቸው። **14** ስለዚህም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል "በዚህ ቃል ተናግራችኋልና ተመልከት፣ በአፍህ ውስጥ ቃሌን
አኖራለሁ። እንደ እሳት ይሆናል፣ ይህም ሕዝብ እንደ እንጨት ይሆናል! እሳቱም ይበላቸዋል። **15** ተመልከቱ! የእስራኤል ቤት ሆይ፣ ሕዝብን ከሩቅ
አመጣባችኋለሁ፣ ይላል እግዚአብሔር፤ ኃያል ጥንታዊ ሕዝብ ነው! ቋንቋቸውንም የማታውቋቸው፣ የሚናገሩትንም የማታስተውሉት ሕዝብ ነው። **16**
የፍላጻቸውም ሰገባ እንደ ተከፈተ መቃብር ነው። ሁሉም ኃያላን ናቸው። **17** መከሮቻችሁንና እንጀራችሁን ይበላሉ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁንም ይበሏቸዋል፤
በጎችንና ላሞቻችሁንም ይበላሉ፤ ወይናችሁንና በለሶቻችሁንም ይበላሉ። የምትታመኗቸውን የተመሸጉ ከተሞችን በሰይፍ ይደበድባሉ። **18** ነገር ግን በዚያ ዘመን
እንኳን ይላል እግዚአብሔር፣ ፈጽሜ ላጠፋችሁ አላስብም። **19** እንዲህም ይሆናል፤ እናንተ እስራኤል እና ይሁዳ፣ 'አምላካችን እግዚአብሔር ይህን ነገር ሁሉ
ስለምን አደረገብን?' ስትሉ፣ አንተ ኤርምያስ ያን ጊዜ፣ 'እግዚአብሔርን እንደተዋችሁ እና በምድራችሁም ሌሎችን አማልክት እንዳመለካችሁ፣ እንዲሁ ለእናንተ
ባልሆነ አገር ለሌሎች ሰዎች በባርነት ትገዛላችሁ' ትላቸዋለህ። **20** ይህን ለያዕቆብ ቤት አውሩ፣ በይሁዳም ይሰማ። **21** ይህን ስሙ፣ እናንተ ሰነፎች! ጣዖታት
ፈቃድ የላቸውምና፤ ዐይን አለባቸው፣ ነገር ግን ሊያዩ አይችሉም። ጆሮዎችም አሉባቸው፣ ነገር ግን አይሰሙም። **22** እኔን አትፈሩኝምን? በፊቴስ
አትደነግጡምን? ይላል እግዚአብሔር፤ የአሸዋን ድንበር እንዳይተላለፈው በማይቋረጥ ትእዛዝ በባሕሩ ላይ አድርጌአለሁ። የባህሩ ነውጥ ቢጮኽም
አያቋርጠውም። **23** ነገር ግን ይህ ሕዝብ ግን ዐመፀኛ ልብ አለው። በዐመፅ ሸፍቶ ሄዷል። **24** በልባቸውም፣ 'የፊተኛውንና የኋለኛውን ዝናብ በትክክለኛው ጊዜ
የሚሰጠውን፣ ለመከርም የተመደቡትን ወራት የሚጠብቅልንን አምላካችንን እግዚአብሔርን እንፍራ አላሉም። **25** በደላችሁ እነዚህ እንዳይሆኑ አስቀርታለች።
ኃጢአታችሁም መልካምን ነገር ወደ እናንተ እንዳይመጣ አስቆመ። **26** በሕዝቤ መካከል ክፉዎች ሰዎች ተገኝተዋል። አንድ ሰው ወፎችን ለመያዝ ሲያደባ
እንደሚመለከቱ፣ ወጥመድን ይዘረጋሉ ሰዎችንም ያጠምዳሉ። **27** ዋሻ ወፎችን እንደሚሞላ፣ እንዲሁ ቤታቸው ሸንገላን ሞልታለች። እንዲሁም ተልቀዋል፣ ባለ
ጠጎችም ሆነዋል። **28** ወፍረዋል፣ በደህንነታቸውም ያብረቀርቃሉ። ክፋታቸውንም ያለ ልክ አብዝተዋል። ለሰዎች፣ ወይም ለወላጅ አልባዎች ነገር
አልተምዋገቱላቸውም። ለችግረኞች ፍትሕን ባያደርጉም እንኳን በልጽገዋል። **29** ስለእነዚህ ነገሮች አልቀጣምን? ይላል እግዚአብሔር፤ እንደዚህ ባለ ሕዝብ ላይ
ለራሴ አልበቀልምን? **30** በምድር ላይ የምታስደንቅና የምታስደነግጥ ነገር ሆናለች፤ **31** ነቢያት በሐሰት ትንቢት ይናገራሉ፣ ካህናትም በገዛ ኃይላቸው ይገዛሉ።
ሕዝቤም እንዲህ ያለውን ነገር ይወድዳሉ፣ ነገር ግን በፍጻሜው ምን ይፈጠራል?

Jeremiah 5:1

አጠቃላይ መረጃ፦
ኤርምያስ ብዙ ጊዜ ትንቢቱን የሚፈጽመው በግጥም ቅርጽ ነው። የዕብራውያን ግጥም የተለያዩ ትይዩነቶችን ይጠቀማል። (ግጥም እና ትይዩነት/ ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

በመንገዶች እስቲ ውጡ
“በመንገዶቹ በፍጥነት ሂዱ”

ተመልከቱ አስቡም
“መመልከትና ማግኘት”

የከተማዋ አደባባዮች
በከተማ ውስጥ ሰዎች የሚሰባሰቡበት ሰፊና ክፍት ቦታዎች

ፍትህን የሚያደርግ ማን ነው
“ፍትህ የሆነውን የሚያደርግ ማን ነው”

ምንም እንኳ እነርሱ ቢናገሩም
“እነርሱ” የሚለው ቃል የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል።

ሕያው እግዚአብሔርን
“እግዚአብሔር በእርግጠኝነት ሕያው እንደሆነ ሁሉ።” ሕዝቡ ይህን መግለጫ የሚጠቀሙት ቀጥለው የሚናገሩት ነገር በእርግጠኝነት እውነት እንደሆነ ለማሳየት ነው። ይህ የማይናወጥ ቃል ኪዳን የማድረግ መንገድ ነው። ይህን ኤርምያስ 4:2 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔ በማይናወጥ መልኩ እምላለሁ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ዓይኖችህ እውነትን አይመለከቱምን?
ኤርምያስ ይህን ጥያቄ የሚጠቀመው እግዚአብሔር የሚፈልገው ታማኝነት እንደሆነ አጽንዖት ለመስጠት ነው። ሰዎች ታማኞች እንዲሆኑ መፈለግ ታማኝነትን መፈለግ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “አንተ ታማኝነትን ትፈልጋለህ” ወይም “አንተ ሰዎች ታማኞች እንዲሆኑ ትፈልጋለህ።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አንተ ሕዝቡን መታሃቸው እነርሱ ግን አልተሰማቸውም
እግዚአብሔር ሕዝቡን በተለያዩ መንገዶች ቀጥቷቸዋል። እዚህ ላይ እርሱ እንደመታቸው ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ ሕዝቡን ቀጣሃቸው፣ ነገር ግን ምንም ትኩረት አልሰጡም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ግን አሁንም ለመታረም እምቢ አሉ
እዚህ ላይ “ለመታረም” የሚለው ትክክለኛውን ነገር ለማድረግ ከቅጣት መማርን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ትምህርታቸውን ለመማር አሁንም እምቢ አሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ፊታቸውን ከድንጋይ የበለጠ አጠነከሩ
ጠንካራ ፊቶች ትዕቢተኞች እንደሆኑ የሚያሳይ በፊታቸው ያለውን ሁኔታ የሚወክል ነው። “ከድንጋይ የበለጠ ማጠንከር” የሚለው ተነጻጻሪ ዘይቤ ሰዎቹ እጅግ በጣም ትዕቢተኞች እንደሆኑ የሚያሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ እጅግ በጣም ትዕቢተኞች ናቸው” (ምትክ ስም እና ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 5:4

ስለዚህ እንዲህ አልሁ
ኤርምያስ እየተናገረ ነው።

እነዚህ ግን ቀንበሩን በአንድነት ሰብረዋል፥ እነዚህ ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስተሳስራቸውን ሰንሰለት ቄርጠዋል።
ቀንበርና ሰንሰለት እግዚአብሔርንና ሕዝቡን የሚያስተሳስረውን ሕጉን ይወክላል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህ አንበሳ ... ተኩላ ... የሚያደባ ተኩላ
እነዚህ ሰዎችን መግደል የሚችሉ አደገኛ እንስሳት ናቸው። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ይህ በእርግጥ የሚናገረው ሰዎችን ስለሚገድሉ ስለ የዱር እንስሳት ነው ወይም 2) እነዚህ የዱር እንስሳት ለጠላት የጦር ሰራዊት ተለዋጭ ዘይቤ ናቸው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህ አንበሳ ... ተኩላ ... የሚያደባ ተኩላ ... ይቦጫጭቃቸዋል
ለዚህ ተቀባይነት ያለው አንዱ ትርጉም እነዚህ እንስሳት ይሁዳን የሚያጠቃው የጠላት ጦር ሰራዊት ተለዋጭ ዘይቤ ናቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “ከዱር እንደሚወጣ አንበሳ፣ ከበረሃ እንደሚመጣ ተኩላ እና እንደሚያደባ ነብር የጠላት ጦር ሰራዊት ወደ ከተማቸው ይመጣል፣ ያጠቃቸዋል፣ ደግሞም ያጠፋቸዋል። ከከተማው ወጥቶ የሚሄድ ማንኛውም ሰው ይገደላል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዱር
በአንድ ላይ ተጠጋግተው የሚበቅሉ የቁጥቋጡ ክምችት።

ተኩላ
ትልቅ የዱር አደገኛ ውሻ

የሚያደባ
ለማጥቃት አጋጣሚን ለመጠቀም አድፍጦ ማየት

ነብር
ትልቅ የዱር አደገኛ ድመት

በደላቸው በዝቶአልና
“በደላቸው” የሚለው ረቂቅ ስም “ኃጢአት ሰሩ” በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ብዙ ኃጢአት ሰርተዋልና” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የክህደታቸው ተግባር እጅግ ብዙ ነው
“የክህደታቸው ተግባር” የሚለው ረቂቅ ስም “እነርሱ የሰሯቸው ያለመታመን ድርጊቶች” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል።” አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ የሰሯቸው ያለመተመን ድርጊቶች ብዙ ናቸው” ወይም “ብዙ ያለመታመን ድርጊቶች ሰርተዋል” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 5:7

እነዚህን ሰዎች ይቅር የምላቸው ለምንድን ነው?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው እነዚህን ሰዎቹ ይቅር ለማለት ምንም ዓይነት ምክንያት እንደሌለው አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ከሰራቸው ስራዎች የተነሳ እነዚህን ሰዎች ይቅር ልላቸው አልችልም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ ሰዎች
የኢየሩሳሌም ሕዝብ

ወንዶች ልጆቻችሁ
እግዚአብሔር ለኢየሩሳሌም ልጆች ያላት ሴት እንደሆነች አድርጎ እየተናገረ ነው። የኢየሩሳሌም “ወንዶች ልጆች” የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የኢየሩሳሌም ሕዝብ” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ እስኪጠግቡ ድረስ መገብኋቸው
የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ መስጠት እነርሱን እንደመመገብ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሚያስፈልጋቸውን ማኛውንም ነገር ሰጠኋቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ አመነዘሩ፣ ወደ ሴተኛ አዳሪዎች ቤቶች ብዙ ሆነው ተንጋጉ
ይህ ምናልባት ለእግዚአብሔር ታማኝ ላለመሆንና ጣዖቶችን ለማምለክ ተለዋጭ ዘይቤ ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን የጣዖቶች አምልኮ አመንዝራነትን ያካትታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ ለእኔ ታማኞች አልነበሩም፣ ወደ ሴተኛ አዳሪዎች ቤቶች ብዙ ሆነው ተንጋጉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ሴተኛ አዳሪዎች ቤቶች ብዙ ሆነው ተንጋጉ
“ወደ ሴተኛ አዳሪዎች ቤቶች ብዙ ሆነው ሄዱ” ወይም “ብዙ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ወደ ሴተኛ አዳሪዎች ቤቶች ሄዱ”

እንደ ተቀለቡ ፈረሶች ሆኑ ... ከጎረቤቶቻቸው ሚስቶች ኋላ አሸካኩ
ምክንያቱም እግዚአብሔር ስለ እነርሱ ሲናገር ከሌሎች ፈረሶች ጋር ወሲብ ለመፈጸም የሚፈልጉ ፈረሶች እንደሆኑ አድርጎ ገልጾአቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “እንደ ተቀለቡ ፈረሶች ሆኑ ... ከጎረቤቱ ሚስት ኋላ አሸካካ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በፍትወት የጋሉ
ወሲብ ለማድረግ የተዘጋጁ

ወሲብ ማድረግ
እንስሳት ለመራባት ወሲብ በሚያደርጉበት ጊዜ

እያንዳንዱ ሰው ከጎረቤቱ ሚስት ጋር አሸካካ
ወንድ ፈረሶች ከሴት ፈረሶች ጋር ወሲብ መፈጸም ሲፈልጉ በታላቅ ጩኸት ያሸካካሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ከአንድ ሴት ፈረስ በላይ ወሲብ እንደሚፈጽም ወንድ ፈረስ እነዚህ ሰዎች ከሌሎች ወንዶች ሚስቶች ጋር ለመተኛት ይፈልጋሉ። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህ አልቀጣቸውምን? ... እኔ ራሴ እንደዚህ ዓይነቱን ሕዝብ አልበቀልምን?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የሚጠቀመው እነርሱ የሰሯቸው ነገሮች በጣም መጥፎ ከመሆናቸው የተነሳ እርሱ ምህረት አይኖረውም ነገር ግን ይቀጣቸዋል የሚለውን ሃሳብ አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህን ነገሮች በማድረጋቸው ምክንያት እኔ እቀጣቸዋለሁ ... እኔ ራሴ በእርግጠኝነት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በእነርሱ ላይ እበቀላለሁ።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 5:10

አያያዥ ሀሳብ፦
እግዚአብሔር መናገሩን ቀጥሏል። እዚህ ላይ የሚናገረው ለእስራኤል ጠላቶች ነው።

ወደ ወይን አትክልቷ ወደ ላይ ሂዱ
ከቁጥር 10-13 እግዚአብሔር የሚናገረው ለእስራኤል ጠላቶች ነው። ይህ በትምህርተ ጥቅስ ግልጽ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እናንተ የእስራኤል ጠላቶች፣ ወደ ወይን አትክልቷ ወደ ላይ ሂዱ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ወይን አትክልቷ ወደ ላይ ሂዱና አፍርሱት
እግዚአብሔር ሲናገር እስራኤልና ይሁዳ የወይን አትክልት እንደሆኑ በዚያ የሚኖሩት ሰዎች ደግሞ ወይን እንደሆኑ አድርጎ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “ለእኔ እንደ ወይን አትክልት ወደሆኑት ወደ እስራኤልና ይሁዳ ወደ ላይ ሂዱና አጥፏቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን ፈጽማችሁ አታጥፏቸው
“ሙሉ በሙሉ አታጥፏቸው”

የእነርሱን የወይን ቅርንጫፎች ገነጣጥሉ፣ እነዚህ የወይን ቅርንጫፎች ከእግዚአብሔር አይደሉምና
“የእነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የወይን አትክልቱን ነው። እግዚአብሔር የእስራኤልና የይሁዳ ሕዝቦች ወይን እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “በወይን አትክልት ያለውን ወይን እንደሚቆርጡ ገበሬዎች፣ የእስራኤልንና የይሁዳን ሰዎች ልታስወግዳቸው ይገባል ምክንያቱም የእግዚአብሔር አይደሉምና” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእስራኤልና ለይሁዳ ቤቶች
“ቤት” የሚለው ቃል ለሰውየው ልጆች ምትክ ስም ነው። በዚህ ዓውድ ይህ የሚያመለክተው ለእስራኤልና ለይሁዳ መንግስት ሕዝቦች ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ለእስራኤልና ለይሁዳ ሕዝቦች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ላይ ሐሰትን ተናገሩ ፤ እንዲህም አሉ
“እንዲህ በማለት በእግዚአብሔር ላይ ሐሰትን ተናገሩ”

ክፉ ነገርም በእኛ ላይ አይመጣብንም፣ ሰይፍንና ራብንም አናይም
እነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች የሚናገሩት ተመሳሳይ ነገር ነው፣ ሁለተኛው ከአንደኛው ይልቅ ግልጽ ነው። (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉ ነገርም በእኛ ላይ አይመጣብንም
“በእኛ ላይ አይመጣብንም” የሚለው ፈሊጥ “በእኛ ላይ አይሆንም” ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በእኛ ላይ መምንም ጉዳት አይደርስብንም” ወይም “ማንም አይጎዳንም” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰይፍንና ራብንም አናይም
እዚህ ላይ “ማየት” የሚለው በሁኔታ ውስጥ ለማለፍ ተለዋጭ ዘይቤ ነው፣ “ሰይፍ” ደግሞ ለጦርነት ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በጦርነት ወይም በረሃብ ውስጥ አናልፍም” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ነቢያቱ ነፋስ ይሆናሉ
እዚህ ላይ “ነቢያት” የሚለው ነቢያቱ ለሚናገሩት ነገር ምትክ ስም ነው፣ “ነፋስ” የሚለው ደግሞ ምንም ለማይሰራ ነገር ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የነቢያቱ ቃላት እንደሚጮህ ነፋስ ነው” ወይም “ነቢያቱ እንደ ነፋስ ይጮኻሉ፣ ነገር ግን የሚተነብዩት ነገር አይፈጸምም” (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቃሉ በውስጣቸው የለም
እዚህ ላይ “ቃሉ” የሚለው የእግዚአብሔርን መልእክት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “የእግዚአብሔር መልእክት በእነርሱ ውስጥ የለም” ወይም “እነርሱ የሚናገሩት መልእክት ከእግዚአብሔር አይደለም” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህ ያሉት ሁሉ በእነርሱ ላይ ይፈጸም
ነቢያቱ ስለ ምን ዓይነት ነገሮች እየተናገሩ እንደነበር በግልጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ስለዚህ ነቢያቱ ይመጣል ብለው የተናገሩት ክፉ ነገር በእነርሱ ላይ ይምጣባቸው” ወይም “ነቢያቱ በእኛ ላይ ክፉ ነገር ይመጣል ብለው ስለተናገሩ፣ እነዚህ ክፉ ነገሮች በነቢያቱ ላይ ይምጡባቸው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 5:14

ምክንያቱም እናንተ
“እናንተ” የሚለው ቃል የእስራኤልንና የይሁዳ ሕዝብን ያመለክታል።

እንዲህ ብላችሁ ተናራችሁ
ሕዝቡ ምን እንደተናገሩ በኤርምያስ 5:12 ላይ ተመልከቱ።

Jeremiah 5:16

አያያዥ ሀሳብ፦
እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል።

የፍላጻቸውም ሰገባ .... ሁሉም ወታደሮች ናቸው
እዚህ ላይ “የፍላጻቸውም ሰገባ” የሚለው የጠላት መንግስት ጦር ሰራዊትን ይወክላል፣ በሰገባው ውስጥ ያለው ፍላጻ ደግሞ በጦር ሰራዊቱ ውስጥ ያሉትን ወታደሮች ይወክላል። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ሰገባ
ፍላጻ ለመያዝ የሚጠቅም እቃ

የፍላጻቸውም ሰገባ እንደተከፈተ መቃብር ነው
የተከፈተ መቃር ብዙ አስከሬኖች በአንድ ላይ እንዲቀበሩበት የተዘጋጀ ነው። የጠላት ጦር ብዙ ሰዎችን ይገድላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የዚያ መንግስት ጦር ሰራዊት ፍላጻቸውን ተጠቅመው ብዙ ሰዎችን ይገድላሉ” ወይም “በጦር ሰራዊቱ ፍላጻዎች ምክንያት ብዙ ሰዎች ይገደላ ደግሞም ይቀበራ” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ስለዚህ ምርትህን፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆችህንና ምግብህን ይበላሉ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ለወንዶችና ለሴቶች ልጆቻቸው ጥቅም ይውል የነበረው ምርታቸውና ምግባቸው ይጠፋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለዚህ ለወንዶችና ለሴቶች ልጆችህ ሊሆን የሚገባው ምርትህና ምግብህ ይተፋል” ወይም 2) ምርታቸው፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸው እና ምግባቸው ይጠፋል። ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸው “መጥፋታቸው” ሃሳቡ ይገደላሉ ለሚለው ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለዚህ ምርታችሁና ምግባችሁ ይጠፋል፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ደግሞ ይገደላሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህ ምርታችሁ ይጠፋል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለዚህ የዚያ መንግስት ጦር ሰራዊት ልትሰበስበው ከምትጠብቀው ምርት የሚገኘውን ምግብ ይበላዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በተጨማሪ ወንዶችና ሴቶች ልጆችህና ምግብህ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ወንዶችና ሴቶች ልጆችህ ሊበሉት የሚገባውን ምግብ ጠላቶችህ ይበሉታል፤ ወይም 2) ጠላቶችህ ወንዶችና ሴቶች ልጆችህን ያጠፉአቸዋል፣ ምግብህን ደግሞ ይበሉታል።

እነርሱ ይበሉታል
“እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የዚያን መንግስት ጦር ሰራዊት ነው።

የተመሸጉ ከተሞችህን በሰይፍ ይመታሉ
ሰይፍ የሚለው የዚያ መንግስት ሕዝብ ለሚጠቀምባቸው የተለያዩ የጦር መሳርያዎች ወካይ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ይጠብቁኛል ብለህ የምትተማመንባቸውን ጠንከራ ከተሞች ለመያዝ የጦር መሳርያዎቻቸውን ይተቀማሉ (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ የተመሸጉ ከተሞች
የተመሸጉ ከተሞች በውስጣቸው ለሚኖሩ ሰዎች ከውጭ ከሚመጡ ጠላቶቻቸው ለመከላከል በዙርያቸው የግንብ አጥር ነበራቸው።

አንተ የምትተማመንባቸው
“አንተን በደህንነት ለመጠበቅ በጥንካሬ ብቁ ናቸው ብለህ የምታስባቸውን”

Jeremiah 5:18

አያያዥ ሀሳብ፡-
እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብና ለኤርምያስ መናገሩን ቀጥሏል።

በእነዚህ ቀናት
“በእነዚህ ቀናት” የሚለው ሀረግ ከሩቅ አገር ባዕድ መንግስት የሚመጣበትንና የእስራኤልን ሕዝብ የሚያጠቃበትን ጊዜ የሚያመለክት ነው።

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ፈጽሜ አላጠፋችሁም
“አላጠፋችሁም”

እነዚህ ነገሮችች በሙሉ በእኛ ላይ ሆኑ
“እነዚህ ነገሮች” የሚለው ሀረግ እነርሱን ለማጥቃት የጦር ሰራዊት መላን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህ ነገሮች ሁሉ የሆኑት እኛን ለመጉዳት ነው” ወይም “እኛን ለማጥቃት የውጭ ጦር ሰራዊት ተላከ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እናተ በምድራችሁ ባዕድ እንዳገለገላችሁ እንደዚሁ እንግዶችን ሕዝቦች ማገልገል አለባችሁ
እዚህ ላይ “ባዕድ አማልክት አገለገላችሁ” የሚለው ባዕድ አማልክት ማምለካቸውን የሚወክል ነው። ባዕድ አማልክትን በማምለካቸው ምክንያት ባዕድ ሕዝብን እንዲያገለግሉ በማድረግ እግዚአብሔር ይቀጣቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “እናንተ በምድራችሁ ባዕድ አማልክትን ስላመለካችሁ ባዕድ ሕዝብን ታገለግላላችሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 5:20

አያያዥ ሀሳብ፡-
እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል።

ይህን አውሩ
“ይህን ተናገሩ”

የያዕቆብ ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ምትክ ስም ነው። በዚህ ሁኔታ ይህ የሚያመለክተው የያዕቆብን ልጆች ነው። በኤርምያስ 2:4 ላይ እንዳደረግኸው “የያዕቆብ ቤት” ብለህ ተርጉመው። አማራጭ ትርጉም፡- “የያዕቆብ ልጆች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ በይሁዳ ይሰማ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በይሁዳ ያሉት ይህን ይስሙት” ወይም “በይሁዳ ምድር ይህን አውጁ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ማስተዋል የሌላችሁ
“የማታውቁ” ወይም “ምንም ነገር የማታስተውሉ”

ማየት አትችሉም
እዚህ ላይ “ማየት አትችሉም” የሚለው አታስተውሉም ለሚለው ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እናንተ አታስተውሉም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

መስማት አትችሉም
እዚህ ላይ “መስማት አትችሉም” የሚለው አለማስተዋልን ይወክላል። “አማራጭ ትርጉም፡- “እናንተ አታስተውሉም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

በውኔ እኔን አትፈሩም ... ፊቴስ?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመበት ሕዝቡ ከመጠን በላይ ሞኝ መሆናቸውን አጽንዖት ለመስጠት ነው፣ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ፍርሃት ስለሌላቸው ነው። አማራጭ ትርጉም፡- እኔን አለመፍራታችሁ ሞኝነት ነው ... ፊቴስ!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ከፊቴስ አትደነግጡምን
መደንገጡ በፍርሃት ምክንያት ነው፣ “ከፊቴ” መሆን የሚለው እግዚአብሔር ማን እንደሆነ መገንዘብን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- "ከእኔ የተነሳ በፍርሃት ተንቀጥቀጡ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ለባህር ዳርቻ በአሸዋ አድርጌለታለሁ
“እኔ አሸዋን ለባህር ዳርቻ እንዲሆነው አስቀምጬለታለሁ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በዘላለም ትዕዛዝ እንዳያልፍ
እግዚአብሔር ውቅያኖስን ከአሸዋ ዳርቻው አልፎ ስላለመሄዱ ሲናገር ዳርቻው እንደ ሕግ፣ ውቅያኖሰ ደግሞ ሕጉን እንደሚታዘዝ ሰው አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እንዳያልፍ የዘላለም ዳርቻ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቢነሳና ቢወድቅም
“ወደኋላ እና ወደፊት ቢንቀሳቀስም”

ዳርቻውን ጥሶ አያልፍም
“ውቅያኖስ ሕጌን ፈጽሞ አያፈርስም።” እግዚአብሔር ስለ ውቅያኖሱ ከዳርቻው አልፎ አለመሄድ ሲናገር ዳርቻው ሕግ እንደሆነ፣ ውቅያኖሱ ደግሞ ሕጉን እንደሚያከብር ሰው አድርጎ ገለጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- ዳርቻውን አልፎ መሄድ አይሳካለትም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 5:23

አጠቃላይ መረጃ፡-
እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል።

ይህ ሕዝብ ትዕቢተኛ ልብ አለው ... ሄደውማል
የሕዝቡ ልብ ለእግዚአብሔር ያላቸውን አመለካከት ይወክላል። እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚናገር ከሆነ “እናንተ” በሚለው ቃል ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን እናተ ሕዝቦች እልከኛ ልብ አላችሁ። እናንተ ሄዳችኋል” ወይም “ነገር ግን እናንተ ሕዝቦች እልከኛ ናችሁ። እናንተ ሄዳችኋል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ በአመጽ መንገድ ወጥቶ ሄዷል
“እርሱ” የሚለው ቃል ሕዝቡን ያመለክታል። እዚህ ላይ “ሄዷል” የሚለው እግዚአብሔርን አለመታዘዝ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አምጸዋል ደግሞም እኔን አልታዘዝም ብለዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በልባቸው እንዲህ አላሉም
እዚህ ላይ “በልባቸው” የሚለው “ሃሳባቸውን” ይወክላል፣ “አላሉም” የሚለው ደግሞ “ማሰብን” ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ አያስቡም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለመከርም የተመደቡትን ሳምንቶች ለእኛ የሚጠብቅልንን
እዚህ ላይ “ለመከርም የተመደቡትን ሳምንቶች የሚጠብቅልን” የሚለው እነዚህ ሳምንቶች በትክክለኛው ጊዜ ለመከሰታቸው ማረጋገጥን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህ የመከር ሳምንቶች ሊከሰቱ በሚገባበት ጊዜ እንዲመጡ ለእኛ የሚያረጋግጥልን” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የእናተ በደል
“የእናተ” የሚለው ቃል የያዕቆብን ልጆችና የይሁዳ ሕዝብን ያመለክታል።

እነዚህ ነገሮች
ይህ ዝናቡንና መከሩን ያመለክታል።

ኃጢአታችሁ መልካም ነገር ወደ እናንተ እንዳይመጣ ከለከለቻችሁ
መልካም ነገር “መምጣት” የሚለው መልካም ነገር መከናወንን ይወክላል። “በኃጢአታችሁ ምክንያት መልካ ነገር በእናንተ እንዳይሆን ከለከላችሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 5:26

አጠቃላይ መረጃ፡-
እግዚአብሔር መናገሩን ቀጥሏል።

በሕዝቤ መካከል ክፉዎች ሰዎች ተገኝተዋል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በሕዝቤ መካከል ክፉ ሰዎች አግኝቻለሁና” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ወፎችን ለመያዝ እንደሚያደፍጥ ሰው ይመለከታሉ
እግዚአብሔር አንድን ሰው ለመጉዳት ስለሚፈልጉ ክፉ ሰዎች ሲናገር ወፎችን ለመያዝ እንደሚያደፍጥ ሰው አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ወፎችን ለመያዝ እንደሚያደፍጥና እንደሚጠብቅ ሰው” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወጥመድን ይዘረጋሉ ሰዎችንም ያጠምዳሉ
እግዚአብሔር ሌሎች ሰዎችን ሆን ብለው ስለሚጎዱ ስለክፉ ሰዎች ሲናገር ወጥመድ እንደሚዘረጉ አድርጎ ይገልጻቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “በሰዎች ጉዳት እነርሱ እንዲጠቀሙ ነገሮችን ያመቻቻሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወፎች እንደሞሉት ጎጆ፣ ቤታቸው በማጭበርበር የተሞላ ነው
እዚህ ላይ “ማጭበርበር” የሚለው በማጭበርበር የተወሰዱ ነገሮችን የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በአዳኝ እጅ እንዳለ ወፎች እንደሞሉት ጎጆ የክፉ ሰዎች ቤቶች ሰዎችን በማጭበርበር በወሰዱአቸው ነገሮች የተሞላ ነው” (ተነፃፃሪ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ከብረዋል ባለጠጎችም ሆነዋል
እዚህ ላይ “ከብረዋል” የሚለው ኃይለኛ መሆናቸውን የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህ ክፉ ሰዎች ኃይለኛና ባለጠጋ ሆነዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወፍረዋል ሰብተዋልም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) በሚበሉት ጤናማ ምግብ ምክንያት ቆዳቸው ያብረቀርቃል፣ ወይም 2) በአጥንታቸውና በቆዳቸው መካከል ባለው ጡንቻን ስብ ምክንያት ሰውነታቸው ለስላሳ ነው። እነዚህ ሰዎች በሚገባ እንደሚበሉ ያመለክታል።

የክፋትን ዳርቻ ሁሉ አልፈው ሄደዋል
ሁሉንም ዓይነት ክፋት መስራት በአንዳንድ ክፉ ነገሮችና በሌሎች እጅግ በጣም ክፉ በሆኑ ነገሮች መካከል የሚለይ ዳርቻ እንዳለ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ እጅግ በጣም ክፉ የሆነውንም ነገር ይሰራሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሕዝቡ ወይም የወላጅ አላባዎችን ጉዳይ መልካም እንዲሆንላቸው አልተምዋገቱላቸውም
“ለሕዝቡና ለወላጅ አልባዎች የሚያስፈልጋቸውን እንዲሰጡአቸው በገዢዎች ፊት አልተምዋገቱላቸውም” ወይም ““ለሕዝቡና ለወላጅ አልባዎች ፍትህ እንዲሰጡአቸው በገዢዎች ፊት አልተምዋገቱላቸውም”

ለድሆች ፍትህን አልሰጡአቸውም
“ለድሆች ፍትሃዊ የሆነውን ነገር በማድረግ እነርሱን አልረዱአቸውም”

እንደዚህ ያለውን ሕዝብ ልቀጣው አይገባኝምን?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው እነርሱ የሚሰሯቸው ነገሮች በጣም መጥፎ ስለሆኑ በእነርሱ ላይ ምህረት እንደማያደርግ ይልቁንም እንደሚቀጣቸው አጽንዖት ለመስጠት ነው። በኤርምያስ 5:9 ላይ እንዲህ ዓይነት ተመሳሳይ ዓረፍተ ነገር እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለዚህ እኔ እቀጣቸዋለሁ፣ ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው። እኔ በእርግጠኝነት እነርሱን እበቀላቸዋለሁ።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ

እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 5:30

አጠቃላይ መረጃ፡-
እግዚአብሔር መናገሩን ቀጥሏል።

ግፍና አሰቃቂ ነገር ተከስቷል
ይህ በገቢር ቅርጽ የበለጠ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች በጣም አስደንጋጭና አሰቃቂ ነገሮች ይፈጽማሉ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በምድሪቱ
እዚህ ላይ “ምድሪቱ” የሚለው የአስራኤልን ምድር ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በእስራኤል ምድር” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ነቢያት በማጭበርበር ትንቢት ይናገራሉ፣ ካህናትም በራሳቸው ኃይል ያስተዳድራሉ
እነዚህ በቁጥር 30 ላይ የተነገሩት ግፎችና አሰቃቂ ነገሮች ናቸው።

ነቢያት በማጭበርበር ትንቢት ይናገራሉ
“ነቢያቱ የሐሰት ትንቢት ይናገራሉ” ወይም “ነቢያቱ ትንቢት ሲናገሩ ውሸትን ይናራሉ”

ካህናትም በራሳቸው ኃይል ያስተዳድራሉ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ካህናቱ ለእግዚአብሔር ስልጣን ራሳቸውን አላስገዙም። አማራጭ ትርጉም፡- “ካህናቱ በራሳቸው ስልጣን ያስተዳድራሉ” ወይም 2) ካህናቱ ነቢያቱ በሚሰጡአቸው መመርያ መሰረት ያስተዳድራሉ (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን በመጨረሻ ምን ይሆናል?
“ነገር ግን ይህ ከሆነ በኋላ በመጨረሻ ምን ታደርጋላችሁ?” እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው እርሱ ለሰሩት ስራ ሲቀጣቸው ክፉ ስለመሆናቸው እንደሚጸጸቱ አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን በመጨረሻ እኔ እቀጣችኋለሁ፣ እናንተም ስለ ክፉ ድርጊታችሁ ትጸጸታላችሁ” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 6

1 እናንተ የብንያም ሕዝቦች፣ ከኢየሩሳሌም በመሸሽ ደህንነትን አግኙ። በቴቁሔ መለከትን ንፉ። ታላቅ ጥፋት የሆነ ክፉ ነገር ከሰሜን እየመጣ ነውና
በቤትሐካሬም ላይ ምልክትን አንሡ። **2** የተዋበችውና ሰልካካዋን የጽዮንን ልጅ እደመስሳለሁ። **3** እረኞችና መንጐቻቸው ወደ እርስዋ ይሄዳሉ፣ በዙሪያዋም
ድንኳኖቻቸውን ይተክሉባታል፣ እያንዳንዱም እረኛ በገዛ እጁ መንጋውን ይጠብቃል። **4** ነገሥታት "ለአማልክቶቻችሁ እንድትዋጉ ራሳችሁን አስገዙ። ተነሡ፣
በቀጥርም እናጥቃ። ቀኑ እየመሸ መሆኑ፣ የማታውም ጥላ እየረዘመ መሆኑ እጅግ መጥፎ ነው። **5** ነገር ግን በሌሊትም እናጥቃ፣ አምባዎችዋንም እናፍርስ። **6**
የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፦ ዛፎችዋን ቍረጡ፥ በኢየሩሳሌምም ላይ የከበባ አፈርን ደልድሉ፤ ይህች በግፍ የተሞላች ከተማ በመሆኗ
ለማጥቃት ትክክለኛዋ ከተማ ነች። **7** ጕድጓድ ውኃ ማፍለቁን እንደሚቀጥል፣ እንዲሁ ይህች ከተማ ክፋትን ማፍለቋን ትቀጥላለች። ዐመጽና ሥርዓተቢስነት
በእርስዋ ዘንድ ይሰማል። መከራና መቅሠፍትም ሳይቋረጥ በፊቴ አለ። **8** ኢየሩሳሌም ሆይ፣ ከአንቺ እንዳልለይ፣ አንቺንም ባድማና ወና እንዳላደርግሽ፣
ተግሣጽን ተቀበዪ።" **9** የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "ሰው ወይኑን እንደሚለቅም፣ እንዲሁ ከእስራኤል የቀሩትን በእርግጥ ይቃርሟቸዋል፤
በድጋሚ እጅህን ዘርግተህ ወይንን ከግንዱ እንደሚለቅም አድርግ። **10** ይሰሙኝስ ዘንድ ለማን እናገራለሁ፣ ለማንስ አስጠነቅቃለሁ? ተመልከቱ! ጆሮአቸው
ያልተገረዘ ነው፤ በትኩረት ለመስማት አይችሉም! ተመልከቱ! የእግዚአብሔር ቃል ሊያቀናቸው መጥቶባቸዋል፣ ነገር ግን አይፈልጉትም።" **11** ነገር ግን
በእግዚአብሔር ቍጣ ተሞልቻለሁ። በውስጤ ይዤ ልታገሠው ደክሜአለሁ። እንዲህ አለኝ፣ "በጎዳና ሕፃናት ላይ፣ እንዲሁም በወጣቶችም ስብስብ ላይ
አፍስሰው። እያንዳንዱ ባል ከሚስቱ ጋር እድሜ ጠገቡ ሽማግሌም ከጎበዙ ጋር ይወሰዳልና። **12** ቤቶቻቸው እርሻዎቻቸውም ሚስቶቻቸውም በአንድነት
ለሌሎች ይሆናሉ። በምድር የሚገኙ ነዋሪዎችን አጠቃለሁና ይላል እግዚአብሔር። **13** ከታናሻቸው ጀምሮ እስከ ታላቃቸው ድረስ እያንዳንዳቸው በኃቅ ላልሆነ
ትርፍ ስስታሞች ናቸው። ከነቢዩም ጀምሮ እስከ ካህኑ ድረስ እያንዳንዳቸው በተንኰል ይመላለሳሉ። **14** የሕዝቤንም ስብራት የሚፈውሱት ግን በጥቂቱ ነው፣
ሰላም ሳይኖር 'ሰላም ሰላም!' ይላሉ። **15** ርኩስን ነገር ስለሠሩ አፍረዋልን? በጭራሽ አልፈሩም፣ ማንኛውንም እፍረት አላወቁም። ስለዚህ በምቀጣቸው ጊዜ
ከሚወድቁ ጋር ይወድቃሉ። ይገለበጣሉ፣" ይላል እግዚአብሔር። **16** እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "በመንገድ ማቋረጫ ላይ ቁሙና ተመልከቱ፣
የቀደመችውንም መንገድ ጠይቁ። 'መልካሚቱ መንገድ ወዴት ናት?' በሉና በእርስዋ ላይ ሄዳችሁ ለነፍሳችሁ ዕረፍትን አግኙ። ሕዝቡ ግን፣ 'አንሄድባትም' አሉ።
17 እኔም የመለከቱን ድምፅ እንዲያደምጡ ጠባቂ ጉበኞችን ሾምሁላችሁ። እነርሱ ግን፣ 'አናደምጥም' አሉ። **18** አሕዛብ ሆይ፣ አድምጡ! ተመልከቱ፣
በእነርሱ ላይ የሚደርስባቸውን ትመሰክራላችሁ። **19** ምድር ሆይ፣ ስሚ! ተመልከቺ፣ የአሳባቸው ፍሬ የሆነ ጥፋትን በዚህ ህዝብ ላይ ላመጣ ነው። ለቃሌ
ወይም ለህጌ ምንም ትኩረት አልሰጡም፣ ነገር ግን ከዚያ ይልቅ አጣጣሉት።" **20** ከሳባ የሚቀርበው ዕጣን ለእኔ ምን ማለት ነው? ወይስ ከሩቅም አገር
የሆነው ጣፋጭ ሽታ ምንድነው? የሚቃጠለውን መሥዋዕታችሁን፣ እንዲሁም መስዋዕቶቻችሁን አልቀበለውም። **21** ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
'ተመልከቱ፣ በዚህ ሕዝብ ፊት ዕንቅፋቶችን አደርጋለሁ። አባቶችና ልጆች በአንድነት ይሰናከሉባቸዋል። ነዋሪዎችና ጎረቤቶቻቸው ይጠፋሉ። **22** እግዚአብሔር
እንዲህ ይላል 'ተመልከቱ፣ ሕዝብ ከሰሜን ምድር ይመጣል። ታላቅ ሕዝብም ከምድር ዳርቻ ይነሣል። **23** ቀስትንና ጦርን ያነሣሉ። ጨካኞች ናቸው፣ ምሕረትንም
የላቸውም። ድምፃቸው እንደ ባሕር ጩኸት ነው፣ በጽዮን ሴት ልጅ ላይ እንደሚዋጉ በፈረሶችም ላይ ይጋልባሉ።" **24** ስለ እነርሱ ወሬውን ሰምተናል። እጃችን
በጭንቀት ዝላለች። ምጥ ወላድን ሴት እንደሚይዛት ጭንቀት ይዞናል። **25** የጠላት ሰይፍና ሽብር ስለከበባችሁ ወደ ሜዳ አትውጡ፣ በመንገድም ላይ
አትሂዱ። **26** የሕዝቤ ሴት ልጅ ሆይ፣ ማቅ ልበሺና ለብቸኛ ልጅ መቀበሪያ አፈር ውስጥ ተንከባለዪ። አጥፊው በድንገት ይመጣብናልና ለራስሽ መራራ የሆነ
የቀብር ለቅሶን አድርጊ። **27** "ኤርምያስ፣ መንገዳቸውን እንድትመረምርና እንድትፈትን በሕዝቤ መካከል ብረትን እንደሚፈትን አድርጌሃለሁ። **28** እነርሱ ሁሉ
ሌሎችን የሚወነጅሉ እጅግ ዐመፀኞች ናቸው። በብልሹነት የሚመላለሱ ናስና ብረት ናቸው። **29** ወናፍ በሚያቃጥላቸው እሳት አናፋ፣ እርሳሱም በእሳቱ ቀለጠ።
ክፋት ስላልተወገደ፣ የማጥራቱ ሥራ በመካከላቸው ይቀጥላል። **30** እግዚአብሔር ጥሎአቸዋልና የተጣለ ብር ብለው ይጠሯቸዋል።"

Jeremiah 6:1

አጠቃላይ መረጃ፦
እግዚአብሔር እየተናገረ ነው።

ከኢየሩሳሌም በመሸሽ ... ደህንነትን አግኙ
እዚህ ላይ “ደህንነትን አግኙ” የሚለው ለመዳን እንዲችሉ ማድረግ የሚችሉትን ሁሉ ማድረግ እንዳለባቸው የሚያሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ኢየሩሳሌምን ለቅቆ በመውጣት ... ከአደጋ ዳኑ” ወይም “ከአደጋ መዳን እንድትችሉ ... ከኢየሩሳሌም ለቅቃችሁ ውጡ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

የቢኒያም ሕዝብ
እግዚአብሔር የሚናረው ለእነዚህ ነው።

በቴቁሔ መለከት ንፉ
መለከት ሰዎች ጥቃት እንደሚደርስባቸው ለማስጠንቀቅ የሚነፋ መሳርያ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ጥቃት እንደሚደርስባቸው ለሕዝቡ ለማስጠንቀቅ በቴቁሔ መለከትን ንፉ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ቴቁሔ
ይህ ከደቡባዊ ኢየሩሳሌም 18 ኪሎ ሜትር ያህል የሚርቅ የከተማ ስም ነው። የከተማው ስም ትርጉም “የሚነፋ መለከት” ማለት ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በቤትሐካሪም ላይ ምልክት ከፍ አድርጋችሁ አሳዩ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) ምልክቱ ከእሳት የሚወጣ ጢስ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ጠላት እየመጣ እንደሆነ ሕዝቡን ለማስጠንቀቅ ጢስ ወደ ላይ እንዲወጣ ለማድረግ በቤትሐካሪም እሳት አንድዱ” ወይም “ 2) ምልክቱ ሰንደቅ ዓላማ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ጠላት እየመጣ እንደሆነ ሕዝቡን ለማስጠንቀቅ በቤትሐካሪም ከተማ ሰንደቅ ዓላማ ከፍ አድርጉ”

ቤትሐካሪም
ይህ ከደቡባዊ ኢየሩሳሌም 10 ኪሎ ሜትር ያህል የሚርቅ የከተማ ስም ነው። የከተማው ስም ትርጉም “የወይን አትክልት ቦታ” ማለት ነው።

ክፋት ከሰሜን ይመጣል
እዚህ ላይ “ክፋት” የሚለው ጥፋትና ጥፋቱን የሚያመጡትን ሰዎች የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ጠላቶች ከሰሜን ይመጡና በእናንተ ላይ ጥፋት እንዲመጣ ያደርጋሉ” ወይም “ከሰሜን የሚመጡ ጠላቶች ያጠፉአችኋል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ታላቅ ጥፋት ይመጣል
ጥፋቱ እንዴት እንደሚመጣ በግልጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላቶች ይመጡና ያጠፉአችኋል” ወይም “ጠላቶች ይመጡና ያፈርሷችኋል” “(ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የጽዮን ሴት ልጅ፣ ውብና ሽሙንሙን
ጽዮን ለኢየሩሳሌም ሌላኛው ስም ነው። እግዚአብሔር ስለ ኢየሩሳሌም ሲናገር ሴት እንደሆነች አድርጎ ይገልጻታል። እርሱ ለኢየሩሳሌም ያለውን ፍቅር ለማሳየት እንደ ሴት ልጅ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእኔ ውድ ጽዮን፣ እንደ ውድና ሽሙንሙን ሴት የመሰልሽ” ወይም “የእኔ ውድ ጽዮን” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እረኞችና በጎቻቸው ወደ እነርሱ ይሄዳሉ
ብዙ ጊዜ ነገስታት የሕዝባቸው እረኞች እንደሆኑ ተደርጎ ይነገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገስታቱና ወታደሮቻቸው ወደ እነርሱ ይሄዳሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሷ ላይ በዙርያዋ በሙሉ ድንኳኖቻቸውን ይተክላሉ
“በእርሷ ላይ” የሚለው ቃል “ጽዮንን ለማጥቃት” ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሷን ለማጥቃት እነርሱ በጽዮን ዙርያ በሙሉ ድንኳኖችን ይተክላል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እያንዳንዱ መንጋውን ያሰማራል
እግዚአብሔር ነገስታቱ ምድሪቱን ለማጥፋት ጦር ሰራዊቶቻቸውን ስለመምራታቸው ሲናገር ሳር እንዲግጡ መንጎቻቸውን እንሚያሰማሩ እረኞች አድርጎ ገልጾአቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “እያንዳንዱ ንጉስ እንደ እረኛ ጦር ሰራዊቱን ይመራል” ወይም “እያንዳንዱ ንጉስ ጦር ሰራዊቱን ይመራል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በራሱ እጅ
እዚህ ላይ “እጅ” የሚለው አንድ ሰው በእጁ እንዲወስደው የተመደበለት የአንድ ነገር ድርሻ ይወክላል። እዚህ ላይ ንጉስ አሸንፎ እንዲይዘው የተመደበለት የመሬት ድርሻ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የመሬት ድርሻውን አሸንፎ ይይዛል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 6:4

አጠቃላይ መረጃ፡-
ከሚያጠቃው ጦር ሰራዊት ወገን የሆነው ንጉስ ከስልጣኑ ስር ላሉት ሰዎች ይናገራል።

ራሳችሁን አቅርቡ
ነገስታቱ ይህን እንደተናገሩ በግልጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገስታቱ ለጦር ሰራዊታቸው፣ ራሳችሁን አቅርቡ ብለዋቸዋል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ጦርነቱን ለማካሄድ ለአማልክቶቻችሁ ራሳችሁን አቅርቡ
የሚያጠቃው ጦር ሰራዊት ለአማልክቶቻቸው የአምልኮ ስርዓት በመፈጸምና መስዋዕት በማቅረብ አማልክቶቻቸው በጦርነቱ ጊዜ እንዲረዷቸው ማረጋገጫ ለመስጠት እየሞከሩ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ራሳችሁን በማንጻትና ለአማልክቶቻችሁ መስዋዕት በማቅረብ ለጦርነቱ ተዘጋጁ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ተነሱ፣ እናጥቃቸው
መነሳት ወይም መቆም መመልከትንና ማሰብን በማቆም ይልቁንም እርምጃ መውሰድ መጀመርን የሚያሳይ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ማሰብ እናቁምና ለማጥቃት እንጀምር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በቀትር እናጥቃ
“ኢየሩሳሌምን በቀትር እናጥቃት”

ቀኑ እየመሸ መሆኑ በጣም መጥፎ ነው፣ የማታውም ጥላ ረዝሟል
ምንም እንኳ ቀኑ እየጨለመ ቢመጣም ጦር ሰራዊታቸው መዋጋቱን እንዲቀጥል በሚፈልጉበት ጊዜ ነገስታቱ በቀኑ መጨረሻ ይህን ንግግር ይናገራሉ”

ቀኑ እየመሸ ነው
የቀኑ የመጨረሻው ብርሃን እየጨለመ ከመምጣቱ ጋር ተነጻጽሮ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ቀኑ እያለቀ ነው” ዌም “መጨለም ጀምሯል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ረዝሟል
“በጣም እየተለወጠ ነው” ወይም “በጣም እየረዘመ ነው”

በሌሊት
“ቢጨልምም በሌሊት ወቅት”

የእርሷ ምሽጎች
ሰዎች ብዙ ጊዜ ስለ ከተሞች ሲናገሩ ሴቶች እንደሆኑ አድርገው ይናገራሉ። እዚህ ላይ “የእርሷ” የሚለው ኢየሩሳሌምን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “የኢየሩሳሌም ጠንካራ ሕንጻዎች” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 6:6

የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙ ጊዜ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ጠቃሚ መልእክት ለማስተዋወቅ እነዚህን ቃላት ይጠቀማል።

የእርሷን ዛፎች ቁረጡ
እግዚአብሔር ይህንን የተናገረው ኢየሩሳሌምን ለማጥቃት ለሚመጣው ጦር ሰራዊት ነው። “የእርሷ” የሚለው የሚያመለክተው ኢየሩሳሌምን ነው፣ ብዙ ጊዜ ከተቲሞች ሴቶች እንደሆኑ ተደርጎ ይነገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “በኢየሩሳሌም ዙርያ ያሉትን ዛፎች ቁረጡ” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በኢየሩሳሌም ዙርያ የአፈር ድልድል ስሩ
የአፈር ድልድል ወደ ከተማይቱ ግንብ ጫፍ ላይ ወጥቶ በከተማይቱ ውስጥ ያለውን ሕዝብ ለማጥቃት ጠላት ከከተማይቱ ውጭ የሚገነባው ከፍተኛ የቆሻሻ ክምር ወይም በእንጨት የተሰራ መሰላል ነው።

ምክንያቱም በግፍ ተሞልታለች
እዚህ ላይ “በግፍ ተሞልታለች” የሚለው በዘያ የሚኖሩ ሰዎች ሁልጊዜ ሰዎችን መጨቆናቸውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ምክንቱም የእርሷ ሰዎች ሁልጊዜ እርስ በርሳቸው አንዱ ሌላውን ይጨቁናሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የውሃ ጉድጓድ ንጹህ ውሃ እንደሚያመነጭ፣ ይህች ከተማም እንዲሁ ክፋቷን ታፈልቃለች
እዚህ ላይ “ይህች ከተማም ክፋቷን ታፈልቃለች” የሚለው በከተማይቱ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ክፉ ነገሮችን መስራት መቀጠላቸውን ይወክላል” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዓመጽና ትርምስ በእርሷ ውስጥ ይሰማል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ በእርሷ ውስጥ ዓመጽና ትርምስ እሰማለሁ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በሽታና ቁስልም ሁልጊዜ በፊቴ ናቸው
እነዚህ ነገሮች በእግዚአብሔር ፊት “መሆናቸው” እርሱ እነዚህን ነገሮች ማየቱን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ ሁልጊዜ በሽታና ቁስል እመለከታለሁ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ኢየሩሳሌም ሆይ፣ ተግሳጽን ተቀበይ ... ማንም ሊኖርባት እስከማይችል ድረስ ምድርሽን ባዶ አደርጋለሁ
እዚህ ላይ እግዚአብሔር ለኢየሩሳሌም ሕዝብ ሲናገር ለከተማዋ ለራሷ እንሚናገር አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ተግሳጽ ተቀበይ፣ የኢየሩሳሌም ሕዝብ ሆይ ... ሰው እስከማይኖርባት ድረስ ምድርሽን ባዶ አደርጋለሁ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ተግሳጽ ተቀበይ
እዚህ ላይ “ተግሳጽ ተቀበይ” የሚለው ከተግሳጽ መማርን የሚያሳይ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ከተቀበልሽው ተግሳጽ ተማሪ” ወይም “እኔ አንቺን ስቀጣሽ ትክክለኛ የሆነውን ነገር ለማድረግ ተማሪ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ሰው የማይኖርባት ምድር
“በውስጧ የሚኖርባት ሰው የሌላት ምድር”

Jeremiah 6:9

ሰው ወይኑን እንደሚቃርም፣ እንደዚሁ እነርሱ ከእስራኤል የቀሩትን ሰዎች ፈጽሞ ይቃርሟቸዋል
እግዚአብሔር በምድሪቱ የቀሩትን ሰዎች ስለሚያጠቃው ጠላት ሲናገር በወይን አትክልቱ ውስጥ ያለውን ወይን ሌሎች ከሰበሰቡት በኋላ የቀረውን ወይን ጠላት እንደሚቃርም አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እስራኤልን ካጠፉ በኋላ፣ በዚያ በሕይወት የሚኖሩትን ሰዎች ለማጥቃት በእርግጠኝነት እንደገና ተመልሰው ይመጣሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ በእርግጠኝት
እዚህ ላይ “እነርሱ” የሚለው ቃል እስራኤልን ለማጥፋት እግዚአብሔር የሚልከውን ጠላት ያመለክታል።

ከወይን ቅርንጫፎቹ ወይን ለመልቀም እጅህን ወደ ቅርንጫፎቹ ደጋግመህ ዘርጋ
ሌሎች በወይን አትክልቱ ውስጥ ያለውን ወይን ከሰበሰቡ በኋላ ጠላት በዚያ የቀረውን የወይን ቃርሚያ እንደሚቃርም አድርጎ በማሳየት በእስራኤል የቀሩትን ሰዎች ጠላት እንዲያጠቃቸው እግዚአብሔር ትዕዛዝ ሰጥቷል። አማራጭ ትርጉም፡- “እንደገና መጥታችሁ የቀሩትን የእስራኤል ሰዎች አጥቋቸው” ወይም “የወይን ቃርሚያ ከቅርንጫፎቹ ለመቃረም አስቀድመው ወይን ወደሰበሰቡበት የወይን ቅርንጫፍ ተመልሰው እንደሚሄዱ ሰዎች እንደዚሁ እንደገና መጥታችሁ የቀሩትን ሰዎች አጥቋቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይሰሙ ዘንድ ለማን እናገራለሁ? ለማንስ አስጠነቅቃለሁ?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ከጠላቶቻቸው ጥቃት ከተረፉ በኋላም እንኳ ቢሆን ከእስራኤል ሰዎች አንዳቸውም እርሱን እንዳልሰሙት አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- ምናልባት ለሚሰሙ ሰዎች ይናገርና ያስጠነቅቅ ዘንድ አንድም ሰው ለእኔ አልቀረልኝም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ተመልከት
“እናንተ ራሳችሁ ማየት ትችላላችሁ”

የእነርሱ ጆሮዎች አልተገረዙም
ይህ እግዚአብሔርን ለመስማት እልኸኝነት የተሞላ እምቢተኝነታቸውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጆሮዎቻቸው ዝግ ናቸው” ወይም “ለመስማት እምቢ ብለዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የእነርሱ ጆሮዎች
“የእነርሱ” የሚለው ቃለ የእስራኤልን ሕዝብ ይወክላል።

የእግዚአብሔር ቃል ወደ እነርሱ መጥቷል
ይህ ፈሊጥ ጥቅም ላይ የዋለው እግዚአብሔር ለእነርሱ መልእክት እንደሰጣቸው ለማወጅ ነው። ይህን ያደረገው ደግሞ በነቢያት በኩል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ለእነርሱ መልእክት ልኳል” ወይም “እግዚአብሔር ለእነርሱ ተናግሯል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ይህን አይፈልጉትም
“የእግዚአብሔርን ቃል መስማት እነርሱ አይፈልጉም”

Jeremiah 6:11

ነገር ግን እኔ በእግዚአብሔር ቁጣ ተሞልቻለሁ
ይህን የሚናገረው ኤርምያስ ነው። እግዚአብሔር የተሰማውን ዓይነት ተመሳሳይ ቁጣ ኤርምያስም ተሰምቶታል። በጣም መቆጣቱን ሲናገር ውስጡ በቁጣ እንደተሞላ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔም እንደ እግዚአብሔር በጣም ተቆጥቻለሁ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ከመታገስ ደክሜአለሁ
ኤርምያስ የእግዚአብሔርን ቁጣ አለመግለጹ ቁጣውን በራሱ ውስጥ አምቆ እንደያዘው አድርጎ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይህን ቁጣ ባለመግለጥ እጅግ ደክሜአለሁ” ወይም “ስለዚህ ቁጣ አንዳችም ነገር ባለማድረጌ በጣም ደክሜአለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በመንገድ ላይ በሚገኙ ልጆችና በተሰበሰቡ ወጣቶችም ላይ አፍስሰው
እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ስለመቅጣቱ ሲናገር የእርሱ ቁጣ ኤርምያስ በሕዝቡ ላይ ሊያፈስሰው የፈለገው ፈሳሽ ነገር እነንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በመንገድ ላይ የሚገኙትን ልጆችና የተሰበሰቡትን ወጣቶች በቁጣ ቅጣቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እያንዳንዱ ባል ከሚስቱ ጋር ይወሰዳል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ምክንያቱም ጠላቶች እያንዳንዱን ባል ከሚስቱ ጋር ይይዟቸዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ረጅም ዓመታት የኖረ እያንዳንዱ ሽማግሌ ይወሰዳል
“ይወሰዳል” የሚለውን ቃል ከቀደመው ሀረግ በግልጽ መረዳት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ብዙ ዓመታት የኖረ እያንዳንዱ ሽማግሌ ይወሰዳል” ወይም “ብዙ ዓመታት የኖረውን እያንዳንዱ ሽማግሌ እነርሱ ይወስዱታል” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ረጅም ዓመታት የኖረ እያንዳንዱ ሽማግሌ ይወሰዳል
“ረጅም ዓመታት የኖረ” የሚለው ሀረግ ፈሊጥ ሲሆን ትርጉሙም “በጣም ያረጀ” ማለት ነው። ይህ “ሽማግሌ” የሚለውን ቃል ያጠናክረዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “እንዳንዱ በጣም ያረጀ ሰው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ቤቶቻቸው ለሌሎች ይሆናሉ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ቤቶቻቸው የሌሎች ሰዎች ንብረት ይሆናሉ” ወይም “የእነርሱ ሰዎች ቤቶቻቸውን ይወስዱታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሻዎቻቸውና ሚስቶቻቸውን በአንድ ላይ ለሌሎች ይሆናሉ
“ለሌሎች ይሆናሉ” የሚለው ሀረግ ከበፊቱ ሀረግ በሚገባ መረዳት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በተጨማሪ እርሻዎቻቸውና ሚስቶቻቸው ለሌሎች ይሆናሉ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

የምድሪቱን ነዋሪዎች በእጄ አጠቃቸዋለሁ
እዚህ ላይ “እጄ” የሚለው የእግዚአብሔርን ኃይል ይወክላል። የባዕድ ጦር ሰራዊት እስራኤልን ያጠቃበት ምክንያት እግዚአብሔር ይህን እንዲፈጽሙ ስላደረጋቸው ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በምድሪቱ የሚኖሩትን ሰዎች እኔ በራሴ ኃይል አጠቃቸዋለሁ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 6:13

ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ ሁሉም ስስታሞች ናቸው
“ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ” የሚለው ሀረግ የእስራኤል ሕዝብ በሙሉ ያለምንም ደረጃ ልዩነት “ሁሉ” በሚለው ቃል ውስጥ መካተታቸው የሚያሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ሁሉም፣ አነስተኛ ስልጣን ያለው ጨምሮ፣ እያንዳዱ ሰው ስስታም ነው” (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ታናሽ
ይህ አነስተኛ ስልጣን ያላቸውንና በሰዎች ፊት ብዙ ተቀባይነት የሌላቸውን ሰዎች ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “አነስተኛ ኃይል ያላቸው ሰዎች” (የስም ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)

ታላቅ
ይህ ከፍተኛ ስልጣንና ደረጃ ያላቸውን ሰዎች ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው ሰዎች” ወይም “በጣም ኃይለኛ የሆኑ ሰዎች” (የስም ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉም
“የእስራኤል ሕዝብ በሙሉ”

ተገቢ ላልሆነ ጥቅም ሲሉ ስስታሞች ናቸው
“ጥቅም” የሚለው ረቂቅ ስም “የበለጠ ገንዘብ ማግኘት” ወይም “የበለጠ ቁሳቁሶች ማግኘት” በሚለው ሀረግ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ለሰዎች ውሸትን በመናገር የበለጠ ገንዘብ ማግኘት ይፈልጋሉ” ወይም “የበለጠ ቁሳቁሶችን ማግኘት በጥብቅ ይፈልጋሉ፣ ከዚህ የተነሳ ይህን ለማግኘት ሲሉ ሰዎችን ያታልላሉ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉም ተንኮል ያደርጋሉ
“ሁሉም ሰዎችን ያታልላሉ” ወይም “ሁሉም ውሸታሞች ናቸው”

የሕዝቤን ቁስል በጥቂቱ ይፈውሳሉ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) ቁስል ከኃጢአታቸው የተነሳ የሚገጥማቸውን ችግር የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የሕዝቤ ችግር ቀለል እንደሆነ ያስባሉ” ወይም 2) ቁስል የሕዝቡን ኃጢአት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የሕዝቤ ኃጢአት እንደ ትንሽ ቁስል ቀላል እንደሆነ ያስባሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቁስልን በጥቂቱ ይፈውሳሉ
እዚህ ላይ “ጥቂት” የሚለው ቃል ቁስል ቀላል እንደሆነና ብዙ አስቸጋሪ እንዳልሆነ አድርገው በማየት ተገቢ እንክብካቤ አለመስጠትን ይወክላል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰላም ሳይሆን ‘ሰላም፣ ሰላም’ ይላሉ
“‘ሁሉም ደህና ነው፣ ሁሉም ደህና ነው’ ይላሉ፣ ነገር ግን ደህና አይደለም”

አስጸያፊ ነገሮችን ሲሰሩ አፍረዋልን?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ሕዝቡ በኃጢአታቸው ባለማፈራቸው ምክንያት ቁጣውን ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በጣም አስደንጋጭ ኃጢአት ሰርተዋል፣ ነገር ግን ምንም አያፍሩም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

እንዴት ማፈር እንዳለባቸው አያውቁም
ሰው ሲያፍር ብዙ ጊዜ ፊቱ ይቀላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ፊታቸው እንኳ ፈጽሞ አልቀላም”

ከሚወድቁት ጋር ይወድቃሉ
እዚህ ላይ “ይወድቃሉ” የሚለው ይገደላሉ የሚለውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ከተገደሉት ጋር አብረው አንድ ላይ ይገደላሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በምቀጣቸውም ጊዜ ይዋረዳሉ
እዚህ ላይ “ይዋረዳሉ” የሚለው መጥፋትን ይወክላል። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በምቀጣቸው ጊዜ አጠፋቸዋለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 6:16

እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
እግዚአብሔር ይህን ለማን እንደሚናር በግልጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ይህን የሚናገረው ለእስራኤል ሕዝብ ነው” ወይም “እግዚአብሔር ይህን የሚናገረው ለሕዝቡ ነው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መንታ መንገድ ላይ ቁሙ ተመልከቱም ... በእርሷ አንሄድባትም
መንገድ ሰዎች የሚኖሩበትን የሕይወት ዘይቤ የሚያመለክት ነው። እግዚአብሔር የእስራኤል ሕዝብ ሕይወታቸውን የሚኖሩበትን መልካሚቱን የሕይወት መንገድ ምን እንደሆነች እንዲጠይቁና በዚያ መንገድ እንዲኖሩ መጠየቅ ይፈልጋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መንታ መንገድ
ይህ ሁለት መንገዶች የሚገናኙበት ቦታ ያመለክታል።

የቀደመችውን መንገድ ጠይቁ
የቀደመችው መንገድ የአባቶቻቸውን ባህርይ፣ ከረጅም ጊዜ በፊት አባቶቻቸው እንዴት እንደኖሩ የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “አባቶቻችሁ ስለሄዱበት መንገድ ጠይቁ” ወይም “አባቶቻችሁ እንዴት እንደኖሩ ጠይቁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ መልካም መንገድ ወዴት ነው?
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) “ይህ መልካም መንገድ” ሊኖሩበት የሚገባውን መልካም የሕይወት መንገድ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ልንርበት የሚገባ ይህ መልካም መንገድ ወዴት አለ?” ወይም 2) “ይህ መልካም መንገድ” በረከት የሚያመጣውን የሕይወት መንገድ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “መልካ ወደሆነው ነገር የሚወስደን መንገድ ወዴት አለ” ወይም “ልንኖርበት የሚገባ በረከት የሚያመጣው መንገድ ወዴት አለ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንግዲያው በእርሷ ሂዱ
“እንግዲያው በዚያች መንገድ ሂዱ።” በዚያች መንገድ መሄድ በዚያች መንገድ መኖርን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እንግዲያው በዚያ መንገድ ኑሩ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ አንሄድም
ይህ በዚያች መንገድ አለመኖርን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እኛ በዚያች መንገድ አንኖርም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የመለከት ድምፅን እንድትሰሙ ጠባቂዎችን አቆምሁላችሁ
እግዚአብሔር በአደጋ ላይ ያሉትን ሕዝብ ለማስጠንቀቅ ነቢያቱ የተላኩ ጠባቂዎች እንደሆኑ አድርጎ ይናራል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለእናንተ አቆምሁላችሁ
“እናንተ” የሚለው ቃል የእስራኤልን ሕዝብ ያመክለታል።

መለከቱን እንድትሰሙ
“የመለከቱን ድምጽ እንድትሰሙ።” እግዚአብሔር ለነቢያቱ ስለሰጠው የማስጠንቀቂያ መልእክት ሲናገር መልእክቱ ስለሚመጣው አደጋ ሕዝቡን ለማስጠንቀቅ የሚነፋ መለከት እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። ነቢያቱ ይህንን ማስጠንቀቂያ ሊሰሙና ስለሁኔታው ለሕዝቡ ሊናገሩ ይገባል።

እንግዲህ ሕዝቦች ሆይ ስሙ! እናተ ምስክሮች ሕዝቡ ምን እንደሚገጥማቸው አስተውሉ፣ ምድር! ተመልከቺ
እነዚህ ሦስት አረፍተ ነገሮች በሙሉ እግዚአብሔር በአመጸኛው በይሁዳ ሕዝብ ላይ የሚያደርገውን ነገር ምስክር እንዲሆኑ ለሌሎች መንግስታት ሕዝቦች የሚናገሩ ናቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “እናንተ ሌሎች ሕዝቦች፣ በሕዝቤ ላይ የማደርገውን ነገር ተመልከቱ” (ትይዩነት/ተመሳሳይነት እና እንቶኔ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንግዲህ ሕዝቦች ሆይ ስሙ!
“እንግዲህ ሕዝቦች ሆይ፣ እኔ የምናገረውን ስሙ”

እኔ በዚህ ሕዝብ ላይ ጥፋትን አመጣባቸዋለሁ
“በቅርቡ ይህን ሕዝብ በጽኑ እቀጣዋለሁ”

እናንተ ምስክሮች
“እናተ ምስክሮች የሆናችሁ”

በእነርሱ ላይ ምን እንደሚሆን
“እነርሱ” የሚለው ቃል የእስራኤልን ሕዝብ ይወክላል።

ምድር ስሚ
“ምድር” የሚለው ቃል በምድር የሚኖሩትን ሕዝብ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በምድር የምትኖሩ ሕዝቦች ስሙ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የሃሳባቸው ፍሬ
እዚህ ላይ “ፍሬ” የሚለው ቃል የሚያስከትለውን ውጤት ወይም መዘዝ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሃሳባቸው የሚያስከትለው መዘዝ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለቃሌ ወይም ለሕጌ ትኩረት ስላልሰጡ ይልቁንም ደግሞ ስላልተቀበሉት
እዚህ ላይ “ለቃሌ ትኩረት ስላልሰጡት” የሚለው እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር አለመስማታቸውን የሚያመለክት ሲሆን “ስላልተቀበሉት” የሚለው ደግሞ የእግዚአብሔርን ሕግ ለመታዘዝ አለመፈለጋቸውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ የተናገርሁትን አይሰሙም። ይልቁንም ሕጌን አልታዘዙም” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 6:20

ዕጣን ከሳባ ምድር፣ ጣፋጭ ቅመም ከሩቅ አገር ቢመጣ ምን ይጠቅመ**m**ኛል?
እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመገሰጽ እነዚህን ጥያቄዎች ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፡- “ዕጣን ከሳባ ምድርና ከሩቅ አገር የሚመጣው ጣፋጭ ቅመም ለእኔ ምንም አይጠቅመኝም።” ወይም “ከሩቅ አገር የመጣው የቅመማችሁ ጣፋጭ ሽታ አልፈልገውም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ ጣፋጭ ሽታዎች
ሰዎች ጣፋጭ ሽታ ያላቸው ቅመሞችን ለእግዚአብሔር እንደ መስዋእት ያቃጥሉ ነበር።

በእኔ ዘንድ ተቀባይነት የላቸውም
“እኔን አያስደስተኝም” ወይም “እኔን ደስ አያሰኘኝም”

ተመልከቱ፣ እኔ
“አስተውሉ፣ ምክንያቱም እኔ የምናገረው እውነት በጣም ጠቃሚ ነው፣ እኔ”

በዚህ ሕዝብ ላይ መሰናክልን አስቀምጣለሁ
“በዚህ ሕዝብ ፊት ለፊት መሰናክል አስቀምጣለሁ።” እግዚአብሔር በእስራኤል ሕዝብ ላይ እንዲመጣ ስለሚያደርገው ችግር ሲናገር ሰዎች ተደናቅፈው የሚወድቁበት እንቅፋት አድርጎ ገልጾታል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ በዚያ ላይ ይደናቀፋሉ
እዚህ ላይ “ይደናቀፋሉ” የሚለው በችግሮቹ ምክንያት እንደሚጎዱ የሚያሳይ ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አባቶችና ወንዶች ልጆች በአንድ ላይ
“ይደናቀፋሉ” የሚለውን ሃሳብ ከቀደመው ቃል መረዳት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- አባቶችና ወንዶች ልጆች በአንድ ላይ ይደናቀፋሉ” ወይም “አባቶችና ወንዶች ልጆች በአንድ ላይ ይጎዳሉ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ነዋሪዎችና ጎረቤቶቻቸው
“ጎረቤቶችና ጓደኞቻቸው”

ሕዝብ እየመጣ ነው
የእነርሱ ዓላማ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሕዝብ እናተን ለማጥቃት እየመጣ ነው” ወይም “ጦር ሰራዊት እየመጣ ነው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ታላቅ ሕዝብ
እዚህ ላይ “ሕዝብ” የሚለው የሕዝቡን ጦር ሰራዊት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የታላቅ ሕዝብ ጦር ሰራዊት” (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከምድሪቱ ሩቅ ክፍል እየተነሳሳ ነው
“እየተነሳሳ” የሚለው አንድን ነገር ለማድረግ መዘጋጀትን የሚወክል ነው። ማራጭ ትርጉም፡- “ከምድሪቱ ሩቅ ክፍል ለመምጣት እየተዘጋጀ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 6:23

ቀስትና ጦር ይዘዋል
“ወታደሮቹ ቀስትና ጦር ይይዛሉ”

ድምጻቸው እንደተናወጠ ባህር ነው
ወታደሮቹ የሚኖራቸው ትልቅ ድምጽ ከባህር ከሚነሳው ታላቅ ድምጽ ጋር ተነጻጽሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “የጩኸታቸው ድምጽ በጣም ከፍተኛ ነው፣ እንደ ባህር ድምጽ ነው” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በፈረሶች ላይ ሆነው ይጋልባሉ፣ ለጦር እንደተዘጋጀ ሰው ተሰለፉ
“ተሰለፉ” የሚለው ራሳቸውን አቀናጅተዋል፣ ፈረሶቻቸውን በሰልፍ ይጋልባሉ ማት ነው። “ለጦር እንደተዘጋጀ ሰው” የሚለው ለመዋጋት መዘጋጀታቸውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በተመደበላቸው ሰልፍ ፈረሶቻቸውን ይጋልባሉ፣ እናንተን ለመዋጋት ተዘጋጅተዋል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ ሰምተናል
“እኛ” የሚለው ምናልባት ኤርምያስንና የይሁዳ ሕዝብን ሳያመለክት አይቀርም።

እጆችን በጭንቀት ደክማለች
“እጆቻችን ከጭንቀት የተነሳ ደክመዋል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጭንቀት ይዞናል
የነበራቸው ከፍተኛ የጭንቀት ስሜት ሲገለጽ ጭንቀቱ እንደያዛቸው ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “በጣም አስደንጋጭ ጭንቀት ይሰማናል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ልጅ እንደምትወልድ ሴት
ጠላት እነርሱን ለማጥቃት ከመምጣቱ የተነሳ የተሰማቸው ጭንቀት አንዲት ሴት ልጅ ለመውለድ ምጥ ሲይዛት ከሚሰማት ስሜት ጋር ተነጻጽሯል። አማራጭ “ልጅ ለመውለድ እንደምታምጥ ሴት” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 6:25

አጠቃላይ መረጃ፡-
ኤርምያስ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ ይናገራል። አንዳንድ ትርጉሞች እግዚአብሔር ለኢየሩሳሌም ሕዝብ እየተናገረ ነው ብለው ተርጉመውታል።

የጠላት ሰይፍና ድንጋጤ ከብቧችኋል
“የጠላት ሰይፍ” የሚለው ሀረግ ከሰይፎቻቸው ጋር ለማጥቃት የተዘጋጁ ጠላቶችን ይወክላል። “ድንጋጤ” የሚለው ረቂቅ ስም ሰዎች እንዲፈሩ የሚያደርጉ ነገሮችን ያመለክታል። ይህ ደግሞ ከቅጽል ጋር ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላቶች ከሰይፎቻቸው ጋር በሁሉም ስፍራ ስላሉ እያንዳንዱ ሰው በፍርሃት ይንቀጠቀጣል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ and ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የሕዝቤ ሴት ልጅ
እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንደ ሴት ጠርቶ በመናገር ለእነርሱ ያለውን ፍቅር ኤርምያስ ያሳያል። ይህን ተመሳሳይ ሀረግ በኤርምያስ 4:11 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ “እናንተ ለእኔ እንደ ሴት ልጅ የሆናችሁ ሕዝቤ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ማቅ ልበሺ በአመድም ላይ ተንከባለይ
ሕዝብ እነዚህን ነገሮች የሚያደርገው ከመጠን በላይ የሆነ ሃዘን እንደተሰማቸው ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ማቅ በመልበስና በአመድ ላይ በመንከባለል ከመጠን በላይ እንዳዘንሽ አሳዪ” (ምሳሌያዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ለአንድያ ልጅ እንደሚደረግ ልቅሶ፣ መራራ ልቅሶ አልቅሺ
ኤርምያስ የሕዝቡን ታላቅ ሃዘን እናት አንድያ ልጇ ሲሞትባት ከሚሰማት ሃዘን ጋር ያነጻጽረዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድያ ልጅሽ እንደሞተባት እናት ሆነሽ መራራ ልቅሶ አልቅሺ” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አጥፊው በድንገት በላያችን ይመጣልና
“ምክንያቱም የጠላት ጦር ሰራዊት እኛን ለማጥቃት በድንገት ይመጣልና”

Jeremiah 6:27

አጠቃላይ መረጃ፡-
x

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 7

1 ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ኤርምያስ የመጣ ቃል ይህ ነው፣ **2** በእግዚአብሔር ቤት በራፍ ላይ ቁም! እንዲህ በል፣ 'ይሁዳ ሁሉ ሆይ፣ እግዚአብሔርን ልታመልኩ በእነዚህ በራፎች የምትገቡ ሆይ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ። **3** የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ መንገዳችሁንና ሥራችሁን መልካም አድርጉ፣በዚህም ስፍራ መኖር እንድትቀጥሉ አደርጋችኋለሁ። **4** ራሳችሁን አታላይ በሆኑ ቃሎች ላይ ታምናችሁ፣ "የእግዚአብሔር መቅደስ! የእግዚአብሔር መቅደስ! የእግዚአብሔር መቅደስ!" አትበሉ። **5** መንገዳችሁንና ሥራችሁን ፈጽማችሁ መልካም ብታደርጉ፤ በሰውና በጎረቤቱ መካከል ቅን ፍርድ ብትፈርዱ፤ **6** በምድሪቱ የሚቆየውን እንግዳ፣ ወላጅ አልባውን፣ ወይም መበለቲቱንም ባትበዘብዙ፣ በዚህም ስፍራ ንጹሕ ደምን ባታፈስሱ፣ ለገዛ ጉዳታችሁ እንዲሆንባችሁ ሌሎች አማልክትን ባትከተሉ፤ **7** ያን ጊዜ ከጥንቱ ጊዜ ጀምሮ እስከ ለዘላለም ለአባቶቻችሁ በሰጠኋቸው ምድር በዚህ ስፍራ አሳድራችኋለሁ። **8** እነሆ! በማይረዳችሁ የሐሰት ቃል እየታመናችሁ ናችሁ። **9** ትሰርቃላችሁ፣ ትገድላላችሁ፣ ታመነዝራላችሁ? ደግሞም በሐሰትም ትምላላችሁ፣ ለበኣልም ታጥናላችሁ፣ የማታውቋቸውንም ሌሎች አማልክት ትከተላላችሁ? **10** ከዚያም መጥታችሁ ስሜም በተጠራበት በዚህ ቤት በፊቴ ቆማችሁ፣ እነዚህን ሁሉ ጥፋቶች ማድረግ እንድትችሉ "ድነናል፣" አላችሁ። **11** ይህስ ስሜ የተጠራበት ቤት በዓይናችሁ ፊት የሌቦች ዋሻ ሆኖአልን? ነገር ግን፣ እነሆ፣ እኔ አይቻለሁ፣ ይላል እግዚአብሔር። **12** 'ስለዚህ በቀድሞ ዘመን ስሜን ከመጀመሪያ ወዳሳደርሁበት በሴሎ ወደ ነበረው ስፍራዬ ሂዱ፣ ከሕዝቤም ከእስራኤል ክፋት የተነሣ ያደረግሁበትን እዩ። **13** ስለዚህ አሁንም፣ ይህን ሥራችሁን ሁሉ ስላደረጋችሁ፣ በተደጋጋሚ ጊዜ ተናገርኳችሁ፣ እናንተ ግን አልሰማችሁም። በጠራኋችሁም ጊዜ፣ አልመለሳችሁም። **14** ስለዚህ፣ በሴሎ እንዳደረግሁ፣ እንዲሁ ስሜ በተጠራበት በምትታመኑበት ቤት፣ ለእናንተና ለአባቶቻችሁም በሰጠኋችሁ ስፍራ ላይ እንዲሁ አደርጋለሁ። **15** የኤፍሬምንም ዘር የሆኑትን ወንድሞቻችሁን ሁሉ እንደ ጣልሁ፣ እንዲሁ ከፊቴ እጥላችኋለሁ። **16** ደግሞም አንተ፣ ኤርምያስ አልሰማህምና ለዚህ ሕዝብ አትጸልይ፣ ስለ እነርሱም ልመናና ጸሎት አታድርግ፣ አትማልድላቸው። **17** እነርሱ በይሁዳ ከተሞች ውስጥና በኢየሩሳሌም ጎዳናዎች ላይ የሚያደርጉትን አታይምን? **18** ያስቈጡኝ ዘንድ፣ ለሰማይ ንግሥት እንጐቻ እንዲያደርጉ ለሌሎችም አማልክት የመጠጥ ቍርባን እንዲያፈስሱ፣ ልጆች እንጨት ይሰበስባሉ፣ አባቶችም እሳት ያነድዳሉ፣ ሴቶችም ዱቄት ያቦካሉ። **19** በእውነት እኔን ያስቈጣሉን? ይላል እግዚአብሔር፤ ለእነርሱስ እፍረት እንዲሆንባቸው የሚያስቆጡት ራሳቸውን አይደለምን? **20** እንግዲያው ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ 'ተመልከቱ፣ ቍጣዬና መዓቴ በዚህ ስፍራ ላይ ይፈስሳል፣ በሰውና በአውሬው ላይ፣ በዱር ዛፎችና በምድር ፍሬ ላይ ይፈስሳል። ይነድዳል፣ መቼም አይጠፋም።' **21** የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ 'ለመሥዋዕታችሁ የሚቃጠለውን መሥዋዕታችሁን ጨምሩ፣ ከዚያም ላይ ሥጋውን ጨምሩ። **22** አባቶቻችሁን ከግብጽ ምድር ባወጣኋቸው ቀን፣ የትኛውንም ነገር ከእነርሱ አልጠየቅሁም። ስለሚቃጠል መሥዋዕትና ስለ ሌላ መሥዋዕት አላዘዝኋቸውምም። **23** ይህንን ትእዛዝ ብቻ ሰጠኋቸው፣ "ቃሌን ስሙ፣ እኔም አምላክ እሆናችኋለሁ እናንተም ሕዝብ ትሆኑኛላችሁ። መልካምም ይሆንላችሁ ዘንድ ባዘዝኋችሁ መንገድ ሁሉ ሂዱ።" **24** ነገር ግን በክፉ ልባቸው አሳብና እልከኝነት ሄዱ ወደ ፊትም ሳይሆን ወደ ፊታቸው ሳይሆን ወደ ኋላቸው ሄዱ እንጂ አልሰሙም ጆሮአቸውንም አላዘነበሉም። **25** አባቶቻችሁ ከግብጽ ምድር ከወጡበት ቀን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ፣ አገልጋዮቼን፣ ነቢያትን ሁሉ ልኬባችሁ ነበር። እነርሱን ተግቼ ላክሁባችሁ። **26** ነገር ግን አልሰሙኝም። ምንም ትኩረት አልሰጡም። ይልቁን፣ አባቶቻቸውም ካደረጉት ይልቅ የባሰ አደረጉ። **27** እነዚህን ቃሎች ሁሉ ንገራቸው፣ ነገር ግን አይሰሙህም። እነዚህን ነገሮች አውጅላቸው፣ ነገር ግን አይመልሱልህም። **28** የአምላኩን የእግዚአብሔርን ቃል ያልሰማ፣ ተግሣጽንም ያልተቀበለ ሕዝብ ይህ ነው። እውነት ጠፍቶአል ከአፋቸውም ተቈርጦአል በላቸው። **29** ፀጕርሽን ቍረጪ፣ ተላጪው፣ ጣዪውም። በወናዎች ኮረብቶችም ላይ ሙሾን አውጪ። እግዚአብሔር በቍጣው ይህንን ትውልድ ጥሎአልና፣ ትቶታልምና ። **30** የይሁዳ ልጆች በፊቴ ክፉን ነገር ሠርተዋል፣ ይላል እግዚአብሔር፤ ያረክሱትም ዘንድ ስሜ በተጠራበት ቤት ርኵሰታቸውን አኑረዋል። **31** ከዚያም ቶፌት ውስጥ በቤን ሄኖም ሸለቆ መስገጃዎችን ገነቡ። እኔም ያላዘዝሁትንና ፈጽሞ በልቤ ያላሰብሁትን ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን በእሳት ያቃጥሉ ዘንድ ይህንን አድርገዋል። **32** ስለዚህ፣ ተመልከቱ፣ ቶፌት ወይም የቤን ሄኖም ሸለቆ ተብሎ ዳግመኛ አይጠራም። የእርድ ሸለቆ ይባላል፤ የሚተርፍ ስፍራ እስኪታጣ ድረስ በቶፌት በድኖችን ይቀብራሉ ይላል እግዚአብሔር። **33** የዚህም ሕዝብ ሬሳ ለሰማይ ወፎችና ለምድር አራዊት መብል ይሆናል፣ የሚያስፈራራቸውም አይኖርም። **34** ምድሪቱም ወና ትሆናለችና ከይሁዳ ከተሞችና ከኢየሩሳሌም ጎዳናዎች ላይ የእልልታን ድምፅና የደስታን ድምፅ፣ የወንድ ሙሽራን ድምፅና የሴት ሙሽራን ድምፅ አጠፋለሁ።

Jeremiah 7:1

ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ኤርምያስ የመጣው ቃል እንዲህ የሚል ነው፣ ቁም
ይህ ፈሊጥ ጥቅም ላይ የዋለው ከእግዚአብሔር የመጣውን ልዩ መልእክት ለማስተዋወቅ ነው። ይህን ተመሳሳይ ሀረግ በኤርምያስ 1:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ለኤርምያስ የሰጠው መልእክት ይህ ነው። እርሱ እንዲህ አለ ‘ቁም’” ወይም “እግዚአብሔር ለኤርምያስ የተናገረው መልእክት ይህ ነው፦ ‘ቁም’” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳ ሕዝብ ሁላችሁ
“እናንተ የይሁዳ ሕዝብ ሁላችሁ”

Jeremiah 7:3

አያያዥ ሀሳብ፦
እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ የሚነገረውን መልእክቱን ለኤርምያስ መስጠቱን ቀጥሏል።

የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙ ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከእግዚአብሔር የመጣውን በጣም ጠቃሚ መልእክት ለማስተዋወቅ ነው። ይህንን በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

መንገዳችሁንና ሥራችሁን አሳምሩ እኔም እንድትኖሩ አደርጋችኋለሁ
“መንገዳችሁንና ሥራችሁን የምታስተካሉ ከሆነ እኔም እንድትኖሩ አደርጋችኋለሁ

በዚህ ስፍራ
ይህ በይሁዳ ምድር ማለት ነው፣ በቤተ መቅደስ አይደለም

እያላችሁ ራሳችሁ በሐሰት ቃል አትታመኑ
ይህ “ራሳችሁ” የሚለው ከባለቤቱ ጋር የሚጣቀስ ተውላጠ ስም ለእስራኤላውያን ወደፊት የሚመጣ የግል አደጋ እንዳለ አጽንዖት የሚሰጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እያላችሁ፣ እናንተን እንዲጠብቃችሁ በሐሰት ቃል አትታመኑ” (ከባለቤቱ ጋር የሚጣቀስ ተውላጠ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ!የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ! የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ!
ቤተ መቅደሱ ባለቤቱ እግዚአብሔር ስለሆነና የእርሱን ሕልውና የሚወክል ስለሆነ እርሱ ይጠብቀዋል፣ የይሁዳም ሕዝብ ደህንነት ይሆንለታል። “የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ” የሚለው ለምን ሦስት ጊዜ እንደተደጋገመ ተቀባይነት ሊኖራቸው የሚችሉት ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፡- 1) የተደጋገመው አጽንዖት ለመስጠት ነው ወይም 2) የተደጋጋመው እንደ ቤተ መቅደሱ ስነ ስርአት ተደርጎ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ይህ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነው ስለዚህ አንድም ሰው ሊያፈርሰው እንደማይችል ሙሉ በሙሉ እርግጠኞች ነን፤ እኛ ደግም እንጠበቃለን።” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 7:5

አያያዥ ሀሳብ፡-
እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ የሚነገረውን መልእክቱን ለኤርምያስ መስጠቱን ቀጥሏል።

መንገዳችሁንና ስራችሁን አሳምሩ
“መንገዳችሁንና ስራችሁን አስተካክሉ።” ይህንን በኤርምያስ 7:3 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

ሙሉ በሙሉ ትክክለኛ ፍትህ አድርጉ
“ፍትህ” የሚለው ረቂቅ ስም “ፍረዱ” በሚለው ግስ በመጠቀም መተርጎም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በትክክል ፍረዱ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

መጻተኛውን አትጨቁኑ
“መጻተኛውን በአግባቡ ያዙ”

ወላጅ አልባ
ወላጆቹ የሞቱበት ልጅ

ንጹህ ደም ባታፈስሱ
እዚህ ላይ ንጹህ ደም ማፍሰስ ሞት የማይገባቸውን ሰዎች መግደልን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ንጹህ ሰዎችን መግደል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ሌሎች አማልክት መከተል
እዚህ ላይ መከተል የሚለው ለማገልገልና ለመታዘዝ ዓላማ አድርጎ ተከትሎ ለመሄድ ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሌሎች አማልክትን ማገልገል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እናተን የሚጎዳችሁ
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚያ እናንተን ይጎዷችኋልና” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚህ ስፍራ
እዚህ ላይ “በዚህ ስፍራ” የሚለው የይሁዳን ምድር ያመለክታል።

አኖራችኋለሁ
“መኖር እንድትቀጥሉ አደርጋችኋለሁ”

ከጥንት ጀምሮ እስከ ዘላለም
“ከጥንት ጀምሮ እንዲሁም በቀጣይነት።” የእነርሱ ቋሚ ንብረት ትሆን ዘንድ እግዚአብሔር ምድሪቱን ለይሁዳ ሕዝብ ሰጥቷል ማለት ነው።

Jeremiah 7:8

አያያዥ ሀሳብ፡-
እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ የሚነገረውን መልእክቱን ለኤርምያስ መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡-
በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ “እናንተ” የሚለው ቃል የይሁዳ ሕዝብን ያመለክታል።

እነሆ!
እዚህ ላይ “እነሆ” የሚለው ቃል ከዚህ በኋላ የሚከተለውን መረጃ እንደሚገባ ልብ እንድንል ያነቃናል።

ትሰርቃላችሁ፥ ትገድላላችሁ፥ ታመነዝራላችሁ? በሐሰትም ትምላላችሁ፥ ... የማታውቋቸውንም እንግዶች አማልክት ትከተላላችሁ?
እየፈጸሟቸው ያሉትን ኃጢአቶች እግዚአብሔር የሚያውቅ መሆኑን አስረግጦ ለማለፍ እነዚህ ጥያቄዎች አዎንታዊ መልስ ይጠብቃሉ። ይህ እንደ አረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ትሰርቃላችሁ፥ ትገድላላችሁ፥ ታመነዝራላችሁ። በሐሰት ትምላላችሁ፥ ... የማታውቋቸውንም እንግዶች አማልክት ትከተላላችሁ።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በሐሰት ትምላላችሁ
“በመኃላችሁ እንኳ ትዋሻላችሁ”

እንግዶች አማልክት ትከተላላችሁ
እዚህ ላይ መከተል ለማገልገልና ለመታዘዝ ዓላማ በማድረግ ተከትሎ ለመሄድ ምትክ ስም ነው። ይህንን በኤርምያስ 7:6 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “ሌሎች አማልክት ታገለግላላችሁ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ታዲያ መጥታችሁ በፊቴ ትቆሙና ... እነዚህን አስጸያፊ ነገሮች ሁሉ ታደርጋላችሁ?
በቃልና በድርጊት የሚፈጽሙትን ግብዝነት እግዚአብሔር የሚያውቅ መሆኑን አስረግጦ ለማለፍ እነዚህ ጥያቄዎች አዎንታዊ መልስ ይጠብቃሉ። ይህ እንደ አረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እንደዚያ ከሆነ መጥታችሁ በፊቴ ትቆማላችሁ ... እነዚህን አስጸያፊ ነገሮች ሁሉ ታደርጋላችሁ።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በስሜ በሚጠራው ቤት
ይህ ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የእኔ የሆነው ቤት” ወይም “እኔን የምታመልኩበት ቤተ መቅደስ” (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ በስሜ የሚጠራው ቤት በእናንተ ዓይን የወንበዴዎች ዋሻ ሆኖአልን?
እነርሱ ስለ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ምን እንደሚያስቡ እግዚአብሔር የሚያውቅ መሆኑን አስረግጦ ለማለፍ እነዚህ ጥያቄዎች አዎንታዊ መልስ ይጠብቃሉ። ይህ በዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስሜን የተሸከመው ይህ ቤት በእናንተ ዓይን የወንበዴዎች ዋሻ ነው!” ወይም “በስሜ የተጠራው ይህ ቤት ወንበዴዎች ሊሔዱና ሊሸሸጉ የሚችሉበት ስፍራ እንደሆነ የምታስቡ ትመሰስላላችሁ!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ስሜን የተሸከመው ይህ ቤት
የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የእግዚአብሔርን ስም እንደተሸከመ ተደርጎ ተነግሯል። ይህ ከዚህ በፊት ካው ጥቅስ “በስሜ በተጠራው ይህ ቤት” ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ወንበዴዎች
የሚሰርቁና የሚዘርፉ ሃይለኛ ሰዎች

ነገር ግን እነሆ አይቻለሁ
“ነገር ግን እኔ በእርግጠኝነት እናንተ የምትሰሩት ምን እንደሆነ ተመልክቻለሁ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 7:12

አያያዥ ሀሳብ፡-
እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ የሚያስተላልፈውን መልእክት ለኤርምያስ መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡-
በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ያሉት “እናንተ” እና “የእናንተ” የሚሉት ቃላቶች የይሁዳን ሕዝብ ያመለክታሉ።

በቀድሞ ዘመን ስሜ እንዲያድርበት ወደፈቀድሁበት በሴሎ ወደነበረው ስፍራ ሂዱ
እዚህ ላይ “ስሜ እንዲያድርበት ወደፈቀድሁበት” የሚለው ፈሊጥ ሲሆን ይህ ስፍራ እግዚአብሔር ይመለክበት የነበረ ነው የሚል ትርጉም አለው። አማራጭ ትርጉም፡- “ቀድሞ ሕዝቤ እኔን ለማምለክ እኔ ወደፈቀድሁበት በሴሎ ወዳለው ስፍራ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህን ነገሮች ሁሉ ስላደረጋችሁ
“ምክንያቱም እነዚህን ነገሮች ሁሉ ስታደርጉ ስለነበራችሁ”

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደገና ደግሜ ደጋግሜ
እነዚህ ሁለት የተጣመሩ ስሞች ፈሊጥ ሲሆኑ አንድ ነገር ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ ተደርጓል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በተደጋጋሚ” ወይም “ያለማቋረጥ” (ጥምር ቃል እና ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ በስሜ የተጠራው ቤት
ይህ ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ምትክ ስም ነው። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። ይህንን በኤርምያስ 7:10 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “የእኔ የሆነው ይህ ቤት” ወይም “እኔን የምታመልኩበት ይህ ቤተ መቅደስ” (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 7:16

አጠቃላይ መረጃ፡-
እግዚአብሔር ስለ ይሁዳ ሕዝብ ለኤርምያስ ይነግረዋል። በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ “ይህ ሕዝብ” የሚለው የይሁዳ ሕዝብን ያመለክታል።

ለዚህ ሕዝብ አትጸልይ፣ የልቅሶ ልመና ወደ እኔ አታቅርብ ወይም እነርሱን ወክለህ ጸሎት አታድርግ፣ ወደ እኔ አቤቱታ አታቅርብ
እነዚህ አራት ነገሮች እያንዳንዱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ የተደጋገሙት አጽንዖት ለመስጠት ነው። (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

የልቅሶ ልመና ማቅረብ
“በሃዘን መጮህ”

እነርሱን ወክለህ
“ለእነርሱ ጥቅም” ወይም “ለእነርሱ”

አቤቱታ ወደ እኔ ማቅረብ
“ወደ እኔ መማለድ”

በይሁዳ ከተሞችና በኢየሩሳሌም መንገዶች ላይ ምን እንደሚሰሩ አትመለከትምን?
ይህ ጥያቄ አዎንታዊ መልስ ይጠብቃል፤ ጥያቄው የተጠየቀው እነዚህን ነገሮች በኤርምያስ ዘንድ ትኩረት እንዲያገኙ ለማድረግ ነው። ይህ እንደ አረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በይሁዳ ከተሞችና በኢየሩሳሌም መንገዶች ላይ ምን እንደሚሰሩ ተመልከት!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

እሳቱን ማንደድ
“እሳቱን መጀመር”

ዱቄት ይለውሳሉ
በእጅ ሊጥ ማዋሃድ

ሊጥ
ለመጋገር የሚጠቅም የዱቄትና የፈሳሽ ወፍራም ውህድ

የሰማያት ንግስት
ይህ የሐሰተኛ አምላክ ስም ነበር። አማራጭ ትርጉም፡- “‘የሰማያት ንግስት’ የምትባል ሐሰተኛ አምላክ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔን ያናድዳሉ
“እኔን ያስቆጣሉ”

Jeremiah 7:19

አያያዥ ሀሳብ፡-
እግዚአብሔር ስለ ይሁዳ ሕዝብ ለኤርምያስ መናገር ቀጥለሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡-
በእነዚህ ጥቅሶች “እነርሱ” እና “ራሳቸው” የሚሉት የይሁዳን ሕዝብ ያመለክታል።

በእውነት እነርሱ እኔን ያስቆጡኛልን?
ይህ ጥያቄ አሉታዊ መልስ ይጠብቃል። ይህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ በእርግጥ ሊያስቆጡኝ አይችሉም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
ኤርምያስና የይሁዳ ሕዝብ እርሱ የሚናገረውን ነገር በጥንቃቄ ይሰሙ ዘንድ እግዚአብሔር ስለራሱ ሲናገር ሌላ ሰው እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። ይህንን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ያወጀው ይህን ነው” ወይም “ “እግዚአብሔር የተናገረው ይህን ነው” (ተውላጠ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እፍረታቸው በራሳቸው ላይ ይሆን ዘንድ እኔን ያስቆጡኝ እነርሱ ራሳቸው ኤይሉምን?
ይህ ጥያቄ አዎንታዊ መልስ ይጠብቃል። ይህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እፍረታቸው በራሳቸው ላይ ይሆን ዘንድ ራሳቸውን እያስቆጡ ነው” ወይም “እነርሱ ራሳቸውን ችግር ውስጥ እያስገቡና በራሳቸው ላይ እፍረት እያመጡ ነው!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች እና ከባለቤቱ ጋር የሚጣቀስ ተውላጠ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እፍረት በእነርሱ ላይ ነው
“እፍረት” የሚለው ረቂቅ ስም “አፈሩ” በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ አፈሩ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ተመልከት
ይህ ቃል እዚህ ላይ የአንድ ሰውን ትኩረት ቀጥሎ ወደሚነገረው ቁም ነገር ለመሳብ ጥቅም ላይ ውሏል። አማራጭ ትርጉም፡- “እድምጥ” ወይም “እኔ ለአንተ ለምነግርህ ነገር ትኩረት ስጥ”

ቁጣየና መዓቴ በዚህ ስፍራ ላይ ይጎርፋል
እግዚአብሔር ስለ ቁጣው ሲገልጽ ሊፈስ የሚችል ነገር እንደሆነ አድርጎ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ ይህን ስፍራ እቀጣለሁ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ቁጣና መዓት
እነዚህ ቃላቶች በመሰረታዊነት ተመሳሳይነት ያላቸው ሲሆኑ የእግዚአብሔርን ቁጣ ጥልቀት አጽንዖት ይሰጣሉ። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

አጎርፋለሁ
“አፈስሳለሁ”

ይነድዳል ደግሞም አይጠፋም
እግዚአብሔር ስለ ቁጣው ሲናገር ቁጣው ሊጠፋ የማይችል እሳት እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ቁጣየን አንድም ሰው ሊያስቆመው አይችልም” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ፈጽሞ አይጠፋም
“ፈጽሞ መንደድ አይቆምም”

Jeremiah 7:21

አያያዥ ሀሳብ፡-
እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ ያለውን መልእክት ለኤርምያስ መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡-
በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ “እናንተ” እና “የእናንተ” የሚሉት የይሁዳን ሕዝብ ያመለክታሉ።

የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙ ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከእግዚአብሔር የመጣውን በጣም ጠቃሚ መልእክት ለማስተዋወቅ ነው። ይህንን በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

የሚቃጠለውን መስዋዕታችሁን በሌሎች መስዋዕታችሁ ላይ ጨምሩ፣ ስጋውንም ራሳችሁ ብሉ
ይህ መስዋዕታቸው በሙሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንደሌለው አጽንዖት የሚሰጥ ምጸታዊ ዓረፍተ ሃሳብ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሂዱና የሚቃጠል መስዋዕቶቻችሁን ከመስዋዕታችሁና ከስጋው ጋር አብራችሁ ብሉት” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

ድምጼን ስሙ
እዚህ ላይ የእግዚአብሔርን ድምጽ መስማት ቃሉን መስማትና ለተናገረው ደግሞ መታዘዝ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የተናገርሁትን ስሙ ደግሞም ታዘዙ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ባዘዝኋችሁ መንገድ ሁሉ ሂዱ
እግዚአብሔር ቃሉን ስለመታዘዝ ሲናገር ሰው በመንገድ እንደሚሄድ እንደዚሁ አንድ ሰው በቃሉ መሄድ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ ያዘዝኋችሁን ሁሉ አድርጉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 7:24

አያያዥ ሀሳብ፡-
እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ ያለውን መልእክት ለኤርምያስ መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡-
በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ “እናንተ” እና “የእናንተ” የሚሉት የይሁዳን ሕዝብ ያመለክታሉ። “እነርሱ” የይሁዳ ሕዝብ አባቶችን የሚያመለክት ነው።

እነርሱ አይሰሙም ወይም ትኩረት አይሰጡም
እነዚህ ሀረጎች የሚናገሩት ስለ አንድ ነገር ነው፣ የተደጋገሙት አጽንዖት ለመስጠት ነው። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

በክፉ ልባቸው አሳብና እልከኝነት
“በራሳቸው እቅድ ምክንያቱም ክፉና እልኸኞች ነበሩ”

ወደፊት ሳይሆን ወደኋላ ሄዱ
ይህ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) እርሱን በጉጉት ከመታዘዝ ይልቅ ለእግዚአብሔር ትኩረት ለመስጠት እምቢተኞች ሆኑ። አማራጭ ትርጉም፡- “ወደ እኔ ከመቅረብ ይልቅ ከእኔ ርቀው ሄዱ” ወይም 2) ከማሻሻል ይልቅ በክፋታቸው እየጨመሩ ሄዱ። አማራጭ ትርጉም፡- “የተሻሉ ከመሆን ይልቅ በክፋታቸው እየጨመሩ ሄዱ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አባቶቻችሁ ከግብጽ ምድር ከወጡበት ቀን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ
ይህ ጅምላ ገለጻ ሲሆን ሃሳቡም በዚህ የጊዜ ርዝመት በየቀኑ ለማለት ሳይሆን በጥቅሉ በዚህ ሁሉ የጊዜ ርዝመት ለማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አባቶቻችሁ ከግብጽ ምድር ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ” (ግነት/ግነታዊ ቋንቋ እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱን በቋሚነት ልኬባችኃለሁ
“እነርሱን ደጋግሜ ልኬአቸዋለሁ” ወይም “እነርሱን በተደጋጋሚ ልኬአቸዋለሁ”

እነርሱ አንገታቸውን አደነደኑ
ይህ ፈሊጥ ሲሆን ግትሮች ነበሩ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ግትሮች ሆኑ” ወይም “እኔን ተቋቋሙኝ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

የባሰ ክፉ ነበሩ
“እያንዳንዱ ትውልድ የበለጠ ክፉ ነበረ”

Jeremiah 7:27

አያያዥ ሀሳብ፡-
እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ ያለውን መልእክት ለኤርምያስ መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡-
በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ “ለእነርሱ” እና “እነርሱ” የሚሉት ቃላቶች የይሁዳን ሕዝብ ያመለክታሉ።

ስለዚህ እነዚህን ቃላት በሙሉ ለእነርሱ ትናገራለህ ነገር ግን አንተን አይሰሙህም። እነዚህን ነገሮች ለእነርሱ ትናገራለህ ነገር ግን ለአንተ አይመልሱህም።
እነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ሃሳብ አላቸው፣ ሁለተኛው ለመጀመርያው መልእክት አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእኔን መልእክት ንገራቸው ነገር ግን እነርሱ አንተን አይሰሙህም ለአንተም አይመልሱልህም” (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

የአምላኩ የእግዚአብሔር ድምጽ
እዚህ ላይ “የአምላኩ የእግዚአብሔር ድምጽ” የሚለው እግዚአብሔር የተናገረውን ይወክላል። ይህን በኤርምያስ 3:25 ላይ እንዴት እንደተረገምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “አምላኩ እግዚአብሔር የተናገረው ነገር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እውነት ጠፍቶአል ከአፋቸውም ተቈርጦአል
እግዚአብሔር ስለ እውነት ሲናገር ሕዝቡ ሊያጠፉት የሚችሉትና መነገሩንም ሊያስቆሙት የሚችሉት ነገር እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሕዝቡ እውነትን አጥፍተዋል፣ ከአፋቸውም ቆርጠውታል” ወይም “ሕዝቡ ውሸት ብቻ ይናገራሉ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

እውነት ጠፍቶአል
“እውነት” የሚለው ረቂቅ ስም “እውነተኛ” በሚለው ቅጽል በመጠቀም ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እውነተኛ የሆነው ነገር ጠፍቶአል” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 7:31

አያያዥ ሀሳብ፡-
እግዚአብሔር የይሁዳ ሕዝብ የሰራቸውን ክፉ ነገሮች መግለጹን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡-
በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ “እነርሱ” እና “የእነርሱ” የሚሉት ቃላቶች የይሁዳን ሕዝብ ያመለክታሉ።

የቶፌት ከፍተኛ ስፍራዎች
ይህ የእስራኤል ሕዝብ ልጆቻቸውን በእሳት በማቃጠል ለሐሰተኛ አማልክት መስዋዕት አድርገው ያቀረቡበት የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የቤን ሄኖም ሸለቆ
ይህ ሕዝቡ ለሐሰተኛ አማልክት መስዋዕት ያቀረቡበት ከኢየሩሳሌም ከተማ በደቡብ በኩል የሚገኝ የሸለቆ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በእሳት
ይህ አመልካች መረጃ ለሐሰተኛ አማልክት እንደ መስዋዕት ይቃጠሉ እንደነበር የሚያሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እንደ መስዋዕት” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከቶ በአእምሮየ ያለሰብሁትን
እዚህ ላይ “አእምሮ” የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ሃሳብ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከቶ ስለዚህ ነገር ፈጽሞ አላሰብሁም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህ ተመልከቱ
እዚህ ላይ “ተመልከቱ” የሚለው ቃል ለሚከተለው ነገር አጽንዖትን ይጨምራል። አማራጭ ትርጉም፡- “በእርግጥ”

የማይባልበት ቀናቶች ይመጣሉ
የወደፊት ጊዜ “ቀናቶች እየመጡ እንደሆነ” ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለወደፊት እንዲህ የማይባልበት” ወይም “እንዲህ የማይባልበት ጊዜ ይኖራል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህ ወዲህ ... ተብሎ አይጠራም
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች ከእንግዲህ እንዲህ ... ብለው አይጠሩትም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

አስከሬኖች ይቀብራሉ
“የሞቱ ሰዎችን ይቀብራሉ”

የሚቀር ምንም ክፍል የለም
“የሚቀር ምንም ቦታ የለም”

Jeremiah 7:33

አያያዥ ሀሳብ፡-
እግዚአብሔር በይሁዳ ሕዝብ ላይ የሚያመጣውን ፍርድ መናገሩን ቀጥሏል።

አስከሬኖች
“የሞቱ አካላት”

ይህ ሕዝብ
“የይሁዳ ሕዝብ”

የሰማይ ወፎች
“የሰማያት ወፎች” የሚለውን በኤርምያስ 4:25 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

የምድር አውሬዎች
“የምድሪቱ የዱር እንስሳት”

የሚያባርራቸው
“የሚያስፈራራቸው”

አጠፋለሁ
“አስወግዳለሁ”

የደስታ ድምጽና የተድላ ድምጽ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ሙሉ በሙሉ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ የተደጋገሙት አጽንዖት ለመስጠት ነው። “ደስታ” እና “ተድላ” የሚሉት ረቂቅ ስሞች “መደሰት” በሚለው ግስ እና “ደስተኛ” በሚለው” ቅጽል በመmጠቀም ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “የሚደሰቱ እና የደስተኛ ሰዎች ድምጽ” (ጥምር ቃል የሚለውን እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የሙሽራ ድምጽ እና የሙሽሪት ድምጽ
ይህ በሰርግ ስነ ስርዓት ላይ ለሚከናወኑ ነገሮች ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰርግ ስነ ስርዓት የሚያከብሩ ሰዎች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ባድማ ትሆናለች
“ባድማ” የሚለው ረቂቅ ስም “ሰው የማይኖርበት” በሚለው ቅጽል በመጠቀም ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰው የማይኖርባት ትሆናለች” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 8

1 በዚያን ዘመን፥ የይሁዳን ነገሥታት አጥንትና የመኳንንቶቹን አጥንት፥ የካህናቱን አጥንትና የነቢያቱን አጥንት፥ የኢየሩሳሌምንም ሰዎች አጥንት ከመቃብራቸው ያወጣሉ ይላል እግዚአብሔር። **2** በተከተሉአቸው፣ ባገለገሏቸውና በፈለጉአቸው፣ ባመለኳቸውም በፀሐይና በጨረቃ በሰማይም ሠራዊት ሁሉ ፊት ይዘረጉአቸዋል። አጥንቶቻቸው አይሰባሰቡም ወይም በድጋሚ አይቀበሩም። በምድር ፊት ላይ እንደ ጕድፍ ይሆናሉ። **3** እኔም ባሳደድኋቸው ስፍራ ሁሉ የቀሩት፣ ከዚህ ክፉ ሕዝብ የተረፉት ቅሬታዎች ሁሉ፣ ከሕይወት ይልቅ ሞትን ይመርጣሉ ይላል የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር። **4** እንዲህም ትላቸዋለህ፣ 'እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ የትኛውም የወደቀ ሰው አይነሣምን? የጠፋስ ለመመለስ አይሞክርምን? **5** ይህ የኢየሩሳሌም ሕዝብ ዘላቂ በሆነ አለመታመን ስለ ምን ወደ ኋላው ይመለሳል? ተንኰልን ይዞአል ንስሃ ለመግባትም እንቢ ብሎአል። **6** አደመጥሁ ሰማሁም፣ ትክክለኛ ነገር አልተናገሩም፤ ማንም ስለ ክፋቱ ንስሃ አልገባም፣ ማንም "ምን አድርጌአለሁ?" አላለም። ወደ ጦርነት እንደሚሮጥ ፈረስ ሁላቸውም በየመንገዳቸው ሄዱ። **7** ሽመላ በሰማይ ትክክለኛ ጊዜዋን አውቃለች፤ ዋኖስና ጨረባ ዋልያም ያውቃሉ። እነርሱ ወደ ሚሰደዱበት የሚሄዱት በትክክለኛ ጊዜ ነው፣ ሕዝቤ ግን የእግዚአብሔርን ፍርድ አላወቁም። **8** እናንተስ፣ "ጥበበኞች ነን! የእግዚአብሔርም ሕግ ከእኛ ጋር ነው" እንዴት ትላላችሁ? በእርግጥ ተመልከቱ! የአታላይ ጸሐፊ ብዕር ማታለልን አድርጎአል። **9** ጥበበኞች ያፍራሉ። ደንግጠውማል ተጠምደዋል። ተመልከቱ! የእግዚአብሔርን ቃል ጥለዋል፣ ስለዚህ ጥበባቸው ምን ጥቅም አለው? **10** ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ ሁሉ ስስታሞች ናቸውና፣ ከነቢዩም ጀምሮ እስከ ካህኑ ድረስ ሁሉ ያታልላሉና፣ ስለዚህ ሚስቶቻቸውን ለሌሎች፥ እርሻቸውንም ለሚወርሱባቸው እሰጣለሁ። **11** ቀላል ነገር እንደሆነ በማድረግ የሕዝቤን ሴት ልጅ ስብራት በጥቂቱ ይፈውሳሉ። ሰላም ሳይሆን፣ "ሰላም፣ ሰላም" ይላሉ። **12** አስጸያፊ ነገርን ስለ ሠሩ አፍረዋልን? ምንም አላፈሩም። ትሕትናም አልነበራቸውም። ስለዚህ በሚቀጡ ጊዜ ቀድሞውኑ ከወደቁት ጋር ይወድቃሉ ይላል እግዚአብሔር። **13** ፈጽሜ አጠፋችኋለሁ፣ ይላል እግዚአብሔር፤ በወይን ላይ ፍሬ፣ በበለስ ዛፍ ላይ በለስ አይሆንም። ቅጠልም ይረግፋልና የሰጠኋቸውም ያልፋልና። **14** ለምን ዝም ብለን እንቀመጣለን? በአንድነት ኑ፤ ወደ ተመሸጉ ከተሞች እንሂድ፣ በዚያም በሞት ዝምተኞች እንሆናለን። እግዚአብሔር ዝም ያሰኘናልና። ስለ በደልነው መርዝ አጠጥቶናል። **15** ሰላምን በተስፋ ተጠባበቅን፣ ነገር ግን መልካም ነገር አልተገኘም። የፈውስ ጊዜን በተስፋ ተጠባበቅን፣ ነገር ግን ሽብር እንደሆነ ተመልከቱ። **16** የፈረሰኞች ድምጽ ከዳን ተሰማ። ከአርበኞች ፈረሶች ማሽካካት የተነሣ ምድር ሁሉ ተንቀጠቀጠች። ምድሪቱንና በእርስዋም ያለውን ሁሉ፥ ከተማይቱንና የሚኖሩባትንም ሊበሉ ይመጣሉና። **17** ተመልከቱ፣ አስማት የማይከለክላቸውን እባቦችንና እፉኝቶችን እሰድድባችኋለሁ። እነርሱም ይነድፉአችኋል" ይላል እግዚአብሔር። **18** ኅዘኔ ፍጻሜ የለውም፣ ልቤም ታምሞአል። **19** ተመልከቱ! እግዚአብሔር በጽዮን የለምን? ወይስ ንጉሥዋ በእርስዋ ዘንድ የለምን? የሚል የሕዝቤ ሴት ልጅ ጩኸት ድምፅ ከሩቅ ምድር ተሰማ። በተቀረጹ ምስሎቻቸውና በባዕድ ከንቱ ጣዖታት ያስቈጡኝ ስለ ምንድር ነው? **20** መከሩ አልፎአል፣ በጋው አብቅቷል። እኛ ግን አልዳንነም። **21** በሕዝቤ ሴት ልጅ ስብራት እኔ ተሰብሬአለሁ። በደረሰባት ነገር በጭንቀት አለቅሳለሁ፤ ጠቁሬማለሁ። **22** በገለዓድ መድኃኒት የለምን? ወይስ በዚያ ፈዋሽ የለምን? የሕዝቤ ሴት ልጅ ፈውስ ስለ ምን አልሆነም?

Jeremiah 8:1

አያያዥ ሀሳብ፦
እግዚአብሔር በይሁዳ ሕዝብ ላይ የሚያመጣውን ፍርድ መናገሩን ቀጥሏል።

በዚያን ጊዜ
በኤርምያስ 7:32 እስከ 34 ውሰጥ ያሉት ክስተቶች በሚፈጸሙበት ጊዜ።

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ያመጡአቸዋል
እዚህ ላይ “እነርሱ” የሚለው ቃል የይሁዳን ሕዝብ ጠላቶች ይወክላል።

መኳንንቶቻቸው
“ነገስታቶቻቸው” ወይም “መሪዎቻቸው”

እነርሱን ይዘረጉአቸዋል
“እነርሱን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በቀደመው ጥቅስ የተዘረዘሩትን ሰዎች አጥንቶች ነው።

እነርሱ በተከተሏቸውና በአገለገሏቸው እንዲሁም አብረው በተጓዟቸውና በፈለጓቸው፣ ባመለኳቸው
እዚህ ላይ “እነርሱ” የሚለው ቃል የይሁዳ ሕዝብን የሚያመለክት ነው። እነዚህ ሦስት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ የተደጋገሙት አጽንዖት ለመስጠት ነው።

አብረው በተጓዟቸው
ይህ ለማገልገልና ለማምለክ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። ይህንን በኤርምያስ 2:23 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አጥንቶች አይሰበሰቡም ወይም እንደገና አይቀበሩም
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አጥንቶቻቸውን ማንም ሰው አይሰበስበውም ወይም እንደገና አይቀብሯቸውም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ተጣለ ጕድፍ በምድር ገጽ ላይ ይበተናል
አጥንቶች በምድር ላይ ካለ ጕድፍ ተነጻጽረዋል፣ ይህ ንጽጽር አጥንቶቹ አስጸያፊ እንደሚሆኑና እንደገና እንደማይቀበሩ አጽንዖት ለመስጠት ነው። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በምድረ ገጽ ላይ
“በምድር ዙርያ ሁሉ”

እነርሱን ባሳደድኋቸው ስፍራ ሁሉ
“እነርሱን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የይሁዳ ሕዝብን ነው።

ከዚህ ክፉ ሕዝብ አሁንም የቀሩት ሁሉ ከሕይወት ይልቅ ለራሳቸው ሞትን ይመርጣሉ
“ከዚህ ክፉ ሕዝብ የቀሩት ሁሉ በሕይወት ከሚኖሩ መሞት ይፈልጋሉ”

ይህ የሰራዊት ጌታ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ተመሳሳይ ቃላትን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Jeremiah 8:4

አያያዥ ሀሳብ፡-
እግዚአብሔር በይሁዳ ሕዝብ ላይ የሚያመጣውን ፍርድ መናገሩን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡-
በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ “ለእነርሱ” እና “እነርሱ” የሚሉት ቃላቶች የይሁዳን ሕዝብ ያመለክታሉ።

ለእነርሱ እንዲህ በላቸው
እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ ምን መናገር እንዳለበት ለኤርምያስ እየነገረው ነው።

የወደቀ ሰው አይነሳምን? የሳተስ ሰው ለመመለስ አይሞክርምን? ታዲያ የኢየሩሳሌም ሕዝብ ዘወትር ስለ ምን ባለመታመን ፊቱን አዙሮ ወደ ኋላው ይመለሳል?
እነዚህ ጥያቄዎች የይሁዳ ሕዝብ ይኖሩበት የነበረው መንገድ ትርጉም የሚሰጥ እንዳልሆነ ዋነኛ ነጥቡን በሚገባ ግልጽ አድርገዋል። እነዚህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ሰው ሲወድቅ እንደገና ሊነሳ እንደሚችል፣ አንድ ሰው ከመንገድ ሲስት እንደገና ወደ መንገዱ ለመመለስ እንደሚሞክር ታውቃላችሁ። ይህ የኢየሩሳሌም ሕዝብ ባለመታመን ፊቱን አዙሮ ወደ ኋላው መሄዱ ትርጉም የማይሰጥ ነው።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ኢየሩሳሌም
እዚህ ላይ “ኢየሩሳሌም” የሚለው ቃል የይሁዳን ሕዝብ በሙሉ ወካይ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ይሁዳ” (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ተንኮልን የሙጥኝ ብለው ይዘዋል
የይሁዳ ሕዝብ ይሰሩት የነበረው ነገር ተንኮልን አጥብቀው እንደያዙና ሊተዉት ፈቃደኛ እንዳልሆኑ ተደርጎ ተነግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ተንኮልን የሙጥኝ ብለው ይዘዋል
“ተንኮል” የሚለው ረቂቅ ስም ሰው ሊይዘው የሚችለው አንድ ግዑዝ ቁስ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። ይህ “አታለለ” በሚለው ግስ በመጠቀም ሊተረጎም ይችላል። አንድን ነገር የሙጥኝ ብሎ መያዝ ለመውደድ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ከሚያታልላቸው ነገር ነገር ለመመለስ እምቢ አሉ” ወይም “የሚያታሉሏቸውን ሰዎች ወደዱ” (ረቂቅ ስሞች እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 8:6

አያያዥ ሀሳብ፡-
እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ የሚናገረውን መልእክት ለኤርምያስ መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡-
በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ “እነርሱ” እና “ለእነርሱ” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት የይሁዳ ሕዝብን ነው።

አደመጥሁ ሰማሁም
እነዚህ ሁለት ነገሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ የተደጋገሙት አጽንዖት ለመስጠት ነው። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ትክክለኛውን ነገር አይናገሩም
“ትክክለኛውን ነገር አይሉም”

ስለ ክፋቱ
“ክፋት” የሚለው ረቂቅ ስም “ክፉ” የሚለውን ቅጽል በመጠቀም መተርጎም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ በመሆኑ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ምን አድርጌአለሁ?
ይህ አመልካች መረጃ የሚያሳየው ይህ ጥያቄ የይሁዳ ሕዝብ ሊጠይቀው የሚገባ እንደነበር ነው። ይህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ ክፉ ስራ ሰርቻለሁ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ እና መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ወደፈለጉት ይሄዳሉ
“በራሳቸው መንገድ ይሄዳሉ”

ወደ ጦርነት እንደሚሮጥ ፈረስ
ሕዝቡ የራሳቸውን መንገድ ለመከተል የነበራቸው ጉጉት ወደ ጦርነት ለመሮጥ ከተዘጋጀ ፈረስ ጉጉት ጋር ተነጻጽሯል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ፈረስ
ወንድ ጎልማሳ ፈረስ

ሽመላ እንኳ በሰማይ የተወሰነ ጊዜዋን ታውቃለች፤ ዋኖስ፣ ጨረባና ዋርዳም
ይህ አመልካች መረጃ የሚያሳየው እንደነዚህ የመሳሰሉ አእዋፍ የሚሰደዱበትን ማለትም በተለያዩ የዓመቱ ወቅት ምግብ ለመፈለግና ለመባዛት ከአንድ ስፍራ ወደ ሌላ ስፍራ የሚጓዙበትን ትክክለኛ ጊዜ እንደሚያውቁ ነው። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሽመላ ... ዋኖስ፣ ጨረባና ዋርዳ
እነዚህ በሙሉ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚሰደዱ የተለያዩ ዓይነት አእዋፍ ናቸው። (የማይታወቁ ነገሮችን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ በትክክለኛው ጊዜ ወደ ስደት ይሄዳሉ፤ ነገር ግን ሕዝቤ የእግዚአብሔርን ስርዓት አያውቁም።
ይህ አመልካች መረጃ የሚያሳየው ሕዝቡ በተፈጥሮ የእግዚአብሔርን ስርዓት ማወቅ እንደነበረባቸው ነው። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ስደታቸው ይሄዳሉ
“ስደት” የሚለው ረቂቅ ስም “ተሰደዱ” በሚለው ግስ በመጠቀም መተርጎም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ ይሰደዳሉ” ወይም “ከአንድ ክልል ወደ ሌላ ክልል ይበርራሉ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 8:8

አያያዥ ሀሳብ፡-
እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ የሚናገረውን መልእክት ለኤርምያስ መስጠቱን ቀጥሏል።

“ጥበበኞች ነን፣ የእግዚአብሔር ሕግ ከእኛ ጋር ነው” እንዴት ትላላችሁ?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የሚጠይቀው የይሁዳ ሕዝብ ምን እየተናገሩ እንደነበር እንዲያስቡ ለማድረግ ነው። ይህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እናንተ ጥበበኞች እንደሆናችሁ ታስባላችሁ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ሕግ ከእናንተ ጋር በመኖሩ ነው።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ እንዴት ትላላችሁ
“እናንተ” የሚለው የይሁዳ ሕዝብን ይወክላል።

በእርግጥ፣ ተመልከቱ!
እነዚህ ቃላቶች አድማጩ ለሚቀጥለው መልእክቶች የቅርብ ትኩረት እንዲሰጥ የሚናገር ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የጸሐፊዎቻችሁ ሐሰተኛ እስክርቢቶ
እስክርቢቶ ጸሐፊዎች የሚጽፉአቸውን ቃላት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጸሐፊዎቻችሁ የሚጽፉአቸው የሐሰት ነገሮች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ሐሰትን ፈጥረዋል
“ሐሰተኛ ሃሳቦች ለእናንተ ሰጥተዋል”

ጥበበኛ ሰዎች ያፍራሉ
ይህ ምጸት ነው ምክንያቱም ጥበበኞች ሰዎች ሁልጊዜ ስለ ጥበባቸው ይከበራሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህ ጥበበኞች እንደሆኑ የሚያስቡ ሰዎች ሃፍረት ይሰማቸዋል” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

ደንግጠዋል
ፈርተዋል ወይም ተርበድብደዋል

እነሆ!
“ትኩረት ስጡ!

ስለዚህ ጥበባቸው ምን ይጠቅማቸዋል?
ይህ ጥያቄ አሉታዊ መልስ ይጠብቃል፤ ዓላማውም አድማጮቹ የእግዚአብሔርን ቃል ተቃውመው እያሉ እነርሱ ጥበብ ብለው የሚናገሩት በእርግትም ጠቃሚነቱ ምን ያህል ትንሽ እንደሆነ እንዲያስቡት ለመማድረግ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ ጥበብ ነው ብለው የሚያስቡት ነገር ምንም መልካም ነገር አይሰራላቸውም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ምክንያቱም ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ ሁሉ ተገቢ ላልሆነ ጥቅም ስስታሞች ናቸው ከነቢዩም ጀምሮ እስከ ካህኑ ድረስ ሁሉ በተንኰል ያደርጋሉና
ይህን በኤርምያስ 6:13 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልክት።

ምክንያቱም ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ ሁሉ ስስታሞች ናቸው
“ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ” የሚለው ሀረግ የይሁዳ ሕዝብ በሙሉ ያለ ምንም የማንነትና የኑሮ ደረጃ ልዩነት “ሁሉ” በሚለው ቃል ውስጥ መካተታቸውን የሚያሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- ምክንያቱም ስልጣን ያላቸው፣ ስልጣን የሌላቸውና ሌሎቹንም እያንዳንዳቸውን ጨምሮ ሁሉም ስስታሞች ናቸው” (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ታናሹ
ይህ ከፍተኛ ስፍራ የሌላቸውና በሰው እይታ ግምት ውስጥ የማይገቡ ሰዎችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- ዝቅተኛ ስልጣን ያላቸው” (የስም ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)

ታላቁ
ይህ ከፍተኛ ስፍራ ያላቸውንና በሰው ዘንድ ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸውን ሰዎች ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከፍተኛ ስልጣን ያላቸው ሰዎች” ወይም “ከፍተኛ ኃይል ያላቸው ሰዎች” (የስም ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉም
“የይሁዳ ሕዝብ በሙሉ”

ተገቢ ላልሆነ ጥቅም ሲሉ ስግብግብ ናቸው
“ጥቅም” የሚለው ረቂቅ ስም “የበለጠ ገንዘብ ማግኘት” ወይም “የበለጠ ቁሳቁስ ለማግኘት” በሚሉት ሀረጎች ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለሰዎች ውሸት በመናገር ብዙ ገንዘብ ያገኛሉ” ወይም “ብዙ ቁሳቁስ ለማግኘት በብርቱ ይፈልጋሉ፣ እነዚህን ለማግኘት ደግሞ ሰዎችን ያታልላሉ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉም ያጭበረብራሉ
“ሁሉም ሰዎችን ያታልላሉ” ወይም “ሁሉም ውሸታሞች ናቸው”

Jeremiah 8:11

አያያዥ ሀሳብ፡-
እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ የሚናገረውን መልእክት ለኤርምያስ መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡-
በእነዚህ ጥቅሶች “እነርሱ”፣ የእነርሱ” እና ለእነርሱ” የሚሉት ቃላት የይሁዳን ሕዝብ ያመለክታሉ።

የሕዝቤን ቁስል በጥቂቱ ይፈውሳሉ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ቁስል ከኃጢአታቸው የተነሳ የሚገጥማቸውን ችግር የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የሕዝቤ ችግር ቀለል እንደሆነ ያስባሉ” ወይም 2) ቁስል የሕዝቡን ኃጢአት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሕዝቤ ኃጢአት እንደ ትንሽ ቁስል ቀላል እንደሆነ ያስባሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቁስልን በጥቂቱ ይፈውሳሉ
እዚህ ላይ “ጥቂት” የሚለው ቃል ቁስል ቀላል እንደሆነና ብዙ አስቸጋሪ እንዳልሆነ አድርገው በማየት ተገቢ እንክብካቤ አለመስጠትን ይወክላል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰላም ሳይሆን ‘ሰላም፣ ሰላም’ ይላሉ
“‘ሁሉም ደህና ነው፣ ሁሉም ደህና ነው’ ይላሉ፣ ነገር ግን ደህና አይደለም”

አስጸያፊ ነገሮችን ሲሰሩ አፍረዋልን?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ሕዝቡ በኃጢአታቸው ባለማፈራቸው ምክንያት ቁጣውን ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በጣም አስደንጋጭ ኃጢአት ሰርተዋል፣ ነገር ግን ምንም አያፍሩም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

እንዴት ማፈር እንዳለባቸው አያውቁም
“ፊታቸው እንኳ ፈጽሞ አልቀላም።” ሰው ሲያፍር ብዙ ጊዜ ፊቱ ይቀላል።

ከሚወድቁት ጋር ይወድቃሉ
እዚህ ላይ “ይወድቃሉ” የሚለው ይገደላሉ የሚለውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከተገደሉት ከሌሎቹ ጋር አብረው አንድ ላይ ይገደላሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በምቀጣቸውም ጊዜ ይዋረዳሉ
እዚህ ላይ “ይዋረዳሉ” የሚለው መጥፋትን ይወክላል። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ በምቀጣቸው ጊዜ አጠፋቸዋለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ቅጠሉ ይረግፋል
“ቅጠሉ ይደርቃል”

እኔ የሰጠኋቸው ሁሉ ከእነርሱ ይወሰድባቸዋል
እዚህ ላይ የመጀመርያው ጽሑፍ ትርጉም ምን እንደሆነ እርግጠኛ መሆን አይቻልም።

Jeremiah 8:14

አያያዥ ሀሳብ፡-
የይሁዳ ሕዝብ በሚቀጡበት ጊዜ ምን እንደሚሉ ለእኛ በመንገር እግዚአብሔር መልእክቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡-
“እኛ”፣ “ለእኛ” እና “የእኛ” የሚሉት ቃላት የይሁዳ ሕዝብን ያመለክታሉ።

ለምን እዚህ እንቀመጣለን?
ይህ ጥያቄ የተጠየቀው የድርጊት እርምጃን ለማነሳሳት ነው። ይህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እዚህ መቆየት የለብንም።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በአንድነት ወደዚህ ኑ፤ ወደ ተመሸጉት ከተሞች እንሂድ
`የተመሸጉ ከተሞች” ከፍተኛ የግንብ አጥር እና ጠንካራ ከለላ የነበራቸው ከተሞች ናቸው። እነዚህ ተመሳሳይ ሀረጎች በኤርምያስ 4:5 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸቸው ተመልከት።

በዚያ እንሞታለን፣ ድምጻችንንም እናጠፋለን
እዚህ ላይ “ድምጻችንንም እናጠፋለን”የሚለው መሞት ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እዚያ እንሙት” ወይም “በዚያ እንዲገድሉን ጠላቶቻችንን እንጠብቅ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር አምላካችን እንድንጠፋ አድርጎናል
እዚህ ላይ “እንድንጠፋ” የሚለው የሞት ፍርድ እንደተላለፈባቸው የሚያሳይ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር አምላካችን የሞት ፍርድ ስላስተላለፈብን” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መርዝ እንድንጠጣ ያደርገናል
ይህ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ያስተላለፈውን ፍርድ የሚያሳይ ፈሊጥ ነው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን መልካም ነገር አይኖርም
“ነገር ግን አንድም መልካም ነገር አይሆንም”

ነገር ግን ተመልከቱ
“ነገር ግን አስተውሉ”

Jeremiah 8:16

አያያዥ ሀሳብ፡-
እግዚአብሔር በይሁዳ ላይ ስለሚመጣው ቅጣት መልእክቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡-
በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ “የእርሱ” እና “እነርሱ” የሚሉት ቃላት የይሁዳ ጠላቶችን ያመለክታል።

የፈረሶቹ ፉርፉርታ ከዳን ተሰማ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የፈረሶቹን ፉርፉርታ የዳን ሕዝብ ሰምተውታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ፉርፉርታ
ፈረስ በአፍንጫው የሚያሰማው ከፍ ያለ ድምጽ

ፈረሶች
ጎልማሳ ወንዶች ፈረሶች

ምድር ሁሉ ተንቀጠቀጠች
ይህ ግነት ሲሆን የይሁዳ ሕዝብ በፍርሃት ለመንቀጥቀጣቸው ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- የምድሪቱ ሕዝቦች በሙሉ በፍርሃት ተንቀጠቀጡ” (ግነት/ግነታዊ ቋንቋ እና ጅምላ ፍረጃ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በጠንካራ ፈረሶቹ የማሸካካት ድምጽ
“የጠላትን ጠንካራ ፈረሶች ድምጽ በሰሙ ጊዜ”

ማሸካካት
ፈረስነየሚያሰማው ድምጽ

እነርሱ ይመጡና ይውጡአችኋል
እዚህ ላይ “ይውጡአችኋል” የሚለው ቃል መብላት ማት ነው። ይህ ጠላቶች እንዴት እንደሚመጡና ምድሪቱንና በእርሷ የሚኖሩትን ሰዎች እንደሚያጠፉ የሚያሳይ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ ይመጡና ያጠፉአችኋል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ተመልከቱ
“አሁን አስተውሉ”

እኔ በመካከላችሁ መርዘኛ እባቦች፣ በአስማት ብልሃት ልትከለክሉአቸው የማትችሉአቸውን እፉኝቶች እልክባችኋለሁ
እባቦቹና እፉኝቶቹ የጠላትን ወታደር ይወክላሉ፣ መንከሳቸው ደግሞ የጠላትን ጥቃት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ በመካከላችሁ ከቁጥጥራችሁ በላይ የሆኑ የጠላት ወታደሮችን እልካለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በአስማት ብልሃት ልትከለክሉአቸው የማትችሉአቸውን እፉኝቶች
እዚህ ላይ አስማት ማድረግ የሚለው ሀረግ እባቦችን ለመቆጣጠር መዘመር ወይም ሙዚቃ ማሰማት ነው።

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 8:18

አጠቃላይ መረጃ፡-
ኤርምያስና እግዚአብሔር ስለ ይሁዳ ሕዝብ ንግግር ያደርጋሉ።

የእኔ ሃዘን አያልቅም
እዚህ ላይ “የእኔ” የሚለው ኤርምያስን ያመለክታል። የመጀመርያው የተጻፈበት ሃሳብ ግልጽ አይደለም ስለዚህ በዘመኑ ባሉት ትርጉሞች በተለያዩ መንገዶች ተተርጉሟል።

አያልቅም
ይህ ቃል የኤርምያስን ጥልቅ ሃዘን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለ ግነት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በጣም ታላቅ” ነው። (ግነት/ግነታዊ ቋንቋ እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ልቤ ትምሟል
እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ኤርምያስን የሚወክል ሲሆን እርሱ የተሰማውን ነገርና ስሜቱን አጽንዖት የሚሰጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ በጥልቅ የውስጥ ማንነቴ ሕመም ይሰማኛል” (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እነሆ!
ይህ ከዚህ ቀጥሎ ለሚነገረው ነገር አንባቢው ትኩረት እንዲሰጥ የሚያነቃ ነው። “ትኩረት ስጥ”

የሕዝቤ ሴት ልጅ
ኤርምያስ ለሴት ልጅ የሚገባውን ዓይነት ፍቅሩን ለይሁዳ ሕዝብ በሚያሳይበት መንገድ ስለ እነርሱ ይናገራል። ይህንን በኤርምያስ 4፡11 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “የእኔ ውድ ሕዝቤ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከሩቅ አገር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ከግዞት። አማራጭ ትርጉም፡- “ከግዞት ከሩቅ አገር” ወይም 2) ከይሁዳ ምድር በሙሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “በምድራችን ዙርያ ሁሉ”

እግዚአብሔር በጽዮን የለምን? ወይስ ንጉስዋ በእርስዋ ዘንድ የለምን?
እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። የይሁዳ ሕዝብ እግዚአብ|ሔር ለምን እነርሱን እንዳላዳናቸው ግራ እንደተጋቡ የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር በጽዮን ንጉስ ከሆነ ለምን እርሱ እኛን አላዳነንም?” (ትይዩነት/ተመሳሳይነት እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ እና መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በተቀረጹ ምስሎቻቸውና እንዲሁም ከንቱ በሆኑ ባዕዳን ጣዖታት እኔን ለምን አስቆጡኝ?
“እኔን” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ያመለክታል። ይህ ጥያቄ በዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ እኔ እንዳድናቸው የሚፈልጉ ከሆነ በተቀረጹ ምስሎቻቸው እኔን ሊያስቆጡኝ አይገባም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 8:20

አያያዥ ሀሳብ፡-
ኤርምያስ ስለ ይሁዳ ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡-
“እኛ” የሚለው ቃል የይሁዳ ሕዝብን ያመለክታል። “እኔ” እና “የእኔ” የሚሉት ቃላት ኤርምያስን ያመለክታሉ።

መከሩ አልፎአል
“የመከር ጊዜ አልፎአል”

ነገር ግን እኛ አልዳንንም
ኤርምያስ የይሁዳ ሕዝብ የሚናገሩትን ያስተላልፋል። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን እግዚአብሔር እኛን አላዳነንም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በሕዝቤ ሴት ልጅ ስብራት እኔም ተሰብሬአለሁ፣ ጠቁሬማለሁ። በእርስዋ ላይ በሆኑት አስከፊ ነገሮች እኔ አዝኛለሁ፤ እኔ ተስፋ ቆርጫለሁ
እነዚህ ዓረፍተ ሃሳቦች አጽንዖት ለመስጠት ከአንድ በላይ መንገድ በመጠቀም ተመሳሳይ ሃሳብ ይገልጻሉ። (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

በገለዓድ መድኃኒት የለምን? ወይስ በዚያ ሐኪም የለምን? የወገኔ ሴት ልጅ ፈውስ ስለምን አልሆነም?
እነዚህ ጥያቄዎች የጠጠየቁት የይሁዳ ሕዝብ እንዳልዳኑ ዋናውን ነጥብ ለማስተላለፍ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በገለዓድ መድኃኒት አለ፣ በዚያ ሐኪሞች አሉ፣ ስለዚህ የውድ ሕዝቤ ፈውስ ለምን እንደማይከናወን ንገሩኝ።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 9

1 ተወግተው ስለ ሞቱ ስለ ሕዝቤ ሴት ልጅ ሰዎች ሌሊትና ቀን አለቅስ ዘንድ ራሴ ውኃ፣ ዓይኔም የእንባ ምንጭ በሆነልኝ! **2** ሁሉም አመንዝሮች፣ የከዳተኞች ጉባኤ በመሆናቸው ሕዝቤን እተዋቸው ዘንድ ከእነርሱም እለይ ዘንድ በምድረ በዳ የመንገደኞች ማደሪያን ማን በሰጠኝ! **3** "አታላይ ቀስታቸው በሆነው በምላሳቸው ሐሰት ተናገሩ፣ ነገር ግን በምድር ላይ በታማኝነት ግሩም አይደሉም። ከክፋት ወደ ክፋት ይሄዳሉ። እኔንም አላወቁምና፣" ይላል እግዚአብሔር። **4** እያንዳንዱ ወንድም ሁሉ ያታልላልና፣ እያንዳንዱ ጎረቤትም ሁሉ ሐሜተኛ ስለሆነ እናንተ ሁሉ ከጎረቤቶቻችሁ ተጠንቀቁ፣ በወንድሞቻችሁም አትታመኑ። **5** እያንዳንዱ ሰውም ሁሉ ጎረቤቱን ያታልላል በእውነትም አይናገርም። ምላሶቻቸው የማታለል ነገሮችን ያስተምራል። በደልንም በማድረግ ይደክማሉ። **6** በማታለል መካከል ትኖራላችሁ፣ ከሽንገላም የተነሣ እኔን ያውቁኝ ዘንድ እንቢ ብለዋል፣ ይላል እግዚአብሔር። **7** ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "ተመልከቱ፣ እፈትናቸዋለሁ። እመረምራቸዋለሁ። ስለ ሕዝቤ ሴት ልጅ ክፋት ከዚህ ሌላ የማደርገው ምንድር ነው? **8** ምላሳቸው የተሳለ ፍላጻ ነው፤ ያልታመኑ ነገሮችን ይናገራሉ። ከጎረቤቶቻቸው ጋር በአንደበታቸው በሰላም ይናገራሉ፣ በልባቸው ግን ያደቡበታል። **9** በውኑ ስለዚህ ነገር አልቀጣቸውምን? ይላል እግዚአብሔር፤ እንደዚህስ ባለ ሕዝብ ላይ አልበቀልምን? **10** ለተራሮች የልቅሶና የዋይታን ዝማሬ እዘምራለሁ፣ ለምድረ በዳ ማሰማርያዎችም የቀብር ዋይታን እዘምራለሁ። ማንም ሰው እንዳያልፍባቸው በእሳት ተቃጥለዋልና። ሰዎችም የየትኛውንም ከብት ድምፅ አይሰሙም። የሰማይ ወፎች ጀምሮ እስከ እንስሳ ድረስ ሁሉ ሸሽተው ሄደዋል። **11** ኢየሩሳሌምን የፍርስራሽ ክምር፣ የቀበሮም ማደሪያ አደርጋታለሁ። የይሁዳንም ከተሞች ሰው የማይኖርባት ወና አደርጋቸዋለሁ። **12** ይህን የሚያስተውል ጠቢብ ሰው ማን ነው? ለሌሎች እንዲነግር የእግዚአብሔር አፍ ምን ተናገረው? ምድሪቱስ ስለምን ጠፋች? ማንም እንደማያልፍባት እንደ ምድረ በዳስ ስለ ምን ተደመሰሰች? **13** እግዚአብሔርም እንዲህ አለ፣ "በፊታቸው የሰጠኋቸውን ሕጌን ስለተዉ፣ ድምጼንም አልሰሙምና ወይም አልተጓዙበትምና። **14** አባቶቻቸው እንዳስተማሯቸው በልባቸውን ምኞት ተመላልሰዋልና፣ በኣሊምን ተከትለዋልና። **15** ስለዚህ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል 'ተመልከቱ፣ ይህን ሕዝብ እሬትን አበላዋለሁ የተመረዘንም ውኃ አጠጣዋለሁ። **16** እነርሱና አባቶቻቸውም ባላወቁአቸው አሕዛብ መካከል እበትናቸዋለሁ፣ እስካጠፋቸውም ድረስ በበስተኋላቸው ሰይፍን እሰድድባቸዋለሁ።" **17** የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "ይህንን አስቡ፦ የቀብር አስለቃሾችን ጥሩ፤ ይምጡ። ወደ ብልሃተኛ አልቃሾች ላኩ። **18** ይፍጠኑና ዓይኖቻችንም እንባ እንዲያፈስሱ የዓይናችንም ሽፋሽፍቶች ውኃን እንዲያፈልቁ የለቅሶ ዝማሬን ይዘምሩልን። **19** 'እንዴት ተበዘበዝን። ቤቶቻችን ስለፈረሱ ምድሪቱንም ትተናልና እንዴት አፈርን!' የሚል የልቅሶ ድምፅ በጽዮን ተሰምቶአል። **20** ስለዚህ እናንተ ሴቶች ሆይ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ፣ ከአፉ ለሚወጣው ቃል ትኩረት ስጡ። ከዚያም ለሴቶች ልጆቻችሁም የልቅሶውን ዝማሬ አስተምሩ፣ ለእያንዳንዷም የጎረቤታችሁ ሴት የቀብሩን ሙሾ አስተምሩ። **21** ሞት ወደ መስኮታችን መጥቷልና፤ ወደ ቤተ መንግሥቶቻችን ሄዷል። ሕፃናቱን ከውጪ፣ ወጣቶቹንም ከከተማይቱ አደባባይ ያጠፋል። **22** 'የሰውም ሬሳ በሜዳ ላይ እንደ ጕድፍ፣ ከአጫጆች በኋላ እንደሚቀር ቃርሚያ ይወድቃል፣ ማንምም አይሰበስበውም። **23** እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "ጠቢብ በጥበቡ እንዲመካ አትፍቀዱ፣ ወይም ጦረኛ በኃይሉ አይመካ። ባለ ጠጋም በብልጥግናው እንዲመካ አትፍቀዱ። **24** ሰው በየትኛውም ነገር የሚመካ ከሆነ፣ በዚህ ይሁን፣ ማስተዋል ያለውና የሚያውቀኝ በመሆኑ። የኪዳን ታማኝነት፣ ፍትሕንና ጽድቅንም በምድር ላይ የማደርግ እኔ እግዚአብሔር ነኝና። ደስ የሚያሰኙኝ እነዚህ ናቸውና፣ ይላል እግዚአብሔር። **25** ተመልከቱ፣ በሰውነታቸው ብቻ የተገረዙትን እቀጣለሁ። **26** ግብጽንና ይሁዳን፣ የአሞን ሕዝቦች የሆኑትን ኤዶምያስና ሞዓብንም፣ እንዲሁም በምድረ በዳም የተቀመጡትን ፀጉራቸውን የተላጩትን ሁሉ፣ ባለመገረዛቸው ምክንያት የምቀጣበት ዘመን እነሆ ይመጣል። እነዚህ ሁሉ ሕዝቦች ያልተገረዙ ናቸውና፣ ደግሞም የእስራኤል ልብ አልተገረዘምና" ይላል እግዚአብሔር።

Jeremiah 9:1

አጠቃላይ መረጃ፦
እግዚአብሔርና ኤርምያስ ስለ ይሁዳ ሕዝብ መነጋገር ቀጥለዋል።

ምነው ራሴ የውሃ ምንጭ በሆነ! ምነው ዓይኖቼ የውሃ መጉረፊያ በሆኑልኝ!
ይህን የሚናገረው ኤርምያስ ነው። እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ኤርምያስ ምን ያህል እያለቀሰ እንደሆነ አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “የበለጠ እንባ ማፍሰስ ብችል እመኝ ነበር” (ትይዩነት/ተመሳሳይነት እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀንና ሌሊት
“ቀን” እና “ሌሊት” የሚሉትን በመጥቀስ ይህ ሀረግ ሁልጊዜ የሚል ትርጉም ይኖረዋል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሁልጊዜ” ወይም “ያለማቋረጥ” (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሕዝቤ ሴት ልጅ
እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ሲናገር እንደ ሴት ልጅ በመግለጽ ለእነርሱ ያለውን ጥልቅ ፍቅር ያሳያል። እዚህ ላይ ኤርምያስ እግዚብሔር የተጠቀመበትን ተመሳሳይ ሀረግ ሕዝቡን ለመግለጽ ይጠቀማል። ይህንን በኤርምያስ 4፡11 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ የእግዚአብሔር ሴት ልጅ የመሰሉትን ሕዝቤ” ወይም “ውድ ሕዝቤ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የተገደሉትን
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ጠላት የገደላቸው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ሰው ቢሰጠኝ ኖሮ
“አንድ ሰው ቢሰጠኝ ኖሮ እመኝ ነበር።” አሁንም የሚናገረው ኤርምያስ ነው።

በምድረ በዳ ለሚጓዙ መቆያ የሚሆን ስፍራ
ይህ የሚወክለው በምድረ በዳ ለሚጓዙ ሰዎች ከጉዞአቸው ቆመው ሌሊቱን ተኝተው የሚያሳልፉበትን ሕንጻ ነው።

ሕዝቤን ትቼ
“ሕዝቤን ተውኳቸው”

የአታላዮች መንጋ
“ሌሎች ሰዎችን የሚያታልሉ የሰዎች ስብስብ”

እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
“ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው” የሚለውን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

ሐሰትን ለመናገር ምላሳቸውን እንደ ቀስት ገተሩ
ውሸትን መናገር በክፉዎች ምላስ እንደሚሰራ ተደርጎ ተነግሯል። በተጨማሪ የተነገረ ውሸት ወደኋላ መመለስ ስለማይቻል ውሸትን መናገር ቀስትን እንደ መወርወር ተደርጎ ተነግሯል። ቀስትን የሚጠቀሙ ሰዎች የቀስቱን ገመድ ለማሰር ቀስታቸውን መያዝ አለባቸው፣ ስለዚህ እዚህ ላይ ውሸታሞች

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምላሳቸውን በመጠቀም ምላሳቸውን እንደሚገትሩ ተደርገው ተጠቅሰዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ውሸታቸው በምላሳቸው እንደሚወረወር ቀስት ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን በምድር የበረቱት በታማኝነታቸው ምክንያት ፈጽሞ አይደለም
“በምድር የበረቱት ለእግዚአብሔር ታማኞች በመሆናቸው ምክንያት አይደለም፣ እነርሱ ክፉዎች ናቸውና” እና “ይህ ማለት ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ታማኞች አይደሉም ማለት ነው፣ ነገር ግን እንዲያውም እነርሱ ክፉዎች ናቸውና ኃይላቸውን ያገኙት በክፋታቸው ነው” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

ከአንድ የክፋት ተግባር ወደ ሌላ የክፋት ተግባር ይሄዳሉ
አንድን ክፉ ተግባር ከሌላው ክፉ ተግባር ቀጥሎ ስለመፈጸም ሲናገር ክፉ አድራጊዎች ከአንድ ድርጊት ወደ ሌላ ድርጊት እንደሚሄዱ ተደርጎ ተገልጦአል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ነገሮችን በማድረግ ቀጥለዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 9:4

አጠቃላይ መረጃ፡-
እግዚአብሔር ስለ ይሁዳ ሕዝብ ከኤርምያስ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።

እናንተ እያንዳንዳችሁ
“እናንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የይሁዳን ሕዝብ ነው።

ከጎረቤቶቻችሁ ተጠብቀቁ፣ በወንድሙም ላይ አይታመን
“አብረዋችሁ ያሉትን እስራኤላውያንን ከማመን ተጠንቀቁ፣ የራሳችሁን ወንድም ቢሆንም አትመኑ”

እያንዳንዱ ጎረቤት በሐሜት ይመላለሳል
እዚህ ላይ “ይመላለሳል” የሚለው ፈሊጥ ሲሆን መኖርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እያንዳንዱ ጎረቤት አንዱ ሌላውን ያማል” ወይም “እያንዳንዱ ጎረቤት ሐሜተኛ ነው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

እያንዳንዱ ሰው በጎረቤቱ ላይ ያፌዛል፣ እውነትን ደግሞ አይናገርም
“ሁሉም ሰዎች እርስ በርሳቸው ያፌዛሉ፣ እውነትን ደግሞ አይናገሩም”

ምላሶቻቸው ሐሰተኛ ነገሮችን ያስተምራሉ
እዚህ ላይ ለንግግራቸው አጽንዖት ለመስጠት ሲባል ሰዎች “በምላሶቻቸው” ተወክለዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ ሐሰተኛ ነገሮችን ያስተምራሉ” (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉንም በማድረግ ደክመዋል
“ብዙ ኃጢአት በማድረግ ደክመዋል”

መኖርያችሁ በሸንገላ መካከል ነው
እግዚአብሔር በውሸታሞች መካከል መኖር በሸንገላ መካከል መኖር እንደሆነ አድርጎ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “መኖርያችሁ በውሸታሞች መኖርያ መካል ነው” ወይም “እናንተ የምትኖሩት በውሸታሞች መካከል ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በሸንገላቸው
“እነዚህን ሁሉ ውሸቶች በመናገር”

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 9:7

አጠቃላይ መረጃ፡-
እግዚአብሔር ስለ ይሁዳ ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል።

ተመልከት
እዚህ ላይ እግዚአብሔር ይህን ቃል የተጠቀመው የኤርምያስን ትኩረት ቀጥሎ ወደሚናገረው ንግግር ለመሳብ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አድምጥ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱን ለማንጠር
እግዚአብሔር ሕዝቡን ስለመፈተንና ክፉ መንገዳቸውን ፊት ለፊት ስለመጋፈጥ ሲናገር እነርሱ ብረት እንደሆኑና እርሱ የብረቱን ቆሻሻ ለማስወገድ ብረቱን በማቅለጫ እንደሚያቀልጠው አድርጎ ገልጾታል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሕዝቤ በሰሩት ኃጢአት ምክንያት ምን ማድረግ እችላለሁ?
እግዚአብሔር ይህን መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ የተጠቀመው ከሰሩት ስራ የተነሳ ሕዝቡን ሊጋፈጥ የሚያስፈልገው በዚህ መንገድ እንደሆነ ለመግለጽ ነው። ይህ ጥያቄ እንደ ዐረፍተ ሃሳብ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከሰሩት ስራ የተነሳ ከሕዝቤ ጋር መጋፈጥ የሚገባኝ እንደዚህ ነው” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ምላሶቻቸው የተሳሉ ቀስቶች ናቸው
ይህን የሚናገረው ሰዎች በሚናገሩት ንግግር ሌሎች ሰዎችን በጣም ሲለሚጎዱ የሰዎች ምላሶቻቸው የተሳሉ ቀስቶች እንደሆኑ ተደርገው ተገልጸዋል። እዚህ ላይ ንግግራቸው “በምላሶቻቸው” ተወክሏል። አማራጭ ትርጉም፡- “ቃላቶቻቸው ሌሎች ሰዎችን እንደሚጎዱ እንደተሳሉ ቀስቶች ናቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በአንደበቶቻቸው ከባልንጀሮቻቸው ጋር ሰላምን ይናገራሉ
እዚህ ላይ የሰዎች ንግግር “በአንደበቶቻቸው” ተወክሏል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከባልንጀሮቻቸው ጋር ሰላም እንፈልጋለን እያሉ ይናገራሉ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን በልባቸው አድብተው ይጠብቁአቸዋል
እዚህ ላይ የሰዎች ፍላጎት “በልባቸው” ተወክሏል። አደን ወጥቶ ለመብላት የሚፈልገውን ለማጥቃት እንደሚያደፍጥና እንደሚጠብቅ እንስሳ እንደዚሁ እነርሱም ባልንጀሮቻቸውን ለመጉዳት የሚፈልጉ እንደሆኑ አድርጎ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን እነርሱ የሚፈልጉት ነገር ባልንጀሮቻቸውን ማጥፋት ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ታዲያ ስለነዚህ ነገሮች ልቀጣቸው አይገባኝምን? ... እኔ ራሴስ እንደዚህ ዓይነቱን ሕዝብ አልበቀልምን?
እግዚአብሔር እነዚህን መልስ የማይሰጥባቸውን ጥያቄዎች የተጠቀመው እነርሱ የሰሯቸው ነገሮች በጣም መጥፎ ከመሆናቸው የተነሳ በእነርሱ ላይ ምህረት እንደማይኖረውና እነርሱን ከመቅጣት ራሱን እንደማያስቆም አጽንዖት ለመስጠት ነው። እነዚህን ተመሳሳይ ቃላት በኤርምያስ 5:9 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ እነዚህን ነገሮች ከማድረጋቸው የተነሳ እኔ እቀጣቸዋለሁ ... እኔ ራሴ በእርግጠኝነት በእነርሱ ላይ እበቀላለሁ።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Jeremiah 9:10

አጠቃላይ መረጃ፡-
እግዚአብሔር ስለ ይሁዳ ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል። በቁጥር 12 ኤርምያስ አስተያየት ይሰጣል።

እኔ የሃዘን ልቅሶ አለቅሳለሁ ... ለማሰማርያዎቹ የቀብር ልቅሶ ይለቀሳል
የሞተች ሰው እንደሆነች በማሰብ እንደዚሁ እግዚአብሔር ለእስራኤል ምድር ያለቅሳል። (ትይዩነት/ተመሳሳይነት እና ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የቀብር ልቅሶ ይለቀሳል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ የቀብር ልቅሶ አለቅሳለሁ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ማሰማሪያዎቹ
“እንስሳት ሳር የሚግጡበት የግጦሽ ስፍራ”

እነርሱ ተቃጥለዋልና
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ምክንያቱም ሰው ማሰማሪያዎቹንና የግጦሽ መሬቱን አቃጥሎአቸዋልና” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የአንድም ከብት ድምጽ ፈጽመው አይሰሙም
“በዚያ ስፍራ አንድም ሰው የከብት ድምጽ አይሰማም”

የቀበሮ መሸሸጊያ
“ቀበሮዎች የሚደበቁበት ስፍራ።” ቀበሮዎች እጅግ በጣም ኃይለኛ የዱር ውሾች ናቸው።

ሰው የማይኖርበት ስፍራ
“አንድም ሰው የማይገኝበት ስፍራ”

ይህን የሚያስተውል ጠቢብ ሰው ማን ነው?
እግዚአብሔር ይህን መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ የተጠቀመው እርሱ የተናገራቸውን ነገሮች መረዳት የሚችል ሰው በጣም ጥበበኛ ሰው ብቻ እንደሆነ አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህን ነገሮች መረዳት የሚችሉ በጣም ጥበበኛ የሆኑ ሰዎች ብቻ ናቸው።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ያወራስ ዘንድ የእግዚአብሔር አፍ ለማን ተናገረ
እግዚአብሔር ይህን መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ የተጠቀመው እነዚህን ነገሮች መናገር የሚችሉት እርሱ የተናገራቸው ሰዎች ብቻ እንደሆኑ አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህን ነገሮች ለሌሎች ማብራራት የሚችሉት ከእግዚአብሔር የተማሩ ብቻ ናቸው” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር አፍ
እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ንግግር በእርሱ “አፍ” ተወክሏል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር” (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰው እንዳያልፍባት ምድሪቱ ለምን ጠፋች፣ ለምንስ ወና ሆነች?
እግዚአብሔር ይህን መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ የተጠቀመው ምድሪቱ ለምን እንደጠፋች ማብራራት የሚችለው ጥበበኛ ሰው ብቻ እንደሆነ አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰው እንዳያልፍባት ምድሪቱ ለምን እንደጠፋች እና ወና እንደሆነች ማብራራት የሚችለው ጥበበኛ ሰው ብቻ ነው።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሪቱ ጠፍታለች ደግሞም ወና ሆናለች
ይህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊጻፍ ይችላል። “ጠፋች” እና “ወና ሆነች” የሚሉት ሁለቱም ምድሪቱ ወና እንደሆነች የሚያብራሩ ናቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “ምድሪቱ ወና ሆናለች” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 9:13

አጠቃላይ መረጃ፡-
እግዚአብሔር ስለ ይሁዳ ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል።

ምክንያቱም
“እነዚህ ነገሮች ይሆናሉ ምክንያቱም”

ሕጌን ትተዋልና
እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ሕጉን አለመታዘዝ ሲናገር ከሕጉ ርቀው እንደሄዱ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሕጌን ትተውታል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ድምጼን አይሰሙም
እዚህ ላይ የእግዚአብሔር “ድምጽ” እርሱ የተናገረውን ነገር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ ለእነርሱ ለነገርኋቸው ነገሮች ምንም ትኩረት አልሰጡም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ወይም በእርሱ አልሄዱም
እዚህ ላይ “መሄድ” ፈሊጥ ሲሆን “መኖርን” የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ወይም እኔ እንዲኖሩ በነገርኋቸው መንገድ አልኖሩም” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ በልባቸው እልከኝነት ሄዱ
እዚህ ላይ የሕዝቡ “እልከኛ ልቦች” እልከኛ ፍላጎታቸውንና እልከኛ ፈቃዳቸውን ይወክላል። እዚህ ላይ “መሄድ” መኖርን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ እልከኞች ነበሩና ሊኖሩ በሚፈልጉት መንገድ ኖሩ” (ምትክ ስም እና ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

በኣሊምን ተከተሉ
“በኣልን አመለኩ”

Jeremiah 9:15

አጠቃላይ መረጃ፡-
እግዚአብሔር ስለ ይሁዳ ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል።

የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ከእግዚአብሔር የመጣውን በጣም አስፈላጊ መልእክት ለማስተዋወቅ ብዙ ጊዜ እነዚህን ቃላት ይጠቀማል። ይህን በኤርምያስ 6፡6 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

ተመልከቱ
እግዚአብሔር ይህን ቃል የተጠቀመው ከዚህ ቀጥሎ ለሚናገረው ነገር የሰዎችን ትኩረት ለመሳብ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አዳምጡ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

እሬት
በጣም መራራ ጣዕም ያለው ተክል

እነርሱን በማያውቋቸው ሕዝቦች መካከል እበትናቸዋለሁ
“ከዚያም እኔ ይህን ምድር እንዲለቁና በብዙ የተለያዩ አገሮች እንዲኖሩ አስገድዳቸዋለሁ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እነርሱም ሆኑ አባቶቻቸው
ግልጽ የሆነ ግስ መጠቀም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ ወይም የእነርሱ አባቶች አያውቁም” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእነርሱ በኋላ ሰይፍን እልካለሁ
እዚህ ላይ “ሰይፍ” የሚለው ቃል የጠላትን ጦር ሰራዊት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱን እንዲዋጉአቸው ወታደራዊ ሰራዊት እልክባቸዋለሁ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ እነርሱን ሙሉ በሙሉ አጥፍቻቸዋለሁ
ይህ እግዚአብሔር ሕዝቡን ጠላቶቻቸው እንዲያጠፉአቸው ለማድረጉ ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- እኔ ጠላቶቻቸው ሙሉ በሙሉ እንዲያጠፉአቸወ አድርጌአለሁ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 9:17

አጠቃላይ መረጃ፡-
እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ ለሚመጣው ለምድሪቱ ጥፋት እንዲያለቅሱ ይነግራቸዋል።

የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ከእግዚአብሔር የመጣውን በጣም አስፈላጊ መልእክት ለማስተዋወቅ ብዙ ጊዜ እነዚህን ቃላት ይጠቀማል። ይህን በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

የቀብር አልቃሾችን ጥሩ፤ ይምጡ ... የሰለጠኑ ሙሾ አውራጆችን አስመጡ፤ ይምጡ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። እነዚህ ሀረጎች የቀብር አልቃሾች እንዲያመጡ ሊጠሩአቸው እንደሚገባ አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “የሰለጠኑ አልቃሽ ሴቶች ፈልጋችሁ አግኙና እነዚህን ሴቶች ወደዚህ አምጡአቸው” (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

የቀብር አልቃሾችን ጥሩ
“በቀብር ላይ ሙሾ የሚያወጡ የሰለጠኑ አልቃሽ ሴቶች ጥሩ”

ይምጡ
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እንዲመጡ ለሴቶቹ ንገሯቸው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰለጠኑ ሙሾ አውራጅ ሴቶችን ለመፈለግ ሰው ላኩ
“ሰው ላኩ” የሚለው ሀረግ ፈሊጥ ነው። አማራጭ “የልቅሶ ሙሾ በማውረድ የሰለጠኑ ሴቶችን ለማግኘት ሰዎችን ላኩ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የእኛ የዓይናችን ሽፋሽፍቶች ውኃን እንዲያፈልቁ ፈጥነው ለእኛ ልቅሶውን ይያዙ
x

Jeremiah 9:19

አጠቃላይ መረጃ፡-
እዚህ ላይ እግዚአብሔር የሚናገረው እርሱ ምድሪቱን ሲያጠፋ ወደፊት የይሁዳ ሕዝብ የሚናገረውን ነው።

በጽዮን የልቅሶ ድምፅ ተሰምቶአል
ይህ የጽዮን ሕዝብ ከፍ ባለ ድምጽ ማልቀሱን የሚያመለክት ሲሆን በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የጽዮን ሕዝብ ከፍ ባለ ድምጽ ያለቅሳሉ፣ እንዲህ እያሉ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ እንዴት ፈራረስን
ምድሪቱ በምትጠፋበት ጊዜ የይሁዳ ሕዝብ ወደፊት የሚናገረውን እግዚአብሔር ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኛ በጣም ተበሳጭተናል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ቤቶቻችንን ስላፈረሱና ምድሪቱን ስለተውን እኛ እጅግ በጣም አፍረናል
“እፍረታችን እጅግ ታላቅ ነው፣ ምክንያቱም ጠላቶች ቤቶቻችንን አፍርሰውታል የእስራኤልን ምድር ደግሞ ለቅቀን መውጣት አለብን”

የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ፤ ከአፉ ለሚመጣው መልእክት ተገቢ ትኩረት ስጡ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ እግዚአብሔር ቃሉን እንዲያደምጡ ለሰጠው ትእዛዝ አጽንዖት ይሰጣሉ። በሁለተኛው ሀረግ የእግዚብሔ “አፍ” ለራሱ ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረውን አድምጡ። ለቃሉ ትኩረት ስጡ” (ትይዩነት/ተመሳሳይነት እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እያንዳንዱ የጎረቤት ሴቶች የቀብር ልቅሶውን
ግልጽ የሆነ ግስ መጠቀም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለእያንዳንዱ የጎረቤት ሴቶች የቀብር ልቅሶውን አስተምሩአቸው” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 9:21

አጠቃላይ መረጃ፡-
እዚህ ላይ እግዚአብሔር የሚናገረው እርሱ ምድሪቱን ሲያጠፋ ወደፊት የይሁዳ ሕዝብ የሚናገረውን ነው።

ወጣት ወንዶች ... በከተማይቱ አደባባይ ... ሞት በመስኮታችን በኩል መጥቶአል
የይሁዳ ሕዝብ ለወደፊት ሞትን በመስኮት ዘልሎ በመግባት በቤት ውስጥ ያሉትን ሰዎች ለማጥቃትና በቤተ መንግሰት፣ በመንገዶችና በከተማ አደባባዮች ያሉትን ሰዎች ከሚያጠቃ ሰው ጋር ያነጻጽሩታል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቤተ መንግስታት
ነገስታት የሚኖሩበት በጣም የሚያምሩ ቤቶች። ሞት በተመሳሳይ መልኩ ወደ ባለጠጎችና ድሆች ይመጣል።

የከተማይቱ አደባባይ
የገበያ ስፍራዎች

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰውም ሬሳ እንደ ጉድፍ ... ከአጫጆች በኋላ እንደሚቀር ቃርሚያ ይወድቃል
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ የሰው ሬሳ እጅግ በጣም ብዙ መሆኑን አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “የሰዎች ሬሳ በየቦታው ይወድቃል” (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

የሰውም ሬሳ እንደ ጉድፍ በእርሻ ላይ ይወድቃል
ሰውነታቸውን በእርሻ ላይ ከሚወድቀው ጉድፍ ጋር በማነጻጸር የሚሞተውን በጣም ብዙ ቁጥር ያለውን ሕዝብ ይገልጻል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእንስሳት አዛባ በየሜዳው እንደሚወድቅ እንደዚሁ የሰዎች ሬሳ በየቦታው ይወድቃል” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከአጫጆች በኋላ እንደሚቀር ቃርሚያ
ይህ ሰውነታቸውን ከአጫጆች በኋላ ከሚቀረው ቃርሚያ ጋር በማነጻጸር የሚሞተውን በጣም ብዙ ቁጥር ያለውን ሕዝብ ይገልጻል። አማራጭ ትርጉም፡-

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

“ገበሬዎች ሰብላቸውን ካጨዱ በኋላ በየቦታው ወድቆ እንደሚቀር ቃርሚያ” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱን ለመሰብሰብ አንድም ሰው አይኖርም
“የሞቱትን ሰዎች ሬሳ ለመሰብሰብ አንድም ሰው አይኖርም”

Jeremiah 9:23

አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ የእግዚአብሔር ቃላት ናቸው።

ጠቢብ በጥበቡ አይመካ
“ጠቢብ ጥበበኛ ስለሆነ በጥበቡ ሊመካ አይገባውም”

ወይም ጦረኛ በኃይሉ አይመካ
ግልጽ የሆነ ግስ መጠቀም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ወይም ጦረኛ በኃይሉ ይመካ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ባለ ጠጋም በብልጥግናው አይመካ
“ሀብታም ሰው ሀብታም ስለሆነ በሃብቱ አይመካ”

በማስተዋሉና እኔን በማወቁ
“እኔ ማን እንደሆንሁ በማስተዋሉና እኔን በማወቁ።” እነዚህ ሁለቱም ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። እግዚአብሔር ማን እንደሆነ ያወቁና እርሱ ማን እንደሆነ ያስተዋሉ ሰዎችን አጽንዖት ይሰጣሉ። (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 9:25

አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ የእግዚአብሔር ቃላት ናቸው።

ተመልከቱ
እግዚአብሔር እዚህ ላይ ይህን ቃል የተጠቀመው ከዚህ ክፍል ቀጥሎ የሚናገረውን ንግግር ሰዎች ትኩረት እንዲሰጡት ለማድረግ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አድምጡ” ወይም “በእርግጥ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀናት እየመጡ ነው
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ጊዜ ይኖራል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ስጋቸውን ብቻ የተገረዙትን
ይህ በስጋቸው በመገረዝ ወደ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን የገቡትን ነገር ግን የእርሱን ሕግ በመከተል ውስጣዊ ማንነታቸውን ያልለወጡ የእስራኤልን ሕዝብ የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ውጫዊ ሰውነታቸውን በመገረዝ የለወጡ ነገር ግን ውስጣዊ ማንነታቸውን ያልለወጡ ሕዝብ በሙሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በራሳቸው ላይ ያለውን ጸጉር በአጭሩ የሚቆረጡ ሕዝቦች በሙሉ
ይህ ምናልባት የሚያመለክተው የአሕዛብ ጣዖት ለማክበር ሲሉ ጸጉራቸውን በአጭሩ የሚቆረጡ ሕዝቦችን ነው። አንዳንድ አዳዲስ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ይህን የዕብራይስጥ አገላለጽ “በምድረ በዳ ጫፍ ላይ የሚኖሩ ሕዝቦች በሙሉ” ብለው ተርጉመውታል።

እነዚህ ሕዝቦች የተገረዙ አይደሉምና
እዚህ ላይ “ሕዝቦች” የሚለው ቃል በእነዚህ ስፍራዎች የሚኖሩትን ሕዝቦች ነው። ያልተገረዙ እንግዳ ሰዎች በእግዚአብሔር ኪዳን ውስጥ ያልተካተቱ ለመሆናቸው ምልክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የእነዚህ መንግስታት ሕዝቦች በመገረዝ ወደ እግዚአብሔር ኪዳን አልገቡም” (ምትክ ስም እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ቤት በሙሉ ያልተገረዘ ልብ አላቸው
“ልብ” የሰውን ፈቃድና ፍላጎት ይወክላል። “ያልተገረዘ ልብ” እግዚአብሔርንና ሕጉን የማይከተል ሰው ባህርይ ይወክላል። ከዚህ በተጨማሩ የእስራኤል “ቤት” የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእስራኤልን ሕዝብ በሙሉ የተገረዙት በውጫዊው ሰውነታቸው ብቻ ነው፣ ልባቸው ግን አልተለወጠም” (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 10

1 እናንተ የእስራኤል ቤት ሆይ፣ እግዚአብሔር ለእናንተ የተናገረውን ቃል ስሙ። 2 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ 'የአሕዛብን መንገድ አትማሩ፣ ከሰማይ
በሚሆኑት ምልክቶችም አትፍሩ፣ አሕዛብ እነዚህን ይፈራሉና። 3 የአሕዛብ ልማድ ከንቱ ነውና። አንድ ሰው ዛፍን ከጫካ ይቈርጣል፤ የሠራተኛም እጅ
በመጥረቢያ ይህንን ይሠራል። 4 ከዚያም በብርና በወርቅ ያስጌጡታል። እንዳይወድቅም በመዶሻና በሚስማር ይቸነክሩታል። 5 እነዚህ ጣዖታት ምንም ማለት
ስለማይችሉ፣ በዱባ ማሳ ላይ እንደ ተቀረጸ ዓምድ ናቸው። ጨርሶ መራመድ ስለማይችሉ ሊይሸከሟቸው ይገባል። ክፉ መሥራት አይቻላቸውምና፣ ደግምም
የትኛውንም መልካም ነገር ይሠሩ ዘንድ አይችሉምና አትፍሩአቸው። 6 እግዚአብሔር ሆይ እንደ አንተ ያለ የለም። አንተ ታላቅ ነህ፣ ስምህም በኃይል ታላቅ ነው። 7
የአሕዛብ ንጉሥ ሆይ፣ የማይፈራህ ማነው? በአሕዛብ ጥበበኞች ሁሉ መካከል ወይም በታማኝ መንግሥታቸውም ሁሉ መካከል እንደ አንተ ያለ ስለሌለ፣ አንተ
ይህ ይገባሃል። 8 እነርሱ ሁሉም ተመሳሳይ ናቸው፣ ደንዝዘዋል፣ ደንቊረውማል፤ እንጨት ብቻ እንጂ ምንም ላልሆኑ ጣዖቶቻቸው ደቀመዛሙርት ናቸው። 9
ከጠርሴስ አንጥረኛ የቀጠቀጠውን ብር፣ ከአፌዝም ወርቅ ያመጣሉ። ልብሳቸውም ሰማያዊና ቀይ ግምጃ ነው። ብልሃተኞች ሰዎቻቸው እነዚህን ሁሉ ነገሮች
ይሠራሉ። 10 እግዚአብሔር ግን እውነተኛ አምላክ ነው። እርሱም ሕያው አምላክና የዘላለም ንጉሥ ነው። ከቊጣው የተነሣ ምድር ትንቀጠቀጣለች፣ አሕዛብም
ቊጣውን መቋቋም አይችሉም። 11 እናንተም "ሰማይንና ምድርን ያልፈጠሩ አማልክት ከምድር ላይ ከሰማይም በታች ይጠፋሉ" ትሏቸዋላችሁ። 12 ምድርን
በኃይሉ የፈጠረው፣ ደረቊን ምድር በጥበቡ የመሠረተው ሰማያትንም በማስተዋሉ የዘረጋ እርሱ ነው። 13 ድምፁ በሰማይ የውኾችን ድምፅ ይፈጥራል፣
ከምድርም ጠርዝ ደመናትን ከፍ ያደርጋል። ለዝናቡም መብረቅን ያደርጋል፣ ነፋስንም ከግምጃ ቤቱ ያወጣል። 14 እያንዳንዱ ሰው እውቀት አጥቶ አላዋቂ ሆኗል።
እያንዳንዱ አንጥረኛ ቀልጦ የተሠራ ምስሉ ውሸት ነውና፣ ሕይወትም የለባቸውምና በቀረጸው ጣዖት አፍሮአል። 15 እነርሱ ጥቅም የለሽ፣ የቀልደኞች ሥራ
ናቸው፤ በሚቀጡበት ጊዜ ይጠፋሉ። 16 የያዕቆብ እድል ፈንታ እንደ እነዚህ አይደለም፣ እርሱ የሁሉ ፈጣሪ ነውና። እስራኤልም የርስቱ ነገድ ነውና፤ የሠራዊት
ጌታ እግዚአብሔር ስሙ ነው። 17 በከበባ ውስጥ የምትኖሩ እናንተ ሕዝቦች፣ ዕቃችሁን ሰብስቡና ምድሪቱን ትታችሁ ውጡ። 18 እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፣
"ተመልከቱ፣ በዚህ ጊዜ በምድሪቱ የሚኖሩትን ልወረውራቸው ነው። አስጨንቃቸዋለሁ፣ እንደዚያም ሆኖ ያገኙታል። 19 ስለ ተሰበረው አጥንቴ ወየልኝ! ቊስሌም
መርቅዟል። ስለዚህ እኔ፣ "በእውነት ይህ የመከራ ጩኸቴ ነው ልሸከመውም ይገባኛል" አልሁ። 20 ድንኳኔ ተበዘበዘ፣ አውታሬም ሁሉ ለሁለት ተቈረጠ።
ልጆቼም ከእኔ ወሰዷቸው፣ ስለዚህ ከእንግዲህ የሉም። ድንኳኔንም ከእንግዲህ ወዲህ የሚዘረጋ መጋረጃዎችንም የሚያነሣ የለም። 21 እረኞች ደንቆሮዎች
ሆነዋል። እግዚአብሔርን አልፈለጉትምና። ስኬት አልሆነላቸውም፤ መንጎቻቸውም ሁሉ ተበትነዋል። 22 የወሬን ድምፅ ስሙ፣ "ተመልከቱ! እየመጣ ነው!
የይሁዳን ከተሞች ባድማና የቀበሮ ማደሪያ ያደርጋቸው ዘንድ ከሰሜን ጽኑ የምድር ነውጥ መጥቶአል።" 23 እግዚአብሔር ሆይ፣ የሰው መንገድ ከራሱ
እንዳይመጣ አውቃለሁ። የሚራመድ የትኛውም ሰው የገዛ አካሄዱን አያቀናም። 24 እግዚአብሔር ሆይ እንዳታጠፋኝ በቊጣህ ሳይሆን በፍትህ ቅጣኝ። 25
በማያውቁህ አሕዛብ፣ ስምህንም በማይጠሩ ወገኖች ላይ መዓትህን አፍስስ። ያዕቆብን በልተውታልና፣ ፈጽመው ሊያጠፉት ውጠውታልና ማደሪያውንም
አፍርሰዋልና።

Jeremiah 10:1

አጠቃላይ መረጃ፡-
እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ እንደዚሁም ለግብጽ፣ ኤዶም፣ አሞን፣ ሞአብ እና ለሁሉም ሕዝቦች እንደሚቀጡ አሳስቦአቸዋል።

ቃሉን ስሙ
“መልእክቱን ስሙ”

የእስራኤል ቤት
እዚህ ላይ “የእስራኤል ቤት” የሚለው የእስራኤልን ሕዝብ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእስራኤል ሕዝብ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የአሕዛብን መንገድ አትማሩ
“ሌሎች ሕዝቦች እንደሚያደርጉት እናንተ አታድርጉ”

መፍራት
መጨነቅ ወይም መሸበር

በሰማይ ምልክቶች
“በሰማይ በምታዩት እንግዳ ነገሮች”

አሕዛብ በእነዚህ ይፈራሉና
እዚህ ላይ “አሕዛብ” የሚለው በውስጣቸው የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላል። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አሕዛብ በሰማይ የተመለከቱአቸውን እንግዳ ነገሮች ይፈራሉ” (ገቢር/አድርጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 10:3

አጠቃላይ መረጃ፡-
እግዚአብሔር የአህዛብን መንገድ እንዳይማሩና በሰማይ በሚከናወኑ ነገሮች እንዳይጨነቁ አሳስቦአቸዋል።

አናጺ
በስራው ባለሞያ የሆነ ሰው

በእጃቸው የሚሰሩት ነገር በእርሻ መሃል እንደቆመ የወፎች ማስፈራርያ ነው
የወፎች ማስፈራርያ ወፎችን ለማስፈራራት በሰው ምስል የተሰራ ነገር ሲሆን ወፎች እህል እንዳይበሉ እነርሱን ይከላከላል። እዚህ ላይ እግዚአብሔር ጣዖቶችን በእርሻ መሃል ከሚቆም የወፎች ማስፈራርያ ጋር ያነጻጽረዋል ምክንያቱም እነርሱ ምንም ነገር ለማድረግ ችሎታ ስለሌላቸው ነው። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዱባ
ረጅም፣ አረንጓዴ ቅርፊትና ውስጡ ነጭ አካል ያለው ብዙ ውኃ የሚይዝ አትክልት ነው

ተሸካሚ ያስፈልጋቸዋል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች ሊሸከሙአቸው ያስፈልጋቸዋል” (ገቢር/አድርጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 10:6

አጠቃላይ መረጃ፡-
ኤርምያስ ስለ ጣዖት አምልኮ እየተናገረ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ስምህም በኃይል ታላቅ ነው
እዚህ ላይ የእግዚአብሔር “ስም” ራሱንና ዝናውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “አንተ በጣም ኃያል ነህ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የአሕዛብ ንጉሥ ሆይ፥ አንተን የማይፈራ ማን ነው?
ኤርምያስ ይህን መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ የሚጠይቀው ማንኛውም ሰው እግዚአብሔርን ሊፈራ እንደሚገባው አጽንዖት ለመስጠት ነው። እዚህ ላይ ኤርምያስ እግዚአብሔርን “የሕዛብ ንጉስ” እንደሆነ በግልጽ አስቀምጦታል። ይህ ጥያቄ በዓረፍተ ሃሳብ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የአሕዛብ ንጉሥ ሆይ፥ እያንዳንዱ ሰው ሊፈራህ ይገባል።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የሚገባህ ነው
“አንተ ለራስህ ያዘጋጀኸው ነው”

Jeremiah 10:8

ሁሉም አንድ ናቸው፣ እነርሱ ጅሎችና ሞኞች ናቸው
“ጅሎች” እና “ሞኞች” የሚሉት ቃላት በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ሕዝቡ እነዚህን ጣዖቶች በማምለካቸው ምን ያህል ሞኞች እንደሆኑ አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “እነርሱ ሁሉም ጅሎች ናቸው፣ ደቀ መዛሙርት ናቸው” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ከንቱ የሆኑና ከእንጨት የተሰሩ የጣዖቶች ደቀ መዛሙርት ናቸው
“የእንጨት ቁራጭ ከሆነው ከጣዖት ለመማር ይሞክራሉ”

ተርሴስ ... አፌዝ
ብርና ወርቅ የሚወጣባቸው ስፍራዎች ናቸው (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በባለሞያና በአንጥረኛ እጅ የተሰራ ወርቅ ከአፌዝ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላ። በተጨማሪ አንጥረኛዎቹ እዚህ ላይ “በእጃቸው” ተወክለዋል ምክንያቱም ስራቸውን የሚሰሩት በእጃቸው ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የሰለጠኑ ባለሞያና አንጥረኛ የሰሩት ወርቅ ከአፌዝ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ብልኀተኞች
“የሰለጠኑ አናጺዎች”

አንጥረኞች
ማንኛውምንም ወርቅ ያልሆነውን ነገር ለመለየት ወርቅን የሚያቀልጡ ሰዎች

ልብሳቸውም ሰማያዊና ቀይ ግምጃ ነው
“ሰዎች ጣዖቶችን ሰማያዊና ቀይ ግምጃ ያለብሱአቸዋል”

ከቊጣው የተነሣ ምድር ትንቀጠቀጣለች
ይህ የሚናገረው ለእግዚአብሔር ቁጣ ስሜታዊ ምላሽ በመስጠት መሬት ስለመንቀጥቀጥዋ ነው፣ በእርግጥ ይህ የሚሆነው እግዚአብሔር ምድር እንድትንቀጠቀጥ ሲያደርጋ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እርሱ በሚቆጣበት ጊዜ ምድር ትንቀጠቀጣለች” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መንቀጥቀጥ
“መናወጥ”

Jeremiah 10:11

አጠቃላይ መረጃ፦
እግዚአብሔር ለኤርምያስ እየተናገረው ነው።

እናንተም ለእነርሱ እንዲህ ብላችሁ ትነግሩአቸዋላችሁ
“እናንተ” የሚለው ቃል እስራኤላውያንን ይወክላል፣ “እነርሱን” የሚለው ደግሞ የሌሎች መንግስታት ሕዝቦችን ይወክላል።

ከምድር ይጠፋሉ
ይህ ጣዖቶቹ እንደሞቱ ተቆጥረው ስለ መጥፋታቸውና ጠቃሚነታቸውን ስለ ማጣታቸው ይናገራል። ይህ እነርሱ ኃይል እንደሌላቸው አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፦ “ከምድር ይጠፋሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰማያትንም የዘረጋ
ይህ እርሱ እንደዘረጋው እንደ ትልቅ አንሶላ እግዚአብሔር ሰማያትን እንደፈጠረ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰማጣትን ፈጠረ” ወይም “ሰማይን ፈጠረ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ድምጹ በሰማያት ያሉ ውሆች እንዲናወጡ ያደርጋል
እዚህ ላይ ለንግግሩ አጽንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር “በድምጹ” ተወክሏል። “ውሆች” እንዲናወጡ የሚለው ሀረግ ታላቅ ጩኸት ያለውን ማዕበል ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “የእርሱ ድምጽ በሰማይ ማዕበል ይፈጥራል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ጉምን ከምድርም ዳር ወደ ላይ እንዲወጣ ያደርገዋል
ይህ እርሱ ጉም ወደ ላይ እንዲተንንና ደመና እንዲፈጠር ያደረርጋል ማለት ነው። “ከምድርም ዳር” የሚለው ሀረግ ምድርን ሁሉ የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እርሱ በማንኛውም የምድሪቱ ክፍል ሁሉ ደመና እንዲፈጠር ያደርጋል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ነፋስንም ከግምጃ ቤቱ ይልካል
ይህ እግዚአብሔር ነፋሳትን እንዲነፍሱ ስለማድረጉ ሲናገር ነፋሱ በግምጃ ቤት እንደተቀመጠና እርሱ ሲፈልግ እንደሚወጣ ተደጎ ተገልጦአል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ግምጃ ቤት
የተለያዩ ቁሳቁሶች የሚቀመጡበት ሕንጻ

Jeremiah 10:14

እውቀት አጥቶአል
“እውቀት የለውም” ወይም “አያውቅም”

እያንዳንዱ አንጥረኛ ከቀረጸው ጣዖት የተነሣ አፍሮአል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የእያንዳንዱ አንጥረኛ ጣዖት አሳፍሮታል” ወይም ““የእያንዳንዱ አንጥረኛ በተመለከተ ጣዖቱ አሳፍሮታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በሚቀጡበት ጊዜ እነርሱ ይጠፋሉ
ይህ ስለ ጣዖቶቹ የመጨረሻ ጥፋት ይናራል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር እነርሱን የሚያጠፋበት ጊዜ ይመጣል” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የያዕቆብ እድል ፈንታ
እዚህ ላይ “ያዕቆብ” የእስራኤልን ሕዝብ ይወክላል። እግዚአብሔር የእነርሱ “እድል ፈንታ” መሆኑ ፈሊጥ ሲሆን እርሱንያመልኩታል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የእስራኤል እድል ፈንታ” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ የሚያመልኩት” (ምትክ ስም እና ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

የሁሉ ነገር የቀረጸ
“የሁሉ ነገር ፈጣሪ” ወይም “ሁሉን ነገር የፈጠረ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እስራኤልም የርስቱ ነገድ ነው
ይህ እስራኤል የእግዚአብሔር እንደሆነች የሚናገር ሲሆን እግዚአብሔር በውርስ ያገኛት ነገር እንደሆነች ተደርጎ ተገልጦአል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእስራኤልም ነገድ የእግዚአብሔር ናት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 10:17

ዕቃሽን ሰብስቢ
“ንብረትሽን ሰብስቢ”

በከበባና በጦርነት ስር የምትኖሪ
“ከተማሽ በጠላቶችሽ ጦር ሰራዊት የተከበበ” ወይም “የጠላቶችሽ ጦር ሰራዊት ከተማሽን ከብቦ ሳለ በከተማሽ ውስጥ ስትኖሪ የነበርሽ”

ተመልከቱ
እግዚአብሔር እዚህ ላይ ይህን ቃል የተጠቀመው ከዚህ ክፍል ቀጥሎ የሚናገረውን ንግግር ሰዎች ትኩረት እንዲሰጡት ለማድረግ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አዳምጡ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ በምድሪቱ የሚኖሩትን ሰዎች በዚህ ጊዜ ወደ ውጪ እወረውራቸዋለሁ
እዚህ ላይ እግዚአብሔር ሕዝቡ ምድሪቱን ለቅቀው እንዲወጡ እንደሚያደርጋቸው ሲናገር እነርሱ ከእቃ ማስቀመጫ ውስጥ አውጥቶ የሚወረውራቸው እቃዎች እንደሆኑ አድርጎ ገልጦታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ በምድሪቱ የሚኖሩትን ሰዎች ያችን ምድር እንዲለቅቁ አደርጋቸዋሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በምድሪቱ የሚኖሩትን ሰዎች
“በምድሪቱ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች”

ጉዳት
ታላቅ ስቃይ ወይም መከራ

Jeremiah 10:19

አጠቃላይ መረጃ፡-
ኤርምያስ እርሱ መላው የእስራኤል ነገድ እንደሆነ አድርጎ ይናራል። (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ወየልኝ! በተሰበሩ አጥንቶቼ ምክንያት፣ ቁስሌ የማይድን ነው
ኤርምያስ ስለ ሕዝቡ ጉዳት ሲናገር በተሰበሩ አጥንቶችና በማይድን ቁስል በአካል እንደተጎዱ አድርጎ ተናግሮታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኛ ወየልን! የተሰበረ አጥንትና የማይድን ቁስል እንዳለን ያህል ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን ልሸከመው ይገባኛል
እዚህ ላይ ኤርምያስ የእስራኤልን መላውን ነገድ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን ልንሸከመው ይገባናል” (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ድንኳኔ ፈርሷል፣ የድንኳኔ ገመዶች ሁሉ ለሁለት ተቆርጠዋል
እዚህ ላይ ኤርምያስ ጠላት ከተማቸውን ስለማፍረሱ ሲናገር ድንኳኑ እንደፈረሰ አድርጎ ተናግሮታል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእኛ ታላቅ ድንኳን የፈረሰ ያህል ነው፤ ድንኳኑን የሚያያይዙት ገመዶች ተቆርጠዋል” ወይም “ጠላት ከተማችንን ሙሉ በሙሉ አፍርሷታል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ድንኳኔ ፈርሷል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላቴ ድንኳኔን አፍርሶታል” ወይም “የእኛ ጠላት ድንኳናችንን አፍርሶታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ልጆቼን ከእኔ አርቀው ወስደዋቸዋል
እዚህ ላይ ኤርምያስ የእስራኤልን መላውን ነገድ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእኛ ጠላቶች ልጆቻችንን ከእኛ አርቀው ወሰደዋቸዋል” (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ አይኖሩም
ልጆቹ ከእንግዲህ ወዲህ አይኖሩም የሚለው ወላጆች ከእንግዲህ ወዲህ እንደገና ሊያያዩአቸው እንደማይችሉ ለመግለጥ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ከእንግዲህ ወዲህ እንደማይኖሩ ዓይነት ነው” ወይም “እነርሱ እንደገና ፈጽሞ አይመለሱም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህ ወዲህ ድንኳኔን የሚዘረጋ ወይም የድንኳኔን መጋረጃዎች የሚያነሣ ማንም የለም
እዚህ ላይ ኤርምያስ ከተማቸውን እንደገና ለመገንባት አንድም ልጅ እንደማይኖርላቸው ስለ እነርሱ ሲናገር ከተማቸው እንደገና ልትገነባ የሚገባት ድንኳን እንደነበረች አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከተማችንን እንደገና ለመገንባት አንድም ሰው አይኖርም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 10:21

እረኞቹ ጅሎች ናቸውና ... መንጎቻቸውም ሁሉ ተበትነዋል
እዚህ ላይ የእስራኤል መሪዎች እረኞች እንደሆኑና የእስራኤል ሕዝብ ደግሞ የበግ መንጋዎች እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሕዝባችን እረኞች ጅሎች ናቸውና ... የሕዝባችን መንጎች በሙሉ ተበትነዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መንጎቻቸውም ሁሉ ተበትነዋል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእነርሱ ጠላቶቻቸው መንጎቹን በሙሉ በትነዋቸዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ተመልከቱ! እየመጣ ነው፣ ታላቅ የመሬት መንቀጥቀጥ እየመጣ ነው
እዚህ ላይ እየመጣ ያለው የጠላት ጦር ሰራዊት የመሬት መንቀጥቀጥ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። “ተመልከቱ!” የሚለው ቃል ፈሊጥ ሲሆን ቀጥሎ ለሚነገረው ነገር የአድማጮችን ትኩረት ለመሳብ ጥቅም ላይ የዋለ ነው። አማራጭ ትርጉ፡- “ተመልከቱ! የጠላት ጦር ሰራዊት እየመጣ ነው፣ በሚመጡበት ጊዜ እንደ ታላቅ የመሬት መንቀጥቀጥ ድምጽ ይኖራቸዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀበሮዎች
ቀበሮዎች እጅግ በጣም ኃይለኛ የዱር ውሾች

Jeremiah 10:23

አጠቃላይ መረጃ፡-
ኤርምያስ ለእስራኤል ሕዝብ ይጸልያል።

የሰው መንገድ ከራ አይደለም። የሚራመድ ሰው እንዱም ቢሆን የራሱን መንገድ አያቀናም
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ይህን ሲል አንድ ሰው በሕይወት ጉዞው በእርሱ ላይ በሚሆኑት በተለያዩ ነገሮች ላይ በበላይነት ራሱ ሊቆጣጠረው አይችልም ለመለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ማንም ሰው በእርሱ ላይ የሚሆነውን ነገር መቆጣጠር አይችልም፣ ማንም ሰው በሕይወቱ የሚከናወነውን ነገር ራሱ አቅጣጫ ማስያዝ አይችልም” (ትይዩነት/ተመሳሳይነት እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ቁጣህን በመንግስታት ላይ አፍስሰው
እዚህ ላይ “መንግስታት” የሚለው በውስጣቸው የሚኖሩትን ሕዝብ የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በቁጣህ መንግስታትን ቅጣቸው” ወይም “በቁጣህ የሕዝቦችን መንግስታት ቅጣቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱጉም፡-

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ስምህን በማይጠሩ
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “አንተን የማያመልኩ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ያዕቆብን አሟጥጠው ስለበሉት፣ ፈጽመው ስለዋጡት፣ ሙሉ በሙሉ እርሱን ስላጠፉት
እነዚህ ሶስት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። እስራኤልን ሙሉ በሙሉ መጥፋት አጽንዖት ጠት ኤርምያስ ይህንን ሃሳብ ሶስት ጊዜ ደጋግሞታል። ይህ የሚናገረው የእስራኤልን ሕዝብ ስላጠቁት የጠላት ጦር ሰራዊት ሲሆን ጦር ሰራዊቱ የሚበላውን እንስሳ ፈልጎ እንደሚያጠቃና እንደሚበላ ሃይለኛ ተናካሽ እንስሳ ተደርጎ ተገልጦአል። አማራጭ ትርጉም፦ “እነርሱ የእስራኤልን ሕዝብ በሃይል አጥቅተውታልና ደግሞም እነርሱን ሙሉ በሙሉ ለማጥፋ በልተዋቸዋልና” (ትይዩነት/ተመሳሳይነት እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መኖርያቸውን ወና አድርገውታል
“ቤታቸውን ወና አድርገውታል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 11

1 ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ኤርምያስ የመጣው ቃል ይህ ነው፣ እንዲህም አለ። **2** የዚህን ቃል ኪዳን ቃል ስማ፣ ለእያንዳንዳቸው የይሁዳ ሰዎች፣ በኢየሩሳሌምም ለሚኖሩትም ተናገር፥ **3** እንደዚህም በላቸው 'የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ የዚህን ቃል ኪዳን ቃል የማይሰማ ሰው ርጉም ይሁን። **4** ከግብጽ አገር ከሚቀልጠው የብረት ምድጃ ባወጣኋቸው ቀን ለአባቶቻችሁ ያዘዝሁበት ኪዳን ይህ ነው። "ድምፄን ስሙ፣ ያዘዝኋችሁንም ነገሮች ሁሉ አድርጉ፣ እናንተ ሕዝብ ትሆኑኛላችሁ፣ እኔም አምላክ እሆናችኋለሁና።" **5** ይህም ዛሬ የምትኖሩባትን ወተትና ማር የምታፈስሰውን ምድር እሰጣቸው ዘንድ ለአባቶቻችሁ የማልሁትን መሐላ አጸና ዘንድ ነው።" ከዚያ እኔ ኤርምያስ "አዎን፣ እግዚአብሔር ሆይ!' ብዬ መለስሁለት። **6** እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ፣ "ይህችን ቃል ሁሉ በይሁዳ ከተሞችና በኢየሩሳሌም ጎዳናዎች ተናገር። እንዲህ በል፣ 'የዚህን ቃል ኪዳን ቃል ስሙ ፈጽሙትም። **7** አባቶቻችሁን ከግብጽ ምድር ካወጣሁበት ቀን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ፥ "ቃሌን ስሙ" በማለት በጽናት አስጠንቅቄአቸው ነበር። **8** እነርሱ ግን አልሰሙም ወይም ትኩረት አልሰጡም። እያንዳንዱ ሰው በክፉ ልባቸው እልከኝነት ሄዱ። ስለዚህ እንዲመጡባቸው ያዘዝኋቸውን እርግማን ሁሉ አመጣሁ። ሕዝበ ግን እንደዚያም ሆኖ አልታዘዙም።" **9** ቀጥሎ እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ፣ "በይሁዳ ሰዎችና በኢየሩሳሌም በሚኖሩ ዘንድ አድማ ተገኝቶአል። **10** ቃሌንም ይሰሙ ዘንድ እንቢ ወዳሉ፣ ይልቁንም ያመልኩአቸው ዘንድ እንግዶችን አማልክት ወደተከተሉ ወደ አባቶቻቸው ኃጢአት ተመለሱ። የእስራኤል ቤትና የይሁዳ ቤት ከአባቶቻቸው ጋር ያደረግሁትን ቃል ኪዳን አፈረሱ። **11** ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ 'ተመልከቱ፣ ሊያመልጡት የማይችሉትን ጥፋት አመጣባቸዋለሁ። ከዚያም ወደ እኔ ይጮኻሉ፣ እኔ ግን አልሰማቸውም። **12** የይሁዳ ከተሞችና በኢየሩሳሌም የሚኖሩት ሄደው ወደሚሰዉላቸው አማልክት ይጮኻሉ፤ ነገር ግን በጥፋታቸው ጊዜ ከቶ አያድኑአቸውም። **13** ይሁዳ፣ አማልክትህ እንደ ከተሞችህ ቍጥር እንዲሁ ጨምረዋል። በኢየሩሳሌምም መንገዶች ቍጥር ልክ አሳፋሪ መሠዊያ፣ ለበዓለም የማጠኛ መሠዊያ አድርጋችኋል። **14** ስለዚህ አንተ ራስህ፣ ኤርምያስ፣ ለዚህ ሕዝብ ልትጸልይ አይገባም። ስለእነርሱ አታልቅስ ወይም አትጸልይ። በጥፋታቸው ጊዜ ወደ እኔ ሲጮኹ አልሰማቸውምና። **15** እጅግ ብዙ ክፉ ፍላጎት የነበረው ተወዳጁ ሕዝቤ በቤቴ ውስጥ ያለው ለምንድነው? ለመስዋዕታችሁ የተጠበቀው ሥጋ ክፋትን አድርጋችኋልና ሊረዳችሁ አይችልም፣ ከዚያም በዚያ ደስተኛ አትሆኑም። **16** በጥንቱ ጊዜ እግዚአብሔር በተወዳጅ ፍሬ የተዋበች የለመለመች የወይራ ዛፍ ብሎ ጠራሽ። ሆኖም ግን እንደ ዐውሎ ነፋስ ጩኸት እሳትን አነደደባት፣ ቅርንጫፎችዋም ተሰብረዋል። **17** ለበኣልም በማጠናቸው ያስቈጡኝ ዘንድ ለራሳቸው ስለ ሠሩአት ስለ እስራኤልና ስለ ይሁዳ ቤት ክፋት የተከለሸ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ክፉን ነገር ተናግሮብሻል። **18** እግዚአብሔርም እነዚህን ነገሮች አውቃቸው ዘንድ አስታወቀኝ፤ አንተ እግዚአብሔር ሥራቸውን እንዳይ አደረግኸኝ። **19** እኔም ለመታረድ እንደሚነዳ እንደ የዋህ የበግ ጠቦት ሆንሁ። እነርሱም፣ "ዛፉን ከፍሬው ጋር እንቍረጥ! ስሙም ከእንግዲህ ወዲህ እንዳይታሰብ ከሕያዋን ምድር እናጥፋው" ብለው ምክርን እንዳሰቡብኝ አላወቅሁም ነበር። **20** ይሁን እንጂ፣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር አእምሮንና ልብን ይመረምራል፣ በቅንም ይፈርዳል። ጉዳዬን አቅርቤልሃለሁና በእነርሱ ላይ በቀልህን እመሰክራለሁ። **21** ስለዚህም 'በእጃችን እንዳትሞት በእግዚአብሔር ስም ትንቢት አትናገር' ብለው ነፍስህን ስለሚሹ ስለ ዓናቶት ሰዎች እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። **22** ስለዚህ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ይህንን ይላል፣ 'ተመልከት፣ እቀጣቸዋለሁ። ኃያላን ወጣቶቻቸው በሰይፍ ይሞታሉ። ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውም በረሃብ ይሞታሉ። **23** በምቀጣቸውም ዓመት በዓናቶት ሰዎች ላይ ክፉ ነገር አመጣባቸዋለሁና ማንም ከእነርሱ የሚቀር የለም።

Jeremiah 11:1

ስማ የሚል፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ኤርምያስ የመጣው ቃል ይህ ነው
ይህ ፈሊጥ ከእግዚአብሔር የመጣውን ልዩ መልእክት ለማስተዋወቅ ጥቅም ላይ የዋለ ነው። ይህን ተመሳሳይ ሀረግ በኤርምያስ 7:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “ይህ እግዚአብሔር ለኤርምያስ የሰጠው መልእክት ነው። ስማ አለው፣” ወይም “ይህ እግዚአብሔር ለኤርምያስ የተናገረው መልእክት ነው። ስማ፣” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች
“በኢየሩሳሌም ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች”

Jeremiah 11:3

ማንኛውም ሰው የተረገመ ነው
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔ ማንኛውንም ሰው እረግማለሁ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ከግብጽ አገር ከብረት ማቅለጫው ምድጃ
ይህን የሚናገረው እስራኤላውያንን ከብረት ማቅለጫ ምድጃ ጋር በማነጻጸር እስራኤላውያን ይኖሩ የነበረውን አስከፊ ሁኔታና ጭቆና ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የግብጽ። በግብጽ ምድር በእነርሱ የሆነው እጅግ በጣም አስከፊ ነበር፤ ይህ ሁኔታቸው አነርሱ በጣም በጋለ ምድጃ ውስጥ ይኖሩ እንደነበር ያህል ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ማቅለጥ
ብረትን ወደ ፈሳሽ ለመለወጥ ማቅለጥ

ድምጼን አድምጡ
“ድምጽ” የሚለው ተናጋሪው በድምጹ ለተናገረው ነገር ምትክ ስም ነው፣ “አድምጡ” የሚለው ደግሞ “ለመታዘዝ” ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የምናገረውን ታዘዙ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 11:6

የተከበረ
ትኩረት የሚሰጠውና በጣም ጠቃሚ

የዚህን ቃል ኪዳን ቃል
“የዚህ ቃል ኪዳን ውሎች”

አድርጉት
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ታዘዙአቸው” (የሚለውን ይመልከቱ)

ድምጼን ስሙ
እዚህ ላይ “ድምጽ” የሚለው ቃል ተናጋሪው በድምጹ ለተናገረው ነገር ምትክ ስም ነው፣ “ስሙ” የሚለው ደግሞ “ለመታዘዝ” ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የተናገርሁትን ታዘዙ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እያንዳንዱ ሰው በክፉ ልቡ እልከኝነት ይመላለስ ነበር
እዚህ ላይ “መመላለስ” የሚለው አንድ ሰው ለሚኖርበት የኑር ዘይቤ ፈሊጥ ነው። “ልብ” የሚለው ደግሞ ለሰው ፍላጎትና ስሜት ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እያንዳንዱ ሰው ለመለወጥ ፈቃደኛ አልሆነም፣

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይልቁንም በራሱ ክፉ ፍላጎት ይኖር ነበር” ወይም “እያንዳንዱ ሰው ለመለወጥ ፈቃደኛ አልሆነም፣ ይልቁንም ማድረግ የሚፈልጉትን ክፉ ነገሮች ማድረግ ቀጠሉ” (ፈሊጥ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህ በእነርሱ እንዲመጡ ያዘዝኋቸውን በዚህ ቃል ኪዳን ያሉትን እርግማን ሁሉ አመጣሁባቸው
“ስለዚህ እነርሱ እንዲታዘዙት በነገርኋቸው በዚህ ቃል ኪዳን ውስጥ ባሉት እርግማኖች ሁሉ ቀጣኋቸው”

Jeremiah 11:9

አድማ ተገኝቷል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አድማ አለ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

አድማ
ጉዳት የሚያደርስ ወይም ሕገ ወጥ የሆነ ስራ ለመስራት ያነጣጠረ ምስጢራዊ እቅድ

የኢየሩሳሌም ነሪዎች
“በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሕዝቦች”

ወደ ቀድሞ አባቶቻቸው ሓጢአት ተመለሱ
“ተመለሱ” የሚለው ቃል ፈሊጥ ሲሆን አንድን ነገር ለመስራት እንደገና መጀመር ማት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የቀደሙት አባቶቻቸው የፈጸሙትን ተመሳሳይ ኃጢአት እነርሱም ወደ ማድረግ ተመለሱ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ተከተሉ
“ከኋላ ተከተሉ”

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩት ቤተሰቦች ምትክ ስም ነው። እዚህ ላይ የእስራኤልን መንግስት ያመለክታል። ይህን በኤርምያስ 3:18 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እስራኤል” ወይም “የእስራኤል መንግስት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳ ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩት ቤተሰቦች ምትክ ስም ነው። እዚህ ላይ የይሁዳንና የቢንያምን ልጆች የሚያካትተውን የይሁዳን መንግስት ያመለክታል። ይህን በኤርምያስ 3:18 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “ይሁዳ” ወይም “የይሁዳ መንግስት” ወይም “የይሁዳ ሕዝብ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 11:11

ተመልከቱ
ይህ ቃል እዚህ ላይ ጥቅም ላይ የዋለው ቀጥሎ የሚናገረውን ንግግር ሰዎች ትኩረት እንዲሰጡት ለማድረግ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አዳምጡ” ወይም “ለምነግራችሁ ነገር ትኩረት ስጡ”

የይሁዳ ከተሞችና የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች
እዚህ ላይ “የይሁዳ ከተሞች” የሚለው በከተሞቹ ውስጥ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በይሁዳ ከተሞችና በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን በእርግጠኝነት በእነርሱ በኩል አይድኑም
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን አማልክቶቻቸው ፈጽሞ ሊያድኗቸው አይችሉም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እኩል
“የእነርሱን ቁጥር ያህል”

መንገዶቿ
“በኢየሩሳሌም ውስጥ ያሉ መንገዶች”

Jeremiah 11:14

ስለ እነርሱ ልትማጠን አይገባህም
“ታላቅ የሃዘን ልቅሶ ልታለቅስ አይገባህም”

ወዳጄ፣ እጅግ በጣም ብዙ ክፉ ሃሳብ የነበራት በቤቴ ውስጥ ምን አላት?
እግዚአብሔር ይህን መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ የተጠቀመበት የይሁዳ ሕዝብ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ለወደፊት ለመገኘት ምንም ዓይነት መብት እንደሌለው አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- ወዳጄ፣ እጅግ በጣም ብዙ የክፋት ሃሳብ የነበራት፣ በቤቴ ውስጥ ልትገኝ አይገባትም።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ይህች ወዳጄ፣ የነበራት
የይሁዳ ሕዝብ እጅግ እንደተወደደች እንደ አንዲት ሴት ተደርጋ ተነግራለች። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ የምወዳቸው ሕዝቤ፣ የነበራቸው” ወይም “እኔ የምወዳቸው የይሁዳ ሕዝብ፣ የነበራቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ባለፉት ዘመናት እግዚአብሔር የለመለመ የወይራ ዛፍ ብሎ ጠርቶሽ ነበር
በብሉይ ኪዳን ሰዎች ብዙ ጊዜ ከዛፎችና ከተክሎች ጋር ይነጻጸሩ ነበር። ፍሬያማና ጤናማ የነበሩት የለመለሙና ጤናማ ዛፎች እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ባለፉት ዘመናት እግዚአብሔር እናተ እንደለመለመ የወይራ ዛፍ እንደነበራችሁ ተናግሯል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሷ ላይ እሳት ያነድድባታል
ይህ ገለጻ የዛፉን ተለዋጭ ዘይቤ ተከትሎ የተነገረ ነው። እሳቱ የሚወክለው የሕዝቡን መጥፋት ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህም የታላቅ ዓውሎ ነፋስ ድምጽ ይኖረዋል
ይህ የአስከፊውን እሳት ድምጽ ከኃይለኛ ዓውሎ ነፋስ ድምጽ ጋር ያገጻጽረዋል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቅርንጫፎቹ ይሰባበራሉ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ቅርንጫፎችሽን ይሰባብራቸዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 11:17

አንቺን የተከለሽ
ይህ እግዚአብሔር የእስራኤልንና የይሁዳን ሕዝቦች ልክ እግዚአብሔር እንደተከላቸው ዛፎች እንደሆኑ አድርጎ በመግለጽ በሚኖሩበት ስፍራ እንዳስቀመጣቸው ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ገበሬ ዛፍ እንደሚተክል እንደዚሁ አንቺን የተከለሽ” ወይም “በእስራኤልና በይሁዳ ምድር እንድትኖሪ በዚያ ያስቀመጠሽ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በአንቺ ላይ ክፉ ነገር አውጀውብሻል
“በአንቺ ላይ ክፉ ነገር እንዲመጣ አውጀውብሻል”

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩት ቤተሰቦች ምትክ ስም ነው። እዚህ ላይ የእስራኤልን መንግስት ያመለክታል። ይህን በኤርምያስ 3:18 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እስራኤል” ወይም “የእስራኤል መንግስት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የይሁዳ ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩት ቤተሰቦች ምትክ ስም ነው። እዚህ ላይ የይሁዳንና የቢንያምን ልጆች የሚያካትተውን የይሁዳን መንግስት ያመለክታል። ይህን በኤርምያስ 3:18 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “ይሁዳ” ወይም “የይሁዳ መንግስት” ወይም “የይሁዳ ሕዝብ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 11:18

እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች እንዳውቃቸው አደረገኝ፣ እኔም አወቅኋቸው
“አንተ ነገሮችን ለእኔ ገለጥህልኝ፣ እኔም አወቅኋቸው።” ይህ ጠላቶቹ እርሱን ለመግደል እያቀዱ እንደነበረ እግዚአብሔር ለኤርምያስ መግለጡን የሚያመለክት ነው።

ስራቸውን እንድመለከት አደረግኸኝ
ይህ ጠላቶቹ እርሱን ለመግደል እያቀዱ እንደነበረ እግዚአብሔር ለኤርምያስ መግለጡን የሚያመለክት ነው። እዚህ ላይ የተነገረው ኤርምያስ የእነርሱን ስራዎች እንደተመለከተ አድርጎ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የእነርሱን ክፉ እቅዶች ለእኔ ገለጠልኝ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔም ለመታረድ እንደሚነዳ እንደ የዋህ በግ ጠቦት ሆንሁ
ይህ ኤርምያስን ለመታረድ ከሚነዳ ከየዋህ በግ ጋር በማነጻጸር ኤርምያስ እርሱን ለመግደል ጠላቶቹ ያቀዱትን እቅድ አለማወቁን ይናገራል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለመታረድ ወደ እርድ ቦታ እንደሚነዳ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላቶቼ ወደ እርድ ቦታ እየመሩኝ ነው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ዛፉን ከፍሬው ጋር እንቍረጥ
እዚህ ላይ የኤርምያስ ጠላቶች እርሱን ለመግደል ስለማሰባቸው ሲናገር ኤርምያስ እነርሱ ሊያጠፉት ያቀዱት የፍሬ ዛፍ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱን ከሕያዋን ምድር እናጥፋው
“እናጥፋው” የሚለው ቃል እርሱን ማጥፋት ማለት ነው። በተጨማሪ “ሕያዋን” የሚለው ሕያዋን ሕዝብን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በእነዚህ በሕይወት በሚኖሩ ሰዎች ምድር ከእንግዲህ ወዲህ እንዳይኖር እንግደለው” ወይም “በሕይወት በሚኖሩ ሰዎች ዓለም መካከል ከእንግዲህ ወዲህ እንዳይኖር እናጥፋው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ስሙም ከእንግዲህ ወዲህ እንዳይታሰብ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች ከእንግዲህ ወዲህ ስሙን አያስታውሱትም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ልብንና አእምሮን
“ልብ” የሚለው ሰው ለሚሰማው ስሜትና ለሚፈልገው ነገር ምትክ ስም ነው፣ “አእምሮ” ደግሞ ሰው ለሚያስበውና ለሚወስነው ነገር ምትክ ስም ነው።

አማራጭ ትርጉም፡- “የሰው ስሜትና ሃሳብ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በቀልህን እኔ እመሰክራለሁ
እዚህ ላይ “በቀል” የሚለው ቃል በግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ ስትበቀል እኔ እመለከትሃለሁ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 11:21

ዓናቶት
ይህ ካህናት የሚኖሩበት የተለየ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሕይወትህን ለሚፈልጓት
ይህ ሀረግ የሚያመለክተው አንድን ሰው ለመግደል መፈለግ ወይም መሞከር ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተን ለመግደል መፈለግ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህ አሉ
“ለእኔ እንዲህ አሉኝ።” ሰዎቹ ለኤርምያስ እየተናገሩ ነው።

በእጃችን ትሞታለህ
እዚህ ላይ ሰዎቹ “እጃችን” የሚለውን ቃል የተጠቀሙት እነርሱ ራሳቸው እርሱን ለመግደል ማቀዳቸውን አጽንዐት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እኛ ራሳችን እንገድልሃለን” (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ከእግዚአብሔር የመጣውን በጣም አስፈላጊ መልእክት ለማስተዋወቅ ብዙ ጊዜ እነዚህን ቃላት ይጠቀማል። ይህን በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

ተመልከቱ
ይህ ቃል እዚህ ላይ ጥቅም ላይ የዋለው ቀጥሎ የሚናገረውን ንግግር ሰዎች ትኩረት እንዲሰጡት ለማድረግ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አዳምጡ”

ኃይለኛ ወጣት ወንዶች
እነዚህ በጣም ጠንካራ በሚሆኑበት የሕይወት እድሜ የሚገኙ ናቸው

በሰይፍ ይሞታሉ
እዚህ ላይ “ሰይፍ” ጦርነትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በጦርነት ውስጥ ይሞታሉ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

አንዳቸውም አይተርፉም
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ አንዳቸውንም አልተዋቸውም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በሚቀጡበት ዓመት
እዚህ ላይ “ዓመት” የሚለው ቃል ፈሊጥ ሲሆን እግዚአብሔር የወሰነውን የተለየ ጊዜ የሚገልጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ በሚቀጡበት ጊዜ” ወይም “እነርሱ የሚቀጡበት ጊዜ እየመጣ ነው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 12

1 እግዚአብሔር ሆይ፣ ከአንተ ጋር በተሟገትሁ ጊዜ አንተ ጻድቅ ነህ። የማጉረመርምበትን ምክንያት በእርግጥ ልነግርህ ይገባኛል። የኃጢአተኞች መንገድ ስለምን ይሳካል? እምነት-የለሽ የሆኑት ሁሉ ተሳክቶላቸዋል። **2** አንተ ተክለሃቸዋል፣ እነርሱም ሥር ሰድደዋል። ፍሬ ማፍራታቸውን ቀጥለዋል። በአፋቸው አንተ ቅርብ ነህ፣ ከልባቸው ግን ሩቅ ነህ። **3** ይሁን እንጂ አንተ እግዚአብሔር ታውቀኛለህ። አይተኸኛል፣ ልቤንም ፈትነሃል። እንደ ሚታረዱ በጎች ለያቸው። ለመታረድም ቀን ነጥላቸው። **4** ምድሪቱ የምታለቅሰው፣ የአገሩ ሣርስ ሁሉ ከነዋሪዎቹ ክፋት የተነሣ የሚደርቀው እስከ መቼ ነው? አራዊት እና ወፎች ተወስደዋል። በእርግጥም ሕዝቡ "በእኛ ላይ የሚሆነውን እግዚአብሔር አያውቅም፤" ብለዋል። **5** "አንተ ኤርምያስ ከእግረኛ ወታደሮች ጋር በሮጥህ ጊዜ እነርሱ ቢያደክሙህ፣ ከፈረሶች ጋር መወዳደር እንዴት ትችላለህ? በአስተማማኝ የገጠር ምድር ውስጥ ብትሰናከል፣ በዮርዳኖስ ጥሻዎች ውስጥ እንዴት ትሆናለህ? **6** ወንድሞችህና የአባትህ ቤት እነርሱ ጭምር አሳልፈው ሰጥተውሃልና፣ ጮኸው ክደውሃልና። መልካም ነገሮችንም ቢናገሩህ አትታመናቸው። **7** ቤቴን ትቼአለሁ፣ ርስቴንም ጥያለሁ። ተወዳጁን የገዛ ሕዝቤን በጠላቶቹ እጅ አሳልፌ ሰጥቻለሁ። **8** ርስቴ በጥሻ እንዳለ አንበሳ ሆናብኛለች፤ ድምፅዋን አንሥታብኛለችና ስለዚህ ጠልቻታለሁ። **9** ርስቴ እንደ ጅብ ሆነችብኝ፣ ዝንጉርጉር አሞሮችም ለማጥመድ በላይዋ ይዞራሉ። ሂዱ፣ የምድር አራዊትን ሁሉ ከሜዳ ሰብስቡና ይበሉም ዘንድ አምጡአቸው። **10** ብዙ እረኞች የወይኑን ቦታዬን ደምስሰዋል። እድል ፈንታዬ የሆነውን ምድር ሁሉ ረግጠዋል፤ የምደሰትበትን እድል ፈንታ ወና ምድረ በዳ አድርገውታል። **11** ባድማ አድርገውታል። ፈርሳለችና አለቅስላታለሁ። ምድር ሁሉ ባድማ ሆናለች በልቡም የሚያስባት የለም። **12** በወና ኮረብቶች ሁሉ ላይ አጥፊዎች መጥተዋል፣ የእግዚአብሔር ሰይፍ ከአንደኛው የምድር ዳር ጀምሮ እስከ ሌላኛው የምድር ዳር ድረስ ይበላልና። በሕይወት ላለ ሥጋ ለባሽ ሁሉ ደህንነት የለም። **13** ስንዴን የዘሩ ቢሆንም እሾህን አጨዱ። በሥራቸው ደከሙ፣ ምንም አላገኙም። ስለዚህ ከእግዚአብሔር ቍጣ የተነሣ ባገኛችሁት ፍሬ ታፍራላችሁ። **14** ሕዝቤ እስራኤል እንዲወርስ ያደረግሁትን ርስት ለሚነኩት ክፉዎች ጐረቤቶች ሁሉ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "ተመልከቱ፣ ከገዛ ምድራቸው የምነቅላቸው እኔ ነኝ፣ የይሁዳንም ቤት ከመካከላቸው እነቅለዋለሁ። **15** ከነቀልኋቸውም በኋላ መልሼ እራራላቸዋለሁ፣ እያንዳንዱንም ወደ ርስቱ እያንዳንዱንም ወደ ምድሩ እመልሳለሁ። **16** በበኣል ይምሉ ዘንድ ሕዝቤን እንዳስተማሩት ሁሉ እነዚያው ሕዝቦች 'ሕያው እግዚአብሔርን!' ብለው ይምሉ ዘንድ የሕዝቤን መንገድ በጥንቃቄ ቢማሩ፣ በዚያን ጊዜ በሕዝቤ መካከል ይመሠረታሉ። **17** ነገር ግን ማናቸውም ባይሰሙኝ ያንን ሕዝብ ፈጽሜ እነቅለዋለሁ። በእርግጥም ይነቀላል፣ ይጠፋማል" ይላል እግዚአብሔር።

Jeremiah 12:1

አጠቃላይ መረጃ፦
ኤርምያስ ለእግዚአብሔር እየተናገረ ነው።

ክፉዎች
ይህ ክፉ ሰዎችን ይወክላ። አማራጭ ትርጉም፦ “ክፉ ሰዎች” ወይም “ክፉ የሆኑ ሰዎች” (የስም ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ተክለሃቸዋል፣ ስርም ሰድደዋል። ፍሬ ማፍራትንም ቀጥለዋል
እዚህ ላይ ኤርምያስ ስለ ክፉ ሰዎች ሲናገር የፍሬ ዛፎች እንደሆኑ አድርጎ ገልጦአቸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ “አንተ እንደተከልሃቸው፣ እንዲለመልሙ እንዳደረግሃቸውና ብዙ ፍሬ እንዲያፈሩ እንዳደረግሃቸው ፍሬ እንደሚሰጥ ዛፍ ናቸው (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በአፋቸው አንተ ቅርብ ነህ፣ ከልባቸው ግን ሩቅ ነህ
እዚህ ላይ “አፋቸው” የሚለው ሰው የሚናገረውን ነገር ይወክላል። “ልባቸው” የሚለው ደግሞ ሰው የሚያስበውንና ስሜቱን ይወክላል። በተጨማሪ ታማኝ መሆን ለሰው ቅርብ መሆን እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል፣ ታማኝ አለመሆን ደግሞ ከሰው በጣም ሩቅ መሆን እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “እነርሱ ስለ አንተ ሁልጊዜ ጥሩ ነገር ይናራሉ ነገር ግን አንተን አይወዱህም ደግሞም አያከብሩህም” (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 12:3

አጠቃላይ መረጃ፦
ኤርምያስ ለእግዚአብሔር መናገሩን ቀጥሏል።

ልቤ
እዚህ ላይ “ልብ” የሰውን ሃሳብና እውነተኛ ስሜት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የእኔ ሃሳቦች” ወይም “የእኔ የውስጥ ስሜት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ዕርድ ቦታ እንደሚወሰዱ በጎች ውሰዳቸው
እዚህ ላይ ኤርምያስ ክፉ ሰዎችን ለመቅጣት እንዲዘጋጅ እግዚብሔርን ሲጠይቅ እነርሱ ለመታረድ እንደሚወሰዱ በጎች እንደሆኑ አድርጎ ገልጾአቸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ “ክፉ ሰዎችን ለመታረድ እንደሚነዱ በጎች ውሰዳቸው” ወይም “ክፉ ሰዎችን ለመቅጣት ተዘጋጅ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የዕርድ ቀን
“እነርሱ የሚጠፉበት ቀን”

በእርሷ ከሚኖሩት ሰዎች ክፋት የተነሳ ምድሪቱ የምትደርቀው እስከ መቼ ነው?
በሰዎች ክፋት ምክንያት ቅጣት ስለተላለፈባቸው ምድራቸው ደርቃለች፣ ዝናብ ደግሞ አይዘንብም።

መጠውለግ
መድረቅ

እንስሳቱና ወፎቹ ተወስደዋል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እንስሳቱና ወፎቹ ሄደዋል” ወይም “እንስሳቱና ወፎቹ በሙሉ ሞተዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር በእኛ ላይ የሚሆነውን ነገር አያይም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) ሕዝቡ በወደፊት ሕይወታቸው በእነርሱ ላይ ምን ነገሮች እንደሚፈጸሙ እግዚአብሔር አያውቅም እያሉ ይናገራሉ ወይም 2) እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን አያውቅም። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር እኛ የምንሰራቸውን ኃጢአት የተሞሉ ነገሮችን አያይም”

Jeremiah 12:5

ከፈረሰኞች ጋር እንዴት ልትወዳደር ትችላለህ
ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ የሚያመለክተው እርሱ ከፈረሶች ጋር ሊሮጥ እንደማይችል ነው። ይህ ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ ከፈረሶች ጋር ፈጽሞ ልትወዳደር አትችልም።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ብትወድቅ
ይህ ሰው እየሮጠ ቢወድቅ የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እየሮጥህ እያለህ ብትወድቅ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰላም ምድር
ይህ በፍጥነት ለመጓዝ ቀላል የሆነውን የተመቻቸ ሜዳ የሚያመለክት ሲሆን ለመንቀሳቀስ በጣም አስቸጋሪ ከሆኑት በዮርዳኖስ ወንዝ ዙርያ ካሉት የቁጥቋጦ ጥሻዎች ጋር እያነጻጸረ ነው። ይህ ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በዮርዳኖስ ዙርያ ባሉት የቁጥቋጦ ጥሻዎች መካከል በእርግጠኝነት መሮጥ አትችልም”

በዮርዳኖስ ወንዝ ዙርያ ባሉት የቁጥቋጦ ጥሻዎች እንዴት ታደርጋለህ?
ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ የሚያመለክተው በዮርዳኖስ ወንዝ ዙርያ ባሉት የቁጥቋጦ ጥሻዎች መካከል ሊሮጥ እንደማይችል ነው። ይህ ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በዮርዳኖስ ወንዝ ዙርያ ባሉት የቁጥቋጦ ጥሻዎች መካከል ልትሮጥ በእርግጥ አትችልም።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የቁጥቋጦ ጥሻዎች
ብዙ ቁጥቋጦ ወይም ትንንሽ ዛፎች በአንድነት ተጠጋግተው የበቀሉበት

ተወግዘሃል
አንድን ሰው በአደባባይ በሕዝብ ፊት መወንጀል

Jeremiah 12:7

ቤቴን ትቼአለሁ፣ ርስቴንም ጥያለሁ። የምትወድዳትን በጠላቶችዋ እጆች አሳልፌ ሰጥቻለሁ።
እነዚህ ሶስት ዓረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። አንደኛውና ሁለተኛው ዓረፍተ ነገሮች የሶስተኛውን ሃሳብ ያጠናክራሉ። (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

ቤቴን ትቼአለሁ፣ ርስቴንም ጥያለሁ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ሲናገር “ቤቱ” እና “ርስቱ” እንደሆኑ አድርጎ የገለጸበት ተለዋጭ ዘይቤ ናቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “ለእኔ እንዲሆኑ የመረጥኋቸውን የእኔ የሆኑትን የእስራኤልን ሕዝብ ትቻቸዋለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በጠላቶችዋ እጆች
እዚህ ላይ “እጆች” የሚለው በቁጥጥር ስር ማድረግን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በጠላቶቿ ለመሸነፍ” ወይም “በጠላቶቿ ቁጥጥር ስር እንድትሆን” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሷ ... እርሷ ተነሳችብኝ ... ከእርሷ ጋር ... እርሷን ጠላኋት
እዚህ ላይ ሕዝቡን የአንስታይ ጾታ ተውላጠ ስም በመጠቀም እግዚአብሔር ሕዘቡን እንደ ሴት ይጠራዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእነርሱ ... እነርሱ ... ራሳቸውን አዘጋጁ ... ከእነርሱ ጋር ... እነርሱን ጠላኋቸው” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሷ በራሷ ድምጽ በእኔ ላይ ተነሳችብኝ
ይህ የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንደ አንበሳ አድርጎ መናገሩን ቀጥሏል። ይህ ሕዝቡ በእግዚብሔር ላይ እንደሚያገሱ አድርጎ በመግለጽ እነርሱ በእግዚብሔር ላይ እንደተነሱ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔን ለመቃወም በእኔ ላይ እንደምታገሳ ሆናለች”

የተወደደች ርስቴ ሌሎች አሞሮች ሊበሏት እንደ ከበቧት እንደ ዝንጉርጉር አሞራ አልሆነችምን?
እግዚአብሔር ይህን መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ የተጠቀመው ሕዝቡ በጠላቶቻቸው እንደተከበቡ አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የተወደደች ርስቴ በዙርያዋ ሁሉ እንደተከበበች እንደ ዝንጉርጉር አሞራና ሌሎች የሚታደኑ ወፎች ሆናለች።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የተወደደች ርስቴ
እዚህ ላይ እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ሲናገር የእርሱ “የተወደዱ ርስት” እነደሆኑ ገልጾአቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእኔ ሕዝብ፣ የተወደዱ ሕዝቤ ... አይደሉምን” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሌሎች አሞሮች ሊበሏት እንደ ከበቧት እንደ ዝንጉርጉር አሞራ አልሆነችምን?
እዚህ ላይ እግዚአብሔር በአደጋ ላይ ስላለውና በጠላቶቹ ስለተከበበው ስለ ሕዝቡ ሲናገር በአዳኝ ወፎች እንደተከበበ እንደ ዝንጉርጉር አሞራ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሷ እንደ ዝንጉርጉር አሞራ ሆነች፣ ጠላቶቿም ደግሞ በሁሉም አቅጣጫ እርሷን እንደሚያጠቁ እንደ አዳኝ ወፎች ሆነዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዝንጉርጉር አሞራ
“ያልተለመደ መልክ ያለው እንግዳ ወፍ።” ይህ ብዙ ጊዜ በሌሎች ወፎች የሚታደንና የሚበላ ወፍን ያመለክታል።

አደን የሚድኑ አሞሮች
እንስሳትን የሚያጠቁና የሚበሉ ወፎች

ሂዱ፥ የምድር አራዊትን ሁሉ ሰብስቡ፥ ይበሏትም ዘንድ አምጡአቸው
እዚህ ላይ እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር ለማጠናከር በትዕዛዝ መልክ ይናገራል። ይህ ትዕዛዝ የተሰጠው ለተወሰነ ግለሰብ አይደለም ስለዚህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በሜዳ ያሉ የምድር አራዊት ሁሉ ይምጡና ይብሏት” (እንቶኔ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 12:10

ብዙ እረኞች የወይኑን ቦታዬን አጥፍተውታል
እዚህ ላይ እግዚአብሔር ምድሩና ሕዝቡ በጠላቶች ስለ መጥፋታቸው ሲናገር ሕዝቡ እረኛው እንዳጠፋው እንደ ወይን ቦታ አድርጎ ገልጦአቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሕዝቤና ምድሬ ብዙ እረኞች እንዳጠፉት የወይን ቦታ ናቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ብዙ እረኞች አጥፍተውታል
እዚህ ላይ “እረኞች” የሚለው ቃል በጎቻቸውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ብዙ እረኞች በጎቻቸው እንዲያጠፉት ፈቅደውላቸዋል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉንም ረጋግጠውታል
“በእግራቸው ረጋግጠውታል”

እድል ፈንታዬ የሆነው ምድር
“እኔ የተከልሁት ቦታ” ወይም “የእኔ እርሻ”

ምድሪቱ ባድማ ሆናለች
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ምድሪቱ በሙሉ ባድማ ሆናለች” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በልቡ የሚያስባት
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የሚንከባከባት” ወይም “ትኩረት የሚሰጣት” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 12:12

አጥፊው መጥቷል
“የሚያጠፋ ጦር ሰራዊት መጥቷል”

በምድረ በዳ ባሉት ወና ኮረብቶች
“ምንም ነገር በማይበቅልባቸው በምድረ በዳ ያሉ ስፍራዎች”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የእግዚአብሔር ሰይፍ ይበላልና
እዚህ ላይ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመቅጣት ስለሚጠቀምባቸው ጦር ሰራዊቶች ሲናገር እነርሱ የእርሱ “ሰይፍ” እንደሆኑ አድርጎ ገልጾታል። እዚህ ላይ የእግዚአብሔር “ሰይፍ” ሕዝቡን የሚያጠቃና የሚበላ በጣም ትልቅ እንስሳ እንደሆነ ተደርጎ ተገልጦአል። አማራጭ ትርጉም፦ “”ጦር ሰራዊቶች እናንተን ለመቅጣት የምጠቀምባቸው የእኔ ሰይፍ ናቸው” ወይም “እናንተን እንዲያጠቁ የሚያጠፋ ጦር ሰራተዊት ልኬባችኋለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከምድር ዳር ጀምሮ እስከ ምድር ዳር ድረስ
ይህ የሚያመለክተው የሕዝቡ ርስት የሆነውን መሬት በሙሉ ነው።

እነርሱ ስንዴን ዘሩ ነገር ግን እሾህን አጨዱ
“እነርሱ ስንዴን ዘሩ ነገር ግን እሾህን አጨዱ እንጂ ሌላ ነገር ምንም አልሰበሰቡም”

እነርሱ
“የእኔ ሕዝብ”

የእሾህ ጥሻ
ዙርያው በእሾህ የተሞላ ትልቅ ተክል

ደከሙ
የበለጠ ለመስራት አለመቻል፣ አቅምና ጉልበት ማጣት

ከእግዚአብሔር ጽኑ ቍጣ የተነሳ ምንም ስላላገኛችሁ ታፍራላችሁ
“ስለዚህ እግዚአብሔር እናንተን ስለተቆጣ የሰበሰባችሁት በጣም ትንሽ ስለሆነ ታፍራላችሁ።” እዚህ ላይ “የሰበሰባችሁት” የሚለው ቃል ትልቅ መጠን ያለው ማለት አይደለም፣ ነገር ግን የሚያመለክተው እጅግ በጣም ትንሽ ነገር ነው።

Jeremiah 12:14

ርስታቸውን ለመንጠቅ
“ምድሪቱን ለመውሰድ እየሞከሩ ነው”

ለሕዝቤ ለእስራኤል ያወረስሁትን ርስት
“ለሕዝቤ ለእስራኤል እንደ ርስት የሰጠሁትን”

ተመልከቱ
ይህ ቃል እዚህ ላይ ጥቅም ላይ የዋለው ቀጥሎ የሚናገረውን ንግግር ሰዎች ትኩረት እንዲሰጡት ለማድረግ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “አዳምጡ” ወይም “ለምነግራችሁ ነገር ትኩረት ስጡ”

እነርሱን ከምድራቸው ለመንቀል
እግዚአብሔር ሕዝቡ ምድራቸውን እንዲለቅቁ ስለማስገደዱ ሲናገር እነርሱ ከምድር እንደሚነቅላቸው ተክሎች እንደሆኑ አድርጎ ገልጾአቸዋል። ይህንን ሃሳብ በኤርምያስ 1:10 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ የራሳቸውን ምድር እንዲለቅቁ ለማድረግ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳንም ቤት ከመካከላቸው እነቅለዋለሁ
እዚህ ላይ እግዚአብሔር የይሁዳ ሕዝብ የሎሎችን ሕዝቦች ምድር እንዲለቅቁ እንደሚያደርጋቸው ሲናገር ከምድር እንደሚነቅላቸው ተክሎች እንደሆኑ አድርጎ ገልጾአቸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔ የይሁዳን ቤት ምድራቸውን እንዲለቅቁ አደርጋቸዋለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነቅለዋለሁ
x

Jeremiah 12:16

አጠቃላይ መረጃ፦
ስለ ይሁዳ ጎረቤቶች የተነገረ የእግዚአብሔር ቃል

እንዲህ ይሆናል
“እንዲህ ይፈጸማል”

ሕያው እግዚአብሔርን
“እግዚአብሔር በእርግጠኝነት ሕያው እንደሆነ ሁሉ።” ሕዝቡ ይህን መግለጫ የሚጠቀሙት ቀጥለው የሚናገሩት ነገር በእርግጠኝነት እውነት እንደሆነ ለማሳየት ነው። ይህ የማይናወጥ ቃል ኪዳን የማድረግ መንገድ ነው። ከበኣል ስም ይልቅ በእግዚአብሔር ስም መማል እነርሱ ከበኣል ይልቅ እግዚአብሔርን እንደሚያመልኩ ያመለክታል። ይህን ኤርምያስ 4:2 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔ በማይናወጥ መልኩ እምላለሁ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

በሕዝቤ መካከል ይመሠረታሉ
ይህ የሚናገረው ስለ ሕዝቡ ባለጠጋ መሆን ሲሆን የተገነባ ሕንጻ እንደሆኑ ተደርገው ተገልጸዋል። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔ እነርሱን በሕዝቤ መካከል እመሰርታቸዋለሁ” ወይም “እኔ እነርሱን ባለጠጋ አደርጋቸዋለሁ፣ እነርሱም በሕዝቤ መካከል ይኖራሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

መካከል
መኃል

ያንን ሕዝብ ፈጽሜ እነቅለዋለሁ። በእርግጠኝነት ይነቀላል፣ ይጠፋልም
እግዚአብሔር ሕዝቡ ምድራቸውን እንዲለቅቁ ስለማስገደዱና መንግስታቸውን ስለማጥፋቱ ሲናገር ከመሬት ነቅሎ እንደሚያወጣቸው ተክሎች እንደሆኑ አድርጎ ገልጾአቸዋል። እነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው ስለዚህ አንድ ላይ ሊጣመሩ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔ ይህን ሕዝብ በእርግጠኝነት በግዞት እንዲኖር አደርጋለሁ መንግስቱንም አጠፋለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

በእርግጠኝነት ይነቀላል፣ ይጠፋልም
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔ በእርግጠኝነት እነቅለዋለሁ፣ አጠፋውማለሁ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 13

1 እግዚአብሔር እንዲህ ይለኛል፣ "ሂድ፣ ከተልባ እግር የተሠራ የውስጥ ሱሪ ግዛና ወገብህን ታጠቅ፤ ነገር ግን አስቀድመህ በውኃ ውስጥ አትንከረው። **2** ስለዚህ እግዚአብሔር እንዳለው የውስጥ ሱሪን ገዛሁና ወገቤን ታጠቅሁበት። **3** ከዚያም የእግዚአብሔር ቃል ለሁለተኛ ጊዜ ወደ እኔ መጣና እንዲህ አለኝ፣ **4** በወገብህ ያለውን የገዛሃውን መታጠቂያ ወስደህ ተነሥና ወደ ኤፍራጥስ ሂድ። በዚያም በተሰነጠቀ ዓለት ውስጥ ሸሽገው" አለኝ። **5** እግዚአብሔርም እንዳዘዘኝ ሄድሁና በኤፍራጥስ ሸሸግሁት። **6** ከብዙ ቀንም በኋላ፣ እግዚአብሔር፣ "ተነሥተህ ወደ ኤፍራጥስ ሂድ። በዚያም እንድትሸሽገው ያዘዝሁህን የውስጥ ሱሪ ከዚያ ውሰድ" አለኝ። **7** እኔም ወደ ኤፍራጥስ ሄድሁ ቆፈርሁም፣ ከሸሸግሁበትም ስፍራ የውስጥ ሱሪውን ወሰድሁ። ነገር ግን እነሆ! የውስጥ ሱሪው ተበላሽቶ ነበር፣ ለምንም የማይጠቅም ሆኖ ነበር። **8** ከዚያም የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ በድጋሚ መጣና እንዲህ አለኝ፣ **9** "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እንዲሁ የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን ታላቅ እብሪት አጠፋለሁ። **10** ቃሌን ይሰሙ ዘንድ እንቢ የሚሉ፣ በልባቸውም እልከኝነት የሚሄዱ፣ ያመልኩአቸውና ይሰግዱላቸው ዘንድ ሌሎችን አማልክት የሚከተሉ እነዚህ ክፉ ሕዝብ አንዳች እንዳማይረባ እንደሆነው እንደዚ የውስጥ ሱሪ ይሆናሉ። **11** የውስጥ ሱሪው በሰው ወገብ ላይ እንደሚጣበቅ፣ እንዲሁ ሕዝብና ስም ምስጋናና ክብር ይሆኑልኝ ዘንድ የእስራኤልን ቤት ሁሉ የይሁዳንም ቤት ሁሉ ከእኔ ጋር አጣብቄአለሁ ይላል እግዚአብሔር። ነገር ግን አልሰሙኝም። **12** ስለዚህ ይህንን ቃል ለእነርሱ ልትናገር ይገባል፣ 'የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ማድጋ ሁሉ የወይን ጠጅ ይሞላል።' እነርሱም 'ማድጋ ሁሉ የወይን ጠጅ እንዲሞላ በውኑ እኛ አናውቅምን?' ይሉሃል። **13** ስለዚህ እንዲህ በላቸው፣ 'እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ተመልከቱ፣ በዚህች ምድር የሚኖሩትን ሁሉ፣ በዳዊት ዙፋን የሚቀመጡትን ነገሥታት፣ ካህናቱን፣ ነቢያቱንና በኢየሩሳሌምም የተቀመጡትን ሁሉ በስካር እሞላቸዋለሁ።' **14** ሰውንም በሰው ላይ፣ አባቶችንና ልጆችን በአንድ ላይ፣ እቀጠቅጣለሁ፣ ይላል እግዚአብሔር፤ አጠፋቸዋለሁ እንጂ አልራራም፣ አላዝንላቸውም፣ አልምርም።" **15** ስሙ፣ አድምጡም። እግዚአብሔር ተናግሮአልና እብሪተኞች አትሁኑ። **16** ሳትጨልም እግራችሁም በጨለመችው ተራራ ላይ ሳትሰናከል፥ በተስፋ የምትጠባበቁትን ብርሃን ለሞት ጥላና ለድቅድቅ ጨለማ ሳይለውጠው ለአምላካችሁ ለእግዚአብሔር ክብርን ስጡ። **17** ይህን ባትሰሙ፣ ስለ ትዕቢታችሁ ብቻዬን አለቅሳለሁ። የእግዚአብሔርም መንጋ ተማርኮአልና ዓይኔ ታነባለች፣ እንባንም ታፈስሳለች። **18** ለንጉሡና ንግሥቲት ለሆነችው እናት፣ 'የክብራችሁ አክሊል ከራሳችሁ ወርዶአልና ራሳችሁን አዋርዳችሁ ተቀመጡ' በል። **19** የደቡብ ከተሞች ተዘግተዋል፣ የሚከፍታቸውም የለም። ይሁዳ ሁሉ ተማርኮአል፣ ፈጽሞ ተማርኮአል። **20** ዓይናችሁን አንሥታችሁ እነዚህን ከሰሜን የሚመጡትን ተመልከቱ፤ ለአንቺ የሰጠው መንጋ፣ ለአንቺ የተዋበው መንጋሽ ወዴት አለ? **21** ወዳጆችሽ እንዲሆኑ ያስተማርሻቸውን እግዚአብሔር በራስሽ ላይ አለቆች ባደረጋቸው ጊዜ ምን ትያለሽ? እንደ ወላድ ሴት ምጥ አንቺንም የሚይዝሽ የምጥ ስቃይ ጅማሬ አይደለምን? **22** በልብሽም፣ 'እንዲህ ያለ ነገር ስለ ምን ደረሰብኝ?' ብትዪ፣ የቀሚስሽ ዘርፍ ተገልጦ የተገፈፍሽው ከብዙ ኃጢአትሽ የተነሣ ነው። **23** የኩሽ ሕዝቦች የቆዳ ቀለማቸውን፣ ወይስ ነብር ዝንጕርጕርነቱን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን? ከሆነ፣ በዚያን ጊዜ ክፋትን የለመዳችሁ እናንተ ደግሞ መልካምን ማድረግ ትችላላችሁ። **24** ስለዚህ እንደሚያልፍ እብቅ በምድረ በዳ ነፋስ እበትናቸዋለሁ። **25** ረስተሽኛልና፣ በሐሰትም ታምነሻልና የሰጠኹሽ፣ የደነገግሁልሽም እድል ፈንታ ይህ ነው፣ ይላል እግዚአብሔር። **26** ስለዚህም የቀሚስሽን ዘርፍ እኔ ራሴ በፊትሽ እገልጣለሁ፣ የእፍረት አካልሽም ይታያል። **27** አስጸያፊ ሥራሽን፣ ምንዝርናሽን፣ ማሽካካትሽን፣ የግልሙትናሽንም መዳራት በኮረብቶች ላይ በሜዳም የሆኑትን እነዚህን አስፀያፊ ነገሮች እንዲታዩብሽ አደርጋለሁ! ወዮልሽ፣ ኢየሩሳሌም! አልነፃሽም። ይህስ እስከ መቼ ይቀጥላል?"

Jeremiah 13:1

የተልባ እግር
በጣም ቀጭንና ስስ የሆነ ልብስ

መታጠቂያ
ሰዎች ከልብሳቸው በታች የሚለብሱት፣ የውስጥ ልብስ

ወገብ
ብዙ ጊዜ ቀጭንና ጠባብ የሆነው በዳሌና በደረት መካከል ያለው የሰው አካል መካከለኛው ክፍል

በመጀመርያ በውኃ ውስጥ አትንከረው
“አትጠበው ወይም እርጥበት አታስነካው

ለሁለተኛም ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ
“የእግዚአብሔር ቃል መጣ” የሚለው ፈሊጥ ሲሆን ከእግዚብሔር ዘንድ የመጣውን ልዩ መልእክት ለማስተዋወቅ የሚጠቅም ነው። ይህንን በኤርምያስ 1:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። እንደ አስፈላጊነቱ ማንኛውንም ለውጥ አድርግ። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ለሁለተኛ ጊዜ መልእክት ሰጠኝ። እንዲህም አለኝ፦“ ወይም “እግዚአብሔር ይህን ሁለተኛውን መልእክት ለእኔ ተናገረኝ፦“ (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

የዓለት ንቃቃት
በውስጡ አንድ ነገር ለማስቀመጥ የሚበቃ በአለት መካከል ያለ ክፍት ቦታ ወይም በአለት ላይ ያለ ስንጥቅ

Jeremiah 13:8

የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ
“የእግዚአብሔር ቃል መጣ” የሚለው ፈሊጥ ሲሆን ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣውን ልዩ መልእክት ለማስተዋወቅ የሚጠቅም ነው። ይህንን በኤርምያስ 1:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከትና እንደ አስፈላጊነቱ ማንኛውንም ለውጥ አድርግ። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ለሁለተኛ ጊዜ መልእክት ሰጠኝ። እንዲህም አለኝ፦“ ወይም “እግዚአብሔር ይህን ሁለተኛውን መልእክት ለእኔ ተናገረኝ፦“ (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳና የእስራኤል
እዚህ ላይ የይሁዳና የኢየሩሳሌም የሚለው የሚያመለክተው በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የይሁዳና የኢየሩሳሌም ሕዝብ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ቃሌን ለመስማት
“እኔ የተናገርሁትን ለመታዘዝ”

በልባቸውም እልከኝነት የሚሄዱ
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በጣም እልከኞች የሆኑና ምኞታቸውን ብቻ የሚያደርጉ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደምትጣበቅ ... ከእኔ ጋር አጣብቄአለሁ
“እንደሚለጠፍ ... ከእኔ ጋር ተለጥፈዋል” ወይም “ተጠግተው እንደሚቆዩ ... ከእኔ ጋር ተጠግተው ቆይተዋል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ቤት ሁሉ ... ቤት ሁሉ
“ሕዝብ ሁሉ ... ሕዝብ ሁሉ”

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩት ቤተሰቦች ምትክ ስም ነው። እዚህ ላይ የእስራኤልን መንግስት ያመለክታል። ይህን በኤርምያስ 3:18 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እስራኤል” ወይም “የእስራኤል መንግስት” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳ ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩት ቤተሰቦች ምትክ ስም ነው። እዚህ ላይ የይሁዳንና የቢንያምን ልጆች የሚያካትተውን የይሁዳን መንግስት ያመለክታል። ይህን በኤርምያስ 3:18 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “ይሁዳ” ወይም “የይሁዳ መንግስት” ወይም “የይሁዳ ሕዝብ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 13:12

ማድጋ ሁሉ በወይን ጠጅ ይሞላል ... ማድጋ ሁሉ በወይን ጠጅ ይሞላል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ማንኛውም የወይን አቁማዳ ሁሉ በወይን ጠጅ ይሞላል ... ማንኛውም የወይን አቁማዳ ሁሉ በወይን ጠጅ ይሞላል” ወይም “ማንኛውም የወይን ማሰሮ ሁሉ በወይን ጠጅ ይሞላል ... ማንኛውም የወይን ማሰሮ ሁሉ በወይን ጠጅ ይሞላል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ተመልከቱ
ይህ ቃል እዚህ ላይ ጥቅም ላይ የዋለው ቀጥሎ የሚናገረውን ንግግር ሰዎች ትኩረት እንዲሰጡት ለማድረግ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አዳምጡ” ወይም “ለምነግራችሁ ነገር ትኩረት ስጡ”

በዚህች ምድር የሚኖሩትን ሁሉ በስካር እሞላቸዋለሁ
“የዚህችን ምድር ነዋሪዎች በሙሉ እንዲሰክሩ አደርጋቸዋለሁ”

በዳዊት ዙፋን የሚቀመጡትን ነገሥታት
እዚህ ላይ የይሁዳ ንጉስ የሚቀመጥበት ዙፋን “የዳዊት ዙፋን” በሚለው ተወክሏል። አማራጭ ትርጉም፡- “በይሁዳ ዙፋን የሚቀመጡ ነገስታት” ወይም “የይሁዳ መንግስት ነገስታት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እያንዳንዱን ሰው ከሌላው ሰው ጋር፣ አባቶችንና ልጆችን በአንድ ላይ፣ እቀጠቅጣለሁ
እዚህ ላይ “እያንዳንዱ ሰው” የሚሉት ቃላቶች ወንዶችንና ሴቶችን በሙሉ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከዚያም እኔ ሕዝቡ እርስ በርሳቸው እንዲጣሉ አደርጋቸዋለሁ፣ ወላጆችና ልጆች ሳይቀር እርስ በርሳቸው ይጣላሉ” (የተባዕት ቃላት ሴቶችንም ሲያካትት የሚለውን ይመልከቱ)

አባቶችና ልጆች በአንድ ላይ
ግልጽ የሆነው መረጃ ሊቀርብ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አባቶችንና ልጆችን በአንድ ላይ እቀጠቅጣቸዋለሁ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

አላዝንላቸውም
“ሃዘን ፈጽሞ አይሰማኝም”

ከጥፋት አላድናቸውም
“ቅጣቱን ከእነርሱ አልመልስም።” ይህ በአዎንታዊ መልኩ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እንዲጠፉ እፈቅዳለሁ”

Jeremiah 13:15

ትዕቢት
አንድ ሰው ከእውነታው ውጭ በጣም ጠቃሚ እንደሆነ ስለራሱ ማሰብ

እርሱ ጨለማ ያመጣል
“እርሱ ጨለማ እንዲመጣ ያደርጋል።” እዚህ ላይ ችግርና ተስፋ መቁረጥ “ጨለማ” እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ ጨለማና ተስፋ መቁረጥ ያመጣል” ወይም “ትልቅ መከራ እንዲመጣ ያደርጋል”

እርሱ እግራችሁ እንዲሰናከል ከማድረጉ በፊት
እዚህ ላይ ሰው እየተራመደ እንደሆነ አጽንዖት ለመስጠት “በእግሩ” ተገልጾአል። አማራጭ ትርጉም፡- “እንድትራመድና ስትራመድ ተሰናክለህ እንድትወድቅ ከማድረጉ በፊት” (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ብርሃን ድንግዝግዝ ሲል
ማለዳ ወይም ምሽት በከፊል ጨለማ ሲሆን፣ ጸሐይ መውጣት ስትጀምር ወይም ጸሐይ መግባት ስትጀምር

ብርሃንን ተስፋ ታደርጋላችሁ፣ ነገር ግን እርሱ ስፍራውን ወደ ድቅድቅ ጨለማ ይለውጠዋል፤ ድቅድቅ ደመናም ያደርገዋል
ይህ መልካምነትንና በረከትን እንደ “ብርሃን” መከራና ተስፋ መቁረጥን ደግሞ እንደ “ጨለማ” ይገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “እናንተ ብርሃንና በረከት ተስፋ ታደርጋላችሁ፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ጨለማንና ታላቅ ተስፋ መቁረጥ ይሰጣችኋል፣ በድቅድቅ ደመናም እንደተከበባችሁ ይሰማችኋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔርም መንጋ ተማርኮአልና
x

Jeremiah 13:18

አጠቃላይ መረጃ፡-
እግዚአብሔር ለኤርምያስ መናገሩን ቀጥሏል። እርሱ ለይሁዳ ንጉስና ለንጉሱ እናት ምን እንደሚላቸው ለኤርምያስ እየነገረው ነው።

ንግስት እናት
የንጉስ እናት

የክብራችሁ አክሊል ከራሳችሁ ወርዶአልና
ንጉሱና ንግስቲቱ እናት እንደ ንጉስና እንደ ንግስት እናት ንጉሳዊ ስልጣናቸውን እንዲወክል አክሊል በራሳቸው ላይ ያደርጋሉ። በተጨማሪ ይህ ክስተት ገና አልተፈጸመም ነገር ግን እዚህ ላይ ግን ክስተቱ እንደከናወነ ተደርጎ ተጽፏል። ይህ በወደፊት ጊዜ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከእንግዲህ ወዲህ ንጉስና ንግስት እናት አትሆኑም፤ አክሊሎቻችሁ፣ ኩራታችሁና ክብራችሁ በሙሉ ይወድቃል” (ምሳሌያዊ ድርጊት እና የተፈጸመ ትንቢታዊ ንግግር የሚለውን ይመልከቱ)

በኔጌቭ ያሉ ከተሞች ይዘጋሉ፣ የሚከፍታቸውም አይኖርም
ይህ ከተሞቹ ማንም ሰው ወደ ውስጥ እንዳይገባ ወይም ከከተሞቹ እንዳይወጣ ለመከልከል በጠላቶቻቸው ይከበባሉ ማለት ነው። አማራጭ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ትርጉም:- “በኔጌቭ ያሉ ከተሞች ይዘጋሉ፣ አንድም ሰው ወደ ከተሞቹ መግባት ወይም ከእነርሱ መውጣት አይችልም” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በኔጌቭ ያሉ ከተሞች ይዘጋሉ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ጠላቶቻችሁ በላይ በኔጌቭ ያሉትን ከተሞች ይዘጓቸዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ይሁዳ በሙሉ ይማረካል፣ ሙሉ በሙሉ ምርኮኛ ሆኖ ይወሰዳል
እዚህ ላይ “ይሁዳ” በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላል። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ጠላቶች የይሁዳን ሕዝብ በሙሉ ምርኮኛ አድርገው ወደ ግዞት ይወስዷቸዋል” (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 13:20

አጠቃላይ መረጃ:-
እግዚአብሔር ለኢየሩሳሌም ሕዝብ እየተናገረ ነው።

ዓይናችሁን አንሥታችሁ እነዚህን ከሰሜን የሚመጡትን ተመልከቱ
እዚህ ላይ “ተመልከቱ” የሚለው ፈሊጥ ሲሆን ትኩረት ስጡና ምን እየሆነ እንዳለ አስተውሉ ማለት ነው። በተጨማሪ “ዓይናችሁን አንሥታችሁ” የሚለው ወደ አንድ ነገር መመከልት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “ትኩረት ስጡና እነዚህ ከሰሜን የሚመጡትን አስተውሉ” (ፈሊጥ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህን ከሰሜን የሚመጡትን
ይህ ከሰሜን የሚመጣውን የጠላት ጦር ሰራዊት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም:- “ከሰሜን የሚመጣውን የጠላት ጦር ሰራዊት” ወይም “ከሰሜን የሚዘምተውን የጠላት ጦር ሰራዊት” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ለአንቺ የሰጠሽ መንጋ፥ ለአንቺ የተዋበ መንጋ የነበረው ወዴት አለ?
ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ የተጠየቀው የይሁዳ ሕዝብ በጠላት ጦር ሰራዊት እንደሚማረክ አጽንዐት ለመስጠት ነው። ምንም እንኳ ይህ ክስተት ገና የተከናወነ ባይሆንም ይህ ጥያቄ የተጠየቀው የይሁዳ ሕዝብ እንደተማረኩ ተደርጎ ነው። ይህ ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ሃሳብና እንደ ወደፊት ጊዜ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “እኔ የይሁዳን ሕዝብ እንደ ተወደዱ የበጎች መንጋ እንድትጠብቂያቸው ለአንቺ ሰጥቼሽ ነበር ነገር ግን የጠላት ጦር ሰራዊት ይማርካቸዋል።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች እና የተፈጸመ ትንቢታዊ ንግግር የሚለውን ይመልከቱ)

መንጋ
ይህ የይሁዳ መሪዎች እነርሱን ሊንከባከቧቸውና ሊጠብቋቸው እንደሚገባ አጽንዖት ለመስጠት የይሁዳን ሕዝብ እንደ በጎች “መንጋ” አድርጎ ይገልጻቸዋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወዳጆችሽ እንዲሆኑ ያስተማርሻቸውን እግዚአብሔር በራስሽ ላይ አለቆች ባደረጋቸው ጊዜ ምን ትያለሽ?
ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ ጥቅም ላይ የዋለው የይሁዳ መሪዎች ይመሩት የነበረው ሕዝብ ከሚያሸንፏቸው መንግስታት ጋር ሰላም እንደሆኑ ያስቡ እንደነበር አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “የእናንተ ወዳጆች እንደሆኑ ያሰባችኋቸው ሕዝብ ያሸንፏችኋል ደግሞም በእናንተ ላይ ባለስልጣን ይሆናሉ።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ ነገሮች እንደምትወልድ ሴት አንቺን የሚይዙ የምጥ ጣር ጅማሬዎች አይደሉምን?
እግዚብሔር ይህን መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ የተጠቀመው መማረካቸው የሚያልፉበት መከራ ጅማሬ እንደሆነ ለሕዝቡ ለመንገር ነው። ይህ ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “እነዚህ አንቺ የምትሰቃይባቸው ነገሮች ሴት ልጅ ስትወልድ የሚገጥማት የምጥ ሕመም ጅማሬ ዓይነት ነው።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 13:22

አጠቃላይ መረጃ:-
እግዚአብሔር ለኤርምያስ መናገሩን ቀጥሏል። እርሱ ለይሁዳ ንጉስና ለንጉሱ እናት ምን እንደሚላቸው ለኤርምያስ እየነገረው ነው።

የልብስሽ ዘርፍ ተገልጦአል ተረከዝሽም ተገፍፎአል
ይህ የጠላት ጦር ሰራዊት አባላት የይሁዳን ሴቶች ይደፍሯቸዋል ማለት ነው። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “የጠላት ጦር ሰራዊት አባላት የሴቶቻችሁን ቀሚስ እየገለቡ ይደፍሯቸዋል። (ለስላሴ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በውኑ የኩሽ ሕዝብ የቆዳውን ቀለም ወይስ ነብር ዝንጕርጕርነትን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን?
ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ ጥቅም ላይ የዋለው የአንድ የማይቻልን ነገር ምሳሌ ለመግለጽ ነው። ይህ ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊጻፍ ይችላል። በተጨማሪ “ይችላል” የሚለው ግልጽ ግስ በሁለተኛው ሀረግ ሊቀርብ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “የኩሽ ሕዝብ የቆዳውን ቀለም ሊለውጥ አይችልም፣ ነብር ደግሞ ዝንጕርጕርነትን ይለውጥ ዘንድ አይችልም።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች እና አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህ ከሆነ ምንም እንኳ ክፋትን የለመዳችሁ ብትሆኑም እናንተ ደግሞ በጎ ለማድረግ ትችላላችሁ
ይህ ዓረፍተ ሃሳብ ምጸታዊ ነው ምክንያቱም ስለ ኩሽ ሕዝብና ስለ ነብር የተሰጠው ምሳሌ የማይቻሉ ሁኔታዎች ናቸው። እነዚህ የማይቻሉ ነገሮች የተቻሉ ከሆነ እነርሱም መልካም ማድረግ እንደሚችሉ ያብራራል። አማራጭ ትርጉም:- “እነዚህ ነገሮች የማይቻሉ እንደሆኑ እንደዚሁ ሁልጊዜ ክፋትን ማድረግ ለለመዳችሁ ለእናንተ መልካምን ማድረግ አይቻላችሁም” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

የምድረ በዳ ነፋስ ብትንትኑን እንደሚያወጣው ገለባ እንዲሁ እበታትናችኋለሁ
“በነፋስ እንደሚበታተን ገለባ እንዲሁ እበታትናችኋለሁ።” ገለባ በነፋስ እንደሚበታተን እንደዚሁ እግዚአብሔር ሕዝቡን በዓለም ዙርያ እንደሚበታትናቸው እየተናገረ ነው። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 13:25

እኔ ለአንቺ የሰጠሁሽ፣ ለአንቺ ያወጅኩልሽ ድርሻሽ ይህ ነው
እነዚህ ሁለቱ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን በይሁዳ ሕዝብ ላይ እግዚአብሔር እንዲሆንባቸው የወሰነው እነዚህ ነገሮች እንደሆኑ አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጉም:- “በእናንተ ላይ እንዲሆን ያደረግሁት ነገር ይህ ነው” (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ራሴ የልብስሽን ዘርፍ በፊትሽ እገልጣለሁ እፍረትሽም ይታያል
ይህ እግዚአብሔር እፍረት እንዲሰማቸው ያደርጋቸዋል ማለት ነው። ይህን ሲል በየትኛውም መንገድ ይደፍራቸዋል ማለት አይደለም። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ማንኛውም ሰው እፍረትሽን እንዲያይና እፍረት እንዲሰማሽ ለማድረግ እኔ ራሴ የልብስሽን ዘርፍ በፊትሽ እንደሚገልጥ እሆናለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ማሸካካት
ይህ ወንድ ፈረስ ሴት ፈረስን ሲፈልግ የሚሰማው ድምጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “መመኘት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 14

1 ስለ ድርቅ ወደ ኤርምያስ የመጣው የእግዚአብሔር ቃል ይህ ነው፣ 2 "ይሁዳ ታልቅስ፣ ደጆችዋም ይውደቁ። ስለ ምድራቸው እያለቀሱ ናቸው፤ ለኢየሩሳሌም የሚያለቅሱት ከፍ ብሎአል። 3 ኃያላኖቻቸውም አገልጋዮቻቸውን ለውኃ ሰደዱ። ወደ ጕድጓድ ሲመጡ ውኃ ሊያገኙ አልቻሉም። ሁሉም ሳይሳካላቸው ተመለሱ፤ አፍረውና ተዋርደው ራሳቸውን ተከናነቡ። 4 ከዚህ የተነሣ በምድሪቱ ላይ አልዘነበምና መሬቱ ስንጥቅጥቅ ሆነ። አራሾች አፈሩ ራሳቸውንም ተከናነቡ። 5 ዋላ በምድረ በዳ ወልዳ ሣር ባለመኖሩ ግልገልዋን ተወች። 6 የሜዳ አህዮችም በወና ኮረብታ ላይ ቆመው እንደ ቀበሮ ወደ ነፋስ አለከለኩ። ልምላሜ የለምና ዓይኖቻቸው ፈዘዙ። 7 ኃጢአታችን ቢመሰክርብንም፣ እግዚአብሔር ስለ ስምህ ሥራ። ያልታመንንባቸው ተግባራቶቻችን ጨምረዋልና፣ በአንተ ላይ ኃጢአት ሠርተናል። 8 የእስራኤል ተስፋ ሆይ፣ በጭንቀት ጊዜ የምታድነው አምላክ ወደ ማደሪያ ዘወር እንደሚል መንገደኛ በምድሪቱ ላይ ለምን እንደ እንግዳ ትሆናለህ? 9 ግራ እንደተጋባ ሰው፣ ያድንም ዘንድ እንደማይችል ኃያል ለምን ትሆናለህ? አንተ ግን፣ በመካከላችን ነህ፣ እግዚአብሔር ሆይ እኛም በስምህ ተጠርተናል። አትተወን። 10 እግዚአብሔር ለዚህ ሕዝብ እንዲህ ይላል፣ "መቅበዝበዝን ወድደዋልና፣ እግራቸውንም እንዲህ ከማድረግ አልከለከሉም፤" ስለዚህ እግዚአብሔር በእነርሱ ደስ አላለውም። አሁን በደላቸውን ያስባል ኃጢአታቸውንም ይቀጣል። 11 እግዚአብሔርም፣ "ለዚህ ሕዝብ መልካም እንዲሆንላቸው አትጸልይላቸው። 12 ቢጾሙ ጸሎታቸውን አልሰማም፣ የሚቃጠለውን መሥዋዕትና የእህሉን ቊርባን ባቀረቡ ጊዜ አልቀበላቸውም። በሰይፍና በራብ በቸነፈርም አጠፋቸዋለሁ አለኝ። 13 ከዚያም፣ "ኦ፣ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፣ ወዮ! እነሆ! ነቢያት ለሕዝቡ፣ 'በዚህ ስፍራ በእውነት ሰላምን እሰጣችኋለሁ እንጂ ሰይፍን አታዩም፣ ራብም አያገኛችሁም ይሉአቸዋል" እያሉ ናቸው። 14 እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ፣ "ነቢያቱ በስሜ የውሸት ትንቢት ይናገራሉ። አልላክኋቸውም፣ አላዘዝኋቸውም፣ አልተናገርኳቸውምም። ነገር ግን፣ የውሸት ራእይና ጥቅም የለሽ የሆነ ከንቱ ምዋርትን፣ የልባቸውንም ሽንገላ ይተነብዩላችኋል።" 15 ስለዚህ እግዚአብሔር፣ "በዚህች አገር ሰይፍና ራብ አይሆንም ስለሚሉ፣ ነገር ግን በስሜ ትንቢት ስለሚናገሩ ስላልላክኋቸው ነቢያት እንዲህ ይላል፦ እነዚህ ነብያት በሰይፍና በራብ ይጠፋሉ። 16 ትንቢት የሚናገሩላቸውም ሰዎች ከራብና ከሰይፍ የተነሣ በኢየሩሳሌም አደባባይ ይበተናሉ፤ ክፋታቸውንም አፈስስባቸዋለሁ እነርሱንና ሚስቶቻቸውን፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውንም የሚቀብራቸው አይገኝም። 17 ይህንን ቃል ንገራቸው፦ 'ዐይኖቼ ሌሊትና ቀን ሳያቋርጡ እንባ ያፍስሱ። ድንግሊቱ የሕዝቤ ልጅ በታላቅ ስብራትና እጅግ ክፉ በሆነ ቊስል ተሰብራለችና ። 18 ወደ ሜዳ ብወጣና ባይ! በሰይፍ የሞቱ አሉ። ወደ ከተማም ብገባ፣ ያኔም በራብ የታመሙ አሉ። ነቢዩና ካህኑም ወደማያውቁት አገር ሄደዋል።" 19 በውኑ ይሁዳን ፈጽመህ ጥለኸዋልን? ጽዮንንስ ጠልተሃታልን? ፈውስ በማይኖረን ጊዜ ስለ ምን መታኸን? ሰላምን በተስፋ ተጠባበቅን፣ መልካምም አልተገኘም፤ ፈውስን በተስፋ ተጠባበቅን፣ ተመልከቱ፣ ያለው ግን ድንጋጤ ብቻ ነው። 20 እግዚአብሔር ሆይ፣ በአንተ ላይ ኃጢአትን ሠርተናልና ክፋታችንንና የአባቶቻችንን በደል እናውቃለን። 21 አትጣለን! ስለ ስምህ፣ የክብርህንም ዙፋን አታስነውር። ከእኛ ጋር ያደረግኸውን ቃል ኪዳንህን አስብ እንጂ አታፍርስ። 22 በውኑ በአሕዛብ ጣዖታት መካከል የጸደይን ዝናብ ከሰማይ ያዘንብ ዘንድ የሚችል ይገኛልን? ይህንን የምታደርግ አምላካችን እግዚአብሔር አንተ አይደለህምን? እነዚህን ሁሉ አድርገሃልና ስለዚህ አንተን ተስፋ እናደርጋለን።

Jeremiah 14:1

አጠቃላይ መረጃ፦
እግዚአብሔር በነቢዩ በኤርምያስ በኩል ስለ ሕዝቡ አመንዝራነት ተናግሯል።

ወደ ኤርምያስ የመጣው የእግዚአብሔር ቃል ይህ ነው
ይህ ፈሊጥ ሲሆን ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣውን ልዩ መልእክት ለማስተዋወቅ ጥቅም ላይ ውሏል። ይህን ተመሳሳይ ሀረግ በኤርምያስ 1:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “ይህ እግዚአብሔር ለኤርምያስ የሰጠው መልእክት ነው” ወይም “ይህ እግዚአብሔር ለኤርምያስ የተናገረው መልእክት ነው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ይሁዳ ታልቅስ
እዚህ ላይ “ይሁዳ” በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የይሁዳ ሕዝብ ያልቅስ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ደጆችዋም ይፈራርሱ
እዚህ ላይ “ደጆች” የሚለው ጠላቶችን ወደ ከተማ እንዳይገቡ የሚከለክልና ሰዎች የንግድና የመንግስት ስራ የሚሰሩበት ሲሆን ለይሁዳ ከተሞች ወካይ ነው፣ የይሁዳ ከተሞች ደግሞ በውስጣቸው ለሚኖሩ ሕዝቦች ምትክ ስም ናቸው። አማራጭ ትርጉም፦ “ከተሞቿ ይፈራርሱ” ወይም “በከተሞቿ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ራሳቸውን ለመከላከል የሚችሉ አይሁኑ” (ወካይ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ይፈራርሱ
“ፍርስራሽ ወደመሆን ይለወጡ”

ለኢየሩሳሌም የሚያደርጉት ጩኸት ከፍ ከፍ ብሎአል
“ከፍ ብሏል” የሚለው ሀረግ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ለኢየሩሳሌም በጸሎት በታላቅ ጩኸት እየተጣሩ ነው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ታላላቆቻቸው
“ባለጠጋ ሰዎች”

አፈሩም ተዋረዱም
እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ በአንድ ላይ ባሪያዎቹ ውሃ ለማግኘት ስላልቻሉ እንዳፈሩ አጽንዖት ይሰጣሉ። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ራሳቸውን ይከናነባሉ
በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ሰዎች እፍረታቸውን ለማሳየት ራሳቸውን የሚሸፍኑበት ልብስ ይለብሱ ነበር። (ምሳሌያዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 14:4

አጠቃላይ መረጃ፦
እግዚአብሔር በነቢዩ በኤርምያስ በኩል ስለ ድርቅ ለሕዝቡ መናገሩን ቀጥሏል።

አራሾች አፈሩ ራሳቸውንም ተከናነቡ
በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ሰዎች እፍረታቸውን ለማሳየት ራሳቸውን የሚሸፍኑበት ልብስ ይለብሱ ነበር። (ምሳሌያዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

የሜዳ አጋዘን ግልገሎቿን በሜዳ ተወች፣ ግልገሎቿን ተወቻቸው
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ የሚበላ ነገር ባለመኖሩና ልትሰጣቸው ስላልቻለች የሜዳ አጋዘን ግልገሎቿን በሜዳ እንደ ተወች

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “የሜዳ አጋዘን ግልገሎቿን በሜዳ ተወች” (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

ሳር የለምና
ለአጋዘን የሚሆን የሚበላ ሳር የለም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ለእነርሱ የሚሆን የሚበላ ሳር የለምና” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ቀበሮም በነፋስ ውስጥ አለከለኩ
ይህ እንደ ቀበሮ አለከለኩ በማለት አህዮች ማለክለካቸው ይናገራል ምክንያቱ ደግሞ ጥም ስለበረታባቸው ነው። ቀበሮ ብዙ የሚያለከልኩ በጣም አደገኛ የሆኑ የዱር ውሻዎች ናቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “እንደ ተጠማ ቀበሮ በነፋስ ውስጥ ያለከልካሉ” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አትክልት የለምና ዓይኖቻቸው ፈዘዙ
“የሚበሉት ሳር ስለሌለ ታወሩ”

Jeremiah 14:7

አጠቃላይ መረጃ፡-
እግዚአብሔር በነቢዩ በኤርምያስ በኩል ለሕዝቡ ስለ ድርቅ ተናግሯቸዋል።

ኃጢአታችን በእኛ ላይ ይመሰክርብናል
እዚህ ላይ “ኃጢአቶች” ስለ ክፉ ስራቸው በእነርሱ ላይ የሚመሰክሩ ሰዎች እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ኃጠአታችን ለክፉ ስራችን ማስረጃ ይሰጣሉ” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ ስምህ ብለህ
እዚህ ላይ የእግዚአብሔር “ስም” መልካም ማንነቱን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለ መልካም ማንነትህ ብለህ” ወይም “ማንኛውም ሰው አንተ በጣም ታላቅና ቃል ኪዳንህን የምትጠብቅ እንደሆንህ ማየት ይችል ዘንድ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ተስፋ
ይህ የእግዚአብሔር ሌላ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ የእስራኤል ተስፋ ነህ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ በምድር እንደ እንግዳ ለምን ትሆናለህ ... ግራ እንደተጋባ ሰው ለምን ትሆናለህ
እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ሁለቱም ጥያቄዎች እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ግድ የማይሰኝ እንደሆነና እነርሱን ለመርዳት የማይችል እንደሆነ ይጠይቃሉ። (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ በምድር እንደ እንግዳ ለምን ትሆናለህ፣ እንደ ባዕድ መንገደኛ ... አንድ ሌሊት ብቻ
ይህ ጥያቄ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመርዳት ቸልተኛ የሆነበት ሁኔታ እንዳለ ሲናገር እርሱ በዚያ ስፍራ ስለሚኖሩ ሰዎች ግድ የሌለው በዚያ መንገድ የሚያልፍ እንግዳ መንገደኛ እንደሆነ ተደርጎ ተገልጾአል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚያ የሚያልፍና አንድ ሌሊት ብቻ የሚያድር ሰው
ሁለቱም ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው ስለዚህ በአንድ ላይ ሊጣመሩ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ለአንድ ሌሊት ብቻ የሚቆይ” (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

ግራ እንደተጋባ ሰው፣ ወይም ያድን ዘንድ እንደማይችል ተዋጊ ስለ ምን ትሆናለህ?
ይህ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመርዳት ያልቻለበት ሁኔታ እንዳለ ሲናገር እርሱ ማንንም ሰው ማዳን ያልቻለ ግራ የተጋባ ተዋጊ እንደሆነ ተደርጎ ተገልጾአል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ግራ መጋባት
አንድን ነገር ለመረዳት ወይም በግልጽ ለማሰብ አለመቻል

ስምህ በእኛ ላይ ተጠርቷል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። ይህ ስሙ በእነርሱ ላይ እንደተጠራ በመናገር ሕዝቡ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደሆኑ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስምህን ተሸክመናል” ወይም “እኛ የአንተ ሕዝብ ነን” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ and ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 14:10

አጠቃላይ መረጃ፡-
ኤርምያስ እግዚአብሔር ሕዝቡን ብቻቸውን እንዳይተዋቸው ይጸልያል ደግሞም እግዚአብሔርን ይጠይቃል።

መቅበዝበዝን ይወድዳሉ
“ከእኔ ርቀው ሄደው መቅበዝበዝን ይወድዳሉ።” ይህ የሚናገረው ለእግዚአብሔር ታማኞች ስላልሆኑ እርሱን ስለማይታዘዙት ሕዝብ ነው፣ ሕዝቡን እርሱ ከሚኖርበት ቦታ ርቀው በመሄድ እንደተቅበዘበዙ አድርጎ ገልጦአቸዋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እግራቸውንም አልከለከሉም
እዚህ ላይ ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ርቀው መሄዳቸውን አጽንዖት ለመስጠት “እግሮቻቸው” በሚለው ቃል ተገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ራሳቸውን አልጠበቁም” (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ያስባል
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ያስታውሳል” ወይም “አይረሳም” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ፤ በ ... ስም
“መደገፍ” ወይም “መርዳት”

ማልቀስ
በሃዘን ምክንያት በታላቅ ጩኸት ማልቀስ

ለእነርሱ ፍጻሜ አበጅላቸዋለሁ
ይህ ለስላሴ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ እንዲሞቱ አደርጋቸዋለሁ” (ለስላሴ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰይፍ
እዚህ ላይ ጦርነት “በሰይፍ” ተወክሏል፣ ሰይፍ በውጊያ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውል የተለመደ መሳሪያ ነበር። አማራጭ ትርጉም፡- “በጦርነት” ወይም “በውጊያ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 14:13

አጠቃላይ መረጃ፡-
እግዚአብሔር ለኤርምያስ ለይሁዳ ሕዝብ እንዳይጸልይላቸው ነገረው።

ሰይፍ አታዩም
እዚህ ላይ “ሰይፍ” ጦርነትን ይወክላል፣ “ማየት” ደግሞ በሁኔታው ውስጥ ማለፍን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በአንድም ጦርነት ውስጥ አታልፉም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እውነተኛ ደህንነት እሰጣችኋለሁ
እዚህ ላይ “ደህንነት” አንድ ሰው ለሌላ ሰው ሊሰጠው የሚችለው እቃ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ በደህንነት እድትኖሩ እፈቅድላችኋለሁ” ወይም “እኔ በሰላም እንድትኖሩ እፈቅድላችኋለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የውሸት ትንቢት ይናገራሉ
“ውሸት” የሚለው ቃል እንደ ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በመዋሸት ይተነብያሉ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በስሜ
ይህ ሀረግ በእግዚአብሔር ኃይልና ስልጣን ወይም እንደ እርሱ ወኪል መናገርን ያመለክታል። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ እነርሱን አልላክኋቸውም
ይህ እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንዲያስተላልፉ መልእክት ሰጥቶ አልላካቸውም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ ለሌሎች ሰዎች ትንቢት እንዲናገሩ አልላክኋቸውም” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከራሳቸው አእምሮ የሚወጣ
እዚህ ላይ “አእምሮ” ሃሳብን የማሰብ ችሎታ ሳይሆን የሆነ ስፍራ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ ራሳቸው ያሰቡትን” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 14:15

አጠቃላይ መረጃ፡-
ኤርምያስ ሐሰተኛ ነቢያቶች ስለሚተነብዩት ነገሮች ለእግዚአብሔር እየተናገረ ነበር።

በስሜ
ይህ ሀረግ በእግዚአብሔር ኃይልና ስልጣን ወይም እንደ እርሱ ወኪል መናገርን ያመለክታል። ይህን በኤርምያስ 14:14 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ምንም ሰይፍ አይኖርም ... ሰይፍ አይኖርም
እዚህ ላይ “ሰይፍ” ጦርነትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ምንም ጦርነት አይኖርም ... ጦርነት አይኖርም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በዚያን ጊዜ ትንቢት የተነገረላቸውም ሕዝብ ከራብና ከሰይፍ የተነሣ በኢየሩሳሌም መንገዶች ላይ ይበተናሉ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። ይህ ማለት የቤተሰብ አባላት በሙሉ ይሞታሉ፣ ሕዝቡም አስከሬኖቻቸውን ከመቅበር ይልቅ በመንገዶቹ ላይ ይጥላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “በዚያን ጊዜ ትንቢት የተነገረላቸው ሕዝብ በራብና በሰይፍ ይሞታሉ፣ ሕዝቡም አስከሬኖቻቸውን በኢየሩሳሌም መንገዶች ላይ ይጥሉአቸዋል” (ገቢር/አድርጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ሚስቶቻቸውን፣ ወንዶች ልጆቻቸውን ወይም ሴቶች ልጆቻቸውን
ይህ የሚያብራራው “እነርሱ” በሚለው ቃል የተመለከቱትን ሰዎች ነው፣ ይህም በራብና በሰይፍ የሞቱትን ሰዎች በሙሉ ማለት ነው።

እኔ ክፋታቸውን በእነርሱ ላይ አፈስስባቸዋለሁ
እዚህ ላይ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደ ክፋታቸው መጠን እንደሚቀጣቸው ሲናገር የሕዝቡ ክፋት ፈሳሽ እንደሆነና እርሱ ይህን ፈሳሽ በእነርሱ ላይ እንደሚያፈስስባቸው አድርጎ ይገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ ሊቀጡ እንደሚገባቸው እኔ እቀጣቸዋለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 14:17

ቀንና ሌሊት
እዚህ ላይ ሁልጊዜ ለማለት የቀኑ ሁለት ተቃራኒ ጊዜያቶች ተሰጥተዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሁልጊዜ፣ ቀንና ሌሊት በሙሉ” (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሕዝቤ ድንግል ሴት ልጅ
እዚህ ላይ እግዚአብሔር የእርሱ ሕዝብ ለእርሱ ብርቅየና የተወደደ እንደሆነ ሲናገር እነርሱ የእርሱ ድንግል ሴት ልጅ እንደሆኑ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እንደ ድንግል ሴት ልጅ የምሳሳላቸው ሕዝቤ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የማይፈወስ ቁስል
ሊፈወስ የማይችል በቆዳ ላይ የሚከሰት መቆረጥ ወይም ስብራት

በሰይፍ የሞቱ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። በተጨማሪ “ሰይፍ” እዚህ ላይ ጦርነትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በሰይፍ የሞቱ ሰዎች” ወይም “በጦርነት የሞቱ ሰዎች” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በረሃብ ምክንያት የመጡ በሽታዎች አሉ
እዚህ ላይ “በሽታዎች” የሚለው በረሃብ ከመሰቃየታቸው የተነሳ እነዚህ በሽታዎች ያሉባቸውን ሰዎች ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከረሃብ የተነሳ የታመሙ ሰዎች አሉ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ይቅበዘበዛሉ
ያለ ዓላማ ወዲህና ወዲያ መንቀሳቀስ

አያውቁም
እነርሱ ምን እንደማያውቁ መግለጹ ሊጠቅም ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ምን እንደሚሰሩ አያውቁም” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 14:19

የፈውስ ጊዜ
ግልጽ የሆነው መረጃ ሊቀርብ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የፈውስ ጊዜን ተስፋ አደረግን” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ሆይ፥ በአንተ ላይ ኃጢአትን ሠርተናልና ክፋታችንንና የአባቶቻችንን በደል እናውቃለን
“እግዚአብሔር ሆይ፣ እኛ የሰራነውን ኃጢአትና የአባቶቻችንን በደል እናውቃለን”

Jeremiah 14:21

አጠቃላይ መረጃ፡-
ኤርምያስ ወደ እግዚአብሔር መጸለዩን ቀጥሏል።

ስለ ስምህ ብለህ
እዚህ ላይ የእግዚአብሔር “ስም” መልካም ማንነቱን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለ መልካም ማንነትህ ብለህ” ወይም “ማንኛውም ሰው አንተ በጣም ታላቅና ቃል ኪዳንህን የምትጠብቅ እንደሆንህ ማየት ይችል ዘንድ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የክብርህ ዙፋን
የእግዚአብሔር “ዙፋን” በጽዮን ማለትም በኢየሩሳሌም ተወክሏል። በተጨማሪ የእርሱ “ዙፋን” እርሱ እንደ ንጉስ የሚገዛበትን ስፍራ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የአንተ የክብር ዙፋን የሚገኝባትን ጽዮንን ታዋርዳታለህን” ወይም “አንተ እንደ ንጉስ ተቀምጠህ የምትገዛባትን ጽዮንን አታዋርዳት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ሰማያት በራሳቸው ዝናብ ማፍሰስ ይችላሉን
“ሰማያት ዝናብ መቼ ማፍሰስ እንዳለባቸው በራሳቸው መወሰን ይችላሉን?”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 15

1 እግዚአብሔርም እንደዚህ አለኝ፣ "ሙሴና ሳሙኤል በፊቴ ቢቆሙም እንኳን፣ ለዚህ ሕዝብ አላደላም። እንዲወጡ ከፊቴ አባርራቸው። 2 እነርሱም፣ 'ወዴት እንሂድ?' ቢሉህ፣ ያኔ አንተ 'እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ለሞት የተወሰኑት ወደ ሞት፣ ለሰይፍም የተወሰኑት ወደ ሰይፍ፣ ለራብም የተወሰኑት ወደ ራብ፣ ለምርኮም የተወሰኑት ወደ ምርኮ' ትላቸዋለህ። 3 አራቱን ዓይነት ጥፋት አዝዝባቸዋለሁ፣ እነርሱም አንዳንዶችን የሚገድል ሰይፍ፣ አንዳንዶችን የሚጎትቱ ውሾችን፣ አንዳንዶችን የሚበሉ የሰማያትን ወፎች፣ የምድርንም አራዊት ናቸው ይላል እግዚአብሔር። 4 የይሁዳም ንጉሥ የሕዝቅያስ ልጅ ምናሴ በኢየሩሳሌም ስላደረገው ሁሉ ለምድር መንግሥታት ሁሉ መጨነቂያ አደርጋቸዋለሁ። 5 ኢየሩሳሌም ሆይ የሚራራልሽ ማን ነው? የሚያዝንልሽስ ማን ነው? ወይስ ስለ ደኅንነትሽ ይጠይቅ ዘንድ ዘወር የሚል ማነ ነው? 6 አንቺ እኔን ጥለሻል፣ ይላል እግዚአብሔር፣ ወደ ኋላሽም ተመልሰሻል። ስለዚህ እጄን በአንቺ ላይ ዘርግቼ እመታሽና አጠፋሻለሁ። ለአንቺ ምሕረት ማድረግ አድክሞኛል። 7 በአገርም ደጆች ውስጥ በመንሽ አበጥራቸዋለሁ። ልጆቻቸውንም እነጥቃለሁ። ከመንገዳቸውም አልተመለሱምና ሕዝቤን አጠፋለሁ። 8 መበለቶቻቸውን ከባሕር አሸዋ ይልቅ አበዛለሁ። በቀትር ጊዜ ላይ በብላቴኖች እናት ላይ አጥፊውን እልካለሁ። ድንጋጤና ሽብር በድንገት እንዲወድቅባቸው አደርጋለሁ። 9 ሰባት የወለደች ትደክማለች። ታለከልካለች። ገና ቀን ሳለ ፀሐይዋ ትገባባታለች። የተረፉትንም በጠላቶቻቸው ፊት ለሰይፍ አሳልፌ እሰጣለሁና ታፍራለች፣ ትዋረድማለች። 10 እናቴ ሆይ፣ ወዮልኝ! በምድሪቱ ሁሉ የክርክርና የጥል ሰው የሆንሁትን እኔን ወልደሽኛልና። አላበደርሁም፣ ከማንም አልተበደርኩም፣ ነገር ግን ሁሉ ይረግመኛል። 11 እግዚአብሔር እንዲህ አለ፦ "በእውነት ለደኅንነትህ አልታደግህምን? በእርግጥ በመከራና በጭንቅ ጊዜ ጠላቶችህ እንዲለምኑህ አደርጋለሁ። 12 ሰው ብረትን ይሰብራልን? በተለይ ከሰሜን የሆነውን ከናስ ጋር የተቀየጠውን ብረት የሚሰብር አለን? 13 ባለጠግነትህንና መዝገብህን ለመበዝበዝ በነፃ እሰጣለሁ። ይህንንም የማደርገው በድንበሮችህ ሁሉ ስለፈጸምከው ኃጢአትህ ሁሉ ነው። 14 ከዚያም፣ ጠላቶችህ ወደማታውቀው ምድር እንዲወስዱህ አደርጋለሁ፣ የምታቃጥላችሁ እሳት ከቍጣዬ ትነድዳለችና። 15 አንተ ራስህ ታውቃለህ፣ እግዚአብሔር ሆይ! አስበኝ እርዳኝም። የሚያሳድዱኝንም ተበቀላቸው። በትእግሥትህ አታርቀኝ። ስለ አንተ ነቀፌታን እንደ ጠገብሁ እወቅ። 16 ቃሎችህ ተገኝተዋል እኔም በልቼያቸዋለሁ። የሠራዊት አምላክ ሆይ፣ በስምህ ተጠርቻለሁና ቃሎችህ ሐሤትና የልብ ደስታ ሆኑልኝ። 17 በሚፈነድቁትና በደስተኞች ዙሪያ አልተቀመጥሁም። በቍጣህ ሞልተኸኛልና በኃይለኛው እጅህ ፊት ለብቻዬ ተቀመጥሁ። 18 ስለ ምን ሕመሜ አዘወተረኝ፣ ቍስሌስ ስለ ምን ፈውስን የማይቀበልና የማይሽር ሆነ? በውኑ እንደ አታላይ ምንጭ፣ እንደደረቅ ውኃ ትሆናለህን? 19 ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "ኤርምያስ ሆይ፣ ንስሃ ብትገባ፣ እንደ ቀድሞው እመልስሃለሁ፣ በፊቴም ቆመህ ታገለግለኛለህ። የተዋረደውንም ከከበረው ብትለይ፣ እንደ አፌ ትሆናለህ። ሕዝቡ ወደ አንተ ይመለሳሉ፣ አንተ ራስህ ግን ወደ እነርሱ አትመለስም። 20 ለዚህም ሕዝብ የማይጣስ የናስ ቅጥር አደርግሃለሁ፣ ይዋጉሃል። ነገር ግን እኔ ላድንህ ከአንተ ጋር ነኝና አያሸንፉህም ይላል እግዚአብሔር። 21 ከክፉ ሰዎችም እጅ እታደግሃለሁ፣ ከጨካኞችም ቡጢ እቤዥሃለሁ።

Jeremiah 15:1

አጠቃላይ መረጃ:
ኤርምያስ ወደ ያህዌ ጸለየ

በእኔ ፊት ቢቆሙ እንኳን፣ ለዚህ ህዝብ አልራራም
ይህ የሚያመለክተው ያህዌ ህዝቡን እንዲያድን እንደሚለምኑ ነው:: "ይህንን ህዝብ እንዳድን በፊቴ ቢቀሙ እንኳን፣ እኔ ለእነርሱ አልራራም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእኔ ይርቁ ዘንድ ከፊቴ አስወጣቸው
ያህዌ ለነገሩ ትኩረት ለመስጠት ህዝቡን ከእርሱ የማራቅን ሀሳብ ደግሞ ይናገራል

እነዚያን የተውኳቸውን
"እንዲርቁ እኔ ያንን የወሰንኩባቸውን"

ወደ ሞት መነዳት/መሄድ አለባቸው
ይህ የተነገረው ሞት ሰዎች ሊሄዱ እንደሚችሉበት ቦታ ተደርጎ ነው:: "መሞት ይገባቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለሰይፍ የተመደቡት ወደ ሰይፍ መሄድ አለባቸው
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚወክለው ጦርነትን ነው:: "ለ ሰይፍ" የተመደቡ ማለት እግዚአብሔር በጦርነት ውስጥ እንዲሞቱ የወሰነባቸው ማለት ነው:: "እኔ በጦርነት እንዲሞቱ የወሰንኩባቸው ለሞት ወደ ጦርነት መሄድ አለባቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለረሃብ የተመደቡት ወደ ረሃብ መሄድ አለባቸው
ይህ ማለት ያህዌ እነዚህ በረሃብ እንዲሞቱ ወስኖባቸዋል፣ እናም እነዚህ ቃላት በረሃብ መሞትን "ረሃብ" ሰዎች የሚሄዱበት ስፍራ አድርጎ ይገልጻል:: "በረሃብ እንዲሞቱ የወሰንኩባቸው፣ ሄደው በረሃብ መሞት አለባቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ምርኮ መነዳት/መሄድ አለባቸው
"ወደ ምርኮኝነት መሄድ አለባቸው/መማረክ አለባቸው"

Jeremiah 15:3

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ አንዳንዶቹን ወደ ሞት፣ አንዳንዶቹን በሰይፍ እንዲሞቱ፣ አንዳንዶቹ በረሃብ እንዲሞቱ፣ ደግሞም አንዳንዶቹ ምርኮኞች እንዲሆኑ ተናገራቸው::

እኔ ለአራት አይነት ወገን አደርጋቸዋለሁ
ይህ ማለት ያህዌ ህዝቡን እንዲያጠፉ አራት ወገኖችን በአንድነት ይልካል:: "እነርሱን ያጠፉ ዘንድ አራት ወገኖችን እልካለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው:: ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ:: "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሰይፍ
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚያመለክተው የጠላትን ወታደሮች ነው። "የጠላት ወታደሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እነርሱን...አደራጋቸዋለሁ
እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የይሁዳ ሰዎችን እንጂ በቀደመው ሀረግ የተዘረዘሩትን አራቱን ወገኖች አይደለም

ምናሴ በኢየሩሳሌም... ከፈጸመው የተነሳ
ምናሴ በኢየሩሳሌም ብዙ ክፉ ነገሮችን ያደረገ በጣም ክፉ ንጉሥ ነበር። "ምናሴ በኢየሩሳሌም... ከፈጸማቸው ክፉ ነገሮች የተነሳ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 15:5

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ የሚያጠፏቸው አራት ወገኖችን እንደሚሰድባቸው ነገራቸው- ሰይፍን፣ ውሾችን፣ ወፎችን እና አራዊቶችን።

ኢየሩሳሌም ሆይ፣ ለአንቺ ማን ይራራልሻል? ማንስ ለአንቺ ያለቅስልሻል?
ያህዌ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ማንም ለኢየሩሳሌም እንደማያለቅስላት ትኩረት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ኢየሩሳሌም ሆይ፣ ማንም ለአንቺ አይራራልሽም። በመጥፋትሽ ማንም አያዝንም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ኢየሩሳሌም ሆይ፣ ለአንቺ
እዚህ ስፍራ "ኢየሩሳሌም" የሚለው ቃል የሚያመለክተው በዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ነው። "በኢየሩሳሌም የምትኖሩ እናንተ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አንቺ እኔን ትተሸኛል... ከእኔ ርቀሽ ሄደሻል
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው፣ በእርግጥም ህዝቡ ያህዌን ቸል ማለቱን ትኩረት ይሰጣሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእኔ ርቀዋል
"እኔን ትተዋል" ወይም "ከእኔ ርቀው ሄደዋል"

በእጄ እመታችኋለሁ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚወክለው ሀይልን ነው። "እናንተን ለመምታት ሀይሌን እጠቀማለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

መንሽ
ረጅም እጀታ እና የብረት ጣቶች ያለው በአየር ላይ ወደ ላይ በማንሳት እና በመጣል ጥራጥሬን ለመለየት የሚያገለግል የገበሬ መሳሪያ

ሀዘንተኛ አደርጋቸዋለሁ
"ልጆቻቸው እንዲሞቱ አደርጋለሁ" ወይም "ጠላቶቻቸው ልጆቻቸውን እንዲገድሉ አደርጋለሁ"

Jeremiah 15:8

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ማንም ሰው ለእነርሱ ግድ እንደማይለው እና ከክፉ መንገዳቸው እስካልተመለሱ ድረስ ህዝቡን እንደሚያጠፋ ተናገራቸው።

ባሎቻቸው የሞቱባቸው ሴቶች
ባሎቻቸው የሞቱባቸው ሴቶች

ከባህር ዳርቻ አሸዋ ይበልጥ
"በባህር ዳርቻ ከሚገኝ አሸዋ ይበልጥ።" ይህ ንጽጽር የማይቆጠር የሚለውን አጋኖ መግለጫ ነው። "ልትቆጥሩት ከምትችሉት በላይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

በእኩለ ቀን አጥፊውን በወጣት ወንዶች እናቶች ላይ እልካለሁ
ይህ ማለት እናቶቻቸው ታላቅ ሀዘን ያዝኑ ዘንድ፣ ያህዌ ወጣት ወንዶችን የሚገድሉ የጠላት ወታደሮችን ይልካል ማለት ነው። "በእኩለ ቀን ወጣት ወንዶችን ለማጥፋት እና እናቶቻቸው እንዲያለቅሱ ለማድረግ እኔ የጠላት ሰራዊት እልካለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ) በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በእነርሱ ላይ ይወድቃል
ይህ ፈሊጥ ነው። "በእነርሱ ላይ ይደርሳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሷ ታፍራለች ደግሞም አንገቷን ትደፋለች
"እፍራት" እና "አንገት መድፋት" የሚሉት ቃላት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው የሀፍረቱን ደረጃ/ጥልቀት ትኩረት ይሰጣሉ። "እርሷ ፍጹም ታፍራለች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ይጠፋሉ
ይፍ ፈሊጥ ነው። "ጥፋታቸው መጥኖ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ገና ቀን ሳለ ፀሐይዋ ትጠልቃለች
ይህ የሚናገረው ልጆቿ ስለሞቱባት ሀዘንተኛ ስለምትሆን ሴት ነው፤ ይህም የእርሷ ህይወት ፀሐይ ቀድማ እንደጠለቀች እና ሰዓቱ ሳይደርስ እንደ ጨለመ ሆኖ ተገልጽዋል። እዚህ ስፍራ ጨለማ ሀዘንን ይወክላል። "ከሀዘንዋ የተነሳ፣ ፀሐይ እንደጠለቀች እና ቀኗ እንደጨለመ ያህል ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የተረፉትን በጠላቶቻቸው ፊት ለሰይፍ አሳልፌ እሰጣለሁ
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚወክለው የጠላትን ወታደሮች ነው። ይህ ማለት ያህዌ የጠላት ወታደሮች የቀሩትን ልጆችዋን ሁሉ እንዲገድሉ ይፈቅዳል ማለት ነው። "የጠላት ወታደሮች ከልጆችዋ በህይወት የተረፉትን እንዲገድሉ እኔ እፈቅዳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Jeremiah 15:10

አጠቃላይ መረጃ:
በእነዚህ ቁጥሮች ኤርምያስ ስለ መከራው ወደ ያህዌ ይጮሃል/ይናገራል ያህዌም ይመልስለታል።

አወይ ለእኔ፣ ምነው እናቴ
ኤርምያስ እንዴት እንዳዘነ ለማጉላት የሚገልጽበት መንገድ ለእናቱ የሚናገር ይመስላል። (አጋኖ የሚለውን ይመልከቱ)

አነጋጋሪ እና የክርክር ሰው
"አነጋጋሪ" እና "አከራካሪ" የሚሉት ቃላት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። በአንድነት ኤርምያስ ምን ያህል እንደሚከራከር ትኩረት ይሰጣሉ። "የሰው ሁሉ መነጋገሪያ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ለማንም አላበደርኩም፣ ወይም ማንም አላበደረኝም
ይህ የሚያመለክተው ለሰዎች ገንዘብ ማበደርን ነው። ብዙውን ጊዜ ገንዘብ ማበደር ሰዎች እርስ በእርሳቸው እንዲጋጩ ያደርጋል። "እኔ ለማንም ገንዘብ አላበደርኩም፣ አሊያም ማንም ለእኔ ገንዘብ አላበደረኝም" ወይም "ከብድር የተነሳ ማንንም አላስቆጣሁም ወይም ገንዘብ ተበድሬ ከዚያ የተነሳ ከማንም ጋር አልተጣላሁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለመልካም አልታደግህምን?
ለዚህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በውስጠ ታዋቂነት የሚሰጠው ምላሽ "አዎን" የሚል ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "በእርግጥ ለመልካም እታደግሃለሁ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ ጠላቶች
ከትንቢቱ ጋር የማይስማሙት እነዚያ የኤርምያስ ጠላቶች ናቸው

በመከራ እና በጭንቀት ጊዜ
እዚህ ስፍራ "መከራ/መቅሰፍት" እና "ጭንቀት/ስቃይ" የሚሉት ቃላት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። በአንድነት ሆነው የስቃዩን መጣን ያጎላሉ። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ብረትን የሚያደቅ አለን? በተለይም ከነሐስ ጋር የተደባለቀን የሰሜን ብረት መስበር የሚችል ሰው አለን?
በእነዚህ ጥያቄዎች ያህዌ፣ የይሁዳ ጠላቶችን ጥንካሬ ከነሐስ ጋር እንደ ተደባለቀ ብረት አድርጎ ይናገራል። ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ማንም ብረትን መስበር አይችልም፣ በተለይም ከነሐስ ጋር እንደ ተደባለቀው የሰሜን ብረት ያለውን ማንም አይሰብረውም።" ወይም "ነገር ግን እንደ ብረት ወይም ነሀስ ጠንካራ ሆኑት ጠላቶቹ ይሁዳን ከሰሜን ያጠቁታል፣ ደግሞም ማንም ሊያስቆማቸው አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 15:13

አጠቃላይ መረጃ:
በእነዚህ ቁጥሮች፣ ያህዌ የእስራኤልን ህዝብ እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራል።

ሀብት እና ንብረት
"ሀብት" እና "ንብረት" የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ የሚያመለክቱትም ሰዎች ሰዎች ዋጋ አላቸው ብለው የሚቆጥሯቸውን ነገሮች ነው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ዝርፊያ
አንድን ከተማ ከወረሩ በኋላ በሃይል የተወሰዱ/የተሰረቁ ነገሮች

የፈጸምካቸው ኃጢአቶች በሙሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የፈጸምካቸው በደሎች በሙሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በድንበሮችሁ ውስጥ ሁሉ
"በመላው አገርህ"

የማታውቀው ምድር
"ለአንተ ባዕድ በሆነ ምድር"

እሳት ይቀጣጠላል፣ በአንተ ላይ ቁጣዬ ይነዳል
እዚህ ስፍራ ያህዌ ቁጣውን እሳት እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። "ቁጣዬ በአንተ ላይ እንደማነደው እሳት ነው" ወይም "በቁጣዬ እመጣብሃለሁ፣ ደግሞም ቁጣዬ እንደሚነድ እሳት ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ማንደድ/ማቀጣጠል
እሳት መለኮስ

Jeremiah 15:15

አጠቃላይ መረጃ:
ኤርምያስ ለያህዌ እንዲህ አለ

አንተ ታጋሽ ነህ፣ ነገር ግን እኔን እንዲወስዱኝ/እንዲገድሉኝ አትፍቀድላቸው
ኤርምያስ ያህዌን የእርሱን ጠላቶች ኃጢአት እንዳይታገስ ይጠይቃል። "ውሰደኝ" የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው የእርሱን ወደ ሞት መሄድ ነው። "እባክህ እነርሱን መታገስህ ደግሞም እነርሱ እኔን እንዲገድሉ ፈቃድህ አይሁን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ እና ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚሉትን ይመልከቱ)

ቃሎችህ ተገኝተዋል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "መልዕክትህን አድምጫለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ በልቼዋለሁ
ኤርምያስ የያህዌን መልዕክት ስለ መስማት እና መረዳት እንደ ተመገበው ምግብ አድርጎ ይናገራል። "መልዕክትህን ተረድቼዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የልቤ ደስታ
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚወክለው የአንድን ሰው ስሜቶች እና የሚሰሙትን ስሜቶች ነው። "ከሁሉም ይልቅ ይበልጥ የምወደው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ የአንተን ስም ተሸክሜያለሁ
"እኔ አንተን እንዳገለገልኩ ሰዎች ያውቃሉ"

Jeremiah 15:17

ከ... ጋር አልተቀመጥኩም:
ይህ ፈሊጥ ነው። "እኔ ከ... ጋር ጊዜ አላጠፋሁም" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከሀይለኛው እጅህ
እዚህ ስፍራ የያህዌ "ሀይለኛ እጆች" የሚለው የሚያመለክተው የእርሱን በኤርምያስ ላይ ቁጥጥር ማድረግ እና ተጽዕኖ ማሳረፍ ነው። "አንተ በሀይል ተጫንከኝ" ወይም "በማደርገው ላይ ተጽዕኖ/ቁጥጥር ያደረግከው አንተ ነህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ስቃዬ ስለምን በዛ፣ ቁስሌስ ለምን የማይድን ሆነ?
ኤርምያስ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ስቃዩን አጉልቶ ለመግለጽ ነው። ስለ ስቃዩ የሚናገረው አካላዊ ቁስል እንደሆነ አድርጎ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መለክ ሊጻፍ ይችላል። "ስቃዬ ቀጥሏል፣ እንደማይድን ቁስል ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ለመፈወስ አልወደደም
ይህ የኤርምያስ ቁስል መፈወስ እንዳልወደደ ሰው ተደርጎ ተገልጽዋል። ይህ አድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የማይፈወስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

አንተ ለእኔ እንደሚያታልል እና እንደሚደርቅ ውሃ ትሆንብኛለህን?
ኤርምያስ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው በያህዌ ላይ መደገፍ እንደማይችል ሆኖ የተሰማውን ስሜት ለማጉላት ነው። ይህንን የተናገረው ያህዌ እንደሚደርቅ ወራጅ እንደሆነበት አጉልቶ ለመናገር ነው። "አንተ ለእኔ ሊታመኑበት እንደማይችለሁት፣ ውሃ ልቀዳ ሄጄ ደርቆ እንዳገኘሁት ወራጅ እንደሆንክብኝ ያህል ተሰምቶኛል።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 15:19

እንደ አፌ ትሆናለህ
ኤርምያስ ከያህዌ አፍ ጋር የተነጻጸረው የእርሱን መልዕክት ስለሚናገር ነው። "ለእኔ ትመሰክራለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ራስህ
እዚህ ስፍራ "አንተ ራስህ" የሚለው ተውላጠ ስም የዋለው መልዕክቱ በተለይ ለኤርምያስ እንደ ተሰጠ ትኩረት ለማድረግ ነው። (ደጋጋሚ ተውላጠ ስሞች)

ለዚህ ህዝብ እንደማይደፈር የነሐስ ግድግዳ
ያህዌ ኤርምያስን ከግድግዳ ጋር የሚያነጻጽርበት ምክንያት ሰዎች እርሱን ማሸነፍ ስለማይችሉ ነው። "እንደ ነሐስ ግርግዳ ጠንካራ አደርግሃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በአንተ ላይ ጦርነት ያደርጋሉ
ይህ የሚገልጸው ሰዎች ከኤርምያስ ጋር እርሱ አንድ ሰራዊት የሆነ ያህል ጦርነት እንደሚያውጁበት ነው። "በአንተ ላይ ይነሳሉ" ወይም "ይቃወሙሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ማዳን እና መታደግ
"ማዳን" እና "መታደግ" የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው እግዚአብሔር የገባውን ቃል ኪዳን ያጎላሉ። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተን ከ...ይታደግሃል... ደግሞም ከ...ይቤዥሃል
እነዚህ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ ደግሞም በአንድነት ሆነው እግዚአብሔር የሚያደርገውን ጥበቃ ለማጉላት ውለዋል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የክፉዎች እጅ...የጨካኝ አምባገነኖች እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል የዋለው ቁጥጥርን ለመግለጽ ነው። "የክፉዎች ጭካኔ/ቁጥጥር... የጨካኝ አምባገነኖች ቁጥጥር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ጨካኝ
ይህ ክፉ ሰዎችን ያመለክታል። "ክፉ ሰዎች" ወይም "ክፉ የሆኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ጨካኝ አምባገነኖች
ለሚገዛቸው ሰዎች አንዳች ወዳጅነት የማያሳይ ፍጹም መታዘዝን ብቻ የሚጠይቅ መሪ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 16

1 ከዚያም የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፣ 2 "በዚህ ስፍራ ሚስት አታግባ፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆችም አይኑርህ። 3 እግዚአብሔር በዚህ ስፍራ ስለ ተወለዱ ወንዶችና ሴቶች ልጆች፣ ስለወለዱአቸውም ስለ እናቶቻቸው፣ በዚህችም ምድር እንዲወለዱ ስላደረጉ አባቶቻቸው እንዲህ ይላል፣ 4 በበሽታ ሞት ይሞታሉ። አይለቀስላቸውም ወይም አይቀበሩም። በመሬትም ላይ እንደ ጕድፍ ይሆናሉ። በሰይፍና በራብ ይጠፋሉ፣ ሬሳቸውም ለሰማይ ወፎችና ለምድር አራዊት መብል ይሆናሉ።' 5 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ 'ልቅሶ ወዳለበት የትኛውም ቤት አትግባ። ታለቅስም፣ ታዝንም ዘንድ አትሂድ። ሰላሜን፣ ቸርነትና ምሕረትን፣ ከዚህ ሕዝብ አስወግጄአለሁና! 6 ታላላቆችና ታናናሾች በዚህች ምድር ይሞታሉ። አይቀበሩም፣ ሰዎችም አያለቅሱላቸውም። ስለ እነርሱም ገላን አይነጩላቸውም ራስንም አይላጩላቸውም። 7 ሰዎችም ስለ ሞቱት ለማጽናናት የእዝን እንጀራን ሊካፈሉ አይገባም፣ ለአባታቸውና ለእናታቸውም ማንም የመጽናናት ጽዋ ሊሰጧቸው አይገባም። 8 ትበላና ትጠጣ ዘንድ ከእነርሱ ጋር ለመቀመጥ ወደ ግብዣ ቤት አትግባ።' 9 የእስራኤል አምላክ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፣ 'ተመልከት፣ በዐይናችሁ ፊት በዘመናችሁም የእልልታን ድምፅና የደስታን ድምፅ፣ የወንድ ሙሽራን ድምፅና የሴት ሙሽራን ድምፅ ከዚህ ስፍራ አስቆማለሁ።' 10 ከዚያም ለዚህ ሕዝብ ይህን ቃል ሁሉ በተናገርህ ጊዜ፣ 'እግዚአብሔር ይህን ሁሉ ታላቅ የሆነ ክፉ ነገር ለምን ተናገረብን? በደላችንስ ምንድር ነው? በአምላካችንስ በእግዚአብሔር ላይ የሠራነው ኃጢአታችን ምንድር ነው? ሲሉህ፣ 11 እንዲህ በላቸው፣ 'አባቶቻችሁ እኔን ስለ ተው ነው፣ ይላል እግዚአብሔር፤ እነርሱም ሌሎችን አማልክት ተከተሉ አመለኩአቸውም ሰገዱላቸውም። እነርሱም ትተውኛል፣ ሕጌንም አልጠበቁም። 12 ነገር ግን፣ እናንተ ራሳችሁ ከአባቶቻችሁ ይልቅ ክፉ አድርጋችኋል፤ ተመልከቱ፣ እያንዳንዱ ሰው በክፉ ልብ እልከኝነት ሄዷል፣ እኔንም የሚሰማ የለም። 13 ስለዚህ ከዚህች ምድር እናንተና አባቶቻችሁ ወዳላወቃችኋት ምድር እጥላችኋለሁ፣ ሞገስን አላደርግላችሁምና በዚያ ሌሎችን አማልክት ቀንና ሌሊት ታመልካላችሁ። 14 ስለዚህ ተመልከቱ! ከእንግዲህ 'የእስራኤልን ልጆች ከግብጽ ምድር ያወጣ ሕያው እግዚአብሔርን!' የማይባልበት ዘመን ይመጣል፣ ይላል እግዚአብሔር። 15 ነገር ግን፣ የእስራኤልን ልጆች ከሰሜን ምድር፣ ካሳደዳቸውም ምድር ሁሉ ያወጣ ሕያው እግዚአብሔርን ይባላል፤ እኔም ለአባቶቻቸው ወደ ሰጠኋት ወደ ምድራቸው እመልሳቸዋለሁ። 16 ተመልከቱ! ብዙ ዓሣ አጥማጆችን እሰድዳለሁ፣ ይላል እግዚአብሔር፤ እነርሱም ሕዝቡን ሊያወጡ ያጠምዱአቸዋል። ከዚህም በኋላ ብዙ አጥማጆችን እሰድዳለሁ፣ እነርሱም ከየተራራውና ከየኮረብታው ሁሉ ከየድንጋዩም ስንጣቂ ውስጥ ያጠምዷቸዋል። 17 ዓይኔ በመንገዳቸው ሁሉ ላይ ነውና፤ ከፊቴም ሊሰወሩ አይችሉም። በደላቸውም ከዓይኔ ሊሰወር አይችልም። 18 በተጠሉ ጣዖቶቻቸው ሬሳዎች ምድሬን አርክሰዋልና፣ ርስቴንም አስጸያፊ በሆኑ ነገሮች ሞልተዋልና፣ አስቀድሜ የበደላቸውንና የኃጢአታቸውን ዕዳ ሁለት እጥፍ እከፍላቸዋለሁ።" 19 እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ ምሽጌ፣ አምባዬ፣ በመከራም ቀን መጠጊያዬ ነህ። አሕዛብ ከምድር ዳርቻ ወደ አንተ ሄደው፣ "በእርግጥ አባቶቻችን ውሸትን ወርሰዋል። ባዶ ናቸው፤ በእነርሱ ዘንድ ትርፍ የለም ይላሉ። 20 በውኑ ሕዝቦች አማልክት ያልሆኑትን ለራሳቸው አማልክትን አድርገው ይሠራሉን? 21 ስለዚህ ተመልከቱ! በዚህ ጊዜ አስታውቃቸዋለሁ፣ እጄንና ኃይሌን አስታውቃቸዋለሁ፤ ከዚህም የተነሣ ስሜ እግዚአብሔር እንደ ሆነ ያውቃሉ።"

Jeremiah 16:1

የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ "...አታድርግ
ይህ ፈሊጥ የዋለው ከያህዌ ዘንድ የመጣ ልዩ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:4 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ መልዕክት ሰጠኝ። እንዲህም አለኝ፣ "...አታድርግ" ወይም "ያህዌ ይህን መልዕክት ተናገረኝ/ያህዌ እንዲህ አለኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ በበሽታ ይሞታሉ
"በሚገድል ክፉ በሽታ ይሞታሉ"

አይለቀስላቸውም ወይም አይቀበሩም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ማንም ሰው አያለቅስላቸውም ወይም ማንም አይቀብራቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በምድር ላይ እንደ ፍግ ይሆናሉ
በምድሪቱ የተወለዱ ወንዶች እና ሴቶች ልጆች በምድር ላይ ከሚገኝ ፍግ ጋር የተነጻጸሩት አስጸያፊ እንደሚሆኑ እና ማንም እንደማይቀብራቸው ትኩረት ለመስጠት ነው። ተመሳሳዩ ሀረግ በኤርምያስ 8:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰይፍ እና በረሃብ መጨረሻቸው ይሆናል
"መጨረሻቸው ይሆናል" የሚለው ሀረግ ይሞታሉ የሚለው ቀለል ባለ መንገድ/በጨዋ አነጋገር የተገለጸበት ነው። "ሰይፍ" የሚለው ቃል የሚገልጸው በሰይፍ የሚዋጋን ሰራዊት ወታደሮች ነው። ሀረጉ በጦርነት ውስጥ መሞትን ይገልጻል። "በጦርነት ውስጥ ወይም በረሃብ ይሞታሉ" (ዩፊምዝም/የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 16:5

የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ "...አታድርግ
ይህ ፈሊጥ የዋለው ከያህዌ ዘንድ የመጣ ልዩ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:4 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ መልዕክት ሰጠኝ። እንዲህም አለኝ፣ "...አታድርግ" ወይም "ያህዌ ይህን መልዕክት ተናገረኝ/ያህዌ እንዲህ አለኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ልቅሶ ባለበት ስፍራ
"ልቅሶ" የሚለው ቃል በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "ሰዎች በሚያለቅሱበት ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰላሜን ከዚህ ህዝብ ወስጃለሁ... ደግሞም የጸናውን ፍቅር እና ምህረት
ያህዌ ለህዝቡ ከእንግዲህ ሰላም፣ የጸና ፍቅር እና ምህረት እንዳሌለው የገለጸው እነዚህ ከእነርሱ እንደተወሰዱ ነገሮች አድርጎ ነው። "ከእንግዲህ ለእነርሱ ሰላም አላደርግላቸውም... ወይም የጸና ፍቅር እና ምህረት አላደርግላቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ታላላቆችም ታናናሾችም ሁሉም...
ይህ የሚያመለክተው ሁሉንም አይነት ሰው ሲሆን፣ የሰዎቹ ደረጃ የተገለጸው በመጠን ነው። "ታላላቆችም ታናናሾችም" ወይም "ከደረጃቸው ባሻገር ብዙ ሰዎች፣..." (ሜሪዝም/ከዳር እስከ ዳር/ከጽንፍ እስከ ጽንፍ)

አይቀበሩም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ማንም አይቀብራቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ማንም... ሰውነቱን የሚቧጥጥላቸው ወይም ፀጉሩን የሚላጭላቸው አይኖርም
ራስን መቧጠጥ/መቁረጥ እና የራስ ፀጉርን መላጨት ከፍተኛ ሀዘንን የመግለጫ ምልክታዊ ድርጊቶች ነበሩ፤ በተለይም በጣም የሚወዱት ሰው ሲሞት ይህ ይደረግ ነበር። (ምልክታዊ/ትዕምርታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 16:7

በደረሰባቸው የሞት ሀዘን ማንም አንዳች ምግብ ለሀዘኑ እነርሱን ለማጽናናት አያካፍላቸው...
ማንም ለአባቱ ወይም ለእናቱ የማጽናኛ ዋንጫ/ጽዋ አይስጥ
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። እግዚአብሔር በመሰረቱ ተመሳሳይ የሆኑትን ነገሮች ሁለቴ የተናገረው ትኩረት ለመስጠት ነው። ምግብ ወይም መይን ጠጅ ዘመድ ወደሞተባቸው ሰዎች መውሰድ የተለመደ ነበር። ያህዌ ከሰዎቹ ማጽናኛዎችን ሁሉ ያስወገደው በኃጢአታቸው ምክንያት ነበር። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ማንም የማጽናኛ ዋንጫ/ጽዋ አይስጣቸው
እዚህ ስፍራ "ዋንጫ/ጽዋ" የሚለው ቃል የሚወክለው ዋንጫው/ሲኒ በውስጡ የያዘውን መጠጥ ነው። "ማንም የመጽናኛ መጠጥ አይስጣቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ድግስ ቤት
"ሰዎች ግብዣ የሚያደርጉበት ቤት"

የጭፍሮች አለቃ ያህዌ... እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት ከእግዚአብሔር ዘንድ መልዕክትን ሲያመጣ ለማስተዋወቅ ይጠቀምባቸዋል። ይህ በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

እነሆ/እዩ
"ተመልከቱ" ወይም "አድምጡ" ወይም "ቀጥሎ ለምናገረው ትኩረት ስጡ"

የእናንተ ዐይኖች እየተመለከቱ
እዚህ ስፍራ "የእናንተ" የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተውም የእስራኤልን ሰዎች ነው። የፈሊጣዊ አነጋገሩ ትርጉም ያህዌ ይህን የሚያደርገው እነርሱ ማየት በሚችሉበት ስፍራ ነው። "በእናንተ ፊት ለፊት" ወይም "እናንተ ማየት በምትችሉበት ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንተ የሚለው ተውላጠ ስም መልኮች እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

በእናንተ ቀናት/ዘመን
የዚህ ፈሊጥ ትርጉም በእነርሱ የህይወት ዘመን ማለት ነው። "በእናንተ የህይወት ዘመን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሀሴት እና የደስታ ድምጽ ፣ የሙሽራውና የሙሽራቱ ድምጽ
ይህ በኤርምያስ 7:34 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

Jeremiah 16:10

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

አመለካችኋቸው ወድቃችሁ ሰገዳችሁላቸው
"ወድቃችሁ ሰገዳችሁ" የሚሉት ቃላት "አመለካችሁ" ከሚለው ጋር በመሰረቱ ተመሳሳይ ነው፤ ደግሞም ሰዎች በአምልኮ ጊዜ ሚኖራቸውን የሰውነት አቋም ይገልጻል። እግዚአብሔር በመሰረቱ ተመሳሳይ የሆነውን ነገር ሁለት ጊዜ የተናገረው ትኩረት ለመስጠት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 16:12

አባቶቻችሁ፣ እንዳደረጉት፣ እያንዳንዱ ሰው
"አባቶቻችሁ። እነዚህን ሰዎች ተመልከቱ እናንተም እያንዳንዱ ሰው... ትመልከታላችሁ/ይደርስባችኋል"

እንደ እልከኛ ልቡ ፈቃድ አደረገ
ያህዌ የአንድን ሰው ድርጊት ያ ሰው በጎዳና እንደሚሄድ አድረጎ ይናገራል። እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚለው ቃል የሚወክለው ሀሳብን ወይም ፍቃድን ነው። ተመሳሳይ የሆነው ሀረግ በኤርምያስ 11:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ማድረግ የሚፈልገውን ክፉ ነገር እንደ እልከኛ ልቡ ፈቃድ አደረገ" (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

እኔን የሚሰማ
"አድርግ የምለውን የሚያደርግ"

ከዚህች ምድር አስወጣችኋለሁ
ያህዌ የሚናገረው ህዝቡን ከምድሪቱ እንደሚወረውራቸው ባለ መንገድ በሀይል ስለማስወጣት ነው። "ይህን ምድር ለቃችሁ እንድትወጡ እና እንድትሄዱ አስገድዳችኋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በቀን እና በሌሊት
የ"ቀን"እና "ሌሊት" የሁለቱም መጠቀስ የሚገልጸው ሁልጊዜ የሚለውን ነው። "ሁሌም" ወይም "ሳያቋርጥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜሪዝም/ከዳር እስከ ዳር/ከጽንፍ እስከ ጽንፍ)

Jeremiah 16:14

እነሆ
እዚህ ስፍራ "እነሆ" የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚመጣው መረጃ ትኩረት እንድንሰጥ ንቁ ያነቃናል።

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ መነገር በሚያበቃበት ጊዜ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች ከእንግዲህ እንዲህ በማይሉበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ህያው ያህዌን/ በህያው ያህዌ ህይወት
"የያህዌ ህያውነት እርግጠኛ የሆነውን ያህል::" ሰዎችን ይህንን አገለለጽ የሚጠቀሙት ቀጥሎ የሚናገሩት ነገር በእርግጥ እውነት መሆኑን ለማሳየት ነው:: ይህ ጠንካራ/የከበረ ቃል ኪዳን የሚገባበት መንገድ ነው:: ይህ በኤርምያስ 4:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ:: "ሕያው እግዚአብሔርን/በክብር እምላለሁ/" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 16:16

ብዙ አሳ አጥማዶችን እልካለሁ... እነርሱም ህዝቡን ያጠምዳሉ
ያህዌ ህዝቡን የሚያጠቃውን እና የሚገድለውን የጠላትን ሰራዊት አሳ እንደሚይዙ አሳ አጥማጆች አድርጎ ይናገራል:: (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው:: ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ:: "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

በመሃላቸው ሆነው እንዲያድኗቸው ብዙ አዳኞችን እልካለሁ
ያህዌ ህዝቡን የሚያጠቃውን እና የሚገድለውን የጠላትን ሰራዊት እንስሳትን እንደሚየድኑ አዳኞች አድርጎ ይናገራል:: (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ዐይኖቼ በመንገዶቻቸው ሁሉ ላይ ነው
እዚህ ስፍራ "ዐይን" የሚለው ቃል የሚወክለው የሚያደርጉትን ሁሉ የሚመለከተውን ያህዌን ነው:: "የሚያደርጉትን ነገር ሁሉ እመለከታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ከእኔ ፊት መሰወር አይችሉም
"እነርሱ" የሚለው ቃል ሰዎቹን ወይም ድርጊታቸውን ሊያመለክት ይችላል:: ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል:: "እነርሱ ከእኔ ሊሰወሩ/ሊደበቁ አይችሉም" ወይም "መንገዳቸውን ከእኔ ሊደብቁ አይችሉም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ክፋታቸው ከዐይኖቼ ፊት ሊሸሸጉ አይችሉም
እዚህ ስፍራ "ዐይኖች" የሚለው የሚወክለው ሁሉን የሚመለከተውን ያህዌን ነው:: ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል:: "ከእኔ ሊደበቁ አይችሉም" ወይም "መንገዳቸውን ከእኔ ሊደብቁ አይችሉም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሬን አርክሰዋል
ያህዌ ህዝቡ ምድሪቱን እንዳረከሱ አድርጎ፣ በፊት ተቀባይነት ማጣቷን ይናገራል:: "የእነርሱ እርክሰት" የሚሉት ቃላት በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል:: "ምድሬን ስላረከሷት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

ለእነርሱ ስሜቶች ርስቴን በአስጸያፊ ጣኦቶቻቸው ስለሞሏት
"መሙላት" የሚለው ፈሊጥ በምድሪቱ ላይ ብዙ ጣኦታትን አደረጉ ማለት ነው:: "ለእነርሱ ስሜቶች" የሚሉት ቃላት በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል:: "የእኔን ርስት በአስጸያፊ ጣኦቶቻቸው በመሙላታቸው ምክንያት" ወይም "አስጸያፊ ጣኦቶቻቸው ርስቴ ባለበት ስፍራ ሁሉ በመደረጋቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

የእኔ ርስት
ያህዌ ምድሪቱ እንደ ቋሚ ሀብቱ አድርጎ የቆጠራት የእርሱ ርስት እንደሆነች አድርጎ ይናገራል:: "የእኔ ርስት የሆነችው ምድር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 16:19

ያህዌ፣ አንተ ጠንካራ ምሽጌ ነህ
እዚህ ስፍራ ኤርምያስ ለያህዌ መናገር ይጀምራል::

ምሽጌ እና መሸሸጊያዬ፣ የደህንነቴ ስፍራ
ኤርምያስ ያህዌ ለእርሱ ጠላቶቹ ሊያጠቁት የማይችሉበት ስፍራ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል:: አንዱን ሃሰብ ሶስት ጊዜ ይደጋግማል:: (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ጥንድ ትርጉም የሚሉትን ይመልከቱ)

ህዝቦች ወደ አንተ ይሄዳሉ
እዚህ ስፍራ "ህዝቦች" የሚለው ቃል የሚወክለው የተለያዩ አገራት ሰዎችን ነው:: "የተለያዩ አገራት ሰዎች ወደ አንተ ይሄዳሉ" ወይም "የአገራት ሰዎች ወደ አንተ ይመጣሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ሄደ እና መጣ የሚሉት ቃላት አገባብ የሚሉትን ይመልከቱ)

የምድር ዳርቻ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን በምድር ላይ ሩቅ የሆነው ስፍራ ማለት ነው:: ሁለቱን ጫፎች በማመሳከር፣ በመሃል የሚገኙትን ስፍራዎች ሁሉ ያመለክታል:: "በምድር ሩቅ የሆነው ስፍራ" ወይም "በምድር በሁሉም ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ፈሊጣዊ አነጋገር እና (ሜሪዝም/ከዳር እስከ ዳር/ከጽንፍ እስከ ጽንፍ የሚሉትን ይመልከቱ))

አባቶቻችን የሚያታልሉትን ሀሰተኞች ወረሱ
እዚህ ስፍራ "ማታለል" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሀሰተኛ ጣዖቶች ነው:: "አባቶቻችን አንዳች የማይጠቅሙ ሀሰተኛ ጣዖቶችን ወረሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ሄደ እና መጣ የሚሉት ቃላት አገባብ የሚሉትን ይመልከቱ)

እነርሱ ባዶናቸው፤ ከእነርሱ አንዳች ጥቅም አይገኝም
እዚህ ስፍራ "የእነርሱ" እና "ከእነርሱ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት አባቶች ያምኑባቸውን ጣዖቶች ነው:: ሁለቱ ሀረጋት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው፤ ሁለተኛው እንዴት "ከንቱ እንደሆኑ ያብራራል" (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰዎች ለራሳቸው አማልክትን ያበጃሉን? ነገር ግን እነርሱ አማልክት አይደሉም
ሰዎች ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠይቁት ሰዎች ለራሳቸው አማልክት ሊያበጁ እንደማይችሉ ትኩረት ለመስጠት ነው:: ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል:: "ሰዎች ለራሳቸው አማልክትን ሊያበጁ አይችሉም:: ያበጇቸው ነገሮች አማልክት አይደሉም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ቃለምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህ ያያሉ
"ስለዚህ፣ በእርግጥ::" እዚህ ስፍራ ያህዌ መናገር ይጀምራል:: "ያያሉ" የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚሆነው ትኩረት ይሰጣል

እነርሱ እንዲያውቁ አደርጋለሁ
እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የአገሩን ሰዎች ነው:: ያህዌ ይህንን ሀረግ የሚደግመው ትኩረት ለመስጠት ነው::

የእኔ እጅ እና የእኔ ሀይል
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሀይልን እና ስልጣንን ነው:: ሁለቱ ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ደግሞም ለያህዌ ታላቅ ሀይል ትኩረት ይሰጣሉ:: "ታላቁ ሀይሌ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው::

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

(ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ጥንድ ትርጉም የሚሉትን ይመልከቱ)

ስሜ ያህዌ እንደሆነ ያውቃሉ
እዚህ ስፍራ " ስም" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የያህዌን ማንነት ነው። "እኔ እውነተኛ አምላክ የሆንኩ ያህዌ እንደሆንኩ ያውቃሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 17

1 "የይሁዳ ኃጢአት የሾለ አልማዝ ባለው የብረት ብዕር ተጽፎአል። በልባቸው ጽላትና በመሠዊያቸው ቀንዶች ላይ ተቀርጾአል። 2 ልጆቻቸውም ከለመለሙ
ዛፎች በታችና በከፍተኞቹ ኮረብቶች ላይ ያሉትን መሠዊያቸውንና አሼራ የምትባለውን ጣዖታቸውን ያስባሉ። 3 በገጠር ባሉት ተራሮች ላይ ያሉትን
መሠዊያዎቻቸውን ያስታውሳሉ። ባለጠግነታችሁንና መዝገባችሁን ሁሉ፣ የኮረብታውን መስገጃዎቻችሁንም በኃጢአታችሁ ምክንያት እንዲበዘበዙ አደርጋለሁ።
4 አናንተም የሰጠኋችሁን ርስት ትለቅቃላችሁ። በማታውቋትም ምድር ለጠላቶቻችሁ ባሪያ አደርጋችኋለሁ፤ ለዘላለም የሚነድደውን እሳት በቍጣዬ
አንድዳችኋልና። 5 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "በሰው የሚታመን፣ ሥጋ ለባሹንም ብርታቱ የሚያደርግ፣ ልቡን ግን ከእግዚአብሔር የሚመልስ ሰው ርጉም
ነው። 6 በአረብ ምድር እንዳለ ትንሽ ቍጥቋጦ ይሆናል፣ የሚመጣውንም መልካም ነገር አያይም። ሰውም በሌለበት ዐለታማ ምድር ውስጥ ደረቅ በሆነ ምድረ
በዳ ይቀመጣል። 7 ነገር ግን በእግዚአብሔር የታመነ፣ የልበ-ሙሉነቱ ምክንያት እግዚአብሔር ነውና ቡሩክ ነው። 8 በውኃ አጠገብ እንደ ተተከለ፣ በወንዝም ዳር
ሥሩን እንደሚዘረጋ ተክል ይሆናልና። ሙቀት ሲመጣ አያይም፣ ቅጠሉ ይለመልማልና። ከዚያም፣ በድርቅ ዓመት ላይ አይሠጋም፣ ማፍራቱንም አያቋርጥም። 9
ልብ ከየትኛውም ነገር ይልቅ ተንኰለኛ ነው። በሽተኛ ነው፤ ማንስ ያስተውለዋል? 10 ለሰው ሁሉ እንደ መንገዱ፣ እንደ ሥራው ፍሬ ልሰጥ ልብን የምመረምር፣
ኵላሊትንም የምፈትን እግዚአብሔር እኔ ነኝ። 11 ያልጣለችውን እንቁላል እንደምታቅፍ ቆቅ፣ እንዲሁ አንድ ሰው ያለፍትህ ባለጠጋ ይሆን ይሆናል። ነገር ግን
በእኩሌታ ዘመኑ ላይ ብልጥግናው ይተወዋል፣ በፍጻሜውም ሰነፍ ይሆናል። 12 የመቅደሳችን ስፍራ ከመጀመሪያም ጀምሮ ክፍ ያለ የክብር ዙፋን ነው። 13
እግዚአብሔር የእስራኤል ተስፋ ነው። አንተን የሚተዉህ ሁሉ ያፍራሉ። ከአንተም የሚለዩ የሕይወትን ውኃ ምንጭ እግዚአብሔርን ትተዋልና በምድር ላይ
ይቆረጣሉ። 14 እግዚአብሔር ሆይ፣ ፈውሰኝ እኔም እፈወሳለሁ! አድነኝ እኔም እድናለሁ። አንተ የምስጋናዬ ዝማሬ ነህና። 15 ተመልከቱ፣ 'የእግዚአብሔር ቃል
ወዴት ነው? ይምጣ!' ይሉኛል። 16 እኔም አንተን ተከትዬ እረኛ ከመሆን አልሮጥሁም። የመከራንም ቀን አልታገሥሁም። ከከንፈሬ የመጣውን አንተ ታውቃለህ።
በህልውናህ ፊት ተነግረዋል። 17 መሸበሪያ አትሁንብኝ። በመከራ ቀን አንተ መጠጊያዬ ነህ። 18 አሳዳጆቼ ይፈሩ፣ እኔ ግን አልፈር። እነርሱ ይደንግጡ፣ እኔ ግን
አልደንግጥ። የጥፋትን ቀን አምጣባቸው፣ በሁለት እጥፍ ጥፋት አጥፋቸው። 19 እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ፦ "ሂድና የይሁዳም ነገሥታት በሚገቡበትና
በሚወጡበት የሕዝቡ በር፣ ከዚያም በኢየሩሳሌምም በሮች ሁሉ ቁም። 20 እንዲህም በላቸው፣ 'በእነዚህ በሮች የምትገቡ እናንተ የይሁዳ ነገሥታት፣ የይሁዳም
ሕዝብ ሁሉ፣ የኢየሩሳሌምም ነዋሪዎች ሁሉ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ። 21 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "ለራሳችሁ ሕይወት ተጠንቀቁ፥ በኢየሩሳሌምም
በሮች እንድታገቡ በሰንበት ቀን ሸክምን አትሸከሙ። 22 በሰንበት ቀን ከቤቶቻችሁ ሸክምን አታውጡ። የትኛውንም ሥራ ሁሉ አትሥሩበት፣ ነገር ግን
አባቶቻችሁንም እንዳዘዝሁት የሰንበትን ቀን ቀድሱ።" 23 እነርሱ ግን ትኩረት ሰጥተው አልሰሙም፣ እንዳይሰሙና ተግሣጽን እንዳይቀበሉ አንገታቸውን
አደነደኑ። 24 እኔን ፈጽሞ ብትሰሙ ይሆናል፤ ይላል እግዚአብሔር፤ ደግሞም በሰንበት ቀን በዚህች ከተማ በሮች ሸክም አታምጡ፣ ይልቁንም የሰንበትን ቀን
ለእግዚአብሔር ቀድሱ የትኛውንም ሥራ አትሠሩበት፤ 25 በዳዊት ዙፋን ላይ የሚቀመጡ ነገሥታትና መሳፍንት በሰረገሎችና በፈረሶች ላይ እየተቀመጡ በዚህች
ከተማ በሮች ይገባሉ፣ እነርሱና መሳፍንቶቻቸው የይሁዳም ነዋሪዎች በኢየሩሳሌምም የሚቀመጡ ይመጣሉ። ይህችም ከተማ ለዘላለም የሰው መኖሪያ ሆና
ትቀራለች። 26 የሚቃጠለው መሥዋዕትና ሌላ መሥዋዕትን የእህሉንም ቍርባን ዕጣኑንም የምስጋናውንም መሥዋዕት ይዘው ከይሁዳ ከተሞች ከኢየሩሳሌምም
ዙሪያ ከብንያምም አገር ከቈላውም ከደጋውም ከኔጌብም ወደ እግዚአብሔር ቤት ይመጣሉ። 27 ነገር ግን የሰንበትን ቀን ልትቀድሱ፣ በሰንበትም ቀን ሸክምን
ተሸክማችሁ በኢየሩሳሌም በሮች ልትገቡ የነገርኋችሁን ባትሰሙኝ፣ እሳትን በበሮችዋ ላይ እለኩሳለሁ፣ የኢየሩሳሌምንም ምሽጎች ትበላለች፣ እሳቱም
አይጠፋም።

Jeremiah 17:1

አጠቃላይ መረጃ:
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ ትንቢት የሚጽፈው በግጥም መልክ ነው። የዕብራውያን ስነግጥም የተለያዩ ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤዎችን ይጠቀማል። (ስነግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

የይሁዳ ኃጢአት... በመሰዊያዎቻችሁ ቀንዶች ላይ ተጽፏል
ያህዌ ስለ ይሁዳ ኃጢአት እጅግ ታላቅ መሆን አንድ ሰው ኃጢአታቸውን በቋሚነት እንደቀረጸው እና እነርሱም ሊያቆሙት እንደማይችሉ አድርጎ ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳ ኃጢአት ተጽፏል
እዚህ ስፍራ "ይሁዳ" የሚለው ቃል የሚወክለው የይሁዳን ሰዎች ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የይሁዳ ኃጢአት ተጽፏል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ተቀርጾዋል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ይህ ተቀርጾዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በልባቸው ጽላት ላይ ተቀርጾዋል
የህዝቡ ኃጢአተኝነት ልምዶች የተገለጸው በየራሳቸው ልቦች ላይ እንደተቀረጸ ተደርጎ ነው። "ልቦች" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሰውን ሁለንተና፡ ማለትም ሀሳብ፣ ስሜት እና ድርጊቶች ነው። "በማንነታቸው ላይ ተቀርጾዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በመሰዊያዎቻችሁ ቀንዶች ላይ
"ቀንዶች" የሚለው ቃል የሚያመለክተው በመሰዊያዎች ጠርዝ የሚገኙትን ጉጦች ነው።

Jeremiah 17:3

ሀብታችሁ እና ንብረታችሁ
"ሀብት" እና "ንብረት" የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ የሚያመለክቱትም ዋጋ አላቸው ብለው የሚቆጥሯቸውን ነገሮች ነው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ዝርፊያ
ይህ የሚያመለክተው ሰዎች የሰረቋቸውን ወይም በሀይል የወሰዷቸውን ነገሮች ነው።

ለእናንተ የሰጠኋችሁን ርስት ታጣላችሁ
ያህዌ ምድሪቱን በቋሚነት ለይሁዳ እንደሰጠው ርስት አድርጎ ይናገራል። "ርስት አድርጌ የሰጠኋችሁን ርስት ታጣላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በቁጣዬ ላይ ለዘለዓለም የሚነድ እሳት ለኮሳችሁ
ያህዌ የቁጣውን ታላቅነት እርሱ የተቆጣቸውን እንደሚያቃጥል እሳት አድርጎ ይናገራል። "ቁጣዬ ለዘለዓለም የሚነድ እሳት እስኪመስል ድረስ እጅግ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አስቆጥታችሁኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 17:5

በሰው ልጅ ላይ የሚታመን የተረገመ ነው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እኔ በሰው ልጅ ላይ የሚታመንን ማንኛውንም ሰው ረግመዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ስጋን ሀይሉ ያደርጋል
እዚህ ስፍራ "ስጋ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሰው ልጅን/ሰዎችን ነው። "እርሱ ለጥንካሬው በሰው ላይ ይታመናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ልቡን ከያህዌ ዞር ያደርጋል
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሀሳብን እና ስሜትን ነው። "መሰጠቱን/ጥሞናውን ከያህዌ ያርቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ትንሽ ቁጥቋጦ
ከያህዌ ይልቅ በሰው የሚታመን ሰው ለም ባልሆነ መሬት ላይ ለማደግ እንደሚታገል ተክል ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰው የማይኖርበት፣ ምድረ በዳ እና ጠፍ ምድር
"ሰው የማይኖርበት ጠፍ ምድር" የሚለው "ምድረበዳ" ከሚለው ጋር በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አለው። "ጠፍ ምድረ በዳ ማንም የማይኖርበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 17:7

በውሃ ዳር እንደ ተተከለ ዛፍ ይሆናል
በወንዝ ዳርቻ እንደ ተተከለዛፍ በያህዌ የሚታመን ሰው ሁልጊዜ ይበለጽጋል። ዝናብ በማይኖር ጊዜ አይጎዳም። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እርሱ በውሃ ዳር እንደተተከለ ዛፍ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ድርቅ ሲሆን አይፈራም... በድርቅ አመት አይሰጋም
ያህዌ ከወንዝ ውሃ ስለሚያገኝና በሙቀት እና ድርቅ ስለማይጎዳ ዛፍ፣ ከእነዚህ ነገሮች የተነሳም ዛፉ እንደማይፈራ አድርጎ ይናገራል። "ድርቅ ሲሆን አይጎዳም... በድርቅ አመትም ጉዳት አይደርስበትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 17:9

ልብ ይበልጥ አስመሳይ ነው
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሰዎችን አይምሮ እና ሀሳብ ነው። "የሰው ልብ ይበልጥ አስመሳይ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ማን ሊረዳው ይችላል
x

Jeremiah 17:12

የቤተ መቅደሳችን ስፍራ የክብር ዙፋን ነው
ኤርምያስ ቤተ መቅደሱ "የክብር ዙፋን" እንደሆነ አድርጎ ይገልጻል፤ ምክንያቱም ያህዌ የሚኖረው እና የሚገዛው በዚያ ስለሆነ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የቤተ መቅደሳችን ስፍራ
ይህ የሚያመለክተው በእየሩሳሌም የጽዮንን ተራራ ነው

አንተን የተዉ/ቸል ያሉ ሁሉ
እዚህ ስፍራ "አንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ያህዌን ነው።

በምድሪቱ የሚኖሩ ከአንተ ፊታቸውን የመለሱ ሁሉ በምድር ይጻፋሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ከአንተ ፊታቸውን ያዞሩትን ሁሉ በአፈር ላይ ትጽፋቸዋለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በምድር ይጻፋሉ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ አንድ ሰው ስሙን በአፈር ላይ ቢጽፍ እነዚያ ስሞች በፍጥነት እንደሚጠፉ ሁሉ ያህዌ እንዚህ ሰዎች ሞተው እንደሚረሱ የገለጸበት ዘይቤ ነው። "አንድ ሰው በአፈር ላይ እንደ ጻፋቸው ስሞች ይጠፋሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) "ምድር" የሚለው ቃል ሙታን ለሚገኙበት ስፍራ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ሀረጉ ያህዌ አንድ ሰው ሙታንን በመዝገብ እንደጻፈ አድርጎ የተናገረበት ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "በሙታን ስፍራ ያሉትን ይገናኛሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

ያህዌ፣ የህይወት ውሃ ምንጭ
ኤርምያስ ያህዌ የህይወት መገኛ መሆኑን የሚገልጸው የህይወት ውሃ መንጭ እንደሆነ አድርጎ ነው። "ያህዌ፣ እንደ ህይወት ውሃ ምንጭ የሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የህይወት ውሃ ምንጭ
ኤርምያስ ንጹህ እና ወራጅ ውሃን የህይወት ውሃ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። "ንጹህ ወራጅ የውሃ ምንጭ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ እፈወሳሉ... እኔ እድናለሁ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንተ በእርግጥ ትፈውሰኛለህ... አንተ በእርግጥ ታድነኛለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራተጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ የውዳሴዬ ዝማሬ ነህ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "እኔ የማወድስህ አንተ ነህ" ወይም 2) "በውዳሴ ለመዘመሬ ምክንያቱ አንተ ነህ"

Jeremiah 17:15

ተመልከት
"እይ" ወይም "አድምጥ" ወይም "ልነግርህ ለተዘጋጀሁት ትኩረት ስጥ"

እነርሱ እኔን እንዲህ ይሉኛል
እዚህ ስፍራ "እኔ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኤርምያስን ሲሆን "እነርሱ" የሚለው ጠላቶቹን ያመለክታል።

የያህዌ ቃል ወዴት አለ?
ሰዎቹ ይህንን ጥያቄ ያነሱት/የተጠቀሙበት በኤርምያስ ላይ ለመሳለቅ ነው፤ ምክንያቱም የተናገራቸው ነገሮች ገና አልተፈጸሙም ነበር። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክም ሊተረጎም ይችላል። "ያህዌ የነገረህ ነገሮች መች ተፈጸሙ" ወይም "ያህዌ ይሆናሉ ብሎ የነገረህ ነገሮች አልተፈጸሙም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ይህ ይምጣ
"ያህዌ የተናገረው ይሁን"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አንተን በመከተል እረኛ ከመሆን አልሸሸም
ኤርምያስ ህዝቡን መምራትን እና መሸከምን የሚገልጸው ራሱን በጎችን እንደሚሸከም እረኛ አድርጎ ነው። ያንን ስራ መተውን የሚገልጸው ከስራው እንደመሸሸ አድርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ አልመኘውም
"እኔ አልፈልገውም"

ከከንፈሮቼ የወጡ ትዕዛዛት/ቃላት
እዚህ ስፍራ "ከንፈሮች" የሚለው ቃል የሚወክለው ተናገሪውን ኤርምያስን ነው። "ትዕዛዝ/ቃል" የሚለው በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "የተናገርኩት አዋጅ" ወይም "እኔ ያወጅኳቸው/የተናገርኳቸው ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

እነርሱ ተደርገዋል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እኔ አደረግኳቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 17:17

አንተ የእኔ መሸሸጊያ ነህ
ኤርምያስ ያህዌን ጠላቶቹ እርሱን ሊያጠቁት የማይችሉበት ስፍራ አድርጎ ይገልጸዋል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በመከራ ቀን
"በመከራ ጊዜያት"

አሳዳጆቼ ይፈሩ፣ እኔ እንዳፍር ግን አታድርግ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በአሳዳጆቼ ላይ እፍረት አምጣባቸው፣ በእኔ ላይ ግን ሀፍረት አታድርስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ይጨነቁ፣ እኔን ግን እንድጨነቅ አታድርግ
ይህ ሀረግ በመሰረቱ ከቀደመው ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው፤ ደግሞም በኤርምያስ ጸሎት ላይ ትኩረት ይጨምራል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እጅግ አስፈራቸው፣ እኔን ግን እንድፈራ አታድርገኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

በእጥፍ መጠን ጥፋት ሰባብራቸው
ኤርምያስ ያህዌ ጠላቶቹን እንደ ዕቃ እንዲሰባብራቸው ይናገራል። "እጥፍ መጠን" የሚለው ፈሊጥ ሁለቴ ያህል ማድረግ የሚል ትርጉም አለው። "በሙሉ ጥፋት ሰባብራቸው" ወይም "ሁለቴ ያህል አጥፋቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ፈሊጥ የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 17:19

ከዚያ በእየሩሳሌም ሌሎች በሮች ሁሉ
ግሱ ከቀደመው ሀረግ ለገኝ ይችላል። "ከዚያ ወደ ሌሎች የእየሩሳሌም በሮች ሄደህ ቁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኢሊፕሲስ/የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 17:21

ለህይወታችሁ ስትሉ
"ህይወታችሁን ለመጠበቅ/ለማዳን"

እነርሱ አያደምጡም ወይም ትኩረት አይሰጡም
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው ሰዎቹ መስማት ያለመፍቀዳቸውን ትኩረት ይሰጣሉ። "መስማት አልፈቀዱም" ወይም "መታዘዝ አልፈቀዱም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

አንገታቸውን አደነደኑ
ኤርምያስ የሰዎቹን ግትር መሆን አንገታቸውን እንደ ገተሩ እና የማይንቀሰዳቀስ እንዳደረጉ አድርጎ ይገልጻል። "ግትር ሆኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 17:24

ይህ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

በዳዊት ዙፋን ላይ የተቀመጡ እነርሱ
እዚህ ስፍራ የይሁዳ ንጉሥ የተቀመጠበት ዙፋን የሚለው የቀረበው "የዳዊት ዙፋን" በሚል ነው። ይህ በኤርምያስ 13:13 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "በይሁዳ ዙፋን ላይ የተቀመጡ" ወይም "የይሁዳ አገር ነገሥታት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከተማይቱ ለዘለዓለም የሰዎች መኖሪያ ትሆናለች
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች ለዘለዓለም በዚህች ከተማ ይኖራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 17:26

በበሮችዋ ላይ እሳት አነዳለሁ
"የእየሩሳሌም በሮችን በእሳት አነዳለሁ"

ይህም ሊጠፋ አይችልም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች ሊያጠፉት አይችሉም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 18

1 ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ኤርምያስ የመጣው ቃል እንዲህ አለው፣ **2** "ተነሥተህ ወደ ሸክላ ሠሪው ቤት ውረድ፣ በዚያም ቃሌን አሰማሃለሁና። **3** ስለዚህም ወደ ሸክላ ሠሪው ቤት ወረድሁ፣ ሸክላ ሠሪውም ሥራውን በመንኰራኩር ላይ ይሠራ ነበር። **4** ከጭቃም ይሠራው የነበረ ዕቃ በሸክላ ሠሪው እጅ ተበላሸ፣ ሸክላ ሠሪውም እንደ ወደደ መልሶ ሌላ ዕቃ አድርጎ ሠራው። **5** የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፣ **6** "የእስራኤል ቤት ሆይ፣ ይህ ሸክላ ሠሪ እንደሚሠራ በውኑ እኔ በእናንተ ዘንድ መሥራት አይቻለኝምን? ይላል እግዚአብሔር። ተመልከቱ! ጭቃው በሸክላ ሠሪ እጅ እንዳለ፣ እንዲሁ እናንተ በእኔ እጅ ውስጥ አላችሁ። **7** በአንድ ወቅት፣ አባርር፣ አፈርስ፣ ወይም አጠፋ ዘንድ ስለ ሕዝብ ወይም ስለ መንግሥት አንዳች ነገር እናገር ይሆናል። **8** ነገር ግን ያንን የተናገርኩበት ሕዝብ ከክፋቱ ቢመለስ፣ ያኔ እኔ ላደርግበት ያሰብሁትን ክፉ ነገር እተወዋለሁ። **9** በሌላ ጊዜ፣ ስለ ሕዝብ ወይም ስለ መንግሥት እንደምሠራው ወይም እንደምተክለው እናገራለሁ። **10** ነገር ግን ድምፄን ባለመስማት በፊቴ ክፉን ነገር ቢያደርግ፣ ያኔ እኔ ላደርግለት የተናገርሁትን መልካም ነገር አቆማለሁ። **11** አሁን እንግዲህ፣ ለይሁዳ ሰዎችና በኢየሩሳሌም ለሚኖሩ ተናገርና እንዲህ በላቸው፣ 'እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ተመልከቱ፣ ክፉ ነገር ልፈጥርባችሁ ነው። እቅድንም ላወጣባችሁ ነው። መንገዶቻችሁ እና ልምምዶቻችሁ መልካምን እንዲያመጡላችሁ፣ እያንዳንዱ ሰው ከክፉ መንገዱ ንስሃ ይግባ' **12** እነርሱ ግን፣ 'ይህ ጥቅም የለውም። እንደ እቅዶቻችን እናደርጋለን። እያንዳንዳችን ክፉ የሆነው ልባችን እንደተመኘው እልከኝነትን እናደርጋለን' አሉ። **13** ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ 'እንዲህ ያለውን ነገር ማን ሰምቷል ብላችሁ አሕዛብን ጠይቁ። የእስራኤል ድንግል አስደንጋጭ ነገርን አድርጋለች። **14** በውኑ የሊባኖስ በረዶ በሜዳ ያሉትን ድንጋያማ ኮረብቶች ይተዋልን? ወይስ ከሩቅ የምትመጣው ቀዝቃዛይቱ ፈሳሽ ውኃ ትደርቃለችን? **15** ሕዝቤ ግን ረስተውኛል። ጥቅም ለሌላቸው ጣዖታት ሠውተዋል፤ ከመንገዳቸውም ተሰናክለዋል፤ በአነስተኞቹ መንገዶች ለመሄድ ሲሉ የቀደሙትን መንገዶች ትተዋል። **16** ምድራቸው ለመደንገጪያና ለዘላለም ማፍዋጫ ይሆናል። የሚያልፍባት ሁሉ ይደነቃል፣ ራሱንም ይነቀንቃል። **17** እንደ ምሥራቅ ነፋስ በጠላቶቻቸው ፊት እበትናቸዋለሁ። በጥፋታቸውም ቀን ፊቴን ሳይሆን ጀርባዬን አሳያቸዋለሁ።" **18** እነርሱም፣ "ሕግ ከካህናት፣ ወይም ምክር ከጠቢባን፣ ወይም ቃልም ከነቢያት አይጠፋምና ኑ፣ በኤርምያስ ላይ እናሲር። ኑ፣ በቃላችን እናጥቃው፣ የሚናገረውንም ሁሉ ትኩረት አንስጠው" አሉ። **19** እግዚአብሔር ሆይ፣ አድምጠኝ! የጠላቴንም ድንፋታ ስማ። **20** ጉድጓድ ቈፍረውልኛልና መልካም ስለሆንኩላቸው ከእነርሱ የሚሆን ጥፋት ክፍያዬ ይሆናልን? ለደህንነታቸው ለመናገር፣ ከእነርሱ ቊጣህን ለመመለስ በፊት እንደቆምኩ አስታውስ። **21** ስለዚህ ልጆቻቸውን ለራብ ስጥ፣ ለሰይፍም ኃይል አሳልፈህ ስጣቸው። ሚስቶቻቸውም የወላድ መካንና መበለቶች ይሁኑ፣ ወንዶቻቸውም ይገደሉ፣ ወጣቶቻቸውም በጦርነት ጊዜ በሰይፍ ይመቱ። **22** ሊይዙኝ ጉድጓድ ቆፍረዋልና፣ ለእግሮቼም ድብቅ ወጥመድ አኑረዋልና በላያቸው ጭፍራን በድንገት ባመጣህ ጊዜ፣ ከቤታቸው ጩኸት ይሰማ። **23** አንተ ግን፣ እግዚአብሔር ሆይ፣ ይገድሉኝ ዘንድ በላዬ ያቀዱትን ዕቅድ ሁሉ ታውቃለህ። በደላቸውንና ኃጢአታቸውን ይቅር አትበል። ኃጢአታቸውንም ከአንተ ዘንድ አትደምስስ። ይልቅ፣ በፊትህ ይውደቁ። በቊጣህ ጊዜ እንዲሁ አድርግባቸው።

Jeremiah 18:1

ከያህዌ ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል የመጣ ቃል፣ "ተነስ"
ይህ ፈሊጥ የዋለው ከእግዚአብሔር ልዩ መልዕክት ለማምጣት ነው። ተመሳሳይ የሆነው ሀረግ በኤርምያስ 7፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ለኤርምያስ የሰጠው መልዕክት ይህ ነው። እንዲህ አለ፣ 'ተነስ" ወይም "ያህዌ ለኤርምያስ የተናገረው መልዕክት ይህ ነው፡ 'ተነስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሸክላ ሰሪው ቤት
"የሸክላ ሰሪው የስራ ስፍራ።" ሸክላ ሰሪ ከጭቃ ሸክላ የሚሰራ ሰው ነው።

እነሆ!
"እነሆ" የሚለው ቃል በታሪኩ ውስጥ አዲስ ሰው እንደሚገባ ያነቃናል። የእናንተ ቋንቋ ለዚህ የራሱ የሆነ አገላለጽ ሊኖረው ይችላል።

በሸክላ ሰሪው መንኮራኩር
የሸክላ ሰሪው መንኮራኩር የሚሽከረከር ትንሽ ጠረጴዛ ነው።

የሚሰራው ጭቃ በእጁ ላይ ተበላሸ
"ተበላሸ" የሚለው ቃል የሚሰራው ቁስ ብልሽት አለበት ማለት ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በእጁ ላይ የነበረው የሚያበጀመው የሸክላ እቃ ጥሩ አልነበረም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ያበጀው የነበረው
"ይሰራው የነበረው" ወይም "ቅርጽ ይሰጠው የነበረው"

ስለዚህም ሀሳቡን ቀየረ
የዚህ ፈሊጥ ትርጉም ሌላ ነገር ለመስራት መወሰን ማለት ነው። "ስለዚህ የተለየ ምርጫ አደረገ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ ዐይኖች ለማድረግ መልካም ሆኖ የታየውን
እዚህ ስፍራ "ዐይኖች" የሚለው የሚወክለው ማየትን ሲሆን ማየት ደግሞ የሚገልጸው አስተያየትን/ሃሳብን ነው። "ለማድረግ መልካም ሆኖ እንዳሰበው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 18:5

ከያህዌ ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል የመጣ ቃል፣ "መናገር አለብህ"
ይህ ፈሊጥ የዋለው ከእግዚአብሔር ልዩ መልዕክት ለማምጣት ነው። ተመሳሳይ የሆነው ሀረግ በኤርምያስ 1፡4 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ መልዕክት ሰጠኝ። እንዲህ አለ፣ 'መናገር አለብህ" ወይም "ያህዌ ይህን መልዕክት ለእኔ ተናገረ፡ 'መናገር አለብህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ቤት ሆይ እኔ በእናነተ ላይ እንደዚህ ሸክላ ሰሪ ማድረግ አልችልምን?
በዚህ ጥያቄ ያህዌ በእስራኤል ላይ ደስ የሚያሰኘውን ለማድረግ ስልጣን እንዳለው ትኩረት ይሰጣል። "የእስራኤል ቤት ሆይ፣ ሸክላ ሰሪው በሚሰራው ሸክላ ላይ ስልጣን እንዳለው እኔ በእናንተ ላይ ማድረግ እችላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ቤት
"ቤት" የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። በዚህ ሁኔታ ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን መንግሥት ነው። ይህ በኤርምያስ 3፡18 ላይ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እስራኤል" ወይም "የእስራኤል መንግሥት" ወይም "የእስራኤል ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ
"የምናገረው እውነተኛ እና ጠቃሚ ስለሆነ ትኩረት ሰጥተህ ስማ"

በሸክላ ሰሪው እጅ እንደሚገኝ ጭቃ - እናንተ በእኔ እጅ እንደዚያ ናችሁ
ሸክላ ሰሪው ይሆናል በሚለው መንገድ በእጁ ያለውን ጭቃ ዳግም መስራት እንደሚችል ያህዌ አስራኤልን ዳግም መስራት እንደሚችል ያነጻጽራል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይንደዋል፣ ወይም ያፈርሰዋል
እነዚህ ሁለት አገላለጾች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። በመጀመሪያው ገለጻ፣ ያህዌ አንድን መንግሥት ያ መንግሥት ተክል እንደሆነ ወይም የሚያፈርሰው ህንጻ አድርጎ ይናገራል። (ጥንድ ትርጉም እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ይቅር እላለሁ
"አስቀርለታለሁ" ወይም "አላመጣበትም"

Jeremiah 18:9

እንነባታለሁ ወይም እተክላታለሁ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ያህዌ መንግሥታትን ስለ ማጠናከር የሚናገረው እርሱ እንደሚገነባቸው ህንጻዎች፣ እና እንደሚተክላቸው ተክሎች አድርጎ ነው። (ጥንድ ትርጉም እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

በእኔ ዐይኖች ፊት እርሷ ክፉ ብታደርግ
እዚህ ስፍራ "እርሷ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው አገሪቱን ወይም መንግሥቷን ነው፣ ይህም በዚያች አገር ለሚኖሩ ሰዎች ወይም መንግሥት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ዐይኖች" የሚለው ቃል የሚወክለው ማየትን ሲሆን፣ ማየት ደግሞ ሀሳብን ወይም ፍርድን ይወክላል። "የዚያች አገር ሰዎች እኔ ክፉ ነው የምላቸውን ነገሮች ቢያደርጉ " በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ድምጼን ባትሰሙ
እዚህ ስፍራ "ድምጽ" የሚለው ቃል የሚወክለው የያህዌን ንግግር ነው። እዚህ ስፍራ፣ "አለ መስማት" አለመታዘዛቸውን የሚያሳይ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ለነገርኳችሁ ባትታዘዙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 18:11

እዩ/እነሆ
ይህ አንባቢው ቀጥሎ ለሚሆነው ትኩረት እንዲሰጥ ያደርጋል። "ተመልከቱ" ወይም "አድምጡ" ወይም "ለምነግራችሁ ነገር ትኩረት ስጡ"

በእናንተ ላይ ጥፋት ለማድረስ ተነስቻለሁ። በእናንተ ላይ የጥፋት እቅድ አዘጋጅቻለሁ
ያህዌ ጥፋት ሊያመጣ መነሳቱን የገለጸው ሸክላ ሰሪው ሸክላ እንደሚያበጅ ጥፋት እርሱ የሚያበጀው አካል እንደሆነ አድርጎ ነው። ሁለተኛው ዐረፍተ ነገር የመጀመሪያው የተለያዩ ቃላትን እንደተጠቀመ ሁሉ ተመሳሳይ ሃሳብን ይደግማል። "እኔ በእናንተ ላይ ጥፋት ለማምጣት ተነስቻለሁ/እቅድ አድርጌያለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

እቅድ ማዘጋጀት
"እቅድ ማውጣት"

የእርሱ ክፉ መንገድ
ያህዌ የአንድን ሰው የህይወት ዘይቤ የዚያ ሰው "መንገድ" ወይም የሚሄድበት መንገድ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። "ክፉ የህይወት መንገዱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህ የእናንተ መንገዶች እና ልምምዶቻችሁ መልካም ነገር ያመጡላችኋል
"መንገዶች" እና "ልምምዶች" የሚሉት ቃላት ሁለቱም የአንድን ሰው ድርጊቶች እና አጠቃላይ የህይወት ዘይቤ ያመለክታሉ። "ስለዚህ ድርጊቶቻችሁ መልካም እንዲሆንላችሁ ያደርጋሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን እነርሱ እንዲህ ይላሉ
"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የይሁዳን እና የእየሩሳሌምን ነዋሪዎች ነው።

ይህ ጥቅም የለውም
ለዚህ ፈሊጥ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ህዝቡ ኤርምያስ ለሚነግራቸው ጥንቃቄ አያደርጉም/ደንታ ቢስ ናቸው። "አንተ ለምትናገረው ግድ የለንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) ህዝቡ ኤርምያስ የሚናገራቸውን በማድረግ መልካም እንደሚሆን አያስቡም። "የምተናገረው የሚሆን ነገር አይደለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ ክፉ፣ እና ግትር ልብ የሚፈልገው
"ልብ" የሚለው ቃል የሚወክለው የሰውየውን አይምሮ እና ፈቃድ ነው። "የእርሱ ክፉ፣ እና ግትር አይምሮ/አስተሳሰብ የሚፈልገው" ወይም "በግትርነት ማድረግ የምንፈልገው ማናቸውም አይነት ክፉ ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 18:13

እንደዚያ ያለ ነገር የሰማ ህዝብ ይኖር እንደሆነ ጠይቁ?
እዚህ ስፍራ "ህዝብ" የሚለው ቃል የሚወክለው በአገራት ውስጥ የሚገኙ ሰዎችን ነው። ያህዌ ይህንን ጥያቄ የሚያቀርበው የይሁዳን ህዝብ ለመገሰጽ ነው። "አንዳቸውም እንዲህ ያለ ነገር ሰምተው ያውቁ እንደሆነ እስቲ አገራትን ጠይቁ።" ወይም "በምድር ላይ በየትኛውም ስፍራ ማንም እንዲህ ያለ ነገር ሰምቶ አያውቅም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ድንግሊቱ እስራኤል አሰቃቂ ድርጊት ፈጸመች
አገራትን በሴት መግለጽ የተለመደ ነበር። ያህዌ እስራኤልን ለእርሱ ንጽህት እና ታማኝ እንደሆነች ሲገልጽ ድንግል እንደሆነች አድርጎ ሲሆን የእስራኤልን ለእርሱ ታማኝ አለመሆን የሚገልጸው "አሰቃቂ ድርጊት እንደፈጸመች" በማድረግ ነበር። "እንደ ድንግል የሆነችው እስራኤል፣ አሰቃቂ ድርጊት ፈጸመች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ እና ዘይቤያው አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

የሊባኖስ ተራራ አለታማ ኮረብቶች በረዶ ተለይቷቸው ያውቃልን?
ያህዌ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠይቀው በተራሮቹ ላይ የሚገኘው በረዶ እንደማይቀልጥ ትኩረት ለመስጠት ነው። "በሊባኖስ የሚገኘው በረዶ በጎኖቹ የሚገኙትን አለታማ ኮረብቶች ተለይቶ አያወቅም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በጎኖቹ የሚገኙ አለታማ ኮረብቶች
"የአለታማ ኮረብቶች ተረተር/ጎኖች"

ከተራራ የሚወርዱ፣ ከርቀት የሚመጡ እነዚያ ቀዝቃዛ ምንጮች ሊጠፉ ይችላሉን?
ያህዌ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚያነሳው የተራራ ምንጮች መፍሰሳቸውን በፍጹም እንደማያቋርጡ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። ምንጮቹ የሚደርቁት ከጠፉ እንደሆነ ይናገራል። "ከርቀት የሚመጡት እነዚያ ቀዝቃዛ የተራራ ምንጮች መፍሰሳቸውን በፍጹም አያቆሙም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 18:15

በመንገዶቻቸው እንዲደነቃቀፉ ይሆናሉ
ያህዌ የአንድን ሰው የህይወት ዘይቤ እንደሚሄድበት መንገድ አድርጎ ሲናገር፣ ለእርሱ ታማኝ ያልሆነ ሰው በመንገዱ ላይ እየተደነቃቀፈ እንደሆነ አድርጎ ይገልጻል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ይህ በመንገዳቸው እንዲደነቃቀፉ ያደርጋል" ወይም "ይህ በመንገዳቸው እንዲደነቃቀፉ ያደርጋል" ወይም "ይህ በመንገድ ላይ ሲራመዱ እንደሚደነቃቀፉ ያለ ይሆናል" (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ዝቅ ባለ መንገድ ለመሄድ የጥንቶቹን መንገዶች ተዉ
ያህዌ የአንድን ሰው የህይወት ዘይቤ እንደሚሄድበት መንገድ አድርጎ ይናገራል። እዚህ ስፍራ "የጥንቶቹ መንገዶች" የሚለው የሚወክለው ያህዌ አባቶቻቸው እንዲኖሩበት የነገራቸውን መንገድ ሲሆን "አነስተኛ/ዝቅ ያሉ መንገዶች" የሚለው ደግሞ የሚወክለው ለያህዌ በታማኝነት አለመኖርን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አስፈሪ ሆኑ
"አስፈሪ" የሚለው ቃል በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "ሰዎችን የሚያስፈራ ነገር ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ዘለዓለማዊ የጥላች ድምጽ አካል
"የጥላች ድምጽ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጠንካራ የሆነ ያለ መቀበልን መግለጫ ድምጽ ሲሆን በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "ሰዎች ሁሌም የጥላቻ ድምጽ የሚያሰሙበት ነገር"

በአጠገቧ ሲያልፉ
እዚህ ስፍራ "እርሷ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ምድራቸውን ነው።

በጠላቶቻቸው ፊት እንደ ምስራቅ ነፋስ እበትናቸዋለሁ
ያህዌ ህዝቡን፣ አብዋራን እና ፍርስራሽን እንደሚበትን የምስራቅ ነፋስ ሆኖ በጠላቶቻቸው ፊት እንደሚያሳድዳቸው ይናገራል። "እንደ ምስራቅ ነፋስ ሆኜ በጠላቶቻቸው ፊት እበትናቸዋለሁ" ወይም "የምስራቅ ነፋስ አብዋራን እና ፍርስራሽን እንደሚበትን በጠላቶቻቸው ፊት እበትናቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱን እበትናለሁ
እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው "የእኔ ህዝብ/ህዝቤ" የሚለውን ነው።

ጀርባዬን እንጂ ፊቴን አያዩም
"በእነርሱ ላይ ጀርባዬን አዞራለሁ፣ እንጂ ፊቴን አያዩም።" በአንድ ሰው ላይ ጀርባን ማዞር አለመቀበልን የሚያመለክት ሲሆን ወደ አንድ ሰው ፊትን መመለስ መቀበልን/ሞገስ ማግኘትን የሚያመለክት ተምሳሌታዊ ድርጊት ነው። "እኔ አልቀበላቸውም ለእነርሱ ሞገስ አልሰጥም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 18:18

በኤርምያስ ላይ እናሲር/እንማከር
"ኤርምያስን ለመጉዳት እቅድ እናውጣ"

ህጉ ከካህናቱ በፍጹም አይጠፋም፣ ወይም ምክር ከጠቢባን፣ ወይም ቃል ከነቢያት
"በፍጹም አይጠፋም" የሚሉት ቃላት በእነዚህ በእያንዳንዳቸው ሀረጋት ውስጥ ሊጨመር ይችላል። ይህ በአዎንታዊ ቃላትም ለገለጽ ይችላል። "ህጉ በፍጹም ከነቢያት ሊጠፋ፣ ደግሞም ምክር ከጠቢባን ሰዎች ሊጠታጣ፣ እና ከነቢያት ቃል ሊታጣ አይችልም" ወይም "ካህናቱ ሁሌም ህጉ ይኖራቸዋል፣ ጠቢባኑ ሰዎች ሁሌም ምክር ሊያቀርቡ፣ እና ነቢያቱ ሁሌም ቃል ይናገራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

ቃላት ከነቢያቱ
እዚህ ስፍራ "ቃላት" የሚወክለው ነቢያት የሚናገሩትን ከያህዌ ዘንድ የሆነ መልዕክት ነው። "ከነቢያቱ የያህዌ ቃላት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱን በቃላችን እናጥቃው
ሰዎቹ በኤርምያስ ላይ የሚጎዱ ቃላትን መናገርን እርሱን እንደሚያጠቁበት መሳሪያ አድርገው ይናገራሉ። "እርሱን የሚጎዱ ነገሮችን ተናገሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለእኔ ትኩረት ስጥ/ወደ እኔ አድምጥ
እዚህ ስፍራ ኤርምያስ ለያህዌ መናገር ይጀምራል።

ለእነርሱ መልካም በመሆኔ፣ በእውኑ ከእነርሱ የሚመጣው ጉዳት ለእኔ ሽልማት ነውን?
ኤርምያስ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው መልካም ድርጊቶች ምላሻቸው ክፉ መሆን እንደማይገባው ትኩረት ለመስጠት ነው። "ከእነርሱ የሚደርስብኝ ጉዳት ለእነርሱ መልካም የመሆኔ ምላሽ መሆን የለበትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ለእኔ ጉድጓድ ቆፈሩ
ኤርምያስ ጠላቶቹ እርሱን ለመግደል ማቀዳቸውን እርሱን ለማጥመድ ጉድጓድ እንደቆፈሩ አድርጎ ይናገራል። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ቁጣህን ከእነርሱ አትመልስ
እዚህ ስፍራ "ቁጣ" የሚለው ቃል የሚወክለው ያህዌ በእነርሱ ላይ ሊያደርስ ያቀደውን ቅጣት ነው። ኤርምያስ ያህዌ የእርሱን ጠላቶች አለመቅጣቱን የሚገልጸው ቁጣውን ከእነርሱ እንዳራቀ አድርጎ ነው። "ስለዚህ በቁጣህ አትቀጣቸውም/አትገስጻቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 18:21

ልጆቻቸውን ለረሃብ አሳልፈህ ስጣቸው
"አሳልፈህ ስጣቸው" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር አንድን ሰው በሌላው ሀይል ስር ማድረግ የሚል ትርጉም አለው። ኤርምያስ ስለ "ረሃብ/ችጋር" የሚናገረው በሌላው ሰው ላይ ስልጣን እንዳለው ሰው አድርጎ ነው። "ልጆቻቸው በረሃብ እንዲሞቱ አሳልፈህ ስጣቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ሰይፍ ለያዙ እጆች አሳልፈህ ስጣቸው
እዚህ ስፍራ "እጆች" የሚለው ቃል የሚወክለው ሀይልን ነው። "ሰይፍ የያዙ በእነርሱ ላይ ሀይል እንዲኖራቸው አድርግ" ወይም "በጦር ሜዳ ይሙቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሴቶቻቸው ሀዘንተኞች እና መበለቶች ይሁኑ
"የሴቶቻቸው ባሎች እና ልጆቻቸው ይሙቱ። "ሀዘንተኞች" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ልጆቻቸው የሞቱባቸውን ሴቶች ነው።

ወንዶቻቸው ይገደሉ
ምናልባት ግሡ ከቀደመው ሀረግ ሊገኝ ይችላል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች ወንዶቻቸውን ይገደሏቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ወጣት ወንዶቻቸው በጦርነት በሰይፍ ይገደሉ
ምናልባት ግሡ ከቀደመው ሀረግ ሊገኝ ይችላል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች ወጣት ወንዶቻቸውን በጦር ሜዳ በሰይፍ ይግደሏቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

የጥፋት ጩኸት ይሰማ
"የጥፋት ጩኸት" የሚለው ቃል በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል።ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች የጭንቀት ጩኸትን ይስሙ" ወይም "ሰዎች የሌሎችን የጭንቀት ጩኸት ይስሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔን ለማጥመድ ጉድጓድ ቆፍረዋል፣ ለእግሬም ወጥመድ አበጅተዋል
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ኤርምያስ ጠላቶቹ እርሱን ለመግደል እያቀዱ መሆኑን የገለጸው የሚወድቅበትን ጉድጓድ እንደቆፈሩ እና እርሱን ለማጥመድ ወጥመድ እንዳዘጋጁ አድርጎ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ጉድጓድ ቆፍረዋል
ይህ በኤርምያስ 18:20 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ለእግሬ ወጥመድ አዘጋጅተዋል
እዚህ ስፍራ "እግር" የሚለው ቃል የሚወክለው ኤርምያስን ነው። "ለእኔ ወጥመድ አዘጋግተዋል/አጥምደዋል" ወይም "ውድቀቴን ለማፍጠን ወጥመድ አጥምደዋል" (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ኃጢአታቸውን ከአንተ ዘንድ አትደምስስላቸው
ኤርምያስ ያህዌ የእርሱን ጠላቶች ኃጢአት ይቅር ማለቱን አንድ ሰው የእነርሱን ኃጢአት እንደመዘገበ እና ያህዌ ይንን እንደሚያጠፋው አድርጎ ይገልጸዋል። የዚህ ሀረግ ትርጉም ከቀደመው ሀረግ ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው። "ኃጢአታቸውን ይቅር አትበል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከአንተ ፊት የተጣሉ ይሁኑ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች በፊትህ የተጣሉ ያድርጓቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በቁጣህ ቀን
"ቁጣ" የሚለው ቃል በግስ መልኩ ሊተረጎም ይችላል። "አንተ በእነርሱ ላይ ተቆጥተህ ሳለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 19

1 እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ፣ "ሂድና ከሸክላ ሠሪ ገምቦ ግዛ፤ ከሕዝቡም ሽማግሌዎችና ከካህናት ሽማግሌዎች ከአንተ ጋር ውሰድ። 2 የገል በር
በሚከፈትበት ወዳለው ወደ ሄኖም ልጅ ሸለቆ ሂድ፣ በዚያም የምነግርህን ቃል ተናገር። 3 እንዲህም በል፣ 'ይሁዳ ነገሥታትና በኢየሩሳሌም የምትኖሩ ሆይ፣
የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ! የእስራኤል አምላክ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "ተመልከቱ! የሰማውን ሰው ጆሮ የሚያስጨንቅ ክፉ ነገር በዚህ
ስፍራ አመጣለሁ። 4 ይህንን የማደርገው ስለተዉኝና ይህንን ስፍራ የባዕድ አማልክት አድርገውታልና ነው። እነርሱና አባቶቻቸው ለማያውቋቸው ለሌሎች
አማልክት አጥነዋል፣ የይሁዳም ነገሥታት ይህንን ስፍራ በንጹህ ደም ሞልተዋል። 5 እኔም ያላዘዝሁትን የሚቃጠል መሥዋዕት አድርገው ወንዶች ልጆቻቸውን
ለበኣል በእሳት ያቃጥሉ ዘንድ የበኣልን የኮረብታውን መስገጃዎች ሠርተዋል። ይህንን እንዲያደርጉ አልተናገርኳቸውም፣ በልቤም አላሰብሁትም። 6 ስለዚህም፣
ተመልከቱ፣ ይህ ስፍራ የእርድ ሸለቆ ይባላል እንጂ ከእንግዲህ ቶፌት ወይም የሄኖም ልጅ ሸለቆ የማይባልበት ዘመን ይመጣል ይላል እግዚአብሔር። 7 በዚህ
ስፍራ የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን እቅድ ከንቱ አደርጋለሁ። በጠላቶቻቸው ፊት በሰይፍና ነፍሳቸውን ደግሞ በሚሹት እጅ እጥላቸዋለሁ። ከዚያም ሬሳቸውንም
ለሰማይ ወፎችና ለምድር አራዊት መብል አድርጌ እሰጣለሁ። 8 ከዚያም ይህችን ከተማ አጠፋና መደነቂያ አደርጋታለሁ፣ ስለ ተደረገባት መቅሠፍት ሁሉ
የሚያልፍባት ሁሉ ይደነቃል፣ ከንፈሩንም ይመጥጣል። 9 የወንዶችና የሴቶች ልጆቻቸውንም ሥጋ አበላቸዋለሁ፣ ሁሉም ጠላቶቻቸውንና ነፍሳቸውን የሚሹት
በሚያስጨንቋቸው ጭንቀትና መከበብ የጎረቤቶቻቸውን ሥጋ ይበላሉ። 10 ከዚያም ገምቦውን ከአንተ ጋር በሚሄዱ ሰዎች ፊት ትሰብራለህ። 11 እንዲህም
ትላቸዋለህ፣ 'የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ የሸክላ ሠሪውን ዕቃ ኤርምያስ እንደሰባበረው፣ ደግሞም በድጋሚ ይጠገን ዘንድ እንደማይቻል፣
እንዲሁ ይህን ሕዝብና ይህችን ከተማ እሰብራለሁ፤ የሚቀብሩበትም ስፍራ እስከማይኖር ድረስ በቶፌት ይቀበራሉ። 12 ይህችንም ከተማ እንደ ቶፌት ሳደርግ
ለዚህ ስፍራና በሚኖሩበት ላይ የማደርገው ይህንኑ ነው ይላል እግዚአብሔር። 13 የረከሱትም የኢየሩሳሌም ቤቶችና የይሁዳ ነገሥታት ቤቶች፣ እነዚያ
በሰገነታቸው ላይ ለሰማይ ከዋክብት ሁሉ ያጠኑባቸው ለሌሎችም አማልክት የመጠጥን ቍርባን ያፈሰሱባቸው ቤቶች ሁሉ፣ እንደ ቶፌት ስፍራ ይሆናሉ።" 14
ከዚያም ትንቢት እንዲናገር እግዚአብሔር ልኮት ከበረው ስፍራ፣ ከቶፌት ኤርምያስ መጣ። በእግዚአብሔርም ቤት አደባባይ ቆሞ ለሕዝብ ሁሉ እንዲህ አለ፣ 15
"የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ 'ቃሌን እንዳይሰሙ አንገታቸውን አደንድነዋልና፣ በዚህች ከተማና በመንደሮችዋ ሁሉ ላይ የተናገርሁባትን ክፉ
ነገር ሁሉ አመጣለሁ።"

Jeremiah 19:1

የቤን ሄኖም ሸለቆ
ይህ ሰዎች ለሀሰተኛ አማልዕክት የሚሰዉበት፣ ከእየሩሳሌም ከተማ በስተ ደቡብ የሚገኝ ሸለቆ ስም ነው። ይህ በኤርምያስ 7:31 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

እዩ
"ተመልከቱ" ወይም "አድምጡ" ወይም "ለምነግራችሁ ነገር ትኩረት ስጡ"

ይህን የሚሰሙ ሁሉ ጆሮዎቻቸው ጭው ይላል
እዚህ ስፍራ "ጆሮዎች... ጭው ይላሉ" የሚለው ፈሊጥ ትርጉም እያንዳንዱ በሚሰማው ይረበሻል የሚል ነው። "ይህንን የሰማ ሁሉ ይረበሻል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጭው ይላል
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ይጮህባቸዋል" 2) "ይንቀጠቀጣሉ"

Jeremiah 19:4

እነርሱ እኔን ትተዋል
እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የይሁዳን ሰዎች ነው።

ይህንን ስፍራ በንጹሃን ደም ሞልተውታል
እዚህ ላይ "የንጹሀን ደም" የሚለው የሚወክለው የንጹሃን ሰዎችን መገደል ነው። ያህዌ የብዙ ሰዎችን መገደል አንድን ስፍራ በደም መሙላት አድርጎ ይናገራል። "በዚህ ስፍራ ብዙ ንጹሃን ሰዎችን ገድላችኋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ይህ ወደ አይምሮዬ አልገባም/አላሰብኩትም
እዚህ ስፍራ "አይምሮ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የያህዌን ሃሰብ/ፈቃድ ነው። በኤርምያስ 7:31 ላይ ይህ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እኔ በፍጹም ስለዚህ አስቤ አላውቅም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

(ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 19:6

እዩ
"ተመልከቱ" ወይም "አድምጡ" ወይም "ለምነግራችሁ ነገር ትኩረት ስጡ"

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ስፍራ ከእንግዲህ አይጠራም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች ከእንግዲህ ይህን ስፍራ አይጠሩትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ቶፌት... የቤን ሄኖም ሸለቆ...የእርድ ሸለቆ
ይህ በኤርምያስ 7:31 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

እኔ በጠላቶቻቸው ፊት በሰይፍ እንዲወድቁ አደርጋለሁ
"በሰይፍ እንዲወድቁ" የሚለው ፈሊጥ በጦርነት ውስጥ እንዲሞቱ ማለት ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ጠላቶቻቸው በሰይፍ እንዲገድሏቸው አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

እኔ እነርሱን...አደርጋለሁ
"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የይሁዳን እና እየሩሳሌምን ህዝቦች ነው።

ህይወታቸውን በሚፈልጉ ሰዎች እጅ
ግሡ ከቀደመው ሀረግ ሊወሰድ ይችላል። "በ...እጅ መውደቅ" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር በሰው መገደል የሚል ትርጉም ሲኖረው፣ "እጅ" ከሚለው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ቃል ጋር የሚወክለው የሰውየውን ሁለንተና ነው። "ሊገድሏችሁ የሚፈልጉ ሁሉ እንዲገድሏቸው አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/ የተተወ እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እንደዚሁም ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

የጥላች ድምጽ አካል
"የጥላች ድምጽ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጠንካራ የሆነ ያለ መቀበልን መግለጫ ድምጽ ሲሆን በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "ሰዎች ሁሌም የጥላቻ ድምጽ የሚያሰሙበት ነገር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲበሏቸው አደርጋቸዋለሁ
"በእየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎችን እንዲበሉ አደርጋለሁ"

በዚህ ከበባ
"በከበባው ምክንያት"

ከጠላቶቻቸው በደረሰባች ጭንቀት እና ህይወታቸውን በሚፈልጉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ከጠላቶቻቸው እና ህይወታቸውን ከሚፈልጉ የተነሳ በላያቸው ጭንቀት ይመጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 19:10

ከአንተ ጋር በሄዱ ሰዎች እየተመለከቱ
"ማየት" የሚለው ረቂቅ ስም "መመልከት" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "ከአንተ ጋር የሄዱ ሰዎች እየተመለከቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙ ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክት ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ እንደገና ሊጠገን አይችልም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ማንም ይህን እንደገና ሊጠግነው አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 19:12

ይህ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳ ነገሥታት
"ቤቶች" የሚለው ቃል እዚህ ስፍራ ሊገባ ይችላል። "የይሁዳ ነገሥታት ቤቶች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

ንጹህ ያልሆኑ ሰዎች
ለእግዚአብሔር አላማ ተቀባይነት ያላገኙ ሰዎች የተገለጹት በአካል ንጹህ እንዳልሆኑ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 19:14

የሰራዊት ጌታ ያህዌ...እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክት ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

እዩ
"ተመልከቱ" ወይም "አድምጡ" ወይም "ለምነግራችሁ ነገር ትኩረት ስጡ"

አንገታቸውን አደነደኑ ለማድመጥ እንቢ አሉ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ሁለቱም ግትር ስለሆኑ ሰዎች ይናገራሉ። በመጀመሪያው ሀረግ፣ ያህዌ ደንዳና ስለሆኑ ሰዎች አንገታቸውን እንደ ገተሩ አድርጎ ይገልጻል። "በግትርነት ለማድመጥ እምቢ አሉ" በመሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 20

1 በእግዚአብሔርም ቤት የተሾመው አለቃ የካህኑ የአሜር ልጅ ጳስኮር ኤርምያስ በዚህ ነገር ትንቢት ሲናገር ሰማ። **2** ስለዚህ ጳስኮር ነቢዩን ኤርምያስን መታው፣ በእግዚአብሔርም ቤት ውስጥ ባለው በላይኛው የብንያም በር በእግር ግንድ አሰረው። **3** በቀጣዩ ቀን ጳስኮር ኤርምያስን ከግንድ እስር አወጣው። ከዚያም ኤርምያስ እንዲህ አለው፣ "እግዚአብሔር ስምህን፣ ማጎርሚሳቢብ እንጂ ጳስኮር ብሎ አይጠራህም። **4** እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፣ 'ተመልከት፣ ለራስህና ለወዳጆችህ ሁሉ ፍርሃት አደርግሃለሁ፤ እነርሱም በጠላቶቻቸው ሰይፍ ይወድቃሉና ዓይኖችህም ያንን ያያሉ። ይሁዳንም ሁሉ በባቢሎን ንጉሥ እጅ አሳልፌ እሰጣለሁ። እርሱም በባቢሎን ምርኮኛ ያደርጋቸዋል ወይም በሰይፍ ይገድላቸዋል። **5** የዚህችንም ከተማ ባለጠግነት ሁሉ ጥሪትዋንም ሁሉ ክብርዋንም ሁሉ የይሁዳንም ነገሥታት መዝገብ ሁሉ በጠላቶቻቸው እጅ አሳልፌ እሰጣለሁ። እነዚህን ነገሮች በጠላቶቻችሁ እጅ አኖራለሁ፣ እነርሱም ይይዟቸዋል። እነርሱም ይወስዷቸዋል ደግሞም ወደ ባቢሎን ያመጧቸዋል። **6** አንተ ግን፣ ጳስኮር ሆይ፣ በቤትህም የሚኖሩት ሁሉ ተማርካችሁ ትሄዳላችሁ። ወደ ባቢሎን ትሄዳለህ ደግሞም በዚያ ትሞታለህ። አንተና የሚያታልሉ ነገሮችን የተነበይክላቸው ወዳጆችህ ሁሉ በዚያ ትቀበራላችሁ።" **7** እግዚአብሔር ሆይ፣ አሳመንኸኝ፣ እኔም አምኛለሁ። ያዝኸኝ ደግሞም አሸነፍኸኝ። መላገጫ ሆኛለሁ። ሕዝቡ በየቀኑ፣ ቀኑን ሁሉ ይሳለቁብኛል። **8** በተናገርሁ ቍጥር፣ 'ግፍና ጥፋት' ብዬ እጮኻለሁ። የእግዚአብሔርም ቃል ቀኑን ሁሉ ነቀፌታና ዋዛ ሆኖብኛልና። **9** እኔም፣ 'ከእንግዲህ ወዲህ የእግዚአብሔርን ስም አላስብም። ከእንግዲህ ወዲህም ስሙን አላውጅም' ብል፣ ያን ጊዜ በአጥንቶቼ ውስጥ እንደሚነድድ፣ በልቤ ውስጥ እንዳለ እሳት ሆነብኝ። ስለዚህ ልሸከመው ታገልሁ፣ ነገር ግን አልቻልሁም። **10** በዙሪያዬ ካሉ ብዙ ሰዎች የሚያሸብር አሉባልታን ሰምቻለሁ። የቅርቤ ሰዎች የሆኑት ውድቀቴን ለማየት ጠበቁ፣ 'ምናልባት እንበረታበት እንደ ሆነ፣ ከዚያም እንበቀለው እንደ ሆነ 'ክሰሱት፣ እኛም እንከስሰዋለን' ይላሉ። **11** እግዚአብሔር ግን እንደ ኃያል ጦረኛ ከእኔ ጋር ነው፤ ስለዚህ አሳዳጆቼ ይሰናከላሉ። አያሸንፉኝም። አይከናወንላቸውምና፣ በእጅጉ ያፍራሉ። መቼም የማይረሳ በሚሆን እፍረት የማያበቃ እፍረት ያፍራሉ። **12** ጻድቅን የምትመረምር፣ አእምሮንና ልብን የምትመለከት የሠራዊት ጌታ ሆይ፣ ክርክሬን አሳይቼሃለሁና በላያቸው በቀልህን ልይ። **13** ለእግዚአብሔር ዘምሩ! እግዚአብሔርን አመስግኑ! የተጨቆኑትን ሰዎች ሕይወት ከክፉ አድራጊዎች እጅ አድኖአልና። **14** የተወለድሁባት ቀን የተረገመች ትሁን። እናቴ እኔን የወለደችባት ቀን የተባረከች አትሁን። **15** 'ወንድ ልጅ ተወልዶልሃል' ብሎ ለአባቴ የነገረው ሰው የተረገመ ይሁን። **16** ያም ሰው እግዚአብሔር ያለምሕረት እንደ ገለበጣቸው ከተሞች ይሁን። በማለዳም እርዳታ የሚለምን ጩኸትን በቀትርም የጦርነት እሪታን ይስማ። **17** እግዚአብሔር በማኅፀን ውስጥ አልገደለኝምና ወይም እናቴን መቃብሬ አላደረገኝምና፣ ይህ ይከሰት። **18** ችግርንና ጣርን አይ ዘንድ፣ ዘመኔም በእፍረት ይሞላ ዘንድ ለምን ከማኅፀን ወጣሁ?

Jeremiah 20:1

አጠቃላይ መረጃ:
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ ትንቢት የሚጽፈው በሥነ ግጥም መልክ ነው። የዕብራውያን ስነግጥም የተለያዩ የትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ አይነቶችን ይጠቀማል። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ጳስኮር... አሜር
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ጳስኮር ኤርምያስን መታው
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ጳስኮር ራሱ ኤርምያስን መታው ማለት ሊሆን ይችላል። ወይም 2) ጳስኮር ሌሎች ሰዎች ኤርምያስን እንዲመቱት አዘዘ ማለት ሊሆን ይችላል። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ማሰሪያ/እግር ግንድ
ማሰሪያ ግንድ፣ ከእንጨት የተሰራ በመሃሉ ቀዳዳያለው ሰዎች የእስረኞችን እጆች፣ እግር፣ እና ጭንቅላት ለማሰሪያ/ለመጠረቅ የሚጠቀሙበት ግንድ ነው።

የላይኛው የብንያም በር
ይህ በር በከተማይቱ ቅጥር መግቢያ ከሚገኘው ተመሳሳይ ስም ካለው በር ይለያል

Jeremiah 20:3

እንዲህ ሆነ
ይህ ሀረግ እዚህ ስፍራ የዋለው ድርጊቱ የት ላይ እንደ ጀመረ ለማመልከት ነው። የእናንተ ቋንቋ ይህ የሚገልጽበት መንገድ አዚህ ስፍራ ያንን መጠቀም ትችላላችሁ።

አንተ ማጎር ሚሳቢብ ነህ
የዚህ ስም ትርጉም "በሁሉም በኩል ሽብር" ወይም "በሽብር መከበብ" ማለት ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እዩ፣
ይህ ቃል ቀጥሎ ለሚነገረው ትኩረት ይጨምራል። "ቀጥሎ ለምናገረው ትኩረት ስጥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እነርሱ በጠላቶቻቸው ሰይፍ ይወድቃሉ
"በሰይፍ መውደቅ" የሚለው ፈሊጥ ትርጉም በጦርነት ይሞታሉ ማለት ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ጠላቶቻቸው በሰይፍ ይገድሏቸዋል" ወይም "ጠላቶቻቸው በጦርነት ውስጥ ይገድሏቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ዐይኖችህ ይህንን ይመለከታሉ
እዚህ ስፍራ "ዐይኖች" የሚለው ቃል የሚወክለው ጳስኮርን ነው። "አንተ ይህን ትመለከታለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

መላዋን ይሁዳ ለባቢሎን ንጉሥ እጅ አሳልፌ እሰጣለሁ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል ሀይልን ያመለክታል። "የባቢሎን ንጉሥ መላውን ይሁዳ እንዲማርክ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 20:5

እኔ ለእርሱ እሰጠዋለሁ
እዚህ ስፍራ "እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የባቢሎንን ንጉሥ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መላው ሀብት... መላው ብልጽግናዋ፣ መላው ውድ ንብረቶቿ እና ጠቅላላ ንብረቷ
ያህዌ መሰረታዊ የሆነውን ተመሳሳይ ሀሳብ አራት ጊዜ የደገመው ትኩረት ለመስጠት ነው። ባቢሎን የእስራኤልን ጠቅላላ ሀብት፣ የንጉሡን ንብረቶች ጨምሮ ይወስዳል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህን ነገሮች በጠላቶችህ እጅ ላይ አደርጋለሁ
ነገሮችን በሰዎች እጅ ላይ ማድረግ የሚወክለው ነገሮችን ለሰዎች አሳልፎ መስጠትን ወይም ሰዎች ነገሮችን እንዲወስዱ መፍቀድን ነው። "እነዚህን ነገሮች ለጠላቶቻችሁ እሰጣለሁ" ወይም "ጠላቶቻችሁ እነዚህ ሀብቶች እንዲወስዱ እፈቅዳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ እና ሀሰተኛ ትንቢት የተናገርክላቸውን የምትወዳቸውን በሙሉ በዚያ ይቀበራሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በዚያ፣ ሰዎች አንተን እና የምትወዳቸውን ሀሰተኛ ነገሮችን የተናገርክላቸውን ሁላችሁምን ይቀብሯችኋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 20:7

አጠቃላይ መረጃ:
ኤርምያስ ወደ ያህዌ ይናገራል

ያህዌ፣ አንተ አታለልከኝ፣ ደግሞም እኔም ተታልዬ ነበር
አንዳንድ ዘመናዊ ቅጂዎች ይህንን የዕብራይስጥ አገላለጽ "ያህዌ፣ አንተ አሳመንከኝ፣ እኔም ደግሞ አመንኩህ" በማለት ይተረጉሙታል።

እኔ ተታልዬ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንተ እኔን አታለልከኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀኑን በሙሉ መሳለቂያ ሆንኩ፤ ሁሉም በእኔ ላይ ያፌዛል
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው ሌሎች በእርሱ ላይ ያፌዙበትን መንገድ ትኩረት ይሰጣል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መሳለቂያ
ይህ ሌሎች የሚስቁበት እና የሚያፌዙበት ሰው ነው

ተጣራሁ ደግሞም አወጅኩ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ እናም የያህዌን መልዕክት በድፍረት ማወጁን ትኩረት ይሰጣሉ። "በግልጽ አወጅኩ" ወይም "ጮክ ብዬ አወጅኩ/ተናገርኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌ ቃል በየቀኑ ዘለፋ እና መቀለጃነት አስከተለብኝ
እዚህ ስፍራ "ቃል" የሚያመለክተው የያህዌን መልዕክት ነው። "ዘለፋ" እና "ፌዝ" የሚሉት ቃላት በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "ሰዎች በየቀኑ እኔን ይዘልፋሉ ደግሞም ያፌዙብኛል፤ ይህም የያህዌን መልዕክት ስላወጅኩ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

ለእኔ መሳለቂያን ፌዝ ሆነ
"መሳለቂያ" እና "ፌዝ" የሚሉት ቃላት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው ኤርምያስን የያህዌን መልዕክት በማወጁ ሰዎች መሳለቂያ እንዳደረጉት ትኩረት ይሰጣሉ። "ሰዎች በእኔ ላያ የተሳለቁበት ምክንያት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህ በእርሱ ስም አልናገርም
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "በፍጹም ያህዌን አልጠቅስም ወይም ስለ እርሱ ምንም ነገር አልናገርም" ወይም 2) "ስም"የሚለው ቃል ስልጣንን ይወክላል። "ከእንግዲህ የእርሱ መልዕክተኛ ሆኜ አልናገርም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በልቤ ልክ እንደ እሳት፣ በአጥንቴ ውስጥ እንደሚገኝ ሆነብኝ
እዚህ ስፍራ "ልብ" እና "አጥንት" የሚሉት ቃላት የሚወክሉት የኤርምያስን እጅግ ውስጣዊ ማንነት ነው። ኤርምያስ የያህዌን መልዕክት አለመናገር እንደማይችል የገለጸው መልዕክቱ በውስጥ እንደሚነድ እሳት መሆኑን በመግለጽ ነው። "የያህዌ ቃል በውስጤ እንደሚነድ እሳት ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 20:10

ዘገባ! እኛ ይህን መዘገብ አለብን
የኤርምያስ ጠላቶች እነዚህን ቃሎች ይናገራሉ።

የእኔን መውደቅ ለማየት ይጠባበቃሉ
ኤርምያስ ጠላቶቹ እርሱን ለመክሰስ ስህተት ይሰራል ብለው እንደሚጠባበቁ የሚናገረው ከፍ ካለ ስፍራ ላይ እንደሚወድቅ ሰው አይነት እንደሆነ ይገልጻል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ምናልባት ይታለል ይሆናል... በእርሱ ላይ የበቀል እርምጃ እንወስዳለን
እነዚህን ቃሎች የሚናገሩት የኤርምያስ ጠላቶች ናቸው።

ምናልባት ይታለል ይሆናል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ምናልባት እኛ ልናታልለው እንችል ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ እንደ ሀያል ጦረኛ ከእኔ ጋር ነው
ኤርምያስ ያህዌ እርሱን መርዳቱን እና ከጠላቶቹ እርሱን ማዳኑን ያነጻጸረው ከታላቅ ጦረኛ ጋር ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሚያሳድዱኝ ይሰናከላሉ
ኤርምያስ ለጎዱት የሚፈልጉት ጠላቶቹ እርሱን እንደሚያሳድዱት እና እርሱን ለመጉዳት አለመቻላቸውን ደግሞ እንደተሰናከሉ አድርጎ ይገልጻል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ እጅግ ያፍራሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ያህዌ በእነርሱ ላይ ታላቅ ሀፍረት ያመጣባቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ፈጽሞ የማይረሳ ይሆናል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች ይህንን ፈጽሞ አይረሱም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 20:12

ልባቸውንና ሀሳባቸውን ተመልከት
"ሃሳብ/አእምሮ" የሚለው ቃል አንድ ሰው የሚያስበውን እና ውሳኔውን የሚገልጽ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። "ልብ" የሚለው ቃል ደግሞ አንድ ሰው የሚሰማውን እና መሻቱን የሚገልጽ ሜቶኖሚ ነው። "የእያንዳንዱን ሰው ሃሳብ እና ስሜት ታውቃለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Jeremiah 20:14

አጠቃላይ መረጃ:
ኤርምያስ ከያህዌ ጋር መነጋገርን ቀጥሏል።

የተወለድኩበት ቀን የተረገመ ይሁን
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የተወለድኩበትን ቀን ይርገሙት" ወይም "ሰዎች እኔ የተወለድኩበትን ቀን ይርገሙት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ለአባቴ የነገረው ሰው የተረገመ ይሁን
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ለአባቴ የነገረውን ሰው እርገሙት" ወይም "ሰዎች ለአባቴ የነገረውን ሰው ይርገሙት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 20:16

ያ ሰው
ይህ የሚያመለክተው ለኤርምያስ አባት የኤርምያስን መወለድ የነገረውን ሰው ነው

ያህዌ የጣላቸው ከተሞች
ይህ የሚያመለክተው ሰዶምን እና ገሞራን ነው።

እርሱ ርህራሄ የለውም
እዚህ ስፍራ "እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ያህዌን ነው።

እርሱ የለቅሶ ድምጽ ይስማ
እዚህ ስፍራ "እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው "ያንን ሰው" ነው።

እናቴን መቃብሬ አላደረግኽም
ኤርምያስ ገና እናቱ አርጋዛው ሳለች ቢሞት ይሻለው እንደነበረ የተናገረው የእናቱን ማህጸን እንደ መቃብሩ በማድረግ ነበር። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለዘለዓለም ከማህጸን ባልወጣሁ
ኤርምያስ ነብሰጡር እናቱ ለዘለዓለም ሳትወልደኝ እንዳረገዘችኝ በኖረች ብሎ ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መከራ እና ጭንቀት...ሀፍረት ለማየት ለምን ከማህጸን ወጣሁ?
ኤርምያስ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ለመወለድ ምንም መልካም ምክንያት እንዳልነበረ ለማማረር ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "መከራ እና ጭንቀት... እንዲሁም ሀፍረት ለማየት ካልሆነ በስተቀር እኔ የምወለድበት ምንም መልካም ምክንያት አልነበረም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

መከራ እና ጭንቀት ለማየት
"መከራ" እና "ጭንቅ" የሚሉት ቃላት በመሰሩ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው የአበሳውን መጠን እና ጥልቀት ያጎላሉ። "ብዙ መከራ ለመቀበል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ቀኖቼ በሀፍረት ተሞሉ
እዚህ ስፍራ "ቀኖች" የሚለው ቃል የሚወክለው የኤርምያስን የህይወት ዘመን ነው። "ህይወቴ በሀፍረት ተሞላ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 21

1 ንጉሥ ሴዴቅያስ የመልክያን ልጅ ጳስኮርንና ካህኑን የመዕሤያን ልጅ ሶፎንያስ ወደ ኤርምያስ በላከ ጊዜ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ኤርምያስ የመጣው ቃል ይህ ነው። **2** "የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ይወጋናልና ስለ እኛ፣ እባክህ፣ እግዚአብሔርን ጠይቅ። ምናልባት ከእኛ ይመለስ ዘንድ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር እንደ ተአምራቱ ሁሉ ያደርግ ይሆናል።" **3** ስለዚህ ኤርምያስ እንዲህ አላቸው፣ "ለሴዴቅያስ እንዲህ በሉት፣ **4** 'የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ተመልከት፣ የባቢሎንን ንጉሥ ከቅጥርም ውጭ የከበቡአችሁን ከለዳውያንን የምትወጉበትን በእጃችሁ ያለውን ዕቃ ጦራችሁን እመልሰዋለሁ! እነዚያንም ወደዚህች ከተማ አማከይ እሰበስባቸዋለሁ። **5** ያን ጊዜ እኔ ራሴ በተዘረጋች እጅና በብርቱ ክንድ፣ በቍጣና በመዓት በታላቅም መቅሠፍት እወጋችኋለሁ። **6** በዚህችም ከተማ የሚኖሩትን፣ ሰዎችንና እንስሶችን እመታለሁ፣ በጽኑም መቅሰፍት ይሞታሉ። **7** ከዚህ በኋላ፣ ይላል እግዚአብሔር፣ የይሁዳ ንጉሥ ሴዴቅያስን፣ ከቸነፈርና ከሰይፍ ከራብም በዚህች ከተማ የቀሩትንም ባሪዎቹንና ሕዝቡን፣ በባቢሎን ንጉሥ በናቡከደነፆር እጅ በጠላቶቻቸውና ነፍሳቸውንም በሚሹት እጅ አሳልፌ እሰጣቸዋለሁ። ከዚያም እርሱ በሰይፍ ስለት ይመታቸዋል። አያዝንላቸውም፣ አይራራላቸውም፣ ወይም አያዝንላቸውም።' **8** ከዚያም ለዚህ ሕዝብ እንዲህ ልትል ይገባል፣ 'እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ተመልከቱ፣ የሕይወትን መንገድና የሞትን መንገድ በፊታችሁ አደርጋለሁ። **9** በዚህች ከተማ ውስጥ የሚቆይ የትኛውም ሰው በሰይፍ፣ በራብ፣ በመቅሠፍትም ይሞታል፤ ነገር ግን ወጥቶ ወደ ከበቡአችሁ ወደ ከለዳውያን የሚገባ ግን በሕይወት ይኖራል። በሕይወትም ያመልጣል። **10** መልካምን ሳይሆን ጥፋትን ለማምጣት ፊቴን በዚህች ከተማ ላይ አድርጌአለሁ፣ ይላል እግዚአብሔር። ለባቢሎን ንጉሥ እጅ ተሰጥታለች፣ እርሱም በእሳት ያቃጥላታል።' **11** የይሁዳ ንጉሥ ቤትን በተመለከተ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ። **12** የዳዊት ቤት ሆይ፣ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ 'በማለዳ ፍርድን አድርጉ። የተዘረፈውንም ከአጨቋኙ እጅ አድኑ፣ አሊያ ቊጣዬ እንደ እሳት ይወጣና ያቃጥላል። ከሥራችሁ ክፋት የተነሣ ሊያጠፋው የሚችል ማንም አይኖርም። **13** ተመልከቱ፣ የሸለቆው ነዋሪዎች! በሜዳው ላይ ያለው ዓለት ሆይ በእናንተ ላይ ነኝ ይላል እግዚአብሔር። "ሊያጠቃን በእኛ ላይ የሚወርድ ማነው?" ወይም "ወደ ቤታችን የሚገባ ማን ነው?" ለምትሉት፣ እኔ በእናንተ ላይ ነኝ። **14** የሥራችሁ ፍሬ በእናንተ ላይ እንዲመጣባችሁ መድቤያለሁ ይላል እግዚአብሔር፤ በዱርዋም ውስጥ እሳትን አነድዳለሁ፣ በዙሪያዋም ያለውን ሁሉ ይበላል።

Jeremiah 21:1

ከያህዌ ዘንድ ወደ ኤርምያስ የመጣ ቃል
ይህ ፈሊጥ የዋለው ከእግዚአብሔር ዘንድ ልዩ መልዕክት ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 7፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ተመልክተው እንደ አስፈላጊነቱ ለውጥ አድርጉ። "ያህዌ ለኤርምያስ መልዕክት ሰጠው" ወይም "ያህዌ ለኤርምያስ መልዕክት ነገረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጳስኮር
ይህ በኤርምያስ 20፡1 ላይ የተጠቀሰው ጳስኮር አይደለም

ጳስኮር...መዕሤያን...መልክያ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ደግሞም እነርሱ እንዲህ አሉ
"ጳስኮር እና ሶፎንያስ ኤርምያስን እንዲህ አሉት"

በእኛ ምትክ ሆነህ ከያህዌ ዘንድ ምክር ፈልግልን... ጦር መጥቶብናል
ይህ በጭንቅ ሰዓት በትህትና የቀረበ ጥያቄ ነው። "እባክህ ስለ እኛ ያህዌን ለምንልን... እያጠቁን ነው"

እንዳለፈው ዘመን
"ባለፈው ዘመን እንዳደረገው"

ከእኛ እርሱን እንዲያርቀው
"እርሱ ከእኛ እንዲመልስ"

Jeremiah 21:3

እዩ
ይህ አድማጩ ቀጥሎ ለሚሆነው ልዩ ትኩረት እንዲሰጥ ይናገራል

ወደ ኋላ መዘር
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ዋጋ ቢስ ለማድረግ ወይም 2) ወደ ከተማ መልሶ ለመላክ

በእጅህ የሚገኙ የጦር መሳሪያዎች
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የጦር መሳሪያዎች የሚለው የሚያመለክተው እነርሱን የያዙ ወታደሮች ሲሆን "እጅ" የሚወክለው መቆጣጠርን ነው። "አንተ የምታዛቸው ወታደሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) የጦር መሳሪያዎች በቀጥታ መሳሪያዎች ማለት ሊሆን ሲችል "እጅ" የሚለው የሚያመለክተው ንጉሡን እና ወታደሮቹን ሁለትንም ነው። "አንተ እና የአንተ ወታደሮች የያዛችሁት መሳሪያዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከለዳውያን
እዚህ ስፍራ ይህ ቃል ባቢሎናውያን ለሚለው ሌላው ስያሜ ነው።

እናንተን ይከባሉ
"ወደ እናንተ ይገባሉ/ይመጣሉ"

እኔ እሰበስባቸዋለሁ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ያህዌ ባቢሎናውያን ወደ ከተማይቱ እንዲገቡ ይፈቅዳል ወይም 2)ያህዌ እስራኤላውያን መሳሪያዎቻቸውን ወደ ከተማይቱ መሃል መልሰው እንዲያመጡ ያደርጋል

ከዚያም እኔ ራሴ
ይህን የሚያደርገው ያህዌ መሆኑን አጽንኦት እና ትኩረት ሰጥቶ ይገልጻል። (ደጋጋሚ ተውላጠ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በተዘረጋ እጅ እና ጠንካራ ክንድ
እነዚህ ሁለቱም ሀረጎች ታላቅ ሀይልን የሚያመለክቱ ፈሊጣዊ አገላለጾች ናቸው። "በጣም በትልቅ ሀይል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ጥንድ ትርጉም የሚሉትን ይመልከቱ)

በሀይል፣ በንዴት እና በታላቅ ቁጣ
እነዚህ ቀላት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም የያዙ ናቸው። በአንድነት ሆነው የእርሱን ቁጣ ታላቅ ጥልቀት ያጎላሉ። "እጅግ ከፍ ባለ ታላቅ ቁጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Jeremiah 21:6

የዚህች ከተማ ኗሪዎች
"በእየሩሳሌም የሚኖሩ"

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰይፍ/ሰይፉ
እዚህ ስፍራ ይህ የሚያመለክተው ሰይፍ የሚጠቀሙበትን ጦርሜዳ ነው። "ጦርነቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ለ..እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚያመለክተው ጠላት በእነርሱ ላይ ያለውን ሀይል ነው። "ለ...ሀይል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነጾር... የእነርሱ ጠላቶች... ህይወታቸውን የሚፈልጉ
እነዚህ ሀረጎች ሁሉ ናቡከደነጾርን እና የእርሱን ሰራዊት ያመለክታሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ህይወታቸውን የሚፈልጉ
"እነርሱን ለመግደል የሚፈልጉ"

በሰይፍ ስለት
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ በጦርነት ስለ መሞት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "በጦርነት/ጦር ሜዳ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) በራሱ በሰይፍ ይገደላሉ። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አይራራላቸውም፣ አይምራቸውም፣ ወይም ርህራሄ አይኖረውም
እነዚህ ሶስት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ደግሞም ናቡከደነጾር ያለ ርህራሄ እንደሚጨክንባቸው አጽንኦት ይሰጣሉ። "አንዳች ምህረት አያሳያቸውም ወይም በፍጹም ርህራሄ አያሳያቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 21:8

ይህ ህዝብ
"የእየሩሳሌም ሰዎች"እኔ በፊታችሁ የህይወትን እና የሞትን መንገድ አስቀምጣለሁ ያህዌ ለእስራኤል ሰዎች በህይወት የሚኖሩበትን ወይም የሚሞቱበትን ምርጫ ያቀርብላቸዋል።

በሰይፍ፣ ረሃብ፣ እና መቅሰፍት
በሰይፍ መሞት የሚያመለክተው በጦርነት መሞትን ነው። "በጦርነት እና በድርቅ ደግሞም በመቅሰፍት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በጉልበቱ ፊት ለፊት መውደቅ
ይህ ተምሳሌታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚወክለው ሙሉ ለሙሉ መሸነፍን ነው። "ለ...መሸነፍ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትምዕርታዊ/ ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

በእናንተ ላይ ተነስተዋል
"ከተለያየ አቅጣጫ ይከቧችኋል"

ህይወቱን ብቻ ይዞ ያመልጣል
ለባቢሎናውያን የተማረከ፣ ሀብቱን ቢያጣም ህይወቱን ያተርፋል።

ፊቴን በዚህች ከተማ ላይ አደርጋለሁ
የዚህ ፈሊጥ ትርጉም "በጽኑ ወስኛለሁ" ማለት ነው። "ይህችን ከተማ ለመቅጣት በጽኑ ወስኛለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ፊቴን በእነርሱ ላይ አድርጌያለሁ
"በሁሉም ላይ በቁጣ ተነስቻለሁ"

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሷ ተሰጥታለች
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኔ አሳልፌ ሰጥቻታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ለንጉሡ እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚወክለው ንጉሡ ከተማይቱን ለማጥፋት ያለውን ሀይልን ነው። "ለንጉሡ ሀይል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 21:11

የይሁዳን ንጉሥ ቤት በሚመለከት፣ የያህዌን ቃል አድምጡ
ይህ ከኤርምያስ 21:12-23 ድረስ ላለው ክፍል አርእስት ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። "ያህዌ ስለ ይሁዳ ንጉሥ፣ ስለ ቤተሰቡ እና ስለ አገልጋዮቹ የሚናገረውን አድምጡ"

የይሁዳ ንጉሥ ቤት
"ቤት" የሚለው ቃል በንጉሡ ቤት ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። በዚህ ሁኔታ ይህ የሚያመለክተው ንጉሡን እና ቤተሰቡን ነው። "የይሁዳ ንጉሥ እና ቤተሰቡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የዳዊት ቤት
ይህ የሚያመለክተው "በይሁዳ ንጉሥ ቤት" እንደሚላቸውን ተመሳሳይ ሰዎች ነው። መላው የይሁዳ ነገሥታት የዳዊት ትውልድ ናቸው። "የዳዊት ትውልዶች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በማለዳ ፍትህ ይሆናል
"ፍትህ" የሚለው ረቂቅ ስም ድርጊት ተደርጎ ሊገለጽ ይችላል። "ሁልጊዜም የምትገዟቸውን ሰዎች በትክክል አስተዳድሯቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የጨቋኝ እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚወክለው ሀይልን ነው። "እነርሱን የጨቆነው ሀይል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ቁጣዬ እንደ እሳት ወጥቶ ይነዳል
እዚህ ስፍራ የያህዌ ቁጣ የተነገረው ክፉ የሰሩትን እንደሚያቃጥል አሳት ተደርጎ ነው። "እናንተን በቁጣዬ በቶሎ አንዳችሁንም ሳላስቀር ቀጥቼ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አጠፋችኋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህን ማስቀረት የሚችል የለም
ኤርምያስ በተነጻጻሪ ዘይቤ የቀረበውን የያህዌን ቅጣት በውሃ ሊጠፋ እንደማይችል ታላቅ እሳት መግለጹን ቀጥሏል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 21:13

እየ
ይህ ሰሚው ሁሉ ቀጥሎ ሊሆን ላለው ነገር ትኩረት እንዲሰጥ ያነቃዋል። "ትኩረት ስጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

የሸለቆው ነዋሪት
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ እየሩሳሌም እንደሚለው፣ ከሸለቆብ በላይ የሚገኘውን የእየሩሳሌም ክፍል ሊያመለክት ይችላል፣ ምክንያቱም "ነዋሪት" ነጠላ ቁጥር ሴቴ ጾታ ነው ወይም 2) ይህ ሌላ ከተማን ወይም ቡድን ሊያመለክት ይችላል። ብዙ ቅጂዎች ከተማይቱን ለይቶ ከማሳወቅ ይልቅ ዋናውን መልክ ይተዉታል።

እኔ እቃወማለሁ
"እቃወማለሁ" ወይም "እኔ እቀጣለሁ"

በሜዳ የሚገኘው አለት
x

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 22

1 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "ወደ ይሁዳ ንጉሥ ቤት ውረድና በዚያም ይህን ቃል ተናገር። 2 እንዲህም በል፣ 'በዳዊት ዙፋን የምትቀመጥ የይሁዳ ንጉሥ
ሆይ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ስማ። አንተና የእርሱ ባርያዎች የሆናችሁ፣ በእነዚህም በሮች የመትገቡት ሕዝቦቹ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ። 3 እግዚአብሔር
እንዲህ ይላል፣ "ፍርድንና ጽድቅን አድርጉ፣ የተዘረፈውንም ከጨቋኙ እጅ አድኑ። በምድራችሁ ያለውን እንግዳ፣ ወይም የትኛውንም ወላጅ አልባ ወይም መበለቲቱን
አትበድሉ። አታምፁባቸው፣ ወይም በዚህ ስፍራ ንጹሕ ደምን አታፍስሱ። 4 እነዚህንም ነገሮች ብታደርጉ፣ ያን ጊዜ በዳዊት ዙፋን የሚቀመጡ ነገሥታት
በሰረገሎችና በፈረሶች ላይ ተቀምጠው በዚህ ቤት በሮች ይገባሉ። እርሱም፣ ባርያዎቹም፣ ሕዝቡም እንዲሁ ይገባሉ! 5 ነገር ግን ከእኔ የተነገሩትን እነዚህን
ቃሎች ባትሰሙ፣ ይህ ንጉሣዊ ቤተመንግሥት እንደሚጠፋ በራሴ ምያለሁ" ይላል እግዚአብሔር። 6 እግዚአብሔር ስለ ይሁዳ ንጉሥ ቤት እንዲህ ይላልና፣
'አንተ በእኔ ዘንድ እንደ ገለዓድ፣ ወይም እንደ ሊባኖስ ራስ ነህ። ነገር ግን፣ በእርግጥ ምድረ በዳ፣ ማንም እንደማይቀመጥባቸው ከተሞች አደርግሃለሁ። 7
እንዲመጡባችሁ አጥፊዎችን በእናንተ ላይ አዘጋጅቻለሁ! የተመረጡትንም የዝግባ ዛፎቻችሁን ይቈርጣሉ፣ በእሳትም ውስጥ ይጥሉአቸዋል። 8 ከዚያም ብዙ
አሕዛብ በዚህች ከተማ አጠገብ ያልፋሉ። ሁሉም ባልንጀሮቻቸውን፣ "እግዚአብሔር በዚህች ታላቅ ከተማ ለምን እንዲህ አደረገ?" ይላሉ። 9 ሌላኛውም፣
"የአምላካቸውን የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ትተው ለሌሎች አማልክት ስለ ሰገዱ ስላመለኩአቸውም ነው" ብለው ይመልሳሉ። 10 ለሞተው አታንቡ።
አታልቅሱለትም። ነገር ግን ከእንግዲህ ወዲህ አይመለስምና፣ የተወለደባትንም አገር አያይምና ወደምርኮ ለሚሄደው በእርግጥ አልቅሱ። 11 በአባቱ በኢዮአስ
ፋንታ ስለ ነገሠው ከዚህም ስፍራ ስለ ወጣው ስለ ይሁዳ ንጉሥ ስለ ኢዮስያስ ልጅ ስለ ሰሎ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። 12 'በተማረከባት አገር ይሞታል
እንጂ ወደዚህ አይመለስም፣ ይህችንም አገር ከእንግዲህ ወዲህ አያይም።' 13 ቤቱን ያለ ጽድቅ ሰገነቱንም በግፍ ለሚሠራ፣ ሌሎችንም አሠርቶ፣ ክፍያ
ለማይሰጣቸው። 14 'ለራሴ ሰፊ የላይኛ ቤት፣ ትልቅም ሰገነት እሠራለሁ ለሚል፣ መስኮትንም ለሚያወጣ፣ በዝግባም ሥራ ለሚያስጌጥ፣ በቀይ ቀለምም
ለሚቀባው ወዮለት።' 15 የዝግባ እንጨት እንዲኖርህ ስለፈለግህ መልካም ንጉሥ የሚያደርግህ ይህ ነውን? በውኑ አባትህ አይበላምና አይጠጣም ነበርን፣
ፍርድንና ጽድቅንስ አያደርግም ነበርን? በዚያም ጊዜ ነገሮች መልካም ሆነውለት አልነበረምን። 16 ለድሀውና ችግረኛው ፍርድን ይፈርድ ነበር። በዚያም ጊዜ
መልካም ሆኖለት ነበር። እኔን ማወቅ ማለት ይህ አይደለምን? ይላል እግዚአብሔር። 17 ዓይንህና ልብህ ግን ለስስት፣ ንጹሕ ደምንም ለማፍሰስ፣ ዓመፅንና
ግፍንም ለመሥራት ብቻ ካልሆነ በቀር ሌላ ነገር የለውም። 18 ስለዚህ እግዚአብሔር ስለ ይሁዳ ንጉሥ ስለ ኢዮስያስ ልጅ ስለ ኢዮአቄም እንዲህ ይላል፦
"ወዮ፣ ወንድሜ ሆይ!" ወይም፣ "ወዮ፣ እኅቴ ሆይ!' እያሉ አያለቅሱለትም፣ ወይም 'ወዮ፣ ጌታዬ!' አሊያም 'ወዮ፣ ግርማዊነትዎ!' እያሉ አያለቅሱለትም። 19
በአህያ ቀብር ይቀበራል፣ ከኢየሩሳሌምም በር ወደ ውጭ ተጐትቶ ይጣላል። 20 ወደ ሊባኖስ ወጥተሽ ጩኺ። በባሳን ድምፅሽን አንሺ። ውሽሞችሽ ሁሉ
ይጠፋሉና ከበዓባሪም ተራሮች ሆነሽ ጩኺ። 21 በደኅንነትሽ ጊዜ ተናገርሁሽ፣ አንቺ ግን 'አልሰማም' አልሽ። ከወጣትነትሽ ጀምሮ ቃሌን አለመስማትሽ
ልማድሽ ነው። 22 በግ ጠባቂዎችሽን ሁሉ ነፋስ ይጠብቃቸዋል፣ ውሽሞችሽም ተማርከው ይሄዳሉ። በዚያን ጊዜም ስለ ክፋትሽ ሁሉ ታፍሪያለሽ ትዋረጂማለሽ።
23 አንቺ በሊባኖስ የምትቀመጪ፣ በዝግባ ዛፍም ውስጥ ጎጆሽን የምትሠሪ ሆይ፣ ምጥ እንደ ያዛት ሴት ሕማም በያዘሽ ጊዜ እንዴት ታኒሪያለሽ።" 24 "እኔ
ሕያው ነኝና የይሁዳ ንጉሥ የኢዮአቄም ልጅ ኢኮንያን የቀኝ እጄ ማኅተም ቢሆን ኖሮ እንኳ፣ ከዚያ እነቅልህ ነበር፤ ይላል እግዚአብሔር። 25 ነፍስህንም ለሚሹት
ለምትፈራቸውም እጅ፣ ለባቢሎን ንጉሥ ለናቡከደነፆር ለከለዳውያንም እጅ እሰጥሃለሁ። 26 አንተንም የወለደችህንም እናትህን ወዳልተወለዳችሁባት ወደ ሌላ
አገር እጥላችኋለሁ፣ በዚያም ትሞታላችሁ። 27 ይመለሱባትም ዘንድ ወደሚመጇት ወደዚያች ምድር ተመልሰው አይመጡም። 28 በውኑ ይህ ሰው ኢዮአቄም
የተናቀና የተሰበረ የሸክላ ዕቃ ነውን? ወይስ እርሱ ለአንዳች የማይረባ የሸክላ ዕቃ ነውን? እርሱና ዘሩስ በማያውቋት ምድር ስለ ምን ተጥለው ወደቁ? 29 ምድር
ሆይ፣ ምድር ሆይ፣ ምድር ሆይ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ስሚ! 30 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ 'ከዚህ ሰው ዘር የሚከናወን በዳዊትም ዙፋን ላይ የሚቀመጥ
በይሁዳም የሚነግሥ እንግዲህ አይገኝምና። መካን በዘመኑም የማይከናወንለት ሰው ብላችሁ ጻፉ።"

Jeremiah 22:1

የይሁዳ ንጉሥ ቤት
"የይሁዳ ንጉሥ ቤተ መንግሥት።" "ቤት" የሚለው ቃል የተለያዩ ሰፊ ትርጉሞች ሊኖሩት ይችላል። በዚህ ሁኔታ ይህ የሚያመለክተው ንጉሡ የሚኖርበትን ንጉሣዊ ቤተመንግስት ነው።

ይህን ቃል ተናገረ/አወጀ
"ይህን መልዕክት አወጀ"

የያህዌን ቃል ስሙ
"ለያህዌ ቃል ትኩረት ስጡ"

በዳዊት ዙፋን የተቀመጥህ አንተ
ይህ የሚያመለክተው የይሁዳን ንጉሥ ነው።

በዳዊት ዙፋን ላይ የተቀመጥህ
"ዙፋን" የሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሚያመለክተው ዳዊት እንደነበረው እንደ ንጉሥ ያለን ስልጣን ነው። "ከአንተ በፊት እንደነበረው እንደ ንጉሥ ዳዊት አስተዳድር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በእነዚህ በሮች የሚገቡ የአንተ ሰዎች
እነዚህ በሮች የሚለው የንጉሡ ቤተ መንግስት በሮችን ነው። "ወደ ንጉሡ የሚመጡ የአንተ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ህትህን እን ጽድቅን አድርጉ
"ፍትህ" እና "ጽድቅ" የሚሉት ረቂቅ ስሞች እንደ ድርጊቶች ለገለጹ ይችላሉ። "ፍትሃዊ እን ትክክለኛ ድርጊት ፈጽሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ማንም የተዘረፈውን ከጨቋኝ እጅ አድኑት
"የተጠቃውን ከጨቋኞች እጅ አድኑ"

የጨቋኝ እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚገልጸው ሀይልን ወይም መቆጣጠርን ነው። "የጨቋኙ ሀይል" ወይም "እርሱን ሊጎዳው የሚችል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አትበድሉ
"በክፉ መንገድ አታድርጉ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የሙት ልጅ
ወላጅ የሌለው ልጅ

ንጹህ ደም... አታፍስሱ
እዚህ ስፍራ "ደም...ማፍሰስ" የተያያዘው ከግድያ ጋር ነው፣ "ደም" የሚያመለክተው የተገደሉ የሰዎችን ነው። "ንጹሃን ሰዎችን... አትግደሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

በዚህ ስፍራ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እየሩሳሌም ወይም 2) መላው የይሁዳ አገር። ይህ ሰዎችን በሌላ ስፍራዎች መግደል መልካም ነው የሚል ትርጉም አይሰጥም።

Jeremiah 22:4

በዳዊት ዙፋን ላይ የሚቀመጡ ነገሥታት
"ዙፋን" የሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሚያመለክተው ዳዊት የነበረውን አይነት ንጉሣዊ ስልጣን ነው። "በፊታቸው እንደ ዳዊት የሚመሩ ነገሥታት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የዚህ ቤት በሮች
ይህ ወደ ቤተመንግሥቱ አደባባይ የሚያስገቡ በሮችን ያመለክታል

በሰረገሎች እና ፈረሶች የሚሄዱ
ይህ ሀረግ ንጉሦቹን እንደ ሀያል እና ባለጸጋ የሚገልጽ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ፣ የእርሱ አገልጋዮች፣ እና የእርሱ ሰዎች/ህዝብ
ይህ ዐረፍተ ነገር ሀያል እና ባለጸጋ የሚሆኑትን በሙሉ ይዘረዝራል። ይህ ይበልጥ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "እርሱ፣ የእርሱ አገልጋዮች፣ እና የእርሱ ህዝብ በሰረገላ እና በፈረሶች ወደ ቤተ መንግሥት ይገባሉ። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ ባትሰሙ
"ትኩረት አንሰጥም ብትሉ" ወይም "እናንተ ባትታዘዙ"

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ንጉሣዊ ቤት
እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ በተለይ የሚያመለክተው ንጉሣዊ ቤተመንግስትን ነው።

Jeremiah 22:6

የይሁዳ ንጉሥ ቤት
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ የሚያመለክተው ንጉሡ የሚኖርበትን ንጉሣዊ ቤተ መንግሥት ወይም 2) "ቤት" በቤቱ ለሚኖሩ የይሁዳ ነገሥታት ንጉሳዊ ዝርያ ላላቸው ቤተሰቦች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። "የይሁዳ ንጉሣዊ ስርወ መንግሥት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ እንደ ገለዓድ፣ ወይም እንደ ሊባኖስ ከፍተኛ ስፍራ ነህ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "አንተ እንደ ገለዓድ ወይም እንደ ሊባኖስ ጫፍ ውብ ነህ" ወይም 2) "ገለዓድ ወይም የሊባኖስ ጫፍ እንደሚሰጠኝ ያህል ደስታ ትሰጠኛለህ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ምድረበዳነት እለውጥሃለሁ/ምድረበዳ አደርግሃለሁ
አስቀድሞ ውብ የነበረው ጠፍ እና በረሃ እንደሚሆን ተነገረ። "እንደ በረሃ ባዶ ስፍራ እንድትሆን አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አጥፊዎችን በአንተ ላይ አስነሳለሁ
"አንተን እንዲያጠቁ ሰራዊት መርጫለሁ"

ምርጥ የሆኑት ጥዶችህ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የቤተመንግሥቱ አምዶች ወይም 2) የንጉሣዊ ቤተሰብ መሪ የሆኑ ወንዶች። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እሳት ይጣላሉ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የቤተ መንግሥቱን አምዶች የሚያቃጥል እሳት ወይም 2) የንጉሣዊ ቤተሰቦች ጥፋት የተገለጸው በእሳት እንደሚቃጠሉ ተገርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 22:8

ከዚያም የብዙ አገራት ህዝቦች በዚህች ከተማ ውስጥ ያልፋሉ
እዚህ ስፍራ "ህዝቦች" የሚለው የሚያመለክተው ከእነዚያ አገራት በከተማይቱ የሚያልፉትን ሰዎች ነው። "ከዚያም ከተለያዩ አገሮች ብዙ ህዝብ በዚህች ከተማ ውስጥ ያልፋሉ" (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ወድቀው እየሰገዱ ሌሎችን አማልዕክት አመለኩ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። "ወድቀው እየሰገዱ" የሚለው የሚገልጸው ሰዎቹ ሲያመልኩ ያላቸውን አቋም ነው። "ሌሎችን አማልክትን አመለኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም እና ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 22:10

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ የይሁዳን ንጉሥ ከመናገር ዞር ብሎ ጠቅላላ ህዝቡን መናገር ጀመረ።

የሞተው
ይህ ነጠላ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተውም የተገደለውን ንጉሥ ኢዮስያስን ነው።

የሸሸው እርሱ
ይህ የሚያመለክተው ወደ ግብጽ የተሰደደውን ንጉሥ ኢዮአካዝን ነው።

በፍጹም ተመልሶ የትውልድ አገሩን አያይም
"በፍጹም ተመልሶ ዳግም የእስራኤልን ምድር አያይም" ወይም "በፍጹም ዳግም የትውልድ አገሩን አያይም"

Jeremiah 22:11

ኢዮአካዝ
ይህ ስም በዕብራይስጥ "ሰሎ፣" ነው፣ ነገር ግን ይበልጥ የሚታወቀው ኢዮአካዝ በሚለው ነው።

በአባቱ በኢዮስያስ ምትክ ንጉሥ ሆኖ ያገለገለው
"አባቱ ኢዮስያስ ሲሞት በምትኩ የነገሰው"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Jeremiah 22:13

ቤቱን የገነባው እርሱ...እንዲህ ይላል
እነዚህ የሚያመለክቱት አዮአቄምን ነው።

ቤቱን በግፍ፣ የላይኛውን ክፍሎች/ሰገነት በፍትህ አልባነት የሰራው
"ግፍ" እና "ፍትህ አልባነት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው የተደገሙት ትኩረት ለመስጠት ሲሆን እንደ ድርጊቶች ሊገለጽ ይችላል። "ቤቱን እና የላይኛውን ክፍሎች/ሰገነቱን ለመስራት ሰዎችን በፍትህ አልባነት አስገደደ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

ቤቱ
"ቤት" የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። በዚህ ሁኔታ ይህ ንጉሥ ኢዮአቄምን እና ቤተሰቡን ያመለክታል። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በሰገነቱ ላይ ሰፊ ክፍሎች ያሉት ትልቅ ቤት... ሰፋፊ መሰወኮቶች ...ጥድ
እነዚህ ባህሪያት ሁሉም በጣም ውድ የሆነን ቤት ይገልጻሉ።

Jeremiah 22:15

የጥድ ሳንቃ እንዲኖርህ የፈለከው ይህ መልካም ንጉሥ የሚያደርግህ ሆኖ ነውን?
ያህዌ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠይቀው ኢዮአቄምን ስለ ውድ ቤተመንግሥቱ ለመገሰጽ ነው። "ከጥድ የተሰራ ቤተመንግሥት መልካም ንጉሥ አያደርግህም።" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

አባትህም አልበላም አልጠጣምን.... ይህን በማድረጉ ከጽድቅ ጎደለን?
ያህዌ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠይቀው ኢዮአቄምን ስለ አባቱ ስለ ንጉሥ ኢዮስያስ አርአያነት ሊያስታውሰው ነው። "አባትህ ንጉሥ ኢዮስያስ፣ መልካም ህይወት ኖሯል፣ ሆኖም...ይህ ጽድቅ ከማድረግ አላገደውም።" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ፍትህን እና ጽድቅን አደረገ
እነዚህ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ረቂቅ ስሞች የተደገሙ ትኩረት ለማድረግ ሲሆን እንደ ድርጊቶች ተደርገው ሊጻፉ ይችላሉ። "በፍትሃዊነት እና በትክክል አደረገ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 22:17

ሌሎችን በማጥፋትህ... ከጭንቀት በስተቀር በዐይኖችህን እና በልብህ ምንም አይኖርም
እዚህ ስፍራ "ዐይኖች" የሚለው ማየት ለሚለው ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሲሆን "ልብ" የሚለው ለማሰብ ሜቶኖሚ/ ነው። "ሌሎችን ከማጥፋት ... በስተቀር በፍጹም ምንም ነገር አታይም ወይም አታስብም" ወይም "የምትመለከተው እና የታስበው ሁሉ ሌሎችን ስለ ምታታልልበት መንገድ ንጹህ ደም የምታፈስበትን፣ ደግሞም ሌሎችን የምትጨቁንበትን እና የምታጠፋበትን መንገዶች ነው" በሚሉት ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ተገቢያልሆነ ትርፍ
ይህ በማታለል ወይም ተገቢያልሆኑ መንገዶችን በመጠቀም ገንዘብ ማግኘት ነው።

የንጹሃንን ድም ማፍሰስ
እዚህ ስፍራ "ድም...ማፍሰስ" የሚለው የተያያዘው ከግድያ ጋር ነው፤ "ደም" የሚያመለክተው የተገደሉትን ሰዎች ነው። "የዋህ ሰዎችን መግደል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

ሌሎችን ማጥፋት
"ገንዘብ ለማግኘት በሌሎች ላይ የሃይል ድርጊት መፈጸም"

ለእርሱ አያለቅሱለትም
በቁጥር 18 ላይ፣ ያህዌ በቀጥታ ለኢዮአቄም መናገሩን አቁሞ ለሌሎች ሰዎች መናገር ይጀምራል። እዚህ ስፍራ "ለቅሶ" የሚለው የሚያመለክተው በኢዮአቄም ሞት ማዘንን ነው። "ኢዮአቄም በሚሞትበት ጊዜ አያለቅሱለትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

አህያ እንደሚቀበር ይቀበራል፤ ጎትተው አውትተው ይጥሉታል
የኢዮአቄም ቀብር የተገለጸው ሰዎች አህያ በሚቀብሩበት መንገድ እንደሚደረግ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በድኑን የአህያ በድን በሚቀብሩበት መንገድ ይቀብራሉ፤ እየጎተቱ ወስደው ይጥሉታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 22:20

አጠቃላይ መረጃ፡
እዚህ ስፍራ ያህዌ ለኢየሩሳሌም ሰዎች፣ እንደሚጠፉ እየተናገረ ይመስላል።

ድምጻችሁን አንሱ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር መጮህን ያመለክታል። በዚህ ሁኔታ፣ በሀዘን እያለቀሱ ነው። "ጩሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የዓባሪም ተራሮች
በእየሩሳሌም ደቡብ ምስራቅ የሚገኝ የተራራ ሰንሰለት (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰላም በነበርክበት ጊዜ ከአንተ ጋር ተነጋግሬያለሁ
"መልካም ታደርግ በነበረበት ጊዜ ከአንተ ጋር ተነጋግሬያለሁ"

ልምድህ ይህ ነበር
"የአኗኗርህ መንገድ እንደዚህ ነበር"

ድምጼን አልሰማህም
መስማት ለመታዘዝ ሜቶኖሚ/ ነው። "አንተ እኔን አልታዘዝክም" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 22:22

ነፋስ እረኞችሽን ሁሉ ነድቶ ይወስዳቸዋል
የህ ቃላትን በመደጋገም የሚደረግ ገለጻ ነው - ያህዌ "እረኛ" የሚለውን ሃሳብ በተለያዩ ሁለት መንገዶች ተጠቅሞበታል። እዚህ ስፍራ "እረኞች" የሚለው ለእየሩሳሌም መሪዎች የዋለ ዘይቤ ነው፣ እናም ነፋስ "ነድቶ" ይወስዳቸዋል። ነፋስ ያህዌን ይወክላል። "እኔ መሪዎችሽን ነፋስ ነድቶ የወሰዳቸው ይመስል ጠርጌ እወስዳቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወደ ምርዶ ይወሰዳሉ
"ምርኮኛ ይሆናሉ" ወይም "በስደት ይሄዳሉ"

አንተ በ'ሊባኖስ' የኖርክ ቤትህን በጥድ ቤት የሰራህ
ያህዌ ንጉሣዊውን ቤተመንግሥት እንደ 'ሊባኖስ' እና 'የጥድ ቤት' የገለጸው በብዙ ጥድ የተሰራ በመሆኑ ነው። "አንተ በሊበሰኖስ ጥድ በተሰራ በቤተ መንግሥት የምትኖር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ በ ...የምትኖር
ይህ "አንተ" የሚለው ተውላጠ ስም ነጠላ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተው ንጉሡን ነው። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)

አንተ እንዴት ታዝናለህ
የዕብራይስጡ ትርጉም ግልጽ አይደለም። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "እነርሱ እጅግ ለአንተ ያዝናሉ" ወይም 2) "አንተ ታላቅ የጭንቀት ድምጽ ታሰማለህ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በወሊድ ላይ እንደምትገኝ ሴት የምጥ ስቃይ ሲደርስብህ
ጠላቶቹ ሲያሸንፉት ንጉሡ የሚሰማው ስቃይ ሴት ልጅ ስትወልድ እንደሚሰማት ስቃይ ጠንካራ ይሆናል። "ሴት በምጥ ሰአት እንደሚደርስባት ያለ ስቃይ በሚደርስብህ ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 22:24

እኔ ህያው እንደሆንኩ
"በእርግጥ እኔ ህያው እንደሆንኩ።"ያህዌ ይህንን አገላለጽ የተጠቀመው እርሱ ቀጥሎ የሚናገረው በእርግጥ እውነት ለመሆኑን ለማሳየት ነው" ይህ ጸና መሃላ የሚደረግበት መንገድ ነው። "እኔ በህያውነቴ እምላለሁ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ምንም እንኳን አንተ... የቀኝ እጄ ማህተም ብትሆንም
ያህዌ ኢኮንያንን የእጁ ቀለበት ሊሆን ይችል እንደነበር ይነግረዋል። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በቀኝ እጄ ያለው ማህተም
የቀለበት ማህተም አንድ ንጉሥ በመዛግብት ላይ የስልጣን ማህተሙን ለማሳረፍ ይገለገልበት ነበር። ስለዚህም የቀለበት ማህተም የአገዛዝ ስልጣንን ይወክላል። ቀኝ እጅም ደግሞ የመግዛት ስልጣንን ይወክላል። "ንግሥናዬን ስልጣን የሚያመለክተው በቀኝ እጄ ያለው የቀለበት ማህተም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ እጥልሃለሁ
"እኔ ከእጄ እጥልሃለሁ" ወይም "እኔ በፍጥነት ከእጄ እጥልሃለሁ"ህይወትህን ለሚፈልጓት አሳልፌ ሰጥቼሃለሁ ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ህይወትህን የሚፈልጓት እንዲማርኩህ አገርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ለ...እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሚወክለው ሀይል እና ቁጥጥርን ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ህይወትህ ለሚፈልጉ
ይህ ሀረግ የሚወክለው አንድን ሰው ለመግደል መፈለግን ወይም መሞከርን ነው። ይህ ሀረግ በኤርምያስ 11:21 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "አንተን ለመግደል የሚሞክሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 22:27

ሊመለሱባት የሚፈልጉት ይህች ምድር
ይህ የሚያመለክተው የይሁዳን ምድር ነው።

ይህ የተናቀ እና የተሰበረ ዕቃ/ገንቦ ነውን?... አታውቅምን?
በቁጥር 28 ላይ የተናጋሪው ማን እንደሆነ ግልጽ አይደለም።

ይህ የተናቀ እና የተሰበረ ዕቃ/ገንቦ ነውን? ይህ ኢኮንያን የተባለ ሰው ማንንም ደስ የማያሰኝ ገንቦ ነውን?
ኢኮንያን የተገለጸው አንዳች ጥቅም እንደማይሰጥ ገንቦ እና በማንም እንደማይወደድ ሰው ተደርጎ ነው። ጥያቄዎቹ የሚያጎሉት ምንም ዋጋ ወይም ወዳጅ እንደሌለው ነው። "ኢኮንያን የተሰበረ ዕቃ ያህል ዋጋ የሌለው እና በእርሱ ማንም ደስ የማይሰኝበት ሰው ነው።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

እነርሱን አውጥታችሁ ጣሏቸው
ኢኮንያን እና የእርሱ ትውልዶች የተገለጹት ከእቃ ወጥቶ እንደሚጣል ቆሻሻ ወደ ሌላ አገር እንደተጣሉ ተደርገው ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 22:29

ምድር፣ ምድር፣ ምድር
ያህዌ መልዕክቱን ለምድሪቱ ሰዎች ሁሉ የተናገረው የምኖሩባትን ምድር በመጣራት ነው። ርዕሱ የተደጋገመው ለመልዕክቱ ትኩረት ለመስጠት ነው። (ቃለ አጋኖ የሚለውን ይመልከቱ)

ልጅ አልባ ይሆናል
ኢኮንያን በርካታ ልጆች ነበሩት። ስለዚህ የዚህ ሀረግ ትርጉም ልጆች የሌሉት ተደርጎ ይቆጠራል ማለት ነው። ልጆቹ በእርሱ ስፍራ ተክተውት አልነገሡም። "አንዳች ልጅ እንደሌለው ይሆናል" (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በዳዊት ዙፋን ላይ መቀመጥ
በዙፋን ላይ መቀመጥ በንግሥና መግዛት ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "መንገሥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 23

1 "የማሰማርያዬን በጎች ለሚያጠፉና ለሚበትኑ እረኞች ወዮላቸው! ይላል እግዚአብሔር።" 2 ስለዚህ፣ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለሚጠብቁ
እረኞች እንዲህ ይላል፣ "በጎቼን በትናችኋል ደግሞም አባርራችኋቸዋል። በጭራሽ አልተንከባከባችኋቸውም። ይህንን እወቁ! ለሥራችሁ ክፋት መልሼ
እከፍላችኋለሁ፣ ይላል እግዚአብሔር 3 እኔ ራሴ የመንጋዬን ቅሬታ ካባረርኋቸው ምድር ሁሉ እሰበስባለሁ፣ ፍሬያማ ወደሚሆኑበትና ወደሚበዙበት ወደ
መሠማሪያቸው እመልሳቸዋለሁ። 4 ከዚያም ከእንግዲህ ወዲህ እንዳይፈሩና እንዳይደነግጡ የሚጠብቋቸውን እረኞች አስነሣላቸዋለሁ። ከእነርሱ አንዳቸውም
አይጐድሉም፣ ይላል እግዚአብሔር። 5 ተመልከቱ፣ ለዳዊት ጻድቅ ቅርንጫፍን የማስነሣበት ዘመን ይመጣል፣ ይላል እግዚአብሔር። እርሱም እንደ ንጉሥ
ይገዛል፤ ብልፅግናን ያመጣል፣ በምድሪቱም ላይ ፍትህንና ጽድቅን ይፈጽማል። 6 በዘመኑም ይሁዳ ይድናል፣ እስራኤልም በአስተማማኝ ደህንነት ይቀመጣል።
የሚጠራበትም ስም፦ እግዚአብሔር ጽድቃችን ነው ተብሎ ነው። 7 ስለዚህ፣ ተመልከቱ፣ ከእንግዲህ 'የእስራኤልን ልጆች ከግብጽ ምድር ያወጣ ሕያው
እግዚአብሔርን!' የማይባልበት ዘመን ይመጣል፣ ይላል እግዚአብሔር። 8 ይልቊን፣ 'የእስራኤልን ቤት የዘር-ሐረግ ከሰሜን ምድርና ከተሰደዱባቸው ምድሮች
ሁሉ ያወጣና የመራ ሕያው እግዚአብሔርን!' ይባላል፤ እነርሱም በገዛ ራሳቸው ምድር ይቀመጣሉ።" 9 ስለ ነቢያት፣ ልቤ በውስጤ ተሰብሮአል፣ አጥንቶቼም
ሁሉ ታውከዋል። ከእግዚአብሔር እና ከቅዱስ ቃሉም የተነሣ እንደ ሰካራም ሰው፣ የወይን ጠጅ እንዳሸነፈውም ሆኛለሁ። 10 ምድር በአመንዝሮች ተሞልታለችና።
ከዚህ መርገም የተነሣ ምድር አለቀሰች። የምድረ በዳ ማሰማርያዎች ደርቀዋል። የእነዚህ ነብያት አካሄድ ክፉ ነው፤ ኃይላቸውም በትክክለኛው መንገድ ጥቅም
ላይ አልዋለም። 11 "ነብያትና ካህናትም ረክሰዋል። እንደውም፣ በቤቴ ውስጥ ክፋታቸውን አግኝቻለሁ! ይላል እግዚአብሔር። 12 ስለዚህ መንገዳቸው
በጨለማ እንዳለች ድጥ ስፍራ ትሆንባቸዋለች። እነርሱም ይገፈተሩበታል። በውስጧም ይወድቁባታል። እኔም በምቀጣቸው ዓመት ክፉ ነገርን እልክባቸዋለሁ፣
ይላል እግዚአብሔር። 13 በሰማርያ ነቢያት ላይ የሚያስቀይም ነገርን አይቻለሁ። በበኣል ትንቢት ይናገራሉ፣ ደግሞም ሕዝቤንም እስራኤልን ያስታሉ። 14
በኢየሩሳሌምም ነቢያት ላይ የሚያስደነግጥ ነገሮችን አይቻለሁ፦ ያመነዝራሉ ደግሞም በሐሰት ይመላለሳሉ። የክፉ አድራጊዎችን እጅ ያበረታሉ፤ ማንም ከክፋቱ
አልተመለሰም። ሁሉም እንደ ሰዶም ነዋሪዎቿም እንደ ገሞራ ሆኑብኝ!" 15 ስለዚህ ነብያትን በተመለከተ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "ተመልከቱ፣
ከኢየሩሳሌም ነቢያት ዘንድ ርኩሰት በምድር ሁሉ ላይ ወጥቶአልና እሬትን አበላቸዋለሁ የተመረዘንም ውኃ አጠጣቸዋለሁ።" 16 የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር
እንዲህ ይላል፣ "ትንቢት የሚናገሩላችሁን የነቢያትን ቃል አትሰሙ። ሐሰተኝነትን ያስተምሩአችኋል! ከእግዚአብሔር አፍ ሳይሆን ከገዛ አሳባቸው የወጣውን ራእይ
ይናገራሉ። 17 ያለማቋረጥ ለሚንቁኝ እንዲህ ይላሉ፣ 'እግዚአብሔር ሰላም ይሆንላችኋል ብሎአል።' በገዛ ራሱ የልብ እልከኝነት ለሚሄድ ሁሉ፣ 'ክፉ ነገር
አያገኛችሁም።' ይላሉ። 18 ይሁን እንጂ ቃሉን ያይና ይሰማ ዘንድ በእግዚአብሔር ምክር የቆመ ማን ነው? ለቃሉ አትኩሮት ሰጥቶ የሰማ ያደመጠስ ማን ነው?
19 ተመልከቱ፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ እየመጣ ያለ ዐውሎ ነፋስ አለ! የእርሱም ቊጣና የሚገለባብጥ ዐውሎ ነፍስ ወጥቶአል። በዓመፀኞች ራስ ላይ
ይገለባበጣል። 20 የእግዚአብሔር ቊጣ የልቡን አሳብ ሠርቶ እስኪፈጽም ድረስ አይመለስም። በመጨረሻው ዘመን፣ ትገነዘቡታላችሁ። 21 እነዚህን ነብያት እኔ
አልላክኋቸውም። በድንገት ተገኙ። ምንም አልነገርኳቸውም፣ ነገር ግን እንደዚያም ሆኖ ትንቢትን ተናገሩ። 22 በምክሬ ግን ቆመው ቢሆን ኖሮ፣ ለሕዝቤ ቃሌን
ባሰሙ ነበር፤ ከክፉም ቃሎቻቸው እንዲሁም ከብልሹ ሥራቸው በመለሱአቸው ነበር። 23 እኔ የቅርብ አምላክ ብቻ ነኝ ደግሞም የራቀ አምላክ አይደለሁም?
ይላል እግዚአብሔር። 24 ሰው ላየው እንዳልችል በስውር ሊሸሸግ ይችላልን? ሰማይንና ምድርንስ አልሞላምን? ይላል እግዚአብሔር። 25 በስሜ ሐሰትን
የሚናገሩት የነብያት ያሉትን ነገር ሰምቻለሁ። እነርሱም 'ህልም አልሜ ነበር! ህልም አልሜ ነበር!' ብለዋል። 26 ሐሰትን ከአሳባቸው በሚተነብዩ፣ የልባቸውንም
ማታለል በሚተነብዩ ነቢያት ይህ የሚቀጥለው እስከ መቼ ነው? 27 በሚናገሯቸው ሕልሞች ሕዝቤ ስሜን እንዲረሳ ለማድረግ ያቅዳሉ፣ እያንዳንዱ ለጎረቤቱ
ልክ አባቶቻቸው ለበኣል ሲሉ ስሜን እንደ ረሱ ያደርጋሉ። 28 የሚያልም ነቢይ ሕልሙን ይናገር። ነገር ግን ቃሌን የነገርኩት፣ ቃሌን በእውነተኝነት ይናገር። ገለባ
ከስንዴ ጋር ምን አለው? ይላል እግዚአብሔር። 29 ቃሌ እንደ እሳት፣ ድንጋዩም እንደሚያደቅቅ መዶሻ አይደለችምን? ይላል እግዚአብሔር። 30 ስለዚህ፣
ተመልከቱ፣ እኔ ቃልን ከሌላኛው ሰው ሰርቆ ቃሉ ከእኔ ዘንድ መጥቷል በሚሉት ነብያት ላይ ነኝ፣ ይላል እግዚአብሔር። 31 ተመልከቱ፣ ትንቢትን ለማወጅ
ምላሳቸውን በሚጠቀሙት ነብያት ላይ ነኝ፣ ይላል እግዚአብሔር። 32 ተመልከቱ፣ በሐሰት በሚያልሙ፣ ከዚያም በሚናገሩትና በዚህም መልኩ በሐሰታቸውና
በትምክህታቸውም ሕዝቤን በሚያስቱ በነቢያት ላይ ነኝ፣ ይላል እግዚአብሔር። እኔም አልላክኋቸውምና ትእዛዛትንም አልሰጠኋቸውምና በእነርሱ ላይ ነኝ።
ስለዚህም ለዚህ ሕዝብ በእርግጥም አይጠቅሟቸውም ይላል እግዚአብሔር። 33 ይህ ሕዝብ ወይም ነቢይ ወይም ካህን፣ 'የእግዚአብሔር ዐዋጅ ምንድር ነው?'
ብለው ቢጠይቁህ፣ 'እናንተን ትቻችኋለሁና የምን ዐዋጅ ነው?' ይላል እግዚአብሔር ልትላቸው ይገባል። 34 'የእግዚአብሔር ዐዋጅ ይህ ነው፣' የሚሉትን
ነብያትን፣ ካህናትን እና ሕዝቡን በተመለከተ፣ ያን ሰውና ቤቱን እቀጣለሁ። 35 እያንዳንዱ ሰው ለጎረቤቱ፣ እንዲሁም እያንዳንዱ ሰው ለወንድሙ፣ 'እግዚአብሔር
የመለሰው ምንድር ነው?' ደግሞስ 'እግዚአብሔር ምን ዐወጀ?' ማለትህን ቀጥል። 36 ከእያንዳንዱ ሰው የሆነው እያንዳንዱ ዐዋጅ የገዛ ራሱ መልእክት
ይሆንበታልና፣ እንዲሁም የሕያው እግዚአብሔርን ቃል ለውጣችኋልና፣ ስለ እግዚአብሔር ዐዋጅ ከእንግዲህ ልትናገሩ አይገባችሁም። 37 ለነቢዩ የምትጠይቀው
ይህንን ነው፣ 'እግዚአብሔር ምን መለሰልህ? እግዚአብሔር ምን ዐወጀ?' 38 ከዚያም፣ ከእግዚአብሔር የሆነውን ዐዋጅ ትናገራለህ፣ ነገር ግን እግዚአብሔር
ይህንን ይላል፣ "ይህ የእግዚአብሔር ዐዋጅ ነው አትበሉ።" ብዬ ትእዛዝን የላክሁባችሁ ቢሆንም፣ እናንተ ግን "የእግዚአብሔር ዐዋጅ ይኸውላችሁ፣" አላችሁ።
39 ስለዚህም፣ ተመልከቱ፣ አንሥቻችሁ ለእናንተና ለአባቶቻችሁ ከሰጠሁት ከተማ ጋር ከእኔ ዘንድ ልወረውራችሁ ነው። 40 ከዚያም የማይረሳ ዘላለማዊ
እፍረትን እና ስድብን አኖርባችኋለሁ።"

Jeremiah 23:1

አጠቃላይ መረጃ:
ከቁጥር 1-4 ፣ ያህዌ እስራኤልን እንደ መሰማሪያው፣ የእስራኤልን ህዝብ እንደ በጎቹ እንደዚሁም የእስራኤልን መሪዎች እንደ እረኞች አድርጎ ይገልጻል። እረኞች በጎችን የመጠበቅ ሃላፊነት አለባቸው፤ ነገር ግን መሪዎቹ ይህንን አያደርጉም ነበር። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መንጋዬን በተናችሁ ደግሞም ነዳችኋቸው
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ሁለተኛው በመጀመሪያው ሀረግ ላያ የለውን ሀሳብ ያጠናክራል። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 23:3

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ እስራኤል ህዝብ እነርሱ የእርሱ በጎች እንደሆኑና የእስራኤል መሪዎች ደግሞ የእርሱ እረኞች እንደሆኑ አድርጎ መናገሩን ቀጥሏል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ መሰማሪያቸው ስፍራ
ያህዌ የእስራኤልን ምድር የህዝቡ መልካም መሰማሪያ አድርጎ ይገልጻል። ይህ መልካም መሰማሪያ ፍላጎታቸውን የሚያገኙበት ለመሆኑ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ወደ መልካም መስክ" ወይም "የሚፈልጉትን ሁሉ የሚያገኙበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

ፍሬያማ ይሆናሉ ደግሞም ይበዛሉ
"መብዛት/መጨመር" የሚለው ቃል እንዴት "ፍሬያማ" እንደሚሆኑ ያብራራል። "እነርሱ በቁጥር በብዙ ይጨምራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ አስነሳለሁ
"እኔ እሾማለሁ"

ከእንግዲህ አይፈሩም ወይም አይጎዱም
"አይጎዱም"የሚለው ቃል አንድ ሰው እንዲፈሩ አድርጓቸዋል ማለት እና በመሰረቱ "ፍርሃት" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ከእንገዲህ ማንም አያስፈራቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከእነርሱ አንዳቸውም
"ከህዝቤ አንዱም"

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
x

Jeremiah 23:5

እዩ
ይህ ቃል ቀጥሎ ለሚነገረው አስደናቂ መረጃ ትኩረት ለመስጠት የሚያነቃ ነው።

ቀናት እየመጡ ነው
መጪው ጊዜ የተነገረው ወደ ተናጋሪው ወይም ወደ አድማጩ እንደሚመጣ አካል ተደርጎ ነው። "ጊዜው ይመጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ አስነሳለሁ
የዚህ ፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉም እርሱ ተከታይ ሚሆነውን ይሾማል ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የጽድቅ ቅርንጫፍ
ይህ የዳዊት ትውልድ የሆነ መጪው ንጉሥ የተገለጸው በዛፍ ላይ እንዳደገ ቅርንጫፍ ተደርጎ ነው። "ጻድቅ ትውልድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የጽድቅ ቅርንጫፍ
አንዳንድ ዘመናዊ ቅጂዎች ይህንን "የዙፋኑ ህጋዊ ወራሽ" በሚል ይተረጉሙታል።

በምድሪቱ ፍርድን እና ጽድቅን ያደርጋል
"ፍርድ" እና "ጽድቅ" የሚሉት ረቂቅ ስሞች እንደ ድርጊቶች ሊገለጹ ይችላሉ። "ሰዎች በፍትህ እና በጽድቅ እንዲያከናውኑ ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በምድሪቱ
እዚህ ስፍራ "ምድር" የሚያመለክተው በምድሪቱ የሚኖሩ ሰዎችን ነው። "በአገሪቱ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ይሁዳ ይድናል
እዚህ ስፍራ "ይሁዳ" የሚለው የሚያመለክተው የይሁዳ ህዝብ ነው። "የይሁዳ ሰዎች ይድናሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ይሁዳ ይድናል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እርሱ ይሁዳን ከጠላቶቻቸው ያድናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

እስራኤል በሰላም ይኖራል
እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚለው የሚያመለክተው የእስራኤልን ህዝብ ነው። "የእስራኤልን ህዝብ በሰላም ይኖራል" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ይጠራል
ይህ ንጉሡን ያመለክታል

ያህዌ ጽድቃችን ነው
"ጽድቅ" የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ድርጊት/ተግባር ሊገለጽ ይችላል። " ለእኛ ትክክል የሆነው የሚያደርግ፣ ያህዌ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 23:7

አጠቃላይ መረጃ:
እነዚህ ቁጥሮች ምንም እንኳን በኤርምያስ 16:14-15 ላይ ከሚገኘው ጋር ፍጹም አንድ ባይሆኑም በጣም ተመሳሳይ ናቸው። እነዚያ እንዴት እንደተተረጎሙ ያነጻጽሩ።

እዩ
ይህ ቃል ቀጥሎ ለሚነገረው አስደናቂ መረጃ ትኩረት ለመስጠት የሚያነቃ ነው።

ቀናት እየመጡ ነው
መጪው ጊዜ የተነገረው ወደ ተናጋሪው ወይም ወደ አድማጩ እንደሚመጣ አካል ተደርጎ ነው። "ጊዜው ይመጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ህያው እንደሆንኩ
"እኔ ያህዌ በእርግጥ ህያው እንደሆንኩ።" ሰዎች ይህንን አገላለጽ የሚጠቀሙት ቀጥሎ የሚናገሩት ነገር በእርግጥ እውነት መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ ጽኑ ቃል ኪዳን የማድረግ ምልክት ነው። ይህ በኤርምያስ 4:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።"እኔ በእርግጥ በክብሬ እምላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሚያመጣ እና የሚመልስ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ይሰጣሉ ደግሞም ሊጣመሩ ይችላሉ። "የሚመልስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ቤት
"ቤት" የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። በዚህ ሁኔታ ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን መንግሥት ነው። ይህ በኤርምያስ 3:18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እስራኤል" ወይም "የእስራኤል መንግሥት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሰሜናዊ ምድር እና እነርሱ የተሰደዱበት ምድር
ይህ የሚያመለክተው አስሩ ሰሜናዊ የእስራኤል ነገዶች ምርኮኛ የሆኑበትን እና በአካባቢያቸው በሚገኙ አገራት ውስጥ የተበተኑበትን መንገድ ነው።

ከዚያ በገዛ ምድራቸው ይኖራሉ
ይህ እስራኤላውያን ከየት እንደ ተበተኑ ያመለክታል። ይህ ይበልጥ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "ከዚያ ዳግም በገዛ ምድራቸው ይኖራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 23:9

አጠቃላይ መረጃ:
ከቁጥር 9-13 ድረስ ኤርምያስ የያህዌን መልዕክት ለሀሰተኛ ነቢያት እና ካህናት ያደርሳል። ኤርምያስ በቁጥር 9 ላይ ይናገራል፣ ነገር ግን በቁጥር 10 ላይ የሚገኘው ቃል የኤርምያስ ይሁን የያህዌ ግልጽ አይደለም።

ነቢያትን በሚመለከት፣ ልቤ በውስጤ ተሰብሯል፣ ደግሞም አጥንቶቼ ሁሉ ተንቀጥቅጠዋል
ነቢዩ ልቡ እንደተሰበረ እና አጥንቶቹ እንደ ተንቀጠቀጡ የሚናገረው ከሀሰተኛ ነቢያት የተነሳ የሚደርስበትን ቅጣት በመፍራት ነው። "ከሀሰተኛ ነቢያት የተነሳ በሚደርሰው ታላቅ ፍርሃት አድሮብኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ልቤ በውስጤ ተሰበረ
ፈሊጡ የሚናገረው ጥልቅ ሀዘንን ነው። "በጣም አዝኛለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አጥንቶቼ ሁሉ ተንቀጠቀጡ
እዚህ ስፍራ ምንቀጥቀጥ የተያያዘው ከፍርሃት ጋር ነው። "በጣም ፈርቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ሰከረ ሰው ሆንኩ፣ ወይን ጠጅ እንደተሞላ ሰው ሆንኩ
የሰከሩ/የጠጡ ሰዎች ራሳቸውን መቆጣጠር አይችሉም። እንደዚሁ ሁሉ፣ ኤርምያስ የያህዌን ቅጣት ከመፍራት የተነሳ ራሱን መቆጣጠር ተስኖታል። "እኔ እንደ ጠጣ ሰው ሆኛለሁ፣ ራሴን መቆጣጠር ተስኖኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሪቱ በምንዝርና ተሞልታለች
ምድሪቱ መያዣ ዕቃ ተደርጋ እና አመንዝሮች ደግሞ ዕቃውን ሙሉ ለሙሉ እንደሞሉ ቁሶች ተደርጎ ተገልጽዋል። ያም ማለት፣ በምድሪቱ የሚገኝ እያንዳንዱ ሰው ዘማዊ ሆኖ ሲገለጽ፣ ይህም በተራው በጣም ብዙ ሰዎች ዘማዊ እንደሆኑ አጋኖ ይገልጻል። (ግነት እና አጠቃላ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

አመንዝሮች
እዚህ ስፍራ ይህ ቃል ምናልበት ሁለት ስሜቶች አሉት። በቀጥታ ሲተረጎም በአገሪቱ የሚገኙ ወንዶች በገዛ ሚስቶቻቸው ላይ አመንዝረውባቸዋል ማለት ሲሆን፣ በዘይቤያዊ ትርጉሙ ጣኦት ለማምለክ ሲሉ ያህዌን ተተውታል የሚል ትርጉምም አለው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሪቱ ደረቀች
አንዳንድ ዘመናዊ ቅጂዎች ይህንን የዕብራይስጥ ሀረግ "ምድሪቱ አለቀሰች" በማለት ይተረጉሙታል።

የእነዚህ ነቢያት መንገዶች ክፉ ናቸው
የሀሰተኛ ነቢያት ክፉ ድርጊቶች የተገለጹት በክፉ መንገድ ላይ እንደተራመዱ ተደርጎ ነው። "እነዚህ ነቢያት ክፉ የሆኑ ነገሮችን እያደረጉ ነው" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 23:11

አያያዥ ሃሳብ:
ኤርምያስ ስለ ሀሰተኛ ነቢያት እና ካህናት በ23:9 ላይ የጀመረውን የያህዌ መልዕክት ማድረሱን ይቀጥላል።

ነቢያቱ እና ካህናቱ ተበክለዋል
ውሃ በቆሻሻ እንደሚበከል ነቢያቱ እና ካህናቱ በኃጢአት ረክሰዋል። "ነቢያቱ እና ካህናቱ ኃጢአተኞች ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ክፋታቸውን በቤቴ እንኳን አግኝቼዋለሁ!
"ክፋት" የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ድርጊት ለገለጽ ይችላል። "በቤተ መቅደሴ ጭምር ክፉ ድርጊት እንደፈጸሙ አውቃለሁ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በእኔ ቤት
ይህ የሚያመለክተው በእየሩሳሌም የሚገኘውን ቤተ መቅደስ ነው

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

መንገዳቸው በጨለማ ውስጥ በድጣማ ስፍራ እንደመሄድ ይሆናል
የድርጊታቸው አደገኛነት የተገለጸው በጨለማ በሚያድጥ የገደል ጠርዝ ተንሸራቶ እንደመውደቅ እና ራሳቸውን እንደመጉዳት ተደርጎ ነው። "ድርጊቶቻቸው በሚያድጥ ስፍራ በጨለማ እንደመራመድ ያልተረጋጉ እና አደገኞች ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በእነርሱ ላይ ጥፋት እልካለሁ
ያህዌ ጥፋትን የሚገልጸው ካህናቱን እና ሀሰተኛ ነቢያቱን እንዲያጠቃ እንደሚልከው ጠላት አድርጎ ነው። "ጥፋት እንዲሰርስባቸው አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ቅጣት በሚደርስባቸው አመት
"የሚቀጡበት ጊዜ ሲመጣ" ወይም "እኔ እነርሱን የምቀጣበት ጊዜ ሲደርስ"

Jeremiah 23:13

አያያዥ ሃሳብ፡
ኤርምያስ ስለ ሀሰተኛ ነቢያት እና ካህናት በ23፡9 ላይ የጀመረውን የያህዌ መልዕክት ማድረሱን ይቀጥላል።

ህዝቤን ከትክክለኛ መንገድ አውጥተዋል
የህዝቡ በሀሰተኛ ነቢያት መታለል የተነገረው በተሳሳተ መንገድ እንደ መምራት ተደርጎ ነው። "ህዝቤን እስራኤላውያንን አስተዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ዝሙት ፈጽመዋል
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ለሚስቶቻቸው ታማኞች አልነበሩም ወይም 2) ሌሎች አማልዕክትን ማምለካቸው እንደ መንፈሳዊ ዘማዊነት ተነግሯል

በማታለል ተራምደዋል
የዚህ ፈሊጥ ትርጉም የማታለል ህይወት ኖረዋል። "ከታማኝነት ውጭ መኖር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የክፉ አድራጊዎችን ክንዶች አበርትተዋል
እዚህ ስፍራ "እጆች" የሚለው የሚያመለክተው ጠቅላላውነ የአንድን ሰው ማንነት ነው። "ክፉ የሚያደርጉትን አበርትተዋል" ወይም "ክፉ የሚያደርጉ ሰዎችን አበረታተዋል" (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ማንም ከክፉ ድርጊቱ አልተመለሰም
ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊገለጽ ይችላል። "እያንዳንዱ ክፉ ስራው ቀጠለ"

ሁሉም እንደ ሰዶም ... እንደ ገሞራ ሆኑ
ሰዶም እና ገሞራ እግዚአብሔር ከሰማይ ሆኖ በእሳት ያጠፋቸው እጅግ ክፉ የሆኑ ከተሞች ነበሩ። "ሁሉም እንደ ሰዶም...እንደ ገሞራ ክፉ ሆኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
ብዙውን ጊዜ አርምያስ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ ሀሳብን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6፡6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

እዩ
እዚህ ስፍራ "እዩ" የሚለው ቃል አድማጩን ቀጥሎ ለሚነገረው ጠቃሚ መረጃ ትኩረት ለመስጠት የሚያነቃ ነው።

እኔ መራራ እንጨት/ሬት እንዲበሉ እና የተመረዘ ውሃ እንዲጠጡ አደርጋቸዋለሁ
መራራ እንጨት ለመብላት ደስ የማያሰኝ በጣም መራራ የሆነ ተክል። ይህ ሀረግ የሚገልጸው ያህዌ በክፉ ነቢያት ላይ የሚያመጣውን ቅጣት ነው። በተመሳሳይ መንገድ መራራው እንጨት መራራ ሲሆን ውሃመውም የተመረዘ ነበር፣ የያህዌም ቅጣት በክፉ ነቢያት ላይ እንዲህ ያለ ይሆናል።

ላደርገው ነው
"በቶሎ አደርገዋለሁ"

ከነቢያቱ መርዝ ወጥቷል
እዚህ ስፍራ የካህናቱ ክፉ ትምህርት እና ሀሰተኛ ትንቢቶች የተገለጹት ምድሪቱን እንደሚበክሉ ቆሻሻ ነገሮች ተደርገው ነው። "ከነቢያት ክፉ መጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ብክለት
የሚገኙበትን አየርን፣ ውሃን፣ ወይም አፈርን የሚበክሉ ቆሻሻ እና ጤናማ ያልሆኑ ነገሮች

Jeremiah 23:16

አያያዥ ሃሳብ፡
ኤርምያስ ስለ ሀሰተኛ ነቢያት እና ካህናት በ23፡9 ላይ የጀመረውን የያህዌ መልዕክት ማድረሱን ይቀጥላል።

የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
ብዙውን ጊዜ አርምያስ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ ሀሳብን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6፡6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

እነርሱ አሞኝተዋችኋል!
"ነቢያቱ እውነት ያልሆነውን ነገር እንድታምኑ አድርገዋል!"

ከአይምሯቸው የፈለቀውን ቅዠት
እዚህ ስፍራ "አይምሮ" የሚለው የሚያመለክተው የሀሰተኛ ነቢያትን ሀሳብ ነው። "እነርሱ የሚገምቱት ቅዠት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከያህዌ አፍ ያልሆነ
እዚህ ስፍራ "አፍ" የሚያመለክተው ያህዌ የተናገረውን ነው። "ያህዌ ያልተናገረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ሳያቋርጡ ይናገራሉ
"ሳያቋርጡ" የሚለው ቃል ይህ ሁሌም የሚናገሩት ነገር እንደሆነ አጋኖ በትኩረት ለመግለጽ ነው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

በእናንተ ላይ ጥፋት አይመጣም
"በእናንተ ላይ ምንም ክፉ ነገር አይደርስም"

ነገር ግን በያህዌ ምክር ላይ ማን ተገኝቷል?የእርሱን ቃል ማን አይቷል ማንስ ሰምቷል? ለእርሱ ቃል ማን ልቡን ሰጥቶ ሰምቷል?
እነዚህ ጥያቄዎች የዋሉት ካህናቱ እና ሀሰተኛ ነቢያቱ ያህዌን ባለመታዘዛቸው ለመገሰጽ ነው። "ማንም ያህዌን አላማከረውም። ማንም ያህዌ የተናገረውን አልተረዳም። ማንም የያህዌን ትዕዘዞች አልታዘዘም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ለእርሱ ቃላት ትኩረት ስጡ፣ አድምጡም
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ነገር ይገልጻሉ። በአንድ ሀረግ ሊጠቃላሉ ይችላሉ። "ሙሉ ለሙሉ ለቃሉን ታዘዙ"

Jeremiah 23:19

አያያዥ ሃሳብ፡
ኤርምያስ ስለ ሀሰተኛ ነቢያት እና ካህናት በ23፡9 ላይ የጀመረውን የያህዌ መልዕክት ማድረሱን ይቀጥላል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይህ ከያህዌ ዘንድ የመጣ መዕበል ነው...ቁጣው እየወጣ ነው... አውሎ ነፋስ በሃይል እየተሽከረከረ እየነፈሰ ነው
እነዚህ ሶስት ሀረጎች ሁሉም ታላቅ ማዕበልን ሲገልጹ ይህም የያህዌን ቁጣ የሚገልጽ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። ይህ በተነጻጻሪ ዘይቤ ሊገለጽ ይችላል። "የያህዌ ቁጣ እንደ ታላቅ ማዕበል፣ በቁጣ ወጥቶ እንደ አውሎ ነፋስ በሀይል እየተሽከረከረ እየመጣ ነው" (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

አውሎ ነፋስ
ሀይለኛ የነፋስ ማዕበል

በክፉዎች ራስ ላይ በሃይል እየተሽከረከረ የነፍሳል
የያህዌ ቁጣ የተነገረው በክፉዎች ዙሪያ እንደሚነፍስ አውሎነፋስ ነው። "እንደ አውሎ ነፋስ በክፉዎች ላይ እየመጣ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ እስኪሆን የያህዌ ቁጣ አይመለስም
የያህዌ ቁጣ የተነገረው በራሱ ህይወት እንዳለው እና ማድረግ እንደሚችል ተደርጎ ነው። "ይህ እስኪሆን የያህዌ ቁጣውን አይመልስም/አያቆምም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በልቡ ያለውን ፈቃዱን ይፈጽማል
እዚህ ስፍራ "የልብ ፈቃድ" የሚለው የሚያመለክተው ያህዌ እንዲሆኑ የሚፈልጋቸውን ነገሮች ነው። "ያቀደውን ቅጣት ሁሉ ፈጽሞ ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የኋልኛው ዘመን
"መጪው ጊዜ"

Jeremiah 23:21

አያያዥ ሃሳብ፡
ኤርምያስ ስለ ሀሰተኛ ነቢያት እና ካህናት በ23፡9 ላይ የጀመረውን የያህዌ መልዕክት ማድረሱን ይቀጥላል።

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ከቁጥር 21-40 ይናገራል፡፤

እነርሱ አሁንም ትንቢት ይናገራሉ
ሀሰተኛ ትንቢት መናገራቸው ግልጽ ነው። ይህ ይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ሆኖም የሀሰት ትንቢት ይናገራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ምክሬ ባለበት ቢቆሙ/ቢገኙ ኖሮ
ያህዌ እነዚህ ካህናት እና ሀሰተኛ ነቢያት የያህዌ ምክር በሚገኝበት በሰማይ ቢገኙ ምን ሊሆን ይችል እንደነበረ ይናገራል። ይህ መላምታዊ ሁኔታ ሊሆን የማይችል ነው። "በእውነት ሰምተውኝ ቢሆን ኖሮ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ የምገኝበት ምክር
በጥንቱ ዘመን፣ እግዚአብሔር በሰማይ ከመላዕክት ጋር ስብሰባ ያደርጋል ተብሎ ይታሰብ ነበር። ያህዌ የሚጠቅሰው ሰዎች ሊገኙበት የማይችሉትን እንደዚህ አይነቱን ስብሰባ ነው። ይህ በኤርምያስ 23:18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ከዚህ ዘወር ማለት
የዚህ ፈሊጥ ትርጉም እነርሱ እነዚህን ነገሮች ማድረግ ያቆማሉ ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 23:23

አያያዥ ሃሳብ፡
ያህዌ ስለ ሀሰተኛ ነቢያት እና ካህናት በ23፡9 ላይ የጀመረውን እና በኤርምያስ 23፡40 ላይ የሚጨርሰውን መልዕክቱን ማድረሱን ይቀጥላል።

እኔ የቅርብ አምላክ ብቻ ነኝን... የሩቅስ አምላክ አይደለሁምን?
ያህዌ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው ካህናቱ እና ሀሰተኛ ነቢያቱ እርሱ በሁሉም ስፍራ እንደሚገዛ አለማሰባቸውን ለመገሰጽ ነው። "እኔ እዚህ በእየሩሳሌም ውስጥ ብቻ የምገኝ አምላክ አይደለሁም... ነገር ግን እኔ በሁሉም ስፍራ እገኛለሁ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ልመለከተው በማልችለው ስፍራ ሊደበቅ የሚችል አለን?
ያህዌ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው ካህናቱ እና ሀሰተኛ ነቢያቱ እነርሱ የሚያደርጉት ክፉ ነገር እርሱ እንደማይመለከት አድርገው በማሰባቸው ሊገስጻቸው ነው። "ማንም እኔ ልመለከተው በማልችለው ስውር ስፍራ መደበቅ አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ሰማይንና ምድርን የሞላሁ አይደለሁምን?
ያህዌ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው እርሱ በሰማይ እና በምድር በሁሉም ስፍራ እንደሚገኝ ለማጉላት ነው። "እኔ በሰማይ እና በምድር በሁሉም ስፍራ እገኛለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 23:25

አያያዥ ሃሳብ፡
ያህዌ ስለ ሀሰተኛ ነቢያት እና ካህናት በ23፡9 ላይ የጀመረውን እና በኤርምያስ 23፡40 ላይ የሚጨርሰውን መልዕክቱን ማድረሱን ይቀጥላል።

በሀሰት ይተነብያሉ
"ማታለል" የሚለው ቃል በገላጭ ወይም ተውሳከ ግስ ሊገለጽ ይችላል። "የሚያታልሉ/ሀሰተኛ ነገሮችን እየተነበዩ" ወይም "በሀሰት/በማታለል እየተነበዩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በእኔ ስም/በስሜ
ይህ ሀረግ የሚያመለክተው በያህዌ ሀይል እና ስልጣን ወይም እንደ እርሱ ተወካይ መናገርን ነው። ይህ ሀረግ በኤርምያስ 14:14 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ህልም አለኝ!
ይህ ህልም ከእግዚአብሔር ነው ማለታቸው ነው። ይህ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ከያህዌ ዘንድ የሆነ/የመጣ ህልም አለኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከራሳቸው አይምሮ ሀሰትን የሚተነብዩ ነቢያት፣ እና በልባቸው ውስጥ ካለው ሽንገላ የሚተነብዩ ነቢያት ትንቢት እስከ መቼ ይቀጥላል?
ያህዌ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ነቢያቱ ይህንን ማድረጋቸውን መቀጠል እንደሌለባቸው ትኩረት ለመስጠት ነው።"ነቢያት ራሳቸው ያበጇቸውን

ሀሰተቶች ማወጃቸው መቀጠል የለበትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ከራሳቸው አይምሮ የሆነ የሀሰት ትንቢት... በልቦቻቸው ካለ ሸንገላ የሆነ ትንቢት
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው ሀሰተኛ ነቢያት ትንቢቶቻቸውን ራሳቸው እንደሚያበጇቸው ትኩረት ይሰጣሉ። "ከራሳቸው አይምሮ ብቻ የሚመነጩ ትንቢታዊ ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ስሜን ረሱ... ስሜን ረስተዋል
እዚህ ስፍራ "ስም" የሚለው ቃል በአጠቃላይ የያህዌን ማንነት ያመለክታል። "ህዝቤ እኔን ከማምለክ ይልቅ በኣልን እንደሚያመልክ አድርገዋል/ መርተውታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የበኣልን ስም በመምረጥ
እዚህ ስፍራ "የበኣል ስም" የሚያመለክተው በኣል የተባለውን ጣኦት ነው። "ህዝቤ እኔን ከማምለክ ይልቅ በኣልን እንዲያመልክ መርተውታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 23:28

አያያዥ ሃሳብ፡
ያህዌ ስለ ሀሰተኛ ነቢያት እና ካህናት በ23:9 ላይ የጀመረውን እና በኤርምያስ 23:40 ላይ የሚጨርሰውን መልዕክቱን ማድረሱን ይቀጥላል።

ገለባ ከፍሬ ጋር ምን ግንኙነት አለው?
ገለባ ገበሬዎች ዋጋ ያለውን ፍሬ ከለዩ በኋላ የሚቀረው ዋጋ የሌለው አገዳ ነው። ይህ ጥያቄ ትኩረት የሚሰጠው በሀሰተኛ መልዕክት እና ከያህዌ ዘንድ በሆነው መልክት መሃል ያለውን ልዩነት ነው። "ገለባ እና ፍሬ ሙሉ ለሙሉ የተለያዩ ሁለት ነገሮች ናቸው።" ወይም "ጥቅም የሌለው ገለባ በፍጹም ዋጋ እንዳለው ፍሬ አይደለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

ቃሌ እንደ እሳት አይደለምን?... አለትን ሰባብሮ እንደሚያደቅ መዶሻስ አይደለምን?
ያህዌ እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመው ቃሉ ከሰዎች ተራ ቃል እጅግ እንደሚበልጥ ትኩረት ለመስጠት ነው። በዚህ መንገድ የእርሱ ቃል እንደ እሳት ወይም መዶሻ ነው። "ቃሌ እንደ እሳት ሀያል ነው... ደግሞም አለትን ሰባበብሮ እንደሚያደቅ መዶሻ ሀይለኛ ነው።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ እቃወማለሁ
"እኔ ከዚህ በተቃራኒ ነኝ"

ከሌላ ሰው ቃላት ይሰርቃሉ
ይህ የሚያመለክተው ሀሰተኛ ነቢያት ሌቦች መሆናቸውን ነው። የራሳቸውን ሀሰተኛ መልዕክት ከማዘጋጀት እንኳን አልፈው እርስ በእርሳቸው መልዕክቶችን ያለፈቃድ እስኪሰራረቁ ድረስ እጅግ ክፉዎች ናቸው።

Jeremiah 23:31

አያያዥ ሃሳብ፡
ያህዌ ስለ ሀሰተኛ ነቢያት እና ካህናት በ23:9 ላይ የጀመረውን እና በኤርምያስ 23:40 ላይ የሚጨርሰውን መልዕክቱን ማድረሱን ይቀጥላል።

እዩ
ይህ ቃል ቀጥሎ ለሚነገረው አስደናቂ መረጃ ትኩረት ለመስጠት የሚያነቃ ነው። "ትኩረት ስጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

በነቢያት ላይ መነሳት
"ነቢያትን በመቃወም"

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ምላሶቻቸውን የሚጠቀሙ
እዚህ ስፍራ "ምላሶች" የሚለው የመናገርን ችሎታ የሚገልጽ ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በሀሰት የሚያልሙ
"ከእግዚአብሔር ዘንድ ህልም አለን የሚሉ፣ ነገር ግን ከእግዚአብህር ዘንድ ያልሆኑ ናቸው"

Jeremiah 23:33

አያያዥ ሃሳብ፡
ያህዌ ስለ ሀሰተኛ ነቢያት እና ካህናት በ23:9 ላይ የጀመረውን እና በኤርምያስ 23:40 ላይ የሚጨርሰውን መልዕክቱን ማድረሱን ይቀጥላል።

አጠቃላይ መረጃ፡
ከቁጥር 33-40 ድረስ "ሸክም" የሚለውን ቃል በመደጋገም የሚደረግ አገላለጽ አለ። አንዳንዴ "መልዕክተኛ" ማለት ሲሆን በሌላ ጊዜ "ለመሸከም ከባድ የሆነ ሸክም" ማለት ይሆናል። ከተቻለ ይህ የቃላት ድግግም አገላለጽ እንዳለ ሊጠበቅ ይገባዋል።

አንተን እጠይቅሃለሁ... አንተ እንዲህ ትላለህ
በእነዚህ ሁለት ሁኔታዎች "አንተ" የሚሉት ነጠላ ቁጥር ሲሆኑ ኤርምያስን ያመለክታሉ። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)

የያህዌ ሸክም ምንድን ነው?
እዚህ ስፍራ "ሸክም" ማለት ከያህዌ ዘንድ የሆነ መልዕክት ወይም ትንቢት ማለት ነው።

ሸክሙ እናንተ ናችሁ... እናንተን አስወግዳለሁ
እነዚህ "እናንተ" የሚሉት ሁለት ሁኔታዎች ብዙ ቁጥር ሲሆኑ የሚያመለክቱት ሀሰተኛ ነቢያትን እና ካህናትን ነው። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)

ሸክሙ እናንተ ናችሁ
እዚህ ስፍራ "ሸክም" ማለት ከባድ ሸክም ነው። ይህ ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ እነርሱ ያህዌን ያስቆጣሉ እርሱም ከእንግዲህ ከእነርሱ ጋር መሆን አይፈቅድም ማለት ነው። "እኔ እናንተን በመሸከም ያደከማችሁኝ ሸክሞች ናችሁ" በሚለው ወስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ ሸክም ነው
እዚህ ስፍራ "ሸክም" ከያህዌ ዘንድ የሆነ መልዕክት ወይም ትንቢት ነው።

የእርሱ ቤት/ቤቱ
እዚህ ስፍራ "ቤት" በውስጡ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። "የእርሱ ቤተሰብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 23:35

አያያዥ ሃሳብ፡
ያህዌ ስለ ሀሰተኛ ነቢያት እና ካህናት በ23፡9 ላይ የጀመረውን እና በኤርምያስ 23፡40 ላይ የሚጨርሰውን መልዕክቱን ማድረሱን ይቀጥላል።

አጠቃላይ መረጃ፡
ከቁጥር 33-40 ድረስ "ሸክም" የሚለውን ቃል በመደጋገም የሚደረግ አገላለጽ አለ። አንዳንዴ "መልዕክተኛ" ማለት ሲሆን በሌላ ጊዜ "ለመሸከም ከባድ የሆነ ሸክም" ማለት ይሆናል። ከተቻለ ይህ የቃላት ድግግም አገላለጽ እንዳለ ሊጠበቅ ይገባዋል።

እናነተ እንዲህ ማለታችሁን ትቀጥላላችሁ... ‘ያህዌ የተናገረው ምንድን ነው?'
ይህን ዐረፍተ ነገር መመዝገብ አስፈላጊ ይሆናል። "እያንዳንዱ ሰው ወዳጁን እና ወንድሙን ‘ያህዌ ምን ምላሽ ሰጠ?' ደግሞም ‘ያህዌ ምን ትዕዛዝ ሰጠ/ ምን አለ?'" ብሎ መጠየቁን ይቀጥላል።

ነገር ግን ከእንግዲህ በኋላ ‘ስለ ያህዌ ሸክም መናገር አይኖርባችሁም፣ ምክንያቱም ሸክሙ የእያንዳንዱ ሰው ቃል የራሱ ሸክም ነው፣ እናም
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሁለቱም "የሸክም" ሁኔታዎች ትርጉማቸው "መልዕክት" ማለት ነው። "ከእንግዲህ ህልማችሁን ‘የያህዌ ሸክም' ብላችሁ መጥራት የለባችሁም ምክንያቱም እነዚያ የእያንዳንዱ ሰው የራሱ ቃሎች ብቻ ናቸው፣ እናም" ወይም 2) የመጀመሪያው ‘ሸክም' የሚለው ትርጉም "መልዕክት" ማለት ሲሆን የሁለተኛው ትርጉም "ከባድ ሸክም" ማለት ነው። "ከእንግዲህ ‘ስለ ያህዌ መልዕክት' መናገር የለባችሁም ምክንያቱም እያንዳንዳችሁ የምትናገሯቸው ቃላት በዚህ መንገድ ‘ከባድ ሸክም' የሆኑ ናቸው።"

እናንተ የአምላካችንን ቃሎች... ገልብጣችኋል
አንድን ነበር "መገልበጥ" ያንን ነገር ማጣመም ወይም መልኩን ማበላሸት ነው። "እግዚአብሔር የተናገረውን ሳይሆን እናንተ ማለት የፈረጋችሁትን ለመናገር የሰራዊት ጌታ የህያው እግዚአብሔርን መልዕክት ቀይራችኋል"

Jeremiah 23:37

አያያዥ ሃሳብ፡
ያህዌ ስለ ሀሰተኛ ነቢያት እና ካህናት በ23፡9 ላይ የጀመረውን መልዕክት ያጠናቅቃል።

አጠቃላይ መረጃ፡
ከቁጥር 33-40 ድረስ "ሸክም" የሚለውን ቃል በመደጋገም የሚደረግ አገላለጽ አለ። አንዳንዴ "መልዕክተኛ" ማለት ሲሆን በሌላ ጊዜ "ለመሸከም ከባድ የሆነ ሸክም" ማለት ይሆናል። ከተቻለ ይህ የቃላት ድግግም አገላለጽ እንዳለ ሊጠበቅ ይገባዋል።

አንተ የምትናገረው ይህንን ነው
እዚህ ስፍራ "አንተ" የሚለው ነጠላ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተው ኤርምያስን ነው። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)

ነገር ግን እንዲህ ብትሉ... ምክንያቱም እንዲህ ብላችኋል...እኔ በምልካችሁ ጊዜ... እንዲህ አትሉም... እናንተን አነሳለሁ... እጥላችኋለሁ... መሳለቂያ አደርጋችኋለሁ
በእነዚህ ሁኔታዎች ሁሉ "እናንተ" የሚለው ብዙ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተው ካህናትን እና ሀሰተኛ ነቢያትን ነው። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)

ስለዚህ፣ እነሆ
"ስለዚህ ተጠንቀቁ" ይህ አንባቢው ቀጥሎ ለሚሆነው ልዩ ትኩረት እንዲሰጥ ያነቃዋል።

እኔ እናንተን አንስቼ ከእኔ አርቄ ልጥላችሁ ነው
ያህዌ የሚናገረው እነዚህን ካህናት እና ሀሰተኛ ነቢያት እንደሚጣል እቃ እንደሚጥላቸው እና ሩቅ ስፍራ ወደ ስደት እንደሚጥላቸው ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ለእናንተ የሰጠኋት ከተማ
ይህ እየሩሳሌምን ያመለክታል።

የማይረሳ ዘላለማዊ ሀፍረት እና ስድብ አድረግባችኋለሁ
"ለዘለዓለም በሚኖር በሀፍረት እሸፍናችኋለሁ፣ የማትረሱትን ስድብ አደርስባችኋለሁ" ወይም "ሰዎች ለዘለዓለም እንዲሳለቁባችሁ አደርጋለሁ። ሰዎች ውርደታችሁን በፍጹም አይረሱም።" "ያህዌ የካህናቱን እና የሀሰተኛ ነቢያቱን ውርደት የሚናገረው ሀፍረትን እና ስድብን እንደ ልብስ በላያቸው እንደሚደርብ አድርጎ ነው።

ያ አይረሳም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ያ ለዘለዓለም ይኖራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 24

1 እግዚአብሔር አንድ ነገር አሳየኝ። እነሆ፣ በእግዚአብሔር መቅደስ ፊት ሁለት ቅርጫት በለስ ተቀምጠው ነበር። (ይህ ራእይ የታየው የባቢሎን ንጉሥ
ናቡከደነፆር የይሁዳን ንጉሥ የኢዮአቄምን ልጅ ኢኮንያንን፣ የይሁዳንም አለቆች፣ ጠራቢዎችንና ብረት ሠራተኞችን ከኢየሩሳሌም ማርኮ ወደ ባቢሎን ካፈለሳቸው
በኋላ ነበር።) 2 በአንደኛው ቅርጫት አስቀድሞ እንደበሰለ በለስ የሚመስል እጅግ መልካም በለስ ነበረበት፤ ነገር ግን በሁለተኛው ቅርጫት ውስጥ ከክፋቱ
የተነሣ ይበላ ዘንድ የማይቻል እጅግ ክፉ በለስ ነበረበት። 3 እግዚአብሔርም፣ "ኤርምያስ ሆይ፣ ምንታያለህ?" አለኝ። እኔም፣ "በለስን። እጅግ መልካም የሆነ
በለስ፣ ከክፋቱም የተነሣ ይበላ ዘንድ የማይቻል እጅግ ክፉ የሆነ በለስ አያለሁ።" አልሁ። 4 የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፣ 5 "የእስራኤል
አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እንደዚህ እንደ መልካሙ በለስ፣ እንዲሁ ከዚህ ስፍራ ወደ ከለዳውያን ምድር የሰደድሁትን የይሁዳን ምርኮ ለጥቅማቸው
እመለከተዋለሁ። 6 ዓይኔንም ለመልካም በእነርሱ ላይ አደርጋለሁ፣ ወደዚህችም ምድር እመልሳቸዋለሁ። እገነባቸዋለሁ እንጂ አላፈርሳቸውም። እተክላቸዋለሁ፣
እንጂ አልነቅላቸውም። 7 ከዚያም፣ እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ የሚያውቅ ልብ እሰጣቸዋለሁ፣ እኔ እግዚአብሔር ነኝና። በፍጹምም ልባቸው ወደ እኔ
እንዲመለሱ፣ ሕዝብ ይሆኑኛል፣ እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ። 8 ነገር ግን ከክፋቱ የተነሣ ይበላ ዘንድ እንደማይቻል እንደ ክፉው በለስ፣ እንዲሁ የይሁዳን ንጉሥ
ሴዴቅያስን አለቆቹንም በዚህችም አገር የሚቀሩትን የኢየሩሳሌም ቅሬታ በግብጽም አገር የሚቀመጡትን እጥላቸዋለሁ፣ ይላል እግዚአብሔር። 9
በማሳድዳቸውም ስፍራ ሁሉ ለስድብና ለምሳሌ፣ ለማላገጫና ለእርግማን ይሆኑ ዘንድ በምድር መንግሥታት ሁሉ ለመበተን አሳልፌ እሰጣቸዋለሁ። 10
ለእነርሱና ለአባቶቻቸውም ከሰጠኋቸው ምድር እስኪጠፉ ድረስ በመካከላቸው ሰይፍንና ራብን፣ ቸነፈርንም እሰድዳለሁ።"

Jeremiah 24:1

እኔ
የዚህ ተውላጠ ስም ሁኔታዎች ሁሉ ኤርምያስን ያመለክታሉ

እነሆ
እዚህ ስፍራ "እነሆ" የሚለው ቃል የሚያሳየው ኤርምያስ አስደሳች የሆነ ነገር እንደተመለከተ ነው።

ይህ ራዕይ የተፈጸመው... እነርሱን ወደ ባቢሎን
ይህ የታሪኩ ክፍል የዋለው የተፈጸሙ ድርጊቶች የተፈጸሙበትን ታሪካዊ መረጃ ለመስጠት ነው። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

አናጺዎች
ነገሮችን ለመገንባት/ለማነጽ ችሎታ ያላቸው ሰዎች

ብረት ቀጥቃጮች
የተለያዩ የብረት ዕቃዎችን የሚሰሩ ሰዎች

ሊበሉ አይችሉም... አይበሉም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ማንም ሊበላቸው አይችልም... ማንም አይመገባቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 24:4

የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ፣ "ያህዌ
ይህ ፈሊጥ የዋለው ከያህዌ ዘንድ የተለየ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:4 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ መልዕክት ሰጠኝ። እንዲህ አለ፣ ‘ያህዌ" ወይም "ያህዌ ይህንን መልዕክት እንዲህ ሲል ተናገረኝ፦ ‘ያህዌ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳን ስደት ለእነርሱ ጥቅም ስል እመለከታለሁ
እዚህ ስፍራ "መመልከት" የሚለው ያህዌ ለእነርሱ ይጠነቀቃል የሚል ትርጉም አለው። "እኔ ለተሰደዱት ይሁዳ በመልካም ጥንቃቄ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

ልክ እንደ እነዚህ መልካም በለሶች
መልካሞቹ በለሶች የሚወክሉ ወደ ከለዳዊያን ምድር በስደት የሄዱትን አይሁዶች ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ዐይኖቼን ለመልካም በእነርሱ ላይ አደርጋለሁ
እዚህ ስፍራ "ዐይኖቼን አደርጋለሁ" ማለት እርሱ ያያቸዋል ማለት ነው። እነርሱን ማየት ለእነርሱ ጥንቃቄ ማድረግ ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "እኔ እባርካቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ መልሼ እሰበስባቸዋለሁ፣ አላፈርሳቸውም። እኔ እተክላቸዋለሁ፣ አልነቅላቸውም
እነዚህ ሁለት ዘይቤዎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ሁለተኛው የመጀመሪያውን ያጠናክራል። "በከለዳዊያን አገር እንዲበለጽጉ እረዳቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ መልሼ እሰበስባቸዋለሁ፣ አላፈርሳቸውም።
ያህዌ ስለ ስደተኞቹ በመልካም መሬት ላይ እንደሚተክላቸው እንጂ እንደማይነቅላቸው ተክሎች አድርጎ ይናገራል። "በምድሪቱ ላይ አንጻቸዋለሁ፣ እንጂ አላስወግዳቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔን እንዲያውቁኝ ልብ እሰጣቸዋለሁ
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚለው የሚያመለክተው የእነርሱን ፍላጎቶች ነው። "እኔን ማወቅ እንዲፈልጉ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በሙሉ ልባቸው ወደ እኔ ይመለሳሉ
እዚህ ስፍራ "ሙሉ ልባቸው" የሚለው "ሙሉ ለሙሉ" ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ሙሉ ለሙሉ ወደ እኔ ይመለሳሉ" ወይም "ያለመቆጠብ ወደ እኔ ይመለሳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 24:8

ነገር ግን ለመበላት እጅግ መጥፎ እንደሆኑት መጥፎ በለሶች
ይህ ተነጻጻሪ ዘይቤ በእየሩሳሌም ስላሉ ክፉ ባለስልጣናት ለመበላት እጅግ እንደ ተበላሹ እንደ መጥፎ በለሶች አድርጎ ይገልጻል። መጥፎ በለሶች አንዳች ጥቅም እንደሌላቸው ሁሉ፣ እነዚህ ያህዌን የማይከተሉ ሰዎችም ጥቅም የሌላቸው ናቸው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ አስፈሪ ነገር ወደ ጥፋት እለውጣቸዋለሁ... የተዋረዱ እና መነጋገሪያ፣ መነረጓጠጫ እና ለእርግማን አደርጋቸዋለሁ
እነዚህ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው፣ ያህዌ የእየሩሳሌምን ሰዎች እንዴት በጥብቅ እንደሚፈርድባቸው ትኩረት ይሰጣሉ። ሌሎች ሰዎች

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የደረሰባቸውን ሲመለከቱ ይፈራሉ። (ጥንድ ትርጉም እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

በእነርሱ ላይ ሰይፍ፣ ችጋር፣ እና መቅሰፍት እልክባቸዋለሁ
"በጦርነት፣ በችጋር እና በበሽታ አገድላቸዋለሁ"

ሰይፍ እሰዳለሁ
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" ጦርነትን እና የጠላትን ሰራዊቶች ያመለክታል። "እኔ የጠላትን ሰራዊት እልካለሁ" ወይም "ጦርነት እሰዳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሰይፍ፣ ችጋር፣ እና መቅሰፍት
እነዚህ ነገሮች የተነገሩት የእየሩሳሌምን ሰዎች ሊያጠቁ እንደሚችሉ ህይወት እንዳላቸው ነገሮች ተደርገው ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ከምድሪቱ ተደምስሰዋል
"አንዳቸውም በምድሪቱ አልቀሩም"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 25

1 በይሁዳ ንጉሥ በኢዮስያስ ልጅ በኢዮአቄም በአራተኛው ዓመት፣ በባቢሎን ንጉሥ በናቡከደነፆር በመጀመሪያው ዓመት፣ ስለ ይሁዳ ሕዝብ ሁሉ ወደ ኤርምያስ
የመጣው ቃል ይህ ነው። 2 ይህንም ቃል ነቢዩ ኤርምያስ ለይሁዳ ሕዝብ ሁሉና በኢየሩሳሌም ለሚኖሩ ሁሉ እንዲህ ሲል ተናገረ። 3 "ከይሁዳ ንጉሥ ከአሞጽ
ልጅ ከኢዮስያስ አሥራ ሦስተኛው ዓመት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ባሉት በእነዚህ በሀያ ሦስቱ ዓመታት፣ የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ ሲመጣ ነበር። እነግራችሁም
ነበር። እነግራችሁ ነበር፣ ነገር ግን አልሰማችሁም። 4 እግዚአብሔርም ባርያዎቹን ነቢያትን ሁሉ ወደ እናንተ ላከ። እነርሱም ለመውጣት ጉጉዎች ነበሩ፣ ነገር ግን
እናንተ አላደመጣችሁም ትኩረትም አልሰጣችሁትም። 5 እነዚህ ነብያት፣ 'እያንዳንዱ ሰው ከክፉ መንገዱና ከሥራችሁ ብልሹነት ተመለሱና እግዚአብሔር
ከጥንት ጊዜያት ጀምሮ ቋሚ ስጦታ አድርጎ ለእናንተና ለአባቶቻችሁ በሰጣችሁ ምድር ተቀመጡ። 6 ታመልኩአቸው፣ ትሰግዱላቸውም ዘንድ ሌሎችን አማልክት
አትከተሉ፣ ክፉም እንዳያደርግባችሁ በእጃችሁ ሥራ አታስቈጡኝ አለ። 7 ለእናንተ ጉዳት እንዲሆን በእጃችሁ ሥራ ታስቈጡኝ ዘንድ አልሰማችሁኝም፣ ይላል
እግዚአብሔር። 8 ስለዚህ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ 'ቃሌን አልሰማችሁምና፣ 9 ተመልከቱ፣ የሰሜንን ወገኖች ሁሉ ባርያዬ ከሆነው ከባቢሎን
ንጉሥ ናብከደነፆር ጋር ለመሰብሰብ ትእዛዝን እልካለሁ፤ በዚህችም ምድር በሚቀመጡባትም ሰዎች፣ በዙሪያዋም ባሉ በእነዚህ አሕዛብ ሁሉ ላይ
አመጣቸዋለሁ። ለማጥፋትም እለያቸዋለሁ። ለመጨነቂያና ለማፍዋጫም ለዘላለምም ባድማ አደርጋቸዋለሁ። 10 ከእነርሱም የእልልታን ድምፅና የደስታን
ድምፅ፣ የወንድ ሙሽራን ድምፅና የሴት ሙሽራን ድምፅ፣ የወፍጮንም ድምፅ የመብራትንም ብርሃን አጠፋለሁ። 11 ከዚያም ይህች ምድር ሁሉ ባድማና
መደነቂያ ትሆናለች፣ ከዚያም እነዚህ አሕዛብ ለባቢሎን ንጉሥ ሰባ ዓመት ይገዛሉ። 12 ሰባው ዓመትም የሚፈጸምበት ጊዜ ይመጣል፣ የባቢሎንን ንጉሥና ያንን
ሕዝብ፣ የከለዳውያንን ምድር ስለ ኃጢአታቸው እቀጣለሁ፣ የማያበቃ ባድማ አደርጋታለሁ፣ ይላል እግዚአብሔር። 13 በዚያችም ምድር ላይ የተናገርሁትን ቃሌን
ሁሉ፣ እንዲሁም፣ ኤርምያስ በአሕዛብ ሁሉ ላይ የተነበየውን በዚህች መጽሐፍ የተጻፈውን ሁሉ በዚያች ምድር አመጣለሁ። 14 ብዙ ሌሎች አሕዛብና ታላላቆች
ነገሥታት ከእነዚህ ሕዝቦች ውስጥ ባርያዎችን ያደርጋሉ። እኔም ስለ አደራረጋቸውና ስለ እጃቸው ሥራ እከፍላቸዋለሁ።" 15 የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር
እንዲህ ይለኛል፣ "የዚህን ቊጣ የወይን ጠጅ ጽዋ ከእጄ ውሰድ፣ አንተን ለምሰድድባቸው አሕዛብ ሁሉ አጠጣቸው። 16 ከምሰድድባቸውም ሰይፍ የተነሣ
ይጠጣሉ፣ ይሰናከላሉ፣ በእብደት ይለፈልፋሉ። 17 ስለዚህ ጸዋውን ከእግዚአብሔር እጅ ወሰድሁ፣ ከዚያም እግዚአብሔርም እኔን ለላከባቸው አሕዛብ ሁሉ
አጠጣኋቸው። 18 በዚህ ዛሬ እንደሆኑት ሁሉ ባድማና መደነቂያ፣ ማፍዋጫም፣ እርግማንም አደርጋቸው ዘንድ ኢየሩሳሌምንና የይሁዳን ከተሞች፣
ነገሥታትዋንም፣ አለቆችዋንም አጠጣኋቸው። 19 ሌሎች ሕዝቦችም እንዲሁ ሊጠጡት ይገባል፦ የግብጽ ንጉሥ ፈርዖንና ባርያዎቹ፤ አለቆቹና ሕዝቦቹ ሁሉ፤ 20
የተደባለቀ ቅርስ ሕዝቦች ሁሉ፣ የዖፅ ምድር ነገሥታት ሁሉ፣ የፍልስጥኤም ምድር ነገሥታትንም ሁሉ፣ አስቀሎና፣ ጋዛ፣ አቃሮን የአዞጦን ቅሬታ ሁሉ፤ 21
ኤዶምያስ፣ ሞዓብ፣ እና የአሞንም ሕዝቦች፤ 22 የጢሮስና ሲዶና ነገሥታት፣ በባህሩ ማዶ ያለች የደሴት ነገሥታትም፣ 23 ድዳን፣ ቴማን፣ ቡዝን፣ በራሳቸው ጎንና ጎን
ጠጕራቸውን የሚቈርጡትን ሁሉ። 24 እነዚህም ሕዝቦች እንዲሁ ሊጠጡት ይገባል፦ የዓረብ ነገሥታት ሁሉ፣ በምድረ በዳ የሚኖሩት የድብልቅ ቅርስ ሕዝብ
ነገሥታት ሁሉ፣ 25 የዘምሪ ነገሥታት ሁሉ፣ የኤላም ነገሥታት ሁሉ፣ የሜዶን ነገሥታት ሁሉ፤ 26 የቀረቡና የራቁ፣ አንዱ ከሌላው ጋር ያሉ የሰሜን ነገሥታትንም
ሁሉ፣ በምድር ገጽ ላይ ያሉ የዓለም መንግሥታት ሁሉ አጠጣኋቸው። በመጨረሻም፣ የባቢሎን ንጉሥ ከእነርሱ በኋላ ይጠጣል። 27 "'የእስራኤል አምላክ
የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በመካከላችሁ ከምሰድደው ሰይፍ የተነሣ ጠጡ፣ ስከሩ፣ አስታውኩ፣ ውደቁ፣ ከእንግዲህም ወዲህ አትነሡ'
በላቸው፤ አለኝ። 28 እንዲጠጡ ጽዋውን ከእጅህ ለመቀበል እንቢ ቢሉ፣ 'የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በእርግጥ ትጠጡታላችሁ፤ በላቸው።
29 ተመልከቱ፣ ስሜ በተጠራባት ከተማ ላይ ጥፋትን አመጣለሁ፣ እናንተ ራሳችሁ ያልተቀጣችሁ ትሆናላችሁን? በምድር በሚኖሩ ሁሉ ላይ ሰይፍን እጠራለሁና
ከቅጣት ነፃ አትሆኑም፣ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።' 30 ስለዚህ፣ አንተ ራስህ፣ ኤርምያስ እነዚህን ቃሎች ሁሉ ትተነብይባቸዋለህ፣ እንዲህም
ትላቸዋለህ፦ 'እግዚአብሔር ከበላይ ሆኖ ይጮኻል፣ ከቅዱስ ማደሪያውም ሆኖ ድምፁን ያሰማል። በማደሪያው ላይ እጅግ ይጮኻል፣ ወይንን ሲሚጠምቁ
እንደሚዘምሩት በምድር በሚኖሩ ሁሉ ላይ ይጮኻል። 31 እግዚአብሔር ከአሕዛብ ጋር ክርክር አለውና ድምፅ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ይደርሳል። ከሥጋ ለባሽ
ሁሉ ጋር በፍትህ ይፋረዳል። ኃጢአተኞችንም ለሰይፍ አሳልፎ ይሰጣል፣ ይላል እግዚአብሔር።' 32 የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ 'ተመልከቱ፣
ጥፋት ከሕዝብ ወደ ሕዝብ ይወጣል፣ ደግሞም ጽኑም ዐውሎ ነፍስ ከሩቅ የምድር ዳርቻ ይነሣል። 33 ያን ጊዜ የእግዚአብሔር ግዳዩች ከምድር ዳር ጀምሮ
እስከ ምድር ዳር ድረስ ይበዛሉ፤ አይለቀስላቸውም፤ አይሰበሰቡም፣ ወይም አይቀበሩም። በምድር ላይ እንደ ጉድፍ ይሆናሉ። 34 እረኞች አልቅሱ፣ ለእርዳታም
ጩኹ! በመንጋው ውስጥ አውራ የሆናችሁት ሕዝቦች በመሬት ላይ ተንከባለሉ። ትታረዱና ትበተኑ ዘንድ ቀናችሁ መጥቷልና። እንደ ተመረጡ በጎች
ትወድቃላችሁ። 35 ወደእረኞች ለመሸሸግ ማምለጥ ይቀራል። 36 እግዚአብሔር ማሰማርያቸውን አጥፍቶአልና የእረኞች ጩኸት ድምፅ፣ የመንጋ አውራዎችም
ልቅሶ ሆኖአል። 37 ከእግዚአብሔር ጽኑ ቊጣ የተነሣ የሰላም ማሰማሪያ ይፈርሳል። 38 እንደ ታዳጊ አንበሳ መደቡን ለቅቆአል፣ ከአስጨናቂውም ሰይፍና ከጽኑ
ቊጣው የተነሣ ምድራቸው አስፈሪ ሆናለችና።"

Jeremiah 25:1

ወደ ኤርምያስ የመጣው ቃል ይህ ነው
ወደ ኤርምያስ የመጣው ቃል ከያህዌ ዘንድ መሆኑ ተጠቁሟል። ይህ ፈሊጥ የዋለው ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣውን ልዩ መልዕክት ለማስተዋወቅ ነው። ተመሳሳይ የሆነው ሀረግ በኤርምያስ 7:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ይህ ያህዌ ለኤርምያስ የሰጠው መልዕክት ነው" ወይም "ይህ ያህዌ ለኤርምያስ የተናገረው መልዕክት ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አራተኛው... የመጀመሪያው
(ተከታታይ ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 25:3

አሞን
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 25:5

እያንዳንዱ ሰው ከክፉ መንገዱ እና ከብልሹ ምልልሱ ይመለስ
ኤርምያስ ሰዎች ይፈጽሙት የነበሩትን ድርጊት ስላቆሙ ሰዎች የሚናገረው እነዚያ ሰዎች ከዚያ ድርጊት ዞረው እንደተመለሱ አድርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ክፉ መንገዱ እና የልምምዶቹ ብልሽት
"ክፉ መንገድ" እና "የልምምዶቹ ብልሽቶች" የሚሉት አገላለጾች ተመሳሳ ትርጉም ሲኖራቸው የሚያደረጓቸውን ክፉ ነገሮች ሁሉ ያመለክታሉ። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

የልምምዶቹ ብልሹነቶች
"ብልሹ ድርጊቶቹ"

ሌሎች አማልዕክትን አትከተሉ
ኤርምያስ ራሱን ለጣኦት አሳላፎ የሰጠን ሰው የሚገልጸው ያሰው ያንን ጣኦት ተከትሎ እንደሄደ አድርጎ ነው። "ራሳችሁን ለሌሎች አማልዕክት አሳልፋችሁ አትስጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእጆቻችሁ ስራ እርሱን አታስቆጡት/አታነሳሱት
"እርሱን" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ያህዌን ነው። "የእጆቻችሁ ስራ" የሚለው ሀረግ ሊሰጠው የሚችሉት ትርጉሞች 1) ይህ የሚያመለክተው ሰዎች በእጆቻቸው የሚሰሯቸውን ጣኦታት ነው። "ያህዌን በሰራችሁት ጣኦት አታስቆጡት/አታነሳሱት" ወይም 2) "እጆች" ከሚለው ቃል ጋር እነዚያን ድርጊቶችን የሚወክል ሴኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/በመሆን የአንድን ሰው ድርጊት የሚያመለክት ፈሊጥ ነው። "በምታደርጓቸው ነገሮች ያህዌን አታስቆጡት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ እንዲሁም ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 25:7

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

በእጆቻችሁ ስራ እናንተን እንድቀጣ አነሳስታችሁኛል
በኤርምያስ 25:6 ላይ የሚገኘው ተመሳሳይ ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "የእጆቻችሁ ስራ" ለሚለው ሀረግ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሰዎች በእጆቻቸው ለሰሯቸው ጣኦታት ማሳያ/ማመሳከሪያ ነው። "በእጆቻችሁ በሰራችኋቸው ጣኦታት ምክንያት እናንተን እንድቀጣችሁ አነሳስታችሁኛል" ወይም 2) "እጆች" ከሚለው ቃል ጋር እነዚያን ድርጊቶችን የሚወክል ሴኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/በመሆን ይህ አንድ ሰው የፈጸመውን ድርጊት የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው "በምታደርጓቸው ነገሮች ያህዌን አታስቆጡት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ እንዲሁም ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

እናንተን እንድቀጣ
"በእናንተ ላይ ቅጣት እንዳደርስ"

የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

እዩ
"ተመልከቱ" ወይም "አድምጡ" ወይም "ቀጥሎ ለምነግራችሁ ነገር ትኩረት ስጡ"

እነርሱን በእዚህ ምድር ላይ አመጣለሁ
"በዚህ ምድር ላይ...ማምጣት" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉም፣ እነርሱ በምድሪቱ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን ያጠቃሉ ማለት ነው። "ይህንን ምድር እንዲያጠቁ እነርሱን አመጣለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ለጥፋት እነርሱን አለያቸዋለሁ
"ለጥፋት ... መለየት" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉም አንድን ነገር ሙሉ ለሙሉ ማጥፋት ማለት ነው። "እኔ እነርሱን ሙሉ ለሙሉ አጠፋቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ማስፈራሪያ አደርጋቸዋለሁ
"ማስፈራሪያ" የሚለው ቃል በግሳዊ ሀረግ ምልክ ሊተረጎም ይችላል። "እኔ እነርሱን ሰዎችን የሚያስፈራሩ ነገሮች አደርጋቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ለጥላቻ አደርጋቸዋለሁ
"ጥላቻ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጠንካራ ተቀባይነትን የማጣት ድምጽ የሚያመለክት ሲሆን በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "ሰዎች የሚጠሉት አካል"

Jeremiah 25:10

የወፍጮ ድንጋዮች
እነዚህ ሁለት ትላልቅ ክብ ድንጋዮች ሲሆን እህል ለመፍጨት ያገለግላሉ

የደስታ እና የሀዘን ድምጽ፣ የሙሽራው እና የሙሽራይቱ ድምጽ
ይህ በኤርምያስ 7:34 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ይህ ምድር በሙሉ ሰው የማይኖርበት እና የሚያስፈራ ይሆናል
"ሰው የማይኖርበት" እና "የሚያስፈራ" የሚሉት ቃላት በግሳዊ ሀረጎች ሊተረጎሙ ይችላሉ። "እኔ ይህ ምድር ሰው የማይኖርበት እና ሰዎችን የሚያስፈራ እንዲሆን አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 25:12

ሰባው አመት ሲፈጸም
"ከሰባዎቹ አመታት በኋላ" ወይም "ሰባ አመታት ካለፉ በኋላ"

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እስከ ወዲያኛው ሰው የማይኖርበት
"ሰው የማይኖርበት/ጠፍ" የሚለው ስም በቅጽል መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ለዘለዓለም ሰው የማይኖርበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጻፈው ነገር ሁሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ኤርምያስ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የጻፋቸው ነገሮች ሁሉ" ወይም "አንድ ሰው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የጻፋቸው ነገሮች በሙሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እኔ እንደ ስራቸው መጠን እንደ እጆቻቸው ስራዎች እመልስላቸዋለሁ
ያህዌ የአገሪቱን ህዝቦች ስላደረጉት ነገር የሚያደርስባቸውን ቅጣት የሚገልጸው ለእነርሱ መልሶ ክፍያ እንደሚያደርግ አድርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ ድርጊቶች እና የእጆቻቸው ስራዎች
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። "የእጆቻቸው ስራ" የሚለው ፈሊጥ "እጆች" ከሚለው ቃል ጋር ሰውየውን የሚወክል ሴኔቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ በመሆን የሚያመለክተው የአንድን ሰው ድርጊቶች ነው። "እነርሱ ያደረጓቸው ነገሮች በሙሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም እና ፈሊጣዊ አነጋገር እንዲሁም ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 25:15

ይህንን የቁጣ ወይን ጠጅ ጽዋ ውሰዱ
ያህዌ እጅግ ከፍ ያለውን ቁጣውን የገለጸው በወይን እንደተሞላ ጽዋ አድርጎ ነው። "ቁጣዬን የሚወክሙን ይህን የወይን ጽዋ ውሰዱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አገራቱ ሁሉ ... እንዲጠጡት አድርጉ
"አገራት" የሚለው ቃል የሚወክለው የአገራቱን ሰዎች ነው። ያህዌ ህዝቡ ቁጣው እንደሚደርስበት የገለጸው በዋንጫው ውስጥ ያለውን ወይን እንደሚጠጡ አድርጎ ነው። "የአገራቱ ሰዎች ሁሉ ... ወይኑን እንዲጠጡ አድርጉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ይጠጣሉ ከዚያም ይንገዳገዳሉ በብስጭት ይጮሃሉ
ያህዌ ህዝቡ ስለ ቁጣው መፍራቱን የገለጸው ህዝቡ የጽዋውን ወይን ጠጥቶ እንደ ሰከረ አድርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በመካከላቸው ከምልከው ሰይፍ አስቀድሞ
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚለው ቃል የሚወክለው ጦርነትን ነው። "በመሃላቸው እንዲደርስ ከምፈቅደው ጦርነቶቹ የተነሳ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 25:17

አያያዥ ሀሳብ፡
ይህ ምንባብ የያህዌን እጅግ ከፍ ያለ ቁጣ፣ የአገራቱ ህዝቦች ከጽዋው እንደ ጠጡ አድርጎ በዘይቤ መግለጹን ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ መላው አገራት ... ከዚያ እንዲጠጡ አድርጌያለሁ
"አገራት" የሚለው ቃል የሚወክለው የአገራቱን ህዝቦች ነው። "እኔ የሁሉም አገር ሰዎች ... ከጽዋው ወይኑን እንዲጠጡ አድርጌያለሁ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አስፈሪ የሆነ ነገር
"አስፈሪ" የሚለው ቅጽል በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "ሰዎችን የሚያስፈራ ነገር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ለጥናቻ እና እርግማ የሚዳርግ ነገር
"ጥላቻ" የሚለው ቃል የሚገልጸው ጠንካራ ነቀፌታን/ተቀባይነት ማጣትን የሚያመለክት ድምጽን ነው። "ጥላቻ" እና "እርግማን" የሚሉት ሁለቱም በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "ሰዎች የሚጠሉት እና የሚረግሙት ነገር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እነርሱ በዚህ በዛሬው ቀን እየሆኑ ናቸው
ለዚህ ሀረግ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የኤርምያስ መጽሐፍ የተጻፈበትን ጊዜ እና ኤርምያስ ይህንን ትንቢት ከተናገረ በኋላ ያለውን ጥቂት ጊዜ ይመልከቱ። ወይም 2) ይህ ማለት ኤርምያስ እዚህ ስፍራ የተነበያቸው ነገሮች መሆን ጀምረዋል።

Jeremiah 25:19

አያያዥ ሀሳብ፡
ይህ ምንባብ የያህዌን እጅግ ከፍ ያለ ቁጣ፣ የአገራቱ ህዝቦች ከጽዋው እንዲጠጡ እንዳደረጋቸው በዘይቤ መግለጹን ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንደዚሁም ደግሞ ሌሎችም አገራት ሊጠጡት ይገባል
"አገራት" የሚለው ቃል የሚወክለው የአገራቱን ህዝቦች ነው። "ከሌላ አገር የሆኑ ሰዎችም ደግሞ ከጽዋው ወይን መጠጣት ይኖርባቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የተደባለቀ ቅርስ ያላቸው ህዝቦች
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) አባቶቻቸው ከተለያየ የህዝብ ወገን የሆኑ ሰዎች። ወይም 2) በግብጽ የሚኖሩ የባእድ አገር ሰዎች።

ፆጽ
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 25:22

አያያዥ ሀሳብ፡
ይህ ምንባብ የያህዌን እጅግ ከፍ ያለ ቁጣ፣ የአገራቱ ህዝቦች ከጽዋው እንዲጠጡ እንዳደረጋቸው በዘይቤ መግለጹን ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ባህሩ
ይህ የሜዲትራንያንን ባህር ያመለክታል

ድዳን፣ቴማን፣ እና ቡዝ
እነዚህ የቦታዎች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የጭንቅላቶቻቸውን ፀጉር ከጎን እና ጎን የሚቆረጡ ሁሉ
ይህ ምናልባት ሰዎች ፀጉራቸውን በአጭር የሚቆረጡ፣ የአህዛብን አምላክ ለማክበር ሊሆን እንደሚችል ያመለክታል። አንዳንድ ዘመናዊ ቅጂዎች ይህንን የዕብራይስጥ አገላለጽ "በበረሃማው ዳርቻ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ" በሚል ይተረጉሙታል። ተመሳሳይ የሆነው ሀረግ በኤርምያስ 9:26 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

እነርሱም ደግሞ ይህን መጠጣት አለባቸው
"እነርሱም ደግሞ ከጽዋው መጠጣት አለባቸው"

Jeremiah 25:24

አያያዥ ሀሳብ፡
ይህ ምንባብ የያህዌን እጅግ ከፍ ያለ ቁጣ፣ የአገራቱ ህዝቦች ከጽዋው እንዲጠጡ እንዳደረጋቸው በዘይቤ መግለጹን ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ዘምሪ
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እያንዳንዱ ከወንድሙ ጋር
ይህ ከአንዱ በመቀጠል ሌላው እያንዳንዱ ሰው የሚል ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ከአንዱ በመቀጠል ሌላው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉም ጽዋውን ከያህዌ እጅ መጠጣት አለባቸው
እዚህ "ጽዋው" በውስጡ ለያዘው ወይን ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ/ ነው። "እነዚህ ሁሉ ሰዎች በያህዌ እጅ ካለው ጽዋ መጠጣት አለባቸው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 25:27

አያያዥ ሀሳብ፡
ይህ ምንባብ የያህዌን እጅግ ከፍ ያለ ቁጣ፣ የአገራቱ ህዝቦች ከጽዋው እንዲጠጡ እንዳደረጋቸው በዘይቤ መግለጹን ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰራዊት ጌታ ያህዌ... እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

በመካከላችሁ ከምልከው ሰይፍ አስቀድሞ
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚለው ቃል የሚወክለው ጦርነትን ነው። "በመካከላችሁ እንዲደርስ ከምፈቅደው ጦርነቶቹ አስቀድሞ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በእኔ ስም የተጠራችው ከተማ
ይህ እየሩሳሌምን ሲያመለክት በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽም ይችላል። "በስሜ የተጠራችው ከተማ" ወይም "በስሜ የጠራኋት እየሩሳሌም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እናም እናንተ ራሳችሁ ከቅጣት ነጻ መሆን ይገባችኋልን?
ያህዌ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ህዝቡን ለመገሰጽ እና እንደሚቀጣቸው ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። "ስለዚህም እናንተ ራሳችሁ ከቅጣት ነጻ እንሆናለን ብላችሁ ታስባላችሁ?" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በምድሪቱ ነዋሪዎች ላይ ሁሉ ሰይፍ እጠራለሁ
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚለው ቃል የሚወክለው ጦርነትን ነው። ያህዌ በህዝቡ ላይ ጦርነት ማወጅን የተናገረው በእነርሱ ላይ ሰይፍ እንደሚጠራ አድርጎ ነው። "እኔ በምድሪቱ ነዋሪዎች ላይ ሁሉ ጦርነት አውጃለሁ" ወይም "እኔ በምድሪቱ ነዋሪዎች ላይ ሁሉ ጦርነት አመጣለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 25:30

ያህዌ እንደ አንበሳ ይጮሃል
ኤርምያስ የያህዌን በጣም መጮህ የተናገረው እንደ አንበሳ እንደሚያገሳ አድርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከፍ ካሉ ስፍራዎች
ይህ ሀረግ ለሰማይ ሜቶኖሚ ነው። "ከሰማይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ መንጋ/ህዝብ ላይ እጅግ ይጮሃል
ኤርምያስ ስለ ያህዌ እርሱ አንበሳ እንደሆነ እና የእርሱ ህዝብም የበግ መንጋ እንደሆነ አድርጎ ነው። በጎች አንበሳ ሲያጠቃቸው ተስፋ ቢስ እንደሚሆኑ፣ ህዝቡ ያህዌ ሊቀጣቸው ሲመጣ ተስፋ ቢስ ይሆናሉ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የወይን ፍሬ የሚረግጡ
ይህ በወይን መጭመቂያ በእግራቸው ወይን ስለሚጨምቁ ሰዎች ይናገራል።

እስከ ምድር ዳርቻ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን በምድር ዳርቻ የሚገኝ ስፍራ የሚል ትርጉም አለው። ሁለቱንም ጫፎች በማመላከት፣ በመሃል የሚገኙ ስፍራዎችን ሁሉ ያሳያል። "በምድር ላይ የሚገኝ ሩቅ ስፍራ" ወይም "በምድር ላይ ወደ ሁሉም ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣው አነጋገር እና ከአጽናፍ አጽናፍ የሚሉትን ይመልከቱ)

በስጋ ለባሽ ላይ ሁሉ
እዚህ ስፍራ "ስጋ" የሚለው የሚወክለው ሰብአዊነትን ነው። "በሁሉም የሰው ልጅ" ወይም "በሁሉም ሰው ላይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ለሰይፍ የሚዳርጋቸው ክፉዎች
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚለው ቃል ወታደሮች እንደ ጦር መሳሪያ የሚጠቀሙበትን መሳሪያ ሲያመለክት ይህም ጦርነትን ይወክላል። "ለሰይፍ መዳረግ" የሚወክለው ሰዎች በጦር ሜዳ መሞታቸውን ነው። "ክፉ ሰዎች በጦር ሜዳ እንዲሞቱ ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 25:32

የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

እዩ
"ተመልከቱ" ወይም "አድምጡ" ወይም "ቀጥሎ ለምነግራችሁ ነገር ትኩረት ስጡ"ጥፋት ከአገር ወደ አገር ይዛመታል ያህዌ በእያንዳንዱ አገር ታላቅ ጥፋት እንደሚሆን "ጥፋትን" ከአንድ አገር ወደሌላ አገር እንደሚሄድ ሰው አድርጎ ይናገራል። "በየአገሩ ታላቅ ጥፋት ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ታላቅ ነፋስ ከምድር ዳርቻ ይነሳል
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ያህዌ ስለ በቢሎናውያን ሰራዊት እና ስለሚያደርሱት ጥፋት እንደ ታላቅ ማዕበል አድርጎ ይናገራል። ወይም 2) ያህዌ ታላቅ ቁጣውን ብዙ ጥፋት እንደሚያደርስ ታላቅ ማዕበል አድርጎ ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በያህዌ የተገደሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ማንም አያለቅስላቸውም፣ አይሰበስባቸውም፣ ወይም አይቀብራቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በምድር ላይ እንደ ፍግ ይሆናሉ
በድኖቹ በምድር ላይ ከወደቀ ፍግ ጋር የተነጻጸሩት፣ አስጸያፊ እንደሚሆኑ እና ማንም የማይቀብራቸው ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። በኤርምያስ 16:4 ላይ የሚገኘው ተመሳሳይ ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይልከቱ። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 25:34

እረኞች
ያህዌ ስለ እስራኤል መሪዎች ለህዝቡ ሃላፊነት እንዳለባቸው እና አንደሚጠብቁት እረኞች አድርጎ እና በውስጠ ታዋቂነት እነርሱ በጎች እንደሆኑ ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በአፈር ላይ ተንከባለሉ
ይህ የሀዘን፣ ለቅሶ ወይም ጭንቀት ምልክት ነው። (ምልክታዊ/ትምዕርታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ የመንጋው ጠባቂዎች
ይህም ሀረግ እንደዚሁ፣ ህዝቡን ለመጠበቅ ሃላፊነት ያለባቸውን እና እንደ በግ መንጋ የተገለጸውን ህዝብ የሚጠብቁትን የእስራኤልን መሪዎች ያመለክታል። "እናንተ የእስራኤል መሪዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የመታረጃችሁ ቀን ቀርቧል
ብዙውን ጊዜ የሚታረዱት በጎች ናቸው፣ ነገር ግን እዚህ ስፍራ ያህዌ እረኞቹን አርዳለሁ ይላል። "መታረድ" የሚለው ቃል በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "እናንተን የማርድበት ጊዜ ደርሷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምጸት እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

እንደ ውብ ሸክላ ስትወድቁ ትበታተናላችሁ
ያህዌ ስለ እስራኤል መሪዎች መጥፋት መሬት ላይ ወድቆ እንደ ደቀቀ የሸክላ ስብርባሪ አድርጎ ይናገራል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እንደ ውብ ሸክላ ትወድቃላችሁ የደቀቀ ስብርባሪያችሁ ምድር ላይ ይበታተናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ያህዌ መሰማሪያቸውን ይደመሰሳል
መሪዎቿ በሰላም እየኖርን ነው ብለው

ያህዌ መሰማሪያቸውን ያጠፋል
ያህዌ መሪዎቿ መንጋውን የሚንከባከቡበት "መሰማሪያ" መልካም እንደሆነ እና በሰላም እየኖሩ እንደሆነ ስለሚያስቡ መሪዎች ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 25:37

ስለዚህ ሰላማዊዎቹ መሰማሪያዎች ይደመሰሳሉ
ያህዌ ለእስራኤል መሪዎች እረኞች እንደሆኑ አድርጎ መናገሩን ይቀጥላል። እዚህ ስፍራ አገሪቱ እነርሱ በሰላም እየኖሩባት እንደሆነ የሚያስቧት "መሰማሪያ" እንደሆነች ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሰላማዊዎቹ መሰማሪያዎች ከያህዌ ታላቅ ቁጣ የተነሳ ይደመሰሳሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ከእርሱ ታላቅ ቁጣ የተነሳ ያህዌ ሰላማዊዎቹን መሰማሪያዎች ይደመስሳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ እንደ ደቦል አንበሳ፣ ከዋሻው ወጥቷል
ያህዌ ህዝቡን በከፍተኛ ቁጣ መቅጣቱ የተገለጸው፣ ያህዌ አደን ለማደን ከዋሻው እንደወጣ አንበሳ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ምድራቸው ማስደንገጫ/ማስፈራሪያ ይሆናል
"አስፈሪ/አሰቃቂ" የሚለው ቃል በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "ምድራቸው ሰዎችን የሚያስፈራ ስፍራ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የጨቋኖች ቁጣ
ይህ የእስራኤልን ጠላቶች ቁጣ ያመለክታል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 26

1 በይሁዳ ንጉሥ በኢዮስያስ ልጅ በኢዮአቄም መንግሥት መጀመሪያ ይህ ቃል ከእግዚአብሔር ዘንድ መጣና እንዲህ አለ፣ **2** እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በቤቴ አደባባይ ቁም፣ በእግዚአብሔርም ቤት ውስጥ ይሰግዱ ዘንድ ለሚመጡት ለይሁዳ ከተሞች ሁሉ ንገራቸው። እንድትነግራቸው ያዘዝሁህን ቃል ሁሉ ንገራቸው። አንዲትም ቃል አትጉደል! **3** ምናልባት ይሰሙ፣ ከክፉ መንገዳቸውም ይመለሱ ይሆናል፤ እኔም ስለ ሥራቸው ክፋት ያሰብሁባቸውን ክፉ ነገር እተዋለሁ። **4** ስለዚህ እንዲህ በላቸው፣ 'እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በፊታችሁ በሰጠኋት ሕጌ ትሄዱ ዘንድ ባትሰሙኝ፣ **5** በጽናት ወደ እናንተ የላክኋቸውን የባሪያዎቼን የነቢያትን ቃል ባትሰሙ፣ ነገር ግን አላደመጣችኋቸውም! **6** ያኔ ይህንን ቤት እንደ ሴሎ አደርገዋለሁ፤ ይህችንም ከተማ ለምድር አሕዛብ ሁሉ እርግማን አደርጋታለሁ።" **7** ኤርምያስ በእግዚአብሔር ቤት ይህንን ቃል ሲናገር ካህናቱ፣ ነቢያቱ፣ ሕዝቡም ሁሉ ሰሙ። **8** ኤርምያስም ለሕዝቡ ሁሉ ይናገር ዘንድ እግዚአብሔር ያዘዘውን ነገር ሁሉ በፈጸመ ጊዜ፣ ካህናት፣ ነቢያትና ሕዝቡም ሁሉ፣ ያዙትና "በእርግጥ ትሞታለህ! **9** በእግዚአብሔር ስም ተንብየህ ይህ ቤት እንደ ሴሎ ይሆናል፣ ይህችም ከተማ ነዋሪ የማይገኝባት ወና ትሆናለች ብለህ ለምን ትንቢት ተናገርህ?" አሉት። ሕዝቡም ሁሉ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ በኤርምያስ ላይ በዐመጽ ተሰብስበው ነበር። **10** ከዚያም የይሁዳ አለቆች ይህን ሰሙና ከንጉሥ ቤት ወደ እግዚአብሔር ቤት ሄዱ። በአዲሱም በእግዚአብሔር ቤት ደጅ መግቢያ ተቀመጡ። **11** ካህናቱና ነብያቱም ለአለቆቹና ለሕዝቡ ሁሉ ተናገሩ። እንዲህም አሉ፣ "በጆሮአችሁ እንደ ሰማችሁ በዚህች ከተማ ላይ ትንቢት ተናግአልና ይህ ሰው ሞት የሚገባው ነው!" አሉ። **12** ስለዚህ ኤርምያስ ለአለቆችና ለሕዝቡ ሁሉ እንዲህ ብሎ ተናገረ፣ "በሰማችሁት ቃል ሁሉ፣ በዚህች ቤትና በዚህች ከተማ ላይ ትንቢት እናገር ዘንድ እግዚአብሔር ልኮኛል። **13** አሁንም መንገዳችሁንና ሥራችሁን አሳምሩ፣ እግዚአብሔርም የተናገረባችሁን ጥፋት እንዲታው፣ የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ድምፅ ስሙ። **14** ተመልከቱኝ! እኔ ራሴ በእጃችሁ ነኝ። በዐይናችሁ ፊት መልካምና ቅን የመሰላችሁን አድርጉብኝ። **15** ነገር ግን ይህን ቃል ሁሉ በጆሮአችሁ እናገር ዘንድ በእውነት እግዚአብሔር ወደ እናንተ ልኮኛልና ብትገድሉኝ ንጹሕ ደምን በራሳችሁና በዚህች ከተማ በሚኖሩባትም ላይ እንድታመጡ በእርግጥ እወቁ።" **16** አለቆቹና ሕዝቡም ሁሉ ለካህናትና ለነቢያት፣ "ይህ ሰው በአምላካችን በእግዚአብሔር ስም ተናግሮናልና ለሞት አይገባውም" አሉ። **17** ከዚያም ከምድሪቱ ሽማግሌዎች ሰዎች ተነሥተው ለመላው የሕዝቡ ጉባኤ ሁሉ እንዲህ ብለው ተናገሩ። **18** እነርሱም፣ "ሞሬታዊው ሚክያስ በይሁዳ ንጉሥ በሕዝቅያስ ዘመን ይተነብይ ነበረ። ለይሁዳም ሕዝብ ሁሉ ተንብዮ 'የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ጽዮን እንደ እርሻ ትታረሳለች፣ ኢየሩሳሌም የፍርስራሽ ክምር ትሆናለች፣ የቤተመቅደሱም ተራራ እንደ ዱር ከፍታ ይሆናል' ብሎ ተናገረ። **19** በውኑ የይሁዳ ንጉሥ ሕዝቅያስና ሕዝቡ ሁሉ ገደሉትን? በውኑ እግዚአብሔርን አልፈራምን? ወደ እግዚአብሔርስ አልተማለሉምን? እግዚአብሔርስ የተናገረባቸውን ክፉ ነገር አይተውምን? እኛም በገዛ ሕይወታችን ላይ ታላቅ ክፋት እናደርጋለንን?" **20** ደግሞም በእግዚአብሔር ስም ትንቢት የተናገረ አንድ ሰው ነበረ፣ እርሱም የቂርያትይዓሪም ሰው የሸማያ ልጅ ኦርዮ ይባል ነበር፤ በዚህችም ከተማ በዚህችም ምድር ላይ ከኤርምያስ ቃል ጋር የተስማማ ትንቢት ተናገረ። **21** ነገር ግን ንጉሡ ኢዮአቄም እና ወታደሮቹ ሁሉ እንዲሁም አለቆቹም ሁሉ ቃሉን በሰሙ ጊዜ ንጉሡ ሊገድለው ሞከረ፤ ነገር ግን ኦርዮም ይህን ሲሰማ ፈርቶ ሸሽ ወደ ግብጽም ገባ። **22** ንጉሡም ኢዮአቄም የዓክቦርን ልጅ ኤልናታንን ከእርሱም ጋር ሌሎችን ሰዎች ወደ ግብጽ ላካቸው፤ **23** ኦርዮንን ከግብጽ አውጥተው ወደ ንጉሡ ኢዮአቄም ይዘውት መጡ። ከዚያም ኢዮአቄም በሰይፍ ገደለውና ሬሳውን ተራ በሆኑ ሰዎች መቃብር ውስጥ ጣለው። **24** ነገር ግን በሕዝቡ እጅ እንዳይሰጥና እንዳይገድሉት የሳፋን ልጅ የአኪቃም እጅ ከኤርምያስ ጋር ነበረች።

Jeremiah 26:1

ይህ ቃል እንዲህ ሲል ከያህዌ ዘንድ መጣ
ይህ ፈሊጥ የዋለው ከያህዌ ዘንድ ልዩ መልዕክት ለማስተዋወቅ ነው። በኤርምያስ 18፡1 ላይ የሚገኘው ተመሳሳይ ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ተመልክተው እንደ አስፈላጊነቱ ለውጥ ያድርጉ። "ይህ መልዕክት የመጣው ከያህዌ ዘንድ ነው። እርሱ እንዲህ አለ" ወይም "ያህዌ ይህን መልዕክት ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ቃል እንዲህ ሲል ከያህዌ ዘንድ መጣ
ያህዌ መልዕክቱን ለማን እንደ ሰጠ፣ ይህ በግልጽ ሊጸፍ ይችላል። "ይህ ቃል ወደ ኤርምያስ ከያህዌ ዘንድ እንዲህ ሲል መጣ" ወይም "ያህዌ ይህን መልዕክት ለኤርምያስ ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳ ከተሞች
"ከተሞች" የሚለው ቃል በከተማዋ ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። "ከይሁዳ ከተማ የመጡ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከነገርኩህ ቃል አንዳች አታጉድል!
"ከነገርኩህ አንዳች ነገር አታስቀር!"

እያንንዱ ሰው ከክፉ መንገዱ ይመለሳል
ያህዌ የአንድ ሰው የአኗኗር ስልት "መንገድ" እንደሆነ ወይም ሰውየው የሚጓዝበት ጎዳና እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። "እያንዳንዱ ሰው ክፉ የአኗኗር መንገዱን ያቆማል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህም ከማደርሰው ጥፋት እመለሳለሁ/ይቅር እላለሁ
ይህ ሁኔታን መሰረት ያደረገ ጥፋት/ቅጣት ነው። ይሁዳ ንስሃ ከገባ፣ እግዚአብሔር ጥፋት አያደርስም ይልቁንም ያድናቸዋል።

የልምምዶቻቸው ክፋት
"እነርሱ የሚኖሩበት ክፉ ምነገድ" ወይም "እነርሱ የሚያደረጓቸው ክፉ ነገሮች"

Jeremiah 26:4

በፊታችሁ ባስቀመጥኩት በህጌ ለመሄድ እናንተ እኔን የማትሰሙኝ ካልሆነ
ያህዌ የሰውን የህይወት ስልት ያሰው እንደሚሄድበት ጎዳና አድርጎ ይናገራል። "እኔን ያማትታዘዙኝ እና የሰጠኋችሁን ህግ የማትጠብቁ ከሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህንን ቤት እንደ ሴሎ አደርጋለሁ
ያህዌ በሴሎ የሚገኘውን የማምለኪያ ስፍራ አጥፍቷል፣ ደግሞም ይህንን የአምልኮ ስፍራ ማስፈራሪያ አድርጎታል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይህችን ከተማ ለእርግማን አደርጋታለሁ
ያህዌ ከተማይቱን ወደ ምን እንደሚለውጥ የተነገረው ከተማይቱን ለምን እንደሚያውላት የተነገረ ሜቶኖሚ/ ነው። "ይህችን ከተማ ሌሎች መቀጣጫ/ ይህችን ከተማ ባጠፋሁበት መንገድ ሌሎችን ከተሞች አንዳጠፋ ሰዎች እንዲጠይቁኝ አደርጌ/ እንድትሆን አድርጌ አጠፋታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በምድር ላይ በሚገኙ አገራት ሁሉ ፊት
"በምድር ላይ የሚገኙ አገራት ሁሉ እኔ ይህንን ሳደርግ ይመለከታሉ"

Jeremiah 26:7

የያህዌ ቤት
ቤተ መቅደሱ

ሰዎች ሁሉ እርሱን ይዘውት እንዲህ ይላሉ፣ "በእርግጥ አንተ ትገደላለህ!"
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ህዝቡ የሀሰት ሰላምን እውሸት ማመን መረጠ እንጂ ከእውነቱ ጋር መጋጠምን አልወደደም፣ ወይም 2) ህዝቡ ሌሎች ነቢያት የሚናገሩትን ሀሰተኛ ሰላም አመነ፣ ኤርምያስን ግን መወገር እንደሚገባው ህዝቡን ከትክክለኛ መንገድ እንዳወጣ ሀሰተኛ ነቢይ ተመለከተው።

ከበውት...ለምን ትንቢት ትናገራለህ? አሉት
ይህ ግሳጼ በዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ከበውት....ይህን ትንቢት መናገር አልነበረብህም" አሉት። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 26:10

አዲሱ በር
ሰዎች ወደ ቤተ መቅደሱ የሚገቡበት የአዲሱ በር ስም።

በገዛ ጆሯችሁ እንነተው ሰምታችኋል
"እናንተ ሰምታችኋል"

ይህ ቤት እና ይህ ከተማ
"በያህዌ ቤተመቅደስ የሚያመለኩ ሰዎች እና በእየሩሳሌም ከተማ የሚኖሩ"

Jeremiah 26:13

መንገዶቻችሁ...ልምምዶቻችሁ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። "እናንተ የምታደረጎቸው ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌን ድምጽ ስሙ
ድምጽ ለሰውየው ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ነው፤ ደግሞም ይኸው ቃል "አድምጡ" ወይም "ታዘዙ" በሚል ሊተረጎም ይችላል። "ያህዌን ታዘዙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በዐይኖቻችሁ መልካም እና ትክክል ሆኖ የሚገኘውን ለእኔ አድርጉ
"መልካም" እና "ትክክል" የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ዐይን የሚለው ለሰው አስተሳሰብ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። "ማድረግ ይገባል የምትሉትን ትክክለኛ ለገር ለእኔ አድርጉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

የንጹሃንን ደም በራሳችሁ፣ በከተማይቱ እና በነዋሪዎቿ ላይ እያመጣችሁ ነው
ደም በግፍ ለሚደርስ ሞት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሲሆን፣ በአንድ ሰው ላይ ደም ማምጣት በጥቃት ለደረሰ ሞት ተጠያቂ ማድረግ ነው። "ራሳችሁን እና ይህችን ከተማ እንዲሁም ነዋሪዎቿን በግፍ ለሚደረግ የንጹሃን ሰዎች ሞት ተጠያቂ እያደረጋችሁ ነው።" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ይህች ከተማ እና ነዋሪዎቿ
እነዚህ አንድ ህዝብ የተገለጸበት ተመሳሳይ መንገድ ናቸው። ይህም ምናልባት በመጀመሪያ እንደ ቡድን ከዚያም እንደ ግለሰቦች የተነገረ ነው። ከተማይቱ የሚለው በከተማዋ ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ ነው። "በከተማይቱ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ እና በዚህ የሚኖሩ እያንዳንዳቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ለጆሯችሁ
ጆሮ የሚለው ጆሮ ለሚሰማው ሜቶኖሚ/ ነው። "እናንተ እንድትሰሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 26:16

በያህዌ በአምላካችን ስም
የሰው ስም ለስልጣኑ ሜቶኖሚ/ ነው። "በእግዚአብሔር በአምላካችን በያህዌ ስልጣን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 26:18

አጠቃላይ መረጃ:
ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ

ሞሬታዊ
ከሞሬት ከተማ ወይም አካባቢ የሆነ/የመጣ ሰው

የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ጽዮን እንደ እርሻ ትታረሳለች...የቤተ መቅደሱ ተራራ ዳዋ የወረሰው ኮረብታ ይሆናል
"ጽዮን " እና "የቤተ መቅደሱ ኮረብታ" የሚሉት የሚያመለክቱት አንድን ስፍራ ነው። ገበሬ መሬቱን ሲያርስ አፈሩን ይገለብጣል፣ በእርሻው ውስጥ የሚገኙ ቅጠላ ቅጠሎች ሁሉ ይነቃቅላል። ቁጥቋጦ ማንም ለምንም የማይፈልጋቸውን አረሞች የያዘ ነው። እነዚህ ሁለት ዘይቤዎች በተመሳሳይ ጊዜ ቃል በቃል እውነተ ተደርገው አይወሰዱም፣ ነገር ግን ይህ አገላለጽ ያህዌ ወራሪዎች የቤተ መቅደሱን አካባቢ ሙሉ ለሙሉ መደምሰስ እንዲችሉ እንደሚፈቅድላቸው በትኩረት ይገልጻል። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ሕዝቅያስ... ለሞት ተሰጠን?
ተናጋሪዎቹ አድማጮቻቸው እነርሱ የሚናገሩትን እንዲሰሟቸው እየሞከሩ ነው። "ሕዝቅያስ ራሱን ለሞት አሳልፎ እንዳልሰጠ... እናተ ራሳችሁ በሚገባ ታውቃላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

መላው ይሁዳ
ምድሪቱ የሚለው ለመላው በዚያ ለሚኖረው ህዝብ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "መላው የይሁዳ ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ...እርሱስ ያህዌን አልፈራምን፣ ደግሞስ የያህዌን ፊት በትህትና አልፈለገምን?
ተናጋሪዎቹ አድማጮቻቸው እነርሱ የሚናገሩትን እንዲሰሟቸው እየሞከሩ ነው። "እነርሱ...ሕዝቅያስ ራሱን ለሞት አሳልፎ እንዳልሰጠው እናተ ራሳችሁ በሚገባ

ታውቃላችሁ ስለዚህም ያህዌ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌን ፊት በትህትና ፈለገ
ፊት የሚለው መላ ሰውነትን የሚገልጽ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "የያህዌ ቁጣ እንዲበርድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ በገዛ ህይወታችን ላይ የባሰ ጥፋት እንፈጽማለን?
ተናጋሪዎቹ አድማጮቻቸው እነርሱ ከሚናገሩት ጋር እንዲስማሙ ለማድረግ እየሞከሩ ነው። "ህይወታችን" የሚለው ቃል ለሰዎቹ ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ኤርምያስን ብንገድለው፣ በራሳችን ህይወት ላይ የከፋ ክፉ ነገር እንፈጽማለን" ወይም "በራሳችን ላይ የከፋ ነገር ማድረግ አንፈልግም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 26:20

አያያዥ ሀሳብ፡
ኤርምያስ ስለ ራሱ ህይወት መናገሩን አቁሞ በሌሎች ነቢያት ላይ የሆነውን መናገር ይጀምራል

በመሃል እንዲህ ነበር
"እኔ የምናገራችሁ እየተፈጸመ ሳለ፣ እንዲህ ነበር

በያህዌ ስም
የአንድ ሰው ስም ለስልጣኑ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ይህ በኤርምያስ 26:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "በያህዌ ስልጣን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በዚህች ከተማ እና በዚህች ምድር ላይ የተነገረ ትንቢት
"ከተማ" እና "ምድር" የሚሉት ቃላት በዚያ ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ናቸው። "በዚህች ከተማይቱ እና በዚህች ምድር ላይ መጥፎ ነገሮች እንደሚደርሱ ትንቢት ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱን ቃል ሰማ
"እርሱ የተናገረውን ነገር ሰማ"

Jeremiah 26:22

አያያዥ ሀሳብ፡
ይህ የኦርዮ ታሪክ መጨረሻ ነው

ኤልናታን...ዓክቦር...አኪቃም... ሳፋን
የወንድ ስሞች ናቸው (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አስክሬን/ሬሳ
የሞተ ሰውነት

የአኪቃም እጆች... ከኤርምያስ ጋር ነበር
እጅ የሚለው እጅ ለሚሰራው ሜቶኖሚ/ ነው። አኪቃም ወታደር አልነበረም፣ ስለዚህም ምናልባት እርሱ ከህዝቡ ጋር እየተነጋገረ ሀሳባቸውን እንዲቀይሩ ማድረግ ሳይችል አልቀረም። "አኪቃም ... ኤርምያስን መርዳት ችሎ ነበር" ወይም "አኪቃም... ሰዎች በኤርምያስ ላይ ጉዳት እንዳያደርሱበት ሊጠብቀው ችሎ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ለመገደል/ለሞት ለሰዎች እጅ አልተሰጠም ነበረ
እጅ የሚለው እጅ ለሚሰራው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አኪቃም ሰዎች ኤርምያስን ለመግደል ሀይል እንዲኖራቸው አልፈቀደላቸውም" ወይም "ህዝቡ ኤርምያስን መግደል አልቻለም ምክንያቱም አኪቃም ይህን እንዲያደርጉ ሀይል አልሰጣቸወም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 27

1 በይሁዳ ንጉሥ በኢዮስያስ ልጅ በኢዮአቄም መንግሥት መጀመሪያ ይህ ቃል ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ኤርምያስ መጣ። **2** እግዚአብሔር እንዲህ ይለኛል፣ "እስራትና ቀንበር ለራስህ ሥራ። በአንገትህም ላይ አድርግ። **3** ከዚያም ወደ ይሁዳ ንጉሥም ወደ ሴዴቅያስ፣ ወደ ኢየሩሳሌም በመጡት መልእክተኞች እጅ ወደ ኤዶምያስ ንጉሥ፣ ወደ ሞዓብም ንጉሥ፣ ወደ አሞንም ልጆች ንጉሥ፣ ወደ ጢሮስም ንጉሥ፣ ወደ ሲዶናም ንጉሥ ላካቸው። **4** ለጌቶቻቸውም እንዲነግሩ እንዲህ ብለህ እዘዛቸው፣ 'የእስራኤል አምላክ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ለጌቶቻችሁ ልትነግሯቸው የሚገባው ይህንን ነው፣ **5** እኔ ራሴ ምድሪቱን በታላቅ ኃይሌና በተዘረጋችው ክንዴ ፈጥሬአለሁ። በምድርም ፊት ላይ ያሉትን ሰዎችንና እንስሶችን ጭምር ፈጥሬያለሁ። በዐይኔም ዘንድ ትክክል ለሆነው ለማንኛውም ሰው እሰጣታለሁ። **6** አሁንም፣ እነዚህን ምድሮች ሁሉ ለባርያዬ ለባቢሎን ንጉሥ ለናቡከደነፆር እጅ አሳልፌ እሰጣታለሁ። እንዲሁም ያገለግሉት ዘንድ በሜዳዎች ያሉትን ሕያዋን ነገሮችን ደግሞ ሰጥቼዋለሁ። **7** የገዛ ራሱም ምድር ፍጻሜ እስኪመጣ ድረስ አሕዛብ ሁሉ ለእርሱና ለልጅ ልጅ ልጁም ይገዛሉ። ከዚያም ብዙ አሕዛብና ታላላቆች ነገሥታት እርሱን ያስገዙታል። **8** ለባቢሎን ንጉሥም ለናቡከደነፆር የማያገለግለውን፣ ከባቢሎንም ንጉሥ ቀንበር በታች አንገቱን ዝቅ የማያደርገውን ሕዝብና መንግሥት፣ ያን ሕዝብ በእጁ እስካጠፋው ድረስ በሰይፍና በራብ፣ በመቅሰፍትም እቀጣለሁ፣ ይላል እግዚአብሔር። **9** እናንተ ደግሞ! 'ለባቢሎን ንጉሥ አታገልግሉ' የሚሉአችሁን ነቢያቶቻችሁን፣ ሟርተኞቻችሁን፣ ሕልም አላሚዎቻችሁንና ቃላተኞቻችሁን፣ መተተኞቻችሁንም መስማት አቁሙ። **10** ከምድራቸሁ አርቀው ሊልኳችሁ፣ እኔም እንዳሳድዳችሁ፣ እናንተም እንድትሞቱ ሐሰተኛ ትንቢትን ይናገሩላችኋልና። **11** ነገር ግን ከባቢሎን ንጉሥ ቀንበር በታች አንገቱን ዝቅ የሚያደርገውንና የሚያገለግለውን ሕዝብ በአገሩ ላይ እተዋቸዋለሁ፤ እነርሱም ያርሱአታል ቤቶችንም ይሠሩባታል።" **12** ለይሁዳ ንጉሥ ለሴዴቅያስም በዚህ ቃል ተናገርሁ ይህንንም መልእክት ሰጠሁት፣ "ከባቢሎን ንጉሥ ቀንበር በታች አንገታችሁን ዝቅ አድርጉና ለእርሱና ለሕዝቡ አገልግሉ፣ በሕይወትም ትኖራላችሁ። **13** ለባቢሎን ንጉሥ ይገዛ ዘንድ እንቢ ስላለ ሕዝብ እግዚአብሔር እንደ ተናገረ፣ አንተና ሕዝብህ በሰይፍና በራብ በመቅሰፍትም ለምን ትሞታላችሁ? **14** ሐሰተኛን ትንቢት ይናገሩላችኋልና፣ 'ለባቢሎን ንጉሥ አታገልግሉ' የሚሉአችሁን የነቢያትን ቃል አትስሙ። **15** 'እኔ አልላክኋቸውምና፤ ነገር ግን እኔ እንዳሳድዳችሁ፣ እናንተና ትንቢት የሚናገሩላችሁ ነቢያትም እንድትጠፉ በስሜ ሐሰተኛ ትንቢትን ይናገራሉ፣' ይላል እግዚአብሔር።" **16** ይህንን ለካህናትና ለዚህ ሕዝብ ሁሉ እንዲህ ብዬ ተናገርሁ፣ "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ተንብየውላችሁ 'ተመልከቱ! የእግዚአብሔር ቤት ዕቃ አሁን ከባቢሎን ይመለሳል!' የሚሉአችሁን የነቢያቶቻችሁን ቃል አትስሙ። እነርሱ ውሸትን ይተነብዩላችኋል። **17** እነርሱንም አትስሟቸው። የባቢሎንን ንጉሥ ልታገለግሉና በሕይወት ልትኖሩ ይገባችኋል። ይህችስ ከተማ ስለ ምን ባድማ ትሆናለች? **18** እነርሱ ግን ነቢያት ከሆኑ፣ የእግዚአብሔርም ቃል በእውነት ወደእነርሱ ቢመጣ፣ በእግዚአብሔር ቤትና በይሁዳ ንጉሥ ቤት በኢየሩሳሌምም የቀረችው ዕቃ ወደ ባቢሎን እንዳትሄድ ወደ ሠራዊት ጌታ ወደ እግዚአብሔር ይለምኑ። **19** የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር የይሁዳን ንጉሥ የኢዮአቄምን ልጅ ኢኮንያንንና የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን ከበርቴዎች ሁሉ ማርኮ **20** ከኢየሩሳሌም ወደ ባቢሎን ባፈለሳቸው ጊዜ ስላልወሰዳቸው ዓምዶች ስለ ኩሬውም፣ ስለ መቀመጫዎቹም በዚህችም ከተማ ስለ ቀረች ዕቃ ሁሉ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። **21** በእግዚአብሔር ቤትና በይሁዳ ንጉሥ ቤት በኢየሩሳሌምም ስለ ቀረችው ዕቃ የእስራኤል አምላክ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ **22** 'እነርሱ ወደ ባቢሎን ትወሰዳለች እስከምጐበኛትም ቀን ድረስ በዚያ ትኖራለች፣ ይላል እግዚአብሔር፤ ከዚያም አወጣታለሁ ወደዚህም ስፍራ እመልሳታለሁ።"

Jeremiah 27:1

ማነቆ
አንድ ሰው በነጻነት አንዳይንቀሳቀስ የሚከለክል ነገር

ከዚያም በኋላ አስወጣቸዋለሁ
ይህ ኤርምያስ በርካታ ማነቆ እና ቀንበር በዝርዝር ወደ ተጠቀሱት መንግስታት ይልካል ለማለት የተነገረ ይመስላል። ነገር ግን በአንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች ይህን "ከዚያም መልዕክት ላከ" በማለት ተተርጉሟል።

በእነዚያ ንጉሦች አምባሳደሮች እጅ ... ወደ ይሁዳ ላካቸው
እጅ የሚለው ለሰውየው ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ነው። " ወደ ይሁዳ፣ ... በእነዚያ ነገስታት አምባሳደሮች በኩል ውሰዳቸው" (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእነርሱ ለአለቆቻቸው ትዕዛዞችን ስጥ
ኤርምያስ ብዙ ሰንሰለቶችን እና ቀንበር ለእያንዳንዱ አምባሳደር/መልዕክተኛ እንደዚሁም ሰንሰለቶቹን እና ቀንበሩን በተመለከተ ለእያንዳንዱ ንጉሥ መልዕክት ይልካል።

የሰራዊት ጌታ ያህዌ... እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

Jeremiah 27:5

በታላቁ ሀይሌ እና በተዘረጉ ክንዶቼ
"የተዘረጉ/የተመሱ እጆች" የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው ታላቅ ሀይልን ሲሆን የመጀመሪያውን ሀረግ ያጠናክራል። "በጣም ታላቅ በሆነው ሀይሌ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ጥንድ ትርጉም የሚሉትን ይመልከቱ)

በዐይኖቼ ፊት ትክክለኛ ለሆነው ይህን እሰጠዋለሁ
ሌላው ሊሰጥ የሚችለው ትርጉም "እኔ ለማንኛውም ለወደድኩት ሰው ይህን እሰጣለሁ"

እኔ... እነዚህን ምድሮች ሁሉ ለናቡከደነጾር ... ለአገልጋዬ ሰጥቼዋለሁ
እጅ የሚለው በእጅ ለሚሰራው ሀይል የተሰጠ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ሲሆን፣ "ምድር" በእነዚያ ምድሮች ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ ነው። "እኔ... በዚህ ምድር የሚኖሩ ሰዎችን በባሪያዬ... በናቡከደነጾር ስልጣን ስር አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ለእርሱ ምድር ጊዜው ደርሷል
የጊዜውን ባህርይ ግልጽ ማድረግ ሊያስፈልግ ይችላል። "የእርሱን ምድር የምደመስስበት ጊዜ ደርሷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለእርሱ ይገዛሉ
እዚህ ስፍራ "እርሱ" የሚለው የሚያመለክተው የባቢሎንን መንግስት የሚወክለውን ናቡከደነጾርን ነው። "ባቢሎንን ይረታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 27:8

ያ አንገቱን በንጉሡ ቀንበር ስር አያደርግም
የንጉሡ ባሪያ መሆን የተገለጸው እንስሳ እንደመሆን እና ከባድ ስራ ይሰራ ዘንድ ንጉሡ በአንገቱ ላይ ቀንበር እንደጫነበት ሰው ተደርጎ ነው። "ደግሞስ የማን ህዝብ በፈቃዱ ለንጉሡ ባሪያ ሳይሆን ይቀራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ እጅ እኔ ይህን ደምስሻለሁ
እዚህ ስፍራ እጁ የሚለው ለናቡከደነጾር ሀይል ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው፣ ወይም ለናቡከደነጾር ሰራዊት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ሊሆን ይችላል። "ይህንን ለማጥፋት የናቡከደነጾርን ሀይል ተጠቅሜያለሁ" ወይም "የናቡከደነጾር ሰራዊት ይህንን ማጥፋት እንዲችል አቅም ሰጥቼዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 27:9

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ በኤርምያስ በኩል ለይሁዳ ህዝብ መናገሩን ቀጥሏል።

ሟርተኛ ትንቢት ተናጋሪ
ወደፊት የሚሆነውን የሚናገሩ ሟርተኛ ሰዎች

አንገቱን በንጉሡ ቀንበር ስር የሚደርግ አገር
የንጉሡ ባሪያ መሆን የተገለጸው በትከሻው ላይ ንጉሡ ለከባድ ስራ ቀንበር እንደጫነበት እንስሳ ተደርጎ ነው። ተመሳሳይ የሆኑት ቃላት በኤርምያስ 27:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ። "በፈቃደኝነት የንጉሡ ባሪያ የሆኑ አገራት ህዝቦች" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በአንገቱ ላይ የሚያደርግ አገር
እዚህ ስፍራ አገር የሚለው ለዚያ አገር ህዝብ ሜቶኖሚ/ ነው። "አንገቱን ዝቅ የሚያደርግ ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ማልማት/ማረስ
ይህ ማለት መሬትን የምግብ እህል ለማብቀል ማዘጋጀት ማለት ነው

በውስጧ ቤታቸውን ይሰራሉ
"በራሳቸው ምድር ቤቶቻቸውን ይሰራሉ"

Jeremiah 27:12

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ በኤርምያስ በኩል ለይሁዳ ንጉሥ መናገሩን ቀጥሏል።

አንገታችሁን ከባቢሎን ንጉሥ ቀንበር በታች አድርጉ
እዚህ ስፍራ የንጉሡ ባሪያ መሆን የተገለጸው ከባድ ስራ ይሰራ ዘንድ ንጉሡ በትከሻው ላይ ቀንበር እንደጫነበት እንስሳ ተደርጎ ነው። ተመሳሳይ የሆኑት ቃላት በኤርምያስ 27:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

የእናንተን አንገታችሁን ዝቅ አድርጉ
"የእናንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሴዴቅያስን እና የይሁዳን ሰዎች ስለሆነ ብዙ ቁጥር ነው። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)

የባቢሎን ንጉሥ... ለምን ትሞታለህ?
ኤርምያስ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው የንጉሡ ድርጊት ወደ ሞት ስለሚመራው ሊያስጠነቅቀው ነው። "ንጉሥ ሆይ...ይህንን ሳታደርግ ብትቀር፣ በእርግጥ ትሞታለህ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 27:14

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ በኤርምያስ በኩል ለይሁዳ ንጉሥ እና ህዝብ መናገሩን ቀጥሏል።

ቃሎቻቸውን አትስሙ
ያህዌ ህዝቡን ስለ ሀሰተኛ ነቢያት እርሱ እንዳልላካቸው እና እየዋሸዋቸው እንደሆነ ያስጠነቅቃል።

እኔ ወደ እናንተ አልላኳቸውም
"እኔ እነርሱን ስላልላኳቸው"

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

በስሜ ሀሰትን ይተነብያሉ
"በስሜ" የሚለው ሀረግ የሚወክለው በያህዌ ሀይል እና ስልጣን ወይም የእርሱ ወኪል ሆኖ መናገርን ነው። እዚህ ስፍራ እነዚህ ነቢያት መልዕክታቸውን ከያህዌ እንደተቀበሉ ይናገራሉ፣ ነገር ግን ከእርሱ አልተቀበሉም። "ሀሰት/ ማታለል" የሚለው ረቂቅ ስም "ያታልላሉ" በሚል ግስ ሊተረጎም ይችላል። "በሀሰት ተንቢት ሲናገሩ ከእኔ ተቀብለው እንደሚናገሩ ወራሉ፣ ሆኖም ግን እያታለሏችሁ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

እኔ አባርራችኋለሁ
"እኔ አገራችሁን ለቃችሁ እንድትወጡ አስገድዳችኋለሁ"

Jeremiah 27:16

አጠቃላይ መረጃ:
ኤርምያስ የያህዌን ቃል መናገሩን ቀጥሏል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የያህዌ ቤት እቃዎች አሁን ከባቢሎን መመለስ ይጀምራሉ!
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል:: "ሰዎች ከያህዌ ቤተ መቅደስ የወሰዷቸውን የወርቅ እቃዎች መመለስ ይጀምራሉ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለምን ይህች ከተማ ትፈራርሳለች?
ያህዌ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ህዝቡን ለማስጠንቀቅ ነው:: "ያህዌ እንድታደርጉ የሚፈልገውን ማድረግ ብትጀምሩ ይህችን ከተማ ከመፍረስ ልታድኑ ትችላላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)እነርሱ ነቢያት ከሆኑ እና፣ በእውነት የያህዌ ቃል ወደ እነርሱ መጥቶ ከሆነ እነርሱ ይለምኑ ይህ ያህዌ እውነት እንዳልሆነ የሚያውቀው መላምታዊ ሁኔታ ነው:: "ነቢያት ቢሆኑ እና የያህዌ ቃል በእርግጥ ወደ እነርሱ መጥቶ ቢሆን፣ ይለምኑ ነበር" ወይም "ነቢያት ስላልሆኑ እና በእውነት የያህዌ ቃል ወደ እነርሱ ስላልመጣ አይለምኑም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌ ቃል በእርግጥ ወደ እነርሱ መጥቶ ቢሆን ኖሮ
"የያህዌ ቃል" የሚለው ሀረግ የሚለው የሚያመለክተው ከእግዚአብሔር ዘንድ የሀነን መልዕክት ነው:: "በእውነት ያህዌ መልዕክት ሰጥቷቸው ቢሆን ኖሮ" ወይም "በእውነት ያህዌ ለእነርሱ መልዕክት ተናግሮ ቢሆን ኖሮ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው::

የያህዌ ቃል... የሰራዊት ጌታ ያህዌን አለመኑም
ያህዌ ራሱን በሶስተኛ መደብ ይገልጻል:: "የእኔ ቃል... የእኔ ነው፣ የሰራዊት ጌታ ያህዌን አልለመኑም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳ ንጉሥ ቤት
"ቤት" የሚለው ቃል የተለያዩ ሰፊ ትርጉሞችን ይይዛል:: በዚህ ሁኔታ ንጉሡ የሚኖርበትን ንጉሳዊ ቤተመንግስትን ያመለክታል:: "የይሁዳ ንጉሥ ቤተ መንግስት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው::

Jeremiah 27:19

አጠቃላይ መረጃ:
ኤርምያስ የያህዌን መልዕክት ማምጣቱን ቀጥሏል::

የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው:: ይህ በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ::

አምዶቹ፣ "ባህር/ገንዳ" ተብለው የሚታወቁት ትላልቆቹ ሳህኖች እና የእርሱን መሰረት
እነዚህ በቤተ መቅደስ ውስጥ የሚገኙ እቃዎች ነበሩ:: "ባህሩ" ትልቅ የነሐስ ጎድጓዳ ሣህን ነው::

ኢዮአኪን
የዕብራይስጡ ጽሁፍ "ኢኮንያን" ይላል፣ ይህ "ኢዮአኪን" ለሚለው የተሰጠ አማራጭ ስም ነው:: ብዙ ዘመናዊ ቅጂዎች ነገሩን ግልጽ ለማድረግ ያው ንጉሥ የተጠቀሰበትን "ኢዮአኪን" የሚለውን ስም ይጠቀማሉ::

Jeremiah 27:21

አጠቃላይ መረጃ:
ኤርምያስ የያህዌን ቃሎች መናገሩን ቀጥሏል::

የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው:: ይህ በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ::

የይሁዳ ንጉሥ ቤት
"ቤት" የሚለው ቃል የተለያዩ ሰፊ ትርጉሞችን ይይዛል:: በዚህ ሁኔታ ንጉሡ የሚኖርበትን ንጉሳዊ ቤተመንግስትን ያመለክታል:: "የይሁዳ ንጉሥ ቤተ መንግስት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው::

ወደ ባቢሎን ይመጣሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል:: "ሰዎች እነርሱን ወደ ባቢሎን ያመጧቸዋል" ወይም "እኔ ወደ ባቢሎን አመጣቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው:: ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ:: "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ እነርሱን እመልሳቸዋለሁ
አንባቢ ያህዌ የሚረዳው ህዝብ እንዳለ ይረዳል::

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 28

1 በዚያም ዓመት በይሁዳ ንጉሥ በሴዴቅያስ መንግሥት መጀመሪያ በአራተኛው ዓመት በአምስተኛው ወር ነቢዩ የገባዖን ሰው የዓዙር ልጅ ሐናንያ በእግዚአብሔር
ቤት በካህናትና በሕዝብ ሁሉ ፊት እንዲህ ብሎ ተናገረኝ። **2** "የእስራኤል አምላክ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ይናገራል፣ የባቢሎን ንጉሥ
ያኖረውን ቀንበር ሰብሬአለሁ። **3** የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ከዚህች ስፍራ ወደ ባቢሎን ያጋዛትን የእግዚአብሔርን ቤት የሆኑትን ዕቃዎች ሁሉ በሁለት ዓመት
ውስጥ ወደዚህች ስፍራ እመልሳታለሁ። **4** ከዚያም ወደ ባቢሎንም የሄዱትን የይሁዳን ንጉሥ የኢዮአቄምን ልጅ ኢኮንያንንና የይሁዳን ምርኮ ሁሉ ወደዚህች
ስፍራ እመልሳቸዋለሁ፤ የባቢሎንን ንጉሥ ቀንበር እሰብራለሁና።" **5** ነቢዩ ኤርምያስም በካህናቱና በእግዚአብሔር ቤት በቆሙት ሕዝብ ሁሉ ፊት ለነቢዩ ሐናንያ
ተናገረ። **6** ነብዩም ኤርምያስ እንዲህ አለ፣ "እግዚአብሔር እንዲህ ያድርግ! የእግዚአብሔርን ቤት ዕቃ ምርኮውንም ሁሉ ከባቢሎን ወደዚህ ስፍራ በመመለስ
እግዚአብሔር የተናገረውን ትንቢት ይፈጽም። **7** ይሁን እንጂ፣ በጆሮህና በሕዝብህ ጆሮ ሁሉ የምናገረውን ይህን ቃል ስማ። **8** ከጥንት ከእኔና ከአንተ በፊት
የነበሩ ነብያት በብዙ አገርና በታላላቅ መንግሥታት ላይ ስለ ሰልፍና ስለ ክፉ ነገር፣ ስለ መቅሰፍትም ትንቢት ተናገሩ። **9** ስለዚህም ሰላም እንደሚኖር የተናገረ
ነቢይ፣ የነቢዩ ቃል በተፈጸመ ጊዜ፣ ያኔ እግዚአብሔር በእውነት የሰደደው ነቢይ እንደ ሆነ ይታወቃል።" **10** ነቢዩም ሐናንያ ቀንበሩን ከነቢዩ ከኤርምያስ አንገት
ወስዶ ሰበረው። **11** ከዚያም ሐናንያ በሕዝብ ሁሉ ፊት፣ "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ልክ እንደዚሁ፣ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ የባቢሎንን ንጉሥ
የናቡከደነፆርን ቀንበር ከአሕዛብ ሁሉ አንገት እሰብራለሁ" አለ። ከዚያም ነብዩ ኤርምያስ መንገዱን ሄደ። **12** ነቢዩም ሐናንያ ቀንበሩን ከነቢዩ ከኤርምያስ አንገት
ከሰበረ በኋላ፣ የእግዚአብሔር ቃል ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ፣ **13** "ሂድና ለሐናንያ እንዲህ ብለህ ንገረው፣ 'እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ አንተ
የእንጨት ቀንበርን ሰብረሃል፣ እኔ ግን በእርሱ ፋንታ የብረትን ቀንበር እሠራለሁ።' **14** የእስራኤልም አምላክ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፦
ለባቢሎን ንጉሥ ለናቡከደነፆር እንዲያገለግሉ የብረትን ቀንበር በእነዚህ አሕዛብ ሁሉ አንገት ላይ አድርጌአለሁ። እነርሱም ያገለግሉታል። እንዲገዛቸውም የምድረ
በዳ አራዊትን ደግሞ ሰጥቼዋለሁ።" **15** ቀጥሎ፣ ነብዩ ኤርምያስ ነብዩን ሐናንያን፣ "ሐናንያ ሆይ፣ አድምጥ! ይህ ሕዝብ በሐሰት እንዲታመን አድርገሃል እንጂ
እግዚአብሔር አልላከህም። **16** ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ተመልከት ከምድር ላይ እሰድድሃለሁ። በእግዚአብሔር ላይ ዐመፅን ተናግረሃልና በዚህ
ዓመት ትሞታለህ።" አለው። **17** ነብዩም ሐናንያ በዚያው ዓመት በሰባተኛው ወር ሞተ።

Jeremiah 28:1

አጠቃላይ መረጃ:
ሐናንያ ከእግዚአብሔር እንደሆነ ይናገራል

በአራተኛው አመት በአምስተኛው ወር
ይህ በዕብራውያን ዘመን አቆጣጠር አምስተኛው ወር ነው። ይህም በበጋ ወራት ነው። ምዕራባውያን ቀን መቁጠሪያ በሐምሌ መጨረሻ እና በነሐሴ መጀመሪያ ላይ ነው። (የዕብራውያን ወሮች እና ተከታታይ ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

ዓዙር
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰራዊት ጌታ ያህዌ... እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

እኔ በባቢሎን ንጉሥ የተጫነውን ቀንበር ሰብሬያለሁ
ሐናንያ ህዝቡ በባርነት ውስጥ መሆኑን የተናገረው እነርሱን ከባድ ስራ ይሰሩ ዘንድ ባቢሎናውያን ቀንበር እንደጫኑባቸው በሬዎች አድርጎ ነው። "ከእንግዲህ ወዲያ ለባቢሎን ንጉሥ ባሮች እንዳትሆኑ አድርጌያለሁ" ወይም "ከባቢሎን ንጉሥ ባርነት ነጻ አውጥቻችኋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 28:3

አጠቃላይ መረጃ:
ሐናንያ መናገሩን ቀጥሏል

ኢዮአኪን
የዕብራይስጡ ጽሁፍ "ኢኮንያን" ይላል፣ ይህ "ኢዮአኪን" ለሚለው የተሰጠ አማራጭ ስም ነው። ብዙ ዘመናዊ ቅጂዎች ነገሩን ግልጽ ለማድረግ ያው ንጉሥ የተጠቀሰበትን "ኢዮአኪን" የሚለውን ስም ይጠቀማሉ።

የተላኩት
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኔ የላኳቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 28:5

ያህዌ የተናገርከውን ትንቢት ያጽና
"ያህዌ በእውነት የተናገርከውን ትንቢት ያረጋግጥ"

Jeremiah 28:8

ከረጅም ዘመን በፊት ከእኔ እና ከአንተ አስቀድሞ የኖሩ ነቢያት
"ከእኔ እና ከአንት ከዘመናት በፊት የኖሩ ነቢያት"

ይህ ሲሆን እርሱ በእርግጥ ያህዌ የላከው ነቢይ መሆኑ ይታወቃል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ይህ ሲሆን እርሱ በእርግጥ ያህዌ የላከው እውነተኛ ነቢይ መሆኑ ታውቃለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 28:10

ልክ እንደዚህ
"ልክ ሐናንያ በኤርምያስ አንገት ላይ ያለውን ቀንበር እንዳነሳ"

ከእያንዳንዱ ህዝብ አንገት በባቢሎን ንጉሥ በናቡከደነጾር የተጫነውን ቀንበር እኔ እሰብራለሁ
ሐናንያ በባርነት ውስጥ የሚገኘው ህዝብ እንደ በሬዎች እንደሆነ እና ባቢሎናውያን ህዝቡ ላይ ለከባድ ስራ ቀንበር እንደጫኑበት አድርጎ ይናገራል። "እኔ መላው ህዝብ ከእንግዲህ የንጉሥ ናቡከደነጾር ባሪያ እንዳይሆን አደርጋለሁ" ወይም "እኔ እያንዳንዱን አገር ከባቢሎን ንጉሥ ከናቡከደነጾር

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ባርነት ነጻ አወጣለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እያንዳንዱ አገር
"አገር" የሚለው ቃል ለዚያ አገር ህዝብ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። "የሁሉም አገር ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በባቢሎን ንጉሥ በናቡከደነጾር የተጫነ ቀንበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነጾር የጫነው ቀንበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የተጫነ
በህዝብ ላይ የተደረገ

Jeremiah 28:12

የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል ወደ ኤርምያስ መጣ፣ "ሂድ
"ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር የዋለው ከእግዚአብሔር ዘንድ ልዩ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ተመሳሳይ የሆነው ሀረግ በኤርምያስ 1:4 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ለኤርምያስ መልዕክት ሰጠው። እንዲህም አለው፣ ‘ሂድ" ወይም "ያህዌ ይህንን መልዕክት ለኤርምያስ ነገረው፡ 'ሂድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ የእንጨቱን ቀንበር ሰብረሃል፣ ነገር ግን እኔ በምትኩ የብረት ቀንበር አደርጋለሁ
"አንተ ደካማውን ቀንበር ሰበርክ ነገር ግን እኔ ይህንን አንተ ልትሰብረው በማትችለው ቀንበር እተካለሁ"

የሰራዊት ጌታ ያህዌ... እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ናቡከደነጾርን እንዲያገለግሉት በእነዚህ ሁሉ አገራት አንገት ላይ የብረት ቀንበር አድርጌያለሁ
ያህዌ አገራትን የናቡከደነጾር ባሪያዎች እንደሚያደርግ የሚናገረው ከባድ ስራ እንዲሰሩ በበሬዎች ላይ ቀንበር እንደሚጭንባቸው አይነት አድርጎ ነው። "እኔ እነዚህን ሁሉ አገራት ባሮች አድርጌያለሁ፣ እናም እነርሱ ናቡከደነጾርን ማገልገል ይኖርባቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 28:15

እናንተ በያህዌ ላይ አምጻችኋል
"ያህዌ ለምን ስለ ራሱ በስም እንደተናገረ ግልጽ አይደለም። "አንተ ሰዎች በእኔ ላይ እንዲያምጹ ገፋፍተሃቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሦስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰባተኛው ወር
ይህ በዕብራውያን የወራት አቆጣጠር ሰባተኛው ወር ነው። ይህ በምዕራባውያን ወራት አቆጣጠር የመስከረም ወር መጨረሻ እና የጥቅምት ወር መጀመሪያ ነው። (የዕብራውያን ወሮች እና ተከታታይ ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 29

1 ነቢዩ ኤርምያስ ከምርኮ ሽማግሌዎች መካከል ወደ ተረፉት፣ ወደ ካህናቱም፣ ወደ ነቢያቱም፣ ናቡከደነፆር ከኢየሩሳሌም ወደ ባቢሎን ማርኮ ወዳፈለሰውም
ሕዝብ ሁሉ ከኢየሩሳሌም የላከው የደብዳቤው ቃል ይህ ነው። 2 ይህም የሆነው ንጉሡ ኢኮንያን፣ እቴጌይቱ እናቱ፣ ከፍተኛ መኮንኖቹ፣ የይሁዳና የኢየሩሳሌም
አለቆች፣ ጠራቢዎችና ብረት ሠራተኞችም ከኢየሩሳሌም ከወጡ በኋላ ነው። 3 ኤርምያስ የይሁዳ ንጉሥ ሴዴቅያስ ወደ ባቢሎን ንጉሥ ወደ ናቡከደነፆር
በላካቸው በሳፋን ልጅ በኤልዓሣና በኬልቅያስ ልጅ በገማርያ እጅ ደብዳቤውን እንዲህ ሲል ላከው። 4 ጥቅሉ እንዲህ ይላል፣ "የእስራኤል አምላክ የሠራዊት
ጌታ እግዚአብሔር ከኢየሩሳሌም ወደ ባቢሎን ላስማረክኋቸው ምርኮኞች ሁሉ እንዲህ ይላል፣ 5 'ቤት ሠርታችሁ ኑሩባቸው፣ አታክልትም ተክላችሁ ፍሬዋን ብሉ፤
6 ሚስቶችን ውሰዱ፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆችንም ውለዱ፤ ከዚያም ለወንዶች ልጆቻችሁ ሚስቶችን ውሰዱ፣ ሴቶች ልጆቻችሁንም ለባሎቻቸው ስጡ። እነርሱም
ወንዶችንና ሴቶችን ልጆች ይውለዱ፤ ከዚያም ተባዙ ጥቂቶችም አትሁኑ። 7 በእርስዋም ሰላም ይሆንላችኋልና ወደ እርስዋ ላስማርክኋችሁ ከተማ ሰላምን
ፈልጉ፣ ከእኔ ዘንድ ማልዱ።' 8 የእስራኤልም አምላክ፣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፣ 'በመካከላችሁ ያሉት ነቢያቶቻችሁና ምዋርተኞቻችሁ
አያታልሉአችሁ፣ እናንተም ራሳችሁ የምታልሙትን ሕልም አትስሙ። 9 በስሜ ሐሰተኛ ትንቢትን ይናገሩላችኋልና። እኔም አልላክኋቸውም። ይላል እግዚአብሔር።'
10 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ 'ባቢሎን ለሰባ ዓመታት በገዛቻችሁ ጊዜ፣ ወደዚህም ስፍራ እመልሳችሁ ዘንድ እረዳችኋለሁ፣ ደግሞም መልካሚቱን ቃሌን
እፈጽምላችኋለሁ። 11 ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ ራሴ አውቃለሁ፤ ይላል እግዚአብሔር፤ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የጥፋት
አይደለም። 12 እናንተም ወደ እኔ ትጠራላችሁ፣ ሄዳችሁም ወደ እኔ ትጸልያላችሁ፣ እኔም እሰማችኋለሁ። 13 እናንተ ትሹኛላችሁ፣ በፍጹም ልባችሁም ከሻችሁኝ
ታገኙኛላችሁ። 14 ከእናንተም ዘንድ እገኛለሁ፣ ይላል እግዚአብሔር፤ ምርኮአችሁንም እመልሳለሁ፤ ከአሕዛብም ሁሉ ዘንድ እናንተንም ከበተንሁበት ስፍራ ሁሉ
እሰበስባችኋለሁ፣ ይላል እግዚአብሔር፤ እናንተንም ለምርኮ ወዳፈለስሁበት ስፍራ እመልሳችኋለሁ።' 15 እናንተም፣ እግዚአብሔር በባቢሎን ነቢያትን
አስነሥቶልናል ብላችኋልና፣ 16 እግዚአብሔር በዳዊት ዙፋን ስለ ተቀመጠ ንጉሥ፣ በዚያች ከተማ ለቆዩት ሕዝቦች ሁሉ፣ ከእናንተም ጋር ስላልተማረኩት
ወንድሞቻችሁ፣ እንዲህ ይላል። 17 የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ 'ተመልከቱ፣ ሰይፍንና ራብን፣ በሽታንም እሰድድባቸዋለሁ። ከክፋቱም የተነሣ
ይበላ ዘንድ እንደማይቻል እንደ ክፉ በለስ አደርጋቸዋለሁ። 18 በሰይፍም፣ በራብም፣ በመቅሠፍትም አሳዳድዳቸዋለሁ፣ ባሳደድሁባቸውም አሕዛብ ሁሉ ዘንድ
ለመጠላት፣ ለመደነቂያ፣ ለማፍዋጫም፣ ለመሰደቢያም እንዲሆኑ በምድር መንግሥታት ሁሉ ዘንድ ለመበተን አሳልፌ እሰጣቸዋለሁ። 19 ይህም የሆነው ቃሌን
ስላልሰሙ ነው፣ ይላል እግዚአብሔር፤ በማለዳ ተነሥቼ ባሪያዎቼን ነቢያትን ወደ እነርሱ ሰድጃለሁና፤ በተደጋጋሚ ላክኋቸው፣ እናንተ ግን አልሰማችሁም፣ ይላል
እግዚአብሔር።' 20 ስለዚህ ከኢየሩሳሌም ወደ ባቢሎን የሰደድኋችሁ ምርኮኞች ሁሉ ሆይ፣ እናንተ ራሳችሁ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ፣ 21 'የእስራኤል
አምላክ፣ እኔ፣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር በስሜ ሐሰተኛ ትንቢትን ስለሚናገሩላችሁ ስለ ቆላያ ልጅ ስለ አክዓብና ስለ መዕሤያ ልጅ ስለ ሴዴቅያስ እንዲህ
እላለሁ፦ ተመልከቱ፣ በባቢሎን ንጉሥ በናቡከደነፆር እጅ አሳልፌ እሰጣቸዋለሁ። በዓይኖቻችሁም ፊት ይገድላቸዋል። 22 ከዚያም በባቢሎን ያሉ የይሁዳ
ምርኮኞች ሁሉ ስለ እነዚህ ሰዎች እርግማንን ይናገራሉ። እርግማኑም፦ እግዚአብሔር የባቢሎን ንጉሥ በእሳት እንደ ጠበሳቸው እንደ ሴዴቅያስና እንደ አክዓብ
ያድርግህ የሚል ነው። 23 በእስራኤል ዘንድ ስንፍና አድርገዋልና፣ ከጎረቤቶቻቸውም ሚስቶች ጋር አመንዝረዋልና፣ ያላዘዝኋቸውንም ቃል በስሜ በሐሰት
ተናግረዋልና ይህ ይሆናል። እኔም አውቃለሁ ምስክርም ነኝ፣ ይላል እግዚአብሔር።" 24 "ለኔሔላማዊው ለሸማያ እንዲህ በል፦ 25 'የእስራኤል አምላክ
የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በኢየሩሳሌም ወዳለው ሕዝብ ሁሉ፣ ወደ ካህኑም ወደ መዕሤያ ልጅ ወደ ሶፎንያስ፣ ወደ ካህናቱም ሁሉ
ደብዳቤዎችን በገዛ ስምህ እንዲህ ስትል ልከሃል፣ 26 "እያበደ ትንቢት የሚናገርን ሰው ሁሉ በእግር ግንድና በሠንሰለት ታኖረው ዘንድ በእግዚአብሔር ቤት
አለቃ እንድትሆን እግዚአብሔር በካህኑ በዮዳሄ ፋንታ ካህን አድርጎሃል። 27 አሁንስ፣ ትንቢት ተናጋሪውን የዓናቶቱን ሰው ኤርምያስን ስለ ምን አትገሥጸውም? 28
እርሱ፣ 'ጊዜው የረዘመ ነው። ቤት ገንቡና በውስጡ ኑሩበት፣ አትክልትንም ተክላችሁ ፍሬዋን ብሉ' ብሎ ወደ እኛ ወደ ባቢሎን ልኮአል።" 29 ካህኑም ሶፎንያስ
ይህን ደብዳቤ ነብዩ ኤርምያስ እየሰማ አነበበው። 30 የእግዚአብሔርም ቃል ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ፣ 31 "'እግዚአብሔር ስለ ኔሔላማዊው ስለ
ሸማያ እንዲህ ይላል፣ ብለህ ወደ ምርኮኞች ሁሉ ላክ፦ 'እኔ ሳልልከው ሸማያ ትንቢት ተናግሮላችኋልና፣ በሐሰትም እንድትታመኑ አድርጎአችኋልና፤ 32 ስለዚህ
እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ተመልከቱ፣ ኔሔላማዊውን ሸማያንና ዘሩን እቀጣለሁ። እኔም የማደርግላችሁን መልካሙን ነገር የሚያይ አንድም የእርሱ ሰው
በመካከላችሁ አይኖርም። ለሕዝቤ የማደርገውን አንዱንም መልካም ነገር አያይም ይላል እግዚአብሔር። እርሱ በእኔ፣ በእግዚአብሔር ላይ በእምነት ያልሆነ
ነገርን ተናግሯልና።"

Jeremiah 29:1

ከእየሩሳሌም የወጣ
"ከእየሩሳሌም የታወጀ"

የቀሩት ሽማግሌዎች
"አሁንም ገና በህይወት የሚገኙ ሽማግሌዎች"

ኢዮአኪን
የዕብራይስጡ ጽሁፍ "ኢኮንያን" ይላል፣ ይህ "ኢዮአኪን" ለሚለው የተሰጠ አማራጭ ስም ነው። ብዙ ዘመናዊ ቅጂዎች ነገሩን ግልጽ ለማድረግ ያው ንጉሥ የተጠቀሰበትን "ኢዮአኪን" የሚለውን ስም ይጠቀማሉ።

እቴጌይቱ እናቱ
የንጉሡ እናት

ከፍተኛ መኳንንት/ባለስላጣናት
"ዋና ዋና ባለስልጣናት"

በኤልዓሣ እጅ
ኤርምያስ የመጽሐፍ ጥቅልሉን ወደ ባቢሎን እንዲወስድ ለኤልዓሣ ሰጠው። አንባቢው ምናልባት ኤልዓሣ በመንገድ ሲጓዝ የጥቅልሉን መጽሐፍ ደህንነት ለመጠበቅ ሲል በመያዣ እንደጠበቀው ሊረዳ ይችላል። (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ኤልዓሣ...ሳፋን...ገማርያ...ኬልቅያስ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Jeremiah 29:4

የሰራዊት ጌታ ያህዌ፣ የእስራኤል አምላክ ...ለምርኮኞች ሁሉ እንዲህ ይላል
ሰዎች በዚያ ማህበረሰብ ደብዳቤ ሲጽፉ፣ መጀመሪያ ስማቸውን ይጽፋሉ፣ ከዚያም የሚጽፉለትን ሰው ስም፣ ቀጥሎም የደብዳቤውን ዋና ክፍል ይጽፋሉ። ያህዌ ራሱ ደብዳቤውን እንደጻፈ አድርጎ በስም ይናገራል።

የሰራዊት ጌታ ያህዌ... እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ቤቶችን በስራታችሁ ኑሩባቸው። ተክል ተክላችሁ ፍሬዎቻቸውን ብሉ
ያህዌ በዚያ ስፍራ ለረጅም ጊዜ እንደሚኖሩ እየነገራቸው ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 29:6

ለወንዶች ልጆቻችሁ ሚስቶችን ውሰዱ፣ ደግሞም ልጆቻችሁን ለባል ስጡ
ወላጆች የልጆቻቸውን ጋብቻ መምረጣቸው የተለመደ ነበር

የከተማይቱን ሰላም ፈልጉ
የከተማይቱ ሰላም ለሰዎች በሰላም መኖር ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። "የከተማይቱ ሰዎች በሰላም እንዲኖሩ የምትችሉትን ነገር ሁሉ አድርጉ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከተማይቱ...ለእሰረሷ...እርሷ ሰላም እንድትሆን
እነዚህ ቃላት የባቢሎንን ከተማ ያመለክታሉ

Jeremiah 29:8

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለተማረኩ እስራኤላውያን መናገሩን ይቀጥላል።

የሰራዊት ጌታ ያህዌ... እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

እናንተ ለራሳችሁ ያሏችሁ
ሌላው ሊሰጥ የሚችለው ትርጉም 1) እነዚህ ቃላት የሚያመለክቱት ህልሞችን ሳይሆን ሀሰተኛ ነቢያቱን እና ጠንቋዮችን ወይም 2) "በሀሰት ይተነብያሉ" የሚለው የሚያመለክተው ህልሞችን ሲሆን "እኔ አልልክኋቸውም" የሚለው ነቢያቱን እና ጠንቋዮቹን ያመለክታል።

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 29:10

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ምርኮኛ በሆኑ እስራኤላውያን ላይ ምን እንደሚደርስ መናገሩን ቀጥሏል

እናንተ
ምርኮኛ የሆኑ እስራኤላውያን

ሰባ አመታት
"70 አመታት" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 29:12

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ምርኮኛ በሆኑ እስራኤላውያን ላይ ምን እንደሚደርስ መናገሩን ቀጥሏል

ወደ እኔ ትጣራላችሁ
ጸሎት የተገለጸው በከፍተኛ ድምጽ እንደመጣራት ተደርጎ ነው

እኔም እሰማችኋለሁ
ይህ የሚያመለክተው ያህዌ እነርሱ የሚፈልጉትን እንደሚሰጣቸው ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ ትፈልጉኛላችሁ
ያህዌ የሚጠይቀውን ለማወቅ መፈለግ የተገለጸው ያህዌ የት እንዳለ ለማግኘት እንደ መሞከር ተደርጎ ነው። "እኔ እንድታደርጉ የምጠይቀውን፣ እናንተ ለማድረግ ትፈልጋላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ በሙሉ ልባችሁ እኔን ትፈልጋላችሁ
"እናንተ እኔን የምትፈልጉት ሙሉ ለሙሉ በቅንነት ይሆናል"

ለእናንተ እገኛለሁ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኔን እንድትፈልጉኝ እፈቅድላችኋለሁ" ወይም "እኔን ማግኘት ትችላላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመለከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እድል ፈንታችሁን ዳግም እመልሳለሁ
"ነገሮች ዳግም ለእናንተ መልካም እንዲሆኑ አደርጋለሁ" ወይም "ዳግም መልካም ህይወት እንድትኖሩ አደርጋለሁ"

እንድትሰደዱ አደርጋለሁ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ወደ ስደት እልካችኋለሁ" ወይም "ስደተኞች እንደትሆኑ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመለከቱ)

Jeremiah 29:15

አጠቃላይ መረጃ:
ኤርምያስ ምርኮኛ ለሆኑ እስራኤላውያን መናገሩን ቀጥሏል

በዳዊት ዙፋን ላይ ሚቀመጠው ንጉሥ
በዙፋን ላይ መቀመጥ ንጉሥ ሆኖ መግዛት ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። "እስራኤላውያንን ዳዊት

ይገዛ እንደነበረው የሚገዛ ንጉሥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

እዩ
ይህ አንባቢውን ቀጥሎ ለሚሆነው ነገር ያነቃዋል። "ተመልከቱ" ወይም "አድምጡ" ወይም "ትኩረት ስጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እኔ ሰይፍ፣ ረሃብ፣ እና ጥፋት በእነርሱ ላይ ልልክባቸው ነው
"ሰይፍ" የሚለው ቃል ለጦርነት ሜቶኖሚ/ነው። ሰይፍ፣ ረሃብ እና ጥፋት የተነገሩት እስራኤልን ለመጉዳት ያህዌን እንደሚታዘዙ ሰዎች ተደርገው ነው። "እኔ በጦርነት፣ በረሃብ፣ እና በበሽታ እንዲሞቱ ልቀጣቸው ተነስቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ለመበላት እንደማይችል እጅግ እንደ ተበላሸ በለስ አደርጋቸዋለሁ
የተበላሸ በለስ ጥቅም የለውም ምክንያቱም ሊበላ አይችልም፣ እንደዚያው ያህዌ የእስራኤልን ህዝብ ምንም የማይጠቅም አድርጎ አይቶታል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 29:18

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ በእስራኤላውያን ላይ የሚሆነውን መናገሩን ቀጥሏል።

ለድንጋጤ፣ ለእርግማን እና ንቀት እንዲሁም ለሀፍረት
እነዚህ ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ሲይዙ፣ የሌላ አገር ሰዎች ያህዌ በይሁዳ ህዝብ ላይ ያደረሰውን ሲሰሙ ምን ምላሽ እንደሚሰጡ ይገልጻል

ንቀት
ሰዎች አንድን ነገር ሳይቀበሉ ሲቀሩ የሚያሰሙት ድምጽ ነው

እናንተ አትሰሙም
"እናንተ አትታዘዙም"

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 29:22

ስለ እነዚህ ሰዎች መረገም በባቢሎን በተማረኩ አይሁዶች ዘንድ ሁሉ ይወራል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በባቢሎን የሚገኙ የይሁዳ ምርኮኞች ስለ እነዚህ ሰዎች መረገም ይናገራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የተጠበሰ
ይህ ቃል ብዙውን ጊዜ ምግብን ሙሉ በሙሉ ማቃጠልን ሳይሆን፣ በሚነድ እሳት ላይ ወይም በመጥበሻ ከሚገባው በላይ ማብሰልን ያመለክታል። ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ የፊደምዝም/የማያስደስትን ቃል ሻልባለ ቃል መተካት/ ነው። "እስከ ሞት መቃጠል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) የንጉሡ ወታደሮች እሳቱ ቀስ በቀስ ጠብሶ እስከሚገድላቸው ድረስ በምሰሶ ላይ አስረው ወደ እሳቱ አቅረበው ይለበልቧቸዋል፣ ነገር ግን አካላቸውን ሙሉ ለሙሉ እንዳያቃጥለው ከእሳቱ ራቅ ያደረጓቸዋል። (የፊደምዝም/የማያስደስትን ቃል ሻልባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ አውቃለሁ፣ እኔ ምስክር ነኝ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ያህዌ የሚደጋግማቸው ትኩረት ለመስጠት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 29:24

ሸማያ...መዕሴያ...ዮዳሄ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ኔሔላማዊ
ይህ የሰዎች ቡድን የወል ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰራዊት ጌታ ያህዌ... እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

በገዛ ራስህ ስም
"ስም" የሚለው ቃል ለየሰዎች ስልጣን እና ክብር ያመለክታል። "በራስህ ስልጣን እና ክብር ላይ ተመስርተህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ማሰሪያ/የእንጨት ቀንበር
በቅጣት ላይ የሚገኝን ሰው እግርን እና እጆችን ወይም ጭንቅላትን ውስጡ አስገብቶ ማሰሪያ ከእንጨት የተሰራ ቀንበር

Jeremiah 29:27

አጠቃላይ መረጃ፡
ይህ እየሩሳሌም ወደሚገኙ ሰዎች ሸማያ የላከውን ደብዳቤ ያጠናቅቃል

የሚቃወምህን...የዓናቶቱን ኤርምያስ ለምን አልገሰጽከውም?
ሸማያ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው የእየሩሳሌም ሰዎች ኤርምያስን ባለመቃወማቸው ሊገስጻቸው ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጽ ይችላል። "የሚቃወምህን...ዓናቶቱን ኤርምያስን እንድትገስጽ እፈልጋለሁ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እኛ ልኳል
ኤርምያስ ምን እንደላከ ይበልጥ ግልጽ ማድረግ ሊያስፈልግ ይችላል። "እርሱ ወደ እኛ መልዕክት ልኳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ቤቶችን በስራታችሁ ኑሩባቸው። ተክል ተክላችሁ ፍሬዎቻቸውን ብሉ
ተመሳሳይ የሆኑ ቃላት በኤርምያስ 29:5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

ነቢዩን ኤርምያስን በመስማት
"ስለዚህም ነቢዩ ኤርምያስ፣ እርሱ ይህን ሲያነብ ሊሰማ ይችላል ::" ተመሳሳይ የሆኑ ቃላት በኤርምያስ 2:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ::

Jeremiah 29:30

የያህዌ ቃል ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ፣ ''ላክ
ይህ ፈሊጥ የዋለው ከእግዚአብሔር ዘንድ ልዩ መልዕክት ለማስተዋወቅ ነው:: ተመሳሳይ የሆኑ ቃላት በኤርምያስ 1:4 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ:: "ያህዌ ለኤርምያስ መልዕክት ሰጠው:: እርሱ እንዲህ አለ፣ 'ላክ" ወይም "ያህዌ ለኤርምያስ ይህንን መልዕክት ነገረው፡ 'ላክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ፈሊጣዊ አነጋጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኔሔላማዊ ሸማያ
ይህ የወንድ ስም በኤርምያስ 29:24 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ::

መልካም የሆነው
ይህ እንደ ስማዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል:: "መልካም የሆኑት ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው:: ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ:: "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ በያህዌ ላይ አመጽ ተናግሯል
ያህዌ ስለ ራሱ ለምን በስም እንደተናገረ ግልጽ አይደለም:: "እርሱ ሰዎች በእኔ ላይ እንዲያምጹ አነሳስቷል" (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 30

1 ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ኤርምያስ የመጣው ቃል ይህ ነው፣ እንዲህም አለ፣ **2** "የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ 'የነገርኩህን ቃል ሁሉ በጥቅልል ላይ ጻፈው። **3** ተመልከት፣ የሕዝቤን የእስራኤልንና የይሁዳን ምርኮ የምመልስባት ዘመን ይመጣልና፣ ይላል እግዚአብሔር። ለአባቶቻቸውም ወደ ሰጠኋት ምድር እመልሳቸዋለሁ፣ እነርሱም ይገዙአታል። **4** እግዚአብሔር ስለ እስራኤልና ስለ ይሁዳ የተናገረው ቃል ይህ ነው፣ **5** "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ 'የሚያስፈራ ድምፅ ሰምተናል፤ የፍርሃት ነው እንጂ የሰላም አይደለም። **6** ጠይቁ፣ ወንድ ይወልድ እንደ ሆነ ተመልከቱ። እያንዳንዱ ወጣት ሰው እጁን በወገቡ ላይ ያደረገው ለምንድነው? እንደ ወላድ ሴት፣ ፊታቸው ሁሉ ወደ ጥቁረት የተለወጠው ለምንድነው? **7** ወዮ! ያ ቀን ታላቅ ይሆናልና፣ እርሱንም የሚመስል የለምና። ያ የያዕቆብ የመከራ ዘመን ነው፣ ነገር ግን ከእርሱ ይድናል። **8** በዚያ ቀን እንዲህ ይሆናል፣ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፤ ቀንበርን ከአንገትህ እሰብራለሁ፣ እስራትህንም እበጥሳለሁ፣ ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ ለሌላ አትገዛም። **9** ነገር ግን ለአምላካቸው ለእግዚአብሔር፣ በእነርሱ ላይ ንጉሥ ለማደርግላቸው ለንጉሣቸው ለዳዊትም ያገለግላሉ። **10** ስለዚህ፣ ባሪያዬ ያዕቆብ ሆይ፣ አትፍራ፣ ይላል እግዚአብሔር፤ አንተም እስራኤል ሆይ፣ አትደንግጥ። ተመልከቱ፣ አንተን ከሩቅ፣ ዘርህንም ከምርኮ አገር አድናለሁና። ያዕቆብም ይመለሳል ሰላምም ይሆናል፤ ደህንነቱም ይጠበቃል፣ ከዚያም በኋላ ማንም አያስፈራውም። **11** አድንህ ዘንድ ከአንተ ጋር ነኝና፣ ይላል እግዚአብሔር። አንተንም የበተንሁባቸውን አሕዛብ ፍጹም ማብቂያቸው እንዲመጣ አደርጋለሁ። አንተን ግን ፈጽሜ አላጠፋህም፣ በፍትህ እቀጣሃለሁ፣ ያለ ቅጣትም ከቶ አልተውህም።' **12** እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ 'ስብራትህ የማይፈወስ፣ ቍስልህም ያመረቀዘ ነው። **13** ጉዳይህን የሚሟገትልህ የለም፣ ቍስልህንም የሚፈውስ መድኃኒት የለህም። **14** አፍቃሪዎችሽ ሁሉ ረስተውሻል። አይፈልጉሽምም፣ በደልሽ ታላቅ ስለሆነ ኃጢአትሽም ስለ በዛ፣ በጠላት ማቍሰልና በጨካኝ አሠሪ ቅጣት አቍስዬሻለሁና። **15** ሕመምሽ የማይፈወስ ሆኖአልና ስለ ስብራትሽ ለምን ትጮያለሽ? በደልሽ ታላቅ ስለሆነ ኃጢአትሽም ስለ በዛ፣ ይህን አድርጌብሻለሁ። **16** ስለዚህ የሚበሉሽ ሁሉ ይበላሉ፣ ጠላቶችሽም ሁሉ ወደ ምርኮ ይወሰዳሉ። የዘረፉሽም ይዘረፋሉ፣ የበዘበዙሽንም ሁሉ ለመበዝበዝ አሳልፌ እሰጣለሁ። **17** እኔ ጤናሽን እመልስልሻለሁ ቍስልሽንም እፈውሳለሁ፣ ይላል እግዚአብሔር፤ ይህንንም የማደርገው፦ ማንም የማይሻት፤ የተጣለች ጽዮን" ብለው ጠርተውሻልና። **18** እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "ተመልከቺ፣ የያዕቆብን ድንኳን ምርኮ እመልሳለሁ፣ ለቤቱም እራራለሁ። ከተማይቱም በፍርስራሽ ጉብታዋ ላይ ትሠራለች፣ ምሽጉም እንደ ዱሮው ይሆናል። **19** ከዚያም ከእርሱ ዘንድ የምስጋናና የዘፋኞች ድምፅ ይወጣል፣ እኔም አበዛቸዋለሁ አላሳንሳቸውም፤ እንዳይዋረዱ እኔ አከብራቸዋለሁ። **20** ከዚያም ሕዝቦቻቸው እንደ ቀድሞ ይሆናሉ፣ ማኅበራቸውም በፊቴ ጸንቶ ይኖራል፤ የሚያስጨንቋቸውንም ሁሉ እቀጣለሁ። **21** መሪያቸው ከእነርሱ ውስጥ ይወጣል። እኔ ሳቀርበውና እርሱም ሲቀርበኝ ከመካከላቸው ይወጣል። ይህንን ባላደርግ፣ ወደ እኔ ለመቅረብ የሚደፍር ማን ነው? ይላል እግዚአብሔር። **22** እናንተም ሕዝብ ትሆኑኛላችሁ፣ እኔም አምላክ እሆናችኋለሁ። **23** ተመልከቱ፣ የእግዚአብሔር ዐውሎ ነፋስ፣ ቍጣው ወጥቷል። ሳይቋረጥ የሚያገለባብጥ ዐውሎ ነፋስ ወጥቶአል። የክፉዎችንም ራስ ይገለባብጣል። **24** የእግዚአብሔር ጽኑ ቍጣ የልቡን አሳብ ሠርቶ እስኪፈጽም ድረስ አይመለስም። በመጨረሻው ዘመን ታስተውሉታላችሁ።"

Jeremiah 30:1

ከያህዌ ዘንድ ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል፣ የመጣ ቃል
ፈሊጡ የዋለው ከእግዚአብሔር ዘንድ ልዩ መልዕክት ለማስተዋወቅ ነው። ተመሳሳይ የሆነ ሀረግ በኤርምያስ 1:4 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፤ እንደ አስፈላጊነቱም ግልጽ አድርጉት። "ያህዌ ለኤርምያስ የሰጠው መልዕክት ይህ ነው። እንዲህ አለ" ወይም "ያህዌ ለኤርምያስ ይህንን መልዕክት ሰጠው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ ተመልከት
"በጥንቃቄ አድምጥ ::" ይህ ሀረግ ያህዌ ቀጥሎ የሚናገረውን በጥንቃቄ ለመስማት ትኩረት ይፈጥራል

እኔ ሀብታችሁን የምመልስበት...ቀናቱ እየቀረቡ ነው
የሀብት/ዕድል ጊዜ የተገለጸው "ቀናት እየመጡ" እንደሆነ ተደርጎ ነው። ይህ ዘይቤ በኤርምያስ 7:32 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ወደፊት ... እድላችሁን አድሳለሁ" ወይም "እድላችሁን የማድስበት ጊዜ ይመጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

የህዝቤን የእስራኤልን እና ይሁዳን እድል ፈንታ አድሳለሁ
"ለህዝቤ ለእስራኤል እና ለይሁዳ ነገሮች ዳግም፣ መልካም እንዲሆኑ አደርጋለሁ" ወይም "ህዝቤ እስራኤል እና ይሁዳ ዳግም መልካም ህይወት እንዲኖሩ አደርጋለሁ።" በኤርምያስ 29:14 ላይ ተመሳሳይ የሆኑ ቃላት እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

Jeremiah 30:4

አጠቃላይ መረጃ:
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ መልዕክቱን የሚጽፈው በግጥም ነው። የዕብራውያን ስነግጥም የተለያዩ የትይዩ ንጽጽራዊ ግጥም መልኮችን ይጠቀማል። (ስነግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ ሰምተናል
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እነዚህ የያህዌ ራሱን "እኛ" ሲል የሚገልጽባቸው ቃሎች ናቸው። "እኔ ሰምቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) "አናንተ በከንቱ ትጮሃላችሁ ምክንያቱም አንዳች ሰላም የለም።"

Jeremiah 30:6

ወንድ አምጦ ይወልድ እንደሆነ ጠይቃችሁ እወቁ
"ወንድ አምጦ እንደማይወልድ ታውቃላችሁ"

እያንዳንዱ ወንድ ስለምን እጁን በወገቡ ላይ አድርጎ ልጅ ለመውለድ እንደምታምጥ ሴት ሆኖ እመለከታለሁ? ለምንስ የሁሉም ፊት ገረጣ?
ልትወልድ የምታምጥ ሴት አንዳች ነገር ማድረግ የምትችል ስትሆን፣ ታላቅ ስቃይም ይሰማታል። ወጣት ወንዶች በታላቅ ፍርሃት ውስጥ ሆነው መዋጋት ተስኗቸዋል። "ወጣት ወንዶች በምጥ ላይ እንደምትገኝ ሴት ወገባቸውን ይዘዋል፣ ደግሞም እጅግ ስለፈሩ የታመሙ ይመስላሉ። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የያቆብ ትውልድ ግን ከመከራ ይተርፋል
ያዕቆብ የሚለው ስም ለያዕቆብ ትውልዶች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "የያዕቆብን ትውልድ ግን እኔ ከዚህ አድናለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 30:8

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለእስራኤላውያን መናገሩን ቀጥሏል።

የአንገታችሁን ቀንበር እሰብራለሁ፣ ደግሞም ሰንሰለታችሁን እበጥሳለሁ
ባሪያ መሆን የተገለጸው እንደ እንስሳ ቀንበር እንደ መጫን እና እንደ እስረኛ ሰንሰለት እንደመልበስ/በሰንሰለት እንደ መታሰር ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አምላካቸውን ያህዌን ያመልኩታል... ንጉሣቸው... በእነርሱ ላይ
ያህዌ ስለ ያዕቆብ ትውልድ መናገሩን ቀጥሏል። "አምላካችሁን ያህዌን ታመልኩታላችሁ... ንጉሣችሁ... በእናነት ላይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሣቸው ዳዊት
ይህ ከዳዊት ትውልዶች ለአንዱ ሜቶኖሚ/ ነው። "ከንጉሣቸው ከዳዊት ትውልድ የሆነ " በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 30:10

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለእስራኤላውያን መናገሩን ቀጥሏል።

ባሪያዬ ያዕቆብ... እስራኤል
"ያዕቆብ" እና "እስራኤል" የእስራኤላውያን አባቶች ስሞች ናቸው፣ ደግሞም እነዚህ ስሞች ለእስራኤላውያን ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ናቸው። "እናንተ የእስራኤል ሰዎች ...የያዕቆብ ትውልዶች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

አትጨነቁ
"ተስፋ አትቁረጡ"

እነሆ እኔ እንደሆንኩ እዩ
"እኔ ለምን እኔ ነኝ እንደምል በጥንቃቄ አድምጡ"

ከምርኮ ምድር
"ምርኮ" የሚለው ረቂቅ ስም፣ "ምርኮኛ" የሚለውን ስም በመጠቀም መተረጎም ይችላል። "ምርኮኛ ከነበሩበት ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ያዕቆብ ይመለሳል... እርሱ በሰላም ይቀመጣል
የያዕቆብ ስም ለትውልዶቹ ሜቶኖሚ/ ነው። ያህዌ ለያዕቆብ የሚናገረው ለሌላ ሰው እንደሚናገር አድርጎ ነው። ያዕቆብ ወዴት እንደሚመለስ ይበልጥ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። "ያዕቆብ ወደ ራሱ ምድር ይመለሳል... በሰላም ይጠበቃል" ወይም "የያዕቆብ ትውልዶች ይመለሳሉ... ደህንነታቸው ይጠበቃል" ወይም "እናንተ የያዕቆብ ትውልዶች ትመለሳላችሁ... ደህንነታችሁ ይጠበቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

አስተማማኝ
"በደህና መጠበቅ"

እኔ እናንተን ከበተንኩበት
"እኔ ከላክኋችሁ ስፍራ"

ነገር ግን በእርግጥ እኔ አላጠፋችሁም
"ነገር ግን እኔ ሙሉ ለሙሉ አላጠፋችሁም" (ዩፊምዝም/የማያስደስትን ቃል ሻልባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

በእርግጥ ሳልቀጣችሁ አልቀርም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "በእርግጥ እቀጣችኋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አሉታዊ ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 30:12

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለእስራኤላውያን መናገሩን ቀጥሏል።

ጉዳታችሁ የማይድን ነው ቁስላችሁ መርቅዟል...ለቁስላችሁ ፈውስ የለውም
ይህ ማለት ያህዌ እነርሱን ማንም ሊረዳቸው የሚችል እስማይገኝ ድረስ እጅግ በጣም ቀጥቷቸዋል ማለት ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ እናንተ የሚማጸን አይኖርም
"ምህረት እንዳደርግላችሁ ስለ እናንተ ወደ እኔ ልመና የሚያቀርብ ማንም የለም"

Jeremiah 30:14

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለእስራኤላውያን መናገሩን ቀጥሏል።

ወዳጆቻችሁ ሁሉ
ያህዌ የእስራኤልን ሰዎች ከባሏ ውጭ ሌሎች ፍቅረኞችን እንደምትይዝ ታማኝ ያልሆነች ሚስት ይገልጻቸዋል። እዚህ ስፍራ "ፍቅረኞች" የሚለው የሚያመለክተው ሌሎች ሀገራትን ነው። እስራኤላውያን በያህዌ ከመታመን ይልቅ ከእነርሱ ጋር ተባብረው ጣኦቶቻቸውን ያመልካሉ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ እናንተን አይፈልጉም
"እነርሱ ከእንግዲህ የእናንተ ወዳጆች መሆን አይፈልጉም"

ጠላት እንደሚያቆስል አቆሰልኳችሁ
ያህዌ በጠላቶቹ ላይ እንደሚያደርግ በህዝቡ ላይ አደረገባቸው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የጨካን ጌታ ቅጣት/እርምት
ያህዌ ህዝቡን ጨካኝ ጌታ አመጸኛ ባሪያን እንደሚቀጣ ቀጣቸው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ ደረሰባችሁ ጉዳት ለምን ለእርዳታ ትጣራላችሁ?
እዚህ ስፍራ ያህዌ ጥያቄ የሚጠይቀው ህዝቡ ለምን አሁን እርዳታ እንደሚጠይቁት እንዲያስቡ ለማድረግ ነው። "ጉዳት የደረሰባችሁ እና አሁን እርዳታ ለማግኘት የምትጣሩት እኔን ባለመታዘዛችሁ ምክንያት ነው" ወይም

"በደረሰባችሁ ጉዳት እርዳታ ለማግኘት ጥሪ አታሰሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለምልልሰዳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ከቁጥር ያለፈው ኃጢአታችሁ
"የእናንተ ኃጢአት ለመቁጠር እጅግ ብዙ ነው"

Jeremiah 30:16

ስለዚህም እናንተን የሚፈጅ/የሚበላ ሁሉ ይፈጃል/ይበላል
ህዝቡን ማጥፋት የተገለጸው እርሱን እንደ መፍጀት ወይም መብላት ተደርጎ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ስለዚህም እናንተን ያጠፉትን፣ ጠላቶቻቸው ደግሞ እነርሱን ያጠፏቸዋል" ወይም "እናንተን ያጠፉትን ሁሉ እኔ አጠፋቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመለከቱ)

የዘረፏችሁ...ይዘረፋሉ/ይቀማሉ
መዝረፍ ማለት ከሰላማዊ ህዝብ ሀይል ተጠቅሞ መቀማት/መስረቅ ሲሆን ዝርፊያ ሰዎች የቀሙት ነገር ነው።

ማበላሸት...ብልሹ
እዚህ ስፍራ ማበላሸት ማለት አንድ ወገን ካሸነፈው ጠላት መውሰድ ሲሆነ፣ የተወሰዱት ነገሮች የተበላሹ ናቸው።

መፈወስ...ቁስሎች
እነዚህ ቃላት በኤርምያስ 30:12 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ እናንተን፡ የተናቁ ይሏችኋል
የተናቀ ማለት ሌሎች ሰዎች የማይቀበሉት ወይም ከእነርሱ ጋር ህብረት እንዲያደርግ የማይፈቅዱለት ሰው ማለት ነው። "የተናቁ ብለው ይጠሯችኋል" ወይም "እነርሱ፣ ‘ማንም እናንተን አይፈልግም' ይላሉ"

ማንም ለዚህች ለጽዮን ግድ አይለውም
"ጽዮን" የሚባለው ስፍራ ስም በጽዮን ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ ነው። "ማንም ለጽዮን ሰዎች ግድ የለውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

Jeremiah 30:18

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለእስራኤላውያን መናገሩን ቀጥሏል።

እዩ/እነሆ
"ተመልከቱ" ወይም "አድምጡ" ወይም " ቀጥሎ ለምነግራችሁ ነገር ትኩረት ስጡ"

የያዕቆብን ድንኳን ዕድል ፈንታ እመልሳለሁ፣ ለቤቱም እራራለሁ
ሰዎች የሚኖሩበት ስፍራ በነዚያ ፍራዎች ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። "የያዕቆብን ትውልድ እድል ፈንታ ልመልስ ተዘጋጅቻለሁ፣ ደግሞም ለእነርሱ እራራለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያም በፍርስራሾች ክምር ላይ ከተማ ይመሰረታል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። የሚገነቧት ከተማ እየሩሌም እንደሆነች ግልጽ ማድረግ ሊያስፈልግ ይችላል። "ከዚያም እየሩሳሌምን በፍርስራሾቿ ላይ ይመሰርታሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያም የምስጋና ዝማሬ እንደዚሁም የደስታ ድምጽ ከእነርሱ ዘንድ ይሰማል
"ከዚያም እነርሱ የምስጋና እና ሀሴት መዝሙሮችን ይዘምራሉ"

እኔ አበዛቸዋለሁ እንጂ አላሳንሳቸውም
"በቁጥር እንዲበዙ አደርጋለሁ እንጂ እንዲመናመኑ አላደርግም"

ስለዚህም ዝቅዝቅ አይሉም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ማንም ዝቅ አድርጎ አይመለከታቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 30:20

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለእስራኤላውያን መናገሩን ቀጥሏል።

ማህበራቸው በፊቴ ይጸናል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እኔ በፊቴ እንደ ህዝብ አጸናቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እኔ በድፍረት መቅረብ የሚችል ማን ነው?
ያህዌ ይህን ጥያቄ የተጠቀመው እርሱ ካላቀረበው በስተቀር ማንም ደፍሮ ወደ እርሱ መቅረብ እንደማይችል ትኩረት ለመስጠት ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 30:23

እነሆ፣ የያህዌ ፈተና፣ የእርሱ ቁጣ፣ ወጥቷል
ይህ የእግዚአብሔርን ቁጣ እና ቅጣት ማዕበል እንደሆነ አድርጎ ይገልጻል። ይህ የእርሱን ክፉ ሰዎችን የማጥፋት ሀይል እና ችሎታ ያጎላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የልቡ ሃሳብ
"ሀሳብ/ፈቃድ" የሚለው ረቂቅ ስም "አሰበ" የሚለውን ግስ ተጠቅሞ መተርጎም ይቻላል። ልብ የሚለው ቃል ለጠቅላላው የሰው ማንነት ሴኔቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ነው። "እርሱ ሊያደርግ ያሰበው/የፈቀደው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 31

1 "በዚያን ዘመን፣ ይላል እግዚአብሔር፣ ለእስራኤል ወገኖች ሁሉ አምላክ እሆናቸዋለሁ እነርሱም ሕዝብ ይሆኑኛል።" 2 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣
"እስራኤልን ለማረድ ከመጣው ሰይፍ የተረፈው ሕዝብ በምድረ በዳ ሞገስ አገኘ።" 3 እግዚአብሔር በኃላፊው ጊዜ ተገለጠልኝና እንዲህ አለኝ፣ "እስራኤል
ሆይ፣ በዘላለም ፍቅር ወድጄሻለሁ። ስለዚህ በኪዳን ታማኝነት ወደራሴ ሳብሁሽ። 4 የእስራኤል ድንግል ሆይ፣ እንደ ገና እነነባሻለሁ አንቺም ትገነቢያለሽ። እንደ
ገናም ከበሮሽን አንሥተሽ ከዘፋኞች ጋር ወደ ደስታ ጭፈራሽ ትወጫለሽ። 5 እንደ ገናም በሰማርያ ተራሮች ላይ የወይን ቦታዎችን ትተክያለሽ፤ ገበሬዎች
ይተክላሉ፣ ፍሬውንም በመልካም ይጠቀሙበታል። 6 በኤፍሬምም ተራሮች ላይ ያሉ ተመልካቾች፣ 'ተነሡ፣ ወደ ጽዮን ወደ አምላካችን ወደ እግዚአብሔር
እንውጣ.' ብለው የሚጮኹበት ቀን ይመጣልና።" 7 እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፣ "ስለ ያዕቆብ በደስታ ጩኹ! ስለ አሕዛብም አለቆች በደስታ ጩኹ!
ምስጋና ይሰማ። 'እግዚአብሔር ሕዝቡን፣ የእስራኤልን ቅሬታ አድኖአል' በሉ። 8 ተመልከቱ፣ ከሰሜን ምድር አመጣቸዋለሁ። ከምድርም ዳርቻ እሰበስባቸዋለሁ።
በመካከላቸውም ዕውሩና አንካሳው፣ ያረገዙ ሴቶችና ሊወልዱ ያሉ ሴቶች በአንድነት ይሆናሉ። ታላቅ ጉባኤ ሆነው ወደዚህ ይመለሳሉ። 9 በልቅሶ መጡ፤
ልመናቸውን ሲያደርጉ እመራቸዋልሁ። በወንዝ ዳር በቀጥተኛ መንገድ አስኬዳቸዋለሁ። በእርሱም አይሰናከሉም፣ እኔ ለእስራኤል አባት እሆናለሁና፣ ኤፍሬምም
በኵሬ ነውና።" 10 "አሕዛብ ሆይ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ፣ በሩቅም ላሉ ደሴቶች አውሩ። እናንተ አህዛብ፣ "እስራኤልን የበተነ እርሱ ይሰበስባታል፣ እረኛም
መንጋውን እንደሚጠብቅ ይጠብቃታል" በሉ። 11 እግዚአብሔር ያዕቆብን ተቤዠቶታል፣ ከበረታበትም እጅ አድኖታል። 12 ከዚያም ይመጡና በጽዮን ተራራ
ይፈነድቃሉ። ወደ እግዚአብሔርም መልካምነት፣ ወደ እህልና ወደ ወይን ጠጅ፣ ወደ ዘይትም፣ ወደ በጎችና ወደ ላሞች ይሰበሰባሉ። ነፍሳቸውም እንደ ረካች ገነት
ትሆናለች፣ ከእንግዲህም ወዲህ ኃዘን አይሰማቸውም። 13 በዚያን ጊዜ ደናግሉ በዘፈን ደስ ይላቸዋል፣ ወጣቶቹና ሽማግሌዎቹም በአንድ ላይ ይሆናሉ።
ለቅሷቸውን ወደ ክብረ-በዓል እለውጣለሁና። እራራላቸዋለሁ፣ ከኅዘናቸውም ይልቅ እንዲፈነድቁ አደርጋቸዋለሁ። 14 ከዚያም የካህናቱን ነፍስ በብዛት
አረካታለሁ። ሕዝቤም መልካምነቴን ይጠግባል ይላል እግዚአብሔር።" 15 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "የዋይታና የመራራ ለቅሶ ድምፅ በራማ ተሰማ። ስለ
ልጆችዋ የምታለቅሰው ራሔል ናት። ከእንግዲህ አይኖሩምና ስለ ልጆችዋ መጽናናትን እንቢ አለች።" 16 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "ድምፅሽን ከለቅሶ፣
ዐይንሽንም ከእንባ ከልክዪ፤ ምክንያቱም ለመከራሽ ካሳ አለ፤ ልጆችሽ ከጠላት ምድር ይመለሳሉ። 17 ለፍጻሜሽ ተስፋ አለ፣ ይላል እግዚአብሔር፤ ልጆችሽም
ወደ ዳርቻቸው ይመለሳሉ።" 18 "ኤፍሬም፣ 'ቀጣኸኝ፣ እኔም ተቀጣሁ። እንዳልተገራ ወይፈን መልሰህ አምጣኝ፣ አንተ እግዚአብሔር አምላኬ ነህና እኔም
እመለሳለሁ። 19 ወደ አንተ ከተመለስሁ በኋላ፣ ተጸጸትሁ፤ ከሠለጠንሁም በኋላ፣ በኃዘን ጭኔን መታሁ፤ በወጣትነቴ በደልን ተሸክሜአለሁና አፈርሁ፣
ተዋረድሁ።' 20 ኤፍሬም ለእኔ የከበረ ልጅ አይደለምን? ወይስ የምደሰትበት ሕጻን ነውን? በእርሱ ላይ በተናገርሁ ቍጥር፣ እንደዚያም ሆኖ በፍቅር
አስበዋለሁ። በዚህ መልኩ ልቤ ትናፍቀዋለች። በእርግጥም እራራለታለሁ ይላል እግዚአብሔር።" 21 ለራስሽ የመንገድ ምልክት አድርጊ። ለራስሽም መንገድን
የሚመሩ ዓምዶችን ትከዪ። አሳብሽንም ልትሄጂበት ወደሚገባው ትክክለኛ መንገድ አድርጊ። የእስራኤል ድንግል ሆይ፣ ተመለሺ! ወደ እነዚህም ወደ ከተሞችሽ
ተመለሺ። 22 አንቺ እምነት የለሽ ልጅ ሆይ፣ እስከ መቼ ትቅበዘበዣለሽ? እግዚአብሔር በምድር ላይ አዲስ ነገር ፈጥሮአልና፤ ብርቱ ወንዶችን ለመጠበቅ ሴቶች
ይከብባሉ። 23 የእስራኤል አምላክ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "ሕዝቡን ወደ ምድራቸው ባመጣኋቸው ጊዜ፣ በይሁዳ ምድርና በከተሞችዋ
እንዲህ ይላሉ፣ 'እርሱ የሚኖርብሽ የጽድቅ ማደሪያ፣ የቅድስና ተራራ ሆይ፣ እግዚአብሔር ይባርክሽ።' 24 ይሁዳና ከተሞቹ ሁሉ በአንድነት በእርስዋ ይኖራሉ።
ገበሬዎችና እረኞች ከመንጎቻቸው ጋር በዚያ ይገኛሉ። 25 ለደከሙት የሚጠጡትን ውሃ እሰጣለሁና፣ በጥማት የሚሰቃዩትን ሁሉ በእርካታ እሞላለሁ። 26
ከዚህም በኋላ ነቃሁ፣ እንቅልፌ የሚያነቃ እንደሆነ አስተዋልኩኝ። 27 "ተመልከቱ፣ የእስራኤልን ቤትና የይሁዳን ቤት በሰውና በእንስሳ ዘር የምዘራበት ዘመን፣
እንደሚመጣ ተመልከቱ ይላል እግዚአብሔር። 28 እንዲህም ይሆናል፣ አፈርሳቸውና፣ ክፉ አድርግባቸው ዘንድ እንደ ተጋሁባቸው፣ ነገር ግን በሚመጡት
ዘመናት፣ እንዲሁ እሠራቸውና፣ እተክላቸው ዘንድ አተጋለሁ፤ ይላል እግዚአብሔር። 29 በዚያ ዘመን ሰው ዳግመኛ እንዲህ አይልም፣ 'አባቶች መራራ የወይን ፍሬ
በሉ፣ ነገር ግን የልጆች ጥርሶች ጠረሱ።' 30 ነገር ግን ሰው ሁሉ በገዛ በደሉ ይሞታል፤ መራራውን የወይን ፍሬ የሚበላ ሁሉ ጥርሶቹ ይጠርሳሉ። 31
ተመልከቱ፣ ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል፣ ይላል እግዚአብሔር። 32 ከግብጽ ምድር አወጣቸው ዘንድ
እጃቸውን በያዝሁበት ቀን ከአባቶቻቸው ጋር እንደ ገባሁት ያለ ቃል ኪዳን አይደለም። ምንም እንኳን እኔ ባላቸው ብሆንም፣ እነርሱ ኪዳኔ ላይ ዐምጸዋልና፣ ይላል
እግዚአብሔር። 33 ከእነዚያ ወራት በኋላ ከእስራኤል ቤት ጋር የምገባው ቃል ኪዳን ግን ይህ ነውና፣ ይላል እግዚአብሔር፦ ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፣
በልባቸውም እጽፈዋለሁ፤ እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ፣ እነርሱም ሕዝብ ይሆኑኛል። 34 ከዚያም እያንዳንዱ ሰው ባልንጀራውን፣ ወይም እያንዳንዱ ሰው
ወንድሙን፣ 'እግዚአብሔርን እወቅ ብሎ አያስተምርም፤ ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ ሁሉ ያውቁኛልና፣ ይላል እግዚአብሔር። በደላቸውን እምራቸዋለሁና፣
ኃጢአታቸውንም ከእንግዲህ ወዲህ አላስብምና።" 35 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ ፀሐይን በቀን የጨረቃንና የከዋክብትን ሥርዓት በሌሊት ብርሃን አድርጎ
የሚሰጥ እግዚአብሔር ነው። እንዲተምሙም የባሕርን ሞገዶች የሚያናውጥ እርሱ ነው። ስሙ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው። እርሱ እንዲህ ይላል፣ 36
"እነዚህ ቋሚ ነገሮች ከእይታዬ ቢወገዱ፣ ይላል እግዚአብሔር፣ በዚያን ጊዜ ደግሞ የእስራኤል ዘር በፊቴ ሕዝብ እንዳይሆን ለዘላለም ይቀራል።" 37
እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "ከፍ ያሉት ሰማያት ሊለኩ ቢችሉ፣ የምድርም መሠረት ከታች ቢመረመር፣ በዚያን ጊዜ ስላደረጉት ነገር ሁሉ የእስራኤልን ዘር ሁሉ
እጥላለሁ፣ ይላል እግዚአብሔር።" 38 "ተመልከቱ፣ ከሐናንኤል ግንብ ጀምሮ እስከ ማዕዘኑ በር ድረስ ከተማ ለእግዚአብሔር የሚሠራበት ዘመን ይመጣል፣
ይላል እግዚአብሔር። 39 የተለካበትም ገመድ ወደ ጋሬብ ኮረብታ በቀጥታ ወደ ፊት ይሄዳል፣ ወደ ጎዓም ይዞራል። 40 የሬሳም ሸለቆ ሁሉ የአመድም እርሻ ሁሉ
እስከ ቄድሮን ወንዝ ድረስ በምሥራቅ በኩል እስካለው እስከ ፈረሰ በር ማዕዘን ድረስ ለእኔ፣ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ይሆናል። ከእንግዲህም ወዲህ ለዘላለም
አይነቀልም አይፈርስምም።"

Jeremiah 31:1

አጠቃላይ መረጃ:
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ ትንቢቱን የሚጽፈው በግጥም መልክ ነው። የዕብራውያን ስነግጥም የተለያዩ ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤዎችን ይጠቀማል። (ስነግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

በዚያን ጊዜ
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ክፉዎችን የሚቀጣበትን ጊዜ ነው።

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ከሰይፍ የተረፉት በበረሃ ሞገስ ያገኛሉ
"ሞገስ ማግኘት" የሚለው ሀረግ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ከሰይፍ ላመለጡ ሰዎች እኔ በበረሃ ስፍራ ጸጋን በእነርሱ ላይ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከሰይፍ ያመለጡ
"ሰይፍ" የሚለው ቃል ጦርነት ለሚለው ሜቶኖሚ/ ነው። "ከጦርነት ያመለጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በበረሃ ለእስራኤል እረፍት ለመስጠት እወጣለሁ
ሊሰጥ የሚችለው አማራጭ ትርጉም "እስራኤል ረፍት ለማግኘት ወደ በረሃ ይወጣል"

ያህዌ ለእኔ ተገለጠልኝ
ኤርምያስ ስለ እራሱ፣ እርሱ የእስራኤል ህዝብ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በቃል ኪዳን ታማኝነት እኔ አንቺን ወደ ራሴ ሳብኩሽ
"ታማኝነት" የሚለው ረቂቅ ስም "ታማኝ" ወይም "በታማኝነት" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "እኔ ለቃል ኪዳኔ ታማኝ ሆኜ ወደ ራሴ አቀረብኩሽ" ወይም "እኔ በታማኝነት ወድጄ ወደ ራሴ አቀረብኩሽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 31:4

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለእስራኤል ህዝብ መናገሩን ይቀጥላል።

እኔ ዳግመኛ እስራሻለሁ አንቺም ትጸኛለሽ
ያህዌ በአላማ እስራኤልን እንደሚያጸና ትኩረት ለምጠት ሃሳቡን ይደግማል። ቋንቋችሁ የድርጊት ግስን ብቻ የሚጠቀም ከሆነ እና ለሃሳቡ ትኩረት ለምጠት ሌላ አማራጭ መንገድ ካላችሁ እዚህ ሰስፍራ ይህን መጠቀም ትችላላችሁ። "እኔ እናንተን ዳግም አጸናለሁ። ይህን አስታውሱ: እኔ አጸናችኋለሁ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ድንግሊቱ እስራኤል
አገራትን በሴት መግለጽ የተለመደ ነገር ነበር። ሆኖም፣ "ድንግል" የሚለው ቃል አንድን ሰው አግብታ ስለማታውቅ ወጣት ሴት እና ለባል ታማኝ ለመሆን እድል አግኝታ ስለማታውቅ ሴት እንዲያስብ ያደርገዋል። ስለዚህ እስራኤልን ድንግል ብሎ መጥራት ምጸታዊ የሆነ አነጋገር ነው። ይህ በኤርምያስ 18:13 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "በሀሰት ለእኔ ራሷን ሙሉለሙሉ ታማኝ አድርጋ እንዳቀረበች የምታስመስለው እስራኤል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ እና ምጸት የሚሉትን ይመልከቱ)

ከበሮ መሰል የሙዚቃ መሳሪያ/ታምቦሪኒ
አናቱ ከበሮ የሚመስል ቁርጥራጭ ብረቶች ከጎኑ ያሉት እና ሲመቱት ብረቶቹ እየተንቃጨሉ ድምጽ የሚሰጥ የሙዚቃ መሳሪያ። (የማይታወቁ ነገሮችን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 31:7

የደስታ ጩኸት ጩኹ... እልል በሉ...ምስጋና ይሰማ...በሉ
ያህዌ ለመላው የዓለም ህዝብ በአጋኖ ይናገራል፣ ለዚህ እነዚህ ግሶች ብዙ ቁጥር ናቸው። (አጋኖ እና ተውላጠ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

የአገራቱ አለቆች
"የአገራቱ ታላላቅ ሰዎች የሚባሉ የህዝብ ክፍሎች" ወይም "ከሌላው ይልቅ ከፍ ያለ ስፍራ የተሰጣቸው የህዝብ ክፍሎች"

ምስጋና ይሰማ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እያንዳንዱ ድምጻችሁን እንዲሰማ አድርጉ"በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 31:8

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ እንዴት የእስራኤልን ህዝብ ከተማረኩበት ከባቢሎን እንደሚመልስ መናገሩን ቀጥሏል።

እነሆ
"ተመልከቱ" ወይም "አድምጡ" ወይም "ቀጥሎ የምነግራችሁን ለመስማት ትኩረት ስጡ"

እነርሱን ለማምጣት
"እስራኤላውያንን ለማምጣት"

ደስታቸውን ሲገልጹ እኔ እመራቸዋለሁ
ያህዌ ይመራቸዋል እነርሱም ወደ ያህዌ ይጸልያሉ። አንዳንድ ጥንታዊ ቅጂዎች፣ "ያህዌ ይመራቸዋል ደግሞም ያጽናናቸዋል" ይላሉ።

እኔ ለእስራኤል አባት እሆናለሁ፣ ኤፍሬም በኩሬ ይሆናል
እዚህ ስፍራ "ኤፍሬም" ለ "እስራኤል" ሌላው ስሙ ነው። "ለእስራኤል ህዝብ እንደ አባት እሆናለሁ፣ እነርሱም ለእኔ እንደ በኩር ልጅ ይሆኑኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

የመጀመርያ ልጄ/ የኩር ልጄ
የበኩር ልጅ ልዩ ክብር እና ሀላፊነት አለበት

Jeremiah 31:10

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ እንዴት የእስራኤልን ህዝብ ከተማረኩበት ከባቢሎን እንደሚመልስ መናገሩን ቀጥሏል።

አድምጡ ... ተናገሩ
ያህዌ ለአገራት ይናገራል፣ ስለዚህ እነዚህ ግሶች ብዙ ቁጥር ናቸው። (ተውላጠ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እስራኤልን የበተናት እርሱ መልሶ ይሰበስባታል ደግሞም ይተብቃታል
ያህዌ ስለ ራሱ እንደ ሌላ አድርጎ ይናገራል፤ ስለ እስራኤል ህዝብ ደግሞ እርዳታ ያጣች ሴት አድርጎ ይናገራል። "እኔ ህዝቤ እስራኤል በአገራት መሃል እንዲበተን አድርጌያለሁ፣ ነገር ግን አሁን ወደ ቤታቸው እመልሳቸዋለሁ ደግሞም እጠብቃቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተውላጠ ስሞች እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

እረኛ በጎቹን እንደሚጠብቅ
እረኛ በጎቹን ይጠብቃል ይንከባከባልም፣ እናም ያህዌ እስራኤላውያንን እንደሚንከባከብ እና እንደሚጠብቅ ቃል እየገባ ነው።" (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ ያዕቆብን እንደ ተቤዠ ለእርሱ እጅግ ከባድ ከሆነበት እጅ እንዳዳነው
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው፣ የእስራኤልን ህዝብ የታደገው ያህዌ እንደሆነ ትኩረት ይሰጣሉ። "ያህዌ የእስራኤልን ህዝብ እጅግ ከባድ ከሆኑባቸው "ጠላቶቻቸው ታድጓል በሚለው ውስጥ

እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 31:12

በጽዮን ኮረብቶች/ከፍታዎች
"በጽዮን፣ በከፍታ ስፍራ" ወይም "በጽዮን ተራራ።" ከኮረብታ ጫፍ መሆን ለድተኛነት ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። የእናንተ ቋንቋ የተራራን ጫፍ ከሀዘን ጋር የሚያያይዝ ከሆነ፣ እዚህ ስፍራ ይህንን ዘይቤ አለመጠቀም ይመረጣል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በውሃ እንደ ረሰረሰ የአትክልት ስፍራ
ይህ ማለት ጠንካራ እና ጤናማ ይሆናሉ፣ እንዲሁም ይበለጽጋሉ ማለት ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህ ዳግም በፍጹም ሀዘንተኛ አይሆኑም
"በፍጹም" የሚለው ቃል አጠቃላይ አስተያየት ነው። እስራኤላውያን ከእንግዲህ ከሞላ ጎደል ሁሌም ደስተኞች ይሆናሉ። (ኩሸት እና አጠቃላ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 31:13

ሀዘናቸውን እኔ ወደ ደስታ/በዓል እለውጣለሁ
"ሀዘን" እና "ደስታ/በዓል" የሚሉት ረቂቅ ስሞች በግስ መልክ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "ከእንግዲህ እንዲያዝኑ አላደርግም በዚህ ፈንታ ደስተኛ አደርጋቸዋለሁ" ወይም "ከእንግዲህ አያዝኑም ነገር ግን ደስተኛ አደርጋቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እኔ አደርጋለሁ/እለውጣለሁ
"ያህዌ ይለውጣል"

የካህናቱን ህይወት አትረፍርፌ እሞላለሁ
"መትረፍረፍ" የሚለው ረቂቅ ስም "ብዙ መላካም ነገሮች" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። የካህናቱ ህይወት የተነገረው ዝናብ አግኝቶ ሙሉ ለሙሉ ለምለም እንደሆነ መስክ ነው። ህይወት የሚለው ለሰውየው ሜቶኖሚ/ ነው። "እኔ ለካህናቱ የሚፈልጉትን መልካም ነገር ሁሉ እሰጣቸዋለሁ" ወይም "ካህናቱን በመልካም ነገሮች አረካለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ዘይቤያዊ አነጋገር እንደዚሁም ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

ህዝቤ በመልካምነቴ ራሳቸውን ይሞላሉ
"መልካምነቴ ህዝቤን ያረካል"

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 31:15

በራማ ድምጽ ተሰማ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እኔ በራማ ድምጽ ሰማሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ራሄል ለልጆችዋ አለቀሰች
ራሄል የያዕቆብ/እስራኤል ሚስት ነበረች፤ ደግሞም የዮሴፍ እና ብንያም ነገዶች እናት ነበረች። የእርሷ ስም በባቢሎናውያን ልጆቻቸውን ለገደሉባቸው ወይም ማርከው ለወሰዱባቸው የእስራኤል እናቶች ሜቲኖሚ/ ነው።

(ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በህይወት የሉምና ስለ እነርሱ መጽናናት አልቻለችም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ልጆቿ ሞተዋልና፣ ማንም እንዲያጽናናት አልፈቀደችም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 31:16

ድምጽሽን ከልቅሶ ከልክይ፣ ዐይኖችሽንም ከእንባ
ድምጽ እና ዐይኖች የተገለጹት ራሄል ከመንቀሳቀስ እንዲገቱ እንደምትፈልጋቸው ሰዎች ተደርገው ነው። "ጮክ ብለሽ ማልቀስሽን አቁሚ፣ በጩኸት ማንባትሽንም አቁሚ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ድምጽሽን ያዢው...ዐይኖችሽ... ስራሽ...ልጆችሽ... እድልሽ... ትውልድሽ
ያህዌ ለእስራኤላውያን የሚናገረው ለራሄል እንደሚናገራት አድርጎ ነው (ኤርምያስ 31:15)፣ ስለዚህ ሁሉም "የአንቺ" የሚሉት ሁኔታዎች እና ትዕዛዞች ነጠላ ቁጥር ናቸው። (አንተ/አንቺ የሚለው ተውላጠ ስም መልኮች እና አጋኖ የሚሉትን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 31:18

በእርግጥ የኤፍሬምን ሀዘን ሰምቻለሁ
ኤፍሬም በእስራኤል የነበረው ትልቅ ነገድ አባት ነበር። የእርሱ ስም ለእስራኤል ህዝብ ሜቶኖሚ/ ነው። "እኔ በእርግጥ የኤፍሬምን ትውልዶች ሀዘን ሰምቻለሁ" ወይም "እኔ በእርግጥ የእስራኤልን ህዝብ ሀዘን ሰምቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ቀጣኸኝ፣ እኔም ተቀጣሁ
ተናጋሪው ሀረጉን የሚደግመው፣ አንድም ያህዌ እርሱን እጅግ እንደቀጣው ለማሳየት ወይም ያህዌ እርሱን በቅጣት ሊያስተምረው የፈለገውን ማወቁን/መረዳቱን ለመናገር ነው። "እኔ ተቀጣሁ" የሚለው ቃል በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንተ እኔን ቀጣኸኝ። አዎን፣ አንተ እኔን ክፉኛ ቀጣኸኝ" ወይም "አንተ ቀጣኸኝ፣ እኔም ከአንተ የተማርኩት ስትቀጣኝ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

እንዳልተገራ ወይፈን ተቀጣሁ
ሰዎች ወይፈን ሲገሩ፣ ይገርፏቸዋል፣ ካልሆነ እንዲጨነቁ ያደርጋሉ። ያህዌ የእስራኤልን ህዝብ እንዲጨነቅ አድርጓል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መቅጣት
ሌላው አማራጭ ትረጉም "ስርአት ማስያዝ" ነው

ጭኔን ጻፍሁ/ጭኔን በእጄ መታቱ
በሀዘን። በእናንተ ቋንቋ ሰዎች ማዘናቸውን ለመግለጽ የተለየ ሀረግ ወይም ድርጊት የሚጠቀሙ ከሆነ እዚህ ስፍራ ያንን ተክታችሁ መጠቀም ትችላላችሁ። "ግንባሬን ፈተግሁ" በሚለውውጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ አፈርኩ ተዋረድኩም
"ሀፍረት" እና "ውርደት" የሚሉት ቃላት በመረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ ሀፍረት የሚለውን ሀሳብ ያጎላሉ። "እኔ ሙሉ ለሙሉ አፍሬ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ኤፍሬም የእኔ ውድ ልጄ አይደለምን? እርሱ ለእኔ ውድ አይደለምን፣ አስደሳች ልጄ አይደለምን?
ያህዌ ህዝቡን ለማጽናናት እየሞከረ በማባባት ይናገራል። እነዚህ ጥያቄዎች በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጹ ይችላሉ። "ኤፍሬም ወድ ልጄ ነው። እርሱ የእኔ ውድ ነው፣ ደስ የምሰኝበት ልጄ ነው። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 31:21

አጠቃላይ መረጃ:
እግዚአብሔር ከቁጥር 7 ቀጥሎ መናገሩን ይቀጣላል።

ለራስሽ የመንገድ ምልክት አድርጊ...መንገድን የሚመሩ ዓምዶችን ትከይ...አዕመሮሽን አረጋጊ.. መውሰድ ይኖርብሻል... እንደገና ተመለሽ
"አንቺ ራስሽ" እና "የአንቺ" እና "አንቺ" የሚሉት እነዚህ ትዕዛዞች እና ሁኔታዎች የሚያመለክቱት "ድንግሊቱን እስራኤልን" ሲሆን ሁሉም ነጠላቁጥር ናቸው። (ተውላጠ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ድንግሊቱ እስራኤል ሆይ፣ ተመለሽ!
እግዚአብሔር የተለወጠችውን እስራኤል እያመለከተ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አንቺ እምነት የለሽ ልጄ እስከ መቼ ታወላውያለሽ?
ያህዌ ለህዝቡ እነር በለመታዘዛቸው ምክንያት መታገሱ እያበቃ እንደሆነ ይናገራል። "እኔን መታዘዝ ለመጀመር አታቅማሙ" በሚለው ውስጥ እደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ማወላወል
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ምን ማድረግ እንደሚገባ መወሰን አለመቻል 2) ብዙውን ጊዜ በትክክለኛው መንገድ ውጭ መሄድ፣ ሲሆን ይህ ያህዌን ያለመታዘዝ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በምድር ላይ እንግዳ/አዲስ ነገር - አንዲት ሴት ብርቱ ወንድን ስትጠብቅ/ስትከብ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሰዎች ሴቶችን ለመጠበቅ ማንም ባያስፈልጋቸው ደህንነት ይሰማቸዋል ወይም 2) ይህ ማንም የማይጠብቀውን ነገር ለመግለጽ ፈሊጥ ነው። "በምድር ላይ አዲስ ነገር - ሴት አንድን ወንድ እንደ መጠበቅ የመሰለ እንግዳ ነገር" በሚለው ውስጥ እደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 31:23

የሰራዊት ጌታ ያህዌ... እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ህዝቡ
እዚህ ስፍራ ይህ የይሁዳን ሰዎች ያመለክታል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ የሚኖርባችሁ እናንተ የተቀደሳችሁ ስፍራዎች፣ እናንተ የተቀደሳችሁ ተራሮች፣ ያህዌ ይባርካችሁ
እየሩሳሌም በተራራ ላይ ስትሆን፣ መቅደሱ የታነጸው በእየሩሳሌም ከፍተኛ ስፍራ ነበር። "ያህዌ መቅደሱ በሚገኝበት ከእርሱ ጋር በእየሩሳሌም የሚኖሩትን ይባርክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አጋኖ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

አንቺ የተቀደሰሽ ተራራ
መቅደሱ የቆመበባት የጽዮን ተራራ

ይሁዳ እና መላው ዜጎችዋ በአንድነት በዚያ ይኖራሉ
ይሁዳ የተባለው ሰው ስም፤ የእርሱ ትውልዶች፣ የይሁዳ ነገድ የሆኑ ሰዎች የሚኖሩባት፣ እና የይሁዳ ከተማ፣ ይሁዳ የተባለው ሰው ቤተሰብ እንደሆኑ ተደርጎ፣ በይሁዳ ምድር "በዚያ" የሚኖሩ በሙሉ የተገለጹበት ሜቶኖሚ/ ነው። "ይህ ምድሪቱን ይሁዳ ከቤተሰቡ ጋር እንደኖርባት ቤት ያደርጋታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ገበሬዎች እና ከከብቶቻቸው ጋር የወጡ ይገኛሉ
"ደግሞም ገበሬዎች እና ከከብቶቻቸው ጋር የወጡ እነርሱም ደግሞ በዚያ ይኖራሉ"

ከከብቶቻቸው ጋር የወጡ
በጎችን እና ፍየሎችን የሚጠብቁ ሰዎች

ያድሱ ነበር
"እኔን አደሱኝ"

Jeremiah 31:27

ተመልከቱ
"ትኩረት ስጡ" ወይም "አድምጡ"

እኔ የማይበት...ቀናት እየደረሱ ነው
መጪው ጊዜ የተገለጸው "ቀናት እየመጡ" እንደሆነ ተደርጎ ነው። ይህ ዘይቤ በኤርምያስ 7:32 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "በመጪው ጊዜ ... እኔ አያለሁ" ወይም "እኔ የማይበት... ጊዜ ይኖራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ከሰው እና አራዊት ዘር ጋር የእስራኤልን እና የይሁዳን ቤቶች እመለከታለሁ
"ቤት" የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖር ቤተሰብ ሜቶኖሚ/ ነው፤ በዚህ ሁኔታ እነዚህ የእስራኤል እና የይሁዳ ሰዎች ሰዎች ናቸው። ቤት በተራው ያህዌ ዘር የሚዘራበት ሜዳ ሆኖ ሲገለጽ፣ ለምግብ፣ ለወተት፣ እንደዚሁም ለቆዳ የሚያሳድጓቸው እንስሳት እንዲሁም በቁጥር የሚበዛው ህዝብ ያን ዘር እንደሆኑ ተደርጎ ተገልጽዋል። "የይሁዳ እና የእስራኤል ሰዎች እንዲበዙ እና አያሌ ከብቶች እንዲኖራቸው አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

እነርሱን እነቅላቸው ዘንድ በእይታ ስር እጠብቃቸዋለሁ
"እነርሱን የምነቅልበትን መንገድ እመለከታለሁ"

መንቀል... ማስወገድ...መጣል...ማጥፋት
እነዚህ ሀሳቦች በኤርምያስ 1:9 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

እነርሱን አንጽ እና እተክል ዘንድ
ያህዌ እስራኤላውያንን ቤት ወይም የምግብ ሰብል እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። "እነርሱን አበረታ እና አበዛ ዘንድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 31:29

አባቶች የኮመጠጠ የወይን ፍሬ በሉ፣ ነገር ግን የልዶች ጥርስ ደነዘዘ/ጠረሰ
እነዚህ ቃላት፣ ያህዌ በአባቶች ጥፋት ልጆችን መቅጣቱን በማማረር ሰዎች ሲናገሩ ኤርምያስ የሰማው ምሳሌያዊ አነጋገር ነው። (ምሳሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የቆመጠጠ የወይን ፍሬ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) በውስጡ ብዙ አሲድ የያዘ የወይን ፍሬ። ወይም 2) ያልበሰለ/ያልደረሰ የወይን ፍሬ። በባህላችሁ ወይን ተክል ከሌለ፣ ፍራፍሬ የሚለውን አጠቃላይ ቃል መጠቀም ሊያስፈልግ ይችላል።

ጥርስ ጠረሰ/ደነዘዘ
ለዚህ ሰዎች ጎምዛዛ ፍራፍሬ ወይም ያልበሰለ ፍራፍሬ ሲመገቡ አፋቸውን የሚሰማቸውን ስሜት የሚገልጽ በቋንቋችሁ የሚገኝ የተለመደ ቃል ተጠቀሙ

እያንዳንዱ ሰው በጥፋቱ/ኃጢአቱ ይሞታል
"እያንዳንዱ ሰው በራሱ ኃጢአት ምክንያት ይሞታል"

የጎመዘዘ የወይን ፍሬ የሚበላ ሰው ሁሉ፣ ጥርሱ ይጠርሳል/ይደነዝዛል
ኤርምያስ ሰዎች ከገዛ ባህሪያቸው የተነሳ እንደሚጨነቁ ለመግለጽ ምሳሌያዊ አነጋገሩን ይጠቀምበታል። (ምሳሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 31:31

ተመልከቱ
"አድምጡ" ወይም "ቀጥሎ ለምነግራችሁ ትኩረት ስጡ"

የምሰራባቸው ቀናት... እየመጡ ነው
የወደፊቱ ጊዜ የተገለጸው "ቀናት እየመጡ" እንደሆነ ተደርጎ ነው። ይህ ዘይቤያዊ አነጋገር በኤርምያስ 7:32 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ወደፊት... እኔ አንጻለሁ" ወይም "እኔ የማንጽበት ጊዜ...ይመጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ቤት
"ቤት" የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። በዚህ ሁኔታ ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን መንግሥት ነው። ይህ በኤርምያስ 3:18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እስራኤል" ወይም "የእስራኤል መንግሥት" ወይም "የእስራኤል ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳ ቤት
"ቤት" የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። በዚህ ሁኔታ ይህ የሚያመለክተው፣ የይሁዳን እና የብንያምን ትውልድ የሚያጠቃልለውን የይሁዳን መንግሥት ነው። ይህ በኤርምያስ 3:18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ይሁዳ" ወይም "የይሁዳ መንግሥት" ወይም "የይሁዳ ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እጃቸውን እይዛለሁ
አፍቃሪ ባል አብረው ሲራመዱ የሚስቱን እጅ እንደሚይዝ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 31:33

የእስራኤል ቤት
"ቤት" የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። በዚህ ሁኔታ ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን መንግሥት ነው። ይህ በኤርምያስ 3:18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እስራኤል" ወይም "የእስራኤል መንግሥት" ወይም "የእስራኤል ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ህጌን በእነርሱ መሃል አደርጋለሁ፣ ደግሞም በልባቸው ላይ እጽፈዋለሁ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው፣ የያህዌ ህግ የእነርሱ አንድ ክፍል እንጂ በድንጋይ ላይ ተጽፎ የተቀመጠ ብቻ አለመሆኑን ትኩረት ይሰጣሉ። እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚወክለው "ስሜትን" ወይም "ሀሳብን/ አእምሮን" ነው። "ህጌ የሃሳባቸው እና ስሜታቸው ክፍል ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

ከእነርሱ ከታናናሾቹ ጀምሮ እስከ ታላላቆቹ ድረስ
ይህ ሀረግ ከታናሹ እስከ ታላላቆች ድረስ እያንዳንዱን ሰው ያመለክታል። "አንድም ሳይቀር እያንዳንዳቸውን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ከአጽናፍ አጽናፍ/ከዳር እስከ ዳር የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 31:35

እነዚህ ዘላቂ ነገሮች ከጠፉ ብቻ...የእስራኤል ትውልዶች አገር ከመሆን ለዘለዓለም ያቆማሉ
ይህ ያህዌ ፈጽሞ ይሆናል የማይለው መላምታዊ ሁኔታ ነው። "እነዚህ ዘላቂ ነገሮች በፍጹም አይጠፉም...እንደዚሁ ሁሉ የእስራኤል ትውልዶች አገር ከመሆን በፍጹም አያቆሙም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 31:37

ከፍ ያሉት ሰማያት መለካት ከተቻሉ ብቻ፣ እና ታች ያሉ የምድር መሰረቶች መታወቅ ከቻሉ ብቻ ያኔ እኔ የእስራኤልን ትውልድ እጥላለሁ
ይህ ያህዌ ፈጽሞ ይሆናል የማይለው መላምታዊ ሁኔታ ነው። "በከፍታ ያሉ ሰማያት በፍጹም ሊለኩ አይችሉም፣ ከታች የሚገኙ የምድር መሰረቶችም በፍጹም ሊታወቁ አይችሉም፣ እንደዚሁ ሁሉ የእስራኤልን ትውልዶች እኔ ፈጹሞ አልተውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በከፍታ ያሉ ሰማያት...የምድር መሰረቶች
እነዚህ ሀረጎች መላውን ፍጥረት ያመለክታሉ። (ከአጽናፍ አጽናፍ/ከዳር እስከ ዳር የሚለውን ይመልከቱ)

ከታች የሚገኙ የምድር መሰረቶች ሊታወቁ ይችላሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "አንድ ሰው እስከ ምድር መሰረት ድረስ ሊቆፍር ይችላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ከታች የሚገኝ መሰረት
"ጥልቁ ስፍራ።" "መሰረት" የቤቱ ሌሎች ክፍሎች ሁሉ የሚያርፉበትነው።

መጣል
መወርወር ወይም አለመቀበል

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 31:38

ተመልከቱ፣ ቀኖች እየመጡ ነው
"በቶሎ እንደሚሆን እኔ ለምናገረው ነገር ትኩረት ስጡ!"

ከተማይቱ የምትገነባበት... ቀናት እየመጡ ነው
መጪው ጊዜ የተገለጸው "ቀናት እየመጡ" እንደሆነ ተደርጎ ነው። ይህ ዘይቤያዊ አነጋገር በኤርምያስ 7:32 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "በመጪው ጊዜ ... ከተማይቱ ዳግም ትገነባለች" ወይም "እኔ ያህዌ የተናገርኩት/ያወጅኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ከተማይቱ ዳግም ለእኔ ትሰራለች/ትታነጻለች
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እነርሱ ከተማይቱን ዳግም ለእኔ ይገነባሉ" ወይም "እኔ ከተማዋን ዳግም እንዲገነቡ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የሐናንኤል ግንብ...የማዕዘን በር...የጋሬብ ኮረብታ...ጎዓ...ቄድሮን ሸለቆ...ፈረስ በር
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

መላው ሸለቆ... ለያህዌ የተለየ ይሆናል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "መላውን ሸለቆ ለእኔ... ይለያሉ/ይቀድሳሉ" ወይም "መላውን ሸለቆ ... ለእኔ ይቀድሳሉ/ይለያሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ይለያሉ
"ይቀድሳሉ"

ከተማይቱ ዳግም አትጠፋም ወይም አትፈርስም
ከተማይቱ የተገለጸችው ተክል እንደሆነች እና አንድ ሰው ከመሬት ሊነቅላት አንደሚችል፣ ወይም ግንብ ሆና ሊያፈርሳት እንደሚችል ተደርጋ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ዳግም ማንም ከተማይቱን እንዲያፈርሳት ወይም እንዲነቅላት እኔ አልፈቀድም" ወይም "ማንን ከተማይቱን ዳግም አያጠፋትም ወይም አይደመስሳትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 32

1 በይሁዳ ንጉሥ በሴዴቅያስ በዐሥረኛው ዓመት፣ በናቡክደነፆር በዐሥራ ስምንተኛው ዓመት፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ኤርምያስ የመጣው ቃል ይህ ነው። 2 በዚያን ጊዜ፣ የባቢሎን ንጉሥ ሠራዊት ኢየሩሳሌምን ከብቦ ነበር፤ ነቢዩም ኤርምያስ በይሁዳ ንጉሥ ቤት በነበረው በግዞት ቤት አደባባይ ታስሮ ነበር። 3 የይሁዳ ንጉሥ ሴዴቅያስ በእስር አቆይቶት እንዲህ አለው፣ "ለምን እንዲህ ብለህ ትንቢት ትናገራለህ፣ 'እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ተመልከት፣ ይህችን ከተማ ለባቢሎን ንጉሥ እጅ አሳልፌ እሰጣለሁ፣ እርሱም ይይዛታል። 4 የይሁዳም ንጉሥ ሴዴቅያስ ከከለዳውያን እጅ አያመልጥም፣ በእውነት በባቢሎን ንጉሥ እጅ አልፎ ይሰጣል፣ አፉ ለአፉ ይናገረዋል፣ ዐይኑም የንጉሡን ዐይን ያያል። 5 ሴዴቅያስ ወደ ባቢሎን ይሄዳል፣ እኔም እስክጐበኘው ድረስ በዚያ ይሆናል፤ ይላል እግዚአብሔር፤ ከከለዳውያን ጋር ብትዋጉ አይሳካላችሁም።'" 6 ኤርምያስም እንዲህ አለ፣ "የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፣ 7 'ተመልከቱ፣ የአጐትህ የሰሎም ልጅ አናምኤል ወደ አንተ መጥቶ፣ "ትገዛው ዘንድ መቤዠቱ የአንተ ነውና በዓናቶት ያለውን እርሻዬን ግዛ ይልሃል።" 8 ከዚያም፣ እግዚአብሔር እንደተናገረው ቃል፣ የአጐቴ ልጅ አናምኤል እኔ ወዳለሁበት ወደ ግዞቱ ቤት አደባባይ መጥቶ እንዲህ አለኝ፣ 'በብንያም አገር በዓናቶት ያለውን እርሻዬን፣ እባክህ ግዛ፤ የርስት መብቱ የአንተ ነውና፣ የመቤዠቱ መብትም የአንተ ነውና ለአንተ ግዛው።' ያን ጊዜ ይህ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ አወቅሁ። 9 ስለዚህ፣ በዓናቶት ያለውን እርሻ ከአጐቴ ልጅ ከአናምኤል ገዛሁ፣ ዐሥራ ሰባት ሰቅል ብርም መዘንሁለት። 10 በውሉም ወረቀት ላይ ፈረምሁ አተምሁትም፣ ምስክሮችም እንዲመሰክሩ አስደረግሁ። ከዚያም ብሩን በሚዛን መዘንሁለት። 11 ቀጥሎ፣ የታተመውንና የተከፈተውን የግዢ ውል ወረቀት ወሰድሁ፤ 12 የአጐቴም ልጅ አናምኤል፣ የውሉንም ወረቀት የፈረሙ ምስክሮች፣ በግዞትም ቤት አደባባይ የተቀመጡ አይሁድ ሁሉ እያዩ የውሉን ወረቀት ለመሕሤያ ልጅ ለኔርያ ልጅ ለባሮክ ሰጠሁት። 13 በፊታቸውም እንዲህ ብዬ ባሮክን አዘዝሁት። 14 'የእስራኤል አምላክ፣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፣ እንዲህ ይላል፦ የታተመውንና የተከፈተውን ይህን የውል ወረቀት ውሰድ። ብዙ ቀን እንደተጠበቀ እንዲቆዩ በሸክላ ዕቃ ውስጥ አኑራቸው። 15 የእስራኤል አምላክ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፦ ሰዎች በዚህች ምድር ቤትን፣ እርሻን፣ የወይን ቦታንም እንደ ገና ይገዛሉ።' 16 ለኔርያ ልጅ ለባሮክም የውሉን ወረቀት ከሰጠሁት በኋላ፣ እንዲህ ብዬ ወደ እግዚአብሔር ጸለይሁ፣ 17 'ወዮ፣ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ! ተመልከቱ! አንተ ብቻህን ሰማይንና ምድርን በታላቅ ኃይልህና በተዘረጋች ክንድህ ፈጥረሃል። ለአንተም እንደሚያቅትህ የተናገርከው ነገር የለም። 18 ለብዙ ሺህ ምሕረት ታደርጋለህ፣ የአባቶችንም በደል ከእነርሱ በኋላ በልጆቻቸው ጭን ላይ ትመልሳለህ። ስምህ ታላቅና ኃያል አምላክ፤ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው። 19 በጥበብ ታላቅ በአደራረግም ብርቱ ነህ፣ ለሁሉም እንደ መንገዱና እንደ ሥራው ፍሬ ትሰጥ ዘንድ ዐይኖችህ በሰዎች መንገድ ሁሉ ላይ ተገልጠዋል። 20 እስከ ዛሬም ድረስ ምልክትንና ድንቅን ነገር በግብጽ ምድር አድርገሃል። እስከዛሬ ድረስ፣ በዚህ በእስራኤልና በሌሎች ሰዎች ሁሉ መካከል ስምህን አግንነሃል። 21 በምልክትና በድንቅ ነገር፣ በብርቱ እጅና በተዘረጋች ክንድ በታላቅም ግርማ ሕዝብህን እስራኤልን ከግብጽ ምድር አውጥተሃልና። 22 ከዚያም ትሰጣቸውም ዘንድ ለአባቶቻቸው የማልህላቸውን፣ ወተትና ማርን የምታፈስሰውን ምድር፣ ሰጠሃቸው። 23 እነርሱም ገብተው ወረሱአት። ነገር ግን ቃልህን አልሰሙም ለሕግህም በመታዘዝ አልሄዱም። ይደረግ ዘንድ ካዘዝሃቸው ሁሉ ምንም አላደረጉም፣ ስለዚህ ይህን ጥፋት ሁሉ አመጣህባቸው። 24 ተመልከቱ! የአፈር ድልድል ሊይዙአት እስከ ከተማይቱ ድረስ ቀርበዋል። ከሰይፍ፣ ከራብና፣ ከመቅሠፍት የተነሣ፣ ከተማይቱ ለሚዋጓት ለከለዳውያን እጅ ተሰጥታለች። እንደሚሆን የተናገርኸው ሆኖአልና፣ ደግሞም ተመልከቱ፣ አንተ ታየዋለህ። 25 ከዚያም አንተ ራስህ፣ "ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፣ ምንም እንኳን ይህች ከተማ ለከለዳውያን እጅ ተላልፋ የምትሰጥ ቢሆንም፣ እርሻውን በብር ግዛ ምስክሮችንም ጥራ" አልኸኝ። 26 ወደ ኤርምያስ የመጣው የእግዚአብሔር ቃል ይህ ነው፣ እንዲህም አለ፣ 27 "ተመልከቱ! የሰው ዘር ሁሉ አምላክ እግዚአብሔር እኔ ነኝ። እፈጽመው ዘንድ የሚያቅተኝ ነገር አለን? 28 ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ 'ተመልከቱ፣ ይህችን ከተማ ለከለዳውያን እጅና ለባቢሎን ንጉሥ ለናቡከደነፆር እጅ አሳልፌ እሰጣለሁ። እርሱም ይይዛታል። 29 ይህችን ከተማ የሚወጉ ከለዳውያን መጥተው በእሳት ያነድዱአታል፣ ያስቈጡኝም ዘንድ በሰገነታቸው ላይ ለበኣል ካጠኑባቸው፣ ለሌሎችም አማልክት የመጠጥን ቍርባን ካፈሰሱባቸው ቤቶች ጋር ያቃጥሉአታል። 30 የእስራኤል ልጆችና የይሁዳ ልጆች ከወጣትነታቸው ጀምሮ በዐይኔ ፊት ክፉ ነገርን ብቻ አድርገዋል። የእስራኤልም ልጆች እኔን በእጃቸው ሥራ ከማስቈጣት በቀር ሌላ ሥራ አላደረጉምና፣ ይላል እግዚአብሔር። 31 ከፊቴ አስወግዳት ዘንድ ይህች ከተማ ከገነቧት ቀን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ቍጣዬንና መዓቴን ለማነሣሣት ሆናለችና። ስለዚህም ከፊቴ አስወግዳታለሁ። 32 ምክንያቱም እኔን ያስቈጡኝ ዘንድ፣ እነርሱና ነገሥታቶቻቸው፣ አለቆቻቸውም፣ ካህናቶቻቸውም፣ ነቢያቶቻቸውም፣ የይሁዳም ሰዎች፣ በኢየሩሳሌምም የሚኖሩ፣ ስላደረጉት ስለ እስራኤል ልጆችና ስለ ይሁዳ ልጆች ክፋት ሁሉ ነው። 33 ምንም እንኳን በጉጉት ያስተማርኳቸው ቢሆንም፣ ፊታቸውን ሳይሆን ጀርባቸውን ወደ እኔ መለሱ። ላስተምራቸው ሞከርኩ፣ ነገር ግን ተግሣጽን ይቀበሉ ዘንድ አንዳቸውም እንኳን አልሰሙም። 34 ከዚያም፣ ያረክሱት ዘንድ፣ ስሜ በተጠራበት ቤት ውስጥ ርኩሰታቸውን አኖሩ። 35 ቀጥሎም ይሁዳን ኃጢአት እንዲሠራ ለማድረግ፣ ይህንን ርኩሰት ያደርጉ ዘንድ፣ እኔ ያላዘዝሁትንና በልቤ ያላሰብሁትን ነገር፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን ለሞሎክ በእሳት ያሳልፉ ዘንድ፣ በሄኖም ልጅ ሸለቆ ውስጥ ያሉትን የበኣልን የኮረብታውን መስገጃዎች ሠሩ። 36 አሁን እንግዲህ፣ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር፣ አንተ ስለ እርስዋ፣ 'በሰይፍና በራብ በመቅሰፍትም ለባቢሎን ንጉሥ እጅ ተሰጥታለች' ስለምትላት ከተማ እንዲህ ይላል። 37 ተመልከቱ፣ በቍጣዬ፣ በመዓቴና በታላቅም መቅሠፍቴ እነርሱን ካሳደድሁባት አገር ሁሉ እሰበስባቸዋለሁ። ወደዚህም ስፍራ እመልሳቸዋለሁ፣ ተዘልለውም እንዲኖሩ አደርጋለሁ። 38 ከዚያም እነርሱ ሕዝብ ይሆኑኛል፣ እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ። 39 ለእነርሱም፣ ከእነርሱም በኋላ ለልጆቻቸው መልካም ይሆንላቸው ዘንድ ለዘላለም እንዲፈሩኝ አንድ ልብና አንድ መንገድ እሰጣቸዋለሁ። 40 ለእነርሱም ከማደርገው በጎነት አልመለስም ስል፣ ከእነርሱ ጋር የዘላለምን ቃል ኪዳን እገባለሁ። መፈራቴን በልባቸው ውስጥ አኖራለሁ። ከዚህ የተነሣ እኔን ከመከተል አይመለሱም። 41 ከዚያም ለእነርሱ መልካምን በማድረግ ደስ ይለኛል። በታማኝነት በፍጹም ልቤና በፍጹም ነፍሴ በዚህች ምድር እተክላቸዋለሁ። 42 እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፣ 'ይህን እጅግ ክፉ ነገር ሁሉ በዚህ ሕዝብ ላይ እንዳመጣሁ፣ እንዲሁ እንደማደርግላቸው የተናገርሁላቸውን በጎነት ሁሉ አመጣላቸዋለሁ። 43 ከዚያም፣ እናንተ፣ "ይህች ያለ ሰውና ያለ እንሰሳ ያለች ባድማ ምድር ናት። ለከለዳውያንም እጅ ተሰጥታለች።" በምትሉአት ምድር እርሻን ይገዛሉ። 44 ምርኮኞቻቸውንም እመልሳለሁና፣ በብንያም አገር በኢየሩሳሌምም ዙሪያ ባሉ ስፍራዎች፣ በይሁዳም ከተሞች በደጋውም ባሉ ከተሞች በቈላውም ባሉ ከተሞች፣ በደቡብም ባሉ ከተሞች፣ ሰዎች እርሻውን በብር ይገዛሉ በውሉም ወረቀት ፈርመው ያትማሉ ምስክሮችንም ይጠራሉ።"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Jeremiah 32:1

ይህ ከያህዌ ዘንድ ወደ ኤርምያስ የመጣ ቃል ነው
ይህ ፈሊጥ የዋለው እግዚአብሔር ለኤርምያስ መልዕክት እንደ ሰጠው ለማወጅ ነው። ተመሳሳይ የሆነው ሀረግ በኤርምያስ 1:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ለኤርምያስ መልዕክት ሰጠው" ወይም "ያህዌ ኤርምያስን ተናገረው/እንዲህ አለው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳ ንጉሥ ሴዴቅያስ በነገሰ በአስረኛው አመት፣ በናቡከደነጾር አስራ ስምንተኛ አመት
"ሴዴቅያስ ለዘጠኝ አመታት የይሁዳ ንጉሥ ከሆነ በኋላ እና ናቡከደነጾር ከአስራ ሰባት አመታት በላይ ከነገሰ በኋላ"

ነቢዩ እርምያስ ታስሮ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ኤርምያስን እስረኛ አድርገውት ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ነቢዩ እርምያስ ታስሮ ነበር
እዚህ ስፍራ ኤርምያስ ለምን ራሱን በስም እንደሚጠቅስ ግልጽ አይደለም። በዩዲቢ ውስጥ እንደሚገኘው የመጀመሪያ መደብ በመጠቀም መተርጎም ትችላላችሁ። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚሉትን ይመልከቱ)

በይሁዳ ንጉሥ ቤት የንጉሡ ዘብ ጠባቂዎች አደባባይ
ይህ በግንብ የተከበበ እና እስረኞችን የሚጠብቁበት/የሚያስሩበት ከንጉሡ ቤተመንግስት ጋር የተያያዘ ክፍት ስፍራ ነው።

Jeremiah 32:3

የይሁዳ ንጉሥ ሴዴቅያስ እርሱን አስሮት ነበር
ሴዴቅያስ ይህንን እንዲያደርግ ሌሎች ሰዎች ረድተውት እንደነበረ አንባቢው ይረዳ ዘንድ መተረጎሙ ይመረጣል። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱን አስሮት ነበር
አዚህ ስፍራ "እርሱን" የሚለው የሚያመለክተው ኤርምያስን ነው። እዚህ ስፍራ ኤርምያስ ለምን ራሱን በስም እንደሚጠቅስ ግልጽ አይደለም። በዩዲቢ ውስጥ እንደሚገኘው የመጀመሪያ መደብ በመጠቀም መተርጎም ትችላላችሁ። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚሉትን ይመልከቱ)

ለምን እንዲህ ብለህ፣ ትንቢት ተናገራለህ
ሴዴቅያስ ጥያቄውን የሚጠቀምበት ኤርምያስን ለመገሰጽ ነው። "ትንቢት መናገርህን መቀጠልህ ስህተት ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህችን ከተማ ለባቢሎን ንጉሥ ለናቡከደነጾር እጅ አሳልፌ ልሰጣት ነው
ያህዌ ስለ ከተማይቱ፣ አንድ ሰው ለሌላው ሊያቀብለው እንደሚችለው ትንሽ እቃ አድርጎ ይናገራል። "እጅ" የሚለው ቃል እጅ ለሚሰራው ስራ ሀይል ወይም ቁጥጥር ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት / ነው። "ይህችን ከተማ በባቢሎን ንጉሥ ቁጥጥር ስር ላደርጋት ነው" ወይም " የባቢሎን ንጉሥ በዚህች ከተማ ላይ ያሻውን እንዲፈጽም ልፈቅድለት ተነስቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር ወይም ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

እርሱ ይማርካታል
አንባቢው የባቢሎን ንጉሥ ከተማይቱን እንዲቆጣጠር ሌሎች ሰዎች እንደረዱት ይገነዘብ ዘንድ መተርጎሙ ይመረጣል።

ለእርግጥ ለባቢሎን ንጉሥ እጅ ተላልፎ ይሰጣል
"እጅ" የሚለው ቃል ለሀይል ወይም እጅ የሚሰራውን ለመቆጣጠር ሜቶኖሚ/ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኔ በእርግጥ በባቢሎን ንጉሥ ቁጥጥር ስር አደርገዋለሁ" ወይም "እኔ በእርግጥ የባቢሎን ንጉሥ በእርሱ ላይ ያሻውን እንዲፈጽም እፈቅዳለሁ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከንጉሡ ጋር አፍ ለአፍ ይናገራል፣ ደግሞም ዐይኖቹ የንጉሡን ዐይን ይመለከታሉ
እዚህ ስፍራ "አፍ" እና "ዐይን" የሚወክሉት መላውን ሰውነት ነው። "ሴዴቅያስ ራሱ ንጉሥ ናቡከደነጾርን ይመለከተዋል በቀጥታም ከእርሱ ጋር ይነጋገራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ ትዋጋላችሁ
እዚህ ስፍራ "እናንተ" የሚለው ብዙ ቁጥር ነው። (አንተ የሚለው ተውላጠ ስም መልኮች የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 32:6

ኤርምያስ እንዲህ አለ፣ "የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ፣ ‘እነሆ፣ የአጎትህ የሰሎም ልጅ አናምኤል ወደ አንተ መጥቶ፣ "በዓናቶት ያለውን የእኔን መሬት ለራስህ ግዛ፣ ይህን የመግዛቱ መብት የአንተ ነውና" ይልሃል።"'"
ይህንን ቀጥተኛ ወዳልሆነ ንግግር መተርጎም ሊያስፈልግ ይችላል። "ኤርምያስ እንዲህ አለ፣ የያህዌ ቃል ወደ እርሱ መጥቶ በዓናቶት ያለውን የአጎቱን የሰሎምን ልጅ የአናምኤልን መሬት ለራሱ ይገዛ ይህን መሬት መግዛት መብቱ የኤርምያስ ነውና" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቀጥተኛ የሆነ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅሶች የሚለውን ይመልከቱ)

ኤርምያስ እንዲህ አለ
እዚህ ስፍራ ኤርምያስ ለምን ራሱን በስም እንደሚጠቅስ ግልጽ አይደለም። በዩዲቢ እንደ ተተረጎመው አንደኛ መደብን በመጠቀም መተርጎም ይቻላል። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌ ቃል እነሆ፣ እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ
ይህ ፈሊጥ የዋለው ከያህዌ ዘንድ ልዩ መልዕክት ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:4 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ እንዲህ ሲል፣ መልዕክት ሰጠኝ። 'ተመልከት/እነሆ" ወይም "ያህዌ ይህን መልዕክት ለእኔ ነገረኝ፡ 'እነሆ/ተመልከቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አናምኤል... ሰሎም
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ዓናቶት
ይህ የቦታ ስም ነው። ይህ በኤርምያስ 1:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 32:8

አጠቃላይ መረጃ:
ኤርምያስ መናገሩን ቀጥሏል፣ ነገር ግን ስለ ራሱ የሚናገረው በአንደኛ መደብ ነው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሶስተኛ መደብ የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የዘብ ጠባቂዎች አደባባይ
ይህ በግንብ የተከበበ እና እስረኞችን የሚጠብቁበት ከንጉሡ ቤተመንግስት ጋር የተያያዘ ክፍት ስፍራ ነው። ይህ በኤርምያስ 32:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

አስራ ሰባት ሰቅሎች
አንድ ሰቅል 11 ግራም ነው። "17 ሰቅል" ወይም "187 ግራም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መጽሐፍ በተጻፈበት ጊዜ የገንዘብ መጠን መለኪያ እና ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 32:10

አጠቃላይ መረጃ:
ኤርምያስ መናገሩን ቀጥሏል።

ጥቅልሉ ታትሞበት፣ ደግሞም ምስክሮች ምስክርነት ሰትተውበት
ይህ የሚያመለክተው አንድ ሰው መሬት ለመግዛት በሰነዱ ላይ የሚያደርገውን ፊርማ ነው። ኤርምያስ ይህንን መሬት መግዛን ለማረጋገጥ ሌሎች ሰዎች ምስክሮች ይሆናሉ።

ምስክሮች ምስክር ይሆናሉ
"መሬቱን ስገዛ ሰዎች ተመልክተዋል፣ ስለዚህ እኔ መሬቱን ለመግዛቴ ለሌሎች መናገር ይችላሉ"

የታተመ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እኔ እንዳተምኩት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ያልታተመበት ሰነድ
"ክፍት ቅጂ" ወይም "በላዩ ማህተም የሌለበት ሰነድ"

ባሮክ...ኔርያ...መሕሤያ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የዘብ ጠባቂዎች አደባባይ
ይህ በግንብ የተከበበ እና እስረኞችን የሚጠብቁበት ከንጉሡ ቤተመንግስት ጋር የተያያዘ ክፍት ስፍራ ነው። ይህ በኤርምያስ 32:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

Jeremiah 32:13

አጠቃላይ መረጃ:
ኤርምያስ መናገሩን ቀጥሏል።

በእነርሱ ፊት
እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው የሚያመለክተው አናምኤልን፣ ምስክሮችን፣ እና በዚያ የነበሩ አይሁዳውያንን ነው።

የሰራዊት ጌታ ያህዌ... እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ቤቶች፣ እርሻዎች፣ እና የወይን ቦታዎች ዳግም በዚህ ስፍራ ይገዛሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "የእስራኤል ሰዎች ዳግም በዚህ ምድር ቤቶችን፣ የወይን ቦታዎችን እና እርሻዎችን ይገዛሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ እና ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 32:16

አጠቃላይ መረጃ:
ኤርምያስ መናገሩን ቀጥሏል። ረጅም ጸሎት ጀመረ፣ ከረጅም እንጉርጉሮ ጋር ምስጋና ጭምር አቀረበ።

የግዝ ደረሰኝ
ይህ ማለት የታተመው ጥቅልል እና ያልታተመ ጥቅልል ነው

አወይ፣ ጌታ ያህዌ! እነሆ!
እዚህ ስፍራ "አወይ/ወየው" የሚለው ቃል በዚህ ጸሎት ኤርምያስ ማዘኑን፣ ማጉረምረሙን እና እንጉርጉሮ ማሰማቱን ያመለክታል። "እነሆ/እዩ" የሚለው ቃል ቀጣዮቹ ቃላት ለጸሎቱ በጣም አስፈላጊ የሆነ መግቢያ ወይም ዳራ መሆኑን ያመለክታል። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

በታላቅ ጥንካሬህ እና በተነሳው ክንድህ
"የተነሳ ክንድ" የሚለው ሀረግ ለክንድ ጥንካሬ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው፤ ስለዚህም "ታላቁ ጥንካሬህ" የሚሉት ቃላት እና "የተነሱት ክንዶችህ" የሚለው ጥንድ ትርጉምን ይሰጣል። "በታላቁ ሀይልህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ጥንድ ትርጉም የሚሉትን ይመልከቱ)

አንተ የቃል ኪዳን ታማኝነትን ለሺህዎች አሳይተሃል
"ታማኝነት" የሚለው ረቂቅ ስም "ታማኝ" ወይም "በታማኝነት" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "አንተ ለሺህዎች ለቃል ኪዳንህ ታማኝ ነህ" ወይም "አንተ ቃል ኪዳንህን ትጠብቃለህ፣ ደግሞም ሺህዎችን በታማኝነት ትወዳለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የሰዎችን ጥፋት ከእነርሱ በኋላ በሚመጡት ልጆቻቸው ጭን ላይ አፍስስ
"ጥፋት" የሚለው ቃል ያህዌ ህዝቡን ለመቅጣቱ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው፤ ምክንያቱም እነርሱ ክፉ ነገሮችን በማድረግ ጥፋተኞች ናቸው። የያህዌ ህዝቡን መቅጣት የተገለጸው ፈሳሽ በትልቅ ማጠራቀሚያ የሞላ ፈሳሽን እንዳፈሰሰባቸው ወይም በተቀመጡበት በጭናቸው ላይ ትንንሽ እቃዎችን እንደጣለባቸው ተደርጎ ተገልጽዋል። "አንተ ልጆችን በወላጆቻቸው ኃጢአት ምክንያት ትቀጣለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 32:19

አጠቃላይ መረጃ:
ኤርምያስ ለእንጉርጉሮው መግቢያ የሚሆነውን ጸሎት ወደ ያህዌ ማቅረቡን ቀጥሏል

ዐይኖችህ ለሰዎች መንገዶች ሁሉ የተከፈቱ ናቸው
የተከፈቱ ዐይኖች ሰው ለሚመለከተው ነገር ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት / ነው። ሰው እንዴት እንደሚኖር የተገለጸው በጎዳና ላይ እንደሚራመድ ተደርጎ ነው። "አንተ ሰዎች የሚያደርጉትን ነገር ሁሉ ትመለከታለህ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ለእያንዳንዱ ሰው ለባህሪው እና ለተግባሩ የሚገባውን መስጠት
ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው "ባህሪይ" እና "ተግባር/ድርጊት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች በግስ መልካቸው ሊተረጎሙ ይችላሉ። "እናም ለእያንዳንዱ ሰው እንደ ስራው መልካምነት ወይም ክፋት ይከፍለዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ጥንድ ትርጉም የሚሉትን ይመልከቱ)

አንተ በግብጽ ምድር ድንቅ እና ምልክቶችን አድርገሃል
ይህ እግዚአብሔር በቀድሞው ዘመን ሀይሉን ተጠቅሞ የእስራኤልን ህዝብ ከግብጽ ባርነት ነጻ ያወጣበትን ድርጊት ያመለክታል።

እስከ ዛሬዋ ቀን ድረስ
"እስከዚህ ቀን"

በሰው ልጆች ሁሉ መሃል
"በሰዎች ሁሉ መሃል"

ስምህን ታዋቂ አደረግህ
እዚህ ስፍራ "ስም" የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ክብር ነው። "እራስህን ገናና አደረግህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በብርቱ እጅ፣ በተዘረጋ ክንድ
"በብርቱ እጅ" የሚለው ለጥንካሬ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሲሆን፤ "የተዘረጋ ክንድ" የሚለው ለክንድ ጥንካሬ ሜቶኖሚ/ ነው። ስለዚህም "በብርቱ እጅ" የሚለው ሀረግ እና "የተዘረጋ ክንድ" የሚሉት ሀረጎች ጥንድ ትርጉም ይሰጣሉ። "በታላቁ ጥንካሬህ/ ሀይልህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ጥንድ ትርጉም የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 32:22

አጠቃላይ መረጃ:
ኤርምያስ ወደ ያህዌ መጸለዩን ቀጥሏል። የእንጉርጉሮ ለቅሶውን ማቅረቡን ጨረሰ። ("ወየው፣" ኤርምያስ 32:17) "ከዚህ ርስት ወሰዱ" ከሚሉት ቃላት ጋር "ነገር ግን እነርሱ አልታዘዙም" በሚለው ሰቆቃውን ይጀምራል።

ለእነርሱ ሰጠሃቸው
"ለእስራኤል ሰዎች ሰጠህ"

ማር እና ወተት የምታፈስ ምድር
"ማር እና ወተት የሚፈስባት ምድር።" እግዚአብሔር ምድሪቱ ለተክሎች እና ለእንስሳት መልካም እንደሆነች የተናገረው ከእነዚያ እንሳሳት እና ተክሎች የሚገኘው ወተት እና ማር በምድሪቱ ላይ እንደሚፈስ አድርጎ ነው። ኤርምያስ 11:5 ላይ ይህ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ከብት ለማርባት እና ተክል ለማብቀል እጅግ ምቹ የሆነ ምድር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን እነርሱ ድምጽህን አልታዘዙም
ድምጹ ተናጋሪው ለሰጠው መልዕክት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ነገር ግን እነርሱ አንተ የተናገርከውን አልታዘዙም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 32:24

አጠቃላይ መረጃ:
ኤርምያስ ወደ ያህዌ መጸለዩን ቀጥሏል።

የአፈር ቁልሉ እርሷን ለመያዝ እስከ ከተማይቱ ደርሷል
የአፈሩ ቁልል እና ጠላት በላያቸው ቆሞ ሊያጠቃት በከተማይቱ ዙሪያ ገነባው፣ የተገለጸው አጥቂዎቹ ራሳቸው ከተማይቱን ለመውረር እንደ ደረሱ ተደርጎ ነው። "ጠላት ያበጀው አፈር ቁልል፣ ጠላት ሊይዛት እስከሚያስችለው ለከተማይቱ እጅግ ቅርብ ነው" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከሰይፍ የተነሳ
"ሰይፍ" የሚለው ቃል ወታደሮች ሰይፍ በሚጠቀሙበት፣ ለጦርነት ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ምክንያቱም ወታደሮች ጥቃት ያደርሳሉ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ረሃብ፣ እና መቅሰፍት
እነዚህ ረቂቅ ስሞች በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "ህዝቡ የሚመገበው ምግብ የለውም፣ ደግሞም እያንዳንዱ ሰው ከህመም የተነሳ ደካማ ሆኗል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ከተማይቱ ለከለዳውያን እጅ ተላልፋ ተሰጥታ ነበር
እዚህ ስፍራ "እጅ" ማለት ሀይል ወይም መቆጣጠር ማለት ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "አንተ እየሩሳሌምን ለከለዳውያን ወታደሮች አሳልፈህ ሰጥተሃታል" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ይህ ይሆናል፣ አንተ ታያለህ
"አንተ በግልጽ እንደምታየው፣ ይህ ይሆናል"

ምስክሮች ይህን መስክረዋል
"አንተ መሬን ስትገዛ ሰዎች ተመልክተዋል፣ ስለዚህም እነርሱ ለሌሎች ሰዎች አንተ መሬቱን እንደገዛህ መናገር/መመስከር ይችላሉ"

ከተማይቱ ተሰጥታለች
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እኔ ይህችን ከተማ ልሰጣት ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 32:26

የያህዌ ቃል ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ፣ "ያህዌ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር የዋለው ከእግዚአብሔ ዘንድ ልዩ መልዕክት ለማስተዋወቅ ነው። በኤርምያስ 1:4 ላይ ተመሳሳይ የሆነው ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ለኤርምያስ፣ እንዲህ ሲል መልዕክት ሰጠው። 'ያህዌ" ወይም "ያህዌ ይህንን መልዕክት ለኤርምያስ ሰጠው፡ 'ያህዌ"

ወደ ኤርምያስ መጣ
እዚህ ስፍራ ኤርምያስ ለምን ራሱን በስም እንደጠቀሰ ግልጽ አይደለም። በዩዲቢ እንደ ተተረጎመው አንደኛ መደብን በመጠቀም መተረጎም ይቻላል። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚሉትን ይመልከቱ)

ለእኔ እጅግ ከባድ የሆነ ነገር አለን?
ያህዌ ጥያቄ የተጠቀመው እርሱ ማንኛውንም ነገር ማድረግ እንደሚችል ትኩረት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ለእኔ እጅግ ከባድ የሆነ ነገር የለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ፣ እኔ አሳልፌ እሰጣታለሁ
"በጥንቃቄ አድምጡ! አሳልፌ የምሰጣት እኔ ነኝ"

ይህችን ከተማ ለከለዳውያን እጅ እሰጣለሁ
ያህዌ ስለ ከተማይቱ፣ ትንሽ እቃ እንደሆነች እና ለሰው እጅ እንደሚሰጣት አድረጎ ይናገራል። "እጅ" የሚለው ቃል እጅ ወደ ድርጊት ለሚለውጠው ሀይል ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ይህችን ከተማ በከለዳውያን ሀይል ስር አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 32:29

አጠቃላ መረጃ:
ያህዌ ለኤርምያስ መናገሩን ቀጥሏል።

እኔን ለማነሳሳት
"እኔ በጣም እቆጣ ዘንድ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በዐይኖቼ ፊት ክፉ ያደርጋሉ
እዚህ ስፍራ "ዐይኖች" የሚለው ሜቶኖሚ የሚወክለው እግዚአብሔር የተመለከተውን ነገር ነው። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "እኔ ክፉ የምለውን ነገር ማድረግ" ወይም 2) "እኔ እየተመለከትኩ መሆኑን እያወቁ ክፉ ማድረግ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከወጣትነታቸው አንስቶ
የአንድ ሰው ወጣት መሆን ለእስራኤል ህዝብ በመጀመሪያ አገር መሆን ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "ወጣት ከነበሩበት ጊዜ አንስቶ" ወይም "አገር ሆነው ከተመሰረቱበት ጊዜ አንስቶ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእጆቻቸው ልምምዶች
"እጆች" የሚለው ቃል አንድ ሰው በእጆቹ ለሚሰራቸው ነገሮች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ያደረጎቸው ክፉ ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 32:31

አጠቃላ መረጃ:
ያህዌ ለኤርምያስ መናገሩን ቀጥሏል።

ይህች ከተማ ከተመሰረተችበት ጊዜ አንስቶ የእኔን ቁጣ እና ንዴት ታነሳሳ ነበር
እዚህ ስፍራ "ከተማ" የሚለው በውስጧ ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ ነው። "ቁጣ" እና "ንዴት" በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲይዙ ምን ያህል በጣም እንደተቆጣ ያጎላሉ። "የእየሩሳሌም ሰዎች ከተማቸውን ከገነቡበት ጊዜ አንስቶ እኔን በጣም አስቆጥተውኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ጥንድ ትርጉም የሚሉትን ይመልከቱ)

እኔን የሚያነሳሳ ነበር
"ማነሳሳት" የሚለው ረቂቅ ስም በግስ መልኩ ሊተረጎም ይችላል። "የሚያነሳሳ ነገር ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ እስከ ዛሬው ቀን ድረስ ቀጥሏል
"አሁን ድረስ እኔን ማስቆጣታቸውን ቀጥለዋል"

ከገጽታዬ ፊት/ከፊቴ
ፊት ለአንድ ሰው መገኘት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ከእኔ መገኘት" ወይም "ሙሉ ለሙሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 32:33

አጠቃላ መረጃ:
ያህዌ ለኤርምያስ የእስራኤል ህዝብ ስላደረገው ነገር መናገሩን ቀጥሏል።

ከፊታቸው ይልቅ ጀርባቸውን አዙረውብኛል
አንድ ሰው ፊቱን ወደ ሌላ ሰው ማድረጉ እየማ መሆኑን ያሳያል፣ ጀርባውን መስጠቱ ደግሞ ለመስማት አለመፍቀዱን ያሳያል። "እኔን በጥንቃቄ ከመስማት ይልቅ፣ ሙሉ ለሙሉ ሊሰሙኝ አልፈቀዱም" ወይም "እኔን ለመስማት አልፈቀዱም/ለመስማት ተቃወሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/ ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

እርማትን/ተግሳጽን ለመቀበል
"በትክክል ምላሽ መስጠትን ለመማር"

አስጸያፊ ጣኦቶቻቸው
"እኔ የምጠላቸው ጣኦቶቻቸው"

በስሜ የተጠራው ቤቴ
እዚህ ስፍራ "ስም" የሚወክለው ያህዌን ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "የእኔ የሆነው ቤት" ወይም "እነርሱ እኔን የሚያመልኩበት ህንጻ/ቤት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

የሄኖም ሸለቆ
ይህ በኤርምያስ 7:31 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ይህን በፍጹም በልቤ አላሰብኩም/ወደ አዕምሮዬ አልገባም
እዚህ ስፍራ "ልብ/አዕምሮ" የሚያመለክተው የያህዌን ፈቃድ/ሀሳብ ነው። "እኔ በፍጹም አላሰብኩም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 32:36

እናንተ የተናገራችሁት
እዚህ ስፍራ "እናንተ" የሚለው ብዙ ቁጥር ነው። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ኤርምያስን እና ከእርሱ ጋር የነበሩትን ይገልጻል፣ ወይም 2) ሁሉንም ሰዎች ያመለክታል። (አንተ/አንቺ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)

እርሷ ለባቢሎን ንጉሥ እጆች ተሰጠች
እዚህ ስፍራ "እጅ" ማለት ሀይል ወይም ቁጥጥር ማለት ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ያህዌ ለባቢሎን ንጉሥ እርሷን/ከተማይቱን እንዲገዛ ሀይል ሰጠው" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

እነርሱን ለመሰብሰብ
"የእኔን ህዝብ ለመሰብሰብ"

ንዴት፣ መዓት፣ እና ታላቅ ቁጣ
ሶስቱም ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ሲይዙ እርሱ ምን ያህል እንደተቆጣ ትኩረት ይሰጣሉ። "ከመጠን ያለፈ ቁጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

በደህንነት
"እነርሱ በሰላም ባሉበት"

Jeremiah 32:38

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ መናገሩን ቀጥሏል።

እኔን ለማክበር አንድ ልብ እና አንድ መንገድ
የእስራኤል ሰዎች ያህዌን ለማክበር በአንድነት መስራት ይፈልጋሉ። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ዘለዓለማዊ ቃል ኪዳን
"ዘለዓለማዊ ስምምነት"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መልካም ከማድረግ ወደ ኋላ አልመለስም
"መልካም ማድረግን አላቆምም"

በእነርሱ ልብ ለእኔ ክብርን አኖራለሁ
ክብር የተገለጸው ጠጣር አካል እንደሆነ እና ማንም ከዚያ ሊያሰወግደው እንዳይችል ተደርጎ በመያዣ ውስጥ እንደተቀመጠ ተደርጎ ነው። "እነርሱ ሁልጊዜም እንዲያከብሩኝ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዜቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚህ የተነሳ እነርሱ በፍጹም ከእኔ ፊታቸውን አይመልሱም
"ከዚህ የተነሳ እኔኝ መታዘዝ እና ማምለክ በፍጹም አያቆሙም"

Jeremiah 32:41

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ መናገሩን ቀጥሏል።

ለእነርሱ መልካም ማድረግ
እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው የሚያመለክተው እስራኤላውያንን ነው።

እኔ እነርሱን በዚህች ምድር በታማኝነት እተክላቸዋለሁ
ያህዌ የእርሱ ህዝብ ህይወት በአትክልት ስፍራ እንደተከለው ተክል ለዘለአለም እንደሚኖር አድርጎ ይናገራል። "እኔ እስራኤላውያንን በቋሚነት በዚህ ምድር አስቀምጣቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በሙሉ ልቤ እና በህይወቴ ሁሉ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በአንድነት የአንድን ሰው ሁለንተና የሚያመለክት ፈሊጣዊ አገላለጽን ይሰጣሉ። "በፍጹም ማንነቴ" ወይም "በሙሉ ልቤ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

እኔ እነዚህን ሁሉ ታላላቅ ጥፋቶች በዚህ ህዝብ ላይ አምጥቻለሁ፣ እንደዚሁ ደግሞ መልካም ነገሮችን ሁሉ ለዚህ ህዝብ አደርጋለሁ
"እነዚህ ሁሉ መጥፎ ነገሮች በዚህ ህዝብ ላይ እንዲደርስ አድርጌያለሁ፣ አሁን ደግሞ መልካም ነገሮች እንዲሆንላቸው አደርጋለሁ"

Jeremiah 32:43

ከዚያ የእርሻ መሬቶች በዚህ ምድር ይገዛሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ከዚያ ሰዎች በዚህ ምድር የእርሻ መሬት ይገዛሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ እንደዚህ ትላላችሁ
እዚህ ስፍራ "እናንተ" የሚለው የሚያመለክተው የእስራኤል ሰዎችን ነው። (አንተ/አንቺ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)

ለከለዳውያን እጆች ተሰጥታ ነበር
እዚህ ስፍራ "እጅ" ለሀይል ወይም ቁጥጥር ሜቶኖሚ/ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ያህዌ ለከለዳውያን ይህን ሰጣቸው" ወይም "ያህዌ ለከለዳውያን በእርሷ ላይ ሀይል ሰጣቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ))

በታተሙ ጥቅልሎች ላይ ጻፉ። ምስክሮችን ይጠራሉ
"የታተሙ ጥቅልሎች" አንድ ሰው መሬት ለመግዛት የሚፈርምበት ውል ነው። ሌሎች ሰዎች ግዢውን ለማረጋገጥ ምስክር ይሆናሉ።

እድል ፈንታቸውን/ሀብታቸውን እመልስላቸዋለሁ
"ነገሮች ተመልሰው መልካም እንዲሆንላቸው አደርጋለሁ" ወይም "ዳግም ወደ መልካም ህይወት እመልሳቻለሁ" ተመሳሳይ የሆኑ ቃሎች በኤርምያስ 29:14 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 33

1 ኤርምያስ ገና በግዞት ቤት አደባባይ ታስሮ ሳለ የእግዚአብሔር ቃል ሁለተኛ ጊዜ መጣለትና እንዲህ አለው፣ **2** "ስሙ እግዚአብሔር የሆነ፣ ያደረገው እግዚአብሔር፣ ያጸናውም ዘንድ የሠራው እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። **3** 'ወደ እኔ ጩኽ፣ እኔም እመልስልሃለሁ። አንተም የማታስተውለውን ታላቅና ኃይለኛ ነገርን አሳይሃለሁ።' **4** የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር፣ ለአፈር ድልድልና ለምሽግ ስለ ፈረሱ ስለዚህች ከተማ ቤቶች፣ ስለ ይሁዳም ነገሥታት ቤቶች እንዲህ ይላልና። **5** 'ስለ ክፋታቸው ሁሉ ፊቴን ከዚህች ከተማ ስሰውር፣ ከለዳውያን ለመዋጋትና በቊጣዬ፣ እንዲሁም በመዓቴ በምገድላቸው ሰዎች ሬሳዎች ሊሞሏቸው እየመጡ ናቸው። **6** ነገር ግን ተመልከቱ፣ ፈውስንና መድኃኒትን አመጣላታለሁ፣ እፈውሳቸውማለሁ፤ መትረፍረፍንም አመጣላቸዋለሁ፣ ሰላምንና የታማኝነትን ብዛት አመጣላቸዋለሁ። **7** የይሁዳን ምርኮና የእስራኤልን ምርኮ መልሼ አመጣለሁ፣ ቀድሞም እንደ ነበሩ አድርጌ እሠራቸዋለሁ። **8** እኔንም ከበደሉበት ኃጢአት ሁሉ አነጻቸዋለሁ። እኔንም የበደሉበትን ያመፀብኝንም ኃጢአታቸውን ሁሉ ይቅር እላለሁ። **9** ይህችም ከተማ እኔ የምሠራላቸውን በጎነት ሁሉ በሚሰሙ እኔም ስላመጣሁላቸው መልካምነትና ሰላም ሁሉ በሚፈሩና በሚደነግጡ አሕዛብ ሁሉ ፊት ለደስታ ስም ለምስጋናም ለክብርም ትሆናለች። **10** እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ እናንተ፣ "ያለ ሰውና ያለ እንስሳ ያለች ባድማ ናት በምትሉአት በዚህች ስፍራ፣ የሚቀመጥባቸው በሌላ፣ ያለ ሰውና ያለ እንስሳ ባድማ በሆኑ በይሁዳ ከተሞችና በኢየሩሳሌም ጎዳናዎች ጥፋት ሆኗል።" **11** የሐሤት ድምፅና የደስታ ድምፅ፣ የወንድ ሙሽራ ድምፅና የሴት ሙሽራ ድምፅ፣ "እግዚአብሔር ቸር ነውና፣ ምሕረቱም ለዘላለም ነውና የሠራዊትን ጌታ እግዚአብሔርን አመስግኑ" የሚሉ ድምፅ በድጋሚ ይሰማል። ወደ እግዚአብሔርም ቤት የምስጋናን መሥዋዕት አምጡ፣ የምድርን ምርኮ ቀድሞ እንደ ነበረ አድርጌ እመልሳለሁና፣' ይላል እግዚአብሔር። **12** የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ 'ባድማ ሆኖ፣ ያለ ሰውና ያለ እንስሳ ባለው በዚህ ስፍራ፣ በከተሞችም ሁሉ መንጎቻቸውን የሚያሳርፉት የእረኞች መኖሪያ ይሆናል። **13** በደጋው ላይ ባሉ ከተሞች፣ በቈላውም ባሉ ከተሞች፣ በደቡብም ባሉ ከተሞች፣ እንዲሁም በብንያምም ምድር በኢየሩሳሌምም ዙሪያ ባሉ ስፍራዎች፣ በይሁዳም ከተሞች መንጎቹ በተቈጣጣሪው እጅ እንደ ገና ያልፋሉ፣' ይላል እግዚአብሔር። **14** 'ተመልከቱ! ስለ እስራኤል ቤትና ስለ ይሁዳ ቤት የተናገርሁትን መልካም ቃል የምፈጽምበት ዘመን ይመጣል፤ ይላል እግዚአብሔር። **15** በዚያም ዘመን በዚያም ጊዜ ለዳዊት የጽድቅን ቍጥቋጥ አበቅልለታለሁ፣ እርሱም ፍትህንና ጽድቅን በምድር ላይ ያደርጋል። **16** በዚያም ዘመን ይሁዳ ይድናል ኢየሩሳሌምም በአስተማማኝ ሁኔታ ትቀመጣለች፤ የምትጠራበትም ስም፣ "እግዚአብሔር ጽድቃችን" ተብሎ ነው። **17** እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፦ 'በእስራኤል ቤት ዙፋን ላይ የሚቀመጥ ሰው ከዳዊት ዘንድ አይታጣም፤ **18** የሚቃጠለውንም መሥዋዕት የሚያቀርብ፣ የእህሉንም ቍርባን የሚያቃጥል፣ ሁልጊዜም የሚሠዋ ሰው ከሌዋውያን ካህናት ዘንድ በእኔ ፊት አይታጣም።" **19** የእግዚአብሔርም ቃል ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ፣ **20** "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ 'ቀንና ሌሊት በወራቱ እንዳይሆን የቀን ቃል ኪዳኔንና የሌሊት ቃል ኪዳኔን ማፍረስ ብትችሉ፣ **21** ያኔ በዙፋኑ ላይ የሚነግሥ ልጅ ከእንግዲህ እንዳይሆንለት ከባሪዬ ከዳዊት ጋር፣ ከአገልጋዮቼም ከሌዋውያን ካህናት ጋር ያለው ቃል ኪዳኔ ደግሞ ይፈርሳል። **22** የሰማይ ሠራዊት መቊጠር፣ የባሕርንም አሸዋ መስፈር እንደማይቻል፣ እንዲሁ የባሪያዬን የዳዊትን ዘርና የሚያገለግሉኝን ሌዋውያንን አበዛለሁ።" **23** የእግዚአብሔር ቃል ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ፣ **24** "ይህ ሕዝብ፣ 'እግዚአብሔር መርጧቸው የነበሩትን ሁለቱን ወገን ጥሎአቸዋል፤' ያለውን ነገር አትመለከትምን? በዚህ መልኩ በፊታቸው ከእንግዲህ ወዲህ ሕዝብ እንዳይሆን ሕዝቤን አቃልለዋል። **25** እኔ፣ እግዚአብሔር እንዲህ እላለሁ፣ 'የቀንና የሌሊት ቃል ኪዳኔ የማይኖሩ ከሆነ፣ ወይም የሰማይንና የምድርንም ሥርዓት ያልጠበቅሁ እንደሆነ፣ **26** ያን ጊዜ በአብርሃም፣ በይስሐቅና፣ በያዕቆብም ዘር ላይ ገዦች ይሆኑ ዘንድ ከዘሩ እንዳልወስድ፣ የያዕቆብንና የባሪያዬን የዳዊትን ዘር እጥላለሁ። ምርኮአቸውን እመልሳለሁና፣ እምራቸውማለሁና።"

Jeremiah 33:1

አጠቃላይ መረጃ፡
ስነግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ

የያህዌ ቃል ለሁለተኛ ጊዜ፣ በዘብ ... በነበረበት ጊዜ ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ፣ ''ያህዌ
"የያህዌ ቃል ወደ... መጣ" የሚለው ፈሊጥ የዋለው ከእግዚአብሔር ዘንድ ልዩ መልዕክት ለማስተዋወቅ ነው። በኤርምያስ 1:13 ላይ የሚገኘው ተመሳሳይ ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ኤርምያስ በዘብ... በነበረበት ጊዜ ያህዌ ለኤርምያስ እንዲህ ሲል ለሁለተኛ ጊዜ መልዕክት ሰጠው። 'ያህዌ" ወይም "ኤርምያስ በዘብ... በነበረበት ጊዜ ያህዌ ይህን ሁለተኛ መልዕክት ለኤርምያስ ሰጠው፡ 'ያህዌ"... በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ኤርምያስ መጣ
እዚህ ስፍራ ኤርምያስ ለምን ራሱን በስም እንሚጠቅስ ግልጽ አይደለም። አንደኛ መደብን በመጠቀም መተረጎም አስፈላጊ አይደለም። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ሊያጸናቸው ያበጃቸው ማን ነው
ነገሮች ለዘለዓለም ይኖሩ ዘንድ የፈጠራቸው ማን ነው

እስከዚህ ድረስ ተዘግቶበት ነበር
"እስከ አሁን ድረስ እስረኛ ነበር"

የዘብ ጠባቂዎች አደባባይ
ይህ በግንብ የተከበበ እና እስረኞችን የሚጠብቁበት/የሚያስሩበት ከንጉሡ ቤተመንግስት ጋር የተያያዘ ክፍት ስፍራ ነው። ይህ በኤርምያስ 32:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

Jeremiah 33:4

ከወወጊያ እና ከሰይፍ የተነሳ ከፈራረሱት
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሰዎቹ ከለዳውያንን ለመከላከያ ቅጥር ለመገንባት ቤቶችን አፈረሱ። "ከውጊያ እና ሰይፍ ራሳቸውን ለመከላከል ሰዎች የከተማዋን ቤቶችን አፈራረሱ" ወይም 2) "ጦርነት ለማድረግ ሲሉ በጦርነት ከበባ አመጽ ለማነሳሳት ከለዳውያን ያፈራረሷቸው ቤቶች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰይፍ
ይህ ወታደሮች በሰይፍ ሲገድሉ ለሰዎች በጥቃት መገደል ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በቁጣዬ እና በመአቴ
"ቁጣ" እና "መአት" የሚሉት ቃላት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው የቁጣውን ታላቅነት ያጎላሉ። "ከመጠን በላይ በሆነው ቁጣዬ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ፊቴን እሰውራለሁ/እደብለሁ
ያህዌ በ"ፊቱ" ተወክሏል። ይህ ሀረግ የሚያሳየው የያህዌን በከተማይቱ ደስ አለመሰኘት ነው። "እኔ ከእናንተ ዞር ብያለሁ" ወይም "ከእንግዲህ ለእናንተ ጥበቀ አላደርግም/እተዋችኋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 33:6

የይሁዳን እና እየሩሳሌምን ሀብት/ምርኮ እመልሳለሁ
"ለይሁዳ እና እስራኤል ነገሮች መልካም እንዲሆኑ አደርጋለሁ" ወይም "ይሁዳ እና እስራኤል ዳግም በመልካም እንዲኖሩ አደርጋለሁ።" ተመሳሳይ የሆኑ ቃላት በኤርምያስ 29:14 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

ይህች ከተማ... ለእርሷ ያደረግኩትን... ለራሷ የሰጠሁትን
ከተማይቱ የሚለው በከተማዋ ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ ነው። "በዚህች ከተማ የሚኖሩ ሰዎች ...በዚያ ለሚኖሩ ሰዎች የማደርገው... በዚያ ለሚኖሩ ሰዎች የምሰጠው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ለመላው የምድር አገራት የውዳሴ እና ክብር ዝማሬ
"ዝማሬ" የሚለው ቃል ሰዎች ስለ ሚዘምሩት ዝማሬ አካል ሜቶኖሚ/ ነው። "የምድር ወገኖች ሁሉ የውዳሴ እና ክብር ዝማሬ ለእኔ ለያህዌ ስለሚያቀርቡት ነገር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ይፈራሉ ይንቀጠቀጡማል
"ፍርሃት እና መንቀጥቀጥ" የሚለው ሄንዲየዲስ/ሁለት በ'እና' የሚገኙኙ ቃላት አንድን ጥልቅ ሀሳብ የሚገልጹበት ዘይቤያዊ አነጋገር/ በአንድ ግስ ሊተረጎም ይችላል። "በፍርሃት ይንቀጠቀጣሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሄንዲየዲስ/ሁለት በ'እና' የሚገኙኙ ቃላት አንድን ጥልቅ ሀሳብ የሚገልጹበት ዘይቤያዊ አነጋገር/ የሚለውን ይመልከቱ)

ፍርሃት
ሌላው ሊሰጥ የሚችለው ትርጉም "አክብሮታዊ ፍርሃት" የሚል ነው።

ለእርሷ ከምሰጠው ሰላም እና መልካም ነገሮች ሁሉ የተነሳ
"ሰላም" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ለእርሷ ከምሰጠው ሰላም እና መልካም ነገሮች ሁሉ የተነሳ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 33:10

ሰውም እንስሳም የማይኖርባት ምድረ በዳ ናት፣" ምድረ በዳ በሆኑት በይሁዳ ከተሞች፣ እና በእየሩሳሌም መንገዶች ሰውም ሆነ እንስሳት አይኖሩም
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው ይሁዳ ምድረበዳ መሆኗን ያጎላሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌ ቤት
በእየሩሳሌም የሚገኘው ቤተ መቅደስ

የምድሪቱን እደል ፈንታ አድሳለሁ
"ምድር" የሚለው ቃል በምድሪቱ ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ዳግም በምድሪቱ ለሚኖሩ ሰዎች ነገሮችን መልካም አደርጋለሁ" ወይም "በምድሪቱ የሚኖሩ ሰዎችን ዳግም በመልካም እንዲኖሩ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ተመሳሳይ የሆኑ ቃላት በኤርምያስ 29:14 ላይ እንዴት እንደተተረጎሙ ይመልከቱ። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ አስቀድሞ ወደ ነበሩበት
ይህ ወደ ባቢሎን ከመሰደድ አስቀድሞ የነበረውን ጊዜ ያመለክታል። ይህ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "እነርሱ አስቀድመው ወደ ነበሩበት፣ እስራኤላውያንን ለምርኮ ወደ ባቢሎን እሰዳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 33:12

የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ከብቶች ዳግም በሚቆጥሯቸው እጅ ስር ያልፋሉ
ይህ የእረኞች በጎቻቸው ከእጃቸው ስር ሲሄዱ የሚያደርጉትን በጎቻቸውን የመቁጠር እና የመጠበቅ ልምምድ ያመለክታል። "እረኞች በጎች በሚያልፉበት ጊዜ እንደ ቀድሞው በጎቻቸውን ይቆጥራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 33:14

እነሆ/እዩ
"በጥንቃቄ አድምጡ"

እኔ የምሰራባቸው...ቀናት እየመጡ ነው
መጪው ጊዜ የተነገረው "ቀናት እየመጡ" እንደሆነ ተደርጎ ነው። ይህ ዘይቤ በኤርምያስ 7:32 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እኔ በመጪው ጊዜ... እሰራለሁ" ወይም "እኔ የምሰራበት...ጊዜ ይኖራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ቤት
"ቤት" የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። በዚህ ሁኔታ ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን መንግሥት ነው። ይህ በኤርምያስ 3:18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እስራኤል" ወይም "የእስራኤል መንግሥት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳ ቤት
"ቤት" የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። በዚህ ሁኔታ ይህ የሚያመለክተው፣ የይሁዳን እና የብንያምን ትውልድ የሚያጠቃልለውን የይሁዳን መንግሥት ነው። ይህ በኤርምያስ 3:18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ይሁዳ" ወይም "የይሁዳ መንግሥት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በእነዚያ ቀናት ወይም በዚያን ጊዜ
"በዚያን ጊዜ" የሚለው ሀረግ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖረው "በእነዚያ ቀናት" የሚለውን ሀረግ ያጠናክራል። "በእነዚያው በራሳቸው ቀናት" ወይም "በዚያኑ በራሱ ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለዳዊት የጽድቅ ቅርንጫፍ እንዲበቅል አደርጋለሁ
ያህዌ የዳዊትን ትውልድ የሚገልጸው የዛፍ ግንድ ቅርንጫፍ እንደሆነ አድርጎ ነው። "እኔ ጻድቅን ሰው ከዳዊት እንዲመጣ እና ለዳዊት ዘር ክብር እንዲያመጣ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሪቱ
የእስራኤል ህዝብ። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ይሁዳ... እየሩሳሌም
እነዚህ ሁለት የከተሞች ስሞች በእነዚያ ከተሞች ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ናቸው። "የይሁዳ ሰዎች... የእየሩሳሌም ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ይሁዳ ይድናል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እኔ ይሁዳን አድነዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እየሩሳሌም በደህንነት/በሰላም ትኖራለች
"የእየሩሳሌም ሰዎች ከጠላቶቻቸው የተጠበቁ ይሆናሉ"

እርሷ የምትጠራበት ይህ ይሆናል
ያህዌ ስለ እየሩሳሌም ከተማይቱ ሴት እንደሆነች አድርጎ ይናገራል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እርሷን የሚሯት እንዲህ ብለው ነው" ወይም "እኔ ከተማይቱን የምጠራት እንዲህ ብዬ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 33:17

ከዳዊት ትውልድ የሆነ ሰው አይታጣም
"ሁልጊዜም ከዳዊት ትውልድ የሆነ ሰው ይገኛል"

ከዳዊት ትውልድ የሆነ ሰው
ወንድ የሆነ የንጉሥ ዳዊት ትውልድ

በእስራኤል ቤት ዙፋን ላይ ለመቀመጥ
ዙፋን ለንጉሡ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "በእስራኤል ቤት ላይ ንጉሥ ለመሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ቤት
"ቤት" የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። በዚህ ሁኔታ ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን መንግሥት ነው። ይህ በኤርምያስ 3:18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እስራኤል" ወይም "የእስራኤል መንግሥት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የሚቃጠል መስዋዕት በፊቴ ለማንሳት/ለማቅረብ ከሌዊ ካህናት መሃል ሰው አይታጣም
"ሁሉም ከሌዊ ካህናት የሚቃጠል መስዋዕት የሚያነሳ ሰው አይታጣም"

የሚቃጠል መስዋዕት የሚያነሳ/የሚያቀርብ
"የሚቃጠሉ መስዋዕቶች የሚያቀርብ"

Jeremiah 33:19

የያህዌ ቃል ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ፣ "ያህዌ
x

Jeremiah 33:23

የያህዌ ቃል ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ፣ "እንዲህ አለኝ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር የዋለው ከእግዚአብሔ ዘንድ ልዩ መልዕክት ለማስተዋወቅ ነው። በኤርምያስ 1:4 ላይ ተመሳሳይ የሆነው ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ለኤርምያስ፣ እንዲህ ሲል መልዕክት ሰጠው። 'እንዲህ አለኝ" ወይም "ያህዌ ይህንን መልዕክት ለኤርምያስ ሰጠው፡ 'እንዲህ አለው"

ወደ ኤርምያስ
እዚህ ስፍራ ኤርምያስ ለምን ራሱን በስም እንደጠቀሰ ግልጽ አይደለም። አንደኛ መደብን በመጠቀም መተረጎም አያስፈልግም። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ህዝብ እንዲህ ሲል አላስተዋልክም፣ ‘የ... እነርሱ።'"
ያህዌ ህዝቡ ምን እንዳለ ኤርምያስ እንዲያስተውል ፈልጓል። ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ይህ ህዝብ ‘የ... እነርሱ' ሲል ምን እየተናገረ እንደጀሆነ ልታስተውል ይገባሃል" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚህ መንገድ፣ አይታዩም... እያሉ ህዝቤን አዋርደዋል
"በእርግጥ እነርሱ እየተናገሩ የሚገኙት ህዝቤ እርባና ቢስ እና ዳግም አገር ሆኖ የማይቆም እንደሆነ አድርገው ነው"

ህዝቤ... በእነርሱ እይታ ከእንግዲህ አገር አይሆንም
እይታ ማሰብ ለሚለው ሜቶኖሚ/ ነው። "ከእንግዲህ ህዝቤን እንደ አገር አያስቡም/አያዩም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 33:25

እኔ አልመሰረትኳቸውም... እናም አኔ ካላጸናኋቸው...እኔ እጥላቸዋለሁ...እናም አልመልሳቸውም
ይህ ያህዌ በፍጹም ይሆናል የማይለው መላምታዊ ሁኔታ ነው። "እኔ መስርቻለሁ... እና እና አጸንቻለሁ... ስለዚህ እኔ በፍጹም አልጥልም ... እናም እኔ እመልሳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

እድል ፈንታቸውን /ሀብታቸውን እመልሳለሁ
"ዳግም ነገሮች ለእነርሱ መልካም እንዲሆኑ አደርጋለሁ" ወይም "እኔ እነርሱ ዳግም በመልካም እንዲኖሩ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ተመሳሳይ የሆኑ ቃላት በኤርምያስ 29:14 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

ለ...ምህረት አሳያለሁ
"በ...ላይ ርህራሄ አለኝ" የሚለው በ(ኤርምየስ 30:18) ላይ እንደተተረጎመው ይተርጉሙት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 34

1 ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ኤርምያስ የመጣ ቃል ይህ ነው። ይህ ቃል የመጣው የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆርና ሠራዊቱ ሁሉ፣ ከእጁም ግዛት በታች ያሉ
የምድር መንግሥታት ሁሉ አሕዛብም ሁሉ ኢየሩሳሌምንና ከተሞችዋን ሁሉ ይወጉ በነበረ ጊዜ ነበር። 2 'የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ሂድ
ለይሁዳም ንጉሥ ለሴዴቅያስ ተናገር እንዲህም በለው፣ "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ተመልከት፣ ይህችን ከተማ በባቢሎን ንጉሥ እጅ አሳልፌ እሰጣለሁ።
በእሳትም ያቃጥላታል። 3 አንተም በእርግጥ ትያዛለህ፣ በእጁም ተላልፈህ ትሰጣለህ እንጂ ከእጁ አታመልጥም። ዐይንህም የባቢሎንን ንጉሥ ዐይን ታያለች፤
ወደ ባቢሎን ስትሄድ፣ እርሱ ከአንተ ጋር አፍ ለአፍ ይነጋገራል።' 4 የይሁዳ ንጉሥ ሴዴቅያስ ሆይ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ስማ! ስለ አንተ እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል፣ 'በሰይፍ አትሞትም። 5 በሰላም ትሞታለህ። እንደ አባቶችህ የቀብር መቃጠል፣ ከአንተ በፊት እንደነበሩት ነገሥታት፣ እንዲሁ አካልህን ያቃጥላሉና።
"ወየው፣ ጌታ ሆይ!" እያሉ ያለቅሱልሃል። አሁን እኔ ቃልን ተናግሬአለሁና፣ ይላል እግዚአብሔር።" 6 ነቢዩ ኤርምያስ እነዚህን ቃሎች ሁሉ ለይሁዳ ንጉሥ
ለሴዴቅያስ በኢየሩሳሌም ነገረው። 7 የባቢሎንም ንጉሥ ሠራዊት ኢየሩሳሌምንና የቀሩትን የይሁዳን ከተሞች ሁሉ፦ ለኪሶንና ዓዜቃን ወጋ። እነዚህ የይሁዳ
ከተሞች የተመሸጉ ከተሞች ሆነው ቀሩ። 8 ንጉሡ ሴዴቅያስ በኢየሩሳሌም ከነበሩ ሕዝብ ሁሉ ጋር ነፃነትን ለማወጅ ስምምነት ካደረገ በኋላ፣ ከእግዚአብሔር
ዘንድ ወደ ኤርምያስ የመጣው ቃል ይህ ነው። 9 እያንዳንዱ ሰው እስራኤላዊ የሆነውን ወንድ ባርያውንና ሴት ባርያውን ነፃነት ሊለቅ ይገባል። ማንም ሰው
ከእንግዲህ ወዲህ በይሁዳ ውስጥ መሰል እስራኤላዊን ባርያ ሊያደርግ አይገባም። 10 ስለዚህም ስምምነቱን የተቀላቀሉት መሪዎች ሁሉ እና ሕዝቡ ታዘዙ።
እያንዳንዱ ሰው ወንድ እና ሴት ባርያዎቻቸውን ከእንግዲህ ወዲህ ባርያ ላያደርጓቸው ነፃ አደረጓቸው። እነርሱም ሰሙ፣ ሰደዷቸውም። 11 ነገር ግን ከዚህ በኋላ
አሳባቸውን ቀየሩ። ነፃነት የለቀቋቸውን ባርያዎቻቸውን መልሰው አመጡ። በድጋሚ ባርያዎች እንዲሆኑ አስገደዷቸው። 12 ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል
ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ፣ 13 "የእስራኤል አምላክ፣ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ 'አባቶቻችሁን ከባርነት ቤት ከግብጽ አገር
ባወጣኋቸው ቀን ከእነርሱ ጋር እንዲህ ብዬ ቃል ኪዳን አደረግሁ። 14 "ሰባት ዓመት በተፈጸመ ጊዜ፣ ራሱን የሸጠላችሁን፣ ስድስትም ዓመት የተገዛላችሁን
ዕብራዊ ወንድማችሁን እያንዳንዳችሁ ነፃነት ልታወጡት ይገባል። ነፃ አድርጋችሁ ስደዱት።" ነገር ግን አባቶቻችሁ አልሰሙኝም ጆሮአቸውንም አላዘነበሉም። 15
እናንተም ዛሬ ተመልሳችሁ ሰው ሁሉ ባልንጀራውን አርነት ለማውጣት ዐዋጅ በመንገር ለዐይኔ ትክክል የሆነውን ነገር አድርጋችሁ ነበር። በስሜም በሚጠራበት
ቤት ውስጥ በፊቴ ቃል ኪዳን አድርጋችሁ ነበር። 16 ነገር ግን ያን ጊዜ ተመልሳችሁ ስሜን አስነቀፋችሁ፤ እያንዳንዳችሁም በፈቃዳቸው እንዲሄዱ ነፃነት
ያወጣችኋቸውን ወንድና ሴት ባርያዎቻችሁን አስመለሳችሁ። በድጋሚ ወንዶችና ሴቶች ባርያዎች እንዲሆኑላችሁ አስገደዳችኋቸው።' 17 ስለዚህ እግዚአብሔር
እንዲህ ይላል፣ 'እናንተ ራሳችሁ አልሰማችሁኝም። እያንዳንዳችሁ፣ ለወንድሞቻችሁና ለመሰል እስራኤላውያን ነፃነትን ልታውጁ በተገባ ነበር። ስለዚህ
ተመልከቱ! እኔ ለሰይፍ፣ ለመቅሰፍት፣ ለራብም የነፃነት ዐዋጅ እናገርባችኋለሁ፣ ይላል እግዚአብሔር፤ በምድርም መንግሥታት ሁሉ መካከል አስደንጋጭ ነገር
አደርጋችኋለሁ። 18 ከዚያም ቃል ኪዳኔን የተላለፉትን ሰዎች፣ እንቦሳውንም ቄርጠው በቀሩጩ መካከል ባለፉ ጊዜ በፊቴ ያደረጉትን የቃል ኪዳንን ቃል
ያልፈጸሙትን እቀጣለሁ፤ 19 ከዚያም የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን አለቆች ጃንደረቦችን ካህናትንም፣ በእንቦሳም ቀሩራጭ መካከል ያለፉትን የአገሩን ሕዝብ ሁሉ።
20 ለጠላቶቻቸው እጅ፣ ሕይወታቸውንም ለሚሹአት ሰዎች እጅ አሳልፌ እሰጣለሁ። ሬሳቸውም ለሰማይ ወፎችና ለምድር አራዊት መብል ይሆናል። 21
የይሁዳንም ንጉሥ ሴዴቅያስንና አለቆቹን ለጠላቶቻቸው እጅ፣ ሕይወታቸውንም ለሚሹአት እጅ፣ ከእናንተም ለተመለሱት ለባቢሎን ንጉሥ ሠራዊት እጅ አሳልፌ
እሰጣለሁ። 22 ተመልከቱ፣ ትእዛዝ እሰጣለሁ፣ ይላል እግዚአብሔር፤ ጦርነትን እንዲከፍቱባትና እንዲወስዷት፣ እንዲያቃጥሏትም ወደዚህች ከተማ
እመልሳቸዋለሁ። የይሁዳንም ከተሞች ሰው የሌለበት ባድማ አደርጋቸዋለሁ።"

Jeremiah 34:1

ናቡከደነጾር የእርሷ ከተሞች... በነበረ ጊዜ፣ ከያህዌ ዘንድ ወደ ኤርምያስ የመጣው ቃል እንዲህ ሲሉ፦''ያህዌ
"ከያህዌ ዘንድ ወደ ኤርምያስ የመጣ ቃል" የሚለው ይህ ፈሊጥ የዋለው ከያህዌ ዘንድ ልዩ መልዕክት ለማሰተዋወቅ ነው። ተመሳሳይ የሆነው በኤርምያስ 7:1 ላይ የሚገኘው ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎም ይመልከቱ እና እንደ አስፈላጊነቱ ለውጥ አድርጉበት። "ይህ ናቡከደነጾር የእርሷን ከተሞች በ.... ጊዜ ያህዌ ለኤርምያስ የሰጠው መልዕክት ነው" እንዲህም አለ፣ 'ያህዌ'' ወይም ‘‘ናቡከደነጾር የእርሷን ከተሞች በ...ጊዜ፣ ያህዌ ለኤርምያስ ይህን መልዕክት ሰጠው፦ 'ያህዌ'' በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ኤርምያስ
እዚህ ስፍራ ኤርምያስ ለምን ራሱን በስም እንደጠቀሰ ግልጽ አይደለም። አንደኛ መደብን በመጠቀም መተረጎም አያስፈልግም። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ጦርነት ማወጅ
"መዋጋት"

የእርሷ ከተሞች ሁሉ
ይህ የሚያመለክተው በኢየሩሳሌም ዙሪያ የሚገኙ ከተሞችን ሁሉ ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ይህችን ከተማ አሳልፎ ለመስጠት
ይህ በኤርምያስ 32:28 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ

ለባቢሎን ንጉሥ እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል እጅ ለሚሰራው የመቆጣጠር ስራ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። "ከእርሱ ቁጥጥር አታመልጥም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በእርግጥ ትያዛለህ ደግሞም ተላልፈህ ትሰጣለህ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ባቢሎናውያን በእርግጥ ይይዙሃል፣ አንተም አልፈህ ተሰጣለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 34:4

በሰይፍ አትሞትም።
"ሰይፍ" የሚለው ቃል በጦርነት ለመሞት ሜቶኖሚ/ ነው። "በጦርሜዳ አትሞትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ለአባቶችህ ቀብር የሚነድ እሳት
ሰዎቹ በቅርቡ ለሞቱ ሰዎች ክብር ቅመም ያቃጥላሉ። የሞቱትን ሰዎች አካል/ አስክሬን አያቃጥሉም።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 34:6

ለኪሶ እና ዓዜቃ
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ የይሁዳ ከተሞች የተመሸጉ ከተሞች ሆነው ይኖራሉ
"ባቢሎናውያን ገና ያልያዝዋቸው ብቸኞቹ የተመሸጉ የይሁዳ ከተሞች"

Jeremiah 34:8

ከያህዌ ዘንድ ወደ ኤርምያስ የመጣ ቃል
ይህ ፈሊጥ የዋለው ከያህዌ ዘንድ ልዩ መልዕክት ለማሰተዋወቅ ነው። በእርግጥ ሊተላለፍ የተፈለገው መልዕክት እሰከ ኤርምያስ 34:12 ድረስ አልጀመረም። ተመሳሳይ የሆነው ሀረግ በኤርምያስ 7:1 እንዴት እንደ ተተረጎም ይመልከቱ። "ያህዌ ለኤርምያስ መልዕክት ሰጠው" ወይም "ያህዌ ለኤርምያስ መልዕክት ነገረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ቃል
መልዕክት

ንጉሥ ሴዴቅያስ ቃል ኪዳን ካደረገ በኋላ...የእርሱ ወንድም
እነዚህ ቃላት ሁሉም በኋላ ለሚገለጹ ድርጊቶች የመረጃ ዳራ/መነሻ ይሰጣሉ። (የመረጃ ዳራ/ የመረጃ መነሻ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 34:10

አያያዥ ሀሳብ፡
ኤርምያስ በኤርምያ 354:8 ላይ የሚጀምረውን የመረጃ ዳራ መስጠቱን ይቀጥላል።

Jeremiah 34:12

አያያዥ ሀሳብ፡
በኤርምያስ 34:8-11 ውስጥ ከሚገኘው የመረጃ ዳራ በኋላ ኤርምያስ ታሪኩን ከኤርምያስ 34:8 እንደገና ይጀምራል።

የያህዌ ቃል ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ፣ "ያህዌ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር የዋለው ከእግዚአብሔ ዘንድ ልዩ መልዕክት ለማስተዋወቅ ነው። በኤርምያስ 1:4 ላይ ተመሳሳይ የሆነው ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ለኤርምያስ፣ እንዲህ ሲል መልዕክት ሰጠው። 'ያህዌ" ወይም "ያህዌ ይህንን መልዕክት ለኤርምያስ ሰጠው፡ 'ያህዌ'' (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የባርነት ቤት
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ባሮች የነበራችሁበት ስፍራ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እያንዳንዱ ሰው ወንድሙን፣ ራሱን ለእናንተ የሸጠውን ዕብራዊ ወገን እና የሚያገለግለውን ነጻ ማድረግ አለበት
"እያንዳንዳችሁ ወገናችሁ የሆኑትን ራሳቸውን ለእናንተ የሸጡትን እና ለእናንተ ባሪያ የነበሩትን ነጻ ማውጣት አለባችሁ"

ነጻነቱን ሰጥቶ ይልቀቀው
"እናንተ ከማገልገል ነጻ እንዲወጡ ልትለቋቸው ይገባል"

ጆሯቸውን ወደ እኔ...አላዘነበሉም
በተሻለ ሁኔታ ለማድመጥ ወደ ተናጋሪው ጭንቅላትን ማዘንበል፣ ጆሮን ማስጠጋት፣ ተናጋሪው ለሚናገረው ትኩረት ለመስጠት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "እኔ ለተናገርኩት ...ትኩረት አልሰጡም" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 34:15

አሁን እናንተ ራሳችሁ ንስሃ ገባችሁ
እዚህ ስፍራ "አሁን" የሚለው ቃል የዋለው ቀጥሎ ለሚሆነው ጠቃሚ ነገር ነው።

በትክክል በእኔ ዐይኖች
እዚህ ስፍራ "ዐይኖች" የሚለው ለአንድ ሰው አስተያየት ወይም ሀሳብ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሆኖ የቀረበ ነው። "እኔ ትክክል ነው የምለው" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በስሜ የተጠራው ቤት
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "የእኔ የሆነው ቤት" ወይም "እነርሱ እኔን የሚያመልኩበት ቤት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው (አድራጊ ወይም ተደርጊ የሚለውን ይመልከቱ)

መልሳችሁ ስሜን አረከሳችሁ
የአንድ ሰው ስም ሰዎች ስለዚያ ሰው ለሚያስቡት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። "ትክክል የሆነውን ማድረግ አቁማችሁ፣ በምትኩ ሰዎች እኔ ክፉ እንደሆንኩ እንዲያስቡ የሚያደርጉ ነገሮችን አደረጋችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 34:17

ስለዚህም እነሆ!
"አድምጡ!" ወይም "ቀጥሎ ልነግራችሁ ላለው ጠቃሚ ነገር ትኩረት ስጡ!"

እኔ ለእናንተ ነጻነትን ላውጅ ነው...ለሰይፍ፣ ለመቅሰፍት፣ እና ረሃብ ነጻ መሆንን
ኤርምያስ "ነጻነት" የሚለውን የተጠቀመው በምጸት ነው፤ ሰዎች በመከራ ሃሴት እንደሚያደርጉ በምጸት ይናገራል። "ለእናንተ አበሳን አውጃለሁ... በሰይፍ፣ በመቅሰፍት፣ እና ችጋር የሚደርስ አበሳ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ለእናንተ ነጻነት ማወጅ
"እናንተ ነጻ እንደሆናችሁ ማወጅ"

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰይፍ
ይህ ሰይፍ ለያዙ ወታደሮች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። "የጠላት ወታደሮች እናንተን ለመግደል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በምድር ግዛት ሁሉ ፊት በእናንተ ላይ አሰቃቂ ነገር አደርሳለሁ
እዚህ ስፍራ "እይታ" የሚወክለው ፍርድን ወይም ሚዛንን ነው። "ግዛት" የሚለው ቃል በግዛቶቹ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን ነው። "በእያንዳዱ ምድር ግዛት የሚኖር ህዝብ እናንተ በአሰቃቂ ሁኔታ እንደምትኖሩ እንዲያስቡ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

ወይፈን ሲያርዱ ... ሲያልፉ... በወይፈኑ መሃል ሲያልፉ
ይህ ምንባብ የሚገልጸው ሰዎች ቃል ኪዳኑን እንዴት እንደሚፈጽሙ ነው። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

በእኔ ፊት ይፈጽማሉ
"ከእኔ ጋር ይስማማሉ" ወይም "እኔ እየተመለከትኩ ይፈጽማሉ"

Jeremiah 34:20

ለጠላቶቻቸው እጅ አሳልፌ እሰጣቸዋለሁ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል ጠላቶች በእጆቻቸው ተጠቅመው በሀይል ለሚፈጽሙት ወይም ለሚያደርጉት ቁጥጥር ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። "ጠላቶቻቸው በእነርሱ ላይ ሙሉ ሀይል እንዲኖራቸው እፈቅዳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይመልከቱ።

ህይወታቸውን ይፈልጋሉ
ለገድሏቸው ይፈልጋሉ የሚለውን ሻል ባለ አነጋገር መግለጫ ነው። (ዩፊምዝም/የማያስደስትን ቃል ሻልባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ለጠላቶቻቸው እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል የሚወክለው በቁጥጥር ስር ማድረግን ነው። "በጠላቶቻቸው እንዲያዙ" ወይም "በጠላቶቻቸው ስር እንዲሆኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ይነሳሉ
"ለመዋጋት ይመጣሉ"

አመጣቸዋለሁ
የባቢሎንን ሰራዊት አመጣለሁ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 35

1 በይሁዳ ንጉስ በኢዮስያስ ልጅ በኢዮአቄም ዘመን ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ኤርምያስ የመጣ ቃል ይህ ነው፣ እንዲህም አለ፣ 2 "ወደ ሬካባውያን ወገን ሄደህ አነጋግራቸው። ወደ ቤቴ፣ ከክፍሎቹ ወደ አንዱቱ፣ አግባቸው የወይን ጠጅም አጠጣቸው።" 3 የከባስንን ልጅ የኤርምያስን ልጅ ያእዛንያን፣ እንዲሁም ወንድሞቹን፣ ልጆቹንም ሁሉ፣ ብሎም የሬካባውያንን ወገን ሁሉ ወሰድኋቸው። 4 ወደ እግዚአብሔር ሰው ወደ ጌዴልያ ልጅ ወደ ሐናን ልጆች ጓዳ ወሰድኳቸው። እነዚህ ክፍሎች የእግዚአብሔር ቤት በበረኛው በሰሎም ልጅ በመዕሤያ ጓዳ በላይ ባለው የአለቆች ክፍል አጠገብ ነበሩ። 5 በሬካባውያንም ልጆች ፊት የወይን ጠጅ የሞላባቸውን ማድጋዎችንና ጽዋዎችን አኑሬ፣ "ጥቂት የወይን ጠጅ ጠጡ፤" አልኳቸው። 6 እነርሱ ግን እንዲህ አሉ፣ "የትኛውንም የወይን ጠጅ አንጠጣም፣ አባታችን የሬካብ ልጅ ኢዮናዳብ 'እናንተና ልጆቻችሁ ለዘላለም የወይን ጠጅ አትጠጡ' ብሎ አዝዞናልና። 7 እንደ እንግዶች በምትኖሩባት ምድር ላይ ብዙ ዘመን እንድትኖሩ፣ በዕድሜአችሁ ሙሉ በድንኳን ውስጥ ተቀመጡ እንጂ ቤትን አትሥሩ፣ የትኛውንም ዘር አትዝሩ፣ የትኛውንም ወይን አትትከሉ፣ ይህ ለእናንተ አይደለም።' 8 እኛም የአባታችንን የሬካብ ልጅ የኢዮናዳብን ቃል ባዘዘን ነገር ሁሉ ታዝዘናል፤ እኛም፣ ሚስቶቻችንም፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችንም፣ ዕድሜአችንን ሙሉ የወይን ጠጅ አልጠጣንም። 9 የምንቀመጥበትንም ቤት አልሠራንም፣ የወይን ቦታና እርሻ ዘርም የለንም። 10 በድንኳንም ውስጥ ኖረናል፣ አድምጠናል፣ አባታችንም ኢዮናዳብ ያዘዘንን ሁሉ አድርገናል። 11 ነገር ግን የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ምድሪቱን ባጠቃ ጊዜ፣ 'ኑ ከከለዳውያን ሠራዊትና ከሦርያ ሠራዊት ፊት የተነሣ ወደ ኢየሩሳሌም እንሂድ' አልን። ስለዚህ በኢየሩሳሌም እየኖርን ነን።" 12 ከዚያም የእግዚአብሔርም ቃል ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ፣ 13 "የእስራኤል አምላክ፣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፣ እንዲህ ይላል፣ 'ሂድና ለይሁዳ ሰዎችና በኢየሩሳሌም ለሚኖሩ ተናገር እንዲህም በላቸው፣ "ቃሌን ትሰሙ ዘንድ ተግሣጽን አትቀበሉምን? ይላል እግዚአብሔር። 14 ልጆቹ የወይን ጠጅ እንዳይጠጡ የሬካብ ልጅ ኢዮናዳብ ያዘዛቸው ቃል እስከ ዛሬ ድረስ ተፈጸመ። ለአባታቸውም ትእዛዝ ታዝዘዋል። እኔ ግን በተደጋጋሚ ተናግሬአችኋለሁ፣ ሆኖም አልሰማችሁኝም። 15 'እያንዳንዳችሁ ከክፉ መንገዳችሁ ተመለሱ፣ ሥራችሁንም አሳምሩ፤ ታመልኩአቸውም ዘንድ ሌሎችን አማልክት አትከተሉ፣ ለእናንተና ለአባቶቻችሁም በሰጠሁት ምድር ትቀመጣላችሁ እያልሁ በተደጋጋሚ ባርያዎቼን፣ ነቢያትን ሁሉ ልኬባችሁ ነበር። እናንተ ግን ጆሯችሁን አላዘነበላችሁም፣ ወይም እኔንም አልሰማችሁኝም። 16 የሬካብ ልጅ የኢዮናዳብ ልጆች አባታቸው ያዘዛቸውን ትእዛዝ ፈጽመዋልና፣ ይህ ሕዝብ ግን ሊሰማኝ አልፈለገም።" 17 ስለዚህ፣ የእስራኤል አምላክና የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ 'ተመልከቱ፣ በተናገርኋቸው ጊዜ አልሰሙምና፣ በጠራኋቸውም ጊዜ አልመለሱልኝምና የተናገርሁባቸውን ክፉ ነገር ሁሉ በይሁዳ ላይ፣ በኢየሩሳሌምም በሚኖሩት ሁሉ ላይ አመጣባቸዋለሁ።" 18 ኤርምያስም ለሬካባውያን ቤተሰብ እንዲህ አላቸው፣ "የእስራኤል አምላክ፣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ለአባታችሁ ለኢዮናዳብ ትእዛዝ ታዝዛችኋልና፣ ትእዛዙንም ሁሉ ጠብቃችኋልና፣ ያዘዛችሁንም ፈጽማችኋልና፤ 19 ስለዚህ፣ 'በፊቴ የሚቆም ሰው፣ ከሬካብ ልጅ ከኢዮናዳብ ወገን ለዘላለም አይታጣም።" ይላል የሠራዊት አምላክ፣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።

Jeremiah 35:1

በይሁዳ ንጉሥ .... ከእግዚአብሔር ዘንድ እንዲህ የሚል ቃል ወደ ኤርምያስ መጣ፡ ወደ ሬካባውያን ሄደህ...
‹‹ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንዲህ የሚል ቃል ወደ ኤርምያስ መጣ›› የሚለው ዐረፍተነገር የተጠቀመው ከእግዚአብሄር ለየት ያለ መልዕክት እንዳለ ለማሳየት ነው። በኤርምያስ 1:4 ላይ ተመሳሳይ መልዕክት የያዘ ዐረፍተነገር አለ። ‹‹ እግዚአብሄር በይሁዳ ንጉስ ዘመን ለኤርምያስ መልዕክት ሰጠ..... እርሱም ‹ሂድ› ወይም ‹‹ በይሁዳ ንጉስ ዘመን እግዚአብሄር ለኤርሚያስ እንዲህ ሲል ተናገረ....‹ሂድ› ›› (ዐረፍተነገሩን ተመልከት)

ለኤርምያስ
ኤርምያስ ለምን ራሱን በስሙ እንደገለጸ ግልፅ አይደለም። በመጀመሪያ መደብ በመጠቀም መተርጎም ይቻላል

ሬካባውያን
ይህ አንድን ህዝብ የሚያመለክት ነው (ስም አተረጓጎም የሚለውን ተመልከት)

የእኔ ቤት
መቅደሱን

Jeremiah 35:3

ያእዛንያን.....ካባስ.....ሃናን.....ጌዴልያም....መዕሤያ.....ሰሎም
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው

Jeremiah 35:5

ሬካባውያን
ኤርምያስ 35:2 የተተረጎመበትን ይመልከቱ

ኢዮናዳብ.....ሬካብ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው

በምትኖሩባት ምድር ላይ ብዙ ዘመን እንድትኖሩ
‹‹በምትኖሩባት ምድር ላይ ብዙ ዘመን እንድትኖሩ›› ‹‹ዘመን›› የሚለው ጊዜን አመላካች ነው

Jeremiah 35:8

የኢዮናዳብን ቃል
‹‹ቃል›› የሚለው የኢዮናዳብን ትእዛዝ ለማመልከት ነው።

ዕድሜያችንን ሁሉ
‹‹ዕድሜያችንን ሁሉ›› የሚለው ጊዜን አመላካች ነው

Jeremiah 35:12

የእግዚአብሄር ቃል ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ ‹‹.....እግዚአብሄር...››
ይህ ዐረፍተነገር የተጠቀመው ከእግዚአብሄር ለየት ያለ መልዕክት እንዳለ ለማሳየት ነው። ኤርምያስ 1:4 ላይ ተመሳሳይ ጥቅሶች የተተረጎመበትን መንገድ ይመልከቱ። ‹‹እግዚአብሄር ለኤርምያስ መልዕክት ሰጠው። እርሱም ‹እግዚአብሄር...› አለ ወይም ‹እግዚአብሄር ይህንን መልዕክት ለኤርምያስ ተናገረ፡ ‹እግዚአብሄር....›››

ለኤርምያስ
ኤርምያስ ለምን ራሱን በስሙ እንደገለጸ ግልፅ አይደለም። በመጀመሪያ መደብ በመጠቀም መተርጎም ይቻላል

የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር እንዲህ ይላል
ኤርምያስ እነዚህን ቃላቶች በአብዛኛው የሚጠቀመው ከእግዚአብሄር ቁልፍ መልዕክቶችን ማስተላለፍ ሲኖርበት ነው። ኤርምያስ 6:6 የተተረጎመበትን መንገድ ይመልከቱ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ቃሌን ትሰሙ ዘንድ ተግሳጽን አትቀበሉምን?
እግዚአብሄር እስራኤልን ተግሳጹን እንዲሰሙት እየተናገራቸው ነው። ‹‹ ተግሳጼን መቀበል እዲሁም ቃሌን መስማት አለባችሁ››

ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ የገለጸበት ምክንያት ቃሉን አስረግጦ ለመናገር ስለፈለገ ነው።፤ ኤርምያስ 1:8 የተተረጎመበትን መንገድ ይመልከቱ። ‹‹እግዚአብሄር የተናገረው ይህንን ነው›› ወይም ‹‹እኔ እግዚአብሄር የተናገርኩት ይህንን ነው››

የሬካብ ልጅ ኢዮናዳብ ልጆቹ የወይን ጠጅ እንዳይጠጡ ያዘዛቸው ቃል ተፈጸመ
ይህ ሲተረጎም ‹‹የሬካብ ልጅ የሆነው የኢዮናዳብ ልጆች አባታቸው የወይን ጠጅ እንዳይጠጡ ያዘዛቸውን ፈጽመዋል››

ኢዮናዳብ.....ሬካብ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው

Jeremiah 35:15

ታመልኳቸው ዘንድ ሌሎች አማልክትን አትከተሉ
ሌሎች አማልክትን መከተል ማለት የአማልክቱን ህግጋት መከተል/መተግበር ማለት ነው

Jeremiah 35:17

ተመልከት
ቃሉ አንባቢው ትኩረት ሰጥቶ እንዲመለከተው አመላካች ነው

Jeremiah 35:18

ኤርምያስም አለ
ኤርምያስ ለምን ራሱን በስሙ እንደገለጸ ግልፅ አይደለም። በመጀመሪያ መደብ በመጠቀም መተርጎም ይቻላል

ሬካባውያን
ይህ አንድን ህዝብ የሚያመለክት ነው ኤርምያስ 35:2 የተተረጎመበትን ይመልከቱ

የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር እንዲህ ይላል
ኤርምያስ እነዚህን ቃላቶች በአብዛኛው የሚጠቀመው ከእግዚአብሄር ቁልፍ መልዕክቶችን ማስተላለፍ ሲኖርበት ነው። ኤርምያስ 6:6 የተተረጎመበትን መንገድ ይመልከቱ

ኢዮናዳብ.....ሬካብ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 36

1 እንዲህም ሆነ፣ በይሁዳ ንጉሥ በኢዮስያስ ልጅ በኢዮአቄም በአራተኛው ዓመት ይህ ቃል ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ኤርምያስ መጣ፣ እንዲህም አለው፣ 2
"ለራስህ አንድ የመጽሐፍ ጥቅልል ውሰድና በእስራኤልና በይሁዳ ላይ፣ በአሕዛብም ሁሉ ላይ የተናገርሁህን ቃል ሁሉ ጻፍበት። ከኢዮስያስ ዘመን ጀምሮ እስከ
ዛሬ ድረስ ለአንተ የተናገርሁትን ጻፍበት። 3 ምናልባት የይሁዳ ሕዝብ እኔ አደርግባቸዋለሁ ያልሁትንና ያሰብሁትን ክፉ ነገር ሁሉ ይሰሙ ይሆናል። ከክፋ
መንገዳቸው ይመለሱ፣ እኔም በደላቸውንና ኃጢአታቸውን ይቅር እል ዘንድ። 4 ኤርምያስም የኔርያን ልጅ ባሮክን ጠራ፣ ባሮክም ከኤርምያስ አፍ እግዚአብሔር
ለእርሱ የተናገረውን ቃል ሁሉ በመጽሐፉ ጥቅልል ላይ ጻፈ። 5 ቀጥሎም ኤርምያስ ለባሮክ እንዲህ ሲል አዘዘው። "እኔ በእስር ላይ ስለሆንኩ ወደ
እግዚአብሔር ቤት መሄድ አልችልም። 6 ስለዚህ አንተ መሄድና ከአፌም የጻፍኸውን የእግዚአብሔርን ቃል ልታነብብ ይገባል። በጾም ቀን፣ በእግዚአብሔር ቤት
ሕዝቡ እየሰሙ አንብብ፣ ደግሞም ከከተሞቻቸው የሚወጡ የይሁዳ ሰዎች ሁሉ እየሰሙ አንብበው። እነዚህን ቃሎች አውጅላቸው። 7 ምናልባት የምሕረት
ልመናቸው በእግዚአብሔር ፊት ትመጣ ይሆናል። እግዚአብሔር በዚህ ሕዝብ ላይ የተናገረው ቊጣውና መዓቱ ታላቅ ነውና፣ ሁሉም ከክፉ መንገዱ ይመለስ
ይሆናል።" 8 ስለዚህ የኔርያም ልጅ ባሮክ ነቢዩ ኤርምያስ ያዘዘውን ሁሉ አደረገ። በእግዚአብሔርም ቤት የእግዚአብሔርን ቃል በመጽሐፉ አነበበ። 9 በይሁዳ
ንጉሥ በኢዮስያስ ልጅ በኢዮአቄም በአምስተኛው ዓመት በዘጠነኛው ወር በኢየሩሳሌም የተቀመጡ ሕዝብ ሁሉ ከይሁዳም ከተሞች ወደ ኢየሩሳሌም የመጡ
ሕዝብ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ለመጾም አዋጅ ነገሩ። 10 ባሮክም የኤርምያስን ቃል በእግዚአብሔር ቤት በላይኛው አደባባይ በእግዚአብሔር ቤት በአዲሱ በር
መግቢያ ባለው በጸሐፊው በሳፋን ልጅ በገማርያ ጓዳ ሕዝቡ ሁሉ እየሰሙ መጽሐፉን አነበበ። 11 የሳፋንም ልጅ የገማርያ ልጅ ሚክያስ የእግዚአብሔርን ቃል
ሁሉ ከመጽሐፉ ጥቅልል ሰማ። 12 ወደ ንጉሡ ቤት ወደ ጸሐፊው ክፍል ወረደ። በዚያም፣ አለቆች ሁሉ፦ ጸሐፊው ኤሊሳማ፣ የሸማያ ልጅ ድላያ፣ የዓክቦር ልጅ
ኤልናታን፣ የሳፋን ልጅ ገማርያ፣ የሐናንያ ልጅ ሴዴቅያስ፣ እንዲሁም አለቆቹ ሁሉ በዚያ ተቀምጠው ነበር። 13 ሚክያስም ሕዝቡ እየሰሙ ባሮክ ከመጽሐፉ
ባነበበ ጊዜ የሰማውን ቃል ሁሉ ነገራቸው። 14 አለቆቹም ሁሉ፣ "በሕዝቡ ጆሮ ያነበብኸውን ጥቅልል በእጅህ ይዘህ ና" የሚል መልእክት በኩሲ ልጅ፣
በሰሌምያ ልጅ፣ በናታንያ ልጅ፣ በይሁዲ እጅ፣ ወደ ባሮክ ላኩ። ስለዚህ የኔርያ ልጅ ባሮክ ጥቅልሉን በእጁ ይዞ ወደ እነርሱ ሄደ። 15 ከዚያም፣ "ተቀመጥና
እየሰማንህም ይህንን አንብብልን፤" አሉት። ባሮክም በጆሮአቸው አነበበው። 16 እነዚህን ቃሎች ሁሉ በሰሙ ጊዜ ፈሩና እርስ በእርሳቸው ተመካከሩ፣ ባሮክንም፣
"ይህን ቃል ሁሉ በእርግጥ ለንጉሡ ልንናገር ይገባል" አሉት። 17 ከዚያም ባሮክን፣ "ይህን ሁሉ ቃላት ከኤርምያስ አፍ እንዴት እንደ ጻፍኸው ንገረን" ብለው
ጠየቁት። 18 ባሮክም፣ "ይህን ቃል ከአፉ ይነግረኝ ነበር፣ እኔም በመጽሐፍ ጥቅልል ላይ በቀለም እጽፍ ነበር" ብሎ መለሰላቸው። 19 አለቆቹም ለባሮክ፣
"አንተና ኤርምያስ ሄዳችሁ ተሸሸጉ። የት እንደሆናችሁ ማንም አይወቅ" አሉት። 20 ወደ ንጉሡም ሸንጎ ገቡና ቃሉን ሁሉ ንጉሡ እየሰማ ተናገሩ። ነገር ግን
አስቀድመው ጥቅልሉን በጸሐፊው በኤሊሳማ ክፍል አኑረውት ነበር። 21 ከዚያም ንጉሡ ጥቅልሉን ያመጣ ዘንድ ይሁዲን ላከ። እርሱም ከጸሐፊው ከኤሊሳማ
ክፍል ወሰደው። ከዚያም ይሁዲ ንጉሡና በንጉሡ አጠገብ የቆሙት አለቆች ሁሉ እየሰሙ አነበበው። 22 ያኔ፣ ንጉሡ በዘጠነኛው ወር በክረምት ቤት ተቀምጦ
ነበር፣ በፊቱም በምድጃ ውስጥ እሳት ይነድድ ነበር። 23 ይሁዲ ሦስት ወይም አራት ዓምድ ያህል ባነበበ ቊጥር፣ ንጉሡ በካራ እየቀደደ ጥቅልሉ በምድጃ
ውስጥ ባለው እሳት ፈጽሞ እስኪቃጠል ድረስ በምድጃ ውስጥ ወዳለው እሳት ጣለው። 24 ነገር ግን ንጉሡ ወይም ይህንን ቃል ሁሉ የሰሙ ባሪያዎቹ ሁሉ
አልፈሩም፣ ልብሳቸውንም አልቀደዱም። 25 ነገር ግን ኤልናታን፣ ድላያና፣ ገማርያ ጥቅልሉን እንዳያቃጥል ንጉሡን ለመኑት፣ እርሱ ግን አልሰማቸውም። 26
ንጉሡም ጸሐፊውን ባሮክንና ነብዩን ኤርምያስን ይይዙ ዘንድ የንጉሡን ልጅ ይረሕምኤልን፣ የዓዝርኤልን ልጅ ሠራያን፣ የዓብድኤልንም ልጅ ሰሌምያን አዘዘ፣
እግዚአብሔር ግን ሰውሯቸው ነበር። 27 ከዚያም ንጉሡ ጥቅልሉንና ባሮክ ከኤርምያስ አፍ እየቀዳ የጻፈውን ቃል ካቃጠለ በኋላ፣ የእግዚአብሔር ቃል ወደ
ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ። 28 "ዳግመኛ ሌላ ጥቅልል ውሰድ፣ የይሁዳም ንጉሥ ኢዮአቄም ባቃጠለው ጥቅልል ላይ የነበረውን የቀድሞውን ቃል ሁሉ
ጻፍበት። 29 ከዚያም፣ የይሁዳን ንጉሥ ኢዮአቄምን እንዲህ በለው፦ 'እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ አንተ፣ "የባቢሎን ንጉሥ በእርግጥ ይመጣል ይህችንም አገር
ያፈርሳታል ከሰውና ከእንስሳም ባዶ ያደርጋታል" ብለህ ለምን ጻፍህበት? ብለህ ይህን ጥቅልል አቃጥለሃል።" 30 ስለዚህ፣ ስለ አንተ፣ የይሁዳ ንጉሥ፣ ስለ
ኢዮአቄም እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ "በዳዊት ዙፋን ላይ ተቀማጭ አይኖርለትም። ሬሳውም በቀን ለትኩሳት፣ በሌሊትም ለውርጭ ይጣላል። 31 ስለ
ኃጢአታቸውም እርሱንና ዘሩን፣ ባሪያዎቹንም እቀጣለሁ። እነርሱም አልሰሙምና የተናገርሁባቸውን ክፉ ነገር ሁሉ በእነርሱ ላይና፣ በኢየሩሳሌም በሚቀመጡ፣
በይሁዳም ሰዎች ላይ አመጣለሁ። 32 ሰለዚህ ኤርምያስ ሌላ ጥቅልል ወሰደ ለኔርያም ልጅ ለጸሐፊው ለባሮክ ሰጠው። እርሱም የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአቄም
በእሳት ያቃጠለውን የመጽሐፉን ቃል ሁሉ ከኤርምያስ አፍ እየቀዳ ጻፈበት። በተጨማሪም፣ ከቀድሞው ቃል ጋር የሚመሳሰል ብዙ ቃል ተጨመረበት።

Jeremiah 36:1

አጠቃላይ መረጃ
ግጥምና ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ

እንዲህም ሆነ
ይህን ቃል የተጠቀመው አዲስ የታሪክ ጅማሬ ለማሳየት ነው።

በይሁዳ ንጉስ....በኢዮአቄም በአራተኛው ዓመት...
ኢዮአቄም ከሶስት ዓመት በላይ የይሁዳ ንጉስ ሆኖ ቀይቶ ነበር። ኤርምያስ 25፡1 የተተረጎመበትን ይመልከቱ

ይህ ቃል
‹‹ይህ ቃል›› የሚለው ቀጣዩን መልዕክት የሚያመለክት ነው

ለኤርምያስ
ኤርምያስ ለምን ራሱን በስሙ እንደገለጸ ግልፅ አይደለም። በመጀመሪያ መደብ በመጠቀም መተርጎም ይቻላል

እርሱም አለ
‹‹ እግዚአብሄርም አለ››

‹‹በአሕዛብም ሁሉ ላይ››
‹‹አሕዛብ ሁሉ››

ከተናገርኩበት ቀን
‹‹ለአንተ ከተናገርኩበት ቀን››

ከኢዮስያስ ዘመን ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ
‹‹ ኢዮስያስ ንጉስ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬዋ ቀን ድረስ ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምናልባት የይሁዳ ቤት
ምናልባት የይሁዳ ህዝቦችን

አደርግባችኋለሁ
x

Jeremiah 36:4

ኤርምያስም..... ለኤርምያስ አፍ..... አዘዘው.....
ኤርምያስ ለምን ራሱን በስሙ እንደገለጸ ግልፅ አይደለም። በመጀመሪያ መደብ በመጠቀም መተርጎም ይቻላል

ባሮክም እግዚአብሄር ለእርሱ የተናገረውን ቃል ሁሉ ከኤርምያስ አፍ በመጽሐፍ ከርታስ ጻፈ
እግዚአብሄር ለኤርምያስ የተናገረውን ኤርምያስ ሲናገር ባሮክ በመጽሐፍ ከርታስ ጻፈ

በክርታሱ አንብብ
‹‹ከክርታሱ ላይ ጮክ ብለህ አንብብ›› ወይም ‹‹ከክርታሱ ላይ አውጅ›› ለማለት ነው

አንብበው
‹‹ጮክ ብለህ አንብብ›› ወይም ‹‹ አውጅ››

በእግዚአብሄር ቤት በሕዝቡ ጆሮ
‹‹በእግዚአብሄር ቤት ውስጥ ያሉ ሕዝቦች ይሰሙ ዘንድ›› ኤርምያስ 2፡2 የተተረጎመበትን መንገድ ተመልከት

በከተሞቻቸው በሚወጡ በይሁዳ ሰዎች ሁሉ ጆሮ
‹‹ከከተሞቻቸው የመጡ የይሁዳ ሰዎች ሁሉ ይሰሙ ዘንድ›› ኤርምያስ 2፡2 የተተረጎመበትን መንገድ ተመልከት

Jeremiah 36:7

አጠቃላይ መረጃ
ኤርምያስ ለባሮክ ትዕዛዙን ይቀጥላል

ምናልባት ጸሎታቸው በእግዚአብሄር ፊት ትወድቅ ይሆናል
እግዚአብሄር ጸሎታቸውን ሰምቶ ይፈጽምላቸዋል

ጸሎታቸው
‹‹ጸሎታቸው›› ሲል የእግዚአብሄር ቤት ሕዝቦችን እንዲሁም ከከተሞቻቸው የመጡትን የይሁዳን ሕዝቦችን ለማመልከት ነው

ሁሉም ከክፉ መንገዱ
‹‹መንገዱ›› ሲል የአንድን ሰው የህይወት መርህን ወይም አንድ ሰው የሚመራበትን መንገድ ለመግለጽ ነው። ኤርምያስ 18፡11 የተተረጎመበትን መንገድ ተመልከት

ቁጣው እና መአቱ
ከፍተኛ ቁጣ

Jeremiah 36:9

እንዲህም ሆነ
ኤርምያስ 36፡1 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

በኢዮአቄም በአምስተኛው ዓመት በዘጠነኛው ወር...በይሁዳ ንጉስ
ይህ ዘጠነኛው ወር በእብረውያን የቀን መቁጠሪያ ሲሆን ይህም በምእራባውያን የቀን አቆጣጠር ላይ የኖቨምበር መጨረሻዎቹ ላይ እና ዲሴምበር መጀመሪያዎቹ ላይ ይገኛል። “ኢዮአቄም በይሁዳ ንጉስ ከሆነ ከአራት አመት በላይ ሲሆን በዘጠነኛው ወር አካባቢ ነው”

በይሁዳ ንጉሥ በኢዮስያስ ልጅ በኢዮአቄም
ኤርምያስ 25፡1 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

አዋጅ ነገሩ።
ለሁሉም ሰው በፍጥነት እየሄዱ እነደሆነ ተናገሩ

የኤርምያስ ቃል
ኤርምያስ ለምን ራሱን በስሙ እንደገለጸ ግልፅ አይደለም።

በሳፋን ልጅ በገማርያ
ይህ የሰው ስም ነው

ፀሃፊው
ፀሃፊ የነበረው

በእግዚአብሔር ቤት በአዲሱ በር መግቢያ
አዲሱ የእግዚአብሄር ቤት መግቢያ በር

አነበበ
ድምፁን ከፍ አድርጎ የኤርምያስን ቃል አነበበ

በህዝቡ ሁሉ ጆሮ
ሁሉም ህዝብ እንዲሰሙት። ተመሳሳይ ቃላትን በኤርምያስ 2፡2 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

Jeremiah 36:11

ጊዜ
ይህን ቃል የተጠቀመው ቀጥሎ የተነሳውን ሃሳብ ትኩረት እንዲሰጠው ለማድረግ ነው

የሳፋንም ልጅ የገማርያ ልጅ ሚክያስ
ሚክያስ የገማርያ ልጅ ነው ገማርያ የሳፋን ልጅ ነው።

ሚክያስ
ይህ የሰው ስም ነው

እነሆም
ተመልከት ወይም ልብ በል

ኤሊሳማ...ድላያ
ይህ የሰዎች ስም ነው

ሸማያ
በኤርምያስ 26፡20 እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት

የአክቦር ልጅ ኤልናታን
በኤርምያስ 26፡22 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

የሳፋን ልጅ ገማርያ
በኤርምያስ 36፡10 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ሴደቅያስ
በኤርምያስ 1፡3 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ሐናንያ
በኤርምያስ 28፡1 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

አለቆቹም ሁሉ
ሁሉም አለቆች

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Jeremiah 36:13

ሚክያስ
የዚህን ሰው ስም በኤርምያስ 36፡11 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

የሰማውን ቃል ነገራቸው
ይህ ለአለቆቹ እንደተናገረ በኤርምያስ 36፡12 ያመለክታል

በህዝቡ ጆሮ
ህዝቡ እንዲሰሙ። ተመሳሳይ ቃላት በኤርምያስ 2፡2 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ይሁዲ...ናታንያ...ሰሌምያ...ኩሲ
እንዚህ የሰው ስሞች ናቸው

በህዝቡ ጆሮ
ህዝቡ እንዲሰሙ። ተመሳሳይ ቃላት በኤርምያስ 2፡2 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ክርታሱን...አነበበው
ድምፁን ከፍ አድርጎ ክርታሱን አነበበው

Jeremiah 36:16

...ጊዜ
ይህን ቃል ሲጠቀም በታሪኩ ውስጥ ትኩረት የሚሰጠውን ታሪክ ለማሳየት ነው

በሰሙ ጊዜ
ይህ ቃል የሚያመለክተው አለቆቹን ነው

ይህንን ቃል ሁሉ
የባሮክ ቃል ከክርታሱ ተነበበ

እንዴት እንደፃፍከው ንገረን
እንዴት ፃፍከው

ይህን ቃል ከአፉ ይነግረኝ ነበር፥ እኔም በመጽሐፉ ላይ በቀለም እጽፍ ነበር
በኤርምያስ 36፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ከአፉ ይነግረኝ
ኤርምያስ ሲነግረው ባሮክ የሚናገረው ይፅፍ ነበር

በቀለም እፅፍ ነበር
ቀለምን ተጠቅሜ እፅፍ ነበር

ቀለም
ጠቆር ያለ ፈሳሽ ለመፃፊያ የሚያገለግል

አንተና ኤርምያስ
አንተ ብቻ ሳይሆን ኤርምያስም ጭምር መሸሸግ አለበት።

ወዴት እንደሆናችሁ
ይህ ባሮክንና ኤርምያስን ያመለክታል።

Jeremiah 36:20

..ገቡ
ይህ ቃል የሚያመለክተው አለቆቹን ነው

ክርታሱንም በጸሐፊው በኤሊሳማ ጓዳ አኑረውት
በፀሃፊው በኤሊሳም ክፍል ክርታሱን አስገቡት

ፀሀፊው ኤሊሳም
ፀሀፊው ኤሊሳም የሚለውን በኤርምያስ 36፡12 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ይሁዲ
የዚህን ሰው ስም በኤርምያስ 36፡14 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

በንጉሡና በንጉሡ አጠገብ በቆሙት አለቆች ሁሉ ጆሮ አነበበው
ንጉሱ ሊሰማው በሚችልበት ቦታ ላይ። ተመሳሳይ ቃላት በኤርምያስ2፡2 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

በዘጠነኛው ወር
በእብራውያን የቀን አቆጣጠር ዘጠነኛው ወር ሲሆን የሚዘሩበት ጊዜ አልቆ ቀዝቃዛው ጊዜ መጀመሪያ አካባቢ ነው። እንደ ምእራባውያን የቀን አቆጣጠር የኖቬምበር መጨረሻዎቹ እና የዲሴምበር መጀመሪያዎቹ ላይ ነው።

በፊቱም በምድጃ ውስጥ እሳት ይነድድ ነበር።
የሚነደው እሳት በምድጃ ውስጥ ሆኑ ከፊት ለፊቱ ነበር

ምድጃ
የእሳት ማንደጃ ሲሆን ሰዎች ከቦታ ቦታ ያንቀሳቅሱታል

Jeremiah 36:23

ባነበበ ቁጥር..
ይህን ቃል ሲጠቀም በታሪኩ ላይ ትኩረት ለመስጠት ነው (ታሪካዊ ዳራውን ተመልከት)

ይሁዲም
በኤርምያስ 36፡14 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

አምድ
እነዚህ በክርታሱ የሚገኙ የቃላት አምድ ነው

ቀደደው
ክርታሱን ቀደደው

በካራ
ፀሀፊዎች የሚጠቀሙትን ካራ ተጠቅሞ ቀደደው

በምድጃ
በኤርምያስ 36፡22 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ክርታሱም በምድጃ ውስጥ ባለው እሳት ፈፅሞ እኪቃጠል ድረስ
ክርታሱ ሙሉ በሙሉ እስኪጠፋ ድረስ

ይህን ቃል ሁሉ
ኤርምያስ ሲናገር ባሮክ ክርታስ ላይ የፃፈው ቃል ነው።

ልብሳቸውንም አልቀደዱም
ሰዎች ልብሶቻቸውን የሚቀዱት እጅግ በጣም ሲያዝኑ ነው። “ልብሳቸውን በመቅደድ አላዘኑም”

Jeremiah 36:25

ኤልናታንና ድላያ ገማርያም
እነዚህን ስሞች በኤርምያስ 36፡12 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ንጉሱን ለመኑት
ንጉሱን ለመኑት

ይረሕምኤልንና የዓዝርኤልን ...ሠራያን የዓብድኤልንም...ሰሌምያን
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው

ልጅ ነብዩን ኤርምያስ...ሰወራቸው
ኤርምያስ ለምን ራሱን በስሙ እንደገለጸ ግልፅ አይደለም። በመጀመሪያ መደብ በመጠቀም መተርጎም ይቻላል

Jeremiah 36:27

ባሮክ ከኤርምያስ አፍ የጻፈውን ቃል ካቃጠለ በኋላ የእግዚአብሔር ቃል ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ
“የእግዚአብሄር ቃል ወደ” የሚለው ቃል ልዩ የሆነ መልእክት ለመናገር ሲፈልግ የሚጠቀመው ነው። ተመሳሳይ አረፍተነገር በኤርምያስ 1:4 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት። “እግዚአብሄር ለኤርምያስ እንዲህ ሲል ተናገረ”

ከኤርምያስ አፍ የጻፈውን...ወደ ኤርምያስ መጣ
ኤርምያስ ለምን ራሱን በስሙ እንደገለጸ ግልፅ አይደለም። በመጀመሪያ መደብ በመጠቀም መተርጎም ይቻላል

ከኤርምያስ አፍ የጻፈውን
በኤርምያስ 36:4 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ዳግመኛ ሌላ ክርተስ ውሰድ
ለራስህ ሌላ ክርታስ ውሰድ

ክርታስ ላይ የነበረውን የቀድሞውን ቃል
የመጀመሪያው ክርታስ

ከሰውና ከእንስሳም ባዶ ያደርጋታል ብለህ ለምን ጻፍህበት?
ኢዮአቄም ይህንን ጥያቄ ኤርምያስ የባቢሎን ንጉስ መጥቶ እንደሚያጠቃቸው መፃፍ እንዳልነበረበት ለማሳየት ነው። “መፃፍ አልነበረብህም”

ያፈርሳታል
እርሱ ያጠፋታል

Jeremiah 36:30

ዳዊት ዙፋን ላይ ተቀማጭ አይኖርለትም
ተቀማጭ የሚለው ንጉስ ሆኖ የሚመራ ማለት ነው። “ዳዊት ዙፋን ላይ ተቀማጭ አይኖርለትም” የሚለውን በኤርምያስ 29:16 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት። “ዳዊት እስራኤላውያንን እንደመራቸው አይኖርም”

ሬሳውም...ይጣላል
“ሰዎች ሬሳን ወደውጭ ይጥሉታል”

ሬሳውም
የሞተው ሰውን

በቀን ለትኩሳት
ቀን ባለው ደረቅ ሙቀት ይጋለጣል

ውርጭ
በቀዝቃዛ ሌሊቶች ላይ በሳር ላይ በረዶ የሚሰራ

ሁሉ በእነርሱ ላይ
ሁሉ በእነርሱ ላይ

Jeremiah 36:32

ወስጄ...እርሱም በቃል የነገርኩትን ሁሉ ፃፈበት
ኤርምያስ ለምን ራሱን በስሙ እንደገለጸ ግልፅ አይደለም። በመጀመሪያ መደብ በመጠቀም መተርጎም ይቻላል

ለባሮክ ሰጠሁት እርሱም በቃል የነገርሁትን ሁሉ ፃፈበት
በኤርምያስ 25:4 ላይ እንዴት እንደተረጎመወ ተመልከት። “ኤርምያስ ሲናገር ባሮክ ፃፈው”

የይሁዳ ንጉስ ኢዮአቄም ባቃጠለው
የይሁዳ ንጉስ ኢዮአቄም በእሳት ውስጥ ያቃጠለው

ተፅፎ የነበረውንና እኔም እንደገና በተጨማሪ የነገርሁትን ተመሳሳይ ቃል ሁሉ ፃፈበት
“ኤርምያስ እና ባሮክ ክርታሱላይ ብዙ ቃላቶችን ከመጀመሪያው ክርታስ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ጨምረናል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 37

1 የባቢሎንም ንጉሥ ናቡከደነፆር በይሁዳ ያነገሠው የኢዮስያስ ልጅ ሴዴቅያስ በኢዮአቄም ልጅ በኢኮንያን ፋንታ ነገሠ። **2** ነገር ግን ሴዴቅያስም ሆነ ባርያዎቹ፣ የአገሩም ሕዝብ በነቢዩ በኤርምያስ እጅ የተናገረውን የእግዚአብሔርን ቃል አልሰሙም። **3** ስለዚህ፣ ንጉሡ ሴዴቅያስ፣ የሰሌምያን ልጅ ዮካልንና ካህኑን የመዕሤያን ልጅ ሶፎንያስን ወደ ነቢዩ ወደ ኤርምያስ ላከ። እነርሱም "ወደ አምላካችን ወደ እግዚአብሔር ስለ እኛ ጸልይ" አሉት። **4** በግዞት ቤት ገና አላገቡትም ነበርና ኤርምያስ በሕዝቡ መካከል ይወጣና ይገባ ነበር። **5** የፈርዖንም ሠራዊት ከግብጽ ወጣ፣ ኢየሩሳሌምንም ከብበዋት የነበሩ ከለዳውያን ይህን ወሬ በሰሙ ጊዜ ከኢየሩሳሌም ተመለሱ። **6** ከዚያም፣ የእግዚአብሔር ቃል ወደ ነቢዩ ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ፣ **7** "የእስራኤል አምላክ፣ እግዚአብሔር፣ እንዲህ ይላል፦ ከእኔ ትጠይቁ ዘንድ የላካችሁን የይሁዳን ንጉሥ እንዲህ በሉት፦ 'ተመልከቱ፣ ሊረዳችሁ የወጣው የፈርዖን ሠራዊት ወደገዛ ምድሩ ወደ ግብጽ ይመለሳል። **8** ከለዳውያንም ይመለሳሉ። ይህችን ከተማ ይዋጉአታል፣ ይይዟትማል፣ በእሳትም ያቃጥሉአታል።' **9** እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ስለማይሄዱ 'ከለዳውያን በእርግጥ ከእኛ ዘንድ ይሄዳሉ' ብላችሁ ራሳችሁን አታታልሉ። **10** እናንተም የሚዋጉትን የከለዳውያንን ሠራዊት ሁሉ አሸንፋችሁ ቢሆን እንኳን፣ ከእነርሱም የቆሰሉት ብቻ በድንኳኖቻቸው ቀርተው ቢሆን ኖሮ፣ይህችን ከተማ በእሳት ባቃጠሉአት ነበር። **11** ስለዚህ የከለዳውያን ሠራዊት ከፈርዖን ሠራዊት ፊት የተነሣ ከኢየሩሳሌም በተመለሰ ጊዜ፣ **12** ያኔ ኤርምያስ ወደ ብንያም አገር ሊሄድ ከኢየሩሳሌም ወጣ። እርሱ የርስቱን እድል ፈንታ በዚያ ከሕዝቡ መካከል ይቀበል ዘንድ ፈለገ። **13** በብንያምም በር በነበረ ጊዜ፣ የዘበኞች አለቃ በዚያ ነበር። ስሙም የሐናንያ ልጅ የሰሌምያ ልጅ የሪያ ነበረ። እርሱም "ወደ ከለዳውያን መኰብለልህ ነው" ብሎ ነቢዩን ኤርምያስን ያዘው። **14** ኤርምያስ ግን፣ "ይህ እውነት አይደለም። ወደ ከለዳውያን መኰብለሌ አይደለም" አለ። ነገር ግን የሪያ አልሰማውም። ኤርምያስንም ይዞ ወደ አለቆች አመጣው። **15** አለቆችም በኤርምያስ ላይ ተቈጡ። መቱትና የጸሐፊውንም የዮናታንን ቤት እስር ቤት አድርገውት ነበርና በዚያ አኖሩት። **16** ስለዚህ ኤርምያስ ብዙ ቀናት በተቀመጠበት ከምድር በታች ባለ ክፍል ተጣለ፤ **17** ከዚያም ንጉሡ ሴዴቅያስ አንድ ሰው ልኮ ወደ ቤተመንግሥት አስመጣው። ንጉሡም በቤቱ፣ "በውኑ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነ ቃል አለን?" ብሎ በድብቅ ጠየቀው። ኤርምያስም፣ "አዎን አለ፦ ለባቢሎን ንጉሥ እጅ አልፈህ ትሰጣለህ" አለ። **18** ከዚያም ኤርምያስ ንጉሡን ሴዴቅያስን፣"በእስር ቤት የጣላችሁኝ አንተን፣ ወይስ ባርያዎችህን፣ ወይስ ሕዝብህን ምን በድያችሁ ነው? **19** የባቢሎን ንጉሥ በእናንተና በዚህች ምድር አይመጣባችሁም ብለው ትንቢት ይናገሩላችሁ የነበሩ ነቢያቶቻችሁ ወዴት አሉ? **20** ንጉሡ ጌታዬ ሆይ፣ እንድትሰማኝ እለምንሃለሁ! ልመናዬ ወደ አንተ ይድረስ። በዚያ እንዳልሞት ወደ ጸሐፊው ወደ ዮናታን ቤት አትመልሰኝ።" **21** ስለዚህ ንጉሡ ሴዴቅያስ አዘዘ። አገልጋዮቹም ኤርምያስን በግዞት ቤት አደባባይ አኖሩት። እንጀራም ሁሉ ከከተማ እስኪጠፋ ድረስ ዕለት ዕለት አንድ አንድ እንጀራ ከጋጋሪዎች መንገድ ይሰጡት ነበር። ስለዚህ ኤርምያስ በእስር ቤት አደባባይ ተቀምጦ ነበር።

Jeremiah 37:1

ኢኮንያን
በዕብራይስጡ ጽሁፍ ‹‹ኮንያ›› የሚለው ቃል ይገኛል። ይህም የኢኮንያን ሌላ ስም ሲሆን ብዙ አዲስ ትርጉሞች ተመሳሳይ ንጉስን ለማመልከት ‹‹ኢኮንያን›› የሚለውን ስም ይጠቀማሉ

የአገሩም
የይሁዳ ምድር

በነብዩ በኤርምያስ እጅ የተናገረውን
እጅ የሚለው ሰውን ያመለክታል። “ኤርምያስ እንዲናገር አደረገው”

የተናገረውን
እግዚአብሄር የተናገረውን

ነብዩ ኤርምያስ
ኤርምያስ ራሱን በስሙ የሚጠራው ምክንያቱ ግልፅአደለም

Jeremiah 37:3

ዬካልን
የሰው ስም ነው

ሰሌምያ
ይህን የሰው ስም በኤርምያስ 36፡14 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ካህኑን የመዕሤያን ልጅ ሶፎንያስን
የነዚህ ሰዎች ስም በኤርምያስ 21፡1 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ስለ እኛ
“ለኛ” ወይም “ለኛ ጥቅም” “እኛ” የሚለው ቃል ንጉስ ሴዴቅያስ እና የተቀሩት የይሁዳ ህዝብን ነው

ኤርምያስ በሕዝቡ መካከል ይወጣና ይገባ ነበር።
“ይወጣና ይገቡ” የሚለው በነፃነት መንቀሳቀሱን ያሳያል። “ኤርምያስ መሄድ የፈለገበት ቦታ እንደ ልቡ ይንቀሳቀሳል”

በግዞት ቤት ገና አላገቡትም ነበርና
“ምክንያቱም ማንም እስርቤት አላስገባውም እና”

ይወጣና ይገባ ነበር
በሕዝቡ መካከል ይመላለስ ነበር

ከብበዋት
ኤርምያስ 32፡2 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል ወደ ኤርምያስ መጣ።
“የእግዚአብሄር ቃል ወደ” የሚለው ቃል ልዩ የሆነ መልእክት ለመናገር ሲፈልግ የሚጠቀመው ነው። ተመሳሳይ አረፍተነገር በኤርምያስ 1፡4 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት። “እግዚአብሄር ለኤርምያስ እንዲህ ሲል ተናገረ”

እንዲህ በሉት
ይህ ንጉስ ሴዴቅያስ ወደ ኤርምያስ የላካቸውን ሁለት ሰዎችን ያመለክታል። የሰሌምያን ልጅ ዮካልንና ካህኑን የመዕሴያን ልጅ ሶፎንያስን

ከእኔ ትጠይቁ ዘንድ
“እኔ” የሚለው ቃል እግዚአብሄርን ያመለክታል

እነሆ
ተመልከት ወይም ልብ በል

ይህችን ከተማ ይዋጉአታል ይይዙአትማል በእሳትም ያቃጥሉአታል
ጦርነት መዋጋት መያዝ እና ማቃጠልን ከኤርምያስ 34፡22 ጋር አነፃፅር

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Jeremiah 37:9

ራሳችሁን አታታሉ
“ራሳችሁን” የሚለው ቃል ንጉስ ሴዴቅያስ እና የተቀሩትን የይሁዳ ህዝብን ያመለክታል።

ከለዳውያን በእርግጥ ከእኛ ዘንድ ይሄዳሉ
የይሁዳ ህዝብ ከለዳውያን ስለሄዱ ሰላም እናገኛለን ብለው ያስባሉ። “ሰላም እንሆናለን ምክንያቱም ከለዳውያን ከእኛ ዘንድ ሄደዋልእና”

ተነስቶ
የተወጉት ይነሱ ነበር

Jeremiah 37:11

በተመለሰ ጊዜ
ይህን ቃል ሲጠቀም የአዲስ ታሪክ መጀመሪያ እንደሆነ ለማመልከት ነው

የርስት እድል ፈንታ
ትንሽ መሬት ወይም ጥቂት መሬት

በህዝቡ መካከል
በዘመዶቹ መካከል። ኤርምያስ በቢኒያም የምትገኝ አናቶ ከምትባል ከተማ ነው። ኤርምያስ 1፡1 ተመልከት

ብንያምም በር
የመግቢያ በር ስም ነው

የሪያ
ይህ ሰው ስም ነው

ሰሌምያ
የዚህን ሰው ስም እንዴት እንደተተረጎመ በኤርምያስ 36፡14 ተመልከት

ሐናንያ
የዚህን ሰው ስም በኤርምያስ 28፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

መኮብለልህ
ችግርን መሸሸ እና እርዳታ የሚፈልጉ ሰዎችን ትቶ መሄድ

Jeremiah 37:14

መኮብለሌ
ችግርን መሸሸ እና እርዳታ የሚፈልጉ ሰዎችን ትቶ መሄድ

የሪያ
ይህ ሰው ስም ነው

አለቆች
ኤርምያስ 1፡18 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

የፀሀፊውን የዮናታንን
ፀሀፊ የነበረውን ዮናታንን። ይህ የሰው ስም ነው

Jeremiah 37:16

ኤርምያስም ወደ ጉድጓድ ቤት ወደ ጓዳዎቹ ገባ
“አለቆችም ኤርምያስን ወደ ጉድጓድ ቤት ወደ ጓዳዎቹ አስገቡት”

አስመጣው
ኤርምያስን አስመጣው

በቤቱ
የንጉሱ ሴዴቅያስ ቤተመንግስት

በባቢሎን ንጉሥ እጅ አልፈህ ትሰጣለህ አለ
“እጅ” የሚለው ጉልበትን ወይም በእጅ ያለን ቁጥጥርን ያመለክታል። ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ቃላት በኤርምያስ 32፡4 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት። “በባቢሎን ንጉስ ቁጥጥር ስር አሳልፌ እሰጥሃለሁ” ወይም “የባቢሎን ንጉስ የወደደውን እንዲያደርግ እፈቅዳለሁ”

Jeremiah 37:18

በግዞት ቤት ... ምን በድያችሁ ነው?
ኤርምያስ ይህን ጥያቄ ምንም ጥፋት እንዳላጠፋ ለመናገር ይጠቀማል። “ምንም በደል አላደረኩባችሁም...በግዞት ቤት”

ህዝብህን
የይሁዳ ህዝብ

የጣላችሁኝ
ያስቀመጣችሁኝ

ትንቢት ይናገሩላችሁ የነበሩ ነቢያቶቻችሁ ወዴት አሉ?
ኤርምያስ ይህን ጥያቄ ትንቢት የተናገሩት ውሸታቸውን እንደሆነ እና እርሱ እውነቱን ስለተናገረ ሌላ ምንም ስህተት እንዳላደረገ ለማሳየት የጠየቀው ነው። “የናንተ ነቢያት ትንቢት የሚናገሩላችሁ...በዚህ ከተማ ላይ ስህተት ነው ነገር ግን እኔ እውነቱን ነው የተናገርኩት”

ነቢያቶቻችሁ
ይህ ቃል የሚያመለክተው ንጉስ ሴዴቅያስ እና የይሁዳ ህዝብን ነው

እናንተና በዚህች አገር አይመጣባችሁም
እናንተን እና አገራችሁን አያጠቃችሁም

ልመናዬ ወደ አንተ ይድረስ
ለምህረትህ ልመናዬን ስማኝ ወደ አንተም ይድረስ። ለምህረትህ ልመናቸው ወደ እግዚአብሄር ይድረስ የሚለውን በኤርምያስ 36፡7 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት።

የፀሀፊው ወደ ዮናታን ቤት
ፀሀፊ ወደ ሆነው ዮናታን ቤት። ኤርምያስ 37፡15 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት።

ከግዞት ቤት አደባባይ
ይህ ከንጉሱ ቤተመንግስት ጋር አብሮ ያለ ሰፊ ክፍት ቦታ ሲሆን ይህም ደግሞ ለእስረኞች የተዘጋጀ ቦታ ነው። ኤርምያስ 32፡2 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

እንጀራም...ይሰጡት ነበር
“ሰራተኞቹ ለኤርምያስ እንጀራ ይሰጡት ነበር”

ከጋጋሪዎች መንገድ ይሰጡት ነበር
ጋጋሪዎች ከሚሰሩበት መንገድ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 38

1 ኤርምያስም ለሕዝቡ ሁሉ የተናገረውን ቃል የማታን ልጅ ስፋጥያስ፣ የጳስኮርም ልጅ ጎዶልያስ፣ የሰሌምያም ልጅ ዮካል፣ የመልክያም ልጅ ጳስኮር ሰሙ።
ኤርምያስ እንዲህ ሲል ነበር፣ 2 "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በዚህች ከተማ የሚቀመጥ ማንኛውም ሰው በሰይፍ፣ በራብ፣ በመቅሠፍትም ይሞታል። ወደ
ከለዳውያን የሚወጣ ግን በሕይወት ይኖራል። ሕይወቱንም ያስመልጣል፣ በሕይወትም ይኖራል። 3 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ይህች ከተማ በባቢሎን
ንጉሥ ሠራዊት እጅ በእርግጥ ትሰጣለች፣ እርሱም ይይዛታል።" 4 ስለዚህ አለቆቹ ለንጉሡ እንዲህ አሉት፣ "ይህን የመሰለውን ቃል ሲነግራቸው በዚህች ከተማ
የቀሩትን የሰልፈኞቹን እጅ የሕዝቡንም ሁሉ እጅ ያደክማልና ይህ ሰው ይገደል። ይህ ሰው ጥፋትን እንጂ ለዚህ ሕዝብ ሰላምን አያበጅለትምና እነዚህን ቃሎች
እየተናገረ ነው። 5 ስለዚህ ንጉሡ ሴዴቅያስ፣ "ተመልከቱ፣ እናንተን የሚቋቋም ንጉሥ የለምና፣ በእጃችሁ ነው" አለ። 6 ከዚያም ኤርምያስን ወሰዱትና ወደ
ንጉሡ ልጅ ወደ መልክያ ጕድጓድ ጣሉት። ጕድጓዱ በእስር ቤቱ አደባባይ ነበረ። ኤርምያስንም በገመድ አወረዱት። በጕድጓድም ውስጥ ውኃ አልነበረበትም፣
ነገር ግን ጭቃማ ነበርና ኤርምያስ ጭቃው ውስጥ ገባ። 7 ኩሻዊ የሆነው አቤሜሌክ በንጉሡም ቤት ከነበሩት ጃንደረቦች አንዱ ነበር። ኤርምያስን በጕድጓዱ
ውስጥ እንዳኖሩት ሰማ። ንጉሡም በብንያም በር ተቀምጦ ነበር። 8 ስለዚህ አቤሜሌክ ከንጉሡ ቤት ወጥቶ ከንጉሡ ጋር ተነጋገረ። 9 "ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፣
እነዚህ ሰዎች ነቢዮን ኤርምያስን በጕድጓድ ውስጥ በመጣላቸው ክፉ አድርገዋል። በከተማይቱም ውስጥ እንጀራ ስለሌለ በዚያ በራብ እንዲሞት ወደ ጕድጓድ
ጥለውታል።" 10 ከዚያም ንጉሡ ለኩሻዊው አቤሜሌክ ትእዛዝ ሰጠ። "ከአንተ ጋር ሠላሳ ሰዎች ከዚህ ውሰድ፣ ነብዩ ኤርምያስ ሳይሞት በፊት ከጕድጓድ
አውጣው" ብሎ አዘዘው። 11 ስለዚህ አቤሜሌክ ከእርሱ ጋር ሰዎችን ይዞ ሄደና ከቤተ መዛግብቱም በታች ወደ ነበረው ወደ ንጉሥ ቤት ገባ። ከዚያም አሮጌ
ጨርቅና እላቂ ልብስ ወሰደና ወደ ኤርምያስ ወደ ጕድጓድ ውስጥ በገመድ አወረደው። 12 ኩሻዊው አቤሜሌክ ኤርምያስን፣ "ይህን አሮጌ ጨርቅና እላቂውን
ልብስ በብብትህ እና ከገመዱ በታች አድርግ" አለው። ስለዚህ ኤርምያስ እንዲሁ አደረገ። 13 ከዚያም ኤርምያስን በገመዱ ጐተቱት። በዚህ መልኩ ከጕድጓድ
አወጡት። ስለዚህ ኤርምያስ በግዞት ቤት አደባባይ ተቀመጠ። 14 ከዚያም ንጉሡ ሴዴቅያስ ልኮ በእግዚአብሔር ቤት ወደ ነበረው፣ ወደ ሦስተኛው መግቢያ፣
ወደ እርሱ ነቢዩን ኤርምያስን አስመጣው። ንጉሡም ኤርምያስን፣ "አንዲት ነገር ልጠይቅህ እፈልጋለሁ። መልሱን አትደብቅብኝ" አለው። 15 ኤርምያስም
ሴዴቅያስን፣ "ብመልስልህ፣ በእርግጥ አትገድለኝምን? ምክር ብሰጥህም፣ አትሰማኝም" አለው። 16 ንጉሡ ሴዴቅያስ ግን "እኛን የፈጠረንን ሕያው
እግዚአብሔርን፣ አልገድልህም፣ ወይም ነፍስህን ለሚሹ ለእነዚህ ሰዎች እጅ አሳልፌ አልሰጥህም" ብሎ በድብቅ ለኤርምያስ ማለ። 17 ስለዚህ ኤርምያስ
ሴዴቅያስን፣ የእስራኤል አምላክ፣ የሠራዊት አምላክ፣ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ወደ ባቢሎን ንጉሥ አለቆች ብትወጣ፣ በሕይወት ትኖራለህ፣ ይህችም
ከተማ አትቃጠልም። አንተና ቤተሰብህ በሕይወት ትኖራላችሁ። 18 ነገር ግን ወደ ባቢሎን ንጉሥ አለቆች ባትወጣ ግን፣ ይህች ከተማ በከለዳውያን እጅ
ትሰጣለች። በእሳትም ያቃጥሉአታል፣ አንተም ከእጃቸው አታመልጥም" አለው። 19 ንጉሡ ሴዴቅያስም ኤርምያስን፣ "ነገር ግን ወደ ከለዳውያን ክፉኛ
እንዲያፌዙብኝ፣ በኰበለሉት በአይሁድ እጅ አሳልፈው ይሰጡኛል ብዬ እፈራለሁ" አለው። 20 ኤርምያስም እንዲህ አለው፣ "ለእነርሱ አሳልፈው አይሰጡህም።
እኔ እየነገርኩህ ያለሁትን የእግዚአብሔርን መልእክት ታዘዝ፤ ነገሮችም መልካም ይሆኑልሃል፣ በሕይወትም ትኖራለህ። 21 ነገር ግን ትወጣ ዘንድ እንቢ ብትል፣
እግዚአብሔር ያሳየኝ ይህንን ነው፦ 22 ተመልከት! በይሁዳ ንጉሥ ቤት የቀሩትን ሴቶች ሁሉ ወደ ባቢሎን ንጉሥ አለቆች ያወጣሉ። እነዚያም ሴቶች ለእንተ፣
"ወዳጆችህ አታልለውሃል፤ አበላሽተውህማል። እግሮችህ ግን አሁን በጭቃ ውስጥ ሰጥመዋል፣ ወዳጆችህም ይሸሻሉ።' 23 ሚስቶችህንና ልጆችህንም ሁሉ
ወደ ከለዳውያን ያወጣሉ፣ አንተም ራስህ አታመልጥም። በባቢሎን ንጉሥ እጅ ትያዛለህ ይህችም ከተማ በእሳት ትቃጠላለች።" 24 ከዚያም ሴዴቅያስ
ኤርምያስን እንዲህ አለው፣ "እንዳትሞት ስለእነዚህ ቃሎች ለማንም አትናገር። 25 አለቆቹ ግን እኔ ከአንተ ጋር እንደ ተነጋገርሁ ከሰሙ፣ ወደ አንተ መጥተው፣
'ለንጉሡ የነገርከውን ንገረን። ከእኛም አትሸሽገን፣ አሊያ እንገድልሃለን። ንጉሡ ደግሞ ያለህን ንገረን' ቢሉህ፣ 26 ያን ጊዜ 'በዚያ እሞት ዘንድ ወደ ዮናታን ቤት
አትመልሰኝ' ብዬ በንጉሡ ፊት ለመንሁ" በላቸው። 27 ከዚያም አለቆቹ ሁሉ ወደ ኤርምያስ መጥተው ጠየቁት፣ ንጉሡም እንዳዘዘው እንደዚህ ቃል ሁሉ
ነገራቸው። በኤርምያስና በንጉሡ መካከል የነበረው ውይይት አልተሰማምና ከእርሱ ጋር መነጋገርን ተዉ። 28 ስለዚህ፣ ኢየሩሳሌም እስከ ተያዘችበት ቀን ድረስ
ኤርምያስ በእስር ቤት አደባባይ ተቀመጠ።

Jeremiah 38:1

ሰፋጥያስ...ማታን...ጎዶልያስ...ጳስኮርም...ዮካል...ሰሌምያም...ጳስኮር...መልክያም
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው

በዚህች ከተማ የሚቀመጥ በሰይፍና በራብ በቸነፈርም ይሞታል
“በዚህች ከተማ የሚቀመጥ በሰይፍ በረሃብ እና በቸነፈር ይሞታል” ወይም “በዚህች ከተማ የሚቀመጥ በሰይፍ በረሃብ እና በቸነፈር እገድላለሁ”

ነፍሱም እንደ ምርኮ ትሆንለታለች
ለባቢሎናውያን እጅ የሚሰጥ በህይወት ይሆናል ምንም ያለውን ነገር በሙሉ ቢያጣም። በኤርምያስ 21:9 ላይ እንዴት እንደ ተረጎመው ተመልከት

ይህች ከተማ በባቢሎን ንጉሥ ሠራዊት እጅ በእርግጥ ትሰጣለች
“እጅ” የሚለው ጉልበትን ወይም በእጅ ያለን ቁጥጥርን ያመለክታል። “የባቢሎን ሰራዊት ኢየሩሳሌምን እንዲያሸንፉ እፈቅዳለሁ”

እርሱም ይይዛታል
አንባቢው ሊረዳው የሚገባው ነገር ሌሎችም የባቢሎን ንጉስ ከተማዋን ሲይዝ እንዳገዙት ነው። “ሰራዊቱ ይይዙአቸዋል”

Jeremiah 38:4

ይህ ሰው እንዲገደል
ይህን ሰው ለማስገደል ማዘዝ

በዚህች ከተማ የቀሩትን የሰልፈኞቹን እጅ የሕዝቡንም ሁሉ እጅ ያደክማልና
እጅ ያደክማል የሚለው የሚፈራን ሰው ያመለክታል። “በዚህች ከተማ የቀሩትን ሰልፈኞዎችን ድፍረታቸውን እያጡ ነው”

ይህ ሰው ክፋትን እንጂ ለዚህ ሕዝብ ሰላምን አይመኝለትምና አሉት
“ኤርምያስ ህዝቡ ሰላም እንዲሆኑ አይመኝም ነገር ግን በህዝቡ ላይ ከፉ ነገር እንዲሆን ነው የሚመኘው”

በእጃችሁ ነው
እጅ የሚለው እጅ ያለውን ሃይል የሚያሳይ ነው። “በእሱ ላይ ማድረግ የፈለጋችሁትን አድርጉ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Jeremiah 38:6

በግዞት ቤቱም አደባባይ ወደ ነበረው ወደ ንጉሡ ልጅ ወደ መልክያ ጕድጓድ ውስጥ ጣሉት
ኤርምያስን በገመድ ወደታች ላኩት። ነገር ግን ጣሉት የሚለው ጥሩ እንክብካቤ በጎደለበት በመጥፎ ቦታ እንዳስገቡት አግንኖ እየተናገረ ነው። “ኤርምያስን ወደ ጉድጓድ ገፈተሩት”

ጉድጓድ
ጥልቅ የተቆፈረ ሰዎች የዝናብ ውሃ የሚያጠራቅሙበት እና የሚቀዱበት ቦታ

ከግዞት ቤት አደባባይ
ይህ ከንጉሱ ቤተመንግስት ጋር አብሮ ያለ ሰፊ ክፍት ቦታ ሲሆን ይህም ደግሞ ለእስረኞች የተዘጋጀ ቦታ ነው። ኤርምያስ 32:2 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ኤርምያስን በገመድ አወረዱት
ወደ ጉድጓዱ እንዴት እንደጣሉት ይናገራል

Jeremiah 38:7

አቤሜሌክ
በንጉሱም ቤት የነበረው...አቤሜሌክ የሚለውን ቃል ሲጠቀም የአዲስ ታሪክ ጅማሬን ሊያመለክት ፈልጎ ነው

ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ
የኢትዮጲያዊ ሰው ስም ነው።

ንጉሱም...
ይህን ቃል ሲጠቀም በታሪኩ ውስጥ ትኩረት የሚሰጠውን ታሪክ ለማሳየት ነው (ታሪካዊ ዳራውን ተመልከት)

በቢንያም በር ተቀምጦ
ንጉስ ሴዴቅያስ ፍርድ እየሰጠ እና ክስ እየሰማ ይሆናል።

ብንያም በር
ይህ የኢየሩሳሌም መግቢያ ሲሆን በያዕቆብ ልጅ በብንያም ስም ተሰይሟል

Jeremiah 38:10

ሰላሳ ሰዎች
ሰላሳ ሰዎች

በገመድ አወረደው
ገመድን በመጠቀም ወደታች አወረደው

Jeremiah 38:12

በብብትህ ከገመዱ በታች አድርግ
በእጅህ እና በገመዱ መሃከል አድርግ

ኤርምያስን በገመዱ ጎተቱት
ኤርምያስን የጎተቱት ከአቤሜሌክ ጋር አብረው የነበሩት ሰላሳ ሰዎች ናቸው

ከግዞት ቤት አደባባይ
ይህ ከንጉሱ ቤተመንግስት ጋር አብሮ ያለ ሰፊ ክፍት ቦታ ሲሆን ይህም ደግሞ ለእስረኞች የተዘጋጀ ቦታ ነው። ኤርምያስ 32:2 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

Jeremiah 38:14

ብነግርህ በውኑ አትገድለኝምን?
ኤርምያስ ይህን ጥያቄ የጠየቀው እውነቱን መልስ ቢነግረው ንጉሱ እንደሚገድለው ስላሰበ ነው። “እውነቱን ብነግርህ አንተ እኔን ትገድለኛለህ”

ሕያው እግዚአብሔርን!
“እግዚአብሄር አምላክ ህያው እንደሆነ”። ህዝቡ ይህን የሚናገሩት ቀጥለው የሚናገሩት እውነት እንደሆነ ለመግለፅ ነው። “ህያው እግዚአብሄር” ኤርምያስ 4:2 ።

ለእነዚህ ሰዎች እጅ አሳልፌ አልሰጥህም
“እጅ” የሚለው ቃል ሃይል ስላላቸው ሰዎች ይናገራል። “ሰዎች እንዲይዙአችሁ አለፈቅድም”

ነፍስህን ለሚሹ
ይህ ሀረግ አንድስ ሰው ለመግደል መፈለግን ያመለክታል። በኤርምያስ 11፡21 እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።

Jeremiah 38:17

የእስራኤል አምላክ
“የእስራኤል ህዝብ አምላክ”

ይህችም ከተማ በእሳት አትቃጠልም
“የባቢሎናውያን ሰራዊት ከተማዋን አያቃጥሉአትም”

ይህች ከተማ በከለዳውያን እጅ ትሰጣለች
“እጅ” የሚለው ቃል ሃይል ወይም እጅ የሚለማመደው ስልጣንን ነው። ኤርምያስ 38:2 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት። “ከለዳውያን ይህንን ከተማ እንዲያሸንፉ እፈቅዳለሁ” ወይም “በዚህ ከተማ ላይ የፈለጉትን እንዲያደርጉ ለከለዳውያን እፈቅዳለሁ”

ከእጃቸው አታመልጥም
“እጅ” የሚለው ቃል ሃይል ወይም እጅ የሚለማመደው ስልጣንን ነው። “ከእነርሱ ጉልበት ልታመልጥ አትችልም”

Jeremiah 38:19

በኮበለሉት
ችግርን ማምለጥ እና እርዳታ የሚፈልጉ ሰዎችን ትቶ መሄድ። ኤርምያስ 37፡13 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

እጅ አሳልፈው ይሰጡኛል
“እጅ” የሚለው ቃል ሃይል ወይም እጅ የሚለማመደው ስልጣንን ነው። “ከለዳውያን በኮበለሉት በይሁዳ ቁጥጥር ስር አሳልፎ ይሰጡኛል” ወይም “ከለዳውያን ለኮበለሉት ለይሁዳ ህዝብ የፈለጉትን እንዲያደርጉ አሳልፎ ይሰጡኛል”

እነርሱም ያፌዝቡኛል
“እነርሱም” የሚለው ቃል የኮበለሉትን የይሁዳ ህዝብን ነው።

Jeremiah 38:20

አሳልፈው አይሰጡህም
“ከለዳውያን ለይሁዳ አሳልፈው አይሰጡህም” “አይሰጡህም” ሲል ሴዴቅያስን ነው።

እግዚአበሄር ያሳየኝ ቃል ነው
ይህ አረፍተነገር የሚያሳየው ኤርምያስ ቀጥሎ ሊናገር ያለውን ነገር ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Jeremiah 38:22

አጠቃላይ ሀሳብ
ኤርምያስ ከንጉስ ሴዴቅያስ መነጋገሩን ቀጠለ

የቀሩትን ሴቶች ሁሉ...ወደ ባቢሎን ንጉሥ አለቆች ያወጣሉ
አንባቢው ሊረዳው የሚገባው ነገር አለቆች እነዚህን ሴቶች እንደ ባሪያ አድርገው ነው የወሰዱአቸው። “የቀሩትን ሴቶች ሰራዊቱ ያመጣቸዋል... ከባቢሎን ንጉስ አለቆች”

ባለምዋሎችህ አታልለውሃል
“ጓደኞችህ አታልለውሃል”

እግሮችህ ግን አሁን በጭቃ ውስጥ ከገቡ
ንጉሱ ከአሁን በኋላ የሚያደርገው ምንም ነገር የለም

ሚስቶችህንና ልጆችህንም ሁሉ ወደ ከለዳውያን ያወጣሉ
አንባቢው ሊረዳው የሚገባው ነገር አለቆች እነዚህን ሰዎች እንደ ባሪያ አድርገው ነው የወሰዱአቸው። “ሰራዊቱ ሚስቶችህንና ልጆችህን ወደ ከለዳውያን ያመጡአቸዋል”

ከእጃቸው አታመልጥም
“እጅ” የሚለው ቃል ሃይል ወይም እጅ የሚለማመደው ስልጣንን ነው። “ከሃይላቸው ልታመልጥ አትችልም”

በባቢሎን ንጉሥ እጅ ትያዛለህ እንጂ ከእጃቸው አታመልጥም ይህችም ከተማ በእሳት ትቃጠላለች።
“እጅ” የሚለው ቃል ሃይል ወይም እጅ የሚለማመደው ስልጣንን ነው። አንባቢው ሊረዳው የሚገባው ንጉሱ ይህን ለማድረግ ሌሎች እንደረዱት ነው። “አንተን የባቢሎን ንጉሱ ሰራዊቶች ይይዙሃል ደግሞም ከተማዋን በእሳት ያነዱታል።”

Jeremiah 38:24

ዮናታን
የዚህን ሰው ስም በኤርምያስ 37:15 እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት

Jeremiah 38:27

ከእርሱ ጋር መነጋገርን ተው
“ንጉሱና ኤርምያስ እርስ በእርስ የተነጋገሩትን ነገር”

ከግዞት ቤት አደባባይ
ይህ ከንጉሱ ቤተመንግስት ጋር አብሮ ያለ ሰፊ ክፍት ቦታ ሲሆን ይህም ደግሞ ለእስረኞች የተዘጋጀ ቦታ ነው። ኤርምያስ 32:2 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ኢየሩሳሌም እስከተያዘችበት ቀን ድረስ
“የባቢሎን ሰራዊት ኢየሩሳሌምን እስከሚይዝበት ቀን ድረስ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 39

1 ኢየሩሳሌምም በተያዘች ጊዜ፣ በይሁዳ ንጉሥ በሴዴቅያስ በዘጠነኛው ዓመት በዐሥረኛው ወር የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ከሠራዊቱ ሁሉ ጋር ወደ
ኢየሩሳሌም መጥተው ከበቡአት። 2 በሴዴቅያስም በዐሥራ አንደኛው ዓመትና በአራተኛው ወር ከወሩም በዘጠነኛው ቀን ከተማይቱ ተሰበረች። 3 ከዚያም
የባቢሎን ንጉሥ አለቆች ሁሉ፣ ኤርጌል ሳራስር፣ ሳምጋርናቦና፣ ዋና አለቃው ሠርሰኪም፤ ኤርጌል ሳራስር በከፍተኛ ደረጃ ያለ አለቃ ነበርና ከቀሩት የባቢሎን
ንጉሥ አለቆች ሁሉ ጋር ገብተው በመካከለኛው በር ውስጥ ተቀመጡ። 4 የይሁዳ ንጉሥ ሴዴቅያስ፣ ሰልፈኞቹም ሁሉ፣ ባዩአቸው ጊዜ ሸሹ። በሌሊትም
በንጉሡ አትክልት መንገድ በሁለቱ ቅጥር መካከል ከነበረው ደጅ ከከተማይቱ ወጡ። ንጉሡ በዓረባ መንገድ ወጣ። 5 ነገር ግን የከለዳውያን ሠራዊት
ተከታተላቸውና ሴዴቅያስን በኢያሪኮ ሜዳ አቅራቢያ ባሉት የዮርዳኖስ ሸለቆ ሜዳዎች ላይ አገኙት። ከዚያም ይዘውት በሐማት ምድር ወዳለችው ወደ ሪብላ ወደ
ባቢሎን ንጉሥ ወደ ናቡከደነፆር አመጡት፣ እርሱም ፍርድን በእርሱ ላይ ተናገረ። 6 የባቢሎንም ንጉሥ የሴዴቅያስን ልጆች በገዛ ዐይኑ ፊት በሪብላ አረዳቸው።
እርሱም የይሁዳን ከበርቴዎች ሁሉ ገደለ። 7 ከዚያም የሴዴቅያስን ዐይን አወጣና ወደ ባቢሎን ሊወስደው በመዳብ ሰንሰለት አሰረው። 8 ከዚያም ከለዳውያን
የንጉሡንና የሕዝቡን ቤቶች በእሳት አቃጠሉ። የኢየሩሳሌምንም ቅጥር አፈረሱ። 9 የዘበኞቹም አለቃ ናቡዘረዳን በከተማይቱ የቀሩትን ሕዝብ፣ ወደ እርሱም
የኰበለሉትን ሰዎች፣ የቀረውንም የሕዝቡን ቅሬታ ወደ ባቢሎን ማረካቸው። 10 አንዳች የሌላቸውን የሕዝቡን ድሆች ግን የዘበኞቹ አለቃ ናቡዘረዳን በይሁዳ አገር
ተዋቸው። የወይኑን ቦታና እርሻውን በዚያው ቀን ሰጣቸው። 11 የባቢሎንም ንጉሥ ናቡከደነፆር ስለ ኤርምያስ፣ 12 "ውሰደውና በመልካም ተንከባከበው።
አትጉዳው። የሚነግርህንም የትኛውንም ነገር አድርግለት።" ብሎ የዘበኞቹን አለቃ ናቡዘረዳንን አዘዘ። 13 ስለዚህ የዘበኞቹ አለቃ ናቡዘረዳን ላከ፣ የጃንደረቦች
አለቃ ናቡሽዝባን፣ ዋናው አለቃ ራፋስቂስም ኤርጌል ሳራስርም፣ ራብማግም የባቢሎንም ንጉሥ ዋና ዋና አለቆች ሁሉ ሰዎችን ላኩ። 14 ሰዎቻቸውም
ኤርምያስን ከግዞት ቤት አደባባይ አወጡት፣ ወደ ቤቱም ይወስደው ዘንድ ለሳፋን ልጅ ለአኪቃም ልጅ ለጎዶልያስ ሰጡት፤ ስለዚህ ኤርምያስ በሕዝብ መካከል
ተቀመጠ። 15 በግዞትም ቤት አደባባይ ታስሮ ሳለ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል ወደ ኤርምያስ መጣ፣ 16 "ለኩሻዊው ለአቤሜሌክ እንዲህ በለው፣
'የእስራኤል አምላክ፣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፣ እንዲህ ይላል፦ ተመልከት፣ ለበጎነት ሳይሆን ለጥፋት ቃሌን በዚህች ከተማ ላይ አመጣለሁ። በዚያም ቀን
በፊትህ እውነት ሆኖ ይፈጸማል። 17 ነገር ግን በዚያ ቀን እታደግሃለሁ፣ ይላል እግዚአብሔር፤ በምትፈራቸው ሰዎች እጅ አልሰጥህም። 18 በእርግ አድንሃለሁ
ነፍስህም እንደ ምርኮ ትሆንልሃለች እንጂ በሰይፍ አትወድቅም። በእኔ ታምነሃልና፣ ይላል እግዚአብሔር።"

Jeremiah 39:1

ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው
ኢየሩሳሌምን ሊወጉ መጡ

በይሁዳ ንጉስ በሴዴቅያስ በዘጠነኛው አመት በአስረኛው ወር
ይህ ሴዴቅያስ ከነገሰ በእብራውያን ቀን መቁጠሪያ ከስምንት አመት እና ከአስረኛው ወር በኋላ ነው።

ዘጠነኛው...አስረኛው...አስረአንደኛው...አራተኛው
ቁጥሮች ናቸው

በሴዴቅያስም በአሥራ አንደኛው ዓመት በአራተኛው ወር ከወሩም በዘጠነኛው ቀን
ይህ በዕብራውያን የቀን መቁጠሪያ የይሁዳ ንጉስ ሴዴቅያስ ከነገሰ ከአስር አመት እና አራተኛው ወር በኋላ ነው። አስረአንደኛው ቀን ማለት እንደ አውሮፕያን ቀን አቆጣጠር የጁላይ ወር መጀመሪያ አካባቢ ነው። “ሴዴቅያስ ከነገሰ ከአስራአንደኛው አመት አራተኛው ወር እና ዘጠኛው ቀን”

ሳርሳር ሳምጋርናቦ እና ሠርሰኪም
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው

በመካከለኛው በር
የከተማዋ የመካከለኛው በር። በመሪዎች የከተማው መግቢያ በር ጋር በመቀመጥ አስፈላጊ ነገሮች ላይ መወያት የተለመደ ነው

Jeremiah 39:4

በሌሊትም በንጉሡ አትክልት መንገድ በሁለቱ ቅጥር መካከል ከነበረው ደጅ ከከተማይቱ ወጡ በዓረባም መንገድ ወጡ
በንጉሱ የአትክልት መንገድ በለሊት ወጡ

በኢያሪኮ ሜዳ
ቀጥ ያለ ሰፊ ሜዳ ሲሆን ከሸለቆ መጨረሻ በስተደቡብ ላይ ይገኛል

በሃማት ምድር ወዳለችው ሪብላ
ሪብላ የሃማት ክልል ውስጥ የምትገኝ ከተማ ስትሆን ሶሪያ የሚባለው ነው።

ተከታተላቸው...አገኙት ይዘውም
ተከትሎ ያዛቸው

ፍርድን በእርሱ ላይ ተናገረ
እንዴት እንደሚቀጣው ወሰነ

Jeremiah 39:6

የሴዴቅያስን ልጆች በዓይኑ ፊት በሪብላ ገደላቸው
በአይኑ የሚወክለው ሙሉ ሰውን ሲሆን አንባቢበው ሊረዳ ሚገባው ሌሎችም የሃቢሎን ንጉስ የሴዴቅያስን ልጅ ሲገድል እንደረዱት ነው። “ሴዴቅያን በማስገደድ የንጉሱ ሰራዊት ልጁን ሲገድሉ ተመለከተ”

የሴዴቅያስንም አይን አወጣ
የንጉሱ ሰዎች የሴዴቅያስን አይነ ስውር ሆነ። የባቢሎን ንጉስ የሴዴቅያስን አይን ከጭንቅላቱ ማውጣቱን ግልፅ አደለም። አንባቢው ሊረዳው የሚገባው ነገር ሌሎች የባቢሎንን ንጉስ የሴዴቅያስን አይን ሲያጠፋ እንደአገዙት ነው።

Jeremiah 39:8

የንጉሱን...ቤቶች
የሴዴቅያስን ቤት

የህዝቡን ቤቶች
የኢየሩሳሌም ህዝብ ቤቶች

ናቡዘረዳን
ይህ የሰው ስም ነው

የዘበኛ አለቃ
የናቡዘረዳን ዘበኛ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በከተማይቱ የቀሩትን ህዝብ
“በከተማዋ እየኖሩ ያሉ ህዝቦችን”

ድሆች
“ምንም ነገር የሌላቸው”

Jeremiah 39:11

ናቡሽዝባንም...ጎዶልያስ...አኪቃም...ሳፋን
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው

...ዋና ዋና አለቆች ሁሉ ላኩ
ሰዎቹን የላኩት ኤርምያስን ይዘው እንዲያወጡት ነው።

ከግዞት ቤት አደባባይ
ይህ ከንጉሱ ቤተመንግስት ጋር አብሮ ያለ ሰፊ ክፍት ቦታ ሲሆን ይህም ደግሞ ለእስረኞች የተዘጋጀ ቦታ ነው። ኤርምያስ 32:2 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

በህዝብ መካከል
“በይሁዳ በቀሩት በህዝብ መካከል”

Jeremiah 39:15

አጠቃላይ ሃሳብ
ይህ የተፈፀመው በምእራፉ የመጀመሪያ ክፍል ነው።

..ታስሮ ሳለ
ይህንን ቃል ሲጠቀም ወደ ዋና ታሪኩ ለመመለስ ነው። ጸሐፊው ናቡከነደፆር ኤርምያስን እንዲይዙት ከሰጠው ትእዛዝ በኋላ እግዚአብሄር ለኤርምያስ የተናገረውን ለመግለጽ ነው። (ታሪካዊ ዳራ እና የጊዜ ቅደም ተከተል የሚለውን ተመልከት)

የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል ወደ ኤርምያስ መጣ።
“የእግዚአብሄር ቃል ወደ” የሚለው ቃል ልዩ የሆነ መልእክት ለመናገር ሲፈልግ የሚጠቀመው ነው። ተመሳሳይ አረፍተነገር በኤርምያስ 1:4 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት። “እግዚአብሄር ለኤርምያስ እንዲህ ሲል ተናገረ “ውሰድ””

በግዞትም ቤት አደባባይ
ይህ ከንጉሱ ቤተመንግስት ጋር አብሮ ያለ ሰፊ ክፍት ቦታ ሲሆን ይህም ደግሞ ለእስረኞች የተዘጋጀ ቦታ ነው። ኤርምያስ 32:2 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ለኢትዮጵያዊውም ለአቤሜሌክ
የዚህን ሰው ስም በኤርምያስ 38:7 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት።

የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር
ኤርምያስ ማስተዋል ያለብንን መልእክት ሲያስተላልፍ የሚጠቀመው ሀረግ ነው። ኤርምያስ 6:6 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ለበጎነት ሳይሆን ለክፋት ቃሌን በዚህች ከተማ ላይ አመጣለሁ
ክፉን ነገር በዚህች ከተማ ላይ አመጣለሁ እንደተነገርኩት ለክፋት ይሆናል።

በዚያን ቀን በፊትህ ይፈፀማል
በዛች ቀን ላይ የሚፈጠረውን ታያለህ

Jeremiah 39:17

አጠቃላይ ሀሰብ
እግዚአብሄር ለኤርምያስ መናገር ቀጠለ

በዚያ ቀን
ይህ የሚያመለክተው ባቢሎናውያን የኢየሩሳሌምን ግንብ አፍርሰው ከተማዋን የሚያጠፉባት ቀን ነች

ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ የገለጸበት ምክንያት ቃሉን አስረግጦ ለመናገር ስለፈለገ ነው።፤ ኤርምያስ 1:8 የተተረጎመበትን መንገድ ይመልከቱ። ‹‹እግዚአብሄር የተናገረው ይህንን ነው›› ወይም ‹‹እኔ እግዚአብሄር የተናገርኩት ይህንን ነው››

በምትፈራቸው ሰዎች እጅ አልሰጥህም
“እጅ” የሚለው ሃይል እና ጉልበትን ያመለክታል። “የምትፈሩአቸው ሰዎች አይነኩአችሁም” ወይም “እናንተ በምትፈሩት በማንም ስልጣን ስር እንድትሆኑ አልፈቅድም”

በሰይፍ አትወድቅም
ሰይፍ የሚለው በጦርነት መሞትን ያመለክታል። “ማንም በሰይፍ አይገድሏችሁም” ወይም “በጦርነት አትሞቱም”

እድንሃለሁ ነፍስህም
በሂወት ትሆናለህ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 40

1 ወደ ባቢሎን በተማረኩት በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ምርኮኞች መካከል የዘበኞቹ አለቃ ናቡዘረዳን፣ከራማ ከለቀቀው በኋላ፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ
ኤርምያስ መጥቶ የነበረው ቃል ይህ ነው። ኤርምያስ ተወስዶ የነበረው ወደዚህ ቦታ የነበረ ሲሆን፣ እርሱም በሠንሰለት ታስሮ ነበር። እርሱ በምርኮ ከተወሰዱት
የኢየሩሳሌም እና ይሁዳ ምርኮኞች ሁሉ መካከል አንዱ ነበር። 2 የዘበኞቹም አለቃ ኤርምያስን ወሰደውና እንዲህ አለው፣ "አምላክህ እግዚአብሔር ይህን ክፉ
ነገር በዚህ ስፍራ ላይ ተናገረ። 3 ስለዚህ እግዚአብሔር ነገሩን አመጣው። እናንተ ሕዝቦች በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ሠርታችኋልና፣ እንደ ተናገረው አደረገ።
ይህ ነገር እየሆነባችሁ ያለው፣ ቃሉን አልሰማችሁምና ነው። 4 አሁን ግን ተመልከት! እጅህ የታሰረችበትን ሰንሰለት ዛሬ ፈታሁልህ። ከእኔ ጋር ወደ ባቢሎን
መምጣት በዐይኖችህ ዘንድ መልካም መስሎ ቢታይህ፣ ና፣ እኔም እንከባከብሃለሁ። ነገር ግን ከእኔ ጋር ወደ ባቢሎን መምጣቱ በዐይኖችህ ዘንድ መልካም
መስሎ ባይታይህ ግን፣ አትምጣ። በፊትህ ያለችውን ምድር ሁሉ ተመልከት። በዐይኖችህ ዘንድ ልትሄድበት መልካም መስሎ ወደሚታይህና ትክክል
ወደሚመስልህ ስፍራ ሂድ።" 5 እርሱም ገና መልስ ሳይሰጥ፣ ናቡከደነፆር "የባቢሎን ንጉሥ በይሁዳ ከተሞች ላይ ወደ ሾመው ወደ ሳፋን ልጅ ወደ አኪቃም
ልጅ ወደ ጎዶልያስ ተመለስ። ከእርሱም ጋር በሕዝቡ መካከል ተቀመጥ ወይም ልትሄድበት ደስ ወደሚያሰኝህ ስፍራ ሁሉ ሂድ" አለው። የዘበኞቹም አለቃ
የምግብ ስንቅና ስጦታ ሰጥቶ አሰናበተው። 6 ስለዚህ ኤርምያስ የአኪቃም ልጅ ጎዶልያስ ወዳለበት ወደ ምጽጳ ሄደ። ከእርሱም ጋር በአገሩ ውስጥ በቀሩት
ሕዝብ መካከል ተቀመጠ። 7 በየገጠሩ የነበሩት የጭፍራ አለቆችና ሰዎቻቸው ሁሉ የባቢሎን ንጉሥ የአኪቃምን ልጅ ጎዶልያስን በምድር ላይ እንደ ሾመ ሰሙ።
እንዲሁም ወደ ባቢሎን ያልተማረኩ የምድሪቱ ድሆች የሆኑት ወንዶች፣ ሴቶችና ልጆች ላይ እንደሾመው ሰሙ። 8 ስለዚህ ወደ ጎዶልያስ ወደ ምጽጳ መጡ።
እነዚህም ሰዎች የናታንያ ልጅ እስማኤል፣ የቃሬያም ልጅ ዮሐናንና ዮናታን፣ የተንሑሜትም ልጅ ሠራያ፣ የነጦፋዊውም የዮፌ ልጆች፣ የማዕካታዊውም ልጅ
ያእዛንያ፣ እነርሱና ሰዎቻቸው ነበሩ። 9 የሳፋንም ልጅ የአኪቃም ልጅ ጎዶልያስ ለእነርሱና ለሰዎቻቸው ማለ፣ እንዲህም አላቸው፣ "ለከለዳውያን አለቆች
ለማገልገል አትፍሩ። በምድሪቱ ላይ ተቀመጡ ለባቢሎንም ንጉሥ አገልግሉ፣ መልካምም ይሆንላችኋል። 10 ተመልከቱ፣ ወደ እኛ ከሚመጡት ከለዳውያን ጋር
ለመገናኘት ምጽጳ ውስጥ እኖራለሁ፤ እናንተ ግን ወይንን፣ የበጋ ፍሬንና፣ ዘይትን በየዕቃዎቻችሁ አከማቹ። በያዛችኋቸውም ከተሞቻችሁ ውስጥ ኑሩ።" 11
በሞዓብ፣ በአሞንም ልጆች መካከል፣ እንዲሁም በኤዶምያስና በእያንዳንዱ ምድር ሁሉ ላይ የነበሩ አይሁድ ሁሉ የባቢሎን ንጉሥ የይሁዳን ቅሬታ እንዳስቀረ፣
የሳፋንንም ልጅ የአኪቃምን ልጅ ጎዶልያስን በላያቸው እንደ ሾመው ሰሙ። 12 ስለዚህ አይሁድ ሁሉ ከተበተኑበት ስፍራ ሁሉ ተመለሱ። ጎዶልያስ ወዳለበት፣
ወደ ይሁዳ ምድር፣ ወደ ምጽጳ መጡ። ወይንና የበጋንም ፍሬ በመሰብሰብ እጅግ ብዙ አከማቹ። 13 የቃሬያም ልጅ ዮሐናን፣ በየገጠሩም የነበሩ የጭፍራ አለቆች
ሁሉ ወደ ጎዶልያስ ወደ ምጽጳ መጡ። 14 "የአሞን ልጆች ንጉሥ በኣሊስ ይገድልህ ዘንድ የናታንያን ልጅ እስማኤልን እንደ ሰደደ ታውቃለህን?" አሉት።
የአኪቃም ልጅ ጎዶልያስ ግን አላመናቸውም። 15 ስለዚህ፣ የቃሬያም ልጅ ዮሐናን ምጽጳ ላይ ጎዶሊያስን እንዲህ በማለት በሚስጢር አነጋገረው፣"ሄጄ ማንም
ሳያውቅ የናታንያን ልጅ እስማኤልን እንድገድለው ፍቀድልኝ። ማንም አይጠረጥረኝም። ለገድልህ የሚገባው ለምንድነው? ወደ አንተ የተሰበሰቡ አይሁድ ሁሉ
እንዲበተኑ፣ የይሁዳም ቅሬታ እንዲጠፋ ለምን ትፈቅዳለህ?" 16 ነገር ግን የአኪቃም ልጅ ጎዶልያስ ግን የቃሬያን ልጅ ዮሐናንን፣ "በእስማኤል ላይ ሐሰት
ተናግረሃልና ይህን ነገር አታድርግ" አለው።

Jeremiah 40:1

ከእግዚአብሄር ዘንድ ወደ ኤርምያስ የመጣ ቃል ይህ ነው።
ይህ አረፍተነገር እግዚአብሄር ለኤርምያስ የሰጠው መልእክት እንደሆነ ይናገራል። ኤርምያስ 32:1 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት። “እግዚአብሄር ለኤርምያስ መልእክት ሰጠው” ወይም “እግዚአብሄር ለኤርምያስ ተናገረ”

ናቡዘረዳን
ይህ የሰው ስም ነው። ኤርምያስ 39:9 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ወደ ባቢሎን በተማረኩት
“የጦር ሰራዊቱ በምርኮ ወደ ባቢሎን ሊወስዱአቸው ”

Jeremiah 40:3

ይህ ነገር
ክፉ ነገር

አሁንም እነሆ
ናቡዘረዳን ለኤርምያስ ስለ አሉበት ጊዜ ልብ እንዲል የተናገረው ነው።

መልካም መስሎ ወደሚታይህ
“ወደሚታይህ” ሲል አንድ ሰው ምን እንደሚያስብ ለመግለፅ ነው። “ትክክል ነው ብለህ የምታስበውን”

Jeremiah 40:5

ጎዶልያስ...አኪቃም...ሳፋን
እነዚህ የሰዎች ስም ናቸው። ኤርምያስ 39:14 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

በህዝቡ መካከል
ከይሁዳውያን መካከል

መልካም መስሎ ወደሚታይህ
“ወደሚታይህ” ሲል አንድ ሰው ምን እንደሚያስብ ለመግለፅ ነው። “ትክክል ነው ብለህ የምታስበውን”

በአገሩ ውስጥ በቀሩት
በይሁዳ የቀሩት

Jeremiah 40:7

...በሰሙ ጊዜ
ይህን ቃል የአዲስ ታሪክ ጅማሬን ያመለክታል

ወደ ባቢሎን ያልተማረኩትን
“የጠላት ሰራዊት ወደ ባቢሎን ያልተላኩ”

እስማኤል...ናታንያ...ዮሀናን..ዮናታን..ቃሬያም...ሰራያ...ተንሑሜትም...የዮፌ...ያእዛንያ
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው።

የነጦፋዊውም...የማዕካታዊው
የነጦፋ እና የማዕካታ አካባቢ ህዝቦች

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Jeremiah 40:9

እንዲህ ብሎ ማለ
“ለይሁዳዊ አለቃ ማለ”

እነሆ
ተመልከት ወይም ልብ በል

የበጋ ፍሬ
በበጋ ጊዜ የሚያፈራ ፍሬ

በያዛችኋቸውም
በናንተ ቁጥጥር ስር አርጋችኋል። “በያዛችኋቸውም” የሚለው የወታደሮች ቃል ሲሆን ገዳሊያሰራዊትን እየወሰደ ነበር (ኤርምያስ 40:7) ያሸነፋችሁ ከሆነ ነው ካልሆነ ሙሉ ከተማው ትወሰዳለች

Jeremiah 40:11

የይሁዳን ቅሬታ
የይሁዳ ህዝብ ቅሬታ

እንደ ሾመው... በላያቸው
“እንዳስቀመጠው...እንዲቆጣጠር እንዲመራ”

ሳፋንንም ልጅ የአኪቃምን ልጅ ጎዶልያስን
ኤርምያስ 39:14 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

በላያቸው
በይሁዳ ህዝብ ላይ

ሁሉ ከተሰደዱበት ስፍራ ሁሉ
“ባቢሎናውያን ካሳደዱአቸው ቦታ”

ወይንና የበጋንም ፍሬ እጅግ ብዙ አከማቹ
እጅግ ብዛት ያለቸውን ወይንና የበጋ ፍሬዎችን

የበጋ ፍሬ
በበጋ ጊዜ የሚያፈራ ፍሬ

Jeremiah 40:13

ዮሀናን...ቃሬያም
እነዚህ ስሞች በኤርምያስ 40:8 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ጎዶልያስ
የዚህን ሰው ስም እንዴት እንደተረጎመው በኤርምያስ 39:14 ላይ ተመልከት

የአሞን ልጆች ንጉሥ በኣሊስ ይገድልህ ዘንድ የናታንያን ልጅ እስማኤልን እንደ ሰደደ ታውቃለህን?
ዮሃናን እና የሰራዊት አዛዦች ጎዶልያስን እንዲጠነቀቅ የጠየቁት ጥያቄ ነው። “የአሞን ህዝብ ንጉስ በኦሊስ አንተን ለመግደል የናታንያን ልጅ እስማኤልን እንደላከ ልትረዳ ይገባል።”

በኦሊስ
ይህ የሰው ስም ነው

እስማኤል... ናታንያን
በኤርምያስ 40:8 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

አኪቃም
ይህ ስም በኤርምያስ 26:24 እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት

Jeremiah 40:15

ዮሃናን... ቃሬያም
እነዚህን የሰው ስሞች በኤርምያስ 40:8 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ጎዶልያስ
ይህን ስም በኤርምያስ 39:14 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

እስማኤል... ናታንያን
በኤርምያስ 40:8 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ማንም ሳያውቅ
ማንም እኔ እንዳረኩት አያቅም

ነፍስህን ስለ ምን ይገድላል
ዮሃናን የጎላድያስን አስተሳሰብ ለመቀየር የሞከረበት ጥያቄ ነው። እርሱ እንዲገድልህ ልትፈቅድለት አይገባም

እሱ ከገደለህ እኮ በዙሪያህ ለተሰበሰቡት የአይሁድ መበታተን ምክንያት ይሆናል በይሁዳ ምድር ከምርኮ በቀሩትም ህዝብ ላይ ታላቅ መቅሰፍትን በማምጣት ያጠፋቸዋል
ዮሃናን ጎላድያስ ሊያደር ያቀዳቸውን ነገሮች ካደረገ ምን ሊሆን እንደሚችል ጎላድያስ እንዲያስብ ይናገራል። “ይህን ካደረክ ባንተ የተሰበሰበው ይሁዳ ይበታተናል ቀሪው ይሁዳ ደግሞ ይጠፋል”

አይሁድ
ብዙ የአይሁድ ህዝብን ያመለክታል

በዙሪያ ለተሰበሰቡት
“ወዳንተ ለመጡት” ወይም “እግዚአብሄር ወዳንተ ያመጣቸው”

መበታተን
“ከለዳውይን እንዲበትኑአቸው” ወይም “ወደ ተለያዩ ብዙ ምድር እንዲሄዱ”

በይሁዳ ምድር ከምርኮ በቀሩትም ህዝብ ላይ ታላቅ መቅሰፍትን በማምጣት ያጠፋቸዋል
“ከለዳውያን የቀሩትን ይሁዳን ያጠፋሉ” ወይም “የይሁዳን የቀሩትን ያጠፋል”

በይሁዳ...የቀሩትን
በይሁዳ የቀሩትን ህዝብ። በኤርምያስ 40:11 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

አኪቃም
ይህን ስም እንዴት እንደተረጎመው በኤርምያስ 26:24 ላይ ተመልከት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 41

1 በሰባተኛውም ወር ከመንግሥት ወገንና፣ ከንጉሡ ዋና ዋና አለቆች አንዱ የኤሊሳማ ልጅ የናታንያ ልጅ እስማኤል ከዐሥር ሰዎች ጋር ወደ ምጽጳ ወደ አኪቃም ልጅ ወደ ጎዶልያስ መጣ። በዚያም በምጽጳ በአንድ ላይ እንጀራ በሉ። **2** የናታንያም ልጅ እስማኤል፣ ከእርሱም ጋር የነበሩት ዐሥሩ ሰዎች ተነሥተው የሳፋንን ልጅ የአኪቃምን ልጅ ጎዶልያስን በሰይፍ መቱ። የባቢሎን ንጉሥ በአገሩ ላይ የሾመውን እስማኤል ገደለው። **3** ከዚያም እስማኤል ከጎዶልያስ ጋር በምጽጳ የነበሩትን አይሁድ ሁሉ፣ በዚያም የተገኙትን የከለዳውያንን ሰልፈኞች ሁሉ ገደላቸው። **4** ጎዶልያስን ከገደለ በኋላ ሁለት ቀን ሆነ፣ ነገር ግን ማንም አላወቀም ነበር። **5** ጢማቸውን ላጭተው፣ ልብሳቸውንም ቀድደው፣ ገላቸውንም ነጭተው፣ ወደ እግዚአብሔር ቤት ያቀርቡ ዘንድ የእህል ቍርባንና ዕጣን በእጃቸው እየያዙ፣ ሰማንያ ሰዎች ከሴኬም፣ ከሴሎና፣ ከሰማርያ መጡ። **6** የናታንያም ልጅ እስማኤል ከምጽጳ ወጥቶ እያለቀሰ ሊገናኛቸው ሄደ። ባገኛቸውም ጊዜ፣ "ወደ አኪቃም ልጅ ወደ ጎዶልያስ ኑ!" አላቸው። **7** ወደ ከተማም መካከል በመጡ ጊዜ፣ የናታንያ ልጅ እስማኤል ከእርሱም ጋር የነበሩ ሰዎች አረዷቸውና በጉድጓድ ውስጥ ጣሉአቸው። **8** ነገር ግን በመካከላቸው እስማኤልን፣ "የምንሰጥህ በሜዳ የተሸሸገ ስንዴ፣ ገብስ፣ ዘይትና፣ ማር ስላለን አትግደለን" የሚሉት ዐሥር ሰዎች ነበሩ። እርሱም ከሌሎች ወዳጆቻቸው ጋር አልገደላቸውም። **9** ጉድጓዱ እስማኤል ከጎዶልያስ ጋር የገደላቸውን የሰዎች ሬሳ ሁሉ የጣለበት ጕድጓድ ነበር። ይህ ጥልቅ ጉድጓድ ንጉሡ አሳ የእስራኤልን ንጉሥ ባኦስን ስለ ፈራ የሠራው ጉድጓድ ነበረ። የናታንያም ልጅ እስማኤል የገደላቸውን ሞላበት። **10** ቀጥሎ እስማኤል በምጽጳ የነበረውን የሕዝቡን ቅሬታ ሁሉ፣ የንጉሡን ሴቶች ልጆች፣ የዘበኞቹም አለቃ ናቡዘረዳን ለአኪቃም ልጅ ለጎዶልያስ የሰጠውን በምጽጳ የቀሩትን ሕዝብ ሁሉ ማረካቸው። ስለዚህ የናታንያም ልጅ እስማኤል ማርኮ ወደ አሞን ልጆች ይሄድ ዘንድ ተነሣ። **11** የቃሬያም ልጅ ዮሐናን፣ ከእርሱም ጋር የነበሩት የጭፍራ አለቆች ሁሉ የናታንያ ልጅ እስማኤል ያደረገውን ክፋት ሁሉ ሰሙ። **12** ስለዚህ ሰዎቻቸውን ሁሉ ይዘው ከናታንያ ልጅ ከእስማኤል ጋር ሊዋጉ ሄዱ። በገባዖንም ባለው በታላቁ የውኃ ጕድጓድ አጠገብ አገኙት። **13** ከዚያም ከእስማኤል ጋር የነበሩት ሕዝብ ሁሉ የቃሬያን ልጅ ዮሐናንን፣ ከእርሱም ጋር የነበሩትን የጭፍራ አለቆችን ሁሉ ሲያዩ እጅግ ደስ አላቸው። **14** ስለዚህ እስማኤል ከምጽጳ የማረካቸው ሕዝብ ሁሉ ዞረው ወደ ቃሬያም ልጅ ወደ ዮሐናን ሄዱ። **15** ነገር ግን የናታንያ ልጅ እስማኤል ከስምንት ሰዎች ጋር ከዮሐናን አመለጠ። ወደ አሞንም ሕዝቦች ሄደ። **16** የቃሬያም ልጅ ዮሐናን፣ ከእርሱም ጋር የነበሩት የጭፍራ አለቆች ሁሉ የአኪቃምን ልጅ ጎዶልያስን በምጽጳ ከገደለው በኋላ ከናታንያ ልጅ ከእስማኤል ያስመለሱአቸውን የሕዝቡን ቅሬታ ሁሉ፣ ከገባዖን ያስመለሱአቸውን ሰልፈኞች፣ ሴቶችንም፣ ልጆችንም፣ ጃንደረቦችንም፣ ወሰዱ። **17** ከዚያም ሄደው ለተወሰነ ጊዜ በቤተልሔም አቅራቢያ ባለው በጌሮት ከመዓም ተቀመጡ። ሊሄዱ የነበረው ወደ ግብጽ ነበር። **18** ይህም ከከለዳውያን ፍርሃት የተነሣ ነበር። የባቢሎን ንጉሥ በአገሩ ላይ የሾመውን የአኪቃምን ልጅ ጎዶልያስን እስማኤል ስለ ገደለው ፈሯቸው።

Jeremiah 41:1

በሰባተኛውም ወር
በእብራውያን ቀን አቆጣጠር ሰባተኛው ወር ነው። ይህም እንደ ምዕራባውያን አቆጣጠር የሴፕቴምበር መጨረሻዎቹ ላይ እና ኦክቶበር መጀመሪያዎቹ ላይ ነው።

የኤሊሳማ ልጅ የናታንያ
እነዚህን ስሞች በኤርምያስ 40:8 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

እስማኤል
ይህ የሰው ስም ነው

የሳፋንን ልጅ የአኪቃምን ልጅ ጎዶልያስን
የእነዚህን ሰዎች ስም በኤርምያስ 39:14 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

በአገሩ ላይ የሾመውን
“በአገሩ” የሚለው ህዝቡን ያመለክታል። “በይሁዳ ህዝብ ላይ ሾመው”

እስማኤልም....ገደላቸው
“እስማኤል” የሚለው ቃል ራሱን እና ከእርሱ ጋር የነበሩትን አስር ሰዎችን ያመለክታል። “እስማኤል እና አስር ሰዎች...ገደሉአቸው”

በዚያም የተገኙትን የከለዳውያንን ሰልፈኞች
“በዛም ያሉትን የከለዳውያን ሰራዊቶችን”

Jeremiah 41:4

በሁለተኛው ቀን
“ሁለተኛው” የሚለው ሁለት ቁጥርን ሲያመለክት ሊሆን የሚችለው ትርጉሙ ደግሞ 1) ከቀን በኋላ ወይም 2) ከሁለት ቀናት በኋላ ነው

ሰማንያ ሰዎች
ሰማንያ ሰዎች

ጢማቸውን ላጭተው ልብሳቸውንም ቀድደው ገላቸውንም ነጭተው
ይህ የሚያመለክተው ሰዎቹ ሃዘን ላይ እንደሆኑ ነው።

በእጃቸው
በእጃቸው መያዝ በቁጥጥር ስር ማዋል ወይም መሸከምን ያመለክታል። “በቁጥጥራቸው ስር”

ወደ እግዚአብሄር ቤት ያቀርቡ ዘንድ
እግዚአብሄርን በመቅደሱ ውስጥ ማምለክ

Jeremiah 41:6

ሊገናኛቸው
ሰማንያ ሰዎቹን ሊገናኝ

የናታንያ ልጅ እስማኤል ከእርሱም ጋር የነበሩ ሰዎች ገደሉአቸው፥ በጕድጓድም መካከል ጣሉአቸው
በኤርምያስ 41:8 ላይ እስማኤል እና አብረውት ያሉ ሰዎች ሰማንያ ሰዎችን አልገደሉአቸውም ነበር። እነዚህ ሰማንያ ሰዎችን አብዛኛውን መግደላቸውን መናገር ይቻላል። “የናታንያ ልጅ እስማኤል እና አብረውት የነበሩ ሰዎች አብዛኛዎችቹን ሰማንያ ሰዎችን ገደሉአቸው እናም ጉድጓድ ውስጥም ጣሉአቸው”

Jeremiah 41:8

አስር ሰዎች ተገኙ
ከሰማንያ ሰዎቹ መሃል እንደተገኙ ይናገራል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በሜዳ የተሸሸገ ስንዴና ገብስ ዘይትና ማርም አለንና
ይህ የሚያመለክተው ስንዴና ገብስ ዘይትና ማርም ለእስማኤል እና ከእርሱ ጋር አብረው ለነበሩት ሰዎች እንደሚሰጡ ያሳያል። “በሜዳ የተሸሸገ ስንዴና ገብስ ዘይትና ማርም አለንና እሱን እንሰጣችኋለን”

በሜዳ የተሸሸገ ስንዴና ገብስ ዘይትና ማርም አለንና
ለወደፊት የቀመጠ አስፈላጊ ነገሮች

እስማኤልም ከጎዶልያስ ጋር የገደላቸውን የሰዎች ሬሳ የጣለበትን ጉድጓድ ...የእስራኤልን ንጉሥ ባኦስን
ይህ የኋላ ታሪክ ሲናገር እስማኤል የተጠቀመውን የውሃ ጉድጓድ ያመለክታል። ንጉስ አሳ ንጉስ ባኦስ ሲያጠቁአቸው የራሱ ሰዎች ውሃ እንዲያገኙ ሰዎቹን ያስቆፈራቸው ጉድጓድ ነው።

ንጉስ አሳ...የሰራው ጉድጓድ
“ንጉስ አሳ” የሚለው የሱን ሰዎችን ያመለክተል። “ንጉስ አሳ ሰዎቹን እንዲቆፍሩ አዘዘ”

የእስራኤል ንጉስ ባኦስን
“ንጉስ በኦስ” ራሱን እና ሰራዊቱን ይወክላል። “የእስረኤል ንጉስን ባኦስንነ ሰራዊቱን”

የናታንያም ልጅ እስማኤል...ሞላበት
“እስማኤል” ራሱን እና አብረውት ያሉትን ሰዎችን ያመለክታል። “እስማኤልና አብረውት ያሉት ሰዎች...ሞሉት”

በሞቱት
“የሞቱት” ወይም “እነርሱ በገደሉአቸው”

Jeremiah 41:10

እስማኤል ማርኮ
“እስማኤል” ራሱን እና አብረውት ያሉትን ሰዎችን ያመለክታል። “እስማኤልና አብረውት ያሉት ሰዎች ማርከው”

ናቡዘረዳን
የዚህ ሰው ስም በኤርምያስ 39:9 እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት

ወደ አሞን ልጆች ይሄድ ዘንድ ተነሣ
ወደ አሞናውያን ምድር ተጓዘ

Jeremiah 41:11

ዮሀነን...ቃሬያም
የእነዚህን ሰዎች ስም በኤርምያስ 40:13 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት።

የናታንያ ልጅ እስማኤል...በሰሙ ጊዜ
“እስማኤል” ራሱን እና አብረውት ያሉትን ሰዎችን ያመለክታል። “እስማኤል እና አብረውት የነበሩት ሰዎች...በሰሙ ጊዜ”

Jeremiah 41:13

ከእስማኤል ጋር የነበሩት ህዝብ ሁሉ
“ህዝብ” የሚለው እስማኤል እና አብረውት ያሉት ሰዎች የማነረኩአቸውን ያመለክታል።

እስማኤል...የማረካቸው
“እስማኤል” የሚለው ቃል ራሱን እና አብረውት የነበሩትን ሰዎችን ሁሉ ነው። “እስማኤል እና አብረውት ያሉት ሰዎች የማረኩአቸውን”

Jeremiah 41:15

ወደ አሞን ልጆች ሄደ
“ሄደ” የሚያመለክተው እስማኤልን ሲሆን ይህም ደግሞ ራሱን እና አብረውት ያሉትን ስምንት ሰዎችን ያመለክታል። “ወደ አሞን ልጆች ሄዱ”

ያስመለሱአቸውን
“ያስመለሱአቸውን”

የአኪቃምን ልጅ ጎዶልያስን በምጽጳ ከገደለው በኋላ
ፀሃፊው ታሪኩን ቆም ያደረገው የበፊቶቹን ድርጊቶችን ለማመልከት ሲሆን የድርጊቶቹ አቀማመጥ ለመረዳት እንዲሆን አድርጎ ነው።

ሰልፈኞች
የጦር ሰራዊቱን ያመለክታል

ከገባኦን ያስመለጡአቸውን
“ከገባኦን ያስመለጡአቸውን”

Jeremiah 41:17

ይሄዱ ዘንድ
ዮሀናን አብረውት ያሉት እና ያመለጡት ህዝቦች ሁሉ ሄዱ

በጌሮት ከመዓም
ይህ የቦታ ስም ነው

ከለዳውያንን ፈርተዋልና
ይህ የሚያመለክተው ከለዳውያን እንዳያጠቁአቸው መፍራታቸውን ነው። “ከለዳውያን ያጠቁናል ብለው አስበውዋልና”

በአገሩ ላይ የሾመውን
“አገሩ” የሚለው ቃል ሕዝብን ያመለክታል። “በይሁዳ ህዝብ ላይ የሾመውን”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 42

1 ከዚያም የጭፍራ አለቆች ሁሉ፣ የቃሬያም ልጅ ዮሐናን፣ የሆሻያም ልጅ ያእዛንያ፣ ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ ያሉት ሕዝብ ወደ ነብዩ ኤርምያስ ቀረቡ። **2** እንዲህም አሉት፣ "ልመናችን በፊትህ ይድረስ። እንዳየኸው ከብዙዎቹ መካከል የቀረነው ጥቂቶች ነንና፣ **3** የምንሄድበትን መንገድና፣ የምናደርገውን ነገር እንዲያሳየን ስለ እኛና ስለዚህ ቅሬታ ሕዝብ ወደ አምላክህ እግዚአብሔር ጸልይ" አሉት። **4** ስለዚህ ነቢዩ ኤርምያስ፣ "ሰምቻችኋለሁ። ተመልከቱ፣እንደጠየቃችሁት ወደ አምላካችሁ ወደ እግዚአብሔር እጸልያለሁ። እግዚአብሔርም የሚመልስላችሁን ሁሉ እነግራችኋለሁ። ከእናንተ ምንም አልሸሸግም፤" አላቸው። **5** እነርሱም ለኤርምያስ፣ "አምላክህ እግዚአብሔር ወደ እኛ የላከውን ነገር ሁሉ ባናደርግ፣ እግዚአብሔር በመካከላችን እውነተኛና ታማኝ ምስክር ይሁን። **6** የአምላካችንን የእግዚአብሔርን ቃል በመስማታችን መልካም እንዲሆንልን፣ መልካም ወይም ክፉ ቢሆን፣ አንተን ወደ እርሱ የምንልክህ የአምላካችንን የእግዚአብሔርን ድምፅ እንሰማለን አሉት።" **7** ከዚያም ከዐሥር ቀን በኋላ፣ የእግዚአብሔር ቃል ወደ ኤርምያስ መጣ። **8** ስለዚህ ኤርምያስ የቃሬያንም ልጅ ዮሐናንን ከእርሱም ጋር የነበሩትን የሠራዊቱን አለቆች ሁሉ ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ ሕዝቡንም ሁሉ ጠራ። **9** እንዲህ አላቸው፣ "ጸሎታችሁን በፊቱ አቀርብ ዘንድ ወደ እርሱ የላካችሁኝ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ **10** 'በእናንተ ላይ ያመጣሁባችሁን ጥፋት እመልሳለሁና ተመልሳችሁ በዚህች ምድር ብትኖሩ፣እሠራችኋለሁ እንጂ አላፈርሳችሁም፣ እተክላችኋለሁ እንጂ አልነቅላችሁም። **11** የምትፈሩትን የባቢሎን ንጉሥ አትፍሩ። አድናችሁ ዘንድ፣ ከእጁም አስጥላችሁ ዘንድ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝና አትፍሩ፣ ይላል እግዚአብሔር። **12** ምሕረትን እሰጣችኋለሁና። እርሱ እንዲምራችሁ ወደ ምድራችሁም እንዲመልሳችሁ እኔ እራራላችኋለሁ። **13** እናንተ ግን፣"በዚህች ምድር አንቀመጥም" ብትሉ፣ የእኔን የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ቃል ባትሰሙ፣ **14** እናንተም፣ "አይሆንም! የትኛውንም ጦርነት ወደማናይባት፣ የመለከትም ድምፅ ወደማንሰማባት፣ ወደማንራብባት ወደ ግብጽ ምድር እንሄዳለን። በዚያ እንኖራለን" ብትሉ፣ **15** አሁን የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ፣ እናንተ የይሁዳ ቅሬታ የሆናችሁ። የእስራኤል አምላክ፣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ 'ወደ ግብጽ እንድትገቡ፣ በዚያም እንድትኖሩ በእርግጥ ፊታችሁን ብታቀኑ፣ **16** ያኔ የምትፈሩት ሰይፍ በዚያ በግብጽ ምድር ያገኛችኋል። የምትደነግጡበት ረሃብ በዚያ በግብጽ ይደርስባቸኋል። በዚያም ትሞታላችሁ። **17** ስለዚህ ወደ ግብጽ እንዲገቡ፣ በዚያም እንዲኖሩ ፊታቸውን የሚያቀኑ ሰዎች ሁሉ በሰይፍ፣ በረሃብ፣ ወይም በመቅሠፍት፣ ይሞታሉ። እኔም ከማመጣባቸው ክፉ ነገር ማንም አይተርፍም፣ ማንም አያመልጥም። **18** የእስራኤል አምላክ፣የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፣ እንዲህ ይላልና፦ ቊጣዬና መዓቴ በኢየሩሳሌም በሚኖሩ ላይ እንደ ፈሰሰ፣ እንዲሁ ወደ ግብጽ የምትገቡ ከሆነ መዓቴ ይፈስስባችኋል። እናንተም ለእርግማንና ለመደንገጫያ፣ ለመረገሚያና ለመዋረጂያ ትሆናላችሁ። ደግሞም ይህንን ስፍራ ከእንግዲህ ወዲህ አታዩትም።" **19** ከዚያም ኤርምያስ እንዲህ አለ፣ "እናንተ የይሁዳ ቅሬታዎች፣ እግዚአብሔር፣ ወደ ግብጽ አትሂዱ ብሎ ተናግሯችኋልና ዛሬ ምስክር እንደሆንኩባችሁ በእርግጥ እወቁ። **20** 'ስለ እኛ ወደ አምላካችን ወደ እግዚአብሔር ጸልይ። አምላካችንም እግዚአብሔር የሚናገርህን ሁሉ ንገረን፣ እኛም እንፈጽመዋለን' ብላችሁ ወደ እግዚአብሔር ወደ አምላካችሁ ስትልኩኝ የሕይወት ዋጋ የሚያስከፍላችሁን ነገር አድርጋችኋልና። **21** እኔም ዛሬ ነግሬአችኋለሁ፣ ወደ እናንተም በላከኝ ነገር ሁሉ የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ቃል አልሰማችሁም። **22** ስለዚህ፣ አሁንም ሄዳችሁ እንድትኖሩበት በወደዳችሁበት ስፍራ በሰይፍ፣ በራብ፣ በቸነፈር እንድትሞቱ በእርግጥ እወቁ።"

Jeremiah 42:1

ዮሀናን ቃሬያም
እነዚህን ሰዎች በኤርምያስ 40:13 እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት

ያእዛንያ...ሆሻያም
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው

ሕዝብም ሁሉ ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ
ይህ በህዝቡ ያሉ የተለያዩ ደረጃ ያላቸው ሰዎችን ያመለክታል። “ታናሹም” እና “ታላቁ” የሚለው በጣም አስፈላጊ ሰዎችን እና ተራው ሰውን ያመለክታሉ። “በሁሉም ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎችን በአጠቃላይ” ወይም “በጣም አስፈላጊው ሰው እና ተራው ሰው ሁሉ”

ህዝብ ሁሉ
ይህ ሁሉንም ግለሰብ ላያካትት ይችላል። “ሁሉ” ሲል ብዙ ህዝቦች ለማለት ፈልጎ ነው። “ብዙ ህዝብ”

ልመናችን፣ እባክህ፣ በፊትህ ትድረስ
“እባክህን ልመናችንን ስማን”

Jeremiah 42:4

እነሆ
ተመልከት ወይም ልብ በል

ከእናንተም ምንም አልሸሸግም
“ከእናንተም ምንም አልሸሸግም” የሚለው ሀረግ ሁሉንም ነገር በግልፅ መንገር ማለት ነው። “እግዚአብሄር የነገረኝን ሁሉንም ነገር እነግራችኋለሁ”

አምላክህ እግዚአብሄር
ይህ ቃል ለመግባት መጀመሪያ ነው።

እውነተኛ እና ታማኝ
እነዚህ ሁለት ቃላት አንድ ሃሳብ ይጋራሉ። እንዚህ ቃላት እግዚአብሄር እንደ አውነተኛ ማንም እንደ ማይቃወመው ምስክር አርጎ ይናገራል። “ታማኝነት”

መልካም ወይም ክፉ ቢሆን
ህዝቡ የእግዚአብሄር መልስ ምንም ቢሆን ምን እንደሚታዘዙ አስረግጠው እንደሚናገሩ ያሳያል። “ምንም አይነት መልስ ቢሰጠን”

የአምላካችንን የእግዚአብሄር ቃል እንሰማለን።
“ቃል” የሚለው እግዚአብሄር የሚናገረውን ያመለክታል። “አምላካችን እግዚአብሄር የሚናገረውን” ወይም “አምላካችንን እግዚአብሄር እንታዘዛለን”

Jeremiah 42:7

የእግዚአብሔር ቃል ወደ ኤርምያስ መጣ።
ይህ አረፍተነገር እግዚአብሄር ለኤርምያስ የሰጠው መልእክት እንደሆነ ለማሳየት ነው። እንደዚህ ተመሳሳይ አረፍተነገር በኤርምያስ 1:2 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት። “እግዚአብሄር ለኤርምያስ መልእክትን ሰጠው”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ
ይህ በህዝቡ ያሉ የተለያዩ ደረጃ ያላቸው ሰዎችን ያመለክታል። “ታናሹም” እና “ታላቁ” የሚለው በጣም አስፈላጊ ሰዎችን እና ተራው ሰውን ያመለክታሉ። “በሁሉም ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎችን በአጠቃላይ” ወይም “በጣም አስፈላጊው ሰው እና ተራው ሰው ሁሉ”

ህዝቡንም ሁሉ ጠራ
ይህ ሁሉንም ግለሰብ ላያካትት ይችላል። “ሁሉ” ሲል ብዙ ህዝቦች ለማለት ፈልጎ ነው። “ብዙ ህዝብ”

ጸሎታችሁን በፊቱ አቀርብ ዘንድ
“ጸሎታችሁን ሁሉ ወደሱ አቀርባለሁ” ህዝቡን ለእግዚአብሄር እንዲጠይቁ እንደ ኤርምያስ የህዝቡን ፀሎት ይዞ ወደ እግዚአብሄር እንደሚቀርብ አርጎ መስሎ ይናገራል። “ፀሎታችሁን እነግርላችኋለሁ”

እሰራችኋለሁ እንጂ አላፈርሳችሁም
እግዚአብሄር የእስራኤልን ህዝብ እንደ ሚገነባ እና እንደ ሚፈርስ አድርጎ መስሎ ይናገራል። “አበለፅጋችኋለሁ እንጂ አላጠፋችሁም”

እተክላችኋለሁ እንጂ አልነቅላችሁም
እግዚአብሄር የእስራኤል ህዝብን እንዴት እንደ ሚበለፅጉ እና እነደማይጠፉ በሌላ አነጋገር ይናገራል። እንደ ተክል መስሎ ይናገራል ልክ እንደ ግንብ እንደመሰላቸው።

ስላደረግሁባችሁ ክፉ ነገር ተጸጽቻለሁና
ክፉ ነገር የሚለው አንድ ሰው ሌለ አንድ ሰው ላይ የሚየመጣው ነገር ነው። “የመጣባችሁን ክፉ ነገር እከለክላለሁ”

Jeremiah 42:11

ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ የገለጸበት ምክንያት ቃሉን አስረግጦ ለመናገር ስለፈለገ ነው።፤ ኤርምያስ 1:8 የተተረጎመበትን መንገድ ይመልከቱ። ‹‹እግዚአብሄር የተናገረው ይህንን ነው›› ወይም ‹‹እኔ እግዚአብሄር የተናገርኩት ይህንን ነው››

አድናችሁ ዘንድ ... አስጥላችሁ
“አድናችሁ” እና “አስጥላችሁ” የሚሉት ቃላት አንድ አይነት ሃሳብ ሲኖራቸው እግዚአብሄር የእውነት እንደሚያድን የሚናገር ነው። “ሙሉ በሙሉ እንዲያድናችሁ”

ከእጁም አስጥላችሁ ዘንድ
“እጅ” የሚለው ቃል ሀይል ወይም ስልጣንን ያመለክታል። “ከህይሉ እስጥላችሁ ዘንድ” ወይም “ከእርሱ አስጥላችሁ ዘንድ”

Jeremiah 42:13

የአምላካችሁንም የእግዚአብሔርን ቃል ባትሰሙ
“ቃል” የሚለው ትእዛዙን ያመለክታል። አለመታዘዝ ህዝቡ የእግዚአበሄርን ትእዛዛቱን አለመስማት አንደሆነ ይናገራል። “የእኔ አምላካችሁን እግዚአብሄር ትእዛዝ እነኳን ባታከብሩም”

ሰልፍ ወደማናይባት የመለከትም ድምፅ ወደማንሰማባት
ሁለቱም ቃላት የሚናገሩት ጦርነት ላይ ስለሚታየው እና ስለሚሰማው ነው። “ጦርነትን የማናይበት ወደማያጋጥመን”

ወደማንራብባትም
መራብ የሚለው ድርቅን ለማመልከት ይጠቀማል።

Jeremiah 42:15

አሁን
“አሁን” የሚለው ቃል የአሁኑን ጊዜ ሳይሆን የሚያመለክተው ወደ ትኩረት ወደ ሚሻ ነጥብ እንሚያመራ ለማተኮር ነው።

የእግዚአብሄርን ቃል
የእግዚአብሄርን መልእክት

የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር
ኤርምያስ ማስተዋል ያለብንን መልእክት ሲያስተላልፍ የሚጠቀመው ሀረግ ነው። ኤርምያስ 6:6 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

የምትፈሩት ሰይፍ በዚያ በግብጽ ምድር ያገኛችኋል
“ሰይፍ” የሚለው ጦርነትን ያመለክታል። እስራኤላውያን ግብፅ ቢሄዱም ጦርነት እዛም ተከትሎአቸው እንደሚሄድ እና እንደሚደርስባቸው መስሎ ይናገራል። “የጦርነት መጥፎ ገፅታውን ታዩታላችሁ”

የምትደነግጡበት ራብ በዚያ በግብጽ ይደርስባቸኋል፥
እስራኤላውያን ረሃብ ይመጣባቸዋል ግብፅ ቢሆኑም እንኳን። “በእስራኤል የምትደነግጡበት ረሃብ ግብፅ ብትሄዱ እንኳን በዛ በረሃብ ትሰቃያላችሁ”

በሚያቀኑ ሰዎች ሁሉ
ሰዎች የሚለው ሁሉንም ህዝብ ያመለክታል ምክንያቱም የቤተሰቦቻቸው መሪዎች ናቸውና። “የሚያቀና ማንም ሰው”

ይገቡ ዘንድ በዚያም ይቀመጡ ዘንድ ፊታቸውን
ትቶ መውጣት

ከማመጣባቸው ክፉ ነገር
ክፉ ነገርን ማምጣት እነደ አንድ እቃ ወደ ሰው እንደ ማምጣት መስሎ ይናገራል። “በነሱ ላይ የማመጣውን ክፉ ነገር”

Jeremiah 42:18

የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር
ኤርምያስ ማስተዋል ያለብንን መልእክት ሲያስተላልፍ የሚጠቀመው ሀረግ ነው። ኤርምያስ 6:6 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ቍጣዬና መዓቴ በኢየሩሳሌም በሚኖሩ ላይ እንደ ፈሰሰ
እግዚአብሄር በቁጣ ህዝቡን ሲቀጣ እነደ መአት እና ቁጣው ፈሳሽ ነገር እንደሆኑና በህዝቡ ላይ እንደሚያፈሰው ይናገራል። “እጅግ በጣም ስለተቆጣሁ የኢየሩሳሌምን ህዝብ እቀጣለሁ”

መዓቴና ቁጣዬ
ሁለቱም ቃላት አንድ አይነት ነገር ሲያመለክቱ ምን ያህል እንደተቆጣ አግንኖ ያሳያል። “ከባዱ መዓቴ”

እንዲሁ...መዓቴ ይፈስስባችኋል
እግዚአብሄር በቁጣ ህዝቡን ሲቀጣ እነደ መአት እና ቁጣው ፈሳሽ ነገር እንደሆኑና በህዝቡ ላይ እንደሚያፈሰው ይናገራል። “እጅግ በጣም ስለተቆጣሁ የኢየሩሳሌምን ህዝብ እቀጣለሁ”

እናንተም ለጥላቻና ለመደነቂያ ለመረገሚያና ለመሰደቢያ ትሆናላችሁ
እነዚህ ሁሉ የሚናገሩት አንድ አይነት ሃሳብ ሲሆን ሌሎች ከተማዎች የይሁዳን ህዝብ እግዚአብሄር ከቀጣቸው በኋላ እንዴት እንደ ሚንቁአት ይናገራል። “በናተ ላይ የደረሰውን ክፉ ነገር ሲያዩ ህዝብ ሁሉ ይደነቃል አነሱም ይረግሟቹአል ደግሞም መሰደቢያ ትሆናላችሁ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንዳስጠነቀቅኋችሁ በእርግጥ እወቁ
ይህ አረፍተ ነገር የሚያመለክተው እያስጠነቀቃቸው መሆኑን ነው። “አስጠንቅቄአችኋለሁ”

Jeremiah 42:20

እኛም እናደርገዋለን
“እኛ እናደርገዋለን”

አልሰማችሁም
ልብ ብላችሁ አልሰማችሁም

የአምላካችሁን የእግዚአብሄርን ቃል
“ቃል” የሚለው ትእዛዙን ያመለክታል። “አምላካችሁ እግዚአብሄርን ያዘዘውን ትእዛዝ”

አሁን
“አሁን” የሚለው ቃል የአሁኑን ጊዜ ሳይሆን የሚያመለክተው ወደ ትኩረት ወደ ሚሻ ነጥብ እንሚያመራ ለማተኮር ነው።

በሰይፍና በራብ እንድትሞቱ
“ሰይፍ” የሚለው ጦርነትን ያመለክታል። “በጦርነት ትሞታላችሁ”

ሄዳችሁ እንድትቀመጡ በወደዳችሁበት ስፍራ
የወደዱት ስፍራ ግብፅ ነው። “በግብፅ ሰላም ነው ብላችሁ የምታስቡት ምድር እንኳን”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 43

1 ኤርምያስ አምላካቸው እግዚአብሔር ለእነርሱ የላከውን ይህንን የአምላካቸውን የእግዚአብሔርን ቃል ሁሉ፣ለሕዝቡ ሁሉ ተናግሮ ጨረሰ። **2** የሆሻያ ልጅ ዓዛርያስ፣ የቃሬያም ልጅ ዮሐናን፣ ትዕቢተኞችም ሰዎች ሁሉ ኤርምያስን፣ "ሐሰትን እየተናገርክ ነህ። አምላካችን እግዚአብሔር፣ 'በዚያ ትቀመጡ ዘንድ ወደ ግብጽ አትግቡ ብሎ አልላከህም፤' **3** ነገር ግን ከለዳውያን እንዲገድሉን ወደ ባቢሎንም እንዲማርኩን በእጃቸው አሳልፈህ ትሰጠን ዘንድ የኔርያ ልጅ ባሮክ በላያችን ላይ አነሣሥቶሃል" አሉት። **4** ስለዚህ የቃሬያ ልጅ ዮሐናን፣ የጦር ሠራዊቱ አለቆች ሁሉ፣ ሕዝቡም ሁሉ በይሁዳ ምድር ይኖሩ ዘንድ የእግዚአብሔርን ቃል አልሰሙም። **5** የቃሬያም ልጅ ዮሐናን የጭፍራ አለቆችም ሁሉ በይሁዳ ምድር ለመኖር ከተሰደዱባቸው ከአሕዛብ ሁሉ የተመለሱትን የይሁዳን ቅሬታ ሁሉ ወሰዱ። **6** እነርሱም ወንዶችንና ሴቶችን ልጆችን፣ የንጉሡንም ሴቶች ልጆች፣ የዘበኞቹንም አለቃ ናቡዘረዳን፣ ከሳፋን ልጅ፣ ከአኪቃም ልጅ ከጎዶልያስ ጋር የተዋቸውን ሰዎች ሁሉ፣ ነቢዩንም ኤርምያስን የኔርያንም ልጅ ባሮክን ወሰዱ። **7** የእግዚአብሔርንም ቃል ስላልሰሙ ወደ ግብጽ ምድር ሄዱ፣ እስከ ጣፍናስ ድረስ መጡ። **8** ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል በጣፍናስ ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ፣ **9** "ታላላቆችን ድንጋዮች በእጅህ ውሰድ፣ የይሁዳም ሰዎች እያዩ በጣፍናስ ባለው በፈርዖን የጡብ ቤት ደጅ መግቢያ ሸሸጋቸው።" **10** ከዚያም እንዲህ በላቸው፣ "የእስራኤል አምላክ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ 'ተመልከቱ፣ የባቢሎንን ንጉሥ ናቡከደነፆርን አገልጋዬ ለማድረግ መልእክተኛ እልክበታለሁ። ዙፋኑንም አንተ፣ ኤርምያስ በሸሸግሃቸው በእነዚህ ድንጋዮች ላይ አኖራለሁ። ናቡከደነፆር ማለፊያ ድንኳኑን በላያቸው ይዘረጋል። **11** መጥቶም የግብጽን ምድር ያጠቃል። ለሞት የተመደበውን ለሞት ይሰጣል። ለምርኮም የተመደበው ለምርኮ ይወሰዳል። ለሰይፍ የተመደበው ለሰይፍ ይሰጣል። **12** ከዚያም፣ በግብጽ አማልክት ቤቶች ላይ እሳትን አነድዳለሁ። ናቡከደነፆር ያቃጥላቸዋል ወይም ይማርካቸዋል። እረኞች ከደበሏቸው ተባይን እንደሚያራግፉ፣ እንዲሁ የግብጽን አገር ያጸዳል። ከዚያም ሰፍራ በድል ይወጣል። **13** በግብጽም ምድር ያለውን የሄልዮቱን ከተማ ሐውልቶች ይሰብራል። የግብጽንም አማልክት ቤቶች በእሳት ያቃጥላል።"

Jeremiah 43:1

በፈጸመ ጊዜ
ይህ ሃረግ የአንድን ታሪክ ጅማሬን ያመለክታል።

አዛርያስ
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች 1) ይህ የኤርምያስ ሌላኛው ስሙ ነው ኤርምያስ 42፡1 ወይም 2) የህ የዮሃናን ሌላ ልጁ ነው።

ሆሻያ
በኤርምያስ 42፡1 ላይ የዚህ ሰው ስም እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት

የቃሬያም... ዮሀናን
በኤርምያስ 40፡13 ላይ የነዚህ የሰዎች ስም እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።

አነሳስቶአል
ሰው ላይ መጥፎ ነገርን ለማድረግ ማነሳሳት

ከለዳውያን...በእጃቸው አሳልፍ ትሰጠን ዘንድ
“እጅ” የሚለው ቃል ሃይልን ወይም ጉልበትን ያመለክታል። “ለከለዳውያን አሳልፎ ትሰጠን ዘንድ”

እንዲገድሉን ወደ ባቢሎንም እንዲማርኩን
“እንዲገድሉን” መግደልን ያመለክታል። “ከለዳውያን እንዲገድሉን ወይም ደግሞ በባቢሎን እንድንማረክ”

Jeremiah 43:4

ሁሉ ህዝቡም
ይህ ሁሉንም ግለሰብ ላያካትት ይችላል። “ሁሉ” ሲል ብዙ ህዝቦች ለማለት ፈልጎ ነው። “ብዙ ህዝብ”

የእግዚአብሔርን ቃል አልሰሙም
“ቃል” የሚለው የእግዚአብሄርን ትዕዛዛትን ነው። “አልሰሙም” የሚለው ቃል አለማክበርን ያመለክታል። “የእግዚአብሄርን ትእዛዛት አላከበሩም”

በአህዛብ መካከል ተበታትነው ከቆዩ
“እግዚአብሄር በታተናቸው”

ናቡዘረዳን
የዚህን ሰው ስም እንዴት እንደተረጎመው በኤርምያስ 39፡9 ተመልከት

ጎዶሊያስ...አኪቃም...ሳፋን
የነዚህን ሰዎች ስም እንዴት እንደተረጎመው በኤርምያስ 39፡14 ተመልከት

ጣፍናስ
የዚህን የከተማ ስም በኤርምያስ 2፡16 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

Jeremiah 43:8

በጣፍናስም የእግዚአብሔር ቃል ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ...ውሰድ
“የእግዚአብሄር ቃል ወደ” የሚለው ቃል ልዩ የሆነ መልእክት ለመናገር ሲፈልግ የሚጠቀመው ነው። ተመሳሳይ አረፍተነገር በኤርምያስ 1፡4 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት። “እግዚአብሄር ለኤርምያስ እንዲህ ሲል ተናገረ “ውሰድ””

የይሁዳም ሰዎች እያዩ
“የይሁዳም ሰዎች እየተመለከቱ”

ጭቃ
ድንጋይን ለማጣበቅ የሚጠቀሙበት ነው

በፈርዖን ቤት ደጅ
የፈርዖን የንጉሱ ቤት

የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር
ኤርምያስ ማስተዋል ያለብንን መልእክት ሲያስተላልፍ የሚጠቀመው ሀረግ ነው። ኤርምያስ 6፡6 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ባሪያዬን የባቢሎንን ንጉሥ ናቡከደነፆር አመጣለሁ፥ ዙፋኑንም እኔ በሸሸግኋቸው በእነዚህ ድንጋዮች ላይ አኖራለሁ እርሱም ማለፊያውን ድንኳኑን በላያቸው ይዘረጋል
“ዙፋኑን” የሚለው የንግስናው ስልጣንን ያመለክታል። “በግብፅ ህዝብ ላይ ንጉስ እንዲሆን አደርጋለሁ። ዙፋኑን እና ድንኳኑን እናንተ በቀበራችሁት ድንጋይ ላይ ይሆናል።”

ዳስ
ትልቅ ድንኳን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Jeremiah 43:11

አጠቃላይ ሀሳብ
እግዚአብሄር መልእክቱን መናገሩን ቀጠለ

መጥቶም
ይህ የሚያመለክተው የናቡከደነፆር ሙሉ ሰራዊትን ነው። “የናቡከደነፆር ሰራዊት ይመጣል”

ለሞትም የሚሆነውን ለሞት
“ይሞታል ብዬ የወሰንኩት ሁሉ ይሞታል”

ለምርኮ የሚሆነውን ለምርኮ
“ይማረካል ብዬ የወሰንኩት ሁሉ ባቢሎናውያን ይማረካል”

ለሰይፍም የሚሆነውን ለሰይፍ አሳልፎ ይሰጣል
“ሰይፍ” ጦርነትን ያመለክታል። “በጦርነት ይሞታል ብዬ የወሰንኩ በጦርነት ይሞታል”

እሳትን ያነዳል
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሄር እየተናገረ እንደሆነ ነው። እግዚአብሄር የባቢሎን ሰራዊት ልኮ እሳት እንደሚያነደዱ ይናገራል። “የባቢሎን ሰራዊት እሳት እንዲያነዱ አደርጋለሁ”

ያቃጥላቸውማል ይማርካቸውማል
የግብፅ ጣኦቶችን ያቃጥላሉ ወይም ይወስዱአቸዋል።

እረኛም ደበሎውን እንደሚደርብ እንዲሁ የግብጽን አገር ይደርባል
በግብፅ ያለውን ማጥፋት እና መውሰድ እነደ እረኛ ደበሎውን እነደሚደርበ መስሎ ይናገራል። “እርሱ ግብፅ ያላትን ነገር ሁሉ ይወስዳል ወይም ያጠፋዋል ልክ አንደ እረኛ ደበሎውን እንደሚደርብ”

ሄልዮቱን
ይህ የከተማ ስም ነው። ይህ ስም “የፀሀይ ከተማ” ማለት ነው። በዚህች ከተማ የፀሃይ አምላክ ጣኦት የሚያመልኩበት ቤተ መቅደስ ነበር።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 44

1 በግብጽ ምድር በሚግዶልና በጣፍናስ በሜምፎስም በጳትሮስም አገር ስለ ተቀመጡ አይሁድ ሁሉ ወደ ኤርምያስ የመጣው ቃል ይህ ነው። 2 "የእስራኤል አምላክ፣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ከተሞች ሁሉ ያመጣሁትን ክፉ ነገር ሁሉ እናንተ ራሳችሁ አይታችኋል። ተመልከቱ፣ ዛሬ ጠፍተዋል። የሚኖርባቸው የለም። 3 ይህም የሆነው ለሌሎች አማልክት በማጠንና በማምለክ ያስቀይሙኝ ዘንድ ስላደረጉት ክፋት ነው። እነዚህም አማልክት እነርሱ ራሳቸው፣ አንተም ራስህ፣ እንዲሁም አባቶቻቸው የማያውቋቸው ናቸው። 4 ስለዚህ በተደጋጋሚ ባርያዎቼን ነብያትን ሁሉ ሰደድሁባችሁ። 'እንደነዚህ ያሉ የጠላኋቸውን ርኩስ ነገሮች ማድረጋችሁን አቁሙ' ልላቸው ላክኋቸው። 5 ነገር ግን አልሰሙም። ከክፋታቸው ተመልሰው ለሌሎች አማልክት እንዳያጥኑ አትኩሮታቸውን ለመስጠት አልፈለጉም። 6 ስለዚህ መዓቴና ቊጣዬ በይሁዳ ከተሞችና በኢየሩሳሌም ጎዳናዎች ላይ ፈሰሱ፣ ደግሞም እንደ እሳት ተቀጣጠሉ። ዛሬም እንደ ሆነው ፈረሱ፣ ባድማም ሆኑ።" 7 አሁንም ቢሆን፣ የእስራኤል አምላክ የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "ወንድንና ሴትን፣ ብላቴናንና ሕፃንን ከይሁዳ እንድታጠፉ ይህን ታላቅ ክፋት በራሳችሁ ላይ ለምን ታደርጋላችሁ? ከመካከላችሁ የአንዳችሁም ቅሬታ አይተርፍም። 8 ሰውነታችሁንም ታጠፉ ዘንድ፣ በምድርም አሕዛብ ሁሉ መካከል መረገሚያና መሰደቢያ ትሆኑ ዘንድ፣ ለመቀመጥ በገባችሁባት በግብጽ ምድር ለሌሎች አማልክት በማጠናችሁ በእጃችሁ ሥራ ለምን ታስቈጡኛላችሁ? 9 በይሁዳ ምድርና በኢየሩሳሌም አደባባይ ያደረጉትን የአባቶቻችሁን ክፋት፣ የይሁዳንም ነገሥታት ክፋት፣ የሚስቶቻቸውንም ክፋት፣ የእናንተንም ክፋት፣ የሚስቶቻችሁንም ክፋት ረስታችሁታልን? 10 እስከ ዛሬ ድረስ ትሑታን አልሆኑም። በእነርሱና በአባቶቻቸውም ፊት ያኖርሁትን ሕጌን ወይም ሥርዓቴን አላከበሩም፣ አልሄዱበትም።" 11 ስለዚህም የእስራኤል አምላክ፣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፣ እንዲህ ይላል፦ "ተመልከቱ፣ በእናንተ ላይ ጥፋትን ለማድረግ እና ይሁዳን ሁሉ ላጠፋ ፊቴን በላያችሁ ላይ አደርጋለሁ። 12 ወደ ግብጽ ሄደው በዚያ እንዲኖሩ ፊታቸውን ያቀኑትን የይሁዳን ቅሬታ እወስዳለሁና። ይህን የማደርገው ሁሉም በግብጽ ምድር እንዲጠፉ ነው። እነርሱ በሰይፍና በራብ ይጠፋሉ። ከታናሹም ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ በሰይፍና በራብ ይሞታሉ፤ ለጥላቻና ለመደነቂያ፣ ለመረገሚያና ለመሰደቢያ ይሆናሉ። 13 ኢየሩሳሌምን በሰይፍ፣ በረሃብ እና በመቅሠፍት እንደ ቀጣሁ፣ እንዲሁ በግብጽ ምድር የሚኖሩትን እቀጣለሁ። 14 በዚያ ለመኖር ወደ ግብጽ ምድር ከሄዱ እንኳን ወደ ይሁዳ አገር ተመልሰው በዚያ ይኖሩ ዘንድ ከሚወድዱ ከይሁዳ ቅሬታ ወገን የሚያመልጥና የሚቀር፣ ወደዚያም የሚመለስ የለም። ከዚህ ከሚያመልጥ በቀር ማንም አይመለስም።" 15 ከዚያም ሚስቶቻቸው ለሌሎች አማልክት ማጠናቸውን ያወቁ ሰዎች ሁሉ፣ በዚያም የቆሙ ሴቶች ሁሉ፣ በግብጽ ምድር በጳጥሮስ የተቀመጡ ሕዝብ ሁሉ፣ ታላቅ ጉባኤ ሆነው እንዲህ ሲሉ ለኤርምያስ መለሱለት። 16 እነርሱም እንዲህ አሉ፣ "በእግዚአብሔር ስም የነገርኸንን ቃል አንሰማህም። 17 እኛና አባቶቻችን፣ ነገሥታቶቻችን፣ አለቆቻችንም በይሁዳ ከተሞች በኢየሩሳሌም አደባባይ እናደርገው እንደ ነበረ፣ ለሰማይ ንግሥት እናጥን ዘንድ የመጠጥንም ቊርባን እንድናፈስስላት ከአፋችን የወጣውን ቃል ሁሉ በእርግጥ እናደርጋለን። ያን ጊዜ እንጀራ እንጠግባለን፣ ደግሞም የትኛውም ጥፋት ሳይደርስብን እንበለጽጋለን። 18 ለሰማይ ንግሥት ማጠንን ለእርስዋም የመጠጥን ቊርባን ማፍሰስን ከተውን ወዲህ ግን፣በድህነት ተሰቃይተናል፣ ደግሞም በሰይፍና በረሃብ አልቀናል።" 19 ሴቶቹም እንዲህ አሉ፣ "እኛስ ለሰማይ ንግሥት ባጠንንላት፣ የመጠጥንም ቊርባን ባፈሰስንላት ጊዜ፣ ባሎቻችን ሳያውቁ ምስልዋን ለማበጀት እንጐቻ አድርገንላት ኖሮአልን? የመጠጥንም ቊርባን አፍስሰንላት ኖሮአልን?" 20 ኤርምያስም ይህን ቃል ለመለሱለት ሕዝብ ሁሉ፣ ለወንዶቹና ለሴቶቹ፣ ለሕዝቡም ሁሉ፣ መለሰላቸው እንዲህም አለ፣ 21 "እናንተና አባቶቻችሁ፣ ነገሥታቶቻችሁና አለቆቻችሁም፣ የምድርም ሕዝብ በይሁዳ ከተሞችና በኢየሩሳሌም አደባባይ ያጠናችሁትን ዕጣን እግዚአብሔር ያሰበው በልቡም ያኖረው አይደለምን? 22 ከክፉ ልምምዳችሁ የተነሣ፣ ከእንግዲህ ወዲህ የሥራችሁን ክፋትና ያደረጋችሁትን ርኵሰት እግዚአብሔር ይታገሥ ዘንድ አልቻለም። ስለዚህ ምድራችሁ ባድማ፣ መደነቂያ፣ መረገሚያም ሆናለች ዛሬም እንደሆነው የሚኖርባት የለም። 23 እጣን ስላጠናችሁና በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ስለሠራችሁ፣ ድምፁንም ስላልሰማችሁ፣ በሕጉ፣ በሥርዓቱና በምስክሩም ስላልሄዳችሁ፣ ዛሬ እንደሆነው ይህች ክፉ ነገር አግኝታችኋለች።" 24 ከዚያም ኤርምያስ ለሕዝቡ ሁሉ፣ ለሴቶቹም ሁሉ እንዲህ አለ፣ "በግብጽ ምድር የምትኖሩ ይሁዳ ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ። 25 የእስራኤል አምላክ፣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ 'እናንተና ሚስቶቻችሁ በአፋችሁ፣ "ለሰማይ ንግሥት እንድናጥን፣ የመጠጥንም ቊርባን እንድናፈስስላት የተሳልነውን ስእለታችንን በእርግጥ እንፈጽማለን።" ብላችሁ በእጃችሁ አደረጋችሁት፤ እንግዲህ ስእለታችሁን አጽኑ፣ ፈጽሙትም።' 26 ስለዚህ፣ እናንተ በግብጽ ምድር የምትኖሩ ይሁዳ ሁሉ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ፣ 'ተመልከቱ፣ በግብጽ ምድር ሁሉ በሚኖር በይሁዳ ሰው ሁሉ አፍ ስሜ ከእንግዲህ ወዲህ፣ "ሕያው እግዚአብሔርን!" ተብሎ እንዳይጠራ በታላቅ ስሜ ምያለሁ፤" ይላል እግዚአብሔር። 27 ተመልከቱ፣ ለመልካም ሳይሆን ለጥፋት እተጋባቸዋለሁ። በግብጽ ምድር ያሉት የይሁዳ ሰዎች ሁሉ እስኪጠፉ ድረስ በሰይፍና በራብ ያልቃሉ። 28 ከዚያም ከሰይፍ የሚያመልጡ ጥቂት ሰዎች ብቻ ሆነው ከግብጽ ምድር ወደ ይሁዳ ምድር ይመለሳሉ። ሊቀመጡም ወደ ግብጽ ምድር የገቡት የይሁዳ ቅሬታ ሁሉ ከእኔ ወይም ከእነርሱ የማናችን ቃል እንዲጸና ያውቃሉ። 29 ቃሌም በላያችሁ ለክፋት እንዲጸና ታውቁ ዘንድ በዚህች ስፍራ እንድቀጣችሁ ምልክታችሁ ይህ ነው፣' ይላል እግዚአብሔር። 30 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ 'ተመልከቱ፣ የይሁዳን ንጉሥ ሴዴቅያስን ጠላቱ ለሆነው፣ ነፍሱንም ለሚፈልገው ለባቢሎን ንጉሥ ለናቡከደነፆር እጅ አሳልፌ እሰጣለሁ። ሁኔታው የግብጹን ንጉሥ ፈርዖን ሖፍራንን ለጠላቶቹ ነፍሱንም ለሚፈልጉ እጅ አሳልፌ እንደሰጠሁት ይሆናል።"

Jeremiah 44:1

ወደኤርምያስ የመጣ ቃል ይህ ነው
ይህ የሚያመለክተው ከእግዚአብሄር ለኤርምያስ የተሰጠው ቃል ነው። ይህ ከእግዚአብሄር የተላከ ቁልፍ የሆነ መልእክትን ለማስተላለፍ ይጠቀማል። ኤርምያስ 7:1 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት። “ይህ መልእክት እግዚአብሄር ለኤርምያስ የተናገረው ነው”

ሚግዶል
ይህ የከተማ ስም ነው።

በጣፍናስ በሜምፎስም
ኤርምያስ 2:16 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

በግብፅ ምድር
ይህ የግብፅን ደቡብ ክፍል ያመለክታል። አልፎ አልፎ “ጳትሮስ” ተብሎ ይጠራል

የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር
ኤርምያስ ማስተዋል ያለብንን መልእክት ሲያስተላልፍ የሚጠቀመው ሀረግ ነው። ኤርምያስ 6:6 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ሁሉ አይታችኋል
ይህ የሚያመለክተው በግብፅ ምድር የሚኖሩ የይሁዳን ህዝብን ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በይሁዳ ከተሞች ሁሉ ያመጣሁትን ክፉ ነገር
ክፉ ነገርን ልክ እንደ የሆነ ነገር ላይ እንደሚቀመጥ እቃ መስሎ ይናገራል። “በኢየሩሳሌም እና በይሁዳ ከተማ ያመጣሁትን ክፉ ነገር”

እነሆ
ተመልከት ወይም ልብ በል

ያስቆጡኝ
የኢየሩሳሌም ህዝብ እና የይሁዳ ከተማ አስቆጥተውኛል

Jeremiah 44:4

ወደ እናንተ ከመላክ አልተቆጠብኩም
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሄርን ነው።

ከክፋታቸውም ተመልሰው ለሌሎች አማልክት እንዳያጥኑ ጆሮአቸውን አላዘነበሉም
አንድን ነገር ማድረግ ማቆም እንደ ከአንድ ቦታ እንደዞረ መስሎ ይናገራል።

መዓቴና ቁጣዬ ፈሰሱ
ህዝቡን መቅጣት እና በህዝቡ ላይ መቆጣት እንደ መዓትና ቁጣው ፈሰሽ እንደሆኑ እና እንደሚፈሱ መስሎ ይናገራል። “እጅግ በጣም ተቆጣሁ እናም ቀጣኋቸው”

መዓቴና ቁጣዬ
ሁለቱም ቃላት አንድ አይነት ነገር ሲያመለክቱ ምን ያህል እንደተቆጣ አግንኖ ያሳያል። “ከባዱ መዓቴ”

ነደዱ
እግዚአብሄር በይሁዳ ህዝብ ላይ መቆጣትን እንደ ቁጣው እና መዓቱ እንደ እሳት መስሎ ይናገራል። “መዓቴ እና ቁጣዬ እንደ እሳት ነው” ወይም “የኔ ቅጣት እንደ እሳት ነበር”

እንደ ሆነው ፈረሱ ባድማም ሆኑ
እነዚህ አንድ አይነትን ሲመለክቱ በአንድ ላይ የኢየሩሳሌምንና የይሁዳን መጥፋት አጠንክሮ ይናገራል። “በአጠቃላይ ይፈራርሳሉ”

ዛሬም
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብ...ሄር አሁን ላይ ይህን መልዕክት እየተናገረ ያለበትን ጊዜ ነው።

Jeremiah 44:7

ለምን ታደርጉታላችሁ...በራሳችሁለምን ታደርጋላችሁ...ህፃንን
እግዚአብሄር እነዚህን ጥያቄዎች ህዝቡን ከሚሰሩት ስራ እንደሚቀጣቸው ለመገሰፅ ይጠቀመዋል። “እያረጋችሁ ነው...በራሳችሁ ታደርጋላችሁ...እና ህፃንን”

ታላቅ ክፋት በራሳችሁ ላይ ለምን ታደርጋላችሁ?
“ክፋት” የሚለው ቃል ክፉ ነገርን ያመለክታል። “ለምንድን ነው ራሳችሁን የሚጎዳ ነገር የምታደርጉት” ወይም “በናንተ ላይ እየደረሰ ያለው ክፉ ነገር እናንተ በምትሰሩት ክፉ ነገሮች ነው።”

ከይሁዳ ወገን ቅሬታ እንዳይቀርላችሁ... ህፃንን
ከይሁዳ ህዝብ መለየት እንደ ህዝብ ከይሁዳ እንደሚቆረጥ ልክ አንድ ሰው ከወይን ግንድ ቅርንጫፉን እንደሚቆርጠው አድርጎ በመመሰል ይናገራል። “ለምን ከይሁዳ ህዝብ እንድለያችሁ ታደርጉኛላችሁ...ህፃንን”

አማልክት በማጠናችሁ በእጃችሁ ሥራ ለምን ታስቈጡኛላችሁ?
“እጃችሁ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሙሉ ሰውን ነው። “በሰራችሁት ስራ እጅግ በጣም ተቆጥቻለሁ”

ሰውነታችሁንም ታጠፉ ዘንድ
“አራሳችሁን ታጠፋላችሁ” ወይም “እኔ እንዳጠፋችሁ ታደርጉኛላችሁ”

በምድርም አሕዛብ ሁሉ መካከል መረገሚያና መሰደቢያ ትሆኑ ዘንድ
“በምድር አህዛብ” የሚለው ህዝብን ያመለክታል። “በምድር ያሉ ህዝቦች ሁሉ ይረግሙአችኋል ይተሉአችኋልም።”

Jeremiah 44:9

የአባቶቻችሁን ክፋት፥ የይሁዳንም ነገሥታት ክፋት፥ የሚስቶቻቸውንም ክፋት፥ የእናንተንም ክፋት፥ የሚስቶቻችሁንም ክፋት ረስታችሁታልን?
እግዚአብሄር ህዝቡን አባቶቻቸው ስላደረጉት ክፋት ባለማሰባቸው ይገስፃቸዋል እና እንዴት እግዚአብሄር እንደ ሚቀጣቸው ያሳያል። “አባቶቻችሁ፣ የይሁዳ ነገስታት እና ሚስቶቻቸው ባደረጉት ክፋት የደረሰባቸውን ነገር አስቡ።”

በውኑ በይሁዳ ምድርና በኢየሩሳሌም አደባባይ ያደረጉትን...የእናንተንም ክፋት፥ የሚስቶቻችሁንም ክፋት ረስታችሁታልን?
እግዚአብሄር ህዝቡን የራሳቸውን የክፋት ድርጊታቸውን አለማሰባቸው እና እግዚአብሄር እንዴት እንደቀጣቸው ይገስፃል። “እናንተ እና ሚስቶቻችሁ በይሁዳ ምድር እና በኢየሩሳሌም አደባባይ ያደረጋችሁትን ክፉ ነገር ስታደርጉ የደረሰባችሁን ነገሮች አስቡብት”

የኢየሩሳሌም አደባባይ
ኢየሩሳሌም የሚለው የሚያመለክተው የከተማዋ ክፍል ህዝቡ ሚረማመድበት ቦታ ነው። ይህ ማለትም ህዝቡ ክፉን ነገር ብዙሰው ባለበት ቦታ አድርገዋል ማለት ነው። “ኢየሩሳሌም” ወይም “በኢየሩሳሌም ብዙሰው የሚበዛበት”

እስከ ዛሬ ድረስ አልተዋረዱም
“የይሁዳ ህዝብ እስከ ዛሬ ድረስ አልተዋረዱም”። እግዚአብሄር ለይሁዳ ህዝብ እየተናገረ ነው። “እናነተ እስከ ዛሬ ድረስ አልተዋረዳችሁም”

አልሄዱም
ስርአቱን እና ህጉን መከተል ልክ እንደ ህጉ እና ስርአቱ ላይ እንደሚራመድ መስሎ ይናገራል። “አልተከተሉትም” ወይም “አላከበሩትም”

የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር
ኤርምያስ ማስተዋል ያለብንን መልእክት ሲያስተላልፍ የሚጠቀመው ሀረግ ነው። ኤርምያስ 6:6 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ፊቴን ለክፋት በላያችሁ አደርጋለሁ
ይህ የሚያሳየው ቆርጦ እንደወሰነ ነው። ኤርምያስ 21:10 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት። “እናንተ ላይ ተነስቻለሁ”

ፊቴን...በላያችሁ አደርጋለሁ
በቁጣ እመለከታችሁአለሁ

አጠፋ ዘንድ
“እናንተ ላይ ጥፋትን አመጣባችኋለው”

ይወድቃሉ በሰይፍና በራብ ይጠፋሉ
“ይጠፋሉ” ይሞታሉ ማለት ነው። “ሰይፍ” የጦር መሳሪያ የያዙ ሰራዊቶችን ያመለክታል። “የጠላት ሰራዊት የተወሰኑትን ይገድላሉ የተቀሩት በረሃብ ይሞታሉ”

ከታናሹም ጀምሮ እሰከ ታላቁ ድረስ
ይህ በህዝቡ ያሉ የተለያዩ ደረጃ ያላቸው ሰዎችን ያመለክታል። “ታናሹም” እና “ታላቁ” የሚለው በጣም አስፈላጊ ሰዎችን እና ተራው ሰውን ያመለክታሉ። “በሁሉም ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎችን በአጠቃላይ” ወይም “በጣም አስፈላጊው ሰው እና ተራው ሰው ሁሉ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለጥላቻና ለመደነቂያ ለመረገሚያና ለመሰደቢያ ይሆናሉ
“በይሁዳ ህዝብ ላይ የሚደርሰውን ሲሰሙ ህዝቡ ይፈራሉ ይንቁአቸዋል ደግሞም ይረግሙአቸዋል።”

Jeremiah 44:11

ኢየሩሳሌምን እንደቀጣሁ
“ኢየሩሳሌም” ህዝቡን ያመለክታል። “የኢየሩሳሌም ህዝብን እቀጣለሁ”

በሰይፍና በራብ በቸነፈርም
“ሰይፍ” የጦር መሳሪያ የያዙ ሰራዊቶችን ያመለክታል። “አንዳንዱን በጠላት ሰራዊት ይሞታሉ፣ አንዳንዱ በረሃብ ይሞታሉ አንዳንዶቹ በቸነፈር ይሞታሉ”

Jeremiah 44:13

ኢየሩሳሌምን እንደቀጣሁ
“ኢየሩሳሌም” ህዝቡን ያመለክታል። “የኢየሩሳሌም ህዝብን እቀጣለሁ”

በሰይፍና በራብ በቸነፈርም
“ሰይፍ” የጦር መሳሪያ የያዙ ሰራዊቶችን ያመለክታል። “አንዳንዱን በጠላት ሰራዊት ይሞታሉ፣ አንዳንዱ በረሃብ ይሞታሉ አንዳንዶቹ በቸነፈር ይሞታሉ”

Jeremiah 44:15

ታላቅ ጉባኤ
ትልቅ የህዝብ ቁጥር

በሰሜን ግብፅ
ይህ ከግብፅ በስተሰሜን የሚገኝ ክልል ነው

በደቡብ ግብፅ
ከግብፅ በደቡብ የሚገኝ ክልል ሲሆን ጳትሮስ ተብሎ ይጠራል።

አንተ በእግዚአብሔር ስም የነገሮኽንን ቃል አንሰማህም።
“በእግዚአብሄር ስም” በእግዚአብሄር ስልጣን ወይም የእግዚአብሄር ተወካይ ማለት ነው። “እግዚአብሀሄር ለኛ እንድትነግር የሰጠህን ትዕዛዝ አንከተልም አንሰማህም”

ለሰማይ ንግስት
ይህ የይሁዳ ህዝብ የሚያመልኩት የጣኦት ስያሜ ነው። ይህ ጣኦት “አሄራ” በመባል ይጠራል።

የኢየሩሳሌም አደባባይ
ኢየሩሳሌም የሚለው የሚያመለክተው የከተማዋ ክፍል ህዝቡ ሚረማመድበት ቦታ ነው። ይህ ማለትም ህዝቡ ክፉን ነገር ብዙሰው ባለበት ቦታ አድርገዋል ማለት ነው። “ኢየሩሳሌም” ወይም “በኢየሩሳሌም ብዙሰው የሚበዛበት”

በዚያን ጊዜም እንጀራ እንጠግብ ነበር፥ መልካምም ይሆንልን ክፉም አናይም ነበር።
የይሁዳ ህዝብ የሰማይን ንግስትን ካመለኩአት በመልካም ነገር ትባርከናለች ብለው ያስቡ ነበር

እንጀራ እንጠግብ ነበር
“የምንበላው ምግብ ብዙ ይሆናል”

Jeremiah 44:18

አጠቃላይ ሃሳብ
በግብፅ የቀሩት ህዝቦች መናገር ቀጠሉ። በኤርምያስ 44:19 መጀመሪያ ላይ ሴቲቷ ለኤርምያስ ተናገረች።

በሰይፍና በራብ አልቀናል
“ሰይፍ” የሚለው የጦር መሳሪያ የያዙ ሰራዊትን ያመለክታል። “የጠላት ሰራዊት አንዳንዶቻችንን ሲገድሉን ነበር አንዳንዶቻችን ደግሞ በረሃብ እየሞትን ነው”

ያለ ባሎቻችን ምስልዋን ለማበጀት እንጐቻ አድርገንላት
ይህቺ ሴት ባሎቻቸው በሚያደርጉት ነገር ፈቃደኛ ስለሆኑ ነፃ ነኝ እያለች ነው።

እንጎቻ
ይህ ትናንሽ በኮኮብ መልክ የሚጋገሩ ናቸው።

Jeremiah 44:20

እግዚአብሄር ያሰበውን...የምድርም
ኤርምያስ ህዝቡን በዚህ ጥያቄ ገሰፀ። “እግዚአብሄር ያውቃል... የምድርም”

እግዚአብሄር ያሰበው ፡ በልቡም ያኖረው
እነዚህ ቃላት ትርጉማቸው አንድ አይነት ነው። ሁለቱም እግዚአብሄር ህዝቡ የውሸት አማልክትን ያመልኩ እንደነበር ማወቁን ያመለክታሉ።

Jeremiah 44:22

ርኩሰት ይታገሥ ዘንድ አልቻለም
ከእንግዲህ ወዲያ ሊታገስ አልቻለም

ያደረጋችሁትን ርኩሰት
“ርኩሰት” የሚለው “የማይወደው የሚጠላው ነገር” ነው። “እርሱ የሚጠላውን ነገር አድርጋችኋል እና”

ስለዚህ ምድራችሁ ባድማ መደነቂያም መረገሚያም ሆናለች ዛሬም እንደ ሆነ የሚኖርባት የለም።
“እግዚአብሄር ማንም በምድሪቷ ላይ እንዳይኖር አድርጓል። ባድማ እና አስፈሪ ቦታ አድርጎአታል ስሟም ለእርግማን ያረጉታል ይህ ዛሬም ቢሆን እንደዚሁ።”

ስላጠናችሁ
“ለጣኦት አማልክት እጣን ያጨሳሉ”

የእግዚአብሔርንም ቃል ስላልሰማችሁ
ይህ የእግዚአብሄርን ትእዛዛትን ይናገራል። “ትእዛዙን አትታዘዙም።”

Jeremiah 44:24

ይሁዳ ሁሉ
“ይሁዳ” የሚለው ህዝቡን ያመለክታል። “የይሁዳ ህዝብ ሁሉ”

የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር
ኤርምያስ ማስተዋል ያለብንን መልእክት ሲያስተላልፍ የሚጠቀመው ሀረግ ነው። ኤርምያስ 6:6 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

በእርግጥ እንፈጽማለን አላችሁ በእጃችሁም አደረጋችሁት
እጃችሁም የሚለው ሙሉ ሰውን ይወክላል። “የተናገራችሁትን ሁሉ በገባችሁት ቃል መሰረት አድርጋችሁአል።”

ስእለታችሁን አፅኑ
ስእለታችሁን አሟሉ

ስእለታችሁን አጽኑ ስእለታችሁንም ፈጽሙ።
ይህ የሚገርም ፅሁፍ ነው። እግዚአብሄር ለጣኦቶቻቸው ስእለታቸውን እንዲፈፅሙ አይፈልግም ነገር ግን እግዚአብሄር እንደማይሰሙት ስለሚያውቅ እንዲያደርጉት ተናገራቸው። “እናንተ ማድረግ የምትፈልጉት ስእለታችሁን ማፅናት እና ስእለታችሁንም መፈፀም ከሆነ በሉ አድርጉ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Jeremiah 44:26

ይሁዳ ሁሉ
“ይሁዳ” የሚለው ህዝቡን ያመለክታል። “የይሁዳ ህዝብ ሁሉ”

በታላቅ ስሜ ምያለሁ
የእግዚአብሄር “ታላቅ ስም” የሚለው ያለውን ገናናነት እና ሙሉነትን ያመለክታል። “በራሴ እምላለሁ” ወይም “በራሴ ሃይለኛ ስም እምላለሁ።”

በግብጽ ምድር ሁሉ በሚኖር በይሁዳ ሰው ሁሉ አፍ ስሜ ከእንግዲህ ወዲህ
“ስሜ” የሚለው እግዚአብሄርን ራሱን ያመለክታል። “አፍ” የሚለው ሙሉ ሰውን ያመለክታል። “በግብፅ ምድር ሁሉ በሚኖር በይሁዳ ሰው ሁሉ እኔን አይጠሩኝም”

ሕያው እግዚአብሔርን!
“እግዚአብሄር አምላክ ህያው እንደሆነ”። ህዝቡ ይህን የሚናገሩት ቀጥለው የሚናገሩት እውነት እንደሆነ ለመግለፅ ነው። “ህያው እግዚአብሄር” ኤርምያስ 4:2 ።

በግብጽም ምድር ያሉት የይሁዳ ሰዎች ሁሉ እስኪጠፉ ድረስ በሰይፍና በራብ ያልቃሉ።
“ሰዎች ሁሉ” የሚለው ቃል “እጅግ በጣም ብዙ ሰዎችን” ያመለክታል። “ሰይፍና” የሚለው ቃል የጦር መሳሪያ የያዙ የጠላት ሰራዊቶችን ያመለክታል። “በግብፅ ምድር እና የይሁዳ ህዝብ ሁሉ ብዙዎቹ በጠላቶቻቸው ይሞታሉ ብዙዎቹ ደግሞ በረሃብ ይሞታሉ”

ከሰይፍም የሚያመልጡ
“ሰይፍ” የሚለው ቃል የጦር መሳሪያ የያዙ የጠላት ሰራዊቶችን ያመለክታል። “ጠላቶቻቸው ያልገደሉአቸው”

Jeremiah 44:29

ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ የገለጸበት ምክንያት ቃሉን አስረግጦ ለመናገር ስለፈለገ ነው።፤ ኤርምያስ 1:8 የተተረጎመበትን መንገድ ይመልከቱ። ‹‹እግዚአብሄር የተናገረው ይህንን ነው›› ወይም ‹‹እኔ እግዚአብሄር የተናገርኩት ይህንን ነው››

...እንድቀጣችሁ
እግዚአብሄር እንደተቃወማቸውና እንደሚቀጣቸው እየተናገረ ነው

ቃሌም በላያችሁ ለክፋት እንዲጸና ታውቁ ዘንድ
እግዚአብሄር በቃሉ ክፋትን እንደሚያፀና ሲናገር እንደ ቃሉ እንደ ሚያጠቃቸው መስሎ ይናገራል። “እኔ የተናገርኩት ይሆናል ክፉም ነገር ይሆንባችኋል”

እነሆ
ተመልከት ወይም ልብ በል

የግብጹን ንጉሥ ፈርዖን ሖፍራን ለጠላቶቹ ነፍሱንም ለሚፈልጉ እጅ አሳልፌ እሰጠዋለሁ
“እጅ” የሚለው ሀይል ወይም ጉልበትን ያመለክታል። “የግብጹን ንጉሥ ፈርዖን ሖፍራን እንዲያሸንፉት እሱን ለመግደል የሚፈልጉት ለጠላቶቹ እፈቅዳለሁ”

ሖፍራን
ይህ የሰው ስም ነው።

የይሁዳን ንጉሥ ሴዴቅያስን ጠላቱ ለሆነው ነፍሱንም ለፈለገው ለባቢሎን ንጉሥ ለናቡከደነፆር እጅ አሳልፌ እንደ ሰጠሁት
“እጅ” የሚለው ሀይል ወይም ጉልበትን ያመለክታል። ናቡከደነፆር የሚያመለክተው አጠቃላይ ሰራዊቱን ነው። “ነፍሱን ለፈለገው” የሚለው ቃል መግደልን ያመለክታል። “የናቡከደነፆር ሰራዊት የይሁዳን ንጉስ ሴዴቅያስን እንዲያሸንፉ ሳደርግ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 45

1 ኤርምያስ ለኔርያ ልጅ ለባሮክ የነገረው ቃል ይህ ነበር። ይህም የሆነው በይሁዳ ንጉሥ በኢዮአቄም በአራተኛው ዓመት ኤርምያስ እየነገረው
በመጽሐፍ በጻፋቸው ጊዜ ነበር፤ እርሱም እንዲህ አለ፣ **2** "ባሮክ፣ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይልሃል፦ **3** አንተ፣ 'እግዚአብሔር በሕመሜ ላይ
ኀዘንን ጨምሮብኛልና ወዮልኝ። በልቅሶዬ ጩኸት ደክሜአለሁ፤ ዕረፍትንም አላገኘሁም' ብለሃል። **4** ልትለው የሚገባህ ይህንን ነው፦ 'እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል፦ ተመልከት፣ የሠራሁትን፣ አሁን እያፈረስኩ ነው። የተከልሁትንም፣ እየነቀልሁ ነው። ይኽም በምድር ሁሉ ላይ እውነት ነው። **5** ነገር ግን ለራስህ ታላቅ ነገር
ተስፋ ታደርጋለህን? ያንን ተስፋ አታድርግ። በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ ክፉ ነገርን እንደማመጣ ትመለከታለህና አትፈልገው፣ ይላል እግዚአብሔር። ነገር ግን
በሄድህበት ስፍራ ሁሉ ነፍስህን እንደ ምርኮ አድርጌ እሰጥሃለሁ።"

Jeremiah 45:1

ኤርምያስ የተናገረው ቃል ይህ ነው
ኤርምያስ እንዲፅፍ የተነገረው ነው

በኢዮስያስ ልጅ በኢዮአቄም በአራተኛው ዓመት
ይህ የተቀመጠው በመጀመሪያው ነው 45፡1 ላይ ይገኛል።

በኢዮአቄም በአራተኛው ዓመት
ይህ ቃል የግዛቱን ያሳየናል። “በኢዮአቄም አራተኛው አመት ግዛት”

አራተኛው አመት
“አራተኛው” የሚለው አራት ቁጥርን ያመለክታል

የተናገረው
ኤርምያስ ለባሮክ ተናገረ

እግዚአብሄር በህመሜ ላይ ሀዘንን ጨምሮብኛልና
“በህመም ውስጥ ነበርኩ አሁን እግዚአብሄር ሀዘንን አመጣብኝ”

በለቅሶዬ ደክሜአለሁ
“በለቅሶዬ” የሚለው ቃል ሀዘንን እና ለቅሶን ያመለክታል። “በለቅሶዬ ምክንያት አሁን ደክሜአለሁ”

Jeremiah 45:4

እንዲህ በለው
እግዚአብሄር ኤርምያስን ለባሮክ እንዲናገረው አዘዘው።

የሠራሁትን አፈርሳለሁ፥ የተከልሁትንም እነቅላለሁ
ሁለቱም የሚናገሩት አንድ አይነት ሀሳብ አላቸው። እግዚአብሄር የይሁዳን ከተማና ህዝብ እንደሚያጠፋ ልክ እነደ ሚፈራርስ ግንብ እና ሊነቀል እንደሚችል ተክል መስሎ ይናገራል። “ይህ ከተማ ልክ እኔ እንደገነባሁት አፈራርሰዋለሁ፤ ልክ እንደተከልኩት ተክል አሁን ከተተከለበት እነቃቅለዋለሁ።”

ለራስህ ታላቅን ነገር ትፈልጋለህን?
እግዚአብሄር ይህን ጥያቄ ባሮክ ሌሎች በጥሩ ሁኔታ እንዲንከባከቡት መፈለጉን ለማመልከት ይጠቀመዋል። “ለራስህ ጥሩን ነገር እንደምትፈልግ አውቃለሁ” ወይም “ሌሎች እንዲያከብሩህ እንደምትፈልግ አውቃለሁ”

እነሆ
ተመልከት ወይም ልብ በል

በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ፥ እነሆ፥ ክፉ ነገርን አመጣለሁና
ክፉ ነገርን አመጣለሁ ሲል እንደ ሚጓዝ እና የሆነ ቦታ እንደሚደርስ ነገር መስሎ ይናገራል። “ስጋ የለበሰን ሁሉ ክፉ ነገርን እንዲገጥመው አደርጋለሁ”

ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ የገለጸበት ምክንያት ቃሉን አስረግጦ ለመናገር ስለፈለገ ነው።፤ ኤርምያስ 1:8 የተተረጎመበትን መንገድ ይመልከቱ። ‹‹እግዚአብሄር የተናገረው ይህንን ነው›› ወይም ‹‹እኔ እግዚአብሄር የተናገርኩት ይህንን ነው››

ነፍስህን እንደ ምርኮ አድርጌ እሰጥሃለሁ።
ባሮክን እንዲያመልጥና በህይወት መኖሩን እንደ ተማረከ መስሎ ይናገራል። “ነገር ግን በሄድክበት ቦታ ሁሉ እጠብቅሀለሁ እናም በህይወት ትኖራለህ”

ምርኮ
በሃይል እና በጉልበት መውሰድ

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 46

1 ስለ አሕዛብ ወደ ነቢዩ ወደ ኤርምያስ የመጣው የእግዚአብሔር ቃል ይህ ነው። 2 ስለ ግብጽ፦ "ይህ በኤፍራጥስ ወንዝ አጠገብ በከርከሚሽ ስለ ነበረው ሠራዊት ነው። በይሁዳ ንጉሥ በኢዮስያስ ልጅ በኢዮአቄም በአራተኛው ዓመት የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ስለ መታው ስለ ግብጽ ንጉሥ ስለ ፈርዖን ኒካዑ ሠራዊት፦ 3 ትንንሾቹን እና ትልልቆቹን ጋሻዎች አዘጋጁና ወደ ውጊያ ሂዱ። 4 ፈረሰኞች ሆይ፣ ፈረሶችን ለጉሙና ውጡ፣ ራስ ቍርንም ደፍታችሁ ቁሙ። ጦርንም ሰንግሉ፣ የጦር ዕቃንም ልበሱ። 5 በዚህ የማየው ምንድነው? ወታደሮቻቸው ተሸንፈዋልና፣ በፍርሃት ተሞልተው ወደ ኋላ ተመለሱ። ወደ ኋላቸውም ሳይመለከቱ ፈጥነው ሸሹ። ድንጋጤ በሁሉ ቦታ አለ፣ ይላል እግዚአብሔር። 6 ፈጣኑ ሊሸሽ አይችልም፣ ወታደሮችም ሊያመልጡ አይችሉም። በሰሜን ተሰናከሉ፣ በኤፍራጥስ ወንዝ በኩል ደግሞ ወደቁ። 7 ይህ እንደ አባይ ወንዝ የሚነሣ፣ ውኃውም እንደ ወንዝ የሚናወጥለት ማን ነው? 8 ግብጽ እንደ አባይ ወንዝ ይነሣል፣ ውኃውም እንደ ወንዙ ይናወጣል። እርሱም፣' እነሣለሁ ምድርንም ሁሉ እከድናለሁ። ከተሞችንና የሚኖሩባቸውን አጠፋለሁ ብሎአል። 9 ፈረሶች ሆይ፣ ውጡ። ሠረገሎችም ሆይ፣ ንጐዱ፤ ጋሻም የሚያነግቡ የኢትዮጵያና የፋጥ ኃያላን፣ ቀስትንም ይዘው የሚስቡ የሉድ ኃያላን ይውጡ።' 10 ያ ቀን የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር የበቀል ቀን ነው፣ ደግሞም ጠላቶቹን እርሱ ራሱ ይበቀላቸዋል። ሰይፍ በልቶ ይጠግባል። ደማቸውንም ተሞልቶ ይጠጣል። ለሠራዊት ጌታ ለእግዚአብሔር በሰሜን ምድር በኤፍራጥስ ወንዝ አጠገብ መሥዋዕት አለውና። 11 ድንግሊቱ የግብጽ ሴት ልጅ ሆይ፣ ወደ ገለዓድ ውጪና መድኃኒት ውሰጂ። መድኃኒትን በራስሽ ላይ ማብዛትሽ ጥቅም የለሽ ነገር ነው። ለአንቺ የሚሆን ፈውስ የለም። 12 ወታደሩ በወታደሩ ላይ ተሰናክሎ፣ ሁለቱ በአንድነት ወድቀዋልና አሕዛብ እፍረትሽን ሰምተዋል። ምድር በለቅሶሽ ተሞልታለች።" 13 የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር መጥቶ የግብጽን ምድር ሲያጠቃ እግዚአብሔር ለነብዩ ኤርምያስ የተናገረው ቃል ይህ ነው። 14 "ለግብጽ ተናገሩ፣ በሚግዶልና በሜምፎስ ይሰማ። በጣፍናስ 'ሰይፍ በዙሪያህ ያለውን በልቶአልና፣ ተነሥተህ ተዘጋጅ' ብለዋል። 15 የከፍታ አምላክሽ ለምን ሸሸ? በበሬ የተመሰለው ጣዖትሽስ ለምን አይቆምም? እግዚአብሔር ገፍትሮ ጥሎታል። 16 እርሱ የሚሰናከሉትን ቊጥር ያበዛል። እያንዳንዳቸው ወታደሮች አንዱ በሌላው ላይ ይወድቃል። እነርሱም፣ "ተነሡ። ወደቤት እንጂድ። ወደገዛ ሕዝባችን፣ ወደ ተወለድንባት ምድር እንሂድ። ይህንን እየቀጠቀጠን ያለውን ሰይፍ ትተን እንሂድ።" ይላሉ። 17 በዚያም፣ 'የግብጽ ንጉሥ ፈርዖን ያገኘውን ዕድል የሚያሳልፍ ጐከተኛ ብቻ ነው" ብለው ይናገራሉ። 18 "እኔ ሕያው ነኝና በተራሮች መካከል እንዳለ እንደ ታቦር፣ በባሕርም አጠገብ እንዳለ እንደ ቀርሜሎስ፣ እንዲሁ በእውነት ይመጣል፣ ይላል ስሙ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የተባለው ንጉሥ። 19 አንቺ በግብጽ የምትቀመጪ ልጅ ሆይ፣ ለምርኮ የምትሄጂበትን ዕቃ አዘጋጂ። ሜምፎስ የምትሸበር ትሆናለችና፣ ማንም በዚያ የማይኖርባት እንድትሆን ትፈራርሳለችና። 20 ግብጽ እጅግ የተዋበች ጊደር ናት፣ ነገር ግን ከሰሜን በኩል የሚያሰቃይ መዥገር ይመጣባታል። 21 በመካከሏም ያሉ ቅጥረኛ ወታደሮች እንደ ሰቡ ወይፈኖች ናቸው፣ ነገር ግን እነርሱም እንዲሁ ይመለሱና ይሸሻሉ። የጥፋታቸው ቀን እየመጣባቸው ነውና፣ የቅጣታቸው ጊዜ መጥቶባቸዋልና በአንድነት አይቆሙም። 22 ጠላቶቿ በእርሷ ላይ ይሰለፉባታልና ግብጽ እንደ እባብ ድምፅ ትጮኻለች፣ በደረቷም ተስባ ትሸሻለች። በመጥረቢያ እንደሚቆርጡ እንደ እንጨት ቈራጮች ሆነው ይመጡባታል። 23 በጣም ጥቅጥቅ ያሉ ቢሆኑም እንኳን ጫካዎቿን ይቈርጣሉ፣ ይላል እግዚአብሔር። ጠላቶቿ ሊቆጠሩ እስከማይችሉ ድረስ ከአንበጣ ይልቅ ብዙ ይሆናሉና። 24 የግብጽ ሴት ልጅ እንድታፍር ትደረጋለች። ከሰሜን ለሚሆኑ ሕዝቦች እጅ ተላልፋ ትሰጣለች።" 25 የእስራኤል አምላክ፣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፣ እንዲህ ይላል፣ 'ተመልከቱ፣ የኖእ አሞንን፣ ፈርዖንንም፣ ግብጽንና አማልክቶችዋን፣ ፈርዖን ነገሥታቶችዋንና በእርሱም የሚታመኑትን እቀጣለሁ። 26 ነፍሳቸውንም በሚፈልጉ ሰዎች እጅ፣ በባቢሎን ንጉሥ በናቡክደነፆር እንዲሁም በባርያዎቹም እጅ አሳልፌ እሰጣቸዋለሁ። ከዚያም በኋላ አንደ ቀድሞው ዘመን የሰው መኖሪያ ትሆናለች፣" ይላል እግዚአብሔር። 27 "ነገር ግን፣ አንተ ባርያዬ ያዕቆብ ሆይ፣ አትፍራ። አንተም እስራኤል ሆይ፣ አትደንግጥ። እነሆ፥ አንተን ከሩቅ ዘርህንም ከተማረከባት ምድር አድናለሁ። ከዚያም፣ ያዕቆብ ይመለሳል፣ ሰላም ያገኛል፣ በዋስትናም ይቀመጣል፣ የሚያስፈራራው ማንም አይገኝም። 28 አንተ፣ ባርያዬ ያዕቆብ፣ እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ፣ ይላል እግዚአብሔር፤ አንተን ያሰደድሁባቸውን አሕዛብን ሁሉ ፈጽሜ አጠፋለሁና አትፍራ ይላል እግዚአብሔር። ነገር ግን አንተን ፈጽሜ አላጠፋህም። በመጠን እቀጣሃለሁ፥ ያለ ቅጣትም አልተውህም።"

Jeremiah 46:1

አጠቃላይ ሀሳብ
ኤርምያስ በብዛት ትንቢትን በግጥም መልክ ይፅፋል። የእብረዊያን ፀሀፊዎች የተለያዩ ንፅፅር ይጠቀሙ ነበር።

ወደ ነብዩ ወደ ኤርምያስ የመጣው የእግዚአብሄር ቃል ይህ ነው።
ይህ ልዩ የእግዚአብሄር ቃል እንደሆነ ይናገራል። ኤርምያስ 14፡1 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት። “ይህ የእግዚአብሄር ቃል ለኤርምያስ የተሰጠ ነው”

ስለ ግብፅ
ይህ ሀረግ የግብፅ ከተማን ያመለክታል

ኒካዑ
ይህ የወንድ ስም ነው

ከርከሚሽ
ይህ በኤፍራጥስ በስተምእራብ በኩል የሚገኝ ከተማ ነው።

የባቢሎን ንጉስ ናቡከደነፆር
ናቡከደነፆር የሚለው ሰራዊቱን ያመለክታል። “የባቢሎን የንጉስ ናቡከደነፆር ሰራዊት”

በኢዮአቄም በአራተኛው አመት
ይህ ከኢዮአቄም አራተኛ አመት ንግስና ነው። “ኢዮአቄም ከነገሰ በአራተኛው አመት ”

አራተኛው አመት
አራተኛው የሚለው አራት ቁጥርን ያመለክታል።

ፈረሰኞች ሆይ፥ ፈረሶችን ለጉሙና ውጡ
ልጉዋም ማለት ፈረሶች ላይ የመታሰር ሲሆን ይህም ሰረገላውን ለመጎተት ይጠቅማል። “ፈረሰኞች ሆይ፥ ፈረሶችን ለጉሙና ውጡ” ሲል ሰራዊቶቹ ሰረገላው ሆነው ፈረሶቹ ሰረገላውን ይጎትቱታል።

ራስ ቁርንም
በጦርነት ጊዜ የራስ ክፍልን ከአደጋ ለመከላከል የሚጠቅም ነው።

ጦርንም ሰንግሉ
ይህ ሀረግ ጦሮቻችሁን ሳሉ ማለት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Jeremiah 46:5

አጠቃላይ ሀሳብ
የኤርምያስ ራዕይ ለግብፅ ቀጠለ

ለምን አየሁ
እግዙአብሄር እንደተናገራ ያሳየናል። እግዚአብሄር ይህ አይነት ጥያቄዎች የሚታየውን እና ቀጣይ የሚናገረውን ልብ እንዲሉ የሚጠቀመው ነው። “እየተፈጠረ ያለውን ተመልከቱ”

ፈርተው ወደ
“የግብፅ ሰራዊቶች ፈርተዋል”

በዚያ ድንጋጤ አለ
“በዙሪያቸው ያለው ሁሉ ያስደነግጣል”

ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ የገለጸበት ምክንያት ቃሉን አስረግጦ ለመናገር ስለፈለገ ነው።፤ ኤርምያስ 1:8 የተተረጎመበትን መንገድ ይመልከቱ። ‹‹እግዚአብሄር የተናገረው ይህንን ነው›› ወይም ‹‹እኔ እግዚአብሄር የተናገርኩት ይህንን ነው››

ፈጣኑ አያመልጥም ኃያሉም አይድንም
እነዚህ ሁለት ሀረጎች አንድ ሀሳብ ሲኖራቸው ይህም ማንም ፈጣኑ እና ሃያሉም ማምለጥ አይችሉም። “ፈጣኖቹ ሰራዊቶች ማምለጥ አይችሉም”

በኤፍራጥስ ወንዝ በኩል ተሰናክለው ወደቁ
በጦርነቱ መውደቅ እና መሞት እነደ ሰራዊቱ ተሰናክለው እንደ ወደቁ መስሎ ይናገራል። “የግብፃውያን ሰራዊት በኤፍራጥስ ወንዝ በኩል በሸንፈት እና ሞት ደረሰባቸው”

Jeremiah 46:7

አጠቃላይ ማብራሪያ
ኤርምየስ ለግብፅ ከተማ እግዚአብሄር እየተናገረ መሆኑን ይናገራል።

ይህ እንደ ግብጽ ወንዝ የሚነሣ...ማን ነው...እንደ ወንዝ
አግዚአብሄር ይህንጥያቄ ስለ ግብፅ የሚናገረውን ልብ እንዲሉ የሚጠቀመው ነው። “እንደ ግብፅ ወንዝ የሚነሳውን ተመልከቱ”

ግብጽ እንደ ግብጽ ወንዝ ይነሳል
በአመት አንድ ጊዜ የግብፅ ወንዝ ይሞላል ደግሞም በዙሪያው ያለውን ቦታ በውሃ ያጥለቀልቃል። እግዚአብሄር ግብፅን እንደ የግብፅ ወንዝ መስሎ ይናገራል ምክንያቱም የግብፅ ሕዝቦች ከተማ እና መሬቶችን የሚያጠፉ ሃያሎች ነን ብለው ስለሚያስቡ ነው።

ግብፅ...ብሎአል
ግብፅ የሚለው ቃል የግብፅ ህዝብን ያመለክታል። “ግብፃውያን... ግብፃውያን ብለዋል”

ፈረሶች ሆይ ውጡ ሰረገሎችም ሆይ ንጎዱ
“ፈረሶች” እና “ሰረገሎች” የሚያመለክቱት ፈረስ እና ሰረገላ የሚጠቀሙ ሰራዊቶችን ነው። የግብፅ መሪዎች ሰራዊታቸውን ለጦርነት ተነሱ ብለው አዘዙ። “እናንተ በፈረስ ያላችሁ ሰራዊቶች በሰረገላ ላይም ያላችሁ ሰራዊቶች ወደጦርነት ውጡ”

ጋሻም የሚያነግቡ የኢትዮጵያና የፋጥ ኃያላን
ይህ ትዕዛዝ ቀጥታ ለሰራዊቱ የታዘዘ ነው። “እናንተ ጋሻ የምታነግቡ የኢትዮጲያና የፋጥ ሃያላን ወደ ጦርነት ውጡ”

ኢትዮጲያና የፋጥ
እነዚህ የኢትዮጲያና ሊቢያ ከተማ ስሞች ናቸው

ቀስትንም ይዘው የሚስቡ የሉድ ኃያላን ይውጡ
ከበፊቱ አረፍተነገር ሰራዊቶች ወደ ጦርነት እንዲወጡ እንረዳለን። እነዚህ ሊደጋገሙ ይችላሉ። የህም ትዕዛዝ ቀጥጣ ለሰራዊት ወታደሮች የተሰጠ እንደሆነ ያሳያል። “የሉድ ሃያላን ቀስትንም የምትስቡ ወደ ጦርነት ውጡ”

ሉድ
ይህ በሉድ ከተማ የሚገኙ ህዝቦች ስም መጠሪያ ሲሆን በመፅሀፍ ቅዱስ ላይ ሊዲያ የሚለው ስም ነው።

ቀስትንም ይዘው የሚስቡ
ይህ ሀረግ ለመተኮስ ቀስትን አስገብተው የሚስቡ ማለት ነው። “ቀስትንም የሚስቡ ሃያላን”

Jeremiah 46:10

አጠቃላይ ሃሳብ
ኤርምያስ እግዚአብሄር ለግብፅ የተናገረውን መናገሩን ቀጠለ

ያ ቀን
ይህ ሀረግ ግብፃውያን በባቢሎናውያን የሚሸነፉበትን ቀን ያመለክታል።

የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር የበቀል ቀን
“ለእኔ ሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር የበቀል ቀን ነው”

ሰይፍ በልቶ ይጠግባል በደማቸውም ይሰክራል
የእግዚአብሄ ሰይፍ እንደ ህዝቡን እንደሚበላ እና ደማቸውን እንደ ሚጠጣ መስሎ ይናገራል። ሁለቱም ሀረጎች የሚናገሩት አንድ አይነት ሃሳብ ሲሆን ይህም ሙሉ በሙሉ እንደሚያጠፋ አግንኖ ይናገራል። “ሰራዊቱን ሙሉ በሙሉ አጠፋለሁ ልክ እንደ ሰይፍ እንደሚበላቸው እና በደማቸውንም እንደሚሰክር”

ሰይፍ በልቶ
እግዚአብሄር ጠላቶቹን እንደሚቀጣ እና እንደሚገድል እንደ ሰይፍ ይዞ እንደሚገድላቸው መስሎ ይናገራል።

መስዋዕት አለውና።
እግዚአብሄር ግብፃውያን በባቢሎን እንዲሸነፉ በማድረግ መበቀሉን ልክ እንደ ግብፃውያን ለእግዚአብሄር እንደሚሰዋ መስዋእት መስሎ ይናገራል። “ግብፃውያን እንደ መስዋእት ይሆናሉ”

Jeremiah 46:11

አጠቃላይ ሃሳብ
እግዚአብሄር ለግብፅ የሚናገረውን ጨረሰ

ወደ ገለዓድ ውጪ የሚቀባንም መድኃኒት ውሰጂ
ገለዓድ የሚባለው ስፍራ ታዋቂ የሆነ መድሃኒት የሚቀምሙ ሰዎች ያሉበት ስፍራ ሲሆን እግዚአብሄር መድሃኒት እንደማረዳቸው እያወቀ መድሃኒት ውሰዱ እያለ ይቀልድባቸዋል።

ድንግሊቱ የግብፅ ልጅ ሆይ
የግብፅ ሀገር ህዝቦች እንደ ድንግል ልጅ መስሎ ይናገራል። “የግብፅ ህዝቦች”

ጉስቁልና
ይህ ክብር ማጣት ወይም የማፈር ስሜት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለቅሶሽም ምድርን ሞልቶአታል
“ምድርን” ሲል በምድር ላይ ያሉ ሰዎችን እና በግብፅ ላይ የደረሰውን የሚያውቁ ህዝቦችን ነው። የግብፃውያንን ለቅሶ የሚሰሙ ህዝቦች ሁሉ እንደ ለቅሶአቸው ምድርን እንደሞላ መስሎ ይናገራል። “በምድር ላይ ያሉ ህዝቦች ሁሉ ለቅሶሽን ይሰሙታል”

ኃያሉ በኃያሉ ላይ ተሰናክሎ ሁለቱ በአንድነት ወድቀዋልና
ሃያላን በጦርነት መሞታቸውን እንደ ተሰናክለው እንደወደቁ መስሎ ይናገራል። “የጦር ሰራዊታችሁ በጦርነት ይሞታሉ”

Jeremiah 46:13

የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር
ናቡከደነፆር የሚለው ሰራዊቱን ያመለክታል። “የባቢሎን የንጉስ ናቡከደነፆር ሰራዊት”

የግብፅን ምድር
“ምድር” የሚለው ህዝብን ያመለክታል። “የግብፅ ህዝቦች” ወይም “ግብፃውያን”

ሚግዶልም
ኤርምያስ 44፡1 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

በሚምፎስና በጣፍናስ
እነዚህን ስሞች ኤርምያስ 2፡16 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት።

ሰይፍ በዙሪያህ ያለውን በልቶአልና
“ሰይፍ” የሚለው ቃል የጦር መሳሪያ የያዙ ሰራዊቶችን ያመለክታል። የጠላት ሰራዊ ህዝቡን መግደሉን እንደ ሰይፍ ህዝቡን እንደበላ መስሎ ይናገራል። “ጠላቶቻችሁ በዙሪያችሁ ያሉህዝቦችን ሁሉ ይገድላሉ”

Jeremiah 46:15

ኃይለኞችህ ስለ ምን ተወገዱ? እግዚአብሔር ስላደከማቸው አልቆሙም
አንዳንድ የመፅሀፍ ቅዱስ ትርጉም “ሃያሉ አምላካችሁ አጲስ ስለምን ወደቀ እግዚአብሄ ስለመታው አደልምን” ብሎ ይተረጉመዋል። አጲስ የሚለው የበሬ ቅርፅ ያለው የግብፃውያን ጣኦት ነው። ይህ በሬ አብዛኛውን ጊዜ ሃይልን ያመለክታል። ለዚህም ነው አንዳንድ የመፅሀፍ ቅዱስ ትርጉሞች ሃይሎች ወይም ብርቱዎች የሚሉትን ቃሎች ሰራዊቱን እንደሚያመለክት ያሳያል።

ኃይለኞችህ ስለ ምን ተወገዱ? እግዚአብሔር ስላደከማቸው አልቆሙም
እግዚአብሄር ይህን ጥያቄ የግብፃውያንን ሰራዊት ሃይል ላይ ለመቀለድ ሲጠቀም ያሳያል። “ሰራዊቶችህ ተወግደዋል ደግሞም እንደወደቁ ይቀራሉ አይነሱም”

ብዛታቸውም ተሰናከለ፣ ሰውም አንዱ በአንዱ ላይ ወደቀ
እግዚአብሄር ብዙ ሰራዊቶችን እርስ በእርስ እንዲወድቁ አደረገ

ከሚያስጨንቅ ሰይፍ ፊት ወደ ወገናችን ወደ ተወለድንባት ምድር እንመለስ
“ሰይፍ” የሚለው የጦር እቃ የያዙ ሰራዊቶችን ያመለክታል። “ከሚያስጨንቀን ከጠላቶቻችን ፊት ወደ ወገናችን ወደ ተወለድንባት ምድር እንመለስ”

...ጠሩት
ጠሩት ሲል የሚያመለክተው (1) በግብፅ ያሉትን ሰዎች ሁሉ (2) ወደሀገራቸው ይሸሹ የነበሩትን የኩሽ፣ ፑት እና የሉድ ሰራዊትን

የግብሥ ንጉሥ ፈርዖንን፦ ሰዓቱን የሚያሳልፍ ጉረኛ ብለው ጠሩት
“ጉረኛ” የሚለው አንድ ሰው አደርጋለሁ ብሎ የሚናገር ነገር ግን የተናገረውን የማያደርግ ሲሆን ነው። “ፈንኦን አደርጋለሁ እያለ ያወራል ነገር ግን አያደርግም”

Jeremiah 46:18

እኔ ህያው ነኝ
“እኔ ህያው ነኝ” የሚለውን እግዚአብሄር ቀጥሎ የሚናገረው ነገር እውነት እንደሆነ ለማሳወቅ ነው።

ንጉስ ነኝ
“ንጉስ” የሚለው ቃል እግዚአብሄርን ያመለክታል።

እንደ ታቦር፣ በባሕርም አጠገብ እንዳለ እንደ ቀርሜሎስ
ይህ የባቢሎን ከተማን ሲያመለክት እንደ ሁለቱ ተራሮች እንደተከበበ መሬት በግብፅ ከተማ ይደነቃሉ።

ታቦር
በእስራኤል በስተሰሜን የሚገኝ የተራራ ስም ነው።

ለምርኮ የሚሆን ዕቃ አዘጋጂ
ለምርኮ ተዘጋጁ

Jeremiah 46:20

ግብጽ የተዋበች ጊደር ናት
ሃያል እና የበለፀገች ግብፅ እንደ የተዋበች ጊደር መስሎ ይናገራል። “ግብፅ እንደ ተዋበች ጊደር ናት”

ጥፋት ግን ይመጣል
ግብፅን ለማጥፋት የሚመጣ ጠላት እንደ ተናካሽ ነፍሳት መስሎ ይናገራል። “ሃያሉ ጠላት እንደ ተናካሽ ነፍሳት ነው”

በእርስዋም ያሉ የተቀጠሩ ሠራተኞች እንደ ሰቡ ወይፈኖች ናቸው
ፀሀፊው ወታደሮችን ከ ሰቡ ወይፈኖች ጋር ያወዳድራል ይህም ወታደሮቹ በግብፃውያን እንክብካቤ ስለነበሩ ከገበሬ በሬውን እንደሚንከባከብ እና እንደ ሚያወፍረው አርጎ ይናገራል።

በአንድነትም ሸሹ አልቆሙምም
አንድንነት የሚለው በህብረት ማለት ሲሆን ፀሀፊው ወታደሮቹ በግል አይዋጉም ነገር ግን ራሳቸውን ለማዳን ግን ይሸሻሉ።

የመጐብኘታቸው ጊዜ መጥቶባቸዋልና
ጊዜ የሚለው ቃል የሚገጓዝ እና የሆነ ቦታ የሚደርስ አርጎ ይናገራል። “በዛች ቀን የከፋ ነገር ይደርስባቸዋል።”

ከሠራዊትም ጋር ይሄዳሉና ድምፅ እንደ እባብ ይተምማል
ግብፃውያን ጠላቶቻቸውን ማስቆም አለመቻላቸው እንደ እባብ ድምፅ እንደሚተምም።

እንደ እንጨት ቈራጮችም በምሳር ይመጡባታል።
ግብፃውያንን ሊያጠፋ የጦር መሳሪያ ይዞ የሚመጣ ጠላት እንደ እንጨት ለመቁረጥ እንደሚመጡ እንጨት ቆራጭ መስሎ ይናገራል።

Jeremiah 46:23

ይቈጠሩ ዘንድ የማይቻሉትን የዱርዋን ዛፎች ይቈርጣሉ... ይቈጠሩ ዘንድ የማይቻሉትን የዱርዋን ዛፎች ይቈርጣሉ
የግብፃውያን ጠላት ግብፅን በመውጋት እና መግደል ልክ እንደ ጠላት ሰራዊቱን እንደ እንጨት ቆራጭ መስሎ ይናገራል። “የጠላት ሰራዊት ግብፅን ይገድላል እንደ እንጨት ቆራጮች ዛፎችን እንደሚቆሩጡ”

ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ የገለጸበት ምክንያት ቃሉን አስረግጦ ለመናገር ስለፈለገ ነው።፤ ኤርምያስ 1:8 የተተረጎመበትን መንገድ ይመልከቱ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

‹‹እግዚአብሄር የተናገረው ይህንን ነው›› ወይም ‹‹እኔ እግዚአብሄር የተናገርኩት ይህንን ነው››

አንበጣ
ይህ የ ነፍሳት ዘር ሲሆን እጅግ በጣም ብዙ ሆነው የሚጓዙ እና በእህል ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚየሥከትሉ ናቸው።

ቁጥርም የላቸውም
“ማንም ሊቆጥራቸው አይችልም”

የግብፅ ልጅ ታፍራለች
የግብፅ ህዝቦች አንደ የግብፅ ልጆች አድርጎ ይናገራል። “የጠላት ሰራዊት የግብፅ ህዝብን ያዋርዳል።”

በሰሜን ሕዝብ እጅ አልፋ ትሰጣለች።
“እጅ” የሚለው ሀይል ወይም ጉልበትን ያመለክታል። “እኔ እግዚአብሄር ከሰሜን ያሉ ህዝቦች ግብፅን እንዲያሸንፉ አዛለሁ።”

Jeremiah 46:25

የቴብስ አምላክ የሆነውን አሞንን
“አሞን” የግብፃውያን ጣኦት ንጉስ ነው። “ቴብስ” ከግብፅ በስተሰሜን የምትገኝ ከተማ ስትሆን ቴብስ የሚለው በቴብስ የሚገኙ ህዝቦችን ነው። “አሞን የቴብስ ጣኦት” ወይም “የቴብስ ህዝብ ጣኦት አሞን”

ግብፅንም አማልክተዋንና ነገስታቶችዋንም
ግብፅ የሚለው ህዝቡን ያመለክታል። “የግብፅ ህዝብ እና አማልክቶቻቸው”

ነፍሳቸውንም በሚፈልጉ ሰዎች እጅ...አሳልፌ እሰጣቸዋለሁ
“እጅ” የሚለው ቃል ሀይል ወይም ጉልበትን ያመለክታል። “ነፍሳቸውንም በሚፈልጉ” ሲል ሰውን መግደል መፈለግ ማለት ነው። “እናንተን መግደል ለሚፈልጉ አሳልፌ እሰጣችሁአለሁ።”

በባቢሎን ንጉስ በናቡከደነፆር እጅ በባሪያዎቹም
“እጅ” የሚለው ቃል ሀይል ወይም ጉልበትን ያመለክታል። “ናቡከደነፆር... ባሪያዎቹም” የሚለው “ነፍሳቸውን የሚፈልጉ” ያመለክታል። “የባቢሎን ንጉስ ናቡከደነፆር እና ባሪዎቹ ግብፃውያንን እንዲያሸንፉ አስልፌ እሰጣቸዋለሁ”

ከዚያም በኋላ አንደ ቀድሞው ዘመን የሰው መኖሪያ ትሆናለች
“ከዚህም በኋላ ሰዎች በግብፅ ከተማ መኖር ይጀምራሉ”

Jeremiah 46:27

ነገር ግን አንተ ባሪያዬ ያዕቆብ ሆይ፥ አትፍራ፥ አንተም እስራኤል ሆይ፥ አትደንግጥ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች አንድ ሀሳብ ሲኖራቸው “ያዕቆብ” እና “እስራኤል” የሚያመለክቱት የእስራኤል ህዝብን ነው። እግዚአብሄር ህዝቡ መፍራት እንደሌለባቸው አግንኖ ይናገራል። “የእስራኤል ህዝብ ሆይ ባሪያዎቼ አትፍሩ”

ከተማረከባት ምድር
የተማረኩበት ምድር

አህዛብን ሁሉ ፈፅሜ አጠፋለሁ
“ሙሉ በሙሉ ከተማዎችን ሁሉ አጠፋለሁ”

ያለ ቅጣትም አልተውህም
“ቀጣትን እቀጣሃለሁ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 47

1 ስለ ፍልስጥኤማውያን ወደ ነቢዩ ወደ ኤርምያስ የመጣው የእግዚአብሔር ቃል ይህ ነው። ይህ ቃል ወደ እርሱ የመጣው ፈርዖን ጋዛን ሳይመታ በፊት ነው። **2** "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ተመልከት፣ ውኃ ከሰሜን ይነሣል። እነርሱም እንደሚያጥለቀልቅ ፈሳሽ ይሆናሉ! ከዚያም በምድሪቱና በመላዋ ሁሉ፣ በከተማይቱና በሚኖሩባት ላይ ይጐርፋሉ! ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው ለእርዳታ ይጮኻል፣ በምድሪቱም የሚኖሩ ሁሉ ያለቅሳሉ። **3** ከኃይለኞች ፈረሶች ከኮቴያቸው መጠብጠብ ድምፅ፣ ከሰረገሎቹና ከጎማዎቻቸውም መሸከርከር ሁከት የተነሣ፣ አባቶች በገዛ ራሳቸው ድካም ምክንያት ልጆቻቸውን አይረዱም። **4** ይህም የሚሆነው ፍልስጥኤማውያንን ሁሉ ያጠፋ ዘንድ የቀሩትንም ረዳቶች ሁሉ ከጢሮስና ከሲዶና የሚቆርጥ ቀን ስለሚመጣ ነው። እግዚአብሔር ፍልስጥኤማውያንና የከፍቶርን ደሴት ቅሬታ ያጠፋልና። **5** ራሰ ቡሀነት በጋዛ ላይ መጥቶአል። አስቀሎናን በተመለከተ፣ በሸለቋቸው የተተዉት ሕዝብ ዝም እንዲሉ ይደረጋሉ። እስከ መቼ ድረስ በለቅሶ ራሳችሁን ትነጫላችሁ? **6** ወዮ፣ የእግዚአብሔር ሰይፍ! ዝም እስከምትል ምን ያክል ትቆያለህ? ወደ ሰገባህ ተመለስ! ቊም ደግሞም ጸጥ በል። **7** እግዚአብሔር አዝዞሃልና እንዴት ዝም ልትል ትችላለህ። በአስቀሎናና በባሕር ዳር ላይ ጥቃት እንድትፈጽም አዘጋጅቶሃልና።"

Jeremiah 47:1

ወደ ነብዩ ወደ ኤርምያስ የመጣው የእግዚአብሄር ቃል ይህ ነው።
ይህ ልዩ የእግዚአብሄር ቃል እንደሆነ ይናገራል። ኤርምያስ 14፡1 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት። “ይህ የእግዚአብሄር ቃል ለኤርምያስ የተሰጠ ነው”

የመጣው...ቃል ይህ ነው።
ይህ የሚያመለክተው ከእግዚአብሄር ለየት ያለ መልእክት መናገር ሲፈልግ የሚጠቀመው ነው። “እግዚአብሄር ለኤርምያስ ይህን ቃል ሰጠው”

ፈርኦንም
“ፈርኦን” የሚለው ስም የግብፃውያንን ሠራዊት ያመለክታል። “የፈርኦን ሰራዊት”

እነሆ
“እነሆ” የሚለው ቃል ቀጣይ ለሚለው ነገር እንዲያስተውሉ ይናገራል።

ውኃ ከሰሜን ይነሣል የሚያጥለቀልቅም ፈሳሽ ይሆናል
እነዚህ ሁለት ሀረጎች አንድ አይነት ሀሳብ የያዙ ሲሆን የጠላት ሰራዊት ደግሞ እንደ የሚያጥለቀልቅ ፈሳሽ መስሎ ይናገራል። “ከሰሜን ያለ ጠላት እነደ የሚያጥለቀልቅ ፈሰሽ ይመጣል”

በከተማይቱና በሚኖሩባት ላይ ይጐርፋል
ከሰሜን የሚመጣው ጠላት እንደ የሚጥለቀለቅ ፈሳሽ መስሎ ይናገራል። “አንደ ሚጥለቀለቅ ፈሳሽ ከሰሜን የሚመጣው ጠላት ከተማዋን ያጠፋታል”

Jeremiah 47:3

ከኃይለኞች ፈረሶች ከኮቴያቸው መጠብጠብ ድምፅ፣ ከሰረገሎቹም መሸከርከር፣ ከመንኰራኵሮቹም መትመም
የሚሰማው ድምፅ እየመጣ ያለ ሰራዊት እንዳለ ያመለክታል።

ከሰረገሎቹም መሸከርከር፣ ከመንኰራኵሮቹም መትመም
እነዚህ ሁለቱ አንድን ነገር ሲገልፁ ይህም የሚናገረው በአንድላይ የሚያሰሙትን ከፍተኛ ድምፅ ለመግለፅ ነው።

ፍልስጥኤማውያንን ሁሉ ያጠፋ ዘንድ የቀሩትንም ረዳቶች ሁሉ ከጢሮስና ከሲዶና ይቈርጥ ዘንድ ስለሚመጣው ቀን
ቀን የሚለው ተንቀሳቅሶ እንደሚደርስ መስሎ ይናገራል። “በዚያች ቀን የጠላት ሰራዊት ፍልስጥኤማውያንን ሁሉ ያጠፋል ከጢሮስ ይቆርጠዋል።”

የቀሩትንም ረዳቶች ሁሉ ከጢሮስና ከሲዶና ይቈርጥ ዘንድ
አንድን ሰው ማስወገድ እነደ ቅርንጫፍ ከዛፍ ላይ እንደሚቆረጥ አርጎ ይመስለዋል። “ጢሮስና ከሲዶና የሚረዳ ሁሉ ይወገዳል”

ከፍቶርን
ከፍልስጤም በስተሰሜን የምትገኝ ዳርቻ ነው።

Jeremiah 47:5

ቡሀነት በጋዛ ላይ መጥቶአል
ቡሀነት የሚለው መላጣን ያመለክታል። ጋዛ የሚለው ደግሞ ህዝቡን ያመለክታል። “የጋዛ ህዝቦች የራሳቸው ፀጉር ያልቃል”

ቡሀነት
እንደ ፊሊስጤም ከተማ ለጣኦት አምለኮ እና ለትልቅ ሀዘን ተብሎ የራስ ፀጉርን መላጨት።

ዝም ትላለህ
ይህም ትርጉሙ 1) ህዝቡ ከሀዘን የተነሳ ዝም ይላሉ 2) የጠላት ሰራዊት ይገድላቸዋል።

እስከ መቼ ድረስ ገላችሁን ትነጫላችሁ?
እግዚአብሄር ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው የአስቀሎ ህዝቦችን ማልቀስ እንደማያቆሙ ለማሳየት ነው። እግዚአብሄር ህዝቡን ሲናገር ለሴት እነደሚናገር አርጎ ነው የሚያሳየን። ይህችም ከተማዋን እነደሆነ ይናገራል።

ገላችሁን ትነጫላችሁ
ቆዳን መቆራረጥ ሲሆን ጣኦትን ለማምለክ እና ለሞተ ሰው ለማልቀስ የሚደረግ ልምምድ ነው።

በባህር ዳር ላይ ትዕዛዝ ሰጥቷል...
እዚህ ላይ ፍልስጤማውያን እየተናገሩ እንደሆነ ይመስላል። (ታሪካዊ መላምት የሚለውን ተመልከት)

አንተ የእግዚአብሔር ሰይፍ ሆይ፥ ዝም የማትለው እስከ መቼ ነው? ወደ ሰገባህ ግባ ጸጥ ብለህም ዕረፍ።
ፍልስጤማውያን የእግዚአብሄር ሰይፍ እንደሚሰማ መስለው ይናገራሉ። “እግዚአብሄር ሰይፍህን የያዝከው ምቼ ነው በሰይፍህ ዝም ማትለው”

የእግዚአብሄር ሰይፍ
እግዚአብሄር ፍልስጤማዋውያንን ሲቀጣ ከሰሜን የጦር ሰራዊትን ይልካል ይህም እግዚአብሄር ሰይፉን አንደዘረጋ መስሎ ይናገራል።

ዝም የማትለው እስከ መቼ ነው?
የፍልስጤም ህዝቦች በጠላቶቻቸው በሚደርሰው ጥፋት ፍርሃታቸውን በዚህ ጥያቄ ይናገራል።

ጸጥ ብለህም
ሰይፍ በቆራረጠ ቁጥር ድምፅ ያሰማል። የሰይፉን ድምፅ ፀጥ አሰኝ ሲል መገዳደሉን እና መቆራረጡን አስቁምልን ማለታቸው ነው። “አሳርፍ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሰገባህ
ሰይፍ መያዣ እቃ

እንዴት ዝም ትላለህ...በባህር ዳር ላይ
ኤርምያስ መናገሩን ቀጥሎአል። የእግዚአብሄር ሰይፍ አንደሚያርፍ መስሎ ይናገራል። እግዚአብሄር ፍልስጤምን ከሰሜን የጠላት ሰራዊትን በመላክ ቀጣቸው።

እግዚአብሔር በአስቀሎናና በባሕር ዳር ላይ ትእዛዝ ሰጥቶአልና፥ በዚያም አዘጋጅቶታልና
እንዴት ዝም ትላለህ?
ኤርምያስ ይህን ጥያቄ ሰይፉ ማቆም እንደማይችል አንዴ እግዚአብሄር አዞታልና መግደሉን እንደማያቆም ለማሳየት ይጠቀመዋል። “እግዚአብሄር አዞታል እና ማቆም አይችልም”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 48

1 ስለ ሞዓብ፣ የእስራኤል አምላክ፣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "ናባው ጠፍታለችና ወዮላት። ቂርያታይም ተይዛለች አፍራለችም። ምሽጓ
ተደምስሷል፣ ተዋርዷልም። 2 ከእንግዲህ ወዲህ ሞዓብ ትምክሕት የላትም። በሐሴቦን ያሉ ጠላቶቿ በእርሷ ላይ ጥፋትን አሲረዋል። 'ኑ ሕዝብ እንዳትሆን
እናጥፋት። ማድሜንም እንዲሁ ትጠፋለች፣ ሰይፍም ይከታተልሻል።' ብለዋል። 3 አድምጡ! መፍረስና ታላቅ ጥፋት ያለበት የጩኸት ቃል ከሖሮናይምም ተሰማ።
4 ሞዓብ ጠፍታለች። ልጆችዋም ጩኸታቸውን አሰምተዋል። 5 በሉሒት ኮረብታ ለቅሶ እያለቀሱ ይወጣሉ፣ ከጥፋቱም የተነሣ፣ በሖሮናይምም ቍልቍለት
ጩኸትን ሰምተዋል። 6 ሽሹ! ሕይወታችሁን አድኑና በምድረ በዳ እንዳለ ቊጥቋጦ ሁኑ። 7 በሥራሸና በኃብትሽ ታምነሻልና፣ አንቺ ደግሞ ትያዢያለሽ።
ከዚያም፣ ካሞሽ ከካህናቱና ከመሪዎቹ ጋር በአንድነት ወደ ምርኮ ይሄዳል። 8 አጥፊው ወደየከተማው ሁሉ ይመጣል፣ አንዲትም ከተማ አታመልጥም። ስለዚህ
እግዚአብሔርም እንደ ተናገረው ሸለቆው ይጠፋል፣ ሜዳውም ይበላሻል። 9 በእርግጥም በርራ እንድትጠፋ ለሞዓብ ክንፍ ስጡአት። ከተሞችዋ በውስጣቸው
አንድም የማይኖርባቸው ወና ይሆናሉ። 10 የእግዚአብሔርን ሥራ በስንፍና የሚሠራ ርጉም ይሁን! ሰይፉን ደም ከማፍሰስ የሚከለክል ርጉም ይሁን! 11 ሞዓብ
ከወጣትነቱ ጀምሮ ደህንነት ይሰማው ነበር። እርሱ ከዕቃ ወደ ዕቃ ተገላብጦ እንደማያውቀው ወይኑ ነው። ወደ ምርኮም ሄዶ አያውቅም። ስለዚህ ጣዕሙ
ከመቼውም ጊዜ በላይ መልካም ነው፣ መዓዛውም አልተለወጠም። 12 ስለዚህ ተመልከቱ፣ የሚያገላብጡትን ሰዎች የምልክበት ዘመን ይመጣል፣ ይላል
እግዚአብሔር፤ እነርሱም እያፈሰሱ ጋኖቹን ባዶ ያደርጋሉ፣ መስቴዎቹንም ይሰብራሉ። 13 የእስራኤል ቤት ከታመነበት ቤተል እንዳፈረ ሁሉ፣ እንዲሁ ሞዓብ
ከታመነበት ካሞሽ ያፍራል። 14 እናንተ፣ 'እኛ ወታደሮች ነን፣ ጽኑዓን ተዋጊዎች ነን' እንዴት ትላላችሁ? 15 ሞዓብ ይፈርሳል፣ ከተሞቹም ጥቃት ይፈጸምባቸዋል።
የተመረጡትም ጕልማሶች ወደ መታረድ ወርደዋል። ይህ የንጉሡ አዋጅ ነው! ስሙም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው። 16 የሞዓብ ጥፋት ሊመጣ
ቀርቦአል፤ መከራውም እጅግ ይፈጥናል። 17 በሞዓብ ዙሪያ ያላችሁ ሁሉ፣ አልቅሱ። ዝናውንም የምታውቁ ሁሉ፣ 'ብርቱው በትር፣ የከበረው ሽመል ተሰብሯልና
ወዮለት' ብላችሁ አልቅሱለት። 18 በዲቦን የምትኖሪ ሴት ልጅ ከክብር ስፍራሽ ውረጂና በደረቅ መሬት ላይ ተቀመጪ። ሞዓብን የሚያጠፋው፣ ምሽግሽንም
የሚሰብረው ወጥቶብሻልና። 19 በአሮዔር የምትኖሩ ሕዝቦች በመንገድ አጠገብ ቆማችሁ ተመልከቱ። እየሸሹ ያሉትንና የሚያመልጡትን ጠይቁ። 'ምን
ተፈጠረ?' በሉ። 20 ሞዓብም ፈራርሷልና አፈረ። አልቅሱ፣ ጩኹ፣ ለእርዳታም ተጣሩ። ሞዓብ እንደ ተዘረፈ በአርኖን አጠገብ ለሰዎች አውሩ። 21 አሁን
በኮረብታማው ገጠር ላይ ባሉት በሖሎን፣ በያሳ፣ በሜፍዓት ላይ፣ 22 በዲቦን፣ በናባው፣ በቤት ዲብላታይም ላይ፣ 23 በቂርያታይም፣ በቤትጋሙል፣ 24
በቤትምዖን ላይ፣ በቂርዮት፣ በባሶራ፣ እና በሞዓብ ምድር ባሉ የቅርብና ሩቅ ከተሞች ሁሉ ላይ ቅጣት መጥቶአል። 25 የሞዓብ ቀንድ ተቈረጠ፤ ክንዱም
ተሰበረ፣ ይላል እግዚአብሔር። 26 በእኔ በእግዚአብሔር ላይ ኰርቷልና አስክሩት። እንግዲህ ሞዓብ በገዛ ራሱ ትውከቱ ላይ በጥላቻ እጆቹን ያጨበጭባል፣
ደግሞም መሳለቂያ ይሆናል። 27 እስራኤል ለአንተ መሳለቂያህ አልሆነምን? ወይስ ስለ እርሱ በተናገርህ ጊዜ ሁሉ ራስህን እንድትነቀንቅ በሌቦች መካከል
ተገኝቶአልን? 28 እናንተ በሞዓብ የምትኖሩ ሆይ፣ ከተሞችን ትታችሁ በቋጥኝ ውስጥ ተቀመጡ። በዐለታማ ገደል አፋፍ ቤትዋን እንደምትሠራ ርግብ ሁኑ። 29
እጅግ እንደ ታበየ ስለ ሞዓብ ትዕቢት፣ ስለ ትምክህቱም፣ ስለ ኩራቱም፣ ራሱን ስለማክበሩም፣ ስለ ልቡም ትዕቢት ሰምተናል። 30 ምንም ሆኖ የማይቆጠረውን
የድንፋታ ንግግሩን እኔ ራሴ አውቃለሁ፣ ይላል እግዚአብሔር፤ ፉከራው ምንም አልሠራም። 31 ስለዚህ ለሞዓብ አለቅሳለሁ፣ በኃዘኔታ ለመላዋ ሞዓብ
እጮኻለሁ። ለቂርሔሬስ ሰዎች አለቅሳለሁ። 32 አንቺ የሴባማ ወይን ሆይ፣ ከኢያዜር ልቅሶ ይልቅ ለአንቺ አለቅሳለሁ! ቅርንጫፎችሽ የጨው ባሕርን ተሻግረው
ወደ ኢያዜር ባሕር ደርሰዋል። አጥፊዎች በሰብልሽና በወይንሽ ላይ ጥቃት ፈጽመዋል። 33 ክብረ-በዓላዊ ሐሤትና ፍንደቃ ከፍሬያማው እርሻና ከሞዓብ ምድር
ጠፍተዋል። የወይን ጠጁን ከመጥመቂያው አጥፍቻለሁ። ጠማቂውም በደስታ እልልታ አይጠምቅም። እልልታቸውም የደስታ እልልታ አይሆንም። 34
ከሐሴቦን ጩኸት እስከ ኤልያሊና፣ እስከ ያሀጽ ድረስ ድምፃቸውን ሰጥተዋል፤ ከዞዓር እስከ ሖሮናይምና እስከ ዔግላት ሺሊሺያ ድረስ ይደርሳል፤ የኔምሬም
ውኃዎች ደርቀዋልና። 35 በኮረብታው መስገጃ ላይ የሚሠዋውን ለአማልክቱም የሚያጥነውን ከሞዓብ ፍጻሜያቸውን አደርጋለሁ ይላል እግዚአብሔር። 36 ልቤ
ለሞዓብ እንደ እንቢልታ ይጮኻል። ልቤም ለቂርሔሬስ ሰዎች እንደ እንቢልታ ይጮኻል። ያገኙት ትርፋቸው ጠፍቶባቸዋልና። 37 ራስ ሁሉ መላጣ፣ ጢምም ሁሉ
የተላጨ ነውና። በእጅም ሁሉ ላይ ክትፋት በወገብም ላይ ማቅ አለና። 38 በሞዓብ ሰገነት ሁሉ ላይ፣ በእያንዳንዱም የተደላደለ ጣራ እና በሁሉም የሞዓብ
አደባባዮች ላይ ለቅሶ አለ። ሞዓብን ማንም እንደማይፈልጋቸው የሸክላ ዕቃዎች ሰብሬአለሁና፣ ይላል እግዚአብሔር። 39 እንዴት ተገለበጠ! ከለቅሶም የተነሣ
ሞዓብ እያፈረ ጀርባውን እንዴት መለሰ! ብላችሁ አልቅሱ። ስለዚህ ሞዓብ በዙሪያው ላሉት ሁሉ መሳቂያና ድንጋጤ ይሆናል።" 40 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣
"ተመልከቱ፣ ጠላት እንደ ንስር እየበረረ፣ ክንፉንም በሞዓብ ላይ እየዘረጋ ይመጣል። 41 ከተሞቹ ተይዘዋል፣ ምሽጎቹም ተይዘዋል። በዚያም ቀን የሞዓብ
ወታደሮች ልብ ምጥ እንደ ያዛት ሴት ልብ ይሆናል። 42 ስለዚህ ሞዓብ በእኔ በእግዚአብሔር ላይ እብሪተኛ ሆኗልና ሕዝብ ከመሆን ይጠፋል። 43 በሞዓብ
የምትኖሩ ሆይ፣ ፍርሃትና ጉድጓድ፣ ወጥመድም በእናንተ ላይ አለ፣ ይላል እግዚአብሔር። 44 በፍርሃት የሸሸ በጉድጓድ ውስጥ ይወድቃል፥ ከጉድጓድም የወጣ
በወጥመድ ይያዛል፤ በሞዓብ ላይ የምበቀልበትን ዓመት አመጣበታለሁና፣ ይላል እግዚአብሔር። 45 የሸሹ ያለ ምንም ብርታት ከሐሴቦን ጥላ በታች ቆመዋል፤
እሳት ከሐሴቦን፣ ነበልባልም ከሴዎን ወጥቶአልና፣ የሞዓብንም ማዕዘን የሤትንም ልጆች አናት በልቶአልና። 46 ሞዓብ ሆይ፣ ወዮልህ! የካሞሽ ሕዝብ
ተደምስሰዋል፣ ወንዶች ልጆችህ ተማርከዋልና፣ ሴቶች ልጆችህም ወደ ምርኮ ሄደዋልና። 47 ነገር ግን በኋለኛው ዘመን የሞዓብን ምርኮ እመልሳለሁ፣ ይላል
እግዚአብሔር።" የሞዓብ ፍርድ እዚህ ላይ ያበቃል።

Jeremiah 48:1

አጠቃላይ ሀሳብ
ኤርምያስ በብዛት ትንቢትን በግጥም መልክ ይፅፋል። የእብረዊያን ፀሀፊዎች የተለያዩ ንፅፅር ይጠቀሙ ነበር።

ሞአብ
ሞአብ ሕዝቡን ያመለክታለ። “ለሞአብ ህዝቦች”

የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር
ኤርምያስ ማስተዋል ያለብንን መልእክት ሲያስተላልፍ የሚጠቀመው ሀረግ ነው። ኤርምያስ 6፡6 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ናባው ጠፍታለችና ወዮላት
ናባው ሕዝቡን ያመለክታል። “በናባው ያሉ ህዝቦች ጠፍተዋል እና ወዮውላቸው”

ናባው
በሞአብ ናባው ተራራ አካባቢ የሚገኝ ከተማ ነች።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ቂርያታይም አፍራለች
“ቂርያታይም አፍራለች” የሚለው ህዝቡ ማፈሩን ይናገራል። “የቂርያታይም ከተመ በጠላት ከተማረኩ በኋላ ህዝቡን አሳፈሩአቸው”

ቂርያታይም
በሞአብ የምትገኝ ከተማ ነች።

ብርቱ የሆኑ ምሽጎችዋም ይደመሰሳሉ ህዝብዋም በሀፍረት ላይ ይወድቃሉ
ይህ ህዝቡ በሀፍረት እንደወደቁ ያሳያል። “ጠላት የቂርያታይምን ብርቱ ምሽጎችን ይፈርሳሉ ህዝቦችዋም ያፍራሉ”

የሞአብ ትምክት የለም
ህዝቦች ሞአብን አይመኩባትም

ሐሴቦን
ይህ የከተማ ስምነው።

ኑ ህዝብ እንዳትሆን እናጥፋ ብለው ክፉ ነገር አስበዋል።
ይህ የሞአብ ህዝብን ያመለክታል።

ሰይፍም ያሳድድሻል
“ሰይፍ” የጦር መሳሪያቸውን የያዙ ሰራዊትን ያመለክታል። “ጠላቶችህ ያሳድዱአችሁአል እናም ይገድሏቹሃል”

Jeremiah 48:3

አጠቃላይ ሀሳብ
ኤርምያስ በሞአብ ላይ የሚመጣውን ውድቀት መናገሩን ቀጠለ

ሖሮናይም
ይህ በደቡብ ሞአብ የምትገኝ የከተማ ስም ነች።

መፍረስና ታላቅ ጥፋት
እነዚህ ሁለት ቃላት አንድ ሃሳብ ሲኖራቸው በአንድነት ትልቅ ጥፋት እንደሆነ አግንኖ ያሳያል

ሞአብ ጠፍታለች
“የጠላት ሰራዊት ሞአብን አጥፍቶአታል”

ልጆችዋም
የዚህ ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) በሞአብ የሚኖሩ ልጆችን ነው 2) “ልጆች” የሚለው የሞአብ ህዝቦችን ያመለክታል። “የሞአብ ህዝቦች”

ሉሒት
ይህ በሞአብ የሚገኝ ቦታ ነው

የጥፋትና የመባባትን
የጥፋትና የሚለው መጥፋታቸውን ያመለክታል። “ከተማዎቻቸው ጠፍተዋልና”

Jeremiah 48:6

ራሳችሁን አድኑ
ይህ የሞአብ ህዝብን ይናገራል

በምድረበዳ እንዳለ ቁጥቋጦ ሁኑ
ከከተማቸው ወደ በረሃ የሸሹ ሕዝቦች እነደ በበረሃ ላይ እንደምታድግ ቁጥቋዋጦ መስሎ ይናገራል። “በምድረበዳ እንደሚበቀል ቁጥቋጦ ሁኑ”

በመዝገብሽ ታምነሻልና
“ታማኝ ሆነሻል እና”

በስራሽና
በሰራሽው ስራ ወይም ባሳየሽው የስራ ጥረት

አንቺ ደግሞ ትያዢያለሽ
“የጠላት ሰራዊት ይይዝሻል”

ካሞሽም ከካህናቱና ከአለቆቹ ጋር በአንድነት ይማረካል።
“ካሞሽ” የሞአብያን ዋና ጣኦት ነው። ይህም ማለት ህዝቡ ለማምለክ የሰሩቱን ጣኦት የጠላት ሰራዊት ማርኮ ይወስድባቸዋል። “የጠላት ሰራዊት የምታመልኩትን ጣኦት ካሞሽ ማርኮ ይወስዳል።”

Jeremiah 48:8

አጥፊ ወደ ከተማ ሁሉ ይመጣል
“አጥፊ” የሚለው የሚያመለክተው የጠላትን ሰራዊት ነው። “የጠላት ሰራዊት ወደ ከተማ ሁሉ ይመጣል እርሱም ያጠፋቸዋል።”

አንዲትም ከተማ አትድንም
“ከተማ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ቃል ህዝቡን ነው። “ማንም ህዝብ አይድንም።”

ሸለቆውም ይጠፋል ሜዳውም ይበላሻል።
“ሜዳው” እና “ሸለቆው” የሚሉት ቃላት ከተማዋን እና በዛ ስፍራ ያሉ ህዝቦችን ያመለክታሉ። “የጠላት ሰራዊት በሸለቆም ሆነ በሜዳ ላይ ያሉትን ሁሉ ያጠፋሉ”

በርራ እንድትወጣ ለሞአብ ክንፍ ስጡአት
ህዝቡን መርዳት እንደ ክንፍ ተሰጥቶአቸው ህዝቡ እንዲበር መስሎ ይናገራል። “እንደ ክንፍ ሰጥታችሁአቸው እንዲበሩ ያህል በሞአብ ያሉ ህዝቦችን እንዲሸሹ እርዱአቸው”

በርራ እንድትወጣ ለሞአብ ክንፍ ስጡአት
የዚህ የዋናው ቋንቋ ትርጉም ግልፅ አደለም። አንዳንድ የመፅሀፍ ቅዱስ ትርጉም “ለሞአብ ህዝብ መቃብርን አዘጋጁ የጠላት ሰራዊት ስለሚያጠፉአቸው” ይላሉ አንዳንዶች ደግሞ “በሞአብ ላይ ጨው ጨምሩ የጠላት ሰራዊት ያጠፉአቸዋልና” ጠላቶቻቸው ያጠፉአቸው ጊዜ መልሰው በዛ ስፍራ እንዳይኖሩ ይናገራሉ።

ከደም የሚከለክል
“ደም” የሰውን ሕይወት ያመለክታል። “የሚከለክል” መግለደልን ያመለክታል።”ሰውን የሚገድል”

Jeremiah 48:11

ከልጅነት ጀምሮ የተረጋጋ ነበር... የወይን ጠጅ...የምልክበት
እግዚአብሄር በነዚህ ሀረጎች ለሞአብ የሚናገረው እንደ አንድ ሰው አርጎ ሲናገር የሞአብን ህዝብ ያመለክታል። “ከልጅነት ጀምሮ የተረጋጉ ነበሩ...የወይን ጠጅ...የምልካቸው።”

ከእቃ ወደ እቃ አልተገላበጠም
ወይን ጥሩ ጣእም እንዲሰጥ ከተቀመጠበት መንቀሳቀስ እና ከአንድ እቃ ወደ ሌላ እቃ መገልበጥ የለበትም። እግዚአብሄር የሞአብ ህዝብን ማንም ስላላሸነፈ እና ማንም ያለቸውን ማርኮ ስላልወሰደ ብልፅግናቸውን እንደ ማይገላበጥ የወይን ጠጅ መስሎ ይናገራል።

ስለዚህ እነሆ የሚያገላብጡትን የምልክበት ዘመን ይመጣል
በደንብ አድምጡ አስተውሉ ምክንያቱም ያቺ ጊዜ ትመጣለችና

ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ የገለጸበት ምክንያት ቃሉን አስረግጦ ለመናገር ስለፈለገ ነው።፤ ኤርምያስ 1:8 የተተረጎመበትን መንገድ ይመልከቱ።

‹‹እግዚአብሄር የተናገረው ይህንን ነው›› ወይም ‹‹እኔ እግዚአብሄር የተናገርኩት ይህንን ነው››

እነርሱም ያገላብጡታል ጋኖቹንም ባዶ ያደርጋሉ፥ መስቴዎቹንም ይሰብራሉ
የጠላት ሰራዊት የሞአብን ህዝብን ማሸነፍ እና መማረክ እንደ ወይን ጠጅ መስሎ ሌሎች መተው ይቀድዋቸዋል ባዶ ያደርጉአቸውና የወይን እቃውን ይሰብሩታል ብሎ ይናገራል። “እነሱን የሚያጠፉ ሰራዊትን እልካለሁ እነሱም እንደ ወይን ጠጅ ያገላብጡአቸው እና እቃውን ይሰብሩታል”

Jeremiah 48:13

እንዲሁ ሞዓብ
“ሞዓብ” ህዝቡን ያመለክታል። “እንዲሁ የሞአብ ህዝቦች”

ከካሞሽ
“ካሞሽ” የሞአባውያን ዋና ጣኦት ነው። ኤርምያስ 48:7 እንዴት ይህን ስም እንደተረጎመው ተመልከት

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤት ውስጥ የሚኖሩ ቤተሰቦችን ነው። በዚህ ጊዜ ቤት የሚለው የሚያመለክተው የእስራኤላውያን ዘሮችን ነው።ኤርምያስ 2:4 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት። “እስራኤላውያን” ወይም “የእስራኤላውያን ህዝብ ዘር”

ቤተል
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) እስራኤላውያን የወርቅ ጥጃ ሰርተው ሲያመልኩባት የነበረችው ቤተል ከተማን ነው። 2) ቤተል የሚለው እስራኤላውያን የሚያመልኩት የውሸት ጣኦት ስም ነው።

እኛ ኃያላን በሰልፍም ጽኑዓን ነን እንዴት ትላላችሁ?
እግዚአብሄር የሞአብን ወታደሮችን እያናገራቸው መሆኑን ያሳያል። እግዚአብሄር ይህን ጥያቄ ወታደሮችን ለመገሰፅ ሲጠቀም ያሳያል። “ከዚህ በሁላ “እንኛ ሃያላል በሰልፍም ፅኑአን ነን” ማለት አትችሉም”

Jeremiah 48:15

ሞአብ ፈርሶአል ከተሞቹም ጠፍተዋል
“የጠላት ሰራዊት መሞአብን ያፈራርሳል ከተሞቹም ያጠፋሉ”

የተመረጡትም ጕልማሶች ወደ መታረድ ወርደዋል
የተመረጡ የሞአብ ሰዎች ወደጦርነት ሄደው እንደ ሚሞቱ ልክ እንደ ወደ ማረጃ ቦታ የሚሄድ እንስሳን ይመስለዋል።“የተመረጡትም ጎልማሶች ይታረዳሉ።”

ይላል ስሙ የሰራዊተ ጌታ እግዚአብሄር የሆነ ንጉስ
“ንጉስ” የሚለው እግዚአብሄርን ነው። ኤርምያስ 46:18 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት። “ይህ እኔ ንጉሱ እግዚአብሄር የተናገርኩት ነው”

የሞዓብ ጥፋት ሊመጣ ቀርቦአል መከራውም እጅግ ይፈጥናል።
እነዚህ ሁለት አረፍተ ነገሮች አንድ አይነት ሀሳብ ያላቸው ሲሆን የሞአብን መጥፋት አግንኖ ያሳያል። “የሞአብ ጠላቶች በቅርብ ያጠፉአታል”

መከራውም እጅግ ይፈጥናል።
መከራ በቅርብ ጊዜ ውስጥ እነደሚፈጠር ልክ እንደ መከራ በፍጥነት ወደ ሆነቦታ እንደሚሄድ መስሎ ይናገራል። “መጥፎ ነገሮች በቅርብ ጊዜ ይፈጠራል”

ብርቱው በትር፥ የከበረው ሽመል፥ እንዴት ተሰበረ!
“በትር” እና “ሽመል” የሚሉት ቃሎች ሀይል እና ሞኣብ ለሌሎች ከተማዎች የምትሰጠው እርዳታን ያመለክታል። “የሞአብ ጠላት ሃያልነቷን ወስዶባታል።”

Jeremiah 48:18

በዲቦን የምትኖሪ ሆይ
በዲቦን የሚገኙ ህዝቦችን እንደ ዲቦን ሴት ልጅ መስሎ ይናገራል። “በዲቦን የምትኖሩ ህዝቦች”

ዲቦን
ይህ በሞአብ የምትገኝ ከተማ ነች።

ሞአብን የሚያጠፋ ወጥቶብሻልና
“የጠላት ሰራዊት ሞአብን ሊያጠፉአት ነው”

በአሮዔር
ይህ በሞአብ የምትገኝ ከተማ ነች

ብለሽ ጠይቂ
“ህዝቡን ጠይቂ” ወይም “ወንዱን እና ሴቱን ጠይቂ”

ሞአብ ፈርሶአልና አፈረ
“ሞአብ” የሚለው ህዝቡን ያመለክታል። “ሞአብ በጠላት ሰራዊት ፈርሶአል ህዝቡም አፍሮአል”

አልቅሱም ጩኹም
በከፍተኛ ድምፅ በምሬት እና በንዴት አለቀሱ

የሞአብ መደምሰስ
“የጠላት ሰራዊት ሞአብን ደመሰሰ”

Jeremiah 48:21

በሞዓብም ምድር ከተሞች ሁሉ ቅርብና ሩቅ በሆኑ ላይ ፍርድ መጥቶአል።
የእግዚአብሄር ቅጣት በሞአብ ከተማዎች ላይ መምጣቱን እንደ ቅጣቱ ከቦታ ቦታ እየተንቀሳቀሰ የሚቀጣ አርጎ ይናገራል። “በሞዓብም ምድር ከተሞች ሁሉ ቅርብና ሩቅ እግዚአብሄር ይቀጣል”

ሆሎን፣ ቢያሳ እና በሜፍዓት...ባሶራ
እነዚህ በሞአብ የሚገኙ ከተማዎች ናቸው።

የሞአብ ቀንድ ተቆረጠ ክንዱም ተሰበረ
ሁለቱም አረፍተ ነገሮች አንድ ሃሳብ ሲኖራቸው “ቀንድ” እና “ክንዱም” የሚሉት የሚያመለክቱት ስልጣን ወይም ሀይል ነው። እነዚህን ተቆረጡ ሲል የነበረውን ስልጣን ወይም ሀይል ተወሰደባቸው ማለት ነው። “ሞአብ ደካማ ሆነዋል ህዝቡም መዋጋት አቅቶታል።”

ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ የገለጸበት ምክንያት ቃሉን አስረግጦ ለመናገር ስለፈለገ ነው።፤ ኤርምያስ 1:8 የተተረጎመበትን መንገድ ይመልከቱ። ‹‹እግዚአብሄር የተናገረው ይህንን ነው›› ወይም ‹‹እኔ እግዚአብሄር የተናገርኩት ይህንን ነው››

Jeremiah 48:26

በእግዚአብሔር ላይ ኰርቶአልና አስክሩት
እግዚአብሄር እየተናገረ ነው። “አስክሩት” የሚለው ትእዛዝ እግዚአብሄር ሊያመጣ ያለውን ነገር ያሳያል። በዚህ ላይ ሞአብን የሚያመለክት ሲሆን ሞአብ ሲል ደግሞ የሞአብ ህዝብን ያመለክታል። “እኔ እግዚአብሄር የሞአብ ህዝቦችን አሰክራለሁ በኔ ላይ ኮርተዋል እና”

አስክሩት
የእግዚአብሄር ቅጣት እንደ ወይን ስካር ሲመስለው የሚያረጉት ሁሉ በሞኝነት ስለሚሆን ሰዎች ይስቁባቸዋል። “እንደ ሰከረ ሰው አደርጋችኋለሁ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሞአብም በጥፋቱ ላይ ይነከባለላል..መሳቂያ ይሆናል
አሁንም እግዚአብሄር የሞአብ ህዝብን እንደ ሰከረ ሰው ይመስላቸዋል። “የሞአብ ህዝቦች በትፋቱ ላይ እንደሚንከባለል ይሆናሉ… መሳቂያም ይሆናሉ”

መሳቂያም ይሆናል
“ሰዎች ይስቁበታል”

እስራኤል ለአንተ መሳቂያ አልሆነምን?
ይህን ጥያቄ እግዚአብሄር ለሞአብ ህዝብ እስራኤላውያንን እንዴት ጨቆኑ ለማስታወስ ሲጠቀም ያሳያል። “በእስራኤል ህዝብ ላይ ስትስቁ ነበር”

እስራኤል...ተገኝቶአልን...አልሆነምን...ስለ እርሱ
“እስራኤል” የሚለው የእስራኤል ህዝብን ያመለክታል። “የእስራኤል ህዝብ…ተገኝተዋል…አልሆኑምን…ስለ እነርሱ”

በሌቦች መካከል ተገኝቶአልን? ስለ እርሱ በተናገርህ ጊዜ ራስህን ትነቀንቃለህ
ይህ ጥያቄ እግዚአብሄር የሞአብ ህቦችን በእስራኤላውያን ላይ ምንም ሳያረጉ እንዳሳፈሩአቸው ለመገሰፅ ይጠቀማል። “ምንም ሌቦች ባይሆኑም እንኳን ስለ እርሱ ራስህን ትነቀንቃለህ”

እርሱ በተናገርህ ጊዜ ራስህን ትነቀንቃለህ
ይህ አንድን ሰው ደስ በማይል አይን በመመልከት የምናሳየው ስሜት።

Jeremiah 48:28

በዓለት ውስጥ
ይህ ቃል የተራራን ገደላማ ገጽታ ያመለክታል

በገደል አፋፍም ቤትዋን እንደምትሠራ እንደ ርግብ ሁኑ
አረፍተ ነገሩ አግንኖ የሚያሳየው ህዝቡ ከተማዎቻቸውን ለቀው ወደ ድንጋያማ ተራራ ላይ ሄደው ከጠላቶቻቸው እንዲደበቁ ነው።

በገደል አፋፍ
“በገደል አፋፍ” የሚለው የዋሻ መግቢያ እንደሆነ ይናገራል። “በዋሻው መግቢያ ላይ”

ሰምተናል
ይህ የሚያመለክተው በዚያ አካባቢ ዙሪያ ያሉ ሁሉንም ሰዎች ነው።

ስለ ትምክህቱም ስለ ኩራቱም ስለ መጓደዱም ስለ ልቡም ትዕቢት
እነዚህ ቃላቶች ሁሉም አንድ ሃሳብን ያሳያሉ: በአንድነት የሞአብ ህዝብ የትእቢቱን እና የኩራቱን ግዝፈት ያመለክታል።

ስለ ልቡም ትዕቢት
“ልቡም” የሚው የሰውን የውስጥ ማንነት ይናገራል።

Jeremiah 48:30

ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ የገለጸበት ምክንያት ቃሉን አስረግጦ ለመናገር ስለፈለገ ነው።፤ ኤርምያስ 1:8 የተተረጎመበትን መንገድ ይመልከቱ። ‹‹እግዚአብሄር የተናገረው ይህንን ነው›› ወይም ‹‹እኔ እግዚአብሄር የተናገርኩት ይህንን ነው››

እልኸኝነታቸውን አውቃለሁ
ይህ አረፍተነገር እግዚአብሄር የሞአብን እልኸኝነት የሚያሳይ ነው።

እልኸኝነታቸው... ትምክህታቸው
እነዚህ የሚያመለክቱት የሞአብ ከተማ ህዝቦችን ነው።

እልኸኝነታቸው
“ትእቢታቸው” ወይም “የትእቢትን ቃላት ተናገሩ”

ስለዚህ ለሞዓብ አለቅሳለሁ ለሞዓብም ሁሉ እጮኻለሁ
ሁለቱም አረፍተ ነገሮች አንድን ሃሳብ ይጋራሉ። “ለሞአብ ህዝቦች አለቅሳለሁ እጮኻለሁ”

አለቅሳለሁ
ይህ የሚያመለክተው 1) ኤርምያስን ያመለክታል 2) እግዚአብሄርን ያመለክታል

አለቅሳለሁ
በከፍተኛ ድምፅ እና ረጅም የሆነ ለቅሶ ሲሆን ምን ያህል እንዳዘነ ያሳያል

ቂርሔሬስ
ይህ የሞአብ የድሮ ዋና ከተማ ስም ነው።

ኢያዜር ... ሴባማ
እነዚህ የሞአብ ከተማ ስሞች ናቸው።

አንቺ የሴባማ ወይን ሆይ...ቅርንጫፎችሽ ባህርን ተሻግረዋል... ወይንሽ
ሴባማ የምትባለው ከተማ ብዙ የወይን እርሻ አላት። እዚህ እግዚአብሄር ለሴባማ ህዝብን እንደ ወይን መስሎ ይናገራል። “የሴባማ ህዝብ ሆይ…”

አጥፊው በሰብልሽና በወይንሽ ላይ መጥቶአል።
እግዚአብሄር የሴባማ ህዝቦችን እንደ ወይን መስሎ ይናገራል። “አጥፊው በሰብልሽ እና በወይንሽ ላይ መጥቶ ወስዶብሻል”

አጥፊው
የጠላት ስራዊት

Jeremiah 48:33

ሐሤትና ደስታ ከፍሬያማው እርሻና ከሞዓብ ምድር ጠፍተዋል
“ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የሞአብ ህዝቦች ሐሴትና ደስታ አይኖራቸውም ይህም በፍሬአማ እርሻቸው ምክንያት”

ጠጁን ከመጥመቂያው አጥፍቻለሁ
ወይን ጠጅ መጥመቂያውን ከልክያለሁ ወይም “ህዝቡ ወይን እንዳያጠምቁ አስቁሚያለሁ”

አጥፍቻለሁ
ይህ የሚናገረው እግዚአብሄር እንደሆነ ያመለክታል።

አይጠምቁም
ወይን አጥማቂዎች የወይን ዘለላዎቹ ላይ በመርገጥ ጭማቂ ያወጣሉ።

Jeremiah 48:34

ሐሴቦን
በኤርምያስ 48:2 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ኤልያሊና...ያህፅ...ዞዓር...ሀሮናይም...ዔግላት ሺሊሺያ
እነዚህ በሞአብ የሚገኙ የከተማዎች ስም ነው

ኔምሪም
በሙት ባህር አካባቢ የሚገኝ የወንዝ ስም ነው።

ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ የገለጸበት ምክንያት ቃሉን አስረግጦ ለመናገር ስለፈለገ ነው።፤ ኤርምያስ 1:8 የተተረጎመበትን መንገድ ይመልከቱ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

‹‹እግዚአብሄር የተናገረው ይህንን ነው›› ወይም ‹‹እኔ እግዚአብሄር የተናገርኩት ይህንን ነው››

Jeremiah 48:36

ልቤ ለሞዓብ እንደ እንቢልታ ይጮኻል
“ልብ” የሚለው ሙሉ ሰውን ሲወክል የሰውን የሀዘን ለቅሶ እንደ እንቢልታ ድምፅ መስሎ ይመስለዋል። ”ለሞአብ በሀዘን አለቅሳለሁ። ለቅሶዬም እንደ እምቢልታ ድምፅ ነው”

ልቤም
ይህ የሚያመለክተው 1) ኤርምያስን ያመለክታል 2) እግዚአብሄርን ያመለክታል

ቂርሔሬስ
ቂርሔሬስ የድሮ የሞአብ ዋና ከተማ ነው። ኤርምያስ 48:13 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ራስ ሁሉ መላጣ ጢምም ሁሉ የተላጨ ነውና በእጅም ሁሉ ላይ ክትፋት በወገብም ላይ ማቅ አለና
እነዚህ ሁሉ የሞአብ ህዝብ በሀዘን ላይ የሚደርጉት ድርጊቶች ነው።

ክትፋትም
ቆዳን መቆራረጥ

Jeremiah 48:38

በሁሉም ቦታ ለቅሶ አለ
“ሁሉም ቦታ ህዘቡ ያለቅሳል”

ሰገነት ሁሉ
የሁሉም የቤት ጣራ

በአደባባዩ
ክፍት የሆነ የህዝብ ቦታዎች እንደ ገበያ

ሰብሬአለሁና
ይህ ቃል እግዚአብሄርን እንደተናገረ ያመለክታል

ይላል እግዚአብሄር
x

Jeremiah 48:40

እንደ ንስር ይበርራል ክንፉንም በሞዓብ ላይ ይዘረጋል
እነዚህ ሀረጎች ንስር የሚበላውን ዞሮ እንደ የሚይዘው ሁሉ ሀያል ሰራዊት ሞአብን እንደሚያሸንፍ ይናገራል

ከተማዎቹ ተይዘዋል አምባዎቹም ተወስደዋል
“የጠላት ሰራዊት ከተማዎቹን ይዘዋል አምባዎቹንም ወስደዋል”

ቂርዮት
ይህ በሞአብ የሚገኝ የከተማ ስም ነው። ኤርምያስ 48:24 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

በዚያም ቀን የሞዓብ ኃያላን ልብ ምጥ እንደ ያዛት ሴት ልብ ይሆናል
ይህ አረፍተነገር የሞአብ ሰራዊትን ፍራቻ ሴት ልጅ በምጥ ላይ ካላት ከሚሰማት ፍራቻ ጋር ያወዳድረዋል።

በዚያም ቀን የሞዓብ ኃያላን ልብ ምጥ እንደ ያዛት ሴት ልብ ይሆናል
“ልብ” የሚለው የአንድ ሰውን ስሜት ይናገራል። “የሞአብ ሰራዊት ፍራቻ እንደ ምጥ ውስጥ እንዳለች ሴት ልጅ ነው”

Jeremiah 48:42

ህዝብ ከመሆን ይጠፋል
“የጠላት ሰራዊት ሞአብ ህዝብ እንዳይሆን ያጠፉአቸዋል”

ፍርሃትና ጉድጓድ ወጥመድም በአንተ ላይ አለ
“በአንተ ላይ አለ” የሚለው አንድን ነገር መለማመድን ያመለክታል። “ፍርሃትና ጉድጓድ ወጥመድም ትለምዳችኋላችሁ”

በሞአብ የምትኖሪ ሆይ
ይህ የሚያመለክተው አጠቃላይ ሞአብ ላይ የሚኖሩትን ነው። “የሞአብ ህዝብ ሆይ”

ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ የገለጸበት ምክንያት ቃሉን አስረግጦ ለመናገር ስለፈለገ ነው።፤ ኤርምያስ 1:8 የተተረጎመበትን መንገድ ይመልከቱ። ‹‹እግዚአብሄር የተናገረው ይህንን ነው›› ወይም ‹‹እኔ እግዚአብሄር የተናገርኩት ይህንን ነው››

በጉድጓድ ውስጥ ይወድቃል... በወጥመድ ይያዛል
ጉድጓድ እና ወጥመድ የሚሉት ቃላት በህዝቡ ላይ መጥፎ ነገር እንደሚሆን የሚናገሩ ናቸው። ህዝቦች ሊፈጠር ካለ መጥፎ ነገር ሊሸሹ እና ሊያመልጡ ይችላሉ ነገር ግን ሌላ መጥፎ ነገር ይገጥማቸዋል።

አመት
“አመት” የሚለው “ጊዜ” “ወቅት” ወደ ሚለው ሊተረጎም ይችላል

Jeremiah 48:45

የሸሹ
ይህ ሞአብ በምትፈራርስበት ጊዜ መሸሸ የቻሉ ሰዎችን ነው።

ከሀሴቦን ጥላ በታች ቆመዋል
“ጥላ በታች” የሚለው መጠለያ ወይም መከለያ ነው። “ለመጠለያ በሀሴቦን ይሸፈናሉ”

እሳት ከሐሴቦን ነበልባልም ከሴዎን ወጥቶአል
እነዚህ ሁለት ሀረጎች አንድ አይነት ሀሳብ ሲይዙ እነዚህም የሞአብ ውድቀት ከሐሴቦን ሲጀምር ንጉሱ ሴዎን ነበረ።

ሐሴቦን
ኤርምያስ 48:2 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ሴዎን
ይህ ሐሴቦን ሲመራ እና ሲያስተዳድር የነበረ የአሞራዊ ንጉስ ስም ነው።

የሞዓብንም ማዕዘን የሜትንም ልጆች አናት በልቶአል።
“አናት” የሚለው ቃል የሞአብ ህዝቦችን በአጠቃላይ ያመለክታል። “በኩራት የሚጮሁትን የሞአብ ህዝብን በእሳት ይነዳሉ”

አናት
ከአይኖች ከፍ ብሎ የሚገኝ ከፀጉር ክፍል ደግሞ ዝቅ ብሎ የሚገኝ የፊት ክፍል ነው።

Jeremiah 48:46

የካሞሽ ወገን ጠፍቶአል
“የጠላት ሰራዊ ካሞሽን የሚያመልኩትን ህዝቦች አጠፋ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ካሞሽ
“ካሞሽ” የሞአብያን ዋና ጣኦት ነው። ኤርምያስ 48:07 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ወንዶች ልጆችህ ተማርከዋልና፥ ሴቶች ልጆችህም ወደ ምርኮ ሄደዋልና
“የጠላት ሰራዊት ወንድ እና ሴት ልጆችህን ማርከው ወስደዋቸዋል።”

የሞአብን ምርኮ እመልሳለሁ
የሞአብ የነበረው ጥሩ ነገርን እመልሳለሁ። ኤርምያስ 29:14 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

በኋላኛው ዘመን
የወደፊቱ

ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ የገለጸበት ምክንያት ቃሉን አስረግጦ ለመናገር ስለፈለገ ነው።፤ ኤርምያስ 1:8 የተተረጎመበትን መንገድ ይመልከቱ። ‹‹እግዚአብሄር የተናገረው ይህንን ነው›› ወይም ‹‹እኔ እግዚአብሄር የተናገርኩት ይህንን ነው››

የሞአብ ፍርድ እስከዚህ ድረስ ነው።
ይህ ስለ ሞአብ ኤርምያስ የተናገረው የመጨረሻው ትንቢት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 49

1 ስለ አሞን ልጆች፣ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "እስራኤል ልጆች የሏትምን? ወይስ የትኛውንም ነገር ከእስራኤል የሚወርስ የላትምን? ሚልኮም ጋድን
ለምን ወረሰ? ሕዝቡስ በከተሞቿ ላይ ስለ ምን ተቀመጠ? 2 ስለዚህ ተመልከቱ፣ በአሞን ልጆች ከተማ በረባት ላይ የጦርነት ውካታን የማሰማበት ዘመን
ይመጣል፣ ይላል እግዚአብሔር፤ የፍርስራሽ ክምርም ትሆናለች፣ ሴቶች ልጆችዋም በእሳት ይቃጠላሉ። እስራኤልም የወረሷትን ትወርሳለች፣" ይላል
እግዚአብሔር። 3 "ሐሴቦን ሆይ፣ ጋይ ፈርሳለችና አልቅሺለት! እናንተም የረባት ሴቶች ልጆች ጩኹ! ማቅ ልበሱ። ሚልኮም ካህናቱና አለቆቹም በአንድነት
ይማረካሉና ጩኹ፣ ማቅም ታጠቁ፣ አልቅሱም፣ በቅጥሮችም መካከል ተሯሯጡ። 4 ማን ይመጣብኛል ብለሽ በብርታትሽ የታመንሽ አንቺ ከዳተኛ ልጅ ሆይ፣
በሸለቆችሽ፣ ውኃ በሚያረካቸው ሸለቆችሽ፣ ስለ ምን በብርታትሽ ትመኪያለሽ? 5 ተመልከቺ፣ ሽብርን አመጣብሻለሁ፣ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፤ ይህ
ሽብር በዙሪያሽ ከከበቡሽ ሁሉ ዘንድ ይሆናል። እያንዳንዳችሁም በፊታችሁ ወዳለው ስፍራ ትበተናላችሁ። የሚሸሹትንም የሚሰበስብ አይኖርም። 6 ነገር ግን
ከዚያ በኋላ የአሞንን ልጆችን ምርኮ እመልሳለሁ፣ ይላል እግዚአብሔር።" 7 ስለ ኤዶምያስ፣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "በውኑ በቴማን
ከእንግዲህ ጥበብ አይገኝምን? ማስተዋል ካላቸውስ መልካም ምክር ጠፍቶአልን? ጥበባቸው ተበላሽቷልን? 8 ሸሹ! ተመለሹ! እናንተ በድዳን የምትኖሩ
ሆይ፣ በጥልቅ ውስጥ ተቀመጡ። የዔሳውን ጥፋት እርሱን በምቀጣበት ጊዜ አመጣበታለሁና 9 የወይን አዝመራ ለቃሚዎች ወደ አንተ ቢመጡ፣ቃርሚያውን
አይተውልህምን? ሌቦችስ በሌሊት ቢመጡ፣ የሚሠርቁት እስኪበቃቸው ድረስ አይደለምን? 10 እኔ ግን ዔሳውን ዕራቁት አሁት። የተሸሸገበትንም ስፍራዎች
ገለጥሁ። ስለዚህ ይሸሸግ ዘንድ አይችልም። ልጆቹ፣ ወንድሞቹ፣ እንዲሁም ጎረቤቶቹ ጠፍተዋል፤ እርሱም የለም። 11 ድሀ አደጎችህን ተዋቸው። እኔም
ለሕይወታቸው እንክብካቤ አደርጋለሁ፤ መበለቶችህም በእኔ ሊታመኑ ይችላሉ።" 12 እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፣ "ተመልከቱ ያልተገባቸው ሰዎች ጽዋውን
በእርግጥም ሊጠጡት ይገባቸዋል። አንተም ሳትቀጣ የምትቀር ይመስልሃልን? በእርግጥ ትጠጣለህ እንጂ ያለ ቅጣት አትቀርም። 13 ባሶራ መደነቂያና
መሰደቢያ፣ መረገሚያም እንድትሆን በራሴ ምያለሁ፣ ይላል እግዚአብሔር። ከተሞችዋም ሁሉ ለዘላለም ባድማ ይሆናሉ። 14 ከእግዚአብሔር ዘንድ ወሬ
ሰምቻለሁ፣ መልእክተኛም በአሕዛብም መካከል ተልኳል፣ 'ተሰብሰቡ፣ እርስዋንም አጥቁ። ለጦርነትም ተነሡ' ይላል። 15 "ተመልከቱ፣ በንጽጽር ስትታይ
በአሕዛብ ዘንድ የተጠቃህ፣ በሰዎችም ዘንድ የተናቅህ አድርጌሃለሁ። 16 በዓለት ንቃቃት ውስጥ የምትኖር፣ የተራራውን ከፍታ የምትይዝ ሆይ፣ ድፍረትህና
የልብህ ኵራት አታልለውሃል። ቤትህን ምንም እንደ ንስር ከፍ ብታደርግ፣ ከዚያ አወርድሃለሁ፤ ይላል እግዚአብሔር። 17 ኤዶምያስም የሚያልፉባት ሁሉ
እስኪደነቁ ድረስ መሸበሪያ ትሆናለች። ስለ መጣባትም መቅሠፍት ሁሉ እንዲህ ያሉ ሰዎች ሁሉ ተደናግጠው ያፍዋጩባታል። 18 "ሰዶምና ገሞራ፣ በእነርሱም
አጠገብ የነበሩት ከተሞች እንደ ተገለበጡ፣" ይላል እግዚአብሔር፣ "እንዲሁ በዚያ ሰው አይቀመጥም የሰው ልጅም አይኖርባትም። 19 ተመልከቱ፣ ከእርስዋ
ዘንድ በቶሎ አባርራቸዋለሁና በጠነከረው አምባ ላይ ከዮርዳኖስ ትዕቢት እንደ አንበሳ ይወጣል፤ የተመረጠውንም በእርስዋ ላይ እሾመዋለሁ፤ እንደ እኔ ያለ ማን
ነው? ወይስ ለእኔ ጊዜ የሚወስን ማን ነው? ወይስ ፊቴን የሚቃወም እረኛ ማን ነው? 20 "ስለዚህ እግዚአብሔር በኤዶምያስ ላይ የመከረባትን ምክር፣
በቴማንም በሚኖሩ ሰዎች ላይ ያሰባትን አሳብ አድም። በእውነት ትንንሽ መንጎች ሳይቀሩ ይጐተታሉ። በእውነት ማደሪያቸውን ባድማ ያደርግባቸዋል። 21
ከመውደቃቸው ድምፅ የተነሣ ምድር ተናወጠች። የጩኸታቸውም ድምፅ በቀይ ባሕር ተሰማ። 22 ተመልከቱ፣ አንዱ መጥቶ እንደ ንስር ወጥቶ ያጠቃል፣
እያንዣበበ ክንፉን በባሶራ ላይ ይዘረጋል። ያን ጊዜ በዚያ ቀን፣ የኤዶምያስ ወታደሮች ልብ ምጥ እንደ ያዛት ሴት ልብ ይሆናል።" 23 ስለ ደማስቆ፣ "ክፉ ወሬ
ሰምተዋልና ሐማትና አርፋድ አፈሩ። ቀለጡ! ሊረጋጋ በማይችል ባሕር ላይ ኅዘን አለ። 24 ደማስቆ እጅግ ደከመች። ትሸሽም ዘንድ ዘወር አለች፤ ሽብር ያዛት፣
እንደ ወላድም ሴት ጣርና ምጥ ያዛት። 25 ሕዝቦቿም፣ 'የተመሰገነችው ከተማ፣ የደስታዬ ከተማ፣ ስፍራውን ሳትለቅቅ እንዴት ቀረች?' ይላሉ። 26 ስለዚህ
ጐበዛዝትዋ በአደባባይዋ ላይ ይወድቃሉ፣ በዚያም ቀን ተዋጊዎቿ ሁሉ ይጠፋሉ፣ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።" 27 "በደማስቆም ቅጥር ላይ እሳት
አነድዳለሁ፣ የወልደ አዴርንም አዳራሾች ትበላለች።" 28 የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ስለ መታ ስለ ቄዳርና ስለ አሶር መንግሥታት፤ እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል፦ "ተነሡ ወደ ቄዳርም ውጡ፣ የምሥራቅንም ልጆች አጥፉ። 29 ጦር ሠራዊቱ ድንኳናቸውንና መንጋቸውን ይወስዳል፤ መጋረጆቻቸውንና ዕቃቸውን ሁሉ
ግመሎቻቸውንም ለራሳቸው ይወስዳሉ። በዙሪያቸውም ሁሉ ጥፋትን ጥሩባቸው፣ 'ሽብር በዙሪያቸው ሁሉ አለ!" 30 ሸሹ! በሩቅ ቦታም ተቅበዝበዙ! እናንተ
በአሶር የምትኖሩ ሆይ፣ የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ተማክሮባችኋልና፣ አሳብም አስቦባችኋልና በጥልቅ ውስጥ ተቀመጡ፣ ይላል እግዚአብሔር። ሸሹ! ዙሩና
ተመለሱ! 31 ዕርፊት ወዳለበት በዋስትናም ወደ ተቀመጠው፣ ደጅና መወርወሪያ ወደሌለው ብቻውንም ወደ ተቀመጠው ሕዝብ ውጡ፣ ተነሡ! አጥቁ!። 32
ግመሎቻቸው ይበዘበዛሉ፣ የእንስሶቻቸውም ብዛት በጦርነት ይማረካል። ጠጉራቸውንም በዙሪያ የሚላጩትን ሰዎች ወደ ነፋሳት ሁሉ እበትናቸዋለሁ፤
ከየዳርቻቸውም ሁሉ ጥፋት አመጣባቸዋለሁ፥ ይላል እግዚአብሔር። 33 አሶርም የቀበሮ መኖሪያና የዘላለም ባድማ ትሆናለች። በዚያም ሰው አይኖርም፣ የሰው
ልጅም አይቀመጥባትም።" 34 ስለ ኤላም ወደ ነቢዩ ወደ ኤርምያስ የመጣው የእግዚአብሔር ቃል ይህ ነው። ይህ የሆነው በይሁዳ ንጉሥ በሴዴቅያስ
መንግሥት መጀመሪያ ነው። እንዲህም አለ፣ 35 "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ዋና የኃይላቸው መሣሪያ የሆነውን የኤላምን ቀስት እሰብራለሁ።
36 ከአራቱም ከሰማይ ማዕዘናት አራቱን ነፋሳት በኤላም ላይ አመጣለሁ፣ የኤላምን ሕዝብ ወደ እነዚያ ነፋሳት ሁሉ እበትናቸዋለሁ። ከኤላም የተሰደዱ ሰዎች
የማይበተኑበት ሕዝብ አይገኝም። 37 ስለዚህ በጠላቶቻቸውና ነፍሳቸውን በሚሹአት ፊት ኤላምን አስደነግጣለሁ። ክፉ ነገርን እርሱም ጽኑ ቍጣዬን
አመጣባቸዋለሁና፣ ይላል እግዚአብሔር። እስካጠፋቸውም ድረስ በኋላቸው ሰይፍ እሰድድባቸዋለሁ። 38 ከዚያም፣ ዙፋኔንም በኤላም አኖርና ንጉሡን
ከእነአለቆቹ አጠፋለሁ፣ ይላል እግዚአብሔር። 39 ነገር ግን በኋለኛው ዘመን የኤላምን ምርኮ እመልሳለሁ፣ ይላል እግዚአብሔር።"

Jeremiah 49:1

አጠቃላይ ሀሳብ
ግጥም ሚለውን ተመልከት

እግዚአብሄር እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ማስተዋል ያለብንን መልእክት ሲያስተላልፍ የሚጠቀመው ሀረግ ነው። ኤርምያስ 6:6 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ለእስራኤል ልጆች የሉትምን ወይስ ወራሽ የለውምን? ስለ ምን ሚልኮም ጋድን ወረሰ? ሕዝቡስ በከተሞቹ ላይ ስለ ምን ተቀመጠ?
እግዚአብሄር ይህን ጥያቄ ለእስራኤል ልጆች በጋድ እንዲኖሩ እንጂ ሚልኮን በሚየመልኩት እንዳይሆን ይናገራል። “በእስራኤል ምድር ውስጥ ብዙ ወራሽ እስራኤላውያን አሉ”

ስለምን ምልኮም
የሚያመለክተው ሚልኮምን የሚያመልኩ ሰዎችን ያመለክታል። “ለምን ሰዎች ሚልኮምን ያመልካሉ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ስለዚህ
ይህ ቀጣዩን አጉልቶ ያሳያል

ዘመን ይመጣል
“ዘመን ይመጣል” የሚለው የወደፊቱን ጊዜ ይናገራል። ኤርምያስ 7:32 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ በመጥራት ያዛል። ኤርሚያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

የሰልፍ ውካታን የማሰማበት
እግዚአብሄር ሰራዎቱን ማወኩን እንደ ለጦርነት የድምፅ ምልክትን እንደሰጠ አርጎ ይናገራል።

ሴት ልጆችዋም በእሳት ይቃጠላሉ
የጠላት ሰራዊት ከተማዋን ያቃጥሉአታል

እስራኤልም የወረሱትን ይወርሳል
እስራኤል የእስራኤል ህዝብን ያመለክታል። የአሞን ልጆች ከእስራኤል ምድር የወሰዱትን ያመለክታል። “የእስራኤል ህዝብ የአሞን ህዝብ የወሰደውን ምድር ይወርሳል”

Jeremiah 49:3

ማቅም ታጠቁ
ከፍተኛ ለቅሶ እና ሀዘን

ሐሴቦን
ይህ የከተማ ስም ነው እንደ ኤርምያስ 48:2 አተረጓጎም። ሐሴቦን የሚለው እዚህ ላይ ህዝቡን ያመለክታል

ጋይ ፈርሳለችና
ጠላቶችህ ጋይን ያፈራርሷታል።

የረባት ሴቶች ልጆች ሆይ
ይህ የሚኖረው ትርጉም 1) “ሴት ልጆች” የሚለው በረባት የሚኖሩ ሴቶችን ያመለክታል። “የረባት ሴቶች” 2) ሁሉም ሰዎች በአጠቃላይ እንደ ረባት ሴት ልጅ አርጎ ይናገራል። “የረባት ህዝብ”

ሚልኮም ካህናቱና አለቆቹም በአንድነት ይማረካሉና
“ጠላቶችህ ጣኦታችሁን ሚልኮምን ይማርኩና ይወስዱታል”። ይህም ጠላቶቻቸው ጣኦታቸውን ሚልኮምን ወደ ምድራቸው ይወስዱታል።

በሸለቆችሽ ውሃ... ስለምን ትመኪያለሽ
እግዚአብሄር ህዝቡ እንዲያስተውል ለምን ባላቸው ትላልቅ ፍራፍሬ እና ሸለቆ እንደሚመኩ ይጠይቃል። “ባላቹህ ሸለቆ አትመኩ”

በሸለቆችሽ፥ ውኃ በሚያረካቸው ሸለቆችሽ፥ ስለ ምን ትመኪያለሽ?
አንዳንድ መፅሀፍ ቅዱስ ሲተረጉመው “ስለምን ትመፃደቃላችሁ ሃይላችሁ ተንከታክቶአል”

ከዳተኛ ልጅ ሆይ
የአሞን ህዝቦች እንደ ሴት ልጅ ይመስላል። “ከዳተኛ ህዝብ” ወይም “አመፀኛ ህዝብ”

ማን ይመጣብኛል ብለሽ
አሞናውያን ይህን ጥያቄ ማንም እንደማያሸንፋቸው ስለሚያምኑ የሚጠይቁት ነው። “ማንም አያሸንፈንም የሚል የስህተት ሀሳብ ነው”

Jeremiah 49:5

ፍርሀትን አመጣብሻለሁ
ፍርሀት “ፍራቻ” ማለት ይቻላል። “ፍራቻን በናተ ላይ አመጣለሁ”

አመጣብሻለሁ
ይህ የአሞንን ህዝብ ያመለክታል

ይላል የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ በመጥራት ያዛል። ኤርሚያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

እነሆ፥ በዙሪያሽ ካሉት ሁሉ ዘንድ ፍርሃትን አመጣብሻለሁ... እያንዳንዳችሁም በፊታችሁ ወዳለው ስፍራ ትሰደዳላችሁ፥ የሚሸሹትንም የሚሰበስብ የለም
ፍርሀት “ፍራቻ” ማለት ሲሆን ይህም “በፊታችሁ ወዳለው ስፍራ ትሰደዳላችሁ፤ ሁላችሁም ትበታተናላችሁ”

ከዚያ በኋላ የአሞንን ልጆች ምርኮ እመልሳለሁ
ከዚህ በኋላ የአሞንን ልጆች መልካም ኑሩ ይኖራሉ። ኤርምያስ 29:14 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

Jeremiah 49:7

የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ማስተዋል ያለብንን መልእክት ሲያስተላልፍ የሚጠቀመው ሀረግ ነው። ኤርምያስ 6:6 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

በውኑ በቴመን ጥበብ የለምን
እግዚአብሄር በቴመን ከተማ ያሉ ህዝቦችን ጥበበኛ ባለመሆናቸው የሚጠይቀው ጥያቄ ነው

ቴመን
ይህ በኤዶም የሚገኝ ክልል ነው

ምክር ጠፍቶአልን ጥበባቸውስ አልቆአልን
አንድ አይነት ሀሳብ በሁለት መልኩ ይናገራል

ከብልሀተኞችስ ምክር ጠፍቶአልን
እግዚአብሄር ይህን ጥያቄ ለህዝቡ ጠየቀ። “በቴማን ክልል ውስጥ ብልህ ሰዎች የሉም ማለት ነው።”

ጥበበቸውስ አልቆአልን
እግዚአብሄር ለህዝቡ ጥያቄ ጠየቀ።”ምክራቸውም የጥበብ አደለም”

ድዳን
ይህ በኤዶምያስ የምትገኝ የከተማ ስም ነው

የኤሳው ጥፋት የምጎበኝበትን ጊዜ አመጣበታለሁና
ኤሳው የኤዶምያስ ህዝብን ያመለክታል። “የኤዶም ህዝቦችን በምቀጣበት ጊዜ ጥፋትን አመጣለሁ”

የኤሳውን ጥፋት
እግዚአብሄር የኤዶምን ህዝቦችን እየተናገረ ነው። “እናንተን እቀጣለው”

Jeremiah 49:9

አጠቃላይ ሀሳብ
እግዚአብሄር በኤዶም ላይ የሚፈጠረውን መናገር ቀጠለ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወይን ለቃሚዎች...አይተውልህምን
እግዚአብሄር ይህን ጥያቄ ህዝቡ እንዴት ለቃሚዎች ወይን እንደሚተው እንዲያስብ የጠየቀው ሲሆን።

ሌቦችስ በለሊት ቢመጡ የሚያጠፉት እስኪበቃቸው ድረስ አይደለምን
እግአብሄር ይህን ጥያቄ ህዝቡ ሌቦች የሚፈልጉትን ብቻ እንደሚወስዱ ለማሳወቅ ነው። "ሌቦችስ በሌሊት ቢመጡ የፈለጉትን ይወስደሉ"

እኔ ግን ኤሳውን አረቆትሁት
እግዚአብሄር የጠላትን ሰራዊት ያላቸውን ሁሉ መውሰዱን እነደ ኤሳው እራቁቱን እንዳስቀረው አርጎ ይመስለዋል። "እኔ ግን የኤሳውን ሁሉን ነገር ወሰድኩበት"

ኤሳው... ይሸሸግም... አይችልም... ዘሩም ወንድሞቹም... ጠፍተዋል
ኤሳው የኤዶም ህዝብን ያመለክታል። "የኤዶም ህዝቦች...መሸሸጊያቸው... አይችሉም...ዘሮቻቸውም ወንድሞቻቸውም...ጠፍተዋል"

ይሸሸግም ዘንድ አይችልም
ለጠላት የኤዶም ህዝብ የሚሸሸግበትን ቦታ አሳውቂያለሁ

Jeremiah 49:12

አጠቃላይ ሀሳብ
እግዚአብሄር ኤዶም ላይ የሚሆነውን መናገር ቀጠለ

እነሆ
"እነሆ" የሚለው ቃል ቀጣይ ለሚለው ነገር እንዲያስተውሉ ይናገራል።

ፅዋውን ያልተገባቸው ሰዎች ጠጥተውታል...በእርግጥ ትጠጣለህ
"ፅዋ" የሚለው ቃል ሰዎች ለመጠጣት የሚጠቀሙበት እቃ ሲሆን ህዝቡ የእግዚአብሄርን ቅጣት እንደ ፈሳሽ በፅዋ ላይ እነዳለ አድርጎ እየጠጡት እንደሆነ ይናገራል። "አሁንም መቅጣቴን አላቆምም... በእርግጥ እናተንም እቀጣለሁ"

አንተም ሳትቀጣ ትቀራለህን
እግዚአብሄር ይህን ጥያቄ ሀጥያትን ለሰሩት እና ለሚቀጡት ለኤዶም ህዝቦች መጠቀሙን ያሳያል። "ለሰራችሁት ሀጥያት ቅጣትን እንደምትቀጡ ልታውቁ ይገባል"

አንተም
ይህ ቃል ኤዶምን ሲያመለክት ይህም ደግሞ የኤዶምን ህዝብ ያመለክታል። "አንተም" የሚለው የኤዶም ህዝቦችን ትኩረተቸውን ለመያዝ ተጠቅሞታል።

ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ በመጥራት ያዛል። ኤርሚያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ቦሶራ መደነቂያና መሰደቢያ መረገሚያም እንድትሆን በራሴ ምያለሁ
ህዝቦች ቦሶራን ሲመለከቱ መሰደቢያ መደነቂያና መረገሚያ መሆኑዋን ይመለከታሉ። እነሱም ያሾፉባታል ስሟንም ለስድብ ይጠቀሙባታል።

ቦሶራ
ይህ በኤዶም የምትገኝ ከተማ ነች

ከተማዎችም ሁሉ
የኤዶም ከተማዎች ሁሉ

Jeremiah 49:14

አጠቃላይ ሀሳብ
ኤርምያስ የኤዶም ህዝቦችን ይናገራል

ወሬ ሰምቻለሁ
"ሰምቻለሁ" ብሎ የተናገረው ኤርምያስ ነው።

መልእክተኛ ተልኮአል
እግዚአብሄር መልእክተኛ ልኮአል

በአህዛብ መካከል። ተሰብሰቡ ... ለሰልፍም ተነሱ
ተሰብሰቡ የሚለው የመልእክተኛው መጀመሪያ ነው።

በእርሱዋም ላይ
ኤዶምን ያመለክታል

አድርጌሃለሁ
እግዚአብሄር ለኤዶም ከተማ ተናገረ

ደካማ እንድትሆነኚ
ይህ ፖለቲካዊ ተፈለጊነቷ ቀንሷል። "ተፈለጊነትሽን ቀንሼዋለሁ"

በሰዎችም የተናቅህ
ሰዎችም ይንቁሀል

Jeremiah 49:16

አጠቃላይ ሀሳብ
እግዚአብሄር ኤዶም ላይ የሚሆነውን መናገር ቀጠለ

የምትጠብቂውም ያህል ክብር
"ምንም ሰዎች ቢፈሩሽም" ወይም "ምንም ለሌሎች አስፈሪ ብትሆኝም"

የልብህ ኩራት አታልለውሃል።
"ልብህ" የሚለው ሙሉ ሰውን ሲወክል ህዝቡ ራሳቸውን አታለዋል እነደ ኩራት እንዳታለላቸው አርጎ ይናገራል። "ኩራተኛ ሆነሃል ነገር ግን እራሳችሁን አታላችኋል"

ቤትህን ምንም እንደ ንስር ከፍ ብታደርግ
ህዝቦች ከጠላታቸው ሸሽት ቤታቸውን በከፍታ ላይ ያደርጋሉ። "ምንም መኖሪያችሁ እንደ ንስር ከፍታ ላይ ቢሆንም እንኳን"

ንስር
ይህ ትልቅ፣ ሀይለኛ የወፍ ዝርያ ነው። ኤርምያስ 4:13 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ በመጥራት ያዛል። ኤርሚያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

Jeremiah 49:17

አጠቃላይ ሀሳብ
እግዚአብሄር ለኤዶም ህዝቦች መናገር ቀጠለ

ኤዶምያስም መደነቂያ ትሆናለች፥ የሚያልፍባትም ሁሉ ይደነቃል
የሚያልፍባት ሰው ሁሉ ድንጋጤ እና ፍርሃት ያሸብረዋል

ያፏጭባታል
ፍርሃት እና ድንጋጤን ያመለክታል። "በፍርሃት እና በድንጋጤ ይንቀጠቀጣሉ"

እንዲሁ በዚያ ሰው አይቀመጥም የሰው ልጅም አይኖርባትም
እግዚአብሄር አንድ ሃሳብን በሁለት ነገር ሲናገር ኤዶም ውስጥ ምንም ነገር እንደማይኖር አግንኖ ለማሳየት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Jeremiah 49:19

አጠቃላይ ሃሳብ
እግዚአብሄር ኤዶም ላይ የሚሆነውን መናገር ቀጠለ

እነሆ
“እነሆ” የሚለው ቃል ቀጣይ ለሚለው ነገር እንዲያስተውሉ ይናገራል።

በጠነከረው አምባ ላይ ከዮርዳኖስ ትዕቢት ውስጥ እንደ አንበሳ ይወጣል
ይህ የሚናገረው እግዚአብሄር የኤዶም ህዝብን ሲቀጣ ከባድና ድንገተኛ እንደሆነ እና ልክ እንደ አንበሳ በጎችን ሊበላ እንደሚወጣ ነው። “የኤዶም ህዝብን ስቀጣ ድንገተኛ እና ከባድ ልክ እንደ በጎች የተሰማሩበት ስፍራ ላይ አንበሳ እንደሚመጣ ነው።”

ለምለሙ መስክ
ለምለም መሬት ሲሆን እንስሳዎች የሚመገቡበት አረንጓዴ ቦታ ነው።

በቶሎ አባርራቸዋለሁ
የኤዶምን ህዝብ ሲያመለክት ከራሳቸው ምድር እንደሆነ ያሳያል። “የኤዶም ህዝቦች ከራሳቸው መሬት አባርራቸዋለሁ”

የተመረጠውንም
እኔ የምመርጠውን

እንደኔ ያለ ማን ነው ወይስ ለእኔ ጊዜ የሚወስን ማን ነው
እግዚአብሄር ይህን ጥያቄ እንደሱ ያለ ማንም እንደሌለ ለማሳየት ይጠቀማል። “እንደኔ ያለ ማንም የለም፣ ማንም ለኔ ጊዜ የሚወስን የለም ”

ለእኔ ጊዜ የሚወስን ማን ነው
“ማን ነው ከእኔ ጋር ሊወዳደር የሚፈልግ”

ፊቴን የሚቃወም እረኛ ማን ነው
እግዚአብሄር ይህን ጥያቄ እንደሱ ያለ ማንም እንደማያሸንፈው ለማሳየት ሲጠቀም እረኛ የሚለው ንጉስ ወይም መሪ ለማመልከት ይጠቀማል። “የትኛውም ንጉስ ሊቃወመኝ አይችልም”

Jeremiah 49:20

በቴማንም በሚኖሩ ሰዎች
በቴማን ከተማ የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታል

ቴማን
ይህ በኤዶም የሚገኝ ክልል ነው

በእውነት የመንጋ ትንንሾች ይጐተታሉ
እግዚአብሄር የኤዶም ህዝቦችን እንደሚቀጣ ይናገራል። ልክ እንደ አንበሳ የበግ መንጋን እነደሚያጠቃ መስሎም ይናገራል። “ትንንሾችን መንጋ ይጎትታቸዋል ”

የመንጋ ትንንሾች
ወጣት እና ደካማ የኤዶም ህዝብን እንደ ትንንሽ የበግ መንጋ አርጎ ይናገራል። “ደካማ እና ትንንሽ ሰዎችን”

በእውነት ማደሪቸውን ባድማ ያደርግባቸዋል።
የኤዶም ምድር ለመንጋው መልካም ማደሪያ እንደሆነች ይናገራል። “መልካሙን ማደሪያቸውን ባድማ ይሆናል”

Jeremiah 49:21

ከመውደቃቸው የተነሳ ምድር ተናወጠች
የኤዶም ውድቀትን እነደ መሬት የሚያናውጥ ውድቀት አርጎ ይናገራል። “ኤዶምን ሊያጠፉ ጠላቶቿ ሲመጡ ድምፁአ ከፍተኛ ነው ይህም የመሬት መናወጥን ያስከትላል”

የጩኸታቸውም ድምፅ በኤርትራ ባሕር ተሰማ።
“በኤርትራ ባህር ያሉ ህዝቦች የኤዶምን ድምፅ ይሰማሉ”

እነሆ
“እነሆ” የሚለው ቃል ቀጣይ ለሚለው ነገር እንዲያስተውሉ ይናገራል።

እንደ ንስር ወጥቶ ይበራል ክንፉንም በባሶራ ላይ ይዘረጋል
ይህ የጠላታቸው ሰራዊት ሲያጠቁ ድንገተኛ እንደሆነ ያሳያል።

በባሶራ
የከተማ ስም ነው። ኤርምያስ 48:24 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት።

የኤዶምያስ ኃያላን ልብ ምጥ እንደ ያዛት ሴት ልብ ይሆናል
“ልብ” የሚለው ቃል የሰውን ውስጣዊ ስሜት ያሳያል። ኤርምያስ 48:41 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት። “የኤዶም ሀያላን ምጥ እንደያዛት ሴት በፍርሃት ይሞላሉ።”

Jeremiah 49:23

አጠቃላይ ሀሳብ
እግዚአብሄር ለደማስቆ ህዝቦች የሚሆነውን ተናገረ

ሐማትና አርፋድ አፈሩ ቀለጡም
“ሐማት” እና ”አርፋድ” በውስጣቸው የሚኖሩትን ህዝቦች ያመለክታል። “በሐማት እና አርፋድ የሚኖሩ ህዝቦች አፈሩ ቀለጡም”

ሐማትና አርፋድ
በሶሪያ የሚገኙ ከተማዎች ናቸው

ይቀልጣሉ
የአንድ ሰው ፍራቻን እንደ መቅለጥ መስሎ ይናገራል። “እጅግ በጣም ይፈራሉ”

በባህርም ላይ ሀዘን አለ ታርፍም ዘንድ አትችልም
የባህር ውሃ ሁልጊዜ ይንቀሳቀሳል አያርፍምም። ይህን ከሚሰማው መጥፎ ዜና እና ጭንቀት የተነሳ የማያርፉትን ህዝቦች ጋር ያነፃፅራል።

ደማስቆ ደከመች ትሸሸም ዘንድ ዘወር አለች
ደማስቆ የሚለው በውስጡ የሚኖሩትን ህዝቦች ያመለክታል። “የደማስቆ ህዝቦች ደከሙ ይሸሹም ዘንድ ዘወር አሉ”

እንቅጥቅጥም ያዛት
እንቅጥቅጥም የሚለው ፍራቻን ያመለክታል። “የደማስቆ ህዝብም ፍራቻ አደረባቸው”

እንደ ወላድም ሴት ጣርና ምጥ ያዛት።
ህዝቡ እንደ ምጥ ውስጥ እንዳለች ሴት አርጎ ይናገራል ይህም ያለውን ጭንቀት እና ፍርሃት አጉልቶ ያሳያል። “እንደ ወላድ ሴት ምጥ እንደያዛት ህዝቡ በትልቅ ጭንቀት እና ፍርሃት ላይ ናቸው”

የተመሰገነችው ከተማ የደስታዬ ከተማ ሳትለቀቅ እንዴት ቀረች
እግዚአብሄር እንዲህ አይነት ጥያቄዎችን ህዝቡ ከተማዋን እንዲለቁ የሚናገር ነው። “ይህ የተመሰገነች ከተማ የደስታዬ ከተማ አሁን ከተማዋን ህዝቡ ይልቀቅ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የተመሰገነችው ከተማ የደስታዬ ከተማ ሳትለቀቅ እንዴት ቀረች
አንዳንዶች የደማስቆ ህዝቦች እንደተናገሩት ይገመታል። “የደማስቆ ህዝቦች እንዲህ አሉ “የተመሰገነችው ከተማ የደስታዬ ከተማ አሁን ባዶ ቀረች””

Jeremiah 49:26

አጠቃላይ ሀሳብ
እግዚአብሄር ለደማስቆ ህዝቦች የሚሆነውን መናገር ቀጠለ።

በአደባባይዋ ላይ
ደማስቆ እና ህዝቦችዋን ያመለክታል።

ጎበዛዝትዋ በአደባባይ ላይ ይወድቃሉ
የጎበዛዝትዋ መሞት እንደ ውድቀት አድርጎ ይናገራል። “ጎበዛዝትዋ በአደባባይ ላይ ይሞታሉ”

ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ በመጥራት ያዛል። ኤርሚያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

እሳት አነድዳለሁ
የጠለት ሰራዊቶች እሳትን ማንደድ ልክ እግዚአብሄ ራሱ እሳት እንዳነደደ አርጎ ይናገራል። “የጠላት ሰራዊት እሳትን እንዲያነዱ አረጋለሁ”

አዳራሾችን ትበላለች
ሙሉ በሙሉ ይቃጠላል

የወልደ አዴርንም
ይህ የደማስቆ የንጉስ ስም ወይም መጠሪያ ነው።

Jeremiah 49:28

አጠቃላይ ሀሳብ
ኤርምያስ በቄዳር ላይ የሚፈፀመውን ተናገረ

ቄዳር
ይህ በእስራኤል በሩቅ ምስራቅ የሚገኝ መሬት ነው። ኤርምያስ 2:10 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

አሶር
ይህ በእስራኤል በሩቅ ምስራቅ የሚገኝ መንግስት ወይም ክልል መጠሪያ ነው

ናቡከደነፆር ስለ መታ
ይህ ስለናቡከደነፆር ያለፈውን ሃሳብ ይናገራል።

የባቢሎን ንጉስ ናቡከደነፆር ስለ መታ
ናቡከደነፆር ሰራዊቱን ያመለክታል። “የባቢሎን ንጉስ የናቡከደነፆር ሰራዊት ስለመታ”

ድንኳናቸውንና መንጋቸውን ይወስዳሉ መጋረጆቻቸውንና እቃቸውን ሁሉ
“ያንተ ሰራዊት ድንኳናቸውንና መንጋቸውን ይወስዳሉ መጋረጆቻቸውንና እቃቸውን ሁሉ”

ግመሎቻቸውንም ለራሳቸው ይወስዳሉ
“ያንተ ሰራዊት ግመሎቻቸውንም ለራሳቸው ይወስዳሉ”

በዙሪያቸው ሁሉ ጥፋትን ጥሩባቸው።
የዚህ ሀረግ ትርጉም ሊሆን የሚችለው 1) በጠላት የሚጠቁ ሰዎችን ያመለክታል። “ህዝቡን “በዙሪያችን በሚፈጠረው ነገር ሁሉ ተሸብረናል”” 2) እነዚህ የሚማረኩ ሰራዊቶች ናቸው። “ሰራዊቱም “ፍሩ እኛ በዙሪያችሁ ነን””

Jeremiah 49:30

አጠቃላይ ሀሳብ
እግዚአብሄር በቄዳር እና በአሶር መንግስት ላይ የሚሆነውን መናገር ቀጠለ።

ሽሹ ወደ ሩቅም ሂዱ
እግዚአብሄር ለቄዳር ህዝቦች ተናገረ

በአሶር የምትኖሩ
በአሶር የሚኖሩ ህዝቦችን ያመለክታል።

ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ በመጥራት ያዛል። ኤርሚያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ተማክሮባችሁአልና
ሴራ አስቦአል

ተነሱ ዕርፊት ወዳለበት...
እግዚአብሄር ናቡከደነፆር አንደሚሰማው አድርጎ ሲናገር ያሳያል።

ተነሡ፥ ዕርፊት ወዳለበት ተዘልሎም ወደ ተቀመጠው
ይህ በዛች ከተማ የሚኖሩትን ህዝቦች ያመለክታል። ”ተነሡ፥ ዕርፊት ወዳለበት ተዘልሎም ወደ ተቀመጠው”

ተቀመጠው
ይህ ተዘልሎ የተቀመጠውን ህዝብ ያመለክታል።

Jeremiah 49:32

አጠቃላይ ሀሳብ
እግዚአብሄር ለናቡከደነፆር የቄዳር ህዝብና የአሶር መንግስትን እንዲወጋው መናገሩን ቀጠለ።

ግመሎቻቸው ይበዘበዛሉ የእንስሶቻቸውም ብዛት ይማረካል
እግዚአብሄር ለናቡከደነፆር እየተናገረው ነው። “የጦር ሰራዊትህ ግመሎቻቸው ይበዘበዛሉ የእንስሶቻቸውም ብዛት ይማረካል”

ነፋሳትን ሁሉ እበትናለሁ
ነፋሳት ከተማን ያመለክታል። “ከተማዋን እበታትናለሁ”

ጠጉራቸውንም በዙሪያ የሚላጩትን
ይህ የአረማውያንን ጣኦት በማክበር ፀጉራቸውን የሚያሳጥሩ ሰዎችን ይናገራል። ኤርምያስ 9:26 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ከደርቻቸውም ሁሉ ጥፋት አመጣባቸዋለሁ
“ጠላቶቻቸውን ከሁሉም ዳርቻ እንዲያጠፉአቸው አመጣባቸዋለሁ”

ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ በመጥራት ያዛል። ኤርሚያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

የቀበሮ መኖሪያና
ቀበሮ የሚኖርበት ቦታ። ቀበሮ የዱር ውሻ በመባል ይታወቃሉ። ኤርምያስ 9:11 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

በዚያም ሰው አይኖርም የሰው ልጅም አይቀመጥባትም
እንዚህ ሁለት ሀረጎች አንድ አይነት ነገር የሚያሳዩ ሲሆን በአሶር ላይ ምንም አይነት ነገር እንደማይኖር ይናገራል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Jeremiah 49:34

አጠቃላይ ሀሳብ
እግዚአብሄር በኤላም ላይ ሊፈጠር ያለውን ይናገራል

ወደ ነቢዩ ወደ ኤርምያስ የመጣው የእግዚአብሔር ቃል ይህ ነው
ይህ ልዩ የእግዚአብሄር ቃል እንደሆነ ይናገራል። ኤርምያስ 14፡1 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት። “ይህ የእግዚአብሄር ቃል ለኤርምያስ የተሰጠ ነው”

Jeremiah 49:37

አጠቃላይ ሀሳብ
እግዚአብሄር በኤላም ላይ ሊፈጠር ያለውን ይናገራል

ኤላምን አስደነግጣለሁ
እግዚአብሄር ኤላምን ለጠላት አሳልፎ እንደሚሰጥ ይናገራል። “የኤላም ጠላት ኤላምን እንዲያጠፋ አደርጋለሁ”

ኤላም
የኤላም ህዝቦች

ነፍሳቸውን በሚሹአት ፊት
አንድን ህይወት ለማጥፋት መፈለግ ማለት ነው።

ክፉ ነገርን እርሱም...አመጣባቸዋለሁ
ክፉን ነገርን እንደሚሆንባቸው ልክ እግዚአብሄር እነዚህን ክፉ ነገሮች እንደሚያመጣባቸው አርጎ ይናገራል። ”ክፉ ነገር በእነርሱ ላይ ይሆናል”

ቁጣዬን አመጣባቸዋለሁ
እግዚአብሄር የኤላም ህዝብን የሚያጠፋበት ምክንያት ነው። “በቁጣዬ ምክንያት”

ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ በመጥራት ያዛል። ኤርሚያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

እስካጠፋቸው ድረስ በኋላቸው ሰይፍ እሰድድባቸዋለሁ
“ሰይፍ” የጠላት ሰራዊት የጦር መሳሪያን ይዘው ያመለክታል። “የጠለት ሰራዊትን እንዲያጠፋቸው እልካለሁ”

ዙፋኔን በኤላም አኖራለሁ
“ዙፋኔን” የሚለው የእግዚአብሄር እንደ ንጉስ የመፍረድ ስልጣኑን ያሳያል። “እኔ በኤላም ህዝብ ላይ እፈርዳለሁ”

በኋላኛው ዘመን
የወደፊቱ ጊዜ

የኤላምን ምርኮ እመልሳለሁ
“ለኤላም ህዝብ መልካም እንዲሆን እመልሳለሁ” ወይም “ለኤላም መልካም እንዲኖሩ አደርጋለሁ”። ኤርምያስ 29፡14 እንዴት እነደተረጎመው ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 50

1 እግዚአብሔር ስለ ከለዳውያን ምድር ስለ ባቢሎን በነቢዩ በኤርምያስ የተናገረው ቃል ይህ ነው፣ 2 "በአሕዛብ መካከል ተናገሩና እንዲሰሙ አድርጉ።
ዓላማውን አንሡና እንዲሰሙ አውሩ። አትደብቁት። 'ባቢሎን ተወሰደች። ቤል አፈረ። ሜሮዳክ ደነገጠ። ጣዖቶችዋ አፈሩ። ምስሎችዋ ደነገጡ' በሉ። 3 ሕዝብ
ከሰሜን ወጥቶባታል ምድርዋንም ባድማ ያደርጋል፣ የሚቀመጥባት እንዳይገኝባት። ከሰው ጀምሮ እስከ እንስሳ ድረስ በውስጥዋ አይኖሩም። ሸሽተው ሄደዋል።
4 በእነዚያም ወራት፣ በዚያም ጊዜ፣ ይላል እግዚአብሔር፣ የእስራኤል ልጆችና የይሁዳ ልጆች በአንድነት ሆነው እያለቀሱና አምላካቸውን እግዚአብሔርን እየፈለጉ
ይመጣሉ። 5 ፊታቸውንም ወደጽዮን አቅንተው ይሄዳሉ። ከቶ በማይረሳ በዘላለም ቃል ኪዳን ወደ እግዚአብሔር ሄደው ራሳቸውን ከእግዚአብሔር ጋር ያገኛሉ።
6 ሕዝቤ የጠፉ በጎች ሆነዋል። እረኞቻቸው በተራሮች ላይ አስተው አቅበዘበዟቸው፤ ከኮረብታ ወደ ኮረብታ አለፉ። ሄዱ፣ የኖሩበትንም በረታቸውን ረሱ። 7
ሲሄዱባቸው ያገኙአቸው ሁሉ በሉአቸው። ጠላቶቻቸውም፣ 'በጽድቅ ማደሪያ በእግዚአብሔር ላይ፣ በአባቶቻቸው ተስፋ በእግዚአብሔር ላይ፣ ኃጢአት ስለ ሠሩ
እኛ አልበደልንም' አሉ። 8 ከባቢሎን መካከል ሽሹ፤ ወደ ከከለዳውያን ድር ውጡ፤ በመንጎችም ፊት እንደ አውራ ፍየሎች ሁኑ። 9 ተመልከቱ፣ ከሰሜን ምድር
የታላላቅ አሕዛብን ጉባኤ አስነሣለሁ በባቢሎንም ላይ አመጣቸዋለሁ። በእርስዋም ላይ ይሰለፋሉ። ባቢሎን ከዚያ ስፍራ ትወሰዳለች። ፍላጾቻቸውም ባዶውን
እንደማይመለስ እንደ ተካነ ተዋጊ ፍላጻ ናቸው። 10 የከላውዴዎንም ምድር ትበዘበዛለች። የሚበዘብዙአትም ሁሉ ይጠግባሉ፣ ይላል እግዚአብሔር። 11 ርስቴን
የምትበዘብዙ እናንተ፣ ደስ ይበላችሁ፤ በመስክ ላይም እንዳለች ጊደር ሆናችሁ ሐሤት እያደረጋችሁ ዝለሉ፤ እንደ ብርቱ ፈረሶች አሸካኩ። 12 እንዲሁ እናታችሁ
በእጅጉ ታፍራለች፤ የወለደቻችሁም ትጐሰቍላለች። ተመልከቱ፣ በአሕዛብ መካከል አነስተኛይቱ ትሆናለችና፣ ምድረ በዳና ደረቅ ምድር፣ በረሀም ትሆናለች። 13
ከእግዚአብሔር ቍጣ የተነሣ ባድማ ትሆናለች እንጂ ሰው አይኖርባትም። በባቢሎንም በኩል የሚያልፍ ሁሉ ይደነቃል፣ በመጣባትም መቅሠፍት ሁሉ
ያፍዋጫል። 14 በባቢሎን ላይ በዙሪያዋ ተሰለፉ። እናንተ ቀስትን የምትገትሩ ሰዎች ሁሉ። በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ሠርታለችና ወርውሩባት ፍላጾችንም
አትመልሱ። 15 የእግዚአብሔር በቀል ነውና ድል እያደረጋችሁ በዙሪያዋ ጩኹባት። እጅዋን ሰጠች፤ ግንቦችዋ ወደቁ፣ ቅጥሮችዋም ፈረሱ ይህ የእግዚአብሔር
በቀል ነውና። እርስዋን ተበቀሉ! እንደ ሠራችውም ሥሩባት። 16 ዘሪውንና በመከር ጊዜ ማጭድ የሚይዘውን ከባቢሎን አጥፉ። ከሚያስጨንቅ ሰይፍ ፊት
እያንዳንዱ ወደ ወገኑ ይመለሳል እያንዳንዱም ወደ አገሩ ይሸሻል። 17 እስራኤል ባዝኖ የተበተነ በግ እና አንበሶች ያሳደዱት ነው። መጀመሪያ የአሦር ንጉሥ
በላው፤ በመጨረሻም የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር አጥንቱን ቈረጠመው። 18 ስለዚህ የእስራኤል አምላክ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦
ተመልከቱ፣ የአሦርን ንጉሥ እንደ ቀጣሁ፣ እንዲሁ የባቢሎንን ንጉሥና ምድሩን እቀጣለሁ። 19 እስራኤልንም ወደ ማሰማርያ ምድሩ እመልሳለሁ፤ በቀርሜሎስና
በባሳንም ላይ ይሰማራል። በኤፍሬም ተራራና በገለዓድ ላይ ይጠግባል። 20 በእነዚያም ቀኖች፣ በዚያ ጊዜ፣ እነዚህን ያስቀረኋቸውን ይቅር እላቸዋለሁና፣ ይላል
እግዚአብሔር፣ የእስራኤል በደል የይሁዳም ኃጢአት ይፈለጋል ምንም አይገኝም።" 21 "በምራታይም ምድር ላይ፣ በፋቁድም በሚኖሩት ላይ ተነሥና ውጣ፤
ግደላቸው ፈጽመህም አጥፋቸው፤ ይላል እግዚአብሔር፣ እንዳዘዝሁህም ሁሉ አድርግ። 22 የሰልፍና የታላቅ ጥፋት ውካታ በምድሪቱ ላይ አለ። 23 የምድር ሁሉ
መዶሻ እንዴት ደቀቀ እንዴትስ ተደመሰሰ። ባቢሎንስ በአሕዛብ መካከል እንዴት መሸበሪያ ሆነች። 24 ባቢሎን ሆይ፣ አጥምጄብሻለሁ። አንቺም ሳታውቂ
ተይዘሻል፤ ከእኔ ከእግዚአብሔር ጋር ስለ ተዋጋሽ ተገኝተሻል ተይዘሽማል። 25 እግዚአብሔር ዕቃ ቤቱን ከፍቶ የቍጣውን ዕቃ ጦር አውጥቶአል። የሠራዊት ጌታ
እግዚአብሔር በከለዳውያን ምድር ይሠራ ዘንድ ሥራ አለውና። 26 ከየበኩሉ በእርስዋ ላይ ጥቃትን ፈጽሙ። ጎተራዎችዋንም ክፈቱ። እንደ ክምርም አድርጓት፣
ፈጽማችሁም አጥፉአት። አንዳችም አታስቀሩላት። 27 ወይፈኖችዋን ሁሉ እረዱ። ወደ መታረድም ስፍራ ላኳቸው። ቀናቸው፣ የመቀጣታቸው ጊዜ፣ ደርሶአልና
ወየላቸው! 28 የአምላካችንን የእግዚአብሔርን በቀል፣ የመቅደሱንም በቀል በጽዮን ይነግሩ ዘንድ ሸሽተው ከባቢሎን አገር ያመለጡት ሰዎች ድምፅ
ተሰምቶአል።" 29 ቀስትን የሚገትሩትን ቀስተኞችን ሁሉ በባቢሎን ላይ ጥሩአቸው። በዙሪያዋ ስፈሩባት፣ አንድም አያምልጥ። በእስራኤል ቅዱስ ላይ
በእግዚአብሔር ላይ ኰርታለችና እንደ ሥራዋ መጠን መልሱላት። እንዳደረገችም ሁሉ አድርጉባት። 30 ስለዚህ ጐበዛዝትዋ በአደባባይዋ ላይ ይወድቃሉ፣
በዚያም ቀን ሰልፈኞችዋ ሁሉ ይጠፋሉ፣ ይላል እግዚአብሔር።" 31 ትዕቢተኛው ሆይ፣ አንተን የምቀጣበት ጊዜ፣ ቀንህ ደርሶአልና በአንተ ላይ ነኝ፣ ይላል
የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር። 32 ስለዚህ ትዕቢተኞቹ ተሰናክለው ይወድቃሉ። የሚያነሣቸው ማንም አይኖርም። በከተሞቻቸውም ውስጥ እሳት አነድዳለሁ፤
በዙሪያቸው ያለውን ሁሉ ትበላለች። 33 የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ የእስራኤል ልጆችና የይሁዳ ልጆች በአንድነት ተጨቊነዋል።
የማረኳቸውም ሁሉ አሁን ድረስ በኃይል ይዘዋቸዋል፤ ይለቅቁአቸውም ዘንድ እንቢ ብለዋል። 34 የሚቤዣቸው ብርቱ ነው። ስሙም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር
ነው። ምድርንም ያሳርፍ ዘንድ፣ በባቢሎንም የሚኖሩትን ያውክ ዘንድ መግታቸውን ፈጽሞ ይሟገታል። 35 ሰይፍ በከለዳውያንና በባቢሎን በሚኖሩ ላይ፣
በአለቆችዋና በጥበበኞችዋ ላይ አለ፣ ይላል እግዚአብሔር። 36 ጥንቆላን በሚናገሩት ላይ ሰይፍ አለ፣ ራሳቸውን ሰነፎች አድርገው ይገልጣሉ። ሰይፍም
በጦረኞችዋ ላይ አለ፣ እነርሱም በሽብር ይሞላሉ። 37 ሰይፍ በፈረሶቻቸውና በሰረገሎቻቸው ላይ በመካከልዋም ባሉት በልዩ በልዩ ሕዝብ ሁሉ ላይ አለ፣
እነርሱም እንደ ሴቶች ይሆናሉ። ሰይፍ በቤተ መዛግብቷ ላይ አለ፣ ለብዝበዛም ይሆናል። 38 እርስዋ የተቀረጹ ምስሎች ምድር ናት፣ እነርሱም በጣዖታት
ይመካሉና ድርቅ በውኆችዋ ላይ ይሆናል እነርሱም ይደርቃሉ። 39 ስለዚህ የምድረ በዳ አራዊት ከተኵላዎች ጋር ይኖሩባታል፣ ሰጐኖችም ይኖሩባታል፤ ሰውም
ከዚያ ወዲያ ለዘላለም አይኖርባትም፣ እስከ ልጅ ልጅም ድረስ የሚኖርባት የለም። 40 ሰዶምንና ገሞራን በአጠገባቸውም የነበሩትን ከተሞች እግዚአብሔር እንደ
ገለበጣቸው፣ ይላል እግዚአብሔር፣ እንዲሁ ሰው በዚያ አይኖርም የሰውም ልጅ አይኖርባትም።" 41 "ተመልከቱ፣ ሕዝብ ከሰሜን ይመጣል፣ ታላቅ ሕዝብና
ብዙ ነገሥታትም ከምድር ሩቅ ዳርቻዎች ይነሣሉ። 42 ቀስትንና ጦርን ይይዛሉ። ጨካኞች ናቸው ምሕረትም አያደርጉም። ድምፃቸው እንደ ባሕር ይተምማል፣
በፈረሶችም ላይ ይቀመጣሉ፤ የባቢሎን ሴት ልጅ ሆይ፣ ለሰልፍ እንደ ተዘጋጀ ሰው እያንዳንዳቸው በአንቺ ላይ ተሰለፉ። 43 የባቢሎን ንጉሥ ወሬአቸውን
ሰምቶአል፣ እጁም ዝላ ደክማለች። ጭንቀትም ይዞታል፣ ምጥ ወላድ ሴትን እንደሚይዛት ጭንቀት ይዞታል። 44 ተመልከቱ! ከእርስዋ ዘንድ በቶሎ
አባርራቸዋለሁና በጠነከረው አምባ ላይ ከዮርዳኖስ ትዕቢት ውስጥ እንደ አንበሳ ይወጣል። የተመረጠውንም በእርስዋ ላይ እሾመዋለሁ። እንደ እኔ ያለ ማን
ነው? ወይስ ለእኔ ጊዜ የሚወስን ማን ነው? ወይስ ፊቴን የሚቃወም እረኛ ማን ነው? 45 ስለዚህ እግዚአብሔር በባቢሎን ላይ የመከረባትን ምክር፣
በከለዳውያንም ምድር ላይ ያሰባትን አሳብ ስሙ። በእውነት የመንጋ ትናንሾች ሳይቀሩ ይጎተታሉ። በእውነት ማደሪያቸውን ባድማ ያደርግባቸዋል። 46 ከባቢሎን
መያዝ ድምፅ የተነሣ ምድር ተናወጠች፤ ጩኸትም በአሕዛብ መካከል ዘንድ ተሰማ።"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Jeremiah 50:1

አጠቃላይ ሀሳብ
እግዚአብሄር ለኤርምያስ ስለ ባቢሎን መልእክት ሰጠው።

እግዚአብሄር...የተናገረው ቃል ይህ ነው።
እግዚአብሄር የተናገረው ልዩ መልእክት እንደሆነ ያመለክታል። “ይህ እግዚአብሄር የተናገረው ቃል ነው”

በነብዩ ኤርምያስ
ኤርሚያስ 37፡2 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

በአህዛብ መካከል ተናገሩ አውሩም
ይህ ሀረግ አስፈላጊ የሆነ መልእክት እንደሆነ ያሳያል።

ዓላማውንም አንሱ
ምልክታችሁንም ከፍ አድርጉት

ባቢሎን ተወሰደች
ባቢሎን ተሸንፋለች

ቤል አፈረ ሜሮዳክ ደነገጠ ምስሎችዋ አፈሩ ጣዖታትዋ ደነገጡ
እግዚአብሄር የባቢሎንን ጣዖቶችን እንዳሳፈረ ይናገራል

ቤል... ሜሮዳክ
እነዚህ ሁለት ስሞች የባቢሎን ዋና ጣኦት ስሞች ናቸው

Jeremiah 50:3

ወጥቶባታል...የሚቀመጥባትም
ሁለቱም ቃላቶች ባቢሎንን ያመለክታል

ምድርዋንም
ይህ ቃል ባቢሎንን ያመለክታል

ባድማ ያደርጋል
ባድማ የሚለው ጥፋትን ሲያሳይ ምድሪቱን ያጠፋታል ሚለውን ያመለክታል።

በዚያም ወራት በዚያም ጊዜ
ይህ ሀረግ የወደፊቱን አስፈላጊነት አግንኖ የሚያሳይ ነው። ኤርምያስ 33፡15 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ በመጥራት ያዛል። ኤርሚያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

እግዚአብሄርን ይፈልጋሉ
ይህ የሚያመለክተው 1) እግዚአብሄርን እንዲረዳቸው ይጠይቁታል 2) ስለእግዚአብሄር ማሰብ እና እሱን መታዘዝን ያመለክታል

ይጠይቃሉ
ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌም የሚመለሱትን የእስራኤል ልጆች ወይም የይሁዳ ልጆችን ያመለክታል

ወደ እግዚአብሄር ተጠጉ
ከእግዚአብሄር ጋር ያለውን መንፈሳዊ ግንኙነትን ያመለክታል

ከቶ በማይረሳ
የእግዚአብሄር ቃል ኪዳን ለዘላለም የሚጠበቅ ቃል ኪዳን እንደሆነ ይናገራል።

Jeremiah 50:6

ህዝቤ የጠፉ በጎች ሆነዋል
የእስራኤል ህዝብ እንደ ጠፉ በጎች ይመስላቸዋል።

እረኞቻቸው
የእስራኤል ህዝብ መሪዎች እንደ የሰዎች እረኞች ይመስላቸዋል።

ከተራራ ወደ ኮረብታ አለፉ
በብዙ ቦታዎች እየመሩ ወሰዱአቸው

በሉአቸው
የእስራኤልን ህዝብ መውጋት ልክ እንደ አውሬ እንደበላቸው ይመስላል።

ኃጢአት ስለሰሩ
የእስራኤል ህዝብን ያመለክታል

በፅድቅ ማደሪያ በእግዚአብሄር ላይ
እግዚአብሄር የሚጠብቅ እና ማረፊያ ቦታ የሚያዘጋጀው እርሱ እንደሆነ ያሳያል።

በአባቶቻቸው ተስፋ በእግዚአብሄር ላይ
እግዚአብሄር የሚተማመኑበት ምንጭ እንደሆነ ሲናገር “ተስፋ” የሚለው ቃል ድርጊትን ያሳያል።

Jeremiah 50:8

አጠቃላይ ሀሳብ
እግዚአብሄር ህዘቡን በባቢሎን እንደተማረኩ ይናገራል።

ከባቢሎን መካከል ሽሹ
ይህ ትዕዛዝ ከባቢሎን ለወጡ የእስራኤል ልጆች የተሰጠ ትእዛዝ ነው

እነደ አውራ ፍየሎች
አውራ ፍየሎች በብዛት ጥገኛ አደሉም ከሌሎቹ መንጋ ሲነፃፀሩ። ለዚህም የሚሆን ትርጉም 1) የመጀመሪያዎቹ ባቢሎንን ጥለው የወጡ መሆን አለባቸው 2) ቀሪው እስራኤላውያንን ከባቢሎን እየመሩ ማሸሽ አለባቸው።

እነሆ
“እነሆ” የሚለው ቃል ቀጣይ ለሚለው ነገር እንዲያስተውሉ ይናገራል።

አስነሳለሁ
አነሳሳለሁ

የከላውዴዎንም ምድር ትበዘበዛለች
እንዚህ ከተማዎች ባቢሎንን ይበዘብዛሉ

ከዚያም
1) ከሰሜን 2) ከጦርነት ቦታቸው

ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ በመጥራት ያዛል። ኤርሚያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ፍላፃዎቻቸውም ባዶውን እነደማይመለስ አንደ ብልህ ጀግነ ፍላፃ ናቸው።
የጠላቶቻቸው ከተማ ቀስቶች ስኬት ልክ የተሰጠውን አላማ ያሳካ ወታደር አርጎ ይመስለዋል። “ባዶውን” ማለት ያለምንም ውጤት ለማለት ነው።

የከለዳዊያን ምድር ተበዘበዛለች
የከለዳውያንን ምድር ባድማ ያደርጉታል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Jeremiah 50:11

አጠቃላይ ማብራሪያ
እግዚአብሄር ለባቢሎን ተናገረ

ደስ ብሎአችኃልና ሀሴትንም አድርጋችኁልና
እነዚህ ቃላቶች እስራኤልን በማሸነፋቸው ምን ያህል ደስ እንደተሰኙ አግንኖ የሚያሳዩ ናቸው።

ደስ ብሎአችኁልና...በመስክ ላይም እንዳለች ጊደር ሆነችሁ...አሸካክታችኁልና
ከላይ ያሉት የባቢሎንን ህዝብ ያመለክታል።

በመስክ ላይም እንዳለች ጊደር ሆነችሁ
የባቢሎን ህዝብ ደስታ ልክ በመስክ ላይ እንዳለች ጊደር ይመስለዋል።

ተቀናጥታችኁልና
ይህ ጊደር መሬት በመርገጥ የምተሳየው ድርጊት ነው።

እንደ ብርቱዎችም ፈረሶች አሸካክተችኁልና
የባቢሎን ህዝቦች ልክ እንደ ደስተኛ ፈረሶች ከፍ ያለ ድምፅ እንዳሰሙ አርጎ ይመስላቸዋል።

እናታችሁ እጅግ ታፍራለች የወለደቻችሁም ትጎሳቆላለች
ይህ ሀረግ እፍረቷን አግንኖ የሚያሳይ ሲሆን “እናታችሁ” እና “የወለደቻችሁም” ባቢሎናውያንን ወይም የባቢሎን ከተማን ያመለክታል።

በአህዛብ መካከል ኋለኛይቱ
የማትፈለገዋ ከተማ

ምድረበዳና ደረቅ ምድር በረሀም
እነዚህ ቃሎች የአንድ ምድርን ባዶነት አግንኖ የሚያሳይ ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘ ትርጉማቸው 1) ለኑሮ ምቹ ያለሆነ ቦታን ሲያሳይ 2) ባቢሎን ወደ በረሃነት እና ባዶነት አየሆነች መሆኑን ያሳያል

ባድማ ትሆናለች
ትጠፋለች

ይደነቃል
በፍራቻ ይንቀጠቀጣሉ

ያፍዋጫል
እባብ የሚያወጣውን አይነት ድምፅ ሲሆን ትልቅ ውድቀትን ያመለክታል

Jeremiah 50:14

አጠቃላይ ሀሳብ
እግዚአብሄር ሌሎችን ከተማዎችን ባቢሎንን እንዲያጠቁ ይናገራል

በባቢሎን ላይ በዙሪያዋ ተሰለፉ
እግዚአብሄር ለባቢሎን ጠላት እየተናገረ ነው። “እናንተ የባቢሎን ጠለቶች በዙሪያዋ ተሰለፉ”

Jeremiah 50:16

አጠቃላይ ሀሳብ
እግዚአብሄር ለሌሎች ከተሞች ባቢሎንን እንዲያጠፉ መናገሩን ቀጠለ።

ዘሪውንና በመከር ጊዜ ማጭድ የሚይዘውን
እነዚህ ሰዎች የባቢሎንን ገበሬ እና ዘሪን ይመስላል

ዘሪውንና በመከር ጊዜ ማጭድ የሚይዘውን
ማጭድ የግብርና እቃ ሲሆን እህል ለማጨድ ይጠቅማል። እግዚአብሄር በባቢሎን የመዝራት እና የማጨድ ጊዜ ይቆማል።

እያንዳንዱ ወደ ወገኑ ይመለሳል እያንዳንዱም ወደ አገሩ ይሸሻል
ይህ ሌሎች ህዝቦች ከባቢሎን ከተመ እንዲሸሹ አጥብቆ ይናገራል።

ከሚያስጨንቅ ሰይፍ ፊት
ሰይፍ ባቢሎንን የሚያጠቁ ሰራዊቶችን ያመለክታል።

Jeremiah 50:17

አጠቃላይ ሀሳብ
እግዚአብሄር ለኤርምያስ ስለ እስራኤል ተናገረው።

እስራኤል የባዘነ በግ ነው አንበሶች አሰደዱት...
እግዚአብሄር እስራኤል ከተራቡ አንበሶች ለማምለጥ የሚጥሩ እንደሆኑ ይናገራል።

እስራኤል
ይህ የእስራኤል ህዝቦችን ያመለክታል

የአሦር ንጉሥ
ይህ የአሶር ንጉስ ሰራዊትን ያመለክታል

በላው
የእስራኤል ውድቀት ልክ እስረኤል እነደ በግ በአሶር እንደተበላ አርጎ ያሳያል

የባቢሎን ንጉስ ናቡከደነፆር
የባቢሎን ንጉስ ናቡከደነፆር ሰራዊትን ያመለክተል

አጥንቱን ቆረጣጠመው
የእስራኤል ውድቀት በናቡከደነፆር ልክ እንደ አነበሳ የበግ አጥንት እንደመቆረጣጠም አርጎ ይመስለዋል።

Jeremiah 50:19

አጠቃላይ ሀሳብ
እግዚአብሄር ለኤርሚያስ ስለ እስራኤል መናገሩን ቀጥሎአል።

እመልሳለሁ
ይህ ቃል እግዚአብሄርን ያመለክታል

እስራኤልንም ወደ ማሰማሪው... ትጠግባለች
ይህ የእስራኤል ህዝቦችን ያመለክታል። “የእስራኤል ህዝብን ወደ ማሰማሪያው...የእስራኤል ህዝብ ይጠግባል”

በቀርሜሎስና በባሳንም ላይ ይሰማራል።
እስራኤልን እንደ ሳር እንደሚበላ በግ አርጎ ይመስለዋል። “እነሱም በበቀርሜሎስና በባሳንም የሚበቅለውን ይመገባሉ”

በዚያን ወራት በዚያም ዘመን
እነዚህ ሀረጎች የወደፊቱን ጊዜ አግንኖ የሚያሳይ ነው። ኤርምያስ 33:15 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

የእስራኤል በደል የይሁዳም ኃጢአት ይፈለጋል ምንም አይገኝም
ከላይ ያሉት ሃረጎች አንድን ነገር ሲያመለክቱ አንድላይ እግዚአብሄር የእስራኤል ህዝቦችን ሀጥያት ይቅር ብሎአል።

የእስራኤል በደል... ይፈለጋል ምንም አይገኝም
እግዚአብሄር የእስራኤልን በደል ቢፈልግ ምንም አያገኝም

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እናዚህን ያስቀረኋቸውን
በባቢሎን መጥፋትን ያመልጣሉ። “ከባቢሎን ጥፋት እንዲያመልጡ እፈቅዳለሁ”

Jeremiah 50:21

አጠቃላይ ሀሳብ
እግዚአብሄር ስለ ባቢሎን ጠላቶች ለ ኤርምያስ ተናገረ

በሚኖሩት ላይ ውጣ
እግዚአብሄር ለባቢሎን ጠላቶች እየተናገረ ነው። “እናንተ የባቢሎን ጠላቶች ሆይ በሚኖሩት ላይ ውጡ”

ምራታይም
ይህ የባቢሎን ሌላ ስም ሲሆን ትርጉሙም “እጥፍ አመፅ” ማለት ነው።

በፋቁድም
ይህ የከለዳውያን ሌላ ስም ሲሆን ትርጉሙም ጉብኝት

አጥፋቸው
ሰይፍ በነሱ ላይ አርግ ወይም ግደላቸው

አጥፋቸው
እዚህ ጋር የሚያሳየው ጦርነትን ሲሆን እግዚአብሄር ባቢሎናውያን በጠላቶቻቸው እንደሚጠፉ ይናገራል

ግደላቸው ፈፅመህ አጥፋቸው
ሙሉ በሙሉ ማጥፋትን ያመለክታል። ኤርምያስ 25:9 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ በመጥራት ያዛል። ኤርሚያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

የሰልፍና የታላቅ ጥፋት ውካታ በምድር ላይ አለ።
ይህ ውካታ በጦርነት መሃል የሚሰማ ሰሆን አሁን እንደተፈጠረ አርጎ የሚያሳየው በቅርብ እንደሚሆን ለማሳየት ነው።

Jeremiah 50:23

አጠቃላይ ማብራሪያ
እግዚአብሄር ለባቢሎን ህዝቦች ተናገረ

የምድር ሁሉ መዶሻ እንዴት ደቀቀ እንዴትስ ተሰበረ
የባቢሎን ሰራዊት ልክ እንደ መዶሻ ሲመስለው የሠራዊቱ ውድቀት ልክ እንደ ደቀቀ መዶሻ ይመስለዋል።

ባቢሎንስ በአህዛብ መካከል እንዴት ባድማ ሆነች
ባቢሎን ልክ እንደ ሌሎቹ ከተማዎች ነበረች ነገር ግን ሙሉ በሙሉ ትጠፋለች።

አጥምጄብሻለሁ አንቺም ሳታውቂ ተይዘሻል
እግዚአብሄር የባቢሎን መጥፋት ልክ በወጥመድ እንደተያዘ እንስሳ አርጎ ይመስለዋል።

ተይዘሻል...ተገኝተሻል ተይዘሽማል
እኔ ይዤሻለሁ...እኔ አግኝቼሻለሁ ሳታውቂም ይዤሻለሁ

Jeremiah 50:25

እግዚአብሔር ዕቃ ቤቱን ከፍቶ የቍጣውን ዕቃ ጦር አውጥቶአል።
የእግዚአብሄርን ቁጣ በባቢሎን ላይ ጠላቶቿን ላከ።እግዚአብሄር ልክ የጦር እቃ እንዳለው መስሎ ይናገራል። “አውጥቶአል” የሚለው ቃል ለጦርነት መዘጋጀትን ያመለክታል።

እቃ ቤቱን
ለጦርነት የሚያገለግሉ የጦር እቃ የሚቀመጡበት ክፍል ነው

በእርሱዋ ላይ ውጡ
እግዚአብሄር ለባቢሎን ጠላቶች ተናገረ። “የባቢሎን ጠላት ሆይ በእርሱዋ ላይ ውጡ”

ጎተራዎችዋንም ክፈቱ
ይህ የሚያመለክተው በባቢሎንን የተቀመጠ ሀብትን ነው። “ሀብቷ የተከማቸበትን ቦታ አጥቁአት”

ጎተራ
እህል የሚከማችበት ስፍራ

እንደ ክምርም አድርጓት
ይህ የሚያመለክተው 1) ከተማዋን እንደ ፕላስቲክ ክምር አርጎ መቀነስ 2) ከተማዋ ያላትን ሀብት ልክ እንደ እህል ክምር መከመር

አጥፉአት
ይህ የሚያመለክተው ሙሉ በሙሉ አጥፉአት ማለት ነው።ኤርምያስ 25:9 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

አንዳችም አታስቀሩላት
ሙሉ በሙሉ አጥፉ የሚለውን አግንኖ የሚያሳይ ነው። “ሁሉንም በውስጧ ያሉትን ሰዎች አጥፉ”

Jeremiah 50:27

አጠቃላይ ሀሳብ
እግዚአብሄር የባቢሎን ሰዎች እና ከለዳውያን እንዴት እንደሚጠፉ ይናገራል

ወይፈኖችዋን ሁሉ እረዱ ወደ መታረድም ይውረዱ ቀናቸው
“ወይፈኖችዋን” የሚለው 1) ወታደሮችን 2) ብርቱ ወንዶችን ሲያመለክት እነሱንም መግደል ልክ እንደ ማረጃ ቦታ እንደመውሰድ ነው።

ወይፈኖችዋን ሁሉ እረዱ
እግዚአብሄር ለባቢሎንን ጠላቶች የተናገረው ነው። “እናንተ የባቢሎን ጠላቶች ወይፈኖችዋን ሁሉ እረዱ”

ወይፈኖችዋን
ይህ ቃል ባቢሎንን እንደሆነ ያመለክታል

ይውረዱ...
ይህ ቃል የሚያሳየው የበቢሎን ህዝብን ነው

ቀናቸው የመጎብኘተቸው ጊዜ ደርሶአልና
እነዚህ ሀረጎች አንድ አይነት ሲየሳዩ “የቅታት ጊዜአቸው ደርሶአል”

ያመለጡት ሰዎች ድምፅ ተሰምቶአል።
አድምጡ ሲያመልጡ ትሰማላችሁ

ሸሽተው...ያመለጡትን
እነዚህ ቃላት ከባቢሎን የሸሹ እና የዳኑ ስለ እግዚአብሄር ለሌሎች የሚናገሩ ናቸው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የአምላካችን የእግዚአብሄር በቀል የመቅደሱንም በቀል በፅዮን ይንገሩ
በቀል ድርጊትን ሲያመለክት “አምላካችን እግዚአብሄር በፅዮን እና በመቅደሱ ላይ የፈፀሙትን ተበቀለ”

Jeremiah 50:29

አጠቃላይ ሀሳብ
እግዚአብሄር ባቢሎንና ከለዳውያንን እንዴት እንደሚጠፉ መናገሩን ቀጠለ

ቀስትን የሚገትሩን... ቀስተኞችን
እነዚህ ሀረጎች አንድ አይነት ሰዎችን ይገልፃል

በዙሪያዋ...ኮርታለችና
እነዚህ ቃላቶች የሚያመለክቱት ባቢሎንን ነው

አንድም አያምልጥ
ሁሉንም ያዙ እና አጥፉአቸው

እንደ ስራዋ መጠን መልሱላት
ባቢሎናውያን እስራኤል ላይ የሰሩት መጥፎ ነገሮች እንደተመዘነ አርጎ ይናገራል።

ጎበዛዝትዋ በአደባባይዋ ላይ ይወድቃሉ
ጎበዛዝትን ይገድሉአቸዋል።

ሰልፈኛዎችዋ ሁሉ ይጠፋሉ
ተዋጊ ሰዎችዋን ሁሉ አጠፋለሁ

ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ በመጥራት ያዛል። ኤርሚያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

Jeremiah 50:31

እነሆ በአንተ ላይ ነኝ
እግዚአብሄር ለባቢሎን ህዝቦች ተናገረ። “በአንተ ላይ ነኝ የባቢሎን ህዝብ ሆይ”

እነሆ
ይህ አንባቢው እንዲያስተውል ይነግራል

ትዕቢተኛው ሆይ
እግዚአብሄር ባቢሎንን ሲናገር

ይላል የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ በመጥራት ያዛል። ኤርሚያስ 2:19 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት። “ይህ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር የተናገረው ነው”

ቀንህ ደርሶአልና እነሆ...የመጎብኘትህ ጊዜ
ሁለተኛው ሀረግ ላይ ጊዜ የሚለው በመጀመሪያው ሀረግ ላይ ቀንን ይናገራል። “የምጎበኝህ ጊዜ ደርሶአል”

በዚያም ቀን
ይህ በባቢሎን ላይ የሚመጣ አስፈሪ የፍርድ ጊዜን ያመለክታል

ትዕቢተኛው ተሰናክሎ ይወድቃል
“ተሰናክሎ ይወድቃል” የሚለው ሽንፈት እና ሞትን ያመለክታል። ትእቢተኛውን እንዲሸነፍ እና እንዲሞቱ አደርጋለሁ

በዙሪያውም ያለውን ሁሉ ትበላለች
ባቢሎን ከተማን የሚያነድ እሳት ልክ እንደ ሚባላ እንስሳ አርጎ ይናገራል

በዙሪያውም
ይህ የሚያመለክተው “ትዕቢተኛውን” ሲሆን ይህም ባቢሎንን ነው፡

Jeremiah 50:33

አጠቃላይ ሀሳብ
እግዚአብሄር በኤርምያስ ስለ እስራኤል እና ስለ ይሁዳ ተናገረ

Jeremiah 50:35

ሰይፍ...ላይ...ሰይፍ በሚጓደዱት ላይ
ሰይፍ የሚለው ጦርነት ያመለክታል።

ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ በመጥራት ያዛል። ኤርሚያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ሰነፎችም ይሆናሉ
ድርጊታቸው የስንፍና ሲሆን ሁሉም ስንፍናቸውን ይመለከታል።

እነርሱም ይደነግጣሉ
በድንጋጤ ይሞላሉ

እነርሱም እንደ ሴቶች ይሆናሉ
የባቢሎን ሰራዊት ድክመት ልክ እንደ ሴት አርጎ ይናገራል። ይህም “እነርሱም እንደ ሴቶች ደካማ ይሆናሉ”

በመዝገብዋ
አስፈላጊ ወይም ውድ እቃዎች የሚቀመጡበት ቦታ ነው።

ለብዝበዛም ይሆናል
የጠላት ወታደሮች ይብዘብዙአቸዋል።

Jeremiah 50:38

ድርቅ በውሆችዋ ላይ ይሆናል
ውሀዎችዋን የሚያጠቃ ድርቅ ይሆናል

ውሀዎችዋ
ይህ የባቢሎንን ሁሉንም የውሃ ምንጭ ሲሆን በተለይ ደግሞ በከተማዋ የሚያቋርጡ ወንዞችን ነው።

የምድረበዳ አራዊት ከተኩላዎች ጋር
ይህ ሊያመለክት የሚችለው 1) የዱር እንስሳት እና ጅብን ነው 2) መጥፎ መንፈሶች እና ሰይጣንን ነው

ተኩላ
የዱር ውሻ ተብሎ ሚታወቅ ሲሆን የሚገኘውም በኤዥያ እና አፍሪካ ውስጥ ነው

ሰጎኖችም
መብረር የማይችሉ ትላልቅ የአፍሪካ ወፎች ናቸው።

ይቀመጡባታል
የባቢሎን ከተማን ያመለክታል።

ከዚያም ወዲያ ለዘላለም አይቀመጥባትም እስከ ልጅ ልጅም ድረስ የሚኖርባት የለም።
ይህ ባቢሎን ሙሉ በሙሉ እንደምትጠፋ እና ማንም እንደማይኖርባት አግንኖ ይናገራል። “ከእንግዲህ ወዲህ ሰዎች አይኖሩባትም”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የሚኖርባትም አይኖርም
ማንም አይኖርባትም

ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ በመጥራት ያዛል። ኤርሚያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ሰው በዚያ አይቀመጥም የሰውም ልጅ አይኖርባትም
በባቢሎን ከተማ ማንም እንደማይኖር እና ለመኖር የማትሆን ከተማ እንደምትሆን አግንኖ የሚያሳይ ነው። “ማንም በዚያ አይኖርባትም”

Jeremiah 50:41

አጠቃላይ ሀሳብ
ይህ መልዕክት በ ኤርምያስ 6:22 እና ኤርምያስ 6:23 ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ እንዴት እንደ ተተረጎመ ተመልከት

እነሆ ህዝብ ከሰሜን ይመጣል
እግዚአብሄር ለባቢሎን ህዝቦች ተናገረ። “የባቢሎን ህዝብ ከሰሜን ይመጣል”

እነሆ ህዝብ
ልብ በሉ ምክንያቱም አሁን የምናገረው እውነት እና አስፈላጊ ነውና።

ታላቅ ህዝብና ብዙ ነገስታትም
ይህ ሀረግ ፐርዢያን እና ሜድስ ባቢሎንን በ 539 ከክርስቶስ ልደት በፊት ያሸነፉበትን ጊዜ ሲያመለክት “ነገስታትም” የሚለው ደግሞ የጦር ሰራዊትን ያመለክታል።

ከምድር ዳርቻም ይነሳሉ
ይህ እርምጃ መውሰድን ያመለክታል።

ቀስትንና ጦርን ይይዛሉ
ወታደሮቹ ቀስትና ጦርን ይይዛሉ

ድምፃቸው እንደ ባህር ይተምማል
ወታደሮች የሚያሰሙት ከፍተኛ ድምፅን ያመለክታል። “የሚያሰሙት ድምፅ እንደ ባህር ከፍ ያለ ድምፅ ነው”

በፈረሶችም ላይ ይቀመጣሉ...ለሰልፍ እንደ ተዘጋጀ ሰው
“ለሰልፍ እንደ ተዘጋጀ” ራሳቸው አስተካክለው ለጦርነት ተሰልፈዋል ሲሆን ለጦርነት ዝግጁ ናቸው ሚለውን ያመለክታል

የባቢሎን ሴት ልጅ ሆይ
ይህ ሀረግ የባቢሎን ህዝብን ያመለክታል።

አጠቃላይ ሀሳብ
ይህ ቁጥር ከ ኤርምያስ 6:24 ጋር አንድ አይነት ሃሳብ ስላለው እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት

እጆም ደክማለች
በጭንቀት ምክንያት እጁ ደክማለች

ጭንቀትም ይዞታል
የጭንቀት ስሜትም ንጉሱን ልክ እንደያዘው አርጎ ይናገራል።

ጭንቀት
ችግር እና እንባ የሚያመጣ ሃዘን

ምጥ ወለድ ሴትን እንደሚይዛት
ጠላቶቻቸው መጥተው እንደሚያጠቁአቸው ያለው ጭንቀት ልክ ልጅ ልትወልድ በምጥ ውስት እንዳለች ያህል ጭንቀት ውስጥ ናቸው።

Jeremiah 50:44

አጠቃላይ ሀሳብ
ይህ ቁጥር ከኤርምያስ 49:19 ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት

እነሆ
“እነሆ” አንባቢው ቀጣዩን ነገር በማስተዋል እንዲያይ ይናገራል።

በጠነከረው አምበ ለይ ከዮርዳኖስ ትዕቢት ውስጥ እንደ አንበሳ ይወጣል
እግዚአብሄር የባቢሎን ህዝብን ሲቀጣ ልክ እንደ አንበሳ በድንገት በጎችን ሊበላ እንደሚወጣ ነው። “የባቢሎን ህዝብን ስቀጣ ልክ እንደ ከተራራ ላይ በጎችን ሊበላ እንደመጣ ድንገተኛ አንበሰ ነው።”

ጥቅጥቅ ካለ ደን ወደ ለምለም መስክ
በሳር እና ሳር በል በሆኑ እንሳዎች የተሞላ መሬት

ወጥተው እንዲባረሩ አደርጋለሁ
የባቢሎናውያን ህዝብን ያመለክታል።

በእረሱዋ ላይ እሾመዋለሁ
“እኔ የምሾመው”

እንደ እኔ ያለ ማን ነው? ሊቋቋመኝ የሚችልስ ማን ነው?
እግዚአብሄር እነዚህን ጥያቄዎች እንደሱ ያለ ማንም እንደሌለ አግንኖ የሚያሳይ ነው።

ሊቋቋመኝ የሚችልስ ማን ነው?
ማን ነው እኔን ሊቀይረኝ የሚችለው።

የሚቃወመኝ እረኛ ማን ነው
እግዚአብሄር ይህን ጥያቄ ማንም እነደማያሸንፈው ለማሳየት ሲሆን “እረኛ” የሚለው ደግሞ ንጉስ የሚለውን እንደሆነ ያሳያል።

Jeremiah 50:45

አጠቃላይ ሀሳብ
እነዚህ ቁጥሮች ከኤርምያስ 49:20 እና ኤርምያስ 49:21 ጋር ተመሳሳይ ሀሳብ ስላላቸው እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

እግዚአብሔር በባቢሎን ላይ የመከረባትን ምክር፥ በከለዳውያንም ምድር ላይ ያሰባትን አሳብ
እነዚህ ሀረጎች አንድ አይነት ትርጉም ቢኖራቸውም በአንድ ላይ ሲሆኑ ግነትን ያሳየናል። “እግዚአብሄር ለባቢሎን ህዝብ እና ለከለዳውያን ህዝብ ሃሳብ አስቦአል። ”

በእውነት የመንጋ ትናንሾች ይጎተታሉ
እግዚአብሄር የባቢሎንን ህዝብ እንደሚቀጣ መናገሩን ቀጥሎአል። “ትንሹዋ መንጋ ራሱ ይጎትታታል”

የመንጋ ትናንሾች
ትናንሽ እና ደካማ የባቢሎን ህዝብ እንደ ትንሽ የበግ መንጋ አርጎ ይናገራል። “ትናንሾችና ደካሞችም”

ማደሪያቸውን ባድማ ያደርግባቸዋል
የባቢሎን ምድር እንደ የመንጋ ማደሪያ አርጎ ይናገራል። “መልካሙን ማደሪያ ባድማ ያደርገዋል።”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከባቢሎን መያዝ ድምፅ የተነሳ ምድር ተናወጠች
ይህ ባቢሎን ሀያል ከተማ እንደሆነች እና የሷ ድምፅ መሬትን አንቀጠቀጠ።
”የባቢሎን ውድቀት እነደ መሬት መናወጥ ነው”

ድንጋጤ
ህመም ወይም ደስተኛ አለመሆን

የድንጋጤ ጩኸት
የህመም ወይም የስቃይ ጩኸት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 51

1 "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ ተመልከቱ፣ በባቢሎን ላይና በከለዳውያን ምድር በሚኖሩት ላይ አጥፊውን ነፋስ አስነሣለሁ። 2 በባቢሎንም ላይ የውጪ
ሰዎች እልካለሁ። እነርሱም ይበትኗታል፣ ምድርዋንም ባዶ ያደርጋሉ፤ በመከራም ቀን በዙሪያዋ ይከብቡአታል። 3 በወርዋሪው ላይ በጥሩርም በሚነሣው ላይ
ቀስተኛው ቀስቱን ይገትር፤ ለጐበዛዝትዋ አትዘኑ፣ መላውን ሠራዊትዋንም አጥፉ። 4 የቆሰሉት ሰዎች በከለዳውያንም ምድር ተገድለው፣ በሜዳዋም ላይ
ተወግተው ይወድቃሉና። 5 ምድራቸው በእስራኤል ቅዱስ ላይ በተሠራው በደል ምንም እንኳ የተሞላች ብትሆን፣ እስራኤልም ሆነ ይሁዳ በአምላኩ በሠራዊት
ጌታ በእግዚአብሔር ዘንድ አልተጣለም። 6 ከባቢሎን ውስጥ ሽሹ፤ እያንዳንዳችሁም ራሳችሁን አድኑ። በበደልዋ አትጥፉ። የእግዚአብሔር የበቀል ጊዜ ነውና።
እርሱም ብድራትዋን ይከፍላታል። 7 ባቢሎን በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ ምድርን ሁሉ ያሰከረች የወርቅ ጽዋ ነበረች፣ አሕዛብም ከጠጅዋ ጠጥተዋል፤ ስለዚህ
አሕዛብ እብድ ሆነዋል። 8 ባቢሎን በድንገት ወድቃ ጠፍታለች። ለእርሷ አልቅሱላት! ትፈወስም እንደ ሆነ ለቍስልዋ መድኃኒት ውሰዱላት። 9 'ባቢሎንን
ለመፈወስ ተመኘን፣ እርስዋ ግን አልተፈወሰችም። ፍርድዋ እስከ ሰማይ ደርሶአልና፣ እስከ ደመናም ድረስ ከፍ ከፍ ብሎአልና ትታችኋት እያንዳንዳችን ወደ
ምድራችን እንሂድ።' 10 እግዚአብሔር ጽድቃችንን አውጥቶአል። ኑ፣ በጽዮን የአምላካችንን የእግዚአብሔርን ሥራ እንናገር።' 11 ፍላጾችን ሳሉ ጋሻዎችንም
አዘጋጁ። እግዚአብሔር ያጠፋት ዘንድ አሳቡ በባቢሎን ላይ ነውና የሜዶንን ነገሥታት መንፈስ አስነሥቶአል፤ የእግዚብሔር በቀል፣ የመቅደሱ መጥፊያ በቀል
ነውና። 12 በባቢሎን ቅጥር ዓላማውን አንሡበት፣ ጥበቃን አጽኑ። ተመልካቾችን አቁሙ፣ ከከተማዋ የሚወጡትን ለመያዝ ድብቅ ጦር አዘጋጁ። እግዚአብሔር
በባቢሎን በሚኖሩት ላይ የተናገረውን አስቦአልና፣ አድርጎአልምና። 13 አንቺ በብዙ ውኃ አጠገብ የተቀመጥሽ፣ በመዝገብም የበለጠግሽ፣ እንደ ስስትሽ መጠን
ፍጻሜሽ ደርሶአል። 14 የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ሲል በራሱ ምሏል፣ 'በእውነት ሰዎችን እንደ አንበጣ እሞላብሻለሁ፣ እነርሱም የጦርነት ጩኸት
ያነሡብሻል።' 15 ምድርን በኃይሉ ፈጠረ፤ ዓለሙን በጥበቡ መሠረተ። ሰማያትንም በማስተዋሉ ዘረጋ። 16 ድምጹን ባሰማ ጊዜ ውኆች በሰማይ ይታወካሉ፣
ከምድርም ዳር ደመናትን ከፍ ያደርጋል። ለዝናብም መብረቅን ያደርጋል፣ ነፍስንም ከቤተ መዛግብቱ ያወጣል። 17 ሰው ሁሉ እውቀት አጥቶ እንደ እንስሳ ሆኗል፤
እያንዳንዱ አንጥረኛ ሁሉ ከቀረጸው ምስል የተነሣ አፍሮአል። ቀልጦ የተሠራ ምስሉ ውሸት ነውና፤ እስትንፋስም የላቸውምና። 18 እነርሱም ምናምንቴና፣ የቀልድ
ሥራ ናቸው፤ በሚቀጡበት ጊዜ ይጠፋሉ። 19 የያዕቆብ እድል ፈንታ እንደ እነዚህ አይደለም፣ እርሱ የሁሉ ፈጣሪ ነውና። እስራኤልም የርስቱ ነገድ ነው፤ ስሙም
የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው። 20 አንቺ መዶሻዬና የጦር መሣሪያዬ ነሽ። በአንቺ አሕዛብን እሰባብራለሁ፤ በአንቺም መንግሥታትን አጠፋለሁ። 21 በአንቺ
ፈረሱንና ሠረገላውን እሰባብራለሁ፤ 22 በአንቺም በላዩ የሚቀመጡትን ወንድ እና ሴት እሰባብራለሁ፤ በአንቺም ሽማግሌውንና ብላቴናውን እሰባብራለሁ።
በአንቺም ጐልማሳውንና ልጃገረዲቱን እሰባብራለሁ። 23 በአንቺም እረኛውንና መንጋውን እሰባብራለሁ፤ በአንቺም አራሹንና ጥማጁን እሰባብራለሁ፤ በአንቺም
አለቆችንና ሹማምቶችን አሰባብራለሁ። 24 በጽዮን በዓይናችሁ ፊት ስለሠሩት ክፋታቸው ሁሉ በባቢሎንና በከለዳውያን ምድር በሚኖሩ ሁሉ ላይ ፍዳቸውን
እከፍላለሁ፣ ይላል እግዚአብሔር። 25 "ተመልከት፣ አንተ ምድርን ሁሉ የምታጠፋ አጥፊ ተራራ ሆይ፣ እኔ በአንተ ላይ ነኝ፣ ይላል እግዚአብሔር። እጄንም
እዘረጋብሃለሁ፣ ከድንጋዮችም ላይ አንከባልልሃለሁ። የተቃጠለም ተራራ አደርግሃለሁ። 26 ከአንተም ለማዕዘንና ለመሠረት የሚሆን ድንጋይ አይወስዱም፣
ለዘላለምም ባድማ ትሆናለህ፣ ይላል እግዚአብሔር። 27 "በምድር ላይ ዓላማን አንሡ። በአሕዛብም መካከል መለከት ንፉ። እንዲያጠቋት አሕዛብን
አዘጋጁባት፤ የአራራትንና የሚኒን የአስከናዝንም መንግሥታት ሰብስቡባት፣ አለቃንም በላይዋ አቁሙ። እንደ ጠጉራም አንበጣ ኩብኩባ ፈረሶችን በላይዋ
አውጡ። 28 አሕዛብን የሚዶንንም ነገሥታት አለቆችንም ሹማምቶችንም ሁሉ የግዛታቸውንም ምድር ሁሉ አዘጋጁባት። 29 ማንም እንዳይቀመጥባት
የባቢሎንን ምድር ባድማ ያደርጋት ዘንድ የእግዚአብሔር አሳብ በባቢሎን ላይ ጸንቶአልና ምድር ተናወጣለች ታመመችም። 30 የባቢሎን ወታደሮች መዋጋትን
ትተዋል፤ በምሽጎቻቸውም ውስጥ ተቀምጠዋል። ኃይላቸውም ጠፍቶአል እንደ ሴቶችም ሆነዋል። ማደሪያዎችዋም ነድደዋል፣ መወርወሪያዎችዋም ተሰብረዋል።
31 ከዳር እስከ ዳር ድረስ ከተማው እንደ ተያዘች መልካምዎችዋም እንደ ተያዙ፣ ቅጥርዋም በእሳት እንደ ተቃጠለ፣ ሰልፈኞችም እንደ ደነገጡ 32 ለባቢሎን
ንጉሥ ይነግር ዘንድ ወሬኛው ወሬኛውን፣ መልእክተኛውም መልእክተኛውን ሊገናኝ ይሮጣል።" 33 የእስራኤል አምላክ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ
ይላልና፣ አውድማ እንደ ተረገጠ ጊዜ፣ እንዲሁ የባቢሎን ልጅ ናት። ጥቂት ቈይታ የመከር ጊዜ ይደርስላታል። 34 ኢየሩሳሌም፣ 'የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር
በላኝ። አድርቆ አሟጠጠኝ፣ እንደ ባዶ የሸክላ ዕቃም አደረገኝ። እንደ ዘንዶም ዋጠኝ። ከሚጣፍጠውም ምግቤ ሆዱን ሞላ። እኔንም ወደ ውጪ ጣለኝ።' አለች።
35 የጽዮን ነዋሪዎች እንዲህ ይላሉ፣ 'በእኔና በሥጋዬ የተደረገ ግፍ በባቢሎን ላይ ይሁን።' ኢየሩሳሌምም፣ 'የሚፈስሰው ደሜ ጥፋት በከለዳውያን ምድር
በሚኖሩት ላይ ይሁን" ትላለች። 36 ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ተመልከቺ፣ እምዋገትልሻለሁ በቀልሽንም እበቀልልሻለሁ። ባሕርዋንም ድርቅ
አደርገዋለሁ፣ ምንጭዋንም አደርቀዋለሁ። 37 ባቢሎንም የድንጋይ ቍልልና የቀበሮ ማደሪያ፣ መደነቂያም ማፍዋጫም ትሆናለች፤ የሚቀመጥባትም ሰው
አይገኝም። 38 በአንድነትም እንደ አንበሶች ያገሣሉ። እንደ አንበሳም ደቦሎች ያጒረመርማሉ። 39 በስስት በሞቃቸው ጊዜ ደስ እንዲላቸው፣ ለዘላለምም
አንቀላፍተው እንዳይነቁ፣ የመጠጥ ግብዣ አደርግላቸዋለሁ፣ አሰክራቸውማለሁ፣ ይላል እግዚአብሔር። 40 እንደ ጠቦቶችና እንደ አውራ በጎች እንደ አውራ
ፍየሎችም ወደ መታረድ አወርዳቸዋለሁ።" 41 "ባቢሎን እንዴት ተያዘች! የምድርም ሁሉ ምስጋና እንዴት ተወሰደች። ባቢሎንም በአሕዛብ መካከል መደነቂያ
እንዴት ሆነች። 42 ባሕር በባቢሎን ላይ ወጣ! በሞገዱም ብዛት ተከደነች። 43 ከተሞችዋ ባድማና ደረቅ ምድር ምድረ በዳም፣ ሰውም የማይኖርበት፣ የሰውም
ልጅ የማያልፍበት ምድር ሆኑ። 44 በባቢሎንም ውስጥ ቤልን እቀጣለሁ፤ የዋጠውንም ከአፉ አስተፋዋለሁ፣ አሕዛብም ከዚያ ወዲያ ወደ እርሱ አይሰበሰቡም።
የባቢሎንም ቅጥር ይወድቃል።" 45 "ሕዝቤ ሆይ፣ ከመካከልዋ ውጡ። እያንዳንዳችሁም ከእግዚአብሔር ጽኑ ቍጣ ራሳችሁን አድኑ። 46 በምድርም ከሚሰማ
ወሬ የተነሣ አትፍሩ፣ ልባችሁም የዛለ አይሁን፤ በአንድ ዓመት ወሬ ይመጣል፣ ከዚያም በኋላ በሌላው ዓመት ወሬ፣ በምድርም ላይ ግፍ ይመጣል፣ አለቃም
በአለቃ ላይ ይነሣል። 47 ስለዚህ፣ ተመልከቱ፣ የተቀረጹትን የባቢሎን ምስሎች የምቀጣበት ዘመን ይመጣል። ምድርዋም ሁሉ ታፍራለች፣ ተወግተውም የሞቱት
ሁሉ በመካከልዋ ይወድቃሉ። 48 አጥፊዎች ከሰሜን ይመጡባታልና ሰማይና ምድር በእነርሱም ያለው ሁሉ ስለ ባቢሎን እልል ይላሉ፣ ይላል እግዚአብሔር።
49 ባቢሎንም ከእስራኤል ተወግተው የሞቱት እንዲወድቁ እንዳደረገች፣ እንዲሁ በባቢሎን ከምድሩ ሁሉ ተወግተው የሞቱት ይወድቃሉ።" 50 "ከሰይፍ
ያመለጣችሁ፣ ሂዱ! ተረጋግታችሁ አትቁሙ። እግዚአብሔርን ከሩቅ ጥሩት፤ ኢየሩሳሌምንም በልባችሁ አስቡ። 51 ስድብን ስለ ሰማን አፍረናል፤ ባዕዳን
ሰዎችም ወደ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ገብተዋልና ነውር ፊታችንን ከድኖታል።" 52 "ስለዚህ፣ ተመልከቱ፣ የተቀረጹትን ምስሎችዋ የምቀጣበት ዘመን
ይመጣል፣ ይላል እግዚአብሔር፤ በምድርዋም ላይ ሁሉ የተወጉት ያንቋርራሉ። 53 ባቢሎን ምንም ወደ ሰማይ ብትወጣ፣ የኃይልዋንም ምሽጎች ብታጸና፣ ከእኔ
ዘንድ አጥፊዎች ይመጡባታል፣ ይላል እግዚአብሔር።" 54 ከባቢሎን ጩኸት፣ ከከለዳውያንም ምድር የታላቅ ጥፋት ድምፅ ተሰምቶአል። 55 እግዚአብሔር
ባቢሎንን አጥፍቶአታልና፣ ከእርስዋም ታላቁን ድምፅ ዝም አሰኝቶአልና፤ ሞገዳቸውም እንደ ብዙ ውኆች ይተምማል፣ የድምፃቸውም ጩኸት በብርቱ
ተሰምቶአል። 56 አጥፊው በባቢሎን ላይ መጥቶባታልና፣ ኃያላኖችዋ ተያዙ፣ ቀስታቸውም ተሰባበረ፤ እግዚአብሔር ፍዳን የሚከፍል አምላክ ነውና፣ ፍዳንም
በእርግጥ ይከፍላል። 57 "መሳፍንቶችዋንና ጥበበኞችዋን፣ አለቆችዋንና ሹማምቶችዋን፣ ወታደሮችዋንም አሰክራለሁ፥ ለዘላለምም አንቀላፍተው አይነቁም፣

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይላል ስሙ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የተባለው ንጉሥ።" 58 "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ሰፊው የባቢሎን ቅጥር ፈጽሞ ይፈርሳል፤ ረጃጅሞችም በሮችዋም በእሳት ይቃጠላሉ፤ የወገኖችም ድካም ከንቱ ትሆናለች፣ የአሕዛብም ሥራ ሁሉ ለእሳት ትሆናለች፤ እነርሱም ይደክማሉ።" 59 የመሕሤያ ልጅ የኔርያ ልጅ ሠራያ የይሁዳ ንጉሥ ሴዴቅያስ በነገሠ በአራተኛው ዓመት ከእርሱ ጋር ወደ ባቢሎን በሄደ ጊዜ ነቢዩ ኤርምያስ ያዘዘው ቃል ይህ ነው፣ ያን ጊዜ ሠራያ የቤት አዛዥ ነበረ። 60 በባቢሎንም ላይ የሚመጣውን ክፉ ነገር ሁሉ፣ ስለ ባቢሎን የተጻፈውን ይህን ቃል ሁሉ፣ ኤርምያስ በመጽሐፍ ላይ ጻፈው። 61 ኤርምያስም ሠራያን እንዲህ አለው፣ "ወደ ባቢሎን በገባህ ጊዜ ይህ ቃል ሁሉ መነበቡን እርግጠኛ ሁን። 62 አንተም ደግሞ፣ 'ከሰው ጀምሮ እስከ እንስሳ ድረስ ማንም እንዳይቀመጥባት፣ ለዘላለምም ባድማ እንድትሆን ታጠፋት ዘንድ በዚህች ስፍራ ላይ ተናግረሃል' በል። 63 ከዚያም ይህንን ጥቅልል መጽሐፍ ማንበብ ከፈጸምህ በኋላ፣ ድንጋይን እሰርበትና በኤፍራጥስ ወንዝ መሃከል ጣለው። 64 አንተ፣ 'እኔ ከማመጣባት ክፉ ነገር የተነሣ እንዲሁ ባቢሎን ትሰጥማለች፣ አትነሣምም" በል። የኤርምያስ ቃል እዚህ ላይ ያበቃል።

Jeremiah 51:1

አጠቃላይ ሐሳብ
ኤርሚያስ በብዛት የሚፅፋቸው ትንቢቶች በግጥም መልክ ነው።

እነሆ
ይህ ቃል ቀጥሎ ለሚናገረው ነገር በማስተዋል እንዲሰሙ ያመለክታል

አጥፊውን ነፋስ
የሚያጠፋ ነፋስ ወይም ደግሞ የሚያጠፋ መንፈስ። ይህ ማለት እግዚአብሄር የጠላት ሰራዊት ሄደው ባቢሎንን እነዲያጠቁ ያስነሳል።

ከለዳውያን
በባቢሎን ክልል የሚገኙ ህዝቦች ናቸው።

በባቢሎንም ላይ የሚዘሩትን ሰዎች ... በዙሪያዋ ይከብቡአታል
“በዙሪያዋ” ብሎ የሚያመለክተው ባቢሎንን ሲሆን በባቢሎን ለሚኖሩ ሰዎች መጠሪያቸው ነው።

በመከራም ቀን
ይህ ሀረግ “መከራ ቀን” የሚለው በእብራውያን “መቼ” ሚለውን ያመለክታል።

Jeremiah 51:3

ቀስተኛው ቀስቱን ይገትር ለጐበዛዝትዋ አትዘኑ
እግዚአብሄር በድንገተኛ እንዲያጠቁ ስለፈለገ ለቀስተኛው ለጦርነት የዝግጅት ጊዜ የላቸውም።

“በከለዳውያን ምድር ተገድለው”
ጠላቶቻቸው የገደሉአቸውን ያመለክታል

Jeremiah 51:5

“...እስራኤልም ሆነ ይሁዳ በአምላኩ በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ዘንድ አልተጣለም”
“እስራኤል” እና “ይሁዳ” ብሎ ሲናገር በእስራኤል እና በይሁዳ የሚገኙ ሰዎችን ለማመልከት ነው።

ምድራቸው በእስራኤል ቅዱስ ላይ በተሠራው በደል ምንም እንኳ የተሞላች ብትሆን፥
በዚህ ክፍል የተናገረው ምድር ላይ የሚኖሩት ሰዎች ከሰሩት በደል የተነሳ ልክ እቃ ማጠራቀሚያን እንደሚሞላ እነሱም ምድርን ሞሉአት።

በበደልዋ አትጥፉ
ይህ ሐረግ ባቢሎን ልክ እነደ ሴት አርጎ ሲናገር እግዚአብሄር ባቢሎንን ሊያጠፋ እንደሆነ ያመለክታል።

እርሱም ብድራትዋን ይከፍላታልና
በዚህ ሀረግ ባቢሎን ልክ እንደ ሴት አረጎ ሲናገር ህዝቡ ከሰራው በደል ምክንያት እግዚአብሄር የሚገባቸውን ቅጣት እንደሚቀጣቸው ያመለክታል

Jeremiah 51:7

ባቢሎን በእግዚአብሄር እጅ ውስጥ ምድርን ሁሉ ያሰከረች የወርቅ ፅዋ ነበረች
“ምድርን ሁሉ” ሲል በባቢሎን ዙሪያ የሚኖሩ ሰዎችን ሲሆን የሚያመለክተውም 1) “ያሰከረች” ብሎ ሲናገር እግዚአብሄር ለባቢሎን አሳልፎ ስለሰጣቸው ከተሞች ነው 2) ሌላው ደግሞ ከባቢሎን ጋር አብሮ በመሆን ጣኦት አምልኮ ሲጀምሩ እና ጦርነት ሲሆን ነው

ባቢሎን በእግዚአብሄር እጅ ውስጥ ... የወርቅ ፅዋ ነበረች
ባቢሎን እግዚአብሄር ለራሱ አላማ የሚጠቀምባት ከተማ ነበረች። በእርሱም እጅ እንዳለ የወርቅ ፅዋ እንደሆነች ይናገራል።”እጅ” የሚለው ቃል የእግዚአብሄርን ሃይል ወይም ሃያልነት ያመለክታል።

አሕዛብም ከጠጅዋ ጠጥተዋል ስለዚህ አሕዛብ አብደዋል
የዚህ ትርጉም ሊሆን የሚችለው 1) ባቢሎን ሌሎች ከተማዎችን አሸንፈው እና አጥፍተዋል 2) ሌሎች ከተሞች በእሷ ሀብት እና ሀያልነት ክፉ ሆነዋል።

አብደዋል
በትክክል ማሰብ አለመቻል

ባቢሎን በድንገት ወድቃ ጠፍታለች
እግዚአብሄር ባቢሎንን አጠፋ

“...አልቅሱላት”
በከፍተኛ ድምፅ እና ረጅም የሆነ ለቅሶ ሲሆን ምን ያህል እንዳዘነ ያሳያል

“...ትፈወስም እንደሆነ”
ምናልባት እግዚአብሄር ከፈወሳት

Jeremiah 51:9

አጠቃላይ ሐሳብ
እግዚአብሄር ባቢሎንን ተጠቅሞ ይሁዳን ሲቀጣ ወይ የይሁዳ ህዝቦችን ወይም በዚህ ክፍል የተጠቀሱት ቃሉን የሚናገሩትን ሰዎችን ነው።

“ባቢሎን... እርስዋ ግን አልተፈወሰችም ፍርድዋ እስከ ሰማይ ደርሶአልና፥ እስከ ደመናም ድረስ ከፍ ከፍ ብሎአልና ትታችኋት..”
ባቢሎን የሚለው የሚያመለክተው በውስጧ የሚኖሩት ህዝቦችን ሲሆን ልክ እንደ ሴት መስሏታል።

“..እርስዋ ግን አልተፈወሰችም”
እኛ ግን ልናድናት አልቻልንም።

“...ፍርድዋ እስከ ሰማይ ደርሶአልና፥ እስከ ደመናም ድረስ ከፍ ከፍ ብሎአልና”
ፍርድዋ ልክ እነደ እቃ ተከምሯል። “...ሰማይ ደርሶአልና እስከ ደመናም ድረስ..” ሲል ግነት ሲሆን ይህም ምን ያህል በጣም ከፍታን ያመለክታል

እግዚአብሔር ጽድቃችንን አውጥቶአል
እግዚአብሄር እስራኤላውያንን በሰሩት ሀጥያት ቅጣት ቀጥቶአቸው ነበር አሁን ግን ወደሱ መልሶአቸዋል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Jeremiah 51:11

አጠቃላይ ሀሳብ
ኤርሚያስ ለባቢሎን ሰዎች እና ለጠላቶቻቸው እንደሚናገር ያህል ለኢየሩሳሌም ሰዎች እግዚአብሄር ባቢሎንን እንደሚያጠፋ እና ባቢሎናዊያንን ከጦርነት ከመዘጋጀታቸው በፊት እንደሚሸነፉ ሲናገር ነበር።

“በባቢሎን ቅጥር ዓላማውን አንሡበት”
የባቢሎን ቅጥርን ለመምታት ምልክት ሰጠ

ጥበቃን አፅኑ
ጥበቃዎቹ ጠንካራ እና ጥሩ መሳሪያ ያላቸው መሆኑን አረጋግጡ

“ተመልካቾችን አቁሙ”
በቂ ከተማዋን የሚመለከቱ ሰዎች መኖራቸውን አረጋግጡ

ድብቅ ጦር አዘጋጁ
ይህ ድንገት ከከተማዋ ሸሽቶ የሚያመልጥ ካለ ለመያዝ አዘጋጁ

Jeremiah 51:13

አጠቃላይ ሀሳብ
ኤርሚያስ በኢየሩሳሌም ያሉ ህዝቦችን ልክ ሲናገር እንደማይሰሙት የባቢሎን ህዝቦች መናገሩን ቀጥሎአል።

ፍጻሜሽ ደርሶአል
“ፍፃሜሽ ደርሶአል” የሚለው ሐረግ እግዚአብሄር ህዝቡ የሚጠፋበት ጊዜ እንደቀረበ ይናገራል።

እንደ አንበጣ..
ከተማዋን የሚወሩ እጅግ በጣም ብዙ ሰራዊትን ያመለክታል

እነሱም ጩኸት ያነሱብሻል
የሠራዊቱ ጩኸትን ያመለክታል።

Jeremiah 51:15

ድምፁን ባሰማ ጊዜ ውሆች በሰማይ ይታወካሉ
የእግዚአብሄር ድምፅን ከመብረቅ ነጎድጓድ ድምፅ እና ከዝናብ ጋር ያነፃፅረዋል።

ከቤተ መዛግብቱ
ይህ ስፍራ ወደፊት እንጠቀምበታለን ብለው የሚያስቡትን ሚቀመጥበት ቦታ ነው።

Jeremiah 51:17

አጠቃላይ ሐሳብ
በኤርሚያስ 10፡14-16 ላይ እንዳለው ተተርጉሟል

“ሰው ሁሉ እውቀት አጥቶ ሰንፎአል”
የእውቀት ማጣት ወይም አለማወቅ

አንጥረኛም ሁሉ ከቀረፀው ምስል...
አንጥረኛ የተባለ ሁሉ የሰሩት እና የቀረፁት የጣኦት ምስል አሳፍሮአቸዋል

በተጐበኙ ጊዜ ይጠፋሉ
የተቀረፁት ምስሎች እግዚአብሄር እንደሚያጠፋቸው ወይም እንደሚያፈራርሳቸው ያመለክታል።

የያእቆብ እድል ፈንታ
“ያዕቆብ” የሚለው ስም የሚያመለክተው የእስራኤል ህዝብን ሲሆን እግዚአብሄር እድል ፈንታቸው ሲሆን እርሱን ያመልኩታል

የሁሉ ፈጣሪ
እርሱ ሁሉንም የፈጠረ ነው

እስራኤልም የርስቱ ነገድ ነው።
እስራኤልን እግዚአብሄር ወርሶታል ይህም እስራኤል የ እግዚአብሄር ነገድ ነው።

Jeremiah 51:20

አንቺ
የባቢሎን ሰራዊትን ያመለክታል

እሰባብራለሁ
እግዚአብሄር ህዝቡን እንደሚቀጣ ይናገራል

በአንቺ
እጠቀምብሻለሁ እያለ ነው

Jeremiah 51:22

በአንቺም...እሰባብራለሁ
እግዚአብሄር ህዝቡን እንደሚቀጣ ይናገራል (ኤርሚያስ 51:20 ተመልከት)

በአንቺ
እጠቀምብሻለሁ እያለ ነው (ኤርሚያስ 51:20 ተመልከት)

Jeremiah 51:24

በአይናችሁ ፊት... እከፍላለሁ
የስራቸውን ስከፍላቸው በአይናችሁ ታያላችሁ

ይላል እግዚአብሄር
ይህ ሀረግ እግዚአብሄር እራሱ በስሙ ጠርቶ ያዛል።

Jeremiah 51:25

አጠቃላይ ሀሳብ
እግዚአብሄር ለሚሰሙት የኢየሩሳሌም ህዝቦች ልክ እንደ ማይሰሙት የባቢሎን ህዝቦች ይናገራል። የባቢሎን ህዝቦችን ልክ እንደ እራሳቸው ሲናገር ከተማዋን ደግሞ ልክ እንደ ተራራ ይናገራል።

አንተ...አጥፊ ተራራ
ይህ የሚያመለክተው 1) እግዚአብሄር ባቢሎን ልክ ህዝቦችን እና ንብረቶችን እንደ ሚያጠፋ ተራራ ይናገራል። 2) ባቢሎን ወንበዴዎች የሚኖሩበት እና የሚደበቁበት ተራራ

እጄንም አዘረጋብሃለሁ
“እጄንም” ሲል የእግዚአብሄርን ሀይል ለማመልከት ነው።

ከድንጋዮችም ላይ አንከባልልሃለሁ
እግዚአብሄር ባቢሎንን እንደ ተራራ መናገር ትቶ እንደ ሚያፈራርሰው እና እንደሚጥለው ቤት ይናገራል

ከድንጋዮቹም
ይህ የሚያመለክተው የተራራ ጫፍ ነው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የተቃጠለም ተራራ አደርግሀለሁ
እግዚአብሄር ባቢሎንን እንደ ሚያጠፋ ትልቅ ተራራ ሳይሆን እርሱ እንዳጠፋው ተራራ አርጎ ይናገራል።

ለዘላለም ባድማ ትሆናለህ
ማንም መልሶ እንዳይገነባህ ለዘላለም አጠፋሀለሁ

ይላል እግዚአብሄር
ይህ ሀረግ እግዚአብሄር እራሱ በስሙ ጠርቶ ያዛል።

Jeremiah 51:27

በምድር ላይ ዓላማን አንሡ በአሕዛብም መካከል መለከት ንፉ
ሁለቱም “መለከት ንፉ” እና “አላማን አንሱ” ሰራዊቱን ለውጊያ ተነሱ ማለት ነው።

አላማን አንሱ
ትልቅ “የጦር ሜዳ ባንዲራ” ሲሆን ወታደሮቹ ጦርሜዳላይ የሚከተሉት ነው።

አህዛብንም አዘጋጁባት
የባቢሎን ከተማ እንደ ሴት መስሎአት ሲናገር የባቢሎንን ህዝብ ውጉአቸው እያለ ነው

አራራት...ሚኒን...አስከናዝ
እነዚህ የሀገራት ስሞች ናቸው

እነደ ጠጉራም ኩብኩባ ፈረሶችን በላይዋ አውጡ
እግዚአብሄር ቁጥራቸው ብዙ የሆኑ ፈረሶች ከሰራዊቶች ጋር አምጡ ይላል

ነገሥታት አለቆችንም ሹማምቶችንም
ኤርሚያስ 51:23 ተመልከት

Jeremiah 51:29

ምድር ተናወጣለች ታመመችም
“ምድር” የሚለው በባቢሎን የሚኖሩትን ህዝቦችን ሲያመለክት በባቢሎን የሚኖሩ ህዝቦች በፍርሀት እና ጭንቀትን እንደሚናወጡ ያመለክታል።

ታመመችም
ስቃይ እና የሚያስነባ ለቅሶ

በባቢሎን ላይ
ይህ በባቢሎን ያሉ ህዝቦችን ላይ መሆኑን ያመለክታል

ባድማ ያደርጋት
ምንም ህይወት አይኖርም ትጠፋለች

Jeremiah 51:30

አጠቃላይ ሀሳብ
እግዚአብሄር ገና ወደፊት የሚፈፀመውን እንደተፈፀመ አርጎ ይናገራል።

ማደሪያዎችዋም ነድደዋል መወርወሪያዎችዋም ተሰብረዋል
ከተማዋን በሴት መስሏታል

ከተማው እንደ ተያዘች...
ሙሉ ከተማዋን ጠላቶቿ አሸንፈው ያዙአት

መልካምዎችዋም እንደ ተያዙ
መልካምዎችዋም እንደ ተያዙ

መልካምዎችዋም
ከወንዝ በላይ ያለ ድልድይ

ቅጥርዋም
እርጥበት ያለበት ቦታ ላይ ሳር እና ጥልቅ የሆነ ጭቃ ሲኖር

ደነገጡ
ግራ መጋባት

Jeremiah 51:33

የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር እንዲህ ይላልና
ኤርሚያስ በብዛት ይህን ሀረግ ከእግዚአብሄር የተላከ ቁልፍ መልእክት ለማሳወቅ ይጠቀማል።

የባቢሎን ልጅ ናት
ይህ የባቢሎን ህዝቦች ስም ነው።

አውድማ
እነደ አውድማ እግዚአብሄር የባቢሎን ህዝብ እንደሚቀጣ ያሳያል

አውድማ እንደ ተረገጠ ጊዜ
እግዚአብሄር የባቢሎን ልጅን እንደ ቀጣ ይናገራል

የመከር ጊዜ ይደርስባታል
“መከር” የሚለው የሰሩትን የሚያገኙበት ጊዜን ያመለክታል። ባቢሎን የሃጥያቷን ዋጋ ትቀበላለች:

Jeremiah 51:34

አጠቃላይ ሐሳብ
እዚህ ላይ እንደ ሴት መስሎ የሚናገረው የኢየሩሳሌምን ከተማ ሲሆን የኢየሩሳሌም ከተማ ደግሞ የኢየሩሳሌምን ህዝብ ይመስላል።

ከፋፈለኝም
የዚህ ትርጉም ይሆናል ተብሎ ሚታሰበው 1) በትክክል ማሰብ እንዳልችል አደረገኝ 2) ጎዳኝ

እንደ ባዶ ዕቃም አደረገኝ
ባቢሎን ከእስራኤል ያላትን ሁሉ ወሰደችባት

እንደ ዘንዶም
ባቢሎንን በዘንዶ ይመስላታል

ዋጠኝ
የኢየሩሳሌምን ውድቀት በመዋጥ ይመስለዋል

ከሚጣፍጠውም ምግቤ ሆዱን ሞላ
ባቢሎን በዘንዶ መስሎ ኢየሩሳሌም ያላትን በሙሉ እንደወሰዳት ከዚህ ቀደም ባለው ሃሳብ አይተናል። “ጣፋጭ ምግብ” ኢየሩሳሌም የነበራትን ጥሩ ጥሩ ነገሮች ያመለክታል

እኔንም ጣለኝ
ናቡከደነፆር የሚፈልገውን ወስዶ የማይፈልገውን ደግሞ ጣለው።

በፅዮን የምትቀመጥ
በፅዮን የምትቀመጥ

በእኔ በስጋዬ...ደሜ
እነዚህ ሀረጎች ሴትን ያመለክታል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በከለዳውያን ምድር በሚኖሩት
ከለዳውያን ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች

Jeremiah 51:36

አጠቃላይ ሐሳብ
እግዚአብሄር ለእስራኤላውያን በቁጥር 34 እና 35 ባቀረቡት ጥያቄ ምላሽን ይሰጣል

እነሆ፥ እምዋገትልሻለሁ በቀልሽንም እበቀልልሻለሁ
ፍርድቤት እንዳለ ጠበቃ እግዚአብሄር ለእስራኤላውያን ይሟገታል።

የድንጋይ ቍልልና
የድንጋይ ክምር የሆኑ ቤቶች

የቀበሮ ማደሪያ
የቀበሮ መኖሪያ

መደነቂያም
የሚያስፈራ ነገር

ማፍዋጫም
ሰዎች እጅግ በጣም የማይወዱትን ነገር በድምፅ ሚያሳውቁበት

የሚቀመጥባትም ሰው አይገኝም
ምንም አይነት ህይወት ያለው አይኖርም

Jeremiah 51:38

ያገሳሉ
ከፍተኛ የሆነ አንበሶች የሚያሰሙት ጩኸት

ያጉረመርማሉ
እንስሶች በፍራቻ ሰዓት የሚያሰሙት ድምፅ ነው

ደስ እንዲላቸው
ወታደር ጠላቶቹን ሲያሸንፍ ደስ እንደሚለው ሌላው ሊሆን የሚችለው ትርጉም ደግሞ ሰክረው ነበር

ለዘላለምም አንቀላፍተው እንዳይነቁ
ይሞታሉ

ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ በመጥራት ያዛል። ኤርሚያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

እንደ ጠቦቶችና... አውራ ፍየሎችም
ጠቦት እና ፍየሎች ለመታረድ እየሄዱ ነገር ግን አያቁም ልክ እንደዚሁ ባቢሎናውያንን እግዚአብሄር እንደሚያጠፋቸው አያውቁም

Jeremiah 51:41

ሼሻክ(ባቢሎን) እንዴት ተያዘች...ባቢሎንም በአህዛብ መካከል መደነቂያ እንዴት ሆነች
“እንዴት” የሚለው ቃል በሰው አይን ከባድ የሆነ ነገር መፈፀሙን የሚያመለክት ነው። “ሼሻክ(ባቢሎን) እንዴት ተያዘች...ባቢሎንም በአህዛብ መካከል መደነቂያ እንዴት ሆነች” ይህን ሐረግ “ባቢሎን የተበላሸ እና የፈራረሰች ከተማ ትሆናለች ብለን አናስብም ነበረ” እንደማለት ነው።

የምድርን ሁሉ ምስጋና እንዴት ወሰደች
“ምስጋና” የሚለው ሰዎች የሚያመሰግኑት ሲሆን “ምድርም” ሲል በምድር ላይ የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታል። ይህም “በምድር ላይ ሁሉ የምትመሰገነው ባቢሎን በጠላቶቿ ተያዘች” እንደማለት ነው።

ባህር በባቢሎን ላይ ወጣ በሞገዱም ብዛት...
የባቢሎን ጠላት አሸነፉአት “በሞገዱም” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ብዛት ያለው ህዝብ ሲያሸንፍ ሲሆን “ባህር” እና “ውሃ” ደግሞ በብዛት የሚያመለክተው ከተማን ወይም ሀገርን ያመለክታል።

በሞገዱም ብዛት ተከደነች
ይህ “ሞገዱ ባቢሎንን ሸፈነ ወይም ከደነ” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል።

Jeremiah 51:43

ከተሞችዋ
የባቢሎን ከተሞች

ቤልን እቀጣለሁ
ቤል በባቢሎን ከተማ ሙሉ የሚመለክ ጣኦት ነው።

የዋጠውንም ከአፉ አስተፋዋለሁ
የሚሰዋውን መስዋዕት በሙሉ ቤል እንደበላ እግዚአብሄር ያመለክታል።

አህዛብም ከዚያ ወዲያ ወደእርሱ አይሰበሰቡም
በተለያዩ ከተማዎች የሚገኙ አህዛቦች ወደባቢሎን መጥተው መስዋእትን መሰዋትን ያቆማሉ።

Jeremiah 51:45

በምድርም ከሚሰማ ወሬ
በምድር ላይ ወሬ ስትሰሙ በማለት መተርጎም ይቻላል።

አለቃም በአለቃ ላይ ይነሳል
አለቃ ከተማን ያመለክታል

Jeremiah 51:47

እነሆ
ተመልከቱ ወይም በማስተዋል አድምጥ

የምቀጣበት ዘመን ይመጣል
የምቀጣበት ጊዜው ይደርሳል...እቀጣለሁ ኤርሚያስ 7:32 እንዴት እነደተረጎመው ተመልከት

የተቀረፁትን የባቢሎን ምስሎችን የምቀጣበት ዘመን ይመጣል
የተቀረፁ ምስሎችን እንደሚያጠፋ እግዚአብሄር ይናገራል።

ባቢሎን... ምድርዋም ሁሉ...ተወግተው የሞቱት ሁሉ በመካከልዋ...እንዲሁ በባቢሎን
በባቢሎን ያሉ ህዝቦችን እንደ ባቢሎን ከተማ ይመስላል የባቢሎንን ከተማ ደግሞ እንደ ሴት ይመስላል።ይህም”የባቢሎን ህዝቦች...ምድራቸውም ሁሉ...ተወግተው የሞቱት ሁሉ በባቢሎን መካከል”

ሰማይና ምድር
“ሰማይና ምድር” እነደ ሰው ይመስላቸዋል።

ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ በመጥራት ያዛል። ኤርሚያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አጥፊዎች...ይመጡባታል
የባቢሎናዊያን ጠላቶች ምድሪቱን ሊያፈአት ይመጣሉ

Jeremiah 51:50

አጠቃላይ ሀሳብ
ኤርሚያስ በቁጥር 50 ላይ ለእስራኤላውያን ይናገራል

ከሰይፍ ያመለጣችሁ ሆይ
“ሰይፍ” የሚለው ወታደሮች የሚዩዝትን ሰይፍ ሲሆን ጦርነትን ያመለክታል።

እግዚአብሄርን ከሩቅ አስቡ ኢየሩሳሌምንም በልባችሁ አስቡ
“ከሩቅ አስቡ” እና “በልባችሁ አስቡ” የሚሉት ሀረጎች አስታውሱ የሚለውን ያመለክታል

ስድብን
ሰውን ሊያሳዝን እና የሚያስከፋ ቃላት

ነውር ፊታችንን ከድኖታል
ተናጋሪው የአለመቀበል ምላሹን እየተናገረ ያለው ፊቱን የሸፈነው ሸፋን እንዳለ አርጎ ነው።

Jeremiah 51:52

እነሆ
ተመልከቱ ወይም በማስተዋል አድምጥ

የምቀጣበት ዘመን ይመጣል
የምቀጣበት ጊዜው ይደርሳል...እቀጣለሁ ኤርሚያስ 7:32 እንዴት እነደተረጎመው ተመልከት

ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ በመጥራት ያዛል። ኤርሚያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

የተቀረፁትን ምስሎችን የምቀጣበት ዘመን ይመጣል
የተቀረፁ ምስሎችን እንደሚያጠፋ እግዚአብሄር ይናገራል።

የተቀረፁ ምስሎችዋን... በምድርዋም ላይ...ባቢሎን...ከፍታ ብታፀና... ይመጡባታል
የባቢሎን ህዝቦችን እንደ ከተማ መስሎ ሲናገር ከተማዋን ደግሞ እንደ ሴት ይመስላል። ”የተቀረፁ ምስሎቻቸውን...በምድራቸው ላይ... ባቢሎናውያን....ከፍታ ቢያፀኑም...ወደነሱ ይመጡባቸዋል”

ያንቋርራሉ
ከህመም እና ማዘን ብዛት የሚመጣ ለቅሶ

ባቢሎን ምንም ወደ ሰማይ ብትወጣ...ከፍታ ብታፀና... አጥፊዎች ይመጡባታል
ይህ የማይሆነውን ቢሆን እንኳን እያለ ያወራል። “ባቢሎን ወደ ሰማይ አትወጣም... ከፍታ አታፀናም... ቢሆንም ግን አጥፊዎች ከኔ ይመጡባታል”

Jeremiah 51:54

ከባቢሎን ጩኸት፥ ከከለዳውያንም ምድር የታላቅ ጥፋት ድምፅ ተሰምቶአል።
አንድ ሃሳብ በሁለት መንገድ አግንኑ ያሳያል

ባቢሎንን አጥፍቶአታልና... ከእርሷም ታላቁን ድምፅ
የባቢሎን ህዝቦችን እንደ ከተማ መስሎ ሲናገር ከተማዋን ደግሞ እንደ ሴት ይመስላል። “የባቢሎን ህዝቦችን አጥፍቶአቸዋልና... ከእነርሱም ታላቁን ድምፅ...”

ሞገዳቸውም...የድምፃቸው ጩኸት ተሰምቶአል።
“ሞገዳቸውም” የሚለው የባቢሎን ህዝብ ጠላትን ሲያመለክት “የድምፃቸው ጩኸት ተሰምቶአል” የሚለው የጠላቶቻቸውን ድምፅ ያመለክታል።

ሞገዳቸውም እንደ ብዙ ወኖች ይተምማል
ይህ ጠላቶቻቸው ልክ እነደ ውቅያኖስ እና እንደ ወንዝ ሞገድ ከፍተኛ ድምፅ እያሰሙ እንደሚመጡ ያመለክታል

በባቢሎን ላይ መጥቶባታልና...በባቢሎን ላይ... ሓያላኖችዋ
የባቢሎን ህዝቦችን እንደ ከተማ መስሎ ሲናገር ከተማዋን ደግሞ እንደ ሴት ይመስላል።

ሃያላኖችዋ ተያዙ
ጠላቶቿ ያላትን ሃያላኖችዋን ተያዙ

Jeremiah 51:57

መሳፍንቶችዋንና ጥበበኞችዋንም አለቆችዋንና ሹማምቶችዋን ሃያላኖችዋንም...ረጃጅሞችም በሮችዋ
የባቢሎን ህዝቦችን እንደ ከተማ መስሎ ሲናገር ከተማዋን ደግሞ እንደ ሴት ይመስላል። “መሳፍንቶቻቸውንና ጥበበኞቻቸውንም አለቆቻቸውንና ሹማምንቶቻቸውን ሃያላኖቻቸውንም...ረጃጅም በሮቻቸው” ብሎ ማንበብ ይቻላል።

ለዘለአለም አንቀላፍተው አይነቁም
ይሞታሉ። ኤርሚያስ 51:39 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄ እንዲህ ይላል፦
ኤርምያስ በብዛት እግዚአብሄር የሚናገረውን ቁልፍ መልእክት ለማሳየት የሚጠቀመው ነው። ኤርሚያስ 6:6 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ሰፊው የባቢሎን ቅጥር ፈፅሞ ይፈርሳል
የባቢሎን ሰፊው ቅጥር ወራሪዎች ፈፅሞ ያፈራርሱታል

ረጃጅሞችም በሮችዋ በእሳት ይቃጠላሉ
ረጃጅም በሮችዋን በእሳት ያቃጥሉባቸዋል

ሁሉም በእሳት የይጋያል
ከተማዋ ለማድረግ የምትሞክረው በሙሉ በእሳት ይነዳል።

Jeremiah 51:59

ሠራያ...ኔርያ...መህሴያ
የወንድ ስሞች ናቸው።

በነገሰ በአራተኛው አመት
ሶስት አመት ነግሶአል ይህ አራተኛው አመቱ ነው

ስለ ባቢሎን የተፃፈው
እርሱ ስለ ባቢሎን የፃፈው

Jeremiah 51:61

እንስሳ
የቤት እንስሳን ያመለክታል ምክንያቱም ኤርምያስ 51:37 ባቢሎናውያን የቀበሮ ማደሪያ እነደሆነች ይናገራል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Jeremiah 51:63

አትነሳምም
ከተማ አትሆንም

ባቢሎን ትሰጥማለች
በዙሪያዎቿ ያሉ ድንጋዮች ከውሃ በታች ይሆናሉ ባቢሎንም ከተማ መምሰሏን
ቀርቶ በውሃ ትሰጥማለች

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 52

1 ሴዴቅያስ መንገሥ በጀመረ ጊዜ የሀያ አንድ ዓመት ጕልማሳ ነበረ፤ በኢየሩሳሌምም አሥራ አንድ ዓመት ነገሠ። እናቱም አሚጣል የምትባል ነበረች፤ እርሷ የሊብና ሰው የኤርምያስ ልጅ ነበረች። **2** ኢዮአቄምም እንዳደረገ ሁሉ እርሱም በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገርን አደረገ። **3** ከፊቱም አውጥቶ እስኪጥላቸው ድረስ ይህ በእግዚአብሔር ቍጣ፣ በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ላይ ሆኖአልና። ከዚያም ሴዴቅያስ በባቢሎን ንጉሥ ላይ ዐመፀ። **4** ሴዴቅያስም በነገሠ በዘጠነኛው ዓመት በዐሥረኛው ወር፣ ከወሩም በዐሥረኛው ቀን፣ የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆርና ሠራዊቱ ሁሉ በኢየሩሳሌም ላይ መጥተው ከበቡአት፤ በዙሪያዋም ቅጥር የሚሆን ግድግዳ ገነቡ። **5** ስለዚህ ከተማይቱ እስከ ንጉሡ እስከ ሴዴቅያስ እስከ ዐሥራ አንደኛው ዓመት ድረስ ተከብባ ነበር። **6** በአራተኛውም ወር፣ በዐመቱ ዘጠነኛ ቀን፣ በከተማይቱ ራብ ጸንቶ ነበር። ለምድሪቱም ሰዎች እንጀራ ታጣ። **7** ከተማይቱም ተሰበረች፣ ተዋጊዎች ሁሉ ሸሹ፣ በሁለቱም ቅጥር መካከል ባለው በር ወደ ንጉሡ አትክልት በሚወስደው መንገድ በሌሊት ከከተማይቱ ወጡ። ከለዳውያንም በከተማይቱ ዙሪያ ነበሩ። ስለዚህ በዓረባ መንገድ ሄዱ። **8** ነገር ግን የከለዳውያን ሠራዊት ንጉሡን ተከታተሉት፣ በኢያሪኮም ሜዳ ሴዴቅያስን ያዙ። ሠራዊቱም ሁሉ ከእርሱ ዘንድ ተበትነው ነበር። **9** ንጉሡንም ይዘው የባቢሎን ንጉሥ ወዳለባት በሐማት ምድር ወዳለችው ወደ ሪብላ አመጡት፤ እርሱም ፍርድን በእርሱ ላይ ተናገረ። **10** የባቢሎንም ንጉሥ የሴዴቅያስን ልጆች በዐይኖቹ ፊት ገደላቸው፣ የይሁዳንም አለቆች ሁሉ ደግሞ በሪብላ ዐረዳቸው። **11** ከዚያም የሴዴቅያስን ዐይኖች አወጣ፣ የባቢሎንም ንጉሥ በሰንሰለት አሰረው። ወደ ባቢሎንም ወሰደው፣ እስኪሞትም ድረስ በግዞት ቤት አኖረው። **12** በባቢሎን ንጉሥ በናቡከደነፆር በዐሥራ ዘጠነኛው ዓመት በአምስተኛው ወር፣ ከወሩም በዐሥረኛው ቀን፣ በባቢሎን ንጉሥ ፊት የቆመው የዘበኞቹ አለቃ ናቡዘረዳን ወደ ኢየሩሳሌም መጣ። **13** የእግዚአብሔርን ቤትና የንጉሡን ቤት አቃጠለ፤ የኢየሩሳሌምንም ቤቶች ሁሉ፣ ታላላቆችን ቤቶች ሁሉ፣ በእሳት አቃጠለ። **14** ከዘበኞቹም አለቃ ጋር የነበረው የከለዳውያን ሠራዊት ሁሉ የኢየሩሳሌምን ቅጥር ሁሉ ዙሪያዋን አፈረሱ። **15** የዘበኞቹም አለቃ ናቡዘረዳን የሕዝቡን ድኆች፣ በከተማም ውስጥ የቀረውን ሕዝብ፣ ሸሽተውም ወደ ባቢሎን ንጉሥ የተጠጉትን፣ የሕዝቡንም ቅሬታ አፈለሰ። **16** ነገር ግን የዘበኞቹ አለቃ ናቡዘረዳን ከአገሩ ድኆች ወይን ተካዮችና አራሾች እንዲሆኑ አስቀረ። **17** ከለዳውያንም በእግዚአብሔር ቤት የነበሩትን የናስ ዓምዶች፣ በእግዚአብሔርም ቤት የነበሩትን መቀመጫዎችና የናሱን ኲሬ ሰባበሩ፣ ናሱንም ወደ ባቢሎን ወሰዱ። **18** ምንቸቶቹንና መጫሪያዎችንም፣ መኰስተሪያዎችንና ድስቶችን፣ ጭልፋዎችንም የሚያገለግሉበትንም የናስ ዕቃ ሁሉ ወሰዱ። **19** የዘበኞቹም አለቃ ጽዋዎቹንና ማንደጃዎቹን፣ ድስቶቹንና ምንቸቶችን፣ መቅረዞችንና ጭልፋዎቹን፣ መንቀሎችንም፣ የወርቁን ዕቃ በወርቅ፣ የብሩንም ዕቃ በብር፣ አድርጎ ወሰደ። **20** ንጉሡ ሰሎሞንም ለእግዚአብሔር ቤት ያሠራቸውን ሁለቱን ዓምዶች፣ አንዱንም ኲሬ፣ ከመቀመጫዎቹም በታች የነበሩትን ዐሥራ ሁለቱን የናስ በሬዎች ወሰደ፤ ለእነዚህ ዕቃዎች ሁሉ ናስ ሚዛን አልነበረም። **21** ዓምዶቹም የአንዱ ዓምድ ቁመት ዐሥራ ስምንት ክንድ ነበረ። የዙሪያውም መጠን ዐሥራ ሁለት ክንድ ነበረ። ውፍረቱም አራት ጣት ያህል ነበረ፣ ባዶም ነበረ። **22** የናሱም ጕልላት በላዩ ነበረ። የአንዱም ጕልላት ቁመት አምስት ክንድ ነበረ፣ በጕልላቱም ላይ በዙሪያው ሁሉ ከናስ የተሠሩ መረበብና ሮማኖች ነበሩበት። በሁለተኛውም ዓምድ ደግሞ እንደዚህ ያለ ነገርና ሮማኖች ነበሩበት። **23** በስተውጭም ዘጠና ስድስት ሮማኖች ነበሩ። በመረበቡም ዙሪያ የነበሩ ሮማኖች ሁሉ አንድ መቶ ነበሩ። **24** የዘበኞቹም አለቃ ታላቁን ካህን ሠርያን ሁለተኛውንም ካህን ሶፎንያስን ሦስቱንም በረኞች ወሰደ። **25** ከከተማይቱም በሰልፈኞች ላይ ተሹመው ከነበሩት አንዱን ጀንደረባ፣ በከተማይቱም ከሚገኙት በንጉሡ ፊት ከሚቆሙት ሰባቱን ሰዎች፣ የአገሩንም ሕዝብ የሚያሰልፈውን የሠራዊቱን አለቃ ጸሐፊ፣ በከተማይቱም ከተገኙት ከአገሩ ሕዝብ ስድሳ ሰዎች ወሰደ። **26** የዘበኞቹም አለቃ ናቡዘረዳን ወስዶ የባቢሎን ንጉሥ ወዳለበት ወደ ሪብላ አመጣቸው። **27** የባቢሎንም ንጉሥ ገደላቸው፣ በሐማትም ምድር ባለችው በሪብላ ገደላቸው። እንዲሁ ይሁዳ ከአገሩ ተማረከ። **28** ናቡከደነፆር የማረከው ሕዝብ ይህ ነው፤ በሰባተኛው ዓመት፣ 3, 023 አይሁድ፤ **29** ናቡከደነፆርም በአሥራ ስምንተኛው ዓመት 832 ሰዎችን ከኢየሩሳሌም ማርኮአል፤ **30** በናቡከደነፆር በሀያ ሦስተኛው ዓመት የዘበኞቹ አለቃ ናቡዘረዳን ከአይሁድ 745 የይሁዳ ሰዎችን ማርኳል። የተማረኩት ሰዎች ሁሉ 4, 600 ነበሩ። **31** እንዲህም ሆነ፤ የይሁዳ ንጉሥ ዮአኪን በተማረከ በሠላሳ ሰባተኛው ዓመት፣ በአሥራ ሁለተኛው ወር ከወሩም በሀያ አምስተኛው ቀን፣ የባቢሎን ንጉሥ ዮርማሮዴክ በነገሠ በአንደኛው ዓመት የይሁዳን ንጉሥ የዮአኪንን ራስ ከፍ ከፍ አደረገ ከወህኒም አወጣው። **32** በመልካምም ተናገረውና ዙፋኑን ከእርሱ ጋር በባቢሎን ከነበሩት ነገሥታት ዙፋን በላይ አደረገለት። **33** ክፉው ዮርማሮዴክ በወህኒ ውስጥ ዮአኪን ለብሶት የነበረውን ልብስ ለወጠለት፣ ዮአኪንም በሕይወቱ ዘመን ሁሉ በፊቴ ሁልጊዜ እንጀራ ይበላ ነበር። **34** የባቢሎንም ንጉሥ በሕይወቱ ዘመን ሁሉ እስኪሞት ድረስ የዘወትር ቀለብ ዕለት ዕለት ይሰጠው ነበር።

Jeremiah 52:1

አጠቃላይ ሐሳብ
በ ኤርሚያስ51:64 ላይ “የኤርምያስ ቃል እስከዚህ ድረስ ነው።” ብሎ ስለሚያልቅ እና በስር ያሉ ቃላቶች በሌሎች የመፅሀፍ ክፍሎች ስለሚገኙ ብዙ ምሁራን ይህ ምዕራፍ በኤርምያስ ብቻ እንዳልተፃፈ ይናገራሉ። ከዚህም ጋር በተያያዘ ኤርሚያስ እና ባሮክ እንደፃፉት ይታሰባል።

አሚጣል
ይህ የሴት ስም ነው።

ሊብና
ይህ የቦታ ስም ነው።

ኤርሚያስ
ኤርሚያስ የሚለው ስም ይህን መፅሀፍ የፃፈው ነብዩ ኤርሚያስን ሳይሆን ሌላ ኤርሚያስ የሚባል ሰውን ነው ሚያመለክተው

በእግዚአብሔር ፊት ክፉ አደረገ።
“የእግዚአብሄር ፊት” የሚያመለክተው የእግዚአብሄርን ፍርድ ወይም እይታ ነው።

Jeremiah 52:4

ሴዴቅያስም በነገሠ በዘጠነኛው ዓመት በአሥረኛው ወር ከወሩም በአሥረኛው ቀን
ሴዴቅያስም ከነገስ ከስምንት አመት በአስረኛው ወር እና ወሩ ከገባ በአስረኛው ቀን

በዘጠነኛው አመት
“ዘጠነኛው አመት”

በአሥረኛው ወር ከወሩም በአሥረኛው ቀን
በእብራውያን የቀን መቁጠሪያ አስረኛው ቀን ነው። አስረኛው ቀን በፈረንጆች ቀን አቆጣጠር ጃንዋሪ የሚባለው ወር ጋር ይጠጋል።

በኢየሩሳሌም ላይ መጥተው ከበቡአት
የናቡከደነፆር ሠራዊት ኢየሩሳሌምን ከበቡአት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እስከ ንጉሠ እስከ ሴዴቅያስ እስከ አሥራ አንደኛው ዓመት
ሴዴቅያስ ከነገሰ ጀምሮ ከ አስር አመት በላይ

አስራ አንደኛው አመት
አስራ አንደኛው አመት

ከተማይቱም ... ተከብባ ነበር።
ከተማይቱ በሰራዊቱ ተከብባ ነበር

Jeremiah 52:6

በአራተኛውም ወር በዘጠነኛው ቀን
በእብራውያን የቀን አቆጣጠር አራተኛው ወር ሲሆን ይህም በበጋ ወቅት ነው። ዘጠነኛው ቀንም እንደ አውሮፕያን አቆጣጠር ጁላይ ወር አካባቢ ይገኛል። ሴዴቅያስም ለ አስር አመት ሶስት ወር ስምንት ቀናት ነግሶ ነበር።

በከተማይቱ
ይህ ኢየሩሳሌም ከተማን ያመለክታል።

ከተማይቱ ተሰበረች
ባቢሎናዊያን የከተማዋን ግንብ አፈራርሰው ገቡ።

በሁለቱም ቅጥር
የንጉሱ የአትክልት ስፍራ ቅጥር እና የከተማዋ ቅጥር።

ሜዳ
ቀጥ ያለ መሬት

ሠራዊቱም ሁሉ ከእርሱ ዘንድ ተበትነው ነበር
የከለዳዊያን ሰራዊት በሙሉ ተበተኑ፣ ሙሉ ሰራዊቱ በተለያየ አቅጣጫ ተበተኑ።

Jeremiah 52:9

በሐማት ምድር ወዳለችው ወደ ሪብላ
ሪብላ በሃማት ክልል የምትገኝ ከተማ ነች

ፍርድን በእርሱ ላይ ተናገረ
እንዴት እንደሚቀጣ ወሰነ

የሴዴቅያስን ልጆች በፊቱ ገደላቸው
“በፊቱ ገደላቸው” ሲል አይኑ እያየ ለማለት ነው። አንባቢው ጨምሮ ሊረዳው ያለበት ነገር ሌሎችም የባቢሎን ንጉስ የሴዴቅያስን ልጆች ሲገድል እጃቸው ነበረ።

የሴዴቅያስንም ዓይኖች አወጣ
የንጉሱ ሰዎች ሴዴቅያስን አይነ-ስውር አረጉት። የባቢሎን ንጉስ የሴዴቅያስን አይን ከጭንቅላቱ ማውጣቱን የሚያስረዳ ግልፅ ነገር የለም። ሌላው አንባቢው ጨምሮ ሊረዳው ያለበት ነገር ሌሎችም የባቢሎን ንጉስ የሴዴቅያስን አይን ሲያጠፋ እጃቸው ነበረ።

እስኪሞትም ድረስ
ሴዴቅያስ እከሞተበት ቀን ድረስ

Jeremiah 52:12

በባቢሎን ንጉሥ በናቡከደነፆር በአሥራ ዘጠነኛው ዓመት በአምስተኛው ወር ከወሩም በአሥረኛው ቀን
ንጉስ ናቡከደነፆር ለአስራ ስምንት አመታት አራት ወር እና ለዘጠኝ ቀን ነግሶ ነበር። በእብራውያን ቀን አቆጣጠር አምስተኛው ወር ሲሆን ወቅቱም በጋ ነው። አስረኛው ቀን ደግሞ እንደ አውሮፕያውያን ቀን አቆጣጠር በነሱ ኦውገስት ተብሎ የሚጠራው ወር መጀመሪያ አካባቢ ይገኛል።

አስራ ዘጠነኛው አመት
በአስራ ዘጠነኛው አመት

ናቡከደነፆር
ይህ የሰው ስም ነው።

ዘበኞች
እነዚህ ስራቸው አንድን ነገር መጠበቅ ነው።

Jeremiah 52:15

የእጅ ጥበብ አዋቂዎች
እግዚአብሄርን ለማምለክ የሚጠቅሙ ውብ የሆኑ እቃዎችን የሚሰሩ ሰዎች ናቸው።

ናቡዘረዳን
ይህ የሰው ስም ነው

የምድርን ድሆች
“በምድር ላይ የሚኖሩ ድሆች”

Jeremiah 52:17

አንዱ ኩሬ
እግዚአብሄር የሚመለክበት የገንዳ ውሃ ነው።

Jeremiah 52:20

አሥራ ስምንት ክንድ - አሥራ ሁለት ክንድ
1 ክንድ 46 ሳንቲሜትር ርዝመት አለው። “18 ክንድ...12 ክንድ” ወይም “ወደ 8.3 ሜትር...5.5 ሜትር”

“ባዶ”
አምዶቹ ውስጣቸው ባዶ ነበሩ

Jeremiah 52:22

ጉልላት
የናሱ የላይኛው ክፍል

5 ክንድ
1 ክንድ 46 ሳንቲሜትር ርዝመት አለው።”5 ክንድ” ወይም “2.3 ሜትር”

Jeremiah 52:24

ሠራያን
የወንድ ስም ናቸው (ኤርምያስ 36፡26 ተመልከት)

በረኞች
የከተማዋን ዋና መግቢያ በር የሚጠብቁ

... ሰዎች ወሰደ
ሰዎችን ለውጊያ ወሰደ

Jeremiah 52:26

ናቡዘረዳን
የወንድ ስም ነው(ኤርምያስ 39፡9 ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሪብላ
ይህ የከተማ ስም ነው።

Jeremiah 52:28

በሰባተኛው - አስራስምንተኛ- ሃያ ሶስተኛ
ተራ ቁጥሮች ናቸው

ናቡዘረዳን
የወንድ ስም ነው(ኤርምያስ 39፡9 ተመልከት)

3,023 ... 832 ... 745 ... 4,600
“ሶስት ሺህ ሃያሶስት- ስምንት መቶ ሰላሳ ሁለት - ሰባት መቶ አርባ አምስት - አራት ሺህ ስድስት መቶ”

Jeremiah 52:31

ዮአኪን በተማረከ በሠላሳ ስድስት ዓመት
ዮአኪን ከተማረከ 36 አመታት ተቆጥረዋል

በአሥራ ሁለተኛው ወር ከወሩም በሀያ አምስተኛው ቀን
በእብራውያን ካላንደር አስራ ሁለተኛው ወር የመጨረሻው ወር ነው። ሃያምስተኛው ቀን በ ውጮቹ ማርች መሀከል ላይ ይገኛል።

እንዲህም ሆነ
ይህ ሃረግ የአንድ ታሪክ መጀመሪያን ያመለክታል

ዮርማሮዴክ
በባቢሎን ከንጉስ ናቡዘረዳን ቀጥሎ ነገሰ።

Jeremiah 52:32

በመልካምም ተናገረው
“ዮርማሮዴክ ዮአኪንን በመልካም ተናገረው”

ዙፋኑንም ከእርሱ ጋር በባቢሎን ከነበሩት ነገስታት ዙፋን በላይ አደረገለት
“ዙፋኑን ከንጉሱ ከዮርማሮዴክ ጋር አስጠጋው”

በወህኒም ውስጥ ለብሶት የነበረውን ልብስ ለወጠለት
አንባቢው ሊረዳው የሚገባው ነገር “በወህኒም ውስጥ ለብሶት የነበረውን ልብስ ለወጠለት”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Lamentations

Lamentations

Chapter 1

[1] በሰዎች ተሞልታ የነበረችው ከተማ አሁን ፈጽማ ብቻዋን ተቀምጣለች! ኃያል የነበረችው አገር እንደ መበለት ሆናለች! በሕዝቦች መካከል እንደ ልዕልት ነበረች፥ አሁን ግን በባርነት ውስጥ ወድቃለች! [2] በሌሊት ታለቅሳለች፥ታነባለችም፤እንባዎቿም ጉንጮቿን ከድነዋል። ከፍቅረኞቿ መካከል የሚያጽናናት የለም። ጓድኞቿ ሁሉ አሳልፈው ሰጧት። ጠላቶቿም ሆነዋል። [3] ከድህነቱና ከመከራዉ የተነሳ ይሁዳ ወደ ምርኮ ሄደች። በሕዝቦች መካከል ኖረች፥ ዕረፍትንም አላገኘችም። በጭንቀቷ ጊዜ አሳዳጆቿ ሁሉ በረቱባት። [4] ወደ ተቀጠሩት በዓላት የሚመጣ የለምና የጽዮን መንገዶች ያለቅሳሉ። ደጆቿ ሁሉ ባዶ ናችው። ካህናቶቿ ይቃትታሉ። ደናግሎቿ ሐዘንተኞች ናቸዉ፥እራስዋም በፍጹም ጭንቀት ውስጥ አለች። [5] ባላንጣዎቿ ጌቶቿ ሆኑ፥ጠላቶቿ በለጸጉ። ስለ ብዙ ኃጢአቷ እግዚአብሔር መከራን አመጣባት። ልጆቿ ለጠላቷ ተማርከው ወደ ግዞት ሄዱ። [6] የጽዮን ሴት ልጅ ውበቷ ተለያት። ልዑላኖቿ መሰማሪያ እንዳላገኙ አጋዘኖች ሆኑ፥ በአሳዳጆቻቸው ፊት በድካም ሄዱ። [7] በመከራዋና ቤት አልባ በሆነችባቸው ቀናት፥ ኢየሩሳሌም በቀደሙት ቀናት የነበሯትን የከበሩ ነገሮች ታስባለች፤ሕዝቦቿ በጠላት እጅ በወደቁ ጊዜ ማንም የረዳት አልነበረም። ጠላቶቿ ተመለከቷት፥ በጥፋቷም ሳቁ። [8] ኢየሩሳሌም ታላቅ ኃጢአት ሠርታለች፥ ስለዚህ እንደ አደፈ ነገር ተንቃለች። ዕርቃናዋን ከተመለከቱበት ጊዜ አንስቶ ያከበሯት ሁሉ ናቋት። ታጉተመትማለች፥ ዘወር ለማለትም ትሞክራለች። [9] ከቀሚሷ በታች አድፋለች። የወደፊቷን አላሰበችም። አወዳደቋ አስፈሪ ነበር። የሚያጽናት ማንም አልነበረም። «እግዚአብሔር ሆይ፥ መከራዬን ተመልከት፥ ጠላት እጅግ ታላቅ ሆኖአልና» እያለች ትጮኻለች!። [10] ጠላት በከበረ ነገሯ ሁሉ ላይ እጁን አደረገ። ወደ ጉባዔህ እንዳይገቡ አዝዘህ የነበረ ቢሆንም እንኳን፥ ሕዝቦች ወደ መቅደሷ ሲገቡ አየች። [11] ሕዝቦቿ ሁሉ ምግብ እየፈለጉ ይጮኻሉ። ሕይወታቸውን ለማቆየት የከበረ ኃብታቸውን ስለ ምግብ ይሰጣሉ። የማልጠቀም ሆኜለሁና፥ እግዚአብሔር ሆይ ተመልከት አስበኝም። [12] እናንተ መንገደኞች ሁሉ ይህ ለእናንተ ምንም አይደለምን? እግዚአብሔር እኔን መቅጣት ከጀመረበት ከጽኑ ቁጣው ቀን አንስቶ፥ የደረሰብኝን ሐዘን የሚመስል የማንም የሌላ ሰው ሐዘን ካለ ተመልከቱ፥ እዩም። [13] ወደ ዉስጥ ወደ አጥንቶቼ ከላይ እሳት ላከ፥ አሸነፋቸዉም። ለእግሮቼ መረብን ዘረጋ ወደ ኋላም መለሰኝ። ያለማቋረጥ ባዶና ደካማ አደረገኝ። [14] የመተላለፌ ቀንበር በእጆቹ በአንድ ላይ ታስረዋል። በአንድ ላይ ተገምደዋል፥በአንገቴም ላይ ተደርገዋል። ብርታቴን ከንቱ አደረገው። ጌታ በእጃቸው አሳልፎ ሰጠኝ፥ መቆምም አልችልም። [15] ጌታ፥የሚመክቱልኝን ኃያላን ወንዶች ሁሉ ወዲያ ጣላቸው። ጽኑዓን ወንዶቼን ለማድቀቅ ጉባዔን በላዬ ጠራብኝ። ጌታ ድንግሊቱን የይሁዳ ልጅ በወይን መጥመቂያ እንዳለ ወይን ረገጣት። [16] ስለ እነዚህ ነገሮች አለቅሳልሁ። ሕይወቴን የሚያድሳት አጽናኙ ከእኔ ርቋልና ከዓይኖቼ ውኃ ይፈሳል፥ ከዓይኖቼ። [17] ጽዮን እጆቿን እጅግ ዘረጋች፥ የሚያጽናናት ማንም የለም። እግዚአብሔር በያዕቆብ ዙሪያ ያሉ ጠላቶቹ እንዲሆኑ አዘዘ። ኢየሩሳሌም በእነርሱ ዘንድ እንደ ርኩስ ነገር ተቆጠረች። [18] በትዕዛዙ ላይ ዐመጽ አድርጌአለሁና እግዚአብሔር ጻድቅ ነው። እናንተ ሕዝቦች ሁሉ ስሙ፥ ሐዘኔንም ተመልከቱ። ደናግሎቼና ኃያላን ወንዶቼ ተማርከዉ ሄደዋል። [19] ፍቅረኞቼን ጠራኋቸው፥ ነገር ግን ከዳተኞች ሆኑብኝ። ካህናቶቼና ሽማግሌዎቼ ሕይወታችውን ለማኖር ምግብ እየፈለጉ በከተማ ውስጥ ሞቱ። [20] እግዚአብሔር ሆይ ተጨንቄአለሁና ውስጤም ተንጦአልና ተመልከት። እጅግ ዓመጽ አድርጌአለሁና ልቤ በውስጤ ታውኮአል። በመንገዶች ላይ ሰይፍ ልጆቻችንን ይነጥቃል፥በቤትም እንደ ሙታን መንደር ነው። [21] ሲቃዬን ስማ። የሚያጽናናኝ ማንም የለም። ጠላቶቼ ሁሉ ስለ መከራዬ ሰምተዋል። አንተ ስለ አደረግከው ደስ አላቸው። እነርሱም እንደ እኔ ይሆኑ ዘንድ ያወጅክባቸውን ቀን አምጣ። [22] ክፋታቸው ሁሉ በፊትህ ይታይ። መቃተቴ ብዙ ነውና፥ ልቤም ደክሞአልና፤ስለ መተላለፌ ሁሉ እንዳሰቃየኸኝ አሰቃያቸው።

Lamentations 1:1

ብቻዋን . . . ተቀመጠች
ይሄ የሚያመላክተው የእየሩሳሌም ከተማ ባዶዋን መቅረቷን ነው፤ በቻዋን ከተቀመጠች ሴት ጋር ንጽጽርን ያደርጋል። “የተተወች ሆና ቀረች”

ተቀመጠች
“ቀረች” የሰቆቃወ ጸሓፊ የእየሩሳሌምን ከተማ በሴት ይመስላታል።

እንደ መበለት
ይህ እየሩሳሌም ያለ ከለላ እንደቀረች አድርጎ ይናገራል፤ ስጋት ውስጥ ያለች እና የተጋለጠች መበለት።

በአውራጆች መካከል ልዕልት የነበረች
እየሩሳሌም እንደ ልዕልት የተከበረች እንደነበረች ይናገራል። “በሕዝቦች መሃከል እንደ ልእልት ነበረች።”

ተገዢ ሆናለች
“ባሪያ ሆናለች” በሌላ መልኩም ሊገለፅ ይችላል። “ባሪያ ለመሆን ተገዳለች።”

እጅግ ታላቅሳለች፥ እንባዋም በጉንጭዋ ላይ አለ
ጸሃፊው እየሩሳሌምን ስሜት እንዳለው ሰው አደርጎ ይገልፃታል። ከተማዋ ሲባል ግን በውስጧ የሚኖሩ ሰዎችንም ይወክላል። “በእርሷ የሚኖሩ እጅግ ያለቅሳሉ፥ እምባቸውም በጉንጫቸው ላይ አለ።”

የሰቆቃ ድምፅ ታሰማለች ታለቅሳለች
የሰቆቃ ድምፅ ማሰማት ማለት አንድ ሰው ጮክ ብሎ ሲያለቅስ የሚያሰማው ደምፅ ነው። “ጮክ ብላ ታለቅሳለች።”

ከውሽሞችዋ ሁሉ የሚያጽናናት የለም፤ ወዳጆችዋ ሁሉ ወነጀሉአት ጠላቶችም ሆኑአት
ይህ የሚናገረው ለእየሩሳሌም ታማኝ የነበሩ አሁን ግን የከዷት የሰዎች ስብስብ እንዳለ ነው፤ እነኚህ ሰዎችም በአፍቃሪዎች እና ጓደኞች ተመስለዋል።

Lamentations 1:3

መጨነቅና ስለ ባርነት ብዛት
“በመከራና በመረገጥ ብዛት”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይሁዳ ተሰዷል
እዚህ ጋር ይሁዳ የሚለው የሚናገረው ስለ ነዋሪዎችዋ ነው። “የይሁዳ ሰዎች ወደ ስደት ሄደዋል።” ወይንም “ የይሁዳ ሰዎች ወደ ባዕድ ሃገር ተወስደዋል።”

ትኖራለች. . .ተቀመጠች
እዚህ ጋር ይሁዳ በሴት ትመሰላለች። “እርሷ” የሚለው የይሁዳ ነዋሪዎችንም ያመላክታል። “ህዝቦቿ ይኖራሉ. . . ይቀመጣሉ።“

የምታርፍበት ቦታ አጣች
”አላረፈችም“ ወይንም ”ሁልግዜ በፍርሃት ውስጥ ነች።“

በጭንቀቷ መካከል ሳለች አሳዳጆቿ ሁሉ አገኟት።
ይህ የሚናገረው የይሁዳ ሰዎች አንዲት ሴት በሚያሳደዷት እና በሚፈልጓት ሰዎች እንደምትያዝ ተያዙ የሚለውን ነው።

አሳዳጆቿ ሁሉ አገኟት።
“ያሳድዷት የነበሩ ሁሉ ሊይዟት ቻሉ።” ወይንም “ያድናት የነበሩ ሁሉ አገኟት።”

በጭንቀቷ መካከል
“ጭንቅ” የሚለው ቃል በሌላ መልኩ ሲገለጥ፤ “የሚያስጨንቁአት ሁሉ ተጨንቃ አገኙአት”

Lamentations 1:4

የጽዮን መንገዶች ያለቅሳሉ
ወደ ጽዮን የሚወስዱ መንገዶች ሰው እንደሚያለቅስ ያለቅሳሉ ይላል።

በዓላቷን ለማክበር
“እግዚአብሔር እንዲያከብሩ የነገራቸው በዓላት።”

በበሮቿ የሚገባና የሚወጣ የለም
“እርሷ” የሚለው ጽዮንን ያመላክታል። “የጽዮን ደጆች ባዶ ናቸው።”

ደላግሏ ክፉኛ አዘነዋል፤ እርሷም በምሬት ትሰቃያለች።
የጽዮን ሕዝቦች ስቃይ እንደ ሴት ልጅ ስቃይ ተገልጿል። “ደናግሎችዋም ተጨነቁ እርስዋም በምሬት አለች”

ባላጋሮቿ ገዦቿ ሆኑ፤ ጠላቶቿ ተመችቶአቸዋል።
“አስጨናቂዎችዋ ራስ ሆኑ ጠላቶችዋም ተከናወነላቸው፤”

ከኀጢአቷ ብዛት የተነሣ፤ እግዚአብሔር ከባድ ሐዘን አምጥቶባታል።
ይህ የሚናገረው እግዚአብሔር ስለ ጽዮን ሕዝቦች በደል ሲል ሴት ልጅን እደሚቀጣ ጽዮንን እደቀጣ ነው። “ስለ ኃጢአትዋ ብዛት እግዚአብሔር አስጨንቆአታል”

ልጆችዋ በጠላት ፊት ተማርከው፤ ወደ ግዛት ሄደዋል።
“ተማርከው” የሚለው ቃል በግስ መልኩም ሊገለጽ ይችላል። “ሕፃናቶችዋ በአስጨናቂዎች ፊት ተማርከዋል”

Lamentations 1:6

የጽዮን ሴት ልጅ: ግርማ ሞገሷ ሁሉ ተለይቶአታል።
ይህ የአንድ ሰውን ውበት በሚመስል መልኩ በጽዮን የነበረው ውብ ነገር ሁሉ እንደ ጠፋ ይናገራል። “ከጽዮን ሴት ልጅ ውበትዋ ሁሉ ወጥቶአል”

የጽዮን ሴት ልጅ
ይህ በዘይቤአዊ አገላለፅ የእየሩሳሌምን ስም እንደ ሴት ሲመሰል ነው።

መሳፍንቶቿ መሰማርያ እንዳጣ ዋልያ ናቸው።
ይህ የጽዮንን መሳፍንቶች የሚበላውን ሳር እንዳጣ ዋልያ የገልፃቸዋል። “አለቆችዋ ማሰማርያ እንደማያገኙ ዋላዎች ሆኑ”

ዋልያ
ዋልያ መካከለኛ መጠን ያለው፤ ሳር በል፤ በሰዎች ለምግብነት የሚታደን እንስሳ ሲሆን፤ ለማየትም የሚማርክ እንስሳ ነው።

በድካም ሸሹ
“ተዳክመው ሄዱ” ወይንም “ለመሮጥ እንኳን የበረቱ አይደሉም።

አሳዳጆቻቸው
“ከሚያባርሩአቸው ፊት”

Lamentations 1:7

በተጨነቀችባቸውና በተንከራተተችባቸው ቀናት
“በጭንቀትዋና በመከራዋ ወራት”

ኢየሩሳሌም . . . ታስባለች፤
እዚህ ግር “እስራኤል” የሚለው በውስጧ የሚኖሩትን ሕዝቦች ነው። “ታስባለች” የሚለው ገላጭ ነው። “ኢየሩሳሌም . . . አሰበች”

የከበረን ነገር ሁሉ
ዋጋ ያላቸውን “ሀብት” ያመላክታል። በጭንቀትዋና በመከራዋ ወራት የነበረላትን

ከጥንት ጀምሮ
“በጥንት ዘመን” ይህ የሚያመላክተው እስራኤላውያን ከመማረካቸው በፊት ያለውን ነው። “ይህ መከራ ከመድረሱ በፊት”

ሕዝብዋ በአስጨናቂዎች እጅ በወደቀ ጊዜ የሚረዳትም በሌላት ጊዜ
”እጅ“ የሚለው ቃል የጠላቶችዋን መያዝ ያሳያል። “ሕዝቦቿ በጠላት እጅ በወደቁ ጊዜ፣ የረዳት ማንም አልነበረም”

አስጨናቂዎች አዩአት በመፍረስዋም ሳቁ
ይህ የሚያመላክተው በእየሩሳሌም መፍረስ መሳለቃቸው እና መደሰታቸውን ነው።

በመፍረስዋም
”መፍረስ“ የሚለውን ቃል እንደ ግስ ልንጠቀመው እንችላለን።
“በመፈራረሷ“ ወይንም “በሚያፈራርሷት ወቅት”

Lamentations 1:8

ኢየሩሳሌም እጅግ ኃጢአት ሠርታለች፤ ስለዚህ ረክሳለች።
ይህ ስለእየሩሳሌም እድፈት ሲናገር ከሴት ልጅ የወር አበባዋን የምታይበትን ወቅት አንፃር ይናገረዋል። በሙሴ ሕግ መሰረት፤ የኢየሩሳሌም እድፈት ከሴት ልጅ የወር አበባ እድፈት ትይዩ ይታያል። “ኢየሩሳሌም ከባድ ኀጢአት ሠርታለች፤ ስለዚህም የረከሰች ሆናለች”

ኢየሩሳሌም እጅግ ኃጢአት ሠርታለች፤
ይህ ክፍል እየሩሳሌምን በሴት ይመስላል፤ ክፍሉም እስራኤላውያንን ይወክላል። “የኢየሩሳሌም ሠዎች ከባድ ኀጢአት ሠርተዋል”

ረክሳለች
“እየረከሰች ነው” ተበሎም ሊገለፅ ይችላል።

ኀፍረተ ሥጋዋ
“ዕራቍቷ” በዚህ ክፍል እየሩሳሌምን ኀፍረተ ሥጋዋ በተጋለጠባት እና በተዋረደች ሴት ይመስላታል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አደፍዋ በልብስዋ ዘርፍ ነበረ
በሙሴ ሕግ መሰረት፤ ሴት ልጅ የወር አበባዋን የምታይበትን ወቅት እንደ እድፈት ይታያል። ይህንንም የኢየሩሳሌም እድፈት ከሴት ልጅ የወር አበባ አንፃር ይናገረዋል። “ርኩሰቷ በቀሚሷ ላይ ታየ“

አደፍዋ
እግዚአብሔር በመንፈሳዊ መልኩ ተቀባይነት የሌለው ወይንም የተበላሸ ሰውን፤ በአካሉ እንደ ቆሸሸ የገልፀዋል።

አወዳደቋ አስደንጋጭ ሆነ
”አወዳደቋ“ የሚለው ቃል ዘይቤአዊ ቃል ነው

አቤቱ . . . መከራዬን ተመልከት
ሊሆን የሚችሉት ትርጓሜዎች፤ 1 እዚህ ጋር የሰቆቃወ ጸሓፊ በቀጥታ እግዚአብሔርን ያናግራል። ወይንም 2 ኢየሩሳሌም ሰው እግዚአብሔርን እንደሚያናግር ስታወራ ተገልፃለች።

ተመልከት
“ልብ በል”

ጠላት ከፍ ከፍ ብሎአል
ይህ የሚያመላክተው የጠላት ሠራዊት በጣም እንደበዛ እና እንዳየለ፤ ኢየሩሳሌምንም እንዳሸነፈ ነው። “ጠላት ድል አድርጎአልና”

Lamentations 1:10

እጁን ዘረጋ
ይህ ዘይቤአዊ አባባል ሲሆን፤ “ወሰደ” ወይንም “ሠረቀ”

በከበረ ነገርዋ
ይህ የሚያመላክተው የከበረ ሃብቷን ነው።

አይታለች
“እርሷ” የሚለው እየሩሳሌምን ነው።

አሕዛብ
ይህ የተለያዩ ሌላ ህዝቦችን ያመላክታል፤ እንጂ በዛ የሚኖሩትን ሕዝቦች በሙሉ ማለቱ አይደለም።

ያዘዝሃቸው
አንተ የሚለው ቅላፄ ለእግዚአብሔር የተጠቀሰ ነው።

Lamentations 1:11

እንጀራ
ይህ በአጠቃላዩ ስለ ምግብ ይናገራል። “ምግብ”

የከበረ ሀብታቸውን ስለ መብል ሰጥተዋል
ይህ የሚያሳየው ሀብታቸውንና ንብረታቸውን ለምግብ ለውጠዋል። “የከበረ ሀብታቸውን በምግብ ይለውጣሉ”

የከበረ ሀብት
ዋጋ ያለውን ንብረት ያመላክታል።

ሰውነታቸውን ለማበርታት
”በሕይወት ለመኖር“ ወይንም “ጉልበታቸውን ለመመለስ”

አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ፤ አስበኝ፤ ተመልከተኝም
እዚህ ጋር እስራኤል በቀጥታ እግዚአብሔርን ታናግራለች።

እናንት መንገድ ዐላፊዎች ሁሉ፤ ይህ ለእናንተ ምንም አይደለምን?
ይህ በእየሩሳሌም ጎን ለሚያልፉ እና ለማይገዳቸው ሰዎች እንደ ክስ የሚቀርብ አባባል እንጂ መልስ የሚጠበቅለት ጥያቄ አይደለም “እናንተ መንገድ አላፊዎች ሁሉ፥ በእናንተ ዘንድ ምንም የለምን?”

ለእናንተ ምንም አይደለምን
አሁንም ኢየሩሳሌም ትናገራልች፤ የማትናገረው ግን ለእግዚአብሔር ሳይሆን በጎን ለሚያልፉ ሰዎች ነው።

ተመልከቱ፥ እዩ
እነኚህ ቃላት በትርጉም ተመሳሳይ ሲሆኑ፤ በአንድ ላይ አንባቢውን አይቶ ማንም ብዙ እንዳልተጎዳ እንዲረዳ ይጋብዛል።

በእኔ ላይ እንደ ተደረገው እንደ እኔ መከራ
አሁን እየሆነ እያለ ተደርጎም ሊገለፅ ይችላል፤ “እግዚአብሔር በእኔ ላይ እያመጣ ያለው መከራ።”

በጽኑ ቍጣው ቀን
እዚህ ጋር “ቀን” የሚለው ዘይቤአዊ ገላጭ ነው።

Lamentations 1:13

ከከፍታ
ይሄ ዘይቤአዊ አገላለፅ ነው። “ሠማይ”

እሳትን ወደ አጥንቴ ሰደደ በረታችበትም
ይህ እግዚአብሔር እስራኤልን ሰውን በእሳት እንደሚቀጣ እየቀጣ እንደሆነ ያመላክታል። “ህመም ያለበትን ቅጣት ወደ ውስጥ ሰውነቴ ልኳል፤ እርሱም አጥፍቶኛል“ ወይንም “እርሱ የጥፍት ቅጣትን ወደ መሃል እስራኤል ልኳል፤ ከተማዋንም አፈራርሷታል”

እሳትን ወደ አጥንቴ ሰደደ
እዚህ ጋር “እሳት” ህመምን ይወክላል “አጥንትም” የውስጥ ሰውነትን። “ወደ አጥንቴ ህመምን ልኳል” ወይንም “ወደ ውስጥ ሰውነቴ ህመምን ልኳል”

ለእግሬ ወጥመድ ዘረጋ
ይሄ የሚያመላክተው የእግዚአበሔር እስራኤልን እንደሰው ውጠመድን በማዘጋጀት መቅጣት ነው። ብዚውን ግዜ እንስሳት ለማጥመድ የሚጠቀሙበትን ዓይነት ወጥመድ።

ወደ ኋላም መለሰኝ
ይሄ ዘይቤአዊ አገላለፅ ነው። “አልፎ ከመራመድ ከለከለኝ”

የኃጢአቶቼ ቀንበር በእጁ ተይዛለች፤ ታስረው በአንገቴ ላይ ወጥተዋል
x

Lamentations 1:15

ኃያላኖቼ
“እጅግ ጠንካራዎቹ ወታደሮች”

ጉባኤን
እስራኤልን ሊወጋ የመጣው ሰራዊት የተገለጸው አንድን ሰው ሊከሱ እና ሊኮንኑ በአንድ ላይ እንደተሰበሰቡ ሰዎች ነው። “ታላቅ ሰራዊት”

ጕልማሶቼን ያደቅቅ ዘንድ
ይህ የሚናገረው የጠላት ሰራዊት የእስራኤልን ሰራዊት የማድቀቅ ያህል እንደረታ ነው። “ጕልማሶቼን ይረታ ዘንድ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጕልማሶቼን
በጉብዝና ወቅታቸው ላይ ያሉ ወንዶች።

ጌታ . . . በመጥመቂያ እንደሚረገጥ አድርጎ ረገጣት
የእግዚአብሔር ቅጣት የተመሰለው፤ በመጠመቅያ ውስጥ የወይንን ጭምቂ ለማውጣት ውይንን በሚረግጥ ሰው ነው። “እግዚአብሔር በወይን መጭመቂያ ውስጥ ረገጣት”

ድንግሊቱን የይሁዳን ልጅ
ይህ ቅኔአዊ የእየሩሳሌም ስም አገላለፅ ሲሆን፣እዚህ ጋር በሴት ይመስላታል።

Lamentations 1:16

ሊያጽናናኝ የቀረበ፣ መንፈሴንም ሊያረጋጋ የሞከረ ማንም የለም
እየሩሳሌም ተሚያጽናናት እንደሌለ እና ቢኖርም ይረዳት ዘንድ በአካባቢው እንደሌለ “ነፍሴንም የሚያበረታት፤ መንፈሴን የሚያረጋጋ”

መንፈሴንም ሊያረጋጋ
“ነፍሴንም የሚያበረታት”

ጽዮን እጆቿን ዘረጋች
ጸሓፊው እየሩሳሌምን በሦስተኛ ወገን በሴት የመስላታል። “እየሩሳሌም እጆችዋን እርዳታ ፍለጋ ዘርግታለች።

በያዕቆብ ዙሪያ ያሉትን
“በያዕቆብ ዙሪያ ያሉት ሰዎች” ወይንም “በያዕቆብ ዙሪያ ያሉ አሕዛብ”

በያዕቆብ ዙሪያ ያሉትን እንዲያስጨንቁት አዘዘ
እዚህ ጋር ያዕቆብ የሚለው የሚያመላክተው ከእርሱን ትውልድ ነው። “በያዕቆብ ዘር ዙሪያ ያሉት ጠላቶቻቸው ሳይሆኑ አይቀርም”

ርኩስ
በመንፈሳዊ መልኩ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ወይንም ሰወነቱ እንደ ቆሸሸበት ሰው የቆሸሸ።

Lamentations 1:18

እግዚአብሔር ጻድቅ ነው
ይህ የሚያመላክተው እግዚአበሔር የደረገውን ነገር ሲሆን፤ ያደረገውንም የደረገው ፃድቅ ስለሆነ ነው። “እግዚአበሔር የደረገውን ከፅድቁ ተተነሳ አደረገ” ወይንም ”እግዚአበሔር ያደረገው ትክክል ነው።“

መከራዬንም ተመልከቱ
“መከራዬ” የሚለው ቃል “ሃዘን” መሚለው ሊገለፅ ይችላል። “ምን ያህል እንዳዘንኩኝ ተመልከት”

ደናግሎቼና ጐበዛዝቴ ተማርከው ሄዱ
እዚህ ጋር ከእየሩሳሌም በምርኮ የተወሰዱት ሁሉ የተወከሉት “ደናግሎቼ” እና “ጐበዛዝቴ” በሚለው ነው። “አብዛኞቹ ሕዝቦቼ፤ ደናግሎቼ እና ጐበዛዝቴን ጨምሮ በምርኮ ተወሰዱ።”

ጐበዛዝቴ
ይህ የሚያመላክተው በዘመናቸው ጉብዝና ዘመናት ያሉትን ወንዶችን ነው።

ወዳጆቼን ጠራኋቸው
“ወዳጆቼን እንዲረዱኝ ተጣራሁ” ወይንም “ውሸሞቼን ለዕርዳታ ተጣራሁ”

እነርሱም አታለሉኝ
ይህ የሚያመላክተው መክዳታቸውን ነው። “እነርሱ ግን ከዱኝ”

ሰውነታቸውን ያበረቱ ዘንድ
“ሕይወታቸውን ለማትረፍ” ወይንም “ጉልበታቸውን ለመመለስ”

Lamentations 1:20

አቤቱ፥ ተጨንቄአለሁና፥ ተመልከት
እየሩሳሌም ስለራሷ እንደሴት ሆና መናገሯን ቀጥላለች። እዚህ ጋር ድግሞ እግዚአብሔርን በቀጥታ ታዋራዋለች።

አንጀቴም ታውኮብኛልና
“መታወክ” የሚለው ቃል የሚያመላክተው የሚረብሽ እንቅስቃሴን ሲሆን። ይህም በቀጥታ የአንጀትን መንቀሳቀስ ለማመላከት ሳይሆን በሴት የተመሰለችው እየሩሳሌም እየተሰማት ያለውን ስሜት ለማሳየት ነው። “ውስጤን ይቆርጠኛል” ውይንም “ሆዴን ያመኛል”

ልቤ በውስጤ ተገላበጠብኝ
በእየሩሳሌም የተመሰለችው ሰው፤ ስሜቷን ለመግለፅ ወደ “ልቧ” ታመላክታላች። “ልቤ ተሰብሯል” ወይንም “እጅጉን አዝኛለሁ”

በውጭ ሰይፍ ይፈጃል
“ሰይፍ” የሚለው የሚያመላክተው ጠላትን ነው። ”ሰይፍ ልጆቼን አጠፋ”

በቤትም ሞት አለ
ሊሆን የሚችሉት ትርጉሞች 1 “በቤት ውስጥ ያሉ ሰዎች ሁሉ እየሞቱ ነው” ውይንም 2 “የሞቱት ሰዎች በቤት ውስጥ ተደርገዋል”

Lamentations 1:21

እኔ እየጮኽሁ እንደማለቅስ ሰምተዋል
“ሰዎች የሥቃይ ልቅሶዬን ሰሙ” እየሩሳሌም በሴት ተመስላ መናገርዋን ቀጥላለች።

አንተ አድርገኸዋል
“አንተ” የሚለው የሚያመላክተው እግዚአብሔርን ነው።

የተናገርኸውን ቀን ታመጣለህ
“ቀን” የሚለው ዘይቤአዊ ገላጭ ሲሆን፤ የሆነ ክስተትን ያመላክታል። “ቃል እንደ ገባኸው አድርገሃል።”

እነርሱም እንደ እኔ ይሆናሉ
እስራኤል መከራን እንደተቀበለች የእስራኤል ጠላቶችም መከርን እንዲቀበሉ የቀረበ ጥያቄ ነው። “እነርሱም እንደ እኔ ይሁኑ”

ክፋታቸው ሁሉ ወደ ፊትህ ይድረስ
ይህ እግዚአብሔር የእስራኤል ጠላቶች ላይ ስለ ክፋታቸው እንዲፈርድ የቀረበ ጥያቄ ነው። “ወደ ፊትህ ይድረስ” የሚለው ዘይቤአዊ አገላለፅ ነው። “ያደረጉትን ክፋት ሁሉ ልብ በል” ወይንም “ስለክፋታቸው ሁሉ ፍረድባቸው።”

ስለ ኃጢአቴ ሁሉ እንዳደረግህብኝ አድርግባቸው
ይህ እግዚአብሔር የእስራኤል ሕዝቦችን እንደቀጣ ጠላቶቻቸውን እንዲቀጣ የቀረበ ጥያቄ ነው። ”በእኔ ላይ እንዳደረግኽብኝ፣በእነርሱም ላይ አድርግባቸው“

ልቤም ደክሞአል
እዚህ ጋር “ልብ” የሚለው ሙሉ ሰውን ያመላክታል። “ደክምያለሁ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 ጌታ በቁጣው ጥቁር ደመና የጽዮንን ሴት ልጅ ፈጽሞ ከደናት! የእስራኤልን ውበት ከሰማይ ወደ ምድር ጣለ፥ በቁጣው ቀን የእግሩን መር ግጫ ችላ አለ። 2 ጌታ የያዕቆብን ከተማዎች ሁሉ ዋጠ፥ ርኅራኄም አልነበረውም። በቁጣው የጽዮንን ሴት ልጅ የተመሸጉ ከተማዎች ጣለ፤ መንግሥቱ ንና ልዑላኗን አቃለለ፥አዋርዶ ወደ ምድር መትቶ ጣላችው። 3 በብርቱ ቁጣው የእስራኤልን ብርታት ሁሉ ቆረጠ፥ ከጠላት ፊት ቀኝ እጁን ወደ ኋላ መለሰ፥ በዙሪያው ያለውን ሁሉ እንደሚበላ የሚንጦገቦግ እሳት ያዕቆብን አቃጠለ። 4 እንደ ጠላት ቀስቱን በእኛ ላይ ገተረ፥ እንደ ባላጋራ ወርውሮ ሊገድል እጆቹ ተዘጋጅተው በተጠንቀቅ ቆመ። ለዓይን እጅግ የከበሩትን ሰዎች ሁሉ አረደ፥ በጽዮን ሴት ልጅ ድንኳን ውስጥ ቁጣውን እንደ እሳት አፈሰሰ። 5 ጌታ እንደ ጠላት ሆነ። እስራኤልን ዋጠ። ቤተ መንግሥቶቿን ሁሉ ዋጠ፤ምሽጎቿን አጠፋ። በይሁዳ ሴት ልጅ ውስጥ ለቅሶንና ሰቆቃን አበዛ። 6 ድንኳኑን እንደ አትክልት ቦታ አጠፋ። የታላቁን ጉባዔ ስፍራ አፈረሰ። በቁጣው ትኩሳት ንጉሡንና ካህኑን ንቋልና እግዚአብሔር በጽዮን ታላቁን ጉባዔና ሰንበትን እንዲረሱ አደረገ። 7 ጌታ መሠዊያውን ጣለ፥ መቅደሱን አልተቀበለም። የቤተ መንግሥቶቿን ግንቦች በጠላት እጅ አሳልፎ ሰጠ። በታላቅ ጉባዔ ቀን እንደሚሆን በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የድል ድምጽ አሰሙ። 8 እግዚአብሔር የጽዮንን ሴት ልጅ የከተማ ቅጥር ለማፍረስ ወሰነ። የመለኪያውን ገመድ ዘረጋ፥ቅጥሩን ከማፍረስ እጁን አልመለሰም። ምሽጎቿ እንዲያለቅሱ፥ቅጥሮቿ አቅመ አልባ እንዲሆኑ አደረገ። 9 በሮቿ ወደ መሬት ሰመጡ፥ የበሮቿን መቀርቀሪያዎች አጠፋ፥ ሰበረም።ንጉሧና ልዑላኖቿ የሙሴ ሕግ በሌለበት በአሕዛብ መካከል ናቸው። ነቢያቶቿም እንኳን ሳይቀሩ ከእግዚአብሔር ዘንድ ራዕይ አላገኙም። 10 የጽዮን ሴት ልጅ ሽማግሌዎች መሬት ላይ ተቀምጥዋል፥ በዝምታም ይቆዝማሉ። በራሳቸው ላይ አቧራ ነሰነሱ፥ የሐዘንም ልብስ ለበሱ። የኢየሩሳሌም ደናግል ራሳቸውን ወደ መሬት ዝቅ አደረጉ። 11 እንባዬ ደረቀ፥ዓይኖቼ ቀሉ፥ የውስጥ ሰዉነቴ ታወከ። ልጆችና የሚያጠቡ ሕጻናት በመንደሮች መንገዶች ላይ ያለ ምንም ተስፋ ደክመዋልና፥ የሕዝቤም ሴት ልጆች ደቅቀዋልና ጉበቴ በመሬት ላይ ተዘረገፈ። 12 በከተማይቱ መንገዶች ላይ እንደ ቆሰለ ሰው ዝለው ሳሉ፥ በእናቶቻቸው እቅፍ ነፍሳቸው እየፈሰሰች ሳሉ፥ እናቶቻቸውን፦ «እሕሉና ወይኑ የት አለ?» ይላሉ። 13 የኢየሩሳሌም ሴት ልጅ ሆይ፥ ስለ አንቺ ምን ማለት እችላለሁ? የጽዮን ድንግል ሆይ አጽናናሽ ዘንድ ከምን ጋር አመሳስልሻለሁ? ውድቀትሽ እንደ ባሕር ታላቅ ነው። ሊፈውስሽ የሚችል ማነው? 14 ነቢያቶችሽ የሚያስትና ከንቱ ራዕይ አይተውልሻል። በረከትሽን ይመልሱ ዘንድ በደልሽን አለገለጡም፤ ነገር ግን የሚያስት ትንቢትና የሚያጠምድ ራዕይ ተቀበሉ። 15 በመንገድ የሚያልፉ ሁሉ እጃቸውን በአንቺ ላይ ያጨበጭባሉ። በኢየሩሳሌም ሴት ልጅ ይዝታሉ፥ራሳቸውንም ይነቀንቃሉ፥ ደግሞም «'የውበት ሁሉ መጨረሻ'፥ 'የምድር ሁሉ ደስታ' ብለው የሚጠሯት ከተማ ይህቺ ናትን?» ይላሉ። 16 ጠላቶችሽ ሁሉ አፋቸውን እጅግ ይከፍታሉ፥ ያላግጡብሻልም። እያፏጩና ጥርሳቸውን እያፋጩ፦ «ዋጥናት! በእርግጥም የተጠባበቅናት ቀን ይህቺ ናት! አገኘናት! አየናትም!» ይላሉ። 17 እግዚአብሔር የወሰነውን አደረገ። ከረዥም ጊዜ በፊት ያወጀውን ቃሉን ፈጸመ። አፈረሰ፥ርኅራኄም አልነበረውም፤ ጠላትሽ በአንቺ ላይ እንዲደሰት ፈቀደ፥ የጠላቶሽን ብርታት ከፍ ከፍ አደረገ። 18 ልባቸው ወደ ጌታ ጮኽ፤የጽዮን ሴት ልጅ ቅጥር ሆይ እንባሽ እንደ ወንዝ ቀንና ሌሊት ይፍሰስ። ለራስሽ የእፎይታ ጊዜ አትስጪ። የአይኖችሽን ማፍሰስ አታስቁሚ። 19 በሌሊት ተነሺና ጩኺ፥ ከሌሊቱ መጀመሪያ አንስቶ በጌታ ፊት ልብሽን እንደ ውኃ አፍስሺ። በየመንገዱ ራስ ላይ በረሀብ ደክመው ስለወደቁት ልጆችሽ ሕይወት እጆችሽን ወደ እርሱ አንሺ። 20 እግዚአብሔር ሆይ ተመልከት፥ ጽኑ መከራን ስላመጣህባቸው ስለ እነዚያ ሰዎች ግድ ይበልህ። ሴቶች የራሳቸውን ፍሬ፥ የሚሳሱላቸውን ልጆቻቸውን ይብሉን? ካህኑና ነቢዩ በጌታ መቅደስ ውስጥ ይታረዱን? 21 ወጣቱና ሽማግሌው በአንድነት በየመንገዶቹ በመሬት ላይ ወደቁ። ደናግሎቼና ኃያላን ወንዶቼ በሰይፍ ወደቁ። በቁጣህ ቀን አረድሃቸው፥በጭካኔ ገደልካቸው፥ ርኅራኄም አልነበረህም። 22 በከበረው ጉባዔ ቀን እንደሚሆን ከዙሪያው ሁሉ ሽብርን ጥራህብኝ፤ ማንም አላመለጠም፥ በእግዚአብሔር ቁጣ ቀን የተረፈ ማንምአልነበረም። የተንከባከብኳቸውንና ያሳደግኋቸውን ጠላቴ አጠፋቸው።

Lamentations 2:1

ጌታ በቍጣው የጽዮንን ሴት ልጅ እንደ ምን አደመናት

እግዚአብሔር ለእየሩሳሌም ያለውን ቁጣ በጥቁር ደመና ይመስለዋል። ሊኖሩት የሚችሉት ትርጉሞች፤ 1 እግዚአብሔር በእየሩሳሌም ባሉ ሰዎች ላይ ጥፋትን እንደሚያመጣ እየዛተ ነው ወይንም 2 እግዚአብሔር ሐዝቦቹ ላይ ጥፋትን አምጥቷል

የጽዮንን ሴት ልጅ ... የይሁዳን ሴት ልጅ

እነኚህ ለእየሩሳሌም የተሰጡ ቅኔአዊ ስሞች ሲሆኑ፤ በሴትም መስሏቸዋል።

የእስራኤልን ውበት ከሰማይ ወደ ምድር ጣለ

“የእስራኤል ውበት” የሚለው እየሩሳሌምን ነው። በእስራኤል ያሉ ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን እንዳጡ፤ እናም እርሱ ከመገኘቱ አውጥቶ እንደጣላቸው ይናገራል። “ከሰማይ ወደ ምድር” የሚለው የሚያሳየው በእግዚአብሔር ዘንድ ምን ያህል ሞገስን እንዳጡ ነው። “የእስራኤል ውበት የሆነችው እየሩሳሌም በእግዚአብሔር ፊት ሁሉንም ሞገስን አጥታለች” ወይንም “እየሩሳሌም ሁሉንም ሞገስዋን በእግዚአብሔር ፊት አጥታለች“

የእግሩን መረገጫ አላሰበም

ከዚህ በፊት እግዚአብሔር እየሩሳሌምን “የእግሩ መረገጫ” ብሏት እንደሚያውቅ ሲያመላክት፣ የሚወክለውም በእነርሱ ላይ የነበረውን ሥልጣን እና እነርሱም መገዛታቸውን ነው። እግዚአብሔር የእየሩሳሌምን የእግር መረገጫነት መርሳቱን እና መሻሩን ያመላክታል። “እየሩሳሌም የእግሩ መቀመጫ ከመሆን ሽሯታል።

አላሰበም

እግዚአብሔር እየሩሳሌምን የረሳት ያህል ችላ እንዳላት ያመላክታል። “ችላ ብሏታል” ወይንም “ትኩረት አልሰጣትም።

በቍጣውም ቀን

እዚህ ጋር ቀን የሚለው የተወሰነን የግዜ ክፍልን የሚያመላክትበት ዘይቤአዊ አገላለፅ ነው። “ቍጣውን በሚገልጽበት ግዜ . . . በቍጣውም ግዜ” ወይንም “ቁጣውን በሚያሳይበት ግዜ. . . በቁጣው ግዜ”

ዋጠ

እግዚአብሔርን በሚባላ እንስሳ መስሎ ከተማይቷን ፈጽሞ እንዳጠፋት የሚያሳይበት መንገድ ነው። “ፈጽሞ አጥፍቷት”

የያዕቆብን ማደሪያዎች ሁሉ

እዚህ ጋር “የያዕቆብ ማደሪያዎች” የሚለው በከተማው ይኖሩ የነበሩ የእርሱን ትውልዶች ያሳያል።

በመዓቱ የይሁዳን ሴት ልጅ አምቦች አፈረሰ

ሊኖረው የሚችለው ትርጉም 1 በይሁዳ የፈራረሱ ከተሞች 2 የፈራረሱ የእየሩሳሌም ቅጥሮ ች።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Lamentations 2:3

በጽኑ ቍጣው የእስራኤልን ቀንድ ሁሉ ቀጠቀጠ
ይሄ የሚናገረው እግዚአብሔር የእስራኤልን ቀንድ ሰበረ የሚለው ኋይሏን ወሰደ እንደማለት ነው። “ቀንድ” የሚለው የእንስሳን ቀንድ ነው። “የእስራኤልን ጉልበት ወሰደ”

ቀኝ እጁን ከጠላት ፊት ወደ ኋላ መለሰ
እዚህ ጋር የእግዚአብሔር “ጠበቃ በቀኝ እጁ” የወከላል፤ “እግዚአብሄር እኛን መጠበቅ አቁሟል”

በዙሪያውም እንደሚባላ እንደ እሳት ነበልባል ያዕቆብን አቃጠለ
በእሳት የተቃጠለ ያህል እግዚአብሔር በቁጣው ያዕቆብን አጥፍቷል። “በእሳት እንደሚቃጠል እግዚአብሔር በቁጣው ያዕቆብን አጥፍቷል።”

ያዕቆብ
“ያዕቆብ” የሚለው የእርሱ ትውልዶች የሚኖሩበት ነው። “እስራኤል”

ቀስቱን እንደ ጠላት ገተረ፥ እንደ አስጨናቂ ቀኝ እጁን አጸና
አንድ ወታደር ቀስቱን ለመወንጨፍ መገተር ይኖርበታል፤ እናም እዚህ ጋር እግዚአብሔር እስራኤልን ለመውጋት እየተዘጋጀ እንደሆነ ይገልፃል። “እንደ ጠላት ቀስቱን ገተረ፤ ቀኝ እጁ ተዘጋጅታለች”

በጽዮን ሴት ልጅ ድንኳን
“የጽዮን ሴት ልጅ” የእየሩሳሌም ዘይቤያዊ ሰም ሲሆን፣ በሴትም ይመስላታል። “በጽዮን ሴት ልጅ ድንኳን” የሚለው እየሩሳሌምን እንደድንኳን ሲገልፃት ሰዎቻቸው እንደዛ እንዲሚኖሩ ያሳያል። “በእየሩሌም የሚኖሩት”

Lamentations 2:5

ዋጠ
እግዚአብሔርን በሚባላ እንስሳ መስሎ ከተማይቷን ፈጽሞ እንዳጠፋት የሚያሳይበት መንገድ ነው።

አዳራሾችዋን ... አምቦችዋን
እስራኤልን በሴት ይመስላታል

በይሁዳም ሴት ልጅ ኀዘንና ልቅሶ አበዛ
“ኀዘን”ና “ልቅሶ” የሚሉትን ቃላት በድርጊት መልኩ ሊገለፁ ይችላሉ። “የይሁዳ ሴት ልጆች ብዙ እንዲያዝኑ እና እንዲያለቅሱ ብዙ ብዙ አድርጓል።”

በይሁዳም ሴት ልጅ
ይሄ ቅኔአዊ በሴት የተመሰለ የእየሩሳሌም ስም ነው። “ይሁዳ”

ማደሪያውን እንደ አትክልት ስፍራ ባዶ አደረገ
ማደርያው እንደ አትክልት ሥፍራ በቀላሉ መነቀሉን ያሳያል። እግዚአብሔር የእስራኤል ጠላቶች እንዲያጠፉት ፈቀደ። እርሱ እራሱ አይደለም ያጠፋው። “ጠላቶቻቸው ማደሪያውን በቀላሉ እንደ አትክልት ሥፍራ እንዲጠፋ ያደረገው እርሱ ነው“

አትክልት ስፍራ
ትንሽ የአትክልት እና እርሻ ሥራ መስሪያ ዕቃዎች ማስቀመጫ ወይንም የሰራተኛው መጠለያ።

የበዓሉን ስፍራ አጠፋ
እግዚአብሔር የእስራኤል ጠላቶች እንዲያጠፉት ፈቀደ። እርሱ እራሱ አይደለም ያጠፋው። “የበዓሉን ስፍራ እንዲጠፋ ያደረገው እርሱ ነው” ወይንም “የእስራኤል ጠላቶች የበዓሉን ስፍራ እንዲያጠፉት ፈቀደ”

በጽዮን ዓመት በዓሉንና ሰንበቱን አስረሳ
በቀጠታ መልኩ መገለፅ ይችላል። “የጽዮን ሕዝብ በዓሉንና ሰንበቱን እንዲረሱ አደረጋቸው”

በጽኑ ቍጣው
“በእነርሱ ላይ እጅጉን ስለተቆጣ”

Lamentations 2:7

የቤተ መንግሥቶቿን ቅጥሮች፣ ለጠላት አሳልፎ ሰጠ
ለጠላት የሚለው ወደ ጠላትእጅ ታልፎ መሰጠትን የመላክታል። “እግዚአብሔር ጠላቶቻቸው የቤተመንግስቶቿን ቅጥር እንዲይዙ ፈቅዷል”

የቤተመንግሥቶቿን ቅጥሮች
“እሷ” የሚለው የሚናገረው ሰል ማደሪያው ወይንም ስለ እየሩሳሌም ነው። 1 “የማደሪያው ቅጥሮች” ወይንም 2 “የእየሩሳሌም ቤተመንግስቶች ቅጥር” “ቅጥር” የሚለው ቃል ለሙሉ ሕንፃው ምትክ ሲሆን ሕንፃው ደግሞ ለሙሉ እየሩሳሌም።

በዓመት በዓል ቀን እንደሚደረገው በእግዚአብሔር ቤት በኀይል ጮኹ
ይሄ ምፀታዊ የእስራኤል ደስታ፣ በዓል ማክበር እና የባቢሎናውያን የድል ጩኸት ንፅፅር ነው። “በእግዚአብሔር ቤት ድምጻቸውን ከፍ አደረጉ፤ እስራኤላውያኑ በበዓላቸው ያደርጉት እንደነበረ”

በኀይል ጮኹ
ይህ ዘይቤአዊ አገላለፅ ነው። “ባማየል ጮኸ”

Lamentations 2:8

በጽዮን ሴት ልጅ ዙሪያ ያለውን ቅጥር፣ እግዚአብሔር ለማፍረስ ወሰነ
እግዚአብሔር የእየሩሳሌም ጠላቶች ቅጥሮቿን እንዲያፈርሱ መረጠ። እርሱ እራሱ ግን አላጠፋትም።

በጽዮን ሴት ልጅ
ይህ በቅኔአዊ አገላለፅ የእየሩሳሌምን ስም እንደ ሴት ሲመሰል ነው።

የመለኪያ ገመድ ዘረጋ
ከማጥፋቱ በፊት ቅጥሯን ምን ያህል እንደ ሚያፈርሰው ለማወቅ እንደሚለካ ሰው ይናገራል። “ቅጥሯን እንደለካ ሰው”

ከማጥፋትም እጆቹን አልሰበሰበም
ያለ ሁለት አሉታዊ አገላለፅ ለዘገብም ይችላል። ብሎም እግዚአብሔር የተመሰለው በእጆቹ ነው። “በእጆቹ ቅጥሮቿን አፍርሷል” ወይንም “ቅጥሮቿን አፍርሷል”

ምሽጎችና ቅጥሮች እንዲያለቅሱ አደረገ ፤ በአንድነትም ጠፉ
ምሽጎቿና ቅጥሮቿ በሰው ተመስለው፣ እንዳለቀሱ እና እንደሞቱ አድርጎ ይናገራል። “ምሽጎችና ቅጥሮቿን ስላጠፋ፤ አልቅሰው እንደደከሙ ሰዎች ሆነዋል“

ምሽጎች
ጥንታዊ ከተሞች ከአጥቂዎች የሚለይ ዋና “ቅጥር” ነበራቸው በውጪም በኩል ከ ቅጥሩ የሚከለክል ምሽግ።

Lamentations 2:10

የጽዮን ሴት ልጅ
ይሄ ቅኔአዊ የእየሩሳሌም ስም ሲሆን ፣ እዚህ ጋር በሴት ይመስላታል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ዝም ብለው በመሬት ላይ ተቀምጠዋል
ብዙ ግዜ ሰዎች በመንገድ ዳር የሚቀመጡት ሃዘን ላይ ሲሆኑ ነው። “አዝነው በጸጥታ መንገድ ላይ ተቀምጠዋል”

ትቢያን በራሳቸው ላይ ነሰነሱ
ይሄ የማልቀስ እና የማዘን ምልክት ነው። “ሃዘናቸውን ለማሳየት በራሳቸው ላይ ዐመድ ነስንሰው እና ማቅ ለብሰው”

ራሳቸውን ወደ ምድር አዘነበሉ
ይሄ የማዘን ምልክት ነው። “በአዘኔታ አንገታቸውን ወደ መሬት አቀርቅረው”

Lamentations 2:11

ዐይኔ በለቅሶ ደከመ
ይሄ ዘይኔአዊ አገላለፅ ነው። “ማልቀስ እስከማልችል ድረስ አለቀስኩ”

አንጀቴም ታወከ
“መታወክ” ማለት በኋይል መንቀሳቀስ ማለት ነው፤ ብዙውን ግዜ በክብ መሽከርከር ነው። አንጀቱ የእውነትም ተሸከርክሯል ማለት አይደለም ነገርግን ጸሓፊ የተሰማው ስሜት ነው። “ ”ጎኔን አመመኝ” ወይንም “ሆዴን አመመኝ”

ጉበቴ በምድር ላይ ተዘረገፈ
ጸሓፊው በውስጥ ሰውነቱ የተሰማውን ሃዘን፤ የውስጥ ክፍሎቹ መሬት ላይ የተዘረገፉበት ያህል እንደሆነ ይናገራል። “መላ ሰውኔቴ ሃዘን ላይ ነው”

ስለ ወገኔ ሴት ልጅ
ይሄ ቅኔአዊ የእየሩሳሌም ስም ሲሆን ፣ እዚህ ጋር በሴት ይመስላታል።

እህልና የወይን ጠጅ ወዴት አለ?
ይሄ መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ ዓይነት ሲሆን፤ የሚበላን መፈለግ ላይ ያተኩራል። ልጆቹ ለእናታቸው ምግብ እንደሚፈልጉ እየተናገሩ ነው። እህልና የወይን ጠጅ የ ሚለው የ ሚያሳየው ምግብ እና መጠጥን ነው። ጥያቄው በሌላ መልኩ ሊጻፍ ይችላል። “የምንበላውን እና የ ምንጠጣውን ስጡን”

እንደ ተወጋ ሰው በዛሉ ጊዜ
ከረሃብ የተነሳ ሕፃናቱ እንደቆሰለ ሰው ዝለዋል።

ነፍሳቸውም በእናቶቻቸው ብብት በወጣች ጊዜ
የሕፃናቶቹን መሞት እንደሚፈስ ፈሳሽ ይመስለዋል። “በእናታቸው እጅ ቀስ ብለው ይሞታሉ”

Lamentations 2:13

የኢየሩሳሌም ሴት ልጅ ሆይ፥ ምን እመሰክርልሻለሁ?
እየሩሳሌምን ለመርዳት ምን ማድረግ እንዳለበት እንዳላወቀ ለማስታወቅ የሚጠይቀው ጥያቄ ነው እንጂ መልስ የሚጠይቅበት ጥያቄ አይደለም። ጥያቄ ባልሆነ መልኩ ሊጻፍም ይችላል፤ “ልለው የምችለው ነገር የለም. . . እየሩሳሌም”

የኢየሩሳሌም ሴት ልጅ ... ድንግሊቱ የጽዮን ልጅ ሆይ
ይሄ ቅኔ አዊ የእየሩሳሌም ስም ሲሆን ፣ እዚህ ጋር በሴት ይመስላታል። “ጽዮን” ሌላው የእስራኤል ስም ነው

በምንስ እመስልሻለሁ? ድንግሊቱ የጽዮን ልጅ ሆይ
እየሩሳሌምን ለማጽናናት ምን ማድረግ እንዳለበት እንዳላወቀ ለማስታወቅ የሚጠይቀው ጥያቄ ነው እንጂ መልስ የሚጠይቅበት ጥያቄ አይደለም። ጥያቄ ባልሆነ መልኩ ሊጻፍም ይችላል፤ “ላወዳድርሽ የምችለው ነገር የለም. . . ጽዮን ሆይ”

ስብራትሽ እንደ ባሕር ታላቅ ነው
ባህር ታላቅ እንደ ሆነ የእየሩሳሌምም ስብራት እና ሰቆቃ እንዲሁ ነው። “ጉዳትሽ እንደ ባህር ታላቅ ነው”

የሚፈውስሽ ማን ነው?
“ማን ይፈውስሻል” ቀድሞ እንደነበረው ሊመልሳት የሚችል ማንም እንደ ሌለ ለመግለጽ የተጠቀመበት መንገድ ነው እንጂ መልስ የሚጠብቅ ጥያቄ አይደለም። በሌላ መልኩም ሊጻፍ ይችላል፤ “ማንም ሊፈውስሽ አይችልም” ወይንም “ማንም ሊመልስሽ አይችልም”

ምርኮሽንም ይመልሱ ዘንድ በደልሽን አልገለጡም
“ምርኮኛነትሽን ለማስቀረት፣ ኀጢአትሽን አይገልጡም”። “ምርኮሽን” ይሚለው የሰውን ሃብት እና ብልፅግና ያሳያል።

ከንቱና የማይረባ ነገርንም አይተውልሻል
አይተውልሻል የሚለው ”ተናግረዋል“ በሚለው ሊገለጽ ይችላል። “ከንቱና የማይረባ ነገርንም ተናግረውልሻል”

Lamentations 2:15

እጃቸውን ... ያፍዋጫሉ ፥ ራሳቸውንም ያነቃንቃሉ
ሌሎችን ለመስደብ እና እነርሱ ላይ ለማሾፍ የሚደረጉ ድርጊቶች ናቸው። “እጃቸውን እያጨበጨቡ. . . እያፏጩ እና ራሳቸውንም ያነቃንቃሉ”

በኢየሩሳሌም ሴት ልጅ
ይሄ ቅኔአዊ የእየሩሳሌም ስም ሲሆን ፣ እዚህ ጋር በሴት ይመስላታል።

በውኑ የውበት ፍጻሜና የምድር ሁሉ ደስታ የሚሉአት ከተማ ይህች ናትን?
ይሄ ምላሽ የማይጠብቀው ጥያቄ የፌዝ ንግግር ነው። ጥያቄ ባልሆነ መልኩ ሊጻፍ ይችላል። ““የውበት ፍጻሜ” እና “የምድር ሁሉ ደስታ” የተባለችው ከተማ ውበትም ድስታም የለባትም።

የውበት ፍጻሜ
በፍፁም ውብ

ጥርሳቸውን እያፋጩ
ይሄ የሰውን ቁጣ እና በሌላው ላይ ማፌዝን ነው የሚያሳየው።

ውጠናታል
እንስሳ ምግቡን እንደሚውጥ እየሩሳሌምን አጥፍተናታል። “እየሩሳሌምን ሙሉ ለሙሉ አጥፍተናታል”

አግኝተናታል አይተናትማል
ይህ ዘይቤአዊ አገላለጽ ነው። “ሲፈፀም ለማየት እጅግ ጓጉተን ነበር”

Lamentations 2:17

አፈረሰሽ
“አፈረሰ”

ደስ አሰኘብሽ
ጠላት ስላሸነፈሽ ተደሰተብሽ ለማለት ነው። “አንቺን በማሸነፍ መደሰት”

የሚያስጨንቁሽንም ቀንድ ከፍ ከፍ አደረገ
“ቀንድ” የእንስሳ የሚያሳየው ጥንካሬን ነው። “የጠላቶቻችንን ጉልበት ጨመርህ”

Lamentations 2:18

ልባቸው ወደ ጌታ ጮኸ
የሰውን የውስጥ ማንነትን ለመወከል ነው “ልብ” ያለው። ሊንረው ይሚችለው ትርጉም 1 የእየሩሳሌም ሠዎች፤ “የእየሩሳሌም ሠዎች ከውስጥ ማንነታቸው ወደ ጌታ ጮኑ” ወይንም 2 ቅጥሩን በሰው ይወክለዋል፤ “ቅጥሮቻችሁ፣ ከውስጥ ማንነታቸው ወደ እግዚአብሔር ይጮሃሉ”

የጽዮን ሴት ልጅ ቅጥር ሆይ፥ እንባሽን ... አፍስሺ ... በጐዳና ሁሉ
ጸሓፊው ስለ እየሩሳሌም ቅጥር መናገር ፈልጓል። ቅጥርሽ ብሎ የሚናገረውን የእየሩሳሌም ሠዎ ች እንዲናገሩ የ ሚፈልገውን ነው። “እናንተ የጽዮን ሴት ልጅ ቅጥር” የሚለው በቀጥታ ለ“ቅጥሯ” ሲሆን ሌላው ግን ለሠዎቹ የተነገረ ነው።

የጽዮን ሴት ልጅ
ይሄ ቅኔአዊ የእየሩሳሌም ስም ሲሆን ፣ እዚህ ጋር በሴት ይመስላታል።

እንባሽን እንደ ፈሳሽ አፍስሺ
ሠዎቹ እጅግ ስላለቀሱ እምባቸው እንደ ወራጅ ውሃ ነው። “እጅግ ብዙ ብዙ አለቀሱ”

ቀንና ሌሊት
ሁለቱ ተቃራኒ የግዜ መለክያዎች የተገለጹት ሁል ግዜ ለማለት ነው። “ሁል ግዜ”

ለሰውነትሽ ዕረፍት አትስጪ ፤ የዓይንሽ ብሌን አታቋርጥ
“ለራስሽ ዕረፍትን አትስጪ፣ ዐይኖችሽ ከማንባት አያቋርጡ ”

በሌሊት በመጀመሪያ ክፍል
“በሌሊቱ ብዙውን ግዜ” ይሄ የሚያመላክተው ጠባቂ በሚመጣበት የትያውም ግዜ።

በጌታም ፊት ልብሽን እንደ ውኃ አፍስሺ
“ልብሽን እንደ ውኃ አፍስሺ” የሚለው ዘይቤአዊ አገላለጽ ነው። የእግዚአብሔርን መገኘት ለመግለፅ በፊት ይገለፃል። “በውስጥ ሰውነታችሁ የሚሰማችሁን ለእግዚአብሔር ንገሩት”

እጆችሽን ወደ እርሱ አንሺ
x

Lamentations 2:20

ፍሬያቸውን
ስለ ልጆ ች እየተናገረ ሲሆን ከእናታቸው ማህፀን እንደወጣ ፍሬ ይመስላቸዋል። “የወለዷቸውን ሕፃናት” ወይንም “የራሳቸውን ልጅ”

በውኑ ካህኑና ነቢዩ በጌታ መቅደስ ውስጥ ይገደላሉን?
ይሄ ጥያቄ ምላሽን የሚጠብቅ ጥያቄ ሳይሆን፤ ካህናት እና ነብያት ሊገደሉ እንደማይገባ ለማስረገጥ ነው። በሌላ መልኩ ሲፃፍ “ካህናቱ እና ነብያቱ በእግዚአብሔር ማደሪያ ሊገደሉ አይገባም”

በውኑ ካህኑና ነቢዩ ... ይገደላሉን?
በቀጥታ መልኩ ሲፃፍ “ጠላቶቻችን ካህናቱን እና ነብያቱ ሊገድሉ ይገባልን”

Lamentations 2:21

ብላቴናውና ሽማግሌው በመንገዶች ላይ ተጋደሙ
እዚህ ጋር የሚናገረው ስለ ሞቱ ሰዎች እንደሆነ ያመላክትል። “የብላቴኖች እና ሽማግሌዎች ሬሳ በመንገዶች ላይ ተጋድሟል”

ብላቴናውና ሽማግሌው
ይሄ ክፍል የሚናገረው ስለ ሰዎች ነው። ሁለቱ ተቃራኒ የእድሜ ክልል የተጠቀሱት ሁሉንም ሰዎ ች ለመወከል ነው። “ወጣቱም ሽማግሌውም” ወይንም “በሁሉም የ ዕድሜ ክልል ያሉ ሰዎች”

ደናግሎቼና ጐበዛዝቴ በሰይፍ ወድቀዋል
ሰይፍ የሚለው የሚወክለው ጠላቶቹን ነው። የተገደሉትም በጠላቶቻቸው ነው። “ደናግሎቼና ጐበዛዝቴ በጠላቶቻቸው ተገድለዋል”ወይንም “ጠላቶቼ ደናግሎቼን እና ጐበዛዝቴን ገድለዋቸዋል”

ገደልሃቸው
እግዚአብሔር እራሱ የገደላቸው ያህል ሰዎቹ እንዲገደሉ መፍቀዱን ይናገራል። “እንዲገደሉ ፈቀድክ” ወይንም “ይሄ እንዲፈጠር ፈቀድክ”

እንደ በዓል ቀን ... ከዙሪያዬ ጠራህ
“ሊቡሉ እንደሚመጡ” ይቡሉ ዘንድ እንደሚመጠ እግዚአብሔር እንዴት ጠላቶቹን እንደጠራ።

የሚያስፈሩኝን
ጸሓፊው የሚፈራቸው ሰዎች “የሚያስፈራሩኝ” በሚል ተገልጿል። “የፈራኋቸው አጥቂዎቼ”

ከዙሪያዬ
ዘይቤአዊ አገላለጽ ነው። “በሁሉም አቅጣጫ”

በእግዚአብሔር ቍጣ ቀን
“ቀን” የሚለው በዘይቤአዊ አገላለጽ የተጻፈ ሲሆን የተወሰነ ግዜን የወክላል። “በእግዚአብሔር በቍጣው በተገለጠ ግዜ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 በእግዚአብሔር የቁጣ በትር መከራ ያየ ሰው እኔ ነኝ። 2 አባረረኝ፥ በብርሃን ሳይሆን በጨለማ እንድሄድ አደረገኝ። 3 በእርግጥ ሊቃወመኝ ወደ እኔ ዘወር አለ፥ ቀኑን ሙሉ እጁን በላዬ መለሰ። 4 ሥጋዬንና ቆዳዬን ቀደደ፥ አጥንቶቼን ሰበረ። 5 ቅጥር በዙሪያዬ ገነባብኝ፥ በምሬትና በመከራም ከበበኝ። 6 ከሞቱ ረዥም ጊዜ እንደሆናቸው በጨለማ ስፍራ እንድኖር አደረገኝ። 7 በዙሪያዬ ቅጥርን ገነባ፥ ማምለጥም አልችልም። የእግሬን ሰንሰለት አከበደ። 8 ለርዳታ ብጮኽና ብጣራም ጸሎቴን ዘጋ። 9 ከጥርብ ድንጋይ በተሰራ ቅጥር መንገዴን ዘጋ፤የምሄድብት የትኛውም መንገድ ጠማማ ሆን። 10 መንገዴን ቀየረው። 11 ገነጣጠለኝ፥ብቸኛም አደረገኝ። 12 ቀስቱን ለጠጠ፥ ለፍላጻውም የዒላማ ምልክት አደረገኝ። 13 ቀስቱን ለጠጠ፥ ለፍላጻውም የዒላማ ምልክት አደረገኝ። ለሰዎች ሁሉ መሳለቂያ፥ ዘወትርም ለሽሙጥ ጫ ዝማሬያቸው ምክንያት ሆንኩ። ምሬት ሞላብኝ፥ እሬት እንድጠጣ አስገደደኝ። 14 ለሰዎች ሁሉ መሳለቂያ፥ ዘወትርም ለሽሙጥ ጫ ዝማሬያቸው ምክንያት ሆንኩ። 15 ምሬት ሞላብኝ፥ እሬት እንድጠጣ አስገደደኝ። 16 ጥርሴን በድንጋይ ሰበረ፥ ወደ መሬት ውስጥ ረገጠኝ። 17 ሰላምን ከሕይወቴ አስወገድክ፤ ከእንግዲህ መቼም የትኛዉንም ደስታ አላስብም። 18 ስለዚህም«ጽናቴ ጠፍቷል፥ በእግዚአብሔር ላይ ያለ ተስፋዬም ሄዷል» አልሁ። 19 መከራዬንና እሬትና ምሬት ወደ አለበት መጥፋቴን አስባለሁ። 20 በእርግጥ አስበዋለሁ፥ተስፋ በመቁረጥ በውስጤ አቀረቀርኩ ። 21 ነገር ግን ይህን አስባልሁ፥ ተስፋ ሊኖረኝ የቻለውም ከዚህ የተነሳ ነው። 22 ያልጠፋነው ከእግዚአብሔር የኪዳኑ ታማኝነት የተነሳ ነው፥ የምሕረቱ ሥራዎች አያልቁምና። 23 የምሕረቱ ሥራዎች ማለዳ ማለዳ አዲስ ናችው፤ ታማኝነትህ ምንኛ ታላቅ ነው! 24 ለራሴ እንዲህ አልኩ «እግዚአብሔር ዕጣ ክፍሌ ነው» ስለዚህ ተስፋ አደርገዋለሁ። 25 ለምጠብቀው፥ ለምትፈልገውም ሕይወት እግዚአብሔር መልካም ነው። 26 የእግዚአብሔርን ማዳን በዝምታ መጠበቅ መልካም ነው። 27 በወጣትነቱ ቀንበርን ቢሸከም ለሰው መልካም ነው። 28 እግዚአብሔር አሸክሞታልና ለብቻው ይቀመጥ ዝምም ይበል። 29 ምናልባት ተስፋ ሊኖር ይችላልና አፉን በአፈር ዉስጥ ያኑር። 30 ለሚመታው ጉንጩን ይስጥ። ዉርደትንም ይጥገብ፤ 31 እግዚአብሔር ለዘላለም አይጥለውምና! 32 ሐዘንን ቢያመጣም እንኳን ከታላቁ የኪዳኑ ታማኝነት በሚሆን ርኅራኄ ይራራል። 33 ምክንያቱም ከልቡ አይጨቁንም፥ወይንም የሰዎችን ልጆች አያሰቃይም። 34 በምድር ያሉ ምርኮኞችን ሁሉ ከእግሩ በታች ሲያደቅቅ፥ 35 በልዑል ፊት የሰውን ፍርድ ሲያጣምም፥ 36 ፍትህ ፈላጊውን ሲያፍን- ጌታ አያይምን? 37 ጌታ ካላዘዘው በቀር የሚናገርና የሚፈጽመው ማን ነው? 38 ጥፋትና ስኬት ከልዑል አፍ የሚወጡ አይደሉምን? 39 ታዲያ ማንም ሕያው የሆነ ሰው እንዴት ሊያጉረመርም ይችላል? ማንም ሰው ስለ ኃጢአቱ ቅጣት እንዴት ሊያጉረመርም ይችላል? 40 መንገዳችንን እንፈትን እንመርምርም፥ ወደ እግዚአብሔርም እንመለስ። 41 ልባችንንና እጃችንን በሰማይ ወደ አለው ወደ እግዚአብሔር እናንሣና እንዲህ ብለን 42 እንጽልይ፦ተላልፈናል በአንተም ላይ ዐምፀናል፥ስለዚህ ይቅር አላልከንም። 43 ራስህን በቁጣ ሸፈንክ አሳደድከንም። አረድከን፥ አራራህልንምም። 44 ራስህን በደመና ሸፈንክ፥ስለዚህም ማለፍ የሚችል ጸሎት የለም። 45 በአሕዛብም መካከል ቆሻሻና ውዳቂ አደረግኽን ። 46 ጠላቶቻችን በእኛ ላይ በማላገጥ አፋቸውን ከፈቱ። 47 የአሳር ጉድጓድ ፥የባዶነትና የጥፋት ፍርሃት መጣብን። 48 ስለ ሕዝቤ ሴት ልጅ ጥፋት ዓይኔ ያለማቋርጥ ውኃ አፈሰሰች። 49 ዓይኖቼ ያፈሳሉ አያቆሙምም፥ለለቅሷቸውም ፍጻሜ የለውም፥ 50 እግዚአብሔር ውደ ታች እስኪመለከት ከሰማይም እስኪያይ ድረስ። 51 ከከተማዬ ሴቶች ልጆች የተነሳ ዓይኔ ጽኑ ስቃይ በሕይወቴ ላይ አመጣች። 52 ጠላቶቼ ያለ ምንም ምክንያት፥ያለመታከት እንደ ወፍ አደኑኝ። 53 ሕይወቴን በጉድጓድ ዉስጥ አጠፉ፥ ድንጋይንም በላዬ ከመሩ። 54 ውኖች በራሴ ላይ አለፉ፤እኔም፦ «ተቆርጨአለሁ!» አልኩ። 55 እግዚአብሔር ሆይ፥ ከጥልቅ ጉድጓድ ስምህን ጠራሁ። 56 «እርዳታ ፈልጌ ስጮህ፥እረፍት ፈልጌ ስጣራ ጆሮህን አትሰውር» ባልኩኝ ጊዜ ድምጼን ሰማህ። 57 በጠራሁህ ቀን ወደ እኔ ቀርበህ «አትፍራ» አልከኝ። 58 ጌታ ሆይ በተከሰስሁ ጊዜ ስለ ነፍሴ ተሟገትህ፤ ሕይወቴንም አዳንክ። 59 እግዚአብሔር ሆይ እንዴት እንደ ጨቆኑኝ አይተሃል፥ ክርክሬን በጽድቅ ፍረድልኝ። 60 በእኔ ላይ የዶለቱትን ሁሉ፥የበቀላቸውን ሥራ ሁሉ አይተሃል። 61 እግዚአብሔር ሆይ በእኔ ላይ የዶለቱትን ሁሉና እሽሙጥጫቸውን ሰምተሃል። 62 በእኔ ላይ የተነሱብኝን ከንፈሮች ሰምተሃል፤ቀኑን ሁሉ እኔን በመቃወም የሚያስቡትን ጥልቅ አሳቦች ሰምተሃል። 63 እግአብሔር ሆይ! ተመልከት፥ በመቀመጣቸውም ሆነ በመነሳታችው የስላቅ ዘፈናቸው ምክንያት ነኝ። 64 እግዚአብሔር ሆይ እጆቻቸው እንዳደረጉት ክፉ ነገር እንደዚያው መልሰህ ክፈላቸው። 65 ፍርሃትን በልባቸው አድርግ፥ ርግማንህንም በላይቸው አድርግ። 66 እግዚአብሔር ሆይ! በቁጣህ አሳድዳችው፥ከሰማይት በታች በየስፍራው አጥፋቸው።

Lamentations 3:1

መከራ ያየ
“ያየ” ልምድ ያለውን ያሳል። “መከራን የተለማመደ” ወይንም “የተጎዳ”

በቁጣው በትር
“በትር ስር” የሚለው በበትር መመታትን ያሳያል። የእግዚአብሔርን ቅጣት በእርሱ በትር እንደመመታት ይተካዋል። “እግዚአብሔር እጅግ ስለተቆጣ በበትር መጥቶኛል” ወይንም “እግዚአብሔር እጅግ ስለተቆጣ በኋይል ቀጣኝ”

ከፊቱ አስወጣኝ
“ከእርሱ እንደሄድ አደረገኝ”

በብርሃን ሳይሆን በጨለማ እንድሄድ አደረገኝ
“ጨለማ” የሚለው የሚወክለው መከራን ነው። “በብርሃን ሳይሆ ን በጨለማ እንደሚሄድ ሰው ያለ ምንም ተስፋ እጅጉን እንድጎዳ አደረገ”

እጁን በላዬ ላይ መለሰ
“እጁን በላዬ ላይ መለሰ” የሚለው እርሱን ማጥቃትን ይወክላል። ጸሓፊው እግዚአብሔር መጠፎ ነገርን እንዲደርስበት መፍቀዱን እንዳጠቃው አድርጎ ይናገራል። “አጥቅቶኛል” ወይንም “ሰውን እንደሚያጠቃ ብዙ መጥፎ ነገሮች እንዲደርስብኝ አድርጎኛል”

ሥጋዬንና ቁርበቴን አስረጀ፥ አጥንቴን ሰበረ
ሊሆን የሚችሉት ትርጉሞች፤ 1 ከመደብደብ የተነሳ የሚሆን ነገር ነው ወይንም 2 እግዚአብሔር እርሱን የቀጣበት ሌላ መንገድ ነው።

Lamentations 3:5

ቅጥር ሠራብኝ
የቅጥር ሥራ የሚለው ቅጥር ያላቸው ከተማዎች ላይ ተንጠላጠሎ ለመውረር እንዲያስችላቸው የሚሰሩት ነው።

ቅጥር ሠራብኝ
ሊሆን የሚችሉት ትርጉሞች፤ 1 ጸሓፊው እግዚአብሔር በከተማ ላይ መጣፎ ነገር ላማድረስ እንደሚቀጥር ክፋት እንዲደርስበት እንዳደረገ ይናገራል። “ጠላት በከተማ ላይ ጥቃትን ለማድረስ እንደ ሚቀጥርእግዚአብሔር

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አጠቃኝ” ወይንም 2 ጸሓፊው እግዚኣብሔር ጠላት እየሩሳሌምን እንደሚወር እንደፈቀደ እግዚአብሔር አጠቃኝ ለማለት ነው። “ጠላት በዙሪያዬ ቅጥርን እንዲሰራ እግዚአብሔር አደረገ”

በምሬትና በድካም ዙሪያዬንም ከበበኝ
እግዚአብሔር ምሬትና ድካምን እዲለማመዱ ፈቅዷል። “ምሬትና ድካምን እድለማመድ አድርጓል” ወይንም “መከራን እና ብዙ ችግር እንዲደርስብኝ አድርጓል”

ምሬት
“ምሬት” የሚለው መከራን ያሳያል።

ከሞቱ ብዙ ጊዜ እንደሆናቸው፣ በጨለማ እንድኖር አደረገኝ።
“ጨለማ” የሚለው የሚናገረው ስለ መከራ ነው። ጸሓፊው የደረሰበትን መከራ መጠን ለመግለፅ ቀድሞ የሞቱ ሰዎች ከተለማመዱት ድቅድቅ ጨለማ ጋር ያወዳድረዋል። “እንዲደርስብኝ ያደረገው መከራ በመቃብር ውስጥ እንዳለ ጨለማ ነው” ወይንም “ ቀድማውንም የሞቱ ሰዎች ያሉበት ጨለማ ውስጥ ያለው ያህል እጅጉን መከራ ያደርስብኛል”

በቅጥር ውስጥ ዘጋብኝ፤ ስለዚህ ማምለጥ አልቻልሁም፤ የእስር ሰንሰለቴንም አከበደብኝ።
ይሄ ከእስር ቤት ማምለጥ እንዳቃተው ሰው ቀጣይነት ያለውን መከራ መቀበልን ያሳያል። ጸሓፊው መከራውን ማስቆም አልቻለም። “መከራዬ ቀጥሏል፤ በዙሪያዬ ቅጥርን የሰራ፣ ከባድ ሰንሰለትን ያደረገንኝ ያህል ነው፤ ማምለጥ ተስኖኛል”

ብጣራና ብጮኽ እንኳ . . . መስማት አልፈለገም
ጸሓፊው እግዚአብሔር ጸሎቱን ጆሮውን ደፍኖ አልሰማም እንዳለው ያህል እንደማይሰማው ይናገራል። “ጸሎቴን አልሰማም ይላል”

Lamentations 3:9

መንገዴን . . . ዘጋ
ጸሓፊው ስለ እግዚአብሔር የሚናገረው ከመከራው እንዳያመልጥ መንገዱን እንደዘጋ ነው። “መንገዴን እደዘጋ ነው”

በተጠረቡ ድንጋዮች ዘጋ
“የተጠረቡ ድንጋዮች” አንድ ላይ አድርገው ሕንፃን ለመገንባት ሰዎች ድንጋይን ይጠርባሉ።

ጐዳናዬንም አጣመመ
የተጣመሙ መንገዶች ሠዎችን ወደ ሚፈልጉበት ቦታ አያደርሱም። እዚህ ጋር መከራን ለማምለጥ የሚሆን መንገድን ይወክላሉ። “መንገዴን እንዳጣመመ ነው” ወይንም “መከራዬ እንዲያቆም ለማድረግ ሞክሪያከሁ፤ ነገር ግን ለማምለጥ የሚሞክርን ሰው መንገድ እንደሚያጣምም እግዚአብሔር ከለከለኝ”

አሸምቆ እንደ ተኛ ድብ፣ እንደ አደባም አንበሳ
ጸሃፊው እግዚአብሔር ክፋት እንዲሆንበት ሊያደርግ፤ አውሬ ለአደን እንደሚያደፍጥ ተዘጋጅቶ እየጠበቀ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል።

መንገድ ጐትቶ አስወጣኝ፤ ቄራረጠኝም፤
ሊኖረው የሚችለው ትርጉም 1 “ከመንገድ አወጣኝ” ወይንም 2 “መንገዴ በተሳሳተ መታጠፍያ እንዲታጠፍ አደረክ”

ያለ ረዳትም ተወኝ
“ተስፋ ቢስ አደረገኝ” ወይንም “ምንም እርዳታን እንናገኝ አልፈቀደም”

Lamentations 3:12

ቀስቱን ገተረ፤
አንድ ወታደር ቀስቱን ለመወንጨፍ መገተር ይኖርበታል፤ እናም እዚህ ጋር እግዚአብሔር እስራኤልን ለመውጋት እየተዘጋጀ እንደሆነ ይገልፃል። “እግዚአብሔር ቀስቱን ገተረ፤ ለማጥቃት እጁ ተዘጋጅታለች”

የሰገባውን ፍላጻዎች በኩላሊቴ ውስጥ ተከለ
ጸሓፊው የተሰማውን የውስጥ ኃዘን ለመግለፅ እግዚአብሄር ኩላሊቱን በቀስት እንደወጋ ያህል ይገልጸዋል። “ሓዘኔ ታላቅ ነው፤ ኩላሊቴ በቀስት እንደተወጋ ያህል ነው”

ኩላሊቴ
ኩላሊት የሚያሳየው የሰውን ስሜት ነው። ትርጓሜውም “በጥልቅ ሰውኔቴ ውስጥ” ወይንም “ልቤ”

ሰገባ
ከኋላ የሚታጠቁት ፍላፃ ማስቀመጫ ቦርሳ

ለወገኔ ሁሉ ማላገጫ
“ሁሉ” የሚለው አብዛኛውን ያመላክታል። “ለአብዛኛው ሰው ማላገጫ” ወይንም “ሁሉም ሰው የሚያሾፍበት”

ማላገጫ
ብዙ ሰዎች የሚያሾፉበት ሰው

ምሬት ሞላብኝ
እዚህ ጋር “ምሬት” የሚለው መከራ መቀበልን ይወክላል። ጸሓፊውን የሚያጠግብ ነገር የሆነ ያህል ድረስ። “እጅግ በጣም መከራን እንዲደርስብኝ አድርጓል ”

በእሬትም አጠገበኝ
ከአበባ እና የተወሰነ አትክልት የሚሰራ መራራ መጠጥ ነው። የሄንን መጠጥ መጠጣት መከራ መቀበልን ያመላክታል። “በጣም መራራ ነገርን እንድጠጣ እንዳስገደደኝ ያህል ነው”

Lamentations 3:16

ጥርሴን በድንጋይ ሰበረ
ሊኖረው የሚችለው ትርጉም 1 ድንጋይ እዲያኝክ ያደረገው እስኪመስለው ያህል እግዚአብሔር እንዳዋረደው። “አዋርዶኛል፤ ሌላን ሰው ድንጋይ እንዲበላ እንዳደረገ ሰው” ወይንም 2) ጸሓፊው እግዚአብሔር ፊቱን ከመሬት ጋር አጣብቆ እንዳዋረደው አድርጎ ነው የገለጸው። ““አዋርዶኛል፤ የሌላን ሰው ፊትን ከመሬት ጋር እንዳጣበቀ ሰው””

በትቢያ ውስጥ ረጋገጠኝ
ጸሓፊው እግዚአብሔር ወደ ትቢያ ውስጥ እንደገፋው እና እንዳዋረደው አድርጎ ይናገራል።

በትቢያ
ሊዋጋው የማይችለው ነገር ከመሆኑ የተነሳ እራሱን ሊያሳንስበት የሚችለው ትንሹ ደረጃ ለማለት ነው።

ነፍሴ ሰላምን አጣች
ሊኖረው የሚችለው ትርጉም 1 የጸሓፊው ልምምድ ሰላማዊ አይደሉም “በሕይወቴ ሰላም የለኝም” ወይንም ጸሓፊው ሰላም አይሰማውም “በነፍሴ ሰላም አይሰማኝም”

ኋይሌ፤ ከእግዚአብሔርም ተስፋ ያደረግሁት ሁሉ ሄዶአል
ጸኋፊው መከራን መቋቋም ስለሚያስችለው ኋይሉ ይናገራል፤ ብሎም በእግዚአብሔር ላይ ስላለው ተስፋ ሊናገር ሕይወት እንዳላቸው እና አሁን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንደሞቱ ነገሮች አድርጎ ይናገራል። “ከዚህ በላይ መከራን መቀበል እና በእግዚአብሔር እንደሚረዳው ተስፋ ማድረግን እንዳቃተው”

ኃይሌ
አንዳንድ ቅጂዎች “ክብሬ” ወይንም “ተድላዬ”

Lamentations 3:19

እሬትንና ሐሞት
እሬት የሚለው ከተወሰነ ተክል የሚነኝ ውስጡ መራራ ሰሳች የሚነኝ። “እሬትን” እና “ሐሞት” የሚሉት በአንድ ላይ መከራን ይወክላሉ።

ነፍሴም በውስጤ ተዋርዳለች
ጸሓፊው ስለ ጥልቅ ኋዘኑ እና ምስቅልቅሉ፤ አንገቱን እንዳቀረረ ሆኖ ይናገራል። “ደብሮኛል” ወይንም “ተስፋ ቆርጫለሁ”

ሆኖም ይህን አስባለሁ
ሆን ብሎ ስለአንድ ነገር ማሰብን ያሳያል። “ይህን” የሚለው ጸሓፊው በመቀጠል ሊናገር ስለሚያስብበት ነገር ነው። “ስለዚህ ነገር ላስብ ወሰንኩኝ” ወይንም “ይህንን አስታውሳለሁ”

ተስፋ አለኝ
“ተስፋ አደርጋለሁ”

Lamentations 3:22

ከእግዚአብሔር ታላቅ ፍቅር የተነሣ
“ታላቅ ፍቅር” የሚለው “ባታማኝነት መውደድ” በሚለው ሊገላጽ ይችላል። “እግዚአብሔር ህዝቡን በታማኝነት መውደዱን አያቆምም”

ርኅራኄው አያልቅም
“ርኅራኄው” የሚለው ቃል “ግድ ማለት” በሚለው ሊተረጎም ይችላል። “መከራን ለሚቀበሉ ግድ መሰኘትን አያቆምም”

ማለዳ ማለዳ አዲስ ነው
“ነው” ይሚለው የእግዚአብሔርን “ታላቅ ፍቅር” እና “ርኅራኄ” ነው። አዲስ ነው ማለቱ እግዚአብሔር እነርሱን ማድረግ አ ለማቆሙን ያሳያል።

ታማኝነትህም
“የአንተ” የሚለው እግዚአብሔርን ነው።

እግዚአብሔር ዕድል ፈንታዬ ነው
እግዚአብሔር ለሁሉም የ እስራኤል ነገድ መሬትን ሲሰጥ “ዕድል ፈንታ” ነው ነበር ያለው። የሚያስፈልገው ዕድል ፈንታ እግዚአብሔር እንደሆነ ነው ስለ እግዚአብሔር የሚናገረው። “እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ስለሆነ፤ የሚያስፈልገኝ ሁሉ አለኝ ”

Lamentations 3:25

እርሱን ተስፋ ለሚያደርጉት
ሊኖረው የሚችለው ትርጉም 1 “በእሩሱ ላይ የሚደገፉ ሁሉ” ወይንም 2 “እርሱ የሆነ ነገርን እስከሚያደርግ ድረስ የሚጠብቅ”

ለሚፈልገውም ሰው
“መፈለግ” የሚለው ሊኖረው የሚችለው ትርጉም 1 እግዚአብሔርን ዕርዳታ መጠየቅ 2 እግዚአብሔርን ለማወቅ መፈለግ

በወጣትነቱ ቀንበር ቢሸከም
ቀንበር የሚለው የሚያመላክተው መከራን ነው። “በወጣትነት” የሚለው ልጅነትን ያመላክታል። “በልጅነት ግዜው የደረሰበት መከራ

ብቻውን ዝም ብሎ ይቀመጥ
“ዝም ብሎ” የሚለው አለመናገርን ያመላክታል። እዚህ ጋር አለማጉረምረምን ለማለት ነው። “ያለመናገር በቻውን ይቀመጥ” ወይንም “ሳያጉረመርም ብቻውን ይቀመጥ”

አሸክሞታልና
“ቀንበሩ ሲጫንበት” ቀንበር የሚለው የሚያመላክተው መከራን ነው። “መከራን ሲቀበል”

ፊቱን በዐቧራ ውስጥ ይቅበር
ፊትን በዐቧራ መቅበር አንገትን ወደ ምድር ማቀርቀርን ያመላክታል። “እዛው ፊቱን ወደ መሬት አዘቅዝቆ ይቆይ”

Lamentations 3:30

ጉንጩን ለሚመታው ሰው ይስጥ
በውስጥ ታዋቂነት “እርሱ” የሚለው መከራን የሚቀበል ወይንም እግዚአብሔርን የሚጠባበቅ ማንንም ነው። “ጉንጩን ይስጥ” የሚለው የሚወክለው ሰው ጉንጩን እንዲመታ መስጠትን ነው። “ፊቱን እንዲመቱት ለሰዎች ይፍቀድ”

ውርደትንም ይጥገብ
ጸሓፊው የሚናገረው በውስጡ እንደ ውሃ ውርደትን ለሞላ እንደሚችል ዕቃ ነው። በውርደት መሞላት ማለት በጣም መዋረድ ማለት ነው። ማስተላለፍ የፈለገው በዚህ ግዜ መታገስ እንዳለበት ነው። “ብዙ ይዘለፍ” ወይንም “ሰዎች ሲያዋርዱት ይታገስ”

መከራን ቢያመጣ እንኳ
“እግዚአብሔር ሰዎች መከራ እንዲደርስባቸው በያረግም” ወይንም “ሰዎችን ቢቀጣም”

ይራራል
“በእነርሱ ላይ ርህራሄ ይኖረዋል”

ሆን ብሎ ችግርን፣ ወይም መከራን አያመጣምና
“ሆን ብሎ” የሚለው ፍላጎትን እና እርካታን ያመላክታል፤ “በሰዎች ላይ መከራን በማምጣት ደስ አይለውም” ወይንም “ሰዎችን በመቅጣት እርካታን አያገኝም”

በሰው ልጆች ላይ
ይሄ በአጠቃላይ ስለ ሰዎች ይናገራል። “ሰዎች” “የሰው ልጆች”

Lamentations 3:34

ሰው መብቱ ሲነፈገው ... ሰው ፍትሕ ሲጓደልበት፣
“ሰዎች ሲደቁ...የሰውን ፍትህ ሲለነፍግ... ፍትህ ሲለነፍጉ”

በእግር ሲረገጡ
እዚህ ጋር “በእግር ሲረገጡ” የሚለው ሰዎችን ማንገላታትን እና ማጉላላትን ያሳያል። “ማንገላታት” ወይንም “ማጉላላት”

ሰው መብቱ ሲነፈገው፣
ይሄ ሰው የሚገባውን ነገር መንፈግን ያመላክታል። “የሰውን መብት ምከልከል” ወይንም “ሰው የሞ ገባውን ነገር እንዳያገኝ መከልከል”

በልዑል ፊት
“በልዑል ፊት” አንድን ነገር ማድረግ የሚወክለው እግዚአብሔር እያየ ማለት ነው። ““በልዑል እያየ እንደሆነ እያወቅሁ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሰው ፍትሕ ሲጓደልበት፣
“ፍትሕ ሲጓደል” ማለት ፍትኋዊ ነገርን አለማድረግ ማለት ነው። “አንድን ሰው በህግ ፊት በስህተት መዳኘት ማለት ነው” ወይንም “በዳኛ ፊት የሚቀርብን ሰው ፍርድ እንዳያገኝ ማድረግ ማለት ነው”

Lamentations 3:37

ጌታ ያላዘዘውን የሚልና የሚፈጽም ማን ነው?
ጸሓፊው ምላሽ የማይሰጠውን ጥያቄ የሚጠቀመው እግዚአብሔር እንዲሆን የተናገረው ነገር ብቻ እንደሚሆን ነው። “ማንም ተናግሮ አልሆነም፤ እግኤአብሔር ካላለው በስተቀር” ወይንም “እግዚአብሔር ካላዘዘው በስተቀር ሰው ስላለው የሆነ ነገር የለም”

Lamentations 3:40

ወደ እግዚአብሔርም እንመለስ
“ወደ እግዚአብሔርም እንመለስ” የሚለው የሚወክለው ለእርሱ መገዛትን ነው። “እንደገና ለእግዚአብሔር እንገዛ”

ልባችንን ከእጆችን ጋር . . . በሰማይ እናንሣ
“እጅን ወደ ሰማይ ከፍ ማድረግ” የሚያሳየው ከልብ መጸለይን ነው። ለእስራኤላውያን እጅን ወደላይ ከፍ አድርጎ መጸለይ ልማድ ነበረ። “እጆችንን ወደ ላይ ከፍ አድርገን ከልባችን እንጸልይ” ወይንም “ወደላይ ከፍ ባለ እጅ ከልባችን እንጸልይ”

ዐምፀናል፤ ኀጢአትም ሠርተናል
ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ቃላት ሲሆኑ፤ “ማመጽ” እና “ኃጥያት” መስራት ሁለቱም እግዚአብሔር ላይ ማመጽ እንደሆኑ ያሳያል።

ራስህን በቊጣ ከደንህ
እዚህ ጋር ቁጣን እግዚአብሔር የሚደርበው ልብስ አድርጎ ይናገረዋል። ብዙውን ግዜ በዕብራይስጥ ስሜት እንደ ልብስ ይገለፃል። “እጅግ በጣም ተናደሃል”

ገደልኸን
“ብዙዎቻችንን ገደልኸን”

ያለ ርኅራኄም
“ርኅራኄ” የሚለው የሚያሳየው ማዘንን ነው። “አላዘንክልንም”

Lamentations 3:44

ጸሎት እንዳያልፍ፣ ራስህን በደመና ሸፈንህ
ይሄ የሚያመላክተው እግዚአብሄር ላለመስማት እንደወሰነ ነው። “ጸሎታችንን አልሰማም አልክ፤ ጸሎታችንም አንተ ጋር እንዳይደርስ በዙሪያህ ደመናን ሸፈንክ”

በአሕዛብ መካከል አተላና ጥራጊ አደረግኸን
ሊኖረው የሚችለው ትርጉም 1 እግዚአብሔር እስራኤላውያን በአሕዝብ ዘንድ ዋጋ ቢስ እንዲባሉ አደረክ። “አሕዛብ እንደ አተላ እና ቆሻሻ እንዲታሰቡ አደረክ” ወይንም 2) እግዚአብሔር ሕዝቡን በአሕዛብ መሃከል እንዲኖሩ ማድረጉ እንደ ቆሻሻ መጣል ነው። “እንደቆሻሻ በአሕዛብ መሃከል ጣልከን”

በችግርና በሸብር ተሠቃየን
“ችግር” እና ““ሸብር” ፥ “ጥፋት” እና “በመፈራረስ” የሚሉት በድርጊት መልኩ ሊገለፅ ይችላል። “እየተሸበርን ነው፤ ተጠምደናል እና እየፈረስን እና እየጠፋን ነው” ወይንም “ተሸብረናል ተጠምደናል። በአጠቃላይም ልንጠፋ ነው”

በችግር
ይሄ የሚያመላክተው ወደ ጉድጓድ መውደቅን ያመላክታል። በሁሉም መልኩ መጠመድን ያመላክታል።

በእኛ ላይ
“በእኛ ላይ የሆነው”

በጥፋትና በመፈራረስ፣
ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ቃላት ሲሆኑ፤ የእየሩሳሌምን መፍረስ ያመላክታሉ። “የሙሉ ለሙሉ ጥፋት”

Lamentations 3:48

የእንባ ጐርፍ ከዐይኔ ፈሰሰ
ጸሓፊው የተሰማውን ሃዘን እና ያለቀሰውን በማጋነን፤ እንደጎርፍ የሚያክል ለቅሶ እንዳለቀሰ ይገልጻል። “ውሃ በወንዝ እንደሚፈስ እምባዬ ከዓይኖቼ ይፈሳል”

ሕዝቤ አልቋልና
በቀጠታ መልኩ መገለፅ ይችላል። “ጠላቶቼ ሕዝቤን አጠፋ”

ያለ ዕረፍት፣ ያለ ማቋረጥ
ሁለቱም ቃላት ትርጉማቸው አንድ ዓይነት ነው። ጸሓፊው ማልቀሱን እንደቀጠለ እና ዓይኑን በማልቀስ ዕረፍት ባጣ ሰው ይወክለዋል። “ያለ ማቆም”

እግዚአብሔር ከላይ፣ ከሰማይ እስኪያይ ድረስ
ጸሓፊው እግዚአብሔር ቢያይ በሎ ምን ተስፋ እንደሚያደርግ በግልፅ ጽፏል። “እግዚአብሔር ከላይ፣ ከሰማይ ሕዝቡ ላይ የደረሰውን እስኪያይ ድረስ”

Lamentations 3:51

ማየቴ፣ ነፍሴን አስጨነቃት
ማየቴ የሚለው የሚወክለው የሚያየውን ነገር ነው። “የማየው ነገር ነፍሴን አስጨነቃት”

በከተማዬ ባሉት ሴቶች ሁሉ ላይ የደረሰውን
የከተማው ሴት ልጆች መከራን እየተቀበሉ መሆኑ ግልጽ ነው። “የከተማዬ ሴት ልጅ ች መከራን እየተቀበሉ ስለሆነ” ወይንም “የከተማዬ ሴት ልጆች መከራን ሲቀበሉ ስለማይ”

በከተማዬ ባሉት ሴቶች ሁሉ
ሊኖረው የሚችለው ትርጉም 1 የእየሩሳሌም ሴቶች ወይንም 2 በእየሩሳሌም የሚኖሩ ሁሉ

ያለ ምክንያት ጠላቶቼ የሆኑ፣ እንደ ወፍ አደኑኝ
ጸሓፊው ሰዎች የሚያድኑትን እንስሳ ለገድሉ እንደሚፈልጉ እርሱንም እንደ ሚፈልጉት ይናገራል። በቀጥታ መልኩ “የሚያድኑትን ወፍ እንደ ሚፈልጉ ጠላቶቼ ሊገድሉኝ ፈለጉኝ”

ሕይወቴን በጕድጓድ ውስጥ ሊያጠፉ
“ወደ ጉድጓድ ወረወሩኝ” ወይንም “ወደ ጉድጓድ ጣሉኝ”

ድንጋይም በላዬ አደረጉ
ሊኖረው የሚችለው ትርጉም 1 “ወደ እኔ ድንጋይን ወረወሩ” ወይንም 2 “ጉድጓዱን በድንጋይ ሸፈኑ”

ውሃ ሞልቶ በዐናቴ ላይ ፈሰሰ
“በጉድጓዱ ያለው ውሃ ከአናቴ በላይ ወጣ”

ጠፍቻለሁ ብዬ
“ጠፍቻለሁ” የሚለው መገደልን ይወክላል። በጣም ቶሎ መሞትን ያሳያል “ልሞት ነው”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Lamentations 3:55

የአንተን ስም ጠራሁ
የእግዚአብሔር ስም ማለት ባህሪውን ይወክላል። “ስም መጥራት” የሚለው የእግዚአብሔርን ባህሪ ማመንን እና መጣራትን የመላክታል።

በጥልቁ ጉድጓድ ውስጥ
ሊኖረው የሚችለው ትርጉም 1 ጸሓፊው የተወረወረበትን ጉድጓድ ያመላክታል “ከተወረወርኩበት ጉድጓድ ስር” ወይንም 2 ጸሓፊው በቅርብ እንዳይሞት ስለፈራ፤ ከሞቱ ሰዎች ጋር እንደሆነ አድርጎ ይናገራል “ከሙታን መሃከል”

ልመናዬን ሰምተሃል
“ልመና” የሚለው የተናገረውን ነገር ያሳያል። “ያልኩትን ሰማህ”

ጆሮህን አትከልክል
“ጆሮህን መከልከል” የሚለው ለመስማት አለመፈለግን ያመላክታል። “አልሰማም አትበል”

ቀረብኸኝ
ብዙውን ግዜ ሰዎች ሊረዱት የሚፈልጉትን ሰው ይቀርባሉ። “ቀረበኝ” የሚለው መርዳትን ያመለክታል “ረዳኸኝ”

Lamentations 3:58

ጌታ ሆይ፤ ለእኔ ተሟገትኽልኝ፤ ሕይወቴንም ተቤዠህ
እግዚአብሔር በፍርድ ፊት እንዳይሞት እንደተሟገተለት፤ ጸሓፊው እግዚአብሔር ጠላቶቹ እንዳይገሉት እንዳደረገ ይናገራል። “ሕይወቴን ከጠላቶቼ አዳንካት። በፍርድ ፊት እንደተሟገትክልኝ ነው”

ለእኔ ተሟገትኽልኝ፤
“ተሟገትክልኝ” የሚለው እርሱን ወክሎ እንደተከራከረለት ይናገራል። “ለእኔ ስትል ጉዳዬን ተከራከልክ”

ፍርዴን ፍረድልኝ
እዚህ ጋር እግዚአብሔር ጠበቃ መሆኑ ይቀርና ዳኛ ይሆናል። እግዚአብሔር ለእርሱ እንዲፈርድለት እየጠየቀ እንደሆነ ያስታውቃል። “ስለ እኔ ውሳኔን ወስን፤ እናም ትክክል እንደሆንኩኝ ለጠላቶቼ አስታውቅልኝ”

በቀላቸውን ሁሉ፣ በእኔም ላይ ያሰቡትን ዐድማ አየህ
“ስድባቸው” የሚለው ቃል እና ወይንም “ዕቅዳቸውን” የሚለው በድርጊታዊ ቃል ሊገለፅ ይችላል። “እንዴት እንደሰደቡኝ አይተሃል ምን ያህንም በእኔ ላይ እንደዶለቱ”

ስድባቸውን ሁሉ፣ በእኔ ላይ ያሰቡትን ዐድማ ሁሉ ሰማህ
“ስድባቸው” የሚለው ቃል “ፌዛቸው” ወይንም “ትንኮሳቸው” በሚለው ቃል ሊገለጽ ይችላል። ሊጎዱት ዕቅድ እንደነበራቸው በግልጽ ሊባል ይችላል። “እንዴ እንደተነኮሱኝ አይተሃል. . . ለእኔም የነበራቸውን ዕቅድ እንዲሁ” ወይንም “ሲያፌዙብኝ አይተሃል. . . ሊጎዱኝ ዕናቀዱብኝም እንዲሁ”

Lamentations 3:62

ይህም ቀኑን ሙሉ በእኔ ላይ፣ ጠላቶቼ የሚያውጠነጥኑትና የሚያንሾካሹኩት ነው
ጸሓፊው የጠላቶቹን ክስ ቀኑን ሙሉ ሊዋጋ እንደሚመጡ ጦሮች ያስመስለዋል። “ጠላቶቼ በእኔ ላይ ሲናገሩ እና ሲከሰኝ ይውላሉ”

ጠላቶቼ የሚያውጠነጥኑት
የሚያውጠነጥኑት የሚለው የሚሉትን ያሳያል። “የጠላቶቼ ቃላት”

ቆመውም ሆነ ተቀምጠው
ሁለቱ ድርጊቶች ሰዎች የሚያደርጉትን ነገር ይገልፃሉ። “የሚያደርጉት ሁሉ”

Lamentations 3:64

የሚገባውን መልሰህ ክፈላቸው
“መልሰህ ክፈላቸው” የሚለው መቀጣታቸውን ያሳያል። ያደረጉት ነገር በግልጽ ሊዘረዘር ይችላል። “ እግዚአብሄር ሆይ ባደረጉት መጠን ቅጣቸው” ወይንም “እግዚአብሔር ሆይ፤ እኔን አሳዝነውኛል እና እባክህ አሳዝናቸው”

በልባቸው ላይ መጋረጃን ዘርጋ
“ልብ” የሚለው የሰዎቹን ስሜት እና አመለካከት ብሎም “ኋፍረት ማጣት” ለማለት ሲሆን ትርጉም በኋጥያታቸው ማፈር ያለባቸውን ያህል አለማፈርን ያሳያል። አለማፈራቸውም እግዚአብሔር ይበልጥ እንዲቀጣቸው ያደርጋል። “ስለ ኋጥያታቸውም እንዳያፍሩ ታደርጋቸዋልህ”

ርግማንህም በላያቸው ይሁን
ርግማን የሚለው “መርገም” ወይንም “መኮነን” ሊባል ይችላል። “እርገማቸው” ወይንም “ኮንናቸው”

ከ . . . ሰማያት በታች
“ከሠማይ በታች” የሚለው “በምድር ላይ ያሉት ነገሮች በሙላ” ማለት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 ወርቁ ፈጽሞ ደበዘዘ፤ ንጹሁ ወርቅ ተለወጠ! የተቀደሱት ድንጋዮች በየመንገዱ ዳር ተበተኑ። **2** የጽዮን ልጆች የከበሩ፥ከንጹህ ወርቅ በላይ የሚቆጠሩ ነበሩ። አሁን ግን በሸክላ ሠሪ እጅ እንደተሠሩ የሸክላ ዕቃዎች እንጂ ከምንም አልተቆጠሩም። **3** ቀበሮዎች እንኳን ግልገሎቻቸውን ለማጥባት ጡቶቻቸውን ይገልጣሉ፥የሕዝቤ ሴት ልጅ ግን እንደ ምድረ በዳ ሰጎን ጨካኝ ሆነች። **4** ከጥም የተነሳ የሚጠባው ሕጻን ምላስ ከላንቃው ጋር ተጣበቀ፤ሕጻናት እንጀራ ለመኑ፥ ነገር ግን የሚሰጣችው የለም። **5** በውድ ዋጋ የሚገዛ ምግብ ይመገቡ የነበሩ ተጥለዋል፥ በየመንገዱ ተርበዋል፤ቀይ ግምጃ ይለብሱ የነበሩ አሁን በቆሻሻ ክምር መካከል ናቸው። **6** ምንም እጅ ሳይወድቅባት በድንገት ከተገለበጠች ከሰዶም ኃጢአት ይልቅ የሕዝቤ ሴት ልጅ ኃጢአት ታላቅ ነው። **7** መሪዎቿ እንደ በረዶ የሚያንጸባርቁ ነበሩ፥እንደ ወተትም ነጭ ነበሩ። ሰውነታቸው ከቀይ ዕንቁ ይልቅ ቀይ ነበረ፥ መልካቸውም እንደ ሰንፔር ነበረ። **8** አሁን ጨለማው ገጽታቸውን አጥቁሮታል፥ ቆዳቸው ከመነመኑ አጥንቶቻቸው ጋር ስለተጣበቀም በመንገዶች ላይ ማንነታቸው አልታወቀም። **9** በሰይፍ የተገደሉት በረሃብ ከሞቱት ይሻላሉ፥አንዳችም ሰብል ከእርሻ በመጥፋቱ በረሃብ ተወግተው ከተወገዱት ይሻላሉ። **10** የርኅሩኖቹ ሴቶች እጆች የገዛ ልጆቻቸውን ቀቀሉ፤ በሕዝቤ ሴት ልጅ የጥፋት ቀን እነዚህ ልጆች መብል ሆኑአቸው። **11** እግዚአብሔር ቁጣውን አረካ። ጽኑ ቁጣውን አፈሰሰ፤ በጽዮን እሳትን አያያዘ፥ መሠረትዋንም በላ። **12** የምድር ነገሥታት ወይም በዓለም ከሚኖሩ ማናቸውም፥ ባላጋራ ወይም ጠላት በኢየሩሳሌም በሮች ይገባል ብለው አላመኑም። **13** ነገር ግን የጻድቅን ደም በመካከልዋ ካፈሰሱ ከነቢያቶቿ ኃጢአትና ከካህናቷ በደል የተነሳ ይህን አደረጉ። **14** አሁን እነዚያ ነቢያትና ካህናት እንደ ዓይነ ስውራን ሰዎች በየጎዳናዎቹ ይቅበዘበዛሉ። ማንም ልብሶቻቸውን መንካት እስከማይችል ድረስ በደም ረክሰዋል። **15** «እናንተ ርኩሳን ለቃችሁ ሂዱ!» እያሉ በነቢያቱና ካህናቱ ላይ ይጮሁባቸዋል።«ለቃችሁ ሂዱ፥ለቃችሁ ሂዱ! አትንኩን!» ይሏቸዋል። ስለዚህ ወደ ሌላ ምድር ይቅበዘበዛሉ፥ ነገር ግን አሕዛብ እንኳን፥«ከእንግዲህ ወድያ በዚህ እንደ እንግዳ መኖር አይችሉም» ይላሉ። **16** እግዚአብሔር ከማደሪያው በትኖአቸዋል፥ ከእንግዲህ ወድያ ወደ እነርሱ በርኅራኄ አይመለከትም። ማንም ከእንግዲህ ወድያ ካህናቱን በምንም መልኩ አክብሮ አይቀበላቸውም፥ ለሽማግሌዎቹም ግድ አልተሰኙም። **17** የማይጠቅሙ ረዳቶችን እንኳ ለማግኘት ዓይኖቻችን ድከሙ፤ሊያድነን ወደማይችል ሕዝብ በጉጉት ተመለከቱ። **18** በመንገዶቻችን ሁሉ እርምጃዎቻችንን ተከታተሉ። ፍፃሜያችን መጥቶአልና መጨረሻችን ቀርቦአል፥ ቀኖቻችንም አልቀዋል። **19** አሳዳጆቻችን ከሰማይ ንስሮች ይልቅ ፈጣኖች ናቸው። በተራሮች ላይ አሳደዱን በምድረ በዳም ሸመቁብን። **20** በእግዚአብሔር የተቀባው ንጉሣችን፥ የአፍንጫችን እስትንፋስ፥ በጉድጓዳቸው ተያዘ፤«በአሕዛብ መካከል በጥበቃው ሥር እንኖራልን» ብለን የተናገርንለት ንጉሣችን ነበር። **21** በዖፅ ምድር የምትኖሪ የኤዶም ሴት ልጅ ሆይ፥ጽዋው ወደ አንቺም ያልፋልና ደስ ይበልሽ ሐሴትም አድርጊ። ትሰክሪያልሽ፥ እርቃንሽንም ትቀሪያልሽ። **22** የጽዮን ሴት ልጅ ሆይ በደልሽ ተፈጸመ። ከእንግዲህ ወዲያ በምርኮ አያኖርሽም። ነገር ግን የኤዶም ሴትልጅ ሆይ በደልሽን ይቀጣል። ኃጢአትሽንም ይገልጣል።

Lamentations 4:1

ወርቁ እንዴት ደበሰ! ንጹሑስ ወርቅ እንዴት ተለወጠ!
የእስራኤል ሕዝብን ማንፀባረቁን ባቆመ ወርቅ ይመስለዋል፣በዚህም ምክንያት ዋጋውን አጥቷል። “የእስራኤል ሕዝብ ማንፀባረቁን እንዳቆመ ወርቅ ነው፤ ውበቱን እንዳጣ ንጹህ ወርቅ ናቸው።”

ንጹሑስ ወርቅ እንዴት ተለወጠ!
ይህ ጸሓፊው ነተፈጠረው ነገር እንዴት እንዳዘነ በአንክሮ ሲገልፅ ነው።

የከበሩ ድንጋዮች፣ በየመንገዱ ዳር ተበታትነዋል
ቤተመቅደሱ በመፍረሱ የከበሩ ድንጋዮች በከተማው ተበትነዋል። የሰዎችንም መበተን የሚያሳይ ዘይቤአዊ አገላለጽ ሊሆ ን ይችላል።

በየመንገዱ ዳር
“መንገዶች በሚገጥምብቸው ቦታዎች በሙሉ” ወይንም “በ ሁሉም መንገዶች”

የከበሩ የጽዮን ወንዶች ልጆች
በከተማው ያሉ ሰዎች በከተማው ወንድ ልጆች ተመስለዋል። ሊኖሩትም የሚችሉት ትርጉም 1 የእየሩስሌምን ወጣት ወንዶች ብቻ ማለቱ ነው ወይንም 2 ሁሉንም በእየሩሳሌም ያሉ ሰዎች ለማለት ነው

የሸክላ ሠሪ እጅ እንደ ሠራው፣ እንዴት አሁን እንደ ሸክላ ዕቃ ሆኑ
ጸሓፊው የጽዮንን ልጆች ዋጋ ባጡ የሸክላ ዕቃዎች ይመስላቸዋል። “ሰዎች ዋጋ እንደሌላቸው የሸክላ ዕቃዎች ቆጠሯቸው”

Lamentations 4:3

ቀበሮዎች እንኳን ግልገሎቻቸውን ለማጥባት
ይሄ የቀበሮዎች ግልገሎቻቸውን ማጥባት ያሳያል

ቀበሮዎች
ኋይለኛ የዱር ውሾች

የወገኔ ልጅ ግን እንደ ምድረ በዳ ሰጎን
በእየሩሳሌም ያሉ ሰዎች ለልጆቻቸው ክፉ ስለሆኑ በሰጎን ተመስለዋል።

የወገኔ ልጅ
ይሄ ቅኔአዊ የእየሩሳሌም ስም ሲሆን ፣ እዚህ ጋር በሴት ይመስላታል።
“ሕዝቤ”

ሰጎን
እንቁላሎቻቸውን ትተው የሚሄዱ ትልቅ የወፍ ዝርያ።

Lamentations 4:4

ጡት የሚጠባው የሕፃን ምላስ ከጥም የተነሣ ወደ ትናጋው ተጣበቀ
“ከውሃ ጥም የተነሣ፣ የሕፃናት ምላስ ከላንቃቸው ጋር ተጣበቀ”

ይበሉ
“ይመገቡ”

በመንገድ ጠፉ
“እነኚህ ሰዎ ች ቤት የላቸውም ስለዚህም በየመንገዱ ላይ ተንከራተቱ”

ሐምራዊ ግምጃ ለብሰው ያደጉ
በቀጥታ መልኩ “በቀይ ግምጃ ለብሰው ያድጉ” ወይንም ”ሲያድጉ ሐምራዊ ግምጃ ይለብሱ የነበሩ“

ሐምራዊ ግምጃ
ይሄ ልብስ የሚወክለው ውድ፣ የከበረ እና ምቹ ልብስ ማለት ነው። ስለዛ ቢያንስ ከመሃከል ላይ ሓምራዊ ልብስ ነበረ። “የተቀማጠለ ውድ ልብስ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

“በዐመድ ክምር ላይ ተኙ”
የሚኖሩበት ቤት ስለሌላቸው ነው። “የፍግ ክምር አቀፉ”

Lamentations 4:6

ከሰዶም ኃጢአት ይልቅ የወገኔ ሴት ልጅ ኃጢአት በዛች
ኃጥያት የሚለው ቅጣት በሚለው ሊተካ ይችላል። “የወገኔ ሴት ልጅ ከሰዶም ይልቅ ተቀጣ”

የወገኔ ሴት ልጅ
ይሄ ቅኔአዊ የእየሩሳሌም ስም ሲሆን በሴት መስለዋታል።

ድንገት ከተገለበጠች
ተገለበጠች የሚለው ሰዶምን ነው። በቀጥታ መልኩም ሊገለፅ ይችላል፤ “እግዚአብሔር በቅጽበት እንዳጠፋት”

የማንም እጅ ሳይወድቅባት
በቀጥታ መልኩም ሊገለፅ ይችላል፤ “ማንም እጁን ሳያሳርፍባት”

የማንም እጅ ሳይወድቅባት
ሰዎች አንዳንድ ግዜ ሲጨንቃቸው እና ነገሮችን ማስተካከል ሲያቅጣቸው፥ እጃቸውን ያሻሉ ያስተካክላሉ። በውስጥ ታዋቂነት እሷ የሚለው፣ እየሩሳሌምን ነው። “ስለሷ ማንም አልገደደውም ”

Lamentations 4:7

አለቆችዋ ከበረዶ ይልቅ ጥሩ፥ ከወተት ይልቅ ነጭ ነበሩ
ሊኖረው የሚችለው ትርጉም 1 የእየሩሳሌም መሪዎች ጤነኛ ስለነበሩ ለመመልከት እራሱ የሚያምሩ ነበሩ ወይንም 2 መሪዎችዋ በህሊናቸው እንደ በረዶ ንፁህ እና እንደ ወተት የነጡ ናቸው።

አለቆችዋ
“የእየሩሳሌም መሪዎች”

ገላቸው ከቀይ ዕንቊ ይልቅ ቀይ ነበረ
“ሰውነታቸው ከቀይ ዕንቊ የቀላ” ይሄ ጤንነታቸውን ያመለክታል። “ሰውነታቸው ጤነኛ እና ቀይ ነበረ”

ከቀይ ዕንቊ
ጠንካራ ቀይ ከባህር የሚገኝ ለማስጌጥ የሚጠቅም ድንጋይ

ሰንፔር
ውድ ሰማያዊ ቀለም ያለው የከበረ ድንጋይ ለማጌጫነት የሚውል።

ፊታቸው ከጥቀርሻ ይልቅ ጠቊሮአል
ይሄ ሊሆን የሚችልበት ምክንያት ፡ 1 የመሪዎቻቸውን ቆዳ ፀሓይ አጥቁሮታል ወይንም 2 እየሩሳሌም ስትቃጠል የነካቸው ጭስ ፊታቸውን አጥቁሯቸዋል።

በመንገድም አልታወቁም
በቀጥታ መልኩ ፡ “ማንም አይቶ ሊለያቸው አልቻለም” ሊባል ይችላል።

ቁርበታቸው ወደ አጥንታቸው ተጣብቆአል
ከቆዳቸው ሥር ጮማም ሆነ ጡንቻ እንዳልነበረ ያሳያል።

ደርቆአል፤ እንደ እንጨት ሆኖአል
የደረቀው ቆዳቸው ከእንጨት ጋር ተመስሏል

Lamentations 4:9

በሰይፍ የሞቱ
“ሰይፍ” የሚለው የጠላታቸውን እነርሱን መውጋት ያመላክታል። በቀጥታ መልኩ “የጠላት ሰራዊት የገደላቸው” ሊባል ይችላል።

በራብ ከሞቱት
“ራብ” የሚያሳየው መራብን ነው። በቀጥታ መልኩ “በምግብ ማጣት የሞቱት” ሊባል ይችላል።

ደርቀው ያልቃሉ
“እጅግ በጣም የደረቁት እና የደከሙት”

እነዚህ የምድርን ፍሬ አጥተው ተወግተውም ቀጥነዋል
“የምድርን ፍሬ” የሚለው ስለ ምግብ መብላት የሚናገር ነው። የምግብ ማጣት ሰዎችን እንደሚወጋ ሰይፍ ተደርጎ ነው የተገለፀው። “ይበሉ ዘንድ በቂ ምግብ ስላልነበረ ነው የሞቱት”

የርኅሩኆች ሴቶች እጆች
እዚህ ጋር ሴቶቹ “በእጆች” ነው የተመሰሉት። እጅግ ተርበው ስለነበረ ድሮ በመልካምነት ይታወቁ የነበሩት እና ለልጆቻቸው ርህራሄን ያደርጉ የነበሩት፤ አሁን ልጆቻቸውን ለምግብነት ቀቀሏቸው። “ርህሩህ ሴቶች” ወይንም “ከዚህ በፊት ርህሩህ ሆነው የሚያውቁ ሴቶች”

መብል ሆኑአቸው
“ልጆቻቸው ለሴቶቹ ምግብ ሆኑ”

የወገኔ ሴት ልጅ
ይህ ቅኔአዊ የእየሩሳሌም ስም አገላለፅ ሲሆን፣እዚህ ጋር በሴት ይመስላታል። “ሕዝቤ”

Lamentations 4:11

እግዚአብሔር መዓቱን ፈጽሞአል፥ ጽኑ ቊጣውን አፍስሶአል
እግዚአብሔር በጣም ተቆጠቷል፤ መቆጣቱንም ለማሳያት ሁሉንም አድርጓል።

ጽኑ ቊጣውን አፍስሶአል
የእግዚአብሔር ሕዝቡን መቃጣት የእርሱ ቁጣ እየተቃጠለ በሚፈስ ፈሳሽ ተገልጿል። “እጅግ ከመናደዱ የተነሳ፤ ሕዝቡን ቀጣ” ወይንም “በታላቅ ቁጣ ለሕዝቡ ምላሽን ሰጠ”

እሳትን በጽዮን ውስጥ አቃጠለ
እግዚአብሔርን ሲወክል፤ እርሱም የእስራኤል ጠላቶች እሳትን እንዲጀምሩ አድርጓል። “በጽዮን እሳት እንዲጀምር አድርጓል ”

መሠረትዋንም በላች።
“መሠረትዋ” የሚለው የሚወክለው ሙሉ ከተማዋን ይወክላል፤ በስተመጨረሻ ሊፈርስ የሚችለውንም ክፍል ጨምሮ። “ከተማዋን ያቃጠለው፣እስከ መሰረትዋ”

Lamentations 4:12

የምድር ነገሥታት በዓለምም የሚኖሩ ሁሉ . . . አላመኑም
“የምድር ነገሥታት፣ ወይም ከዓለም ሕዝብ አንዳቸውም አላመኑም”

አስጨናቂና ጠላት
ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ቃላት ሲሆኑ ጸሓፊው ማስረገጥ የሚፈልገው እየሩሳሌምን ሊጎዱ የሚፈልጉ ጠላቶች እንዳሉ ነው። “ጠላቶችም ሆኑ ወራሪዎች” ወይንም “የትኛውም ዓይነት የእየሩሳሌም ጠላት”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ስለ ነቢያቶችዋ ኃጢአትና ስለ ካህናቶች በደል
ሁለቱ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ቃላት ናቸው። “ከነቢያት ኀጢአት፣ ከካህናቷም መተላለፍ የተነሣ”

የጻድቃንን ደም በውስጥዋ ስላፈሰሱ
ካህናቱም ነብያቱም ሰው በመግደል ወንጀለኞች ሆኑ። “ደም ማፍሰስ የሚለው” መግደልን ይወክላል። “የጻድቃንን ደም አፍስሰዋልና”

Lamentations 4:14

ታውረው በመንገድ ላይ ተቅበዘበዙ
ካህናቶቹ እና ነብያቱ የሚሄዱበትን ባለማወቅ በመንገድ ላይ ስለሚባዝኑ በዓይነ ስውር ተመስለዋል። “እንደ ዓይነ ስውር በመንገድ ላይ ይባዝናሉ”

በደም እጅግ ረክሰዋል
“ረክሰዋል” የ ሚለው በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ለማለት ነው። ካህናቶቹ እና ነብያቱ ሰዎችን የገደሉ በመሆናቸው በስርዓት ቆሽሸዋል፤ እግዚአብሔርንም ለማምለክ ወይንም ከሰዎች ጋር ለመሆን አይችሉም።

በደም እጅግ ረክሰዋል
“ባፈሰሱት ደም ረክሰዋል” ሊኖረው የሚችለው ትርጉም 1 ደማቸው በልብሳቸው ላይ አለ ወይንም 2 “ደም” የሚለው መግደልን ለማመልከት ነው

እናንተ ርኩሳን፣ ራቁ
“ሂዱ! እናንት ርኩሳን”

ርቃችሁም ሂዱ፣ አትንኩ
“ወግዱ! ወግዱ! አትንኩ”

Lamentations 4:16

በተናቸው
“ነብያት እና ካህናቱን በትኖአቸዋል”

ከእንግዲህ ወዲህ አይመለከታቸውም
“ከእንግዲህ ወዲያ አይጠብቃቸውም”

Lamentations 4:17

ዓይናችን ወደ ከንቱ ረዳታችን ገና ሲመለከት ጠፍቶአል
“በከንቱ ርዳታን ስንጠባበቅ፣ዐይኖቻችን ደከሙ”

ረዳታችን
“ርዳታን” ወይንም “ሠዎች እንዲረዱን”

በከንቱ
“ወደ ከንቱ”

ማዳን የማይቻለውን ሕዝብ ጠብቀናል
ሌላ ሕዝብ መጥቶ እንዲታደጋቸው ተስፋን አድርገው እንደነበረ ያሳያል። “ሊያድን ከማይችል ሕዝብ ርዳታ ጠበቅን”

ፍለጋችንን ተከተሉ
ጠላቶቻችን “እግር እግራችንን ተከታተሉን”

ፍጻሜያችን ቀርቦአል
“መጨረሻችን ቀርቦአል” ወይንም “ጠላቶቻችን በቅርቡ ያጠፉናል“

ፍጻሜያችን
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1 “መጨረሻችን” ከተማቸውን ሲያመላክት፣ ጠላቶቻቸው ከተማዋን ስለሚያጠፏት እና ስለሚማርኳቸው ሊኖሩባት አይችሉም፤ “መጨረሻችን” ወይንም ”ጥፋታችን“ 2 “ፍጻሜያችን” የሚለው የሕይወታቸውን ፍፃሜ ያሳያል፤ “ሞታችን” ወይንም “የመሞቻችን ግዜ”

ቀኖቻችንም ተቈጥረዋል
መቆጠር ማለት ትንሽ መሆንን ያሳያል። “ዕድሜያችን አልቆአል”

ፍጻሜያችን ደርሶአል
“ደርሷል” የሚለው ሊመጣ ይችል እንደነበረ እንደሚጠብቁት ያሳያል። “ፍጻሜያችን መጥቶአልና” ወይንም ”ጠላቶቻችን ይዋጉን ነበር“

Lamentations 4:19

ከሰማይ ንስሮች ይልቅ፣ ጠላቶቻችን ፈጣኖች ናቸው
አሳዳጆቻችን ከሰማይ ንስር ይልቅ ፈጣኖች ሆኑ። ንስር ሌላ እንስሳን ለማደን በጣም ፈጣን ናቸው። “የሚያሳድዱን ከንስር ይልቅ ፈጣን ናቸው”

በምድረ በዳ ሸመቁብን
“ሊያጠቁን አደቡብን”

የሕይወታችን እስትንፋስ
ይሄ ክፍል የሚናገረው ስለ ንጉሱ ነው። እስትንፋስ እንደ ሆነ ተመስሎ ይናገራል፤ እስትንፋስ ሰውነትን በሕይወት ያኖራል፥ እናም ንጉሱ እየገዛቸው እና ከጠላት እየጠበቃቸው ሕዝቡን በ ሕይወት ያኖራቸዋል። “እንደ እስትንፋሳችን የሆነው እርሱ” ወይንም “ሕይወታችንን የሚጠብቀው እርሱ”

በእግዚአብሔር የተቀባው
“መቀባት” የሚለው የሚወክለው ንግስናን ነው። እግዚአብሔር ንጉስ እንዲሆን የሚፈልገውን እንዲቀቡለት ተናግሯል። “እግዚአብሔር ንጉስ ይሆን ዘንድ እንዲቀባ የመረጠው ” ወይንም “እግዚአብሔ ር የመረጠው ንጉስ”

በወጥመዳቸው ተያዘ
“ወጥመዳቸው” የሚለው ጠላቶቹ ሊይዙ ያቀዱበትን ያሳያል። በቀጣታ መልኩም እንዲህ ሊገለጽ ይችላል፤ “በእቅዳቸው መሰረት ጠላቶቻችን የያዙት እርሱን ነው” ወይንም “ንጉሳችንን ለመያዝ ጠላቲቻችን እቅድን አወጡ፤ ደግሞም ያዙት ”

ብለን አስበን ነበር
ይሄ አባባል ስለንጉሱ ይበልጥ እንድናውቅ ያደርገናል። ንጉሱ ከመጠመዱ በፊት ያደርግልናል ብለው ተስፋ አድርገው የነበረውን ያሳያል። በቀጥታ መልኩም ሊገለፅ ይችላል፤ “ስለ እርሱ እንዲህ ብለን ቢሆንም ኖሮ ”

በጥላው ሥር በአሕዛብ መካከል እንኖራለን
“ጥላው” የሚለው የእርሱን ጥበቃ ያመለክታል። “በእርሱ ጥበቃ በአሕዛብ መሃከል እንኖራለን” ወይንም “በአሕዛብ መሃከል መኖር ቢኖርብንም፤ እርሱ ይጠብቀናል”

ደስ ይበልሽ፤ ሐሴትም አድርጊ
“ደስ” እና “ሓሴት” ማድረግ ማለት ተመሳሳይ ነገር ሲሆን የተደገመውም ጉዳዩ ላይ ትኩረት ለመስጠት ነው። ጸሓፊው እነኝህን ቃላት የሚጠቀመው ሰዎቹላይ እንደማፌዝ ነው። ኤዶማውያን በእስራኤል መፍረስ ደስ እንዲሚሰኙ ያውቃል። “እጅግ ደስ ይበላችሁ”

Lamentations 4:21

የኤዶምያስ ሴት ልጅ
በኤዶም ይኖሩ የነበሩ ሰዎች በሴት ተመስለዋል። የእስራኤላውያን ጠላቶች ነበሩ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ነገር ግን ለአንቺም ደግሞ ጽዋው ይደርስሻል
ጽዋ የሚለው የሚያሳየው ቅጣትን ነው። “ነገር ግን እግዚአብሔር እራሱ ይቀጣችኋል”

የጽዮን ልጅ ሆይ
የእየሩሳሌም ሰዎች በሴት ተመስለዋል።

ቅጣትሽ ያበቃል
“ቅጣትሽ ያበቃል” ቅጣት የሚለው ቃል በቀጥታ፥ በ“መቅጣት“ ሊተካ ይችላል። “እግዚአብሔር ይቀጣችኋል“

የስደትሽን ዘመን አያራ ዝምም
“እግዚአብሔር የስደትሽን ዘመን አያራ ዝምም” ወይንም እግዚአብሔር ከዚህ በላይ በስደት እንድትቆዪ አያደርግም“

ክፋትሽንም ይፋ ያወጣል
በሌሎች የማይታወቁ ኃጥያቶች በሆነ ነገር እንደተሸፈኑ ናቸው። መሸፈኛውን ማንሳት ማለት ሌሎች ሰዎች እንዲያውቁት ማድረግ ማለት ነው። “ኃጥያትሽን ይገልጠዋል“ ወይንም “ኃጥይት እንደሰራሽ ሌሎች ሰዎች እንዲያውቁ ያደርጋል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 5

1 እግዚአብሔር ሆይ የሆነብንን አስብ። እፍረታችንን እይ፥ተመልከትም። **2** ርስታችን ለእንግዶች፥ ቤቶቻችን ለባዕዳን ታልፈው ተሰጡ። **3** አባቶች ስለሌሉ፥ እናቶቻችንም መበለቶች ስለሆኑ ወላጅ አልባ ሆን። **4** ለመጠጣት ውኃችን የብር ዋጋ ጠየቀ፥ የገዛ እንጨታችንም ተሸጠል ን። **5** ጠላቶቻችን ያሳድዱናል፥ አንገታችንም ላይ ደርሰዋል። እኛ ደክመናል፥ ዕረፍትም የለንም። **6** ምግብ ለመጥገብ ለግብፃውያንና ለአሦራውያን እጃችንን ሰጠን። **7** አባቶቻችን ኃጢአት ሠሩ፤ እነርሱ የሉም፥እኛ ግን ኃጢአታቸውን ተሸከምን። **8** ባሮች ይገዙናል፥ ከእጃቸውም የሚያድነን የለም። **9** ከምድረ በዳው ሰይፍ የተነሳ እንጀራ ለማግኘት በሕይወታችን ፈረድን። **10** ቆዳችን እንደ ምድጃ ሆኖአል፥ ከረሃቡ ትኩሳት የተነሳ ተቃጥሎአል። **11** በጽዮን ሴቶችን፥ በይሁዳ ከተሞች ደናግላንን ደፈሩ። **12** በገዛ እጆቻቸው ልዑላኑን ሰቀሉ፥ሽማግሌዎችንም አላከበሩም። **13** ኃያላን ወንዶችን ወደ ወፍጮ ቤት አመጡአቸው፥ ወጣት ወንዶችም ከእንጨት በታች ተንገዳግዱ። **14** ሽማግሌዎችን ከከተማይቱ ደጅ፥ ኃያላን ወንዶችንም ከዘፈናቸው አስወገዷቸው። **15** የልባችን ደስታ ተወግዶአል፥ ጭፈራችንም ወደ ለቅሶ ተለውጦአል። **16** አክሊል ከራሳችን ወድቋል! ወዮልን! ኃጢአት ሠርተናልና! **17** ልባችን ታምሞአል፥ዓይኖቻችንም ፈዝዘዋል፤ **18** ምክንያቱም ባድማ በሆነችው በጽዮን ተራራ ላይ ቀበሮዎች ፈንጭተውበታልና። **19** ነገር ግን አንተ እግዚአብሔር ነህ፤ ለዘላለም ትገዛለህ፥ ዙፋንህ ከትውልድ እስከ ትውልድ ነው። **20** ስለ ምን ለዘላለም ትረሳናለህ? ለረዥም ዘመናትስ ትተወናለህን? **21** እግዚአብሔር ሆይ፥ወደ አንተ መልሰን፥እኛም ንስሐ እንገባልን። ቀኖቻችንን እንደ ጥንቱ ዘመን አድስ፥ **22** ፈጽመህ ካልጣልከንና እጅግም ካልተቆጣኽን።

Lamentations 5:1

አቤቱ፥ የሆነብንን አስብ
“አስብ” የሚለው ዘይቤአዊ አገላለፅ ነው። “አቤቱ፥ የሆነብንን አስታውስ”

ተመልከት ስድባችንንም እይ
“ውርደታችንን እይ፤ ተመልከትም”

ርስታችን ለመጻተኞች፣ ቤቶቻችን ለባዕዳን ዐልፈው ተሰጡ
በቀጠተኛ አገላለፅም ሊቀመጥ የሚችል ዓረፍተ ነገር ነው። “ርስታችን ለእንግዶች፥ ቤቶቻችን ለሌሎች አሳልፈህ ሰጠህ” ወይንም “ርስታችን ለእንግዶች፥ ቤቶቻችን ለሌሎች ታልፈው እንዲሰጡ ፈቀድክ።

ወላጅ አልባና አባት የሌላቸው ሆንን ፤ እናቶቻችን እንደ መበለቶች ሆኑ
የእየሩሳሌም ሰዎች ለጠብቃቸው የሚችል ማንም የለም፤ ምክንያቱም ወንዶች ልጆቻቸው ወይ በጦርነት ላይ ሞተዋል አልያም ደግሞ በምርኮ ተወስደዋል። ይህ ደግሞ የሚያመላክተው በእስራኤል የቀሩት ወላጅ አልባዎች እና መበለቶች መሆናቸውን ነው።

ወላጅ አልባና አባት የሌላቸው
እነኚህ ቃላት አንድ አይነት ትርጉም ሲኖራቸው፤ አባት የሌላቸው ሰዎችን ያመላክታል

ውኃችንን በብር ጠጣን እንጨታችንን በዋጋ ገዛን
ይህ የሚያሳየው በአንድ ግዜ በነፃ ይጠቀሙ የነበሩትን ውሃ እና እንጨት ጠላቶቻቸው እያስከፈሏቸው እንደሆነ ነው። “የራሳችን የሆነውን ውሃ ለመጠጣት እና የራሳችንን እንጨት ለመጠቀም መክፈል አለብን”

እንጨታችንን በዋጋ ገዛን
ይሄ በቀጥታ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። “ጠላቶታችን የገዛ እንጨታችንን ይሸጡልናል”

Lamentations 5:5

አሳዳጆቻችን
“የሚያሳድዱን ጠላቶቻችን” ይሄ የሚያመላክተው ባቢሎናውያንን ነው።

ዕረፍትም የለንም
ይህ አባባል “ዕርፍትን” ተፈልጎ እንደሚገኝ ቁስ አድርጎ ይገልፀዋል። “ማረፍ አልቻልንም”

እንጀራ እንጠግብ ዘንድ፣ ለአሦርና ለግብፅ እጃችንን ሰጠን
”ሰጠን“ የሚለው ዘይቤአዊ አገላለፅ ነው። “የምንበላውን እናገኝ ዘንድ ከአሦርና ከግብፅ ጋር ስምምነትን አደረግን” ወይንም “በሕይወት እንኖር ዘንድ እንድንበላ ዘንድ ለአሦርና ለግብፅ ተማርከናል”

የሉም
ይህ የሚያመላክተው መሞታቸውን ነው። “አለፉ” ወይንም “ሞተዋል”

እኛም በደላቸውን ተሸከምን
“በደል” የሚለው ከአባቶቻቸው ኃጥያት ምክንያት የመጣ ቅጣትን ያመላክታል። ”የኃጥያታቸውን ቅጣት ተሸክመናል“

Lamentations 5:8

ባሪያዎች ሠልጥነውብናል
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1 “በእኛ ላይ እየሰለጠኑ ያሉት እራሳቸው በባቢሎን ሐገር ጌቶች ያላቸው ሰዎች ናቸው።” 2 በባቢሎን ሃገር ባርያ የነበሩ ሰዎች ናቸው አሁን በእኛ ላይ የሰለጠኑት“

ከእጃቸው የሚታደገን
“እጅ” የሚለው ቃል የሚያመላክተው ቁጥጥርን ነው። “ከቁጥጥራቸው የሚታደገን”

እንጀራ
“እንጀራ” የሚለው በአጠቃላይ ምግብን ነው የሚያመላክተው። “ምግብ”

ከምድረ በዳ ሰይፍ የተነሣ
በሰይፍ የሚገድሉ ወንበዴዎች ናቸው ሰይፍ ተበለው የተገለፀው “በምድረበዳ በሰይፍ የሚገድሉ ወንበዴዎች ስላሉ”

ከሚያቃጥል ከራብ ትኩሳት የተነሣ ቁርበታችን እንደ ምድጃ ጠቁረ
ይሄ የሚያመላክተው ከሰዎቹ የቆዳ ትኩሳት የተነሳ ሰውነታቸው ተቃጥሏል። ከረሃባቸው የተነሳ ትኩሳት ይዟቸዋል። “ቆዳችን የምጣድ ያህል ያተኩሳል፤ መቃጠላችንም ከረሃባችን የተነሳ ነው”

Lamentations 5:11

ሴቶች በጽዮን፣ ደናግል በይሁዳ ከተሞች ተደፈሩ
ሁለቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው፤ ማለት የሚፈልጉትም የሴቶቻቸው ክብር መነካቱን ነው። ተደፈሩ የሚለውም ለጽዮን ሴት ልጆችም ለደናግሎቹም ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሴቶች ... ደናግል ... ተደፈሩ
በቀጥታም አገላለፅ ለቀመጥ ይችላል፤ “ጠላቶቻችን ሴቶቻችንን ደፈሩ. . . ድንግሎቻችንንም” ወይንም “ጠላቶቻችን የሴቶቻችንን ክብር ነክተዋል . . . የደናግሎቻችንንም“

አለቆች በእጃቸው ተሰቀሉ
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1 “እነርሱ” የሚለው በውስጥ ታዋቂ ያለው ቃል የሚናገረው ስለጠላቶ ቻቸው ነው ፤ “በእነርሱ እጅ አለቆች ተሰቀሉ” 2 የአለቆቹን እጆች አስረው፤ እግራቸውን ከመሬት ከፍ አርገው አንጠልጥለው አሰሯቸው።

ሸማግሌዎችም አልተከበሩም
በቀጠታ መልኩም ሊገለፅ ይችላል፤ “ለሸማግ ሌዎቹም ምንም ክብር አላሳዮአቸውም”

Lamentations 5:13

ጐልማሶች ... ተገደዱ
ይህ በቀጠታ መልኩም ሊገለፅ ይችላል፤ “ጎልማሶቹንም አስገደዷቸው”

ወንዶች ልጆች በዕንጨት ሸክም ተንገዳገዱ
ወንዶች ልጆች የዕንጨት ሸክም እንዲሸከሙ ተገደዱ። “ከባድ የእንጨት ሸክም በመሸከማቸው ወንዶች ልጆች ተንጎደጎዱ” ወይንም “ወንዶች ልጆች የዕንጨት ሸክም እንዲሸከሙ በመገደዳቸው ተንጎደጎዱ”

ከከተማዪቱ በር
ሸማግሌዎች ሕጋዊ ምክር የሚሰጡበት ቦታ ሲሆን፤ ሰዎችም ለማህበራዊ ግንኙነቶች ይገናኙበታል።

ጐልማሶች ዝማሬያቸውን አቁመዋል
በከተማይቱ በር ላይ በሚደረጉ ማህበራዊ ግንኙነቶች ላይ ሙዚቃ መጫወት አንዱ ልማድ ሲሆን፤ አሁን ግን ጎልማሶቹ ትተዉታል። “ ጐልማሶች ሙዚቃ መጫወት አቁመዋል”

Lamentations 5:15

የልባችን ደስታ
”ልብ” የሚለው ሙሉ ሰውነትን ሲያመላክት ስሜትን ግን በይበልጥ ያመላክታል። “ደስታችን”

አክሊል ከራሳችን ወድቆአል
ሊኖረው የሚችለው ትርጉም፤ 1 ለበዓል በራሳችን ላይ አበባን አናደርግም ወይንም 2 “አክሊል” የሚለው የሚያመላክተው ንጉሶቻቸውን ሲሆን “ራስ” የሚለው ደግሞ የሥልጣን ቦታን ያሳያል። “ንጉስ አልባ ሆነናል።”

Lamentations 5:17

ከዚህ የተነሣ ልባችን ደከመ
“ልብ” የሚለው ስሜትን ሲያመላክት፤ በስሜት የመታመም ያህል ተስፋ መቁረጥን ያሳያል። “በዚህም ምክንያት ተስፋ ቆርጠን ነበር”

ከእነዚህ የተነሣም ዐይናችን ፈዘዘ
ከማልቀሳቸው የተነሳ ማያት አቃታቸው። “እንባ ከመሙላታቸው የተነሳ ማያት አልቻልንም”

ስለ ጽዮን ተራራ፥ ባድማ ሆናለችና
ባዶዋን የቀረችው የጽዮን ተራራ

ቀበሮች
እነዚህ ኋይለኛ የዱር ውሾች ናቸው።

Lamentations 5:19

አንተ ለዘላለም ትገዛለህ
ይሄ የሚያመላክተው ንግስናን እና መግዛትን ነው። “እንደ ንጉስ ግዛ ”

ከትውልድ እስከ ትውልድ
ዘይቤአዊ አገላለጽ ሲሆን። “ሁልግዜ” ለማለት ነው

ለምን ፈጽመህ ትረሳናለህ? ስለምንስ ለረዥም ጊዜ ትተወናለህ?
እግዚአብሔር እረስቶናል የሚለውን ሃሳብ ለማስተለለፍ ጸሓፊው ምልሽ የማይሰጠው ጥያቄን ይጠይቃል። በዓረፍተ ነገር መልኩም ሊጻፍ ይቻላል። “ለዘላለም ልትረሳን የመስላል፤ ተመለሰህም ለረጅም ግዜ ላትመጣ።”

ወደ አንተ መልሰን
”ወደራስህ መልሰን“

ዘመናችንን እንደ ቀድሞው አድስ
ዘመናችን የሚለው ሕይወታቸውን ነው። “ሕይወታችንን ቀድሞ እንደነበረው መልካም አድርገው” ወይንም “ቀድሞ ታላቅ እንደነበርነው ታላቅ አርገን”

ፈጽመህ ካልጣልኸን፣ ከመጠን በላይ ካልተቈጣኸን
ሊኖር የሚችለው ትርጉም፤ 1 ጸሓፊው እግዚአብሔር አይመልሳቸው ዘንድ ተቆጥቶ እንዳይሆን ፈርቷል ወይንም 2 ጸሓፊው ማለት የፈለገው እግዚአብሔር እጅግ በጣም ስለተቆጣ አይመልሳቸውም

ከመጠን በላይ ካልተቈጣኸን
ይህ የሚያመላክተው የእግዚአብሔርን ሊለካ የማይችን የህል የተለቀ ቁጣ ነው። የማጋነን ዓይነት አገላለለፅ ነው። “እጅግ ተቆጣኸን”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Ezekiel

Ezekiel

Chapter 1

1 በሰላሳኛው ዓመት ክአመቱም በአራተኛው ወር ከወሩም በአምስተኛው ቀን በኬብሮን አጠገብ ከምርኮኞቹ ጋር አብሬ እየኖርኩኝ ሳለሁ ሰማያት ተክፍተው
የእግዚአብሔርን ራዕይ አየሁ። 2 ንጉስ ኢዮአኬም በተማረከበት በአምስተኛው ቀን በከለዳዊያን አገር በኬብሮን ወንዝ አጠገብ 3 የእግዚአብሔር ቃል ወደ ካህኑ
ወደ ኡዝ ልጅ ወደ ሕዝቅኤል በኃይል መጣ። የእግዚአብሔር እጅ በእኔ ላይ ነበረች። 4 እኔም በውስጡ የእሳት ነበልባል ያለበት ዙሪያውና ውስጡ የሚያበራ
ታላቅ ደመና የሚመስል አውሎ ነፋስ ከሰሜን አቅጣጫ ሲመጣ አየሁ፣ በደመናው ውስጥ ያለው እሳት ቀለሙ ቢጫ ነበር። 5 መካከል ላይ የአራት ህያዋን
ፍጡራን ምስል ነበር። ፍጥረታቱ የሰው መልክ ነበራቸው፣ 6 ነገር ግን እያንዳንዳቸው አራት አራት ፊቶችና አራት አራት ክንፎች ነበሩዋቸው። 7 እግሮቻቸው ቀጥ
ያሉ ነበሩ፣ ነገር ግን የእግሮቻችው ኮቴ እንደ ነሀስ የሚያበራ የጥጃ ኮቴ ያለ ነበር። 8 ከክንፎቻቸው ስር በአራቱም አቅጣጫ የሰው እጅ ነበራቸው። 9
በክንፎቻቸው ተነካክተው ወደ ኋላ ሳይገላመጡ ቀጥ ብለው ወደፊት ይራመዱ ነበር። 10 መልካቸውም በአንድ በኩል የሰው፥ በቀኝ በኩል የአንበሳ፣ በግራ
በኩል የበሬና በሌላ በኩል ደግሞ የንስር ነበር። 11 መልካቸው ያንን ይመስል ነበር፣ ክንፎቻቸውም ተዘርግተው ነበር፣ በሁለት ክንፎቻቸው እርስ በርሳቸው
ተነካክተው ነበር፣ በሁለት ክንፎቻቸው ደግሞ ሰውነታቸውን ይሸፍኑ ነበር። 12 እያንዳንዳቸው ሳይገላመጡ ወደፊት ይራመዱ ነበር፣ መንፈስ ወደመራቸው
ሳይገላመጡ ይሄዱ ነበር። 13 ህያዋን ፍጡራን የከሰል ፍም እሳት ወይም ችቦ ይመስሉ ነበር፣ ከህያዋን ፍጡራኑ ጋር ደማቅ እሳት ይንቀሳቀስ ነበር፣ የመብረቅ
ብልጭታዎችም ነበሩ። 14 ህያዋን ፍጡራኑ በዝግታ ወደ ኋላና ወደ ፊት ይንቀሳቀሱ ነበር፣ እንደ መብረቅም ነበሩ። 15 ወዲያውም ወደ ህያዋን ፍጥረታቱ
ተመለከትኩ፣ በምድር ላይ ከእያንዳንዱ ፍጡር አጠገብ አንዳንድ መንኮራኩር ነበረ። 16 የመንኮራኩረቹ መልክ የሚከተለውን ይመስል ነበር፡ እንደ ብርሌ
ያንጸባርቁ ነበር፣ አራቱም አንድ አይነት ነበሩ፣ አንዱም በአንዱ ላይ የተስካ ይመስል ነበር። 17 መንኮራኩሮቹ በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ ፍጡራኑ ወደየትኛውም
አቅጣጫ ሳይገላመጡ ይሄዱ ነበር። 18 ዙሪያውን በዓይን የተሞላ ስለሆነ የመንኮራኩሮቹ ጠርዝ ርጅምና አስፈሪ ነበር። 19 ህያዋን ፍጡራኑ በሚንቀሳቀሱበት
ጊዜ መንኮራኩሮቹ አብረው ይንቀሳቀሱ ነበር፣ ህያዋን ፍጥረታቱ ወደ ላይ ከፍ ሲሉ መንኮራኩሮቹም ከፍ ይሉ ነበር። 20 መንፈስ ወደሚሄድበት ሁሉ ይሄዱ
ነበር፣ የህያዋን ፍጡራኑ መንፈስ ስላለባቸው መንኮራኩሮቹ አብረው ወደ ላይ ከፍ ይሉ ነበር። 21 የፍጡራኑ መንፈስ ስላለባቸው ፍጡራኑ ሲሄዱ
መንኮራኩሮቹም ከአጠገባቸው ይሄዱ ነበር፣ ሲቆሙ እነርሱም ይቆሙ ነበር፣ ከምድር ወደ ላይ ከፍ ሲሉ እነርሱም ከፍ ይሉ ነበር። 22 ከህያዋን ፍጡራኑ ራስ
በላይ ጠፈር የሚምስል ነገር ነበረ፤ ያም ጠፈር የሚመስል ነገር በህያዋን ፍጡራኑ ራስ በላይ እንደ አስፈሪ በረዶ ዙሪያቸውን ነበረ። 23 ከጠፈሩ በታች
የእያንዳንዱ ህያው ፍጡር ክንፍ ቀጥ ብሎ ተዘርግቶ የአንደኛው ፍጡር ክንፍ ከሌላው ፍጡር ክንፍ ጋር ተነካክቶ ነበር። እያንዳምዱ ፍጡር ሰውነቱን
የሚሸፍንበት ሁለት ክንፍ ነበረው። 24 ህያዋን ፍጡራኑ በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ ሁሉ የክንፎቻቸው ድምጽ ይሰማኝ ነበር፣ ድምጹም እንደ ውሃ ጎርፍ፣እንደ ህያው
አምላክ ድምጽ፣ እንደ ሠራዊት ድምጽ፣ እንደ ዝናብ ውሽንፍር ነበረ! በሚቆሙበት ጊዜ ክንፎቻችውን ያጥፉ ነበር። 25 በሚቆሙበትና ክንፎቻቸውን
በሚያጥፉበት ጊዜ ከራሶቻቸው በላይ ካለው ጠፈር ድምጽ ይመጣ ነበር። 26 ከራሶቻቸው በላይ ከሚገኘው ጠፈር በላይ ዕንቁ የሚመስል የዙፋን አምሳያ
ነበር፣ በዙፋኑም አምሳያ ላይ ሰው የሚመስል ተቀምጦ ነበር። 27 ከወገብ በላይ በእሳት የጋለ ብረት ከወገቡ በታች ደግሞ እሳት የሚመስል ምስል አየሁ። 28
በዝናብ ጊዜ እንደሚታይ ቀስተ ደመና ይመስል ዙሪያውም ደማቅ ብርሀን ነበረ። ባየሁትም ጊዜ በግንባሬ ተደፋሁ፣ ወዲያውም የሚያናግረኝ ድምጽ ሰማሁ።

Ezekiel 1:1

በሠላሳኛው ዓመት
ይህ የሕዝቅኤል ሠላሳኛው ዕድሜ ነው። (ደረጃን የሚያሳይ ቁጥር የሚለውን ተመልከት)

አራተኛው ወር፣ የወሩም አምስተኛው ቀን
“የአራተኛው ወር አምስተኛው ቀን”። ይህ በዕብራውያን የቀን አቆጣጠር አራተኛው ወር ነው። በምዕራባውያኑ አቆጣጠር አምስተኛው ቀን የሰኔ ወር መጨረሻ አካባቢ ነው። (የዕብራውያን ወራት እና ደረጃን የሚያሳይ ቁጥር የሚለውን ተመልከት)

እንዲህ ሆነ
እዚህ ጋ ይህ ሐረግ ጥቅም ላይ የዋለው በታሪኩ ውስጥ አስፈላጊ የሆነውን ሁነት ለማመላከት ነው። የአንተ ቋንቋ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ ጋ መጠቀም እንደምትችል አስብ።

በምርኮኞቹ መካከል እኖር ነበር
“እኔ” የሚለው ቃል ሕዝቅኤልን ያመለክታል። “እኔ ከምርኮኞቹ አንዱ ነበርኩኝ”

የእግዚአብሔርን ራዕዮች አየሁ
“እግዚአብሔር ያልተለመዱ ነገሮችን አሳየኝ”

ንጉሡ ዮአኪን የተማረከበት አምስተኛ ዓመት ነበር
በመጽሐፉ ሁሉ፣ ሕዝቅኤል ትንቢቶቹን መናገር የሚጀምረው ዮአኪን ኢየሩሳሌምን ለቆ እንዲሄድ ባቢሎናውያን ካስገደዱት ጊዜ ጀምሮ ነው።

ወደ ሕዝቅኤል ... በዚያ በእርሱ ላይ
ሕዝቅኤል ሌላ ሰው ይመስል ስለ ራሱ ይናገራል። አ.ት፡ “ወደ እኔ ወደ ሕዝቅኤል ... በዚያ በእኔ ላይ” (ተውላጾ ስም የሚለውን ተመልከት)

የእግዚአብሔር ቃል ወደ ሕዝቅኤል መጣ
“የእግዚአብሔር ቃል ወደ -- መጣ” የሚለው የአነጋገር ዘይቤ ጥቅም ላይ የዋለው ከእግዚአብሔር የመጣውን ልዩ መልዕክት ለማሳወቅ ነው። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ለሕዝቅኤል መልዕክት ሰጠው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ቡዝ
የአንድ ሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የኮቦር ቦይ
ይህ ከለዳውያን የአትክልት ቦታቸውን ለማጠጣት የቆፈሩት ወንዝ ነው። “የኮቦር ወንዝ”

የእግዚአብሔር እጅ በእርሱ ላይ ነበረች
አብዛኛውን ጊዜ “እጅ” ጥቅም ላይ የዋለው የአንድን ሰው ኃይል ወይም ተግባር ለማመልከት ነው። አንድ ሰው እጁን በሌላው ላይ ሲያደርግ፣ በዚያ ሰው ላይ ኃይል ይኖረዋል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር እየተቆጣጠረው ነበር” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ያህዌ
ይህ በብሉይ ኪዳን ራሱን ለሕዝቡ የገለጠበት የእግዚአብሔር ስም ነው። ይህንን እንዴት መተርጎም እንደሚኖርብህ ለማወቅ ስለ እግዚአብሔር የቃል ገጽን ትርጉም ተመልከት።

Ezekiel 1:4

ዐውሎ ንፋስ
ይህ ከፍተኛ የንፋስ ግፊት ያለበት ዐውሎ ነው።

ከሰሜን ይመጣ ነበር
ሰሜን ማለት ፀሐይ ስትወጣ በምታያት ጊዜ በስተግራህ ያለ አቅጣጫ ማለት ነው።

በውስጡ እሳት የሚነድበት ታላቅ ደመና
ይህ እንደ አዲስ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። “ዐውሎው በውስጡ እሳት የሚነድበት በጣም ታላቅ ደመና ነበረው”

እሳት የሚነድበት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “የመብረቅ ብልጭታ” ወይም 2) “የማያቋርጥ መብረቅ” የሚሉት ናቸው።

ብሩህነት ዙሪያውን ከቦት እና ውስጡን ሞልቶት
“በጣም ብሩህ የሆነ ብርሃን በደመናው ዙሪያና በውስጡም ነበር”

የሙጫ መልክ
“እንደ ሙጫ ያለ ብሩህ ቢጫ” ወይም “ብሩህ ቢጫ” ወይም “ደማቅ ቢጫ”

ሙጫ
ጌጣ ጌጥን ለማስዋብ ጥቅም ላይ የሚውል ደማቅ ቢጫ ሙጫ

በመካከል
“በዐውሎው መካከል”

የአራት ሕያው ፍጡር አምሳያ
እዚህ ጋ የነገር ስም የሆነው “አምሳያ” ትርጉሙ ሕዝቅኤል ያያቸውን እንደ እነዚህ ያሉ ነገሮችን የሚመስሉትን ነው። ቃሉ ከግሣዊ ሐረግ ጋር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “አራት ሕያዋን ፍጡራንን የሚመስሉ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

መልካቸው ይህንን ይመስል ነበር
የነገር ስም የሆነው “መልክ” እንደ ግሣዊ ሐረግ ሆኖ መተርጎም ይችላል። አ.ት፡ “ይህንን ይመስሉ ነበር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

የሰው መልክ ነበራቸው
የነገር ስም የሆነው “መልክ” እንደ ግሣዊ ሐረግ ሆኖ መተርጎም ይችላል። አ.ት፡ “አራቱ ፍጡራን ሰዎችን ይመስሉ ነበር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ሆኖም እያንዳንዳቸው አራት ፊት ነበራቸው፣ ለእያንዳንዱ ፍጡርም አራት ክንፍ ነበራቸው
“ሆኖም እያንዳንዳቸው አራት የተለያየ ፊትና አራት ክንፍ ነበራቸው”። እያንዳንዱ ፍጡር በፊት ለፊቱ፣ በስተኋላውና ከራሱ ሁለት ወገን ላይ ፊት ነበረው።

Ezekiel 1:7

ሆኖም የእግሮቻቸው መዳፍ የጥጃ ኮቴዎችን ይመስል ነበር
“ሆኖም እግሮቻቸው የጥጃ ኮቴዎችን ይመስሉ ነበር” ወይም “ሆኖም እግሮቻቸው የጥጆችን እግር ይመስል ነበር”

የጥጃ ኮቴዎች
የጥጃ እግር ጠንካራው ክፍል

እንደ ተወለወለ ነሐስ ያብለጨልጭ ነበር
“እንደ ተወለወሉ ነሐሶች ያብለጨልጩ ነበር”። ይህ የፍጡራኑን እግሮች ይገልጻል። አ.ት፡ “እንደ ተወለወለ ነሐስ ያብለጨልጩ ነበር”

በአራቱም በኩል
“በአካላቸው በአራቱም በኩል”

የአራቱም ፊታቸውና ክንፎቻቸው ይህንን ይመስል ነበር
“የአራቱ ፍጡራን ክንፎችና እግሮች ይህንን ይመስል ነበር”

በሚሄዱበት ጊዜ ዘወር አይሉም ነበር
“ፍጡራኑ በሚጓዙበት ጊዜ ዘወር አይሉም ነበር”

Ezekiel 1:10

የፊታቸው መልክ የሰውን ፊት ይመስል ነበር
ሕዝቅኤል የፍጡራኑን የፊት ለፊት ገጽታቸውን ይገልጻል። የነገር ስም የሆነው “መልክ” ማለት ለሕዝቅኤል የሰው ፊት መስሎ የታየው ነው። ቃሉ ወደ ግሣዊ ሐረግ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “የእያንዳንዱ ፍጡር ፊት የሰውን ፊት ይመስል ነበር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

በስተቀኛቸው አራቱም የአንበሳ ፊት ነበራቸው
“በእያንዳንዳቸው ራስ በስተቀኝ ያለው ፊታቸው የአንበሳ ፊት ይመስል ነበር”

በስተግራቸው አራቱም የበሬ ፊት ነበራቸው
“በእያንዳንዳቸው ራስ በስተግራ ያለው ፊታቸው የበሬ ፊት ይመስል ነበር”

አራቱም የንስር ፊት ደግሞ ነበራቸው
“በእያንዳንዳቸው ራስ በስተኋላ ያለው ፊታቸው የንስርን ፊት ይመስል ነበር”

እያንዳንዱ ፍጡር የሌላውን ፍጡር ክንፍ የሚነኩ ጥንድ ክንፎች ነበሩት፣ ክንፎቻቸው ወደ ላይ ተዘርግቶ ነበር
“እያንዳንዱ ፍጡር ሁለት ክንፎች ነበሩት፣ አንደኛው ክንፉ በአንድ በኩል ያለውን ፍጡር ክንፍ ይነካ ነበር፣ ሌላኛው ክንፉ በሌላ በኩል ያለውን ፍጡር ክንፍ ይነካ ነበር”

ደግሞም በጥንድ ክንፎቻቸው አካላቸውን ይሸፍኑ ነበር
ይህ እንደ አዲስ ዐረፍተ ነገር መተርጎም ይችላል። “የእያንዳንዱ ፍጡር ሁለት ክንፎቻቸው አካሉን ይሸፍኑት ነበር”

እያንዳንዱ ወደ ፊት ቀጥ ብሎ ይሄድ ነበር
“እያንዳንዱ ፍጡር ወደ ፊት እያየ ይጓዝ ነበር”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ezekiel 1:13

የሕያዋን ፍጡራኑን መልክ አስመልክቶ፣ ገጽታቸው የእሳት ፍም ይመስል ነበር
የነገር ስም የሆነው “መልክ” ማለት እነዚህ ነገሮች ምን እንደሚመስሉ ሕዝቅኤል ያያቸው ናቸው። “መልክ” እና “ገጽታ” ሁለቱም የነገር ስም ሲሆኑ ወደ ግሥነት ሊተረጎሙ ይችላሉ። አ.ት፡ “የሕያዋን ፍጡራኑ መልክ ከእሳት ፍም ጋር የሚመሳሰል ነበር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

የመብረቅ ብልጭታዎች ነበሩ
“ከእሳቱ መብረቅ ወጣ”

ሕያዋኑ ፍጡራን በዝግታ ወደ ፊትና ወደ ኋላ ይሄዱ ነበር፣ መብረቅ ይመስሉም ነበር
መብረቁ ይበራና ወዲያው ይጠፋ ነበር፣ ፍጡራኑም ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላው በፍጥነት ይንቀሳቀሱ ነበር። የነገር ስም የሆነው “ገጽታ” እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ሕያዋኑ ፍጡራን በዝግታ ወደ ፊትና ወደ ኋላ ይሄዱ ነበር፣ መብረቅ ይመስሉም ነበር” (Simile እና የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 1:15

የመንኩራኩሮቹ ገጽታና መዋቅር ይህንን ይመስል ነበር
“የመንኩራኩሮቹ መልክና አሠራር ይህንን ይመስል ነበር”

እንደ ቢረሌ
ቢረሌ በአብዛኛው ቢጫ ወይም ወርቃማ ቀለም ያለው ንጹሕ የከበረ የድንጋይ ዓይነት ነው። “እንደ ቢረሌ ድንጋይ ንጹሕና ቢጫ” ወይም “እንደ ከበረ ድንጋይ ንጹሕና ቢጫ”

አራቱም ተመሳሳይ መልክ ነበራቸው
እዚህ ጋ፣ የነገር ስም የሆነው “መልክ” አራቱ መንኩራኩሮች ምን ይመስሉ እንደነበር ያመለክታል። ቃሉ ከግሣዊ ሐረግ ጋር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “አራቱም መንኩራኩሮች ይመሳሰሉ ነበር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ገጽታቸውና አሠራራቸው አንዱ መንኩራኩር ከሌላው መንኩራኩር ጋር ተላልፎ የተያዘ ይመስል ነበር
“ገጽታ” እና “አሠራር” የሚሉት የነገር ስሞች እንደ ግሥ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አ.ት፡ “አንደኛው መንኩራኩር በሌላኛው መንኩራኩር ውስጥ አልፎ የተሠራ ይመስል ነበር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 1:17

በየትኛውም በአራቱ አቅጣጫዎች ይሄዱ ነበር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “የእነርሱ” የሚያመለክተው ፍጡራኑን ነው። አ.ት፡ “ፍጡራኑ ወደሚመለከቷቸው ከአራቱ አቅጣጫዎች በየትኛውም ቀጥ ብለው ይሄዱ ነበር” ወይም 2) “የእነርሱ” የሚያመለክተው መንኩራኩሮቹን ነው የሚሉት ናቸው።

የክበብ ጠርዛቸው
“የመንኩራኩሮቹ ክበብ ጠርዛቸው ይህንን ይመስል ነበር”

ረጅምና አስፈሪ ነበሩ
“የክበቦቹ ጠርዞች በጣም ረጅምና አስገራሚ ነበሩ” ወይም “የክበቦቹ ጠርዞች ረጅምና አስፈሪ ነበሩ”

የክበቦቹ ጠርዞች ዙሪያቸውን በዐይን የተሞሉ ነበሩ
“ምክንያቱም በአራቱም መንኩራኩሮች ዙሪያ በክበቦቹ ጠርዞች ላይ በጣም ብዙ ዐይኖች ነበሩባቸው”

Ezekiel 1:19

ሕያዋኑ ፍጡራን ከመሬት በሚነሡበት ጊዜ
ፍጡራኑ ምድርን ከለቀቁ በኋላ በአየር ላይ ይበሩ ነበር። አ.ት፡ “ፍጡራኑ ምድርን ለቀው ወደ አየር በሚወጡበት ጊዜ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

መንኩራኩሮቹም ደግሞ ወደ ላይ ተነሡ
“መንኩራኩሩም ደግሞ ምድርን ለቆ ወደ አየር ወጣ”

መንፈስ ወደሚሄድበት ሁሉ እነርሱም ሄዱ
“እነርሱ” የሚለው ቃል ፍጡራኑን ያመለክታል።

በአጠገባቸው መንኩራኩሮቹ ተነሡ
“መንኩራኩሮቹ ከሕያዋን ፍጡራኑ ጋር ወደ አየር ላይ ወጡ”

የሕያው ፍጡሩ መንፈስ በመንኩራኩሮቹ ውስጥ ነበር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሕዝቅኤል አንድ ፍጡር የሆኑ በሚመስል መልኩ የሚናገረው በቁጥር 19 ስላሉት “ፍጡሮች” ነው። አ.ት፡ “የሕያዋን ፍጡራኑ መንፈስ በመንኩራኩሮቹ ውስጥ ነበር” ወይም 2) ሕዝቅኤል የአነጋገር ዘይቤን ይጠቀማል። አ.ት፡ “የሕይወት መንፈስ በመንኩራኩሮቹ ውስጥ ነበር” ወይም “ሕያው መንፈስ በመንኩራኩሮቹ ውስጥ ነበር” ወይም 3) በፍጡራኑና በመንኩራኩሮቹ ውስጥ የነበረው መንፈስ አንድ ነበር። አ.ት፡ “ለፍጡራኑ ሕይወት የሰጣቸው ያው መንፈስ ለመንኩራኩሮቹም ደግሞ ሕይወትን ሰጣቸው” የሚሉት ናቸው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 1:22

የተስፋፋ የጠፈር መልክ
እዚህ ጋ፣ የነገር ስም የሆነው “መልክ” ማለት “የተስፋፋ የጠፈር መልክ” መስሎ ለሕዝቅኤል የታየው ነው። ቃሉ በግሣዊ ሐረግ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “የተስፋፋ ጠፈር ይመስል የነበረው” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

የተስፋፋ ጠፈር
ጠፈሩ በግማሽ የተቆረጠ ክፍት ኳስ ይመስል ነበር። “የተስፋፋ” ማለት በጣም ሰፊ ማለት ነው። “ከላይ ወደ ታች የተደፋ ትልቅ ጓድጓዳ ሳህን”

ግርምት ቀስቃሽ መስታወት መሰል ድንጋይ
“ግርምት ቀስቃሽ በረዶ” ወይም “ሰዎች በሚያዩት ጊዜ እንዲደነቁ የሚያስደርጋቸው መስታወት መሰል ድንጋይ”

ከራሳቸው በላይ ተዘርግቷል
“ተስፋፊው ጠፈር ከፍጡራኑ ራስ በላይ ተዘርግቶ ነበር” ወይም “ተስፋፊው ጠፈር ከፍጡራኑ ራስ በላይ ሰፊ ቦታ ይዞ ነበር”

ከጠፈሩ ስር
“ከጠፈሩ በታች”

እያንዳንዱ ሕያዋን ፍጡራን ደግሞ ራሳቸውን የሚሸፍኑበት ጥንድ ክንፍ ነበራቸው፤ እያንዳንዱ የራሱን አካል የሚሸፍንበት ጥንድ ክንፍ ነበረው
“እያንዳንዱ ሕያው ፍጡር አካላቸውን የሚሸፍኑባቸው ሌላ ሁለት ክንፍ ነበራቸው”

Ezekiel 1:24

ከዚያም የክንፎቻቸውን ድምፅ ሰማሁ። እንደ ብዙ ውኆች ድምፅ ያለ፣ በሚሄዱበት ሁሉ እንደ ሁሉን ቻዩ ድምፅ ያለ።
“በሚሄዱበት ቦታ ሁሉ” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቷቸው ሊሆኑ የሚችሉ ሌሎች ትርጉሞች 1) በዚህ ቁጥር ፊት ያሉት ቃላት ሁሉ “በሚሄዱበት ቦታ ሁሉ የክንፎቻቸውን ድምፅ ሰማሁ። እንደሚጎርፍ ውሃ ድምፅ ያለ፤ እንደ ሁሉን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ቻዩ ድምፅ ያለ፤” ወይም 2) “ክንፎች፣ እንደሚጎርፍ ውሃ ድምፅ ያለ፤ እንደ ሁሉን ቻዩ ድምፅ ያለ፤ በሚሄዱበት ቦታ ሁሉ እንደ --- ያለ ድምፅ” የሚሉት ቃላት ይከተሏቸዋል የሚሉት ናቸው።

እንደ ... ውኖች። እንደ ... የሚሄዱበት። እንደ ... የዝናብ ማዕበል። እንደ ... ሰራዊት።
ሕዝቅኤል ባየው ነገር መደነቁን በማሳየት ላይ ስለ ነበር እነዚህ ዐረፍተ ነገሮች የተሟሉ አይደሉም። እንደ ሙሉ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎሙ ይችላሉ፡ “ክንፎቹ እንደ ... ውሃ ድምፅ ነበር። በሚሄዱበት እንደ ... ድምፅ ነበር። እንደ ... የዝናብ ማዕበል ድምፅ ነበር። እንደ ... ሰራዊት ድምፅ ነበር” (See: Simile)

ብዙ ውኖች
ይህ ማለት በቀላሉ “ብዙ ውሃ” ማለት ነው። ይህ ከፍተኛ ድምፅ ያለውን ወንዝ ወይም ታላቅ ፏፏቴን ወይም በውቅያኖስ ላይ የሚጋጩ ሞገዶችን ሊያመለክት ይችላል። እነዚህ ሁሉ ከፍተኛ ድምፅ ያላቸው ናቸው።

እንደ ሁሉን ቻዩ ድምፅ ያለ
መጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ጊዜ ነጎድጓድን እንደ “የሁሉን ቻዩ ድምፅ” አድርጎ ያመለክታል። አ.ት፡ “ድምፁ የሁሉን ቻዩን አምላክ ድምፅ ይመስል ነበር” ወይም “እርሱ የሁሉን ቻዩን ነጎድጓድ ድምፅ ይመስል ነበር” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እንደ ዝናብ ማዕበል ድምፅ ያለ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “እንደ ታላቅ ማዕበል ድምፅ ያለ” ወይም 2) “እንደ ብዙ ሕዝብ ድምፅ ያለ” የሚሉት ናቸው። አ.ት፡ “እንደ ታላቅ ማዕበል ድምፅ ያለ ታላቅ ድምፅ ነበር” ወይም “እንደ ብዙ ሕዝብ ድምፅ ያለ ታላቅ ድምፅ ነበር” (See: Simile)

በሚቆሙበት ጊዜ ሁሉ
“ፍጡራኑ እንቅስቃሴያቸውን በሚያቆሙበት ጊዜ ሁሉ”

ክንፎቻቸውን ዝቅ ያደርጉ ነበር
“ፍጡራኑ ክንፎቻቸው በጎናቸው እንዲወርዱ ያደርጉ ነበር”። ይህንን ያደረጉት ክንፎቻቸውን ለመብረር በማይጠቀሙበት ጊዜ ነበር።

ከጠፈሩ በላይ አንድ ድምፅ መጣ
“ከጠፈሩ በላይ የነበረ አንድ ሰው ተናገረ”። ይህ የማን ድምፅ እንደሆነ መናገር ከፈለግህ ምናልባት የእግዚአብሔር ድምፅ እንደሆነ መግለጽ ይኖርብሃል (ሕዝቅኤል 1፡3)።

Ezekiel 1:26

ከራሳቸው በላይ
“ከፍጡራኑ ራስ በላይ”

የዙፋን መልክ ነበረው
እዚህ ጋ፣ የነገር ስም የሆነው “መልክ” ማለት ሕዝቅኤል ዙፋን መስሎ የታየው ነበር። ቃሉ በግሣዊ ሐረግ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ዙፋን ይመስል ነበር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ሰንፔር
የጠራ ሰማያዊና በጣም አንጸባራቂ የሆነ በጣም ውድ ድንጋይ

የዙፋን መልክ በነበረው ላይ
የነገር ስም የሆነው “መልክ” በግሣዊ ሐረግ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ዙፋን በሚመስለው ላይ --- ነበር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

መልኩ የሰው ገጽታ ያለው የሚመስል
የነገር ስሞች የሆኑት “መልክ” እና “ገጽታ” በግሣዊ ሐረጎች ሊተረጎሙ ይችላሉ። ይህ ማን እንደሆነ መናገር ከፈለግህ ምናልባት እግዚአብሔር እንደሆነ መናገር ይኖርብሃል (ሕዝቅኤል 1፡3)። አ.ት፡ “ሰውን መስሎ ከሚታየው ጋር የሚመሳሰል አንዳች ነገር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 1:27

ከወገቡ በላይ ያለው ገጽታ
ከወገቡ በላይ ያለው የሰውየው አካል እሳት ያለበት የጋለ ብረት ይመስል ነበር። የነገር ስም የሆነው “ገጽታ” እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ከወገቡ በላይ ይታይ የነበረው” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ከወገቡ በታች ያለው ገጽታ ዙሪያው በሙሉ የእሳትና የብርሃን ገጽታ ነበረው
“ገጽታ” የሚለው የነገር ስም እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ወገቡ መስሎ ከሚታይ ገጽታው በታች ዙሪያው እሳትና ብሩህ ብርሃን የሚመስል አየሁ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

በዝናባማ ቀን በደመና ውስጥ የሚታይ የቀስተ ደመና ገጽታን የሚመስል ብሩህ ብርሃን ከቦት ነበር
“ገጽታ” የሚለው የነገር ስም እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “የከበበው ብሩህነት ልክ በዝናባማ ቀን በደመና ውስጥ የሚታየውን ቀስተ ደመና ይመስል ነበር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ቀስተ ደመና
ፀሐይ ከተመልካቹ በስተኋላ በምትወጣበት ጊዜ በዝናብ ውስጥ የሚታይ ልዩ ልዩ የብርሃን ቀለማት

እርሱም የእግዚአብሔር መልክ አምሳያ ነበር
“አምሳያ” የሚለው የነገር ስም ትርጉሙ ሕዝቅኤል ሲያየው የእግዚአብሔርን ክብር ይመስል የነበረው ነው። “አምሳያ” እና “መልክ” ሁለቱም ከግሣዊ ሐረግ ጋር ሊተረጎሙ ይችላሉ። አ.ት፡ “የእግዚአብሔርን ክብር መስሎ ይታይ ነበር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

በግንባሬ ተደፋሁ
“በምድር ላይ ሰገድሁ” ወይም “በምድር ላይ ተጋደምሁ”። ሕዝቅኤል የወደቀው በአደጋ ምክንያት አይደለም። ወደ ምድር ዝቅ ያለው እግዚአብሔርን መፍራቱንና ማክበሩን ለማሳየት ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

አንድ የሚናገርን ድምፅ ሰማሁ
“ድምፅ” የሚለው ቃል ሰውን የሚወክል ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “አንድ ሰው ሲናገር ሰማሁ” ወይም “አንድ ሰው ተናገረ፣ እኔም ድምፁን ሰማሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 "የሰው ልጅ ሆይ ተነስና ቁም ክዚያም አነጋግርሃልሁ" አለኝ። **2** እየተናገረኝ ሳለ መንፈስ አንስቶ በእግሮቼ አቆመኝ የናገረኝንም ሰማሁ። **3** "የሰው ልጅ ሆይ አመፀኛ ወደሆኑትና በእኔ ላይ ወዳመፁት ወደ እስራኤል ህዝብ እልክሃለሁ፦ እነርሱና የቀደሙ አባቶቻችው እስከዚች ቀን ድረስ በድለውኛል! **4** ልጆቻቸው የተጨማደደ ፊትና ደንዳና ልብ አላቸው። አንተም እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ትላቸዋለህ። **5** አመጸኛ ቤት ስለሆኑ ወይ ይሰሙሃል አሊያም አይሰሙህም። ነገር ግን ቢያንስ ነቢይ በመካከላቸው እንዳለ ያውቃሉ። **6** አንተም የሰው ልጅ ሆይ እነርሱንም ሆነ ቃላቸውን አትፍራ። በእሾሆች፣በኩርንችት እና በጊንጦች መካከል ብትቀመጥም አትፍራ። አመጸኛ ቤቶች ስለሆኑ ቃላቸውን አትፍራ ፊታቸውን አይተህ አትደንግጥ። **7** እጅግ አመጸኞች ስለሆኑ ቢሰሙህም ባይሰሙህም ቃልን ትነግራቸዋለህ። **8** ነገር ግን አንተ የሰው ልጅ የምነግርህን ስማ። አንተም እንደአመጸኞቹ ሰዎች አመጸኛ አትሁን። አፍህን ክፈትና የምሰጥህን ብላ። **9** ጽሁፍ የተጻፈበት ጥቅል የያዝ እጅ ወደኔ ሲዘረጋ አየሁ። **10** በፊቴም ዘረጋው ክፊትና ከኋላው ተጽፎበት ነበር፤ በሀዘን፣ በልቅሶና በዋይታ የተሞላ ነበር።

Ezekiel 2:1

ተናገረኝ
የአንተ ቋንቋ ተናጋሪውን መለየት ካለበት “አንድ ሰውን የሚመስል” በማለት ቢለየው ይመረጣል (ሕዝቅኤል 1:26)። ያ “መንፈስ ቅዱስ” አልነበረም።

የሰው ልጅ
“የሰብዓዊ ፍጡር ልጅ” ወይም “ከሰው የተወለደ ልጅ”። ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን አፅንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ በማለት ይጠራዋል። እግዚአብሔር ዘላለማዊና ኃያል ነው፣ ሰዎች ግን አይደሉም። አ.ት፡ “ሟች ሰው” ወይም “ሰው”

መንፈስ ቅዱስ
ሊሆኑ የሚችሉ ሌሎች ትርጉሞች 1) “መንፈስ” ወይም 2) “ንፋስ” የሚሉት ናቸው።

ወደ እስራኤል ሕዝብ፣ በእኔ ላይ ወዳመፀው ወደ አመፀኛው ሕዝብ
“ወደ እስራኤላውያን፣ በእኔ ላይ ወዳመፁት አመፀኛ ሕዝቦች”። “የእስራኤል ሕዝብ” እና “አመፀኛ ሕዝብ” ሁለቱም ሐረጎች የሚያመለክቱት አንዱን ሕዝብ ነው። አ.ት፡ “ወደ እስራኤል ሕዝብ፣ በእኔ ላይ ወዳመፀው ሕዝብ” (See: Doublet)

እስከዚህ ቀን ድረስ
“አሁን እንኳን” ወይም “ዛሬም እንኳን”። ይህ ማለት የእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔርን ባለመታዘዝ ቀጥለዋል።

Ezekiel 2:4

ልጆቻቸው
በእግዚአብሔር ላይ አምፀው የነበሩትን የቀደመውን የእስራኤል ትውልድ ልጆች ሲሆን ሕዝቅኤል በሚጽፍበት ወቅት በእስራኤል የሚኖረውን ሕዝብ ያመለክታል።

የእልኸኝነት ፊት አላቸው
“እልኸኛ መሆናቸውን የሚያሳይ የፊት ገጽታ አላቸው”

እልኸኛ ፊትና ደንዳና ልብ
“እልኸኛ ፊት” የሚሉት ቃላት ውጫዊ እንቅስቃሴ የሚያደርጉበትን መንገድ የሚያመለክት ሲሆን “ደንዳና ልብ” የሚሉት ቃላት ደግሞ የሚያስቡበትንና የሚሰማቸውን መንገድ የሚያመለክቱ ናቸው። (See: Doublet)

እልኸኛ
ይህ የሚያስበውን ወይም የሚያደርገውን ለመቀየር እምቢተኛ የሚሆንን ሰው ይገልጻል።

ደንዳና ልብ
ዐለቶች መቼም ቢሆን እንደማይለወጡና እንደማይለሰልሱ ሁሉ እነዚህ ሰዎችም አይለወጡም፣ ክፉ ነገር በሚያደርጉበት ጊዜም አይጸጸቱም። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ቤት
ይህ በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በመካከላቸው ነቢይ ነበረ
“ሊሰሙት ያልፈቀዱት ያ ሰው ነቢይ ነበር”

Ezekiel 2:6

የሰው ልጅ
“የሰብዓዊ ፍጡር ልጅ” ወይም “ከሰው የተወለደ ልጅ”። ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን አፅንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ በማለት ይጠራዋል። እግዚአብሔር ዘላለማዊና ኃያል ነው፣ ሰዎች ግን አይደሉም። ይህንን በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ሟች ሰው” ወይም “ሰው”

ኩርንችትና እሾህ ... ጊንጥ
እነዚህ ቃላት ሕዝቅኤል እግዚአብሔር የሚለውን በሚነግራቸው ጊዜ የእስራኤል ሕዝብ በቅንነት እንዳልተቀበሉት ይገልጻል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ኩርንችትና እሾህ
ኩርንችት ቅርንጫፉ የሚዋጋ ጫፍ ያለው ቁጥቋጦ ነው። በቅንርጫፉ ላይ ያሉት ሹሎች እሾህ ተብለው ይጠራሉ።

ጊንጥ
ጊንጥ ሁለት የፊት ለፊት ጥፍሮች፣ ስድስት እግሮችና አለብላቢ መናደፊያ ረጅም ጅራት ያለው ትንሽ እንስሳ ነው። ሲናደፍ በጣም ያሳምማል።

ቃላቸውን አትፍራ
“እነርሱ የሚናገሩትን አትፍራ”

ከፊታቸው የተነሣ አትደንግጥ
“ፊታቸው” የሚለው ቃል ሕዝቡ በፊት ገጽታቸው የሚያስተላልፉትን መልዕክት የሚያሳይ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “አንተን ከሚያዩበት መንገድ የተነሣ እኔን ለማገልገል ያለህ ፍላጎት አይጥፋብህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ezekiel 2:7

እጅግ አመፀኞች ናቸው
“በጣም አመፀኞች ናቸው” ወይም “በእኔ ላይ ፈጽመው አምፀውብኛል”

ቤት
ይህ በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 2:5 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 2:9

አንድ እጅ ወደ እኔ ተዘርግቶ ነበር
ይህ፣ 1) በሰማያት ውስጥ ያለ አንድ ሰው እጁን ወደ ሕዝቅኤል ዘርግቶለታል፤ ሕዝቅኤል ማየት የቻለው ከእጁ እስከ ክርኑ ወይም እስከ ትከሻው ያለውን ብቻ ነው፣ ወይም 2) “የሰው ልጅ የሚመስለው” እጁን ዘርግቷል (ሕዝቅኤል 1፡26)።

የተጻፈበት ጥቅልል
“ጽሑፍ ያለበት ጥቅልል”

ዘረጋው
በውስጠ ታዋቂ ያለው “እርሱ” የሚያመለክተው “የሰው ልጅ የሚመስለውን” ነው (ሕዝቅኤል 1:26)።

በፊት ለፊቱና በጀርባው ላይ በሁለቱም በኩል ተጽፎበት ነበር
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “አንድ ሰው በፊት ለፊቱና በስተጀርባው በሁለቱም በኩል ጽፎበት ነበር” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በላዩ ላይ ሙሾ፣ ለቅሶና ዋይታ ተጽፎበት ነበር
ይህ የነገር ስም የሆኑትን “ሙሾ”፣ “ለቅሶ”፣ እና “ዋይታ”ን ለማስቀረት እንደገና መነገር ይችላል። አ.ት፡ “እነዚህ ሰዎች እንደሚያሟሹ፣ አንድ የሚወዱት ቢሞትባቸው እንደሚሆኑት ሁሉ እንደሚያዝኑና የከፋ ነገር እንደሚደርስባቸው አንድ ሰው ጽፎበት ነበር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 የሰው ልጅ ሆይ ያገኘኽውን ብላ ይህን የመጽሀፍ ጥቅል ብላ ሄደህም ለእስራኤል ህዝብ ተናገር። **2** አፌንም ከፈትኩ የመጽሀፉን ጥቅል አጎረሰኝና **3** "የሰው ልጅ ሆይ በሰጠሁህ በዚህ የመጽሀፍ ጥቅል ሆድህን ሙላ" አለኝ። እኔም በላሁት እንደማርም ጣፈጠኝ። **4** ከዚያም "የሰው ልጅ ሆይ ወደ እስራኤል ህዝብ ሄደህ ቃሌን ንገራቸው" አለኝ። **5** ምክንያቱም የተላከው ቋንቋቸው ወደማይታወቅ ወይም አስቸጋሪ ወደሆን ህዝብ አይደለም፦ **6** እንግዳ ቋንቋ ወደሚናገር ታላቅ ህዝብ ወይም የቋንቋቸውን ቃላት መረዳት ወደሚያስቸግር ህዝብ አላኩህም። ወደዚህ ዓይነት ህዝብ ብልክህ ኖሮ ይሰሙህ ነበር። ነገር ግን የእስራኤል ህዝብ እኔን መስማት ስለማይፈልጉ አይሰሙህም። **7** የእስራኤል ህዝብ ሁሉ ግንባረ ጠንካራና አንገተ ደንዳና ናቸው። **8** እነሆ! ፊትህን እንድፊታቸው ግንባርህንም እንደግንባራቸው ጠንካራ አደርገዋለሁ። **9** ግንባርህን ከባልጩት ድንጋይ ይልቅ እንደሚጠነክር እንደ አልማዝ አድርጌዋለሁ! ስለዚህ የእሴራኤል ህዝብ አመጸኞች ስለሆኑ አትፍራቸው ፊታቸውንም አይተህ አትደንግጥ። **10** ቀጥሎሜ እንዲህ አለኝ "የሰው ልጅ ሆይ የነገርኩህን ቃል ስማ በልብህም ተቀበለው። **11** ከዚያም በምርኮ ወዳሉት ህዝብህ ሂድና ቢሰሙህም ባይሰሙህም 'እግዚአብሔር እንዲህ ይላል' በላቸው።" **12** መንፈስም ከምድር ከፍ አደረግኝ ከኋላዬም የእግዚአብሔር ክብር በማደሪያው ይባረክ የሚል እንደ ምድር መናወጥ ዓይነት ድምጽ ሰማሁ። **13** ወዲያውም የህያው ፍጥርታቱ ክንፎች ሲነካካ የሚፈጠረውን ድምጽ፣ አብረዋቸው ያሉትን መንኮራኩሮች ድምጽ፥ እና የምድር መናወጥ ድምጽ ሰማሁ። **14** መንፈስም አንስቶ ወሰደኝ፤ የእግዚአብሔርም እጅ በእኔ ላይ ከብዶ ስለነበር የምሄደው በምሬትና በጋለ መንፈስ ነበር። **15** ከዚያም በኬብሮን ወንዝ አጠገብ ወደሚኖሩት በቴላቢብ ወደሚገኙት ምርኮኞች ሄጄ በድንጋጤና በመደነቅ ተሞልቼ በመካከላቸው ሰባት ቀን ተቀመጥኩ። **16** ከሰባት ቀንም በኋላ እንዲህ ሆነ፥ **17** "የሰው ልጅ ሆይ አንተን ለእስራኤል ህዝብ እንደጠባቂ አድርጌሀለሁ፥ ስለዚህ የአፌን ቃል ስማና የእኔን ማስጠንቀቂያ ንገራቸው! **18** ኃጢአተኛውን 'በእርግጥ ትሞታለህ' ብለህ ንገረው ብዬህ አንተ ግን ባትነግረው ከክፉ መንገዱም እንዲመለስ ባታስጠነቅቀው እርሱ በኃጢአቱ ይሞታል ደሙን ግን ከእጅህ እፈልጋለሁ። **19** ነገር ግን ኃጢአተኛውን ብታስጠነቅቀው እርሱ ግን ከክፋቱና ከመጥፎ ተግባሩ ባይመለስ በኃጢአቱ ይሞታል አንተም ነፍስህን ታድናለህ።" ብሎ እግዚአብሔር ሲናገረኝ ሰማሁ። **20** ደግሞም አንድ ጻድቅ ሰው ጽድቅ ማድረግን ቢተው እኔም በፊቱ መሰናክል ሳስቀምጥ እርሱ በኃጢአቱ ይሞታል። አንተ ስላላስጠነቀከው እርሱ በኃጢአቱ ይሞታል፣ ቀድሞ የሰራውንም የጽድቅ ስራ አላስብለትም፣ ነገር ግን አንተን የሞቱ ተጠያቂ አደርግሀለሁ። **21** ነገር ግን አንድ ጻድቅ ሰው ኃጢአት መስራቱን እንዲያቆም ብታስጠነቅቀው ከማስጠንቀቂያው የተነሳ በእርግጥኝነት በህይወት ይኖራል፣ አንተም የራስህን ህይወት ታድናለህ።" **22** ደግሞም የእግዚአብሔር እጅ በላዬ መጣ፣ እግዚአብሔርም ፣ "ተነሳ! ወደ ሜዳማው ቦታ ሂድ፣ በዚያ የምነግርህ ነገር አለ" አለኝ። **23** እኔም ተነስቼ ወደ ሜዳማው ቦታ ሄድኩ፥ በዚያም በኬብሮን ወንዝ አጠገብ ያየሁት ዓይነት የእግዚአብሔር ክብር ነበረ፣ ስለዚህም በግንባሬ ተደፋሁ። **24** የእግዚአብሔርም መንፈስ መጥቶ በእግሮቼ አቆመኝና እንዲህ ሲል ተናገረኝ "ወደ ቤትህ ሂድና በር ዘግተህ ተቀመጥ፣ **25** ምክንያቱም አሁን የሰው ልጅ ሆይ በመካከላቸው እንዳትንቀሳቀስ በገመድ ያስሩሀል። **26** አመጸኛ ህዝብ ስለሆኑ እንዳትገስፃቸው እኔ ምላስህን ከላንቃህ ጋር አጣብቀዋለሁ አንተም ዲዳ ትሆናለህ። **27** ነገር ግን እኔ ስናገርህ አፍህን እከፍታለሁ አንተም 'ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል' ትላቸዋለህ፤ አመጸኛ ህዝብ ስለሆኑ የሚሰማ ይሰማህል የማይሰማ አይሰማህም!"

Ezekiel 3:1

ተናገረኝ
“እርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው “አንድ ሰው የሚመስል” የተባለለትን ነው (ሕዝቅኤል 1፡26)

የሰው ልጅ
“የሰብዓዊ ፍጡር ልጅ” ወይም “ከሰው የተወለደ ልጅ”። ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን አፅንኦት ለመስጠት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ በማለት ይጠራዋል። እግዚአብሔር ዘላለማዊና ኃያል ነው፣ ሰዎች ግን አይደሉም። ይህንን በሕዝቅኤል 2፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ሟች ሰው” ወይም “ሰው”

ያገኘኽውን
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር እየሰጠው ያለውን የመጽሐፍ ጥቅል ነው (ሕዝቅኤል 2፡9ን ተመልከት)

የእስራኤል ቤት
ይህ በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። አ.ት፡ “እስራኤላውያንን” ወይም “የእስራኤላውያንን የሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ያ ጥቅልል
ብዙ ትርጉሞች “ጥቅልሉ” ወይም “ይህ ጥቅልል” የሚል አላቸው።

በዚህ ጥቅልል ሆድህን መግበው፣ ጨጓራህንም ሙላው
“ሆድ” የሚለው ቃል ሰዎች ከውጭ ሊያዩት የሚችሉትን የሰውነት ክፍል ያመለክታል። “ጨጓራ” የሚለው ቃል ደግሞ በሆድ ውስጥ ያለውን ውስጣዊ ብልት ያመለክታል።

እርሱም እንደ ማር ይጣፍጥ ነበር
ማር ይጣፍጣል፣ ጥቅልሉም ይጣፍጥ ነበር።

Ezekiel 3:4

ተናገረኝ
የአንተ ቋንቋ ተናጋሪውን መለየት ካለበት “አንድ ሰውን የሚመስል” በማለት ቢለየው ይመረጣል (ሕዝቅኤል 1፡26)። እርሱ “መንፈስ ቅዱስ” አልነበረም።

የእስራኤል ቤት
ይህ በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እስራኤላውያንን” ወይም “የእስራኤላውያንን የሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እንግዳ ንግግር ወይም አስቸጋሪ ቋንቋ
“እንግዳ ወይም አስቸጋሪ ቋንቋ የሚናገር”

እንግዳ ንግግር ወደሚናገሩ ወደ ብዙ ሰዎች አይደለም
“ሕዝባቸው እንግዳ ቋንቋ ወደሚናገር ብርቱ ሕዝብ አልካሁህም”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወደ እነርሱ ብልክህ ኖሮ ይሰሙህ ነበር
ይህ ሊሆን የሚችል፣ ነገር ግን ያልሆነ መላ ምታዊ ሁኔታ ነው። እግዚአብሔር የሕዝቅኤልን ቋንቋ መረዳት ወደማይችሉ ሕዝቦች አልላከውም።

ወደ እነርሱ ብልክህ ኖሮ
“እነርሱ” የሚለው ቃል ከእስራኤል ሌላ ብርቱ የሆነን ሕዝብ ያመለክታል።

ግንባረ ጠንካራ እና ልበ ደንዳና
በመሠረቱ የሁለቱም ትርጉም ተመሳሳይ ነው። አ.ት፡ “በጣም አመፀኞች” ወይም “በጣም እልኸኞች”

ግንባረ ጠንካራ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ለለውጥ ፈቃደኛ አለመሆን” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ልበ ደንዳና
ይህ ሐረግ ሕዝቡ እግዚአብሔርን እንደተቋቋሙትና ሊታዘዙት ፈቃደኞች አለመሆናቸውን ይጠቁማል። ሕዝቡ ለማድረግ የሚፈልጉትን የሚወስኑበትን በአካል ውስጥ የሚገኘውን ስፍራ ለመገለጽ ልብ ጥቅም ላይ ውሏል። ይህንን በሕዝቅኤል 2:4 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 3:8

ተመልከት!
እዚህ ጋ፣ “ተመልከት” የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚመጣው አስገራሚ መረጃ ትኩረት እንዲሰጥ ሕዝቅኤልን ያነቃዋል።

ፊትህን እንደ ፊታቸው እልኸኛ አድርጌዋለሁ
“ፊት” እና “ፊታቸው” የሚሉት ቃላት ጥቅም ላይ የዋሉት ዐረፍተ ነገሩ ስለሚናገርላቸው ሕዝብ ነው። አ.ት፡ “አንተንም እንደ እነርሱ እልኸኛ አድርጌሃለሁ” (See: Synecdoche)

ግንባርህን እንደ ግንባራቸው ጠንካራ አድርጌአለሁ
“ግንባር” ፊት ለፊት ወይም ከቅንድብ በላይ ያለው ክፍል ሲሆን ሰውየው ስለሚያስበው ነገር ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ጠንካራ አድርጌሃለሁ . . . ስለዚህ የምትሠራውን ሥራ አታቆምም” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ግንባርህን ከባልጩት ይልቅ እንደሚጠነክር እንደ አልማዝ አድርጌዋለሁ
“ግንባርህን ከባልጩት ይልቅ ጠንካራ እንደሆነ ድንጋይ አድርጌአለሁ”

ባልጩት
ከጥንካሬው የተነሣ ከብረት ወይም ከሌላ ድንጋይ ጋር ሲያጋጩት እሳት የሚፈጥር ጠንካራ ድንጋይ

ቤት
ይህ በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 2:5 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 3:10

በልብህ ተቀበላቸው፣ በጆሮዎችህም አድምጣቸው
እዚህ ጋ፣ “ልብ” የሰውን አዕምሮ ይወክላል። አ.ት፡ “በጥንቃቄ አድምጣቸው፣ አስታውሳቸውም” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከዚያም ወደ ምርኮኞቹ ሂድ
“ምርኮኞች” የሚለው ቃል በባቢሎን የሚኖሩትን የእስራኤል ሕዝብ ያመለክታል።

ሕዝብህ
“የሕዝብህ ወገን”፣ ባቢሎናውያን ወደ ባቢሎን ሳይወስዱት በፊት ሕዝቅኤል በይሁዳ ይኖር ነበር።

ጌታ እግዚአብሔር
ይህንን በሕዝቅኤል 2:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Ezekiel 3:12

“የእግዚአብሔር ክብር ከስፍራው ይባረክ!” የሚል ታላቅ የመሬት መንቀጥቀጥ ድምፅ ከበስተኋላዬ ሰማሁ
አንዳንድ ትርጉሞች “ስፍራ … ይባረክ!” የሚሉትን ቃላት “ታላቅ የመሬት መንቀጥቀጥ” የተናገረው አድርገው ይወስዳሉ፤ “’የእግዚአብሔር ክብር ከስፍራው ይባረክ!’ የሚለውን ታላቅ የምድር መንቀጥቀጥ ድምፅ ከበስተኋላዬ ሰማሁ”። ሌሎች የምድር መንቀጥቀጡን ድምፅ የእግዚአብሔር ክብር ከስፍራው ሲለቅ የነበረው ድምፅ አድርገው ይረዳሉ፣ “የእግዚአብሔር ክብር ስፍራውን ሲለቅ ከበስተኋላዬ ታላቅ የምድር መንቀጥቀጥ ድምፅ ሰማሁ”።

ታላቅ የመሬት መንቀጥቀጥ ድምፅ
ድምፁ ከመሬት መንቀጥቀጥ፣ እንደ መሬት መንቀጥቀጥ ከፍ ካለ ድምፅ፣ ወይም ከክንፎችና ከመንኩራኩሮች መጥቶ እንደሆን ግልጽ አይደለም። አ.ት፡ “ታላቅ የመሬት መንቀጥቀጥ ድምፅን የሚመስል ድምፅ” ወይም “የሚናገርን ድምፅ፤ ታላቅ የመሬት መንቀጥቀጥ ድምፅን የሚመስል ድምፅ” ወይም “ከፍ ያለ የጉርምርምታ ድምፅ”

የእግዚአብሔር ክብር
ይህንን በሕዝቅኤል 1:28 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ታላቅ የመሬት መንቀጥቀጥ ድምፅ
“እንደ መሬት መንቀጥቀጥ ድምፅ ያለ ከፍተኛ፣ ጥልቅና ኃይለኛ የጉርምርምታ ድምፅ”

Ezekiel 3:14

በሩቅ፣ እኔም በመንፈሴ ቁጣ በምሬት ሄድኩኝ
“ምሬት” እና “ቁጣ” የሚሉት ቃላት የቁጣ ዓይነቶች ናቸው። ይህ እንደ ሁለት ዐረፍተ ነገር ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በሩቅ። መራራ ነበርኩኝ፣ መንፈሴም ቁጣን ተሞልቶ ነበር” ወይም “በሩቅ። በጣም መራራና ቁጡ ነበርኩኝ”

ምሬት
ሕዝቅኤል አፉ ላይ መጥፎ ጣዕም የተሰማው እግዚአብሔር መጥፎ ጣዕም ያለውን ነገር እንዲበላ ስላስገደደው ይመስል በእግዚአብሔር ላይ ስለመቆጣቱ ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የእግዚአብሔር እጅ በኃይል ተጭኖኝ ነበር
ለማድረግ የማይፈልጋቸውን ነገሮች እንዲያደርግ እግዚአብሔር ያዘዘውና ወደ ምድር የገፋው ይመስል ሕዝቅኤል ማዘኑንና መድከሙን ይናገራል።(ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የእግዚአብሔር እጅ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “እጅ” የሚለው ቃል አብዛኛውን ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውለው የአንድን ሰው ኃይል ወይም ተግባር ለማመልከት ነው። አ.ት፡ “የእግዚአብሔር ኃይል” ወይም 2) ለተማረኩት እስራኤላውያን ይናገር ዘንድ እግዚአብሔርን ስላልታዘዘ እግዚአብሔር እንደ ተቆጣው ሕዝቅኤል አውቋል የሚሉት ናቸው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ቴል አቪቭ
በባቢሎን ያለች መንደር ስትሆን ከዋና ከተማዋ በስተደቡብ - ምስራቅ 80 ኪ.ሜ ላይ የምትገኝ፣ ባቢሎን በመባልም ትጠራ ነበር (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የኮቦር ቦይ
ይህ ከለዳውያን የእትክልት ቦታቸውን ለማጠጣት ቆፍረውት የነበረ ወንዝ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 1:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

በመገረም ፈዘዝኩኝ
“እጅግ ስለተገረምኩኝ ምንም ለማድረግ አልቻልኩም”

Ezekiel 3:16

የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ጠባቂ
የአንድ ከተማ ሕዝብ እንዲዘጋጅና እንዲድን ጠባቂው ጠላት በመምጣት ላይ መሆኑን እንደሚያስጠነቅቅ ሁሉ ሕዝቅኤል የእስራኤልን ሕዝብ እንዲያስጠነቅቅ እግዚአብሔር ነግሮታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እስራኤላውያንን” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ኃጢአተኛው በሕይወት ይኖር ዘንድ ስለ ክፉ ሥራው ማስጠንቀቂያ
ኃጢአተኛው ክፉ ሥራ መሥራቱን ማቆም እንዳለበት ግልጽ ማድረግ ይኖርብሃል። አ.ት፡ “ኃጢአተኛው በሕይወት ይኖር ዘንድ ክፉ ሥራውን ከመሥራት እንዲያቆም ማስጠንቀቂያ”

ኃጢአተኛው
“ክፉ ሕዝብ”

ደሙን ከእጅህ እፈልጋለሁ
ይህ አንድን ሰው በግድያ ወንጀል በኃላፊነት ወይም በበደለኝነት ስለመያዝ የተነገረ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “አንተ ራስህ እንደገደልከው ቆጥሬ እፈርድብሃለሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ከኃጢአቱ ወይም ከክፉ ሥራው አይመለስም
“ከክፉ ሥራው” የሚለው ሐረግ ትርጉሙ “ከኃጢአቱ” ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው። አ.ት፡ “ክፉ ነገሮችን ማድረጉን አያቆምም”

Ezekiel 3:20

በፊቱ ማሰናከያ ማስቀመጥ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “ክፉ ነገር እንዲደርስበት አድርግ” ወይም 2) “በግልጽ ኃጢአትን እንዲሠራ አድርገው” የሚሉት ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በኃጢአቱ ይሞታል
“እንደ ኃጢአተኛ ይሞታል” ወይም “እኔን ስላልታዘዘኝ እንደ በደለኛ ሰው ይሞታል”

ደሙን ከእጅህ እፈልጋለሁ
ይህ አንድን ሰው በግድያ ወንጀል በኃላፊነት ወይም በበደለኝነት ስለመያዝ የተነገረ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3:18 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “አንተ ራስህ እንደገደልከው ቆጥሬ እፈርድብሃለሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶታልና
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “አስጠንቅቀኸዋልና” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 3:22

የእግዚአብሔር እጅ
“እጅ” የሚለው ቃል አብዛኛውን ጊዜ የአንድን ሰው ኃይል ወይም ተግባር ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል። አ.ት፡ “የእግዚአብሔር ኃይል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የእግዚአብሔር ክብር
ይህንን በሕዝቅኤል 1:28 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።

የኮቦር ቦይ
ይህ ከለዳውያን የእትክልት ቦታቸውን ለማጠጣት ቆፍረውት የነበረ ወንዝ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 1:1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።

በግንባሬ ተደፋሁ
“በምድር ላይ ሰገድሁ” ወይም “በምድር ላይ ተጋደምኩ”። ሕዝቅኤል የወደቀው በአደጋ ምክንያት አይደለም። እርሱ በምድር ላይ የወደቀው ለእግዚአብሔር ያለውን አክብሮትና ፍርሐት ለማሳየት ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 1:28 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 3:24

ተናገረኝ
የአንተ ቋንቋ ተናጋሪውን መለየት ካለበት “አንድ ሰውን የሚመስል” በማለት ቢለየው ይመረጣል (ሕዝቅኤል 1:26)። እርሱ “መንፈስ ቅዱስ” አልነበረም።

በላይህ ላይ ገመድ ዘርግተው ያስሩሃል፣ ስለዚህ በመካከላቸው መውጣት አትችልም
ይህ በቀጥታ መተርጎሙ እጅግ የተሻለ ነው።

Ezekiel 3:26

የአፍህን ላንቃ
“ከውስጥ የአፍህን የላይኛውን ክፍል”

ዲዳ ትሆናለህ
“መናገር አትችልም”

ቤት
ይህ በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 2:5 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አፍህን እከፍተዋለሁ
“መናገር እንድትችል አደርግሃለሁ”

የማይሰማ አይሰማም
“ለመስማት እምቢተኛ የሆነ አይሰማም”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጌታ እግዚአብሔር
ይህንን በሕዝቅኤል 2:4 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 አንተ ግን የሰው ልጅ ሆይ ሸክላ ውሰድና የኢየሩሳሌምን ካርታ ሳልበት። የጦር ከበባ አድርግባት፣ **2** ምሽግም ስራባት፣ ዙሪያውን በአፈር ደልድለው፣ ትልቅ ቅጥር ና የጦር ሰፈሮችን አስቀምጥ ፣ ቅጥር መደርመሻ ግንዶች ዙሪያውን አስቀምጥ። **3** ክዚያም ብረት ምጣድ ለራስህ ውሰድና በአንተና በከትማይቱ መካከል በብርት አጥር ምሳሌ አቁመው። ትከበባለችና ፊትህንም ወደከትማይቱ አዙር ክበባትም! ይህም ለእስራኤል ህዝብ ምልክት ይሆናል። **4** ክዚያም በግራ ጎንህ ተኛና የእስራኤልን ህዝብ ኃጢአትም ተሸከም፤ በእስራኤል ህዝብ ፊት በግራ ጎንህ በተኛህበት ቀን ቁጥር ልክ ኃጢአታቸውን ትሸከማለህ። **5** አንድ ቀን የሚቀጡበትን አንድ አመት እንዲወክል እኔ ራሴ መድቤልሀለሁ፡ 390 ቀናት! በዚህ መልኩ የእስራኤልን ህዝብ ኃጢአት ትሸከማለህ። **6** እነዚህን ቀናት ስትጨርስ በቀኝ ጎንህ ትተኛና የይሁዳን ህዝብ ኃጢአት ለአርባ ቀናት ትሸከማለህ። አንድ ቀን አንድ አመት እንዲወክል መድቤልሀለሁ። **7** እጅህን ክልብስህ ውስጥ አውጥተህ ፊትህን ወደተከበበችው ኢየሩሳሌም ከተማ አድርገህ ትንቢት ትናገርባታለህ። **8** እነሆ! የሜርኮው ዘመን እስኪፈጸም ድረስ ከአንድ ጎን ወደ ሌላ ጎን እንዳትዞር ቀንበርን አድርጌብሀለሁ። **9** ስንዴ፣ገብስ፣ባቄላ፣ ምስር፣ ጤፍና አጃ ወስደህ በአንድ ዕቃ ውስጥ አድርገህ በጎንህ በምትተኛባቸው ቀናት ቁጥር ልክ ዳቦ ትጋግራልህ። ለ390 ቀናት ትመገበዋለህ! **10** በየቀኑ ሃያ ሃያ ሰቅል የሚመዝን ዳቦ ትበላለህ። በየጊዜውም ትመገበዋለህ። **11** አንድ ስድስተኛ ኢን ውሃም ትጠጣለህ። በየጊዜውም ትጠጣዋለህ። **12** እንደ ገብስ ቂጣ አድርገህ ትበላዋለህ፣ የምትጋገረው ግን በሰው ዓይነ ምድር ነው። **13** እግዚአቤሔር "በበተንኳቸው አህዛብ መካከል የእስራኤል ህዝብ የሚመገቡት ዳቦ ርኩስ ይሆናል።" ይላል። **14** እኔም "ወየው ጌታ እግዚአብሔር ሆይ ረክሼ አላውቅም! የሞተ ወይም በአውሬ የተገደለ በልቼ አላውቅም፣ የረከሰ ሥጋም ወደ አፌ ገብቶ አያውቅም!" አልኩኝ። **15** እርሱም "እነሆ በሰው ዓይነ ምድር ፋንታ የከብት ፍግ ስጥቼሀለሁ ዳቦውን በእርሱ መጋገር ትችላለህ" አለኝ። **16** ደግሞም "የሰው ልጅ ሆይ! ከኢየሩሳሌም የእንጀራን በትር እሰብራለሁ፣ ህዝቡም እንጀራን በጭንቅ ውሃም በስስት ይጠጣሉ። **17** የምግብና የውሃ እጥረት ስለሚኖር ሰው ወንድሙን በድንጋጤ ይመለከተዋል፣ ከኃጢአታቸው የተነሳ ይመነምናሉ።" አለኝ።

Ezekiel 4:1

የሰው ልጅ
“የሰብዓዊ ፍጡር ልጅ” ወይም “ከሰው የተወለደ ልጅ”። ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን አፅንኦት ለመስጠት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ በማለት ይጠራዋል። እግዚአብሔር ዘላለማዊና ኃያል ነው፣ ሰዎች ግን አይደሉም። ይህንን በሕዝቅኤል 2፡1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ሟች ሰው” ወይም “ሰው”

የኢየሩሳሌምን ከተማ ቅረጽ
ሕዝቅኤል ሥዕል ሊሥል እንደሆነ ግልጽ ማድረግ ይኖርብህ ይሆናል። አ.ት፡ “የኢየሩሳሌምን ከተማ ሥዕል ሣል”

በእርሷ ላይ ከበባን አድርግባት
“ከተማይቱን ለመማረክ ክበባት”

በእርሷ ላይ ምሽግን ሥራባት
“በእርሷ ላይ ጠንካራ ግንብ ሥራባት”። ሕዝቡ ከተማይቱን ትቶ እንዳይወጣ ግንቡ ያግደዋል።

በእርሷ ላይ የማጥቂያ መሰላል አቁምባት
“ጠላት እንዲገባባት በስተውጪዋ መሰላል ሥራባት”። ኢየሩሳሌም በውስጧ የሚኖረውን ሕዝብ ለመከላከል በዙሪያዋ ቅጥር ነበራት። ጠላት ወደ ውስጥ መግባት የሚችለው በቅጥሩ ላይ መዝለል የሚያስችለው መሰላል ከኖረው ብቻ ነበር።

በዙሪያዋ የግንብ ማፍረሻ መሣሪያ አኑርባት
“ሰዎች በሮቹን ሰብረው ወደ ውስጥ መግባት እንዲችሉ ትላልቅ ግንዶችን በዙሪያዋ አስቀምጥ”። “ግንብ ማፍረሻ መሣሪያዎች” ሰብረው ወደ ውስጥ መግባት እንዲቻላቸው በውትድርና ውስጥ ያሉ በርካታ ወንዶች አንሥተው ግንቡን ወይም በሩን የሚመቱባቸው ረጃጅም ዛፎች ወይም ምሶሶዎች ናቸው።

ፊትህን በእርሱ አቅጣጫ አዙር
ይህ በከተማይቱ ምሳሌ ላይ አፍጥጦ እንዲመለከት የተሰጠ ትዕዛዝ ከተማይቱ የመቀጣቷ ምልክት ነው። አ.ት፡ “በከተማይቱ ላይ አፍጥጥባት” ወይም “ጉዳት ይደርስባታልና በከተማይቱ ላይ አፍጥጥባት”

ፊትህን አቅና
እዚህ ጋ “ፊት” ፍላጎትን ወይም አትኩሮትን የሚወክል ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን “ፊትህን አቅና” የሚያመለክተው በአንድ ነገር ላይ በቀጥታ ማተኮርን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እስራኤላውያንን” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 4:4

የእስራኤልን ቤት ኃጢአት በእርሱ ላይ አኑርበት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “ስለ እስራኤላውያኑ ኃጢአት ቅጣቱን በምልክትነት ተሸከም” ወይም 2) “በኃጢአታቸው ምክንያት በጎንህ በመተኛት መከራን ተቀበል” የሚሉት ናቸው።

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እስራኤላውያንን” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ኃጢአታቸውን ትሸከማለህ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “በኃጢአታቸው ምክንያት አንተ በደለኛ ትሆናለህ” ወይም 2) “በኃጢአታቸው ምክንያት ትቀጣለህ”። ከእነዚህ ትርጉሞች ሁለቱም ክፍት በሆነው ተለዋዋጭ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ላይ እንደተመለከተው በ”ምልክታዊነት” ይገለጻል።

የእስራኤልን ቤት በመቃወም ተጋደም
“የእስራኤልን መንግሥት በቁጣ እያየህ ተጋደም”

የሚቀጡባቸውን ዓመታት እንዲወክል አንድን ቀን የምመድብልህ እኔው ራሴ ነኝ
“በምቀጣቸው ዓመታት ቁጥር ልክ ተመሳሳይ ቀናትን በጎንህ እንድትተኛ የማዝህ እኔው ራሴ ነኝ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በእያንዳንዱ በሚቀጡበት ዓመት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) በየዓመቱ ስለ ኃጢአታቸው ይቀጣሉ ወይም 2) በየዓመቱ ኃጢአትን ሠርተዋል የሚሉት ናቸው።

390 ቀናት
“ሦስት መቶ ዘጠና ቀናት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 4:6

በእነዚህ ቀናት
የእስራኤል መንግሥት እንደምትከበብ ለማመልከት ሕዝቅኤል በግራ ጎኑ የሚተኛባቸው ቀናት

ኃጢአትን ትሸከማለህ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ስለ ኃጢአት በደለኛ ትሆናለህ” ወይም 2) “ስለ ኃጢአት ተቀጣለህ”። ከእነዚህ ትርጉሞች ሁለቱም ክፍት በሆነው ተለዋዋጭ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ላይ እንደተመለከተው በ”ምልክታዊነት” ይገለጻል። እነዚህን ቃላት በሕዝቅኤል 4:4 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።

የይሁዳ ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የይሁዳን ዘሮች ያመለክታል። እነዚህን ቃላት በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። አ.ት፡ “የይሁዳ ሕዝብ ወገን” ወይም “የይሁዳ ሕዝብ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ለእያንዳንዱ ዓመት አንድ ቀን መድቤልሃለሁ
“ይህንን አንድ ቀን እኔ ለምቀጣቸው ለእያንዳንዱ ዓመት እንድታደርገው አደርግሃለሁ”

ፊትህን በተከበበችው በኢየሩሳሌም አቅጣጫ አድርግ
ይህ በኢየሩሳልም ምሳሌ ላይ አፍጥጦ እንዲመለከት የተሰጠ ትዕዛዝ ኢየሩሳሌም የመቀጣቷ ምልክት ነው። ተመሳሳዩን ሐረግ በሕዝቅኤል 4:3 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “በተከበበችው በኢየሩሳሌም ከተማ ላይ አፍጥጥባት” ወይም “ጉዳት ይደርስባታልና በተከበበችው በኢየሩሳሌም ከተማ ላይ አፍጥጥባት”

ፊትህን አቅና
እዚህ ጋ “ፊት” ፍላጎትን ወይም አትኩሮትን የሚወክል ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን “ፊትህን አቅና” የሚያመለክተው በአንድ ነገር ላይ በቀጥታ ማተኮርን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእርሱ ላይ ትንቢት ተናገር
“በኢየሩሳሌም ላይ ሊመጡ ስላሉት መጥፎ ነገሮች ትንቢት ተናገር”

እይ
“ተመልከት” ወይም “አድምጥ” ወይም “የምነግርህን ልብ በል”

ማሰሪያ እጥልብሃለሁ
ማሰሪያ አንድን ሰው ከመንቀሳቀስ የሚገድቡ ገመዶች ወይም ሰንሰለቶች ናቸው። “ማሰሪያ” የሚለው ቃል እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን ያሰረበትን አንዳች ነገር አመልካች ዘይቤአዊ አነጋገር ወይስ በቀጥታ የሚታይ ገመድ ተጠቅሞ እንደሆነ ግልጽ አይደለም። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 4:9

ስንዴ፣ ገብስ ... ማሽላ፣ ---
እነዚህ የተለያዩ የጥራጥሬ ዓይነቶች ናቸው።

ባቄላ
ሐረግ፣ ዘሩ ሊበላ የሚችል፣ በተናጠል የሚያድግ ያለበለዚያ ፍሬ አልባ የሚሆን

ምስር
ይህም እንደ ባቄላ ነው፣ ነገር ግን ዘሩ በጣም ትንሽ፣ ክብና በመጠኑ ጠፍጠፍ ያለ ነው። (የማይታወቁትን መተርጎም የሚለውን ተመልከት)

390 ቀናት
“ሦስት መቶ ዘጠና ቀናት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

በቀን ሃያ ሰቅል
“በቀን 20 ሰቅል”። አንድ ሰቅል የ11 ግራም ያህል ክብደት አለው። አ.ት፡ “በየቀኑ 200 ግራም እንጀራ” (ቁጥሮች እና ክብደት በመጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ተመልከት)

የኢን ስድስተኛ
“1/6ኛ ኢን” ወይም “የኢን ስድስተኛ ክፍል” ወይም “ግማሽ ሊትር ገደማ”

አንድ ኢን
አንድ ኢን 3.7 ሊትር ነው።

Ezekiel 4:12

ትበላዋለህ
“እርሱን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እንጀራን ነው (ሕዝቅኤል 4:9)።

የገብስ እንጀራ
ከገብስ የሚዘጋጅ ዝርግ እንጀራ (ሕዝቅኤል 4:9) (የማይታወቁትን መተርጎም የሚለውን ተመልከት)

ከሰው በሚወጣ ሰገራ ትጋግረዋለህ
“በደረቅ የሰው ሰገራ እሳት በማንደድ ታበስልበታለህ”። የአንተ ቋንቋ ይህንን በትህትና የሚገልጽበት መንገድ ይኖረው ይሆናል።

ይወገዳሉ
በኃይል ይባረራሉ

Ezekiel 4:14

ኦ! ጌታ እግዚአብሔር
“ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፣ ይህንን ማድረግ አይገባኝም”። ጌታ እንዲያደርግ ባዘዘው ነገር ሕዝቅኤል በጣም ተረብሿል።

ጌታ እግዚአብሔር
ይህንን በሕዝቅኤል 2:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። እዚህ ጋ ሕዝቅኤል እየተናገረ ያለው ለጌታ ነው።

የተበከለ ሥጋ ወደ አፌ ከቶ ገብቶ አያውቅም
“የተበከለ ሥጋ ከቶ በልቼ አላውቅም”

የተበከለ ሥጋ
“አስቀያሚ፣ እርኩስ ሥጋ”። ይህ በበሽታ ወይም በእርጅና ምክንያት ከሞተ ወይም በሌላ እንስሳ ከተገደለ እንስሳ የመጣ እርኩስ ሥጋን ያመለክታል።

ተመልከት
“ስማ” ወይም “አሁን ለምነግርህ ጠቃሚ ነገር ትኩረት ስጥ”

ሰጥቼሃለሁ
“እንድትጠቀምበት እፈቅድልሃለሁ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የከብት ፍግ
ከከብቶች የሚገኝ ኩበት። የአንተ ቋንቋ ይህንን የሚገልጽበት የትህትና አገላለጽ ይኖረው ይሆናል።

የሰው ሰገራ
ከሰው የሚወጣ ጠጣር ሰገራ። የአንተ ቋንቋ ይህንን የሚገልጽበት የትህትና አገላለጽ ይኖረው ይሆናል። ይህንን በሕዝቅኤል 4፡12 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።

Ezekiel 4:16

እነሆ
“ተመልከት” ወይም “ስማ” ወይም “የምነግርህን ልብ በል”

በኢየሩሳሌም የእንጀራን በትር እሰብራለሁ
“የኢየሩሳሌምን የምግብ አቅርቦት አቆማለሁ”

የእንጀራ በትር
አቅርቦቱ በትር ተብሎ ተጠርቷል፤ ምክንያቱም አንዳንድ ሰዎች መንገድ ለመሄድና ሥራቸውን ለመሥራት ምርኩዝ እንደሚፈልጉ ሁሉ ሰዎች በሕይወት ለመኖር ምግብ ይፈልጋሉ። እንጀራ ሁሉንም ዓይነት ምግብ ይወክላል። አ.ት፡ “የምግብ አቅርቦት” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና Synecdoche የሚለውን ተመልከት)

እንጀራን በስጋት መጥነው ይበላሉ
እንጀራውን ለምን እንደሚመጥኑት ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። “ላይበቃቸው እንደሚችል በማሰብ እንጀራቸውን በጥንቃቄ ይከፋፍላሉ”

መመጠን
ለብዙ ሰዎች የማይበቃ ሲሆን የአንድን ነገር አነስተኛ መጠን መስጠት ነው።

እርሱን በመንቀጥቀጥ መመጠን
“መደንገጥ” የሚለው ቃል የመፍራት ዘይቤአዊ አነጋገር ሲሆን “መንቀጥቀጥ” ፍርሃትን ይወክላል። አ.ት፡ “እየደነገጡ መመጠን” ወይም “እየፈሩ መመጠን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እያንዳንዱ ሰው በወንድሙ ተስፋ ይቆርጣል፣ መንምኖም ይጠፋል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “እያንዳንዱ ወንድሙ ምን ያህል ምግብ በመብላት መንምኖ እንደሚጠፋ በማየት ይጨነቃል”

መንምኖ መጥፋት
“መንምኖ መጥፋት” የሚለው ሐረግ በአብዛኛው ጥቅም ላይ የሚውለው ለሥጋ ወይም ለሚበሰብስ እንጨት ነው። እዚህ ጋ በዘይቤአዊ አነጋገር ክፉ ሰዎች ምግብ ስለሌላቸው እንደሚከሱና እንደሚሞቱ ያሳያል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 5

1 "ከዚያም የሰው ልጅ ሆይ ጎራዴን እንደጢም መላጫ ተጠቀመህ ራስህንም ጢምህንም ተላጨው፣ በመቀጠልም ሚዛን ተጠቅመህ ጠጉሩን ትከፍለዋለህ። **2** የምርኮው ዘመን ሲያበቃ የጠጉሩን አንድ ሶስተኛ በከተማው መካከል በእሳት ታቃጥለዋለህ። አንድ ሶስተኛውንም ወስደህ በክተማይቱ ዙሪያ አስቀምጠህ በሰይፍ ትመታዋለህ። ከዚያም አንድ ሶስተኛውን ወደ ነፋስ ትበትነዋለህ፣ እኔም ህዝቡን አሳድድ ዘንድ ሰይፌን እመዛለሁ። **3** ነገር ግን ጥቂት ጠጉሮችን ወስደህ በጋቢህ ጫፍ ላይ ትቋጥረዋለህ። **4** ክዚያም በርከት ያለ ጠጉር ወስደህ ወደ እሳቱ መሀል ጥለህ በእሳቱ አቃጥለው፤ በእሳት ውስጥ ይቃጠል፤ ከዚያም ውስጥ እሳት ወደ እስራኤል ህዝብ ሁሉ ይወጣል።" **5** ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "ይህች በሌሎች አገሮች ዙሪያዋን እንድትዋሰን ያደረኳት፣ በአህዛብ መካከል ያለች ኢየሩሳሌም ናት። **6** ነግር ግን ከሌሎች አህዛብ ይልቅ ከኃጢአታቸው የተነሳ ትዕዛዛቴን አቃለዋል፣ በዙሪያቸው ካሉ አገሮች ይልቅ ህጌን ተላልፈዋል። ፍርዴን አቃለዋል በህጌም አልኖሩም!" **7** ስለዚህም ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "በዙሪያቹ ካሉ አገሮች ይልቅ አመጸኞች ስለሆናችሁና በህጌ ስላልኖራችሁ ተግባራችሁም እንድትዕዛዛቴ ስላልሆነ ይባስ ብሎ የምታደርጉት ሁሉ በዙሪያችሁ እንዳሉት አግሮች ትዕዛዝ ስለሆነ ።" **8** ስለዚህም ይላል ጌታ እግዚአብሔር "እነሆ! እኔ እራሴ በእናንተ ላይ እነሳለሁ! አህዛብ ሁሉ ያዩ ዘንድ ፍርዴን በመካከልሽ አመጣለሁ። **9** ከጸያፍ ተግሮችሽ የተነሳ አድርጌ የማላውቀውን ደግሜም የማላደርገውን ነገር በአንቺ ላይ አደርጋለሁ። **10** ስለዚህም በመካከልሽ አባቶች ልጆቻችውን ልጆችም አባቶቻቸውን ይበላሉ፣ ፍርድንም አመጣብሻለሁና የተርፉትን በየአቅጣጫው እበትናቸዋለሁ! **11** ስለዚህም በራሴ እምላለሁ፦ ይህ የጌታ የእግዚአብሄር አዋጅ ነው- ቤተመቅደሴን በሚያስጠሉ ነግሮችና በሚያጸይፉ ተግባራት ሞልታችሁታልና ከቁጥር አጎድላችኋለሁ፤ ፊቴን አልመልስልሽም፣ አልራራልሽምም። **12** አንድ ሶስተኛችው ህዝብ በመቅሰፍት ይሞታል በመካከልሽም በረሀብ ያልቃሉ፣ አንድ ሶስተኛው ደግሞ በከበቡሽ ጠላቶች ሰይፍ ይገደላሉ። ቀሪውን አንድ ሶስተኛ ደግሞ በየአቅጣጫው እበትናቸዋለሁ አሳድዳቸውም ዘንድ ሰይፌን ከሰገባው እመዛለሁ። **13** ከዚያም ቁጣዬ ይፈጸማል፣ በእነርሱም ላይ የነበረኝ ንዴት ይበርዳል። በእነርሱ ላይ የነበረኝ ንዴቴ በተፈጸመ ጊዜ እኔ እግዚአብሄር በቁጣዬ እንደተናገርኳቸው ያውቃሉ። **14** ዙሪያሽን በከበቡሽ አህዛብና በአላፊ አግዳሚው ሁሉ የተዋረድሽና አሳፋሪ አድርግሻለሁ። **15** ስለዚህ ኢየሩሳሌም በሌሎች የምትወገዝና መቀለጃ በዙሪያዋ ላሉ አህዛብ ቁጣና ድንጋጤ ትሆናልች። ፍርዴን በንዴትና በቁጣ በጽኑ ተግሳጽም አመጣባችኋለሁ- እኔ እግዚአብሔር ይህን ተናግሬአለሁ። **16** የርሀብን አስከፊ ቀስቶች እሰድባችኋለሁ፣ ያም እናንተን የማጠፋበት መሳሪያ ይሆናል። ርሀብን አበዛለሁ የእንጀራ በትራችሁንም እሰብራለሁ። **17** ልጆች አልባ እንድትሆኑ ርሀብና አደጋን እልክባችኋለሁ። መቅሰፍትና ደም በመካከላችሁ ያልፋል ሰይፍንም አመጣባችኋለሁ -- እኔ እግዚአብሄር ይህን ተናግሬአልሁ!"

Ezekiel 5:1

የሰው ልጅ
“የሰብዓዊ ፍጡር ልጅ” ወይም “ከሰው የተወለደ ልጅ”። ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን አፅንኦት ለመስጠት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ በማለት ይጠራዋል። እግዚአብሔር ዘላለማዊና ኃያል ነው፣ ሰዎች ግን አይደሉም። ይህንን በሕዝቅኤል 2፡1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ሟች ሰው” ወይም “ሰው”

የጸጉር ቆራጭ ምላጭ
“ጸጉር ለመቁረጥ የሚያገለግል ምላጭ”

በራስህና በጺምህ ላይ ምላጭ አሳልፍ
“ጸጉርህንና ጺምህን ተላጨው” ወይም “ከራስህ ላይ ጸጉርህን፣ ከፊትህም ላይ ጺምህን አስወግድ”

አንድ ሦስተኛውን አቃጥለው
“ከጸጉርህ አንድ ሦስተኛውን አቃጥለው”)

መካከል
መካከል

የከበባዎቹ ቀናት በሚያበቁበት ጊዜ
“የኢየሩሳሌም የከበባዎቹ ቀናት ባበቃ ጊዜ” ወይም “ኢየሩሳሌም እንዴት በከበባ ስር እንደምትወድቅ የምታሳይበት ቀናት በሚያበቁበት ጊዜ”

አንድ ሦስተኛውን ጸጉር ውሰድ
“ከሦስቱ የጸጉር ክምሮች አንደኛውን ውሰድ”

እርሱን በከተማይቱ ዙሪያ ሁሉ በሰይፍ ምታው
“እርሱን በከተማው ሁሉ ላይ በሰይፍህ ምታው”

Ezekiel 5:3

ነገር ግን ውሰድ ... ከዚያም ውሰድ
ሕዝቅኤል ጸጉሩንና ጺሙን በተላጨ ጊዜ ጸጉሩን ከማቃጠሉ በፊት ይህንን ማድረግ ነበረበት (ሕዝቅኤል 5፡1-2)። እነዚህን ቁጥሮች ከእነዚያ ቁጥሮች በፊት ማድረግ ይኖርብህ ይሆናል። “ይሁን እንጂ ጸጉርህንና ጺምህን በምትላጭበት ጊዜ ከማቃጠልህ በፊት . . . ውሰድ። ከዚያም ጸጉሩን በንፋስ ላይ ከበተንከው በኋላ ውሰድ” (የሁነቶች ቅደም ተከተል እና የቁጥር መሸጋገሪያ የሚለውን ተመልከት)

ከእነርሱ ላይ ጥቂት ቁጥር ያለውን ጸጉር
“ከክምሩ ላይ ጥቂት ጸጉሮችን”

በአንድ ላይ እሰራቸው
“እነርሱን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጸጉሮቹን ነው። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ጸጉሮቹ ሕዝቅኤል ሊያስራቸው እስኪችል ድረስ ረጅም ነበሩ ወይም 2) ሕዝቅኤል ጸጉሮቹን በአንድ ላይ መስፋት ወይም ማጣበቅ ነበረበት 3) ሕዝቅኤል ጸጉሮቹን በልብስ እጥፋት ውስጥ ማስቀመጥ ነበረበት የሚሉት ናቸው።

በልብስህ እጥፋት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “በክንድህ ላይ ያለ ልብስ” (“የልብስህ እጅጌዎች”) ወይም 2) “የልብስህ ዘርፍ” (“የልብስህ ጠርዝ”) ወይም 3) መታጠቂያ ላይ የሚሸጎጥበት የልብስ እጥፋት የሚሉት ናቸው።

እሳት ከዚያ ወደ እስራኤል ቤት ሁሉ ይወጣል
“እሳት ከዚያ ይስፋፋል፣ የእስራኤልን ሕዝብ በሙሉ ያቃጥላል”። እስራኤል በዚያ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ቤተሰቦች የሆኑ ያህል (ይሁን እንጂ በዚያን ጊዜ ከቤቱ ውጭ ነበሩ) እግዚአብሔር በቤቱና በእስራኤል ሕዝብ ላይ እሳት በመለኮስ እስራኤልን እንዴት እንደሚቀጣት ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እስራኤላውያንን” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 5:5

ጌታ እግዚአብሔር
ይህንን በሕዝቅኤል 2:4 እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።

ይህቺ ኢየሩሳሌም ናት
“ይህ ቅርጽ ኢየሩሳሌምን ይወክላል” (ሕዝቅኤል 4:1)

በሀገሮች መካከል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) በኢየሩሳሌም ዙሪያ ሁሉ ሌሎች ሀገሮች ነበሩ ወይም 2) “ከሌሎች ሀገራት ሁሉ ይልቅ በጣም ጠቃሚ” የሚሉት ናቸው።

አስቀምጫታለሁ
ኢየሩሳሌም “እርሷ” እና “የእርሷ” ተብላ ተመልክታለች (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

ሌሎች ምድሮች
“አጎራባች ሀገሮች” ወይም “በዙሪያዋ ያሉ ሀገሮች”

ሕዝቡ ፍርዴን አልተቀበሉም
“ኢየሩሳሌምና የእስራኤል ሕዝብ ፍርዴን ለመታዘዝ እምቢ ብለዋል”

Ezekiel 5:7

ጌታ እግዚአብሔር
ይህንን በሕዝቅኤል 2:4 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት

ምክንያቱም አንቺ ከማንም ይልቅ አስቸጋሪ ነሽ
“ምክንያቱም ኃጢአተኝነትሽ ከማንም ይልቅ የከፋ ነው” ወይም “ምክንያቱም ከማንም ይልቅ ሲበዛ የማትታዘዢ ነሽ”

የከበቡሽ ሁሉ
“በዙሪያሽ ያሉ ሁሉ”

በሕጌ አልሄዱም
መሄድ የአንድን ሰው የሕይወት አኗኗር የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “በሕጌ መሠረት አልኖሩም” ወይም “ሕጌን አልታዘዙም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ወይም በድንጋጌዬ መሠረት አድርገዋል
“ወይም ድንጋጌዎቼን ታዘዋል”

እነሆ!
“ተመልከቱ!” ወይም “ስሙ!” ወይም “የምነግራችሁን ልብ በሉ!”

ፍርዴን በመካከላችሁ እፈጽማለሁ
“በተለያየ መንገድ እፈርድባችኋለሁ” ወይም “እቀጣችኋለሁ”።

Ezekiel 5:9

ያላደረግሁትንና ዳግመኛም የማላደርገውን
“ቀድሞ ያላደረግሁትንና ዳግመኛ በተመሳሳይ መንገድ የማላደርገውን” ወይም “ቀድሞ ከቶ ያላደረግሁትንና ዳግመኛም ከቶ የማላደርገውን”።

በአስጸያፊ ተግባሮችሽ ሁሉ ምክንያት
“በምታደርጊያቸው አስጸያፊ ነገሮች ሁሉ ምክንያት”። ሕዝቡ ጣዖታትንና ሐሰተኞች አማልክትን ያመልኩ ስለ ነበር እግዚአብሔር ተቆጥቷል።

በመካከልሽ አባቶች ልጆቻቸውን ይበላሉ፣ ወንዶቹ ልጆችም አባቶቻቸውን ይበላሉ
ሕዝቅኤል የሚነግራቸው ምናልባት ሕዝቡ የሚበሉትን ምግብ በሚያጡበት ጊዜ በእርግጠኝነት ምን ሊሆን እንዳለ ነው።

ፍርድን እፈጽምብሻለሁ
“እፈርድብሻለሁ” ወይም “የከፋ ቅጣት እቀጣሻለሁ”

የቀራችሁትን ሁሉ በተለያየ አቅጣጫ እበትናችኋለሁ
“የቀራችሁትን ሁሉ ወደ ተለያዩ ቦታዎች እንድትሄዱ አስገድዳችኋለሁ”

Ezekiel 5:11

ሕያው እንደ መሆኔ
“ሕያው መሆኔ እርግጥ የመሆኑን ያህል”። እግዚአብሔር ቀጥሎ የሚናገረው የተረጋገጠ እውነት መሆኑን ለማሳየት ይህንን አገላለጽ ይጠቀማል። ይህ ጽኑ ተስፋ የመስጫ መንገድ ነው። አ.ት፡ “ጽኑ መሐላ አደርጋለሁ” (የአነጋገርዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ይህ የጌታ እግዚአብሔር ቃል ነው
እግዚአብሔር የንግግሩን እርግጠኝነት ለመግለጽ የራሱን ስም በመጥራት ይናገራል። አ.ት፡ “ጌታ እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን ነው” ወይም “እኔ፣ ጌታ እግዚአብሔር የተናገርኩት ይህንን ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

ጌታ እግዚአብሔር
ይህንን በሕዝቅኤል 2:4 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት

ማርከስ ... መቅደስ
እግዚአብሔር ለራሱ አገልግሎት ብቻ የለየውን ስፍራ አበላሽተውታል

በሚያስጠሉ ነገሮቻችሁ ሁሉ
“ከምጠላቸው ነገሮቻችሁ ሁሉ ጋር”። ይህ ጣዖታትን እንደሚያመለክት ግልጽ ማድረግ ይኖርብህ ይሆናል። “ከምጠላቸው ጣዖቶቻችሁ ሁሉ ጋር” ወይም “አስጸያፊ ከሆኑት ጣዖቶቻችሁ ሁሉ ጋር”

አስጸያፊ ከሆኑት ተግባሮቻችሁ ሁሉ ጋር
“እናንተ ከምታደርጓቸው አስጸያፊ ነገሮቻችሁ ሁሉ ጋር”

ዓይኔ አይራራልሽም
ዓይን ባለቤቱ ስለሆነው ስለ ሰው የተነገረ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “አልራራልሽም”

አልምርሽም
“ያለ ጥርጥር እቀጣሻለሁ”

በመካከልሽ በረሃብ ይጠፋሉ
“በረሃብ ምክንያት ከእነርሱ ብዙዎቹ ይሞታሉ”

Ezekiel 5:13

ቁጣዬ ይፈጸማል
“ተቆጥቼ ለማድረግ የፈለግሁትን ሁሉ ስላደረግሁ ከዚህ በኋላ አልቆጣም”

ንዴቴ በእነርሱ ላይ እንዲበርድ አደርጋለሁ
“ንዴት” የሚለው ቃል ብርቱ ቁጣ ማለት ሲሆን እዚህ ጋ ቅጣትን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። “በሚገባ ስለቀጣኋቸው እነርሱን መቅጣቴን አቆማለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ረክቻለሁ
እግዚአብሔር ለምን እንደሚረካ ግልጽ ማድረግ ይኖርብህ ይሆናል። አ.ት፡ “በበቂ ሁኔታ ስለቀጣኋቸው እረካለሁ”

በእነርሱ ላይ ንዴቴን በምፈጽምበት ጊዜ
“እነርሱን መቅጣቴን በምጨርስበት ጊዜ”

Ezekiel 5:15

በቁጣና በንዴት
“ቁጣ” እና “ንዴት” የሚሉት ቃላት መሠረታዊ ትርጉማቸው አንድ ነገር ሲሆን እግዚአብሔር በጣም ስለመቆጣቱ አጽንዖት ይሰጣሉ። አ.ት፡ “በጣም ስለተቆጣሁሽ”

የረሃብን አሰቃቂ ፍላጻዎች በአንቺ ላይ እወረውራለሁ
“ፍላጻዎች” የሚለው ቃል ሕዝቡ ለረጅም ጊዜ ምግብ በሚያጡበት ጊዜ የሚሰማቸውን ብርቱ ህመም የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “የጽኑ ረሃብ ህመም እንዲሰማችሁ አደርጋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ረሃብን አበዛባችኋለሁ
“ረሃባችሁን አስከፊ አደርገዋለሁ” ወይም “ረሃባችሁ ለረጅም ጊዜ እንዲቆይ አደርጋለሁ” ወይም “የምትበሉት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያነሰባችሁ እንደሚሄድ እርግጠኛ ሁኑ”

የእንጀራችሁን በትር መስበር
“በትር” ሰዎች ለድጋፍ የሚመረኮዙት ነገር ነው። ይህ ሐረግ ሕዝቡ የተማመነበትን የምግብ አቅርቦት የማስወገድ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። “የእንጀራ በትር” በሕዝቅኤል 4:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ተመልከት። አ.ት፡ “የምግብ አቅርቦታችሁን አቋርጣለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በመካከላችሁ ቸነፈርና ደም ያልፋል
በሽታና አስከፊ ሞት በከተማው ውስጥ በመዘዋወር ያገኙትን ሁሉ በሚገድሉ ወታደሮች ተመስለዋል። አ.ት፡ “ብዙ ሰዎች በበሽታ ይሞታሉ፣ ሌሎች ብዙዎች ደግሞ በጦርነት ይሞታሉ” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

በእናንተ ላይ ሰይፍን አመጣለሁ
“ሰይፍ” የሚለው ቃል ሰይፍን በመጠቀም ሰዎችን የሚገድሉትን ወታደሮች የሚያመለክት ፊሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “እኔ ራሴ ወታደሮች መጥተው እንዲገድሏችሁ አደርጋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 6

1 የእግዚአብሄር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ **2** "የሰው ልጅ ሆይ ፊትህን ወደ እስራኤል ተራሮች አዙርና ትንቢት ተናገር። **3** እንዲህም በላቸው 'የእስራኤል ተራሮች ሆይ የጌታ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ! ጌታ እግዚአብሔር ለተራሮች፣ ለኮረብቶች፣ ለሸንተረሮችና ለሸለቆዎች እንዲህ ይላል፡ እነሆ ሰይፍን አመጣባችኋለሁ ከፍታችሁን ሁሉ አጠፋለሁ። **4** መሰዊያዎቻችሁ ባድማ ይሆናሉ የዕጣን መሰዊያዎቻችሁም ይደመሰሳሉ የሞቱ ሰዎቻችሁን ሬሳዎች በጣዖቶቻቸው ፊት እጥላለሁ። **5** የእስራኤልን ህዝብ ሬሳዎችን በጣዖቶቻቸው ፊት አጋድማለሁ፣ አጥንቶቻችሁንም በመሰዊያዎቻችሁ ዙሪያ እበትናለሁ። **6** መሰዊያዎቻችሁ የተጣሉና ባድማ እንዲሆኑ የምትኖሩባቸው ከተሞች ሁሉ የተጣሉ የማምለኪያ ኮረብቶቻቸው ሁሉ ባድማ ይሆናሉ፣ እንዳልነበሩም ሆነው ይጠፋሉ፤ የዕጣን መሰዊያዎቻችሁ ይወገዳሉ ሥራቼሁ ሁሉ ተጠርጎ ይጠፋል። **7** የሰዎች ሬሳ በመካከላችሁ ይወድቃል ያን ጊዜ እኔ እግዚአብሔር እንደሆንኩ ታውቃላችሁ! **8** ነገር ግን ቅሬታዎችን አስቀራለሁ፣ እናንተ በየአገሩ ስትበተኑ ከአህዛብ መካከል ከሰይፍ የሚያመልጡ ይኖራሉ። **9** እነዚያ ያመለጡትም በምርኮ አገር ሆነው ከእኔ ዘወር ካለው አመንዝራ ልባቸውና ወደ ጣዖታቶቻቸው ከሚያየው አመንዝራ ዓይናቸው የተነሳ ምን ያህል እንዳዝንኩ ስለእኔ ያስባሉ። ባደረጉት ክፋትና ርኩሰት መጸጸታቸው ከፊታቸው ይነበባል። **10** ስለዚህም እኔ እግዚአብሔር እንደሆንኩ ያውቃሉ። ይህን ክፉ ነገር አመጣባቸዋለሁ ብዬ አስቀድሜ የተናገርኩት በዓላማ ነው። **11** ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡ ከፈጸሙት አስነዋሪ ተግባር የተነሳ የእስራኤል ህዝብ በሰይፍ፣ በረህብና በቸነፈር ይጠፋሉና በእጅህ እያጨበጭችብክ በእግርህም መሬቱን እየመታህ "ወዮ" እያልክ ጩህ! **12** በሩቅ ያለው በቸነፈር በቅርብ ያለው በሰይፍ ይጠፋሉ። ከዚያ የተረፉት ደግሞ በርህብ ያልቃሉ፤ በዚህ መንገድ ቁጣዬን በእነርሱ ላይ እፈጽማለሁ። **13** በጣዖቶቻቸው መካከል፣ በመሰዊያዎቻቸው ዙሪያ፣ ከፍ ባሉ ተራሮቼ አናት ላይ፣ እንዲሁም በለመለመ ዛፍ ሁሉና በግዙፍ ዋርካ ስር- ለጣዖቶቻቸው በሚያጤኑበት ሥፍራ ሁሉ የተገደሉ ሰዎቻቸው ተጥለው ሲያዩ ያን ጊዜ እኔ እግዚአብሔር እንደሆንኩ ያውቃሉ። **14** በገዛ እጄ እመታችኋለሁ የሚኖሩብትን ስፍራ ሁሉ ከምድረ በዳ እስከ ዲብላህ ድረስ ምድሪቱን የተጣለችና ባድማ አደርጋታለሁ።"

Ezekiel 6:1

የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንዳች ነገር መናገሩን ለማስታወቅ ጥቅም ላይ የዋለ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት: “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እግዚአብሔር እነዚህን ቃላት ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የሰው ልጅ
“የሰብዓዊ ፍጡር ልጅ” ወይም “ከሰው የተወለደ ልጅ”። ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ በማለት ይጠራዋል። እግዚአብሔር ዘላለማዊና ኃያል ነው፣ ሰዎች ግን አይደሉም። ይህንን በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት: “ሟች ሰው” ወይም “ሰው”

ፊትህን በእስራኤል ተራሮች ላይ አንሣ
ይህ በዚያ ያሉትን ሰዎች ስለ መቅጣቱ ምሳሌ ይሆን ዘንድ በተራሮቹ ላይ እንዲያፈጥ የተሰጠ ትዕዛዝ ነው። ተመሳሳዩን ሐረግ በሕዝቅኤል 4:3 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት: “በእስራኤል ተራሮች ላይ አፍጥጥ” ወይም “በዚያ የሚኖሩት ሰዎች ጉዳት ያገኛቸው ዘንድ በእስራኤል ተራሮች ላይ አፍጥጥ”

ፊትህን በእስራኤል ተራሮች ላይ አቅና
ፊትህን በእስራኤል ተራሮች ላይ አቅና የእስራኤል ተራሮች የሚገኙት ርቀት ላይ ነበር፤ በመሆኑም ሕዝቅኤል ሊያያቸው አይችልም፤ ነገር ግን በዚያ አቅጣጫ ማፍጠጡ የመጎዳታቸው ምልክት ነበር። አ.ት: “ወደ እስራኤል ተራሮች ዙርና አፍጥጥባቸው” ወይም “በዚያ ያሉ ሰዎች ጉዳት እንዲደርስባቸው በእስራኤል ተራሮች አቅጣጫ አፍጥጥ”

ፊትህን አቅና
እዚህ ጋ “ፊት” የትኩረት ወይም የመመልከት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የእስራኤል ተራሮች
“በእስራኤል ምድር ያሉ ተራሮች”

እነሆ!
“ተመልከቱ!” ወይም “ስሙ!” ወይም “የምነግራችሁን ልብ በሉ!”

ጌታ እግዚአብሔር
ይህንን በሕዝቅኤል 2:4 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።

ሰይፍን አመጣባችኋለሁ
“ሰይፍ” የሚለው ቃል ሰይፍን በመጠቀም ሰዎችን የሚገድሉትን ወታደሮች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት: “ወታደሮች መጥተው እንዲገድሏችሁ እጠራቸዋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 6:4

ከዚያም መሰዊያዎቻችሁ ወና ይሆናሉ፣ ዐምዶቻችሁም ይሰባበራሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት: “ወደ ፊት ሰዎች በመሰዊያዎቻችሁ ላይ አይሰዉም፣ ጠላቶቻችሁም ዐምዶቻችሁን ይሰባብራሉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እጥላለሁ ... አጋድማለሁ ... እበትናለሁ
እግዚአብሔር ወደ እነዚህ ነገሮች ወታደሮችን እንደሚልክ ይናገራል (ሕዝቅኤል 6:3)። አ.ት: “... እንዲጥሉ ወታደሮችን እልካለሁ፤ እነርሱ ... ያጋድማሉ ... ይበትናሉም”

ሙታናችሁን
“የሞቱትን ሰዎቻችሁን”

Ezekiel 6:6

ከተሞች ባድማ ይሆናሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት: “የጠላት ወታደሮች ከተሞቻችሁን ባድማ ያደርጋሉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ይሰበራሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት: “የጠላት ወታደሮች መሰዊያዎቻችሁን ይሰባብራሉ” ወይም “የጠላት ወታደሮች ይሰባብሯቸዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ዐምዶቻችሁ ይቆራረጣሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። “ዐምዶች”ን በሕዝቅኤል 6:4 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት: “ዐምዶቻችሁን ይቆራርጧቸዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሥራዎቻችሁ ተጠርገው ይወሰዳሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ሥራዎቻችሁን ማንም አያስብም” ወይም “የሠራችኋቸውን ሁሉ ያጠፉታል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ሙታን በመካከላችሁ ይጋደማሉ
“ጠላት ብዙ ሰዎችን ሲገድል ታያላችሁ”

እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ታውቃላችሁ
እግዚአብሔር ሰዎች እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን ያውቃሉ ብሎ በሚናገርበት ጊዜ እርሱ ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለው ብቸኛው እውነተኛ አምላክ መሆኑን ሰዎች ያውቃሉ ማለቱ ነው። አ.ት፡ “እውነተኛው አምላክ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ትረዳላችሁ” ወይም “ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለኝ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ትገነዘባላችሁ”

Ezekiel 6:8

ከሰይፍ ያመለጡ ጥቂቶች
“ሰይፍ” የሚለው ቃል ሰይፍን በመጠቀም ሰዎችን የሚገድሉ ወታደሮችን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ወታደሮቹ የማይገድሏቸው ጥቂቶች” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በየሀገሩ በምትበተኑበት ጊዜ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “በተለያዩ ሀገሮች በምበትናችሁ ጊዜ” ወይም “በሌሎች ሀገሮች እንድትኖሩ በማስገድዳችሁ ጊዜ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ከእኔ በራቀው ሴሰኛ ልባቸው አዝኛለሁ
እግዚአብሔር ከብዙ ሰዎች ጋር እንደምትተኛ እንደ አንዲት ሴት አድርጎ የተናገረው ስለ እስራኤል ነው። አ.ት፡ “ልክ ሚስቴ እኔን ትታ ከሌሎች ወንዶች የተኛች ያህል አዝኛለሁ”)

ከጣዖቶቻቸው ኋላ በሚያመነዝሩ ዓይኖቻቸው
እግዚአብሔር አንዲት ያገባች ሴት ሌሎች ወንዶችን እንደምታይና ከእነርሱ ጋር ለመተኛት እንደምትመኝ አድርጎ የሚናገረው ስለ እስራኤላውያን ነው። አ.ት፡ “በነገራችን ላይ ጣዖታትን ለማምለክ በብርቱ ተመኝተዋል”

ስለ ሠሩት ክፋት የጥላቻ ፊት ያሳያሉ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ባደረጓቸው ክፉ ነገሮች ምክንያት ራሳቸውን መጥላታቸውን የፊት ገጽታቸው ያሳያል” ወይም 2) “ያደረጓቸውን ክፉ ነገሮች መጥላታቸውን ፊታቸው ያሳያል” የሚሉት ናቸው።

Ezekiel 6:11

ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
እርሱ የሚናገረው አስፈላጊ መሆኑን ለሕዝቅኤልና ለሕዝቡ ለማስታወስ እግዚአብሔር ስለ ራሱ በስሙ ይናገራል። አ.ት፡ “እኔ ጌታ እግዚአብሔር ይህንን እናገራለሁ” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

ጌታ እግዚአብሔር
ይህንን በሕዝቅኤል 2:4 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።

እጆችህን አጨብጭብ፣ በእግሮችህም እርገጥ
ሕዝቅኤል የሕዝቡን ትኩረት ለማግኘት ይህንን ምልክታዊ ተግባር ይፈጽም ነበር። ይህ የድጋፍ ጭብጨባ አልነበረም።

ወይኔ
ይህ ቃል የተነገረው በእነዚያ ክፉ ነገሮችን የሚሠሩ ሰዎችን ባዩት እና በክፉ አድራጊዎች ላይ ክፉ ነገሮች ውጤት ሆነው እንደሚደርሱባቸው በተገነዘቡ ሰዎች ነው። የአንተ ቋንቋ ተመሳሳይ ቃል ካለው እዚህ ጋ ልትጠቀምበት ያስፈልግህ ይሆናል።

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እስራኤላውያንን” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በሰይፍ፣ በረሃብ እና በቸነፈር ይወድቃሉ
“መውደቅ” “መሞት”ን በጨዋነት የመግለጫ ቃል ነው። “ሰይፍ” የሚለው ቃል ሰይፍን በመጠቀም ሰዎችን የሚገድሉ ወታደሮችን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው።

በእነርሱ ላይ ንዴቴን እፈጽማለሁ
“በእነርሱ ላይ ቁጣዬን አረካለሁ” ወይም “ዳግመኛ እስከማልቆጣ ድረስ እቀጣቸዋለሁ”

Ezekiel 6:13

ከፍ ባለው ኮረብታ ሁሉ ላይ በመሰዊያዎቻቸው ዙሪያ
“ከፍ ባለ ኮረብታ ሁሉ ላይ ባሉት በመሰዊያዎቻቸው ዙሪያ” የሚለው ሌላው ሊሆን የሚችል ትርጉም ነው።

ኮረብታ -- በተራሮቹ ጫፍ ሁሉ ላይና ከለመለሙት ዛፎችና ቅጠሉ ጥቅጥቅ ያለ ዋርካ ስር
“ኮረብታ፣ በተራሮች ጫፍ ሁሉ ላይ፣ ከእያንዳንዱ የለመለመ ዛፍ ስር እና ከእያንዳንዱ ቅጠሉ ጥቅጥቅ ያለ ዋርካ ስር”

የለመለመ
ጤናማና የሚያድግ

ዋርካ
ለአምላኪዎች ጥላ የሚሰጣቸው ጠንካራ እንጨት ያለው ረጅም ዛፍ

ሪብላ
የአንዲት ከተማ ስም (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 7

1 የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፣ 2 "አንተ የሰው ልጅ ሆይ -- ጌታ እግዚአብሔር ለእስራኤል ምድር የሚለው እንዲህ ነው፣ 'መጨረሻ! በምድሪቱ አራቱም ማዕዘን መጨረሻ መጥቷል! 3 ቁጣዬን ስለላኩባችሁ መጨረሻችሁ ቀርቧል፣ እኔም እንደመንገዳችሁ እፈርድባችኋለሁ፤ ክፉ ሥራችሁን ሁሉ በእናንተ ላይ እመልስባችኋለሁ። 4 በርህራሄ አላያችሁም ምህረትም አላደርግላችሁም፤ ነገር ግን መንግዳችሁን እመልስባችኋለሁ፣ ጥፋታችሁ በመካከላችሁ ይሆናል፥ በዚያን ጊዜ እኔ እግዚአብሔር እንደሆንኩ ታውቃላችሁ! 5 ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡ መዓት! በመዓት ላይ መዓት! እነሆ እየመጣ ነው! 6 መጨረሻ በእርግጥ እየመጣ ነው፤ መጨረሻው ወደ እናንተ እየተራመደ ነው! እነሆ እየመጣ ነው! 7 በምድሪቱ በምትኖሩት ላይ ፍርድ እየመጣ ነው። ጊዜው ደርሷል፤ የጥፋት ቀን ቀርቧል፤ ተራሮች ከእንግዲህ ለደስታ አይሆኑም። 8 በቅርቡ እንደ መንገዳችሁ በምፈረድባችሁ ጊዜና ክፋታችሁን በመለስኩባችሁ ጊዜ መዓቴን አፈስባችኋለሁ ቁጣዬም በላያችሁ ይሆናል። 9 ዓይኔ አይራራላችሁም ምህረትም አላደርግላችሁም። እንዳደርጋችሁብኝ አደርግባችኋለሁ፤ የምቀጣችሁ እኔ እንደሆንኩ ታውቁ ዘንድ ክፋታችሁም በመካከላችሁ ይሆናል። 10 እነሆ ቀኑ እየደረሰ ነው። ጥፋት ወጥቷል። በትሩ በትዕቢት አበባ ፈክቷል። 11 አመጽ ወደ ኃጢአት በትርነት አድጓል-- አንዳቸውም፣ ከህዝባቸውም ማንም፣ የትኛውም ሀብታቸው፣ የትኛው ጠቃሚ ነገራቸው አይተርፍም። 12 ቀኑ እየመጣ ነው፤ ቀኑ እየቀረበ ነው። ቁጣዬ በህዝቡ ሁሉ ላይ ስለሆነ ንብረት የገዛ አይደሰት፣ የሸጠም አይዘን! 13 ምክንያቱም በህይወት ዘመናቸው ሁሉ ሻጭ የሸጠውን አያስመልስም፣ ራዕዩ ለመላው ህዝብ ነው። በኃጢአቱ የሚጸና አይበረታምና አይመለሱም። 14 መለከት ነፉ የሚያስፈልገውን ሁሉ አዘጋጁ ነገር ግን ቁጣዬ በህዝቡ ሁሉ ላይ ነውና ለጦርነት የከተተ አንድም የለም! 15 በውጭ ሰይፍ በውስጥ ደግሞ ረሀብና ቸነፈር አለ። በእርሻ ቦታ ያሉ በስይፌ ይወድቃሉ፥ ረሀብና ቸነፈር ደግሞ በከተማ ያሉትን ይፈጃል። 16 ነገር ግን ከእነርሱ ጥቂቶች ተርፈው ወደ ተራሮች ይሄዳሉ። ሁሉም ስለኃጢአታቸው እያንዳንዱም ስለስንፍናው እንደ ደሸለቆ እርግብ ያለቅሳሉ። 17 እጅ ሁሉ ይቀልጣል ጉልበትም ሁሉ እንደ ውሀ ይደክማል፣ 18 ማቅም ይለብሳሉ ድንጋጤም ይከባቸዋል፤ ፊት ሁሉ በእፍረት ይሸፈናል ራስም ሁሉ ጠጉር አልባ ይሆናል። 19 ብራቸውን በጎዳናዎቹ ላይ ይጥላሉ ወርቃቸውም እንደ ጉድፍ ይሆናል በእግዚአብሔር መዓት ቀን ብራቸውና ወርቃቸው ያድናቸው ዘንድ አይችልም። እርሱ የኃጢአታቸው ዕንቅፋት ሆኖአልና ሰውነታቸውን አያጠግቡም ሆዳቸውንም አይሞሉም 20 የክብሩ ጌጦችንም በማንአለብኝነት ወስደው ክፋታቸውንና የፈጸሙትን አመጻ የሚያሳዩ የምንዝርና ምስሎችን አበጁ፣ ስለዚህ እኔ እነዚህን ምስሎች ርኩስ እድርጌባቸዋለሁ። 21 በባዕድም እጅ ለንጥቂያ፥ በምድር ኃጢአተኞችም እጅ ለብዝበዛ አሳልፌ እሰጣቸዋለሁ እነርሱም ያረክሱአቸዋል። 22 የተቀድሰውን ቦታዬን ባረከሱ ጊዜ ፊቴንም አዞርባቸዋለሁ፥ ወንበዴዎችም ይገቡባታል ያረክሱትማል። 23 ምድሪቱ ደም ባመጣው ፍርድ፥ ከተማዪቱም በግፍ ተሞልታለችና ሰንሰለት ሥራ። 24 ስለዚህም ከአሕዛብ ዘንድ ከሁሉ የሚከፉትን አመጣለሁ ቤቶቻቸውንም ይወርሳሉ፣ መቅደሶቻቸው ስለሚረክሱ የኃያላንንም ትዕቢት ወደ ፍጻሜ አመጣለሁ። 25 ፍርሀት ይመጣል! ሰላምን ይሻሉ ነገር ግን ምንም ሰላም አይገኝም። 26 ድንጋጤ በድንጋጤ ላይ ወሬም በወሬ ላይ ይመጣል! ከነቢዩም ዘንድ ራዕይን ይሻሉ ነገር ግን ከካህኑም ዘንድ ህግ፥ ከሽማግሌዎችም ዘንድ ምክር ይጠፋል። 27 ንጉሡም ያለቅሳል፥ ልዑሉም ውርደትን ይለብሳል፥ የምድሪቱም ሕዝብ እጆቹ በፍርሀት ይንቀጥቀጣሉ። እንደ መንገዳቸውም መጠን ይህን አደርግባቸዋለሁ! እኔ እግዚአብሔር እንድሆንኩ እስኪያውቁ ድረስ በፍርዳቸውም መጠን እፈርድባቸዋለሁ ።

Ezekiel 7:1

የእግዚአብሔር ቃል መጣ
x

Ezekiel 7:3

ፍጻሜው በአንቺ ላይ ነው
ስለ “ፍጻሜ” የተነገረው ዘራፊ ሰዎችን እንደሚያጠቃቸው ተደርጎ ነው። አ.ት፡ “ሕይወትሽ አልቋል” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

ቁጣዬን እልክብሻለሁ
“ቁጣ” እግዚአብሔር በሰዎቹ ላይ እንደሚወረውረው ፍላጻ ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “ተቆጥቻለሁ፣ ስለዚህ እቀጣሻለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እንደ መንገዶችሽ
“እንደምትሠሪያቸው ነገሮች” ወይም “በምትሠሪው ክፉ ነገሮች ምክንያት”

አስጸያፊነትሽን በሙሉ በአንቺ ላይ አመጣለሁ
“እነዚያን እጅግ የምጠላቸውን ነገሮች በማድረግሽ እቀጣሻለሁ”

ዓይኖቼ አይራሩልሽም
ዓይን ባለቤቱ የሆነውን ሰውን ይወክላል። አ.ት፡ “አልራራልሽም”

መንገድሽን በአንቺ ላይ አመጣለሁ
አንድ ሰው የሕይወት ዘይቤው እንደሚሄድበት ጎዳና ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “ስላደረግሻቸው ነገሮች እቀጣሻለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አስጸያፊነትሽ በመካከልሽ ይሆናል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “በአስጸያፊነታችሁ ምክንያት ሁላችሁንም እቀጣችኋለሁ” ወይም 2) “ጣዖታትን ማምለካችሁን እስከ ቀጠላችሁ ድረስ ይህ ይደርስባችኋል” የሚሉት ናቸው።

እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ዕወቁ
እግዚአብሔር ሰዎች እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን ያውቃሉ ብሎ በሚናገርበት ጊዜ እርሱ ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለው ብቸኛው እውነተኛ አምላክ መሆኑን ሰዎች ያውቃሉ ማለቱ ነው። አ.ት፡ “እውነተኛው አምላክ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ተረዱ” ወይም “ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለኝ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ተገንዘቡ”

Ezekiel 7:5

ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
እርሱ የሚናገረው አስፈላጊ መሆኑን ለሕዝቅኤልና ለሕዝቡ ለማስታወስ እግዚአብሔር ስለ ራሱ በስሙ ይናገራል። ይህንን በሕዝቅኤል 6፡11 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እኔ ጌታ እግዚአብሔር ይህንን እናገራለሁ” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

ጌታ እግዚአብሔር
ይህንን በሕዝቅኤልል 2፡4 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጥፋት! ለየት ያለ ጥፋት! እነሆ መጥቶአል
እነዚህ ቃለ-አጋኖዎች ምንባቡን በጣም ከባድ ያደርጉታል ማለት ነው። አ.ት፡ “እነሆ፣ ቀድሞ ማንም ያልተለማመደው ዓይነት አስከፊ ጥፋት እየመጣ ነው”

እነሆ፣ እርሱ
“እርሱ እንደሚሆን በፍጹም አትጠራጠሪ”

ፍጻሜ በአንቺ ላይ ተነሣሥቶአል
እየመጣ ያለው ፍርድ ከእንቅልፉ በሚነቃ ጠላት ተመስሎ ተነግሯል። (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

ከእንግዲህ ተራሮች ደስተኞች አይሆኑም
“ተራሮች” የሚለው ቃል በተራሮች ላይ የሚኖሩትን ሰዎች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “በተራሮች ላይ የሚኖሩት ሰዎች ከእንግዲህ ምንም ደስታ አይኖራቸውም” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 7:8

ብዙም ሳይቆይ
“በጣም በቅርቡ”

በአንቺ ላይ ንዴቴን አፈሳለሁ፣ በላይሽ ላይ ቁጣዬን እሞላለሁ
እግዚአብሔር በእንስራ ውስጥ እንደሚያፈሰው ውሃ “አፈሳለሁ” እና “እሞላለሁ” የሚሉትን ቃላት የሚጠቀመው ስለ ቁጣው ለመናገር ነው። እነዚህ ሐረጎች እግዚአብሔር ሕዝቡን በአስከፊ ሁኔታ እንደሚቀጣቸው አጽንዖት ይሰጣሉ። አ.ት፡ “በጣም ስለተቆጣሁ በብርቱ እቀጣችኋለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና Parallelism የሚለውን ተመልከት)

ንዴት
“ቁጣ” ወይም “ታላቅ ቁጣ”

ዐይኔ በርኅራኄ አይመለከትም
ዓይን ባለቤቱ የሆነውን ሰውን ይወክላል። አ.ት፡ “በርኅራኄ አልመለከታቸውም” ወይም “አልራራላቸውም”

አልምርሽም
“ያለ ቅጣት አልተውሽም” ወይም “እቀጣሻለሁ”

እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ታውቂ ዘንድ አስጸያፊ ተግባርሽ በመካከልሽ ይሆናል
ይህንን በሕዝቅኤል 7:4 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት

Ezekiel 7:10

እነሆ ቀኑ! እነሆ ደርሷል!
“እነሆ! ቀኑ እየደረሰ ነው!” የትኛው ቀን እየደረሰ እንዳለ ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። አ.ት፡ “እነሆ! አንቺን የምቀጣበት ቀን እየደረሰ ነው!”

እነሆ
“ተመልከት” ወይም “ስማ” ወይም “የምነግርህን ልብ በል”

የጥፋት ፍርድ ወጥቶ ሄዷል
“ጥፋት ወደ እስራኤል መምጣት ጀምሯል” ወይም “በጣም አስፈሪ ነገሮች መምጣት ጀምረዋል”

በትሩ አብቧል፣ እብሪት እምቡጥ ይዟል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “የእስራኤል ሕዝብ ትዕቢታቸውን አብዝተዋል” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ በጣም ቁጡና ትዕቢተኛ ሆነዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ጭካኔ ወደ አመፅ በትርነት አድጓል
“የሕዝቡ አመፅ በይበልጥ ክፉ ነገሮችን ወደ ማድረግ መርቷቸዋል”

Ezekiel 7:12

ጊዜው ደርሷል፤ ቀኑ ቀርቧል
“ጊዜው” እና “ቀኑ” ሁለቱም እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ የሚቀጣበትን ጊዜ ያመለክታሉ። አ.ት፡ “የእስራኤል ቅጣት በቅርቡ ይደርሳል”

ቁጣዬ በመላው ሕዝብ ላይ ነው
“በመላው ሕዝብ ላይ ተቆጥቻለሁ”

በርካታ ሕዝብ
በጣም ብዙ ቁጥር ያለው ሕዝብ። እዚህ ጋ፣ ቃሉ የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው።

ሁለቱም በሕይወት እስካሉ ድረስ
“ገዢው” እና “ሻጩ” (7፡12) ሁለቱም በሕይወት እስካሉ ድረስ

መላውን ሕዝብ የሚመለከተው ራዕይ አይለወጥም
“እግዚአብሔር ያሳየኝን በመላው ሕዝብ ላይ በእርግጥ ያደርጋል”

አንዳቸውም አይበረቱም
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ማናቸውንም አያበረታም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 7:14

መለከቱን ነፍተዋል
“ከጠላት ጋር እንዲዋጉ ሕዝቡን ለመጥራት መለከቱን ነፍተዋል”

ቁጣዬ በመላው ሕዝብ ላይ ነው
“በመላው ሕዝብ ላይ ተቆጥቻለሁ” ይህንን በሕዝቅኤል 7:12 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።

ሰይፉ በስተውጭ ነው
“ሰይፍ” የሚለው ቃል ሰይፍን በመጠቀም ሰዎችን የሚገድሉ ወታደሮችን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡

ሕንጻው
ከተማው

ረሃብና ቸነፈር በከተማው ውስጥ ያሉትን በማጥፋት ላይ እያለ
“ማጥፋት” የሚለው ቃል “ፈጽሞ መደምሰስ” ለሚለው ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “በከተማይቱ ውስጥ ያለው አብዛኛው ሕዝብ በረሃብና በበሽታ ይሞታል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በሽለቆ እንዳሉ እርግቦች ሁሉም ያለቅሳሉ
እርግቦች አንድ ሰው በማያቋርጥ ሕመም ወይም ጥልቅ ሐዘን ውስጥ ሲሆን የሚያሰማውን ዓይነት የማቃሰት ድምፅ በዝግታ ያወጣሉ። አ.ት፡ “ሁሉም እጅግ አዝነው ያለቅሳሉ፣ ድምፃቸውም የእርግብ መንጋ ድምፅ ይመስላል”

Ezekiel 7:17

እጅ ሁሉ ይዝላል፣ ጉልበትም ሁሉ እንደ ውሃ ይሆናል
እጆችና ጉልበቶች ስለ ሕዝቡ ስለ ራሱ የሚወክሉ ናቸው። አ.ት፡ “መሥራት እስከማይችሉ ድረስ ሁሉም እጅግ ይፈራሉ፣ ጉልበታቸውም መቆም እስከማይችል ድረስ ደካማ ይሆናል”

መዛል
መደረግ ያለበትን ለማድረግ አለመቻል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጉልበት ሁሉ እንደ ውሃ ይሆናል
ሊሆን የሚችለው ሌላው ትርጉም፣ ሰዎቹ ሁሉ እጅግ ስለ ፈሩ ፊኛዎቻቸውን መቆጣጠር እንዳቃታቸው የሚያሳየው “ጉልበት ሁሉ ከውሃ ጋር ይንሳፈፋል” የሚለው ነው።

ጉልበት ... እንደ ውሃ የደከመ
ውሃ ሊቆም አይችልም፣ ጉልበታቸው እጅግ ስለሚደክም ሕዝቡ በእግሮቻቸው ለመቆም አይችሉም። (See: Simile)

ሸብር ይሸፍናቸዋል
ሸብር እንደ ልብስ ተደርጎ ተነግሮለታል። አ.ት፡ “ምን ያህል እንደ ፈሩ ሁሉም ያያል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በራሳቸው ሁሉ ላይ በራነት
ጸጉርን መላጨት የሐዘን ምልክት ነበር። አ.ት፡ “ሁሉም ጸጉራቸውን ይላጫሉ”

በእግዚአብሔር የመዓት ቀን
“እግዚአብሔር በቁጣው በሚሠራበት ቀን” ወይም “እግዚአብሔር በሚቀጣቸው ጊዜ”

ቀኑ
ይህ 24 ሰዓት ካለው ቀን የበለጠ ወይም ያነሰ ጊዜ ሊሆን ይችላል።

ረሃባቸው አይረካም
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ረሃባቸውን ለማርካት አይችሉም” ወይም “ያላቸውን ሁሉ ከበሉ በኋላ እንኳን ገና የተራቡ ይሆናሉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ኃጢአታቸው ማሰናከያ ሆኖባቸዋል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ምክንያቱም የነበራቸው ብዙ ወርቅና ብር ወደ ኃጢአት መርቷቸዋል” ወይም 2) “ክፉዎች ስለሆኑ፣ ምን ያህል ክፉዎች እንደሆኑ ለማሳየት ኃጢአትን ይሠራሉ” የሚሉት ናቸው።

Ezekiel 7:20

ከእነርሱ ጋር
ከተዋቡ ዕንቁዎቻቸው ጋር

እነዚያን ነገሮች በእንግዶች እጅ አሳልፌ እሰጣለሁ
“እጅ” የሚለው ቃል ቁጥጥርን ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል። “እነዚያን ጣዖታት የማያውቋቸው ሰዎች በቁጥጥራቸው ስር እንዲያደርጉት እሰጣቸዋለሁ” ወይም “እነዚያን ጣዖታት ለማያውቁ ሰዎች እሰጣቸዋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ብዝበዛ
በጉልበት የተወሰዱ ወይም የተሰረቁ ነገሮች ናቸው

ያረክሷቸዋል
የእስራኤል ሕዝብ የሠሯቸውን ጣዖታት እንግዶቹና ክፉዎቹ ሰዎች ያረክሷቸዋል።

ፊቴን እሰውራለሁ
“ትኩረት አልሰጥም” ወይም “በሌላ አቅጣጫ እመለከታለሁ” ወይም “ልብ አልልም”

የከበረ ስፍራዬ
“የምወደው ስፍራ”። ይህ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ያመለክታል።

ሸፍቶች
የሚሰርቁና የሚያጠፉ ጨካኞች

Ezekiel 7:23

ሠንሠለት አዘጋጅ
ሰንሰለት ባሮችን ወይም እስረኞችን ለማሰር ጥቅም ላይ ይውላል። እግዚአብሔር ይህንን የሚለው ሕዝቡ ባሮች ወይም እስረኞች እንደሚሆኑ ለማሳየት ነው።

ምድሪቱ በደም ፍርድ ተሞልታለች
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ሌሎችን በጭካኔ ገድለዋለና እግዚአብሔር በሀገሪቱ ሁሉ ላይ ይፈርዳል” ወይም 2) “በሀገሪቱ ውስጥ በየቦታው ያሉ ፍርድ ቤቶች ሰዎችን በመግደል ላይ ናቸው”። እዚህ ጋ፣ “ደም” የሚለው ቃል ግድያና ሞትን ይወክላል የሚሉት ናቸው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከተማይቱ ጭካኔን ተሞልታለች
ከተማይቱ የዕቃ መያዣ በምትመስልበት መልኩ ተነግሮላታል፣ ጭካኔም በዕቃ መያዣ ውስጥ እንደሚደረግ ቁስ ተነግሮለታል። የነገር ስም የሆነው “ጭካኔ” እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “በከተማይቱ ውስጥ ጭካኔ በየስፍራው አለ” ወይም “በከተማይቱ የሚኖሩ ብዙ ሰዎች በሌሎች ላይ የጭካኔ ተግባር እየፈጸሙባቸው ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና የነገር ስም የሚለውን ተመልከት))

እነርሱ ቤቶቻቸውን ይወርሳሉ
ክፉዎች የእስራኤላውያኑን ቤት ይወስዳሉ

ለኃያላኑ ትዕቢት መጨረሻን አደርጋለሁ
“በእስራኤል ውስጥ ያሉ ብርቱ ሰዎች በራሳቸው መመካታቸውን እንዲያቆሙ አደርጋለሁ”

ቅዱስ ስፍራዎቻቸው ሁሉ ይረክሳል!
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “የአምልኮ ስፍራዎቻቸውን ጠላት ያረክሳቸዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የተቀደሱ ስፍራዎቻቸው
ጣዖታትን የሚያመልኩባቸውን ስፍራዎች

ፍርሐት ይመጣል
“ሕዝቡ ይፈራል”

ሰላምን ይፈልጋሉ
“ከጠላቶቻቸው ጋር ሰላምን ለመፍጠር ይሞክራሉ”

ነገር ግን አንዱም አይሆንም
“ነገር ግን ከጠላቶቻቸው ጋር ሰላምን ለመፍጠር አይችሉም”

Ezekiel 7:26

ጥፋት በጥፋት ላይ ይመጣል
ጥፋት በራሱ ሊንቀሳቀስ እንደሚችል ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ከአንዱ ኋላ ሌላኛው ጥፋት ይመጣል” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

ከነቢይ ራዕይን ይፈልጋሉ
“ነቢያት ምን ዓይነት ራዕይ እንዳዩ ይጠይቋቸዋል”

ሕጉ ከካሕናት፣ ምክርም ከሽማግሌዎች ይጠፋል
“ካሕናቱ ሕጉን አያስተምሩም፣ ሽማግሌዎቹም ጥሩ ምክር ለመስጠት አይችሉም”። ይህ የሚሆነው እግዚአብሔር ጥበብን ስለማይሰጣቸው ነው።

መስፍኑ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “የንጉሡ ወንድ ልጅ” ወይም 2) ከንጉሡ ውጪ የንጉሣዊ ቤተሰብ አባላት የሆኑ ወንዶች ሁሉ የሚሉት ናቸው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ተስፋ መቁረጥን ይለብሳሉ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ልብስ አንድ ሰው “ተስፋ አይኖራቸውም” ለሚል ስሜቱ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው ወይም 2) “በማልቀስ ላይ መሆኑን የሚያሳይ ልብስ ይለብሳል” የሚሉት ናቸው። (የአነጋገር ዘይቤ እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የምድሪቱ ሰዎች እጆቻቸው በፍርሐት ይንቀጠቀጣል
“እጆች” የሚለው ቃል ሕዝቡን ይወክላል። አ.ት፡ “የምድሪቱ ሕዝብ እጆቻቸው እስኪንቀጠቀጡ ድረስ እጅግ ይፈራሉ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 8

1 በስድስተኛውም ዓመት በስድስተኛው ወር ከወሩም በአምስተኛው ቀን በቤቴ ተቀምጬ ሳለሁ የይሁዳም ሽማግሌዎች በፊቴ ተቀምጠው ሳሉ፥ በዚያ የጌታ የእግዚአብሔር እጅ እንደገና በእኔ ላይ ወደቀች። **2** እኔም አየሁ፥ እነሆም፥ የሰው አምሳያ ነበረ ከወገቡም በታች እሳት ይመስል ነበረ፥ ከወገቡም በላይ የቀለጠ ብረት የሚመስል የሚያብለጨልጭ ነበር። **3** ከዚያም እጅ የሚመስል ነገር ዘረጋ በራስ ጠጕሬም ያዘኝ፤ መንፈስም በምድርና በሰማይ መካከል አነሣኝ፥ በእግዚአብሔርም ራእይ ወደ ኢየሩሳሌም ወደ ሰሜን ወደሚመለከተው ወደ ውስጠኛው አደባባይ በር መግቢያ አመጣኝ በዚያም ቅንዓት የሚያነሣሣ የቅንዓት ጣዖት ተተክሎ ነበር። **4** እነሆም፥ በቈላው እንዳየሁት ራእይ አይነት የእስራኤል አምላክ ክብር በዚያ ነበረ። **5** እርሱም፦ "የሰው ልጅ ሆይ፥ ዓይንህን ወደ ሰሜን አንሣ አለኝ።" ዓይኔንም ወደ ሰሜን መንገድ አነሣሁ እነሆም፥ በመሠዊያው በር በሰሜን በኩል መግቢያው ላይ የቅንዓት ጣዖት ነበረ። **6** የእግዚአብሔርም መንፈስ፦ "የሰው ልጅ ሆይ፥ አየህ የሚያደርጉትን? ይህ ከመቅደሴ ያርቁኝ ዘንድ የእስራኤል ቤት በዚህ የሚያደርጉት ታላቁን ርኵሰት ነው! ግን ዞረህ ስታይ ከዚህ የበለጠ ታላቅ ርኵሰት ታያለህ አለኝ!" **7** ወደ አደባባዩም መግቢያ አመጣኝ ፥ በግንቡ ውስጥ ቀዳዳ እንዳለ አየሁ። **8** እርሱም፦ "የሰው ልጅ ሆይ፥ ግንቡን ንደለው አለኝ ግንቡንም በነደልሁት ጊዜ መግቢያ በር አገኘሁ። **9** እርሱም፦ "ግባና የሚያደርጉትን የከፋ ርኵሰት እይ አለኝ። **10** እኔም ገባሁና እነሆ፥ በግንቡ ዙሪያ ላይ የሚሳብና አስቀያሚ አውሬ ምስል አየሁ! በግንቡም ዙሪያ የእስራኤል ቤት ጣዖታት ሁሉ ተስለው አየሁ። **11** ሰባ እስራኤል ቤት ሽማግሌዎች በዚያ ቆመው ነበር፥ በመካከላቸውም የሳፋን ልጅ ያእዛንያ ቆሞ ነበር፥ በምስሎቹም ፊት ቆመው ነበር ። እያንዳንዱ ሰው በእጁ ጥናውን ይዞ ነበር፥ የዕጣኑም ጢስ ሽቱ ይወጣ ነበር። **12** እርሱም፦ "የሰው ልጅ ሆይ፥ የእስራኤል ቤት ሽማግሌዎች በጨለማ የሚያደርጉትን አየህ? 'እግዚአብሔር አያየንም እግዚአብሔር ምድሪቱን ትቶአታል' ብለው ሁሉም ሰው ይህን የሚያድርገው በየራሱ ስውር ቦታ ከጣዖቱ ጋር ሆኖ ነው። **13** እርሱም፦ "ደግሞ ወደኋላ ዙርና እያደረጉ ያለውን ከዚህ የበለጠውን ሌላ ታላቅ ርኵሰት እይ" አለኝ። **14** ከዚያም ወደ በሰሜን አቅወጣጫ ወዳለው ወደ እግዚአብሔር ቤት በር መግቢያ አመጣኝ፣ እነሆም! ሴቶች ለተሙዝ እያለቀሱ በዚያ ተቀምጠው ነበር። **15** እርሱም፦ "የሰው ልጅ ሆይ፥ ይህን ታያለህ? ደግሞ ተመልሰህ ከዚህ የበለጠ ርኵሰት ታያለህ አለኝ። **16** ደግሞም ወደ እግዚአብሔር ቤት ወደ ውስጠኛው አደባባይ አመጣኝ፥ እነሆም፥ በእግዚአብሔር መቅደስ መግቢያ በወለሉና በመሠዊያው መካከል ሀያ አምስት የሚያህሉ ሰዎች ጀርባቸው ወደ እግዚአብሔር መቅደስ ፊታቸውም ወደ ምሥራቅ ሆኖ ሸሚሸ ለተሰኘው ጣዖት ይሰግዱ ነበር። **17** እርሱም፦ የሰው ልጅ ሆይ፥ ይህን ታያለህ? በዚህ የሚያደርጉት ይህ ርኵሰት ለይሁዳ ቤት እንድ ቀላል ነገር ነውን? ምድሪቱን በግፍ ሞልተዋታል ያስቈጡኝም ዘንድ ተመልሰዋል፥ ቅርንጫፎችንም ወደ አፍንጫዎቻቸው አቅርበዋል። **18** ስለዚህ እኔ ደግሞ በመካከላቸው እንቀሳቀሳለሁ ዓይኔ አይራራም ፣አላዝንላቸውም። ወደ ጆሮዬም በታላቅ ድምፅ ቢጮኹ አልሰማቸውም አለኝ።

Ezekiel 8:1

እንዲህ ሆነ
እዚህ ጋ፣ ይህ ሐረግ ጥቅም ላይ የዋለው የታሪኩን አዲስ ክፍል ጅማሬ ለማመልከት ነው። የአንተ ቋንቋ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለ እዚህ ጋ ልትጠቀምበት እንደምትችል አስብ።

በስድስተኛው ዓመት
ይህ ስድስተኛ ዓመት የትኛውን ጊዜ እንደሚያመለክት ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። አ.ት፡ “ንጉሡ ኢዮአቄም በተማረክ በስድስተኛ ዓመት”

በስድስተኛው ወር፣ በወሩም በአምስተኛው ቀን
ይህ በዕብራውያኑ የቀን አቆጣጠር ስድስተኛ ወር ነው። በምዕራባውያኑ አቆጣጠር አምስተኛው ቀን የመስከረም ወር መጀመሪያ አቅራቢያ ነው። አ.ት፡ “የስድስተኛው ወር አምስተኛ ቀን” (የዕብራውያን ወራት እና ደረጃን አመልካች ቁጥር የሚለውን ተመልከት)

የጌታ እግዚአብሔር እጅ እንደገና በእኔ ላይ ወደቀች
ኋላ ላይ ሕዝቅኤል እጅ የሚመስል ነገር ስለሚያይ ይህ በቀጥታ መተርጎም ይኖርበታል። ሌሎች እጁን የእግዚአብሔርን ኃልዎት ወይም ኃይል የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር አድርገው ይመርጡት ይሆናል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ጌታ እግዚአብሔር
ይህንን በሕዝቅኤል 2:4 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።

በእኔ ላይ ወደቀች
“ያዘችኝ”

አንድ የሰው መልክ አምሳያ
እዚህ ጋ፣ የነገር ስም የሆነው “መልክ” ማለት ለሕዝቅኤል ሰው መስሎ የታየው ነገር ነው። “መልክ” እና “አምሳያ” ሁለቱም ከግሳዊ ሐረግ ጋር ሊተረጎሙ ይችላሉ። አ.ት፡ “አንድ ሰው የሚመስል ታይቶ ነበር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

የጋለ ብረት
ብረት በጣም ሲሞቅ ይግልና ቢጫ ወይም ብርቱካናማ ቀለም ይኖረዋል።

የወገቡ አምሳያ ... የሚያንጸባርቅ ነገር አምሳያ
የነገር ስም የሆነው “አምሳያ” እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ወገቡን መስሎ የታየው ... አንጸባራቂ ነገር መስሎ የታየው” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 8:3

ያዘ
“እርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ምናልባት “ሰው የሚመስለውን ምስል” ይሆናል (ሕዝቅኤል 8፡2)።

በሰማይና በምድር መካከል
“በመሬትና በጠፈር መካከል”

ከእግዚአብሔር በሆነው ራዕይ ወደ ኢየሩሳሌም አመጣኝ
“በራዕይ” የሚለው ቃል ትርጉም፣ ይህ ልምምድ የመጣው በሕዝቅኤል አሳብ ውስጥ ነው ማለት ነው። እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች በሚያሳየው ጊዜ አካሉ በዚያው በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ ይሆናል ማለት ነው።

ሰሜናዊ ውስጠኛው በር
“የቤተ መቅደሱ ሰሜናዊ ውስጠኛው በር”። ቤተ መቅደሱ ውስጠኛና ውጪኛ በሆኑ ሁለት ግምቦች የተከበበ ነበር። ይህ በር በስተሰሜን በውስጠኛው ግምብ ላይ ነበረ።

ታላቅ ቅንዓት የሚያነሣሣው ጣዖት
“እግዚአብሔር በጣም እንዲቀና የሚያደርገው ጣዖት”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሜዳው ላይ ዐይቼው እንደነበረው ራዕይ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ሜዳው ላይ በነበርኩበት ጊዜ በራዕይ ዐይቼው የነበረውን ያንኑ የሚመስል” ወይም 2) “ሜዳው ላይ በነበርኩበት ጊዜ ያየሁትን ያንኑ የሚመስለውን” የሚሉት ናቸው።

ሜዳው
ጥቂት ዛፎች ያሉበት ዝርግ የሆነ ሰፊ መሬት

Ezekiel 8:5

የሰው ልጅ
“የሰብዓዊ ፍጡር ልጅ” ወይም “ከሰው የተወለደ ልጅ”። ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን አፅንኦት ለመስጠት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ በማለት ይጠራዋል። እግዚአብሔር ዘላለማዊና ኃያል ነው፣ ሰዎች ግን አይደሉም። ይህንን በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ሟች ሰው” ወይም “ሰው”

ዓይኖችህን አንሣ ... ዓይኖቼን አነሣሁ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ የሚያሳየው ወደ አንድ ነገር መመልከት እንደነበረበት ነው። አ.ት፡ “ወደ ላይ እይ ... ወደ ላይ አየ” ወይም “ፊትህን አዙርና ተመልከት ... ፊቴን አዙሬ ተመለከትኩ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ወደ መሰዊያው ወደሚያመራው በር
“ሰዎች ወደ መሰዊያው ለመድረስ አልፈው የሚሄዱበት በር”

የሚያደርጉትን ታያለህ?
የሕዝቅኤልን ትኩረት ሰዎቹ ወደሚያደርጉት ነገር ለማምጣት እግዚአብሔር ይህንን ጥያቄ ይጠቀማል። አ.ት፡ “ሰዎቹ እዚህ ጋ የሚያደርጉትን ነገር የምጠላበትን ምክንያት እንድትረዳ እፈልጋለሁ” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እስራኤላውያንን” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 8:7

አደባባዩ
የትኛው አደባባይ መሆኑን ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። “የቤተ መቅደሱ አደባባይ”

Ezekiel 8:10

እነሆ
ይህ ቃል የሚያሳየው ሕዝቅኤል ባየው ነገር መደነቁን ነው። የአንተ ቋንቋ ይህንን ለማሳየት ሌላ ቃል ይኖረው ይሆናል።

የተለያዩ በደረታቸው የሚሳቡ ነገሮች እና እርኩሳን አራዊት
“በግድግዳው ላይ የተቀረጹ፣ የተለያዩ በደረታቸው የሚሳቡ እንስሶች እና እርኩሳን አራዊት”። “በደረታቸው የሚሳቡ ነገሮች” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ነፍሳትን እና ሌሎች ትናንሽ እንስሶችን ነው።

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እስራኤላውያንን” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ዙሪያውን በግንቡ ላይ
የትኛው ግንብ እንደሆነ ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። አ.ት፡ “በቤተ መቅደሱ ዙሪያ ባለው ግንብ ላይ”

ያዕዛንያ ... ሳፋን
የወንዶች ስም ነው (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የዕጣን ማጨሻ
ሰዎች እግዚአብሔርን ወይም ሐሰተኞች አማልክትን በሚያመልኩበት ጊዜ ዕጣን የሚያጨሱበት ጎድጎድ ያለ ዕቃ

Ezekiel 8:12

የእስራኤል ቤት ሽማግሌዎች በጨለማው ውስጥ የሚያደርጉትን ታያለህ?
ሽማግሌዎቹ የሚያደርጉትን እንዲያይ እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እያዘዘው ነው። አ.ት፡ “የእስራኤል ቤት ሽማግሌዎች በጨለማው ውስጥ የሚያደርጉትን እይ”። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እስራኤላውያንን” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በጣዖቱ ድብቅ ጓዳ
“ጣዖቱን ሲያመልክ ማንም ሊያየው የማይችልበት ክፍል”

Ezekiel 8:14

በሰሜን ወዳለው የእግዚአብሔር ቤት መግቢያ በር
ይህ በሕዝቅኤል 8:3. ያለው ዓይነት ሳይሆን የሰሜኑ ውጫዊ በር ነበር

እነሆ!
ይህ ቃል የሚያሳየው ሕዝቅኤል ባየው ነገር መደነቁን ነው።

ለተሙዝ ማልቀስ
ሐሰተኛው አምላክ ተሙዝ ሞቶ ስለነበረ አዘኑ (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

አንተ ሰው ... ይህንን ታያለህ?
ሕዝቅኤል እያየ ስላለው ነገር እንዲያስብ እግዚአብሔር ያዘዋል። አ.ት፡ “አንተ ሰው ... ስለዚህ ነገር አስብ” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 8:16

እነሆ!
ይህ ቃል የሚያሳየው ሕዝቅኤል ባየው ነገር መደነቁን ነው።

መተላለፊያ
በረድፍ ወይም በቋሚ እንጨት ድጋፍ የመግቢያውን ፊት የሚሸፍን

ፊታቸው ወደ ምስራቅ ዞሮ
“ወደ ምስራቅ ይመለከቱ ነበር”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ezekiel 8:17

አንተ ሰው ... ይህንን ታያለህ?
ሕዝቅኤል እያየ ስላለው ነገር እንዲያስብ እግዚአብሔር ያዘዋል። አ.ት፡ “ አንተ ሰው ... ስለዚህ ነገር አስብ” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

በዚህ ቦታ እነዚህን አስጸያፊ ነገሮች ማድረጋቸው ለይሁዳ ቤት ይህ ቀላል ነገር ነው?
እግዚአብሔር በይሁዳ ቤት ላይ መቆጣቱ ትክክል መሆኑን ለማሳየት ይህንን ጥያቄ ያቀርባል። አ.ት፡ “በዚህ ቦታ በሚያደርጓቸው በእነዚህ አስጸያፊ ተግባሮች ምክንያት በይሁዳ ቤት ላይ ብቆጣ ልክ ነኝ” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

የይሁዳ ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የይሁዳን ዘሮች ያመለክታል። እነዚን ቃላት በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምካቸው ተመልከት። አ.ት፡ “የይሁዳ ሕዝብ ወገን” ወይም “የይሁዳ ሕዝብ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ምድሪቱን በአመፅ ሞልተዋታል
“በሀገሩ ሁሉ የአመፅን ተግባር ይፈጽማሉ” ወይም “በሀገሪቱ ሁሉ እርስ በእርሳቸው ይገዳደላሉ”

ቁጣዬን ለማነሣሣት
“እንድቆጣ ለማድረግ”

ቅርንጫፉን ወደ አፍንጫዎቻቸው አቅርበዋል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሰዎቹ ለሐሰተኛ አምልኮ ቅርንጫፎችን ይጠቀሙ ነበር ወይም 2) ሰዎቹ በእግዚአብሔር ላይ ማመፃቸውን ለማሳየት ቅርንጫፎቹን ይጠቀሙባቸው ነበር የሚሉት ናቸው። “ቅርንጫፍ... ወደ አፍንጫዎቻቸው” የሚሉት ቃላት ምናልባት በቀጥታ የዛፍ ቅርንጫፍና አፍንጫን ያመለክት ይሆናል ወይም የእጅ እንቅስቃሴን የሚገልጽ ስያሜ ይሆናል። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ዓይኔ ርኅራኄ አይኖረውም
ዓይን ባለቤቱ የሆነውን ሰውን ይወክላል። አ.ት፡ “በርኅራኄ አልመለከታቸውም” ወይም “አልራራላቸውም”

አልምራቸውም
“ገና እቀጣቸዋለሁ”

በታላቅ ድምፅ በጆሮዬ ላይ ቢጮኹም እንኳን
“በታላቅ ድምፅ በጸሎታቸው ወደ እኔ ቢጮኹም”

አልሰማቸውም
“አላዳምጣቸውም”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 9

1 ከዚያም "ጠባቂዎች የሚያጠፋ መሣሪያን በእጃቸው ይዘው ወደ ከተማይቱ ይቅረቡ" ብሎ በታላቅ ድምፅ በጆሮዬ ጮኸ። **2** እነሆም፥ እያንዳንዳቸው አጥፊውን መሣሪያ በእጃቸው ይዘው ስድስት ሰዎች በሰሜን አቅጣጫ ካለው ከላይኛው በር በኩል መጡ፣ በመካከላቸውም የበፍታ ልብስ የለበሰ የጸሐፊም ቀለም ቀንድ በወገቡ የያዘ አንድ ሰው ነበረ። እነርሱም ገብተው በናሱ መሠዊያ አጠገብ ቆሙ። **3** የእስራኤልም አምላክ ክብር በበላዩ ከነበረበት ከኪሩብ ላይ ተነሥቶ ወደ ቤቱ መድረክ ሄደ። በፍታም የለበሰውን የጸሐፊውንም ቀለም ቀንድ በወገቡ የያዘውን ሰው ጠራ። **4** እግዚአብሔርም "በኢየሩሳሌም ከተማ መካከል እለፍ፥ በመካከልዋም ስለ ተሠራው ርኩሰት ሁሉ በሚያለቅሱና በሚተክዙ ሰዎች ግምባር ላይ ምልክት አድርግ" አለው። **5** እኔም እየሰማሁ ለሌሎቹ "እርሱን ተከትላችሁ በከተማይቱ መካከል እለፉ ግደሉም! ዓይናችሁ አይራራ አትዘኑም **6** ሽማግሌውንና ጐበዙን ቈንጆይቱንም ሕፃናቶቹንና ሴቶቹን ፈጽማችሁ ግደሉ! ነገር ግን ምልክቱ ወዳለበት ሰው ሁሉ አትቅረቡ። ከመቅደሴም ጀምሩ!" አላቸው። በቤቱም አንጻር ባሉ ሽማግሌዎች ጀመሩ። **7** እርሱም "ቀጥሉ! ቤቱን አርክሱ፥ አደባባዮቹንም በሬሳ" አላቸው። እነርሱም ወጥተው በከተማይቱ ላይ ጥቃት ፈጸሙ። **8** ጥቃቱን እየፈጸሙ ሳሉ እኔ ብቻዬን እንደቀረሁ ሳይ በግምባሬ ተደፍቼ "ጌታ እግዚአብሔር ሆይ ወዮ! መዓትህን በኢየሩሳሌም ላይ ስታፈስስ የእስራኤልን ቅሬታ ሁሉ ታጠፋለህን?" ብዬ ጮኽሁ። **9** እርሱም፦ "'እግዚአብሔር ምድሪቱን ትቶአታል እግዚአብሔርም አያይም!' እያሉ የእስራኤልና የይሁዳ ቤት ኃጢአት እጅግ በዝቶአል ምድሪቱም ደም፥ ከተማይቱም ዓመፅን ተሞልታለች ። **10** እኔም ደግሞ ዓይኔ አትራራላቸውም አላዝንምም። ይልቁኑ መንገዳቸውን በራሳቸው ላይ እመልሳለሁ" አለኝ። **11** እነሆም፥ በፍታ የለበሰው የቀለም ቀንድም በወገቡ የያዘው ሰው ተመልሶ መጣና "ያዘዝኸኝን አድርጌአለሁ" የሚል ሪፖርት አቀረበ።

Ezekiel 9:1

እኔ እየሰማሁ ጮኸ
“ሲጣራ ሰማሁት”

ጮኸ
(በሕዝቅኤል 8:2) “ሰው የሚመስለው” ጮኸ

የጥፋት መሣሪያ
ሰዎችን ወይም ነገሮችን ለማጥፋት የሚያገለግል የጦር መሣሪያ

ማረጃ የጦር መሣሪያ
ብዙ ሰዎችን መግደያ የጦር መሣሪያ

እነሆ
“እይ” ወይም “ስማ” ወይም “የምነግርህን ልብ በል”

ወደ ሰሜን ወደሚመለከተው የላይኛው በር
“የላይኛው የሰሜኑ በር” ወይም “የውስጠኛው አደባባይ የሰሜኑ በር”

በፍታ
ከእጽዋት የሚሠራ ጠንካራና ለስላሳ ጨርቅ። በሞቃታማ አካባቢ በሚኖሩ በርካታ ሰዎች የሚለበስ። አ.ት፡ “ለስላሳ ጨርቅ” (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)

የጸሐፊ ዕቃ
ጸሐፊ የሚጽፍባቸው የጽሕፈት መሣሪያዎች

ነሐስ
ደማቅ ያልሆነ ወርቃማ ቀለም ያለው ብረት። ለጥንካሬ ቆርቆሮ ተጨምሮበት በአብዛኛው ከመዳብ የሚሠራ (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 9:3

ከነበረበት ከኪሩቤል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “አራት ክንፍ ካላቸው ፍጡራን ከበላያቸው” (ሕዝቅኤል 1:5) ወይም 2) በቤተ መቅደሱ ውስጥ በቅድስተ ቅዱሳኑ ስፍራ ከሁለት ኪሩቤሎች መካከል የሚሉት ናቸው። ይህንን በቀጥታ ለመተርጎም ሞክር።

የቤቱ መግቢያ በር
“ቤት” የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ያመለክታል።

በፍታ
ይህንን በሕዝቅኤል 9:2 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ትመልከት።

የጸሐፊ ዕቃ
ጸሐፊ የሚጽፍባቸው የጽሕፈት መሣሪያዎች። ይህንን በሕዝቅኤል 9:2 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።

አቃስትና በረጅሙ ተንፍስ
እነዚህ ድምፆች ሰዎች በጣም ሐዘን በሚሰማቸው ወይም ስለ አንድ ነገር በሚተክዙበት ጊዜ የሚያሰሟቸው ናቸው።

በከተማይቱ መካከል ስለተፈጸመው አስጸያፊ ተግባር
“በከተማይቱ ስለተፈጸመው አስፈሪ ነገሮች” ወይም “በከተማይቱ ውስጥ ሰዎች ስለሚያደርጓቸው አስከፊ ነገሮች”

Ezekiel 9:5

እኔ እየሰማሁ ለሌሎቹ ተናገራቸው
“ሌሎች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በሕዝቅሌ 9:1 ያሉትን ጠባቂዎች ነው።

ዓይኖችህ አይራሩ
ዓይን ባለቤቱ የሆነውን ሰውን ይወክላል። አ.ት፡ “አትራራላቸው” (See: and Synecdoche)

አትማራቸው
“ከመግደል አትመለስ”

በራሱ ላይ ምልክት አድርግ
እነዚህ በኢየሩሳሌም ስለተፈጸሙ አስጸያፊ ተግባሮች ሲያለቅሱ የነበሩ ሰዎች ናቸው። “ምልክት” የሚለውን በሕዝቅኤል 9:4 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።

በመቅደሴ ጀምሩ
ሰዎቹ በመቅደስ ምን ማድረግ እንደሚጀምሩ ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። አ.ት፡ “በመቅደሴ ምልክቱ የሌለበትን ሰው መግደል ጀምሩ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሽማግሌዎቹ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ሰባዎቹ የእስራኤል ቤት ሽማግሌዎች” (ሕዝቅኤል 8፡11) ወይም 2) የትኛውም “ሽማግሌ” (የቁጥሩን መጀመሪያ ተመልከት)።

Ezekiel 9:7

ቤቱ
ቤተ መቅደሱ

ከተማይቱን አጠቁ
“ከተማ” የሚለው ቃል በከተማይቱ ለሚኖሩ ሰዎች ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “በከተማይቱ ውስጥ ያሉትን ሰዎች አጠቁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በግንባሬ ተደፋሁ
“በምድር ላይ ሰገድሁ” ወይም “በምድር ላይ ተጋደምኩ”። ሕዝቅኤል የወደቀው በአደጋ ምክንያት አይደለም። እርሱ ምድር ላይ የወደቀው እግዚአብሔርን መፍራቱንና ማክበሩን ለማሳየት ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 1፡28 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ኦ፣ ጌታ እግዚአብሔር
ሕዝቅኤል ይህንን የሚለው ሰዎቹ በኢየሩሳሌም ላይ እንዲያደርጉት ጌታ በነገራቸው ነገር ምክንያት በጣም ስለ ደነገጠ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 4፡14 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

በኢየሩሳሌም ላይ መዓትህን በማፍሰስ የእስራኤልን ትሩፋን በሙሉ ታጠፋለህ?
እግዚአብሔር ትሩፋኑን እንዳያጠፋቸው ሕዝቅኤል እየለመነ ነው። አ.ት፡ “እባክህን፣ በኢየሩሳሌም ላይ መዓትህን በማፍሰስ የእስራኤልን ትሩፋን በሙሉ አታጥፋቸው!” (የአነጋገር ዘይቤ እና ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

በኢየሩሳሌም ላይ መዓትህን በማፍሰስ
መዓት እግዚአብሔር ከዕቃ ውስጥ አውጥቶ እንደሚያፈስሰው ፈሳሽ ተደርጎ ተነግሯል። “ኢየሩሳሌም” የሚለው ቃል በከተማይቱ የሚኖሩትን ሰዎች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። የነገር ስም የሆነው “ማፍሰስ” እንደ ግሥ ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “መዓትህን በኢየሩሳሌም ላይ በምታፈስበት ጊዜ” ወይም “በጣም ስለ ተቆጣኻቸው የኢየሩሳሌምን ሰዎች በምትቀጣቸው ጊዜ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 9:9

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እስራኤላውያንን” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እጅግ ታላቅ
“በጣም ታላቅ”

ምድሪቱ በደም፣ ከተማይቱም በጥመት የተሞላች ናት
እዚህ ጋ፣ “ምድር” በደም እንደ ተሞላች ዕቃ ተደርጋ ተነግሮላታል። “ደም” እዚህ ጋ የመግደል ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። “ከተማ” በውስጡ “ጥመት”ን እንደ ያዘ ዕቃ ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “በምድሪቱ ሁሉ ላይ ሰዎች ንጹሐንን እየገደሉ ነው፣ በከተማው ሁሉ ላይ ሰዎች አስከፊ ነገሮችን እያደረጉ ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ዐይኔ አይራራም
ዐይን ባለቤቱ የሆነውን ሰውን ይወክላል። አ.ት፡ “በርኅራኄ አላያቸውም” ወይም “አልራራላቸውም”

ሁሉንም በራሳቸው ላይ አመጣለሁ
የአንድን ሰው ተግባር በራሱ ላይ ማምጣት የሚወክለው እርሱን ስለ ክፉ ተግባሩ መቅጣትን ነው። አ.ት፡ “የሚገባቸውን ቅጣት መስጠት”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 10

1 ከዚያም በኪሩቤል ራስ ላይ ወደ ነበረው ጠፈር ተመለከትኩ። በላያቸው እንደ ሰንፔር ድንጋይ ያለ እንደ ዙፋን የሚመስል መልክ ተገለጠ። 2 እግዚአብሔርም
በፍታም የለበሰውን ሰው "በመንኰራኵሮች መካከል ከኪሩብ በታች ግባ፥ ከኪሩቤልም መካከል ካለው እሳት ፍም እጆችህን ሙላ በከተማይቱም ላይ በትነው"
አለው። ሰውዬውም እያየሁት ገባ። 3 ሰውዬውም ሲገባ ኪሩቤል በቤቱ ቀኝ በኩል ቆመው ነበር፥ ደመናም ውስጠኛውን አደባባይ ሞላው። 4 የእግዚአብሔር
ክብርም ከኪሩቤል ወጥቶ በቤቱ መድረክ ላይ ቆመ፤ ቤቱም በደመናው ተሞላ፥ አደባባዩም በእግዚአብሔር ክብር ፀዳል ተሞላ። 5 ሁሉንም የሚችል አምላክ
እንደሚናገረው ያለ ጽምፅ እንዲሁ የኪሩቤል ክንፎችን ድምፅ ክውጭው አደባባይ ሰማሁ። 6 እግዚአብሔርም በፍታ የለበሰውን ሰው "ከመንኰራኵሮች
ከኪሩቤል መካከል እሳት ውሰድ" ብሎ ባዘዘው ጊዜ ሰውዬው ገብቶ በአንደኛው መንኰራኵር አጠገብ ቆመ። 7 ኪሩብም ከኪሩቤል መካከል እጁን በኪሩቤል
መካከል ወዳለው እሳት ዘርግቶ ከዚያ ወሰደ፥ በፍታም በለበሰው ሰው እጅ አኖረው እርሱም ይዞ ወጣ። 8 በኪሩቤልም ከክንፎቻቸው በታች የሰው እጅን መሳይ
አየሁ። 9 እኔም አየሁ፥ እነሆም፥ በኪሩቤል አጠገብ አራት መንኰራኵሮች ነበሩ አንዱ መንኰራኵር በአንዱ ኪሩብ፥ አንዱ መንኰራኵር በአንዱ ኪሩብ አጠገብ
ነበረ። የመንኰራኵሮቹም መልክ እንደ ቢረሌ ድንጋይ ነበረ። 10 የአራቱም መልክ አንድ ይመስል ነበር፥ መልካቸውም በመንኰራኵር ውስጥ እንዳለ
መንኰራኵር ነበረ። 11 ሲንቀሳቀሱም ወደየትኛውም አቅጣጫ ይሄዱ ነበር፤ ፊት ለፊት ስለሚሄዱ ሲሄዱ አይገላመጡም ነበር። ሲሄዱም አይገላመጡም
ነበር። 12 ሰውነታቸው ሁሉ ማለትም ጀርባቸው፣ እጃቸውና ክንፋቸው በዓይን ተሞልቶ ነበር፣ አራቱ መንኰራኵሮችም ዙሪያቸውን በዓይኖች ተሞልተው ነበር። 13
መንኰራኵሮችም እኔ እየሰማሁ "ተሽከርካሪዎች" ተብለው ተጠሩ። 14 ለእያንዳንዱም አራት አራት ፊት ነበሩት አንደኛው ፊት የኪሩብ ፊት፥ ሁለተኛውም የሰው
ፊት፥ ሦስተኛው የአንበሳ ፊት፥ አራተኛውም የንስር ፊት ነበረ። 15 ከዚያም ኪሩቤል ማለትም በኮቦር ወንዝ ያየኋቸው ህያዋን ፍጥረታት ከፍ ከፍ አሉ 16
።ኪሩቤል በተንቀሳቀሱ ጊዜ ሁሉ መንኰራኵሮቹ በአጠገባቸው ይሄዱ ነበር፤ ኪሩቤልም ከምድር ከፍ ከፍ ይሉ ዘንድ ክንፎቻቸውን ሲዘረጉ መንኰራኵሮች
ደግሞ ከአጠገባቸው ፈቀቅ አይሉም ነበር። 17 የህያዋኑ ፍጥረታት መንፈስ በመንኰራኵሮች ውስጥ ስለነበረ ኪሩቤል ሲቆሙ መንኮራኩሮችም ይቆሙ
ነበር፥ ከፍ ከፍ ሲሉም መንኮራኩሮቹም ከእነርሱ ጋር ከፍ ከፍ ይሉ ነበር። 18 የእግዚአብሔርም ክብር ከቤቱ መድረክ ላይ ወጥቶ በኪሩቤል ላይ ቆመ። 19
ኪሩቤልም ክንፎቻቸውን ዘረጉ እኔም እያየሁ ከምድር ከፍ ከፍ አሉ በወጡም ጊዜ መንኰራኵሮች በአጠገባቸው እንደዚያው አደረጉ። በእግዚአብሔርም ቤት
በምሥራቁ በር መግቢያ ቆሙ፥ የእስራኤልም አምላክ ክብር በላያቸው ወረደ። 20 እነኚህም በኮቦር ወንዝ ከእስራኤል አምላክ በታች ያየኋቸው ህያዋን
ፍጥረታት ስለነበሩ ኪሩቤልም እንደ ነበሩ አውቄ ነበር። 21 ለእያንዳንዱ አራት አራት ፊትና አራት አራት ክንፍ ነበሩት፥ የሰውም እጅ አምሳያ ከክንፎቻቸው በታች
ነበረ። 22 ፊቶቻቸውም በኮቦር ወንዝ በራዕይ ያየኋቸውን ፊቶች ይመስሉ ነበር ፣ እያንዳንዱም አቅንቶ ወደ ፊት ይሄድ ነበር።

Ezekiel 10:1

በጉልላቱ አቅጣጫ
“በክቡ ጣራ አቅጣጫ”

ኪሩቤል
ይህንን በሕዝቅኤል 9፡3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሰንፔር የሚመስል
ጠቃሚ የሆነ ሰማያዊ ወይም አረንጓዴ የከበረ ድንጋይ

የዙፋን አምሳያ
“የሆነ ነገር የሚመስል፣ ዙፋን የሚመስል”። ሕዝቅኤል ዙፋን ስለመሰለው ነገር በእርግጠኝነት ለመናገር አይፈልግም።

በፍታ
ከእጽዋት የሚሠራ ጠንካራና ለስላሳ ጨርቅ። በሞቃታማ አካባቢ በሚኖሩ በርካታ ሰዎች የሚለበስ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 9፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ለስላሳ ጨርቅ” (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)

በመንኩራኩሮቹ መካከል ሂድ
“መንኩራኩሮች” የሚለውን ቃል በሕዝቅኤል 1፡15 እንዳለው አድርገህ ተርጉመው።

የሚነድ ከሰል
ከሰል እሳት ከነደደ በኋላ የሚቀር የተቃጠለ የእንጨት ቁርጥራጭ ነው። ጥቁር ቢሆንም በእሳት በሚያያዝበት ጊዜ ቀይና ብርቱካናማ ቀለም ይኖረዋል፤ ከሰል በመባልም ይታወቃል።

በከተማይቱ ላይ በትነው
“በከተማይቱ ላይ እርጨው” ወይም “በከተማይቱ ላይ አሰራጨው”

Ezekiel 10:3

በውስጠኛው አደባባይ ... ኪሩቤል ቆመ
ይህ ቀጥሎ ለሚመጡት ሁነቶች ዳራዊ መረጃ ነው። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ኪሩቤል
ይህንን በሕዝቅኤል 9፡3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

በስተቀኙ
አንድ ሰው ወደ ምስራቅ በሚመለከትበት ጊዜ የደቡቡ አቅጣጫ “በስተቀኙ” ይሆናል። አ.ት፡ “በደቡብ በኩል”

ቤቱ
ቤተ መቅደሱ

የእግዚአብሔር ክብር
ይህንን በሕዝቅኤል 1፡28 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሞላው
የእግዚአብሔር ክብር ሞላው

Ezekiel 10:6

እንዲህ ሆነ
ይህ ሐረግ እዚህ ጋ ጥቅም ላይ የዋለው እንቅስቃሴው የሚጀምርበትን ጊዜ ለማመልከት ነው። የአንተ ቋንቋ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለ እዚህ ጋ ልትጠቀምበት እንደምትችል አስብበት።

እግዚአብሔር በፍታ የለበሰውን ሰውዬ -- ብሎ ባዘዘው ጊዜ
ይህ በሕዝቅኤል 10፡2 ተሰጥቶ የነበረው መረጃ የተደገመበት ነው። ሕዝቅኤል በ10፡3-5 ስለ ኪሩቤል እና ስለ እግዚአብሔር ክብር ከተናገረ በኋላ ላይነን ለብሶ ስለነበረው ሰው ወደ መናገሩ ይመለሳል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በፍታ የለበሰው ሰው
“በፍታ”ን በሕዝቅኤል 9:1 እንዳለው አድርገህ ተርጉመው።

በመንኩራኩሮቹ አጠገብ
“መንኩራኩር”ን በሕዝቅኤል 1:15 እንዳለው አድረገህ ተርጉመው።

በኪሩቤል ላይ አንድ የሰው እጅ የሚመስል ከክንፎቻቸው ሥር አየሁ
“ኪሩቤል ከክንፎቻቸው ሥር የሰው እጅ የሚመስል ነገር ኖሮአቸው አየሁ”

Ezekiel 10:9

እነሆ
ሕዝቅኤል ባየው ተደንቋል

መንኩራኩሮች
ይህንን በሕዝቅኤል 1:15 ላይ እንዴት እንደተርጎምከው ተመልከት።

ኪሩቤል
ይህንን በሕዝቅኤል 9:3 ላይ እንዴት እንደተርጎምከው ተመልከት።

ኪሩብ
ይህ የ”ኪሩቤል” ነጠላ ቁጥር ነው።

የመንኩራኩሮቹ አምሳያ ልክ እንደ ቢረሌ ድንጋይ አንጸባራቂ ነበር
“አምሳያ” የሚለው የነገር ስም እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “መንኩራኩሮቹ የቢረሌ ድንጋይ መስለው ይታዩ ነበር” ወይም “መንኩራኩሮች ሆነው የታዩት የቢረሌ ድንጋይ ይመስሉ ነበር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

የቢረሌ ድንጋይ
እዚህ ጋ የተጠቀሰው “ቢረሌ” በጣም ከባድና ዋጋ ያለው ድንጋይ ነው። ይህ ቢረሌ ምናልባት አረንጓዴ ወይም ሰማያዊ ነበር። (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)

የአራቱም አምሳያ አንድ ዓይነት መልክ ነበር
“አምሳያ” የሚለው የነገር ስም እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። “መልክ” የሚለው የነገር ስም እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “አራቱም ተመሳሳይ መልክ ነበራቸው” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

አንደኛው መንኩራኩር በሌላኛው መንኩራኩር ተሰባጥሮ
“መሰባጠር” የሚለው ቃል “ማቋረጥ” ወይም “በሌላው ሥር ማለፍ” ማለት ነው።

በየትኛውም በአራቱ አቅጣጫ ይሄዱ ነበር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “የእነርሱ” የሚያመለክተው ፍጡራኑን ነው። አ.ት፡ “ፍጡራኑ በሚመለከቱባቸው ከአራቱ በየትኛውም አቅጣጫ ቀጥ ብለው ይሄዱ ነበር” ወይም 2) “የእነርሱ” የሚያመለክተው መንኩራኩሮቹን ነው የሚሉት ናቸው።

ራሳቸው የዞረበትን የትኛውንም አቅጣጫ ይከተሉ ነበር
“ራስ” ለሚለው ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ክንፍ ያላቸውን ፍጡራን ይመለከታል። አ.ት፡ “ክንፍ ያላቸው ፍጡራን በሚመለከቱበት በየትኛውም አቅጣጫ ይሄዱ ነበር” ወይም 2) ይህ የሚያመለክተው ከፊት ያለውን መንኩራኩር ነው የሚሉት ናቸው። አ.ት፡ “የፊተኛው መንኩራኩር በሚሄድበት በየትኛውም አቅጣጫ ይከተሉት ነበር”።

Ezekiel 10:12

አካላቸው በሙሉ
“የኪሩቤል ሙሉ አካላቸው”

መንኩራኩሮች
“መንኩራኩሮች” የሚለውን ቃል በሕዝቅኤል 1:15 እንዳለው አድርገህ ተርጉመው።

መንኩራኩሮቹ “ተሽከርካሪ” ተብለው ተጠሩ
“ተሽከርካሪ” ማለት “መሾር” ማለት ነው። እዚህ ጋ ይህ የመንኩራኩሮቹ ስም ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አንድ ሰው መንኩራኩሮቹን ‘ተሽከርካሪ’ ብሎ ጠርቷቸዋል” ወይም “የመንኩራኩሮቹ ስም ‘ተሽከርካሪ’ ነበር” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እያንዳንዳቸው አራት ፊት ነበራቸው
“እያንዳንዱ ኪሩብ አራት ፊት ነበረው” ወይም “ለእያንዳንዱ ኪሩቤል አራት ፊት ነበራቸው”። እያንዳንዱ ፍጥረት በፊት ለፊቱ፣ በስተኋላው፣ በራሱ ግራና ቀኝም ፊት ነበረው። ይህንን በሕቅኤል 1:6 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Ezekiel 10:15

ኪሩቤል
ይህንን በሕዝቅኤል 9:3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሕያዋን ፍጡራን
ይህንን በሕዝቅኤል 1:13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የኮቦር ቦይ
ይህ ከለዳውያን የአትክልት ቦታቸውን ለማጠጣት የቆፈሩት ወንዝ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 1:3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

ተነሣ
“ወደ ሰማይ ወጣ”

በአጠገባቸው ገና ቆመው ነበር
“መንኩራኩሮቹ ከኪሩቤል ጋር ነበሩ”። አ.ት፡ “መንኩራኩሮቹ ከኪሩቤል ጋር ተንቀሳቀሱ”

ጸንተው ቆሙ
“ጸንተው ቆዩ” ወይም “አልተንቀሳቀሱም”

የሕያው ፍጡሩ መንፈስ በመንኩራኩሮቹ ውስጥ ነበር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሕዝቅኤል በቁጥር 15 ላይ ስለ “ፍጡራን” የሚናገረው አንድ ፍጡር እንደሆነ አድርጎ ነው። አ.ት፡ “የሕያዋን ፍጡራኑ መንፈስ በመንኩራኩሮቹ ውስጥ ነበር” ወይም 2) ሕዝቅኤል የሚጠቀመው የአነጋገር ዘይቤን ነው። አ.ት፡ “የሕይወት መንፈስ በመንኩራኩሮቹ ውስጥ ነበር” ወይም “ሕያው መንፈስ በመንኩራኩሮቹ ውስጥ ነበር” ወይም 3) በፍጡራኑ እና በመንኩራኩሮቹ ውስጥ ያለው መንፈስ አንድ ነው የሚሉት ናቸው። ይህንን በሕዝቅኤል 1:22 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ለፍጡራኑ ሕይወት የሰጣቸው ያው መንፈስ ለመንኩራኩሮቹ ደግሞ ሕይወትን ሰጣቸው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 10:18

የእግዚአብሔር ክብር
ይህንን በሕዝቅኤል 1:28 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ቤቱ
ቤተ መቅደሱ

በላዩ ቆመ
“በላዩ ቆየ” ወይም “በላዩ ላይ ጠበቀ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከላይ መጣባቸው
“ከኪሩቤል በላይ ወጣ”

Ezekiel 10:20

ሕያዋን ፍጡራን
ይህንን በሕዝቅኤል 1:13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የኮቦር ቦይ
ይህ ከለዳውያን የአትክልት ቦታቸውን ለማጠጣት የቆፈሩት ወንዝ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 1:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የሰው እጅ የሚመስል
እዚህ ጋ የነገር ስም የሆነው “መምሰል” ሕዝቅኤል ሲያየው የሰው መስሎ የታየው ነገር ማለት ነው። ቃሉ ከግሣዊ ሐረግ ጋር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “የሰው እጅ የሚመስል ነገር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

የፊታቸው መልክ ቀድሞ ያየሁትን የሚመስል ነበር
የነገር ስም የሆነው “መምሰል” ከግሣዊ ሐረግ ጋር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ፊታቸው ቀድሞ ያየሁትን ፊት ይመስላል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ቀጥ ብለው ወደፊት ሄዱ
“ወደፊት እያዩ” ወይም “በቀጥታ ወደፊት እያዩ”

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ጠቃሚ የሆኑ ስዕላዊ ንግግሮች በዘይቤአዊ አነጋገር ተነግረዋል
በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎች ዘይቤአዊ አነጋገር በመጠቀም “ይህቺ ከተማ ማሰሮ ናት፣ በማሰሮው ውስጥ ያለው ሥጋም እኛ ነን” ይሉ ነበር፣ ትርጉሙም በኢየሩሳሌም ምንም ጉዳት አይደርስባቸውም ማለት ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 11

1 መንፈስም አነሣኝ ወደ ምስራቅ መውጫ ወደሚመለከት ወደ እግዚአብሔር ቤት ምሥራቅ በር አመጣኝ። እነሆም፥ በበሩ መግቢያ ሀያ አምስት ሰዎች ነበሩ፥ በመካከላቸውም የሕዝቡን አለቆች የዓዙርን ልጅ ያእዛንያንና የበናያስ ልጅ ፈላጥያን አየሁ። 2 እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ፥ "የሰው ልጅ ሆይ፥ እነዚህ ክፋትን የሚያስቡ በዚህችም ከተማ ክፉን ምክር የሚመክሩ ሰዎች ናቸው። 3 እነርሱም 'ቤቶችን የምንሠራበት ዘመን አይደለም። ይህች ከተማ ድስት እኛም ሥጋ ነን' ብለዋል። 4 ስለዚህ፥ የሰው ልጅ ሆይ፥ ትንቢት ተናገርባቸው፣ ትንቢት ተናገር። 5 የእግዚአብሔርም መንፈስ በኔ ላይ ሆኖ እንዲህ አለኝ፥ "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ብለህ ተናገር። የእስራኤል ቤት ሆይ፥ ይህን ነገር ተናግራችኋል፥ እኔም የልባችሁን አሳብ አውቃለሁ። 6 በዚህች ከተማ ውስጥ ብዙ ሰዎችን ገድላችኋል ጎዳናዎችዋንም በሬሳዎቻቸው ሞልታችኋል። 7 ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በአየሩሳሌም ከተማ መካከልም ሬሳዎቻቸው ያኖራችኋቸው የገደላቹኋቸው ሰዎች ሥጋው ሲሆኑ፥ ይህችም ከተማ ድስቱ ናት። እናንተን ግን ከከተማዋ መካከል ተነቅላችሁ ትወጣላችሁ። 8 ሰይፍን ፈርታችኋል እኔም ሰይፍን አመጣባችኋለሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፦ 9 ከከተማይቱ መካከል አወጣችኋለሁ፥ በእንግዶችም እጅ አሳልፌ እሰጣችኋለሁ፥ በላያችሁም ፍርድ አመጣባችኋለሁ። 10 በሰይፍ ትወድቃላችሁ በእስራኤልም ድንበር ውስጥ እፈርድባችኋለሁ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ። 11 ይህች ከተማ የማብሰያ ድስት አትሆንላችሁም እናንተም በመካከልዋ ሥጋ አትሆኑም፣ እኔም በእስራኤል ድንበር ውስጥ እፈርድባችኋለሁ። 12 እኔም በትዕዛዙ ያልሄዳችሁለት ፍርዱንም ያላደረግችሁለት እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ። ይልቁኑ በዙሪያችሁ እንደሚኖሩት እንደ አሕዛብ ሕግ አድርጋችኋል። 13 እንዲህም ሆነ ትንቢትም በተናገርሁ ጊዜ የበናያስ ልጅ ፈላጥያ ሞተ፣ እኔም በግምባሬ ተደፍቼ "ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፥ ወዮ! በውኑ የእስራኤልን ቅሬታ ፈጽመህ ታጠፋለህን?" ብዬ በታላቅ ድምፅ ጮኽሁ። 14 የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ 15 "የሰው ልጅ ሆይ፥ ወንድሞችህ! አዎ ወንድሞችህ! ዘመዶችህ በኢየሩሳሌምም የሚኖሩ ሁሉ! 'እነርሱ ከእግዚአብሔር የራቁ ናቸው! ይህች ምድር ርስት ሆና ለእኛ ተሰጥታለች' የሚሉአቸው ናቸው። 16 ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል በላቸው፣ 'ምንም እንኳ እኔ በሩቅ ወዳሉ አሕዛብ ባርቃቸውና ወደ አገሮችም ብበትናቸውም በሄዱባቸው አገሮች ለጥቂት ጊዜ ቤተ መቅደስ ሆኜላቸዋለሁ' ። 17 ስለዚህም ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል በላቸው 'ከአሕዛብ ዘንድ አከማቻችኋለሁ ከተበተናችሁባቸውም አገሮች እሰበስባችኋለሁ፥ የእስራኤልንም ምድር እሰጣችኋለሁ። 18 ወደዚያም ይመጣሉ፥ ጸያፉንና ርኩሰንም ነገር ሁሉ ከዚያች ምድር ያስወግዳሉ። 19 ወደኔ ሲቀርቡ አንድ ልብ እሰጣቸዋለሁ፥ በውስጣቸውም አዲስ መንፈስ አስቀምጣለሁ፤ 20 ከሥጋቸውም ውስጥ ድንጋዩን ልብ አውጥቼ የሥጋን ልብ እሰጣቸዋለሁ፣ ይህም በትእዛዜም እንዲሄዱና ፍርዴንም እንዲጠብቁና እንዲያደርጉት ነው። በዚያን ጊዜ እነርሱ ሕዝብ ይሆኑኛል እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ። 21 በልባቸው ወደ ጸያፍና ርኩስ ነገሮቻቸው በሚሄዱት ላይ መንገዳቸውን ወደራሳቸው እመልሳለሁ። ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው። " 22 ኪሩቤልም ክንፎቻቸውንና በአጠገባቸው የነበሩትን መንኰራኵሮች ከፍ አደረጉ፣ የእስራኤልም አምላክ ክብር በላያቸው ላይ ነበረ። 23 የእግዚአብሔርም ክብር ከከተማይቱ ውስጥ ተነሥቶ በከተማይቱ ምሥራቅ በኩል ባለው ተራራ ላይ ቆመ። 24 መንፈስም አነሣኝ፥ ከእግዚአብሔርም ዘንድ በሆነ ራእይ ምርኮኞቹ ወዳሉበት ወደ ከላውዴዎን ምድር አመጣኝ። ያየሁትም ራእይ ከእኔ ተለየ። 25 ከዚያም እግዚአብሔር ያሳየኝን ነገር ሁሉ ለምርኮኞች ነገርኳቸው።

Ezekiel 11:1

ወደ ምስራቅ ወደሚመለከተው ወደ ምስራቁ የእግዚአብሔር ቤት መግቢያ
ይህ በር የቤተ መቅደሱን አካባቢ የሚከበው ግንብ አካል ነው። ኢ.ት፡ “በምስራቁ በኩል የእግዚአብሔርን ቤት በሚከበው ግንብ ላይ ያለው በር” ወይም “በቤተ መቅደሱ አደባባይ በምስራቁ ግንብ ላይ ያለው በር”

የእግዚአብሔር ቤት
ይህንን በሕዝቅኤል 8:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

እነሆ
እዚህ ጋ፣ “እነሆ” የሚለው ቃል የሚቀጥለው አስገራሚ መረጃ ላይ እንድናተኩር ያነቃናል።

ሃያ አምስት ሰዎች
“25 ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

የዓዙር ልጅ ያእዛንያ እና የበናያስ ልጅ ፈላጥያ
እነዚህ የወንዶቹ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

በመካከላቸው
“በሃያ አምስቱ ሰዎች መካከል”

Ezekiel 11:2

የሰው ልጅ
“የሰብዓዊ ፍጡር ልጅ” ወይም “ከሰው የተወለደ ልጅ”። ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን አፅንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ በማለት ይጠራዋል። እግዚአብሔር ዘላለማዊና ኃያል ነው፣ ሰዎች ግን አይደሉም። ይህንን በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ሟች ሰው” ወይም “ሰው”

ቤቶች የሚሠሩበት ጊዜ አሁን አይደለም
ይህ ሕዝቡ ደህንነት ስለተሰማቸው አሁን ላይ ቤት ለመሥራት እንዳላሳሰባቸው ያሳያል። ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች “ቤቶቻችንን የምንሠራበት ጊዜ አሁን ነው” የሚል ይነበብባቸዋል። ይህም ማለት፣ ሕዝቡ ደህንነት ስለተሰማቸው ቤቶችን ለመሥራት ፈልገዋል።

ይህቺ ከተማ ማሰሮ ናት፣ እኛም ሥጋ ነን
ሕዝቡ ስለ ራሳቸው የተከተፈ ሥጋ እንደሆኑና ከተማይቱም እንደ ሥጋ ማስቀመጫ ወይም ማብሰያ ማሰሮ እንደሆነች አድርገው ይናገራሉ። ዘይቤአዊው አነጋገር በከተማይቱ ውስጥ እነርሱ አስፈላጊዎችና ጉዳት የማይደርስባቸው መሆናቸውን ይጠቁማል። አ.ት፡ “ማሰሮ ሥጋን እንደሚከልል ይህቺም ከተማ እንደ ማሰሮ ትከልለናለች” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ማሰሮው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሥጋ ለማስቀመጥ የሚያገለግል ማሰሮ ወይም 2) ሥጋ ለማብሰል የሚያገለግል ማሰሮ የሚሉት ናቸው።

Ezekiel 11:5

የእግዚአብሔር መንፈስ ወደቀብኝ
ሕዝቅኤል ትንቢት እንዲናገር የእግዚአብሔር መንፈስ እርሱን ማነሣሣቱና ማስታጠቁን የእግዚአብሔር መንፈስ እንደወደቀበት አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “የእግዚአብሔር መንፈስ ሥልጣንን ሰጠኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የምትናገሩት ይህንን ነው
“እነዚህን ነገሮች ተናግራችኋል”። ይህ ሕዝቡ በሕዝቅኤል 11:3 ይናገሩት የነበረውን ያመለክታል።

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ በዓመታት ውስጥ የነበሩትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እስራኤላውያን” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሥጋው የገደላችኋቸው ሰዎች ናቸው፣ ማሰሮው ደግሞ ከተማይቱ ናት
እግዚአብሔር የተገደሉትን ሰዎች እንደ ተከተፈ ሥጋ፣ ከተማይቱንም ሥጋው እንደሚቀመጥበት ወይም እንደሚበስልበት ማሰሮ አድርጎ ይናገራል። ይህንን ዘይቤአዊ አነጋገር በሕዝቅኤል 11:3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የገደላችኋቸው ሰዎች በማሰሮ ውስጥ ያለ ሥጋ የሚመስሉ ናቸው፣ ከተማይቱም ማሰሮ ትመስላለች። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እናንተ ግን ከውስጧ ልትወጡ ነው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ይሁን እንጂ ከውስጧ ላወጣችሁ ነው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 11:8

ሰይፍን ፈርታችኋል፣ ሆኖም ሰይፍን አመጣባችኋለሁ
“ሰይፍ” የሚለው ቃል በሰይፎቻቸው ሰዎችን የሚገድሉትን ወታደሮችን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ጦርነትን ፈርታችኋል፣ ሆኖም የሚወጋችሁን የጠላት ሰራዊት አመጣባችኋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ይህ የጌታ እግዚአብሔር መግለጫ ነው
እግዚአብሔር የሚናገረው የሚፈጸም መሆኑን ለመግለጽ ስለ ራሱ በስሙ ይናገራል። ይህንን በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ጌታ እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን ነው” ወይም “ይህንን የተናገርኩት እኔ ጌታ እግዚአብሔር ነኝ” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

በባዕዳን እጅ አሳልፌ እሰጣችኋለሁ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ኃይልን ወይም መቆጣጠርን ይወክላል። አ.ት፡ “በባዕዳን ኃይል ሥር አደርጋችኋለሁ” ወይም “ባዕዳን እንዲይዙአችሁ አደርጋቸዋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በሰይፍ ትወድቃላችሁ
“ሰይፍ” የሚለው ቃል በሰይፎቻቸው ሰዎችን የሚገድሉትን ወታደሮችን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “በሰይፎቻቸው ይገድሏችኋል” ወይም “በጦርነት ትሞታላችሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ዕወቁ
እግዚአብሔር ሰዎች እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን ያውቃሉ ብሎ በሚናገርበት ጊዜ እርሱ ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለው ብቸኛው እውነተኛ አምላክ መሆኑን ሰዎች ያውቃሉ ማለቱ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 6:7 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እውነተኛው አምላክ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ተረዱ” ወይም “ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለኝ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ተገንዘቡ”

Ezekiel 11:11

ይህቺ ከተማ የማብሰያ ማሰሮ አትሆንላችሁም፣ እናንተም ሥጋ አትሆኑም
ሕዝቡ ስለ ራሳቸው የተከተፈ ሥጋ እንደሆኑና ከተማይቱም እንደ ሥጋ ማስቀመጫ ወይም ማብሰያ ማሰሮ እንደሆነች አድርገው ተናግረው ነበር። እግዚአብሔር ይህ እውነት አይደለም ይላል። ይህንን ዘይቤአዊው አነጋገር በሕዝቅኤል 11:3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ማሰሮ ሥጋን እንደሚከልል ይህቺም ከተማ እንደ ማሰሮ አትከልላችሁም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእስራኤል ድንበር ውስጥ
“በእስራኤል ምድር”

በትዕዛዛቱ አልሄዳችሁም
ሰው በመንገድ ላይ እንደሚሄድ ትዕዛዛቱን የሚጠብቁ በእነርሱ ላይ እንደሚሄዱ አድርጎ እግዚአብሔር ይናገራል። አ.ት፡ “ትዕዛዛቱን ያልጠበቃችሁለት እርሱ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 11:13

እንዲህ ሆነ
እዚህ ጋ፣ ይህ ሐረግ ጥቅም ላይ የዋለው እንቅስቃሴው የሚጀምርበትን ጊዜ ለማመልከት ነው። የአንተ ቋንቋ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለ እዚህ ጋ ልትጠቀምበት እንደምትችል አስብበት።

የበናያስ ልጅ ፈላጥያ
ይህ የአንድ ሰው ስም ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 11:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

በግንባሬ ተደፋሁ
“በምድር ላይ ሰገድሁ” ወይም “በምድር ላይ ተጋደምኩ”። ሕዝቅኤል የወደቀው በአደጋ ምክንያት አይደለም። እርሱ በምድር ላይ የወደቀው ለእግዚአብሔር ያለውን አክብሮትና ፍርሐት ለማሳየት ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ኦ፣ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ
“ኦ” የሚለው ቃል ፍርሐትንና ሐዘንን የሚገልጽ ድምፅ ነው። አ.ት፡ “ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፣ አይሁን” ወይም “አይ፣ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ” (ቃልአጋኖ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 11:14

የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ወንድሞችህ! ወንድሞችህ!
ይህ አጽንዖት ለመስጠት ሁለት ጊዜ ተነግሯል

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እነዚያ ሁሉ በኢየሩሳሌም በሚኖሩት የተነገረላቸው ናቸው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎች ስለ እነርሱ ስለ ሁሉም ይናገራሉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እነዚያ ሁሉ የተነገረላቸው ናቸው
አንዳንድ ትርጉሞች “ሁሉም የእነርሱ ናቸው” የሚል አላቸው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይህቺ ምድር ርስታችን ሆና ተሰጥታናለች
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህቺን ምድር ርስት አድርጎ ሰጥቶናል” ወይም “ይህቺ ምድር ርስታችን ሆናለች” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 11:16

መቅደሳቸው ሆኜ ነበር
እግዚአብሔር በምርኮ ባለው ሕዝብ መካከል ማደሩን ሲገልጽ መቅደስ እንደሆነላቸው አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “ከእነርሱ ጋር ነበርኩ” ወይም “እንደ አምልኮ ስፍራቸው ነበርኩ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከሕዝቦች መካከል እሰበስባችኋለሁ፣ ከየሀገራቱም መልሼ አከማቻችኋለሁ
በመሠረቱ የእነዚህ ሁለት ሐረጎች ትርጉም አንድ ነው። ድግግሞሹ አጽንዖት የሚሰጠው እግዚአብሔር ምርኮኞቹን ወደ እስራኤል ምድር ለመመለስ የሰጠው ተስፋ እርግጥ መሆኑን ነው። አ.ት፡ “ከየሀገራቱ ሁሉ መልሼ አመጣችኋለሁ”

ከተበተናችሁበት
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እናንተን ከበተንኩበት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የሚያስከፋውን ነገር ሁሉ እና የሚያስጸይፈውን ተግባር ሁሉ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ እግዚአብሔር ጣዖታትን ሁሉ ከእስራኤል እንደሚያስወግድ አጽንዖት ይሰጣሉ።

የሚያስከፋውን ነገር ሁሉ
ይህ ማለት የሚያስጠሉ ወይም የሚያስቀይሙ ነገሮችን ማለት ነው። እዚህ ጋ፣ ይህ የሚያመለክተው ጣዖታትን ነው።

Ezekiel 11:19

አንድ ልብ እሰጣቸዋለሁ ... የሥጋ ልብ እሰጣቸዋለሁ
እግዚአብሔር አንድ ልብና አንድ መንፈስ እንዳለው እንደ አንድ ሰው አድርጎ የሚናገረው በምርኮ ስላሉት እስራኤላውያን ሁሉ ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አንድ ልብ እሰጣቸዋለሁ
እዚህ ጋ “ልብ” የሚለው ፈሊጣዊው አነጋገር የሚወክለው ፈቃድን እና ስሜትን ነው። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ሁሉ አንድ ልብ የሰጣቸው ያህል ተመሳሳይ የሆነ አዲስ ስሜት እንደሚጋሩ ይናገራል (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አዲስን መንፈስ በውስጣቸው አደርጋለሁ
እዚህ ጋ “መንፈስ” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር አሳብንና ጸባይን ይወክላል። እግዚአብሔር ለሕዝቡ አዲስ መንፈስ የሰጣቸው ያህል አዳዲስ አሳቦችን እንዲያስቡ እንደሚያደርጋቸው ይናገራል። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከሥጋቸው ውስጥ የድንጋይን ልብ አወጣለሁ፣ የሥጋንም ልብ እሰጣቸዋለሁ
ሕዝቡ የድንጋይ ልብ ስለነበራቸው እልኸኛ እንደሆኑና የሥጋ ልብ ሲኖራቸው በፈቃደኝነት የሚታዘዙ እንደሚሆኑ እግዚአብሔር ይናገራል። ሁለቱን ልቦች በማቀያየር በፈቃደኝነት የሚታዘዙ እንደሚያደርጋቸው ይናገራል። አ.ት፡ “እልኸኛ መሆናቸውን እንዲያቆሙ አደርጋቸዋለሁ፣ በምትኩም በፈቃደንነት እንዲታዘዙኝ አደርጋቸዋለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በትዕዛዛቴ ይሄዳሉ፣ ሕግጋቴንም ይፈጽማሉ፣ ያደርጓቸዋልም
እነዚህ ሐረጎች ሁሉ ሕዝቡ እግዚአብሔር እንዲያደርጉት ያዘዛቸውን እንደሚታዘዙ የሚገልጽ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። የተደጋገሙት አጽንዖት ለመስጠት ነው። (See: Parallelism)

በትዕዛዛቴ ይሄዳሉ
እግዚአብሔር የእርሱን ትዕዛዛት መጠበቅ አንድ ሰው በመንገድ ላይ እንደሚሄድ ሁሉ በትዕዛዛቱ ላይ እንደ ሄደ አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “ትዕዛዛቴን ይጠብቃሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ወደ አስከፊ ነገሮቻቸው በውዴታ የሚሄዱትን እነዚያን
እግዚአብሔር ስለ አንድ ሰው ሥራ ሲናገር ያ ሰው ተራምዶ እንደሚሄድ አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “ሕይወታቸውን አስከፊ የሆኑ ነገሮቻቸውን ለመሥራት በትጋት የሚሰጡትን እነዚያን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የሚያስከፉ ነገሮች
ይህ የሚያስጠሉና የሚያስቀይሙ ነገሮችን ማለት ነው። እዚህ ጋ፣ ይህ የሚያመለክተው ጣዖታትን ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 11:18 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሥራቸውን በራሳቸው ላይ አመጣባቸዋለሁ
እዚህ ጋ “ሥራ” የሚለው ፈሊጣዊው አነጋገር የሚወክለው የድርጊቶቻቸውን ውጤት ነው። “በራሳቸው ላይ አመጣባቸዋለሁ” የሚለው የአነጋገር ዘይቤ ትርጉሙ ውጤቱን ይቀበላሉ የሚል ነው። አ.ት፡ “በድርጊቶቻቸው ምክንያት በውጤቱ መከራን እንዲቀበሉ አደርጋቸዋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 11:22

ኪሩቤል
ይህንን በሕዝቅኤል 9:3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Ezekiel 11:24

ያየሁት ራዕይ ከእኔ ላይ ተነሥቶ ወደ ላይ ሄደ
ሕዝቅኤል ስለ ራዕዩ ማብቃት ሲናገር በእርሱ ላይ እንደነበረና ከዚያም ተለይቶት እንደ ሄደ እንደ አንዳች ቁስ አድርጎ ይገልጸዋል። አ.ት፡ “ያየሁት ራዕይ አበቃ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 12

1 የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፣ 2 "የሰው ልጅ ሆይ፥ የምትኖረውዓመጸኞች ከመሆናቸው የተነሳ አይን እያላቸው በማያዩ ጆሮ እያላቸው በማይሰሙ በዓመፀኛ ሰዎች መካከል ነው! 3 አንተ ግን የሰው ልጅ ሆይ፥ ለስደት ተዘጋጅ ምክንያቱም በፊታቸውም በጠራራ ፀሀይ ከስፍራህ ወደ ሌላ ስፍራ ተማርከህ እንድትሄድ አደርጋለሁ። ምናልባት ይህን ሲያዩ ዓመፀኛ ቤት እንደ ሆኑ ያስተውሉ ይሆናል። 4 እቃዎችህን ሰብስበህ በቀን በፊታቸው ለስደት ተዘጋጅ፤ በማታም ጊዜ በፊታቸው ልክ ስደተኞች እንደሚያደርጉት ሂድ። 5 እያዩህም ግንቡን ፈንቅለውና በእዚያ በኩል ውጣ። 6 እያዩህም እቃዎችህን በጫንቃህ ላይ ተሸከምና በጨለማ ውጣ። ለእስራኤልም ህዝብ ምልክት አድርጌሃለሁና ምድሪቱን እንዳታይ ፊትህን ሸፍን። 7 እንዳዘዘኝም አደረግሁ። በቀንም የስደት እቃዬን ወስጄ ማታ ላይ ግንቡን በእጄ ፈነቀልኩና በጨለማ አወጣቼ እያዩኝ በጫንቃዬ ላይ ተሸከምሁት። 8 በነጋታውም የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ። 9 "የሰው ልጅ ሆይ፥ ዓመፀኛው የእስራኤል ቤት 'የምታደርገው ምንድር ነው?' ብለው ጠየቁህን? 10 አንተም ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል 'ይህ ትንቢታዊ ጉዳይ በኢየሩሳሌም የሚኖረውን አለቃና በመካከላቸውም የሚኖሩትን የእስራኤል ቤትን ሁሉ የሚመለከት ነው' በላቸው። 11 ደግሞም፦ እኔ ምልክታችሁ ነኝ እኔ እንዳደረግሁ እንዲሁ ይደረግባቸዋል፥ እነርሱም በስደት ወደ ምርኮ ይሄዳሉ በላቸው። 12 በመካከላቸውም የሚኖረው አለቃ ንብረቱን በጫንቃው ላይ ተሸክሞ ግንቡን ፈንቅሎ በጨለማ ይወጣል። ንብረታቸውን ለማውጣት ግንቡን ይፈነቅላሉ። አለቃውም በዓይኑ ምድሪቱን እንዳያይ ፊቱን ይሸፍናል። 13 መረቤንም በእርሱ ላይ እዘረጋለሁ በወጥመዴም ይያዛል፥ ወደ ከለዳውያንም ምድር ወደ ባቢሎን አመጣዋለሁ ሆኖም አያያትም በዚያም ይሞታል። 14 ሊረዱትም በዙሪያው ያሉትን ሁሉና ወታደሮቹን ሁሉ በየእቅጣጫው እበትናቸዋለሁ፣ከኋላቸውም ሰይፍ እልክባቸዋለሁ። 15 በአሕዛብም መካከል በበተንኋቸው ጊዜ፥ በአገሮችም በዘራኋቸው ጊዜ፥ እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ። 16 ነገር ግን በሚሄዱባቸውም አሕዛብ መካከል ርኩሰታቸውን ሁሉ እንዲመዘግቡ ከሰይፍና ከራብ ከቸነፈርም ጥቂቶች ሰዎችን ከእነርሱ አተርፋለሁ፣ ከዚያም እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ። 17 የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፣ 18 "የሰው ልጅ ሆይ፥ እንጀራህን በመረበሸ ብላ ውኃህንም በመንቀጥቀጥና በኀዘን ጠጣ። 19 ለምድሪቱም ሕዝብ 'ጌታ እግዚአብሔር ስለኢየሩሳሌም ነዋሪዎችና ስለ እስራኤል ምድር እንዲህ ይላል 'ክሚኖሩባት ሰዎች አመጽ የተንሳ ምድሪቱ ሞላዋ ስለምትጠፋ እንጀራቸውን በመረበሸ ወኃቸውንም በድንጋጤ ይጠጣሉ። 20 ሰዎች የሚኖሩባቸው ከተሞች ባድማ ይሆናሉ ምድሪቱም ውድማ ትሆናለች እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ በላቸው። 21 የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ, 22 "የሰው ልጅ ሆይ፥ በእስራኤል ምድር የሚነገረው'ዘመኑ ረዝሞአል ራእዩም ሁሉ ጠፍቶአል' የሚለው ምሳሌ ምንድር ነው? 23 ስለዚህ እንዲህ በላቸው 'ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ክዚህ በኋላ የእስራኤል ህዝብ እንዳይጠቀሙበት ይህን ምሳሌ አስቀረዋለሁ ።' ከዚያም እንዲህ በላቸው "ዘመኑ ቀርቦአል እያንዳንዱ ራዕይም ይናገራል!' 24 ምክንያቱም ከዚህ በኋላ በእስራኤል ቤት መካከል ከንቱ ራእይና ውሸተኛ ምዋርት አይሆንም። 25 እኔ እግዚአብሔር ነኝና! እናገራለሁ የተናገርኩትንም ቃል እፈጽማለሁ። ነገሩ ከእንግዲህ አይዘገይም። እናንተ ዓመፀኛ ቤት ሆይ፥ በዘመናችሁ ቃሌን እናገራለሁ እፈጽመውማለሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር።" 26 የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል እንደገና መጣ፣ 27 "የሰው ልጅ ሆይ፥ እነሆ፥ የእስራኤል ቤት 'ይህ ያየው ራእይ ገና ስለወደፊቱ ነው ስለሩቅ ዘመንም ትንቢት ይናገራል' ብለዋል። 28 ስለዚህ እንዲህ በላቸው 'ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ የምናገረው ቃል ይፈጸማል እንጂ ከዚህ በኋላ አይዘገይም' ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው!"

Ezekiel 12:1

የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የሰው ልጅ
“የሰብዓዊ ፍጡር ልጅ” ወይም “ከሰው የተወለደ ልጅ”። ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን አፅንኦት ለመስጠት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ በማለት ይጠራዋል። እግዚአብሔር ዘላለማዊና ኃያል ነው፣ ሰዎች ግን አይደሉም። አ.ት፡ “ሟች ሰው” ወይም “ሰው”

አመፀኛ ቤት
አመፀኛ ቤት “ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ በዓመታት ውስጥ የነበሩትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 2:5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “አመፀኛ ሕዝብ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሊያዩበት ዐይን አላቸው ነገር ግን አያዩም ... መስሚያ ጆሮ አላቸው ነገር ግን አይሰሙም
የሕዝቡ የእግዚአብሔርን መልዕክትና እርሱ እየሠራ ያለውን ለመረዳት አለመቻል በአካላቸው ለማየትና ለመስማት እንዳልቻሉ ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 12:3

ስለዚህ አንተ
“በመሆኑም፣ የምነግርህ ይህንን ነው”

በዐይናቸው ፊት
“እነርሱ እያዩህ”

ምናልባት ማየት ይጀምሩ ይሆናል
ሕዝቡ የእግዚአብሔርን መልዕክትና እርሱ እየሠራ ያለውን ለመረዳት መቻላቸው በአካላቸው ማየት እንደቻሉ ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አመፀኛ ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 2:5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “አመፀኛ ሕዝብ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 12:4

በዐይናቸው ፊት
“እነርሱ እያዩህ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንደ ምልክት አድርጌሃለሁ
እዚህ ጋ “ምልክት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ለሚመለከቱት የተለየ ማስጠንቀቂያን የሚያስተላልፍን ነገር ነው። ሕዝቅኤል የሚናገረውንና የሚያደርጋቸውን ነገሮች እነዚህን እግዚአብሔር ማስጠንቀቂያ መሆናቸውን ይናገራል። አ.ት፡ “ማስጠንቀቂያ እንድትሆን አድርጌሃለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የእስራኤል ቤት
x

Ezekiel 12:7

ልክ እንደታዘዝኩት
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ልክ እግዚአብሔር እንዳዘዝኝ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ግድግዳውን በእጅ በመቆፈር ንደለው
“ግድግዳውን በእጆቼ በመቆፈር ነደልኩት”

በጨለማ ውስጥ
“በምሽት”

Ezekiel 12:8

የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የሰው ልጅ ሆይ፣ ያ አመፀኛው ቤት፣ የእስራኤል ቤት ‘የምታደርገው ምንድነው’ ብለው አይጠይቁህም?
ሕዝቡ ይህንን ጥያቄ ሕዝቅኤልን ጠይቀውት ስለነበረ -- ቀድሞውኑ የሚያውቀውን አንድ ነገር ለማስታወስ እግዚአብሔር ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ይጠይቀዋል። አ.ት፡ “የሰው ልጅ ሆይ፣ ያ አመፀኛው የእስራኤል ቤት ‘የምታደርገው ምንድነው?’ ብሎ እየጠየቀ ነው” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

የእስራኤል ቤት፣ ያ አመፀኛ ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። “አመፀኛ ቤት” የሚለውን በሕዝቅኤል 2፡5 ላይ እንዳለው አድርገህ ተርጉመው። አ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ፣ ያ አመፀኛ ሕዝብ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የምታደርገው ምንድነው
ሕዝቡ ሕዝቅኤል ሲያደርግ የነበረውን ስላዩ፣ ጥያቄአቸው ያንን ለምን እንዳደረገ የማወቅ ፍላጎታቸውን ያመለክታል። አ.ት፡ “የምታደርጋቸው ነገሮች ትርጉማቸው ምንድነው?”

በመካከሏ ያሉት
“በመካከሏ” የሚለው ቃል ኢየሩሳሌምን ሲያመለክት፣ “እነርሱ” የሚያመለክተው “የእስራኤል ቤት”ን ነው። አ.ት፡ “በኢየሩሳሌም ያሉትን”

Ezekiel 12:11

እኔ ምልክታችሁ ነኝ
እዚህ ጋ “ምልክት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ለሚያዩት አንድ የተለየ ማስጠንቀቂያ የሚያስተላልፍን ነገር ነው። ሕዝቅኤል ስለ ራሱና ስለሚያደርጋቸው ነገሮች ያ ማስጠንቀቂያ እርሱ መሆኑን ይናገራል። አ.ት፡ “እኔ ለእናንተ ማስጠንቀቂያ ነኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እንዲሁ ይደረግባቸዋል
“እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በኢየሩሳሌም የሚኖሩትን ሕዝብ ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሌሎች እንዲሁ ያደርጉባቸዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በጨለማ
“በምሽት”

ግድግዳውን ይነድላሉ
“እነርሱ” የሚለው ቃል በኢየሩሳሌም የሚኖሩትን ሕዝብ ያመለክታል።

ፊቱን ይሸፍናል
“መስፍኑ ፊቱን ይሸፍናል”

መረቤን በእርሱ ላይ እዘረጋለሁ፣ በወጥመዴም ይያዛል
እግዚአብሔር ከለዳውያን መስፍኑን እንዲይዙት ማስቻሉን፣ እርሱ ራሱ ባጠመደው ወጥመድ መስፍኑን እንደሚይዘው አድርጎ ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ወደ ባቢሎን አመጣዋለሁ
እግዚአብሔር ከለዳውያን መስፍኑን ወደ ባቢሎን እንዲያመጡት ማስቻሉን እርሱ ራሱ መስፍኑን ወደዚያ እንደሚያመጣው አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “ከለዳውያን ወደ ባቢሎን እንዲያመጡት አደርጋቸዋለሁ”

Ezekiel 12:14

ከበስተኋላቸው ሰይፍን እሰዳለሁ
“ሰይፍ” የሚለው ቃል በሰይፎቻቸው የሚገድሉትን የጠላት ሰራዊት የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “በሰይፍ የሚያሳድዷቸውን ሰራዊት እልክባቸዋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እኔ እግዚአብሔር እንደሆንኩ ያውቃሉ
እግዚአብሔር ሰዎች እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን ያውቃሉ ብሎ በሚናገርበት ጊዜ እርሱ ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለው ብቸኛው እውነተኛ አምላክ መሆኑን ሰዎች ያውቃሉ ማለቱ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 6፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እውነተኛው አምላክ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ይረዳሉ” ወይም “ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለኝ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ይገነዘባሉ”

በሀገራት መካከል በምበትናቸውና በምድር ሁሉ ላይ በምዘራቸው ጊዜ
የእነዚህ ሁለት ሐረጎች መሠረታዊ ትርጉማቸው አንድ ነው። አ.ት፡ “እርስ በእርሳቸው እንዲለያዩና በተለያየ ሀገር እንዲኖሩ በማደርጋቸው ጊዜ”

ከሰይፍ፣ ከረሃብና ከቸነፈር አድናቸዋለሁ
“ሰይፍ” የሚለው ቃል ሰይፎቻቸውን በመጠቀም ሰዎችን የሚገድሉ ወታደሮችን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። በረሃብ ወይም በቸነፈር ስላለመሞታቸው ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። አ.ት፡ “በጦርነት፣ በረሃብ እና በበሽታ ምክንያት ከመሞት እጠብቃቸዋለሁ”

Ezekiel 12:17

የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ezekiel 12:19

ምድሪቱ ፈጽማ ትበዘበዛለች
“ፈጽማ” የሚለው ቃል በምድሪቱ ያለውን ሁሉ ያመለክታል። “ትበዘበዛለች” ማለት ሕዝቡ በምድሪቱ ላይ ያለውን ሁሉ ያወድማሉ ማለት ነው። ይህ በአድርጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በምድሪቱ ያለውን ሁሉ ሌሎች ያወድሙታል” (አድርጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ሰዎች ይኖሩባቸው የነበሩ ከተሞች ወና ይሆናሉ
ይህ በአድርጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሰዎች የኖሩባቸው ከተሞች ባድማ ይሆናሉ” (አድርጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 12:21

የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በእስራኤል ምድር፣ “ቀኖቹ ረዝመዋል፣ ራዕይም ሁሉ ከንቱ ሆኗል” የሚለው ይህ ምሳሌአችሁ ምንድነው?
ሕዝቅኤል አስቀድሞ የሚያውቀውን አንድ ነገር ለማስታወስ እግዚአብሔር ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ይጠይቀዋል። ጥያቄው ምሳሌውን ለሚጠቀሙ ሰዎች ለስለስ ያለ ተግሳጽ ነው። አ.ት፡ “በእስራኤል ምድር የሚኖሩ ሰዎች እንዲህ የሚል ምሳሌ አላቸው፣ ‘ቀኖቹ ረዝመዋል፣ ራዕይም ሁሉ ከንቱ ሆኗል’” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ቀኖቹ ረዝመዋል፣
የዚህ አነጋገር ዘይቤ ትርጉም ብዙ ቀናት አልፈዋል የሚል ነው። አ.ት፡ “ብዙ ቀናት አልፈዋል” ወይም “ሰዓቱ አልፏል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ራዕይም ሁሉ ከንቱ ሆኗል
ይህ ማለት ነቢያቱ ተቀብለው ለሕዝቡ ያስተላለፏቸው ራዕዮች ሳይፈጸሙ ቀርተዋል ማለት ነው። አ.ት፡ “ትንቢታዊ ራዕዮች ሁሉ ሳይፈጸሙ ቀርተዋል”

ቀኖቹ ቀርበዋል
ይህ ሐረግ የሚያመለክተው እስራኤል የሚፈረድባት ጊዜ መድረሱን ነው። አ.ት፡ “የፍርድ ቀን በቶሎ ይመጣል”

ራዕይ ሁሉ ይፈጸማል
ይህ በአድርጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ራዕይን ሁሉ እፈጽማለሁ” (አድርጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 12:24

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እስራኤላውያንን” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የምናገረውን ቃል እፈጽማለሁ
የዚህ የአነጋገር ዘይቤ ትርጉም እግዚአብሔር የሚናገረውን ይፈጽማል የሚል ነው። አ.ት፡ “የምናገራቸውን ነገሮች አደርጋቸዋለሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ከዚህ በኋላ ጉዳዮቹ አይዘገዩም
“ጉዳይ” የሚያመለክተው እግዚአብሔር ይሆናሉ ያላቸውን ነገሮች ነው። አ.ት፡ “ከዚህ በኋላ የተናገርኩት አይዘገይም” ወይም “የተናገርኩት በቶሎ ይፈጸማል”

ይህንን ቃል እናገራለሁ
“ይህንን መልዕክት እናገራለሁ” ወይም “ይህንን ትንቢት እናገራለሁ”

በዘመናችሁ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ የሚያመለክተው አንድ ሰው የሚኖርበትን የሕይወት ዘመን ነው። አ.ት፡ “በሕይወት እያላችሁ” ወይም “በሕይወት በምትኖሩበት ዘመን” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

አመፀኛ ቤት
ይህ በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 2፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “አመፀኛ ሕዝብ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ይህ የጌታ እግዚአብሔር ቃል ነው
እግዚአብሔር የንግግሩን እርግጠኝነት ለመግለጽ የራሱን ስም በመጥራት ይናገራል። ይህንን በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ጌታ እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን ነው” ወይም “እኔ፣ ጌታ እግዚአብሔር የተናገርኩት ይህንን ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 12:26

የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

እነሆ
እዚህ ጋ፣ “እነሆ” የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚመጣው አስገራሚ መረጃ ትኩረት እንድንሰጥ ያነቃናል።

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እርሱ የሚያየው ራዕይ ከአሁን በኋላ ለረጅም ዘመን የሚሆን ነው፣ የሚተነብየውም ለሩቅ ዘመን ነው
ሁለቱም ሐረጎች የሕዝቅኤል ማስጠንቀቂያ በሩቅ ዘመን እንጂ በእነርሱ የሕይወት ዘመን እንደማይደርስ የእስራኤል ሕዝብ የተናገሩባቸው መንገዶች ናቸው።

ከእንግዲህ ቃሎቼ አይዘገዩም፣ ነገር ግን እኔ የተናገርኩት ቃል ይፈጸማል
እነዚህ ሐረጎች በሁለቱም መንገድ እግዚአብሔር የሰጣቸው ማስጠንቀቂያዎች በቶሎ እንደሚፈጸሙ ለእስራኤል ሕዝብ የተናገረበት ነው።

ከእንግዲህ ቃሎቼ አይዘገዩም
ይህ በአድርጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ከእንግዲህ የተናገርኩትን ቃል አላዘገይም” ወይም “ከእንግዲህ አደርገዋለሁ ብዬ የተናገርኩትን ከማድረግ አልዘገይም” (አድርጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እኔ የተናገርኩት ቃል ይፈጸማል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የተናገርኩትን ቃል እፈጽማለሁ” ወይም “የተናገርኩትን አደርገዋለሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 13

1 የእግዚአብሔርም ቃል እንደገና ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ። **2** የሰው ልጅ ሆይ፥ ትንቢት በሚናገሩ በእስራኤል ነቢያት ላይ ትንቢት ተናገር፥ ከገዛ ልባቸውም ትንቢት የሚናገሩትን 'የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ! **3** ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ምንምን ሳያዩ የገዛ መንፈሳቸውን ለሚከተሉ ለሰነፎች ነቢያት ወዮላቸው! **4** እስራኤል ሆይ፥ ነቢያትህ በምድረ በዳ እንደሚኖሩ ቀበሮች ናቸው። **5** ፥ በእግዚአብሔርም ቀን በሰልፍ ትቆሙ ዘንድ ልትጠግኑት ወደ ፈረሰው ቅጥር አልወጣችሁም ። **6** እግዚአብሔር ሳይልካቸው "እግዚአብሔር እንዲህና እንዲህ ይላል" የሚሉ ሰዎች ውሸተኛ ትንቢትንና ውሸተኛ ራዕይን አይተዋል። ያም ሆኖ ግን ቃላቸው እንደሚፈጸም ተስፋ ያደርጋሉ። **7** እኔም ሳልናገር "እግዚአብሔር እንዲህ ብሎአል" የምትሉ እናንተ ከንቱ ራእይን ያያችሁ ውሸተኛንም ትንቢትን መናገራቼሁ አይደለምን? **8** ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ውሸተኛ ራእይንም ስላያችሁ ውሸት ስለተናገራችሁ ጌታ እግዚአብሔር በእናንተ ላይ የሚናገረው ይህ ነው፡ **9** እጄም ከንቱ ራእይን በሚያዩ፥ የውሸት ትንቢት በሚናገሩ ነቢያት ላይ ይሆናል። እነርሱም በሕዝቤ ጉባኤ ውስጥ አይገኙም፥ በእስራኤልም ቤት መዝገብ ላይ አይጻፉም፥ ወደ እስራኤልም ምድር አይገቡም እኔም ጌታ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ! **10** በዚህም ምክንያት ሰላም ሳይኖር "ሰላም ነው!" እያሉ ሕዝቤን መረን ሰደዋል፣ ገለባ በሌለበት ጭቃ የተመረገ ቅጥር ይገነባሉ። **11** ቅጥሩን ገለባ በሌለበት ጭቃ ለሚመርጉት ሰዎች እንዲህ በላቸው 'ቅጥሩ ይወድቃል፤ የሚያሰጥም ዝናብ ይዘንባል፥ ቅጥሩኔ ለማፍረስ ታላቅም የበረዶ ድንጋይ እልካለሁ፥ እንዲያደቀውም ዐውሎ ነፋስን እልካለሁ። **12** እነሆ፥ ግንቡ በወደቀ ጊዜ። የመረጋችሁት ጭቃ ወዴት አለ? አይሉአችሁምን? **13** ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል 'በመዓቴ ዐውሎ ነፋስ አመጣለሁ ፥ በቍጣዬም ዶፍ ዝናብ ይዘንባል! በመዓቴም ታላቅ የበረዶ ድንጋይ ፈጽሞ ያወድመዋል። **14** ገለባም በሌለበት ጭቃ የመረጋችሁትን ቅጥር አፈርሳለሁ ወደ ምድርም እጥለዋለሁ፥ መሠረቱም ይታያል። እርሱም ይናዳል እናንተም በመካከሉ ትጠፋላችሁ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ። **15** በመዓቴም ግንቡንና ገለባ በሌለው ጭቃ የመረጉትን ሰዎችአጠፋለሁ። ግንቡም ሆነ መራጊዎቹ የሉም እላችኋለሁ። **16** እነርሱም ስለ ኢየሩሳሌም ትንቢት የሚናገሩ የሰላምን ራእይ የሚያዩላት የእስራኤል ነቢያት ናቸው። ሰላምም የለም፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር" **17** አንተም፥ የሰው ልጅ ሆይ፥ ከገዛ ልባቸው ትንቢት በሚናገሩ በሕዝብህ ሴቶች ልጆች ላይ ፊትህን አድርግ ትንቢትም ተናገርባቸው፥ **18** እንዲህም በል፣ 'ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ነፍስን ለማጥመድ በመላ እጆቸው የጥንቆላ መከዳ ለሚሰፉ ለራሶቻቸውም የተለያየ መጠን ያላቸው ሸፋን ለሚሠሩ ሴቶች ወዮላቸው! የሕዝቤንም ነፍስ ብታጠምዱ በውኑ ነፍሳችሁን ታድናላችሁን? **19** ውሸታችሁን ለሚሰሙት ሕዝቤ እየዋሻችሁ ለጭብጥ ገብስና ለቍራሽ እንጀራ ብላችሁ መሞት የማይገባቸውን ለመግደል በሕይወትም መኖር የማይገባቸውን በሕይወት በማኖር በሕዝቤ ፊትአርክሳችሁኛል። **20** ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፦እነሆ፥ እኔ ነፍሳትን እንደ ወፍ በምታጠምዱባት በአስማት መተቶቻችሁ ላይ ነኝ፥ ከክንዳችሁም ወስጄ እቀደዋለሁ፥ እንደ ወፍም ያጠመዳችኋቸውን ህዝብ ነጻ አወጣለሁ። **21** ሸፋኖቻችሁንም እቀድዳለሁ ሕዝቤንም ከእጃችሁ አድናለሁ፥ ከዚያም ወዲያ በእጃችሁ አይጠመዱም እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ። **22** እኔም እንዲያዝን የማልፈልገውን የጻድቁን ልብ በውሸታችሁ አሳዝናችኋልና፥ በተቃራኒው ደግሞ ከክፉ መንገዱ ተመልሶ በሕይወት እንዳይኖር የኃጢአተኛውን ተግባር አበረታታችኋልና **23** ሕዝቤን ከእጃችሁ ስለማድን ክእንግዲህ ከንቱን ራእይ አታዩም የውሸት ትንቢትም አትናገሩም፥ ምክንያቱም እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ።

Ezekiel 13:1

የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የሰው ልጅ
“የሰብዓዊ ፍጡር ልጅ” ወይም “ከሰው የተወለደ ልጅ”። ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን አፅንኦት ለመስጠት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ በማለት ይጠራዋል። እግዚአብሔር ዘላለማዊና ኃያል ነው፣ ሰዎች ግን አይደሉም። ይህንን በሕዝቅኤል 2፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ሟች ሰው” ወይም “ሰው”

ከገዛ ስሜታቸው ተነሥተው የሚተነብዩ
“የሚሰማቸውን ነገር ብቻ የሚተነብዩ”

የገዛ ራሳቸውን መንፈስ የሚከተሉ
እዚህ ጋ፣ “መንፈስ” የሚለው ቃል የሚወክለው የሰውየውን አሳብና አስተሳሰብ ነው። “መከተል” ማለት አሳባቸው እንዲያደርጉት የሚያመለክታቸውን እንደሚያደርጉ የሚያሳይ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “እንደ ገዛ አሳባቸው የሚያደርጉ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በወና ምድር እንዳሉ ቀበሮዎች
ምግብ እንደሚለቃቅሙና ወና ሆነው በተተዉ ከተሞች መካከል መጠለያ እንደሚፈልጉ ቀበሮዎች ነቢያቱ ለራሳቸው ትርፍ ሲሉ በኢየሩሳሌም መፍረስ እየተጠቀሙባት ነው። (See: Simile)

ቀበሮዎች
ከውሾች ጋር የሚዛመዱና ወና በሆኑ አካባቢዎች ምግባቸውን የሚለቃቅሙ የዱር እንስሳዎች ናቸው።

Ezekiel 13:5

በእስራኤል ቤት ዙሪያ ያለውን ግንብ
ይህ የኢየሩሳሌምን ከተማ የሚከብበውን ግንብ ያመለክታል።

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በጦርነት መቋቋም
እዚህ ጋ ግልጽ ያልተደረገውን መረጃ መጨመር ትችላለህ። አ.ት፡ “የጠላትን ሰራዊት መቋቋም” ወይም “ከተማይቱን መከላከል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የእግዚአብሔር ቀን
ይህ እግዚአብሔር በጠላት ሰራዊት አማካይነት በሕዝቡ ላይ የሚፈርድበትን ጊዜ ያመለክታል። አ.ት፡ “የእግዚአብሔር የፍርድ ቀን” ወይም “እንዲወጓችሁ እግዚአብሔር የጠላትን ሰራዊት በመላክ በእናንተ ላይ የሚፈርድበት ቀን”

እኔ ራሴ ባልተናገርኩበት ጊዜ ሐሰተኛ ራዕዮች አልነበሯችሁም?
ሐሰተኞቹን ነቢያት ለመገሰጽ እግዚአብሔር በጥያቄ መልክ ይናገራል። አ.ት፡ “እኔ ራሴ ያልተናገርኩት . . . ሐሰተኛ ራዕዮች ነበሯችሁ” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ሐሰተኛ ራዕዮች ነበሯችሁ፣ የውሸት ትንቢትም ተናገራችሁ
x

Ezekiel 13:8

ይህ የጌታ እግዚአብሔር ንግግር ነው
እግዚአብሔር የንግግሩን እርግጠኝነት ለመግለጽ የራሱን ስም በመጥራት ይናገራል። ይህንን በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።አ.ት፡ “ጌታ እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን ነው” ወይም “እኔ፣ ጌታ እግዚአብሔር የተናገርኩት ይህንን ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

እጄ በነቢያት ላይ ትሆናለች
እዚህ ጋ፣ “እጅ” የሚለው ቃል የሚወክለው የእግዚአብሔርን ኃይል ነው። እጁ በእነርሱ ላይ መሆኗ ዘይቤአዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙም እርሱ በኃይሉ ይቀጣቸዋል ማለት ነው። አ.ት፡ “ነቢያትን እቀጣቸዋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በሕዝቤ ጉባዔ ውስጥ አይሆኑም
ይህ ማለት እግዚአብሔር እነዚህን ሐሰተኞች ነቢያት የእስራኤል ሕዝብ አካል አድርጎ አይቆጥራቸውም።

ወይም በእስራኤል ቤት መዝገብ አይጻፉም
ይህ ምናልባት የእስራኤል ዜጎች የሚመዘገቡበትን መንግሥታዊ መዝገብ ያመለክት ይሆናል። ይህ በአድርጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በእስራኤል ቤት መዝገብ ላይ ማንም ስማቸውን አይጽፍም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እኔ ጌታ እግዚአብሔር መሆኔን ታውቃላችሁ
እግዚአብሔር ሰዎች እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን እንደሚያውቁ በሚናገርበት ጊዜ እርሱ ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለው ብቸኛው እውነተኛ አምላክ መሆኑን ያውቃሉ ማለቱ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 6፡7 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እውነተኛው አምላክ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ትረዳላችሁ” ወይም “ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለኝ እኔ ጌታ እግዚአብሔር መሆኔን ትገነዘባላችሁ”

Ezekiel 13:10

በዚህ ምክንያት
“በዚህ” የሚለው ቃል ሐሰተኛ ራዕዮችን ለሕዝቡ የሚያስታውቁትንና ውሸትን የሚነግሯቸውን ነቢያት ያመለክታል።

ሕዝቤን አስተዋል
ነቢያቱ ሕዝቡ ይሄዱበት ከነበረው መንገድ ላይ ያሳቷቸው ይመስል ሕዝቡን ስለማሳሳታቸውና ውሸትን እንዲያምኑ ስለማድረጋቸው እግዚአብሔር ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በኖራ የሚለስኑትን ግንብ ይገነባሉ
እዚህ ጋ፣ “ግንብ” የቆመው እግዚአብሔር ለሕዝቡ ሊሰጣቸው ቃል ለገባውና ሐሰተኞቹ ነቢያት ለሕዝቡ ለነገሯቸው ለሰላምና ደህንነት ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ኖራ ... በኖራ መለሰን
“ኖራ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የተበላሸውን ለመሸፈንና ገጽታውን ነጭ ለማድረግ ጥቅም ላይ የሚውለውን የነጭ ፈሳሽ ውሁድ ወይም ቀለምን ነው።

እርሱን እንዲጥለው የበረዶ ድንጋይን፣ ሰባብሮ እንዲጥለውም ዐውሎ ነፋስን እልካለሁ
እግዚአብሔር ግንቡን እንደሚያፈራርስ ብርቱ ዐውሎ በሚመስል መልኩ በሕዝቡ ላይ የሚልከውን ፍርዱን ያመለክታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የበረዶ ድንጋይ
በዶፍ ዝናብ ወቅት አንዳንዴ ከሰማይ የሚወድቁ ሁሉም ዓይነት በረዶዎች

ሌሎች፣ “የለሰናችሁበት ኖራ የት አለ?” አላሏችሁም?
ሌሎች ኖራዎቻቸው ምን እንደሆነባቸው ነቢያቱን እንደሚጠይቋቸው አጽንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ይጠይቃል። አ.ት፡ “ያለ ጥርጥር ሌሎች እንዲህ ይሏችኋል፣ ‘የለሰናችሁበት ኖራ የት አለ’ “(ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

የለሰናችሁበት ኖራ የት አለ?
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ ሕዝቡ የሚገምተውና የሚመልሰው ቅንነት ያለበት ጥያቄ ነው ወይም 2) ይህ ሕዝቡ በፌዝ የሚጠይቀው ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ነው የሚሉት ናቸው። አ.ት፡ “የለሰናችሁበት ኖራ ምንም አልጠቀመም”። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 13:13

ዐውሎ ንፋስ አመጣለሁ ... ፈጽሞ ያጠፋዋል።
እግዚአብሔር ግንቡን የሚያፈራርስ ብርቱ ዐውሎ በሚመስል መልኩ በሕዝቡ ላይ የሚልከውን ፍርድ ያመለክታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በመዓቴ ... በቁጣዬ ... በመዓቴ
“በመዓቴ ምክንያት ... በቁጣዬ ምክንያት ... በመዓቴ ምክንያት”

ተገልጦ ይቀራል
“አይሸፈንም”

በመካከሏም ድምጥማጣችሁ ይጠፋል
“በመካከሏ” የሚለው ቃል እግዚአብሔር የሚያፈርሰውን የግንቡን ድንጋዮች ያመለክታል። ግንቡ በሚፈርስበት ጊዜ ይገድላቸው ይመስል እግዚአብሔር ሕዝቡን በፍርዱ እንደሚያጠፋቸው ይናገራል።(ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ድምጥማጣቸው ይጠፋል
“ይጠፋሉ”

እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንኩ ያውቃሉ
እግዚአብሔር ሰዎች እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን ያውቃሉ ብሎ በሚናገርበት ጊዜ እርሱ ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለው ብቸኛው እውነተኛ አምላክ መሆኑን ሰዎች ያውቃሉ ማለቱ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 6፡7 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እውነተኛው አምላክ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይረዳሉ” ወይም “ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለኝ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ይገነዘባሉ”

Ezekiel 13:15

በቁጣዬ ድምጥማጣቸውን አጠፋለሁ
“በጣም ስለ ተቆጣሁ ድምጥማጣቸውን አጠፋለሁ”

በኖራ ለስነውታል
“ኖራ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የተበላሸውን ለመሸፈንና ገጽታውን ነጭ ለማድረግ ጥቅም ላይ የሚውለውን የነጭ ፈሳሽ ውሁድ ወይም ቀለምን ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 13:10 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።

ስለ ኢየሩሳሌም ትንቢት የተናገሩና የሰላምን ራዕይ ያዩላት የእስራኤል ነቢያት
ይህ ሐረግ “በኖራ የተለሰኑት ሰዎች” እነማን እንደ ሆኑ ያብራራል።

ለእርሷ የሰላምን ራዕይ
“እርሷ” የሚለው ቃል ኢየሩሳሌምን ያመለክታል።

Ezekiel 13:17

ፊትህን በሴቶቹ ልጆች ላይ አቅና
ይህ ሴቶቹን የመቅጣት ምልክት ይሆን ዘንድ እነርሱን አፍጥጦ እንዲመለከት የተሰጠ ትዕዛዝ ነው። “በእነርሱ ላይ ፊትህን አቅና” የሚለውን በሕዝቅኤል 4:3 ላይ እንዳደረግኸው ተርጉም። አ.ት፡ “በሴቶቹ ልጆች ላይ አፍጥጥባቸው”

በእነርሱ ላይ ፊትህን አቅና
እዚህ ጋ “ፊት” በትኩረት ወይም በጥሞና የመመልከት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፣ “ፊትህን አቅና” የሚወክለው አፍጥጦ መመልከትን ነው። አ.ት፡ “አፍጥጠህ እይ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የሕዝብህ ሴቶች ልጆች
የአነጋገር ዘይቤው እንደ ሕዝቅኤል ሁሉ የዚያው ሕዝብ ወገን የሆኑትን ሴቶች ያመለክታል። አ.ት፡ “የእስራኤል ሴቶች” ወይም “የሀገርህ ሴቶች” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ከራሳቸው አዕምሮ አውጥተው ይተነብያሉ
“በገዛ ራሳቸው አዕምሮ ያሰቧቸውን ነገሮች ብቻ እየተነበዩ” ተመሳሳዩን ሐረግ በሕዝቅኤል 13:2 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።

በ -- ላይ ትንቢት ተናገር
“ስለሚደርሱባቸው አስከፊ ነገሮች ትንቢት ተናገር”። ይህንን በሕዝቅኤል 4:7 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።

በእጆቻቸው ሁሉ ላይ የአስማት ክታብ ሰፍተዋል
ይህ ማለት የአስማቱን ክታቦች በአንድ ላይ በመስፋት በእጆቻቸው ላይ አስረውታል ማለት ነው እንጂ በቀጥታ በእጆቻቸው ላይ ሰፍተውታል ማለት አይደለም።

ክታብ
አስማታዊ ኃይል አለው ተብሎ የሚታመንበት ቁስ

ሰዎችን ለማጥመድ ተጠቅመውበታል
እግዚአብሔር ስለ እነዚህ ሴቶች በክታቦቻቸው አማካይነት እንስሶችን አድነው ያጠምዱ ይመስል ሰዎችን ለማሳሳት ውበታቸውን፣ ምስጢራቸውንና ውሸታቸውን እንደሚጠቀሙ እግዚአብሔር ይናገራል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሰዎችን ለማጥመድ የሚጠቀሙባቸው” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ለራሳቸው የተለያየ መጠን ያለው መሸፈኛ ያበጃሉ
ይህ ማለት የተለያየ ቁመት ባላቸው ሰዎች ራስ ላይ ለማድረግ መሸፈኛዎችን ያበጃሉ። አ.ት፡ “የተለያየ ቁመት ላላቸው ሴቶች ራስ መሸፈኛዎችን ያበጃሉ”

ሕዝቤን አጥምዳችሁ የገዛ ራሳችሁን ሕይወት ታድናላችሁ?
እነዚህን ነገሮች የሚያደርጉትን ሴቶች ለመገሰጽ እግዚአብሔር ይህንን እንደ ዋነኛ ጥያቄ አድርጎ ይጠይቃል። ይፋ ያልሆነው መልስ “አይደለም” የሚል ነው። አ.ት፡ “ሕዝቤን ካጠመዳችሁ በኋላ የገዛ ራሳችሁን ሕይወት ማዳን እንደምትችሉ አታስቡ!” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 13:19

እፍኝ ገብስና ቁራሽ እንጀራ
ገብስ እንጀራ ለመጋገር የሚያገለግል ጥራጥሬ ሲሆን “ቁራሽ” የሚለው ቃል አነስተኛ መጠን ያለው እንጀራ ነው። ሁለቱም ሐረጎች አነስተኛ የምግብ መጠን ሲሆኑ ሴት ነቢያቱ ምን ያህል አነስተኛ ክፍያ እንደሚከፈላቸው አጽንዖት ለመስጠት ጥቅም ላይ ውለዋል።

Ezekiel 13:20

ወፎችን ይመስል የሕዝቡን ሕይወት ለማጥመድ የምትጠቀሙበት የአስማት ክታብ
ሰዎቹ ሴቶች በክታቦቻቸው የሚያጠምዷቸውን ወፎች ይመስል እግዚአብሔር የአስማት ክታባቸውን በመጠቀም ሰዎችን ስለሚያሳስቱ ስለ እነዚህ ሴቶች ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ክታብ
አስማታዊ ኃይል አላቸው ተብለው የሚታመኑ ቁሳቁሶች

ለማጥመድ
“ለመያዝ” “በወጥመድ ለመያዝ”

ከክንዳችሁ ላይ እቀድዳቸዋለሁ
“ክታቦቹን ከክንዶቻችሁ ላይ እቀድዳለሁ”

ሕዝቤን ከእጃችሁ አድናቸዋለሁ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚለው ቃል የሚወክለው ኃይልን ወይም መቆጣጠርን ነው። አ.ት፡ “ሕዝቤን ከኃይላችሁ አድናቸዋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከእንግዲህ በእጆቻችሁ አይጠመዱም
እዚህ ጋ “እጅ” የሚለው ቃል የሚወክለው ኃይልን ወይም መቆጣጠርን ነው። ሴቶቹ ሰዎቹን በእጆቻቸው ያጠመዷቸው ይመስል ሰዎቹ በእነዚህ ሴቶች ቁጥጥር ስር ስለ መሆናቸው እግዚአብሔር ይናገራል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በእጆቻችሁ እንዳለ የሚታደን እንስሳ ከእንግዲህ አታጠምዷቸውም” ወይም “ከእንግዲህ በኃይላችሁ አትቆጣጠሯቸውም” (ፈሊጣዊ አነጋገር፣ ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 13:22

የጻድቁን ሰው ልብ ተስፋ ስላስቆረጣችሁ
እዚህ ጋ “ልብ” የሚወክለው ሰውየውንና ስሜቶቹን ነው። አ.ት፡ “ጻድቁን ሰው ተስፋ ማስቆረጥ”

ከመንገዱ ተመልሶ
የሚያደርገውን ነገር ማቆሙ ወደ ሌላ አቅጣጫ እንደ መመለስ ተመልክቷል። አ.ት፡ “የሚያደርገውን ማቆም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የሐሰት ራዕዮች ወይም መተንበይን መቀጠል
እነዚህ ሁለቱም ሐረጎች የሚያመለክቱት ወደ ፊት እንደሚሆን መናገርን ነው። አ.ት፡ “የሐሰት ትንቢቶችን መናገር ቀጥሉ”

ሕዝቤን ከእጃችሁ አድናቸዋለሁ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚለው ቃል የሚወክለው ኃይልን ወይም መቆጣጠርን ነው። ተመሳሳዩን ሐረግ በሕዝቅኤል 13:21 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ተመልከት። አ.ት፡ “ሕዝቤን ከኃይላችሁ አድናቸዋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር
የሚለውን ተመልከት)

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 14

1 ከእስራኤልም ሽማግሌዎች መካከል የተወሰኑ ሰዎች ወደ እኔ መጥተው በፊቴ ተቀመጡ። 2 ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ። 3 የሰው ልጅ ሆይ፥ እነዚህ ሰዎች ጣዖቶቻቸውን በልባቸው አኑረዋል የበደላቸውንም መቅሠፍት በፊታቸው አቁመዋል ታዲያ እኔ ከእነርሱ ጥያቄ መቀበል አለብኝ? 4 ስለዚህ፦ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፦ ከእስራኤል ቤት ጣዖቶቹን በልቡ የሚያኖር፥ የበደሉንም መቅሠፍት በፊቱ የሚያቆም ሰው ሁሉ ወደ ነቢዩ በመጣ ጊዜ፥ እኔ እግዚአብሔር እንደ ጣዖታቱ ብዛት እመልስለታለሁ። 5 ይህንንም የማደርገው ሁሉም በጣዖቶቻቸው ምክንያት ከእኔ በጣም በራቀው በልባቸው የእስራኤልን ቤት እንደገና ለመመለስ ነው!' ብለህ ንገራቸው። 6 ስለዚህ ለእስራኤል ቤት እንዲህ በል፣ 'ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ንስሐ ግቡ ከጣዖቶቻችሁም ተመለሱ፥ ፊታችሁንም ከርኵሰታችሁ ሁሉ መልሱ። 7 ከእስራኤልም ቤት፥ በእስራኤልም ዘንድ ከሚቀመጡ መጻተኞች ማንም፥ ከእኔ ተለይቶ ጣዖቶቹን በልቡ ያኖረ፥ የበደሉንም መቅሠፍት በፊቱ ያቆም ሰው ሁሉ፥ ጥያቄ ይዞ ወደ ነቢዩ ቢመጣ ፥ እኔ እግዚአብሔር እራሴ እመልስለታለሁ! 8 ፊቴንም እዞርበታለሁ ከሕዝቤም መካከል አጠፋውና መቀጣጫና ምሳሌም አደርገዋለሁ ፣ በዚያን ጊዜ እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ! 9 ነቢዩም ስቶ ሳለ መልዕክትን ቢናገር፥ እኔ እግዚአብሔር ያንን ነቢይ አስተዋለሁ፥ እጄንም በእርሱ ላይ እዘረጋለሁ ከሕዝቤም ከእስራኤል መካከል አጠፋዋለሁ። 10 ኃጢአታቸውን ይሸከማሉ፤ የነቢዩ ኃጢአት መልዕክት ፍለጋ ወደእርሱ የሄደ ሰው ኃጢአት አንድ ይሆናል። 11 በዚህም ምክንያት ከዚህ በኋላ የእስራኤል ቤት ከእኔ ርቀው አይቅበዘበዙም በኃጢአታቸውም ሁሉ አይረክሱም። እነርሱም ሕዝብ ይሆኑኛል እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር።" 12 የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ። 13 የሰው ልጅ ሆይ፥ ምድር በማመፅ በእኔ ላይ ኃጢአት ብትሠራ፥ እኔም እጄን ብዘረጋባት የእንጀራዋንም በትር ብሰብር ራብን ብሰድድባት ሰውንና እንስሳውንም ከእርስዋ ባጠፋ፥ 14 እነዚህም ሦስት ሰዎች፥ ኖኅ፣ ዳንኤልና ኢዮብም፥ በመካከልዋ ቢገኙ እነርሱ በጽድቃቸው ሊያዱኑ የሚችሉት የገዛ ነፍሳቸውን ብቻ ነበር፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፦ 15 ክፉዎቹን አራዊት በምድር ባሳልፍ እነርሱም ልጆችዋን ቢያጠፉ ስለ አራዊትም ማንም እንዳያልፍባት ባድማ ብትሆን፥ 16 እነዚህም ሦስት ሰዎች ቢኖሩባት፥ እኔ ሕያው ነኝና እነርሱ ብቻቸውን ይድናሉ እንጂ ወንዶችንና ሴቶች ልጆቻቸውን አያድኑም፥ ምድሪቱም ባድማ ትሆናለች፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፦ 17 ወይም በዚያች ምድር ላይ ሰይፍ አምጥቼ። ሰይፍ ሆይ፥ በምድሪቱ ላይ እለፊ ብል፥ ሰውንና እንስሳውንም ከእርስዋ ባጠፋ፥ 18 እነዚህም ሦስት ሰዎች ቢኖሩባት፥ እኔ ሕያው ነኝና እነርሱ ብቻቸውን ይድናሉ እንጂ ወንዶችንና ሴቶች ልጆቻቸውን አያድኑም፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፦ 19 ወይም በዚያች ምድር ላይ ቸነፈር ብሰድድ ሰውንና እንስሳውንም ከእርስዋ ለማጥፋት መዓቴን በደም ባፈስስባት፥ 20 ኖኅና ዳንኤል ኢዮብም ቢኖሩባት፥ እኔ ሕያው ነኝና በጽድቃቸው ነፍሳቸውን ብቻ ያድናሉ እንጂ ወንዶችንና ሴቶች ልጆቻቸውን አያድኑም፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፦ 21 ጌታ እግዚአብሔርም እንዲህ ይላል። ይልቁንስ ሰውንና እንስሳን ከእርስዋ አጠፋ ዘንድ በኢየሩሳሌም ላይ አራቱን ክፉ ፍርዶቼን፥ ሰይፍንና ራብን ክፉዎችንም አውሬዎች ቸነፈርንም፥ በመስደድ ነገሮች እንዲከፉ አደርጋለሁ። 22 ነገር ግን፥ እነሆ! ከወንዶችና ሴቶች ልጆች ጋር የሚያመልጡ ቅሬታዎች ይተርፉላታል። እነሆ! ወደ እናንተ ይወጣሉ እናንተም መንገዳቸውንና ሥራቸውን ታያላችሁ በኢየሩሳሌምም ላይ ስላመጣሁት ቅጣት በምድሪቱም ላይ ስላመጣሁባት ነገር ሁሉ ትጽናናላችሁ ። 23 መንገዳቸውንና ሥራቸውን ባያችሁ ጊዜ ያጽናኑአችኋል ያደረግሁባትንም ሁሉ በከንቱ እንዳላደረግሁባት ታውቃላችሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር።

Ezekiel 14:1

ከእስራኤል ሽማግሌዎች ጥቂቶቹ ወደ እኔ መጥተው በፊት ተቀመጡ
ሽማግሌዎቹ በሕዝቅኤል ፊት የተቀመጡት በእርሱ አማካይነት ጌታን ለመጠየቅ ነው።

የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የሰው ልጅ
“የሰብዓዊ ፍጡር ልጅ” ወይም “ከሰው የተወለደ ልጅ”። ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን አፅንኦት ለመስጠት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ በማለት ይጠራዋል። እግዚአብሔር ዘላለማዊና ኃያል ነው፣ ሰዎች ግን አይደሉም። አ.ት፡ “ሟች ሰው” ወይም “ሰው”

ጣዖቶቻቸውን በልባቸው አኑረዋል
ሽማግሌዎቹ “ጣዖቶቻቸውን በልባቸው” ያኖሩ ይመስል እግዚአብሔር ሽማግሌዎቹ ራሳቸው ጣዖታትን ስለ ማምለካቸው ይናገራል። አ.ት፡ “ራሳቸውን ለጣዖታት ሰጥተዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በገዛ ፊታቸው ላይ የኃጢአታቸውን ማሰናከያ አስቀምጠዋል
እግዚአብሔር ሽማግሌዎቹ የሚያመልኳቸውን ጣዖታት የሚሰናከሉባቸው መሰናከያዎች እንደ ሆኑ፣ እነዚያን ጣዖታት ለማምለክ መጨከናቸውንም ማሰናከያዎቹን በፊታቸው እንዳስቀመጡ አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “ወደ ኃጢአት የሚመራቸውን ነገሮች ለማምለክ ያለ ማወላወል ጨክነዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የኃጢአታቸውን ማሰናከያ
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች 1) ጣዖታቱ ሽማግልዎቹን ወደ ኃጢአት የሚመሩ ማሰናከያዎች ናቸው ወይም 2) ጣዖታትን ማምለክ ሽማግሌዎቹ እንዲሰናከሉ የሚያደርጋቸው ኃጢአት ነው የሚሉት ናቸው።

ከቶ በእነርሱ ልጠየቅ ይገባል?
ሽማግሌዎቹ ሊጠይቁት እንደማይገባቸው አጽንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ይጠይቃቸዋል። ይህ ጥያቄ እንደ ንግግር ለተረጎም ይችላል። ደግሞም ይህ በአድራጊ ድምፅ ለተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እንዲጠይቁኝ ከቶውኑ ልፈቅድላቸው ይገባኛል?” ወይም “ከቶ ሊጠይቁኝ አይገባቸውም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 14:4

ስለዚህ ይህንን አስታውቃቸው
“እነርሱ” የሚለው ቃል “ከእስራኤል ሽማግሌዎች የሆኑትን ሰዎች” ያመለክታል።

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጣዖታቱን በልቡ የሚያኖር እርሱ
እግዚአብሔር፣ ሕዝቡ ጣዖታትን ለማምለክ ራሳቸውን መስጠታቸውን፣ ጣዖቶቻቸውን በልባቸው እንዳኖሩት አድርጎ ይናገራል። ይህንን ዘይቤአዊ አነጋገር በሕዝቅኤል 14:3 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ራሱን ለጣዖታት የሚሰጥ እርሱ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የኃጢአቱን ማሰናከያ በፊቱ የሚያስቀምጥ
እግዚአብሔር ሕዝቡ የሚያመልኳቸውን ጣዖታት የሚሰናከሉባቸው መሰናከያዎች እንደ ሆኑ፣ እነዚያን ጣዖታት ለማምለክ መጨከናቸውንም ማሰናከያዎቹን በፊታቸው እንዳስቀመጡ አድርጎ ይናገራል። ይህንን ዘይቤአዊ አነጋገር በሕዝቅኤል 14:3 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ወደ ኃጢአት የሚመራቸውን ነገሮች ለማምለክ ያለ ማወላወል የጨከኑ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከዚያም ወደ ነቢይ መጥቶ
ጌታን ለመጠየቅ ወደ ነቢይ የሚሄድ ሰው

እኔ እግዚአብሔር፣ እንደ ጣዖታቱ ብዛት እመልስለታለሁ
ይህ ሐረግ ሕዝቡ የሚያመልኳቸውን ብዙ ጣዖታት ያመለክታል። የእግዚአብሔር ምላሽ አስከፊነት የሚያመልኳቸውን የጣዖታት ብዛት ያህል ታላቅ እንደሚሆን ያመለክታል። አ.ት፡ “ብዙ ጣዖታትን ያመልካልና እኔ እግዚአብሔር ተገቢውን መልስ እሰጠዋለሁ”

የእስራኤልን ቤት ልብ እመልስ ዘንድ
እዚህ ጋ “ልብ” የሚለው ቃል የሚወክለው የሕዝቡን አዕምሮና ፍቅር ነው። እግዚአብሔር ልባቸውን ይማርከቸው ይመስል ልባቸው እንደገና ለእርሱ የተሰጠ እንዲሆን እንደሚያደርገው ይናገራል። አ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ እንደገና ለእኔ የተሰጡ እንዲሆኑ አደርጋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በጣዖቶቻቸው ከእኔ ርቆ የነበረውን ልባቸውን
እዚህ ጋ “ልብ” የሚለው ቃል የሚወክለው የሕዝቡን አዕምሮና ፍቅር ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ጣዖቶቻቸውን ለማምለክ እኔን የተዉኝን ሁሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 14:6

ንስሐ ግቡ፣ ከጣዖቶቻችሁም ተመለሱ! አስጸያፊ ከሆኑ ተግባሮቻችሁ ሁሉ ፊታችሁን መልሱ
እነዚህ ሁለቱም ሐረጎች ለእስራኤል ሕዝብ ጣዖታትን ማምለካቸውን እንዲያቆሙ የተነገሯቸው መንገዶች ናቸው።

ንስሐ ግቡ፣ ተመለሱም
“ንስሐ ግቡ” እና “ተመለሱ” የሚሉት ቃላት መሠረታዊ ትርጉማቸው አንድ ነው። በአንድነት የሚያጠናክሩት ጣዖታትን ማምለካችሁን አቁሙ የሚለውን ትዕዛዝ ነው።

ፊታችሁን መልሱ
እዚህ ጋ “ፊት” የሚለው ቃል የሚወክለው ሕዝቡን ነው። አ.ት፡ “ተመለሱ”

Ezekiel 14:7

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ጣዖታቱን በልቡ የሚያኖረውን
እግዚአብሔር፣ ሕዝቡ ጣዖቶቻቸውን በልባቸው እንዳኖሩ አድርጎ ጣዖታትን ለማምለክ ራሳቸውን ስለ ሰጡ ሰዎች ይናገራል። ይህንን ዘይቤአዊ አነጋገር በሕዝቅኤል 14:3 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ራሱን ለጣዖታት የሚሰጥ እርሱ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የኃጢአቱን ማሰናከያ በፊቱ የሚያስቀምጥ
እግዚአብሔር ሕዝቡ የሚያመልኳቸውን ጣዖታት የሚሰናከሉባቸው መሰናከያዎች እንደ ሆኑ፣ እነዚያን ጣዖታት ለማምለክ መጨከናቸውንም ማሰናከያዎቹን በፊታቸው እንዳስቀመጡ አድርጎ ይናገራል። ይህንን ዘይቤአዊ አነጋገር በሕዝቅኤል 14:3 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ወደ ኃጢአት የሚመራውን ነገሮች ለማምለክ ያለ ማወላወል የሚጨክን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ፊቴን በዚያ ሰው ላይ አደርጋለሁ
እግዚአብሔር ፊቱን በዚያ ሰው ላይ በሚያደርግበት መልኩ ያንን ሰው እንደሚቃወመው ይናገራል። አ.ት፡ “በዚያ ሰው ላይ እሆናለሁ” ወይም “ያንን ሰው እቃወማለሁ”

ፊቴን አደርጋለሁ
እዚህ ጋ “ፊት” ትኩረትን ወይም በአትኩሮት መመልከትን እና “ፊቴን አደርጋለሁ” የሚያመለክተው አፍጥጦ ማየትን ነው። አ.ት፡ “ማፍጠጥ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ምልክትና ምሳሌ አደርገዋለሁ
እዚህ ጋ “ምልክት” የሚለው ቃል ለሚያዩት የተለየ ማስጠንቀቂያ የሚያስተላልፍ አንድን ነገር ያመለክታል። ምሳሌ የሚለው ቃል፣ ሰዎች ያንን ምልክት በሚያዩበት ጊዜ ስለ እርሱ የሚናገሩትን ያመለክታል። አ.ት፡ “ያ ሰው ማስጠንቀቂያና ምሳሌ እንዲሆን አደርገዋለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከሕዝቤ መካከል አስወግደዋለሁ
እግዚአብሔር ከእንግዲህ የራሱ ሕዝብ ወገን እንዳይሆን የሚያደርገውን ያንን ሰው አንድ ሰው ቅርንጫፍን ከዛፍ ላይ እንደሚቆርጥ ከሕዝቡ እንደሚቆርጠው ይናገራል። አ.ት፡ “ከእንግዲህ የሕዝቤ አካል እንዳይሆን አደርገዋለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ታውቃላችሁ
እግዚአብሔር ሰዎች እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን ያውቃሉ ብሎ በሚናገርበት ጊዜ እርሱ ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለው ብቸኛው እውነተኛ አምላክ መሆኑን ሰዎች ያውቃሉ ማለቱ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 6:7 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እውነተኛው አምላክ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ትረዳላችሁ” ወይም “ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለኝ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ትገነዘባላችሁ”

Ezekiel 14:9

እጄን በእርሱ ላይ አነሣለሁ
የእግዚአብሔር “እጅ” እርሱ የሚሠራውን ያመለክታል። አ.ት፡ “በእርሱ ላይ ክፉ አደርጋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የራሳቸውን ኃጢአት ይሸከማሉ
እዚህ ጋ “ኃጢአት” የሚለው ቃል የሚወክለው ሰዎች ኃጢአትን በማድረጋቸው በራሳቸው ላይ የሚያመጡትን በደል ነው። ሕዝቡ ኃጢአትን ይሸከሙት ይመስል እግዚአብሔር የሚናገረው በኃጢአታቸው ምክንያት ስለሚደርስባቸው መከራ ነው። አ.ት፡ “በገዛ ራሳቸው የኃጢአት ውጤት ምክንያት መከራን ይቀበላሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እኔን ከመከተል አይባዝኑም
እርሱን ከማምለክ በስተቀር ከእንግዲህ እርሱን ባለ መከተል እንደማይባዝኑ እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ይናገራል። አ.ት፡ “ከእንግዲህ እኔን ማምለካቸውን አያቆሙም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ይህ የጌታ እግዚአብሔር ቃል ነው
እግዚአብሔር ስለሚናገረው ቃል እርግጠኝነት ለመግለጽ የራሱን ስም በመጥራት ይናገራል። ይህንን በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ጌታ እግዚአብሔር የተናገረውን ይህንን ነው” ወይም “እኔ ጌታ እግዚአብሔር የተናገርኩት ይህንን ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 14:12

ምድር በእኔ ላይ ኃጢአትን ስትሠራ
“ምድር” የሚለው ቃል የሚወክለው በምድሪቱ ላይ የሚኖሩትን ሰዎች ነው። አ.ት፡ “በምድሪቱ ላይ የሚኖሩት ሰዎች በእኔ ላይ ኃጢአትን በሚሠሩበት ጊዜ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የእንጀራውን በትር እሰብራለሁ
በትር ይመስል እግዚአብሔር የሚናገረው ስለ እንጀራ አቅርቦት ነው። “እንጀራ” የሚለው ቃል ሁሉንም ዓይነት ምግብ ይወክላል። ተመሳሳዩን ሐረግ በሕዝቅኤል 4:16 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የምግብ አቅርቦቱን አቋርጣለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሰውንና እንስሳን ከምድሪቱ ላይ እቆርጣለሁ
ሰው ቅርንጫፍን ከዛፍ እንደሚቆርጥ ይቆርጣቸው ይመስል እግዚአብሔር ሰዎችንና እንስሳትን እንደሚገድላቸው ይናገራል። አ.ት፡ “በምድሪቱ የሚኖረውን ሰውንና እንስሳን ሁሉንም ግደል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 14:15

እነዚህ ሦስት ሰዎች
ኖኅ፣ ዳንኤል እና ኢዮብ

ሕያው እንደ መሆኔ
“ሕያው መሆኔ እርግጥ የመሆኑን ያህል”። እግዚአብሔር ቀጥሎ የሚናገረው የተረጋገጠ እውነት መሆኑን ለማሳየት ይህንን አገላለጽ ይጠቀማል። ይህ ጽኑ ተስፋ የመስጫ መንገድ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ጽኑ መሐላ አደርጋለሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የገዛ ራሳቸውን ሕይወት ብቻ ያድናሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የገዛ ራሳቸውን ሕይወት ብቻ ማዳን ይችላሉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 14:17

በምድሪቱ ላይ ሰይፍን ባመጣ
“ሰይፍ” የሚለው ቃል ሰይፍን በመጠቀም ሰዎችን የሚገድሉ ወታደሮችን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “

ሰይፍ ሆይ በምድሪቱ መካከል እለፍ
እዚህ ጋ “ሰይፍ” የሚለው ቃል የሚወክለው በሰይፍ የሚገድሉ የጠላት ሰራዊት ወታደሮችን ነው። አ.ት፡ “ሰራዊት ሆይ፣ በምድሪቱ መካከል እለፍ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከእርሱ ላይ ሰውና እንስሳውን ቁረጥ
ሰው ቅርንጫፍን ከዛፍ እንደሚቆርጥ ይቆርጣቸው ይመስል እግዚአብሔር ስለ ሰዎችና እንስሳት መገደል ይናገራል። አ.ት፡ “በምድሪቱ የሚኖረውን ሰውንና እንስሳን ሁሉንም ግደል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እነዚህ ሦስት ሰዎች
ኖኅ፣ ዳንኤል እና ኢዮብ

የእነርሱ ሕይወት ብቻ ይድናል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የራሳቸውን ሕይወት ብቻ ማዳን ይችላሉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 14:19

መዓቴን ባፈስ
ከመያዣ ዕቃው የሚያፈስሰው ፈሳሽ ይመስል እግዚአብሔር መዓቱን ስለሚገልጽበት ሁኔታ ይናገራል። አ.ት፡ “መዓቴን እገልጣለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሰውንና እንስሳን ቁረጥ
ሰው ቅርንጫፍን ከዛፍ እንደሚቆርጥ ይቆርጣቸው ይመስል እግዚአብሔር ሰዎችንና እንስሳትን ስለ መግደል ይናገራል። አ.ት፡ “ሰውንና እንስሳን ሁሉንም ግደል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የእነርሱ ሕይወት ብቻ ይድናል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የራሳቸውን ሕይወት ብቻ ማዳን ይችላሉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 14:21

ሰውንና እንስሳን ከእርሷ ለመቁረጥ
ሰው ቅርንጫፍን ከዛፍ እንደሚቆርጥ ይቆርጣቸው ይመስል እግዚአብሔር ሰዎችንና እንስሳትን ስለ መግደል ይናገራል። “እርሷ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢየሩሳሌምን ነው። አ.ት፡ “በኢየሩሳሌም የሚኖረውን ሰውና እንስሳ በሙሉ ለመግደል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 14:22

እነሆ
እዚህ ጋ፣ “እነሆ” የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚመጣው አስገራሚ መረጃ ትኩረት እንድንሰጥ ያነቃናል።

በውስጧ የቀረ ... በእርሻ ላይ የተደረገ
“እርሷ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢየሩሳሌምን ነው።

መንገዳቸውንና ተግባራቸውን
እነዚህ ሁለቱም ሐረጎች የሚያመለክቱት የእስራኤል ሕዝብ ያደረጉትን ነው። አ.ት፡ “የአኗኗር መንገዳቸው” ወይም “የሚያደርጓቸው ነገሮች”

ስለ ቅጣቱ ተጽናኑ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ስለ ቅጣቱ ያጽናኗችኋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 15

1 የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ። **2** "የሰው ልጅ ሆይ፥ የወይን ግንድ፥ በዱር ዛፎች መካከል ካለ ቅርንጫፎቼ ካሉት ማንኛውም ዛፍ ብልጫው ምንድር ነው? **3** በውኑ ሥራ የሚሠራበትን እንጨት ከወይን ግንድ ይወስዳሉን? ወይስ ሰዎች ዕቃ የሚንጠለጠልበትን ችካል ከእርሱ ይወስዳሉን? **4** እነሆ፥ ለመቃጠል በእሳት ላይ ቢጣል ፥ እሳቱም ሁለቱን ጫፎቹንና በልቶአል፥ መካከሉንም ቢያቃጥለው በውኑ ለሥራ ይጠቅማልን? **5** እነሆ፥ ደህና ሳለ ለሥራ ካልጠቀመ፥ ይልቁንስ እሳት ከበላው እርሱም ከተቃጠለ በኋላ ለምንም አይጠቅምም! **6** ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በዱር ዛፎች መካከል ካሉት ዛፎች ይልቅ የወይን ግንዱን እሳት ይበላው ዘንድ እንደ ሰጠሁት፥ እንዲሁ በኢየሩሳሌም የሚኖሩትን አሳልፌ እሰጣለሁ። **7** ፊቴንም በእነርሱ ላይ አደርጋለሁ ከእሳትም ይወጣሉ፥ እሳት ግን ይበላቸዋል ፊቴንም በእነርሱ ላይ ባደረግሁ ጊዜ እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ። **8** ዓመፅን አድርገዋልና ምድሪቱን ባድማ አደርጋለሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር!"

Ezekiel 15:1

የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የሰው ልጅ
“የሰብዓዊ ፍጡር ልጅ” ወይም “ከሰው የተወለደ ልጅ”። ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን አፅንኦት ለመስጠት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ በማለት ይጠራዋል። እግዚአብሔር ዘላለማዊና ኃያል ነው፣ ሰዎች ግን አይደሉም። አ.ት፡ “ሟች ሰው” ወይም “ሰው”

በደን ውስጥ በዛፎች መካከል ከሚገኙ ቅርንጫፎች ካሏቸው ዛፎች ሁሉ የወይን ሐረግን የተሻለ የሚያደርገው ምንድነው?
ሕዝቅኤል አስቀድሞ ስለሚያውቀው ስለ አንድ ነገር ለማስታወስ እግዚአብሔር ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ይጠይቀዋል። ይህ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “የወይን ሐረግ በደን ውስጥ ከሚገኝ ቅርንጫፍ ካለው ከየትኛውም ዛፍ የተሻለ አይደለም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ሰዎች የሆነ ነገር ለመሥራት ከወይን ሐረግ እንጨትን ይወስዳሉ?
ሕዝቅኤል አስቀድሞ ስለሚያውቀው ስለ አንድ ነገር ለማስታወስ እግዚአብሔር ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ይጠይቀዋል። ይህ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ሰዎች የሆነ ነገር ለመሥራት ከወይን ሐረግ እንጨትን አይወስዱም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

የትኛውንም ነገር ያንጠለጥሉበት ዘንድ ከእርሱ መስቀያ ያበጁበታል?
ሕዝቅኤል አስቀድሞ ስለሚያውቀው ስለ አንድ ነገር ለማስታወስ እግዚአብሔር ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ይጠይቀዋል። ይህ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ነገሮችን በእርሱ ላይ ለመስቀል ከእርሱ መስቀያን አያበጁም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት

እንዲነድ እሳት ላይ ቢጥሉት ... ለአንዳች ነገር ይጠቅማል?
ሕዝቅኤል አስቀድሞ ስለሚያውቀው ስለ አንድ ነገር ለማስታወስ እግዚአብሔር ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ይጠይቀዋል። ይህ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እንዲነድ እሳት ላይ ቢጥሉት ... ለምንም አይጠቅምም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት

እንዲነድ እሳት ላይ ቢጥሉት
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አንድ ሰው እንዲነድ እሳት ላይ ቢጥለው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 15:7

ፊቴን በእነርሱ ላይ አደርጋለሁ
እግዚአብሔር ፊቱን በእነርሱ ላይ በማድረጉ እንደሚቃወማቸው ይናገራል። አ.ት፡ “በእነርሱ ላይ እሆናለሁ” ወይም “እቃወማቸዋለሁ”

ፊቴን --- አደርጋለሁ
እዚህ ጋ “ፊት” የትኩረት ወይም የአስተውሎት ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን “ፊቴን -- አደርጋለሁ” የሚያመለክተው ማፍጠጥን ነው። አ.ት፡ “ማፍጠጥ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እኔ እግዚአብሔር እንደሆንኩ ያውቃሉ
እግዚአብሔር ሰዎች እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን ያውቃሉ ብሎ በሚናገርበት ጊዜ እርሱ ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለው ብቸኛው እውነተኛ አምላክ መሆኑን ሰዎች ያውቃሉ ማለቱ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 6፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እውነተኛው አምላክ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ይረዳሉ” ወይም “ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለኝ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ይገነዘባሉ”

ከእሳቱ ቢወጡም እሳቱ ገና ያቃጥላቸዋል
በእሳት የሚቃጠሉ በሚመስልበት ሁኔታ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ስለሚያመጣው ቅጣት ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እሳቱ ያቃጥላቸዋል
እነርሱም በእሳት የሚቃጠሉ ይመስል እግዚአብሔር ነገሮችን ስለሚያቃጥል እሳት ይናገራል። አ.ት፡ “እሳቱ ያጠፋቸዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ኃጢአትን አድርገዋል
“በዚያ የሚኖሩ ሰዎች ኃጢአትን አድርገዋል” ወይም “በዚያ የሚኖሩት ሰዎች ኃጢአትን ሠርተዋል”

ይህ የጌታ እግዚአብሔር ቃል ነው
እግዚአብሔር የንግግሩን እርግጠኝነት ለመግለጽ የራሱን ስም በመጥራት ይናገራል። ይህንን በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ጌታ እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን ነው” ወይም “እኔ፣ ጌታ እግዚአብሔር የተናገርኩት ይህንን ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 16

1 የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ። 2 የሰው ልጅ ሆይ፥ ለኢየሩሳሌም ርኵሰትዋን አስታውቃት፥ 3 እንዲህም በል፣ "ጌታ እግዚአብሔር ለኢየሩሳሌም እንዲህ ይላል፡ ዘርሽና ትውልድሽ ከከነዓን ምድር ነው አባትሽ አሞራዊ ነበረ እናትሽም ኬጢያዊት ነበረች። 4 በተወለድሽ ጊዜ እናትሽ እትብትሽን አልቆረጠችም ፣ በውኃ አላጠበችሽም ወይም በጨው አላሸችሽም፣ በጨርቅም አልጠቀለለችሽም። 5 ከእነዚህ ነገሮች አንዱን እንኳ ሊያደርግልሽ ማንም አልራራልሽም! በተወለድሽበት ቀን በሜዳ ላይ ተጣልሽ። 6 እኔ ግን በአንቺ ዘንድ ባለፍሁ ጊዜ በደምሽም ውስጥ ተለውሰሽ አየሁ፤ ስለዚህም በደምሽ እንዳለሽ "በሕይወት ኑሪ!" አልሁሽ። 7 በእርሻ ላይ እንዳለ ቡቃያ አሳደግሁሽ። አንቺም አደግሽ ታላቅም ሆንሽ፥ በእጅጉም አጌጥሽ። ጡቶችሽም አኰጠኰጡ ጠጕርሽም አደገ፥ ነገር ግን ዕርቃንሽን ሆነሽ፥ ተራቊተሽም ነበር። 8 እንደገና በአንቺ ዘንድ ባለፍሁና ባየሁሽ ጊዜ፥ እነሆ፥ ጊዜሽ የፍቅር ጊዜ ነበረ እኔም መጐናጸፊያዬን በላይሽ ዘርግቼ እራቁትነትሽን ሸፈንኩ።ከዚያም ማልሁልሽ ከአንቺም ጋር ቃል ኪዳን ገባሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፥ አንቺም ለእኔ ሆንሽ። 9 በውኃም አጠብሁሽ ከደምሽም አጠራሁሽ በዘይትም ቀባሁሽ። 10 በወርቅ የተንቆጠቆጠ ልብስም አለበስሁሽ ከቆዳ የተሰራ ጫማ አደረግሁልሽ፤ በጥሩ በፍታ አስታጠቅሁሽ በሐርም ከደንሁሽ። 11 በጌጥም አስጌጥሁሽ በእጅሽም ላይ አንባር በአንገትሽም ላይ ድሪ አደረግሁልሽ። 12 በአፍንጫሽም ቀለበት በጆሮሽም ጕትቻ በራስሽም ላይ የክብር አክሊል አደረግሁ። 13 በወርቅና በብር አጌጥሽ፤ ልብስሽም ጥሩ በፍታና ሐር ወርቀ ዘቦም ነበረ፤ አንቺም መልካምን ዱቄትና ማርን ዘይትንም በላሽ እጅግ በጣም ውብ ነበርሽ ከዚያም ንግሥት ሆንሽ። 14 ባንቺ ላይ ካኖርኋት ከክብሬ የተነሣ ውበትሽ ፍጹም ነበረና ዝናሽ በአሕዛብ መካከል ወጣ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፡- 15 ነገር ግን በውበትሽ ታምነሻል ስለ ዝናሽም አመንዝረሻል ምንዝርናሽንም ከመንገድ አላፊ ሁሉ ጋር አበዛሽ። የእነርሱም ንብረት ሆንሽ! 16 ከልብስሽም ወስደሽ በኮረብቶች ላይ በዝንጕርጕር ልብስ ያስጌጥሻቸውን መስገጆች ለራስሽ ሠራሽ በዚያም ገለሞትሽ። እንዲህም ያለ ነገር ከአሁን በፊት አልነበረም፥ ከእንግዲህም ወዲያ አይሆንም። 17 ከሰጠሁሽም ከወርቄና ከብሬ የተሠራውን የክብርሽን ዕቃ ወስደሽ የወንድ ምስሎች ለራስሽ አድርገሻል አመንዝረሽባቸውማል። 18 ወርቀዘቦውን ልብስሽንም ወስደሽ ደረብሽላቸው፥ ዘይቴንና ዕጣኔንም በፊታቸው አኖርሽ። 19 የሰጠሁሽንም እንጀራዬን ያበላሁሽንም መልካሙን ዱቄትና ዘይቱን ማሩንም ጣፋጭ ሽታ አድርገሽ በፊታቸው አኖርሽ፥ ይህ በእርግጥ ሆኖአል! ይላል ጌታ እግዚአብሔር፡- 20 ለእኔም የወለድሻቸውን ወንዶችና ሴቶች ልጆችሽን ወስደሽ መብል ይሆኑ ዘንድ ለጣዖታቱ ሠዋሽላቸው። በውኑ የግልሙትና ተግባርሽ እንደ ቀላል የሚታይ ነገር ነውን? 21 ልጆቼን አረድሽ ለእነርሱም የሚቃጠል መስዋዕት አድርገሽ አቀረብሽ 22 በዚህ ሁሉ የርኵሰትና የግልሙትና ተግባርሽ ወቅት ዕርቃንሽን ተራቊተሽ በደምሽም ተለውሰሽ የነበርሽበትን የሕፃንነትሽን ወራት አላሰብሽም። 23 ወዮ! ወዮልሽ! ይላል ጌታ እግዚአብሔር 24 ከክፋትሽም ሁሉ በኋላ የጣዖት ማምለኪያ ስፍራ፥ በየአደባባዩም አጸዶችን ሠራሽ። 25 በየመንገዱ ራስ ከፍ የማምለኪያ አጸዶችን ሠራሽ፥ ለመንገድ አላፊም ሁሉ እግርሽን በመግለጥና በርካታ የግልሙትና ተግባራት በመፈጸም ውበትሽን አረከስሽ ። 26 እጅግ የሴሰኝነት ፍላጎት ካላቸው ከጐረቤቶችሽ ከግብጻውያን ጋር አመነዘርሽ፥ እኔንም ታስቈጭ ዘንድ ግልሙትናሽን አበዛሽ። 27 ስለዚህ፥ በእጄ አደቅሻለሁ እህልንም ከአንቺ ዘንድ አጠፋለሁ። ለሚጠሉሽም ከክፉ ምኞትሽ የተነሣ ለውርደት ለሚዳርጉሽ ለፍልስጥኤም ሴቶች ልጆች ፈቃድ አሳልፌ ሰጥቼሻለሁ። 28 አልጠገብ ብለሽ ከአሦራውያን ጋር ደግሞ ገለሞትሽ። ያም ሆኖ ግን አሁንም አልበቃሽም። 29 እስከ ነጋዴዎች ምድር እስከ ከላውዴዎን ድረስ ግልሙትናሽን አበዛሽ። አሁንም ግን ገና አልጠገብሽም። 30 የማታፍረውን የጋለሞታን ሥራ ሁሉ ሠርተሻልና ልብሽ ምንኛ ደካማ ነው? ይላል ጌታ እግዚአብሔር፡- 31 በየመንገዱ ራስ የምንዝርናሽን ስፍራ ሠርተሻል በየአደባባዩም ከፍ ያለውን ቦታሽን አድርገሻል። ዋጋዋን እንደምትንቅ እንደ ጋለሞታ አልሆንሽም። 32 አንቺ ዘማዊ ሴት በባልሽ ፋንታ ሌሎች እንግዳ ሰዎች ተቀበልሽ። 33 ሰዎች ለጋለሞቶች ሁሉ ዋጋ ገንዘብ ይከፍላሉ አንቺ ግን ለውሽሞችሽ ገንዘብ ትከፍያለሽ፥ ከአንቺም ጋር ለማመንዘር ከአካባቢው ሁሉ ወድ እንቺ እንዲምጡ ማባበያ ትሰጫቸዋለሽ። 34 ግልሙትናሽ ከሌሎች ሴቶች ፈጽሞ የተለየ ነው፥ ምክንያቱም ማንም ከአንቺ ጋር ልትኛ ብሎ የሚጠይቅሽ የለም። ይልቁኑ አንቺ ትከፍያቸዋለሽ እንጂ የሚክፍልሽ የለም። 35 ስለዚህ፥ ጋለሞታ ሆይ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ስሚ! 36 ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ከውሽሞችሽና ከአጽያፊ ጣዖታትሽ ጋር ባደረግሽው ግልሙትና አማካኝነት ክፉ ምኞትሽን በማፍሰስሽና ኀፍረተ ሥጋሽንም በመግለጥሽ እንዲሁም ለጣዖታትሽ በሰጠሻቸው በልጆችሽ ደም ምክንያት፥ 37 እነሆ፥ ከእነርሱ ጋር ደስ ያለሽን የወደድሻቸውንም ውሽሞችሽና የጠላሻቸው ሁሉ ከሁሉም አቅጣጫ በአንቺ ላይ እንዲነሱ እሰበስባቸዋለሁ። እራቁትነትሽን እንዲያዩ በፊታቸው ኀፍረተ ሥጋሽን እገልጣለሁ። 38 ስለምንዝርናሽና ደም ማፍሰስሽ እቀጣሻለሁ፥ በቁጣዬና በቅንዓቴ ደም መፋሰስን አመጣብሻለሁ። 39 በእጃቸውም አሳልፌ እሰጥሻለሁ፥ የምንዝርናሽንም ስፍራ ያፈርሳሉ ከፍ ያለውንም ቦታሽን ይገለብጣሉ ልብስሽንም ይገፉሻል የክብርሽንም ጌጥ ይወስዳሉ፥ ዕርቃንሽን አድርገው ዕራቁትሽን ይተዉሻል። 40 ህዝብንም ያስነሱብሻል በድንጋይም ይወግሩሻል፥ በሰይፋቸውም ይሰነጥቁሻል። 41 ቤቶችሽንም በእሳት ያቃጥላሉ በብዙም ሴቶች ፊት ብዙ ቅጣቶችን ይፈጽሙብሻል፥ ግልሙትናሽንም አስተውሻለሁ፥ ከእንግዲህ ለእነርሱ ዋጋ አትሰጭም! 42 መዓቴንም በአንቺ ላይ እጨርሳለሁ ቅንዓቴም ከአንቺ ይርቃል፥ እኔም እረካለሁ፣ከዚያ በኋላም አልቈጣም። 43 በእንዚህ ነገሮች ሁሉ ስታስቆጪኝ የሕፃንነትሽን ወራት አላሰብሽምና፥ ስለዚህ፥ እነሆ፥ እኔ እራሴ ለፈጸምሽው ጥፋት ቅጣትን በአንቺ ላይ አመጣለሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፥ ከዚህ በኋላ በአስነዋሪ መንገድሽ በክፋት አትሄጂም። 44 እነሆ፥ በምሳሌ የሚናገር ሁሉ፥ "ልክ እንደ እናቲቱ ሴት ልጂቱ እንደዛው ናት" እያለ ምሳሌ ይመስልብሻል። 45 አንቺ ባልዋንና ልጆችዋን የጠላች የእናትሽ ልጅ ነሽ፤ ደግሞም ባሎቻቸውንና ልጆቻቸውን የጠሉ የእኅቶችሽ እኅት ነሽ። እናታችሁ ኬጢያዊት ነበረች አባታችሁም አሞራዊ ነበረ። 46 ታላቂቱም እኅትሽ ከሴቶች ልጆችዋ ጋር በስተ ሰሜን የምትኖረው ሰማርያ ናት ታናሺቱም እኅትሽ ከሴቶች ልጆችዋ ጋር በስተ ምዕራብ የምትኖረው ሰዶም ናት። 47 አንቺ ግን በመንገዳቸው አልሄድሽም እንደ ርኵሰታቸውም አላደረግሽም የእነርሱ ድርጊት ለአንቺ ጥቂት ነበረና። ይልቁኑ በመንገድሽ ሁሉ ከእነርሱ የከፋሽ ሆንሽ። 48 በህያውነቴ እምላለሁ አንቺና ሴቶች ልጆችሽ ያደርጋችሁትን ክፋት ያህል ሰዶምና ሴቶች ልጆችዋ አላደረጉም! ይላል ጌታ እግዚአብሔር። 49 እነሆ፥ የእኅትሽ የሰዶም ኃጢአት ይህ ነበረ፡ በሥራ ፈትነት የበረታች፣ ስለምንም ነገር የማይሰማት ግድ የለሽት ነበረች። የችግረኛውንና የድሀውንም እጅ አላበረታችም ። 50 ትዕቢተኛ ነበረች በፊቴም ርኩስ ነገሮችን አደረገች፣ እንዳየሽውም አጠፋኋቸው። 51 ሰማርያም የኃጢአትሽን እኵሌታ እንኳ አልሠራችም ፤ አንቺ ግን ከእኅቶችሽ ይልቅ ርኵሰትሽን አበዛሽ፥ በሠራሽውም ርኵሰት ሁሉ እህቶችሽ ካንቺ እንድሚሻሉ አሳየሽ። 52 አሁንም ለእኅቶችሽ ስለ ፈረድሽ እፍረትሽን ተሸከሚ ከእነርሱ የባሰ ኃጢአት ሠርተሻልና ከአንቺ ይልቅ የተሻሉ ሆነው ታይተዋል። እህቶችሽ ካንቺ እንድሚሻሉ በማሳየትሽ እፈሪ ። 53 የሰዶምና የሴቶች ልጆችዋን ምርኮ፥ የሰማርያንና የሴቶች ልጆችዋንም ምርኮ እመልሳለሁ፤ ነገር ግን የአንቺ ምርኮ በእነርሱ መካከል ይሆናል። 54 በእዚህም ነገሮች ቀመር እፍረትሽን ታሳዪአለሽ ስለ አደረግሽውም ሁሉ ታፍሪያለሽ፣ በዚህም ምክንያት ለእነርሱ መጽናኛ ትሆኚያለሽ። 55 እኅቶችሽም ሰዶምና ሴቶች ልጆችዋ ወደ ቀድሞ ሁኔታቸው ይመለሳሉ፥ ሰማርያና ሴቶች ልጆችዋም ወደ ቀድሞ ሁኔታቸው ይመለሳሉ። ከዚያም አንቺና ሴቶች ልጆችሽ ወደ ቀድሞ ሁኔታችሁ ትመለሳላችሁ። 56 ኩሩ በነበርሽ ጊዜ ስለ እኅትሽ ሰዶም ተናግረሽ አታውቂም ነበር፥ 57 ክፋትሽ ከመገለጡ በፊትማለት ነው። አሁን ግን ለኤዶም ሴቶች ልጆችና በጎረቤቶችዋ ላሉ የፍሊስጤማውያን ልጆች ሁሉ፥ የውርደት ምሳሌ ሆነሻል። ሰው ሁሉ ይንቅሻል። 58 ምንዝርነትሽንና ርኵስነትሽን ይገለጣል ፥ ይላል እግዚአብሔር፡- 59 ጌታ እግዚአብሔርም እንዲህ ይላል። ቃል ኪዳንን ለማፍረስ መሐላን በሚንቅ ሁሉ ላይ የማደርገውን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በአንቺም ላይ አደርጋለሁ። **60** ነገር ግን በሕፃንነትሽ ወራት ከአንቺ ጋር ያደረግሁትን ቃል ኪዳኔን እኔ እራሴ አስባለሁ የዘላለምንም ቃል ኪዳን ከአንቺ ጋር እገባለሁ። **61** እኅቶችሽንም ታላቂቱንና ታናሺቱን በተቀበልሽ ጊዜ መንገድሽን ታስቢያለሽ ታፍሪማለሽ። ለአንቺም ልጆች ይሆኑ ዘንድ እሰጣቸዋለሁ፥ ይህን የማደርገው ግን ስለ ቃል ኪዳንሽ አይደለም። **62** ቃል ኪዳኔን ከአንቺ ጋር አጸናለሁ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቂያለሽ! **63** በዚህም ምክንያት ስላደረግሽውም ሁሉ ይቅር ባልሁሽ ጊዜ፥ ያደርግሽውን ሁሉ አስበሽ ታፍሪያለሽ ከዚያም ወዲያ ለምናገር አፍሽን አትከፍቺም፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፦

Ezekiel 16:1

የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የሰው ልጅ
“የሰብዓዊ ፍጡር ልጅ” ወይም “ከሰው የተወለደ ልጅ”። ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን አፅንኦት ለመስጠት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ በማለት ይጠራዋል። እግዚአብሔር ዘላለማዊና ኃያል ነው፣ ሰዎች ግን አይደሉም። አ.ት፡ “ሟች ሰው” ወይም “ሰው”

ጅማሬሽና ልደትሽ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ይጋራሉ። ሰዎች ከተማይቱን በመሠረቱ ጊዜ የከተማይቱ ልደት እንደ ሆነ አድርጎ እግዚአብሔር ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አባትሽ አሞራዊ ነበረ፣ እናትሽም ኬጢያዊት ነበረች
የእስራኤል ሕዝብ ምድሪቱን ድል ከማድረጋቸው በፊት ጣዖት አምላኪ የሕዝብ ወገን የሆኑት አሞራውያንና ኬጢያውያን በምድሪቱ ይኖሩ ነበር። ኢየሩሳሌም በዝሙት መወለዷን ለመግለጽ አባትና እናቷ የዚህ ሕዝብ ወገን እንደ ነበሩ እግዚአብሔር ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 16:4

እናትሽ እንብርትሽን አልቆረጠችውም
እዚህ ጋ “እንብርት” የሚያመለክተው ከእንብርት ጋር የተያያዘውን እትብት ያመለክታል። አ.ት፡ “እናትሽ እትብትሽን አልቆረጠችውም”

የማንም ዐይን አልራራልሽም
እዚህ ጋ “ዐይን” የሚለው ቃል የሚወክለው የሚያየውን ሰው ነው። አ.ት፡ “ካየሽ ሁሉ የራራልሽ የለም”

ሕይወትሽ የተጠላ
“ወላጆችሽ ጠልተውሽ ስለ ነበር”

ሜዳ ላይ ተጥለሽ ነበር
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ወላጆችሽ ሜዳ ላይ ጥለውሽ ነበር” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 16:6

በአጠገብሽ ሳልፍ
እግዚአብሔር አዲስ በተወለደችው ሕፃን አጠገብ ያልፍ ነበር

በደምሽ እንዳለሽ ተናገርኩሽ
ግልጽ ያልሆነው መረጃ ከቀደም ካለው ሐረግ ሊሟላ ይችላል። አ.ት፡ “በደምሽ ላይ ተጋድመሽ እያለሽ ተናገርኩሽ”

በእርሻ ላይ እንዳለ ተክል እንድታድጊ አደረግሁሽ
እዚህ ጋ፣ እግዚአብሔር በፍጥነት ማደጓን በቶሎ ከሚያድጉ ተክሎች ጋር ያነጻጽራል።

በዛሽ፣ ታላቅም ሆንሽ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ይጋራሉ። ሁለቱም የሚያመለክቱት ማደጓንና መርዘሟን ነው። አ.ት፡ “ጎለመስሽ፣ ረዘምሽም”

የዕንቁዎች ዕንቁ ሆንሽ
እዚህ ጋ፣ ኢየሩሳሌምን የምትወክለው ሴት ከሴቶች ሁሉ እጅግ የተዋበች ይመስል ከዕንቁዎች ሁሉ ብልጫ ያላት ተደርጎ ተነግሮላታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የዕንቁዎች ዕንቁ ሆንሽ
አንዳንድ የቅርብ ጊዜ ትርጉሞች “በዕንቁ ለማጌጥ በቃሽ” ይላሉ።

ዕርቃንሽን እና ራቁትሽን
የሁለቱም ቃላት ትርጉም አንድ ነው። አ.ት፡ “ባዶ ዕርቃን”

Ezekiel 16:8

ተመልከት!
እዚህ ጋ “ተመልከት” የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚመጣው አስገራሚ መረጃ ትኩረት እንድንሰጥ ያነቃናል።

የፍቅር ጊዜ መጣልሽ
ይህ አባባል ወጣቷ ሴት ለጋብቻ ዕድሜ መድረሷን እግዚአብሔር ዓይቷል ለማለት ነው።

ይህ የጌታ እግዚአብሔር ቃል ነው
እግዚአብሔር የንግግሩን እርግጠኝነት ለመግለጽ የራሱን ስም በመጥራት ይናገራል። ይህንን በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ጌታ እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን ነው” ወይም “እኔ፣ ጌታ እግዚአብሔር የተናገርኩት ይህንን ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 16:9

ባለ ጥልፍ ልብስ
“የተዋቡ ልብሶች”። መጥለፍ ማለት በቁርጥራጭ ጨርቆች የተሠራውን ንድፍ በአንድ ላይ መስፋት ነው።

በጌጣጌጥ አስዋብኩሽ
“ጌጣ ጌጥ አደርግሁልሽ”

Ezekiel 16:13

በወርቅና በብር አጌጥሽ፣ የተመረጠ በፍታም ለበስሽ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በወርቅና በብር አስጌጥኩሽ፣ የተመረጠ በፍታም አለበስኩሽ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በሀገራት መካከል ዝናሽ ወጣ
“በብዙ ሀገር የሚኖሩ ብዙ ሕዝቦች ማን እንደ ነበርሽ አወቁ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እርሱም ፍጹም ነበር
“ውበትሽ ፍጹም ነበር”

Ezekiel 16:15

በገዛ ራስሽ ውበት ታመንሽ
“የገዛ ውበትሽን መተማመኛሽ አደረግሽው”

እንደ አመንዝራ ሴት አደረግሽ
ከተማይቱ ገንዘብ ለመቀበል በምትኩ ከሌሎች ወንዶች ጋር በመተኛት ታማኝነቷን እንዳጎደለች ሚስት አድርጎ እግዚአብሔር ስለ ኢየሩሳሌም ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የአመንዝራነት ሥራሽን አፈሰስሽ
እግዚአብሔር ግብረ ገብነት የጎደለውን የኢየሩሳሌምን ተግባር በፈሳሽ ይመስለውና እነዚያን ተግባራት በተደጋጋሚ መፈጸሟን ፈሳሾቹን ከመያዣው ማፍሰስ እንደ ሆነ አድርጎ ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ውበትሽ የእርሱ እንዲሆን
ይህ የዕብራይስጡ ሐረግ በዘመናዊ ትርጉሞች ውስጥ በብዙ የተለያዩ መንገዶች ተተርጉሟል። ለምሳሌ፣ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች “ራስሽን ትሰጪው ዘንድ” ወይም “የእርሱ ሆንሽ”

Ezekiel 16:17

የወንድ ምስሎች
“የወንዶች ሐውልት” ወይም “ወንዶችን የሚመስሉ ጣዖታት”

አመንዝራ ሴት እንደምታደርገው ከእነርሱ ጋር አደርግሽ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) ይህ ወጣቷ ሴት ከወንድ ምስሎች ጋር ስለ መተኛቷ የትህትና አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ከእነርሱ ጋር ተኝተሻል” ወይም 2) ይህ ምስሎቹን ማምለኳ ከእነርሱ ጋር እንደ ተኛች አድርጎ እግዚአብሔር የተናገረበት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “አመለክሻቸው” (Euphemism እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከምርጥ ዱቄት ጋር ዘይትና ማር አደረግሽላቸው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በምርጥ ዱቄት የጋገርኩትን እንጀራ፣ ዘይትና ማር” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በፊታቸው አቀረብሽላቸው
“በፊት ለፊታቸው መስዋዕት አድርገሽ አቀረብሽላቸው”

Ezekiel 16:20

ለእኔ የወለድሻቸውን
“ልጆቼ የነበሩትን”

እንደ ምግብ እንዲበሏቸው ለምስሎቹ ሰዋሻቸው ... በእሳት እንዲያልፉ አደርግሻቸው
እዚህ ጋ፣ እግዚአብሔር የእስራኤል ሕዝብ ስላደረጉት አንድ ነገር ይናገራል። ልጆቻቸውን ለአሕዛብ ጣዖታት ሰውተዋል።

እንደ ምግብ እንዲበሏቸው ለምስሎቹ ሰዋሻቸው
በእነዚህ ጥንታዊ የጣዖት አምላኪዎች መስዋዕት አማልክቱ የሚቀርብላቸውን ምግብ እንደሚበሉ ሰዎች ያምኑ ነበር። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ምስሎቹ እንደ ምግብ እንዲበሏቸው ለእነዚያ ምስሎች መስዋዕት አደረግሻቸው”

የአመንዝራነትሽ ሥራ አነስተኛ ጉዳይ ነው? አረድሻቸው
ሴቲቱ አመንዝራነቷ ሳያንሳት ልጆቿን ደግሞ ለመሰዋት መወሰኗ ላይ አጽንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ያረድሻቸው የአመንዝራነትሽ ሥራ አነስተኛ ጉዳይ እንደ ሆነ ስላሰብሽ መሆን አለበት” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

በእሳት እንዲያልፉ አደርግሻቸው
ለምስሎቿ የሚቃጠል መስዋዕት እንዲሆኑ እሳት ውስጥ እንደጨመረቻቸው ግልጽ አይደለም። አ.ት፡ “የሚቃጠል መስዋዕት አድርጋ ሰዋቻቸው”

ዕርቃንሽን እና ራቁትሽን
የእነዚህ የሁለቱም ቃላት ትርጉም አንድ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 16፡7 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ባዶ ዕርቃን”

Ezekiel 16:23

ይህ የጌታ እግዚአብሔር ቃል ነው
እግዚአብሔር የንግግሩን እርግጠኝነት ለመግለጽ የራሱን ስም በመጥራት ይናገራል። ይህንን በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ጌታ እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን ነው” ወይም “እኔ፣ ጌታ እግዚአብሔር የተናገርኩት ይህንን ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

በየአደባባዩ ለራስሽ የማምለኪያ አዳራሽ ሠራሽ
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፣ 1) ጣዖታቷን የምታመልክበት ወይም 2) የዝሙት ተግባሯን የምትፈጽምበት ሥፍራ ሠርታለች የሚሉት ናቸው።

Ezekiel 16:25

በየመንገዱ ራስ ላይ
እግዚአብሔር የመንገድ መጀመሪያን ራስ እንደ ሆነ አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “በየመንገዱ መጀመሪያ ላይ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 16:27

ተመልከት!
እዚህ ጋ “ተመልከት” የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚመጣው አስገራሚ መረጃ ትኩረት እንድንሰጥ ያነቃናል።

በእጄ እመታሻለሁ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው ኃይልን ነው። አ.ት፡ “እንቺን ለመምታት ኃይሌን እጠቀማለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ምግብሽን እቆርጣለሁ
እግዚአብሔር የምግብ አቅርቦት ማቋረጥን ምግብን እንደ መቁረጥ አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “የምግብ አቅርቦትሽን አቆማለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሕይወትሽን አሳልፌ እሰጣለሁ
እዚህ ጋ “ሕይወት” ሰውን ይወክላል። አ.ት፡ “አሳልፌ እሰጥሻለሁ”

ለፍልስጥኤማውያን ሴቶች ልጆች
እዚህ ጋ የፍልስጥኤምን ከተሞች እግዚአብሔር እንደ ፍልስጥኤም ሴቶች ልጆች አድርጎ ይናገራል። ከተሞቹ በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላሉ። አ.ት፡ “የፍልስጥኤም ሰዎች” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 16:30

እነዚህን ሁሉ ነገሮች፣ እፍረት ዐልባ የአመንዝራነት ሥራ የምትሠሪው . . . ልብሽ ምን ያህል ታማሚ ቢሆን ነው?
እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ለመገሰጽ ምላሽ የማይሻውን ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እነዚህን ሁሉ ነገሮች፣ እፍረት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ዐልባ የአመንዝራነት ተግባር የምትፈጽሚው ልብሽ በጣም ስለ ታመመ መሆን አለበት!” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ልብሽ ምን ያህል ታማሚ ቢሆን ነው
እዚህ ጋ “ልብ” የሚለው ቃል ፈቃድን እና ስሜትን ይወክላል። ልቧ የታመመ ይመስል ፍላጎቷን ለመቆጣጠር እንዳልቻለች እግዚአብሔር ይናገራል። አ.ት፡ “ፈቃድሽ ምን ያህል ደካማ የሆነ ሰው ነሽ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በየጎዳናው ራስ ላይ
እግዚአብሔር የጎዳናን መጀመሪያ ራስ እንደ ሆነ አድርጎ ይናገራል። ተመሳሳዩን ሐረግ በሕዝቅኤል 16፡25 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “በየጎዳናው መጀመሪያ ላይ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የማምለኪያ አዳራሾችሽን ሠራሽ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) ጣዖታቷን የምታመልክበት ወይም 2) የዝሙት ተግባሯን የምትፈጽምበት ሥፍራ ሠርታለች የሚሉት ናቸው። ይህንን በሕዝቅኤል 16፡24 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።

Ezekiel 16:32

ከባልሽ ይልቅ እንግዶችን ትቀበያለሽ
ይህ አንድን ሰው ከእርሷ ጋር እንዲተኛ እንደምትቀበለው ያመለክታል። አ.ት፡ “በአልጋሽ ላይ ከባልሽ ይልቅ እንግዶችን ትቀበያለሽ”

Ezekiel 16:35

ዝሙትሽን አፈሰስሽ
ፈሳሽ የሆነ ይመስል እግዚአብሔር ስለ ኢየሩሳሌም ዝሙት ይናገራል፤ ይህንን ብርቱ የዝሙት ፍላጎትዋን ለማርካት ደጋግማ መፈጸሟን ደግሞ ከዕቃ መያዣው እንደሚፈስ ፈሳሽ አድርጎ ይገልጸዋል። አ.ት፡ “የዝሙት ፍላጎትሽን ለማርካት በተደጋጋሚ ፈጸምሽው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ዝሙትሽን አፈሰስሽ
አንዳንድ የቅርብ ዓመታት ትርጉሞች “ብልጽግናሽን አፈሰስሽ” ብለው ይተረጉሙታል።

የልጆችሽን ደም ሰጠሻቸው
ይህ የሚያመለክተው ለጣዖታት መስዋዕት እንዲሆኑ የተገደሉትን ልጆች ነው።

እነሆ
እዚህ ጋ፣ “እነሆ” የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚመጣው አስገራሚ መረጃ ትኩረት እንድንሰጥ ያነቃናል።

ስለዚህ ሙሉ ራቁትነትሽን ያያሉ
በሌሎች ፊት የአንድን ሰው ልብስ መግፈፍ ያንን ሰው ለማዋረድ በማሰብ የሚደረግ ተግባር ነው። “ራቁትነት” የሚለው ቃል እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ስለዚህ ሙሉ በሙሉ ራቁትሽን መሆንሽን ማየት ይችላሉ”

Ezekiel 16:38

የደም መፍሰስ
ይህ ሐረግ በየትኛውም መልኩ የተፈጸመ ግድያን ይወክላል። አ.ት፡ “ግድያ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ስለ ደም መፋሰስ ቁጣዬን እና ርኅራኄዬን በአንቺ ላይ አመጣለሁ
እዚህ ጋ “ደም መፋሰስ” በየትኛውም መልኩ የተፈጸመ ግድያን ይወክላል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እግዚአብሔር የደም መፋሰስን በእርሷ ላይ ያመጣ ይመስል ስለ ግድያዋ እንደሚቀጣት ይናገራል። አ.ት፡ “ነፍስ ስለ ማጥፋትሽ በቁጣዬና በርኅራኄዬ እቀጣሻለሁ” ወይም 2) እግዚአብሔር የደም መፋሰስን በእርሷ ላይ ያመጣ ይመስል እርሷን ስለ መግደል ይናገራል። አ.ት፡ “በቁጣዬና በርኅራኄዬ ደምሽን አፈስሳለሁ” የሚሉት ትርጉሞች ናቸው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእጃቸው እሰጥሻለሁ
እዚህ ጋ “እጆች” የሚወክሉት ኃይልን ወይም ቁጥጥርን ነው። አ.ት፡ “በቁጥጥራቸው ስር እንድትሆኚ አደርግሻለሁ” ወይም “በአንቺ ላይ ኃይል እንዲኖራቸው እፈቅድላቸዋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የማምለኪያ አዳራሽሽን አፈርሰዋለሁ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) ጣዖታቷን ያመለከችበትን ወይም 2) የዝሙት ተግባሯን የፈጸመችበትን ሥፍራ ያጠፉታል የሚሉት ናቸው። በሕዝቅኤል 16፡24 ላይ “የማምለኪያ አዳራሽ” የሚለውን እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።

ዕርቃንሽን እና ራቁትሽን
የሁለቱም ቃላት ትርጉም አንድ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 16፡7 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ባዶ ዕርቃን”

Ezekiel 16:40

በአንቺ ላይ ብዙ የቅጣት ዓይነት እፈጽምብሻለሁ
“ቅጣት” የሚለው ቃል ከግሣዊ ሐረግ ጋር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “በተለያየ መንገድ እቀጣሻለሁ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

በብዙ ሴቶች ፊት
“ብዙ ሴቶች ሊያዩአት በሚችሉበት ስፍራ” ወይም “ብዙ ሴቶች እያዩአት”

በአንቺ ላይ ንዴቴን አበርዳለሁ፤ ቁጣዬም ይተውሻል
“ንዴት” እና “ቁጣ” የሚሉት ቃላት እግዚአብሔር ስለ ተቆጣ የሚፈጽማቸው ቅጣቶች መሆናቸውን ያመለክታል። በመሠረቱ የሁለቱም ሐረጎች ትርጉም አንድ ነው። አ.ት፡ “ከእንግዲህ ስለማልቆጣሽ አንቺን መቅጣቴን አቆማለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 16:43

ልብ በይ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ትርጉሙ ማስታወስ ማለት ነው። አ.ት፡ “አስታውሽ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ስለ እነዚህ ነገሮች ሁሉ በቁጣ እንድንቀጠቀጥ አድርገሽኛል
እዚህ ጋ “መንቀጥቀጥ” የሚያመለክተው አንድ ሰው እጅግ በሚቆጣበት ጊዜ የሚታይበትን አካላዊ ምላሽ ያመለክታል። ኢየሩሳሌም እነዚህን ነገሮች ስታደርግ ልጅ በነበረችበት ጊዜ እግዚአብሔር ያደረገውን አላሰበችም።

እነሆ
እዚህ ጋ፣ “እነሆ” የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚመጣው አስገራሚ መረጃ ትኩረት እንድንሰጥ ያነቃናል።

ስላደረግሽው ነገር እኔ ራሴ ቅጣቱን በራስሽ ላይ አመጣለሁ
“በራስሽ ላይ አመጣለሁ” የሚለው የአነጋገር ዘይቤ ይህንን ቅጣት ትቀበላለች ማለት ነው። ይህንን የአነጋገር ዘይቤ በሕዝቅኤል 11፡21 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ስለ ጸባይሽ በምትቀበይው ቅጣት እንድትሰቃዪ አደርግሻለሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 16:44

እነሆ
እዚህ ጋ፣ “እነሆ” የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚመጣው አስገራሚ መረጃ ትኩረት እንድንሰጥ ያነቃናል።

ባሏን የጠላችውን
“ባሏን የጠላችውን”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እናትሽ ኬጢያዊት ነበረች፣ አባትሽም አሞራዊ ነበር
የእስራኤል ሕዝብ ምድሪቱን ድል ከማድረጋቸው በፊት ጣዖት አምላኪ የሕዝብ ወገን የሆኑት አሞራውያንና ኬጢያውያን በምድሪቱ ይኖሩ ነበር። ኢየሩሳሌም በዝሙት መወለዷን ለመግለጽ አባትና እናቷ የዚህ ሕዝብ ወገን እንደ ነበሩ እግዚአብሔር ይናገራል። እነዚህን ሐረጎች በሕዝቅኤል 16:3 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምካቸው ተመልከት። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 16:46

ታላቅ እህትሽ ሰማርያ ነበረች ... ታናሽ እህትሽ በስተደቡብ የምትኖረዋ ናት፣ እርሷም ሰዶም ናት
ሰማርያና ሰዶም ሁለቱም በጣዖት አምልኮአቸውና በኃጢአታቸው ምክንያት እግዚአብሔር የፈረደባቸው ከተማዎች ነበሩ። እግዚአብሔር እነዚህ ከተሞች ኢየሩሳሌም የጣዖት አምላኪዎችና የኃጢአተኞች ቤተሰብ መሆኗን ለመግለጽ እህቶቿ መሆናቸውን ይናገራል።

Ezekiel 16:47

በመንገዳቸው ብቻ አልሄድሽም
የአንድ ሰው የአኗኗር መንገድ ያ ሰው በጎዳና ላይ እንደሚሄድ ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “እንደ እነርሱ ብቻ አላደረግሽም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የእነርሱን ጠባይና ልምምድ ቀዳሽ
እዚህ ጋ “ጸባይ” እና “ልምምድ” የሚሉት ቃላት መሠረታዊ ትርጉማቸው አንድ ነው። አ.ት፡ “ሲያደርጓቸው የነበሩትን ነገሮች ቀዳሽ”

ሕያው እንደ መሆኔ
“ሕያው መሆኔ እርግጥ የመሆኑን ያህል”። እግዚአብሔር ቀጥሎ የሚናገረው የተረጋገጠ እውነት መሆኑን ለማሳየት ይህንን አገላለጽ ይጠቀማል። ይህ ጽኑ ተስፋ የመስጫ መንገድ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ጽኑ መሐላ አደርጋለሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 16:49

በእርጋታዋ እብሪተኛ፣ ስለ የትኛውም ነገር ቸልተኛና ግድ የለሽ
እግዚአብሔር ሰዶምን ከበቂ በላይ ምግብ እንዳላትና ያለ ሥጋት እንደምትኖር ባለጸጋ ሴት አድርጎ ይገልጻታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የድኾችንና የችግረኞችን እጅ አላበረታችም
እዚህ ጋ “እጅ” የሚለው ቃል የሚወክለው በእጆቻቸው የሚሠሩትን ሰዎች ነው። “ድኻ” እና “ችግረኛ” የሚሉት ቃላት እንዲህ ያሉት ሰዎች ራሳቸውን መርዳት የማይችሉ መሆናቸው ላይ አጽንዖት የሰጣሉ። አ.ት፡ “ራሳቸውን መረዳት ያልቻሉትን ሰዎች አልረዳቻቸውም” (See: Synecdoche and Doublet)

Ezekiel 16:51

እህቶችሽ ከአንቺ ይሻሉ እንደነበር አሳይተሻል
ኃጢአተኞቹ ሰማርያና ሰዶም ከኢየሩሳሌም ይልቅ ጻድቅ እንደ ነበሩ አጽንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ይህንን ሐረግ ሦስት ጊዜ ይጠቀማል።

በተለይ አንቺ፣ የገዛ ራስሽን ኃፍረት አሳየሽ
የኢየሩሳሌም ሰዎች ምን ያህል ያለ እፍረት እንዳደረጉ አጽንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ይህንን ሐረግ ሁለት ጊዜ ይጠቀማል።

የገዛ ራስሽን ኃፍረት አሳየሽ
“እፈሪ” ወይም “ውርደትሽን ተሸከሚ”

Ezekiel 16:53

ምርኮአቸውን
“ሀብታቸውን”

ኃፍረትሽን ታሳያለሽ
“ታፍሪአለሽ” ወይም “ውርደትሽን ትሸከሚያለሽ”

ትዋረጃለሽ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አዋርድሻለሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

መጽናናት ትሆኛቸዋለሽ
“መጽናናት” የሚለው ስም ከግሣዊ ሐረግ ጋር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ሰዶምና ሰማርያን ታጽናኚአለሽ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

እህትሽ ሰዶምና ሴት ልጆቿ ወደ ቀድሞው ሁኔታቸው ይመለሳሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እህትሽን ሰዶምን እና ሴት ልጆቿን ወደ ቀድሞ ሁኔታቸው እመልሳለሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ሰማርያና ሴቶች ልጆቿ ወደ ቀድሞው ይዞታቸው ይመለሳሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እህትሽን ሰዶምን እና ሴት ልጆቿን ወደ ቀድሞ ይዞታቸው እመልሳለሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ይዞታ
x

Ezekiel 16:56

እህትሽ ሰዶም እንኳን በአፍሽ አልተጠራችም
እዚህ ጋ “አፍ” የሚለው ቃል የሚወክለው ተናጋሪውን ሰው ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የእህትሽን የሰዶምን ስም እንኳን አልጠራሽም” (Synecdoche እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ኃጢአተኝነትሽ ከመገለጡ በፊት
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ኃጢአተኝነትሽን ከመግለጥሽ በፊት” ወይም “ኃጢአተኝነትሽን ከመግለጤ በፊት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

አንቺ መሣለቂያ ነሽ
ይህ ሰዎች ስለ አንዳች ነገር በመጥፎ የሚናገሩላትን ኢየሩሳሌምን ያመለክታል።

ለኤዶም ሴቶች ልጆችና ለፍልስጥኤም ሴቶች ልጆች በሙሉ
እዚህ ጋ የኤዶምና የፍልስጥኤማውያን ሴቶች ልጆች የሆኑ ይመስል እግዚአብሔር የሚናገረው ስለ ኤዶምና ፍልስጥኤም ነው። ከተሞቹ በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላሉ። አ.ት፡ “ኤዶማውያን እና የፍልስጥኤም ሰዎች በሙሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መናቅ
በጣም መጥላት

ይህ የጌታ እግዚአብሔር ቃል ነው
እግዚአብሔር የንግግሩን እርግጠኝነት ለመግለጽ የራሱን ስም በመጥራት ይናገራል። ይህንን በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ጌታ እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን ነው” ወይም “እኔ፣ ጌታ እግዚአብሔር የተናገርኩት ይህንን ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ezekiel 16:59

ቃል ኪዳንን በማፍረስ መሐላሽን ንቀሻል
ኢየሩሳሌም ከእግዚአብሔር ጋር ላደረገችው መሐላ ግድ የለሽነቷን በማሳየት ከእርሱ ጋር የነበራትን የጋብቻ ቃል ኪዳን አፍርሳለች። አ.ት፡ “ከእኔ ጋር የገባሽውን ቃል ኪዳን በማፍረስ የማልሽልኝን መሐላ ንቀሻል”

Ezekiel 16:60

ልብ በይ
የዚህ የአነጋገር ዘይቤ ትርጉም ማስታወስ ነው። አ.ት፡ “አስታውሽ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በወጣትነትሽ ቀናት ያደረግሁትን
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ወጣት በነበርሽበት ጊዜ ከአንቺ ጋር ያደረግሁትን” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 16:62

እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ታውቃላችሁ
እግዚአብሔር ሰዎች እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን ያውቃሉ ብሎ በሚናገርበት ጊዜ እርሱ ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለው ብቸኛው እውነተኛ አምላክ መሆኑን ሰዎች ያውቃሉ ማለቱ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 6፡7 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እውነተኛው አምላክ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ይረዳሉ” ወይም “ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለኝ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ይገነዘባሉ”

ሁሉንም ነገር አስታውሺ
የዚህ የአነጋገር ዘይቤ ትርጉም ማስታወስ ማለት ነው። አ.ት፡ “ሁሉንም ነገር አስታውሺ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ከእፍረትሽ የተነሣ ከእንግዲህ ወዲህ አፍሽን አትከፍቺም
ይህ ማለት ኢየሩሳሌም ለመናገር እጅግ ታፍራለች።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 17

1 የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፣ **2** የሰው ልጅ ሆይ፥ በእንቈቅልሽ አጫውት እንዲህም ብለህ ለእስራኤል ቤት ምሳሌ ንገራቸው ፥ **3** ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ታላቅ ክንፍ ረጅምም ማርገብገቢያ ያለው ላባም የተሞላ፥ መልከ ዝንጉርጉር ታላቅ ንስር ወደ ሊባኖስ መጣ፥ የዛፍ ቅርንጫፍን ጫፍ ወሰደ። **4** የቅርንጫፉን ጫፍ ወደ ከነዓንም ምድር ወሰደው በነጋዶችም ከተማ ተከለው። **5** ከዚያም ምድር ዘር ወሰደ በፍሬያማ እርሻም ተከለው። በብዙም ውኃ አጠገብ እንደ አኻያ ዛፍ አኖረው። **6** በበቀለም ጊዜ ቁመቱ ያጠረ አረጉም ወደ እርሱ የሚመለስ ሥሩም በበታቹ የነበረ ሰፊ ወይን ሆነ። **7** ታላቅ ክንፍና ብዙ ላባም ያለው ሌላ ታላቅ ንስር ነበረ። እነሆም፥ ውሀ ያጠጣው ዘንድ ይህ ወይን ሥሩን ወደ እርሱ አዘነበለ አረጉንም ከተተከለበት ከመደቡ ወደ እርሱ ሰደደ። **8** አረግም ያወጣ ፍሬም ያፈራ የከበረም ወይን እንዲሆን በመልካም ላይ በብዙም ውኃ አጠገብ ተተክሎ ነበር። **9** ለህዝቡም እንዲህ በል፥ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በውኑ ይከናወንለት ይሆንን? ይደርቅስ ዘንድ፥ አዲስ የበቀለውስ ቅጠሉ ይጠወልግ ዘንድ ሥሩን አይነቅለውምን? ፍሬውንስ አይለቅመውምን? የትኛውም ጠንካራ ክንድ ወይም ብዙ ህዝብ ሥሩን ሊነቅል አይችልም። **10** እነሆ፥ ከተተከል በኋላስ ይከናወንለት ይሆንን? የምሥራቅ ነፋስ ባገኘው ጊዜ ፈጽሞ አይደርቅምን? በተተከለበት መደብ ላይ ይደርቃል። **11** የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ። **12** "ለዓመፀኛ ቤት፥ 'የዚህ ነገር ትርጓሜ ምን እንደ ሆነ አታውቁምን? እነሆ፥ የባቢሎን ንጉሥ ወደ ኢየሩሳሌም መጣ፥ ንጉሥዋንና መኳንንቶችዋንም ማረከ፥ ወደ እርሱም ወደ ባቢሎን ወሰዳቸው። **13** ከንጉሳዊያን ዘር የሆነውን ወስዶ ቃል ኪዳን ከእርሱ ጋር አደረገ አማለውም። የምድሪቱንም ኃያላን ወሰደ **14** ይኸውም ቃል ኪዳኑን በመጠበቅ እንድትጸና እንጂ መንግሥቱ እንድትዋረድና ከፍ እንዳትል ነው። **15** የኢየሩሳሌም ንጉስ ግን በእርሱ ላይ ሸፈተ ፈረሶችንና ብዙንም ሕዝብ ይሰጡት ዘንድ መልእክተኞችን ወደ ግብጽ ላከ። በውኑ ይከናወንለት ይሆንን? ይህንስ ያደረገ ያመልጣልን? ቃል ኪዳንንስ አፍርሶ ያመልጣልን? **16** በህያውነቴ እምላለሁ! ባነገሠውና መሐላውን በናቀበቱ፥ ቃል ኪዳኑንም ባፈረሰበቱ ንጉሥ ምድር ይሞታል። በባቢሎን መካከል ይሞታል፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፦ **17** የባቢሎን ሠራዊት ብዙዎችን ነፍሳት ለማስወገድ አፈርን በደለደሉ ምሽግም በሠሩ ጊዜ፥ ፈርዖን ከብዙ ሠራዊቱና ከታላቁ ጉባኤው ጋር የኢየሩሳሌምን ንጉሥ በሰልፍ አይረዳውም። **18** ይህም የሚሆነው መሐላውን ንቆ ቃል ኪዳኑንን በማፍረሱ ነው። ለቃል ኪዳን እጁን ዘርጋ፥ ነገር ግን እነዚህን ነገሮች አደረገ። ስለዚህ አያመልጥም። **19** ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በህያውነቴ እምላለሁ የናቀው መሐላዬን ያፈረሰበ ቃል ኪዳኔን አይደለምን? ስለዚህ ቅጣትን በርሱ ላይ አመጣለሁ! **20** መረቤንም በእርሱ ላይ አዘረጋለሁ በማጥመጃ መረቤም ይያዛል። ወደ ባቢሎንም አመጣዋለሁ በእኔም ላይ ስላደረገው ዓመፅ በዚያ በእርሱ ላይ እፈርዳለሁ። **21** ጭፍሮቹም ሁሉ በሰይፍ ይወድቃሉ፥ የቀሩትም ሁሉ በየአቅጣጫው ይበታተናሉ። እኔም እግዚአብሔር እንደሆንኩ ይህም እንደሚሆን እንደ ተናገርሁ ታውቃላችሁ!' **22** ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፥ 'እኔ እራሴ ከረጅሙ ዝግባ ጫፍ ላይ ቀንበጥን እወስዳለሁ ከለምለም ቅርንጫፎቹ አርቄ እተክለዋለሁ። ቀንጥቤ እኔ እራሴ በረጅምና በታላቅ ተራራ ላይ እተክለዋለሁ! **23** ከፍ ባለው በእስራኤል ተራራ ላይ እተክለዋለሁ፥ ቅርንጫፎችም ያወጣል ፍሬም ያፈራል የከበረም ዝግባ ይሆናል በበታቹም በክንፍ የሚበርሩ ወፎች ሁሉ ያርፋሉ፥ በቅርንጫፎቹም ጥላ ውስጥ ጎጆአቸውን ይሰራሉ። **24** በዚያን ጊዜ የዱር ዛፎች ሁሉ እኔ እግዚአብሔር እንደሆንኩ ያውቃሉ። ረጅሙን ዛፍ ዝቅ አደርጋለሁ፥ አጭሩንም ዛፍ ከፍ አድርጋለሁ! የለመለመውንም ዛፍ አደርቃለሁ፥ የደረቀውንም ዛፍ አለመልማለሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ይህ እንደሚሆን ተናግሬአለሁ እኔም አድርጌዋለሁ።

Ezekiel 17:1

የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የሰው ልጅ
“የሰብዓዊ ፍጡር ልጅ” ወይም “ከሰው የተወለደ ልጅ”። ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን አፅንኦት ለመስጠት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ በማለት ይጠራዋል። እግዚአብሔር ዘላለማዊና ኃያል ነው፣ ሰዎች ግን አይደሉም። አ.ት፡ “ሟች ሰው” ወይም “ሰው”

ዕንቆቅልሽ አቅርብላቸው፣ በምሳሌም ተናገር
“ስለ እርሱ እንዲያስቡ ዕንቆቅልሽን ስጣቸው” ወይም “ይህንን ታሪክ እንደ ማብራሪያ ንገራቸው”

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በላባ የተሞሉ ረጃጅም ክንፎች
“የክንፎቹ ጫፎች ረጃጅምና በላባ የተሞሉ ነበሩ”። “ክንፍ” የሚለው ቃል በዚህ ስፍራ ትርጉሙ የክንፎቹን ውጫዊ ጫፍ ማለት ነው።

ዥንጉርጉር ነበር
የንስሩ ላባዎች ብዙ የተለያዩ ቀለማት ነበሩት።

እርሱ የቅርንጫፉን ቀንበጥ ሰበረ
“እርሱ የዛፉን የላይኛውን ጫፍ ሰበረ”

ወሰዳቸው
“የዛፉን ጫፍ ወሰደ” ወይም “ጫፎቹን ወሰዳቸው”

እርሱን በነጋዴዎች ከተማ ተከለው
“እርሱን ብዙ ነጋዴዎች በነበሩባት ከተማ ተከለው”። ነጋዴ ሸቀጦችን የሚሸጥ ሰው ነው።

Ezekiel 17:5

ደግሞም እርሱ ወሰደ
“እርሱ” የሚለው ቃል በምሳሌው ውስጥ ንስሩ ነው።

ለም ዐፈር
“ጥሩ መሬት”

ብዙ ውሃ ባለበት አጠገብ አኖረው
“ንስሩ ዘሩን ብዙ ውሃ ባለበት ቦታ ላይ ተከለው”

እንደ ውሃ ዳር ዛፍ . . . ተከለው
የውሃ ዳር ዛፍ የሚበቅለው ብዙ ውሃ ባለበት ስፍራ ነው። ንስሩ ዘሩን እንደ ውሃ ዳር ዛፍ ከተከለው ይህ ማለት ብዙ ውሃ ባለበት ቦታ ላይ ተክሎታል ማለት ነው። አ.ት፡ “አንድ ሰው የውሃ ዳርን ዛፍ በውሃ አጠገብ እንደሚተክል ዘሩን ተክሎታል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከዚያም አነነቆለ
“ከዚያም ዘሩ ወደ ተክልነት ማደግ ጀመረ”

የወይኑ ሐረግ በምድር ላይ ተዘረጋ
“በምድር ላይ የሚስፋፋ የወይን ሐረግ”

ቅርንጫፎቹ ወደ እርሱ ተመለሱ
የወይኑ ቅርንጫፎች ወደ ንስሩ አቅጣጫ ተመለሱ። ይህ ማለት ወደ ላይ ወደ ሰማይ ማደግ ጀመሩ።

ሥሮቹ ከበታቹ አደጉ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ሥሮቹ ከበታቹ ወዳለው መሬት ውስጥ አደጉ” ወይም “የወይን ሐረጉ ሥሮች ከንስሩ በታች አደጉ”።

ከዚያም የወይን ተክል ሆነ
“የወይን ተክል የሚያድገው እንደዚህ ነው”

ቅርንጫፎችን አወጣ፣ ለምለም ቅጠሎችንም አስረዘመ
“ቅርንጫፎች አሳደገ፣ ለምለም ቅጠሎቹንም አስፋፋ”

Ezekiel 17:7

ሌላ ታላቅ ንስር
“ሌላ ግዙፍ ንስር”

እነሆ
እዚህ ጋ፣ “እነሆ” የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚመጣው አስገራሚ መረጃ ትኩረት እንድንሰጥ ያነቃናል።

ይህ የወይን ተክል ሥሮቹን ወደ ንስሩ መለሰ
እግዚአብሔር የሚናገረው እንደ ሰው ማድረግ ይችል ይመስል አስፈላጊውን ምግብ ከእርሱ ያገኝ ዘንድ ሥሮቹን ሆን ብሎ ወደ ሌላኛው ንስር ስለሚያዞረው ስለ ወይን ተክል ነው። (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

ውሃ ያጠጡት ዘንድ ተተክሎ ከነበረበት ስፍራ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ውሃ ያገኝ ዘንድ የመጀመሪያው ንስር ተክሎ ከነበረበት ስፍራ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ተተክሎ ነበር
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የወይኑን ተክል የመጀመሪያው ንስር ተክሎት ነበር” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 17:9

ይሳካለት ይሆን?
አሉታዊው ምላሽ ላይ አጽንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ይህንን ዋነኛ ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “አይሳካለትም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

እንዲጠወልግና ቀንበጡ ሁሉ እንዲደርቅ ከሥሩ አይነቀለም? ፍሬውስ አይረግፍም?
በወይኑ ተክል ላይ በእርግጠኝነት እንደሚፈረድበት አጽንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ይጠይቃል። ጥያቄው እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል፤ ደግሞም በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አንድ ሰው ሥሮቹን ይነቅላል፣ የቅጠሎቹ ዕድገት በሙሉ እንዲጠወልግም ፍሬዎቹን ይቀጥፋል” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እርሱን ለመንቀል ብርቱ ክንድ ወይም ብዙ ሰዎች አያስፈልጉም
“ብርቱ ክንድ” የሚለው ሐረግ ብርቱ ሰውን ይወክላል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እርሱን ለመንቀል ብርቱ ሰው ወይም ብዙ ሰዎች አያስፈልጉም” (Synecdoche እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እነሆ
“ተመልከቱ” ወይም “ስሙ” ወይም “የምነግራችሁን ልብ በሉ”

ያድግ ይሆን?
አሉታዊው ምላሽ ላይ አጽንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ይህንን ዋነኛ ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ ጥያቄ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “አያድግም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

የምስራቅ ንፋስ በሚነካው ጊዜ እርሱ አይጠወልግም?
ይህ በእርግጥ እንደሚሆን አጽንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይቻላል። አ.ት፡ “የምስራቅ ንፋስ በሚነካው ጊዜ ይጠወልጋል”። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

የምስራቅ ንፋስ በሚነካው ጊዜ
“የምስራቅ ንፋስ በሚነፍስበት ጊዜ”

Ezekiel 17:11

የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንዳች ነገር መናገሩን ለማስታወቅ ጥቅም ላይ የዋለ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እግዚአብሔር እነዚህን ቃላት ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

አመጸኛው ቤት
ይህ በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 2:5 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “አመጸኛ ሕዝብ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የእነዚህን ነገሮች ትርጉም አታውቁም?
እግዚአብሔር መልሱን ለመስጠት ይህንን መሠረታዊ ጥያቄ ይጠይቃል። ጥያቄው እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “የእነዚህ ነገሮች ትርጉም ይህ ነው”። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

እነሆ
“ተመልከቱ” ወይም “ስሙ” ወይም “የምነግራችሁን ልብ በሉ”

ንጉሥዋ እና ልዑላኖቿ
“የእርሷ” የሚለው ቃል ኢየሩሳሌምን ያመለክታል።

Ezekiel 17:13

በመሐላ ቃል አስገባው
“መሐላ እንዲምል አደረገው”

መንግሥቱ እንዲዋረድና እንዳያንሰራራ
ያነሰና ደካማ መንግሥት እንደ ተዋረደ፣ ታላቅና ኃያል የሆነው ራሱን እንዳንሰራራ ተነግሯል። አ.ት፡ “መንግሥቱ ታናሽ ሆኖ እንዲቀርና ታላቅ እንዳይሆን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ምድሪቱ ትድናለች
እዚህ ጋ “ምድር” የሚለው ቃል የይሁዳን መንግሥትና በእርሱ የሚኖረውን ሕዝብ ይወክላል። አ.ት፡ “መንግሥቱ መኖሩን ይቀጥላል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ezekiel 17:15

ይሳካለት ይሆን?
አሉታዊው ምላሽ ላይ አጽንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ይህንን ዋነኛ ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “በእርግጠኝነት አይሳካለትም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

እነዚህን ነገሮች የሚያደርግ እርሱ ያመልጥ ይሆን?
አሉታዊው ምላሽ ላይ አጽንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ይህንን ዋነኛ ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እነዚህን ነገሮች የሚያደርግ እርሱ አያመልጥም”። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ቃል ኪዳኑን ቢያፈርስ፣ እርሱ ያመልጣል?
አሉታዊው ምላሽ ላይ አጽንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ይህንን ዋነኛ ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ቃል ኪዳኑን ቢያፈርስ ፈጽሞ አያመልጥም”። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ሕያው እንደ መሆኔ
“ሕያው መሆኔ እርግጥ የመሆኑን ያህል”። እግዚአብሔር ቀጥሎ የሚናገረው የተረጋገጠ እውነት መሆኑን ለማሳየት ይህንን አገላለጽ ይጠቀማል። ይህ ጽኑ ተስፋ የመስጫ መንገድ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ጽኑ መሐላ አደርጋለሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ይህ የጌታ እግዚአብሔር ቃል ነው
እግዚአብሔር የንግግሩን እርግጠኝነት ለመግለጽ የራሱን ስም በመጥራት ይናገራል። ይህንን በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ጌታ እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን ነው” ወይም “እኔ፣ ጌታ እግዚአብሔር የተናገርኩት ይህንን ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

እርሱን ያነገሠችው የንጉሡ ምድር፣ መሐላውን ያቃለለ ንጉሥ
“እርሱን በይሁዳ ላይ ያነገሠው የባቢሎን ንጉሥ ምድር፣ መሐላውን ያቃለለው የባቢሎን ንጉሥ”

Ezekiel 17:17

ብርቱ ሰራዊቱና ታላቅ አጀቡ
የእነዚህ ሁለት ሐረጎች መሠረታዊ ትርጉም አንድ ሲሆን የፈርዖን ሰራዊት ምን ያህል ብዙና ጠንካራ እንደ ሆነ አጽንዖት ይሰጣል።

እርሱን አይረዳውም
እዚህ ጋ “እርሱን” የሚለው ቃል የይሁዳን ንጉሥ ያመለክታል።

ቅጥሩን መመሸግ
ይህ የሚያመለክተው መሰላሎች ያሉትን ግምብ ሲሆን ግምቡ ላይ በማስደገፍ ወታደሮች በእርሱ ላይ በመውጣት ወደ ከተማይቱ ለመግባት ያስችላቸዋል።

የብዙዎችን ሕይወት ለመቁረጥ
“ብዙ ሰዎችን ለመግደል”

እነሆ፣ እጁን ዘረጋ
“ከዚያ እንኳን የከፋውን ነገር አደረገ፤ እጁን ዘረጋ”

ቃል ኪዳን ለማድረግ እጆቹን ዘረጋ
ይህ የሚያመለክተው የወዳጅነትና የስምምነት ምልክት እንዲሆን የሌላውን ሰው እጅ መያዝን ነው። እዚህ ጋ ቃሉ የሚወክለው ከባቢሎን ንጉሥ ጋር ያደረገውን የቃል ኪዳን መሐላ ነው። (See: Symbolic Action)

Ezekiel 17:19

የናቀው የእኔን መሐላ፣ ያፈረሰውም የእኔን ቃል ኪዳን አይደለም?
አዎንታዊው ምላሽ ላይ አጽንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ይህንን ዋነኛ ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “የኢየሩሳሌም ንግሥ የናቀው የእኔን መሐላ፣ ያፈረሰውም የእኔን ቃል ኪዳን ነበር”። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ቅጣቱን በራሱ ላይ አመጣለሁ
“በራሱ ላይ አመጣለሁ” የሚለው የአነጋገር ዘይቤ ትርጉም ይህንን ቅጣት ይቀበላል ማለት ነው። ይህንን የአነጋገር ዘይቤ በሕዝቅኤል 11፡21 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የቅጣቱን መከራ እንዲቀበል አደርገዋለሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በእርሱ ላይ መረቤን እዘረጋለሁ፣ በማጥመጃ መረቤም ይያዛል
እግዚአብሔር ንጉሠን በመረብ የሚያጠምደው በሚመስልበት ሁኔታ የጠላት ሰራዊት ንጉሠን እንዲይዙት እንደሚያስችላቸው ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በማጥመጃ መረቤ ይያዛል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “በማጥመጃ መረቤ እይዘዋለሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ጥገኞቹ ሁሉ . . . ሰራዊት በሰይፍ ይወድቃል
“መውደቅ” የሚለው ቃል “መሞት” ለሚለው የለዘበ ቃል ነው። እዚህ ጋ “ሰይፍ” የሚለው ቃል በሰይፎቻቸው ሰዎችን የሚገድሉ ወታደሮችን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ወታደሮች ጠገኞቹን ሁሉ . . . ሰራዊቱን ይገድሏቸዋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የተረፉትም በየአቅጣጫው ይበተናሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በሕይወት የተረፉት በየአቅጣጫው ይሸሻሉ” ወይም “በሕይወት የሚተርፉትን የጠላት ወታደሮች በየአቅጣጫው ይበትኗቸዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ታውቃላችሁ
እግዚአብሔር ሰዎች እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን ያውቃሉ ብሎ በሚናገርበት ጊዜ እርሱ ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለው ብቸኛው እውነተኛ አምላክ መሆኑን ሰዎች ያውቃሉ ማለቱ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 6፡7 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እውነተኛው አምላክ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ትረዳላችሁ” ወይም “ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለኝ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ትገነዘባላችሁ”

Ezekiel 17:22

ቅርንጫፎችን ያወጣል
“አዳዲስ ቅርንጫፎችን ያበቅላል”

Ezekiel 17:24

ከዚያም በሜዳ ላይ ያሉ ዛፎች ሁሉ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ያውቃሉ
እንደ ሰዎች እርሱ ማወቅ ይችሉ ይመስል እግዚአብሔር የሚናገረው ስለ ዛፎች ነው። ዛፎች የሚወክሉት በእነርሱ ውስጥ የሚኖሩትን ሀገራትንና ሕዝቦችን ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከፍ ያሉትን ዛፎች ዝቅ አደርጋቸዋለሁ፣ ዝቅ ያሉትንም ዛፎች ከፍ አደርጋቸዋለሁ
“ረጃጅሞቹን ዛፎች እቆርጣቸዋለሁ፣ ትንንሾቹ ዛፎች እንዲያድጉ አደርጋቸዋለሁ”

መጠውለግ
ተክሎች በሚደርቁበትና በሚሞቱበት ጊዜ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 18

1 የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ። 2 "ስለ እስራኤል ምድር፥ 'አባቶች መራራ የወይን ፍሬ በሉ፥ የልጆችም ጥርሶች ጠረሱ' ብላችሁ
የምትመስሉት ምሳሌ ምንድር ነው? 3 በህያውነቴ እምላለሁ እንግዲህ ወዲህ ይህን ምሳሌ በእስራኤል የምትናገሩበት ሁኔታ አይኖርም ይላል ጌታ
እግዚአብሔር። 4 እነሆ፥ ነፍስ ሁሉ የእኔ ነው! የአባት ነፍስ የእኔ እንደ ሆነች የልጅም ነፍስ የእኔ ናት! ኃጢአት የሚሰራ ሰው ይሞታል! 5 ሰውም ጻድቅ ቢሆን
ፍርድንና ቅን ነገርን ቢያደርግ፥ 6 በተራራም ላይ ባሉ የጣዖት አምልኮ ስፍራ ባይበላ ዓይኞቹንም ወደ እስራኤል ቤት ጣዖታት ባያነሣ የባልንጀራውንም ሚስት
ባያረክስ በወር አበባ ላይ ወዳለች ሴት ባይቀርብ 7 ሰውንም ባያስጨንቅ ለባለ ዕዳም መያዣውን ቢመልስ የሌባ ተቀባይ ባይሆን ከእንጀራውም ለተራበ ቢሰጥ
የተራቈተውንም ቢያለብስ 8 በአራጣ ባያበድር፥ የማይገባ ትርፍን ባይወስድ፥ ፍትህን ቢያደርግ፥ በሰውና በሰው መካከልም መተማመንን ቢፈጥር 9 በትእዛዜም
ቢሄድ፥ እውነትንም ለማድረግ ፍርዴን ቢጠብቅ፥ ይህ ሰው ጻድቅ ነው፤ ፈጽሞ በሕይወት ይኖራል! ይላል ጌታ እግዚአብሔር፡- 10 እርሱም ቀማኛና ደም አፍሳሽ
ልጅ ከዚህም ሁሉ አንዳቸውን የሚያደርገውን ቢወልድ፥ 11 እርሱም ጻድቅ አባቱ የሠራውን ሁሉ ባይሠራ በተራራምላይ ባሉ የጣዖት አምልኮ ስፍራ ላይ ቢበላ
የባልንጀራውንም ሚስት ቢያረክስ፥ 12 ድሀውንና ችግረኛውንም ቢያስጨንቅ ቢቀማም መያዣውንም ባይመልስ ዓይኖቹንም ወደ ጣዖታት ቢያነሣ ወይም ርኩስን
ነገር ቢያደርግ፥ 13 በአራጣ ቢያበድር፥ የማይገባ ትርፍ ቢወስድ፥ በውኑ እርሱ በሕይወት ይኖራልን? በሕይወት አይኖርም! ይህን ርኩሰት ሁሉ አድርጎአልና
ፈጽሞ ይሞታል ደሙም በላዩ ላይ ይሆናል። 14 እነሆም፥ ልጅ ቢወልድ፥ እርሱም አባቱ የሠራውን ኃጢአት አይቶ ቢፈራ እንዲህም ባይሠራ፥ 15 በተራራ ባሉ
የጣዖት አምልኮ ስፍራዎች ላይ ባይበላ ዓይኖቹንም ወደ እስራኤል ቤት ጣዖታት ባያነሣ የባልንጀራውንም ሚስት ባያረክስ፥ 16 ሰውንም ባያስጨንቅ መያዣውን
ባይወስድ ባይቀማም ከእንጀራውም ለተራበ ቢሰጥ ለተራቈተውም ልብስን ቢያለብስ፥ 17 እጁንም ድሀን ከመበደል ቢመልስ፥ በአራጣ ባያበድር የማይገባ
ትርፍንም ባይወስድ፤ ፍርዴንም ቢያደርግ በትእዛዜም ቢሄድ፥ እርሱ ፈጽሞ በሕይወት ይኖራል እንጂ በአባቱ ኃጢአት አይሞትም። 18 አባቱ ግን ፈጽሞ
በድሎአልና፥ ወንድሙንም ዘርፏልና፥ በሕዝቡም መካከል ክፉን ነገር አድርጎአልና እነሆ፥ እርሱ በበደሉ ይሞታል። 19 እናንተ ግን፥ 'ልጅ የአባቱን ኃጢአት ስለ
ምን አይሸከምም? ትላላችሁ። ልጅ ፍርድንና ቅን ነገርን ባደረገ ትእዛዜንም ሁሉ በጠበቀና ባደረገ ጊዜ ፈጽሞ በሕይወት ይኖራል! 20 ኃጢአትን ያደረገ ሰው
ይሞታል። ልጅ የአባቱን ኃጢአት አይሸከምም፥ አባትም የልጁን ኃጢአት አይሸከምም። የጻድቁ ጽድቅ በራሱ ላይ ይሆናል፥ የኃጢአተኛውም ኃጢአት በራሱ ላይ
ይሆናል። 21 ኃጢአተኛውም ካደረጋት ኃጢአት ሁሉ ቢመለስ ትእዛዜንም ሁሉ ቢጠብቅ ፍርድንና ቅን ነገርንም ቢያደርግ ፈጽሞ በሕይወት ይኖራል እንጂ
አይሞትም። 22 የበደለው በደል ሁሉ አይታሰብበትም በሠራው ጽድቅ በሕይወት ይኖራል። 23 በውኑ ከመንገዱስ ቢመለስና በሕይወት ቢኖር እንጂ
በኃጢአተኛ ሞት እደሰታለሁን? ይላል ጌታ እግዚአብሔር 24 ጻድቁ ግን ከጽድቁ ቢመለስ ኃጢአትንም ቢሠራ ኃጢአተኛውም እንደሚያደርገው ርኩሰት ሁሉ
ቢያደርግ፥ በሕይወት ይኖራልን? የሠራት ጽድቅ ሁሉ አትታሰብለትም ባደረገው ዓመፅና በሠራት ኃጢአት በዚያች ይሞታል። 25 እናንተ ግን፥ 'የጌታ መንገድ
የቀናች አይደለችም' ትላላችሁ። የእስራኤል ቤት ሆይ፥ እንግዲህ ስሙ! በውኑ መንገዴ የቀናች አይደለችምን? ይልቅስ የእናንተ መንገድ ያልቀናች
አይደለችምን? 26 ጻድቁ ከጽድቁ ቢመለስ፥ ኃጢአትንም በሠራ ጊዜ፥ በዚያም ቢሞት፥ እርሱ ባደረገው በደል ይሞታል። 27 ኃጢአተኛውም ከሠራው ኃጢአት
ቢመለስ ፍርድንና ቅን ነገርንም ቢያደርግ ነፍሱን ያድናል። 28 አስቦ ከሠራው በደል ሁሉ ተመልሶአልና ፈጽሞ በሕይወት ይኖራል እንጂ አይሞትም። 29 ነገር
ግን የእስራኤል ቤት፥ 'የጌታ መንገድ የቀናች አይደለችም!' ይላል። የእስራኤል ቤት ሆይ፥ መንገዴ የቀናች ያልሆነው እንዴት ነው? የእናንተ መንገድስ የቀናች
የሆነችው እንዴት ነው? 30 የእስራኤል ቤት ሆይ፥ ስለዚህ በመካከላችሁ በእያንዳንዱ ሰው እንደ መንገዱ እፈርድበታለሁ! ይላል ጌታ እግዚአብሔር። ንስሐ
ግቡ ኃጢአትም ዕንቅፋት እንዳይሆንባችሁ ከኃጢአታችሁ ሁሉ ተመለሱ። 31 የበደላችሁትን በደል ሁሉ ከእናንተ ጣሉ አዲስ ልብና አዲስ መንፈስም ለእናንተ
አድርጉ። የእስራኤል ቤት ሆይ፥ ስለ ምን ትሞታላችሁ? 32 የምዋቹን ሞት አልፈቅድምና፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር ስለዚህ ተመለሱና በሕይወት ኑሩ።

Ezekiel 18:1

የእግዚአብሔር ቃል ዳግመኛ ወደ እኔ መጣ
“የእግዚአብሔር ቃል መጣ” የሚለው ሐረግ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ ስለ አንድ ነገር የነገራቸውን ለማሳወቅ ጥቅም ላይ የዋለ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “እንደገና እግዚአብሔር ተናገረኝ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

‘አባቶች ጎምዛዛ የወይን ፍሬ በሉ፣ የልጆችም ጥርስ ደነዘ’. . . ይህንን ምሳሌ የምትጠቀሙ ምን ማለታችሁ ነው?
ሕዝቅኤል አስቀድሞ ስለሚያውቀው አንድ ነገር ለማስታወስ እግዚአብሔር ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ይጠይቃል። ጥያቄው ምሳሌውን ለሚጠቀሙ ሰዎች ተግሳጽ ነው። አ.ት፡ “በእስራኤል ምድር የሚኖሩ ሰዎች ይህ ምሳሌ አላቸው፣ . . . ‘አባቶች ጎምዛዛ የወይን ፍሬ በሉ፣ የልጆችም ጥርስ ደነዘ’”።(ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ይህንን ምሳሌ የምትጠቀሙ ምን ማለታችሁ ነው?
እዚህ ጋ “እናንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው።

የእስራኤል ምድር
ይህ የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አባቶች ጎምዛዛ የወይን ፍሬ በሉ፣ የልጆችም ጥርስ ደነዘ
የዚህ ምሳሌ ትርጉም ልጆች የሚለማመዱት የአባቶቻቸውን የሥራ ውጤ ነው የሚል ነው። (ምሳሌዎች የሚለውን ተመልከት)

የልጆችም ጥርስ ደነዘ
“ጥርሶች ደነዙ” የሚለው የአነጋገር ዘይቤ አንድ ሰው ያልበሰለውን ወይም የሚጎመዝዘውን ፍሬ ሲበላ አፉ ላይ የሚሰማውን የመጎምዘዝ ስሜት ያመለክታል። አ.ት፡ “ልጆች አፋቸው ውስጥ ጎምዛዛ ጣዕም ተሰማቸው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 18:3

ሕያው እንደ መሆኔ
“ሕያው መሆኔ እርግጥ የመሆኑን ያህል”። እግዚአብሔር ቀጥሎ የሚናገረው የተረጋገጠ እውነት መሆኑን ለማሳየት ይህንን አገላለጽ ይጠቀማል። ይህ ጽኑ ተስፋ የመስጫ መንገድ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ጽኑ መሐላ አደርጋለሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ይህ የጌታ እግዚአብሔር ቃል ነው
እግዚአብሔር የንግግሩን እርግጠኝነት ለመግለጽ የራሱን ስም በመጥራት ይናገራል። ይህንን በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ጌታ እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን ነው” ወይም “እኔ፣

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጌታ እግዚአብሔር የተናገርኩት ይህንን ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

እነሆ!
እዚህ ጋ፣ “እነሆ” የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚመጣው አስገራሚ መረጃ ትኩረት እንድንሰጥ ያነቃናል።

ኃጢአትን የምትሠራ ነፍስ
እዚህ ጋ “ነፍስ” የሚለው ቃል የሚወክለው ሰውን ነው። አ.ት፡ “ኃጢአትን የሚሠራው ሰው”

Ezekiel 18:5

በተራሮች ላይ አይበላም
ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ በተራሮች ላይ የአሕዛብን አማልክት ያመልኩና መሥዋዕትም ያቀርቡላቸው ነበር። እንዲህ ያለው ሰው እነዚህን በመሳሰሉ የአሕዛብ የአምልኮ ሥርዓቶች ላይ እንዳልተሳተፈ ያመለክታል።

ዓይኖቹን ወደ ጣዖታት አያነሣም
“ዓይኖችን ማንሣት” የሚለው የአነጋገር ዘይቤ ወደ አንድ ነገር መመልከትን ያመለክታል። ወደ ጣዖታት የማመልከቱ አኳኋን የሚወክለው ጣዖታትን ማምለክን ወይም ወደ እነርሱ መጸለይን ነው። አ.ት፡ “ጣዖታትን ማምለክ” ወይም “ወደ ጣዖታት መጸለይ”

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በወር አበባዋ ወቅት ወደ ሴት ቀርቧል
ከእርሷ ጋር ለመተኛት ወደ ሴቲቱ አለመቅረቡ ግልጽ አይደለም። አ.ት፡ “በወር አበባዋ ወቅት ከእርሷ ጋር ለመተኛት ወደ ሴት ቀርቧል”

Ezekiel 18:7

በመያዣነት የወሰደውን ለተበዳሪው ይመልስለታል
“ተበዳሪው ለብድሩ በመያዣነት የሰጠውን ዕቃ ለተበዳሪው ይመልስለታል”

ወለድ
ይህ ቃል ተበዳሪው ለተበደረው ገንዘብ የሚከፍለውን ገንዘብ ያመለክታል። ይሁን እንጂ አንዳንድ አዳዲስ ትርጉሞች በዚህ ምንባብ ያለውን “የትኛውም ወለድ” የሚለውን “እጅግ የበዛ ወለድ” ብለው ይተረጉሙታል።

በሰዎች መካከል ታማኝነትን ይፈጥራል
ይህ ማለት በሰዎች መካከል የሚነሡትን አለመግባባቶች በፍትሐዊነት ይዳኛል።

ያ ሰው በሥርዓቶቼ ይሄዳል
ሥርዓቶቹ ሰውየው የሚሄድበት መንገድ የሆነ ይመስል እግዚአብሔር ሥርዓቶቹን ስለሚታዘዝ ሰው ይናገራል። አ.ት፡ “ያ ሰው ሥርዓቶቼን ይታዘዛል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 18:10

ደምን የሚያፈስ
ይህ ሐረግ በየትኛውም መልክ የሚፈጸም ግድያን ይወክላል። አ.ት፡ “የሚገድል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከእነዚህ ነገሮች የትኛውንም
ይህ እግዚአብሔር በሕዝቅኤል 18፡5 መጀመሪያ ላይ የጠቀሰውን ኃጢአታዊ ተግባር ያመለክታል።

በተራሮች ላይ ይበላል
ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ በተራሮች ላይ የአሕዛብን አማልክት ያመልኩና መሥዋዕትም ያቀርቡላቸው ነበር። እንዲህ ያለው ሰው እነዚህን በመሳሰሉ የአሕዛብ የአምልኮ ሥርዓቶች ላይ እንደተሳተፈ ያመለክታል። ተመሳሳዩን ሐረግ በሕዝቅኤል 18፡5 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “በተራሮቹ ላይ ለጣዖታት የተሰዋውን ሥጋ ይበላል”

Ezekiel 18:12

ድኻውና ችግረኛው
“ድኻ” እና “ችግረኛ” የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ እነዚህ ራሳቸውን መርዳት የማይችሉ ሰዎች ስለ መሆናቸው አጽንዖት ይሰጣል።

ዓይኖቹን ወደ ጣዖታት ያነሣል
“ዓይኖቹን ያነሣል” የሚለው የአነጋገር ዘይቤ ወደ አንድ ነገር መመልከትን ያመለክታል። ወደ ጣዖታት የማመልከቱ አኳኋን የሚወክለው ጣዖታትን ማምለክን ወይም ወደ እነርሱ መጸለይን ነው። በሕዝቅኤል 18፡6 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ጣዖታትን ያመልካል” ወይም “ወደ ጣዖታት ይጸልያል”

ወለድ
ይህ ቃል ተበዳሪው ለተበደረው ገንዘብ የሚከፍለውን ገንዘብ ያመለክታል። ይሁን እንጂ አንዳንድ አዳዲስ ትርጉሞች በዚህ ምንባብ ያለውን “የትኛውም ወለድ” የሚለውን “እጅግ የበዛ ወለድ” ብለው ይተረጉሙታል።

ያ ሰው በሕይወት መኖር አለበት? በእርግጥ አይኖርም!
እግዚአብሔር በአሉታዊው ምላሽ ላይ አጽንዖት ለመስጠት ይህንን እንደ መሪ ጥያቄ አድርጎ ይጠይቃል። አ.ት፡ “ያለ ጥርጥር በሕይወት አይኖርም!” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ደሙ በራሱ ላይ ይሆናል
እዚህ ጋ “ደም” የሚለው ቃል የሚወክለው ሞትን ነው። ደም በአንድ ሰው ራስ ላይ ይሆናል የሚለው የአነጋገር ዘይቤ ለዚያ ሞት ሰውየው ኃላፊነቱን ይወስዳል ማለት ነው። አ.ት፡ “ለራሱ ሞት ኃላፊነቱን ይወስዳል” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 18:14

እነሆ!
እዚህ ጋ፣ “እነሆ” የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚመጣው አጽንዖት ይሰጣል።

ያ ልጅ በተራሮች ላይ አይበላም
ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ በተራሮች ላይ የአሕዛብን አማልክት ያመልኩና መሥዋዕትም ያቀርቡላቸው ነበር። እንዲህ ያለው ሰው እነዚህን በመሳሰሉ የአሕዛብ የአምልኮ ሥርዓቶች ላይ እንዳልተሳተፈ ያመለክታል። በሕዝቅኤል 18 ፡6 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ያ ልጅ በተራሮች ላይ ለጣዖታት የተሰዋውን ሥጋ አይበላም”

ዓይኖቹን ወደ ጣዖታት አያነሣም
“ዓይኖቹን ማንሣት” የሚለው የአነጋገር ዘይቤ ወደ አንድ ነገር መመልከትን ያመለክታል። ወደ ጣዖታት የማመላከቱ አኳኋን የሚወክለው ጣዖታትን ማምለክን ወይም ወደ እነርሱ መጸለይን ነው። በሕዝቅኤል 18፡6 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ጣዖታትን አያመልክም” ወይም “ወደ ጣዖታት አይጸልይም”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 18:16

ወለድ
ይህ ቃል ተበዳሪው ለተበደረው ገንዘብ የሚከፍለውን ገንዘብ ያመለክታል። ይሁን እንጂ፣ አንዳንድ አዳዲስ ትርጉሞች በዚህ ምንባብ ያለውን “የትኛውም ወለድ” የሚለውን “እጅግ የበዛ ወለድ” ብለው ይተረጉሙታል።

እንደ ሥርዓቴ ይሄዳል
ሥርዓቶቹ ሰውየው የሚሄድባቸው መንገዶች የሆኑ ይመስል እግዚአብሔር ሥርዓቶቹን ስለሚታዘዝ ሰው ይናገራል። አ.ት፡ “ሥርዓቶቼን ይታዘዛል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 18:18

በኃይል ማስከፈል
ከአንድ ሰው አንድን ነገር በማስፈራራት ወይም በማስገደድ መውሰድ

ወንድሙን ዘርፏል
“እስራኤላዊ ባልንጀራውን ዘርፏል”

እነሆ፣ እርሱ
“ልብ በሉ፣ ምክንያቱም የምነግራችሁ እውነትና አስፈላጊም ነው፡ እርሱ”

በኃጢአቱ
“በኃጢአቱ ምክንያት”

Ezekiel 18:19

የአባቱን ኃጢአት ልጁ የማይሸከመው ለምንድነው?
ኃጢአት ሰውዬው የሚሸከመው ቁስ በሚመስልበት መልኩ እግዚአብሔር ስለ ኃጢአቱ ኃላፊ ወይም በደለኛ ስለሚሆን ሰው ይናገራል። አ.ት፡ “ልጁ ስለ አባቱ ኃጢአት ኃላፊ የማይሆነው ለምንድነው?” ወይም “ልጁ ስለ አባቱ ኃጢአት በደለኛ የማይሆነው ለምንድነው?” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በትክክል የሚያደርግ ጽድቁ በራሱ ላይ ይሆናል
ጽድቅ በአንድ ሰው ላይ የመሆኑ የአነጋገር ዘይቤ ትርጉም ሰውዬው ስለዚያ ጽድቅ ኃላፊ ነው ማለት ነው። አ.ት፡ “በትክክል የሚያደርግ ለራሱ ጽድቅ ኃላፊ ይሆናል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የኃጢአተኛው ኃጢአት በራሱ ላይ ይሆናል
ኃጢአት በሰው ራስ ላይ ይሆናል የሚለው የአነጋገር ዘይቤ ትርጉም ሰውዬው ስለዚያ ኃጢአት ኃላፊ ነው ማለት ነው። አ.ት፡ “ኃጢአተኛው ሰው ስለ ራሱ ኃጢአት ኃላፊ ነው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 18:21

ያደረገው መተላለፍ ሁሉ በእርሱ ላይ አይታሰብበትም
“አይታሰብበትም” የሚለው የአነጋገር ዘይቤ ትርጉም አይታሰብበትም የሚል ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እርሱ ያደረገውን መተላለፍ ሁሉ አላስብበትም፣ በእርሱም ላይ አልይዝበትም” (የአነጋገር ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ስላደረገው ጽድቅ
“ባደረገው የጽድቅ ነገር ምክንያት”

Ezekiel 18:23

እኔ ከመንገዱ ተመልሶ በሕይወት እንዲኖር እንጂ በኃጢአተኛው ሞት እጅግ ደስ ይለኛልን?
እግዚአብሔር ተቃራኒው ላይ አጽንዖት ለመስጠት ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ይጠይቃል። አ.ት፡ “በኃጢአተኛው ሞት እጅግ ደስ አይለኝም. . . ነገር ግን እጅግ ደስ የሚለኝ በሕይወት ይኖር ዘንድ ከመንገዱ ከተመለሰ ነው” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ይህ የጌታ እግዚአብሔር ቃል ነው
እግዚአብሔር የንግግሩን እርግጠኝነት ለመግለጽ የራሱን ስም በመጥራት ይናገራል። ይህንን በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ጌታ እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን ነው” ወይም “እኔ፣ ጌታ እግዚአብሔር የተናገርኩት ይህንን ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

ከመንገዱ በመመለሱ አይደለም
ሰውዬው የሚሄድበት መንገድ በሚመስልበት መልኩ እግዚአብሔር የሚናገረው ስለ ሰው የአኗኗር ዘይቤና ጸባይ ነው። ከአንድ ነገር “መመለስ” የሚለው የአነጋገር ዘይቤ ትርጉሙ ያንን ነገር ማድረግ ማቆም ማለት ነው። አ.ት፡ “ይኖርበት የነበረውን መንገድ በመተዉ አይደለም” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 18:24

ከዚያ በሕይወት ይኖራል?
አሉታዊው መልስ ላይ አጽንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ይጠይቃል። አ.ት፡ “ከዚያም በእርግጥ በሕይወት አይኖርም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

እርሱ ያደረገው ጽድቅ ሁሉ አይታሰብም
“መታሰብ” የሚለው የአነጋገር ዘይቤ ትርጉሙ ማስታወስ ማለት ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ያደረገውን ጽድቅ ሁሉ አላስታውስም” (የአነጋገር ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ክህደት
ታማኝ ተደርጎ በተቆጠረ ሰው አማካይነት በሀገር ወይም በእግዚአብሔር ላይ የተፈጸመ ወንጀል

እርሱ በኃጢአቱ ይሞታል
“እርሱ በኃጢአቱ ምክንያት ይሞታል”

Ezekiel 18:25

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መንገዶቼ ፍትሐዊ አይደሉም?
አሉታዊው መልስ ላይ አጽንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ይጠይቃል። አ.ት፡ “መንገዶቼ ፍትሐዊ ናቸው” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ፍትሐዊ ያልሆነው የእናንተ መንገድ አይደለም?
አዎንታዊው መልስ ላይ አጽንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ይጠይቃል። አ.ት፡ “ፍትሐዊ ያለሆነው የእናንተ መንገድ ነው” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

በእነርሱ ምክንያት ይሞታል . . . ባደረገው ኃጢአት ይሞታል
እነዚህ ሐረጎች የሚደጋግሙት በኃጢአቱ ምክንያት የሞተውን ሰው አሳብ ነው፤ ይኸውም፣ ሞቱ የእርሱ እንጂ የሌላ የማንም ስሕተት አለመሆኑን ለመግለጽ ነው።

Ezekiel 18:27

ዓይቶአል
እግዚአብሔር ስለ አንድ ነገር ስለሚያስብና ስለሚገነዘብ ሰው ሲናገር ያ ሰው እያየ እንዳለ አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “ከግምት አስገብቷል” ወይም “ተረድቷል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 18:29

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የጌታ መንገድ ፍትሐዊ አይደለም . . . መንገዴ ፍትሐዊ ያልሆነው እንዴት ነው . . . ፍትሐዊ ያልሆነው የእናንተ መንገድ ነው
ድርጊቶች ወይም ጸባዮች ሰው እንደሚጓዝባቸው መንገዶች ተደርገው ተነግረዋል። አ.ት፡ “ጌታ በፍትሐዊነት አያደርግም . . . በፍትሐዊነት የማላደርገው እንዴት ነው . . . በፍትሐዊነት የማታደርጉ እናንተ ናችሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እንደ መንገዶቹ
እግዚአብሔር በመንገድ ላይ እንደሚሄድ ሰው አድርጎ የሚናገረው ስለ ሰው ሥራ ነው። አ.ት፡ “እንደ ሥራው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የኃጢአት ማሰናከያ እንዳይሆኑባችሁ ከመተላለፋችሁ ሁሉ ተመለሱ
ሰዎች የሚሰናከሉበት ማሰናከያ የሆነ ይመስል እግዚአብሔር ሰዎች በእርሱ ላይ እንዲያምጹ ስለሚያደርጋቸው “መተላለፍ” ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የኃጢአት ማሰናከያ እንዳይሆኑባችሁ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ማሰናከያ ሰውዬው የበለጠ ኃጢአት እንዲሠራ ምክንያት ይሆነዋል። አ.ት፡ “የበለጠ ኃጢአት እንድትሠሩ ምክንያት የሚሆንባችሁን ማሰናከያ” ወይም 2) “ኃጢአት” የሚለው ቃል አንድ ሰው ስለ ኃጢአቱ ለሚቀበለው ቅጣት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ወደ ቅጣታችሁ የሚመራችሁን ማሰናከያ” የሚሉት ናቸው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 18:31

ያደረጋችሁትን መተላለፍ ሁሉ ከራሳችሁ ላይ ጣሉት
መተላለፍ እንደ ልብስ አውልቀው የሚጥሉት ቁስ ይመስል ሕዝቡ የሚያደርገውን መተላለፍ ለማቆም እንዲወስን እግዚአብሔር ይናገራል። አ.ት፡ “ካደረጋችሁት መተላለፍ ሁሉ ራቁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ለራሳችሁ አዲስ ልብና አዲስ መንፈስ አድርጉ
እዚህ ጋ “ልብ” የሚለው ቃል የሚወክለው ፈቃድንና ስሜትን ሲሆን “መንፈስ” የሚለው ቃል ደግሞ አሳብንና ጸባይን ይወክላል። አ.ት፡ “ለራሳችሁ አዲስ ስሜትና አዲስ አስተሳሰብ ይኑራችሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የእስራኤል ቤት ሆይ፣ ለምን ትሞታላችሁ?
እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ለማጽናናት ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ይጠይቃል። አ.ት፡ “የእስራኤል ቤት ሆይ፣ የምትሞቱበት ምንም ምክንያት የለም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እስራኤላውያንን” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 19

1 አንተም በእስራኤል አለቆች ላይ ይህን ሙሾ አሙሽ፥ እንዲህም በል፥ **2** 'እናትህ ማን ነበረች? አንበሳ ነበረች ከአንበሳ ደቦል ጋር ተጋደመች ግልገሎችዋን አሳደገች። **3** ከግልገሎችዋም አንዱን ደቦል አንበሳ እንዲሆንና ጠላቶቹን የሚቆራርጥ እንዲሆን አሳደገችው። ሰዎችንም በላ። **4** አሕዛብም ወሬውን ሰሙ እርሱም በወጥመዳቸው ተያዘ፥ በሰንሰለትም አድርገው ወደ ግብጽ ምድር ወሰዱት። **5** እርስዋም ይመለሳል ብላ ብትጠብቅም ተስፋዋ እንደ ጠፋ ባየች ጊዜ፥ ከግልገሎችዋ ሌላን ወስዳ ደቦል አንበሳ እንዲሆን አሳደገችው። **6** ደቦል አንበሳውም በአንበሶች መካከል ተመላለሰ ደቦል አንበሳም ሆነ ንጥቂያም ተማረ፥ ሰዎችንም በላ። **7** መበለቶቻቸውን አስነወረ፥ ከተሞቻቸውንም አፈረሰ ከግሣቱም ድምፅ የተነሣ ምድሪቱና በሞላ ሰው አልባ ሆነች። **8** አሕዛብም ከየአገሩ ሁሉ ተሰበሰቡ፤ መረባቸውንም በእርሱ ላይ ዘረጉ በወጥመዳቸውም ተያዘ። **9** በሰንሰለትም አድርገው በሳጥን አድርገው ወደ ባቢሎን ንጉሥ አመጡት። ድምፁም በእስራኤል ተራሮች ላይ ከዚያ ወዲያ እንዳይሰማ ወደ አምባ አመጡት። **10** እናትህ በውኃ አጠገብ በደምህ ውስጥ እንደ ተተከለች ወይን ነበረች። ከውኃም ብዛት የተነሣ ፍሬያማና በቅርንጫፍ የትሞላች ነበረች ። **11** ለእርስዋም ብርቱዎች በትሮች ነበሩአት እነርሱም ለነገሥታት በትሮች ነበሩ። ቁመቷም በዛፎች ቅርንጫፎች መካከል ከፍ አለ። **12** ነገር ግን በመዓት ተነቀለች ወደ መሬትም ተጣለች የምሥራቅም ነፋስም ፍሬዋን አደረቀ። ብርቱዎች ቅርንጫፎቿተሰበሩና ደረቁ፥ እሳትም በላቻው። **13** አሁን በምድረ በዳ፥ በደረቅና ውሀ በሌለው መሬት ተተክላለች። **14** ከቅርንጫፎቿ እሳት ወጥቶ ፍሬዋ በላ፥ ጠንካራ ቅርንጫፍ የለባትም የነገሥታትም በትር ሊሆን የሚችልም የለም።' ይህ ሙሾ ነው፥ የልቅሶ ዝማሬም ይሆናል።

Ezekiel 19:1

ሙሾ አውጣ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ትርጉሙ ሙሾ አንጎራጉር ማለት ነው። አ.ት፡ “ሙሾ አንጎራጉር” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

እናትሽ ማን ነበረች?
እግዚአብሔር መልሱን ለማስታወቅ ይህንን መሪ ጥያቄ ይጠይቃል። አ.ት፡ “እናትሽ ይህቺ ናት” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

አንበሲት
ሴት አንበሳ

በወጥመዳቸው ተያዘ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በወጥመዳቸው ያዙት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 19:5

መበለቶቻቸውን ያዘ
“የበላቸውን የሰዎቹን መበለቶች ያዘ”

ምድርና ሞላዋ ተተዉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሰዎች ምድሪቱንና ሞላዋን ተዉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ሞላዋ
“በእርሷ ውስጥ ያለው ነገር ሁሉ”

Ezekiel 19:8

በዙሪያ ካሉ አውራጃዎች
“የእስራኤልን ምድር ከሚከቡ አውራጃዎች”

በወጥመዳቸው ተያዘ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በወጥመዳቸው ያዙት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ከዚያ በኋላ ድምፁ አልተሰማም
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ከዚያ በኋላ ሰዎች ድምፁን አልሰሙም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 19:10

በደምሽ ላይ የተተከለ የወይን ተክል
“ደም” ሊወክል የሚችልባቸው ትርጉሞች 1) ሰዎችን የገደሉት የይሁዳ ንጉሥታት ሁከት። አ.ት፡ “ሁከትን በመጠቀም የተተከለ የወይን ተክል” ወይም 2) የብልጽግና ምልክት የሆነው የይሁዳ የተትረፈረፈ ወይን። አ.ት፡ “በብልጽግናችሁ የተተከለ የወይን ተክል”

ለበትረ መንግሥትነት ጥቅም ላይ የዋሉ ጠንካራ ቅርንጫፎች
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሰዎች በትረ መንግሥት ለመሥራት የተጠቀሙበት ጠንካራ ቅርንጫፍ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ርዝመቱ በቅጠላ ቅጠሉ ታላቅነት ይታይ ነበር
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በቅጠላ ቅጠሎቹ ታላቅነት ሰዎች ምን ያህል ረጅም እንደነበረ ማየት ይችሉ ነበር” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 19:12

የወይኑ ተክል በንዴት ተነቀለና ተጣለ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር የወይኑን ተክል በንዴት ነቀለና ጣለው” ወይም “የወይኑን ተክል ሰዎች በንዴት ነቀሉና ጣሉት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ጠንካራ ቅርንጫፎቹ ተሰበሩና ጠወለጉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ጠንካራ ቅርንጫፎቹን ሰበራቸውና ጠወለጉ” ወይም “ሰዎች ጠንካራ ቅርንጫፎቹን ሰበሯቸውና ጠወለጉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በድርቅ እና በጥማት ምድር
በጣም የደረቀው ምድር እንደ ተጠማ ተደርጎ ተነግሮለታል። አ.ት፡ “በጣም በደረቀው የድርቅ ምድር ላይ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 19:14

ለመግዛት በትረ መንግሥት የለም
ግልጽ ያልሆነውን መረጃ ምናልባት ከሕዝቅኤል 19፡11 ላይ ማሟላት ይቻላል። አ.ት፡ “ለገዢው በትረ መንግሥት የሚሆን ጠንካራ የሆነ ቅርንጫፍ የለም”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንደ ሙሾ ይዜማል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እንደ ሙሾ ማዜም አለባችሁ”
(አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 20

1 እንዲህም ሆነ በሰባተኛው ዓመት በአምስተኛው ወር ከወሩም በአሥረኛው ቀን የእስራኤል ሽማግሌዎች እግዚአብሔርን ሊጠይቁ መጥተው በፊቴ ተቀመጡ።
2 የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፥ 3 "የሰው ልጅ ሆይ፥ ለእስራኤል ሽማግሌዎች ተናገር፥ እንዲህም በላቸው። 'ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እኔን ትጠይቁ ዘንድ መጥታችኋልን? በህያውነቴ እምላለሁ በእናንተ አልጠየቅም! ይላል ጌታ እግዚአብሔር፦ 4 ትፈርድባቸዋለህን? የሰው ልጅ ሆይ፥ በውኑ ትፈርድባቸዋለህን? የአባቶቻቸውን ርኵሰት አስታውቃቸው! 5 እንዲህም በላቸው፥ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እስራኤልን በመረጥሁበት ለያዕቆብም ቤት ዘር እጄን አንስቼ በማልሁበት ቀን በግብጽም ምድር በተገለጥሁላቸውና። እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ ብዬ በማልሁላቸው ጊዜ፥ 6 በዚያ ቀን ከግብጽ ምድር በጥንቃቄ ወደመረጥኩላቸው፥ ወተትና ማር ወደምታፈስሰው፥ የምድርም ሁሉ ጌጥ ወደምትሆን ምድር እንደማወጣቸው ማልሁላቸው! 7 እኔም፥ "ከእናንተ እያንዳንዱ ርኩስ ነገርንና የግብጽን ጣዖታት ከዓይኑ ፊት ያስወግድ። ራሳችሁን አታርክሱ፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ።" አልኋቸው። 8 እነርሱ ግን ዐመፁብኝ ሊሰሙኝም አልወደዱም። እያንዳንዱ ርኩስ ነገሮችን ከአይኑ ፊት አላስወገደም የግብጽንም ጣዖታት አልተወም በዚህም ጊዜ። በግብጽ ምድር መካከል ቍጣዬን ልፈጽምባቸው መዓቴንም ላፈስባቸው ወሰንኩ። 9 ነገር ግን በመካከላቸው በሚኖሩበት ህዝብ መካከል እንዳይረክስ ስለ ስሜ ሰራሁ። ከግብጽ ምድር በማውጣት ራሴን በአይናቸው ፊት ገለጥኩላቸው። 10 ከግብጽም ምድር አወጣኋቸው ወደ ምድረ በዳም አመጣኋቸው። 11 ሰው ቢያደርገው በሕይወት የሚኖርበትን ሥርዓቴንም ሰጠኋቸው፥ ፍርዴንም አስታወቅኋቸው። 12 ለራሴ የለየኋቸው እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቁ ዘንድ፥ በእኔና በእነርሱ መካከል ምልክት እንዲሆን ሰንበታቴን ሰጠኋቸው። 13 ነገር ግን የእስራኤል ቤት በምድረ በዳ ዐመፁብኝ። በትዕዛዜም አልሄዱም፤ ይልቁኑ ሰው ቢያደርገው በሕይወት የሚኖርበትንም ፍርዴን ጣሉ። ሰንበታቴንም ፈጽመው አረከሱ፥ ስለዚህም አጠፋቸው ዘንድ ቍጣዬን በምድረ በዳ አፈስስባቸዋለሁ አልሁ። 14 ነገር ግን በፊታቸው ባወጣኋቸው በአሕዛብ ፊት ስሜ እንዳይረክስ ብዬ ስለ ስሜ ሠራሁ። 15 ወተትና ማርም ወደምታፈስሰው የምድር ሁሉ ጌጥ ወደምትሆን ልሰጣቸው ወዳሰብኩት ምድር አላመጣቸውም ብዬ በምድረ በዳ ማልሁባቸው። 16 ይህን የማልኩት ልባቸው ጣዖቶቻቸውን ስለተከተሉ፥ ፍርዴንም ስለጣሉ ፥ በሥርዓቴም ስላልሄዱ፥ ሰንበታቴንም ስላረከሱ ነው። 17 ነገር ግን ዓይኔ ራራችላቸው እኔም አላጠፋኋቸውም፥ በምድረ በዳም ፈጽሜ አልፈጀኋቸውም። 18 ለወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸው በምድረ በዳ እንዲህ አልኋቸው፥ "በአባቶቻችሁ ሥርዓት አትሂዱ፤ ወጋቸውንም አትጠብቁ በጣዖቶቻቸውም አትርከሱ። 19 እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ! በትእዛዜ ሂዱ ፍርዴንም ጠብቁ አድርጓትም! 20 በእናንተና በእኔ መካከል ምልክት እንዲሆኑና እኔም እግዚአብሔር አምላካችሁ እንደ ሆንሁ እንድታውቁ ሰንበታቴን ጠብቁ።" 21 ነገር ግን ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸው ዐመፁብኝ። በሥርዓቴም አልሄዱም ወይም ሰው ቢፈጽመው በሕይወት የሚኖርባትን ፍርዴን አልጠበቁም። ሰንበታቴንም አረከሱ ስለዚህም በምድረ በዳ መዓቴን ላፈስባቸው ቍጣዬንም ልፈጽምባቸው ወሰንክ። 22 ነገር ግን እጄን መለስሁ፥ በፊታቸውም ባወጣኋቸው በአሕዛብ ፊት ስሜ እንዳይረክስ ብዬ ስለ ስሜ ሠራሁ። 23 ደግሞም ወደ አሕዛብ ልበትናቸው ፥ በአገሮችም መካከልም ለነቀፋ ላደርጋቸው በምድረ በዳ እጄን አንስቼ ማልሁባቸው። ፍርዴን አላደረጉምና 24 ሥርዓቴንም ጥሰዋልና ሰንበታቴንም አርክሰዋልና ዓይናቸውም የአባቶቻቸውን ጣዖታቶች ተከትለዋልና ይህን ላደርግባቸው ወሰንኩ። 25 ደግሞም መልካም ያልሆነውን ሥርዓት በሕይወት የማይኖሩበትንም ህግ ሰጠኋቸው። 26 እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ እንዲያውቁ አጠፋቸው ዘንድ፥ ማኅፀን የሚከፍተውን በኩር ሁሉ በእሳት ባሳለፉ ጊዜ፥ በመባቸው አረከስኋቸው። 27 ስለዚህ፥ የሰው ልጅ ሆይ፥ ለእስራኤል ቤት ተናገር፥ እንዲህም በላቸው፥ 'ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡ በዚህም ደግሞ አባቶቻችሁ ባደረጉት ዓመፅ አስቈጡኝ። 28 እሰጣቸውም ዘንድ ወደ ማልሁላቸው ምድር ባገባኋቸው ጊዜ፥ በኮረብታ ላይ ያለውን የጣዖት ማምለኪያ ሁሉና ቅጠልማውንም ዛፍ ባዩ ጊዜ፥ በዚያ መሥዋዕታቸውን ሠዉ በዚያም የሚያስቈጣኝን ቍርባናቸውን አቀረቡ። በዚያም ደግሞ ጣፋጩን ሽታቸውን አደረጉ በዚያም የመጠጥ ቍርባናቸውን አፈሰሱ። 29 እኔም፥ "እናንተ ወደ እርሱ የምትሄዱበት ኮረብታማ ሥፍራ ምንድር ነው?" አልኋቸው። እስከ ዛሬም ድረስ ስሙ ባማ ተብሎ ተጠርቶአል። 30 ስለዚህ ለእስራኤል ቤት እንዲህ በላቸው፥ 'ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እንደ አባቶቻችሁ ልማድ ለምን ትረክሳላችሁ? ለምን እንደአመንዝራ የሚያጸይፍ ተግባር ታከናውናላችሁ? 31 ቍርባናችሁን ስታቀርቡ፥ ልጆቻችሁንም በእሳት ስታሳልፉ፥ እስከ ዛሬ ድረስ በጣዖቶቻችሁ ትረክሳላችሁ። ታዲያ የእስራኤል ቤት ሆይ፥ ከእናንተስ ዘንድ እጠየቃለሁን? በህያውነቴ እምላለሁ ከእናንተ ዘንድ አልጠየቅም-ይላል ጌታ እግዚአብሔር። 32 እናንተ "እንጨትና ድንጋይ እንድሚያመልኩት ወገኖች እንደ ሌሎች አሕዛብ እንሁን" ብላችሁ ያሰባችሁት ሀሳብ ይፈጸማል። 33 በህያውነቴ እምላለሁ በበረታች እጅና በተዘረጋች ክንድ በእናንተ ላይ በፈሰሰችም መዓት እነግሥባችኋለሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር! 34 ከአሕዛብም ዘንድ አወጣችኋለሁ ከተበተናችሁባትም አገር ሁሉ በበረታች እጅና በተዘረጋች ክንድ በፈሰሰችም መዓት እሰበስባችኋለሁ። 35 ወደ አሕዛብም ምድረ በዳ አመጣችኋለሁ በዚያም ፊት ለፊት ከእናንተ ጋር እፋረዳለሁ። 36 በግብጽ ምድረ በዳ በአባቶቻችሁ ላይ እንደፈረድኩ እንዲሁ በእናንተ ላይ እፋረዳለሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር። 37 ከበሬም በታች አሳልፋችኋለሁ ወደ ቃል ኪዳንም እስራት አገባችኋለሁ፤ 38 ከእናንተም መካከል ዓመፀኞችንና የበደሉኝን እለያለሁ። በእንግድነት ከኖሩባትም ምድር አወጣቸዋለሁ፥ ወደ እስራኤል ምድር ግን አይገቡም። እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ! 39 ጌታ እግዚአብሔርም እንዲህ ይላል። እናንተ የእስራኤል ቤት ሆይ፥ እያንዳንዳችሁ ወደየጣዖቶቻችሁ ሂዱ፥ ከዚህም በኋላ እኔን መስማት ካልፈለጋችሁ እነርሱን አምልኩ። ነገር ግን ከእንግዲህ ወዲህ በቍርባናችሁና በጣዖቶቻችሁ ቅዱሱን ስሜን አታረክሱም። 40 ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል- በቅዱሱ ተራራዬ፥ ከፍ ባለው በእስራኤል ተራራ ላይ፥ በዚያ የእስራኤል ቤት ሁሉ ሁላቸው በምድራቸው ያመልኩኛል። በዚያም ቍርባናችሁን በኵራታችሁንም የቀደሳችሁትንም ነገር ሁሉ በደስታ እቀበላለሁ። 41 ከአሕዛብም ዘንድ ባወጣኋችሁ ጊዜ ከተበተናችሁባትም አገር ሁሉ በሰበሰብኋችሁ ጊዜ እንደ ጣፋጭ ሽታ እቀበላችኋለሁ፥ በአሕዛብም ፊት እቀደስባችኋለሁ። 42 ለአባቶቻችሁም እሰጣት ዘንድ ወደ ማልሁላቸው ምድር ወደ እስራኤል አገር ባገባኋችሁ ጊዜ፥ እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ። 43 በዚያም የረከሳችሁባትን መንገዳችሁንና ሥራችሁን ሁሉ ታስባላችሁ ስለ ሠራችሁትም ክፋት ሁሉ ራሳችሁን ትጸየፋላችሁ። 44 ስለዚህም የእስራኤል ቤት ሆይ፥ እንደ ክፉ መንገዳችሁና እንደ ርኩስ ሥራችሁ ሳይሆን ስለ ስሜ ብዬ ይህን ባደረኩላችሁ ጊዜ፥ እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር። 45 የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፥ 46 "የሰው ልጅ ሆይ፥ ፊትህን ወደ ደቡብ አቅና በደቡብ ላይ ተናገር፤ በኔጌብ ዱር ላይ ትንቢት ተናገር 47 ለኔጌብም ዱር፥ 'የእግዚአብሔርን ቃል ስማ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እነሆ፥ በአንተ ውስጥ እሳት አነድዳለሁ። በውስጥህም ያለውን የለመለመውንና የደረቀውን ዛፍ ሁሉ ይበላል። የሚንበለበለው እሳትም አይጠፋም፤ ከደቡብም ጀምሮ እስከ ሰሜን ድረስ ያለው ገጽታ ሁሉ ይቃጠላል። 48 እሳቱን ስለኩሰውና ሳይጠፋ በሚነድበት ጊዜ ሥጋ ለባሽ ሁሉ እኔ እግዚአብሔር እንደሆንኩ ያያል።'" 49 እኔም፥ "ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፥ ወዮ! እነርሱ ስለ እኔ፥ "ይሄ ምሳሌን ብቻ ተናጋሪ አይደለም እንዴ?" ይላሉ አልሁ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ezekiel 20:1

እንዲህ ሆነ
ይህ ሐረግ ጥቅም ላይ የዋለው የታሪኩን የአዲስ ክፍል ጅማሬ ለማመልከት ነው።

በሰባተኛው ዓመት
ግልጽ ያልሆነው መረጃ መሞላት አለበት። አ.ት፡ “ንጉሡ ኢዮአቄም በተማረከ በሰባተኛው ዓመት”

የአምስተኛው ወር አሥረኛው ቀን
ይህ በዕብራውያኑ የቀን መቁጠሪያ አምስተኛው ወር ነው። በምዕራባውያኑ አቆጣጠር አስረኛው ቀን የነሐሴ ወር መጀመሪያ አቅራቢያ ነው። (የዕብራውያን ወራት እና ደረጃን አመልካች ቁጥር የሚለውን ተመልከት)

በፊቴ
“በእኔ ፊት ለፊት”

Ezekiel 20:2

የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የሰው ልጅ
“የሰብዓዊ ፍጡር ልጅ” ወይም “ከሰው የተወለደ ልጅ”። ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን አፅንኦት ለመስጠት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ በማለት ይጠራዋል። እግዚአብሔር ዘላለማዊና ኃያል ነው፣ ሰዎች ግን አይደሉም። ይህንን በሕዝቅኤል 2፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ሟች ሰው” ወይም “ሰው”

ሕያው እንደ መሆኔ
“ሕያው መሆኔ እርግጥ የመሆኑን ያህል”። እግዚአብሔር ቀጥሎ የሚናገረው የተረጋገጠ እውነት መሆኑን ለማሳየት ይህንን አገላለጽ ይጠቀማል። ይህ ጽኑ ተስፋ የመስጫ መንገድ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ጽኑ መሐላ አደርጋለሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ከእኔ ልትጠይቁ መጣችሁ?
ሽማግሌዎቹ እርሱን ሊጠይቁት እንደማይገባቸው አጽንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ይጠይቃል። አ.ት፡ “እኔን ለመጠየቅ መምጣት የለባችሁም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

በእናንተ አልጠየቅም
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እንድትጠይቁኝ አልፈቅድላችሁም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ይህ የጌታ እግዚአብሔር ቃል ነው
እግዚአብሔር የንግግሩን እርግጠኝነት ለመግለጽ የራሱን ስም በመጥራት ይናገራል። ይህንን በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ጌታ እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን ነው” ወይም “እኔ፣ ጌታ እግዚአብሔር የተናገርኩት ይህንን ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 20:4

ትፈርድባቸዋለህ? የሰው ልጅ ሆይ፣ ትፈርዳለህ?
ሕዝቅኤል ፍርድን ለማስታወቅ ያለውን መሰጠት እንዲጠብቀው እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን አንዱን ጥያቄ ሁለት ጊዜ ይጠይቀዋል። አ.ት፡ “የሰው ልጅ ሆይ፣ በእነርሱ ላይ ፍርድን ለማስታወቅ ዝግጁ ነህ?”

እኔ . . . መሐላ ለመማል እጄን እንሥቻለሁ
እዚህ ጋ “እጄን አንሥቻለሁ” የሚለው ሐረግ ለማድረግ የማለውን ቃል ያለ ጥርጥር እንደሚያደርገው የሚያሳይ ምልክታዊ ድርጊት ነው። አ.ት፡ “እኔ . . . ጽኑ መሐላ ምያለሁ”

የያዕቆብ ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮችን ያመለክታል። “የ-- ቤት” የሚለውን በሕዝቅኤል 3፡1 ላይ እንዳለው አድርገህ ተርጉመው። አ.ት፡ “የያዕቆብ ዘር” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ወተትና ማር የምታፈስ
“ብዙ ወተትና ማር የሚፈስባት ምድር ነበረች”። ወተቱና ማሩ ከእነዚያ እንስሳትና እጽዋት በምድሪቱ ላይ የሚፈስ በሚመስልበት መልኩ ምድሪቱ ለእንስሳትና ለእጽዋት ጥሩ መሆኗን እግዚአብሔር ይናገራል። አ.ት፡ “ከብት ለማርባትና እህል ለማብቀል ምድሪቱ እጅግ በጣም ጥሩ ነበረች” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በምድሪቱ መካከል ሁሉ እጅግ ያማሩ ጌጣ ጌጦች
ሰዎች የሚኖሩባት ምድር ጌጣ ጌጦች ወይም ሌላ ለማየት የሚያስደስቱ ነገሮችን በሚመስሉበት ሁኔታ ተነግሮላቸዋል። አ.ት፡ “ከምድር ሁሉ እጅግ ያማረች” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 20:7

ለእነርሱ
“ለያዕቆብ ቤት ዘሮች”

በዓይኖቹ ፊት አስከፊ የሆኑ ነገሮች
እነዚያን ጣዖታት በዓይኖቻቸው ፊት ያስቀመጡ ይመስል እግዚአብሔር አስከፊ የሆኑትን ነገሮች ስለሚያመልኩ ሰዎች ይናገራል። አ.ት፡ “የሚያመልከውን አስከፊ ነገሮች” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የግብፅን ጣዖታት
“የግብፅን ጣዖታት ጣሉ”

ራሳችሁን አታርክሱ
ለእግዚአብሔር ዓላማ ተቀባይነት የሌለው ሰው በአካሉ ጭምር እርኩስ እንደ ሆነ ተቆጥሮ ተጽፏል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 20:8

በእኔ ላይ አመፁብኝ
“እነርሱ” የሚለው ቃል የ “ያዕቆብ ቤት ዘሮች”ን ያመለክታል።

ሊሰሙኝ አይፈቅዱም ነበር
“አይታዘዙኝም ነበር”

በዓይኖቹ ፊት አስከፊ ነገሮችን
እነዚያን ጣዖታት በዓይኖቻቸው ፊት ያስቀመጡ ይመስል እግዚአብሔር አስከፊ የሆኑትን ነገሮች ስለሚያመልኩ ሰዎች ይናገራል። አ.ት፡ “ያመለካቸውን አስከፊ ነገሮች” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ንዴቴን በላያቸው ላፈስ
ንዴቱ በእነርሱ ላይ የሚያፈሰው ፈሳሽ ይመስል እግዚአብሔር እነርሱን በመቅጣት ንዴቱን እንደሚገልጽ ይናገራል። አ.ት፡ “በእነርሱ ላይ ንዴቴን አሳያለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ስለ ስሜ ስል
እዚህ ጋ “ስም” የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ዝና ይወክላል። አ.ት፡ “ስለ ዝናዬ ስል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በሀገራቱ ዐይን ፊት እንዳይሰደብ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በሀገራቱ ዐይን ፊት ሰዎች እንዳይሰድቡት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በዐይኖች ፊት
ዐይኖች የሚወክሉት ማየትን፣ ማየትም ማሰብን ወይም መወሰንን ይወክላል። አ.ት፡ “በአመለካከት” ወይም “በውሳኔ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሀገሮች
“ሀገሮች” የሚለው ቃል በሀገራት ውስጥ የሚኖሩትን ሰዎች የሚገልጽ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “በሌሎች ሀገሮች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ይቆዩ ነበር
“ይኖሩ ነበር”

በዐይኖቻቸው ፊት ራሴን አስታወቅኋቸው
እዚህ ጋ “እነርሱን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሕዝቦችን ነው። “በዐይኖቻቸው ፊት” የሚያመለክተው ሰዎች ሊያዩ በሚችሉበት አኳኋን መሆንን ነው። አ.ት፡ “በመካከላቸው እራሴን ገለጥሁላቸው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ሳመጣቸው
“የእስራኤልን ሕዝብ ሳመጣ”

Ezekiel 20:10

ላክኋቸው
“እነርሱን” የሚለው ቃል የ “ያዕቆብን ቤት ዘሮች” ያመለክታል።

እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ታውቃላችሁ
እግዚአብሔር፣ ሰዎች እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን እንደሚያውቁ በሚናገርበት ጊዜ፣ እርሱ ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለው ብቸኛው እውነተኛ አምላክ መሆኑን ያውቃሉ ማለቱ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 6፡7 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እውነተኛው አምላክ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ትረዳላችሁ” ወይም “ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለኝ እኔ ጌታ እግዚአብሔር መሆኔን ትገነዘባላችሁ”

Ezekiel 20:13

በሥርዓቴ አልሄዱም
ሥርዓቶቹን መታዘዝ አንድ ሰው የሚራመድባቸው መንገዶች የሆኑ ይመስል እግዚአብሔር ሥርዓቶቹን ስለ መታዘዝ ይናገራል። አ.ት፡ “ሥርዓቶቼን አልታዘዙም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ንዴቴን በላያቸው ላይ አፈሳለሁ
ንዴቱ በእነርሱ ላይ የሚያፈሰው ፈሳሽ ይመስል እግዚአብሔር እነርሱን በመቅጣት ንዴቱን እንደሚገልጽ ይናገራል። ይህንን በሕዝቅኤል 20፡8 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “በእነርሱ ላይ ንዴቴን አሳያለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እነርሱን ለመጨረስ
“ለመጨረስ” የሚለው ቃል እነርሱን መግደልን ያመለክታል። አ.ት፡ “እነርሱን ለመግደል” (See: Euphemism)

ስለ ስሜ ስል አደረግሁ
እዚህ ጋ “ስም” የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ዝና ይወክላል። ይህንን በሕዝቅኤል 20፡9 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ስለ ዝናዬ ስል አደረግሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በሀገሮች ዓይን ፊት እንዳይሰደብ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ይህንን በሕዝቅኤል 20፡9 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “በሀገሮች ዓይን ፊት ሰዎች እንዳይሰድቡት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በሀገራቱ ዐይን ፊት
እዚህ ጋ “ሀገሮች” የሚያመለክተው በእነዚያ ቦታዎች የሚኖረውን ሕዝብ ነው። ዐይኖች ማየትን፣ ማየትም ማሰብን ወይም መወሰንን ይወክላሉ። ይህንን በሕዝቅኤል 20፡9 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “በሌሎች ሀገሮች በሚኖሩ ሰዎች አስተሳሰብ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከግብፅ ባወጣኋቸው ዐይን ፊት
“ሕዝቤን ከግብፅ አውጥቼ በእነርሱ ፊት ያመጣሁ”

Ezekiel 20:15

እኔ ራሴ ደግሞ መሐላ ለመማል እጄን እንሥቻለሁ
እዚህ ጋ “እጄን አንሥቻለሁ” የሚለው ሐረግ ለማድረግ የማለውን ቃል ያለ ጥርጥር እንደሚያደርገው የሚያሳይ ምልክታዊ ድርጊት ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 20፡5 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እኔ ራሴ ጽኑ መሐላ ምያለሁ”

ለእነርሱ
“ለእስራኤል ቤት”

ወተትና ማር የምታፈስ ምድር
“ብዙ ወተትና ማር የሚፈስባት ምድር”። ወተቱና ማሩ ከእነዚያ እንስሳትና እጽዋት በምድሪቱ ላይ የሚፈስ በሚመስልበት መልኩ ምድሪቱ ለእንስሳትና ለእጽዋት ጥሩ መሆኗን እግዚአብሔር ይናገራል። ይህንን በሕዝቅኤል 20፡6 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ከብት ለማርባትና እህል ለማብቀል ምድሪቱ እጅግ በጣም ጥሩ ነበረች”

በምድሪቱ መካከል ሁሉ እጅግ ያማሩ ጌጣ ጌጦች
ሰዎች የሚኖሩባት ምድር ጌጣ ጌጦች ወይም ሌላ ለማየት የሚያስደስቱ ነገሮችን በሚመስሉበት ሁኔታ ተነግሮላቸዋል። ይህንን በሕዝቅኤል 20፡6 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ከምድር ሁሉ እጅግ ያማረች” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በሥርዓቴ አልሄዱም
ሥርዓቶቹን መታዘዝ አንድ ሰው የሚራመድባቸው መንገዶች የሆኑ ይመስል እግዚአብሔር ሥርዓቶቹን ስለ መታዘዝ ይናገራል። አ.ት፡ “ሥርዓቶቼን አልታዘዙም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ልባቸው ጣዖታቸውን ተከተለ
እዚህ ጋ “ልብ” የሚለው ቃል የሰውዬውን አሳብና ስሜት ይወክላል። የሰው ልብ ተከትሏቸው ይሄድ ይመስል እግዚአብሔር ለጣዖታት የተሰጡ ስለመሆናቸው ይናገራል። አ.ት፡ “ጣዖታቶቻቸውን ለማምለክ ራሳቸውን ሰጡ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ዐይኔ አዳናቸው
እዚህ ጋ “ዐይን” የሚለው ቃል የሚወክለው እግዚአብሔርን ነው። አ.ት፡ “አዳንኳቸው” (See: Synecdoche)

Ezekiel 20:18

በአባቶቻችሁ ሥርዓት አትሂዱ፣ . . . በእኔ ሥርዓት ሂዱ
ሥርዓቶቹ አንድ ሰው የሚራመድባቸው መንገዶች የሆኑ ይመስል እግዚአብሔር ሥርዓቶቹን ስለሚታዘዝ ሰው ይናገራል። አ.ት፡ “የወላጆቻችሁን ሥርት አትታዘዙ . . . የእኔን ሥርዓት ታዘዙ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የእኔን ሕግጋት ጠብቋቸው፣ ታዘዟቸውም
የእግዚአብሔርን ሕግጋት “መጠበቅ” “እነርሱን ከመታዘዝ” ጋር አንድ ነው። (See: Doublet)

Ezekiel 20:21

በሥርዓቶቼ አልሄዱም
ሥርዓቶቹ አንድ ሰው የሚራመድባቸው መንገዶች የሆኑ ይመስል እግዚአብሔር ሥርዓቶቹን ስለሚታዘዝ ሰው ይናገራል። አ.ት፡ “ሥርዓቶቼን አልታዘዙም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ንዴቴን በእነርሱ ላይ ለማፍሰስ
ንዴቱ በእነርሱ ላይ የሚያፈሰው ፈሳሽ የሆነ ይመስል እግዚአብሔር እነርሱን በመቅጣት ንዴቱን እንደሚገልጽ ይናገራል። ይህንን በሕዝቅኤል 20፡8 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “በእነርሱ ላይ ንዴቴን አሳያለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እጄን አራቅሁ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚለው ቃል የሚወክለው እግዚአብሔርን ሲሆን እጁን ማራቅ ማለት ሊያደርግ የነበረውን አላደረገም ማለት ነው። አ.ት፡ “ነገር ግን ያንን አላደረግሁም” (Synecdoche እና የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ስለ ስሜ ስል
እዚህ ጋ “ስም” የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ዝና ይወክላል። አ.ት፡ “ስለ ዝናዬ ስል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በሀገራቱ ዐይን ፊት እንዳይሰደብ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ይህንን በሕዝቅኤል 20፡9 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “በሀገራቱ ዐይን ፊት ሰዎች እንዳይሰድቡት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በሀገራቱ ዐይን ፊት
እዚህ ጋ “ሀገሮች” የሚያመለክተው በእነዚያ ቦታዎች የሚኖሩትን ሕዝቦች ነው። ዐይኖች ማየትን፣ ማየትም ማሰብን ወይም መወሰንን ይወክላሉ። አ.ት፡ “በሌሎች ሀገሮች በሚኖሩ ሰዎች አስተሳሰብ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 20:23

እኔ ራሴ ደግሞ ለመማል እጄን እንሥቻለሁ
እዚህ ጋ “እጄን አንሥቻለሁ” የሚለው ሐረግ ለማድረግ የማለውን ቃል ያለ ጥርጥር እንደሚያደርገው የሚያሳይ ምልክታዊ ድርጊት ነው። አ.ት፡ “እኔ ራሴ ጽኑ መሐላ ምያለሁ”

በሀገራት መካከል በምበትናቸውና በምድር ሁሉ ላይ በምዘራቸው ጊዜ
የእነዚህ ሁለት ሐረጎች መሠረታዊ ትርጉማቸው አንድ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 12፡15 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እርስ በእርሳቸው እንዲለያዩና በተለያየ ሀገር እንዲኖሩ አደርጋቸዋለሁ”

ዐይኖቻቸው የአባቶቻቸውን ጣዖታት ይናፍቃሉ
እዚህ ጋ “ዐይኖች” የሚለው ቃል የሚወክለው ያመልካቸው ዘንድ ጣዖታትን የሚመለከትን ሰው ነው። አ.ት፡ “የአባቶቻቸውን ጣዖታት ይናፍቁ ነበር”

Ezekiel 20:25

ከዚያም እኔ ደግሞ መልካም ያልሆኑትን ሥርዓቶችና ሊኖሩበት ያልቻሉባቸውን ሕግጋት ሰጠኋቸው
በዚህ ሐረግ ውስጥ ያለው ሥርዓቶች የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ሕግ አያመለክትም። መልካም ባልሆኑት በሰዎች ሕጎችና ፍርዶች እንዲኖሩ እግዚአብሔር ፈቀደላቸው።

ሰጣቸው
“እነርሱ” የሚለው ቃል እግዚአብሔር ከግብፅ ያወጣቸውን የእነርሱን ልጆች ያመለክታል።

በስጦታዎቻቸው
እዚህ ጋ “ስጦታዎች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰዎች ለሚያመልኳቸው ጣዖታት የሚያቀርቧቸውን መስዋዕት ነው። አ.ት፡ “በመስዋዕቶቻቸው ምክንያት” ወይም “ለጣዖታት ስጦታን ስለ ሰጡ”

የማህፀንን በኩር ሁሉ መስዋዕት አደረጉ
“የማህፀን በኩር” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ከሴት የሚወለደውን የመጀመሪያ ልጅ ነው። “መስዋዕት አደረጉ” የሚለው ሐረግ “መስዋዕት” ከሚለው ግሥ ጋር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “የእያንዳንዷን ሴት የመጀመሪያ ልጅ ሰዉ”

በእሳት እንዲያልፉ አደረጓቸው
ለጣዖቶቻቸው የሚቃጠል መስዋዕት ይሆኑ ዘንድ ልጆቻቸውን በእሳት እንዲያልፉ ማድረጋቸው ግልጽ አይደለም። አ.ት፡ “እንደሚቃጠል መስዋዕት አድርገው ሰዉአቸው”

Ezekiel 20:27

ቁርባን የምታቀርቡበት ይህ ኮረብታ ምንድነው?
እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመገሰጽ ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። አ.ት፡ “ቁርባን የምታመጡበት ይህ ኮረብታ አይደለም!” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ስሙ ባማ ተብሎ ተጠራ
“ባማ” የሚለው ስም ትርጉም ጣዖታት የሚመለኩበት ስፍራ፣ “ኮረብታ” ማለት ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሰዎች ያንን ስፍራ ባማ ብለው ጠርተውታል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 20:30

በአባቶቻችሁ መንገድ ራሳችሁን የምታረክሱት ለምንድነው?
እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመገሰጽ ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። አ.ት፡ “አባቶቻችሁ ያደረጓቸውን ነገሮች በማድረግ ራሳችሁን ማርከስ የለባችሁም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ራሳችሁን የምታረክሱት ለምንድነው
ለእግዚአብሔር ዓላማ ተቀባይነት የሌለው ያ ሰው በአካሉ ጭምር እንደ ረከሰ ተደርጎ ተነግሮለታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አስከፊ ነገሮችን በመፈለግ እንደ ዝሙት አዳሪ የምታደርጉት ለምንድነው?
እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመገሰጽ ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። አ.ት፡ “አስከፊ ነገሮችን እንደምትፈልግ ዝሙት አዳሪ ልታደርጉ አይገባችሁም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

እንደ ዝሙት አዳሪ የምታደርጉት ለምንድነው
ካላገቧት ወንዶች ጋር እንደምትተኛ ሴት ሕዝቡ ታማኝ ስላለመሆኑ እግዚአብሔር ይናገራል። (See: Simile)

ወንዶች ልጆቻችሁ በእሳት እንዲያልፉ በምታደርጉበት ጊዜ
“ወንዶች ልጆቻችሁን እሳት ውስጥ በምትጨምሩበት ጊዜ”። የሚቃጠል ቁርባን አድርገው ወንዶች ልጆቻቸውን እሳት ውስጥ ይጨምሩ እንደነበር ግልጽ አይደለም። ይህ ሐረግ ስጦታቸውን እንዴት አድርገው ይሠዉ እንደ ነበረ ያብራራል

የእስራኤል ቤት ሆይ፣ ታዲያ ትፈልጉኝ ዘንድ ለምን እፈቅድላችኋለሁ?
እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመገሰጽ ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። አ.ት፡ “የእስራኤል ቤት ሆይ፣ እንድትቀርቡኝ አልፈቅድላችሁም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ሕያው እንደ መሆኔ
እግዚአብሔር ቀጥሎ የሚናገረው የተረጋገጠ እውነት መሆኑን ለማሳየት ይህንን አገላለጽ ይጠቀማል። ይህ ጽኑ ተስፋ የመስጫ መንገድ ነው። አ.ት፡ “ጽኑ መሐላ አደርጋለሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 20:33

ሕያው እንደ መሆኔ
“ሕያው መሆኔ እርግጥ የመሆኑን ያህል”። እግዚአብሔር ቀጥሎ የሚናገረው የተረጋገጠ እውነት መሆኑን ለማሳየት ይህንን አገላለጽ ይጠቀማል። ይህ ጽኑ ተስፋ የመስጫ መንገድ ነው። አ.ት፡ “ጽኑ መሐላ አደርጋለሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በብርቱ እጅ፣ በተዘረጋችም ክንድ
“እጅ” እና “ክንድ” የሚሉት ቃላት ሁለቱም የሚወክሉት ኃይልን ነው። አ.ት፡ “በጣም ታላቅ በሆነ ኃይል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእናንተ ላይ የሚፈሰውን ቁጣ
በሕዝቡ ላይ የሚያፈሰው ቁጣው ፈሳሽ የሆነ ነገር ይመስል እግዚአብሔር ቁጣውን ስለ መግለጽ ይናገራል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በእናንተ ላይ የማፈሰው ቁጣ” ወይም “በእናንተ ላይ ቁጣዬን እገልጻለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በተበተናችሁባቸው መካከል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እናንተን በበተንኩባቸው መካከል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 20:36

በበትሬ ስር እንድታልፉ አደርጋችኋለሁ
ይህ በጎቹን በበትሩ ስር እንዲያልፉ በማድረግ የሚቆጥራቸውንና የሚቆጣጠራቸውን የእረኛ ተግባር ያመለክታል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እግዚአብሔር ከየሀገሩ የሚሰበስባቸውን ሕዝቦቹን ሁሉም መኖራቸውን ለማረጋገጥ ይቆጥራቸዋል። አ.ት፡ “እረኛ በጎቹን እንደሚቆጥራቸው በጥንቃቄ እቆጥራችኋለሁ” ወይም 2) ከበትሩ ስር በሚያልፉበት ጊዜ ታማኙን ታማኝ ካልሆነው ለመለየት እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው ይቆጣጠራል። አ.ት፡ “እረኛ በጎቹን እንደሚቆጣጠር በጥንቃቄ እቆጣጠራችኋለሁ” የሚሉት ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 20:39

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እንዲሰሙኝ
“እንዲታዘዙኝ” ወይም “እንዲያደምጡኝ”

ቅዱስ ስሜን መስደብ
እዚህ ጋ “ስም” የሚለው ቃል ራሱን እግዚአብሔርን ይወክላል። አ.ት፡ “እኔን ማዋረድ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 20:40

ይህ የጌታ እግዚአብሔር ቃል ነው
እግዚአብሔር የንግግሩን እርግጠኝነት ለመግለጽ የራሱን ስም በመጥራት ይናገራል። ይህንን በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ጌታ እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን ነው” ወይም “እኔ፣ ጌታ እግዚአብሔር የተናገርኩት ይህንን ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

ቁርባናችሁን ለመጠየቅ
“ቁርባናችሁን እንድታቀርቡ እናንተን ለመጠየቅ”

የመታሰቢያችሁን የመጀመሪያ ፍሬ
እግዚአብሔር ለእርሱ ከሚሰጡት ሁሉ ላይ እጅግ ስለተመረጡት ነገሮች “የመጀመሪያ ፍሬዎች” እንደ ሆኑ አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “እጅግ የተመረጠ ስጦታዎቻችሁን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ቅዱስ ነገራችሁን
“ለእኔ ለመስጠት የለያችኋቸውን ቁርባኖች”

መልካም መዓዛ እንዳለው ዕጣን እቀበላችኋለሁ
እግዚአብሔር ሕዝቡ ራሱ የዕጣን ቁርባን እንደሆኑለት አድርጎ እርሱን ስለሚያመልከው ሕዝቡ ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከሕዝቦች አውጥቼ አመጣችኋለሁ፣ ከየሀገራቱም እሰበስባችኋለሁ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚሉት ተመሳሳይ ነገር ሲሆን እግዚአብሔር ሕዝቡን ከበተነበት ሀገር ሁሉ መልሶ እንደሚያመጣቸው አጽንዖት ይሰጣሉ። ይህንን በሕዝቅኤል 20:34 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። (See: Parallelism)

ከተበተናችሁበት
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እናንተን ከበተንኩበት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 20:42

ለመማል እጄን አንሥቻለሁ
እዚህ ጋ “እጄን አንሥቻለሁ” የሚለው አባባል ለማድረግ የማለውን ነገር በእርግጠኝነት እንደሚያደርገው የሚያሳይ ምልክታዊ ድርጊት ነው። አ.ት፡ “በጽኑ መሐላ ምያለሁ” (See: Symbolic Action)

ትዝ ይላችኋል
የዚህ የአነጋገር ዘይቤ ትርጉም ማስታወስ ማለት ነው። አ.ት፡ “ታስታውሳላችሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ራሳችሁን አርክሳችኋል
ለእግዚአብሔር ዓላማ ተቀባይነትን ያላገኘ ያ ሰው እንደ ረከሰ ተቆጥሮ ተነግሮለታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በዐይኖቻችሁ ፊት ራሳችሁን ትንቃላችሁ
እዚህ ጋ ዐይን ማየትን፣ ማየትም አሳብን ወይም ውሳኔን ይወክላል። አ.ት፡ “ራሳችሁን ትጠላላችሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ስለ ስሜ ስል
እዚህ ጋ “ስም” የሚለው ቃል የሚወክለው የእግዚአብሔርን ዝና ነው። አ.ት፡ “በዝናዬ ምክንያት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 20:45

የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ፊትህን ወደ ደቡቡ ምድር አቅና
ይህ በዚያ የሚኖረውን ሕዝብ የመቅጣት ምልክት ይሆን ዘንድ በደቡቡ ምድር ላይ እንዲያፈጥ የተሰጠ ትዕዛዝ ነው። ተመሳሳዩን ሐረግ በሕዝቅኤል 4፡3 ላይ እንድት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “በደቡቡ ምድር ላይ አፍጥጥ” ወይም “ጉዳት ይደርስባቸው ዘንድ በደቡቡ ምድር ላይ አፍጥጥ” (See: Symbolic Action)

ፊትህን አቅና
እዚህ ጋ “ፊት” ትኩረት የመስጠት ወይም የማፍጠጥ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን “ፊትህ አቅና” ማፍጠጥን ይወክላል። አ.ት፡ “አፍጥጥ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የሚንበለበለውን እሳት አያጠፉትም
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የሚንበለበለው እሳት አይጠፋም” ወይም “የሚንበለበለውን እሳት ማንም ሊያጠፋው አይችልም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ከደቡብ እስከ ሰሜን ያለው ፊት ሁሉ ይቃጠላል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እሳቱ ከደቡብ እስከ ሰሜን ያለውን ፊት ሁሉ ያቃጥላል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ከደቡብ እስከ ሰሜን ያለው ፊት ሁሉ
እዚህ ጋ “ፊት” የሚለው ቃል ሰውዬውን ይወክላል። እግዚአብሔር ተቃራኒዎቹን አቅጣጫዎች በመጥቀሱ በሰሜንና በደቡብ የሚኖሩትን ሁሉ እንዲሁም በመካከል የሚኖሩትን ሁሉ ያመለክታል።

Ezekiel 20:48

ሥጋ ሁሉ ያያል
እዚህ ጋ “ሥጋ” የሰውን ዘር በሙሉ ይወክላል። “ማየት” የሚለው የአነጋገር ዘይቤ መረዳት የሚል ትርጉም አለው። አ.ት፡ “ሰዎች ሁሉ ይረዳሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

አያጠፉትም
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አይጠፋም” ወይም “ማንም አያጠፋውም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ወይኔ!
ጭንቀትን ወይም ሀዘንን የሚገልጽ ቃል ነው

እርሱ ምሳሌ ብቻ የሚናገር አይደለም?
ሕዝቡ ሕዝቅኤልን ለመስደብና የሚነግራቸውን ውድቅ ለማድረግ ይህንን ጥያቄ ይጠቀማሉ። አ.ት፡ “እርሱ የሚናገረው ምሳሌ ብቻ ነው” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 21

1 የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ። 2 "የሰው ልጅ ሆይ፥ ፊትህን ወደ ኢየሩሳሌም አቅና በመቅደሶችም ላይ ተናገር፤ በእስራኤልም ምድር ላይ
ትንቢት ተናገር። 3 ለእስራኤልም ምድር እንዲህ በል፥ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እነሆ፥ በእናንተ ላይ ነኝ፥ ሰይፌንም ከሰገባው እመዝዘዋለሁ፥ ጻድቁንና
ክፉውንም ከእናንተ ዘንድ አጠፋለሁ። 4 እኔም ጻድቁንና ክፉውን ከእናንተ ዘንድ ስለማጠፋ፥ ሰይፌ ከደቡብ ጀምሮ እስከ ሰሜን ድረስ ባለ በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ
ከሰገባው ይመዘዛል። 5 ሥጋ ለባሹም ሁሉ እኔ እግዚአብሔር ሰይፌን ከሰገባው እንደ መዘዝሁ ያውቃል፥ ስይፌም ከእንግዲህ አይመለስም! 6 ስለዚህም፥
አንተ የሰው ልጅ ሆይ፥ አልቅስ ወገብህን በማጕበጥ በፊታቸው ምርር ብለህ አልቅስ። 7 እነርሱም 'ስለ ምን ታለቅሳለህ?' ብለው ይጠይቁሀል፥ አንተም እንዲህ
ትላቸዋለህ፥ 'ስለሚምጣው ክፉ ዜና ነው፥ ምክንያቱም ልብ ሁሉ ይቀልጣል፥ እጆችም ሁሉ ይዝላሉ፥ ነፍስም ሁሉ ትደክማለች፥ ጕልበትም እንደ ውኃ ይፈስሳል።
እነሆ፥ ይመጣል ይፈጸምማል፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር'" 8 የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ። 9 የሰው ልጅ ሆይ፥ 'እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል ብለህ ትንቢት ተናገር ሰይፍ! ሰይፍ! የተሳለና የተወለወለ ሰይፍ በል። 10 ለታላቅ ግድያ ተስሎአል! እንደመብረቅም እንዲያብረቀርቅ ይወለወላል!
በልጄን በትረ መንግስት ደስ ሊለን ይገባልን? የሚመጣው ስይፍ የዚህ አይነቱን በትር ይጠላል። 11 ሰይፉም እንዲወለወልና በእጅ እንዲያዝ ይሰጣል! ሰይፉ
የትሳል ነው! ለገዳይም ሊስጥ ተወልውሎ ተዘጋጅቷል!' 12 የሰው ልጅ ሆይ፥ ሰይፉ እየመጣ ያለው በሕዝቤ ላይ ነውና፥ ለሰይፉም የሚሰጡት የእስራኤል
አለቆች ሁሉ ናቸውና ለእርዳታ ተጣራ፥ አልቅስ! ሕዝቤ ነበሩና ስለዚህ ጭንህን በምሬት ጽፋ! 13 ፈተና ደርሶአል፥ በትረ መንግስት ቢጸና ምን ዋጋ አለው? ይላል
ጌታ እግዚአብሔር፦ 14 ስለዚህ፥ አንተ የሰው ልጅ፥ ትንቢት ተናገር፥ እጅህን አጨብጭብ ሰይፍ ለሶስተኛ ጊዜ ጥቃት ይፈጽማልና! ለሚታረዱ የተዘጋጅ ስይፍ!
ሰውነታቸውን ሁሉ ሊወጋ ለሚታረዱ ለብዙዎች ሰዎች የተመደበ ሰይፍ ነው! 15 ልባቸው እንዲቀልጥ መሰናክላቸውም እንዲበዛ የሚገድለውን ሰይፍ
በበሮቻቸው ሁሉ ላይ አድርጌአለሁ! ወዮ! እንድመብረቅ ሆኗል እንዲገድልም ነጻ ተለቋል። 16 ሰይፍ ሆይ ተዘጋጅ! ስለትህ ወደፈቀደው ወደ ቅኝም ወደ ግራም
ምታ። 17 እኔ ደግሞ በእጄ አጨበጭባለሁ መዓቴንም እፈጽማለሁ! እኔ እግዚአብሔር ተናግሬአለሁ።" 18 የእግዚአብሔርም ቃል እንደገና ወደ እኔ እንዲህ
ሲል መጣ፥ 19 "አንተም የሰው ልጅ ሆይ፥ የባቢሎን ንጉሥ ሰይፍ ይመጣ ዘንድ ሁለት መንገዶችን አድርግ። ሁለቱም መንገዶች ከአንድ ምድር ይነሳሉ፥
የመንገድ ምልክቱም አንደኛው መንገድ ወደ ከተማ እንድሚወስድ ያሳያል። 20 አንዱ መንገድ የባቢሎን ጦር ወደ አሞናዊያን ከተማ ወድ ረባት እንድሚወስድ
አመልክት። ሌላኛው መንገድ ወደ ይሁዳ ወደ ተመሸገች ወደ ኢየሩሳሌም እንድሚወስድ አመልክት። 21 የባቢሎን ንጉሥ የጥንቆላ ምሪት ለማግኘት በመንታ
መንገድ መታጠፊያ ላይ ይቆማል። ፍላጾችን ይወዘውዛል፥ ከጣዖታቱም ምሪት ይጠይቃል። ጉበትም ይመለከታል። 22 የቅጥሩን ማፍረሻ ያደርግ ዘንድ፥
አፍንም በጩኸት ይከፍት ዘንድ፥ በውካታም ድምፅን ከፍ ያደርግ ዘንድ፥ የቅጥሩን ማፍረሻ በበሮች ላይ ያደርግ ዘንድ፥ አፈርን ይደለድል ዘንድ፥ ምሽግም ይሠራ
ዘንድ የኢየሩሳሌም ዕጣ በቀኝ እጁ ውስጥ ነበረ። 23 በኢየሩሳሌም ላሉ ለባቢሎናዊያን መሐላን ማሉ ዓይን ፊት የሐሰት ምዋርት ይመስላል፥ ነገር ግን ንጉሱ
እንዲያዙ ለማድረግ ስምምነታችሁን አፍርሳችኋል ብሎ ይከሳቸዋል። 24 ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ኃጢአታችሁን እንዳስብ ስላደርጋችሁኝ
መተላለፋችሁ ይገለጣል! ኃጢአታችሁም በሥራችሁ ሁሉ ይታያል! በዚህም ምክንያት በጠላቶቻችሁ እጅ እንደተያዛችሁ ስውን ሁሉ ታሳስባላችሁ! 25 አንተም
የምትቀጣበት ቀን የደረስብህ ፥ አመጻ የማድረጊያ ዘመን ያበቃብህ፥ አመጸኛና ክፉ የእስራኤል አለቃ ሆይ፥ 26 ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦
መጠምጠሚያውን አውልቅ፥ ዘውዱንም ከራስህ ላይ አንሳ! ከእንግዲ ነገሮች እንደነበሩ አይቀጥሉም! የተዋረደውን ከፍ አድርግ፥ ከፍ ያለውንም አዋርድ። 27
ባድማ፥ ባድማ፥ ሁሉንም ባድማ አደርጋለሁ! የሚገባው ሰው እስኪመጣና ለእርሱ እስከምሰጠው ድረስ ንግስና ከእንግዲህ አይኖርም። 28 አንተም የሰው ልጅ
ሆይ፥ 'ጌታ እግዚአብሔር ስለሚመጣባቸው ውርደት ለአሞን ልጆች እንዲህ ይላል፡ ሰይፍ፥ ሰይፍ ተመዟል! ለማጥፋትና ለመግደል ተስሏል፤ እንደመብረቅም
ያብለጨልጫል! 29 ነቢያት ባዶ ራዕይ እያዩልህና ምዋርት እያሟረቱልህ ሳለ ይህ ሰይፍ ሊገደሉ ባሉት የሚቀጡበት ቀን በደረሰባቸው የእመጽ ዘመናቸው
ባበቃባቸው ሰዎች አንገት ላይ ያርፋል። 30 ሰይፉን ወደ ሰገባውም መልሰው። በተፈጠርህበት ስፍራ በተወለድህባትም ምድር እፈርድብሃለሁ! 31 ቊጣዬንም
አፈስስብሃለሁ! የመዓቴም እሳት አናፋብሃለሁ፥ በማጥፋት ለተካኑ ለጨካኞች ሰዎች እጅ አሳልፌ እሰጥሃለሁ! 32 ለእሳት ማገዶ ትሆናለህ! ደምህም
በምድሪቱ መካከል ይፈሳል፥ መታሰቢያም አይኖርህም፥ እኔ እግዚአብሔር ተናግሬአለሁና።

Ezekiel 21:1

የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የሰው ልጅ
“የሰብዓዊ ፍጡር ልጅ” ወይም “ከሰው የተወለደ ልጅ” ወይም “ሟች ሰው” ወይም “ሰው”። ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን አፅንኦት ለመስጠት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ በማለት ይጠራዋል። እግዚአብሔር ዘላለማዊና ኃያል ነው፣ ሰዎች ግን አይደሉም። ይህንን በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ፊትህን በኢየሩሳሌም አቅጣጫ አቅና
ይህ በዚያ የሚኖሩ ሰዎች እንደሚቀጡ ምልክት ይሆናቸው ዘንድ በኢየሩሳሌም አቅጣጫ እንዲያፈጥ የተሰጠ ትዕዛዝ ነው። አ.ት፡ “በኢየሩሳሌም ላይ አፍጥጥ” ወይም “በዚያ የሚኖሩ ሰዎች ጉዳት እንዲደርስባቸው በኢየሩሳሌም ላይ አፍጥጥ”

ፊትህን በኢየሩሳሌም አቅጣጫ አቅና
ኢየሩሳሌም ርቀት ላይ ነበረች፣ በመሆኑም ሕዝቅኤል ሊያያት አይችልም፣ ነገር ግን በዚያ አቅጣጫ ማፍጠጡ እርሷን የመጉዳት ምልክት ይሆናል። ተመሳሳዩን ሐረግ በሕዝቅኤል 6:2 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ወደ ኢየሩሳሌም ዙርና አፍጥጥ” ወይም “በዚያ ያሉ ሰዎች ጉዳት እንዲደርስባቸው በኢየሩሳሌም አቅጣጫ አፍጥጥ”

ሰይፌን ከሰገባው እመዛለሁ፣ ከአንቺም ጻድቁንና ክፉዉን ሰው እቆርጣለሁ
ይህ፣ እግዚአብሔር እነዚህን ሰዎች በራሱ ሰይፍ የገደላቸው በሚመስልበት መልኩ እንዲሞቱ እንደሚያደርጋቸው ይናገራል። አ.ት፡ “እናንተን ተቃውሜአለሁ፤ ይኸውም፣ በመካከላችሁ ያሉትን ጻድቃኑንና ክፉዎቹን ሰዎች ለመግደል ሰይፌን ከሰገባው የመዘዝኩ ያህል ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ጻድቁንና ክፉዉን ሰው
“ጻድቅ ሰዎችና ክፉዎች ሰዎች”። ይህ የሚያመለክተው አንድ ጻድቅን እና አንድ ክፉ ሰውን ብቻ ሳይሆን በጣም ብዙ ሰዎችን ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሰገባ
ማንም በማይጠቀምበት ጊዜ ሰይፉን የሚይዘውና የሚሸፍነው ነገር ነው

ቁረጥ
ይህ የግደል ሻል ያለ ቃል ነው። አ.ት፡ “ግደል”

Ezekiel 21:4

ቁረጥ
ይህ የግደል ሻል ያለ ቃል ነው። አ.ት፡ “ግደል”

ጻድቁ . . . ክፉዉ
ይህ የሚያመለክተው ጻድቅና ክፉ የሆኑትን ሰዎች ነው። አ.ት፡ “እነዚያ ጻድቃን የሆኑትን … እነዚያ ክፉ የሆኑትን” ወይም “ጻድቅ ሕዝቦች … ክፉዉች ሕዝቦች” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

ከእናንተ
“በመካከላችሁ”

በእነርሱ ላይ ሰይፌ ይመዘዛል
ይህ እግዚአብሔር በራሱ ሰይፍ የገደላቸው በሚመስልበት መልኩ እነዚህ ሰዎች እንዲሞቱ እንደሚያደርጋቸው ይናገራል። አ.ት፡ “ይኸውም፣ ሰይፌን ከሰገባው መዝዤ የመታኋቸው ያህል ይሆናል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሥጋ ሁሉ
እዚህ ጋ “ሥጋ” በፈሊጣዊ አነጋገር “ሰዎች” የሚለውን ያመለክታል። አ.ት፡ “ሰዎች ሁሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከደቡቡ እስከ ሰሜኑ
ይህ የሰሜኑን እና የደቡቡን እንዲሁም በመካከል ያለውን ሁሉ የሚያመለክት አነጋገር ነው። አ.ት፡ “በሁሉም አቅጣጫ” ወይም “በሁሉም ቦታ”

እኔ እግዚአብሔር ሰይፌን ከሰገባው መዝዣለሁ
ይህ እግዚአብሔር በራሱ ሰይፍ የገደላቸው በሚመስልበት መልኩ እነዚህ ሰዎች እንዲሞቱ እንደሚያደርጋቸው ይናገራል። አ.ት፡ “እርሱም፣ እኔ እግዚአብሔር ሕዝቡን በሰይፌ የገደልኳቸው ያህል ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ወደ ኋላ አይመለስም
ይህ፣ ሰይፉ ከማጥቃት የማይመለስ ሰውን ይመስል፣ የእግዚአብሔር ሰይፍ ሕዝቡን ከመግደል እንደማይመለስ ይናገራል። አ.ት፡ “ዳግመኛ ወደ ሰገባው አልመልሰውም” ወይም “ሰዎችን ከመግደል አልመለስም” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 21:6

ወገቡ እንደ ተቆረጠ ሰው አቃስት
የመልዕክቱ አጃቢ ምልክት እንዲሆንለት ያቃስት ዘንድ እግዚአብሔር ለሕዝቅኤል ይነግረዋል። ሆዱን በብርቱ የታመመ ያህል በኃይል እንዲያቃስት ይነግረዋል። “ወገብህ በታላቅ ሕመም ላይ እንዳለ ያህል በኃይል አቃስት” ወይም “ከታላቅ ሀዘን ጋር በኃይል አቃስት”(የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በምሬት አቃስት
“ከታላቅ ሀዘን ጋር” ወይም “በመሪር ሀዘን”

በዐይኖቻቸው ፊት
እዚህ ጋ እስራኤላውያን ስላዩት ነገር አጽንዖት ለመስጠት በ”ዐይኖቻቸው” ተወክለዋል። አ.ት፡ “በፊታቸው” ወይም “በእስራኤል ሕዝብ ፊት”

እየመጣ ያለው ወሬ
ይህ በቶሎ ወደ እነርሱ እንደሚመጣ ሰው ተደርጎ የተነገረው ስለ “ወሬ” ነው። አ.ት፡ “በቅርቡ የሚሰሙት ወሬ” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

ልብ ሁሉ ይቀልጣል
ይህ ልባቸው የሚቀልጥ ይመስል ሰዎች እንደሚፈሩ ይናገራል። በተጨማሪም፣ ይህ ከፍርሐት የተነሣ ራሳቸውን እንደሚስቱ ይናገራል። አ.ት፡ “እያንዳንዱ ይፈራል” (Synecdoche እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ይደናቀፋል
“ይደክማል”

መንፈስ ሁሉ ይዝላል
ይህ የሚናገረው መንፈሳቸው ይዝል ይመስል ሰዎች በመንፈሳቸው እንደሚፈሩ ይናገራል። አ.ት፡ “ሁሉም በውስጥ ሰውነቱ ይፈራል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ጉልበት ሁሉ እንደ ውሃ ይፈሳል
“ጉልበት ሁሉ እንደ ውሃ ይደክማል”። ይህ ሰዎች ከብርቱ ፍርሐታቸው የተነሣ ፊኛቸውን መቆጣጠር ተስኗቸው በራሳቸው ላይ እንደሚሸኑ የሚያመለክት አነጋገር ነው። አ.ት፡ “እግር ሁሉ በሽንት ይረጥባል” ወይም “እያንዳንዱ ሽንቱን መቆጣጠር ያቅተዋል”

ይህ የጌታ እግዚአብሔር ቃል ነው
እግዚአብሔር የንግግሩን እርግጠኝነት ለመግለጽ የራሱን ስም በመጥራት ይናገራል። ይህንን በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ጌታ እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን ነው” ወይም “እኔ፣ ጌታ እግዚአብሔር የተናገርኩት ይህንን ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 21:8

የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ሰይፍ! ሰይፍ! ተስሏል፣ ተወልውሏልም
ይህ ምንባብ እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ለማጥቃት የሚጠቀምባቸውን የጠላት ሰራዊት በዘይቤአዊ አነጋገር የእግዚአብሔርን ሰይፍ በማለት ይገልጸል።ይህ ዘይቤአዊ አነጋገር እዚህ ጋ ይጀምርና እስከ ሕዝቅኤል 21፡17 ድረስ ይቀጥላል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ተስሏል፣ ተወልውሏልም
ይህ ሐረግ የሚያመለክተው ሰይፉ አንድ ሰው እንዲጠቀምበት መዘጋጀቱን ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የተሳለና የተወለወለ ነው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ተወልውሏል
አንድ ሰው በሻካራ ነገር በመጥረግ ሰይፉ ስለታም፣ አንጸባራቂና ንጹሕ እንዲሆን አድርጎታል።

Ezekiel 21:10

ተስሏል፣ … ለድረግ ተወልውሏል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እስለዋለሁ… ያደርግ ዘንድ እወለውለዋለሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መብረቅ እንዲመስል
ይህ ማለት ሰይፉ በቀላሉ ብርሃን ማንጸባረቅና ፈክቶ መታየት የሚችል አንጸባራቂ ይሆናል። አ.ት፡ “እንደ መብረቅ እንዲያብረቀርቅ” ወይም “ብርሃን በእርሱ ላይ እንደ መብረቅ እንዲያንጸባርቅበት” (See: Simile)

በልጄ በትረ መንግሥት መደሰት ይኖርብናል?
ይህ ምላሽ የማይሻ ጥያቄ “ሰይፍ” መቋቋም ስለማይችል የእስራኤል ሕዝብ የንጉሣቸውን ሥልጣን እንደማያከብሩ አጽንዖት ይሰጣል። አ.ት፡ “የይሁዳ ሕዝብ የንጉሣቸውን በትረ መንግሥት አያከብሩም” ወይም “የንጉሣችንን በትረ መንግሥት ኃይል ማክበር የለብንም”። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ይኖርብናል?
“እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሕዝቅኤልን እና የእስራኤልን ሕዝብ ነው። (See: Inclusive “We”)

በልጄ በትረ መንግሥት
እዚህ ጋ እግዚአብሔር የይሁዳን ንጉሥ እንደ ልጁ አድርጎ ያመለክታል። የንጉሡ በትረ መንግሥት ንጉሣዊ አገዛዙን ይወክላል። እዚህ ጋ “እንዲህ ያለው በትር ሁሉ” የሚሉት ቃላት በትረ መንግሥትን ስለሚያመለክቱ የንጉሡን በትረ መንግሥት ምስል ማቆየቱ አስፈላጊ ነው። አ.ት፡ “በንጉሡ በትረ መንግሥት” ወይም “የንጉሡ በትረ መንግሥት በሚወክለው ሥልጣን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የሚመጣው ሰይፍ እንዲህ ያሉትን በትሮች ሁሉ ይጠላል
እዚህ ጋ “ሰይፍ” ሰዎችን ሊያጠቃ እንደሚመጣ በሰውኛ ተገልጿል። ይህ፣ “ሰይፍ” የንጉሡን በትረ መንግሥት የጠላው ይመስል፣ ንጉሡ “ሰይፍ”ን መቋቋም ያለመቻሉን ይናገራል። አ.ት፡ “ሰይፍ እንደ ማንኛውም ገዢ በእርሱ በትረ መንግሥት ላይ የበላይ ይሆናል” ወይም “ንጉሡ ሰይፍ በሚመጣበት ጊዜ መቋቋም አይችልም” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

እንዲህ ያለው በትር
ይህ ሐረግ በንጉሡ በትረ መንግሥት ላይ “በትር” ብሎ ለመሳለቅ ጥቅም ላይ ውላል። አ.ት፡ “እንዲህ ያለው በትረ መንግሥት” (ምጸት የሚለውን ተመልከት)

ሰይፉ እንዲወለወል ይሰጣል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሰይፉን እወለውለዋለሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ከዚያም በእጅ የሚያዝ ይሆናል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ከዚያም ተገቢነት ያለው ሰው በእጁ ይይዘዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እርሱም በሚገድለው ሰው እጅ ላይ ይሰጣል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ገዳዩ እንዲጠቀምበት ተዘጋጅታል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 21:12

ያ ሰይፍ በሕዝቤ ላይ መጥቷል! እርሱ በሁሉ ላይ ነው
ሰይፍ በራሱ ገዳይ የሆነ ይመስል ይህ የሚናገረው ሕዝቡን ስለሚገድለው የእግዚአብሔር ሰይፍ ነው። አ.ት፡ “ሕዝቤን ለመግደል ሰይፌን እጠቀምበታለሁ! እርሱን በሁሉም ላይ አመጣዋለሁ” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

እነርሱ ከሕዝቤ ጋር ለሰይፍ ተጥለዋል
ለሰይፍ የተጣሉ በሚመስልበት ሁኔታ ይህ የሚናገረው በሰይፍ ስለ ተገደሉት የእስራኤል መሪዎች ነው። አ.ት፡ “እነርሱ ከሕዝቤ ጋር በሰይፍ ተገድለዋል” ወይም “ሰይፍ ከሕዝቤ ጋር ይገድላቸዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ታፋህን ምታ
በሕዝቅኤል ባህል አንድ ሰው ታፋውን መምታቱ የሀዘን ምልክት ነበር። አንዳንድ ትርጉሞች በብዙዎች ባህል የሀዘን ምልክት የሆነውን ደረት መምታትን ይጠቀማሉ። አ.ት፡ “ደረትህን ምታ” (ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ተመልከት)

ይሁንና በትረ መንግሥቱ ዘለቄታ ባይኖረውስ?
ይህ ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ጥቅም ላይ የዋለው አድማጮች ምን ሊሆን እንደሚችል እንዲያስቡ ለማድረግ ነው። ይህ ጥያቄ እንደ ንግግር ሊጻፍ ይችላል። አ.ት፡ “በትረ መንግሥቱን ሰይፍ የሚያጠፋው ከሆነ በጣም አስፈሪ ይሆናል” ወይም “ይሁን እንጂ ንጉሡ ሊቋቋመው ካልቻለ በጣም አስፈሪ ይሆናል”። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

በትረ መንግሥቱ
x

Ezekiel 21:14

በሁለት እጆችህ አጨብጭብ
ይህ የሀዘኑ ምልክት እንዲሆን እጆቹን ያጨበጭባል ማለት ነው። አ.ት፡ “በጣም ማዘንህን ለማሳየት እጆችህን አጨብጭብ” (ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ተመልከት)

ለሦስተኛ ጊዜ እንኳን
ይህ ብዙ ጊዜ የማለት የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ደጋግመህ” (ደረጃን አመልካች ቁጥሮች እና የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ሊታረድበት ያለ ሰይፍ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሰዎችን ለማረድ የሆነ ሰይፍ ነው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ብዙዎች ሊታረዱበት ያለ ሰይፍ ነው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ብዙ ሰዎችን ለማረድ የሆነ ሰይፍ ነው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በየስፍራው የሚወጋቸው
“ከየአቅጣጫው የሚወጋቸው”። ይህንን አንዳንድ መጽሐፍ ቅዱሶች “ወደ ክፍሎቻቸው የሚገቡ” ብሎ ይተረጉመዋል። ይህ፣ ሰይፉ ስለሚገድላቸው የትም ቢደበቁ ችግር የለውም ማለት ነው።

የሚወጋቸው
“እነርሱን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የኢየሩሳሌምን ሕዝብና የእስራኤልን ምድር ነው።

Ezekiel 21:15

ልባቸውን ለማቅለጥ
ይህ ልባቸው ይቀልጥ ይመስል ሕዝቡ በጣም እንዲፈሩ እንደሚያደርጋቸው ይናገራል። አ.ት፡ “በሽብር እንዲሞሉ” ወይም “እንዲፈሩ ለማድረግ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የሚወድቁት እንዲበዙ
እዚህ ጋ “መውደቅ” የሚያመለክተው በጦርነት የሚሞቱትን ሰዎች ነው። ይህ ማለት እጅግ ብዙ ቁጥር ያለው ሕዝብ ይገደላል። አ.ት፡ “በመካከላቸው ብዙ ሕዝብ ለመግደል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሰይፉን ለማረድ አስቀምጫለሁ
እዚህ ጋ የእግዚአብሔር ሰይፍ ኢየሩሳሌምን በሰይፍ የሚያጠቁ ሰዎችን ይወክላል። ደግሞም፣ “ማረድ” የሚለው ቃል እንደ ግሥ ሊገለጽ ይችላል። አ.ት፡ “ሕዝቡን ለማረድ ሰይፍ የታጠቁ ወታደሮች በሮቻቸው ላይ ሰፍረዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

በሮቻቸው
“የእነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ነው።

እንደ መብረቅ ተደርጓል
ይህ ሰይፉ በሚገባ መወልወሉንና ብርሃንን እንደ መብረቅ እንደሚያንጸባርቅ ያነጻጽራል። አ.ት፡ “ሰይፌ ተወልውሏል፣ እንደ መብረቅም ያብረቀርቃል” ወይም “እርሱ ተወልውሏል፣ እንደ መብረቅም ብርሃንን ያንጸባርቃል”

ለማረድ ተይዟል
የእግዚአብሔር ሰይፍ ኢየሩሳሌምን በሰይፍ የሚያጠቁ ሰዎችን ይወክላል። አ.ት፡ “ሕዝቡን ለማረድ ተለቋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አንተ ሰይፍ! ወደ ቀኝ ምታ! ... ፊትህ በዞረበት አቅጣጫ ሁሉ ሂድ
እዚህ ጋ ሰይፍ የሚሰማውና በጦርነቱ ጥቅም ላይ ይውል ይመስል እግዚአብሔር የሚናገረው ሕዝቡን ስለሚያጠቁት ስለ እነዚያ ሰዎች ነው። ይህንን ያደረገው በጦርነቱ ጊዜ የሚሆነውን እርሱ እንደሚቆጣጠረው አጽንዖት ለመስጠት ነው። “ፊትህ በዞረበት አቅጣጫ ሁሉ” የሚለው ሐረግ “ልትሄድ ወደምትፈልግበት ሁሉ” ለሚለው የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “በሰይፍ ለሚያጠቁት ለእነርሱ እነግራቸዋለሁ፣ ‘ወደ ቀኝ ምቱ! ... በየአቅጣጫው አጥቁ’” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ሁለቱን እጆቼን አጋጨሁ
“እጆቼን አጨበጨብኩ”። እዚህ ጋ እጆችን ማጨብጨብ ድል የማድረግ ምልክት ነው። አ.ት፡ “በድል አድራጊነት እጆቼን አጨበጨብኩ” (ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 21:18

የእግዚአብሔር ቃል እንደ ገና ወደ እኔ መጣ
“የእግዚአብሔር ቃል መጣ” የሚለው ሐረግ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 18፡1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እግዚአብሔር እንደገና ተናገረኝ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የባቢሎን ንጉሥ ሰይፍ
“ሰይፍ” የሚለው ቃል ሰይፍን በመጠቀም ሰዎችን የሚገድሉትን ወታደሮች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “የባቢሎን ንጉሥ ወታደሮች” ወይም “የባቢሎናውያን ሰራዊት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከእነርሱ አንዱ ወደ ከተማ የሚመራቸው የመንገድ ምልክት ይሆናል
ይህ መንገዱ ለሁለት በሚከፈልበት ቦታ ላይ የሚደረግ ምልክት ነው። አ.ት፡ “መንገዱ ወደ ሁለት መንገድነት በሚከፈልበት ቦታ ላይ ምልክት ይቆማል”

Ezekiel 21:21

በመስቀለኛው መንገድ፣ በመጋጠሚያው ላይ
እነዚህ ሁለቱም ሐረጎች የሚያመለክቱት ሁለት መንገዶች የሚገናኙበትን ስፍራ ነው። አ.ት፡ “በመስቀለኛ መንገድ ላይ”

ጥቂት ቀስቶችን ይወዘውዛል፣ ከአንዳንድ ጣዖታቱ ምሪት ይጠይቃል፣ ጉበትንም ይመረምራል
እነዚህ የጥንቆላ ልምምዶች ናቸው።

በቀኝ እጁ ላይ የኢየሩሳሌም ምልክት ይኖራል
ይህ ማለት በቀኝ እጁ በኢየሩሳሌም ላይ እንደ ምልክት ያነበበውን፣ ከጥንቆላ ዕቃዎቹ አንዱን ይይዛል። አ.ት፡ “በኢየሩሳሌም ላይ ምልክት የተደረገበት ከጥንቆላ ዕቃዎቹ አንዱ በቀኝ እጁ ላይ ይሆናል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ቅጥር መደርመሻ
ቅጥር መደርመሻ የተቆረጠ ዛፍ ወይም ጫፉ የሾለ ረጅም ምሶሶ ወይም ጫፉ በብረት የተሸፈነ ነው። ይህ ጫፉን ግንቡ ላይ ለማስደገፍ ብዙ ሰዎች የሚጎትቱት ነበር።

መወጣጫ ለመሥራት
እነዚህ ባቢሎናውያን ወታደሮች በኢየሩሳሌም ግንቦች ላይ መውጣት እንዲችሉ የሠሯቸው ረጃጅም የቆሸሹ መወጣጫዎች ነበሩ።

ማማዎችን መመሸግ
እነዚህ ባቢሎናውያን ወታደሮች የኢየሩሳሌምን ግንብ አሳልፈው ቀስቶችን ለማስወንጨፍ እንዲያስችላቸው በኢየሩሳሌም ዙሪያ የሠሯቸው የእንጨት ማማዎች ነበሩ።

በኢየሩሳሌም ባለ ሰው ዐይን ፊት
ዐይን ማየትን፣ ማየትም አሳብን ወይም ውሳኔን ይወክላል። አ.ት፡ “በኢየሩሳሌም በሚኖሩ ሰዎች አስተሳሰብ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 21:24

ምክንያቱም በደላችሁ እንዲታሰብ አድርጋችኋል
“ምክንያቱም ኃጢአታችሁን እንዳስብ አድርጋችሁኛል”

በምትሠሩት ሁሉ ኃጢአታችሁ ይታይ ዘንድ መተላለፋችሁ እንዲገለጥ በማድረግ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በሥራዎቻችሁ ሁሉ እያንዳንዱ ኃጢአታችሁን ማየት ይችል ዘንድ መተላለፋችሁን በመግለጥ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 21:25

የመቀጣቱ ቀን የደረሰበት
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “እግዚአብሔር አሁን የሚቀጣው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ኃጢአት የመሥሪያ ጊዜው ያበቃለት
“እግዚአብሔር ኃጢአትን በሚያስቀርበት ጊዜ”

ጥምጥም
“የንጉሥ ጥምጥም”። ጥምጥም ነገሥታት የሥልጣናቸው ምልክት እንዲሆን በራሳቸው ላይ የሚለብሱት የተዋበ አነስተኛ ጨርቅ ነው።

ዝቅ ያለው ... ከፍ ያለው
ይህ የሚያመለክተው ዝቅ ያለ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉትን ሰዎችና የከበሩትን ሰዎች ነው። አ.ት፡ “እነዚያ ዝቅ ያሉትን ... እነዚያ ከፍ ያሉትን” ወይም “እነዚያ ዝቅ ያለ የኑሮ ደረጃ ያላቸውን ... እነዚያ ከፍ ያለ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉትን” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

አይታደስም
እዚህ ጋ ዘውድ የንጉሡን ኃላፊነት ይወክላል። መሲሑ እስኪመጣ ድረስ ንግሥና አይታደስም። አ.ት፡ “ከዚያ በኋላ ንጉሥ አይኖርም” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የተመደበው እርሱ ይመጣል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እኔ የመደብኩት ይመጣል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ezekiel 21:28

ሰይፍ፣ ሰይፍ ተመዟል! እርሱ ለአራጁ ተስሏል
ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ሰይፍ ሲሆን በዘይቤአዊ አነጋገር ለእርሱ ያልታዘዙትን ብዙ ሰዎች እንዲገድሉ እግዚአብሔር የሚጠቀምባቸውን ወታደሮች ነው። አ.ት፡ “ሰይፍ! ወታደሮቼ ሰይፋቸውን መዘዋል! ለእርዱ ተስለዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ተመዟል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ከሰገባው ወጥቷል”

ይበላ ዘንድ ለማረድ ተስሏል
ይህ የሚናገረው ያደኑትን የሚበሉ እንስሶችን ይመስል ሰዎችን ስለሚገድሉ ወታደሮች ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እርሱ ሰዎችን ለማረድና ለመግደል የተሳለ ነው”

እርሱ እንደ መብረቅ ነው
ይህ ማለት ሰይፉ ብርሃንን በቀላሉና በብሩህነት የሚያንጸባርቅ በጣም አብረቅራቂ ነው። አ.ት፡ “ብርሃን በእርሱ ላይ ሲያርፍበት የመብረቅ ያህል ብሩህነቱን ያንጸባርቃል” (See: Simile)

ለእናንተ ባዶ ራዕዮችን ... ለእናንተ ከውሸት ጋር
“ለእናንተ ለአሞናውያን ባዶ ራዕዮችን ... ለእናንተ ለአሞናውያን ከውሸት ጋር”። “እናንተ” የሚለው ቃል የአሞንን ሕዝብ ያመለክታል። በመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋ፣ “የእናንተ” የሚለው ቃል ነጠላ እንስታይ ጾታ ሲሆን የሚያመለክተው የአሞንን ሀገር ነው። አብዛኛውን ጊዜ ሀገራት በሴት ይታሰቡ ነበር። (ተባዕታዊ ቃል ሴቶችን ሲጨምር የሚለውን ተመልከት)

ባዶ ራዕዮች
ይህ በባዶ ዕቃ በተመሰሉበት ሁኔታ ውሸትና ትርጉም የለሽ ስለሆኑ ራዕዮች ይናገራል። አ.ት፡ “እውነት ያልሆኑ ራዕዮች” ወይም “ሐሰተኛ ራዕዮች” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ክፉዎቹ
ይህ ክፉ ሰዎችን ያመለክታል። አ.ት፡ “እነዚያ ክፉ የሆኑት”(ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

ሊገደሉ ያሉት
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሊሞቱ ያሉት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የቅጣታቸው ቀን የደረሰና የኃጢአት ጊዜአቸው የሚያበቃላቸው
“የ-- ቀን” እና “የ-- ጊዜ” የሚሉት ሐረጎች የአነጋገር ዘይቤዎች ናቸው። አ.ት፡ “የሚቀጡበት ጊዜ መጥቷል፣ ኃጢአታቸው የሚያበቃበትም” ወይም “ልቀጣቸው ጊዜዬ ደርሷል፣ ለእነርሱ ደግሞ ከእንግዲህ ክፋትን ማድረግ ላይችሉ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 21:30

ሰይፉን ወደ ሰገባው መልሰው
“በኋላ ሰይፉ ወደ ሰገባው ውስጥ ተመልሶ ይከተታል”። የእግዚአብሔር ሰይፍ ወደ ሰገባው ተመልሶ ይከተታል በማለት ወታደሮች ኢየሩሳሌምን ከማጥቃት እንደሚመለሱ ይህ ይናገራል። አ.ት፡ “በኋላ ግን የማረድ ጊዜ ስለሚያበቃ ወታደሮች ሰይፎቻቸውን ወደ ሰገባዎቻቸው ይመልሳሉ”

ሰገባ
ማንም በማይጠቀምበት ጊዜ ሰይፉን የሚይዘውና የሚሸፍነው ነገር ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 21:3 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።

በተፈጠርክበት ቦታ
“መፈጠር” የሚለው ቃል ምናልባት እንደ ግሥ መገለጽ ይኖርበታል። አ.ት፡ “አንተን በፈጠርኩበት ቦታ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

መዓቴን አፈስብሃለሁ
ይህ የእግዚአብሔር መዓት ፈሳሽ ሆኖ ከመያዣ ዕቃው ውስጥ በእነርሱ ላይ የሚያፈሰው በሚመስልበት መልኩ ከመዓቱ የተነሣ እርሱ ባቢሎናውያንን እንደሚቀጣቸው ይናገራል። አ.ት፡ “በአንተ ላይ ከሚሆነው መዓት የተነሣ እቀጣሃለሁ” ወይም “ከቁጣዬ የተነሣ እቀጣሃለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በአንተ ላይ የቁጣዬን እሳት አረግባለሁ
ይህ የእግዚአብሔርን ቁጣ ከሚያቃጥል እሳት ጋር ያወዳድራል። አ.ት፡ “በአንተ ላይ ቁጣዬን እንደሚንቀለቀል እሳት አመጣለሁ” ወይም “በብርቱ ቁጣዬ እቀጣሃለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የጨካኞች እጅ
የሰዎች “እጅ” የሚያመለክተው ቁጥጥራቸውን ነው። አ.ት፡ “የጨካኞች ቁጥጥር” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በጥፋት የተካኑ ሰዎች
“ለታላቅ ጥፋት ምክንያት የሚሆኑ ሰዎች”

Ezekiel 21:32

ለእሳት ማገዶ ትሆናለህ
“ሰውነትህን እሳት ያቃጥለዋል”

ደምህ በምድሪቱ መካከል ይሆናል
“የምድርህ ዐፈር በደም ይርሳል

አትታሰብም
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ማንም አያስታውስህም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 22

1 የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፥ **2** "አንተም የሰው ልጅ ሆይ፥ ትፈርዳለህን? ደም በምታፈስስ ከተማ ላይ ትፈርዳለህን? ርኵሰትዋን ሁሉ አስታውቃት። **3** እንዲህም ልትላት ይገባል፥ 'ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡ ይህች ጊዜዋ እንዲደርስ በመካከልዋ ደምን የምታፈስ፤ እንድትረክስም ጣዖታትን የምታደርግ ከተማ ናት! **4** ስላፈሰሰሽው ደም በደለኛ ነሽ ፥ ባደረግሽውም ጣዖታት ረክሰሻል! ቀንሽን አቀረብሽ ዘመንሽንም አሳጠርሽ። ስለዚህ ለአሕዛብ መሰደቢያ ለአገሮችም ሁሉ መሳለቂያ አደርግሻለሁ። **5** አንቺ ስምሽ የረከሰ ግራ መጋባት የሞላብሽ ሆይ፥ በቅርብም በሩቅም ያሉ ይሳለቁብሻል። **6** እነሆ፥ የእስራኤል አለቆች እያንዳንዳቸው በኃይላቸው መጠን ደም ያፈስሱ ዘንድ በአንቺ ውስጥ ነበሩ። **7** በውስጥሽ አባቶችንና እናቶችም አቃለሉ፥ በመካከልሽ በመጻተኛው ላይ በደልን አደረጉ። በአንቺ ውስጥ ድሀ አደጉንና መበለቲቱን አስጨነቁ። **8** ቅዱሳቴንም ናቅሽ ሰንበታቴንም አረከስሽ! **9** ደምን ያፈስሱ ዘንድ ቀማኞች ሰዎች በአንቺ ውስጥ ነበሩ በተራሮችም ላይ በሉ። በመካከልሽ ክፋትን አደረጉ። **10** በአንቺ ውስጥ የአባቶቻቸውን ኀፍረተ ሥጋ ገለጡ በአንቺም ውስጥ በወር አበባ ላይ ያለችን ሴት አዋረዱ። **11** በባልንጀራቸው ሚስቶች ጋር ርኵሰትን ያደርጉ፥ የልጆቻአውን ሚስቶች ያረከሱ፥ የገዛ አባቶቻቸውን ሴት ልጆች እህቶቻችውን ያስነወሩ፥ እንዲህ ያሉ ስዎች ሁሉ በአንቺ ውስጥ አሉ። **12** በአንቺ ውስጥ ደምን ለማፍሰስ ጉቦን ይቀብላሉ። አንቺም አራጣና አላስፈላጊ ትርፍ ወስደሻል፥ ጎረቤቶችሽን በጭቆና ጎዳሻቸው ፥ እኔንም ረሳሽኝ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር። **13** ስለዚህ፥ እነሆ፥ ያለቅንነት የሰበሰብሽውን ሀብት በመካከልሽ ያለውን ደም ማፍሰስ በእጄ እቀጣለሁ። **14** በውኑ እኔ ይህን በማደርግብሽ ወራት ልብሽ ይታገሣልን? ወይስ እጅሽ ትጸናለችን? እኔ እግዚአብሔር ተናግሬአለሁ አደርገውማለሁ። **15** ወደ አሕዛብም እበትንሻለሁ ወደ አገሮችም እዘራሻለሁ። በዚህ መንገድ ርኵሰትሽን ከአንቺ ዘንድ አጠፋለሁ። **16** በአሕዛብም ፊት አንቺ የረከሽ ትሆኚያለሽ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቂአለሽ። **17** ቀጥሎም የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፥ **18** የሰው ልጅ ሆይ፥ የእስራኤል ቤት ለእኔ እንደ ዝቃጭ ሆኑብኝ። እነርሱ ሁሉ በእንቺ ውስጥ የመዳብና የቆርቆሮ ፥ የብረትና የእርሳስ ተረፍ ምርት ናቸው። እነርሱ በማቅለጫ ውስጥ የብር ዝቃጭ ናቸው። **19** ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ሁላችሁ ዝቃጭ ሆናችኋልና ስለዚህ፥ እነሆ፥ በኢየሩሳሌም ውስጥ እሰበስባችኋለሁ። **20** እንዲያቀልጡት እሳት ያናፉበት ዘንድ ብርንና መዳብን ብረትንና እርሳስን ቄርቄሮንም በከውር እንደሚሰበስቡ፥ እንዲሁ አቀልጣችኋለሁ። ስለዚህ በቍጣዬና በመዓቴ እሰበስባችኋለሁ፥ በዚያም ውስጥ እጨምራችኋለሁ እሳትም አናፋባችኋለሁ አቀልጣችሁማለሁ። **21** ስለዚህም አሰበስባችሁማለሁ የመዓቴንም እሳት አናፋባችኋለሁ በውስጡም ትቀልጣላችሁ። **22** ብርም በማቅለጫ ውስጥ እንደሚቀልጥ፥ እንዲሁ በውስጧ ትቀልጣላችሁ እኔም እግዚአብሔር መዓቴን እንዳፈሰስሁባችሁ ታውቃላችሁ። **23** የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፥ **24** የሰው ልጅ ሆይ እንዲህ በላት 'አንቺ ያልነጻሽ ምድር ነሽ። በቍጣ ቀን ዝናብ የለም! **25** በውስጥዋ ያሉ ነቢያት እንደሚጮኽና እንደሚናጠቅ አንበሳ አንድ ሆነው ተማምለው ህይወት ያጠፋሉ፥ ከፍ ያለ ብልጥግና ይወስዳሉ! በውስጥዋም መበለቶችን ያበዛሉ! **26** ካህናቶችዋም ሕጌን አቃለዋል ቅድሳቴንም አርክሰዋል። ቅዱስ በሆነና ቅዱስ ባልሆነ መካከልም አይለዩም፥ በንጹሕና በርኩስ መካከል ያለውን ልዩነት አያስተምሩም። ፊታቸውንም ከሰንበታቴ መለሱ እኔም በመካከላቸው ረከስሁ። **27** በውስጥዋ ያሉ አለቆችዋ እንደሚናጠቁ ተኵላዎች ናቸው። የስስትን ትርፍ ለማግኘት ሲሉ ደምን ያፈሳሉ ህይወትንም ያጠፋሉ። **28** እግዚአብሔርም ሳይናገር ነቢያቶችዋ፥ 'ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል" እያሉ ከንቱን ራእይ በማየት የሐሰትንም ምዋርት ለእነርሱ በማምዋረት ያለ ገለባ በጭቃ ይመርጓቸዋል። **29** የምድሪቱም ሕዝብ በማስፈራራት ግፍ አደረጉ ዘረፉ ፈጸሙ፥ ድሆችንና ችግረኞችን አስጨነቁ፥ ያለ ፍትህ መጻተኛውንም በደሉ። **30** ቅጥርን የሚጠግንን፥ ምድሪቱንም እንዳላጠፋት በፈረሰበት በኩል በፊቴ የሚቆምላትን ሰው በመካከላቸው ፈለግሁ፥ ነገር ግን አንድም ሰው አላገኘሁም። **31** ስለዚህ ቍጣዬን አፈስባቸዋልሁ፥ በመዓቴም እሳት አጠፋቸዋለሁ መንገዳቸውንም በራሳቸው ላይ እመልሳለሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር።"

Ezekiel 22:1

የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

አሁንም አንተ፣ የሰው ልጅ ሆይ፣ ትፈርዳለህ? በደም ከተማ ላይ ትፈርዳለህ?
ይህ ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እንደ ትዕዛዝ ያገለግላል። አ.ት፡ “የሰው ልጅ ሆይ፣ ሂድና ፍረድ። ሂድና በደም ከተማ ላይ ፍረድ”። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

የሰው ልጅ
“የሰብዓዊ ፍጡር ልጅ” ወይም “ከሰው የተወለደ ልጅ”። ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን አፅንኦት ለመስጠት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ በማለት ይጠራዋል። እግዚአብሔር ዘላለማዊና ኃያል ነው፣ ሰዎች ግን አይደሉም። ይህንን በሕዝቅኤል 2፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ሟች ሰው” ወይም “ሰው”

የደም ከተማ
“ደም” የሚለው ቃል የመግደል ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ብዙ ሰዎች ባልንጀሮቻቸውን የሚገድሉባት ከተማ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እርሷ ... ራሷ
“እርሷ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢየሩሳሌምን ነው። አብዛኛውን ጊዜ ከተሞች እንደ ሴት ይታሰቡ ነበር። ይህ እስከ ቁጥር 32 ይቀጥላል። (ተባዕት ቃል ሴትን በሚጨምርበት ጊዜ እና ሰውኛ የሚለውን ተመልከት))

በመካከሏ ... የምታፈስ ይህቺ ከተማ ናት
እዚህ ጋ “ከተማ” በዚያ የሚኖረውን ሕዝብ ይወክላል። አ.ት፡ “በዚህ ከተማ የሚኖሩ ሰዎች . . . በመካከሏ ያፈሳሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በመካከሏ ደም የሚያፈሱ
“ደም” የሚለው ቃል የመግደል ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ብዙ ሰዎች ባልንጀሮቻቸውን የሚገድሉበት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ጊዜዋ እንዲመጣ
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር እነርሱን የሚያጠፋበትን ጊዜ ነው። አ.ት፡ “የመጥፊያዋ ጊዜ ይመጣ ዘንድ” ወይም “የምትጠፋበት ጊዜ ይመጣባት ዘንድ”

እርኩስ
እግዚአብሔር በመንፈሳዊ ሁኔታው ተቀባይነት የለውም ወይም እረክሷል የሚለው አንድ ሰው፣ እርሱ በአካሉም የረከሰ ያህል ተቆጥሮ ተነግሮለታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ezekiel 22:4

ባፈሰስሽው ደም
ይህ ሰዎችን መግደል ደምን እንደ ማፍሰስ መሆኑን ይናገራል። አ.ት፡ “ንጹሐን ሰዎችን ስለ ገደልሽ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እርኩስ
እግዚአብሔር በመንፈሳዊ ሁኔታው ተቀባይነት የለውም ወይም እረክሷል የሚለው አንድ ሰው፣ እርሱ በአካሉም የረከሰ ያህል ተቆጥሮ ተነግሮለታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ቀንሽን አቅርበሻል፣ የዘመንሽ መጨረሻም መጥቷል
የቀኖች መቅረብና የዘመን መጨረሻ መምጣት ምስሎች ሁለቱም የአነጋገር ዘይቤዎች የሚወክሉት በሞት ወይም በመደምሰስ መጥፋትን ነው። ኢየሩሳሌም ቀኖቿን አቅርባለች በማለት በሕዝቡ ኃጢአት ምክንያት ኢየሩሳሌም በቶሎ እንደምትጠፋ እግዚአብሔር ያመለክታል። አ.ት፡ “ባደረግሻቸው በእነዚህ ነገሮች ምክንያት ወደ ፍጻሜሽ ቀርበሻል” ወይም “ሕልውናሽ እንዲያበቃ አድርገሻል”

ቀንሽን አቅርበሻል
“መጨረሻሽን አምጥተሻል” ወይም “ሕይወትሽን ጨርሰሻል”

ለሀገሮች ዘለፋ ለምድርም ሁሉ መሳለቂያ አደርግሻለሁ
ስም የሆኑት “ዘለፋ” እና “መሳለቂያ” እንደ ግሥ ይገለጹ ዘንድ ይህ እንደገና ሊጻፍ ይችላል። አ.ት፡ “ሀገራት እንዲዘልፉሽ፣ ምድርም ሁሉ እንዲስቁብሽ አደርጋቸዋለሁ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ዘለፋ
ሰዎች የሚቃወሙት ወይም የሚገስጹት ሰው

መሳለቂያ
ሰዎች የሚያሞኙት ወይም የሚያሾፉበት ሰው

ለምድር ሁሉ
ይህ ጥቅል አስተያየት የሚያመለክተው ለኢየሩሳሌም ቅርበት ያላቸውን ቦታዎችና በእነዚህ ቦታዎች ላይ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላል። አ.ት፡ “በአቅራቢያ ምድር ከሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ላይ” (ግነት እና ጥቅል አስተያየት የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 22:6

እነሆ
“ተመልከቺ” ወይም “ስሚ” ወይም “የምነግርሽን ልብ በይ”

እያንዳንዱ በራሱ ኃይል መጥቷል
“እያንዳንዳቸው ወደ አንቺ ለመምጣት ሥልጣናቸውን ተጠቅመዋል”

ወደ አንቺ መጥተዋል ... በመካከልሽ
“ወደ ከተማሽ መጥተዋል ... በከተማሽ ውስጥ”። “አንቺ” እና “የአንቺ” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ኢየሩሳሌምን ነው።

ደም ለማፍሰስ
ይህ ደምን ማፍሰስ የሚናገረው ሰዎችን ስለ መግደል ነው። አ.ት፡ “ሰዎችን ለመግደል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በአንቺ ውስጥ ያሉትን አባቶችና እናቶች አዋርደዋል
“የኢየሩሳሌም ሰዎች አባቶቻቸውንና እናቶቻቸውን አዋርደዋል”። “እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የኢየሩሳሌምን ሰዎች ነው።

ጭቆናን ፈጽመዋል
“ጨቁነዋል”

በተራሮቹ ላይ ይበላሉ
እዚህ ጋ “ተራሮቹ” የሚያመለክቱት በተራሮቹ ላይ ለጣዖታቱ የተለዩትን መሰዊያዎች ነው። ወንዶቻቸው ከሐሰተኞቹ አማልክት በረከትን ለማግኘት ለጣዖታቱ የሚሰዋውን ሥጋ ይበላሉ። አ.ት፡ “ለጣዖታት የተሰዋ ሥጋ ይበላሉ”

በመካከልሽ ክፋትን ይፈጽማሉ
“በመካከልሽ ክፉ ነገሮችን ያደርጋሉ”

Ezekiel 22:10

በውስጥሽ
በዚህ ሐረግ በየትኛውም አገባብ፣ ጸሐፊው የኢየሩሳሌምን ሰዎች ከተማውን ራሱን እንደ ሆኑ፣ የኢየሩሳሌም ከተማንም ሴት እንደሆነች አድርጎ ያመለክታል። አ.ት፡ “በዚህች ከተማ ውስጥ” ወይም “በእናንተ በኢየሩሳሌም ሰዎች መካከል” (Apostrophe፣ ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ወንዶች የአባቶቻቸውን ራቁትነት ገልጠዋል
ይህ ማለት ወንዱ ልጅ ከአባቱ ሚስት ጋር ይተኛል። አ.ት፡ “ከአባቶቻቸው ሚስቶች ጋር የሚተኙ ወንዶች አሉ”

በወር አበባቸው ወቅት የረከሱትን ሴቶች አስገድደዋል ... ከባልንጀሮቻቸው ሚስቶች ጋር አስጸያፊ ተግባር ፈጽመዋል ... የልጆቻቸውን ሚስቶች በሚያሳፍር ሁኔታ አርክሰዋል ... የገዛ እህቶቻቸውን አስነውረዋል
ወንዶቹ ሊያደርጉት የማይገባቸውን ከሴቶች ጋር በመተኛታቸው፣ ተግባራቸው ምን ያህል ኃጢአትን የተሞላ እንደሆነ እነዚህ ሁሉ መግለጫ መንገዶች ናቸው። አ.ት፡ “በወር አበባቸው ወቅት የረከሱትን ሴቶች ደፍረዋል ... ከባልንጀሮቻቸው ሚስቶች ጋር በመተኛት አስጸያፊ ተግባር ፈጽመዋል ... ከእነርሱ ጋር በመተኛታቸው የልጆቻቸውን ሚስቶች በሚያሳፍር ሁኔታ አርክሰዋቸዋል ... የገዛ እህቶቻቸውን ደፍረዋል”

እርኩስ
እግዚአብሔር በመንፈሳዊ ሁኔታው ተቀባይነት የለውም ወይም እረክሷል የሚለው አንድ ሰው፣ እርሱ በአካሉም የረከሰ ያህል ተቆጥሮ ተነግሮለታል። ሴቶች በወር አበባቸው ወቅት እርኩስ እንደሆኑ ይቆጠሩ ነበር። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ደም ለማፍሰስ
ይህ ደምን ማፍሰስ የሚናገረው ሰዎችን ስለ መግደል ነው። አ.ት፡ “ሰዎችን ለመግደል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ወለድ
ይህ ቃል ተበዳሪው ለተበደረው ገንዘብ የሚከፍለውን ገንዘብ ያመለክታል። ይሁን እንጂ፣ አንዳንድ አዳዲስ ትርጉሞች በዚህ ምንባብ ያለውን “የትኛውም ወለድ” የሚለውን “እጅግ የበዛ ወለድ” ብለው ይተረጉሙታል።

ባልንጀሮችሽን በመጨቆን ጎድተሻቸዋል
ይህ ማለት እጅግ የበዛ ወለድ በማስከፈል ባልንጀሮቻቸውን ጨቁነዋል። አ.ት፡ “ባልንጀሮቻችሁን በመጨቆን ድኻ አ”ድርጋችኋቸዋል” ወይም “እጅግ ብዙ ወለድ በማስከፈል ባልንጀሮቻችሁ እንዲደኸዩ አድርጋችኋል”

እረስተሽኛል
እግዚአብሔርን ለመታዘዝ እምቢ ማለት የእርሱን መኖር እንደ መርሳት ማለት ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ይህ የጌታ እግዚአብሔር ቃል ነው
እግዚአብሔር የንግግሩን እርግጠኝነት ለመግለጽ የራሱን ስም በመጥራት ይናገራል። ይህንን በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ጌታ እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን ነው” ወይም “እኔ፣ ጌታ እግዚአብሔር የተናገርኩት ይህንን ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ezekiel 22:13

እጄን አማታሁ
“በአንቺ ላይ ቡጢዬን ወዝውዣለሁ” ወይም “በአንቺ ላይ እጆቼን አጨብጭቤአለሁ”። ይህ ቁጣንና ተቃውሞን የሚያሳይ ምልክታዊ ድርጊት ነው። አ.ት፡ “በአንቺ ላይ ቁጣዬንና ተቃውሞዬን አሳይቻለሁ” (ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ተመልከት)

በመካከልሽ የተደረገውን ደም ማፍሰስ
“በውስጥሽ ያሉ ሰዎች የፈጸሙት ግድያ”

እኔ ራሴ ከአንቺ ጋር በምነጋገርበት ጊዜ በልበ ሙሉነት ትቆሚያለሽ? በእነዚያ ቀናት እጆችሽስ ይጠነክራሉ?
እግዚአብሔር በሚቀጣቸው ጊዜ ምን ያህል እንደሚጎዱ አጽንዖት ለመስጠት ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ ጥያቄ ምናልባት እንደ ንግግር ሊጻፍ ይችላል። አ.ት፡ “እኔ ራሴ ከአንቺ ጋር በምነጋገርበት ቀን በልበ ሙሉነት አትቆሚም፣ እጆችሽም አይጠነክሩልሽም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

በልበ ሙሉነት ትቆሚያለሽ?
እዚህ ጋ ስሜቱና ፈቃዱ ላይ አጽንዖት ለመስጠት ሙሉው ሰው “ልብ” በሚል ቃል ተመላክቷል። እዚህ ጋ የ “መቆም” አሳብ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን በድፍረት ማለት ነው። አ.ት፡ “ትቆሚያለሽ?” ወይም “ደፋር ትሆኛለሽ?” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

እጆችሽስ ይጠነክራሉ?
እዚህ ጋ ሙሉው ሰው በ “እጆቹ” ተመላክቷል። አ.ት፡ “ብርቱ ትሆኛለሽ?” (See: Synecdoche)

ስለዚህ በሀገራት መካከል እበትንሻለሁ፣ በምድር ሁሉ ላይ እበታትንሻለሁ
የእነዚህ ሁለት ሐረጎች መሠረታዊ ትርጉማቸው አንድ ነው። ተመሳሳዩን ሐረግ በሕዝቅኤል 12:15 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “ስለዚህ እርስ በእርሳቸው እንዲለያዩና በተለያየ ሀገር እንዲኖሩ አደርጋቸዋለሁ”

ማጽዳት
አንድ የማይፈለግን ነገር ማስወገድ

እርኩስ
እግዚአብሔር በመንፈሳዊ ሁኔታው ተቀባይነት የለውም ወይም እረክሷል የሚለው አንድ ሰው፣ እርሱ በአካሉም የረከሰ ያህል ተቆጥሮ ተነግሮለታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ስለዚህ፣ በሀገሮች ዐይን ፊት እርኩስ ትሆኛለሽ
እዚህ ጋ “ሀገሮች” የሚያመለክተው በእነዚያ አካባቢዎች የሚኖሩትን ሰዎች ነው። “ዐይን” ማየትን፣ ማየትም አሳብን ወይም ውሳኔን ይወክላል። አ.ት፡ “ስለዚህ፣ ሀገሮች እርኩስ እንደሆንሽ ይቆጥራሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሀገሮቹ
እዚህ ጋ “ሀገሮች” የሚያመለክተው በእነዚያ አካባቢዎች የሚኖሩትን ሰዎች ነው። አ.ት፡ “በሌሎች ሀገሮች የሚኖሩ ሰዎች” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እኔ እግዚአብሔር እንደሆንኩ ያውቃሉ
እግዚአብሔር ሰዎች እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን ያውቃሉ ብሎ በሚናገርበት ጊዜ እርሱ ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለው ብቸኛው እውነተኛ አምላክ መሆኑን ሰዎች ያውቃሉ ማለቱ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 6:7 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እውነተኛው አምላክ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ይረዳሉ” ወይም “ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለኝ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ይገነዘባሉ”

Ezekiel 22:17

የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የእስራኤል ቤት አለው
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እስራኤላውያን አላቸው” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ ወገን አላቸው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ጉድፍ ሆኑብኝ
ጉድፍ፣ ብር ወይም ወርቅ በምድጃ ላይ ከነጠረ በኋላ የሚቀር ብካይ ነው። እዚህ ጋ ሕዝቡ እንደ ጉድፍ እንደማይጠቅሙት እግዚአብሔር ይናገራል። አ.ት፡ “ለእኔ እንደ ጉድፍ የማይጠቅሙኝ ሆነዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሁሉም ከነሐስና ከቆርቆሮ እንደሚተርፍ ... በምድጃችሁ እንዳለ የብር ጉድፍ ናቸው
ሕዝቡ ጉድፍ የሆኑ ይመስል ምንም የማይጠቅሙት እንደሆኑበት እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጣላል። አ.ት፡ “ሁሉም ምድጃ ውስጥ ብርን ካቀለጥከው በኋላ ከነሐስና ከቆርቆሮ፣ ከብረትና ከእርሳስ እንደሚቀር ትራፊ የማይጠቅሙ ናቸው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እነሆ
“ተመልከቱ” ወይም “ስሙ” ወይም “የምነግራችሁን ልብ በሉ”

Ezekiel 22:20

በቁጣዬና በመዓቴ አሰበስባችኋለሁ
በ “ቁጣዬ” እና “መዓቴ” የሚሉት ሐረጎች በአንድ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት እርሱ እጅግ መቆጣቱን አጽንዖት ለመስጠት ነው። አ.ት፡ “በታላቁ ቁጣዬና መዓቴ ምክንያት እሰበስባችኋለሁ” ወይም “በብርቱ ተቆጥቼ እሰበስባችኋለሁ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

እሰበስባችኋለሁ፣ የቁጣዬንም እሳት አነድባችኋለሁ
ይህ ብረታ ብረቱን ወደ ምድጃው የሚሰበስበውንና እንዲግል እሳት የሚያነድበት ሰው ምስል ነው። እንዲግል የሚያነደው እሳት የሆነ ይመስል እግዚአብሔር የሚናገረው ስለ ቁጣው ታላቅነት ነው። አ.ት፡ “እሰበስባችኋለሁ፣ ቁጣዬንም በእናንተ ላይ እንደ እሳት አነደዋለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእርሱ ትቀልጣላችሁ
“በእርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢየሩሳሌምን ነው።

ቁጣዬን አፍስሼባችኋለሁ
እግዚአብሔር ቁጣው በእነርሱ ላይ የሚያፈሰው ፈሳሽ የሆነ ይመስል ሕዝቡን ስለ መቅጣት ይናገራል። አ.ት፡ “በቁጣዬ ቀጥቻችኋለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 22:23

የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወይም “እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

አንቺ ያላነጹሽ ምድር ነሽ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። እዚህ ጋ፣ “ምድር” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እስራኤልንና በዚያ የሚኖሩትን ሕዝብ ነው። አ.ት፡ “ንጹሕ ያልሆነው ምድርና ሕዝብ አንቺ ነሽ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ያላነጹሽ
እግዚአብሔር በመንፈሳዊ ሁኔታው ተቀባይነት እንደሌለው ወይም እንደ ረከሰ የሚቆጥረው ሰው ያ ሰው በአካሉም እንደ ረከሰ ተቆጥሮ ተነግሮለታል።(ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በቁጣ ቀን ምንም ዝናብ የለም
ዝናብ የእግዚአብሔር በረከት ምሳሌ ሆኖ ጥቅም ላይ ውሏል። አ.ት፡ “በቁጣ ቀን ምንም በረከት የለም” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በመካከሏ የነቢያቶቿ ሤራ አለ
“እርሷ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እስራኤልን ነው። አ.ት፡ “በእስራኤል ያሉ ነቢያት ሤራዎችን አሲረዋል”

ሤራ
ሕገ ወጥ ወይም የሚጎዳ ነገር ለማድረግ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች በምስጢር የሚደረግ ዕቅድ

ልክ እያገሳ ንጥቂያውን እንደሚቦጫጭቅ አንበሳ ሕይወትን ያጠፋሉ፣ የከበረውን ሀብትም ይወስዳሉ
ይህ የእስራኤልን ነቢያት ንጥቂያዎቻቸውን ከሚያጠቁና ከሚገድሉ አናብስት ጋር ተነጻጽረዋል። አ.ት፡ “ያደኑትን እንደሚያጠቁና እንደሚገድሉ የሚያገሱ አንበሶች ሰዎችን ይገድላሉ። የሰዎችን የከበሩ ሀብቶች ይወስዳሉ”

በውስጣ ብዙ መበለቶች እንዲኖሩ ያደርጋሉ
“እርሷ” የሚለው ቃል እስራኤልን ያመለክታል። ያገቡትን ወንዶች በመግደል “ብዙ መበለቶች እንዲኖሩ ያደርጋሉ”። አ.ት፡ “ባሎቻቸውን በመግደል ብዙ ሴቶችን መበለቶች ያደርጓቸዋል”

Ezekiel 22:26

እርሷ
ይህ ተውላጠ ስም ኢየሩሳሌምን ያመለክታል።

በሕጌ ላይ ያምፃሉ
“ሕጌን አይታዘዙም”

እርኩሱ እና ንጹሑ
ይህ እርኩስና ንጹሕ የሆኑ ነገሮችን ያመለክታል። እግዚአብሔር በመንፈሳዊ ሁኔታው ተቀባይነት የለውም ወይም እረክሷል የሚለው አንድ ነገር፣ እርሱ በአካሉም የረከሰ ያህል ተቆጥሮ ተነግሮለታል። አ.ት፡ “እርኩስ የሆኑና ንጹሕ የሆኑ ነገሮች” (ስማዊ ቅጽል እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ዐይኖቻቸውን ከሰንበቶቼ ይደብቃሉ
ሕዝቡ ዐይኖቻቸውን ከሰንበት ይደብቁ ይመስል ይህ የሚናገረው ሰንበትን ቸል ስለማለታቸውና ስላለመጠበቃቸው ነው። አ.ት፡ “ሰንበቶቼን ቸል ይላሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ስለዚህ በመካከላቸው ተንቄአለሁ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በመካከላቸው ይንቁኛል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

መሳፍንቶቿ በውስጧ ልክ ንጥቂያቸውን እንደሚቦጫጭቁ ተኩላዎች ናቸው
ይህ የእስራኤልን መሳፍንት ንጥቂያዎቻቸውን ከሚያጠቁና ከሚገድሉ ተኩላዎች ጋር ያነጻጽራቸዋል።

ደም ያፈሳሉ፣ ሕይወትንም ያጠፋሉ
በመሠረቱ የእነዚህ ሁለት ሐረጎች ትርጉም አንድ ሲሆን መሳፍንቱ በሚፈጽሟቸው ግፎች ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ። አ.ት፡ “ሰዎችን ይገድላሉ”

ነቢያቶቿ በኖራ ቀብተዋቸዋል
ይህ የሚናገረው ነቢያቱ በኖራ እንደሚቀቡት አንዳች ነገር እነዚህን ኃጢአቶች ለመደበቅ መሞከራቸውን ነው። አ.ት፡ “ነገሩ ነቢያቶቿ ኃጢአታቸውን በኖራ የቀቡት ያህል ነው” ወይም “ነቢያቶቻቸው እነዚህን ክፉ ነገሮች ለመደበቅ ይሞክራሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ኖራ
ይህ ከነጭ ቀለም ጋር ተመሳሳይ ሲሆን አንዳንድ ነገሮችን ነጭ ለማድረግ የሚቀባ ውሁድ ነው።

ሐሰትን ተንብየውላቸዋል
x

Ezekiel 22:29

ተጨቁነዋል ... ተበዝብዘዋልም
የታወቁት ቃላት መረጃ ሊጨመርባቸው ይችላል። አ.ት፡ “ሰዎችን ጨቁነዋል ... ሌሎችንም በዝብዘዋል”

መቀማት
ይህ የሚያመለክተው አንድ ሰው ሌላውን ገንዘብ እንዲሰጠው የሚያስፈራራበትን ወይም የሚጎዳበትን ሁኔታ ነው።

ድኻውንና ችግረኛውን
ይህ ድኾችንና ችግረኞች ሰዎችን ያመለክታል። አ.ት፡ “እነዚያ ድኻና ችግረኛ የሆኑ ሰዎች” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 22:30

ቅጥርን የሚሠራ ከእነርሱ አንድ ሰው
ይህ የሚናገረው ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ለመከላከል ቅጥር የሚሠራ ሰውን ይመስል ስለ ሕዝቡ ለመጸለይና ወደ ንስሐ ሊመራቸው ኃላፊነት ስለሚወስድ አንድ ሰው። አ.ት፡ “ከመካከላቸው ልክ ቅጥርን እንደሚሠራ የሚያደርግን ሰው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በፈረሰው በኩል በፊቴ የሚቆም
“በፈረሰው” የሚያመለክተው በቅጥሩ መካከል ያለውን ክፍተት ነው። ይህ የሚናገረው ከተማይቱን ለመከላከል በፈረሰው በኩል እንደሚቆም ተዋጊ ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ስለሚከላከል ሰው ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እንዳላጠፋት ስለምድሪቱ
እዚህ ጋ፣ “ምድር” በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላል። አ.ት፡ “እንዳላጠፋቸው ስለ ሕዝቡ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መዓቴን አፈስባቸዋለሁ
መዓቱ በእነርሱ ላይ የሚያፈሰው ፈሳሽ የሆነ ይመስል ይህ የሚናገረው እግዚአብሔር ሕዝቡን ስለሚቀጣበት ሁኔታ ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መዓት
ፍትሕ በማጣት የሚሰቃይ ሰው ቁጣ

በመዓቴ እሳት እጨርሳቸዋለሁ
ይህ የእግዚአብሔር ፍርድ ምን ያህል ከባድ እንደ ሆነ ከእሳት ጋር በማነጻጸር ይናገራል። እዚህ ጋ፣ ሕዝቡን ማጥፋት እነርሱን እንደ “መጨረስ” ተደርጎ ተመልክቷል። አ.ት፡ “እንደሚንበለበል እሳት ብርቱ በሆነው ቁጣዬ አጠፋቸዋለሁ” ወይም “በቁጣዬ አጠፋቸዋለሁ”

መንገዳቸውን በራሳቸው ላይ አመልሳለሁ
አንድን ነገር በሰው ራስ ላይ ማስቀመጥ ሸክም እንዲሸከሙ ወይም ስለ ጉዳዩ ኃላፊነት እንዲወስዱ ማድረግን ያመለክታል። አ.ት፡ “ስላደረጉት ነገር ኃላፊነት እንዲወስዱ አደርጋቸዋለሁ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 23

1 የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፥ 2 የሰው ልጅ ሆይ፥ የአንዲት እናት ልጆች የሆኑ ሁለት ሴቶች ነበሩ። 3 በግብጽ አገር በኰረዳነታቸው ዕድሜ
አመነዘሩ በዚያ ገለሞቱ። በዚያ ጡቶቻቸው ምዋሸሹ በዚያም የድንግልናቸው ጡቶች ተዳበሱ። 4 ስማቸውም የታላቂቱ ኦሖላ የታናሽ እኅትዋም ኦሖሊባ ነበረ።
ለእኔም ሆኑ ወንዶችና ሴቶች ልጆችንም ወለዱ። ኦሖላ ሰማርያ ናት ኦሖሊባ ደግሞ ኢየሩሳሌም ናት። 5 ኦሖላም የእኔ ሆና እያለ ገለሞተችብኝ፤ ውሸሞችዋንም
ኃያላኑን ጎረቤቶችዋን አሦራውያንን በሴሰኝነት ተከተለቻቸው። 6 እነርሱም ሰማያዊ ሐር የለበሱ አለቆችና ሹማምቶች፥ መልከ መልካሞች ጐበዛዝት፥ በፈረስ ላይ
የሚቀመጡ ፈረሰኞች ነበሩ። 7 ስለዚህ ራሷን ለተመረጡ ለአሦር ሰዎች ሁሉ ለግልሙትና ሰጠቻቸው ፥ በሴሰኝነት በተከተለቻቸውም ጣዖቶቻቸው ሁሉ
ረከሰች። 8 በግብጽም የነበረውን ግልሙትናዋን አልተወችም በዚያ በኰረዳነትዋ ጊዜ ከእርስዋ ጋር ተኝተው ነበር፥ የድንግልናዋንም ጡቶች ዳብሰው ነበር፥
ግልሙትናቸውንም አፍስሰውባት ነበር። 9 ስለዚህ በፍቅር በተከተለቻቸው በውሸሞችዋ በአሦራውያን እጅ አሳልፌ ሰጠኋት። 10 እነርሱም ኅፍረተ ሥጋዋን
ገለጡ ወንዶችና ሴቶች ልጆችዋንም ማርከው ወሰዱ፥ እርስዋንም በሰይፍ ገደሉ በሌሎች ሴቶች ዘንድ መተረቻ ሆነች ስለዚህም ፈረዱባት። 11 እኅትዋም
ኦሖሊባ ይህን አየች ሆኖም ከእርስዋ ይልቅ በሴሰኝነቷ በረታች፥ ግልሙትናዋም ከእኅትዋ ግልሙትና ይልቅ በዛ። 12 አለቆችንና ሹማምቶችን ጎረቤቶችዋን
ጌጠኛ ልብስ የለበሱትን በፈረሶች ላይ የሚቀመጡትን ፈረሰኞች፥ ሁሉም መልከ መልካሞችን ጐበዛዝት አሦራውያንን በሴሰኝነት ተከተለቻቸው። 13
የረከሰችም እንደ ሆነች አየሁ። የሁለቱም አእህትማማቾች ሁኔታ አንድ ነው። 14 ግልሙትናዋንም አበዛች! በቀይ ቀለምም የተሳለውን የከለዳውያንን ስዕል፥
በግድግዳ ላይ የተሳሉትን ሰዎች አየች። 15 በወገባቸው ዝናር የታጠቁ ራሳቸውንም በቀለማዊ መጠምጠሚያ የጠመጠሙ ነበሩ! ሁሉም የከለዳዊያን
ተወላጆችና የሠረገላ አዛዦች ይመስሉ ነበር። 16 ባየቻቸውም ጊዜ ለክፉ ተመኘቻቸው፥ ወደ ከላውዴዎን ምድር ወደ እነርሱ መልእክተኞችን ላከች። 17
የባቢሎንም ሰዎች ወደ እርስዋ ወደ ሴሰኝነት መኝታ መጡ በግልሙትናቸውም አረከሱአት እርስዋም ከእነርሱ ጋር ረከሰች በውርደትም ከእነርሱ ተለየች። 18
ግልሙትናዋንም ገለጠች ኅፍረተ ሥጋዋንም አሳየች ነፍሴም ከእኅትዋ እንደ ተለየች እንዲሁ ነፍሴ ከእርስዋ ተለየች። 19 ነገር ግን በግብጽ ምድር
የገለሞተችበትን የኰረዳነትዋን ዘመን በማሰላሰል ግልሙትናዋን አበዛች። 20 የወንድ ብልቶቻቸው እንደ አህዮች የወንድ ዘራቸውም እንደ ፈረሶች ዘር የሆነውን
ውሸሞቿን በሴሰኝነት ተከተለቻቸው። 21 ስለ ኰረዳነትሽ ምክንያት ግብጻውያን ጡቶችሽን የዳበሱበትን ጊዜ የኰረዳነትሽን ሴሰኝነት ተመኘሽ። 22 ስለዚህ፥
ኦሖሊባ ሆይ፥ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል 'የተለየሻቸውን ውሸሞችሽን አስነሣብሻለሁ! ከሁሉም አቅጣጫ በአንቺ ላይ አመጣቸዋለሁ! 23 እነርሱም
የባቢሎን ሰዎች ከለዳውያንም ሁሉ፥ ፋቁድ፥ ሱሔ፥ ቆዓ፥ ከእነርሱም ጋር አሦራውያን ሁሉ፥ መልከ መልካሞች ጐበዛዝት፥ አለቆችና ሹማምቶች ሁሉ፥
መሳፍንቶችና አማካሪዎች ሁሉ፥ በፈረስ ላይ የተቀመጡ ናቸው። 24 በመሣሪያና በሰረገላ በመንኰራኵርም በብዙ ሠራዊትም ይመጡብሻል! ታላላቅና
አነስተኛ ጋሻና ራስ ቍርም ይዘው በዙሪያሽ ይዘጋጁብሻል! እንዲቀጡሽ እድልን እሰጣቸዋለሁ፥ በተግባራቸውም ይቀጡሻል! 25 ቅንዓቴንም በአንቺ ላይ
ስለማደርግ በመዓትም ስለሚገናኙሽ አፍንጫሽንና ጆሮሽንም ከአንቺ ይቈርጣሉ፥ ከአንቺም የቀረ በሰይፍ ይወድቃል ወንዶችና ሴቶች ልጆችሽንም ማርከው
ይወስዳሉ፥ ከአንቺም የቀረውን እሳት ትበላቸዋለች! 26 ልብስሽንም ይገፍፉሻል ጌጣጌጥሽንም ይወስዳሉ! 27 አሳፋሪ ባህሪሽን፥ ከግብጽ ምድር ያመጣሽውን
ግልሙትናሽንም ከአንቺ አስወግዳለሁ። ዓይንሽንም ወደ እነርሱ በናፍቆት አታነሺም ግብጽንም ከዚያ ወዲያ አታስቢም። 28 ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፥
'እነሆ፥ በጠላሻቸው እጅ፥ በተለየሻቸውም እጅ አሳልፌ እሰጥሻለሁ! 29 እነርሱም በጥላቻ ይገናኙሻል፥ ንብረትሽን ሁሉ ይወስዳሉ፥ ዕራቁትሽንና ዕርቃንሽን
ይተዉሻል። የግልሙትናሽም ነውር፥ ሴሰኝነትሽና ግልሙትናሽም ሁሉ ይገለጣል። 30 ከአሕዛብ ጋር ስላመነዘርሽ በጣዖቶቻቸውም ስለ ረከስሽ ይህ ነገር
ይደርስብሻል። 31 በእኅትሽ መንገድ ሄደሻል ስለዚህ የቅጣት ጽዋዋን በእጅሽ እሰጥሻለሁ። 32 ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ 'የጠለቀውንና የሰፋውን
ብዙም የሚይዘውን የእኅትሽን ጽዋ ትጠጪአለሽ መሳቂያና መሳለቂያም ትሆኛለሽ! 33 በእኅትሽ በሰማርያ ጽዋ፥ በድንጋጤና በጥፋት ጽዋ፥ በስካርና በውርደት
ትሞያለሽ! 34 ትጠጪዋለሽ ትጨልጪውማለሽ መጠጫውንም ትሰባብሪዋለሽ በስብርባሪውም ጡትሽንም ትሸነትሪዋለሽ እኔ ተናግሬአለሁና፥ ይላል
እግዚአብሔር፦ 35 ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ 'ረስተሽኛልና፥ ወደ ኋላሽም ጥለሽኛልና አንቺ ደግሞ የሴሰኝነትሽንና የግልሙትናሽን ውጤት
ተሸከሚ። 36 እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ፥ "የሰው ልጅ ሆይ፥ በኦሖላና በኦሖሊባ ትፈርዳለህን? እንግዲያውስ አሳፋሪ ተግባራቸውን አስታውቃቸው 37
አመንዝረዋልና፥ ደምም በእጃቸው አለና! ከጣዖቶቻቸውም ጋር አመንዝረዋልና፥ ለእኔም የወለዱአቸውን ልጆቻቸውን ለእሳት መቃጠል አሳልፈዋቸዋልና። 38
ይህን በእኔ ላይ ማድረጋቸውን ቀጥለዋል፡ በዚያ ቀን መቅደሴን አርክሰዋል ሰንበታቴንም ሽረዋል! 39 ልጆቻቸውንም ለጣዖቶቻቸው በሠዉበት በዚያው ቀን
ያረክሱት ዘንድ ወደ መቅደሴ ገቡ! እነሆም፥ በቤቴ ውስጥ ያደረጉት ይህ ነው። 40 ደግሞ ከሩቅም ወደሚመጡ ሰዎች መልእክተኛ ልከሻቸዋል። እነርሱም
መጥተዋል! እነሆም መጡ፥ አንቺም ታጠብሽና ዓይኖችሽን ትኩለሽ አጊጠሽም ጠብቅሻቸው። 41 ከፊት ለፊቱ ገብታ በተዘጋጀበት በክብር አልጋ ላይ
ተቀመጥሽ፥ ዕጣኔንና ዘይቴንም አኖርሽበት። 42 በጭንቀት የተሞላ የህዝብ ድምፅ በአንቺ ዘንድ ነበረ፥ ሰካራሞችም ከሌሎች ምናምንቴ ሰዎች ጋር ከምድረ
በዳ መጡ። በእጅሽም ላይ አንባር በራስሽም ላይ የተዋበ አክሊል አደረጉ። 43 እኔም በምንዝር ስለሻገተችው ፥ 'አሁን ከእርስዋ ጋር ያመነዝራሉ እርስዋም
ከእነርሱ ጋር ታመነዝራለች' አልሁ።' 44 ወደ ጋለሞታም እንደሚገቡ ወደ እርስዋ ገቡ እንዲሁ ይሴስኑ ዘንድ በግልሙትና በደለኛ ወደሆኑት ወደ ኦሖላና ወደ
ኦሖሊባ ገቡ። 45 ሴቶቹ አመንዝሮች ናቸውና፥ በእጃቸውም ደም አለና ጻጽቃን ሰዎች ለአመንዝሮቹና ለደም አፍሳሾቹ የተመደበውን ቅጣት ያስተላልፉባቸዋል።
46 ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ታላቅ ጦር አመጣባቸዋለሁ፥ ለመበተንና ለመበዝበዝም አሳልፌ አሰጣቸዋለሁ። 47 ሠራዊቱም በድንጋይ
ይወግሩአቸዋል በሰይፋቸውም ይቈርጡአቸዋል። ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውንም ይገድላሉ፥ ቤቶቻቸውንም በእሳት ያቃጥላሉ። 48 ከእንግዲህ ሴቶች ሁሉ
የሴሰኝነት ተግባር እንዳይፈጽሙ ሴሰኝነትን ከምድሪቱ ላይ አጠፋለሁ። 49 ሴሰኝነታችሁንም በላያችሁ ላይ ይመልሳሉ። እናንተም ኃጢአታችሁንና
ጣዖቶቻችሁን ትሸከማላችሁ በዚህ መንገድ እኔ ጌታ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ።

Ezekiel 23:1

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ በዘይቤ ኢየሩሳሌምን እና ሰማርያ ከተሞችን ለእርሱ እንዴት ታማኝ እንዳልሆኑ እንደ ሁለት ዘማዊያት እህትማማቾች አድርጎ ይናገራል። ይህ ዘይቤ እስከ ሕዝቅኤል 23:34 ድረስ ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌ ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለህዝቡ የተናገረውን አንዳች ነገር ለማስተዋወቅ ያገለገለ ፈሊጥ ነው ። ይህ በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህን መልዕክት ተናገረ" ወይም "ያህዌ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እነዚህን ቃላቶች ተናገረ/ያህዌ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን ይህን ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው እንጂ ሌላ አለመሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰብአዊ ፍጡር ግን እንዲያ አይደለም። ይህ በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ጡቶቻቸው ተዳበሰዋል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ወንዶች ጡቶቻቸውን ዳበሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ እና ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የድንግልና ጡቶቻቸው አጎጠጎጤአቸው ተዳብሷል
ይህ ሀረግ ከመጀመሪያው ሀረግ ጋር በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አለው፤ ትኩረት የሚሰጠውም የሁለቱን ወጣት ሴቶች ስነምግባር የጎደለው ባህርይ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ወንዶቻቸው የድንግልና ጡቶቻቸውን አጎጠጎጤ ዳበሱ" (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

መዳበስ
በፍቅር ወይም በልስላሴ መነካት

እነርሱ የእኔ ሆኑ
ይህ ማለት እርሱ አገባቸው ደግሞም ሚስቶቹ ሆኑ። "እነርሱ የእኔ ሚስቶች ሆኑ" (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የስሞቻቸው ትርጉም ይህ ነው፡ ኦሖላ ማለት ሰማርያ ማለት ሲሆን፤ ኦሖሊባ ማለት ኢየሩሳሌም ናት።
"ኦሖላ ሰማርያን ትወክላለች፤ ኦሖሊባ ደግሞ ኢየሩሳሌምን ትወክላለች።" በዚህ ዘይቤ ሰማርያ የተገለጸችው ኦሖላ እንደሆነች እና ኢየሩሳሌም ደግሞ ኦሖሊባ እንደሆነች ተደርጎ ነው። ይህ የመሚገልጸው እነዚህ ከተሞች ታማኝ እንዳልሆኑ ሚስቶች እንዴት ለያህዌ ታማኞች እንዳልነበሩ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኦሖላ
ይህ የሴት ስም ሲሆን ትርጉሙ "የእርሷ ድንኳን" ማለት ነው ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ኦሖሊባ
ይህ የሴት ስም ሲሆን ትርጉሙ "የእኔ ድንኳን በእርሷ ነው" (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 23:5

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ የኢየሩሳሌም እና ሰማርያ ከተሞችን እንደ ሁለት አመንዝሮች አድርጎ በዘይቤ መግለጹን ቀጥሏል። ይህ ዘይቤ እስከ ሕዝቅኤል 23:34 ድረስ ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሷ የእኔ በነበረች ጊዜ
ይህ የሚያመለክተው እርሷ መቼ የእርሱ ሚስት እንደነበረች ነው። "እርሷ የእኔ ሚስት እስከ ነበረች ጊዜ ድረስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በላያቸው የነበሩ
"ይገዟቸው የነበሩ"

የአሶር ምርጥ ወንዶች የነበሩ ሁሉ
ይህ የሚገልጸው "እነርሱ" የሚለው ቃል ማንን እንደሚያመለክት ነው።

አብራቸው ካመነዘረቻቸው እና ከጣኦቶቻቸው ጋር ሁሉ ረክሳለች
ይህ የሚያመለክተው ከእነዚህ ሁሉ ወንዶች ጋር መተኛቷን እና ጣኦቶቻቸውን ማምለኳን ነው። "ከሁሉም ጋር በመተኛት እና ጣኦቶቻቸውን በማምለክ ራሷን አርክሳለች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መርከስ/ንጹህ አለመሆን
እግዚአብሔር በመንፈሳዊ ነገር ንጹህ አድርጎ የማይቆጥረው ወይም የረከሰ ሰው በአካል እንደቆሸሸ ተደርጎ ይገለጻል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 23:8

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ የኢየሩሳሌም እና ሰማርያ ከተሞችን እንደ ሁለት አመንዝሮች አድርጎ በዘይቤ መግለጹን ቀጥሏል። ይህ ዘይቤ እስከ ሕዝቅኤል 23:34 ድረስ ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በላይዋ የሴሰኝነት ባህሪያቸውን መፈጸም
ይህ የሚናገረው ወንዶቹ በእርሷ ላይ የፈጸሙት የሴሰኝነትን ባህርይ በላይዋ እንዳፈሰሱት ታላቅ የጎርፍ ውሃ ተደርጎ ነው። "በእርሷ ላይ ሴሰኝነት መፈጸም" ወይም "በእርሷ ላይ ማመንዘር" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሷ ላይ ፍርድ ፈጸሙ
ይህ ፈሊጥ ነው። "ስለ መዋረዷ አወሩ" ወይም "በእነርሱ መሃል መጥፎ ስም ነበራት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 23:11

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ የኢየሩሳሌም እና ሰማርያ ከተሞችን እንደ ሁለት አመንዝሮች አድርጎ በዘይቤ መግለጹን ቀጥሏል። ይህ ዘይቤ እስከ ሕዝቅኤል 23:34 ድረስ ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኦሖሊባ
ይህ የሴት ስም ሲሆን ትርጉሙ "የእኔ ድንኳን በእርሷ ነው" ማለት ነው። ይህ ስም በሕዝቅኤል 23:7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

መርከስ/ንጹህ አለመሆን
እግዚአብሔር በመንፈሳዊ ነገር ንጹህ አድርጎ የማይቆጥረው ወይም የረከሰ ሰው በአካል እንደቆሸሸ ተደርጎ ይገለጻል። ይህ ስም በሕዝቅኤል 23:7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ለሁለቱም እህትማማቾች ተመሳሳይ/አንድ ነበር
ይህ የሚያመለክተው ሁለቱም እንዴት ራሳቸውን እንዳረከሱ ነው። "ሁለቱም እህትማማቾች በምንዝርና ተግባራቸው ረክሰዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 23:14

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ የኢየሩሳሌም እና ሰማርያ ከተሞችን እንደ ሁለት አመንዝሮች አድርጎ በዘይቤ መግለጹን ቀጥሏል። ይህ ዘይቤ እስከ ሕዝቅኤል 23:34 ድረስ ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጥምጥም
ከረጅም ጨርቅ የተሰራ እንደ ባርኔጣ በወንድ በራስ ላይ የሚጠቀለል

የሰረገለ አዛዦች መልክ እና አምሳያ ያላቸው ወጣቶች ቡድን
"መልክ" እና "አምሳያ" የሚሉት ረቂቅ ስሞች በግሳዊ ሀረጎች ሊተረጎሙ ይችላሉ። "የሰረገላ አዛዦች ቡድኖች ያላቸውን መልክ የያዙ እና የወጣትነት መልክ ያላቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የሰረገለኞች ቡድን
ሰረገላ የሚነዱ እና ከሰረገለው ፊት እና ጎን የሚሮጡ ወታደሮች

የባቢሎን ወንዶች ልጆች
"ባቢሎናውያን"

Ezekiel 23:16

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ የኢየሩሳሌም እና ሰማርያ ከተሞችን እንደ ሁለት አመንዝሮች አድርጎ በዘይቤ መግለጹን ቀጥሏል። ይህ ዘይቤ እስከ ሕዝቅኤል 23:34 ድረስ ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የምንዝርናዋ መኝታ
ይህ የሚያመለክተው ከወንዶች ጋር ያመነዘረችበትን ስፍራ እና የዝሙት ተግባሯን ነው። "ያመነዘረችበት መኝታ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መርከስ/ንጹህ አለመሆን
እግዚአብሔር በመንፈሳዊ ነገር ንጹህ አድርጎ የማይቆጥረው ወይም የረከሰ ሰው በአካል እንደቆሸሸ ተደርጎ ይገለጻል። ይህ ስም በሕዝቅኤል 23:7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህም ራሷን ከእነርሱ ዘወር አደረገች
ይህ ፈሊጥ ነው። "ስለዚህም እነርሱን ተወች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 23:18

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ የኢየሩሳሌም እና ሰማርያ ከተሞችን እንደ ሁለት አመንዝሮች አድርጎ በዘይቤ መግለጹን ቀጥሏል። ይህ ዘይቤ እስከ ሕዝቅኤል 23:34 ድረስ ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 23:20

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ የኢየሩሳሌም እና ሰማርያ ከተሞችን እንደ ሁለት አመንዝሮች አድርጎ በዘይቤ መግለጹን ቀጥሏል። ይህ ዘይቤ እስከ ሕዝቅኤል 23:34 ድረስ ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አባላዘራቸው እንደ አህያ የሆነ
የወንዶችን አባላዘር መጠን ከአህያ ጋር የሚያነጻጽረው የኦሖሊባ ፍላጎት ምን ያህል ክፉ እንደነበር ለማሳየት ነው። ይህ ግነት ነው፤ የእነርሱ እንደ አህያ ማከል አይችልም። "አባላዘራቸው እንደ አህያ በጣም ትልቅ የሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ኩሸት እንደዚሁም አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

የዘር ፍሰታቸው እንደ ፈረስ የሆነ
x

Ezekiel 23:22

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ የኢየሩሳሌም እና ሰማርያ ከተሞችን እንደ ሁለት አመንዝሮች አድርጎ በዘይቤ መግለጹን ቀጥሏል። ይህ ዘይቤ እስከ ሕዝቅኤል 23:34 ድረስ ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ!
"አድምጡ!" እዚህ ስፍራ "እነሆ!" የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚመጣው አስደናቂ መረጃ ትኩረት እንድንሰጥ ያነቃናል።

በአንቺ ላይ ከየስፍራው እነርሱን አስነሳብሻለሁ
"ከሁሉም አቅጣጫ እንዲነሱብሽ አደርጋለሁ"

ከእነርሱ ጋር ባቢሎናውያንን እና ከለዳውያንን፣ የፋቁድ፣ ሱሔ፣ እና ቆዓ እንደዚሁም አሶራውያንን ሁሉ
ይህ የሚያመለክተው በእነዚህ ስፍራዎች የሚኖሩትን ህዝቦች ሁሉ ሳይሆን፤ ነገር ግን የእነዚህ ስፍራዎችን ወታደሮች ነው። " ከእነርሱ ጋር የባቢሎን እና የከለዳውያን፣ የፋቁድ፣ ሱሔ፣ እና ቆዓ እንደዚሁም የአሶር ወታደሮችን ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

ፋቁድ፣ ሱሔ፣ እና ቆዓ
እነዚህ ባቢሎን ውስጥ የሚገኙ ቦታዎች ስሞች ናቸው። እነዚህ ስፍራዎች ከዚያ አስፍራ የመጡ ወታደሮችን ይገልጻሉ። " ከፋቁድ፣ ሱሔ፣ እና ቆዓ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

ሁሉም ፈረስ ጋላቢ የሆኑ... ጠንካራ፣ ውብ ወንዶች፣ ገዢዎች እና አዛዦች
ይህ ከአሶር የመጡ ኦሖላ አብራቸው የተኛቻቸው አሁን ግን በእርሷ ላይ የተነሱባትን ወንዶች መግለጫ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 23:6 ላይ ከተሰጠው መግለጫ ጋር ተመሳሳይ ነው።

Ezekiel 23:24

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ የኢየሩሳሌም እና ሰማርያ ከተሞችን እንደ ሁለት አመንዝሮች አድርጎ በዘይቤ መግለጹን ቀጥሏል። ይህ ዘይቤ እስከ ሕዝቅኤል 23:34 ድረስ ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በአንቺ ላይ ይመጡብሻል
ይህ ፈሊጥ ነው። "ጥቃት ያደርሱብሻል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መሳሪያ ይዘው
እዚህ ስፍራ "መሳሪያ" ተብሎ የተተረጎመው የዕብራይስጥ ቃል የተለመደ አይደለም። በርካታ ዘመናዊ ትርጉሞች በዚህ መንገድ ይተረጉሙታል፣ ሆኖም ግን አንዳንድ ቅጂዎች ይህንን ሀረግ ያስወጡታል።

ትላልቅ ጋሻዎችን፣ ትንንሽ ጋሻዎችን፣ እና የወታደር ቆቦችን በዙሪያሽ ሁሉ ያመጣሉ
እነዚህ የመከላከያ ዕቃዎች የተለያዩ የወታደር ክፍሎችን ለማመልከት ያገለግላሉ። "ትላልቅ ጋሻዎችን፣ ትንንሽ ጋሻዎችን የያዙ እና ቆብ የደፉ ወታደሮች ጥቃት ያደርሱብሻል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በአንቺ ላይ የቅናቴን ቁጣ አመጣለሁ፣ በሀይል ይነሱብሻል
እዚህ ስፍራ ያህዌ ወታደሮች እንዲያጠቋቸው የሚፈቅደው በእነርሱ ላይ ስለተቆጣ ሲሆን ቁጣውም ተገለጸው በላያቸው እንዳስቀመጠው ነገር ተደርጎ ነው። "በእናንተ በጣም ስለቀናሁ፣ በሀይል እንዲያጠቋችሁ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አፍንጮቻችሁን እና ጆሮቻችሁን ይቆርጣሉ
ይህ በባቢሎን ውስጥ ያገባች ሴት ስታመነዝር የሚደርስባትን ቅጣት የሚገልጽ ነው። "አፍንጫሽን እና ጆሮዎችሽን በመቁረጥ እንደ ዘማዊ ሴት ይቀጡሻል" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የቀሩት ሰዎችሽ በሰይፍ ይወድቃሉ
"መውደቅ" የሚለው ቃል "መሞት" ለሚለው ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት ሲሆን፤ "ሰይፍ" የሚለው ቃል በሰይፍ ለሚገድሉ ወታደሮች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት ነው። (ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

የቀሩት ሰዎችሽ/ትሩፋኑ በእሳት ይበላሉ
ይህ ትሩፋኑ በእሳት እንደሚቃጠሉ ይገልጻል፤ እዚህ ስፍራ እሳት እንደሚያጠቃቸው እና እንደሚበላቸው እንስሳ ተደርጎ ተነግሯል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በህይወት የተረፉት በእሳት ይቃጠላሉ" ወይም "እሳት በህይወት የተረፉትን ያቃጥላቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

Ezekiel 23:26

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ የኢየሩሳሌም እና ሰማርያ ከተሞችን እንደ ሁለት አመንዝሮች አድርጎ በዘይቤ መግለጹን ቀጥሏል። ይህ ዘይቤ እስከ ሕዝቅኤል 23:34 ድረስ ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከግብጽ ምድር
ይህ የሚያመለክተው ዘማዊነቷ ከግብጽ እንደ ጀመረ ነው። "በግብጽ ምድር የጀመርሽው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እነርሱ ዐይኖችሽን በምኞት አታነሽም
ይህ አንድ ነገር ለመመልከት ጭንቅላታቸውን የሚያዞሩ ሰዎችን ለማመልከት የሚውል መንገድ ነው። እዚህ ስፍራ መመልከት የሚወክለው ፍላጎትን ነው። "በምኞት ወደ እነርሱ አትመለከችም" ወይም "እነዚህን መገሮች አትፈልጊም/ አትመኚም" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህ ወዲያ ስለ ግብጽ አታስቢም
እዚህ ስፍራ "ግብጽ" የምትወክለው በግብጽ ውስጥ ያደረገቻቸውን አሳፋሪ ነገሮች ነው። "ከእንግዲህ ወዲያ በግብጽ ውስጥ ያደረግሻቸውን ነገሮች አታስቢም" ወይም "ከዚህ በኋላ በግብጽ ያደረግሽውን አታስቢም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 23:28

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ የኢየሩሳሌም እና ሰማርያ ከተሞችን እንደ ሁለት አመንዝሮች አድርጎ በዘይቤ መግለጹን ቀጥሏል። ይህ ዘይቤ እስከ ሕዝቅኤል 23:34 ድረስ ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ!
"ትኩረት ስጡ፣ ምክንያቱም ቀጥሎ የምናገረው እውነተኛ እና ጠቃሚ ነገር ነው"

ለምትጠሏቸው እጅ አሳልፌ እሰጣችኋለሁ...አምልጣችኋቸው ለነበሩት እጅ መልሼ እሰጣችኋለሁ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ይህ ማለት ያመነዝሩባቸው በነበሩ ሰዎች ይያዛሉ። "የምትጠሏቸው እና ከእጃቸው አምልጣችሁ የነበሩት መልሰው እንዲይዟችሁ እፈቅዳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

(ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እጃቸው
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል መቆጣጠርን/መልሶ መያዝን ያመለክታል። "በቁጥጥራቸው ስር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እርቃን እና መራቆት
እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ ሙሉ ለሙሉ እርቃን መቅረቷን ትኩረት ይሰጣል። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

እርቃንሽ አይሸፈንም
x

Ezekiel 23:30

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ የኢየሩሳሌም እና ሰማርያ ከተሞችን እንደ ሁለት አመንዝሮች አድርጎ በዘይቤ መግለጹን ቀጥሏል። ይህ ዘይቤ እስከ ሕዝቅኤል 23:34 ድረስ ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ ነገሮች በድርጊቶችሽ በአንቺ ላይ ይፈጸሙብሻል
"እነዚህ ነገሮች በአንቺ ላይ ከድርጊትሽ የተነሳ ይፈጸምብሻል" ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እነዚህ ነገሮች በአንቺ ላይ ይሆናሉ ምክንያቱም አንቺ የፈጸምሽው አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ አመንዝራ ማድረግ፣ ህዝቦችን ተከትሎ ማመንዘር
ሕዝቅኤል ይሁዳን ስለምትወክለው (ሕዝቅኤል 23:4) ኦሖሊባ፣ ለገንዘብ ስትል ከተለያዩ አገራት ህዝቦች ወንዶች ጋር እንደምትተኛ ሴት አድርጎ ይናገራል። ሕዝቅኤል፣ የይሁዳ ሰዎች የሌሎችን አገራት ሀብት እና ሀይል ለማግኘት ሲሉ የእነርሱን አማልክት በማምለካቸው ምክንያት ያህዌ እንደሚቀጣቸው እንዲያውቁ ይፈልጋል። "ከሌሎች አገራት ወንዶች ጋር በመዘሞት እንደ አመንዝራ ሴት ይፈጽማሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በጣኦቶቻቸው ረከሰች
ጣኦትን በማምለክ ረከሰች። "ጣኦቶቻቸውን በማምለክ ረከሰች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መርከስ/ንጹህ አለመሆን
እግዚአብሔር በመንፈሳዊ ነገር ንጹህ አድርጎ የማይቆጥረው ወይም የረከሰ ሰው በአካል እንደቆሸሸ ተደርጎ ይገለጻል። ይህ ስም በሕዝቅኤል 23:7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ስዚህ የእርሷን የቅጣቷን ጽዋ በእጅሽ አስጨብጥሻለሁ
ይህ የሚያመለክተው ኦሖሊባ የምትቀበለው ቅጣት የወይን ጽዋ እንደሆነ ተደርጎ ነው። "ስለዚህ እህትሽ በተቀጣችበት ተመሳሳይ መንገድ እንድትቀጪ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 23:32

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ የኢየሩሳሌም እና ሰማርያ ከተሞችን እንደ ሁለት አመንዝሮች አድርጎ በዘይቤ መግለጹን ቀጥሏል። ይህ ዘይቤ እስከ ሕዝቅኤል 23:34 ድረስ ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አንቺም የእህትሽን ጽዋ ትጎነጫለሽ/ትጠጫለሽ
እዚህ ስፍራ ያህዌ ቅጣትን ሴቲቱ የምትጠጣው የወይን ጽዋ አድርጎ ይናገራል። "እንደ እህትሽ አንቺም ተመሳሳይ የቅጣት ጽዋ ትጠጫለሽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የእህትሽ ጽዋ ይኸውም
እዚህ ስፍራ "ጽዋው" የሚወክለው በጽዋው ውስጥ የሚገኘውን ነው። "ከእህትሽ ጽዋ ይኸውም" ወይም "በእህትሽ ጽዋ ውስጥ ሚገኘውን ሁሉ፣ ደግሞም የእርሷ ጽዋ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

መሳቂያ... መሳለቂያ
እነዚህ ሁለቱም ሀረጎች ከሞኝነት ባህሪው የተነሳ የሚሳቅበት እና የሚተች ሰው ባህሪን ያመለክታሉ። መናቅ በአንድ ነገር ወይም በአንድ ሰው ላይ ማፌዝ ወይም ማወረድ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ጽዋ ብዙ መጠን ይይዛል
ይህ ዐረፍተ ነገር በጽዋው ውስጥ የሚገኘው አይልም ምክንያቱም ሕዝቅኤል 23 31 ላይ ያለውን በማንበብ ይታወቃል። "ይህ ጽዋ ብዙ መጠን ያለው ቅጣት ይዟል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 23:33

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ የኢየሩሳሌም እና ሰማርያ ከተሞችን እንደ ሁለት አመንዝሮች አድርጎ በዘይቤ መግለጹን ቀጥሏል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በስካር እና በሀዘን ትሞያለሽ
ይህ ጠጪነት እና ሀዘን ሰውነቷን እንደተቆጣጠረው አድርጎ በጣም ጠጪ እና ሀዘንተኛ ስለመሆን ይናገራል። "በጣም ሰካራም እና ሀዘንተኛ ትሆኛለሽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የፍራቻ እና የጥፋት ጽዋ
"ፍራቻ እና ጥፋት የሚያስከትል ጽዋ።" እዚህ ስፍራ "ፍራቻ" እና "ጥፋት" የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው ቅጣቷ ምን ያህል ከባድ እንደሚሆን ትኩረት ይሰጣሉ። "በዚያ ጽዋ ውስጥ የሚገኘው ፍራቻን እና ጥፋትን ያስከትላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

የእህትሽ የሰማርያ ጽዋ
የኦሖሊባ እህት የሆነችው ኦሖላ የምትወክለው ሰማርያን ነው። ሰማርያ የተጠራችው በስሟ ነው፤ ነገር ግን እንደ እህት ተጠቅሳለች። ጽዋው እርሷ ለምትቀበለው ቅጣት ምልክት ነው። "ይህ ሰማርያን የምትወክለው እህትሽ የምትጠጣው ራሱ ያው የቅጣት ጽዋ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጡቶችሽን ብጪ
"ጥቶችሽን ቁረጪ"

ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ/አዋጅ ነው
ያህዌ ስለሚያዘው/አዋጁ እርግጠኝነት ለመናገር በራሱ ይምላል/በስሙ ያውጃል። ይህ በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "የጌታ የያህዌ አዋጅ ይህ ነው" ወይም "እኔ፣ ጌታ ያህዌ ያወጅኩት/ቃሌ ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 23:35

ከኋላሽ ጥለሽኛል
ያህዌ እርሱ በእርሷ እንተተወ እና ኦሖሊባ እንደ ረሳችው አድርጎ ይናገራል። "እኔን ትተሻል/ጥለሽኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 23:36

የሰው ልጅ፣ በኦሖላ እና ኦሖሊባ አትፈርድምን?
ያህዌ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ለሕዝቅኤል እንደ ተሰጠ ትዕዛዝ ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። የኢየሩሳሌም እና የሰማርያ ከተሞች በኦሖላ እና ኦሖሊባ ተወክለዋል። "የሰው ልጅ ሆይ፣ በኦሖላ እና ኦሖሊባ አትፈርድም!" ወይም "የሰው ልጅ ሆይ፣ በኦሖላ እና ኦሖሊባ በተወከሉት በእነዚያ ሁለት ከተሞች ህዝቦች ላይ ፍረድ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

በእጆቻቸው ላይ ደም አለ
ይህ ፈሊጥ ነው። "እነርሱ ሰዎችን ገድለዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 23:38

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ የኢየሩሳሌም እና የሰማርያ ሰዎች እንዴት ለእርሱ ታማኞች እንዳልሆኑ ይናገራል።

መርከስ/ንጹህ አለመሆን
እግዚአብሔር በመንፈሳዊ ነገር ንጹህ አድርጎ የማይቆጥረው ወይም የረከሰ ሰው በአካል እንደቆሸሸ ተደርጎ ይገለጻል። ይህ ስም በሕዝቅኤል 23:7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሰንበቴን ባረከሱበት በዚያው ቀን
"በዚያው ቀን" የሚለው ሀረግ "ቤተ መቅደሴን አረከሱ" የሚለውን የቀደመውን ሀረግ ያመለክታል። "ቤተ መቅደሴን ባረከሱበት በዚያው ቀን ሰንበቴንም አረከሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ!
"ትኩረት ስጡ፣ ምክንያቱም ቀጥሎ የምናገረው እውነተኛ እና ጠቃሚ ነገር ነው"

በቤቴ መሃል
ይህ በአጠቃላይ ቤቱን ያመለክታል። "መሃል" የሚለው ትኩረት የሚሰጠው የተደረገው የሆነው በግልጽ በቤተ መቅደስ ሲሆን መላውን ስፍራ አርክሷል። "በቤቴ/በራሴ ቤት" (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 23:40

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ዳግም የኢየሩሳሌም እና የሰማርያ ከተሞችን ሁለት ዘማዊያን እንደሆኑ አድርጎ ይገልጻል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መልዕክተኛ ወደሚላክላቸው፣ ከሩቅ አገር ለሚመጡ ወንዶች መልዕክተኛ ላክሽ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ይህ ማለት ወደ እነርሱ እንዲመጡ ሩቅ አገር ወዳሉ ወንዶች መልዕክተኛ ላኩ። "ከሩቅ ስፍራ ወደሚመጡ ወንዶች መልዕክተኞች ላክሽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ!
"ተመልከቱ" ወይም "አድምጡ" ወይም "ቀጥሎ ለምነገረራችሁ ትኩረት ስጡ"

ገላሽን ታጠብሽ፣ ዐይንሽን ተኳልሽ፣ ደግሞም ራስሽን በጌጣጌጥ አስዋብሽ
እነዚህ ነገሮች አንዲት ሴት ራሷን ለአንድ ወንድ ይበልጥ ውብ ሆና ለማሳየት የምታደርጋቸው ነገሮች ናቸው።

አንቺ ገላሽን ታጠብሽ...ተቀመጥሽ
እዚህ ስፍራ "አንቺ" የሚለው ቃል ወደ ነጠላ ቁጥር ይለወጣል፣ እናም አንደኛይቱን እህት ያመለክታል፣ ነገር ግን ሁኔታው ምናልባት ለሁለቱም ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል። በእናንተ ቋንቋ ሀሳቡን ለመግለጽ አንዲቱ እህት መለየት የሚኖርባት ከሆነ ኦሖሊባ መሆኗን ጥቀሱ። (አንተ/አንቺ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይምልከቱ)

ቅመሜ እና ዘይቴ
እነዚህ ነገሮች ያህዌን ለማምለክ የሚያገለግሉ ነገሮች ናቸው።

Ezekiel 23:42

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ዳግም የኢየሩሳሌም እና የሰማርያ ከተሞችን ሁለት ዘማዊያን እንደሆኑ አድርጎ ይገልጻል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህም የብዙ ህዝብ ጩኸት በዙሪያዋ ነበር
የብዙ ህዝብ ጩኸት የሰዎቹን ብዛት ያመለክታል። "ስለዚህም ብዙ የሚጮሁ ሰዎች ድምጽ በዙሪያዋ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በዙሪያዋ ነበር... በእጆቻቸው ላይ
"በዙሪያዋ ነበር... በእርሷ እና በእህቷ እጆች ላይ።" ይህ ሀረግ የሚጀምረው አንደኛይቱን እህት በማመልከት ነው፤ ነገር ግን ሁኔታው ለሁለቱም እህትማማቾች ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል።ይችላል። በእናንተ ቋንቋ ሀሳቡን ለመግለጽ አንዲቱ እህት መለየት የሚኖርባት ከሆነ እዚህ ስፍራ ኦሖሊባን ጥቀሱ። በሀረጉ ሁለተኛ ክፍል "የእነርሱ" በሚለው ቃል ሁለቱንም እህትማማቾች ወደማመልከት ይመጣል

ሳባውያን ይመጡ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሳባውያን" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ለሳባ መምጣታቸውን ነው። "ሳባውያን ይመጡ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚሉትን ይመልከቱ)

አምባር ያደርጉ ነበር
"እነርሱ" የሚለው ቃል ወንዶችን ያመለክታል።

Ezekiel 23:43

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ዳግም የኢየሩሳሌም እና የሰማርያ ከተሞችን ሁለት ዘማዊያን እንደሆኑ አድርጎ ይገልጻል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የተተወችው እርሷ...ከእርሷ ጋር፣ ደግሞም እርሷ ከእነርሱ
ይህ የሚያመለክተው ከሁለቱ እህትማማቾች አንዷን ሲሆን ነገር ግን ሁኔታው ማናልባት ለሁለቱም ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል። በቋንቋችሁ አንደኛው እህት ተለይታ መገለጽ ካለባት ኦሖሊባን ጥቀሱ።

እነርሱ ወደ እርሷ ሄደው ወንዶች ወደ ዘማዊት ሴት እንደሚሄዱ ከእርሷ ጋር ተኙ
ይህ የሚያነጻጽረው ወንዶች ከዘማዊት ሴት ጋር እንደሚተኙ በዚያው መንገድ ከእርሷ ጋር ማድረጋቸውን ነው። "ወንዶች ከዘማዊት ሴት ጋር እንደሚተኙበት መንገድ ከእርሷ ጋር ተኙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እርሷ ሄዱ/ገቡ
"እርሷ ወደ ነበረችበት ስፍራ ሄዱ" ወይም "ወደ እርሷ ሄዱ"

በዚህ መንገድ ከኦሖላ እና ከኦሖሊባ ጋር ተኙ
"ከኦሖላ እና ከኦሖሊባ ጋር የተኙት እንደዚህ ነው"

ፍርድ ስጥ/አሳልፍ
ይህ ፈሊጥ ነው። "ኮንን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ደም ያፈሰሱ...ደም በእጃቸው አለ
ይህ ፈሊጥ ነው። "ሰዎችን የገደሉ...ነብሰ ገዳዮች" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 23:46

ሰዎችን አስነሳባቸው
"አስነሳባቸው" የሚለው ሀረግ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ብዙ ህዝብ ሰብስብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእነርሱ ላይ ደግሞም አሳልፈህ ስጣቸው
"በኢየሩሳሌም እና ሰማርያ ላይ ደግሞም አሳልፈህ ስጣቸው"

እነርሱን አሳልፈህ ስጣቸው
ያህዌ ለእነርሱ ጥበቃ ማድረጉን ትቷል ደግሞም ለመከራ አሳልፎ ሰጥቷቸዋል

እንዲሸበሩ እና ለዝርፊያ/እንዲዘረፉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች እንዲያሸብሯቸው እና እንዲዘርፏቸው" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱን ቆርጦ መጣል
ይህ ፈሊጥ ነው። "እንዲገድሏቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 23:48

ስለዚህ እነርሱ የእናንተን...ያደርጋሉ
"ስለዚህም ሰዎቹ የእናንተን ...ያደርጋሉ" እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው በሕዝቅኤል 23:47 የተጠቀሱትን "ሰዎች" ነው።

ነውረኛ ባህሪሽን በአንቺ ላይ ያደርጉብሻል
ይህ ፈሊጥ ነው። "አሳፋሪ ባህሪሽ የሚያስከትልብሽ ጥፋት እንዲደርስብሽ ያደርጋሉ" ወይም "በአሳፋሪ ባህሪሽ ይቀጡሻል" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የኃጢአታችሁን ዋጋ ከጣኦቻችሁ ጋር ተቀበሉ
"ከጣኦቶቻችሁ ጋር ኃጢአታችሁ የሚያስከትልባችሁን ሀላፊነት ተቀሉ።" ይህ የሚያመለክተው በኃጢአጣታቸው እንደሚቀጡ ነው። "ጣኦቶቻችሁን በማምለክ ለፈጸማችሁት ኃጢአት ቅጣታችሁን ተቀበሉ" በሚለው ውስጥ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት
የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 24

1 በዘጠነኛው ዓመት በአሥረኛው ወር ከወሩም በአሥረኛው ቀን የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ። **2** "የሰው ልጅ ሆይ፥ በዚህ ቀን የባቢሎን ንጉሥ ኢየሩሳሌምን ከቧልና የዚህን ቀን፥ የዛሬን ቀን ስም ጻፍ ። **3** ለዓመፀኛውም ቤት ምሳሌን ተናገር እንዲህም በላቸው፥ 'ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ድስቱን ጣድ! ጣደው! ውኃም ጨምርባት! **4** የምግብ ፍራፍሬዎችን በውስጡ ጨምር፥ ጭኑንና ወርቹን በእርስዋ ውስጥ ሰብስብ፥ የተመረጡትንም አጥንቶች ሙላባት! **5** ከመንጋው የተመረጠውን ውሰድ፥ አጥንቶቹም እንዲበስሉ እንጨት በበታችዋ ማግድ አጥንቶቹም በውስጥዋ ቀቅል። **6** ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ዝገት ላለባት ዝገትዋም ለማይለቃት ምንቸት፥ ለደም ከተማ ወዮላት! ጥቂት ጥቂት ከውስጡ ውሰድ፥ ነገር ግን ዕጣ አታውጣላት። **7** ደምዋ በውስጥዋ አለና! በተራቈተ ድንጋይ ላይ አደረገችው እንጂ በአፈር ይከደን ዘንድ በመሬት ላይ አላፈሰሰችውም **8** ይህም መዓትን አመጣባት። ደምዋም እንዳይከደን በተራቈተ ድንጋይ ላይ አፈሰስኩት! **9** ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ለደም ከተማ ወዮላት! እኔ ደግሞ የማገዶውን ክምር አሳድጋለሁ። **10** እንጨቱን ጨምር! እሳቱን አንድድ! ሥጋውን ቀቅል መረቁን አጣፍጠው! አጥንቶቹም በደንብ ይቃጠሉ። **11** እንድትሞቅና እንድትግል በውጧ ያለው ርኵሰትዋ በውስጥዋ ይቀልጥ ዘንድ ዝገትዋም ይጠፋ ዘንድ ባዶዋን ድስት በፍም ላይ ጣዳት። **12** በከንቱ ደከመች ሆኖም ዝገትዋ በእሳት ስንኳ አልለቀቀም። **13** አሳፋሪው ተግባርሽ በርኵሰትሽ ውስጥ ነው። እኔ ባነጻሽም አልነጻሽም። መዓቴን በላይሽ እስክጨርስ ድረስ ከርኵሰትሽ አትነጺም። **14** እኔ እግዚአብሔር ይሆናል ብዬ ተናግሬአለሁ ፥ እኔም አደርገዋለሁ! አልመለስም፥ ፥ አልጸጸትምም። እንደ መንገድሽና እንደ ሥራሽ ይፈርዱብሻል! ይላል ጌታ እግዚአብሔር።" **15** የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፥ **16** "የሰው ልጅ ሆይ፥ እነሆ፥ የዓይንህን አምሮት በመቅሠፍት እወስድብሃለሁ አንተም ማዘንም ሆነ ማልቀስ የለብህም እንባህንም አታፍስስ። **17** በቀስታ ተክዝ። ለምዋቾችም የቀብር ሥርዓትም አታዘጋጅ። መጠምጠሚያህን በራስህ ላይ አድርግ፥ ጫማህንም በእግርህ አጥልቅ፥ ጢምህን አትሸፍን ወይም ሚስቶቻቸው በመሞታቸው ምክንያት እያዘኑ ያሉ ሰዎችን እንጀራ አትብላ። **18** እኔም በማለዳ ለሕዝቡ ተናገርሁ፥ ምሽት ላይም ሚስቴ ሞተች። በነጋውም እንደ ታዘዝሁ አደረግሁ። **19** ሕዝቡም፥ "ይህ የምታደርገው ነገር ምን እንደ ሆነ አትነግረንምን?" አሉኝ። **20** እኔም እንዲህ አልኋቸው፥ "የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፥ **21** ለእስራኤል ቤት ተናገር እንዲህም በል፥ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እነሆ፥ የኃይላችሁ ትምክሕት፥ የዓይናችሁ አምሮት፥ ክፉ ምኞታችሁ መቅደሴን አርክሰዋል! ያስቀራችኋቸውም ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ በሰይፍ ይወድቃሉ። **22** እኔም እንዳደረግሁ እናንተ ታደርጋላችሁ ጢማችሁን አትሸፍኑም የኃዘንተኛ ሰዎችንም እንጀራ አትበሉም! **23** ይልቁኑ መጠምጠሚያችሁም በራሳችሁ ጫማችሁም በእግራችሁ ይሆናል፤ አታዝኑም ወይም አታለቅሱምም በኃጢአታችሁም ትሰለስላላችሁና እያንዳንዱ ሰው ስለወንድሙ ያቃስታል። **24** ይህ በሚሆንባችሁ ጊዜ ሕዝቅኤልም ምልክት ይሆናችኋል እርሱ እንዳደረገ ሁሉ እናንተ ታደርጋላችሁ። ከዚያም እኔ ጌታ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ። **25** አንተም የሰው ልጅ ሆይ፥ ደስታቸው፥ ትምክህታቸው የሆነውን መቅደሳቸውንና የሚያዩትና የተመኙትን በያዝኩ ጊዜ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን በወሰድሁባቸው ቀን፥ **26** በዚያ ቀን ያመለጠ ሰው ይህን ሊነግርህ ይመጣል። **27** በዚያ ቀን አፍህ አምልጦ ለመጣው ይከፈታል፥ አንተም ትናገራለህ ከዚያ ወዲያም ዝም አትልም። ምልክትም ትሆናቸዋለህ፥ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ።

Ezekiel 24:1

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ሕዝቅኤልን እንዲህ አለው/ተናገረው

የያህዌ ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነብዩ ወይም ለህዝቡ አዲስ ነገርን ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጥ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ተናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ/ያህዌ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በዘጠነኛው አመት
"በ9 ነኛው አመት።" ይህ የሚያመለክተው በንጉሥ ኢዮአቄም አገዛዝ ስር ለምን ያህል ጊዜ በስደት እንደቆዩ ነው። "በንጉሥ ኢዮአቄም ስደት በዘጠነኛው አመት" (ተከታታ ቁጥሮች እና (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ))

አስረኛው ወር፣ በወሩ በአስረኛው ቀን
"በአስረኛው ወር በወሩ በአስረኛው ቀን" ወይም "በ10ኛው ወር በ10ኛው ቀን።" ይህ በዕብራውያን ዘመን አቆጣጠር አስረኛው ወር ነው። (የዕብራውያን ወሮች እና ተከታታ ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር"

የባቢሎን ንጉሥ ከቧታል
የባቢሎን ሰራዊት የተገለጸው በመሪው ነው። "የባቢሎን ንጉሥ ሰራዊት ከቧታል" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 24:3

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል በምሳሌ ኢየሩሳሌምን ስለሚወክል የማብሰያ ማሰሮ ይናገረዋል። ይህ ምሳሌ እስከ ሕዝቅኤል 24:14 ድረስ ይቀጥላል። (ምሳሌዎች/በምሳሌ መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ አመጸኛ ቤት
ይህ በቤቱ ውስጥ ስለሚኖር ቤተሰብ፣ በዚህ ሁኔታ ለዘመናት የያዕቆብ ትውልድ ስለሆነው ስለ እስራኤል የተነገረ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 2:5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ይህ አመጸኛ ህዝብ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ቅንጥብጣቢውን ምግብ ሰብስቡ
እዚህ ስፍራ "ምግብ" በተለይ የሚያመለክተው ስጋን ነው። "ቅንጥብጣቢውን ስጋ አስቀምጡ" (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ከመንጋው ምርጡን
እዚህ ስፍራ "መንጋ" የሚያመለክተው በጎችን ነው፣ የወፍ መንጋን አይደለም።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከስሩ የአጥንት ክምር
በአንዳንድ ባህል ከእንጨት ይልቅ አጥንት ረጅም ጊዜ መንደድ ስለሚችል እሳት ውስጥ አጥንት ይጨምራሉ። ይህ የሚገልጸው ምርጥ የሆኑት አጥንቶች በማሰሮ ውስጥ ከተጨመሩ በኋላ የሚቀሩትን አጥንቶች ነው። "የተቀሩትን አጥንቶች እሳቱን ለማቀጣጠል ከማሰሮው ስር ጨምር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 24:6

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል በምሳሌ ኢየሩሳሌምን ስለሚወክል የማብሰያ ማሰሮ ይናገረዋል። ይህ ምሳሌ እስከ ሕዝቅኤል 24:14 ድረስ ይቀጥላል። (ምሳሌዎች/በምሳሌ መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የደም ከተማ
እዚህ ስፍራ "ደም" የሚያመለክተው "ግድያን" ነው። "የነብሰ ገዳዮች ከተማ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ማብሰያ ማሰሮ
ያህዌ ኢየሩሳሌምን ከማብሰያ ማሰሮ ጋር ማነጻጸሩን ይቀጥላል። "እንደ ማብሰያ ማሰሮ ናት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ዝገት
በብረት ላይ የሚገኝ ቀላ ያለ ነገር። ዝገት ብረትን በመብላት ቀስ በቀስ ያጠፋዋል።

ጥቂት በጥቂቱ ውሰድ
ያህዌ ይህንን ትዕዛዝ ለአንድ የተወሰነ ሰው አልሰጠም። ይህ በዚህ ዘይቤያዊ አነጋገር ለአንድ የተወሰነ ሰው ያልተሰጠ አጠቃላይ ትዕዛዝ ነው።

ዕጣ አትጣል፣ ሁሉንም አውጣ
ዕጣ መጣል/ማውጣት የትኛው ቁራጭ ስጋ እንደሚወጣ የመምረጫ መንገድ ነበር፣ ነገር ግን ያህዌ ሁሉም ቁርጥራጭ ስጋ እንዲወጣ ስለፈለገ ዕጣ መጣል አላስፈለገም።

Ezekiel 24:7

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል በምሳሌ ኢየሩሳሌምን ስለሚወክል የማብሰያ ማሰሮ ይናገረዋል። ይህ ምሳሌ እስከ ሕዝቅኤል 24:14 ድረስ ይቀጥላል። (ምሳሌዎች/በምሳሌ መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሷ ደም በመሀሏ ነው
ይህ ማለት በኢየሩሳሌም የተገደሉት ሰዎች ደም እስከ አሁን በዚያ አለ። "ከእርሷ መሃል የተገደሉት ሰዎች ደም እስከ አሁን በዚያ አለ" (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሷ
"የእርሷ" የሚለው ቃል፣ በማብሰያ ማሰሮ የተገለጸችውን ኢየሩሳሌምን ያመለክታል

በአፈር እንዲሸፈን በመሬት ላይ አላፈሰሰችውም፣ ነገር ግን በጠፍጣፋው አለት ላይ አደረገችው
ይህ ኢየሩሳሌምን ሰዎችን እንደገደለች እና ደማቸውንም የት ማፍሰስ እንደመረጠች አድርጎ በሰውኛ ይገልጻታል። "የተገደሉት በጠፍጣፋ አለት ላይ እንጂ፣ ደማቸውን ሊደብቅ በሚችል በአፈር ላይ አልነበረም" ወይም "ደማቸው በጠፍጣፋ አለት ላይ እንጂ አፈር ሊሸፍነው በሚችለው ስፍራ ላይ አልፈሰሰም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በጠፍጣፋ አለት ላይ አፈሰሰችው
"ደማቸውን በገላጣ አለት ላይ አፈሰሰች"

ስለዚህም ቁጣዬን ለበቀል አነሳሳች
እዚህ ስፍራ ያህዌ ራሱ በኢየሩሳሌም ሰዎችን በገደሉ ላይ በቀልን ስለመውሰዱ ይናገራል። "እኔ ራሴ ተመልክቼ በቁጣዬ እበቀል ዘንድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህም መሸፈን አይችል ዘንድ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ስለዚህም ምንም ይሸፍነው ዘንድ እንዳይችል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 24:9

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል በምሳሌ ኢየሩሳሌምን ስለሚወክል የማብሰያ ማሰሮ ይናገረዋል። ይህ ምሳሌ እስከ ሕዝቅኤል 24:14 ድረስ ይቀጥላል። (ምሳሌዎች/በምሳሌ መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የደም ከተማ
እዚህ ስፍራ "ደም" የሚያመለክተው "ግድያን" ነው። "የነብሰ ገዳዮች ከተማ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የእንጨት ክምሩንም አበዛለሁ
የእንጨት ክምር ኢየሩሳሌምን በሚወክለው የማብሰያ ገንቦ ስር እንደሚገኝ ተጠቁሟል። "ከስርሽ በሚገኘው እሳት ከቀድሞ የበለጠ የእንጨት ክምር አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እሳቱን አንድድ
"እሳቱን ቆስቁስ"

አጥንቶቹ ይረሩ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አጥንቶቹን አቃጥል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 24:11

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል በምሳሌ ኢየሩሳሌምን ስለሚወክል የማብሰያ ማሰሮ ይናገረዋል። ይህ ምሳሌ እስከ ሕዝቅኤል 24:14 ድረስ ይቀጥላል። (ምሳሌዎች/በምሳሌ መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

መለብለብ
የአንድን ነገር ገጽ/ላዩን ማቃጠል

በመሆኑም በላዩ የሚገኘው ንጹህ ያልሆነ ነገር ይቀልጣል፣ ዝገቱም በእሳቱ ይበላል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የሚገኝበትን ንጹህ ያልሆነ ነገር ማቅለጥ እና ዝገቱን በእሳት መብላት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

መርከስ/ንጹህ አለመሆን
እግዚአብሔር በመንፈሳዊ ነገር ንጹህ አድርጎ የማይቆጥረው ወይም የረከሰ ሰው በአካል እንደቆሸሸ ተደርጎ ይገለጻል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የብረት ዝገት
ዝገት

ተበላ
ተቃጥሎ አለቀ

እርሷ ደከመች
እዚህ ስፍራ "እርሷ የሚለው ቃል የማብሰያ ገንቦን ያመለክታል። ይህች የማብሰያ ገንቦ በዘይቤ ኢየሩሳሌምን የምትወክል ናት። "ኢየሩሳሌም ደከመች" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ልፋት
ከባድ ስራ

ነገር ግን ዝገቷ በእሳትም አለቀቃትም
"አለቀቃትም/ለቋት አልሄደም" የሚለው ሀረግ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ነገር ግን እሳቱ ዝገቷን ከእርሷ አቃጥሎ አላስወገደም" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 24:13

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል በምሳሌ ኢየሩሳሌምን ስለሚወክል የማብሰያ ማሰሮ ይናገረዋል። ይህ ምሳሌ እስከ ሕዝቅኤል 24:14 ድረስ ይቀጥላል። (ምሳሌዎች/በምሳሌ መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ቁጣዬን በአንቺ ላይ እስካበርድ ድረስ
ይህ ያህዌ በቁጣው ህዝቡን እንደሚቀጣ እና ህዝቡን የሚቀጣው "ቁጣው" እንደሆነ አድርጎ ይገልጸል። "እናንተን ቀጥቼ እስካበቃ እና በእናንተ ላይ መቆጣቴን እስክጨርስ ድረስ" ወይም "እናንተን እስክቀጣ ድረስ እና በእናንተ ላይ መቆጣቴን እስካበቃ ድረስ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 24:14

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል በምሳሌ ኢየሩሳሌምን ስለሚወክል የማብሰያ ማሰሮ ይናገረዋል። ይህ ምሳሌ እስከዚህ ቁጥር መጨረሻ ድረስ ይቀጥላል። (ምሳሌዎች/በምሳሌ መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

አሊያም ይህን ከማድረግ አላርፍም/አላቆምም
"አሊያም እናንተን ከመቅጣት አላርፍም።" እዚህ ስፍራ "ይህን" የሚለው የሚያመለክተው ያህዌ ህዝቡን መቅጣቱን ነው።

እንደ መንገድሽ እና እንደ ስራሽ ይከፍሉሻል/ይፈርዱብሻል
ይህ የሚገልጸው ያህዌ ህዝቡን የሚቀጣው/የሚፈርድባቸው በመንገዳቸው ምክንያት ሲሆን፤ "መንገዳቸው" ራሱ እንደሚፈርድባቸው አድርጎ ነው። "በተግባራችሁ እና በመንገዳችሁ እፈርድባችኋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የጌታ ያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ የተናገረውን እርግጠኝነት ለማጽናት በራሱ ይምላል/ በስሙ ይምላል። ይህ በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህ ነው" ወይም "እኔ፣ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚሉትን ይመልከቱ)

Ezekiel 24:15

የያህዌ ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የተናገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጥ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህን መልዕክት ተናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የዐይኖችህ መሻት ከ...
ይህ የሚያመለክተው የሕዝቅኤልን ሚስት ነው። ያህዌ ሕዝቅኤልን ሚስቱን በሚመለከትበት የሰውነቱ ክፍል ያመለክታል። "ከ...በጣም የምትወዳት፣ ሚስትህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በመቅሰፍት
"በበሽታ"

ማዘን ወይም ማልቀስ የለብህም፣ እምባህ መፍሰስ የለበትም
እነዚህ ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ይሰጣሉ፤ ትኩረት የሚሰጡት ሕዝቅኤል ሚስቱ በሞተች ጊዜ ማልቅስ እንደሌለበት ነው። "ማዘን ወይም ማልቀስ የለብህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሞተው/ራሳው
ይህ የሚያመለክተው የሞተችውን ሚስቱን ነው። "የሞተችው ሚስትህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)

ጥምጥም
በጭንቅላት ላይ የሚጠቀለል ከረጅም ጨርቅ የተሰራ የራስ መሸፈኛ

ነጠላ ጫማ/ሰንደል
በቁርጭምጭሚት ዙሪያ ማሰሪያ ያለው የሚጫሙት ቀላል ጫማ።

የፊትህን ጸጉር/ጺምህን አትሸፍን
በእስራኤል ወንዶች ሀዘናቸውን ለመግለጽ ጺማቸውን ይላጫሉ፣ ከዚያም ጺማቸው መልሶ እስኪበቅል ድረስ ፊታቸውን ይሸፍናሉ። ያህዌ ሕዝቅኤልን ጺሙን እንዳይሸፍን አዘዘው፤ ይህም ሀዘኑን ለመግለጽ ጺሙን አለመላጨቱን ለማሳየት ነው። "ጺምህን በመሸፈን አታልቅስ" ወይም "ጺምህን በመላጨት እና በመሸፈን አትዘን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትምዕርታዊ/ ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 24:18

በማለዳ/በጥዋት
"በማግስቱ ጠዋት"

Ezekiel 24:19

አጠቃላይ መረጃ:
የእስራኤል ሰዎች ሕዝቅኤልን ይጠይቁታል፣ሕዝቅኤል ደግሞ ያህዌ ለእነርሱ የተናገረውን ይነግራቸዋል።

የያህዌ ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የተናገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጥ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህን መልዕክት ተናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ቤት
"ቤት" የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት ሲሆን በዚህ ሁኔታ ለብዙ ዘመናት የያቆብ ትውልድ የሆኑትን እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህ በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እስራኤላውያን" ወይም "የእስራኤል ወገን ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ
እዚህ ስፍራ "እነሆ" የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚመጣው መረጃ ንቁ ሆነን እንድንጠብቅ ያደርጋል።

የነፍሳችሁን ኩራት... ቤተመቅደስን አረክሳለሁ - ደግሞም ልጆቻችሁ
"የነፍሳችሁ... ኩራት የሆነውን ቤተ መቅደሴን አረክሳለሁ። ልጆቻችሁ..."

የሃይላችሁ ኩራት
ይህ የሚገልጸው የቤተመቅደሱ ህንጻ ህዝቡ የሚኮራበት ነገር መሆኑን ነው። ይህ የተገለጸው ለኩራታቸው መነሻ ከመሆን አልፎ "ኩራታቸው" እንደሆነ ነው። "የምትመኩበት/የምትኮሩበት ህንጻ" ወይም "የብርቱ ኩራታችሁ ምክንያት/መገኛ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የዐይኖቻችሁ ምኞት
እዚህ ስፍራ ያህዌ ህዝቡን የገለጸው "በዐይኖቻቸው" ነው። "ዐይኖቻችሁን ልታሳርፉባቸው የምትወዷቸው ህንጻዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የነፍሳችሁ ናፍቆት
እዚህ ስፍራ ያህዌ ለውስጣዊ ስሜታቸው ትኩረት በመስጠት ህዝቡን የሚገልጸው "በነፍሳቸው" ነው። "በእርግጥ የምትወዱት ህንጻ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ወንዶች እና ሴቶች ልጆቻችሁ... በሰይፍ ይወድቃሉ
ይህ ጠላቶቻቸውን በሰይፎቻቸው ይገልጻል። "ወንዶች እና ሴቶች ልጆቻችሁ... በጦርነት ይገደላሉ" ወይም "ጠላቶቻችሁ ወንዶች እና ሴቶች ልጆቻችሁን... በሰይፍ ይገድላሉ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 24:22

ትቀልጣላችሁ
እዚህ ስፍራ "መቅለጥ" የሚለው እየሟሸሹ መምጣትንና መሞትን የሚገልጽ ዘይቤ ነው። "በጣም ትከሳላችሁ ደግሞም ቀስ በቀስ ትሞታላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በኃጢአታችሁ/በበደላችሁ
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር የእነዚህን ሰዎች ኃጢአት ይቅር እንደማይል ነው። "ኃጢአታችሁን ይቅር አልልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ማቃሰት
ይህ እርዳታ የሚፈልግ እና በብዙ ስቃይ ውስጥ የሚገኝ መናገር ያቃተው ሰው የሚያሰማው ድምጽ ነው።

ስለዚህም ሕዝቅኤል ለእናንተ ምልክት ይሆናል
እዚህ ስፍራ "ምልክት" የሚለው ቃል ለሚመለከቱት ሰዎች ልዩ ማስጠንቀቂያ የሚያስተላልፍን ነገር ያመለክታል። ያህዌ ስለ ሕዝቅኤል እና የሚወስዳቸውን እርምጃዎች እንደዚህ ማስጠንቀቂያ አድርጎ ይናገራል። ይህ ዘይቤ በሕዝቅኤል 12:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ስለዚህም ሕዝቅኤል ለእናንተ ማስጠንቀቂያ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 24:25

የምይዘው መቅደሳቸው
እዚህ ስፍራ ያህዌ ቤተመቅደሳቸውን መደምሰሱን እንደሚይዘው አንድ ሰው አድርጎ ይናገራል። "ቤተመቅደሳቸውን እኔ እደመስሰዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ደስታቸው እና ኩራታቸው የሆነውን
"ደስታ/ሀሴት" እና "ኩራት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች በስማዊ ሀረጎች ሊተረጎሙ ይችላሉ። "ደስታ የሚያደርጉበት እና የሚኮሩበት/የሚመኩበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ስደተኛ
በጦርነት ወይም በሌላ ጥፋት መከራ ምክንያት አገራቸውን ለቀው ለመሄድ የተገደዱ

አፎቻችሁ ይከፈታሉ
ይህ በአድርጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። ሕዝቅኤል የተሰጠው መረዳት እና የመናገር ችሎታ በአፉ መከፈት ተገልጽዋል። "እኔ አፍህን እከፍተዋለሁ" ወይም "መናገር የሚገባህን ታውቃለህ" ወይም "ምን መናገር እንዳለብህ እንድታውቅ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድርጊ ወይም ተደራጊ እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

አንተ ትናገራለህ - ከእንግዲህ ወዲያ ዝም አትልም
እነዚህ ሁለቱም ሀረጎች ሕዝቅኤል ይናገራል የሚለውን ይገልጻሉ። መናገሩ እንደማይቀር ትኩረት ለመስጠት በሁለተኛው ሀረግ በአሉታ ተገልጽዋል። (ምጽት/ላይዶክስ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእነርሱ ምልክት ትሆናለህ
እዚህ ስፍራ "ምልክት" የሚለው ቃል ለሚመለከቱት ልዩ ማስጠንቀቂያ እንደሚያስተላልፍ ያመለክታል። ያህዌ ሕዝቅኤልን እና ድርጊቱን እንደዚህ ማስጠንቀቂያ አድርጎ ይናገራል። ይህ ዘይቤ በሕዝቅኤል12:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "አንተ ለእነርሱ ማስጠንቀቂያ ትሆናለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ
ያህዌ ይህንን ሲናገር ሰዎች እርሱ ያህዌ እንደሆነ ያውቃሉ፤ የመጨረሻው ከፍተኛ ስልጣን እና ሀይል ያለው እውነተኛው አምላክ እርሱ ብቻ እንደሆነ ማወቅ እንደሚገባቸው እየተናገረ ነው። ይህ በሕዝቅኤል6:7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ብቸኛው እውነተኛ አምላክ እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ" ወይም "እኔ ያህዌ የመጨረሻው ስልጣን እና ሀይል እንዳለኝ እወቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 25

1 የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፥ **2** "የሰው ልጅ ሆይ፥ ፊትህን ወደ አሞን ልጆች አቅንተህ ትንቢት ተናገርባቸው። **3** ለአሞንም ሰዎች እንዲህ በል፥ 'ጌታን የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል: መቅደሴ በረከሰ ጊዜ የእስራኤልም ምድር ባድማ በሆነች ጊዜ የይሁዳም ቤት በተማረኩ ጊዜ ስለ እነርሱ "እሰይ!" ብላችኋል። **4** ስለዚህ፥ እነሆ፥ ርስት አድርጌ ለምሥራቅ ሰዎች ርስት አድርጌ አሳልፌ አሰጣችኋለሁ፥ እነርሱም በእናንተ ላይ ምሽግን ይሰራሉ ፥ ድንኳኖቻቸውንም በእናንተ ዘንድ ይተክላሉ። ፍሬያችሁን ይበላሉ ወተታችሁንም ይጠጣሉ! **5** የአሞንን ከተማ ለግመሎች ማሰማርያ፥ የአሞንንም ልጆች ለመንጋ መመሰጊያ አደርጋለሁ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ። **6** ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፥ በእጃችሁ አጨብጭባችኋልና፥ በእግራችሁም አሸብሽባችኋልና፥ በእስራኤልም ምድር ላይ በነፍሳችሁ ንቀት ሁሉ ደስ ብሏችኋልና **7** ስለዚህ፥ እነሆ፥ በእጄን እመታችኋለሁ፥ ለአሕዛብም ለብዝበዛ አሳልፌ እሰጣችኋለሁ፥ ከአሕዛብም ለይቼ እቄርጥሃለሁ፥ ከአገሮችም አጠፋሃለሁ እፈጅህማለሁ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃለህ። **8** ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ 'ሞዓብና ሴይር እነሆ፥ "የይሁዳ ቤት ያው እንደ ሌሎቹ አሕዛብ ሁሉ ነው!" ብለዋልና **9** ስለዚህ፥ እነሆ፥ የሞዓብን ጫንቃ ከከተሞቹ፥ በዳርቻው ካሉት የምድሩ ትምክሕት ከሆኑት ከተሞቹ፥ ከቤትየሺሞት፥ ከበኣልሜዎን፥ **10** ከቂርያታይም፥ ከአሞን ልጆች ጋር ለምሥራቅ ልጆች እከፍታለሁ። የአሞን ህዝብ በአሕዛብ መካከል ከእንግዲህ ወዲህ እንዳይታሰቡ ርስት አድርጌ አሳልፌ እሰጣቸዋለሁ። **11** በሞዓብም ላይ ፍርድን አደርጋለሁ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ። **12** ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ 'ኤዶምያስ በይሁዳ ቤት ላይ በቀል አድርጎአል፥ ይህን በማድረጉም ስህተት ፈጽሟል። **13** ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እጄን በኤዶምያስ ላይ እዘረጋለሁ ከእርስዋም ዘንድ ሰውንና እንስሳን አጠፋለሁ። ከቴማንም ጀምሮ እስከ ድዳንም ድረስ ባድማ አደርጋታለሁ፥ በሰይፍም ይወድቃሉ። **14** በሕዝቤ በእስራኤል እጅ ኤዶምያስን እበቀላለሁ እንደ ቍጣዬና እንደ መዓቴም መጠን በኤዶምያስ ያደርጋሉ በቀሌንም ያውቃሉ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር!' **15** ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል 'ፍልስጥኤማውያን በንቀት በቀልን አድርገዋልና፥ ይሁዳንም ከውስጣቸው ለማጥፋት ደጋግመው ሞክረዋልና **16** ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እነሆ፥ እጄን በፍልስጥኤማውያን ላይ እዘረጋለሁ፥ ከሊታውያንንም እቄርጣለሁ፥ የባሕሩንም ዳር ቅሬታ አጠፋለሁ። **17** በመዓት መቅሠፍትም ታላቅ በቀል አደርግባቸዋለሁ በቀሌንም በላያቸው ባደረግሁ ጊዜ፥ እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ።

Ezekiel 25:1

የያህዌ ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የተናገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጥ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህን መልዕክት ተናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ወደ አሞን ሰዎች ፊትህን አዙር
አሞን ሩቅ ስፍራ ነበር፣ ስለዚህ ሕዝቅኤል በዚያ የሚገኙ ሰዎችን ማየት አይችልም፣ ነገር ግን ወደዚያ አቅጣጫ መመልከት ያንን ህዝብ የመጉዳት ምልክት ይሆናል። በሕዝቅኤል 6:2 ላይ የሚገኘው ተመሳሳይ ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ወደ አሞን ህዝብ ዞረህ ተመልከት" ወይም "በዚያ ያለው ህዝብ ጥፋት እንዲደርስበት ወደ አሞን አቅጣጫ ተመልከት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/መልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

የአሞን ህዝብ
"የአሞን ትውልድ" ወይም "በአሞን ምድር የሚኖሩ"

በእነርሱ ላይ ትንቢት ተናገር
"በእነርሱ ላይ ስለሚደርስባቸው ክፉ ነገሮች ትንቢት መናገር።" ይህ ማለት በአሞን ሰዎች ላይ ስለሚደርስ አስከፊ/አስጨናቂ ነገሮች ትንቢት መናገር ማለት ነው። በሕዝቅኤል 4:7 ላይ የሚገኘው ተመሳሳይ ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

Ezekiel 25:3

አጠቃላይ መረጃ:
ለአሞን ሰዎች ምን መናገር እንዳለበት ያህዌ ለሕዝቅኤል ይነግረዋል።

የጌታ የያህዌን ቃል ስሙ
"ይህን ከጌታ ያህዌ ዘንድ የመጣ መልክዕክት ስሙ"

እናንተ፣ "አሃ!" ብላችኋል
"አዳንቃችኋል።" እዚህ ስፍራ "አሃ" የሚለው ቃል ሰዎች በአንዳች ነገር ደስ ሲሰኙ የሚያሰሙት ነው። በዚህ ሁኔታ ሰዎች ደስ የተሰኙት በእስራኤል እና ይሁዳ ላይ ክፉ ነገር ስለደረሰ ነው።

መቅደሴ በረከሰ ጊዜ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የጠላት ሰራዊት ባረከሰው ጊዜ በመቅደሴ ላይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሪቱን በመቃወም ...ቤቱን በመቃወም
"በምድሪቱ ላይ.. በቤቱ ላይ"

የይሁዳ ቤት
"ቤት" የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሲሆን በዚህ ሁኔታ ለብዙ ዘመናት የይሁዳ ትውልድ የሆኑትን ያመለክታል። ይህ በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "የይሁዳ ወገን ህዝብ" ወይም "የይሁዳ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ
"ተመልከቱ" ወይም "ቀጥሎ ለምናገረው ትኩረት ስጡ"

በምስራቅ ለሚኖሩ ሰዎች ርስታቸው አድርጌ እሰጣችኋለሁ
ይህ የሚናገረው የአሞንን ምድር የሚወረው እና የምድሪቱን ሀብት እንደዚሁም በላይዋ የሚገኘውን ነገር ሁሉ የሚወስደው የጠላት ሰራዊት የአሞንን ህዝብ ርስቱ አድርጎ እንደወሰደ እንደሚቆጠር አድርጎ ነው። እዚህ ስፍራ የጠላት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሰራዊት የአሞንን ህዝብ ባሪያ እንደሚያደርግ አያመለክትም። "ከእናንተ በስተ ምስራቅ የሚመጣ ሰራዊት እንዲወራችሁ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእናንተ ላይ ይሰፍራሉ፤ ደግሞም በመሃላችሁ ድንኳናቸውን ይጥላል
"ድንኳን ጥለው በአገራችሁ ይኖራሉ"

የምድራችሁን ፍራፍሬ ይበላሉ፤ ወተታችሁንም ይጠጣሉ
የፍራፍሬውን እና ወተቱን መገኛ ለይቶ መናገር ሊጠቅም ይችላል። "ከዛፎቻችሁ ፍሬዎችን ይበላሉ የከብቶቻችሁን ወተት ይጠጣሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የአሞን ሰዎች የመንጋ መሰማሪያ
እዚህ ስፍራ "የአሞን ሰዎች" የሚለው የሚያመለክተው የአሞን ሰዎችን ምድር ነው። እንደዚሁም በዚህ ሀረግ መነሻ ላይ በውስጠ ታዋቂነት የሚገኘው መረጃ ሊጨመር ይችላል። "የቀረውን የአሞን ሰዎች ምድር የመንጋ መሰማሪያ አደርገዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና የተዘለለ/የተተወ የሚሉትን ይመልከቱ)

እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ
ያህዌ ይህንን ሲናገር ሰዎች እርሱ ያህዌ እንደሆነ ያውቃሉ፤ የመጨረሻው ከፍተኛ ስልጣን እና ሀይል ያለው እውነተኛው አምላክ እርሱ ብቻ እንደሆነ ማወቅ እንደሚገባቸው እየተናገረ ነው። ይህ በሕዝቅኤል6:7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ብቸኛው እውነተኛ አምላክ እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ" ወይም "እኔ ያህዌ የመጨረሻው ስልጣን እና ሀይል እንዳለኝ እወቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 25:6

እጃችሁን አጨብጭባችኋል፣ በእግራችሁም መሬቱን መትታችኋል/ደቅታችኋል
እነዚህ ድርጊቶች ብርቱ ስሜትን መግለጫ ናቸው። በዚህ ሁኔታ ሰዎቹ ተደስተዋል በእስራኤል ላይ ያላቸውን ንቀትም አሳይተዋል። (ትምዕርታዊ/ ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

በውስጣችሁ በእስራኤል ላይ ያለ ንቀት በሙሉ
እዚህ ስፍራ "የእስራኤል ምድር" የሚለው ሀረግ የሚገልጸው በዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ነው። "በእስራኤል በሚኖሩ ሰዎች ላይ ያላችሁ ጥላቻ ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና የተዘለለ/የተተወ የሚሉትን ይመልከቱ)

እነሆ
"ተመልከቱ" ወይም "ቀጥሎ ለምናገረው ትኩረት ስጡ"

በእጄ አኔ እመታችኋለሁ
"በሀይለኛው እጄ እኔ እመታችኋለሁ" እዚህ ስፍራ ያህዌ ህዝቡን በቀጥታ በእጁ እንደሚመታቸው አድርጎ ይናገራል። "እኔ እቀጣችኋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተን ለህዝብ/አገራት ዝርፊያ አድርጌ እሰጣችኋለሁ
"እናንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የአሞን ሰዎችን ሲሆን ነገር ግን ለምድራቸው እና ሀብታቸውም ደግሞ ሜቶኖሚ/ ነው። "ጠላት እንደያሸንፋችሁ ደግሞም ምድራችሁን እና ሀብታችሁን እንዲዘርፍ አደርጋለሁ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተን ከህዝቡ እለያለሁ... ከአገራት መሃል እንድጥጠፉ አደርጋለሁ
በመሰረቱ እነዚህ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው ፤ ከእንግዲህ አገር ሆነው እንደማይቀጥሉ እና ያህዌ የአሞንን ሰዎች ሙሉ ለሙሉ እንደሚያጠፋ ትኩረት ይሰጣሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 25:8

ሞአብ እና ሴይር
እነዚህ ስፍራዎች በውስጣቸው የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታሉ። "የሞአብ እና ሴይር ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ ተመልከቱ! የይሁዳ ቤት እንደ...ነው
"የይሁዳን ቤት ተመልከቱ። እንደ...ነው"

የይሁዳ ቤት...ነው
"ቤት" የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሲሆን በዚህ ሁኔታ ለብዙ ዘመናት የይሁዳ ትውልድ የሆኑትን ያመለክታል። ይህ በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "የይሁዳ ወገን ህዝብ" ወይም "የይሁዳ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ! እኔ እከፍታለሁ
"ተመልከት! እኔ እከፍታለሁ" ወይም "ስማ! እኔ እከፍታለሁ" ወይም "ቀጥሎ ለምናገረው ትኩረት ስጥ! እኔ እከፍታለሁ"

ከከተማው ዳርቻ ጀምሬ፣ የሞአብን ቁልቁለቶች እከፍታለሁ
ይህ ማለት እርሱ ሞአብን ራሷን ለማጥቃት በመጀመሪያ ለታደሮች መንገዱን ለመጥረግ በሞአብ ዳርቻ የሚገኙ ከተሞችን ያጠፋል። "በድንበሮቿ የሚገኙ ከተሞችን በማጥፋት/በመደምሰስ ወደ ሞአብ የሚወስደውን ጥርጊያ እከፍታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእርሱ ከተሞች በመጀመር
እዚህ ስፍራ የሞአብ ከተማ የተነገረው ወንዴ በሆነ ተውላጠ ስም "የእርሱ" በሚለው ነው። "በእርሱ ከተሞች በመጀመር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የቤት የሺሞት፣ በአልሜዎን፣ እና ቂርያትይም
"ከታላቂቆቹ ከተሞች ከቤት የሺሞት፣ አልሜዎን፣ እና ቂርያትይም እጀምራለሁ።" እነዚህ ሶስት ስፍራዎች ከተሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በአሞን ህዝቦች ላይ የተነሱትን የምስራቅ ሰዎች
"አሞንን ያጠቁትን ከምስራቅ ሰዎች የሆኑትን እነዚያኑ ሰራዊት እልካለሁ"

እነርሱን እንደ ንብረት/ሃብት አድርጌ እሰጣለሁ
እዚህ ስፍራ ያህዌ አሞንን ከምስራቅ ለመጣው ሰራዊት እንደ ንብረት አድርጎ አሳልፎ እንደ ሰጠ ይናገራል። "ሰራዊት እነርሱን እንዲይዝ እፈቅዳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህም አሞን ሰዎች በአገራት መሃል መታሰቢያ አይኖራቸውም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ስለዚህም አገራት የአሞንን ሰዎች አያስታውሱም/ይረሳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 25:12

ኤዶም ተቀብሏል
እዚህ ስፍራ "ኤዶም" የሚያመለክተው በዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ነው። "የኤዶም ሰዎች ተቀብለዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የይሁዳ ቤት
"ቤት" የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሲሆን በዚህ ሁኔታ ለብዙ ዘመናት የይሁዳ ትውልድ የሆኑትን ያመለክታል። ይህ በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "የይሁዳ ወገን ህዝብ" ወይም "የይሁዳ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ኤዶምን በእጁ እመታለሁ
እዚህ ስፍራ ያህዌ ህዝቡን በቀጥታ በእጁ እንደሚመታ አድርጎ ይናገራል። ተመሳሳይ ሆነው ሀረግ በሕዝቅኤል 25:7 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ። "እኔ ኤዶምን እቀጣለሁ። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከቴምና ጀምሮ እስከ ድዳን...አጠፋቸዋለሁ
"ኤዶምን ከቴምና እስከ ድዳን...አጠፋለሁ።" እነዚህ በኤዶም ሁለት ጫፎች በተቃራኒ አቅጣጫ የሚገኙ ከተሞች ናቸው። ይህ ማለት ያህዌ መላዋን ኤዶምን ያጠፋታል ማለት ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰይፍ ይወድቃሉ
"መውደቅ" የሚለው ቃል የሚወክለው መገደልን ሲሆን "ሰይፍ" የሚለው በጦርነት የሚያጠፏቸውን ጠላቶቻቸውን ያመለክታል። "ጠላቶቻቸው በሰይፍ ይገድሏቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Ezekiel 25:14

በቀሌን በኤዶም ላይ በህዝቤ በእስራኤል አማካይነት አወርድባቸዋለሁ
እዚህ ስፍራ የእስራኤል "እጅ" የሚለው የእስራኤልን ሰራዊት የሚገልጽ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ያህዌ በኤዶም ህዝብ ላይ በቀል ስለመፈጸም የሚናገረው እንደ ብርድልብስ ሆኖ ቁጣው እንደሚሸፍናቸው አድርጎ ነው። "በቀል" የሚለው ረቂቅ ስም "ቀጣ" በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። "ህዝቤ እስራኤል የኤዶምን ህዝብ እንዲቀጣ እጠቀምበታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በኤዶም ላይ እንደ ቁጣዬ እና ሀይሌ ያደርጉባቸዋል
"ለኤዶማውያን ቁጣዬን እና ሀይሌን ያሳያሉ" ወይም "ኤዶማውያንን እንደ ቁጣዬ እና ሀይሌ ይቀጧቸዋል"

ቁጣዬ እና ሀይሌ
"ሀይል/ንዴት" የሚለው ቃል በመሰረቱ "ቁጣ" የሚለውን ተመሳሳይ ነገር አጠናክሮ ይገልጻል። "ሀይሌ እና ቁጣዬ" ወይም "እጅግ ከፍ ያለው ቁጣዬ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

በቀሌን ያውቃሉ
"በቀል" የሚለው ረቂቅ ስም "ቀጣ" በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። "የኤዶም ሰዎች እኔ እንደቀጣኋቸው ያውቃሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ራሱን በስሙ የሚገልጸው/የሚምለው፤ የተናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳወቅ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ። "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 25:15

ፍልስጤማውያን በክፋት ተነስተው በቀል ፈጸሙ፤ ደግሞም ከራሳቸው ውስጥ ይሁዳን ደጋግመው ለማጥፋት ሞከሩ
"ከራሳቸው ውስጥ" የሚለው አገልለጽ ፈሊጣዊ ነው። "ፍልስጤማውያን ይሁዳን ስለሚጠሉ በራሳቸው ሀይል ደጋግመው ሊያጠፏቸው ሞከሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይሁዳን ለማጥፋት
እዚህ ስፍራ "ይሁዳ" የሚለው የሚያመለክተው በዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ነው። "ዛሬ የይሁዳ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ
ይህ አንባቢው ቀጥሎ ለሚመጣው ልዩ ትኩረት እንዲሰጥ ይነግረዋል። "ተመልከቱ" ወይም "አድምጡ" ወይም "ልነግራችሁ ላለው ነገር ትኩረት ስጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

በፍልስጤማውያን ላይ እጄን እዘረጋለሁ
እዚህ ስፍራ የያህዌ ሀይል የተወከለው በእርሱ "እጅ" ነው። "ሀይለኛው እጄን በፍልስጤማውያን ላይ አዞራለሁ" ወይም "ታላቁን ሀይሌን በፍልስጤማውያን ላይ አዞራለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ እቆርጣለሁ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "እኔ እደመስሳለሁ" ወይም "እኔ አስወግዳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከሊታውያን
ፍልስጤም ውስጥ በከሊታ ከተማ የሚኖሩ ሰዎች (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 26

1 እንዲህም ሆነ በአሥራ አንደኛው ዓመት ከወሩ በመጀመሪያው ቀን የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፡ **2** "የሰው ልጅ ሆይ፥ ጢሮስ በኢየሩሳሌም ላይ። 'እሰይ፥ የአሕዛብ በር የነበረች ተሰብራለች ወደ እኔም ተመልሳለች እርስዋ ፈርሳለችና እኔ እሞላለሁ!' ብላለች። **3** ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፥ "ጢሮስ ሆይ፥ እነሆ፥ በአንቺ ላይ ነኝ፥ ባሕርም ሞገድዋን እንደምታወጣ እንዲሁ ብዙ ህዝቦችን በአንቺ ላይ አስነሳልሁ። **4** የጢሮስንም ቅጥሮች ያጠፋሉ ግንቦችዋንም ያፈርሳሉ ትቢያዋንም ከእርስዋ እጠርጋለሁ፥ የተራቈተ ድንጋይም አደርጋታለሁ። **5** በባሕር ውስጥ የመረብ ማስጫ ትሆናለች እኔ ተናግሬአለሁና፥ ይላል እግዚአብሔር ለአሕዛብም ብዝበዛ ትሆናለች። **6** በሜዳ ያሉትም ሴቶች ልጆችዋ በሰይፍ ይገደላሉ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ። **7** ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና። እነሆ፥ ከሰሜን የነገሥታት ንጉሥ የባቢሎንን ንጉሥ ናቡከደነፆርን ከፈረሶችና ከሰረገሎች ከፈረሰኞችም ከብዙ ሕዝብ ጋር በጢሮስ ላይ አመጣለሁ። **8** በሜዳ ያሉትን ሴቶች ልጆችሽን በሰይፍ ይገድላቸዋል፥ ምሽግም ይሠራብሻል አፈርንም ይደለድልብሻል ጋሻም ያነሣብሻል። **9** ማፍረሻውን በቅጥርሽ ላይ ያደርጋል፥ መሳሪያውም ግንቦችሽንም ያፈርሳል! **10** ከፈረሶቹም ብዛት የተነሣ ትቢያቸው ይከድንሻል! ሰዎችም በፈርሰ ቅጥር በኩል ወደ ከተማ እንደሚገቡ እርሱ በበሮችሽ ሲገባ፥ ከፈረሰኞችና ከመንኰራኵሮች ከሰረገሎችም ድምፅ የተነሣ ቅጥርሽ ይናወጣል። **11** በፈረሶቹ ኮቴ ጎዳናዎችሽን ሁሉ ይረመርማል፤ ሕዝብሽንም በሰይፍ ይገድላል፥ የብርታትሽም ሐውልት ወደ ምድር ይወድቃል። **12** በዚህ መንገድ ብልጥግናሽንም ሸቀጥሽንም ይዘርፋሉ! ቅጥርሽንም ያፈርሳሉ፥ ተድላ የምታደርጊባቸውን ቤቶችሽን ያጠፋሉ ድንጋይሽንና እንጨትሽን መሬትሽንም በባሕር ውስጥ ይጥላሉ። **13** የዝማሬ ጩኸትሽን ዝም አሰኛለሁ የክራሮች ድምፅ ከዚያ ወዲያ አይሰማም! **14** የተራቈተ ድንጋይ አደርግሻለሁ የመረብም ማስጫ ትሆኛለሽ። ከእንግዲህ እንደገና አትገነቢም እኔ እግዚአብሔር ተናግሬአለሁና፥ ይላል እግዚአብሔር! **15** ጌታ እግዚአብሔር ጢሮስን እንዲህ ይላታል፥ 'በውስጥሽ እልቂት በሆነ ጊዜ በውድቀትሽ ጩኸትና በቆሰሉ ሰዎች የሥቃይ ድምጽ የተወጉት ባንቋረሩ ጊዜ፥ ፥ ከውድቀትሽ ድምፅ የተነሣ ደሴቶች አይነዋወጡምን? **16** የባሕርም አለቆች ሁሉ ከዙፋኖቻቸው ይወርዳሉ መጐናጸፊያቸውን ያወጣሉ ወርቀ ዘቦ ልብሳቸውንም ያወልቃሉ መንቀጥቀጥን ለብሰው በመሬት ላይ ይቀመጣሉ፥ ሁልጊዜም ይንቀጠቀጣሉ ስለአንቺም ይፈራሉ። **17** በአንቺም ላይ ሙሾ ያሞሻሉ፥ እንዲህም ይሉሻል። የመርከበኞች መኖሪያ የነበርሽ እንዴት ወደምሽ! ዝናሽ የወጣ ጠንካራ ከተማ አሁን ግን ከባህር ጠፋሽ! በአንድ ወቅት በእርሷ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ አስፍሪነታቸው በዙሪያቸው ባሉ ሁሉ ላይ ነበር። **18** አሁን በውድቀትሽ ቀን የባህር ዳርቻዎችይንቀጠቀጣሉ፥ በባሕርም ውስጥ ያለ ደሴቶች ከመጥፋትሽ የተነሣ ይደነግጣሉ። **19** ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፡ ሰው እንደሌለባቸው ከተሞች ባድማ ከተማ ባደረግሁሽ ጊዜ፥ ቀላያትንም ባንቺ ላይ ባስነሳሁብሽ ጊዜ ብዙ ውኆችም በከደኑሽ ጊዜ፥ **20** ያኔ ወደ ጉድጓድ እንደወረዱ ሰዎች ወደ ጥንት ሰዎች አወርድሻለሁ፤ እንደ ጥንት ዘመን ፍርስራሾች በምድር ጥልቅ ውስጥ እንድትኖሪ አደርግሻልችሁ። ከዚህ የተነሳ ሰዎች ወደሚኖሩበት **21** ጥፋትን አመጣብሻለሁ ለዘላለምም ትጠፊያለሽ፤ ይፈልጉሻል ነገር ግን ለዘላለም አያገኙሽም፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።

Ezekiel 26:1

በአስራ አንደኛው አመት
"በ11ኛው አመት።" ይህ ማለት ንጉሥ ኢዮአቄም በምርኮ ወደ ባቢሎን ከተወሰደ ከአስራ አንድ አመት በኋላ ማለት ነው። "ከንጉሥ ኢዮአቄም ስደት፣ በአስራ አንደኛ አመት" (ተከታታይ ቁጥር እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

በወሩ የመጀመሪያ ቀን
"በወሩ 1ኛ ቀን።" ሕዝቅኤል በዕብራዊያን የወር አቆጣጠር የትኛው ወር ማለቱ እንደሆነ እርግጠኛ መሆን አይቻልም። (ተከታታይ ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ጢሮስ ኢየሩሳሌምን በመቃወም ተናግሯል
እዚህ ስፍራ "ጢሮስ" እና "ኢየሩሳሌም" የሚሉት የከተማ ስሞች በእነዚያ ከተሞች ነዋሪዎች የሆኑ ሰዎችን ይወክላል። "የጢሮስ ሰዎች ጠኢየሩሳሌምን ሰዎች በመቃወም ተናገሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አሃ!
"አሃ" የሚለው ቃል ሰዎች አንዳች ነገር ሲያገኙ የሚያሰሙት ድምጽ ነው። "አዎን" ወይም "ይህስ ታላቅ ነገር ነው!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ አጋኖ የሚለውን ይመልከቱ)

የህዝብ መግቢያ በሮች ተሰበሩ
የጢሮስ ሰዎች እነዚህን ቃላት የተጠቀሙት ኢየሩሳሌም በዙሪያዋ የሚገኙ አገራት ነጋዴች የሚያልፉባት ከተማ በር እንደሆነች ለመግለጽ ነው። ይህ በአድራጊ አረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰራዊቶች የህዝብ መግቢ በሮችን ደረመሱ/ደመሰሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

እርሷ ፊቷን ወደ እኔ መለሰች
እዚህ ስፍራ "እርሷ" የሚለው ቃል በማጠፊያዎቻቸው ወደ ጢሮስ ለመክፈት "የዞሩትን" የከተማይቱን "በሮች" የሚለውን ቃል ያመለክታል። የዚህ ሀረግ ትርጉም አሁን ጢሮስ ኢየሩሳሌምን ተክታ የብዙ አገራት ነጋዴዎች በውስጧ የሚተላለፉባት ከተማ ሆነች ማለት ነው። "በሮቹ ለእኔ ተከፈቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ እጠግባለሁ/እሞላለሁ
እዚህ ስፍራ "መጥገብ/መሞላት" የሚለው የሚገልጸው መበልጸግን ነው። "እኔ እበለጽጋለሁ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እርሷ ፈረሰች
"ኢየሩሳሌም ፈረሰች"

Ezekiel 26:3

እነሆ
"አድምጡ" ወይም "ልነግራችሁ ላለው ነገር ትኩረት ስጡ!"

በባህር ላይ እንደሚነሳ ማዕበል ብዙ አገራትን በእናንተ ላይ አስነሳለሁ
እዚህ ስፍራ "አገራት" የሚለው ቃል ጠላቶቻቸውን ያመለክታል። "በማዕበል እንደሚናወጥ ባህር ከተለያዩ አገራት በእናንተ ላይ ሰራዊት አስነስቼ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንዲመቷችሁ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከላይዋ አቧራዋን ጠርጌ እንደተጋለጠ አለት አደርጋታለሁ
ያህዌ እንዴት ጢሮስን ሙሉ ለሙሉ እንደ ሚደመስስ ይናገራል። "ሰራዊት ሙሉ ለሙሉ ከተማይቱን እንዲደመስስ እና በዚያ አንዳች እንዳያስቀሩ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 26:5

አያያዥ ሀሳብ
"ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል"

እርሷ ትመጣለች
የጢሮስ ከተማ እዚህ ቦታ የተነገረችው ሴት እንደሆነች ተደርጎ ነው። "ጢሮስ ትመጣለች" ወይም "እርሷ ትመጣለች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በባህሩ መሃል መረብ የማድረቂያ ስፍራ
የጢሮስ ከፊሉ ስፍራ ደሴት ነበር። ይህ አገላለጽ በጢሮስ ላይ ጥፋት ያስከተለውን የሚገልጽ ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "የአሳ ማጥመጃ መረቦችን ለማድረቂያ የሚያገለግል ባዶ ደሴት" ወይም "ሰው የማይኖርበት ሰዎች አሳ ማጥመጃ መረባቸውን የሚያደርቁበት ደሴት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ራሱን በስሙ የሚገልጸው/የሚምለው፤ የተናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳወቅ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ። "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ለአገራት ዝርፊያ/ብዝበዛ ትሆናለች
"ዝርፊያ" ማለት ሰዎች ሰርቀው ወይም በሃይል የሚወስዷቸው ነገሮች ማለት ነው። እዚህ ስፍራ ጢሮስ ተዘረፈች የሚለው የሚወክለው ሀብቷ በሌሎች አገራት መወሰዱን የሚገልጽ ነው። "የአገራት ሰራዊቶች ከጢሮስ ውድ የሆኑ ሀብቶቿን ሁሉ ይወስዳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በሜዳ ያሉ ልጆችዋ ሁሉ በሰይፍ ይታረዳሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የጠላት ሰራዊቶች በሜዳዎች ያሉ ልጆችዋን በሰይፍ ያርዳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በሜዳ ያሉ ሴት ልጆችዋ
x

Ezekiel 26:7

አያያዥ ሀሳብ
"ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል"

እነሆ
"ተመልከቱ" ወይም "አድምጡ" ወይም "ልነግራችሁ ላለው ነገር ትኩረት ስጡ!"

የነገሥታት ንጉሥ፣ የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነጾር
"የነገሥታት ንጉሥ" የሚለው ሀረግ እርሱ ሌሎች ነገስታት ሁሉ የሚታዘዙት ከነገሥታቱ በላይ ታላቅ እንደሆነ የሚያሳይ ማዕረግ ነበር። "ታላቁ የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነጾር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በብዙ ህዝብ ላይ ታላቅ
ይህ የሚያጎላው የናቡከደነጾርን ሰራዊት ብዛት ነው

እርሱ ይፈጃል
እዚህ ስፍራ "እሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ናቡከደነጾርን ሲሆን ለእርሱ ሰራዊት ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "የእርሱ ሰራዊት ይገድላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የእናንተ ሴቶች ልጆች በመስክ ውስጥ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "የእናንተ ሴቶች ልጆች" የሚያመለክተው በመስክ የሚሰሩትን የጢሮስን ወጣት ሴቶች ወይም 2) "የእናንተ ሴቶች ልጆች" የሚለው የጢሮስን ዋና ከተማ ለሚደግፉ በአቅራቢያ ለሚገኙ ከተሞች እና መንደሮች የዋለ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። በሕዝቅኤል 26:6 ላይ የሚገኘው ተመሳሳይ ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "በደሴቱ ዳርቻ ባለው መሬት የሚገኙ ሴቶች ልጆቻችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 26:9

አያያዥ ሀሳብ
"ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል"

አጠቃላይ መረጃ:
በዚህ ሀረግ "እርሱ" እና "የእርሱ" የሚሉት ቃላት ይህ ድርጊት የሚፈጽሙትን የባቢሎንን ንጉሥ ናቡከደነጾርን እና በናቡከደነጾር ሰራዊት ውስጥ የሚገኙ ወታደሮችን ያመለክታሉ። "የእናንተ" የሚለው ቃል ጢሮስ ከተማን ያመለክታል። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በግድግዳ ማፍረሻ ቅጥራችሁን ያፈርሳል፣ መዶሻውም/መሳሪያ ማማችሁን ያደቃል
ምንም እንኳን ግድግዳ ማፍረሻ እና መዶሻው/መሳሪያ የጢሮስን ቅጥር እና ማማ እንደሚያፈርስ ተደርጎ ቢነገርም፣ የናቡከደነጾር ወታደሮች ቅጥሮችንና ማማዎችን ለማፍረስ ይጠቀሙባቸው ነበር። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ግድግዳ ማፍረሻ መሳሪያ
"ግድግዳ ማፍረሻ" በሰራዊት ውስጥ የሚገኙ ብዙ ወንዶች ቅጥሮችን ወይም በሮችን ሰብረው ወደ ውስጥ ለመግባት የሚይዟቸው ትላልቅ እንጨቶች ወይም ግንዶች ናቸው።

መሳሪያዎች/መዶሻ
ከብረት የተሰራ ማማዎችን ለማፍረስ የሚያገለግል መሳሪያ/መዶሻ

ወደ በራችሁ ሲገባ፣ ቅጥራቸው ወደ ፈረሰባቸው ሰዎች ከተማ እንደሚገቡ ወንዶች ሆኖ ይገባል
እዚህ ስፍራ ያህዌ የናቡደነጾር ሰራዊት ወደ ጢሮስ ከተማ የሚገባበትን ሁኔታ የገለጸው በተነጻጻሪ ዘይቤ ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቅጥሮቻቸው የፈረሱባቸው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ቅጥሮቿን ካፈረሱ በኋላ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ezekiel 26:12

አያያዥ ሀሳብ
"ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል" በዚህ ሀረግ "እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው በናቡከደነጾር ሰራዊት ውስጥ የሚገኙ ወታደሮችን ነው። "የእናንተ" እና "እናንተ" የሚለው የሚያመለክተው የጢሮስ ከተማን ነው።

ሃብታችሁን እና ሸቀጣሸቀጣችሁን ይቀማሉ ይዘርፋሉ
"ሃብታችሁን ይዘርፋሉ" እና "እና ሸቀጣሸቀጣችሁን ይቀማሉ" የሚሉት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው የተደጋገሙት ትኩረት ለመስጠት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቅንጦት
ውድ እና ምቾት የሚሰጥ

ድንጋዮቻችሁ/የድንጋይ ፍርስራሻችሁ፣ ሳንቃዎቻችሁ፣ እና ሸክላዎቻችሁ
ይህ የሚያመለክተው ቅጥሮች እና ቤቶች ከፈራረሱ በኋላ የሚቀረውን ነው

በውሃ ውስጥ
"በባህር"

የበገናችሁ ድምጽ ከእንግዲህ አይሰማም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ከእንግዲህ በገናችሁ አይሰማም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በገላጣ ሜዳ ላይ እንደሚገኝ አለት አደርጋችኋለሁ
ይህ ዘይቤ የሚገልጸው ያህዌ ጢሮስን ከደመሰሰ በኋላ የሚሆነውን ነው። በሕዝቅኤል 26:4 ላይ የሚገኘው ተመሳሳይ ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የአሳ መረብ ለመድረቅ የሚሰጣበትን ቦታ ትሆናላችሁ
ይህኛውም ዘይቤ ያህዌ ጢሮስን ካጠፋ በኋላ ውጤቱን ይገልጻል። በሕዝቅኤል 26:5 ላይ የሚገኘው ተመሳሳይ ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መረቦች.... ስፍራ ትሆናላችሁ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "መረቦች... ስፍራ አደርጋችኋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 26:15

አያያዥ ሀሳብ
"ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል"

ደሴቲቱ... በመሃላችሁ አንቀጠቀጥምን?
ይህ ጥያቄ አዎንታዊ ምላሽ ይጠብቃል፤ ደግሞም የጢሮስን ውድመት አጉልቶ ያሳያል። ይህ በዐረፍተ ነገር መልል ሊተረጎም ይችላል።"ደሴቲቱ በመሃላችሁ... ትንቀጠቀጣለች።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ደሴቶቹ አይንቀጠቀጡምን
እዚህ ስፍራ "ደሴቶቹ" የሚለው የሚወክለው በደሴቶቹ የሚኖሩ ሰዎችን ነው።"በደሴቶቹ የሚኖሩ ሰዎች በፍርሃት አይንቀጠቀጡምን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የባህሩ ልዑላን
"የባህሩ ዳርቻዎች ልዑላን"

እየተንቀጠቀጡ ይለብሳሉ
ይህ ዘይቤ ልዑላኑ ፍርሃትን ልብሳቸው ያደረጉት ይመስል በፍርሃት መንቀጥቀጣቸውን ይገልጻል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእናንተ ምክንያት ይደነግጣሉ
"በእናንተ ላይ ከደረሰው ክፉ ነገር የተነሳ መናገር ይሳናቸዋል"

Ezekiel 26:17

አያያዥ ሀሳብ:
"ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል"

አጠቃላይ መረጃ:
በእነዚህ ሀረጎች፣ "እነርሱ" የሚለው የሚያመለክተው "የባህሩን ዳርቻ ልዑላን" ሲሆን በቀደመው ሀረግ ደግሞም "እናንተ" የሚለው ጢሮስን ያመለክታል።

"ድምጽን ማሰማት"
"መዘመር"

በመርከበኞች የተያዛችሁት እናንተ እንዴት እንደተደመሰሳችሁ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በመርከበኞች የተያዛችሁትን - እናንተን ¬እንዴት ጠላቶቻችሁ እንዳጠፏችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በአካባቢያቸው በሚኖሩ ላይ ሁሉ ስለ ራሳቸው ሽብር ያሰራጫሉ
"ሽብር" የሚለው ረቂቅ ስም "መሸበር" በሚለው ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። "በዚሪያቸው ያሉ ሰዎች ሁሉ እንዲሸበሩ አደረጉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በውድቀታችሁ ቀናት የባህር ዳርቻዎቹ ይናወጣሉ። የባህሩ ደሴቶች በስፍራችሁ ከመጥፋታችሁ የተነሳ በፍርሃት ይዋጣሉ
እነዚህ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች በትረጉም ተመሳሳይ ናቸው፤ ደግሞም በጢሮስ ጥፋት በዙሪያ ያሉ ሰዎች የሚያሳዩትን ምላሽ ያጎላሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የባህር ዳርቻዎቹ ይናወጣሉ
እዚህ ስፍራ "የባህር ዳርቻ" የሚለው የሚወክለው በዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ነው። "የባህሩ ዳርቻ ነዋሪዎች ተናወጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህ በስፍራችሁ አትገኙም
የጢሮስ ጥፋት እንደ ሰው ሞት ሆኖ ተገልጽዋል። " እናንተ ጠፍታችኋል" ወይም "ከእንግዲህ በህይወት አትቀጥሉም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 26:19

አያያዥ ሀሳብ:
"ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል"

እኔ አንቺን ሳበጅህ
እዚህ ስፍራ "አንቺ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የጢሮስ ከተማን ነው። በተጻፈበት ቋንቋ "አንቺ" የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር ሴቴ ጾታን ያመለክታል።

እንደ ሌሎች ሰው የማይኖርባቸው ከተሞች ሳደርግሽ
እዚህ ስፍራ ጢሮስ ከሌሎች ሰው ከማይኖርባቸው ከተሞች ጋር ተነጻጽራለች። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጥልቆቹ
እዚህ ስፍራ "ጥልቆቹ" ማለት የባህር ጥልቅ ውሃ ማለት ነው። "ጥልቅ ውሃ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ጥንቱ ጊዜ ፍርስራሽ በምድር ዝቅተኛ ስፍራ እንድትኖሪ፣ ወደ ጉድጓድ እንደሰመጡት እንደ ጥንት ዘመን ህዝብ ዝቅ አደርግሻለሁ
ያህዌ በጢሮስ ላይ የሚያደርሰው ወደ መቃብር ከወረዱ ሰዎች ጋር እና ከፈራረሱ ከተሞች ጋር ተነጻጽሯል። (ሰውኛ ዘይቤ እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ጉድጓድ
ይህ ከመቃብር ጋር ይነጻጸራል። ምክንያቱም መቃብር ወደ ሙታን ዓለም መግቢ ተደርጎ ይታሰብ ነበር፣ እንደዚሁም ደግሞ ጉድጓድ ያንን ዓለም ይወክላል። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በህያዋን ምድር መቆም
ይህ የሚወክለው የከተማይቱን የቀደመ መልክ መታደስ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በአንቺ ላይ ጥፋት አመጣለሁ
"ጥፋት" የሚለው ረቂቅ ስም "አሳዛኝ" በሚለው ቅጽል ወይም "ደመሰሰ" በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። "ፍጻሜሽን አሳዛኝ አደርገዋለሁ" ወይም "እኔ አንቺን እደመስሳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያ በኋላ ዳግም ህልውና የምታገኚ አትሆኝም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች ይፈልጉሻል ነገር ግን ፈጽሞውኑ ዳግም ሊያዩሽ/ሊያገኙሽ አይችሉም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 27

1 የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፥ **2** "አንተ የሰው ልጅ ሆይ እንግዲህ ፥ ስለ ጢሮስ ሙሾ ጀምር ጢሮስንም እንዲ በላት **3** 'አንቺ በባሕር መግቢያ የምትኖሪ በብዙም ደሴቶች ላይ ከሚኖሩ ህዝቦች ጋር ንግድን የምታደርጊ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ጢሮስ ሆይ፥ አንቺ። 'በውበት ፍጹም ነኝ ብለሻል! **4** ዳርቻሽ በባሕር ውስጥ ነው የሰሩሽ ፍጹም ውብ አድርገውታል። **5** ሳንቃዎችሽን ሁሉ ከሳኔር ጥድ ሠርተዋል፥ ደቀልንም ሊሰሩልሽ ከሊባኖስ ዝግባ ወስደዋል። **6** ከባሳን ዛፍ መቅዘፊያሽን ሠርተዋል፥ በዝሆን ጥርስ ከታሸበ ከኪቲም ደሴቶች ዛፍ የመርከብ ወለሎችሽን ሠርተዋል። **7** የመርከብሽ ሸራ ልክ እንደ ሰንደቅ ዓላማሽ የግብጽ ባለብዙ ቀለማት በፍታ ጨርቆች ነበሩ። **8** የሲዶናና የአራድ ሰዎች ቀዛፎችሽ ነበሩ፤ የጢሮስ ጥበበኞችሽ በአንቺ ዘንድ ነበሩ የመርከቦችሽም መሪዎች ነበሩ። **9** ልምድ ያላቸው ጥበበኞች መጋጠሚያዎችሽን ሞልተዋል። የባሕር መርከቦች ሁሉና መርከበኞቻቸው የንግድ እቃዎችሽን ለንግድ ያጓጉዙልሻል። **10** ፋርስና ሉድ ፉጥም በሠራዊትሽ ውስጥ ነበሩ፥ ጋሻና ራስ ቍርም በአንቺ ውስጥ ያንጠለጥሉ ነበር፥ እነርሱም ውበትሽን አሳዩ። **11** በሠራዊትሽ ውስጥ የነበሩት የአራድ እና የኤሌክ ሰዎች በቅጥሮችሽ በዙሪያ ነበሩ፥ ገማዳውያንም በግንቦችሽ ውስጥ ነበሩ! ጋሻቸውንም ዙሪያውን በቅጥርሽ ላይ አንጠለጠሉ! ውበትሽንም ፍጹም አደረጉት! **12** በብዙ ዓይነት ማለትም በብር፥ በብረት ፥ በቄርቄሮና በእርሳስ ካለሽ ብልጥግና ብዛት የተነሣ ተርሴስ የንግድ ደንብኛሽ ነበረች። ሸቀጥሽን ይገዙና ይሸጡ ነበር። **13** ያዋንና ቶቤል ሞሳሕም ባሮችንና ከናስ የተሰሩ እቃዎችን ይነግዱ ነበር። ንግድሽን የሚመሩት እነርሱ ነበሩ። **14** ከቤተ ቴርጋማም መጋዣዎችን፥ የጦር ፈረሶችንና በበቅሎዎችን ወደ ንግድሽ አመጡ። **15** የድዳን ሰዎች በብዙ ዳርቻዎችሽ የንግድ አጋሮችሽ ነበሩ። ንግድ በእጅሽ ነበረ፤ በሸቀጥሽ ምላሽ የዝሆን ጥርስና ዞጲ ይልኩልሽ ነበር። **16** ሶርያ የብዙ ምርቶችሽ ተጠቃሚ ነበረች። በልዋጩም የከበረ ድንጋይ፥ የወይን ጠጅ፥ ባለ ብዙ ቀለም ልብሶች፥ ያማሩ ጨርቆች፥ በዛጎል እና ቀይ ዕንቍም ያቀርቡ ነበር። **17** ይሁዳና የእስራኤል ምድር የንግድ አጋሮችሽ ነበሩ። የሚኒትን ስንዴ ጣፋጭም እንጐቻ፥ ማር ዘይትም በለሳንም ያቀርቡ ነበር። **18** ደማስቆ የምርትሽ ሁሉ፥ ተዝቆ የማያልቅ ሀብትሽ እንዲሁም የኬልቦን የወይን ጠጅና የዘሀርን የበግ ጠጕር ይነግዱ ነበር። **19** ዌንዳንና ያዋን ከአንቺ ጋር ይነግዱ ነበር። ቀልጦ የተሠራ ብረት፥ ብርጕድና ቀረፋም ያቀርቡ ነበረ። ይህም ላንቺ ንግድ ሆነልሽ **20** ድዳን የግላስ ንግድ ከአንቺ ጋር ነበራት። **21** ዓረብና ሌሎች የቄዳር አለቆች ሁሉ የንግድ አጋሮችሽ ነበሩ፤ ጠቦቶች፥ አውራ በጎችና ፍየሎችን ለንግድ ያቀርቡልሽ ነበር። **22** የሳባና የራዕማ ነጋዴዎች ምርጥ የሆነ የቅመም ሽቱ ሁሉና ብዙ ዓይነት የከበሩ ድንጋዮች ሊሸጡልሽ ይመጡ ነበር። ወርቅም ይነግዱ ነበር። **23** ካራንና ካኔ ዔድንም ከሳባ፥ ከአሦርና ከኪልማድ በመሆን የንግድ አጋሮችሽ ነበሩ። **24** እነዚህ ባማረ ልብስ በሰማያዊ ካባ በወርቀ ዘቦም፥ በዝግባ በተሠራች በገመድም በታሰረች በግምጃም በተሞላች ሳጥን ይነግዱ የነበሩ ናቸው። **25** የተርሴስ መርከቦች የሸቀጥሽ ማጓጓዣዎች ነበሩ። አንቺም በባህር መካከል ተሞልተሽ በጭነትም ከብደሽ ነበር። **26** ቀዛፊዎችሽ ወደ ስፊ ባህሮች አመጡሽ፤ የምሥራቅ ነፋስም በባህሮቹ መካከል ሰበረሽ። **27** በውድቀትሽ ቀን ብልጥግናሽ፥ ሸቀጥሽና የንግድ ዕቃዎችሽ፤ የመርከብ ነጂዎችሽ፥ መርከበኞችሽም መርከብ ሠሪዎችሽ፤ ነጋዴዎችሽ ሁሉ በአንቺም ውስጥ የነበሩ ሰዎች ሁሉ በውስጥሽ ካሉት ሠራተኞች ጋር ወደ ባሕር ጥልቅ ይወድቃሉ። **28** ከመርከብ መሪዎች ጩኸት ድምፅ የተነሣ በባህር አጠገብ ያሉ ከተሞች ይንቀጠቀጣሉ። **29** ቀዛፊዎችም ሁሉ መርከበኞችም መርከብ መሪዎችም ሁሉ ከመርከቦቻቸው ወርደው በመሬት ላይ ይቆማሉ። **30** ከዚያም ድምፃቸውን እንድትሰሚ ያደርጉሻል ምርር ብለውም ይጮኻሉ፥ ፤ በራሳቸውም ላይ ትቢያ ይነሰንሳሉ፥ በአመድም ውስጥ ይንከባለላሉ **31** ስለ አንቺም የራሳቸውን ጠጕር ይላጫሉ ማቅም ይታጠቃሉ በምሬትም ስለአንቺ ያነባሉ ይጮኹሉ። **32** በትካዜያቸውም ልቅሶ ያነሡልሻል፥ ስለ አንቺም ሙሾ ያሞሻሉ እንዲህም ይላሉ። በባሕር መካከል ጠፍቶ እንደ ቀረ እንደ ጢሮስ ያለ ማን ነው? **33** ሸቀጥሽ ከባሕር በወጣ ጊዜ ብዙ አሕዛብን ያጠግብ ነበር በብልጥግናሽና በንግድሽ ብዛት የምድርን ነገሥታት ባለ ጠጎች አድርገሻል። **34** ነገር ግን በጥልቅ ውኃ ውስጥ በባህር በተሸፈንሽ ጊዜ ንግድሽና ሠራተኞችሽ ሁሉ ሰጠሙ! **35** በባህር ዳርቻ የሚኖሩ ሁሉ ተደንቀውብሻል፥ ነገሥታቶቻቸውም በፍርሀት ተንቀጥቅጠዋል። ፊታቸውም ደንግጧል። **36** የአሕዛብ ነጋዴዎች አፍዋጩብሽ፤ ለድንጋጤ ሆነሻል፥ ከእንግዲህ በኋላም አትኖሪም።

Ezekiel 27:1

የያህዌ ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የነገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጥ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ተናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

የእንጉርጉሮ እርዳታ
"እንጉርጉሮ" የሚለው ይህ ረቂቅ ስም "ለቅሶ" በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። "አልቃሽ መሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ለጢሮስ እንዲህ በል
እዚህ ስፍራ "ጢሮስ" የሚለው ቃል በጢሮስ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን ይወክላል። "ለጢሮስ ሰዎች እንዲህ በላቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በባህሩ መግቢያ በሮች ለሚኖሩ
"በባህሩ በሮች ለሚኖሩ" ወይም "በባህሩ መግቢያ ለሚኖሩ"

ጢሮስ ሆይ፣ እንዲህ ብለሻል
እዚህ ስፍራ "ጢሮስ" የሚለው ቃል በጢሮስ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን ይወክላል። "የጢሮስ ሰዎች፣ እንዲህ ብላችኋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ በውበት ፍጹም ነኝ
"ውበት" የሚለው ረቂቅ ስም "ውብ" በሚለው ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። "እኔ ፍጹም ውብ ነኝ" ወይም "ሙሉ ለሙሉ/እንከን የለሽ ውብ ነኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 27:4

አያያዥ ሀሳብ፡
"ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል"

አጠቃላይ መረጃ፡
በእነዚህ ሀረጋት "የአንቺ" እና "አንቺ" የሚሉት የሚያመለክቱት ጢሮስን ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አጠቃላይ መረጃ:
የጢሮስ ከተማ እዚህ ስፍራ እና በተከታዮቹ ጥቅሶች የተገለጸችው ውብ መርከብ ተደርጋ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ወደቦችሽ
"ድንበሮችሽ"

የባህር ልብ
"የባህር መሃል"

ሳንቃ/ጣውላ
ረጅም፣ ጠፍጣፋ እንጨት፣ ወፍራን ሳንቃ

መስቀያ
የመርከብ ሸራ የሚይዙ በመርከብላ ላይ የሚገኙ ብዙ ሰዎች

Ezekiel 27:6

አያያዥ ሀሳብ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል። የጢሮስ ከተማ ውብ መርከብ እንደሆነች ተደርጎ መብራራቱ ቀጥሏል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ:
በእነዚህ ሀረጋት "እነርሱ" የሚለው የሚያመለክተው ጢሮስን የሚገነቡትን ነው። "የአንቺ" የሚለው ጢሮስን ያመለክታል።

የጀልባ መቅዘፊያዎች
ሰዎች ጀልባ ለመቅዘፍ የሚገለገሉበት ረጅም የሆነ በአንድ ጫፉ ጠፍጣፋነት ያለው እንጨት።

የጀልባ ወለል
ሰዎች ሊራመዱበት የሚችሉት የጀልባዋ ክፍል

እነርሱን ይሸፍናሉ
"ይሸፍኗቸዋል"

ከዝሆን ጥርስ
ነጭ፣ ውብ፣ እና ጠንካራ ከእንስሳ ጥርስ የተሰራ ነገር

የመርከብ ሸራ
ረጅም የሆነ ነፋስ መርከቧን እንዲያንቀሳቅስ የሚያደርግ ሸራ

የመርከቦችሽ ሸራ ቀላማቸው ውብ የሆኑ ከግብጽ በመጣ የሀር ጨርቅ ነው
የመርከቦች ሸራ ከጢሮስ አርማ ወይም ባንዲራ ጋር ተነጻጸሯል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመለከቱ)

Ezekiel 27:8

አያያዥ ሀሳብ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል። የጢሮስ ከተማ ውብ መርከብ እንደሆነች ተደርጎ መብራራቱ ቀጥሏል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ:
"አንቺ" እና "የአንቺ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ጢሮስን ነው።

አራድ
ይህ ስም የሲዶና አነስተኛ የባርህ ዳርቻ ስያሜ ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የጢሮስ ጠቢባን
"የጢሮስ አዋቂዎች"

መርከበኛ/መርከብ መሪ
የመርከብ መሪ መርከቢቱ ወደምትሄድበት ስፍራ እየተቆጣጠረ የሚነዳ ሰው ነው

ባይብሎስ
ይህ የሶሪያ ባህር ዳርቻ የሆነች ከተማ ስያሜ ነው። ሌሎች ቅጂዎች ጌባል ብለው ይጠሯታል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ እና የቅጂ ልዩነቶች የሚሉትን ይመልከቱ)

መገጣጠሚያሽን ደፈኑ
"ስንጥቅሽን ጠገኑ" ወይም "ሽንቁርሽን ጠገኑ"

መርከበኞች
መርከበኛ በመርከብ ላይ ከሚሰሩ ሰዎች አንደኛው ነው

Ezekiel 27:10

አያያዥ ሀሳብ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ:
"አንቺ" እና "የአንቺ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ጢሮስን ነው።

ፋርስ፣ ሉድ... ሊቢያ...አራድ...ሔሌክ...ገማድ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የአንቺ የጦር ሰዎች
"በአንቺ ጦር የሚዋጉ ወንዶች" ወይም "ጦረኞችሽ/ሰራዊትሽ ሆነው የሚያገለግሉ"

ድምቀትሽ/ሞገስሽ የሆኑ
"ድምቀት" የሚለው ረቂቅ ስም "መድመቅ" በሚለው ቅጽል ተተክቶ ሊተረጎም ይችላል። "እንደምን ድምቀት/ሞገስ ነበረሽ" ወይም "ምንኛ ግርማ ነበረሽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ውበትሽን ደመደሙ/ፈጸሙ
"ውበት" የሚለው ረቂቅ ስም "ውብ" በሚለው ቅጽል ተተክቶ ሊተረጎም ይችላል። "ውበትሽን ደመደሙ" ወይም "ፍጹም ውብ አደረጉሽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 27:12

አያያዥ ሀሳብ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ:
በእነዚህ ሀረጋት ውስጥ "የአንቺ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጢሮስን ነው።

ብር፣ ብረት፣ ቆርቆሮ፣ እና እርሳስ
በዚያን ወቅት ያገለግሉ የነበሩ ብረታ ብረቶች ናቸው

ዕቃዎችሽ
"ለገበያ/ሽያጭ የምታቀርቢያቸው ነገሮች"

ያዋን
ይህ የባህር ዳርቻ የሆነ ስፍራ ነው ዴዳን ተብሎም ይታወቃል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የሸቀጥ ንግድሽን ይለዋወጡ ነበር
"በሸቀጣሸቀጥሽ ይነግዱ/ይለዋወጡ ነበር"

Ezekiel 27:14

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡
በእነዚህ ሀረጋት ውስጥ "የአንቺ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጢሮስን ነው።

ቤት ቴርጋማ...ሮሆደስ
እነዚህ የቦታ ስሞች ነበሩ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ያልተኮላሸ ፈረስ
ወንድ ፈረስ

ንግዱ በእጆችሽ ላይ ነበር
እዚህ ስፍራ ነገሮች በእጅ ላይ መሆን የሚለው ምናልባትም እነዚያን ነገሮችን መያዝን በዘይቤ የሚገልጽ ወይም የእነዚያ ነገሮች ባለቤት መሆንን ሊያመለክት ይችላል። "ለእነርሱ ልትሸጭላቸው የምትችያቸው ነገሮች ባለቤት ነበርሽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ቀንድ
የአንዳንድ እንስሳትን ረጅም ጥርስ ያመለክታል

ጥቁር እንጨት
ጥቁር ቡናማ በጣም ከባድ እና ጠንካራ የሆነ እንጨት

Ezekiel 27:16

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡
"አንቺ" እና "የአንቺ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ጢሮስን ነው።

አራም ነጋዴ ነበረች
እዚህ ስፍራ "አራም" የሚለው የሚያመለክተው የአራም ሰዎችን ነው። "የአራም ሰዎች ነጋዴዎች ነበሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ነጋዴ
"በንግድ የተሰማራ"

ብሩህ አረንጓዴ የከበረ ድንጋይ/ዛጎል
እጅግ ውድ የሆነ የከበረ አረንጓዴ ድንጋይ ነው

ሀምራዊ
እዚህ ስፍራ ሀምራዊ ጨርቅ ወይም ሱፍ ክር የሚያመለክተው የዕቃውን ቀለም ነው። "ሀምራዊ ጨርቅ" ወይም "ሀምራዊ ክር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)

ሉል
ነጭ እና ጠንካራ የሆነ በባህር ውስጥ ከሚገኙ ፍጥረቶች የሚገኝ ውብ ዶቃ

ቀይ እንቁ
ቀይ እንቁ፣ ውድ ዋጋ ያለው እጅግ ውድ ድንጋይ

ይሁዳ እና የእስራኤል ምድር ከአንቺ ጋር ይገበያዩ ነበር
እዚህ ስፍራ "ይሁዳ እና የእስራኤል ምድር" የሚሉት የሚያመለክቱት የእነዚያን ስፍራዎች ሰዎች ነው። "የይሁዳ እና የእስራኤል ሰዎች ከአንቺ ጋር ይገበያዩ/ይነግዱ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሚኒት...ኬልቦን...ዛሐር
እነዚህ የቦታዎች ስሞች ነበሩ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ጣፋጭ/ኬክ
እዚህ ስፍራ "ጣፋጭ/ኬክ" ተብሎ የተተረጎመው የዕብራይስጡ ቃል ትርጉም በእርግጠኝነት አይታወቅም። ሌሎች ትርጉሞች ሌላ አይነት ምግብ አድርገው ሊተረጉሙት ይችላሉ።

እጣን
ጣፋጭ ማዕዛ ያለው ከዛፍ የሚገኝ ሙጫ

የተትረፈረፈ ሀብት
"ብዙ ሀብት" ወይም "ታላቅ ንብረት"

Ezekiel 27:19

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡
"አንቺ" እና "የአንቺ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ጢሮስን ነው።

ዳን..ያዋን...ኦሴል..ድዳን..ዐረብ.. ቄዳር
እነዚህ የቦታዎች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ዳን እና ያዋን
ይህ ለዳን እና ያዋን ነዋሪዎች ሜቶናሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት ነው። "የዳን እና ያዋን ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የሚቀጠቀጥ/የሚጠፈጠፍ ብረት
በመዶሻ ቅርጽ ሊይዝ የሚችል የብረት አይነት

ቀረፋ
ከዛፍ ቅርፊት የሚገኝ የቅመም አይነት። "ብርጉድ" የዚህ አይነቱ ቅመም ሌላ ስም ነው። (በእርግጠኝነት የማይታወቁትን ነገሮች መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

ጠጅ ሳር
እንደ ሸቶ የሚያገለግል እና ሰዎች ለመድሀኒትነት የሚጠቀሙበት የሳር አይነት

ደዳን ...ነበረች
ይህ ለድን ሰዎች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት ነው። "የድዳን ሰዎች ... ነበሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የኮርቻ ጨርቅ/ምንጣፍ
የኮርቻ ምንጣፍ በፈረስ ወይም ከኮርቻ ስር የሚደረግ ለመቀመጫነት የሚውል ቁራጭ ጨርቅ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አረብ
ለአረብ ሰዎች የሚውል ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ ነው። "የአረብ አገር ሰዎች" ወይም "አረቦች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 27:22

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡
"አንቺ" እና "የአንቺ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ጢሮስን ነው።

ሳባ...ራዕማ...ካራን...ካኔ...ዔደን... ሳባ...አሦር...ኪሌማድ
እነዚህ የቦታዎች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የከበሩ ድንጋዮች
"ውድ ዋጋ ያላቸው ድንጋዮች"

ካራን፣ ካኔ እና ዔደን፤ ከአንቺ ጋር የሚነግዱት ከሳባ፣ አሦር እና ኪልማድ ጋር በመሆን ነበር
ይህ ከእነዚህ ስፍራዎች የሆኑ ሰዎችን ያመለክታል። የካራን፣ ካኔ እና የዔደን ሰዎች፤ ከሳባ፣ አሦር እና ኪልማድ ሰዎች ጋር በመሆን አብረውሽ ይነግዱ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 27:24

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡
"አንቺ" እና "የአንቺ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ጢሮስን ነው።

ከአንቺ ጋር የሚነግዱት እነዚህ ነበሩ
"እነርሱ ከአንቺ ጋር ይነግዳሉ"

ባለ ብዙ ጌጥ ሀምራዊና በሚያምሩ ቀለማት ተጠለፉ ልብሶች
"ብዙ ቀለም ያላቸው እና ጌጠኛ ሀምራዊ ልብሶች"

በብዙ ቀለማት ያጌጡ፣ ጥልፎች፣ እና አምረው የተሰሩ ካባዎች
"ከፍተኛ ጥራት ያላቸው ባለ ብዙ ህብር ካባዎች"

የጢሮስ መርከቦች ነጋዎችሽን ያመላልሱ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የጢሮስ መርከቦች ነጋዴዎችሽን ያጓጉዙ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እጅግ በሀብት በተሞሉ ጭነቶች በልጽገሽ/ተሞልተሽ ነበር
የጢሮስ ብልጽግና የተገለጸው በጭነት እንደተሞላች መርከብ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የባህሮች ልብ
"በባህር መሃል።" ይህ በሕዝቅኤል 27፡4 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።

Ezekiel 27:26

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡
"አንቺ" እና "የአንቺ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ጢሮስን ነው።

አጠቃላይ መረጃ፡
የጢሮስ ከተማ እዚህ ስፍራ እና በተከታዮቹ ቁጥሮች ውስጥ የተገለጸችው እንደ ፈራረሰች መርከብ ተደርጋ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አስጨናቂዎችሽ
"አንቺን የሚያስጨንቁሽ ሰዎች"

ሰፊ ባህር
"ታላቅ ውሃ"

የምስራቅ ነፋስ
"ከምስራቅ የሚነፍስ ጠንካራ ነፋስ"

በእነርሱ መሃል
"የባህር ልብ" ወይም "በባህሩ መሃል።" ይህ በሕዝቅኤል 27፡4 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።

ባህረኞች
ጀልባ የሚቀዝፉ ሰዎች/ መርከብ የሚነዱ ወንዶች

ቡድን
በቡድን የሚሰሩ ሰራተኞች

የባህር ጥልቀት
"የባህር ልብ" ወይም "በባህሩ መሃል።" ይህ በሕዝቅኤል 27፡4 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።

በጥፋትሽ/በምትደመሰሽበት እለት
x

Ezekiel 27:28

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል። የጢሮስ ከተማ የተሰበረች መርከብ ሆና መገለጽዋ ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡
"አንቺ" እና "የአንቺ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ጢሮስን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በባህሩ የሚገኙ ከተሞች ይንቀጠቀጣሉ
እዚህ ስፍራ "በባህሩ የሚገኙ ከተሞች" የሚለው የሚወክለው በእነዚያ ከተሞች የሚኖሩ ሰዎችን ነው። "በባህሩ በሚገኙ ከተሞች የሚኖሩ ሰዎች ይንቀጠቀጣሉ/በጭንቀት ይርዳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

መቅዘፊያውን የሚይዙ ሰዎች በሙሉ
"አስጨናቂዎች ሁሉ"

በምሬት ያለቅሳሉ
"በከፍተኛ ሀዘን ያለቅሳሉ"

በራሳቸው ላይ ትቢያ ይነሰንሳሉ። በአመድ ላይ ይንከባለላሉ
እነዚህ የሀዘን እና በምሬት የማልቀስ መገለጫዎች ናቸው። (ትምዕርታዊ/ ምልክታዊ ድርጊቶች የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 27:31

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል። የጢሮስ ከተማ የተሰበረች መርከብ ሆና መገለጽዋ ቀጥሏል።(ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ፡
በዚህ ቁጥር "እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው በቁጥር 28 እና 29 ላይ የተጠቀሱትን ሰዎች ነው። "አንቺ" እና "የአንቺ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ጢሮስን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ አንቺ ራሳቸውን ይላጫሉ፣ ደግሞም ማቅ ይለብሱልሻል
እነዚህ የሀዘን እን ልቅሶ መገለጫዎች ናቸው። (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

መላጨት
በራስ ላይ ምንም ፀጉር ያለማስቀረት

የሰቆቃቸውን ጩኸት ያሰማሉ
"ሰቆቃ" የሚለው ረቂቅ ስም "አለቀሱ" በሚል ግስ ሊተረጎም ይችላል። "ጮኸው ያለቅሳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ሙሾ አወጡ
"በቀብር ላይ የሚከናወን የለቅሶ ግጥም"

አሁን በባህሩ መሃል ዝምታ ውስጥ የገባ እንደ ጢሮስ ያለ ማን ነው?
ይህ ጥያቄ አሉታዊ ምላሽ ሲጠብቅ፣ ለጢሮስ ከሌሎች ከተሞች ሁሉ የተለየ ትኩረት ይሰጣል። ጥያቄው በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጽ ይችላል። "የትኛውም ሌላ አሁን ከተማ በባህሩ መሃል ዝምታ ውስጥ እንደገባችው እንደ ጢሮስ አይደለም።" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

አሁን ዝምታ ውስጥ የገባች
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል።"አሁን ጠላቶቿ ጸጥ ያሰኟት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 27:34

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል። የጢሮስ ከተማ የተሰበረች መርከብ ሆና መገለጽዋ ቀጥሏል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ፡
በእነዚህ ቁጥሮች "አንቺ" እና "የአንቺ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ጢሮስን ነው።

በጥልቁ ውሃ፣ በወንዙ በተንኮታኮትሽ/በጠፋሽበት ጊዜ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ባህሩ፣ ጥልቁ ውሃ በከደነሽ ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

መንኮታኮት
"መንኮታኮት" ወደ ቁርጥራጭነት መሰባበር ነው።

ቡድን
በቡድን የሚሰሩ ሰራተኞች

በአንቺ ላይ በደረሰው ደነገጡ
"በአንቺ ላይ በደረሰው ደንግጠውና በፍርሃት ተውጠው ነበር"

ንጉሦቻቸው በፍርሃት ተንቀጠቀጡ
"ፍርሃት" የሚለው ረቂቅ ስም "በፍርሃት" በሚለው ተውሳከ ግስ ሊተረጎም ይችላል። "ንጉሦቻቸው በፍርሃት ተንቀጠቀጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ፊታቸው ተንቀጠቀጠ
እዚህ ስፍራ "ፊት/ገጽ" የሚለው የሚወክለው የአንደን ሰው ሁለንትና ነው። "ይንቀጠቀጡ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በአንቺ ላይ በአድናቆት አፏጩ
ማፏጨት በጥርስ መሃል የፉጨት ድምጽ ማሰማት ነው። በስጋት፣ በሃዘን ወይም በአድናቆት ጊዜ ሊሰማ ይችላል። (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ማስፈራሪያ/ለድንጋጤ ሆንሽ
"ፍርሃት" የሚለው ረቂቅ ስም "አሰቃቂ" በሚለው ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አሰቃቂ/አስፈሪ ሆንሽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 28

1 የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ። 2 የሰው ልጅ ሆይ፥ የጢሮስን ገዥ እንዲህ በለው፥ 'ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ልብህ ኰርቶአል፥ አንተም "እኔ አምላክ ነኝ! በባሕር መካከል በአማልክት ወንበር ላይ እቀመጣለሁ!" ብለሃል። ነገር ግን አንተ ሰው እንጂ እግዚአብሔር ባትሆንም ልብህን እንደ አምላክ ልብ አደረግህ። 3 እነሆ፥ ከዳንኤል ይልቅ ጥበበኛ እንደሆንክ ምንም ሚስጢር ከአንተ እንደማይሰወር አሰብክ። 4 በጥበብና በማስተዋል ራስህን አበልጽገሀል፥ ወርቅና ብርም በግምጃ ቤትህ ውስጥ ሰብስበሃል! 5 በታላቅ ጥበብና በንግድህ ብልጥግናህን አብዝተሃል ከብልጥግናህም የተነሳ ልብህ ኰርቶአል! 6 ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ልብህን እንደ አምላክ ልብ አድርገሃልና 7 ስለዚህ፥ እነሆ፥ እንግዳ ሰዎችን፥ የአሕዛብን ጨካኝ ሰዎችን አመጣብሃለሁ! ሰይፋቸውንም በጥበብህ ውበት ላይ ይመዝዛሉ፥ ክብርህንም ያዋርዳሉ! 8 ወደ ጕድጓድ ያወርዱሃል፥ በባህር ልብ ውስጥ የሞቱትን ሰዎች ሞት ትሞታለህ። 9 በውኑ በገዳይህ ፊት፥ "እኔ አምላክ ነኝ" ትላለህን? አንተ ሰው ነህ እንጂ አምላክ አይደለህም፥ በሚቆራርጡህ እጅ ትወድቃለህ። 10 በእንግዶች ሰዎች እጅ ያልተገረዙትን ሰዎች ሞት ትሞታለህ እኔ ተናግሬአለሁና፥ ይላል እግዚአብሔር!" 11 የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ። 12 የሰው ልጅ ሆይ፥ በጢሮስ ንጉሥ ላይ ሙሾ አሞሽተህ እንዲህ በለው፥ 'ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡ጥበብን የተሞላህ የፍጽምና መደምደሚያ በውበትህም ፍጹም ነበርክ! 13 በእግዚአብሔር ገነት በዔድን ነበርህ! በከበረ ዕንቊስ ሁሉ፥ ሰርድዮን፥ ቶጳዝዮን፥ አልማዝ፥ ቢረሌ፥ መረግድ፥ ኢያስጲድ፥ ሰንፔር፥ በሉር፥ የሚያብረቀርቅ ዕንቊ፥ ወርቅ፥ ተሸፍነህ ነበረ። እነዚህ የከበሩ ድንጋዮች በወርቅ ዕቃ በፊትህ ተቀምጠው ነበር። አነዚህም በተፈጠርህበት ቀን እንድትለብሳቸው ተዘጋጅተው ነበር! 14 የሰውን ዘር እንዲጋርድ እንደቀባሁት ኪሩብ በተቀደሰው በእግዚአብሔር ተራራ ላይ አኖርሁህ! ትመላለስባቸው በነበሩ የእሳት ድንጋዮች መካከል ነበርክ። 15 ከተፈጠርህበት ቀን ጀምረህ በደል እስኪገኝብህ ድረስ በመንገድህ ፍጹም ነበርህ። 16 በንግድህ ብዛት በአምጽ ተሞላህ ስለዚህም ኃጢአትን ሠራህ! ስለዚህ እንደ ርኩስ ነገር ከእግዚአብሔር ተራራ ጣልሁህ የምትጋርድ ኪሩብ ሆይ፥ ከእሳት ድንጋዮች መካከል አጠፋሁህ። 17 በውበትህ ምክንያት ልብህ ኰርቶአል፤ ከክብርህ የተነሣ ጥበብህን አረከስህ! ወደ ምድርም ጣልሁህ! ያዩህም ዘንድ በነገሥታት ፊት አስቀመጥኩህ። 18 በበደልህ ብዛት ቅን ባልሆነው ንግድህም ቅዱስ ስፍራህን አረከስህ! ስለዚህ እሳትን ከውስጥህ አውጥቻለሁ እርስዋም ትበላሀለች። በሚያዩህም ሁሉ ፊት በምድር ላይ አመድ አደርግሀለሁ። 19 በአሕዛብም ውስጥ የሚያውቁህ ሁሉ ይደነቁብሃል፤ ይደነግጣሉ ፥ አንተም እስከ ዘላለምም አትገኝም። 20 የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፥ 21 "የሰው ልጅ ሆይ፥ ፊትህን ወደ ሲዶና አቅንተህ ትንቢት ተናገርባት! እንዲህም በል፥ 22 'ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ሲዶና ሆይ፥ እነሆ፥ በአንቺ ላይ ነኝ፥ ፍርድን በውስጥሽ በማደርግበት ጊዜ ህዝብሽ እኔ እግዚአብሔር እንድሆንኩ እንዲያውቁ በመካከልሽ ክብሬን አገልጣለሁ። ቅዱስ መሆኔም ይገለጣል። 23 ቸነፈርንም በአንቺ ላይ፥ ደምንም በጎዳናሽ ላይ እሰድዳለሁ፥ በሰይፍ የታረዱ በመካከልሽ ይወድቃሉ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቂያለሽ! 24 እኔ ጌታ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ እንዲያውቁ ከእንግዲህም ወዲያ ለእስራኤል ቤት የሚወጋ እሾህ፥ በዙሪያቸውም ካሉ ከናቋቸው ሁሉ የሚያቈስል ኵርንችት አይሆንም 25 ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ የእስራኤልን ቤት ከተበተኑባቸው አሕዛብ ዘንድ በሰበሰብሁ ጊዜ፥ በአሕዛብም ፊት በተቀደስሁባቸው ጊዜ፥ ለባሪያዬ ለያዕቆብ በሰጠኋት ምድራቸው ይቀመጣሉ። 26 በውስጧም ተዘልለው ይቀመጡባታል ቤቶችንም ይሠራሉ ወይኑንም ይተክላሉ በዙሪያቸውም ባሉ በሚንቋቸው ሁሉ ላይ ፍርድን ባደረግሁ ጊዜ ተዘልለው ይቀመጣሉ እኔም እግዚአብሔር አምላካቸው እንደ ሆንሁ ያውቃሉ።

Ezekiel 28:1

የያህዌ ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የነገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጥ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ተናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ልብህ ታበየ
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚወክለው የጢሮስን ገዢ ፈቃድ ወይም ሀሳብ ነው። "አንተ ትዕቢተኛ ነህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ትዕቢተኛ
በስህተት ስላ ራስ ጠቃሚነት አለአግባብ ከፍ አድርጎ ማሰብ።

በአማልክት ስፍራ ወንበሬን አስቀምጣለሁ
"በአማልዕክት ዙፋን እቀመጣለሁ።" እዚህ ስፍራ በአማልዕክት ወንበር መቀመጥ የሚለው የሚወክለው፤ ራሱን ከአማልዕክት አንዱ አድርጎ በመቁጠር በተመሳሳይ ከፍ ባለ ስፍራ እቀመጣለሁ ማለቱን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የባህሮች ልብ
"በባህሮች መሃል።" ይህ በሕዝቅኤል 27:4 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ልብህን እንደ አምላክ ልብ አድርገሃል
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚወክለው አዕምሮን ወይም ሃሳብን ነው። አምላክ ራሱን ከሰዎች የተሸለ አድርጎ ያስባል። "የአምላክ አዕምሮ አለኝ ብለህ ታስባለህ" ወይም "ራስህን ከሌሎች ሰዎች የተሻለ አድርገህ ለማሰብ ፈቅደሃል" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከዳንኤል ይልቅ ብልህ እንደሆንክ ታስባለህ
እዚህ ስፍራ የጢሮስ ገዢ ምን ያህል ብልህ እንደሆነ እንደሚያስብ ራሱን ከነቢዩ ዳንኤል ጋር አነጻጽሯል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 28:4

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ በሕዝቅኤል፣ ለጢሮስ ገዢ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡
በእነዚህ ቁጥሮች "አንተ" እና "የአንተ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት የጢሮስን ገዢ ነው።

ራስህን በጥበብ እና ችሎታ ባለጸጋ አድርገሃል
"ጥበብ" እና "ችሎታ" የሚሉት ረቂቅ ስሞች "ጠቢብ" እና "አዋቂ/ክህሎት ያለው" የሚሉ ቅጽሎችን በመጠቀም መተርጎም ይቻላል። "በራስህ ጥበብና ችሎታ ባለጸጋ ሆነሃ" ወይም "ጠቢብ እና አዋቂ በመሆን ባለጸጋ ሆነሃል"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ገላጭ ተውላጠ ስሞች እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

ወርቅ እና ብር አከማችተሃል
"ወርቅና ብር ሰብስበሃል"

ግምጃ ቤት
ውድ የሆኑ ነገሮች የሚቀመጡበት አስተማማኝ ስፍራ

በታላቅ ጥበብህ እና በንግድህ ሀብትህን አብዝተሃል፣ ስለዚህም ከሃብት ብዛት የተነሳ ልብህ ኮርቷል
"ጥበብ" እና "ሀብት" የሚሉትን ረቂቅ ስሞች "ጠቢብ" እና "ሃብታም" የሚሉ ቅጽሎችን በመጠቀም መተርጎም ይቻላል። "በጣም ጠቢብ በመሆን እና በንግድህ ሀብትህ እየጨመረ ሄዷል፤ በሀብትህ ብዘትም ምክንያት ልብህ ይበልጥ ታብይዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ልብህ ትዕቢተኛ ነው
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚወክለው የጢሮስን ገዢ ፈቃድ ወይም ሃሳብ ነው። "አንተ ትዕቢተኛ ነህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 28:6

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ በሕዝቅኤል፣ ለጢሮስ ገዢ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡
በእነዚህ ቁጥሮች "አንተ" እና "የአንተ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት የጢሮስን ገዢ ነው።

ልብህን እንደ አምላክ ልብ አድርገሃል
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚወክለው አዕምሮን ወይም ሃሳብን ነው። ስለ ራሱ ከሰዎች እንደሚሻል እና አምላክ ነኝ ስለሚል ሰው። በሕዝቅኤል 28:2 ላይ የሚገኘው ተመሳሳይ ቁጥር እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

የጥበብህ ውበት
"ውበት" እና "ጥበብ" የሚሉት ረቂቅ ስሞች "ውብ" በሚል ቅጽል እና "በጥበብ" የሚል ተውሳከ ግስ በመጠቀም መተርጎም ይቻላል። "አንተ በጥበብህ የፈጸምካቸው ውብ ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ክብርህን ያዋርዳሉ
"ድምቀት/ክብር" የሚለው ረቂቅ ስም "ደማቅ" የሚለውን ቅጽል በመጠቀም ሊተረጎም ይችላል። "ክብርህ ምንኛ ተዋረደ" ወይም "ግርማህ ምንኛ ረከሰ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 28:8

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ በሕዝቅኤል፣ ለጢሮስ ገዢ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡
"እነርሱ" የሚለው ቃል የባዕዳንን ሰራዊት ያመለክታል። በእነዚህ ቁጥሮች "አንተ" እና "የአንተ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት የጢሮስን ገዢ ነው።

ጥልቅ ወደ ጉድጓድ
እዚህ ስፍራ "ጉድጓድ" የሚያመለክተው ወቃብርን ወይም ወደ ሲኦል መውረድን ነው። "ወደ መቃብር መውረድ"በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በባህሮች ልብ
"በባህሮች መሃል"

በእውነት አንተ፣ በገዳይህ ፊት ቆመህ "እኔ አምላክ ነኝ ትላለህን?"
ይህ ጥያቄ፣ አምላክ ነኝ የሚል በሰው የሚጠፋ መሆኑን የሚያጎላው ይህ ምጸት አሉታዊ ምላሽ ይጠብቃል። ጥያቄው በዐረፍተ ነገር መለክ ሊጻፍ ይችላል። "በገዳይህ ፊት ቆመህ 'አምላክ ነኝ' አትልም!" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ምጸት የሚሉትን ይመልከቱ)

በ...ፊት
እዚህ ስፍራ ፊት የሚወክለው ሌላ ሰው በሚገኝበት መገኘትን ነው። "በ... መገኘት" ወይም "ፊት ለፊት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በ...እጅ
እዚህ ስፍራ በአንድ ሰው እጅ መሆን የሚወክለው/የሚገልጸው በእነርሱ ቁጥጥር ስር መውደቅን ነው። "በ...ቁጥጥር ስር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በባዕዳን እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የባዕዳን ሰራዊትን ድርጊት የሚገልጽ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት ነው። "በባዕዳን ሰራዊት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ራሱን በስሙ የሚገልጸው/የሚምለው፤ የተናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳወቅ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ። "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 28:11

ዳግም የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ፣ የሰው ልጅ
"የያህዌ ቃል ዳግም ወደ...መጣ" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ከእግዚአብሔር ዘንድ ልዩ መልዕክት ለማስተዋወቅ ውሏል። ይህ ተመሳሳይ ቃል በሕዝቅኤል 18:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ዳግም መልዕክት ሰጠኝ። እንዲህም አለኝ፣ የሰው ልጅ ሆይ" ወይም "ያህዌ ይህን ሁለተኛ መልዕክት ተናገረኝ፦' የሰው ልጅ ሆይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ተነስ
"ዘምር"

አንተ የፍጹምነት ተምሳሌት ነበርክ
"ተምሳሌት" እን "ፍጹምነት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች "ሙሉ ለሙሉ" እና "ፍጹም" የሚሉ ቃላትን በመጠቀም ሊተረጎሙ ይችላሉ። "አንተ ሙሉ ለሙሉ ፍጹም ነበርክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ውድ የሆኑ የከበሩ ድንጋዮች ሸፍነውህ ነበር
"ውድ የሆኑ ድንጋዮችን ሁሉ ለብሰህ ነበር"

ቀይ እንቁ፣ ቶጳዝዮን፣ አልማዝ፣ በርሌ፣ መረግድ፣ ኢያስጲድ፣ ሰንፔር፣ በሉር እና የሚያብረቀርቅ ዕንቁ
እነዚህ የተለያየ ቀለም ያላቸው የከበሩ ድንጋዮች ናቸው። (የማይታወቀውን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

የሚገኙባቸው እና በብዛት ያሉባቸው
ውድ የሆኑትን የከበሩ ድንጋዮች የያዙ ቁርጥራጭ ብረቶች

የተዘጋጁት በተፈጠርክበት ቀን ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንተን በፈጠርኩበት ቀን እነዚህን እኔ አዘጋጀኋቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ዝግጁ
"ዝግጁ ማድረግ"

Ezekiel 28:14

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ በሕዝቅኤል፣ ለጢሮስ ንጉሥ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡
በእነዚህ ቁጥሮች "አንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የጢሮስን ንጉሥ ነው።

ኪሩቤል
ይህ በሕዝቅኤል 10፡9 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

የእሳት ፍም የመሰሉ ድንጋዮች
"የእሳት ድንጋዮች።" ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) በሕዝቅኤል 28፡13 ላይ ለሚገኙት ውብ ቀለም እና ብሩህነት ላላቸው ድንጋዮች የተሰጠ ዘይቤያዊ አነጋር ወይም 2) "በቅዱሱ የእግዚአብሔር ተራራ" ላይ የሚገኙ ሌሎች እሳታማ ድንጋዮች (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ከተፈጠርክበት ቀን አንስቶ በውሰስጥህ ጥፋት እስከ ተገኘብህ ድረስ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንተን ከፈጠርኩበት ቀን አንስቶ በውስጥህ ጥፋት እስካገኘሁበት ድረስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 28:16

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ በሕዝቅኤል፣ ለጢሮስ ንጉሥ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡
በእነዚህ ቁጥሮች "አንተ" እና "የአንተ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት የጢሮስን ንጉሥ ነው።

ታላቅ ንግድ
"ብዙ የንግድ ዕቃ"

በጥቃት ተሞልተህ ነበር
ያህዌ ስለ ጢሮስ ንጉሥ በጥቃት እንደ ተሞላ እቃ መያዣ አድርጎ ይናገራል። ንጉሡ ለራሱ እና ለህዝቡ ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ነው።"ጥቃት" የሚለው ረቂቅ ስም "አጥቂ" የሚለውን ቅጽል በመጠቀም ሊተረጎም ይችላል። "አንተ እና የአንተ ህዝብ ሙሉ ለሙሉ አጥቂዎች ነበራችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

(ዘይቤያዊ አነጋገር እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እንደዚሁም ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

ጠባቂ ኪሩብ
"ኪሩብን የሚጠብቅ"

የእሳት ድንጋዮች
"የእሳት ድንጋይ።" ይህ በሕዝቅኤል 28፡14 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) 1) በሕዝቅኤል 28፡13 ላይ ለሚገኙት ውብ ቀለም እና ብሩህነት ላላቸው ድንጋዮች የተሰጠ ዘይቤያዊ አነጋር ወይም 2) "በቅዱሱ የእግዚአብሔር ተራራ" ላይ የሚገኙ ሌሎች እሳታማ ድንጋዮች (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ልብህ ትዕቢተኛ ነበር
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚወክለው በሃሳቡ ላይ ትኩረት በማድረግ የሰውን ሁለንተና ነው። "አንተ ትዕቢተኛ ነበርክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ትዕቢተኛ
በስህተት ራስን ከአግባብ ውጭ ጠቃሚ አድርጎ መቁጠር።

በውበትህ ልብህ ታብዮ ነበር፤ ከድምቀትህ የተነሳ ጥበብህን አበላሸህ
"ውበት"፣ "ጥበብ" እና "ድምቀት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች "ውብ"፣ "ብልህ" እና "ደማቅ" በሚሉ ቅጽሎች ሊተረጎሙ ይችላሉ። "ውብ ስለነበርክ ልብህ ታበየ፤ ድምቀት ስለነበረህ በመኩራራትህ ጥበብ የሌለህ ሆንክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በንጉሦች ፊት
"በንጉሦች ፊት ለፊት"

ስለዚህም ይመለከቱህ ይሆናል
"ለዚህም እነርሱ አንተን ይመለከቱ ይሆናል"

Ezekiel 28:18

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ በሕዝቅኤል፣ ለጢሮስ ንጉሥ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡
በእነዚህ ቁጥሮች "አንተ" እና "የአንተ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት የጢሮስን ንጉሥ ነው።

አንተን ይፈጅሃል
"አንተን ይበላሃል።" እዚህ ስፍራ እሳቱ የተገለጸው እርሱን ጨርሶ እንደሚበላው ተደርጎ ነው። "አቃጥሎ ይጨርስሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ አመድነት ይለውጥሃል
የዚህ ፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉም አመድ ብቻ እስኪቀር ድረስ መቃጠል ማለት ነው። "አመድ ያደርግሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መራድ
መናወጥ ወይም በፍርሃት መንቀጥቀጥ

ከእንግዲህ ለዘለዓለም አትገኝም
ይህ በሕዝቅኤል 27፡36 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ezekiel 28:20

የያህዌ ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የነገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጥ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ተናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ፊትህን በሲዶን ላይ አድርግ
ሲዶን ሩቅ ነበረች፣ ስለዚህም ሕዝቅኤል ሊመለከታት አይችልም ነበር፣ ነገር ግን ወደዚያ አቅጣጫ ማየት በዚያ የሚኖሩ ሰዎችን የመጉዳት ምልክት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። በሕዝቅኤል 6:2 ላይ የሚገኘው ተመሳሳይ ሃሳብ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ወደ ሲዶን ፊትን አዙረህ ተመልከት" ወይም "በዚያ የሚኖሩ ሰዎች ጥፋት ይደርስባቸው ዘንድ ወደ ሲዶን ተመልከት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ዳግም ትንቢት ተናገር
"ሊደርሱ ስላሉት መጥፎ ነገሮች ትንቢት ተናገር" ይህ በሕዝቅኤል 4:7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

እነሆ!
"ተመልከት!" ወይም "አድምጥ!" ወይም "ቀጥሎ ለምነግርህ ትኩረት ስጥ!"

በመሃላችሁ ክብር አገኛለሁ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በመሃላችሁ ክብሬን እገልጻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ
ያህዌ ይህንን ሲናገር ሰዎች እርሱ ያህዌ እንደሆነ ያውቃሉ፤ ሰዎች እርሱ ብቻ ሉዓላዊ/የመጨረሻው ከፍተኛ ስልጣን እና ሃይል ያለው መሆኑን እንደሚያውቁ እያመለከተ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 6:7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እኔ ብቸኛው እውነተኛ አምላክ፣ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ" ወይም "እኔ፣ ያህዌ ሉዓላዊ ሀይል እና ስልጣን እንዳለኝ እወቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በመሃላችሁ ፍትህ ሳደርግ
"ፍትህ" የሚለው ረቂቅ ስም "ፈረደ" የሚለውን ግስ በመጠቀም መተርጎም ይቻላል። "እኔ በምፍርድባችሁ ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በእናንተ ዘንድ ቅዱስ መሆኔን አሳቀውቃለሁ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኔ ቅዱስ መሆኔን ለማሳየት በአንተ እጠቀምብሃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 28:23

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል፣ ስለ ሲዶን መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡
በእነዚህ ቁጥሮች "አንቺ" እና "የአንቺ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ሲዶንን ነው።

በጎዳናዎችሽ ደም
እዚህ ስፍራ "ደም" የሚለው የሚያመለክተው የሲዶንን ሰዎች ደም እና ጠላቶቻቸው የሚገድሏቸውን ሰዎች ደም ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የታረዱት ይወድቃሉ
እዚህ ስፍራ "የታረዱ" የሚለው ጠላቶቻቸው የሚገድሏቸው የሲዶን ሰዎች ማለት ነው። "የታረዱት ሰዎች ይወድቃሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)

ሰይፍ በላያችሁ ሲመጣ
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የጠላትን ሰራዊት ስለ ማጥቃት የሚውል ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "የጠላት ሰራዊት ሲያጠቃችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ህዝቧን ከሚንቁ በዙሪያዋ ከሚገኙ የእስራኤልን ቤት በእሾህ እና አሜኬላ ከሚወጉ
እዚህ ስፍራ እሾህ እና አሜኬላ የሚወክለው ስቃይና መከራ የሚያስከትሉ ነገሮችን ነው። "በእስራኤል ቤት ዙሪያ በሁሉም ስፍራ የሚገኙ ሰዎች እንደ እሾክ ይሆኑባቸዋል፣ እንደ እሾህ ይወጓቸዋል ደግሞም ያዋርዷቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ቤት
"ቤት" የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት ነው። በዚህ ሁኔታ የእስራኤል ትውልጆች ያመለክታል።ይህ በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እስራኤላውያን" ወይም "የእስራኤል ህዝብ ወገን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 28:25

የእስራኤል ቤት
"ቤት" የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት ነው። በዚህ ሁኔታ የእስራኤል ትውልጆች ያመለክታል።ይህ በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እስራኤላውያን" ወይም "የእስራኤል ህዝብ ወገን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ከተበተኑበት
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኔ እነርሱን ከበተንኩበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህም አገራት ሊመለከቱ ይችላሉ
"በዚህ አይነት መንገድ አገራት እንደሚመለከቱት"

ባሪያዬ ያዕቆብ
እዚህ ስፍራ "ያዕቆብ" የሚወክለው የያዕቆብን ትውልድ ነው። "የባሪያዬ የያዕቆብ ትውልጆች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በውስጧ
"በምድሪቱ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ፍርዴን በሁሉም ላይ ስፈጽም
"ፍርድ" የሚለው ረቂቅ ስም "ፈረደ" የሚለውን ግስ በመጠቀም ሊተረጎም ይችላል። "በሁሉም ላይ በምፈርድበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
(ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 29

1 በአሥረኛው ዓመት በአሥረኛው ወር ከወሩም በአሥራ ሁለተኛው ቀን የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ። **2** የሰው ልጅ ሆይ፥ ፊትህን በግብጽ ንጉሥ በፈርዖን ላይ አድርግ፥ በእርሱና በግብጽ ሁሉ ላይም ትንቢት ተናገር፥ **3** እንዲህም በል። ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በወንዞች መካከል የምትተኛና። ወንዙ የእኔ ነው ለራሴም ሠርቼዋለሁ የምትል ታላቅ የባህር ውስጥ ፍጥረት፥ የግብጽ ንጉሥ ፈርዖን ሆይ፥ እነሆ፥ በአንተ ላይ ነኝ። **4** በመንጋጋህ መቃጥን አገባብሃለሁ፥ የወንዞችህንም ዓሦች ወደ ቅርፊትህ አጣብቃለሁ በቅርፊትህ ላይ ከተጣበቁ ዓሦች ሁሉ ጋር ከወንዞችህም መካከል አወጣሃለሁ። **5** አንተንና የወንዞችህን ዓሦች ሁሉ ወደ ምድረ በዳ እጥላለሁ፥ በምድርም ፊት ላይ ትወድቃለህ እንጂ አትከማችም አትሰበሰብም። መብልም አድርጌ ለምድር አራዊትና ለሰማይ ወፎች እሰጥሀለሁ። **6** ለእስራኤል ቤት የሸንበቆ በትር ሆነዋልና በግብጽም የሚኖሩ ሁሉ እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ። **7** በእጅ በያዙህ ጊዜ ተሰበርህና ተሰነጣጥቅህ ትከሻቸውን ትወጋለህ፤ በተደገፉብህም ጊዜ እግራቸውን ትሰባብራለህ ወገባቸውንም እንዲንቀጠቀጥ ታደርጋለህ። **8** ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እነሆ፥ ሰይፍ አመጣብሃለሁ፥ ሰውንና እንስሳንም ከአንተ ዘንድ አጠፋለሁ። **9** የባህር ጭራቁ "ወንዙ የእኔ ነው የሠራሁትም እኔ ነኝ" ብሏልና የግብጽ ምድር ባድማና ውድማ ትሆናለች፥ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ አንተ። **10** ስለዚህ፥ እነሆ፥ በአንተና በወንዞችህ ላይ ነኝ፥ የግብጽንም ምድር ከሚግዶል ጀምሮ እስከ ሴቄኔና እስከ ኢትዮጵያ ዳርቻ ድረስ ውድማና ባድማ አደርጋታለሁ። **11** የሰው እግር አያልፍባትም የእንስሳም ኮቴ አያልፍባትም፥ እስከ አርባ ዓመትም ድረስ ማንም አይኖርባትም። **12** ባድማም በሆኑ ምድሮች መካከል የግብጽን ምድር ባድማ አደርጋታለሁ፥ በፈረሱትም ከተሞች መካከል ከተሞችዋ አርባ ዓመት ፈርሰው ይቀመጣሉ ግብጻውያንንም ወደ አሕዛብ እበትናቸዋለሁ በአገሮችም እዘራቸዋለሁ። **13** ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ከአርባ ዓመት በኋላ ግብጻውያንን ከተበተኑባቸው አሕዛብ ዘንድ እሰበስባለሁ **14** የግብጽንም ምርኮ እመልሳለሁ፥ ወደ ተወለዱባትም ምድር ወደ ጳትሮስ እመልሳቸዋለሁ በዚያም የተዋረደች መንግሥት ይሆናሉ። **15** ከሌሎች መንግሥታት ሁሉ ይልቅ የተዋረደች ትሆናለች ከእንግዲህ ወዲያ ከአሕዛብ መካከል ከፍ አትልም።ከእንግዲህም በአሕዛብም ላይ እንዳይገዙ አሳንሳቸዋለሁ። **16** ግብጻውያን ከእንግዲህ ለእስራኤል ቤት የትምክህት ምክንያት አይሆኑም። ይልቁኑ እስራኤል ለእርዳታ ፊቷን ወደ ግብጽ ባዞረች ጊዜ የፈጸመችውን በደል የሚያሳስቡ ይሆናሉ።እኔም ጌታ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ። **17** እንዲህም ሆነ በሀያ ሰባተኛው ዓመት በመጀመሪያው ወር ከወሩም በመጀመሪያው ቀን የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ። **18** የሰው ልጅ ሆይ፥ የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር በጢሮስ ላይ ጽኑ ሥራ ለማሰራት ሠራዊቱን ሰበሰበ። ራስ ሁሉ ተላጭቶ ጫንቃም ሁሉ ተልጦ ነበር፥ ነገር ግን በላይዋ ስላገለገለው አገልግሎት እርሱና ሠራዊቱ ምንም አይነት ደመወዝ ከጢሮስ አልተቀበሉም። **19** ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እነሆ፥ የግብጽን ምድር ለባቢሎን ንጉሥ ለናቡከደነፆር እሰጠዋለሁ፥ ብዛትዋንም ይወስዳል ምርኮዋንም ይማርካል ብዝበዛዋንም ይበዘብዛል ይህም ለሠራዊቱ ደመወዝ ይሆናል። **20** ለእኔ ለሠሩት ሥራ ደመወዝ አድርጌ የግብጽን ምድር ሰጥቼዋለሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፦ **21** በዚያ ቀን ለእስራኤል ቤት ቀንድን አበቅላለሁ፥ በመካከላቸውም ለአንተ የተከፈተ አፍን እሰጣለሁ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ።

Ezekiel 29:1

በአስረኛው አመት
ይህ ዮአኪን በስደት ላይ የነበረበት አስረኛው አመት መሆኑ በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "ንጉሥ ዮአኪን በስዳት ላይ በነበረበት በአስረኛው አመት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተከታታይ ቁጥሮች እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

በአስረኛው ወር፣ በወሩ አስራ ሁለተኛ ቀን
"በአስረኛው ወር በአስራ ሁለተኛው ቀን።" ይህ በዕብራውያን የወራት አቆጣጠር አስረኛው ወር ነው። አስራ ሁለተኛው ቀን በምዕራባዊያኑ አቆጣጠር ወደ ጥር መጀመሪያ አካባቢ ነው። (የዕብራዊያን ወራት እና ተከታታይ ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

የያህዌ ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የነገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጥ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ተናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ፊትህን በፈርኦን ላይ አድርግ
ይህ ፈርኦንን እና ህዝቡን ለመቅጣት ወደ ፈርኦን እንዲመለከት በምልክትነት የተሰጠ ትዕዛዝ ነው። ፈርኦን የሚገኘው በርቀት ነበር፣ ሕዝቅኤል ሊመለከተው አይችልም ነበር። ነገር ግን እርሱ ወዳለበት መመልከቱ ፈርኦንን እና ህዝቡን ለመቅጣት እንደ ምልክት ተደርጎ ይወሰድ ነበር። በሕዝቅኤል 6:2 ላይ የሚገኘው ተመሳሳይ ሃሳብ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ወደ ፈርኦን አቅጣጫ ዞረህ ተመልከቱ" ወይም "እርሱ እና ህዝቡ ይቀጡ ዘንድ ፈርኦን ወደሚገኝበት አቅጣጫ ተመልከት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ እና በመላው ግብጽ ላይ ትንቢት ተናገር
"በእርሱ እና በግብጽ በሚገኙ ላይ ሁሉ ስለሚደርሱ አስጨናቂ ነገሮች ተናገር"

ታላቁ የባህር አውሬ
"በውሃ ውስጥ የሚኖር ትልቅ ፍጡር።" ያህዌ ፈርኦንን በውሃ ውስጥ የሚኖር ትልቅ አውሬ ብሎ ይጠራዋል። አውሬው ምናልባት አዞ ሊሆን ይችላል። (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ አገላለጽ/ቋንቋ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 29:4

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል፣ ስለ ፈርኦን መልዕክት መስጠቱን፤ ፈርኦን በውሃ ውስጥ እንደሚኖር አውሬ መሆኑን እና የግብጽ ሰዎች አሳ መሆናቸውን መናገሩን ቀጥሏል። (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ አገላለጽ/ቋንቋ የሚለውን ይመልከቱ)

መንጠቆዎች
ስል እና ቆልመም ያለ ቁራጭ ብረት፣ ወይም ሰዎች አሳ እና በውሃ ውስጥ የሚኖሩ ሌሎች እንስሳትን የሚያጠምዱበት እንጨት

ቅርፊት
በአሳ፣ አዞ፣ እና ሌሎች እንስሳት ላይ የሚገኝ ጠንካራ ቁርጥራጭ ቆዳ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የሚያነሳችሁ አይኖርም፣ ወይም ማንም አያነሳችሁም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። ይህ በሜዳ/በዱር የሚሞቱ መሆኑን ያሳያል። "ማንም በድናችሁን አንስቶ ወይም ሰብስቦ አይቀብርም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

Ezekiel 29:6

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል፣ ስለ ፈርኦን መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል

እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ
ያህዌ ይህንን ሲናገር ሰዎች እርሱ ያህዌ እንደሆነ ያውቃሉ፤ ሰዎች እርሱ ብቻ ሉዓላዊ/የመጨረሻው ከፍተኛ ስልጣን እና ሃይል ያለው መሆኑን እንደሚያውቁ እያመለከተ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 6፡7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እኔ ብቸኛው እውነተኛ አምላክ፣ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ" ወይም "እኔ፣ ያህዌ ሉዓላዊ ሀይል እና ስልጣን እንዳለኝ እወቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ የሸምበቆ አገዳ ነበሩ
"እነርሱ" የሚለው ቃል የግብጽን ነዋሪዎች ያመለክታል። የሸምበቆ አገዳ አስተማማኝ አይደለም ምክንያቱም በቀላሉ ተሰባሪ ነው። ያህዌ እነርሱን እንደ ሸምበቆ አገዳ የሚገልጻቸው፣ ግብጻውያን በጦርነት ወቅት እነርሱን እንዲረዱ ስለጠየቋቸው እና ግብጻውያን ስላልረዷቸው ነው። "እነርሱ እንደ ሸምበቆ አገዳ ሊታመኑባቸው የማይቻል ነበሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሸምበቆ
በውሃ አጠገብ የሚበቅል እና ረጅም ሳር የመሰለ ተክል ነው

አገዳ
ረጅም በትር የሚመስል የቄጤማው ክፍል ነው። ሰዎች እንደ በትር ሊጠቀሙባቸው ሲችሉ ነገር ግን እንደ እንጨት በትር ቄጤማ ጠንካራ ባለመሆኑ በቶሎ ተሰባሪ ነው።

እነርሱ በእጃቸው እናንተን ሲይዟችሁ
እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በግብጻውያን ላይ መታመናቸው ተሰባሪ የሸምበቆ ምርኩዝ እንደመደገፍ አድርጎ ይናገራል። "እነርሱ በአንተ ሲታመኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ አንተን ሲደገፉ
"እነርሱ" የሚለው ቃል እስራኤላውያንን ሲይመለክት "አንተ" የሚለው ፈርኦንን ወይም ፈርኦንን እና ግብጽን ያመለክታል።

እግራቸው እንዳይጸና አደረግህ
ግብጽ እስራኤላውያንን ስላልረዳች፣ እስራኤላውያን ጠላቶቻቸውን ባቢሎናውያንን መቋቋም አልቻሉም። እግዚአብሔር ራሳቸውን መከላከል አለመቻላቸውን የገለጸው እግራቸው መጽናት እንዳልቻለ አድርጎ ነው። "እግራቸው መጽናት እንዳልቻለ ሰው አደረግሃቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 29:8

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል፣ ስለ ፈርኦን መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል

እነሆ!
"ተመልከት!" ወይም "አድምጥ!" ይህ ቃል ቀጥሎ ለሚነገረው ትኩረት ይሰጣል። ይህ ጌታ ለፈርኦን ያለው መልዕክት ነው። "ቀጥሎ ለምነግርህ ትኩረት ስጥ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

በአንተ ላይ ሰይፍ አመጣለሁ
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" ለጦርነት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት ሲሆን/፣ "በአንተ ላይ ሰይፍ አመጣለሁ" የሚለው የጠላት ሰራዊት ግብጽን ለመውጋት ለመምጣቱ ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። "ጠላቶችህ አንተን ለመውጋት እንዲመጡ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በአንተ ላይ ሰይፍ
"አንተ" የሚለው ቃል ግብጽን ያመለክታል። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)

ከአንተ ሰውንና አራዊትን በአንድነት እቆርጣለሁ
እዚህ ስፍራ "ሰውንና አራዊትን እቆርጣለሁ" የሚለው ሰዎችንና እንስሳትን ለማጥፋት የዋለ ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። እግዚአብሔር የጠላት ሰራዊት ይህንን እንዲያደርግ በማድረግ ይፈጽመዋል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ በአንተ እና በወንዝህ ላይ ተነስቻለሁ
"አንተ" የሚለው ቃል ፈርኦንን ያመለክታል። እግዚአብሔር ፈርኦንን በወንዝ ውስጥ እንደሚኖር አውሬ ይገልጸዋል።

የግብጽን ምድር ሰው የማይኖርበት እና የጠፋ አደርገዋለሁ
"ግብጽን ለጥፋት እና ውድመት ሀይል እሰጣለሁ" ሰው የማይኖርበት እና የጠፋ የሚሉት የተገለጹት በግብጽ ላይ ሀይል እንዳላቸው ሰዎች ተደርገው ነው። "ግብጽ ሰው የማይኖርባት እና የጠፋች እንድትሆን አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ የጠፋ ምድር ትሆኛለህ
እዚህ ስፍራ "አንተ" ፈርኦንን ሲያመለክት የሚገዛትን ግብጽንም ይወክላል። "አገርህ የጠፋ ምድር ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከሚግዶል እስከ ሲና ደግሞም እስከ ኩሽ ድንበሮች ድረስ
ይህ መላውን ግብጽ ያመለክታል። እነዚህ ስፍራዎች የት እንደሆኑ ይበልጥ በግልጽ ሊጻፉ ይችላል። "በሰሜን ከሚግዶል በደቡብ እስከ ሲና ደግሞም ሩቅ በስተ ደቡብ እስከ ኩሽ ድንበር ድረስ በመላው ግብጽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጽንፍ/ከዳር እስከ ዳር እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ሚግዶል
ይህ በግብጽ በስተሰሜን ዳርቻ የሚገኝ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሲና
ይህ በደቡባዊ ግብጽ የሚገኝ ከተማ ስም ነው። አሁን አስዋን ተብላ ትጠራለች። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የኩሽ ድንበሮች
እነዚህ የኩሽ ድንበሮች በሲና በስተ ደቡብ ነበሩ። አንዳንድ ቅጂዎች በዘመናችን ከግብጽ በስተደቡብ የሚገኙትን አገራት በመጠቀም ሱዳን ወይም ኢትዮጵያ ይላሉ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 29:11

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል፣ ስለ ፈርኦን መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል

የማንም ሰው እግር/ኮቴ በላይዋ አያልፍም
እዚህ ስፍራ "የሰው እግር" የሚለው የሚወክለው ሰዎችን ነው። "ማንም ሰው በግብጽ ምድር በኩል አያልፍም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ የግብጽን ምድር ሰው የማይኖርበት/ ምድረ በዳ አደርጋለሁ
"ባድማ/ሰው የማይኖርበት/" የሚለው "ጠፍ/ባድማ" በሚለው ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። "የግብጽን ምድር ባድማ አደርጋታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ግብጽን ከአገራት መሃል አጠፋታለሁ/እበትናታለሁ
እዚህ ስፍራ "ግብጽ" የምትወክለው የግብጽን ህዝብመ ሲሆን፣ "መበተን" የሚገልጸው የእነርሱን ወደ ሌላ ስፍራ መሄድ ነው። "ግብጻውያንን በአገራት መሃል እበትናቸዋለሁ" ወይም "የግብጽ ሰዎች ወደ ሌሎች አገራት ሄደው እንዲኖሩ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Ezekiel 29:13

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል፣ ስለ ፈርኦን መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል

ግብጽን እሰበስባለሁ/እጠራለሁ
እዚህ ስፍራ "ግብጽ" ለግብጽ ህዝብ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሲሆን፣ "መሰብሰብ" የሚለው ደግሞ ወደ ግብጽ ለመመለሳቸው ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "የግብጽን ህዝብ ወደ ግብጽ እንዲመለስ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

እነርሱ ከተበተኑበት
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኔ እነርሱን ከበተንኩበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የግብጽን አድል ፈንታ እመልሳለሁ
"የግብጽ አድል ፈንታ" የሚለው ሀረግ ወደ ሌሎች አገራት ለተወሰደው የግብጽ ህዝብ ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። "የግብጽን ህዝብ ወደ ነበረበት እመልሳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የጳትሮስ ግዛት
ጳትሮስ በኩሽ ምድር እና በደለሉ መሃል የሚገኘው የግብጽ ደቡባዊ ክፍል ነው። ይህ የላይኛው ግብጽ ተብሎም ይጠራል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ዝቅተኛው ግዛት
እዚህ ስፍራ "ዝቅተኛ" የሚለው የሚወክለው የማይጠቅም የሚለውን ነው። "ታናሽ መንግስት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 29:15

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል፣ ስለ ፈርኦን መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል

ከመንግሥቱ አናሳ
እዚህ ስፍራ "አናሳ" የሚለው የሚወክለው ከሁሉም ዝቅ ያለ ዋጋ ስፍራ የያዘ መሆኑን ነው። "ከመንግሥታት ዝቅተኛው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከመንግሥታት መሃል ከእንግዲህ ወዲያ አይነሳም
እዚህ ስፍራ "መነሳት" የሚለው የሚወክለው ጠቃሚ መሆንን ነው። "ከእንግዲህ ወዲያ ዳግም በመንግስታት መሃል ጠቃሚ አይሆንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ አጠፋቸዋለሁ
"እኔ ትንሽ አደርጋቸዋለሁ።" እዚህ ስፍራ "እነርሱን አጠፋለሁ" የሚለው የሚወክለው ግብጽን ደካማ እና ጥቅም የሌላት ማድረግን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህ ግብጻውያን ለእስራኤል ቤት የኩራት ምክንያት አይሆኑም
"ኩራት" የሚለው ረቂቅ ስም "መታመኛ" ወይም "መደገፊያ" በሚል ግስ ሊተረጎም ይችላል። "የእስራኤል ቤት ከእንግዲህ በግብጻውያን አይታመንም/ አይደገፍም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው የሚወክለው የእስራኤልን ሰዎች ነው። "የእስራኤልን ሰዎች" ወይም "የእስራኤል ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ እስራኤል ለፈጸመው በደል ማስታወሻ ይሆናሉ
ግብጽ እንዴት ማስታወሻ እንደምትሆን በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "ማስታወሻ" እና "ኃጢአት/በደል" የሚሉት ረቂቅ ስሞች "አስታውስ" እና "ኃጢአት" በሚሉ ግሶች ሊገለጹ ይችላሉ። "እኔ በግብጽ ላይ ያደረግኩትን ሲመለከት እስራኤል እንዴት አስራኤልን እንደበደለ ያስታውሳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

እነርሱ ለእርዳታ ወደ ግብጽ ሲመለሱ
እዚህ ስፍራ "ለእርዳታ ...መመለስ" የሚለው "እርዳታ ...መጠየቅ" ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ግብጻውያን እንዲረዷቸው በጠየቁ ጊዜ ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 29:17

እንዲህም ሆነ
እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ውስጥ የተፈጸመን ጠቃሚ ትዕይንት ለማጉላት/ለማመልከት ነው። በእናንተ ቋንቋ ይህን ለማድረግ የሚጠቀምበት መንገድ ካለ እዚህ ስፍራ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ።

በሃያ ሰባተኛው አመት
ይህ ንጉሥ ዮአኪን እና የይሁዳ ህዝብ በስደት ወደ ባቢሎን ከተወሰደ በኋላ ነበር። "ንጉሥ ዮአኪን በተሰደደ በሃያ ሰባተኛው አመት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተከታታይ ቁጥሮች እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በመጀመሪያው ወር መጀመሪያ
"በመጀመሪያው ወር በመጀመሪያው ቀን::" ይህ በዕብራውያን ወር አቆጣጠር የመጀመሪያው ወር ነው:: የመጀመሪያው ቀን በሚያዚያ መጀመሪያ አካባቢ ነው:: (የዕብራውያን ወሮች እና ተከታታይ ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

የያህዌ ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የተናገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው:: ይህ በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ:: "ያህዌ ይህንን መልዕክት ነናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ/ያህዌ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ::" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው:: እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም:: ይህ በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ:: "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው::

በጢሮስ ላይ ከባድ ስራ መስራት
የሚሰሩት ከባድ ስራ አይነቱ በግልጽ ሊቀርብ ይችላል:: "ጢሮስን ለማጥቃት በከባድ መስራት:: በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እያንዳንዱ ራስ... እያንዳንዱ ትከሻ
ይህ የባቢሎንን ወታደሮች ራሶች/ጭንቅላቶች እና ትከሻዎች ያመለክታል::

እያንዳንዱ ራስ እስኪመለጥ ድረስ ይፈቀፈቅ ነበር
የወታደር ኮፍያቸው ወይም በጭንቅላታቸው ላይ የሚሸከሟቸው ከባድ ነገሮች ፀጉራቸውን ከራሳቸው ላይ ይመልጠው ነበር

እያንዳንዱ ትከሻ ይቆስል ነበር
የጦር ዕቃቸው ወይም በትከሻቸው የሚሸከሟቸው ከባድ ነገሮች የትከሻቸውን ቆዳ ይመልጠው ነበር:: "እያንዳንዱ ትከሻ እስኪቆስል ድረስ ይላጥ ነበር" ወይም "እያንዳንዱ ትከሻ ተፈግፍጎ ይቆስል ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው::

እርሱ እና የእርሱ ሰራዊት ከጢሮስ ምንም ክፍያ አልተቀበሉም
እዚህ ስፍራ "ክፍያ" የሚወክለው የናቡከደነጾር ሰራዊት ጢሮስን በማሸነፉ የሚበዘብዘውን ነው:: እግዚአብሔር ስለእነዚህ ነገሮች እነርሱ ለእርሱ በመስራታቸው እንደሚከፍላቸው አድርጎ ይናገራል:: "እርሱ እና ሰራዊቱ ከጢሮስ እንደ ሽልማት አንዳች ዋጋ ያለው ነገር አላገኙም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 29:19

እነሆ!
"ተመልከት!" ወይም "አድምጥ!" ይህ ቃል ቀጥሎ ለሚነገረው ትኩረት ይሰጣል::"ቀጥሎ ለምነግርህ ትኩረት ስጥ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው::

የግብጽን ምድር ለባቢሎን ንጉሥ ለናቡከደነጾር እሰጣለሁ
ያህዌ የባቢሎን ሰራዊት ግብጽን እንዲያሸንፍ ማድረጉን፣ እግዚአብሔር ግብጽን ለናቡከደነጾር እንደሚሰጥ አድርጎ ይናገራል:: "የናቡከደነጾር ሰራዊት፣ የባቢሎን ንጉሥ ግብጽን እንዲያሸንፍ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የሰራዊቱ ደሞዝ ይሆናል
እግዚአብሔር ስለእነዚህ ነገሮች፤ የናቡከደነጾር ሰራዊት ለእርሱ በመስራታቸው የሚከፍላቸው ነገር እንደሆነ አድርጎ ይናገራል:: "የእርሱ ሰራዊት እነዚህን ነገሮች ክፍያው እንደሆነ አድርጎ ይቀበላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ራሱን በስሙ የሚገልጸው/የሚምለው፤ የተናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳወቅ ነው:: ይህ በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ:: "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 29:21

እኔ ለእስራኤል ቤት ቀንድ አበቅላለሁ
የእንስሳ ቀንድ እንስሳውን ጥንካሬ ይወክላል፣ ስለዚህም ቀንድ ለጥንካሬ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው:: እግዚአብሔር እስራኤልን ማጠንከሩን እስራኤል በእንስሳ በመመሰል እና እርሱ ቀንድ እንድታበቅል ማድረጉን ይናገራል:: "እኔ የእስራኤልን ህዝብ አበረታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

የእስራኤል ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው በቤቱ ለሚኖሩ ሜቶኖሚ/ ነው:: እዚህ ስፍራ ይህ የሚወክለው እግዚአብሔር እስራኤል ብሎ የሚጠራቸውን የያቆብ ትውልድ ነው:: "የእስራኤልን ሰዎች" ወይም "የእስራኤል ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በመሃላቸው መናገር
"ለእነርሱ መናገር"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 30

1 የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ። **2** የሰው ልጅ ሆይ፥ ትንቢት ተናገር እንዲህም በል። ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ዋይ! በሉ፥ ለቀኑ ወዮ! **3** ቀኑ ቅርብ ነው፥ የእግዚአብሔር ቀን ቅርብ ነው፥ የደመና ቀን፥ ለአሕዛብም ክፉ ወቅት ይሆናል። **4** ሰይፍ በግብጽ ላይ ይመጣል፥ የተገደሉት ሰዎች በግብጽ ውስጥ ሲወድቁ ሀብቷን ሲወስዱ መሠረትዋም ሲፈርስ በኢትዮጵያ ውስጥ ሁከት ይሆናል! **5** ኢትዮጵያ፥ ፉጥና ሉድም እንግዶችም የቃል ኪዳንም ህዝቦች ከእነርሱ ጋር በሰይፍ ይወድቃሉ። **6** እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ግብጽን የሚደግፉ ይወድቃሉ፥ የኃይልዋም ትምክህት ይወርዳል። ከሚግዶል ጀምሮ እስከ ሴዌኔ ድረስ ወታደሮቻቸው በሰይፍ ይወድቃሉ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር! **7** ባድማም በሆኑ አገሮች መካከል ይሸበራሉ፥ ከተሞቻቸውም እንደ ፈረሱት ከተሞች ይሆናሉ። **8** እሳትንም በግብጽ ባነደድሁ ጊዜ ረዳቶችዋም ሁሉ በጠፉጊዜ፥ እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ! **9** በዚያ ቀን መልእክተኞች ተዘልለው የሚኖሩትን ኢትዮጵያውያንን ለማስፈራት ከፊቴ በመርከብ ይወጣሉ በግብጽም ጥፋት ቀን ሁከት ይሆንባቸዋል። እነሆ፥ ይመጣልና! **10** ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በባቢሎን ንጉሥ በናቡከደነፆር እጅ የግብጽን ህዝብ ፍጻሜ አመጣለሁ። **11** የአህዛብ ድንጋጤ የሆኑት እርሱና ሠራዊቱ ምድሪቱን ለማጥፋት ይመጣሉ፤ ሰይፋቸውንም በግብጽ ላይ ይመዝዛሉ ምድሪቱንም በሞቱ ሰዎች ይሞላሉ! **12** ወንዞችን ደረቅ መሬት አደርጋለሁ ምድሪቱንም ለክፉ ሰዎች እሸጣለሁ። ምድሪቱንና ሙላዋንም በእንግዶች እጅ ባድማ አደርጋለሁ! እኔ እግዚአብሔር ተናግሬያለሁ! **13** ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ጣዖቶችን አጠፋለሁ እርባና ቢስ የሆኑትን የሜምፎስ ጣዖታት እሸራለሁ። ከእንግዲህ ወዲያ በግብጽ ምድር አለቃ አይገኝም ፥ በግብጽም ምድር ላይ ሽብርን አደርጋለሁ! **14** ጳትሮስንም አፈርሳለሁ፥ በጣኔዎስም እሳትን አነድዳለሁ፥ በኖእ ላይም ፍርድን አደርጋለሁ። **15** በግብጽም ምሽግ በሲን ላይ መዓቴን አፈስሳለሁ፥ የኖእንም ህዝብ አጠፋለሁ። **16** ከዚያም በግብጽ እሳትን አነድዳለሁ። ሲንም ትጨነቃለች ኖእም ትሰበራለች፥ ሜምፎስም በየቀኑ ጠላቶች ይነሱባታል! **17** የሄልዮቱና የቡባስቱም ወጣቶች በሰይፍ ይወድቃሉ ከተሞቻቸውም ይማረካሉ። **18** በዚያ የግብጽን ቀንበር በሰበርሁ ጊዜ በጣፍናስ ቀኑ ይጨልማል የኃይልዋም ትዕቢት ይጠፋል። ደመናም ይጋርዳታል፥ ሴቶች ልጆችዋም ይማረካሉ። **19** እንዲሁ በግብጽ ላይ ፍርድን አደርጋለሁ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ። **20** እንዲህም ሆነ በአሥራ አንደኛው ዓመት በመጀመሪያው ወር ከወሩም በሰባተኛው ቀን የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ። **21** የሰው ልጅ ሆይ፥ የግብጽን ንጉሥ የፈርዖንን ክንድ ሰብሬያለሁ።። እነሆም፥ እንዲድን በጨርቅ አልታሰረም በመቃም አልታሰረለትም ስለዚህም ሰይፍን ለመያዝ የሚያስችል ጥንካሬ የለውም። **22** ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እነሆ፥ እኔ በግብጽ ንጉሥ በፈርዖን ላይ ተነስቻለሁ! ጠንካራውንም የተሰበረውንም ክንዱን እሰብራለሁ፥ ሰይፉንም ከእጁ አስጥላለሁ። **23** ግብጻውያንንም ወደ አሕዛብ እበትናለሁ ወደ አገሮችም እዘራቸዋለሁ። **24** የፈርዖንን ክንድ ለመስበር የባቢሎንን ንጉሥ ክንድ አበረታለሁ ሰይፌንም በእጁ እሰጣለሁ። በባቢሎን ንጉሥ ፊት ለሞት እንድሚያጣጥር ሰው ያጓራል። **25** የባቢሎንንም ንጉሥ ክንድ አጸናለሁ የፈርዖን ክንድ ግን ይወድቃል። ሰይፌንም በባቢሎን ንጉሥ እጅ በሰጠሁ ጊዜ እርሱም በሰጠሁት ሰይፍ የግብጽን ምድር በሚመታ ጊዜ እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ። **26** ግብጻውያንንም ወደ አሕዛብ እበትናለሁ ወደ አገሮችም እዘራቸዋለሁ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ።

Ezekiel 30:1

አጠቃላይ መረጃ፡
ሕዝቅኤል ያህዌ ስለ ሰጠው መልዕክት ይናገራል።

የያህዌ ቃል መጣ
x

Ezekiel 30:4

አጠቃላይ መረጃ፡
እነዚህ ያህዌ ስለ ግብጽ የተናገራቸው ቃላት ናቸው።

ከዚያም በግብጽ ላይ ሰይፍ ይሆናል/ይመጣል
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚለው ቃል የሚወክለው ጥፋት ሚያደርስን ሰራዊት ወይም ጦርነት ነው። "በግብጽ ላይ ጦርነት ይሆናል" ወይም "የጠላት ሰራዊት ግብጽን ያጠቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በኩሽ ጭንቀት ይሆናል
"ጭንቀት" የሚለው ረቂቅ ስም ሰዎች እንዴት እንደሚሰማቸው በመግለጽ መተርጎም ይቻላል። "የኩሽ ሰዎች በጣም ያዝናሉ" ወይም "የኩሽ ሰዎች ይጨነቃሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የተገደሉ ሰዎች በግብጽ ሲወድቁ
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "መውደቅ" መሞት ለሚለው ዩፊሚዝም/የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል ተክቶ መጠቀም/ ነው። "የግብጽ ሰዎች በጦርነት ሲሞቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) "መውደቅ" በድናቸው ወድቆ በምድር ላይ ሲጋደም። "በግብጽ የሚኖሩ ሰዎች በጦርነት ሲሞቱ እና ሲወድቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊሚዝም/የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል ተክቶ መጠቀም የሚለውን ይመልከቱ)

ሀብቷን ሲዘርፉ
"ጥቃት አድራሾች የግብጽን ሀብት ሲዘርፉ"

መሰረቶቿ ሲፈርሱ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "አጥቂዎች በግብጽ የሚገኙ ቅጥሮችን/ህንጻዎችን መሰረቶች ሲደመስሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ኩሽ እና ፉጥ፣ ልድያና መላው አረብ፣ እንዲሁም ሊብያ
እነዚህ ስሞች የእነዚህን አገራት ሰዎች ያመለክታሉ። "የኩሽ እና ፉጥ፣ ልድያና መላው አረብ፣ እንዲሁም ሊብያ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሊብያ
ሊብያ ከግብጽ በስተ ምዕራብ የምትገኝ አገር ናት። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ልድያ
ይህ ምናልባት አሁን ቱርክ ውስጥ የምትገኘውን የልድያን ግዛት ሊያመለክት ይችላል።

የቃል ኪዳን ህዝብ
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ቃለ ኪዳኑ" የሚያመለክተው ያህዌ ከእስራኤላውያን ጋር ያደረገውን ስምምነት ነው። "በግብጽ የሚኖሩ አይሁዶች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) "ቃለ ኪዳኑ" የሚያመለክተው ግብጽ ከሌሎች አገራት ጋር ያደረገችውን ስምምነት ነው። "ከግብጽ ጋር ቃል ኪዳበን ያላቸው የአገራት ህዝቦች" ወይም "የግብጽ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ተባባሪዎች/አጋሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉም በሰይፍ ይወድቃሉ
እዚህ ስፍራ ሰይፍ የሚወክለው ጦርነትን ነው። "ሁሉም በጦርነት ይወድቃሉ" ወይም "ሁሉም በጦርነት ይሞታሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉም በሰይፍ ይወድቃሉ
እዚህ ስፍራ "ሁሉም" የሚለው ቃል አጠቃላይ ነው። ይህ ማለት ብዙ ሰዎች ይሞታሉ ማለት ነው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት ሚሉትን ይመልከቱ)

Ezekiel 30:6

ያህዌ ይህን አለ
"ያህዌ የተናገረው ይህ ነው/ ያህዌ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ይህ ዐረፍተ ነገር ያህዌ ሊናገር ያለውን ያስተዋውቃል።

ስለዚህ እነዚያ
"ሰዎች በዚህ መንገድ" ወይም "አገራት በዚህ ሁኔታ"

ግብጽን የሚደግፍ
"ግብጽን የሚረዳ"

ይወድቃሉ
"ይሞታሉ" ወይም "ወደ ጥፋት/መበስበስ ይመጣሉ"

የጥንካሬዋ ኩራት ይዋረዳል
ይህ የሚወክለው ግብጽ ከእንግዲህ በሀይላቸው እንደማይመኩ ነው። የማይኩራሩበት ምክንያት ከእንግዲህ አቅም ስለማይኖራቸው ነው። "ግብጽ ከእንግዲህ በሃይላቸው አይኩራሩም" ወይም "ከእንግዲህ ግብጽ የሚኮሩበት አቅም አይኖራቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከሚግዶል እስከ ሲና
ሕዝቅኤል በግብጽ ድንበሮች የሚገኙ ከተሞችን የሚጠቅሰው መላውን ግብጽ ለማመልከት ነው። "በመላው ግብጽ" ወይም "ከግብጽ ሰሜናዊ ድንበር አንስቶ እስከ ግብጽ ደቡባዊ ድንበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜሪዝም/ከዳር እስከ ዳር/ከጽንፍ እስከ ጽንፍ)

ወታደሮቻቸው በሰይፍ ይወድቃሉ
እዚህ ስፍራ "መውደቅ" የሚለው የሚወክለው መሞትን ሲሆን፣ "ሰይፍ" ጦርነትን ይወክላል። "የግብጽ ወታደሮች በጦርነት ያልቃሉ" ወይም አጥቂ ሰራዊት የግብጻውያንን ወታደሮች በጦርነት ይፈጃሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ራሱን በስሙ የሚገልጸው/የሚምለው፤ የተናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳወቅ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ። "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

በተተወው ምድር/ባድማ መሃል ሆነው ይደነግጣሉ
"የግብጽ ተባባሪ አገሮች ወታደሮች በምድረበዳው/ባድማ ላይ ሲቀሩ ይደነግጣሉ"

በ...መሃል
"መካከል" ወይም "በመከበብ"

ከተሞቻቸው ከፈራረሱ ከተሞች መሃል ይሆናሉ
በፈራረሱ ከተሞች "መሃል" መሆን የሚለው የሚወክለው እንደ ሌሎች አገሮች የፈራረሱ ከተሞች መፈራረስን ነው። "ከተሞቻቸው እንደ ሌሎች አገሮች ከተሞች ይፈራርሳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 30:8

አጠቃላይ መረጃ:
እነዚህ ያህዌ ስለ ግብጽ የተናገራቸው ቃላት ናቸው።

ከዚያም እነርሱ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ከዚያም ሰዎች" ወይም 2) "ከዚያም ግብጻውያን"

እነርሱ እኔ ያህዌ እንደሆንኩ ያውቃሉ
ያህዌ እርሱ ብቻ የበላይ እና ስልጣን ያለው መሆኑን እንደሚያውቁ እያመለከተ ነው። ይህ ተመሳሳይ ሀረግ በሕዝቅኤል 6:7 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ። "እውነተኛው ብቸኛ እኔ ያህዌ እንደሆንኩ ያውቃሉ" ወይም "እኔ፣ ያህዌ ሉዓላዊ ሀይል እና ስልጣን እንዳለኝ ይረዳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በግብጽ ላይ እሳት ሳስቀምጥ
እዚህ ስፍራ "በግብጽ ላይ እሳት ማስቀመጥ" የሚለው የሚወክለው ወደ ግብጽ ለጥቃት ወታደሮችን መላክ እና እሳት መለኮስን ነው። "ወደ ግብጽ ግብጽን እንዲያቃጥሏት ወታደሮችን ስልክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ረዳቶቿ ሁሉ ተደምስሰዋል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የግብጽን አጋሮች ሁሉ እደመስሳለሁ" ወይም "ወታደሮች ግብጽን የሚረዱትን ሁሉ ሲደመስሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

መልዕክተኞች አርፈው የተቀመጡትን ኩሽ ለማሸበር ከእኔ ፊት በመርከብ ይወጣሉ
መልዕክተኞች በወሬው የሚደናገጡትን፣ የግብጽን ጥፋት ወደ ኩሽ ይዘው ያመጣሉ

አርፈው የተቀመጡ ኩሽን ለማሸበር
"ተረጋግተው የተቀመጡትን ኩሽ ለማስፈራራት"

በግብጽ የጥፋት ቀን በመሃላቸው ጭንቀት ይሆናል
"ጭንቀት" የሚለው ረቂቅ ስም እና "ጥፋት" የሚሉት "መከራ" እና "ቅጣት" በሚሉ ቃላት ሊተረጎሙ ይችላሉ። "የኩሽ ሰዎች ግብጽን በምቀጣበት ቀን መከራ ይቀበላሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ!
እዚህ ስፍራ "እነሆ" የሚለው ቃል ቀጥሎ የሚሆነውን ያጎላል። "በእርግጥ!" ተብሎም ሊተረጎም ይችላል።

ይህ እየመጣ ነው
"ይህ" የሚለው የሚያመለክተው ግብጽ በምትቀጣበት ጊዜ ኩሽ አብሮ ሲቀጣ የሚደርስበትን "ታላቁን ስቃይ" ወይም "ታላቅ ሀዘን" ነው።

Ezekiel 30:10

ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
"እንዲህ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ቀጥሎ ምን እንደሚሆን ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5፡5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ተመልከቱ።

በብዙ ግብጻውያን ላይ ፍጻሜ አደርጋለሁ
"ከእንግዲህ ግብጽ ብዙ ህዝብ እንዳይኖራት ይህን አደርጋለሁ"

በናቡከደነጾር እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚወክለው የናቡከደነጾርን ወታደራዊ ሀይል ነው።ይህንን ቅጣት የሚያደርሰው ናቡከደነጾር ይሆናል።

እርሱ እና ከእርሱ ጋር ያለው ሰራዊቱ...ምድሪቱን ያጠፏታል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኔ ናቡከደነጾርንና ሰራዊቱን... ምድሪቱን እንዲያጠፉ አመጣቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ እና የእርሱ ሰራዊት...ምድሪቱን ለመደምሰስ ይመጣሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እርሱ እና የእርሱ ሰራዊት ... የግብጽን ምድር እንዲያጠፉ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ እና ከእርሱ ጋር ያለ ሰራዊቱ፣ ለምድሪቱ ድንጋጤ ይሆናሉ
ያህዌ ናቡከደነጾርን "ለምድሪቱ ድንጋጤ" የሚለው መላው አገር የእርሱን ሰራዊት እጅግ ስለሚፈራ ነው። "እርሱ እና ከእርሱ ጋር ያለ ሰራዊቱ፣ ብዙ አገራትን ያስሸበሩ ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰይፋቸውን በግብጽ ላይ ይመዛሉ
እዚህ ስፍራ " ሰይፋቸውን ይመዛሉ" የሚለው የሚወክለው በሰይፋቸው መዋጋታቸውን ነው። "ሰይፋቸውን ይዘው ግብጽን ይወጋሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሪቱን በተገደሉ ሰዎች ሙሏት
ይህ ባቢሎናውያን በጣም ብዙ ግብጻውያንን እንደሚገድሉ በግነት የተነገር ነው። የግብጽን ምድር የሚሞላ እስኪመስል ድረስ እጅግ ብዙ ግብጻውያን ይገደላሉ። "በድን በየስፍራው እስኪገኝ ድረስ እጅግ ብዙ ሰዎችን ግደሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

Ezekiel 30:12

አጠቃላይ መረጃ:
እነዚህ ያህዌ ስለ ግብጽ የተናገራቸው ቃላት ናቸው።

እኔ ወንዞች ደረቅ ምድር አደርጋለሁ
"የግብጽን ወንዞች አደርቃለሁ"

ምድርቱን ለክፉ ሰዎች እጅ አሳልፌ እሸጣለሁ
አንድ ሰው የሸጠውን እቃ ለገዢው አሳልፎ እንደሚሰጥ ያህዌ ግብጽን ባቢሎናውያን እንዲቆጣጠሯት አሳልፎ ይሰጣታል። "ምድሪቱን ክፉ ሰዎች እንዲቆጣጠሯት አሳልፌ እሰጣታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሷ ሙላት
"በምድሪቱ የሚገኝ ነገር ሁሉ"

Ezekiel 30:13

ጌታ ይህዌ እንዲህ ይላል
"እንዲህ" የሚለው ቃል ቀጥሎ የሚሆነውን ያመለክታል። ይህ በሕዝቅኤል 5፡5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ዋጋ ቢስ ለሆኑ ጣኦቶች ፍጻሜ አመጣለሁ
"ዋጋ ቢስ የሆኑ ጣኦቶችን አጠፋለሁ"

ሜምፌስ
ሜምፊስ በግብጽ ውስጥ የሚገኝ ትልቅ ከተማ ነበር። በአሁኗ ካይሮ አቅራቢያ ትገኝ ነበር። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በግብጽ ምድር የሚገኝ ልዑል /የግብጽ ልዑል
"በግብጽ ምድር ከፍተኛ መሪ"

በግብጽ ምድር ሽብር እሰዳለሁ
እዚህ ስፍራ "በምድሪቱ ሽብት መስደድ" የሚለው የሚወክለው የምድሪቱ ሰዎች በጣም እንዲፈሩ ማድረግን ነው። "የግብጽ ሰዎች በጣም እንዲፈሩ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጳትሮስ
ይህች በደቡብ ግብጽ የምትገኝ አካባቢ ነበረች

በጣኔዎስ እሳት አነዳለሁ
"ጣኔዎስን በእሳት አቃጥላለሁ"

ጣኔዎስ
ጣኔዎስ በግብጽ ትገኝ የነበረች ሌላዋ ትልቅ ከተማ ነበረች

በቴቤስ የፍርድን ተግባር እፈጽማለሁ
"የፍርድን ተግባር" የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው ቅጣትን ነው። "ቴቤስን እቀጣለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ቴቤስ
ይህች የደቡባዊ ግብጽ ዋና ከተማ ነበረች

Ezekiel 30:15

አጠቃላይ መረጃ:
እነዚህ ያህዌ ስለ ግብጽ የተናገራቸው ቃላት ናቸው።

በፔሉሲየም ላይ ቁጣዬን አፈሳለሁ
እዚህ ስፍራ "ቁጣዬን አፈሳለሁ" የሚለው የሚገልጸው ከታላቅ ቁጣው የተነሳ ህዝቡን መቅጣቱን ነው። "ፔሉሲየምን በታላቅ ቁጣ እቀጣለሁ" ወይም "እጅግ ከመቆጣቴ የተነሳ፣ ፔሉሲየምን እጅግ አድርጌ እቀጣለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ፔሉሲየም
በሰሜናዊ ግብጽ የምትገኝ የምሽግ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የቴቤስን አእላፋት/አያሌ እቆርጣለሁ
እዚህ ስፍራ "መቁረጥ" የሚለው የሚገልጸው ሰዎችን መግደልን ነው። "በቴቤስ በጣም ብዙ ቁጥር ያላቸውን ሰዎች እገድላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ቴቤስ
ይህች የደቡባዊ ግብጽ ዋና ከተማ ነበረች።ይህ በሕዝቅኤል 3፡14 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ፔሉሲየም በታላቅ ስቃይ ውስጥ ትገባለች
እዚህ ስፍራ "ፔሉሲየም" በፔሉሲየም ከተማ ዙሪያ ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሲሆን፤ "በታላቅ ስቃይ ውስጥ መሆን" የሚለው "ተሰቃዩ" በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። " የፔሉሲየም ሰዎች እጅይ ይሰቃያሉ" ወይም " የፔሉሲየም ሰዎች ከፍተኛ ስቃይ ያገኛቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

ቴቤስ ትንኮታኮታለች/ትሰባበራለች
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ጠላት የቴቤስን ቅጥሮች እና ግንቦች ይሰባብራል" ወይም "ጠላት ቴቤስን ያጠፋታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ሜምፊስ ጠላት በየቀኑ ይገጥማታል
እዚህ ስፍራ "የጠላት መግጠም" የሚወክለው ጠላት ማየትን ወይም የጠላትን መኖር ነው። የከተማይቱ ስም በከተማይቱ ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። "የሜምፊስ ሰዎች በየዕለቱ ጠላት ይገጥማቸዋል" ወይም "ጠላት በየእለቱ የሜምፊስን ሰዎች ይዋጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሜምፊስ
ሜምፊስ በግብጽ በጣም ትልቅ ከተማ ነበረች። ይህ በሕዝቅኤል 30፡13 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

Ezekiel 30:17

አጠቃላይ መረጃ፡
እነዚህ ያህዌ ስለ ግብጽ የተናገራቸው ቃላት ናቸው።

ሄልዮቱ እና ቡባስቱ
እነዚህ በሰሜን ግብጽ የነበሩ ከተሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰይፍ ይወድቃሉ
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ውጊያን ወይም ጦርነትን ነው። "በውጊያ ይሞታሉ" ወይም "በጦርነት ይሞታሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ጣፍናስ
ይህ በሰሜን ግብጽ የሚገኝ ትልቅ ከተማ ነበር።

ቀኑ ብርሃኑን አይሰጥም
ቀኑ የተገለጸው ራሱ ብርሃኑን ይዞ እንደሚያስቀር ተደርጎ ነው። "ቀኑ ይጨልማል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የብርታቷ ኩራት ያበቃል
ይህ የሚወክለው ግብጽ ከእንግዲህ በጥንካሬዋ ልትመካ እንደማትችል ነው። ከእንግዲህ ሊኮሩ የማይችሉበት ምክንያት አቅም ስለሚያጡ ነው። "ከእንግዲህ ግብጽ በብርታቷ አትመካም" ወይም "ከእንግዲህ ግብጻውያን የሚኮሩበት ብርታት አይኖራቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ደመና ይሸፍናታል
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ጥቁር ጨለማ የሚወክለው የግብጽ ሰዎች ምን ያህል ሀዘን እንደሚወድቅባቸው ነው። "በግብጽ ላይ ደመና ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) ከሚደመሰሰው ነገር ላይ ሁሉ ከሚነሳው አቧራ በግብጽ ላይ ደመና ይሆናል። "በግብጽ ላይ የደመና አብዋራ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሴት ልጆቿ
x

Ezekiel 30:20

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ የፈርኦንን ሰራዊት ደካማ እንደሚያደርግ የሚናገረው፣ የፈርኦንን ክንድ እንደ መስበር እና የተሰበረው የፈርኦን ክንድ ፈውስ እንደሌለው እንደዚህም ሰራዊቱ ዳግም ጠንካራ ሊሆን እንደማይችል አድርጎ ነው። (ምሳሌዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያም እንዲህ ሆነ
ይህ ሀረግ እዚህ ስፍራ የዋለው የታሪኩን አዲስ ክፍል ጅማሬ ለማመልከት ነው። ቋንቋችሁ ይህን ለማድረግ መንገድ ካለው፣ እዚህ ስፍራ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

አስራ አንደኛው አመት
ይህ ንጉሥ ዮአኪን በስደት ወደ ባቢሎን በሄደ አስራ አንደኛው አመት ነው። ይህ በሕዝቅኤል 26፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

በመጀመሪያው ወር፣ በወሩ ሰባተኛ ቀን
"በመጀመሪያው ወር በሰባተኛው ቀን።" ይህ በዕብራውያን የወር አቆጣጠር የመጀመሪያው ወር ነው። ሰባተኛው ቀን በምዕራባዊያን አቆጣጠር ሚያዚያ መጀመሪያ አካባቢ ነው። (የዕብራውያን ወሮች እና ተከታታይ ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

የያህዌ ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የተናገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ነናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ/ያህዌ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እኔ የፈርኦንን ክንድ ሰብሬያለሁ
እዚህ ስፍራ "ክንድ" የሚወክለው የንጉሥን ጠንካራ ሰራዊት ነው። (ምሳሌዎች እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

እነሆ
"ቀጥሎ የምናገረው እውነተኛ እና ትልቅ ነገር ስለሆነ ትኩረት ስጡት"

ክንዱ አልተጠቀለለም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ክንዱን ማንም አላሰረውም" ወይም "ማንም ክንዱን አልጠቀለለውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወይም እንዲፈወስ በጨርቅ/ፋሻ አልታሰረም
እዚህ ስፍራ "እንዲፈወስ በጨርቅ/ፋሻ መጠቅለል" የሚለው የሚያመለክተው አጥንቱ መልሶ እንዲጠገንእና እንዲፈወስ ክንዱን ጠበቅ አደርጎ በፋሻ መጠቅለልን ነው።

Ezekiel 30:22

አጠቃላይ መረጃ:
እግዚአብሔር ስለ ፈርኦን ሰራዊት እንደ ተሰበረ ክንድ አድረጎ መናገሩን ቀጥሏል። እንደዚሁም ደግሞ የባቢሎንን ሰራዊት ማጠንከርን የባቢሎን ንጉሥን ክንድ እንደ ማጠንከር አድርጎ ይናገራል።

ጌታ ያህዌ ይህን አለ/ያህዌ እንዲህ አለ
ይህ በሕዝቅኤል 3፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ጠንካራው እና የተሰበረው ሁለቱም
"ጤነኛ የሆነው ክንድ እና አስቀድሞ የተሰበረው ክንድ ሁለቱም"

ሰይፉ ከእጁ እንዲወድቅ አደርጋለሁ
"ከፈርኦን እጅ ሰይፉን መትቼ አስጥለዋለሁ"

ግብጽን በህዝቦች መሃል እበትናለሁ፣ እናም እነርሱን በምድር ዙሪያ እበትናቸዋለሁ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። በሕዝቅኤል 12፡15 ላይ ተመሳሳይ ሆነው ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በምድር ዙሪያ
"ሰዎች በሚኖሩበት ስፍራ ሁሉ"

የባቢሎንን ንጉሥ ክንዶች አበረታለሁ
"የባቢሎንን ንጉሥ ክንዶች ጠንካራ አደርጋለሁ"

በባቢሎን ንጉሥ ፊት ያቃስታል
"የባቢሎን ንጉሥ ግብጽን ሊያጠቃ ሲመጣ፣ ፈርኦን ያቃስታል።"

ማቃሰት
ማቃሰት ሰዎች ብዙ ስቃይ ሲደርስባቸው ወይም ሲያጣጥሩ የሚያሰሙት ድምጽ ነው።

የሚያጣጥር ሰው ማቃሰት
"ሰው እያጣጣረ ሲያቃስት" ወይም "እያጣጣረ እንደሚገኝ ሰው"

Ezekiel 30:25

አጠቃላይ መረጃ:
እግዚአብሔር ስለ ግብጽ እና ባቢሎን ሰራዊቶች የንጉሦቻቸው ክንድ እንደሆኑ አድርጎ መናገሩን ቀጥሏል። እንደዚሁም የባቢሎንን ሰራዊት ሌሎችን ለማጥቃት እንዲችሉ እርሱ ሰይፍ እነዳለውና ሰይፉንም በባቢሎናውያን ንጉሥ እጅ ላይ እንዳስቀመጠው አድርጎ ይናገራል። (ምሳሌዎች የሚለውን መልከቱ)

እኔ የባቢሎን ንጉሥን ክንዶች አጠነክራለሁ
እዚህ ስፍራ "ክንዶች" የሚለው ለሰራዊቱ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "የባቢሎንን ንጉሥ ሰራዊት አበረታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የፈርኦን ክንዶች በሚወድቁበት ጊዜ
እዚህ ስፍራ "የፈርኦን ክንዶች" የሚለው ለእርሱ ሰራዊት ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። "በሚወድቁበት ጊዜ" የሚለው የሚወክለው መድከምን ነው። "ነገር ግን የፈርኦን ሰራዊት ጠላት ማሸነፍ የማይችሉ ይሆናሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያም እነርሱ
"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ተከታዩን ሊሆን ይችላል 1) "ግብጻውያንን" ወይም 2) "ያህዌ ያደረገውን የሰሙትን ሰዎች ሁሉ"

ከዚህ ጋር እርሱ የግብጽን ምድር ያጠቃል
"እናም የባቢሎን ንጉሥ በእኔ ሰይፍ የግብጽን ምድር ያጠቃል"

ግብጽን በህዝብ መሃል እበትናለሁ ደግሞም በምድር ሁሉ እበትናቸዋለሁ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ይህ በህዝቅኤል 12፡15 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 31

1 እንዲህም ሆነ በአሥራ አንደኛው ዓመት በሦስተኛው ወር ከወሩም በመጀመሪያው ቀን የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ። **2** የሰው ልጅ ሆይ፥ የግብጽን ንጉሥ ፈርዖንንና በዙሪያው ያሉትን አገልጋዮቹን እንዲህ በላቸው። 'በታላቅነትህ ማንን ትመስላለህ? **3** እነሆ፥ አሦር ጫፉ እንደ ተዋበ፥ ችፍግነቱ ጥላ እንደ ሰጠ፥ ቁመቱም እንደ ረዘመ፥ ራሱም በደመናዎች መካከል እንደ ነበረ እንደ ሊባኖስ ዝግባ ነበረ። **4** ውኆችም አበቀሉት፥ ቀላይም ግዙፍ አደረገው። ወንዞችም በተተከለበት ዙሪያ ይጐርፉ ነበር፥ መስኖዎቻቸውን በሜዳ ወዳሉ ዛፎች ይሰዳሉ። **5** ቁመቱ ከምድረ በዳ ዛፍ ሁሉ ከፍ ያለ ነበር አለ፤ ቅርንጫፎቹም ከብዙ ውኖች የተነሣ ረዘሙ። **6** የሰማይ ወፎች ሁሉ ጎጆቻቸውን በቅርንጫፎቹ ላይ አደረጉ፥ የምድርም አራዊት ሁሉ ከጥላው በታች ተዋለዱ። ታላላቅ ህዝቦች ከጥላውም በታች ኖሩ። **7** ሥሩም በብዙ ውኃ አጠገብ ነበረና በታላቅነቱና በቅርንጫፎቹ ርዝመት የተዋበ ነበረ። **8** በእግዚአብሔር ገነት የነበሩ ዝግባዎች አልተካከሉትም! ጥዶችም ቅርንጫፎቹን አይመስሉትም አስታ የሚባለውም ዛፍ ቅርንጫፎቹን አይተካከሉም! በእግዚአብሔርም ገነት ካሉ ዛፎች በውበቱ ሊተካከለው አልቻለም! **9** በቅርንጫፎቹ ብዛት ውብ አደረግሁት፤ በእግዚአብሔርም ገነት በዔድን የነበሩ ዛፎች ሁሉ ቀኑበት። **10** ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ቁመቱ ከፍ ከፍ ብሎአልና፥ ጫፎቹንም ከቅርንጫፎች በላይ አድርጎአልና፥ **11** ልቡም በቁመቱ ልክ ኰርቶአልና ከአሕዛብ ሁሉ በላይ ኃይለኛ ገዢ እጅ አሳልፌ እሰጠዋለሁ! ይህም ገዢ ይቃወመዋል እንደ ክፋቱም መጠን ያሳድደዋለሁ። **12** የአህዛብ ድንጋጤ የሆኑ የሌላ አገር ሰዎች፥ አስወግዱት ፈጽሞም ጣሉት። ቅርንጫፎቹ በተራሮችና ላይና በሸለቆች ውስጥ ወደቁ፥ ቅርንጫፎቹም በምድር ፈሳሾች ሁሉ ላይ ተሰባበሩ። የምድርም አሕዛብ ሁሉ ከጥላው ወጥተው ጥለውት ሄዱ። **13** የሰማይ ወፎች ሁሉ በግንዱ ላይ ይቀመጣሉ የምድርም አራዊት ሁሉ በቅርንጫፎቹ ላይ ይቀመጣሉ። **14** ይህም የሆነው ወደ ጕድጓድ በሚወርዱ በሰው ልጆች መካከል ሁላቸው ለታችኛው ምድር ለሞት አልፈው ተሰጥተዋልና ውሀ ሲጠጡ ከነበሩት ዛፎች ውስጥ አንዳቸውም ረጅም ሆነው እንዳያድጉ፥ ጫፎቻቸውም ከቅጠሎች በላይ እንዳይሆኑ፥ በውኃ አጠገብ ያሉ ዛፎች ሁሉ ከእንግዲህ በቁመታቸው እንዳይረዝሙ ነው። **15** ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ወደ ሲኦል በወረደበት ቀን ልቅሶን ወደ ምድር አመጣሁ። በቀላያትም ሸፈንኩት፥ የውቅያኖስ ፈሳሾቹንም ከለከልሁ። ታላላቆችም ውኖች ከለከልኩ፥ ለባኖስንም ስለ እርሱ አሳዘንሁት! የዱርም ዛፎች ሁሉ ስለ እርሱ አለቀሱ። **16** ወደ ጕድጓድ ከሚወርዱ ጋር ወደ ሲኦል በጣልሁት ጊዜ ክአውዳደቁ ድምፅ የተነሣ በአሕዛብ ላይ መንቀጥቀጥን አመጣሁ! በምድር ዝቅተኛ ቦታ የኤደን ዛፎችን ሁሉ አጽናናለሁ! እነርሱም ውኃ የሚጠጡ ፥ ምርጦችና መልካካሞች የሊባኖስ ዛፎች ናቸው። **17** ክንዱም ወደ የነበሩት በአሕዛብም መካከል በጥላው ሥር የተቀመጡት፥ በሰይፍ ወደ ተገደሉት ሰዎች ወደ ሲኦል ከእርሱ ጋር ወርደዋልና። **18** በክብርና በታላቅነት በዔድን ዛፎች መካከል ማን ይመስልህ ነበር? ነገር ግን ከዔድን ዛፎች ጋር ወዳልተገረዙት መካከል ወደ ታችኛው ምድር ያወርዱሃል፤ በሰይፍም ከተገደሉት ጋር ትኖራለህ! እነርሱም ፈርዖንና አገልጋዮቹ ናቸው ይላል ጌታ እግዚአብሔር!"

Ezekiel 31:1

እንዲህም ሆነ
እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ውስጥ የተፈጸመን ጠቃሚ ትዕይንት ለማጉላት/ለማመልከት ነው። በእናንተ ቋንቋ ይህን ለማድረግ የሚጠቀምበት መንገድ ካለ እዚህ ስፍራ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ።

በአስራ አንደኛው አመት
"በ11ኛ አመት።" ይህ ማለት ንጉሥ ዮአኪን ባቢሎን በስደት ከተወሰደ ከአስራ አንድ አመት በኋላ ማለት ነው። ይህ በህዝቅኤል 26፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ንጉሥ ዮአኪን በተሰደደ በአስራ አንደኛው አመት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተከታታይ ቁጥሮች እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

በሶስተኛው ወር፣ በወሩ ሶስተኛ ቀን
"በሶስተኛው ወር በመጀመሪያው ቀን።" ይህ በዕብራውያን አቆጣጠር ሶስተኛው ወር ነው። ይህ የመጀመሪያ ቀን በምዕራባውያን አቆጣጠር በሰኔ መጀመሪያ አቅራቢያ ነው። (የዕብራውያን ወሮች እና ተከታታይ ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

የያህዌ ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የተናገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ነናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ/ያህዌ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

በታላቅነትህ፣ ማንን ትመስላለህ?
"እንዳንተ ታላቅ ማን ነው?" ያህዌ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው አዲስ ርዕስ ለማስተዋወቅ ነው። ፈርኦን የእርሱ አገር ከሁሉም ታላቅ እንደሆነ ያስባል፣ እግዚአብሔር ግን ስለ ሌላ ታላቅ አገር ሊናገር ነው። "አንተ ሀይሉ እንደ አንተ አገር ታላቅ የሆነ ሌላ አገር እንደሌለ ታስባለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 31:3

አጠቃላይ መረጃ:
እነዚህ ስለ አሦር እግዚአብሔር ለፈርኦን የተናገራቸው ቃሎች ናቸው። እግዚአብሔር በትልቅ በጥድ ዛፍ መልክ በምሳሌ መልዕክቱን ተናግሯል። (ምሳሌዎች የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ!
"ተመልከት!" ወይም "አድምጥ!" ወይም "ልነግርህ ስላለው ነገር ትኩረት ስጥ!"

አሦር የጥድ ዛፍ ነበር
በዚህ ምሳሌ፣ እግዚአብሔር ስለ አሦር ታላቅ ዛፍ እንደነበረ በመናገር ስለ አሦራውያን ምን ያህል ታላቅ እና ሀይለኛ እንደነበሩ አጉልቶ ይናገራል። ምሳሌው አስከ ሕዝቅኤል 31:9 ድረስ ይቀጥላል። "አሦር እንደ ጥድ ዛፍ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምሳሌዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ቅርንጫፎቹ የዛፉን አናት አበጁ
"አናቱ ከሌሎች ዛፎች በላይ ነበር።" አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች ይህንን "የዛፉ ጫፍ ደመና ደርሷል" በማለት ተርጉመውታል።

በብዙ ውሃ አድጓል
"ጥድ ብዙ ውሃ ስላላው፣ በጣም ትልቅ ሆኖ ያድጋል"

ጥልቁ ውሃ ግዙፍ አድርጎታል
"ከምድር ጥልቅ ስፍራ የሚገኘው ውሃ ጥድ በጣም ትልቅ ሆኖ እንዲያድግ አድርጓል"

ጅረቶች በሜዳ ወደሚገኙ ዛፎች ሁሉ ፈሰሱ
"የወንዞች ምንጮች በሜዳ ወደሚገኙ ዛፎች ሁሉ ይፈሳሉ"

Ezekiel 31:5

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ ጥድ የሚናገረው ምሳሌ ቀጥሏል።

ታላቅ ቁመቱ በሜዳ ከሚገኙ ሌሎች ዛፎች ሁሉ ይበልጣል
"ጥዱ ከማናቸውም በሜዳ ከሚገኙ ዛፎች ይልቅ ትልቅ ነበር"

ቅርንጫፎቹ በጣም ብዙ ይሆናሉ
"በጣም ብዙ ቅርንጫፎችን ያበቅላል"

በሚያድጉበት ጊዜ ከሚያገኙት ብዙ ውሃ የተነሳ
"ብዙ ውሃ ስላለው"

እያንደንዱ የሰማይ ወፍ በቅርንጫፎቹ ላይ ጎጆ ይሰራል
"በሰማይ የሚበሩ ሁሉም አይነት ወፎች በቅርንጫፎቹ ላይ ጎጆ ይሰራል"

የሜዳ ፍጥረታት ሁሉ በጥላው ስራ ልጆቻቸውን ሲወልዱ
"እናም በሜዳ የሚኖሩ ሁሉም ፍጥረታት ከጥድ ዛፍ ቅርንጫፍ በታች ሲወልዱ"

ከጥላው ስር የሚኖሩ ህዝቦች ሁሉ
"በዚያ ዛፍ ስር የሚኖሩ ታላላቅ ህዝቦች ሁሉ።" እዚህ ስፍራ "ህዝቦች" የሚለው የሚወክለው በዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ነው። "ከነዚያ አገራት ሁሉ የሆኑ ሰዎች በዚያ ዛፍ ጥላ ስር ይኖራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በታላቅነቱ እና በቅርንጫፎቹ ርዝመት ውብ ነበር
"በጣም ትልቅ እና ቅርንጫፎቹም በጣም ረጃጅም ስለነበሩ ውብ ነበር።"

Ezekiel 31:8

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ ጥድ የሚናገረው ምሳሌ ቀጥሏል።

በእግዚአብሔር ገነት ያሉ ዝግባዎች/ ጥዶች ሊስተካከሉት አይችሉም
እነዚህ እግዚአብሔር ለፈርኦን የተናገራቸው ቃላት እንደመሆናቸው፣ በመጀመሪያ መደብ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "በገነቴ የሚገኙ የጥድ ዛፎች እንደነዚያ ዛፎች ያህል ትልልቅ አልነበሩም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ገነት
ይህ "ኤደን ገነት" ለሚለው ሌላው የአገላለጽ መንገድ ነው።"

ከጥድ ዛፎች መሃል የትኛውም ቅርንጫፉ
ያህዌ ዛፎቹ ምን ያህል ቅርንጫፍ እንዳላቸው እያነጻጸረ ነበር። "ከአስታ ዛፎቹ የትኛውም እንደ ጥድ ዛፍ ብዙ ቅርንጫፎች የሉትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ዝግባ ዛፎች
የዝግባ ዛፍ በጣም ብዙ ቅርንጫፎች አሉት። በጣም ሊያድጉ ይችላሉ። "ዝግባ" በህዝቅኤል 27:5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ

ተራው/ማናቸውም ዛፍ የእርሱን ያህል ቅርንጫፍ አይኖረውም
ያህዌ የጥድን ዛፍ ረጅም ቅርንጫፎች ከተራ ዛፎች ቅርንጫፎች ጋር እያነጻጸረ መሆኑ ተጠቅሶ ነበር። "ማናቸውም ዛፍ እንደ ጥድ ዛፍ ያህል ቅርንጫፍ የለውም" ወይም "የትኛውም ዛፍ የጥድ ዛፍን ያህል ረጅም ቅርንጫፎች የለውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ተራ ዛፍ
ተራ ዛፍ ረጅም፣ቅጠላማ ጠንካራ ቅርንጫፍ ያለው ዛፍ ነው። ከበርሰነት ዛፍ ጋር ተመሳሳይ ነው። (የማይታወቀውን መተረጎም የሚለውን ይመልከቱ)

በውበቱ እርሱን የሚመስል ነበር
"የጥድ ዛፍን ያህል ውበት አለው"

ከብዙ ቅርንጫፎቹ ጋር ውብ አድርጌ ሰራሁት
"ብዙ ረጃጅም ቅርንጫፎችን በማድረግ ጥድን አስዋብኩት"

ቀኑበት
"በጥድ ዛፍ ቀኑበት"

Ezekiel 31:10

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ ጥድ የሚናገረው ምሳሌ ቀጥሏል።

ስለዚህም ጌታ ያህዌ እንዲህ አለ
ያህዌ እስከ ተናገረ ድረስ ይህ በአንደኛ መደብ ሊጸፍ ይችላል። "ስለዚህ፣ ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

የዛፉን ጭንቅላት በቅርንጫፎቹ መሃል አደረገ
"ጫፉ ከሌሎች ዛፎች ቅርንጫፎች በላይ ነበር።" አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች "የዛፉ ጭንቅላት እስከ ደመና ደርሶ ነበር" ሲሉ ተርጉመውታል።

ለታላላቅ አገራት እጅ አሳላፌ ሰጥቼዋለሁ
"እጅ" የሚለው ቃል በቁጥጥር ስር ማድረግን ይወክላል። "በጠንካራ አገራት ሀይል ስር አድርጌዋለሁ" ወይም "የታላላቅ አገሮችን ሀይል በላዩ አምጥቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አውጥቼ ጥየዋለሁ
"ክፉ ከመሆኑ የተነሳ፣ ጥዱን ከሚበቅልበት ምድር አውጥቼ ጥየዋለሁ"

Ezekiel 31:12

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ ጥድ የሚናገረው ምሳሌ ቀጥሏል።

ለሁሉም ህዝብ ሸብር የሆነው ማን ነበር
"ሸብር" የሚለው ረቂቅ ስም "ፍርሃት" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። እዚህ ስፍራ "አገሮች" የሚለው የሚወክለው የአገሮችን ህዝቦች ነው። "የአገራትን ህዝቦች ያስፈራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

እቆርጠዋለሁ
"ጥዱን ቆርጬ እጥለዋለሁ"

ትልቁ ቅርንጫፍ ተገንጥሎ ይወድቃል
"ባዕዳን የጥዱን ትልቅ ቅርንጫፍ ይሰብሩታል"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ትልቅ ቅርንጫፍ
ትልቅ ቅርንጫፍ በጣም ትልልቅ የሆኑ የዛፉ ቅርንጫፎች ናቸው። ብዙውን ጊዜ፣ በርካታ ትንንሽ ቅርንጫፎች በላዩ ይበቅሉበታል።

ከጥላው ስር ይወጣሉ
"የጥዱን ጥላ ይተዋሉ"

Ezekiel 31:13

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ ጥድ የሚናገረው ምሳሌ ቀጥሏል።

የሰማይ ወፎች ሁሉ
"በሰማይ ላይ የሚበሩ ወፎች ሁሉ"

ግንድ
ግንድ ከምድር በላይ የሚገኘው በጣም ወፍራም የሆነ ሌላውን የዛፉን ክፍል የሚሸከም ነው።

እያንዳንዱ የሜዳ እንስሳ ከቅርንጫፉ ስር ይሰበሰባል
"የዱር እንስሳት በጥድ ቅርንጫፍ መሃል ይኖራሉ"

የትኞቹም ሌሎች ዛፎች በውሃ እንደ እርሱ አላደጉም
"ሌሎች የትኞቹም አይነት ዛፎች እንደ እርሱ ብዙ ውሃ አላገኙም"

ቅርንጫፋቸውን ከሁሉም ከፍ እስካሉት ዛፎች ድረስ ከፍ ያደርጋሉ
"ከሌሎች ዛፎች ቅርንጫፎች በላይ ያድጋሉ።" አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ይህንን "ጫፋቸውን በደመና መሃል ያደርጋሉ" ብለው ይገልጻሉ።

በውሃ ዳርቻ ያደጉ ሌሎች የትኞቹም ዛፎች እስከዚያ ድረስ ከፍ ብለው አያድጉም
"የትኞቹም ብዙ ውሃ ያገኙ ሌሎች ዛፎች ዳግም እስከዚያ ከፍታ ድረስ አያድጉም"

ሁሉም ከምድር በታች እንዲሆኑ ሞት ተፈርዶባቸው ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። ደግሞም "ሞት" የሚለው ረቂቅ ስም "ሞተ" ሊባል ይችላል። "ስለዚህም እኔ ሁሉም እንዲሞቱ እና ከምድር በታች እንዲወርዱ አደረግሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

ወደ ምድር ጥልቅ ከወረዱ፣ ከሰው ልጆች መሃል
"ከሞቱ እና ወደ መቃብር ከወረዱ ሰዎች ጋር መሆን"

ወደ ጉድጓድ
ይህ መቃብርን ያመለክታል፤ ምክንያቱም መቃብር ወደ ሞት ዓለም መግቢያ ተደርጎ ይታሰብ ነበር፣ ጉድጓድም ደግሞ ያንን ዓለም ይወክላል። ይህ በሕዝቅኤል 26:20 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 31:15

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ ጥድ የሚናገረው ምሳሌ ቀጥሏል። እዚህ ስፍራ፣ ያህዌ ውሃዎች፣ ሊባኖስ፣ እና የዱር ዛፎች ሁሉም ለጥዱ እንዳዘኑ አድርጎ፤ በተቆረጠው ጥድ ምክንያት ስለተፈጠረው ታለቅ ሀዘን ይናገራል።

ጥዱ ወደ ሲኦል በወረደ ቀን
"ወደ ሲኦል መውረድ" የሚለው ሀረግ "መሞት" ማለት ነው። "ጥዱ በሚሞትበት ቀን" ወይም "ጥዱ በሚቆረጥበት ቀን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ወደ ምድር ሀዘንን አመጣለሁ
"ሀዘን" የሚለው ረቂቅ ስም በግስ መልክ ሊገለጽ ይችላል። "ምድር እንድታዝን አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ ላይ ጥልቅ ውሃ እከድናለሁ
"መክደን" የሚለው ቃል ምናልባት ሊያመለክት የሚችለው ለሀዘን ልብስ መልበስን ይሆናል። "የምንጮች ውሃ ለጥዱ እንዲያዝን አደርጋለሁ" ወይም "የሚያጠጣው የምንጭ ውሃ ለእርሱ እንዲያዝን አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የውቅያኖስ ውሆችን ወደ ኋላ እመልሳለሁ
"በውቅያኖስ ያለ ውሃ ምድርን እንዳያጠጣ አደርጋለሁ"

ታላላቅ ውሆችን እይዛለሁ
"ከእንግዲህ በቂ ውሃ እንዳይገኝ አደርጋለሁ"

ለእርሱ ወደ ሊባኖስ ሀዘን አመጣለሁ
"ሀዘን" የሚለው ረቂቅ ስም በግስ መልኩ ሊገለጽ ይችላል። "እኔ ሊባኖስ ለጥዱ እንዲያዝን አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 31:16

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ ጥድ የሚናገረው ምሳሌ ቀጥሏል።

ወደ ጉድጓድ ከወረዱት ጋር ወደ ሲኦል ስጥለው
እዚህ ስፍራ "ወደ ሲኦል መጣል" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ መግደል ማለት ነው። "ጉድጓዱ" የሚያመለክተው መቃብርን ነው፤ ምክንያቱም መቃብር ወደ ሙታን ዓለም መግቢያ ተደርጎ ሲታሰብ፣ ጉድጓድም ደግሞ ያንን ዓለም ይወክላል። ይህ በሕዝቅኤል 31:14 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እኔ ጥዱን ስገድል እና እርሱም ከሞቱት ጋር ሁሉ ወደ ሲኦል ሲወርድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

በምድር ታችኛው ክፍል
"እነዚያ ቀድሞውኑ በምድር ጥልቅ ስፍራ ያሉ ናቸው።" ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ቀድሞውኑ ሞተው የነበሩ እና አሁን በሲኦል የሚገኙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የተመረጡ እና የሊባኖስ ምርጥ ዛፎች፤ ውሃ በሚገባ የጠጡ ዛፎች
"ውሃ በሚገባ ያገኙ፣ ሁሉም የሚፈልጋቸው የሊባኖስ ምርጥ ዛፎች" ይህ በምድር ታችኛው ስፍራ የሚገኙ የኤደንን ዛፎች መግለጽ ነው።

የተመረጠ
ይህ በጣም ጥሩ ስለሆነ ሁሉም የሚፈልገው ነገር ነው

Ezekiel 31:17

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ ጥድ የሚናገረው ምሳሌ ቀጥሏል።

እነርሱም ደግሞ ከእርሱ ጋር ወደ ሲኦል ይወርዳሉ
እዚህ ስፍራ "ወደ ሲኦል... ይወርዳሉ" የሚለው መሞት ለሚለው ፈሊጣዊ አገላለጽ ነው። "እነዚያ የሊባኖስ ዛፎች ይሞታሉ፣ ደግሞም ከጥዱ ጋር ወደ ሲኦል ይወርዳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በሰይፍ የተገደሉ
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚለው የሚወክለው በጦርነት የተዋጓቸውን ጠላቶቻቸውን ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ጠላት በሰይፍ የገደላቸው" ወይም "በጦርነት የሞቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ደራጊ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 32

1 እንዲህም ሆነ በአሥራ ሁለተኛው ዓመት በአሥራ ሁለተኛው ወር ከወሩም በመጀመሪያው ቀን የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ። 2 የሰው ልጅ
ሆይ፥ ስለ ግብጽ ንጉሥ ስለ ፈርዖን ሙሾ አሙሽ፥ እንዲህም በለው፥ 'በእህዛብ መካከል እንደ አንበሳ ደቦል በባህር እንዳለ አስፈሪ ፍጥረት ነበርክ፤ ውሃውን
አናወጥከው፥ ውሆችን በእግርህ በጥብጠህ አጨቀየሀቸው። 3 ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በብዙ አሕዛብ ጉባኤ መረቤን እዘረጋብሃለሁ፥ እነርሱም
በመረቤ ይይዙሀል! 4 በምድርም ላይ እተውሃለሁ፥ በምድረ በዳም ፊት እጥልሃለሁ፥ የሰማይንም ወፎች ሁሉ አሳርፍብሃለሁ፥ የተራቡ ምድርን አራዊት በአንተ
አጠግባቸዋለሁ። 5 ሥጋህን በተራሮች ላይ አደርጋለሁ ሸለቆቹንም በትል በተሞላ ሬሳህ እሞላለሁ! 6 ደምህንም በተራሮች ላይ አፈሳለሁ መስኖችም በደምህ
ይሞላሉ። 7 መብራትህን ባጠፋህ ጊዜ ሰማዮችን እሸፍናለሁ፥ ከዋክብቶችንም አጨልማለሁ። ፀሐይንም በደመና እሸፍናለሁ ጨረቃም ብርሃኗን አትሰጥም! 8
የሰማይን ብርሃኖች ሁሉ በላይህ አጨልማለሁ፥ በምድርህም ላይ ጨለማ አደርጋለሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፦ 9 በአሕዛብ መካከል ጥፋትህን በማመጣ ጊዜ
የማታውቃቸውን የብዙ ሕዝብን ልብ አስደነግጣለሁ። 10 ብዙም አሕዛብን ስለዘንተ አስደንቃለሁ፤ ሰይፌንም በፊታቸው ባወዛወዝሁ ጊዜ ነገሥታቶቻቸው ስለ
አንተ እጅግ አድርገው ይፈራሉ። በውድቀትህም ቀን እያንዳንዱ በአንተ ምክንያት ይንቀጠቀጣል። 11 ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና። የባቢሎን ንጉሥ
ሰይፍ ይመጣብሃል። 12 አገልጋዮችህ የአህዛብ ድንጋጤ በሆኑ ጦርኞች ሥይፍ እንዲወድቁ አደርጋልሁ! የግበጽንም ትዕቢት ያውርዳሉ ህዝቧንም ሁሉ
ያጠፋሉ! 13 እንስሶችን ከብዙ ውኃ አጠገብ አጠፋለሁ፤ ከእንግዲህም ወዲያ የሰው እግርም ሆነ የእንስሳት ኮቴ ውሃውን አያደፈርስም! 14 በዚያን ጊዜ
ውኃቸውን አረጋጋለሁ፥ እንደ ዘይትም እንዲፈስሱ አደርጋለሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፦ 15 ሙሉ የነበረውን የግብጽን ምድር ባድማና ውድማ ባደረግሁ ጊዜ፥
የሚኖሩባትንም ሁሉ በቀሠፍሁ ጊዜ፥ እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ! 16 የአሕዛብ ቄነጃጅት ያለቅሱበታል ያለቅሱባታልና ሙሾ ይሆናል፥ ነው ስለ
ግብጽና ስለአገልጋዮቿ ሁሉ ያለቅሳሉ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፦ 17 እንዲህም ሆነ በአሥራ ሁለተኛው ዓመት ከወሩም በአሥራ አምስተኛው ቀን የእግዚአብሔር
ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ። 18 የሰው ልጅ ሆይ፥ ስለ ግብጽ አገልጋዮች አልቅስ፥ እርስዋንና የብርቱዎችን አሕዛብ ሴቶች ልጆች ወደ ጕድጓድ ከሚወርዱ
ጋር ወደ ታችኛው ምድር ጣላቸው። 19 እንዲህ ብለህ ጥይቃቸው፥ 'ከማንም ይልቅ በውበት ትበልጣላችሁን? ውረዱና ካልተገረዙትም ጋር ተኙ! 20 በሰይፍ
በተገደሉት መካከል ይወድቃሉ፤ ጥላቶቿ እርሷንና አገልጋዮቿን ይይዛሉ! 21 በሲኦል የኃያላን አለቆች ስለ ግብጽ ፥ "ወደዚህ ወደ ሲዖል መጥተዋል! በሰይፍ
ከተገደሉ ካልተገርዙት ጋር ይተኛሉ!' ብለው ይናገራሉ። 22 አሦርና ጉባኤዋ ሁሉ በዚያ አሉ መቃብሮችም ከበዋታል፤ ሁሉም በሰይፍ የተገደሉ ናቸው። 23
መቃብራቸው በጕድጓዱ በውስጠኛው ክፍል የሆኑትም ከእርሷ ጉባኤ ሁሉ ጋር በዚያ አሉ! መቃብሯ በተገደሉ፥ በሰይፍ በወደቁ እንዲሁም በሕያዋን ምድር
ፍርሀትን ባመጡ ተከቧል። 24 ኤላምም ከአገልጋዮቿ ጋር በዚያ አለች፤ መቃብሮቿም ከበዋታል። ሁሉም የተገደሉ ናቸው። እነርሱም በሕያዋን ምድር ያስፈሩ ሁሉ
፥ ሳይገረዙም ወደ ታችኛው ምድር የወረዱ፥ በህያዋን ምድር ሸብርን ያመጡና ወደ ጕድጓድም ከሚወርዱ ጋር እፍረታቸውን የተሸከሙ ናቸው። 25 በተገደሉት
መካከል ለኤላምና ለአገልጋዮቻ መኝታን አድርገውላታል፤ መቃብርዋ በዙሪያዋ ነው! ሁሉም ያልተገረዙና በህያዋን ምድር ሸብርን በማምጣታቸው በሰይፍ
የተገደሉ ናቸው! ወደ ጕድጓድም ከሚወርዱ ጋር እፍረታቸውን ተሸክመዋል። ኤላምም በተገደሉትም መካከል ነች። 26 ሞሳሕና ቶቤል ብዛታቸውም ሁሉ በዚያ
አሉ መቃብራቸውም በዙሪያቸው ነው ሁሉም ያልተገረዙ ሲሆኑ በሕያዋን ምድር ሸብር ያመጡ ስለነበር በሰይፍ የተገደሉ ናቸው! 27 በሕያዋንም ምድር ኃያላኑን
ያስፈሩ ነበርና መሣሪያቸውን ይዘው ወደ ሲኦል ከወረዱ፥ ሰይፋቸውንም ከራሳቸው በታች ካደረጉ፥ ካልተገረዙ ኃያላን ጋር አልተኙምን? በህያዋን ምድር አስፈሪ
ተዋጊዎች በመሆናቸው ጋሻቸውም በአጥንታቸው ላይ ነው ። 28 አንቺም ግብጽ ባልተገረዙት መካከል ትሰበሪያለሽ! በሰይፍም ከተገደሉት ጋር ትተኚያለሽ።
29 ኤዶምያስ ከነገሥታቶችዋና ከአለቆችዋ ሁሉጋር በዚያ አሉ። ኃያላን ነበሩ፥ ነገር ግን አሁን በሰይፍ ከተገደሉትና ካልተገረዙት ወደ ጕድጓድ ከሚወርዱ ጋር
ይተኛሉ ። 30 የሰሜን አለቆች ሁሉ ከሙታን ጋር የወረዱ ከሲዶናውያንም በዚያ አሉ! ኃያላን ነበሩ፥ አሁን ግን በዚያ በእፍረት ፥ በሰይፍ ከተገደሉት ጋር ሳይገረዙ
ተኝተዋል። እፍረታቸውን ወደ ጕድጓድም ከሚወርዱት ጋር ይሸከማሉ። 31 ፈርዖንም ይመለከታል በሠይፍ ስለተገደሉት አገልጋዮቹ ይጽናናል ይላል ጌታ
እግዚአብሔር። 32 መፈራቱን በሕያዋን ምድር አድርጌአለሁ፥ ነገር ግን በሰይፍ በተገደሉት ባልተገረዙት መካከል ይተኛል፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር!"

Ezekiel 32:1

እንዲህም ሆነ
እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ የዋለው የታሪኩን አዲስ ክፍል ጅማሬ ለማመልከት ነው። የእናንተ ቋንቋ ይህንን ለማድረግ የሚችልበት መንገድ ካለው እዚህ ስፍራ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ።

በአስራ ሁለተኛው ወር... በወሩ መጀመሪያ
ይህ በዕብራውያን አቆጣጠር አስራ ሁለተኛው እና የመጨረሻው ወር ነው። የመጀመሪያው ቀን በየካቲት መጨረሻ አቅራቢያ ነው። (የዕብራውያን ወራት እና ተከታታይ ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

በአስራ ሁለተኛው ወር
ይህ የሚያመለክተው የንጉሥ ዮአኪንን ግዛት አስራ ሁለተኛ አመት ነው። "በንጉሥ ዮአኪን ስደት አስራ ሁለተኛ አመት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተከታታይ ቁጥሮች እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

የያህዌ ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የተናገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ነናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ/ያህዌ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ከፍ ማድረግ
"መዘመር"

አንተ ልክ እንደ ደቦል አንበሳ ነህ... በባህር ውስጥ እንደሚኖር አውሬ
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እርሱ እንደ አንበሳ ነኝ ብሎ ያስብ ነበር፣ ነገር ግን እርሱ በእርግጥ እንደ አውሬ ብቻ ነበር፣ ወይም 2) እርሱ እንደ አንበሳ እና አውሬ ነበር።

በአገራት መሃል እንደ ደቦል አንበሳ
አንበሶች ከሌሎች እንስሳት ይልቅ ጠንካራ እንደሆኑ፣ ግብጽ ከሌሎች አገራት ይልቅ ጠንካራ ነበረች። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በባህሮች ውስጥ እንዳለ አውሬ
ፈርኦን ሀያል ነበር፣ ነገር ግን እርሱ በውሃ ውስጥ እንዳለ እንደዚህ አውሬ ለሌሎች ችግር ምክንያት ነበር። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አውሬ
አውሬ ትልቅ እና አደገኛ እንስሳ ነው። ይህኛው አዞ ሊሆን ይችላል። ይህ በሕዝቅኤል 29:3 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።

Ezekiel 32:3

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ፣ አውሬ እንደሆነ፣ ምናልባት በውሃ ውስጥ የሚኖር አዞ እንደሆነ አድርጎ መናገሩን ቀጥሏል

ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
ይህ በሕዝቅኤል 5:5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

በብዙ ጉባኤ ፊት በአንተ ላይ ወጥመዴን እዘረጋለሁ
እግዚአብሔር ፈርኦንን የሚቀጣበት መንገድ የተገለጸው ንጉሡ አውሬ ሆኖ በወጥመድ እንደሚያዝ ተደርጎ ነው። "ስለዚህም እኔ ብዙ ህዝብ ሰብስቤ በፊታቸው ወጥመዴን በአንተ ላይ እዘረጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በሜዳ ላይ እተውሃለሁ
"በሜዳ ላይ ያለ ተስፋ እጥልሃለሁ።" በውሃ ውስጥ በነበረበት ጊዜ አስፈሪ እና ሀይለኛ የነበረው አውሬ፤ በደረቅ ምድር ላይ ሲጣል አንዳች ማድረግ አይችልም።

የሰማይ ወፎች ሁሉ
"በሰማይ ላይ የሚበሩ ወፎች በሙሉ"

በምድር ላይ የሚኖሩ እንስሳች ሁሉ ረሃብ አንተን በመብላት ይረካል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የምድር እንስሶች ሁሉ እስኪጠግቡ ድረስ በድንህን እንዲመገቡ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 32:5

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ ፈርኦን መናገሩን እና ፈርኦንን በውሃ ውስጥ ከሚኖረው አውሬ ጋር ማነጻጸሩን ቀጥሏል።

በትል የተሞላው ሬሳህ
ትሎች እርሳህ እንዲበሰብስ ያደርጋሉ። "የበሰበሰው በድንህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የምንጭ ዳርቻዎች በደምህ ይሞላሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ምንጮችን በደምህ እሞላቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 32:7

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ በግብጽ ላይ የሚያደርገውን ለፈርኦን መናገሩን ቀጥሏል።

እኔ አንተን በማጠፋበት ጊዜ
የሰውን ህይወት እንደሚጠፋ ሻማ አድርጎ መናገር የተለመደ ነበር። "እኔ አንተን በምደመስስበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ሰማያትን እከድናለሁ
ያህዌ ሰማያትን ሸፍኖ ከዋክብትን እንደሚያጨልም አድርጎ ይናገራል። "በሰማይ ያለው ነገር ሁሉ እንዲጨልም አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በምድርህ ላይ ጨለማ አመጣለሁ
ጨለማ የተገለጸው አንድ ሰው በሁሉም ነገር ላይ እንደሚዘረጋው ነገር ተደርጎ ነው። "ምድርህን ጨለማ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ራሱን በስሙ የሚገልጸው/የሚምለው፤ የተናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳወቅ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ። "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 32:9

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለፈርኦን መናገሩን ቀጥሏል።

በብዙ ሰዎች ላይ ፍርሃት አመጣለሁ
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚወክለው የሰዎችን ስሜት ነው። "የብዙ ሰዎች ልብ እንዲፈራ/እንዲሸበር አደርጋለሁ" ወይም "ብዙ ሰዎች እንዲፈሩ/እንዲሸበሩ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ በማታውቀው ምድር
ያህዌ ግብጽን የሚያጠፋበት መንገድ፣ ፈርኦን በማያውቃቸው የተለያዩ አገሮች የሚኖሩ ሰዎች ጭምር እንዲፈሩ ያደርጋል።

በአገራት መሃል አንተን የምጥልበት ጊዜ ሲመጣ
በንጉሡ የተመሰለው የግብጽ ህዝብ የተገለጸው እንደሚናድ ህንጻ ተደርጎ ነው። "አገራት እኔ አንተን የጣልኩበትን መንገድ ሲሰሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሰይፌን ሳወዛውዝ
እዚህ ስፍራ ሰይፍ ማወዛወዝ የሚወክለው ሰይፍን መጠቀምን ነው። "ሰይፌን ስጠቀምበት/በሰይፌ ስበቀል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በእያንዳንዱ ቅጽበት ሁሉም በአንተ ምክንያት ይንቀጠቀጣሉ
እዚህ ስፍራ "መንቀጥቀጥ" ሰዎች በጣም በፈሩ ጊዜ የሚሆኑትን ያሳያል። "እያንዳንዳቸው ከፍረሃታቸው የተነሳ መንቀጥቀጣቸው ይቀጥላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

አንተ በምትወድቅበት ቀን
መውደቅ የሚለው ሀሳብ ("መውደቅ") የሚወክለው መሞትን ነው። "እኔ አንተን በማጠፋበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 32:11

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለፈርኦን መናገሩን ቀጥሏል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የባቢሎን ንጉሥ ሰይፍ በአንተ ላይ ይመጣል
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚወክለው ሰራዊትን ነው። "የባቢሎን ሰራዊት ንጉሥ አንተን ያጠቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እያንዳንዱ ተዋጊ ለህዝብ ሽብር ይሆናል
"ሽብር" የሚለው ረቂቅ ስም "አሸባሪ" ወይም "አስፈሪ" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "እያንዳንዱ ተዋጊ ህዝብን ያሸብራል" ወይም "ከእነርሱ እያንዳንዱ ህዝቡ እንዲፈራ ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የግብጽን ኩራት ከንቱ ያደርጋል
"መኩራት" የሚለው ረቂቅ ስም "ኩራት" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "ከእንግዲህ ግብጻውያን እንደይኮሩ ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

አእላፋቶቿን ያጠፋል
እዚህ ስፍራ "ሁሉ" የሚለው ምናልባት የንጉሡን ብዙ ቁጥር ያለውን ወታደር፣ እና ምናልባትም ሌሎች ሰዎችንም ጨምሮ ሊሆን ይችላል። "በግብጽ የሚኖሩ አያሌ ሰዎችን ይገድላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

Ezekiel 32:13

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ መናገሩን ቀጥሏል።

ከብዙ ውኆች አጠገብ
"ብዙ ውሃ በሚገኝበት ስፍራ"

የሰው እግር ውኆችን አያናውጥም
እዚህ ስፍራ እግር ለሰው ሁለንተና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ነው። "ከእንግዲህ ሰዎች በእግራቸው ውኆችን አይበጠብጡም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ውኆችን መበጥበጥ
ንጹሁን ውሃ ማደፍረስ

የከብቶች ኮቴ ይበጠብጣቸዋል
ኮቴ ለከብቶች ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ነው። "ከብቶች በኮቴያቸው ይበጠብጧቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያም ውሃቸውን አጠራለሁ
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ውሃውን የጠራ አደርገዋለሁ" ወይም 2) "ውሃውን ንጹህ አደርጋለሁ።" ማንም ውሃውን በማይበጠብጠው ጊዜ፣ ዝቃጩ ከታች ይቀመጣል፣ ውሃውም ንጹህ ይሆናል"

ወንዛቸው እንደ ዘይት እንዲፈስ አደርጋለሁ
ዘይት በቀስታ እና በእርጋታ ይፈሳል። "ወንዞቹ እንደ ዘይት በቀስታ እንዲፈሱ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 32:15

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ መናገሩን ቀጥሏል።

የግብጽን ምድር የተረሳች/የተተወች በማደርግበት ጊዜ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የግብጽን ምድር ማንም የማይኖርበት በማደርግበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሪቱ ፍሬያማነቷን ባጣች ጊዜ
"አገሪቱ ሀብቷን እንድታጣ ባደረግሁ ጊዜ"

በውስጧ የሚኖሩትን በጠቃሁ ጊዜ
እዚህ ስፍራ ማጥቃት የሚለው ሀሳብ የሚወክለው ማጥፋትን/መደምሰስን ነው። "በውስጧ የሚኖሩትን ሁሉ ባጠፋሁ ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሷ ውስጥ... በእርሷ ላይ
በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ቋንቋ አገራትን እና ምድርን በሴት ጾታ መግለጽ የተለመደ ነበር። "በእርሷ ውስጥ.. በእርሷ ላይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ
ያህዌ እርሱ ያህዌ እንደሆነ ሰዎች ያውቃሉ ሲል፣ የመጨረሻው ከፍተኛ ስልጣን እና ሀይል ያለው እውነተኛው አምላክ እርሱ ብቻ እንደሆነ ማወቅ እንደሚገባቸው እየተናገረ ነው። ይህ በሕዝቅኤል6:7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ብቸኛው እውነተኛ አምላክ እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ" ወይም "እኔ ያህዌ የመጨረሻው ስልጣን እና ሀይል እንዳለኝ እወቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የህዝቦች ሴት ልጅ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "የሌሎች አገራት ሴቶች" ወይም 2) "የሌሎች አገራት ሰዎች"

በግብጽ ላይ፣ በእርሷ አእላፋት/ብዙዎች ላይ
"ስለ ግብጽ፣ ስለ እርሷ አእላፋት/ብዙዎች" ወይም "በግብጽ ላይ ስለሚደርስ ጥፋት፣ በአእላፍቶቿ/በበርካታ ሰዎቿ ላይ ስለሚደርስ ጥፋት"

Ezekiel 32:17

እንዲህም ሆነ
እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ የዋለው የታሪኩን አዲስ ክፍል ጅማሬ ለማመልከት ነው። የእናንተ ቋንቋ ይህንን ለማድረግ የሚችልበት መንገድ ካለው እዚህ ስፍራ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ።

በአስራ ሁለተኛው አመት
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ ባቢሎናውያን እስራኤላውያንን ወደ ባቢሎን በወሰዱ በአስራ ሁለተኛው አመት ሆነ ወይም 2) ይህ ባቢሎናውያን ዮአኪንን ወደ ባቢሎን በወሰዱ በአስራ ሁለተኛው አመት ሆነ። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌ ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የተናገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ነናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ/ያህዌ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ

አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እነርሱን አዋርዳቸው - እርሷ እና የግርማዊ ህዝቦቿን ሴት ልጆቿ
እግዚአብሔር ለህዝቅኤል ይህ ይሆን ዘንድ ትንቢታዊ ትዕዛዝ እየሰጠው ሊሆን ይችላል

የእርሷ
ዳግም፣ የግብጽ ምድር በሴት ተገልጻለች

የግርማዊ ህዝቧቿ ሴት ልጆች
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "የሃያላን ሀገሮች ህዝቦች" ወይም 2) "ሌሎች ሀያልን ሀገሮች"

የታችኛው ምድር
"ከምድር በታች የሚገኝ ስፍራ።" ሰዎች ሲሞቱ፣ ምድር ውስጥ ይቀበራሉ። ስለዚህ "ወደታች ከምድር በታች... አውርዳቸው" ማለት "ገደላቸው" ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ጉድጓድ ከወረዱት ጋር
"ከሌሎች ከሞቱት ከእያንዳንዳቸው እና ወደ አፈር ከገቡት ጋር"

ጉድጓዱ
"ጉድጓዱ" የሚለው የሚያመለክተው መቃብርን ነው፣ ምክንያቱም መቃብር ወደ ሞት ዓለም መግቢያ ተደርጎ ይታሰብ ነበር፣ እንደዚሁም ደግሞ ጉድጓድ ያንን ዓለም ይወክላል። ይህ በሕዝቅኤል 31:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 32:19

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል መናገሩን ቀጥሏል። ስለ ግብጽ ህዝብ በሴት ጾታ ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ በእርግጥ ከሌሎቹ በውበት ትበልጣላችሁን? ታች ወርዳችሁ ካልተገረዙት ጋር ተጋደሙ።
ይህ ጥያቄ ነው ደግሞም ነቢዩ ግብጻውያንን እንዲጠይቅ ያዛል። "ወደ ታች ውረዱ፣ ደግሞም ካልተገረዙት ጋር ተጋደሙ። ሁሉንም እንዲህ ብለህ ጠይቅ፡ ‘እናንተ ከሁሉም ይልቅ የተዋባችሁ ናችሁን?’" (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ታች ውረዱ
ወደ ታች ወደ ሲኦል መውረድ እንዳለባቸው ያመለክታል። "ወደ ታች ወደ ሲኦል ውረዱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ተጋደሙ
በሞት እንደሚሆነው። የእናንተ ቋንቋ ሞተው ለተጋደሙ ሰዎች በህይወት እያሉ ከተጋደሙ ሰዎች የተለየ ቃል ካለው እዚህ ስፍራ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ።

እናንተ በእርግጥ ከሌላው ይልቅ የተዋባችሁ ናችሁን?
ይህ ጥያቄ በእርግጥ ዐረፍተ ነገር ይሰራል። "እናንተ ከማንም ይልቅ ውብ አይደላችሁም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ይወድቃሉ
"ግብጽ እና ህዝቧ ይወድቃሉ"

በሰይፍ የተገደሉ
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚለው የሚወክለው በጦርነት የተዋጓቸውን ጠላቶቻቸውን ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ጠላት በሰይፍ የገደላቸው" ወይም "በጦርነት የሞቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

ሰይፍ ተመዘ ነበር!
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" በሰይፎች ስለሚዋጉ ሰዎች ለጦርነት ሜቶኖሚ/ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ጦርነት ተጀመረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ለሰይፍ ተሰጥታ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ግብጽን ለሰይፍ አሳልፌ ሰጥቻታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሷን እና አእላፋቷን ይይዛሉ
"ጠላቶቿ ግብጽን እና ህዝቧን ይይዛሉ"

ስለ ግብጽ እና ረዳቶቿ
"ስለ ግብጻውያን እና ከእነርሱ ጋር ስለሚተባበሩ"

Ezekiel 32:22

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል በሲኦል ስለሚገኙ ህዝቦች መናገሩን ቀጥሏል። ምክንያቱም ያህዌ ለሕዝቅኤል ለወደፊቱ ጊዜ፣ ወይም ስለአሁን ጊዜ ወይም ስለ መጪው ጊዜ የሚያሳየው ለእነዚህ ቁጥሮች እና ለተከታዮቹ ቁጥሮች ተስማሚ ሊሆን ይችላል።

አሦር ከመላው ጉባኤዋ ጋር በዚያ ናት
የአሦር ምድር በሴት ተገልጻለች። "የአሦር ህዝብ እና መላው ሰራዊቷ በዚያ በሲኦል አሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሷ ጉባኤ
"የእርሷ ሰዎች ሁሉ በአንድነት"

ሁሉም በሰይፍ ተገደሉ
"ሰይፍ" የሚለው ቃል ሰዎችን ለመግደል ሰይፍ ለሚጠቀሙ ወታደሮች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ወታደሮች እነርሱን በሙሉ ለመግደል ሰይፍ ተጠቅመዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

በጉድጓዱ ስርጓድ ተጨመሩ
"ጉድጓዱ" የሚለው የሚያመለክተው መቃብርን ነው፣ ምክንያቱም መቃብር ወደ ሞት ዓለም መግቢያ ተደርጎ ይታሰብ ነበር፣ እንደዚሁም ደግሞ ጉድጓድ ያንን ዓለም ይወክላል። ይህ በሕዝቅኤል 31:18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በሰይፍ የወደቁት፣ የተገደሉት ሁሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በጦርነት የተገደሉ ተላቶች ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

በሰይፍ የወደቁ
እዚህ ስፍራ "መውደቅ" የሚለው ቃል "ሞት" ለሚለው ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት/ ነው። (ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

በህያዋን ምድር ይሸብር የሚያመጡ
"ሸብር" የሚለው ረቂቅ ስም "ፍርሃት" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "በህይወት ባለሁበት ጊዜ ሰዎች እጅግ እንዲፈሩ ምክንያት የነበሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የህያዋን ምድር
ይህ የሚወክለው በህይወት የነበሩተን ሰዎች ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 32:24

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል በሲኦል ስለሚገኙ ህዝቦች መናገሩን ቀጥሏል።

ኤላም በዚህ ናት
እዚህ ስፍራ "ኤላም" የዚያን አገር ሰዎች ያመለክታል። "የኤላም ሰዎችም በዚያ በሲኦል አሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሷ አእላፋት
ሊሰጡ የሚችሉት ትርጉሞች 1) የእርሷ አያሌ ሰዎች ወይም 2) የእርሷ ሰራዊት

መቃብሯ ዙሪያዋን ከቧታል
ይህ በሕዝቅኤል 32:22 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ሁሉም ተገደሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የእርሷ ጠላቶች ሁሉንም ገደሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚያ በሰይፍ የወደቁ
በሕዝቅኤል 32:23 ላይ እንደሚገኘው "በሰይፍ የወደቁ" በሚል ይተርጎም።

በሰይፍ
እዚህ ስፍራ "በሰይፍ" የሚለው ሰዎችን ለመግደል ሰይፍ ለሚጠቀሙ ወታደሮች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "በጦርነት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሳይገረዙ ወደ ታች የወረዱ
"ወደ ታች ሲወርሱ ያልተገረዙ የነበሩ"

ወደ ምድር ታችኛው ክፍል
"በምድር ጥልቅ ታችኛው ስፍራ ማኖር/ማድረግ" ወይም "በምድር ጥልቅ ታች" በሕዝቅኤል 26:20 ላይ የሚገኘው "በምድር ታችኛው ስፍራ" የሚለው እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ሸብር ያመጡ
"ሸብር" የሚለው ረቂቅ ስም "ፍርሃት" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "ሸብር ያመጡ" የሚለው በሕዝቅኤል 32:23 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመለከቱ። "በህይወት በነበሩበት ጊዜ ሰዎች እጅግ እንዲፈሩ ምክንያት የሆኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የህያዋን ምድር
ይህ በህይወት የነበሩ ሰዎችን ያመለክታል። "የህያዋን ምድር" የሚለው በሕዝቅኤል 32:23 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመለከቱ። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የራሳቸውን ሀፍረት የተሸከሙ
ሀፍረት የተገለጸው አንድ ሰው በሄደበት ተሸክሞት እንደሚንቀሳቀስ ነገር ተደርጎ ነው። "ሀፍረት የተሰማቸው" ወይም "አሁን የተዋረዱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ጉድጓዱ
"ጉድጓዱ" የሚለው የሚያመለክተው መቃብርን ነው፣ ምክንያቱም መቃብር ወደ ሞት ዓለም መግቢያ ተደርጎ ይታሰብ ነበር፣ እንደዚሁም ደግሞ ጉድጓድ ያንን ዓለም ይወክላል። ይህ በሕዝቅኤል 32:23 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ለኤላም እና ለአእላፋቷ የሚተኙበት አልጋ አዘጋሁላቸው
ለሙታን በሲኦል የተዘጋጀላቸው ስፍራ የተገለጸው ሙታኑ የሚተኙበት አልጋ እንደተሰጣቸው ተደርጎ ነው። ለኤላም እና ለመላው ሰዎቿ አልጋ አዘጋጅተዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በግድያው መሃል
"በተገደሉት ሰዎች ሁሉ መሃል"

ሁሉም ያልተገረዙ ነበሩ
እስራኤላውያን ያልተገረዙ ሰዎችን አያከብሩም። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰይፍ ተወጉ፣ ምክንያቱም
እዚህ ስፍራ "ተወጉ" የሚለው ቃል "ተገደሉ" ለሚለው ሜቶኖሚ/ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ጠላቶቻቸው በሰይፍ ገደሏቸው ምክንያቱም..." በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ኤላም በተገደሉት ሁሉ መሃል ናት
ይህ ከመጀመሪያው የቁጥሩ ክፍል ጋር በጣም ተመሳሳይ ነው። "የሞቱ ሰዎች በመሃላቸው እንድትጋደም ለኤላም ስፍራ ሰጧት"

Ezekiel 32:26

አያያዥ ሀሳብ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል በሲኦል ስለሚገኙ ሰዎች መናገሩን ቀጥሏል

ሞሳህ...ቶቤል
እነዚህ ስሞች በሕዝቅኤል 27:13 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

በሰይፍ የተገደሉ
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚወክለው ጦርሜዳን ነው። "በጦር ሜዳ የተገደሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሸብራቸውን ወደ ህያዋን ምድር አመጡ
ሰዎች እንዲፈሩ ማድረግ የተገለጸው አንደን አካል ወደ እነርሱ እንደ ማምጣት ድርጊት ተደርጎ ነው። "ሸብር" የሚለው ረቂቅ ስም በግስ መልኩ ሊተረጎም ይችላል። "በህያዋን ምድር የሚገኙትን ሁሉ አሸበሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉም... የህያዋን ምድር
በሕዝቅኤል 32:25 ላይ የሚገኘው "ሁሉም... የህያዋን ምድር" የሚለው እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

በደላቸው በአጥንቶቻቸው ላይ
ምንም እንኳን አንድ ሰው ጋሻዎቻቸው በሞታቸው እንደሚጋርዳቸው ቢያስብም፣ የጦረኞች በደል አካላቸውን ሸፍኗል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ በህያዋን ምድር የጦረኞች ሽብር ነበሩ
"በህይወት ሳሉ፣ ጦረኞችን በጣም ያስፈራሉ"

በህያዋን ምድር
እነዚህ ጦረኞች ይኖሩበት የነበረበት ጊዜ የተገለጸው ስፍራ ተደርጎ ነው። "በህይወት በነበሩበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 32:28

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ መናገሩን ቀጥሏል።

እናንተ... ትሰበራላችሁ
እዚህ ስፍራ "ትሰበራላችሁ" የሚለው የሚወክለው "መደምሰስን" ነው። ይህ በዐድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እኔ እደመስሳችኋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

በ...መሃል
"በ...መካከል

ተወግተው የነበሩ
እዚህ ስፍራ "ተወግተው" የሚለው ቃል "ተገድለው" ለሚለው ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። ይህ በሕዝቅኤል 32:25 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ጠላቶቻቸው የገደሏቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በሰይፍ
ይህ የሚወክለው በጦርነት ውስጥ መሆንን ነው። "በጦር ሜዳ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ኤዶም ከነገሥታቷ እና መሪዎቿ ጋር በዚያ አለች
እዚህ ስፍራ "ኤዶም" የምትወክለው የኤዶምን ሰዎች ነው። "የኤዶም ሰዎች ከነገሥታቶቻቸው እና ከመሪዎቻቸው ጋር በሲኦል ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ጉድጓዱ
"ጉድጓዱ" የሚለው የሚያመለክተው መቃብርን ነው፣ ምክንያቱም መቃብር ወደ ሞት ዓለም መግቢያ ተደርጎ ይታሰብ ነበር፣ እንደዚሁም ደግሞ ጉድጓድ ያንን ዓለም ይወክላል። ይህ በሕዝቅኤል 32:25 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 32:30

የሰሜኑ ልዑላን
"በሰሜን ያለውን ህዝብ የሚገዙ ልዑላን"

በዚያ አሉ
"በሲኦል ናቸው"

ወደ ታች ወረዱ
"ወደ ሲኦል ወረዱ"

ተወግተው ነበር
እዚህ ስፍራ "ተወግተው" የሚለው ቃል "ተገድለው" ለሚለው ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት / ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። ተመሳሳዩ ቃላቶች በህዝቅኤል 32:25 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ጠላቶች በሰይፍ ከገደሏቸው ጋር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በሰይፍ
ይህ የሚወክለው በጦርነት ውስጥ መሆንን ነው። "በጦር ሜዳ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የራሳቸውን ሀፍረት የተሸከሙ
ሀፍረት የተገለጸው አንድ ሰው በሄደበት ተሸክሞት እንደሚንቀሳቀስ ነገር ተደርጎ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 32:25 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሀፍረት የተሰማቸው" ወይም "አሁን የተዋረዱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጉድጓዱ
"ጉድጓዱ" የሚለው የሚያመለክተው መቃብርን ነው፣ ምክንያቱም መቃብር ወደ ሞት ዓለም መግቢያ ተደርጎ ይታሰብ ነበር፣ እንደዚሁም ደግሞ ጉድጓድ ያንን ዓለም ይወክላል። ይህ በሕዝቅኤል 32:29 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

Ezekiel 32:31

ፈርኦን ይመለከታል/ያያል
ይህ ፈርኦንንነ ማንን እንደሚመለከት በመግለጽ ይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል።"ፈርኦን ከሌሎች አገራት የሆኑትን የሞቱ ሰዎች ሁሉ ይመለከታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ አእላፋቶቹ ይጽናናል
ፈርኦን የሚጽናናው የሌሎች ታላላቅ ነገሥታት ሰራዊትም ጭምር በመገበላቸው መሆኑ ተጠቁሟል። "መላው ሰራዊቱ የተገደለበት እርሱ ብቻ ባለመሆኑ ራሱን ያጽናናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰይፍ የተወጉ
በሕዝቅኤል 31:17 ላይ "በሰይፍ የተገደሉ" የሚለው እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

በህያዋን ምድር ማሸበሪያ አደረግሁት
"ፈርኦን ገና በህይወት ሳለ፣ ሰዎችን መሸበሪያ አደረግሁት"

ባላተገረዙት መሃል ይጋደማል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሌሎች ባልተገረዙት መሃል ያጋድሙታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ ሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 33

1 የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፥ **2** "የሰው ልጅ ሆይ፥ ለሕዝብህ ልጆች ተናገር እንዲህም በላቸው፥ 'ሰይፍን በምድር ላይ ባመጣሁ ጊዜ፥ የምድር ሕዝብ ከመካከላቸው ሰውን ወስደው ለራሳቸው ጕበኛ ያድርጉ። **3** ሰይፍ በመጣ ጊዜ ይመልከት ቀንደ መለከቱንም በመንፋት ህዝቡን ያስጠንቅቅ! **4** ህዝቡም የመለከቱን ድምፅ ሰምተው ባይጠነቀቁ ፥ ሰይፍ መጥቶ ቢገድላቸው እያንዳንዱ ሰው ደሙ በራሱ ላይ ይሆናል። **5** አንድ ሰው የመለከቱን ድምፅ ሰምቶ ባይጠነቀቅ ደሙ በራሱ ላይ ይሆናል፤ ነገር ግን ቢጠነቀቅ የራሱን ህይወት ያድናል። **6** ጕበኛው ግን ሰይፍ ሲመጣ ቢያይ መለከቱንም ባይነፋ ሕዝቡንም ባያስጠነቅቅ ሰይፍም መጥቶ አንድን ሰው ቢገድል እሱ በኃጢአቱ ይሞታል፥ደሙን ግን ከጕበኛው እጅ እፈልጋለሁ። **7** አንተም፥ የሰው ልጅ ሆይ፥ ለእስራኤል ቤት ጕበኛ አድርጌሃለሁ፤ ከአፌ ቃሌን ስማ እኔን ወክለህ አስጠንቅቃቸው። **8** ኃጢአተኛውን "ኃጢአተኛ ሆይ፥ በእርግጥ ትሞታለህ!" ባልኩት ጊዜ፥ ኃጢአተኛውን ከመንገዱ እንዲመለስ ለማስጠንቀቅ ባትናገር ያ ኃጢአተኛ በኃጢአቱ ይሞታል፥ ደሙን ግን ከእጅህ እፈልጋለሁ። **9** ነገር ግን ከመንገዱ እንዲመለስ ኃጢአተኛውን ብታስጠነቅቀው እርሱ ግን ከመንገዱ ባይመለስ በኃጢአቱ ይሞታል አንተ ግን ነፍስህን አድነሃል። **10** አንተም፥ የሰው ልጅ ሆይ፥ የእስራኤልን ቤት እንዲህ በላቸው፥ 'እናንተ በደላችንና ኃጢአታችን በላያችን አሉ እኛም ሰልስለንባቸዋል እንዴትስ በሕይወት እንኖራለን? ብላችኋል' ። **11** 'እኔ ሕያው ነኝና ኃጢአተኛው ከመንገዱ ተመልሶ በሕይወት እንዲኖር እንጂ ኃጢአተኛው እንዲሞት አልፈቅድም፥ የእስራኤል ቤት ሆይ ንስሀ ግቡ! ስለ ክፉ መንገዳችሁ ንስሀ ግቡ ለምን ትሞታላችሁ ይላል ጌታ እግዚአብሔር?' በላቸው። **12** አንተም፥ የሰው ልጅ ሆይ፥ ህዝብህን እንዲህ በላቸው፥' ጻድቅ ቢበድል ጽድቁ አያድነውም! ኃጢአተኛም ከኃጢአቱ ቢመለስ በኃጢአቱ አይጠፋም። ጻድቁም ኃጢአት ቢስራ በጽድቁ በሕይወት ሊኖር አይችልም። **13** እኔ ጻድቁን፥ "በእርግጥ በሕይወት ይኖራል!" ባልሁ ጊዜ፥ እርሱ በጽድቁ ታምኖ ኃጢአት ቢሠራ በሠራው ኃጢአት ይሞታል እንጂ ጽድቁ አላስብለትም። **14** እኔም ኃጢአተኛውን። በእርግጥ ትሞታለህ ባልሁ ጊዜ፥ እርሱ ከኃጢአቱ ተመልሶ ፍርድንና ቅን ነገርን ቢያደርግ፥ **15** ኃጢአተኛውም የብድር መያዣን ቢመልስ የነጠቀውንም ቢመልስ ሕይወት በሚሰጡ ትእዛዛት ቢራመድ ከዚያም በኋላ ኃጢአት ባይሠራ፥ በእርግጥም በሕይወት ይኖራል እንጂ አይሞትም። **16** የሠራው ኃጢአት ሁሉ አይታሰብበትም። ፍርድንና ቅን ነገርን አድርጎአል በእርግጥ በሕይወት ይኖራል። **17** ነገር ግን ሕዝብህ ፥ "የጌታ መንገድ የቀና አይደለም!" ይላሉ ነገር ግን ቅን ያልሆነው የእናንተ መንገድ ነው! **18** ጻድቅ ከጽድቁ ተመልሶ ኃጢአትን ቢሠራ በኃጢአቱ ይሞታል! **19** ኃጢአተኛውም ከኃጢአቱ ተመልሶ ፍርድንና ቅን ነገርን ቢያደርግ ባደረጋቸው ነገሮች ምክንያት በሕይወት ይኖራል። **20** እናንተ ግን፥ "የጌታ መንገድ የቀና አይደለም!" ትላላችሁ። የእስራኤል ቤት ሆይ፥ በእያንዳንዳችሁ ላይ እንደ መንገዳችሁ እፈርድባችኋለሁ። **21** እንዲህም ሆነ በተማረክን በአሥራ ሁለተኛው ዓመት በአሥረኛው ወር ከወሩም በአምስተኛው ቀን ከኢየሩሳሌም ያመለጠ አንድ ሰው ወደ እኔ መጥቶ "ከተማይቱ ተያዘች!"አለኝ። **22** ሰውዬው ከመምጣቱ በፊት ባለው ምሽት የእግዚአብሔር እጅ በእኔ ላይ ነበረች፥ ሰውዬው በምሽት ወደ እኔ በመጣ ጊዜ አፌ ተከፍቶ ነበር። ስለዚህም አፌ ተከፍቶ ነበር ከዚያም በኋላ እኔ ዲዳ አልሆንሁም። **23** የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ። **24** የሰው ልጅ ሆይ፥ በእስራኤል ምድር ባሉ በባድማ ስፍራዎች የተቀመጡ፥ 'አብርሃም ብቻውን ሳለ ምድሪቱን ወረሰ እኛም ብዙዎች ነን ምድሪቱም ርስት ሆና ለእኛ ተሰጥታለች' ይላሉ። **25** ስለዚህ እንዲህ በላቸው፥'ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ከደም ጋር ትበላላችሁ፥ ዓይናችሁንም ወደ ጣዖቶቻችሁ ታነሣላችሁ፥ የስዎችንም ደም ታፈስሳላችሁ። በውኑ ምድሪቱን ትወርሳላችሁን? **26** በሰይፋችሁ ተማምናችሁ፥ ርኩስ ነገርን ታደርጋላችሁ፥ የባልንጀሮቻችሁንም ሚስቶች ታስነውራላችሁ። በውኑ ምድሪቱን ትወርሳላችሁን? **27** እንዲህም በላቸው፥ 'ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እኔ ሕያው ነኝና በባድማ ስፍራዎች ያሉ በሰይፍ ይወድቃሉ፥ በምድረ በዳ ያለውን ለአራዊት መብል አድርጌ እሰጣለሁ፥ በአምባዎችና በዋሾች ያሉ በቸነፈር ይሞታሉ። **28** ምድሪቱንም ባድማና ውድማ አደርጋታለሁ በኃይሏም መመካቷ ይቀራል፥ የእስራኤልም ተራሮች ማንም የማያልፍባቸው በረሀ ይሆናሉ፥ ። **29** ስላደረጉትም ርኩሰት ሁሉ ምድሪቱን ባድማና ውድማ ባደርግሁ ጊዜ፥ እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ። **30** አንተም፥ የሰው ልጅ ሆይ፥ ሕዝብህ በቅጥር አጠገብና በቤት ደጆች ውስጥ ስለ አንተ ይናገራሉ፥ እርስ በርሳቸውም፥ አንዱ ከአንዱ ጋር፥ 'ወደ ነቢዩ እንሂድና እግዚአብሔር ያለው ቃል ምን እንደ ሆነ እንስማ!' እያሉ ይነጋገራሉ። **31** ስለዚህ ሕዝቤ ብዙ ጊዜ እንደሚያደርጉት መጥተው በፊትህ ይቀመጣና ቃልህንም ይሰማሉ ነገር ግን አያደርጉትም። ትክክለኛው ቃል በፍቸው ነው ፥ ልባቸው ግን ቅንነት የሌለበትን ትርፍ ትከተላለች። **32** እነሆ፥ አንተ መልካም ድምፅ እንዳለው እንደሚወደድ መዝሙር ማለፊያም አድርጎ እንደሚጫወቱት በገና ሆነህላቸዋል ስለዚህም ቃልህን ይሰማሉ ነገር ግን አንዳቸውም አያደርጉትም። **33** እነሆ፥ ይህ ይመጣል በመጣም ጊዜ እነርሱ ነቢይ በመካከላቸው እንደ ነበረ ያውቃሉ።"

Ezekiel 33:1

የያህዌ ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የተናገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ነናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ/ያህዌ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

በማናቸውም ምድር ሰይፍ ይሆናል
"ሰይፍ" የሚለው ቃል ጥቃት የሚያደርስን የጠላት ሰራዊት ያመለክታል። እንደዚሁም ደግሞ "ምድር" በዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታል። "የማናቸውንም ምድር ሰዎች የሚያጠቃ ሰራዊት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱን ጠባቂ/ጉበኛ ማድረግ
"እርሱን እንደ ዘብ መሾም" ወይም "እርሱን ጠባቂ/ጉበኛ ማድረግ"

ሰይፍ ይመለከታል
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የጠላትን ሰራዊት ይወክላል። "የጠላትን ሰራዊት ያያል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ትኩረት አትስጡ
"ማጠንቀቂያውን ቸል በሉ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የእያንዳንዱ ደም በገዛ ራሱ ላይ ነው
እዚህ ስፍራ "ደም" ሞትን ይወክላል። "በገዛ ራሱ ላይ" የሚለው ሀረግ ያ ሰው ተጠያቂ ይሆናል ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ቢሞቱ ተጠያቂነቱ የራሳቸው ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Ezekiel 33:5

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለእስራኤላውያን በሕዝቅኤል በኩል መልዕክቱን መስጠቱን ቀጥሏል

ደሙ በእርሱ ላይ ነው
እዚህ ስፍራ "ደም" የአንድን ሰው ሞት ይወክላል። "በእርሱ ላይ" የሚለው ሀረግ ሰውየው ሃላፊነቱን ይወስዳል ለሚለው ፈሊጥ ነው። "ቢሞት የራሱ ጥፋት ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

የገዛ ህይወቱን ያተርፋል
"ራሱን ከሞት ይጠብቃል"

ሰይፍ በሚመጣበት ጊዜ
"ሰይፍ" የሚለው ቃል የጠላትን ሰራዊት ያመለክታል። "የጠላት ሰራዊት እየመጣ ሳለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሰዎች ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ባለመደረጉ ምክንያት
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ደግሞም እርሱ ሰዎችን አላስጠነቀቀም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰይፍ መጣ ደግሞም ሳይመርጥ ህይወት ቀጠፈ
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የጠላትን ሰራዊት ይወክላል። "የጠላት ሰራዊት መጥቶ ሁሉንም ገደለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ያ ሰው በራሱ ኃጢአት ይሞታል
"ያ ሰው በራሱ ኃጢአት ምክንያት ይሞታል"

የእርሱን ደም ከጠባቂው/ጉበኛው እፈልጋለሁ
እዚህ ስፍራ "ደም" የአንድን ሰው ሞት ይወክላል። "ደሙን ከእርሱ እፈልጋለሁ" የሚለው ሀረግ የአንድን ሰው ሀላፊነት የሚመለከት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "የዚያን ሰው ሞት የጉበኛው ጥፋት አድርጌ እውደዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Ezekiel 33:7

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል መናገሩን ቀጥሏል።

የእስራኤል ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው የሚወክለው ሰዎችን ነው። "የእስራኤል ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ከአፌ ቃሎቹን ትሰማለህ፣ ደግሞም በእኔ ምትክ ሆነህ ታስጠነቅቃቸዋለህ
እዚህ ስፍረ "አፍ" የሚለው የሚወክለው ያህዌ የተናገረውን ነገር ነው። "እኔ የምናገረውን መልዕክት አንተ ትሰማለህ፣ ከዚያም በእኔ ምትክ ሆነህ እነርን ታስጠነቅቃቸዋለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በእኔ ምትክ ሆነህ አስጠንቅቃቸው
"የእኔ ተወካይ ሆነህ አስጠንቅቃቸው" ወይም "የእኔን ማስጠንቀቂያ ስጣቸው"

ይህንን አታውጅ
"ይህንን አትናገር"

ስለ እርሱ መንገድ
"እርሱ የሚያደርግበት መንገድ" ወይም "እርሱ የሚያደርጋቸው ነገሮች" በሕዝቅኤል 7:3 ላይ "የአንተ መንገዶች" የሚለው እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ደሙን ከእጅህ እፈልጋለሁ
እዚህ ስፍራ "ደም" የሚወክለው የአንድን ሰው ሞት ነው። "ከእጅህ... እፈልጋለሁ" የሚለው ሀረግ አንድ ሰው ሀላፊነት አድርጎ መውሰድን/ መጠየቅን የሚገልጽ ፈሊጥ ነው። "አንተን ለእርሱ ሞት ተጠያቂ አድርጌ እወስዳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

እርሱ ምናልባት ከዚያ ይላል፣ ከመንገዱ ሳይመለስ ቢቀር
በተለመደ መንገድ ያደርገው የነበረውን ማድረግ ያቆመ አንድ ሰው የተገለጸው በአካል ዞሮ ወደ ኋላ መሄድ እንደጀመረ ተደርጎ ነው። "ክፉ ነገሮችን ማድረግን ሊያቆም ይችላል፣ እናም ክፉ ነገሮችን ማድረግ ባያቆም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የራስህን ህይወት ታድናለህ
"ራስህን በህይወት ትጠብቃለህ"

Ezekiel 33:10

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለእስራኤላውያን በሕዝቅኤል በኩል መልዕክቱን መስጠቱን ቀጥሏል

የእስራኤል ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው የሚወክለው ሰዎችን ነው። "የእስራኤል ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ይህን ትናገራለህ
"አንተ የተናገርከው ይህ ነው"

መተላለፋችን እና ኃጢአታችን በላያችን ነው
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "በእኛ ላይ" የሚለው ስለ መተላለፋቸው እና ኃጢአታቸው በደለኛነት ተሰምቷቸዋል የሚል ትርጉም የያዘ ዘይቤ ነው ወይም 2) "በእኛ ላይ" የሚለው ስለ መተላለፋቸው እና ኃጢአታቸው ያህዌ እንደሚቀጣቸው ተረድተዋል የሚል ትርጉም የያዘ ዘይቤ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእነርሱ ዘንድ ሸታችን እየተበላሸ ነው
"በእነርሱ ምክንያት የእኛ ሸታ እየተበላሸ እየሄደ ነው።" በኃጢአት ምክንያት መጥፋት የተገለጸው የሰው ስጋ አየበሰበሰ እንደሆነ ተደርጎ ነው። "እነርሱ እያጠፉን ነው" ወይም "እየገደሉን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእነርሱ ዘንድ
"በእነርሱ ምክንያት"

እንዴት በህይወት መኖር እንችላለን?
ሰዎቹ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቁት የመኖር ተስፋ እንደሌላቸው ትኩረት ሰጥተው ለመናገር ነው። "አንዳች የመኖር ተስፋ የለንም።" ወይም

"በእርግጥ እንሞታለን።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በህያውነቴ እምላለሁ
"እኔ በእርግጥ ህያው እንደሆንኩ።" ያህዌ ይህንን አገላለጽ የሚጠቀመው ቀጥሎ የሚናገረው በእርግጥም እውነት መሆኑን ለማሳየት ነው። ይህ የጸና ቃል ኪዳን የመግባት ምልክት ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።" በህያውነት እምላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ራሱን በስሙ የሚገልጸው/የሚምለው፤ የተናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳወቅ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ። "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ከበደለኛው ሰው ሞት ምክንያት ደስ አልሰኝም
"ሞት" የሚለው ረቂቅ ስም "ሞተ" ተብሎ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "በደለኛው" የሚለው ስማዊ ቅጽል "በደለኛ ሰዎች" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "በደለኛ ሰዎች በመሞታቸው እኔ ደስ አልሰኝም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ስማዊ ቅጽሎች የሚሉትን ይመልከቱ)

ክፉ ሰው በንስሃ ከመንገዱ ቢመለስ
እዚህ ስፍራ "መንገድ" የሚለው የሚወክለው አንድ ሰው የሚያደርገውን ነገር የሚያደርገው እንዴት እንደሆነ ነው። "በደለኛው ክፉ ነገሮችን ማድረጉን ቢተው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ቤት ሆይ፣ ስለምን ትሞታላችሁ?
ያህዌ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው የእስራኤል ሰዎች እንዲሞት እንደማይፈልግ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። "የእስራኤል ቤት ሆይ፣ ሞትን አትምረጡ!" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 33:12

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለእስራኤላውያን በሕዝቅኤል በኩል መልዕክቱን መስጠቱን ቀጥሏል

ጻድቁ ሰው ኃጢአት ቢሰራ የቀደመው ጽድቁ አያድነውም!
"ጽድቅ" የሚለው ረቂቅ ስም "ትክክለኛ" በሚለው ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። ከእግዚአብሔር ቅጣት እንደማይተረፉ ተጠቁሟል። "ጻድቃን ሰዎች ኃጢአት ማድረግ ቢጀምሩ፣ አስቀድሞ የሰሩት ትክክለኛ ነገር እነርን ከመቅጣት አያቆመኝም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

የክፉ ሰው የቀደመ ክፋት እንዲጠፋ አያደርገውም
"ክፋት" የሚለው ረቂቅ ስም "ክፉ" በሚለው ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። "ክፉ ያሆነ ነገር ያደረገ ሰው በቀደመው ክፋቱ አይጠፋም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ጽድቁ ቢመለስ/ቢዞር
ሰውየው ያንን የሚያስበው አስቀድሞ ትክክለኛ ስለነበረ ነው፤ ቢበድል እንኳን ያህዌ እርሱን አያጠፋውም። "ጽድቅ" የሚለው ረቂቅ ስም "ትክክለኛ" በሚል ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። "አስቀድሞ በሰራቸው ትክክለኛ ነገሮች ላይ ቢጸና" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ኢፍትሃዊ ነገሮችን ቢያደርግ
"ክፉ የሆነውን ቢያደርግ" ወይም "ክፉ ነገሮችን ቢያደርግ"

እኔ አላስበውም
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ስለዚያ ነገር አላስብም" ወይም "አላስታውስበትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 33:14

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለእስራኤላውያን በሕዝቅኤል በኩል መልዕክቱን መስጠቱን ቀጥሏል

ለክፉዎች
"ክፉዎች" የሚለው ስማዊ ቅጽል "ክፉ ሰው" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "ለክፉ ሰው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)

ለብድር መያዣ የያዘውን ቢመልስ
"የብድር መያዣውን መልሶ ቢሰጥ"

የብድር መያዣ
አንድ ሰው ለሌላው ሰው የተበደረውን እንደሚመልለት ለማረጋገጥ አበዳሪው ዘንድ የሚተወው አንዳንድ ነገር

ለሰረቀው የሚያቀርበው ካሳ
"የሰረቀውን መመለስ" ወይም "ለሰረቀው ዋጋውን መልሶ መክፈል"

ህይወት በሚሰጥ ደረጃ መራመድ
በአንድ ሁኔታ ማድረግ ወይም ማከናወን መራመድ እንደሆነ ተደርጎ ተገልጽዋል። "ህይወት በሚሰጡ ህጎች መሰረት መኖር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 33:17

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለእስራኤላውያን በሕዝቅኤል በኩል መልዕክቱን መስጠቱን ቀጥሏል

የአንተ ህዝብ
እነዚህ የእስራኤል ሰዎች ናቸው። "የአንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሕዝቅኤልን ነው።

የጌታ መንገድ... ተገቢ ያልሆኑ የእናንተ መንገዶች
ባህሪያት ወይም ድርጊቶች የተገለጹት አንድ ሰው የሚሄድበት መንገድ ወይም ጎዳና እንደሆኑ ተደርጎ ነው። "ይህ ጌታ ያደረገው... እናንተ ያደረጋችሁት ተገቢ ያልሆኑ ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን እነዚህ የእናንተ መንገዶች ናቸው
"የእናንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእስራኤልን ሰዎች ነው። ይህ በሶስተኛ መደብ ሊገለጽ ይችላል። "ነገር ግን ይህ የእነርሱ መንገድ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ከጽድቁ ቢመለስ
ከዚያ በኋላ አንድ ነገር አለማድረግ የተገለጸው በአካል ከአንድ ነገር ዞሮ እንደ መመለስ ተደርጎ ነው። "ትክክለኛ የሆነውን ነገር ማድረግ ማቆም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በዚያው ውስጥ ሆኖ መሞት
"በኃጢአቱ ምክንያት መሞት"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከክፉ ስራው ቢመለስ
ከዚያ በኋላ አንድ ነገር አለማድረግ የተገለጸው በአካል ከአንድ ነገር ዞሮ እንደ መመለስ ተደርጎ ነው። "ትክክለኛ የሆነውን ነገር ማድረግ ማቆም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእነዚያ ነገሮች ምክንያት
"ፍትሃዊ እና ትክክለኛ ነገር በማድረጉ ምክንያት"

የአንተ ህዝብ/ህዝብህ
እነዚህ የእስራኤል ሰዎች ናቸው

የእስራኤል ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው የሚወክለው ሰዎችን ነው። "የእሰስራኤል ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 33:21

እንዲህም ሆነ
እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ የዋለው የታሪኩን አዲስ ክፍል ጅማሬ ለማመልከት ነው። የእናንተ ቋንቋ ይህን ለማድረግ የሚችልበት መንገድ ካለው እዚህ ስፍራ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ።

አስራ ሁለተኛው አመት... አምስተኛው ቀን... አስረኛው ወር
12ኛ አመት... 5ተኛ ቀን... 10ኛ ወር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተከታታይ ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በአስረኛው ወር በአምስተኛው ቀን
ይህ በዕብራውያን አቆጣጠር አስረኛው ወር ነው። አምስተኛው ቀን በምዕራባውያን ዘመን አቆጠጠር ጥር መጀመሪያ አካባቢ ነው። (የዕብራውያን ወራት እና ተከታታይ ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

የእኛ ምርኮኛ
እዚህ ስፍራ "እኛ ራሳችን" የሚለው የሚያመለክተው በባቢሎናውያን ንጉሥ ዮአኪን ኢየሩሳሌምን ለቆ እንዲወጣ ካደረጉት ጊዜ አንስቶ በባቢሎን የነበሩትን ሕዝቅኤልን እና እስራኤላውያንን ነው። "እኛ ምርኮኛ ከሆንን በኋላ" ወይም "ባቢሎናውያን እኛን ወደ ምርኮ ከወሰዱን በኋላ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አካታች ያልሆነ እና የሆነ "እኛ" እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከኢየሩሳሌም ያመለጠ ሰው ወደ እኔ መጣ
"ከኢየሩሳሌም ያመለጠ አንድ ሰው ወደ እኔ መጣ" ባቢሎናውያን ኢየሩሳሌምን ደምስሰው ህዝቧን ሲገድሉ ጥቂት ሰዎች ብቻ አመለጡ።

ከተማይቱ ተያዘች
"ከተማይቱ" የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው "ኢየሩሳሌምን" ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ባቢሎናውያን ኢየሩሳሌምን ደመሰሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌ እጅ በእኔ ላይ ነበረች
x

Ezekiel 33:23

የያህዌ ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የተናገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ነናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ/ያህዌ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚያ ፍርስራሾች
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "እነዚያ የግንብ ፍርስራሾች" 2) "እነዚያ የፈራረሱ ከተሞች"

እርሱ ምድሪቱን ወረሰ
ያህዌ ምድሪቱን ለአብርሃም መስጠቱ የተገለጸው አብርሃም ምድሪቱን እንደ ወረሰ ተደርጎ ነው። "ያህዌ ምድሪቱን ለእርሱ ሰጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሪቱ
"የእስራኤል ምድር"

ምድረቱ ለእኛ ተሰጥታ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ያህዌ ምድሪቱን ለእኛ ሰጠን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ርስት አድርጎ
"ርስት" የሚለው ረቂቅ ስም "መውረስ" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "ስለዚህም እኛ እርሷን መውረስ እንችል ዘንድ" (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 33:25

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ በእስራኤል ፍርስራሽ ላይ ስለሚኖሩ ሰዎች ለሕዝቅኤል መናገሩን ቀጥሏል።

እናንተ ደም በላችሁ
በውስጡ ደም ያለበትን/ ደሙ ገና ከውስጡ ያልወጣን ስጋ መብላታቸው ተጠቅሷል። ያህዌ በስጋ ውስጥ ያለ ደም ተንጠፍጥፎ እንዲወጣ አዟቸው ነበር። "በውስጡ ደም ያለበትን ስጋ በላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ዐይኖቻችሁን ወደ ጣኦቶቻችሁ አነሳችሁ
"ወደ ጣኦቶቻችሁ ተመለከታችሁ" ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ጣኦቶቻችሁን አመለካችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰዎችን ደም አፈሰሳችሁ
እዚህ ስፍራ "ደም" የሚወክለው የሰውን ህይወት ነው። ደም ማፍሰስ መግደል ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ሰዎችን ገደላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

በእርግጥ ምድሪቱን መውረስ ይገባችኋልን?
ያህዌ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት ህዝቡን ለመገሰጽ ነው። "ይህንን ምድር መውረስ አይገባችሁም!" ወይም "ይህ ምድር አይገባችሁም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰይፎቻችሁ ተማምናችኋል
እዚህ ስፍራ "ሰይፎች" የሚያመለክተው የጥቃት ተግባር መፈጸምን ነው። "የምትፈልጉትን ለማግኘት በሰይፎቻችሁ የጥቃት ተግባር ፈጽማችኋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አስጸያፊ ተግባር ፈጽማችኋል
"እኔ በጣም የምጠላውን ተግባር አድርጋችኋል"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እያንዳንዱ ወንድ የጎረቢቱን ሚስት አርክሷል
የጎረቢቶቻቸውን ሚስቶች አብረው በመተኛት ማርከሳቸው ተጠቁሟል። "እያንዳንዱ ወንድ ከጎረቢቱ ሚስት ጋር ተኝቷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 33:27

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ በእስራኤል ፍርስራሽ ላይ ስለሚኖሩ ሰዎች ለሕዝቅኤል መናገሩን ቀጥሏል።

በህያውነቴ
"እኔ ህያው እንደሆንኩ።" ያህዌ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው ቀጥሎ የሚናገረው በእርግጥ እውነት መሆኑን ለማሳየት ነው። ይህ የከበረ ቃል መግቢያ መንገድ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "በክብሬ እምላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በፍርስራሹ የቀሩት በቀስት ይወድቃሉ
"በቀስት ይወድቃሉ" የሚለው ሀረግ ፈሊጣዊ ነው። "ጠላት በፍርስራሽ ውስጥ የቀሩትን ይገድላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በምሽጎች እና በዋሻዎች ውስጥ የተደበቁት በመቅሰፍት ይሞታሉ
"መቅሰፍት በምሽጎች እና በዋሻዎች ውስጥ የሚኖሩትን ይገድላቸዋል"

ምሽጎች
ምሽግ ሰዎች ራሳቸውን ከሚያጠቋቸው ጠላቶች ለመጠበቅ የሚገነቡት ግንብ ነው

ዋሻዎች
ዋሻዎች በተራራ አተገብ/ጎን ወይም ከምድር በታች ሚገኙ የተፈጥሮ አዳራሾች/ቤቶች ናቸው። ብዙውን ጊዜ ከአለት የተሰሩ ናቸው።

እርሷ ኩራቷ ያበቃል
"እርሷ" የሚለው ቃል ምድሪቱን ያመለክታል፣ ይህም የምድሪቱን ነዋሪዎች የሚያመለክት ነው። "የምድሪቱ ሰዎች ከእንግዲህ ጠንካራ ነን ብለው የሚኮሩበት ነገር አይኖርም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ተራሮች ይደመሰሳሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ከእንግዲህ በእስራኤል ተራሮች ማንም አይኖርም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በእነርሱ በኩል የሚያልፍ አይኖርም
"በምድሪቱ ወይም በተራሮቿ ላይ አቋርጦ የሚጎዝ አይኖርም"

እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ
ያህዌ እርሱ ያህዌ እንደሆነ ሰዎች ያውቃሉ ሲል፣ የመጨረሻው ከፍተኛ ስልጣን እና ሀይል ያለው እውነተኛው አምላክ እርሱ ብቻ እንደሆነ ማወቅ እንደሚገባቸው እየተናገረ ነው። ይህ በሕዝቅኤል6፡7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ብቸኛው እውነተኛ አምላክ እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ" ወይም "እኔ ያህዌ የመጨረሻው ስልጣን እና ሀይል እንዳለኝ እወቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የፈጸሙት ከፍተኛ ጥላቻ ሁሉ
"ጥላቻ" የሚለው ረቂቅ ስም "የምጠላቸው ነገሮች" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "እነርሱ ያደረጓቸው እኔ የምጠላቸው ነገሮች በሙሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ አድርገዋቸዋል
"ሰዎቹ አድርገዋቸዋል/ፈጽመዋቸዋል"

Ezekiel 33:30

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል መናገሩን ቀጥሏል።

ከያህዌ ዘንድ የወጣ
"ይናገር ዘንድ ያህዌ ለእርሱ የሰጠው" ወይም "ያህዌ ለእርሱ የሰጠው"

ትክክለኛ ቃላት በአፋቸው አለ፣ ነገር ግን ልባቸው ፍትሃዊ ያልሆነ ጥቅምን ይከተላል
እዚህ ስፍራ "አፎች" የሚለው የሚወክለው ንግግርን ነው። ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "እነርሱ እኔን ስለ መውደዳቸው ይናገራሉ፣ ልባቸው ግን ፍትሃዊ ያልሆነ ጥቅምን ይከተላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ልባቸው ፍትሃዊ/ተገቢ ያልሆነ ጥቅምን ይከተላል
እዚህ ስፍራ "ልቦች" የሚለው የሚወክለው ፍላጎትን ነው። "በልቦቻቸው ትክክለኛ ያልሆነ ጥቅምን ለማግኘት ይፈልጋሉ" ወይም "ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ ነገሮችን ለማግኘት ይፈልጋሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 33:32

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ እስራኤል ሰዎች መናገሩን ቀጥሏል።

አንተ ለእነርሱ ደስ እንደሚያሰኝ መዝሙር ሆነህላቸዋል
እዚህ ስፍራ "አንተ" የሚለው የሚያመለክተው ሕዝቅኤልን ሲሆን፣ እርሱ ደግሞ የተናገረውን መልዕክት ይወክላል። ይህ የሕዝቅኤልን መልዕክት ደስ ከለሚያሰኝ ዝማሬ ጋር ያነጻጽራል፤ ይህም ማለት ሰዎች እርሱን መስማት ያስደስታቸዋል፣ ነገር ግን መልዕክቱን ለመታዘዝ ስፍራ አይሰጡም። "ቃሎችህ ደስ የሚያሰኝ ዝማሬ እንደሆነ አድርገው ያስባሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ደስ የሚያሰኝ ዝማሬ
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ውብ ዝማሬ" ወይም 2) "የፍቅር ዝማሬ" ወይም "ስለ ፍቅር የተዘመረ"

በክር የሙዚቃ ማሳሪያ በሚገባ የተጫወቱት
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንድ ሰው በክር የሙዚቃ መሳሪያ በሚገባ የተጫወተው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የክር ሙዚቃ መሳሪያ
ሰዎች ሙዚቃ ለመጫወት የሚጠቀሙበት የክር ሙዚቃ መሳሪያ

ይህ ሁሉ በሚሆንበት ጊዜ
"ይህ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔር የተናገራቸው ነገሮች ሁሉ እንደሚፈጸሙ እና ሕዝቅኤል ስለ ነገሩ ለህዝቡ እንደተናገረ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እነሆ!
እዚህ ስፍራ "እነሆ!" የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚሆነው ነገር ትኩረት ይሰጣል። "በእርግጥ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

በመሃላቸው ነቢይ እንዳለ
"እኔ አንተን ወደ እነርሱ በእርግጥ ነቢይ አድርጌ እንደ ላክሁህ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 34

1 የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፥ 2 "የሰው ልጅ ሆይ፥ በእስራኤል እረኞች ላይ ትንቢት ተናገር፥ እረኞችንም እንዲህ በላቸው፥ 'ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ራሳቸውን ለሚያሰማሩ ለእስራኤል እረኞች ወዮላቸው! እረኞች በጎችን ያሰማሩ ዘንድ አይገባቸውምን? 3 ጮማውን ትበላላችሁ ጠጕሩንም ትለብሳላችሁ! ከመንጋው መካከል የወፈሩትን ታርዳላችሁ! በጎቼን ግን ፈጽሞ አታሰማሩም። 4 የደከመውን አላጸናችሁትም የታመመውንም አላከማችሁትም የተሰበረውንም አልጠገናችሁትም የባዘነውንም አልመለሳችሁትም የጠፋውንም አልፈለጋችሁትም በኃይልና በጭቈናም ገዛችኋቸው። 5 ያለ እረኛም በማጣት ተበተኑ፥ ከተበተኑም በኋላ ለምድር አራዊት ሁሉ መብል ሆኑ። 6 በጎቼ በተራሮች ሁሉና በረዘሙ ኮረብቶች ሁሉ ላይ ተቅበዝብዘዋል፥ በምድርም ፊት ሁሉ ላይ ተበትነዋል። የሚፈልጋቸውም የለም። 7 ስለዚህ፥ እረኞች ሆይ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ 8 ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እኔ ሕያው ነኝና እረኛ ስለሌለ እረኞቼም በጎቼን ስላልፈለጉ እረኞችም ራሳቸውን እንጂ በጎቼን ስላላሰማሩ፥ በጎቼ ንጥቂያና፥ ለምድር አራዊት ሁሉ መብል ሆነዋልና 9 ስለዚህ፥ እረኞች ሆይ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ 10 ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እነሆ፥ በእረኞች ላይ ነኝ፥ በጎቼንም ከእጃቸው እፈልጋለሁ፥ በጎቼንም ከማሰማራት አስተዋቸዋለሁ። ከዚያም ወዲያ እረኞች ራሳቸውን አያሰማሩም በጎቼንም ከአፋቸው አድናለሁ፥ መብልም አይሆኑላቸውም። 11 ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና። እነሆ፥ እኔ ራሴ በጎቼን እሻለሁ አሰማራቸውማለሁ። 12 እረኛ በተበተኑት በጎች መካከል ባለ ጊዜ መንጋውን እንደሚፈልግ፥ እንዲሁ በጎቼን እፈልጋለሁ በደመናና በጨለማ ቀን ከተበተኑት ስፍራ ሁሉ አድናቸዋለሁ። 13 ከአሕዛብም መካከል አወጣቸዋለሁ ከአገሮችም እሰበስባቸዋለሁ፥ ወደ ገዛ አገራቸውም እሰበስባቸዋለሁ። በእስራኤልም ተራሮች ላይ በፈሳሾችም አጠገብ በምድርም ላይ ሰዎች በሚኖሩበት ስፍራ ሁሉ አሰማራቸዋለሁ። 14 በመልካም ማሰማርያ እሰማራቸዋለሁ የእስራኤል ረጃጅም ተራሮች የግጦሽ ቦታቸው ይሆናል። በዚያ በለመለመ መስክ በመልካምም የግጦሽ ሥፍራ ያርፋሉ፥ በእስራኤልም ተራሮች ላይ ይግጣሉ። 15 እኔ ራሴ በጎቼን አሰማራለሁ አስመስጋቸውማለሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፦ 16 የጠፋውንም እፈልጋለሁ የባዘነውንም እመልሳለሁ የተሰበረውንም እጠግናለሁ የደከመውንም አጸናለሁ የወፈረውንና የበረታውንም አጠፋለሁ! በመልካም አሰማራለሁ። 17 ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እናንተም መንጋዬ ሆይ፥ እነሆ፥ በበግና በበግ መካከል፥ በአውራ በግና በአውራ ፍየልም መካከል፥ እፈርዳለሁ። 18 የቀረውን ማሰማርያችሁን በእግራችሁ የረገጣችሁት፥ በመልካሙ ማሰማርያ መሰማራታችሁ አልበቃ ብሏችሁ ነው? የቀረውንስ ውኃ በእግራችሁ ያደፈረሳችሁት፥ ጥሩውን ውኃ መጠጣታችሁ አልበቃ ብሏችሁ ነው? 19 በጎቼም በእግራችሁ በረገጣችሁት ይሰማራሉ በእግራችሁም ያደፈረሳችሁትን ይጠጣሉ። 20 ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላቸዋል፥ እነሆ፥ እኔ በወፈሩት በጎችና በከሱት በጎች መካከል እፈርዳለሁ። 21 ይህም እስክትበትኑአቸው ድረስ በእንቢያና በትከሻ ስለምትገፉአቸው የደከሙትንም ሁሉ በቀንዳችሁ ስለምትወጉአቸው ነው። 22 ስለዚህ መንጋዬን አድናለሁ፥ ከእንግዲህ ወዲህም ለንጥቂያ አይሆኑም። በበግና በበግ መካከልም እፈርዳለሁ። 23 በላያቸውም አንድ እረኛ አቆማለሁ እርሱም ያሰማራቸዋል፥ እርሱም ባሪያዬ ዳዊት ነው! ያሰማራቸዋል እረኛም ይሆናቸዋል። 24 እኔም እግዚአብሔር አምላክ እሆናቸዋለሁ ባሪያዬም ዳዊት በመካከላቸው አለቃ ይሆናል እኔ እግዚአብሔር ተናግሬአለሁ። 25 የሰላምን ቃል ኪዳን ከእነርሱ ጋር እገባለሁ ክፉዎችንም አራዊት ከምድሪቱ አጠፋለሁ፥ በጎቼም ተጠብቀው በምድረ በዳ ይኖራሉ በዱርም ውስጥ ይተኛሉ። 26 በእነርሱና በዙሪያ ባሉ ኮረብቶቼ በረከቴን አፈሳለሁ፥ ዝናቡንም በጊዜው እልካለሁ። ይህም የበረከት ዝናብ ይሆናል። 27 የምድረ በዳም ዛፍ ፍሬውን ይሰጣል ምድርም ቡቃያዋን ትሰጣለች፥ በጎቼ በምድራቸው ተዘልለው ይኖራሉ የቀንበራቸውንም ማነቆ በሰበርሁ ጊዜ ከሚገዙአቸውም እጅ ባዳንኋቸው ጊዜ፥ እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ። 28 እንግዲህም ለአሕዛብ ንጥቂያ አይሆኑም የምድርም አራዊት አይበሉአቸውም ተዘልለውም ይቀመጣሉ የሚያስፈራቸውም የለም። 29 መልካም የእርሻ ቦታ አዘጋዝጅላቸዋልሁ፥ ከእንግዲህም ከራብ የተነሣ በምድሪቱ አያልቁም አሕዛብም ከእንግዲህ ወዲህ አይሰድቧቸውም። 30 እኔ እግዚአብሔር አምላካቸው ከእነርሱ ጋር እንዳለሁ ያውቃሉ። የእስራኤል ቤት ሕዝቤ እነርሱ ህዝቤ ናቸው ይላል ጌታ እግዚአብሔር። 31 እናንተም በጎቼ፥ የማሰማርያዬ በጎች፥ ህዝቤ ናችሁ እኔም አምላካችሁ እሆናለሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር"

Ezekiel 34:1

አጠቃላይ መረጃ፡

በምዕራፍ 34፣ ያህዌ፣ የእስራኤል ህዝብ እንደ በግ መንጋ እንደሆኑ እና የእስራኤል መሪዎች ደግሞ መንጋውን እንደሚጠብቁ እረኞች ተደርገው ነገር ግን ድርሻቸውን ሳይወጡ እንደቀሩ ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌ ቃል መጣ

ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የተናገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ነናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ/ያህዌ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ

"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

የእስራኤል ጠባቂ

የእስራኤል መሪዎች እረኞች እንደሆኑ ተደርጎ ተገልጸዋል። እረኛ መንጋውን እንደሚንከባከብ የህዝባቸው ጠባቂ እንዲሆኑ ይጠበቅባቸው ነበር። "እንደ እረኞች የሆኑ የእስራኤል መሪዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እራሳቸውን ይንከባከቡ ነበር

መሪዎቹ ህዝቡን ከመጠበቅ ይልቅ የራሳቸውን ምኞት መጠበቃቸው የተገለጸው ራሳቸውን እንደሚጠብቁ ተደርጎ ነው። "ራሳቸውን ይመግባሉ፣ ራሳቸውንም ብቻ ይንከባከባሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እረኞች መንጋውን ሊጠብቁ አይገባምን?

ያህዌ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት መሪዎች ህዝቡን ባለመንከባከባቸው ለጋስጻቸው ነው። "እረኞች መንጋውን ሊመግቡ፣ ሊንከባከቡትም ይገባል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ ስቡን ተመገባችሁ... ሐር ለበሳችሁ

የእስራኤል መሪዎች እንደ መጠፎ እረኛ ከመንጋው ምርጡን እያረዱ የሚበሉና የበጉን ጸጉር እየለበሱ ለመንጋው ግን ገድ እንደማየላቸው ተደርጎ መገለጹ ቀጥሏል። "እናንተ ለመንጋው ግድ እንደሌለው የሰባውን እንደሚመገብ...

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሱፉን እንደሚለብስ እረኛ ብቻ ናችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ ስቡን ተመገባችሁ
የሰባው ክፍል የሚገኘው ከበጎች እና ፍየሎች ነው። "የቡን እና ፍየሉን ስብ ክፍል ትመገባላችሁ" ወይም "እናንተ የበጎቹን እና ፍየሎቹን ምርጥ ክፍል ትመገባላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሱፉን ትለብሳላችሁ
"ከበጎች የሚገኘውን ሱፍ ትለብሳላችሁ"

የሰባውን
"የሰባውን የበግ እና ፍየል ጠቦት"

ፈጽሞውኑ አትጠብቋቸውም
"መንጋውን አትመግቡም፣ እንክብካቤም አታደርጉለትም"

Ezekiel 34:4

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ በሕዝቅኤል በኩል ለእስራኤል መሪዎች መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ እስራኤል ሰዎች እንደ በጎች መንጋ፣ የእስራኤል መሪዎችን ደግሞ ለመንጋው ግድ እንደማይላቸው እረኞች አድርጎ መናገሩን ቀጥሏል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በሽታ ይዟቸዋል
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ታመዋል" ወይም 2) "ደካማ ናቸው"

የተሰበሩትን አልጠገናችሁም
"ለቆሰሉት በተሰበሩ አጥንቶቻቸው ዙሪያ ጨርቅ አልጠቀለላችሁም"

እነዚያ የተሰበሩት
"አጥንታቸው የተሰበረ በጎች" ወይም "የተጎዱ በጎች"

አልጠገናችኋቸውም
"አልመለሳችኋቸውም"

የተረሱት
"የተተዉ በጎች" ወይም "ሌሎች ያባረሯቸው"

የጠፉ
"በተጎቹ ወይም ፍየሎቹ" የሚሉት ቃላት ከዚህ ሀረግ ወጥተዋል/ተትተዋል፣ ነገር ግን በውስጠ ታዋቂነት እንደሚታወቁ ይታሰባል። "የጠፉት በጎች ወይም ፍየሎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

በጥንካሬ እና በሃይል
"በሀይል እና በጭካኔ"

ከዚያም ያለ እረኛ ተበተኑ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ከዚያም ተበተኑ፣ ምክንያቱ እረኛ ስላልነበራቸው ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በሜዳ ላሉ አምሪዎች ሁሉ ምግብ ሆኑ
"የዱር እንስሳት ሁሉ ሊያጠቋቸው እና ሊበሏቸው ይችላሉ"

በምድር ላይ ሁሉ ተበተኑ
"መንጋዬ በምድር ላይ ሁሉ ተበተነ"

Ezekiel 34:7

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ በሕዝቅኤል በኩል ለእስራኤል መሪዎች መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ እስራኤል ሰዎች እንደ በጎች መንጋ፣ የእስራኤል መሪዎችን ደግሞ ለመንጋው ግድ እንደማይላቸው እረኞች አድርጎ መናገሩን ቀጥሏል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌን ቃል ስሙ
ይህ ከያህዌ ልዩ መልዕክት ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጥ ነው። "የያህዌን መልዕክት አድምጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በሕያውነቴ
"እኔ ሕያው እንደሆንኩ።" ያህዌ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው ቀጥሎ የሚናገረው በእርግጥ እውነት መሆኑን ለማሳየት ነው። ይህ የከበረ ቃል መግቢያ መንገድ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "በክብሬ እምላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ራሱን በስሙ የሚገልጸው/የሚምለው፤ የተናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳወቅ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ። "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

መንጋዬ ስለተዘረፈ እና በሜዳ ለሚገኝ አውሬ ምግብ ስለሆነ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በሜዳ ያሉ አውሬዎች ሁሉ መንባዬን ስለሰረቁ እና ስለበሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ዝርፊያ
የተሰረቁ ነገሮች

በሜዳ ያሉ አውሬዎች ሁሉ
እዚህ ስፍራ "ሁሉ" የሚለው በግ የሚበሉ የዱር እንስሳትን ሁሉ የሚያመለክት አጠቃላይ መገለጫ ነው። "በሜዳ የሚገኙ የዱር እንስሳት ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

እረኛ ባለመኖሩ ምክንያት
"እረኛ ስለ ሌላቸው"

ከእረኞቼ አንዱም መንጋዬን አልተመለከተም
"ከእረኞቼ አንዱም መንጋዬን ለማግኘት አልሞከረም"

ራሳቸውን ጠበቁ
"ራሳቸው ተንከባከቡ" ወይም "ራሳቸውን መገቡ፣ ለራሳቸው እንክብካቤ አደረጉ"

የእኔን መንጋ አልጠበቁም
"የእኔን መንጋ አልመገቡም፣ መንጋዬን አልተንከባከቡም"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ezekiel 34:9

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ በሕዝቅኤል በኩል ለእስራኤል መሪዎች መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ እስራኤል ሰዎች እንደ በጎች መንጋ፣ የእስራኤል መሪዎችን ደግሞ ለመንጋው ግድ እንደማይላቸው እረኞች አድርጎ መናገሩን ቀጥሏል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌን ቃል ስሙ
"የያህዌን መልዕክት አድምጡ።" ይህ ከያህዌ ልዩ መልዕክት ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጥ ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
ይህ በአንደኛ መደብ ሊገለጽ ይችላል። "እኔ፣ ጌታ ያህዌ እንዲህ እላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ!
እዚህ ስፍራ "እነሆ!" የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚሆነው ነገር ትኩረት ይሰጣል። "በእርግጥ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እኔ በእረኞች ላይ ተነስቻለሁ
"እኔ እረኞችን እቃወማለሁ"

በጎቼን ከእጃቸው እጠይቃለሁ
"ከእጃቸው...መጠየቅ" የሚለው ሀረግ አንድን ሰው ለአንድ ነገር ተጠያቂ ወይም በሀላፊነት ተጠያቂ ማድረግ ማለት ነው። "በመንጋዬ ላይ ለደረሰው ከፉ ነገር ሁሉ ተጠያቂ አደርጌ እይዛቸዋለሁ" ወይም "በመንጋዬ ላይ እንዲደርስ ላደረጉት ክፉ ነገር ሁሉ እቀጣቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መንጋውን ከመጠበቅ ሃላፊነት ላይ እደመስሳቸዋለሁ
"ከእንግዲህ መንጋውን እንዲጠብቁ አልፈቀድላቸውም" ወይም "ከዚህ በኋላ የመንጋው ጠባቂ እንዲሆኑ አልተዋቸውም/አላደርግም"

ራሳቸውን ተንከባከቡ/ጠበቁ
"ራሳቸውን መገቡ ወይም ለራሳቸው እንክብካቤ አደረጉ"

ከእነርሱ አፍ
እዚህ ስፍራ "አፍ" የሚወክለው መብላትን ነው። "ከእንግዲህ አይበሏቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

መንጋዎቼ ከእንግዲህ ለእነርሱ ምግብ አይሆኑም
"እረኞቹ ከእንግዲህ የመንጋዬን በጎች እና ፍየሎች አይበሉም"

Ezekiel 34:11

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ በሕዝቅኤል በኩል ለእስራኤል መሪዎች መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ እስራኤል ሰዎች እንደ በጎች መንጋ አድርጎ መናገሩን ቀጥሏል። እዚህ ስፍራ ስለ ራሱ የእነርሱ እረኛ እንደሆነ እና እንደሚንከባከባቸው ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
ይህ በአንደኛ መደብ ሊገለጽ ይችላል። "እኔ፣ ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ!
እዚህ ስፍራ "እነሆ!" የሚለው ቃል እረኞች ቀጥሎ ለሚሆነው አስደናቂ መረጃ ትኩረት እንዲሰጡ ያነቃል።

የሚሆነውን ይመረምራሉ
"ወደፊት ይመለከታሉ"

በተበተኑ መንጋዎቹ መሃል
"በተበታተኑ መንጋዎቹ ጋር"

ተበታትነው ነበር
በመንጋው ውስጥ የሚገኙ እንስሳት መበታተናቸው ተጠቁሟል፣ ምክንያቱ የሚጠብቃቸው ወይም የሚንከባከባቸው እረኛ አለመኖሩ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የሚንከባከባቸው እረኛ በማጣታቸው ተበታተኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ እንዲሁም አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ደመና እና ጨለማ በሆነ ቀን
"በደማናማ እና ጨለማ ቀን።" ጥፋቶች የተገለጹት የጨለማ ቀን እንደሆኑ እንደሆኑ ተደርጎ ነው። "ችግር እና ጥፋት በደረሰባቸው ቀን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አምጧቸው
"በጎቼን እና ፍየሎቼን አምጧቸው" ወይም "መንጋዬን አምጡ"

ከህዝብ መሃል
"ከሌሎች ህዝቦች ጋር ከሚኖሩበት ስፍራ"

በለመለመ መስክ አሰማራቸዋለሁ... በምድሪቱ ማረፊያ ሁሉ
ያህዌ ህዝቡን ከስደት ወደ ምድራቸው ይመልሳቸዋል። ይህም በመሆኑ እርሱ ሊንከባከባቸው እና በደህንነት ሊጠብቃቸው እንደሚችል የተገለጸው፣ ብዙ ስፍራ፣ ምግብ እና ውሃ በሚያገኙበት የሚያስቀምጣቸው እረኛቸው እንደሆነ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መሰማሪያ
በጎች እና ፍየሎች ሊበሉት የሚችሉት ሳር እና ቅጠል/ትንንሽ ተክል የሚገኝበት መሬት

መስፈሪያ
ይህ ሰዎች የሚኖሩበት ቦታ ነው። ብዙውን ጊዜ ሰዎች ሲሰፍሩ ቤት ሰርተው ይቀመጣሉ

Ezekiel 34:14

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ በሕዝቅኤል በኩል ለእስራኤል መሪዎች መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ እስራኤል ሰዎች እንደ በጎች መንጋ አድርጎ መናገሩን ቀጥሏል። እዚህ ስፍራ ስለ ራሱ የእነርሱ እረኛ እንደሆነ እና እንደሚንከባከባቸው ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የግጦሽ ስፍራቸው
"ለሚመገቡ/ለግጡ የሚችሉበት ስፍራ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሰፊ መሰማሪያ
"ብዙ ሳር እና ተክል የሚገኝበት እንስሳት ግጦሽ መሬት"

መጋጥ
እንስሳት ሳር እና ሌሎች ተክሎች ማግኘታቸው

እኔ ራሴ
"እኔ ራሴ" የሚለው ትኩረት ይጨምራል። እግዚአብሔር ይህን የሚያደርገው እረኞች ያንን ባለማድረጋቸው ነው። (ደጋጋሚ ተውላጠ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እረኞች... ይሆን
"ይመግቧቸው እና ይንከባከቧቸው...ይሆን

እንዲጋደሙ ያደርጉ ይሆን
"እንዲያርፉ ይተዋቸው ይሆን"

የጠፉት
"በጎቹ ወይም ፍየሎች" የሚሉት ቃላት በእዚህ ሀረግ ተዘለዋል/ተትተዋል፤ ሆኖም ግንዛቤ እንደሚያገኙ ይታሰባል። "የጠፉት በጎች ወይም ፍየሎች" (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

የተጣሉትን ጠግኑ
"ሌሎች ያባረሯቸውን/ያስወጧቸውን መልሷቸው"

የተሰበሩትን በጎች ጠግኑ
"የተሰበረውን በግ አጥንቱን በጨርቅ ጠቅልሉ" ወይም "የማናቸውንም በግ ቁስል ዙሪያውን በጨርቅ ጠቅልሉ"

የሰባውን እና ጠንካራውን/ጤናማውን
"በግ" የሚለው ቃል በውስጠ ታዋቂነት አለ። "የሰባው እና ጠንካራው/ጤናማውን በግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 34:17

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ በሕዝቅኤል በኩል ለእስራኤል መሪዎች መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ መልዕክቱን ለሕዝቅኤል መስጠቱን ቀጥሏል። አሁን መልዕክቱ ለእስራኤል ህዝብ ነው።

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ እስራኤል ሰዎች እንደ በጎች መንጋ፤ ስለ ራሱ የእነርሱ እረኛ እንደሆነ ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
ይህ በአንደኛ መደብ ሊገለጽ ይችላል። "እኔ፣ ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ፣ እኔ
"ትኩረት ስጡ፣ ምክንያቱም እኔ የምናገረው እውነተኛም ጠቃሚም ነውና"

እኔ በበጎች እና በበጎች መሃል ዳኛ እሆናለሁ
"እኔ በአንደኛው በግ እና በሌላኛው መሃል ዳኝነት እሰጣለሁ"

አውራ በጎች እና ወንድ ፍየሎች
ወንድ በጎች እና ፍየሎች ብዙውን ጊዜ በመንጋው ውስጥ ጠንካሮቹ ናቸው፤ ደግሞም የሚፈልጉትን በመንጋው ውስጥ ከሚገኙት እንስሳት ያገኛሉ።

ይህ ... በቂ አይደለምን
እግዚአብሔር እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመው፣ በመንጋው ውስጥ የሚገኙትን፤ ለደካሞቹ በማያዝኑ ጠንካራ እንስሳት የተገለጹትን የእስራኤል መሪዎችን ለመገሰጽ ነው። ይህንን በዩዲቢ እንደሚገኘው በዐረፍተ ነገር መልክ መተረጎም ይቻላል። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Ezekiel 34:20

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ እስራኤል ሰዎች እንደ በጎች መንጋ፤ ስለ ራሱ የእነርሱ እረኛ እንደሆነ መግለጹን ቀጥሏል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
ይህ በአንደኛ መደብ ሊገለጽ ይችላል። "እኔ፣ ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእነርሱ
"ለመንጋዬ"

እነሆ!
እዚህ ስፍራ "እነሆ" የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚሆነው ትኩረት ይጨምራል። "በእርግጥ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እኔ ራሴ
"እኔ ራሴ" የሚለው ፍርድ የሚሰጠው ያህዌ ለመሆኑ ትኩረት ይሰጣል። (ደጋጋሚ ተውላጠ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በሰቡት በጎች እና በከሱት መሃል ይፈርዳል
"የሰቡት በጎች እና ፍየሎች የከሱትን በጎች እና ፍየሎች መንከባከባቸውን እና እርስ በእርሳቸው በሚገባ መተያየታቸውን ያረጋግጣል"

የሰቡት በጎች እና የከሱት በጎች
በእስራኤል መሪዎች እና ጠንካራ ሰዎች፣ በመንጋው ውስጥ እንደሚገኙ ወፍራም እና ጠንካራ እንስሳ ተደርገው ይገለጻሉ። ደሃ እና ደካማ ሰዎች በመንጋው ውስጥ እንደሚገኙ የከሱ እና ደካማ እንስሳ ይገለጻሉ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለእናንተ
"እናንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሌሎችን በጎች እና ፍየሎች በሚገባ ያልተንከባከቡ በጎችን እና እንስሳትን ነው።

በአጠገባችሁ
"በአካላችሁ ጎን"

ወጉ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ቀጡ" ወይም "ገፉ" 2) "በሱ" ወይም "ጠረቆሱ"

በተኗቸው
"በተለያዩ አቅጣጫዎች እንዲበታተኑ አደረጓቸው"

ከምድሪቱ እንዲሄዱ
"ከእስራኤል ምድር እንዲሰደዱ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ezekiel 34:22

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ እስራኤል ሰዎች እንደ በጎች መንጋ፤ ስለ ራሱ የእነርሱ እረኛ እንደሆነ መግለጹን ቀጥሏል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህ አይበዘበዙም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ማንም እንዲበዘብዛቸው አልፈቅድም" ወይም "ማንም እንዲሰርቃቸው አልፈቅድም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚህ በኋላ ዘረፋ አይሆንም
"ከዚህ በኋላ የሚሰረቅ ነገር አይኖርም።" እረኞቹ እና የዱር እንስሳቱ ከያህዌ መንጋ በጎቹን እና ፍየሎቹን ይሰርቁ ነበር።

በላያቸው አንድ እረኛ አስቀምጣለሁሁ
"በላያቸው አስቀምጣለሁ" የሚለው ሀረግ ፈሊጥ ሲሆን ትርጉሙ አንድ ሰው ሌላውን እንዲያስተዳድር ማድረግ ማለት ነው። "አንድ እረኛ በበጎቼ እና ፍየሎቼ ላይ እሾማለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አገልጋዬ ዳዊት
እዚህ ስፍራ "ዳዊት" የተጠቀሰው ለዳዊት ትውልድ ነው። "የአገልጋዬ የዳዊት ትውልድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ እረኛ ይሆናቸዋል
በእስራኤል ህዝብ ላይ ንጉሥ የሚሆነው የዳዊት ትውልድ የተገለጸው የእነርሱ እረኛ እንደሚሆን ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእነርሱ መሃል ልዑል/ገዢ ይሆናል
"ገዢያቸው ይሆናል"

Ezekiel 34:25

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ እስራኤል ሰዎች መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ እስራኤል ሰዎች እንደ በጎች መንጋ አድርጎ መግለጹን ቀጥሏል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰላም ቃል ኪዳን
"ሰላም የሚያመጣ ቃል ኪዳን"

ክፉ የዱር እንስሳት
እነዚህ በጎችን እና ፍየሎችን መግደል የሚችሉ የዱር እንስሳት ናቸው።

እኔ በእነርሱ እና በኮረብቶቼ ዙሪያ በሚገኙ ስፍራዎች በረከትንም ጭምር አመጣለሁ
አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ይህንን "እነርሱን እና በኮረብቶቼ ዙሪያ የሚገኙ ስፍራዎችን ወደ በረከት እለውጣቸዋለሁ" ብለው ይተረጉማሉ።

የእኔ ኮረብታ
ይህ የሚያመለክተው የጽዮንን ተራራ ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ዝናብን እልካለሁ
"እንዲዘንብ አደርጋለሁ"

በጊዜው
"በትክክለኛው ጊዜ"

እነዚህም የበረከት ዝናብ ይሆናሉ
"ይህ ዝናብ በረከት ይሆናል"

ምድር ፍሬዋን ትሰጣለች
"ምድር የሚበላ ታበቅላለች" ወይም "ምግብ በምድር ይበቅላል"

አስተማማኝ ይሆናል
"ደህና ይሆናል"

እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ
ያህዌ እርሱ ያህዌ እንደሆነ ሰዎች ያውቃሉ ሲል፣ የመጨረሻው ከፍተኛ ስልጣን እና ሀይል ያለው እውነተኛው አምላክ እርሱ ብቻ እንደሆነ ማወቅ እንደሚገባቸው እየተናገረ ነው። ይህ በሕዝቅኤል6:7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ብቸኛው እውነተኛ አምላክ እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ" ወይም "እኔ ያህዌ የመጨረሻው ስልጣን እና ሀይል እንዳለኝ እወቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የቀንበራቸውን እስራት ስሰብር
ባርነት የተገለጸው እንደ አንዳንድ እንስሳት ሰዎች ላይ ቀንበር እንደሚጫንባቸው ተደርጎ ነው። "ከባርነት ነጻ ሳወጣቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በባርነት ከያዝዋቸው እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚወክለው ሀይልን ወይም መቆጣጠርን ነው። "ባሪያ አድርገው ከተቆጣጠሯቸው እጅ" ወይም "እነርሱን ባሪያዎች ካደረጓቸው እጅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 34:28

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ እስራኤል ሰዎች መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

ከእንግዲህ ወዲያ ለአገራት ብዝበዛ አይሆኑም
እዚህ ስፍራ "አገራት" የሚለው የሚወክለው የአገራትን ህዝቦች ነው። "የተለያዩ አገራት ሰዎች ከዚህ በኋላ እነርሱን አይበዘብዙም/አይሰርቁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ዝርፊያ
እነዚህ የተሰረቁ ወይም በሀይል የተወሰዱ ነገሮች ናቸው። "ዝርፊያ" የሚለቀው በሕዝቅኤል 7:21 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

የችጋር ምርኮኛ መሆን
"መራብ" ወይም "ከምግብ እጥረት የተነሳ ረሀብተኛ መሆን"

የአገራትን ንቀት አይሸከሙም
እዚህ ስፍራ "አገራት" የሚለው የሚገልጸው የአገራት ህዝቦችን ነው። "ንቀት" የሚለው ረቂቅ ስም በግስ መልክ ሊገለጽ ይችላል። "ከእንግዲህ የተለያዩ አገራት ሰዎች አይሰድቧቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

Ezekiel 34:30

እኔ፣ ያህዌ አምላካቸው እኔ ከእነርሱ ጋር ነኝ
እዚህ ስፍራ "እኔ...ከእነርሱ ጋር ነኝ" የሚለው ያህዌ ይረዳቸዋል ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "እኔ፣ ያህዌ አምላካቸው፣ እኔ እረዳቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከእነርሱ ጋር። እነርሱ የእኔ ህዝብ ናቸው
ይህ በአንድ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እነርሱ የእኔ ህዝብ ናቸው፣ እኔ ከእነርሱ ጋር እሆናለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚወክለው ሰዎችን ነው። "የእስራኤል ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ለእናንተ ለበጎቼ፣ ለመሰማሪያ መንጋዎቼ
ይህ የእስራኤል ህዝብ ለእርሱ የበጎች መንጋ እንደሆኑ እና ያህዌ እረኛቸው እንደሆነ ይገልጻል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 35

1 የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፥ **2** "የሰው ልጅ ሆይ፥ ፊትህን ወደ ሴይር ተራራ አድርግ፥ ትንቢትም ተናገርበት፥ **3** እንዲህም በለው 'ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ የሴይር ተራራ ሆይ፥ እነሆ፥ በአንተ ላይ ነኝ፥ በእጄ እመታሀለሁ ባድማና ድንጋጤ አደርግሃለሁ። **4** ከተሞችህንም አፈራርሳቸዋለሁ፥ አንተም ባድማ ትሆናለህ፥ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃለህ። **5** ለእስራኤልን ህዝብ ሁል ጊዜ ጥላቻ ስላለህ በመከራቸውም ጊዜ በጽኑ ቅጣት በተቀጡበት ጊዜ የእስራኤልን ልጆች በሰይፍ እጅ ጥለሃቸዋልና **6** ስለዚህ እኔ ሕያው ነኝና ለደም መፋሰስ አሳልፌ እሰጥሃለሁ ደም መፋሰስም ያሳድድሃል፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር ደም መፋሰስን ስላልጠላህ ደም መፋሰስ ያሳድድሃል። **7** በእርሱ የሚያልፈውንም ሆነ ወደ እርሱ የሚመለስ እንዳይኖሬ በማድረግ የሴይርን ተራራ ውድማ አደርገዋለሁ ። **8** ተራሮቹንም በተገደሉት ሰዎች እሞላለሁ በኮረብቶችህና በሸለቆችህ በፈሳሾችህም ሁሉ ላይ በሰይፍ የተገደሉት ሁሉ ይወድቃሉ። **9** ለዘላለምም ባድማ አደርግሃለሁ ከተሞችህም ሰው የማይኖርባቸው ይሆናሉ፥ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ። **10** አንተ፥ "እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋሬ ቢሆንም እነዚህ ሁለቱ ሕዝቦች እነዚህም ሁለቱ አገሮች ለእኔ ይሆናሉ እኛም እንወርሳቸዋለን" ብለሃል። **11** ስለዚህ እኔ ሕያው ነኝና እንደ ቍጣህ መጠን እነርሱንም ጠልተህ እንዳደረግኸው እንደ ቅንዓትህ መጠን እኔ አደርግብሀለሁ፥ በፈረድሁብህም ጊዜ በእነርሱ ዘንድ የታወቅሁ እሆናለሁ ይላል ጌታ እግዚአብሔር ። **12** ስለዚህም እኔ እግዚአብሔር እንደሆንኩ ታውቃለህ። በእስራኤል ተራሮች ላይ "ፈርሰዋል! መብልም ሆነው ለእኛ ተሰጥተዋል" ብለህ የተናገርኸውን ስድብ ሁሉ ሰምቻለሁ። **13** በአፋህም በእኔ ላይ የተናገርከውን ትምክህት የተሞላ ንግግር ሰምቻለሁ፤ በኔ ላይ ብዙ ነገሮችን ተናገርክ።፥ እኔም ሰምቼዋለሁ። **14** ጌታ እግዚአብሔርም እንዲህ ይላል። ምድር ሁሉ ደስ ሲለት አንተን ባድማ አደርግሃለሁ። **15** የእስራኤል ቤት ርስት ባድማ ስለ ሆነ አንተ ደስ እንዳለህ፥ እንዲሁ አደርግብሃለሁ። የሴይር ተራራ ሆይ፥ አንተና ኤዶምያስ ሁሉ ሁለንተናውም ባድማ ትሆናላችሁ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ።

Ezekiel 35:1

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል ትንቢት እንዲናገር ይነግረዋል። ሕዝቅኤል ለሴይር ተራራ መናገር ይኖርበታል፣ ነገር ግን መልዕክቱ ለመላው የኤዶም ህዝብ ነው።

የያህዌ ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የተናገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ነናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ/ያህዌ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ፊትህን ወደ ሴይር ተራራ መልስ
የሴይር ተራራ ሩቅ ነው፣ ስለዚህ ሕዝቅኤል ሊመለከተው አይችልም፤ ነገር ግን ያህዌ በዚያ ላሉ ሰዎች ቅጣት እንዲደርስባቸው እንደ ምልክት ወደዚያ አቅጣጫ እንዲያይ ያዘዋል። ተመሳሳይ የሆነው ሀረግ በሕዝቅኤል 6:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ወደ ሴይር ተራራ ዞረህ ትኩር ብለህ ተመልከት" ወይም "በዚያ የሚኖሩ ጥፋት ይደርስባቸው ዘንድ ወደ ሴይር ትኩር ብለህ ተመልከት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

የሴይር ተራራ እና በእርሱ ላይ የተነገረ ትንቢት
"የሴይር ተራራ።" ያህዌ ለሕዝቅኤል የሚሰማ ይመስል ለሴይር ተራራ እንዲናገር ይናገረዋል። መልዕክቱ ለመላው የኤዶም ህዝብ ነው። "የሴይር ተራራ እና የኤዶም ሰዎች ከፈጸሙት ነገር የተነሳ በእርሱ ላይ የተነገረ ትንቢት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእርሱ
"ለተራራው" ወይም "ለኤዶም ሰዎች"

የሴይር ተራራ ሆይ እነሆ! እኔ በአንተ ላይ ነኝ፣ በእጄ እመታሃለሁ ደግሞም ጠፍ እና ምድረበዳ አደርግሃለሁ
ያህዌ ለሕዝቅኤል ለሴይር ተራራ ልክ እንደሚሰማው አድርጎ እንዲናገር ያዘዋል። መልዕክቱ ለመላው የኤዶም ህዝብ ነው። "የሴይር ተራራ ሆይ ስማ፣ በእጄ እመታሃለሁ ደግሞም የአንተ ህዝብ ካደረገው የተነሳ ጠፍ እና ምድረበዳ አደርግሃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ!
እዚህ ስፍራ "እነሆ!" የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚሆነው ትኩረት ይጨምራል። "አድምጡ!" ወይም "በእርግጥ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እኔ በእናንተ ላይ ነኝ
"እኔ ጠላታችሁ ነኝ" ወይም "እኔ እቃመዋችኋለሁ"

በእጄ እመታችኋለሁ
እዚህ ስፍራ "እጅ" ሀይልን ይወክላል። "እናንተን ለመምታት ሀይሌን እጠቀማለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሰው የማይኖርበት ምድር/ጠፍ አደርግሃለሁ
"ጠፍ/ምድረበዳ" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል ሊተረጎም ይችላል። "ምድረ በዳ አደርግሃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 35:4

አጠቃላይ መረጃ:
ሕዝቅኤል ለሴይር ተራራ የሚናገረውን መልዕክት ይቀጥላል። መልዕክቱ ለመላው የኤዶም ሰዎች ነው።

እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ
ያህዌ እርሱ ያህዌ እንደሆነ ሰዎች ያውቃሉ ሲል፣ የመጨረሻው ከፍተኛ ስልጣን እና ሀይል ያለው እውነተኛው አምላክ እርሱ ብቻ እንደሆነ ማወቅ እንደሚገባቸው እየተናገረ ነው። ይህ በሕዝቅኤል6:7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ብቸኛው እውነተኛ አምላክ እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ" ወይም "እኔ ያህዌ የመጨረሻው ስልጣን እና ሀይል እንዳለኝ እወቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለሰይፍ እጅ አሳልፈህ ሰጠሃቸው
የዚህ ዘይቤ ትረጉም ሊሆኑ የሚችሉት 1) "በሰይፍ ለሚገድሏቸው ጠላቶቻቸው አሳልፈህ ሰጠሃቸው" ወይም 2) "በሰይፍ ገደልካቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በጉዳታቸው ጊዜ
"በጥፋት ጊዜ"

በህያውነቴ
"እኔ ህያው እንደሆንኩ።" ያህዌ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው ቀጥሎ የሚናገረው በእርግጥ እውነት መሆኑን ለማሳየት ነው። ይህ የከበረ ቃል መግቢያ መንገድ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "በክብሬ እምላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ራሱን በስሙ የሚገልጸው/የሚምለው፤ የተናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳወቅ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ። "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ለደም ማፍሰስ አዘጋጃችኋለሁ
እዚህ ስፍራ "ደም ማፍሰስ" መግደል ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ለጠላቶቻችሁ ብዙዎቻችሁን መግደልን ቀላል አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ደም ማፍሰስ ይከተላችኋል
እዚህ ስፍራ "ደም መፍሰስ" መግደል ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ያህዌ ስለ ደም ማፍሰስ የሚናገረው ሊያባርራቸው እንደሚችል ሰው አድርጎ ነው። "ጠላቶቻችሁ ቁልቁል አሳደው ይገደሏችኋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ደም ማፍሰስን አልጠላችሁምና
እዚህ ስፍራ "ደም መፍሰስ" መግደል ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ጠላት የእስራኤልን ህዝብ በጭካኔ ሲገድል ይህን ድርጊት አልጠላችሁምና" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 35:7

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ ሕዝቅኤል ለሴይር ተራራ የሚናገረውን መልዕክት ይቀጥላል። መልዕክቱ ለመላው የኤዶም ሰዎች ነው።

ከእርሱ በዚያ የሚያልፈውንም ቆርጬ ስጥል እና እንደ ገና ስመለስ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ቆርጦ መጣል" የሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን ማጥፋት/መደምሰስ ማለት ነው። "ወደ እርሱ የሚገቡትንም ሆነ የሚወጡትን ሁሉ አጠፋለሁ ወይም 2) "ቆርጦ መጣል" አንድ ሰው አንድ ነገር እንዳያደርግ ማስቆም ለሚለው ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። "ሰዎች ወደ እርሱ እንዳይገቡና እንዳይወጡ/እንዳይመላለሱ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በሰይፍ የተገደሉ
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚለው የሚወክለው በጦርነት የተዋጓቸውን ጠላቶቻቸውን ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። ይህ በሕዝቅኤል 31፡17 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ጠላት በሰይፍ የገደላቸው" ወይም "በጦርነት የሞቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

ለአንዱው ጠፍ የሆነ
"እስከ ወዲያኛው ምድረ በዳ የሆነ።" ይህ ጥፋቱን ትኩረት ሰጥቶ ለማጋነን የተነገረ ሊሆን ይችላል። "ከእንግዲህ ሰዎች በእናንተ ከተሞች ውስጥ አይኖሩም" (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት ሚሉትን ይመልከቱ)

ነገር ግን እናነተ ታውቃላችሁ
"እናንተ" የሚለው ብዙ ቁጥር ነው። እግዚአብሔር በአንድ ተራራ ለሚኖሩ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ በሴይር ተራሮች ለሚኖሩ ሰዎች እየተናገረ ነው። (አንተ/ አንቺ የሚለው ነጠላ ቁጥር ተውላጠ ስም መልኮች)

Ezekiel 35:10

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ ሕዝቅኤል ለሴይር ተራራ የሚናገረውን መልዕክት ይቀጥላል። መልዕክቱ ለመላው የኤዶም ሰዎች ነው።

አንተ እንዲህ ብለሃል
"አንተ" የሚለው ቃል የሴይር ተራሮችን ያመለክታል። ሕዝቅኤል ለተራራው የሚናገረው ተራራው እንደሚሰማው አድርጎ ነው። መልዕክቱ ለኤዶም ሰዎች ነው። "ህዝቦችህ እንዲህ ብለዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ ሁለት ምድሮች
"የእስራኤል እና ይሁዳ ምድሮች"

የእኔ ይሆናሉ
"የእኔ" የሚለው ቃል በብዙ ቁጥር ሊገለጽ ይችላል። "የእኛ ይሆናሉ"

እኛ
"እኛ" የሚለው ቃል የኤዶምን ሰዎች ያመለክታል።

ያህዌ ከእነርሱ ጋር በነበረበት ጊዜ እንኳን
ያህዌ እስራኤልን እና ይሁዳን ይጠብቅ እንደነበር ተጠቁሟል። "ነገር ግን ያህዌ እስራኤልን እና ይሁዳን እየጠበቀ በዚያ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ቁጣችሁ እና ቅናታችሁ አደርግባችኋለሁ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "በቁጣችሁ እና ቅናታችሁ ምክንያት እቀጣችኋለሁ" ወይም 2) "በቁጣና ቅናት በእስራኤል ህዝብ ላይ እንዳደረጋችሁት ልክ እንደዚያው እኔም በእናንተ ላይ በቁጣ እና ቅናት አደርግባችኋለሁ"

Ezekiel 35:12

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ ሕዝቅኤል ለሴይር ተራራ የሚናገረውን መልዕክት ይቀጥላል። መልዕክቱ ለመላው የኤዶም ሰዎች ነው።

በእስራኤል ተራሮች ላይ
እዚህ ስፍራ "ተራሮች" የሚለው የሚወክለው መላውን የእስራኤል ምድር ነው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ተደምስሰዋል
ይህ ሀረግ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በፍርስራሾች ስር ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እነርሱ እንድንበላቸው ለእኛ ተላልፈው ተሰጥተዋል
የሴይር ተራሮች ህዝብ የእስራኤልን ምድር ወስደው ለራሳቸው መጠቀሚያ ማድረጋቸው የተገለጸው የዱር እንስሳት እንደሆኑ እና የእስራኤል ተራሮችን እንደሚበሉ ተደርጎ ነው። "እነርሱ በዚህ ያሉት እኛ እንደንበላቸው ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

Ezekiel 35:14

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ ሕዝቅኤል ለሴይር ተራራ የሚናገረውን መልዕክት ይቀጥላል። መልዕክቱ ለመላው የኤዶም ሰዎች ነው።

ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
ይህ በአንደኛ መደብ ሊገለጽ ይችላል። "እኔ፣ ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተን ምድረ በዳ/ጠፍ ምድር አደርግሃለሁ
እዚህ ስፍራ "አንተ" የሚለው የሴይር ተራሮችን ነው፣ ነገር ግን መልዕክቱ ለኤዶም ሰዎች ነው። "ጠፍ/ሰው የማይኖርበት ምድር" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል መልክ ሊጻፍ ይችላል። "የአንተ ህዝብ ባደረገው ነገር ምክንያት አንተን ሰው የማይኖርበት ምድረ በዳ አደርግሃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

መላዋ መሬት ሀሴት ታደርጋለች
እዚህ ስፍራ "መሬት" የሚለው ቃል የሚወክለው የምድር ሰዎችን ነው። "መላው" የሚለው ቃል በሴይር ተራሮች አቅራቢያ ብቻ የሚኖሩ ሰዎችን የሚያመለክት ማጠቃለያ ነው። "እኔ የአንተን ደስታ መደምሰሴን የሚያውቁ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እስራኤል ሰው የማይኖርባት በመሆኗ ምክንያት በህዝቧ ርስት አንተ ሀሴት በምታደርግበት ጊዜ
ይህ የሚገልጸው ያህዌ ለእስራኤላውያን ርስት አድርጎ የሰጣቸውን ምድር ነው። "የእስራኤልን ምድር ሰው የማይኖርበት ባደረግሁ ጊዜ አንተ ሀሴት እንዳደረግህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በአንተ ላይም እንደዚያው አደርጋለሁ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "እኔ ምድርህን ሰው የማይኖርበት አደርጋለሁ" ወይም 2) "የአንተ ምድር ሰው የማይኖርበት በሚሆንበት ጊዜ እኔ ሀሴት አደርጋለሁ" ወይም 3) "አንተ ጠፍ/ሰው የማይኖርበት ስፍራ በመሆንህ ምክንያት ሌሎች ደስ እንዲላቸው አደርጋለሁ"

የሴይር ተራራ እና መላው ኤዶም፣ ሰው የማይኖርበት ትሆናላችሁ
ያህዌ ለህዝቅኤል ለሴይር ተራራ መስማት እንደሚችል አድርጎ መናገሩን እንዲቀጥል ይነግረዋል። መልዕክቱ ለኤዶም ህዝብ ሁሉ ነው። "የሴይር ተራራ እና መላውን ኤዶም ሰው የማይኖርባቸው አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያ... እነርሱ ያውቃሉ
"እነርሱ" የሚለው ቃል ሊያመለክት የሚችለው 1) "የመሬት ሰዎች" ወይም 2) "የእስራኤል እና የይሁዳ ሰዎች"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 36

1 አንተም፥ የሰው ልጅ ሆይ፥ ለእስራኤል ተራሮች ትንቢት ተናገር እንዲህም በላቸው ፥ 'የእስራኤል ተራሮች ሆይ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ!' 2 ጌታ
እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ጠላት በእናንተ ላይ "እሰይ! የጥንት ከፍታዎች ለእኛ ርስት ሆነዋል" ብሎአል። 3 ስለዚህ ትንቢት ተናገር እንዲህም በል፥ 'ጌታ
እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ባድማ በመሆናችሁና ከሁሉም አቅጣጫ ከመጣባችሁ ጥቃት የተነሳ ለሌሎች አሕዛብ ርስት ሆናችኋል፤ የተናጋሪዎች ከንፈር
መተረቻና የአሕዛብ ማላገጫም ሆናችኋል። 4 ስለዚህ፥ እናንተ የእስራኤል ተራሮች ሆይ፥ የጌታን የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ፥ ጌታ እግዚአብሔር ለተራሮችና
ለኮረብቶች፥ ለፈሳሾችና ለሸለቆች ለምድረ በዳዎች ባዶ ለሆኑትም በዙሪያ ላሉት ለቀሩት አሕዛብ ምርኮና መሳቂያ ለሆኑት ከተሞች እንዲህ ይላል 5 ስለዚህ
ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ያሳድዱአትና ይበዘብዙአት ዘንድ በልባቸው ሁሉ ደስታና በነፍሳቸው ንቀት ምድሬን ርስት አድርገው ለራሳቸው በወሰዱ
በቀሩት አሕዛብና በኤዶምያስ ሁሉ ላይ በቅንዓቴ እሳት ተናግሬአለሁ 6 ስለዚህ ስለ እስራኤል ምድር ትንቢት ተናገር፥ ለተራሮችና ለኮረብቶችም ለፈሳሾችና
ለሸለቆችም እንዲህ በል። ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እነሆ፥ የአሕዛብን ስድብ ስለ ተሸከማችሁ በቅንዓቴና በመዓቴ ተናግሬአለሁ 7 ስለዚህ ጌታ
እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በዙሪያችሁ ያሉ አሕዛብ ስድባቸውን በእርግጥ ይሸከማሉ ብዬ ምያለሁ። 8 እናንተ የእስራኤል ተራሮች ግን ወደ እናንተ
ተመልሰው የሚመጡበት ቀን ቀርቧልና፥ ቅርንጫፎቻችሁን ታቈጠቍጣላችሁ፥ ለሕዝቤ ለእስራኤልም ፍሬአቸሁን ትሰጣላችሁ። 9 እነሆ፥ እኔ ለእናንተ ነኝና ወደ
እናንተም እመለከታለሁ፥ እናንተም ትታረሳላችሁ ይዘራባችሁማል። 10 ስለዚህም እናንተ ተራሮች ሆይ በእስራኤል ቤት ሁሉ ሰዎችን አበዛባችኋለሁ። ሁሉም!
ከተሞች የሰዎች መኖሪያ ይሆናሉ ባድማዎቹም ስፍራዎች ይሠራሉ። 11 እናንተ ተራሮች ሆይ ሰውንና እንስሳውንም አበዛባችኋለሁ፥ እነርሱም ይበዛሉ ያፈሩማል።
ቀድሞ እንደነበራችሁት የሰዎች መኖሪያ አደርጋችኋለሁ፥ ከቀድሞ ይልቅ አበለጥጋችኋለሁ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ። 12 በእናንተ ላይ
እንዲረማመዱ የሕዝቤን የእስራኤልን ሰዎችን አመጣቸዋለሁ። እነርሱም ይወርሱዋቸዋል ርስትም ትሆኑላቸዋላችሁ፥ ከእንግዲህም የልጆቻቸው ሞት ምክንያት
አትሆኑም። 13 ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እነርሱ "እናንተ ሰው በሊታ ናችሁ የሕዝባችሁም ልጆች አልቀዋል" ብለዋችኋልና 14 ስለዚህ ከእንግዲህ
ወዲያ ሰው በሊታ አትሆኑም፥ ዳግመኛም ሕዝብችሁን በሚሞቱ ሰዎች ምንንያት እንዲያለቅሱ አታደርጉም ይላል ጌታ እግዚአብሔር። 15 ዳግመኛም የአሕዛብን
ስድብ አላሰማብሽም፤ ዳግመኛም የአሕዛብን ስድብ አትሸከሚም፥ ዳግመኛም ሕዝብሽን አታሰናክዪም፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር። 16 የእግዚአብሔርም ቃል
ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፥ 17 "የሰው ልጅ ሆይ፥ የእስራኤል ቤት በምድራቸው በተቀመጡ ጊዜ በመንገዳቸውና በሥራቸው አረከሱአት፥ መንገዳቸውም
በፊቴ እንደ መርገም አደፍ ነበረ። 18 በምድሪቱም ላይ ስላፈሰሱት ደም በጣዖቶቻቸውም ስላረከሱአት መዓቴን አፈሰስሁባቸው። 19 ወደ አሕዛብም
በተንኋቸው ወደ አገሮችም ተዘሩ እንደ መንገዳቸውና እንደ ሥራቸው መጠን ፈረድሁባቸው። 20 ወደ ሌሎች ሕዝቦች ሄዱ። በሄዱም ጊዜ ሰዎች ስለነርሱ 'አሁን
እነዚህ ከአገራቸው የተፈናቅሉ የእግዚአብሔር ሕዝብ እነዚህ ናቸው?' በማለታቸው ቅዱስ ስሜን አረከሱ። 21 እኔ ግን የእስራኤል ቤት በመጡባቸው በአሕዛብ
መካከል ስላረከሱት ስለ ቅዱስ ስሜ ስል ራራሁላቸው። 22 ስለዚህ ለእስራኤል ቤት እንዲህ በል፥ 'ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ የእስራኤል ቤት ሆይ፥
ይህን የማደርገው በሄዳችሁበት በአሕዛብ መካከል ሁሉ ስላረከሳችሁት ስለ ቅዱስ ስሜ ነው እንጂ ስለ እናንተ አይደለም። 23 በአሕዛብም ዘንድ የረከሰውን፥
በመካከላቸው ያረከሳችሁትን ስሜን እቀድሰዋለሁ። በዓይናቸውም ዘንድ በተቀደስሁባችሁ ጊዜ እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ አሕዛብ ያውቃሉ፥ ይላል ጌታ
እግዚአብሔር፦ 24 ከአሕዛብም መካከል እወስዳችኋለሁ ከየአገሩም ሁሉ እሰበስባችኋለሁ ወደ ገዛ ምድራችሁም አመጣችኋለሁ። 25 ከእርኩሰታችሁ ሁሉ
እንድትነጹም ጥሩ ውኃን እረጭባችኋለሁ። ከጣዖቶቻችሁም ሁሉ አጠራችኋለሁ። 26 አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ
የድንጋዩንም ልብ ከሥጋችሁ አወጣለሁ የሥጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ። 27 መንፈሴንም በውስጣችሁ አኖራለሁ በትእዛዜም መሄድ አስችላችኋለሁ ፥ ፍርዴንም
ትጠብቃላችሁ ታደርጉትማላችሁ። 28 ለአባቶቻችሁም በሰጠኋት ምድር ትኖራላችሁ ሕዝቤ ትሆናላችሁ እኔም አምላካችሁ እሆናለሁ። 29 ከርኩሰታችሁም ሁሉ
አድናችኋለሁ እህልንም እጠራዋለሁ አበዛውማለሁ ከእንግዲህም ራብን አላመጣባችሁም። 30 ደግሞም የራብን ስድብ በሕዝቦች መካከል እንዳትሸከሙ
የዛፍን ፍሬና የእርሻውን ቡቃያ አበዛለሁ። 31 ከዚያም ክፉውን መንገዳችሁንና መልካም ያይደለውን ሥራችሁንም ታስባላችሁ፥ ስለ በደላችሁና ስለ
ርኩሰታችሁም ራሳችሁን ትጸየፋላችሁ። 32 ይህን ያደረኩት ስለ እናንተ ብዬ እንዳይደለ እወቁ-ይላል ጌታ እግዚአብሔር። የእስራኤል ቤት ሆይ፥ ስለ
መንገዳችሁ እፈሩና ተዋረዱ። 33 ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ክእርኩሰታችሁ ሁሉ ባነጻኋችሁበት ቀን በከተሞቻችሁ እንድትኖሩ የፈረሱትንም ሥፍራዎች
እንደገና እንድትጠግኑ አደርጋችኋለሁ። 34 ባድማ የነበረች ምድር በመንገደኛ ሁሉ ዓይን ባድማ ባል ድረስ ትታረሳለች። 35 ሰዎችም፥ "ባድማ የነበረች ይህች
ምድር እንደ ዔድን ገነት ሆናለች የፈረሱት ባድማ የሆኑት የጠፉትም ከተሞች ተመሸገዋል ሰውም የሚኖርባቸው ሆነዋል" ይላሉ። 36 በዙሪያችሁም ያሉ አሕዛብ
እኔ እግዚአብሔር የፈረሱትን ስፍራዎች እንደ ሠራሁ ውድማ የሆነውንም እንደገና እንደተከልሁ ያውቃሉ፥ እኔ እግዚአብሔር ተናግሬአለሁ፥ እኔም አደርገዋለሁ።
37 ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ስለዚህ ደግሞ እንደመንጋ እንዳበዛቸው የእስራኤል ቤት ይጠይቁኛል። 38 ለእግዚአብሔሬእንደ ተለዩ በጎች፥
በበዓላቶችዋ ቀን እንደሚሆኑ እንደ ኢየሩሳሌም በጎች፥ እንዲሁ የፈረሱት ከተሞች በሰዎች መንጋ ይሞላሉ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ።

Ezekiel 36:1

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ሕዝቅኤልን ትንቢት እንዲናገር ይነግረዋል። ሕዝቅኤል የሚናገረው ለእስራኤል ተራሮች ነው፣ ነገር ግን ለመላው የእስራኤል ሰዎች ነው።

የሰው ልጅ

"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ለእስረኤል ተራሮች ትንቢት ተናገር

እግዚአብሔር ሕዝቅኤል ለተራሮች ሰዎች እንደሆኑ አድረጎ እንዲናገር ይፈልጋል። መልዕክቱ ለእስራኤል ሰዎች ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አሃ

ይህ የደስታ ስሜት መግለጫ ነው። "በጣም ደስ ተሰኝቻለሁ" ወይም "ይህ ድንቅ ነገር ነው" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል።

ጥንታዊ ከፍተኛ ስፍራዎች

"በጣም ጥንታዊ ተራሮች።" ይህ የእስራኤልን ከፍተኛ ተራሮች ያመለክታል።

የእኛ ርስት ሆንክ

"አሁን የእኛ ሆንክ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አንተ ጠፍ በመሆንህ ምክንያት
"ጠፍ" የሚለው ረቂቅ ስም "ሰው የማይኖርበት" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "አንተ የእስራኤል ተራራ ሰው የማይኖርበት በመሆንህ ምክንያት "በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ከሁሉም አቅጣጫ ከመጣብህ ጥቃት የተነሳ
"ከሁሉም አቅጣጫ ጥቃት ስለደረሰብህ" ወይም "ጠላቶችህ በሁሉም አቅጣጫ ስላጠቁህ"

የሀሜተኛ ከንፈሮች እና ምላሶች መነጋገሪያ፣ የሰዎች መተረቻ ሆንክ
እዚህ ስፍራ፣ "ከንፈሮች" እና "ምላሶች" የሚወክሉት የሰዎችን ንግግር ነው። "ሰዎች ስለ አንተ መጥፎ ነገሮችን ይናገራሉ፣ አገሮችም ደግሞ ስለ አንተ ክፉ ወሬ ያወራሉ" (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 36:4

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ ያህዌ ለሕዝቅኤል ለእስራኤል ተራሮች ትንቢት እንዲናገር መንገሩን ይቀጥላል። መልዕክቱ ለመላው የእስራኤል ሰዎች ነው።

አጠቃላይ መረጃ:
እዚህ ስፍራ፣ ዩዲቢ እንደሚያደርገው፣ ጽሁፉን ይበልጥ በተጠይቃዊ ስርአት ለማቀናጀት አያያዥ ሀረግ መጠቀሙ ተገቢ ሊሆን ይችላል። (ሀረጎችን/ ቁጥሮችን ማቀናጀት የሚለውን ይመልከቱ)

የጌታ ያህዌን ቃል መስማት
"የጌታ ያህዌን መልዕክት መስማት"

ሰው የማይኖርበት ምድረበዳ
"ሰው የማይኖርበት/ጠፍ" የሚለው ረቂቅ ስም "ሰው የማይኖርባቸው ከተሞች" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "በውስጣቸው ምንም ሰው የማይኖርባቸው የጠፉ ከተሞች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰው የለቀቃቸው/የተተዉ ከተሞች
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች ለቀዋቸው የሄዱባቸው ከተሞች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የተዘረፉ
"ጠላት የሰረቃቸው"

በከበቧቸው ሌሎች አገራት ዘንድ መሳለቂያ
"እነዚያ ከበቧቸው ሌሎች አገራት ይሳለቃሉ

በቁጣዬ/በንዴቴ እሳት
ይህ የያህዌን ቁጣ እሳት እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። ያህዌ እስራኤልን በጣም ይወዳታል፣ ስለዚህም ሌሎች አገሮች ሲያላግጡባት ይቀናል ደግሞም ይቆጣል። "በጥልቅ ቅናቴ ምክንያት" ወይም "በታላቅ ቁጣዬ ምክንያት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በኤዶም እና በሁሉም ላይ
"ደግሞም በመላው ኤዶም ላይ"

ምድሬን ሲይዙ በልባቸው ደስታ እና በመንፈሳቸው ንቀት ሁለቱም አለ
"ልብ" እና "መንፈስ" የሰውን ውስጣዊ ማንነት ይወክላሉ። ደስታው እና ንቀት በአንድነት የመኖሩ ሃሳብ "መደሰት" እና "መናቅ" በሚሉ ግሶች ሊገለጽ ይችላል። "የእስራኤልን ህዝብ የሚንቅ እና ምድሬን ሲወስዱ የሚደሰቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እነሆ!
እዚህ ስፍራ "እነሆ" የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚሆነው ትኩረት ይሰጣል። "በእርግጥ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

በሀይሌ/በንዴት እና በቁጣዬ
"ንዴት" እና "ቁጣ" የሚሉት ቃላት በመሰረቱ ተመሳሳይ ነገሮች ናቸው። በአንድነት ሆነው የእርሱን ቁጣ ጥልቀት ይገልጻሉ። "እጅግ በመቆጣቴ ምክንያት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

የሌሎችን አገራት ስድብ ተሸክማችኋል
"ሌሎች አገራት ሰደቧችሁ" ወይም "ሌሎች አገራት ተሳለቁባችሁ"

Ezekiel 36:7

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ ለእስራኤል ተራሮች የያህዌን መልዕክት ይቀጥላል። መልዕክቱ ለእስራኤል ሰዎች የታሰበ ነው።

እኔ እራሴ ለመማል እጄን አነሳለሁ
እዚህ ስፍራ "እጄን አነሳለሁ" የሚለው እርሱ በእርግጥ ለማድረግ የማለውን እንደሚያደርግ የሚያሳይ ምልክታዊ ድርጊት ነው። "እኔ በእርግጥ ምያለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

የከበቧችሁ አገራት በእርግጥ ሀፍረተቸውን ይሸከማሉ
ሀፍረት የሚደርስባቸው ህዝቦች የተገለጹት ሀፍረታቸውን እንደሚሸከሙት ተደርጎ ነው። "እነዚያ የከበቧችሁ ህዝቦች በእርግጥ ያፍራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተን የከበቡ
"እናንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእስራኤልን ተራሮች ነው።

Ezekiel 36:8

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ ለእስራኤል ተራሮች የያህዌን መልዕክት ይቀጥላል። መልዕክቱ ለእስራኤል ሰዎች የታሰበ ነው።

እናንተ ቅርንጫፍ ታበቅላላችሁ ደግሞም ፍሬ ታፈራላችሁ
እዚህ ስፍራ "እናንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእስራኤልን ተራሮች ሲሆን፣ በተራሮቹ ላይ የሚገኙትን ፍሬ የሚሰጡ ዛፎች ይወክላል። "የእናንተ ዛፎች ቅርንጫፍ ያበቅላሉ ደግሞም ፍሬ ይሰጣሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ፣ እኔ
"ትኩረት ስጡ፣ ምክንያቱም እኔ የምናገረው እውነተኛም ጠቃሚም ነው፡ እኔ"

እኔ የእናንተ ነኝ
"እኔ ለእናንተ መልካም ነገሮችን ማድረግ እሻለሁ።" "እናንተ" የሚለው ቃል የእስራኤልን ተራሮች ያመለክታል።

ለእናንተ ሞገስ እሰጣለሁ
"ለእናንተ መልካም እሆናለሁ"

ትታረሳላችሁ ዘርም ይዘራባችኋል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ህዝቤ፣ እስራኤል ምድራችሁን ያርሳል ዘርም ይዘራባችኋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ezekiel 36:10

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ ለእስራኤል ተራሮች የያህዌን መልዕክት ይቀጥላል። መልዕክቱ ለእስራኤል ሰዎች የታሰበ ነው።

ስለዚህ በእናንተ ላይ አበዛለሁ
ያህዌ ለተራሮች እየተናገረ ነው። ይህ ግለጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "ስለዚህ፣ የእስራኤል ተራሮች፣ በእናንተ ላይ አበዛለሁ/ፍሬያማ አደርጋችኋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መላው የእስራኤል ቤት ጭምር
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚወክለው ሰዎችን ነው። "መላው የእስራኤል ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከተማይቱ መልሳ ሰው ይኖርባታል ደግሞም ፍርስራሾቿ ይታደሳሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "መልሶ ሰው የሚኖርባት ከተማ ትሆናለች ደግሞም ፍርስራሾቿን መልሰው ይጠግናሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ይበዛሉ ፍሬያማም ይሆናሉ
እዚህ ስፍራ "ፍሬያማ መሆን" የሚለው ፈሊጥ ሲሆን ትርጉሙ ብዙ ልጆች እና ትውልድ ማግኘት ማለት ነው። "በጣም ብዙ ህዝብ ይሆናሉ ደግሞም ብዙ ልጆች ይኖራቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አስቀድሞ እንደነበራችሁት ብዙ ሆናችሁ ትኖራላችሁ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በእናንተ ተራሮች ላይ አስቀሰድሞ ይኖር እንደነበረው ብዙ ህዝብ ይኖራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ
ያህዌ እርሱ ያህዌ እንደሆነ ሰዎች ያውቃሉ ሲል፣ የመጨረሻው ከፍተኛ ስልጣን እና ሀይል ያለው እውነተኛው አምላክ እርሱ ብቻ እንደሆነ ማወቅ እንደሚገባቸው እየተናገረ ነው። ይህ በሕዝቅኤል6፡7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ብቸኛው እውነተኛ አምላክ እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ" ወይም "እኔ ያህዌ የመጨረሻው ስልጣን እና ሀይል እንዳለኝ እወቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ይወርሷችኋል፣ እናም እናንተ የእነርሱ ርስት ትሆናላችሁ
በተራሮች የሚኖሩ ህዝቦች እና የእስራኤል ምድር በቋሚነት የሚገለጸው ሰዎቹ እነርሱን እንደሚወርሱ ተደርጎ ነው። "አናንተን በቋሚነት/ለሁሌም ይወርሷችኋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህ ልጆቻቸው እንዲሞቱ ምክንያት አትሆኑም
ቀድሞ ልጆች ይሞቱ የነበሩት በምድሪቱ በቂ ምግብ ስላልነበረ እንደሆነ በውስጠ ታዋቂነት ተገልጽዋል። አሁን ምድሪቱ በቂ ምግብ ትሰጣለች። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 36:13

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ ለእስራኤል ተራሮች የያህዌን መልዕክት ይቀጥላል። መልዕክቱ ለእስራኤል ሰዎች የታሰበ ነው።

እነርሱ እንዲህ ይሏችኋል
"ለእናንተ ለተራሮች ሌሎች አገራት እንዲህ ይሏችኋል"

እናንተ ሰዎችን ፈጃችሁ
በእስረኤል በቂ ምግብ ባለመብቀሉ ብዙ ሰዎች መሞታቸው የእስራኤል ተራሮች ሰዎችን እንደበሉ ተደርጎ ተገልጽዋል። "ብዙ ሰዎች እንዲሞቱ ምክንያት ሆናችኋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የአገራችሁን ልጆች አሳዝናችኋል
"የህዝባችሁ ልጆች እንዲሞቱ ምክንያት ሆናችኋል"

ከእንግዲህ ሰዎችን አትፈጁም
በእስራኤል በቂ ምግብ ባለመብቀሉ የሰዎች መሞት የተገለጸው የእስራኤል ተራሮች ሰዎችን እንደፈጁ ተደርጎ ነው። "ከእንግዲህ ሰዎች እንዲሞቱ ምክንያት አትሆኑም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ራሱን በስሙ የሚገልጸው/የሚምለው፤ የተናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳወቅ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ። "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህ የሌሎችን ህዝቦች ስድብ እንድትቀበሉ አልፈቅድም
ይህ ተራሮቹ ሰዎች ሲሰድቧቸው እንደሚሰሙ አድርጎ ይገልጻል። "ከእንግዲህ ሌሎች ህዝቦች እንዲሰድቧችሁ አልፈቅድም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህ የህዝቦችን ሀፍረት አትሸከሙም
ሀፍረት መድረሱ የተገለጸው ተራሮቹ ሀፍረት እንደሚሸከሙ ተደርጎ ነው። "ከእንግዲ ሰዎች እንድታፍሩ አያደርጓችሁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ወይም አገራችሁ እንድትወድቅ ምክንያት...
እዚህ ስፍራ "መውደቅ" የሚለው በጦርነት መሸነፍ ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ወይም ህዝባችሁ በመሸነፍ እንዲሰቃይ ምክንያት..." በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 36:16

የያህዌ ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የተናገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ነናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ/ያህዌ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

የእስራኤል ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው የሚወክለው ሰዎችን ነው። "የእስራኤልን ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በእነርሱ መንገዶች እና በድርጊቶቻቸው
"እነርሱ በሚኖሩበት መንገድ እና በሚያደርጓቸው ነገሮች"

መንገዶቻቸው በፊቴ እንደ ቆሸሸ የሴት የወር አበባ ጨርቅ ነው
ይህ ሰዎች ለቆሸሸ የሴት የወር አበባ ጨርቅ ካላቸውን ምላሽ ጋር ተነጻጽሯል። ይህ ባህሪያቸው ለያህዌ ምን ያህል ደስ እንደማያሰኝ ትኩረት ይሰጣል። "መንገዶቻቸው በወር አበባ እንደቆሸሸ ጨርቅ ደስ የማያሰኙኝ ነበሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሴት ወር አባባ
x

Ezekiel 36:19

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ እስራኤል ለሕዝቅኤል መናገሩን ቀጥሏል።

በአገራት መሃል በትኛቸዋለሁ፤ በምድሪቱ በሙሉ ተበትነዋል
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። በሕዝቅኤል 12፡15 ላይ ተመሳሳይ የሆነው ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እንዲለያዩ እና በተለያየ ምድር እንዲኖሩ አደረግሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በምድር ሁሉ ላይ ተበትነው ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኔ በምድር ሁሉ ላይ በተንኳቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

መንገዶቻቸው እና ድርጊቶቻቸው
እዚህ ስፍራ "መንገዶች" እና "ድርጊቶች" የሚሉት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። "ያደረጓቸው ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ቅዱስ ስሜን ናቁ
እዚህ ስፍራ "ስም" የሚወክለው ያህዌን እና ክብሩን ነው። "በእኔ አፌዙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሰዎች በ...ጊዜ
"ሌሎች ሰዎች...በማለታቸው"

በእርግጥ እነዚህ የያህዌ ህዝቦች ናቸው"
ሰዎች ባዩት ነገር በመደነቃቸው ይህን ጥያቄ ይጠይቃሉ። "እነዚህ የያህዌ ህዝብ መሆናቸውን ላምን አልችልም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእርሱ ምድር ተወርውረው ስለተጣሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ያህዌ ከምድሩ አውጥቶ ስለጣላቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ ምድር
ይህ የእስራኤልን ምድር ያመለክታል

ነገር ግን ወደዚያ በሚሄዱበት ጊዜ የእስራኤል ቤት በአገራት መሃል ስላረከሱት ስለ ቅዱስ ስሜ እጠነቀቃለሁ
እዚህ ስፍራ "ስም" የሚወክለው ያህዌን እና ክብሩን ነው። "የእስራኤል ቤት ወደ ተለያዩ አገራት ሲሄድ፣ እኔ እንድዋረድ ያደርጋሉ፣ ነገር ግን ሰዎች እኔ ቅዱስ መሆኔን እንዲያውቁ እፈልጋለሁ። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ለቅዱሱ ስሜ ጥበቃ አደርጋለሁ
"ለቅዱሱ ስሜ እጠነቀቃለሁ"

የእስራኤል ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው የሚወክለው ሰዎችን ነው። "የእስራኤል ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 36:22

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል መናገሩን ቀጥሏል፤ ደግሞም ለእስራኤል መልዕክት ይሰጠዋል።

የእስራኤል ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው የሚወክለው ሰዎችን ነው። "የእስራኤል ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ እናንተ ስል
"በእናንተ ምክንያት" ወይም "እናንተን ለመርዳት ስል"

ነገር ግን እናንተ በየደረሳችሁበት በህዝቦች መሃል ለናቃችሁት ለቅዱሱ ስሜ
እዚህ ስፍራ "ስም" የሚወክለው ያህዌን እና ክብሩን ነው። "ነገር ግን በእናንተ ምክንያት ያፌዙብኝ የተለያዩ አገራት ሰዎች እኔ ቅዱስ መሆኔን ያውቃሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በሄዳችሁበት አገራት ሁሉ በህዝቦች መሃል ተንቃችኋል
"የአገራት ህዝቦች በየሄዳችሁበት እንዲያፌዙ ምክንያት ሆናችኋል"

Ezekiel 36:24

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለእስራኤል በሕዝቅኤል በኩል መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

ከጉድፋችሁ ሁሉ እንድትነጹ ንጹህ ውሃ እረጫችኋለሁ፣ እናም ከጣኦቶቻችሁ ሁሉ አነጻችኋለሁ
ያህዌ ህዝቡን ይቅር ማለቱ እና ከዚህ በኋላ ከኃጢአት እንዲነጹ ማድረጉ የተገለጸው በውሃ እንደሚያነጻቸው ተደርጎ ነው። "ትነጻላችሁ" የሚለው ሀርግ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በንጹህ ውሃ እንደምረጫችሁ ንጹህ አደርጋችኋለሁ፣ ደግሞም ጣኦቶችን ማምለክ እንድታቆሙ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

እድፈቶቻችሁ ሁሉ
"ንጹህ እንዳትሆኑ የሚያደርጉ ነገሮች ሁሉ"

Ezekiel 36:26

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለእስራኤል በሕዝቅኤል በኩል መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

በውስጠኛው ክፍላችሁ አዲስ ልብ እና አዲስ መንፈስ እሰጣችኋለሁ፤ ደግሞም የስጋ ልብ ስለምሰጣችሁ ከውስጣችሁ የድንጋይ ልብ አወጣለሁ።
ያህዌ ህዝቡ ከእንግዲህ ግትር እንዳይሆን ያደርጋል፤ ያህዌን መውደድ እና ማገልገል የተገለጸው አሮጌ ልባቸውን እንደ ማውጣት እና አዲስ ልብ እና መንፈስ እንደ መስጠት ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አዲስ ልብ እና መንፈስ
እዚህ ስፍራ "ልብ" እና "መንፈስ" የሚለው የሚወክለው የሰውን አስተሳሰብ፣ ዝንባሌ፣ እና ስሜት ነው። "ልብ" እና "መንፈስ" የሚለው በሕዝቅኤል 11:9 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

በውስጠኛው ዋንኛ ክፍላችሁ
"በውስጣችሁ" ወይም "በእናንተ ውስጥ"

የድንጋይ ልብ
ይህ የሚገልጸው ሰዎች ልባቸው ከድንጋይ የተሰራ ይመስል ግትር መሆናቸውን ነው። "የድንጋይ ልብ" የሚለው በሕዝቅኤል 11:19 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እንደ ድንጋይ ጠንካራ የሆነ ልብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ስጋችሁ
"አካላችሁ"

የስጋ ልብ
ሰዎች ያህዌን ለማገልገል ፈቃደኞች መሆናቸው የተገለጸው ልባቸው እንደ ስጋ ለስላሳ እንደሆነ ተደርጎ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 11:19 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እንደ ስጋ ለስላሳ የሆነ ልብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በህጌ እንድትሄዱ አደርጋለሁ
በአንዳች መንገድ የሚሰሩ ወይም የሚያከናውን ሰው የተገለጸው የሰውየው እርምጃ ተደርጎ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 11:20 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "በህጌ እንድትሄዱ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 36:29

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለእስራኤል በሕዝቅኤል በኩል መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

ንጹህ ካልሆናችሁበት ሁሉ አድናችኋለሁ
በያህዌ ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ነገር የተገለጸው በአካል ንጹህ እንዳልሆነ ነገር ተደርጎ ነው። "እንዳልቀበላችሁ ከሚያደርጋችሁ ነገር ሁሉ አነጻችኋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ፍሬውን አሰበስባለሁ
"ፍሬውን እንዲመጣ እጠራዋለሁ።" ይህ ሀረግ ፍሬን የሚያቀርበው እንደ ያህዌ አገልጋይ አድርጎ ነው። "በእስራኤል ምድር ፍሬ እንዲኖር አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህ ረሃብ አላደርግባችሁም
በምድሪቱ የያህዌ ረሃብ ማድረግ የተገለጸው እርሱ በህዝቡ ላይ ረሃብ እንደሚያስቀምጥ ተደርጎ ነው። "ከእንግዲህ በዚያ ረሃብ እንዲኖር አላደርግም" ወይም "ከእንግዲህ በዚያ ምግብ እንዲታጣ አላደርግም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህ በአገራት መሃል የረሃብ ሀፍረት አትሸከሙም
ሀፍረት መደረሱ የተገለጸው ህዝቡ ሀፍረትን እንደሚሸከም ተደርጎ ነው። "ከእንግዲህ አገራት በችጋር በመሰቃየታችሁ ምክንያት ሀፍረት እንዲሰማችሁ አያደርጉም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 36:32

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለእስራኤል በሕዝቅኤል በኩል መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

ለእናንተ ስል
"ለእናንተ"

ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ራሱን በስሙ የሚገልጸው/የሚምለው፤ የተናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳወቅ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ። "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን
"ይህን እወቁ" ወይም "በዚህ እርግጠኛ መሆን ትችላላችሁ።" ያህዌ ይህን የተናገረው እርሱ ህዝቡን የሚያድሰው እነርሱ መልካም ስለሆኑ እንዳልሆነ ትኩረት ለመስጠት ነው። ይህ ሀረግ ወደ ጥቅሱ መጀመሪያ ሊወሰድ ይችላል። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህ እፈሩ ደግሞም ተዋረዱ
"ማፈር" እና "መዋረድ" የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉምን ይጋራሉ። በአንድነት ሆነው የሀፍረቱን ጥልቀት ያጎላሉ። "ስለዚህ በጣም እፈሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ከመንገዶቻችሁ የተነሳ
"ካደረጋችሁት ነገር የተነሳ"

የእስራኤል ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው የሚወክለው ሰዎችን ነው። "የእስራኤል ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የተበላሸውን መሬት ትቆፍራላችሁ
"የተበላሸውን መሬት ታርሳላችሁ"

እያለፋችሁ በሄዱት ሁሉ ዐይን ፊት
ዐይኖች የሚወክሉት እይታን ነው። "አልፈው በሄዱት እና ይህን በሚያዩት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 36:35

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለእስራኤል በሕዝቅኤል በኩል መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

ከዚያም እነርሱ
"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው በእስራኤል በኩል የሚያልፉትን ሰዎች ነው።

ሰው የማይኖርባቸው ፍርስራሾች
"በውስጣቸው ማንም የማይኖርባቸው ፍርስራሾች"

እነርሱ ፈራረሱ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ጠላት ያፈራረሳቸው" ወይም 2) "ሰዎች ሊገቡባቸው የማይችሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አሁን የቀጠሩ እና ሰዎች የሚኖሩባቸው ናቸው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አሁን ህዝቡ ዳግም ገንብቷቸዋል፣ ደግሞም እንደገና በዚያ መኖር ጀምሯል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ፍርስራሻቸውን ጠግኛለሁ
"ጠላት ያፈራረሰውን ከተማ ዳግም ገንብቻለሁ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የተራቆተው ስፍራ ዳግም ተተክሎበታል
"በተራቆተው መሬት እህል ተዘርቶበታል"

Ezekiel 36:37

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል መናገሩን ቀጥሏል።

በእስራኤል ቤት እጠየቃለሁ
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው የሚወክለው ሰዎችን ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የእስራኤል ሰዎች እኔን ይጠይቁኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

እነርሱን እንደ ብዙ ህዝብ ለማብዛት
ያህዌ ህዝቡን በፍጥነት እና በቁጥር ማብዛቱ የተገለጸው እንደ በግ መንጋ እንደበዙ ተደርጎ ነው። በጎች በጣም በፍጥነት ይባዛሉ። "እንደ በግ መንጋ እንዲባዙ ማድረግ" ወይም "ሰዎቹ እንደ በጎች በፍጥነት እንዲባዙ ማድረግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በኢየሩሳሌም ያሉ መንጋዎች፣ በተወሰኑ በዓላት ለመስዋዕት እንደሚለዩ
"ለይቶ ማስቀመጥ" የሚለው ሀረግ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች ለመስዋእት ለይተው እንዳስቀመጧቸው እና ለተወሰነው በዓል ወደ እየሩሳሌም እንደሚያመጧቸው ብዙ ቁጥር ያላቸው በጎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 37

1 የእግዚአብሔርም እጅ በላዬ ነበረ እግዚአብሔርም በመንፈሱ አወጣኝ አጥንቶችም በሞሉባት ሸለቆ መካከል አኖረኝ። **2** ዙሪያውን በመካከላቸው እንዳልፍ አደረገኝ፥ እነሆ በሸለቆው ውስጥ እጅግ ብዙ ነበሩ፥ እነሆም፥ እጅግ ደርቀው ነበር። **3** እርሱም፥ "የሰው ልጅ ሆይ፥ እነዚህ አጥንቶች እንደገና በሕይወት ሊኖሩ ይችላሉን?" አለኝ። እኔም። ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፥ ይህን የምታውቀው አንተ ብቻ ነህ!" አልሁ። **4** እርሱም እንዲህ አለኝ፥ "በእነዚህ አጥንቶች ላይ ትንቢት ተናገር እንዲህም በላቸው፥ 'እናንተ የደረቃችሁ አጥንቶች ሆይ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ሰሙ። **5** ጌታ እግዚአብሔር ለእነዚህ አጥንቶች እንዲህ ይላል። እነሆ፥ መንፈስን አገባባችኋለሁ በሕይወትም ትኖራላችሁ። **6** ጅማትም እሰጣችኋለሁ ሥጋንም አወጣባችኋለሁ በእናንተም ላይ ቁርበትን እዘረጋለሁ ትንፋሽንም አገባባችኋለሁ በሕይወትም ትኖራላችሁ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ። **7** እንዳዘዘኝም ትንቢት ተናገርሁ ስናገርም ፥ እነሆ የሚያናውጥ ድምፅ ሆነ፥ አጥንቶችም አጥንት ከአጥንት ጋር ተቀራረቡ። **8** እኔም አየሁ፥ እነሆም፥ ጅማት ነበረባቸው ሥጋም ወጣ ቁርበትም በላያቸው ተዘረጋ፥ ህይወት ግን አልነበራቸውም። **9** እርሱም፦ የሰው ልጅ ሆይ፥ ትንቢት ተናገር፥ ለነፋስ ትንቢት ተናገር፥ ለነፋስም 'ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦' መንፈስ ቅዱስ! ከአራቱ ነፋሳት ዘንድ ና፥ እነዚህም የተገደሉት በሕይወት ይኖሩ ዘንድ እፍ በልባቸው" በል አለኝ። **10** እንዳዘዘኝም ትንቢት ተናገርሁ፥ የእግዚአብሔርም መንፈስ ገባባቸው ሕያዋንም ሆኑ! እጅግም ታላቅ ሠራዊት ሆነው በእግራቸው ቆሙ። **11** እርሱም እንዲህ አለኝ፥ "የሰው ልጅ ሆይ፥ እነዚህ አጥንቶች የእስራኤል ቤት ሁሉ ናቸው። እነሆ! አጥንቶቻችን ደርቀዋል ተስፋችንም ጠፍቶአል ፈጽመንም ተቈርጠናል ብለዋል። **12** ስለዚህ ትንቢት ተናገር እንዲህም በላቸው፥ 'ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ሕዝቤ ሆይ፥ እነሆ፥ መቃብራችሁን እከፍታለሁ ከመቃብራችሁም አወጣችኋለሁ፥ ወደ እስራኤልም ምድር እመልሳችኋለሁ! **13** ሕዝቤ ሆይ፥ መቃብራችሁን በከፈትሁ ጊዜ ከመቃብራችሁም ባወጣኋችሁ ጊዜ፥ እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ። **14** መንፈሴንም በውስጣችሁ አሳድራለሁ፥ እናንተም በሕይወት ትኖራላችሁ፥ እኔ እግዚአብሔር እንደሆንኩ ባወቃችሁ ጊዜ በገዛ ምድራችሁም እንድታርፉ አደርጋለሁ። እኔ እግዚአብሔር ተናግሬአለሁ አደርገውማለሁ ይላል እግዚአብሔር። **15** የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፥ **16** "አንተ፥ የሰው ልጅ ሆይ፥ አንድ በትር ውሰድና። 'ለይሁዳና ለባልንጀሮቹ ለእስራኤል ልጆች'ብለህ በላዩ ጻፍ። 'ሌላም በትር ውሰድና 'ለኤፍሬም በትር ለዮሴፍና ለባልንጀሮቹ ለእስራኤል ቤት ሁሉ' ብለህ በላዩ ጻፍ። **17** ከዚያም በእጅህ ውስጥ አንድ እንዲሆኑ ሁልቱንም በትሮች በአንድ ላይ ያዛቸው። **18** ሕዝብህም ፥ 'ይህ የምታደርገው ነገር ምን ማለት እንደሆነ አትነግረንምን? ብለው በተናገሩህ ጊዜ፥ **19** አንተ። 'ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እነሆ፥ በኤፍሬም እጅ ያለውን የዮሴፍን በትር ባልንጀሮቹንም የእስራኤልን ነገዶች እወስዳለሁ፥ ከይሁዳ በትር ጋር አጋጥማቸዋለሁ አንድ በትርም አደርጋቸዋለሁ፥ በእጄም ውስጥ አንድ ይሆናሉ' በላቸው። **20** የጻፍክባቸውንም በትሮች በዓይናቸው ፊት በእጅህ ያዛቸው። **21** ከዚያም እንዲህ በላቸው፥ 'ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እነሆ፥ የእስራኤልን ልጆች ከሄዱባቸው ከአሕዛብ መካከል የምወስድበት ጊዜ ደርሷል ከአካባቢው አገሮች ሁሉ እሰበስባቸዋለሁ ወደ ገዛ ምድራቸውም አመጣቸዋለሁ። **22** በምድሪቱም ውስጥ በእስራኤል ተራሮች ላይ አንድ ሕዝብ አደርጋቸዋለሁ፥ አንድ ንጉሥም በሁላቸው ላይ ይነግሣል ከዚያ ወዲያ ሁለት ሕዝብ አይሆኑም፥ ከዚያ ወዲያም ሁለት መንግሥቶች ሆነው አይለዩም። **23** ከዚያ ወዲያም በጣዖቶቻቸውና በርኩሰታቸው በመተላለፋቸውም ሁሉ አይረክሱም፥ ኃጢአትም ከሠሩባት ዓመፅ ሁሉ አድናቸዋለሁ አነጻቸውማለሁ ሕዝብም ይሆኑኛል እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ። **24** ባሪያዬም ዳዊት በላያቸው ይነግሳል። ለሁሉም አንድ እረኛ ይሆንላቸዋል በፍርዴም ይሄዳሉ ትእዛዜንም ይጠብቃሉ ያደርጓትማል። **25** አባቶቻችሁም በኖሩበት ለባሪያዬ ለያዕቆብ በሰጠኋት ምድር ይኖራሉ እነርሱና ልጆቻቸው የልጅ ልጆቻቸውም ለዘላለም ይኖሩባታል ባሪያዬም ዳዊት ለዘላለም አለቃ ይሆናቸዋል። **26** ከእነርሱ ጋር የሰላምን ቃል ኪዳን አደርጋለሁ፥ ከእነርሱም ጋር የዘላለምም ቃል ኪዳን ይሆናል። እኔም አጸናቸዋለሁ አበዛቸውማለሁም መቅደሴንም ለዘላለም በመካከላቸው አኖራለሁ። **27** ማደሪያዬም በእነርሱ ዘንድ ይሆናል፤ ይሆናል እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ እነርሱም ሕዝብ ይሆኑኛል። **28** መቅደሴም ለዘላለም በመካከላቸው በሆነ ጊዜ፥ እኔ እስራኤልን ለራሴ የለየሁ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ አሕዛብ ያውቃሉ።

Ezekiel 37:1

አጠቃላይ መረጃ:
ሕዝቅኤል መናገሩን ቀጥሏል።

የያሕዌ እጅ በእኔ ላይ ነበር
"እጅ" የሚለው ቃል ብዙውን ጊዜ የሚውለው የአንድን ሰው ሀይል ወይም ድርጊት ለማመልከት ነው። የአንድ ሰው እጅ በሌላ ሰው ላይ መሆን፣ የዚያን ሰው በሌላኛው ላይ ሀይል ያለው መሆን ያመለክታል። ተመሳሳይ የሆነው "የያህዌ እጅ በእኔ ላይ ነው" የሚለው በሕዝቅኤል 1:3 ላይ የሚገኘው ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በ...መካከል
"በ...መሃል"

እየዞረ እየዞረ/እየተሽከረከረ
"በሁሉም አቅጣጫ"

እነሆ!
እዚህ ስፍራ "እነሆ!" የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚሆነው አስደናቂ መረጃ ትኩረት እንድንሰጥ ያነቃናል።

የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

Ezekiel 37:4

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል እየተናገረ ነው።

የያህዌን ቃል አድምጡ
"የያህዌን መልዕክት አድምጡ"

እነሆ
"ተመልከቱ" ወይም "አድምጡ" ወይም " ቀጥሎ ለምነግራችሁ ነገር ትኩረት ስጡ"

እስትንፋስ እንድጨምርባችኋለሁ
"እስትንፋስ" የሚለው ስም "ተነፈሰ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "እስትንፋስ እሰጣችኋለሁ/እንድትተነፍስ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እስትንፋስ
በዚህ ሀረግ የሚገኘው "እስትንፋስ" የሚለው የዕብራይስጡ ቃል በጥቂት ዘመናዊ ቅጂዎች "መንፈስ" በሚል ተተርጉሟል። እንደዚሁም በሕዝቅኤል 37:9 እንደሚገኘው "ነፋስ" በሚል ተተርጉሟል።

ጅማቶች
ጡንቻዎችን ከአጥንቶች ጋር የሚያያይዙ የሰውነት ህዋሶች።

እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ
ያህዌ እርሱ ያህዌ እንደሆነ ሰዎች ያውቃሉ ሲል፣ የመጨረሻው ከፍተኛ ስልጣን እና ሀይል ያለው እውነተኛው አምላክ እርሱ ብቻ እንደሆነ ማወቅ እንደሚገባቸው እየተናገረ ነው። ይህ በሕዝቅኤል6:7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ብቸኛው እውነተኛ አምላክ እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ" ወይም "እኔ ያህዌ የመጨረሻው ስልጣን እና ሀይል እንዳለኝ እወቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 37:7

አጠቃላይ መረጃ:
ሕዝቅኤል መናገሩን ቀጥሏል።

እኔ እንደታዘዝኩት
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል።"ያህዌ እናገር ዘንድ እንዳዘዘኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ
እዚህ ስፍራ "እነሆ" የሚለው ቃል ሕዝቅኤል በተመለከተው መደነቁን ያሳያል።

ጅማቶች
ይህ የሚያመለክተው እንደ ጠንካራ ክሮች የሆኑ እና አጥንቶችን እና ጡንቻዎችን በአንድነት የሚያያይዝን የሰውነት ክፍልን ነው። በሕዝቅኤል 37:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ነገር ግን ገና በውስጣቸው ምንም እስትንፋስ አልነበረም
"እስትንፋስ" የሚለው ስም "ተንፈሰ" በሚል ግስ ሊጻፍ ይችላል። "ነገር ግን አይተነፍሱም ነበር" ወይም "ነገር ግን በህይወት አልነበሩም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

Ezekiel 37:9

እስትንፋሱ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች: 1)"እስትንፋስ" ወይም 2) "መንፈስ" ወይም 3) "ነፋስ"

ከአራቱ ነፋሳት
"ነፋስ ሊነፍስበት ከሚችለው አራቱ አቅጣጫዎች።" ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ከሁሉም አቅጣጫዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ ተገድለው የነበሩ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እነዚህ ጠላቶች እና አደጋዎች የገደሏቸው ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ታዝዤ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ያህዌ እኔን እንዳዘዘኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 37:11

መላው የእስራኤል ቤት
"ቤት" የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች፣ በዚህ ሁኔታ ለብዙ ዘመናት የያዕቆብ ትውልድ ለሆኑት እስራኤላውያን ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ!
እዚህ ስፍራ "እነሆ" የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚሆነው ትኩረት ይሰጣል። "በእርግጥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እኛ ተቆርጠን/ተወግደን ነበር
ከምድራቸው ጠፍተው እና ተወግደው የነበሩ ህዝቦች የተገለጹት፣ አንድ ሰው የዛፍ ቅርንጫፍን ወይም ጨርቅን እንደሚቆርጥ እንደተቆረጡ ተደርጎ ነው። "አገራችን/ህዝባችን ጠፍቷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ መቃብራችሁን እከፍታለሁ፣ ከእነርሱም አንስቼ አወጣችኋለሁ
ያህዌ ህዝቡን ማደሱ እና ወደ ምድራቸው መመለሱ የተገለጸው እነርሱን መልሶ ወደ ህይወት እንደሚያመጣቸው ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 37:13

አጠቃላይ መረጃ:
እነዚህ ያህዌ ለእስራኤል ቤት የተናገራቸው ቃላት ናቸው

በመሬታችሁ ለማረፍ
x

Ezekiel 37:15

የያህዌ ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የተናገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ነናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ/ያህዌ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለይሁዳ
እዚህ ስፍራ "ለ"ማለት "መወከል" ማለት ነው። "ይሁዳን መወከል" ወይም "የይሁዳ ወግን መሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ይሁዳ
የይሁዳ ነገድ በደቡባዊ የእስራኤል ግዛት ይሁዳ ተብሎ ኖሯል። እዚህ ስፍራ ስሙ የዋለው መላውን የደቡብ ግዛት ለማመልከት ነው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ሰዎች፣ የእርሱ ተባባሪዎች
ይህ የሚያመለክተው በይሁዳ ደቡባዊ ግዛት የሚኖሩትን እስራኤላውያን ነው። "መላው የይሁዳ ጎሳ" ወይም "የይሁዳ ግዛት ክፍል የሆኑ የእስራኤል ነገዶች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ለዮሴፍ፣ የኤፍሬም ቅርንጫፍ
ዮሴፍ የኤፍሬም አባት ነበር። የኤፍሬም ነገድ በሰሜናዊ የእስራኤል ግዛት ኖሯል። እዚህ ስፍራ ስሞቹ የዋሉት መላውን የሰሜን ግዛት ለመወከል ነው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የእስራኤል ህዝብ፣ የእነርሱ ተባባሪዎች
ይህ የሚያመለክተው በእስራኤል ሰሜናዊ ግዛት ለኖሩ እስራኤላውያን ነው። "መላው የእስራኤል ነገዶች" ወይም "የእስራኤል ግዛት ክፍል የነበሩ እስራኤላውያን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ወደ አንድ በትር
"አንድ በትር ይሆኑ ዘንድ"

Ezekiel 37:18

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል መናገሩን ቀጥሏል።

እነዚህ የአንተ ነገሮች ምንድን ማለት ናቸው
"በትሮችህ ምን ማለት ናቸው" ወይም "እነዚህ በትሮች ለምን ኖሩህ"

እነሆ!
ይህ ለአንባቢው ቀጥሎ ለሚሆነው ነገር ልዩ ትኩረት እንዲሰጥ ይነግሩታል። "ተመልከት!" ወይም "አድምጥ!" ወይም " ቀጥሎ ለምነግርህ ነገር ትኩረት ስጥ!"

የዮሴፍ ቅርንጫፍ
"የዮሴፍ በትር።" ይህ የእስራኤልን መንግሥት ይወክላል። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ያ በኤፍሬም እጅ ነው
"እጅ" የሚለው ቃል ሀይልን ያመለክታል። "ያ የኤፍሬም ሀይል ነው" ወይም "የኤፍሬም ነገድ የሚገዛው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ነገድ የእርሱ ተባባሪዎች
"የእርሱ ተባባሪዎች የሆኑት ሌሎቹ የእስራኤል ነገዶች" ወይም "የዚያ ግዛት ክፍል የሆኑ ሌሎች የእስራኤል ነገዶች"

የይሁዳ ቅርንጫፍ
"የይሁዳ በትር።" ይህ የይሁዳን መንግሥት ይወክላል። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በዐይኖቻቸው ፊት
እዚህ ስፍራ ህዝቦቹ የተወከሉት በ"ዐይኖቻቸው" ሲሆን ይህም ለሚመለከቱት ነገር ትኩረት ለመስጠት ነው። "እናንተን በሚመለከቱበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 37:21

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል መናገሩን ቀጥሏል።

እነሆ
"ተመልከቱ" ወይም "አድምጡ" ወይም " ቀጥሎ ለምነግራችሁ ነገር ትኩረት ስጡ"

እነርሱ የእኔ ህዝብ ይሆናሉ፣ እኔም የእነርሱ አምላክ እሆናለሁ
ይህ በሕዝቅኤል 11:20 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

Ezekiel 37:24

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል መናገሩን ቀጥሏል።

አገልጋዬ ዳዊት
ያህዌ "ዳዊት" ያለው የዳዊትን ትውልድ ለማመልከት ነው። "አገልጋዬ ዳዊት" የሚለው በሕዝቅኤል 34:23 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "የአገልጋዬ የዳዊት ትውልድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በላያቸው አንድ እረኛ
ይህ የሚገልጸው አንድ ህዝብን የሚመራ ንጉሥ በጎችን እንደሚያሰማራ እረኛ እንደነበር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 34:23 እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእነርሱ ላይ
"በእስራኤል ህዝብ ላይ"

እንደ ትዕዛዜ ይራመዳሉ
ይህ የሚገልጸው ልክ እንደ አንድ ሰው እርምጃ ማከናወንን ወይም ማድረግን ነው። "እኔ እንዳዘዝኩት ይኖራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ቆዩ
"ኖሩ"

Ezekiel 37:26

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ እስራኤል ህዝብ እየተናገረ ነው።

እኔ አገነባለሁ
"እኔ አስተካክላለሁ" ወይም "እኔ እፈጥራለሁ"

የሰላም ቃል ኪዳን
"ሰላም የሚያመጣ ቃል ኪዳን።" ይህ በሕዝቅኤል 34:25 እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

እኔ እንደገና እመሰርታቸዋለሁ።
ያህዌ በእስራኤል ምድር እንደገና እንደሚመሰርታቸው ተጠቁሟል። "እኔ በእስራኤል ምድር አስቀምጣቸዋለሁ" ወይም "እኔ በእስራኤል ምድር በደህንነት እንዲኖሩ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አበዛቸዋለሁ
"የእነርሱ ህዝብ እንዲበዛ አደርጋለሁ"

የተቀደሰው ስፍራዬ
"የተቀደሰው መቅደሴ" ወይም "የተቀደሰው ቤተ መቅደሴ"

በእነርሱ መሃል
"በመሃላቸው"

ማደሪያዬ
"እኔ የምኖርበት ስፍራ"

እኔ አምላካቸው እሆናለሁ፣ እነርሱም የእኔ ህዝብ ይሆናሉ
ተመሳሳዩ ሀረግ በሕዝቅኤል 11:20 ላይ እንዴት አንደተተረጎመ ይመልከቱ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 38

1 የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፥ **2** "የሰው ልጅ ሆይ፥ ፊትህን በጎግ ላይና በማጎግ ምድር ላይ፥ በሞሳሕና በቶቤል ዋነኛ አለቃ ላይ አቅናበት፥ ትንቢትም ተናገርበት፥ **3** እንዲህም በል፥ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ የሞሳሕና የቶቢል ዋነኛ አለቃ ጎግ ሆይ፥ እነሆ፥ እኔ በአንተ ላይ ነኝ። **4** እመልስህማለሁ በመንጋጋህም ልጓም አገባብሃለሁ፥ አንተንና ሠራዊትህንም ሁሉ፥ ፈረሶችንና ፈረሰኞችን የጦር ልብስ የለበሱትን ሁሉ፥ ጋሻና ራስ ቍርን ሰይፍንም ያያዙትን ሁሉ፥ ታላቁን ወገን አወጣለሁ! **5** ጋሻና የራስ ቍርን የለበሱት ፋርስን ኢትዮጵያና ፉጥ ከእነርሱ ጋር ናቸው! **6** ጋሜርንና ጭፍሮቹን ሁሉ፥ በሰሜን ዳርቻም ያለውን የቴርጋማን ቤትና ጭፍሮቹን ሁሉ፥ ብዙዎች ሕዝቦች ከእነርሱ ጋር ናቸው። **7** ተዘጋጅ! አዎ፥ ራስህንና ሠራዊትህን አዘጋጅ አለቃም ሁናቸው። **8** ከብዙ ቀናትም በኋላ ትጠራልህ ክተወሰኑ ዓመታት በኋላ ክሠይፍ እያገገመች ወዳለችው፥ ከብዙ ሕዝቦችም መካከል ተሰብስበው ያለማቋረጥ ባድማ በነበሩት በእስራኤል ተራሮች ላይ ዳግም ወደ ተሰበሰቡ ትሄዳለህ። የምድሪቱ ሕዝብ ግን ከሕዝቦች መካከል ወጥተው ሁሉም ሳይፈሩ ይቀመጡባታል። **9** አንተም ትወጣለህ፥ እንደ ዐወሎ ነፋስም ትመጣለህ አንተና ጭፍሮችህ ሁሉ ከአንተም ጋር ብዙ ሕዝብ ምድሪቱን እንደ ደመና ትሸፍናላችሁ። **10** ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በዚያ ቀን በልብህ ታቅዳለህ፥ **11** ክፉ አሳብንም ታስባለህ።' እንዲህም ትላለህ፥ 'ቅጥር ወደሌላቸው መንደሮች እወጣለሁ ተዘልለው ወደሚኖሩ፥ ሁላቸው ሳይፈሩ ያለ ቅጥርና ያለ መወርወሪያ ያለ መዝጊያም ወደሚቀመጡ አገባለሁ **12** ባድማም በነበሩና በቅርቡ ሰዎች በሚኖሩባቸው ስፍራዎች ላይ፥ ከብትና ዕቃንም ይዘው ከአሕዛብም በተሰበሰቡ ሰዎች በምድርም መካከል በሚኖሩ ሕዝብ ላይ እጄን እዘረጋናምርኮን እማርካለሁ ብዝበዛንም እበዘብዛለሁ ። **13** ሳባና ድዳን የተርሴስም ነጋዴዎች ከወጣት ጦረኞቻችው ሁሉ ጋር እንዲህ ይሉሀል፥ 'የመጣኸው ምርኮን ለመማረክ ነው? ጦርህን የሰበሰብከው ብዝበዛን ለመበዝበዝ ብርንና ወርቅንስ ለመውሰድ፥ ከብትንና ዕቃንስ ለመውሰድ እጅግም ብዙ ምርኮ ለመማረክ ነው?'። **14** ስለዚህም የሰው ልጅ ሆይ፥ ትንቢት ተናገር ጎግንም እንዲህ በለው፥ 'ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በዚያ ቀን ሕዝቤ እስራኤል ሳይፈራ በተቀመጠ ጊዜ አንተ ስለእነርሱ አታውቀውምን? **15** አንተም፥ ከአንተም ጋር ብዙ ሕዝብ ሁላቸው በፈረሶች ላይ የተቀመጡ፥ ታላቅ ወገንና ብርቱ ሠራዊት፥ ከሰሜን ዳርቻ ከስፍራችሁ ትመጣላችሁ። **16** ደመና ምድርን እንድሚሸፍን ህዝቤን ታጠቃለህ። ጎግ ሆይ እንዲህ ይሆናል በዓይናቸው ፊት በተቀደስሁብህ ጊዜ አሕዛብ ያውቁኝ ዘንድ በኋለኛው ዘመን በምድሬ ላይ አመጣሃለሁ። **17** ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በእነርሱ ላይ እንደማመጣህ በዚያች ዘመን ብዙ ዓመት ትንቢት በተናገሩ በባሪያዎቼ በእስራኤል ነቢያቶች በቀደመው ዘመን ስለ እርሱ የተናገርሁ አንተ አይደለህምን? **18** በዚያም ቀን ጎግ በእስራኤል ምድር ላይ በመጣ ጊዜ መቅሠፍቴ በመዓቴ ይመጣል፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፦ **19** በቁጣዬ ትኩሳትና በመዓቴ እሳት ተናግሬአለሁ፥ በእርግጥ በዚያ ቀን በእስራኤል ምድር ጽኑ የምድር መናወጥ ይሆናል። **20** የባሕር ዓሣዎችና የሰማይ ወፎች የምድረ በዳም አራዊት በምድርም ላይ የሚንቀሳቀሱ ተንቀሳቃሾች ሁሉ በምድርም ላይ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ በፊቴ ይንቀጠቀጣሉ። ተራሮችም ይገለባበጣሉ ገደላገደሎችም ይወድቃሉ ቅጥርም ሁሉ ወደ ምድር ይወድቃል። **21** በተራሮቼም ሁሉ በእርሱ ላይ ሰይፍን እጠራለሁ፥ የሰውም ሁሉ ሰይፍ በወንድሙ ላይ ይሆናል፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፦ **22** በቸነፈር፥ በደም ፥በዶፍ ዝናብና የድንጋይ እሳት እፈርድባቸዋለሁ። ድኝም በእርሱና በጭፍሮቹ ከእርሱም ጋር ባሉ በብዙ ሕዝብ ላይ አዘንባለሁ። **23** ታላቅነቴንና ቅዱስ መሆኔን አሳያለሁ በብዙ አሕዛብም ዓይን የታወቅሁ እሆናለሁ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ።

Ezekiel 38:1

የያህዌ ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የተናገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ነናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ/ያህዌ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ፊትህ ወደ ጎግ መልስ፣ የማጎግ ምድር ፣ ዋናው ልዑል/አለቃ...ቶቤል
በዚያ ያሉ ሰዎችን ትኩር ብሎ መመልከት ይህ ጎግን እና ማጎግን ለመቅጣት በምልክትነት የተሰጠ ትዕዛዝ ነው። ተመሳሳዩ ሀረግ በሕዝቅኤል 4:3 ላይ እንዴት አንደተተረጎመ ይመልከቱ። "ዋና አለቃውን... ቶቤል፣ የማጎግን ምድር እና ጎግን ትኩር ብለህ ተመልከት" ወይም "ወደ ዋና አለቃው ጎግ፣...ይቀጡ ዘንድ ወደ ቶቤል፣ እና ወደ ማጎግ ምድር ትኩር ብለህ ተመልከት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምልክታዊ/ትዕንርታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ፊትህን አድርግ
እዚህ ስፍራ "ፊት" ለትኩረት ወይም ለመመልከት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ፊትህን አድርግ" የሚለው የሚወክለው ትኩር ብሎ መመልከትን ነው። "ትኩር ብለህ ተመልከት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ጎግ፣ የማጎግ ምድር
ጎግ በሚገዛበት አካባቢ ማጎግ ምድር እንደሆነ በውስጠ ታዋቂነት ተጠቁሟል። "በማጎግ ምድር የሚገዛው ጎግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ጎግ
ይህ በማጎግ ምድር የሚገዛ መሪ ወይም ንጉሥ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 38:4

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለጎግ መናገሩን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡
እነዚህ ሀረጎች የጎግን ሰራዊት የሚተባበሩ የተለያዩ አገራትን ይዘረዝራሉ።

በመንጋጋይ መንጠቆ አስገባለሁ
እዚህ ስፍራ "በመንጋጋህ መንጠቆ" የሚለው የሚወክለው እግዚአብሔር ጎግን አንደሚቆጣጠር ነው። ሰዎች በእንስሳት አፍ ሉጋም የሚያስገቡት ወደሚፈልጉት ስፍራ ለመንዳት ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በሙሉ ትጥቅ...ሰይፍ በመያዝ... በጋሻ እና የብረት ኮፍያ
እነዚህ ሀረጋት ለጦርነት የተዘጋጀን ሰራዊት ይገልጻሉ።

ጎሜር
ከጥቁር ባህር በስተ ሰሜን የሚኖሩ ህዝቦች

የቴርጋማን ቤት
ይህ በሕዝቅኤል 27፡14 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ezekiel 38:7

አያያዥ ሀሳብ፡
x

Ezekiel 38:10

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለጎግ መናገሩን ቀጥሏል።

በዚያን ቀን ያ
"በዚያን ጊዜ"

በልብ ታቅዳለህ ...ክፉ እቅድ ታቅዳለህ
እነዚህ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ይሰጣሉ፤ ደግሞም አንድ ሀረግ ሊሆኑ ይችላሉ። "በጣም ክፉ የሆነ ነገር ለማድረግ ታቅዳለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

በልብህ እቅድ ይኖራል
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚያመለክተው የእርሱን አስተሳሰብ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ስለ እቅዶች ታስባለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ አደርጋለሁ
ጎግ እነዚህን ነገሮች ለብቻው አያደርግም። ብዙዎቹን ነገሮች የሚያደርገው የእርሱ ሰራዊት ነው። "እኔ እና ሰራዊቴ እናደርጋለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 38:13

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለጎግ መናገሩን ቀጥሏል።

ሳባ
ይህ በሕዝቅኤል 27:22 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ድዳን
ይህ በሕዝቅኤል 25:13 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

የመጣኸው ለመዝረፍ ነውን? ብዙ ዝርፊያ ለመሰብሰብ... ሰራዊትህን አሰባስበሃል?
እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች ጎግ እስራኤልን ያለ ምክንያት ለማጥቃት በመነሳቱ እርሱን ለመክሰስ የቀረቡ ናቸው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጽ ይችላል። "ለንጥቂያ፣ ወርቅና ብር ለመውሰድ፣ ከብቶቻቸውን እና ንብረታቸውን፣ እንደዚሁም ብዙ ሀብት ለመዝረፍ ሰራዊትህን መሰብሰብህ ትክክል አይደለም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ከብቶቻቸውን እና ንብረታቸውን... ብዙ ንብረት በዝርፊያ ለመውሰድ
እነዚህ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ እናም በአንድ ሀረግ ሊጠቃለሉ ይችላሉ። "ከብቶቻቸውን ለመንጠቅ እና ከፍ ያለ ዋጋ ያላቸውን ሀብቶቻቸውን ለመዝረፍ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 38:14

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል ለጎግ መናገር ያለበትን ይነግረዋል።

የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

በዚያን ቀን... ስለ እነርሱ ታውቃለህ?
ያህዌ ይህንን ጥያቄ የሚያነሳው ጎግ በእስራኤል ውስጥ ስለሚኖሩ ሰዎች በእርግጥ መስማቱን ትኩረት ለመስጠት ነው። "በዚያን ቀን፣ ህዝቤ እስራኤል ተጠብቀው ሲኖሩ ስለ እነርሱ ትሰማለህ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሪቱን እንደ ሸፈነ ደመና
የዚህ ተነጻጻሪ ዘይቤ ትርጉም ሰራዊቱ መላዋን ምድር እስኪሸፍን ድረስ ብዙ ይሆናል ማለት ነው። ይህ በሕዝቅኤል 38:9 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በኋለኞቹ ቀናት
ይህ የሚያመለክተው ዓለም ከመጥፏትዋ በፊት ያለውን ጊዜ ነው። "በመጨረሻው ቀን" ወይም "በዓለም መጨረሻ"

በኋልኞቹ ቀናት... በዐይኖቻቸው ፊት ቅዱስ እንድሆን
መላው ህዝብ ያህዌ በጎግ ላይ ያደረገውን ሲመለከቱ እርሱ ቅዱስ እንደሆነ ያውቃሉ

ያውቁኛል
"እኔ ማን እንደሆንኩ ያውቃሉ"

Ezekiel 38:17

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል ለጎግ መናገር ያለበትን መናገሩን ይቀጥላል።

በእነርሱ ላይ ያመጣሁህ/ያስነሳሁህ... አንተ አይደለህምን?
ያህዌ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው ጎግን ወደ እስራኤል ምድር ያመጣው እርሱ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። "በእነርሱ ላይ ያመጣሁህ... አንተ ነህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ የተናገርኩህ
"ያ እኔ የተናገርኩት"

በቀደሙት ቀናት
"ባለፈው ዘመን" ወይም "ከረጅም ጊዜ አስቀድሞ"

በአገልጋዬ እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚያመለክተው እነዚህ ነቢያት የያህዌን መልዕክት የመጻፋቸውን እውነታ ነው። "በአገልጋዮቼ አማካይነት" ወይም "በአገልጋዮቼ በኩል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በእነርሱ ላይ/እነርሱን በመቃወም
"በእስራኤል ህዝብ ላይ"

ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ራሱን በስሙ የሚገልጸው/የሚምለው፤ የተናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳወቅ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ። "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ቁጣዬ በንዴት ከፍ ይላል
እዚህ ስፍራ "ከፍ ይላል" ማለት "ይነሳል" ማለት ሲሆን ቁጣው እንደሚጨምር ይገልጻል። "ቁጣ" እና "ንዴት" የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ነገርን ሲገልጹ፣ በአንድነት ቁጣው ምን ያህል ጠንካራ እንደሚሆን ትኩረት ይሰጣሉ። "ቁጣዬ እጅግ ይጨምራል" ወይም "በእናንተ ላይ እጅግ እቆጣለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ጥንድ ትርጉም የሚሉትን ይመልከቱ)

Ezekiel 38:19

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ስለ ጎግ መልዕክቱን ለሕዝቅኤል መስጠቱን ይቀጥላል።

በእኔ ቅናት
እዚህ ስፍራ "ቅናት" የሚለው የሚያመለክተው ክብሩን ከጎግ ጥቃት ለመጠበቅ ያለውን ፍላጎት ነው።

በቁጣዬ እሳት
የያህዌ ቁጣ ታላቅነት የተገለጸው እንደ እሳት የሚፋጅ ተደርጎ ነው። "ቁጣዬ ጠንካራ በመሆኑ ምክንያት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በፊቴ ይንቀጠቀጣሉ
የሚንቀጠቀጡት ስለ ፈሩ ነው። ይህ ይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "በፊቴ በፍርሃት ይንቀጠቀጣሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ተራሮች ወደ ታች ይወረወራሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ያህዌ ተራሮች እንዲወድቁ ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 38:21

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ስለ ጎግ መልዕክቱን ለሕዝቅኤል መስጠቱን ይቀጥላል። ስለ ጎግ ህዝብ አንድ ሰው እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ ላይ ሰይፍ እጠራለሁ
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚለው ቃል ሰዎችን ለመግደል ሰይፍ ለሚጠቀሙ ወታደሮች ሜቴኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ወታደሮች እርሱን እንዲያጠቁ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በሁሉም ተራሮቼ ላይ
ይህ የእስራኤልን ምድር ያመለክታል። "በሁሉም የእስራኤል ተራሮች ላይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የእያንዳንዱ ሰው ሰይፍ በወንድሙ ላይ ይሆናል
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" ለውጊያ ሰይፉን ለሚጠቀምበት ሰው ሜቴኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ወታደሮቹ በሙሉ እርስ በእርሳቸው ይዋጋሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ወንድሙ
"አብሮት የተሰለፈው ወታደር"

በመቅሰፍት እና በደም እፈርድበታለሁ
እዚህ ስፍራ "ደም" ለጉዳት እና ሞት ሜቴኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "በህመም እና ሰራዊት እንዲገድለው በመላክ እፈርድበታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ጎርፍ፣ ከባድ በረዶ እና የሚነድ ድኝ በላዩ አፈሳለሁ
የዐረፍተ ነገሩን ቅደም ተከተል መቀየር ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። የዝናብ ጎርፍ እና ከባድ በረዶ እንዲሁም ድኝ በላዩ አፈሳለሁ"

ከባድ በረዶ
ከሰማይ የሚወርድ በረዶ

ታላቅነቴን እና ቅዱስነቴን አሳያለሁ
"ታላቅነት" እና "ቅዱስነት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች በቅጽል መልክ ሊጻፉ ይችላሉ። "ታላቅ እና ቅዱስ መሆኔን አሳያለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በብዙ ህዝቦች ዐይኖች ፊት ራሴን አሳውቃለሁ
እዚህ ስፍራ "ዐይኖች" የሚለው የሚያመለክተው ለመረዳት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሆነውን እይታን ነው። "ብዙ አገሮች እኔ ማን እንደሆንኩ እንዲያውቁ አደርጋለሁ። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ
ያህዌ እርሱ ያህዌ እንደሆነ ሰዎች ያውቃሉ ሲል፣ የመጨረሻው ከፍተኛ ስልጣን እና ሀይል ያለው እውነተኛው አምላክ እርሱ ብቻ እንደሆነ ማወቅ እንደሚገባቸው እየተናገረ ነው። ይህ በሕዝቅኤል6:7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ብቸኛው እውነተኛ አምላክ እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ" ወይም "እኔ ያህዌ የመጨረሻው ስልጣን እና ሀይል እንዳለኝ እወቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 39

1 አንተም፥ የሰው ልጅ ሆይ፥ በጎግ ላይ ትንቢትን ተናገር እንዲህም በል፥ 'ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፥ የሞሳሕና የቶቤል ዋነኛ አለቃ ጎግ ሆይ፥ እነሆ፥ እኔ በአንተ ላይ ነኝ **2** እመልስሃለሁ፥ እነዳህማለሁ፥ ከሰሜንም ዳርቻ አጐትትሃለሁ፥ ወደ እስራኤልም ተራሮች አመጣሃለሁ። **3** ከግራ እጅህም ቀስትህን አስጥልሃለሁ፥ ከቀኝ እጅህም ፍላጾችህን አስረግፍሃለሁ። **4** የአንተና የጭፍሮች ሁሉ ከአንተም ጋር ያሉ ሠራዊትና ወታደሮች ሬሳ ይገኛል። ለሚናጠቁ ወፎች ሁሉና ለምድር አራዊትም መብል አድርጌ እሰጥሃለሁ። **5** አንተ በምድር ፊት ላይ ትወድቃለህ እኔ ተናግሬአለሁና፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር። **6** በማጎግም ላይ ሳይፈሩም በደሴቶች በሚቀመጡ ላይ እሳትን እሰድዳለሁ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ። **7** ቅዱሱም ስሜ በሕዝቤ በእስራኤል መካከል እንዲታወቅ አደርጋለሁ፥ ቅዱሱንም ስሜን ከእንግዲህ ወዲህ እንዲረክስ አልፈቅድም፤ አሕዛብም እግዚአብሔር፥ የእስራኤል ቅዱስ፥ እኔ እንደ ሆንሁ ያውቃሉ። **8** ያልሁት ቀን እነሆ፥ ይመጣል ይሆንማል፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር ። **9** በእስራኤልም ከተሞች የሚኖሩ ይወጣሉ፥ የጦር መሣሪያዎችን፥ አላባሽ ጋሻንና ጋሻን፥ ቀስትንና ፍላጻዎችን፥ ጎመድንና ጦርንም ያቃጥላሉ፥ ለሰባት ዓመት በእሳት ያቃጥሉአቸዋል። **10** በጦር መሣሪያው እሳትን ያነድዳሉ እንጂ እንጨትን ከምድረ በዳ አይወስዱም ከዱርም አይቈርጡም የገፈፉአቸውንም ይገፍፋሉ የበዘበዙአቸውንም ይበዘብዛሉ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፡- **11** በዚያም ቀን በእስራኤል ዘንድ በባሕር ምሥራቅ የሚያልፉበትን ሸለቆ የመቃብርን ስፍራ ለጎግ እሰጣለሁ፥ የሚያልፉትንም ይከለክላል በዚያም ጎግንና ብዛቱን ሁሉ ይቀብራሉ የሸለቆውንም ስም ሐሞንጎግ ብለው ይጠሩታል። **12** ምድሩንም ያጸዱ ዘንድ የእስራኤል ቤት ሰዎች ሰባት ወር ይቀብሩአቸዋል፥ **13** የምድሪቱም ሰዎች ሁሉ ይቀብሩአቸዋል፥ እኔ የምከብርበት የማይረሳ ቀን ይሆንላችኋል፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፡- **14** ምድርንም ለማጽዳት በምድሩ ላይ ወድቀው የቀሩትን የሚቀብሩ፥ ዘወትር በምድሩ ላይ የሚዞሩትን ሰዎች ይመድባሉ ስራውንም ከሰባት ወርም በኋላ ይጀምራሉ። **15** በምድሩ ላይ እንዲዞሩ የተመደቡት በሚያልፉብት ጊዜ የሰውን አጥንት ካዩ ፥ ቀባሪዎች መጥተው በሐሞን ጎግ ሸለቆ እስኪቀብሩት ድረስ ምልክት አድርገው ያልፋሉ። **16** ስሟ ሐሞና የሚሰኝ ከተማ በዚያ ትገኛለች። በዚህ መንገድ ምድሪቱን ያጸዳሉ። **17** አንተም፥ የሰው ልጅ ሆይ፥ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- ለወፎች ሁሉና ለምድር አራዊት ሁሉ እንዲህ በላቸው፥ 'ኑ፥ ተከማቹ፥ ሥጋንም ትበሉ ዘንድ ደምንም ትጠጡ ዘንድ በእስራኤል ተራሮች ላይ ወደማርድላችሁ ታላቅ መሥዋዕት፥ ከየስፍራው ሁሉ ተሰብሰቡ። **18** የኃያላኑን ሥጋ ትበላላችሁ የምድርንም አለቆች፥ የአውራ በጎችንና የጠቦቶችን፥ የፍየሎችንና የወይፈኖችን፥ የባሳንን ፍሪዳዎች ሁሉ፥ ደም ትጠጣላችሁ። **19** እኔም ከማርድላችሁ መሥዋዕት እስክትጠግቡ ድረስ ጮማ ትበላላችሁ እስክትሰክሩም ድረስ ደም ትጠጣላችሁ። **20** በሰደቃዬም ከፈረሶችና ከፈረሰኞች፥ ከኃያላንና ከሰልፈኞች ሁሉ ትጠግባላችሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር። **21** ክብሬንም በአሕዛብ መካከል አኖራለሁ አሕዛብም ሁሉ ያደርግሁትን ፍርዴን፥ በላያቸውም ያኖርኋትን እጄን ያያሉ። **22** ከእንግዲህም ወዲያ የእስራኤል ቤት እኔ እግዚአብሔር አምላካቸው እንደ ሆንሁ ያውቃሉ። **23** አሕዛብም የእስራኤል ቤት እኔን ባቃለሉበት በኃጢአታቸው ምክንያት እንደ ተማረኩ ያውቃሉ፥ ስለ በደሉኝ እኔም ፊቴን ከእነርሱ ስለ ሸሸግሁ፥ በጠላቶቻቸው እጅ አሳልፌ ሰጠኋቸው፥ እነርሱም ሁሉ በሰይፍ ወደቁ። **24** እንደ ርኩሰታቸውም እንደ መተላለፋቸውም መጠን አደረግሁባቸው ፊቴንም ከእነርሱ ሸሸግሁ። **25** ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- አሁን የያዕቆብን ምርኮ እመልሳለሁ ለእስራኤልም ቤት ሁሉ እራራለሁ፥ ስለ ቅዱስ ስሜም እቀናለሁ። **26** እፍረታቸውንና እኔን የካዱበትን ክህደት ይረሳሉ። ማንም ሳያስፈራቸው በምድራቸው ተዘልለው በተቀመጡ ጊዜ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ይረሳሉ። **27** ከአሕዛብም ዘንድ በመለስኋቸው ጊዜ ከጠላቶቻቸውም ምድር በሰበሰብኋቸው ጊዜ በብዙ አሕዛብም ፊት እቀደሳለሁ። **28** እኔም ወደ አሕዛብ አስማርኬአቸዋለሁና፥ ወደ ገዛ ምድራቸውም ሰብስቤአቸዋለሁና እኔ እግዚአብሔር አምላካቸው እንደ ሆንሁ ያውቃሉ። ከእነርሱም አንድንም ሰው በአሕዛብ መካከል አልተውኩም። **29** ፊቴንም ከእነርሱ ከእንግዲህ ወዲህ አልሸሽግም መንፈሴን በእስራኤል ቤት ላይ አፍስሻለሁና፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር።

Ezekiel 39:1

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ መልዕክቱን ለጎግ ይነግረው ዘንድ ለሕዝቅኤል ሰጠው።

የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እነሆ!
ይህ አንባቢው ቀጥሎ ለሚሆነው ልዩ ትኩረት እንሰጥ ያደርገዋል። "ተመልከት!" ወይም "አድምጥ!" ወይም ቀጥሎ ለምነግርህ ትኩረት ስጥ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እኔ በአንተ ላይ ነኝ
"እኔ ጠላት ሆኜሃለሁ/ተነስቼብሃለሁ"

የሞሳህ እና የቶቤል አለቃ
አንዳንድ ዘመናዊ ቅጂዎች የዕብራይስጡን አገላለጽ "የሮህ፣ ሞሳህ እና ቶቤል አለቃ" ብለው ይተረጉሙታል። ይህ ለጎግ ሌላው መጠሪያ ነው። እነዚህ ስሞች በሕዝቅኤል 38፡2-3 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "የሞሳህ እና ቶቤል ዋና አለቃ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ እመልስሃለሁ፣ ደግሞም እነዳሃለሁ
እግዚአብሔር ጎግን እንደ እንስሳ እንደሚመራው ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ላይ አወጣሃለሁ
በተራሮች ላይ በመገኘቱ እግዚአብሔር ጎግን ወደ "ላይ" ወደ እስራኤል እንደሚያመጣው ይናገራል።

ከግራ እጅህ ደጋንህን እመታለሁ፤ ከቀኝ እጅህም ቀስትህ እንዲወድቅ አደርጋለሁ
የጎግን ደጋን መምታት እና ቀስቶችን ከእጁ ማስጣል የተገለጸው እግዚአብሔር የጎግ ሰራዊት ሀይል እንደሚያጠፋው ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 39:4

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ መልዕክቱን ለጎግ ይነግረው ዘንድ ለሕዝቅኤል መስጠቱን ቀጥሏል።

ሰልፈኞችህ እና ወታደሮችህ
ይህ የሚያመለክተው ተመሳሳይ ሰዎችን ነው። በአንድ ሀረግ ሊገለጽ ይችላል። "ወታደሮችህ ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለሰማይ ወፎች እና ለዱር አራዊት ምግብነት አሳልፌ እሰጥሃለሁ
ስጋ በል አሞሮች የሰዎችን በድን መብላታቸው የተገለጸው ያህዌ ለእነርሱ ምግብ እንደሰጣቸው ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ራሱን በስሙ የሚገልጸው/የሚምለው፤ የተናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳወቅ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ። "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

በማጎግ ላይ እሳት እልካለሁ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ያህዌ በጎግ እና በሰራዊቱ ላይ ተፈጥሯዊውን እሳት ይልካል ወይም 2) "እሳት" ነገሩ ለሚያስከትለው ጥፋት ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ማጎግ
ይህ ምናላባት በአሁኗ ቱርክ ምድር ይኖሩ የነበሩ የጥንት ሰዎች ስም ነው። ማጎግ የሊድያ ጥንታዊ ህዝብ ሊሆን ይችላል። ይህ በሕዝቅኤል 38:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ
ያህዌ እርሱ ያህዌ እንደሆነ ሰዎች ያውቃሉ ሲል፣ የመጨረሻው ከፍተኛ ስልጣን እና ሀይል ያለው እውነተኛው አምላክ እርሱ ብቻ እንደሆነ ማወቅ እንደሚገባቸው እየተናገረ ነው። ይህ በሕዝቅኤል6:7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ብቸኛው እውነተኛ አምላክ እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ" ወይም "እኔ ያህዌ የመጨረሻው ስልጣን እና ሀይል እንዳለኝ እወቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 39:7

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ መልዕክቱን ለጎግ ይነግረው ዘንድ ለሕዝቅኤል መስጠቱን ቀጥሏል።

ቅዱስ ስሜ በህዝቤ በእስራኤል መሃል እንዲታወቅ አደርጋሉ
እዚህ ስፍራ "ቅዱስ ስሜ" የሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሚያመለክተው የያህዌን ባህሪይ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እኔ፣ ህዝቤ እስራኤል፤ እኔ ቅዱስ እንደሆነኩ እንዲያውቅ አደርጋለሁ" በሚው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

እነሆ!
ይህ አንባቢው ቀጥሎ ለሚሆነው ልዩ ትኩረት እንሰጥ ያደርገዋል። "ተመልከት!" ወይም "አድምጥ!" ወይም ቀጥሎ ለምነግርህ ትኩረት ስጥ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እየመጣ ነው... ይሆናል/ይፈጸማል
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ደግሞም ይህ በእርግጥ እንደሚፈጸም ትኩረት ይሰጣሉ። "በእርግጥ ይህ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 39:9

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ መልዕክቱን ለጎግ ይነግረው ዘንድ ለሕዝቅኤል መስጠቱን ቀጥሏል።

ለመለኮስ እና እሳት ለማንደድ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። እስራኤላውያን ከመሳሪያዎች የሚያገኙትን እንጨት ለእሳት መለኮሻ ይጠቀሙበታል። "እሳት ለመለኮስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ትንንሽ ጋሻዎች፣ ትላልቅ ጋሻዎች፣ ደጋኖች፣ ቀስቶች፣ ዱላዎች እና ጦሮች
እነዚህ ዝርዝሮች የዘመኑን አይነተኛ የጦር መሳሪያ አይነቶች ይጨምራል። በአጠቃላይ የጦር መሳሪያዎችን ሊወክል ይችላል።

ዱላዎች
እንደ ጦር መሳሪያ የሚያገለግሉ የእንጨት ብትሮች

ለመቀማት መፈለግ.. ለመዝረፍ መፈለግ
እዚህ ስፍራ "መቀማት" እና "መዝረፍ" የሚሉት ተመሳሳይ ናቸው። ጎግ የእስራኤልን ሀብት ለመውሰድ ፈልጓል፣ ነገር ግን ያህዌ ጎግ ያንን ማድረግ እንዳይችል ከልክሎታል። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ይዘርፋል... መዝረፍ ይፈልጋል
"ዝርፊያ" የሚለውን በሕዝቅኤል 23:46 ላይ እንደ ተተረጎመው ይተርጉሙት።

Ezekiel 39:11

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል በጎግ ላይ የሚደርስበትን መናገር ጀምሯል

በዚያን ቀን እንዲህ ይሆናል
ይህ አስፈላጊ ትዕይንትን ያመለክታል። የእናንተ ቋንቋ ይህ ለማድረግ መንገድ ካለው እዚህ ስፍራ ልትጣሙበት ትችላላችሁ።

ከባህሩ በስተ ምስራቅ
ጥቂት ዘመናዊ ቅጂዎች እዚህ ስፍራ የዕብራይስጡን አገላለጽ "በባህሩ በኩል በስተ ምስራቅ" በማለት ይተረጉሙታል።

ይህ ይገድበዋል
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "መቃብሩ ይገድበዋል" ወይም 2) "የሞተው ሰራዊት ይገድበዋል"

በዚያ እነርሱ
"በዚያ የእስራኤል ቤት"

እነርሱ ይጠሩታል
"ሰዎች ይጠሩታል"

የሐሞን ጎግ ሸለቆ
"የጎግ ታላቅ ሰራዊት ሸለቆ"

Ezekiel 39:12

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል በጎግ ላይ የሚደርስበትን መናገር ቀጥሏል።

ሰባት ወራት
"7 ወራት።" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ቤት
"ቤት" የሚለው በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች በዚህ ሁኔታ ለብዙ ዘመናት የያዕቆብ ትውልድ ለሆኑ እስራኤላውያን ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው።ይህ በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡ "እስራኤላውያን" ወይም "የእስራኤል ወገን ሰዎች"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሪቱን ለማንጻት እነርሱን ይቀብሯቸዋል
በአይሁዶች ህግ፣ የሞተ አካል የሚነካውን ማናቸውንም ነገር ያረክሳል፤ ደግሞም "ያልነጻ" ያደርገዋል። እነዚህን አካሎች መቅበር የሚገለጸው ምድሪቱን እንደ ማንጻት ወይም ንጹህ እንደማድረግ ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱን መቅበር
"የጎግ ሰራዊትን ወታደሮች መቅበር"

ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ራሱን በስሙ የሚገልጸው/የሚምለው፤ የተናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳወቅ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ። "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 39:14

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል በጎግ ላይ የሚደርስበትን መናገር ቀጥሏል።

በምድሪቱ በሙሉ
"በእስራኤል ምድር በሙሉ"

ዘልቀው የተጓዙ፣ ነገር ግን ሞተው በድናቸው በሜዳ የወደቀ
ይህ የሚያመለክተው ወደ እስራኤል ምድር ሲገቡ ያህዌ የገደላቸውን የጎግ ወታደሮች በድን ነው

ስለዚህም እነርሱ ይቀብሯቸው ይሆናል
"ስለዚህም የተሰየሙ/የተቀጠሩ ወንዶች በድኖቹን ይቀብሩ ይሆናል"

ምድሪቱን ለማንጻት ...ምድሪቱን ንጹህ ለማድረግ
በአይሁዶች ህግ፣ የሞተ አካል የሚነካውን ማናቸውንም ነገር ያረክሳል፤ ደግሞም "ያልነጻ" ያደርገዋል። እነዚህን አካሎች መቅበር የሚገለጸው ምድሪቱን እንደ ማንጻት ወይም ንጹህ እንደማድረግ ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባተኛ ወር
ይህ "ሰባተኛ" ለሰባት ተከታታይ ቁጥር ነው። (ተከታታይ ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ማናቸውም የሰው አጥንት
ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ከበድኖች የሚቀረው ነው

መቃብር ቆፋሪዎች መጥተው እስኪቀብሩት ድረስ በዚህ ምልክት ያደርጋሉ
ሁለት ክፍል ሰዎች አሉ። የመጀመሪያዎቹ የበድኖቹን ስፍራ ይለያሉ፣ ሁለተኛው ቡድን በድኖቹን ይቀብራል።

ሐሞን
የዚህ ስም ትርጉም "ታላቅ ሰራዊት" ማለት ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 39:17

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል ወፎች እና የዱር እንስሳት በጎግ ላይ ምን እንደሚያደርጉ መልዕክት ይሰጠዋል።

የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ለመስዋዕት
ለመስዋዕት "ለግብዣ" ወይም "ለእርድ።" ያህዌ ለወፎች እና ለእንስሳት በጣም ጥሩ ምግብ ይሰጣቸዋል ማለት እንጂ እርሱ ያመልካቸዋል ማለት አይደለም።

እነርሱ አውራ በጎች፣ ጠቦቶች፣ ፍየሎች፣ እና ኮርማዎች ይሆናሉ
ያህዌ በምጸት እየተናገረ ነው። በተለመደው ሁኔታ ሰዎች ለእግዚአብሔር መስዋዕት ያቀርባሉ። እዚህ ስፍራ፣ እግዚአብሔር ሰዎችን ለእንስሳት እየሰዋ ነው። "እነርሱ ወንድ በጎች፣ ጠቦቶች፣ ፍየሎች፣ እና ወይፈኖች የሆኑ ይመስል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምጽት የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ሁሉም በባሳን የሰቡ ናቸው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በባሳን ሲግጡ/የተሰማሩት ሁሉም ሰቡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 39:19

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል ወፎች እና የዱር እንስሳት በጎግ ላይ ምን እንደሚያደርጉ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

ለእናንተ እርካታ
"እርካታ" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል ሊገለጽ ይችላል። "እናንተ እስክትረኩ ድረስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እስክትሰክሩ ድረስ
"ስካር" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል ሊገለጽ ይችላል። "እስክትሰክሩ ድረስ" ወይም "እስትሰክሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰረገላ
"ሰረገላ" የሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሚያመለክተው በሰረገላ ውስጥ ያሉትን ወንዶች ነው። "ሰረገላ ነጂ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ጦረኛ፣ እና እያንዳንዱ የጦርነት ሰው
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ የተደጋገሙት ትኩረት ለመስጠት ነው። በአንድ ሀረግ ሊጣመሩ ይችላሉ። "እያንዳንዱ ወታደር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ራሱን በስሙ የሚገልጸው/የሚምለው፤ የተናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳወቅ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ። "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 39:21

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል ለእስራኤል ስለሚሆነው መልዕክት ይነግረዋል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በአገራት መሃል ክብሬን አደርጋለሁ
ያህዌ ስለ ክብሩ የሚናገረው በአገራት መሃል ሊመለከቱት በሚችሉት ስፍራ እንደሚያስቀምጠው አድርጎ ነው። "አገራት ክብሬን እንዲመለከቱ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የምፈጽመው ፍርድ እና በላያቸው የማሳርፈው እጄ
እነዚህ ሁለቱም ሀረጎች ያህዌ በእስራኤል ላይ የሚያደርገውን ፍርድ ያመለክታሉ፤ ገለጻው የተደጋገመው ትኩረት ለመስጠት ነው። በአንድ ሀረግ ሊጠቃለል ይችላል። "በእነርሱ ላይ የምፈርድበት መንገድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

እጄ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሚያመለክተው ለቅጣት ያህዌ የሚጠቀምበትን ሀይል ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በእነርሱ ላይ
"በጎግ እና በሰራዊቱ ላይ"

የእስራኤል ቤት
"ቤት" የሚለው በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች በዚህ ሁኔታ ለብዙ ዘመናት የያዕቆብ ትውልድ ለሆኑ እስራኤላውያን ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው።ይህ በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡ "እስራኤላውያን" ወይም "የእስራኤል ወገን ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 39:23

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለእስራኤል ስለሚሆነው ለሕዝቅኤል መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

የእስራኤል ቤት
"ቤት" የሚለው በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች፣ በዚህ ሁኔታ ለብዙ ዘመናት የያዕቆብ ትውልድ ለሆኑ እስራኤላውያን ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው።ይህ በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡ "እስራኤላውያን" ወይም "የእስራኤል ወገን ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እኔን በመክዳት በፈጸሙት በደላቸው/ኃጢአት ምክንያት
"በደል/ኃጢአት" የሚለው ረቂቅ ስም በግስ ሊገለጽ ይችላል። "ኃጢአት ስለ ሰሩ እና ስለካዱኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ፊቴን ከእነርሱ እሰውራለሁ
እዚህ ስፍራ "ፊት" የሚያመለክተው የያህዌን እርዳታ እና ድጋፍ ነው። "እኔ እነርሱን መጠበቄን እና መንከባከቤን አቆማለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለተቃማሚዎቻቸው እጅ አሳልፌ እሰጣቸዋለሁ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሀይልን ያመለክታል። "በእነርሱ ጠላቶቻቸው ላይ ሀይል እሰጣለሁ/ ጠላቶቻቸው በእነርሱ ላይ ሀይል እንዲያገኙ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉም በሰይፍ ይወድቃሉ
እዚህ ስፍራ መውደቅ የሚወክለው መገደልን ሲሆን፣ ሰይፍ ደግሞ ጦርነትን ይወክላል። ይህ በሕዝቅኤል 32:23 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ጠላቶቻቸው ሁሉንም በጦርነት ገደሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ንጹህ አለመሆናቸው እና ኃጢአቶቻቸው
ይህ የሚገልጸው የሰዎቹን አስጸያፊ ባህሪይ ሲሆን ይህም የተገለጸው ልክ በአካል ንጹህ እንዳልሆኑ ተደርጎ ነው። እዚህ ስፍራ "ንጹህ አለመሆን" ማለት በመሰረቱ "ኃጢአት" እንደ ማለት ነው። "አስጸያፊ ባህሪያቸው እና ኃጢአታቸው" ወይም "ኃጢአቶቻቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ጥንድ ትርጉም የሚሉትን ይመልከቱ)

Ezekiel 39:25

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለእስራኤል ስለሚሆነው ለሕዝቅኤል መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

የያዕቆብን እድል አድሳለሁ/ምርኮ እመልሳለሁ
"እድል ማደስ" የሚለውን በሕዝቅኤል 16:53 ላይ ባለው መሰረት ይተርጉሙት። ሆኖም አንዳንድ ዘመናዊ ቅጂዎች የዕብራይስጡን አገላለጽ እዚህ ስፍራ "ያዕቆብን ከምርኮ እመልሳለሁ" ብለው ይተረጉሙታል።

የእስራኤል ቤት
"ቤት" የሚለው በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች፣ በዚህ ሁኔታ ለብዙ ዘመናት የያዕቆብ ትውልድ ለሆኑ እስራኤላውያን ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው።ይህ በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡ "እስራኤላውያን" ወይም "የእስራኤል ወገን ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ለቅዱስ ስሜ በቅናት እነሳለሁ
"እንደሚያከብሩኝ አረጋግጣለሁ"

ሀፍረታቸውን እና ክህደታቸውን ሁሉ ይሸከማሉ
የትርጉም ባለሙያዎች በዚህ ሀረግ ትርጉም አይስማሙም። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "በሀፍረት እና በክህደታቸው ሁሉ ይጸጸታሉ" ወይም 2) "ሀፍረታቸውን እና ክህደታቸውን ሁሉ ይረሳሉ"

ክህደታቸው
"ታማኝ አለመሆናቸው"

በብዙ አገራት እይታ ቅዱስ መሆኔን አሳያለሁ
እዚህ ስፍራ "እይታ" የሚለው ለመረዳት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ብዙ አገራት ለእስራኤል ቤት ከማደርገው የተነሳ እኔ ቅዱስ መሆኔን ይረዳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 39:28

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለእስራኤል ስለሚሆነው ለሕዝቅኤል መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

ወደ ምርኮ እልካቸዋለሁ... ወደ ምድራቸው እመልሳቸዋለሁ
ሕዝቅኤል በሚጽፍበት ጊዜ፣ እስራኤል ገና በባቢሎን ነበሩ

ከዚህ በኋላ ፊቴን ከእነርሱ አልመልስም
እዚህ ስፍራ "ፊቴን ከእንግዲህ አልሰውርም" የሚለው ፈሊጥ ሲሆን ትርጉሙ ያህዌ እስራኤልን ከእንግዲህ በባቢሎን በስደት አይተውም ማለት ነው። "ከዚህ በኋላ አልተዋቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በእስራኤል ቤት ላይ መንፈሴን ሳፈስ
እዚህ ስፍራ መንፈሱን አብዝቶ መስጠት የተገለጸው መንፈስን እንደ "ማፍሰስ" ተደርጎ ነው። "መንፈሴን በልግስና ለእስራኤል ቤት ስሰጥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ቤት
"ቤት" የሚለው በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች፣ በዚህ ሁኔታ ለብዙ ዘመናት የያዕቆብ ትውልድ ለሆኑ እስራኤላውያን ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው።ይህ በሕዝቅኤል 3፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡ "እስራኤላውያን" ወይም "የእስራኤል ወገን ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ራሱን በስሙ የሚገልጸው/የሚምለው፤ የተናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳወቅ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ። "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 40

1 በተማረክን በሀያ አምስተኛው ዓመት በዓመቱ መጀመሪያ ከወሩ በአሥረኛው ቀን፥ ከተማይቱ ከተመታች በኋላ በአሥራ አራተኛው ዓመት፥ በዚያው ቀን የእግዚአብሔር እጅ በእኔ ላይ ነበረ እርሱም ወደዚያ ወሰደኝ። 2 በእግዚአብሔር ራእይ ወደ እስራኤል ምድር አመጣኝ እጅግም በረዘመ ተራራ ላይ አኖረኝ፥ በዚያም ላይ በደቡብ ወገን እንደ ከተማ ሆኖ የተሠራ ነገር ነበረ። 3 ወደዚያም አመጣኝ፥ እነሆም፥ መልኩ እንደ ናስ መልክ የመሰለ አንድ ሰው በዚያ ነበረ፥ በእጁም የተልባ እግር ገመድና የመለኪያ ዘንግ ነበረ እርሱም በከተማይቱ በር አጠገብ ቆሞ ነበር። 4 ሰውዬውም፥ "የሰው ልጅ ሆይ፥ ወደዚህ ያመጣሁህ ይህን ላሳይህ ስለሆን በዓይንህ እይ በጆሮህም ስማ በማሳይህም ሁሉ ላይ ልብ በል የምታየውንም ሁሉ ለእስራኤል ቤት ንገር አለኝ። 5 እነሆም፥ በቤተመቅደሱ ዙሪያው ቅጥር ነበረ፥ በሰውዬውም እጅ ርዝመቱ ስድስት ክንድ የሆነ የመለኪያ ዘንግ ነበር። እያንዳንዱም ክንድ አንድ ክንድ ከስንዝር ነበረ። ሰውዬውም ቅጥሩን ለካ፤ የቅጥሩም ስፋት አንድ ዘንግ ቁመቱንም አንድ ዘንግ ነበረ። 6 ወደ ምሥራቅ ወደሚመለከተውም በር ሄዶ በደረጃዎቹ ወጣ፥ የመድረኩንም ወለል ለካ፥ ወርዱን አንድ ዘንግ ነበር። 7 የዘበኞቹም ጓዳ ሁሉ ርዝመቱ አንድ ዘንግ፥ ወርዱም አንድ ዘንግ ነበረ በዘበኞቹም ጓዳዎች መካከል አምስት ክንድ ርቀት ነበረ በበሩም ደጅ ሰላም በስተ ውስጥ በኩል የሚገኝ የበሩ የመድረክ ወለል አንድ ዘንግ ነበረ። 8 የበሩን መተላለፊያ ደጅ ለካ ርዝመቱም አንድ ዘንግ ነበር። 9 የበሩን መተላለፊያ ደጅ ለካ፥ ጥልቀቱ አንድ ዘንግ ነበረ። የግንቡንም አዕማድ ወርድ ሁለት ክንድ ነበረ። አድርጎ ለካ ።ይህም በቤተመቅደሱ ትይዩ የሚገኘው ድጅ መተላለፊያ ነበረ። 10 በበሩ አጠገብ የሚገኙት የዘበኛ ጓዳዎች በበሩ በሁለቱም በኩል ሦስት ሦስት ነበሩ፥ የሁሉም መጠን እኩል ነበረ በሁሉም አቅጣጫ የሚለያቸው ግንብም እኩል መጠን ነበረው። 11 ቀጥሎም ሰውዬው የበሩን መግቢያ ወርድ ለካ አሥር ክንድ ሆነ፤ የበሩንም መግቢያ ርዝመት ለካ አሥራ ሦስት ክንድ ሆነ። 12 በእያንዳንዱ በዘበኛ ጓዳ ፊት ከፍታው አንድ ክንድ የሆነ መከለያ ነበረ። የዘበኛ ጓዳዎቹም በሁሉም አቅጣጫ ስድስት ክንድ ከፍታ ነበራቸው። 13 ከአንዱም የዘበኛ ጓዳ ደርብ ጀምሮ እስከ ሌላው ደርብ ድረስ የበሩን ወርድ ሀያ አምስት ክንድ ለካ ይህም ከመጀምሪያው የዘበኞች ጓዳ መግቢያ እስከ ሌላኛው መግቢያ ድረስ ነው። 14 ቀጥሎም በዘበኞች ጓዳ መካከል የሚያልፈውን ግንብ ለካ፤ ስድስት ክንድም ሆነ። እስከ መግቢያው መተላለፊያ ድረስ ለካ ። 15 ከበሩም መግቢያ ፊት ጀምሮ እስከ ውስጠኛው የበሩ መተላለፊያ መጨረሻ ድረስ አምሳ ክንድ ነበረ። 16 በዘበኛ ጓዳዎቹም በበሩ ውስጥ በዙሪያው በነበሩትም በግንቡ አዕማድ ትንንሽ መስኮቶች ነበሩዋቸው። በበሩም ደጅ መተላለፊያ እንደዚያው ነበር። ሁሉም መስኮቶች በውስጥ በኩል ነበሩ። በግንቡም አዕማድ ሁሉ ላይ የዘንባባ ዛፍ ተቀርጾባቸው ነበር። 17 ቀጥሎም ሰውዬው ወደ ውጭውም አደባባይ አመጣኝ። እነሆም፥ በአደባባዩ ዙሪያ ክፍሎችና ወለል ነበሩ። በወለሉም ላይ ሠላሳ ክፍሎች ነበሩ። 18 ወለሉም እስከ በሮቹ ይደርስ ነበር ስፋቱም እንደ በሮቹ ርዝመት መጠን ነበረ። ይህም ታችኛው ወለል ነበር። 19 ከታችኛውም በር ፊት ጀምሮ እስከ ውስጠኛው በር ፊት ድረስ ያለውን ርቀት ለካ፤ በምስራቅ በኩል አንድ መቶ ክንድ በሰሜኑም በኩል ተመሳሳይ ነበረ። 20 ቀጥሎም ከውጭው አደባባይ በሰሜን በኩል ያለውን በር ርዝመትና ስፋት ለካ። 21 በበሩ በዚህና በዚያ የዘበኛ ጓዳዎቹም ነበሩ፥ በሩና መተላለፊያው ከዋናው በር ልኬታቸው እኩል ነበር- ርዝመቱ አምሳ ክንድ ወርዱም ሀያ አምስት ክንድ ነበረ። 22 መስኮቶቹም ፥መተላለፊያዎቹና የዘንባባ ዛፎቹ ወደ ምሥራቅ እንደሚመለከተው በር ጋር ይዋሰኑ ነበር። ወደ እርሱና ወደ መተላለፊያዎቹ የሚያደርሱ ሰባት ደረጃዎች ነበሩ። 23 በውስጠኛውም አደባባይ በሰሜኑና በምሥራቁ በኩል በሌላው በር አንጻር በር ነበረ፤ ሰውዬውም ከአንዱ በር እስከ በር ድረስ ለካ። ርቀቱም አንድ መቶ ክንድ ነበር። 24 ቀጥሎም ሰውዬው ወደ ደቡቡ መግቢያ አመጣኝ፥ እነሆም፥ ግንቡና መተላለፊያዎቹ ከሌላኛው መውጪያው በር ጋር እኩል ልኬት ነበራቸው። 25 በመግቢያውና በመተላለፊያዎቹ እንደዚያኛው በር አይነት ትንንሽ መስኮቶች ነበሩዋቸው። የድቡቡ በርና መተላልፊያው ርዝመቱ አምሳ ክንድ ወርዱም ሀያ አምስት ክንድ ነበረ። 26 ወደ በሩና መተላለፊያዎቹ የሚያደርሱ ሰባት ደረጃዎች ነበሩ፥ በግንቡም አዕማድ ላይ በሁለቱም ወገን የዘንባባ ዛፍ ተቀርጾባቸው ነበር። 27 በደቡብ በኩል ወደ ውስጠኛው አደባባይ የሚያስገባ መግቢያ ነበረ፥ ሰውዬውም ከዚህኛው በር እስከ ደቡቡ መግቢያ ድረስ ለካ፥ ርቀቱ መቶ ክንድ ነበረ። 28 ቀጥሎም ሰውዬው ከሌላኛው በር እኩል ልኬት ባለው በደቡብ በር በኩል ወደ ውስጠኛው አደባባይ አገባኝ ። 29 የዘበኛ ጓዳዎቹንና የግንቡን አዕማድና መተላለፊያዎቹ ከመጀመሪያዎቹ መግቢያዎች እኩል ነበሩ፤ በመተላለፊያዎቹ ዙሪያ መስኮቶች ነበሩ።ውስጠኛው መግቢያና መተላለፊያው ርዝመቱ አምሳ ክንድ ወርዱም ሀያ አምስት ክንድ ነበረ። 30 በውስጠኛው ግንብ ዙሪያውም መተላለፊያዎች ነበሩ። ርዝመታቸውም ሀያ አምስት ክንድ ወርዳቸውም አምስት ክንድ ነበረ። 31 መተላለፊያዎቹም ወደ ውጭው አደባባይ ይመለከቱ ነበር በግንቡም አዕማድ ላይ የዘንባባ ዛፍ ተቀርጾ ነበር ወደ እርሱም የሚያደርሱ ስምንት ደረጃዎች ነበሩ። 32 ቀጥሎም ከሌሎቹ መግቢያዎች እኩል ልኬት ባለው በምስራቁ በር በኩል ወደ ውስጠኛው አደባባይ አገባኝ። 33 የዘበኛ ጓዳዎቹንና የግንቡን አዕማድ መተላለፊያዎቹ ሌኬታቸው ከሌሎቹ መግቢያዎች እኩል ነበር በዙሪያም መስኮቶች ነበሩ። መግቢያውና መተላልፊያው ርዝመቱም አምሳ ክንድ ወርዱም ሀያ አምስት ክንድ ነበረ። 34 መተላለፊያዎቹም በስተ ውጭ ወዳለው አደባባይ ይመለከቱ ነበር በግንቡም አዕማድ ላይ በዚህና በዚያ ወገን የዘንባባ ዛፍ ተቀርጾ ነበር ወደ እርሱም የሚያደርሱ ስምንት ደረጃዎች ነበሩት። 35 በሰሜንም ወዳለው በር አመጣኝ፥ በሩንም ለካው፤ ልኬቱም ከሌሎቹ በሮች እኩል ነበር። 36 የዘበኛ ጓዳዎቹንና የግንቡን አዕማድ መተላለፊያዎቹ ልኬታቸው ከሌሎቹ በሮች እኩል ነበር በዙሪያውም መስኮቶች ነበሩ። ርዝመቱም አምሳ ክንድ ወርዱም ሀያ አምስት ክንድ ነበረ። 37 መተላለፊያውም ወደ ውጭው አደባባይ ይመለከቱ ነበር በግንቡም አዕማድ ላይ በዚህና በዚያ ወገን የዘንባባ ዛፍ ተቀርጾ ነበር ወደ እርሱም የሚያደርሱ ስምንት ደረጃዎች ነበሩት። 38 በእያንዳንዱ ውስጠኛ መግቢያ በር ያላቸው ክፍሎች ነበሩ። ይህም የሚቃጠለውን መሥዋዕት የሚያጥቡበትነበር። 39 የሚቃጠለውንም መሥዋዕት የኃጢአቱንና የበደሉንም መሥዋዕት ያርዱባቸው ዘንድ፥ በበሩ መተላለፊያ በዚህ ወገን ሁለት ገበታዎች፥ በዚያም ወገን ሁለት ገበታዎች ነበሩ። 40 በሰሜን በኩል ባለው በር በስተ ውጭው፥ በመወጣጫው ደረጃዎች አጠገብ፥ በአንድ ወገን ሁለት ገበታዎች ነበሩ፥ በሌላውም ወገን በበሩ መተላለፊያ በኩል ሁለት ገበታዎች ነበሩ። 41 በበሩ በሁለቱም ወገን አራት ገበታዎች ነበሩ፤ በስምንቱም ገበታዎች እንስሳትን ይሰው ነበር። 42 ለሚቃጠለውም መሥዋዕት ርዝመታቸው አነድ ክንድ ተኩል ወርዳቸውም አንድ ክንድ ተኩል ቁመታቸውም አንድ ክንድ የሆኑ ከተጠረበ ድንጋይ የተሠሩ አራት ገበታዎች ነበሩ። በእነርሱም ላይ የሚቃጠለውን መሥዋዕትና ሌላ መሥዋዕቱን የሚያርዱበትን መሳሪያ ያኖሩባቸው ነበር። 43 በዙሪያውም በመተላለፊያው አንድ ጋት የሚርዝም መስቀያዎችነበሩ፥ የመስዋዕቱም ሥጋ የሆነ ክፈፍ በገበታዎቹም ላይ ይቀመጡ ነበር። 44 በውስጠኛው አደባባይ ከውስጠኛው መግቢያም አጠገብ የዘማሪያን ክፍሎች ነበሩ። ከክልሎቹ አንዱ በሰሜን በኩል ነበረ፥ ሌላውም በስተደቡብ ነበረ። 45 ሰውዬውም፥ "ይህ ወደ ደቡብ የሚመለከት ቤት በመቅደሱ ውስጥ ለማገልገል ተረኛ ለሆኑለሚተጉ ካህናት ነው። 46 ወደ ሰሜንም የሚመለከተው ቤት በመሠዊያው ዙሪያ ለሚያገለግሉ ካህናት ነው። እነዚህ ከሌዊ ልጆች መካከል ያገለግሉት ዘንድ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡ የሳዶቅ ልጆች ናቸው" አለኝ። 47 ቀጥሎም አደባባዩን ለካ፥ አራት ማዕዘን ሆኖ ርዝመቱን መቶ ክንድ ወርዱንም መቶ ክንድ ነበረ መሠዊያውም በቤቱ ፊት ነበረ። 48 ከዚያም ሰውዬው ወደ ቤቱ መተላለፊያ አመጣኝ፥ የግንብ አዕማዱንም ለካ፤ ወርድ በዚህ ወገን አምስት ክንድ በዚያም ወገን አምስት ክንድ ነበረ። መግቢያው ራሱ ወርዱ አሥራ አራት ክንድ ነበረ፥ በበሩም በዚህ ወገንና በዚያ ወገን የነበሩት ግንቦች ስፋት ሦስት ሦስት ክንድ ነበር። 49 የቤተ መቅደሱ መተላለፊያ ርዝመት ሀያ ክንድ ወርዱም አሥራ ሁለት ክንድ ነበረ። ወደ እርሱም የሚያደርሱ ደረጃዎች በሁለቱም አቅጣጫ የቆሙ አዕማድ ነበሩ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ezekiel 40:1

ሃያ አምስተኛ...አስረኛ...አስራ አራተኛ
እነዚህ ቃላት የ25፣ 10 እና 14 ተከታታይ ቁጥሮች ናቸው። (ተከታታይ ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

የእኛ ምርኮኞች
እዚህ ስፍራ "የእኛ" የሚለው የሚያመለክተው ባቢሎናውያን ንጉሥ ዮአኪንን አስገድደው ከኢየሩሳሌም ካስወጡበት ጊዜ አንስቶ በባቢሎን የነበሩትን ሕዝቅኤልን እና አስራኤላውያንን እንጂ አንባቢውን አይደለም። "እኛ ምርኮኛ ከሆንን በኋላ" ወይም "ባቢሎናውያን ወደ ባቢሎን ምርኮኛ አድርገው ከወሰዱን በኋላ" (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የአመቱ መጀመሪያ የወሩ አስረኛ ቀን
ይህ በዕብራውያን የወር አቆጣጠር የመጀመሪያው ወር ነው። አስረኛው ቀን በአውሮፓውያን አቆጣጠር በሚያዚያ ነው። (የዕብራውያን ወሮች እና ተከታታይ ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

ከተማይቱ ተይዛ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ባቢሎናውያን የኢየሩሳሌምን ከተማ ያዙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌ እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው የሚያመለክተው ያህዌ ለሕዝቅኤል ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ራዕይ ለማሳየት ያለውን ሀይል ነው። ይህ በሕዝቅኤል 1:3 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

እሱ ወደ እረፍት አመጣኝ
"እሱ እኔን አስቀመጠኝ"

Ezekiel 40:3

እሱ ወደዚያ አመጣኝ
"ያህዌ ቤቶቹ/ህንጻዎቹ ወዳሉበት ስፍራ አመጣኝ"

እነሆ
ሕዝቅኤል በተመለከተው ተደንቆ ነበር

የእርሱ መልክ እንደ ነሐስ መልክ ነበር
"መልክ" የሚለው ረቂቅ ስም በግስ ሊተረጎም ይችላል። "የሚገለጽበት መንገድ ነሐስ በሚገለጽበት መንገድ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የላይነን/ሊኖ ገመድ
"ከላይነን/ሊኖ የተሰራ ገመድ።" ይህ በጣም ረጅም ርቀትን ለመለካት የሚያገለግል መሳሪያ ነው

ላይነን/ሊኖ
ይህ የክር አይነት ነው። ይህ በሕዝቅኤል 9:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ

መለኪያ ዘንግ
ይህ አጭር ርቀትን መለኪያ መሳሪያ ነው

የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

አይምሮህን ትኩረት ስጠው
የዚህ ፈሊጥ ትርጉም "ትኩረት አድርግ" ወይም "አስብ" ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ቤት
"ቤት" የሚለው በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች በዚህ ሁኔታ ለብዙ ዘመናት የያዕቆብ ትውልድ ለሆኑ እስራኤላውያን ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው።ይህ በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡ "እስራኤላውያን" ወይም "የእስራኤል ወገን ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 40:5

የቤተመቅደሱን ዙሪያ የከበበ
"ሙሉ ለሙሉ በቤተ መቅደሱ ዙሪያ"

እያንዳንዱ ረጅም ክንድ፣ አንድ ክንድ ከአንድ የእጅ መዳፍ ያህል ርዝመት አለው
እያንዳንዱ "ረጅም ክንድ" ወደ 54 ሳንቲ ሜትር ያህላል። በዩዲቢ እንደተደረገው ዘመናዊ መለኪያ ከተጠቀሙ "ክንድ" የሚለውን ይህንን መረጃ መስጠት ላያስፈልግ ይችላል። "እነዚህ ረጂም ክንዶች፣ ከአማካዩ የክንድ መጠን የመዳፍ ያህል ተጨማሪ እርዝማት አላቸው" (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

የእጅ መዳፍ የሚያል
"የእጅ ስፋት።" ይህ ወደ 8 ሳንቲ ሜትር ነው። (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ዘንግ
"የአንድ በትር ቁመት" ይህ 3.2 ሜትር ነው።

በምስራቅ ትይዩ ያለው የቤተ መቅደሱ በር/የቤተ መቅደሱ ምስራቅ በር
ይህ በር የቤተ መቅደሱን አካባቢ የከበበው ግድግዳ አንዱ ክፍል/አካል ነበር። የቤተ መቅደሱ ህንጻ አካል አልነበረም። "መቅደሱን የከበበው በስተምስራ በኩል ያለው ግድግዳ መግቢያ" ወይም "በቤተ መቅደሱ ቅጥረ ግቢ ምስራቃዊ ግድግዳ የሚገኘው መግቢያ"

ደረጃዎች ላይ
"የበሩ ደረጃዎች ላይ"

በጥልቀት
"ከመግቢያው በር የፊት ለፊት ጠርዝ እስከ ኋለኛው ጠርዝ"

የዘብ ጠባቂ ቤቶች
እነዚህ በበሮቹ በውስጥ በኩል የተገነቡ ዘቦቹ በሮችን ለመጠበቅ የሚቆዩባቸው ክፍሎች ነበሩ

አምስት ክንድ
ወደ 2.7 ሜትር የሚጠጋ (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

በየሁለት ቤቶቹ/አዳራሽ መካከል አምስት ክንድ ርቀት ነበር
"አጠገብ ላጠገብ በሚገኙ ቤቶች መሃል አምስት ክንድ ርቀት ነበር" ወይም "በአንድ ቤት እና በአጠገቡ በሚገኘው ቤት መሃል አምስት ክንድ ርቀት ነበር

ቤቶቹ/አዳራሾቹ
"ክፍሎቹ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መተላለፊያ
x

Ezekiel 40:8

ወደ ቤተ መቅደሱ የዞረ የበሩ መተላለፊያ
እዚህ ስፍራ "ወደ ቤተ መቅደሱ የዞረ" ማለት መተላለፊያው በቤተ መቅደሱ ቅጥረ ግቢ ከበሩ ጋር የተያያዘ ነበር ማለት ነው። "ቤተ መቅደሱን የከበበው በግድግዳው ውስጠኝ ገጽ የሚገኘው የበሩ መተላለፊያ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

መተላለፊያ
ይህ በበሩ መግቢያ ወይም መውጫ ፊት ለፊት አምዶች ወይም ለድጋፍ የሚያገለግል ምሰሶዎች የሚገኙበት ስፍራ ነበር። ይህ በሕዝቅኤል 8፡16 ላይ አንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

አንድ ዘንግ
ይህ በሕዝቅአል 40፡5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ

ሁለት ክንድ
አንድ ሜትር የሚሆን (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

ክንዶች
በሕዝቅኤል 40፡5 ላይ እነዚህ "ረጅም" ክንዶች የሚለው እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

በተመሳሳይ ለካ
"ተመሳሳይ መጠን ነበረው"

Ezekiel 40:11

መግቢያ በር
"የደጃፉ መግቢያ የነበር በር"

አስር ክንድ
ወደ 5.4 ሜትር (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

ክንዶች
በሕዝቅኤል 40፡5 ላይ እነዚህ "ረጅም" ክንዶች የሚለው እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

አስራ ሶስት ክንድ
ወደ 7 ሜትር

ቤቶቹ/ክፍሎቹ ወደ ስድስት ክንድ ይሆናሉ
"ክፍሎቹ 6 ክንድ ቁመት ነበራቸው"

ክፍሎቹ
"ጓዳዎቹ" ወይም "ክፍሎቹ"

ስድስት ክንድ
ወደ 3.2 ሜትር

አንድ ክንድ
"54 ሴንቲ ሜትር" ወይም "ግማሽ ሜትር የሚሆን"

ሃያ አምስት ክንድ
ወደ 13.5 ሜትር የሚጠጋ (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

ሁለተኛው
"የሁለተኛው ክፍል/ቤት መግቢያ"

Ezekiel 40:14

የዘቦች ክፍሎች
ይህ በሕዝቅኤል 40፡7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ስልሳ ክንድ
ወደ 32 ሜትር የሚጠጋ

ክንዶች
በሕዝቅኤል 40፡5 ላይ እነዚህ "ረጅም" ክንዶች የሚለው እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

መተላለፊያ
በመግቢያው ፊት ለፊት በአምዶች ወይም ለድጋፍ በቆሙ በምሶሶዎች ላይ የሚገኙ ልባሶች። ይህ በሕዝቅኤል 8፡16 ላይ አንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ሃምሳ ክንድ
ወደ 27 ሜትር የሚጠጋ

የተዘጉ መስኮቶች
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "የተዘጉ መስኮቶች" ወይም 2) "መከለያ ያላቸው መስኮቶች" ወይም 3) "ጠባብ መስኮቶች"

ለበረንዳዎችም በዚሁ አይነት
"በረንዳዎችም በዙሪያቸው የተዘጉ መስኮቶች አላቸው"

እያንዳንዱ መቃን
መቃን ከእንጨት የተሰራ ከበር አጠገብ የሚደረግ ክፈፍ ነው

Ezekiel 40:17

አጠቃላይ መረጃ፡
ቤተ መቅደሱን የከበቡ ሁለት ግድግዳዎች ነበሩ። ውጫዊው ግድግዳ ውጫዊውን አደባባይ ይከባል፣ በዚያ ውስጥ ደግሞ ውስጣዊው ግድግዳ ውስጣዊውን አደባባይ ይከባል። ውስጣዊው አደባባይ ከውስጣዊው ቅጥር ግቢ ከፍ ያለ ነበር። እያንዳንዱ ግድግዳ በስተ ምስራቅ፣ ሰሜን እና ደቡብ አቅጣጫዎች በሮች አሉት።

ሰውየው ወደ ቤተ መቅደሱ ውጫዊ አደባባይ አመጣኝ
"ሰውየው ከቤተ መቅደሱ ውጫዊ ስፍራ ወደ ቤተ መቅደሱ ውጫዊ አደባባይ አመጣኝ"

ውጫዊ አደባባይ
ይህ በሕዝቅኤል 10፡5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

እነሆ
እዚህ ስፍራ "እነሆ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሕዝቅኤል አስደሳች ነገር ማየቱን ነው።

የእግረኛ መንገድ
ከአለት/ድንጋይ የተሰራ ጠፍጣፋ ወለል

ከእግረኛው መንገድ አጠገብ ሰላሳ ክፍሎች
"እናም በእረኛ መንገዱ ዙሪያ 30 ክፍሎች ነበሩ" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እስከ... ድረስ ሄደ
"እስከ... ድረስ ሁሉ ሄደ"

የታችኛው መግቢያ ፊት እስከ ውስጣዊ በር ፊት ለፊት ድረስ
የታችኛው በር በውጫዊ አደባባይ ግድግዳ ላይ ሲሆን፣ ውስጣዊው በር በስስጣዊው አደባባይ ግድግዳ ላይ ነበር። "ውጫዊው በር ፊቱ እስከ ውስጣዊ በር ፊት"

አንድ መቶ ከንድ
ወደ 54 ሜትር የሚጠጋ (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

ክንዶች
በሕዝቅኤል 40፡5 ላይ እነዚህ "ረጅም" ክንዶች የሚለው እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

Ezekiel 40:20

ቤቶች
ይህ በሕዝቅኤል 40፡7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ኮሪዶር/መተላለፊያ
ይህ በሕዝቅኤል 8፡16 ላይ አንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

በተመሳሳይ ለካ
"ተመሳሳይ መጠን ነበረው"

ሀምሳ ከንድ
ወደ 27 ሜትር የሚጠጋ (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

ክንዶች
በሕዝቅኤል 40፡5 ላይ እነዚህ "ረጅም" ክንዶች የሚለው እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

ሃያ አምስት ክንድ
ወደ 13.5 ሜትር የሚጠጋ

ዋናው በር
ይህ የሚያመለክተው በውጫዊው አደባባይ ምስራቃዊ አቅጣጫ ሚገኘውን በር ነው። "በውጫዊው ግድግዳ ምስራቃዊ አቅጣጫ የሚገኘው ዋናው በር"

Ezekiel 40:22

አጠቃላይ መረጃ:
ሕዝቅኤል ስለ ቤተ መቅደሱ የሚመለከተውን ራዕይ እና የነሀስ መልክ ያለውን ሰው መግለጹን ቀጥሏል።

የእርሱ መስኮቶች
"የእርሱ" የሚለው ቃል በውጨኛው አደባባይ በስተሰሜን የሚገኘውን በር ያመለክታል። "የሰሜኑ በር መስኮቶች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ቤቶች
ይህ በሕዝቅኤል 40፡7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ወደ ምስራቅ ፊታቸውን ካደረጉ በሮች ትይዩ
"እንደ ምስራቃዊ በር የመሰሉ ነበሩ" ወይም "እንደ ውጫዊ አደባባዩ ምስራቃዊ በር የመሰሉ ነበሩ

ውስጣዊ አደባባይ
ይህ በሕዝቅኤል 8፡16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

በበሩ ፊት ለፊት ወደ በሰሜን አቅጣጫ
"በቀጥታ ከሰሜን በር አቅጣጫ" ወይም "በውጫዊ አደባባይ ከሰሜን በር አንጻር"

ወደ ሰሜን ፊቱን ያደረገ በር
"የውጫዊ አደባባይ በሰሜን በኩል ያለው በር"

እንደዚሁም ደግሞ በምስራቅ በር ነበር
"በውስጣዊ አደባባይ በኩል እንደነበረው ምስራቅ በር ነበረ" ወይም "በምስራቅ በር ፊተ ለፊት እንደነበረ ወደ ውስጣዊ አደባባይ በር ነበረ"

ከአንዱ በር ወደ ሌላኛው በር
"በስተ ሰሜን ካለው ውጫዊው በር፣ በሰሜን እስካለው ውስጣዊ በር"

ክንዶች
በሕዝቅኤል 40፡5 ላይ እነዚህ "ረጅም" ክንዶች የሚለው እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

አንድ መቶ ክንድ
ወደ 54 ሜትር የሚጠጋ

Ezekiel 40:24

እንደ ሌላው ውጫዊ በሮች በተመሳሳይ ለካው
"እንደ ሰሜናዊ እና ምስራቃዊ በሮች ተመሳሳይ መጠን ነበረው"

ክንዶች
በሕዝቅኤል 40፡5 ላይ እነዚህ "ረጅም" ክንዶች የሚለው እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

ሀምሳ ከንድ
ወደ 27 ሜትር የሚጠጋ (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

ሃያ አምስት ከንድ
ወደ 13.5 ሜትር የሚጠጋ

Ezekiel 40:26

ኮሪዶር/መተላለፊያ
ይህ በሕዝቅኤል 8፡16 ላይ አንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

በዚህም በዚያም በኩል
"በሁለቱም በኩል"

ክንዶች
በሕዝቅኤል 40፡5 ላይ እነዚህ "ረጅም" ክንዶች የሚለው እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

አንድ መቶ ክንዶች
ወደ 54 ሜትር የሚጠጋ (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 40:28

ውስጣዊ አደባባይ
ይህ በሕዝቅኤል 8፡16 ላይ አንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

በደቡባዊ በሩ መንገድ በኩል
"በደቡባዊ በሩ በኩል"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ቤቶች
ይህ በሕዝቅኤል 40፡7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ኮሪዶር/መተላለፊያ
ይህ በሕዝቅኤል 8፡16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

በተመሳሳይ ለካ
"ተመሳሳይ መጠን ነበረው"

ክንዶች
በሕዝቅኤል 40፡5 ላይ እነዚህ "ረጅም" ክንዶች የሚለው እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

ሀምሳ ክንድ
ወደ 27 ሜትር የሚጠጋ (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

ሃያ አምስት ክንድ
ወደ 13.5 ሜትር የሚጠጋ

አምስት ክንድ
ወደ 27 ሜትር የሚጠጋ

ይህ ኮሪዶር/መተላለፊያ ፊቱን ወደ ውጫዊ አደባባይ መልሷል
"የመተላለፊያው መግቢያ በውጫዊው አደባባይ በኩል ነበር"

በተቀረጸ የዘንባባ ዛፍ
"ደግሞም የተቀረጸ የዘንባባ ዛፍ መልክ ነበረው"

Ezekiel 40:32

በምስራቁ መንገድ ወደ ውስጣዊ አደባባይ
"በውስጣዊ አደባባይ በስተ ምስራቅ"

ክንዶች
በሕዝቅኤል 40፡5 ላይ እነዚህ "ረጅም" ክንዶች የሚለው እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

ሀምሳ ክንድ
ወደ 27 ሜትር የሚጠጋ (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

ሃያ አምስት ክንድ
ወደ 13.5 ሜትር የሚጠጋ

ይህ መተላለፊያ ፊቱን ወደ ውጫዊ አደባባይ መልሷል
"የመተላለፊያው መግቢያ በውጫዊው አደባባይ በኩል ነበር"

Ezekiel 40:35

በተመሳሳይ ለካ
"ተመሳሳይ መጠን ነበረው"

ክንዶች
በሕዝቅኤል 40፡5 ላይ እነዚህ "ረጅም" ክንዶች የሚለው እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

ሀምሳ ክንድ
ወደ 27 ሜትር የሚጠጋ (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

ሃያ አምስት ክንድ
ወደ 13.5 ሜትር የሚጠጋ

ይህ መተላለፊያ ፊቱን ወደ ውጫዊ አደባባይ መልሷል
"የመተላለፊያው መግቢያ በውጫዊው አደባባይ በኩል ነበር"

በዚህም በዚያም በኩል
"በሁለቱም በኩል"

Ezekiel 40:38

በእያንዳንዱ መግቢያ በር መንገዶች
"በእያንዳንዱ መግቢያ በሮች"

እነርሱ የሚቃጠለውን መስዕት ይለቀልቃሉ
"እነርሱ" ለሚለው ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) መስዋዕቱን የሚያመጡ ሰዎች ወይም 2) እንስሳቱን የሚያርዱ ካህናት

የሚቃጠሉ መስዋዕቶች
የሚታረዱ እና መስዋዕት ሆነው የሚቃጠሉ እንስሳት

በእያንዳንዱ መተላለፊያ/ኮሪደር ላይ ሁለት ጠረጴዛዎች ነበሩ
በእያንዳንዱ መተላለፊያ አጠገብ ሁለት በአጠቃላይ አራት ጠረጴዛዎች ነበሩ

ለሚቃጠል መስዋዕቱ ይታረድ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊቀርብ ይችላል። "የሚቃጠለውን መስዋዕት ያርዳሉ" ወይም "የሚቃጠል መስዋዕት አድርገው የሚያቀርቡትን እንስሳ ያርዳሉ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 40:42

አራት ከተጠረበ ድንጋይ የተሰሩ ጠረጴዛዎች ነበሩ
እነዚህ መስዋዕቹ ከሚታረዱባቸው ስምንት ጠረጴዛዎች በግልጽ የተለዩ ነበሩ። ይህ ይበልጥ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "እንደዚሁም ደግሞ ከተጠረበ ድንጋይ የተሰሩ አራት ጠረጴዛዎች ነበሩ" ወይም "ከተጠረበ ድንጋይ የተሰሩ ሌሎች አራት ጠረጴዛዎች ነበሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከተጠረበ ድንጋይ
"ከተጠረበ ድንጋይ የተሰሩ"

ክንዶች
በሕዝቅኤል 40፡5 ላይ እነዚህ "ረጅም" ክንዶች የሚለው እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

አንድ ክንድ ተኩል
ወደ 0.8 ሜትር (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ክንድ
ወደ ግማሽ ሜትር ያህል

በመተላለፊያው ዙሪያ ቁመታቸው የእጅ መዳፍ የሚያህል ሁለት ጣት ያላው ሜንጦዎች ተሰቅለዋል
"በመተላለፊያው ሁሉ ዙሪያ፣ ሰዎች የእጅ መዳፍ ርዝማኔ ያላቸው፣ እያንዳንዳቸው ባለ ሁለት ጣት የሆኑ ሜንጦዎችን አንጠልጥለዋል"

ሁለት ጣት ያላቸው ሜንጦዎች
ሁለት ረጃጅም የታጠፈ ጫፍ ያላቸው ሰዎች የተለያዩ ነገሮችን የሚሰቅሉባቸው እቃዎች

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ቁመቱ የእጅ መዳፍ የሚያክል
ወደ 8 ሳንቲ ሜትር የሚሆን (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

የመስዋዕቶቹ ስጋ በጠጴዛዎች ላይ ይቀመጣል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ለመስዋዕት የሚቀርበውን ስጋ በጠረጴዛዎች ላይ ያስቀምጣሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 40:44

ውስጠኛው በር
ይህ በስተ ሰሜን የሚገኘው ውስጠኛው በር ነው።

የመዘምራን ክፍሎች/ቤቶች
"ለመዘምራን ክፍሎች።" ሆኖም፣ አንዳንድ ጥንታዊ እና ዘመናዊ ቅጂዎች መዘምራንን የሚለውን ሳይጨምሩ "ክፍሎች" ብቻ ይሉታል።

በሰሜን በኩል የሚገኘው ፊቱ ወደ ደቡብ ሲሆን፣ሌላው በደቡብ በኩል የሚገኘው ፊቱ ሰሜን ነው
"ቤት" ወይም "ክፍል" የሚለው ቃል ከቀደመው ሀረግ ያታወቃል። "ፊቱ ወደ ደቡብ የሆነው" ማለት በሩ በስተደቡብ ነው ማለት ሲሆን፣ "ፊቱ ወደ ሰሜን የሆነው" ማለት በሩ በስተ ደቡብ ነው ማለት ነው። "አንድ በሰሜን በኩል የሚገኝ ክፍል ፊቱ ወደ ደቡብ ሲሆን፣ በደቡብ በኩል የሚገኝ ሌላው ክፍል ፊቱ ወደ ሰሜን ነው" (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ደቡብ የዞረ ይህ ክፈል
ይህ የሚያመለክተው ከውስጣዊው አደባባይ በስተ ሰሜን የሚገኘውን ክፍል ነው። " ይህ በሩ በክፍሉ በስተደቡብ በኩል የሚገኝ" ወይም "ይህ በውስጠኛው አደባባይ ሰሜን በኩል የሚገኝ ክፍል"

በቤተ መቅደስ በአገልግሎት/ በስራ ግዴታ ላይ የሚገኙ
"በቤተ መቅደስ የሚሰሩ" ወይም "ቤተ መቅደሱን ለመጠበቅ ሀላፊነት ያለባቸው"

Ezekiel 40:46

አጠቃላይ መረጃ፡
ሰውየው በራዕይ ከሕዝቅኤል ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል

ወደ ሰሜን ፊቱን ያዞረ ክፍል
ይህ የሚያመለክተው በውስጣዊ አደባባይ በደቡብ በኩል የሚገኘውን ክፍል ነው። የክፍሉ በር ከክፍሉ በስተ ሰሜን ነበር። "ይህ ክፍል በሩ በቤቱ በስተ ሰሜን የሚገኝ ነው" ወይም "ይህ ክፍል በውስጠኛው አደባባይ በስተ ደቡብ ነው"

በመሰዊያው በአገልግሎት/ግዴታ ላይ የሚገኙ ካህናት
"በመሰዊያው ላይ መስዋዕት ያቀርቡ የነበሩ ካህናት"

እርሱን ለማገልገል ወደ ያህዌ ቀረቡ
x

Ezekiel 40:48

መተላለፊያ
ይህ በሕዝቅኤል 8፡16 ላይ አንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ቤቱ
ይህ ቤተ መቅደሱን ያመለክታል።

የቤቱ የበር ቋሚ
"የቤቱ በር ቋሚ"

ክንዶች
በሕዝቅኤል 40፡5 ላይ እነዚህ "ረጅም" ክንዶች የሚለው እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

አምስት ክንድ
ወደ 2.7 ሜትር የሚጠጋ (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

አስራ አራት ክንድ
ወደ 7.5 ሜትር የሚጠጋ

ሶስት ክንድ
ወደ 1.6 ሜትር የሚጠጋ

ሃያ ክንድ
ወደ 11 ሜትር የሚጠጋ

አስራ አንድ ክንድ
ወደ 6 ሜትር የሚጠጋ

አምዶች
የህንጻውን ጣራ የሚደግፉ ረጃጅም እና ጠባብ የሆኑ ደንጋዮች

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 41

1 ከዚያም ሰውዬው ወደ መቅደሱም ቅዱስ ስፍራ አገባኝ፥ የግንቡንም አዕማድ ወርድ በዚህ ወገን ስድስት ክንድ በዚያም ወገን ስድስት ክንድ አድርጎ ለካ። 2 የመግቢያውም ወርድ አሥር ክንድ ነበረ፥ የመግቢያውም መቃኖች በዚህ ወገን አምስት ክንድ በዚያም ወገን አምስት ክንድ ነበሩ።ቀጥሎም ሰውዬው ቅዱስ ስፍራውን ርዝመቱ አርባ ክንድ ወርዱም ሀያ ክንድአድርጎ ለካ። 3 ከዚያም ሰውዬው ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ገባ፥ የመግቢያውንም የግንብ አዕማድ ወርድ ሁለት ክንድ አድርጎ ለካ የመግቢያውም ወርድ ስድስት ክንድ ነበረ። የመግቢያውም ግንብ ወርድ በዚህ ወገን ሰባት ክንድ በዚያም ወገን ሰባት ክንድ ነበረ። 4 የክፍሉንም ርዝመት ወደ መቅደሱ ፊት ለፊት ሀያ ክንድ ወርዱንም ሀያ ክንድ አድርጎ ለካና፥ "ይህ ቅድስተ ቅዱሳን ነው" አለኝ። 5 የመቅደሱንም ግንብ ስድስት ክንድ አድርጎ። በመቅደሱም ዙሪያ ሁሉ ያሉትን የጓዳዎቹን ሁሉ ወርድ አራት ክንድ ነበረ። 6 ጓዳዎቹም አንዱ ከአንዱ በላይ በሦስት ደርብ ነበሩ፥ በእያንዳንዱም ደርብ ሠላሳ ጓዳዎች ነበሩ። በመቅደሱም ግንብ ዙሪያ ድጋፍ የሆኑ መደርደሪያዎች ነበሩ፥ ምክንያቱም በመቅደሱ ግንብ ውስጥ ድጋፎች አልነበሩም። 7 ላይኞቹ ጓዳዎች ከታችኞቹ ጓዳዎች ይበልጡ ነበር ከታችኛውም ደርብ ወደ መካከለኛው ከመካከለኛውም ደርብ ወደ ላይኛው የሚወጣበት ደረጃ ነበረ። 8 በመቅደሱም ዙሪያ የጓዳዎቹም መሠረት የሆነ ከፍ ያለ ወለል እንዳለ አየሁ ቁመቱም ሙሉ ዘንግ የሚያህል ስድስት ክንድ ነበረ። 9 የጓዳዎቹም የውጭው ግንብ ውፍረት አምስት ክንድ ነበረ። በመቅደሱም ጓዳዎች ውጭ የቀረ አንድ ባዶ ስፍራ ነበረ። 10 በዚህም ባዶ ስፍራ በአንድ ወገን የካህናት በረንዳዎች ነበሩ፤ የባዶውም ስፍራ ወርድ በዙሪያ አምስት ክንድ ነበረ። ይህም ባዶ ሥፍራ በመቅደሱ ዙሪያ ወርዱ ሀያ ክንድ ነበረ። 11 በዚህም በባዶው ስፍራ አንዱ በሰሜን በኩል አንዱም በደቡብ በኩል የጓዳዎች መግቢያ ነበረ። የባዶውም ስፍራ ዙሪያ ወርድ አምስት ክንድ ነበረ። 12 በምዕራብም በኩል ባለው ግቢ አንጻር ያለው ህንጻ ስፋቱ ሰባ ክንድ ነበረ። በግቢውም ዙሪያ የነበረ ግንብ ውፍረቱ አምስት ክንድ ርዝመቱም ዘጠና ክንድ ነበረ። 13 የመቅደሱንም ርዝመት መቶ ክንድ፥ የልዩውን ስፍራና ግቢውን ከግንቡ ጋር አንድ መቶ ክንድ አድርጎ ለካ። 14 ደግሞም ከቤተ መቅደሱ ፊት ለፊት የሚገኘው ግቢ የፊት ለፊት ወርዱ አንድ መቶ ክንድ ነበር። 15 ቀጥሎም ሰውዬው ከቤተ መቅደሱ በስተዋላ ያለውን ህንጻ የምዕራብ ክፍል በዚህና በዚያ ከነበሩት ፎቆች ጋር እንዲሁም ቅዱስ ስፍራውና መድረኩን አንድ መቶ ክንድ አድርጎ ለካ። 16 ውስጠኛዎቹ ግድግዳዎች፥ ጠባቦቹን ጨምሮ መስኮቶቹ እንዲሁም በሶስት ደረጃዎች ያሉ ፎቆች በእንጨት ተለብጠው ነበር። 17 ከደጁም በላይ እስከ ውስጠኛው ክፍል ድረስ፥ በውጭም ግንቡ ሁሉ ውስጡም ውጭውም ተለብጦ ነበር። 18 በኪሩቤልና በዘንባባ ዛፎች ተውቦ ነበር የዘንባባውም ዛፍ ከኪሩብና ከኪሩብ መካከል ነበረ እያንዳንዱም ኪሩብ ሁለት ፊት ነበረው። 19 የሰው ፊት የሚመስለው በአንድ ወገን ወዳለው የዘንባባ ዛፍ ይመለከት ነበር፥ የአንበሳ ፊት የሚመስለው ደግሞ በሌላ ወገን ወዳለው የዘንባባ ዛፍ ይመለከት ነበር። ይህም በዙሪያ ያሉትን ቤቶች አስውቦ ነበር። 20 ከመሬት አንሥቶ እስከ ደጁ አናት ድረስ እና በመቅደሱ ላይ በኪሩቤልና በዘንባባ ዛፎች ተውበው ነበር። 21 የመቅደሱ መቃኖችም አራት ማዕዘን ነበሩ፥ ሁሉም ለእርስ በእርስ ትይዩ ነበሩ። 22 ከቅዱሱ ሥፍራ ፊት ለፊት የሚገኘው ከእንጨት የተሰራው መስዋዕት ቁመቱ ሦስት ክንድ ርዝመቱ ሁለት ክንድ ወርዱም ሁለት ክንድ ነበር። ማዕዘኖቹም እግሩም አገዳዎቹም ከእንጨት ተሠርተው ነበር። ሰውዬውም ፥ "ይህች በእግዚአብሔር ፊት ያለችው ገበታ ናት" አለኝ። 23 ለተቀደሰው ስፍራና ለቅድስተ ቅዱሳኑ ሁለት መዝጊያዎች ነበሩአቸው። 24 ለእያንዳንዱ መዝጊያም ሁለት ተዘዋዋሪ ሳንቃዎች ነበሩት ለአንዱ መዝጊያ ሁለት ለሌላውም መዝጊያ ሁለት ሳንቃዎች ነበሩት። 25 ግንቦቹን እንዳስዋቡት ዓይነት በእነዚህ በቅዱስ ስፍራው መዝጊያዎች ላይ ኪሩቤልና የዘንባባ ዛፎች ተቀርጸው ነበር፣ በስተ ውጭም ባለው በደጀ ሰላሙ ፊት የእንጨት ጣራ ነበረ። 26 በደጀ ሰላሙም በሁለቱ ወገን በዚህና በዚያ ጠባብ መስኮቶችና የተቀረጹ የዘንባባ ዛፎች ነበሩበት። እነዚህም የመቅደሱም ጓዳዎች ነበሩ ፥ እነርሱም ተንጠልጣይ ጣሪያዎችም ነበሯቸው።

Ezekiel 41:1

አጠቃላይ መረጃ:
በሕዝቅኤል ራዕይ ውስጥ ያለው ሰው (ሕዝቅኤል 40:3) ለሕዝቅኤል የቤተ መቅደሱን ዙሪያ ማሳየቱን ይቀጥላል።

የመቅደሱ ቅዱስ ስፍራ
በቤተ መቅደሱ "ከቅድስተ ቅዱሳኑ" ፊት ለፊት ያለው ክፍል

በሁለቱም በኩል ስፋቱ ስድስት ክንድ
እነዚህ ክንዶች "ረጅም" ክንዶች ነበሩ (ሕዝቅኤል 40:5) "፤ 54 ሴንቲሜትር የሆነ ክንድ። ይህ በሕዝቅኤል 40:5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "በስፋት በሁለቱም በኩል ስድስት ክንድ ነበሩ"

ስድስት ክንድ
ወደ 3.2 ሜትር የሚጠጋ (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

ክንዶች
እያንዳንዱ ረጅም ክንድ ወደ 54 ሳንቲ ሜትር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 40:5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

አስር ክንድ
ወደ 5.4 ሜትር የሚጠጋ (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

አምስት ክንድ
ወደ 2.7 ሜትር የሚጠጋ (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

ወርድና ስፋት/አውታረ መጠን
"መጠኑ"

አርባ ክንድ
ወደ 22 ሜትር የሚጠጋ (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

ሃያ ክንድ
ወደ 2.7 ሜትር የሚጠጋ (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 41:3

ሁለት ክንድ
ወደ 1.1 ሜትር የሚጠጋ (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

ክንዶች
እያንዳንዱ ረጅም ክንድ ወደ 54 ሳንቲ ሜትር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 40:5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ስድስት ክንድ
ወደ 3.2 ሜትር የሚጠጋ (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባት ክንድ
ወደ 3.8 ሜትር የሚጠጋ (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

ሃያ ክንድ
ወደ 11 ሜትር የሚጠጋ (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 41:5

ቤቱ
ቤተ መቅደሱ

ስድስት ክንድ
ወደ 3.2 ሜትር የሚጠጋ (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

ክንዶች
እያንዳንዱ ረጅም ክንድ ወደ 54 ሳንቲ ሜትር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 40:5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

አራት ክንድ
ወደ 2 ሜትር የሚጠጋ

ሶስት ደረጃዎች/ደርቦች
"ሶስት ደርብ/ፎቅ"

በቤቱ ግድግዳ ዙሪያ ተሸካሚዎች ነበሩ
"ቤቱ ዙሪያውን ለሚገኙ ክፍሎች ሁሉ ተሸካሚ ነበረው።" በዚህ መንገድ በጎን የሚገኙ ክፍሎች በግድግዳው ተሸካሚ ላይ ማረፍ ይችላሉ"

ለመደገፍ
"ተሸካሚዎቹ መደገፍ ይችሉ ዘንድ"

በቤቱ ግድግዳ ውስጥ የተደረገ ድጋፍ አልነበረም
"በቤቱ ገድግዳ ውስጥ ድጋፎች አልነበሩም።" ቤተ መቅደሱን የሚገነቡ ሰዎች ከቅድስተ ቅዱሳኑ ግድግዳ ከጎን የሚገኙ ክፍሎችን ለማገኛኘት የሚደግፉ ድንጋይ ወይም እንጨት አይፈልጉም ነበር።

Ezekiel 41:8

ከፍ ያለ ክፍል
መድረክ

ክፍሎች
ትንንሽ ክፍሎች

ሙሉ ዘንግ
"ዘንግ" የሚለውን በሕዝቅኤል 40:5 መሰረት ይተርጉሙ።

ክንዶች
እያንዳንዱ ረጅም ክንድ ወደ 54 ሳንቲ ሜትር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 40:5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

ስድስት ክንድ
ወደ 3.2 ሜትር የሚጠጋ (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

አምስት ክንድ
ወደ 2.7 ሜትር የሚጠጋ (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 41:10

የካህናት በውጭ በኩል የሚገኙ ክፍሎች
"የካህናት በውጭ በኩል የሚገኙ ክፍሎች ከቅድስተ ቅዱሳኑ የራቁ ነበሩ"

ሃያ ክንድ
ወደ 11 ሜትር የሚጠጋ (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

የዚህ ክፍት አካባቢ ስፋት ዙሪያው አምስት ክንድ ነበር
"በክፍሎቹ እና በቤተ መቅደሱ መሃል ያለው ጠቅላላ ስፍራ በአጠቃላይ በቤተ መቅደሱ ዙሪያ ስፋቱ አምስት ክንድ ነበር"

Ezekiel 41:12

በምዕራብ በኩል ፊቱ ወደ አደባባዩ የሆነው ህንጻ ስፋቱ ሰባ ክንድ ነበር
ይህ በሁለት ዐረፍተ ነገሮች ሊገለጽ ይችላል። "በቤተ መቅደሱ ምዕራብ በኩል ህንጻ ነበር፣ ደግሞም መግቢያው በአደባባዩ በኩል ነበር። ስፋቱ ሰባ ክንድ ነበር።"

ሰባ ክንድ... አምስት ክንድ... ዘጠና ክንድ... አንድ መቶ ክንድ
እያንዳንዱ ረጅም ክንድ ወደ 54 ሴንቲ ሜትር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 40:5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "70 ክንድ... 5 ክንድ... 90 ክንድ... 100 ክንድ" ወይም "ወደ 38 ሜትር... ወደ 2.7 ሜትር... ወደ 49 ሜትር... ወደ 54 ሜትር" (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 41:15

ሰገነቶች
"ሰገነቶች።" ሰገነቶች ከሌሎች ህንጻዎች በላይ ከፍ ተደርገው የሚገነቡ ቦታዎች ነበሩ። ሰዎች ሰገነቶች ላይ ወጥተው የህምጻውን ዋና ወለል ወደ ታች ማየት ይችላሉ።

አንድ መቶ ክንድ
እያንዳንዱ ረጅም ክንድ ወደ 54 ሴንቲ ሜትር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 40:5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "100 ክንድ" ወይም "ወደ 54 ሜትር የሚጠጋ" (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

መተላለፊያ
ይህ በሕዝቅኤል 8:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

Ezekiel 41:18

ጌጠኛ ተደርጎ ነበር
x

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ezekiel 41:21

መልካቸው እንደ እንጨቱ መሰዊያ መልክ ነበር
"መልክ" የሚለው ረቂቅ ስም በግስ ሊተረጎም ይችላል። "የእንጨት መሰዊያ በሚታይበት ተመሳሳይ መንገድ ይታያሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ሶስት ክንድ... ሁለት ክንድ
እያንዳንዱ ረጅም ክንድ ወደ 54 ሴንቲ ሜትር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 40:5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ወደ 1.6 ሜትር የሚጠጋ... ወደ 1.1 ሜትር የሚጠጋ" (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

ለቅድስቱ እና ቅድስተ ቅዱሳኑ ጥንድ በሮች ነበሩ
"ቅዱሱ ስፍራ እና ቅድስተ ቅዱሳኑ ሁለቱም ሁለት በሮች ነበራቸው"

እነዚህ በሮች እያንዳንዳቸው ሁለት የበር ማጠፊያ ነበራቸው
"እያንዳንዱ በር በማጠፊያዎቹ ላይ ሁለት ክፍሎች/አካል ነበረው።" ማጠፊያዎች በሮችን ከግርግዳ ጋር በመያያዝ በሮች እንዲወዛወዙ/እንዲከፈቱና እንዲዘጉ ያደርጋሉ።

ለአንድ በር ሁለት መጠፊያዎች እና ሁለት ማጠፊያዎች ለሌላኛው በር
"ለሁለቱም ቅዱስ ስፍራ ሁለቱም በሮች እና ቅድስተ ቅዱሳኑ ሁለት ክፍሎች/አካል አላቸው"

Ezekiel 41:25

ግርግዳዎቹ እንደተጌጡት
"ግድግዳዎቹ የኪሩቤሎች እና የዘንባባ ዛፎች ቅርጽ ያለባቸው እንደሆነ"

መተላለፊያ
ለድጋፍ

መተላለፊያ
በመግቢያው ፊት ለፊት በአምዶች ወይም ለድጋፍ በቆሙ በምሶሶዎች ላይ የሚገኙ ልባሶች። ይህ በሕዝቅኤል 8:16 ላይ አንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 42

1 በመቀጠልም ሰውዬው በውጭ በሰሜን አቅጣጫ ወደሚገኘው አደባባይ አወጣኝ፥ በልዩውም ስፍራ አንጻርና በሰሜን በኩል ባለው ግቢ ፊት ለፊት ወዳሉ
ክፍሎች አመጣኝ ። **2** ክፍሎቹም በፊት ለፊት ገጽታቸው መቶ ክንድ ስፋታቸውም አምሳ ክንድ ነበረ። **3** ከእነዚህ ክፍሎች አንዳንዶቹ ፊታቸው ወደ ግቢው
ወስጥ ነበር ከቤተመቅደሱም ሃያ ክንድ ይርቁ ነበር። ባለ ሶስት ደርብ ክፍሎችም ነበሩ። ከላይ ያለው ክፍል ወደታችኛው ክፍሎች ይመለከትና ለእነርሱ ክፍት
ነበር መላለፊያ መንገድም ነበረው። የተወሰኑት ክፍሎች ወደ ወደውጪኛው አደባባይ ይመለከቱ ነበረ። **4** ከክፍሎቹም ፊት በስተ ውስጥ ወርዱ አሥር ክንድ
ርዝመቱ መቶ ክንድ የሆነ መተላለፊያ ነበረ። የክፍሎቹም መዝጊያዎች ወደ ሰሜን ይመለከቱ ነበር። **5** ነገር ግን መተላለፊያው ከህንጻው መካከለኛና ከታችኛው
ክፍል በላይ ቦታቸውን የያዘ በመሆኑ የላይኞቹ ክፍሎች ትንንሽ ነበሩ። **6** በሦስት ደርብ በመስራታቸውና በአደባባዩም እንዳሉት አዕማድ ያሉ፥ አዕማድ
ስላልነበሯቸው ላይኞቹ ደርቦች ከመካከለኞቹና ከታችኞቹ ይልቅ ጠባብ ነበሩ **7** የውጪው ግንብ ከክፍሎቹና ከክፍሎቹ ፊት ለፊት ከሚገኘው ክውጭው
አደባባይ ትይዩ ይገኛል ፥ ርዝመቱም አምሳ ክንድ ነበረ። **8** በውጪኛው አደባባይ ርዝመቱ ሃምሳ ክንድ ሲሆን በመቅደሱ ፊት የነበሩት ክፍሎች ደግሞ
ርዝመታቸው መቶ ክንድ ነበረ። **9** ከእነዚህም ዕቃ ቤቶች በታች በስተ ምሥራቅ በኩል፥ ከውጭው አደባባይ የሚጀምር መግቢያ ነበረ። **10** በምስራቅ በኩል
የውጭውን አደባባይ ተከትሎ ከቤተመቅደሱ ውስጠኛ አደባባይ ፊት ለፊት ክፍሎች ነበሩ። **11** በስተ ፊታቸውም የነበረ መንገድ በርዝመቱና በወርዱ በሰሜን
በኩል ከነበሩት ክፍሎች ጋር ተመሳሳይ ሲሆን መግቢያዎቻቸውም በቁጥር እኩል ነበሩ። **12** በደቡብም በኩል ልክ በሰሜን በኩል እንዳለው ወደ ክፍሎቹ
የሚያስገቡ መግቢያዎች አሉ። በውስጥ በኩል ያለው መተላለፊያ ከበላዩ መግቢያ ያለው ሲሆን መተላለፊያው ወደተለያዩ ክፍሎች ያመሩ ነበር። በምስራቅ
በኩል ወደ መተላለፊያው አንደኛው ጫፍ የሚያመራ መግቢያ ነበር። **13** ከዚያም እንዲህም አለኝ፥ "በውጭኛው አደባባይ ፊት ለፊት የሚገኙት የሰሜንና
የደቡብ ክፍሎች ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡ ካህናት ከሁሉ ይልቅ የተቀደሰውን ምግብ የሚበሉባቸው የተቀደሱ ክፍሎች ናቸው። ስፍራው ቅዱስ ስለሆን በዚያ
የተቀደሰውን ነገር የእህሉን ቊርባን የኃጢአቱንና የበደሉን መሥዋዕት ያስቀምጣሉ። **14** ካህናቱም አንድ ጊዜ ወደዚያ ከገቡ ሲያገለግሉ የሚለብሷቸው ልብሶች
ቅዱስ በመሆናቸው ሳያወልቁ ከተቀደሰው ሥፍራ ወደውጭኛው አደባባይ መውጣት የለባቸውም። ስለዚህም ወደ ሕዝቡ ከመጠጋታቸው በፊት ሌላ ልብስ
መልበስ አለባቸው። **15** ውስጠኛውንም ቤት ለክቶ በፈጸመ ጊዜ ወደ ምሥራቅ ወደሚመለከት በር አወጣኝና ዙሪያውን ሁሉ ለካ። **16** የምሥራቁን ወገን
በመለኪያ ዘንግ አምስት መቶ ክንድ አድርጎ ለካ። **17** የሰሜኑንም ወገን በመለኪያ ዘንግ አምስት መቶ ክንድ አድርጎ ለካ። **18** የደቡቡንም ወገን በመለኪያ
ዘንግ አምስት መቶ ክንድ አድርጎ ለካ። **19** ዞረም፥ የምዕራቡንም ወገን በመለኪያ ዘንግ አምስት መቶ ክንድ አድርጎ ለካ። **20** በአራቱ ወገን ለካው።
የተቀደሰውንና ያልተቀደሰውን ይለይ ዘንድ ርዝመቱ አምስት መቶ ክንድ ወርዱም አምስት መቶ ክንድ የሆነ ቅጥር በዙሪያው ነበረ።

Ezekiel 42:1

ውጫዊ አደባባይ
ይህ በሕዝቅኤል 10:5 ላይ አንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

አንድ መቶ ክንድ... ሃምሳ ክንድ... ሃያ ክንድ
እያንዳንዱ ረጅም ክንድ ወደ 54 ሴንቲ ሜትር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 40:5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "100 ክንድ... 50 ክንድ... 20 ክንድ" ወይም "ወደ 54 ሜትር የሚጠጋ... ወደ 27 ሜትር የሚጠጋ... ወደ 11 ሜትር የሚጠጋ" (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

አንዳንዶቹ ክፍሎች ወደ ውስጠኛው አደባባይ ፊታቸውን መልሰዋል
"አንዳንዶቹ ክፍሎች ወደ ውስጠኛው አደባባይ የዞሩ ነበሩ" ወይም "ከእነዚያ ክፍሎች የአንዳንዶቹ መግቢያ ወደ ውስጠኛው አደባባይ የዞረ ነበር"

ውስጠኛው አደባባይ
ይህ በሕዝቅኤል 8:16 ላይ አንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ለእነርሱ የተከፈቱ ነበሩ
"ከውስጠኛው አደባባይ ሲወጣ አየሁ"

መሄጃ መንገድ ነበረው
"በክፍሎቹ መሃል ለመረማመድ ስፍራ ስለነበረ"

አንዳንዶቹ ክፍሎች ወደ ውጫዊው አደባባይ ማየት የሚያስችሉ ነበሩ
"አንዳንዶቹ ክፍሎች ወደ ውጫዊው አደባባይ ፊታቸውን የመለሱ ነበሩ" ወይም "የአንዳንዶቹ በሮች መግቢያዎች ወደ ውጫዊው አደባባይ ፊታቸውን የመለሱ ነበሩ"

Ezekiel 42:4

አስር ክንድ... አንድ መቶ ክንድ... ሃያ ክንድ
እያንዳንዱ ረጅም ክንድ ወደ 54 ሴንቲ ሜትር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 40:5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "10 ክንድ... 100 ክንድ" ወይም "ወደ 5.4 ሜትር የሚጠጋ... ወደ 54 ሜትር የሚጠጋ" (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

ከክፍሉ ጋር ሲነጻጸር በመጠን አነስተኛ
"ከክፍሎቹ ያነሰ"

Ezekiel 42:7

ሃምሳ ክንድ... አንድ መቶ ክንድ
እያንዳንዱ ረጅም ክንድ ወደ 54 ሴንቲ ሜትር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 40:5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "50 ክንድ... 100 ክንድ" ወይም "ወደ 27 ሜትር የሚጠጋ... ወደ 54 ሜትር የሚጠጋ" (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 42:13

የእህል ቁርባን
ህዝቡ እግዚአብሔርን ለማመስገን የሚያቀርበው እህል ወይም ዱቄት

Ezekiel 42:15

ወደ ምስራቅ ወደ ዞረው በር
"ወደ ምስራቅ መውጫ በር" ወይም "በምስራቅ በር በኩል መውጣት"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ezekiel 42:16

እርሱ ለካ
"እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የናስ መልክ ያለውን ሰው ነው። (ሕዝቅኤል 40፡3 ተመልከቱ)

መለኪያ ዘንግ
ይህ በሕዝቅኤል 40፡5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

አምስት መቶ ክንድ
እያንዳንዱ ረጅም ክንድ ወደ 54 ሴንቲ ሜትር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 40፡5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "500 ክንድ" ወይም "ወደ 270 ሜትር የሚጠጋ" (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 43

1 ወደ ምሥራቅም ወደሚመለከተው በር አመጣኝ። **2** እነሆም፥ የእስራኤል አምላክ ክብር ከምሥራቅ በኩል መጣ፤ ድምፁም እንደ ብዙ ውኆች ያለ ነበር፥ ከክብሩም የተነሣ ምድር ታበራ ነበር። **3** ያየሁትም ራእይ ከተማይቱን ለማጥፋት በመጣ ጊዜ እንዳየሁትና በኮበር ወንዝ እንዳየሁት አይነት ራእይ ነበረ- እኔም በግምባሬ ተደፋሁ! **4** የእግዚአብሔርም ክብር ወደ ምሥራቅ በሚመለከት በር ወደ መቅደሱ ገባ። **5** መንፈሱም አነሣኝ ወደ ውስጠኛውም አደባባይ አገባኝ እነሆም፥ የእግዚአብሔር ክብር መቅደሱን ሞልቶት ነበር። **6** ሰውዬው በአጠገቤ ቆሞ ሳለ ከመቅደሱ ውስጥ የሚናገረኝን ሌላ ሰው ሰማሁ። **7** እንዲህም አለኝ፥ "የሰው ልጅ ሆይ፥ ይህ በእስራኤል ልጆች መካከል ለዘላለም የምቀመጥበት የዙፋኔ ስፍራና የእግሬ ጫማ መረገጫ ነው፤ ዳግመኛም የእስራኤል ቤትና ነገሥታቶቻቸው በግልሙትናቸውና በጣዖት ማምለኪያ ቦታዎቻቸው ባለው በነገሥታቶቻቸው ሬሳ ቅዱስ ስሜን አያረክሱም። **8** ከእንግዲህ ግንብ ብቻ በመካከል በማድርግ የጣዖቶቻቸውን መድረክ በመድረኬ አጠገብ፥ የጣዖቶቻቸውን መቃኖች በመቃኔ አጠገብ በማስቀመጥ ቅዱስ ስሜን አያረክሱም። በሠሩትም ርኵሰት ቅዱስ ስሜን አረከሱ ስለዚህ በቍጣዬ አጠፋኋቸው። **9** አሁንም ግልሙትናቸውንና የነገሥታቶቻቸውን ሬሳ ከፊቴ ያርቁ፥ እኔም ለዘላለም በመካከላቸው አድራለሁ! **10** አንተም የሰው ልጅ፥ ከኃጢአታቸው የተነሣ ያፍሩ ዘንድ ለእስራኤል ቤት ራስህ ልትነግራቸው ይገባል። ስለዚህ የቤቱ ዝርዝር መግለጫ ማሰብ አለባቸው። **11** ከሠሩትም ሥራ ሁሉ የተነሣ ቢያፍሩ፥ የቤቱን መልክና ምሳሌውን መውጫውንም መግቢያውንም ሥርዓቱንም ሕጉንም ሁሉ አስታውቃቸው። የቤቱን አሰራርና ሕጉን ሁሉ ይጠብቁ ዘንድ ያደርጉትም ዘንድ በፊታቸው ጻፈው። **12** የቤቱ ሥርዓት ይህ ነው፡ ከተራራው ራስ ጅምሮ በዙሪያው ያለ ዳርቻ ሁሉ እጅግ የተቀደስ ይሆናል። አስተውል! የቤቱ ሥርዓት ይህ ነው። **13** የመሠዊያውም ልክ በረጅም ክንድ ይህ ነው፥ ይህም ማለት አንድ ክንድ ከጋት ነው። በመሰዊያው ዙሪያ ያለው አሸንዳ ቁመቱ አንድ ክንድ ወርዱም አንድ ክንድ ነው። የዙሪያው ጠርዝ አንድ ስንዝር ነው። ይህም የመሰዊያው መሠረት ነው። **14** በመሬቱም ላይ ካለው አሸንዳ ጀምሮ እስከ ታችኛው የመሰዊያው እርከን ድረስ ሁለት ክንድ ወርዱም አንድ ክንድ ነው። ከመሰዊያው ትንሹ ጠርዝ እስከ ትልቁ ጠርዝ ድረስ አራት ክንድ፥ የሰፊው ጠርዝ ስፋትም አንድ ክንድ ነው። **15** ለሚቃጠል መስዋዕት የሚያገለግለው በመሰዊያው ላይ ያለው ምድጃ አራት ክንድ ነው፥ በምድጃውም ላይ ጫፋቸው ወደላይ የቆመ ቀንዶች አሉበት። **16** ምድጃውም አራት ማዕዘን ሆኖ ርዝመት አሥራ ሁለት ክንድ ወርዱም አሥራ ሁለት ክንድ ነው። **17** ጠርዙም በአራቱም ማዕዘን አሥራ አራት ክንድ ወርዱም አሥራ አራት ክንድ ነው፥ በዙሪያውም ያለው ክፈፍ ግማሽ ክንድ ነው። አሸንዳውም ወደምስራቅ ከሚያመለክቱት ደረጃዎቹ ጋር ዙሪያውን አንድ ክንድ ነው። **18** ቀጥሎም እንዲህ አለኝ፥ "የሰው ልጅ ሆይ፥ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ የሚቃጠለውን መሥዋዕት ያቀርቡበት ዘንድ ደሙንም ይረጩበት ዘንድ መሰዊያውን በሚሠሩበት ቀን የመሠዊያው ሕግ ይህ ነው። **19** ያገለግሉኝ ዘንድ ወደ እኔ ለሚቀርቡ ከሳዶቅ ዘር ለሚሆኑ ለሌዋውያኑ ካህናት ለኃጢአት መሥዋዕት የሚሆነውን ወይፈን ትሰጣቸዋለህ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፦ **20** ከደሙም ትወስዳለህ፥ በአራቱ ቀንዶቹም በእርከኑም በአራቱ ማዕዘን ላይ በዙሪያውም ባለው ክፈፍ ላይ ትረጨዋለህ እንዲሁ ታነጻዋለህ ታስተሰርይለትማለህ። **21** ለኃጢአትም መሥዋዕት የሚሆነውን ወይፈን ትወስዳለህ፥ በመቅደሱም ውጭ በተዘጋጀለት ስፍራ ታቃጥለዋለህ። **22** በሁለተኛውም ቀን ለኃጢአት መሥዋዕት የሚሆነውን ነውር የሌለበትን አውራ ፍየል ታቀርባለህ፤ ካህናቱም በወይፈኑ ደም እንዳነጹት እንዲሁ መሠዊያውን ያነጹበታል። **23** ማንጻቱንም ከፈጸምህ በኋላ ነውር የሌለበትን ወይፈንና ከመንጋው የወጣውን ነውር የሌለበትን አውራ በግ ታቀርባለህ። **24** በእግዚአብሔርም ፊት ታቀርባቸዋለህ፥ ካህናቱም ጨው ይጨምሩባቸዋል፥ የሚቃጠለውንም መሥዋዕት አድርገው ለእግዚአብሔር ያቀርቡአቸዋል። **25** ለሰባት ቀንም በየዕለቱ ለኃጢአት መሥዋዕት የሚሆነውን አውራ ፍየልን ታቀርባለህ፥ ካህናቱም ነውርም የሌለባቸውን አንድ ወይፈን ከመንጋውም የወጣውን አንድ አውራ በግ ያቀርባሉ። **26** ሰባት ቀን ለመሠዊያው ያስተሰርያሉ ያነጹትማል፥ እንዲሁም ይቀድሱታል። **27** እነዚህ ቀኖችንም መፈጸም አለባቸው፥ በስምንተኛውም ቀን ከዚያም በኋላ ካህናቱ የሚቃጠለውን መሥዋዕታችሁን የደኅንነትንም መሥዋዕታችሁን በመሠዊያው ላይ ያደርጋሉ እኔም እቀበላችኋለሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፦

Ezekiel 43:1

እነሆ!
እዚህ ስፍራ "እነሆ" የሚለው ቃል አንባቢውን ቀጥሎ ለሚመጣው አስደናቂ መረጃ ያነቃዋል።

ብዙ ውኆች
ይህ "ብዙ ውሃ" ማለት ነው። ሞልቶ የሚፈስን ወንዝ ወይም ታላቅ ፏፏቴን ወይም የውቅያኖስ ማዕበልን ሊያመለክት ይችላል። እነዚህ ሁሉ በጣም ከፍ ያለ ድምጽ የሚያሰሙ ናቸው። ይህ በሕዝቅኤል 1:24 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ምድር በእርሱ ክብር አበራች
"ምድር ከእርሱ ክብር የተነሳ በደማቅ ብርሃን ተሞልታ ነበር"

Ezekiel 43:3

ይህ ነበር
"ከምስራቅ የሚመጣው የእግዚአብሔር ክብር... ነበር"

በራዕዩ በታየው መሰረት
"መታየት" የሚለው ረቂቅ ስም በግስ ሊተረጎም ይችላል። "ልክ በራዕዩ እንደ ታየ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ከተማይቱን ሊያጠፋ በሚመጣበት ጊዜ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "የእስራኤል አምላክ ከተማይቱን ሊያጠፋት በሚመጣበት ጊዜ" ወይም 2) "የእስራኤል አምላክ ከተማይቱን ሲያጠፋት ለማየት እኔ በምመጣበት ጊዜ።"

እነሆ
የእናንተ ቋንቋ ሕዝቅኤል በተመለከተው መደነቁን የሚገልጽበት የተለየ ቃል ሊኖረው ይችላል። እዚህ ስፍራ ይህንን ቃል መጠቀም ትችላላችሁ።

Ezekiel 43:6

የንጉሦቻቸው ሬሳ
የህዝቦች ንጉሦች የሚያመልኳቸው ጣኦቶች የተገለጹት ሬሳዎች/በድን እንደሆኑ ተደርጎ ነው፣ ምክንያቱም ጣኦቶች ህይወት የላቸውም። "ንጉሦቻቸው የሚያመልኳቸው ህይወት የሌላቸው ጣኦቶች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ናቁ/አረከሱ
"እስራኤላውያን ናቁ/አረከሱ"

አስጸያፊ ተግባራት
"እነርሱ ያደረጓቸው አስጸያፊ ነገሮች።" ህዝቡ ጣኦታትን እና ሀሰተኛ አማልክትን በማምለኩ እግዚአብሔር ተቆጥቶ ነበር። ይህ በሕዝቅኤል 5:9 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በቁጣዬ ፈጅኋቸው
እዚህ ስፍራ "ፈጅኋቸው" የሚለው ሀረግ ትርጉሙ "ሙሉ ለሙሉ ማትፋት" ማለት ነው። "እኔ በጣም ተቆጥቼ ስለነበረ ሙሉ ለሙሉ እነርሱን አጠፋኋቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 43:9

የንጉሦቻቸው ሬሳ
የህዝቦች ንጉሦች የሚያመልኳቸው ጣኦቶች የተገለጹት ሬሳዎች/በድን እንደሆኑ ተደርጎ ነው፣ ምክንያቱም ጣኦቶች ህይወት የላቸውም። ይህ በሕዝቅኤል 43:7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።"ንጉሦቻቸው የሚያመልኳቸው ህይወት የሌላቸው ጣኦቶች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 43:10

ይህ ገለጻ
"ይህ አካሄድ/ምሳሌ" ወይም "ይህ እቅድ"

በዐይኖቻቸው ፊት
እዚህ ስፍራ ለተመለከቱት ትኩረት ለመስጠት እስራኤላውያን የተገለጹት "ዐይኖቻቸው" በሚለው ቃል ነው። ይህ በሕዝቅኤል 21:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "በእነርሱ ፊት" ወይም "በእስራኤላውያን ሰዎች ፊት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ንድፉን ሁሉ ይጠብቁ
"አካሄዱን/ምሳሌውን ይከተሉ"

Ezekiel 43:12

ደንቡ
"ትዕዛዙ" ወይም "ህጉ"

የዙሪያው ድንበር
"ድንበር" የሚለው ቃል ምናልባት በቤተ መቅደሱ ዙሪያ የሚገኘውን ግርግዳ/ግንብ ሊያመለክት ይችላል።

Ezekiel 43:13

አንድ ክንድ... ሁለት ክንድ...አራት ክንድ
እያንዳንዱ ረጀም ክንድ ወደ 54 ሴንቲ ሜትር ነው። ዩዲቢ እንዳደረገው "ክንዶች" በሚለው መለኪያ ምትክ ዘመናዊ መለኪያ ከተጠቀሙ ይህንን መረጃ አለማካተት ይችላሉ። ይህ በሕዝቅኤል 40:5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ወደ 54 ሴንቲ ሜትር የሚጠጋ...ወደ 1.1 ሜትር የሚጠጋ...ወደ 2.2 ሜትር የሚጠጋ" (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

በዙሪያው ጠርዝ የወሰኑ ዙሪያ
"በጠርዙ ዙሪያ ወሰ ዳርቻው የሚደርሰው"

አንድ ስንዝር
አንድ ስንዝር የሚባለው 23 ሴንቲ ሜትር ነበር። ዩዲቢ እንዳደረገው "ክንዶች" በሚለው መለኪያ ምትክ ዘመናዊ መለኪያ ከተጠቀሙ ይህንን መረጃ አለማካተት ይችላሉ። "ወደ 23 ሴንቲ ሜትር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የመሰዊያው መሰረት ይሆናል
"እነዚህ የመሰዊያው መሰረት መለኪያዎች ይሆናሉ"

ተሸካሚ
"ጠባብ እና ጠፍጣፋ የሆነ በግርግዳው ላይ ተሰክቶ ወደ ውጭ ወጣ ያለ

Ezekiel 43:15

ምድጃ
መስዋዕት የሚቃጠልበት ወይም የሚበስልበት ስፍራ

አራት ክንድ... አስራ ሁለት ክንድ...አራት ክንድ... አስራ ሁለት ክንድ...ግማሽ ክንድ...አንድ ክንድ
እያንዳንዱ ረጀም ክንድ ወደ 54 ሴንቲ ሜትር ነው። ዩዲቢ እንዳደረገው "ክንዶች" በሚለው መለኪያ ምትክ ዘመናዊ መለኪያ ከተጠቀሙ ይህንን መረጃ አለማካተት ይችላሉ። ይህ በሕዝቅኤል 40:5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ወደ 2.2 ሜትር የሚጠጋ...ወደ 6.5 ሜትር የሚጠጋ...ወደ 7.6 ሜትር የሚጠጋ... ወደ 27 ሴንቲ ሜትር የሚጠጋ... ወደ 54 ሴንቲ ሜትር የሚጠጋ" (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀንዶች
ቀንዶች በአራቱ የመሰዊያው ማዕዘኖች ከሌላው የመሰዊያው አካል በላይ ተጣብቀው የሚገኙ የመሰዊያው ክፍል ናቸው

ደረጃዎቹ ወደ ምስራቅ የዞሩ ናቸው
"ደረጃዎቹ ከመሰዊያው በስተ ምስራቅ ናቸው" ወይም "የመሰዊያዎቹ ደረጃዎች በእርሱ በስተ ምስራቅ ናቸው"

Ezekiel 43:18

እርሱ እንዲህ አለ
"ያህዌ እንዲህ አለ"

የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ደንቦች
"ህጎች" ወይም "ትዕዛዞች"

አንተ ታደርጋለህ
"አንተ" የሚለው ተውላጠ ስም ነጠላ ቁጥር ነው። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስሞች መልኮች ይመልከቱ)

ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ራሱን በስሙ የሚገልጸው/የሚምለው፤ የተናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳወቅ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ። "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 43:20

ከዚያ አንተ ታደርገዋለህ
"አንተ" የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 43:19 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስሞች መልኮች ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አራት ቀንዶች
አራቱ ቀንዶች በአራቱ የመሰዊያው ማዕዘኖች ከሌላው የመሰዊያው አካል በላይ ተጣብቀው የሚገኙ የመሰዊያው ክፍል ናቸው። ይህ በሕዝቅኤል 43፡15 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ።

Ezekiel 43:22

አንተ ታቀርባለህ... አንተ ትጨርሳለህ... ታቀርባለህ... ታቀርባለህ
ሁሉም "አንተ" የሚሉት ተውላጠ ስሞች እና ሕዝቅኤልን የሚያመለክቱት ትዕዛዞች ነጠላ ቁጥር ናቸው። ይህ በሕዝቅኤል 43፡19 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም እና መልኮች ይመልከቱ)

በያህዌ ፊት አቅርባቸው
በሬዎችን እና አውራ በጎችን መስዋዕት አድርገው የሚያቀርቡበት መሰዊያ የሚገኘው፣ የያህዌ መገኘት በሚኖርበት በቤተ መቅደሱ ፊት ለፊት ነው።

Ezekiel 43:25

አንተ ማዘጋጀት አለብህ
ይህ የሚነገረው ለሕዝቅኤል ነው፣ ስለዚህም "አንተ" የሚለው ነጠላ ቁጥር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 43፡19 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም እና መልኮች ይመልከቱ)

ይህ ስለዚያ ይመጣል
x

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 44

1 ወደ ምሥራቅም ወደሚመለከተው በስተ ውጭ ወዳለው ወደ መቅደሱ በር እንደገና አመጣኝ በሩም በጣም ተዘግቶ ነበር። **2** እግዚአብሔርም፥ "ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም፥ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ማንም አይገባበትም፥ በጥብቅ የተዘጋውም ለዚህ ነው **3** የእስራኤል አለቃ በውስጡ ተቀምጦ በእግዚአብሔር ፊት እንጀራ ይበላል። በበሩ ደጀ ሰላም መንገድ ይገባል በዚያም መንገድ ይወጣል። **4** ቀጥሎም ከቤቱ ፊት ለፊት በሰሜኑ በር በኩል አመጣኝ። እኔም አየሁ፥ እነሆም፥ የእግዚአብሔር ክብር የእግዚአብሔርን ቤት ሞልቶት ነበር፥ እኔም በግምባሬ ተደፋሁ። **5** እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ፥ "የሰው ልጅ ሆይ፥ ስለ እግዚአብሔርም ቤት ሥርዓትና ሕግ ሁሉ የምናገርህን ሁሉ ልብ አድርግ ሁሉ በዓይንህም ተመልከት በጆሮህም ስማ። የቤቱንም መግቢያ የመቅደሱንም መውጫ ሁሉ ልብ በል። **6** ለዓመፀኛው ለእስራኤል ቤት እንዲህ በል፥ "ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦እናንተ የእስራኤል ቤት ሆይ፥ **7** እንጀራዬን፥ ስብንና ደምን፥ በምታቀርቡበት ጊዜ በመቅደሴ ውስጥ ይሆኑ ዘንድ ቤቴንም ያረክሱ ዘንድ በልባቸውና በሥጋቸው ያልተገረዙትን እንግዶችን ሰዎች አግብታችኋልና፥ እነርሱም በርኵሰታችሁ ሁሉ ላይ ይጨመሩ ዘንድ ቃል ኪዳኔን አፍርሰዋልና ርኵሰታችሁ ሁሉ ይብቃችሁ። **8** የተቀደሰውን ሥፍራዬን ኃላፊነት ለሌሎች ሰጣችሁ እንጂ ስለእኔ ያለባችሁን ግዴታ አልተወጣችሁም። **9** ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በእስራኤል ልጆች መካከል ካሉት ሁሉ በልቡና በሥጋው ያልተገረዘ እንግዳ ሁሉ ወደ መቅደሴ አይግባ። **10** ከእኔ ዘንድ የራቁ፥ እስራኤልም በሳቱ ጊዜ ጣዖታቸውን ተከትለው ከእኔ ዘንድ የሳቱ ሌዋውያን ኃጢአታቸውን ይሸከማሉ። **11** እነርሱ የመቅደሴ በሮች ጠባቂዎች በመቅደሴም ውስጥ አገልጋዮች ናቸው። ለሕዝቡም የሚቃጠለውን መሥዋዕትና ሌላ መሥዋዕቱን ያርዳሉ፥ ያገለግሉአቸውም ዘንድ በፊታቸው ይቆማሉ። **12** ነገር ግን በጣዖቶቻቸውም ፊት መስዋዕት በማቅረባቸው ለእስራኤልም ቤት የኃጢአት ዕንቅፋት ሆነዋል። ስለዚህ ኃጢአታቸውን ይሸከማሉ ብዬ እጄን አንስቼ ምያለሁ ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር! **13** ካህናትም ይሆኑኝ ዘንድ ወደ እኔ አይቀርቡም፥ ወደ ተቀደሰውም ነገሬና ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ነገር አይቀርቡም እፍረታቸውንና የሠሩትንም ርኵሰታቸውን ይሸከማሉ። **14** ነገር ግን ለአገልግሎቱ ሁሉና በእርሱ ውስጥ ለሚደረገው ሁሉ የቤቱ ሥርዓት ጠባቂዎች አደርጋቸዋለሁ። **15** ነገር ግን የእስራኤል ልጆች ከእኔ በራቁ ጊዜ የመቅደሴን ሥርዓት የጠበቁ የሳዶቅ ልጆች ሌዋውያን ካህናት ያገለግሉኝ ዘንድ ወደ እኔ ይቀርባሉ ስቡንና ደሙንም ወደ እኔ ያቀርቡ ዘንድ በፊቴ ይቆማሉ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር። **16** ወደ መቅደሴም ይገባሉ ያገለግሉኝም ዘንድ ወደ ገበታዬ ይቀርባሉ ሥርዓቴንም ይጠብቃሉ። **17** ወደ ውስጠኛውም አደባባይ በር በገቡ ጊዜ የተልባ እግር ልብስ ይልበሱ ወደ ውስጠኛውም አደባባይ በርና ወደ ቤቱ ውስጥ የሱፍ ልብስ ለብሰው መግባት የለባቸውም። **18** በራሳቸው ላይ የተልባ እግር መጠምጠሚያ ይሁን፥ በወገባቸውም ላይ የተልባ እግር ሱሪ ይሁን የሚያልብ ልብስ መልበስ የለባቸውም። **19** ወደ ውጭውም አደባባይ ወደ ሕዝብ ሲወጡ ሲያገለግሉ ለብሰውት የነበረውን ልብስ ማውለቅ አለባቸው፤ በተቀደሰ ልብሳቸው ነክተው ሕዝቡንም እንዳይቀድሱ አውልቀው በተቀደሰውም ክፍል ውስጥ ያስቀምጡት። **20** ራሳቸውንም አይላጩ የራሳቸውንም ጠጕር ይከርከሙ እንጂ ጠጕራቸውን አያሳድጉ። **21** ካህናቱም ሁሉ በውስጠኛው አደባባይ ሲገቡ የወይን ጠጅ አይጠጡ። **22** መበለቲቱንና የተፈታችይቱን አያግቡ ነገር ግን ከእስራኤል ቤት ዘር ድንግሊቱን ወይም የካህን ሚስት የነበረችይቱን መበለት ብቻ ያግቡ። **23** በተቀደሰውና ባልተቀደሰው መካከል ያለውን ልዩነት ለሕዝቤ ያስተምራሉ፥ ንጹሁን ንጹሕ ካልሆነው መለየት እንዲችሉ ያደርጓቸዋል። **24** ክርክርም በሚያጋጥም ጊዜ በህጌ መሰረት ይፍረዱ፤ ፍትህዊ መሆን አለባቸው። በበዓላቴ ሁሉ ሕጌንና ሥርዓቴን ይጠብቁ፥ ሰንበታቴንም ይቀድሱ። **25** እንዳይረክሱም የአባት ወይም የእናት ወይም የወንድ ልጅ ወይም የሴት ልጅ ወይም የወንድም ወይም ከወንድ ጋር ያሌቱኛች እኅት ካልሆን በስተቀር ወደ ሰው ሬሳ አይቅረቡ፤ ያለዚያ ይረክሳሉ። **26** ካህን ከርከሰ ህዝቡ ሰባት ቀን ይቈጠርለት። **27** በመቅደስም ውስጥ ያገለግል ዘንድ ወደ ውስጠኛው አደባባይ ወደ መቅደሱ ከመግባቱ በፊት፥ የኃጢአትን መሥዋዕት ለራሱ ያቅርብ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፦ **28** ይህም ርስት ይሆንላቸዋል፡ እኔ ርስታቸው እሆንላቸዋለሁ! ስለዚህ በእስራኤል ዘንድ ግዛት አትሰጡአቸው እኔ ግዛታቸው ነኝ። **29** የእህሉን ቊርባንና የኃጢአትን መሥዋዕት የበደልንም መሥዋዕት ይበላሉ በእስራኤልም ለእግዚአብሔር የተለየው ነገር ሁሉ ለእነርሱ ይሆናል። **30** ከበኵራቱ ሁሉ የተሻለው ከየዓይነቱ ከቊርባናችሁም ሁሉ የማንሣት ቊርባን ሁሉ ለካህናት ይሆናል፥ በቤታችሁም ውስጥ በረከት ያድር ዘንድ የዱቄታችሁን በኵራት ለካህናቱ ትሰጣላችሁ። **31** ካህናቱ የሞተ ወይም በአውሬ የተሰበረ ፥ ወፍ ወይም እንስሳ ቢሆን፥ አይበሉም።

Ezekiel 44:1

ገጹ ወደ ምስራቅ የሆነው የቅድስተ ቅዱሳኑ መግቢያ ውጫዊ በር
"በቤተ መቅደሱ ምስራቅ ወደ ውጨኛው የቅድስተ ቅዱሳኑ በር"

እርሱ አይከፈትም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እርሱን ማንም አይከፍተውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል አምላክ
ይህ በሕዝቅኤል 8፡4 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ።

እርሱ በመተላለፊያው በር መንድ ይገባል፣ ደግሞም በተመሳሳይ መንገድ ይወጣል
ወደ አደባባዩ በሌላ በር ይገባል ከዚያም በምስራቅ መተላለፊያ በር ተቀምጦ ይበላል

መተላለፊያ
በመግቢያው ፊት ለፊት በአምዶች ወይም ለድጋፍ በቆሙ በምሶሶዎች ላይ የሚገኙ ልባሶች። በዚህ ሁኔታ፣ መተላለፊያው ወደ አደባባዩ ይከፈታል፣ የሚገኘውም በቤተ መቅደሱ መግቢያ እና በበሩ ውስጠኛ ክፍል መሃል ነው። ይህ በሕዝቅኤል 8፡16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

በያህዌ ፊት
"በያህዌ ፊት ለፊት" ወይም "ያህዌ በሚገኝበት"

Ezekiel 44:4

ከዚያም እርሱ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ከዚያ ሰውየው" ወይም 2) "ከዚያ ያህዌ።"

እነሆ
እዚህ ስፍራ "እነሆ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሕዝቅኤል በተመለከተው ተደንቆ እንደነበረ ነው።

የያህዌ ክብር
ይህ በሕዝቅኤል 1፡28 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

በፊቴ ተደፋሁ
"ወደ መሬት ተደፋሁ" ወይም "በምድር ላይ ወደቅሁ።" ሕዝቅኤል የወደቀው በአደጋ አይደለም። ወደ መሬት የወደቀው ያህዌን መፍራቱን እና ማክበሩን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለማሳየት ነው። ይህ በሕዝቅኤል 1:28 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ልብህን አረጋጋ
"ሃሳብህን ሰብስብ" ወይም "ረጋ ብለህ አስተውል። ይህንን "በሕዝቅኤል 40፡4 ላይ "ልብ ብለህ አስተውል" የሚለው እንደ ተተረጎመ ይተርጉሙት። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ህግጋቱ ሁሉ
"ስለ ያህዌ ቤት ትዕዛዛቱ ሁሉ"

Ezekiel 44:6

የእስራኤል ቤት
"ቤት" የሚለው በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች በዚህ ሁኔታ ለብዙ ዘመናት የያዕቆብ ትውልድ ለሆኑ እስራኤላውያን ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እስራኤላውያን" ወይም "የእስራኤል ወገን ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አስጸያፊ ስራዎቻችሁ ሁሉ ይብቋችሁ
"አስጸያፊ ድርጊቶቻችሁ ከሚገባው በላይ ሆኗል" ወይም "ከመጠን ያለፈ አስጸያፊ ስራ ሰርታችኋል"

አስጸያፊ ድርጊቶች
ይህ በሕዝቅኤል 5:9 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

Ezekiel 44:8

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለእስራኤል ቤት ያለውን መልዕክት ለሕዝቅኤል መስጠቱን ቀጥሏል።

Ezekiel 44:10

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለእስራኤል ቤት ያለውን መልዕክት ለሕዝቅኤል መስጠቱን ቀጥሏል።

ከእኔ ርቀው ሄደዋል...ከእኔ ኮብልለው ወደ ጣኦቶቻቸው ሄደዋል
"አንድ ሰው የሚኖርበት መንገድ የተገለጸው በመንገድ ላይ እንደመራመድ ተደርጎ ነው። "እኔን ማምለክ አቁመዋል... እኔ እንዲያደርጉ የምፈልገውን ማድረግ አቁመዋል። ይልቁንም፣ ጣኦቶቻቸውን ያመልካሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አገልጋዮች በተቀደሰው ስፍራዬ ናቸው
"አገልጋዮች በቤተ መቅደሴ ይሆንሉ"

የቤቱን በሮች መጠበቅ
"በቤቱ በር የጥበቃ ግዴታ ማከናወን"

በህዝቡ ፊት ቆመው ያገለግላሉ
"እነዚህ ሌዋውያን ህዝቡን ያገለግሉ ዘንድ በህዝቡ ፊት ይቆማሉ"

ለእስራኤል ቤት ኃጢአት የማሰናከያ ድንጋይ ይሆናሉ
በዚህ ሁኔታ ለዘመናት የያቆብ ትውልድ ለሆኑት እስራኤላውያን፣"ቤት" የሚለው ቃል፣ በቤቱ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ / ነው።ይህ በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እስራኤላውያኑ" ወይም "የእስራኤል ወገን ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ቤት
"ቤት" የሚለው በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች በዚህ ሁኔታ ለብዙ ዘመናት የያዕቆብ ትውልድ ለሆኑ እስራኤላውያን ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እስራኤላውያን" ወይም "የእስራኤል ወገን ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

መሃላ ለመማል እጄን አነሳለሁ
በእነዚያ ዘመናት አንድ ሰው ለማድረግ የማለውን ባይፈጽም እግዚአብሔር እንደሚቀጣው የተረዳ መሆኑን ለማሳየት ቀኝ እጁን ወደላይ ያነሳል።ይህ በሕዝቅኤል 20:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እጄን አንስቼ እምላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

በእነርሱ ላይ
"እኔ እቀጣቸዋለሁ"

ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ራሱን በስሙ የሚገልጸው/የሚምለው፤ የተናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳወቅ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ። "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ቅጣታቸውን ይቀበላሉ
"ቅጣት" የሚለው ረቂቅ ስም በግስ መልክ ሊተረጎም ይችላል። "እኔ በእርግጥ እቀጣቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 44:13

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለእስራኤል ቤት ያለውን መልዕክት ለሕዝቅኤል መስጠቱን ቀጥሏል።

እነርሱ
ሌዋውያን (ሕዝቅኤል 44:10)

እነርሱ አይቀርቡም
"እኔ እንዲቀርቡ አልፈቅድም።" ያህዌ የሳዶቅ ትውልድ እንደሚያደርጉትና አንድ አገልጋይ ትዕዛዝ ለመቀበል ወደ ንጉሡ በሚቀርብበት መንገድ፣ እነርሱ ወደ እርሱ እንዲመጡ አይፈልግም (ሕዝቅኤል 40:46)

የምግባረ ብልሹነት እና በደለኝነታቸውን ውጤት ይቀበላሉ
"በምቀጣቸው ጊዜ ያፍራሉ ደግሞም መከራ ይቀበላሉ"

አሳፋሪ ድርጊቶች
"ያደረጋችሁት አሳፋሪ ነገሮች።" ህዝቡ ጣኦታትን እና ሀሰተኛ አማልእክትን ስላመለኩ እግዚአብሔር ተቆጥቶ ነበር። ይህ በሕዝቅኤል 5:9 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ።

ጠባቂዎች
ዘብ የሚጠብቁ ወይም ስለ አንድ ነገር ጥንቃቄ የሚያደርጉ ሰዎች

በዚህ ውስጥ የተደረገው ያ ነው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "በዚህ ውስጥ ሊያደርጉ የፈለጉት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ezekiel 44:15

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለእስራኤል ቤት ያለውን መልዕክት ለሕዝቅኤል መስጠቱን ቀጥሏል።

ይህን የሚያሟሉ እነዚያ የሳዶቅ ወንድ ልጆች
"የሳዶቅ ትውልድ የሆኑ እና የሚያሟሉ"

ከእኔ ርቀው ኮብልለው ነበር
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "እኔን መስማት እና መታዘዝ አቁመዋል" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 44:17

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለእስራኤል ቤት ያለውን መልዕክት በክህነት ስለሚያገለግሉት ስለ ሳዶቅ ትውልድ ለሕዝቅኤል መናገሩን ቀጥሏል።

ስለዚህ ይህ ይሆናል
"ስለዚህ"

ውስጠኛው አደባባይ
ይህ በሕዝቅኤል 8፡16 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ።

ሊኖ/በፍታ
ይህ በሕዝቅኤል 9፡2 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ።

ሱፍ
ከበግ ለስላሳ ፀጉር የሚሰራ ልብስ

ጥምጥም
ጥምጥም ከረጅም ጨርቅ የሚሰራ በራስ ላይ የሚጠቀለል የጭንቅላት መሸፈኛ ነው

Ezekiel 44:19

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለእስራኤል ቤት ያለውን መልዕክት በክህነት ስለሚያገለግሉት ስለ ሳዶቅ ትውልድ ግዴታቸውን እንዲወጡ ለሕዝቅኤል መናገሩን ቀጥሏል።

ውጫዊ አደባባይ
ይህ በሕዝቅኤል 10፡5 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ።

Ezekiel 44:20

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለእስራኤል ቤት ያለውን መልዕክት በክህነት ስለሚያገለግሉት ስለ ሳዶቅ ትውልድ ለሕዝቅኤል መናገሩን ቀጥሏል።

የራሳቸውን ፀጉር መከርከም/መስተካከል አለባቸው
"ፀጉራቸውን በንጽህና መያዝ አለባቸው"

ባሏ የሞተባት
ባሏ የሞተባት ሴት

ከእስራኤል ቤት ትውልድ
"የእስራኤል ህዝብ ትውልድ"

የእስራኤል ቤት
"ቤት" የሚለው በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች በዚህ ሁኔታ ለብዙ ዘመናት የያዕቆብ ትውልድ ለሆኑ እስራኤላውያን ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እስራኤላውያን" ወይም "የእስራኤል ወገን ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 44:23

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለእስራኤል ቤት ያለውን መልዕክት በክህነት ስለሚያገለግሉት ስለ ሳዶቅ ትውልድ ለሕዝቅኤል መናገሩን ቀጥሏል።

በክርክር ወቅት በእኔ ትዕዛዛት መሰረት ይፍረዱ
"ሰዎች በሚከራከሩበት ጊዜ፣ ካህናቱ የእኔን ህግ በመጥቀስ ማን ትክክል እንደሆነ ውሳኔ ይስጡ"

Ezekiel 44:25

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለእስራኤል ቤት ያለውን መልዕክት በክህነት ስለሚያገለግሉት ስለ ሳዶቅ ትውልድ ለሕዝቅኤል መናገሩን ቀጥሏል።

ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
x

Ezekiel 44:28

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለእስራኤል ቤት ያለውን መልዕክት በክህነት ስለሚያገለግሉት ስለ ሳዶቅ ትውልድ ለሕዝቅኤል መናገሩን ቀጥሏል።

እናንተ
"እናንተ" የሚለው ቃል የእስራኤልን ሰዎች ያመለክታል፣ ስለዚህም ብዙ ቁጥር ነው። (ተውላጠ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ንብረት
አንድ ሰው በባለቤትነት የሚኖረው መሬት እና ለቤተሰቡ ፍላጎት አቅርቦት የሚጠቀምበት

በእስራኤል
"በእስራኤል ምድር"

Ezekiel 44:30

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለእስራኤል ቤት ያለውን መልዕክት በክህነት ስለሚያገለግሉት ስለ ሳዶቅ ትውልድ ለሕዝቅኤል መናገሩን ቀጥሏል።

እያንዳንዱ አስተዋጽኦ፣ ማናቸውም ከእናንተ አስተዋጽኦ ሁሉ የሚገኝ
"ከስጦታዎቻችሁ ሁሉ የትኛውም የስጦታ አይነት" ወይም "ከስጦታዎቻችሁ ሁሉ የትኛውም የስጦታ አይነት"

ስለዚህ በቤታችሁ በረከት ይሁን
የዚህ ሀረግ ትርጉም "ስለዚህም ቤተሰባችሁን እና የእናንተ የሆነውን ነገር ሁሉ እባርካለሁ።" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ወይም በአውሬ የተቦጨቀ እንስሳ፣ ወፍም ይሁን አውሬ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ወይም ማናቸውም ወፍ/አሞራ ወይም የዱር እንስሳ የቦጨቀው ፍጥረት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 45

1 ርስትም አድርጋችሁ ምድሪቱን በዕጣ በምታካፍሉበት ጊዜ ለእግዚአብሔር መባ ታቀርባላችሁ። ይህም መባ የምድሪቱ የተቀደሰ ሥፍራ ሲሆን ርዝመቱ ሀያ አምስት ሺህ ክንድ ወርዱም ሀያ ሺህ ክንድ ይሆናል በዳርቻው ሁሉ ዙሪያውን የተቀደሰ ይሆናል። **2** ከእርሱም ርዝመቱ አምስት መቶ ወርዱም አምስት መቶ ክንድ አራት ማዕዘን የሆነ ቦታ ለመቅደሱ ይሆናል በዙሪያውም ባዶ ስፍራ የሚሆን አምሳ ክንድ ይሆናል። **3** ከዚያ ቦታ ርዝመቱ ሀያ አምስት ሺህ ክንድ ወርዱም አሥር ሺህ ክንድ የሆነ ስፍራ ትለካለህ፤ እርሱም ቅዱስ ስፍራና ቅድስተ ቅዱሳን ይሆንልሀል። **4** ከምድሪቱም እግዚአብሔርን ለሚያገለግሉና ሊያገለግሉትም ወደ እግዚአብሔር ለሚቀርቡት ለካህናት የተለየ ክፍል ይሆናል። ለቤቶቻቸውም የሚሆን ስፍራ ለመቅደስም የሚሆን የተቀደሰ ስፍራ ይሆናል። **5** ርዝመቱም ሀያ አምስት ሺህ ወርዱም አሥር ሺህ የሆነ ስፍራ ለቤቱ አገልጋዮች ለሌዋውያን ይሆናል፥ ለሚቀመጡባቸውም ከተሞች ለራሳቸውም የርስት ይዞታ ይሆናል። **6** ለከተማ የሚሆን ሥፍራም ከተቀደሰው የዕጣ ክፍል አጠገብ ወርዱ አምስት ሺህ ርዝመቱም ሀያ አምስት ሺህ የሆነውን ስፍራ ትለያላችሁ። ይህም ከተማ ለእስራኤል ቤት ሁሉ ይሆናል። **7** ለአለቃ ይዞታ የሆነው የዕጣ ክፍል በተቀደሰው መባና በከተማይቱ ይዞታ አጠገብ በዚህና በዚያ ይሆናል። በምዕራብና በምሥራቅ ይሆናል። ርዝመቱም እንደ አንድ ነገድ ዕጣ ክፍል ሆኖ ከምድሩ ከምዕራቡ ዳርቻ ጀምሮ እስከ ምሥራቁ ዳርቻ ድረስ ይሆናል። **8** ይህም ለእስራኤል አለቃ ይዞታ ይሆንለታል። አለቆቼም ለእስራኤል ቤት ምድሪቱን እንደ ነገዳቸው መጠን ይሰጡአቸዋል እንጂ ሕዝቤን ከእንግዲህ ወዲህ አያስጨንቋቸውም። **9** ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ የእስራኤል አለቆች ሆይ፥ ይብቃችሁ ግፍንና ብዝበዛን አስወግዱ፥ ፍርድንና ጽድቅንም አድርጉ! ሕዝቤን መቀማት አቁሙ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር! **10** እውነተኛ ሚዛን እውነተኛም የኢፍ መስፈሪያ እውነተኛውም የባዶስ መስፈሪያ ይሁንላችሁ። **11** የኢፍና የባዶስ መስፈሪያ መጠናቸው እኩል ሆኖ የባዶስ መስፈሪያ የቆሮስ መስፈሪያ አንድ አሥረኛ ይሆናል ፥ መስፈሪያው እንደ ቆሮስ መስፈሪያ ይሁን። **12** ሰቅሉም ሀያ አቦሊ ይሁን ሀያ ሰቅል፥ ሀያ አምስት ሰቅል፥ አሥራ አምስት ሰቅል፥ ምናን ይሁንላችሁ። **13** የምታቀርቡት መባ ይህ ነው ከአንድ ቆሮስ መስፈሪያ ስንዴ የኢፍ መስፈሪያ አንድ ስድስተኛ፥ ከአንድም ቆሮስ መስፈሪያ ገብስ የኢፍ መስፈሪያ አንድ ስድስተኛ ትሰጣላችሁ። **14** የዘይቱም ደንብ፥ ከእያንዳንዱ የቆሮስ መስፈሪያ የባዶስን አንድ አሥረኛ ወይም ለእያንዳንዱ ቆሮስ ምክንያቱም አሥር የባዶስ መስፈሪያ አንድ የቆሮስ መስፈሪያ ነው። **15** ውኃም ካለበት ከእስራኤል አውራጃ ከመንጋው ከሁለቱ መቶ አንዱን የበግ ጠቦት ትሰጣላችሁ ይህ ያስተሰርይላችሁ ዘንድ ለእህል ቊርባንና ለሚቃጠል መሥዋዕት ለደኅንነትም መሥዋዕት ይሆናል፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፦ **16** የአገሩም ሕዝብ ሁሉ ይህን መባ ለእስራኤል አለቃ ይሰጣሉ። **17** በየበዓላቱም በየመባቻውም በየሰንበታቱም በእስራኤልም ቤት ዓመት በዓል ሁሉ የሚቃጠለውን መሥዋዕትና የእህሉን ቊርባን የመጠጡንም ቊርባን በየመደቡ ማዘጋጀት የአለቃው ይሆናል። እርሱ የእስራኤል ቤት ወክሎ የኃጢአቱን መሥዋዕትና የእህሉን ቊርባን የሚቃጠለውን መሥዋዕትና የደኅንነቱን መሥዋዕት ያቀርባል። **18** ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በመጀመሪያው ወር ከወሩም በመጀመሪያው ቀን ነውር የሌለበትን ወይፈን ውሰድ ስለ መቅደሱም የኃጢአት መስዋዕት ታቀርባላችሁ። **19** ካህኑም ከኃጢአቱ መሥዋዕት ደም ወስዶ በመቅደሱ መቃኖችና በመሠዊያው እርከን በአራቱ ማዕዘን በውስጠኛውም አደባባይ በበሩ መቃኖች ላይ ይርጨው. **20** ይህንንም ከወሩ በሰባተኛው ቀን ስለ ሳተውና ስላላወቀው ታደርጋለህ። በዚህ መንገድ ለቤተ መቅድሱ ታስተስርያላችሁ። **21** በመጀመሪያ ወር ከወሩም በአሥራ አራተኛው ቀን የፋሲካን በዓል ታደርጋላችሁ። የሰባት ቀንም በዓል ይሆናል። የቂጣ እንጀራም ትበላላችሁ። **22** በዚያም ቀን አለቃው ለራሱና ለአገሩ ሕዝብ ሁሉ የኃጢአት መሥዋዕት የሚሆነውን ወይፈን ያቀርባል። **23** በበዓሉም በሰባቱ ቀኖች የሚቃጠለውን መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ያቅርብ፡ ሰባቱንም ቀኖች በየዕለቱ ነውር የሌለባቸውን ሰባት ወይፈንና ሰባት አውራ በጎች ያቅርብ ለኃጢአትም መሥዋዕት በየዕለቱ አንድ አውራ ፍየል ያቅርብ። **24** ለአንድም ወይፈን አንድ የኢፍ መስፈሪያ ለአንድም አውራ በግ አንድ የኢፍ መስፈሪያ ለአንድም የኢፍ መስፈሪያ አንድ የኢን መስፈሪያ ዘይት ለእህል ቊርባን ያቅርብ። **25** አለቃው በሰባተኛውም ወር ከወሩም በአሥራ አምስተኛው ቀን በበዓሉ ሰባት ቀኖች፥ የኃጢአቱን መሥዋዕት የሚቃጠለውንም መሥዋዕት የእህሉንም ቊርባን ከዘይቱ ጋር እንዲሁ ያቅርብ።

Ezekiel 45:1

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል፣ ለእስራኤል ቤት ያለውን መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

ሃያ አምስት ሺህ ክንድ ቁመት... አስር ሺህ ክንድ ስፋት...አምስት መቶ ክንድ... ሀምሳ ክንድ ስፋት
እያንዳንዱ ረጀም ክንድ ወደ 54 ሴንቲ ሜትር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 40፡5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "25000 ክንድ ቁመት... 10000 ክንድ ስፋት...500 ክንድ... 50 ክንድ ስፋት" ወይም "ወደ 13.5 ኪሎ ሜትር የሚጠጋ ርዝመት...ወደ 5.4 ኪሎ ሜትር የሚጠጋ ስፋት...ወደ 270 ሜትር የሚጠጋ... ወደ 27 ሜትር የሚጠጋ ስፋት"... ወደ 54 ሴንቲ (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

የዚህ ስፍራ ሁሉ አካባቢ
"በተወሰነው አካባቢ ውስጥ የሚገኘው ስፍራ ሁሉ"

Ezekiel 45:3

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል፣ ለእስራኤል ቤት ያለውን መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

ይህ አካባቢ
ቤተ መቅደሱ እና በዙሪያው የሚገኘው ስፍራ

ክፍል
"የመሬቱ ክፍል"

ሃያ አምስት ሺህ ክንድ... አስር ሺህ
እያንዳንዱ ረጀም ክንድ ወደ 54 ሴንቲ ሜትር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 40፡5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "25000 ክንድ ... 10000 ክንድ" ወይም "ወደ 13.5 ኪሎ ሜትር ...ወደ 5.4 ኪሎ ሜትር" (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 45:6

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል፣ ለእስራኤል ቤት ያለውን መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አምስት ሺህ ክንድ... ሃያ አምስት ሺህ
እያንዳንዱ ረጀም ክንድ ወደ 54 ሴንቲ ሜትር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 40፡5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "5000 ክንድ ... 25000 ክንድ" ወይም "ወደ 2.7 ኪሎ ሜትር ...ወደ 13.5 ኪሎ ሜትር" (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

ለቅዱስ ስፍራ የተጠበቀ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "አንተ ለቅዱስ ስፍራ የሰጠኸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ቁመቱ ከእነዚያ ክፍሎች/ድርሻ ቁመት ጋር ይመጣጠናል
ሕዝቅኤል የልዑላኑን መሬት ለእያንዳንዱ ነገድ ከተሰጠው መሬት መጠን ጋር እንደሚያነጻጽር በውስጠ ታዋቂነት ተጠቁሟል። "ቁመቱ ለነገዶቹ ከተሰጠው ድርሻ ቁመት ጋር ተመሳሳይ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከምዕራብ እስከ ምስራቅ
እነዚህ የእስራኤል ምዕራባዊ እና ምስራቃዊ ድንበሮች መሆናቸው በውስጠ ታዋቂነት ተጠቁሟል። "በባህሩ ከሚገኘው ከእስራኤል ምዕራባዊ ዳርቻ በዮርዳኖስ ወንዝ እስከሚገኘው ምስራቃዊ ዳርቻ"

Ezekiel 45:8

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል፣ ለእስራኤል ቤት ያለውን መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

ይህ ምድር ለእስራኤል ልዑላን/ገዢዎች ንብረት ይሆናል
"ይህ የምድሪቱ ክፍል በእስራኤል ህዝብ መሃል ለሚገኙ ልዑላን ንብረት ይሆናል"

Ezekiel 45:9

ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ራሱን በስሙ የሚገልጸው/የሚምለው፤ የተናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳወቅ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ። "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ይበቃችኋል
"በጣም ብዙ መጥፎ ነገሮችን አድርጋችኋል" ወይም "በጣም ለረጅም ጊዜ ክፉ ድርጊቶችን ስታደርጉ ኖራችኋል"

መለኪያዎች
ሰዎች የሚሸጧቸውን ወይም የሚገዟቸውን ነገሮች ለመመዘን ይጠቀሙባቸው የነበሩ መሳሪያዎች

ስለዚህ ባዶስ የሆመር አንድ አስረኛ ነው
"ስለዚህ አስር ባዶስ ከአንድ ሆመር ጋር እኩል ነው"

ሆመር
ወደ 220 ሊትር የሚጠጋ (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የመጠን መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰቅል
ወደ 11 ግራም የሚጠጋ (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የክብደት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

ጌራህ
ወደ 0.55 ግራም የሚጠጋ(መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የክብደት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

ምናን
ወደ 660 ግራም የሚጠጋ (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የክብደት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 45:13

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለእስራኤል ገዢዎች/ልዑሎች መልዕክቱን መስጠቱን ቀጥሏል።

ከእያንዳንዱ ሆመር ስንዴ
ሰዎች የሚሰበስቡት ስንዴ አዝመራ መጠን ይህ መሆኑ ተጠቁሟል። "ከመከሩ ከእያንዳንዱ ሆመር ስንዴ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የዘይት መስዋዕት የሚቀርብበት ህግ የባዶስ አንድ አስረኛ ይሆናል
"የባዶስ አንድ አስረኛ ዘይት ማቅረብ ይኖርባችኋል"

የእስራኤል ውሃማ አካባቢ
"በቂ ውሃ የሚያገኘው የእስራኤል አካባቢ"

ለዚህ ይውላል
x

Ezekiel 45:16

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለእስራኤል ገዢዎች/ልዑሎች መልዕክቱን መስጠቱን ቀጥሏል።

የተወሰኑት በዓላት
በየአመቱ ወይም በየወሩ ወይም በየሳምንቱ በተመሳሳይ ጊዜ የሚከበር በዓል

የእስራኤል ቤት
"ቤት" የሚለው በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች በዚህ ሁኔታ ለብዙ ዘመናት የያዕቆብ ትውልድ ለሆኑ እስራኤላውያን ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እስራኤላውያን" ወይም "የእስራኤል ወገን ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 45:18

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለእስራኤል ገዢዎች/ልዑሎች መልዕክቱን መስጠቱን ቀጥሏል።

ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
ያህዌ ስለ ራሱ በስም የሚናገረው ለሕዝቅኤል እና ለህዝቡ እርሱ የሚናገረው ነገር አስፈላጊ መሆኑን ለማስታወስ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 6:11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እኔ፣ ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

በመጀመሪያው ወር፣ በወሩ በመጀመሪያ ቀን
ይህ በዕብራውያን አቆጣጠር የመጀመሪያው ወር ነው። የመጀመሪያው ቀን በምዕራባውያን አቆጣጠር መጋቢት መጨረሻ ላይ ነው። (የዕብራውያን ወሮች እና ተከታታይ ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

አንተ ትወስዳለህ
"አንተ" የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር ነው፣ የሚያመለክተው በእስራኤል ገዢ/ልዑል የሆነውን ማናቸውንም ገዢ ነው። (አንተ የሚለው ተውላጠ ስም መልኮች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በወሩ ሰባተኛ ቀን
"በመጀመሪያው ወር በሰባተኛው ቀን" (ተከታታይ ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በድንገት ወይም ባለማወቅ ለሚፈጸም ለእያንዳንዱ ሰው በደል
"ሳያውቅ ኃጢአት ለሚፈጽም ወይም ኃጢአት እየፈጸመ እንደሆነ ሳያውቅ ለሚበደል ማናቸውም ሰው" ወይም "በድንገት ወይም ትክክለኛውን ባለማወቅ ኃጢአት ለሚሰራ ለእያንዳንዱ ሰው"

Ezekiel 45:21

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለእስራኤል ገዢዎች/ልዑሎች መልዕክቱን መስጠቱን ቀጥሏል።

በመጀመሪያው ወር፣ በወሩ አስራ አራተኛ ቀን
ይህ በዕብራውያን አቆጣጠር የመጀመሪያው ወር ነው። አስራ አራተኛው ቀን በሚያዚያ መጀመሪያ ላይ ነው። (የዕብራውያን ወሮች እና ተከታታይ ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

ለእናንተ
"እናንተ" የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ነው፤ የሚያመለክተውም ገዢዎችን እና የእስራኤል ቤት ሰዎችን ነው። (አንተ የሚለው ተውላጠ ስም መልኮች የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 45:23

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለእስራኤል ገዢዎች/ልዑሎች መልዕክቱን መስጠቱን ቀጥሏል።

የመብል መስዋዕት
"የእህል መስዋዕት" ተብሎም ይጠራል።

ሰባት ወይፈኖች እና ነውር የሌለባቸው ሰባት አውራ በጎች
"ሰባት ወይፈኖች እና ሙሉ ለሙሉ ጤናማ የሆኑ ሰባት አውራ በጎች"

ኣፍ
ይህን ወደ ዘመናዊ የክብደት መለኪያ መለወጥ ይቻላል። አንድ ኣፍ "ሃያ ሁለት ሊትር" ነው። (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የመጠን መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

ኢን
ይህን ወደ ዘመናዊ የክብደት መለኪያ መለወጥ ይቻላል። አንድ ኢን "አራት ሊትር" ነው። (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የመጠን መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

እያንዳንዱ ኣፍ
ይህን ወደ ዘመናዊ የክብደት መለኪያ መለወጥ ይቻላል። እያንዳንዱ ኣፍ "ሃያ ሁለት ሊትር" ነው። (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የመጠን መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 45:25

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለእስራኤል ገዢዎች/ልዑሎች መልዕክቱን መስጠቱን ቀጥሏል።

በሰባተኛው ወር በወሩ አስራ አምስተኛ ቀን
ይህ በዕብራውያን አቆጣጠር ሰባተኛው ወር ነው። አስራ አምስተኛው ቀን በጥቅምት መጀመሪያ ላይ ነው። (የዕብራውያን ወሮች እና ተከታታይ ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

በበዓሉ ላይ
ይህ ሕዝቅኤል አስቀድሞ ከገለጸው በዓል የተለየ በዓል ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 46

1 ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በውስጠኛው አደባባይ ወደ ምሥራቅ የሚመለከተው በር ሥራ በሚሠራበት በስድስቱ ቀን ተዘግቶ ይቈይ ነገር ግን
በሰንበት ቀንና በመባቻ ቀን ይከፈት። 2 አለቃውም በስተ ውጭ ባለው በር በደጀ ሰላሙ መንገድ ገብቶ ካህናቱም የእርሱን የሚቃጠለውን መሥዋዕትና
የደኅንነቱን መሥዋዕት እስኪያቀርርቡ ድረስ በበሩ መቃን አጠገብ ይቁም። ከዚያም በበሩ መድረክ ላይ ሰግዶ ይውጣ ፥ በሩ ግን እስከ ማታ ድረስ አይዘጋ። 3
የአገሩም ሕዝብ በዚያ በር መግቢያ በእግዚአብሔር ፊት በሰንበታትና በመባቻ ይስገዱ። 4 አለቃውም በሰንበት ቀን ለእግዚአብሔር የሚያቀርበው የሚቃጠል
መሥዋዕት ነውር የሌለባቸው ስድስት የበግ ጠቦቶች ነውርም የሌለበት አንድ አውራ በግ ይሁን 5 የእህሉም ቊርባን ለአውራ በጉ አንድ የኢፍ መስፈሪያ ይሁን፥
ለጠቦቶቹም የእህል ቊርባን የሚቻለውን ያህል ይሁን፥ ለአንዱም የኢፍ መስፈሪያ አንድ የኢን መስፈሪያ ዘይት ያቅርብ። 6 በመባቻም ቀን ከመንጋው መካከል
ነውር የሌለበትን አንድ ወይፈን፥ ነውር የሌለባቸውንም ስድስት ጠቦቶችና አንድ አውራ በግ ያቅርብ 7 ለወይፈኑም አንድ የኢፍ መስፈሪያ ለአውራውም በግ አንድ
የኢፍ መስፈሪያ ለጠቦቶቹም እንደ ተቻለው ያህል፥ የእህል ቊርባን እንዲሁም ለአንዱም የኢፍ መስፈሪያ የእህል ቊርባን አንድ የኢን መስፈሪያ ዘይት ያቅርብ። 8
አለቃውም በሚገባበት ጊዜ በበሩ ደጀ ሰላም መንገድ ይግባ በዚያውም ይውጣ። 9 የአገሩ ሕዝብ ግን በየክብረ በዓሉ ቀን ወደ እግዚአብሔር ፊት በመጡ ጊዜ
በሰሜን በር በኩል ሊሰግድ የሚገባው በደቡብ በር በኩል ይውጣ፥ በደቡብም በር የሚገባው በሰሜን በር በኩል ይውጣ። በፊት ለፊት ይውጣ እንጂ በገባበቱ
በር አይመለስ። 10 በሚገቡበት ጊዜ አለቃው በመካከላቸው ይግባ በሚወጡበትም ጊዜ ይውጣ። 11 በበዓላትም የእህሉ ቊርባን ለወይፈኑ አንድ የኢፍ
መስፈሪያ፥ ለአውራ በጉ አንድ የኢፍ መስፈሪያ፥ ለጠቦቶቹም እንደሚቻለው ያህል፥ ለኢፍ መስፈሪያም አንድ የኢን መስፈሪያ ዘይት ይሆናል። 12 አለቃውም
በፈቃዱ የሚያቀርበውን መሥዋዕት፥ የሚቃጠለውን መሥዋዕት፥ ወይም በፈቃዱ ለእግዚአብሔር የሚያቀርበውን የደኅንነቱን መሥዋዕት፥ ባቀረበ ጊዜ፥
የምሥራቁን በር ይክፈት፥ በሰንበትም ቀን እንደሚያደርግ የሚቃጠለውን መሥዋዕትና የደኅንነቱን መሥዋዕት ያቅርብ ከዚያም በኋላ ይውጣ፥ ከወጣም በኋላ
በሩን ይዝጋ። 13 በየዕለቱም ለሚቃጠል መሥዋዕት ነውር የሌለበትን የአንድ ዓመት በግ ጠቦት ለእግዚአብሔር ታቀርባላችሁ፤ ይህንንም በየማለዳው
ታደርጋለችሁ። 14 ከእርሱም ጋር እንደ ቋሚ ሥርዓት የእህልን ቊርባን፥ በኢን መስፈሪያ ሢሶ ዘይት የተለወሰ የኢፍ መስፈሪያ ስድስተኛ እጅ መልካም ዱቄትን፥
በየማለዳው ታቀርባላችሁ። 15 እንዲሁ ዘወትር ለሚቃጠለው መሥዋዕት ጠቦቱንና የእህሉን ቊርባን ዘይቱንም በየማለዳው ያቅርብ። 16 ጌታ እግዚአብሔር
እንዲህ ይላል፦ አለቃው ከልጆቹ ለአንዱ ከርስቱ ስጦታ ቢሰጥ የልጁ ውርስ ይሆናል። የልጆቹ ንብረት ውርስ ይሆንላቸዋል። 17 ነገር ግን ከባሪያዎቹ ለአንዱ
ከርስቱ ስጦታ ቢሰጥ እስከ ነጻነት ዓመት ድረሰ ለእርሱ ይሁን፥ ከዚያም በኋላ ለአለቃው ይመለስ። ርስቱ ግን ለልጆቹ ይሁን። 18 አለቃውም ሕዝቡን
ከይዞታቸው ያወጣቸው ዘንድ ከርስታቸው በግድ አይውሰድ ሕዝቤ ሁሉ ከይዞታቸው እንዳይነቀሉ ከገዛ ይዞታው ለልጆች ርስትን ይስጥ። 19 ከዚያም ሰውዬው
ወደ ሰሜን ወደሚመለከተው ለካህናት ወደሚሆን ወደ ተቀደሱ ክፍሎች እነሆም፥ በስትምዕራብ በኩል አንድ ስፍራ ነበረ። 20 እርሱም፥ "ካህናቱ ሕዝቡን
ለመቀደስ ወደ ውጭው አደባባይ እንዳያወጡ የበደሉን መሥዋዕትና የኃጢአቱን መሥዋዕት የሚቀቅሉበት፥ የእህሉንም ቊርባን የሚጋግሩበት ስፍራ ይህ ነው
አለኝ። 21 በውጭው አደባባይ አወጣኝ በአደባባይም ወዳለው በአራቱ ማዕዘን በኩል አሳለፈኝ እነሆም፥ በእያንዳንዱ የአደባባዩ ማዕዘን ሌላ አደባባይ እንዳለ
አየሁ። 22 በአደባባዩ በአራቱ ማዕዘን ርዝመቱ አርባ ክንድ ወርዱም ሠላሳ ክንድ የሆነ አደባባይ ነበረ። በማዕዘኑ ላሉ ለእነዚህ ለአራቱ ስፍራዎች አንድ ልኬቱ
እኩል ነበረ። 23 በአራቱም ዙሪያ ሁሉ ግንብ ነበረ፥ በግንቡም ሥር በዙሪያው የመቀቀያ ቦታ ነበረ። 24 ሰውዬውም፥ "እነዚህ የቤቱ አገልጋዮች የሕዝቡን
መሥዋዕት የሚቀቅሉባቸው ስፍራዎች ናቸው አለኝ።

Ezekiel 46:1

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለእስራኤል ገዢዎች/ልዑሎች መልዕክቱን መስጠቱን ቀጥሏል።

ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
ያህዌ ስለ ራሱ በስም የሚናገረው ለሕዝቅኤል እና ለህዝቡ እርሱ የሚናገረው ነገር አስፈላጊ መሆኑን ለማስታወስ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 6፡11 ላይ አንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እኔ፣ ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ፊቱ/ገጹ ወደ ምስራቅ የሆነው የውስጠኛው አደባባይ በር
"በምስራቅ በኩል የሚገኘው የውስጠኛው አደባባይ በር" ወይም "የውስጠኛው አደባባይ የምስራቅ በር"

ውስጠኛ አደባባይ
ይህ በሕዝቅኤል 8፡16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ውስጠኛው በር
ይህ በሕዝቅኤል 8፡19 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

Ezekiel 46:3

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለእስራኤል ገዢዎች/ልዑሎች መልዕክቱን መስጠቱን ቀጥሏል።

በያህዌ ፊት
ይህ በሕዝቅኤል 43፡24 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

Ezekiel 46:6

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለእስራኤል ገዢዎች/ልዑሎች መልዕክቱን መስጠቱን ቀጥሏል።

ነውር የሌለበት
ፍጹም ጤናማ እና ትክክለኛ

መተላለፊያ
በመግቢያው ፊት ለፊት በአምዶች ወይም ለድጋፍ በቆሙ በምሶሶዎች ላይ የሚገኙ ልባሶች። ይህ በሕዝቅኤል 8፡16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ezekiel 46:9

በያህዌ ፊት
"በያህዌ ፊት ለፊት" ወይም "ያህዌ በሚገኝበት።" ይህ በሕዝቅኤል 44:3 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

በተወሰኑት በዓላት
"በተወሰኑ በዓላት" የሚለውን ሕዝቅኤል 36:37 ላይ በተተረጎመው መሰረት ይተርጉሙት።

Ezekiel 46:11

ፊቱ ወደ ምስራቅ የሆነው በር ለእርሱ ይከፈታል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሌዋውያኑ ፊቱ ወደ ምስራቅ የሆነውን በር ለእርሱ ይከፍቱለታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድረጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ፊቱ ወደ ምስራቅ የሆነው በር
"የምስራቁ በር" ወይም "በአደባባዩ በስተ ምስራቅ በኩል የሚገኘው በር"

Ezekiel 46:13

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለእስራኤል ገዢዎች/ልዑሎች መልዕክቱን መስጠቱን ቀጥሏል።

ለማርጠብ
"የሚያርስ"

Ezekiel 46:16

ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
ያህዌ ስለ ራሱ በስም የሚናገረው ለሕዝቅኤል እና ለህዝቡ እርሱ የሚናገረው ነገር አስፈላጊ መሆኑን ለማስታወስ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 6:11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እኔ፣ ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ነጻ የመውጣት አመት
ይህ አንድ አገልጋይ ነጻነት የሚያገኝበት አመት ነው። "የኢዮቤልዩ አመት" በመባልም ይጠራል

Ezekiel 46:19

ወደ ሰሜን ፊቱን የመለሰ
"ዋና መግቢያቸውን ወደ ሰሜን ያደረጉ"

እነሆ!
ሕዝቅኤል አስደሳች ነገር ተመልክቷል።

ውጫዊ አደባባይ
ይህ በሕዝቅኤል 10፡5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

Ezekiel 46:21

ውጫዊ አደባባይ
x

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 47

1 ወደ መቅደሱም መዝጊያ መለሰኝ እነሆም፥ ውኃ ከቤቱ መድረክ በታች ወደ ምሥራቅ ይወጣ ነበር፥ የቤቱ ፊት ወደ ምሥራቅ ይመለከት ነበርና ውኃውም ከመሰዊያው በስተቀኝ በኩል ወደ ቤተመቅደሱ ደቡብ አቅጣጫ ይወርድ ነበር። **2** በሰሜኑም በር በኩል አወጣኝ በስተ ውጭ ባለው መንገድ፥ ወደ ምሥራቅ ወደሚመለከት በስተ ውጭ ወዳለው በር መራኝ እነሆም፥ ውኃው ከበሩ ምዕራብ ወገን ይፈስስ ነበር። **3** ሰውዬውም ገመዱን በእጁ ይዞ ወደ ምሥራቅ ወጣ አንድ ሺህም ክንድ ለካ፥ በውኃውም ውስጥ አሻገረኝ፥ ውኃም እስከ ቍርጭምጭሚት ደረሰ። **4** ደግሞ አንድ ሺህ ለካ በውኃውም ውስጥ አሻገረኝ፥ ውኃውም እስከ ጕልበት ደረሰ። ደግሞም አንድ ሺህ ለካ በውኃውም ውስጥ አሻገረኝ፥ ውኃውም እስከ ወገብ ደረሰ። **5** ደግሞ አንድ ሺህ ለካ ልሻገረውም የማልችለው ወንዝ ሆነ ውኃውም ጥልቅ ነበረ፥ የሚዋኝበትም ውኃ ነበረ ሰው ሊሻገረው የማይችለው ወንዝ ነበረ። **6** ሰውዬውም፥ "የሰው ልጅ ሆይ፥ አይተሃልን?" አለኝ። አመጣኝም፥ ወደ ወንዙም ዳር መለሰኝ። **7** በተመለስሁም ጊዜ፥ እነሆ፥ በወንዙ ዳር በዚህና በዚያ እጅግ ብዙ ዛፎች ነበሩ። **8** እርሱም እንዲህ አለኝ፥ "ይህ ውኃ ወደ ምሥራቅ ምድር ይወጣል ወደ ዓረባም ይወርዳል ወደ ጨው ባሕሩም ወደ መልካም ውሃነቱ ይመልሰዋል። **9** ሕያው ነፍስ ያለው ተንቀሳቃሽ ሁሉ ወንዙ በመጣበት ስፍራ ሁሉ በሕይወት ይኖራል ይህም ውኃ በዚያ ስለ ደረሰ ዓሣዎች እጅግ ይበዛሉ። ጨዋማ ባህርን መልካም ያደርጋል። ወንዙም በሚመጣበት ያለው ሁሉ በሕይወት ይኖራል። **10** የዓይንጋዲ አጥማጆችም በወንዙ ዳር ይቆማሉ በዓይንጋዲ መረብ መዘርጊያ ቦታ ይገኛል። በጨው ባህርም ዓሣዎች እንደ ታላቁ ባሕር ዓሣዎች በየወገናቸው እጅግ ይበዛሉ። **11** ነገር ግን የጨው ባህር እረግረጉና እቋሪው ሥፍራ ጨው ለመስጠት ጨዋማ እንደ ሆነ ይኖራል እንጂ አይቀየርም። **12** በወንዙም አጠገብ በዳሩ ላይ በዚህና በዚያ ፍሬው የሚበላ ዛፍ ሁሉ ይበቅላል። ቅጠሉም አይረግፍም ፍሬውም አይቋረጥም። ውኃውም ከመቅደስ የሚመጣ በመሆኑ ዛፎቹ በየወሩ ፍሬ ያፈራሉ። ፍሬውም ለመብል ቅጠሉም ለመድኃኒት ይሆናል። **13** ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ርስት አድርጋችሁ ለአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች ምድሪቱን የምትከፍሉበት እንደዚህ ነው፡ ለዮሴፍ ሁለት እድል ፈንታ ይሰጠዋል። **14** ለአባቶቻችሁ እሰጣቸው ዘንድ ምዬ ነበርና እናንተ እያንዳንዳችሁ እኩል አድርጋችሁ ትካፈላላችሁ። በዚህም መንገድ ይህች ምድር ርስት ትሆናችኋለች። **15** የምድሪቱም ድንበር ይህ ነው። በሰሜኑ ወገን ከታላቁ ባሕር ጀምሮ በሔትሎን መንገድ ወደ ጽዳድ መግቢያ **16** ሐማት፥ ቤሮታ፥ በደማስቆ ድንበርና በሐማት ድንበር መካከል ያለው ሲብራይም፥ በሐውራን ድንበር አጠገብ ያለው ሐጸርሃቲኮን። **17** ስለዚህም ድንበሩ ከባሕሩ በደማስቆ ድንበር ላይ ያለው ሐጸርዔናን ሐማት ድንበር ይሆናል። ይህ የሰሜኑ ድንበር ነው። **18** የምሥራቁም ድንበር በሐውራን በደማስቆና በገለዓድ በእስራኤልም ምድር መካከል ዮርዳኖስ ይሆናል። ይህም ድንበር እስከ ታማር ደረስ ይሄዳል። **19** የደቡቡም ድንበር ከደቡብ ታማር ጀምሮ እስከ ሜርባ ቃዴስ ውኃ እስከ ግብጽ ወንዝ እስከ ታላቁ ባሕር ደረስ ይሆናል። የደቡቡ ድንበር ይህ ነው። **20** የምዕራቡም ድንበር ከታላቁ ባሕር ጀምሮ እስከ ሐማት መግቢያ አንጻር ደረስ ይሆናል። የምዕራቡ ድንበር ይህ ነው። **21** እንዲሁ ይህችን ምድር እንደ እስራኤል ነገድነታችሁ ለእናንተ ትካፈላላችሁ። **22** ለእናንተና በእናንተ መካከል ለሚቀመጡ በእናንተም መካከል ልጆችን ለሚወልዱ ፥ በእስራኤል ልጆች መካከል እንዳሉ እንደአገር ልጆች ላሉ መጻተኞች ርስት አድርጋችሁ በዕጣ ትካፈሉአታላችሁ ። በእስራኤልም ነገዶች መካከል ለርስት ክፍፍል ዕጣ ትጣላላችሁ። **23** መጻተኛውም በማናቸውም ነገድ መካከል ቢቀመጥ በዚያ ርስቱን ትሰጡታላችሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፦

Ezekiel 47:1

የቤተ መቅደሱ ፊቱ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ ነበር
"የቤተ መቅደሱ ፊት በምስራቅ በኩል ነበር"

ከመሰዊያው በስተ ቀኝ
ይህ አንድ ሰው ፊቱን ወደ ምስራቅ መልሶ ሲመለከተው የመሰዊያው ቀኝ ጎን ነው፤ ስለዚህ ከመሰዊያው ደቡባዊ ጎን ይገኛል ማለት ነው።
"ከመሰዊያውበስተ ደቡብ በኩል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

በስተ ምስራቅ የሚገኘው በር
"ምስራቃዊ በር" ወይም "የውጫዊው ግድግዳ ምስራቃዊ በር"

Ezekiel 47:3

መለኪያ መስመር
ሰዎች ረጅም ርቀትን ለመለካት የሚጠቀሙበት ክር ወይም ገመድ

አንድ ሺህ ክንድ
እያንዳንዱ ረጅም ክንድ ወደ 54 ሴንቲ ሜትር ነው። "1000 ክንድ" ወይም "ወደ 540 ሜትር (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

ማቋረጥ የማይችል ወንዝ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ማንም ሰው በእግሩ ሊያቋርጠው የማይችለው ወንዝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 47:6

የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
"ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ይህን ታየዋለህን?
ያህዌ ሕዝቅኤልን ስለሚመለከተው ነገር እንዲያስብበት እያዘዘው ነው። ይህ በሕዝቅኤል 8፡15 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ስለዚህ ስለምታየው ተረዳ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 47:9

ከዚያ እንዲህ ይሆናል
ይህ በሕዝቅኤል 21፡7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ዓይንጋዲ
ይህ ከጨው ባህር በስተ ምዕራብ በኩል የሚገኝ በጣም ትልቅ ምንጭ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የአሳ ማጥመጃ መረቦች የሚደርቁበት ስፍራ
"ሰዎች የአሳ ማጥመጃ መረቦቻቸውን የሚያደርቁበት ስፍራ ነው"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ዓይንኤግላይም
ይህ ከጨው ባህር በስተ ምስራቅ በኩል የሚገኝ በጣም ትልቅ ምንጭ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 47:11

ረግረግ
ዛፎች የሚበቅሉበት ጥልቀት የሌለው ውሃ ያለበት እና ጭቃማ ስፍራ

አረንቋ
ጥልቅ ያልሆነ ውሃ ያለበት እና ሳር የሚበቅልበት ጭቃማ ስፍራ

Ezekiel 47:13

ዮሴፍ ሁለት እጅ ድርሻ ያገኛል
ይህ ሰው ለእርሱ ትውልድ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "የዮሴፍ ትውልድ ከምድሩ ሁለት አካባቢዎችን ያገኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እጁን ወደ ላይ አንስቼ እምላለሁ
በዚያን ዘመን አንድ ሰው ማሃላውን ሳይፈጽም ቢቀር እግዚአብሔር እንደሚቀጣው እንደሚያውቅ ለማሳየት ቀኝ እጁን ያነሳል። (ትዕምርታዊ/ ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 47:15

ድንበር
የአንድ አካባቢ መሬት ዳርቻ/መጨረሻ

ሔትሎን...ጽዳድ...ቤሮታ...ሲብራይም...ሐጸርሃ ቲኮን..ሐውራን...ሐጸርዔናን
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ድንበር
የሁለት አካባቢ መሬቶች የሚገኛኙበት

Ezekiel 47:18

ሐውራን... ታማር...ሜሪባ ቃዴስ...ሐማት
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የግብጽ ጅረት
በሰሜን ሲና ክፍል የሚገኝ በጣም ረጅም ጠባብ ሸለቆ

Ezekiel 47:21

ከዚያም እንዲህ ሆነ
ይህ በሕዝቅኤል 21፡7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ራሱን በስሙ የሚገልጸው/የሚምለው፤ የተናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳወቅ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ። "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 48

1 የነገዶችም ስም ይህ ነው። የዳን ነገድ አንድ የዕጣ ክፍል ይወስዳል፡ ድንብሩም በሔትሎን መንገድ አጠገብ ወደ ሐማት መግቢያ በደማስቆም ድንበር ባለው በሐጸርዔናን በሐማትም አጠገብ በሰሜን በኩል ካለው ከሰሜን ድንበር ይጀምራል። ወርዳቸውም ከምሥራቅ ጀምሮ እስከ ምዕራብ ድረስ ይሆናል። **2** ከዳንም ድንበር ቀጥሎ ከምሥራቅ ጀምሮ እስከ ምዕራብ ድረስ ለአሴር አንድ የዕጣ ክፍል ይሆናል። **3** ከአሴርም ድንበር ቀጥሎ ከምሥራቅ ጀምሮ እስከ ምዕራብ ድረስ ለንፍታሌም አንድ የዕጣ ክፍል ይሆናል። **4** ከንፍታሌም ድንበር ቀጥሎ ከምሥራቅ ጀምሮ እስከ ምዕራብ ድረስ ለምናሴ አንድ የዕጣ ክፍል ይሆናል። **5** ከምናሴም ደቡብ ድንበር ቀጥሎ ከምሥራቅ ጀምሮ እስከ ምዕራብ ድረስ ለኤፍሬም አንድ የዕጣ ክፍል ይሆናል። **6** ከኤፍሬምም ደቡብ ድንበር ቀጥሎ ከምሥራቅ ጀምሮ እስከ ምዕራብ ድረስ ለሮቤል አንድ የዕጣ ክፍል ይሆናል። **7** ከሮቤልም ድንበር ቀጥሎ ከምሥራቅ ጀምሮ እስከ ምዕራብ ድረስ ለይሁዳ አንድ የዕጣ ክፍል ይሆናል። **8** ከይሁዳም ድንበር ቀጥሎ ከምሥራቅ ጀምሮ እስከ ምዕራብ ድረስ ለመባ የሆነ የዕጣ ክፍል ይሆናል ወርዱ ሀያ አምስት ሺህ ክንድ ይሆናል ርዝመቱም ከምሥራቅ ጀምሮ እስከ ምዕራብ ድረስ ከዕጣ ክፍሎች እንደ አንዱ ይሆናል፥ መቅደሱም በመካከሉ ይሆናል። **9** ለእግዚአብሔር የምታቀርቡት መሬት ርዝመቱ ሃያ አምስት ሺህ ወርዱም ሃያ ሺህ ክንድ ይሆናል። **10** ይዚህም ቅዱስ ስፍራ አገልግሎት ይህ ነው፡ ለካህናቱ በሰሜን በኩል ርዝመቱ ሀያ አምስት ሺህ፥ በምዕራብም በኩል ወርዱ አሥር ሺህ፥ በምሥራቅም በኩል ወርዱ አሥር ሺህ፥ በደቡብም በኩል ርዝመቱ ሃያ አምስት ሺህ ክንድ የሆነ ቦታ ይለይላቸዋል። የእግዚአብሔርም መቅደስ በመካከሉ ይሆናል። **11** ይህም የእስራኤል ልጆች በሳቱ ጊዜ፥ ሌዋውያን እንደ ሳቱት ላልሳቱት ሥርዓቴንም ለጠበቁት ከሳዶቅ ልጆች ወገን ለተቀደሱት ካህናት ይሆናል። **12** ለእነርሱም የሚሆነው መባ እስከ ሌዋውያን ድንበር የሚደርስ የዚህ የተቀደሰ ሥፍራ ክፍል ነው። **13** የሌዋውያን መሬት በካህናቱም ድንበር አንጻር ርዝመቱ ሀያ አምስት ሺህ ወርዱም አሥር ሺህ የሆነ ዕጣ ይሆናል። የእነኚህ ኩታ ገጠም መሬቶች ጠቅላላ ርዝመት ሀያ አምስት ሺህ ወርዱም ሀያ ሺህ ክንድ ይሆናል። **14** ለእግዚአብሔርም የተቀደሰ ነውና ከእርሱ ምንም አይሸጡም አይለውጡምም፥ የምድሩም በኩራት አይፋለስም። **15** የቀረው ሀያ አምስት ሺህ ክንድ ስፋትና አምስት ሺህ ክንድ ርዝመት ያለው ስፍራ ለከተማይቱ የጋራ ጉዳይ ፥ ለመኖሪያና ለማስማርያም ይሆናል ከተማይቱም በመካከሉ ትሆናለች። **16** የከተማይቱም ልኬት ይህ ነው፡ በሰሜን በኩል አራት ሺህ አምስት መቶ፥ በደቡብም በኩል አራት ሺህ አምስት መቶ፥ በምሥራቅም በኩል አራት ሺህ አምስት መቶ፥ በምዕራብም በኩል አራት ሺህ አምስት መቶ ክንድ ይሆናል። **17** ለከተማይቱም በሰሜን በኩል ሁለት መቶ አምሳ፥ በደቡብም በኩል ሁለት መቶ አምሳ፥ በምሥራቅም በኩል ሁለት መቶ አምሳ፥ በምዕራብም በኩል ሁለት መቶ አምሳ ክንድ ጥልቀት ያለው ማሰማርያ ይኖራታል። **18** ቀሪው የተቀደሰው በተቀደሰው የመሬት መባ ርዝመቱ ወደ ምሥራቅ አሥር ሺህ ወደ ምዕራብም አሥር ሺህ ክንድ ይሆናል። ድንበሩም በተቀደሰው የመሬት የተያያዘ ይሆናል። ፍሬውም ከተማይቱን ለሚያገለግሉ ለመብል ይሆናል። **19** ከእስራኤል ነገድ ሁሉ ከተማይቱን የሚያገለግሉ ምድሪቱን ያርሱታል። **20** መባው ሁሉ ርዝመቱ ሀያ አምስት ሺህ ወርዱም ሀያ አምስት ሺህ ክንድ ይሆናል ። በዚህም መንገድ የተቀደሰውን የመሬት መባና የከተማይቱን ይዞታ ታደርጋላችሁ። **21** በተቀደሰው መባና በከተማይቱ ይዞታ በዚህና በዚያ ወገን የቀረው ሥፍራ ለአለቃው ይሆናል። በምስራቅ በኩል ያለው የአለቃው ኩታ ገጠም መሬት ከተቀደሰው የመሬት መባ ሀያ አምስት ሺህ ክንድ ወደ ምሥራቁ ድንበር፥ በምዕራብም በኩል ደግሞ ሀያ አምስት ሺህ ክንድ ወደ ምዕራቡ ድንበር ይዘልቃል። የተቀደሰውም የመሬት መባውና የቤተ መቅደሱ የተቀደሰ ስፍራ በመካከል ይሆናል። **22** የአለቃውም ይዞታው ከሌዋውያን ርስትና ክከተማይቱ ይዞታ መካከል ይሆናል፤ በይሁዳ ድንበርና በብንያም ድንበርም መካከል ይሆናል። **23** ለቀሩትም ነገዶች ድርሻቸው ከምሥራቅ ጀምሮ እስከ ምዕራብ ድረስ ይሆናል። የብንያም ነገድ አንድ የዕጣ ክፍል ይቀበላል። **24** ከብንያምም ደቡባዊ ድንበር ቀጥሎ ከምሥራቅ ጀምሮ እስከ ምዕራብ ድረስ ለስምዖን አንድ የዕጣ ክፍል ይሆናል። **25** ከስምዖንም ደቡባዊ ድንበር ቀጥሎ ከምሥራቅ ጀምሮ እስከ ምዕራብ ድረስ ለይሳኮር አንድ የዕጣ ክፍል ይሆናል። **26** ከይሳኮርም ደቡባዊ ድንበር ቀጥሎ ከምሥራቅ ጀምሮ እስከ ምዕራብ ድረስ ለዛብሎን አንድ የዕጣ ክፍል ይሆናል። **27** ከዛብሎንም ደቡባዊ ድንበር ቀጥሎ ከምሥራቅ ጀምሮ እስከ ምዕራብ ድረስ ለጋድ አንድ የዕጣ ክፍል ይሆናል። **28** ከጋድም ድንበር ቀጥሎ በደቡብ በኩል ድንበሩ ከታማር ጀምሮ እስከ ሜሪባ ቃዴስ ውኃ እስከ ግብጽ ወንዝ እስከ ታላቁ ባሕር ድረስ ይሆናል። **29** ርስት አድርጋችሁ ለእስራኤል ነገዶች በዕጣ የምታካፍሉአት ምድር ይህች ናት፥ ይህም ርስታቸው ይሆናል፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር። **30** የከተማይቱም መውጫዎች እነዚህ ናቸው፡ በሰሜን ወገን ልኩ አራት ሺህ አምስት መቶ ክንድ ነው። **31** የከተማይቱ በሮች ሦስት ሲሆኑ እንደ እስራኤል ነገዶች ስም በሰሜን በኩል አንዱ የሮቤል በር አንዱም የይሁዳ በር አንዱም የሌዊ በር ይሆናሉ። **32** በምሥራቁም ወገን አራት ሺህ አምስት መቶ ክንድ በሚረዝመው ሥፍራ፥ ሦስትም በሮች አሉ፡ አንዱ የዮሴፍ በር አንዱም የብንያም በር አንዱም የዳን በር ይሆናሉ። **33** በምስራቅ ወገን አራት ሺህ አምስት መቶ ክንድ በሚረዝመው ሥፍራ፥ ሦስት በሮች አሉ፡ አንዱ የስምዖን ፥አንዱ የይሳኮር፥ እና አንዱም የዛብሎን በር ናቸው። **34** በምዕራቡም ወገን ልኬቱ አራት ሺህ አምስት መቶ ክንድ ሲሆን፥ በዚያ ሦስት በሮች አሉ፡ አንዱ የጋድ፥ አንዱም የአሴር፥ ሌላውም የንፍታሌም በር ናቸው። **35** የከተማይቱ ዙሪያም አሥራ ስምንት ሺህ ክንድ ይሆናል፥ ከዚያም ቀን ጀምሮ የከተማይቱ ስም "እግዚአብሔር በዚያ አለ" ተብሎ ይጠራል።

Ezekiel 48:1

የመሬት አንድ እጅ/ ክፍል
"የምታከፋፍለው አንድ ቁራጭ መሬት"

ድንበር ይደርሳል... ድንበር ይሄዳል
"ድንበር ይሆናል...ድንበር ይደርሳል"

ሔትሎን...ሌቦ ሐማት...ሐጸርዔና
የከተማ ስሞች።ይህ በሕዝቅኤል 47፡15-17 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

Ezekiel 48:4

አንድ እጅ/ክፍል
በሕዝቅኤል 48፡1 ላይ "የመሬት አንድ እጅ/ ክፍል" የሚለው በተተረጎመበት መልክ ይተርጉሙት።

ከምስራቅ እስከ ምዕራብ ድረስ
ይህ በሕዝቅኤል 48፡3 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

Ezekiel 48:8

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለእስራኤል ህዝብ መልዕክቱን መስጠቱን ቀጥሏል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሃያ አምስት ሺህ ክንድ... አስር ሺህ ክንድ
እያንዳንዱ ረጅም ክንድ ወደ 54 ሴንቲ ሜትር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 40:5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "25000 ክንድ ... 10000 ክንድ" ወይም "ወደ 13.5 ኪሎ ሜትር ...ወደ 5.4 ኪሎ ሜትር" (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 48:10

ካህናት የሚሰጣቸው መሬት ይኖራቸዋል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "የእስራኤላውያን መሪዎች ለካህናት መሬት ይሰጧቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ሃያ አምስት ሺህ ክንድ... አስር ሺህ ክንድ
እያንዳንዱ ረጅም ክንድ ወደ 54 ሴንቲ ሜትር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 40:5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "25000 ክንድ ... 10000 ክንድ" ወይም "ወደ 13.5 ኪሎ ሜትር ...ወደ 5.4 ኪሎ ሜትር" (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

የእነርሱ ድርሻ ከዚህ እጅግ ቅዱስ ከሆነው ምድር ክፍል ይሆናል
"ከተቀረው ቅዱስ ምድር ይበልጥ ቅዱስ የሆነው ፣ ከቅዱሱ ምድር ይህ አነስተኛ ክፍል ለእነዚህ ካህናት ይሆናል"

Ezekiel 48:13

ሃያ አምስት ሺህ ክንድ... አስር ሺህ ክንድ
እያንዳንዱ ረጅም ክንድ ወደ 54 ሴንቲ ሜትር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 40:5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "25000 ክንድ ... 10000 ክንድ" ወይም "ወደ 13.5 ኪሎ ሜትር ...ወደ 5.4 ኪሎ ሜትር" (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የመጀመሪያው ፍሬ
"የመጀመሪያው ፍሬዎች የሆነ ይህ መሬት። እዚህ ስፍራ "ፍሬዎች" የሚለው ምናልባት ከመስዋዕቶቹ ሁሉ ምርጥ የሆኑ ነገሮች ለእግዚአብሔር ለማቅረብ ተለይተዋል ማለት ሊሆን ይችላል። ይህ መሬት የተገለጸው በዚያ መንገድ፣ ለያህዌ ጥቅም እንደተለየ መሬት ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 48:15

አምስት ሺህ ክንድ... ሃያ አምስት ሺህ ክንድ
"5000 ክንድ ... 25000 ክንድ" እያንዳንዱ ረጅም ክንድ ወደ 54 ሴንቲ ሜትር ነው።ይህ በሕዝቅኤል 40:5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ወደ 2.3 ኪሎ ሜትር ...ወደ 13.5 ኪሎ ሜትር" (ቁጥሮች እና መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

ለከተማይቱ የጋር ጥቅም ይሆናል
"ሁሉም የከተማዋ ህዝብ ተካፍሎ የሚጠቀምባት አካባቢ ይሆናል"

4500 ክንዶች
"አራት ሺህ አምስት መቶ ክንድ።" እያንዳንዱ ረጅም ክንድ ወደ 54 ሴንቲ ሜትር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 40:5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ወደ 2.4 ኪሎ ሜትር" (ቁጥሮች እና መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

ቤቶቹ፣ እና የግጦሽ መሬት
"ለቤቶች የሚሆን ስፍራ እና ክፍት ቦታ"

Ezekiel 48:19

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለህዝቅኤል ስለእስራኤል ሰዎች መልዕክቱን መስጠቱን ቀጥሏል

ሃያ አምስት ሺህ ክንድ
እያንዳንዱ ረጅም ክንድ ወደ 54 ሴንቲ ሜትር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 40:5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "25000 ክንድ " ወይም "ወደ 13.5 ኪሎ ሜትር" (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚህ መንገድ ከከተማይቱ መሬት ጋር የምድሪቱን ቅዱስ ስጦታ ታቀርባላችሁ።
"ቅዱሱን ስጦታ እና የከተማይቱን ሀብት ታቀርባላችሁ"

እናንተ
ይህ ብዙ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተው የእስራኤልን ህዝብ ነው። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)

ቅዱስ ስጦታ
የእስራኤል ህዝብ ለሌዋውያን፣ ለካህናት፣ እና ለቤተ መቅደስ እንዲሆን ለእግዚአብሔር የሰጠው መሬት

Ezekiel 48:21

ቅዱስ ስጦታ
ይህ በሕዝቅኤል 48:18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ሃያ አምስት ሺህ ክንድ
እያንዳንዱ ረጅም ክንድ ወደ 54 ሴንቲ ሜትር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 40:5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "25000 ክንድ " ወይም "ወደ 13.5 ኪሎ ሜትር" (መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 48:23

አንድ እጅ
ይህንን በሕዝቅኤል 48:1 ላይ "አንድ እጅ መሬት" የሚለውን በተረጎሙበት መልክ ይትርጉሙት

Ezekiel 48:27

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለህዝቅኤል ስለእስራኤል ሰዎች መልዕክቱን መስጠቱን ቀጥሏል

ታማር...ሜሪባ ቃዴስ
የከተሞች ስም። ይህ በሕዝቅኤል 47:19 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የግብጽ ጅረቶች
በሰሜናዊ ሲና ክፍል የሚገኝ በጣም ረጅም ጠባብ ሸለቆ። ይህ በሕዝቅኤል 47:19 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ
ይህ ብዙ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተው የእስራኤልን ህዝብ ነው። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)

እጣ ጣሉ
ይህ በሕዝቅኤል 45:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ራሱን በስሙ የሚገልጸው/የሚምለው፤ የተናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳወቅ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ። "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 48:30

4500 ክንድ
"አራት ሺህ አምስት መቶ ክንድ።" እያንዳንዱ ረጅም ክንድ ወደ 54 ሴንቲ ሜትር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 40:5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ወደ 2.4 ኪሎ ሜትር" (ቁጥሮች እና መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 48:33

4500 ክንድ
"አራት ሺህ አምስት መቶ ክንድ።" ይህ ወደ 2.4 ኪሎ ሜትር ነው። (ቁጥሮች እና መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የርቀት መለኪያ የነበሩ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Daniel

Daniel

Chapter 1

1 በይሁዳ ንጉሥ በኢዮአቄም ዘመነ መንግሥት በሦሥተኛው ዓመት፥አቅርቦቶቿን ሁሉ ለማስቆም የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ወደ ኢየሩሳሌም መጣ፥
ከበባትም። 2 ጌታም ለናቡከደነፆር በይሁዳ ንጉሥ በኢዮአቄም ላይ ድል ሰጠው፥እርሱም ከእግዚአብሔር ቤት የተቀድሱ ዕቃዎች ጥቂቱን ሰጠው። እርሱም
ወደ ባቢሎን ምድር፥ ወደ አምላኩ ቤት አመጣቸው፥የተቀደሱትንም ዕቃዎች በአምላኩ ግምጃ ቤት ውስጥ አኖራቸው። 3 ንጉሡም ዋና አለቃውን አስፋኔዝን፥
ከነገሥታቱና ከመሳፍንቱ ቤተሰብ የሆኑትን፥ ከእስራኤል ሰዎች አንዳንዶችን፦ 4 ነውር የሌለባቸውን ወጣት ወንድች፥ መልከ መልካሞችን፥ ጥበበኞችን፥
በዕውቀትና በማስተዋል የተሞሉትንና በንጉሡ ቤት ለማገልገል ብቁዎች የሆኑትን እን ዲያመጣ ተናገረው። የባቢሎናውያንን ሥነ ጽሑፍና ቋንቋ
እንዲያስተምራቸው ተናገረው። 5 ንጉሡ ከምግቡና ከሚጠጣው ወይን በየዕለቱ ድርሻ መደበላቸው። እነዚህ ወጣት ወንዶች ለሦሥት ዓመት መሠልጠንና ከዚያ
በኋላ ንጉሡን ማገልገል ይጠበቅባቸዋል። 6 ከእነዚህም መካከል አንዳንድ የይሁዳ ሰዎች፥ ዳንኤል፥ አናንያ፥ ሚሳኤልና አዛሪያ ነበሩ። 7 ዋና አለቃውም ስም
አወጣላቸው፦ ዳንኤልን ብልጣሶር፥ አናንያን ሲድራቅ፥ ሚሳኤልን ሚሳቅ፥ አዛሪያንም አብድናጎ ብሎ ጠራቸው። 8 ነገር ግን ዳንኤል በንጉሡ ምግብና
በሚጠጣውም ወይን ራሱን እንዳያረክስ በውስጡ አሰበ። ራሱን እንዳያረክስ ከዋናው አለቃ ፈቃድ ጠየቀ። 9 ዋና አለቃው ለእርሱ ባለው አክብሮት አማካይነት
እግዚአብሔር ለዳንኤል ሞገስንና ጸጋን ሰጠው። 10 ዋና አለቃውም ዳንኤልን አለው፥ «እኔ ጌታዬን ንጉሥን እፈራለሁ። ምን ዓይነት ምግብና መጥጥ ማግኘት
እንዳለባችሁ አዞኛል። በእናንተ እድሜ ካሉ ወጣቶች ይልቅ ከስታችሁ ስለ ምን ይመለከታል? ንጉሡ ከእናንተ የተነሳ በሞት ይቀጣኝ ይሆናል።» 11 ዳንኤልም
ዋናው አለቃ በዳንኤል፥በአናንያ፥በሚሳኤልና በአዛሪያ ላይ ለሾመው መጋቢ ተናገረ። 12 እርሱም አለ፥«እባክህ፥እኛን አገልጋዮችህን ለአሥር ቀናት ፈትነን።
የምንመገብው ጥቂት አትክልትና የምንጠጣው ውኃ ብቻ ስጠን። 13 ከዚያም የእኛን ፊት የንጉሡን ምግብ ከሚመገቡ ወጣቶች ጋር አስተያይ፥ባየኽውም
መሠረት በአገልጋዮችህ ላይ አድርግ።» 14 መጋቢውም ይህን ለማድረግ ከእርሱ ጋር ተስማማ፥ለአሥር ቀናትም ፈተናቸው። 15 ከአሥርም ቀን በኋላ የንጉሡን
መብል ከተመገቡ ወጣቶች ይልቅ ጤነኞችና የተሻለ የተመገቡ ሆነው ታዩ። 16 ስለዚህ መጋቢው የተመደበላቸውን የተመረጠ ምግብና ወይን አስቀርቶ
አትክልት ብቻ ሰጣቸው። 17 ለእነዚህ አራት ወጣቶች፥ እግዚአብሔር በሁሉም ሥነ ጽሑፍና በጥበብ ዕውቀትና ማስተዋል ሰጣቸው፥ ዳንኤልም ሁሉንም
ዐይነት ራዕይና ሕልም መረዳት ይችል ነበር። 18 እንዲያስገቡአቸው ንጉሡ የመደበው ጊዜ እንዳበቃ፥ዋናው አለቃ በናቡከደነፆር ፊት አቀረባቸው። 19 ንጉሡም
ከእነርሱ ጋር ተነጋገረ፥አብረዋቸው ከነበሩት ሁሉ መካከል ከዳንኤል፥ሐናንያ፥ ሚሳኤልና አዛርያ ጋር የሚወዳድር ማንም አልነበረም። በንጉሡ ፊት ቆሙ፥
ሊያገለግሉት ዝግጁዎች ነበሩ። 20 ንጉሡ በጠየቃቸው የጥበብና የማስተዋል ጥያቄዎች ሁሉ፥በግዛቱ ሁሉ ከሚገኙ አስማተኞችና ሙታን ሳቢዎች አሥር
እጥፍ በልጠው ተገኙ። 21 ዳንኤልም እስከ ንጉሥ ቂሮስ የመጀመሪያ ዓመት ድረስ እዚያው ነበረ።

Daniel 1:1

ናቡከደነፆር የባቢሎን ንጉሥ ....ለነቡከደነዶር ሰጠው
ይሄ የሚያመለክተው ናቡከደነፆርን ብቻ ሣይሆን ናቡከደነፆርንና ወታደሮቹን ጭምር ነው።"የናቡከደነፆር ወታደሮች...እነርሱ" ወይም "የባቢሎን ንጉሥ የሆነው ናቡከደነፆርና ወታደሮቹ"

ወደ እርሷ የሚገቡትን አቅራቦቶች ሁሉ እንዲቋረጡ አደረገ
"ሰዎች ምንም ዓይነት አቅርቦት እንዳያገኙ ማስቆም"

አቅራቦትን ሁሉ ማቋረጥ
"ሰዎች ምንም ዓይነት አቅርቦት እንዳይቀበሉ መከልከል"

ኢዮአቄም የይሁዳ ንጉሥ
ይሄ የሚያመለክተው ኢዮአቄምን ብቻ ሣይሆን ኢዮአቄምንና ወታደሮቹን ጭምር ነው።"የይሁዳ ንጉሥ የኢዮአቄም ጦር"

ሰጠው
ኢዮአቄም ለናቡከደነፆር ሰጠው

አመጣ...አገባው
ምንም እንኳን ናቡከደነፆር እነዚህን ነገሮች ለብቻው ያላደረገው ቢሆንም አንባቢው እንደ ነጠላ ተውላጠ ሥም ቢቀበለው መልካም ይሆናል።"አመጡት...አስገቡት"

አመጣላቸው
እዚህ ላይ"እነርሱ"የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢዮአቄምን፤ሌሎች እሥረኞችንና የተቀደሱ ዕቃዎችን ነው።

ወደ አምላኩ ግምጃ ቤት
ይሄ ለአምላኩ ያለውን መሠጠት የሚገልፅ ነው።

Daniel 1:3

ንጉሡ ተናገረ
ይሄ የሚያመለክተው ናቡከደነፆርን ነው።

አስፋኔዝ
ይሄ ዋናው አለቃ ነው።

አለቃ
የሕብረተሰቡ ከፍተኛው መደብ

ነውር የሌለባቸው
እነዚህ ሁለት አሉታዊ የሆኑ ቃላት በጋራ የሚገልፁት አዎንታዊ ሃሣብን ነው።"ፍፁም በሆነ አቀራረብ"

በዕውቀትና በማስተዋል መሞላት
ይሄ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው።ይሄ የሚያሣየው ስለ ብዙ ነገር የሚያውቁ መሆኑንና መረጃውን የማደራጀትና የመጠቀም ችሎታ ያላቸው መሆኑን ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የንጉሥ ቤተ መንግሥት
ይሄ ታላቅ ቤት የሆነና ንጉሥ ለመኖሪያነት የሚጠቀምበት ሥፍራ ነው።

ሊያስተምራቸው ተዘጋጅቶ ነበር
“አስፋኔዝ ሊያስተምራቸው ተዘጋጅቶ ነበር።”

ንጉሡ ኃላፊነቱን በእነርሱ ላይ ጣለ
የንጉሡ ባለሥልጣናት ይሄንን ተግባር አከናወኑለት።“የንጉሡ ባለሥልጣናት ኃላፊነቱን ወደ እነርሱ አስተላለፉት”

የቅንጦት ነገሮቹ
ንጉሡ ይመገባቸው የነበሩ ልዩ የሆኑ፤እምብዛም የማይገኙና መልካም የሆኑ ምግቦች።

እነዚህ ወጣት ልጆች ሥልጠና መውሰድ ይጠበቅባቸዋል
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ እነዚህን ወጣት ልጆች የማሠልጠን ኃላፊነት ለአስፋኔዝ ተሰጥቶት ነበር።”

ሥልጠና ወሰዱ
“ጥበብን ተማሩ”

Daniel 1:6

ከእነዚህ መካከል
“ከእሥራኤል ወገን ከሆኑት ወጣት ልጆች መካከል”

ዋናው አለቃ
ይሄ የሚያመለክተው የናቡከደነፆር መንግሥት ውስጥ ከፍተኛ ባለሥልጣን የነበረውን አስፋኔዝን ነው።

ብልጣሶር...ሲድራቅ...ሚሳኤል...አናንያ
እነዚህ ሁሉ የሰው ስሞች ናቸው።

Daniel 1:8

ዳንኤል በአዕምሮው አሰበ
እዚህ ላይ “አዕምሮ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ራሱን ዳንኤልን ነው።

ራሱን ማርከስ
አንድን ነገር “እንዲረክስ ማድረግ” ማለት ንፁህ እንዳይሆን ማድረግ ማለት ነው። በእግዚአብሔር ሕግ መሠረት አንዳንድ የባቢሎናውያን ምግቦችና መጠጦች ከአምልኮ ሥርዓት ጋር በተያያዘ ሊያረክሱት ይችላሉ።ይሄ የበለጠ ሊብራራ ይችላል። “ከእግዚአብሔር ሕግ አንፃር የሚታይ ከሆነ ራሱን ለርኩሰት አሣልፎ ይሰጣል ማለት ነው”

ቅንጡ የሆኑ ነገሮች
ይሄ ልዩ የሆኑ፤በተራው ሕዝብ ዘንድ ያልተለመዱና መልካም ምግቦችን የሚመለከት ነው።

ከአንተ ዕድሜ እኩያ ከሆኑ ብላቴኖች ጋር ስትታይ ለምን የተጎዳህ ሆነህ ይመልከትህ?
ኃላፊው ሰው ይህንን ጥያቄ የጠየቀበት ምክኒያት ያለው ነገር ሊከሰት ይችላል ብሎ በማሰቡ ነው።እንደ መግለጫም ሊሆን ይችላል።“ በዕድሜ የአንተ እኩያ ከሆኑ ከሌሎች ወጣት ልጆች በባሰ ሁኔታ ተጎሳቁለህ ሊያይህ አይሻም”

ንጉሡ አንገቴን ሊቆርጠው ይችላል
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው።“ንጉሡ ራሴን ሊቆርጠው ይችላል” ወይም “ንጉሡ ሊገድለኝ ይችላል”

Daniel 1:11

የእኛን ፊት ከሌሎቹ ጋራ አስተያየው
ዳንኤል የጃንደረቦቹን አለቃ ጓደኞቹና ራሱንም ጭምር ከሌሎች ወጣት ልጆች በባሰ ሁኔታ ይጎሳቆሉ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ እንዲመለከት ለመነው።“ከሌሎቹ ይልቅ የከፋ ገፅታ ይኖርን እንደሆነ ተመልከት”

Daniel 1:14

ፈተናቸው...ፊታቸው...ነበሩ...ስጋቸው ወፍሮ...ወይናቸውን
እነዚህ ሁሉ ተውላጠ ስሞች የሚያመለክቱት ዳንኤልን፤ሃናንያን፤ሚሳኤልንና አብደናጎምን ነው።

ተመገቡ
ይሄ የሚያመለክተው ከበሉት ምግብ የተነሣ ጤነኛ መሆንን ነው።

Daniel 1:17

እግዚአብሔር ዕውቀትና ማስተዋልን ሰጣቸው
”ዕውቀት”እና “ማስተዋል”የሚሉት ማሰሪያ አንቀፆች ”መማር”እና “መገንዘብ”በተሰኙ ግሶች ሊተኩ ይችላሉ።“እግዚአብሔር ብሩህ በሆነ ሁኔታ እንዲማሩና ግንዛቤ ይኖራቸው ዘንድ ችሎታን ሰጣቸው”

በትምህርትና በጥበብ ሁሉ
እዚህ ላይ “በሁሉም” የሚለው ቃል አጠቃላይ አነጋገር ሲሆን እጅግ መልካም የሆነ ትምህርትና ግንዛቤ እንዳላቸው ለማመልከት ነው።“ባቢሎናውያን የፃፉትንና ያጠኑትን ብዙ ነገሮች ያወቁ መሆኑ”

ንጉሡ ከእነርሱ ጋር ተነጋገረ
ንጉሡ ከአራቱ “ወጣት ልጆች” ጋር ተነጋገረ። (ትንቢተ ዳንኤል 1፡17)

ከብላቴኖች ሁሉ እንደ ዳንኤልና እንደ አናንያ እነደ ሚሳኤልና እንደ አዛርያ ያለ አልተገኘም
ይሄ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል።“ዳንኤል፤ሚሳኤል፤ሲድራቅና አብደናጎም ከቡድኑ ሁሉ ይልቅ ደስ አሰኙት”

ዳንኤል፤ሚሳኤል፤ሲድራቅና አብደናጎም
እነዚህ የሰዎች ሥሞች ናቸው።

አሥር እጥፍ የበለጠ
“አሥር እጥፍ” የሚለው ተጋንኖ የቀረበው ገለፃ ትልቅ ብቃት እንደነበራቸው ለማሣየት ነው።“እጅግ የተሻለ”

በንጉሥ ቂሮስ የመጀመሪያው ዓመት
“ንጉሥ ቂሮስ ባቢሎንን መግዛት በጀመረ በአንደኛው ዓመት”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 ናቡከደነፆር በነገሠ በሁለተኛው ዓመት ሕልም አለመ፤ አእምሮው ታወከ፥ ሊተኛም አልቻለም። **2** ከዚያም አስማተኞችና ሙታን ሳቢዎች እንዲመጡ አዘዘ፤ ጠንቋዮችንና ጠቢባንን ደግሞ ጠራ፤ ስለ ሕልሙ እንዲነግሩት ፈለጋቸው፤ ስለዚህ ገቡና በንጉሡ ፊት ቆሙ። **3** ንጉሡ አላቸው፥«ሕልም አልሜአልሁ፥ሕልሙም ምን ማለት እንደሆነ ለማወቅ አእምሮዬ ተጨንቋል።» **4** ከዚያም ጠቢባኑ በአረማይክ፥ «ንጉሥ ሆይ ለዘላለም ንገሥ! ሕልሙን ለእኛ ለባሪያዎችህ ተናገር፥ እኛም ፍቺውን እናስታውቅሃለን» ብለው ለንጉሡ ተናገሩ። **5** ንጉሡም ለጠቢባኑ እንዲህ ሲል መለሰላቸው፥«ሕልሙን ካልገለጣችሁልኝና ካልተረጎማችሁት፥ ሰውነታችሁ እንዲቆራረጥና ቤታችሁም የቆሻሻ ክምር እንዲሆን ወስኜአለሁ። **6** ነገር ግን ሕልሙንና ትርጉሙን ከነገራችሁኝ፥ ከእኔ ዘንድ ሥጦታ፥ ሽልማትና ታላቅ ክብር ትቀበላላችሁ። ስለዚህ ሕልሙንና ትርጉሙን ንገሩኝ።» **7** እነርሱም እንደገና እንዲህ ሲሉ መለሱ፥ «ንጉሡ ሕልሙን ለአገልጋዮቹ ይንገር፥ እኛም ትርጉሙን እንነግርሃለን።» **8** ንጉሡም መለሰላቸው፥ «ይህን ጉዳይ በተመለከተ ውሳኔዬ ምን ያህል ጽኑ እንደሆነ ስላወቃችሁ ተጨማሪ ጊዜ ማግኘት እንደምትፈልጉ በእርግጥ አውቃለሁ። **9** ነገር ግን ሕልሙን ባትነግሩኝ፥ ሁላችሁን አንድ ቅጣት ይጠብቃችኋል። ሐሰት የሆኑ አሳች አሳቦችን ለማዘጋጅት ወስናችኋል፥ አሳቤንም እስክለውጥ ድረስ ልትነግሩኝ በአንድነት ተስማምታችኋል። ስለዚህ ሕልሙን ንገሩኝ፥ ያን ጊዜም ልትተረጉሙልኝ እንደምትችሉ አውቃለሁ።» **10** ጠቢባኑም ለንጉሡ እንዲህ ሲሉ መለሱ፥«የንጉሡን ጥያቄ ሊመልስ የሚችል ሰው በምድር አይገኝም። አስማተኞችን፥ ሙታን ሳቢዎችን ወይም ጠቢባንን እንዲህ ዓይነት ጥያቄ የጠየቀ ታላቅና ኃያል ንጉሥ የለም። **11** ንጉሡ የሚጠይቀው ነገር አስቸጋሪ ነው፥ በሰዎች መካከል ከማይኖሩት አማልክት በስተቀር ይህንን ለንጉሡ መንገር የሚችል ማንም የለም። **12** ይህም ንጉሡን አስቆጣው እጅግም አበሳጨው፥ በባቢሎንም በጥበባቸው የሚታወቁትን ሁሉ እንዲያጠፉአቸው አዘዘ። **13** ስለዚህም አዋጁ ወጣ፤ በጥበባቸው የሚታወቁት ሁሉ ሊገድሉ ሆነ፥ ዳንኤልንና ጓደኞቹንም ሊገድሉአቸው ፈለጉአቸው። **14** በዚያን ጊዜ ዳንኤል በባቢሎን በጥበባቸው የሚታወቁትን ሁሉ ሊገድል ለመጣው ለንጉሡ የዘበኞች አዛዥ ለአርዮክ በጥንቃቄና በማስተዋል መለሰለት። **15** ዳንኤልም «የንጉሡ አዋጅ ለምን አስቸኳይ ሆነ?» ሲል የንጉሡን አዛዥ ጠየቀው፤ አርዮክም የሆነውን ለዳንኤል ነገረው። **16** በዚያን ጊዜ ዳንኤል ገባና ትርጉሙን ለንጉሡ የሚያስታውቅበት ቀጠሮ ከንጉሥ እንዲሰጠው ጠየቀ። **17** በዚያን ጊዜ ዳንኤል ወደ ቤቱ ሄደና የሆነውን ለአናንያ፥ ለሚሳኤልና ለአዛርያ ነገራቸው። **18** እርሱም እነርሱም በጥበባቸው ከሚታወቁት ከተቀሩት የባቢሎን ሰዎች ጋር አብረው እንዳይገደሉ፥ ስለዚህ ምሥጢር ከሰማይ አምላክ ምሕረት እንዲለምኑ አጥብቆ ነገራቸው። **19** በዚያች ሌሊት ምሥጢሩ ለዳንኤል በራዕይ ተገለጠለት። በዚያን ጊዜ ዳንኤል የሰማይን አምላክ አመሰገነ፥ አለም፡- **20** «ጥበብና ኃይል የእርሱ ነውና የእግዚአብሔር ስም ከዘላለም እስከ ዘላለም የተባረከ ይሁን።» **21** ጊዜዎችንና ወቅቶችን ይለውጣል፤ነገሥታትን ይሸራል በዙፋናቸውም ነገሥታትን ያስቀምጣል። ጥበብን ለጠቢባን እውቀትንም ለአስተዋዮች ይሰጣል። **22** እርሱ በጨለማ ያለውን ያውቃልና ብርሃንም ከእርሱ ጋር ነውና የጠለቁትንና የተሰወሩትን ነገሮች ይገልጣል። **23** የአባቶቼ አምላክ ስለ ሰጠኸኝ ጥበብና ኃይል አመሰግንሃለሁ፥እባርክሃለሁም። የለመንህን ነገር አስታውቀኸኛል፥ንጉሡን ያሳሰበውን ነገር አስታውቀኸናል። **24** ከዚህም በኋላ ዳንኤል የባቢሎንን ጠቢባን ሁሉ እንዲገድል ንጉሡ ኃላፊነት ወደ ሰጠው ወደ አርዮክ ሄደ። ሄዶም አለው፡-«በባቢሎን የሚገኙትን ጠቢባን አትግደል። ወደ ንጉሡ ይዘኽኝ ግባ እኔም የሕልሙን ትርጉም ለንጉሥ እናገራለሁ።» **25** ከዚያም አርዮክ በፍጥነት ዳንኤልን ወደ ንጉሡ አስገባና አለ፡-«የንጉሡን ሕልም ትርጉም የሚገልጥ ሰው ከይሁዳ ምርኮኞች መካከል አግኝቼአለሁ። **26** ንጉሡም (ብልጣሶር ተብሎ የሚጠራውን) ዳንኤልን አለው፡-«ያየሁትን ሕልምና ትርጉሙን ልትነግረኝ ትችላለህን?» **27** ዳንኤልም ለንጉሡ እንዲህ ሲል መለሰ፡-«ንጉሡ የጠየቀው ምሥጢር ጥበብ ባላቸው፥ በሙታን ሳቢዎች፥ በአስማተኞችና በኮከብ ቆጣሪዎችም ሊገለጥ አይችልም። **28** ነገር ግን ምሥጢር የሚገልጥ አምላክ በሰማያት ውስጥ አለ፤ ንጉሥ ናቡከደነፆር ሆይ! እርሱም በሚመጡት ዘመናት ሊሆን ያለውን አስታውቆሃል። በአልጋህ ላይ ተኝተህ ሳለህ ያየኽው ሕልምህና የአእምሮህ ራዕዮች እነዚህ ናቸው፡- **29** ንጉሥ ሆይ! በአልጋህ ላይ ሆነህ ሊሆኑ ስላሉ ነገሮች ታስብ ነበር፤ ምሥጢርንም የሚገልጠው ሊሆን ያለውን አስታውቆሃል። **30** እኔ ከሌሎች ሰዎች የሚበልጥ ጥበብ ስላለኝ ይህ ምሥጢር አልተገለጠልኝም። ንጉሥ ሆይ! ይህ ምሥጢር ለእኔ የተገለጠው አንተ ትርጉሙን ትረዳ ዘንድና የውስጥ አሳብህንም ታውቅ ዘንድ ነው። **31** ንጉሥ ሆይ! ትልቅ ምስል አየህ ተመለከትህም። ምስሉም እጅግ ታላቅና አንጸባራቂ ነበር፥ በፊትህም ቆሞ ነበር። ማንጸባረቁም አስፈሪ ነበር። **32** የምስሉ ራስ ከወርቅ የተሠራ ነበር። ደረቱና ክንዶቹ ከብር የተሠሩ ነበሩ። ወገቡና ጭኖቹ ከናስ፥ **33** እግሮቹም ከብረት የተሠሩ ነበሩ። መርገጫ እግሮቹ ከፊሉ ከብረት ከፊሉ ከሸክላ የተሠሩ ነበሩ። **34** የሰው እጆች ሳይነኩት ድንጋይ ሲፈነቀል፥ ከብረትና ከሸክላ የተሠሩትንም የምስሉን መርገጫ እግሮች ሲመታቸውና ሲያደቃቸው ተመለከትህ። **35** ከዚያም ብረቱ፥ሸክላው፥ ናሱ፥ ብሩና ወርቁ ወዲያው እንክትክታቸው ወጣ፤ በመከርም ወቅት በአውድማ ላይ እንዳል እብቅ ሆኑ። ነፋሱም ጠርጎ ወሰዳቸው ምልክታቸውም አልቀረም። ነገር ግን ምስሉን የመታው ድንጋይ ታላቅ ተራራ ሆነ ምድርንም ሞላ። **36** ሕልምህ ይህ ነበር። አሁን ትርጉሙን ለንጉሥ እንናገራለን። **37** አንተ ንጉሥ ሆይ! የሰማይ አምላክ መንግስትን፥ ኃይልን፥ብርታትንና ክብርን የሰጠህ የነገሥታት ንጉሥ ነህ። **38** የሰው ልጆች የሚኖሩበትን ስፍራ ሁሉ በእጅህ ሰጠህ። የምድር እንሰሳትንና የሰማያት ወፎችን በእጅህ ሰጠህ፤ በእነርሱ ሁሉ ላይም ግዢ አደረገህ። አንተ የምስሉ የወርቅ ራስ ነህ። **39** ከአንተም በኋላ ከአንተ የሚያንስ ሌላ መንግሥት ይነሳል፤ከዚያም በኋላ በምድር ሁሉ ላይ የሚገዛ ሦሥተኛ የናስ መንግሥት ይነሳል። **40** ብረት ሌሎች ነገሮችን እንደሚሰባብርና ሁሉን ነገር እንደሚያደቅቅ፥እንዲሁ እንደ ብረት ብርቱ የሆነ አራተኛ መንግሥት ይነሳል። እነዚህን ነገሮች ሁሉ ያደቅቃቸዋል ይፈጫቸዋልም። **41** እግሮቹና ጣቶቹ በከፊል ከሸክላ በከፊል ከብረት ተሠርተው እንዳየህ እንዲሁ የተከፋፈለ መንግሥት ይሆናል፤ ለስላሳ ሸክላ ከብረት ጋር ተደባልቆ እንዳየህ እንዲሁ የተወሰነ የብረት ብርታት ይኖረዋል። **42** የእግሮቹ ጣቶች በከፊል ከብረት በከፊል ከሸክላ ተሠርተው እንዳየህ መንግሥቱ በከፊል ብርቱ በከፊል ደካማ ይሆናል። **43** ብረትና ለስላሳ ሸክላ ተደባልቀው እንዳየህ እንዲሁ ሕዝቡም ድብልቅ ይሆናል፤ብረትና ሸክላ እ ንደማይዋሓድ እነርሱም አብረው አይዘልቁም። **44** በእነዚያ ነገሥታት ዘመን የሰማይ አምላክ ፈጽሞ የማይጠፋና በሌላ ሕዝብ የማይሸንፍ መንግሥት ያቆማል። ሌሎቹን መንግሥታት ይፈጫቸዋል ፈጽሞም ያጠፋቸዋል፤ እርሱ ግን ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል። **45** የሰው እጆች ሳይነኩት ድንጋይ ከተራራ ሲፈነቀል እንዳየህ እንዲሁ ነው። እርሱም ብረቱን፥ ናሱን፥ ሸክላውን፥ ብሩንና ወርቁን አደቀቃቸው። ንጉሥ ሆይ! ከዚህ በኋላ ሊሆን ያለውን ታላቁ አምላክ አስታውቆሃል። ሕልሙ እውነተኛ ፍቺውም የታመነ ነው። **46** ንጉሥ ናቡከደነፆርም በዳንኤል ፊት በግንባሩ ተደፋ አከበረውም፤ መሥዋዕትና ዕጣን እንዲይቀርቡለት አዘዘ። **47** ንጉሡ ዳንኤልን እንዲህ አለው፡-«ይህን ምሥጢር መግለጥ ችለሃልና፥ ምሥጢርን ሁሉ የሚገልጠው አምላክህ በእውነት የአማልክት አምላክ፥ የነገሥታት ጌታ ነው።» **48** ከዚያም በኋላ ንጉሡ ዳንኤልን እጅግ አከበረው፥ብዙ አስደናቂ ሥጦታዎችንም ሰጠው። በባቢሎን ክፍለ አገር ሁሉ ላይ ገዢ አደረገው። በባቢሎን ጠቢባን ሁሉ ላይ ዋነኛ አስተዳዳሪ ሆነ። **49** ዳንኤልም ለንጉሡ ጥያቄ አቀረበ፥ ንጉሡም ሲድራቅን፥ሚሳቅንና አብድናጎን በባቢሎን ክፍለ አገር ላይ አስተዳዳሪዎች አድርጎ ሾማቸው። ዳንኤል ግን በንጉሡ ቤተ መንግሥት ተቀመጠ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Daniel 2:1

በሁለተኛው ዓመት
“ሁለተኛው ዓመቱ ላይ ”

ሕልም አለመ
ናቡከደነፆር ሕልም አየ

መንፈሱም ታወከ
እዚህ ላይ “መንፈሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሃሣቡን ነው።“በሃሣቡ ታወከ”

እንቅልፍም ከእርሱ ራቀ
ለጭንቀት የዳረገው ሃሣብ እንቅልፍ ሊያስተኛው አልቻለም።“እንቅልፍ እንዳይተኛ አደረገው”

ከዚያም ንጉሡ መተተኞችን ጠራ
“ከዚያም ንጉሡ ጠንቋዬዮችን ጠራ”

ሙታን
“ሕይወት የሌላቸው ሰዎች”

ወደ ውስጥ ገቡ
“ወደ ቤተመንግሥት ገቡ”

ፊት ቆሙ
“በ….. ፊት ቆሙ”

Daniel 2:3

መንፈሴ ታውኳል
እዚህ ላይ“መንፈሴ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ራሱን ንጉሡን ነው።“ተጨንቄለሁ”

መታወክ
መጨነቅ

አረማይክ
ይሄ ባቢሎናውያን ይነጋገሩበት የነበረ ቋንቋ ነው።

ንጉሥ ሆይ ሺህ ዓመት ንገስ
ሰዎቹ ይሄንን የተናገሩት ለንጉሡ ታማኞች መሆናቸውን ለመግለፅ አስበው ይሆናል።“ንጉሥ ሆይ ለዘላለም እንደምትኖር ተስፋ አለን”

እኛ፤የእርስዎ ባሪያዎች
ሰዎቹ አክብሮትን ለመስጠት ራሣቸውን የንጉሡ ባሪያዎች ብለው ይጠራሉ።

እኛ እናሣያለን
እዚህ ላይ “እኛ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ንጉሡ እያነጋገራቸው ያሉትን ሰዎች ሲሆን ንጉሡን ግን አያካትትም።

Daniel 2:5

ይሄ ጉዳይ ውሳኔ ተሰጥቶበታል
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ይህንን ጉዳይ በሚመለከት ምን መደረግ እንዳለበት ውሳኔ ላይ ደርሼያለሁ”

ትቆረጣላችሁ ቤቶቻችሁም የጉድፍ መጣያ ይሆናሉ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሰውነታችሁን እንዲበጣጥሱትና ቤታችሁንም የቆሻሻ ክምር እንዲደርጉት ወታደሮቼን አዝዛለሁ”

ከእኔ ዘንድ ሽልማትን ታገኛላችሁ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሥጦታን እሰጣችኋለሁ”

Daniel 2:7

ንጉሡ ይንገረን
እነዚህ ጥበበኛ የሆኑ ሰዎች አክብሮታቸውን ለመግለፅ ንግግራቸውን ለሶስተኛ መደብ እንደሚነገር አደርገው ይናገሩታል።

ይህንን ጉዳይ በሚመለከት ውሳኔ ምን ያህል ጠንካራ እንደሆነ አያችሁ
ሊለወጥ የማይችል ውሳኔ ጠንካራ እንደሆነ ተደርጎ ተገልፆአል።

ይህንን በተመለከተ ውሳኔዬን እንደማልለውጥ አያችሁ
ለእናንተ አንድ ቅጣት ብቻ ነው ያለው

የሐሰትና የተንኮል ቃላት
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሳሳይ የሆነ ተርጉም ያላቸው ሲሆን የንጉሱ ሥልጣን ታላቅ እንደሆነ አፅንዖት የሚሰጡ ናቸው።”ለማታለል የታቀዱ ውሸቶች”

Daniel 2:10

ታላቅና ኃያል
እነዚህ ሁለት ቃላት በመሠረቱ አንድ ዓይነት ትርጉም ያላቸው ሲሆን አፅንዖት የሚሰጡትም የንጉሡ ኃይል ታላቅ መሆኑን ነው።“እጅግ ኃያል”

ከአማልዕክት በስተቀር ለንጉሡ ሊናገር የሚችል ማንም የለም
ይሄ አፅንዖትን ለመስጠት ሲባል በአሉታዊ መልኩ ነው የተገለፀው።በአዎንታዊ መልኩም ሊገለፅ ይችላል።“ይህንን ጉዳይ መናገር የሚችሉት አማልዕክት ብቻ ናቸው።”

Daniel 2:12

ተበሳጨ እጅግም ተቆጣ
በመሠረቱ እነዚህ ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ቁጣውን ለመግለፅ ጥቅም ላይ የዋሉ ናቸው።“ከልክ ያለፈ ብስጭት”

በባቢሎን የሚገኙ ሁሉ
“በባቢሎን ያሉ ሰዎች ሁሉ”

ስለሆነም አዋጁ ወጣ
አዋጁ ልክ ሕይወት ያለው ነገር እንደሆነና በራሱ የመጓዝ ችሎታ እንዳለው ዓይነት ተደርጎ ነው የተገለፀው።“ስለሆነም ንጉሡ ትዕዛዝ እንዲወጣ ውሳኔ ላይ ደረሰ”ወይም “ንጉሡ ትዕዛዝ ሰጠ”

ጥበበኞች ናቸው ተብለው የተገመቱ ሰዎች ሁሉ በሞት እንዲቀጡ ተፈረደባቸው
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ወታደሮቹ ጥበበኞች ናቸው ተብለው የተገመቱትን ሰዎች ሁሉ በሕይወት እንዳይኖሩ ሊያደርጓቸው ነው”

ይገደሉ ዘንድ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እንዲገድሏቸው”

Daniel 2:14

በፈሊጥና በማስተዋል
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ስለ አስተዋይነቱ ታላቅነት አፅንዖት የሚሰጡ ናቸው።“ረጋ ያለና ጥንቃቄ የተሞላበት ፍርድ”

አርዮክ
ይሄ የንጉሡ የጦር አዛዥ ሥም ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የዘበኞቹ አለቃ
የእነዚህ ሰዎች ሥራ ንጉሡን መጠበቅ ብቻ ነው።

ለመግደል የወጡት
“ንጉሡ እንዲገድሉ የላካቸው ሰዎች”

ዳንኤል ገባ
ምናልባትም ዳንኤል ወደ ቤተ መንግሥት ሄዶ ሊሆን ይችላል።“ዳንኤል ወደ ቤተ መንግሥቱ ሄደ” ወይም“ዳንኤል ከንጉሡ ጋር ለመነጋገር ሄደ”

ከንጉሡ ጋር ቀጠሮ እንዲሰጠው ጠየቀ
“ከንጉሡ ጋር ለመገናኘት ይችል ዘንድ በተወሰነ ሰዓት ቀጠሮ እንዲሰጠው ጠየቀ”

Daniel 2:17

የእርሱ ቤት
ይሄ የሚመለክተው የዳንኤልን ቤት ነው።

የተከናወነው ነገር
“የንጉሡን አዋጅ በተመለከተ”

ምሕረትን እንዲለምኑ ጠየቃቸው
“ስለ ምሕረት እንዲፀልዩ ጠየቃቸው”

እርሱና እነርሱ ከሞት ያመልጡ ዘንድ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ንጉሡ እንዳይገድላቸው”ወይም “የንጉሡ ወታደሮች እንዳይገድሏቸው”

Daniel 2:19

ምሥጢሩ ሌሊት ተገለጠለት
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በዚያን ሌሊት እግዚአብሔር ምሥጢሩን ገለፀው”

ምሥጢሩ
ይሄ የሚያመለከተው የንጉሡን ሕልምና ትርጉሙን ነው።

የእግዚአብሔርን ሥም አመሰገነ
እዚህ ላይ “ሥም” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ራሱን እግዚአብሔርን ነው።“እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን”

Daniel 2:21

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ጥቅሶች የዳንኤል ፀሎት አንዱ ክፍል ናቸው።

ነገሥታትን ያስወግዳል
“የነገሥታትን የመግዛት ሥልጣን ይነጥቃል” እዚህ ላይ“ዙፋን”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በአንድ ግዛት ላይ የበላይ ሆኖ መግዛትን ነው።

ብርሃንም ከእርሱ ጋር ነው
“ብርሃኑ የሚመጣው እግዚአብሔር ካለበት ሥፍራ ነው”

Daniel 2:23

አጠቃላይ መረጃ
ይሄኛው ጥቅስም የዳንኤል የፀሎቱ አንዱ ክፍል ነው።እግዚአብሔርን በሦስተኛ መደብነት መጥራቱን ያቆምና በጣም ግላዊ ወደ ሆነው ወደ ሁለተኛ መደብ ይለውጣል።

እኛም የለመንህን ነገር አሁን ያሰታወቅኸኝ
“አንተእኔና ጓደኞቼን የጠየቅከንን ነገር ነገረን ”

ንጉሡን ያስጨነቀው ነገር ምን እንደሆነ ግልፅ ሆነልን
“ንጉሡ ምን እንደሚፈልግ አስታወቀን”

Daniel 2:24

አርዮክ
ይሄ የንጉሡ የጦር አዛዡ ሥም ነው።

ጥበበኛ የሆነ ሰው ሁሉ
“ጠቢባን”

Daniel 2:25

ብልጣሶር
ይሄ ባቢሎናውያን ለዳንኤል የሰጡት ሥም ነው።

Daniel 2:27

ንጉሡ የጠየቀውንም ምሥጢር ... በአስማተኞ አይደለም
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ጥበበኛ የሆኑ ሰዎች፤ከሙታን ጋር እንነጋገራለን የሚሉ ሰዎች፤ጠንቋዮችና አስማተኞች ከንጉሡ ዘንድ የተጠየቀውን ጥያቄ ለማወቅ አልቻሉም ”

ንጉሡ የጠየቀውንም ምሥጢር
ይሄ ሐረግ የሚያመለክተው የንጉሡን ሕልም ነው።

Daniel 2:29

አጠቃላይ መረጃ
ዳንኤል ለንጉሡ መናገሩን ይቀጥላል።

ምሥጢርን የሚገልፅ እርሱ
ይሄ ሐረግ የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው።“ምሥጢርን የሚገልፀው እግዚአብሔር” ወይም “ምሥጢራት እንዲታወቁ የሚያደርግ እግዚአብሔር”

ይሄ ምሥጢር ለእኔ አልተገለፀልኝም
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ይሄንን ምሥጢር እግዚአብሔር ለእኔ አልገለፀውም”

ምሥጢሩ ለእኔ የተገለፀልኝ አንተ ....
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ምሥጢሩን ለእኔ ግልፅ ያደረገልኝ አንተ....”

የልብህን ሃሣብ ታወቅ ዘንድ
ይሄ ሐረግ “አንተ” የሚለውን ቃል የሚጠቀመው የሰውዬውን አዕምሮ ለማመልከት ነው።“በውስጠኛው አዕምሮህ ያለውን ነገር ያውቅ ዘንድ”

Daniel 2:31

አጠቃላይ መረጃ
ዳንኤል ለንጉሡ መናገሩን ይቀጥላል።

ከጥሩ ወርቅ የተሰራ ነበር
“ከጥሩ ወርቅ የተሰራ ነበር”ወይም “ንፁህ ወርቅ ነበር”

ግማሹ ከብረት ግማሹ ደግሞ ከሸክላ የተሰራ ነበር
“ገሚሱ ብረት ገሚሱ ደግሞ ሸክላ ነበር”ወይም “ከፊሉ ከብረት ከፊሉ ደግሞ ከሸክላ ነበሩ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Daniel 2:34

አጠቃላይ መረጃ
ዳንኤል ለንጉሡ መናገሩን ይቀጥላል።

እጅም ሳይነካው ድንጋይ ተፈንቅሎ
ይሄ ወደ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች የሚከፈል ከሆነ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“አንድ ሰው ከተራራ ድንጋይ ይፈነቅላል ሆኖም ይህንን የፈነቀለው የሰው ልጆች አልነበሩም።ድንጋዩን”

በመከር ጊዘ በአውድማ ላይ እንዳለ
ይሄ ሐረግ የምሥሉን ቁርጥራጮች በቀላሉ በነፋስ እንደሚበንኑ ትናንሽና ቀላል ነገሮች ያስመስላቸዋል።

የት እንዳሉ እንኳን አልታወቀም
ይሄ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል።“ፈፅሞ ተወገዱ”

ምድርንም ፈፅሞ ሞላ
“በምድሪቱ ውስጥ ሁሉ ተሰራጨ”

Daniel 2:36

አጠቃላይ መረጃ
ዳንኤል ለንጉሡ መናገሩን ይቀጥላል

አሁንም በንጉሡ ፊት እንናገራለን
እዚህ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ዳንኤልን ነው። ምናልባትም የብዙ ቁጥርን የተጠቀመው ለራሱ ላለማድላት ሲልና እግዚአብሔር የገለፀለትን የሕልሙን ትርጉም ስላሳወቀ ከትህትና የተነሣ ያደረገውም ሊሆን ይችላል።

የነገሥታት ንጉሥ
“እጅግ ተፈላጊ የሆነ ንጉሥ” ወይም “በሌሎች ንጉሶች ላይ ገዢ የሆነ ንጉሥ”

ኃይሉ፤ብርታቱ
እነዚህ ቃላት በመሠረቱ ተመሳሳይ ሆነ ትርጉም ነው ያላቸው።

ሥፍራውን ሁሉ በእጅህ አሣልፎ ሰጥቷል
እዚህ ላይ“እጅ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው መግዛትን ነው።“ሥፍራውን በቁጥጥራችሁ ሥር እንድታደርጉ አድርጓችኋል።”

የሰው ልጆች የሚቀመጡበት ሥፍራ
ሥፍራው የሚያመለክተው በዚያ ሥፍራ ነዋሪ የሆኑ ሰዎችን ነው።“የምድሪቱ ሰዎች”

እንስሳትን በእጅህ አሣልፎ ሰጥቷል
እዚህ ላይ“እጅ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው መግዛትን ነው።“በሜዳ ላይ በሚገኙ እንሥሳትና የሰማይ ወፎች ላይ እንድትገዟቸው አሣልፎ ሰጥቷችኋል።”

የሰማይ አዕዋፍ
እዚህ ላይ“የሰማይ”የሚለው ሃሣብ “ሰማያት” የሚለውን ቃል ለመወከል የዋለ ነው።

አንተ የወርቁ ራስ ነህ
በንጉሡ ሕልም ውስጥ የምስሉ ራስ የሚወክለው ንጉሡን ነው።“የወርቅ ምሥሉ የሚወክለው አንተን ነው” ወይም “የወርቁ ራስ የአንተና የሥልጣንህ ምልክት ነው”

Daniel 2:39

አጠቃላይ መረጃ
ዳንኤል ለንጉሡ መናገሩን ይቀጥላል

ሌላ መንግሥት ይነሣል
በንጉሡ ሕልም መሠረት እርሱ መንግሥት ወርቅ ስለሆነ ከእርሱ አነስ የሚለው መንግሥት ደግሞ የመሐስ መንግሥት ነው ማለት ነው።“ሌላ የነሐስ የሆነ መንግሥት ይነሳል” ወይም “የምሥሉን ክፍሎች የሚወክል ሌላ የብር መንግሥት ይነሣል”

ሌላም ሶስተኛ የነሐስ መንግሥት
ይሄ ወደፊት ሊመጣ ያለውን የነሐሱን የሐውልት ክፍሎች የሚገልፅ ምሣሌያዊ አገላለፅ ነው።“ገና በሐውልቱ ክፍሎችን የሚወክል ሶስተኛ መንግሥት”

ሶስተኛ መንግሥት
“መንግሥት ቁጥር ሶስት”

Daniel 2:40

አጠቃላይ መረጃ
ዳንኤል ለንጉሡ መናገሩን ይቀጥላል

አራተኛ መንግሥት ይመጣል
“መንግሥት ቁጥር አራት ይመጣል”

እንደ ብረት ጠንካራ
አራተኛው መንግሥት እንደ ብረት ጠንካራ እንደሆነ ተደርጎ ነው የተገለፀው።

እነዚህን ነገሮች ይቀጠቅጣቸዋል፤ይፈጫቸዋልም
ይሄ ምሣሌያዊ አነጋገር አራተኛው መንግሥት ድል እንደሚያደርግና ሌሎች መንግሥታትን እንደሚተካ የሚያሣይ ነው።

እነዚህ ነገሮች ሁሉ
“የቀደሙት መንግሥታት”

Daniel 2:41

አጠቃላይ መረጃ
ዳንኤል ለንጉሡ መናገሩን ይቀጥላል።

እንዳየህ
ናቡከደነፆር እግሩ የብረትና የሸክላ እንደሆነ ተመልክቷል።እግሩ በተሰራበት ወቅት ግን ሒደቱን አልተመለከተም።

ከፊሉ ከተደባለቀ ሸክላና ከፊሉ ደግሞ ከብረት የተሰራ ነበር
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የሸክላና የብረት ድብልቅ ነበሩ።

በአንድነት አይኖሩም
“ተጣብቀው አይቆዩም”

Daniel 2:44

አጠቃላይ መረጃ
ዳንኤል ለንጉሡ መናገሩን ይቀጥላል።

በእነዚያ ነገሥታት ዘመን
እዚህ ላይ“እነዚያ ነገሥታት”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በምሥሉ የጠተለያዩ ክፍሎች በተምሣሌነት የቀረቡትን የመንግሥታት ገዢዎችን ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የማይፈርስ መንግሥትና ለሌላ ሕዝብ የማይሰጡ ይሆኑ ዘንድ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ማንም ሰው እንዳያጠፋቸውና ሌሎች ሰዎች እንዳያሸንፏቸው”

ድንጋዩ ከተራራው የተፈነቀለው ሰው እጅ ሣይነካው ነው
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የሆነ ነገር ድንጋዩን ከተራራው ላይ የፈነቀለው ቢሆንም የተፈነቀለው ግን የሰው እጅ ሳይነካው ነው።”

የታመነ ነው
እምነት ሊጣልበት የሚችልና ትክክለኛ “በፊቱ መሬት ላይ ወደቀ”

Daniel 2:46

በግንባሩ ተደፋ
ይሄ ድርጊታዊ ተምሣሌት የሚያመለክተው ንጉሡ ዳንኤልን ማክበሩን ነው።

የእህሉንም ቁርባን ዕጣኑንም ያቀርቡለት ዘንድ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የንጉሡ ባሪዎች ለዳንኤል የእህል ቁርባንና ዕጣን አቀረቡለት”

በእውነት አምላካችሁ
“እውነትም አምላካችሁ”

የአማልዕክት አምላክ፤የነገሥታት ንጉሥ
“ከአማልዕክት ሁሉ የበለጠና በሌሎች ነገሥታት ላይ ንጉሥ የሆነ”

ይህንን ምሥጢር የሚገልፅ
“የሕልሜን ምሥጢር ገላጭ”

Daniel 2:48

ከፍ ከፍ አደረገው
“ንጉሡ ዳንኤልን ገዢ አደረገው”

ሲድራቅ...ሚሳቅ...አብደናጎም
እነዚህ ከዳንኤል ጋር ወደ ባሊሎን ለሄዱት ለሶስት አይሁዳውያን የተሰጠ የባቢሎናውያን ሥያሜ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 ንጉሡ ናቡከደነፆር ርዝመቱ ስድሳ ክንድ ስፋቱ ስድስት ክንድ የሆነ የወርቅ ምስል አሠራ። በባቢሎንም ክፍለ አገር በዱራ ሜዳ አቆመው። 2 ከዚያም
ናቡከደነፆር አማካሪዎችን፥ የግምጃ ቤት ኃላፊዎችን፥ ዳኞችን፥ የአጥቢያ ፈራጆችንና የክፍላተ አገር ከፍተኛ ባለ ሥልጣናትን ሁሉ ጨምሮ የክፍለ አገር
አስተዳዳሪዎች፥ የክልል አስተዳዳሪዎችና የአካባቢ አስተዳዳሪዎች ላቆመው ምስል ምረቃ እንዲመጡ፥ በአንድ ላይ እንዲሰበሰቡ መልእክት ላከ። 3 በዚያን
ጊዜም አማካሪዎችን፥ የግምጃ ቤት ኃላፊዎችን፥ ዳኞችን፥ የአጥቢያ ፈራጆችንና የክፍላተ አገር ከፍተኛ ባለ ሥልጣናትን ጨምሮ የክፍለ አገር አስተዳዳሪዎች፥
የክልል አስተዳዳሪዎችና የአካባቢ አስተዳዳሪዎች ናቡከደነፆር ላቆመው ምስል ምረቃ በአንድነት ተሰበሰቡ። በፊቱም ቆሙ። 4 ከዚያም አዋጅ ነጋሪ እየጮኸ
እንዲህ አለ፦ «አሕዛብ፥ መንግሥታትና ልዩ ልዩ ቋንቋ የምትናገሩ ሁሉ፥ 5 የመለከትና የእንቢልታ፥ የመሰንቆና የክራር፥ የበገናና የዋሽንት፥ የዘፈንም ሁሉ ድምፅ
በሰማችሁ ጊዜ ንጉሥ ናቡከደነፆር ላቆመው የወርቅ ምስል ወድቃችሁ እንድትሰግዱ ታዝዛችኋል። 6 ማንም የማይወድቅና የማይሰግድ፥ በዚያው ጊዜ
በሚንቦገቦገው የእሳት እቶን ውስጥ ይጣላል።» 7 ስለዚህም አሕዛብ ሁሉ የመለከቱንና የእንቢልታውን፥ የመሰንቆውንና የክራሩን፥ የበገናውንና የዋሽንቱን፥
የዘፈኑንም ሁሉ ድምፅ በሰሙ ጊዜ አሕዛብ ሁሉ፥ መንግሥታትና ልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገሩ ሁሉ ንጉሡ ናቡከደነፆር ላቆመው የወርቅ ምስል ወድቀው ሰገዱ። 8
በዚህ ጊዜም አንዳንድ ከለዳውያን መጥተው አይሁድን ከሰሱ። 9 ለንጉሡ ናቡከደነፆርም እንዲህ አሉ፦ «ንጉሥ ሆይ ለዘላለም ኑር! 10 ንጉሥ ሆይ፥አንተ
የመለከቱንና የእንቢልታውን፥ የመሰንቆውንና የክራሩን፥ የበገናውንና የዋሽንቱን፥ የዘፈኑንም ሁሉ ድምፅ የሰማ ማንኛውም ሰው ለወርቁ ምስል እንዲውድቅና
እንዲሰግድ ትዕዛዝ አውጥተህ ነበር። 11 ማንም ያልወደቀና ያላመለከ በሚንቦገቦገው የእሳት እቶን ውስጥ ሊጣል ይገባዋል። 12 አሁን ግን በባቢሎን ክፍለ
አገር ጉዳይ ላይ የሾምካቸው፥ ሲድራቅ፥ ሚሳቅና አብድናጎ የሚባሉ አንዳንድ አይሁድ አሉ። ንጉሥ ሆይ፥ እነዚህ ሰዎች አንተን ከምንም አይቆጥሩም።
አማልክትህን አያመልኩም፥ አያገለግሉምም ወይም ላቆምከው የወርቁ ምስል አይሰግዱም።» 13 በዚያን ጊዜም ናቡከደነፆር በቁጣና በብስጭት ተሞላ፤
ሲድራቅን፥ ሚሳቅንና አብድናጎን ወደ እርሱ እንዲያመጡአቸው አዘዘ። ስለዚህም እነዚህን ሰዎች ወደ ንጉሡ ፊት አመጡአቸው። 14 ናቡከደነፆርም
አላቸው፦«ሲድራቅ፥ ሚሳቅና አብድናጎ አማልክቴን አለማምለካችሁ ወይም ላቆምኩት የወርቅ ምስል አለመስገዳችሁ እውነት ነውን? 15 አሁንም የመለከቱንና
የእንቢልታውን፥የመሰንቆውንና የክራሩን፥ የበገናውንና የዋሽንቱን፥ የዘፈኑንም ድምፅ ሁሉ በሰማችሁ ጊዜ ለመውደቅ እና ላሠራሁት ምስል ለመስገድ ዝግጅዎች
ከሆናችሁ ሁሉም መልካም ይሆናል። ካላመለካችሁ ግን ወዲያው ወደ ሚንቦገቦገው የእሳት እቶን ትጣላላችሁ። ከእጄስ ሊያድናችሁ የሚችል አምላክ ማነው?»
16 ሲድራቅ፥ሚሳቅና አብድናጎም ለንጉሡ እንዲህ ሲሉ መለሱ፦«ናቡከደነፆር ሆይ በዚህ ጉዳይ መልስ ልንሰጥህ አያስፈልገንም። 17 መልስ መስጠት
የሚገባን ከሆነ፥ የምናገለግለው አምላካችን ከሚንቦገቦገው የእሳት እቶን ሊያድነን ይችላል፥ ንጉሥ ሆይ፥ ከእጅህም ያድነናል። 18 ነገር ግን ንጉሥ ሆይ ባያድነን
እንኳን፥አማልክትህን እንደማናመልክና ላቆምከውም የወርቅ ምስል እንደማንሰግድ በአንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን። 19 በዚያን ጊዜ ናቡከደነፆር በቁጣ ተሞላ፤
በሲድራቅ፥ በሚሳቅና በአብድናጎ ላይ ፊቱ ተለወጠባቸው። የእቶኑ እሳት ብዙውን ጊዜ ይነድድ ከነበረው ይልቅ ሰባት እጥፍ እንዲነድድ አዘዘ። 20 ከዚያም
ከሠራዊቱ ጥቂት በጣም ብርቱ ሰዎችን፥ ሲድራቅን፥ሚሳቅንና አብድናጎን አሥረው ወደ ሚንቦገቦገው የእቶኑ እሳት እንዲጥሉአችው አዘዘ። 21 እነርሱም
መጎናጸፊያቸውን፥ ቀሚሳቸውን፥ ጥምጥማቸውንና ሌሎች ልብሶቻቸውን እንደ ለበሱ ታስረው ወደ ሚንቦገቦገው የእቶን እሳት ተጣሉ። 22 የንጉሡ ትእዛዝ
ጥብቅ ስለነበረና የእቶኑ እሳት እጅግ ነዶ ስለነበረ፥ ሲድራቅን፥ ሚሳቅንና አብድናጎን የወሰዱአቸውን ሰዎች ነበልባሉ ገደላቸው። 23 እነዚህ ሦሥት ሰዎች እንደ
ታሰሩ በሚንቦገቦገው የእቶን እሳት ውስጥ ወደቁ። 24 ከዚያም ንጉሡ ናቡከደነፆር ተደነቀ፥ ፈጥኖም ተነሣ። አማካሪዎቹንም፦ «ሦሥት ሰዎችን አስረን እሳት
ውስጥ ጥለን አልነበረምን?» ሲል ጠየቃቸው። እነርሱም ለንጉሡ፦ «ንጉሥ ሆይ እርግጥ ነው» ብለው መለሱ። 25 እርሱም፦ «እኔ ግን ያልታሰሩ አራት ሰዎች
በእሳት ውስጥ ሲመላለሱ አያልሁ፥ጉዳትም አላገኛቸውም። የአራተኛው ማንጸባረቅ የአማልክትን ልጅ ይመስላል።» አለ። 26 ከዚያም ናቡከደነፆር ወደ እሳቱ
እቶን በር ቀረቦ፦ «የልዑል አምላክ ባሪያዎች ሲድራቅ፥ ሚሳቅና አብድናጎ ኑ ውጡ! ወደዚህ ኑ!» ብሎ ተጣራ። በዚያን ጊዜም ሲድራቅ፥ ሚሳቅና አብድናጎ
ከእሳቱ ውስጥ ወጡ። 27 በአንድነት የተሰበሰቡት የክፍላተ አገር አስተዳዳሪዎች፥ የክልል አስተዳዳሪዎች፥ ሌሎች አስተዳዳሪዎችና የንጉሡ አማካሪዎች
እነዚህን ሰዎች ተመለከቱ። እሳቱ ሰውነታቸውን አልጎዳውም፥ የራሳቸው ጸጉር አልተቃጠለም፥ መጎናጸፊያቸው አልተጎዳም፥ የእሳቱም ሽታ በላያቸው አልነበረም።
28 ናቡከደነፆርም እንዲህ አለ፦«መልአኩን የላከውንና ለአገልጋዮቹ መልእክቱን የሰጠውን የሲድራቅን፥የሚሳቅንና የአብድናጎን አምላክ እናመስግን። በእርሱ
በመታመን ትእዛዜን ችላ ብለዋል፥ ከአምላካቸውም ሌላ ማንኛውንም ሌላ አምላክ ከማምለክ ወይም ለእርሱ ከመስገድ ይልቅ ሰውነ ታቸውን አሳልፈው
መስጠትን መርጠዋል። 29 ስለዚህ እንደዚህ የሚያድን ሌላ አምላክ የለምና፥በሲድራቅ፥ሚሳቅና አብድናጎ አምላክ ላይ ክፉ የሚናገር ማንኛውም ሕዝብ፥አገር
ወይም ልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገሩ ይቆራረጣሉ፥ቤቶቻቸውም የቆሻሻ ክምር ይሆናሉ ብዬ አዝዤአለሁ። 30 ከዚያም ንጉሡ ሲድራቅን፥ ሚሳቅንና አብድናጎን
በባቢሎን አውራጃ ሾማቸው።

Daniel 3:1

ናቡከደነፆር የወርቅ ምሥል አሰራና አቆመው
ናቡከደነፆር ይህንን ሥራ ያከናወነው ራሱ ሣይሆን የራሱ ሰዎች ሥራውን እንዲያከናውኑ በማዘዝ ነበር።“ናቡከደነፆር የወርቅ ምሥሉን እንዲሰሩ የራሱን ሰዎች አዘዘ….እንዲቆም አደረጉት”

ቁመቱ ስድሳ ክንድ፤ወርዱም ስድስት ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሴንቲ ሜትር ነው።“በግምት 27 ሜትር ቁመት ያለውና ወደ 3 ሜትር የሚጠጋ ስፋት ያለው ነው“

የዱራ ሜዳ
ይሄ ሥፍራ የሚገኘው በባቢሎን የወሰን ክልል ውስጥ ነው።

መኳንንት... ሹማምንቶች...አዛዦች
እነዚህ በግዛቱ ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ የተመደቡ ሰዎች ናቸው።

በጅሮንዶች
እኒዚህ ባለሥልጣናት ኃላፊነታቸው ከገንዘብ ጋር የተያያዘ ነው።

Daniel 3:3

የአውራጃ ገዢዎች፤የክልል አዛዦች...አውራጃ ገዢዎች
በትንቢተ ዳንኤል 3፡1 ላይ እንዴት አድርጋችሁ እንደተረጎማችሁት አስተውሉ።

ናቡከደነፆር ያቆመው ምሥል
ናቡከደነፆር ይህንን ሥራ ያከናወነው ራሱ ሣይሆን የራሱን ሰዎች ሥራውን እንዲከናውኑት በማዘዝ ነበር።“የናቡከደነፆር ሰዎች ያቆሙት ምሥል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አዋጅ ነጋሪ
ይሄ ሰው ይህንን ሥራ እንዲሰራ ኃላፊነት የተሰጠው ለንጉሡ አዋጅ ነጋሪ ነው።

ታዝዛችኋል
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በንጉሡ ታዝዛችኋል።”

ወገኖች፤አህዛብና በልዩ ልዩ ቋንቋዎች የምትናገሩ
እዚህ ላይ “ወገኖች”እና “ቋንቋዎች”የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ከተለያዩ ወገኖች የመጡትንና የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ሰዎችን ነው።“የተለያዩ ቋንቋዎች የሚናገሩና ከተለያዩ ነገዶች የመጡ ሰዎች”

እምቢልታ
እነዚህ የሙዚቃ መሣሪያዎች ከበገና ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ናቸው።ሶስት ማዕዘን የሚመስል ቅርፅ ያላቸው ሆነው አራት ክሮች ያሏቸው ናቸው።

ስገዱ
እዚህ ላይ “ስገዱ” ማለት “መሬት ላይ ተኙ”ማለት ነው።

እንድትደፉ
“በአምልኮ ውስጥ በመሆን ፊታችሁን ወደ ታች አድርጋችሁ መሬት ላይ ተኙ”

Daniel 3:6

ተደፍቶም የማይሰግድ በሚነድ እሳት ውስጥ ይጣላል
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የሙዚቃ መሣሪያውን ድምፅ በተሰማበት ወቅት ተደፍቶ ለምሥሉ የማይሰግድ ሰው ሁሉ በወታደሮች አማካይነት ወደሚነድድ እሣት ይጣላል።“

ተደፉ
እዚህ ላይ “ስትደፉ” ማለት “በፍጥነት ተኙ”ማለት ነው።

የሚነድድ እቶን
ይሄ በእሣት የተሞላ ሠፊ ክፍልን የሚያመለክት ነው።

ወገኖች፤አህዛብና በልዩ ልዩ ቋንቋዎች የምትናገሩ ሁሉ
እዚህ ላይ“ሁሉ“ማለት በሥፍራው የተገኙት ሰዎች ሁሉ ማለት ነው።

ወገኖች፤አህዛብና በልዩ ልዩ ቋንቋዎች የምትናገሩ
እዚህ ላይ “ወገኖች”እና “ቋንቋዎች”የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ከተለያዩ ወገኖች የመጡትንና የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ሰዎችን ነው።ይሄንን በትንቢተ ዳንኤል 3፤4 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት አስተውሉ።“የተለያዩ ነገድ ሰዎችና የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ“

የመለከት...የዋሽንት...የእንቢልታ
እነዚህ የሙዚቃ መሣሪያዎች ናቸው።

ወደቁ
እዚህ ላይ “ስተደፉ” ማለት “በፍጥነት ተኙ”ማለት ነው።

ተደፉ...
ይህንን ያደረጉት ምሥሉን ለማምለክ ሲሉ ነው።“ፊታቸውን ወደ ምድር አድርገው ለአምልኮ ተደፉ“

ንጉሥ ናቡከደነፆር ያቆመው የወርቅ ምሥል
ናቡከደነፆር ይህንን ሥራ ያከናወነው ራሱ ሣይሆን የራሱን ሰዎች ሥራውን እንዲከናውኑለት በማዘዝ ነበር።“ሰዎች ያቆሙት የናቡከደነፆር የወርቅ ምሥል“

Daniel 3:8

አሁንም
ይሄ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው ከዋናው ታሪክ መውጣቱን ለማመልከት ነው። እዚህ ላይ ፀሐፊው በታሪኩ ውስጥ ስለ ጥቂት አዳዲስ ሰዎች ይናገራል።

ንጉሥ ሆይ ሺህ ዓመት ንገሥ
ይሄ ለንጉሡ የተለመደ የሠላምታ አሰጣጥ ሥርዓት ነው።

የመለከት...የዋሽንት...የእንቢልታ
እነዚህ የሙዚቃ መሣሪያዎች ሥሞች ናቸው።ይህንን በትንቢተ ዳንኤል 3፤5 ላይ እንዴት አድርጋችሁ አንደተረጎማችሁት አስተውሉ።

ተደፉ
እዚህ ላይ“ተደፉ“የሚለው ቃል “በፍጥነት መጋደምን“ የሚያመለክት ነው።

የሚነድድ እቶን
ይሄ በእሣት የተሞላ ሠፊ ክፍል ነው።ይህንን በትንቢተ ዳንኤል 3፤6 ላይ እንዴት አድርጋችሁ አንደተረጎማችሁት አስተውሉ።

ጉዳዮች
ከመንግሥት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች

ሲድራቅ...ሚሣቅ..... አብደናጎም
እነዚህ የዳንኤል ጓደኞች የሆኑ ሰዎች የባቢሎናውያን ስሞች ናቸው።እነዚህን በትንቢተ ዳንኤል 3፤7 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት አስተውሉ።

ትዕዛዝህን እምቢ ብለዋል
“ትዕዛዝህን ለመቀበል ፈቃደኞች አይደሉም”

ተደፍቶ መስገድ
ይህንን የሚያደርጉበት ምክኒያት ለምሥሉ ለመስገድ ሲሉ ነው።“በአምልኮ ውስጥ ሆነው ፊታቸውን ወደ መሬት አድርገው ተደፉ”

አንተ ያቆምከው የወርቅ ምሥል
ናቡከደነፆር ይህንን ሥራ እንዲሰሩ የራሱን ሰዎች አዘዘ።“የአንተ ሰዎች ያቆሙት የወርቁ ምሥል”

Daniel 3:13

በብስጭትና በቁጣ ተሞላ
የናቡከደነፆር ብስጭትና ቁጣ እጅግ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሣ ልክእ በሆነ ነገር እንደሞሉት ዓይነት ተደርጎ ተገልፆአል።“ብስጭት” እና“ቁጣ” የሚሉት ቃላት ተመሣሣይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን እነዚህ ቃላት ጥቅም ላይ የዋሉት ንጉሡ ምን ያህል እንደታወከ አፅንዖት ለመሥጠት ነው።“ከገደብ ያለፈ ቁጣ”

ሲድራቅ...ሚሣቅ..... አብደናጎም
እነዚህ የዳንኤል ጓደኞች የሆኑ ሰዎች የባቢሎናውያን ስሞች ናቸው።እነዚህን በትንቢተ ዳንኤል 1፤7 ላይ እንደተረጎማችሁት አስተውሉ።

አሁንም ሃሣባችሁን አልለወጣችሁም?
እዚህ ላይ “ሃሣብ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የመወሰንን ጉዳይ ነው።“ሃሣባችሁን አልለወጣችሁም?”ማለት በውሳኔ መሸፅናትን የሚያመለክት ዘይቤያዊ አነጋገር ነው።“በውሳኔያችሁ እንደፀናችሁ ናችሁ?”

ስገዱ
እነዚህ ሶስት ሰዎች ለምሥሉ አምልኮ ለመስጠት ሲሉ ይሄንን ተግባር ለመፈፀም ፈቃደኞች አይደሉም።“ ፊትን ወደ ታች አድርጎ ለአምልኮ መሬት ላይ መደፋት”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እኔ ላቆምኩት የወርቁ ምሥል
ናቡከደነፆር ይህንን ሥራ ያከናወነው ራሱ ሣይሆን የራሱን ሰዎች ሥራውን እንዲከናውኑለት በማዘዝ ነበር።“የእኔ ሰዎች ያቆሙት የወርቅ ምሥል”

Daniel 3:15

እንቢልታ...በገና....ዋሽንት
እነዚህ የሙዚቃ መሣሪያዎች ናቸው።እነዚህን በትንቢተ ዳንኤል 3፤5 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት አስተውሉ።

መደፋት
እዚህ ላይ “መደፋት”ማለት“በፍጥነት መጋደም” ነው።

መደፋት
ፊታችሁን ወደ ታች አድርጋችሁ መሬት ላይ ለአምልኮ ተደፉ።

መልካም ይሆናል
“ችግር የሚባል ነገር አይኖርም”ወይም “በነፃነት ትሄዳላችሁ” በነፃ ትለቃቃላችሁ።

እኔ የሠራሁት የወርቁ ምሥል
ናቡከደነፆር ይህንን ሥራ ያከናወነው ራሱ ሣይሆን የራሱን ሰዎች ሥራውን እንዲከናውኑት በማዘዝ ነበር።“የእኔ ሰዎች ያቆሙት የወርቅ ምሥል”

በፍጥነት በሚነድድ እሣት ውስጥ ትጣላላችሁ
ይሄ በገቢር መልክ ለገለፅ ይችላል።“ወታደሮቼ ከመቅፅበት ወደሚነድድ እሣት ውስጥ ይጥሏችኋል።”

የሚነድድ እሣት
ይሄ በእሣት የተሞላ ሠፊ ቦታን የሚያመለክት ነው።ይህንን በትንቢተ ዳንኤል 3፤6 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት አስተውሉ።

አምላክ ማን ነው?...የእኔ እጆች
ንጉሡ መልስ እንዲሰጠው አይጠብቅም።ሶስቱን ሰዎች እያስፈራራቸው ነው።“ከእኔ እጅ የሚያድናችሁ አምላክ የለም” እዚህ ላይ“እጅ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የመቅጣት ብቃት ያለው ሥልጣንን ነው።“ከእኔ ቅጣት”

Daniel 3:16

የሚነድድ እሣት
ይሄ በእሣት የተሞላ ሠፊ ቦታን የሚያመለክት ነው።ይህንን በትንቢተ ዳንኤል 3፤6 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት አስተውሉ።

ከአንተ እጅ
እዚህ ላይ“እጅ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የመቅጣት ብቃት ያለው ሥልጣንን ነው።“ከአንተ ቅጣት”

ባያድነን እንኳን በንጉሡ ዘንድ የታወቀ ይሁን
“ንጉሥ ሆይ አምላካችን ባያድነን እንኳን”

ለምሥሉ እንዳንሰግድለት
ሰዎች አማልዕክቶቻቸውን ለማምለክ እንደዚህ ያደርጋሉ።“በአምልኮ ሥርዓት ፊታችንን ወደ ታች አድርገን ራሣችንን መሬት ላይ መጣል”

አንተ ያቆምከው የወርቅ ምሥል
ናቡከደነፆር ይህንን ሥራ ያከናወነው ራሱ ሣይሆን የራሱን ሰዎች ሥራውን እንዲከናውኑት በማዘዝ ነበር።“የወርቁን ምሥል ያቆሙት የአንተ ሰዎች”

Daniel 3:19

ናቡከደነፆር ቁፃ ሞላበት
ንጉሡ ከልክ ያለፈ ከመናደዱ የተነሣ ብስጭቱ እርሱን የሚሞላ በሚመስል መልኩ ተገልፆአል።“ናቡከደነፆር ከመጠን ያለፈ ተበሳጭቶ ነበር”

እሣቱን በፊት ከተለመደው ደረጃ በሰባት እጥፍ እንዲያነዱት ትዕዛዝ ሰጠ
እዚህ ላይ “በሰባት እጥፍ”ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙም እጅግ የሚያቃጥል እንዲሆን አድርጉት ማለት ነው።ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ቀድሞ ያደርጉት ከነበረው በተለየ መልኩ እጅግ የሚያቃጥል አድርገው እሣቱን እንዲያነዱት ሰዎቹን አዘዛቸው”

Daniel 3:21

ሰናፊሎች
ሰናፊል ራስ ላይ የሚደረግና ከተጠቀለለ ጨርቅ የሚሰራ ነገር ነው።

የሚያነድድ እቶን
ይሄ በሚያቃጥል እሣት የተሞላ ሠፊ ክፍል ነው።ይህንን በትንቢተ ዳንኤል 3፤6 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

የንጉሡም ትዕዛዝ አስቸኳይ ስለነበረ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ምክኒያቱም ሰዎቹ ንጉሡ ባዘዘው መሠረት ብቻ ያከናወኑ በመሆኑ ነው።”

Daniel 3:24

ሶስት ሰዎች አስረን በእሣት ውስጥ ጥለን አልነበርንምን?
“ሶስት ሰዎች አስረን ወደ እሣት ውስጥ ወርውረናል።ተሳሳትኩ?”

የአራተኛው መልክ የአማልዕክት ልጅ ይመስላል
አማልዕክት መልክ በብርሃን የሚያንፀባርቅ ነው ተብሎ ይታመን ነበር።“አራተኛው የአማልዕክት ልጅ እንደ ብርሃን ያብረቀርቃል”

Daniel 3:26

መሣፍንቱ...ሹማምንቱ...አዛዦቹ
እነዚህ ሰዎች በተለያዩ የሐገሪቱ ግዛቶች ውስጥ ኃላፊነት የነበራቸው ባለሥልጣናት ናቸው።ይህንን በትንቢተ ዳንኤል 3፤2 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

የራሣቸው ፀጉር አልተቃጠለም
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እሣቱ በራሣቸው ላይ የነበረውን ፀጉር ሊያቃጥለው አልቻለም”

አልተለበለበም
“ትንሽ እንኳን አልተቃጠለም”

ልብሳቸው አልተነካም
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እሣቱ ልብሳቸውን ሊጎዳው አልቻለም”

በእነርሱ ላይ የእሣት ሽታ አልነበረም
“እሣት እሣት አይሸቱም ነበር”

Daniel 3:28

ቃሌን የተላለፉ
ንጉሡን አለመታዘዛቸው ልክ በአካል ቀርቧቸው ከእነርሱ ወደዚያ እንደገፉት በሚመሰል መልኩ ተገልፆአል።“ትዕዛዜን ችላ አሉ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሰውነታቸውን አሣልፈው የሰጡ
ይሄ ሐረግ የሚያመለክተው ላመኑበት ነገር ለመሞት ስለወሰኑት ሶስት ሰዎች ነው።“ለመሞት ፈቃደኞች ነበሩ”

በአርሱ የታመኑትን
ሰዎች አማልዕክቶቻቸውን ለማምለክ እንደዚህ ያደርጋሉ።“በአምልኮ ሥርዓት ፊታችንን ወደ ታች አድርገን ራሣችንን መሬት ላይ መጣል”

ከእነርሱ በቀር ሌላ አምላክ
“ከእነርሱ አምላክ በስተቀር ሌላ ዓይነት አምላክ”

Daniel 3:29

ወገን፤ሕዝብ ወይም በልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገሩ ሁሉ ...ይቆረጣሉ፤ቤቶቻቸውም የጉድፍ መጣያ ይሆናሉ
እዚህ ላይ “ወገን” “ሕዝብ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ የተለያዩ ነገዶችን ነው።ይህንን ተመሳሳይ ሐረግ በትንቢተ ዳንኤል 3፤4 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ። “በየትኛውም አገር ያለ ማንኛውም ሕዝብ ወይም ማንኛውንም ዓይነት ቋንቋ የሚናገሩ ሰዎች”

የስድብን ነገር የሚናገር
“ለእግዚአብሔር ክብር የማይሰጥ ቃላት የሚናገሩትን”

ይቆረጣሉ
“ሰውነታቸው እንዲቆረጥ ይደረጋል”

እንደዚህ የሚያድን አምላክ የለምና
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“መፍትሔ ሊሆን የሚችለው የእነርሱ አምላክ ብቻ ነው”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 ከንጉሥ ናቡከደነፆር፥በምድር ሁሉ ለሚኖሩ አሕዛብ፥ መንግሥታትና ልዩ ልዩ ቋንቋ ለሚናገሩ ሁሉ፦ «ሰላማችሁ ይብዛ። 2 ልዑል አምላክ ስላደረገልኝ
ምልክቶችና ድንቆች እነግራችሁ ዘንድ መልካም ሆኖ ታየኝ። 3 ምልክቶቹ እንዴት ታላላቅ ናቸው! ድንቆቹም እንዴት ብርቱዎች ናቸው! መንግሥቱ የዘላለም
መንግሥት ነው፥ ግዛቱም ከትውልድ እስከ ትውልድ ይኖራል። 4 እኔ ናቡከደነፆር በቤቴ ደስ ብሎኝ፥ በቤተ መንግሥቴም በብልጽግና ፍሥሐ እያደረግሁ እኖር
ነበር። 5 ነገር ግን የአስፈራኝን ሕልም አለምሁ፤ ተኝቼም ሳለሁ ያየኋቸው ምስሎችና የአእምሮዬ ራዕዮች አወኩኝ። 6 ስለዚህ ሕልሙን ይተረጉሙልኝ ዘንድ
የባቢሎንን ጠቢባን ሁሉ በፊቴ እንዲያቀርቧቸው ትእዛዝ አወጣሁ። 7 በዚያን ጊዜ አስማተኞች፥ሙታን ሳቢዎች፥ጠቢባንና ኮከብ ቆጣሪዎች መጡ፤ ሕልሙንም
ነገርኳችው፥ ነገር ግን ሊተረጉሙልኝ አልቻሉም። 8 በመጨረሻም፥ እንደ አምላኬ ስም ብልጣሶር ተብሎ የተጠራውና የቅዱሳን አማልክት መንፈስ ያለበት
ዳንኤል ገባ። ሕልሙን ነገርኩት። 9 «የአስማተኞች አለቃ ብልጣሶር ሆይ፦የቅዱሳን አማልክት መንፈስ እንዳለብህና የሚያስችግርህ ምሥጢር እንደሌለ
አውቄአልሁና፤ በሕልሜ ምን እንዳየሁና ትርጉሙ ምን እንደሆነ ንገረኝ አልኩት። 10 በአልጋዬ ላይ ትኝቼ ሳልሁ በአእምሮዬ ያየኋቸው ራዕዮች እነዚህ ነበሩ፦
ተመለከትኩ፥ በምድርም መካከል ዛፍ ነበረ፥ቁመቱም እጅግ ታላቅ ነበረ። 11 ዛፉ አደገ፥በረታም። ጫፉ ሰማይ ደረሰ፥ እስከ መላው ዓለም ዳርቻ ድርስም
ይታይ ነበረ። 12 ቅጠሎቹ ያማሩ፥ ፍሬዎቹም የተት ረፈረፉ ነበሩ፤ ለሁሉ የሚሆን ምግብም በላዩ ነበረበት። የዱር አራዊት ከበታቹ ጥላ አግኝተው ነበር፥
የሰማያት አእዋፍም በቅርንጫፎቹ ይኖሩ ነበር። ሕያዋን ፍጥረታት ሁሉ ከእርሱ ይመገቡ ነበር። 13 በአልጋዬ ላይ ተኝቼ ሳለሁ በአእምሮዬ አየሁ፥ አንድ ቅዱስ
መልእክተኛም ከሰማያት ወረደ። 14 እርሱም ጮኽ፥ እንዲህም አለ፦ ዛፉንና ቅርንጫፎቹን ቁረጡ፥ ቅጠሎቹን አራግፉ፥ ፍሬውንም በትኑ። አራዊቱ ከሥሩ፥
አእዋፍም ከቅርንጫፎቹ ይሸሹ። 15 የሥሮቹን ጉቶ፥ በሜዳው ለምለም ሳር መካከል በብረትና በናስ ማሰሪያ እንደታሰረ በመሬት ውስጥ ተውት። በሰማያት ጠል
ይረስርስ፥ በምድር ዛፎች መካከል ከአራዊት ጋር ይኑር። 16 አእምሮው ከሰው አእምሮ ይለወጥ፥ ሰባት ዓመታትም እስኪያልፉ ድረስ የአውሬ አእምሮ ይሰጠው።
17 በመልእክተኛው በተነገረው አዋጅ ይህ ውሳኔ ሆነ። ልዑሉ በሰዎች መንግሥታት ላይ እንደሚገዛና እነዚህንም መንግሥታት ለተናቁ እጅግ ትሑታን ለሆኑ
ሰዎች እንኳን ሳይቀር፥ ሊያነግሠው ለወደደው ለማንም እንደሚሰጥ ሕያዋን ሁሉ ያውቁ ዘንድ ይህ የቅዱሱ ውሳኔ ነው። 18 እኔ ንጉሡ ናቡከደነፆር ይህን ሕልም
አልሜአለሁ። አሁንም አንተ ብልጣሶር፥ በመንግሥቴ ካሉ ጠቢባን ሰዎች አንዳቸውም ሊተረጉሙልኝ አልቻሉምና ትርጉሙን ንገረኝ። አንተ የቅዱሳን አማልክት
መንፈስ በውስጥህ ስላለ ልትተረጉም ትችላለህ።» 19 በዚያን ጊዜ ብልጣሶር የተባለው ዳንኤል፥ ለትንሽ ጊዜ እጅግ ታወከ፥ ሐሳቡም አስደነገጠው።
ንጉሡም አለው፦ «ብልጣሶር ሆይ ሕልሙ ወይም ትርጉሙ አያስደንግጥህ።» ብልጣሶርም እንዲህ ሲል መለሰ፥ «ጌታዬ ሆይ፥ ሕልሙ ለሚጠልህ፥
ትርጉሙም ለጠላቶችህ ይሁን። 20 ያየኽው ዛፍ፥ ያድግ የነበረውና የበረታው፥ ጫፉም ወደ ሰማያት የደረሰው፥ እስከ መላው ዓለም ዳርቻ ድረስ የታየው፥ 21
ቅጠሎቹያምሩ የነበሩት፥ ፍሬዎቹም የተትረፈረፉት፥ ስለዚህም ለሁሉ የሚሆን መብል የነበረበት፥ ከበታቹም የምድር አራዊት ጥላ ያገኙበት፥ የሰማያት አእዋፍም
ይኖሩበት የነበረ፥ 22 ያ ዛፍ፥ እጅግ ኃያል የሆንከው ንጉሥ አንተ ነህ። ታላቅነትህ እስከ ሰማያት፥ ሥልጣንህም እስከ ምድር ዳርቻ ደረሰ። 23 አንተ ንጉሥ ሆይ፥
አንድ ቅዱስ መልእክተኛ ከሰማይ ሲወርድና እንዲህ ሲል አየህ፦«ዛፉን ቁረጡና አጥፉት፥ ነገር ግን የሥሮቹን ጉቶ በሜዳው ለምለም ሣር መካከል በብረትና
በናስ ማሰሪያ እንደታሰረ በመሬት ውስጥ ተውት። በሰማያት ጠል ይረስርስ። ሰባት ዓመታት እስኪያልፉ ድረስ ከአራዊት ጋር በሜዳ ይኑር። 24 ንጉሥ ሆይ
ትርጉሙ ይህ ነው። ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፥ ይህ በአንተ ላይ የወጣ የልዑሉ አዋጅ ነው። 25 ከሰዎች መካከል ተለይተህ ትባረራለህ፥ በሜዳም ከአራዊት ጋር
ትኖራለህ። እንደ በሬ ሣር እንድትበላ ትደረጋለህ፥ በሰማያትም ጠል ትረሰርሳለህ፥ ልዑሉ በአሕዛብ መንግሥታት ላይ እንደሚገዛና እንዚህንም መንግሥታት እርሱ
ለወደደው ለማንም ሊሰጣቸው እንደሚችል እስክታውቅ ድረስ ሰባት ዓመታት ያልፉብሃል። 26 የዛፉን የሥሩን ጉቶ ይተዉት ዘንድ እንደታዘዘው፥ እንዲሁ ሰማይ
እንደሚገዛ ከተማርህ በኋላ መንግሥትህ ይመለስልሃል። 27 ስለዚህ ንጉሥ ሆይ ምክሬ በፊትህ ተቀባይነት ያግኝ። ኃጢአት ማድረግህን አቁምና ትክክል
የሆንውን ሥራ። 28 እነዚህ ነገሮች ሁሉ በናቡከደነፆር ላይ ደረሱ። 29 ከዐሥራ ሁለት ወሮች በኋላ በባቢሎን ቤተ መንግሥት ሰገነት ላይ ሲመላለስ፣ 30
“ይህች ለንግሥናዬ መኖሪያ፣ ለክብሬም ግርማ እንድትሆን የመሠረትኋት ባቢሎን አይደለችምን?” አለ። 31 ንጉሡ ይህን ገና ተናግሮ ሳይጨርስ እንዲህ የሚል
ቃል ከሰማይ መጣ፣ “መንግሥትህ ከአንተ እንደ ተወሰደ ተነግሮአል፤ 32 ከሰዎች ትገለላለህ፤ መኖሪያህ ዱር ውስጥ ከአራዊት ጋር ይሆናል። እንደ በሬ ሣር
ትበላለህ። ልዑል በሰዎች መንግሥት ላይ እንደሚገዛና እርሱ ለፈለገው እንደሚሰጥ እስክትገነዘብ ድረስ ሰባት ዓመታት ያልፉብሃል።” 33 ይህ ቃል ናቡከደነፆር
ላይ የተፈጸመው ወዲያውኑ ነበር፤ ከሰዎች ተገለለ፤ እንደ በሬ ሣር በላ፤ ሰውነቱ ከሰማይ በሚወርድ ጠል ረሰረሰ፤ ጠጉሩ እንደ ንስር ላባ፣ ጥፍሩም እንደ ወፍ
ጥፍር ሆነ። 34 ጊዜው ከተፈጸመ በኋላ እኔ ናቡከደነፆር ዐይኖቼን ወደ ሰማይ አነሣሁ፤ አእምሮዬም ተመለሰልኝ። “ልዑልንም ባረክሁት ለዘላለም የሚኖረውን
እርሱን አመሰገንሁት አከበርሁት። እርሱ ለዘላለም ይነግሣልና መንግሥቱም ከትውልድ እስከ ትውልድ ዘመን ነው። 35 የምድር ሕዝቦች ሁሉ እንደ ኢምንት
ይቆጠራሉ፤ በሰማይ ሰራዊትና በምድር ሕዝቦች መካከል የወደደውን ያደርጋል። የሚያስቆመው ወይም የሚከራከረው የለም። “ለምን እንዲህ አደረግህ?”
የሚለውም የለም። 36 አእምሮዬ እንደ ተመለሰልኝ ወዲያውኑ ከመንግሥቴ ክብር ግርማዊነቴና ሞገስ ተመለሰልኝ። አማካሪዎቼና ሹማምንቴ ፈለጉኝ። ወደ
ዙፋኔ ተመለስሁ፤ የበለጠ ታላቅነትም ተሰጠኝ። 37 እኔ ናቡከደነፆር አሁን የሰማይን ንጉሥ እባርካለሁ፤ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ። ሥራዎቹ ትክክል መንገዶችም
ጽድቅ ናቸው። በትዕቢታቸው የሚራመዱትን ያዋርዳል።

Daniel 4:1

አጠቃላይ መረጃ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ናቡከደነፆር እግዚአብሔር ለእርሱ ስላደረገለት ነገር ይናገራል።ከቁጥር1 እስከ 18 ባለው ክፍል ውስጥ ናቡከደነፆር
ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ራዕይ አስመልክቶ በአንደኛ መደብነት ይናገራል። ከቁጥር19 እስከ 33 ድረስ ያለው ክፍል የናቡከደነፆርን ቅጣት ለመግለፅ
ወደ ሶስተኛ መደብነት ይለውጠዋል።ከቁጥር 34 እስከ 37 ባለው ክፍል ውስጥ ናቡከደነፆር የመለሰውን መልስ ሲገልፅ ደግሞ ወደ አንደኛ መደብነት
ይለውጠዋል።

ንጉሥ ናቡከደነፆር ላከ

ይሄ ሐረግ የሚያመለክተው ራሱ ንጉሡን ይምሰል እንጂ የንጉሱን መልዕክተኛ ነው።“ናቡከደነፆር መልዕክተናውን ከ----ጋር ላከው”

ሕዝብ፤ ወገንና ቋንቋዎች

እዚህ ላይ “ወገን” እና“ሕዝብ”የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ የተለያዩ ነገዶችን ነው።ይህንን በትንቢተ ዳንኤል 3፤4
ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“ከተለያዩ አገሮች የመጡና የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ሰዎች”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በምድር ለሚቀመጡ
አብዛኛውን ጊዜ ነገሥታት ግዛታቸው ሠፊ መሆኑን ለመግለፅ በማጋነን ይናገራሉ።ይሄ መፅሐፍ በተፃፈበት ወቅት ናቡከደነፆር አዛኛውን የዓለም ክፍል ይገዛ ነበር።“በባቢሎን ግዛት ይኖር የነበረ”

ሠላም ይብዛላችሁ
ይሄ የተለመደ የሠላምታ አሰጣጥ ሥርዓት ነው።

ምልክቶችና ድንቆች
እነዚህ ቃላት ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን የሚያመለክቱትም እግዚአብሔር ስላከናወናቸው አስደናቂ ነገሮች ነው።

ተአምራቱ እንዴት ታላቅ ነው፤ድንቁም እንዴት ፅኑ ነው
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ጥቅም ላይ እንዲውሉ የተደረጉትም የእግዚአብሔር ተአምራቶችና ድንቆች ምን ያህል ታላቅ እንደሆኑ አፅንዖት ለመስተት ነው።

መንግሥቱም...ለልጅ ልጅ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን የሚደጋገሙትም የእግዚአብሔር ግዛት ዘላለማዊ ስለመሆኑ አፅንዖት ለመስጠት ነው።

Daniel 4:4

አጠቃላይ መረጃ
ከቁጥር 1 እስከ 18 ድረስ ናቡከደነፆር ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ራዕይ በአንደኛ መደብነት ይናገረዋል።

ደስ ብሎኝ እኖር ነበር...በአዳራሼም ተመችቶኝ ነበር
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ናቸው።

ቤቴ...ቤተመንግሥቴ
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው።

ሕልም...ምሥል...ራዕይ
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው።

ጥበብ ያላቸው የባቢሎን ሰዎች ሁሉ
“የባቢሎን ጠቢባን ሁሉ”

Daniel 4:7

አጠቃላይ መረጃ
ከቁጥር1 እስከ 18 ድረስ ባለው ክፍል ውስጥ ናቡከደነፆር ከአግዚአብሔር ስለተቀበለው ራዕይ በአንደኛ መደብነት ይናገራል።

ብልጣሶር የሚባለው
ይሄ በገቢር መልክ ለገለፅ ይችላል።“ብልጣሶር የሚል ሥም ያለው”

ብልጣሶር
ይሄ ባቢሎናውያን ለዳንኤል የሰጡት ሥም ነው።ይህንን በትንቢተ ዳንኤል 1፤7 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

የቅዱሳን አማልዕክት መንፈስ
ናቡከደነፆር የዳንኤል ኃይል የመጣው ናቡከደነፆር ያመልካቸው ከነበሩ የሐሰት አማልዕክት የመጣ መስሎት ነበር።

ከምሥጢር ሁሉ የሚያስቸግርህ እንደሌለ
ይሄ በገቢር መልክ ለገለፅ ይችላል።“የእያንዳንዱን ምሥጢር ትርጉም ማወቅ ትችላለህ”

Daniel 4:10

አጠቃላይ መረጃ
ከቁጥር1-18 ባለው ክፍል ውስጥ ናቦከደነፆር ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ራዕይ በአንደኛ መደብነት ይገልፀዋል።

እይታዎች
የምታይዋቸው ነገሮች

ቁመቱም እጅግ ረዥም ነበረ
“በጣም ረዥም ነበረ”

ቁመቱም እስከ ሰማይ ደረሰ...መልኩም እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ታየ
ይሄ ዛፉ ምን ያህል ረዥምና በሚገባ የሚታወቅ እንደሆነ የሚጋነን በሚመስል መልኩ የቀረበ ተምሣሌታዊ ንግግር ነው።“ጫፉ ወደ ሰማይ የደረሰ ስለሚመስል በዓለም ላይ የሚኖሩ ሁሉ ሊያዩት የሚችሉ ይመስላል። ”

ፍሬውም ብዙ ነበረ
“በዛፉ ላይ ብዙ ፍሬዎች ነበሩበት”

ለሁሉም መብል ነበረበት
“ሰዎችና እንሥሳት የሚመገቡት ምግብ ነበራቸው”

Daniel 4:13

አጠቃላይ መረጃ
ከቁጥር1-18 ባለው ክፍል ውስጥ ናቡከደነፆር ከእግዚአብሔር የተቀበቀውን ራዕይ በአንደኛ መደብነት ይገልፀዋል።

በራሴ ራዕይ አየሁ
ይሄ ሕልም ወይም ራዕይ ማየትን የሚያመለክት ነው።“በሕልሜ ውስጥ አየሁ”

ታላቅ ድምፅ ጮኾ እንዲህ አለ
ቅዱስ የሆነው መልዕክተኛ ይናገር የነበረው ከአንድ ሰው በላይ ለሆኑ ስዎች እንደሆነ ግልፅ ይሆናል።“ለጥቂት ሰዎች እየጮኸ እንዲህ አለ”

አራዊት ይሸሹ... ከቅርንጫፉ
“አራዊትም ከበታቹ ወፎችም ከቅርንጫፉ ይሸሻሉ”

Daniel 4:15

አጠቃላይ መረጃ
ከቁጥር1-18 ባለው ክፍል ውስጥ ናቡከደነፆር ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ራዕይ በአንደኛ መደብነት ይገልፀዋል።

አጠቃላይ መረጃ
በራዕዩ ውስጥ የነበረው ቅዱስ መልዕክተኛ ለጥቂት ሰዎች በጩኸት መናገሩን ይቀጥላል።

ጉቶው
ይሄ አንድ ዛፍ ከከተቆረጠ በኋላ ከመሬቱ በላይ የሚቀረው የዛፉ ክፍል ነው።

ጠል
ማለዳ ሲሆን በመስክ ላይ የሚገኝ ዕርጥበታማ ነገር።

ልቡም ከሰው ልብ ይለወጥ...ሰባት ዓመትም ይለፍበት
ዛፉ የሚወክለው ናቦከደነፆርን እንደመሆኑ በቁጥር 16 ላይ በተባዕት ሥም የሚጠራው“የእርሱ” እና “እርሱ” የሚለው ቃል በቁጥር 15 ላይ ተጠቀሰውን ያንኑ ዛፍ ለማመልከት የዋለ ሥም ነው።“የሰውዬው አዕምሮ ለሰባት ዓመታት ያህል ከሰው አዕምሮ ወደ እንሥሳ አዕምሮ ይለወጣል።”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Daniel 4:17

አጠቃላይ መረጃ
ከቁጥር1-18 ባለው ክፍል ውስጥ ናቡከደነፆር ከእግዚአብሔር የተቀበለቀውን ራዕይ በአንደኛ መደብነት ይገልፀዋል።

ይህም ፍርድ የቅዱሣን ቃል ነው
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ቅዱሣን ይህንን ውሳኔ አሣልፈዋል።”

ቅዱሣኑ
ይሄ ሐረግ መላዕክትን የሚመለከት ሊሆን ይችላል።“ቅዱሣን መላዕክት”

ሕያዋን የሆኑት
“በሕይወት የሚገኝ ነገር ሁሉ” ወይም“ሁሉም”

ይሰጣቸዋል
“ግዛቱን ይሰጣል”

ብልጣሶር
ይሄ ባቢሎናውያን ለዳንኤል የሰጡት ስም ነው።ይህንን በትንቢተ ዳንኤል 1፤7 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

ይህንን ማድረግ ትችላለህ
“ይህንን መተርጎም ትችላለህ”

የቅዱሣን አማልዕክት መንፈስ
ናቡከደነፆር የዳንኤል የዳንኤል ኃይል ሊመጣ የቻለው ራሱ ናቡከደነፆር ያመልካቸው ከነበሩ ጣኦታት እንደመነጨ ነበር ያሰበው።ይሄ በቁጥር 17 ላይ “ቅዱሣን”ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይነት የለውም።

Daniel 4:19

አጠቃላይ መረጃ
ከቁጥር 19 እስከ 33 ድረስ የሚገኙት ክፍሎች የናቡከደነፆርን ቅጣት በሚመለከት ሶስተኛ መደብን በመጠቀም ነው የሚናገሩት።

ብልጣሶር የሚል ስያሜም ያለው
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እኔ ብልጣሶር የሚል ስም የሰጠሁት”

ለጥቂት ጊዜ አሰበ፤ልቡም ታወከ
ዳንኤል የፈራበት ምክኒያት የራዕዩን ትርጉም ስለተረዳ ነው።ይሄ የበለጠ ሊብራራ ይችላል። “የሕልሙ ትርጉም ስላሰጋው ለጥቂት ጊዜ ምንም ነገር አልተናገረም ነበር።”

ሕልሙ ለሚጠሉህ፤ፍቺውም ለጠላቶችህ ይሁን
ምንም እንኳን ሕልሙ ንጉሡን እንደሚመለከት ያወቀ ቢሆንም የዳንኤል ምኞት ግን ሕልሙ ከናቡከደነፆር ጋር የተያያዘ እንዳይሆን ነበር።

Daniel 4:20

አጠቃላይ መረጃ
ከቁጥር 19 እስከ 33 ድረስ የሚገኙት ክፍሎች የናቡከደነፆርን ቅጣት በሚመለከት ሶስተኛ መደብን በመጠቀም ነው የሚናገሩት።

አጠቃላይ መረጃ
አብዛኛዎቹ በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉት ቃላት በትንቢተ ዳንኤል14፡10-12 ድረስ ከሚገኙት ክፍሎች ጋር ተመሳሳይ ነው።

ፍሬውም የበዛው
“ብዙ ፍሬ ያፈራው”

ንጉሥ ሆይ ይሄ ዛፍ አንተ ነህ
“ንጉሥ ሆይ፤ይሄ ዛፍ የሚወክለው አንተን ነው”

ታላቅነትህ የበረታ ነው
ይሄ ሐረግ“የበረታ” የሚለውን ቃል የሚጠቀመው የንጉሡ ታላቅነት መጨመሩን ለመግለጥ ነው።

እስከ ሰማይ ድረስ...እስከ ምድር ዳር ድረስ
እነዚህ ሐረጎች ማንኛውም ሰውና በየትኛውም ሥፍራ ናቡከደነፆር ምን ያህል ገናና እንደሆነ ማወቃቸውን አፅንዖት ለመሥጠት በማጋነን መልክ የቀረበ ነው።

Daniel 4:23

አጠቃላይ መረጃ
ከቁጥር19-33 ድረስ ያለው ክፍል የናቡከደነፆርን ቅታት በሶስተና አካልነት ይገልፃል።

አጠቃላይ መረጃ
ይሄኛው ጥቅስ በትንቢተ ዳንኤል4፡13-14 እና በትንቢተ ዳንኤል 4፡15-16 ካለው ክፍል ጋር ተመሳሳይ ነው።እነዚህን ጥቅሶች እንዴት እንደተረጎማችኋቸው ተመልከቱ።

ጉቶው
ይሄ አንድ ዛፍ ከከተቆረጠ በኋላ ከመሬቱ በላይ የሚቀረው የዛፉ ክፍል ነው።

መስክ ሣር መካከል
“ለምለም በሆነ የመስክ ሣር የተከበበ”

ጠል
ማለዳ ሲሆን በመስክ ላይ የሚገኝ ዕርጥበታማ ነገር።

Daniel 4:24

አጠቃላይ መረጃ
ከቁጥር19-33 ያለው ክፍል የናቡከደነፆርን ቅጣት ለመግለፅ ሶስተኛ መደብን ይጠቀማል።

አጠቃላይ መረጃ
በዚህ ክፍል ውስጥ የሚገኙ አብዛኛዎቹ ጥቅሶች በትንቢተ ዳንኤል 14፡ 15-16ውስጥ ካሉት ጋር ተመሳሳይ ነው።እነዚህን ጥቅሶች እንዴት እንደተረጎማችኋቸው ተመልከቱ።

ያየኸው
“የሰማኸው”

ከሰው ትለያለህ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሰዎች አጠገባቸው እንዳትደርስ አድርገው ያባርሩሃል”

ሣር እንድትበላ ትደረጋለህ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሣር ትበላለህ”

Daniel 4:26

አጠቃላይ መረጃ
ከቁጥር19-33 ያለው ክፍል የናቡከደነፆርን ቅጣት ለመግለፅ ሶስተኛ መደብን ይጠቀማል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሥልጣን ከሰማያት ነው
እዚህ ላይ“ሰማይ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በሰማይ ውስጥ የሚኖረውን ነው።“በሰማይ ውስጥ የሚኖረው እግዚአብሔር የሁሉም ገዢ ነው።”

ምክሬ ደስ ያሰኝህ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እባክህን ምክሬን ተቀበለኝ”

ከበደል ተመለስ
እዚህ ላይ ከበደል ተመለስ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከበደል ዘወር ማለትን ነው።“በደልን ተቃወመው”

የተጨቆኑት
ይሄ መለስተኛ ቅፅል የሚያመለክተው የተጨቆኑ ሰዎችን ነው።“የተበደሉ ሰዎች”

ባለፀግነትህ ይቆይልሃል
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅም ይችላል።“እግዚአብሔር ባለፀግነትህን ሊያራዝመው ይችል ይሆናል”

Daniel 4:28

አጠቃላይ መረጃ
ከቁጥር19-33 ያለው ክፍል የናቡከደነፆርን ቅጣት ለመግለፅ ሶስተኛ መደብን ይጠቀማል።

እነዚህ ነገሮች ሁሉ...በባቢሎን
በትንቢተ ዳንኤል 14:28 ላይያለው መረጃ እንዲቀናበር የተደረገው ትርጉሞቹ የበለጠ ግልፅ እንዲሆኑ ለማስቻል ነው።

አሥራ ሁለት ወራት
“12 ወራት”

ለግርማዬ ክብር እንደትሆን የሰራኋት ይቺ ባቢሎን አይደለችምን?
ናቡከደነፆር ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ለራሱ ክብር አፅንዖት ለመሥጠት ሲል ነው።ይሄ በዓረፍተ ነገር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ይቺ ታላቋ ባቢሎን ናት....ለግርማዬ ክብር”

ለግርማዬ ክብር
“ለሰዎች ክብሬንና ታላቅነቴን ለማሣየት”

Daniel 4:31

አጠቃላይ መረጃ
ከቁጥር19-33 ያለው ክፍል የናቡከደነፆርን ቅጣት ለመግለፅ ሶስተኛ መደብን ይጠቀማል።

ቃሉም ገና በንጉሡ አፍ ሳለ
የዘይቤያዊ አነጋገሩ ፍቺ እየተናገረ እያለ መሆኑን ለመግለፅ ነው።“ንጉሡ በመናገር ላይ ሳለ”

ድምፅ ከሰማይ ወደቀ
“ድምፅን ከሰማይ አዳመጠ”

ንጉሥ ናቡከደነፆር ሆይ ...ከአንተ ተወሰደ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ንጉሥ ናቡከደነፆር ሆይ ይሄ መንግስት ከአንተ እንደተወሰደ አዋጅ ወጥቷል።”

ከሰዎች ተለይተህ ትሰደዳለህ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሰዎች ከአጠገባቸው እንድትሄድላቸው ያስገድዱሃል”

ለሚወድደው
“ለሚፈልገው ሰው”

Daniel 4:33

አጠቃላይ መረጃ
ከቁጥር19-33 ያለው ክፍል የናቡከደነፆርን ቅጣት ለመግለፅ ሶስተኛ መደብን ይጠቀማል።

በዚያም ሰዓት ነገሩ በናቡከደነፆር ላይ ደረሰ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ይሄ በናቡከደነፆር ላይ የወጣው አዋጅ ከመቅፅበት ተከናወነ”

ከሰዎች ተለይቶ ተሰደደ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሰዎች ከአጠገባቸው እንዲርቅ አስገደዱት”

ጥፍሩም እንደ ወፎች እስኪረዝም
“ጥፍሮቹ የወፍ ጥፍሮች መሰሉ”

Daniel 4:34

አጠቃላይ መረጃ
ከቁጥር 34 እስከ 37 ባለው ክፍል ውስጥ ናቡከደነፆር ለእግዚአብሔር የሚሰጠውን ምላሽ በሚመለከት በሶስተኛ መደብነት ይናገራል።

ዘመኑ ከተፈፀመ በኋላ
ይሄ የሚያመለክተው በትንቢተ ዳንኤል 4:32 ላይ ያለውን የሰባት ዓመት ጊዜ ነው።

አዕምሮዬም ተመለሰልኝ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ጤንነቴ ተመለሰልኝ” ወይም “ጤነኛ ሆንኩኝ”

አመሰገንሁ፤አከበርኩም
ሁለቱ ሐረጎች የሚያመለክቱት ተመሳሳይ የሆኑ ድርጊቶችን ነው።

ግዛቱ የዘላለም ግዛት ነውና...መንግሥቱም ለልጅ ልጅ ነውና
በመሠረቱ የእነዚህ ሁለት ሐረጎች ትርጉም ተመሳሳይ ሲሆን የእግዚአብሔር ግዛት ዘላለማዊ ስለመሆኑ አፅንዖት የሚሰጡ ናቸው።“እርሱ ለዘላለም የሚገዛ ሲሆን ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም”

Daniel 4:35

አጠቃላይ መረጃ
ከቁጥር 34 እስከ 37 ባሉት ክፍሎች ውስጥ ናቡከደነፆር ለእግዚአብሔር የሰጠውን ምላሽ ለመግለፅ በሶስተኛ መደብነት ይናገራል።

በምድር የሚኖሩ ሁሉ እንደ ምናምን ይቆጠራሉ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በምድር ነዋሪ የሆኑትን ሁሉ እንደ ምናምን ነው የሚቆጥራቸው”

በምድር የሚኖሩ ሁሉ
“በምድር ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ሁሉ”

የሰማይ ሠራዊት
“በሰማይ ውስጥ የሚገኙ የመላዕክት ሠራዊቶች”

እንደ ፈቃዱ
“ዓላማው ግቡን እስከመታ ድረስ”ወይም “ማከናወን የሚፈልገውን ሁሉ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የሚከለክለው የለም
ተጨማሪ ዝርዝር ነገር መጨመሩ ያስፈልግ ይሆናል።“አንድ ነገር ለማድረግ ከወሰነ ማንም ሊያቆመው አይችልም”

ምን ታደርጋለህ? የሚለው የለም
ይሄ ቀጥተኛ ባልሆነ አባባል ሊገለፅ ይችላል።“አንድ ነገርን ሲያከናውን ጥያቄ ለመጠየቅ የሚደፍር ሰው አይኖርም”

Daniel 4:36

አጠቃላይ መረጃ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።ከቁጥር 34-37 ድረስ ባለው ክፍል ውስጥ ናቡከደነፆር ለእግዚአብሔር የሚሰጠውን ምላሽ በአንደኛ መደብነት ይገልፀዋል።

ጤንነቴ ተመለሰልኝ
እዚህ ላይ ጤንነቱን በተመለከተ የሚገለፀው ልክ ወደ ሥልጣኑ ለመመለስ እንደሚችል ተደርጎ ነው።“ዳግም ጤነኛ ሆንኩ”

ግርማዬና ውበቴ ተመለሰልኝ
እዚህ ላይ ግርማውና ውበቱ የሚገለፁት በራሳቸው ጉልበት የመምጣት ኃይል እንዳላቸው ተደርጎ ነው።“ግርማዬንና ውበቴን በድጋሚ አገኘሁት”

ግርማና ውበት
በመሠረቱ እነዚህ ቃላት ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን የክብሩን ታላቅነት በሚመለከት አፅንዖት ይሰጣሉ።

መኳንንቶቼ ፈለጉኝ
“መነኳንንቶቼ እገዛ እንዳደርግላቸው እንደገና ጠየቁኝ”

ፀናሁ ....ብዙ ክብርም ተጨመረልኝ
እዚህ ላይ “ዙፋን”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ፍፁም ገዢ መሆኑን ነው።“በመንግሥቴ ውስጥ እንደገና መግዛት ጀመርኩ፤ከሚገባው በላይ የሆነ ክብር ተጨመረልኝ”

ማመስገን፤ታላቅ ማድረግ፤ማክበር
በመሠረቱ እነዚህ ሶስቱ ቃላት ተመሳሳይ ሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን እግዚአብሔርን ምን ያህል እንዳመሰገነ አፅንዖት ይሰጣል።

በትዕቢት የሚሄዱትን
ይሄ “የሚሄዱ”የሚለው ቃል የሚኮራን ሰው የሚያመለክት ነው።“የሚኮሩ ሰዎች”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 5

1 ንጉሥ ቤልሻዛር በሺህ ለሚቆጠሩ መኳንንቱ ታላቅ ግብዣ አደረገ፣ በሺሁም ፊት የወይን ጠጅ ይጠጣ ነበር። **2** ቤልሻዘር የወይን ጠጅ እየጠጣ ሳለ፣ አባቱ ናቡከደነፆር ከኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ ያመጣቸውን የወርቅና የብር መጠጫዎችን እርሱና መኳንንቱ፣ ሚስቶቹና ቁባቶቹ ይጠጡባቸው ዘንድ እንዲያመጡለት አዘዘ። **3** አገልጋዮቹም እነዚያን ከኢየሩሳሌም ከእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የተወሰዱትን የወርቅ ዕቃዎች አመጡ፤ ንጉሡና መኳንንቱ፣ ሚስቶቹና ቁባቶቹም ጠጡባቸው። **4** የወይን ጠጁንም እየጠጡ የወርቅና የብር፣ የናስ፣ የብረት፣ የዕንጨትና የድንጋይ አማልክቶቻቸውን አመሰገኑ። **5** በዚያን ቅጽበት የሰው እጅ ጣቶች ታዩ፤ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ በመቅረዙ ትይዩ ባለው በግድግዳው ልስን ላይ ጻፉ፤ ንጉሡም ይጽፍ የነበረውን እጅ አየ፤ **6** በዚያን ጊዜ የንጉሡ ፊት ተለዋወጠ በድንጋጤም ተሞላ፤ እጆቹና እግሮቹ ከዱት፤ ጉልበቶቹም ተብረከረኩ። **7** ንጉሡም ድምፁን ከፍ አድርጎ አስማተኞችን፣ ኮከብ ቆጣሪዎችንና መተተኞችን እንዲያስገቡለት አዘዘ፤ ለባቢሎናውያኑ ጠቢባን ንጉሡ እንዲህ አላቸው፤ “ይህን ጽሕፈት አንብቦ ትርጉሙን የሚነግረኝን ሐምራዊ መጎናጸፊያ አለብሰዋለሁ፤ የወርቅ ሐብልም በዐንገቱ አጠልቅለታለሁ፤ በመንግሥቴም ሥልጣን ሦስተኛውን ማዕረግ ይይዛል።” **8** ከዚያም የንጉሡ ጠቢባን ሁሉ ገቡ፤ ነገር ግን ጽሕፈቱን ሊያነብም ሆነ ትርጉሙ ምን እንደሆነ ለንጉሡ ሊነግር የሚችል ማንም አልነበረም። **9** ንጉሥ ቤልሻዘር ፈራ ፊቱም እጅግ ተለወጠ፤ መኳንንቱም ግራ ግብቶአቸው ተደናገጡ። **10** ንግሥቲቱም የንጉሡንና የመኳንንቱን ድምፅ ሰምታ ወደ ግብዣው አዳራሽ ገባች፤ እንዲህም አለች፤ “ንጉሥ ሆይ፤ ለዘላለም ንገሥ፣ አትደንግጥ፣ ፊትህም አይለዋወጥ **11** በመንግሥትህ ውስጥ የቅዱሳን አማልክት መንፈስ ያለበት አንድ ሰው አለ፤ ይህ ሰው በአባትህ ዘመን እንደ አማልክት ጥበብና ማስተዋል ዕውቀትም የሞላበት ሆኖ ተገኝቶአል፤ አባትህ ንጉሥ ናቡከደነፆርም የጠንቋዮች፣ የአስማተኞች፣ የኮከብ ቆጣሪዎችና የመተተኞች አለቃ አደረገው። **12** ንጉሡ ብልጣሶር ብሎ የጠራው ይህ ዳንኤል መልካም መንፈስ፥ ዕውቀትና ማስተዋል ያለው ሆኖ ተገኘ፤ ሕልምን የመተርጎም፣ እንቆቅልሽን የመፍታትና የተሰወረውን የመግለጥ ልዩ ችሎታም ነበረው። ስለዚህ ዳንኤልን አስጠራ፣ እርሱም የጽሕፈቱን ትርጉም ይነግርሃል።” **13** ዳንኤልንም ወደ ንጉሥ አቀረቡት፤ ንጉሡም እንዲህ አለው፤ “ንጉሡ አባቴ ከይሁዳ ማርኮ ካመጣቸው መካከል አንዱ የሆንኸው ዳንኤል አንተ ነህን? **14** የአማልክት መንፈስ በውስጥህ እንዳለ፣ ዕውቀት፣ ማስተዋልና ልዩ ጥበብ እንዳለህ ሰምቻለሁ፤ **15** ይህን ጽሕፈት አንብበው ትርጉሙ ምን እንደሆነ ይነግሩኝ ዘንድ ጠቢባንና አስማተኞች በፊቴ ቀርበው ነበር፣ ነገር ግን ሊገልጡት አልቻሉም። **16** አንተ ግን መተርጎምና አስቸጋሪ የሆነውን ነገር መፍታት እንደምትችል ሰምቻለሁ። ይህን ጽሕፈት አንብበ ትርጉሙን ብትነግረኝ፣ ሐምራዊ መጎናጸፊያ ያለብሱሃል፣ የወርቅ ሐብል በዓንገትህ ያጠልቁልሃል፣ በመንግሥት ሥልጣንም ሦስተኛውን ማዕረግ እንድትይዝ ትደረጋለህ።” **17** ዳንኤልም ለንጉሡ እንዲህ ሲል መለሰ፤ “ስጦታዎችህን ለራስህ አድርግ፤ ሽልማቶችህንም ለሌላ ሰው ስጥ፤ ይሁን እንጂ ጽሕፈቱን ለንጉሡ አነባለሁ፤ ትርጉሙ ምን እንደሆነም እነግረዋለሁ።” **18** “ንጉሥ ሆይ፤ ልዑል አምላክ ለአባትህ ለናቡከደነፆር ገናናነትንና ታላቅነትን፣ ክብርንና ግርማን ሰጠው። **19** ከሰጠው ታላቅ ሥልጣን የተነሣ ሕዝቦችና መንግሥታት፣ ልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገሩ ሰዎችም ሁሉ ተንቀጠቀጡለት ፈሩትም። ንጉሡም ሊገድል የፈለገውን ይገድል፣ ሊያድን የፈለገውን ሊያድን፣ ሊሾም ይፈለገውን ይሾም፣ ሊያዋርድ የፈለገውንም ያዋርድ ነበር። **20** ነገር ግን ልቡ በትዕቢት በጸናና በእብሪት በተሞላ ጊዜ ከዙፋኑ ተወገደ፤ ክብሩም ተገፈፈ። **21** ከሰው መካከል ተሰደደ፤ የእንስሳም አእምሮ ተሰጠው፤ ከዱር አህዮች ጋር ኖረ፤ እንድች በሬም ሣር በላ፤ ልዑል አምላክ በሰዎች መንግሥት ላይ እንደሚገዛና እነርሱምን ለወደደው እንደሚሰጥ እስኪያውቅ ድረስ ሰውነቱ በሰማይ ጠል ረሰረሰ። **22** “ቤልሻዘር ሆይ፤ አንተ ልጁ ሆነህ ይሁ ሁሉ ብታውቅም፣ ራስህን ዝቅ አላደረግህም፤ **23** ይልቁንም በሰማይ አምላክ ላይ በመታበይ ራስህን ከፍ ከፍ አደረግህ፤ የመቅደሱን መጠጫዎች አስመጣህ፤ አንተና መኳንንትህ፣ ሚስቶችህና ቁባቶችህም የወይን ጠጅ ጠጣችሁባቸው፣ ማየት፣ መስማት፣ ማስተዋልም የማይችሉትን የብርና የወርቅ የናስና የብረት፣ የእንጨትና የድንጋይ አማልክትን አመሰገንህ። ሕይወትህንና መንገድህን ሁሉ በእጁ የያዘውን አምላክ ግን አላከበርህም። **24** ስለዚህ እርሱ ጽሕፈቱን ይጻፈውን እጅ ላከ። **25** የተጻፈውም ጽሕፈት፣ ‘ማኔ፣ ቴቄል፣ ፋሬስ’ ይላል **26** የቃሉም ትርጉም ይህ ነው፤ ‘ማኔ’ ማለት እግዚአብሔር የመንግሥትህን ዘመን ቆጠረው፣ ወደ ፍጻሜም አደረሰው ማለት ነው። **27** ‘ቴቄል’ ማለት በሚዛን ተመዝነህ ቀለህም ተገኘህ ማለት ነው። **28** ‘ፋሬስ’ ማለት መንግሥትህ ተከፈለ፣ ለሜዶናውያንና ለፋርስ ሰዎች ተሰጠ ማለት ነው።” **29** ከዚህ በኋላ በቤልሻዘር ትእዛዝ ዳንኤልን ሐምራዊ መጎናጸፊያ አለበሱት፣ የወርቅ ሐብል በዐንገቱ ላይ አጠለቁለት፣ በመንግሥቱም ሥልጣን ሦስተኛውን ማዕረግ እንዲይዝ እንዲያደርጉት በዐዋጅ አዘዘ። **30** በዚያኑ ሌሊት የባቢሎናውያን ንጉሥ ቤልሻዘር ተገደለ፤ **31** የሥልሳ ሁለት ዓመት ዕድሜ የነበረው ሜዶናዊው ዳርዮስም መንግሥቱን ወሰደ።

Daniel 5:1

ብልጣሶር
ይሄ የናቡከደነፆር ልጅ ሲሆን ከአባቱ ቀጥሎ የንጉስነቱን ሥፍራ የያዘ ሰው ነው።

ለሺህ
ለ1000 ሺህ

በፊታቸውም የወይን ጠጅ ይጠጣ ነበር
“በ.....ፊት የወይን ጠጅ ይጠጣ ነበር።”

ከወርቅና ከብር የተሰሩ ዕቃዎች
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እሥራኤላውያን የሰሯቸው የወርቅና የብር ዕቃዎች”

ዕቃዎች
እነዚህ አንድ ሰው በእጁ ይዞ ሊጠጣባቸው የሚችሉ መጠጫዎችና ሌሎች ዕቃዎች ናቸው።

አባቱ ናቡከደነፆር የወሰዳቸውን
እዚህ ላይ “ናቡከደነፆር” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የናቡከደነፆርንሠራዊት ነው።“የአባቱ የናቡከደነፆርሠራዊት”ወይም “አባቱ የወሰደው የናቡከደነፆር ሠራዊት”

Daniel 5:3

ከእግዚአብሔር ቤተመቅደስ የመጡት የወርቅ ዕቃዎች
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የናቡከደነፆር ወታደሮች ከቤተመቅደስ የወሰዷቸው የወርቅ ዕቃዎች”

ከቤተ መቅደስ ማውጣት፤ከእግዚአብሔር ቤት
“ከእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውጪ” “የእግዚአብሔር ቤት” የሚሉት ሐረጎች ስለ ቤተመቅደሱ የበለጠ ነገር ይነግረናል።

Daniel 5:5

በዚያም ሰዓት
“ያንን ባደረጉበት ቅፅበት” ወይም “በድንገት”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ልስን
በሚደርቅበት ወቅት የለሰለሰ ጠንካራ ገፅታ የሚኖረው ሆኖበግድግዳ ወይም በጣሪያ ላይ የሚለሰን ሲሚንቶ ወይም ጭቃ ነው።

የንጉሡ ፊት ተለወጠ
“ፊቱ ገረጣ” ይሄ የሆነው ከመፍራቱ ተነሳ ነው።

ጉልበቱ
“እግሮቹ”

ጉልበቶቹም ተብረከረኩ
ይሄ የነበረበት የከፍተኛ ፍርሃት ውጤት ነው።

Daniel 5:7

በባቢሎን ውስጥ በጥበባቸው የታወቁትን
ይሄ የሚያመለክተው ከሙታን ጋር እንነጋገራለን የሚሉትን፤ጥበበኞችንና ኮከብ ቆጣሪዎችን ነው።

ይህንን ፅሕፈት ያነበበ ፍቺውንም ያሳየኝ ሐምራዊ ግምጃ ይለብሳል፤የወርቅ ማርዳም በአንገቱ ዙርያ ይደረግለታል
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ይህንን ፅሑፍና ትርጉሙን ለሚያብራራልኝ ለማንኛውም ሰው ሀምራዊ የሆነ አልባሳትና የወርቅ ሠንሠለት በአንገቱ ላይ አደርግለታለሁ።”

ሐምራዊ ግምጃ መልበስ
ሐምራዊ ግምጃ እምብዛም ያልተለመደና ንጉሣዊ ባለሥልጣናት ብቻ የሚያደርጉት ነገር ነው። “ንጉሣዊ አልባሳትን መልበስ”

ሦስተኛ ገዢ
“በደረጃ ሶስተኛ የሆነ ገዢ”

Daniel 5:8

ብልጣሶር
ይሄ የናቡከነፆር ልጅ ሲሆን አባቱ ሲሞት ንግሥናውን የተረከበው ሰው ነው። ይህንን ሥም በትንቢተ ዳንኤል5:1 ላይ እንዴት እንደፃፋችሁት ተመልከቱ።

ፊቱ ተለወጠበት
“ፊቱ ደም ገረጣ” የንጉሡ ፊት በትንቢተ ዳንኤል 5:6 ከነበረው ይልቅ የገረጣ ነበረ።

ሃሣቡ አስቸገረው
ሊገባው አልቻለም፤ግራ ተጋባ።

Daniel 5:10

ንግሥቲቱ
አንዳንድ ዘመናዊ የሆኑ የመፅሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች ይህንን የሚያያይዙት ከንግሥቲቱ ማለትም ከንጉሱ እናት ጋር ነው።በጥንቷ ባቢሎን የንጉሱ እናት ከፍተኛ የሆነ ክብር ይሰጣቸው ነበር።

ንጉሥ ሆይ ሺህ ዓመት ንገስ!
ይሄ ንጉሱን ሠላምታ የማቅረብ የተለመደ ሥርዓት ነው።

ፊትህም አይለወጥ
“ፊትህ እንዲህ የሚገረጣበት ምክኒያት የለም”

Daniel 5:11

የቅዱሳን አማልዕክት መንፈስ
ንግስቲቷ የዳንኤል ኃይል የሚመነጨው ናቡከደነፆር ያመልካቸው ከነበሩት ጣዖታት ነው ብለው ያምኑ ነበር።ይህንን ሐረግ በትንቢተ ዳንኤል 4:8 ላይ እንዴት አድርጋችሁ እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

በአባትህም ዘመን
“አባትህ ይገዛ በነበረበት ወቅት”

እንደ አማልዕክት ያለ ጥበብ፤ማስተዋልና ዕውቀትም ተገኘበት
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ልክ እንደ አማልዕክቶች ያለ ጥበብ፤ማስተዋልና ዕውቀት አለው።”

ንጉሥ ናቡከደነፆር፤ንጉሡ አባትህ
“አባትህ ንጉሡ ናቡከደነፆር”

እነዚህ መልካም ነገሮች ሁሉንጉሱ ብልጣሶር ብሎ በሰየመው በዳንኤል ዘንድ ተገኘ።
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ንጉሡ ብልጣሶሰር ብሎ የሰየመው ይሄው ራሱ ዳንኤል እነዚህ ሁሉ መልካም ነገሮች የሞሉበት ሰው ነበረ።”

የተፃፈውን
“በግድግዳው ላይ የተፃፈውን” በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በግድግዳው ላይ በእጅ የተፃፈው ነገር”

Daniel 5:13

የዚያን ጊዜም ዳንኤል ወደ ንጉሱ ፊት ገባ
“በዚያን ጊዜ ወታደሮቹ ዳንኤልን ወደ ንጉሡ ፊት እንዲቀርብ አደረጉት”

ንጉሡ አባቴ ከይሁዳ የማረካቸው
በዚህ ሐረግ ውስጥ“አባት”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ወታደሮችን ሁሉ ነው።“የአባቴ ወታደሮች ከይሁዳ የማረካቸው።”

የአማልዕክት መንፈስ
የዳንኤል ኃይል የሚመነጨው ራሱ ብልጣሶር ያመልካቸው ከነበሩ ጣዖታት ነው ብሎ ያምን ነበር።ይሄንን በትንቢተ ዳንኤል 14:8 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

ዕውቀት ማስተዋልና ጥበብ በአንተ ውስጥ ተገኝቷል።
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ብሩህ የሆነ አዕምሮና ድንቅ የሆነ ጥበብ ባለቤት ነህ።”

Daniel 5:15

ጠቢባንና አስማተኞች ወደ እኔ ገብተው ነበር
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል። “የታወቁ ሰዎች …በፊቴ ቀርበው ነበር”

ያስታውቁኝ ዘንድ
“እንዲነግሩኝ”

ሐምራዊ ግምጃ ትለብሳለህ፤የወርቅ ማርዳም በአንገትህ ዙሪያ ይደረግልሃል
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሐምራዊ የሆነ ልብስና የአንገት ወርቅ እሰጥሃለሁ”

ሐምራዊ ልብስ መልበስ
ሐምራዊ ልብስ እምብዛም ያልተለመደ ሲሆን ይለብሱ የነበሩትም ንጉሣውያን ባለሥልጣናት ብቻ ነበሩ።“በንጉሣዊ አልባስ መዋብ”

ሶስተኛ ገዢ
“በማዕረግ ሶስተኛ የሆነ ገዢ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Daniel 5:17

ሥጦታህ ለአንተ ይሁን
“ሥጦታህን አልፈልገውም”

ወገኖች፤አህዛብና በልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገሩሁሉ
ይሄ ሐረግ“ሁሉ”የሚለውን ቃል የሚጠቀመው ሠፊ ቁጥር ያለውን ሕዝብ አጠቃልሎ ለመግለፅ ነው።“ከተለያዩ ወገኖች የሆኑና የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ሰዎች”

ወገኖች፤አህዛብና በልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገሩ ሁሉ
እዚህ ላይ “ወገኖች” እና “ቋንቋዎች”የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ከተለያዩ ወገኖች የሆኑና የተለያዩ ቋንቋዎች የሚናገሩ ሕዝቦችን ነው።ትንቢተ ዳንኤል 3፡4ን3 እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ። “ከተለያዩ ወገኖች የሆኑ የተለያዩ ቋንቋዎች የሚናገሩ ሕዝቦች”

ይንቀጠቀጡና ይፈሩ ነበር
በመሠረቱ እነዚህ ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ፍርሃቱ ከፍተኛ ስለመሆኑ አፅንዖት ይሰጣሉ።“በጣም ፈርተውት ነበር”

የፈቀደውን ይገድል
ይሄ ሐረግ ራሱ ናቡከደነፆር ሰዎቹን ገደላቸው ማለቱ ሣይሆን ያዘዛቸው ሰዎች ናቸው ተግባራዊ ያደረጉት ለማለት ነው።“ናቡከደነፆር ለገድላቸው የፈለጋቸውን ሰዎች ወታደሮቹን በማዘዝ እንዲገደሉ አደረጋቸው።”

የፈቀደውን በሕይወት ያኖር
“ከፍ ለማድረግ የፈለገውን ሰው ከፍ ያደርግ ነበር”

የፈቀደውን..የፈለገውን
እነዚህ ቃላት ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው።

የፈቀደውንም ያዋርድ ነበር
“ለማዋረድ የፈለገውን ያዋርድ ነበር”

Daniel 5:20

ልቡ ታበየ
እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ራሱ ንጉሱን ነው።“ንጉሱ ግትር ሰው ነበር”

መንፈሱ በጠነከረ
እዚህ ላይ“መንፈስ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ራሱ ንጉሱን ነው።ግትር መሆኑ የሚገለፀው ልክ ጠንካራ እንደሆነ በሚመስል መልኩ ነው።

በሚያውክ ሁኔታ
ሥርዓት አልባና ከልክ ባለፈ መልኩ በራስ መተማመን

ከመንግሥቱ ዙፋን ተዋረደ
እዚህ ላይ“ዙፋን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ለመግዛት የሚያበቃውን ኃይል ነው።ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሰዎች መንግሥቱን ወሰዱበት”

ከሰው ልጆች ተለየ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሰዎች ከአጠገባቸው እንዲሄድ አስገደዱት”

ልቡም እንደ አውሬ ልብ ሆነ
“ልብ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው አስተሳሰቡን ነው። “ልክ እንደ እንስሳ ማሰብ”

ጠል
ማለዳ በሚሆንበት ወቅት በመሬት ላይ የሚታይ አርጥበታማ ነገር።

የሚወድደውን ሁሉ
“የሚመርጠውን ሁሉ”

Daniel 5:22

ብልጣሶር
ይሄ ከአባቱ በመቀጠል ንጉስ የሆነው የናቡከደነፆር ልጅ ነው።በትንቢተ ዳንኤል 5፡1 ላይ ይህንን ሥም እንዴት እንደፃፋችሁት ተመልከቱ።

ልብህን አላዋረድክም
እዚህ ላይ“ልብ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ወደራሱ ወደ ብልጣሶር ነው።“ራስህን አላዋረድክም”

በሰማይ ጌታ ላይ ኮራህ
በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ ልበ እርሱ ላይ እንደመኩራት ተቆጥሮ ተገልፆአል።“በእግዚአብሔር ላይ አምፀሃል”

ከቤቱ
እዚህ ላይ “ቤቱ”ምንና የት እንደሆነ ግልፅ በሆነ መልኩ ሊገለፅ ይችላል።“በኢየሩሣሌም ውስጥ ከሚገኘው ቤተመቅደሱ”

ትንፋሽህን በእጁ የያዘው እግዚአብሔር
እዚህ ላይ “ትንፋሽ”የሚለው ቃል ሕይወትን የሚያመለክት ሲሆን “እጅ”የሚለው ቃል ደግሞ ሥልጣንን ወይም መግዛትን የሚያመለክት ነው።“ትንፋሽ የሚሰጥህ እግዚአብሔር” ወይም“በሕይወትህ ላይ ሁሉ ገዢ የሆነው እግዚአብሔር”

መንገድህን ሁሉ
“የምታደርገውን ሁሉ”

ይህ ፅሕፈት ተፃፈ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ይህንን መልዕክት ፃፈ”

Daniel 5:25

ይህም ፅሕፈት ተፅፏል
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እጁ የፃፈው መልዕክት ይሄ ነው።”

ማኔ፤ቴቄል፤ፋሬስ
እነዚህ በአረማይክ ቋንቋ ግድግዳው ላይ የተፃፉ ቃላት ናቸው።

“ማኔ”...እግዚአብሔር መንግሥትህን ቆጠረው
“ማኔ”ማለት እግዚአብሔር ቆጠረው ማለት ነው።

“ቴቄል” ተመዘንህ
“ቴቄል”ማለት በሚዛን ተመዘንህ ማለት ነው።

“ፋሬስ” መንግሥትህ
“ፋሬስ”ማለት መንግሥትህ ማለት ነው።

በሚዛን ተመዘንክ ቀለህም ተገኘህ
ንጉሱ ግዛቱን የመግዛቱን ጉዳይ በተመለከተ ጠቃሚ መሆን አለመሆኑን ለመናገር በሚዛን እንደሚመዘን ዓይነት ተደርጎ ነው የተገለፀው። ይሄ ማለት ንጉሱ የመግዛት ብቃት የለውም ማለት ነው።ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር የመግዛት ብቃትህን መዝኖ የመግዛት ብቃት እነደሌለህ ደርሶበታል።”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መንግሥትህ ተከፈለ ለሜዶንና ለፋርስ ሰዎች ተሰጠ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር መንግሥትህ ከፍሎ ለሜዶንና ለፋርስ ሰዎች ሰጥቷቸዋል።”

Daniel 5:29

ብልጣሶር
ይሄ ከአባቱ በመቀጠል ንጉስ የሆነው የናቡከደነፆር ልጅ ነው።በትንቢተ ዳንኤል 5፡1 ላይ ይህንን ሥም እንዴት እንደፃፋችሁት ተመልከቱ።

የወርቅ ማርዳ በአንገቱ ላይ ተደረገለት
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የወርቅ ሠንሠለት በአንገቱ ዙሪያ አደረጉለት”

በመንግሥቱም ላይ ሶስተኛ ገዢ
“ቁጥር ሶስት ገዢ”

መንግሥትን ተረከበ
“የመንግሥቱ ገዢ ሆነ”

ዕድሜው ሰድሳ ሁለት በነበረ ጊዜ
“ዕድሜው ስድሳ ሁለት አካባቢ በነበረ ወቅት”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 6

1 ዳርዮስ በመንግሥቱ ሁሉ ላይ እንዲገዙ አንድ መቶ ሃያ መሳፍንትን መሾም ፈለገ፤ **2** በእነዚህም ላይ ሦስት የበላይ አስተዳዳሪዎችን አደረገ፣ ከእነርሱም አንዱ ዳንኤል ነበረ። ንጉሡ ጉዳት እንዳይደርስበት መሳፍንቱ ተጠሪነታቸው ለሦስቱ የበላይ አስተዳዳሪዎች እንዲሆን ተደረገ። **3** ከመሳፍንቱና ከበላይ አስተዳዳሪዎቹ ሁሉ ይልቅ ዳንኤል ልዩ የጥበብ መንፈስ የሞላበት ሆኖ በመገኘቱ፣ ንጉሡ በመላው ግዛቱ ላይ ሊሾመው አሰበ። **4** በዚህ ምክንያት የበላይ አስተዳዳሪዎቹና መሳፍንቱ ዳንኤል በሚያከናውነው የመንግሥት ሥራ እንከን ለማግኘት ፈለጉ፤ ነገር ግን ዳንኤል ታማኝ ጠንቃቃና በሥራው እንከን የሌለበት ስለነበር በእርሱ ላይ ስህተት ሊያገኙ አልቻሉም። **5** እነዚህም ሰዎች፣ “ከአምላኩ ሕግ ጋር የተያያዘ ጉዳይ ካልሆነ በቀር፣ ይህን ሰው የምንከስበት ምንም ሰበብ አናገኝበትም” አሉ። **6** ከዚያም የበላይ አስተዳዳሪዎቹና አሳፍንቱ ዕቅድ ካወጡ በኋላ በአንድነት ወደ ንጉሡ ሄደው እንዲህ አሉ፤ “ንጉሥ ዳርዮስ ሆይ፤ ለዘላለም ንገሥ! **7** ንጉሥ ሆይ፤ እስከ ሠላሳ ቀን ድረስ ወደ አንተ ካልሆነ በቀር ማንም ሰው ወደ ሌላ አምላክ መጸለይ እንደሌለበት ንጉሡ ዐዋጅ እንዲያወጣ ትእዛዙም እንዲፈጸም፤ ይህንም የተላለፈ ወደ አንበሶች ጉድጓድ እንዲጣል፣ የመንግሥት የበላይ አስተዳዳሪዎች፣ መኳንንት፣ መሳፍንት፣ አማካሪዎችና አገረ-ገዦች ሁሉ በአንድነት ተስማምተዋል፤ **8** ንጉሥ ሆይ፤ ይህን ዐዋጅ አውጣ፤ እንደማይሻረውና እንደማይለወጠው የሜዶንና የፋርስ ሕግ እንዲሆን ትእዛዙን በጽሑፍ አድርገው።” **9** ስለዚህ ንጉሡ ዳርዮስ ዐዋጁ ተጽፎ እንዲወጣ አደረገ። **10** ዳንኤልም ዐዋጁ እንደወጣ ባወቀ ጊዜ ወደ ቤቱ ሄደ፤ መስኮቶቹን በኢየሩሳሌም አንፃር ተከፍተው ባሉበት በሰገነቱ ቀድሞ ያደርግ እንደነበረው በቀን ሦስት ጊዜ ተንበርክኮ ጸለየ አምላኩንም አመሰገነ። **11** ሰዎቹም በአንድ ላይ ሄደው ዳንኤልን ሲጸልይና አምላኩን ሲማጸን አገኙት። **12** ወደ ንጉሡም ሄደው፤ “ንጉሥ ሆይ፤ በሚቀጥሉት ሠላሳ ቀናት ማንም ሰው ወደ አንተ ካልሆነ በቀር ወደ ሰውም ሆነ ወደ ማንኛውም አምላክ ቢጸልይ በአንበሶች ጉድጓድ ውስጥ እንደሚጣል ዐዋጅ አውጥተህ አልነበረምን?” ሲሉ እርሱ ስለወጣው ዐዋጅ ጠየቁት። ንጉሡም፤ “ዐዋጁ እንደማይሻረው እንደ ሜዶንና እንደ ፋርስ ሕግ የጸና ነው” ሲል መለሰ። **13** እርሱም ንጉሡን፤ “ንጉሥ ሆይ፤ ከይሁዳ ምርኮኞች አንዱ የሆነው ዳንኤል፣ አንተም ሆነ በጽሑፍ ያወጣኸውን ዐዋጅ አያከብርም፤ አሁንም በቀን ሦስት ጊዜ ወደ አምላኩ ይጸልያል” አሉት። **14** ንጉሡ ይህን በሰማ ጊዜ እጅግ አዘነ፤ ዳንኤልንም ከዚህ ትእዛዝ የሚያድንበትን መንገድ አሰላሰለ፤ ፀሐይ እስክትጠልቅም ድረስ የተቻለውን ሁሉ አደረገ። **15** ከዚያም ሰዎቹ በአንድ ላይ ወደ ንጉሡ ቀርበው፣ “ንጉሥ ሆይ፤ በሜዶንና በፋርስ ሕግ መሠረት፣ አንድ ንጉሥ የጣው ዐዋጅም ሆነ ትእዛዝ ሊለወጥ እንደማይችል ዕወቅ” አሉት። **16** ስለዚህ ንጉሡ ትእዛዝ ሰጠ፤ እነርሱም ዳንኤልን አመጡት፤ ወደ አንበሶቹም ጉድጓድ ጣሉት። ንጉሡም ዳንኤልን፣ ሁልጊዜ የምታመልከው አምላክህ ያድንህ” አለው። **17** ድንጋይ አምጥተው በጉድጓዱ አፍ ላይ ገጠሙበት፤ ንጉሡም በዳንኤል ላይ የተፈጸመው እንዳይለወጥ በራሱ የቀለበት ማሕተምና በመሳፍንቱ ቀለበቶች አተመበት። **18** ንጉሡም ወደ ቤተ መንግሥቱ ተመለሰ፤ በዚያም ሌሊት ምግብ ሳይበላ፣ የሚያዝናናውም ነገር ሳይቀርብለት ዐደረ፤ እንቅልፍም ከእርሱ ራቀ። **19** በማለዳም ገና ጎሕ ሲቀድ፣ ንጉሡ ተነሥቶ ወደ አንበሶቹ ጉድጓድ እየተጣደፈ ሄደ። **20** ወደ ጉድጓዱም ቀርቦ በሐዘን ድምፅ ዳንኤልን፣ “የሕያው አምላክ አገልጋይ ዳንኤል ሆይ፤ ሁልጊዜ የምታመልከው አምላክህ ከአንበሶቹ ሊያድንህ ችሎአልን?” ብሎ ጠየቀው። **21** ዳንኤልም እንዲህ ብሎ መለሰ፤ “ንጉሥ ሆይ፤ ለዘላለም ንገሥ፤ **22** ንጉሥ ሆይ፤ በፊቱ ቅን ሆኜ ስለተገኘሁ፣ በአንተም ፊት በደል ስላልተገኘብኝ አምላኬ መልአኩን ልኮ የአንበሶቹን አፍ ዘጋ፤ እነርሱም አልጎዱኝም።” **23** ንጉሡ እጅግ ተደሰተ፤ ዳንኤልን ከጉድጓድ እንዲያወጡት አዘዘ። ዳንኤል በአምላኩ ታምኖ ነበርና ከጉድጓድ በመጣ ጊዜ፣ አንዳች ጉዳት አልተገኘበትም። **24** በንጉሡ ትእዛእ ዳንኤልን የከሰሱት ሰዎች ተይዘው እንዲመጡ ተደረገ፤ እነርሱም ተይዘው ከሚስቶቻቸውና ከልጆቻቸው ጋር በአንበሶቹ ጉድጓድ ውስጥ ተጣሉ። ወደ ጉድጓዱም መጨረሻ ገና ሳይደርሱ አንበሶቹ ቦጫጩቋቸው፤ ዐጥንቶቻቸውንም ሁሉ ሰባበሩ። **25** ከዚያ በኋላ ንጉሥ ዳርዮስ፣ በምድር ላይ ለሚኖሩ ሕዝቦች፣ መንግሥታትና ልዩ ልዩ ቋንቋ ለሚናገሩ ሰዎች ሁሉ እንዲህ የሚል መልእክት ጻፈ፤ “ሰላም ይብዛላችሁ! **26** በማንኛውም የመንግሥቴ ግዛት ሰው ሁሉ፣ የዳንኤልን አምላክ እንዲፈራና እንዲያከብር ይህን ዐዋጅ አውጥቻለሁ። “እርሱ ለዘላለም የሚኖር ሕያው አምላክ ነውና መንግሥቱም አይጠፋም፤ ለግዛቱም መጨረሻ የለውም **27** እርሱ ይታደጋል፣ ያድናልም በሰማይና በምድር ምልክቶችንና ድንቆችን ያደርጋል ዳንኤልን ከአንበሶች አፍ አድኖታል። **28** ስለዚህ ዳንኤል በዳርዮስ መንግሥትና በፋርሳዊው በቂሮስ ዘመነ መንግሥት ሁሉ ኑሮው ተሳካለት።

Daniel 6:1

ሃሣብን ማያያዣ
በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሚገኙት ክስተቶች የተከናወኑት ፋርሶች ባቢሎናውያንና ከለዳውያንን ድል ካደረጉ በኋላ ነበር።ሜዶን በባቢሎን ውስጥ መግዛት ጀመረ።

ዳርዮስን ደስ አሰኘው
“ንጉስ ዳርዮስ ውሳኔ አሣለፈ”

120 መሣፍንት
“አንድ መቶ ሃያ የግዛት ባለሥልጣናት”

በእነርሱ ላይ
“በእነርሱ ላይ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው 120ውን የግዛት ባለሥልጣናትን ነው።

ንጉሡም እንዳይጎዳ
“ከንጉሡ ምንም ዓይነት ነገር እንዳይሰረቅ” ወይም “ማንም ሰው ከንጉሱ እንዳይሰርቅ”

በላያቸው አደረገ
“የበላይ እንዲሆን ተደረገ” ወይም “ከ...ይልቅ የበለጠ ብቃት ነበረው”

መልካም የሆነ መንፈስ ነበረው
እዚህ ላይ“መንፈስ” የሚለው ቃል የሚመለክተው ዳንኤልን ነው።እጅግ በተለየ መልኩ ብቃት የነበረው ሰው ነበር ማለት ነው። “ልዩ የሆነ ሰው ነው”

መልካም መንፈስ
ከሌሎች ይልቅ የተሻለ ነገሮችን እንዲያከናውን የሚረዳው መንፈስ።

ይሾመው ዘንድ
“ሥልጣንን ይሰጠው ዘንድ” ወይም “በኃላፊነት ቦታ ላይ ማስቀመጥ”

Daniel 6:4

የዚያን ጊዜ አለቆችና መሳፍንቱ ስለ መንግሥቱ
ሌሎቹ ባለሥልጣናት በዳንኤል ላይ ቀኑበት።ይሄ የበለጠ ሊብራራይችላል።“የዚያን ጊዜ ሌሎች አለቆችና መሳፍንቱ ቀኑበት።ስለሆነም ዳንኤል በሚሰራው የመንግሥት ሥራ ውስጥስህተት መፈለግ ጀመሩ።”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በእርሱ ላይ ሰበብና በደል ሊያገኙበት አልቻሉም
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በሚሰራው ሥራ ላይ ምንም ዓይነት ሰበብና በደል ሊያገኙበት አልቻሉም።”

ችላ ማለት
ኃላፊነትን በአግባቡ አለመገንዘብ

ዳንኤልን በመቃወም ማጉረምረም
“ዳንኤልን በሚመለከት ሰበብ መፈለግ”

Daniel 6:6

አንድ ዕቅድ በንጉሡ ፊት አመጡ
“አንድ ዕቅድ በንጉሱ ፊት አቀረቡ”

ሺህ ዓመት ንገሥ
ለአንድ ንጉሥ የሚሰጥ የተለመደ የሠላምታ አቀራረብ ነው።

ለሰላሣ ቀናት
“ለሠላሳ ቀናት”

ማንም ሰው ልመና ቢለምን
“ማንም ጥያቄ የሚጠይቅ ሰው ቢኖር”

ያ ሰው በአንበሣ ጉድጓድ ውስጥ ይጣል
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ወታደሮችህ ያንን ሰው በአንበሳ ጉድጓድ ውስጥ መጣል ይኖርባቸዋል።”

የአንበሣ ጉድጓድ
ይሄ አንበሶች የሚጠበቁበትን ቤት ወይም ጉድጓድ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።

Daniel 6:8

ሃሣብን ማያያዣ
በቁጥር 8 ላይ አስተዳዳሪዎቹ ለንጉሡ መናገራቸውን ይቀጥላሉ።

በሕጉ በተደነገገው መሠረት
“በሕጎቹ መሠረት”

ሊለወጥ አይችልም
“ሊሰረዝ አይችልም”

አዋጁን በሕግ ማፅናት
“ሥርዓቱን ወደ ሕግ መለወጥ”

Daniel 6:10

ዳንኤልም ሰነዱ ተፈርሞ በሕግነት እንደፀና በወቀ ጊዜ
ዳንኤል ወደ እግዚአብሔር ከመፀለዩ በፊት ስለ አዲሱ ሕግ መውጣት ዕውቀቱ እንደነበረው ግልፅ ማድረጉ ለታሪኩ ጠቃሚ ነው።

የእልፍኙ መስኮቶችም በኢየሩሣሌም አንፃር ተከፍተው ነበር
ይሄ የዳንኤል ጠላቶች ወደ እግዚአብሔር ይፀልይ እንደነበረ ስለማወቃቸው የቆየ መረጃ እንዳላቸው የሚገልፅ ነው።

በአምላኩ ፊት አመሰገነ
“እግዚአብሔርን አመሰገነ”

ሄራ
ለክፋት የታቀደ ዕቅድ

Daniel 6:12

ትዕዛዝ አልፃፍክምን?.....አንበሶች?
ይህንን ጥያቄ የጠየቁበት ምክኒያት ንጉሱ ትዕዛዝ ማውጣቱን እነዲያረጋግጥላቸው ነበር።

ልመና እንዳያቀርብ
“ጥያቄ የሚጠይቅ”

የአንበሶች ጉድጓድ
ይሄ ምናልባትም አንበሶች ተጠብቀው የሚኖሩበትን ክፍል ውስጥ ወይም ጉድጓድ ለማመልከት ሊሆን ይችላል።

በሕጉ እንደተደነገገው
“በሕጉ መሠረት”

Daniel 6:13

ያ ዳንኤል የሚባለው ሰው
ይህ ዳንኤልን በማክበር የሚደረግ ምልከታ አይደለም።ይህንን ሐረግ የተጠቀሙት ዳንኤልን እነደ ከፍተኛ ባለሥልጣንነቱ የሚገባውን ክብር ሆነ ብለው ለመንፈግ ነበር።

የይሁዳ ምርኮኞች ከሆኑት መካከል አንዱ ነው
“ከይሁዳ ተሰድዶ የመጣው”

ትዕዛዝህን ለመቀበል ፈቃደኛ አይደለም
የዚህ ዘይቤያዊ አነጋገር ትርጉም ችላ ይልሃል ማለት ነው።“እርሱ አይታዘዝህም”

በአዕምሮው ያሰበውን አደረገ
እዚህ ላይ “አዕምሮ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው አስተሳሰቡን ነው።“እንዴት ማድረግ እንደሚኖርበት በእጅጉ አሰበበት”

ደከመ
ይሄ የሚያመለክተው አካላዊ ድካምን ሣይሆን የአዕምሮ ድካምን ነው።

Daniel 6:15

ሕጉ ....አይለወጥም
ሰዎቹ የንጉሱ ሕግ ወይም የንጉሱ ትዕዛዝ ሊለወጥ የማይቻል መሆኑን እያሣሰቡ ነው ያሉት።ዳንኤል ወደ አንበሶቹ ግድጓድ መጣል ይኖርበታል። አስፈላጊ ከሁነ ይሄ ሊብራራ ይችላል።“ሕጉ...አይለወጥም።ዳንኤልን ወደ አንበሶች ጉድጓድ መጣል ይኖርባቸዋል።”

Daniel 6:16

ዳንኤልን አመጡት
“ወታደሮቹ ዳንኤልን ሄደው አመጡት”

የአንበሣ ጉድጓድ
ይሄ አንበሶች ተጠብቀው የሚኖሩበትን ክፍል ወይም ጉድጓድ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።ይህንን በትንቢተ ዳንኤል 6:7 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

የምታመልከው አምላክ እርሱ ያድንህ
ንጉሱ ዳንኤልን ለማዳን ያለውን ምኞት እየገለፀ ነው።

ያድንህ
“ከአንበሶች ያድንህ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Daniel 6:17

x
ይሄ አንበሶች ተጠብቀው የሚኖሩበትን ክፍል ወይም ጉድጓድ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።ይህንን በትንቢተ ዳንኤል 6:7 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡

ንጉሱም በዳንኤል ላይ የተደረገው እንዳይለወጥ በቀለበቱና በመኳንንቱ ቀለበት አተመው
በቀለበት የመታተሙ ጠቀሜታ የበለጠ ሊብራራ ይችላል።ንጉሱና መኳንንቱ በሰም በተሰራ ማህተም በቀለበታቸው አተሙት።ንጉሱ ፊርማውን በሰም ውስጥ አድርጎ ካተመ በኋላ መኳንንቶቹም በተመሳሳይ ሁኔታ አደረጉ።ማንም ሰው ቢሆን ዳንኤልን ለመርዳት በሚል ሰበብ ማሕተሙ ያዘለውን ትዕዛዝ ለመሻር አልተፈቀደለትም ነበር።

በዳንኤል ላይ የተወሰነው ነገር እንዳይለወጥ
“ማንም ሰው ቢሆን ዳንኤልን ለማገዝ አይችልም ነበር”

ሳይበላም አደረ
ይህ ድርጊት የሚያሣየው ንጉሱ የዳንኤል ጉዳይ ምን ያህሰል ያስጨነቀው መሆኑን ነው።

የሚያዝናኑ ነገሮች በፊቱአልቀረቡለትም
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የሚያዝናናው ማንም ሰው አልነበረም”

እንቅልፍም ከእርሱ ራቀ
እንቅልፍ ልክ ከንጉሱ እየሮጠ እንደሚሄድ ዓይነት ነገር ነው የተገለፀው።“በዚያን ሌሊት ሁሉ እንቅልፍ ሳይዘው አሳለፈ”

Daniel 6:19

አልበደልሁም
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ምንም ዓይነት ስህተት እንዳልፈፀምኩ ያውቃል።”

ጉዳት አልደረሰበትም
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በዳንኤል ላይ ምንም ቁስል አላገኙበትም”

Daniel 6:24

የአንበሶች ጉድጓድ
ይሄ አንበሶች ተጠብቀው የሚኖሩበትን ክፍል ወይም ጉድጓድ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።ይህንን በትንቢተ ዳንኤል 6:7 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

ወደ ጉድጓዱ መጨረሻ ሳይደርሱ
“በአንበሶቹ ጉድጓድ ወለል ላይ ከመድረሳቸው በፊት”

አጥንታቸውንም ሰባበሩ
“አጥንታቸውን አደቀቁት”

ወገኖች፤አህዛብና ቋንቋዎች
እዚህ ላይ “አህዛብ” እና “ቋንቋዎች”የሚለው ቃል የሚወክለው ከተለያዩ ነገዶች የመጡና የተለያዩ ቋንቋዎች የሚናገሩ ሰዎችን ነው።ይህንን በትንቢተ ዳንኤል 6:7 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ። “ከተለያዩ ነገዶች የመጡና የተለያዩ ቋንቋዎች የሚናገሩ ሰዎች”

በምድር ሁሉ
ንጉሥ ዳርዮስ መልክዕቱን የፃፈው ሠፊ ለነበረው ግዛቱ ሁሉ ነበር።ምንም አንኳን በምድር ላይ የሚገኙትን ሰዎች ሁሉ የሚያጠቃልል ባይሆንም እዚህ ላይ “በምድር ሁሉ”የሚለው ቃል መንግሥቱ ምን ያህል ሠፊ እንደነበረ አፅንዖት ለመሥጠት ነው።“በመንግሥቱ ውስጥ”

ሰላም ይብዛላችሁ
ይሄ በሁሉም የሕይወት ዘርፎች ለአንድ ሰው መለካም ይሆንለት ዘንድ ለመመኘት የሚቀርብ የሠላምታ ዓይነት ነው።

Daniel 6:26

ሐሣብን ማያያዣ
በዚህ ውሰጥ ዳርዮስ በግዛቱ ውስጥ ለሚገኙ ሁሉ መልዕክት ማስተላለፉን ይቀጥላል።

መንቀጥቀጥና መፍራት
እነዚህ ቃላት ተመሳሳይ በመሆናቸው ሊጣመሩ ይችላሉ።“በፍርሃት መራድ”

የዳንኤል አምላክ
“ዳንኤል የሚያመልከው አምላክ”

ሕያው የሆነ አምላክ፤ለዘላለም የሚኖር
“ሕያው የሆነ” እና “ለዘላለም የሚኖር”የሚሉት ሁለት ቃላትእግዚአብሔር ለዘላለም ስለመኖሩ ተመሳሳይ የሆነ ሃሣብን የሚገልፁ ናቸው።

መንግሥቱ...ግዛቱ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“መንግስቱን ማንም አያጠፋውም”ወይም “መንግሥቱ ለዘላለም ይኖራል”

ግዛቱም እስከ መጨረሻ ድረስ ይኖራል
“ለዘላለም ይነግሳል”

ዳንኤልንም ከአንበሶች አፍ አድኖታል
“ኃይለኛ የሆኑ አንበሶች ዳንኤልን እንዲጎዱት አልፈቀደላቸውም”

Daniel 6:28

በዳርዮስ መንግሥትና በፋርሳዊው በቂሮስ መንግሥት
የፋርሱ ቂሮስ ከዳርዮስ በመቀጠል የነገሰ ንጉሥ ነበር።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 7

1 የባቢሎን ንጉሥ ቤልሻዘር በነገሠ በመጀመሪያው ዓመት ዳንኤል በአልጋው ላይ ተኝቶ ሳለ ሕልም አለመ፤ ራእይም አየ፤ የሕልሙንም ዋና ሃሳብ ጻፈው። **2** ዳንኤል እንዲህ አለ፤ “ኣቱ የሰማይ ነፋሳት ታላቁን ባሕር ሲያናውጡት ሌሊት በራእይ አየሁ፤ **3** እርስ በርሳቸው የማይመሳሰሉ አራት ታላላቅ አራዊት ከባሕሩ ወጡ። **4** የመጀመሪያው አንበሳ ይመስል ነበር፤ የንስርም ክንፎች ነበሩት፤ ክንፎቹ እስኪነቃቀሉ ድረስ ትመለከትሁ፤ እንደ ሰው በሁለት እግር እንዲቆም ከመድር ከፍ ከፍ ተደረገ፤ ሰብዓዊ አእምሮ ተሰጠው። **5** እነሆም ሁለተኛው አውሬ ድብ ይመስል ነበር፤ በአንድ ጎኑ ከፍ ብሎአል፤ በአፉ ውስጥ በጥርሶቹ መካከል ሦስት የጎድን አጥንቶች ነበርት። እርሱም፤ “ተነሥ እስክትጠግብ ድረስ ሥጋ ብላ” ተባለ። **6** ከዚህ በኋላ ተመለከትሁ፤ በፊቱ በኩል ነብር የሚመስል ሌላ አውሬ ነበር፤ በጀርባውም በኩል የወፍ ክንፍ የሚመስሉ አራት ክንፎች ነበርት፤ ይህ አውሬ አራት ራስ ነበረው፤ ለመግዛትም ሥልጣን ተሰጠው። **7** ከዚህ በኋላ በሌሊት ራእይ አየሁ፤ በፊቴም የሚያስፈራና የሚያስደነግጥ በጣም ኃይለኛ የሆነ አራተኛ አውሬ ነበር፤ ትልቅ የብረት ጥርሶች ነበሩት፤ ያደቅና ይበላ፣ የቀረውንም ሁሉ በእግሮቹ ይረጋግጥ ነበር። ከእርሱ በፊት ከነበሩት አራዊት ሁሉ የተለየ ሲሆን፤ አሥር ቀንዶች ነበሩት። **8** ስለ ቀንዶቹ ሳስብ ሳለሁ፣ ከመካከላቸው አንድ ሌላ ትንሽ ዘንድ ብቅ ሲል አየሁ፤ ከመጀመሪያዎቹ ቀንዶች ሦስቱ ከፊቱ ተነቃቀሉ፤ ይህም ቀንድ የሰው ዐይኖችን የሚመስሉ ዐይኖች፣ በትዕቢትም የሚናገር አፍ ነበረው። **9** እኔም ስመለከት፣ ዙፋኖች ተዘረጉ፣ ጥንታዊ ጥንቱም ተቀመጠ፣ ልብሱ እንደ በረዶ ነጭ ነበረ፣ የሩስም ጠጉር እንደ ጥጥ ነጭ ነበረ፣ ዙፋኑ የእሳት ነበልባል፣ መንኩራኩሮቹም ሁሉ እንደሚነድ እሳት ነበር፥ **10** የእሳት ወንዝ ከፊት ለፊት ፈልቆ ይፈስ ነበር ሺህ ጊዜ ሺዎች ያገለግሉት ነበር፤ እልፍ ጊዜ እልፍ በፊቱ ቆመዋል፤ የፍርድ ጉባዔ ተሰየመ፤ መጻሕፍትም ተከፈቱ። **11** ቀንዱም ከሚናገረው የትዕቢት ቃል የተነሣ፣ መመልከቴን ቀጠልሁ፣ አውሬው እስኪታረድና እካሉድቆ ወደሚንበለበለው እሳት እስኪጣል ድረስ ማየቴን አላቋርጥሁም። **12** ሌሎቹም አራዊት ሥልጣናቸው ተገፎ ነበር፤ ነገር ግን ለተወሰነ ጊዜና ወቅት በሕይወት እንዲኖሩ ተፈቀደላቸው። **13** ሌሊት ባየሁት ራእይ የሰውን ልጅ የሚመስል ከሰማይ ደመና ጋር ሲመጣ አየሁ፤ ወደ ጥንታዊ ጥንቱ መጣ፤ ወደ ፊቱም አቀረቡት። **14** ሥልጣን፣ ክብርና ታላቅ ኃይል ተሰጠው፤ በልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገሩ ሰዎች፤ መንግሥታትና ሕዝቦች ሰገዱለት፤ ግዛቱም ለዘላለም የማያልፍ ነው፤ መንግሥቱም ፈጽሞ የማይጠፋ ነው። **15** እኔ ዳንኤል በመንፈሴ ታወክሁ፤ ያየሁትንም ራእይ እጅግ አስጨነቀኝ። **16** በዚያ ከቆሙት ወደ አንዱ ቀርቤ የዚህ ሁሉ ትርጕም ምን እንደ ሆነ ጠየቅሁት። **17** “አራቱ ታላላቅ አራዊት ከምድር የሚነሡ መንግሥታት ናቸው፤ **18** ነገር ግን የልዑሉ ቅዱሳን መንግሥቱን ይወስዳሉ፣ ለዘላለምም ይይዙታል። **19** ከዚያም የሚያደቅቀውንና የሚበላውን የቀረውንም ሁሉ በእግሮቹ የሚረጋግጠውን የብረት ጥርሶችና የናስ ጥፍሮች የነበሩትን ከሌሎች የተለየና እጅግ አስፈሪ የሆነውን የአራተኛውን አውሬ ምንነት የበለጠ ማወቅ ፈለግሁ። **20** ደግሞም በራሱ ላይ ስላሉት አሥር ቀንዶች፣ ከመካከላቸው ብቅ ስላለው ቀንድና ከዚሁ ቀንድ ፊት ስለተነቃቀሉት ሦስት ቀንዶች፣ እንደዚሁም ከሌሎች ስለበለጠው የሰው ዓይኖች የሚመስሉ ዓይኖች በትዕቢትም የሚናገር አፍ ስለነበሩት ስለዚሁ ቀንድ ማወቅ ፈለግሁ። **21** እየተመለከትኩም ሳለሁ ይህ ቀንድ በቅዱሳን ላይ ጦርነት ዐውጆ አሸነፋቸው። **22** ይህም የሆነው ጥንታዊ ጥንቱ እስኪመጣና ለልዑሉ ቅዱሳን እስኪፈርድላቸው ድረስ ነበር፤ ኪዝያም የልዑሉ ቅዱሳን መንግሥቱን የሚወርሱበት ዘመን መጣ። **23** እርሱም እንዲህ አለኝ፤ “አራተኛው አውሬ በምድር ላይ የሚነሣ አራተኛው መንግት ነው። ከሌሎች መንግሥታት ሁሉ የተለየ ይሆናል፤ መላውንም ምድር እየረገጠና እያደቀቀ ይበላል። **24** ዐሥሩ ቀንዶች ከዚህ መንግሥት የሚወጡ ዐሥር ነገሥታት ናቸው፤ ከዚያም በኋላ ከእነርሱ የተለየ ሌላ ንጉሥ ይነሣል፤ ሦስቱንም ነገሥታት ያንበረክካል። **25** በልዑል ላይ የዓመፅ ቃል ይናገራል፤ የልዑልንም ቅዱሳን ያስጨንቃል፤ ለበዓላት የተመደበውን ጊዜና ሕግን ለመለወጥ ይሞክራል፤ እነዚህም ነገሮች ለዘመን፣ ለዘመናት፣ ለዘመን እኩሌታም ለእርሱ ዐልፈው ይሰጣሉ። **26** ነገር ግን የፍርድ ዙፋን ይዘረጋል፤ ሥልጣኑም ይወሰድበታል፤ ፈጽሞ ለዘላለም ይደመሰሳል። **27** ከዚያም ከሰማይ በታች ያሉ መንግሥታት ልዕልና፣ ሥልጣንና ታላቅነት ለልዑሉ ሕዝብ ለቅዱሳን ይሰጣል። መንግሥቱ የዘላለም መንግሥት ይሆናል፤ ገዦች ሁሉ ያመልኩታል ይታዘዙታልም። **28** የነገሩ ፍጻሜ ይህ ነው፤ እኔም ዳንኤል በሃሳቤ እጅግ ተጨነቅሁ፤ መልኬም ተለወጠ፤ ይሁን እንጂ ነገሩን በልቤ ጠበቅሁት።

Daniel 7:1

አጠቃላይ መረጃ
ምዕራፍ 7 እና 8 በቅደም ተከተላቸው መሠረት የተቀመጡ አይደሉም። በምዕራፍ 6 ላይ የቀረበው ዳርዮስና ቂሮስ ከመግዛታቸው አስቀድሞ ብልጣሶር ንጉሥ በነበረበት ወቅት የተከናወነ ነው።

አጠቃላይ መረጃ
በዳንኤል ራዕይ ውስጥ ሌሎች ነገሮችን የሚያመላክቱ እንስሳትን ተመለከተ። ከራዕዩ በኋላ የእነዚህን ተምሣሌቶች ትርጉም ያብራራል።

ብልጣሶር
ይሄ ከእርሱ በኋላ ንጉሥ የሆነው የናቡከደነፆር ወንድ ልጅ ሥም ነው።ይህንን አንዴት እንደፃፋችሁት በትንቢተ ዳንአል 5:1 ላይ ተመልከቱ።

ሕልምና ራዕይ
ሁለቱም “ሕልም”እና “ራዕይ” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት በዚህ ምዕራፍ ላይ የተገለፀ ውን ተመሳሳይ ሕልም ነው።“ሕልም ባለመበት ወቅት ያያው ራዕይ”

አራቱ የሰማይ ነፋሳት
“በሥፍራው ያሉ ነፋሳት ሁሉ”ወይም “በአራቱም አቅጣጫዎች ያሉ ኃይለኛ ነፋሳት”

ይጋጩ
“ተላተመ” “ተናወጠ” “ለከፍተኛ ማዕበል መነሳት መንስኤ ሆነ”

Daniel 7:4

መጀመሪያይቱ አንበሣ ትመስል ነበር የንስርም ክንፍ ነበራት
ይሄ ተምሣሌታዊ ፍጥረት እንጂ በምድር ላይ የሚኖር የእንስሳ ዘር አይደለም።

ክንፎችዋም ከእርስዋ እስኪነቀሉ ድረስ አይ ነበር፤ከምድርም ከፍ ከፍ ተደረገች፤እንደ ሰውም በሁለት እግር እንድትቆም ተደረገች
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል። “የሆነ ሰው ክንፎችዋን ነቅሎ ከምድር ላይ ካነሳት በኋላ ልክ እንደ ሰዎች በሁለት እግሮቿ እንድትቆም አደረጋት።”

የሰውም ልብ ተሰጠው
እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው አስተሳሰብን ነው።ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የሆነ ሰው እንደ ሰው የማሰብ ችሎታ እንዲኖራት አደረገ”

ሁለተኛው እንሥሳ...አንደ ድብ
ይሄ በገሃዱ ዓለም የሚገኝ እንስሳ አይደለም።ከድብ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ተምሳሌታዊ አንስሳ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የጎድን አጥንት
ከጀርባ የአጥንት አከርካሪ ጋር የሚገናኙ ሠፊና ጠምዛዛ የሆኑ የደረት አጥንቶች ናቸው።

ተባለላት
ይሄ በገቢር መልክ ለገለፅ ይችላል።“የሆነ ሰው ተናገረው”

Daniel 7:6

ነብር የምትመስል ሌላ እንስሳ
ይሄ በገሃዱ ዓለም የሚገኝ ነብር አይደለም።ከነብር ጋር ተመሳሳይ የሆነ ተምሳሌታዊ አንስሳ ነው።

አራት ክንፎች...አራት ራሶች
አራቱ ክንፎችና አራቱ ራሶች ተምሣሌታዊ ቢሆኑም ትርጉም ግን ግልፅ አይደለም።

አራት ራሶች ነበሩት
“እንስሳው አራት ራሶች ነበሩት”

ግዛትም ተሰጣት
ይሄ በገቢር መልክ ለገለፅ ይችላል።“የሆነ ሰው መግዛት እንደትችል ሥልጣንን ሰጣት”

አራተኛው እንስሳ...አስር ቀንዶች ነበሯት
ይሄኛውም በገሃዱ ዓለም የሚገኝ እንሥሳ አይደለም።ተምሣሌታዊ ፍጥረት ነው።

በእግር ተረገጠ
“በላዩ ላይ ተራምዶ ፈጨው”

Daniel 7:8

አጠቃላይ መረጃ
ዳንኤል በትንቢተ ዳንኤል 7፡7 ስለ አራተኛው እንስሳ በራዕይ የተመለከተውን መግለፁን ይቀጥላል።

ቀንዶቹ
“ቀንዶች የሥልጣን ተምሣሌት ሲሆኑ ኃይለኛ የሆኑ መሪዎችን የሚያመለክት ነው።”

በፊቱም ከቀደሙት ቀንዶች ሶስቱ ከሥራቸው ተነቃቀሉ
ይሄ በገቢር መልክ ለገለፅ ይችላል።“ትንሹ ቀንድ ቀደሙትን ሶስት ቀንዶች ነቃቀላቸው”

ስለ ትላልቅ ነገሮች የሚያወሳ የትዕቢት አፍ
እዚህ ላይ ቀንዱ አፉን በመጠቀም የትዕቢት ንግግር ይናገር ነበር።“ቀንዱ አፍ የነበረው ሲሆን ትላልቅ ነገሮችን እንደሚፈፅም ይናገር ነበር።”

Daniel 7:9

አጠቃላይ መረጃ
አብዛኛዎቹ ከቁጥር 9 እስከ 14 ድረስ ያሉት ክፍሎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ተምሣሌታዊ አነጋገሮች ናቸው።ከዚህ የተነሣ ሌሎች ቅጂዎች በቅኔያዊ ዘይቤ ያቀርቧቸዋል።

ዙፋኖች ተዘረጉ
ይሄ በገቢር መልክ ለገለፅ ይችላል።“የሆነ ሰው ዙፋኖቹን በየሥፍራቸው አስቀመጣቸው።”

በዘመናት መካከል
ይሄ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ሥም ሲሆን ለዘላለም የሚኖር ነው የሚል ፍቺ ያለው ነው።“ለዘላለም የኖረው”ወይም “ዘወትር ሕያው የሆነው”

ተቀመጠ...ልብሱ...የራሱም ጸጉር
ይሄ ዓረፍተ ነገር እግዚአብሔርን ልክ እንደ ሰው ልብስ ለብሶ እንደሚቀመጥ ዓይነት አድርጎ ይገልፀዋል።እግዚአብሔር እንደዚህ ነው ማለት ሣይሆን ዳንኤል እግዚአብሔርን በራዕይ ያየው በዚህ መልኩ ነበር።

Daniel 7:10

አጠቃላይ መረጃ
ዳንኤል በሰማይ የሚካሄደውን ፍርድ በሚመለከት የተመለከተውን ራዕይና በትንቢተ ዳንኤል 17፡7 ላይ ስለተመለከተው አራተኛው እንስሳ የሚሰጠውን መልስ በሚመለከት ገለፃ ማድረጉን ይቀጥላል።

አጠቃላይ መረጃ
ከቁጥር 9 እስከ 14 ውስጥ የሚገኘው ክፍል ተመሳሳይ ትርጉምና ተምሣሌታዊ ቋንቋ ያለው ናቸው።ከዚህ የተነሣ አንዳንድ ቅጂዎች በቅኔያዊ ዘይቤ እንዲቀርብ አድርገውታል።

የውኃ ፈሳሽም ከፊቱ ይወጣ ነበር
ከእግዚአብሔር ፊት እሣቱ በፍጥነት የመውጣቱን ነገር ልክ እሣት ያለበት ወንዝ እንደሚፈስስ ዓይነት ተደርጎ ቀርቧል።“ልክ በወንዝ ውስጥ እንዳለ ውኃ እሣት ከፊቱ ወጣ”

በፊቱ
“በፊቱ” ቃል የሚያመለክተው ራሱን እግዚአብሔርን ነው።በትንቢተ ዳንኤል 7፡9 ላይ ከዘመናት በፊት የሚለውን ይመልከቱ።

ሚሊዮኖች
ይሄ ምናልባት የሚያመለክተው የተወሰነ ቁጥርን ሣይሆን ትልቅ ቁጥር ያለውን ሕዝብ ሊሆን ይችላል። “እልፍ አዕላፋት” ወይም “10 ሺዎች ጊዜ አሥር ሺዎች” ወይም “ለመቁጠር የሚያዳግቱ ሕዝቦች”

ፍርድም ሆነ
ይሄ ማለት ፈራጅ የሆነው እግዚአብሔር ማሰረጃውን ለማጤንና ፍርድ ለመሥጠት ተዘጋጅቷል ማለት ነው።“ፈራጁ ፍርድን ለመሥጠት ተዘጋጅቶ ነበር”ወይም “ዳኛው ተቀምጦ ነበር”

መፃሕፍትም ተገለጡ
እነዚህ መፃሕፍት በፍርድ ዙፋኑ ፊት ጠቃሚ ሆኑ ማስረጃዎችን የያዙ ናቸው።“ማስረጃ የያዙት መፃሕፍት ተከፈቱ”

Daniel 7:11

አጠቃላይ መረጃ
ዳንኤል በሰማይ የሚካሄደውን ፍርድ በሚመለከት የተመለከተውን ራዕይና በትንቢተ ዳንኤል 17፡7 ላይ ስለተመለከተው አራተኛው እንስሳ የሚሰጠውን መልስ በሚመለከት ገለፃ ማድረጉን ይቀጥላል።

አውሬው ተገደለ...እስኪቃጠል ድረስ
ይሄ በገቢር መልክ ለገለፅ ይችላል።“አራተኛውን አውሬ ገደሉት፤አካሉን አጠፉ፤እንዲያቃጥለውም ለሆነ ሰው ሰጡት”

አውሬው ተገደለ
አውሬው የእንዲገደል የተደረገበት ምክኒያት ዳኛው ጥፋተኛ መሆኑን በመወሰኑ ነው። “አውሬውን አረዱት”ወይም “ዳኛው ውሳኔውን ካስተላለፈ በኋላ አውሬውን ገደሉት”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አውሬው
ይሄ የሚያመለክተው አስር ቀንዶች ስለነበሩትና በትዕቢት ይናገር ስለነበረው አውሬ ነው።“እጅግ አስፈሪ የሆነ አውሬ”ወይም “በትዕቢት የተወጠረ ቀንዶች ያሉት”

የቀሩት አራቱ አውሬዎች
“የቀሩት ሶስቱ አውሬዎች” ቢባል የበለጠ ግልፅ ይሆናል።

ግዛታቸውም ተወሰደ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ዳኛው የመግዛት ሥልጣናቸውን ነጠቃቸው” ወይም “የገዢነታቸው ዘመን ተጠናቀቀ”

የሕይወታቸው ዕድሜ እስከ ዘመንና ዘመን ድረስ ተራዘመ
x

Daniel 7:13

አጠቃላይ መረጃ
አብዛኛዎቹ ከቁጥር 9 እስከ 14 ድረስ ያሉት ክፍሎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ተምሣሌታዊ አነጋገሮች ናቸው።ከዚህ የተነሣ ሌሎች ቅጂዎች በቅኔያዊ ዘይቤ ያቀርቧቸዋል።

አንዱ ሲመጣ ተመለከትኩ...የሰው ልጅ የሚመስል
ዳንኤል የተመለከተው ሰው የተለመደው ዓይነት ሰው አይደለም፡፤ነገር ግን የሰው ዓይነት ቅርፅ ነበረው።“በዚያን ሌሊት የሰው ልጅ የሚመስል ሲመጣ ተመለከትኩ።ማለትም የሰው ምስል ነበረው”

ከሰማይ ደመናት ጋር
“በሰማይ ላይ ካሉ ደመናት ጋር”

እስከ ዘመንና ጊዜ ድረስ
ይሄ የሚያመለክተው ዘላለማዊ የሆነውን እግዚአብሔርን ነው።ይህንን በትንቢተ ዳንኤል 7:9 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

ወደ ፊቱም አቀረቡት
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ለዘላለም በሸመገለው ፊት አቀረቡት” ወይም “በፊቱ ቀረበ”

ግዛትና ክብር መንግሥትም “**lk**” ተሰጠው
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የሰው ልጅ የሚመስለው ለመግዛት፤ክብርና መንግሥታዊ ሥልጣን ተሰጠው።”

የመንግሥት ሥልጣን
እዚህ ላይ ይሄ የሚያመለክተው “ሥልጣንን” ነው።

ወገኖች፤አህዛብና ቋንቋዎች
እዚህ ላይ “አህዛብ”እና “ቋንቋ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ የተለያዩ ወገኖችን ነው።ይህንን በትንቢተ ዳንኤል 3:4 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመለከቱ።

የዘላለም ነው ...በፍፁም የማይጠፋ ነው
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው።

Daniel 7:15

በሥጋዬ ውስጥ መንፈሴ ደነገጠች... የራሴም ራዕይ አስቸገረኝ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚያሣዩት ዳንኤል ምን ያህል ጭንቀት ውስጥ የገባ መሆኑን ነው።ሁለተኛው አባባል መንፈሱ ምን ያህል እንዳዘነ በማብራራት ስለ አንደኛው አባባል የበለጠ መረጃ ይሰጠናል።

በሥጋዬ ውስጥ መንፈሴ ደነገጠች
እዚህ ላይ “መንፈስ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ዳንኤል ራሱን ዳንኤልን ነው።“በውስጤ ሐዘን ገባ”

እዚያ ከቆሙት አንዱ
ይሄ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ከሚቆሙት ሰማያዊ ፍጥረታት አንዱ ነው። የዚህ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት 1/እነዚህ መላዕክት፤እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ መናፍስት2/እነዚህ ሞተው የነበሩና አሁን በሰማይ ውስጥ የሚገኙ ናቸው።

እውነቱን ጠየቅኩት
“እንዲነግረኝ”ወይም “እንዲያብራራልኝ”

እነዚህ ነገሮች
“የተመለከትኳቸው ነገሮች”

Daniel 7:17

ቁጥራቸው አራት የሆኑ እነዚህትላልቅ አውሬዎች
“እነዚህ አራት ታላላቅ እንስሳት”

አራት ነገሥታት ናቸው
“አራት ነገሥታትን ይወክላሉ።”

ከምድር የሚነሱ አራት ነገሥታት
እዚህ ላይ“ከምድር”ማለት በእርግጥም ሰዎች ናቸው ማለት ነው።“በምድር ላይ ሥልጣን የሚይዙ አራት ነገሥታት” ወይም“ከሕዝቦች መካካል የሚነሱና ነገሥታት የሚሆኑ አራት ሰዎች።”

ይወርሳሉ
“ይገዙታል”

ከዘላለም እስከ ዘላለም
ይሄሃሣብ የተደጋገመበት ምክኒያት ይሄ መንግሥት መጨረሻ እንደሌለው አፅንዖት ለመሥጠት ነው።

Daniel 7:19

እጅግ የሚያስደነግጥ
“እጅግ የሚያስፈራ”

በእግር መርገጥ
“በላዩ ላይ ተራምዶ አደቀቀው”

በራሱ ላይ አሥር ቀንዶች
“በአራተኛው አውሬ ላይ ያለው አሥር ቀንድ”

አደገ።ሶስቱ ቀንዶች ከመውደቃቸው በፊት
“አደገና ሶስቱም ቀንዶች በፊቱ ወደቁ።”ወይም “አደገና ሶስት ያህል የሚሆኑት ቀንዶች በፊቱ የወደቁት በእርሱ ምክኒያት ነው።”

በፊቱም ሶስት ቀንዶች ስለ ወደቁ
እዚህ ላይ “ወደቀ” የሚለው ቃል እምብዛም ደስ የማያሰኝን ቃል በተሻለ ቃል የመጠቀም ዘዴ ሲሆን ትርጉሙም ፈፅሞ ጠፉ ማለት ነው።“ሶስቱን ቀንዶች ያጠፋው”

በትዕቢት የሚናገር አፍ
“በጉራ የተቃኘው አፉ”ወይም “በጉራ የተሞላው የአዲሱ ቀንድ አንደበት”

አብሯቸው ከነበሩት ይልቅ ታላቅ ይመሰል ነበር
ዓይንና አፍ የነበረው ቀንድ ከሌሎች ቀንዶች ይልቅ ታላቅ ይመሰል ነበር።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Daniel 7:21

ይሄ ቀንድ
“አራተኛው ቀንድ” ይሄ የሚያመለክተው በትንቢተ ዳንኤል 17:20 ላይ የተጠቀሰውን ቀንድ ነው።

በዘመናት የሸመገለው እስኪመጣ ...ፍርድም እስኪሰጥ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የሸመገለው እስከሚመጣና ፍትህ እስኪገለጥ ድረስ”

በዘመናት የሸመገለው
ይሄ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ስያሜ ሲሆን ዘላለማዊ ስለመሆኑ አፅንዖት ለመስጠት ታስቦ የተደረገ ነው።ይሄንን በትንቢተ ዳንኤል 7:9 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

ቅዱሳኑም መንግሥቱን ወሰዱ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር መንግሥቱን ለተቀደሱ ሕዝቦቹ ሰጠ።”

Daniel 7:23

አጠቃላይ መረጃ
ከቁጥር 23 እስከ 27 ድረስ ያለው አብዛኛው ክፍል ተምሣሌታዊ ቋንቋ ነው።

ያ ሰው የተናገረው ይሄንን ነው
ይሄ ሰው በትንቢተ ዳንኤል 7:16 ላይ ዳንኤል የተገናኘው ነው።

ያ ሰው እንዲህ አለ
“ያ ሰው መለሰ”

ስለ አራተኛው አውሬና...ስለ አሥሩ ቀንዶች
“አራተኛውን አውሬ በተመለከተ...አሥሩን ቀንዶች በተመለከተ”ወይም “አሁን፤ስለ አራተተኛው አውሬ...አሁን፤ስለ አሥሩ ቀንዶች”

ይበላል...ያደቅቃትማል
እዚህ ላይ አራተኛው መንግሥት ዓለምን ያጠፋል ማለት ሣይሆን በጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ ያጠቃል፤ድል ያደርጋል እንዲሁም በምድር ላይ የሚገኙትን መንግሥታት ሁሉ ያጠፋል ማለት ነው።

ከዚህ መንግሥት አሥር ነገሥታት ይነሣሉ
አንዱ ሌላው እየተካ ይገዛሉ።ይሄ ግልፅ በሆነ መልኩ ሊገለፅ ይችላል።:”ከዚህ ከአራተኛው መንግሥት በላይ አስር ነገስታት በመከታተል ይነግሳሉ።”

ከእነርሱም በኋላ ሌላ ይነሳል
ይሄ ንጉሥ ከአስሩ መካከል አይደለም።ምናልባትም እርሱን “አስራ አንደኛው ንጉሥ”ማለቱ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።“ከዚያ በመቀጠል አስራ አንደናው ንጉሥ ኃያል እየሆነ ይመጣል”

ከፊተኞቹ የተለየ ይሆናል
“ከሌሎቹ አስር ነገሥታት የተለየ ይሆናል።”

Daniel 7:25

አጠቃላይ መረጃ
ዳንኤል በራዕይ የሚመለከተው ሰው መናገሩን ይቀጥላል።

አጠቃላይ መረጃ
ከቁጥር 23 እስከ 27 ድረስ ያለው አብዛኛው ክፍል ተምሣሌታዊ ቋንቋ ነው።

በልዑልም ላይ ቃልን ይናገራል
ይሄ ማለት አዲሱ ንጉስ ሙሉ በሙሉ የሚቃወምና በልዑሉ ላይ መጥፎ ነገሮችን የሚናገር ነው ማለት ነው።

ቅዱሳን
“የእግዚአብሔር የተቀደሱ ሕዝቦች”

ክብረ በዓላትንና ሕግን ይለውጥ ዘንድ
ሁለቱም ቃላት የሚያመለክቱት የሙሴን ሕግ ነው።በብሉይ ኪዳን ዘመን ክብረ በዓላት የኃይማኖት አስፈላጊ የሆኑ ክፍሎች ነበሩ።

እነዚህ ነገሮች በእጁ ተላልፈው ይሰጣሉ
እዚህ ላይ “በእጁ” የሚለው ቃል በቁጥጥር ሥር ማድረግን የሚያመለክት ነው።ይሄ በገቢር መልክ መገለፅ ይችላል።“አዲሱ ንጉሥ ኃይማኖታዊ ክብረ በዓላትንና ሕጎችን በበላይነት ይቆጣጠራል።”

አንድ ዓመት፤ሁለት ዓመት እና ግማሽ ዓመት
ይሄ “ሶስት ዓመት ተኩል” ማለት ነው።ይሄ እሥራኤላውያን የሚቆጥሩት የተለመደ ዓይነት አቆጣጠር አይደለም።“አንድ ዓመት ሲደመር ሁለት ዓመት ሲደመር ግማሽ ዓመት”

ፍርድም ይሆናል
ይሄ ዳኛው መረጃዎቹን ለመመርመርና ፍርድ ለመስጠት ይዘጋጃል ማለት ነው።“ዳኛው ፍርድን ይፈርዳል” ወይም “ዳኛው ለመፍረድ ይቀመጣል”

መንግሥታዊ ሥልጣኑን ይወስዱበታል
“የፍርድ ቤቱ አባላት ከአዲሱ ንጉስ መንግሥታዊ ሥልጣኑን ይነጥቁታል”

ንጉሣዊ ሥልጣን
አዚህ ላይ ይሄ የሚያመለክተው “ሥልጣንን”ነው።ይሄንን በትንቢተ ዳንኤል 7፡14 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

እስከ ፍፃሜም ድረስ ያፈርሱትና ያጠፉት ዘንድ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በመጨረሻ ያቃጥሉትና ያጠፉት ዘንድ”ወይም “በመጨረሻም ንጉሣዊ ሥልጣኑን ፈፅሞ ያጠፉታል።”

Daniel 7:27

አጠቃላይ መረጃ
በዳንኤል ራዕይ ውስጥ የተከሰተው ሰው ለዳንኤል መናገሩን ይቀጥላል።

አጠቃላይ መረጃ
ከቁጥር 23 እስከ 27 ድረስ ያለው አብዛኛው ክፍል ተምሣሌታዊ ቋንቋ ነው።

መንግሥትም ግዛትም ለሕዝብ ይጥ ዘንድ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር መንግሥትንና ግዛትን ለሕዝቡ ይሰጣል።”

መንግሥትና ግዛት
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ይህም መንግሥታዊ ሥልጣንን ሁሉ የሚመለከት ነው።

የመንግሥቱ ታላቅነት
“ታላቅነት” የሚለው አሕፅሮተ ሥም “ታላቅ” በሚለው ቅፅል ሊተረጎም ይችላል።“ስለ መንግሥታቱ ታላቅ የሆነው ነገር ሁሉ”

ከሰማይም በታች ያሉ መንግሥታት
“ከሰማይ በታች ያሉ ሁሉ” የሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር የሚያመለክተው በምድር ላይ የሚገኙትን መንግሥታት ነው።“.....በምድር ላይ ካሉ መንግሥታት መካከል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መንግሥቱ
“የልዑሉ መንግሥት”

የዘላለም መንግሥት
“ለዘላለም ፀንቶ የሚኖር መንግሥት” ወይም “መጨረሻ የሌለው መንግሥት”

የነገሩም ፍፃሜ እስከዚህ ድረስ ነው
ይሄ ማለት ዳንኤል ራዕዩን ማካፈል አቁሟል ማለት ነው።“በራዕይ ያየሁት ይህንን ነው” ወይም “በራዕይ የተመለከትኩት የመጨረሻው ገለፃዬ እዚህ ላይ ያበቃል”

ፊቴም ተለወጠብኝ
“ፊቴ ገረጣብኝ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 8

1 ንጉሥ ቤልሻዘር በነገሠ በሦስተኛው ዓመት አስቀድሞ ከተገለጠልን ራእይ በኋላ እኔ ዳንኤል ሌላ ራእይ አየሁ። 2 በራእዩም በኤሳም አውራጃ በሱሳ ግንብ ራሴን አየሁት፤ በራእዩም በኡባል የውሃ መውረጃ አጠገብ ነበርሁ፤ 3 ዓይኔን አንስቼ ስመለከት እነሆ፣ ሁለት ቀንዶች ያሉት አውራ በግ በወንቁ አጠገብ ቆሞ አየሁ፤ ቀንዶቹም ረጃጅሞች ነበር፤ ከቀንዶቹም አንዱ ከሌላው ይረዝማል፤ ረጅሙ ቀንድ የበቀለው ዘግይቶ ቢሆንም ከአጭሩ ይልቅ በርዝመቱ የላቀ ነበር። 4 አውራ በጉም ወደ ምዕራብ፣ ወደ ሰሜንና ወደ ደቡብ በቀንዱ ሲጎሽም አየሁ። ምንም ዐይነት እንስሳ ሊቋቋመው አልቻለም፤ ከእጁም ሊያድን የሚችል አልነበረም፤ የፈለገውን ሁሉ አደረገ፤ ታላቅም ሆነ። 5 ስለዚህ ነገር እያሰብሁ ሳለሁ፣ በዐይኖቹ መካከል ትልቅ ቀንድ ያለው አውራ ፍየል፣ መሬት ሳይነካ ምድርን ሁሉ እያቋረጠ በድንገት ከምዕራብ መጣ፤ 6 በወንዙ አጠገብ ቆሞ ወዳየሁት፣ ሁለት ቀንድ ወዳለው አውራ በግ ተንደርድ መጣበት፤ በታላቅ ቁጣም መታው። 7 እየወጋውና ሁለቱን ቀንዶቹን እየሰበረ፣ በጭካኔ አውራውን በግ ሲጎዳው አየሁ፤ አውራ በጉም ለመቋቋም ጉልበት አልነበረውም። ፍየሉ በምድር ላይ ጥሎ ረገጠው፤ አውራ ብጉንም ከፍየሉ እጅ ለማዳን የሚችል አልነበረም። 8 ፍየሉም ታላቅ ሆነ፤ ነገር ግን በኃይሉ በበረታ ጊዜ፣ ትልቁ ቀንዱ ተሰበረ፤ በቦታውም ወደ አራቱ የሰማይ ነፋሳት የሚያመለክቱ አራት ታላላቅ ቀንዶች በቀሉ። 9 ከእነዚህም ቀንዶች መካከል በአንዱ ላይ አንድ ትንሽ ቀንድ በቀለ፤ ወደ ደቡብ፣ ወደ ምሥራቅና ወደ ተከበረችው የእስራኤል ምድር በኃይል አደገ። 10 ከሰማይ ሠራዊት ጋር ጦርነት እስኪገጥም ድረስ አደገ፤ ከሰማይና ከክዋክብት ሠራዊት የተወሰኑትን ወደ ምድር ጣለ፣ ረጋገጣቸውም። 11 ከሰማይ ሠራዊት አለቃ ጋር እስኪተካከል ድረስ ራሱን ከፍ ከፍ አደረገ፤ የልዑሉንም የዘወትር መሥዋዕት ወሰደበት፤ የመቅደሱንም ስፍራ አረከሰ። 12 ከዐመፅ የተነሳም የቅዱሳን ሠራዊት ለፍየሉ ቀንድ አልፎ ተሰጠ፤ የሚቃጠል መሥዋዕቱም እንዲቆም ተደረገ። እውነትን ወደ ምድር ይጥላል የሚያደርገውም ሁሉ ይከናወንለታል። 13 ከቅዱሳኑም አንዱ ሲናገር ሰማሁ፤ ሌላውም ቅዱስ እንዲህ አለው፤ “ስለ ዘወትሩ መሥዋዕት፣ ለጥፋት ምክንያት ስለሆነው ዐመፅ፣ ከእግር በታች እንዲረገጡ ዐልፈው ስለሚሰቱት መቅደስና ሠራዊት የታየው ራእይ የሚፈጸመው መቼ ነው?” 14 እርሱም፣ “እስከ ሁለት ሺህ ሦስት መቶ ምሽቶችና ማለዳዎች ድረስ ይቆያል፤ ከዚያም መቅደሱ እንደገና ይነጻል” አለኝ። 15 እኔ ዳንኤል ራእዩን ስመለከትና ሳስተውል ሳለ፣ ሰውን የሚመስል ከፊት ለፊቴ ቆመ፤ 16 ከኡባልም፣ “ገብርኤል ሆይ፤ ለዚህ ሰው የራእዩን ትርጒም ንገረው” ብሎ የሚጮህ የሰው ድምፅ ሰማሁ። 17 እኔ ወደቆምሁበት እየቀረበ ሲመጣ፣ ደንግጬ በግንባሬ ተደፋሁ፣ እርሱም፣ “የሰው ልጅ ሆይ፤ ራእዩ ስለ ዘመኑ ፍጻሜ እንደሆነ አስተውል” አለኝ። 18 እየተናገረኝ ሳለ፣ በምድር ላይ በግንባሬ ተደፋሁ፤ በከባድ እንቅልፍም ተዋጥሁ፣ እርሱ ግን ዳሰሰኝና በእግሮቼ አቆመኝ። 19 እርሱም እንዲህ አለኝ፤ “ራእዩ በመጨረሻው ዘመን ሊሆን ያለውን የሚያመለክት ስለሆነ፣ በኋላ በቁጣው ዘመን ምን እንደሚሆን እነግርሃለሁ። 20 ያየኸው ሁለት ቀንዶች የነበሩት አውራ በግ፣ የሜዶንና የፋርስን መንግሥታት ያመለክታል። 21 ተባዕቱ ፍየል የግሪክ ንጉሥ ሲሆን፣ በዐይኖቹም መካከል ያለው ትልቁ ቀንድ የመጀመሪያው ንጉሥ ነው። 22 የተሰበረውን ቀንድ የተኩት አራቱ ቀንዶቹ፣ ከመንግሥቱ የሚወጡትን አራት መንግሥታትን ያመለክታሉ፣ ነገር ግን ከእርሱ ጋር የሚተካከል ኃይል አይኖራቸውም። 23 “በዘመነ መንግሥታቸው በስተ መጨረሻ፣ ዐመፀኞች ፍጹም እየከፉ በሚሄዱበት ጊዜ፣ አስፈሪ ፊት ያለው አታላይ ንጉሥ ይነሣል። 24 እጅግ ብርቱ ይሆናል፤ ነገር ግን በገዛ ኃይሉ አይደለም። አሠቃቂ ጥፋት ይፈጽማል፤ የሚያደርገው ሁሉ ይከናወንለታል፤ ኃያላን ሰዎችንና ቅዱሳኑን ሕዝብ ያጠፋል። 25 እጅግም ተንኮለኛ ስለሆነ በማታለል ይበለጽጋል፤ በልዑላን ልዑልም ላይ ይነሣል፤ ይሁን እንጂ እርሱም ይጠፋል ነገር ግን በሰው ኃይል አይደለም። 26 የተሰጠህ የምሽቱና የማለዳው ራእይ እውነት ነው፤ ነገር ግን ከብዙ ዘመን በኋላ የሚሆነውን ስለሚያመለክት ራእዩን ዘግተህ አትምበት።” 27 እኔ ዳንኤል ዐቅሜ ተሟጦ ነበር፤ ለብዙ ቀናት ታመምሁ፣ ተኛሁም። ከዚያም በኋላ ተነሥቼ ወደ ንጉሡ ሥራ ሄድሁ። ባየሁት ራእይ ተደናግጬ ነበር፤ ነገሩም የገባው ማንም አልነበረም።

Daniel 8:1

አጠቃላይ መረጃ
ምዕራፍ 7 እና 8 የተቀመጡት በቅደም ተከተል አይደለም::ይሄ የተከናወነው በምዕራፍ 6 ላይ በተጠቀሰው መሠረት ዳርዮስና ጢሮስ ከመግዛታቸው አስቀድሞና ብልጣሶር ንጉስ ሆኖ ይገዛ በነበረበት ወቅት ነበር::

አጠቃላይ መረጃ
በዳንኤል ራዕይ ውስጥ የሌሎች ነገሮች ተምሣሌቶች የሆኑ አውሬዎችን ተመልክቷል::በኋላ ላይ በራዕዩ ውስጥ የእነዚያን ተምሣሌቶች ትርጉም የሆነ ሰው ያስረዳዋል::

በሶስተኛውም ዓመት
“ሶስት ዓመት ሲሆነው”

ብልጣሶር
ይህ ሰው ከአባቱ በኋላ ንግስናውን የተረከበው የናቡከደነፆር ልጅ ነው::

ከመጀመሪያው በተጨማሪ ሌላ ራዕይ ተገለጥኝ
ይሄ አንባቢው ዳንኤል የተመለከተው ሁለተኛ ራዕዩ እንደሆነ እንዲያውቀት ለማድረግ የተሰጠ መረጃ ነው::“ሁለተኛ ራዕይ ተገለጠልኝ”

ቅጥር
የሚጠበቅና ቁጥጥር የሚደረግለት ቅጥር ያለው ከተማ

ሱሳ...ኤላም...ኡባል ቦይ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው::

ቦይ
ቦይ ጠባብና ሰው ሰራሽ የሆነ የውኃ ማስኬጂያ ነው::

Daniel 8:3

ሁለት ቀንዶች ነበሩት አውራ በግ
አውራ በጎች ሁለተ ቀንዶች እንደሚኖራቸው የታወቀ ነው:: እነዚህ ቀንዶች ግን ተምሣሌታዊ ትርጉም አላቸው::

አንዱ ግን ከሁለተኛው ከፍ ያለ ነበር
“ከአጭሩ ይልቅ ረዘም ያለው አስተዳደጉ ዝግታ ነበረው::አጭር የሆነው ግን ከእርሱ የበለጠ እያደገ ሄደ::”

አውራ በጉ ሲፈተለክ አየሁት
“አውራ በጉ ሲሮጥ አየሁት”ወይም “አውራ በጉነን በጣም ሲሮጥ አየሁት”

ከእጁም የሚያድን አልነበረም
አውራ በጎች እጆች የላቸውም::እዚህ ላይ “እጅ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የአውራውን በግ ኃይል ነው::“ማንንም ቢሆን ከእርሱ እጅ ለማዳን” ወይም “ማንንም ቢሆን ከሥልጣኑ ለማዳን”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Daniel 8:5

በምድር ሁሉ ፊት
“በምድር ሁሉ ፊት” የሚለው ሐረግ ከሩቅ ሥፍራ ነው የመጣው ለሚለው ሃሣብ በተጋነነ መልኩ የቀረበ ነው።“ከምድር ገፅ ፊት ካለ ከሩቅ ሥፍራ”

ፍየሉ በዓይኖቹ መካከል ታላቅ ቀንድ ነበረው
ፍየሎች በራሳቸው ጎንና ጎን ሁለት ቀንዶች አሏቸው።ይሄ ምስል ማብራሪያ የሚያስፈልገው ነው።“ፍየሉ ግንባሩ መሐል ላይ ታላቅ የሆነ ቀንድ ነበረው።”

አውራ በጉን በወንዙ ፊት ቆሞ አየሁት
ይሄ ሐረግ ፍየሉ የት ሥፍራ ላይ እንደነበረ መረጃ ለመስጠት የቀረበ ነው።

በኃይሉም ቁጣ
“በጣም ተበሳጭቶ ነበር”

Daniel 8:7

ረገጠው
አንድን ነገር ረግጦ ማድቀቅ

አውራ በጉ በኃይሉ
“አውራ በጉ ከፍየሉ ይልቅ በበለጠው ኃያልነቱ”

ፍየሉ እጅግ ታላቅ ሆነ
“ፍየሉ ታላቅና ብርቱ ሆነ”

ትልቁ ቀንድ ተሰበረ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ትልቁን ቀንድ የሆነ ነገር ሰበረው”

ወደ አራቱም የሰማይ ነፋሳት
እዚህ ላይ“አራቱ የሰማይ ነፋሳት” ዘይቤያዊ አገላለፅ ሲሆን ነፋሣት የሚነፍሱባቸውን አራቱን ዋና ዋና አቅጣጫዎች የሚያመለክት ነው። (ሰሜን፤ምሥራቅ፤ደቡብ፤ምዕራብ)“ከአራት የተለያዩ አቅጣጫዎች”

Daniel 8:9

እጅግ ታላቅ ሆነ
“ነገር ግን እጅግ ታላቅ ሆነ”

ወደ ደቡብም ወደ ምሥራቅም ወደ መልካሚቱም ምድር
ይሄ ምናልባትም ወደ እነዚያ አቅጣጫዎች ማመልከት ማለት ሊሆን ይችላል።“ደወ ደቡብ አቅጣጫ አመለከተ።ከዚያም ወደ ደቡብ ካመለከተ በኋላ ወደ መልካሚቱ የእሥራኤል ምድር አቅጣጫ ተጓዘ።”

መልካሚቱ ምድር
ይሄ የእሥራኤልን ምድር የሚያመለክት ነው።

እስከ ሠራዊትም አለቃ ድረስ ራሱን ከፍ አደረገ
እዚህ ላይ ቀንዱ የሰው ችሎታ ተሰጥቶት በጦርነት ውስት እንዲሳተፍ ሆኗል።

ከሠራዊቱ የተወሰኑ ከፍሎች ...ወደ ምድር ተጣሉ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ቀንዱ አንዳንድ የሠራዊቱን ክፍሎችና ከዋክብትን ወደ ምድር ጣለ።”

ረገጣቸውም
እዚህ ላይ ቀንዱ የሰው ችሎታ ተሰጥቶት ከዋክብትንና ሠራዊቱን በእግሩ ይረግጣል።

Daniel 8:11

ሃሣብን ማያያዣ
ዳንኤል ቀንዱን በተመለከተ በራዕይ ያየውን ነገር መግለፁን ይቀጥላል።

አጠቃላይ መረጃ
ቀንዱ የሰው ብቃቶች ተሰጥተውታል።

የሠራዊቱ አለቃ
ይሄ የሚያመለክተው የመላዕክት ሠራዊት አለቃ የሆነውን ራሱን አግዚአብሔርን ነው።

ከእርሱን የተነሳ የዘወትሩ መሥዋዕት ተሻረ
“ተሻረ”ማለት ቀንዱ መሥዋዕት ማቅረቡን አቋረጠ ማለት ነው።እዚህ ላይ “እርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሠራዊት አለቃ የሆነውን እግዚአብሔርን ነው።“ሰዎች በየጊዜው የሚያቀርቡለትን መሥዋዕት እንዲቆም አደረገው።”

የመቅደሱ ሥፍራ ፈረሰ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ቤተመቅደሱን አረከሱት”

የሰማይ ሠራዊት ሲረገጡ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል። “ቀንዱ የሰማይ ሠራዊትን ረገጠ”

ሁለት ሺህ ሶስት መቶ ማታና ጥዋት
ይሄ ምናልባትም ወደ እነዚያ አቅጣጫዎች አመለከተ ማለት ሊሆን ይችላል። እዚህ ላይ“ማታና ጥዋት” አጠቃላይ አነጋገር ሲሆን በመሐል ያሉ ነገሮችን ሁሉ የሚያካትት ማለትም ሙሉ ቀን ወይም ሃያ አራት ሰዓት ማለት ነው።“2,300 የፀሐይ መግቢያዎችና የፀሐይ መውጫዎች”

ከዚያም በኋላ መቅደሱ ይነፃል
“መቅደሱ ነፅቶ ዳግም ወደ ተገቢው ሥርዓቱ ይመለሳል”

Daniel 8:15

በኡባል ወንዝ መካከል የሚጮኸውን የሰው ድምፅ
እዚህ ላይድምፁን በመስናት ብቻ የሰው ማንነት እንዲሰጠው ሆኗል።“ከኡባል ወንዝ የሚጮህ ሰው”

የኡባል ቦይ
ቦይ ሰው ሰራሽ የሆነ ጠባብ የውኃ ማስኪያጃ ነው።

በግምባሬ ተደፋሁ
ይሄ አንድ ሰው በመሬት ላይ ሙሉ በሙሉ በሰውነቱ የሚወድቅበት የአምልኮ ዓይነት ነው።

በመጨረሻ ዘመን
“የመጨረሻ ቀናት”ወይም “የዓለም መጨረሻ”። “ይሄ የዓለም መጨረሻ የሚያመለክት ሣይሆን የመጨረሻው ዘመን ከመድረሱ በፊት ሊሆኑ ስላሉ ክስተቶች የሚያወሳ ነው።”

Daniel 8:18

ጥልቅ እንቅልፍ
እንደዚህ ዓይነት እንቅልፍ አንድ ሰው በከባድ እንቅልፍ ከመያዙ የተነሳ ለመንቃት እንኳን የሚያዳግተው የእንቅልፍ ዓይነት ነው።

በመቅሠፍቱ ዘመን
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ፍርድ የሚሰጥበትን ሁኔታ ነው።ይሄ የበለጠ ግልፅ ሊደረግ ይችላል።“እግዚአብሔር በቁጣው ፍርድ በሚፈርድበት ወቅት”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በመጨረሻ ዘመን የሚሆነውን
“የዓለም መጨረሻ በሚሆንበት ወቅት”

Daniel 8:20

አጠቃላይ መረጃ
በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በራዕይ ስላያቸው ተምሣሌታዊ ነገሮች መልአኩ ለዳንኤል ገለፃ ያደርግለታል።በመሠረቱ ቀንዶቹና እንስሳቱ የሚወክሉት የሰው ልጆች የሆኑ ገዢዎችንና መንግሥታትን ነው።

የነበሩ ሁለት ቀንዶች
“ሁለት ቀንዶች...የሚወክሉት”

የሜዶንና የፋርስ ነገሥታት
ለእነዚህ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት፦1/የሜዶንንና የፋርስን ነገሥታት የሚያመለክት ነው። ወይም 2/ይሄ ንጉሱ የሜዶንና የፋርስን መንግስታት የሚያመለክትበት አጠራር ነው።“የሜዶንና የፋርስ መንግሥታት”

በዓይኖቹ መካከል ያለው ታላቅ ቀንድ
“በዓይኖቹ መካከል ያለው ታላቅ ቀንድ የሚወክለው”

Daniel 8:22

አጠቃላይ መረጃ
በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በራዕይ ስላያቸው ተምሣሌታዊ ነገሮች መልአኩ ለዳንኤል ገለፃ ያደርግለታል።በመሠረቱ ቀንዶቹና እንስሳቱ የሚወክሉት የሰው ልጆች የሆኑ ገዢዎችንና መንግሥታትን ነው።

እርሱም በተበረ ጊዜ በእርሱ ፋንታ አራቱ ተነሱ
“ታላቁ ቀንድ በተሰበረ ጊዜ ሌሎች አራት ተነሱ”

ከወገኑ አራት መንግሥታት ይነሳሉ
አራቱ ቀንዶች የሚወክሉት አራቱን አዳዲስ መንግስታትን ነው።ይሄ የለጠ ግልፅ ሊደረግ ይችላል።“አራቱን መንግሥታት የሚወክሉ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ የመጀመሪያው መንግሥት የተከፋፈለ ይሆናል።”

ነገር ግን በኃይል አይተካከሉትም
“ሆኖም በታላቁ ቀንድ ከተመሰለው ንጉስ ጋር የሚመጣጠን ጉልበት አይኖራቸውም።”

በእነዚያ መንግሥታትየመጨረሻ ዘመናቸው
“እነዚያ መንግሥታት መጨረሻቸው ሲደርስ”

በተሞላች ጊዜ
“ሙሉ በሆነ ጊዜ” ወይም“ሥራቸውን ባጠናቀቁ ጊዜ”

ፊተ ጨካኝ
ይሄ የእምቢተኛ ፊት ያለው ወይም ለመታዘዝ ፈቃደኛ ያልሆነ

Daniel 8:24

አጠቃላይ መረጃ
በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በራዕይ ስላያቸው ተምሣሌታዊ ነገሮች መልአኩ ለዳንኤል ገለፃ ያደርግለታል።በመሠረቱ ቀንዶቹና እንስሳቱ የሚወክሉት የሰው ልጆች የሆኑ ገዢዎችንና መንግሥታትን ነው።

በራሱ ኃይል አይደለም
“ኃይሉን የሚያገኘው በሌላ አማካይነት ነው”

ማታለል እየበለፀገ እንዲሄድ ያደርጋል
እዚህ ላይ “ማታለል” የሚለው ቃል የሚገለፀው ባለፀጋ እየሆነ አንደሚሄድ ሰው ነው።“የማታለል መጠኑ እየጨመረ ይሄዳል።”

በእጁ ያከናውናል
እዚህ ላይ“እጅ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው አገዛዙን ነው።“በአገዛዙ ሥር”

የነገሥታት ንጉሥ
ይሄ የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው።

እርሱ ይሰበራል
እዚህ ላይ“እርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሥልጣኑን ነው።ይሄ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል።“በማንም የሰው ጉልበት ሣይሆን”ወይም“በመለኮታዊ ኃይል”

Daniel 8:26

አጠቃላይ መረጃ
መልአኩ ራዕዩን በሚመለከት በሰም ማህተም እንደሚዘጋ የተጠቀለለ ፅሑፍ በሚመስል መልኩ ነው የሚናገረው።ማህተሙ እስኪከፈት ድረስ ይሄንን ፅሑፍ ማንም ሰው እንዳይመለከተው ያግደዋል።“በራዕዩ ተመልክተህ የፃፍከውን ዝጋውና በማሕተም አትመው” ወይም“ራዕዩን በሚመለከት ለማንም ሰው አትናገር”

Daniel 8:27

ተረታሁ፤አያሌ ቀንም ታመምኩ
“ደክሞኝና ሕመም ይዞኝ ለብዙ ቀናት አልጋዬ ላይ ተኛሁ”

የንጉሡን ሥራ ላከናውን ሄድኩ
“ንጉሡ የሰጠኝን ሥራ ላከናውን ሄድኩ”

ስለ ራዕዩም እደነቅ ነበር
“ስለ ራዕዩ እገረም ነበር”ወይም “የሕልሙን ጉዳይ በተመለከተ ግራ ተጋብቼ ነበር”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 9

1 የሜዶናዊው የአርጤክስስ ልጅ ዳርዮስ በባቢሎን በነገሠ በመጀመሪያው ዓመት **2** በዘመነ መንግሥቱ በመጀመሪያው ዓመት፣ እኔ ዳንኤል ለነቢዩ ኤርምያስ በተሰጠው የእግዚአብሔር ቃል መሠረት፣ የኢየሩሳሌም መፈራረስ ሰባ ዓመት እንደሚቆይ ከቅዱሳት መጻሕፍት አስተዋልሁ። **3** ስለዚህ ማቅ ለብሼ በራሴም ላይ ዐመድ ነስንሼ በጾምና በጸሎት፣ በምልጃም ፊቴን ውደ ጌታ አምላክ አቀናሁ። **4** ወደ እምላኬ ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ብዬ ጸለይሁ፣ ተናዘዝሁም፤ “ከሚወዱህና ትእዛዝህን ከሚፈጽሙ ሁሉ ጋር የፍቅር ቃል ኪዳንህን የምትጠብቅ፣ ታላቅና የተፈራህ አምላክ ጌታ ሆይ፤ **5** እኛ ኃጢአት ሠርተናል፣ በድለናልም፣ ክፋትን አድርገናል፣ ዐምፀናልም፣ ከትእዛዝህና ከሕግህ ዘወር ብለናል። **6** ለንጉሦቻችን፣ ለልዑሎቻችንና ለአባቶቻችን እንዲሁም ለምድሪቱ ሕዝብ ሁሉ በአንተ ስም የተናገሩትን አገልጋዮችህን ነቢያትን አልሰማንም። **7** “ጌታ ሆይ፤ አንተ ጻድቅ ነህ፤ ነገር ግን በአንተ ላይ ስለ ሠራነው ታላቅ ክፋት እኛን በበተንህባቸው አገሮች ሁሉ የምንገኝ የይሁዳ ሰዎች፣ የኢየሩሳሌምና የመላው እስራኤል ሕዝብ፣ በሩቅም ሆነ በቅርብ ያለን በዚህ ቀን ኀፍረት ተከናንበናል። **8** እግዚአብሔር ሆይ፤ እኛና ንጉሦቻችን፣ ልዑሎቻችንና አባቶቻችን በአንተ ላይ ኃጢአት ስለ ሠራን ኀፍረት ተከናንበናል። **9** ምንም እንኳ በእርሱ ላይ ያመፅን ብንሆን፣ ጌታ አምላካችን ይቅር ባይና መሐሪ ነው። **10** እግዚአብሔር አምላካችንን አልታዘዝነውም፤ ደግሞም በአገልጋይቹ በነቢያት በኩል የሰጠንን ሕግ አልጠበቅንም፤ **11** መላው እስራኤል አንተን ባለመታዘዝ ሕግህን ተላልፎአል፤ ዘወርም ብሎአል።በአንተ ላይ ላይ ኃጢአትን ስለ ሠራን፣ በእግዚአብሔር አገልጋይ በሙሴ ሕግ የተጸው መሐላና ርግማን ፈሰሰብን። **12** ታላቅ ጥፋት በእኛ ላይ በማምጣት፣ የተነገረውን ቃል ፈጸምህብን፤ በኢየሩሳሌም ላይ የተደረገውን የሚያህል ከሰማይ በታች ከቶ የለም። **13** በሙሴም ሕግ እንደ ተጻፈው፤ ይህ ሁሉ ጥፋት በእኛ ላይ ደረሰ፤ ሆኖም ከኃጢአታችን በመመለስና እውነትህን በመከተል ከአምላካችን ከእግዚአብሔር ምሕረትን አልፈለግንም። **14** አምላካችን እግዚአብሔር በሚያደርገው ሁሉ ጻድቅ ነውና፣ በእኛ ላይ እግዚአብሔር ጥፋት ከማምጣት አልተመለሰም፣ እኛም አልታዘዝነውም። **15** አሁንም ሕዝብህን ከግብፅ ምድር በብርቱ እጅ ያወጣህ፣ እስከዚህም ቀን ድረስ ስምህ እንዲታወቅ ያደረግህ፤ ጌታ አምላካችን ሆይ፤ ኃጢአት ሠርተና፣ አንተንም በድለናል። **16** ጌታ ሆይ እንዳደረግኸው የጽድቅ ሥራህ ሁሉ፣ ከከተማህ ከኢየሩሳሌም፣ ከቅዱሱም ተራራህ ቁጣህን መልስ፣ በእኛ ኃጢአትና በአባቶቻችን በደል ምክንያት ኢየሩሳሌምና ህዝብህ በዙሪያችን ባሉት ዘንድ መሣለቂያ ሆነዋል። **17** አሁንም አምላካችን ሆይ፣ የአገልጋይህን ጸሎትና ልመና ስማ። ጌታ ሆይ፤ ስለ ስምህ ስትል ፊትህን ወደፈረሰው መቅደስ መልስ። **18** አምላክ ሆይ፤ ጆሮህን አዘንብለህ ስማ፣ ዐይንህን ገልጠህ መጥፋታችንንና ስምህ የተጠራበትን ከተማ ተመልከት። ልመናችንን የምናቀርበው ስለ ጽድቃችን ሳይሆን፣ ስለ ታላቅ ምሕረትህ ነው። **19** ጌታ ሆይ፣ አድምጥ! ጌታ ሆይ፤ ይቅር በል! ጌታ ሆይ፤ ስማ! አድርግም፤ ስምህ በከተማንህና በሕዝብህ ላይ ተጠርቶአልና አምላኬ ሆይ፣ ስለ ስምህ ስትል አትዘግይ።” **20** እኔም እየተናገርሁና እየጸለይሁ፣ የራሴንና የሕዝቤን የእስራኤልን ኃጢአት እየተናዘዝሁ፣ ስለ ቅዱስ ተራራውም እግዚአብሔር አምላኬን እየለመንህ **21** እየጸለይሁም ሳለሁ፣ በመጀመሪያው ራእይ አይቼው የነበረው ሰው ገብርኤል፣ በሠርክ መሥዋዕት ጊዜ በፍጥነት እየበረረ ወደ እኔ መጣ። **22** እርሱም እንዲህ ብሎ አስረዳኝ፤ “ዳንኤል ሆይ፣ አሁን ጥበብንና ማስተዋልን ልሰጥህ መጥቻለሁ **23** አንተ እጅግ የተወደድህ ስለሆንህ፣ ገና መጸለይ ስትጀምር መልስ ተሰጥቶአል፣ አኔም ይህን ልነግርህ መጣሁ። ስለዚህ መልእክቱን ልብ በል፤ ራእዩንም አስተውል። **24** ዐመፃን ለማስቆም፣ ኃጢአትን ለማስወገድ፣ በደልን ለማስተሰረይ፣ ዘላለማዊ ጽድቅን ለማምጣት፣ ራእይንና ትንቢትን ለማተምና እጅግ ቅዱስ የሆነውን ለመቀባት ስለ ሕዝብህና ስለ ተቀደሰችው ከተማህ ሰባ ሱባዔ ታውጇል። **25** ይህንን ዕወቅ አስተውለውም፤ ኢየሩሳሌምን ለማደስና ለመጠገን ዐዋጁ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ገዢው መሲሕ እስከሚመጣበት ጊዜ ድረስ ሰባት ሱባዔና ስልሳ ሁለት ሱባዔ ይህናል። ኢየሩሳሌም ከጎዳናዎቿና ከቅጥሮቿ ጋር ትታደሳለች፤ ይህ የሚሆነው ግን በመከራ ጊዜ ነው። **26** ከሥልሳ ሁለት ሱባዔ በኋላ መሲሑ ይገደላል፤ ምንም አይቀረውም። የሚመጣው አለቃ ሰዎችም ኢየሩሳሌምንና ቤተ መቅደሱን ይመደስሳል። ፍጻሜውም እንደ ጎርፍ ይመጣል፤ ጦርነት እስከ መጨረሻው ይቀጥላል፤ ጥፋትም ታውጇል። **27** አለቃው ከብዙዎች ጋር ለአንድ ሱባዔ ቃል ኪዳኑን ያጸናል፤ በሱባዔውም እኩሌታ መሥዋዕትና ቁርባን ማቅረብን ያስቀራል። በርኵሰቱ ጫፍ ላይ ጥፋቱን የሚፈጽመው ይገለጣል። የታወጀው ፍርድ ጥፋትን በሚያመጣው ላይ የሚፈስ ይሆናል።

Daniel 9:1

አጠቃላይ መረጃ
ምዕራፍ 7 ና 8 በቅደም ተከተላቸው መሠረት የተቀመጡ አይደሉም። ብልጣሶር ንጉሥ ከመሆኑ በፊት የተከናወኑ ናቸው።አሁን ደግሞ ምዕራፍ 9 በምዕራፍ 6 ላይ ንጉሥ ወደሆነው ወደ በዳርዮስ ዘመን ወደተከናወኑት ክስተቶች ይመለሳል።

በባቢሎን መንግሥት ላይ ንጉሥ ሆኖ የተሾመው አሕሻዊሮስ ነበረ
ይሄ አሕሻዊሮስ ማን እንደነበረ የጀርባ ታሪኩ መረጃ ለመስጠት ታስቦ የተደረገ ነው።

በባቢሎን መንግሥት ላይ ንጉሥ ሆኖ የተሾመው
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በባቢሎን ግዛት ሁሉ የነገሰው”ወይም “ባቢሎናውያንን ድል የነሳቸው”

በመንግሥቱ
“በአገሩ ላይ”ወይም “በግዛቱ ላይ”

ያህዌ
ይሄ በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ለሕዝቡ የገለፀላቸው ስሙ ነው።

አያሩሣሌም በምትተውበት በሰባው ዓመት
“ከዚህ በኋላ ኢየሩሣሌም ትጠፋለች፤ለሰባ ዓመትም እንደፈረሰች ትቀራለች”

መተው(ተ ይጠብቃል)
ይሄ ማንም ሰው አያግዛትም ወይም በዚያን ወቅት ማንም ቢሆን ኢየሩሣሌምን አያድሳትም ማለት ነው።

Daniel 9:3

ፊቴን ወደ ወደ ጌታ አምላክ አቀናሁ
እዚህ ላይ“ፊት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የዳንኤልን መሻት ነው።“ትኩረቴን በጌታ በእግዚአብሔር ላይ አደረግኩ” ወይም “የሃሣቤን አቅጣጫ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለስ አደረግኩ”

እርሱን ለመፈለግ
እግዚአብሔርን ለማወቅና ርሱን ለማስደሰት የሚፈልጉ ሰዎች እየዘሩ እንደሚፈልጉት ዓይነት ነው የቀረበው።

መፆም፤ማቅ መልበስና በአመድ ላይ መቀመጥ
እነዚህ ንሥሐ የመግባትና የማዘን ተምሣሌታዊ ድርጊቶች ናቸው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ስከ ኃጢአታችን ንሥሐ ገባሁ
“ኃጢአታችንን ተናዘዝኩ”

ቃል ኪዳንንና ምሕረትን የምትጠብቅ
“በቃል ኪዳንህ ውስጥ አደርገዋለሁ ያልከውን ሁሉ የምታደርግና እነዚያን በታማኝነት የምትወዳቸው”

Daniel 9:5

አጠቃላይ መረጃ
ዳንኤል ስለ እሥራኤል ሕዝብ መፀለዩን ይቀጥላል።

በድለናል፤ክፋትንም አድርናል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ቃላት አንድ ሃሣብን የሚያንፀባርቁ ቢሆኑም አፅንዖት ለመሥጠት ሲባል በሁለት የተለያዩ መንገዶች ይገልፁታል።

ትዕዛዛትህና ፍርድህ
“ትዕዛዝ”እና “ፍርድ”የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን የሚያመለክቱትም በአጠቃላይ ሕጉን ነው።

ባሪዎችህን አልሰማንም
እዚህ ላይ“አልሰማንም”ማለት መልዕክታቸውን ሰምተን አልታዘዝንም ማለት ነው።“የነቢያቶችህን መልዕክት አልሰማንም”

በስምህ የተናገሩትን
እዚህ ላይ “ሥም”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ሥልጣን ነው።“በሥልጣን የተነገረ” ወይም“አንተን በመወከል የተናገረ”

ለአገሩም ሕዝብ
እዚህ ላይ“አገሩ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው እሥራኤልን ነው።“የእሥራኤል ሕዝብ”

Daniel 9:7

አጠቃላይ መረጃ
ዳንኤል ስለ እሥራኤል ሕዝብ መፀለዩን ይቀጥላል።

ጌታ ሆይ ፅድቅ ለአንተ ነው
እዚህ ላይ ፃድቅ የሚለው ቃል ልክ “ፅድቅ”እግዚአብሔር ባለቤቱ እንደሆነ ዕቃ ተደርጎ ነው።“ፅድቅ” የሚለው አሕፅሮተ ሥም “ፃድቅ”ተብሎ ሊገለፅ ይችላል።“ጌታ ሆይ አንተ ፃድቅ ነህ”

ለእኛ ዛሬ የፊት ሐፍረት ሆኖብናል...ለሕዝባችን
ሐፍረት የሚለው ቃል እዚህ ሥፍራ ላይ የተገለፀው ልክ“ሐፍረት”ሕዝቡ ባለቤት እንደሆነበት ዕቃ ተደርጎ ነው።“ሐፍረት” የሚለው ተውላጠ ሥም “አፈረ”ተብሎ ሊገለፅ ይችላል።“እኛን በሚመለከት ግን በሰራነው ሥራ አፍረናል...ሕዝቡ”

ዛሬ ያለነው እኛ
“እኛ”የሚለው ቃል ዳንኤልንና እሥራኤልን የሚያካትት ቢሆንም እግዚአብሔርን ግን አያጠቃልልም።

የፊት ሐፍረት ሆኖብናል
ይሄ ዘይቤያዊ አነጋገር ሐፍረታቸው ለሰው ሁሉ የሚታይ ነው ማለት ነው።

በአንተ ላይ በበደልነው በደል ምክኒያት
“ምክኒያቱም በእጅጉ በድለንሃል” ወይም“ ምክኒያቱም ለአንተ ፈፅሞ ታማኞች አልነበርንም።”

Daniel 9:9

አጠቃላይ መረጃ
ዳንኤል ስለ እሥራኤል ሕዝብ ወደ ጌታ መፀለዩን ይቀጥላል።

ምህረትና ይቅርታ ለጌታ ለአምላካችን ናቸው
እነዚህ ባህርያት ስላሉት የጌታ ንብረቶች እንደሆኑ ተደርጎ ነው የሚነገረው።“አምላካችን እግዚአብሔር በምሕረት የተሞላና ይቅር ባይ ነው”

Daniel 9:12

አጠቃላይ መረጃ
ዳንኤል ስለ እሥራኤል ሕዝብ ወደ ጌታ መፀለዩን ይቀጥላል።

ከሰማይ ሁሉ በታች
ይሄ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው።“በዓለም ሁሉ”

ምንም አልደረገም
“ምንም ነገር አልተደረገም።“ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።” “ምንም ነገር አልተከሰተም”

በኢየሩሣሌም እንደተደረገው
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በኢየሩሣሌም ያደረግከው”

በሙሴ ሕግ እንደተፃፈ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሙሴ በሕጉ እንደፃፈው”

ከበደላችን ዘወር እንድንል
እዚህ ላይ ከክፉ ነገር ራስን የማቀብ ድርጊትን ዘወር ከማለት ጋር በማመሳሰል ይነገራል። “ከክፉ ድርጊቶቻችን መታቀብ”

እግዚአብሔር ክፉ ነገርን አዘጋጅቷል
“እግዚአብሔር ይህንን ጥፋት አዘጋጅቷል”

ድምፁን አልታዘዝንም
እዚህ ላይ “ድምፅ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔር ያዘዛቸው ነገሮችን ነው።“እርሱ ያዘዘንን ነገር አላደረግንም”

Daniel 9:15

ኃያል በሆነ እጅ
እዚህ ላይ “ኃያል እጅ”የሚለው ቃል ብርታት ለሚለው ሜቶኒም ነው።

ዛሬም ለራስህ ዝነኛ የሆነ ሥምን አድርገሃል
እነዚህ ሁለት አንቀፆች በመሠረቱ ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን አንድ ላይ እንዲሆኑ የተደረጉት ኃጢአት ምን ያህል ክፉ ነገር እንደሆነ አፅንዖት ይሰጡ ዘንድ ነው።

እኛ ኃጢአትን ሠርተናል፤ክፋትንም አድርገናል
እነዚህ ሁለት አንቀፆች በመሠረቱ ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ቢሆንም “እኛ”የሚለው ቃል እግዚአብሔርን አያካትትም።

ቁጣህና መአትህ
“ቁጣ”እና “መአት”የሚሉት ቃላት በመሠረቱ ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ወደ ድርጊት በሚገባበት ወቅት የእግዚአብሔር ቁጣ ምን ያህል አደገኛ ሊሆን እንደሚችል አፅንዖት ይሰጣል።

የተቀደሰው ተራራህ
ይሄ ተራራ ቅዱስ የሆነበት ምክኒያት እግዚአብሔር መቅደስ እዚያ በመሆኑ ምከኒያት ሊሆን ይችላል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የእኛ ኃጢአት...አባቶቻችን
እዚህ ላይ“ኃጢአት”የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ሣይሆን ዳንኤልንና እሥራኤልን ነው።

መሰደቢያ
“ለአክብሮት ማጣት ዒላማ”

Daniel 9:17

አሁን
እዚህ ላይ “በአሁኗ ደቂቃ”ማለት ሣይሆን የሚቀጥለው የዳንኤል የፀሎት ምዕራፍ ሊጀመር ስለመሆኑ የማሳያ መንገድ ነው።

ባሪያህ...ስለ ምሕረት የሚለምነውን የእርሱን ልመና
“ባሪያህ” እና “የእርሱ”የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ዳንኤልን ነው። እግዚአብሔርን ስለማክበሩ እንደ ምልክት ይሆን ዘንድ ስራሱ በሶስተኛ መደብነት(ሰዋሰው)ይናገራል።

ልመናና ምሕረት
“ስለ ምሕረት መለመን”

ፊትህን አብራ
ፀሐፊው እገዛ በማድረጉ የእግዚአብሔር ፊት እንደ ብርሀን እንዳበራ በሚመስል መልኩ ይናገራል። “በቅንነት እገዛ ማድረግ” ወይም “ማድላት”

መቅደስህ
ይሄ የሚያመለክተው በኢየሩሣሌም ያለውን ቤተመቅደስ ነው።

ጆሮህን አዘንብለህ ስማ
“ጆሮን ማዘንበል”የሚለው ቃል ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን ማዳመጥ ማለት ነው።እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ዳንኤል ለሚፀልየው ፀሎት እግዚአብሔር ትኩረት እንዲሰጠው ላለው ፍላጎት አፅንዖት ይሰጡታል።“እባክህን ስማ“

ዓይንህን ገልጠህ ተመልከት
“ዓይን መግለጥ” የሚለው ቃል ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን ማየት ማለት ነው።“ዓይንን መግለጥ”ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን ማዳመጥ ማለት ነው። እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ዳንኤል ለሚፀልየው ፀሎት እግዚአብሔር ትኩረት እንዲሰጠው ላለው ፍላጎት አፅንዖት ይሰጡታል።“አስበን”ወይም “ተመልከት”

ሥምህ ተጠርቶባታል
እዚህ ላይ“ሥም”የሚወክለው ባለቤት መሆንን ነው።“የአንተ ከተማ ናት” ወይም “አንተ ንብረት ናት”

አትዘግይ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በፍጥነት ወደ ተግባር ግባ”

Daniel 9:20

ሕዝቤ እሥራኤል
“ወገኔ የሆነው የእሥራኤል ሕዝብ”

የእግዚአብሔር የተቀደሰ ተራራ
ተራራዎቹ የተቀደሱ የሚሆኑት በቤተ መቅደሱ ምክኒያት ሊሆን ይችላል።“የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ያለበት ተራራ”

ሰው የሆነው ገብርኤል
የሰው መልክ ይዞ በትንቢተ ዳንኤል18:16 ላይ የተገለጠውም ራሱ መልአኩ ገብርኤል ነው።“ሰው መስሎ የተገለጠው ገብርኤል”

አስቀድሜ በራዕይ ያየሁት
ይሄ ዳንኤል ነቅቶ እያለ የተመለከተው የመጀመሪያው ራዕይን የሚመለከት ሊሆን ይችላል።“ከዚህ በፊት በነበረው ራዕይ”ወይም “የቀደመው ራዕይ”

እየበረረ ወደ እኔ መጣ
“በፍጥነት ወደ እኔ እየበረረ መጣ”

በማታ መሥዋዕት ጊዜ
አይሁድ ሕዝቦች ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት በየምሽቱ ለእግዚብሔር መሥዋዕትን ያቀርቡ ነበር።

Daniel 9:22

ጥበብና ማስተዋል
“ጥበብ”እና“ማስተዋል”የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን መልዕክቱን ሙሉ በሙሉ ለመራድተ እንዲችል ገብርኤል እገዛ እንደሚያደርግለት አፅንዖት ለመሥጠት ነው።

ትዕዛዝ ተሰጠ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር ትዕዛዝን ሰጠ”

ቃሉን መርምር
“ስለ መልዕክቱ አስብ”

ራዕዩ
ይሄ ኤርምያስን በተመለከተ በትንቢተ ዳንኤል 9:2 ላይ ያለውን ትንቢት የሚያስታውስ ነው።

Daniel 9:24

ሰባ ሱባዔዎች...ሰባት ሱባዔዎች...እና ስድሳ ሁለት ሱባዔዎች
ይሄ የእሥራኤላውያን የሚቆጥሩበት የተለመደ ዓይነት አቆጣጠር አይደለም።“ሰባ ጊዜ ሰባት ዓመታት....ሰባት ጊዜ ሰባት ዓመታት....እና ስድሳ ሁለት ጊዜ ሰባት ዓመታት”

በሕዝብህና በቅድስት ከተማህ ላይ ሰባ ሱባዔ ተቆጥሯል
እግዚአብሔር የደነገገው በዚህ ጥቅስ ውስጥ ያሉትን ነገሮች ለሕዝቡና ለእሥራኤል የሚያደርግ መሆኑን ነው።

የአንተ ሕዝብና የአንተ ቅድስት ከተማ
እዚህ ላይ “የአንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ዳንኤልን ነው።ሕዝቡ የእሥራኤል ሕዝብ ሲሆን የተቀደሰችው ከተማ ደግሞ ኢየሩሣሌም ናት።

ዓመፃን ይጨርስ በደልንም ያስተሰርይ ዘንድ
ሃሣቡ የተደጋገመበት ምክኒያት ይሄ ነገር በእርግጥ የሚከናወን መሆኑን አፅንዖት ለመሥጠት ነው።

ራዕይን ተሸክሞ መሄድ
እዚህ ላይ “ተሸክሞ መሄድ”የሚለው ቃል ዘይቤያዊ አገላለፅ ሲሆን ትርጉሙ መፈፀም ማለት ነው።“ራዕዩን ተግባራዊ ማድረግ”

ራዕዩና ትንቢቱ
ከዚህ አውድ አንፃር እነዚህ ቃላት ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው። ለዳንኤ የሚያረጋግጡት ነገር ቢኖር የኤርምያስ ራዕይ በእርግጥም ትንቢት የነበረ መሆኑን ነው።

ማወቅና ማስተዋል
እነዚህ ቃላት በአንድነት ጥቅም ላይ የዋሉት ጣሚነቱን የበለጠ ግልፅ ለማድረስ ነው።“በግልፅ ልትረዳው ያስፈልጋል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የተቀባ
መቀባት አንድ ሰው መመረጡ የሚታወቅበት ምልክት ነው።“እግዚአብሔር የሚቀባው ሰው”

ሰባ ሱባዔዎች...እና ስድሣ ሁለት ሱባዔዎች
እነዚህ ሲደመሩ 69 የሚሆኑ ሲሆን በቁጥር 24 ላይ ከተጠቀሱት 70ዎቹ ውስጥ ናቸው።

ኢየሩሣሌም ትሰራለች
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሰዎች ኢየሩሣሌምን እንደገና ይሠሯታል።”

የምሽግ ጉድጓድ
በከተማ ወይም በሕንፃ ዙሪያ ያለና ብዙ ጊዜ ውኃ ያለበት ጥልቅ ጉድጓድ

የጭንቀት ዘመን
“ታላቅ ችግር ያለበት ዘመን”

Daniel 9:26

ስድሳ ሁለት ሱባዔዎች
ይሄ እሥራኤላውያን የሚቆጥሩበት የተለመደ የአቆጣጠር ዓይነት አይደለም።“ስድሣ ሁለት ጊዜ ሰባት”

መሢሁም ይገደላል፤በእርሱም ዘንድ ምንም አይኖርም
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሰዎች መሢሁን ያጠፉታል፤ምንም ነገር አይቀርለትም”

የተቀባው
መቀባት የሚለው ቃል አንድ ሰው መመረጡን የሚያሣይ ተምሣሌታዊ ድርጊት ነው።“እግዚአብሔር የሚቀባው ሰው” ወይም “እግዚአብሔር የሚመርጠው ሰው ”

የሚመጣው አለቃ
ይሄ ባዕድ የሆነ ገዢ እንጂ “የተቀባው ገዢ”አይደለም።“የሚመጣው ባዕድ ገዢ”ወይም “የሚመጣው ኃይለኛ ገዢ”

ፍፃሜውም በጎርፍ ይሆናል
ሠራዊቱ ከተማዋንና ቅዱስ ሥፍራውን ጎርፍ ነገሮችን እንደሚያጠፋ እንዲሁ ያጠፉታል።

ጥፋትም ተቆጥሯል
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር በከተማዋና በመቅደሱ ላይ ጥፋትን አዝዟል”ወይም “እግዚአብሔር ሠራዊቱ ሁሉንም ነገር እንዲያጠፋ አዝዞታል”

Daniel 9:27

ያደርጋል..ያደርጋል
ይሄ መሢሁን የሚያጠፋውን አዲሱን ገዢ የሚያመለክት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 10

1 የፋርስ ንጉስ ቂሮስ በነገሰ በሦስተኛው ዓመት ብልጣሶር ለተባለው ዳንኤል ራዕይ ታየው መልዕክቱ እውነት ነው፤ ስለ ታላቅ ጦርነትም የሚገልፅ ነበር። መልእክቱንም ይገነዘብ ዘንድ በራዕዩ ማስተዋል ተሰጠው። 2 በዚያ ጊዜ እኔ ዳንኤል ለሦስት ሳምንት አለቀስኩ፤ 3 ሦስቱም ሳምንት እስኪፈፀም ድረስ ጥሩ ምግብ አልበላሁም፤ ስጋም ሆነ የወይን ጠጅ ወደ አፌ አልገባም፤ ቅባትም አልተቀባሁም። 4 በመጀመሪያው ወር አያ አራተኛው ቀን፤ በታላቁ በጤግሮስ ወንዝ ዳር ቆሜ፤ 5 ቀና ብዬ ስመለከት፣ በፊቴ በፍታ የለበሰ እና በወገቡም ላይ ምርጥ የወርቅ ቀበቶ የታጠቀ አንድ ሰው አየሁ። 6 አካሉ እንደ እንቁ፣ ፊቱ እንደ መብረቅ፣ ዐይኖቹ እንደሚንበለበል ፋና፣ ክንዶቹና እግሮቹ እንደ ጋለ ናስ የሚያብረቀርቁ ድምፁም እንደ ብዙ ሕዝብ ድምፅ ነበር። 7 ራዕዩን ያየሁት እኔ ዳንኤል ብቻ ነበርሁ፤ ከእኔ ጋር የነበሩት ሰዎች አላዩም፤ ነገር ግን ታላቅ ፍርሃት ስለ ወደቀባቸው ሸሽተው ተደበቁ። 8 ስለዚህ ይህን ታላቅ ራዕይ እያየሁ ብቻዬን ቀረሁ፤ ምንም ጉልበት አልነበረኝም፤ መልኬ እጅጉን ገረጣ፤ ኃይልም አጣሁ። 9 ከዚያም የቃሉን ድምፅ ሰማሁ፤ የቃሉንም ድምፅ በሰማሁ ጊዜ፣ በግንባሬ በምድር ላይ ተደፍቼ በከባዱ እንቅልፍ ተኛሁ። 10 እነሆም አንድ እጅ ዳሰሰኝ፤ እየተንቀጠቀጥሁም በእጄና በጉልበቴ አቆመኝ፤ 11 እርሱም፤ “ እጅግ የተወደድህ ዳንኤል ሁይ፣ አሁን ወደ አንተ ተልኬአለሁና የምነግርህን አስተውል፤ ቀጥ ብለህም ቁም አለኝ። ይህን ሲለኝም፤ እየተንቀጠቀጥሁ ተነስቼ ቆምሁ። 12 ደግሞም እንዲ አለኝ፤ “ዳንኤል ሁይ፣ አትፍራ ማስተዋልን ለማግኘትና በአምላክህም ፊት ራስህን ለማዋረድ ከወሰንክበት ከመጀመሪያው ቀን አንስቶ ቃልህ ተሰምቷል፤ እኔም የቃልህን መልስ ይዤ መጥቻለሁ። 13 ነገር ግን የፋርስ መንግስት አለቃ ሃያ አንድ ቀን ተቋቋመኝ፤ ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ የሆነው ሚካኤል ሊረዳኝ ወጣ። 14 ራዕዩ ሊፈፀም ገና ብዙ ዘመን ስለሚቀረው ወደፊት በህዝብህ ላይ የሚሆነውን ልገልፅልህ አሁን ወደአንተ መጥቻለሁ።” 15 ይህን እየተናገረኝ ሳለ፣ ፊቴን ወደ ምድር አቀረቀርሁ፣ የምናገረውንም አጣሁ። 16 ከዛም የሰው ልጅ የሚመስል ከንፈሮቼን ዳሰሰ፣ እኔም አፌን ከፈትኩ፣ መናገርም ጀመርኩ፤ በፊቴ የነበረውንም እንዲህ አልኩት፤ “ ጌታዬ ሆዬ ከራዕዩ የተነሳ ተሰቃይቻለሁ ሃይልም አጣሁ፤ 17 ጉልቤቴ ከዳኝ፤ መተንፈስም አቅቶኛል፣ እኔ አገልጋይህ ከአንተ ጋር መነጋገር እንዴት እችላለሁ?” 18 እንደገናም ሰው የሚመስለው ዳሰሰኝ አበረታኝም። 19 እርሱም፤ “እጅግ የተወደድህ ሰው ሆይ፤ አትፍራ፤ ሰላም ላንተ ይሁን፤ በርታ፤ ፅና” አለኝ። እየተናገረኝም ሳለ፣ በረታሁና፣ “ጌታዬ ሆይ፤ አበረታተኸኛልና ተናገር” አልሁት። 20 እርሱም እንዲህ አለኝ፤ “ለምን ወደ አንተ እንደ መጣሁ ታውቃለህ? የፋርስን መንግሥት ለመውጋት እመለሳለሁ፤ እኔም ስሄድ የግሪክ አለቃ ይመጣል። 21 አስቀድሜ ግን በእውነት መጽሐፍ የተጻፈውን እነግርሃለሁ፤ ከእነዚህ አለቆች ጋር ለመዋጋት ከአለቃችሁ ከሚካኤል በስተቀር የሚረዳኝ የለም።

Daniel 10:1

በፋርስ ንጉሥ በቂሮስ በሦስተኛው ዓመት
“የፋርስ ንጉሥ በነገሰ በሦስተኛው ዓመት”

ለዳንኤል ነገር ተገለጠለት
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር ለዳንኤል መልዕክትን ገለጠለት”

ማስተዋል
አንድ ሰው ሊረዳ ከሚችለው በላይ መገንዘብ

Daniel 10:2

ቅንጡ የሆኑ ነገሮች
እነዚህ ውድ የሆኑና በቀላሉ የማይገኙ የምግብ ዓይነቶች ናቸው።

ሶስት ሣምንት ሙሉ እስኪደርስ ድረስ
“ሶስት ሣምንት እስኪጠናቀቅ ድረስ”

Daniel 10:4

ከመጀመሪያውም ወር በሃያ አራተኛው ቀን
ይሄ የዕብራውያን የመጀመሪያ ወር ነው።በምዕራባውያን የቀን አቆጣጠር መሠረት ሃያ አራተኛው ቀን የሚውለው በመጋቢት ወር አጋማሽ አካባቢ ነው።

ወገቡን የታጠቀ
“ቀበቶ አድርጎ ነበር”

አፌዝ
አፌዝ የቦታ ሥፍራ ነው።ያለበት ትክክለኛ ሥፍራ አልተገለፀም።

ሰውነቱ እንደ ቶፓዝ ነበረ
ሰውነቱ ከቶፓዝ የተሰራ ይመስልበሰማያዊና በቢጫ ብርሃን ያብረቀርቅ ነበር።“ሰውነቱ እንደ ቶፓዝ አብረቀረቀ”

ቶፓዝ
ሰማያዊ ወይም ቢጫ የከበረ ድንጋይ ሲሆኑ ቤሪል፤ፔሪዶትና ክራሶላይት በመባልም ይታወቃሉ።

ፊቱም እንደ መብረቅ አምስያ ነበረ
ፊቱ ልክ መብረቅ አበራ።“ልክ እንደመብረቅ ብርሃን ፊቱ በብርሃን ደመቀ”

ዓይኖቹም እንደሚንበለበል ፋና
የሚንበለበሉ ችቦዎች ይመስልዓይኖቹ እጅግ ብሩህ ነበሩ።“ዓይኖቹ ብሩህ ከመሆናቸው የተነሣ ችቦዎች ዓይኖቹ ውስጥ የሚንበለበሉ ይመስል ነበር።”

ክንዶቹና እግሮቹም እንደ ጋለ ናስ
ከተወለወለ ነሐስ የተሰሩ ይመስል ክንዶቹና እግሮቹ ያብረቀርቁ ነበር።“ከንዶቹና እግሮቹ የተወለወለ ነሐስ ይመስል ከውስጣቸው የሚፈልቀው ብርሃን አካባቢውን ሁሉ ያዳርሳል።”

የቃሉም ድምፅ እንደ ብዙ ሕዝብ ድምፅ ነበረ
ድምፁ ከሙጉላቱ የተነሣ ብዙ ሰዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው የሚነጋገሩ ይመስላል። ድምፁ ከመጉላቱ የተነሣ ብዙ ሰዎች በጋራ ጮኸው የሚጣሩ ነው የሚመስለው።

Daniel 10:7

እኔም ብቻዬን ቀርቼ ራዕዩን ተመለከትኩ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ማንም አጠገቤ አልነበረም።እናም አየሁ”

ደም ግባቴም ወደ ማሽብሸብ ተለወጠብኝ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“መልካም የነበረው ገፅታዬ ወደ አስከፊ ገፅታ ተለወጠ”

ደም ግባቴ
ይሄ የሚያመለክተው ጤነኛ የሆነን ሰው ገፅታ ነው።“ጤነኛ ገፅታ ያለው ፊቴ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የፈራረሰ ገፅታ
ጤነኛ ያልሆነና የገረጣ ፊት ከሚፈርስ ሕንፃ ጋር ተመሳስሎ ቀርቧል።“የገረጣ”

የቃሉንም ድምፅ ሰማሁ
ይሄ አንድ ሰው በራዕዩ ውስጥ ያነጋግረው እንደነበረ የሚያሣይ ነው።ይሄ የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“የሆነ ሰው የሚናገረውን ንግግር ሰማሁ”

ደንግጬ በምድር ላይ በግምባሬ ተደፋሁ
ለዚህ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት 1/ዳንኤል ካየው ነገር የተነሳ እጅግ በመፍራቱ በምድር ላይ ተደፍቶ ራሱን ሳተ 2/ዳንኤል ራሱን ከሳተ በኋላ በምድር ላይ ተደፋ።

Daniel 10:10

አንዲት እጅ ዳሰሰችኝ
እዚህ ላይ የሰው እጅ የሚወክለው ያንኑ ሰው ነው።ምናልባትም ዳንኤል በትንቢተ ዳንኤል 10፡5-6 የየው ሰው ሊሆን ይችላል።“አንድ ሰው በእጁ ነካኝ”

እጅግ የተወደድህ ሰው ዳንኤል ሆይ
ይሄኛው በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር እንደ ትልቅ ሰው የሚመለከትህ ዳንኤል ሆይ”

እንደ ትልቅ ሰው የሚመለከትህ
የከበርክና የምትወደድ

Daniel 10:12

የምነግርህን ቃል አስተውል
“ራዕዩን ለመረዳት ዝግጁ ሁን”

ፀሎትህ ተሰምቶልሃል
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር ፀሎትህን ሰምቶታል”

አለቃ
ይሄ የሚያመለክተው በሰው ልጆች ላይ ሥልጣን ያለውን መንፈስ ነው።

የፋርስ ንጉሥታት
ይሄ ምናልባት ለፋርስ ንጉሥ ተገዢ የሆኑ በፋርስ መንግሥት ውስጥ ይገዙ የነበሩትን ነገሥታት የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።

ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ ሚካኤል
“የመላዕክት አለቆች ከሆኑት መካከል አንዱ የሆነው ሚካኤል”

Daniel 10:14

አጠቃላይ መረጃ
መልአኩ ለዳንኤል መናገሩን ይቀጥላል።

ፊቴን ወደ ምድር አቀረቀርኩ
“ወደ ምድር አቀርቅሬ ቀረሁ” ዳንኤል ይህንን ያደረገበት ምክኒያት ከትህትና የተነሳ አክብሮትን ለመሥጠት ወይም ከመፍራቱ የተነሳ ሊሆንም ይችላል።

Daniel 10:16

የሰው ልጅ የሚመስል
ይሄ ምናልባት ከዳንኤል ጋር የተነጋገረውን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። ሆኖም አንዳንድ ቅጂዎች ከሌላ ሰው ጋር እንደተነጋገረ አድርገው ነው የተረጎሙት።“ይሄኛው፤የሰው ልጅ የሚመስለው”

የሰው ልጅ የሚመስለው
ይሄ አገላለፅ የሚያመለክተው በአጠቃላይ የሰው ልጆችን ነው።“እንደ ሰው ልጅ”

ጭንቀት
ብርቱ የሆኑ ስሜታዊ ሕመሞች

ይህ የጌታዬ ባሪያ ከጌታዬ ጋር ይናገር ዘንድ እንዴት ይችላል?
ዳንኤል ይህንን ጥያቄ በሚጠይቅበት ጊዜ እኔ ከመልአክ ጋር በእኩል ደረጃ መነጋገር የምችል ሰው ስላልሆንኩ ከመልአክ ጋር መነጋገር አልችልም ማለቱ ነው።እነዚህ ዓረፍተ ነገሮች ሊጣመሩ ይችላሉ።“የአንተ ባሪያ ስለሆንኩ መልስ ልሰጥህ አልችልም”

እስትንፋስም አልቀረልኝም
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር የሚያመለክተው መተንፈስን ነው።“መተንፈስ አልቻልኩም” ወይም “ለመተንፈስ ከባድ ነው።”

Daniel 10:18

ሰው የሚመስለው
“የሰው ምስል ያለው”

በርታ፤ፅና
“በርታ”የሚሉት ቃላት የተደጋገሙት አፅንዖት ለመስጠት ነው።

የተወደድህ ሰው ሆይ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“አንተ እግዚአብሔር የሚወድህ”

በረታሁ
ይሄኛው በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ጠንካራ ሆንኩ”

Daniel 10:20

የፋርስ አለቃ
“አለቃ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰዎች የሚኖሩበትን ምድር የሚገዛውንና የሚጠብቀውን መንፈስ ነው።“የፋርስ አለቃ መንፈስ”

ነገር ግን እነግርሃለሁ
ይሄ የሚያሳየው ከመሄዱ በፊት መልአኩ ይህንን ጉዳይ ለዳንኤል የሚነግረው መሆኑን ነው።“ነገር ግን በመጀመሪያ እነግርሃለሁ”

በእውነት ፅሑፍ ውስጥ የተፃፈውን
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የእውነት መፅሐፍ የሚናገረው ነገር” ወይም “በእውነት መፅሐፍ ላይ የሆነ ሰው የፃፈው”

ብርቱ መሆኑን ያሣያል
“ብርቱ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ይሰጣል”

ከአለቃችሁ ከሚካኤል በቀር ማንም የሚያፀናኝ የለም
“ከእነርሱ ጋር በምዋጋበት ወቅት ከእኔ ጋር በማበር ብርቱ መሆኑን የሚያሣየኝ የእናንተ አለቃ የሆነው ሚካኤል ብቻ ነው”ወይም “ከእነርሱ ጋር ስዋጋ እገዛ የሚያደርግልኝ የእናንተ አለቃ የሆነው ሚካኤል ብቻ ነው”

አለቃችሁ ሚካኤል
“አለቃችሁ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥርን የሚያመለክት ነው። የሚያመለክተውም ዳንኤልንና የተቀረውን የእሥራኤልን ሕዝብ ነው።“የሕዝባችሁ አለቃ የሆነው ሚካኤል”

አለቃችሁ ሚካኤል
“ጠባቂያችሁ የሆነው መልአኩ ሚካኤል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 11

1 እኔም፣ ሜዶናዊ ዳርዮስ በነገሠ በመጀመሪው ዓመት እርሱን ለማገዝና ለማበርታት በአጠገቡ ቆሜ ነበር። 2 አሁንም እውነቱን እነግርሃለሁ፤ እነሆ ሦስት
ሌሎች ነገስታት በፋርስ ይነሳሉ፤ አልተኛውም ከሌሎቹ ሁሉ ይልቅ እጅግ ባለጠጋ ይሆናል። በባለጠግነቱም እጅግ በበረታ ጊዜ ሌላውን ሁሉ አሳድሞ በግሪክ
መንግስት ላይ ያስነሣል። 3 ከዚያም በታላቅ ኃይል የሚገዛና የወደደውንም ሁሉ የሚያደርግ ሃይል ንጉስ ይነሣል። 4 በኃይሉ እየገነነ ሳለም፣ መንግስቱ
ይፈርሳል፤ ወደ አራቱ የሰማይ ነፍሳትም ይከፋፈላል። መንግስቱ ተወስዶ ለሌሎች ስለሚሰጥ ለዘሩ አይተላለፉም፤ ኃይሉም እንደ መጀመሪያው አይሆንም 5
የደቡብ ንጉስ ይበረታል፤ ነገር ግን ከጦር አዛዦቹ አንዱ ከእርሱ የበለጠ የበረታ ይሆናል፣ ግዛቱም ታላቅ ይሆናል። 6 ከጥቂት ዓመታት በኋላም አመቺ ጊዜ
ሲያገኙ አንድነት ይፈጥራሉ። የደቡብ ንጉስ ሴት ልጅ ስምምነት ለማድረግ ወደ ሰሜኑ ንጉስ ትሄዳለች፤ ነገር ግን ኃይሏን ይዞ መቆየት አትችልም፤ በእነዚያ ቀናት
እርሷ ከቤተ መንግስት አጃቢቿ፣ ከአባቷና ከደጋፊዎቿ ጋር አልፋ ትሰጣለች። 7 ከዘመዶቿ አንዱ ስፍራዋን ሊይዝ ይነሳል፤ የሰሜኑን ንጉስ ሰራዊት ይወጋል፤
ምሽጎቹንም ጥሶ ይገባል፤ ከእነርሱም ጋር ተዋግቶ ድል ያደርጋል። 8 አማልክታቸውን፤ የብረት ምስሎቻቸውን፣ ከክብርና ከወርቅ የተሰሩ የክብሩ ዕቃዎቻቸውን
ይማርካሉ፤ ወደ ግብፅም ይወስዳል። ለጥቂት ዓመታም ከሰሜኑ ንጉስ ጋር ከመዋጋት ይቆጠባል። 9 የሰሜኑም ንጉስ፣ የደቡቡን ንጉስ ግዛት ይወራል፤ ነገር
ግን አፈግፍጎ ወደ ገዛ አገሩ ይመለሳል። 10 ወንዶች ልጆቹም ለጦርነት ይዘጋጃሉ፤ እስከ ጠላት ምሽግ ደርሶ የሚዋጋና ሊቋቋሙት እንደማይቻል ጎርፍ
የሚጠራርግ ታላቅ ሰራዊት ይሰበስባሉ። 11 ከዚያም የደቡቡ ንጉስ በቁጣ ወጥቶ የሰሜኑን ንጉስ ይወጋል። የሰሜኑ ንጉስ ታላቅ ሰራዊት ቢያሰባስብም ሰራዊቱ
ለደቡብ ንጉስ አልፎ የሚሰጥ ይሆናል። 12 ሰራዊቱ በሚማረክበት ጊዜ ልቡ በትዕቢት ይሞላል፤ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችንም ይገድላል፤ ነገር ግን በድል
አድራጊነቱ አይጸናም። 13 የሰሜን ንጉስ ከመጀመሪው የሚበልጥ ታላቅ ሰራዊት ያሰባስባል፤ ከብዙ አመታ በኋላ በትጥቅ እጅግ ከተደራጀ ታላቅ ሰራዊት ጋር
ተመልሶ ይመጣል። 14 በዚያም ዘመን ብዙዎች በደቡብ ንጉስ ላይ ይነሣሉ። ራዕዩ ይፈጸም ዘንድ ከህዝብህ መካከል ዐመፀኛ የሆኑ ሰዎች ይከሣሉ፤ ነገር ግን
ተሰነካክለው ይወድቃሉ። 15 የሰሜኑም ንጉስ መጥቶ የዐፈር ድልድል ይክባል፤ የተመሸገእውንም ከተማ ይይዛል። የደቡቡ ሰራዊትም ለመቋቋም ኃይል
ያጣል፤ የተመረጡት ተዋጊዎቻቸው እንኳ ፀንተው መዋጋት አይችሉም። 16 ነገር ግን የሰሜኑ ንጉስ በደቡቡ ንጉስ ላይ ደስ ያሰኘውን ያደርጋል፤ ማንም
ሊቋቋመው አይችልም። በመልካሚቱ ምድር ላይ ይገዛል እርሷን ለማይፋትም ኃይል ይኖረዋል። 17 የሰሜኑ መንግስት ያለውን ሠራዊት ሁሉ ይዞ ለመምጣት
ይወስናል፤ ከደቡቡም ንጉስ ጋር ይስማል፣ የደቡቡንም መንግስት ለመጣል ሴት ልጁን ይድርለታል፤ ይሁን እንጂ ዕቅዱ አይሳካለትም፤ ያሰበውም ነገር
አይጠቅመውም። 18 ከዚህም በኋላ በባሕር ጠረፍ ወዳሉት አገሮች ፊቱን በመመለስ ብዙዎቹን ይይዛል፤ ነገር ግን አንድ አዛዥ ትዕቢቱን ያከሸፍበታል፤
በራሱም ላይ ይመልስበታል። 19 በገዛ አገሩ ወዳሉት ምሽጎችም ፊቱን ይመልሳል፤ ነገር ግን ተሰናክሎ ይወድቃል፤ ደግሞም አይታይም። 20 በእርሱ ቦታ
የሚተካውም የመንግስቱን ክብር ለማስጠበቅ የሚውል ግብር እንዲከፍል የሚያስገድድ ይሆናል፤ ይሁን እንጂ በቁጣ ወይም በጦርነት ሳይሆን በጥቂት ዓመታ
ውስጥ ይደመሰሳል። 21 በእርሱም ፋንታ የተናቀ ሰው የነግሣል፤ ለእርሱም ሕዝቡ ንጉሳዊ ክር አይሰጡትም፣ በቀስታ ይገባና በተንኮል መንግስቱን ይዛል። 22
ከፊቱ የሚቆመው ሰራዊት እንደ ጎርፍ ተጠራርጎ ይወሰዳል። ሰራዊቱና የቃል ኪዳኑም አለቃ ሳይቀር ይደመሰሳሉ። 23 ከእርሱ ጋር ስምምነት ከተደረገ በኋላ
የማታለል ስራውን ይሰራል፤ ከጥቂት ሰዎችም ጋር በብርታት እየጨመረ ይሄዳል 24 የበለጸጉትን ክፍለ አገሮች በሰላ ሳሉ በድንገት ይወሯቸዋል፤ አባቶቹም ሆኑ
አያቶቹ ያላደረጉትን ነገር ያደርጋሉ፤ ብዝበዛውን ምርኮውንና የተገኘውን ሀብት ሁሉ ለተከታዮቹ ያካፈቸዋል፤ ምሽጎችን ለመጣል ያሤራል፤ ይህን የሚያደርገውም
ለጥቂት ጊዜ ብቻ ነው። 25 “ታላቅ ሠራዊት አደራጅቶ ኀይሉንና ብርታቱን በደቡብ ንጉስ ላይ ይነሳሳል፤ የደቡብ ንጉሱም ብርቱ የሆነ ኃይል ሰራዊት ይዞ
ጦርነትን ያውጃል፤ ከር ግን ከተዶለተበት ሴራ የተነሳ መቋቋም አይእል፣። 26 ከንጉስ ማዕድ አብረውት ሲበሉ የነበሩት፤ ብዙዎቹም በጦርነት ይገደላሉ። 27
አንዳቸው በሌላኛው ላይ ልባቸው ወደ ክፋት ያዘነበለው ሁለት ነገስታት፣ በአንድ ገበታ አብረው ይቀመጣሌ፤ እርስ በእርሳቸውም በከንቱ ውሸት ይነጋገራሉ፤
ምክንያቱም ፍፃሜ የሚሆነው በተወሰነው ጊዜ ነው 28 የሰሜን ንጉስ ብዙ ሃብት ይዞ ወደ ሀዛ አገሩ ይመለሳ፤ ነገር ግ ልቡ በተቀደሰው ኪዳን ላይ ይነሣሣል፤
የወደደውን ያደርጋል፣ ከዚያም ወደ ገዛ አገሩ ይመለሳል። 29 በተወሰነው ጊዜ ይመለስና ደቡቡን እንደ ገና ይወርራል። በዚህ ጊዜ ግን ውጤቱ ከበፊቱ የተለየ
ይሆናል። 30 የኪቲም መርከቦች ይቃወሙታል፤ ልቡም ይሸበራል። ወደ ኋላም ይመለሳል፤ ቁጣውን በተቀደሰው ኪዳን ላይ ይወርዳል፤ ተመልሶም የተቀደሰውን
ኪዳ የተዉትን ይንከባከባል። 31 የጦ ሠራዊቶቹም ቤተ መቅደሱንና ቅጥሩን ያረክሳሉ፤ የዘውትሩንም መስዋዕት ያስቀራሉ፤ በዚያም ፍፁም ጥፋትን
የሚያመጣውን የጥፋት ርኩሰት ይተክላሉ፤ 32 ኪዳኑን የሚተላለፉትን በማታለል ይስታል ይረክስባቸዋልም፤ አምላካቸውን የሚያውቁ ሕዝብ ግን ደንተው
ይቃወሙታል፤ ርምጃም ይወስዳሉ። 33 “ለጊዜው በሰይፍ ቢወድቁም፣ ቢቃጠሉም፣ ቢማረኩና ቢዘረፉም፣ ጥበበኛ የሆኑ ሰዎች ብዙዎችን ያስተምራሉ። 34
በሚወድቁበት ጊዜ መጠነኛ ርዳታ ይገኛሉ፤ እውነተኛ ያልሆኑ ብዙ ሰዎችም ይተባበሯቸዋል። 35 ጥበበኛ ከሆኑ ሰዎች አንዳንዶቹ ይሰናከላሉ፣ ይህም እስከ
ፍፃሜ ዘመን ድረስ የጠሩ፣ የነጠሩና እንከን የሌለባቸው ይሆን ዘንድ ነው፤ የተወሰነው ጊዜ ገና አልደረሰምና። 36 ንጉሱ እንዳለው ያደርጋል፤ ከአማልክት ሁሉ
በላይ ራሱን እጅግ ከፍ በማድረግ በአማልክት አማላክ ላይ አስገራሚ ነገሮችን ይናገራል፤ የቁጣውም ዘመን እስኪፈጸም ይሳካለታል፤ የተወሰነ ነገር ሁሉ መሆን
አለበትና። 37 ሴቶች ለሚወዱትም ሆነ ለአባቶቹ አምላክ ትክብርን አይሰጥም፤ ማንኛውንም አምላክ አያከብርም፤ ነገር ግን ራሱን ከእነዚህ ሁሉ በላይ ከፍ ከፍ
ያደርጋል። 38 በእነርሱም ምትክ የምሽጎችን አምላክ ያደብራል፤ አባቶቹ የማያውቁትን አምላክ በወርቅ፣ በብር፣ በከበሩ ድንጋዮችና በውድ ስጦታዎች ያከብራል።
39 በባዕድ አምላክ ርዳታ ጽኑ ምሽቶችን ይወጋል፤ ለእርሱ የሚገዙትን በእጅጉ ያከበራቸዋል፤ በብዙ ሕዝብ ልያ ገዦች ያደርጋቸዋል፤ ምድሩንም በዋጋ
ያከፋፍላቸዋል። 40 “በመጨረሻው ዘመን የደቡብ ንጉሥም ጦርነት ያውጅበታል፤ የሰሜን ንጉሥም በፈረሰኞችና በሰርጎች በብዙ መርከቦችም እንደ ማዕበል
ይመጣበታል፤ ብዙ አገሮችን ይወራል፤ እንደ ጎርም እየጠራረገ በመካከላቸው ያልፋል። 41 የከበረችውንም ምድር ይወራል፤ በብዙ ሺህ
የሚቆጠሩእስራኤላውያንም ተሰነካክለው ይወድቃሉ፣ ነገር ግን ከኤዶም፣ ከሞዓብ ብዙ ሰዎች እንዲሁም ከአሞን የቀሩት ሕዝብ ከእጁ ያመልጣሉ። 42
ሥልጣኑን በብዙ አገሮች ላይ ያንሰራፋል ግብፅም አታመልጥ። 43 የወርቅና የብር ክምችትን፣ እንዲሁም የግብፅን ሀብት ሁሉ በቁጥጥሩ ሥር ያደርጋል፤
የሊቢያና የኢትዮጵያ ሰዎችም ይገዙታል። 44 ነገር ግን ከምሥራቅና ከሰሜን የሚመጣ ወሬ ያስደነግጠዋል፤ ብዙዎችንም ለማጥፋትና ለመደምሰስ በታላቅ ቁጣ
ይወጣል። 45 ንጉሣው ድንኳኖቹን በባሕሮች መካከል ውብ በሆነው ቅዱስ ተራራ ላይ ይተክላል፤ ይሁን እንጂ ወደ ፍጻሜው ይመጣል፤ ማንም አይረዳውም።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Daniel 11:1

አጠቃላይ መረጃ
በትንቢተ ዳኤል ከምዕራፍ11፡1 እስከ ምዕራፍ 12፡4 ድረስ ባለው ክፍል ውስጥ በምዕራፍ 10 ላይ ለዳንአል የሚናገረው በእውነት መፅሐፍ ላይ የተፃፈውን ነው።ይሄ በትንቢተ ዳንኤል 10፡21 ላይ እፈፀመዋለሁ ብሎ እንደተናገረው ነው።

በዳርዮስ በመጀመሪያ ዓመት
ዳርዮስ የሜዶን ንጉሥ ነበረ።"የመጀመሪያው ዓመት"የሚለው ቃል የሚያመለክተው ንጉሥ የሆነበትን የመጀመሪያውን ዓመት ነው።"በመጀመሪያው በዳርዮስ የአገዛዝ ዘመን"

ሦስት ነገሥታት በፋርስ ይነሣሉ
"ሦስት ነገሥታት በፋርስ ላይ ይነግሳሉ"

አራተኛውም ከሁሉ ይልቅ እጅግ ባለጠጋ ይሆናል
"ከእነርሱ በኋላ ከሦስቱ ይልቅ ብዙ ገንዘብ ያለው አራተኛ ንጉሥ ሥልጣኑን ይይዛል"

ኃይል
ለዚህ ቃል ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት 1/ሥልጣን2/የወታደር ኃይል

ሁሉን ያስነሳል
"ሁሉንም ሰዎች ለመዋጋት ፈቃደኞች እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል"

Daniel 11:3

አጠቃላይ መረጃ
መልአኩ ለዳንኤል መናገሩን ይቀጥላል።

ኃያልም ንጉሥ ይነሣል
አብዛኛውን ጊዜ የመነሣት ወይም የመቆም ሃሣብ የሚነገረው ኃያል እየሆነ ለሚመጣ ሰው ነው።"ኃያል ንጉሥ መግዛት ይጀምራል"

እጅግ ታላቅ የሆነ መንግሥትን የሚገዛ
ይህንን ቃል በአግባቡ ሊገልፁ የሚችሉት "የመንግሥቱ ሥፋት እጅግ ታላቅ ይሆናል" ወይም "ንጉሡ ግዛቱን የሚያስተዳድረው እጅግ ታላቅ በሆነ ኃይል ነው።"

መንግሥቱ ይሰበራል፤ይከፋፈላልም
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።"መንግሥቱ ይሰባበራል"ወይም "መንግሥቱየተቆረረጠ ይሆናል"

አራቱ የሰማይ ነፋሣት
ይህንን በትንቢተ ዳንኤል7፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

ለራሱ ዘር ግን አይደለም
ያለመከፋፈልና ያለመሰጠት ሃሣብ በዚህ ሥፍራ ላይ ይጠቀሳል።"ዘሩ ግን አይከፋፈልም"ወይም "በራሱ ዘር መካከል አይከፋፈልም"

ከራሱ ዘር በስተቀር መንግሥቱ ይነቀላል
እዚህ ሥፍራ ላይ መንግሥቱ ልክ አንድ ሰው ከሥሩ ነቅሎ እንደሚያጠፋው ዕፅዋት ተመስሎ ነው የቀረበው።ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል፡"ሌላ ኃይል መጥቶ ካጠፋውና ከነቀለው በኋላ የእርሱ ዘሮች ልሆኑ ሌሎች ሰዎች መጥተው በበላይነት ይገዛሉ።"

Daniel 11:5

አጠቃላይ መረጃ
መልአኩ ለዳንኤል መናገሩን ይቀጥላል።

ከአለቆቹም አንዱ ይበረታል ይሠለጥንማል
የደቡቡ ንጉሥ የሠራዊት አለቃ የሰሜኑ ንጉሥ ይሆናል።

ሕብረት ይፈጥራሉ
የደቡቡ ንጉሥ ከሰሜኑ ንጉሥጋር ሕብረት ይሄ ሕብረት ሁለቱም አገሮች ሊጠብቁት የሚገባ በሕግ የተደገፈ ሕብረት ነው።"ደቡቡ ንጉሥና የሰሜኑ ንጉሥ በጋራ ለመሥራት ቃል ይገባሉ።"

የደቡብም ንጉሥ ሴት ልጅ ቃል ኪዳን ለማድረግ ወደ ሰሜን ንጉሥ ትመጣለች
የደቡቡ ንጉሥ ሴት ልጁን ለሰሜኑ ንጉሥ ይድራል።ጋብቻው በሁለቱ ነገሥታት መካከል የተደረገውን ሥምምነት ያፀናዋል።

የክንድዋ ኃይል...ክንዱም
እዚህ ላይ"ክንድ"የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሥልጣንን ነው።

ባዶዋን ትቀራለች
ይሄ እርሷንና ሕብረቱን የመሰረቱትን ሰዎች የመግደልን ሄራ የሚያመለክት ይመስላል።ይሄ ሐረግ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።"ባዶዋን ያስቀሯታል"

Daniel 11:7

አጠቃላይ መረጃ
መልአኩ ለዳንኤል መናገሩን ይቀጥላል።

ከሥርዋ ቅርንጫፍ
ቤተሰቡ በዛፍ ተመስሎ ተገልጿል።ሥሩ ቅድመ አያቶቻቸውን የሚያመለክት ሲሆን ቅርንጫፉ ደግሞ ትውልዱን የሚያመለክት ነው።"የቅድመ አያቶቿ ዘር" ወይም "ከትወልዷ አንዱ"

የእርሷ ሥር
"የእርሷ"የሚለው ቃል የሚያመለክተው በትንቢተ ዳንኤል 11፡6 ላይ የተጠቀሰችውን የደቡቡን ንጉሥ ሴት ልጅ ነው።

እርሱ ሠራዊቱን ያጠቃል
"እርሱ"የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእርሷን ዘርና እዘህ ላይ ደግሞ ሠራዊቱን ነው። "እርሱና ሠራዊቱ የሰሜኑን ንጉሥ ያጠቃሉ።"

እነርሱን ይዋጋቸዋል
"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚወክለው ወታደሮችንና የጠላት ሠራዊትን ነው።"የጠላት ወታደሮችን ይዋጋቸዋል።"

ነገር ግን እርሱያፈገፍጋል
"እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሰሜኑን ንጉሥ ነው።

Daniel 11:10

አጠቃላይ መረጃ
መልአኩ ለዳንኤል መናገሩን ይቀጥላል።

ልጆቹም
"የሰሜኑ ንጉሥ ወንድ ልጆች"

ብዙ ሠራዊትን ይሰበስባል
"በውጊ ላይ ሊሣተፉ የሚችሉ ብዙ ሰዎችን ይሰበስባል"

ይጎርፍማል
ብዛትያለው ሠራዊት ምድሪቱን የመሸፈኑ ነገር ከሚጎርፍ ውኃ ጋር ተመሳስሎ ቀርቧል።"ቁጥራቸው እጅግ ብዙ ከመሆኑ የተነሣ ምድሪቱን ይሸፍኗታል።"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Daniel 11:11

አጠቃላይ መረጃ
መልአኩ ለዳንኤል መናገሩን ይቀጥላል።

ብዙ ሕዝብንም ለሠልፍ ያቆማል
“ታላቅ ሠራዊትን ይሰበስባል”

ሠራዊቱም አልፎ በእጁ ይሰጣል
እዚህ ላይ“እጅ”የሚለው ቃል የሚወክለው የሰሜኑ ንጉሥ ተቆጣጣሪ መሆኑን ነው።“ንጉሡ ሠራዊቱን ለደቡቡ ንጉሥ አሣልፎ ይሰጣል።”

ሠራዊቱ ይጋዛል
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችል ይሆናል።“የደቡቡ ንጉሥ የሰሜኑን ሠራዊት ይማርካል”

ይታበያል
ይታበያል የሚለው ቃል የሚያመልከተው እጅግ ኩራተኛ መሆኑን ነው።“እጅግ ይኮራል”

አዕላፋትንም እንዲወድቁ ደርጋል
እዚህ ላይ መውደቅ የሚለው ቃል የሚያመለክተው በጦርነት ውስጥ መሞትን ነው።“ሠራዊቱ ከጠላቶቹ መካከል ብዙ ሺዎችን እንዲገድሉ ያደርጋል።” ወይም “በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ጠላቶቹን የሚገድል ይሆናል።”

አዕላፍ
“ብዙ ሺዎች”

Daniel 11:13

አጠቃላይ መረጃ
መልአኩ ለዳንኤል መናገሩን ይቀጥላል።

ከቀደመውም የበለጠ ብዙ ሕዝብ ለሠልፍ ያቆማል
እዚህ ላይ ማቆም የሚለው ሃሣብ ማመፅን የሚያመለክት ነው።“ብዙ ሕዝብ በንጉሡ ላይ ያምፃል።”

የአመፅ ልጆች
ይሄ አገላለፅ የሚያመለክተው አመፀኛ የሆኑ ሰዎችን ነው።

ያደናቅፋቸዋል
እዚህ ላይ “መደናቀፍ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው መውደቅን ነው።“ስኬታማ አይሆኑም”

Daniel 11:15

አጠቃላይ መረጃ
መልአኩ ለዳንኤል መናገሩን ይቀጥላል።

የሰሜኑም ንጉሥ ይመጣል
“የሰሜኑ ንጉሥ”የሚለው ቃል የእርሱንም ሠራዊት ያካትታል።“የሰሜኑ ንጉሥ ሠራዊት ይመጣል።”

ጉብታዎችን ይወስድ ዘንድ አፈርን ይደለድላል
ይሄ የሚያመለክተው ሠራዊቱ በእነርሱ ላይ ጥቃት ለማድረስ ይችል ዘንድ የከተማዋ ከፍታ ቦታ ላይ ለመድረስ አፈር የመደልደላቸውን ሁኔታ ነው። ወታደሮችን ባሪያዎች በቅርጫት ውስጥ አፈር በማስቀመጥ ወደ ከፍታ ቦታ ላይ ከወሰዱት በኋላ ጉብታ እንዲፈጥርላቸው ይከምሩታል።

ምሽግ መሥራት
አንድን ከተማ ከጠላት ለመከላከል የሚገነባ ቅጥር ወይም በወታደሮች አማካይነት የጠላት ወታደሮችን ለመከላከል የሚገነባ ምሽግ።

በፊቱም የሚቆም የለም
እዚህ ላይ የሚቆም የሚለው ቃል የሚያመለክተው የመዋጋት ብቃቱን ነው።“ከእነርሱ ጋር እየተዋጉ መቀጠል ያዳግታቸዋል።”

በእርሱም ላይ የሚመጣው ግን እንደ ፈቃዱ ያደርጋል
“ወራሪው ንጉሥ በዚያኛው ንጉሥ ላይ የፈለገውን ነገር ሊያደርግ ይችላል።”

ይቆማል
እዚህ ላይ መቆም የሚያመለክተው መግዛትን ነው።“ንጉሱ መግዛት ይጀምራል”

መልካሚቱ ምድር
ይሄ የሚያመለክተው የእሥራኤልን ምድር ነው።ይሄንን በትንቢተ ዳንኤል 8:9 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

በእጁም ውስጥ ጥፋት ይሆናል
እዚህ ላይ “ጥፋት”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የማውደምን ኃይል ነው። የማጥፋት ኃይል የሚለው አባባል አንድ ሰው በእጁ ሊይዘው እንደሚችል ዓይነት ቁስ ተደርጎ ነው የተገለፀው።“ማንኛውንም ነገር የማጥፋት ኃይል አለው።”

Daniel 11:17

አጠቃላይ መረጃ
መልአኩ ለዳንኤል መናገሩን ይቀጥላል።

ፊቱን ያቀናል
ይሄ አንድ ሰው አንድ ነገር ለመፈፀም ከወሰነ በኋላ ውሳኔውን ለመቀልበስ ፈቃደኛ አለመሆኑን የሚገልጥ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው።

ከመንግሥቱም ኃይል ሁሉ ጋር ይመጣ ዘንድ
ይሄ ወታደራዊ ኃይልን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።“ሠራዊቱ ካለው ኃይል ሁሉ ጋር ይመጣል”

የሴት ልጅ
ይሄ ሴት ለሚለው ቃል ውብ የሆነ አገላለፅ ነው።

ዕብሪቱን ያስቆማል
“የሰሜኑ ንጉሥ ዕብሪቱን እንዲያቆም ያደርገዋል።”

ዕብሪቱንም በራሱ ላይ ይመልስበታል
“የሰሜኑ ንጉሥ በሌሎች ላይ ዕብሪተኛ ስለነበረ ለሥቃይ ይዳርገዋል።”

ፊቱን ይመልሳል
“የሰሜኑ ንጉሥ ሃሣቡን ይለውጣል”

አይገኝምም
ይሄ ይሞታል ለሚለው ቃል በሌላ መልክ የቀረበ አገላለፅ ነው።ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ይሰወራል”ወይም“ሕይወቱ ያልፋል”

Daniel 11:20

አጠቃላይ መረጃ
መልአኩ ለዳንኤል መናገሩን ይቀጥላል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በእርሱም ሥፍራ ሌላ ሰው ይነሣል
በንጉሱ ቦታ ላይ ሌላ ሰው ይነሣል ማለት ቀድሞ በነበረው ንጉሥ ቦታ ላይ ሌላ ሰው ይቀመጣል ማለት ነው።“በዚያ ንጉሥ ምትክ ሌላ ሰው የሰሜን ንጉሥ ይሆናል።”

እርሱ ይሰበራል
እዚህ ላይ “እርሱ”የሚለወው ቃል የሚያመለክተው አዲሱን ንጉሥ ነው። መሰበር የሚለው ቃል የሚመለክተው መሞትን ነው።“የአዲሱ ንጉሥ ሕይወት ያልፋል።”

በቁጣ ሣይሆን
ለዚህ ሃሣብ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት 1/ማንም ሰው በንጉሡ ላይ አልተበሳጨም 2/የንጉሱ የሞቱ ሁኔታና ምክኒያት በምሥጢር መያዛቸው።

ሕዝቡ የመንግሥትነትን ሥፍራ ሊሰጠው የማይፈልገው የተጠላ ሰው
የንጉሥ ዘር ባለመሆኑ ምክኒያት ሕዝቡ እርሱን እንደ ንጉሥ ለመቀበል ፈቃደኛ አይሆንም።“የማይቀበሉትና ንጉሥ እንዳይሆን የሚፈልጉት ሰው”

የሚጎርፍም ሠራዊት ከፊቱ ይወሰዳል
ይወሰዳል የሚለው ቃል የሚወክለው ይጠፋል የሚለውን ቃል ነው።“ጎርፍ በሚጓዝበት ነመንገድ ሁሉ ያለውን ነገር እያጠፋ እንደሚሄድ ሁሉ እንደዚሁ እርሱም ታላቅ ሠራዊትን ያጠፋል።”

እርሱና የቃል ኪዳኑ አለቃ ይሰበራሉ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሠራዊቱንና የቃል ኪዳኑን አለቃ ያጠፋል”

የቃል ኪዳኑ አለቃ
የካህናቱ መሪ።“ይሄ ሐረግ እግዚአብሔር በቃል ኪዳኑ ውስጥ እጅግ ከፍተኛ የሆነውን ኃይማኖታዊ ሥልጣን የያዘውን ሰው ማለትም ሊቀ ካህንንየሚያመለክት ነው።”

Daniel 11:23

አጠቃላይ መረጃ
መልአኩ ለዳንኤል መናገሩን ይቀጥላል።

ከእርሱም ጋር ከተወዳጀ በኋላ
ይሄም በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሌሎች ገዢዎች የሠላም ውልበሚያደርጉበት ወቅት”

በተከታዮቹ መካከል ይበትናል
“ለተከታዮቹ ያከፋፍላል”

ብዝበዛውን፤ምርኮውንና ሃብቱን
“እርሱና ሠራዊቱና ድል ካደረጓቸው ሕዝብ ላይ የሚወስዷቸው ውድ የሆኑ ዕቃዎች”

Daniel 11:25

አጠቃላይ መረጃ
መልአኩ ለዳንኤል መናገሩን ይቀጥላል።

ኃይሉንና ልቡን ያነሳል
እዚህ ላይ ኃይልና ልብ(ማለትም ጉብዝና)የሚገለፁት ወደ ድርጊት ለመግባት ይችሉ ዘንድ ሰው እንደሚያነቃቸው ዓይነት ተደርገው ነው።“ራሱን ኃያል ያደርጋል፤ጎበዝም ይሆናል።”

ልብ
እዚህ ላይ ልብ የሚለው ቃል የሚወክለው ጉብዝናን ነው።

ከታላቅ ሠራዊት ጋር
“በሚሰበስበው ታላቅ ሠራዊት”

ጦርነትን ያውጃል
“ከእርሱ ጋር ይዋጋል”

አይቋቋምም
አይቋቋምም የሚለው ቃል የሚያሣየው መሸነፍን ነው።“የሰሜኑ ንጉሥ ይሸነፋል ወይም ሠራዊቱ ይሸነፋል።”

መልካም የሆነውን ምግቡን የሚመገቡ ሰዎች
ይሄ የሚያመለከተው የንጉሡ አማካሪዎችን ነው።እጅግ ታማኝ የሆኑ የንጉሡ አማካሪዎች ከንጉሱ ጋር መብላታቸው የተለመደ ነገር ነበር።“የንጉሱ ምርጥ የሆኑ አማካሪዎች”

ሠራዊቱም ይጎርፋል
እዚህ ላይ የአንድ ሠራዊት ድል መደረግ ልክ ጠራርጎ ከሚወስድ ጎርፍ ጋር ተመሳስሎ ቀርቧል።“ጠላት ሠራዊቱን ፈፅሞ ያጠፋዋል ወይም ጎርፍ በመንገዱ ከላይ የሚያገኘውን ሁሉ ጠራርጎ አንደሚወስድ እንዲሁ ጠላቱ ፈፅሞ ያጠፋዋል።”

ብዙዎች ተገድለው ይወድቃሉ
እዚህ ላይ “ይወድቃሉ”የሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር የሚያመለክተው በጦርነት አውድማ መሞትን ነው።ስለሆነም “መውደቅ”እና “መሞት”የሚሉት ቃላት በመሠረቱ ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው።“ከእርሱ ሠራዊት መካከል ብዙዎቹ በጦርነት ውስጥ ይሞታሉ።”

አንዱ በሌላው ላይ ክፋትን ያደርግ ዘንድ በልቡ ይሻል
እዚህ ላይ “ልብ”የሚለው ቃል የሚወክለው የሰውን መሻቶች ነው።እዚህ ላይ መሻቶች የሚለው ቃል ልክ አንድ ሰው የሆነ ቦታ ላይ ሊያስቀምጠው እንደሚችል ዕቃ ዓይነት ተመስለው ቀርበዋል።“አንዱ በሌላው ላይ ክፋትን ለማድረግ ቁርጥ የሆነ ሃሣብ አላቸው።”

በአንድ ገበታ ይቀመጣሉ
በአንድ ገበታ መቀመጥ የሚለው ቃል የሚያመለክተው በጋራ ሆኖ መወያየትን ነው።

አይከናወንላቸውም
“ውይይታቸው አይጠቅማቸውም”

ፍፃሜው እስከተወሰነ ጊዜ ነው
ይሄ ስብሰባቸው ለምን ሊሰካ እንደማይችል ይገልፃል።“የድርጊታቸው ውጤት የሚመጣው እግዚአብሔር በወሰነው ጊዜ ነው።”

Daniel 11:28

ብዙ ሐብት፤ልቡም በተቀደሰ ቃል ኪዳን ላይ ይሆናል
እዚህ ላይ“ልብ”የሚለው ቃል የሚወክለው አዕምሮን ወይም የአንድን ሰው አስተሳሰቦች ነው።“ልቡም በ...ላይ ይሆናል” የሚለው ቃል አንድን ነገር ለመቃወም መቁረጥ ማለት ነው።ይሄ በአዲስ ዓረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል።“ብዙ ሐብት።የተቀደሰውን ቃል ኪዳን ለመቃወም ቁርጥ ሃሣብ ያደርጋል።”

ልቡም ቃል ኪዳኑን በመቃወም ላይ ይሆናል
ንጉሱ ቃል ኪዳኑን የመቃወም ድርጊቱ የሚያመለክተው እሥራኤላውያን ለቃል ኪዳኑ እንዳይታዘዙ ለማድረግ ያለውን ፍላጎት ነው።“እሥራኤላውያን የተቀደሰው ቃል ኪዳኑን ከመታዘዝ እንዲታቀቡ ለማድረግ ቁርጥ ሃሣብ ማድረግ።”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የተቀደሰው ቃል ከዳን
“ቅዱስ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔር ከእሥራኤላውያን ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳን ነው።ቃል ኪዳኑ ከራሱ ከእግዚአብሔር የመነጨ በመሆኑ መከበርና ለእርሱ መታዘዝ እንደሚገባ የሚያሣይ ነው።“እሥራኤላውያን ሁሉ ሊታዘዙት የሚገባ ቃል ኪዳን”

ያደርጋል
ይሄ የሚያሣየው ንጉሱ በእሥራኤል ላይ የተወሰነ እርምጃ የሚወስድ መሆኑን ነው።“የሚሻውን ነገር በእሥራኤል ላይ ያደርጋል።”

Daniel 11:29

የኪቲም መርከቦች ይመጡበታል
መርከቦቹ የሚያመለክቱት በእነዚያ መርከቦች ውስጥ ሠራዊት የሚመጣ መሆኑን ነው።“ሠራዊቱን ለመዋጋት በኪቲም መርከብ ተጉዞ ሠራዊት ይመጣል።”

ኪቲም
ይሄ በሜዲቴራንያን ባህር ውስጥ በሚገኘው በቆጵሮስ ደሴት ላይ መሥፈርን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።

በቅዱሱም ቃል ኪዳን ላይ ይቆጣል
“ቅዱሱን ቃል ኪዳን ይጠላል”

ለእነዚያ አድልዎ ያደርጋል
“ለእነዚያ ያደላል”ወይም “እነዚያን ይረዳቸዋል”

Daniel 11:31

የእርሱ ሠራዊቶቹ ይቆማሉ
“የእርሱ ሠራዊት ይገለጣል”ወይም “የእርሱ ሠራዊት ይመጣል”

መቅደሱንም ግንቡንም
“ሰዎች እንደ ምሽግ የሚጠቀሙበት ቤተ መቅደስ”

የዘወትሩንም መሥዋዕት ያስቀራሉ
“መሥዋዕት ያስቀራሉ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰዎች መሥዋዕት እንዳያቀርቡ መከልከልን ነው።“ካህናቱ የዘወትር የሚቃጠል መሥዋዕት እንዳያደርጉ ያግዷቸዋል”

ከባድ ሐዘንን የሚያስከትለው በደል
ይሄ የሚያመለክተው ጣኦት ቤተ መቅደስን ለሐዘን እንደሚያደርጋት ማለትም እግዚአብሔር ቤተ መቅደሱን ትቶ እንዲሄድ ማድረጉን ነው።“እግዚአብሔርን በቤተመቀደስ ውስጥ ከመኖር የሚያግደው አስፀያፊ ጣኦት”ወይም “ቤተ መቅደስን የሚያቆሽሸው አስፀያፊ ነገር”

ቃል ኪዳኑን ክፉኛ ተቃወመው
“ቃል ኪዳኑን ክፉኛ ተቃወመው”

እንዲረክሱ ይገፋፋቸዋል
“ወደ ክፋት እንዲያመሩ ይገፋፋቸዋል”

አምላካቸውን የሚያውቁትን
እዚህ ላይ“ማወቅ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው“ታማኝ መሆንን”ነው።“ለአምላካቸው ታማኝ የሆኑ”

ይበረታሉ፤ያደርጋሉም
“ይፀናሉ፤ይቋቋሙዋቸዋልም”

Daniel 11:33

በሰይፍና በእሣት ነበልባል ይወድቃሉ
እዚህ ላይ “መውደቅ”የሚለው ቃል ሞትን ጨምሮ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ጥፋት ሊደርስ የሚችል መሆኑን የሚያመለክት ነው።እዚህ ላይ “ሰይፍ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጦርነትንና በውጊያ ውስጥ መሳተፍን ሲሆን “ነበልባል” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ደግሞ እሣትን ነው።“በውጊያ ውስጥ ሕይወታቸው ያልፋል እንዲሁም ተቃጥለው ይሞታሉ”

እነርሱ
ይሄ የሚያመለክተው ከእሥራኤላውያን መካከል ጥበበኛ የሆኑትን ሰዎች ነው።

በምርኮኝነት ይወድቃሉ፤ለዘመናት ለመበዝበዝ
እዚህ ላይ “መውደቅ”የሚለው ቃል ሞትን ጨምሮ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ጥፋት ሊደርስ የሚችል መሆኑን የሚያመለክት ነው።“መበዝበዝ”የሚለው ሐረግ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ባሪያዎች ይሆናሉ፤ጠላቶቻቸው ለዘመናት ንብረቶቻቸውን ይዘርፋሉ”

በጥቂት ዕርዳታ ይረዳሉ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሌሎች ሰዎች በትንሹ እገዛ ያደርጉላቸዋል”

ብዙ ሰዎች በግብዝነት ወደ እነርሱ ይሰበሰባሉ
ይሄ የሚያመለክተው ጥበበኛ ሰዎችን የሚያግዙ የሚመስሉትን ሰዎች ነው። ሆኖም በእውነትም ሊያግዟቸው ስለፈለጉ አይደለም።

ይሰበሰባሉ
እዚህ ላይ“ይሰበሰባሉ”የሚለው ቃል የሚወክለው “ለመርዳት ይመጣሉ”የሚለውን ሃሣብ ነው።“ሊያግዟቸው ይመጣሉ”

አንዳንድ ጥበበኛ የሆኑ ሰዎች ይወድቃሉ...እስከ ዘመን ፍፃሜ
እግዚአብሔር ይበቃል እስኪል ድረስ ሥቃዩ የሚቀጥል ይሆናል።

አንዳንድ ጥበበኛ የሆኑ ሰዎች ይወድቃሉ
እዚህ ላይ “መውደቅ”የሚለው ቃል ሞትን ጨምሮ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ጥፋት ሊደርስ የሚችል መሆኑን የሚያመለክት ነው።

በእነርሱ ላይ የማጥራት ሥራ ይከናወን ዘንድ
እዚህ ላይ“ዘንድ” ማለት “ከውጤቱ ጋር በተያያዘ”ማለት ነው።“በውጤቱም የማጥራት ሥራ ይከናወንባቸዋል”

ይነጥሩና፡ይጠሩ ዘንድ ይነጡም
ሶስቱ የሥራ ክንውኖች እዚህ ላይ የተገለፁት በዕቃዎች ተመስለው ነው።ሆኖም በፍዝ ወይም በተገብሮ መልክ እንደ ድርጊት ሊገለፁ ይችላሉ።“ይነጥራሉ፡ ይጠራሉ፤ ይነፃሉ” ወይም “የሚደርስባቸው ሥቃይ ያነጥራቸዋል፤ያጠራቸዋል፤ያነፃቸዋል”

ማንጠር
ይሄ ብረትን በእሣት ውስጥ በማቅለጥ የማጥራትን ሂደት የሚያመለክት ነው። እግዚአብሔር የረሱ የሆነው ሕዝብ ታማኝ እንዲሆንለት የማድረጉን ጉዳይ አንድ ሠራተኛ ብረቱ እንዲጠራ ለማድረግ በእሣት ውስጥ ከማስቀመጥ ሁኔታ ጋር አመሳስሎ ነው የተናገረው።

ማንፃት
ይሄ የሚያመለክተው ሰዎችን ከኃጢአትና ከሌሎች ክፉ ዓይነት ድርጊቶች እንዲለዩ በማድረግ ሰዎች፤ሥፍራዎች ወይም ቁሣቁሶች ለእግዚአብሔር የሚመቹ እንዲሆኑ ማድረግን ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ማጥራት
ይሄ ሃሣብ ማንጠር ከሚለው ቃል ጋር ተመሣሣይ ነው።የሚነጥር ብረትን ይጠራል ማለትም ይቻላል።

የፍፃሜ ዘመን
“በማጠናቀቂያ ቀናት” ወይም“የዓለም መጨረሻ”

የተወሰነው ቀን ይመጣል
እዚህ ላይ “የተወሰነው ቀን” ሲል እግዚአብሔር የቀጠሮ ሰዓት መወሰኑን የሚያመለክት ነው።ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር ለወደፊት ቀጠሮ ቀጥሯል”

Daniel 11:36

X
“ንጉሡ የወደደውን ሁሉ ያደርጋል”

ንጉሡ
ይሄ የሚያመለክተው የሰሜኑን ንጉሥ ነው።

ራሱንም ከፍ ከፍ ያደርጋል፤ራሱን ታላቅ ያደርጋል
“ራሱንም ከፍ ከፍ ያደርጋል”የሚለውና ”ራሱን ታላቅ ያደርጋል” የሚለው ቃልተመሳሳይ ዓይነት ትርጉም ያላቸው ሲሆን ንጉሱ እጅግ የሚኮራ እንደሆነ ይጠቁማሉ።

ራሱን ከፍ ከፍ ያደርጋል
እዚህ ላይ ይሄ የሚያመለክተው እጅግ እየኮራ መሆኑን ነው።

ራሱን ታላቅ አደረገ
እዚህ ላይ ይሄ የሚያመለክተው እጅግ አስፈላጊ ሰውና ኃያል ሰው ለመሆን የማስመሰሉን ነገር።

የአማልዕክት አምላክ
ይሄ የሚያመለክተው እውነተኛ ሆነውን አንዱን አምላክ ነው።“ታላቅ የሆነውን እግዚአሔር” ወይም“እርሱ ብቻ እውነት የሆነ አምላክ”

አስገራሚ ነገሮች
“አሰቃቂ ነገሮች”ወይም“አስደንጋጭ ነገሮች”

ቁጣውም አስኪፈፀም ድረስ
ይህ ሐረግ መጋዘኑ ፈፅሞ እስኪሞላ ድረስ ቁጣውን እንደሚያከማችና በኋላም ወደ ተግባር እንደሚገባ ዓይነት አድርጎ ነው የሚገልፀው።“የእግዚአብሔር ቁጣ የመጨረሻ ደረጃ ላይ እስኪደርስ ድረስ”ወይም“እርምጃ ለመውሰድ ይችል ዘንድ የእግዚአብሔር ቁጣ ጫፍ እስኪደርስ ድረስ”

በሴቶች ዘንድ የሚወደድ አማልዕክት
ይሄ የአህዛብ ጣኦት የሆነውንና ታሚዝ በሚል ሥያሜ የሚታወቀውን ጣኦት የሚያመለክት ይመስላል።

የአምባዎች አምላክ
ምናልባትም ይሄ ንጉሥ ይሄ የሐሰት አምላክ የሌሎች ሰዎችን ምሽጎች እያጠቃ የእርሱን ይዞታ ግን በሰላም እንዲጠበቅ የሚያደርግለት መሆኑን አምኖ ሊሆን ይችላል።“ምሽጎችን የሚጠብቅ የጣዖት አምላክ”

በእነዚህ ፋንታ
“እነዚህ”የሚለው ቃል በትንቢተ ዳንኤል 11:37 ላይ የተጠቀሱትን ጣዖታት የሚያመለክት ነው።

ምድርንም በዋጋ ይከፍላል
ለዚህ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት 1/“ምድሪቱን በሥጦታ መልክ ለተከታዮቹ ይሰጣል”ወይም 2/“ለተከታዮቹ መሬቱን ይሸጣል።”

Daniel 11:40

በፍፃሜ ዘመንም
“የመጨረሻ ቀናት”ወይም “የዓለም መጨረሻ”

የደቡቡ ንጉሥ ...የሰሜኑ ንጉሥ
እነዚህ ሐረጎች ነገሥታቱንና ሠራዊታቸውን የሚያመለክቱ ናቸው። “የደቡቡ ንጉሥና ሠራዊቱ ”....“የሰሜኑ ንጉሥና ሠራዊቱ”

እንደ አውሎ ነፋስ ይመጣበታል
ከባድ በሆነ ውጊያ ጠላትን ለማጥቃት ልክ አውሎ ነፋስ እንደተነሳ ተደርጎ ነው የሚነገረው።“እንደ ኃይለኛ አውሎ ነፋስ ጥቃት ይሰነዝርበታል”ወይም “በብርቱ ይዋጋል”

ይጎርፍማል
አንድ ሠራዊት አገሩን ሲወርር ጎርፍ እንደተከሰተ ዓይነት ተደርጎ ነው የሚነገረው።

ያልፍማል
ሠራዊቱን የሚያቆም ኃይል አይኖርም።“ማንም ሊያስቆመው በማይችል መልኩ በምድሪቱ ውስጥ ያልፋል።”

መልካሚቱ ምድር
ይሄ የሚያመለክተው የእሥራኤልን ምድር ነው።

ይወድቃል
እዚህ ላይ መውደቅ የሚለው ቃል የሚያመለክተው የመሞትን ድርጊት ነው።“ይሞታል”

ነገር ግን እነዚህ ከእጁ ይድናሉ
እዚህ ላይ“እጅ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኃይልን ነው።“ነገር ግን እነዚህ ከእርሱ ኃያል ጥቃት ያመልጣሉ”ወይም “ነገር ግን እነዚህን አገሮች ለማጥፋት ይሳነዋል”

Daniel 11:42

አጠቃላይ መረጃ
ይሄ ስለ ሰሜኑ ንጉሥ ብቻ የሚያወሳ ነው።

እጁን በአገሮች ላይ ይዘረጋል
እዚህ ላይ“እጅ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሥልጣንንና በበላይነት መቆጣጠርን ነው።“የቁጥጥር ሥርዓቱን በተለያዩ አገሮች ውስጥ ያስፋፋል”

በአገሮች
እዚህ ላይ ሃሳቡ ብዙ አገሮች ወይም የተለያዩ ምድሮች ለማለት ነው።

የግብፅ ምድርም አትድንም
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የግብፅ ምድር አታመልጥም”

የልብያና የኢትዮጵያ ሰዎችም ይከተሉታል
“የልብያና የኢትዮጵያ ሕዝብ”ልብያ ከግብፅ በስተ ምዕራብ ያለች አገር ስትሆን “ኢትዮጵያ ደግሞ ከግብፅ በስተ ደቡብ የምትገኝ አገር ናት”

Daniel 11:44

አጠቃላይ መረጃ
ይሄ አሁንም የሚያወሳው ስለ ሰሜኑ ንጉሥ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በታላቅ ቁጣ ይወጣል
“ቁጣ” የሚለው አሕፅሮተ ሥም ተናደደ በሚለው ቃል ሊገለፅ ይችላል። ከሠራዊቱ ጋር አብሮ እንደሚሄድ በግልፅ ሊነገር ይችላል።“በጣም ይናደዳል፡ ይወጣልም”ወይም “በጣም ከመናደዱ የተነሣ ከሠራዊቱ ጋር ይወጣል”

መውጣት
“መውጣት”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጠላትን የማጥቃት ድርጊትን ነው።

ብዙዎችንም ያጠፋ ዘንድ
“ብዙ ሰዎችን ያጠፋ ዘንድ”

ንጉሣዊ የድንኳን መኖሪያው
ይሄ ንጉሱ በጦርነት ወቅት ከሠራዊቱ ጋር በሚሆንበት ወቅት የሚኖርባቸው ቅንጡ የሆኑ ድንኳኖችን የሚያመለክት ነው።

በባህርና በከበረው በቅዱስ ተራራ ላይ
ይሄ ምናልባትም በሜዲቴራንያን ባህርና በኢየሩሣሌም ተራራ መካከል የሚገኘውን ግዛት የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።

የከበረው በቅዱስ ተራራ
ይሄ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ የነበረበትን የእሥራኤል ተራራ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 12

1 በዚያን ዘመን ስለ ሕዝብህ የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል። መንግሥታት ከተመሠረቱበት ጊዜ ጀምሮ እስከዚያ ዘመን ድረስ ታይቶ የማይታወቅ ታላቅ የመከራ ጊዜ ይሆናል። ነገር ግን በዚያን ጊዜ ስማቸው በመጽሐፉ ተጽጽፎ የተገኘው ሕዝብህ ሁሉ ይድናሉ። **2** በምድር አፈር ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎች ይነቃሉ፤ አንዳንዶቹ ለዘላለም ሕይወት፣ ሌሎቹም ለውርደትና ለዘላለም ጉስቁልና ይነሣሉ። **3** ጥበበኞች እንደ ሰማይ ጸዳል፣ ብዙዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ክዋክብት ለዘላለም ይደምቃሉ። **4** ዳንኤል ሆይ፣ አንተ ግን፣ እስከ ፍጻሜው ዘመን ድረስ የመጽሐፉን ቃል ዝጋ አትመውም። ብዙዎች ወዲያ ወዲህ ይራወጣሉ ዕውቀትም ይበዛል። **5** እኔም ዳንኤል ተመለከትሁ፤ እነሆ ከፊት ለፊቴ ሌሎች ሁለት ቆመው ነበር፤ አንዱ ከወንዙ በዚህኛው ዳር፣ ሌላው ደግሞ ከወንዙ በዚያኛው ዳር። **6** ከእነርሱም አንዱ፣ ከወንዙ በላይ የነበረውንና በፍታ የለበሰውን ሰው፣ እነዚህ አስደናቂ ነገሮች ሊፈጽሙ ምን ያህል ጊዜ ይቀራል?” አለው። **7** ከወንዙ ውሃ በላይ የነበረው በፍታ የለበሰው ሰው፣ ቀኝ እጁንና ግራ እጁን ወደ ሰማይ አንሥቶ፣ “ለዘመን፣ ለዘመናት፣ ለዘምንም እኩሌታ ማለትም ለሦስት ዓመት ተኩል ይሆናል፤ የተቀደሰው ሕዝብ ኃይል መስበር ሲያከትም፣ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ይፈጸማሉ” ብሎ ለዘላለም በሚኖረው በእርሱ ሲምል ሰማሁ። **8** እኔም ሰማሁ፤ ነገር ግን አላስተዋልሁትም፤ ስለዚህ፣ ጌታዬ፣ የዚህ ሁሉ ፍጻሜ ምንድን ነው?” ብዬ ጠየቅሁ። **9** እርሱም እንዲህ አለኝ፤ “ቃሉ እስከ ፍጻሜው ዘመን ድረስ የተዘጋና የታተመ ስለሆነ ሂድ፤ **10** ብዙዎቹ ይነጻሉ፤ ይጠራሉ እንከን አልባምይሆናሉ፤ ክፉዎች ግን በክፋታቸው ይድናሉ፤ ከክፉዎች አንዳቸውም አያስተውሉም፣ ጠቢባን ግን ያስተውላሉ። **11** “የዘወትሩ መሥዋዕት ከተቋረጠበትና ፍጹም ጥፋት የሚያመጣው አስጸያፊ ርኩሰት ከተተከለበት ጊዜ ጀምሮ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና ቀን ይሆናል። **12** የሚታገሥና እስከ አንድ ሺህ ሦስት መቶ ሰለሳ አምስት ቀን ፍጻሜ የሚደርስ የተባረከ ነው። **13** “አንተ ግን እስከ ፍጻሜ ድረስ ሂድ፣ ታርፋለህ፤ በቀኖች መጨረሻም ተንሥተህ የተመደበልህን ርስት ትቀበላለህ።”

Daniel 12:1

አጠቃላይ መረጃ
በትንቢተ ዳንኤል 10፡5 ላይ ለዳንኤል የተገለጠው መልአክ መናገሩን ይቀጥላል።

ሚካኤል ታላቁ አለቃ
ሚካኤል የመላዕክት አለቃ ነው።“ልዑል የሚል ስምም ተሰጥቶታል”

ሚካኤል...ይነሣል
እዚህ ላይ“ይነሣል”የሚለው ቃል ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙም መገለጥ ማለት ነው።“ሚካኤል...ይገለጣል።”

ሕዝብህ ይድናል
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚያድን ስለመሆኑ የበለጠ ልታብራሩ ትችላላችሁ።“እግዚአብሔር ሕዝብህን ያድናቸዋል”

Daniel 12:3

ጥበበኞችም እንደ ከዋክብት ይደምቃሉ
ይህ የእግዚአብሔር ሰዎች ጥበባቸውን ለሌሎች ሰዎች ማካፈላቸውን የሚያመለክት ነው።

ብዙ ሰዎችንም ወደ ፅድቅ የሚመልሱ
የሚሄዱበትን አቅጣጫ የሳቱ እንደሆኑ ዓይነት በሚመስል አቀራረብ ሌሎች ሰዎች ከእገዚአብሔር መለያየታቸውን እንዲገነዘቡ እገዛ የሚያደርጉ ሰዎችን የሚያመለክት ነው። “ሌሎች ሰዎች በፅድቅእንዲኖሩ የሚያስተምሩ ሰዎች”

የሚመልሱ...ለዘላለም እንደ ከዋክብት ይደምቃሉ
እነዚህ ሰዎች ከሚያበሩ ከዋክብት ጋር ተነፃፅረዋል።“የሚመልሱ...ከዘላለም እስከ ዘላለም እንደ ከዋክብት ያበራሉ”

እነዚህን ቃላት ዝጋ፤መፅሐፉንም አትም
እዚህ ላይ “ቃላት”የሚለው ቃል የሚያመለክተው መፅሐፉን ነው።“ይህንን መፅሐፍ ዘግተህ በማህተም አትመው።”

እስከ ዘመን ፍፃሜ ድረስ
“የማጠናቀቂያ ቀናት”ወይም “የዓለም መጨረሻ”

በብዙ እዚህና እዚያ ይሮጣሉ፤ዕውቀትም ይበዛል
ይህ መፅሐፉ በማህተም በሚዘጋበት“የመጨረሻ ዘመን”ከመድረሱ በፊት የሚከናወን ድርጊት ነው።ይሄ የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“ይሄ ከመሆኑ በፊት ብዙ ሰዎች ተጨማሪ ነገሮችን ለመማርና የበለጠ ነገር ለማወቅ ወደተለያዩ ሥፍራዎች ይጓዛሉ።”

Daniel 12:5

አጠቃላይ መረጃ
በትንቢተ ዳንኤል 10፡1 ላይ ማየት የጀመረውን ራዕይ ቀጣዩን ክፍል መናገር ይቀጥላል።

ሁለት ሌሎች ቆመው ነበር
“ሌሎች ሁለት መላዕክት ቆመው ነበር”

በፍታም የለበሰውን ሰው
ይሄ የሚያመለክትው በወንዙ አጠገብ ቆሞ የነበረውን መልአክ ሣይሆን በትንቢት ዳንኤል1፡5 ላይ ለዳንኤል የተገለጠለትን መልአክ ነው።ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ከተልባ እግር የተሰራ ልብስ ለብሶ የነበረው ሰው”ወይም “መልአኩ በፍታ ለብሶ ነበር”

ከወንዙ ውኃ በላይ
ለዚህ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት 1/ከተልባ እግር የተሰራ ልብስ የለበሰው መልአክ ከወንዙ በላይኛው ክፍል ላይ ነበር።ወይም 2/መልአኩ ከወንዙ ትይዩ ባለው የላይኛው የውኃ ክፍል ላይ ነበር።

የዚህ ድንቅ ፍፃሜ እስከ መቼ ድረስ ነው?
“እነዚህ አስገራሚ የሆኑ ነገሮች እስከ መቼ ድረስ ይቆያሉ?”ይሄ የሚያመለክተው ክንውኖቹ ከጀመሩበት ወቅት አንስቶ እስከ ፍፃሜ ድረስ ያለውን ጊዜ ነው።

እነዚህ አስገራሚ የሆኑ ክንውኖች
መልአኩ ለዳንኤል በተናገረበት ወቅት በዚህ ራዕይ ውስጥ የታዩት ነገሮች አልተከናወኑም ነበር።ይሄ በእርግጥም በትንቢተ ዳንኤል 12፡1-4 ያሉትን ክንውኖች የሚያመለክት ሲሆን ምናልባትም በምዕራፍ 11 ካለው ራዕይ የተከናወኑ ነገሮችን አካትቶ ሊሆን ይችላል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Daniel 12:7

በፍታም ልብስ የለበሰው
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።ነው።ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ከተልባ እግር የተሰራ ልብስ ለብሶ የነበረው ሰው”ወይም “መልአኩ በፍታ ለብሶ የነበረው መልአክ”

ከወንዙ ውኃ በላይ
ለዚህ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት 1/ከተልባ እግር የተሰራ ልብስ የለበሰው መልአክ ከወንዙ በላይኛው ክፍል ላይ ነበር።ወይም 2/መልአኩ ከወንዙ ትይዩ ባለው የላይኛው የውኃ ክፍል ላይ ነበር።

ለዘላለም የሚኖረው
“ለዘላለም ነዋሪ የሆነው እግዚአብሔር”

ለዘመንና ለዘመናት ለዘመንም እኩሌታ
ይሄ የሚጀመርበትን ወቅት አሻሚ እንደሆነ ብንተወው የተሻለ ነው። የሚጀምርበትን ጊዜ ማወቅ ካለባችሁ ምናልባትም ሶስት ተኩሉ ዓመታት የሚጀምሩት በትንቢተ ዳንኤል 12፡1 ላይ ተከናውነው በነበሩ ድርጊቶች ነው።

Daniel 12:8

ጌታዬ
ዳንኤል ለእርሱ ያለውን አክብሮት ለማሣየት ከተልባ እግር የተሰራ ልብስ የለበሰውን መልአክ “ጌታዬ”በማለት ነው የሚገልፀው።

ቃሉ እስከ ፍፃሜ ድረስ የተዘጋና በማሕተም የታተመ ነው
ዳንኤል የተሰጠው ራዕይ ለሌሎች ሰዎች መገለጥ የሌለበት ምሥጢር ነበር። መፅሐፉ በማሕተም የተዘጋ በመሆኑ ማንም ሰው ሊገልጠው አይችልም ነበር።“የፃፍካቸውን ቃላት በማህተም መዝጋት ይኖርብሃል።”

Daniel 12:10

አጠቃላይ መረጃ
የበፍታ ልብስ የለበሰው መልአክ ለዳንኤል መናገሩን ይቀጥላል።

ሰዎች ይጠራሉ፤ይነፃሉ፤ይነጥሩማል
ማጥራቱን የሚያከናውነው እግዚአብሔር ነው።በመሠረቱ እነዚህ ሶስት ቃላት ተመሣሣይ ዓይነት ትርጉም ያላቸው ናቸው።“እግዚአብሔር ያጠራል፤ያነፃል፤ብዙ ሰዎችንም ያነጥራል”

ማንጠር
የዚያ አካል ያልሆነን ማናቸውንም ነገር በማስወገድ እንዲጠራ ማድረግ።

ክፉዎች ግን ክፋትን ያደርጋሉ
ክፉ ሰዎች አመፅን ወይም ኃጢአት የሆኑ ነገሮችን ያደርጋሉ።

ክፉዎችም ሁሉ አያስተውሉም
“እነዚያ ለእግዚአብሔር የሚታዘዙ ጠቢባንና የሚያስተውሉ ናቸው።”

የዘወትሩም መሥዋዕት...ከቆመ
የቤተ መቅደሱን መሥዋዕቶች የሚያስቆመው የሰሜኑ ንጉሥ ነው።“የሰሜኑ ንጉሥ የዘወትሩን መሥዋዕት በማስወገድ በምትኩ ሐዘንን የሚያስከትለውን ርኩሰት ይተክላል።”

ፍፁም ባዶነትን የሚያስከትለው ርኩሰት
ይሄ የሚያመለክተው ጣዖቱ ለቤተ መቅደሱ ባዶ መሆን ምክኒያት እንደሚሆን ማለትም እግዚአብሔር ቤተመቅደሱን የሚተው መሆኑን ነው።“እግዚአብሔር ቤተ መቅደሱን ትቶ እነዲሄድ መንስዔ የሚሆነው አስፀያፊ ጣዖት ”ወይም “ቤተ መቅደሱ እንዲቆሸሽ የሚያደርገው አስፀያፊ ነገር”

1,290 ቀናት
“አንድ ሺህ ሁለት እና መቶ ዘጠና ቀናት”ወይም “አንድ ሺህ ሁለት መቶ ቀናት” እዚህ ላይ “ቀናት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የተወሰኑ ዘመናትን ነው።አብዛኛውን ጊዜ ሰዎች ቀናት የሚለውን ቃል የሚጠቀሙ ቢሆንም ይሄ ዓመታት የሚለውንም ሊያመለክት ይችላል።

Daniel 12:12

አጠቃላይ መረጃ
ከተልባ እግር የተሰራ ልብስ የለበሰው መልአክ ዳንኤልን ማነጋገሩን ይቀጥላል።

የሚታገስም ምስጉን ነው
“በታማኝነት የሚቆይ”

1,335 ቀናት
“አንድ ሺህ ሶስት መቶ ሠላሣ ሶስት ቀናት”ወይም “አንድ ሺህ ሶስት መቶ እና ሠላሣ አምስት ቀናት” እዚህ ላይ “ቀናት”የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ በተለምዶ ቀናት ተብሎ የሚጠራው የተወሰኑ ዘመናትን የሚያመለክት ነው።ይህም ሆኖ ቀናትንም የሚመለከት ነው።

መሄድ ይኖርብሃል
“ዳንኤል መሄድ ይኖርብሃል” ይሄ ዳንኤል ሕይወቱ እስከሚያልፍበት ወቅት ድረስ ነገሥታቱን ማገልገል እንዳለበት የሚያመለክት ነው።

ታርፋለህ
ይሄ “ትሞታለህ”ለማለት ጨዋ የሆነ አነጋገር ነው።

ትቆማለህ
ይሄ የፃድቅ የሆኑ ሰዎች ከሞት የሚነሱበትን የመጀመሪያውን ትንሣኤ የሚያመለክት ነው።

በዕጣ ክፍልህ
“እግዚአብሔር የመደበልህ ሥፍራ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Hosea

Hosea

Chapter 1

1 በይሁዳ ነገሥታት በዖዚያን፥ በኢዮአታም፥ በአካዝና በሕዝቅያስ ዘመን፤በእስራኤልም ንጉሥ በዮአስ ልጅ በኢዮርብዓም ዘመን ወደ ብዔር ልጅ ወደ ሆሴዕ
የመጣው የእግዚአብሔር ቃል ይህ ነው። 2 እግዚአብሔር በሆሴዕ አማካይነት መናገር በጀመረ ጊዜ እንዲህ አለው፦«ምድሪቱ እኔን በመተው ታላቅ ምንዝርናን
እያደረገች ነውና፥ሂድ፥የምንዝርናዋ ፍሬዎች የሆኑ ልጆች ያሏትን ሴተኛ አዳሪዋን ሚስትህ አድርገህ ውሰድ።» 3 ስለዚህም ሆሴዕ ሄዶ የዴቤላይምን ሴት ልጅ
ጎሜርን አገባ፤እርስዋም ጸነሰች፥ ወንድ ልጅም ወለደችለት። 4 እግዚአብሔርም አለው፦ «ከጥቂት ጊዜ በኋላ በኢይዝራኤል ስለነበረው ደም ማፍሰስ የኢዩን
ቤት እቀጣለሁና፥ የቤተ እስራኤልንም መንግሥት እንዲያከትም አደርጋለ ሁና ስሙን ኢይዝራኤል ብለህ ጥራው። 5 ይህም በኢይዝራኤል ሸለቆ ውስጥ
የእስራኤልን ቀስት በምሰብርበት ቀን ይፈጸማል።» 6 ጎሜር እንደገና ጸነሰች፥ ሴት ልጅም ወለደች። በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር ሆሴዕን እንዲህ አለው፦
«ቅንጣት ታህል ይቅር እላቸው ዘንድ ከእንግዲህ ወዲያ የእስራኤልን ቤት አልምርምና ስሟን ሎሩሃማ ብለህ ጥራት። 7 ነገር ግን የይሁዳን ቤት እምራለሁ፥
እኔም እግዚአብሔር አምላካችው በራሴ አድናቸዋለሁ እንጂ በቀስት፥ በሰይፍ፥ በጦርነት፥ በፈረሶች ወይም በፈረሰኞች አላድናቸውም።» 8 ጎሜር፥ ሎሩሃማን
ጡት ካስጣለቻት በኋላ ጸነሰች፥ሌላ ወንድ ልጅም ወለደች። 9 በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር እንዲህ አለው፦«ሕዝቤ አይደላችሁምና፥ እኔም አምላካችሁ
አይደለሁምና ስሙን ሎዓሚ ብለህ ጥራው ።» 10 ነገር ግን የእስራኤል ቤት ቁጥር ሊለካ ወይም ሊቆጠር እንደማይችል የባሕር አሸዋ ይሆናል። «ሕዝቤ
አይደላችሁም» በተባሉበት ቦታ፥«የሕያው አምላክ ሕዝብ ናችሁ» ይባላሉ። 11 የይሁዳ ሕዝብና የእስራኤል ሕዝብ በአንድነት ይሰበሰባሉ። የኢይዝራኤል ቀን
ታላቅ ይሆናልና፥ ለራሳቸው አንድ መሪ ይሾማሉ፥ ከምድሪቱም ይውጣሉ።

Hosea 1:1

የመጣው የያህዌ ቃል
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ያህዌ አምላክ የተናገረው ቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ብኤሪ
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ዖዝያ ... ኢዮአታም ... አካዝ ... ሕዝቅያስ ... ኢዮርብዓም ... ዮአስ
በዚህ መጽሐፍ የተከናወኑ ድርጊቶች በእነዚህ ነገሥታት ዘመን የተፈጸሙ ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ
ይህ እግዚአብሔር ለህዝቡ በብሉይ ኪዳን የገለጸው ስሙ ነው። ይህ እንዴት እንደሚተረጎም ስለ ያህዌ የትርጉም ቃል ገጽን ይመልከቱ።

ታላቅ ምንዝርና
እዚህ ስፍራ "ምንዝርና " ሚለው የሚገልጸው ህዝቡ ለእግዚአብሔር ታማኝ አለመሆኑን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 1:3

ጎሜር ... ዴቤላይም
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የኢዩ ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" ማለት "ቤተሰብ" ማለት ሲሆን የኢዩን ትውልድ ያጠቃልላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ቤት
ይህ አገላለጽ የእስራኤልን መንግሥት ያመለክታል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ቀስት
እዚህ ስፍራ "ቀስት" የሚለው የሚያመለክተው የሰራዊቱን ሃይል ነው። "የእስራኤል የጦር ሃይል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት)

Hosea 1:6

ሎ-ሩሃማ
የዚህ ስም ትርጉም "አልምርም" ማለት ነው። ተርጓሚው ይህንን ትረጉም እንደ ስም አድርጎ ማቅረብን ሊመርጥ ይችላል። "አልምርም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 1:8

ሎ-ሩሃማ
የዚህ ስም ትርጉም "አልምርም" ማለት ነው። ተርጓሚው ይህንን ትረጉም እንደ ስም አድርጎ ማቅረብን ሊመርጥ ይችላል። ይህንን ስም በሆሴዕ 1:6 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። "አልምርም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሎ-ዓሚ
የዚህ ስም ትረጉም " ህዝቤ አይደላችሁም" ማለት ነው። ተርጓሚው ይህንን ትረጉም እንደ ስም አድርጎ ማቅረብን ሊመርጥ ይችላል። ""ህዝቤ አይደላችሁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 1:10

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለሆሴዕ እየተናገረ ነው

እንደ ባህር ዳርቻ አሸዋ
ይህ የእስራኤላዊያንን ቁጥር ብዛት ያጎላል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ/ሲሚሊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሊሰፈር ወይም ሊቆጠር የማይችል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ማንም ሊሰፍረው ወይም ሊቆጥረው የማይችል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ተብሎ በተነገረላቸው ስፍራ ይሆናል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር በተናገራቸው ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእነርሱ በተነገረበት ስፍራ
ይህ አገላለጽ ምናልባት በእስራኤል ነገሥታት ወንጀል በሚፈጸምባት ከተማ እና በእነርሱ ላይ የእግዚአብሔር ቅጣት ምልክት የነበረችን ኢዝራኤልን የሚመለከት ይሆናል።

ለእነርሱ ይህ ይነገራል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር ለእነርሱ ይላቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በአንድነት ይሰባሰባሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር በአንድነት ይሰበስባቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በምድሪቱ ይገናሉ
ይህ አገላለጽ የእስራኤል ህዝብ በምርኮ የነበሩበትን ምድር ያመለክታል

የኢዝራኤል ቀን
ይህ እግዚአብሔር ህዝቡን ወደ እስራኤል ምድር የሚመልስበትን ጊዜ ያመለክታል። የዚህ ሃሳብ የተሟላ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 ወንድሞቻችሁን «ሕዝቤ!»፥ እኅቶቻችሁንም «የተራራላችሁ» በሏቸው። **2** እርሷ ሚስቴ አይደለችምና እኔም ባሏ አይደለሁምና ከእናታችሁ ጋር ተምዋግቱ፥ ተምዋገቱ። ሴተኛ አዳሪነቷን ከፊቷ፥ምንዝርናዋንም ከጡቶቿ መካከል ታስወግድ። **3** አለበለዚያ እርቃንዋን እስክትቀር እገፋታልሁ፥እንደ ተወለደችበትም ቀን እርቃንዋን እገልጣለሁ። እንደ ምድረ በዳ እንደ ደረቅም ምድር አደርጋታለሁ፥ተጠምታ እንድትሞት አደርጋለሁ። **4** የሴተኛ አዳሪነት ልጆች ናቸውና ለልጆቿ ቅንጣት ምሕረት የለኝም። **5** ምክንያቱም እናታቸው ሴተኛ አዳሪ ናትና፥ የጸንሰቻቸውም በአሳፋሪ ተግባር ነውና። እርሷም ፦«እንጀራዬንና ውኃዬን፥ሱፌንና ሐሬን፥ዘይቴንና መጠጤን ይሰጡኛልና ከውሽሞቼ ኋላ እሄዳለሁ» አለች። **6** ስለዚህ መንገድዋን በእሾህ ለመዝጋት አጥር እሠራለሁ። መንገድዋንም እንዳታግኝ ቅጥር እገነባባታለሁ። **7** ውሽሞችዋን ትከታተላቸዋለች ነገር ግን አትደርስባቸውም፤ትፈልጋቸዋለች ነገር ግን አታገኛቸውም። ከዚያም በኋላ ፦«አሁን ካለሁበት የበፊቱ ይሻላልና ወደ መጀመሪያው ባሌ እመለሳለሁ» ትላለች። **8** እህሉን፥አዲሱን ወይን ጠጅና ዘይቱን የሰጠኋት፣ በአልን ያገለገሉበትን ብርና ወርቅ ያበዛሁላት እኔ እንደ ሆንኩ አላወቀችም። **9** ስለዚህ እህሏን በመከር ጊዜ፥ አዲሱንም የወይን ጠጇን በወቅቱ መልሼ እወስዳለሁ። እርቃኗንም የምትሸፍንበትን ሱፌንና ሐሬን መልሼ እወስዳለሁ። **10** ከዚያም ውሽሞችዋ እያዩ እርቃንዋን እስክትቀር ድረስ እገፋታለሁ፥ ከእጄም ማንም አያስጥላትም። **11** ሁሉንም ክብረ በዓላቷን፦ የደስታ በዓላቷን፥የአዲስ ጨረቃ ክብረ በዓላቷን፥ ሰንበታቷንና ዓመታዊ በዓላቷን አስቀራለሁ። **12** «ውሽሞቼ የሰጡኝ ክፍያዎቼ ናቸው» የምትላቸውን ወይንዋንና የበለስ ዛፎችዋን አጠፋለሁ። ጫካ አደርጋቸዋለሁ፥ የዱር አራዊትም ይበሉዋቸዋል። **13** ለበአል አማልክት ዕጣን ስላጠነችባቸው፥ በቀለበቶችዋና በጌጣ ጌጦቿ ራስዋን ስላስዋበችባቸው እና እኔን ረስታ ከውሽሞቿ ኋላ ስልሄደችባችው የደስታ በዓላት አቀጣታለሁ።» ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው። **14** ስለዚህ አመልሳታለሁ፥ ወደ ምድረ በዳ እወስዳታለሁ፥ በፍቅርም አነጋግራታለሁ። **15** የወይን ተክሏን፥ የተስፋ በርም እንዲሆናት የአኮርን ሸለቆ መልሼ እሰጣታለሁ። በዚያም በወጣትነቷ ቀናት፥ ከግብጽ ምድር በወጣችባቸው ቀናት እንዳደረገችው ትመልስልኛለች። **16** የእግዚአብሔር አዋጅ ይህ ነው፦«በዚያን ቀን እንዲህ ይሆናል፥ ባሌ ብለሽ ትጠሪኛለሽ፤ ከእንግዲህ ወዲያም በአሌ ብለሽ አትጠሪኝም። **17** የበአልን አማልክት ስም ከአንደበቷ አስወግዳለሁና ስሞቻቸው ከእንግዲህ ወዲያ አይታሰቡም። **18** በዚያን ቀን ከዱር አራዊት፥ ከሰማይ አእዋፍና በምድር ከሚንቀሳቀሱት ነገሮች ጋር ቃል ኪዳን አደርግላቸዋለሁ። ቀስትን፥ ሰይፍንና ጦርነትን ክምድሪቱ አስወግዳለሁ፥ በሰላምም እንድትጋደሙ አደርጋችኋለሁ። **19** ለዘላለም ባልሽ ልሆን ቃል እገባልሻለሁ። በጽድቅ፥ በፍትሕ፥ በኪዳን ታማኝነትና በምሕረት ባልሽ ልሆን ቃል እገባልሻለሁ። **20** በታማኝነት ባልሽ ልሆን ቃል እገባልሻለሁ። አንቺም እኔን እግዚአብሔርን ታውቂያለሽ። **21** የእግዚአብሔር አዋጅ ይህ ነው፦ በዚያን ቀን እመልሳልሁ። «ለሰማያት እመልሳለሁ፥ እነርሱም ለምድር ይመልሳሉ። **22** ምድርም ለእህሉ፥ ለአዲሱ ወይን ጠጅና ለዘይቱ ትመልሳለች፥ እነርሱም ለኢይዝራኤል ይመልሳሉ። **23** ስለ ራሴ ስል በምድሪቱ ላይ እተክላታልሁ፥ ሎሩሃማንም እምራታለሁ። ሎዓሚንንም፦ አንተ ዓሚ አታህ ነህ እለዋለሁ፤ እነርሱም አንተ አምላካችን ነህ ይሉኛል።»

Hosea 2:1

አያያዥ ሃሳብ
ያህዌ ለሆሴዕ እየተናገረ ነው

ህዝቤ!
ይህ አጋኖ እንደ ሙሉ ሃሳብ ሊገለጽ ይችላል። "እናንተ የእኔ ህዝብ ናችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ አጋኖ የሚለውን ይመልከቱ)

ርህራሄ ተደርጎልሻል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ያህዌ ርህራሄ አድርጎልሻል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ርህራሄ
"ደግነት" ወይም "ምህረተ"

Hosea 2:2

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለሆሴዕ እየተናገረ ነው

መግት
ይህ በህግ አደባባይ አንድ ሰው በሌላ ሰው ላይ የሚያቀርበው ክርክር ነው

እናታችሁ
እዚህ ስፍራ "እናት" የሚለው የሚያመለክተው የእስራኤልን አገር ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሷ ሚስቴ አይደለችም
ያህዌ እስራኤልን እንደ ሴት እየተናገረ ለእርሱ ከእንግዲህ እንደ ሚስት እንዳልሆነች ይነግራታል። ይልቁንም እስራኤል ያህዌን ከመከተል እና ከማምለክ ፊቷን አዙራለች። (ዘይቤያዊ አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔም ባሏ አይደለሁም
ያህዌ ከእንግዲህ ከእስራኤል ጋር ባል ለሚስቱ እንደሚሆነው ግንኙነት ሊኖረው አይችልም። (ዘይቤያዊ አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

የምንዝርና ተግባሯ
አመንዝራ የሆነች ሴት ከሌላ ሰው ጋር ለመተኛት ባሏን ትተዋለች። እስራኤል በያህዌ ላይ ያደረገችው እንደዚሁ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

ከጡቶቿ መካከል
ይህ ምስላዊ ዘይቤ እስራኤል በያህዌ ላይ ሳይሆን በጣኦት መታመኗን ያሳያል። (ዘይቤያዊ አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

ዕርቃኗን ገፍፌ እንደተወለደችበት ቀን እራቁትነቷን እገልጣለሁ
ያህዌ ከእንግዲህ እስራኤልን አይጠብቃትም አይንከባከባትም፤ ምክንያቱም ከእርሱ እርቃለችና። በእስራኤል ባሎች ሚስቶቻቸውን ለማልበስ በህግ ይገደዱ ነበር። አንድ ወንድ ይህንን አለማድረጉ ሚስቱን ያለመቀበሉ ምልክት ነበር። የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። (ዘይቤያዊ አነጋር እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ በረሃ አደርጋታለሁ
ያህዌ እስራኤልን ባዶ እና የማታበቅል በረሃማ ስፍራ እስክትመስል ይለውጣታል።(ተነጻጻሪ ዘይቤ/ሲሚሊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከጥማት የተነሳ እገድላታለሁ
እዚህ ስፍራ "ጥማት" የሚለው የሚያመለክተው በጣኦታተት ላይ ሳይሆን፤ በያህዌ ላይ መታመንና እርሱን ማምለክ ያለውን አስፈላጊነት፣ ካልሆነ እስራኤል እንደ አገር መቀጠል የማትችል መሆኑን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 2:4

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለሆሴዕ እየተናገረ ነው

የምንዝርና ልጆች ናቸውና
እስራኤላዊያን የሚያደርጉት የያህዌ ያልሆኑ ይመስል ነው። አባቶቻቸው እግዚአብሔርን እንዳላመለኩት ሁሉ፣ እነርሱም አላመለኩትም። (ዘይቤያዊ አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

እናቶቻቸው አመንዝሮች እንደነበሩ
ሌሎች አማልዕክትን የተከተሉት የቀደሙት ትውልዶች ለያህዌ ታማኝ ባለመሆናቸው አመንዝሮች ተደርገው ነበር የተቆጠሩት። (ዘይቤያዊ አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

ፍቅረኞቼን ተከትዬ እሄዳለሁ፣ እነርሱ ዳቦዬን እና ውሃዬን፣ የሃር ልብሴን እና ሱፌን፣ ዘይቴን እና መጠጤን ሰጥተውኛልና።
እዚህ ስፈራ "ፍቅረኞቼ" የሚለው የሚያመለክተው እስራኤል ከያህዌ ይልቅ ልታመለክ የመረጠቻቸውን በዓልን እና ሌሎች ሃሰተኛ አማልዕክትን ነው። የተዘረዘሩት ነገሮች ሰዎች ለመኖር የሚያስፈልጓቸው ነገሮች ናቸው። (ዘይቤያዊ አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 2:6

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለሆሴዕ እየተናገረ ነው

ስለዚህ መንገዷን በእሾች ለመዝጋት አጥርባታለሁ። መውጫ መንገድ እንዳታገኝ በዙሪያዋ ግንብ እገነባለሁ።
ይህ ክፍል ህዝቡ ስኬት እና ብልጽግና እንዳያገኝ ያህዌ እንደሚከለክለው ያመለክታል፣ ምክንያቱ እነርሱ ጣኦት ማምለካቸውን መቀጠላቸው ነው። (ዘይቤያዊ አነጋር እና ተመሳሳይ ንጽጽራዊ ዘይቤ/ፓራራሊዝም የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያም እንዲህ ትላለች፣ "ከአሁኑ ይልቅ ለእኔ የመጀመሪያው ባሌ የተሻለ ስለነበረ ወደ እርሱ እመለሳለሁ።"
እስራኤላውያን ወደ ያህዌ የሚመለሱት ለእርሱ ባላቸው ፍቅር ምክንያት ሳይሆን፣ ነገር ግን በበኣል አምልኳቸው ተስፋ ስለቆረጡ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 2:8

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለሆሴዕ እየተናገረ ነው

እርቃኗን ትሸፍንበት የነበረውን ሀር እና ሱፌን መልሼ እወስዳለሁ
ይህ ማለት ማናልባት የእስራኤል መኸር እና ከብቶች ከንቱ ይሆናል ማለት ሊሆን ይችላል። ያህዌ በረከቱን ከእስራኤል ያርቃል፣ ህዝቡም በአደጋ ስጋት ውስጥ ብቻውን ይሆናል። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት)

እራቁትነትዋን ልትሸፍንበት ትጠቀምበት የነበረው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች ራሳቸውን ለመሸፈን ይጠቀሙበት የነበረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 2:10

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለሆሴዕ እየተናገረ ነው

ከዚያም በፍቅረኞቿ ፊት እርቃኗን እገልጣለሁ
ይህ ማለት እግዚአብሔር የእስራኤልን ህዝብ በአካባቢው ባሉ ሌሎች ህዝቦች ፊት ያዋርዳቸዋል። ይህንን በሆሴዕ 2:3 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ዘይቤያዊ አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

ማንም እርሷን ከእጄ አያድናትም
ማንም እስራኤልን ሊረዳት አይሞክርም። እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን የመቅጣት ሃይል ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት)

Hosea 2:12

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ በእራኤል ላይ ስለሚያደርገው ለሆሴዕ እየተናገረ ነው

ፍቅረኞቼ ለእኔ የሰጠኝ ዋጋዎቼ/ክፍያዎቼ እነዚህ ናቸው
ይህ የሚያመለክተው እስራኤል ከሃሰተኛ አማልዕክት ወይም ከበኣል የተቀበለቻቸውን ክፍያዎች ነው። ይህ ቀጥተኛ ጥቅስ ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅስ ሆኖ ሊጻፍ ይችላል። "እንግዲህ እነዚህ ፍቅረኞቿ ለእርሷ የሰጧት ወጋዎች ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋር እና ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ጥቅሶች የሚለውን ይመልከቱ)

ጫካ አደርገዋለሁ
ያህዌ ሌሎች ዛፎች እና አረም እንዲበቅል በመፍቀድ የወይን ተክሉን እና የፍሬ ዛፉን ያጠፋል። (ዘይቤያዊ አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ ነው/ ያህዌ የተናገረው ይህ ነው
ያህዌ የአዋጁን እርግጠኝነት ለመግለጽ ስለ እራሱ በስሙ ተናገረ። "ያህዌ ያወጀው/የተናገረው ይህ ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያወጅኩት/የተናገርኩት ይህ ነው። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 2:14

አያያዥ ሃሳብ:
ያህዌ ስለ እራኤል እየተናገረ ነው።

ስለዚን መልሼ የራሴ ላደርጋት ነው
"እኔ ያህዌ እርሷን ወደ ራሴ እመልሳለሁ"

የአኮር ሸለቆ እንደ ተስፋ በር
ያህዌ እስራኤልን ከግብጽ መርቶ እንዳወጣ፣ እስራኤል ዳግም በያህዌ ተስፋ እንድታደርግ ወደ አኮር ሸለቆ ይመራታል

ከግብጽ እንደ ወጣችበት ወራት፣ በወጣትነት ወራቷ ታደርግ እንደነበረው ከዚያ ሆና ትመልስልኛለች፣
ያህዌ እስራኤል ህዝብ በንስሃ እንደሚመለሱ እና ዳግም እርሱን አምላካቸው አድርገው ማምለክን እንደሚመርጡ ተስፋ ያደርጋል። (ዘይቤያዊ አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

ትመልሳለለች
አንዳንድ ዘመናዊ ትርጉሞች የዕብራይስጡ ቃል "ትዘምራለች" እንደሚል ይወስዱታል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Hosea 2:16

በዚያን ቀን ይሆናል
ይህ የሚያመለክተው እስራኤል ያህዌን ብቻ ማምለክ የምትመርጥበትን ቀን ነው

ይህ የያህዌ አዋጅ ነው/ ያህዌ የተናገረው ይህ ነው
ያህዌ የአዋጁን እርግጠኝነት ለመግለጽ ስለ እራሱ በስሙ ተናገረ። ይህንን በሆሴዕ 2፡13 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። "ያህዌ ያወጀው/ የተናገረው ይህ ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያወጅኩት/የተናገርኩት ይህ ነው። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ባሌ
ይህ ማለት ሚስት ለባሏ እንደምትሆን የእስራኤል ህዝብ ያህዌን የሚወድ እና ለእርሱ ታማኝ ይሆናል። (ዘይቤያዊ አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

በኣሌ
"በኣል" ማለት "ጌታ" ማለት ሲሆን ከነዓናውያን የሚያመልኳቸውን ሀሰተኛ አማልክትንም ያመለክታል። (ዘይቤያዊ አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

ከአንደበቷ የበኣልን ስሞች አስወደግዳለሁ
እስራኤላዊያን ዳግም የበኣልን ስሞች እና ጣዖታትን አይጠሩም። ህዝቡ የተወከለው በአንደበቶቻቸው ነው። "የበኣልን ስሞች እንዳትጠሩ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲኪ/ ዘይቤያዊ አነጋጋር- የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ፤ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 2:18

አያያዥ ሃሳብ
ያህዌ ለእስራኤል ምን እንደሚያደርግ ለሆሴ እየተናገረ ነው

በዚያን ቀን
ይህ ሀረግ በእስራኤል እና በያህዌ መሃል ስላለው የወደፊት መታደስ ለመናገር ውሏል።

ለእነርሱ ቃል ኪዳን አደርጋለሁ
የያህዌ አዲሱ ቃል ኪዳን ለእንስሳት ሳይቀር ሰላምን ይጨምራል

ቀስትን፣ ሰይፍን፣ እና ከምድሪቱ ጦርነትን አስወግዳለሁ፣ እናንተም በደህንነት እንድታርፉ አደርጋለሁ
ያህዌ የእስራኤልን ጠላቶች ከዙሪያቸው ያርቃል፣ ከዚህ በኋላ ጦርነት አይኖርም፣ ህዝቡ በሰላም ይጠበቃል። እዚህ ስፍራ "ቅስት፣ ሰይፍ፣ እና ጦርነት" የሚሉት ቃላት ሁሉም ጦርነት የሚለውን ቃል ይገልጻሉ። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በደህንነት እንዲያርፉ
ይህ አገላለጽ በደህንነት መኖርን ያመለክታል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 2:19

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ምን እንደሚያደርግ ለሆሴ እየተናገረ ነው

ለዘለዓለም ባልሽ ልሆን ቃል ኪዳን እገባልሻለሁ
ያህዌ ልክ እንደ ባል ይሆናል፣ እስራኤል እንደ ያህዌ ሚስት ትሆናለች። (ዘይቤያዊ አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

በጽድቅ፣ በፍትህ፣ ለቃልኪዳን ታማኝ በመሆን፣ እና በምህረት
ይህ ረቂቅ ስሞችን ለማስቀረት እንደገና ሊጻፍ ይችላል። "ትክክል፣ፍትህ ያለበት፣ ታማኝ እና ምህረት የሞላበትን ነገር አድርጉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

አንቺም ያህዌን ታውቂያለሽ
እዚህ ስፍራ "ማወቅ" የሚለው እንደ አምላካቸው ለያህዌ እውቅና መስጠትንና ለእርሱ ታማኝ መሆንን ነው።

Hosea 2:21

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ምን እንደሚያደርግ ለሆሴ እየተናገረ ነው።

ይህ የያህዌ አዋጅ ነው/ ያህዌ የተናገረው ይህ ነው
ያህዌ የአዋጁን እርግጠኝነት ለመግለጽ ስለ እራሱ በስሙ ተናገረ። ይህንን በሆሴዕ 2፡13 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። "ያህዌ ያወጀው/ የተናገረው ይህ ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያወጅኩት/የተናገርኩት ይህ ነው። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ምድር ለእህል፣ አዲስ ወይን፣ እና ለወይራ ዘይት ምላሽ ይሰጣል፤ እነርሱም ለኢይዝራኤል ምላሽ ይሰጣሉ።
ምድር ለእህል፣ አዲስ ወይን፣ እና ለወይራ ዘይት የሚያስፈልገውን ትሰጣለች። እነዚህ ነገሮች ደግሞ የኢዝራኤልን ፍላጎቶች ያሟላሉ። ምድሪቱ እና እነዚህ ምርቶች የሌሎችን ፍላጎት ማሟላት እንደሚችሉ ሰዎች ሆነው ተገልጸዋል። (ሰውኛ የሚለውን ዘይቤ ይመልከቱ)

ኢዝራኤል
እዚህ ስፍራ የዚህ ሸለቆ ሰም መላውን የእስራኤል ህዝብ ይወክላል። (ዘይቤያዊ አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 2:23

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ምን እንደሚያደርግ ለሆሴ እየተናገረ ነው። ለእኔ ለራሴ በምድሪቱ እተክላታለሁ እግዚአብሔር ዳግም ህዝቡን በምድራቸው ደህንነት እና ብልጽግና ሲሰጣቸው፣ እነርሱ የተገለጹት በእርሻ ሰብል ነው። "ገበሬ ሰብሉን ዘርቶ እንደሚንከባከብ እስራኤልን እንከባከባለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

ሎ-ሩሃማ
የዚህ ስም ትርጉም "አልምርም" ማለት ነው። ተርጓሚው ይህንን ትረጉም እንደ ስም አድርጎ ማቅረብን ሊመርጥ ይችላል። ይህንን ስም በሆሴዕ 1፡6 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። "አልምርም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሎ-ዓሚ
የዚህ ስም ትረጉም " ህዝቤ አይደላችሁም" ማለት ነው። ተርጓሚው ይህንን ትረጉም እንደ ስም አድርጎ ማቅረብን ሊመርጥ ይችላል። ይህንን ስም በሆሴዕ 1፡9 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።"ህዝቤ አይደላችሁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ዓሚ አታህ
የዚህ ስም ትረጉም "እናንተ የእኔ ህዝብ ናችሁ" ማለት ነው። ተርጓሚው ይህንን ትረጉም እንደ ስም አድርጎ ማቅረብን ሊመርጥ ይችላል። "እናንተ የእኔ ህዝብ ናችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ፦«እንደገና ሂድ፥ ባልዋ የሚወዳትን ነገር ግን አመንዝራ የሆነችውን ሴት ውደድ። ወድ ሌሎች አማል ክት ዘወር ቢሉና የዘቢብ እንጎቻ ቢወዱም እንኳን፥ እኔ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ እንደምወድ ውደዳት።» **2** ስለዚህ በአሥራ አምስት የብር ሳንቲሞችና በአንድ ቆሮስ ተኩል ገብስ ገዛኋት። **3** እኔም፦ «ከእኔ ጋር ብዙ ቀናት ኑሪ፥ ሴተኛ አዳሪ ወይም የሌላ የማንም ሰው አትሆኚ፥እኔም እንዲዚሁ ከአንቺ ጋር እሆናለሁ» አልኳት። **4** የእስራኤል ሕዝብ ያለ ንጉሥ፥ ያለ መስፍን፥ ያለ መሥዋዕት፥ ያለ ድንጋይ ዓምድ፥ ያለ ኤፉድ ወይም ያለ ቤተሰብ ጣዖት ለብዙ ቀናት ይኖራሉ። **5** ከዚያም በኋላ የእስራኤል ሰዎች ይመለሳሉ፥ እግዚአብሔር አምላካቸውንና ንጉሣቸውን ዳዊትንም ይፈልጋሉ። በመጨረሻዎቹም ቀናት በእግዚአብሔርና በበረከቱ ፊት እየተንቀጠቀጡ ይመጣሉ።

Hosea 3:1

ደግም ሂድ፣ በባሏ የተወደደችን ነገር ግን አመንዝራ የሆነችን ሴት ውደድ
ይህ ተመልሶ በሆሴዕ 1:2 ያለውን ነገር ያመለክታል። ያህዌ ዳግም ሆሴዕን አመንዝራ ሴትን እንዲወድ ይነግረዋል።

እኔ ያህዌ የእስራኤልን ህዝብ እንደምወደው ልክ እንደዚያው አመንዝረይቱን ሴት ውደዳት
አመንዝራዋን ሴት በመውደድ፣ ሆሴዕ ያህዌ ለእስራኤል ላለው ፍቅር ምሳሌ ይሆናል። (ትዕምርታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ወደሌሎች አማልዕከት ዞር ቢሉ እና የዘቢብ ጥፍጥፍ ቢወዱም
ህዝቡ ሀሰተኛ አማልዕክት በሚያመልኩበት በኣላት ወቅት የዘቢብ ወይም በለስ ጥፍጥፍ ይመገባሉ

አስራ አምስት ሰቅል ጥሬ ብር/ አስራ አምስት የብር ቁርጥራጮች/ እና አንድ ቆሮስ/ጋሎን ተኩል መስፈሪያ ገብስ
ይህ አንድ ባሪያ የመግዣ ዋጋ ነበር።

አስራ አምስት ቁርጥራጭ
"15 ቁርጥራጭ" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

እና አንድ ቆሮስ/ጋሎን ተኩል መስፈሪያ ገብስ
ይህ ወደ ዘመናዊ መለኪያ ሊለወጥ ይችላል። ወደ "330 ሊትር ገብስ" (መጽሀፍ ቅዱሳዊ የመጠን መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 3:4

የእስራኤል ህዝብ ያለ ንጉሥ፣ ያለ ልዑል፣ ያለ መስዋዕት፣ ያለ ድንጋይ አምድ፣ ያለ ኤፉድ ወይም ያለ ነፍስ ወከፍ ጣኦታት ለአያሌ ዘመናት ይኖራል
በማመንዘሯ ምክንያት ሆሴዕ ያለ ሚስቱ እንደሚኖር ሁሉ፣ አመንዝራለችና እስራኤል ያለ ንጉሥ እና እግዚአብሔርን ሳታመልክ ትኖራለች።

አምላካቸውን ያህዌን ፈለጉ
እዚህ ስፍረ "ፈለጉ" ማለት እግዚአብሔር እነርሱን እና አምልኳቸውን እንዲቀበል ጠየቁት ማለት ነው

ንጉሣቸው ዳዊት
እዚህ ስፍራ "ዳዊት" የሚወከለው የዳዊትን ትውልዶች ነው። "የዳዊት ዘር ንጉሣቸው እንዲሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት)

በመጨረሻው ቀናት
"በመጪው ዘመን"

እየፈሩ እና እየተንቀጠቀጡ በያህዌ እና በእርሱ መልካምነት ፊት ይቀርባሉ
እዚህ ስፍራ "መንቀጥቀጥ" የሚለው የሚገልጸው የአክብሮትን እና ትህትናን ስሜት ነው። "ወደ ያህዌ ይመለሳሉ፣ ራሳቸውን በፊቱ ያዋርዳሉ፣ እርሱን ያከብራሉ፣ የእርሱን በረከቶችም ይለምናሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 የእስራኤል ሕዝብ ሆይ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ። እውነተኛነት፥ ለኪዳን ታማኝነት፥ እግዚአብሔርን ማወቅ በምድሪቱ የለምና እግዚ አብሔር በምድሪቱ
ከሚኖሩ ጋር ሙግት አለው። **2** መርገም፥ መዋሸት፥ መግደል፥ መስረቅና ማመንዘር በዚያ አለ። ሕዝቡ ስምምነቶችን ሁሉ ያፈርሳሉ፥ ሳያቋርጡ ደም ይፋሰሳሉ።
3 ስለዚህ ምድሪቱ ደረቀች፥ በእርሷ የሚኖሩ ሁሉ መነመኑ፥ የዱር አራዊትና የሰማይ አእዋፍ፥ የባሕርም ዓሦች እንኳን አለቁ። **4** ነገር ግን ማንም ሙግቱን
አያቅርብ፥ማንም ሌላውን ማንንም አይክሰስ። ምክንያቱም እኔ የምከስው እናንተን ካህናቱን ነውና። **5** እናንተ ካህናት በቀን ትሰናከላላችሁ፥ ነቢያቶቹም ከእናንተ
ጋር በሌሊት ይሰናከላሉ፥ እናታችሁንም አጠፋታለሁ። **6** ሕዝቤ ዕውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል። እናንተ ካህናት ዕውቀትን ጥላችኋልና እኔም
እጥላችኋለሁ። እኔ አምላካችሁ ብሆንም ሕጌን ረስታችኋል፥ እኔም ልጆቻችሁን እረሳለሁ። **7** ካህናቱ በበዙ መጠን የሚሠሩብኝ ኃጢአት በዝቶአል። ክብራቸውን
ወደ ውርድት እለውጠዋለሁ። **8** የሕዝቤን ኃጢአት ይመገባሉ፥ ክፋታቸውም እንዲበዛ ይቋምጣሉ። **9** በካህናቱ ላይ እንደሚሆን እንዲሁ በሕዝቡም ላይ
ይሆናል፦ ስለ ልማዶቻቸው እቀጣቸዋለሁ፤ እንደ ሥራቸውም አከፍላቸዋለሁ። **10** ከእኔ ከእግዚአብሔር ርቀው ሄደዋልና ትተውኛልምና፤ይበላሉ ግን
አይጠግቡም፥ ያመነዝራሉ ግን አይበዙም። **11** ሴሰኝነት፥ የወይን ጠጅና አዲስ የወይን ጠጅ ማስተዋላቸውን ወስዶታል። **12** የእንጨት ጣዖቶቻቸውን
ያማክራሉ፥ በትሮቻቸውም ይተነብዩላቸዋል። የሴሰኝነት መንፈስ አስቶአቸዋል፥ እኔን አምላካቸውንም ትተውኛል። **13** በተራሮች ጫፍ ላይ ይሠዋሉ፥ ጥላው
መልካም ነውና ከባሉጥ፥ ከኮምቦልና ከአሆማ ዛፍ በታች በኮረብቶች ላይ ያጥናሉ። ስለዚህ ሴቶች ልጆቻችሁ የዝሙት ርኩሰት ይፈጽማሉ፥ የልጆቻችሁ
ሚስቶች ያመነዝራሉ። **14** ሴቶች ልጆቻችሁ የዝሙት ርኩሰትን በወደዱ ጊዜ፥ ወይም የልጆቻችሁ ሚስቶች ባመነዘሩ ጊዜ አልቀጣቸውም። ምክንያቱም ወንዶቹ
ራሳቸውን ለሴተኛ አዳሪዎች ሰጥተዋልና፥ እንዲሁም ከቤተ ጣዖት ሴተኛ አዳሪዎች ጋር ርኩሰትን ለመፈጸም መሥዋዕት ይሰዋሉና። ስለዚህ ይህ የማያስተውል
ሕዝብ ይጠፋል። **15** እስራኤል ሆይ አንቺ ብታመነዝሪም፥ ይሁዳ በደለኛ አይሁን። እናንተ ሰዎች፥ ወደ ጌልጌላ አትሂዱ፥ ወደ ቤትአዌንም አትውጡ። ሕያው
እግዚአብሔርን ብላችሁም አትማሉ። **16** እስራኤል እንደ እልኸኛ ጊደር በእልኸኝነት ሄዳለችና፤ እንዴት እግዚአብሔር በለመለመ መስክ እንዳ ሉ ጠቦቶች
ያሰማራታል? **17** ኤፍሬም ራሱን ከጣዖታት ጋር አጣምሮአል፤ብቻውን ተውት። **18** አስካሪ መጠጣቸው ባላቀ ጊዜ እንኳን ማመንዘራቸውን አያቆ
ሙም፤ገዢዎቿም ነውራቸውን እጅግ ይወዳሉ። **19** ነፋሱ በክንፎቹ ይጠቀልላታል፥ ከመሥዋዕቶቻቸውም የተነሳ ይፍራሉ።

Hosea 4:1

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ምዕራፍ ታማኝ ባልሆኑት እስራኤላዊያን ላይ የያህዌን ክርክር በማቅረብ ይጀምራል

ያህዌ ከምድሪቱ ነዋሪዎች ጋር ሙግት አለው
ያህዌ የእስራኤል ህዝብ እንደበደለው እና ቃል ኪዳኑን እንዳፈረሰ ይናገራል፤ ያህዌ ይህን የሚናገረው በፍርድ ቤት እንደሚከሳቸው አድርጎ ነው።

መግት
ይህ በህግ አደባባይ አንድ ሰው በሌላ ሰው ላይ የሚያቀርበው ክርክር ነው። ይህንን በሆሴዕ 2፤2 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

ህዝቡ ሁሉንም ወሰኖች ጥሰዋል
እዚህ ስፍራ "ወሰኖች" የሚለው የሚገልጸው ህጉ የሚፈቅደውን መጠን ነው። "ህዝቡ በሁሉም መንገድ ህጉን አልታዘዘም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በደም ማፍሰስ ላይ ደም ማፍሰስ ይጨምራል
እዚህ ስፍራ "ደም ማፍሰስ" የሚለው የሚገልጸው "ግድያን" ነው፤ ይህም ብዙውን ጊዜ የተጠቂውን ደም መፍሰስ ይጨምራል። "በግድያ ላይ ግድያ ጨመራችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት)

Hosea 4:3

ስለዚህም ምድሪቱ ድርቅ እየመታት ነው
ይህ አገላለጽ ለረጅም ጊዜ ዝናብ የታጣበትን የድርቅ ጊዜ ያመለክታል።

እየኮሰመኑ መሄድ
ከህመም እና ምግብ ከማጣት የተነሳ ደካማ እየሆኑ እና እየሞቱ መሄድ

ይወሰዱ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እየሞቱ ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 4:4

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ስለ እስራኤል እየተናገረ ነው

መግት
ይህ በህግ አደባባይ አንድ ሰው በሌላ ሰው ላይ የሚያቀርበው ክርክር ነው።

ማንም ሌላውን አይክሰስ
ማንም ሰው ሌላውን ሰው በማናቸውም ነገር መክሰስ የለበትም፤ ምክንያቱም እያንነዱ ሰው በአንድ ነገር ጥፋተኛ ነውና።

ካህናቶቻችሁ ይደነቃቀፋሉ
እዚህ ስፍራ "መደናቀፍ" የሚለው እግዚአብሔርን አለመታዘዝ ወይም እርሱን መታመን ማቆምን ጭምር ያመለክታል።

Hosea 4:6

አጠቃላይ መረጃ
በምዕራፍ 4፡6 ያህዌ ስለ እስራኤል ህዝብ ለካህናቱ ይናገራል። በምዕራፍ 4፡7 ስለ ካህናቱ እርሱ ይናገራል እንጂ ለእነርሱ አይናገርም። ተርጓሚው የዩዲቢን ምሳሌነትን ሊከተል ይችላል፤ ይህም ያህዌን፣ ለካህናቱ ሲናገር በምዕራፍ 4፡7 እንደሚገልጸው አይነት ነው።

ህዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሳ ጠፍቷል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ህዝቤ ጠፍቷል ምክንያቱም እናንተ፣ ካህናቱ፣ ይታዘዙኝ ዘንድ ስለ እኔ በሚገባ አላስተማራችኋቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ዕውቀት
እዚህ ስፍራ "ዕውቀት" የሚለው የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን እውቀት ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ክብራቸውን በውርደት ለወጡ
አማራጭ ትረጉም ሊሆኑ የሚችሉት1) "ክብር" ያህዌን የሚወክል ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት/ ነው። "ሀፍረት" ጣኦታትን የሚወክል ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት/ ነው። " ታላቁን አምላካቸውን እኔን ማምለክ ትተዋለ፣ አሁን አሳፋሪ ጣኦታቶቻቸውን ያመልካሉ" 2) አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትረጉሞች ይህንን የሚተረጉሙት "ክብራቸውን በውርደት እለውጣለሁ" በሚል ነው። ይህ ማለት ያህዌ ካህናቱ የሚያከሯቸውን ነገሮች ይወስድባቸዋል ደግሞም ካህናቱ እንዲያፍሩ ያደርጋል። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 4:8

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ ካህናቱ መናገሩን ቀጠለ

በህዝቤ ሀጢአት እነርሱ ይባላሉ
ህዝቡ ሲበድል፣ እግዚአብሔር ይቅር እንዲላቸው መስዋዕት ያቀርባሉ። ካህናቱ እነዚህን መስዋዕቶች መብላት ይፈቀድላቸው ነበር። የካህናቱ ለኃጢአት የቀረበውን መስዋዕት መብላታቸው የህዝቡን ኃጢአት እንደተመገቡ ተደርጎ ይነገራል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀትና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ እንዲሁም ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ክፋታቸውን እጅግ ይጨምራሉ
ካህናቱ ህዝቡ በጢአቱ እየከፋ እንዲሄድ ይፈልጋሉ፤ ይህም እነርሱ የሚበሉትን ህዝቡ የሚያቀርበው መስዋዕት እንዲጨምር ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀትና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ)

በካህናቱ ላይ እንደሚሆነው እንደዚያው በህዝቡ ላይ ይሆናል
"ህዝቡና ካህናቱ በተመሳሳይ መንገድ ይቀጣሉ"

ልምምዶቻቸው
"ልምዶቻቸው" ወይም "የእነርሱ ባህርይ"

Hosea 4:10

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ስለ እስራኤል እየተናገረ ነው

ነገር ግን አይበዙም
"ልጆች አይወልዱም"

ርቀው ሄደዋል
ህዝቡ እግዚአብሔርን ማምለክ እና መከተል አቁመዋል።

ከያህዌ
ያህዌ ስለ እራሱ በሶስተኛ መደብ እየተናገረ ነው። ይህ በአንደኛ መደብ ሊጻፍ ይችላል። "ከእኔ" በሚል። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 4:11

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ስለ እስራኤል እየተናገረ ነው ሴሰኝነት፣ አሮጌ ወይን ጠጅ፣ እና አዲስ ወይን ጠጅ ማስተዋላቸውን ወስደውባቸዋል የእስራኤል ሰዎች ከጋብቻ ውጭ ይሴሰናሉ፤ ደግሞም ብዙ የወይን ጠጅ ይጠጣሉ። እነዚህን ነገሮች በማድረግ የያህዌን ትዕዛዛት ረሱ። እዚህ ስፍራ እነዚህ ድርጊቶች የተነገሩት ሌሎች ሰዎች ያህዌን የመታዘዛቸውን ጠቀሜታ እንዳይረዱ እንደሚከላከሉ ሰዎች ተደርገው ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዘንጎቻቸው ትንቢት ለመናገር ምሪት ሆናቸው
ጣኦት አምላኪዎች የወደፊቱን ለመተንበይ ዘንጎችን ይጠቀማሉ። እዚህ ስፍራ ዘንጎች የተነገሩት ትንቢትን እንደሚናገሩ ሰዎች ተደርገው ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሴሰኛ አስተሳሰብ አሳታቸው
ጣኦታትን ማምለክ እና ከቤተ ጣኦት አመንዝሮች ጋር መዘሞታቸው የእስራኤል ሰዎች በእነዚህ መንገዶች ሁሌም በያህዌ ላይ በደል እንዲፈጽሙ ፍላጎት አሳደረባቸው። እዚህ ስፍራ "አስተሳሰብ/አዕምሮ" የተነገረው ህዝቡ ያህዌን እንዳይታዘዝ ማሳመን እንደሚችል አንድ ሰው ተደርገው ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አሳቷቸው
ህዝቡ እንዲበድል አሳመኑ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 4:13

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ስለ እስራኤል እየተናገረ ነው

በተራሮች አናት... በኮረብቶች
ህዝቡ ጣኦታታትን በእነዚህ ስፍራዎች ማኖሩ የተለመደ ነበር፣ በብሉይ ኪዳን እነዚህ ስፍራዎች ብዙውን ጊዜ "ከፍተኛ ስፍራዎች" ተብለው ይጠሩ ነበር።

የተቀደሱ ዝሙት አዳሪዎች
እነዚህ ሴቶች ጣኦታቱን ለማምለክ የሚመጡ ወንዶች ጋር ወሲባዊ ግንኙነት የሚፈጽሙ ነበሩ። ይህ ድርጊት ለሀሰተኛ አማልክቶቻቸው ክብር የሚፈጸም የተቀደሰ ድርጊት ተደርጎ ይታይ ነበር።

ስለዚህ ይህ የማያስተውል ህዝብ ወደ ጥፋት ይሄዳል
ያህዌ የእስራኤልን ህዝብ ያጠፋል ምክንያቱም እነርሱ አያስተውሉም ወይም የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት አይጠብቁም። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 4:15

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ስለ ይሁዳ እና ስለ እስራኤል እየተናገረ ነው

ይሁዳ አይበድል
እግዚአብሔር እስራኤል ምን ያህል በደለኛ እንደሆነች ስላየ ይሁዳ ተመሳሳይ ነገር እንዲፈጽም አልፈለገም

ወደ ጌልገላ አትሂዱ፣ እናንተ ሰዎች ሆይ፣ ወደ ቤትአዌንም አትውጡ
የይሁዳ ህዝብ በእነዚያ ስፍራዎች ጣኦት ለማምለክ ወደ ጌልገላ ወይም ወደ ቤትአዌን ከተሞች እንዳይሄድ ማስጠንቀቂያ ተሰጠው። ጌልገላ በአንድ ወቅት ያህዌ የሚመለክበት ስፍራ ነበር፣ ነገር ግን የጣኦት ማምለኪያ ስፍራ ሆነ።

ቤትአዌን
ይህ ከተማ በእስራኤል ሰሜናዊ ግዛት እና በደቡባዊ ግዛት በቢንያም ነገድ ድንበር መሃል የሚገኝ ነበር። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ እልኸኛ ጊደር
እስራኤል ጌታዋን ከማትታዘዝ ትንሽ ላምጋር ተነጻጽራለች። (ተነጻጻሪ ዘይቤ/ ሲሚሊ የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ እነርሱን እንዴት በለመለመ መስክ እንደሚገኙ ጠቦቶች ያሰማራቸዋል?
ያህዌ ጥያቄውን የተጠቀመበት ህዝቡን መንከባከብ መቀጠል እደማይችል በትኩረት ለመናገር ነው፤ ምክንያቱም ህዝቡ እልከኛ ነው። ያህዌ ከእንግዲህ ህዝቡን አይንከባከበውም የሚለው የተገለጸው ከእልከኝነታቸው የተነሳ እርሱ

በጎቹን ከእንግዲህ ይሰማሩ ዘንድ ወደ መስክ እንደማይወስድ እረኛ ተደርጎ ነው። "ያህዌ የሚያምጽን ህዝብ አያሰማራም" ወይም "ስለዚህም ያህዌ እነርሱን መንከባከቡን አይቀጥልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያው አነጋገር ወይም ቃለ ምልልሳዊ/ሬቶሪካል ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ያህዌ እንዴት
እዚህ ስፍራ ያህዌ በሶስተኛ መደብ ስለ እራሱ እየተናገረ ነው። ይህ በአንደኛ መደብ ሊጻፍ ይችላል። "እኔ እንዴት" በሚል። (አንደኛ፣ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 4:17

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ስለ እስራኤል እየተናገረ ነው

ኤፍሬም ከጣኦት ጋር ተጣምሯል፤ እርሱን ተዉት
እዚህ ስፍራ "ኤፍሬም" መላውን ሰሜናዊ የእስራኤል ግዛት ይወክላል። ይህ አገላለጽ በዚያ የሚኖሩ ሰዎችን የሚገልጽ ሚቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት/ ነው። ያህዌን ከማምለክ ይልቅ ጣኦታትን ማምለክ መረጡ። ያህዌ ሆሴዕን ህዝቡን ከመንገዱ ይመለስ ዘንድ ለመገሰጽ እንዳይሞክር አዘዘው። የእስራኤል ህዝብ አይሰማም። (ስኔክቲኪ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ፤ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚሉትን ዘይቤዎች ይመልከቱ)

መሪዎቿ ሀፍረታቸውን እጅግ ወደዱ
መሪዎቿ ጣኦታትን ሲያመልኩ እና በያህዌ ላይ ፊታቸውን ሲያዞሩ በሚያደርጉት አያፍሩም ነበር

ነፋስ በክንፎቹ ጠቅልሎ ይወስዳታል
እዚህ ስፍራ "ነፋስ" የሚለው የሚወክለው በእስራኤል መንግሥት ላይ የእግዚአብሔርን ፍርድ እና ቁጣ ነው። ያህዌ የጠላት ሰራዊት የእስራኤልን ህዝብ እንዲያሸንፍ እና ምርኮ አድርጎ እንዲውዳቸው ይፈቅዳል። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሚቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚሉትን ዘይቤያዊ አነጋገሮች ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 5

1 በእናንተ በሁላችሁ ላይ ፍርድ እየመጣ ነውና፤ ካህናት ሆይ ይህን ስሙ! የእስራኤል ቤት ሆይ ልብ በሉ! የንጉሡ ቤት ሆይ ስሙ! እናንተ፥ በምጽጳ ላይ ወጥመድ፥ በታቦርም ላይ የተዘረጋ መረብ ሆናችኋል። **2** ዓመጸኞች በማረድ እጅግ በርትተዋል፥ ሁሉንም እገራቸዋለሁ። **3** ኤፍሬምን አውቀዋለሁ፥ እስራኤልም ከእኔ አልተሰወረችም። ኤፍሬም፥ አንተ አሁን እንደ ሴተኛ አዳሪ ሆነሃል፤ እስራኤልም ረክሳልች። **4** ሥራቸው ወደ እኔ ወደ አምላካቸው እንዲመለሱ አይፈቅድላቸውም፥ የአመንዝራነት መንፈስ በውስጣቸው አለ፥ እኔን እግዚአብሔርን አላወቁኝም። **5** የእስራኤል ትዕቢት ይመሰክርባታል፤ ስለዚህ እስራኤልና ኤፍሬም በበደላቸው ይሰናከላሉ፤ ይሁዳም ከእነርሱ ጋር ትሰናከላለች። **6** በጎቻቸውንና ከብቶቸውን ይዘው እግዚአብሔርን ፍልጋ ይሄዳሉ፥ ነገር ግን ከእነርሱ ተለይቶ ተመልሷልና አያገኙትም። **7** ዲቃሎች ልጆችን ወልደዋልና ለእግዚአብሔር ታማኞች አልሆኑም። አሁንም የወር መባቻ በዓላቱ እነርሱን ከእርሻቸው ጋር ይበሉአቸዋል። **8** በጊብዓ መለከትን፥በራማም እንቢልታን ንፉ። «ቢንያም ሆይ እንከተልሃለን!» እያላችሁ የጦርነት ድምጽ አሰሙ። **9** በቁጣው ቀን ኤፍሬም የፈረሰ ይሆናል። በእስራኤል ነገዶች መካከል በእርግጥ ሊሆን ያለውን አውጄአለሁ። **10** የይሁዳ መሪዎች የድምበር ድንጋይ እንደሚነቅሉት ናቸው። ቁጣዬን በላያቸው እንደ ውኃ አፈስሳለሁ። **11** ለጣዖታት ሊሰግድ ወስኖአልና ኤፍሬም ደቀቀ፥ በፍርድ ደቀቀ። **12** እኔ ለኤፍሬም እንደ ብል፥ለይሁዳም ቤት እንደ ነቀዝ እሆናለሁ። **13** ኤፍሬም በሽታውን ባየ ጊዜ፥ ይሁዳም ቁስሉን ባየ ጊዜ፤ኤፍሬም ወደ አሦር ሄደ፥ ይሁዳም ወደ ታላቁ ንጉሥ መልእክተኞችን ላከ። ነገር ግን እርሱ ሊያድናችሁ፥ ቁስላችሁንም ሊፈውስ አልቻለም። **14** ስለዚህ በኤፍሬም ላይ እንደ አንበሳ፥ በይሁዳም ላይ እንደ አንበሳ ደቦል እሆናለሁ። እኔ፥ አዎ እኔ፥ እገነጣጥላለሁ፥ እሄዳለሁ፥ እወስዳቸዋለሁ፥ የሚያድናቸውም ማንም የለም። **15** በደላቸውን እስኪያውቁና ፊቴን እስኪፈልጉ ድርስ፥ በመከራቸው አጥብቀው እስኪፈልጉኝ ድረስ፥ እሄዳለሁ፥ ወድ ስፍራዬም እመለሳለሁ።

Hosea 5:1

አያያዥ ሃሳብ
ያህዌ ስለ እስራኤል እየተናገረ ነው

በምጽጳ መጥመድ፣ በታቦርም ላይ የተዘረጋ መረብ ሆናችኋል
ወጥመድ እና መረብ ሁለትም ነገሮች ታዳኝን ማጥጃ ናቸው። በዚህ ሁኔታ፣ ካህናቱ እና የንጉሥ ቤት ህዝቡን ወደ ጣኦት አምልኮ ሲያማልሉ ከያህዌ ሊያርቋቸው መንገዶችን አበጅተዋል። ምጽጳ እና ታቦር በእስራኤል ምድር ጣኦታት ማምለኪያ ስፍራዎች ነበሩ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

አመፀኞች ለግድያ በርትተዋል
እዚህ ስፍራ "አመፀኞች" የሚለው የሚያመለክተው ከያህዌ ርቆ የሸሸውን ህዝብ ነው፤ "ለግድያ በርትተዋል" የሚለው ንጹሃን ሰዎችን መግደልን ወይም ለአህዛብ ጣኦታት የሚቀርቡ እንስሳትን ማረድን ሊያመለክት ይችላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አመፀኞች
ተርጓሚው ይህንን "እናንተ አመፀኞች፣" ብሎ ሊተካው ይችላል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በትክክል ለአመፀኞች የእስራኤል ሰዎች እየተናገረ ነው።

በማረድ
አንዳንድ ዘመናዊ ትርጉሞች የዕብራይስጡን አገላለጽ ክፋትን እንደሚገልጽ አድርገው ይተረጉሙታል

እኔ ሁሉንም እቀጣለሁ
ተርጓሚው ይህንን "እኔ ሁላችሁንም እቀጣለሁ" ብሎ ሊተካው ይችላል።

Hosea 5:3

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ስለ እስራኤል እየተናገረ ነው

ኤፍሬምን አውቃለሁ፣ እስራኤልም ከእኔ የተሰወረ አይደለም
እዚህ ስፍራ "ኤፍሬም" እና "እስራኤል" ሁለቱም መላውን ሰሜን የእስራኤል መንግሥት እና በዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታሉ። እዚህ ስፍራ እግዚአብሔር እነርሱ ምን አይነት እንደሆኑ እና ምን እያደረጉ እንደሆነ ሁሉን አውቃለሁ ይላል። (ስኔክቲኪ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ፤ ሚቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠትእና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ኤፍሬም፣ አሁን አንተ እንደ አመንዝራ ሆነሃል
ኤፍሬም እንደ አመንዝራ ቀርቧል፣ ምክንያቱም አምንዝራ ሴት ለማንም ወንድ ታማኝ እንደማትሆን ህዝቡ ለእግዚአብሔር የማይታመን ሆኗል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዘማዊ አስተሳሰብ በውስጣቸው ስላል
ይህ ማለት ለእግዚአብሔር ታማኝ ያለመሆን ፍላጎት አላቸው። ጣኦታትን ማምለክ ይፈልጋሉ።

ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ... ያህዌን አያውቁም
ተርጓሚው ይህንን "ወደ እኔ ለመመለስ... እኔን አያውቁም፣" ወይም "ወደ እኔ ለመመለስ... እኔን፣ ያህዌን አያውቁም " በሚል መተካት ይችላል።

ያህዌን አያውቁም
ከእንግዲህ እስራኤል በማናቸውም መንገድ ያህዌን አይታዘዝም። አምላካቸው አድርገው ለያህዌ እውቅና አይሰጡም።

Hosea 5:5

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ስለ እስራኤል እየተናገረ ነው

የእስራኤል ኩራት በራሱ ላይ ይመሰክርበታል
ይህ "ኩራትን" በእስራኤል ህዝብ ላይ በፍርድ ቤት በተቃውሞ እንደሚመሰክር አንድ ሰው አድርጎ ይገልጸዋል። በኩራት የተሞላው ዝንባሌያቸው እና ባህሪያቸው ያህዌን መታዘዝን አሻፈረኝ በማለተቸው ጥፋተኞች መሆናቸውን ያሳያል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ) ስለዚህ እስራኤል እና ኤፍሬም በጥፋታቸው ይሰናከላሉ፤ ይሁዳም ደግሞ አብሯቸው ይሰናከላል ከኩራታቸው እና ከበደላቸው የተነሳ ሁለቱ መንግሥታት ሙሉ ለሙሉ እግዚአብሔርን የማይታዘዙ ይሆናሉ። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለያህዌ ታማኞች አልነበሩም፣ ህጋዊ ያልሆኑ ልጆችን ወልደዋልና
አማራጭ ትርጉሞች ሊሆኑ የሚችሉት 1) ይህ ማለት እስራኤላዊያን ከሌሎች ህዝቦች ጋር ተጋብተው ነበር፤ ከእነርሱም ልጆች ወልደው ነበር ወይም 2) ይህ ማለት እስራኤላዊ ወላጆች ለያህዌ ታማኞች አልነበሩም ደግሞም ልጆቻቸው ጣኦታትን እንዲያመልኩ ያስተምሯቸው ነበር

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የአዲስ ጨረቃ በዓላቸው፣ ከእርሻቸው ጋር እነርሱንም አብሮ ያጠፋቸዋል
የእስራኤል ህዝብ በአዲስ ጨረቃ በዓል ማክበር ይጠበቅባቸው ነበር። በዚህ ስፍራ ይህ አገላለጽ የአዲስ ጨረቃ በዓል፣ ህዝቡን እና እርሻቸውን እንደሚበላ አውሬ የሚገልጸው ይመላል። የሆነ ሆኖ፣ ይህንን አገላለጽ መተረጎም ከባድ ነው፣ ብዙ ትርጎሞች የሚተረጎሙት እንዲህ አይነቱን ስሜት ሳይረዱት ነው። ሆኖም፣ አጠቃላይ ትረጉሙ፤ ለእርሱ ታማኝ ባለመሆኑ እግዚአብሔር ህዝቡን ይቀጣዋል የሚል መሆኑ እርግጥ ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 5:8

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ስለ እስራኤል እየተናገረ ነው በጊብዓ የቀንደ መለከትን ድምጽ፣ በራማ እንቢልታን ንፉ እዚህ ስፍራ "ቀንደ መለከት" እና "እንቢልታ" ማለት ተመሳሳይ ማለት ነገር ነው። ይህ ትዕዛዝ ለጊብዓ እና ራማ ሰዎች የተሰጠው ጠላት እየመጣ እንደሆነ ለማሳወቅ ነው። (ጥንድ ትረጉም/ደብሌት የሚለውን ይመልከቱ)

በቤትአዌን የለቅሶ ድምጽ አሰሙ፡ "ብንያም ሆይ፣ እኛ እንከተልሃለን!" በሉ
እዚህ ስፍራ "ብንያም" የሚለው የሚወክለው ከብንያም ወገን የሆኑ ወታደሮችን ነው።ይህ ምናልባት ህዝቡን ወደ ጦርነት ለመምራት ለእነርሱ የቀረበ ጥያቄ ይሆናል። ነገር ግን ዘመናዊ ትረጉሞች ይህንን አገላለጽ ለመተረጎም የተለያዩ ሙከራዎችን አድረገዋል። (ስኔክቲኪ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ቤትአዌን
ይህ ከተማ በእስራኤል ሰሜናዊ ግዛት እና በደቡባዊ ግዛት በቢንያም ነገድ ድንበር መሃል የሚገኝ ነበር። ይህንን በሆሴዕ 4፤15 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በእስራኤል ነገዶች መሃል በእርግጥ የሚሆነውን አውጃለሁ/ተናግሬያለሁ
"እኔ ያወጅኩትን/የተናገርኩትን ለእስራኤል ነገዶች አደርገዋለሁ"

Hosea 5:10

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ስለ ይሁዳ እና እስራኤል እየተናገረ ነው።

የይሁዳ መሪዎች የድንበር ምልክት የሆነ ድንጋይን እንደሚያነሱ ናቸው
"የድንበር ድንጋይ ማንሳት" የሚለው የሚያመለክተው የአንድ ሰው ድንበር የሆነን በመሬት ላይ የሚገኝ ምልክትን ማንቀሳቀስን ነው፤ ይህ በእስራኤል ህግ ወንጀል ነበር። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቁጣዬን በእነርሱ ላይ እንደ ውሃ አዘንባለሁ
በይሁዳ ላይ የያህዌ ቁጣ እንደሚያጠፋቸው ትልቅ ወራጅ ውሃ ይሆናል። በቅዱሳት መጽሐፍት፣ ስሜቶች እና የስነምግባር ደረጃዎች ብዙውን ጊዜ እንደ ፈሳሽ ሆነው ይገለጻሉ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኤፍሬም የደቀቀ ነው፣ እርሱ በፍርድ የደቀቀ ነው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። ይህ ሃሳብ ትኩረት እንዲያገኝ ሁለት ጊዜ ተደጋግሞ ተጽፏል። እዚህ ስፍራ "ኤፍሬም" የሚለው የእስራኤልን ሰሜናዊ ግዛት ህዝብ ያመለክታል። "እኔ የእስራኤልን ህዝብ ክፉኛ እቀጣለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ፣ (ሲኔክቲኪ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ))

ጣኦታትን ተከትለዋል
እዚህ ስፍራ "ተከትለዋል" የሚለው የሚያመለክተው አምልኮን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጣኦታት
እዚህ ስፍራ "ጣኦታት" ተብሎ በተተረጎመው የዕብራይስጡ ቃል ትረጉሙ እርግጠኛ መሆን አይቻልም፤ በዘመናዊ ትረጉሞች ውስጥ በተለያዩ ብዙ መንገዶች ተተርጉሟል።

Hosea 5:12

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ስለ ይሁዳ እና እስራኤል እየተናገረ ነው።

ለኤፍሬም እንደ ብል፣ ለይሁዳ ቤት እንደ ነቀዝ እሆናለሁ
ብል በቁራጭ ሱፍ ላይ ነቀዝ በቁራጭ እንጨት ላይ ሁለቱም አጥፊዎች ናቸው። ያህዌ ሁለቱንም መንግሥታት ያጠፋል (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ብል...ነቀዝ
እነዚህ ሁለት ቃላት በተለያየ መንገድ ይተረጎማሉ ምክንያቱም የዕብራይስጡ ቃል ትርጉም አንድም በጣም ሰፊ ነው ወይም በእርግጠኝነት ለመተረጎም ያዳግታል።

ኤፍሬም ህመሙን፣ ይሁዳም ቁስሉን አየ
ኤፍሬም (የሰሜን እስራኤል መንግሥት) እና ይሁዳ (የደቡብ እስራኤል መንግሥት) ሁለቱም በአደጋ ውስጥ እንደሆኑ አውቀዋል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለሰውን ይመልከቱ)

ከዚያም ኤፍሬም ወደ አሦር ሄደ፣ ይሁዳም ወደ ታላቁ ንጉሥ መልዕክተኛ ላከ
ኤፍሬም እና ይሁዳ ያህዌን እርዳታ ከመለመን ይልቅ አሦርን እርዳታ ለመኑ። "ታላቅ ንጉሥ" ለአሦር ነገሥታት ማዕረግ ነበር።

እርሱ ግን አልቻለም
እዚህ ስፍራ "እርሱ" የሚለው የሚያመለክተው የአሦርን ንጉሥ ነው

Hosea 5:14

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ስለ ይሁዳ እና እስራኤል እየተናገረ ነው።

ስለዚህ ለኤፍሬም ልክ እንደ አንበሳ እሆናለሁ
ያህዌ ኤፍሬምን ሊከታተል እና እንደ አንበሳ ሊያጠቃው ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በይሁዳ ቤት ላይ እንደ ደቦል አንበሳ
ያህዌ ይሁዳንም በተመሳሳይ መንገድ ሊያየው ነው። ያህዌ በሰሜኑም በደቡቡም መንግስታት አለመደሰት እያሳየ ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ፣ እኔ ራሴ
ያህዌ በህዝቡ ላይ ሁሉ ፍርድ የሚያመጣው እርሱ መሆኑን እያጎላ ነው

እበታተትናለሁ
አንበሳ የሚበላውን እንስሳ እንደሚበታተትን፣ ያህዌ ህዝቡን ከቤታቸውና ከአገራቸው ይበታትናቸዋል

እሄዳለሁ ደግሞም ወደ ስፍራዬ እመለሳለሁ
ያህዌ አመጸኛ ህዝቡን ይተወዋል

ፊቴን ይሻሉ
በአምልኮ እና መስዋዕት በማቅረብ ወደ እግዚአብሔር መገኘት ለመምጣት ሞክሩ። "ለእነርሱ ትኩረት እንድሰጥ ይጠይቁኛል" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከተ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 6

1 ኑ ወደ እግዚአብሔር እንመለስ። እርሱ ገነጣጥሎናል፥ ነገር ግን እርሱ ይፈውሰናል፤ እርሱ አቁስሎናል፥ ነገር ግን እርሱ ቁስላችንን አስሮ ይጠግናል። **2** ከሁለት ቀን በኋላ ያበረታናል፥ በሦሥተኛው ቀን ያሥነሣናል፥ እኛም በፊቱ እንኖራለን። **3** አወጣጡ እንደ ንጋት የታመነ ነው፤ እንደ ካፊያ፥ ምድሪቱን እንደሚያጠጣ እንደ ጸደይ ዝናብ ወደ እኛ ይመጣል። **4** ኤፍሬም ሆይ ምን ላድርግልህ? ይሁዳ ሆይ ምን ላድርግልህ? ታማኝነታችሁ እንደ ማለዳ ደመና፥ በጠዋት እንደሚጠፋ ጤዛ ነው። **5** ስለዚህ በነቢያቱ ቆራረጥኋቸው፥ በአፌም ቃል ገደልኋቸው። ፍርዶችህ እንደሚያንጸባርቅ ብርሃን ናቸው። **6** ታማኝነትን እሻለሁና፥መሥዋዕትንም አይደለም፥ከሚቃጠሉ መሥዋዕቶች ይልቅ እኔን እግዚአብሔርን ማወቅን እሻለሁ። **7** እንደ አዳም ኪዳኑን አፍርሰዋል፤ ለእኔ ያልታመኑ ነበሩ። **8** ገለዓድ የክፉ አድራጊዎች ከተማ ነው፥ በደም ዱካ ተሞልቷል። **9** የቀማኞች ቡድን የሚዘርፉትን አድብተው እንደሚጠባበቁ፥ ካህናቱም በሴኬም መንገድ ላይ ሰው ለመግደል በቡድን ተደራጅተዋል፤ አሳፋሪም ወንጀል ይፈጽማሉ። **10** በእስራኤል ቤት የሚያሰቅቅ ነገር አይቻለሁ፤ በዚያ የኤፍሬም ምንዝርና አለ፥ እስራኤልም ተበክሏል። **11** የሕዝቤን ምርኮ በምመልስበት ጊዜ፥ ይሁዳ ሆይ ለአንተም መከር ተቀጥሮልሃል።

Hosea 6:1

አያያዥ ሃሳብ
የእስራኤል ህዝብ ለመመለስ ፍላጎታቸውን ተናገሩ

እርሱ ሰባብሮናል ... እርሱ አቁስሎናል
እግዚአብሔር የእስራኤልን ህዝብ የቀጣው እርሱን ስላልታዘዙ እና ጣኦታትን ስለመለኩ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ይፈውሰናል... እርሱ ቁስላችንን ይጠግናል
እስራኤል እነርሱ ሲመለሱ እግዚአብሔር ምህረት እንደሚያበዛላቸው እና ከችግራቸው ነጻ እንደሚያወጣቸው ታምናለች። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከሁለት ቀናት በኋላ ያነቃናል፡ በሶስተኛው ቀን ያስነሳናል
ይህ የሚወክለው አጭር ጊዜን ነው። እስራኤል ከጠላቶቻቸው ሊያድናቸው እግዚአብሔር በቶሎ እንደሚመጣ ያምናሉ። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሁለት ቀናት ... በሶስተኛው ቀን
"2 ቀናት ... 3ተኛ ቀን" (ቁጥሮች እና ተከታታይ ቁጥሮች የሚሉትም ይመልከቱ)

ያህዌን እንወቅ
እዚህ ስፍራ "ማወቅ" ማለት የእግዚአብሔርን ባህሪ እና ህጎች ማወቅ ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን ለስርሱ ታማኝ መሆንንም ይጨምራል።

የእርሱ መምጣት እንደ ንጋት የተረጋገጠ ነው
ፀሐይ በየማለዳው መውጣቷ እርግጥ የሆነውን ያህል ያህዌ ህዝቡን ለመርዳት ይመጣል።

Hosea 6:4

አያያዥ ሃሳብ
ያህዌ እየተናገረ ነው

እናንተን ምን ላድርግ?
እግዚአብሔር ትዕግቱ እያለቀ መሆኑን እና የቀረው ፍርድ ብቻ እንደሆነ እየተናገረ ነው። " በእናንተ ላይ ምን እንደሚደረግ ማወቅ አስቸጋሪ ነው!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህም በነቢያቱ ቆራረጥኳቸው
ያህዌ በነቢያቱ አማካይነት፣ አመጸኛ በሆነው ህዝብ ላይ ጥፋትን አወጀ። እዚህ ስፍራ "ወደ ቁርጥራጭ መቆራረጥ" በሚል የተጠቀሰው ጥፋት እንደ ፍርዱ የተረጋገጠ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ድንጋጌዎችህ እንደ ብርሃናት ናቸው
እዚህ ስፍራ ነቢዩ ሆሴዕ ለእግዚአብሔር እየተናገረ ነው። እግዚአብሔር በአንድ ሰው ላይ የሞትን ትዕዛዝ ቅጣት አድርጎ ሲሰጥ እንደ አስደንጋጭ የሚመታ መብረቅ ይመስላል ማለቱ ሊሆን ይችላል። ወይንም ልክ ብርሃን ነገሮች እንዲታዩ እንደሚያደርግ፣ የእግዚአብሔር ትዕዛዛት ሰዎች እውነቱን እንዲያውቁ ያደርጋቸዋል ማለቱ ሊሆን ይችላል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ድንጋጌዎችህ
"የያህዌ ትዕዛዛት"

Hosea 6:6

አያያዥ ሃሳብ
ያህዌ እየተናገረ ነው

እኔ ታማኝነትን እፈልጋለሁ እንጂ መስዋዕትን አይደለም
ይህ ሰዋሰዋዊ አወቃቀር በዕብራይስጡ በዚህ ስፍራ "ይበልጥ" የሚለውን ያመለክታል፤ ተከታዩ መስመር እንደሚያሳየው ("እናም የእግዚአብሔር እውቀት ከሚቃጠል መሰዋዕቶች ይልቅ")። "እኔ ከመስዋዕት ይልቅ ታማኝነትን እሻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እንደ አዳም
አማራጭ ትረጉሞች ሊሆኑ የሚችሉት 1) ይህ የመጀመሪያውን ሰው አዳምን ያመለክታል ወይም 2) እስራኤል ውስጥ አዳም በምትባል ከተማ የሚኖሩ ሰዎችን የሚወክል ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመናት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት/ ነው። "በአዳም ከተማ ውስጥ እንደሚኖሩ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 3) ይህ በአጠቃላይ ሰዎችን ያመለክታል። "አዳም" የሚለው ቃል ትረጉሙ "ሰው" ወይም "የሰው ዘር" ማለት ነው። "እንደ ሁሉም የሰው ዘር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 6:8

አያያዥ ሃሳብ
ያህዌ እየተናገረ ነው

ገለዓድ አንድ ከተማ ናት... በደም የተበከለች
"በደም የተበከለች" ይህ ምናልባት ክፉ አድራጊዎችን እና የእነርሱን የግድያ ተግባር የሚወክል ይሆል። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ካህናቱ በሴኬም መንገድ ለግድያ በአንድነት ተሰበሰቡ
ይህ ምንን እንደሚያመለክት አናውቅም። ካህናቱ በእርግጥ የሃይማኖት እና ፖለቲካ ዋንኛ መአከል ወደ ሴኬም በሚሄዱበት ወቅት መንገድ ላይ ሰዎችን በማጥቃት ጥፋተኞች ነበሩ? ወይስ ነቢዩ ካህናቱ የያህዌን እውነተኛ እውቀት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እና አምልኮ "ገደሉ" እያለ ነውን? ይህንን አገላለጽ የተቻለውን ያህል ግልጽ አድረጎ መተረጎም ይመረጣል

Hosea 6:10

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ እየተናገረ ነው

የኤፍሬም ዘማዊነት
እዚህ ስፍራ "ዘማዊነት" የሚለው የሚያመለክተው የኤፍሬምን ሃሰተኛ አማልዕክት ማምለክ ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እስራኤል ረከሰች
እስራኤል በእግዚአብሔር ፊት የረከሰችው በድርጊቶቿ ምክንያት ነው

ይሁዳ ሆይ፣ ለአንተም የመከር ጊዜ ተመድቦብሃል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። " ይሁዳ ሆይ፣ ለአንተ የመከር ጊዜ መድቤያለሁ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

መከር
እዚህ ስፈፍራ "መከር" የሚለው የሚወክለው በእስራኤል እና በይሁዳ ላይ እግዚአብሔርን የመጨረሻ ፍርድ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እድሎች
ብልጽግና እና ደህንነት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 7

1 ማታለልን ይለማመዳሉና እስራኤልን ለመፈወስ በፈለግሁ ጊዜ ሁሉ የኤፍሬም ኃጢአት፥ የሰማሪያም ክፋት ይገለጣል፤ ሌባ ወደ ውስጥ ይገባል፥ የቀማኞች ቡድን በመንገድ ላይ አደጋ ያደርሳል። **2** ክፋታቸውን ሁሉ እንደማስታውስ በልባቸው አይገነዘቡም። ሥራቸው ከቦአቸዋል፥ በፊቴም ናቸው። **3** በክፋታቸው ንጉሡን፥ በሐሰታቸውም አለቆቹን ደስ ያሰኛሉ። **4** የተቦካው ሊጥ ኩፍ እስኪል ድረስ እሳቱን መቆስቆስ እንድሚያቆም፥ ጋጋሪ እንደሚያነድበት ምድጃ፥ ሁሉም አመንዝራ ናቸው። **5** በንጉሣችን ቀን አለቆች በወይን ጠጅ ትኩሳት ታመሙ። እርሱም ለፌዘኞች እጁን ዘረጋ። **6** እንደ ምድጃ በሆነ ልባቸው፥ አታላይ እቅዶቻችውን ይወጥናሉ። ቁጣቸው ሌሊቱን ሁሉ ይጤሳል፥ በማለዳም እንደሚንቀለቀል እሳት እጅጉን ይነድዳል። **7** ሁሉም እንደ ምድጃ የጋሉ ናቸው፥ ግዢዎቻቸውንም ይበላሉ። ነገሥታቶቻቸው ሁሉ ወደቁ፥ ከመካከላቸውም ማንም ወደ እኔ አልተጣራም። **8** ኤፍሬም ከአሕዛብ ጋር ተደባለቅ፥ ኤፍሬም ያልተገለበጠ ቂጣ ነው። **9** እንግዶች ጉልበቱን በሉት፥ እርሱ ግን አላወቀም። ሽበትም ወጣበት፥ እርሱ ግን አላወቀም። **10** የእስራኤል ትዕቢት ይመሰክርበታል፤ ነገር ግን ወደ አምላካቸው ወደ እግዚአብሔር አልተመለሱም፥ በዚህም ሁሉ አልፈለጉትም። **11** ኤፍሬም ማስተዋል እንደሌላትና ተላላ እንደ ሆነች ርግብ ነው፤ ወደ ግብጽ ይጣራል፥ ወደ አሦርም ይበራል። **12** ሲሄዱ መሬቤን እዘረጋባቸዋለሁ፥ እንደ ሰማይ አዕዋፍ አወርዳቸዋለሁ። እንደ መንጋ በሚተምሙብት እቀጣቸዋለሁ። **13** ወዮ ለእነርሱ! ከእኔ ርቀው ሄደዋልና። ጥፋት ይመጣባቸዋል! በእኔ ላይ አምፀዋል! ላድናቸው ወደድሁ፥ እነርሱ ግን ሐሰትን ተናገሩብኝ። **14** ከልባቸው ወደ እኔ አይጮኹም፥ ነገር ግን በአልጋዎቻችው ላይ ያለቅሳሉ። እህልና አዲስ ወይን ጠጅ ለማግኘት ራሳቸውን ለይተዋል፥ ከእኔም ዘወር ብለዋል። **15** እኔ ባሠለጠናቸውም፥ ክንዶቻችውንም ባበረታ፤ እነርሱ ግን ክፉ ነገርን አሴሩብኝ። **16** ተመልሰዋል፥ ነገር ግን ወደ እኔ ወደ ልዑሉ አልተመለሱም። ሒላማውን እንደ ሳተ ቀስት ናቸው። ከምላሳቸው ነውረኛነት የተነሳ አለቆቻችው በሰይፍ ይወድቃሉ። ይህም በግብጽ ምድር ለመሳለቂያ ይሆንባቸዋል።

Hosea 7:1

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ እየተናገረ ነው

እስራኤልን መፈወስ እፈልጋለሁ
ዳግም እስራኤል ለእግዚአብሔር ታማኝ እንድትሆን ማድረግ እና የእርሱ በረከት ተቀባይነት የተገለጸው እንደ ፈውስ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ማታለንን ይለማመዳሉ
ሰዎች ምርቶችን የሚሸጡት እና የሚገዙት በሃሰት ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የዘራፊ ቡድን
ይህ ያለምክንያት ሌሎች ሰዎችን የሚያጠቃ ቡድን ነው

ድርጊታቸው ከቧቸዋል
እዚህ ስፍራ የሰዎቹ ክፉ ስራዎች የተነገሩት ምናልባት በወንጀላቸው ሊከሷቸው የተዘጋጁ ሌሎች ሰዎች እንደሆኑ ተደርገው ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ በፊቴ ናቸው
እዚህ ስፍራ እግዚአብሔር የተገለጸው፣ መገኘቱን እና ህልውናውን በሚያጎላው በእርሱ "ፊት" ነው። "ደግሞም እኔ ሁሉንም አያለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ ዘይቤያዊ አነጋገር- የአንደን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 7:3

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ እየተናገረ ነው

ንጉሡን በክፋታቸው
የዕብራይስጡ ጽሁፍ በተለያዩ ስፍራዎች ግልጽ አይደለም። ሆኖም፣ ብዙዎች ይህንን የተረጎሙት የንጉሡ መኳንንት ለእግዚአብሔር ታማኝ እንዳልሆኑ በመግለጽ እና እንደዚሁም ንጉሡን ለመግደል እንዳቀዱ፣ ከዚያም በመቀጠል እቅዳቸውን እንደፈጸሙ ነው። ይህ ከአንድ ጊዜ በላይ የሆነ ይመስላል።

እነዚህ ወንጀሎች የተገለጹት አገሪቱ እንደ ሰጠመችበት ክፋት መገለጫ ተደርገው ነው።

እነርሱ ሁሉም ዘማዊያን ናቸው
ጣኦታትን በማምለክ እና ለያህዌ ታማኝ ባለመሆን መንፈሳዊ ዘማዊነት የፈጸሙ ሰዎች። እነዚህ ሰዎች ምናልባትም ከሌሎች ሰዎች ጋር በመተኛት ለባሎቻቸው ወይም ለሚስቶቻቸው ታማኝ ያልነበሩ ናቸው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በዳቦ ጋጋሪው እንደጋለ ምድጃ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። ይህ ማለት ህዝቡ ክፉ ለማድረግ ጽኑ ፍላጎት አለው። "ዳቦ ጋጋሪ እንደሚቆሰቁሰው ምድጃ" (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የሊጡ መቡካት
ይህ ዳቦ የመድፋት ሂደት አንድ ክፍል ነው

በንጉሣችን የበዓል ቀን
ይህ ምናልባት በንጉሡ ተይዞ የሚከበር በዓል ይሆናል

እርሱ በገዛ እጆቹ አደረገ
ይህ ምናልባት ከአንድ ሰው ጋር መተባበር ወይን ማበር ማለት ሊሆን ይችላል። ንጉሡ ከመኳንንቱ ጋር ማፌዝ በሌለበት ነገሮች ወይም ሰዎች ምናልባትም በእግዚአብሔር እንኳ ሳይቀር አፌዘ ማለት ሊሆን ይችላል። (ፈሊጣው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 7:6

አጠቃላይ መረጃ
የቤተ መንግሥት መኳንንት ሴራ ተገልጽዋል። ንጉሣቸውን ለመግደል የገፋፋቸው ቁጣቸው ነው።

ልባቸው እንደ ጋለ ምድጃ ነው
ይህ ማለት በምድጃ ላይ እንደሚነድ እሳት፣ እነዚህ ሰዎች ጠንካራ ክፉ መሻቶች አሏቸው። የሰዎቹ መሻቶች በእነርሱ "ልቦች" ተገጽዋል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

ቁጣቸው ጤሰ
"ጤሰ" የሚለው ቃል ትርጉሙ አንድ ነገር ካለ ነበልባል ቀስ በቀስ ነደደ ማለት ነው። "ቁጣቸው በቀስታ እና በጸጥታ እያደገ ሄደ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንደ ሚንበለበል እሳት ከፍ ብሎ ነደደ
የቁጣቸው ጥንካሬ የተገለጸው እግጅ የሚነድ እሳት እንደሆነ ተደርጎ ነው። "በጣም እየከፋ ሄደ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘ። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ሁሉም እንደ ምድጃ የጋሉ ናቸው
ይህ የእነርሱን ቁጣ ከምድጃ እንደሚወጣ ሙቀት ያነጻጽረዋል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ገዢዎቻቸውን ፈጁ
ይህ የቤተ መንግሥት መኳንንት ነገስታቶቻቸውን ገደሉ ለማለት ይመስላል።

Hosea 7:8

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ እየተናገረ ነው

ኤፍሬም ከአህዛብ ጋር ተደባለቀ
ይህ ምናልባት የሰሜን መንግሥት ነገሥታት፣ ከጥቃት ለመዳን ራሳቸውን ከሌሎች መንግስታት ጋር ለማቆራኘት ያደረጉትን ጥረት የሚያሳይ ይሆናል

ኤፍሬም ያልተገላበጠ ቂጣ ነው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። እዚህ ስፍራ "ኤፍሬም" የሚያመለክተው የእስራኤልን ሰሜናዊ መንግሥት ነው። በምድጃ ውስጥ ለበለጠ ጥንካሬ ተነባብሮ እንዳልተጋገረ ነጠላ ቂጣ፣ መንግሥቱ ደካማ ነው። "የኤፍሬም ሰዎች ማንም እንዳላገላበጠው ቂጣ ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ዘይቤያዊ አነጋገር- የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላው ነገር መሰየም፣ እና ዘይቤያዊ አነጋገር፣ እንዲሁም አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ሸበት ወጣበት
እዚህ ስፍራ "ሸበት" የሚወከወለው የእርጅና ዘመንን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን እርሱ አላወቀም
ሆኖም፣ ይህ "የእርጅና ዘመን" የሚለው የሰሜኑ መንግሥት እየደከመ መምጣቱ በግልጽ መናገሪያ መንገድ ነው፣ ምክንያቱም መንግሥቱ "ማርጀቱን" አላወቀም። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 7:10

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ እየተናገረ ነው

የእሰስራኤል ኩራት በራሱ ላይ ይመሰክርበታል
ይህ "ኩራትን" በፍርድ ቤት በእሰስራኤል ህዝብ ላይ እንደሚመሰክር አንድ ሰው አድርጎ ይገልጸዋል። ይህ ማለት ኩራት የተሞላው ዝንባሌያቸው እና ባህሪያቸው ያህዌን መታዘዝ በማቆም በደለኛ እንዳደረጋቸው ያሳያል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወይም ደግሞ አላዩትም
የእስራኤል በያህዌ ላይ ፍላጎት ማጣት የተገለጸው ልክ እርሱ እንደጠፋ እና እነርሱም ሊፈልጉት ይሞክሩ እንዳልነበረ ነው። "ለእነርሱ ትኩረት እንዲሰጣቸው እነርሱም ሊያገኙት አይሞክሩም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ሁሉ ሆኖ
እዚህ ስፍራ "ይህ" የሚለው የሚያመለክተው እግዚአብሔር ባዕዳን እንዲያሸንፏቸው መፍቀዱን እና እነርሱን ደካማ እንዳደረጋቸው ነው።

ኤፍሬም እንደ ርግብ ነው፣ ንቁ ያልሆነና የሚታለል
ርግብ ሞኝ ወፍ ናት ተብሎ ይታሰብ ነበር። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ግብፅ ... አሦር
እነዚህ እስራኤል እርዳታ ልትጠይቃቸው የምትችላቸው ሃያላን መንግሥታት ነበሩ

Hosea 7:12

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ እየተናገረ ነው

መረቤን በላያቸው እዘረጋለሁ
ይህ ወፎች የሚጠመዱበት መንገድ ነው። ያህዌ የእስራኤልን ህዝብ ከርግብ ጋር ማነጻጸሩን ቀጥሏል። እነርሱ ወደ ግብፅ ወይም አሦር ለእርዳታ ሲሄዱ፣ ያህዌ እነርሱን ይቀጣቸዋል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ሰማይ ወፎች እነርሱን ከላይ አወርዳቸዋለሁ
ያህዌ በእስራኤል ላይ የሚፈርድበትን መንገድ በመረብ የሚያጠምዳቸው ወፎች እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። "አዳኝ ወፎችን እንደሚያጠምድ እኔ እነርሱን አጠምዳቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አብረው ሲበሩ
ይህ አገላለጽ ወፎችን በማጥመድ የተገለጸውን ዘይቤያዊ አነጋገር አስፋፍቶ ያቀርባል።

Hosea 7:14

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ እየተናገረ ነው

በአልጋዎቻቸው ላይ ሆነው ያለቅሳሉ
በጣኦት አምላኪዎች ዘንድ የአምልኮ ምግብን በመከዳቸው ወይም በአልጋቸው ላይ ጋደም ብለው መመገብ የተለመደ ነገር ነበር።

ከእኔ ዘወር ብለዋል
እዚህ ስፍራ እግዚአብሔርን ማምለክ መተዋቸው ከእርሱ ዘወር ማለት በሚል ተነግሯል። "እነርሱ እኔን ማምለክ ትተዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ምንም እንኳን እኔ ባሰለጥናቸው እና እጆቻቸውን ባጠነክርም
እግዚአብሔር እስራኤላዊያን እርሱን እንዲወዱት እና እንዲታዘዙት ያሰለጠነበት መንገድ የተነገረው ወንዶቻቸውን ለጦርነት ያሰለጥን እንደነበር ተደርጎ ነው፤ይህ በወታደራዊ ዘይቤ የቀረበ ሊሆን ይችላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 7:16

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ እየተናገረ ነው

እነርሱ እንደ ረገበ ቀስት ናቸው
ይህም፣ የቀስት መወርወሪያ የሌለው ቀስት ፣ ወይም በሚገባ ያልተወጠረ። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በምላሳቸው ብልግና ምክንያት
እዚህ ስፍራ "ምላስ" የሚለው የሚያመለክተው አለቆቻቸው የሚናበሩትን ነው። "እኔን ስለተሳደቡ" ወይም "እኔን ስለተራገሙ" በሚለው ውስጥ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ በግብፅ ምድር ለእነርሱ መሳለቂያነት የሚውል ይሆናል
"መሳለቂያ" የሚለው ረቂቅ ስም እንደ አድራጊ ሊጸፍ ይችላል። "በግብጽ የሚኖሩ ህዝቦች በእስራኤል ላይ የሚዘብቱት እና የሚሳለቁት ለዚህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስያሜዎች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 8

1 «መለከትን በከንፈሮችህ ላይ አድርግ። በእኔ በእግዚአብሔር ቤት ላይ ንስር እየመጣ ነው። ሕዝቡ ኪዳኔን አፍርሰዋልና በሕጌም ላይ አምጸዋልና ይህ
ይሆናል። **2** 'አምላኬ፥ በእስራኤል ያለን እኛ እናውቅሃለን' እያሉ ወደ እኔ ይጮሃሉ። **3** ነገር ግን እስራኤል በጎ የሆነውን ነገር ጥሎአል፥ ጠላትም ያሳድደዋል። **4**
ነገሥታትን አነገሡ፥ በእኔ ግን አይደለም። እኔም ሳላውቅ መሳፍንቶችን አደረጉ። በብራቸውና በወርቃቸው ለራሳቸው ጣዖታትን ሠሩ፥ ነገር ግን ለጥፋታቸው ብቻ
ነበር።» **5** ነቢዩ፦«ሰማርያ ሆይ ጥጃህን ወዲያ ጥሎታል» አለ። እግዚአብሔር፦«ቁጣዬ በዚህ ህዝብ ላይ ነድዶአል። ሳይነጹ እስከ መቼ ይኖራሉ? አለ። **6**
ይህ ጣዖት ከእስራኤል የመጣ ነው፤ ባለሙያ ሠራው፥ እርሱ አምላክ አይደለም! የሰማርያ ጥጃ ይደቅቃል። **7** ሕዝቡ ነፋስን ዘርተዋል፥ ዐውሎ ነፋስንም
ያጭዳሉ። ያልተሰበሰበው እህል ዛላ የለውም፤ ዱቄትም አይገኝበትም። ለማፍራት ቢደርስም እንኳን እንግዶች ይበሉታል። **8** እስራኤል ተውጦአል፤ በአሕዛብም
መካከል እንደማይጠቅም ነገር ወድቀዋል። **9** ሁሌ ብቻውን እንደሚሆን የዱር አህያ፥ወደ አሦር ሄደዋልና። ኤፍሬም ለራሷ ወዳጆችን ገዛች። **10** በአሕዛብ
መካከል ወዳጆችን ቢገዙም፥ እኔ እሁን አንድ ላይ እሰበስባቸዋለሁ። ከመሳፍንቱ ንጉሥ ጭ ቆና የተነሳም ሊመነምኑ ይጅምራሉ። **11** ኤፍሬም ለኃጢአት
ማስተሰሪያ መሠዊያ ቢያበዛም፥በዚያ ፈንታ ግን የኃጢአት መሥሪያ መሠዊያዎች ሆኑ። **12** ሕጌን አሥር ሺህ ጊዜ ያህል ፃፍሁላቸው፥ እነርሱ ግን እንግዳ እንደ
ሆነ ነገር ተመለከቱት። **13** መሥዋዕቴን ይሠዋሉ፤ ሥጋ ይሠዋሉ፥ ይበሉታልም፤ እኔ እግዚአብሔር ግን አልተቀበልኳቸውም። አሁን ክፋታቸውን አስባለሁ፥
ኃጢአታቸውንም እቀጣለሁ። ወደ ግብጽ ይመለሳሉ። **14** እስራኤል፥ እኔን ሠሪውን ረሳ፥ አብያተ መንግሥትንም ገነባ። ይሁዳ ብዙ ከተሞችን አጸና፥ እኔ ግን
በከተሞቹ ላይ እሳት እሰድዳለሁ፤ ምሽጎቹንም ታጠፋለች።

Hosea 8:1

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ የሰሜኑን መንግሥት ለመውጋት ስለሚመጣው የአሦር ሰራዊት እየተናገረ ነው

ንስር በያህዌ ቤት ላይ እየመጣ ነው
ንስር፣ አዳኝ ወፍ፣ አንዳንድ ጊዜ የእስራኤልን ጠላቶች ለመወከል ያገለግላል። "ንስር ሌላን እንስሳ እንደሚያድን፣ የእስራኤል ጠላቶች ህዝቤን ለመያዝ መጥተዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ቃል ኪዳኔን አፍርሰዋል
እዚህ ስፍራ "አፍርሰዋል" የሚለው የሚገልጸው "አልታዘዙም፣" "ጥሰዋል" የሚለውን ነው (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አንተን ያውቃሉ
"ለአንተ ታማኝ ናቸው"

Hosea 8:4

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ እየተናገረ ነው ነገር ግን የሆነው ይህ ነው፤ ተቆርጠው ሊወድቁ ይችላሉ ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ነገር ግን ውጤቱ የሚሆነው እኔ ህዝቡን ማጥፋቴ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥጃችሁ ተቀባይነት አላገኘም
ሊሰጡ የሚችሉ አማራጭ ትርጓሜዎች 1) ይህ የነቢዩ ንግግር ነው። "ያህዌ የእናንትን ጥጃ አልተቀበለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) ያህዌ እየተናገረ ነው። "እኔ ራሴ የእናንተን ጥጃ አልተቀበልኩም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

የእናንተ ጥጃ
ህዝቡ ጥጃ የሚመስል ጣኦት ያመልካል፣ ስለዚህ ያህዌ ስለአምልኳቸው ራሱን ጥጃውን እንደሆነ አድርጎ እየተናገረ ነው። "ጥጃ ጣኦታችሁን ለምታመልኩ፣ የእናንተ አምልኮ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ቁጣዬ በእነዚህ ህዝቦች ላይ እየነደደ ነው
ቁጣ ብዙውን ጊዜ እንደ እሳት ተደርጎ ይነገራል። "እኔ በዚህ ህዝብ በጣም ተቆጥቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እስከ መቼ በደለኛ ሆነው ይቀጥላሉ?
ያህዌ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ህዝቡ ንጹህ ባለመሆኑ ቁጣውን ለመግለጽ ነው። "በዚህ ህዝብ ላይ ተቆጥቻለሁ ምክንያቱም ንጹህ ለመሆን ምንም ፍላጎት የላቸውም።" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 8:6

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ እየተናገረ ነው

ህዝቡ ነፋስን ይዘራል ዐውሎ ነፋስን ያጭዳል
ነፋስን መዝራት ወይም ነፋስን መትከል እርባና በሌለው ወይም አጥፊ በሆነ መንገድ መስራት ነው። ዐውሎ ነፋስን ማጨድ ከራስ ድርጊት የተነሳ በጥፋት መከራን መቀበል ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የቆመው ተክል ራስ/ዛላ የለውም
እዚህ ስፍራ "ራስ/ዛላ" የሚለው የሚያመለክተው ፍሬ የሚገኝበትን የተክሉን ክፍል ነው። ራስ/ዛላ የሌለው አገዳ ለገበሬም የሚሰው ምንም ነገር የለም። በተመሳሳይ መንገድ፣ የእስራኤ ድርጊቶች አንዳች መልካም ውጤት አያስገኝም። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ መድረስ ቢመጣም እንኳን፣ ባዕዳን ይበሉታል
ማናቸውም የእራኤል ድርጊት ጥሩ ውጤት ማምጣት ቢችል እንኳን፣ የእስራኤል ጠላቶች መጥተው ከእነርሱ ይወስዱታል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 8:8

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ እየተናገረ ነው

እስራኤል ተዋጠች
"ተዋጠች" ማለት መሸነፍ እና በምርኮ መወሰድ ማለት ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የእስራኤል ጠላቶች እስራኤላዊያንን ወደ ሌላ ምድር ወሰዷቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንደ ዱር አህያ ብቻቸውን
ሰዎች ብዙውን ጊዜ አህያን እንደ ደደብ/ግትር ይቆጥራሉ። ይህ ማለት የእስራኤል ህዝብ ያህዌን መስማትን ይቃወማል ነገር ግን በምትኩ ለእርዳታ ወደ አሦር ህዝብ ይሄዳል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ኤፍሬም ለራሱ ፍቅረኞችን ቀጠረ
ኤፍሬም ከሌሎች ህዝቦች ጋር ያለው አንድነት የተገለጸው ኤፍሬም ለዘማዊነቱ እንደከፈላቸው ተደርጎ ነው። "የእስራኤል ህዝብ ለሌሎች አገራት ይጠብቋቸው ዘንድ ለመክፈል ሞከሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በሃያል ንጉሥ ተጽዕኖ ምክንያት
ይህም፣ የአሦር ንጉሥ፣ "ታላቁ ንጉሥ" ተብሎም ይጠራል፤ ህዝቡን ያስጨንቃልና ነው።

Hosea 8:11

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ እየተናገረ ነው

ህጌን ለእነርሱ አስር ሺህ ጊዜ ልጽፍላቸው እችላለሁ፣ እነርሱ ግን
ያህዌ የይሆናል ሁኔታን እየገለጸ ነው። እዚህ ስፍራ "አስር ሺህ ጊዜ" የሚለው የቱንም ያህል ጊዜ ለህዝቡ ህጉን ቢሰጣቸውም እነርሱ ግን እርሱን ለመታዘዝ አለመፍቀዳቸውን በተጋነነ መልክ የሚገልጽ ነው። "ምንም እንኳን ህጌን በጣም ብዙ ጊዜ ብሰጣቸውም፣ እነርሱ ግን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መላምታዊ ሁኔታእና ኩሸት/ሃይፐርቦል-እጅግ የተነጋነነ አገላለጽ እና ማጠቃለያ/ጠቅላላ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

አስር ሺህ
"10,000" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 8:13

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ እየተናገረ ነው

ወደ ግብጽ ይመለሳሉ
በኃጢአታቸው ምክንያት፣ እግዚአብሔር ህዝቡን ለግብፃዊያን እንደ ባሪያ አድርጎ ይሰዳቸዋል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 9

1 እስራኤል ሆይ፥ አንተ የታመንክ አይደለህምና፥ አምላክህንም ትተሃልና፤ ሌሎች ሕዝቦች ደስ እንደሚላቸው፥ ደስ አይበልህ። በአውድዎች ሁሉ ላይ ሴተኛ አዳሪ
የምትጠይቀውን ዋጋ ለመክፈል ወድደሃል። 2 ነገር ግን አውድማውና የወይን መጭመቂያው አይመግባቸውም፥ አዲሱ የወይን ጠጅም ይጥላታል። 3
በእግዚአብሔር ምድር ላይ አይኖሩም፤ ኤፍሬም ወደ ግብጽ ይመለሳል፥ ደግሞም አንድ ቀን በአሦር የረከሰ ምግብ ይበላሉ። 4 ለእግዚአብሔር የወይን ጠጅ
ቁርባን አያፈሱም፤ ደስም አያሰኙትም። መስዋዕታቸው እንደ ሐዘንተኞች ምግብ ይሆንባቸዋል፦ የሚበሉት ሁሉ ይረክሳሉ። ምግባቸው ለእነርሱ ብቻ የሚሆን
ነውና ወደ እግዚአብሔር ቤት ሊመጣ አይችልም። 5 በእግዚአብሔር በዓል ቀን፥ በዓመት በዓል ቀን ምን ታድርጋላችሁ? 6 ተመልከቱ፥ ከጥፋት ቢያመልጡ
እንኳን ግብጽ ትሰበስባቸዋለች፥ ሜፎስም ትቀብራቸዋለች። የብር ክምችታቸውን ሳማ ይውጠዋል፥ድንኳኖቻቸውንም እሾህ ይሞላዋል። 7 የቅጣት ቀን እየመጣ
ነው፥የበቀል ቀን እየመጣ ነው። እስራኤል ሁሉ ይህን ይወቅ። ከክፋትህና ከጠላትነትህ የተነሳ፤ ነቢዩ ሞኝ፥ በመንፈስ የሚነዳውም ሰው እብድ ሆኖአል። 8
ከአምላኬ ጋር የሆነው ነቢይ የኤፍሬም ጠባቂ ነው፤ ነገር ግን የወፍ ወጥመድ በመንገዱ ሁሉ ነው፥በአምላኩም ቤት ጠላትነት አለበት። 9 በጊብዓ ዘመን
እንደነበረው ራሳቸውን እጅግ አርክሰዋል። እግዚአብሔር ክፋታቸውን ያስባል፥ ኃጢአታቸውንም ይቀጣል። 10 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፥«እስራኤልን
ያገኘሁበት ጊዜ፥ በምድረ በዳ ወይን እንደማግኘት ነበረ። እንደ በለስ ዛፍ የፍሬ ጊዜ የመጀመሪያ እሸት አባቶቻችሁን አገኘሁ።ነገር ግን ወደ ብዔልፌጎር
ሄዱ፥ራሳቸውንም ለዚያ አሳፋሪ ጣዖት ሰጡ።እንደወደዱት ጣዖት እነርሱም የተጠሉ ሆኑ። 11 የኤፍሬም ክብር እንደ ወፍ በሮ ይሄዳል።መውለድ፥ ማርገዝና
መፀነስ የለም። 12 ልጆችን ቢያሳድጉ እንኳን፥ አንዳቸውም እሰከማይቀሩላቸው ድረስ እወስድባቸዋለሁ። ከእነርሱ ዘወር ባልሁ ጊዜ፥ ወዮ ለእነርሱ! 13 ኤፍሬም
እንደ ጢሮስ በለምለም ስፍራ ተተክሎ አየሁት፥ ነገር ግን ኤፍሬም ልጆቹን ለሚያርዳቸው አሳልፎ ይሰጣል። 14 እግዚአብሔር ሆይ ስጣቸው፤ ምን
ትሰጣቸዋለህ? የሚጨነገፍ ማኅፀንና ወተት የማይሰጡ ጡቶች ስጣቸው። 15 በጌልጌላ ካደረጉት ክፋታቸው ሁሉ የተነሳ፥ በዚያ እነርሱን መጥላት ጀመርኩ።
ከክፉ ሥራቸው የተነሣ፥ ከቤቴ አስወጣቸዋለሁ። ከእንግዲህ ወዲያ አልወዳቸውም፤ አለቆቻቸው ሁሉ ዓመጸኞች ናቸው። 16 ኤፍሬም በበሽታ
ተመታ፤ሥራቸውም ደረቀ፥ ፍሬም አይሰጡም። ልጆች ቢወልዱም እንኳን፥ የተወደዱ ልጆቻቸውን እገድላለሁ።» 17 አልታዘዙትምና አምላኬ ይጥላቸዋል።
በሕዝቦች መካከል ተንከራታች ይሆናሉ።

Hosea 9:1

አጠቃላይ መረጃ:
ነቢዩ ሆሴዕ እየተናገረ ነው

ነገር ግን የእህል አውድማ እና የወይን መጭመቂያው እነርሱ አይመግባቸውም
ይህ የሚገልጸው የእህል አውድማ እና የወይን መጭመቂያው ራሳቸው ሌላውን የሚመግቡ ሰዎች እንደሆኑ ተድርጎ ነው። ይህ ማለት መከሩ የህዝቡን ፍላጎት ለማሟላት የሚበቃ የፍሬ አይሰጥም፣ የወይን መከሩም በቂ የወይን ጠጅ አይሰጥም ማለት ነው። (ሰውኛ ዘይቤ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

የእህል አውድማ
ይህ እህል ለመውቃት የሚውል ሰፊ ስፈራ ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን ለማህበራዊ እና ሃይማኖታዊ በዓላት ማክበሪያ የሚያገለግል ስፍራም ነው። የቤተ ጣኦት ዘማዊያት ለጣኦት የሚደረገውን የመከር በዓል ለማክበር ወንዶቹን ለመርዳት ይመጣሉ።

አዲሱ ወይን አይበቃቸውም
ወይን ጠጅ ለማዘጋጀት በቂ የወይን ጭማቂ አይኖርም

Hosea 9:3

አጠቃላይ መረጃ:
ነቢዩ ሆሴዕ እየተናገረ ነው

የያህዌ ምድር
ይህ አገላለጽ የሚያመለክተው ያህዌ የእስራኤልን ምድር እንደ እስራኤላውያን ንብረት ሳይሆን እንደ ራሱ ንብረት ማየት መቀጠሉን ነው።

ንጹህ ያልሆነ ምግብ
ይህ እስራኤላውያን በያህዌ ዘንድ ተቀባይነት ያሳጣናል በማለት ሊመገቡት የማይፈቅዱት ምግብ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መስዋዕታቸው እንደ ለቀስተኞች ምግብ ይሆንባቸዋል
እዚህ ስፍራ "የቀስተኞች ምግብ" የሚለው የሚያመለክተው ሰዎች በለቅሶ ላይ በሚሆኑበት ጊዜ የሚመገቡትን ነው፣ ምክንያቱም በልቅሶ ላይ ሲሆኑ ስለሚረክሱ እና በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ስለሚያጡ ነው። ይህ ማለት ያህዌ የህዝቡን መስዋዕት እንደ ረከሰ ይቆጥረዋል ደግሞም እነርሱንም አይቀበላቸውም። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የእነርሱ ምግብ ለእነርሱ ብቻ ይሁናቸዋል፤ ወደ ያህዌ ቤት አይመጣም
የእስራኤል ህዝብ የሚመገቡት ምግብ ይኖራቸዋል፣ ነገር ግን ያህዌ ያንን በመስዋዕትነት አይቀበለውም

ወደ ያህዌ ቤት አይመጣም
ንጹህ ያልሆነው ምግብ ወደ ስፍራዎች በራሱ መሄድ እንደሚችል ተደርጎ ተነግሯል። እወነታው ግን በእርግጥ፣ ሰዎች ይዘውት ሊሄዱ ያስፈልጋል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 9:5

አጠቃላይ መረጃ:
ነቢዩ ሆሴዕ እየተናገረ ነው

በያህዌ በዓል ዕለት፣ በተወሰነው ክብረ በዓል ምን ታደርጋላችሁ?
ሆሴዕ ይህንን ጥያቄ ያነሳው ህዝቡ ክብረ በዓሉን ስለረሳ፣ ጠላቶቻቸው ስላሸንፏቸው እና በምርኮ ስለወስዷቸው፤ በዓሉን ማክበር አለመቻላቸውን ማጉላት ስለፈለገ ነው። "ያህዌ ለእናንተ የወሰነውን ክብረ በዓል ማክበር አትችሉም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የተወሰነው የክብረ በዓሉ ቀን... ለያህዌ ክብረ በዓል ቀን
ሁለቱም አገላለጾች አንድ ትርጉም አላቸው (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቢያመልጡ እንኳን
እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው አሁንም የሚገልጸው የእስራኤልን ህዝብ ነው። ይህንን በሁለተኛ መደብ በመግለጽ መቀጠል ይችላሉ። "አንተ ብታመልጥ" በሚል። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ግብፅ ይሰበስባቸዋል፣ ደግሞም ሜምፎስ ይቀብራቸዋል
ግብፅ እና ሜምፎስ በዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታል። "የግብፅ ሰራዊት ይማርካችኋል። እናንተ በዚያ ትሞታላችሁ፣ በሜምፎስ ከተማ የሚኖሩ ሰዎች ይቀብሯችኋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የብር ሃብታቸውን እሾሃማ ቁጥቋጦ ይወርሰዋል
ቁጥቋጦ እስራኤላውያን ብራቸውን ባከማቹበት ስፍራ ይበቅላል የተባለው ቁጥቋጦ እንደ ሰብአዊ ጠላት ሆኖ ውድ ሃብታቸውን ለራሳቸው እንደወሰዱ የተገለጸበት ነው። "እሾሃማ ቁጥቋጦ የብር ሃብቶቻቸውን ባከማቹበት ስፍራ ይበቅላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እሾሃማ ቁጥቋጦ ይወርሳቸዋል፣ እሾህ ድንኳኖቻቸውን ይሞላዋል
እዚህ ስፍራ "እሾሃማ ቁጥቋጦ" እና "እሾህ" የሚለው ተመሳሳይ ነገርን ይገልጻል። እሾሃማ ቁጥቋጦ እና እሾህ ማደጉ የሚወክለው ሰው የማይኖርበትን ምድር እና በረሃማነትን ነው። (ጥንድ ትረጉም እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

የእነርሱ ድንኳኖች
እዚህ ስፍራ "ድንኳኖች" የሚለው የሚወክለው የእስራኤላውያንን ቤቶች ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

Hosea 9:7

አጠቃላይ መረጃ:
ነቢዩ ሆሴዕ እየተናገረ ነው

የቅጣት ቀናት እየመጡ ነው፣ የፍርድ ቀናትም እየመጡ ነው
ሆሴዕ እነዚህን ሁለት ተመሳሳይ ነገሮች የሚናገረው ያህዌ የእስራኤልን ህዝብ ለክፉ ተግባሮቻቸው በቶሎ እንደሚቀጣ ትኩረት ለመስጠት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን መልከቱ)

ነቢዩ ሞኝ ነው፣ መንፈሳዊ ነኝ ሚለውም ሰው እንደ እብድ ነው
እነዚህ ሀረጋት በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። አማራጭ ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሰዎች ነቢዩን እንደ እብድ ሰው ይቆጥሩታል ወይም 2) ነቢያት ህዝቡ ከሚሰራው ኃጢአት የተነሳ እንደ አብድ ሆንነዋል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ነቢዩ ሞኝ ነው፣ መንፈሳዊ ነኝ ሚለውም ሰው እንደ እብድ ነው
እዚህ ስፍራ "ነቢይ" እና "መንፈሳዊ ሰው" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ከእግዚአብሔር መልዕክት ተቀብያለሁ የሚልን አንድ ሰው ነው። እነዚህ ሰዎች ሃሰተኛ ነቢያት መሆናቸው ተመላክቷል፤ እነርሱ ራሳቸው ብቻ ከእግዚአብሔር መልዕክት ተቀብያለሁ ሲሉ ያስባሉ። (ጥንድ ትረጉም እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

በታላቅ ኃጢአታችሁ እና በታላቅ ጠላትነታችሁ ምክንያት
"ታላቅ ኃጢአት" እና "ታላቅ ጠላትነት" የሚሉት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉምን ይጋራሉ። የህዝቡ ኃጢአተኛነት ራሱን የሚገልጸው በያህዌ እና በነቢያቱ ላይ ባላቸው ጠላትነት ነው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 9:8

አጠቃላይ መረጃ:
ነቢዩ ሆሴዕ እየተናገረ ነው

ነቢዩ በኤፍሬም ላይ ለአምላኬ ዘበኛ ነው
"ዘበኛ" ከከተማ ውጭ ሆኖ አደጋ መምጣት አለመምጣቱን ይጠብቃል። ነቢዩ ህዝቡ ኃጢአት ሲሰራ እና አምላኩ ህዝቡን ሊቀጣ ባለበት ጊዜ ለከተማይቱ እንደ ዘበኛ ሆኖ ያስጠነቅቃል። "ነቢዩ በኤፍሬም ላይ ለእግዚአብሔር እንደ ዘበኛ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ነቢዩ በኤፍሬም ላይ ለአምላኬ ዘበኛ ነው
አንዳንድ ትረጉሞች ይህንን ክፍል "ነቢዩ ከአምላኬ ጋር በኤፍሬም ላይ ዘበኛ ነው" ብለው ይተረጉሙታል።

ነቢዩ ነው
ይህ የሚያመለክተው በአጠቃላይ እግዚአብሔር ለሾማቸው ነቢያት ሁሉ ነው። "ነቢያት ናቸው" ወይም "እውነተኛ ነቢያት ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የጋር/የወል ስማዊ ሀረግ የሚለውን ይመልከቱ)

ኤፍሬም
እዚህ ስፍራ "ኤፍሬም" የሚለው የሚወክለው መላውን የእስራኤል ህዝብ ነው። (ስኔክቲኪ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የወፍ ወጥመድ በመንገዱ ሁሉ ነው
የ "ወፍ ወጥመድ" ወፍን ለመያዝ የሚያገለግል ማጥመጃ ነው። ይህ ማለት የእስራኤል ህዝብ የእግዚአብሔርን ነቢይ ለማስቆም የሚችሉትን ሁሉ ያደርጋሉ። "ህዝቡ በሚሄድበት ሁሉ ለእርሱ ወጥመድን ያስቀምጣሉ" ወይም "ህዝቡ እረሱን ለመጉዳት የሚችሉትን ሁሉ ያደርጋሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በጊብዓ ዘመን እንደነበረው ራሳቸውን እጅግ በኃጢአት በክለዋል
"የእስራኤል ህዝብ ኃጢአት በማድረግ ከዘመናት አስቀድሞ በጊብዓ ዘመን ያደርጉት እንደነበረው እጅግ ረክሰዋል" ይህ ምናልባት በመሳፍንት ምዕራፍ 19 እስከ ምዕራፍ 21 በሚገኘው ታሪክ ውስጥ በብንያም ነገድ ከተፈጸመው አሰቃቂ ድርጊት ጋር የሚነጻር ነው።

Hosea 9:10

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ እየተናገረ ነው

እኔ እስራኤልን ሳገኛት
ይህ የሚያመለክተው ያህዌ ከእስራኤል ህዝብ ጋር እነርሱን የራሱ ልዩ ህዝብ አድርጎ ለይቶ በመጀመሪያ ግንኙነት መጀመሩን ነው።

ይህ በበረሃ ወይን፤ በበለስ ዛፍ ላይ እንደ የወቅቱን የበኩራት ፍሬ እንደማግኘት ነበር።
እነዚህ ሁለቱም ሃሳቦች የሚያጎሉት አንድን ሰው ደስ የሚያሰኙትን ሁኔታዎች ነው። ይህ ማለት ከእስራኤል ህዝብ ጋር ግንኙነት ሲጀመር ያህዌ እጅግ ደስተኛ ነበር። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

በዓል ፌጎር
ይህ በሞዓብ ምድር የሚገኝ የበዓል ሃሰተኛ አማልዕክት ይመለኩበት የነበረበት ተራራ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 9:11

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ እየተናገረ ነው

ክብራቸው እንደ ወፍ በሮ ይጠፋል
የኤፍሬም ወገን፣ ወይም የእስራኤል ሰሜናዊ መንግሥት በሌላው መንግት ዘንድ ክብር ያሰጣቸው የነበረውን ማናቸውንም ነገር ያጣሉ። ወፍ በሮ እንደሚጠፋ ክብራቸው በፍጥነት ይጠፋ። "ክብራቸው ወፍ በሮ እንደሚጠፋ ከእነርሱ ይጠፋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከእነርሱ ዘወር ስል
እግዚአብሔር የሰሜኑን መንግሥት መርዳት ሲያቆም፣ የሚሆነው በአካል ከእነርሱ እንደ ተለያቸው ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 9:13

አጠቃላይ መረጃ:
ነቢዩ ሆሴዕ እየተናገረ ነው

ልክ እንደ ጢሮስ፣ ኤፍሬምን በለምለም መስክ ተተክሎ አየሁት
ይህ ህዝቡ በለምለም መስክ እንደ ተተከለ ዛፍ በመልካም ስፍራ እንደሆነ ይናገራል። "የእስራኤል ህዝብ በአንድ ወቅት እንደ ጢሮስ ከተማ፣ ደግሞም በለመለመ ምስክ እንደ ተተከለ ዛፍ ውብ እና አስደሳች ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኤፍሬም ... ጢሮስ
እዚህ ስፍራ "ኤፍሬም" የሚለው የሚወክለው መላውን የእስራኤል ህዝብ ነው። እነዚህ ስፍራዎች በውስጣቸው የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታሉ። (ስኔክቲኪ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

ነገር ግን ኤፍሬም ልጆቹን አሳልፎ ይሰጣል
"ልጆች" የሚለው ቃል የአገሪቱን ሰዎች ያመለክታል። "ነገር ግን የእስራኤል ሰዎች ልጆቻቸውን አሳልፈው ይሰጣሉ። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚውን ይመልከቱ)

ያህዌ ሆይ አድርግባቸው፣ - ምን ታደርግባቸዋለህ? እባክህ አድርግባቸው
ሆሴዕ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው ያህዌ ለእስራኤል ህዝብ የሚገባቸውን እንዲያደርግባቸው በጉልህ ማሳየት ስለፈለገ ነው። " ያህዌ ሆይ፣ እኔ የምጠይቀው ይህንን ነው፤ እንድታደርግባቸው፣ እባክህን ስጣቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ)

ጽንስ የማይሸከም ማህጸን
"የማይሸከም" ማህጸን ማለት ጽንሱ እንዲጨነግፍ እና የተረገዘው እንዲሞት ማለት ነው። ሆሴዕ የአገሪቱ ሴቶች ሁሉ እንደዚያ እንዲሆኑ እየጠየቀ ነው።

Hosea 9:15

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ እየተናገረ ነው

ከቤቴ አስወጣቸዋለሁ
ያህዌ እስራኤልን ከምድሩ፣ ማለትም ከከነዓን ምድር እንደሚያስወጣቸው እየተናገረ ነው። እዚህ ስፍራ "ቤቴ" የሚለው የሚወክለው ከነዓንን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚውን ይመልከቱ)

መኳንንቶቻቸው
ንጉሡን የሚያገለግሉ ወንዶች

Hosea 9:16

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ በቁጥር 16 ላይ እየተናገረ ነው። ሆሴዕ በቁጥር 17 መናገር ይጀምራል።

ኤፍሬም ታመመ፣ ዛፎችም ስራቸው ደረቀ፤አንዳች ፍሬ አልሰጡም
ያህዌ የእስራኤልን ህዝብ ፍሬ እንደማያፈራ እና ለመቆረጥ እንደተዘጋጀ የታመመ ዛፍ አድርጎ ይናገራል። ይህ ህዝቡ ደካማ እንደሆነ፣ ጠላቶቻቸው በቶሎ እንደሚመጡና እንደሚያሸንፏቸውም የሚናገር ሃሳብ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 10

1 እስራኤል ፍሬውን የሚሰጥ ያማረ ወይን ነው። ፍሬው በበዛ መጠን፥ መሠዊያ አብዝቶ ሠራ። ምድሩ አብዝቶ ባፈራ መጠን፥የተቀደሱ አ ምዶቹን አሳመረ። **2** ልባቸው አታላይ ነው፥ አሁን በደላቸውን ሊሸከሙ ይገባል። እግዚአብሔር መሠዊያዎቻቸውን ያፈርሳል፤ የተቀደሱ አምዶቻቸውን ያጠፋል። **3** አሁንም እነርሱ፦ «እግዚአብሔርን ስላልፈራን፥ ንጉሥ የለንም፤ ንጉሥሥ ምን ሊያደርግልን ይችል ነበር?» ይላሉ። **4** ባዶ ቃላትን ይናገራሉ፥ በሐሠት መሃላም ኪዳን ያደርጋሉ። ስለዚህ ፍትሕ፥ በእርሻ ትልም ላይ እንደሚወጣ መርዛማ አረም ይወጣል። **5** የሰማሪያ ነዋሪዎች ከቤትአዌን ጥጃዎች የተነሳ ይፈራሉ። በእነርሱና በውብታቸው ደስ ይሰኙ የነበሩ እነዚያ ጣዖት አምላኪ ካህናት እንደሚያልቅሱላቸው፣ ሕዝቡም ያለቅሱላቸዋል፤ ከእንግዲህ ወዲያ በዚያ የሉምና። **6** ለታላቁ ንጉሥ እጅ መንሻ ወደ አሦር ይወሰዳሉ። ኤፍሬም ይዋረዳል፥ እስራኤልም የጣዖታትን ምክር በመከተሉ ያፍራል። **7** የሰማርያ ንጉሥ፥ በውኃ ላይ እንዳለ የእንጨት ፍቅፋቂ ይጠፋል። **8** የእስራኤል ኃጢአት የሆኑት፥ የክፋት ቅዱስ ቦታዎች ይጠፋሉ። እሾህና አሜክላ በመሠዊያዎቻቸው ላይ ይበቅላሉ። ሕዝቡ ተራሮችን፥ «ሸፍኑን!»፥ ኮረብታዎችንም፥ «ውደቁብን!» ይላሉ። **9** እስራኤል ሆይ ከጊብዓ ዘመን አንስቶ ኃጢአት ሠራችሁ፥ በዚያም ጸንታችኋል። በጊብዓ ክፉ አድራጊዎች ላይ ጦርነት በድንገት አልደረሰባቸውምን? **10** በወደድሁ ጊዜ እገሥጻቸዋለሁ። ሕዝቦች በአንድነት ይሰበሰቡባቸዋል፥ ስለ ድርብ ኃጢአታቸውም ያስሯቸዋል። **11** ኤፍሬም እህል ማበራየት የምትወድ የተገራ ጊደር ነች፥ ስለዚህ በሚያምር ጫንቃዋ ላይ ቀንበር አኖራለሁ። በኤፍሬም ላይ ቀንበር አኖራለሁ፥ ይሁዳ ያርሳል፥ ያዕቆብም ብቻውን መከስከሻውን ይጎትታል። **12** ጽድቅን ለራሳችሁ ዝሩ፥ የኪዳኑን ታማኝንት ፍሬም እጨዱ። እስኪመጣ፥ ጽድቅንም እስኪያዝንብባችሁ ድረስ እግዚአብሔርን የምትፈልጉበት ጊዜ ነውና፤ ያልታረሰ መሬታችሁን አለስልሱ። **13** ክፋትን አረሳችሁ፥ግፍንም አጨዳችሁ። በስልታችሁና በወታደሮቻችሁ ብዛት ታምናችኋልና፥ የመታለልን ፍሬ በላችሁ። **14** ስለዚህ በሕዝብህ መካከል የጦርነት ሽብር ይነሣል፥ የተመሸጉ ከተሞችህም ሁሉ ይጠፋሉ። እናቶች ከልጆቻቸው ጋር እንደተከሰከሱበት፥ ስልማን በሰልፍ ቀን ቤትአርብኤልን እንዳጠፋበት ጊዜ ይሆናል። **15** ስለዚህ ቤቴል ሆይ፥ ከታላቅ ክፋትሽ የተነሣ በአንቺም ላይ እንዲሁ ይሆናል። ንጋት ላይ የእስራኤል ንጉሥ ፈጽሞ ይጠፋል።»

Hosea 10:1

አጠቃላይ መረጃ:
ሆሴዕ ስለ እስራኤል እየተናገረ ነው።

እስራኤል ብዙ የሚያፈራ የተንዠረገገ የወይን ተክል ነው
እስራኤል የተገለጸችው በጣም ፍሬያማ እንደሆነ የወይን ተክል ነው። ህዝቡ ለጊዜው በለጽጎና ጠንክሮ ነበር። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የተንዠረገገ የወይን ተክል
ይህ ወይን ከተለመደው ይበልጥ ያፈራል ፍሬው በመመረለት መጠን... ምድሩ ብዙ ሲያፈራ እነዚህ ሁለቱም አገላለጾች፤ ህዝቡ ሲበለጽግ፣ እየጠነከረ እና ሃብት እያገኘ ሲመጣ የሚል ተመሳሳይ ትርጉም ይሰጣሉ።

ልባቸው በማታለል የተሞላ ነው
"ልባቸው" የሚለው የሚገለጸው መላው ማንነታቸውን፣ በስሜታቸው እና ፍላጎታቸው ላይ ትኩረት በማድረግ ነው። "እነርሱ አታላዮች ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲኪ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

አሁን ኃጢአታቸውን መሸከም አለባቸው
እዚህ ስፍራ "ኃጢአት" የሚለው ከዚህ ጋር ለተያያዘ የሚደርስ ቅታትን የሚያመለክት ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት/ ነው። ይህ ቅጣት የተገለጸው ለመሸከም ከባድ እንደሆነ ክብደት ነው። "አሁን ያህዌ በኃጢአታቸው ምክንያት የሚቀጣቸው ጊዜ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Hosea 10:3

አጠቃላይ መረጃ:
ሆሴዕ ስለ እስራኤል እየተናገረ ነው።

እናም ንጉሡ - ለእኛ ምን ማድረግ ይችላል?
ህዝቡ ንጉሦቻቸው ሊረዷቸው እንዳልቻሉ ይናገራሉ። "ምንም እንኳን አሁን ንጉሥ ቢኖረንም፣ እኛን ሊረዳን አልቻለም " በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ባዶ/የማይጠቅሙ ቃላትን ይናገራሉ
እዚህ ስፍራ "ባዶ /የማይጠቅሙ ቃላት" የሚለው የሚያመለክተው ሃሰትን ነው። "ሃሰት ይናገራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህ በእርሻ ዳርቻ እንደሚበቅል መርዛማ አረም ፍርድ ፈጥኖ ይበቅላል
እነዚያ ሰዎች በህጎቻቸው እና በህጋዊ ውሳኔዎቻቸው ፍርድ ብለው የሚጠሩት የተገለጸው ፈጥኖ እንደሚያደነቁል/እንደሚበቅል ተክል ነው። "ስለዚህ ውሳኔዎቻቸው ፍትሃዊ አይደሉም፣ ይልቁንም ጎጂዎች ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሻ ዳርቻ እንደሚበቅል መርዛማ አረም
የእነርሱ ሃሰት እና ፍትህ አልባነት በህዝባቸው መሃል ተስፋፍቶ እንደ መርዛማ ተክሎች ሁሉንም ሰው ጎዳው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 10:5

አጠቃላይ መረጃ:
ሆሴዕ ስለ እስራኤል እየተናገረ ነው።

ቤትአዌን
ይህ ከተማ በእስራኤል ሰሜናዊ ግዛት እና በደቡባዊ ግዛት በቢንያም ነገድ ድንበር መሃል የሚገኝ ነበር። ይህንን በሆሴዕ 4:15 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ አሦር በምርኮ ይወሰዳሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አሦራውያን እነርሱን በምርኮ ይወስዷቸዋል" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ኤፍሬም ይዋረዳል፣ እስራኤልም በጣኦቷ ታፍራለች
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ደግሞም የእስራኤል ህዝብ በጣም ያፍራል፤ ምክንያቱም ጣኦታትን አምልኳልና " በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ጣኦቷ
ብዙ ቅጂዎች በዚህ ክፍል የሚገኘውን የዕብራይስጡን ቃል "ምክር፣" "እቅድ፣" ወይም "አስተሳሰብ" ብለው ተርጉመዋል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Hosea 10:7

የሰማርያ ንጉሥ ይደመሰሳል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል:: "አሦራውያን የሰማርያን ንጉሥ ይደመስሳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በውሃ ላይ እንደሚንሳፈፍ ቁራጭ እንጨት
ይህ ማለት የሰማርያ ንጉሥ የውሃ ማዕበል እንደሚያንገላታው ትንሽ ቁራጭ እንጨት አቅመቢስ ይሆናል ማለት ነው:: (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የክፋት ከፍ ያሉ ስፍራዎች ይደመሰሳሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል:: "አሦራውያን የእስራኤል ህዝብ ኃጢአት ያደርግባቸው የነበሩ ከፍተኛ ስፍራዎችን ይደመስሳሉ (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰዎቹ ተራሮችን "ጋርዱን!" ኮረብቶችን "በላያችን ውደቁ!" ይላሉ
በእርግጥ ሰዎች ማሰብ ከማይችሉ ወይም ከማይሰሟቸው ነገሮች ጋር አይነጋገሩም:: ተርጓሚዎች ቋንቋቸው እንዲህ አይነቱን ንግግር የማይፈቅድላቸው ከሆነ ለዚህ ምንባብ የተለየ አቀራረብ ሊመርጡ ይችላሉ:: "ሰዎቹ እንዲህ ይላሉ፣ ‘ተራሮች እንዲሸፍኑን እንፈልጋለን!' ደግሞም ‘ኮረብቶች በእኛ ላይ እንዲወድቁብን እንፈልጋለን!'" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (አፖስተሮፊ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 10:9

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ እየተናገረ ነው

በጊብዓ ዘመን
ይህ ምናልባት በመሳፍንት ምዕራፍ 19 እስከ ምዕራፍ 21 በሚገኘው ታሪክ ውስጥ በብንያም ነገድ ከተፈጸመው አሰቃቂ ድርጊት ጋር የሚነጻር ነው:: ይህንን በሆሴዕ 9:9 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ::

በዚያ እናንተ ታስታውሳላችሁ
ይህ ክፍል ምናልባት በጊዜው የነበሩ ሰዎች አባቶቻቸው በጊብዓ ያደርጉት የበረውን በተመሳሳይ መንገድ ማድረግ ቀጥለው ሊሆን ይችላል:: "እናንተም ልክ እነርሱ ያደርጉት እንደነበረው ታስባላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጦርነት በጊብዓ የኃጢአተኞችን ልጆች አልጨረሰምን?
ያህዌ ጥያቄውን የተጠቀመበት በጊብዓ ኃጢአተኞች በራሳቸው በእርግጥ ጦርነቱን መወጣት እንዳለባቸው በአጽንኦት ለመናገር ነው:: ደግሞም ይህ ሲገለጽ ሰዎቹ ጦርነትን መወጣት ያለባቸው ጠላቶቻቸው ሲመጡባቸው ጦርነት ሰው ሆኖ እንሚይዛቸው ተደርጎ በማቅረብ ነው:: "ጦርነት በእርግጥ በጊብዓ ኃጢአት ባደረጉ ላይ ይመጣባቸዋል" ወይም "ጠላቶች በእርግጥ በጊብዓ ኃጢአት የሰሩትን ያጠፋቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

የኃጢአተኞች ልጆች
እዚህ ስፍራ "የአባቶቻቸው ልጆች" የሚለው ፈሊጥ ነው፤ ትርጉሙ "የአባቶቻቸው ባህሪ ያላቸው" ማለት ነው:: "ኃጢአት ያደረጉ" ወይም "ክፉ አድራጊዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 10:10

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ እየተናገረ ነው

እጥፍ ኃጢአት/በደል
ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን የኃጢአት ብዛት ነው:: ኤፍሬም እንደ ተገራች መውቃት እንደምትወድ ጊደር ነው ጊደር ማበራየት ትወዳለች ምክንያቱም ቀንበር ሳይጫንባቸው በነጻነት በዙሪያ መዞር ይችላሉ:: ያህዌ የእስራኤል ህዝብ ነጻ ሆኖ ያሻውን ደስተኛ ህይወት መኖር ይችላል እያለ ነው:: (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በምቹ ጫንቃዋ ላይ ቀንበር እጭናለሁ፣ በኤፍሬም ላይ ቀንበር አስቀምጣለሁ
እዚህ ስፍራ "ቀንበር" የሚያመለክተው መከራን እና ባርነትን ነው:: ያህዌ ለእስራኤል ህዝብ ደግ ነበር፣ ህዝቡ ግን ለእርሱ ታማኝ አልበረም:: ስለዚህም እርሱ ይቀጣቸዋል ደግሞም ለባርነት አሳልፎ ይሰጣቸዋል:: (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይሁዳ ያርሳል፣ ያዕቆብ መሬቱን ያለሰልሳል
እዚህ ስፍራ "ይሁዳ" የሚያመለክተው የደቡቡን መንግሥት ህዝብ ነው፤ "ያዕቆብ" ደግሞ የሰሜኑን መንግሥት ህዝብ ያመለክታል:: ይህ ማለት እግዚአብሔር በሁለቱም መንግሥታት ላይ አስጫቂ ጊዜን ያመጣል ማለት ነው:: (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

መከስከሻ
መሬትን ለማለስለስ እና ከታረሰ በኋላ ዘርን አፈር ለማልበስ የሚያገለግል መሳሪያ

Hosea 10:12

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ እየተናገረ ነው

ጽድቅን ለራስህ ዝራ፣ የቃል ኪዳንን ፍሬ በታማኝነት እጨድ
ጽድቅ እና የቃል ኪዳን ታማኝነት የተነገሩት እንደሚዘራ እና እንደሚታጨድ እህል ነው:: ረቂቅ ስም የሆኑት "ጽድቅ" እና "ታማኝነት"፤ "ትክክል" እና "ታማኝ" ተብለው ሊጻፉ ይችላሉ:: "አሁን እረስ፣ ደግሞም ትክክል የሆነውን አድርግ፤ ይህ ሲሆን የታማኝነትን ፍቅር ፍሬ ማጨድ ትችላለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

ያልታረሰ መሬታችሁን እረሱ
መሬት "ሳይታረስ ሲቀር" በላዩ ለመዝራት ዝግጁ አልተረገም ማለት ነው:: ያህዌ ህዝቡ ንስሃ እንዲገባ እፈልጋለሁ ማለቱ ነው፤ ስለዚህ ትክክል የሆነውን ማድረግ መጀመር ይችላሉ:: (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኀጢአትን አርሳቸርኋል፤ ኢፍትሃዊነትን አጭዳችኋል
ኀጢአት እና ኢፍትሃዊነት የተገለጹት ሊዘራ እና ሊታጨድ የሚችል ሰብል እንደሆኑ ተደርጎ ነው (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የማታለልን ፍሬ ተመግባችኋል
የማታለል ውጤቱ የተገለጸው ሊበላ እንደሚችል ምግብ ነው:: "አሁን አንዳችሁ ሌላችሁን ማታለላችሁ የሚያስከትለውን የመከራ ውጤት እየተቀበላችሁ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 10:14

አጠቃላይ መረጃ ሰልማን፣ ቤትአርብኤልን በጦርነት ቀን እንዳፈራረሰው ይሆናል
የሚመጣው ጦርነት የተነጻጸረው ከረጅም ጊዜ አስቀድሞ ከተደረገ ጦርነት ጋር ነው::

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሰልማን
ይህ በ740 ዓመተ ዓለም ግድም የቤትአርብኤልን ከተማ የደመሰሰ ንጉሥ ስም ነው። ሰራዊቱ ሴቶችን እና ልጆችን በጥቃቱ ወቅት ፈጅቷል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ቤትአርብኤል
ይህ የንፍታሌም ነገድ ከተማ አይነት ስያሜ ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህም ቤቴል ሆይ፣ ከታላቅ ኀጢአትሽ የተነሳ በአንቺም ላይ እንደዚሁ ይሆናል
እዚህ ስፍራ "ቤቴል" የሚለው የሚወክለው በዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ነው። ነቢዩ የቤቴልን ሰዎች በዚያ ሆነው እንደሚያደምጡት አድርጎ ይናገራል። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት እና አፖስትሮፊ የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 11

1 እስራኤል ወጣት በነበረበት ጊዜ ወደድኩት፥ ልጄንም ከግብጽ ጠራሁት። **2** አብዝቶ በተጠሩ መጠን፥ አብዝተው ራቁ። ለበአል አማልክት ሠው፥
ለጣዖታትም አጠኑ። **3** ሆኖም ግን ኤፍሬምን መራመድ ያስተማርኩት እኔ ነበርኩ። ክንዶቻቸውን ይዤ ያነሳኋቸው እኔ ነበርኩ፥ እነርሱ ግን የተጠነቀቅሁላቸው እኔ
እንደሆንሁ አላወቁም። **4** በሰው ገመድ፥ በፍቅርም ማሰሪያ መራኋቸው። የመንጋጋዎቻቸውን ማሰሪያ እንደሚያላላ ሆንኩላቸው፥ ዝቅ ብዬም መገብኳቸው። **5**
ወደ ግብጽ ምድር አይመለሱምን? ወደ እኔ መመለስን እምቢ በማለታቸው አሦር አይገዛቸውምን? **6** ሰይፍ በከተሞቻቸው ላይ ይወድቃል፥ የበሮቻቸውንም
መቀርቀሪያ ያጠፋል፤ከገዛ ራሳቸው ዕቅድ የተነሳ ያጠፋቸዋል። **7** ሕዝቤ ከእኔ ዘወር ለማለት ቆርጦአል። በከፍታ ወደ አለሁት ወደ እኔ ቢጣሩ እንኳ፥ማንም
አይረዳቸውም። **8** ኤፍሬም ሆይ እንዴት እተውሃለሁ? እስራኤል ሆይ እንዴት አሳልፌ እሰጥሃለሁ? እንዴት እንደ አዳማ አደርግሃለሁ? እንዴትስ እንደ ሲባዮ
አደርግሃለሁ? ልቤ በውስጤ ተለውጦአል፤ መላው ርኅራኄዬ ተነሣሥቷል። **9** ጽኑ ቁጣዬን አላመጣም፤ ኤፍሬምን ዳግመኛ አላጠፋም። እኔ አምላ ክ እንጂ ሰው
አይደለሁምና፥በመካከልህ ቅዱሱ ነኝና፥በቁጣ አልመጣም። **10** እነርሱም ከእኔ ከእግዚአብሔር በኋላ ይመጣሉ። እንደ እንበሳ አገሳለሁ። በእርግጥ አገሳለሁ፥
ሕዝቡም ከምዕራብ እየተንቀጠቀጡ ይመጣሉ። **11** ከግብጽ እንደ ወፍ፥ ከአሦርም ምድር እንደ ርግብ እየተንቀጠቀጡ ይመጣሉ። በየቤቶቻቸውም
አኖራቸዋለሁ።» ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው። **12** «ኤፍሬም በሐሰት፥ የእስራኤልም ቤት በማታለል ከበበኝ። ይሁዳ ግን እስካሁን ከእኔ ከአምላኩ ጋር
ጸንቷል፥ ለእኔም ለቅዱሱ የታመነ ነ ው።»

Hosea 11:1

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ፣ ወላጅ ልጁን እንደሚንከባከብ፤ እስራኤልን ስለመንከባከብ ይናገርል

እስራኤል ወጣት ሰው በነበረበት ወቅት
ያህዌ ስለ እስራኤል ሰዎች ወጣት ሰው እንደሆነች አድርጎ ይናገራል። ያህዌ ከአገሪቱ ጋር በመጀመሪያ ግንኙነት ሲጀምር የነበረውን ሁኔታ ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ልጄን ከግብጽ ጠራሁት
"ወንድ ልጅ" የሚለው የሚያመለክተው የእግዚአብሔር አብን ህዝብ ነው። "ልጄን ከግብጽ አወጣሁት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አብዝተው በተጠሩ መጠን፣ አብዝተው ከእርሱ ራቁ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የእኔ ህዝብ እንዲሆኑ አብዝቼ በጠራኋቸው መጠን፣ አብዝተው ተቃወሙኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 11:3

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለእስራኤል እንዴት እንደሚጠነቀቅ እየተናገረ ነው

እንዴት መራመድ እንደሚችል ለኤፍሬም ያስተማርኩት እኔ ነበርኩ
ያህዌ እስራኤልን መራመድ እንደሚማር ትንሽ ልጅ ይገልጻታል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እጆቻቸውን ይዤ አነሳኋቸው
ይህ አገላለጽ ቀደም ሲል በቀረበው ዘይቤያዊ አነጋገር ላይ የሚቀጥል ነው። "ለእነርሱ ጥንቃቄ አደረግሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

በፍቅር እጅ፣ በሰብአዊነት ገመድ ይዤ መራኋቸው
ያህዌ ህዝቡን ሰው ሊረዳው እና ሊገነዘበው በሚችለው መንገድ ወደዳቸው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ)

ቀንበሩን ከጫንቃቸው እንደሚያቀል ሰው ሆኜላቸው ነበር
ያህዌ የእስራኤልን ህዝብ የሚገልጸው እርሱ ከስራው እንዳሳረፈው ከባድ የስራ ጫና እንዳለበት እንስሳ ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እነርሱ ጎንበስ ብዬ መገብኳቸው
ይህ አገላለጽ እስራኤል እንደ ትንሽ ልጅ የቀረበበትን ዘይቤ የሚቀጠል ነው። ያህዌ ለአካላዊ ፍላጎቶቻቸው የሚያስፈልገውን ሁሉ ይሰታቸዋ ማለት ሊሆን ይችላል።

Hosea 11:5

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለእስራኤል እየተናገረ ነው

ወደ ግብጽ ምድር አይመለሱምን?
ይህ ጥያቄ እስራኤል ዳግም አንድ ጊዜ በግብጽ በነበሩበት ጊዜ እንደነበሩት ባሪያዎች ይሆናሉ ማለትን ያመለክታል። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እኔ መመለስን እምቢ በማለታቸው አሦር አይገዛቸውምን?
የእስራኤል ህዝብ ለያህዌ ታማኝ መሆንን ስላልወደዱ የአሦር ምርኮኛ ይሆናሉ። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በከተሞቻቸው ላይ ሰይፍ ይመጣል
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚለው የሚወክለው የእስራኤልን ከተሞች የሚደምሱ ጠላቶቻቸውን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለው ይመልከቱ)

የበሮቻቸውን መወርወሪያ ደምስሱ
በሮች የከተማዋ ነዋሪዎች ከጠላቶቻቸው በደህንነት እንዲጠበቁ ያደርጋል፣ መወርወሪያዎቹ ደግሞ በሮቹ እንዲቆለፉ ያስችላሉ። መወርወሪያዎቹን መደምሰ ማለት የህዝቡን ደህንነት ማጣት ማለት ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለው ይመልከቱ)

እጅግ ከፍ ወዳለው ቢጠሩም
እዚህ ስፍራ እግዚአብሔር በሶስተኛ መደብ ስለ ራሱ እየተናገረ ነው። ይህ በአንደኛ መደብ ሊጻፍ ይችላል። "እጅግ ከፍ ወዳልኩት ወደ እኔ ቢጠሩም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ)

ማንም ሊረዳቸው አይችልም
ያህዌ እስራኤልን እንዲረዳት አይፈቅድም፤ ምክንያቱም እነርሱ ከእርሱ ፊታቸውን አዙረዋል።

Hosea 11:8

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለእስራኤል እየተናገረ ነው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ኤፍሬም ሆይ፣ እንዴት ልተውህ እችላለሁ? እስራኤል ሆይ፣ እንዴት አሳልፌ ልሰጥሽ እችላለሁ?
ያህዌ ህዝቡን እጅግ ስለሚወድ ሙሉ ለሙሉ አያጠፋውም። ይህ ከጥያቄ መልክ ወጥቶ በዐረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። "ኤፍሬም ሆይ፣ እኔ አልተውህም። እስራኤል ሆይ፣ እኔ አልጥልሽም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

እንዴት እንደ አዳማ አደርግሃለሁ? እንዴትስ እንደ ሲባዩ አድግሃለሁ?
ያህዌ ህዝቡን እጅግ ስለሚወድ ሙሉ ለሙሉ አያጠፋውም። ይህ ከጥያቄ መልክ ወጥቶ በዐረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። "በአዳማ ላይ እንዳደረግኩት በአንተ ላይ ማድረግ አልገልግም ወይም በሶዶም ላይና በሲባዩ ከተሞች ላይ እንዳደረግኩት አላደርግብህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

እኔ እግዚአብሔር እንጂ ሰው አይደለሁም
እግዚአብሔር በፍጥነት ለመበቀል እንደሚወስኑት እንደ ሰዎች አይደለም

ልቤ በውስጤ ተለወጠ
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚለው የሚወክለው የእግዚአብሔርን ፈቃድ እና ውሳኔ ነው (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለው ይመልከቱ)

በቁጣ አልመጣም
"ቁጣ" የሚለው ረቂቅ ስም "ቁጡ" በሚለው ገላጭ ሊጻፍ ይችላል። "ወደ እናንተ መጥቼ በእናንተ ቁጡ አልሆንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 11:10

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ህዝቡን መቼ እንደሚያድስ እየተናገረ ነው

እነርሱ ያህዌን ይከተላሉ
ያህዌን ማምለክ እና ማክበር እርሱን መከተል ሆኖ ቀርቧል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ እንደ አንበሳ ያገሳል
ያህዌ ህዝቡን ወደ ምድሩ መመለስን የሚቻል ነገር አድረጎታል፤ ይህም እርሱ ህዝቡን እየጠራ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ እርግብ ... እንደ ወፍ እየተንቀጠቀጡ ይመጣሉ
ወፍ ወደ ጎጆዋ እንደምትመለስ ወደ አገራቸው በፍጥነት ይመለሳሉ። "መንቀጥቀጥ" ምናልባት የወፍ ክንፎች መርገብገብን ያመለክታል። እንደዚሁም ምናልባት የሰዎችን የትህትና ስሜት እና ለእግዚአብሔር ያላቸውን አምልኮ ያመለክታል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌ አዋጅ/ ያህዌ የተናገረው
"ያህዌ ያወጀው/የተናገረው" ወይም "ያህዌ በታላቅነቱ የተናገረው" ይህንን በሆሴዕ 2:13 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

Hosea 11:12

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ እስራኤል እና ስለ ይሁዳ እየተናገረ ነው

ኤፍሬም በሃሰቱ፣ የእስራኤል ቤትም በማታለሉ ከብቦኛል
የሃሰት እና የማታለል ድርጊቶች የተነገሩት የሰሜን መንግሥት ሰዎች ያህዌን እንደ ከበቡበት ቁሳዊ ነገሮች እንደሆኑ ተደርጎ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ነገር ግን እስከ አሁን ይሁዳ ከእኔ ጋር ነው
እዚህ ፍራ "ይሁዳ" የሚለው የሚያመለክተው በዚያ የሚኖሩ ህዝቦችን ነው። ይህ ከእርሱ ጋር "አብሮ መሄድ" በሚል ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆንን ይገልጻል። ሆኖም፣ ብዙ ቅጂዎች ለዚህ አስቸጋሪ ምንባብ የተለያየ ትርጉም አላቸው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትንው ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 12

1 ኤፍሬም ነፋስ ይመገባል፥ የምሥራቅንም ነፋስ ይከተላል። ሐሰትንና ዓመፅን ያለማቋረጥ ያበዛል። ከአሦር ጋር ኪዳን ያደርጋሉ፥ የወይራ ዘይትም ወደ ግብጽ ይወስዳሉ። **2** እግዚአብሔር ከይሁዳ ጋር ሙግት አለው፥ ያዕቆብንም ስላደረገው ይቀጣዋል፥ እንደ ሥራውም ይከፍለዋል። **3** ያዕቆብ በማሕፀን ውስጥ የወንድሙን ተረከዝ ያዘ፥ በጎልማሳነቱም ከአምላክ ጋር ታገለ።ከመልአኩም ጋር ታግሎ አሸነፈ። **4** አልቅሶም በፊቱ ተቀባይነት እንዲያገኝ ለመነው። በቤቴል ከአምላክ ተገናኘ፥ በዚያም አምላክ ከእርሱ ጋር ተነጋገረ። **5** እርሱም የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር ነው፤የሚጠራበት ስሙም «እግዚአብሔር» ነው። **6** ስለዚህ ወደ አምላካችሁ ተመለሱ። ለኪዳኑ ታማኝነትን፥እንዲሁም ፍትሕን ጠብቁ፤ሁል ጊዜም አምላካችሁን ተስፋ አድርጉ። **7** ነጋዴዎቹ ሐሰተኛ ሚዛኖችን በእጆቻቸው ይዘዋል፤ ማጭበርበርን ይወዳሉ። **8** ኤፍሬምም፦ «በእርግጥ እጅግ ባለጠጋ ሆኜአለሁ፥ ሀብትንም አግኝቼአለሁ። በሥራዬ ሁሉ ኃጢአት የሚሆን ምንም ዓይነት በደል አያገኙብኝም» ይላል። **9** ከግብጽ ምድር አንስቶ ከአናንተ ጋር የሆንኩ አምላካችሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ። እንደ ዓመት በዓላት ቀናት ዳግመኛ በድንኳኖች እንድትኖሩ አደርጋችኋለሁ። **10** ለነቢያቶቹም ተናገርሁ፥ ስለ እናንተም ብዙ ራዕዮችን ሰጠኋቸው። በነቢይቶቹም አማካይነት ምሳሌዎችን ሰጠኋችሁ።» **11** በገለዓድ ኃጢአት ካለ፥ በእርግጥ ሕዝቡ ከንቱ ነው። በጌልጌላ ወይፈኖችን ይሰዋሉ፥ መሠዊያዎቻቸው በታረሰ መሬት ላይ እንዳለ የድ ንጋይ ክምር ይሆናሉ። **12** ያዕቆብ ወደ ሶሪያ ምድር ሸሸ፤ እስራኤልም ሚስት ለማግኘት አገለገለ፥ ሚስትም ለማግኘት የበጎችን መንጋ ይጠብቅ ነበረ። **13** እግዚአብሔር በነቢይ አማካይነት እስራኤልን ከግብጽ አወጣ፥ በነቢይም አማካይነት ተጠነቀቀለት። **14** ነገር ግን እግዚአብሔር ይቆጣ ዘነድ ኤፍሬም ክፉኛ አነሳሳው። ስለዚህ ጌታው የደሙን በደል በእርሱ ላይ ይደርጋል፥ አሳፋሪም ስለ ሆነው ሥራው የሚገባውን ይከፍለዋል።

Hosea 12:1

አጠቃላይ መረጃ:
ነቢዩ ሆሴዕ እየተናገረ ነው

ኤፍሬም ነፋስ ይመገባል
እዚህ ስፍራ "ኤፍሬም" የሚለው የሚወከወለው መላውን የእስራኤል ህዝብ ነው። እንደዚሁም "ነፋስ" የሚለው የሚወከወለው ጥቅም የሌለውን ነገር ወይም ጊዜያዊ የሆነን ነገር ነው። የእስራኤል ህዝብ የሚያደርገው የማይጠቅመው ነገር የተገለጸው ነፋስ እንደሚበሉ ተደርጎ ነው። (ስኔክቲኪ/ዘይቤያዊ አነጋጋር- የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ፤ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

የምስራቅን ነፋስ ይከተላል
የምስራቅ ነፋሳት በጣም ሞቃት እና ምድርን የሚያጠፉ ነበሩ። ራሳቸውን የሚያጠፋ ነገሮችን የሚሰሩት ሰዎች የተገለጹት የምስራቅን ነፋስ እየተከተሉ እንደሆነ ተደርጎ ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

የወይራ ዘይት ወደ ግብጽ ይልካሉ
የእስራኤል ሰዎች ለግብጽ ንጉሥ፣ ይረዳቸው ዘንድ ለማግባባት የእጅ መንሻ አድርገው የወይራ ዘይት ይልካሉ

ያህዌ ከይሁዳ ጋር ሙግት አለው
ያህዌ የይሁዳ ሰዎች እርሱን መበደላቸውን እና ቃል ኪዳኑን ማፍረሳቸውን በፍርድ ቤት እየከሰሳቸው እንደሆነ አድርጎ ይናገራቸዋል። ተመሳሳዩን ሀረግ በሆሴዕ 4:1 እንዴት እንደ ተረጎሙት ይመልከቱ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በይሁዳ ላይ... ያዕቆብን በድርጊቱ ይቀጣዋ ... ለስራውም ይከፍለዋል
እዚህ ስፍራ "ይሁዳ" እና "ያዕቆብ" ሁለቱም የይሁዳን ህዝብ ይወክላሉ። "በይሁዳ ሰዎች ላይ... ለድርጊታቸው እቀጣቸዋለሁ.. ለስራቸውም እከፍላቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

መግት
ይህ በህግ አደባባይ አንድ ሰው በሌላ ሰው ላይ የሚያቀርበው ክርክር ነው። ይህንን በሆሴዕ 2:2 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

Hosea 12:3

አጠቃላይ መረጃ:
ነቢዩ ሆሴዕ የእስራኤላዊያን አባት ስለሆነው ስለ ያዕቆብ እየተናገረ ነው

በማህጸን ሳለ ያዕቆብ የወንድሙን ተረከዝ ያዘ
ያዕቆብ የወንድሙን የብኩርና ስፍራ ለመውሰድ ፈለገ፣ ስለዚህም ወንድሙ በኩር እንዳይሆን ለማድረግ ሞከረ። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከመልአክ ጋር ታግሎ አሸነፈ
ያዕቆብ ይባርከው ዘንድ ከመልአክ ጋር ታገለ። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 12:5

አጠቃላይ መረጃ:
ነቢዩ ሆሴዕ እየተናገረ ነው

እርሱ የሚጠራበት ስሙ ነው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። እዚህ ስፈራ "ስም" የሚለው የሚወክለው የእግዚአብሔርን ባህሪይ ነው። "ስሙ ወደ እርሱ የምንጸልይበት ነው" ወይም "ስሙ እርሱን የምናመልክበት ነው" (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

ቃል ኪዳናዊ ታማኝነትንና ፍትህን መጠበቅ
ይህ የእግዚአብሔርን ህግ መጠበቅን እና ትክክል የሆነውን ማድረግን ያመለክታል

Hosea 12:7

አጠቃላይ መረጃ:
ነቢዩ ሆሴዕ ስለ እስራኤል እየተናገረ ነው

ሃሰተኛ መለኪያዎች/ሚዛን
ነጋዴዎች የሚገዙተን ወይም የሚሸጡትን ምርት በትክክል የማይለካ ሚዛንን ይጠቀማሉ።

ማጭበርበር ይወዳሉ
ነጋዴዎቹ ደንበኞቻቸውን በመዋሸትና መውሰድ ከሚገባቸው ባላይ ገንዘብ በመውሰድ ያታልላሉ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በእርግጥ ባለጸጋ ሆኛለሁ፣ የሚበቃ ሃብት አግኝቻለሁ
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ የኤፍሬም ሰዎች ራሳቸውን ባለጸጋ አድርገው ይቆጥራሉ የሚል ትርጉም አለው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሃብት አግኝቻለሁ
በንግድ ሃብታም መሆን የሚለው ሃብት ማግኘት ተብሎ ተገልጽዋል። "ብዙ ገንዘብ አፍርቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእኔ ዘንድ አንዳች በደል ፣ አንዳች ኀጢአት የሚሆን ነገር አያገኙም
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ የኤፍሬም ሰዎች ራሳቸውን ንጹህ አድርገው ይቆጥራሉ የሚል ትርጉም አለው። አንድ ሰው ሃጢአት አደረገ የሚለውን ማወቅ የተገለጸው በዚያ ሰው ውስጥ ሃጢአት ማግኘት በሚል ነው። " አንዳች ኀጢአት አድርገሃል ብለው ሊናገሩኝ አይችሉም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Hosea 12:9

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለእስራኤል ህዝብ እየተናገረ ነው

ከግብጽ ምድር .... እኔ ያህዌ አምላካችሁ ነኝ
አማራጭ ትርጉሞች የሚሆኑት 1) "አባቶቻችሁን ከግበጽ ምድር ያወጣሁት፣ እኔ ያህዌ አምላካችሁ ነኝ" ወይም 2) "በግብጽ ምድር ከነበራችሁበት ጊዜ አንስቶ አምላካችሁ እኔ እግዚአብሔር ነበርኩ" ወይም 3) "በግብጽ ምድር በነበራችሁበት ወቅት እኔ አምላካችሁ ሆንኩ"

እኔ ዳግም በድንኳኖች እንድትኖሩ አደርጋለሁ
አማራጭ ትርጉሞች የሚሆኑት 1) ያህዌ የእስራኤልን ህዝብ ከቤታቸው በሃይል ለማስወጣትና በድንኳኖች እንዲኖሩ ለማድረግ አስፈራራቸው። ስለዚህ፣ እዚህ ላይ "በድንኳኖች ውስጥ መኖር" የሚለው የሚወክለው በስደት መውጣትን ነው፣ ወይም 2) ይህ ከስደታቸው በኋላ ዳግም በድንኳኖች እንደሚኖሩ ቃል ኪዳን ነው፣ እናም ያህዌ እስራኤላውያን ከግብጽ በወጡ ጊዜ እንዳደረገው እነርሱን ይንከባከባል። ስለዚህ፣ እዚህ ላይ "በድንኳኖች ውስጥ መኖር" የሚለው የሚወክለው ያህዌ ሲንከባከባቸው ወደ መልካም ሁኔታ መመለሳቸውን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በነቢያት እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው የሚገልጸው ድርጊት የሚፈጽምን ነው። "በነቢያት አማካይነት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲኪ/ዘይቤያዊ አነጋጋር- የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ።)

Hosea 12:11

አጠቃላይ መረጃ:
ነቢዩ ሆሴዕ እየተናገረ ነው

መሰዊያዎቻቸው እንደ እርሻዎች ዳርቻ የድንጋይ ክምር ይሆናሉ
ሰዎች የሚያመልኩበት መሰዊያ ይፈራርስና የድንጋይ ክምር ይሆናል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ያዕቆብ ወደ አራም ምድር ኮበለለ፤እስራኤል ሚስት ለማግኘት ተገዛ
እዚህ ስፍራ "ያዕቆብ" እና "እስራኤል" የሚሉት ሁለቱም ቃላት አንድን ሰው ያመለክታሉ። የያዕቆብ ስም ቆይቶ እስራኤል ተባለ።

Hosea 12:13

አጠቃላይ መረጃ:
ነቢዩ ሆሴዕ እየተናገረ ነው

በአንድ ነቢይ
ያ ሰው፣ ሙሴ ነው

በማስመረር
ሰዎቹ ያህዌ እጅግ እንዲቆጣ አደረጉ

ስለዚህ ጌታው ደሙን በእርሱ ላይ ተወው
እዚህ ስፍራ "ደም" የሚለው የሚያመለክተው ህዝቡ ሌሎችን በመግደል በራሱ ላይ ያመጣውን በደል ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሃፍረቱን ወደ ራሱ ይመልስበታል
አንድ ሰው ከራሱ ድርጊት የተነሳ ስቃይ እንዲደርስበት የማድረግ ሃሳብ የተገለጸው፤ እነዚያ ድርጊቶች ቁሳዊ ነገሮች ሆነው፣ በተወረወሩ ጊዜ ተመልው በወርዋሪው ላይ እንደሚወድቁ ተደርጎ ነው። "ከራሱ አሳፋሪ ድርጊቶች የተነሳ እንዲሰቃይ አደርገዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 13

1 «ኤፍሬም በተናገረ ጊዜ መንቀጥቀጥ ነበረ። በእስራኤል መካከል ራሱን ከፍ ከፍ አደረገ፥ ነገር ግን በአልን በማምለኩ በደለኛ ሆነ፥ ሞተም። 2 አሁንም
አብዝተው ኃጢአት ሠሩ። ከብራቸው የተቀረጸ ምስል ሠሩ፥ ጣዖታት በሚቻለው መጠን በጥበብ ተሠርተዋል፥ ሁሉም የባለ ሙያ ሥራ ናቸው። ሕዝቡ ስለ እነርሱ
እንዲህ ይላሉ፦ 'እነዚህ የሚሠው ሰዎች ጥጃዎችን ይስማሉ።' 3 ስለዚህ እንደ ማለዳ ደመና፥በጠዋት እንደሚጠፋ ጤዛ፥ከአውድማ ላይ በነፋስ እንደሚወሰድ
አብቅ፣ከጪስ ማውጫ እንደሚወጣ ጢስ ናቸ ው። 4 ነገር ግን ከግብጽ ምድር ያወጣሁህ አምላክህ እግዚአብሔር እኔ ነኝ። ከእኔ በቀር አምላክ አታውቅም፥
ከእኔም በቀር ሌላ አዳኝ አታውቅም። 5 በምድረ በዳ፥ በታላቅም የድርቀት ምድር አውቅሁህ። 6 መሰማሪያ ባገኘህ ጊዜ ጠገብህ፥ በጠገብህም ጊዜ ልብህ
ታበየ፤ከዚህም የተነሳ ረሳኸኝ። 7 እንደ አንበሳ ሆንኩባቸው፥እንደ ነብርም በመንገዳቸው አደባለሁ። 8 ግልገሎቿን እንደ ተነጠቀች ድብ አጠቃቸዋለሁ።
ደረታቸውን ቀድጄ ከፍታለሁ፥በዚያም እንደ አንበሳ እበላቸዋለሁ፥ እንደ ዱር አራዊትም እነነጣጥላቸዋለሁ። 9 እስራኤል ሆይ በረዳትህ በእኔ ላይ ዓምፀሃልና
ጥፋትህ እየመጣ ነው። 10 በከተማዎችህ ሁሉ ያድንህ ዘንድ ንጉሥህ አሁን ወዴት ነው? ስለ እነርሱ፥ 'ንጉሥና መሳፍንቶች ስጠኝ' ብለህ የተናገርክላቸው፥
ገዢዎችህ ወዴት ናቸው? 11 በቁጣዬ ንጉሥ ሰጠሁህ፥ በመዓቴም አስወገድኩት። 12 የኤፍሬም ክፋት ተደብሮአል፥በደሉም ተደብሮአል። 13 የምጥ ሕመም
ይመጣበታል፥ እርሱ ግን ጥበብ የጎደለው ልጅ ነው፤ ምክንያቱም የሚወለድበት ጊዜ ቢደርስም ከማኅጸን አይወጣም። 14 በእርግጥ ከሲዖል ኃይል
አድናቸዋለሁን? በእርግጥ ከሞትስ አድናቸዋለሁን? ሞት ሆይ መቅሰፍቶችህ ወዴት አሉ? ወደዚህ አምጣቸው። ሲዖል ሆይ ማጥፋትህ ወዴት አለ? ወደዚህ
አምጣው። ርህራሄ ከዓይኖቼ ተሰወረ። 15 ኤፍሬም በወንድሞቹ መካከል ባለጸጋ ቢሆንም እንኳን፥ የምሥራቅ ነፋስ ይመጣል፤ የእግዚአብሔር ነፋስ ከምድረ
በዳ ይነፍሳል። የኤፍሬም ምንጭ ይደርቃል፥ ጉድጓዱም ውኃ አይኖረውም። ጠላቱ የተከበሩ ዕቃዎች ሁሉ ያሉበትን ግምጃ ቤቱን ይበዘብዛል። 16 በአምላኳ ላይ
ዐምፃለችና ሰማሪያ በደለኛ ትሆናለች። በሰይፍ ይወድቃሉ፥ ብላቴኖቻቸውም ይከሰከሳሉ፥ እርጉዝ ሴቶቻቸውም ይቀደዳሉ።

Hosea 13:1

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ እየተናገረ ነው

ፍሬም ሲናገር
ሆሴዕ "ኤፍሬም" የሚለውን ቃል የተጠቀመው፣ ምንም እንኳን ከአስሩ ነገዶች የአንዱ ስም የነበረ ቢሆንም፣ መላውን የሰሜን መንግሥት ለማመልከት ነው። ሆሴዕ እንደ አሁኑ ጊዜ ሳይሆን የሰሜኑ መንግሥት ጠንካራ እና የተከበረ ስለነበረበት ስለ ቆየ የጥንት ዘመን የሚናገር ይመስላል። (ስኔቲክ/ዘይቤያዊ አነጋገር- የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውም ይመልከቱ)

መንቀጥቀጥ ነበር
ህዝቡ ይንቀጠቀጥ እንደነበር ይታወቃል ምክንያቱም ኤፍሬምን ይፈሩት ነበር። ይህ በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "በህዝቡ መሃል መንቀጥቀጥ ነበር" ወይም "ሰዎች በፍርሃት ይንቀጠቀጡ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ራሱን በእስራኤል አላቀ
እዚህ ስፍራ "አላቀ" ማለት ራስን ጠቃሚ አድርጎ ማሳየት ማለት ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን በዓልን በማምለክ ጎጢአተኛ ሆኖ ተገኘ፣ ሞተም
የኤፍሬም ሰዎች በዓልን ምማለክ ሲጀምሩ፣ ደካሞች እየሆኑ ይመጣሉ፤ ጠላቶቻቸውም ያሸንፏቸዋል። እዚህ ስፍራ "ሞተ" የሚለው የሚያመለክተው አገሪቱ እየደከመች መምጣቷን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አሁን በደላቸው እየጨመረ ሄደ
እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው የሚያመለክተው የኤፍሬምን ምሳሌነት የተከተሉትን የኤፍሬምን ነገድ እና መላውን የእስረኤል አገር ነው

እነዚህ ለጣኦት መስዋዕት የሚያቀርቡ ሰዎች ጥጃዎቹን ይስማሉ
የጣኦት አምልኮ አንዱ ክፍል የተቀረጸውን የጥጃ ጣኦት ምስል መሳም ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 13:3

ስለዚህ እንደ ማለዳ ደመና ይሆናሉ... እንደ ጤዛ...እንደ ገለባ.. ከምድጃ እንደሚወጣ ጢስ
እነዚህ አገላለጾች እስራኤል ያህዌን ከማለክ ይልቅ ጣኦት ማምለኩን የሚቀጥል ከሆነ ጊዜያዊ እና በቶሎ የሚጠፋ መሆኑን ያሳያሉ። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ በነፋስ የሚነዳ ነው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ነፋስ ነድቶ የሚወስደው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 13:4

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ህዝቡን በበረሃ የሚንከራተት የበግ መንጋ እንደሆኑ አድርጎ እየተናገረ ነው። እነርሱን በዚያ ስፍራ የኔ ናቸው እንዳለ እየተናገረ ነው።

በበረሃ ሳለህ አውቅሁህ
ያህዌ ዕብራውያንን የራሱ ምርት ህዝብ እንደሆኑ እና እንደ ሚንከባከባቸው ይናገራል።

መሰማሪያ ባገኛችሁ ጊዜ ትረካላችሁ
በበጎች ተምሳሌት የሚነገረው አገላለጽ ቀጥሏል

ልባችሁ ከፍ አለ
ማን አለብኝነት ልብን ከፍ በማድረግ ተገልጽዋል። "ኮራህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 13:7

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ እየተናገረ ነው

እንደ አንበሳ... እንደ ነበር... እንደ ድብ... አንበሳ ይመስል...እንደ ዱር አውሬ
እነዚህ ሌሎችን እንስት የሚያጠቁና የሚገድሉ የዱር እንስሳት ናቸው። ያህዌ ህዝቡን በጎጢአታቸው ምክንያት እንደሚያጠፋቸው መናገሩን ቀጥሏል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ልጇቿን/ግልገሎቿን እንደ ተቀማች ድብ
"ታጠቃለች" የሚለው ቃል የተተወው በውስጠ ታዋቂነት የታወቀ ስለሆነ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ድብ ልጆቿን የወሰደባትን እንስሳ እንደምታጠቃ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኢሊፒሲስ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አንበሳ ይመስል
"ይበላቸዋል" የሚለው የተተወው በውስጠ ታዋቂነት የታወቀ ስለሆነ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንበሳ እንደሚበላቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኢሊፒሲስ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 13:9

አጠቃላይ መረጃ:
አጠቃላይ መረጃ:

ማን ሊረዳህ ይችላል?
ያህዌ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው የእስራኤልን ህዝብ ማንም ሊረዳው እንደማይችል ለማጉላት ነው። "ማንም ሊረዳህ የሚችል የለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለው ይመልከቱ)

በከተሞቻችሁ ሁሉ ውስጥ ሊያድናችሁ የሚችል ንጉሣችሁ አሁን የት አለ? 'ንጉስ እና ልዑል ስጠኝ' ብላችሁ እኔን የጠየቃችኋቸው መሪዎቻችሁ የት አሉ?
ያህዌ እነዚህን ጥያቄዎች የሚጠይቃቸው እስራኤላውያን በእርሱ ላይ ሲያምጹ ማንም ንጉሥ ወይም መሪ ሊያድናቸው እንደማይችል ሊነገራቸው ነው። ከጥፋት ሊያድናቸው የሚችለው ያህዌ ብቻ ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 13:12

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ እየተናገረ ነው

የኤፍሬም በደል ተከማችቷል፣ ኀጢአቱም ሞልቷል
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ናቸው፤ትረጉማቸውም በመሰረታዊነት አንድ አይነት ነገር ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ)

ሞልቷል/ተከማችቷል
የሰሜኑ መንግት ሀጢአት እና በደል ለጉዳይ ሊጠበቅ እንደሚችል ቁሳዊ አካል እንደሆኑ ተደርጎ ቀርቧል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ልጅ የመውለድ ምጥ አይነት ስቃይ በእርሱ ላይ ይመጣል
እዚህ ስፍራ ያህዌ የእስራኤል ህዝብ ሊደርስበት ያለውን መከራ ልጅ ሲወለድ ሴት ያለባትን የምጥ ስቃይ ያህል እንደሆነ ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን እርሱ ብልህ ያልሆነ ልጅ ነው፣ የመወለድ ሰአት በደረሰ ጊዜ፣ ከማህጸን አይወጣም
አሁን ያህዌ የእስራኤልን ህዝብ የሚገልጸው እናት እንደምትወልደው ህጻን ነው። ህጻኑ ብልህ አይደለም ምክንያቱም ለመወለድ አልፈለገም። ህዝቡ ንስሃ ሊገባ እና ያህዌን ሊታዘዝ አልፈለገም። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 13:14

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ እየተናገረ ነው

ከሲኦል እጅ አድናቸዋለሁን? ከሞት እታደጋቸዋለሁን?
ያህዌ እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመባቸው ለእስራኤል ህዝብ ከመሞት እንደማያድናቸው ሊነግራቸው ነው። በእርግጥ ይቀጣቸዋል። "በእርግጥ ከሞትና ወደ ሲኦል ከመውረድ አላድናቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሞት ሆይ መቅሰፍትህ የት አለ? ሲኦል ሆይ ጥፋትህ ወዴት አለ?
ሰዎች የሆኑ ያህል፣ ያህዌ ለ"ሞት" እና "ሲኦል" እየተናገረ ነው። ያህዌ ጥያቄዎቹን የተጠቀመባቸው ሰዎቹን በቶሎ እንደሚያጠፋቸው ለመናገር ነው። "የእስራኤል ሰዎች እንዲሞቱ አሁን መቅሰፍትን አደርጋለሁ። አጠፋቸዋለሁ ደግሞም ወደ ሲኦል እልካቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ፣ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከዐይኖቼ ርህራሄ ተሰውሯል
ርህራሄ እንዳለ እንዳያስቡ ርህራሄ እንደሚደበቅ ነገር ተደረጓ ተገልጽዋል፣ ስለዚህም ሊታይ አይችልም። ረቂቅ ስም የሆነው "ርህራሄ" ከገላጭ ጋር ሊተረጎም ይችላል። "እኔ ለእነርሱ ርህራሄ የለኝም" ወይም "እኔ ለእነርሱ ርህሩህ አልሆንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

Hosea 13:15

አጠቃላይ መረጃ:
ነቢዩ ሆሴዕ እየተናገረ ነው

ወንድሞቹ
ይህ አገላለጽ በሰሜን መንግሥት ዙሪያ ለሚገኙ አገራት፣ በተለይ የደቡብ መንግሥት ለሆነው ለይሁዳ የቆመ ይመስላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የምስራቅ ነፋስ፣ የያህዌ ነፋስ ይመጣል
ከምስራቅ የሚመጣ ነፋስ በጣም ሞቃት እና አጥፊ ነበር። እዚህ ስፍራ ያህዌ የእስራኤልን ሰዎች እንዲየጠፉ ከምስራቅ የሚልካቸውን ወታደሮች ያመለክታል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የኤፍሬም ምንጮች ይደርቃሉ፣ ጉድጓዶቹም ውሃ አይኖራቸውም
ሆሴዕ እግዚአብሔር እንዴት የእስራኤልን ሰዎች እንደሚቀጣ መግለጹን ይቀጥላል። እዚህ ስፍራ ውሃ ህይወትን፣ ጥንካሬን እና ብርታትን ይወከወላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ ግምጃ ቤት
ይህ ሁሉንም የህዝቦች ሃብት ያመለክታል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 13:16

አጠቃላይ መረጃ:
ነቢዩ ሆሴዕ እየተናገረ ነው

በአምላኳ ላይ አምጻለችና ሰማሪያ ኀጢአተኛ ትሆናለች
እዚህ ስፍራ "ሰማርያ" የሚለው በእግዚአብሔር ላይ በማመጽ ሀጢአተኛ የሆኑትን በከተማይቱ የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታል። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ይወድቃሉ
እዚህ ስፍራ "ይወድቃሉ" የሚለው መሞትን ይወከወላል። (ዩፊምዝም/ የማያስድትን ቃለ ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

በሰይፍ
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚለው የሚወክለው በጦርነት ጊዜ ሰይፍ የሚይዙ የጠላት ወታደሮችን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ትንንሽ ልጆቻቸው ተደፍጥጠው ቁርጥራጭ ይደረጋሉ፣ ነብሰጡር ሴቶቻቸው በገሃድ ይደፈራሉ
እነዚህ ሀረጋት በአድርጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፉ ይችላሉ። "ጠላት ትንንሽ ልጆቻቸውን ደፍጥጠው ይቆራርጣሉ፣ ነብሰ ጡር ሴቶችን በገሃድ ይደፍራሉ"

በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 14

1 እስራኤል ሆይ ከክፋትህ የተነሳ ወድቀሃልና ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ተመለስ። **2** የኑዛዜ ቃላት ያዝና ወደ እግዚአብሔር ተመለስ። እንዲህም በሉት፦«የከንፈሮቻችንን ፍሬ ምስጋናችንን እንሰዋልህ ዘንድ፤ክፋታችንን አስወግድ፥በቸርነትም ተቀበለን። **3** አሦር አያድነንም፤ ለጦርነትም ፈረሶችን አንጋልብም። ወይም ከእንግዲህ የእጆቻችንን ሥራዎች 'እናንተ አምላኮቻችን ናችሁ' አንላቸውም፤ አባት አልባው እንኳ በአንተ ዘንድ ርኅራኄን ያገኛልና። **4** ከተውኝም በኋላ ወደ እኔ በተመለሱ ጊዜ እፈውሳቸዋለሁ፤ እንዲያው እወዳቸዋለሁ፥ ቁጣዬ ከእርሱ ተመልሶአልና። **5** እኔ ለእስራኤል እንደ ጠል እሆናለሁ፤ እንደ አበባ ያብባል፥ እንደ ሊባኖስም ዝግባ ሥር ይሰዳል። **6** ቅርንጫፎቹ ይዘረጋሉ፤ ውበቱ እንደ ወይራ ዛፎች፥ ሽታውም እንደ ሊባኖስ ዝግባዎች ይሆናል። **7** ከጥላው በታች ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ይመለሳሉ፤እንደ እህል ይለመልማሉ፥ እንደ ወይንም ያብባሉ።ዝናውም እንደ ሊባኖስ ወይን ጠጅ ይሆናል። **8** ኤፍሬም፦ 'ከእንግዲህ ከጣዖታት ጋር ምን አለኝ?' ይላል። እኔ እመልስለታለሁ፥እጠነቀቅለታለሁም። እኔ ቅጠሎቹ ሁል ጊዜ ለመለም እን ደሆኑ እንደ ጥድ ነኝ፤ ፍሬህም ከእኔ ይመጣል።» **9** እነዚህን ነገሮች ያስተውል ዘንድ ጠቢብ የሆነ ማን ነው? ያውቃቸው ዘንድ እነዚህን ነገሮች የሚያስተውል ማን ነው? የእግዚአብሔር መንገዶች ትክክል ናቸው፥ ጻድቃንም ይሄዱባቸዋል፥ ዓመፀኞች ግን ይሰናከሉባቸዋል።

Hosea 14:1

አጠቃላይ መረጃ:
ነቢዩ ሆሴዕ እየተናገረ ነው

በኀጢአታችሁ ምክንያት ወድቃችኋል
ሃጢአት መስራት እዚህ ስፍራ የተገለጸው መውደቅ እንደሆነ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ቃላቶቻችሁን ይዛችሁ
ይህ ምናልባት በንስሃ የመመለስ እና የውዳ ቃላት ማለት ሊሆን ይችላል። "ኀጢአታችሁን ተናዘዙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የከንፈሮቻችን ፍሬ
አንድ ሰው የሚናገረው የከንፈሩ ፍሬ ይባላል። ዘመናዊ ቅጆዎች ለዚህ አስቸጋሪ ምንባን የተለያዩ ትርጉሞች አሏቸው። "ቃሎቻችን እና የውዳሴ ዝማሬዎቻችን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 14:3

አጠቃላይ መረጃ:
ሆሴዕ እየተናገረ ነው

ለእጆቻችን ስራ
እዚህ ስፍራ ሰዎች ነገሮችን የሚሰሩ ሰዎችን ለማመላከት በ"እጆቻቸው" ተወክለዋል። "ለሰራናቸው ጣኦታት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲኪ/ ዘይቤያዊ አነጋጋር- የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ።)

አባት የሌለው ሰው
ይህ አገላለጽ ምናልባት ለመላውን አገር የሚወክል ይሆናል። ይህ የእግዚአብሔርን ታላቅ ርህራሄ ያመለክታል

ርህራሄ ማግኘት
እዚህ ስፍራ የእግዚአብሔር የርህራሄ ስራ አንድ ሰው በአከል አግኝቶት እንደ ሚለማመደው ነገር ተገልጽዋል። "ርህራሄ" የሚለው ረቂቅ ስም ከገላጭ ጋር ሊተረጎም ይችላል። "ርህራሄ ያለውን ማግኘት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 14:4

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ እየተናገረ ነው እኔ መሸሻቸውን እፈውሳለሁ/አስቀራሉ ህዝቡ ከእግዚአብሔር መሸሹን ማስቆም የተገለጸው እርሱ እንደሚፈውሳቸው ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእነርሱ ፊታቸውን ማዞር
የህዝቡ እግዚአብሔርን አለመታዘዝ የተገለጸው በአካል ከእርሱ ፊታቸውን እንዳዞሩ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ለእስራኤል እንደ ጤዛ እሆናሉ፤ እርሱም ውብ አበባ ይሆናል።
እግዚአብሔር እዚህ ስፍራ የተገለጸው ለተክሎች ተፈላጊውን እርጠበት እንደሚሰጥ ጤዛ ሲሆን፣ እስራኤል አንድ ሰው እንደሆነና እንደሚፈካ አበባ ሆኖ ቀርቧል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

እንደ ሊባኖስ ዝግባ ስር ይሰዳል
እዚህም ስፍራ እንደ ተክል የቀረበው የእስራኤል ስዕል ቀጥሏል፣ በዚህ ጊዜ ግን እስራኤል ሊባኖስ እንደምትታወቅበት እንደ ረጅም የዝግባ ዛፍ ቀርቧል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በሊባኖስ እንደሚገኝ ዝግባ ... ስሮቹ ይዘረጋሉ
ምንባቡ በተመሳሳይ ምስል ይቀጥላል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 14:7

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ እየተናገረ ነው

በጥላው ስር የሚኖረው ህዝብ ይመለሳል
የእስራኤል ህዝብ ዳግም አንደገና በእግዚአብሔር ተጠብቆ ይኖራል። እስራኤል በጥላው ስር እንደምትኖር ተገልጽዋል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ዳግም እንደ እህል ይለመልማሉ እንደ ወይን ተክል ያብባሉ
የእስራኤል አዲሱ ብልጽግናዋ በእርሻ/ግብርና ቃላት ተገልጽዋል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዝናው እንደ ሊባኖስ ወይን ይሆናል
የሊባኖስ ወይን ታዋቂ እንደነበረ ሁሉ፣ እስራኤልም ታዋቂ ይሆናል። "በየስፍራው ያሉ ህዝቦች ስለ እስራኤል ያውቃሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በጣኦታቱ ላይ ሌላ ምን ተጨማሪ ነገር ማድረግ ይኖርብኛል?
ይህ የንባብ ክፍል የሚያጎላው ከዚህ ወዲያ የእስራኤል ህዝብ ጣኦት አምላኪነቱን እንደማይቀጥል ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሌም ቅጠሉ አረንጓዴ የሆነ ዝግባ
ዝግባ አመቱን በሙሉ ቅጠሉ አረንጓዴ የሆነ ዛፍ ነው። ይህ የሚወክለው የያህዌ ለእስራኤል ያለውን በረከት ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የአንቺ ፍሬ ከእኔ የሚመጣ ነው
እዚህ ስፍራ "ፍሬ" የሚወክለው ከያህዌ የሚመጣውን ማናቸውንም መልካም ነገር ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 14:9

አጠቃላይ መረጃ:
ነቢዩ ሆሴዕ እየተናገረ ነው

እነዚህን ነገሮች የሚረዳ ብልህ እርሱ ማን ነው? ያውቃቸው ዘንድ እነዚህን ነገሮች ማን ይረዳል?
ነቢዩ እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመባቸው ብልህ ህዝብ ይረዳል ደግሞም የተነገረውን ይሰማል ለማለት ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

የያህዌ መንገዶች ትክክል ናቸው፣ ጻድቁም በእነርሱ ይሄዳል
የያህዌ ትዕዛዛት የተገለጹት እንደሚሄዱባቸው መንገዶች ተደርገው ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Joel

Joel

Chapter 1

1 ወደ ባቱኤል ልጅ ወደ ኢዩኤል የመጣው የእግዚአብሔር ቃል ይህ ነው። 2 እናንተ ሽማግሌዎች ይህን ስሙ፤በምድሪቱም የምትኖሩ ሁላችሁ አድምጡ። ይህ፥ከዚህ በፊት በእናንተ ወይም በአባቶቻችሁ ዘመን ሆኖ ያውቃልን? 3 ይህንን ለልጆቻችሁ ንገሩ፥ልጆቻችሁም ለልጆቻቸው ይንገሩ፥የእነርሱም ልጆች ለሚቀጥለው ትውልድ ይንገሩ። 4 ከአንበጣ መንጋ የተረፈውን ትላልቁ አንበጣ በላው፥ከትልቁ አንበጣ የተረፈውን ፌንጣ በላው፥ ከፌንጣ የተረፈውን አባ ጨጓሬ በላው። 5 እናንተ ሰካራሞች ተነሡና አልቅሱ! አዲሱ የወይን ጠጅ ከአፋችሁ ተወግዶአልና እናንተ የወይን ጠጅ ጠጪዎች ዋይ በሉ። 6 ቁጥር የሌለው ሕዝብ በምድሬ ላይ መጥቶአልና። ጥርሶቹ የአንበሳ ጥርሶች ናቸው፤የሴት አንበሳም ጥርሶች አሉት። 7 የወይን ቦታዬን አስደንጋጭ ስፍ ራ አደረገው፤የበለስ ዛፌን መልምሎ ባዶውን አስቀረ። ቅርፊቱን ላጠው፥ጣለውም፤ቅርንጫፎቹም ነጡ። 8 ለልጅነት ባሏ ሞት ማቅ እንደ ለበሰች ድንግል አልቅሱ። 9 የእህሉ ቁርባንና የመጠጡ ቁርባን ከእግዚአብሔር ቤት ተወግዷል፤የእ አብሔርም አገልጋዮች ካህናቱ አለቀሱ። 10 እርሻው ጠፍቷል፥ምድሪቱም አለቀሰች። እህሉ ወድሟል፥አዲሱ ወይን ደርቋል፥ዘይቱም ተበላሽቷል። 11 እናንተ ገበሬዎችና የወይን አትክልተኞች ስለ ስንዴዉና ስለ ገብሱ እፈሩ። የእርሻው መከር ጠፍቷልና። 12 ወይኑ ጠውልጓል፥የበለስም ዛፎች ደርቀዋል፤የሮማን፥የተምርና የእንኮይ ዛፎች፥የእርሻው ዛፎች ሁሉ ጠውልገዋል። ደስታም ከሰው ልጆች ርቋል። 13 የእህሉ ቁርባንና የመጠጡ ቁርባን ከአምላካችሁ ቤት ተቋርጧልና፥እናንተ ካህናት ማቅ ለብሳችሁ አልቅሱ! ፥እናንተ የመሠዊያው አገልጋዮች ዋይ በሉ። እናንተ የአምላኬ አገልጋዮች ኑ ሌሊቱን በሙሉ ማቅ ላይ ተኙ። 14 ቅዱስ ጾም አውጁ፥የተቀደሰም ጉባዔ ጥሩ። ሽማግሌዎችንና በምድሪቱ የሚኖሩትን ሁሉ ወደ አምላካችሁ ወደ እግዚአብሔር ቤት ሰብስቡ፤ወደ እግዚአብሔርም ጩኹ። 15 የእግዚአብሔር ቀን ደርሷልና፥ወዮ ለዚያ ቀን! ከእርሱ ጋር ጥፋት ሁሉን ከሚችል አምላክ ይመጣል። 16 ምግብ ከዓይናችን ፊት፥ ደስታና ሐሴት ከአምላካችን ቤት አልተወገደምን? 17 ዘሩ በምድር ውስጥ በስብሷል፤እህሉ ደርቋልና ጎተራዎቹ ባዶ ሆነዋል፥ጎታዎቹም ፈርሰዋል። 18 እንስሳት ምንኛ ጮኹ! መሰማሪያ የላቸውምና የቀንድ ከብት መንጎች ተሰቃዩ። የበግ መንጎችም ተሰቃዩ። 19 እሳቱ የምድረ በዳውን ማሰማሪያ በልቷልና፥ነበልባሉም የጫካውን ዛፎች ሁሉ አቃጥሎአልና፤እግዚአብሔር ሆይ ወደ አንተ እጮሃለሁ። 20 ጅረቶች ሁሉ ስለደረ ቁና እሳ ት የምድረ በዳውን ማሰማሪያ ስለ በላው፥የዱር እንስሳት እንኳን ወደ አንተ አለኽልኹ።

Joel 1:1

አጠቃላይ መረጃ
እግ/ር በሥነ-ግጥም በኢዮኤል በኩል ለእስራኤል ይናገራል

ወደ ኢዮኤል የመጣዉ የእግዚአብሔር ቃል
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር እግዚአብሔርለኢዮኤል የሰጠዉን መልዕክት ለማወጅ ነዉ። ተርጓሚ " እግዚአብሔር (ያህዌ) ለኢዮኤል የሰጠዉ መልዕክት " ወይም "እግዚአብሔር ለኢዮኤል የተናገረዉ መልዕክት " (ፈሊጣዊ ተመልከት)

ያህዌ
ይህ ስም በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር እራሱን ለህዝቡ የገለጠበት ነዉ። (በትርጉም ገፅ ላይ ያህዌ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት)

ባቱኤል
የኢዮኤል አባት (የስም ትርጉም ተመልከት)

ይህ በዘመናችሁ ወይስ በአባቶቻችሁ ዘመን ሆኖ ነበርን?
ኢዮኤል ማለት ያለበትን እንዳያደምጥ ሽማግሌዎችን እያዘጋጀ ነዉ። ይህ በዚህ መልኩ ሊተረጎም ይችላል ተርጓሚ "እንደዚህ አይነት ነበር ፈፅሞ በእናንተም በአባቶቻችሁ ላይ ሆኖ አያዉቅም (የግነት ጥያቄን ተመልከት)

ልጆቻችዉም ለኋለኛዉም ትዉልድ
የጎደሉትን ቃላት መሙላት ይኖርብህ ይሆናል። ተርጓሚ "ልጆቻችዉ ከእነርሱ በኋላ ላሉት ትዉልድ ይንገሩ "

Joel 1:4

የአንበጣ መንጋ
ብዛት ያለዉ የነፍሳት ቁጥር (ቡድን) በአንድ ላይ የሚበር በሰፊ ማሳ ላይ ያለን እህል የሚበላና እንደ ፌንጣ የሆነ ብዛት ያለዉ የነፍሳት ቡድን።

የአንበጣ መንጋ :ትልቁ አንበጣ : ፌንጣ : አባጨጓሬ
በቅድመ ተከተል እነዚህ መብረር የሚችል ትልቅ አንበጣ፣በጣም ትልቅና መብረር የሚችል አንበጣ፣ ክንፍ ያለዉ አንበጣ ነገር ግን በጣም ትንሽ እና ገና የተወለደና ክንፍ የሌለዉ አንበጣ ናቸዉ። (የሚመችህ ስም ተጠቀም)

Joel 1:5

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔርስለ ሚመጣዉ የአንበጣ ሰራዊት (መንጋ) እስራኤልን ያስጠነቅቃል።

እናንተ ሰካራሞች ነቅታችሁ አልቅሱ፤ እናንተም የወይን ጠጅ የምትጠጡ ሁሉ ዋይ በሉ
ለ"ለቅሶና"ዋይታ" አንድ ቃል ብቻ መጠቀም ይቻላል። "እናንተ ወይን የምትወዱ ህዝብ ወይ መራራ ለቅሶን ማልቀስ አለባችሁ።"

ሕዝብ
የአንበጣ መንጋ እን ወረራ ሠራዊት ነዉ። (ዘይቤ ተመልከት)

ጥርሱ..... ጥርስ አለዉ .....አደረገ..... ስንበር /መስመር/ አለዉ
አንበጣዎች እንደ አሕዛብና እንደ አንደ ግለሰብ ናቸው። አሕዛብን ለመግለፅ "እሱ" ወይም ለአንበጣዎች ደግሞ "እነሱ" ወይም ለወራሪዎች እንደ አንድ ግለሰብ ብሎ መጠቀም ይቻላል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጥርሱ **(**ጥርሳቸዉ**)** እንደ አንበሳ ጥርስ መንጋጋቸዉም አንደ እንስቲቱ አንበሳ መንጋጋ ነዉ።
እነዚህ ሁለት መስመሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸዉ የአንበጣዎች ጥርስ እንደ አንበሳ ጥርስ የሳለ ሲሆን ጥርስ የሚያሳየዉ ምን ያህል ፈጣን እንደሆኑና (በማሳ) በምድር ያለን ሰብል እንዴት እንደሚበሉ ለማሳየት ነዉ።

በምድሬ .....ወይኔን .....በለሴንም
የያህዌ ምድር የወይንና የበለስ ምድር ነዉ።

ባዶ
ባዶና ምንም ሕይወት የሌለበት ።

Joel 1:8

(መሬት**)** ምድር አዘነች
ይህ ምድር (መሬት) በሰዉ ተመስላ ነዉ። እነዚህ ቃላት ለሚያዝኑ ህዝቦች እንደ ዘይቤያዊ ንግግር ወይም ከረሀቡ የተነሳ ግዑዝ ነገር እንኳን እዳዘነ ለማሳየት ነዉ። ተርጓሚ - አርሶ አደሮች አዘኑ (ያዝናሉ)። (ፈሊጣዊ ዘይቤ ተመልከት)

እህሉ ጠፍቷልና
ይህ በገቢር ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ - አንበጣዎቹ ሰብሉን ሁሉ አወደሙት

Joel 1:11

ገብስ
እንደስንዴያለየሳእህልሲሆንዳቦ(እንጀራ) ለመጋገርያገለግላል።

ጠውልጎአል
የደረቀናየሞተ

በለስ.....ሮማን .....ቴምር
የተለያዩአይነትፍራፍሬዎች

Joel 1:13

የእህሉ ቁርባንና የመጠጡ ቁርባን
በቤተ - መቅደስውስጥየዘወትርቁርባን (መስዋዕት)

ከአምላካቸው ቤት
በኢሩሳሌምየሚገኝቤተ - መቅደስ

Joel 1:15

እርሱም ሁሉን ከሚችል ከአምላካቸው ዘንድ እንደጥፋት ይመጣል
ጥፋትየሚለውረቂቅስምመጥፋትበሚለውግስሊተረጎምይችላል።
ሁሉንየሚችለውአምላክምንእንደሚያጠፋበግልጽማስቀመጥይችላል።
ተርጓሚ“በዚያንቀንሁሉንየሚችልአምላክጠላቶቹንያጠፋል” (ረቂቅስምተመልከት)

ከአይናችን ፊትምግብ ከአምላካችንም ቤትደስታና እልልታ የጠፋአይደለምን?
እነዚህ ነገሮች ከመሆናቸው
የተነሳጥፋትሁሉንከሚችልአምላክዘንድእንደሚወጣየታወቀነው።
ይህበገቢርመልኩሊተረጎምይችላል ።
ተርጓሚ“ሁሉንየሚችልአምላክየምግብአቅርቦታችንናየደስታችንእልልታችንከእግዚአብሔርቤትስላስቀ

ከአይናችን ፊት
“ከእኛ”- ይህ ቃልሁሉንም የእስራኤል ህዝብይወክላል።

ከአምላካችንቤትደስታናእልልታ
በጎደለው ቦታ መሙላት ትችላለህ።ተርጓሚ - “ደስታና እልልታ ከእግኢአብሔር ቤት ቀርቷል”

ደስታና እልልታ
በመሰረቱ ሁለቱ ቃላት ትርጉምአላቸው።
በአንድላይምንምየሚያስደስትነገርእንደሌለለማሳየትነው።

በሰበሰ**(** ጓል**)**
የብስባሽ

Joel 1:18

እጅግመጮህ
በህመምየተነሳበጣምመጮህ

ፈሳሹውሃ
መለስተኛ ጅረት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 በጽዮን መለከት ንፉ፥ በቅዱስ ተራራዬም ላይ የማስጠንቀቂያ ድምጽ አሰሙ! የእግዚአብሔር ቀን መጥቷልና፥በእርግጥም ቅርብ ነውና፤የም ድሪቱ ነዋሪዎች
ሁሉ በፍርሃት ይንቀጥቀጡ። 2 እርሱም የጨለማና የጭጋግ ቀን፥የደመናና የድቅድቅ ጨለማ ቀን ነው። ንጋት በተራሮች ላይ እንደሚዘረጋ፥ታላቅና ኃያል ሠራዊት
እየመጣ ነው። እርሱን የመሰለ ሠራዊት ከቶ አልነበረም፥ከብዙ ትውልድ በኋላ እንኳን ዳግመኛ አይኖርም። 3 በስተፊቱ እሳት ሁሉን ነገር ይበላል፥በስተኋላውም
ነበልባል ይንቦገቦጋል። በስተፊቱ ምድሪቱ የዔደን ገነትን ትመስላለች፥በስተኋላው የሚገኘ ው ግን ባዶ ምድረ በዳ ነው።በእርግጥ፥ምንም ከእርሱ አያመልጥም።
4 የሠራዊቱ ገጽታ እንደ ፈረስ ነው፥እንደ ፈረሰኛም ይሮጣሉ። 5 በተራሮች ራስ ላይ እንደሚሄድ የሰረገላ ድምጽ፥ገለባውን እንደሚበላ የእሳት ነበለባል ድምጽ
እያሰሙ፥ ለጦርነት እንደ ተዘጋጀ ኃያል ሠራዊት ያኮበኩባሉ። 6 በፊታቸው ሰዎች ይታወካሉ፥የሁሉም ፊት ይገረጣል። 7 እንደ ብርቱ ተዋጊዎች ይሮጣሉ፥እንደ
ወታደሮችም በቅጥሩ ላይ ይዘላሉ፤እያን ዳንዱ እርምጃውን ጠብቆ ፥ሰልፋቸውንም ሳያፈርሱ፤ ይተማሉ። 8 እያንዳንዱ መንገዱን ይሄዳል፥እርስ በእርሳቸው
ሳይገፋፉ ይተማሉ፤ምሽጎችን ሰብረው ያልፋሉ፥ነገር ግን ከመስመራቸው አይወጡም። 9 ከተማን በድንገት ያጠቃሉ፥በቅጥር ላይ ይሮጣሉ፥ቤቶች ላይ
ይወጣሉ፥እንደ ሌቦችም በመስኮቶች ያልፋሉ። 10 ምድር በፊታቸው ትንቀጠቀጣለች፥ሰማያትም ይናወጣሉ፥ ፀሐይና ጨረቃም ይጨልማሉ፥ከዋክብትም
ማብራታቸውን ያቆማሉ። 11 ተዋጊዎቹ እጅግ ብዙ ናቸውና፥ትእዛዙን የሚፈጽሙ ኃያላን ናቸውና፤ እግዚአብሔር በሠራዊቱ ፊት ድምጽን ያሰማል። የእግዚአብሔር
ቀን ታላቅና የሚያስፈራ ነውና፤ ማን ሊቆም ይችላል? 12 «አሁንም እንኳን» ይላል እግዚአብሔር፥«በፍጽም ልባችሁ ወደ እኔ
ተመለሱ፤ጹሙ፥አልቅሱ፥እዘኑም።» 13 ልብሳችሁን ብቻ ሳይሆን ልባችሁንም ቅደዱ፤ ወደ አምላካችሁም ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ። እርሱ ቸርና
መሐሪ፥ለቁጣ የዘገየ፥ፍቅሩ የተትረፈረፈ ነውና፤ስቃይ ካለብት ከዚህ ቅጣት መመለስ ይፈልጋል። 14 ምናልባት ይመለስና ይራራ እንደሆነ፥ለአምላካችሁ
ለእግዚአብሔር የእህል ቁርባንና የመጠጥ ቁርባን የሚሆን በረከት በስተኋላው ያተርፍ እ ንደሆነ ማን ያውቃል? 15 በጽዮን መለከት ንፉ፥የተቀደሰ ጾም አውጁ፥
የተቀደሰም ጉባዔ ጥሩ። 16 ሕዝቡን ሰብስቡ፥የተቀደሰ ጉባዔ ጥሩ። ሽማግሌዎችን፥ልጆችን፥ የሚጠቡትንም ሕጻናት ሰብስቡ። ሙሽራው
ከእልፍኛቸው፥ሙሽራይቱም ከጫጕላ ቤታቸው ይውጡ። 17 የእግዚአብሔር አገልጋዮች፥ ካህናቱ፥ በቤት መቅደሱ መግቢያ ደጅና በመሠዊያው መካከል
ያልቅሱ። እንዲህም ይበሉ፦«እግዚአብሔር ሆይ ለሕዝብህ ራራ፥አሕዛብ ይገዙአቸው ዘንድ ርስትህን ለእፍረት አሳልፈህ አትስጥ።በአሕዛብ መካከል
አምላካቸው ወዴት ነው? ስለ ምን ይበሉ።» 18 እግዚአብሔርም ስለ ምድሩ ቀና፥ለሕዝቡም ራራ። 19 እግዚአብሔርም ለሕዝቡ እንዲህ ሲል መለሰ፦«እነሆ፥
እህል፥አዲስ ወይንና ዘይት እልክላችኋለሁ። እናንተም በእነርሱ ትጠግባላችሁ፥ ከእንግዲህም ወዲያ በአሕዛብ መካከል ለውርደት አላደርጋችሁም። 20
የሰሜንን ጥቃት ፈጸሚዎች ከእናተ አርቃለሁ፥ ወደ ደረቅና ወደ ተተወ ምድር እሰድዳቸዋለሁ። የሠራዊቱ ፊተኛ ጦር ወደ ምሥራቅ ባሕር፥ የሠራዊቱ ኋለኛ ጦር
ወደ ምዕራብ ባሕር ይሄዳል። ግማቱ ይውጣል፥ክርፋቱም ይነሳል፤ታላላቅ ነገሮችንም አደርጋለሁ።» 21 እግዚአብሔር ታላላቅ ነገሮችን አድርጓልና፤ ምድር ሆይ
አትፍሪ፥ ደስ ይበልሽ፥ ሐሴትም አድርጊ። 22 የምድር እንስሶች ሆይ፥ የምድረ በዳ ማሰማሪያዎች ለምልመዋልና፥ ዛፎች ፍሬያቸውን አፍርተዋልና፥ የበለስ ዛፎችና
ወይኖች ሙሉ ፍሬያቸውን ሰጥተዋልና፤አትፍሩ። 23 የበልግን ዝናብ እንደሚገባ ይሰጣአችኋልና፥እንደ ቀድሞ ዘመን የበልግ ዝናብንና የፀደይን ዝናብ
ያካፋላችኋልና፤ የጽዮን ሰዎች ሆይ፥ደስ ይበላችሁ፥ በአምላካችሁም በእግዚአብሔር ሐሴት አድርጉ። 24 አውድማዎቹ በስንዴ ይሞላሉ፥መጥመቂያዎችም
አዲስ ወይን ጠጅና ዘይት ያፈስሳሉ። 25 በመካከላችሁ የላኩት ታላቁ ሠራዊቴ፥ የአንበጣ መንጋ፥ ትልቁ አንበጣ፥ ፌንጣና አባ ጮጋሬ የበሏቸውን የምርት
ዓመታት እመልስላችኋለሁ። 26 ተትረፍርፎ ትበላላችሁ፥ ትጠግባላችሁም፤ በመካከላችሁም ተዓምራት ያደረገውን የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ስም
ታመሰግናላችሁ፤ ከእንግዲህም ወዲያ እፍረትን በሕዝቤ ላይ ከቶውኑ አላመጣም። 27 እኔ በእስራኤል መካከል እንዳለሁ፥ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ
እንደሆንኩ፥ ሌላም እንደሌለ፥ ከእንግዲህም ወዲህ እፍረትን በሕዝቤ ላይ ከቶውን እንደማላመጣ ታውቃላችሁ። 28 ከዚያም በኋላ እንደዚህ ይሆናል፦
መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ፥ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ። ሽማግሌዎቻችሁ ሕልም ያልማሉ፥ጎልማሶቻችሁም ራእይ ያያሉ።
29 በእነዚያ ወራት በወንዶችና ሴቶች ባሪያዎች ላይም መንፈሴን አፈሳለሁ። 30 በሰማያት ድንቆችን፥በምድርም ደም፥እሳትና የጢስ ዓምድ አሳያለሁ። 31
ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ከመምጣቱ በፊት፥ ፀሐይ ወደ ጨለማ፥ጨረቃም ወደ ደም ትለወጣለች። 32 የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ ሁሉ
ይድናል። እግዚአብሔር እንደ ተናገርው፥ በጽዮን ተራራና በኢየሩሳሌም የሚያመልጡ ይኖራሉ፤ከትሩፋኑም መካከል እግዚአብሔር የጠራቸው ይገኛሉ።

Joel 2:1

መለከትንንፉ .....እሪበሉ
ኢዮኤልእስራኤልንየመጥራትናለሚመጣውጥፋትማዘጋጀትአስፈላጊነትአፅንኦትእየሰጠነው።

የጨለማናየጭጋግቀን
ጨለማናጭጋግተመሳሳይትርጉምሲኖራቸው ፣
የጨለማውንብርታትለማሳየትናአፅንኦትለመስጠትነው።
ሁለቱምቃላትየጥፋትጊዜንወይምመለኮታዊፍርድንያመለክታሉ። (ዘይቤአዊንግግርተመልከት)

ጭጋግ
በጣምወይምመለስተኛጨለማ

የደመናናየድቅድቅጨለማቀን
ይህሐረግትርጉምአንድሲሆንከመጀመሪያውሐረግጋርአንድአይነትሀሳብአለው።
ልክእንደመጀመሪያሐረግ“ደመናና”እና“ድቅድቅጨለማ” -
መለኮታዊፍርድንያመለክታል (ይወክላል) (ዘይቤአዊንግግርተመልከት)

ታላቅናብርቱሕዝብበተራሮችላይእንደወገግታተዘርግቷል
ንጋትላይየፀሐይብርሃንበቀጥታስትወጣከላይከተራራውአናትጀምራእስከታችኛውየተራራውክፍልትወ
(ሰራዊት) በሰንሰለታማተራራከላይወደታችይወርዳል (ሲወርድ) ተርጓሚ -
ታላቅናብርቱሠራዊት (ህዝብ) ከላይከተራራውወደመሬትይመጣል።
ልክእንደንጋትፀሀይወደምድርይወርዳሉ(ንፅፅርተመልከት)

ታላቅናብርቱህዝብ
ታላቅናብርቱቃላትተመሳሳይትርጉምሲኖራቸውሕዝቡ(ሠራዊቱ)
በጣምጠንካራይሆናሉብሎአፅንኦትለመስጠትነው። ህዝብ(ሠራዊት)
የሚለውቃል

1. በአንበጣመንጋዘይቤአዊንግግርነው።
2. የሠውሰራዊትንለመግለፅነው።

ከሁለቱአንዱንትርጉምሊወስድይችላል።(ዘይቤአዊተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Joel 2:3

እሳትበፊታቸውትባላለች
እሳትበፊቱያገኘውንሁሉያጠፋል ። ብርቱሕዝብም (ሠራዊትም) የሰዎችንምሆነየአንበጣዎችከፊትለፊቱያገኘውንሁሉያጠፋል። (ዘይቤአዊተመልከት)

በኋላቸውምነበልባልታቃጥላለች
የእሳትነበልባልበደረቅምድርላይያገኘውንደረቅናየሚነድነገርባገኘጊዜከሚነደውደረቅ ምድር ይልቅ የተነሳነበልባልይኖራል። (ዘይቤአዊንግግርተመልከት)

ምድሪቱ....እንደኤደንገነት
የኤደንገነትእንደሚያምርምድሩምያምራል።

Joel 2:4

መልካቸው (የህዝቡወይምሠራዊቱ) እንደፈረስመልክነው።
የአንበጣጭንቅላቱእንደትንሽፈረስጭንቅላትነው። ሕዝቡ (ሠራዊቱ) ልክእንደፈረስፈጣንነው። (ንፅፅርተመልከት)

ፈረሶች
ትልቅ፣ ጠንካራናፈጣንባለአራትእግርእንስሳ

እንደፈረሰኞችምይሮጣሉ
ፈረስየሚጋልብሠውፈጣንእንደሆነሁሉሠራዊትበፍጥነትይራመዳል(ንፅፅርተመልከት)

ይሮጣሉ (ይዘላሉ)
ፈረስበፍጥነትሲሄድይሮጣልወይምይዘላል

የሰረገሎችድምጽ.....እንደእሳትነበልባልድምጽ .....ለሠልፍእንደተዘጋጀእንደብርቱሕዝብ
እነዚህድምጾችለኢዮኤልመጽሀፍአንባቢዎችአስፈሪሊሆኑይችላሉ። አንባቢእነዚህንድምጾችመረዳትካልቻለአጠቃላይሐረግተጠቅሞ“ሁሉንምሠውየሚገልጽ

Joel 2:6

እንደኃያላንይሮጣሉእንደሰልፈኞችምበቅጥሩላይይወጣሉ
የአንበጣመንጋልክእንደእውነተኛወታደር (ሰልፈኛ) ነው። (ንፅፅርተመልከት)

ቅጥር
በከተማዙሪያያለቅጥር

Joel 2:8

በሰልፍመካከልያልፋሉ
ሰልፈኞችንይቋቋማሉከተማውንምይታደጋሉ

Joel 2:10

ምድሪቱምከፊታቸውትናወጣለችሰማያትምይንቀጠቀጣሉ
ኢዮኤልምድርናሰማይልክእንደሰውበፍርሃትእንደሚንቀጠቀጡአድርጎያወራል። ይህሠራዊት(ህዝቡ)
በጣምአስፈሪእንደሆኑናግዑዝነገርእንኳንእንደሚፈራአግንኖመተርጎምወይምበምድሪቱላይየሚፈጸሙአስፈሪክስተቶችንመግለጽ። ተርጓሚ - “በምድርናበሰማይያሉሁሉበጣምፈሩ” (ግነትተመልከት)

ፀሐይናጨረቃምይጨልማሉከዋክብትምብርሃናቸውንይሰውራሉ
ከአንበጣውመንጋየተነሳሠዎችፀሐይንጨረቃንወይምከዋክብትንማየትእንደሚሳናቸው (ግነትተመልከት)

እግዚአብሄርም .....ድምጽ ይሰጣል
“እግዚአብሄር ትዕዛዝ ለምስጠት ድምጹን ከፍ አድርጎ ይናገራል ።”

ታላቅና እጅግ የሚያስፈራ
በዚህ ሐረግ ውስጥ ሁለቱም አገላለፆች በመሰረቱ ተመሳሳይናቸው ። ተርጓሚ - “ በእጅጉ የሚያስፈራ”

ማንስ ይችለዋል?
“ይህ እንደ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ - የእግዚአብሔርን ፍርድ ሊቋቋም የሚችል ማንም ብርቱ የሆነ የለም።”

Joel 2:12

በፍጹም ልባችሁ .....ወደ እኔ ተመለሱ
“ልብ” የአንድን ሰው ሐሳብና ፍቅር (ፍላጎት) መግለጫ ዘይቤአዊ ንግግር ነው። ተርጓሚ - “ከኃጢአታቸው ተመለሱና ፈጽሞ ለእኔ የተገዛችሁ ሁኑ” (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

ልባችሁን እነጂ ልባሳችሁን አትቅደዱ
“ልብ” የአንድን ሐሳብና ፍላጎት መግለጫ ዘይቤአዊ ንግግር ነው። ልብስን መቅደድ የአንድ ሰው የመዋረድና የንሰሃ ውጫዊ ድርጊት ነው። ተርጓሚ - “አስተሳሰብህን ለውጥ(ቀይር) ልብሳችሁን ብቻ አትቅደዱ (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)”

ምህረቱም የበዛ
ተርጓሚ - “ሁልጊዜ ለቃሉ የታመነ” ወይም “ዘወትር ፍቅሩ የታመነ”

ተጸጸተ
አቁሙ

Joel 2:14

የሚመለስና የሚፀፀት እንደሆነ .....ለእግዚአብሄር
ይህ እንደ ዐ.ነገር ሊተረጎመም ይችላል ። ተርጓሚ - “ ምናልባት እግዚአብሄር ይመለሳል (ንፅፅርተመልከት)

ለእግዚአብሄር የእህልና የመጠጥ ቁርባን የሚሆን በረከት የሚያተርፍ
“በረከትን አትርፍለት - ይሄውም የእህልና የመጠጥ ቁርባን” በረከቱ የተትረፈረፈ የእህልና ወይን ሲሆን ህዝቡም የእህልና የመጠጥ ቁርባንን ማቅረብ ይችላል።

Joel 2:15

....ከእልፍኙ .....ጫጉላዋ
ሙሽራውና ሙሽራይቱ በቤተሰቦቻቸው ቤት ሀነው የሰርጋቸውን ሥነ- ሥረዓት ሚጠባበቁበት ክፍል ነው።

Joel 2:17

ርስትህን ለማላገጫ አሳልፈህ አትስጥ
“አህዛብ ርስትህን ዋጋ እንደሌለው አድርገው እንዲያዩት አትፍቀድ”

ርስትህ
የእስራኤል ህዝብ የእግዚአብሔር ርስት እደሆነ የሚያይ ነው ። ተርጓሚ- ተመልከት)

ከአህዛብ መካከል አምላካቸው ወዴት ነው ይላሉ?
ይህ እንደ ዓረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ - “አህዛብ ፤ አምላካቸው አይረዳቸውም” ወይም “አህዛብ ፤የእስራኤል አምላክ ህዝቡን ተቶአል ማለት የለባቸውም”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Joel 2:18

ስለምድሩ
“የእስራኤል ህዝብ”

ሕዝቡ
“የእስራኤል ህዝብ”

ተመልከት
“ሊናገር ስላለው ነገር አትኩሮት ስጥ (ስጡ)”

እናንተም በእርሱ ትጠግባላችሁ
“የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ታገጋላቹ”

መሳደቢያ
“የማይገባ ክብር (ክብር ” (ክብር አለመስጠት))

Joel 2:20

የስሜን ..... የምስራቅ ..... የምዕራብ
"እነዚህ አቅጣጫዎች ከእስራኤል ህዝብ አረፋፋር ለማምከት ነዉ "

የምስራቁ ባህር የሙት ባህር የምዕራቡ ባህር የሜድትራንያ ባህር ታላቅ ነገር አድርጌል
ይህ እግ/ር ታላቅ ነገር አድርጌል ወራር ሰራዊት ሌላኛዉ ፀሐፊዉ የሚናገረዉ ትርጉም ሊሆን ይችላል

Joel 2:21

ምድር ሆይ አትፍሪ
ኢዮኤል ለህዝቡ ሲናገር ልክ ለምድር የሚናገር አስመስሎ ነዉ ተርጌሚ "እናንተ የምድር ህዝብ ፤አትፍሩ "

እናንተ የምድር እንስሶች..... አትፍሩ
ኢዮኤል ከብቶች ስላላቸዉ ሲናገር ልክ ለእንስሳቱ ለራሳቸዉ እንደ ሚናገር አድርጎ ነዉ ተርጌሚእናንተ ከብቶች ያላቸሁ ፤አትፍሩ "

የምድር ባዳዉ ማሳማርያ ለምልምአልና
ማሰማሪያ በማሰማሪያ ቦታ ለሚበቅሉ እጽዋት ዘይቤአዊ ንግግር ነው። ተርጓሚ - ለምግብነት የሚውሉ እጽዋት በምድረ በዳው ማሰማሪያ ለምልመዋል ዝናብ አዝንቦላችኋልና “በመልካም (በጥሩ ሁኔታ) እንድትኖሩ ዝናብን ያዝላችኋል”

የፊተኛው ዝናብና.....የኋለኛው ዝናብ
ዝናብ ወቅት መጀመሪያው ዝናብና የዝናብ ወቅት የጭሻው ዝናብ

Joel 2:24

አያያዥ አረፍተ-ነገሮች
እግዚአብሔር ለእስራኤል ረዘም ያለ ንግግር ጀመረ

መጥመቂያዎች
ትልልቅ የፈሳሽ ነገር ማጠራቀሚያ ዕቃ ኩብኩባና ተምች የበላባችሁን አመታት “ለአመታት የተንከባከባችሁትና የአንበጣ መንጋ በላባችሁን ” የአንበጣ መንጋ ....ትልቅ አንበጣ....በሊታው (አጥፊ አንበጣ) በቅደም ተከተል መብረር የሚችለው ትልቅ አንበጣ፣ በቀላሉ መብረር የሚችል ትልቅ አንበጣ፣ ክንፍ ያለው ለመብረር ግን አነስተኛ አንበጣና ገና የተወለደና ክንፍ ሌለው አንበጣ። ለትርጉም አንዱን መጠቀም ይችላል።

ተዓምራትን የሰራውን የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ስም
እግዚአብሔር ስለራሱና ያለውን በእርግጥ እንደሚያደርግ ይናገራል። ተርጓሚ- “.....ታላቅን ስላደረኩ ስሜም...”

Joel 2:28

ከዚህም በኋላ እንዲህ ይሆናል
“ከዚያም በኋላ የማደርገው ይህን ነው”

መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈሳለሁ
እግዚአብሔር ስለመንፈስ ውሃ አስስሎ ይናገራል። ተርጓሚ - መንፈሴን በልግስና ለሥጋ ለባሽ ሁሉ እሰጣለሁ። (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ሥጋ ለባሽ ሁሉ
እዚህ ጋር ሥጋ ለባሽ የሚወክለው ሰዎችን ነው። ተርጓሚ- ሁሉም ሰው (ህዝብ)

Joel 2:30

ደምና እሳት የጢስም ጭጋግ
“ደም” የሰዎች ሞት ተምሳሌት ነው። ተርጓሚ “ሞት፣ እሳትና የጢስም ጭጋግ” (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት) “ፀሐይ ከእንግዲህ ብርሃኑዋን አትሰጥም”

ጭረቃም ወደ ደም
“ደም” የሚለው ቃል ወደ ቀይ ቀለም የሚለውን ይወክላል። ተርጓሚ - “ጨረቃ እንደ ደም ቀይ ሆና ትወጣለች” (ዘይቤኣዊ ንግግርና ንፅፅ ተመልከት)

Joel 2:32

እንዲህም ይሆናል.....ሁሉ
የሚሆነው ይህ ነው። ሁሉም

የእግዚአብሄርን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል
ስም የሚለው ቃል የአንድ አካል ፈሊጣዊ ንግግር ነው። ይህ በገቢር መልኩ ለተረጎም ይችላል። ተርጓሚ እግዚአብሄር ስሙን የሚጠራ ሁሉ ይድናል ። (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልክት)

በጽዮን ተራራ በእየሩሳሌም
ይህ ጠአንድ ቦታ ስም ነው ። ተርጓሚ - “በጽዮን ተራራ ነእየሩሳሌም”

ከቅሪቶቹ እግዚአብሄር የጠራቸው
“ይገኛሉ” የሚለው ቃል ከበፊቱ ዐረፍተ ነገር መረዳት ይቻላል። እዚህ ጋር ሊደገም ይችላል። ተርጓሚ - “ከቅሪቶቹ መካከል እግዚአብሄር የጠራቸው ይኖራሉ።”

ቅሪቶች
በመከራ ለምሳሌ ጦርነትና ጥፋት መካከል የኖሩ (የተረፉ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 እነሆ፥ በዚያ ወራትና በዚያ ጊዜ፥ የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን ምርኮኞች በምመልስበት ጊዜ፥ **2** አሕዛብን ሁሉ እሰበስባለሁ፥ ወደ ኢዮሳፍጥም ሸለቆ አወርዳቸዋለሁ። በአሕዛብ መካከል ከበተኑአቸው ከሕዝቤና ከርስቴ ከእስራኤል የተነሳ፥ ምድሬን ከመከፋፈላቸው የተነሳ፤ በዚያ እፈር ድባቸዋለሁ። **3** በሕዝቤ ላይ ዕጣ ተጣጣሉ፥ ወንድ ልጅን በሴተኛ አዳሪ ለወጡ፥ ሴት ልጅንም ለወይን ጠጅ ሸጡ፥ ጠጡም። **4** ጢሮስና ሲዶና የፍልስጤምም ክፍለ አገራት ሁሉ፥አሁን በእኔ ላይ መቆጣታችሁ ለምንድ ነው? ብድራትን ትመልሱልኛላችሁን? ብድራትን ብትመልሱልኝ፥ወዲያው ብድራታችሁን በራሳችሁ ላይ እመልሳለሁ። **5** ብሬንና ወርቄን ወስዳችኋል፥የከበረውንም ሀብቴን ወደ ቤተ መቅ ደሳችሁ አግዛችኋል። **6** ከግዛታቸው ልታርቋቸው፥ የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን ሰዎች ለግሪኮች ሸጣችኋል። **7** እነሆ እነርሱን የሸጣችሁብትን ሥፍራ እንዲለቁ አደርጋቸዋለሁ፥ ብድራታችሁንም በራሳችሁ ላይ እመልሳለሁ። **8** ወንዶችና ሴቶች ልጆ ቻችሁን በይሁዳ ሰዎች እጅ እሸጣለሁ። እነርሱም በሩቅ ላለ ሕዝብ፥ለሳባ ሰዎች ይሸጡአቸዋል። እግዚአብሔር ይህን ተናግሮአልና። **9** ይህን በአሕዛብ መካከል አውጁ፦ ለጦርነት ተዘጋጁ፥ኃያላን ሰዎችን አነሣሡ፥ ይቅረቡ፥ ተዋጊዎችም ሁሉ ይውጡ። **10** ማረሻችሁን ሰይፍ፥ ማጭዳችሁን ጦር ለማድረግ ቀጥቅጡ፤ ደካማውም «እኔ ብርቱ ነኝ» ይበል። **11** እናንተ በዙሪያ ያላችሁ አሕዛብ ሁሉ፥ ፈጥናችሁ ኑ፥ በአንድነትም ተሰብሰቡ። እግዚአብሔር ሆይ ኃያላን ተዋጊዎችህን ወደዚያ አውርድ። **12** በዙሪያ ባሉ አሕዛብ ሁሉ ላይ ልፈርድ በዚያ እቀመጣለሁና፤ አሕዛብ ይነሡ፥ ወደ ኢዮሳፍጥም ሸለቆ ይምጡ። **13** መከሩ ደርሶአልና ማጭድ ላኩ፥ የወይኑ መጭመቂያ ሞልቶ እየፈሰሰ ነውና ኑ ወይኑን ርገጡ፥ ክፋታቸው በዝቶአልና። **14** የእግዚአብሔር ቀን በፍርድ ሸለቆ ውስጥ ቀርቦአልና፤ ሁካታ፥ በፍርድ ሸለቆ ውስጥ ሁካታ አለ። **15** ፀሐይና ጨረቃ ይጨልማሉ፥ ከዋክብትም ብርሃናቸውን ይከለክላሉ። **16** እግዚአብሔር ከጽዮን ይጮኻል፥ከኢየሩሳሌም ድምጹን ከፍ አድርጎ ያሰማል። ሰማይና ምድር ይናወጣሉ፥ እግዚአብሔር ግን ለሕዝቡ መጠለያ፥ ለእስራኤልም ሕዝብ መመሸጊያ ይሆናል። **17** «ስለዚህ በተቀደሰ ተራራዬ በጽዮን የምኖር እግዚአብሔር አምላካችሁ እኔ እንደሆንኩ ታውቃላችሁ። ኢየሩሳሌም የተቀደሰች ትሆናለች፥ ዳግመኛም ሠራዊት አያልፍባትም። **18** በዚያን ቀን እንዲህ ይሆናል፥ ተራሮች አዲስ ወይን ጠጅ ያንጠባጥባሉ፥ ኮረብቶችም ወተት ያፈስሳሉ፥የይሁዳ ጅረቶች ሁሉ ውኃ ያጎርፋሉ፥ ከእግዚአብሔር ቤት ምንጭ ይመነጫል፥ የሰጢምንም ሸለቆ ያጠጣል። **19** በይሁዳ ሕዝብ ላይ ግፍ ፈጽመዋልና፥ በምድራቸው የንጽሐንን ደም አፍስሰዋልና፤ ግብጽ ባድማ፥ ኤዶምም ምድረ በዳ ትሆናለች። **20** ነገር ግን ይሁዳ ለዘላለም ይኖራል፥ኢየሩሳሌምም ከትውልድ ትውልድ ትኖራለች። **21** ያልተበቀልኩትን ደማቸውን እበቀላለሁ፤» እግ ዚአብሔር በጽዮን ይኖራል።

Joel 3:1

እነሆም
“አድምጥ ” ወይም “ትኩረት ስጥ”

በዚህ ወራት እና በዚህ ዘመን
በዚህ ወራት የሚለው ሀረግ በነዚያ ቀናት ከሚለው ሀረግ ጋር አንድ ሲሆን ይህንኑ ሀረግ ለማጠንከር ነው። ተርጓሚ “በነዚያ ወሳኝ ቀናት” ወይም “በዚያን ጊዜ”

የይሁዳን እና የኢየሩሳልምን መርኮ በምመልስበት ጊዜ
“ምርኮኞችን ወደ ይሁዳ እና ኢየሩሳሌም በምልክበት ጊዜ”

የኢዮሣፍጥ ሸለቆ
ኢዮሳፈጥ ትርጉሙ እግዚአብሔር ይፈርዳል ማለት ሲሆን የይሁዳ ንጉስ እና ከኢዮኤል በፊት የኖረ ሰው ነው። በዚህ ስም የሚታወቅ ቦታ የለም። የሸለቆው ስምም ከዚህ ኢዮሣፍጥ ከሚባለው ስም የተነሳ ሲሆን በዚህ መልኩ ቢተረጎም መልካም ነው።

ስለ ህዝቤ እና ስለ ርስቴ እስራኤል
እነዚህ ሀረጎች እንዴት እግዚአብሔር እስራኤልን እንደሚያይ እና የራሱ የሆነ ውድ ሕዝብ መሆኑን አጽንኦት ይሰጣል። ተርጓሚ - የእስራኤል ህዝብ ርስቴ (የእኔ ርስት)

ወንድ ልጅን ለጋለሞታ ዋጋ ሰጡ ሴት ልጅን ለወይን ጠጅ ሸጡ ጠጡም
የህ ከፈጸሙአቸው ድርጊቶች መካከል በእነዚህ ሁለት ልጆች ላይ ግን ምን እንዳፈፀሙባቸው አያመለክትም። ተርጓሚ ወንድ ልጅን ለጋለሞተኛ ሴት ልጅን በወይን ይጠጡ ዘንድ ለወጡአቸው።

Joel 3:4

የፍልስጥኤምም . . . ከእናነተ ጋር ለእኔ ምን አለኝ;
እግዚአብሔር የሚሠሙትን ህዝብ ሲያበረታ በሌላ ደግሞ አልሰማ ያሉትን የፍልስጥኤምን ህዝብ ደግሞ የገልጻል። የከተሞቹ ስሞች በከተማው ለሚኖሩ ህዝቦች (አህዘብ) ዘይቤአዊ ንግግር ናቸው። እነዚህ ቃላት እንደ አርፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ “ፍልስጥኤም በእኔ የመናደድ መብት የለህም።”

ብድራትን ትመልሱልኛላችሁ;
“ትበቀሉኛላቹ;” እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ህዝቡ ምን እደረገ እነዳለ እንዲያስብ ነው። ተርጓሚ “እኔ መበቀል የምትችሉ መስላችኋል ነገር ግን አትችሉም”

ፈጥኜ በችኮላ ብድራታጭሁን በራሳችሁ ላይ እመልሳለሁ
"በራሳችሁ" የሚለዉ ቃል ግለሰብን ያመለክታል እግዚአብሄር እንድተመም የፈለጉትን ህመም እርሱ እንድታመም እግዚአብሄር ያደርጋል። ተርጌሚ "ለእኔ ያሰባችሁትን ብድራት ነእናንተ ላይ አደርጋለሁ"

ብድራት
"በቀል " ወይም "መልስ መክፈል"

Joel 3:7

ተመልከት
"ትኩረት ስጥ" ወይም "አድምጥ"

እነርሱን ከሸጣችሁነት ስፍራ
የእስራኤል ህዝብ በባርነት ከነበሩበት ስፍራ ለቀዉ ወደ እስራኤል ምድር ይመለሳሉ።

ብስራታችሁንም ..... እመልሳለሁ
"የሚገባችሁን መልስ መስጠት

ወንዶችና ሴቶች ልጃችሁን በይሁዳ ልጆች እጅ እሸጣለዉ
እጅ የሚለዉ ቃል እጅ ለተለማመሰዉ ሀይል (ጉልበት) ወይም ደግሞ ለሰዉ ዘይቤአዊ አገላለፅ ሊሆን ይችላል ። ተርጌሚ "ወንዶችና ሴቶች ልጃችሁን ሸጩ ይሁዳን የራሴ አደርጋለሁ።"(ፈሊጣዊና ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት

የሳባ ሰዎች
የሳባ ምድር ህዝብ (የስም ትርጉም ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Joel 3:9

ኃያላንን አሥለሱ
"ኃያላንን ለዉጊያ ማዘጋጀት

ማረሻችሁን ሰይፍ ማጭዳችሁንም ጦር ለማድረግ ቀጥቅጡ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸዉ ሁለቱም የእርሻ መሣሪያዎችቻቸዉን ወደ ጦር መሣሪያ እንዲለዉጡ ያስተምራቸዋል።

ማረሻዎች **(**ማረሻ**)**
ዘርን ለመዝራት መሬት የሚታረስበት መሣሪያ

ማጥድ
ቅርንጫፎችን (እህል)ለማጨድ የሚያገለግል

Joel 3:11

ቸኩላችሁ ኑ ተሰብሰቡ
እነዚህ ቃላት በኢዮኤል 3:9 ወስጥ ስለሚጀምረዉ ጦርነት የምፀት ጥሪ ነዉ። (ምፀት ተመልከት)

ተሰብሰቡ
ይህ መሰብሰብ ለዉጊያዉ (ጦርነት) ነዉ። ይህ በግልፅ ሲቀወጥ ተርጌሚ"እራሳችሁን ለጦርነት (ዉጊያ) አሰባስቡ"

አቤቱ ኃያላኖችህን ወደዛያ አዉርድ

1. ኢዮኤል ለይዉዳ ህዝብ በአህዛብ መካከል እንዳያዉጁ እየነገራቸዉ ነዉ። (ኢዮኤል 3:9) ።ወይም
2. ኢዮኤል የእግዛብሔርን ቃልት አቋርጦ አጠረ ያለ ፀሎት ስፀልይ ነዉ። በሁለቱም መልኩ ሊተረጎም ይችላል።

Joel 3:12

አህዛብ ይነሱ **.....** በዙሪያ ባሉ አሕዛብ ሁሉ
"አህዛብ" የሚለዉ ቃልና "በዙሪያ ባሉ አህዛብ " የሚለዉ ሐረግ ስለ አንድ ህዝብ ነዉ የሚናገረዉ። እነዚህም በይሁዳ ዙሪያ ያሉ ናቸው።በኢየሩሳሌም ላይ በፈፀሙት ግፍ ምክኒያት በኢዩሳፍጥ ሸለቆ ይፈርድባቸውል።

የኤዮሳፍጥ ሸለቆ
የኢዮሳፍጥ የስሙ ትርጓሜ እግዚአብሄር ይፈርዳል ማለት ሲሆን ይህ ሰው የየረሁዳ ንጉሥ የነበረና ከኢዮኤል በፊት የኖረ ነው። በዚህ ስም የሚታወቅ ቦታ የለም ሸለቆው ከኢህ ኢዩሳፍጥ ከሚባለው ሰው ስም የተነሳ መሠየሙን መተርጎም የተሻለ ነው። (በኢዮኤል 3:2 ላይ ትርጉም ተመልከት) ማጭድ ስደዱ

ግብፅ ምድረ-በዳ **.....** ይሆናል
"ማንም በዚያ እስከማይኖር ድረስ ሁሉም ግብፅን ለቆ ይወጣል። " ሁሉም

ኤዶሚያስ በረሃ ይሆናል
ማንም ከዚህ በፊት እንዳልኖረበት ሁሉም ኤዶምን ለቆ ይወጣ።

በይሁዳ ልጆች ላይ ስላደረጉት ግፍ
ግብፅና ኤዶም የአመፅን ነገር በይሁዳ ህዝብ ላይ ስላደረጉ

በአገራቸዉ ንፁሐን ደም አፍስሰዋልና
ይህ አረፍተ ነገር የሚገለፀዉ "ኤዶም" ና "ግብፅን" ነዉ። ንፁሐን ደም የሚለዉ ሐረግ እነሱ ስለገደሏዉ ሰዎችን የገለፁበት ዘይቤአዊ ንግግር ነዉ። ተርጌሚ - "የግብፅ ህዝብና የኤዶም ህዝብ የይሁዳ ንፁሐን ሰዎችን ስለገደሉ።"

Joel 3:20

x
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጌሚ-" ሰዎች ለዘላለም በይሁዳ ይኖራሉ።"

ኢየሩሳሌም ለልጅ ልጅ መኖሪያ ይሆናል
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ከትዉልድ ወደ ትዉልድ ሰዎች በእየሩሳሌም ለዘላለም ይኖራሉ።

እኔም ንፁህ ያዳደጉትን ደማቸውን ንፀህ አዲርገዋለዉ
ደም የሞት ዘይቤአዊ ንግግር ነዉ። ተርጌሚ "እስካዛሬ ያልተቀጡ የእስራኤል ህዝብን የገዳሉ ጠለየችን እቀጣቸቀለሁ።"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Amos

Amos

Chapter 1

[1] በቴቁሔ ከነበሩት እረኞች መካከል አንዱ የሆነው አሞጽ፥ ስለ እስራኤል በራዕይ የተቀበላቸው ነገሮች እነዚህ ናቸው። እነዚህንም ነገሮች በይሁዳ ንጉሥ በዖዝያን ዘመነ መንግሥት፥በእስራኤል ንጉሥ በዮአስ ልጅ በኢዮርብዓም ዘመነ መንግሥት፥የምድርም መናወጥ ከመሆኑ ከሁለት ዓ መት አስቀድሞ ተቀበለ። [2] እንዲህም አለ፥«እግዚአብሔር ከጽዮን ይጮኻል፥ ከኢየሩሳሌምም ድምጹን ከፍ አድርጎ ያሰማል። የእረኞች ማሰማሪያ ዎች ያለቅሳሉ፥የቀርሜሎስም ራስ ይደርቃል።» [3] እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦«ገልዓድን በብረት መሣሪያ አድቅቋልና፤ ስለ ደማስቆ ሦሥት ኃጢአቶች፥ይልቁንም ስለ አራቱ ፥ ቅጣቴን አልመልስም። [4] በአዛሄል ቤት ላይ እሳት እልካለሁ፥ የወልደ አዴርንም ምሽጎች ትበላለች። [5] የደማስቆን በር መቀርቀሪያዎች እሰብራኣለሁ፥በአዌን ሸለቆ የሚኖረውን ሰውና በቤተ ኤደንም በትረ መንግሥት የያዘውን ሰው ድል ነሳለሁ፤ የሶርያም ሕዝብ ተማርኮ ወደ ቂር ይሄዳል» ይላል እግዚአብሔር። [6] እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦«ለዔዶም አሳልፈው ሊሰጧቸው ሕዝቡን ሁሉ ማርከው ወስደዋልና፤ ስለ ጋዛ ሦሥት ኃጢአቶች፥ ይልቁን ም ስለ አራቱ ፥ ቅጣቴን አልመልስም። [7] በጋዛ ቅጥሮች ላይ እሳት እልካልሁ፥ምሽጎቹዋንም ይበላል። [8] በአሽዶድ የሚኖረውንና በአስቀሎና በትረ መንግሥት የያዘውን ሰው አጠፋለሁ። እጄን በአቃሮን ላይ እመልሳለሁ፥ የቀሩት ፍልስጤማውያንም ይጠፋሉ»ይላል እግዚአብሔር። [9] እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦«የሕዝብን ወገኖች ሁሉ ለኤዶም አሳልፈው ሰጥተዋልና የወንድማማችነትንም ኪዳን አፍርሰዋልና፥ ስለ ጢሮስ ሦሥት ኃጢአቶች፥ ይልቁንም ስለ አራቱ፥ ቅጣቴን አለመልስም። [10] በጢሮስ ቅጥሮች ላይ እሳት እልካለሁ፥ምሽጎችዋንም ሁሉ ይበላል።» [11] እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ «ወንድሙን በሰይፍ አሳድዶታልና፥ ርኅራኄንም ሁሉ ጥሎአልና፥ ቁጣው ሳያቋርጥ ነዶአልና፥ ቁጣው ለዘላለም ነውና፤ [12] በቴማን ላይ እሳት እልካለሁ፥ የባሶራንም አብያተ መንግሥት አጠፋለሁ።» [13] እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦«ድንበሩን ለማስፋት የገለዓድን እርጉዝ ሴቶች ቀድዶአልና፤ ስለ አሞን ሕዝብ ሦሥት ኃጢአቶች፥ ይልቁንም ስለ አራቱ፥ ቅጣቴን አልመልስም። [14] በረባት ቅጥሮች ላይ እሳት አነድዳለሁ፥ በጦርነት ቀን ከጩኸት ጋር፥ በአውሎ ነፋስም ቀን ከማዕበል ጋር፤ አብያተ መንግሥትን ይበላል። [15] ንጉሣቸው ከአለቆቻቸው ጋር ወደ ምርኮ ይሄዳል» ይላል እግዚአብሔር።

Amos 1:1

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር በአሞፅ አማካይነት ቀኔያዊ በሆነ ቋንቋ ይናገራል።(ቅኔያዊና ፓራሌሊዝም የሚለውን ይመልከቱ)

ከላም ጠባቂዎች መካከል የነበረው አሞፅ ስለ እሥራኤል ያየቀው ቃል ይህ ነው
ተቁሔ በተሰኘ ሥፍራ ውስጥ በእረኝነት ሥራ ላይ ከተሰማሩ ሰዎች መካከል አንዱ የሆነው አሞፅ የእሥራኤልን ጉዳዮች በተመለከተ የተቀበለው ራእይ ነበረ።(አክቲቭ ወይም ፓሲቭ የሚለውን ይመልከቱ)

ጉዳዮቹ እነዚህ ናቸው
“መልዕክቱ ይሄ ነው” በተቁሔ “ተቁሔ”የአንድ ከተማ ወይም መንደር ስም ነው፡

እነዚህን ነገሮች ተቀበላቸው
ይሄ በአድራጊ ግሥ መልኩ ለገለፅ ይችላል።።የአሞፅ ትርጉም “እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች ሰጠው”(አድራጊ ግሥን ወይም ተካፋይ ያልሆነ የሚለውን ይመልከቱ)

በይዳ ንጉሥ በዖዝያን ዘመን፤በእሥራኤልም ንጉስ በዮአስ ልጅ በኢዮርብዓም ዘመን
“በ... ዘመን”የተሰኙት ቃላት ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን እያንዳንዱ ለንግሥናው በራሱ ፈቃድ ሥልጣኑን የሚቀቀበትን ሁኔታ የሚያመለክትነው።።የአሞፅ ትርጉም “ዖዝያን የይሁዳ ንጉሥ በነበረበት ወቅትና ኢዮርብዓም የእስራኤል ንጉሥ በነበረበት ወቅት ነው”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የመሬት መናወጡ ከሆነበት ሁለት ዓመት በፊት
የታሰበው ቀድሞ የሰሙ ሰዎች ግዙፍ የሆነ የመሬት መንቀጥቀጥ በሚከሰትበት ወቅት ሊያወቁ ይችላሉ ተብሎ ነው።።(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና ውስጣዊ ወይም ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር በፅዮን ሆኖ ድምፁን ከፍ አድርጎ ይጮሃል
እነዚህ ሁለት አረፍተ ነገሮች ተመሣሣይ የሆኑ ትርጉሞች ነው ያላቸው። እግዚአብሔር በአንድ አገር ላይ ፍርድን ለመፍረድ በሚዘጋጅበት ወቅት ከፍተኛ ጩኸት የሚያሠማ ስለመሆኑ ሁለቱም በጋራ አፅንኦትን ይሰጣሉ።

እግዚአብሔር ይጮሃል
ፀሐፊው የእግዚአብሔርን ድምፅ ከአንበሣ ማጓራት ጋር ወይም ከመብረቅ ድምፅ ጋር ያመሳስለዋል።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር
ይሄ ሥም እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ዘመን ለሕዝቡ የተገለፀው ሥም ነው፡ ይንንነበዘአግባቡ ለመተርጎም አንዲቻላችሁ የትርጉም ቃላትን ገፅ ይመልከቱ።

Amos 1:3

ስለሶስት ወይም ስለ አራት ኃጢአቶች
ይሄ ቅኔያዊ አነጋገር ነው።።ይሄ የተወሰኑ ኃጢአቶች ብቻ ናቸው የተፈፀሙት ለማለት ሣይሆን ወደ እግዚአብሔር ፍርድ እንዲያመራ ያደረገው የብዙ ኃጢአቶች ድምር መሆኑን ለማመልከት ነው።

ደማስቆ
እዚህ ላይ “ደማስቆ”የሚወክለው በደማስቆ ከተማ ውስጥ ነዋሪ የሆኑትን ሰዎች ነው።።(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

መቅሰፍቴን ከማድረግ አልመለስም
እዚህ ላይ እግዚአብሔርደማስቆ በገለዓድ ላይ የፈፀመችው ነገር እህልን በብረት መንኮራኩር ወይም በመሣሪያ ከማበራየት ጋር ያመሳስለዋል።(ነው።። (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ) ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ገለዓድ
እዚህ ላይ ገለዓድ የሚለው ቃል የገለዓድን ሕዝብ የሚያመለክት ነው።የአሞፅ ትርጉም“ የገለዓድ ሕዝብ” (ነው።(ከዋናው ሃሣብ ጋር የሚገናኙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ))

በአዛሄል ቤት ላይ እሣትን እልካለሁ
እዚህ ላይ እግዚአብሔር ከሚባላ እሣት ጋር በሚመሳሰልበት መልኩ በአዛሄል ቤት ላይ ፍርድን የሚያመጣ ስለመሆኑ ይናገራል።(ምሣሌያዊ አነጋገርን ይመልከቱ)

የአዛሄል ቤት
“ቤት”የሚለው ቃልበቤት ውስጥ ስለሚኖሩ ቤተሰቦች የተነገረ አባባል ነው። (ከዋናው ሃሣብ ጋር የሚገናኙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ) በዚህ አውድ መሠረት ይሄ የሚያመለክተው ደማስቆ በነበረበት ሥፍራ ላይ በአገሪቱ ላይ ገዢ የነበሩትን ትውልዶች ነው።(ከዋናው ሃሣብ ጋር የሚገናኙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

የወልደ አዴርን አዳራሾች ትበላለች
እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ ቅጥርን ከሚበላ እሣት ጋር ተመሳስሎ ነው የተነገረው።(ምሣሌያዊ አነጋገሩን ይመልከቱ)

አዛሄል...ወልደ አዴር
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው።

Amos 1:5

ሃሣብን ማያያዝ
እግዚአብሔር በደማስቆ ላይ የፍርድ መልዕክቱን መናገር ይቀጥላል።

ሰውዬውን አስወግድ
እዚህ ላይ “አስወግድ”ማለት ማጥፋት ወይም ማሳደድ ማለት ነው።የልብስ ቁራጭ እንደሚቆረጥ ወይም አንድ ቅርንጫፍ ከዛፍ ላይ እንደሚቆረጥ ዓይነት ማለት ነው።የአሞፅ ትርጉም “ሰውዬውን ማጥፋት”ወይም “ሰውዬውን ማሳደድ”(-ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የአዌን ሸለቆ
ይሄ የአንድ ቦታ ሥም ሲሆን ትርጉሙም “የክፋት ሸለቆ”ማለት ነው።ለዚህ ፍቺ ሊሆኑ የሚችሉት ነገሮች ደግሞ 1/ይሄ በዚያ ግዛት ሥር የሚገኝ የአንድ ሥፍራ ስም ነው።ወይም 2/ይሄ የደማስቆ ወይም የአካባቢው ግዛት ነው። የአሞፅ ትርጉም “የክፋት ሸለቆ”

በትር የያዘውንም
ይህ የዚያ ከተማ ወይም ግዛት ገዢ የሚለው ቃል ከዋናው ሃሣብ ጋር የሚገናኙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል ነውው።የአሞፅ ትርጉም “የ..... ገዢ”

የኤደን ቤት
ይሄ የአንድ ሥፍራ ስም ሲሆን ትርጉሙም “የደስታ ቤት” ማለት ነው።ለዚህ ፍቺ ሊሆኑ የሚችሉት ነገሮች ደግሞ 1/ይሄ በዚያ ግዛት ሥር የሚገኝ የአንድ ሥፍራ ስም ነው።ወይም 2/ይሄ የደማስቆ ወይም የአካባቢው ግዛት በሌላ ቃል ሲገለፅ ነው።የአሞፅ ትርጉም “የደስታ ቤት”(ስሞችና ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውሉ ቃላት እንዴት ነው መተርጎም የሚኖርባቸው? የሚለውን ይመለከቱ።)

ቂር
ይሄ የሃራም ሕዝብ ከመጀመሪያ አንስቶ የነበሩበት የአንድ ግዛት ሥም ነው።

Amos 1:6

ስለሶስትና ስለአራት ኃጢአቶች
ይሄ ቅኔያዊ አነጋገርነው።የተወሰነ ቁጥር ያላቸው ኃጢአቶች ተፈፅመዋል ማለት ሣይሆን ብዙ ኃጢአቶች የእግዚአብሔር ፍርድ እንዲመጣ ምክኒያት መሆናቸውን ለማመለከት ነው።እነዚህን ቃላት በአሞፅ 1:3 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ይመልከቱ።

ጋዛ
እዚህ ላይ “ጋዛ”የሚለው ቃል የሚወክለው የጋዛ ግዛትን ሕዝብ ነው። የአሞፅ ትርጉም “የጋዛ ሕዝብ”((ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ))

መቅሰፍቴን ከማድረግ አልመለስም
እግዚአብሔር እንደሚቀጣቸው አፅንዖት ለመስጠት ሁለት አሉታዊ ነገሮችን ይጠቀማል።

“አሣልፍህ ስጣቸው”
“አሳልፈህ ስጣቸው” ወይም “ለሸያጭ አቅርባቸው”

“ኤዶምያስ”
እዚህ ላይ“ኤዶምያስ” የሚለው ቃል የኤዶምያስን አገር ሕዝብ የሚወክል ነው።የአሞፅ ትርጉም “የኤዶም ሕዝብ”(ሲኖኒምን ይመልከቱ)

አዳራሾችዋን ትበላለች
እዚህ ላይ የእግዙአብሔር ፍርድ ቅጥርን ከሚበላ እሣት ጋር ተመሳስሎ የተነገረ ነው።(ምሳሌያዊ አነጋገርን ይመልከቱ)

Amos 1:8

ሃሣብን ማያያዝ
እግዚአብሔር በጋዛ ላይ ሊያመጣ ያለውን የፍርድ መልዕክት መናገሩን ይቀጥላል።

ሰውዬውን ቁረጠው
እዚህ ላይ “ቁረጠው”የሚለው ቃል ትርጉም አንድ ሰው የልብስ ቁራጭን እንደሚቆርጥ ወይም ደግሞ ቅርንጫፍን ከዛፍ ላይ እንደሚቆርጥ ማጥፋት ወይም ደግሞ ከሥፍራው ማሳደድ ማለት ነው።የአሞፅ ትርጉም “ሰውየውን አጥፋው” ወይም“ሰውዬውን ከሥፍራው አሳድደው”(ምሣሌያዊ አነጋገርን ይመልከቱ)

በትሩን የሚይዘው ሰው
ይሄ የዚያ ከተማ ወይም ግዛት በሌላ ቃል ሲገለፅ ነው።የአሞፅ ትርጉም “ገዢው”((ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ))

በአቃሮን ላይ እጄን እዘረጋለሁ
እዚህ ላይ“አቃሮን” የሚያመለክተው የአቃሮንን ከተማ ሰዎች ነው።የአሞፅ ትርጉም “የኤክሮን ሕዝብ” ((ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ))

Amos 1:9

ስለ ሶስት ወይም ስለ አራት ኃጢአቶች
ይሄ ቅኔያዊ አነጋገር ነው።የተወሰነ ቁጥር ያላቸው ኃጢአቶች ተፈፅመዋል ማለት ሣይሆን ብዙ ኃጢአቶች የእግዚአብሔር ፍርድ እንዲመጣ ምክኒያት መሆናቸውን የሚያመለክት ነው።ይሄ በአሞፅ 1:3 ላይ እንዴት እንደሚተረጎም ይመልከቱ።

ጢሮስ
እዚህ ላይ“ጢሮስ”የሚለው ቃል የሚመለክተው የጢሮስን ከተማ ሕዝብ ነው።የአሞፅ ትርጉም “የጢሮስ ሕዝብ”(ሜቶኖሚን ይመልከቱ)

መቅሰፍቴን ከማድረግ ልመለስም
እግዚአብሔር ቅጣትን ተግባራዊ እንደሚያደርግ አፅንዖት ለመስጠት ሁለት አሉታዊ ነገሮችን ይጠቀማል። ይሄ በአሞፅ 1:3 ላይ እንዴት እንደሚተረጎም ይመልከቱ።(በተዘዋዋሪ መንገድ ሃሣብን መግለፅ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የወንድማማችነታቸው ቃል ኪዳን
“እንደ ወንድማቸው ለመቁጠር የገቡት ስምምነት”

አዳራሾችዋን በእሣት ይበላል
እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ የሚነገረው ቅጥርን ከሚበላ እሣት ጋር ተመሳስሎ ነው።(ምሣሌያዊ አነጋገርን ይመልከቱ)

Amos 1:11

ስለ ሶስትና ስለ አራት ኃጢአቶች
ይሄ ቅኔያዊ አነጋገር ነው። የተወሰነ ቁጥር ያላቸው ኃጢአቶች ተፈፅመዋል ማለት ሣይሆን ብዙ ኃጢአቶች የእግዚአብሔር ፍርድ እንዲመጣ ምክኒያት መሆናቸውን የሚያመለክት ነው።ይሄ በአሞፅ 1:3 ላይ እንዴት እንደሚተረጎም ይመልከቱ።

ኤዶምያስ
እዚህ ላይ“ኤዶምስ”የሚለው ቃል የኤዶምያስን አገር ሕዝብ የሚያመለክት ነው።የአሞፅ ትርጉም “የኤዶምያስ ሕዝብ ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

መቅሰፍቴን ከማድረግ አልመለስም
እግዚአብሔር ቅጣትን ተግባራዊ የሚያደርግ እንደሆነ አፅንዖት ለመስጠት ሁለት አሉታዊ ነገሮችን ይጠቀማል።ይሄ በአሞፅ 1:3 ላይ እንዴት እንደሚተረጎም ይመልከቱ።(በተዘዋዋሪ መንገድ ሃሣብን መግለፅ የሚለውን ይመልከቱ)

ወንድሙን አሳደደ
የኤዶምያስ ትውልድ ሲወርድ ሲዋርድ የመጣው የእሥራኤል ሕዝብ ዘር ከተመዘዘበት ከያዕቆብ ወንድም ከነበረው ከዔሳው እነው የሚል ግምት አለ። እዚህ ላይ “ወንድሙ”የሚለው ቃል የሚወክለው የእሥራኤልን ሕዝብ ነው። የአሞፅ ትርጉም “የእስራኤልን ሕዝብ አሳደደ” (ግምታዊ ዕውቀት፤ውስጣዊ ወይም ያልተገለፀ መረጃንና ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ ይመልከቱ)

ርህራሄንም ሁሉ ጥሏልና
“ርህራሄን አላሳያቸውም”

ቁጣውም ሁልጊዜ ነድዷልና፤መዓቱንም ለዘላለም ጠብቋልና
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን የቁጣውን መቀጠል አፅንዖት ለመስጠት ይደጋገማሉ።“ንዴት” እና “ቁጣ” የተሰኙት አሕፅሮተ ሥም “የንዴት” እና “የቁጣን” ቅፅል በመጠቀም ሊተረጎሙ ይችላሉ፡የአሞፅ ትርጉም“ ማቋረጫ በሌለው መልኩ ይበሳጭና ዘወትር ይቆጣ ነበር”(ተመሳሳይነትንና አሕፅሮተ ሥምን ይመልከቱ)

ቁጣውም ሁልጊዜ ነድዷልና
ይሄ የማይቋረጥ ቁጣውን ለመግለፅ በማጋነን መልክ የቀረበ ነው።(ሆን ብሎ አጋኖ መናገርንና አጠቃላይነትን ይመልከቱ)

ቴማንና ባሶራ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው።ስሞች እንዴት ሊተረጎሙ እንደሚገባ ተመልከቱ።

የባሶራን አዳራሾች በእሣት ይበላል
እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ አዳራሾችን በእሣት ከሚበላ እሣት ጋር በማመሰሰል ይናገራል።(ምሣሌያዊ አነጋገርን ይመልከቱ)

Amos 1:13

ስለሶስት ወይም ስለአራት ኃጢአት
ይሄ ቅኔያዊ አነጋገር ነው።የተወሰኑ ኃጢአቶች ተፈፅመዋል ማለቱ ሣይሆን ወደ እግዚአብሔር ፍርድ እንዲያመራ ያደረገው የብዙ ኃጢአቶች ድምር መሆኑን ለማመልከት ነው።እነዚህን በአሞፅ 1:3 የሚገኙትን ቃላት እንዴት እንደተረጎማችኋቸው ተመልከቱ።

መቅሰፍቴን ከማድረግ አልመለስም
እግዘዚአብሔርቅጣቱ የሚጠብቃቸው ስለመሆኑ አፅንዖት ለመስጠት ሁለት አሉታዊ ነገሮችን እዚህ ላይ ይጠቀማል።እነዚህን በአሞፅ 1:3 የሚገኙትን ቃላት እንዴት እንደተረጎማችኋቸው ተመልከቱ።(በተዘዋዋሪ መንገድ ሃሣብን መግለፅ የሚለውን ይመልከቱ)

ዳርቻቸውን ያሰፉ ዘንድ
“ድንበራቸውን ማስፋት”ወይም “ግዛታቸውን ማስፋት”

Amos 1:14

ሃሣብን ማያያዝ
እግዚአብሔር የፍርድ መልዕክትን በአሞን ሕዝብ ላይ መናገሩን መቀጠል።

አዳራሾችዋን በእሣት ይበላል
እዚህ ላይ እግዚአብሔር ፍርድ አዳራሾችን በእሣት ከሚበላ እሣት ጋር ተመሳስሎ ይነገራል።(ምሣሌያዊ አነጋገርን ይመልከቱ)

በዓውሎ ነፋስም ቀን በጩኸት
ከአሞን ሕዝብ ጋር የሚደረገውን ግጭት ከአስፈሪ አውሎ ንፋስ ጋር ያመሳስለዋል። “ግጭቱን ከታላቅ አውሎ ንፋስ ጋር ያመሳስለዋል”(ምሣሌያዊ አነጋገርን ይመልከቱ)

ማዕበል ...አውሎ ነፋስ
እነዚህ ሁለት ዓይነት ከባድ አውሎ ነፋሣት ናቸው።

አውሎ ነፋስ
በፍጥነት በሚሽከረከርበትና በሚንቀሳቀስበት ወቅት ጥፋት ሊያደርስ የሚችል አውሎ ነፋስ

ንጉሣቸው ይማረካል
“መማረክ”የሚለው “አሕፅሮተ ሥም ተማረከ”በሚለው ግሥ ሊተረጎም ይችላል።ይሄ እየተከናወነ ያለ ነገርን እንደሚያመለክት ተደርጎ ሊተረጎም ይችላል።የአሞፅ ትርጉም “ጠላቶቻቸው ንጉሱን በማጋዝ እስረኛ አድርገው ይወስዱታል። ”(አሕፅሮተ ሥምን፤ አድራጊ ግሥን ወይም ተካፋይ ያልሆነ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ «አመድ እስኪሆን ድረስ የኤዶምን ንጉሥ አጥንት አቋጥሏልና፤ ስለ ሞዓብን ሦሥት ኃጢአቶች፥ይልቁንም ስለ አራቱ፥ ቅጣቴን አልመልስም። **2** በሞዓብ ላይ እሳት እልካለሁ፥ የቂርዮትንም ምሽጎች ይበላል። ሞዓብ በጩኽትና በመለከትድምጽ፥ በሁካታ ውስጥ ይሞታል። **3** በውስጧ የሚገኝውን ፈራጁን አጠፋለሁ፥ መሳፍንቱን ሁሉ ከእርሱ ጋር እገድላለሁ» ይላል እግዚአብሔር። **4** እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ «የእግዚአብሔርን ሕግ ጥለዋልና፥ ትእዛዙንም አለጠበቁምና ስለ ሦሥት የይሁዳ ኃጢአቶች፥ይልቁንም ስል አራቱ፥ ቅጣቴን አልመልስም። ሐሰታቸው አስቷቸዋልና፥በዚሁ መንገድ አባቶቻቸውም ሄዱ። **5** እሳት በይሁዳ ላይ እልካለሁ፥ የኢየሩሳሌምንም ምሽጎች ይበላል። **6** እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦«ንጹሑን ስለ ብር፥ ችግረኛውንም ስለ ጥንድ ጫማ ሸጠዋልና ፤ስለ እስራኤል ሦሥት ኃጥአቶች፥ ይልቁንም ስለ አራቱ፥ ቅጣቴን አልመልስም። **7** ሰዎች በምድር ላይ ትቢያን እንደሚረግጡ፥ የድኾችን ራስ ይረግጣሉ፤ የተጨቆኑትን ይገፋሉ። አባትና ልጅ ከአንዲት ሴት ጋር ይተኛሉ፥ ቅዱስ ስሜንም ያረክሳሉ። **8** በየመሠዊያው አጠገብ በመያዣነት በተወሰደ ልብስ ላይ ይተኛሉ፥በአምላካቸውም ቤት በመቀጫነት የተወሰደውን ወይን ጠጅ ይጠጣሉ። **9** ነገር ግን ቁመታቸው እንደ ዝግባ፥ጥንካሬያቸው እንደ ባሉጥ ዛፍ የነበረውን አሞራውያንን ከፊታችው አጠፋሁ። ከላይ ፍሬውን፥ ከታችም ሥሩን አጠፋሁ። **10** የአሞራውያንን ምድር እንድትወርሱ እናንተን ከግብፅ አወጣሁ፤ በምድረ በዳ አርባ ዓመት መራሁዋችሁ። **11** ነቢያትን ከወንዶች ልጆቻችሁ፥ናዝራዊያንንም ከጎልማሶቻችሁ መካከል አስነሳሁ። የእስራኤል ህዝብ ሆይ፥ይህ እንደዚህ አይደለም ን? ይላል እግዚአብሔር። **12** «እናንተ ግን ናዝራዊያንን የወይን ጠጅ ይጠጡ ዘንድ አሳባቸውን አስለወጣችሁ፥ነቢያቱንም እንዳይተነብዩ አዘዛችኋቸው። **13** እነሆ፥በእህል የተሞላ ሰረገላ ሰውን እንደሚያደቅቅ እንዲሁ አደቅቃችኋለሁ። **14** ፈጣኑ ሰው አያመልጥም፥ብርቱው ለራሱ ብርታትን አይጨምርም፥ኃያልም ራሱን አያድንም። **15** ቀስተኛው አይቆምም፥ፈጣኑ ሯጭ አያመልጥም፥ፈረሰኛውም ራሱን አያድንም። **16** ጅግኖቹ ተዋጊዎች እንኳን በቀን ዕርቃናቸውን ይሸሻሉ፤ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው።»

Amos 2:1

ስለ ሶስት ወይም ስለ አራት የይሁዳ ኃጢአት ስለ ሶስት ወይም ስለ አራት
ይሄ ቅኔያዊ አነጋገር ነው።የተወሰኑ ኃጢአቶች ተፈፅመዋል ማለቱ ሣይሆን ወደ እግዚአብሔር ፍርድ እንዲያመራ ያደረገው የብዙ ኃጢአቶች ድምር መሆኑን ለማመልከት ነው።እነዚህን በአሞፅ 1:3 የሚገኙትን ቃላት እንዴት እንደተረጎማችኋቸው ተመልከቱ።

ሞአብ
ይሄ የሞዓብን ሕዝብ የሚወክል ነው።የአሞፅ ትርጉም “የሞዓብ ሕዝብ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ ይመልከቱ)

መቅሰፍቴን ከማድረግ አልመለስም
ያእግዚአብሔር ቅጣቱ ተግባራዊ የሚሆንባቸው እንደሆነ አፅንዖት ለመስጠት ሁለት አሉታዊ ነገሮችን እዚህ ላይ ይጠቀማል።እነዚህን በአሞፅ 1:3 የሚገኙትን ቃላት እንዴት እንደተረጎማችኋቸው ተመልከቱ።(በተዘዋዋሪ መንገድ ሃሣብን መግለፅ የሚለውን ይመልከቱ)

አጥንቶችን አቃጠለ
“እነርሱ” የሚለው ቃል ሞአብን የሚያመለክት ነው።የአሞፅ ትርጉም“የሞአብ ሕዝብ አጥንቶችን አቃጠለ”

እስከ መጨረሻ
“ወደ አፈርነት”

Amos 2:2

ሃሣብንማያያዝ
እግዚአብሔር በሞአብ ሕዝብ ላይ የፍርድ መልዕክቱን መናገሩን ይቀጥላል።

ቂርዮት
ይህ የአንድ ከተማ ሥም ነው።(ስሞችን እንዴት እንደምትተረጉሙ አስተውሉ)

ሞአብ ይሞታል
እዚህ ላይ ሞአብ የሚለው ቃል የሞአብን ሕዝብ ይወክላል።የአሞፅ ትርጉም “የሞአብ ሕዝብ ይሞታል”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

በከፍተኛ ውካታ
ውካታና ከፍተኛ ጩኽት ነው።

በውስጧ ያለው ፈራጅ
“የሞአብ ገዢ”

አለቆቿንሁሉሉ
“ባለሥልጣናቱ በሙሉ”ወይም “መሪዎቿ በሙሉ”

Amos 2:4

ስለ ሶስት ወይም ስለ አራት
ይሄ ቅኔያዊ አነጋገር ነው።የተወሰኑ ኃጢአቶች ተፈፅመዋል ማለቱ ሣይሆን ወደ እግዚአብሔር ፍርድ እንዲያመራ ያደረገው የብዙ ኃጢአቶች ድምር መሆኑን ለማመልከት ነው።እነዚህን በአሞፅ 1:3 የሚገኙትን ቃላት እንዴት እንደተረጎማችኋቸው ተመልከቱ።

ይሁዳ
ይሄ የሚወክለው የይሁዳን ሕዝብ ነው።የአሞፅ ትርጉም “የይሁዳ ሕዝብ”ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

መቅሰፍቴን ከማድረግ አልመለስም
እዚህ ላይ እግዚአብሔር ቅጣቱ እንደማይቀርላቸው አፅንዖት ለመስጠት ሁለት አሉታዊ ነገሮችን ይጠቀማል።እነዚህን በአሞፅ 1:3 የሚገኙትን ቃላት እንዴት እንደተረጎማችኋቸው ተመልከቱ።በተዘዋዋሪ መንገድ ሃሣብን መግለፅ የሚለውን ይመልከቱ)

ሐሰታቸው
ይሄ አገላለፅ ምናልባትም የሐሰት አምላኮችንና ጣዖታትን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።የአሞፅ ትርጉም “ጣዖት ማምለካቸው”(ምሣሌያዊ አነጋገርን ይመልከቱ)

መንገዳቸውን ስተው ሄዱ
ጣዖታትን ማምለካቸው ሰዎች ከጀርባቸው ሆነው እንደሚከተሏቸው ዓይነት ተደርጎ ነው የተገለፀው።

የኢየሩሣሌምን አዳራሾች በእሣት ይበላል
እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ አዳራሾችን በእሣት እንደሚበላ እሣት ተመስሎ ነው የተነገረው።(ምሣሌያዊ አነጋገርን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Amos 2:6

ስለ ሶስት ወይም ስለ አራት ኃጢአቶች
ይሄ ቅኔያዊ አነጋገር ነው።እዚህ ላይ የተወሰኑ ኃጢአቶች ተፈፅመዋል ማለቱ ሣይሆን ወደ እግዚአብሔር ፍርድ እንዲያመራ ያደረገው የብዙ ኃጢአቶች ድምር መሆኑን ለማመልከት ነው።እነዚህን በአሞፅ 1:3 የሚገኙትን ቃላት እንዴት እንደተረጎማችኋቸው ተመልከቱ።

እሥራኤል
ይሄ የእሥራኤልን ሕዝብ የሚያመለክት ቃል ነው።

መቅሰፍቴን ከማድረግ አልመለስም
እዚህ ላይ እግዚአብሔር ቅጣቱ እንደማይቀርላቸው አፅንዖት ለመስጠት ሁለት አሉታዊ ነገሮችን ይጠቀማል።እነዚህን በአሞፅ 1:3 የሚገኙትን ቃላት እንዴት እንደተረጎማችኋቸው ተመልከቱ።(በተዘዋዋሪ መንገድ ሃሣብን መግለፅ የሚለውን ይመልከቱ)

ቅንነት ያለው
ይሄ በአጠቃላይ ቅን ሰዎችን የሚያመለክት ነው።

ችግረኞች
ይሄ በአጠቃላይ ችግር ያለባቸውን ሰዎች ይመለከታል።

Amos 2:7

ሃሣብን ማያያዝ
እግዚአብሔር በእሥራኤል ሕዝብ ላይ የፍርድ መልዕክቱን ማስተላለፉን ይቀጥላል።

አጠቃላይ መረጃ
በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ “እነርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእሥራኤልን ሕዝብ ነው።

የድሆችን ራስ በምድር ትብያ ላይ ይረግጣሉ
እሥራኤላውያን ድሆችን የሚይዙበትን አያያዝ ሰዎች መሬትን በእግራቸው በኃይል ከመርገጣቸው ጋር እያነፃፀረ ይናገራል።(ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)

መርገጥ
በተደጋጋሚ በኃይልና በጭካኔ መርገጥ

ድሃው
ይሄ ድሃውን ሕዝብ በአጠቃላይ የሚመለከት ነገር ነው።የአሞፅ ትርጉም “ድሃ ሕዝብ ”(አሕፅሮተ ቅፅል ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

የተጨቆኑ ሰዎችን ይገፋሉ
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር የተጨቆኑ ሰዎች ተገቢ ባልሆነ መልኩ እየተያዝን ነው ብለው አቤት በሚሉበት ወቅት ሊሰሟቸው ፈቃደኛ አለመሆናቸውን የሚያሣይ ነው።(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የተጨቆኑ
ይሄ በአጠቃላይ የተጨቆኑ ሰዎችን የሚያመለክት ነው።የአሞፅ ትርጉም “የተጨቆኑ ሰዎች” (አሕፅሮተ ቅፅል ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

ቅጣት የተጣለባቸው ሰዎች
ይሄ በአድርጊ ግሥ ሊገለፅ ይችላል።የአሞፅ ትርጉም “ቅጣት የጣሉባቸው ሰዎች”(አድርጊ ግሥን ወይም ተካፋይ ያልሆነ የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 2:9

ሃሣብን ማያያዝ
እግዚአብሔር በእሥራኤል ሕዝብ ላይ የፍርድ መልዕክቱን ማስተላለፍ ይቀጥላል።

ቁመቱ እንደ ዝግባ ቁመት፤ብርታቱም እንደ ኮምቦል ዛፍ
ይሄ ግነት ነው።አሞራውያን ምን ያህል ረዣዥሞችና ጠንካሮች እንደነበሩ ለመግለፅ በግዛቱ ውስጥ ከሚገኙ ረዥምና ጠንካራ ዛፎች ጋር ያነፃፅራቸዋል።የአሞፅ ትርጉም “ እንደ ግዙፍ ዛፎች ጠንካራ የነበሩ” (ሆን ብሎ አጋኖ መናገርን፤አጠቃላይነትንና ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)

ዝግባ
የጥድ ዛፎች

ኮምቦል
የሾላ ዛፎች

ፍሬውንም ከላዩ ሥሩንም ከታች አጠፋሁ
አንድ ዛፍ ከላይ ወደ ታች ሊጠፋ እንደሚችል ሁሉ እንዲሁ እግዚአብሔር አሞራውያንን እንዴት ፈፅሞ እንዳጠፋቸው የሚገልፅ ነው።የአሞፅ ትርጉም “ፈፅሜ አጠፋኋቸው”(ፈሊጣዊ አነጋገርንና ምሕፃረ ቃል የሚለውን ተመልከቱ)

Amos 2:11

ሃሣብን ማያያዝ
እግዚአብሔር በእሥራኤል ሕዝብ ላይ የፍርድ መልዕክቱን ማስተላለፍ ይቀጥላል።

አጠቃላይ መረጃ
“የእናንተ”እና “እናንተ”የሚሉት ጥቅሶች የእሥራኤልን ሕዝብ የሚያመለክቱ ናቸው።

ከፍ አለ
“ሹመት ሰጠው”

የእሥራኤል ሕዝብ ሆይ እንደዚህ አይደለምን?
እግዚአብሔር ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው በተናገረው ነገር ላይ አፅንዖት ለመስጠት ነው።ይሄ አድራጊ ግሥ መልክ ሊገለፅ የሚችል ነው።የአሞፅ ትርጉም “እናንተ የእሥራኤል ሕዝብ ሆይ ያልኩት ነገር እውነት እንደሆነ ታውቃላችሁ!”(አድራጊ ግሥን ወይም ተካፋይ ያልሆነ የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ንግግር
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ራሱን የሚገልፀው በስሙ ነው።የአሞፅ ትርጉም “እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን ነው ”ወይም “ይህንን የተናገርኩት እኔ እግዚአብሔር ነኝ”(አንደኛ፤ሁለተኛ፤ሶስተኛ ሰው)

Amos 2:13

ሃሣብን ማያያዝ
እግዚአብሔር በእሥራኤል ሕዝብ ላይ የፍርድ መልዕክቱን ማስተላለፉን ይቀጥላል።

አጠቃላይ መረጃ
በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ “እናንተ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእሥራኤልን ሕዝብ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አስተውል
ይሄ አንባቢው የሚቀጥለው ነገር ምን እንደሆነ ትኩረቱን እንዲያደርግ የሚያሳስብ ነው።የአሞፅ ትርጉም “አዳምጡ”ወይም “ልነግራችሁ ላሰብኩት ነገር ትኩረትን ሥጡ”

እነሆ ነዶ የተሞላች ሠረገላ እንደምትደቅቅ እንዲሁ አደቅቃችኋለሁ
በእሥራኤል ሕዝብ ላይ እግዚአብሔር የሚፈርደውን ፍርድ የሚያነፃፅረው ከባድ በሆነ ነገር ከመፍጨት ጋር ነው።

ደካማ… ብርቱ ፤ኃያል
እነዚህ ቅፅል ስሞች በአጠቃላይ ሕዝብን የሚያመለክቱ ናቸው።የአሞፅ ትርጉም “ደካማ… ብርቱ ፤ኃያል”ወይም ደግሞ “ደካማ ሰው… ብርቱሰው፤ኃያል ሰው” (አሕፅሮተ ቅፅል ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 2:15

ሃሣብን ማያያዝ
እግዚአብሔር በእሥራኤል ሕዝብ ላይ የፍርድ መልዕክቱን ማስተላለፍ ይቀጥላል።

ቀስተኛውም አይቋቋምም
እዚህ ላይ“መቋቋም” ሲባል አንድን ሥፍራ በጦርነት መያዝ ማለት ነው።

በሩጫ ፈጣን የሆነ ሰው አያመልጥም
ለነገር ያታሰበው መረጃ በሩጫ ፈጣን የሆነ ሰው እንኳን ከጠላት አያመልጥም ለማለት ነው።የአሞፅ ትርጉም “ፈጣን ሯጭ የሆነውም ይማረካል”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና ግልፅ የሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ራቁት ሆኖ መሸሽ
ከዚህ ጋር ሊሄዱ የሚችሉ ትርጉሞች 1/ “መሣሪያውን እንደያዘ ሮጠ”የሚል ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ ወይም 2/ዝም ብለን በግርድፉ የምናነበው ከሆነ ደግሞ “ልብሱን ሳይለብስ ሮጠ”ማለትም ነው።(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ ይመልከቱ)

በዚያን ቀን
“በዚያን ጊዜ”

እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ በራሱ ሥም ነው የሚናገረው።በአሞፅ 2፡111 ላይ ይሄንን እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።የአሞፅ ትርጉም “እግዚአብሔር የተናገረው ይሄንን ነው” ወይም “ይህንን የተናገርኩት እኔ እግዚአብሔር ነኝ”(የመጀመሪያውን ሁለተኛውን ወይም ሶስተኛውን አካል ተመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 የእስራኤል ሕዝብ፥ከግብጽ ምድር ያወጣኋችሁ ወገኖች ሁሉ፥እግዚአብሔር በእናንተ ላይ የሚናገረውን ይህን ቃል ስሙ፤ **2** ከምድር ወገኖች ሁሉ እናንተን ብቻ
መረጥሁ። ስለዚህ ስለ ኃጢአታችሁ ሁሉ እቀጣችኋለሁ። **3** ሁለቱ ካልተስማሙ በስተቀር አብረው ይሄዳሉን? **4** አንበሳ የሚሰብረውን ሳያገኝ በጫካ ውስጥ
ያገሳልን? የአንበሳ ደቦል ምንም ሳይዝ በዋ ሻው ውስጥ ያጉተመትማልን? **5** ማታለያ ምግብ ካልተዘጋጀለት በስተቀር ወፍ በምድር ወጥመድ ዉስጥ
ይገባልን? አንዳች ሳይዝ ወጥመድ ከምድር ይፈናጠራልን? **6** በከተማ ውስጥ መለከት ሲነፋ ሕዝቡ አይፈራምን? በከተማ ላይ ጥፋት ከመጣ የላከው
እግዚአብሔር አይደለምን? **7** በእርግጥ ጌታ እግዚአብሔር ሊያደርግ ያለውን ለአልጋዮቹ ለነቢያት ካልገለጠ በስተቀር ምንም አያደርግም። **8** አንበሳው
አገሳ፥የማይፈራ ማነው? ጌታ እግዚአብሔር ተናገረ፥ትንቢት የማይናገር ማነው? **9** ይህንን በአዛጦንና በግብጽ ምሽጎች አውጁ፥ እንዲህም በሉ፦«በሰማሪያ
ተራሮች ላይ ተሰብሰቡ፥ በውስጧ ምን ዓይነት ታላቅ ግራ መጋባትና ጭቆና እንዳለ ተመልከቱ። **10** ቅን ነገርን እንዴት እንደሚያደርጉ አያውቁምና፥ዝርፊያንና
ጥፋትን በምሽጎቻቸው አከማችተዋል።» ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው። **11** ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦«ጠላት ምድሪቱን
ይከብባል፤ምሽጎቻችሁን ያፈርሳል ይበዘብዛልም። **12** እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦«እረኛ ከአንበሳ አፍ ሁለት እግር ብቻ፥ወይንም የጆሮ ቁራጭ እንደሚያድን፥
በመከዳ ጠርዝ ብቻ ወይም በትንሽ የአልጋ ልብስ በሰማሪያ የሚኖሩ የእስራኤል ሰዎች ብቻ ይድናሉ» **13** ስሙ፥በያዕቆብም ቤት ላይ መስክሩ፥ ይላል
የሠራዊት አምላክ ጌታ እግዚአብሔር። **14** የእስራኤልን ኃጢአት በምቀጣበት ቀን የቤቴልን ም መሠዊያዎች እቀጣለሁ። የመሠዊያው ቀንዶች ይቆረጣሉ፥ወደ
ምድርም ይወድቃሉ። **15** የክረምቱን ቤት ከበጋው ቤት ጋር አጠፋለሁ። በዝሆን ጥርስ የተዋቡ ቤቶች ይጠፋሉ፥ታላላቅ ቤቶችም ይደመሰሳሉ፥» ይህ
የእግዚአብሔር አዋጅ ነው።

Amos 3:1

እንዲህ ይላል
“ይህንን መልዕክት አዳምጡ”ወይም “ይሄንን መልዕክት ስሙ”

እግዚአብሔርእናንተን በመቃወም ተናግሯል... በአጠቃላይ ወገኑን በመቃወም
“እግዚአብሔር ስለ እናንተ የተናገረው ይሄ ቃል ... በአጠቃላይ ስለ ወገኑ”ወይም “እግዚአብሔር ለእናንተ ያለው መልዕክት....ስለ ወገናችሁ በአጠቃላይ”

እናንተ የእሥራኤል ልጆች ሆይ .... ከግብፅ ምድር ያወጣኋችሁ ወገን ሁሉ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ስለሆኑ ሁለት ሕዝቦችን የሚያመለክቱናቸው። የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚላቸው ከግብፅ ምድር የወጡትን ትውልዶች ነው።

ወገን ሁሉ
እዚህ ላይ “ወገን ሁሉ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው መላ አገሪቱን ነው። የእሥራኤል ሕዝቦች ሁሉ የያዕቆብ ትውልዶች ናቸው።የአሞፅ ትርጉም “አገሪቱ በአጠቃላይ”ወይም “ነገዱ በአጠቃላይ” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ከምድር ወገን ሁሉ እናንተን ብቻችሁን አውቄችኋለሁ
ይሄ ሊታዘዙለት ይገባቸው እንደነበረ የሚያመለክት ነው።ይሄ ግልፅ በሆነ መልኩ ሊነገር ይችላል።(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትንና ግልፅ የሆነ መረጃ የሚለውን የሚለውን ይመልከቱ)

የምድር ነገዶች ሁሉ
እዚህ ላይ “ነገዶች”የሚለው ቃል አገራትንና ሕዝብን ይወክላል።የአሞፅ ትርጉም “በምድር ላይ ያሉ አገራት ሁሉ”ወይም “በምድር ላይ የሚገኙ ነገዶች ሁሉ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህ ስላደረጋችሁት ኃጢአት ሁሉ እበቀላችኋለሁ።
የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እንዳልተቀበሉ በግልፅ ማወቅ ይቻላል።የአሞፅ ትርጉም “ነገር ግን አልታዘዛችሁኝም።ስለሆነም ስላደረጋችሁት ኃጢአት ሁሉ እቀጣችኋለሁ።”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና ግልፅ የሆነ መረጃ የሚለውን)

በእውነት እግዚአብሔር ሳይናገር ምንም ነገር አይፈፅምም።...ነቢያት
ይሄ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል።የአሞፅ ትርጉም “በእውነትም እግዚአብሔር አምላክ ነገርን ወደ ግልፅ ያመጣዋል...ምንም ነገር ከማድረጉ በፊት ለነቢያት ይናገራል”ወይም “እግዚአብሔር ሰዎችን የሚቀጣው ለአገልጋዮቹ ለነቢያት ዕቅዱን ካሳወቀ በኋላ ነው።”(ሁለት አሉታዊ ነገሮች የሚለውን ይመልከቱ)

አንበሣ ሲያገሳ የማይፈራ ማን ነው?
አሞፅ አንበሣ በሚያጓራበት ወቅት ምን ሊያደርጉ እንደሚችሉ ሰዎችን በጥያቄ መልክ ያሳስባል።ይሄ እንደ መግለጫ ሊወሰድ ይችላል።የአሞፅ ትርጉም “አንበሣው አግስቷል፤ስለሆነም ሁሉም ሰው እንደሚፈራ እናውቃለን።”ወይም “አንበሳ ስላገሳ በእርግጥም ሰው ሁሉ በፍርሃት ይዋጣል።”(የተሳካ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 3:7

ጌታ እግዚአብሔር ተናገረ፤ትንቢትን የማይናገር ማነው?
አሞፅ ይህንን ጥያቄ እዚህ ላይ የሚጠይቀው እግዚአብሔር በሚናገርበት ወቅት ነቢያት የሚያደርጉትን ነገር በተመለከተ ሕዝቡ አስቀድመው ስላወቁት ነገር አፅንዖት ለመስጠት አስቦ ነው።ይሄ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊወሰድ ይችላል።የአሞፅ ትርጉም “እግዚአብሔር አምላክ ስለተናገረ ነቢያት እንደሚተነብዩ እናውቃለን።”ወይም“እግዚአብሔር አምላክ ተናግሯል፤ከዚህ የተነሣ በእርግጥም ነቢያት ይተነብያሉ።”

Amos 3:9

ተሰብሰቡ
ይሄ ትዕዛዝ በአዛጦንና በግብፅ ስላሉት ጠላቶች የተሰጠ ትዕዛዝ ነው።

ይሄ የእግዚአብሔርአዋጅ ነው
“እግዚአብሔር ያወጀው ይህንን ነው”ወይም “ያህዌ በለሆሳስ ያለው ይህንን ነው”ይሄ ሐረግ በሌላው መልዕክት ውስጥ ያለው ነገር ሁሉ እውነተኛ መሆኑን የሚገልፅ ነው።

በመካከልዋም ያለውን ግፍ ተመልከቱ
“በመካከልዋም”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሰማርያን ከተማ ነው። ከተማዎች አብዛኛውን ጊዜ ይጠሩ የነበሩት በሴት ፆታ ነበር።(ግዑዝ ነገሮች ሕይወት እንዳላቸው ተደርገው ሲገለፁ የሚለውን ይመልከቱ)

በመካከልዋም ያለውን ግራ መጋባት ተመልከቱ
እዚህ ላይ “በመካከልዋም ያለውን ግራ መጋባት ተመልከቱ” የሚለው ቃል በዚያ በሚካሄደው ጦርነትና አመፅ መካከል ሰዎች ያለባቸውን ፍርሃት ለማመልከት ነው።“ግራ መጋባት ”የሚለው ቃል ግልፅ የሆነ ትርጉም እንዲይዝ ለማድረግ በግሣዊ ሐረግ መተርጎም ይቻላል።የአሞፅ ትርጉም “በሰማርያ የሚገኙ ሰዎች እንዴት እንዳመፁ”ወይም “የሰማርያ ሰዎች እርስ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በእርሳቸው እንዴት እንደተዋጉ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀት፤ግልፅ የሆነ መረጃ የሚለውንና አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

ምን ዓይነት ነው?
“በውስጧ ያለው ጭቆና”የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው በሰማርያ ውስጥ ሰዎችን ስለሚጨቁኑ መሪዎች ነው።የሆነው “ጭቆና”የሚለው አሕፅሮተ ሥም “መጨቆን”ወይም “ለሥቃይ መዳረግ”ተብሎ ሊገለፅ ይችላል። (አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

ትክክለኛ የሆነ ነገርን ማድረግ አያውቁበትም
እዚህ ላይ “አመፅና ጥፋት”የሚለው ቃል ነገሮችን በአመፅና በማውደም መንጠቅን የሚያመለክት ነው።የአሞፅ ትርጉም “ከሌሎች ላይ በአመፅ የነጠቁትን ገሮች ያከማቻሉ” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 3:11

ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
ይሄንን ለማን ለመናገር እንደፈለገ በግልፅ ማስቀመጥ ይቻላል፡፤የአሞፅ ትርጉም “ስለሆነም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር በሠማርያ ለሚኖሩ እሥራኤላውያን የሚናገረው ይህንን ነው።”

ምድሪቱን ጠላት ይከብባታል።
ምድሪቱ በጠላት ትከበባለች

አዳራሾችዋን ይበዘብዛሉ
“በአዳራሾቻችሁ ውስጥ የሚገኙትን ነገሮች ሁሉ ይሰርቃሉ።”

እረኛ ከአንበሣ አፍ እንደሚድን...እንዲሁየእሥራኤልን ሕዝብ ይታደጋል
ጌታ እግዚአብሔር የእሥራኤልን ሕዝብ መታደግ አንድን እንስሳ ከአንበሣ አፍ ለማዳን ሊሰካ ካልቻለ ጥረት ጋር ያነፃፅረዋል።በከፊል ይድናሉ።(ተነፃፃሪነት የሚለውን ይመልከቱ)

እረኛ ከአንበሣ አፍ ውስጥ ሁለት እግሮችን ወይም የጆሮ ጫፍን ብቻ እንደሚያድን
እዚህ ላይ እረኛው የእንስሳውን ሙሉ አካል ለማስጣል ሙከራ ስለማድረጉ ነው የሚገልፀው።የአሞፅ ትርጉም “እረኛው እንስሳውን ከአንበሣ አፍ ለማስጣል የሞከረ ቢሆንም ለማዳን የቻለው ግን ሁለት እግርና የጆሮን ጫፍ ብቻ ነው።”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና ውስጣዊ ወይም ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ እረኛው ... አንበሳው
እዚህ ላይ“እረኛው” እና “አንበሳው”የተሰኙት ሐረጎች ማንኛውንም እረኛና አንበሳ የሚያመለክቱ ናቸው።(የመጀመሪያ ሥም(ሰዋሰው) ሐረጎች የሚለውን ተመልከቱ)

የአልጋ ማዕዘን ብቻ ይቀርላቸዋል
ይሄ ሐረግ ሙሉ በሙሉ ሊድኑ የማይችሉ መሆኑን ነው የሚያሣየው። ንብረታቸው ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል መልኩ የሚሰረቅ ይሆናል።ይህንን ክፍል በዕብራይስጥ ቋንቋ ለመረዳት አስቸጋሪ ሲሆን አንዳንድ የዘመኑ የትርጉም ቅጂዎች ግን ለየት ባለ መንገድ ይተረጉሙታል።

መከዳ
ይሄ ሰው ሊጋደምበት የሚልና ልስላሴ ያለው ትልቅ ወንበር ነው።

Amos 3:13

የያዕቆብ ቤት
“ቤት”የሚለው ቃል በቤት ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች በሌላ ቃል ለመጥራት የሚውል ነው።በዚህ ሁኔታ ይሄ የሚያመለክተው የያዕቆብን ትውልድ ነው ።የእሥራኤል ሕዝብ ነበሩ።የአሞፅ ትርጉም “የያዕቆብ ትውልዶች”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ሥሙን እየጠራ ስለ ራሱ ይናገራል።“ይሄ የሠራዊት የእግዚአብሔር ንግግር ነው የሚለውን ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ” በአሞፅ 2:11 ላይ ያለውን።የአሞፅ ትርጉም “የሠራዊት የሆነው ጌታ እግዚአብሔር ያወጀው ይህንን ነው ” ወይም “የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን ነው።” (መጀመሪያ፤ሁለተኛና ሶስተኛውን ክፍል የሚለውን ይመልከቱ።)

የእሥራኤልን ኃጢአት በምበቀልበት ቀን
“የእሥራኤልን ኃጢአት ስቀጣ”

የቤቴልን መሠዊያዎች እበቀላለሁ
ሰዎች የሐሰት ጣዖታትን በየመሰዊያዎቻቸው በማምለካቸው በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአትን ሠርተዋል።እዚህ ላይ “መሠዊያዎችን አፈርሳለሁ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሕዝቡን እንደሚቀጣና ጣዖቶቻቸውን የሚያጠፋ መሆኑን ነው።የአሞፅ ትርጉም “በቤቴል ውስጥ የሚገኙትን ጣዖታት አጠፋለሁ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ተመልከቱ)

የመሠዊያው ቀንዶች ይሰበራሉ ወደ ምድርም ይወድቃሉ
ይሄ አድራጊ ግሥ መልክ ሊገለፅ ይችላል።የአሞፅ ትርጉም “ጠላቶች የመሠውያውን ቀንዶች ይሰብራሉ፤ቀንዶችም በምድር ላይ ይወድቃሉ” (አድራጊ ግሥን ወይም ተካፋይ ያልሆነ የሚለውን ይመልከቱ)

የመሠዊያውን ቀንዶች
ሰዎች ጣዖታትን በየመሠዊያዎቻቸው ያመልኩ ነበር።በየመሠዊያዎቹ የማዕዘን ጫፍ ላይ የወይፈን ቀንዶች ምስል ነበረባቸው።እነዚህ ቀንዶች የጣዖቶቻቸው ጥንካሬ መገለጫዎች ነበሩ።

Amos 3:15

የክረምት ቤትና የበጋ ቤት
አንዳንድ ባለፀጋ የሆኑ ሰዎች በአንደኛው ቤታቸው ውስጥ በክረምት ወራት የሚኖሩበት ሲሆን በሁለተኛው ቤታቸው ውስጥ ደግሞ የበጋ ወራት በሚሆንበት ወቅት ይኖሩበታል።ይሄ ማንኛውንም የክረምትና የበጋ ቤቶችን ያመለክታል።የአሞፅ ትርጉም“የመጀመሪያ ሥም(ሰዋሰው) ሐረጎች የሚለውን ተመልከቱ ”

በዝሆን ጥርስ የተሰሩት ቤቶች ይጠፋሉ
እግዚእብሔር ቤቶቹ ሕይወት እንዳላቸውና ሟቾች እንደሆኑ በመቁጠር ይናገራቸዋል።የአሞፅ ትርጉም “በዝሆን ጥርስ የተሰሩት ቤቶች ይጠፋሉ”(ግዑዝ ነገሮች ሕይወት እንዳላቸው ተደርገው ሲገለፁ የሚለውን ይመልከቱ)

በዝሆን ጥርስ የተዋቡ ቤቶች
“በዝሆን ጥርስ የተዋቡ ቤቶች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በየግድግዳዎቻቸውና በቤት ቁሣቁሶቻቸው ላይ በዝሆን ጥርስ የተዋቡትን ነገሮች ነው።የዝሆን ጥርስ እጅግ ውድ ከመሆኑ የተነሳ በዝሆን ጥርስ የተዋቡ ቁሣቁሶች ያሏቸው ሰዎች ባለፀጋ የሆኑ ሰዎች ብቻ ናቸው።

የዝሆን ጥርስ
የግዙፍ እንስሳት ጥርሶችና ቀንዶች

ታላላቅ ቤቶችም ይፈርሳሉ
“ትላልቅ ቤቶች አይኖሩም”እዚህ ላይ “ይፈርሳሉ”የሚለው ቃል የሚወክለው ፈፅመው ይደመሰሳሉ የሚለውን ነው።

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እውነት ስለመሆኑ ማረጋገጫ ለመስጠት ራሱን በተመለከተ በራሱ ሥም ይናገራል።“እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን ነው”

ወይም “ሥላሴዎችየተናገሩት ይህንን ነው።” (የመጀመሪያ፤ሁለተኛና ሶስተኛ
አካል የሚለውን ይመልከቱ)

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 እናንተ የባሳን ላሞች፥በሰማሪያ ተራራ የምትኖሩ፥ድኾችን የምትጨቁኑ፥ችግረኞችን የምታደቅቁ፥ ባሎቻችሁንም «መጠጥ አምጡልን» የምትሉ ይህን ቃል ስሙ። 2 ጌታ እግዚአብሔር በቅድስናው እንዲህ ብሎ ምሎአል፦ «ተመልከቱ፥ እናንተን በመንጠቆ፥ የቀሩትንም በዓሳ መንጠቆ የ ሚወስዱበት ቀናት ይመጣል። 3 በከተማው ቅጥር ፍራሽ በኩል ትወጣላችሁ፥እያንዳንዳችሁ በእርሱ በኩል ወደ ፊት ቀጥ ብላችሁ ትሄዳላችሁ፥ወደ ሬማንም ትጣላላችሁ--ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው።» 4 ወደ ቤቴል ሂዱና ኃጢአት ሥሩ፥ወደ ጌልጌላ ሂዱና ኃጢአት አብዙ። መሥዋዕታችሁን በየማለዳው፥ አሥራታችሁንም በየሦሥተኛው ቀን አቅርቡ። 5 እርሾ ያለበትን የምስጋና መሥዋዕት ሠው፤ እናንተ የእስራኤል ሕዝብ ሆይ፥ ይህ ደስ ያሰኛችኋልና በፈቃዳችሁ የምታቀርቡትን አው ጁ፥ ስለ እነርሱም አውሩ --- ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው።» 6 የጥርስ ንፃትን በከተማዎቻችሁ ሁሉ፥ እንጀራንም ማጣትን በስፍራዎቻችሁ ሁሉ እሰጣችኋለሁ። እናንተ ግን ወደ እኔ አልተመለሳችሁም ---- ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው።» 7 ለመከር ሦሥት ወር ሲቀረው ዝናብ ከለከልኋችሁ። በአንዱ ከተማ ላይ እንዲዘንብ፥ በሌላውም ከተማ ላይ እንዳይዘንብ አደረግሁ። በአንዱ ቁራጭ መሬት ላይ ዘነበበት፥ ያልዘነበበት ቁራጭ መሬት ግን ደረቀ። 8 ሁለት ወይም ሦሥት ከተሞች ውኃ ለመጠጣት ወደ ሌላ ከተማ እየተንገዳገዱ ሄዱ፤ ነገር ግን አልረኩም። ነገር ግን ወደ እኔ አልተመለሳችሁም --- ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው።» 9 በዋግና በአረማሞ መታኋችሁ። የአትክልቶቻችሁን ብዛት፥ ወይኖቻችሁን፥ የበለስና የወይራ ዛፎቻችሁን ሁሉ አንበጦች በሉት። እናንተ ግን ወደ እኔ አልተመለሳችሁም --- ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው።» 10 «በግብጽ ላይ እንዳደረግሁባቸው መቅሰፍት ላክሁባችሁ። ወጣቶቻችሁን በሰይፍ ገደልሁ፥ ፈረሶቻችሁንም አስማረክሁ፥ የሠፈራች ሁንም ግማት ወደ አፍንጫችሁ እንዲደርስ አደረግሁ። እናንተ ግን ወደ እኔ አልተመለሳችሁም --- ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው።» 11 እግዚአብሔር ሰዶምንና ገሞራን እንደገለበጣቸው፥ በመካከላችሁ ከተሞችን ገለበጥሁ።እናንተም ከእሳት እንደተነጠቀ ትንታግ ሆናችሁ፥ እናንተ ግን ወደ እኔ አልተመለሳችሁም፥ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው።» 12 «ስለዚህ እስራኤል ሆይ አስደንጋጭ ነገር አደርግብሃለሁ፥ አስደንጋጭንም ነገር ስለማደርግብህ እስራኤል ሆይ አምላክህን ለመገናኘት ተዘጋጅ! 13 እነሆ፥ ተራሮችን የሠራ፥ነፋስንም የፈጠረ፥ አሳቡንም ለሰው የሚገልጥ፥ ንጋትን ጨለማ የሚያደርግ፥የምድርንም ከፍታዎች የሚረግጥ» ስሙ የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር ነው።

Amos 4:1

እናንተ የባሳን ላሞች ሆይ ፤እናንተ በሰማርያ ተራሮች ላይ የምትኖሩ
አሞፅ በሰማርያ ለምትኖር እሥራኤላዊ ሴት ውስጥ ከጠገቡ ላሞች ጋር በማመሳሰል ይነግራታል።የአሞፅ ትርጉም “በሰማርያ ተራራ ላይ የምትኖሩ እናንተ ባለፀጋ የሆናችሁ ሴቶች፤ ከጠገቡ የባሳን ላሞች ጋር የምትመሳሰሉ”(ምሣሌያዊ አነጋገርን ይመልከቱ)

ድሆችን የምትጨቁኑ
“ድሆች”የሚለው ቃል ድሃ የሆኑ ሰዎችን የሚያመለክት ነው።የአሞፅ ትርጉም “እናንተ ድሃ ሰዎችን የምትጨቁኑ”(አሕፅሮተ ቅፅል ሥምን ይመልከቱ)

ችግረኞችን የምታስጨንቁ
“ማስጨነቅ”የሚለው ቃል ሰዎችን መልካም ባልሆነ አያያዝ መያዝን የሚያመለክት ነው።“ችግረኞች”የሚለው ሐረግ ዕርዳታ የሚሹ ሰዎችን የሚያመለክት ነው።የአሞፅ ትርጉም “እናንተ ችግረኞችን የምታስጨንቁ”ወይም “የተቸገሩ ሰዎችን የምትጎዱ”(ምሣሌያዊ አነጋገርና አሕፅሮተ ቅፅል ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

ጌታ እግዚአብሔር በቅዱስነቱ ምሏል
ይሄ ማለት እግዚአብሔር አንድ ነገር ለማድረግ ቃል መግባቱንና የገባውን ቃል የሚፈፅመው ቅዱስ በመሆኑ ነው ማለት ነው።

እነሆ ቀን በእናንተ ላይ ይመጣል
“እናንተ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በሰማርያ ውስጥ የሚገኙ የእሥራኤል ሴቶችን ሲሆን ወንዶቹንም ያካትታል።

እነርሱ እናንተን በመቃጥን የሚወስዱበት ቀን ይመጣል
ቀናቶቹ ራሣቸው ጥቃት የሚፈፀሙባቸው ይመስል በሕዝቡ ላይ ክፉ ነገሮች እንደሚመጡ ይናገራል።“እነርሱ”የሚለው ቃል ጠላቶቻቸውን የሚያመለክት ነው።የአሞፅ ትርጉም “ጠላቶቻችሁ እናንተን በመጠንቆ የሚወስዱበት ጊዜ ይመጣል” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በወጥመድ ጠምደው ይወስዷችኋል፤ቅሬታችሁንም በዓሣ መያዣ መንጠቆ ይይዛችኋል
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሣሣይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ሰዎች ልክ እንደ ዓሣ በሰዎች ሊያዙ እንደሚችሉ አፅንዖት የሚሰጥ ነው። የአሞፅ ትርጉም “ልክ እንስሳ እንደሚያዝ ይዘው ይወስዷችኋል”ወይም ደግሞ “ክፉኛ ያሸንፏችሁና በጭካኔ እየጎተቱ ይወስዷችኋል”(ንፅፅርንን እና ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 4:3

ሃሣብን ማያያዝ
እግዚአብሔር ለእሥራኤል ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል

በሬማንም ትጣላላችሁ
ይሄ እንደ አድራጊ ግሥ ሊገለፅ ይችላል።የአሞፅ ትርጉም “ወደ ሬማንም ይጥሏችኋል”ወይም “እንድትሄዱ ያስገድዷችኋል” (አድራጊ ግሥን ወይም ተካፋይ ያልሆነ የሚለውን ይመልከቱ)

ሬማን
ይሄ የማናውቀው የአንድ ቦታን ሥም ወይም የሬማን ተራራ የሚያመለክት ነው። አንዳንድ ዘመናዊ የሆኑ ቅጂዎች በዚያ መልኩ ይተረጉሙታል።(ሥሞችን እንዴት እንደምትተረጉሙ ተመልከቱ)

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
የተናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለመግለፅ እግዚአብሔር ስለራሱ የራሱን ስም በመጥቀስ ይናገራል።እነዚህን ቃላት በአሞፅ 2፤11 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።የአሞፅ ትርጉም “እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን ነው”ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርኩት ይህንን ነው”(መጀመሪያ፤ሁለተኛና ሶስተኛ አካል የሚለውን)

Amos 4:4

ሃሣብን ማያያዝ
እግዚአብሔር ለእሥራኤላውያን መናገሩን ይቀጥላል

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር በቁጥር 4 ላይ አጠቃላይ የሆኑ ትዕዛዛትን የሚሰጥ ቢሆንም ይህንን የሚያደርገው ግን መቆጣቱን ለመግለፅ ነው።

ወደ ቤቴል ሄዳችሁ ኃጢአትን ሥሩ፤ወደ ጌልጌላ ሄዳችሁ ኃጢአትን አብዙ
ሰዎች መሥዋዕትን ለማቅረብ ወደ ቤቴልና ወደ ጌልጌላ የሚሄዱ ቢሆንም ይሄንን የሚያከናውኑት ግን ኃጢአትን በመፈፀም ጭምር ነበር።እግዚአብሔር ይሄንን ትዕዛዝ የሚያስተላልፈውእነዚህን ተግባራት በመፈፀማቸው በእነርሱ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ላይ ቁጣውን ለመግለፅ ነው።እነዚህ ትዕዛዛት በመግለጫ መልኩ ሊገለፁ ይችላሉ።የአሞፅ ትርጉም “እናንተ ወደ ቤቴል የምትሄዱት ለአምልኮ ቢሆንም ኃጢአትን ታደርጋላችሁ።አምልን ለማድረግ ወደ ጌልጌላ ትሄዳላች የምትሄዱት ግን የበለጠ ኃጢአትን ለማድረግ ነው።”(ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

በየማለዳውም መሥዋዕታችሁን፤በየሦስተኛውም ቀን አሥራታችሁን አቅርቡ...በፈቃዳችሁም የምታቀርቡትን አውጁና አውሩ
እግዚአብሔር ይህንን ትዕዛዝ የሚያስተላልፈው ምንም እንኳን እነዚህን መልካም የሚመስሉ ነገሮችን ቢያደርጉም በሌላ በኩል ኃጢአት መሥራታቸውን ባለማቋረጣቸው ነው።እነዚህ ትዕዛዛት እንደ መገለጫ ሊወሰዱ ይችላሉ።የአሞፅ ትርጉም“መሥዋታችሁን አምጡ ...በየሶስተኛውም ቀናት የምሥጋና መሥዋዕትን ሰው፤የምታቀርቡትንም አውጁና አውሩ”(ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

በየሶስተኛውም ቀናት
ከዚህ ጋር ሊስማሙ የሚችሉ ትርጉሞች 1/በሶስተኛው ቀን ወይም 2/ በየሶስት ቀናት። እሥራኤላውያን አሥራታቸውን በየሶስት ዓመቱ ያወጡ ስለነበረ አንዳንድ ቅጂዎች “በየሶስት ዓመት”ይሉታል።

አውጁት
“ከእነርሱ የተነሣ ኩሩ”

እናንተ የእሥራኤል ሕዝብ ሆይ ይሄ ያረካችኋል
እግዚአብሔር በሚሰጡት ሥጦታና በሚሰውት መሥዋዕት ስለሚኩራሩ ይገስፃቸዋል።እግዚአብሔር ደስ ይለዋል ብለው ቢያስቡም እርሱ ግን ደስ አልተሰኘባቸውም።የአሞፅ ትርጉም “የእሥራኤል ሕዝብ ሆይ ይሄ ያስደስታችኋል እኔን ግን አያስደስተኝም”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና ግልፅ ያልሆነ መረጃን ይመልከቱ)

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
የተናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለመግለፅ እግዚአብሔር በራሱ ሥም ይናገራል።በአሞፅ 2፤11 ላይ ይሄንን ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።የአሞፅ ትርጉም “ጌታ እግዚአብሔር የሚናገረው ይህንን ነው”ወይም “ይህንን የተናገርኩት እኔ እግዚአብሔር ነኝ”(መጀመሪያ፤ሁለተኛና ሶስተኛ አካል)

Amos 4:6

ሐሣብን ማያያዝ
እግዚአብሔር ለእሥራኤል ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል።

የጥርስ ማጥራትንአደረግኩላችሁ
እዚህ ላይ የጥርስ ማጥራት የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጥርስን ሊያቆሽሽ የሚችል ምግብ በአፍ ውስጥ አለመገባቱን ነው።የአሞፅ ትርጉም “እንድትራቡ አደረግኋችሁ” ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

እንጀራን ማጣት
“እንጀራን ማጣት” ሰጠኋችሁ የሚለው ቃል እንጀራ እንዲያጡ ምክኒያት እንደሚሆንባቸው መግለፁ ሲሆን “እንጀራ”የሚለው ቃል ደግሞ የሚያመለክተው በአጠቃላይ የምግብ ዘርን ነው።

ወደ እኔ አልተመለሳችሁም
ወደ እግዚአብሔር መመለስ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ራስን እንደገና ለእርሱ ማስገዛትን ነው።የአሞፅ ትርጉም “እንደገና ለእኔ አልተገዛችሁም” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከቱ)

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
የተናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለመግለፅ እግዚአብሔር በራሱ ሥም ይናገራል።ይናገራል።እነዚህን ቃላት በአሞፅ 2፤11 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“ጌታ እግዚአብሔር የሚናገረው ይሄንን ነው”ወይም “ይሄንን የተናገርኩት እኔ እግዚአብሔር ነኝ”(መጀመሪያ፤ሁለተኛና ሶስተኛ አካል)

ዝናብም ከለከልኳችሁ
“በሰብላችሁ ላይ ዝናብ እንዳይዘንብ ከለከልኩ”

መከርን ለመሰብሰብ ገና ሶስት ወራት ሲቀሩ
ሕዝቡ ዝናብ እንደሚያስፈልጋቸው በግልፅ ሊነገር ይችላል።የአሞፅ ትርጉም “መከር ለመሰብሰብ ገና ሶስት ወራት በቀረበት ወቅት ሰብሎቻችን ዝናብ ያስፈልጋቸው ነበር” (በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በአንዱ ወገን ዝናብ ዘንቧል
ይሄ በአድርጊ ግሥ ሊገለፅ ይችላል።“አንዱ ወገን”የሚለው ቃል የሚወክለው ማንኛውንም የተወሰነየመሬት ክፍል ነው።የአሞፅ ትርጉም “በቁራጭ መሬት ላይ ዘነበ”ወይም “በተወሰኑ የመሬት ክፍሎች ላይ ዘነበ” (አድርጊ ግሥን ወይም ተካፋይ ያልሆነ የሚለውን ይመልከቱ)

ዝናብ ያልዘነበበት ምድር
ይሄ የሚያመለክተው ዝናብ ያልዘነበበትን ማንኛውንም ሥፍራ ነው።የአሞፅ ትርጉም “ዝናብ ያልዘነበበት የተወሰ የመሬት ክፍል” (የመጀመሪያ ሥም(ሰዋሰው) ሐረጎች የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 4:8

ሁለት ወይም ሶስት የተጎዱ ከተማዎች
እዚህ ላይ “ከተማዎች” የሚለው ቃል የሚመለክተው የዚያ ከተማ ነዋሪዎችን ነው።የአሞፅ ትርጉም “የሁለት ወይም የሶስት ከተማ ሕዝቦች ተንገዳገዱ።”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

በዋግውና በአረማሞ መታኋችሁ
እዚህ ላይ “መታኋችሁ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሰብላቸውን መውደም ነው።”የአሞፅ ትርጉም “እህላችሁን በዋግና በአረማሞ መታሁባችሁ”ወይም“እህላችሁን በዋግና በአረማሞ ደመሰስኩት”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ዋግ
ይሄ ዕፅዋትን የሚደርቅና የሚገድል ነገር ነው።

ወደ እኔ አልተመለሳችሁም
“ወደ እግዚአብሔር መመለስ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ራስን ለእግዚአብሔር ፈፅሞ እንደገና ማስገዛትን ነው።ይሄንን በአሞፅ 4፡6 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።ነው።የአሞፅ ትርጉም“ራሳችሁን እንደገና ፈፅሞ አላስገዛችሁልኝም።” (ምሣሌያዊ አነጋገርን ይመልከቱ)

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
የተናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለመግለፅ እግዚአብሔር በራሱ ሥም ይናገራል።እነዚህን ቃላት በአሞፅ 2፤11 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“ጌታ እግዚአብሔር የሚናገረው ይህንን ነው”ወይም “ይህንን የተናገርኩት እኔ እግዚአብሔር ነኝ”(መጀመሪያ፤ሁለተኛና ሶስተኛ አካል)

Amos 4:10

በግብፅ እነደነበረው ቸነፈርን ሰደድኩባችሁ
“በግብፅ ላይ እንዳደረግኩት እንዲሁ በእናንተም ላይ ቸነፈርን ላክሁ”ወይም “በግብፅ ላይ ቸነፈርን እንደላክሁ እንዲሁ በእናንተም ላይ ቸነፈርን እልካለሁ”

ቸነፈርን ላክሁባችሁ
“በእናንተ ላይ አሰቃቂ ነገር እንዲሆንባችሁ አደረግኩ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጎበዛዝታችሁን በሠይፍ ገደልኩ
እዚህ ላይ“በሠይፍ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጦርነትን ነው። እግዚአብሔር ጠላቶች እንዲነሱባቸውና እንዲዋጉዋቸው በማድረግ በሕይወት እንዳይኖሩ አደረጓቸው።አሞፅ ትርጉም“ጠላቶቻችሁ በጦርነት ወቅት ሰዎቻችሁን እንዲገድሉ አደረግኳቸው።” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ፈረሶቻችሁን ሁሉ በመማረክ ይዘው ሄዱ
እግዚአብሔር ጠላቶቻቸው ፈረሶቻቸውን እንዲወስዱ ማድረጉን ልክ ራሱ እንደፈፀመው ዓይነት አስመስሎ ይናገራል።የአሞፅ ትርጉም “ጠላቶቻችሁ ፈርቸችሁን እንዲወስዱባችሁ አደረግኩ።”

የሠፈራችሁንም ግማት ወደ አፍንጫችሁ እንዲወጣ አደረግኩ
ግማት መጥፎ የሆነ ሽታ ነው።ግማቱ እስከ አፍንጫቸው ድረስ መምጣቱ የሚያመለክተው ፈፅሞ ደስ የማይል ነገር እያሸተተ መሆናቸውን ነው።ሽታው የሚመጣው ከሞቱ ሰዎች አካል እነደሆነ በግልፅ ያመለክታል።የአሞፅ ትርጉም “በሠፈራችሁ ውስጥ ደስ የማይል የሞቱ ሰዎችን አካላት እንድታሸቱ አደረግኳችሁ” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ከእሣት ውስጥ እንደ ተነጠቀ ትንታግ
እዚህ ላይ እግዚአብሔር የሚናገረው በዚያ በጦርነትና በቸነፈር ወቅት ልክ አንድ ሰው በትርን ከእሣት ጎትቶ እንደሚያወጣ በሕይወት ተርፈው ያሉትን ሰዎች የሚመለከት ነው።(አንድ ሰው ከእሣት ውስጥ ጎትቶ እንደሚያወጣው በትር አንዳንዶቻችሁ በሕይወት ቆያችሁ።) (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እኔ አልተመለሳችሁም
ወደ እግዚአብሔር መመለስ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ራስን ለእርሱ እንደገና ፈፅሞ ለእግዚአብሔር ማስገዛትን ነው።ይሄንን በአሞፅ 4:6 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።የአሞፅ ትርጉም“ራሳችሁን እንደገና ፈፅሞ አልተገዛችሁልኝም።” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
የተናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለመግለፅ እግዚአብሔር በራሱ ሥም ይናገራል።እነዚህን ቃላት በአሞፅ 2፤11 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“ጌታ እግዚአብሔር የሚናገረው ይህንን ነው”ወይም “ይህንን የተናገርኩት እኔ እግዚአብሔር ነኝ”(መጀመሪያ፤ሁለተኛና ሶስተኛ አካል)

Amos 4:12

ሃሣብን ማያያዝ
እግዚአብሔር ለእሥራኤል ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል።

አምላካችሁን ለመገናኘት ተዘጋጁ
እግዚአብሔር ይህንን የሚያደርገው በእሥራኤል ሕዝብ ላይ ፍርድ እንደሚፈርድባቸው ለማስጠንቀቅ ነው።(መጀመሪያ፤ሁለተኛና ሶስተኛ አካልና)

እነሆ ተራረሮችን የሠራ ...የልቡንም ሃሣብ የሚገልፅ..ስሙ...ነው
እዚህ ላይ አሞፅ ስለ እግዚአብሔር እንደሚናገር ወይም እግዚአብሐር ስለራሱ እንደሚናገር ግልፅ አይደለም።እግዚአብሔር ስለ ራሱ የሚናገር ከሆነ “እኔ” ወደሚሉ ቃላት ሊተረጎም ይችላል።የአሞፅ ትርጉም “እኔ ተራራሮችን የምሰራ.....ሃሣቤን የምገልፅ...ስሜ .... ነው።”(መጀመሪያ፤ሁለተኛና ሶስተኛ አካልና በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትየሚለውን ይመልከቱ)

ንጋትን ጨለማ የሚያደርግ
ከዚህ ጋር ሊሄዱ የሚችሉ ትርጉሞች 1/እግዚአብሔር የቀን ብርሃን እያለ ከባድ ደመና በማምጣት ቀኑን ድቅድቅ ጨለማ ሊያደርገው ይችላል።የአሞፅ ትርጉም “ማለዳን ጨለማ ሊያደርግ ይችላል።”ወይም 2/እግዚአብሔር ቀናት በአስቸኳይ እንዲያልፉ በማድረግ እያንዳንዱ ቀን ጨለማ እንዲሆን ያደርገዋል።የአሞፅ ትርጉም “ማለዳና ምሽት ያደርጋል”

በምድር ከፍታዎች ላይ የሚረግጥ
እግዚአብሔር በምድር ሁሉ ላይ ገዢ እንደመሆኑ በምድር ከፍታዎች ላይ የሚራመድ እንደሆነ ይናገራል።የአሞፅ ትርጉም “በምድር ሁሉ ላይ ይገዛል”ወይም “በምድር ላይ የሚገኙትንና ከፍታ ያላቸውን ቦታዎች እንኳን ይገዛል።”(ምሣሌያዊን አነጋገርን ይመልከቱ)

ስሙ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው
ሙሉ ስሙን በማወጅ እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች እንደሚፈፅም ይናገራል። ቋንቋችሁ ሰዎች ይህንን እንዲያደርጉ የሚያደርግበት መንገድ ሊኖረው ይችላል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 5

1 የእስራኤል ቤት ሆይ፥ይህን ቃል ይኽውም በእናንተ ላይ የማሰማውን የሐዘን እንጉርጉሮ ስሙ። 2 ድንግሊቱ እስራኤል ወደቀች፤ ከእንግህም ወዲያ አትነሳም፥ በራሷ ምድር ላይ ተተወች፤ የሚያነሳትም ማንም የለም። 3 ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦«ለእስራኤል ቤት ሺህ ታወጣ የነበረች ከተማ መቶ ይቀርላታል፥ መቶም ታወጣ የነበረች ከተማ አሥር ይቀርላታል።» 4 ከዚህ የተነሳ እግዚአብሔር ለእስራኤል ቤት እንዲህ ይላል፦ «እኔን ፈልጉ፥በሕይወትም ኑሩ! 5 ጌልጌላ በእርግጥ ትማረካለችና፥ በቴልም ታዝናለችና፤ ቤቴልን አትፈልጉ፥ወደ ጌልጌላ አትግቡ፥ ወደ ቤርሳቤህም አትሂዱ። 6 እግዚአብሔርን ፈልጉ፥በሕይወትም ኑሩ፤ይህ ካልሆነ በዮሴፍ ቤት ላይ እንደ እሳት ይነሳል። ይበላል፥ በቤቴልም የሚያጠፋው ማንም የለም። 7 እነዚያ ሰዎች ፍትህን ወደ መራራ ነገር ለውጠዋልና፥ ጽድቅንም ወደ ምድር ጥለዋልና። 8 ሰባቱን ከዋክብትና ኦርዮንን የፈጠረ አምላክ፥ ጨለማን ወደ ንጋት ይለውጣል፥ ቀኑን በሌሊት ያጨልማል፥ የባሕርንም ውኃ ጠርቶ በምድር ፊት ላይ ያፈሳቸዋል። ስሙ እግዚአብሔር ነው! 9 ምሽጉ እንዲፈርስ ድንገትኛ ጥፋትን ያመጣል። 10 በከተማይቱ በር ላይ የሚያርማቸውን ማንንም ጠሉ፥ እውነትን የሚናገረውን ማንንም ተጸየፉ። 11 ድኻውን ረግጣችኋልና፥ የስንዴውን ም ድርሻ ከእርሱ ወስዳችኋልና፤ ከተጠረበ ድንጋይ ቤቶችን ብትሠሩም አትኖሩባቸውም። ያማሩ የወይን ተክል ቦታዎች አሉአችሁ፥ የወይን ጠጃቸውን ግን አትጠጡም። 12 እናንተ ጻድቁን የምታጥቁ፥ ጉቦ የምትቀበሉ፥ በከተማይቱም በር ችግረኛውን የምትገለብጡ፤ በደላችሁ እንዴት ብዙ እንደሆን፥ ኃጢአታችሁም እንዴት ታላቅ እንደሆን እኔ አውቃለሁ። 13 ጊዜው ክፉ ነውና፥ አስተዋይ የሆነ ማንም በእንደዚህ ዓይነቱ ጊዜ ዝም ይላል። 14 በሕይወት ትኖሩ ዘንድ መልካሙን ፈልጉ፥ ክፉውንም አይደለም። እርሱም እንደተናገራችሁት ነውና፥ የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር በእርግጥ ከእናንተ ጋር ይሆናል። 15 ክፉውን ጥሉ፥ መልካሙንም ውደዱ፥ በከተማይቱም በር ፍትሕን አጽኑ፤ ምናልባት የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር ለዮሴፍ ቅሬታ ይራራ ይሆናል። 16 ሰለዚህ ጌታ የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ «በአደባባዮቹ ሁሉ ዋይታ ይሆናል፥ በየመንገዶቹ ወዮ! ወዮ! ይላሉ። ገበሬዎችን ለለቅሶ፥ አልቃሾችንም ለዋይታ ይጠራሉ። 17 እኔ በመካከልህ አልፋለሁና፥ በወይን ተክል ቦታዎች ሁሉ ዋይታ ይሆናል» ይላል እግዚአብሔር። 18 የእግዚአብሔርን ቀን ለምትፈልጉ ወዮላችሁ! የእግዚአብሔርን ቀን ለምን ትፈልጋላችሁ? ጨለማ ነው እንጂ ብርሃን አይደለም። 19 አንድ ሰው ከአንበሳ ሲሸሽ ድብ እንደሚያጋጥመው፥ ወደ ቤት ገብቶ እጁን ግድግዳ ላይ ሲያስደግፍ እባብ እንደሚነድፈው ነው። 20 የእግዚአብሔር ቀን ብርሃን ሳይሆን ጨለማ አይደለምን? ብሩህ ሳይሆን ደብዛዛ አይደለምን? 21 ዓመት በዓላችሁን ጠልቼዋለሁ፥ ተጸይፌዋለሁም፤በጉባዔዎቻችሁ ደስ አይለኝም። 22 የሚቃጠለውን መሥዋዕታችሁንና የእህል ቁርባናችሁን ብታቀርቡልኝ እንኳን አልቀበላቸውም፤ ወይም ወደ ሰቡ እንስሶቻችሁ የኅብረት መሥዋዕት አልመለከትም። 23 የመዝሙሮችህን ጩኽት ከእኔ አርቅ፤ የበገናህንም ድምጽ አልሰማም። 24 በዚያ ፈንታ ፍትሕ እንደ ውኃ፥ ጽድቅም ሳያቋርጥ እንደሚመነጭ ምንጭ ይፍሰስ። 25 የእስራኤል ቤት ሆይ በምድረ በዳው ለአርባ ዓመታት መሥዋዕትንና ቁርባንን አቅርባችሁልኝ ነበርን? 26 ለራሳችሁ የሠራችኋቸውን ጣዖታት፥ ሞሎክን እንደ ንጉሣችሁ፥ሬፋን እንደ ኮከብ አምላካችሁ አንሥታችሁ ትሸከማችሁ። 27 ስለዚህ ከደማስቆ ማዶ እስማርካችኋለሁ» ይላል፥ ስሙ የሠራዊት አምላክ የሆነው እግዚአብሔር።

Amos 5:1

የእሥራኤል ቤት
“ቤት”የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች የተሰጠ ሌላ ቃል ነው። በዚህ ሁኔታ የእሥራኤልን ትውልድ ያመለከታል።የአሞፅ ትርጉም “እናንተ የእሥራኤል ሕዝብ”ወይም “እናንተ የእሥራኤል ነገዶች”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

የእሥራኤል ድንግል ወደቀች ...ከእንግዲህ ወዲህ አትነሣም
“ድንግሊቷ እሥራኤል”የሚለው ቃል የእሥራኤልን ሕዝብ የሚያመለክት ነው። አንድ ወጣት ልጅ በውድቀት ውስጥ ሆና የሚታደጋት ሰው እንዳጣች ዓይነት የእሥራኤል ሕዝብ የሚጠፋ እንደሆነና ዳግም ጠንካሮች ሆነው እንዳይወጡ የሚያግዛቸው አገር እንደማይኖር ነው የሚናገረው።ኤቲ “የእሥራኤል ሕዝብ እንደወደቀች ወጣት ልጅ...ከውድቀቷ የሚያነሳት አንድ ሰው እንኳን የለም”(ምሣሌያዊ አነጋገርን ይመልከቱ)

በራሷ አገር ተገፍታለች
ይሄ በአድራጊ ግሥ መልክ ሊገለፅ ይችላል።የአሞፅ ትርጉም “ሰዎች ትተዋታል” ወይም “አግልለዋታል”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 5:3

ሺህ ከሚወጣባት ከተማ መቶ ይቀርላታል፤መቶም ከሚወጣባት ከተማ ለእሥራኤል አሥር ይቀርላታል
እነዚህ ሐረጎች ብዙ ወታደሮችን የሚልኩ ከተማዎችን የሚያመለክት ነው። የአሞፅ ትርጉም “በሺዎች የሚቆጠሩ ተዋጊዎችን ይዛ የወጣች ከተማ ... በመቶዎች የሚቆጠሩ ተዋጊዎችን ይዛ የወጣች”(የመጀመሪያ ሥም(ሰዋሰው) ሐረጎች የሚለውን ይመልከቱ)

በሺዎች የሚቆጠሩ ተዋጊዎችን ይዛ የወጣች ከተማ... በመቶዎች የሚቆጠሩ ተዋጊዎች ብቻ ይቀሩላታል
“በሺዎች”እና “በመቶዎች” የሚሉት ሐረጎች እስከ ሺህና እስከ መቶ የሚደርሱ ወታደሮች መኖራቸውን የሚያመለክት ነው።(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ መቶ ተዋጊዎች ይቀርላታል
“ግድያ ያልተፈፀመባቸው መቶ ተዋጊዎች ይኖራችኋል”ወይም “በሕይወት የሚኖሩ መቶ ተዋጊዎች ብቻ ይኖራችኋል።”እዚህ ላይ “ይቀርላታል” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በጠላት እጅ ያልተገደሉትን ነው።

Amos 5:4

እኔን ፈልጉኝ
እዚህ ላይ“ፈልጉኝ”የሚለው ቃል ወደ ቤቴል በመሄድ እግዚአብሔር እንዲረዳቸው መጠየቅን የሚያመለክት ነው።የአሞፅ ትርጉም “ዕርዳታ ለመሻት ወደ ቤቴል አትሂዱ”(ምሣሌያዊ አነጋገርን ይመልከቱ)

ወደ ጌልጌላም አትግቡ
“እና ወደ ጌልጌላ አትግቡ”

በእርግጥ ጌልጌላ በምርኮነት ትወሰዳለች
እዚህ ላይ “ጌልጌላ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የጌልጌላን ሕዝብ ሲሆን “በምርኮነት መወሰድ” የሚለው ቃል ደግሞ የሚያመለክተው በምርኮኛነት ተይዞ መወሰድን ነው።የአሞፅ ትርጉም“በእርግጥ ጌልጌላ በምርኮነት ትወሰዳለች”ወይም “በእርግጥም ጠላቶቻችሁ የጌልጌላን ሕዝብ በኃይል በመያዝ ይዘዋቸው ይሄዳሉ።”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ቤቴልም ከንቱ ትሆናለች
እዚህ ላይ “ከንቱ ትሆናለች”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጥፋቷን ነው። የአሞፅ ትርጉም “ቤቴል ፈፅሞ ትጠፋለች”ወይም “ጠላቶች ቤቴልን መሉ ለሙሉ ያወድሟታል”(ምሣሌዊ አነጋገርን ይመልከቱ)

Amos 5:6

እግዚአብሔርን ፈልጉት
እዚህ ላይ “እግዚአብሔርን ፈልጉት” የሚለው ቃል ከእርሱ ዕርዳታን መፈለግን የሚያመለክት ነው።የአሞፅ ትርጉም “እግዚአብሔር እንዲረዳችሁ ጥሩት”ወይም “እኔ እግዚአብሔርን ለዕርዳታ ጠይቁኝ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ እሣት ይነሳል
“እንደ እሣት ይነሳል”የሚለው ቃል የሚወክለው እሣት ነገሮችን እንደሚያጠፋ እንዲሁ የነገሮችን መውደም ነው።የአሞፅ ትርጉም ተነፃፃሪ”

የዮሴፍ ቤት
ይሄ ሐረግ ለዮሴፍ የዘር ሐረግ እንደ ሌላ ስም የተሰጠ ነው።እዚህ ላይ የሚያመለክተው አብዛኛው የዘር ሐረጋቸው ከዮሴፍ ትውልድ የሆኑትንና በሰሜኑ የእሥራኤል ግዛት የሚገኙትን ነገዶች ነው።የአሞፅ ትርጉም “የዮሴፍ ትውልዶች”ወይም “እሥራኤል”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ይበላል
“እርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው እሣቱን ሲሆን “ይበላል” የሚለው ቃል የሚመለክተው ደግሞ ሁሉንም ነገር ፈፅሞ የሚያጠፋ መሆኑን ነው። እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር የሚያጠፋ መሆኑን ለማመልከት እሣት ሁሉንም ነገር ከማጥፋቱ ጋር ተነፃፅሯል።የአሞፅ ትርጉም “ሁሉን ነገር ያጠፋል”ወይም “ሙሉ በሙሉ ያጠፋል”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሚያቆመው ሰው አይኖርም
“የሚያቆመው አይኖርም”ወይም “ሁሉንም ነገር ለማጥፋት የሚያቆመው ነገር አይኖርም”

ፍርድን ወደ እሬት ነገር ለወጡ
እዚህ ላይ “እሬት”የሚለው ቃል የሚወክለው ሰዎችን የሚጎዳ ድርጊትን ሲሆን “ፍርድን ወደ እሬት ነገር ለወጡ”የሚለው ቃል ደግሞ መልካም ነገርን ከማድረግ ይልቅ ሰዎችን የመጉዳትን ሃሣብ የሚያመለክት ነው።የአሞፅ ትርጉም “ፍትሃዊ የሚመስል ነገርን እያደረጉ እነርሱ ግን ሰዎችን ይጎዳሉ”ወይም “ትክክለኛ የሆነውን ነገር እየተቃወሙ ከዚያ በተቃራኒው ሰዎችን የሚጎዳ ነገርን ይሰራሉ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ፅድቅንም በምድር ላይ ይጥላሉ
ይሄ የሚያመለክተው ፅድቅን እንደማይረባ ነገር መቁጠራቸውን ነው።የአሞፅ ትርጉም “ፅድቅን አስፈላጊ እንዳልሆነ ቆሻሻ ነገር መቁጠር”ወይም “ፅድቅ የሆነውን ነገር ትፀየፋላችሁ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 5:8

ሰባቱን ከዋክብትና ኦርዮን የተባለውን ኮከብ
ሰዎች በሰማይ ከዋክብት ላይ ያለሉን ሥርዓቶች በመመልከት ስም አውጥተውላቸዋል።ሁለቱ ሥርዓቶች እነዚህ ናቸው።የአሞፅ ትርጉም “ከዋክብቶቹ” እና“የከዋክብት ክምችቶቹ” (ያልታወቁ ነገሮችን ይመልከቱ)

የሞትን ጥላ ወደ ንጋት የሚለውጠው ...ቀኑንም በሌሊት የሚያጨልመው
“የሌሊቱን ጨለማ ማለዳ ያደርገዋል እንዲሁም ቀኑን ጨለማ ያደርገዋል” ይሄ ለወቅቶች የጊዜ መለዋወጥ ምክኒያት የሚሆነውን የሚያመለክት ነው።

የባህሩንም ውሆች ጠርቶ በምድር ላይ የሚያፈስሳቸውን
ይሄ የሚያመለከተው እግዚአብሔር የባህርን ውሃ በዝናብ መልክ በምድር ላይ እንዲዘንብ ማድረጉን ነው።የአሞፅ ትርጉም “የባህር ውሆችን ይወስድና በምድር ገፅ ላይ እንዲዘንቡ ያደርጋቸዋል”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ስሙ እግዚአብሔር ነው
እግዚአብሔር ስሙን በሚያውጅበት ወቅት እነዚህን ነገሮች ተግባራዊ ለማድረግ ኃይሉንና ሥልጣኑን ነው የሚያውጀው።

በብርቱዎች ላይ ድንገተኛ ጥፋትን ያመጣል
“ጥፋት” የሚለው አሕፅሮተ ሥም “ጥፋት ይመጣል”ከሚለው ግሥ አንፃር ሊተረጎም ይችላል።“ብርቱዎች”የሚለው ቃል ጠንካራ የሆኑ ሰዎችን በተለይም ወታደሮችን የሚያመለክት ነው።የአሞፅ ትርጉም “በብርቱዎች ላይ ድንገተኛ ጥፋትን ያመጣል”ወይም “ወታደሮቹን በድንገት ያጠፋቸዋል”(አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

ጥፋት በተቀጠረ ቅጥር ላይ ይመጣ ዘንድ
“ጥፋት” የሚለው -አሕፅሮተ ሥም“ጥፋትን አደረገ”ከሚለው ግሥ አንፃር ሊተረጎም ይችላል።የአሞፅ ትርጉም “ቅጥሮቹ ይደመሰሱ ዘንድ”ወይም “ቅጥሮቹን ያፈርሳል”(አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 5:10

ማንኛውንም ሰው ይፀየፋሉ
“የእሥራኤል ሕዝብ ማንኛውንም ሰው ይፀየፋሉ።”

እናንተ ድሃውን ረግጣችኋልና የስንዴውንም ቀረጥ ከእነርሱ ወስዳችኋልና
“እናንተ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእሥራኤልን ሕዝብ ነው።እዚህ ላይ “እየረገጣችሁ”የሚለው ቃል ደሃ የሆኑ ሰዎች መጥፎ በሆነ ሁኔታ መያዛቸውን ነው።የአሞፅ ትርጉም“ ድሃ ሰዎችን በከፍተኛ ደረጃ እየጨቆናችሁ የተወሰነ ስንዴ ትወስዱባቸዋላችሁ።”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የተወሰነውን የስንዴ ክፍል ከእርሱ ውሰድ
“የተወሰነውን የስንዴ ክፍል እንዲሰጥህ አድርገው”

ድንጋይን ሰሩ
“ድንጋዮችን መጥረብ”ወይም “ሰዎች የጠረቧቸው ”

የእነርሱን የወይን ጠጆች አትጠጡም
“የእነርሱ ” ቃል የሚያመለክተው የወይን እርሻዎችን ነው።ይሄ በመሠረቱ ማንም ሰው ወይንን እንደማይጠምቅና ወይንን ለመጥመቅ ቢፈልጉ እንኳን መልካም የሆነ የወይን ፍሬ ሊገኝ እንደማይችል ለማመልከትም ሊሆን ይችላል። የአሞፅ ትርጉም“በወይን አርሻዎቻችሁ ውስጥ ከሚገኙ ወይኖች ለራሳችሁ ወይንን አትጠምቁም”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 5:12

እውነተኛየሆኑ ሰዎችን አስጨንቁ፤ጉቦን ተቀበሉ እንዲሁም የተቸገረውን ወደ በሩ አደባባይ ውሰዱ
እነዚህ ጥቂት የሆኑ የሰሯቸው የኃጢአቶቻቸው ዝርዝሮች ናቸው።

ትክክለኛ
“ትክክለኛ” የሚለው ቃል እውነተኛ የሆኑ ሰዎችን የሚያመለክት የአሕፅሮተ ቅፅል ሥም(ሰዋሰው) ነው።የአሞፅ ትርጉም “ትክክለኛ ሰዎች”ወይም “ፃድቅ ሰዎች”(አሕፅሮተ ቅፅል ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

ጉቦን ተቀበሉ
“ሰዎች ክፉ ነገሮችን እንድትሰሩ ለማድረግ ጉቦን ይክፈሏችሁ”ወይም “ሰዎች ስለሌላ ሰዎች በውሸት እንድትናገሩ ገንዘብ ይክፈሏችሁ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የተቸገረውን ወደ ከተማው አደባባይ ውሰዱ
እዚህ ላይ “የተቸገረውን ወደ ከተማው አደባባይ ውሰዱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ድሃ ሰዎች ወደ ሌላ ሥፍራ እንዲሄዱ ማስገደድን ነው።ድሃ ሰዎች በከተማው አደባባይ የሆኑበትን ምክኒያት ግልፅ ለማድረግ ይቻላል። የአሞፅ ትርጉም “ድሃ ሰዎች በከተማ ደጅ ውስጥ ለሚገኙ ዳኞች ጉዳያቸውን እንዳያቀርቡ አድርጉ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና ግልፅ ያልሆነ የሚለውን ይመልከቱ)

የተቸገሩ ሰዎች
“የተቸገሩ ሰዎች” የሚለው ቃል የተቸገሩ ሰዎችን የሚያመለክት አሕፅሮተ ቅፅል ሥም ነው።የአሞፅ ትርጉም“የተቸገሩ ሰዎች”(አሕፅሮተ ቅፅል ሥምን ይመልከቱ)

አስተዋይ የሆነ ሰው ሁሉ ዝምይላል
ክፉ ሰዎች እንዳይጎዷቸው የሚፈልጉ ሰዎች ክፉ ሥራዎቻቸውን ተቃውመው ከመናገር ተቆጥበዋል።የአሞፅ ትርጉም “አስተዋይ ሰዎች ክፉ ሰዎች የሚያደርጉትን ክፉ ነገሮች ከመናገር ተቆጥበዋል።”

ክፉ ዘመን ነውና
እዚህ ላይ“ክፉ ዘመን”የሚለው ቃል ሰዎች ክፉ መሆናቸውንና ክፉ ተግባር መፈፀማቸውን የሚያመለክት ነው።(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል)

Amos 5:14

መልካሙን እሹ፤ ክፉውን ነገር ተፀየፉ
“ክፉ ሥራዎችን ተፀየፉ፤መልካም የሆኑ ሥራዎችን ውደዱ” “መልካም” እና “ክፉ”መልካም የሆኑ ድርጊቶችንና ክፉ የሆኑ ድርጊቶችን ይወክላሉ።

በከተማው አደባባይ ፍትህን አድርጉ
እዚህ ላይ “ፍትህን አድርጉ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ፍትህ ስለመረጋገጡ እርግጠኛ መሆንን ነው።የአሞፅ ትርጉም“በከተማው አደባባይ ላይ ፍትህ መከናወኑን እርግጠኛ ሁኑ” ወይም “በእነዚህ የከተማ አደባባዮች ላይ ዳኞቹ ፍትህን ስለ ማድረጋቸው እርግጠኞች ሁኑ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በከተማው አደባባይ ላይ
የከተማው የአደባባይ ደጆች ወፍራምና ጠንካራ በመሆናቸው ሰዎች ከሞቃቱ የፀሐይ ትኩሣት ራሣቸውን የሚያስጠልሉበት ከመሆኑም ባሻገር የንግድ ልውውጥ የሚደረግባቸውና ዳኝነት የሚሰጥባቸው ሥፍራዎች ነበሩ። የአሞፅ ትርጉም “በፍርድ አደባዮቻችሁ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የዮሴፍ ቅሬታ
እዚህ ላይ “ቅሬታ”የሚለው ቃል ሌሎቹ ከተገደሉና በምርኮ ከተወሰዱ በኋላ በእሥራኤል አገር ውስጥ የሚቀሩትን ሰዎች የሚያመለክት ነው።እዚህ ላይ “ዮሴፍ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው አብዛኛዎቹ የዮሴፍ የዘር ሐረግ የሆኑትን በሰሜን ክፍል ያለውን የእሥራኤል ግዛት ነው። በአሞፅ 5፤6 ላይ “የዮሴፍ ቤት”የሚለውን ቃል እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።የአሞፅ ትርጉም “እስከ አሁን ድረስ በሕይወት ያሉ የዮሴፍ የዘር ሐረጎች”ወይም “በሕይወት የተረፉ እሥራኤላውያን” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 5:16

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
“የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የሚናገረው ይሄንን ነው”

በየመንገዱ ሁሉ ላይ ወዮ ወዮ ይባላል
“ሰዎች በየሜዳው ያለቅሳሉ”

ዋይታ
ረዥም ጊዜ የሚወስድ፤ከፍተኛ ድምፅ ያለበት የሚያሳዝን ለቅሶ

በበሩ አደባባይ
በከተማ ውስጥ የሚገኙና ሰዎች የሚሰባበሰቡባቸው ሠፋፊ ሥፍራዎች

አልቃሾችም ወደ ዋይታ ይጠራሉ
“ይጠራሉ”የሚለው ቃል ከዓረፍተ ነገሩ መጀመሪያ ጀምሮ ሃሣቡ ግልፅ ነው። የአሞፅ ትርጉም “አልቃሾችን እንዲያለቅሱ ይጠሯቸዋል”(ምልክቶች እንጂ ቃላት ጥቅም ላይ የማይውሉበት የሚለውን ይመልከቱ)

በመካከላችሁ አልፋለሁ
እግዚአብሔር በተወሰኑ ሰዎች መካከል ወቅት ወደ እነርሱ እንደሚመጣና በመካከላቸው እያለፈ የሚቀጣቸው በሚመስል መልኩ ይናገራል።የአሞፅ ትርጉም “መጥቼ እቀጣችኋለሁ”ወይም “እቀጣችኋለሁ”

Amos 5:18

የእግዚአብሔር ቀን እንዲመጣ ለምን ትናፍቃላችሁ?
እግዚአአብሔር ይሄንን ጥያቄ የእግዚአብሔር ቀን በፍጥነት እንዲመጣ በመናፈቃቸው ሊገስፃቸው የተናገረው ነው።ይሄ እንደ መግለጫ ሊገለፅ ይችላል።የአሞፅ ትርጉም “የእግዚአብሔርን ቀን ናፈቃችሁ” ወይም “የእግዚአብሔርን ቀን መናፈቅ የለባችሁም”(በሙያ የታገዘ ጥያቄ የሚለውን ተመልከቱ)

ጨለማ ነው እንጂ ብርሃን አይሆንም
እዚህ ላይ“ጨለማ”የሚያመለክተው ጥፋት የሚከሰትበትን ወቅት ሲሆን “ብርሃን”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ደግሞ መልካም ጊዜ የሚከሰትበትን ወቅት ነው።የአሞፅ ትርጉም “የጨለማና የጥፋት ጊዜ እንጂ የብርሃንና የበረከት ጊዜ አይሆንም”ወይም “በዚያን ዕለት ጥፋት እንጂ በረከት አይኖርም”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በውኑ የእግዚአብሔር ብርሃን ሣይሆን ጨለማ አይደለምን?
ይሄ ጥያቄ አፅንዖት የሚሰጠው መጥፎ ነገሮች የሚከናወኑ መሆኑን ነው። እንደ መግለጫ ሊገለፅ ይችላል።የአሞፅ ትርጉም “የእግዚአብሔር ቀን በእርግጥም ጨለማ እንጂ ብርሃን አይሆንም”ወይም “በእግዚአብሔር ቀን በእርግጥ መልካም ያልሆኑ ነገሮች ይከሰታሉ”(በሙያ የታገዘ ጥያቄ የሚለውን ተመልከቱ)

ድቅድቅ ጨለማ አንጂ ብርሃን አይሆንም
“በውኑ የእግዚአብሔር ቀን”የሚሉትን ቃላት ከቀደመው ዓረፍተ ነገር መረዳት ይቻላል።ከዚህ በፊት እንደነበረው ጥያቄ በእግዚአብሔር ቀን አሰቃቂ ነገሮች፤መልካም ያልሆኑ ነገሮች እንደሚከሰቱ አፅንዖት ሰጥቶ ይናገራል።ይሄ አንደ መግለጫ ሊነገር ይችላል።“መልካም ነገር ሣይሆን ክፉ ነገሮች የሚከሰቱበት ጊዜ ይሆናል።”(በሙያ የታገዘ ጥያቄንና ተመሣሣይነት የሚለውን ተመልከቱ)

Amos 5:21

ዓመት በዓላችሁን ጠልቼዋለሁ፤ተፀይፌዋለሁም
“ዓመት በዓላችሁን”የሚለው ቃል “ጥላቻ”ለሚለው ቃል ትልቅ መግለጫ ነው።እነዚህ ሁለቱ ቃላት በጋራ ሲነገሩ እግዚአብሔር ዓመት በዓላቸውን ምን ያህል እንደጠላው ትልቅ ማሣያ ነው።የአሞፅ ትርጉም “ዓመት በዓላችሁን በጣም እጠላዋለሁ”

የተቀደሰውም ጉባዔያችሁ ደስ አያሰኙኝም
“የተቀደሱት ጉባዔዎቻችሁ ደስ አያሰኙኝም”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Amos 5:23

የዝማሬህንም ጩኸት ከእኔ ዘንድ አርቅ
ይሄ የዝማሬው ጩኸት ልክ እነደ ዕቃ ወደ ሌላ ሥፍራ ሊወሰድ የሚችል በሚመስል መልኩ ነው የተገለፀው።ይሄ የሚያመለክተው ዝማሬው መቆም ያለበት መሆኑን ነው።የአሞፅ ትርጉም “የጩኸት ዝማሬያችሁን መዘመሩን አቁሙ”

ጩኸት
ደስ የማሰኝ ድምፅ

ነገር ግን ፍርድ እንደ ውኃ፤ፅድቅም እንደማይደርቅ ፈሳሽ ይፍሰስ
ይሄ ቃል የሚያመለክተው ብዙ ፍትህና ፅድቅ እንዲኖር ምክኒያት ስለመሆን ነው።የአሞፅ ትርጉም “እንደሚፈስስ ውኃ ይሆን ዘንድ ብዙ ፍትህ ይኑር፤ሳያቋርጥ እንደሚፈስስ ምንጭ ይሆን ዘንድ ፅድቅ ይኑር” ወይም “ፍትህ እንደ እንደ ፈሳሽ ይክበብ፤ፅድቅም እንደማይቋረጥ ምንጭ ይክበብ።”(ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 5:25

እሥራኤል ሆይ መሥዋዕትን አቅርባችሁኛልን?
የዚህ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉ 1/እግዚአብሔር ይሄንን ጥያቄ ያነሣው መሥዋዕትን ባለማቅረባቸው ሊገስፃቸው ፈልጎ ነው ወይም ደግሞ 2/ እግዚአብሔር ይሄንን ጥያቄ ያነሣው ከእርሱ ጋር ያላቸውን ግንኙነት በተመለከተ መሥዋዕት እጅግ አስፈላጊው ነገር እንዳልሆነ ሊያሳስባቸው ፈልጎ ነው።የአሞፅ ትርጉም“እሥራኤል ሆይ መሥዋዕት ልታመጡልኝ አያስፈልጋችሁም ነበር” (በሙያ የታገዘ ጥያቄ የሚለውን ተመልከቱ)

አቅርባችሁኛልን?
እግዚአብሔር እየተናገራቸው ያሉትን እሥራኤላውያን የሚናገራቸው ልክ በበረሃ ሲጓዙ ከነበሩት ወገኖች ጋር እንደነበሩ አስመሰሎ ነው።የአሞፅ ትርጉም “የቀደሙት አባቶቻችሁ አምጥተውልኛል?” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

የእሥራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤት ወስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ሌላው ሥም ነው። በዚህ አውድ ውስጥ ይሄ የሚያመለክተው የእሥራኤልን ትውልዶች ነው። በአሞፅ 5:1 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።የአሞፅ ትርጉም“እናንተ የእሥራኤል ቤት ሆይ” ወይም “እናንተ የእሥራኤል ነገድ የሆናችሁ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

የሞሎክን ድንኳንና የሬፋን ኮከብ አነሳችሁ
እዚህ ላይ“ኮከብ አነሳችሁ”የሚለው ቃል እነርሱን ማምለካቸውን የሚያመለክት ነው።“የሞሎክን ኮከብ አነሳችሁ ...የሬፋንንንም”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ሞሎክ ...ሬፋን
እነዚህ የሁለት ጣዖታት ሥሞች ናቸው።ሰዎች እነርሱን እንዲወክሏቸው ጣዖታትን ቀርፀዋል።(ሥሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ ተመልከቱ)

ሬፋን
አንዳንድ ቅጂዎች ይሄንን“ኪዩም”ብለው ይተረጉሙታል።

Amos 5:27

መዋቅር ያለውና በሕግ የተገደበ
ከቁጥር 9 እና 10 በስተቀር ይሄ ምዕራፍ በቅኔያዊ ዘይቤ መፃፉን ይቀጥላል።እነዚህ ሁለት ጥቅሶች ብዙ ሳቢ የሆኑ ገፅታዎችን ያዘሉ ናቸው።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሌሎች አስቸጋሪ ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች
ሁኔታው ግልፅ ባለመሆኑና ዝርዝር ነገሮቹን በቀላሉ ማገጣጠም አስቸጋሪ በመሆኑ ቁጥር 9-10ን ለመተርጎም አስቸጋሪ ያደርገዋል።እነዚህን ጥቅሶች በእግባቡ ለመተርጎም ከቀሩት አንዳንድ አጠራጣሪ ነገሮች ጋር አይያዞ መተርጎሙ ይበጃል።እነዚህን ጥቅሶች ከመተርጎም በፊት በቅድሚያ የተለያዩ ቅጂዎችን ማንበቡ ጠቃሚ ይሆናል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 6

1 በጽዮን በምቾት፥በሰማሪያ ተራሮች ላይ ያለ ስጋት ለሚኖሩ፥የእስራኤል ቤት ለርዳታ ወደ እነርሱ ለሚመጡባችው፥ ለታላላቅ የሕዝብ አለቆች ወዮላቸው! 2 መሪዎቻችሁ እንዲህ ይላሉ፦«ወደ ካልኔ ሂዱና ተመልከቱ፥ከዚያም ወደ ታላቂቱ ከተማ ወደ ሐማት እለፉ፥ ከዚያም ወደ ፍልስጤም ጌት ውረዱ። እነርሱ ከእናንተ ሁለት መንግሥታት የተሻሉ ናቸውን? የእነርሱ ድንበር ከእናንተ ድንበር ይሰፋልን?» 3 የጥፋትን ቀን ለምታርቁ፥የግፍንም መንበር ለምታቀርቡ ወዮላችሁ! 4 ከዝሆን ጥርስ በተሠሩ አልጋዎች ላይ ይተኛሉ፥በመከዳዎቻቸውም ላይ ይዝናናሉ። ከበጎች መንጋ ጠቦትን፥ከበረትም ጥጃን ይበላሉ። 5 በበገና ድምጽ ጣዕም የሌለው ዜማ ያዜማሉ፥ እንደ ዳዊት በተገኘው የሙዚቃ መሣሪያ መጫወት ይሻሉ። 6 በዋንጫ የወይን ጠጅ ይጠጣሉ፥ ከሁሉ በተመረጠ ዘይት ይቀባሉ፥ ነገር ግን በዮሴፍ መጥፋት አያዝኑም። 7 ስለዚህ ከመጀመሪያዎቹ ምርኮኞች ጋር ወደ ምርኮ ይሄዳሉ፥ የሚዝናኑቱ ድግሶችና ፈንጠዚያዎች ያከትማሉ። 8 እኔ ጌታ እግዚአብሔር በራሴ ምያለሁ፥ ይህ የሠራዊት አምላክ የጌታ እግዚአብሔር አዋጅ ነው፦«የያዕቆብን ትዕቢት ተጸይፌአለሁ፥ ምሽጎቹንም ጠልቼአለሁ። ስለዚህ ከተ ማይቱን በውስጧ ካሉት ሁሉ ጋር አሳላፌ አሰጣለሁ።» 9 እንዲህም ይሆናል፤ በአንድ ቤት አሥር ሰዎች ቢቀሩ ሁሉም ይሞታሉ። 10 የሰው ዘመድ አስከሬኖቹን ለመውሰድ በመጣ ጊዜ፤ አስከሬኖቹን ከቤት አውጥቶ የሚያቃጥላቸው ሰው፥ በቤት ውስጥ ያለውን ሰው፦«ከአንተ ጋር ሌላ ሰው አለን?» ሲለው፤ ሰውዬውም፦ «ማንም የለም» ብሎ በመለሰለት ጊዜ፥ እርሱም፦«ዝም በል፥ የእግዚአብሔርን ስም መጥራት አይገባንምና» ይለዋል። 11 ተመልከቱ፥ እግዚአብሔር ትዕዛዝ ይሰጣል፤ ትልቁም ቤት ይሰባበራል፥ ትንሹም ቤት ይደቅቃል። 12 ፈረሶች በጭንጫ ላይ ይሮጣሉን? ሰውስ በዚያ ላይ በበሬዎች ያርሳልን? እናንተ ግን ፍትሕን ወደ መርዝነት፥ የጽድቅንም ፍሬ ወደ መራርነት ለውጣችኋል። 13 እናንተ ሎዶባርን በማሸነፋችሁ ደስ ያላችሁ፥ «ቃርናይምን በራሳችን ብርታት አልወሰድንምን?» የምትሉ፤ 14 «ነገር ግን፥ የእስራኤል ቤት ሆይ አነሆ ሕዝብን አስነሣባችኋለሁ»፥ ይህ የሠራዊት አምላክ የጌታ እግዚአብሔር አዋጅ ነው። «ከሐማት መግቢያ አንስቶ እስከ ዓረባ ወንዝ ድረስ ያስጨንቋችኋል።»

Amos 6:1

ተዘልለው ለተቀመጡ
“ተዘልለው የተቀመጡ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰዎች ምቹ ሁኔታ ውስጥ ከመኖራቸው የተነሣ ስለ እግዚአብሔር ፍርድ ብዙም ትኩረት የማይሰጡ መሆኑን ነው።

ምርጥ የሆነው አገር ውስጥ የሚኖሩ የተከበሩ ሰዎች
“በዚህ ታላቅ አገር ውስጥ የሚኖሩ የተከበሩ ሰዎች”የሚለው ቃል ምናልባትም እግዚአብሔር እነዚህ ሰዎች ስለራሣቸው ያላቸውን አስተሳሰብ በተመለከተ በምፀት የሚናገረው ነገር ሊሆን ይችላል።የአሞፅ ትርጉም “ምርጥ በሆነ አገር ውስጥ ምርጥ የሆንን ሰዎች ነን ብለው የሚያስቡ ሰዎች”

የእሥራኤልም ቤት ይመጣል
“ቤት” የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች እንደ አጠቃላይ መጠሪያ ነው።በዚህ አውድ አንፃር የእሥራኤልን የዘር ሐረግ የሚመለከት ነው።የአሞፅ ትርጉም“የእሥራኤል ነገድ እየመጣ ነው።” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ሊረዳ መጣ
እዚህ ላይ“መጣ” የሚለው ቃል “ይሄዳል”ተብሎ ሊገለፅ ይችላል።የአሞፅ ትርጉም “ለመርዳት ይሄዳል” (መሄድና መምጣት የሚለውን ተመልከቱ)

ካልኔ
ይሄ የከተማ ሥም ነው።(ሥሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ ተመልከቱ)

ከሁለቱ መንግሥታቶች ይልቅ የተሻሉ ናቸውን?
ታዋቂ የሆኑ ሰዎች ይህንን ጥያቄ ከሌሎች መንግሥታት ይልቅ የእሥራኤልና የይሁዳ መንግሥታት የተሻሉ ናቸው የሚለውን ሃሣብ አፅንዖት ለመስጠት ይጠቀሙበታል።የአሞፅ ትርጉም “የእናንተ ሁለት መንግሥታት ከእነርሱ ይልቅ የተሻሉ ናቸው”(በሙያ የታገዘ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ድንበራችሁ ከድንበራቸው ይልቅ ይሰፋልን?
ታዋቂ የሆኑ ሰዎች ይህንን ጥያቄ ከሌሎች መንግሥታት ይልቅ የእነርሱ መንግሥታት የተሻሉ ናቸው የሚለውን ሃሣብ አፅንዖት ለመስጠት ይጠቀሙበታል።የአሞፅ ትርጉም“ከእናንተ ይልቅ ድንበሮቻቸው ያነሱ ናቸው”ወይም “እነዚያ አገራት ከይሁዳና ከሰማርያ ይልቅ አነስተኞች ናቸው።”(በሙያ የታገዘ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 6:3

ክፉውን ቀን ከእናንተ ለምታርቁ
እግዚአብሔር ጥፋትን ሊያመጣ አይችልም የሚል አስተሳሰብን ልክ ሰዎች “የጥፋት ቀንን” እንደ ዕቃ ከአጠገባቸው ዘወር እንደሚያደርጉት ዓይነት ነገር ተገልጿል።የአሞፅ ትርጉም “ይሄንን ለማመን የማይፈልጉትን ሰዎች ጥፋትን እንዲለማመዱ አደርጋቸዋለሁ።” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የግፍንም ወንበር ለምታቀርቡ
እዚህ ላይ “ወንበር” የሚለው ቃል ግዛትንንና መግዛትን የሚያመለክት አጠቃላይ ሥም ነው።እዚህ እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ጥፋትን እንዲያመጣ ክፉ ሥራዎቸን የሚሰሩ ሰዎች “አመፅን” በመሥራት አመፁ ራሱ በላያቸው ላይ እንዲሰለጥን እንደፈቀዱ ተደርጎ ነው የተገለፀው።የአሞፅ ትርጉም “ለመሆኑ ክፉ የሆኑ ሰዎች እንዲያጠፏችሁ እንድልክ ምክኒያት የሆኑት ሰዎች እነማን ይሆኑ?” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውለውን ቃል ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለምትተኙ...በምንጣፋችሁ ላይ
በዚያን ወቅት እስራኤላውያን ምግባቸውን የሚመገቡት መሬት ላይ በተነጠፈ ጨርቅ ላይ ወይም ተራ የሆነ መቀመጫን በመጠቀም ነበር።

በዝሆን ጥርስ የተሰሩ አልጋዎች
“በዝሆን ጥርስ የተዋቡ አልጋዎች” ወይም “ውድ የሆኑ አልጋዎች”

የዝሆን ጥርስ
ግዙፍ ከሆኑ እንስሳት የሚገኙ ነጭ ጥርሶችና ቀንዶች (የማይታወቁ የሚለውን ተርጉሙት)

ምንጣፍ
እንደ ሰነፍ ሰዎች መተኛት

መከዳ
ለመተኛት የሚበቃ ለስላሣ የሆነ መቀመጫ

Amos 6:5

የዜማን ዕቃ የምታዘጋጁ
ለዚህ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት 1/አዳዲስ ዝማሬዎችንና እነዚህን ዝማሬዎች በሙዚቃ መሣሪያዎች ለመጫወት አዳዲስ ፈጠራዎችን ይፈጥራሉ።2/ አዳዲስ የሙዚቃ መሣሪያዎችን ይሰራሉ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በፉጋ ወይን ጠጅ ይጠጣሉ
ይሄ የሚያመለክተው ከተለመደው የወይን መጠጫ ይልቅ ትልቅ የወይን መጠጫን ስለሚጠቀሙ ብዙ ወይንን ይጠጣሉ የሚለውን ነው።(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውለውን ቃልና ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ ዮሴፍ መከራ አያዝኑም
እዚህ ላይ“ዮሴፍ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የዘር ሐረጉን ነው።የአሞፅ ትርጉም “በቅርብ ጊዜያት ውስጥ በጠላቶቻቸው ስለሚጠፉት የዮሴፍ ትውልዶች አያዝኑም”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 6:7

ስለዚህ በምርኮ መጀመሪ ይማረካሉ
“ወደ ምርኮ ከሚጋዙት ሰዎች የመጀመሪያዎቹ ይሆናሉ”ወይም “በመጀመሪያ በምርኮነት እልካቸዋለሁ”

ተደላድለው ከተቀመጡበት ዘንድ ዘፈን ይርቃል
“ተዘልለው ድግስ የሚደግሱበት ምቹ የሆነ ጊዜ አይሆንላቸውም”

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
የሚናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ እግዚአብሔር ስለራሱ በራሱ ሥም ይናገራል።በአሞፅ 3፤143 ላይ ይሄንን እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።የአሞፅ ትርጉም“ይሄ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የተናገረው ቃል ነው”ወይም “ይሄ እኔ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የተናገርኩት ቃል ነው።”(መጀመሪያ፤ሁለተኛና ሶስተኛ አካል የሚለውን ይመልከቱ)

የያዕቆብን ትዕቢት ተፀይፌያለሁ
እዚህ ላይ “ያዕቆብ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የያዕቆብን ትውልድ ነው። የአሞፅ ትርጉም “ማስተዋል የሌላቸው ከመሆናቸው የተነሣ የያዕቆብን ቤት ተፀየፍኩ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

አዳራሾቹንም ጠልቻለሁ
እግዚአብሔር አራሾቻቸውን የጠላው አዳራሾቻቸው ለሠላማችን መሠረቶች ናቸው ብለው ስለሚምኑ ነው።የአሞፅ ትርጉም “የእሥራኤልን ሕዝብ የጠላሁበት ምክኒያት በእኔ ሣይሆን በአዳራሾቻቸው ስለሚታመኑ ነው።”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውንና ግልፅ ያልሆነ የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 6:9

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር የእሥራኤልን ሕዝብ ለጠላቶቻቸው አሣልፎ በሚሰጥበት ወቅት ሊፈጠሩ ይችላሉ ብሎ የገመታቸውን ሁኔታዎች በአሞፅ 6:9-10 ላይ ይገልፀዋል።(ግምታዊ ሁኔታዎች የሚሉትን ይመልከቱ)

አሥር ሰዎች በአንድ ቤት ውስጥ ቢቀሩ እነርሱ ይሞታሉ
ይሄ የሚያመለክተው አሰቃቂ ነገር እንደሚከናወንና እነዚህ አሥር ሰዎች ለመደበቅ ወደ ቤት ውስጥ የሚገቡ መሆኑን ነው።የአሞፅ ትርጉም“አሥር ሰዎች ቤት ውስጥ የሚደበቁ ቢሆኑም እንኳን እነርሱም ይሞታሉ።”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውንና ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አጥንቱንም ከቤቱ ያወጡ ዘንድ የሰው ዘመድና አቃጣዩ ባነሱት ጊዜ በቤቱም ውስጥ ያለውን እስከ አሁን ድረስ ገና ሰው በአንተ ዘንድ አለን? ባለው ጊዜ...
የእነዚህ ቃላት ትርጉም ግልፅ አይደለም።ለእነዚህ ፍቺ ሊሆኑ የሚችሉት 1/ “የሰዎቹ ቤተሰብ” የሚባለው ሰው “አካላቸውን ወስዶ” “ሬሣቸውን የሚያቃጥለውን” ሰው ሲሆን ይህ ሰው አሥሩ የቤተሰቡ አባላት ሕይወት ካለፈ በኋላ በቤት ውስጥ ተደብቆ ከነበረ ሰው ጋር እየተነጋገረ ነው ወይም 2/ “ሬሣቸውን ለመውስድ የሚመጣው ሰው”“የሰዎቹ የቅርብ ዘመድ”“ሬሣውን ከሚገንዘው ሰው የተለየ ሰው ነው”እርስ በእርሳቸውም በቤት ውስጥ ይነጋገራሉ።የአሞፅ ትርጉም“የሰዎቹ የቅርብ ዘመዶች ሬሣዎቹን ወስደው ከቤቱ ውስጥ ከወጡ በኋላ ሬሣዎቹን የሚያቃጥለው ሰው ደግሞ ከእነርሱ ጋር አብሮ ይሄዳል...በቤት ውስጥ በነበሩበት ወቅት ቅርብ ዘመዳቸው የሆነው ሰው ሬሣዎቹን ለሚያቃጥለው ሰው “በአንተ ዘንድ አለን?”ብሎታል።

ሬሣን ማቃጠል የሞተን የሰው አካል ማቃጠል ሬሣዎችን ማምጣት
“የሞተ አካልን መሰብሰብ”

የእግዚአብሔርን ሥም እንጠራ ዘንድ አይገባንምና ዝም በል ይለዋል
የዚህ ትርጉም ግልፅ አይደለም።ይሄ ጥያቄውን የጠየቀው ሰው ፍርሃት እንደያዘውና የሚመልሰውም ሰው የእግዚአብሔርን ሥም በግድየለሽነት እንደሚጠራ ነው የሚያመለክተው።ይህንን የሚያደርግ ከሆነ የእግዚአብሔርትኩረት ወደ እነርሱ በመሳብ በሕይወት እንዳይኖሩ ሊያደርጋቸውም ይችላል።(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውንና ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 6:11

ተመልከቱ
“ስሙ”ወይም “ትኩረታችሁን ወደዚህ አድርጉ”

ታላቁንም ቤት በማፍረስ፤ታናሹንም ቤት በመሰባበር ይመታል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆኑ ትርጉሞች ያላቸው ናቸው።“ትልቁ ቤት”እና “ትንሹ ቤት”በሚለው መካከል ያለው ንፅፅር ትርጉም ሁሉንም ቤቶች የሚመለከት ጉዳይ መሆኑን ነው።(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

ታላቁንም ቤት ያፈርሳል
ይሄ በአድራጊ ግሥ ሊገለፅ ይችላል።የአሞፅ ትርጉም“ጠላት ትልቁን ቤት ወደ ፍርስራሽነት ይለውጠዋል።”(አድራጊ ግሥንና ተካፋይ ያልሆነ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ፍርስራሽነት...ወደ አመድነት
ለእነዚህ ሐረጎች ሁለቱንም ቃላት መጠቀም ትችላላችሁ።

ታናሹንም ቤት በመሰባበር
ይሄ ሰዎች በገባቸው መረጃ አኳያ ሊገለፅ የሚችል ነው።የአሞፅ ትርጉም “ጠላቶች ትንሹን ቤት ወደ አመድነት ይለውጡታል።” (ቃላትን ሳይጠቀሙ ሃሣብን በምልቶች(ሥነፅሑፋዊ) መግለፅ የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 6:12

አጠቃላይ መረጃ
ግሣፄን ያደርግ ዘንድ ሃሣባቸውን ወደ እርሱ እንዲሰበስቡ ለማድረግ አሞፅ ሁለት የበሰሉ ጥያቄዎችን ያቀርባል።

ፈረሶች በጭንጫ ላይ ይጋልባሉን?
አንድ ፈረስ ጉዳት ሳይደርስበት በዓለታማ ኮረብታዎች ላይ ሊጋልብ አይችልም።አሞፅ እነዚህን ሁለት የበሰሉ ጥያቄዎችን የጠየቀው አድራጎታቸውን ለመገሰፅ ነው።የአሞፅ ትርጉም “ፈረሶች በዓለታማ ኮረብቶች ላይ ሊሮጡ አይችሉም።”(በሙያ የታገዘ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በሬዎች በዚያ ላይ ያርሳሉን?
ሰው በዓለታማ ሥፍራ ላይ ሊያርስ አይችልም።አሞፅ እነዚህን ሁለት ሪቶሪክ ጥያቄዎችን የጠየቀው አድራጎታቸውን ለመገሰፅ ነው።የአሞፅ ትርጉም “ሰው በዓለታማ ሥፍራ ላይ በበሬ አያርስም።”(በሙያ የታገዘ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ፍርድን ወደ ሀሞት ለውጣችኋል
ትክክለኛ የሆነ ነገርን የማዛባት ጉዳይ መሪዎች“ፍትህን ወደ ሐሞትነት”እንደለወጡ ተደርጎተነፃፅሯል።የአሞፅ ትርጉም“ትክክለኛ የሆነ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ነገርንታጣምማላችሁ” ወይም “ቅን ሰዎችን የሚጎዱ ሕጎችን ታወታላችሁ።”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የፅድቅንም ፍሬ ወደ ሐሞት
ይሄ ከመጀመሪያው የዓረፍተ ነገር ክፍል ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው። ትክክለኛ ነገሮችን ማዛባት ሰዎች የፅድቅን ፍሬ በመውሰድ ወደ መራራ ጣዕም እንደለወጡትተደርጎ ተነፃፅሮ።የአሞፅ ትርጉም “ትክክለኛ የሆነ ነገርን ታጣምማላችሁ ”ወይም “ትክክለኛ ነገር ያደረጉትን ሰዎች ትቀጣላችሁ”(ንፅፅርና ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሐማትና...ዓረባ
እነዚህ የከተማ ስሞች ናቸው።(እነዚህን ስሞች እንዴት እንደምትተረጉሟቸው እዩ)

ዓረባን በኃይላችን ቀንድ ወሰድን አይደለንምን?
ሰዎቹ በራሣቸው ኃይል ከተማዋን እንደወሰዱትአፅንዖት ለመስጠት በጥያቄ መልክ ያቀርባሉ።የአሞፅ ትርጉም “ዓረባን የያዝናት በራሣችን ጉልበት ነው” (በሙያ የታገዘ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 6:14

እዩ
“ስሙ”ወይም “ትኩረት ሥጡ”

የእሥራኤል ቤት
“ቤት ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰዎችን ነው።የአሞፅ ትርጉም“የእሥራኤል ሕዝብ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር እንዲህ ይላል
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ስለ ራሱ በራሱ ሥም ይናገራል።ይሄንን በአሞፅ 3፤13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።የአሞፅ ትርጉም“የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር እንዲህ ይላል”ወይም “ይህንን የተናገርኩት የሠራዊት ጌታ እኔ እግዚአብሔር ነኝ።”(የመጀመሪያ፤ሁለተኛና ሶስተኛ አካልን ይመልከቱ)

ከሐማት ጀምሮ እስከ ዓረባ ወንዝ ድረስ
እዚህ ላይ“ሐማት”የሚለው ቃል የእሥራኤል ሰሜናዊ ክፍልን የሚያመለክት ሲሆን “የዓረባ ወንዝ”ደግሞ ደቡባዊውን ክፍል የሚያመለክት ነው።የአሞፅ ትርጉም “ከሰሜናዊው የአገራቸው ድንበር ጀምሮ እስከ ደቡባዊ ድንበር ድረስ ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)“

የምንጭ ጅረት
በክረምት ወራት ብቻ የሚፈስስ አነስተኛ የሆነ ወንዝ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 7

1 ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ አሳየኝ። እነሆ፥የጸደይ አዝመራ መብቀል በሚጀምርበት ጊዜ የአንበጣን መንጋ ፈጠረ፥ ተመለከትሁም፥ ከንጉሥ አጨዳ በኋላ
ዘግይቶ የበቀለ አዝመራ ነበር። 2 የምድሪቱን ሣር በልተው ከጨረሱ በኋላ፤ «ጌታ እግዚአብሔር ሆይ እባክህ ይቅር በል፥ ያዕቆብ በዚህ ውስጥ እንዴት
ይቆማል? እርሱ ታናሽ ነውና» አልሁ። 3 እግዚአብሔርም ስለዚህ ነገር ተጸጸተ፤ «ይህ አይሆንም» አለ። 4 ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ አሳየኝ፦እነሆ፥ ጌታ
እግዚአብሔር በእሳት ለመፍረድ ጠራ። እርሱም በምድር ውስጥ የሚገኘውን ሰፊና ጥልቅ ውኃ አደረቀ፥ ምድሪቱንም ደግሞ በላ። 5 እኔ ግን፦«ጌታ
እግዚአብሔር ሆይ እባክህ ተው፥ያዕቆብ በዚህ ውስጥ እንዴት ይቆማል? እርሱ ታናሽ ነውና» አልሁ። 6 እግዚአብሔርም ስለዚህ ነገር ተጸጸተ፤ «ይህም ደግሞ
አይሆንም» ይላል ጌታ እግዚአብሔር። 7 እንዲህም አሳየኝ፦ እነሆም ፥ጌታ በእጁ ቱምቢ ይዞ በቅጥሩ አጠገብ ቆሞ ነበር። 8 እግዚአብሔርም፦ «አሞጽ ምን
ታያለህ?» አለኝ፥ እኔም «ቱምቢ» አልሁኝ። ከዚያም ጌታ፦«ተመልከት፥በሕዝቤ በእስራኤል መካከል ቱምቢ አኖራለሁ። ከእንግዲህም ወዲያ አልምራቸውም።
9 የይስሐቅ ከፍታ ቦታዎች ይጠፋሉ፥ የእስራኤል መቅደሶች ይፈርሳሉ፥ በኢዮርብዓምም ቤት ላይ በሰይፍ እነሳለሁ።» 10 ከዚያም የቤቴል ካህን አሜስያስ ወደ
እስራኤል ንጉሥ ወደ ኢዮርብዓም እንዲህ ሲል መልእክት ላከ፦«አሞጽ በእስራኤል ቤት መካከል በአንተ ላይ እያሤረ ነው። ምድሪቱም ቃሎቹን ልትሸከም
አትችልም። 11 አሞጽ እንዲህ ሲል ተናግሮአል፦'ኢዮርብዓም በሰይፍ ይሞታል፥ እስራኤልም በእርግጥ ከምድሩ ተማርኮ ይሄዳል'።» 12 አሜስያስም፥ አሞጽን
እንዲህ አለው፦«ባለ ራዕዩ ሆይ፥ ወደ ይሁዳ ምድር ተመልሰህ ሽሽ፥ በዚያም እንጀራ ብላ ትንቢትም ተናገር። 13 ነገር ግን ቤቴል የንጉሡ መቅደስና
የመንግሥት መኖሪያ ነውና ከእንግዲህ ወደያ በዚህ ትንቢት አትናገር።» 14 ከዚያም አሞጽ አሜስያስን እንዲህ አለው፦ «እኔ ነቢይ ወይም የነቢይ ልጅ
አይደለሁም። እኔ እረኛና የዋርካ ዛፎች ጠባቂ ነኝ። 15 ነገር ግን እግዚአብሔር የበግ መንጋ ከመጠበቅ ወሰደኝና እንዲህ አለኝ፦'ሂድ፥ ለሕዝቤ ለእስራኤል
ትንቢት ተናገር።' 16 አሁን የእግዚአብሔርን ቃል ስማ። አንተ፥ «'በእስራኤል ላይ ትንቢት አትናገር፥ በይስሐቅም ቤት ላይ አትናገር' ትላለህ። 17 ስለዚህ
እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦' ሚስትህ በከተማይቱ ውስጥ ሴተኛ አዳሪ ትሆናለች፥ ወንዶችና ሴቶች ልጆችህ በሰይፍ ይወድቃሉ፥ ምድርህ እየተለካ
ይከፋፈላል፥ በረከሰ ምድር ትሞታለህ፥ እስራኤልም በእርግጥ ከምድሩ ተማርኮ ይጋዛል።»

Amos 7:1

እዩ ....ተመልከቱ
ፀሐፊው አንድ አስገራሚ ነገር ለመናገር የተዘጋጀ እንደሆነ ለአንባቢው ይናገራል።ቋንቋችሁ ይሄንን የሚገልፅበት የተለየ መንገድ ሊኖረው ይችላል።

አንበጣ
በአሞፅ 4፤9 ላይ ይሄንን እንዴት አድርጋችሁ እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

የንጉሡ ሰብል ከታጨደ በኋላ
“ንጉሡ ከታጨደው ውስጥ የእርሱን ድርሻ ከወሰደ በኋላ”

“እባክህ ይቅር በል”
“የአንተ ሕዝብ”እና “እኛ” የሚለው ነገር ግልፅ ነው።የአሞፅ ትርጉም “እባክህ ሕዝብህን ይቅር በል”ወይም “እባክህን ይቅር በለን”(ቃላትን ሳይጠቀሙ በምልክቶች (ሥነፅሑፍ) ሃሣብን መግለፅ የሚለውን ይመልከቱ)

ያዕቆብ እጅግ ታናሽ ነውና እንዴት ይቆማል?
እዚህ ላይ“ያዕቆብ” የሚለው ቃል የእሥራኤልን ትውልድ ለማመልከት የዋለ ቃል ነው።የአሞፅ ትርጉም “እኛ እሥራኤላውያን እንዴት እድርገን ነው በሕይወት የምንቆመው?እኛ እጅግ ታናናሾችና ደካሞች ነን” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 7:4

ተመልከቱ
ፀሐፊውአንድ አስገራሚ ነገር ለመናገር የተዘጋጀ እንደሆነ ለአንባቢው ይናገራል።ቋንቋችሁ ይሄንን የሚገልፅበትየራሱ ሆነ መንገድ ሊኖረው ይችላል።

ጌታ እግዚአብሔር በእሣት ለመፍረድ ጠራ
“ጌታእግዚአብሔር ሰዎችን ለመቅጣት የሚቃጠል እሣትን ተጠቀመ”

ያዕቆብ እጅግ ታናሽ ነውና እንዴት ይቆማል?
እዚህ ላይ “ያዕቆብ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእሥራኤልን ትውልዶች ነው።በአሞፅ 7፤2 ላይ ይሄንን እንዴት አድርጋችሁ እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።የአሞፅ ትርጉም “እሥራኤላውያን እንዴት አድርገው ነው በሕይወት የሚኖሩት?እኛ እጅግ ታናናሾችና ደካሞች ነን።” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 7:7

ቱምቢ
በአንደኛው ጫፍ ላይ ከበድ የሚል ነገር ያለው ሆኖ ግንባታዎች በሚካሄዱበት ወቅት ግድግዳዎቹ ከላይ እስከ ታች ድረስ ቀጥ ብለው እንዲቆሙ ለማድረግ የሚረዳ ገመድ ነው።

የምታየው ምንድነው?
እግዚአብሔር ለአሞፅ ትምህርት ለመሥጠት ጥያቄ በመጠየቅ ይቀርባል። የአሞፅ ትርጉም “የምታየትን ንገሩኝ”(በሙያ የታገዘ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በሕዝቤ በእሥራኤል መካከል ቱምቢ አደርጋለሁ
ሕዝቡ አመፀኞች መሆናቸውን በማየትና ፍርድ ለመሥጠት ያለውን ሃሣብ ለመግለፅ እሥራኤላውያን እንደ ግድግዳ እንደሚመሰሉና እግዚአብሔር ድግሞ ቱምቢን በመጠቀም ግድግዳው ቀጥተኛ እንዳልሆነ ያረጋገጠ በሚመስል መልኩ ነው የሚናገረው።የአሞፅ ትርጉም “ሕዝቤ እሥራኤል አመፀኞች ናቸው።ከላይ እስከ ታች ድረስ እንዳልተስተካከለ ግድግዳዎች ናቸው”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 7:9

የይሥሐቅም የኮረብታው መስገጃዎች ይፈርሳሉ፤የእሥራኤልም መቅደሶች ባድማ ይሆናሉ፤በኢዮርብዓምም ቤት ላይ በሠይፍ እነሣለሁ
እዚህ ላይ “ሠይፍ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጠላትን ነው።ይሄ የራሱ በሆነ አገላለፅ ሊገለፅ ይችላል።የአሞፅ ትርጉም “የኢዮርብዓምን ቤት የሚያጠቃ ሠራዊት እልካለሁ፤እነርሱም የይሥሐቅን የኮረብታ መስገጃዎችና የእሥራኤልን ቤተ መቅደሶች ባድማ ያደርጋሉ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃልን እና አድራጊ ግሥን ወይም ተካፋይ ያልሆነ የሚለውን ይመልከቱ)

ይሥሐቅ ...እሥራኤል
እነዚህ ሁለቱም ቃላት የእሥራኤልን ቤት የሚያመለክቱ ናቸው።የአሞፅ ትርጉም “የይሥሐቅ ትውልድ”...“የእሥራኤል ሕዝብ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የኢዮርብዓም ቤት
እዚህ ላይ “ቤት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ቤተሰብን ነው።በአሞፅ 1፤1 ላይ እንዳደረጋችሁት ሁሉ ኢዮርብዓም የሚለውን ቃልንም ተርጉሙት።የአሞፅ ትርጉም “ኢዮርብዓምና ቤተሰቡ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 7:10

የቤቴል ካህን አሜስያስ
ለዚህ ፍቺ ሊሆኑ የሚችሉት 1/አሜስያስ በቤቴል ውስጥ የቀረ ብቸኛ ካህን ነበር 2/አሜስያስ በቤቴል ውስጥ ለነበሩ ካህናት አለቃ ነበር

አሜስያስ
ይሄ የአንድ ሰው ሥም ነው።(ሥሞች እንዴት ነው መተርጎም የሚኖርባቸው? የሚለውን ይመልከቱ)

አሞፅ በእሥራኤል ቤት መካከል አምፆብሃል
እዚህ ላይ“ቤት” የሚለው ቃል የሚወክለው “ሕዝቦችን” ነው።የአሞፅ ትርጉም “አሞፅ እዚሁ በእሥራኤላውያን መካከል ሆኖ መጥፎ ነገርን እያሴረባችሁ ነው”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሪቱ ቃሉን ሁሉ ልትሸከም አትችልም
እዚህ ላይ“ምድር” የሚለው ቃል የሚያመለክተው “ሕዝቦችን” ነው።እዚህ ላይ “ሠላምን ማናጋት” የሚለው ሃሣብ የተገለፀው አሞፅ ካባድ እንደሆነ ግዑዝ ዕቃ እንደሆነና ምድሪቱ ለመሸከም እንዳቃታት ተደርጎ ነው።የአሞፅ ትርጉም “እርሱ የሚናገረው ቃል የሕዝቡን ሠላም ያናጋል”ወይም “የሚናገረው መልዕክት በሕዝቡ መካከል ችግር እንዲፈጠር ያደርጋል።”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውንና ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ ይመልከቱ)

ኢዮርብዓም በሠይፍ ይሞታል
እዚህ ላይ“ሠይፍ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጠላቶችን ነው።የአሞፅ ትርጉም “ጠላቶች ኢዮርብዓምን ይገድሉታል”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 7:12

በዘያም እንጀራን ብላ በዚያም ትንቢትን ተናገር
እዚህ ላይ “እንጀራን ብላ”የሚለው ቃል የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ትርጉሙም ገንዘብ ማግኘት ወይም አንድ ነገርን በመሥራት ለኑሮ የሚበቃ ነገር ማግኘትን ነው የሚያመለክተው።የአሞፅ ትርጉም “እዚያ ሥፍራ ላይ ትንቢት ስለምትናገር ገንዘብ የሚከፍሉህን ሰዎች ፈልግ”ወይም “እዚያ ሥፍራ ላይ ትንቢት ተናገርና ምግብ ያቅርቡልህ” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

የንጉሥ መቅደስና የመንግሥት ቤት ናትና
እዚህ ላይ“የንጉሥ መቅደስ” እና “የመንግሥት ቤት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ተመሳሳይ ሥፍራዎችን ነው።የአሞፅ ትርጉም “ንጉሡ የሚያመልክበት አገር አቀፉ የመቅደስ ሥፍራ እዚህ ነው።”

Amos 7:14

የከብቶች መንጋ ጠባቂ
በአሞፅ 1፤1 ላይ “እረኛ”ትብሎ ስለሚጠራ ምናልባት “በጎችን”የሚጠብቅ ለማለት ይሆናል።

ዋርካ
ዋርካዎች እስከ 15 ሜትር የሚደርስ ቁመት አላቸው።የአሞፅ ትርጉም“የሾላ ዛፎች)”(የማይታወቁ ነገሮችን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 7:16

አሁን
እዚህ ላይ“አሁን” የሚለው ቃል ተከትለው በሚመጡት ሃሣቦች ላይ ትኩረትን እንዲያደርጉ ለማስቻል ጥቅም ላይ የዋለ ነው።

በይሥሐቅም ቤት ላይ አትስበክ
እዚህ ላይ “ቤት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የይሥሐቅን የትውልድ ሐረግ ነው።የአሞፅ ትርጉም“ ለይሥሐቅ ትውልድ አትስበክ።” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ወንዶችና ሴቶች ልጆችህም በሠይፍ ይወድቃሉ
እዚህ ላይ“ሠይፍ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጠላቶችን ነው።የአሞፅ ትርጉም “ጠላቶች ወንዶችና ሴት ልጆቻችሁን ይገድላሉ።”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን)

ምድርህም በገመድ ተለክታ ትከፈለለች
ይሄ በአድራጊ ግሥ መልክ ሊገለፅ ይችላል።የአሞፅ ትርጉም “ሌሎች ሰዎች ምድራችሁን ይወስዱና ይከፋፈሉታል”(አድራጊ ግሥ ወይም ተካፋይ ያልሆነ የሚለውን ይመልከቱ)

የረከሰች ምድር
በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸው ሕዝብ የሞላበት ምድርን በተመለከተእዚህ ላይ የሚገለፀው ልክ ምድሪቱ እንደረከሰች ተደርጎ ነው። እዚህ ላይ ይሄ የሚያመለክተው የእሥራኤልን ሰሜናዊ ክፍል ነው።የአሞፅ ትርጉም “ባዕድ አገር”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 8

1 ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ አሳየኝ፤ የበጋ ፍሬ ቅርጫት ተመለከትሁ! **2** እርሱም፥ «አሞጽ፥ ምን ታያለህ?» አለኝ። እኔም፥ «የበጋ ፍሬ ቅርጫት» አልሁት። ከዚያም እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ፦ «በሕዝቤ በእስራኤል ላይ ፍጻሜ መጥቶአል፤ ከእንግዲህ ወዲያ አልምራቸውም። **3** የቤተ መቅደሱ ዝማሬ ዋይታ ይሆናል። የጌታ እግዚአብሔር አዋጅ ይህ ነው፥ በዚያን ቀን፥ «አስከሬኑ ብዙ ይሆናል፤ በሁሉ ሥፍራ በዝምታ ይጥሏቸዋል።» **4** እናንተ ችግረኞችን የምትረግጡና የምድሪቱን ድኾች የምታጠፉ ስሙ። **5** እንዲህ ይላሉ፦«እህል እንሸጥ ዘንድ የወር መባቻው መቼ ያልፋል? በሐሰተኛ ሚዛን እያታለልን፥ መስፈሪያውን እያሳነስን፥ ዋጋውን ከፍ እያደረግን፥ ስንዴ ለገበያ እናቀርብ ዘንድ፥ **6** የስንዴውን ግርድ እንሸጥና ደኻውን በብር፥ ችግረኛውንም በጥንድ ጫማ እንገዛ ዘንድ ሰንብት መቼ ያልፋል?» **7** እግዚአብሔር በያዕቆብ ክብር እንዲህ ሲል ምሎአል፦ «በእርግጥ የትኛውንም ሥራቸውን ፈጽሞ አልረሳም።» **8** በዚህ ነገር፥ ምድር አትናወጥምን፥ በውስጧም የሚኖሩ ሁሉ አያለቅሱምን? ሁለመናዋ እንደ አባይ ወንዝ ይነሣል፥ እንደ ግብጽ ወንዝም ወደ ላይ ይወረወራል፥ተመልሶም ይወርዳል። **9** «በዚያን ቀን እንዲህ ይሆናል» ፥የእግዚአብሔር አዋጅ እንዲህ ይላል፥ «ፀሐይ በቀን እንድትጠልቅ አደርጋለሁ፥ በቀንም ብርሃን እያለ ምድርን አጨልማታለሁ»። **10** ዓመት በዓላችሁን ወደ ልቅሶ፥ መዝሙራችሁንም ሁሉ ወደ ዋይታ እለውጣለሁ። ሁላችሁም ማቅ እንድትለብሱ፥ ጸጉራችሁንም እንድትላጩ አደርጋለሁ። ለአንድያ ልጅ እንደሚለቀስ፥ እንደ መራራም ቀን አደርገዋለሁ። **11** ተመልከቱ፥ቀኖቹ እየቀረቡ ናቸው» ፥የእግዚአብሔር አዋጅ እንዲህ ይላል፥ «ረሓብን በምድር ላይ እሰድዳለሁ፥ እርሱም የእግዚአብሔርን ቃል የመስማት ረሓብ እንጂ እንጀራን የመራብ ወይም ውኃን የመጠማት አይደለም። **12** የእግዚአብሔርን ቃል ፍለጋ ከባሕር ወደ ባሕር ይንከ ራተታሉ፥ ከሰሜን ወደ ምሥራቅ ይሮጣሉ፤ ነገር ግን አያገኙትም። **13** በዚያን ቀን ያማሩ ደናግላንና ወጣቶች ከውኃ ጥም የተነሳ ይዝላሉ። **14** 'ዳን ሆይ ሕያው አምላክህን' ድግሞም 'ሕያው የቤርሳቤህ አምላክ' እያሉ በሰማርያ ኃጢአት የሚምሉ ፤ይወድቃሉ፥ዳግመኛም አይነሱም።»

Amos 8:1

የቃርምያ ፍሬ የሞላበትን ዕንቅብ ተመልከት!
እዚህ ላይ“ተመልከት”የሚለው ቃልአሞፅ አንድ ደስ የሚያሰኝ ነገር መመልከቱን ያሣያል::::የአሞፅ ትርጉም“የቃርምያ ፍሬ የሞላበትን ዕንቅብ ተመለከትኩ”

የበጋ ፍሬ
“የደረሰ ፍሬ”

አሞፅ ሆይ የምታየው ምንድነው?
እግዚአብሔር አሞፅን ለማስተማር ጥያቄን ይጠቀማል::የአሞፅ ትርጉም “አሞፅ የምታየው ነገር ምን አንደሆነ ንገረኝ ”(በሙያ የታገዘ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚያን ቀን
“በዚያን ወቅት”

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ስለ ራሱ በራሱ ሥም ይናገራል::ይህንን በአሞፅ 4:5 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ::የአሞፅ ትርጉም “የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የሚናገረው ይሄንን ነው”ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርኩት ይህንን ነው”(መጀመሪያ፤ሁለተኛና ሥስተኛ አካል የሚለውን ይመልከቱ)

ፀጥታ
ለዚህ ፍቺ ሊሆኑ የሚችሉት ነገሮች 1/እግዚአብሔር ሊያመጣ ያለውን ከባድ ቅጣት ፀጥ ብለው እንዲያዳምጡ እየነገራቸው ነው:: ወይም 2/እግዚአብሔር ቅጣቱን ካመጣባቸው በኋላ ከመፀፀታቸው የተነሣ ሰዎች ፀጥ ይላሉ::

Amos 8:4

ይህን ስሙ
አሞፅ እየተናገረ ያለው ድሆችን ስለሚጎዱ ሐብታም ነጋዴዎች ነው::

ችጋረኛውን የምትውጡ የአሩንም ድሃ የምታጠፉ እናንተ ሆይ
ይሄ አሕፅሮተ ቅፅል ሥምን (ሰዋሰው)በማስወገድ “ችግረኛ” እና “ድሃ”የሚለው አፅንዖት ለመሥጠት ይሆናል ይችላል::የአሞፅ ትርጉም “እናንተ ለተቸገሩ ሰዎች እንቅፋት የምትሆኑና በምድሩ ላይ የሚኖሩትን ድሆች በኃይል የምታስወግዱ”(አሕፅሮተ ቅፅል ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ የምትረግጡ
ሰዎችን መጉዳት ሰዎችን በእግር እንደመርገጥ ተደርጎ ተደርጎ ተነግሯል:: የአሞፅ ትርጉም “እናንተ ሰዎችን የምትጎዱ”ወይም “እናንተ ሰዎችን የምታስጨንቁ” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

“እህልን እንሸጥ ዘንድ መባቻው መቼ ያልፋል?ስንዴውን እንደንሸምት ሰንበት መቼ ያልፋል?” ይላሉ::
እነዚህን ጥያቄዎች ነጋዴው የሚጠይቀው ነጋዴዎቹ ዕቃዎቻቸውን የሚሸጡበትን ትክክለኛ ጊዜ እንዲያውቁት አፅንዖት ለመስጠት ነው::ይሄ እንደ ቀጥተኛ ያልሆነ አባባል ይችላል::የአሞፅ ትርጉም“እህልን እንሸጥ ዘንድ መባቻው መቼ ያልፋል?ስንዴውን እንደንሸምት ሰንበት መቼ ያልፋል?የሚል ጥያቄን ዘወትር ይጠይቃሉ::”(በሙያ የታገዘ ጥያቄና ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ አባባሎች የሚለውን ይመልከቱ)

የኢፍ መሥፈሪያውንም እያሳነስን ፤በሐሰተኛም ሚዛን እያታለልን
ነጋዴዎቹ የውሸት ሚዛንን በመጠቀም በፊት ከነበረው ይልቅ ብዙ ነገር እንደሰጡ በማስመሰል ክፍያውንም ከወትሮው እንዲቀንስ ያደርጋሉ ማለት ነው::

ችጋረኛውንም በአንድ ጥንድ ጫማ እንገዛ ዘንድ
“እንገዛ ዘንድ”የሚለው ቃል ግልፅ ነው::የአሞፅ ትርጉም “ችግረኞችን በአንድ ጥንድ ጫማ መግዛት”(ቃላትን ሳይጠቀሙ በምልከቶች ብቻ (ሥነፅሑፍ) ሃሣበን መግለፅ የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 8:7

እግዚአብሔር በያዕቆብ ክብር እንዲህ ብሎ ምሏል
እዚህ ላይ “የያዕቆብ ክብር”የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው::እንዲሁም “ያዕቆብ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእርሱ የዘር ሐረግ የሆኑትን እሥራኤላውያንን ነው::የአሞፅ ትርጉም“እግዚአብሔር በራሱ ሥም እንዲህ ብሎ ምሏል”ወይም “እሥራኤላውያን የሚመኩበት እግዚአብሔር ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

በውኑ ምድሪቱ ስለዚህ ነገር አትናወጥምን?በእርሷም የሚኖር ሁሉአያለቅስምን?
እዚህ ላይ አሞፅ የናይል ወንዝ ማዕበል ከፍና ዝቅ እንደሚል ሁሉ እግዚአብሔር ሕዝቡ ላይ በሚፈርድበት ወቅት ምድሪቱን ከማናወጡ ጋር ያነፃፅረዋል::(ተነፃፃሪ የሚለወን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የግብፅ ወንዝ
ይሄ የናይል ሌላኛው ስሙ ነው።

Amos 8:9

በዚያን ቀን ይመጣል
“በዚያን ዘመን ይፈፀማል”

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ስለ ራሱ በራሱ ሥም ይናገራል።ይሄንን በአሞፅ 4፤5 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።የአሞፅ ትርጉም “የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የሚናገረው ይህንን ነው” ወይም “የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ያለው ይሄንን ነው” (መጀመሪያ፤ሁለተኛና ሦስተኛ የሚለውን ይመልከቱ)

ራስ መንጨትንም በሁሉ ላይ አመጣለሁ
አንድ ሰው ራሱን የሚላጨው ሐዘን ላይ መሆኑን ለመግለፅ ነው።የአሞፅ ትርጉም “ራሣችሁን እንደትላጩ ያደርጋችኋል” (ተምሣሌታዊ ድርጊትን ይመልከቱ)

ለአንድያ ልጅ እንደሚለቀስ ለቅሶ
አንድ ልጅ ብቻ እንዳላቸውና ያ አንዲያ ልጃቸው እንደሞተባቸውየሚገልፅ ነው።የአሞፅ ትርጉም “አንድ ልጅ ብቻ ኖሯቸው ለእርሱ እንደሚያለቀሱ”(ቃላትን ሳይጠቀሙ ሃሣብን መግለፅ የሚለውን ይመልከቱ)

ፍፃሜውንም መራራ አደርገዋለሁ
አሰቃቂና መጥፎ ነገሮች በቀን ብርሃን መከናወናቸው ልክ ቀኑ ራሱ መራራ ጣዕም አንዳለው ዓይነት ተደርጎ ተነግሯል።የአሞፅ ትርጉም“ በዚያን ወቅት የሚከናወኑ ነገሮች ሁሉ ለታላቅ ሐዘን ይዳርጓችኋል።”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 8:11

ዘመን ይመጣል
ይሄ ልክ ቀኑ ራሱ “እየተራመደ እንደሚመጣ” ዓይነት ተገልጿል።የአሞፅ ትርጉም “ቀን ይመጣል” ወይም “ለወደፊቱ” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ስለ ራሱ በራሱ ሥም ይናገራል።ይሄንን በአሞፅ 4፤5 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።የአሞፅ ትርጉም “የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የሚናገረው ይህንን ነው” ወይም “የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ያለው ይሄንን ነው” (የመጀመሪያው፤ሁለተኛውንና ሦስተኛውን ይመልከቱ)

እነሆ በምድር ላይ ራብን በምሰድድበት ዘመን ...የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት እንጂ
ሰዎች ከእግዚአብሔር መልዕክት ለመስማት ፈልገው እግዚአብሔር ለመናገር ፈቃደኛ ስለማይሆንየቃሉ ረሃብ እንደሚመጣባቸው ተደርጎ ነው የተገለፀው። የአሞፅ ትርጉም “በምድሪቱ ውስጥ ከረሃብ ጋር የሚመሳሰል ነገር በማመጣበት ወቅት... ሆኖም የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ቃል
ይሄ በመጀመሪያው ማንነት ሊገለፅ ይችላል።የአሞፅ ትርጉም “ከእኔ የሆነ ቃል፤እግዚአብሔር”ወይም “የእኔ መልዕክቶች” (የመጀመሪያ፤ሁለተኛና ሦስተኛ የሚለውን ይመልከቱ)

ከባህርም እስከ ባህር ድረስ ከሰሜንም እስከ ምሥራቅ ድረስ ይቅበዘበዛሉ
እዚህ ላይ“ከባህር እስከ ባህር”እና “ከሰሜን እስከ ምሥራቅ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእሥራኤልን ምድር ሁሉ ነው።የአሞፅ ትርጉም “የእግዚአብሔርን ቃል ለማግኘት እዚህና እዚያ እያሉ ይቅበዘበዛሉ።”(ምሕፃረ ቃል የሚለውን ይመልከቱ))

ከባህር እስከ ባህር ድረስ
ይሄ የሚያመለክተው በደቡብ በኩል ሙት ባህርንና በምዕራብ በኩል ደግሞ የሜዲቴሪያን ባህርን ነው።(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀት የሚልውን ይመልከቱ)

Amos 8:13

በዚያን ዘመን
“በዚያን ወቅት”

ይዝላሉ
ጉልበት ሁሉ ሲሟጠጥ

በሰማርያ ኃጢአት
እዚህ ላይ “ኃጢአት” የሚለው ቃል ሰዎች በሰማርያ ውስጥ የሚያመልኳቸውን ጣዖታት የሚያመለክት ነው።የአሞፅ ትርጉም “የሰማርያ ጣኦት”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ዳን ሆይ ሕያው አምላክህን
ይሄ ከአምልኮ ጋር በተያያዘ መሐላ የማድረጊያ መንገድ ነው።ሰዎቹ ሕያው ነው የሚሉትን የዳንን አምላክ ማመናቸውን ስላወጁ ቃል የገቡትን ነገር በተግባር እንደሚፈፅሙት አፅንዖት ሰጥተው መናገራቸው ነው።

የቤርሳቤህን መንገድ ብለው የሚሉ
ይሄ ምናልባትም ሰዎች ጣዖታትን ለማምለክ ወደ ቤርሳቤህ ጉዞ በሚያደርጉበት ወቅት የሚያልፉባቸውን መንገዶች የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።እዚህ ላይ እንደገና የሚያሣየው ከአምልኮ ጋር የተያያዘ መሐላ የማድረግ ብቸኛ መንገዳቸው መሆኑን ነው።የተሳሉትን ነገር ለማድረግ ይችሉ ዘንድ ወደ ቤርሳቤህ የሚወስደው መንገድ በእርግጥ አለ ብለው ይናገራሉ።

ይወድቃሉ
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው።የአሞፅ ትርጉም “ይሞታሉ”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 9

1 ጌታን በመሠዊያው አጠገብ ቆሞ አየሁት፥ እንዲህም አለ፦«መሠረቶቹ እንዲናወጡ የአምዶቹን የላይኛውን ጫፍ ምታ። በራሶቻቸው ሁሉ ላይ ሰባብራቸው፥ ከእነርሱም የቀሩትን በሰይፍ እገድላለሁ። ከእነርሱ ማንም አያመልጥም፥ ማንም አይተርፍም። 2 ቆፍረው ወደ ሲዖል ቢወርዱም፥ እጄ ከዚያ ታወጣቸዋለች። ወደ ሰማይ ቢወጡም፥ ከዚያ አወርዳቸዋለሁ። 3 በቀርሜሎስ ራስ ላይ ቢሸሸጉም፥ በርብሬ ከዚያ እወስዳቸዋለሁ። በባሕሩ ሥር ከዓይኔ ቢደበቁም፥ በዚያ እባቡን አዝዛለሁ፥ እርሱም ይነድፋቸዋል። 4 በጠላቶቻቸው ፊት እየተነዱ ወደ ምርኮ ይጋዛሉ፤ በዚያም ሰይፍን አዝዛለሁ፥ እርሱም ይገድላቸዋል። ዓይኔን ለክፉ በእነርሱ ላይ አደርጋለሁ፥ ለመልካምም አይደለም።» 5 ጌታ፥ የሠራዊቱ እግዚአብሔር ምድርን ይዳስሳል፥ እርስዋም ትቀልጣለች፥ በእርስዋም የሚኖሩ ሁሉ ያለቅሳሉ፤ ሁለመናዋ እንደ ወንዝ ወደ ላይ ይወረወራል፥ እንደ ግብጽም ወንዝ ተመልሶ ይሰምጣል። 6 አዳራሹን በሰማይ የሠራ፥ ግምጃ ቤቱን በምድር የመሠረተ እርሱ ነው። የባሕርን ዉኖች ይጠራቸዋል፥ በምድርም ፊት ላይ ያፈስሳቸዋል፥ ስሙም እግዚአብሔር ነው። 7 የእስራኤል ልጆች ሆይ፥ እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን? ይላል እግዚአብሔር። እስራኤልን ከግብጽ፥ፍልስጤማያንን ከከፍቶር፥ ሶርያውያንንም ከቂር አላወጣሁምን? 8 እነሆ፥ የጌታ እግዚአብሔር ዓይኖች በኃጢአተኛ መንግሥት ላይ ናቸው፥ ከምድርም ገጽ አጠፋዋለሁ፣ የያቆብን ቤት ግን ፈጽሜ አላጠፋም፤ ይላል እግዚአብሔር።» 9 እነሆ፥አዝዛለሁ፥ ሰው በወንፊት እህል እንደሚነፋ፥ የእስራኤልን ቤት በአሕዛብ ሁሉ መካከል እነፋለሁ፤ ነገር ግን አንዲትም ቅንጣት በምድር ላይ አትወድቅም። 10 «ጥፋት አይደርስብንም ወይም አያገኘንም» የሚሉ፤ የሕዝቤ ኃጢአተኞች ሁሉ በሰይፍ ይሞታሉ። 11 «በዚያን ቀን የወደቀችውን የዳዊትን ድንኳን አነሳለሁ፥ ሸንቁሩንም እዘጋለሁ። ፍራሽዋንም አነሳለሁ፥ በቀድሞ ዘመን እንደነበረች እን ደገና እሠራታለሁ፤ 12 ይኼውም የኤዶምን ቅሬታ፥ በስሜም የተጠሩትን አሕዛብ ሁሉ ይወርሱ ዘንድ ነው፥ ይላል ይህን የሚያደርግ እግዚአብሔር።» 13 እነሆ፥ አራሹ አጫጁ ላይ፥ ወይን ጠማቂው ዘሪው ላይ የሚደርስበት ጊዜ ይመጣል፥ ይላል እግዚአብሔር። ተራሮቹ ጣፋጩን ወይን ጠጅ ያንጠባጥባሉ፥ ኮረብቶችም ሁሉ ይፈስባቸዋል። 14 ሕዝቤን እስራኤልን ከተማረከበት እመልሰዋለሁ። የፈረሱትን ከተሞች ሠርተው ይኖሩባቸዋል፥ ወይንንም ተከለው የወይን ጠጃቸውን ይጠጣሉ፥አትክልትም ተክለው ፍርውን ይበላሉ። 15 በምድራቸው ላይ እተክላቸዋለሁ፥ ከሰጠኋቸውም ምድር ከቶውን ዳግመኛ አይነቀሉም» ይላል አምላካችሁ እግዚአብሔር።

Amos 9:1

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለአሞፅ ሌላ ራዕይን ያሣየዋል።

በራሣቸውም ሁሉ ላይ ሰባብራቸው
እግዚአብሔር እነዚህን ትዕዛዛት ለማን እንደሚናገር ግልፅ አይደለም።

መድረኮቹ ይናወጡ ዘንድ ፤ጉልላቶቹን ምታ
ይሄ እግዚአብሔር ስለ ጉልላቶቹና ስለ መቅደሱ መሠረቶች በተገናኘ መልኩ የተናገረው ነገር ነው።(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀት የሚለውንና ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መድረኮቹ ይናወጡ ዘንድ
እዚህ ላይ “መድረኮቹ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ቤተ መቅደሱን በአጠቃላይ ነው።የአሞፅ ትርጉም “ቤተ መቅደሱ በሙሉ ይናወጥ ዘንድ”(አጠቃላይ ሃሣቡን በአጭር ንግግር የመግለፅ ዘዴ የሚለውን ይመልከቱ)

በራሳቸውም ላይ ሰባብራቸው
እዚህ ላይ“ራስ”የሚለው ቃል በአጠቃላይ ማንነቱን የሚያመለክት ነው። የአሞፅ ትርጉም “መቅደሱ በሰዎች ላይ ወድቆ ይገድላቸው ዘንድ ጉልላቶቹን ምታ”(አጠቃላይ ሃሣቡን በአጭር ንግግር የመግለፅ ዘዴ የሚለውን ይመልከቱ)

የቀሩትን በሰይፍ እገድላለሁ
እዚህ ላይ“ሰይፍ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ተዋጊዎች በሠይፋቸው የሚያጠቁበትን ሁኔታ ነው።የአሞፅ ትርጉም “የተቀሩትን የሚገድል የጠላት ሠራዊትን እልካለሁ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ሲዖል ቢወርዱ እጄ ከዚያ ታወጣቸዋለች፤ወደ ወደ ሰማይም ቢወጡ ከዚያ አወርዳቸዋለሁ
እግዚአብሔር ወደ ሲዖል የሚሰደዱበትን ሁኔታ ወይም ሞትን ለማምለጥ ሲሉ ወደ ሰማይ የመሄዳቸውን ጉዳይ የተጋነነ በሚመስል መልኩ አቅርቦታል።እዚህ ላይ “ሲዖል” እና “ሰማይ”እንደ ምሕፃረ ቃል ሆኖ ሥፍራዎችን በሙሉ የሚወክል ነው።የአሞፅ ትርጉም “ወደ ሲዖልና ወደ ሰማይ ቢሄዱ እንኳን ከእኔ ሊያመልጡ አይችሉም።” (ሆን ብሎ አጋኖ መናገርን፤አጠቃላይነትንና ምሕፃረ ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

እጄ ከዚያ ታወጣቸዋለች
እዚህ ላይ“እጅ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ኃይል ነው። የአሞፅ ትርጉም “ከዚያ አወጣቸዋለሁ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 9:3

በቀርሜሎስ ራስ ውስጥ ቢሸሸጉ ....በጥልቅ ባህርም ውስጥ ከዓይኔ ቢደበቁ
እግዚአብሔር ወደ ቁርሜሎስ ተራራ ራስ ሊሸሸጉ የሚሮጡትን ወይም ለመደበቅ ወደ ጥልቅ ባህር የሚሄዱትን በሚመለከት የተጋነነ ገፅታን ያቀርባል።እዚህ ላይ “በቀርሜሎስ ራስ”እና “ጥልቅ ባህር”ሥፍራዎችን ሁሉ የሚያመለክቱ ምሕፃረ ቃሎች ናቸው።የአሞፅ ትርጉም “በቁርሜሎስ ራስ ላይ ቢሸሸጉ እንኳን...የማላይ መስሏቸው ወደ ባህር ጥልቅ ለመሄድ ቢሞክሩ እንኳን”(ሆን ብሎ አጋኖ መናገርን፤አጠቃላይነትንና ምሕፃረ ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

እባብ
ያልታወቀ አደገኛ እንስሳ፤በኤደን ገነት የታየው ወይም በተለምዶ የምናውቀው ዓይነት እባብ ያልሆነ።

በጠላቶቻቸውም ተማርከው ቢሄዱ
ይሄ አድራጊ ግሥ መልክ ሊገለፅ ይችላል።የአሞፅ ትርጉም “ጠላቶች ቢማርኳቸውና ወደ ባዕድ አገር ይዘዋቸው ቢሄዱ እንኳን ”(አድራጊ ግሥን ወይም ተካፋይ ያልሆነ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያ ሰይፍን አዝዛለሁ እርሱም ይገድላቸዋል
እዚህ ላይ“ሠይፍ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጠላቶችን ነው።የአሞፅ ትርጉም “እዚያ ጠላቶቻቸው እንዲገድሏቸው አደርጋለሁ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 9:5

ሙላዋም እንደ ወንዝ ትነሣለች እንደ ግብፅ ወንዝም ትወርዳለች
እዚህ ላይ“ወንዙ”እና “የግብፅ ወንዝ” የሚሉት ሁለቱም ቃላት የሚያመለክቱት የናይልን ወንዝ ነው።እግዚአብሔር ምድሪቱ እንድትናወጥ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የሚያደርግበትን መንገድ ከናይል ወንዝ መነሳትና መስጠም ጋር ያነፃፅረዋል። (ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ (ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ))

ደረጃዎቹን በሰማይ ላይ የሰራ
ይሄ ምናልባት የጥንት ሰዎች ወደ እግዚአብሔርቤተመንግሥት የሚያመራው መንገድ በደረጃዎች ነው ብለው ስለሚያስቡ ይሆናል።ሆኖም አንዳንድ ቅጂዎች “ቤተመንግሥት” እና “ክፍሎች”የሚል ትርጉም ባለውበተለየ የዕብራይስጥ ቃል እንዲነበብ ይፈልጋሉ።እዚህ ላይ “ደረጃዎቹ”የሚለው ቃል የእግዚአብሔር መንግሥት ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ሃሣብ ያለው ሊሆን ይችላል።(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ጠፈሩንም በምድር ላይ የመሠረተ
እዚህ ላይ“ጠፈር” የሚለው ቃል የመፅሐፍ ቅዱስ ፀሐፊዎች የሚገልፁት በምድር ላይ እንዳለ ጉልላት ነው።የአሞፅ ትርጉም “ሠማይን በምድር ላይ ይዘረጋል።”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የባህሩንም ውኃ ጠርቶ..... በምድር ፊት ላይ
ይሄ የሚያመለክተው የባህር ውኃ በምድር ላይ እነደ ዝናብ እንዲዘንብ ማድረጉን ነው።በአሞፅ 5፡8 ላይ ይሄንን እንዴት እንደምትተረጉሙት ተመልከቱ።ኤቲ “ውኃውን ወስዶ በምድር ላይ እንዲዘንቡ ያደርጋቸዋል”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ስሙ ነው
እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች ለማከናወን ኃይሉንና ሥልጣኑን ያውጃል።ይሄንን በአሞፅ 2፤111 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።የአሞፅ ትርጉም “አዎ የእሥራኤልን ሕዝብ ከግብፅ ምድር አወጣሁ፤ፍልሥጤማውያንንም ከከፍቶር ሶርያውንንም ከቂር አወጣሁ።”የአሞፅ ትርጉም(በሙያ ላይ የተደገፈ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ቂር
በአሞፅ 1፤5 ላይ የዚህን ሥፍራ ሥም እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

የእግዚአብሔር ዓይኖች በኃጢአተኞች መንግሥት ላይ ናቸው
እዚህ ላይ “ዓይኖች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔር ስለራሱ በሶስተኛ አካልነቱ ሲናገር ነው።የአሞፅ ትርጉም “እኔ እግዚአብሔር የዚህ መንግሥት ሰዎች እጅግ ኃጢአተኞች እንደሆኑ አይቻለሁ” (ሚቶኖሚ አንደኛ፤ሁለተኛና ሶስተኛ አካልን ይመልከቱ)

ከምድርም ፊት አጠፋታለሁ
“ከምድርም ፊት”የሚለው አነጋገር “ሙሉ በሙሉ” ማለት ነው።የአሞፅ ትርጉም“ይህንን መንግሥት ሙሉ ለሙሉ አጠፋዋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገርን ተመልከቱ)

Amos 9:7

የያዕቆብ ቤት
እዚህ ላይ “ቤት” የሚለው ቃል የሚወክለው ቤተሰብን ሲሆን “ያዕቆብ”የሚለው ደግሞ የእርሱን ትውልዶች የሚገልፅ ነው።(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 9:9

የእሥራኤል ቤት
እዚህ ላይ “ቤት” የሚለው ቃል የሚያመለክትው ቤተሰብን ነው።የአሞፅ ትርጉም “የእሥራኤል ሕዝብ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

እህልም በወንፊት አንደሚነፋ የእሥራኤልን ቤት በአህዛብ መካካል እነፋለሁ።ነገር ግን አንዲት ቅንጣት በምድር ላይ አትወድቅም
እዚህ ላይ የሚያሣየው እህል በወንፊት ውስጥ ሲያልፍና ደንጋዮቹ ተንገዋለው ሲቀሩ ነው።የአሞፅ ትርጉም፡- ኃጢአተኛ የሆነውን የእሥራኤልን ሕዝብ እግዚአብሔር ያስወግደዋል የሚል ሃሣብ ነው ያለው።(ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)

ወንፊት
ብዙ ቀዳዳዎች ያሉት ወለል ሲሆን ትልልቅ ነገሮችን በውስጡ የማያሣልፍ ነው።

የሕዝቤ ኃጢአተኞች ሁሉ በሠይፍ ይወድቃሉ
እዚህ ላይ“ሠይፍ” የሚለው ቃል የሚመለክተው ጠላቶችን ነው።የአሞፅ ትርጉም“ጠላቶች የሕዝቤን ኃጢአተኞች ሁሉ ይገድላሉ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉው ነገር አይደርስብንም፤አያገኘንም
ጥፋትን መተግበር ልክ ጥፋት አንድን ሰው እንደሚውጠውና እንደሚያገኘው ተደርጎ ነው የተገለፀው።የአሞፅ ትርጉም “ጥፋት እኛን ሊያገኘን አይችልም”ወይም “መጥፎ ነገር አይደርስብንም” (ሲ ሜታፎር)

Amos 9:11

በዚያ ቀን
“በዚያን ዘመን”

የወደቀችውን የዳዊትን ድንኳን አነሣለሁ
የእሥራኤልን ሕዝብ እንደገና ታላቅ ማድረግን በተመለከተ ልክ የዳዊት ምንግሥት ድንኳን እንደሆነና እግዚአብሔር ደግሞ አንስቶ አንደገና እንደሚተክለው ተደርጎ ቀርቧል።የአሞፅ ትርጉም “የዳዊት ድንኳን ልክ እንደወደቀ ድንኳን ቢሆንም እንኳን እርሱ ግን መልሶ ያቆመዋል።”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የተናደውንም ቅጥሯን እጠግናለሁ
“ቅጥሯን አድሳለሁ”

የፈረሰውንም አድሳለሁ፤እንደ ቀደመውም ዘመን እሠራታለሁ
“የፈሰውን እንደገና አድሼ ከብዙ ዘመን በፊት እንደነበረችው ጠንካራ አድርጌ አቆማታለሁ።”

አዳራሾች
ወድቀው የቀሩ የየአዳራሾቹየተወሰኑ ክፍሎች

የኤዶምያስ ቅሬታ
“የቀረው የኤዶምያስ ግዛት”

ስሜ የተጠራባቸውን አህዛብን ሁሉ
እዚህ ላይ “ስም” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው።“በስሜ የተጠሩት”የሚለው አነጋገር ትርጉሙ በአንድ ወቅት የእግዚአብሔር ንብረት እንደነበሩየሚያሣይ ነው። ይሄ ማለት ባለፉት ጊዜያት ሕዝቡ ድልን አግኝተው እነዚህን ግዛቶች ተቆጣጥረዋቸው ነበር ማለት ነው። የአሞፅ ትርጉም “ለእኔ የነበሩ አህዛብ ሁሉ”ወይም “ባለፉት ጊዜያት እሥራኤላውያን ድል እንዲነሷቸው ያደረግኳቸውን አህዛብ” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል፤ፈሊጣዊ አነጋገር፤በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ስለ ራሱ በራሱ ሥም ይናገራል።ይሄንን በአሞፅ 3፤13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።የአሞፅ ትርጉም “የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የሚናገረው ይህንን

ነው” ወይም “የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ያለው ይሄንን ነው”(የመጀመሪያ፤ሁለተኛና ሦስተኛ የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 9:13

እዩ
ፀሐፊው አንድ አስደናቂ የሆነ ነገርን ሊናገር እንደተዘጋጀ ለአንባቢያን ይናገራል።ምናልባት ቋንቋችሁ ይህንን የሚገልፅበት መንገድ ሊኖረው ይችል ይሆናል።

ወራት ይመጣል... አራሹ
ወደፊት የሚመጡ ቀናቶች “ወራት እንደሚመጡ” በሚመስል መልኩ ተገልጿል።የአሞፅ ትርጉም “ወራት ይመጣል...አራሹ ሰው”ወይም “ወደፊት...አራሹ ሰው”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አራሹ... ዘርን የሚዘራው
እነዚህ እግዚአብሔር በእሥራኤል ውስጥ ባለፀግነትን ዳግም ለማምጣት መፈለጉን የሚያሣዩ ሁለት ገፅታዎች ናቸው።ይሄ የሚያሣየው እህል እጅግ በፍጥነት ከማደጉ የተነሳ ሰዎች እህሉን ለመሰብሰብ የሚያዳግታቸው እንደሆንና ብዙ የወይን ፍሬ ከመኖሩ የተነሳ ሰዎች ወይኑን ገና እየጠመቁ እያሉ ገበሬዎች ሌላ ተጨማሪ የወይን እርሻን የሚያርሱ መሆናቸውን ነው።

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ስለ ራሱ በራሱ ሥም ይናገራል።ይሄንን በአሞፅ 3፤13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።የአሞፅ ትርጉም “የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የሚናገረው ይህንን ነው” ወይም “የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ያለው ይሄንን ነው”(የመጀመሪያ፤ሁለተኛና ሦስተኛ የሚለውን ይመልከቱ)

ተራሮችም በተሃውን የወይን ጠጅ ያንጠባጥባሉ፤ኮረብቶችም ሁሉ ይቀልጣሉ
እነዚህ ሁለት መሥመሮች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው።እጅግ ብዛት ያላቸው የወይን ዘለላዎችና ወይኖች ልክ በተራሮችና በኮረብታዎች ላይ እንደሚፈሰሱ ተደርጎ ነው የቀረበው።(ንፅፅርንን እና ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 9:14

በምድራቸውም እተክላቸዋለሁ፤ከእንግዲህ ወዲህ ከሰጠኋቸው ከምድራቸው አይነቀሉም
ሕዝቡን እንደገና ወደ አገራቸው መመለስንና ከጠላቶቻቸው ተጠብቀው መቆየታቸውን ልክ እሥራኤል አትክልት እንደሆነና እግዚአብሔር ደግሞ በመሬት ውስጥ እንደሚተክለውና ማንም ሊነቅለው እንደማይችል ዓይነት ተመስሎ ተገልጿል።የአሞፅ ትርጉም “ሊነቀል እንደማይችል አትክልት በምድራቸው ለዘላለም እንዲኖሩ አደርጋቸዋለሁ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከምድራቸው አይነቀሉም
ይሄ አድራጊ ግሥ መልክ ሊገለፅ ይችላል።የአሞፅ ትርጉም “ማንም ሰው ቢሆን ከምድራቸው ሊነቅላቸው አይችልም።” (አድራጊ ግሥን ወይም ተካፋይ ያልሆነ የሚለውን ይመልከቱ)

መንቀል
ከመሬት ውስጥ አትክልትና ሥር ሲነቀል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Obadiah

Obadiah

Chapter 1

1 የአብድዩ ራእይ። ጌታ እግዚአብሔር ስለ ኤዶም እንዲህ ይላል፦ከእግዚአብሔር ዘንድ መልእክት ሰምተናል፥ መልእክተኛውም በአሕዛብ መካከል ተልኮ፥«ተነሡ! እርሷን ለመውጋት እንነሣ» ብሎአል። **2** አነሆ፥ በአሕዛብ መካከል ታናሽ አደርግሃለሁ፥እጅግ የተናቅህ ትሆናለህ። **3** አንተ በዓለት ስንጣቂ ውስጥ፥በከፍታ ሥፍራ በሚገኝ ቤት የምትኖር፥ በልብህም «ማን ወደ ምድር ያወርደኛል?» የምትል ሆይ፥የልብህ ኩራት አታልሎሃል። **4** እንደ ንስር እጅግ ከፍ ከፍ ብትል እንኳ፥ጎጆህም በከዋክብት መካከል ቢሆን እንኳ፥እኔ ከዚያ አወርድሃለሁ ይላል እግዚአብ ሔር። **5** ሌቦች ወደ አንተ ቢመጡ፥ዘራፊዎች በሌሊት ቢመጡ (አንተ እንዴት ተቆረጥህ!) ፥የሚበቃቸውን ያህል ብቻ የሚሰርቁ አይደለምን? ወይን ለቃሚዎች ወደ አንተ ቢመጡ ቃርሚያ አያስቀሩምን? **6** ዔሳው ምንኛ ተበረበረ፥የተደበቀ ሀብቱ ምንኛ ተዘረፈ? **7** የተማማልሃቸው ሰዎች፥በጉዞህ ወደ ድንበር ይሰድዱሃል።ከአንተ ጋር መልካም ግንኙነት የነበራቸው ሰዎች አታለሉህ፥አሸነፉህም። እንጀራህን የበሉ ከበታችህ ወጥመድ ዘረጉብህ። በእርሱም ዘንድ ማስተዋል የለም። **8** በዚያ ቀን ከኤዶም ጥበበኞችን፥ ከዔሳውም ተራራ ማስተዋልን አላጠፋምን? ይላል እግዚአብሔር። **9** ቴማን ሆይ፥ ሰው ሁሉ ከዔሳው ተራራ ታርዶ ይጠፋ ዘንድ፤ኃያላንህ ይደነግጣሉ። **10** በወንድምህ በያዕቆብ ላይ ስለ ተፈጸመ ግፍ፥እፍረት ይከድንሃል፥ለዘላለምም ትጠፋለህ። **11** እንግዶች ሀብቱን በዘረፉበት፥ባዕዳንም በበሮቹ በገቡበት፥በኢየሩሳሌምም ላይ ዕጣ በተጣጣሉበት ቀን፤አንተም ገለልተኛ ሆነህ በቆምህበት ቀን፥ ከእነርሱ እንደ አንዱ ሆነሃል። **12** ነገር ግን ወንድምህ በገጠመው ክፉ ቀን ሐሴት ማድረግ አይገባህም ነበር፥በጥፋታቸው ቀን በይሁዳ ሕዝብ ላይ መደሰት አይገ ባህም ነበር፤በጭንቀታቸው ቀን ትኩራራ ዘንድ አይገባህም ነበር። **13** በጥፋታቸው ቀን በሕዝቤ በር ትገባ ዘንድ አይገባህም ነበር፥በጥፋታቸው ቀን በመ ከራቸው ሐሴት ማድረግ አይገባህም ነበር፤በጥፋታቸው ቀን ሀብታቸውን መዝረፍ አይገባህም ነበር። **14** የሸሹትን ለመግደል በመስቀለኛ መንገድ ላይ ትቆም ዘንድ አይገባህም ነበር፤በጭንቀት ቀን የተረፉለትን አሳልፈህ መስጠት አይገባህም ነበር። **15** የእግዚአብሔር ቀን በአሕዛብ ሁሉ ላይ ቀርቦአልና። እንዳደረግኽው እንዲሁ ይደረግብሃል፥ ሥራህ በገዛ ራስህ ላይ ይመለሳል። **16** በቅዱስ ተራራዬ ላይ እንደጠጣችሁ፥ አሕዛብ ሁሉ ዘወትር ይጠጣሉ። ይጠጣሉ፥ ይጨልጡማል፤ ከዚህ በፊት እንዳልሆኑት ይሆናሉ። **17** በጽዮን ተራራ ያመለጡ ይገኛሉ፥ እርሱም ቅዱስ ይሆናል፤ የያዕቆብም ቤት የገዛ ራሱን ርስት ይወርሳል። **18** የያዕቆብ ቤት እሳት፥ የዮሴፍ ቤት ነበልባል፥ የዔሳውም ቤት ገለባ ይሆናሉ፤ያቃጥሉታል፥ይበሉታልም። ከኤሳው ቤት የሚተርፍ አይኖርም፥እግዚአብሔር ተናግሮአልና። **19** የኔጌብ ሰዎች የዔሳውን ተራራ ይወርሳሉ፥የቆላውም ሰዎች፦የፍልስጥኤማውያንን ምድር፥የኤፍሬምን ምድር፥ የሰማሪያንም ምድር ይወርሳሉ፤ብንያምም ገለዓድን ይወርሳል። **20** የእስራኤል ሕዝብ ሠራዊት ምርኮኞች የከንዓንን ምድር እስከ ሰራጵታ ድረስ ይወርሳሉ። በስፋራድም የሚኖሩ የእስራኤል ምርኮኞች የኔጌብን ከተሞች ይወርሳሉ። **21** በዔሳው ተራራ ላይ ይፈርዱ ዘንድ ነጻ አውጪዎች ወድ ጽዮን ተራራ ይወጣሉ፤ መንግሥቱም የእግዚአብሔር ይሆናል።

Obadiah 1:1

የአብድዮ ራዕይ
"ይህ የመፅሐፍ ርዕስ ነዉ " "ራዕይ " የሚለዉ ቃል አጠቃላይ ከያህዌ የሆነ መልዕክት ነዉ እንጂ አብድዮ መልዕክት ወይም የአብድዮ ትንቢት "

ጌታ ያህዌ ስለ ኤዶም ይህን ብሏል
ይህ ለአንባቢዉ የአብዲዮ መፅሐፍ መልዕክት ስለ ኤዶም መሆኑን ነዉ።

ያህዌ
ይህ ስም እግዚብሔር በብሉይ ኪዳን ለህዝቡ እራሱን የገለጠበት ነዉ። (በትርጉም ገፅ ላይ ያለዉን የያህዌን ትርጉም ተመልከት)

- መልክተኛ ተልኳል
ይህ በገቢር መልኩ ልቀመጥ ይችላል ተርጓሚዉ "ያህዌ መልዕክተኛ ልኳል "

ተነስ
"መቆም " ይህ ቃል ህዝብን ዝግጁ ለማድረግ ይጠቅም ነበር።

እሷን ለመቋቋም ተነስ
እሷ የሚለዉ ቃል ኤዶምን ህዝብ ለመግለፅ የተጠቀሰ ሲሆን የኤዶም ህዝብ የቅፅል ስም ነዉ። ስለዚህ " እነሱን" እየተባለ ልተረጎምም ይችላል።

እነሆ እሠራሃለዉ /አበጀሃለዉ /
ቁጥር 2 ስጀምር አብድዮ ያህዌ በቀጥታ ለኤዶም እንደተናገረ ፅፏል።

ተነሽ/ተነስ
ይህ ለአንባቢዉ ምን ልከተል እንደሚችል የተለየ ትኩረት እንዲሰጥ ያነቃዋል። ተርጓሚዉ " ልነግርህ ስላለዉ ነገር ተመልከት ወይም ትኩረት ስጥ"

በአህዛብ መካከል ታናሽ አደርግሃለዉ በአህዛብም ትናቃለህ
እነዚህ ሁለት ሓረጎች በትርጉም አንድ ሲሆን ኤዶም የነበራትን ታላቅነት እንደምታጣ ትኩረት ለመስጠት ነዉ።

በአህዛብ መካከል ታናሽ አደርግሃለዉ
በቀላሉ ልታለዩ የሚችል የሆነስ በመጠን (በይዘት) የማይረባ ስለመሆን ተናግሯል ተርጓሚዉ-- በአህዛብ መካከል የማትረባ አደርግሀለዉ

በብዙ ትናቃለህ(ትናቂያለሽ)
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚው “የሌላ ሀገር ህዝቦች ይጠሉሻል/ሃል”

Obadiah 1:3

አጠቃላይ መረጃ
የአብድዩ ራእይ:አዳምን በተመለከተ ቀጥሏል

የልብህ ትዕቢት አታልሎሃል
“ልብህ ከስሜት ጋር ተመሳስሏል፡ የኤዶማዊያን ትዕቢት ስለ ጥበቃቸው እንዲታለሉ አድርጓቸዋል። ተርጓሚው “ትዕቢትህን አታልሎሀል” ወይንም “ትዕቢትህን የማትረታ አድርገህ እንድታስብ አድርጎሃል ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በተሰነጠቀ ዓለት ውስጥ
“በተሰነጠቀ ዓለት ውስጥ” እዚህ ጋር ሃሳቡ በአለት ስለተከበበ የተጠበቀ ቦታ ነው ።

ከፍ ባለው መኖሪያህ **(**ማደሪያህ**)**
“በከፍታ ቦታ ላይ በተሰራው መኖሪያህ ውስጥ”

በልብህ
እዚህ ጋር “በልብህ” ምሳሌያዊ ንግግር ሲሆን “ለራስህ” ተርጓሚው“ለራስህ ትላለህ” ወይም “ታስባለህ”

ወደ ምድር የሚያወርገኝ ማነው**?**
ይህ ጠያቄ የሚያመለክተው አዳማዊያን ትዕቢተኛና ማነም እንደማይነካቸው ማሰባቸውን ነው። ተርጓሚው - “ማንም ወደ ምድር ሊያወርዳቸው አይችልም” ወይም “ከየትኛው ሰልፍ እድናለው”

እንደ ንስር መጥቀህ ብትወጣ ቤትህም በከዋክብት መካከል ቢሆን
እነዚህ ሁለት ግነቶች ኤዶም በጣም በከፍታ ቦታ ላይ ቤቱን መስራቱን በማንም በማይደረስ ከፍታ ላይ ብሎ ይናገራል። ተርጓሚው “ እረግርሀለሁ ክንፍ ኖሮህና ከንስር በላይ ብትበር ቤትህም በኳክብት መካከል ቢሆን”

ከዚያ አወርድሃለው
ትዕቢት ከከፍታ ጋር ሲመሳሰል ትህትና ደግሞ ዝቅ ከማለት ጋር ተመሳስሏል።”ለማውረድ” ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ አንድን ሰው ትሁት ማድረግ ነው። ተርጓሚው - ትሁት አደርግሃለው (ፈሊጣዊ ትርጉም ተመልከት)

Obadiah 1:5

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ በአብድ በኩል ለኤዶም መልዕክቱን መስጠት ቀጥሏል

ሌቦች ቢመጡብህ ወይም ወንበዴዎች በሌሊት ቢመጡ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ሲሆኑ የሚያመለከክቱትም ለሌቦች ወይም ለሚሰርቁ ሰዎች ትኩረት ለመስጠት ነው። አንድ ላይ መሆንይችላሉ። ተርጓሚው - “ዘራፊዎች ወደ አንድ ሰው ቤት በሌሊት ሰብረው ሲገቡ” (see Hendiadys)

ወንበዴዎች በሌሊት ቢመጡ
ወይም “ወንበዴዎች በሌሊት ቢመጡ”

ወንበዴዎች
ከሌሎች እቃን ወይም ንብረትን የሚሰርቁ ሰዎች

አንተ ግን ምንኛ ጠፋህ!
ያህዌ ይህን ሐረግ በሌላ አረፍተ ነገር መካከል የተጠቀመው ምን ያህል የኤዶም ቅጣት አስደንጋጭ እንደሆነ ለመግለፅ ነው። ተርጓሚው “ፈፅሞ ጠፍተሃል”

ወይንንም የሚጠብቁ ደ አንተ ቢመጡ ቃርሚያ አያስቀሩምን**?**
ይህ ጥያቄ የሚያመለክተው ምን ያህል የያህዌ ቅጣት በኤዶም ላይ ከወይን ቆራጮችም የከፋ መሆኑን ለማመልከት ነው። ይህ በግልፅ ሲቀመጥ ተርጓሚው - ወይን ቆራጮች ወደ አንተ ቢመጡ የተወሰነ ወይን ይተዋሉ; እኔ ግን ሁሉን ከአንተ እወስዳለው።

ኤሳው ምንኛ ተመረመረ፤ የተሸሸገበት ነገር ምንኛ ተፈለገ
ይህ በገቢር ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚው - ወዮ፤ጠላቶች ከኤሳው ሁሉንም ነገር ዘረፉ ፤ የተሸሸገበት ነገሩንም አገኙበት (see Active or Passive)

ኤሳው
የኤዶም ህዝብ ከ ኤሳው የዘር ሐረግ ነበሩ። ስለዚህ ፤ በዚህ መጽሀፍ ውስጥ “ኤዶም” እና “ኤሳው” ሚናገሩት ስለ አንድ ወገን ህዝቦች ነው።

ተመረመረ **(** ምስቅልቅሉ ወጣ**)**
ይህ ጠላቶች የኤሳው ነገር ፈልገው ያለው ውድ ንብረቶች እንደወሰዱበትና ምስቅልቅል እንዳወጡ ወይም እንዳጠፉ ማለት ነው።

Obadiah 1:7

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መልዕክቱን በአብድዩ በኩል ለአሳቢ መስጠቱን ቀጥሏል

የተማማላሃቸው ሰዎች ሁሉ-----ከአንተ ጋር ሰላም የነበሩ -----እንጀራህንም የተመገቡ
ሦስቱም ሐረጎች የሚያመለክቱት ስለ ኤዶም ወዳጆች ነው

ወዳጆችህ **(** የተማማልሃቸው**)**
ወዳጆችህ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ስለ ኤዶም ህዝብ ነው

ወደ ዳርቻ ሰደዱህ
“ከምድራቸው አሳደዱህ” የኤዶም ህዝቦች ወደ ወዳጆቻቸው ምድር ለመሰደድ ይሞክራሉ ነገር ግን ማምን በምድራቸው እንዲቆዩ አልተዋቸውም።

ማስተዋል በእርሱ ዘንድ የለም
በሚከተሉት መልኩ ሊተረጎም ይችላል፡-

1. ወዳጆቹ ስለ ኤዶም ያሉት ተርጓሚ: “ኤዶም ምንም መረዳት የለውም”
2. ስለከዳተኞቹ የተባለው ዓ.ነገር ተርጓሚው “ይህን ለምን እንዳደረጉ ማንም ሊረዳ አይችልም።”

በዚያ ቀን **.....**ከኤሳው ተራራ **.....**አላጠፋምን**?** ይላል እግ/ር
እግ/ር ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው የኤዶምን መጥፋት ለማስረገጥ ነው። ተርጓሚው “በዚየያ ቀን በእርግጥ ከኤሳው ተራራ.... አጠፋለው”

የኤሳው ተራራ
ይህ የሚያስረዳው የኤሳው ምድር በአብዛኛው ተራራማ መሆኑንና ይህም የኤዶምን ምድር ለመግለፅ ነው።

የታመንካቸው ሰዎች አታለሉህ
“ብርቱ ተዋጊዎችህ ይደነግጣሉ ”

ቴማን
ይህ በኤዶም ምድር የሚገኝ ግዛት ነው(ተመልከት የስም ትርጓሜ)

ሰዎች ሁሉ ከኤሳው ተራራ በመገደል ይጠፉ ዘንድ
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚው “ጠላቶች ስለገደሏቸው ሰዎች በኤሳው ተራራ አይኖሩም” ወይም በኤሳው ተራራ የተገኘ ሰው ሁሉ ስለሚገደል (see Active or passive)

ይለያሉ/ ወደ ፍጻሜ ይመጣሉ
“ይጠፋሉ

Obadiah 1:10

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሄር መልእክቱን ለኤዶም በአብድዩ በኩል መስጠቱን ቀጥሏል።

ወንድምህ ያዕቆብ
እዚህ ጋር ያዕቆብ የሚወክለው የዘር ሃረጉን ነው። ምክኒያቱም ያዕቆብ የኤሳው ወንድም ስለሆነ የኤዶም ሰዎች የያዕቆብ ዘር ሐረግ ልጆች ወንድም እንዲሆኑ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ተደርጎ ስለተነገረ ተርጓሚው “ የያዕቆብ ዘር ሃረግ (ነገድ) የሆኑትን ዘመዶችህ”

እፍረት ይከድንሃል
በኣንድ ነገር መከደን የህይወት ልምምድን ማሳያ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። ተርጓሚው - ፈጽሞ ታፍራለህ (ፈሊጣዊ ተመልከት)

ለዘላለም ትጠፋለህ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚው - በፍፁም ዳግመኛ ተመልሶ አይኖርም

በፊቱ አንፃር በቆምህ ቀን
አይቶ ለመረዳት ምንም አለማድረግ

እንግዶች
ለኬላ ወገን የሆኑ ሰዎች

ጭፍራቸውን
ይህ ስለያዕቆብ ሲሆን የእስራኤልን ህዝብ ለመግለፅ ነው።

በኢየሩሳሌምም ዕጣ ተጣጣሉ
ይህ ሐረግ የሚያሳው ከኢየሩሳሌም የዘረፉትን ውድ ንብረቶች ማን እንደሚወስድ ለመወሰን ነው።

ከእነርሱ እንዳንዱ ነበርክ
“አንተ ደግሞ እንደ እንግዶችና እንደ ባዕዳኑ ነበርክ” ይህ የሚያሳየው እስራኤልን አለመረዳታቸው ነው። ቋንቋ ሲቀመጥ፡ ተርጓሚው “አንተም ልክ እንደጠላቶች ነበርክ እስራኤልንም አልረዳህም።”

Obadiah 1:12

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሄር ለኤዶም መልዕክቱን በአብድዩ በኩል መላኩን ቀጥሏል

አጠቃላይ መረጃ
ቁጥር 12፡-14- እግዚአብሄር ለኤዶም ሕዝብ እስራኤልን ባለመንከባከባቸው ተደጋጋሚ ትእዛዝ መስጠቱን የያዘ ክፍል ነው።

ደስ አይበልህ (ደስ ይልህ ዘንድ)
እርካታ አይሰማህ

በመከራ ቀን ወንድምህን
ወንድምህ የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእስራኤልን ህዝብ ነው። ምክኒያቱም ያዕቆብና ኤሳው ወንድማማች ስለነበሩ።

በመከራው ቀን
“ክፉ ነገር ባጋጠመው ጊዜ”

ቀን(ቀኑ)
ይህ ባቢሎን እስራኤልን በተደጋጋሚ ያጠቃበትና ያጠፋበት ቀንን ለማመልከት ነው

በጥፋታቸው ቀን
“ጠላቶቻቸው ባጠፏቸው ጊዜ”

በመከራቸው ቀን
በተጨነቁ ጊዜ

ጥፋት.....ውድመት.....መፈራረስ
ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ቃላት ሲሆኑ አንድ ቃል ብቻ ያለው ቋንቋ በዚያው ቃል ሦስቱንም ትርጉም መጠቀም ይቻላል።

በመከራቸው ላይ
መጥፎ ነገር ስለደረሰባቸው(በእነርሱ ላይ ስለደረሰ)

በሀብታቸው ላይ እጅህን አትዘርጋ
“ሀብታቸውን አትውሰድ” ወይም “ሀብታቸውን አትዝረፍ”

መንታ መንገድ
ሁለት መንገዶች የሚገናኙበት ቦታ

የሸሹትንም ለመግደል
“ለማምለጥ የሚያገለግሉትንም የእስራኤልን ህዝብ ለመግደል” ወይም ለማምለጥ የሚሞክሩትን ለመያዝ

ከእርሱ የቀሩትን አሳልፈህ አትስጥ
“በህይወት ያሉትን ይዘህ ለጠላቶቻቸው አትስጥ”

Obadiah 1:15

አጠቃላይ መረጃ
በቁጥር 15 ላይ እግዚአብሄር መልዕክቱን ያጠቃልላል ከ16-21 በላይ ክፍል ላይ እግዚአብሄር በአብድዩ በኩል ለ ይሁዳ ህዝብ የኤዶም ምድር እንደሚወርሱ ይናገራቸዋል።

የእግዚአብሄር ቀን.....ቀርቧልና.....በራስህ ላይ ይመለሳል
የመጽሀፍ ቅዱስ አዋቂዎች ቁጥር 15 ከቁጥር 14 ጋር ተያያዥነት እንዳለውና የመጀመሪያው ክፍል መደምደሚያ ወይም ለቁጥር 16 የመጀመሪያ ክፍል መሆኑን እርግጠኛ አይደሉም

የእግዚአየእግዚአብሄር ቀን በአህዛብ ሁሉ ላይ ቀርቧልናብሄር ቀን በአህዛብ ሁሉ ላይ ቀርቧልና
“እግዚአብሄር አምላክ ጌታ መሆኑን ለአህዛብ ሁሉ የሚያሳይበት ቀን ጊዜው አሁን ነው ”

አንተ እንዳደረግኸው እንዲሁ ይደረግብሃል
ይህ በገብር መልክ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚው “በሌሎች ያደረግኸውን እንዲሁ በአንተ ላይ አደርጋለሁ።”

ፍዳህንም በራስህ ላይ ይመለሳል
በራስህ ላይ ይመለሳል የሚለው ለነዚያ ነገሮች ይቀጣሉ ማለት ነው። ተርጓሚው “ለሰራኸው ሥራ መከራን ታያለህ”

አንተ
አንተ ሚለው ቃል ብዙ ወይ የወል ሲሆን የእስራኤልን ህዝብ ያመለክታል ተብሎ ይታሰባል

እንደ ጠጣችሁ
ይሁዳ ከጠላቶቹ የተቀበለው ቅጣት ልክ እንደ መራራ(ኮምጣጣ) መጠጥ መሆኑን ለማመልከት ነው። ተርጓሚው “መከራን እንደጠጣችሁ” ወይም “እንደቀጣኋችሁ”

በቅዱስ ተራራዬ
ይህ እየሩሳሌምን ለማለት ነው።

እንዲሁ አህዛብ ሁሉ ዘወትር ይጠጣሉ
እግዚአብሄር በአህዛብ ሲቀጣቸው ተገለፀበትን ንግግር ዘወትር መራራ መጠጥን እንደጠጡ ተደርጎ ተመስለሏል። ተርጓሚ “አህዛብ ሁሉ መከራን ዘወትር ይጠጣሉ” ወይም “አህዛብን ሁሉ ሁሉ ያለማቋረጥ እቀጣለሁ”

ይጠጣሉ፤አዋን ይጠጣሉ ይጨልጡማል እንዳልሆኑም ይሆናሉ
እግዚአብሄር ቅጣትን የመጣበት ዘይቤያዊ አነጋገር ቀጥሏል።ይጨልጣሉ የሚለው ቃል የሚገልፀው ቅጣትን በሙላት ይለማመዳሉ ማለት ሲሆን ውጤቱም ፈጽሞ እንደሚጠፉ ነው። ተርጓሚው “የቅጣቱን ፅዋ ፈጽመው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እስኪጠፋ ይጠጣሉ” ወይም ፈፅሜ እስካጠፋቸው ድረስ በተደጋጋሚ እቀጣቸዋለው”

Obadiah 1:17

አጠቃላይ መረጃ
ከቁጥር 16-21 እግዚአብሔር የይሁዳ ሕዝብ የኤዶምን ምድር እንደሚወርሱ በእብዲዩ በኩል ይናገራል።

የሚያመልጡ ይሆናሉ
እነዚህ እግዚአብሔር ከተማዋን ቀጥቶ ካበቃ በኋላ በሕይወት ያሉ የእሩሳሌም ህዝብ ናቸው ይህም በግልጽ ተርጓሚው “ከእግዚአብሔር ቅጣት ያመለጡ የተወሰኑ የእስራኤል ህዝቦች” ማለት ነው።

እርሱም ቅዱስ ይሆናል
“እርሱ”የሚለው ቃል የፅዮን ተራራን ያመለክታል።

የያዕቆብን ቤት እሳት የዮሴፍን ቤት ነበልባልም
እግዚአብሔር ስለ ያዕቆብና ዮሴፍ ቤት ሲናገር እሳት እንዲሆኑ አድርጎ ነው። ይህም የሆነበት ምክኒያት ኤሳውን ልክ እንደ እሳት ፈጥነው ጨርሰው ስለሚያጠፉ ነው፤

የያዕቆብ ቤት
ቤት የሚለው ቃል ዘይቤያዊ ሲሆን በቤት ውስጥ ስለሚኖረው ነፍስ(ህይወት) ለማለት ነው። በዙህ መልኩ የይዕቆብን የዘር ሐረግ(ነገድ) ለማመልከት ነው። ተርጓሚው - ዬዕቆብ የዘር ሐረግ (ነገድ)

ገለባ
እህል ከተወቃበት (ከተሰበሰበ) በኋላ መሬት ላይ የሚቀር

እነርሱንም
ይህ ቃል የሚያመለክተው የያዕቆብና የዮሴፍ ቤትን ነው።

ያቃጥሏቸዋል
ያቃጥሏቸዋል የሚለው የኤዶም ሕዝብ የሆኑትን ኤሳውን የዘር ሐረግ ይወክላል።

ከኤሳው ቤት ቅሬታ የለውም
“አንድም ሰው ከለኤሳው ቤት አይተርፍም”

የኤሳው ቤት
ቤት የሚለው ቃል ዘይቤያዊ ሲሆን በቤት ውስጥ ስላሉት የቤተሰብ አባላት ነው። ይህም የኤሳው የዘር ሐረግ ይወክላል። ተርጓሚው “የኤሳው የዘር ሃረግ” (ዘይቤን ተመልከት)

እግዚአብሄርም ተናግሯልና
ይህ የቃለ መሃላ ቀመር ሲሆን እግዚአብሄር ስለተናገረ ብቻ የሚፈፅም መሆኑን ነው፤

Obadiah 1:19

አጠቃላየ መረጃ
ከቁጥር 16-21 እግዚአብሄር የይሁዳ ህዝብ የአዳምን ምድር እንደሚወርስ በአብድዩ በኩል ይናገራል።

የደቡብም ሰዎች የኤሳውን ተራራ ይወርሳሉ
“በደቡብም የሚኖሩ እስራኤላውያን የዶማውያንን ምድር ይወስዳሉ”

የቆላውም ሰዎች
በምዕራብ ኮረብታማ የሚኖሩ እስራኤላውያን በምርኮ የፍልስጤማውያንን ምድር በምርኮ ይወርሳሉ ።

ይወርሳሉ
ይህ በአጠቃላይ የእስራኤልን ሕዝብ ለመግለፅ ነው።

ብንያምም ይወርሳል
“የብንያም ጎሳ ይወርሳል” ወይም የብንያም ዘር ሐረግ (ነገድ) ይወርሳል።

Obadiah 1:20

አጠቃላይ መረጃ
ከቁጥር 16-21 እግዚአብሄር የይሁዳ ሕዝብ የኤዶምን ምድር እንደሚወርስ በአብድዩ በኩል ይናገራል።

ይህም የ እስራኤል ልጆች የጭፍራቸው ምርኮ

1. ምርኮኞች ከሰምን የእሰራኤል መንግስት ወደ ሶርያ መወሰዳቸውን
2. ከእየሩሳሌም ውጭ የሚኖሩ ይሁዳ ህዝቦች ወደ በባቢለን ተወስዷል፡፤ ሁለቱም ትርጉም ሊሆን ይችላል፡፤

ጭፍራ
ብዙ ቁጥር ያለው ሕዝብ

እስከ ሰራጵያ ድረስ
ሰራጵያ ከእስረኤል በስተሰቤን በሜርትራንያን ባህር ዳርቻ በጠየርና በሲዶን መካከል የምትገኝ የፎኒሺያን ከተማ ነበረች፡፤

የኢየሩሳሌም ምርኮኞች
ይህ ቡድን ወገን) ከእየሩሳሌም ውጪ የኖሩ ነበሩ ሲሆን ከሰሜን መንግስት ከሆኑት እስራኤላውያን ወይም አይሁድ ህዝብ ይለያሉ፡፤

ስፋራድ
አቅጣጫው የማይታወቅ የቦታ ስም ነው፡፤ አንዳንድ ዋቂዎች እንደሚሉት በሊዲያ ግዛት የምትገኝ የሳርድስ ከተማ ነች (የስም ትርጉም ተመልከት)

በኤሳውያን ተራራ ላይ ይፈርዱ ዘንድ አዳኞች ወደ ፅ ዮን ተራራ ላይ ይወጣሉ።
-አዳኞች እስከ እየሩሳሌም ይሄዳሉ ከዚያም ሆነው ኤዶምን የገዛሉ

አዳኞች

1. ”እግዚአብሄር ኤዶምን ሊቀጣ የሚጠቀምበቸው የተለያዩ የእስራኤል የጦር መሪዎች”
2. .”የተወጁት” እና የተመለሱት የአይሁድ ምርኮኞች ይገልፃል። በሁለቱም መልኩ ሊተረጎም ይችላል።

መንግስቱም ለእግዚአብሄር የሆናል
እግዚአብሄር እራሱ በመንግስት ላይ ገዢ እንደሆነ የሚያሳይ ሀረግ ነው። ተርጓሚው” እግዚአብሄር ንጉሳቸው ይሆናል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Jonah

Jonah

Chapter 1

1 የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል ወደ አማቴ ልጅ ወደ ዮናስ እንዲህ ሲል መጣ፤ **2** «ተነሣና ወደ ታላቋ ከተማ ወደ ነነዌ ሂድ፤ ክፏቷ ወደ ፊቴ ወጥቶአልና በእርሷ ላይ ስበክ።» **3** ዮናስ ግን ከያህዌ ፊት ኮበለለ፤ ወደ ተርሴስ ለመሄድም ተነሣ። ወደ ኢዮጴ ወረደ። ወደ ተርሴስ በምትሄድ መርከብ ተሳፈረ። **4** ያህዌ ግን በባሕሩ ላይ ታላቅ ነፋስ ላከ፤ ከባድ ማዕበልም ተነሥቶ መርከቧን አናወጠ፤ ወዲያውኑ የምትሰበር መስሎ ታየ። **5** መርከበኞቹ በጣም ፈሩ፤ እያንዳንዱ ሰው ወደ አምላኩ ጮኸ ። የመርከቧ ክብደት እንዲቀልል በውስጧ የነበረው ሸክም ወደ ባሕሩ ተጣለ። ዮናስ ግን ወደ መርከቧ ታችኛ ክፍል ሄዶ ተኛ፤ ከባድ እንቅልፍ ላይም ነበር። **6** የመርከቧ አዛዥ ወደ እርሱ መጥቶ፣ «እንዴት ትተኛለህ? ተነሥና አምላክህን ጥራ! ምናልባትም አምላክህ ያስበንና ከጥፋት ያድነን ይሆናል። አለው። **7** እርስ በርሳቸውም፣ ይህ ክፉ ነገር የደረሰብን በማን ኃጢአት መሆኑን እንድናውቅ ኑ፣ ዕጣ እንጣጣል» ተባባሉ። ዕጣ ተጣጣሉ፤ ዕጣውም በዮናስ ላይ ወደቀ። **8** ከዚያም ዮናስን፣ «ይህ ክፉ ነገር የደረሰብን በማን ምክንያት እንደ ሆነ እባክህ ንገረን። ሥራህ ምንድነው? ከወዴትስ መጣህ? አገርህ የት ነው? ከየትኛውስ ሕዝብ ነህ?» አሉት። **9** ዮናስም፣ «እኔ ዕብራዊ ነኝ፤ ባሕሩንና ደረቁን ምድር የፈጠረውን የሰማይን አምላክ ያህዌን አመልካለሁ» አላቸው። **10** እርሱ ራሱ ነግሮአቸው ስለ ነበር ከያህዌ ፊት እየኮበለለ እንደ ነበር አወቁ፤ ስለዚህ የበለጠ ፈርተው፣ «ለመሆኑ፣ ምን እያደረግህ ነው?» አሉ። **11** ባሕሩ ይበልጥ እየተናወጠ በመሄዱ፣ ሰዎቹ ዮናስን፣ «ባሕሩ ጸጥ እንዲልልን አንተ ላይ ምን ብናደርግ ይሻላል?» አሉት። **12** ዮናስም፣ «አንሥታችሁ ወደ ባሕሩ ጣሉኝ፤ ያኔ ባሕሩ ጸጥ ይልላችኃል፤ ይህ ታላቅ ማዕበል የመጣባችሁ በእኔ ምክንያት እንደ ሆነ አውቃለሁ» አላቸው። **13** ሰዎቹ ግን ወደ መሬት ለመመለስ የሚቻላቸውን ያህል ቀዘፉ፤ ይሁን እንጂ ባሕሩ የባሰ ይናወጥ ጀመረ። **14** ስለዚህም፣ «ያህዌ ሆይ፣ በዚህ ሰው ነፍስ ምክንያት እንዳታጠፋን እንለምንሃለን፤ የዚህ ሰው ሞት እኛ ላይ አይሁንብን፤ ምክንያቱም አንተ ያህዌ የወደድኸውን አድርገሃል» በማለት ወደ ያህዌ ጮኹ። **15** ዮናስንም አንሥተው ወደ ባሕሩ ጣሉት፤ ባሕሩም መናወጡ ቆመ። **16** ሰዎቹም ያህዌን እጅግ ፈሩ። ለያህዌ መሥዋዕት አቀረቡ፤ ለእርሱም ስእለትን ተሳሉ። **17** እግዚአብሔር ግን ዮናስን የሚውጥ ትልቅ ዓሣ አዘጋጀ፤ ዮናስም ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ዓሣው ሆድ ውስጥ ኖረ።

Jonah 1:1

የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር መናገሩን የሚያመለክት አባባል ነው። ‹‹እግዚአሔር መልእክቱን ተናገረ››

የእግዚአብሔር ቃል
‹‹የእግዚአብሔር መልእክት››

ያሕዌ
ይህ በብሉይ ኪዳን ለሕዝቡ የገለጠላቸው የእግዚአብሔር ስም ነው። ይህንን ለመተርጎም ስለ ያሕዌ በትርጉም ቃል ገጽ ውስጥ የተሰጠውን ማብራሪያ ተመልከት።

አማቴ
ይህ የዮናስ አባት ስም ነው። (ስሞችን ስለመተርጎም የሚለውን ተመልከት)

ተነሣና ወደ ታላቂቱ ከተማ፣ ወደ ነነዌ ሂድ
‹‹ወደ አስፈላጊዋ ከተማ ወደ ነነዌ ሂድ››

ተነሣና ሂድ
ይህ ወደ ሩቅ ሥፍራ ስለመሄድ የተለመደ አገላለጽ ነው።

በእርስዋ ላይ ስበክ
እግዚአብሔር የሚያመለክተው የከተማዋን ሕዝቦች ነው። በእርስዋ ላይ ‹‹ሕዝቡን አስጠንቅቃቸው››

ክፋታቸው ወደ ፊቴ ወጥቶአል
‹‹ ያለማቋረጥ ኃጢአትን ያደርጉ እንደነበር አውቃለሁ።

ከእግዚአብሔር ፊት ለመሸሽ ተነሣ
‹‹ ከእግዚአብሔር ፊት መሸሽ›› ‹‹ተነሣ›› የሚለው የሚየመለክተው ዮናስ ከነበረበት ሥፍራ መሄዱን ነው።

ከእግዚአብሔር ፊት
እዚህ እግዚአብሔር በሕልውናው ተገልፆአል።

ወደ ተርሴስ ሂደ
‹‹ ወደ ተርሴስም ሂደ።›› ተርሴስ የምትገኘው ከነነዌ በተቃራኒ በኩል ነው። ይህ የበለጠ ግልጽ የሚሆነው ዮናስ ግን ከእግዚአብሔር ፊት ወደ ተርሴስ ይኮበልል ዘንድ ተነሣ በሚለው ላይ ነው።

ወደ ኢዮጴም ወረደ
‹‹ዮናስ ወደ ኢዮጴ ሄደ››

መርከብ
‹‹መርከብ›› በባሕር ላይ ብዙ ተጓዦችን ወይም ከባድ ጭነት ተሸክሞ የሚጓዝ ትልቅ ጀልባ ነው።

ዋጋ ከፈለ
‹‹ዮናስ ለጉዞው ከፈለ››

ወደ መርከቧ ገባ
‹‹ በመርከቧላይ ወጣ››

ከእነርሱ ጋር
‹‹ከእነርሱ ጋር›› የሚለው ቃል በመርከቧ ውስጥ አብረው የሚጓዙትን ያመለክታል።

ከእግዚአብሔር ፊት ኮበለለ
እዚህ ላይ እግዚአብሔር ሕልውናው ፊት በሚለው ቃል ተወክላል። ‹‹ከእግዚአብሔር ፊት ኮበለለ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Jonah 1:4

ወዲያውም እንዲህ ሆነ
መርከቢቱም ልትሰበር ቀረበች በማለት ‹‹ሰዎቹ አሰቡ››

ልትሰበር ቀረበች
ይህ በድርጊታዊ አገላለጽ ሊቀርብ ይችላል። ‹‹ልትሰባበር’

መርከበኞቹ
በመርከቧ ላይ የሚሠሩ

የራሱን አምላክ
እዚህ ላይ ‹‹አምላክ›› የተባለው ሰዎች የሚያመልኳቸውን የስህተት አማልክትና ጣዖታት ለማመልከት ነው።

በመርከቧ ውስጥ የነበረውን ዕቃ ወደ ባሕር ጣሉ
‹‹ሰዎቹ በመርከቧ ውስጥ የነበረውን ከባድ ነገር ወደ ብሕር ውስጥ ጣሉ።›› ይህ የተደረገው መርከቧን ከመስጠም ለመጠበቅ ነው።

ቀላል ለማድረግ
መርከቢቱ ቀላል ስትሆን በተሻለ ሁኔታ ትንሳፈፋለች። ‹‹ መርከቧ በተሻለ ሁኔታ እንድትሳፈፍ››

ነገር ግን ዮናስ ወደ መርከቧ ውስጠኛው ክፍል ውርዶ ነበር።
ዮናስ ይህን ያደረገው ማዕበሉ ከመነሣቱ አስቀድሞ ነበር።

ወደ መርከቧ ውስጠኛው ክፍል
‹‹ወደ መርከቧ ውስጥ››

በዚያ በከባድ እንቅልፍ ተኝቶ ነበር
‹‹በዚያ ከባድ እንቅልፍ ተኝቶ ነበር›› ወይም ‹‹ በዚያ ተኝቶ ነበር ከባድ እንቅልፍም ወስዶት ነበር።›› ከዚህ የተነሳ ማዕበሉ ሊቀሰቅሰው አልቻለም።

Jonah 1:6

የመርከቡም አለቃ ወደ እርሱ መጥቶ እንዲህ አለው
‹‹ የመርከቡ ኃላፊ ወደ ዮናስ ሄዶ እንዲህ አለው››

ተኝተህ ምን ትሠራለህ? ‹‹ስለምን ተኝተሃል?›› ይህን ሓሳባዊ ጥያቄ ያቀረበው ዮናስን ለመውቀስ ነው። ‹‹ማንቀላፋትህን አቁም!››

ተነሣ !
ይህ አንድ ነገርን ለማድረግ መቀስቀስን ያመለክታል። ለዮናስ፣ የመርከቡ አለቃ በሰላም ለመጓዝ ተነሥቶ አምላኩን ይለምን ዘንድ ነገረው።

አምላክህን ጥራ!
‹‹ወደ አምላክህ ጸልይ!›› ‹‹ጥራ›› የሚለው ቃል የአንድን ሰው ቀልብ የሚስብ ነው።

ምናልባት አምላክህ ስለ እኛ አስቦ ከጥፋት እንድን ይሆናል
የዮናስ አምላክ እንደሚያድናቸው በስውር የተገለጸው መረጃ በገሃድ እንዲታወቅ ይሆናል። ‹‹ ምናልናት የአንተ አምላክ ይሰማንና ከጥፋት ያድነናል እንዲህ ከሆነ አንሞትም።››

ሁሉም ለእርስ በርሳቸው ተነጋገሩ
‹‹መንገዶኞችም ሁሉ እርስ በርሳቸው ተነጋገሩ››

ኑ፣ እጣ እንጣጣል፣ ይህ በእኛ ላይ የደረሰብን ክፉ ነገር በማን ምክንያት እንደሆነ እናውቃለን
‹‹ይህን መከራ ማን እንዳመጣብን ለማወቅ እጣ መጣል አለብን›› ሰዎቹ ሊያውቁ የሚፈልጉትን ለማሳወቅ አማልክቱ እጣው በማን ላይ እንደሚወድቅ እነደሚቀጣጠሩ የምናሉ። ይህ መለኮታዊ አሠራር ነው።

ይህ ክፉ
ይህ አስቸጋሪውን ማዕበል ያመለክታል።

እጣው በዮናስ ላይ ወደቀ
‹‹እጣው ዮናስ በደለኛ መሆኑን ያሳያል››

Jonah 1:8

ከዚያም ዮናስን እንዲህ አሉት
‹‹ከዚያም በመርከቧላይ የሚሠሩት ሰዎች ዮናስን እንዲህ አሉት››

ይህ ክፉ ነገር በእኛ ላይ እንዲሆን ምክንያት የሆነው ማን እንደሆነ እባክህ ንገረን።
‹‹ ይህ ክፉ ነገር በእኛ ለላይ እንዲሆን ያደረገው ማን ነው?››

እግዚአብሔርን ፍራ
‹‹መፍራት›› የሚለው ቃል ዮናስ ለእግዚአብሔር ጥልቅ አክብሮት እንዳለው ያመለክታል።

ይህ ያደረግኸው ነገር ምንድን ነው?
በመርከቢቷ ውስጥ የነበሩ ሰዎች ይህንን መልስ የማይፈልጉበትን ጥያቄ ማቅረባቸው በዮናስ ላይ ምን ያህል እንደተበሳጩበት ያሳያል። ‹‹ አስከፊ ነገር አድርገሃል።››

እርሱ ከእግዚአብሔር ፊት ኮብልሎ ነበር
እዚህ ላይ እግዚአብሔር በሕልውናው ተገልጾአል። ዮናስ ከእግዚአብሔር ፊት የኮበለለው እግዚአብሔር ያለው በእስራኤል ምድር ብቻ እንደሆን በማሰብ ነው። ‹‹ ዮናስ ከእግዚአብሔር ፊት እየሸሸ ነበር››

እርሱ ነግሮአቸው ነበርና።
የነገራቸው በግልጽ ሊብራራ ይችላል። ‹‹ለእነርሱ ነግሮአቸዋልና፣ ‹ከእግዚአብሔር ለመሸሽ መከርኩኝ።› ››

Jonah 1:11

ዮናስን እንዲህ አሉት
‹‹በመርከቧ ላይ የነበሩት ሰዎች ዮናስን እንዲህ አሉት›› ወይም ‹‹መርከበኞቹ ዮናስን እንዲህ አሉት››

ባሕሩ ጸጥ እንዲል ምን እናድርግብህ? ‹‹ባሸሩን ጸጥ ለማድረግ በአንተ ላይ ምን እናድርግ››

ባሕሩ የበለጠ መናወጡን ቀጠለ
ምን ማድረግ እንዳለባቸው የጠየቁበት ምክንያት ይህ ነበር። ምክንያት በቁጥር 11 ላይ መጠቀስ ይችላል።

ይህ ታላቅ ሞገድ ያጋጠማችሁ በእኔ ምክንያት እንደሆነ አውቃለሁ
‹‹ይህ ታላቅ ሞገድ የእኔ ስህተት መሆኑን አውቃለሁ››

የሆኖሆኖ ፣ ሰዎቹ ወደ ምድሩ ሊመለሱ አጥብቀው ቀዘፉ
ሰዎቹ ዮናስን ወደ ባሕር ሊጥሉት አልፈለጉም፣ ስለሁነም ልክ ባሕሩን እንደሚቆፍሩ ወደ ምድሩ ለመድረስ አጥብቀው ቀዘፉ።

ባሕሩ እጅግ የበለጠ ይናወጥ ነበር
‹‹ ማዕበሉ የበለጠ የከፋ ሆነ፣ ሞገዱም ከፍተኛ ሆነ››

Jonah 1:14

ስለዚህ
‹‹በዚህ ምክንያት›› ወይም ‹‹ባሕሩ እጅግ በመናወጡ ምክንያት››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወደ እግዚአብሔር ጮሁ
‹‹ሰዎቹ ወደ እግዚአብሔር ጸለዩ››

በዚህ ሰው ነፍስ ምክንያት አታጥፋን
‹‹ይህ ሰው እንዲሞት በማድረጋችን እባክህ አትግደለን›› ወይም ‹‹እኛ ይህ ሰው እንዲሞት ልናደርግ ነው። ነገር ግ እባክህ አትግደለን››

የዚህን ሰው ሞት በደል በእኛ ላይ አታድርግ
‹‹ በእርሱ ሞት እኛን አትውቀሰን›› ወይም ‹‹ይህ ሰው ሲሞት እኛን እንደ በደለኛ አትቁጠረን።›› ጸሐፊው ስለ ‹‹በደል›› በሰው ላይ እንደሚጫን ነገር አድርጎ ይናገራል። ይህም ያንን ሰው ተጠያቂ የሚያደርግ መሆኑን ያመለክታል።

ባሕሩም ከመናወጡ ጸጥ አለ።
‹‹ባሕሩ በአደገኛ ሁኔታ መንቀሳቀሱን አቆመ›› ወይም ‹‹ባሕሩ ተረጋጋ››

እግዚአብሔርን እጅግ ፈሩ
‹‹በእግዚአብሔር ኃይል እጅግ ተደነቁ››

Jonah 1:17

አጠቃላይ መረጃ
አንዳንድ ትርጉሞች ይህንን ቁጥር የምእራፍ 2 የመጀመሪያ ቁጥር ያደርጉታል። የእናንተ ቋንቋ ትርጉም እንደሰጠው ቁጥር ለዚህ ጥቅስ ቁጥር መስጠት ትችላላችሁ።

አሁን
ይህ ቃል በእንግሊዝኛው የታሪኩን አዲስ ጅማሬ ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል።

ሦስት ቀናት እና ሦስት ሌሊቶች
‹‹ሦስት ቀናት እና ሌሊቶች››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 ከዚያም ዮናስ ዓሣው ሆድ ውስጥ ሆኖ ወደ አምላኩ ወደ ያህዌ ጸለየ። **2** እንዲህ አለ፤ «ተጨንቄ ሳለሁ ወደ ያህዌ ተጣራሁ፤ እርሱም መለሰልኝ፤ እርሱ
እንዲረዳኝ ከጥልቁ መቃብር ጮኽኩ አንተም ጩኸቴን ሰማህ። **3** ጥልቅ ወደ ሆነው ወደ ባሕሩ መሠረት ጣልኸኝ፤ ፈሳሾች ዙሪያዬን ከበቡኝ፣ ማዕበልህና
ሞገድህ ሁሉ በላየ አለፈ። **4** እኔም፣ ከፊትህ ጠፋሁ፤ ሆኖም፣ እንደ ገና ወደ ቅዱስ መቅደስህ እመለከታለሁ» አልሁ። **5** ሕይወቴን ለማጥፋት ውሆች ሸፈኑኝ፤
ጥልቁም በዙሪያዬ ነበረ፤ የባሕር ዐረም ራሴ ላይ ተጠመጠመ። **6** ወደ ተራሮች መሠረት ሰመጥሁ የምድርም በር ለዘላለም ተዘጋብኝ፤ ያህዌ አምላኬ ሆይ፣
አንተ ሕይወቴን ከጥልቁ አወጣህ! **7** ነፍሴ በዛለች ጊዜ ያህዌን አሰብሁት፤ ጸሎቴ ወደ አንተ ወደ ቅዱስ መቅደስህ መጣ፤፤ **8** ልባቸውን ከንቱ አማልከት ላይ
የሚያደርጉ ለእነርሱ ያለህን ጸጋ ያጣሉ። **9** እኔ ግን፣ በምስጋና መዝሙር መሥዋዕት አቀርብልሃለሁ፤ የተሳልሁትንም እፈጽማለሁ። ድነት ከያህዌ ዘንድ ነው። **10**
ከዚም ያህዌ ዓሣውን አዘዘ ዮናስንም ደረቁ ምድር ላይ ተፋው።

Jonah 2:1

እግዚአብሔር አምላኩ
ይህ ማለት ‹‹እግዚአብሔር፣ እርሱ የሚያመልከው አምላክ።›› ‹‹የእርሱ›› የሚለው ቃል ዮናስ እግዚአብሔርን የግሉ ብቻ አድርጎታል ማለት አይደለም።

እንዲህ አለ
‹‹ዮናስ አለ››

ስለ መከራዬ ወደ እግዚአብሔር ጮኽሁ
‹‹ስለ ታላቁ መከራዬ ወደ እግዚአብሔር ጸለይሁ።›› ምንም እንኳን ዮናስ ወደ እግዚአብሔር ቢጸልይም፣ እዚህ ላይ የእግዚአብሔርን ስም ተጠቀመ እንጂ ‹‹አንተ›› አላለም። ‹‹ እግዚአብሔር ሆይ፣ ስለ መከራዬ ወደ አንተ እጣራለሁ››

እርሱ መለሰልኝ
‹‹ እግዚአብሔር መለሰልኝ›› ወይን ‹‹ መልስ ሰጠኝ››

ከሲዖል ሆድ ውስጥ
‹‹ከሲዖል መካከል›› ወይም ‹‹ከሲዖል ጥልቀኛው ክፍል።›› እንደሚከተሉት ሊተረጎሙ ይችላል 1. ዮናስ በአሳ አንባሪው ሆድ ውስጥ መሆኑን በሲዖል ውስጥ እንደ ሆነ ይናገራል ወይም 2. ዮናስ ቶሎ እንደሚሞትና ወደ ሲኾል እንደሚወርድ አምኖአል ወይም 3. እንደ ሞተና ወደ ሲዖል እንደወረደ ይናገራል።

Jonah 2:3

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ በዮናስ 2፡2 የተጀመረው የዮናስ ጸሎት ተከታይ ክፍል ነው። በቁጥር 4 ዮናስ ከዚህ ጸሎት በፊት ስለ ጸለየው ጸሎት ይናገራል።

ወደ ጥልቁ፣ ወደ ባሕሩ ልብ
ይህ ዮናስ የነበረበትን የባሕሩን ስፋት ያመለክታል።

ወደ ባሕሩ ልብ ውስጥ
‹‹ ወደ ባሕሩ ታችኛው ክፍል››

ፈሳሾችም በዙሪያዬ ነበሩ
‹‹የባሕሩ ውኃ በዙሪያዬ ከበበኝ››

ማዕበል እና ሞገዶች
እነዚህ በባሕሩ ታችኛ ክፍል ያሉ የሚረብሹ ነገሮች ናቸው።

እኔም ተጣልሁ
ይህ እንደ ተግባር ሊገለጽ ይችላል። ‹‹አንተም አስወገድከኝ›› ወይም ‹‹ወደዚያ ላክኸኝ››

ከዓይኖችህ ፊት
እዚህ ላይ እግዚአብሔር የተገለጸው በ ‹‹ዓይኖቹ›› ነው። ‹‹ ከአንተ››

ነገር ግን ወደ መቅደስህ ደግሞ እመለከታለሁ
ዮናስ ከዚህ ሁሉ ከደረሰበት ባሻገር ፣ ቤተ መቅደሱን እንደሚያይ ተስፋ ያደርጋል።

Jonah 2:5

አጠቃላይ መግለጫ
ይህ በዮናስ 2፡2 የተጀመረው የዮናስ ጸሎት ተከታይ ክፍል ነው።

ውኃዎቹ
‹‹ውኃዎቹ›› ባሕሩን ያመለክታሉ

አንገቴ
አንዳድ ትርጉሞችበዚህ ክፍል የተገለጸውን የዕብራውያኑን ቃል የሚረዱት ‹‹ ሕይወቴ›› በሚል ቃል ነው። በዚህ ትርጉም ውኃዎቹ የዮናስን ሕይወት ሊወስዱ ተቃርበው ነበር።

ጥልቁ ሁሉ በዘዙራዬ ነበር
‹‹የጥልቁ ውኃ በዙሪያዬ ነበር››

የባሕር ሣር
በባሕር ውስጥ የሚበቅል ሣር

በምድርና በመወርወሪያዎችዋ ለዘላለም ተዘጋሁ
ዮናስ መሬትን እንደ እስር ቤት በምሳሌነት ተጠቀመ። ‹‹ መሬት እኔን ለዘላለም ለመዝጋት እንደ እስር ቤት ነበረች››

ነገር ግን አንተ ሕይወቴን ከጉድጓዱ ውስጥ አወጣሃት
ዮናስ የሞትን ሥፍራ ጉድጓድ እንደሆነ ይናገራል። ‹‹ ነገር ግን አንተ ሕይወቴን ከሞት ሥፍራ አዳንሃት›› ወይም ‹‹ ነገር ግን አንተ ሕይወቴን ሙታን ከሚኖሩበት ሥፍራ አዳንሃት››

እግዚአብሔር አምላኬ!
በአንዳንድ ቋንቋዎች፣ ይህንን በአረፍተ ነገሩ መጀመሪያ ወይም ‹‹አንተ›› ከሚለው ቀጥሎ ማስቀመጡ የተለመደ ነው።

Jonah 2:7

የትርጉም ማስታወሻዎች አጠቃላይ መረጃ
ይህ በዮናስ 2፡2 የተጀመረው የዮናስ ጸሎት ተከታይ ክፍል ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እግዚአብሔርን ጠራሁ አሰብሁትም
ዮናስ ወደ እግዚአብሔር ስለጸለየ፣ በአንዳንድ ቋንቋዎች ‹‹ እግዚአብሔር ሆይ ስለ አንተ አሰብኩኝ›› ወይም ‹‹ እግዚአብሔር ሆይ ስለ አንተ አሰብሁኝ›› መባሉ ግልጽ ነው።

ስለዚህ ጸሎቴ ወደ አንተ፣ ወደ ቅዱስ መቅደስህ ገባች
ዮናስ ጸሎቱ ወደ እግዚአብሔር ወደ መቅደሱ እንደሚጓዝ ይናገራል። ‹‹ ስለዚህ አንተ በቅዱስ መቅደስህ ጸሎቴን ሰማህ››

በማይረቡ አማልክት ላይ ትኩረታቸውን አድርገዋል ‹‹ሕዝቡ በማይረቡ አማልክት ላይ ትኩረታቸውን አድርገዋል››

የፍቅር ታማኝነትን ጥለዋል
‹‹ ለእነርሱ ታማኝ የሆንክላቸውን፣ አንተን ትተዋል››

Jonah 2:9

አጠቃላይ መረጃ
ይህ በዮናስ 2:2 የተጀመረው የዮናስ ጸሎት ተከታይ ክፍል ነው።

እኔ ግን፣ እኔ
ይህ አገላለጽ ዮናስ በሚናገርባቸው ሰዎች እና በእርሱ መካከል ያለውን ንጽጽር የሚያሳይ ነው። እነርሱ በማይረቡ አማልክት ላይ ትኩረታቸውን አድርገዋል፣ እርሱ ግን እግዚአብሔርን ያመልካል። ‹‹እኔ ግን››

እኔ ግን በምሥጋና ቃል እሠዋልሃለሁ
ይህም ማለት ዮናስ ለእግዚአብሔር መስዋዕትን እያቀረበ ያመሰግናል ማለት ነው። ዮናስ እግዚአብሔርን በመዝሙር ወይም በእልልታ ለማመስገን የተዘጋጀ ስለመሆኑ ግልጽ አይደለም።

ደኅንነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ይመጣል።
ይህ በተለየ ቃል ሊገለጽ ይችላል ስለዚህ ‹‹ ደኅንነት›› የሚለው ቃል ‹‹መዳን›› ተብሎ መገለጽ ይቻላል። ሰዎችን የሚያድነው ‹‹እግዚአብሔር›› ነው።

በደረቁ ምድር ላይ
‹‹ በመሬቱ ላይ›› ወይም ‹‹ወደ ባሕሩ ዳር››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ዮናስ መጣ፤ **2** «ተነሥተህ ወደ ታላቋ ከተማ ወደ ነነዌ ሂድ፤ እኔ የምነግርህንም መልእክት ስበክላት።» **3** ስለዚህም ዮናስ ለያህዌ ቃል በመታዘዝ ወደ ነነዌ ሄደ። ነነዌ ታላቅ ከተማ ነበረች፤ እርሷን ዳር እስከ ዳር ለማዳረስ ሦስት ቀን ይወስድ ነበር። **4** ዮናስ ወደ ከተማዋ ገባ፤ ከአንድ ቀን ጉዞ በኋላ፣ «ነነዌ በአርባ ቀን ውስጥ ትገለበጣለች» ብሎ ዐወጀ። **5** የነነዌም ሰዎች እግዚአብሔርን አመኑ፤ ጾምንም ዐወጁ። ከታላቁ እስከ ታናሹ ድረስ ሁሉም ማቅ ለበሱ። **6** ወሬውም ወደ ነነዌ ንጉሥ በደረሰ ጊዜ፣ ከዙፋኑ ወረደ፤ ልብሱን አወለቀ፣ ማቅም ለብሶ ዐመድ ላይ ተቀመጠ። **7** ከዚያም እንዲህ የሚል ዐዋጅ በነነዌ አስነገረ፤ «በንጉሡና በመኳንንቱ» ሥልጣን ከነነዌ የወጣ ዐዋጅ፤ ሰውም ሆነ እንስሳ፣ የከብት መንጋም ሆነ የበግ ምጋ ምንም ነገር አይቅመስ አይብላ ውሃም አይጣጣ። **8** ሰውም ሆነ እንስሳ ማቅ ይልበስ፤ አጥብቆ ወደ እግዚአብሔር ይጮኽ። ሰው ሁሉ ከክፉ መንገዱ ይመለስ፤ ግፍ መሥራቱንም ይተው። **9** እኛ እንዳንጠፋ እግዚአብሔር ራርቶ ከጽኑ ቁጣው ይመለስ እንደ ሆነ ማን ያውቃል?» **10** እግዚአብሔርም ያደረጉትን፣ ከክፉ መንገዳቸው መመለሳቸውንም አየ። በእነርሱ ላይ ሊያመጣ ያሰበውንም ጥፋት አላመጣም።

Jonah 3:1

የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ተናገረ የሚለውን የሚገልጽ አባባል ነው። ዮናስ 1:1 ላይ ‹‹እግዚአብሔር መልእክቱን ተናገረ›› የሚለው እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።

የእግዚአብሔር ቃል
እዚህ ላይ ‹‹ቃል›› የሚለው የእግዚአብሔርን መልእክት ይተካል። ‹‹የእግዚአብሔር መልእክት››

ተነሥ፣ ወደ ታላቂቱ ከተማ፣ ወደ ነነዌ ሂድ
‹‹አስፈላጊ ወደሆነችው የነነዌ ከተማ ሂድ››

ተነሥ
ይህ የሚያመለክተው ከሥፍራው በቶሎ እንዲሄድ ነው።

እንድትሰጣት ያዘዝኩህን መልእክት አውጅላት
‹‹እንድትነግራቸው የነገርኩህን ለሸዝቡ ንገራቸው››

ዮናስም ተነሥቶ ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ ወደ ነነዌ ሄደ
‹‹በዚህ ጊዜ ዮናስ እግዚአብሔርን ታዘዘ ወደ ነነዌም ሄደ››

ስለዚህ ዮናስ ተነሣ
‹‹ስለዚህ ዮናስ ከባሕሩ ዳርቻ ሄደ።›› ‹‹ተነሣ›› ´የሚለው ቃል ዮናስ የነበረበትን ሥፍራ ትቶ መሄዱን ያመለክታል።

አሁን
ይህ ቃል ታሪኩን ቆም አድርጎ ስለ ነነዌ መረጃ ለመስጠት ጥቅም ላይ የዋለ ነው።

የሦስት ቀናት የእግር ጉዞ
‹‹የሦስት ቀናት ጉዞ የምትጠይቅ ከተማ።›› አንድ ሰው ከተማይቱን ሙሉ ለሙሉ ለማቋረጥ ሦስት ቀናት መጓዝ አለበት።

Jonah 3:4

ከአንድ ቀን ጉዞ በኋላ በጩኸት ተናገረ
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች:- 1. ‹‹ዮናስ የአንድ ቀን ጉዞ ከተጓዘ በኋላ በጩኸት ተጣራ›› ወይም 2. ዮናስ በመጀመሪያው ቀን እየተጓዘ እያለ፣ በጩኸት ተናገረ።››

ከአንድ ቀን ጉዞ በኋላ
‹‹ አንድ ቀን ያህል ከሄደ በኋላ›› የአንድ ቀን ጉዞ ሰዎች በቀን ውስጥ ተሚሄዱት የተለመደ ጉዞ ነው።

ጮኸ እንዲህም አለ
‹‹አወጀ›› ወይም ‹‹ጮኸ››

አርባ ቀናት
‹‹40 ቀናት››

ሁሉም ማቅ ለበሱ
ሰዎቹ ሁሉ ለምን ማቅ እንደለበሱ የበለጠ ግልፅ ሊደረግ ይችላል። ‹‹ ሁሉም ማቅ የለበሱት ኃጢአት በማድረጋቸው ናዘናቸውን ለማሳየት ነው››

ከታላቁ ጀምሮ እስከ ታናሹ ድረስ
‹‹ በጣም ታላቅ ከሆኑት እስከ ዝቅተኞች ሰዎች ድረስ›› ወይም ‹‹ተላላቆችንና ታናናሾችን ሰዎች ሁሉ ጨምሮ››

Jonah 3:6

ዜናዎች
‹‹የዮናስ መልእክት››

ከዙፋኑ ተነሣ
‹‹ከዙፋኑ ብድግ አለ›› ወይም ‹‹ ከዙፋኑ ብድግ ብሎ ቆመ።›› ነጉሡ ትህትናውን ለማሳየት ዙፋኑን ለቅቆ ወረደ።

ዙፋን
ዙፋን ንጉሥ የሚቀመጥበት ወንበር ነው። ዙፋኑ የተቀመጠበት ንጉሥ መሆኑን ያመለክታል።

እንዲህ የሚለውን አዋጅ አስተላለፈ
‹‹ ይፋ የሆነውን ማስጠንቀቂያ እንዲህ በማለት አስተላለፈ›› ወይም ‹‹ለነነዌ ሰዎች ለመናገር መልእክተኞቹን ላከ››

ሹማምንት
ከተማዋን ለመግዛት እንዲችል ንጉሡን የሚረዱ አስፈላጊ ሰዎች

የቀንድ ከብቶች መንጎች
ይህ ሁለት ዓይነት እንስሶችን ያመለክታል። ‹‹መንጎች ወይም በጎች››

ምንም ይብሉ ውኃም አይጠጡ
‹‹ምንም መብላትና መጠጣት የለባቸውም።›› የማይበሉበትና የማይጠጡበት ምክንያት ‹‹በኃጢአታቸው ማዘናቸውን ለማሳየት ነው›› ተብሎ ተጨማሪ ማብራሪያ መስጠት ያስፈልጋል።

Jonah 3:8

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ ንጉሱ ለነነዌ ሰዎች የነገራቸው ቀጣይ ክፍል ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ነገር ግን ሁለም
‹‹ሁለም››

ሰዎች እና እንስሶች ሁሉም ማቅ ይልበሱ
ይህ በድርጊት ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። ‹‹ሕዝቡና እንስሳቱ ማቅ ይልበሱ›› ወይም ‹‹ ሕዝቡ ራሳቸውንና እንስሶቻቸውን ማቅ ያልብሱ››

እንስሶች
እንስሶች የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰዎች በባለቤነት የያዙአቸው መሆኑን ነው።

ወደ እግዚአብሔር ጮሁ
‹‹ከልባቸው ወደ እግዚአብሔር ጸለዩ።›› ይጸልዩበት የነበረው ምክንያት ግልጽ ነው። ‹‹ወደ እግዚአብሔር ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ምህረትን ጠየቁ››

በእጁ ከነበረው ክፉ ነገር
ይህ ማለት ‹‹ካደረገባቸው ክፉ ነገር››

ማን ያውቃል?
ንጉሡ ይህን ንግግርን የሚያሳምር ጥያቄ የተጠቀመው ሕዝቡ አይቻልም ከሚለው አስተሳሰብ ወጥተው፣ ኃጢአትን ማድረግ ቢተዉ እምደማይገድላቸው እንዲያስቡ ነው። ‹‹አናውቅም።›› ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ወይም ‹‹ምናልባት›› በሚለው ቃል በመግለጽ ከሚቀጥለው ዐረፍት ነገር ጋር ማያያዝ ይቻላለ።

እግዚአብሔር ይጸጸትና ሐሳቡን ይቀይር ይሆናል
‹‹እግዚአብሔር የተለየ ነገር ሊያድርግ ይወስን ይሆናል›› ወይም ‹‹ እግዚአብሔር ሊያደርገው የተናገረውን አያደርግ ይሆናል››

አንጠፋም
‹‹ አንሞትም።›› እዚህ ላይ አንጠፋም የሚለው በባሕር ውስጥ አንሰጥምም ከሚለው ጋር ይስማማል።

Jonah 3:10

እግዚአብሔር ያደረጉትን ተመለከተ
‹‹እግዚአብሔር ከፉ ነገር ማድረጋቸውን እንዳቆሙ ተረዳ››

ከክፉ መንገዳቸው ተመለሱ
ጸሐፊው ሰዎቹ ኃጢአት ማድረጋቸውን ሲናገር ልክ ጀርባቸውን ለአንድ ነገር እንደሰጡ አድርጎ ነው።

እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ እንደሚያመጣ የተናገረውን ቅጣት ከማድረግ ተመለሰ
እዚህ ላይ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ እንደሚያመጣ የተናገረውን ቅጣት፣ ልክ አሳቡን እንደቀየረ፣ ላለማድረግ መወሰኑን ያመለክታል። ‹‹እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ እንደሚያመጣ የተናገረውን ከማድረግ ሓሳቡን ቀይሮ ተመለሰ›› ወይም ‹‹እግዚአብሔር እንደተናገረው ሳይሆን ላይቀጣቸው ወሰነ››

አላደረገውም
እግዚአብሔር ሊያደርግ ያቀደው ግልጽ ተደርጎአል። ‹‹አልቀጣቸውም›› ወይም ‹‹አላጠፋቸውም››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 ይህ ግን ዮናስን ደስ ስላላሰኘው በጣም ተቆጣ። **2** እንዲህ በማለትም ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤ «ያህዌ ሆይ፣ ገና በአገሬ ሳለሁ ያልሁት ይህንኑ አልነበረምን? አንተ ቸርና ርኅሩኅ አምላክ፣ ለቁጣ የዘገየህ ምህረትህም የበዛ፣ ጥፋትን ከማምጣት የምትመለስ አምላክ መሆንህን ስለማውቅ ወደ ተርሴስ ለመኮብለል የሞከርኩት በዚሁ ምክንያት ነበር። **3** አሁንም ያህዌ ሆይ፣ ሕይወቴን እንድትወስድ እለምንሃለሁ፣ በሕይወት ከመኖር መሞት ይሻለኛል» አለ። **4** ያህዌ ግን፣ «መቆጣትህ ተገቢ ነውን?» አለው። **5** ከዚያም ዮናስ ከከተማዋ ወጥቶ በስተ ምሥራቅ በኩል ተቀመጠ። በዚያም ለራሱ ዳስ ሠርቶ በከተማዋ የሚደርሰውን ለማየት ከጥላው ሥር ተቀመጠ። **6** ያህዌ አምላክም አንድ ተክል አብቅሎ፣ የዮናስ ራስ ጥላ እንዲሆንና ትኩሳቱም እንዳያስጨንቀው ከበላዩ እንዲያድግ አደረገ፤ ዮናስም ስለ ተክሉ በጣም ደስ አለው። **7** ነገር ግን በሚቀጥለው ጠዋት ፀሐይ ስትወጣ አንድ ትል አዘጋጅቶ ያንን ተክል እንዲያጠቃ አደረገ፤ ተክሉም ጠወለገ። **8** ፀሐይ ስትወጣ እግዚአብሔር የሚያቃጥል የምሥራቅ ነፋስ አመጣ። ፀሐዩ የዮናስንም ራስ አቃጠለ እርሱም ተዝለፈለፈ። ያኔ ዮናስ መሞት ፈልጐ፣ «ከመኖር መሞት ይሻለኛል» አለ። **9** እግዚአብሔርም ዮናስን፣ «ስለ ተክሉ መቆጣትህ ተገቢ ነውን?» አለው። ዮናስም፣ «አዎን፣ እንዲያውም እስከ ሞት ድረስ መቆጣት ይገባኛል» አለ። **10** ያህዌ እንዲህ አለ፣ «አንተ እንዲበቅል ወይም እንዲያድግ ላልደከምህበት ተክል ይህን ያህል አዝነሃል፤ በአንድ ሌሊት በቀለ፤ በአንድ ሌሊትም ደረቀ። **11** ታዲያ፣ እኔ ቀኝና ግራቸውን ለይተው መናገር የማይችሉ ከአንድ መቶ ሃያ ሺህ በላይ ሰዎችና እንስሶች ለሚኖሩባት ለታላቋ ከተማ ለነነዌ ማዘን የለብኝምን? ::»

Jonah 4:1

አኽ፣ ያሕዌ
‹‹አኽ›› የሚለው ቃል የዮናስን የድንጋጤ ስሜት ያሳያል።

ወደ አገሬ ስመለስ ያልኩት ይሄ አይደለምን?
ዮናስ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው እርሱም ምን ያህል እንደተናደደ ለእግዚአብሔር ለማሳየት ነው። ዮናስ ወደ አገሩ ሲመለስ የተናገረው በግልፅ ሊብራራ ይችላል። ‹‹በአገሬ ሳለሁ እኔ የነነዌን ሕዝብ ባስጠነቅቅ፣ እነርሱ ንስሃ እንደሚገቡ፣ አንተም እንደማታጠፋቸው አውቄ ነበር››

ወደ ተርሴስ ለመኮብለል ፈጥኜ ነበር
የሚከተሉትን ትርጉሞች መጠቀም ይቻላል 1. ‹‹ይህን ለመከላከል ወደ ተርሴስ ለመኮብለል ሞከርኩ›› ወይም 2. ‹‹እኔ በፍጥነት ወደ ተርሴስ ለመኮብለል ሞከርኩ›› ወይም 3. ወደ ተርሴስ ለመኮብለል የቻልኩትን አደረግሁ።››

ከቃል ኪዳኑ ታማኝነት ጋር በጽናት መቆም
‹‹ በጣም ታማኝ›› ወይም ‹‹አንተ ሕዝብን በጣም ትወዳለህ››

ጥፋትን ከመላክ ተመለስክ
ይህ ማለት ‹‹በኃጢአተኞች ላይ ጥፋትን እንደምትልክ ተናግረህ ነበር፣ ነገር ግን ይህን ላማድረግ ወሰንክ።›› ‹‹ኃጢአት ያደረጉትን ሰዎች ላለመቅጣት ወሰንክ››

ነፍሴን ከእኔ ውሰድ
ዮናስ ለመሞት የፈለገበት ምክንያት በግልጽ ሊብራራ ይችላል። ‹‹ነነዌን አጠፋለሁ ብለህ ካላጠፋሃት፣ እኔ እንድሞት ፍቀድልኝ››

ለእኔ ከመኖር መሞት ይሻለኛል
‹‹ከመኖር መሞትን እመርጣለሁ›› ወይም ‹‹ ለመሞት ስለምፈልግ ለመኖር አልፈልግም››

Jonah 4:4

ይህን ያህል ልትናደድ መልካም ነውን?
እግዚአብሔር ይህንን ጥያቄ ያቀረበው ዮናስ ሊቆጣበት በማይገባው ጉዳይ ይህን ያህል በመቆጣቱ ሊወቅሰው ነው። ‹‹መቆጣትህ መልካም አይደለም››

ከከተማዋ ወጥቶ ሄደ
‹‹የነነዌን ከተማ ለቅቆ ሄደ››

በከተማዋ የሚሆነውን
‹‹በከተማዋ ላይ ምን እንደሚሆን።›› ዮናስ እግዚአብሔር ከተማዋን ያጠፋት ወይም አያጠፋት እንደሆነ ለማየት ፈልጎአል።

Jonah 4:6

በዮናስ ላይ እንደ ጥላ ነበረች
‹‹በዮናስ እራስ ላይ ለጥላ››

ጭንቀቱን ለማስታገስ
‹‹ዮናስን ከፀሐይ ትኩሳት ለመከላከል››

ነገር ግን እግዝዚአብሔር ትልን አዘጋጀ
‹‹ እግዚአብሔር ትልን ላከ››

ተክሏን አጠቃቻት
‹‹ትሏ ተክሏን በላቻት››

ተክሏ ጠወለገች
ተክሏ ደረቀች ሞተችም። ‹‹ተክሏ ሞተች››

Jonah 4:8

እግዚአብሔር የምሥራቅን ሞቃት ነፋስ አዘጋጀ
እግዚአብሔር የምሥራቅን ሞቃት ነፋስ በዮናስ ላይ እንዲነፍስበት አደረገው። ነፋስ ሞቃት ወይም ቀዝቃዛ ቢሆን ይህን መሞከር ትችላለህ። ‹‹እግዚአብሔር እጅግ ሞቃት የምሥራቅን ነፋስ በዮናስ ላይ እንዲነፍስ ላከው››

ፀሐይ መታችው
‹‹ፀሐይዋ እጅግ ታቃጥል ነበር››

በዮናስ እራስ ላይ
ዮናስ ጭንቅላቱ በፀሐይዋ ሙቀት ተቃጥሎ ነበር።

ተዝለፍልፎ ነበር
‹‹እጅግ ደክሞ ነበር›› ወይም ‹‹ኃይሉን አጥቶአል››

ለእኔ ከመኖር መሞት ይሻለኛል
‹‹ከመኖር መሞትን እመርጣለሁ›› ወይም ‹‹ለመሞት ስለምፈልግ ለመኖር አልፈልግም›› ዮናስ 4፡3 ን እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይህን ያህል ስለ ተክሏ ልትናደድ መልካም ነውን?
እግዚአብሔር ዮናስን ስለ ተክሏ መሞት እያዘነ ነገር ግን የነነዌን ሰዎች እንዲያጠፋቸው መፈለጉ የማይባ እንደሆን ወቀሰው። ‹‹ስለ ተክሏ ሞት መቆጣትህ መልካም አይደለም››

ይህን ያህል ስለ ተክሏ ልትናደድ መልካም ነውን?
የተደበቀው መረጃ መገለጽ ይችላል። ‹‹ከተክሏ ሞት ይልቅ ለነነዌ ሰዎች ሞት የበለጠ ግድ ሊልህ ይገባሃል።››

እኔ እስከ ሞት ድረስ ልቆጣ መልካም ነው።
‹‹መቆጣቴ መልካም ነው። እኔ አሁን ከልክ በላይ ስለተናደድኩ መሞት እፈልጋለሁ!››

Jonah 4:10

እግዚአብሔር አለ
እግዚአብሔር ዮናስን ማናገሩ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ‹‹እግዚአብሔር ዮናስን አለው››

ለታላቂቱ ከተማ ለነነዌ---ለከብቶቿም አላዝንምን?
እግዚአብሔር ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው እርሱ ለነነዌ ያለውን ጎዘኔታ ለማስገንዘብ ነው። ‹‹ለዚያች ታላቅ ከተማ---ለከብቶቿም ርኅራሔ ሊኖረኝ ይገባል።››

ሌሎችም ብዙዎች አሉ
ይህ ለአዲስ ዐረፍተ ነገር ጅማሬ ሊሆን ይችላል። ‹‹ብዙዎች አሉ።›› ወይም ‹‹ብዙ አለው››

አንድ መቶ ሃያ ሽህ ሰዎች
120,000 ሰዎች

ግራ እና ቀኛቸውን ለማያውቁ
ይህ አባባል ‹‹በትክክል እና ትክክል ባልሆነው መካከል ያለውን ልዩነት ለማያውቁ›› ለማለት የተነገረ ነው።

ብዙ ከብቶችም
ጸሐፊው የነነዌ ንስሃ የመግባት ጥልቀቱ ምን ያህል እንደሆነ ላማሳየት እና እግዚአብሔርም ምን ያህል እንደተገነዘባቸው ያመለከተበት አገላለጽ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Micah

Micah

Chapter 1

1 በይሁዳ ንጉሦች በአዮአታም፣ በአካዝና በሕዝቅያስ ዘመን ወደ ሞሬታዊው ወደ ሚክያስ የመጣው የያህዌ ቃል፣ ስለ ሰማርያና ስለ ኢየሩሳሌም ያየው ራእይ ይህ ነው። 2 እናንት ሕዝቦች ስሙ ምድርና በውስጧ የምትኖሩ ሁሉ አድምጡ። ጌታ ከቅዱስ መቅደሱ፣ ጌታ ያህዌም ይመሰክርባችኋል። 3 ተመልከቱ፤ ያህዌ ከመኖሪያው ስፍራ ይመጣል፤ ‹ወርዶም፣ በምድር ከፍታዎች ላይ ይራመዳል። 4 ተራሮች ከሥሩ ይቀልጣሉ ሸለቆዎች ይሰነጠቃሉ እሳት ፊት እንዳለም ሰም በገደል ላይ እንደሚወርድ ውሆች ይሆናሉ። 5 ይህ ሁሉ የሚሆነው ከያዕቆብ ዐመፅ ከእስራኤልም ቤት ኃጢአት የተነሣ ነው። የያዕቆብ ዐመፅ ምክንያት ምን ነበር? ሰማርያ አይደለችምን? የይሁዳስ ኮረብታ መስገጃ ምንድው? ኢየሩሳሌም አይደለችምን? 6 ስለዚህ ሰማርያን ሜዳ ላይ እንዳለ ፍርስራሽ ክምር፣ ወይን እንደሚተከልባትም ቦታ አደርጋታለሁ። የከተማዋን ፍርስራሽ ድንጋይ ወደ ሸለቆው አወርዳለሁ፤ መሠረቶችዋንም እገልጣለሁ። 7 ምስሎቿ ሁሉ ይሰባበራሉ፤ ለእርሷ የተሰጡ ስጦታዎችም ይቃጠላሉ። ጣዎቶችዋም ሁሉ ለጥፋት ይሆናሉ። እነዚህን የሰበሰበችው ለዝሙት ሥራዋ ካገኘችው ገጸ በረከት እንደ ነበር ሁሉ አሁንም ገጸ በረከትዋ የዝሙት አዳሪነት ዋጋ መቀበያ ይሆናል። 8 በዚህ ምክንያት ዋይ ዋይ እያልሁ አለቅሳለሁ፤ ባዶ እግሬንና ዕርቃኔን እሄዳለሁ፤ እንደ ቀበሮ አላዝናለሁ እንደ ጉጉትም አለቅሳለሁ። 9 ቁስሏ የማይፈወስ ነውና ለይሁም ተርፏል። ወደ ሕዝቤ ደጅ፣ ወደ ኢየሩሳሌም ደርሷል 10 በጌት አታውሩ፣ ከቶም አታልቅሱ በቤትዓፍራ ትቢያ ላይ እንከባለላለሁ 11 እናንት በሻፊር የምትሮሩ ዕርቃናችሁን ሆናችሁ እለፉ። በጸዓናን የሚኖሩ ከዚያ አይወጡም። ቤትዔጼል ሐዘን ላይ ስለሆነች መጠጊያ ልትሆን አትችልም። 12 የማሮት ነዋሪዎች መልካም ዜና ለመስማት እጅግ ጓጉተዋል፤ ምክንያቱም ከያህዌ ዘንድ ጥፋት እስከ ኢየሩሌም ደጆች መጥቷል። 13 እናንት በለኪሶ የምትኖሩ የሰረገሎችን ፈረሶች ለጉሙ፣ ለጽዮን ሴት ልጅ ኃጢአት መጀመሪያ እናንተ ነበራችሁ። የእስራኤልም በደል አንተ ዘንድ ተገኝቷል። 14 ስለዚህ እናንተ ለሞሬሼት ጌት የመሰነባበቻ ስጦታ ትሰጣላችሁ፤ የአክዚብም ከተሞች የእስራኤልን ንጉሦች ያታልላሉ። 15 እናንት በመሪሳ የምትኖሩ ወራሪ አመጣባችኋለሁ። የተከበሩ የእስራኤል መሪዎች በዓዶላም ዋሻ ይሸሸጋሉ። 16 ደስ ትሰኙባቸው ለነበሩ ልጆቻችሁ በማዘን ራሳችሁን ተላጩ ጡራችሁን ተቆረጡ ራሳችሁን እንደ ንስር ራስ ተመለጡት ምክንያቱም ልጆቻችሁ በምርኮ ከእናንተ ይወሰዳሉና።

Micah 1:1

ትንቢተ ሚክያስ **1**:**1** የትርጉም ማስታወሻ
አጠቃላይ መረጃ፡ እግዚአብሔር በሚክያስ አማካይነት በግጥም መልክ ለእስራኤል ሕዝብ ይናገራል።

የመጣው የእግዚአብሔር ቃል ይህ የአነጋገር ዘይቤ እግዚአብሔር ለአንድ ሰው መልዕክት እንደሰጠው ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሏል።

ያህዌ ይህ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያስታወቀው ስሙ ነው። ይህ እንዴት እንደሚተረጎም ለመረዳት የትርጉም ቃል ገጽ የሚለውን ተመልከት።

የሞሬሽታዊው ይህ ማለት በይሁዳ ካለው ከሞሬሽት የመጣ መሆኑን ያመለክታል።

በይሁዳ ነገሥታት በኢዮአታም፣ በአካዝና በሕዝቅያስ ዘመን “ኢዮአታም፣ አካዝና ሕዝቅያስ የይሁዳ ነገሥታት በነበሩበት ጊዜ”

ያየው “በራዕይ የሰማው”

Micah 1:2

x
አጠቃላይ መረጃ፡ ሚክያስ 1:2-7 የሚናገረው በሰማርያ ላይ ሊሆን ስላለው የእግዚአብሔር ፍርድ ነው

ሕዝቦች ሁሉ ስሙ፤ ምድርና በአንቺም ውስጥ ያሉ ሁሉ ስሙ የሚክያስ ትንቢት በዚህ ይጀምራል። ምድር ራሷ እንኳን ትሰማው ይመስል ሚክያስ የሚናገረው በምድር ላይ ለሚኖሩ ሰዎች ሁሉና ለሰማርያ ሕዝብ ነው።

እርሱ ይወርዳል፣ በምድር ከፍታዎችም ላይ ይራመዳል ሚክያስ እግዚአብሔርን ከሰማይ ወርደው በተራሮች አናት ላይ እንደሚሰለፉ ብርቱ ወታደሮች አድርጎ ይናገራል።

… ይራመዳል “… ይሰለፋል”

የምድር ከፍታዎች “ከፍ ያሉ ተራራዎች”

ተራሮች ከበታቹ ይቀልጣሉ፤ ሸለቆዎቹ ሰም በእሳት ፊት እንደሚቀልጥ፣ ውኖችም በጠባብ ስፍራ እንደሚወርዱበት ድንጋይ ይሰነጠቃሉ ሚክያስ ስለ እግዚአብሔር ሲናገር፣ ምድር በምትንቀሳቀስበት ጊዜ በግለቱ እንደሚያቀልጣት አንዳች ጠጣር ነገር ይገልጠዋል። አ.ት፡ “በላያቸው

Micah 1:5

x
በእስራኤል ቤት ኃጢአት ምክንያት “ቤት” የሚለው ቃል በቤት ውስጥ የሚኖሩትን ቤተ ሰቦች፣ በዚህ ስፍራ ደግሞ የእስራኤልን ሕዝብ የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ በእኔ ላይ ኃጢአትን ስላደረጉ”። ይህ ሁሉ “ጌታ ይመጣና ይፈርዳል”

የያዕቆብ በደል ምንድነው? “ያዕቆብ” የሚለው ስም በሰሜናዊ እስራኤል የሚኖሩ ዘሮቹን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው።

ሰማርያ አይደለችምን? እዚህ ጋ “ሰማርያ” በዚያ የሚከናወነውን ክፉ ተግባር ገላጭ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ሚክያስ ሕዝቡ እውነት ምን እንደሆነ እንዲያውቁ አጽንዖት ለመስጠት ጥያቄ ያቀርባል። አ.ት፡ “ሰማርያ መሆኗን ታውቃላችሁ”።

የይሁዳ ከፍ ያለ ቦታ ምንድነው? እዚህ ጋ “ከፍ ያለ ቦታ” ለመላው የጣዖት አምልኮ ልማድ ምሳሌ ነው። “ይሁዳ” በዚያ ለሚኖሩ ሰዎች ምሳሌአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “የይሁዳ ሕዝብ ጣዖትን ለማምለክ የሚሄዱት የት ነው?”

ኢየሩሳሌም አይደለችምን? በዚያ የሚከናወነውን ክፉ ተግባር ገላጭ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ሚክያስ ሕዝቡ እውነት ምን እንደሆነ እንዲያውቁ አጽንዖት ለመስጠት ጥያቄ ያቀርባል። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ኢየሩሳሌም እንደሆነች ታውቃላችሁ”።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Micah 1:6

x
አደርጋለሁ እዚህ ጋ “እኔ” የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው

ሰማርያ … ድንጋዮቿ … መሠረቶቿ … የተቀረጹ ምስሎቿ … የተቀበለቻቸው ስጦታዎች … ጣዖታቷ … ስጦታዎቿን ሰበሰበች … ይሆናሉ እግዚአብሔር ከተማይቱን በሴት በመመሰል ስለ ሰማርያ ይናገራል። አ.ት፡ “ሰማርያ… ድንጋዮቿ … በከተማው ያሉ ቤቶች መሠረታቸው … በከተማው የተቀረጹት ምስሎች … ሰዎች በከተማው ውስጥ ላለው መቅደስ የሰጡት ስጦታ … በከተማው ያሉ ጣዖታት … የከተማው ሕዝብ በልጽጓል … ስጦታዎቹ … ይሆናሉ”።

ድንጋዮቿን እንዳለሁ እዚህ ጋ “እርሷ” የሚያመለክተው የሰማርያን ከተማ ነው።

የተቀረጹት ምስሎቿ ሁሉ ይደቅቃሉ ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “የተቀረጹ ምስሎቿን ሁሉ አደቃለሁ”።

ስጦታዎቿ ሁሉ … በእሳት ይቃጠላሉ ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “የተቀበለችውን ስጦታ በሙሉ በእሳት አቃጥለዋለሁ”

የተቀበለችው “ሰዎች የሰጧትን”

ስጦታዎቿን የዝሙት አዳሪነቷ ዋጋ አድርጋ ስለሰበሰበች አሁንም የዝሙት አዳሪነቷ ዋጋ ይሆናሉ ሰዎች የዝሙት አዳሪን እንደሚከራዩ እግዚአብሔር ለጣዖታት ስጦታዎችን ስለሚሰጡ ሰዎች ይናገራል። አሦራውያን ሰማርያን በሚያጠፉበት ጊዜ የሰማርያ ሰዎች ለጣዖቶቻቸው የሰጧቸውን ስጦታዎች ወስደው ለገዛ ራሳቸው ጣዖታት በስጦታነት ያበረክቷቸዋል።

Micah 1:8

x
ሚክያስ 1:8-16 የሚናገረው በይሁዳ ላይ ስለሚሆነው የእግዚአብሔር ፍርድ ነው።

የሀዘን እንጉርጉሮን አንጎራጉራለሁ እዚህ ጋ “እኔ” የሚያመለክተው ሚክያስን ነው።

የሀዘን እንጉርጉሮን አንጎራጉራለሁ፣ አለቅሳለሁም “የሀዘን እንጉርጉሮ” የሚያመለክተው ውስጣዊውን ሀዘን ሲሆን “ለቅሶ” ደግሞ የሀዘንን ድምፅ በጩኸት የመግለጥን ተግባር ያመለክታል።

ባዶ እግሬንና ራቁቴን እሄዳለሁ ይህ የከፍተኛ ለቅሶና ጉዳት ምልክት ነው። ሌላው አማራጭ ትርጉም “አንድ ሰው ልብሴን የገፈፈኝን ዓይነት ሰው እመስላለሁ፤ ራቁቴን እሆናለሁ”

ራቁት ምናልባት ከወገብ በታች ማገልደም ብቻ ይሆናል

እንደ ቀበሮዎች. . . እንደ ጉጉቶች ቀበሮዎችና ጉጉቶች የሚኖሩት ወና በሆነ ምድር ሲሆን ከፍ ያለው ድምፃቸው ዋይ የሚሉ ወይም የሚያለቅሱ ሰዎችን ድምፅ ይመስላል።

ቁስሏ ሊድን የማይችል ነው እዚህ ጋ “እርሷ” የሚያመለክተው የሰማርያን ከተማ ነው። ይህም የጠላት ሰራዊት በዚያ የሚኖረውን ሕዝብ ከማጥፋት ምንም ነገር ሊገታው አይችልም ማለት ነው።

ወደ ይሁዳ መጥቷል ሚክያስ እግዚአብሔር በይሁዳ ላይ ለመፍረድ የላከውን ሰራዊት ለመግለጽ በዘይቤአዊ አነጋገር ተላላፊ በሽታ የሚለውን ይጠቀማል። እዚህ ጋ “እርሱ” የሚያመለክተው “ቁስል”ን ሲሆን እርሱም እግዚአብሔር ሰማርያን ለመቅጣት የሚጠቀምበት ሰራዊት ነው።

ቤትሌፍራ “ ‘የትቢያ ቤት’ የሚል የከተማ ስም ነው” የሚል የግርጌ ማስታወሻ ልትሰጠው ያስፈልግህ ይሆናል።

በትቢያ ላይ እንከባለላለሁ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች የሆኑ ሰዎች ሀዘናቸውን መሪር በሆነ መንገድ ይገልጻሉ። አ.ት፡ “መሬት ላይ እንከባለላለሁ” ወይም “በጭቃ ላይ እንከባለላለሁ”።

እዚህ ጋ የመንደሮቹ የስማቸው ትርጉም ለሚክያስ አስፈላጊዎች ናቸው። በግርጌ ማስታወሻ ላይ የቦታዎቹን የስማቸውን ትርጉም ማካተት ያስፈልግህ ይሆናል።

Micah 1:11

x
ሻፊር ከ”ራቁትነት እና ኃፍረት” ጋር ሲነጻጸር የከተማይቱ ስም “ውብ” ከሚለው ድምፅ ጋር ይመሳሰላል።

በራቁትነትና ኃፍረት ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሕዝቡ ሙሉ በሙሉ ራቁቱን እንደሚሆን ግልጽ ያደርጋል። አ.ት፡ “ሙሉ በሙሉ ራቁታቸውንና የሚያፍሩ ይሆናሉ”

ጸዓናን የዚህች ከተማ ስም ትርጉሙ “ውጪ” የሚል ነው። ለመውጣትና ለማገዝ እጅግ ፈርተዋል።

ቤትኤጼል የዚህች ከተማ ስም ትርጉም “የምትወሰድ ቤት” ማለት ነው።

መከላከያቸው ተወስዷልና ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ሊከላከልላቸው የሚችለውን ነገር ሁሉ እኔ አስወግጃለሁና”።

ማሮት የዚህች ከተማ ስም ትርጉም “መራራነት” የሚል ነው።

አደጋ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወርዷል “አደጋ” የሚለው የነገር ስም እዚህ ጋ ከኮረብታ ላይ ተንከባሎ እንደሚወርድ ጠጣር ነገር ተገልጿል። እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ክፉ ነገሮች እንዲመጡ አድርጓል”።

Micah 1:13

x
ለኪሶ “ለኪሶ” የሚለው ስም በዕብራይስጥ “ለሰረገሎቹ” ከሚለው ድምፅ ጋር ይመሳሰላል። ሕዝቡ ለውጊያ ሳይሆን ለመሸሽ ሰረገላዎቻቸውን ያስጋልባሉ። ለኪሶ በይሁዳ ከምትኖረው ከኢየሩሳሌም ቀጥሎ እጅግ አስፈላጊ ከተማ ነበረች።

የጽዮን ሴት ልጅ “ሴት ልጅ” የሚለው ቃል ለከተማይቱ ሰዎች የዋለ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “የጽዮን ሕዝብ” ወይም “በጽዮን የሚኖረው ሕዝብ”።

የእስራኤል መተላለፍ በእናንተ ዘንድ ተገኝቷልና ይህ ዘይቤአዊ አነጋገር በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ እንዳደረጉት አልታዘዝ ብላችኋል”።

ሞሬሼትጌት “ ‘ሞሬሼት’ የሚለው ስም ትርጉም ‘መለየት’ ማለት ነው የሚለውን በግርጌ ማስታወሻ ላይ መጨመር ያስፈልግህ ይሆናል። በተጨማሪም ‘ዕጮኛ’ ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ድምፅ አለው”። በዚህ ዘይቤአዊ አነጋገር ሞሬሼት አሦር የሚወስዳት ሙሽሪት ስትሆን የ “መሰናበቻ ስጦታ”ው ወደ ትዳሯ ይዛው እንድትሄድ ቤተ ሰቦቿ የሚሰጧት ስጦታ ነው።

አክዚብ “የዚህች ከተማ ስም በዕብራይስጥ “አታላይ ነገር” ከሚለው አገላለጽ ጋር ፍጹም ተመሳሳይነት አለው” በማለት በግርጌ ማስታወሻ ላይ ልትጨምረው ያስፈልግህ ይሆናል።

Micah 1:15

x
እንደገና አመጣብሻለሁ እዚህ ጋ “እኔ” የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው።

መሪሳ “የዚህ መንደር ስም ‘ድል አድራጊ’ ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል ጋር ተመሳሳይ ድምፅ አለው” በማለት የግርጌ ማስታወሻ ልታደርግለት ያስፈልግህ ይሆናል።

ዓዶላም ይህ በፍልስጥኤም የልዑላኑ ከተማ ስም ነው።

ራስሽን ተላጪ፣ ጸጉርሽንም ተቆረጪ የሚያለቅሱት እስራኤላውያን ራሳቸውን በክብ መላጨት ነበረባቸው። ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፣ 1) “ራሳችሁን በተለመደው ሳይሆን ሰፋፊ ክቦችን በማድረግ ተላጩት” ወይም 2) በቅደም ተከተል ሊሆኑ ያሉትን ነገሮች በመግለጽ “ጸጉራችሁን በሙሉ ተቆረጡት፣ ራሳችሁንም ተላጩት”።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 ክፉ ነገር ለማድረግ ለሚያቅዱ መኝታቸው ላይ ሆነው ተንኰል ለሚያውጠነጥኑ ወዮላቸው። ያን ለማድረግ ሥልጣን ስላላቸው ሌሊቱ ሲነጋ ዕቅዳቸውን ሥራ
ላይ ያውሉታል። **2** የዕርሻ ቦታ ሲፈልጉ፣ ቀምተው ይወስዳሉ ቤት ሲፈልጉ ነጥቀው ይወስዳሉ። የሰው መብት ረግጠው ሀብቱን ይዘርፋሉ **3** ስለዚህ ያህዌ
እንዲህ ይላል በዚያ ሕዝብ ላይ ጥፋት አመጣለሁ ከዚህም ልታመልጡ አትችሉም። ያ የመከራ ጊዜ ስለሚሆን ከእንግዲህ በእብሪት አትኖሩም። **4** በዚያ ቀን
ጠላቶቻችሁ ይሳለቁባችኋል በሐዘን እንጉርጉሮ እንዲህ እያሉ ያፌዙባችኋል እኛ እስራኤላውያን ፈጽሞ ጠፍተናል ያህዌ የሕዝቤን ንብረት ወስዶ ርስታችንንም
ለከሓሂዲዎች አከፋፈለ **5** ስለዚህ እናንተ ባለጸጐች በያህዊ ጉባኤ ውስጥ ርስት በዕጣ የሚከፋፈሉ ልጆች አይኖሯችሁም። **6** «ትንቢት አትናገር» ምንም
ውርደት አይደርስብንም፤ ስለ እነዚህ ነገሮች ትንቢት አትናገር ይላሉ። **7** የያዕቆብ ቤት ሆይ፣ እንደህ መባል ነበረበትን? የያህዌ ትዕግሥት አልቋልን? እነዚህስ
የእርሱ ድርጊቶች ናቸውን? አካሄዳቸው ቀና ለሆነ ሰዎች ቃሎቼ መልካም አያደርጉምን? **8** በመጨረሻ በሕዝቤ ላይ በጠላትነት ተነሥታችኋል ከጦርነት በኃላ
ሰላም ነው ብለው ወደሚያስቡት እንደሚመለሱ ወታደሮች ምንም ሳይጠራጠሩ የሚያልፉ ሰዎችን ልብስ ገፋችኋል። **9** የወገኔን ሴቶች ከሚወዱት ቤታቸው
አባረራችሁ በረከቴን ለዘላለም ከልጆቻቸው ወሰዳችሁ። **10** በርኩሰት ምክንያት ከባድ ጥፋት ስለሚመጣ እዚህ ቦታ መቆየት አትችሉም፤ ስለዚህ ተነሥታችሁ
ሂዱ። **11** አንድ ሰው በሐሰት መንፈስ ተነሣሥቶ «ስለ ወይን ጠጅና ጠንካራ መጠጥ ትንቢት እናገራለሁ» ቢል፤ በእነዚህ ሰዎች ዘንድ እንደ ነቢይ ይቆጠራል።
12 ያዕቆብ ሆ በእርግጥ ሁላችሁንም እሰበስባለሁ፤ የእስራኤልን ትሩፍ ጉረኖ ውስጥ እንዳለ በጐች በመሰማሪያ ላይ እንዳለ መንጋ አመጣቸዋለሁ። ከሕዝቡ
ብዛት የተነሣ ታላቅ ጩኸት ይሆናል። **13** መንገዳቸውን የሚከፍትላቸው መሪ ከእነርሱ ፊት ፊት ይሄዳል እነርሱም ተግተልትለው በበሩ ይወጣሉ ንጉሣቸው ፊት
ፊታቸው ይሄዳል፤ ያህዌ መሪያቸው ይሆናል።

Micah 2:3

x
አንገቶቻችሁን ልታስወጡ ከማትችሉበት እግዚአብሔር ቀንበርን በአንገታቸው ዙሪያ ያደረገ ይመስል ሕዝቡን ስለሚቀጣበት ሁኔታ ይናገራል። አ.ት፡ “ልታመልጡ ከማትችሉበት”።

ስለ አንቺ ይዘፍናሉ “በአንቺ ላይ ለመቀለድ ይዘፍኑብሻል” የሀዘን እንጉርጉሮ አንጎራጉሪ “ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ይጮኻሉ”። የሚወድዷቸው የሞቱባቸው ይመስል ለማልቀስ ያስመስላሉ።

እኛ እስራኤላውያን . . . ለከዳተኞች ይህ ጠላቶቻቸው በእስራኤላውያን ላይ ለመሳቅና በስቃያቸው ለመሳለቅ የሚዘፍኑት ዘፈን ነው።

ከእኔ እንዴት መንጠቅ ይችላል? የእስራኤል መሪዎች ከድኾች የወሰዱባቸውን መሬት እግዚአብሔር ከእነርሱ ወስዶ ለሌላ ሰው በመስጠቱ በሚሰማቸው መደነቅ ላይ ጠላት ይሳለቃል። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ተደርጎ መተርጎም ይችላል። አ.ት፡ “ከእኔ ለመውሰድ ማሰቡ ስሕተት ነው!”

ስለዚህ፣ እናንተ ባለጸጎች በእግዚአብሔር ጉባዔ ውስጥ መሬት የሚካፈል ትውልድ አይኖራችሁም። አማራጭ ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) ሚክያስ ወደ ፊት ከምርኮ በኋላ የሚመለሱት ተመላሾች ምድሪቱን ስለሚከፋፈሉበት ጊዜ ይመለከታል ወይም 2) እርሱ የሚናገረው በዘመኑ ልማድ መሠረት አንድ ነገድ ወይም ጎሳ ምድራቸውን በማከፋፈል ለግለ ሰቦች ስለሚሰጡበት ጊዜ ነው።

Micah 2:9

በረከቴን ከታናናሽ ልጆቻቸው ለዘላለም ትወስዳለህ
ይህ በጥቅሉ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጣቸውን በረከት ያመለክታል። 1) በእስራኤል ባለ ርስት የሆኑትን 2) የወደፊቱን ተስፋ ሰጪ ሁኔታ ወይም 3) የልጆቹን አባቶች፣ አገር ለመገንባት ጠንክረው የሚሠሩትን ገበሬዎች ያመለክት ይሆናል።

በረከቴን
ሚክያስ እርሱ ራሱ እግዚአብሔርን እንደሆነ አድርጎ ይናገራል።

በፍጹም መጥፋት ጠፍቷል
ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ፈጽሜ አጠፋዋለሁ”

ወደ እናንተ ቢመጣ ... ቢተነብይላችሁ
ሚክያስ የሚናገረው ስለ ይሁዳ ሕዝብ ነው፤ ስለዚህ በሁለቱም ጊዜ “እናንተ” ብቁ ቁጥር ነው።

ተቀባይነት ይኖረዋል
ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ሕዝቡ ይቀበለዋል” ወይም “ትቀበሉታላችሁ”።

Micah 2:12

አጠቃላይ መረጃ፡
እግዚአብሔር መናገሩን ቀጥሏል። በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ እግዚአብሔር ራሱን የሕዝቡ ጠባቂ እረኛ አድርጎ ያሳያል። እርሱ የሚናገረው ምናልባትም በተለይ ከአሦር ተመልሰው በኢየሩሳሌም ለሚኖሩት ነው።

ያዕቆብ፣ እናንተን ሁላችሁንም
ሚክያስ የሚናገረው ለአንዳንድ የያዕቆብ ዝርያዎች ሲሆን “እናንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ነው።

ሰባሪው መንገዳቸውን ይከፍታል ... እግዚአብሔር በራሳቸው ላይ ይሆናል።
ይህ ከተከበበ ከተማ ሕዝቡን እየመራ የሚሄደው ንጉሥ ሥዕል ነው።

የሚክያስ **03** ዋና ነጥቦች ፍትሕ የዚህ ምዕራፍ ዋና ጭብጥ ነው
ፍትሐዊ ያልሆነ ማኅበረ ሰብ እንደ ኃጢአተኛ ይቆጠራል። የሙሴን ሕግ እንደሚቃረን ይቆጠርም ነበር። እነዚህ መንግሥታት ፍትሕ ካልነበራቸው ለእግዚአብሔር የማይታዘዙ ነበሩ ማለት ነው።

አስፈላጊ ምሳሌአዊ አነጋገር በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በዘይቤአዊ አነጋገር ቀርቧል
የሕዝቡ መሪዎች እስራኤላውያኑን እንዴት እንደያዟቸው የሚያሳዩ ጉልህ ሥዕሎች በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ጥቅም ላይ ውለዋል። እነዚህ ሁኔታዎች እንደ ዘይቤአዊ አነጋገር ካልተወሰዱ ዘበት ሆነው ይቀራሉ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 ከዚያም እኔ እንዲህ አልሁ፤ «እናንተ የያዕቆብ መሪዎች የእስራኤልም ቤት ገዦች አድምጡ፤ ፍትሕን ማወቅ ይገባችሁ አልነበረምን? **2** እናንተ ግን መልካሙን ጠላችሁ ክፉን ወደዳችሁ ቆዳቸውን ገፈፋችሁ ሥጋቸውን ከአጥንታቸው ጋጣችሁ የሕዝቤን ሥጋ በላችሁ ቆዳቸውን ገፈፋችሁ ዐጥንቶቻቸውን ሰባበራችሁ፤ በመጥበሻ እንደሚጠበስ በድስት እንደሚቀቀል ሥጋ ቆራረጣችኋቸው። **3** እናንተ መሪዎች ወደ ያህዌ ትጮኻላችሁ እርሱ ግን አይሰማችሁም። ከክፉ ሥራችሁ የተነሣ በዚያ ጊዜ ፊቱን ከእናንተ ይሰውራል። **4** ሕዝቤን ስለሚያስቱ ነቢያት ያህዌ እንዲህ ይላል፤ **5** «ጥቅም የሚያገኙበት ሲሆን፣ «ብልጽግና ይሆናል» ይላሉ፤ ጥቅም በማያገኙበት ጊዜ ግን፣ ‹ጦርነት ይመጣባችኋል› እያሉ በማወጅ ሕዝቡን ያስታሉ። **6** ስለዚህ ራእይ የማታዩበት ሌሊት ይሆንባችኋል ሌሊት ስለሚሆንባችሁ ንግርት አታደርጉም። በነቢያት ላይ ፀሐይ ትጠልቅባቸዋለች ቀኑ እነርሱ ላይ ይጨልማል። **7** ባለ ራእዮች ያፍራሉ ንግርተኞችም ይዋረዳሉ ከእኔ ዘንድ መልስ የለምና ሁሉም ፊታቸውን ይሸፍናሉ። **8** እኔ ግን፣ ለያዕቆብ በደሉን ለእስራኤል ኃጢአቱን እንድናገር በያህዌ መንፈስ ኃይል ተሞልቻለሁ ፍትሕና ብርታትንም ተሞልቻለሁ። **9** እናንት የያዕቆብ ቤት መሪዎች ፍትሕ የምትጠሉ፣ ቀና የሆነውን የምታጣምሙ የእስራኤል ቤት ገዦች ይህን ስሙ። **10** ጽዮንን ደም በማፍሰስ ኢየሩሳሌምን በርኩሰት የምትገነቡ ስሙ **11** መሪዎቻችሁ በጉቦ ይፈርዳሉ ካህናቶቻችሁ በዋጋ ያስተምራሉ ነቢያቶቻችሁ በገንዘብ ንግርት ይናገራሉ። ያም ሆኖ በያህዌ በመተማመን፣ «ያህዌ ከእኛ ጋር ስለሆነ ክፉ ነገር አይደርስብንም» ይላሉ። **12** ስለዚህ በእናንተ ምክንያት ጽዮን እንደ ማሳ ትታረሳለች፤ ኢየሩሳሌም የፍርስራሽ ክምር ትሆናለች የቤተ መቅደሱ ኮረብታ ጥቅጥቅ ያለ ደን ይሆናል።

Micah 3:1

ተናግሬአለሁ
እዚህ ጋ በውስጠ ታዋቂነት ያለው “እኔ” የሚያመለክተው ሚክያስን ነው።

ፍትሕን ልታውቁ አይገባችሁም?
ሚክያስ በመሪዎቹ ላይ ይቆጣል። ይህ የማሳመኛ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “አድራጎታችሁ ፍትሕን ማወቅ እንደማያስፈልጋችሁ የምታስቡ ያስመስላችኋል”።

መልካምን ትጠላላችሁ፣ ክፋትንም ትወድዳላችሁ
እነዚህ ስማዊ ቅጽሎች እንደ ቅጽል ሊተረጎሙ ይችላሉ። አ.ት፡ “መልካም የሆነውን ነገር ሁሉ ትጠላላችሁ፣ ክፉ የሆነውን ነገር ሁሉ ትወድዳላችሁ”

እናንተ ቆዳቸውን የምትገፉ፣ ሥጋቸውን ከአጥንታቸው የምትለዩ ... በመጥበሻ እንዳለ ሥጋ
መሪዎቹ በድኾቹ ላይ ያላቸው ጭከና ሥጋ ሻጭ ለሥጋ የሚሆኑትን እንስሳት እንደሚቆራርጥ በዘይቤአዊ አነጋገር ተገልጿል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Micah 3:4

ወደ እግዚአብሔር ጩኹ
“ለዕርዳታ ወደ እግዚአብሔር ተጣሩ”

እርሱ አይመልስላችሁም
“እንዲያደርግ የምትጠይቁትን አያደርግም”

ፊቱን ከእናንተ ይሰውራል
ፊትን መሰወር ለመስማት ያለመፍቀድ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ፊቱን ከእናንተ ይሰውርና ይደብቃል” ወይም “ሊረዳችሁ ፍላጎት እንደሌለው ታያላችሁ”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Micah 3:5

ሕዝቤን የሚያስቱ
በመልካም መንገድ መሄድ እግዚአብሔርን የመታዘዝ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። መሳት ደግሞ እግዚአብሔርን ያለመታዘዝ ዘይቤአዊ አነጋገር ሲሆን በዚህ ጉዳይ ምናልባት ባለማወቅ ይሆናል። አ.ት፡ “ሕዝቤ እንዳይታዘዘኝ የሚመሩት”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አንዱ የሚበሉትን አንዳች ነገር ከሰጣቸው ‘ሰላም’ን ያውጁለታል።
ሚክያስ በእርግጥ ሊሆን ያለውን ሁኔታ ለመግለጽ ዘይቤአዊ አነጋገርን ይጠቀማል። “የሚበሉት አንዳች ነገር” የሚለው ሐረግ አነስተኛ ክፍያን ለመግለጽ የዋለ ምጸታዊ አነጋገር ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ምጸት የሚለውን ተመልከት)

በአፋቸው አንዳች በማያኖር ጦርነት ሊያውጁበት ራሳቸውን ይሰጣሉ
ሚክያስ በእርግጥ ሊሆን ያለውን ሁኔታ ለመግለጽ ዘይቤአዊ አነጋገርን ይጠቀማል። “በአፋቸው አንዳች በማያኖር” የሚለው ሐረግ የፈለጉትን ያለመስጠት መጸታዊ ግነት ነው። አ.ት፡ “ጥቂት የሚከፍሏቸውን ሰዎች ለማጥፋት የሚችሉትን ሁሉ ያደርጋሉ”። (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ምጸት የሚለውን ተመልከት)

ለእናንተ ጨለማ ይሆናል ... በእነርሱ ላይ ቀኑ ይጨልምባቸዋል
ጨለማ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ያለመናገሩ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ራዕይ አይኖራችሁም
“ከእንግዲህ ራዕይ አታዩም”

ባለ ራዕዮች ያፍራሉ፣ ንግርተኞችም ይደናገራሉ
ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ባለ ራዕዮች እንዲያፍሩ አደርጋለሁ፣ ንግርተኞችንም አደናግራቸዋለሁ”።

ሁሉም ከንፈሮቻቸውን ይሸፍናሉ
እዚህ ጋ “ከንፈሮች” መናገርን ይወክላል። አ.ት፡ “ከእንግዲህ አይናገሩም”

ከእኔ ዘንድ ምንም መልስ አይኖርም
“ዝም እላለሁ”

Micah 3:8

እኔ ግን
እዚህ ጋ “እኔ” እውነተኛውን፣ ራሱን ከሐሰተኖች ነቢያት የለየውን ሚክያስን ያመለክታል።

በእግዚአብሔር መንፈስ ኃይልን፣ ፍትሕና ብርታትንም ተሞልቻለሁ
ሚክያስ ራሱን እግዚአብሔር ፈሳሽ እንደሚያፈስበት መያዣ ዕቃ አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “የእግዚአብሔር መንፈስ ኃይልን፣ ፍትሕንና ብርታትን ሰጥቶኛል” ወይም “እንድጠነክር፣ ፍትሕ ምን እንደሆነ እንድሰብክና ብርቱ እንድሆን የእግዚአብሔር መንፈስ አስችሎኛል”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ለያዕቆብ መተላለፉን፣ ለእስራኤልም ኃጢአቱን ለማስታወቅ
እዚህ ጋ “ያዕቆብ” እና “እስራኤል” የያዕቆብን ዘሮች የሚያመለክቱ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ናቸው። ሚክያስ ሁለቱን ስሞች የሚጠቀመው ዘሮቹ ሁሉ በኃጢአት በደለኞች ስለመሆናቸው አጽንዖት ለመስጠት ነው። የነገር ስም የሆኑትን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

“መተላለፍ” እና “ኃጢአት” ግሥ በመጨመር መተርጎም ይቻላል። አ.ት፡ “የያዕቆብ ዘሮች የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መጣሳቸውን ለማስታወቅ፣ የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ኃጢአትን መሥራታቸውን እነግራቸዋለሁ”።

Micah 3:9

የያዕቆብ ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተ ሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። በዚህ ጉዳይ ቃሉ የያዕቆብን ዘሮች ያመለክታል። አ.ት፡ “የያዕቆብ ዘሮች”።

የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የለሚኖሩትን ቤተ ሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። በዚህ ጉዳይ ቃሉ የእስራኤል ሕዝብ የሆነውን የእስራኤልን ዘር ያመለክታል። አ.ት፡ “የእስራኤል ዘሮች” ወይም “እናንት እስራኤላውያን”።

መጥላት
ከፍተኛ ጥላቻ

ጽዮንን በደም፣ ኢየሩሳሌምንም በኃጢአት ትገነባላችሁ
እዚህ ጋ “ደም” በፈሊጣዊ አነጋገር መግደል ማለት ሲሆን “ጽዮን” እና “ኢየሩሳሌም” በሕንጻ ተመስለዋል። ሚክያስ ባለጽጎች ሰዎችን መግደላቸውና ኃጢአት መሥራታቸውን ይናገራል፤ በሌላ አነጋገር ድርጊቶቻቸው ሰዎች ቤቶችን ለመሥራት የሚጠቀሙባቸውን ጡቦችና እንጨቶች ይመስላሉ። አ.ት፡ “ጽዮንን እና ኢየሩሳሌምን ታላቅ ለማድረግ በምትሠሩበት ጊዜ ትገድላላችሁ፣ ሌሎች የከፉ ኃጢአቶችንም ትሠራላችሁ” ወይም “በጽዮን ስታመልኩ ሳላችሁ ትገድላላችሁ፣ በኢየሩሳሌም ስትበለጽጉ ሳላችሁም ሌሎች ኃጢአቶችን ትሠራላችሁ”። (ዘይቤአዊ እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር ከእኛ ጋር አይደለምን?
መሪዎቹ እግዚአብሔር አብሯቸው እንዳለ አጥብቀው ያምናሉ። ይህ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ከእኛ ጋር እንዳለ እናውቃለን!” ወይም “ለማድረግ የምንፈልገውን እንድናደርግ እግዚአብሔር እንደሚረዳን እናውቃለን”።

ክፉ
በሚክያስ 1፡12 “አደጋ”ን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Micah 3:12

በእናንተ ምክንያት
እዚህ ጋ “እናንተ” የሚያመለክተው ካህናቱን፣ ነቢያቱንና መሪዎቹን ነው (ሚክያስ 3፡11)።

ጽዮን የታረሰ እርሻ ትሆናለች ... የመቅደሱም ኮረብታ የቁጥቋጦ ዋሻ ይሆናል
“ጽዮን” እና “የመቅደሱ ኮረብታ” የሚያመለክቱት አንዱን ስፍራ ነው። ገበሬ እርሻ በሚያርስበት ጊዜ ዐፈሩን ይገለብጠዋል፣ በዚያ የበቀሉትን እጽዋት ሥር ሁሉ ይነቅላል። የቁጥቋጦ ዋሻ ለምንም በማይጠቅም በችፍግ የተሞላ ነው። እነዚህ ሁለት ዘይቤአዊ አነጋገሮች በተመሳሳይ ጊዜ ቃል በቃል እውነት ሊሆኑ አይችሉም፣ ነገር ግን እግዚአብሔር የመቅደሱን አካባቢ ፈጽመው እንዲያጠፉ ለወራሪዎቹ እንደሚፈቅድላቸው አጽንዖት ይሰጣሉ። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የታረሰው መሬት
“ገበሬ ያረሰው መሬት”

የቁጥቋጦ ዋሻ
ትናንሽ እንጨትነት ያላቸው እጽዋት የሚበቅሉበት አካባቢ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 በመጨረሻው ዘመን የያህዌ ቤት ተራራ ሌሎች ተራቶች ላይ ይመሠረታል ከኮረብቶችም በላይ ከፍ ይላል ሕዝቦችም ወደ እርሱ ይጐርፋሉ። ብዙ ሕዝቦች መጥተው እንዲህ ይላሉ **2** «ኑ ወደ ያህዌ ተራራ፣ ወደ ያዕቆብ አምላክ ቤት እንሂድ እርሱ መንገዱን ያስተምረናል እኛም በመንገዱ እንሄዳለን። ሕግ ከጽዮን፣ የያህዌም ቃል ከኢየሩሳሌም ይወጣል። **3** እርሱ በብዙ ሕዝብ መካከል ይፈርዳል በሩቅ ባሉ ሕዝቦችም ላይ ይበይናል። ሰይፋቸውን ቀጥቅጠው ማረሻ ጦራቸውንም ማጭድ ያደርጉታል። መንግሥት በመንግሥት ላይ ሰይፍ አያነሣም፤ ከእንግዲህ የጦር ትምህርት አይማሩም። **4** ይልቁን፣ እያንዳንዱ ሰው ከገዛ ወይኑ ሥር ከገዛ በለሱም ሥር ይቀመጣል። የሰራዊት አምላክ ያህዌ ተናግሮአልና የሚያስፈራቸው አይኖርም። **5** ሕዝቦች ሁሉ በአምላኮቻቸው ስም ይሄዳሉ። እኛ ግን በአምላካችን በያህዌ ስም ለዘላለም እንሄዳለን **6** በዚያ ቀን ይላል ያህዌ፣ አንካሳውን እሰበስባለሁ ስደተኞችና ሐዘንተኞች ያደረግኃቸውን እሰበስባለሁ። **7** አንካሳውን ወደ ተረፉት ወገኖች የተገፉትንም ወደ ብርቱ ሕዝብ እመልሳለሁ፤ እኔ ያህዌ በጽዮን ተራራ ከዘላለም እስከ ዘላለም እነግሣለሁ። **8** አንተ የመጠበቂያው ማማ፣ የጽዮን ሴት ልጅ አምባ የቀድሞው ግዛትህ፣ የኢየሩሳሌም ሴት ልጅ መንግሥት ይመለስልሃል። **9** አሁንስ እንደዚህ የምትጮኺው ለምንድነው? በመካከልሽ ንጉሥ የለምን? ምጥ እንደ ያዛት ሴት የምትጨነቂው መካሪሽ ስለጠፋ ነውን? **10** የጽዮን ሴት ልጅ ሆይ፣ ምጥ እንደያዛት ሴት ተጨነቂ፤ አሁን ከከተማ ወጥተሽ ሜዳ ላይ ስፈሪ ወደ ባቢሎንም ትሄጃለሽ። በዚያም ከጠላት እጅ ትድኛለሽ በዚያም እግዚአብሔር ከጠላቶችሽ ይታደግሻል። **11** አሁን ግን፣ ብዙ ሕዝቦች አንቺ ላይ ተሰብስበዋል እነርሱም፣ «የረከሰች ትሁን፤ እኛም መፈራረስዋን እንይ» ብለዋል። **12** ነቢዩ እንዲህ ይላል፤ «የያህዌን ሐሳብ አያወቁም የእርሱንም ዕቅድ አያስተውሉም፤ እርሱ ዐውድማ ላይ እንደ ነዶ ይሰበስባቸዋል።» **13** ያህዌ እንዲህ ይላል፤ «ቀንድሽን እንደ ብረት፣ ሰኮናሽን እንደ ናስ አደርጋለሁ ብዙ ሕዝቦችን ታደቂያለሽ የጽዮን ልጅ ሆይ፣ ተነሥተሽ አበራዪ። በግፍ የሰበሰቡትን ሀብት ለራሴ ሀብታቸውንም ለምድር ሁሉ ጌታ አቀርባለሁ።»

Micah 4:1

ተራሮቹ ... በሌሎች ተራሮች
እግዚአብሔር የቤተ መቅደሱን ተራራ ከሌሎች ተራሮችና ኮረብቶች ሁሉ ማላቁ ቤተ መቅደሱን በምድር ላይ እጅግ አስፈላጊ ቦታ ስለ ማድረጉ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የእግዚአብሔር ቤት ተራራ ይመሠረታል
ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ቤተ መቅደሱ የሚገነባበትን ተራራ ይመሰርታል” ወይም “እግዚአብሔር ቤተ መቅደሱ ታላቅ ሆኖ የሚገነባበትን ተራራ ይሠራል”።

በሌሎች ተራሮች ላይ
የጽዮን ተራራ ከተራሮች ሁሉ እጅግ አስፈላጊው ይሆናል። በተጨማሪም ይህ ተራራ በሚዋሰንበት አካባቢ ብቻ ሳይሆን በዓለም ከፍተኛው ተራራ ይሆናል ማለት ሊሆን ይችላል።

ከኮረብቶች በላይ ከፍ ይላል
ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ከኮረብቶች በላይ ከፍ ያደርገዋል” ወይም “እግዚአብሔር ከኮረብቶች ይልቅ ያልቀዋል”።

ሕዝቦች ወደ እርሱ ይጎርፋሉ
ምንጭ ከተለያየ አቅጣጫ ወደ አንድ ስፍራ ባለማቋረጥ ይጎርፋል። ብዙ ሕዝቦች ከተለያየ አቅጣጫ ወደ ቤተ መቅደሱ ተራራ ይመጣሉ። አ.ት፡ “የአገራቱ ሕዝቦች እንደ ምንጭ ወደ እርሱ ይጎርፋሉ” ወይም “የአገራቱ ሕዝቦች ወደ እርሱ ይሄዳሉ”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Micah 4:2

ብዙ አገሮች
“አገሮች” የሚለው ቃል በፈሊጣዊ አነጋገር የአገራቱን ሕዝቦች ያመለክታል። አ.ት፡ “ሕዝቦች ከብዙ አገራት”።

ይመጣሉ
x

Micah 4:4

ሰዉን ሁሉ ከወይኑ በታች፣ ከበለሱንም በታች ያስቀምጡታል
“ወይን” እና “በለስ” ሁለቱም የብልጽግና ምልክቶች ናቸው። ይህ ሐረግ ሰዎች በብልጽግና እና በሰላም የሚኖሩበትን አኳኋን ይገልጻል። የወይን ፍሬ ወይም የበለስ ዛፍ የማይታወቅ ከሆነ ጠቅለል ባለ መንገድ ልትተርጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “በገዛ ራሳቸው የአትክልት ቦታና በመስኮቻቸው በሰላም ይቀመጣሉ”።

የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር አፍ ተናግሯልና
አፍ የሰውነት መግለጫ ምሳሌ ነው። አ.ት፡ “የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር ተናግሯልና”።

ሕዝቦች በአምላካቸው ስም ይሄዳሉ ... እኛ በእግዚአብሔር ስም እንሄዳለን
በመንገድ መሄድ የአንድን ሰው የሕይወት አኗኗር የሚያሳይ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። በአንዱ ስም መሄድ የማምለክና የመታዘዝ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ሕዝቦች አምላካቸውን ያመልካሉ፣ ይታዘዛሉም ... እኛ እግዚአብሔርን እናመልካለን፣ እንታዘዛለንም”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Micah 4:6

በዚያን ቀን
“በዚያን ጊዜ” ወይም “እነዚያን ነገሮች በማደርግበት ጊዜ”፤ እነዚህ ቃላት “የመጨረሻዎቹን ቀናት” ያመለክታሉ (ሚክያስ 4፡1)። “ቀን” የሚለው ቃል የተወሰኑ ቀናትን ወይም ዓመታትን እንኳን ሊያመለክት ይችላል።

አንካሳው
ይህ በትክክል መራመድ የማይችሉትን ያመለክታል። አንካሳ መሆን የትኛውንም ዓይነት የአካል ጉዳተኝነት የሚያሳይ ምሳሌ ነው።

የተጣሉትን እሰበስባለሁ
“ከኢየሩሳሌም ያስወጣኋቸውን እሰበስባቸዋለሁ”

ተሰደው የወጡትን ወደ ብርቱ ሕዝብ
“እመልሳለሁ” የሚለውን ቃል ቀድም ብሎ ካለው ሐረግ መረዳት ይቻላል። ሊደጋገሙ ይችላሉ። “ተሰደው የወጡትን” የሚለው ሐረግ በገቢራዊ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “አሳድጄ ያስወጣኋቸውን ወደ ብርቱ ሕዝብነት እመልሳቸዋለሁ” ወይም “በግድ ያባረርኳቸውን ብርቱ ሕዝብ እንዲሆኑ አደርጋቸዋለሁ”።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አንተን የመንጋውን መጠበቂያ ማማ፣ የጽዮን ሴት ልጅ ኮረብታ፣ ለአንተ የቀድሞ ግዛትህ ይመለስልሃል
ሚክያስ ይሰማው ይመስል ለቤተ መቅደሱ ተራራ በሚናገርበት ጊዜ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገሩ ነው። ሚክያስ መልዕክቱን ለሕዝቡ ማድረሱን ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። አ.ት፡ “የቤተ መቅደሱን ተራራ በሚመለከት፣ እግዚአብሔር እናንተን የሚመለከትበት ስፍራ፣ በጎቹ፣ የኢየሩሳሌም ሕዝብ ስለ ቀድሞ ግዛቱ የሚመኩበት ስፍራ ይመለሳል”።

ለመንጋው የመጠበቂያ ማማ
በመጠበቂያ ማማው ላይ ሆኖ መንጋውን እንደሚጠብቅ እረኛ የኢየሩሳሌም ሕዝብ በዙሪያቸው የሚኖሩትን ሌሎች ሕዝቦች እንደሚጠብቁ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የጽዮን ሴት ልጅ ... የኢየሩሳሌም ሴት ልጅ
በስፍራው የሚኖሩ ሰዎች ስፍራው እንደ እናት፣ እነርሱ እንደ ሴት ልጆች እንደሆኑ ተቆጥሮ ተነግሯል። አ.ት፡ “በጽዮን የሚኖሩ ሰዎች ... በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎች”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ኮረብታ
አንዳንድ የዘመናችን ትርጉሞች ይህንን የዕብራይስጥ ቃል “ትልቅ ምሽግ” ወይም “ጠንካራ ምሽግ” ማለት እንደሆነ ይረዳሉ።

ለአንተ፣ የቀድሞ ግዛትህ ይመለስልሃል
የነገር ስም የሆነው “ግዛት” እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ቀድሞ ታደርግ እንደነበረው አገሮችን ትገዛለህ” ወይም “ቀድሞ እንዳደረግኸው አገራቱን እንድትገዛ አደርግሃለሁ”።

Micah 4:9

አሁን ድምፅህን ከፍ አድርገህ የምትጮኸው ለምንድነው?
ሚክያስ ሕዝቡ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ለምን እንዲህ ባለ መንገድ እንደሚናገር እንዲያስቡ ለማድረግ በመሞከር በሕዝቡ ላይ ያላግጥባቸዋል። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ምን ያህል እንደምትጮኹ ተመልከቱ” ወይም “በኃይል የምትጮኹት ስለምን እንደሆነ በጥንቃቄ አስቡ”።

በመካከላችሁ ንጉሥ የለም? አማካሪዎቻችሁ ሞተዋል? እንደምታምጥ ሴት ሕመም የያዛችሁ ለዚህ ነው?
ሚክያስ በሕዝቡ ላይ ማላገጡን ቀጥሏል። እነዚህ ጥያቄዎች እንደ መግለጫዎች ሊተረጎሙ ይችላሉ። አ.ት፡ “ንጉሥ አላችሁ፣ ነገር ግን ምንም አይጠቅማችሁም። ጥበበኞቻችሁ ገና በሕይወት አሉ፣ ነገር ግን ምንም የሚነግሯችሁ ጥበብ የላቸውም። ለዚህ ነው ልጅ እንደምትወልድ ሴት ድምፃችሁን አውጥታችሁ የምታለቅሱት”።

እንደምታምጥ ሴት የታመማችሁት
ሚክያስ ጠላት ከከተማቸው እንዲወጡ ሲያስገድዳቸው ሕዝቡ የሚገጥማቸውን ሥቃይ አንዲት ሴት ልጅ በምትወልድበት ጊዜ ከሚሰማት ሕመም ጋር ያነጻጽረዋል።

በዚያ ትድናላችሁ። በዚያ እግዚአብሔር ያድናችኋል
እግዚአብሔር እንደሚያደርግ የተናገረውን እንደሚያደርግ አጽንዖት ለመስጠት በገቢራዊና በኢገቢራዊ ድምፅ በሁለቱም ተመሳሳዩን ነገር ይናገራል። ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “በዚያ እግዚአብሔር ያድናችኋል። በዚያ እርሱ ያድናችኋል”።

ከጠላቶቻችሁ እጅ
“እጅ” ለሚለው ቃል የሚከተሉት ተስማሚ ትርጉሞች ናቸው፣ 1) እጅ ለሚሠራበት ኃይል ፈሊጣዊ አነጋገር ይሆን ይሆናል፣ አ.ት፡ “የጠላቶቻችሁ ኃይል” ወይም 2) ስለ ሰው ምሳሌ ይሆን ይሆናል። አ.ት፡ “ጠላቶቻችሁ”።

Micah 4:11

የረከሰች ትሁን
ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እናርክሳት”።

ዓይኖቻችን በመፈንደቅ ጽዮንን ይዩ
ዐይን የሰውን ሁለንተና የሚወክል ምሳሌ ነው። አ.ት፡ “ጽዮንን በመፈንደቅ እንያት” ወይም “ወራሪዎች ጽዮንን ሲያጠፏት በማየት ደስ ይበለን”።

በዐውድማ ላይ ለመወቃት እንደተዘጋጀ የእህል ክምር አንድ ላይ ሰብስቧቸዋል
ጸሐፊው እግዚአብሔር የእህሉን ክምር ዐውድማው ላይ እንዳደረገና ሊወቃው እንደተዘጋጀ ገበሬ አገሮችን ለማጥፋት መዘጋጀቱን ይናገራል።

Micah 4:13

የጽዮን ሴት ልጅ ሆይ፣ ተነሺ ውቂ ...ቀንድሽ ...ኮቴዎችሽ ... ታደቂያቸዋለሽ
“ያንቺ” እና “አንቺ” የተባሉት ሁሉ እንዲሁም ትዕዛዛት “የጽዮንን ሴት ልጅ” የሚያመለክቱ ሲሆኑ ነጠላ ቁጥርና አነስታይ ናቸው።

የጽዮን ሴት ልጅ ሆይ፣ ተነሺ ውቂ፣ ቀንድሽን ብረት አደርገዋለሁ፣ ኮቴሽንም ነሐስ እንዲሆኑ አደርጋቸዋለሁ
እግዚአብሔር የጽዮንን ሕዝብ ስንዴ እንደሚወቃ ብርቱ በሬ፣ ጠላቱንም እንደ ስንዴ አድርጎ ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር እና የሚለውን ተመልከት)

ቀንድሽን ብረት አደርገዋለሁ፣ ኮቴሽንም ነሐስ እንዲሆኑ አደርጋቸዋለሁ
አንባቢህ በሬን ወይም ብረትን ወይም ነሐስን የማያውቅ ከሆነ ዘይቤአዊውን አነጋገር ልትተወው ትችላለህ። አ.ት፡ “ጠላቶችህን ሁሉ ማሸነፍና ማጥፋት እንድትችል አደርግሃለሁ። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የግፍ ሀብታቸውን
“ግፍን በማድረግ ያገኙትን ሀብት” ወይም “ከሌሎች ሰዎች የሰረቋቸውን ነገሮች”

ሀብታቸውን
የነገር ስም የሆነው “ሀብት” እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “የራሳቸው ያደረጓቸው ነገሮች”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 5

1 አንቺ የወታደር ከተማ ሰራዊትሽን አሰልፊ ከበባ ተደርጐብናልና የእስራኤልን ገዥ ጉንጩን በበትር ይመቱታል። **2** አንቺ ቤተ ልሔም ኤፍራታ ሆይ፣ ከይሁዳ ነገዶች መካከል ትንሿ ብትሆኚም፣ ጅማሬው ከጥንት ከዘላለም ዘመናት የሆነ የእስራኤል ገዥ ከአንቺ ይወጣልኛል። **3** ስለዚህ ያማጠችው ልጅ እስክትወልድ ድረስ እግዚአብሔር ሕዝቡን ይተዋቸዋል የተቀሩት ወንድሞቹም ወደ እስራኤል ሕዝብ ይመለሳሉ። **4** በያህዌ ብርታት፣ በአምላኩ በያህዌ ስም ክብር ጸንቶ ይቆማል፤ መንጋውንም ይጠብቃል። በዚያ ጊዜ ታላቅነቱ እስከ ምድር ዳርቻ ስለሚደርስ ተደላድለው ይኖራሉ። **5** እርሱ ሰላማችን ይሆናል። አሦራውያን ወደ ምድራችን ሲመጡ ወደ ምሽጐቻችንም ሲገሠግሡ ሰባት እረኞችን፣ እንዲሁም ስምንት መሪዎችን እናስነሣባቸዋልን። **6** እነዚህ ሰዎች የአሦርን ምድር በሰይፍ፣ የናምሩዱንም ምድር እጃቸው ላይ ባለው ሰይፍ ይገዛሉ። ወደ ምድራችን ሲመጡ ወደ ድንበራችንም ሲገሠግሡ እርሱ ከአሦራውያን ይድነናል። **7** የያዕቆብ ትሩፍ በብዙ ሕዝብ መካከል ከያህዌ ዘንድ እንደሚወርድ ጠል፣ ሣር ላይ እንደሚጥል ካፊያ ሰውን እንደማይጠብቅ፣ በሰው ልጆችም እንደማይተማመን ሰው ይሆናል። **8** የያዕቆብ ትሩፍ በሕዝቦች መካከል፣ በብዙ ሕዝቦች መካከል ይሆናል፤ በዱር አራዊት መካከል እንዳለ አንበሳ፣ በበጐች መካከል እንዳለ አንበሳ ደቦል ይሆናል። በእግሩ እየረጋገጠ ይቦጫጭቃቸዋል፤ የሚያድናቸውም አይኖርም። **9** እጅህ በጠላቶችህ ላይ ከፍ ከፍ በማለት ያጠፋቸዋል። **10** በዚያ ቀን ይላል ያህዌ «ፈረሶቻችሁን ከመካከላችሁ አጠፋለሁ ሠረገሎቻችሁንም እደመስሳለሁ። **11** የምድራችሁን ከተሞች አጠፋለሁ ምሽጐቻችሁንም ሁሉ አፈርሳለሁ። **12** በምድራችሁ ያለውን ጥንቆላ አጠፋለሁ ከእንግዲህ አታሟርቱም። **13** የተቀረጹ ምስሎቻችሁንና የድንጋይ ዐምዶቻችሁን ከመካከላችሁ አጠፋለሁ። ከእንግዲህ የእጆቻችሁን ሥራ አታመልኩም። **14** የአሼራ ምሰሶዋችሁን ከምድራችሁ እነቅላለሁ ከተሞቻችሁንም አጠፋለሁ። **15** ያልታዘዙኝን ሕዝቦች በቀጣዬና በመዓቴ እበቀላሁ።»

Micah 5:1

የወታደሮቹ ሴቶች ልጆች
የአንዲት ከተማ ሕዝብ እንደ ሴት ተቆጥረው ተነግሮላቸዋል። ወታደሮቹ ከተማይቱን አጥቅተዋታል። አ.ት፡ “ወታደሮቹ የሚያጠቋችሁ የከተማይቱ ሕዝብ”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የእስራኤልን ገዢ ጉንጩን በበትር ይመቱታል
በትር ባለ ማዕረግ የሆነ ሰው የበታቹን የሚቀጣበት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። የአንድን ሰው ጉንጭ መምታት ከመጉዳት ያለፈ ስድብ ነበር። አ.ት፡ “እግዚአብሔር የእስራኤልን ፈራጆች ወራሪዎች እንዲሰድቧቸው በማድረግ ይቀጣቸዋል!”። (ዘይቤአዊ እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የእስራኤል ፈራጅ
ይህ ምጸት ንጉሡ አብላጫውን ኃይልና ሥልጣኑን በማጣቱ ፈራጅ ብቻ መሆኑን ያሳያል።

Micah 5:2

አንቺ ቤተ ልሔም ኤፍራታ
እግዚአብሔር ለቤተ ልሔም ከተማ ለራሷ በሚናገርበት መልኩ ለይሁዳ ሕዝብ፣ በተለይም ለቤተ ልሔም ሕዝብ ይናገራል።

ኤፍራታ
ይህ ቤተ ልሔም የምትገኝበት አካባቢ ስም ወይም የቤተ ልሔም ሌላኛው ስሟ ወይም ይህችኛዋን ቤተ ልሔም ከሌላው መለያ ይሆን ይሆናል። ቤተ ልሔም ከኢየሩሳሌም በስተደቡብ ስድስት ማይል ርቀት ላይ ትገኛለች። የንጉሥ ዳዊት የትውልድ መንደር ነበረች። ተርጓሚዎች የሚከተለውን የግርጌ ማስታወሻ መጨመር ይኖርባቸው ይሆናል፤ “ ‘ኤፍራታ’ የሚለው ስም ትርጉም ‘ፍሬአማ መሆን’ ማለት ነው”።

በይሁዳ ጎሳዎች መካከል ታናሽ ብትሆኚም አንድ ከአንቺ የሚወጣ አለ
“በይሁዳ ጎሳዎች ውስጥ ብዙ ሕዝብ ያለው ሌላ ቢኖርም ከሕዝብሽ የሚመጣው አንድ ነው”

ወደ እኔ ይመጣል
እዚህ ጋ “እኔ” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ያመለክታል።

ጅማሬው ከጥንት ዘመን፣ ከዘላለም የሆነ
ይህ ከንጉሥ ዳዊት ጥንታዊ ቤተ ሰብ የሚመጣውን ገዢ ያመለክታል። “ከጥንት ዘመን” እና “ከዘላለም” የሚሉት ሐረጎች ትርጉማቸው በመሠረቱ አንድ ሆኖ የቤተ ሰቡ የትውልድ ሐረግ ምን ያህል ረጅም መሆኑን አጽንዖት ይሰጣሉ።

ስለዚህ
“የተናገርኩት እውነት ስለሆነ” ወይም “ምክንያቱም በኋላ ይህ ገዢ ይመጣል”

ይተዋቸዋል
የእስራኤልን ሕዝብ ይተዋቸዋል

የምታምጠው እርሷ ልጅ እስከምትወልድበት ጊዜ ድረስ
ይህ ገዢው የሚወለድበትን የተወሰነ ጊዜ ያመለክታል።

የቀሩት ወንድሞቹ
በምርኮ ያሉ “የቀሩት የገዢው እስራኤላውያን ጓደኞች”

Micah 5:4

እርሱ በእግዚአብሔር ኃይል ይቆማል፣ መንጋውንም ይጠብቃል
በጎቹን የሚመግብና የሚጠብቅ እረኛ ለእስራኤል ሕዝብ የሚያስፈልጋቸውን የሚያቀርበውንና የሚጠብቃቸውን ገዢ የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ሕዝቡን እንዲመራለት እግዚአብሔር ኃይልን ይሰጠዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በአምላኩ በእግዚአብሔር ስም ግርማ
የሰውየው ስም ስላለው ሥልጣን ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “አምላኩ እግዚአብሔር እንዲገዛ ሥልጣንን ስለሰጠው ሰዎች ያከብሩታል”። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እነርሱ ይኖራሉ
የእስራኤል ሕዝብ ይኖራሉ

ይኖራሉ
“በሰላም ይኖራሉ”

እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ታላቅ ይሆናል
በየአገሩ ያለ ሕዝብ ሁሉ ለእስራኤል ገዢ ክብርን ይሰጠዋል

ሰባት እረኞችንና ስምንት መሪዎችን እናስነሣባቸዋለን
እዚህ ጋ “እረኞች” የሚለው ቃል በሌላ አነጋገር “ሰዎችን የሚመሩ” ሲሆኑ በፈሊጣዊ አነጋገር “ገዢዎች” ማለት ነው። “ሰባት … እና ስምንት” የሚለው ሐረግ “ከበቂ በላይ” ለሚለው የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “በቂ፣ ከበቂም

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንኳን በላይ የሆኑ መሪዎች” ወይም “በሰዎች ላይ ከበቂ በላይ የሆኑ እረኞችና መሪዎች”

Micah 5:6

የአሦራውያንን ምድር በሰይፍ፣ የናምሩድንም ምድር በበሩ ላይ በእረኝነት ይጠብቃሉ
ሰይፍ በጦርነት ውስጥ ለመግደያነት በፈሊጣዊነት ተነግሯል። እዚህ ጋ እስራኤላውያን በጎችን ከመጠበቅ ይልቅ ያረዷቸው በሚመስል መልኩ በአሦራውያን ላይ ገዢ መሆናቸው በምጸት ተነግሯል። የአሦር ምድር በዚያ ለሚኖሩ ሰዎች ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። የከተሞቹ በሮች ሕጋዊ ንግድ የሚካሄድባቸው ስፍራዎች ነበሩ። አ.ት፡ “የአሦርን ሕዝብ ይወጋሉ፣ የናምሩድን ምድር ከተሞችም ይገዛሉ”። ጦርነት

የናምሩድ ምድርም
“በእረኝነት ይጠብቃሉ” የሚሉትን ቃላት ከዐረፍተ ነገሩ መነሻ መረዳት ይቻላል። ሊደጋገሙ ይችላሉ። አ.ት፡ “የናምሩድን ምድር በእረኝነት ይጠብቃሉ”።

የናምሩድ ምድር
ይህ የአሦር ምድር ሌላው ስሙ ነው። ናምሩድ አደን ያድን የነበረ የቀድሞ ገዢ ነበር። ተርጓሚዎች ይህንን የግርጌ ማስታወሻ መጨመር ይኖርባቸው ይሆናል፤ “ ‘ናምሩድ’ የሚለው ስም ትርጉም ‘ዓመፅ’ ማለት ነው”።

ያድናል
ገዢው ያድናል

ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ጠል፣ በሣሩ ላይ እንደሚወርድ ካፊያ
ጠልና ዝናብ ምድሪቱን በማረስረስ አንዳንድ ነገሮች እንዲበቅሉ ያደርጋሉ። እስራኤላውያን በመካከላቸው የሚኖሩባቸው ሕዝቦች በሰላም እንዲኖሩ ያደርጓቸዋል።

ሰውን የማይጠብቅ ሣር፣ የሰው ልጆችንም አይጠብቁም
“ሣር ሰውን ወይም የሰው ልጆችን አይጠብቅም”፤ ጠልንና ዝናብን የሚያርከፈክፍ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

Micah 5:8

አጠቃላይ መረጃ፡
እግዚአብሔር ሕዝቡን በጦርነት ከቀጣቸው በኋላ በሕይወት ያሉት እስራኤላውያን ጠላቶቻቸውን ፈጽመው ድል እንደሚያደርጉና እንደሚገዟቸው እግዚአብሔር ተስፋ ይሰጣል።

የያዕቆብ ትሩፍ
ከጦርነቱ የሚተርፉ የያዕቆብ ተወላጆች

በአገራት መካከል፣ በብዙ ሕዝቦች መካከል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ ትርጉማቸው አንድ ሲሆን “የያዕቆብ ትሩፍ” በብዙ የተለያዩ አገሮች እንደሚኖሩ አጽንዖት ይሰጣሉ።

በጫካ እንስሶች መካከል እንዳለ አንበሳ፣ በበግ መንጋም መካከል እንዳለ የአንበሳ ደቦል
አናብስት በጫካ የሚኖረውን የትኛውንም እንስሳ መግደልና መብላት ይችላሉ፣ በጎችንም በቀላሉ ይገድላሉ። አ.ት፡ “እንደ ተናካሽ የዱር እንስሳት፣ ምስኪን ከብቶችን እንደሚገድሉ የዱር እንስሶች”

በመካከላቸው በሚሄድበት ጊዜ
የአንበሳ ደቦል በበግ መንጋ መካከል በሚሄድበት ጊዜ

እላያቸው ላይ ይከመርባቸውና ይዘነጣጥላቸዋል
“ይዘልባቸውና ይጥላቸዋል፣ ከዚያም ይዘነጣጥላቸዋል”

እጅህ ... ጠላቶችህ
ጸሐፊው የሚናገረው እግዚአብሔርን ነው፤ በመሆኑም “አንተ” የተሰኙት ሁለቱም ተባዕት ነጠላ ቁጥር ናቸው።

እጅህ በጠላቶችህ ላይ ይነሣል
እጅ በፈሊጣዊ አነጋገር ለመሥራት ያለውን ኃይል ገላጭ ነው ወይም የሰውን ሁለንተና የሚወክል ምልክት ነው። እጅን ማንሣት ኃይልን መግለጥ ነው። አ.ት፡ “ጠላቶችህን ሙሉ በሙሉ ድል ታደርጋቸዋለህ”።

ያጠፋቸዋል
እጅ የሰውን ሁለንተና የሚወክል ምልክት ነው። አ.ት፡ “ታጠፋቸዋለህ”

Micah 5:10

በዚያን ቀን
“በዚያን ጊዜ” ወይም “እነዚያን ነገሮች በማደርግበት ጊዜ”። እነዚህ ቃላት “የመጨረሻዎቹን ቀናት” ያመለክታሉ (ሚክያስ 4፡1)። “ቀን” የሚለው ቃል የተወሰኑትን ቀናት ወይም ዓመታትን እንኳን ሊያመለክት ይችላል።

ከመካከልህ ፈረሶችህን አጠፋለሁ፣ ሰረገላዎችህንም አወድማለሁ
እስራኤላውያን ፈረሶችን እና ሰረገላዎችን ለጦርነት ብቻ ይጠቀሙ ነበር፤ ምናልባት በዙሪያቸው ካሉ አምላክየለሽ አገራት ጋር ተገበያይተው ይሆናል። ሰዎች በእርሱ ከመታመን ይልቅ እንዲጠብቋቸው በጦር መሣሪያዎቻቸው መታመናቸውን እግዚአብሔር አይፈልግም።

ከመካከልህ ፈረሶችህን ... ሰረገላዎችህን ... ምድርህን ... ምሽጎችህን
እግዚአብሔር እንደ አንድ ሰው አድርጎ ለእስራኤል ሕዝብ ይናገራል።

Micah 5:12

በእጅህ ያለውን ጥንቆላ
በ”እጅ” መሆን የሚወክለው ሰውየው የሚያደርገውን ተግባር ነው። አ.ት፡ “አንተ የምታደርገው ጥንቆላ”

እጅህ ... ትፈቅዳለህ ... የተቀረጸው ምስልህ ... ድንጋይህ ...በመካከልህ። ትፈቅዳለህ ... እጆችህ ... አሼራህ ... በመካከልህ ... ከተሞችህ
እግዚአብሔር እንደ አንድ ሰው አድርጎ ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል።

የእጆችህን ሙያ
የንገር ስም የሆነው “ሙያ” “ሥራ” በሚል ግሥ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እጆችህ የሠሩትን”።

የአሼራ ምስልህን ምሶሶ እነቅላለሁ
እግዚአብሔር ከመሬት ውስጥ እንደሚነቅላቸው ዛፎች ስለ አሼራ ምስል ምሶሶ ይናገራል። አ.ት፡ “የአሼራ ምስልህን ምሶሶ ከምድር ውስጥ እነቅላለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 6

1 እንግዲህ ያህዌ የሚናገረውን አድምጡ፤ «ተነሡ፤ ያላችሁንም ቅርታ በተራሮች ፊት አቅርቡ ኮረብቶችም የምትሉትን ይስሙ። **2** እናንተ ተራሮች እናንተ
ጸንታችሁ የቆማችሁ የምድር መሠረቶች ያህዌ የሚያቀርበውን ክስ አድምጡ፤ እርሱ ከእስራኤል ጋር ይፋረዳል።» **3** «ሕዝቤ ሆይ፣ ምን አደረግሁህ?
ያታከትሁህስ በምንድነው? እስቲ መስክርብኝ! **4** እኔ ከግብፅ ምድር አወጣሁህ ከባርነት ቤትም ታደግሁህ። ሙሴን፣ አሮንንና ማርያምን ወደ አንተ ላክሁ። **5**
ሕዝቤ ሆይ፣ የሞዓብ ንጉሥ ባላቅ ያቀደብህን የቢዖር ልጅ በለዓም የመለሰለትን፣ ከሺጡም ተነሥተህ ወደ ጌልጌላ ስትሄድ፣ እኔ፣ ያህዌ ያደረግሁትን የጽድቅ
ሥራ ታውቅ ዘንድ አስታወስ። **6** ለልዑል አምላክ ለመስገድ በምመጣበት ጊዜ፣ ለያህዌ ምን ይዤ ልምጣ? የሚቃጠል መሥዋዕት እንዲሆኑ የአንድ ዓመት
ጥጃ ይዤ ልምጣን? **7** በሺህ የሚቆጠሩ ዐውራ በጎችን ወይስ የአሥር ሺህ ወንዞች የሚያህል ዘይት ባቀርብለት ያህዌ ይደሰት ይሆን? ስለ መተላለፌ የበኩር
ልጄን፣ ስለ ኃጢአቴስ የአካሌን ፍሬ ልስጥን? **8** ሰው ሆይ፣ መልካሙን፣ ያህዌ ከአንተ የሚፈልገውን ነግሮሃል ፍትሕ አድርግ፤ ደግነትን ውደድ፤ ከአምላክህ ጋር
በትሕትና ተመላለስ። **9** የያህዌ ድምፅ ከተማዋን ይጣራል አሁን እንኳ ጥበብ ስምህን ትገነዘባለች በትሩን አስታውስ፤ በቦታው ያደረገው ማን እንደ ሆነ
አስታውስ። **10** ክፉው ቤት ውስጥ በግፍ የተገኘ ሀብት አስጸያፊ የሆነ ሐሰተኛ መስፈሪያ አለ። **11** ዐባይ ሚዛን የሚጠቀመውን ሰው፣ ሐሰተኛ መመዘኛ
በከረጢት የቋጠረውን ሰው ንጹሕ ላድርገውን? **12** ባለ ጠጎች በግፍ ተሞልተዋል በዚያ የሚኖሩ ሐሰት ተናግረዋል ምላሳቸው አታላይ ናት። **13** ስለዚህ በጽኑ
ቁስል መታሁህ ከኃጢአትህ የተነሣም አፈረስሁህ። **14** ትበላለህ ግን አትጠግብም ሁሌም ባዶነት ውስጥህ ይኖራል። ታከማቻለህ ግን አይጠራቀምልህም
ያጠራቀምኸውን ለሰይፍ እዳርጋለሁ። **15** ትዘራለህ ግን አታጭድም የወይራ ፍሬ ትጨምቃለህ፤ ግን ዘይት አትቀባም፤ ወይን ትጨምቃህ ግን ጠጅ
አትጠጣም። **16** የዖምሪን ሥርዐት የአክዓብን ቤት ተግባርም አጥብቀህ ይዘሃል በምክራቸው መሠረት ኖረሃል። ስለዚህ አንተንና ከተማህን ለውድመት
ሕዝብህንም ለመዘባበቻ አሳልፌ እሰጣለሁ በሕዝቤ ላይ የተሰነዘረውን ነቀፋ ትሸከማለህ።

Micah 6:1

መዋቅሩና አቀራረቡ
ይህ ምዕራፍ የተጻፈው እንደ ፍርድ ቤት ጉዳይ ወይም እግዚአብሔር በራሱ ሕዝብ ላይ ሙግት እንዳለው ሆኖ ነው።

በመግቱ ውስጥ ያሉት ስሞች በዚህ ምዕራፍ ለመተርጎም አስቸጋሪ ከሚሆኑት ውስጥ ናቸው
ሙሴ፣ አሮንና ማርያም በእስራኤል ላይ ለእግዚአብሔር ምስክር ሆነው ተጠቅሰዋል። አክዓብና ዖምሪ እግዚአብሔርን እንዳልተከተሉ ክፉ ነገሥታት ሆነው ተጠቅሰዋል። ለሙሴ ሕግ መታዘዝ ለሕጉ ካለመታዘዝ ጋር ተነጻጽሯል።

እንግዲህ ስሙ ... የእግዚአብሔርን ሙግት ስሙ
ሚክያስ ሊሰሙት ይችሉ ይመስል ለተራሮች ሲናገር የሚናገረው ለእስራኤል ሕዝብ ነው፤ ስለዚህ በሁለቱም አገላለጽ “ስሙ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ነው።

ተነሥ ... አቅርብ ... ድምፅህ ...
ሚክያስ እንደ አንድ ሰው አድርጎ ለእስራኤል ሕዝብ ይናገራል፤ ስለዚህ ትዕዛዞቹና “አንተ” የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር ነው።

ተነሥና በተራሮቹ ፊት ነገርህን አቅርብ፤ ኮረብቶቹም ድምፅህን ይስሙ
እግዚአብሔር በፍርድ ቤት እንዳለና ተራሮችና ኮረብቶች ፈራጆቹ እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። የእስራኤል ሕዝብ ያደረጉትን ለምን እንዳደረጉ ለዳኞቹ እንዲናገሩ ያዛቸዋል።

ተራሮቹ ... ኮረብቶቹ ... የጸኑት የምድር መሠረቶች
ሚክያስ ሰዎች እንደሆኑ ቆጥሮ ለእነዚህ ነገሮች ይናገራል። ሚክያስ ተራሮችን፣ ኮረብቶችንና የምድርን መሠረቶች በሕዝቡ ጣዖት አምላኪነት ላይ ዘላለማዊ ምስክር አድርጎ ያቀርባቸዋል።

Micah 6:3

ሕዝቤ ሆይ፣ ምን አድርጌአችኋለሁ? ያደከምኳችሁ በምንድነው? መስክሩብኝ!
እግዚአብሔር መልካም አምላክ ስለመሆኑና ሕዝቡ እርሱን ማምለካቸውን እንዲያቆሙ የሚያስደርግ ምንም ነገር እንዳላደረገ አጽንዖት ለመስጠት ጥያቄ ይጠይቃል። አ.ት፡ “ሕዝቤ ሆይ፣ እኔ ለእናንተ መልካም ነበርኩኝ። በእኔ ምክንያት የምትደክሙበትን ምንም ነገር አላደረግሁም። እንዳደረግሁ ካሰባችሁ አሁን መስክሩብኝ”።

ለእናንተ ... አደከምኳችሁ? መስክሩ ... አመጣኋችሁ ... አዳንኳችሁ ... ማርያምን ለእናንተ ... አስቡ ... ሄዳችሁ ... ታውቁ ዘንድ
ሚክያስ እንደ አንድ ሰው አድርጎ ለሕዝቡ ይናገራል፤ ስለዚህ ትዕዛዞቹ ሁሉና “አንተ” የሚሉት ሁሉ ተባዕታዊ ነጠላ ቁጥር ናቸው።

የባርነት ቤት
ቤት አንድ ሰው ለረጅም ጊዜ የሚኖርበት ስፍራ የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። የንገር ስም የሆነው “ባርነት” “ባሪያዎች ልትሆኑ” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ለረጅም ጊዜ ባሪያዎች ሆናችሁ የኖራችሁበት ስፍራ”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ባላቅ የመከረውን
“ባላቅ እናንተን ለመጉዳት ያቀደውን”

በለዓም እንዴት ... እንደ መለሰለት
1) በለዓም ባላቅ በጠራው ጊዜ በመምጣቱ ለባላቅ ታዞአል። አ.ት፡ “በለዓም ባላቅ እንዲያደርግ የጠየቀውን ... እንዴት እንዳደረገ” ወይም 2) ባላቅ እንዳዘዘው እስራኤላውያንን በመርገም ፈንታ ለምን እንደባረካቸው በለዓም ለባላቅ አብራራለት። አ.ት፡ “በለዓም ለባላቅ የነገረውን” ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች ናቸው።

ቢዖር
ይህ የበለዓም አባት ስም ነው።

ሰጢም
ይህ በሞዓብ የሚገኝ የቦታ ስም ነው።

ስለዚህ የእግዚአብሔርን የጽድቅ ሥራዎች ታውቁ ዘንድ
እግዚአብሔር በገዛ ስሙ ወደ ራሱ ያመለክታል። አ.ት፡ “እኔ እግዚአብሔር ያደረግሁላችሁን የጽድቅ ነገሮች ታስታውሱ ዘንድ”።

Micah 6:6

ወደ እግዚአብሔር ምን ላምጣ ... እግዚአብሔር? አሮጌ ... ልምጣ? ዘይት ...
እግዚአብሔር ደስ ይለዋል? ኃጢአት ... ልስጠው?
ሚክያስ፣ እግዚአብሔር ምን እንዲያደርግ እንደሚፈልግበት በእውነት ለማወቅ እንደሚፈልግ ሰው ሆኖ ይናገራል። ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፣ 1) ጥያቄ ይጠይቅና በቁጥር 8 ለጠየቀው ጥያቄ መልስ ይሰጣል ወይም 2) ሕዝቡን ለማስተማር በጥያቄ ይጠቀማል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ሆይ፣...

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለእግዚአብሔር ምንም ማምጣት እንደማያስፈልገን አውቃለሁ ወይም ልምጣ … አሮጌ፣ እና ዘይት ወይም … ኃጢአት …ብሰጥ”

ሺዎችን አውራ በጎች ... አሥር ሺዎች የዘይት ወንዞችን
“1,000 የአውራ በጎች መንጋ … 10,000 የዘይት ወንዞችን”

እርሱ ነግሯችኋል
“እግዚአብሔር ነግሯችኋል”

ደኅና፣ እግዚአብሔር ከእናንተ የሚፈልገው፤አድርጉ ... እግዚአብሔር
በርካታ ትርጉሞች የሚሉት፣ “ደኅና/ እግዚአብሔር ከእናንተ የሚፈልገው ምንድነው? እግዚአብሔር … እንድታደርጉ ይፈልጋል” ወይም “ደኅና፤ እግዚአብሔር … እንድታደርጉ እንጂ ከእናንተ የሚፈልገው ምንድነው?”

ደግነትን ውደዱ
የነገር ስም የሆነው “ደግነት” ቅጽሉን “ደግ” በመጠቀም መተርጎም ይቻላል። አ.ት፡ “ለሰዎች ደግ መሆንን ውደዱ”።

Micah 6:9

የእግዚአብሔር ድምፅ ከተማይቱን ይጣራል
ድምፅ ሰውየውን ሲወክል ከተማ ደግሞ በውስጡ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ለኢየሩሳሌም ሕዝብ ጥሪ ያስተላልፋል”።

አሁን እንኳን ጥበብ ለስምህ ዕውቅና ትሰጣለች
ጥበብ እንደ ሰው ተነግሮላታል፣ በፈሊጣዊ አነጋገር ጥበበኛን ሰው ያመለክታል። እዚህ ጋ “ስም” የሚለው ቃል ስለ ሰውየው ስለ ራሱና ሰዎች ስለ ሰውየውና ስለ ሥልጣኑ የሚያስቡትን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ጥበበኛው ሰው ይፈራሃል” ወይም “ጥበበኛ ሰው አንተ መልካም መሆንህን ያውቃል፣ ይታዘዝሃልም”።

በትሩንና በስፍራው ያስቀመጠውን እርሱን ልብ በሉ
እዚህ ጋ “በትር” እግዚአብሔር “በስፍራው ያስቀመጠው” እና የራሱን ሕዝብ የሚቀጣበትን የጠላትን ሰራዊት ያመለክታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አታላዮች በሆኑ በክፉዎች ቤት ውስጥ ባለጸግነት አለ
በማታለል የተገኘ ባለጸግነት ሰዎች በማታለል ተግባር ያገኙትን ባለጸግነት የሚያሳይ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። “ክፉው” የሚለው ቃል ክፉዎች ሰዎችን ያመለክታል። ቤቶች አንድ ሰው የራሱ ንብረት የሚያደርጋቸውን ነገሮች ሁሉ የሚያመልክት ምሳሌ ነው። አ.ት፡ “ክፉዎች ሰዎች ባለጸግነትን ለማግኘት የማታለልን ተግባር ፈጽመዋል”።

ሐሰተኛ መለኪያ
ሰዎች ብልጽግናቸውን ለማብዛት የሚገበያዩአቸውን ሌሎች ሰዎች በሚዛን በማጭበርበር የሚጠቀሙበት ትክክለኛ ያልሆነ መስፈሪያ ነው።

Micah 6:11

በ ... የሚመዝነውን ሰው ንጹሕ እንደሆነ ልቁጠረው?
ይህ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “በ … የሚመዝነውን ሰው በእርግጠኝነት ንጹሕ አድርጌ አልቆጥረውም”።

የሚያጭበረብሩ ሚዛኖች
ሻጮች ገዢዎችን የሚያጭበረብሩባቸው ሚዛኖች

ባለጸጋ ሰዎች ሁከትን የተሞሉ ናቸው
ባለ ጸጎች ሰዎች የሆነን ነገር እንደሚይዝ ዕቃ ተቆጥረዋል፤ ሰዎች እርስ በእርሳቸው በቁጣ የሚያደርጉት ነገር በዕቃ ውስጥ እንደሚያኖሩት ፈሳሽ ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ባለ ጸጎች ሰዎች በሁሉም ላይ በቁጣ ያደርጋሉ” ወይም “ባለጸጎች ሰዎች ሁል ጊዜ በቁጣ ያደርጋሉ”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በአፋቸው ውስጥ ያለው ምላሳቸው አታላይ ነው
ምላስ የሰው ምሳሌው ነው። አ.ት፡ “የሚናገሩት ሁሉ ውሸት ነው”

Micah 6:13

አንተን በኃይለኛ ምት እመታሃለሁ
እግዚአብሔር ሕዝቡን በኃይለኛ ምት ይመታቸዋል ማለት እንደሚቀጣቸው የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ክፉኛ ቀጥቻችኋለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ባዶነታችሁ በውስጣችሁ ይኖራል
አንድ ሰው ወይም እንስሳ ሲራብ አንዳች ነገር በዕቃ ውስጥ በሚደረግበት መልኩ ሕዝቡ በመያዣ ዕቃ ተመስለው ተነግሮባቸዋል። አ.ት፡ “ትራባላችሁ፣ ራሳችሁን ለማርካት ጠግባችሁ አትበሉም”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የዖምሪ ሥርዓትና የአክዓብ ቤት ሥራዎች ሁሉ ተጠብቀዋል
ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል፣ አንተም ዋናውን ቃል የገደፉት በገደፉበት ቦታ ቃላቱን ማሟላት ይኖርብህ ይሆናል። አ.ት፡ “ዖምሪ ያዘዘውን ፈጽመሃል፣ የአክዓብ ቤት ያደረጋቸውን እነዚያኑ ነገሮች አድርገሃል”።

ዖምሪ ... አክዓብ
ሁለቱም ሰዎች የሰሜናዊው የእስራኤል መንግሥት ነገሥታት ነበሩ። እግዚአብሔር ሁለቱም እጅግ ክፉዎች እንደነበሩ ተመልክቶአል።

የአክዓብ ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተ ሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “የአክዓብ ዘሮች”።

በምክራቸው ሄደሃል
በመንገድ ላይ መሄድ አንድ ሰው የሚኖረውን ሕይወቱን የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ዖምሪና አክዓብ ሕዝቡ እንዲያደርጉ የነገሯቸውን አንተ ታደርጋለህ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የፈራረሰ ከተማ አደርግሃለሁ፣ እናንተን ነዋሪዎቿንም የመሳለቂያ ምልክት
ሚክያስ ሊሰማው ለማይቻለው ለከተማው ለራሱ የሚናገር ይመስል ሊሰሙት ለሚችሉት ለከተማይቱ ሰዎች ይናገራል። ዋና ቃል ገዳፊዎች የተውአቸውን ቅላት ግልጽ ማድረግ ይኖርብህ ይሆናል። አ.ት፡ “ከተማህን ፍርስራሽ አደርጋታለሁ፣ እናንተን ነዋሪዎቿንም የመሳለቂያ ምልክት አደርጋችኋለሁ” ወይም “የፈራረሰች ከተማ አደርግሃለሁ፣ የከተማይቱ ነዋሪዎች፣ የሚያዩህም ሁሉ እንዲሳለቁብህ አደርጋለሁ” ወይም “ከተማይቱን ፍርስራሽ አደርጋታለሁ፣ በነዋሪዎቿም ላይ ሰዎች እንዲሳለቁ አደርጋለሁ”።

የሕዝቤን ወቀሳ ትሸከማለህ
“ሕዝቤ ስለሚወቅስህ መከራን ታያለህ”

Micah 6:16

የዖምሪ ሥርዓትና የአክዓብ ቤት ሥራዎች ሁሉ ተጠብቀዋል
ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል፣ አንተም ዋናውን ቃል የገደፉት በገደፉበት ቦታ ቃላቱን ማሟላት ይኖርብህ ይሆናል። አ.ት፡ “ዖምሪ ያዘዘውን ፈጽመሃል፣ የአክዓብ ቤት ያደረጋቸውን እነዚያኑ ነገሮች አድርገሃል”።

ዖምሪ ... አክዓብ
ሁለቱም ሰዎች የሰሜናዊው የእስራኤል መንግሥት ነገሥታት ነበሩ። እግዚአብሔር ሁለቱም እጅግ ክፉዎች እንደነበሩ ተመልክቶአል።

የአክዓብ ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተ ሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “የአክዓብ ዘሮች”።

በምክራቸው ሄደሃል
በመንገድ ላይ መሄድ አንድ ሰው የሚኖረውን ሕይወቱን የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ዖምሪና አክዓብ ሕዝቡ እንዲያደርጉ የነገሯቸውን አንተ ታደርጋለህ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የፈራረሰ ከተማ አደርግሃለሁ፣ እናንተን ነዋሪዎቿንም የመሳለቂያ ምልክት
ሚክያስ ሊሰማው ለማይቻለው ለከተማው ለራሱ የሚናገር ይመስል ሊሰሙት ለሚችሉት ለከተማይቱ ሰዎች ይናገራል። ዋና ቃል ገዳፊዎች የተውአቸውን ቅላት ግልጽ ማድረግ ይኖርብህ ይሆናል። አ.ት፡ “ከተማህን ፍርስራሽ አደርጋታለሁ፣ እናንተን ነዋሪዎቿንም የመሳለቂያ ምልክት አደርጋችኋለሁ” ወይም “የፈራረሰች ከተማ አደርግሃለሁ፣ የከተማይቱ ነዋሪዎች፣ የሚያዩህም ሁሉ እንዲሳለቁብህ አደርጋለሁ” ወይም “ከተማይቱን ፍርስራሽ አደርጋታለሁ፣ በነዋሪዎቿም ላይ ሰዎች እንዲሳለቁ አደርጋለሁ”።

የሕዝቤን ወቀሳ ትሸከማለህ
“ሕዝቤ ስለሚወቅስህ መከራን ታያለህ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 7

1 ለእኔ ወዮልኝ! የመከር ጊዜ ፍሬ ተሰብስቦ የወይኑም ቃርሚያ ካበቃ በኃላ እርሻ ውስጥ እንደ ቀረው ፍሬ ሆኛለሁ ከዚያ የሚበላ ወይን ፍሬ አይገኝም
የምጓጓለትና ቶሎ ቀድሞ የሚደርሰው በለስ አይኖርም። **2** ከምድሩ ታማኝ ሰዎች ጠፍተዋል በሰው ልጆች መካከልም ቅን ሰው የለም። ሁሉም ደም ለማፍሰስ
ያደባል እያንዳንዱም የገዛ ወንድሙን በመረብ ያጠምዳል። **3** እጆቻቸው ሌሎችን ለመጉዳት ሠልጠነዋል፤ ገዦቻቸው ገንዘብ ይፈልጋሉ ፈራጁ ጉቦ ይጠብቃል፤
ኃይለኞች ያሻቸውን ያስፈጽማሉ ሁሉም አንድ ላይ ያሤራሉ። **4** ከእነርሱ ይሻላል የተባለው እንደ አሜኬላ እጅግ ቀና የተባለውም እንደ ኩርንችት ነው።
ነቢያቶቻችሁ አስቀድመው የተናገሩለት ቀን እናንተ የምትቀጡበት ቀን ነው። የሚሸበሩበት ቀን ደርሶአል። **5** ጐረቤትህን አትመን፣ ወዳጅህም ላይ አትተማመን።
በዕቅፍህ ከምትተኛዋ እንኳ ለምትናገረው ተጠንቀቅ። **6** ወንድ ልጅ አባቱን ያዋርዳል ሴት ልጅ በእናትዋ ላይ ምራት በአማቷ ላይ ትነሣለች። የሰው ጠላቶች
የገዛ ቤተ ሰቦቹ ይሆናሉ። **7** እኔ ግን ያህዌን ተስፋ አደርጋለሁ። የመድኃኒቴን አምላክ እጠብቃለሁ አምላኬም ይሰማኛል። **8** ጠላቴ፣ ሆይ ብወድቅ እንኳ በእኔ
ደስ አይበልሽ፤ ከወደቅሁበት እነሣለሁ በጨለማ ብቀመጥ እንኳ ያህዌ ብርሃን ይሆንልኛል። **9** ያህዌን ስለ በደልሁ እርሱ እስኪፈርድልኝ ድረስ ቁጣውን
እታገሣለሁ። እርሱ ወደ ብርሃን ያወጣኛል በጽድቁ ሲያድነኝም አያለሁ **10** ጠላቴም ታያለች፣ «አምላክህ ያህዌ የታል?» ያለች ጠላቴ ታፍራለች። እኔም የጠላቴን
ውድቀት አያለሁ፤ መንገድ ላይ እንዳለ ጭቃ ትረገጣለች። **11** ቅጥሮቻችሁን የምትሠሩበት ቀን ይመጣል በዚያን ቀን ድንበራችሁ ይሰፋል! **12** በዚያ ቀን
ሕዝባችሁ ወደ እናንተ ይመለሳል፤ ከአሦርና ከግብፅ ከተሞች ከግብፅ እስከ ታላቁ ወንዝ እስከ ኤፍራጥስ ከባሕር እስከ ባህር፣ ከተራራ እስከ ተራራ ድረስ
ሕዝባችሁ ወደ እናንተ ይመለሳል። **13** ከሚኖሩበት ሰዎች ክፋት የተነሣ ምድሪቱ ወና ትሆናለች። **14** በለመለመ መስክ መካከል ብቻቸውን ዱር ውስጥ ያሉትን
የርስትህ መንጋ የሆኑት ሕዝብህን በበትርህ ጠብቅ። እንደ ቀድሞው ዘመን በባሰንና በገለዓድ አሰማራቸው። **15** ከግብፅ እንደ ወጣችሁበት ዘመን ድንቆችን
አሳያቸዋለሁ። **16** ኃይል ያላቸው ቢሆኑም አሕዛብ ይህን አይተው ያፍራሉ፤ እጃቸውን አፋቸው ላይ ያደርጋሉ ጆሮዋቸውም ይደነቁራል። **17** እንደ እባብ፣ ምድር
ላይ እንደሚርመሰመሱም ፍጥረቶች ትቢያ ይልሳሉ። እየተንቀጠቀጡ ከዋሻዎቻቸው ይወጣሉ አምላካችን ያህዌ ሆይ በፍርሃት ወደ አንተ ይመጣሉ ከአንተ
የተነሣ ይሸበራሉ። **18** ኃጢአትን ይቅር የሚል የርስቱንም ትሩፍ መተላለፍ የሚምር እንደ አንተ ያለ አምላክ ማነው? የኪዳን ታማኝነትህን ለእኛ ማሳየት ደስ
ስለሚልህ አንተ ለዘላለም አትቆጣም። **19** እንደ ገና ትራራልናለህ፤ ርኩሰታችንን በእግሮችህ ትረግጣለህ። ኃጢአታችንን ሁሉ ወደ ባሕሩ ጥልቅ ትጥላለህ። **20**
በቀድሞ ዘመን ለአባቶቻችን በመሐላ እንደ ገባኸው ቃል ለያዕቆብ ታማኝነትን፣ ለአብርሃምም የኪዳን ታማኝነትን ትሰጣለህ።

Micah 7:1

በበጋ የተሰበሰበውን ፍሬ፣ የተለቀመውንም ወይን መስያለሁ
ሚክያስ አጫጆች አጭደው ከጨረሱት በኋላ ምግብ የሚሆነውን እንደሚፈልግ ሰው ታማኝ ሰዎችን እንደፈለገ ነገር ግን አንድም ሰው እንዳጣ ይናገራል። ፍሬ ለመሰብሰብ የሚፈልገው ሰው አሳቡ በግልጽ መቀመጥ መቻል አለበት። አ.ት፡ “የበጋው ፍሬ ከተሰበሰበ በኋላ ፍሬ የሚፈልገውን፣ ወይኑ ከተለቀመም በኋላ ቃርሚያውን እንደሚለቅም ሰው መስያለሁ”።

የወይን ዘለላል የለም ... የበሰለው የመጀመሪያ በለስ የለም
ሚክያስ ለመበላት ጥሩ እንደሆነ ፍሬ ታማኝና ትክክለኛ ስለሆኑ ሰዎች ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ታማኞች ሰዎች ከምድሪቱ ጠፍተዋል፤ አንድም ትክክለኛ የሆነ ሰው የለም ... ሁሉም ደም ለማፍሰስ ያደባሉ፤ እያንዳንዱ ያጠምዳል
እነዚህ ግነቶች ናቸው። አ.ት፡ “ታማኞች ሰዎች ከምድሪቱ እንደ ጠፉ ይሰማኛል፣ ትክክለኛ ሰው የለም፣ ሁሉም ደም ... የሚያደቡ ይመስለኛል፣ እያንዳንዱም ያጠምዳል።

ደም ለማፍሰስ
ደም የንጹሐንን ሞት የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ንጹሐን ሰዎችን ለመግደል”

Micah 7:3

እጆቻቸው በጣም ጥሩዎች ናቸው
እጅ የሰው ምሳሌ ነው። አ.ት፡ “ሕዝቡ በጣም ጥሩዎች ናቸው”።

ከእነርሱ እጅግ የተሻለው እንደ አሜከላ ነው፣ እጅግ ትክክለኛው ከእሾኽ ኩርንችት የከፋ ነው
አሜከላና እሾህ ለምንም የማይጠቅሙና የሚነካቸውን የሚጎዱ ናቸው። እስራኤላውያን ገዢዎች እና ፈራጆች አንዳች መልካም አላደረጉም፣ ሕዝቡንም ጎዱት።

እጅግ ትክክለኛው
“ከእነርሱ መልካም የሆነውን ለማድረግ የሚጥሩት”

በጠባቂዎቻችሁ አስቀድሞ የተነገራችሁ፣ የምትቀጡበት ቀን ይህ ነው
ሚክያስ ለእስራኤል ሕዝብ ይናገራል፣ ስለዚህ በሁለቱም ሁኔታ “የእናንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ነው። “ጠባቂ” የሚለው ቃል ነቢያትን የሚመለከት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ነቢያቶቻቸው እግዚአብሔር እንደሚቀጣቸው ነግረዋቸዋል”።

ግራ የሚጋቡበት ሰዓት አሁን ነው
የነገር ስም የሆነው “ግራ የሚጋቡበት” እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “የሚሆነውን ነገር የማይረዱበት ጊዜ አሁን ነው”።

Micah 7:5

የትኛውንም ባልንጀራችሁን አትታመኑ ... የገዛ ቤቱን ሰዎች
ሚክያስ ከእንግዲ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል አንድም ደግ፣ ታማኝና ለእግዚአብሔር የሚገዛ እንደሌለ ማሳየቱን ቀጥሏል። እዚህ ጋ ጓደኞቻቸውን ወይም ቤተ ሰቦቻቸውን መታመን እንደማይችሉ አጽንዖት ይሰጣል።

ምራት በአማቷ ላይ
“ትነሣለች” የሚለው ቃል ቀደም ብሎ ካለው ሐረግ ምን ማለት እንደሆን መረዳት ይቻላል። እዚህም ሊደገሙ ይችላሉ። አ.ት፡ “ምራት በአማቷ ላይ ትነሣለች”።

የገዛ ቤቱ
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩ ቤተ ሰቦችን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “የገዛ ቤተ ሰቡ”

Micah 7:7

አጠቃላይ መረጃ፡
ሚክያስ በቁጥር 8 ላይ አንዲት ሴት ጠላቷ ለሆነች ለሌላይቱ ሴት በምትናገርበት መልኩ መናገር ይጀምራል። ይህቺ ምናልባት የእስራኤል ሕዝብ የምትወክለው፣ “ለወታደሮቹ ሴት ልጅ” የምትናገር (ሚክያስ 5፡1)፣ እስራኤልን ወግተው የነበሩትን አገሮች የምትወክል የጽዮን ሴት ልጅ ትሆን ይሆናል (ሚክያስ 1፡13)። በእንግሊዝኛው “ዩ” ያሉበት ትዕዛዛቱና ምሳሌዎቹ ሁሉ አነስታይ ጾታ ነጠላ ቁጥር ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለእኔ ግን
እዚህ ጋ “እኔ” የሚያመለክተው ሚክያስን ነው።

የድነቴን አምላክ እጠብቃለሁ
“ድነት” የሚለው የነገር ስም እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “የሚያድነኝን እግዚአብሔርን እጠብቃለሁ” ወይም “አዳኙን እግዚአብሔርን እጠብቃለሁ”።

ይሰማኛል
“መስማት” የሚለው ቃል መስማትንና ማድረግን ይወክላል። አ.ት፡ “ሊረዳን ይነሣል”

መውደቅ ...መነሣት
እነዚህ ቃላት በአደጋ ምክንያት መከራንና ከዚያ ማገገምን የሚያመለክቱ ዘይቤአዊ አነጋገሮች ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በጨለማ መቀመጥ
እነዚህ ቃላት በአደጋ ምክንያት መከራ መሠቃየትን የሚያመለክቱ ዘይቤአዊ አነጋገሮች ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Micah 7:9

ቁጣውን እታገሳለሁ
ቁጣ ሚክያስ በእግዚአብሔር ተገዶ እንደ ተሸከመው ጠጣር ነገር ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “እርሱ ስለተቆጣኝ እሰቃያለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ስለ ጉዳዬ እስኪሟገትልኝና እስኪፈርድልኝ ድረስ
የእስራኤልን ሕዝብ የጎዱትን ሌሎች ሕዝቦች እግዚአብሔር ይቀጣቸዋል።

ይሟገትልኛል
እግዚአብሔር በፍርድ ቤት ለሚክያስ እንደሚከላከልለት ሆኖ ተነግሮለታል። አ.ት፡ “ከሚጎዱኝ ያድነኛል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ይፈርድልኛል
“ፍትሕን ያመጣልኛል”

ወደ ብርሃን ያመጣኛል
ሚክያስን ከጨለማ (ሚክያስ 7፡8) ወደ ብርሃን ማምጣት በመከራው ምክንያት መሰቃየቱ ማብቃቱንና በሰላም ሊኖር መቻሉን የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በፍትሑ ይታደገኛል
“ፍትሕን ያመጣልኛል፣ ይታደገኛልም”

Micah 7:10

አጠቃላይ መረጃ፡
ሚክያስ አንዲት ሴት ጠላቷ ለሆነች ለሌላይቱ ሴት በምትናገርበት መልኩ መናገሩን የቀጠለበትንና በምዕራፍ 7፡8 የጀመረውን ግጥም ይጨርሳል። ይህቺ ምናልባት የእስራኤል ሕዝብ የምትወክለው፣ “ለወታደሮቹ ሴት ልጅ” የምትናገር (ሚክያስ 5፡1)፣ እስራኤልን ወግተው የነበሩትን አገሮች የምትወክል የጽዮን ሴት ልጅ ትሆን ይሆናል (ሚክያስ 1፡13)። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አምላክህ ... ያለች ጠላቴ ... ዓይኖቼ
“ጠላቴ”፣ “ያለች”፣ “ያንተ”፣ እና “የእኔ” የሚሉት ቃላት እዚህ ጋ የሚያመለክቱት በግጥሙ ውስጥ ያለችውን ሴት ሲሆን አነስታይ ነጠላ ቁጥር ነው።

አምላክህ እግዚአብሔር ወዴት ነው?
ጠላት በእስራኤል ሕዝብ ላይ ለመሳለቅ በጥያቄ ይጠቀማል። እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “አምላክህ እግዚአብሔር ሊረዳህ አይችልም”።

ዓይኖቼ
በዚህ ስፍራ ቃሉ የሚያመለክተው የሰውን ሁለንተና ነው። አ.ት፡ “እኔ” ወይም “እኛ”።

ትረገጣለች
ይህ በገቢራዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ጠላቶቿ ይረግጧታል”

በመንገድ እንዳለ ጭቃ
አንዳች ክፉ እንደሚያደርጉ ሳያስቡ በጭቃ ላይ እንደሚሄዱ ሰዎች የእስራኤልን ጠላቶች አንዳች ክፉ እንደሚያደርጉ ሳያስቡ ከሚያጠፉ ጋር ተነጻጽረዋል።

Micah 7:11

ቅጥሮቻችሁን የምትሠሩበት ጊዜ ይመጣል
እዚህ ጋ “ቅጥሮች” የሚያመለክተው ከጠላቶቻቸው ጥበቃና ደህንነት ያገኙባቸውን በከተሞቻቸው ዙሪያ ያሉትን ቅጥሮች ነው።

ዳርቻዎችሽ እስከ ሩቅ ድረስ ይስፋፋል
ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ምድርሽን እጅግ ያሰፋዋል” ወይም “እግዚአብሔር የመንግሥትሽን ስፋት እጅግ ያበዛዋል”

ወንዙ
የወንዙን ስም ግልጽ ማድረግ ይኖርብህ ይሆናል። አ.ት፡ “የኤፍራጥስ ወንዝ”

ከባህር እስከ ባህር
የባህሮቹን ስም ግልጽ ማድረግ ይኖርብህ ይሆናል. “በምዕራብ ካለው ከሜዴትራንያን ባህር በስተምስራቅ እስካለው ሙት ባህር ድረስ”

ከተራራ እስከ ተራራ
“ከአንዱ ተራራ እስከ ሌላኛው”። ሚክያስ ስለ አንድ ስለ ታወቀ ተራራ አይናገርም።

ምድሪቱ ባድማ ትሆናለች
“ምድሪቱ ባዶ ትሆናለች” ወይም “በምድሪቱ ላይ ማንም አይኖርም”

በሥራቸው ፍሬ ምክንያት
ፍሬ የቀደመውን ሥራ ውጤት የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ሥራቸው ባስከተለው ውጤት ምክንያት” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Micah 7:14

ሕዝብህን በበትርህ ጠብቅ፣ የርስትህንም መንጋ
ሚክያስ ወገኖቹን የእስራኤልን ሕዝብ እንደገና እንዲጠብቃቸው በመጠየቅ ወደ እግዚአብሔር ይጸልያል። እረኛ በጎቹን ለመጠበቅና ለመምራት አርጩሜ እንደሚጠቀም ሁሉ እዚህ ጋ “በትር” የእግዚአብሔርን መሪነትና ምሪት ሰጪነት ያመለክታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በጥሻ ውስጥ ለብቻቸው ይኖራሉ፣ በለመለመው መስክ መካከል
ሚክያስ የሚመገቡት ብዙ ሣር ባለበት መስክ እንደሚግጡ ከብቶች ሳይሆን በጫካ ውስጥ እንደሚደበቁ የዱር እንስሳት መስሎ ሕዝቡን ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ጥሻ
አንስተኛ እንጨት ያላቸው ዕጽዋት የሚያድጉበት ስፍራ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ባሳንና ገለዓድ
እነዚህ አካባቢዎች የምግብ እህል ለማብቀል ለም መሬት በመሆናቸው ይታወቃሉ

እንደ ቀደመው ዘመን
ዳዊት ንጉሥ በነበረበት ጊዜ፣ ከብዙ ዓመታት በፊት ባሳንና ገለዓድ የእስራኤል ክፍል ነበሩ

እንደ ቀድሞው ... ተአምራትን
እግዚአብሔር ለሕዝቡ ይናገራል።

Micah 7:16

አገሮች
“አገሮች” የሚለው ቃል በብዙ አገሮች የሚኖሩትን ሰዎች የሚመለከት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “በአቅራቢያ ያሉ አገሮች ሕዝቦች” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እጆቻቸውን በአፋቸው ላይ ይጭናሉ
ስላደረጉት ነገር ማፈራቸውን ለማሳየት ይህንን ያደርጋሉ።

ጆሮዎቻቸው ይደነቁራሉ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ማንኛውም ሰው የሚናገረው የትኛውም ነገር በእነርሱ ላይ ለውጥ አያመጣም።

እንደ እባብ አፈር ይልሳሉ
እባቦች አፈር በላያቸው ላይ እንዲሆን መሬቱን ቀድደው ይገባሉ፣ እዚህጋም ምናልባት አፈር መላሳቸው የተጋነነ ቢሆንም ሰዎች ከእባቦች ጋር ተነጻጽረዋል። እነዚህ ሰዎች 1) ቃል በቃል በእፍረት መሬት ላይ ይቀመጣሉ ወይም 2) በመሬት ላይ የተጋደሙ ያህል በእፍረት ይዋረዳሉ የሚሉት ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች ናቸው።

ዋሻዎቻቸው
ሰዎቹ በእንስሳ ተመስለዋል፣ ምክንያቱም በ”ዋሻ” የሚኖሩ እንስሶች ናቸው። አ.ት፡ “ቤቶቻቸው” ወይም “መደበቂያ ስፍራዎቻቸው”

Micah 7:18

ርስታቸውን ... የሚወስድ እንዳንተ ያለ አምላክ ማነው?
ሚክያስ እንደ እግዚአብሔር ያለ ሌላ አምላክ እንደሌለ አጽንዖት ይሰጣል። ይህ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ርስትን ... የሚወስድ እንዳንተ ያለ አምላክ እንደሌለ አውቃለሁ”።

የርስቱን ትሩፋን
“እነዚያ ከቅጣቱ የተረፉ የእርሱ ምርጥ ሕዝቦች”

አንተ ... የርስቱ ትሩፍ? እርሱ በቃል ኪዳን ታማኝነቱ ደስ ስለሚሰኝ ለዘላለም አይቆጣም
እዚህ ጋ “የእርሱ” እና “እርሱ” የሚሉት ቃላት በሁለተኛ መደብ ሊነገሩ ይችላሉ። አ.ት፡ “አንተ ... የርስትህ ትሩፍ፣ ለዘላለም የማትቆጣው በቃል ኪዳን ታማኝነትህ ደስ ስለምትሰኝ ነው?” ወይም “አንተ ... የርስትህ ትሩፍ ነህ? በቃል ኪዳን ታማኝነትህ ደስ ስለሚልህ ለዘላለም አትቆጣም”

በቃል ኪዳን ታማኝነቱ ደስ ይለዋል
“ታማኝነት” የሚለው የነገር ስም “ታማኝ” ተብሎ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ለቃል ኪዳኑ ታማኝ በመሆን ደስ ይለዋል” ወይም “ለሕዝቡ ታማኝ በመሆኑ ደስ ይለዋል”

ያልፈዋል
ይተወዋል

ቁጣውን አይጠብቅም
“ተቆጥቶ አይቆይም”

Micah 7:19

ትፈቅዳለህ
እዚህ ጋ “አንተ” የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው።

በእኛ ላይ
እዚህ ጋ “በእኛ” የሚያመለክተው ሚክያስንና ሕዝቡን እንጂ እግዚአብሔርን አይደለም።

ያለመታመናችንን በእግርህ ሥር ትረግጠዋለህ። ኃጢአታችንን ወደ ባህሩ ጥልቅ ትጥለዋለህ
አለመታመን እና ኃጢአት እንደ ጠጣር ነገር ተቆጥረው ተነግረዋል። አ.ት፡ “አለመታመናችንን እና ኃጢአታችንን ምንም እንዳልሆኑ ቆጥረህ ትቀበለናለህ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Nahum

Nahum

Chapter 1

1 ስለ ነነዌ የተነገረ ቃል፤ የአልቆሻዊው የናሆም ራእይ መጽሐፍ ይህ ነው። 2 ያህዌ ቀናተኛና ተበቃይ ነው፤ ያህዌ የሚበቀል በመዓትም የተሞላ አምላክ ነው። ያህዌ ባላጋራዎቹን ይበቀላል፤ በጠላቶቹም ላይ ቁጣውን ይወርዳል። 3 ያህዌ ለቁጣ የዘገየ፣ በኃይሉም ታላቅ ነው፤ በምንም ዐይነት ጠላቶቹን ንጹሕ ናችሁ አይልም። ያህዌ በወጀብና በዐውሎ ነፋስ ውስጥ መንገድ አለው፤ ደመናም የእግሩ ትቢያ ነው። 4 ባሕርን ይገሥጻል፤ ያደርቀዋልም፤ እርሱ ወንዞችን ሁሉ ያደርቃል። ባሳንና ቀርሜሎስ ጠውልገዋል፤ የሊባኖስ አበቦችም ረግፈዋል። 5 ተራሮች በእርሱ ፊት ተናወጡ፤ ኮረብቶችም ቀለጡ፤ ምድር በፊቱ፣ ዓለምና በውስጧ የሚኖሩ ሰዎችም ሁሉ ተናወጡ። 6 በቁጣው ፊት ማን መቆም ይችላል? ጽኑ ቁጣውንስ ማን መቋቋም ይችላል? መዓቱ እንደ እሳት ፈሰሶአል፤ ዐለቶችም በፊቱ ተሰነጣጠቁ። 7 ያህዌ መልካም ነው፤ በመከራ ጊዜም መሸሸጊያ ነው፤ በእርሱ ለሚታመኑበት ታማኝ ነው። 8 ጠላቶቹን ግን በኃይለኛ ጐርፍ ያጥለቀልቃቸዋል፤ ወደ ጨለማም ያሳድዳቸዋል። 9 እናንተ ሰዎች ያህዌ ላይ የምታሤሩት ምንድነው? እርሱ ፈጽሞ ያጠፋዋል፤ መከራም ዳግመኛ አይነሣም። 10 እንደ እሾኽ ይጠላለፋሉ፤ በወይን ጠጃቸውም ይሰክራሉ፤ እሳት እንደ ገለባ ይበላቸዋል። 11 ነነዌ ሆይ፣ ያህዌ ላይ የሚያሤር፣ ክፉ ምክር የሚመክር ከመካከላችሁ ወጥቷል። 12 ያህዌ እንዲህ ይላል፤ «ጎይለኞችና ቁጥራቸውም እጅግ የበዛ ቢሆን እንኳ ተቆርጠው ይጠፋሉ፤ ከእንግዲህም ሕዝባቸው አይኖም። ይሁዳ ሆይ፣ ከዚህ በፊት ባስጨንቅህም፣ ከእንግዲህ አላስጨንቅህም። 13 አሁንም ቀንበራቸውን ከአንተ ላይ እሰብራለሁ፤ ስንሰለትህንም በጥሼ እጥላለሁ። 14 ነነዌ ሆይ፣ ስለ አንቺ ያህዌ እንዲህ ብሎ አዝዞአል፤ «ስም የሚያስጠራ ትውልድ አይኖራችሁም። የተቀረጹ ምስሎችና ቀልጠው የተሠሩ ጣዖቶችን ከአማልክቶቻችሁ ቤት አጠፋለሁ። እጅግ ክፉ ነህና መቀበሪያህን እምስልሃለሁ። 15 የምሥራችን የሚያመጣና ሰላምን የሚያውጅ ሰው እግር በተራራው ላይ ናቸው! ይሁዳ ሆይ፣ በዓላትህን አክብር፤ ስእለትህንም ፈጽም፤ ከእንግዲህ ክፉዎች አይወርሩህም፤ እነርሱ ፈጽሞ ይጠፋሉ።

Nahum 1:1

አጠቃላይ መረጃ:
ናሆም የነነዌን መጥፋት የሚገልጸው በግጥም ነው (ተመሳሳይነት የሚለውን ተመልከት)

ስለ ነነዌ የተሰጠ መግለጫ። የኤልቆሻዊው የናሆም የራዕይ መጽሐፍ
እነዚህ ቃላት የመጽሐፉ ሁሉ መግቢያ ናቸው። “ይህ ስለ ነነዌ መግለጫ የሚሰጠው የኤልቆሻዊው የናሆም የራዕይ መጽሐፍ ነው” ተብሎ እንደ ሙሉ ዐረፍተ ነገር ሊቀርብ ይችላል። (የተገመተ ዕውቀትና የተሰወረ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ኤልቆሻዊው
ከኤልቆሼ መንደር የሆነ አንድ ሰው (ስሞች እንዴት እንደሚተርጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Nahum 1:2

አጠቃላይ መረጃ:
ናሆም እግዚአብሔር አምላክ በጠላቶቹ ላይ ሊፈርድና የራሱን ሕዝብ ለማዳን እንደሚመጣ በመግለጽ ይጀምራል። ራዕዩ በዘይቤአዊ ቋንቋ የተሞላና የተለያዩ ተመሳሳይነትን የሚጠቀም ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ተመሳሳይነት የሚለውን ተመልከት)

ያህዌ
ይህ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለሕዝቡ የገለጠላቸው የእርሱ ስም ነው። ይህንን እንዴት መተርጎም እንዳለብህ ለማወቅ ስለ ያህዌ የሚተረጎሙ ቃላትን ገጽ ተመልከት።

ቁጣን የተሞላ
“በጣም ተቆጣ”

ለ--- ቁጣውን ይጠብቃል
“በ--- ላይ መቆጣቱን ይቀጥላል”

ለቁጣ የዘገየ
“በቶሎ የማይቆጣ”

አመጸኛውን ሳይቀጣ አይተወውም
ይህ የተጋነነ አሉታዊ አባባል በአዎንታዊነት ሊተረጎም ይችላል። “እርሱ አመጸኛውን ለመቅጣት ሁሌም እርግጠኛ ነው” ማለት ይቻላል። (ንቀት የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር አምላክ በወጀብና በዐውሎ ነፋስ ውስጥ መንገድ አለው፣ ደመናም የእግሩ ትቢያ ነው
የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች አብዛኛውን ጊዜ የእግዚአብሔር አምላክን ሀልዎት ከብርቱ ማዕበል ጋር ያመሳስሉታል። እዚህጋ እግዚአብሔር አምላክ በሰዎች ላይ ለመፍረድ በሚመጣበት ጊዜ በኃይለኛ የነፋስ ማዕበል ተቀምጦ እግሮቹ ትቢያውን በመርገጣቸው ደመናትን ይፈጥራል። (የተገመተ ዕውቀትና የተሰወረ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

የእግሮቹ ትቢያ
“እግሮቹ በመርገጣቸው የሚነሣ ትቢያ”

Nahum 1:4

አጠቃላይ መረጃ:
ናሆም እግዚአብሔር አምላክ በጠላቶቹ ላይ ለመፍረድና የራሱን ሕዝብ ለማዳን ስለ መምጣቱ መግለጹን ቀጥሏል።

ባሳን ደክሟል፣ ቀርሜሎስም እንዲሁ፤ የሊባኖስ አበቦችም ጠውልገዋል
“ደክሟል” ተብሎ የተተረጎመው ቃል “ጠውልጓል” ወይም “ደርቋል” ማለት ሊሆን ይችላል። ባሳን ሰዎች በጎቻቸውንና ከብቶቻቸውን የሚያሰማሩበት የታወቀ የግጦሽ መሬት ነበር። “ቀርሜሎስ” የቀርሜሎስን ተራራ የሚያመለክት ሲሆን በተክል ዛፎች ይታወቃል፣ ከሊባኖስ ተራሮች የሚወርድበት በረዶ አካባቢው ለምነቱን ጠብቆ እንዲቆይ አድርጎታል። እግዚአብሔር አምላክ ወንዞቹን ሁሉ ስለሚያደርቃቸውና ድርቅን ስለሚያመጣባቸው እነዚህ ለም መሬቶች በለምነታቸው አይቀጥሉም። አ.ት: “የባሳን እርሻዎች ይጠወልጋሉ፣ የቀርሜሎስ ተራራ ዛፎች ይደርቃሉ፣ የሊባኖስ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አበቦችም ይጠወልጋሉ”። (የተገመተ ዕውቀትና የተሰወረ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ኮረብቶች ቀለጡ
አማራጭ የሚሆኑ ትርጉሞች 1) ኮረብቶች እንደ ቀለጡ የተነገረው በመሬት መንቀጥቀጥ ምክንያት ኮረብቶቹ ተገልብጠው ብትንትናቸው በመውጣቱ ወይም 2) ኮረብቶች እንደ ቀለጡ የተነገረው የውሃው ማዕበል በኮረብቶቹ ላይ በሚወርድበት ጊዜ ስለ ሸረሸራቸው ይሆናል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ምድር ትፈርሳለች
1) ተራሮችና ኮረብቶች ይፈርሳሉ ወይም 2) መላው ምድር በኃይል ይናጣል የሚሉት አማራጭ ትርጉሞች ናቸው።

ዓለምና የሚኖሩባት ሰዎች ሁሉ
እዚህ ጋ “ዓለም” የሚለው ቃል በምድር ላይ ሰዎች የሚኖሩበትን ስፍራ ያመለክታል። (መገደፍ የሚለውን ተመልከት)

Nahum 1:6

አጠቃላይ መረጃ፡
ናሆም እግዚአብሔር አምላክ በጠላቶቹ ላይ ለመፍረድና የራሱን ሕዝብ ለማዳን ስለ መምጣቱ መግለጹን ቀጥሏል።

በቁጣው ፊት ማን ይቆማል? የቁጣውንስ ትኩሳት ማን ሊቋቋም ይችላል?
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት የማሳመኛ ጥያቄዎች ትርጉማቸው ተመሳሳይ ነው። በሚከተለው መሠረት ሊተረጎሙ ይችላሉ፤ አ.ት፡ “በቁጣው ፊት ማንም ሊቆም አይችልም! የቁጣውን ትኩሳት ማንም ሊቋቋም አይችልም!” (ተመሳሳይነት እና የማሳመኛ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

የቁጣው ትኩሳት
“የቁጣው ብርታት” ወይም “የቁጣው መጠን”

ቁጣው እንደ እሳት ፈሰሰ
ናሆም የእግዚአብሔርን ቁጣ እንደሚፈስ ፈሳሽና እንደሚያቃጥል እሳት አድርጎ ይናገራል። አ.ት “ቁጣውን እንደ እሳት ያፈሰዋል” ወይም “የቁጣውን ትኩሳት ይገልጣል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ዐለቶችን ይሰባብራቸዋል
ይህ በገቢራዊነት ሊገለጽ ይችላል። አ.ት፡ “ዐለቶችን ይሰባብራቸዋል” ወይም “ዐለቶቹን እንዲሰባበሩ ያደርጋቸዋል” (ገቢራዊ ወይም ተገብሮአዊ የሚለውን ተመልከት)

Nahum 1:7

መሸሸጊያ. . . በእርሱ የሚታመኑትን
ናሆም እግዚአብሔርን ሰዎች ሊጎዱአቸው ከሚፈልጉት እንደሚደበቁበት ስፍራና በእርሱ የሚታመኑትን በዚያ አስተማማኝ ስፍራ ከለላ እንደሚሰጣቸው መስሎ ይናገራል (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በመከራ ቀን
“በመከራ ጊዜ” ወይም “መከራ በሚመጣበት ጊዜ”። እዚህ ጋ “ቀን” የሚለው ቃል አጠቃላዩን ጊዜ ያመለክታል።

ጠላቶቹን ፈጽሞ ያጠፋቸዋል
“ፈጽሞ ያጠፋቸዋል” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ጠላቶቹ እንዲሞቱ እንደሚያደርጋቸው ያመለክታል። አ.ት፡ “ጠላቶቹን ሙሉ በሙሉ ያጠፋቸዋል” ወይም “ጠላቶቹን ሁሉ ይገድላቸዋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በሚያጥለቀልቅ ጎርፍ
እግዚአብሔር ጠላቶቹን በታላቅ የጥፋት ጎርፍ እንደሚያሰጥማቸውና ከሞት ማምለጥ እንዳይችሉ እንደሚያደርጋቸው ናሆም ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ወደ ጨለማ ያሳድዳቸዋል
እዚህ ጋ “ጨለማ” የሚለው ቃል የሙታን መኖሪያ የሆነውን ጨለማ ስፍራ ይወክላል። እግዚአብሔር ጠላቶቹን ወደዚህ ጨለማ ስፍራ እያሳደደ እንደሚገድላቸው ናሆም ይናገራል። አ.ት፡ “ጠላቶቹ ሁሉ እንዲሞቱ ያደርጋቸዋል” (ፈሊጣዊ እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Nahum 1:9

አጠቃላይ መረጃ፡
እግዚአብሔር ምን ሊያደርግባቸው እንዳለ ናሆም ለነነዌ ሕዝብ ይነግራቸዋል

እናንተ ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ የምታሤሩት ምንድነው?
ይህ የማሳመኛ ጥያቄ በእግዚአብሔር ላይ የሚታቀደው ክፉ ዕቅድ ከንቱ መሆኑ ላይ አጽንዖት ይሰጣል። አ.ት፡ “እናንተ ሰዎች፣ በእግዚአብሔር ላይ ማሤራችሁ ከንቱ ነው” (የማሳመኛ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ፈጽሞ ያጠፋል
“ፈጽሞ ያጠፋል” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር አንድ ነገር ዳግመኛ እንዳይኖር እንደሚያደርግ ያመለክታል። አ.ት፡ “የምታደርጉትን ሙሉ በሙሉ ያስቆማችኋል” ወይም “ሤራችሁ እንዲከሽፍ ያደርጋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መከራ ዳግመኛ አይነሣም
1) “መከራ” እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ የሚፈጽመውን ቅጣት የሚያሳይ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ዳግመኛ አይቀጣችሁም” ወይም 2) “መከራ” ሕዝቡ በእግዚአብሔር ላይ በማሤር የሚፈጥሩትን ችግር ያመለክታል። አ.ት፡ “ዳግመኛ ችግር አትፈጥሩም” አማራጭ ትርጉሞች ናቸው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ትመልከት)

እንደ እሾህ ቁጥቋጦ ይጠላለፋሉ
1) አንድ በእሾህ ቁጥቋጦ የተጠላለፈ ሰው ራሱን በቀላሉ ማላቀቅ እንደማይቻለው ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ የሚያሤሩ ሰዎችም እርሱ ከሚያመጣባቸው መከራ ራሳቸውን ማስመለጥ አይቻላቸውም ወይም 2) ልክ የእሾህ ቁጥቋጦዎችን በአንድ ላይ ሲያከማቿቸው ፈጥነው እንደሚነዱ እንደዚሁ እግዚአብሔር በእርሱ ላይ የሚያሤሩትን ፈጥኖ ያጠፋቸዋል የሚሉት ለዚህ ዘይቤአዊ አነጋገር አማራጭ ትርጉሞች ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በገዛ መጠጣቸው ይበከላሉ
በሚያሰክር መጠጥ እጅግ እንደ ሰከሩ ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ የሚያሤሩ በዕቅዳቸው ምክንያት ሥቃይ እንደሚደርስባቸው ናሆም ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እንደ ደረቅ ገለባ በእሳት ይነድዳሉ
እሳት የደረቀውን ገለባ እንደሚያነደው እግዚአብሔርም በእርሱ ላይ ያሤሩትን እሳት በሚያነድዳቸው መልኩ ፈጽሞ እንደሚያጠፋቸው ናሆም ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ገቢራዊ ወይም ተገብሮአዊ የሚለውን ተመልከት)

በእሳት ይነድዳሉ
ናሆም ልክ እሳት አንድን ነገር እንደሚያነድደው ፈጽሞ ስለሚያቃጥለው እሳት ይናገራል (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ክፋትን አበረታተዋል
ሰዎች ክፉ ነገሮችን እንዲያደርጉ አበረታተዋቸዋል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Nahum 1:12

አጠቃላይ መረጃ፡
እግዚአብሔር ስለ ነነዌ ለእስራኤላውያን ይነግራቸዋል

ብርቱዎችና ብዙዎች ቢሆኑም እንኳን
ይህ አሦራውያንን ወይም የነነዌን ሰዎች ያመለክታል

የሆነው ሆኖ ይሸለታሉ
እግዚአብሔር እንደሚሸልታቸው በጎች የነነዌን ሰዎች እንደሚያጠፋቸው ይናገራል። ይህ በገቢራዊነት ሊገለጽ ይችላል። አ.ት፡ “የሆነው ሆኖ እሸልታቸዋለሁ” ወይም “የሆነው ሆኖ አጠፋቸዋለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ገቢራዊ ወይም ተገብሮአዊ የሚለውን ተመልከት)

አሁን የዚያን ሕዝብ ቀንበር ከአንተ ላይ እሰብራለሁ፤ ሰንሰለቶችህንም እበጥሳለሁ
አሦራውያን የጫኑባቸውን ቀንበርና ሰንሰለት በሚሰብርበት መልኩ እግዚአብሔር ይሁዳን ከአሦር ጭቆና ነጻ እንደሚያወጣቸው ይናገራል (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Nahum 1:14

የተቀረጹትን ምስሎችና ቀልጠው የተሠሩትን ምስሎች ከአማልክቶችህ ቤት አጠፋለሁ
አንድ ሰው ቅርንጫፍን ከዛፉ ላይ እንደሚሰብር እግዚአብሔር የአሦራውያንን አማልክት በመሰባበር እንደሚያጠፋ ይናገራል። “ቤት” የሚለው ቃል ሕዝቡ እነዚህን ጣዖታት የሚያመልኩባቸውን መቅደሶች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “በአማልክቶቻችሁ መቅደስ ያሉትን የተቀረጹትንና ቀልጠው የተሠሩትን ምስሎች አጠፋለሁ” (ዘይቤአዊ እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መቃብራችሁን እቆፍራለሁ
ደግሞም እግዚአብሔር በሚቆፍርላቸው መቃብር ውስጥ የሚቀብራቸው ይመስላል። አ.ት፡ “መቃብር እቆፍርላችሁና በዚያ ውስጥ እቀብራችኋለሁ” (የተገመተ ዕውቀትና የተሰወረ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

Nahum 1:15

የምሥራችን የሚያመጣ ሰው እግሮች በተራሮች ላይ ናቸው
እዚህ ጋ “እግሮች” አንድን መልዕክት ለማስታወቅ የሚሮጥን ሰው ይወክላል። አ.ት፡ “የምሥራችን የሚያመጣ አንድ ሰው በተራሮች ላይ ነው”። (ምሳሌአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ክፉው . . . እርሱ
ናሆም የነነዌን ሕዝብ እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይገልጻቸዋል።

እርሱ ፈጽሞ ተቆርጧል
አንድ ሰው ቅርንጫፍን ከዛፍ ላይ እንደሚቆርጥ የነነዌ ሕዝብ በመቆረጥ ፈጽመው እንደሚጠፉ ናሆም ይናገራል። ይህ በገቢራዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ፈጽሞ ጠፍቷል” ወይም “እግዚአብሔር ፈጽሞ አጥፍቶታል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ገቢራዊ ወይም ተገብሮአዊ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 እስክትደቅቂ ድረስ የሚረግጥሽ እርሱ እየመጣ ነው። ስለዚህ ምሽጐችሽን አጠናክሪ መንገድሽን ጠብቂ፤ ወገብሽን ታጠቂ፤ ኃይልሽን ሁሉ አሰባስቢ። **2** አጥፊዎች ባድማ ቢያደርጓቸውም፣ የወይን ተክል ቦታቸውን ቢያጠፉባቸውም እንደ እስራኤል ክብር ሁሉ ያህዌ የያዕቆብንም ክብር ይመልሳል። **3** የወታደሮቹ ጋሻ ቀይ ነው፣ ተዋጊዎቹም ሐምራዊ ልብስ ለብሰዋል ዝግጁ በሆኑበት ቀን የሰረገሎቹ ብረት ያብረቀርቃል የጦሩ ዘንግ ይወዛወዛል። **4** ሰረገሎቹ በየመንገዱ ይከንፋሉ፤ ሰፋፊ በሆኑት መንገዶች በፍጥነት ወዲያ ወዲህ ይላሉ። የሚንቦገቦግ ችቦ ይመስላሉ፤ እንደ መብረቅም ይወረወራሉ። **5** እስክትደቂ ድረስ የሚረግጥሽ እርሱ የጦር ሹማምንቱን ይጠራል እነርሱም እየተደነቃቀፉ ወደ ፊት ይመጣሉ፣ ለማጥቃት ወደ ከተማ ቅጥር ይወጣሉ፤ የሚወረወርባቸውን ፍላጻ በትልቁ ጋሻቸው ይከላከላሉ። **6** በወንዙ በኩል ያሉ በሮች ወለል ብለው ይከፈታሉ ቤተ መንግሥቱም ተደመሰሰ። **7** ንግሥቲቱ ተማርካ ዕርቃኗን ተወሰደች ሴት አገልጋዮቿ ደረታቸውን እየደቁ እንደ ርግብ ያላዝናሉ። **8** ነነዌ ውሃ መያዝ እንደማይችል ኩሬ ናት፤ ሕዝቧም እንደ ፈጣን ወራጅ ውሃ ፈጥኖ ይሸሻል። ሌሎች «ቁሙ ቁሙ» ብለው ይጮኻሉ ዞር ብሎ የሚያይ ግን የለም። **9** የነነዌ ሀብት ስፍር ቁጥር የለውም የከበሩ ድንጋዮቿ የተትረፈረፉ ናቸው ስለዚህ ብሩን ዝረፉ፣ ወርቁንም ንጠቁ። **10** ነነዌ ባዶ ሆነች፣ ተራቆተች። የሰዎች ልብ ቀለጠ፤ የሰው ሁሉ ጉልበት ተብረከረከ ሁሉም ተጨንቀዋል፤ ፊታቸው ገርጥቷል። **11** የአንበሶች ዋሻ፣ የአንበሳ ደቦሎች የሚመገቡበት፣ ወንድ አንበሳና እንስት አንበሳ ምንም ሳይፈሩ ወዲያ ወዲህ ይሉበት የነበረ ቦታ የታል? **12** አንበሳ ለግልገሎቹ የሚበቃውን ያህል ገደለ፤ ለእንስቶቹ የሚበቃውንም ያህል አድኖ ያዘ የገደለውን በዋሻው፣ የነጠቀውንም በመኖሪያ ቦታው ሞልቶአል። **13** የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል፤ ሰረገሎችን አቃጥላለሁ፤ ደቦል አንበሶችህን ሰይፍ ይበላቸዋል። የዘረፍኸውን ከምድርህ አጠፋለሁ፤ ከእንግዲህ የመልእክተኞችህ ድምፅ አይሰማም።»

Nahum 2:1

አጠቃላይ መረጃ:
ናሆም አብዛኛውን ጊዜ ትንቢቱን በግጥም መልክ ይጽፋቸው ነበር። የዕብራይስጡ ግጥም የተለያዩ ተመሳሳይነቶችን ይጠቀማል። እዚህ ጋ የነነዌን መጥፋት መተረክ ይጀምራል። (ግጥም እና ተመሳሳይነት የሚለውን ተመልከት)

አንቺን ረጋግጦ የሚያደቅሽ እርሱ
“አንቺ” የሚለው ቃል ነነዌን ያመለክታል። ናሆም የሸክላ ማሰሮን እንደሚሰባብር ነነዌን በመሰባበር ስለሚያጠፋ ሰራዊት ወይም ወታደራዊ መሪ ይናገራል። አ.ት: “አጥፊሽ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አንቺን የሚረጋግጥሽ እርሱ
“እርሱ” የተባለው ሰው ግልጽ አይደለም፣ ስለዚህ የወል ቃል በመጠቀም ተርጉም። አ.ት: “አንድ አንቺን የሚሰባብርሽ”

በአንቺ ላይ እየመጣ ነው
“በአንቺ ላይ ይመጣል” የሚለው አነጋገር ሊያጠቃሽ ማለት ነው። አ.ት: “ሊያጠቃሽ ተዘጋጅቷል” (አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በከተማው ቅጥር ላይ ሰዎችን አቁሚ፣ መንገዶችሽን ጠብቂ፣ ራስሽን አበርቺ፣ ሰራዊትሽን ሰብስቢ
ናሆም ለነነዌ ሕዝብ ይናገራል። ጠላት ከተማይቱን እንደሚያጠፋት ቢያውቅም ለጦርነት እንዲዘጋጁ ይነግራቸዋል። (ምጸት የሚለውን ተመልከት)

በከተማው ቅጥር ላይ ሰዎችን አቁሚ
ነነዌ የሚከባት ሰፊና ጠንካራ ቅጥር ነበራት። ይህ አጥቂዎችን ለመዋጋት ወታደሮችን በግምቡ ጫፍ ላይ ማስፈር መቻላቸውን ያመለክታል። አስፈላጊ ከሆነ ይህንን ጠቅለል ባለ ሐረግ መተርጎም ይቻላል። አ.ት: “በምሽጎችሽ ላይ ሰው አኑሪ” ወይም “መከላከያሽን አዘጋጂ” (የተገመተ ዕውቀትና የተሰወረ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

መንገዶችሽን ጠብቂ
ይህ ጠላት እንዳይቀርባቸው ለመከላከል ወደ ከተማይቱ የሚወስደውን መንገድ በወታደሮች ማስጠበቅን ያመለክታል።

ራስሽን አበርቺ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙም ራስን ለተግባር ማዘጋጀት ማለት ነው። እዚህ ጋ ቃሉ ለወታደራዊ ተግባር ጥቅም ላይ ውሏል። አ.ት: “ራስሽን ለጦርነት አዘጋጂ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር እንደ እስራኤል ግርማ ሁሉ የያዕቆብን ግርማ ያድሳል
“ያዕቆብ” እና “እስራኤል” የሚሉት ቃላት ከያዕቆብ ለተወለዱት ሕዝቦች ጥቅም ላይ የዋለ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አማራጭ ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፣ 1) “ያዕቆብ” የሚለው ቃል የደቡቡን መንግሥት እና “እስራኤል” የሚለው የሰሜኑን መንግሥት ያመለክታል። አ.ት: “የእስራኤልን ግርማ ለማደስ ቃል እንደገባ ሁሉ የይሁዳንም ግርማ ያድሳል” ወይም 2) “ያዕቆብ” እና “እስራኤል” ሁለቱም የሚያመለክቱት የሰሜኑና የደቡቡ መንግሥት ተደምረውና ሁለቱ የግጥም መስመሮች ተመሳሳይ ሆነው መላውን ሕዝብ ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ተመሳሳይነት የሚለውን ተመልከት)

ዘራፊዎቹ
በተለይ በጦርነት ጊዜ አንዳንድ ነገሮችን በኃይል አስገድደው የሚሰርቁ ሰዎች

የወይን ቅርንጫፎቻቸውን አጥፍተዋል
አማራጭ የሚሆኑት ትርጉሞች 1) እስራኤል ቅርንጫፎቹን አሦራውያን ገነጣጥለው ባዶውን እንዳስቀሩት ወይን አሦራውያን ንብረታቸውን አስገድደው መውሰዳቸውን የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት: “ያለ ቅርንጫፍ እንደ ቀረ ወይን ንብረታቸውን ዘርፈዋቸዋል” ወይም 2) “የወይን ቅርንጫፎች” የሚሉት ቃላት በየአገራቱ ለእርሻ በሚውሉ መስኮች ላይ ናቸው። አ.ት: “የሰብል ማሳዎቻቸውን አጠፉ” (ዘይቤአዊ እና ምሳሌአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Nahum 2:3

የኃያላኑ ጋሻ ቀይ ነው
አማራጭ ትርጉሞቹ 1) ጋሻዎቹ በብረት ገጽታቸው ላይ የፀሐይ ብርሃን በሚያንጸባርቅበት ጊዜ ቀልተው ይታያሉ ወይም 2) ጋሻዎቹ በቀይ ቀለም በተነከሩ ቆዳዎች የተሸፈኑ ናቸው።

ኃያላኑ
ነነዌን “የሚረጋግጡ” እና “ብትንትኗን የሚያወጡ” ወታደሮች ናቸው (ናሆም 2:1)

ሰረገሎቹ በብረቶቻቸው ያብረቀርቃሉ
ይህ የሚያመለክተው ከብረት በተሠሩት ሰረገላዎች ላይ የፀሐይ ብርሃን ማንጸባረቁን ሳይሆን አይቀርም።

እንዲዘጋጁ በተደረጉበት በዚያን ቀን
ይህ በገቢራዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት: “ወታደሮቹ ባዘጋጇቸው ጊዜ” ወይም “ወታደሮቹ እንዲዋጉ ባዘጋጇቸው ጊዜ”። (ገቢራዊ ወይም ተገብሮአዊ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እጀታቸው ከጥድ መሳይ ዛፍ የተሠሩ ጦሮች በአየር ላይ ይወዛወዛሉ
ይህ በገቢራዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ወታደሮቹ ጦራቸውን በአየር ላይ ያወዛውዛሉ” (ገቢራዊ ወይም ተገብሮአዊ የሚለውን ተመልከት)

ጥድ መሳይ ዛፍ
እንጨቱ ለጦር መሳሪያነት የሚመረጥ የዛፍ ዓይነት ነው። (ያልታወቁትን መተርጎም የሚለውን ተመልከት)

ሰረገሎቹ በየጎዳናው ይፈጥናሉ
“ወታደሮቹ ሰረገላዎቹን በጎዳናዎቹ ላይ በስድነት ይነዷቸዋል”

ፋና ይመስላሉ
ናሆም በሰረገላዎቹ ላይ የሚንጸባረቀውን የፀሐይ ብርሃን የእሳት ብርሃን ከሚሰጠው ፋና ጋር ያነጻጽረዋል። (ተነጻጻሪ የሚለውን ተመልከት)

እንደ መብረቅ ይሮጣሉ
ናሆም በሰረገላዎቹ ላይ የሚንጸባረቀውን የፀሐይ ብርሃንና ሰረገላዎቹ የሚያደርጉትን ፈጣን እንቅስቃሴ በሰማይ ላይ በፍጥነት ከሚንጸባረቀው መብረቅ ጋር ያነጻጽራል። (ተነጻጻሪ የሚለውን ተመልከት)

Nahum 2:5

አንቺን ረጋግጦ የሚያደቅሽ እርሱ
“አንቺ” የሚለው ቃል ነነዌን ያመለክታል። ናሆም የሸክላ ማሰሮን እንደሚሰባብር ነነዌን በመሰባበር ስለሚያጠፋ ሰራዊት ወይም ወታደራዊ መሪ ይናገራል። ይህንን በናሆም 2፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የሚያጠፋሽ እርሱ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በዘመቻቸው
(የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

እነዚህን ተዋጊዎች ለመከላከል ታላቁ ጋሻ ተዘጋጅቷል
ይህ በገቢራዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ተዋጊዎቹ ራሳቸውን ለመከላከል ታላቁን ጋሻ ያዘጋጃሉ” (ገቢራዊ ወይም ተገብሮአዊ የሚለውን ተመልከት)

ታላቁ ጋሻ
ይህ በከተማው ውስጥ ያሉት ሰዎች እነርሱን ለማጥቃት ከሚወነጭፏቸው ቀስቶችና ሌሎች ተስፈንጣሪዎች ራሳቸውንና መስበሪያ መሣሪያዎቻቸውን ለመከላከል ከተማውን የከበቡት ሰዎች በፊት ለፊታቸው የሚያደርጉትን ታላቅ መከላከያ ያመለክታል።

Nahum 2:6

የወንዞቹ በሮች ወለል ብለው ተከፈቱ
ይህ በገቢራዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ጠላት የወንዞቹ በሮች እንዲከፈቱ ያስገድዳል” (ገቢራዊ ወይም ተገብሮአዊ የሚለውን ተመልከት)

የወንዞቹ በሮች
ይህ የሚያመለክተው የወንዙን ፍሰትና አቅጣጫ የሚቆጣጠሩትን በሮች ነው።

ሁዛብ ልብሷን ተገፈፈችና ተወሰደች
ይህ በገቢራዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ጠላት የሁዛብን ልብስ ይገፍና ይወስዳታል” (ገቢራዊ ወይም ተገብሮአዊ የሚለውን ተመልከት)

ሁዛብ ልብሷን ተገፈፈችና ተወሰደች
“ሁዛብ” የሚለው ቃል ትክክለኛ ትርጉም በእርግጠኝነት አይታወቅም። ትርጉሞች ሊሆኑ የሚችሉ ሁለቱ፣ 1) በነነዌ የነበረች ንግሥት ስም ይሆንና ዐረፍተ ነገሩ የሚለው አጥቂዎቹ ወታደሮች እርሷን ለማዋረድ ልብሶቿን እንድታወልቅ በማድረግ ወደ ምርኮ ወስደዋታል ወይም 2) የጣዖት ስም ይሆንና ዐረፍተ ነገሩ አጥቂዎቹ ወርቅና ብሩን ከጣዖቱ ላይ በመግፈፍ ወስደውታል ማለት ሊሆን ይችላል። (ያልታወቁትን ተርጉም እና የተገመተ ዕውቀትና የተሰወረ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ሴቶች አገልጋዮቿ እንደ ዕርግብ ያለቃቅሳሉ
የሴት አገልጋዮቹ የሚያሰሙት የልቅሶ ድምፅ ዕርግቦቹ የሚያሰሙትን ድምፅ ይመስላል።

ሴት አገልጋዮቿ
“ሁዛብ” የሚለው ቃል ንግሥቲቱን የሚያመለክት ከሆነ እንግዲያው ይህ ሐረግ የሚጠብቋትን ወጣት ሴቶች ያመለክታል። “ሁዛብ” የሚለው ቃል ጣዖትን የሚያመለክት ከሆነ ይህ ሐረግ የመቅደስ ዝሙት አዳሪ ወጣት ሴቶችን ያመለክታል።

ደረታቸውን እየደቁ
የአንድ ሰው ደረት መደቃት ታላቅ ለቅሶን የሚያመለክት እንቅስቃሴ ነው። (ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ተመልከት)

Nahum 2:8

ነነዌ እንደሚያፈስ የኩሬ ውሃ ናት፣ ሕዝቧም እንደ ውሃ ፈሳሽ ይሸሻል
ናሆም ሕዝቡ ከነነዌ ከተማ የሚሸሽበትን ሁኔታ ግድብ በሚፈርስበት ጊዜ ውሃው ከማከማቻው ጎርፎ ከመውረዱ ጋር ያነጻጽረዋል። (ተነጻጻሪ የሚለውን ተመልከት)

ብሯን በዝብዙ. . . የነነዌን የተዋቡ ነገሮች
እዚህ ጋ ተናጋሪው ማን እንደሆነ ግልጽ አይደለም። ይህ ምናልባት ናሆም ለተዋጊዎቹ አቅጣጫ የሚሰጥበት ይሆን ይሆናል ወይም ምናልባት ተዋጊዎቹ ለእርስ በእርሳቸው አቅጣጫ የሚሰጡበትና የሚነጋገሩበት ሊሆን ይችላል። (ምናባዊውን ሰው መናገር የሚለውን ተመልከት)

ብሩን በዝብዙ፣ ወርቁን በዝብዙ
“በዝብዙ” የሚለው ቃል በማስገደድ የሚሰረቁ ነገሮች፣ አብዛኛውን ጊዜ በጦርነት ወቅት ማለት ነው። አ.ት፡ “ብሩን በብዝበዛ ውሰዱ፣ ወርቁን በብዝበዛ ውሰዱ” ወይም ”ብሩን ውሰዱ፣ ወርቁን ውሰዱ”

ለእርሱም ማብቂያ የለውም
“ማብቂያ የለውም” የሚሉት ቃላት አንድ ነገር በብዛት መኖሩን ለመግለጽ የተነገረ ግነት ነው። አ.ት፡ “እጅግ ብዙ አለ” (ግነት እና ማጠቃለያ የሚሉትን ተመልከት)

የነነዌ የተዋቡ ነገሮች ክብር ሁሉ
ይህ ሐረግ በነነዌ የነበረውን ብር፣ ወርቅ፣ እና ሌሎች ሀብቶች ያመለክታል። ግሱ ምናልባት ቀደም ካለው ሐረግ ሊወሰድ ይችላል። አ.ት፡ “ለነነዌ የተዋበ ሀብት ሁሉ ለክብሩ ማብቂያ የለውም” (መግደፍ የሚለውን ተመልከት)

የእያንዳንዱ ልብ ይቀልጣል
ናሆም ልክ ልባቸው እንደ ሰም የቀለጠ ይመስል ሕዝቡ አቅም እንዳጣ ይናገራል። አ.ት፡ “እያንዳንዱ አቅም አጥቷል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የእያንዳንዱ ጉልበት ይብረከረካል
ይህ በታላቅ ፍርሃት ምክንያት የሚፈጠረውን አካላዊ ምላሽ ያሳያል። የሕዝቡ እግር ያለ መጠን በመንቀጥቀጡ ጉልበቶቻቸው ስለሚጋጩ መራመድም ሆነ መሮጥ አይችሉም።

Nahum 2:11

አጠቃላይ መረጃ፡
በእነዚህ ቁጥሮች ናሆም የነነዌን ሕዝብ በአንበሳ መንጋና የነነዌን ከተማም በአንበሶች ዋሻ መስሎ ይናገራል። ዘይቤአዊው አነጋገር አንበሶች አደን አድነው የገደሏቸውን እንስሶች ወደ ዋሻቸው እንደሚያመጡ አሦራውያን ሕዝቡን ድል

እንደሚያደርጉና ሀብታቸውን የራሳቸው አድርገው እንደሚወስዱ ያሳያል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አንዳች የማይፈሩት. . . የአንበሶቹ ዋሻ ወዴት ነው?
ናሆም በምትጠፋዋ በነነዌ ላይ ለመሳለቅ የማሳመኛ ጥያቄን ይጠቀማል። አ.ት፡ “አንዳች የማይፈሩት. . . የአንበሶቹ ዋሻ የትም አይገኝም” ወይም “አንዳች በማይፈሩት. . . የአንበሶች ዋሻ ላይ የሆነውን ተመልከቱ!”። (የማሳመኛ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ንጥቂያውን አነቀው
“ንጥቂያውን አፈነው” ይህ አንበሶች አብዛኛውን ጊዜ የሚያድኑትን እንስሳ ጉሮሮውን በመንከስ የሚገድሉበትን ሁኔታ ያመለክታል። አ.ት፡ “የነጠቀውን ገደለው” (የተገመተ ዕውቀትና የተሰወረ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ዋሻውን በንጥቂያው ሞልቶታል፣ መኖሪያውንም በእንስሳቱ ቁርጥራጭ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳዩን ነገር በተለያየ መንገድ የሚናገሩ ናቸው። ለሁለተኛው ሐረግ ምናልባት ግስ መጨመር ይኖርበታል። አ.ት፡ “ዋሻውን በንጥቂያው ሞልቶታል፣ መኖሪያውንም በእንስሳቱ ቁርጥራጭ ሞልቶታል”። (ተመሳሳይነት እና መግደፍ የሚለውን ተመልከት)

Nahum 2:13

እነሆ፣ እኔ በእናንተ ላይ ነኝ
እዚህ ጋ እግዚአብሔር መናገር ይጀምራል

እነሆ
“ተመልከቱ” ወይም “አድምጡ” ወይም “የምነግራችሁን ልብ በሉ”።

ደቦል አንበሶቻችሁን ሰይፍ ይበላቸዋል
እዚህ ጋ “ሰይፍ” የሚለው ቃል በሰይፍ የሚዋጉትን ወታደሮች የሚያመለክት ሲሆን ንጥቂያውን ሰው እንደሚበላው ዓይነት ተደርጎ ተነግሯል። ናሆም ደግሞ የነነዌን ሕዝብ እንደ አንበሶች በመቁጠር መናገሩን ቀጥሏል። አ.ት፡ “ተዋጊዎች ሰዎቻችሁን በሰይፍ ይገድላሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር፣ ሰውኛ እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የምትገድሉትን እንስሳ ከምድራችሁ አጠፋለሁ
እግዚአብሔር ሕዝቦችን በሚያድኑ አንበሶች ስለተመሰሉት የነነዌ ሰዎች ይናገራል። አማራጭ የሚሆኑት ትርጉሞች፣ 1) “የሚገደል እንስሳ” የሚሉት ቃላት ካጠቋቸው ላይ የወሰዷቸውን ነገሮች የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ሲሆን የሚገድሉትን እንስሳ እንደሚያጠፋባቸው ሁሉ እግዚአብሔር እነዚያን ነገሮች ከእነርሱ እንደሚወስድባቸው ይናገራል ወይም 2) ታዳኞቻቸው የሆኑ ይመስል የነነዌ ሕዝብ ስለበዘበዟቸው ሕዝቦች እግዚአብሔር ይናገራል፣ እርሱ የሚገድሉትን እንስሳ በሚያጠፋባቸው መልኩ በተጨማሪ ሌሎች ሕዝቦችን እንዳይበዘብዙ ይከለክላቸዋል። አ.ት፡ “ሌላ የትኛውንም ሕዝብ እንዳትገድሉ እከለክላችኋለሁ”። (ዘይቤአዊ እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከእንግዲህ የመልዕክተኞቻችሁ ድምፅ አይሰማም
ይህ አሦራውያን በሌሎች ሕዝቦች እጅ እንዲሰጧቸው ወይም እንዲገብሩላቸው ለመጠየቅ የሚልኳቸውን መልዕክተኞች ሳያመለክት አይቀርም። ይህ በገቢራዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ዳግመኛ የመልዕክተኞቻችሁን ድምፅ የሚሰማ አይኖርም”። (ገቢራዊ ወይም ተገብሮአዊ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 ደም ለሞላባት ከተማ ወዮላት! ሐሰትና የተዘረፈ ንብረት ሞልቶበታል። **2** አሁን ግን የአላንጋ ድምፅና የመንኰራኵር ኳኳታ ድምፅ፣ የፈጣን ፈረስ ኮቴ፣ የሰረገሎች መንጓጓት ይሰማል። **3** የሚያብረቀርቅ ሰይፍና የሚያንጸባርቅ ጦር የያዙ ፈረሰኞች ጥቃት ያደርሳሉ፤ የሞተው ብዙ ነው፤ ሬሳ በሬሳ ተከምሮአል እጅግ ከመብዛቱ የተነሣ አጥቂዎቹ በሞቱት ሰዎች ሬሳ ይሰናከላሉ። **4** ይህ ሁሉ የሆነው ገደብ በሌለው የአመንዝራዋ ፍትወት ምክንያት ነው፤ እርሷ በዝሙቷ መንግሥታን፣ በጥንቆላዋም ሕዝቦችን ባሪያ አድርጋለች። **5** የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል፣ «እኔ በጠላትነት ተነሥቼብሻለሁ ዕርቃንሽን ለሕዝቦች፣ ኅፍረተ ሥጋሽን ለመንግሥታት አሳያለሁ። **6** በጣም የሚያስጸይፍ ቆሻሻ እደፋብሻለሁ፤ እንቅሻለሁ፤ ሰው ሁሉ እንዲሳለቅብሽ አደርጋለሁ። **7** የሚያይሽ ሁሉ ከአንቺ እየሸሸ፣ «ነነዌ ፈራርሳለች፤ ማን ያለቅስላታል? የሚያጽናናትንስ ከወዴት አገኛለሁ?» ይላል። **8** ነነዌ ሆይ፣ ለመሆኑ አንቺ ዐባይ ወንዝ አጠገብ ከተሠራችውና በውሃ ከተከበበችው፣ ወንዙ መከላከያ፣ ባሕሩ ራሱ ቅጥሯ ከሆነለት ከቴብስ ትበልጫለሽን? **9** ኢትዮጵያና ግብፅ ወሰን የለሽ ኃይሏ ነበሩ ፉጥና ሊቢያም ረዳቶቿ ነበሩ። **10** ያም ሆኖ፣ ቴብስ ተጋዘች፤ በምርኮም ተወሰደች ሕፃናቷ በየመንገዱ ማእዘን ላይ ተፈጠፈጡ፤ በመኳንንቷ ላይ ዕጣ ተጣጣሉ፤ ታላላቅ ሰዎቿ ሁሉ በሰንሰለት ታሰሩ። **11** አንቺ ደግሞ ትሰክሪያለሽ መደበቅ ትሞክሪያለሽ ከጠላቶችሽ መሸሸጊያም ትፈልጊያለሽ። **12** ምሽጐችሽ ሁሉ ቀድሞ እንደ ደረሰ፣ ሲነቀነቅ በላተኛው አፍ ውስጥ እንደሚወድቅ የበለስ ፍሬ ሆነዋል። **13** ወታደሮችሽ እንደ ሴት ፈሪዎች ሆነዋል የምድርሽ በሮች ወለል ብለው ለጠላቶችሽ ተከፍተዋል። መዝጊያዎቻቸውን እሳት በልቷቸዋል። **14** ለከበባው ውሃ ቅጂ፣ ምሽጐችሽን አጠናክሪ፤ ጭቃ ረግጠሽ የሸክላ መሥሪያ አዘጋጂ፤ ጡብም ሥሪ። **15** በዚያ እሳት ይበላሻል፤ ሰይፍ ያጠፋሻል፤ አንበጣ ማንኛውንም ነገር እንደሚጠፉ ያጠፋሻል። ስለዚህ እንደ አንበጣ እርቢ እንደ ኩብኩባም ተባዢ። **16** ነጋዴዎችሽን ከሰማይ ከዋክብት ይበልጥ አብዝተሻል፤ ይሁን እንጂ፣ ምድሪቱን እንደ አንበጣ ጋጡ፤ ከዚያም በርረው ሄዱ። **17** መኳንንቶችሽ የአንበጦችን ያህል ብዙ ናቸው፣ የጦር መሪዎችሽ በብርድ ቀን ቅጥር ሥር እንደሚቀመጥ የኩብኩባ መንጋ ናቸው። ፀሐይ ሲወጣ ግን በርረው ይሄዳሉ፤ የት እንደሚሄዱም አይታወቅም። **18** የአሦር ንጉሥ ሆይ፣ እረኞችህ አንቀላፉ መኳንንትህ ዐርፈው ተኙ። ሕዝብህ ሰብሳቢ አጥተው በየተራሮች ተበትነዋል። **19** ቁስልህን መፈወስ የሚችል የለም፤ ቁስልህ እጅግ ጽኑ ነው። ስለ አንተ የሚሰማ ሁሉ በውድቀትህ ደስ ብሎት ያጨበጭባል። ወሰን ከሌለው ጭካኔህ ማን ያመለጠ አለ?

Nahum 3:1

አጠቃላይ መረጃ:
ናሆም አብዛኛውን ጊዜ ትንቢቱን የጻፈው በግጥም መልክ ነው። የዕብራይስጥ ግጥም የተለያዩ ተመሳሳይነትን ይጠቀማል። እዚህ ጋ የነነዌን ጥፋት መግለጹን ይቀጥላል። (ግጥም እና ተመሳሳይነት የሚለውን ተመልከት))

በደም የተሞላች ከተማ
እዚህ ጋ “ደም” የሚለው ቃል የሚወክለው ደም ማፍሰስን ሲሆን ነፍስ ያጠፉትን ሰዎች ያመለክታል። አ.ት፡ “በነፍሰ ገዳዮች የተሞላች ከተማ”። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሐሰትን ሁሉ የተሞላ ነው
እዚህ ጋ “ሐሰት” የሚለው ቃል ውሸትን ለሚናገሩ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “በውሸተኞች የተሞላ ነው”። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የጅራፍ ድምፅና የሚንገጫገጭ መንኩራኩር ጩኸት፣ የፈረሶችና የሰረገላዎች ዝላይ
እነዚህ ሐረጎች ፈረሶቹን በመግረፍ የሚነዷቸው ሰዎች በጎዳናዎቹ በሚገሰግሱበት ጊዜ የሰረገላዎቹን ድምፅ የሚገልጹ ናቸው።

Nahum 3:3

ብዙ ሬሳ፣ እጅግ ብዙ አስክሬን
በመሰረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚናገሩት ስለ አንድ ነገር ሲሆን አጥቂዎቹ የረፈረፏቸው በጣም ብዙ አስክሬኖች እንደነበሩ የሚያመለክት ነው። (ተመሳሳይነት የሚለውን ተመልከት)

ሬሳ
የሞቱ ሰዎች አካል

ለአስክሬኖቹ ስፍር ቁጥር የላቸውም
“ስፍር ቁጥር የላቸውም” የሚሉት ቃላት አጥቂዎቹ የገደሏቸውን እጅግ ብዙ ቁጥር ያለው አስክሬን ለመግለጽ የቀረበ ግነት ነው። አ.ት፡ “ለመቁጠር እጅግ ብዙ የሆኑ አስክሬኖች ነበሩ” ወይም “እጅግ የበዙ አስክሬኖች ናቸው”። (ግነት እና ማጠቃለያ የሚለውን ተመልከት)

የውሷ ዘማዊት የዝሙት ተግባር
ናሆም በውበቷ ወንዶችን እንደምታስት አመንዝራ የነነዌ ከተማ ሌሎች ሕዝቦች እንዲገዙላት ስለምታደርግበት ሁኔታ ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በጥንቆላ የተካነች
ናሆም የነነዌ ከተማ በሌሎች ላይ ድግምት እንደሚያደርግ ጠንቋይ ሌሎች ሕዝቦች እንዲገዙላት ስለምታደርግበት ሁኔታ ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እርሷ አሕዛብን በዝሙትዋ ሕዝቦችንም በጥንቆላዋ የምትሸጥና
እዚህ ጋ “የምትሸጥ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የነነዌ ሰዎች ሌሎች አሕዛቦችንና ሕዝቦችን ለባርነት እንደዳረጓቸው ነው። ነነዌ ውበቷን፣ ኃይሏንና ተጽዕኖ ፈጣሪነቷን ሌሎችን ባሪያዎቿ ለማድረግ ትጠቀምበታለች። አ.ት፡ “በዝሙትዋና በጥንቆላዋ ሌሎች አሕዛቦች ባሪያዎቿ እንዲሆኑ የምታደርግ”።(የተገመተ ዕውቀትና የተሰወረ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

Nahum 3:5

እዩ
“ተመልከቱ” ወይም “አድምጡ” ወይም “የምነግራችሁን ልብ በሉ”

ቀሚስሽን ፊትሽ ላይ እገልበዋለሁ፣ ኃፍረትሽንም ለአሕዛብ አሳያለሁ
ይህ አመንዝራዎችን በማኅበረሰቡ ፊት ለፊት ልብሳቸውን በመግፈፍ በይፋ የማዋረድን ልማድ ያመለክታል። ይህ የነነዌ ከተማ አመንዝራ መሆኗን እግዚአብሔር በዘይቤአዊ አነጋገር መናገሩን የቀጠለበት ነው። አ.ት፡ “አንድ ሰው የአመንዝራይቱን ልብስ ፊቷ ድረስ በመግለብና በሰዎች ሁሉ ፊት ኃፍረቷን በማሳየት እንደሚያዋርዳት በይፋ አዋርድሻለሁ”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እፍረትሽን ለመንግሥታት
ይህ ሐረግ የነነዌን ልብስ የመግለብን ዓላማ ያብራራል። ከበስተኋላው ካለው ሐረግ ግሱን መውሰድ ያስፈልግ ይሆናል። አ.ት፡ “እፍረትሽን ለመንግሥታት አሳያለሁ” (መግደፍ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አስቀያሚ ቆሻሻ እደፋብሻለሁ
“አስቀያሚ ቆሻሻ” የሚሉት ቃላት ልዩ ልዩ ዓይነት ቆሻሻን ያመለክታል። በአንድ ሰው ላይ ቆሻሻ መወርወር የከፍተኛ ንቀት ምልክት ነበር። አ.ት፡ “አንድ ሰው በሌላው ላይ አስቀያሚ ቆሻሻ እንደሚወረውርበት ለአንቺ ያለኝን ንቀት አሳያለሁ”። (ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ተመልከት)

የሚያለቅስላት ማነው?
ሰዎች አሉታዊው መልስ ላይ አጽንዖት ለመስጠት ይህንን የማሳመኛ ጥያቄ ይጠይቃሉ። አ.ት፡ “ማንም አያለቅስላትም”። (የማሳመኛ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ሊያጽናናሽ የሚችልን ሰው ከወዴት አገኛለሁ?
ነነዌን ለማጽናናት የሚችል አንድም እንደማይኖር አጽንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ይህንን የማሳመኛ ጥያቄ ይጠቀማል። አ.ት፡ “የሚያጽናናሽ አንድም አይኖርም”። (የማሳመኛ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

Nahum 3:8

አጠቃላይ መረጃ፡
ናሆም ከተማው ራሱ እነርሱን እንደሆነ አድርጎ ለነነዌ ሕዝብ ይናገራል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አንቺ ከራሷ ከቲቤስ ትሻያለሽ?
ናሆም አስቀድሞ ለተገመተው አሉታዊ ምላሽ አጽንዖት ለመስጠት ይህንን የማሳመኛ ጥያቄ ይጠይቃል። አ.ት፡ “አንቺ ከቲቤስ ከራስዋ አትሻይም”። (የማሳመኛ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ቲቤስ
ይህ አሦራውያን ድል አድርገዋት የነበረችው የግብፅ የቀድሞዋ ዋና ከተማ ነበረች። (‘ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ’ የሚለውን ተመልከት)

በዐባይ ወንዝ ዳር የተሠራች ነበረች
“በዐባይ ወንዝ ዳር የተቋቋመች ነበረች”

ውቅያኖሱ መከላከያዋ የነበረ፣ ባህሩ ራሱም ግድግዳዋ የነበረ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ይጋራሉ። “ውቅያኖስ” እና “ባህር” የሚሉት ቃላት ሁለቱም በከተማይቱ አጠገብ የሚፈሰውን የዐባይን ወንዝ ያመለክታሉ። አ.ት፡ “አንዳንድ ከተሞች ለራሳቸው ቅጥር እንዳላቸው ሁሉ የዐባይ ወንዝ መከላከያዋ ነበር”። (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ተመሳሳይነት የሚለውን ተመልከት)

“ኩሽና ግብፅ ጉልበቶቿ ነበሩ
“ኢትዮጵያና ግብፅ አበረቷት” ወይም “ኩሽና ግብፅ ተባባሪዎቿ ነበሩ”

ለእርሱ ፍጻሜ አልነበረውም
“እርሱ” የሚለው ቃል ኩሽና ግብፅ ለቲቤስ የሰጧትን “ጉልበት” ያመለክታል። ለእርሱ ፍጻሜ አልነበረውም ሲል እጅግ ታላቅ የሆነውን ጉልበት የሚገልጽ ግነት ነው። አ.ት፡ “ኃይላቸው እጅግ ታላቅ ነበር”። (ግነት እና ማጠቃለያ የሚለውን ተመልከት)

ፉጥና ሊቢያ
እነዚህ ለቲቤስ ቅርብ የሆኑ በሰሜን አፍሪካ የሚገኙ የቦታ ስሞች ናቸው። (‘ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ’ የሚለውን ተመልከት)

Nahum 3:10

አጠቃላይ መረጃ፡
ናሆም እነርሱ ከተማይቱን ራሷን እንደሆኑ አድርጎ ስለ ነነዌ ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ይሁን እንጂ ቲቤስ ተወሰደች
“ቲቤስ” የሚለው ቃል በቲቤስ ይኖሩ የነበሩትን ሰዎች ይወክላል። ይህ በገቢራዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ቲቤትን የወጓት ሕዝቧን ወሰዱ”። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ገቢራዊ ወይም ተገብሮአዊ የሚለውን ተመልከት)

ወደ ምርኮ ሄደች
“እርሷ” የሚለው ቃል ቲቤስን ሲያመለክት በእርስዋ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላል። አ.ት፡ “ወደ ምርኮ ሄዱ”። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሕፃናት ልጆቿ ተፈጠፈጡ
ይህ ወታደሮቹ ሕፃናትን ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ መግደላቸውን የሚገልጽ ነው። ይህ በገቢራዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የጠላት ወታደሮች ሕፃናቱን ፈጠፈጧቸው” ወይም “የጠላት ወታደሮች ሕፃናቱን ደብድበው ገደሏቸው”። (ገቢራዊ ወይም ተገብሮአዊ የሚለውን ተመልከት)

በየጎዳናው ራስ ሁሉ ላይ
የጎዳናው ጅማሬ እንደ ራስ ተቆጥሮ ተነግሮለታል። በተጨማሪም፣ “ሁሉ” ማጠቃለያ ሲሆን በከተማው ሁሉ ያሉ በርካታ ስፍራዎች ማለት ነው። አ.ት፡ “በየጎዳናው ማዕዘን ላይ” ወይም “በከተማው ሁሉ ባሉት ጎዳናዎች”። (ዘይቤአዊ አነጋገር፣ ግነት እና ማጠቃለያ የሚለውን ተመልከት)

ታላላቅ ሰዎቿ ሁሉ በሰንሰለት ታሰሩ
ይህ በገቢራዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ታላላቅ ሰዎቿን ሁሉ በሰንሰለት አሰሯቸው”። (ገቢራዊ ወይም ተገብሮአዊ የሚለውን ተመልከት)

አንቺ ደግሞ ትሰክሪያለሽ
እዚህ ጋ “አንቺ” የሚለው ቃል ነነዌን ያመለክታል። ብዙ ወይን ጠጥተው እንደ ሰከሩ ሰዎች የነነዌ ሰዎች በጦርነት እንደሚሰቃዩና እንደሚሞቱ ናሆም ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Nahum 3:12

አጠቃላይ መረጃ፡
ናሆም እነርሱ ከተማይቱን ራሷን እንደሆኑ አድርጎ ስለ ነነዌ ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ምሽጎችሽ ሁሉ
“ምሽጎች” ለሚለው ቃል አማራጭ የሚሆኑት ትርጉሞች 1) እርሱ የነነዌን ከተማ የሚከበውን ቅጥር፣ ምሽግ ያመለክታል። አ.ት፡ “ምሽጎችሽ ሁሉ” ወይም “መከላከያዎችሽ ሁሉ” ወይም 2) እርሱ የአሦርን ድንበር በሚዋሰነው አካባቢ ነነዌን የሚያጠቁትን የጠላት ሰራዊት የሚከላከሉትን የተመሸጉ ከተሞች ያመለክታል። (የተገመተ ዕውቀትና የተሰወረ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ምሽጎችሽ ሁሉ ሊበሉ እንደ ደረሱ የመጀመሪያ የበለስ ዛፍ ናቸው፤ ከተነቀነቁ በበላተኛው አፍ ውስጥ ይወድቃሉ
አንድ ሰው የበሰለውን የበለስ ፍሬ እንዲወርድ ማድረግ እንደሚቀለው ሁሉ ተዋጊዎቹ ነነዌን ድል ማድረጋቸው ቀላል መሆኑን በንጽጽር ይናገራል። አ.ት፡ "አንድ ሰው የበለስን ዛፍ በመነቅነቅ የሚወድቀውን የበሰለ ፍሬ መብላት እንደሚችለው ሁሉ ጠላቶችሽ ምሽጎችሽን በቀላሉ ያፈርሱታል”። (ተነጻጻሪ የሚለውን ተመልከት)

በመጀመሪያ የበሰለውን በለስ
ይህ የሚያመለክተው በዛፉ ላይ በመጀመሪያ የሚበስለውን በለስ ነው። እነዚህ በለሶች በቀላሉ ስለሚወድቁ አንድ ሰው ፍሬዎቹ እንዲወድቁ ለማድረግ ዛፉን መነቅነቅ ብቻ ይኖርበታል። ዘግየት ብለው የሚበስሉትን በለሶች አንድ ሰው ዛፉ ላይ ወጥቶ በእጁ እንዲለቅማቸው ግድ ይሆንበታል። (የተገመተ ዕውቀትና የተሰወረ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከተነቀነቁ
“ዛፎቹ ከተነቀነቁ” ይህ በገቢራዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አንድ ሰው ዛፎቹን ቢነቀንቃቸው”።(ገቢራዊ ወይም ተገብሮአዊ የሚለውን ተመልከት)

በበላተኛው አፍ ውስጥ ይወድቃሉ
“በለሶቹ በበላተኛው አፍ ውስጥ ይወድቃሉ”፣ ይህ ግነት ነው። በለሶቹ ከዛፉ ላይ ወደሚመገበው ሰው አፍ ውስጥ ይወድቃሉ በማለት ናሆም አጽንዖት የሚሰጠው በለሶቹ ወዲያውኑ ለመበላት የተዘጋጁ መሆናቸውን ነው። አ.ት፡ “አንድ ሰው በለሶቹን ወዲያውኑ ሊበላቸው ይችላል”። (ግነት እና ማጠቃለያ የሚሉትን ተመልከት)

በመካከልሽ ያሉት ሰዎች ሴቶች ናቸው
በዚህ ጥንታዊ ባህል በጥቅሉ ሴቶች ከወንዶች ይልቅ በአካላዊ ብቃታቸው ደካሞች መሆናቸውን ጨምሮ በተለያየ ምክንያት ተዋጊዎች አልነበሩም። እዚህ ጋ፣ በከተማው የነበሩት ሰዎች ሁሉ ሴቶች የሆኑ ይመስል ናሆም የነነዌ ተዋጊዎች ለመዋጋት እንደዛሉና ድፍረት እንዳጡ ይናገራል። አ.ት፡ “ሰዎቻችሁ ሁሉ ደካሞችና ራሳቸውን መከላከል የማይችሉ ሴቶችን ይመስላሉ”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የምድርሽ በሮች ለጠላቶችሽ ወለል ብለው ተከፍተው ነበር
ይህ በገቢራዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የምድርሽ በሮች ለጠላቶችሽ ወለል ብለው ተከፍተዋል” ወይም “የሆነ ሰው የምድርሽን በሮች ለጠላቶችሽ ወለል አድርጎ ከፍቶላቸዋል”። (ገቢራዊ ወይም ተገብሮአዊ የሚለውን ተመልከት)

የምድርሽ በሮች ለጠላቶችሽ ወለል ብለው ተከፍተው ነበር
አማራጭ የሚሆኑት ትርጉሞች 1) በቁ. 12 ላይ “ምሽጎች” የሚለው ቃል የነነዌን መከላከያ የሚያመለክት ከሆነ እንግዲያው “የምድርሽ በሮች” የሚለው በነነዌ ዙሪያ ቅጥር ላይ የነበሩትን በሮች ያመለክታል” ወይም 2) በቁ. 12 ላይ “ምሽጎች” የሚለው ቃል አሦርን በሚያዋስነው ድንበር አካባቢ የሚገኙትን የተመሸጉ ከተሞች የሚያመለክት ከሆነ ደግሞ “የምድርሽ በሮች” የሚለው ዘይቤአዊ አነጋገር የጠላት ሰራዊት ወደ ምድሪቱ እንዳይገባ የሚከላከሉት በሮች እነዚያ ከተሞች መሆናቸውን ያመለክታል የሚሉት ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መቆለፊያዎቻቸውን እሳት በልቶታል
አማራጭ የሚሆኑት ትርጉሞች 1) በቁ. 12 ላይ “ምሽጎች” የሚለው ቃል የነነዌን መከላከያ የሚያመለክት ከሆነ እንግዲያው “መዝጊያዎቻቸው” የሚለው በነነዌ ዙሪያ ባለው ቅጥር ላይ በሮቹ የተዘጉባቸውን መቆለፊያዎች ያመለክታሉ” ወይም 2) በቁ. 12 ላይ “ምሽጎች” የሚለው ቃል አሦርን በሚያዋስነው ድንበር አካባቢ የሚገኙትን የተመሸጉ ከተሞች የሚያመለክት ከሆነ ደግሞ “መቆለፊያዎቻቸው” የሚለው ቃል እነዚያ ከተሞች የጠላት ሰራዊት ወደ ምድሪቱ እንዳይገባ የሚከላከሉ የተዘጉ በሮች መሆናቸውን የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እሳት በልቷቸዋል
እሳት ይባላ ይመስል ናሆም ስለማቃጠሉና ስለማጥፋቱ ይናገራል። አ.ት፡ “እሳት አጥፍቶታል” ወይም “እሳት እንድዶታል”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Nahum 3:14

አጠቃላይ መረጃ፡
ናሆም ስለ ነነዌ ሕዝብ እነርሱ ከተማይቱን ራሷን እንደሆኑ አድርጎ መናገሩን ይቀጥላል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ለከበባው ውሃ ለመቅዳት ሂጂ. . . ለጡቦቹ ጭቃ ርገጪ
ናሆም የሚናገረው ለነነዌ ሕዝብ ነው። ጠላት ከተማይቱን እንደሚያጠፋት ቢያውቅም ለጦርነት እንዲዘጋጁና ቅጥሮቹን እንዲጠግኑ ይነግራቸዋል። (ውስጠ ወይራ የሚለውን ተመልከት)

ታላላቅ ምሽጎቻችሁን አጠናክሩ
“ምሽጎቻችሁን ጠግኑ”

የሸክላ ዐፈር ፈልጊና ጭቃውን አቡኪ፤ ለጡቦቹ የሚሆን ቅርፅ አውጪ
እነዚህ ሐረጎች የከተማይቱን ቅጥር ለመጠገን የሚጠቀሙባቸውን የጭቃ ጡብ ስለመሥራታቸው ያመለክታል።

በዚያ እሳት ይበላሻል
እሳት ይባላ ይመስል ናሆም ስለሚያቃጥልና ስለሚያጠፋ እሳት ይናገራል። አ.ት፡ “በዚያ እሳት ያጠፋችኋል” ወይም “በዚያ ጠላቶቻችሁ በእሳት ያነዷችኋል”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሰይፍ ያጠፋሻል
ይህ “ሰይፍ” የሚለው ቃል ጠላቶቻቸው የሚያጠቁባቸውን ሰይፎች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ጠላቶቻችሁ በሰይፎቻቸው ይገድሏችኋል”። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የአንበጣ ኩብኩባ ሁሉን እንደሚበላ ይበላሻል
“እርሱ” የሚለው ቃል የሚገድላቸውን እንደሚበላ በሰውኛ የተነገረለትን “ሰይፍ” ያመለክታል። ወታደሮች ሰይፎቻቸውን በመጠቀም በነነዌ ያሉትን ሁሉ የሚገድሉበት ሁኔታ በመንገዱ ያገኘውን ሰብል ሁሉ ከሚበላው የአንበጣ መንጋ ጋር ተነጻጽሯል። አ.ት፡ “የአንበጣ መንጋ በመንገዱ ያገኘውን ሁሉ በቀላሉ እንደሚበላ የጠላቶቻችሁ ሰይፍ ሁላችሁንም ይገድላችኋል”። (ሰውኛ እና ተነጻጻሪ የሚለውን ተመልከት))

ራስሽን እንደ ኩብኩባ አርቢ፣ እንደ አንበጣም አብዢ
እነዚህ ቃላት ናሆም በነነዌ የሚኖረውን ሕዝብ ቁጥር በመንጋ ውስጥ ካሉት እጅግ ብዙ ቁጥር ካላቸው አንበጣዎች ጋር የሚያነጻጽርበትን አዲስ አንቀጽ ይጀምራሉ።

Nahum 3:16

አጠቃላይ መረጃ፡
ናሆም ስለ ነነዌ ሕዝብ እነርሱ ከተማይቱን ራሷን እንደሆኑ አድርጎ መናገሩን ይቀጥላል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የነጋዴዎችሽን ቁጥር በሰማይ ካሉት ከዋክብት ይልቅ አብዝተሻቸዋል
ይህ ግነት አጽንዖት የሚሰጠው በነነዌ ይኖሩና ይሠሩ በነበሩ እጅግ ብዙ ቁጥር ያላቸው ነጋዴዎች ላይ ነው። አ.ት፡ “በሰማይ ካሉት ከዋክብት ብዛት የሚበልጥ ነጋዴዎች ያሉሽ ይመስል” ወይም “ከብዛታቸው የተነሣ ማንም ሊቆጥራቸው የማይቻለው ነጋዴዎች አሉሽ”። (ግነት እና ማጠቃለያ የሚለውን ተመልከት)

እንደ አንበጣ ኩብኩባ ናቸው፤ ምድሪቱን ይበዘብዙና በረው ይሄዳሉ
ናሆም እነዚህ ነጋዴዎች ሸቀጦቻቸውን በነነዌ ሸጠው ካተረፉ በኋላ ጦርነቱ ሲጀመር ከከተማይቱ መሸሻቸውን በመንገዳቸው ያገኙትን ሰብል ሁሉ ከበሉ በኋላ በረው ከሚሄዱ አንበጣዎች ጋር ያነጻጽራል። (ምስያ የሚለውን ተመልከት)

የጦር አዛዦችሽ በብርድ ቀን በቅጥሩ ስር እንደሚሰፍር የአንበጣ መንጋ ናቸው፤ ነገር ግን ፀሐይ ሲወጣ በረው ይሄዳሉ
ናሆም በነነዌ የሚኖሩ የጦር አለቆች ጦርነቱ ሲጀመር መሸሻቸውን ቅዝቃዜ በሚሆንበት ጊዜ ቆይተው ፀሐይ ሲወጣና አየሩ ሲሞቅ በረው ከሚሄዱ አንበጣዎች ጋር ያነጻጽራቸዋል። (ተነጻጻሪ የሚለውን ተመልከት)

ማንም ወዴት እንደሚሄዱ አያውቅም
“እናም ወዴት እንደሄዱ ማንም አያውቅም”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Nahum 3:18

እረኞችሽ አንቀላፍተዋል፤ ገዢዎችሽ አርፈው ተኝተዋል

እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ይጋራሉ። ናሆም በጎቻቸውን እንደሚንከባከቡ እረኞች በመቁጠር ለአሦር መሪዎች ይናገራል። እርሱ ያንቀላፉ ይመስል ስለ እረኞቹና ስለ ገዢዎቹ ይናገራል። አ.ት፡ “እረኞች የሚመስሉ መሪዎቻችሁ ሞተዋል፤ ገዢዎቻችሁ በሙሉ ሞተዋል” (ተመሳሳይነት እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሕዝብሽ በተራሮች ላይ ተበትኗል

ናሆም እረኞቻቸው ከሞቱ በኋላ እንደተበተኑ በጎች ስለ ነነዌ ሕዝብ ይናገራል። አ.ት፡ “ሕዝብሽ እንደ በጎች በተራሮች ላይ ተበትነዋል”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ቁስልሽ ሊፈወስ የማይችል ነው። ቁስልሽ የከፋ ነው

ንጉሡ በማይድን ቁስል የተሰቃየ ይመስል ናሆም የነነዌ መጥፋትና የንጉሥዋ ድል መደረግ የማይቀር መሆኑን ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ቁስልሽ ሊፈወስ የማይችል ነው

“ፈውስ” የሚለው ቃል በግሳዊ ሐረግ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ቁስልሽን ማንም ሊፈውስ አይችልም”። (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ከጽኑው ክፋትህ ያመለጠ ማነው?

ይህ የማሳመኛ ጥያቄ አጽንዖት የሚሰጠው አስቀድሞ በሚገምተው አሉታዊ ምላሽ ላይ ነው። በአሦር አቅራቢያ ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦች ሁሉ ጽኑ በሆነው በአሦር ክፋት ምክንያት ተሰቃይተው ነበር። አ.ት፡ “ከጽኑው ክፋትህ ማንም ያመለጠ የለም”። (የማሳመኛ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Habakkuk

Habakkuk

Chapter 1

1 ነቢዩ ዕንባቆም የተቀበለው መልእክት፤ **2** «ያህዌ ሆይ፣ ለርዳታ ወደ አንተ ስጮኽ የማትሰማው እስከ መቼ ነው? «ግፍ በዛ!» በማለት ወደ አንተ ጮኽሁ፤ አንተ ግን አላዳንኸኝም። **3** ርኩሰትና በደልን ለምን እንዳይ አደረግኸኝ? ጥፋና ዐመፅ በፊቴ ናቸው፤ ፀብና ጭቅጭቅም እየበዛ ነው! **4** ስለዚህ ሕግ ላልቶአል፤ ፍትሕ ተዛብቶአል። ክፉዎች ጻድቃንን ከብበዋል ስለዚህ ፍርድ ተጣሟል።» ያህዌ እንዲህ በማለት ለዕንባቆም መለሰ **5** «ቢነገራችሁ እንኳ የማታምኑትን አንድ ነገር በዘመናችሁ ስለማደርግ፣ ልብ አድርጋችሁ አሕዛብን እዩ፤ ተመልከቱ፤ እጅግም ተደነቁ። **6** ጨካኞቹንና ችኩሎቹን ከለዳውያንን ላስነሣ ነው፤ የራሳቸው ያልሆኑ ቤቶችን ለመውሰድ በምድሪቱ ስፋትና ርዝመት ይገሠግሣሉ። **7** እነርሱ አስፈሪና አስደንጋጭ ናቸው፤ ፍርዳቸውና ክብራቸው ከራሳቸው ይወጣል። **8** ፈረሶቻቸው ከነብር ይልቅ ፈጣኖች፣ ከማታም ተኩላ ይልቅ፣ አስፈሪዎች ናቸው። ፈረሶቻቸው በፍጥነት ይጋልባሉ፤ ነጥቆ ለመብላት እንደሚቸኩል ንስር ፈረሰኞቻቸው ከሩቅ ይመጣሉ። **9** ሁሉም ለዐመፅ ሥራ ይመጣሉ፤ ሰራዊታቸው እንደ ምድረ በዳ ነፋስ ይገሠግሣል፤ ምርኮኞችንም እንደ አሸዋ ይሰበስባል። **10** ነገሥታት ላይ ይሳለቃሉ፤ ገዥዎች ላይ ያፌዛሉ። በምሽጐች ላይ በመሳቅ ዐፈር ቆልለው ይይዟቸዋል። **11** ከዚያም እንደ ነፋስ አልፈው ይሄዳሉ፤ ጉልበታቸውን አምላካቸው ያደረጉ እነዚያን በደለኞች ይጠራርጋቸዋል። ዕንባቆም ለያህዌ ያቀረበው ሌላው ጥያቄ **12** አንተ የእኔ አምላክ፣ የእኔ ቅዱስ፣ አንተ ከዘላለም ጀምሮ ያለህ አይደለህምን? እኛ አንሞትም። እንዲፈርዱ ያህዌ ሾሟቸዋል፤ አንተ ዐለት ሆይ፣ ይቀጡ ዘንድ ሥልጣን ሰጠሃቸው። **13** ዐይኖችህ እጅግ የነጹ በመሆናቸው ክፉ ነገርን መመልከት አይሆንላቸውም፤ አንተም ክፉ ነገር ሲሠራ ዝም ብለህ አታይም፤ ታዲያ፣ እነዚያን ዐመፀኞች ለምን ዝም ብለህ ትመለከታለህ? ዐመፀኛው ከራሱ ይልቅ ጻድቅ የሆነውን ሰው ሲውጠውስ ለምን ዝም ትላለህ? **14** ሰዎችን ባሕር ውስጥ እንዳለ ዓሣ፣ መሪ እንደሌላቸው በደረታቸው እየተሳቡ እንደሚሄዱ ፍጥረታት የምታደርጋቸው ለምንድነው? **15** ዓሣ በመንጠቆ እንደሚያዝ ሁሉንም በመንጠቆ ይይዟቸዋል፤ ሰዎችን በመረቦቻቸው ይዘው ይሰበሰቧቸዋል። ደስ የሚሰኙትና ሐሤት የሚያደርጉት ከዚህ የተነሣ ነው። **16** የስቡ እንስሳት ድርሻዎቻቸው፣ የጣፈጠውም ሥጋ ምግባቸው ሆናልና ስለዚህ ለመረቦቻቸው ይሠዋሉ፤ ለአሸክላዎቻቸውም ያጥናሉ። **17** ታዲያ፣ መረቦቻቸውን ባዶ እያደረጉ፣ ያለ አንዳች ርኅራኄ ሕዝቦችን መግደል መቀጠል አለባቸውን?»

Habakkuk 1:1

ነቢዩ ዕንባቆም የተቀበለው መልእክት

እነዚህ ቃሎች የመጽሐፉን ሁለት ምዕራፎች ያስተዋውቃሉ። ዕንባቆም ይህን መልእክት ከያህዌ መቀበሉ ይታወቃል። ይህን የተሟላ ዐረፍተ ነገር አድርጐ ማቅረብ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ነቢዩ ዕንባቆም ከያህዌ የተቀበለው መልእክት ይህ ነው።››

ያህዌ

ይህ በብሉይ ኪዳን ለሕዝቡ የተገለጠ የእግዚአብሔር ስም ነው። ይህን እንዴት እንደምትተረጉመው ከቃላት ትርጉም ስለ ያህዌ የተነገረውን ተመልከት።

ለርዳታ እየተጣራሁ አንተ የማትሰማው እስከ መቼ ነው?

ያህዌ እንዲረዳው ዕንባቆም ረጅም ጊዜ ወደ እርሱ ሲጮኽ እንደ ነበር አንባቢ መረዳት አለበት። ተስፋ በመቁረጡና ያህዌ እስኪመልስለት ድረስ ምን ያህል ጊዜ መቆየት እንዳለበት ማወቅ ስለ ፈለገ ይህን ጠይቆአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተ መልስ እስክትሰጠኝ ከእንግዲህ ለርዳታ መጮኽ ያለብኝ ምን ያህል ጊዜ ነው?››

Habakkuk 1:3

አጠቃላይ መረጃ

ዕንባቆም ወደ እግዚአብሔር መጮኹን ቀጥሏል።

ጥፋትና ግፍ በፊቴ አለ

‹‹ጥፋት›› እና ‹‹ግፍ›› የተሰኙትን ቃሎች ግሣዊ ሐረግ አድርጐ መተርጐም ይቻላል። ‹‹በፊቴ›› የሚለው ፈሊጥ እነዚህ ነገሮች የተፈጸሙት ዕንባቆም በዐይኑ እየተመለከተ እንደ ነበር ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ነገሮችን ሲያጠፉና ግፍ ሲፈጽሙ በዐይኔ ዐይቻለሁ›› ጠብና ጭቅጭቅ በዝቶአል ‹‹ጠብ›› የሚለው ቃል በሰዎች መካከል አለ መግባባት መኖሩን የሚያመለክት ሲሆን፣ እንደ ግሣዊ ሐረግ መተርጐም ይቻላል። ልክ አንድ ሰው ወደ ላይ ከፍ ያለ ይመስል ዕንባቆም በሰዎችም መካከል ጠብ ከፍ እያለ መምጣቱን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሰዎች መካከል ጠብ እየበዛ መጥቷል››

ክፉዎች ጻድቃንን ይከባሉ

ክፉዎች ጻድቃንን የመክበበቸውን ያህል ዐመፀኞች ጻድቃን ላይ ብዙ ግፍና መከራ እየፈፀሙ እንደ ሆነ ዕንባቆም ይናገራል።

ሕግ ደክሟል

ሰዎች ለሕጉ አለ መታዘዛቸውን ወይም ተግባር ላይ አለማዋላቸውን ዕንባቆም የሕግ መድከምንና ምንም ማድረግ አለመቻልን ደካማ ከመሆን ጋር አመሳስሎታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ማንም ሕግ አያከብርም››

ሐሰተኛ ፍርድ በዝቶአል

ዳኞች ትክክል የሆነ ፍርድ እንዳደረጉ ቢናገሩም፣ ለሕዝቡ ግን ‹‹ሐሰተኛ ፍርድ›› ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዳኞች በሐሰት ይፈርዳሉ››

Habakkuk 1:5

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ ለዕንባቆም እየመለሰ ነው

ተደነቁ፤ ተገረሙ

‹‹መደነቅ›› እና ‹‹መገረም›› ተመሳሳይ ትርጉም ነው ያላቸው። ሁለቱ በአንድ ሆነው ለጉዳዩ አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጣም ተደነቁ››

በዘመናችሁ

ይህ አነጋገር የሚያመለክተው የዕንባቆምን ሕይወት ዘመን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሕይወት ዘመናችሁ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ቢነገራችሁም እንኳ
ይህን፣ ‹‹አንድ ሰው ቢነግራችሁ እንኳ›› ወይም፣ ‹‹ስለዚያ ስትሰሙ›› በማለት መግለጽ ይቻላል።

ተመልከቱ!
እዚህ ላይ፣ ‹‹ተመልከቱ!›› የሚለው ቃል የማሰሙትን አስደናቂ ነገር ልብ ማለት እንዳለባቸው ያመለክታል።

ከለዳውያንን አስነሣለሁ
ያህዌ ጎይለኞቹ ከለዳውያንን እንደሚያነሣቸው ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከለዳውያንን በጣም ጎይለኛ ሕዝብ አደርጋለሁ››

ጨካኝ
አማራጭ ትርጒሞቹ፣ 1) ‹‹ግፈኛ›› ወይም 2) ‹‹ፈጣን››

በምድሪቱ ስፋት
ይህ ማለት፣ 1) ይሁዳ ውስጥ ማንኛውም ቦታ ወይም 2) በዓለም ውስጥ ባለ ማንኛውም ቦታ ማለት ሊሆን ይችላል። የከለዳውያን ሰራዊት ጎያል እንደ ሆነ አጽንዖት ለመስጠት የታሰበ ግነት ሊሆን ይችላል።

የሚያስፈሩና የሚያስደነግጡ ናቸው
‹‹የሚያስፈሩ›› እኛ፣ ‹‹የሚያስደነግጡ›› የተሰኙት ተመሳሳይ ትርጒም አላቸው። ሁለቱ በአንድነት ሆነው ከለዳውያን ሌሎች ሰዎች ላይ ለሚያሳድሩት ፍርሃት አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሌሎች ሰዎችን እጅግ ያሸብራሉ››

ፍርዳቸውና ክብራቸው ከራሳቸው ይወጣል
‹‹ክብራቸው›› የሚለው ለራሳቸው ካላቸው አመለካከት የሚነሣ ትዕቢትን ይወክላል። ከእነርሱ የሚወጣው ፍርድና ክብር ለራሳቸው ካላቸው አመለካከት የሚነሣ ውጤት እንደ ሆነ ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ትዕቢተኞች በመሆናቸው ምን መፍረድ እንዳለባቸው በራሳቸው ይወስናሉ››

Habakkuk 1:8

ፈረሶቻቸው... ፈረሶቻቸው
የከለዳውያን ሰራዊት ፈረሶች

ነብር
ግዙፍ፣ ፈጠን ድመት

የማታ ተኩላ
ምግባቸውን ማታ ማታ የሚያድኑ ተኩላዎች ያመለክታል።

ፈረሰኞቻቸው
ፈረሶች የሚጋልቡ የከለዳውያን ሰራዊት

ነጥቆ ለመብላት እንደሚቸኩል አሞራ ይበራሉ
አሞራ ምግቡን ለመያዝ ፈጣን እንደ ሆነ ሁሉ፣ ከለዳውያንም ጠላቶቻቸውን ድል ለማድረግ ምን ያህል ፈጣን መሆናቸውን ያህዌ ይናገራል።

ሰራዊታቸው እንደ ምድረ በዳ ነፋስ ወደ ፊት ይገሠግሣል
ምድረ በዳ ላይ እንደሚነፍስ ነፋስ ከለዳውያን ምን ያህል በፍጥነት እንደሚንቀሳቀሱ ያህዌ ይናገራል።

ምርኮኞችን እንደ አሸዋ ይሰበስባል
ይህን፣ 1) አንድ ሰው በእጁ አሸዋ እንደሚያፍስ ከለዳውያንም በቀላሉ ሰዎችን ምርኮኛ እንደሚያደርጉ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አንድ ሰው አሸዋ እንደሚሰበስብ እነርሱም ምርኮኛ ይሰበስባሉ›› ወይም 2) እነዚያ ሰዎች ምድረ በዳ ውስጥ እንዳለ አሸዋ የሆኑ ይመስል፣ ከለዳውያንም እጅግ ብዙ ምርኮኛ ይሰበስባሉ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የምድረ በዳ አሸዋ የሚያህል ምርኮኛ ይሰበስባሉ››

Habakkuk 1:10

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ስለ ከለዳውያን ሰራዊት ገለጻውን ቀጥሏል።

ነገሥታትን ይንቃሉ፤ በገዦችም ላይ ያፌዛሉ
በመሠረቱ የእነዚህ ሐረጎች ትርጒም ተመሳሳይ ነው። ‹‹ማፌዝ›› የሚለውን ቃል፣ ግሣዊ በሆነ ሐረግ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ነገሥታትን ይንቃሉ፤ መሪዎችም ማላገጫዎቻቸው ናቸው።›› ወይም፣ ‹‹እነርሱ የሚያደርጉት፣ ነገሥታትንና ገዦች ላይ ማፌዝ ብቻ ነው››

እንደ ነፋስ አልፈው ይሄዳሉ
በፍጥነት የሚንቀሳቀስ ነፋስ የሆኑ ይመስል፣ የከለዳውያን ሰራዊት እያንዳንዱን ድል በማድረግ ከአንዱ ከተማ ወደ ሌላው እንደሚሸጋገሩ ያህዌ ይናገራል።

ጉልበታቸውን አምላካቸው ያደረጉ በደለኞች ናቸው
ይህ የሚያመለክተው የከለዳውያንን ሠራዊት ነው።

Habakkuk 1:12

አጠቃላይ መረጃ
ዕንባቆም ስለ ከለዳውያን ለያህዌ ይናገራል።

ከዘላለም ጀምሮ ያለህ አይደለህምን? የእኔ አምላክ፣ የእኔ ቅዱስ
ዕንባቆም ይህን መልስ የማያስፈልገው ጥያቄ የሚያቀርበው አዎንታዊ ምላሽ በመጠበቅ ነው። እንደ ዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በእርግጥ አንተ ከዘላለም ጀምሮ ነህ፤ አምላኬ ያህዌ የእኔ ቅዱስ››

ከዘላለም ጀምሮ
‹‹ዘላለማዊ››

እንዲፈርዱ ሾመሃቸዋል፤ ዐለት ሆይ፣ ይቀጡ ዘንድ ሥልጣን ሰጠሃቸው።
የሚናገረው ስለ ከለዳውያን ነው። ‹‹ፍርድ›› እና፣ ‹‹ቅጣት›› የተሰኙትን ቃሎች ግሥ አድርጐ መተርጐም ይቻላል። ከለዳውያን የያህዌ ሕዝብ ላይ እንደሚፈርዱና እንደሚቀጡ አንባቢው መረዳት አለበት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሕዝቡን እንዲቀጡ ሾምሃቸው፤ ዐለት ሆይ፣ ሕዝብህን እንዲቀጡ ሥልጣን ሰጠሃቸው››

ዐለት
ምንም ጉዳት እንዳይደርስበት ያህዌ ጠባቂው መሆኑንና ጠላቶቹ እንዳይደርሱበት የሚቆምት ዐለት መሆኑን ዕንባቆም ይናገራሉ

Habakkuk 1:13

አጠቃላይ መረጃ
ዕንባቆም ስለ ከለዳውያን ለያህዌ መናገሩን ቀጥሏል

ዐይኖችህ... እጅግ ንጹሐን ናቸው
እዚህ ላይ፣ ‹‹ዐይኖች›› ሁሉን የሚያይ ያህዌን ይወክላሉ። ‹‹አንተ እጅግ ንጹሕ ነህ››

ከሐዲዎችን
ይህ የሚያመለክተው ከለዳውያንን ነው። መካድ እምነተ ቢስና የተናገሩትን የሚያጥፉ፣ ሰዎችን ይመለከታል።

ክፉው ከራሱ ይልቅ ጻድቅ የሆነውን ሲውጠውስ ለምን ዝም ትላለህ?
ልክ የሚውጧቸው ይመስል፣ ክፉዎች ሌሎች ሰዎችን እንደሚያጠፉ ዕንባቆም ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ክፉ ሰው ከእርሱ የበለጠ ጻድቅ የሆነውን ሲያጠፋው ለምን ዝም ትላለህ?››

ከእርሱ ይልቅ ጻድቅ የሆነውን
ይህ የሚያመለክተው ዕንባቆም እየተናገረላቸው ያሉትን እስራኤላውያን ነው። እነዚህ ሰዎች ራሳቸው ክፉ መሆናቸውን፣ ሆኖም ከከለዳውያን፣ ‹‹ይልቅ ጻድቅ›› ወይም የከለዳውያንን ያህል ዐመፀኞች አለመሆናቸውን አንባቢው መረዳት አለበት።

በባሕር ውስጥ እንዳለ ዓሣ አደረግሃቸው
ከለዳውያን ምንም ፀፀት ሳይሰማቸው ሌሎችን የሚገድሉበትን መንገድ፣ ዓሣ ሲያጠምዱ ምንም ፀፀት ከማይሰማቸው ሰዎች ጋር አመሳስሎአቸዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ከዓሣ የበለጠ ዋጋ እንዳይኖራቸው አደረግህ››

ገዥ እንደሌላቸውም የሚርመሰመሱ ፍጥረታት አደረግህ
‹‹የሚርመሰመሱ›› የሚለው ጥቃቅን ትሎችንና ፍጥረታት ያመለክታል። የሚርመሰመሱ ፍጥረታት የሚያደራጃቸውና የሚከላክልላቸው እንደሌላቸው ሁሉ፣ ሕዝቡ በከለዳውያን ሰራዊት ፊት መከላከያ የላቸውም። ግሡ ካለፈው ቁጥር ጋር የተያያዘ እንዲሆን ማድረግ ይቻላል። ሰዎች ገዥ እንደሌላቸው የሚርመሰመሱ ፍጥረታት መከላከያ የሌላቸው እንዲሆኑ አደረግህ።

Habakkuk 1:15

x
1፥15-17 ላይ ያለው፣ ‹‹እርሱ›› እና፣ ‹‹የእርሱ›› የሚለው ነጠላ ቁጥር ሁሉንም የባቢሎን ወታደሮች የሚወክል አንድ የባቢሎን ወታደር ያመለክታል። ይህን ተውላጠ ስም ወደ ብዙ ቁጥር መለወጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያመጣናል… ሁላችንንም ይይዘናል››

በመረቡ ይይዛቸዋል፤ በአሸክላው ውስጥ ይሰበስባቸዋል
ይህ የሚናገረው ስለ አጠቃላይ ሰዎች ነው። ይህ ዕንባቆምንም እንዲጨምር አድርጐ ሊተረጐም ይችላል። ‹‹ሁላችንንም በመረቡ ይይዘናል፤ በአሸክላው ውስጥ ይሰበስበናል››

መንጠቆ… መረብ… አሸክላ
እነዚህ ዓሣ ለማጥመድ የሚጠቅሙ ናቸው።

ለመረቡ ይሠዋል፤ ለአሸክላውም ያጥናል
ሕዝብንና መንግሥታትን ድል ለማድረግ ከለዳውያን የሚጠቀሙባቸው መሣሪያዎች ዓሣ ለማጥመድ የሚጠቀሙባቸው መሣሪያዎች ያህል መሆናቸውን ዕንባቆም ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎችን ድል ለማድረግ የሚጠቀሙባቸውን መሣሪያዎች መሥዋዕት ያቀርቡላቸዋል፤ ዕጣን ያጥኑላቸዋል››

ታዲያ መረቡን ባለ ማቋረጥ መጣል ሕዝቦችንስ ያለ ርኅራኄ መግደል አለበትን?
ዕንባቆም ይህን የሚጠይቀው ተስፋ ስለ ቆረጠና ይህ የሚቀጥለው ለምን ያህል ጊዜ መሆኑን ማወቅ ስለ ፈለገ ነው። ያህዌ ከለዳውያን ሕዝቦችንና መንግሥታትን ማጥፋታቸውን እንዲቀጥሉ ይፈቅድላቸዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መረባቸውን ባለ ማቋረጥ እንዲጥሉና ያለ አንዳች ርኅራኄ ሕዝቦችን እንዲያጠፉ ትፈቅድላቸዋለህን?››

መረቡን ባለ ማቋረጥ መጣል
ያለ ማቋረጥ መረቡን እንደሚጥል ዓሣ አጥማጅ፣ ከለዳውያንም ተጨማሪ መንግሥታት ድል ለማድረግ እየተዘጋጁ መሆናቸውን ዕንባቆም ይናገራል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 በጥበቃ ቦታዬ እቆማለሁ፤ በመጠበቂያው ግንብ ላይ ቦታዬን እይዛለሁ፤ ምን እንደሚለኝና ለጥያቄዬ ምን መልስ እንደሚሰጥ እጠባበቃለሁ። **2** ያህዌ
እንዲህ በማለት መለሰልኝ፤ «ይህን ራእይ ጻፈው፤ በቀላሉ እንዲነበብ አድርገህም በጽላት ቅረጸው። **3** ራእዩ የሚናገረው ገና ወደ ፊት ስለሚሆነው ነው።
በመጨረሻም ይፈጸማል እንጂ፣ በፍጹም አይዋሸም። **4** ተመልከት! ጠማማ ሐሳብ ያለው ሰው ታብዮአል። ጻድቁ ግን በእምነቱ ይኖራል። **5** ዐርፎ
እንዳይቀመጥ ወይን ጠጅ ዕብሪተኛውን ወጣት አስቶታል ይልቁን ምኞቱን እንደ መቃብር አስፍቶአል እንደ ሞት በቃኝ ማለትን አያውቅም። ሕዝቦችን ሁሉ ወደ
ራሱ ይሰበስባል ሰዎችንም ሁሉ ማርኮ ይወስዳል። **6** ታዲያ፣ በእንዲህ ዐይነቱ ሰው ላይ በማፌዝና በመዘባበት እንዲህ እያሉ ሁሉም አይሣለቁበትምን?
‹የተሰረቀውን ለራሱ ለሚያከማች፣ ራሱን በዐመፅ ባለጠጋ ለሚያደርግ ወዮለት! ይህ የሚቀጥለውስ እስከ መቼ ነው? **7** በአንተ የተመረሩ ድንገት
አይነሡብህምን፣ አንተን የማያስደነግጡስ አይነቁብህምን? በእጃቸውም ትወድቃለህ። **8** አንተ ብዙ ሕዝብ ስለ ዘረፍህ የተረፉት ሕዝቦች ይዘርፉሃል። የሰው
ደም አፍስሰሃል አገሮች፣ ከተሞችና የሚኖሩባቸው ሰዎች ሁሉ ላይ ግፍ ሠርተሃል። **9** በማጭበርበር በተገኘ ሀብት ቤቱን ለሚገነባ ከክፉ ለማምለጥ ቤቱን
በከፍታ ላይ ለሚሠራ ወዮለት! **10** ብዙ ሰዎችን ለማጥፋት ደባ ፈጽመሃል በገዛ ቤትህ ላይ ውርደትን፣ በራስህም ላይ ኃጢአትን አድርገሃል። **11** ድንጋዮች
በቅጥሩ ውስጥ ይጮኻሉ፣ ከዕንጨት የተሠሩ ተሸካሚዎችም እንዲህ በማለት ይመልሱላቸዋል፣ **12** «ደም በማፍሰስ ከተማን ለሚሠራ፣ በወንጀልም አገርን
ለሚመሠርት ወዮለት!» **13** ሰዎች ለእሳት ማገዶ እንዲሆን እንዲለፉ፣ ሕዝቦችም በከንቱ እንደደከሙ፣ የሰራዊት ጌታ ያህዌ ወስኖ የለምን? **14** ያም ሆኖ፣ ውሃ
ባሕርን እንደሚሞላ ሁሉ ምድርም የያህዌን ክብር በማወቅ ትሞላለች። **15** ጎፍረተ ሥጋቸውን ለማየት ባልንጀሮቹን ለሚያጠጣ፣ እስኪሰክሩም ድረስ ወይን
ለሚያቀርብላቸው ወዮለት!» **16** በክብር ፈንታ ውርደት ትሞላለህ፤ አሁን ተራው የአንተ ነውና ጠጣ፤ ጎፍረተ ሥጋህም ይገለጥ፤ በያህዌ ቀኝ እጅ ያለው ጽዋ
በተራው ይመልስብሃል ክብርህን ውርደት ይሸፍነዋል። **17** ሊባኖስ ላይ ያሠራኸው ግፍ ያጥለቀልቅሃል፤ እንስሶች ላይ የፈጸምኸው ጥፋት ያስደነግጥሃል።
የሰው ደም አፍስሰሃል፤ አገሮች፣ ከተሞችና የሚኖሩባቸው ሰዎች ሁሉ ላይ ግፍ ሠርተሃል። **18** ታዲያ፣ የቀረጽኸው ምስል ምን ይጠቅምሃል? ምስሉን
የቀረጸው፣ ከቀለጠ ብረት ጣዖት የሠራ ሰው የሐሰት መምህር ነው፤ እነዚያን የማይናገሩ አማልክት ሲሠራ በገዛ እጅ ሥራው ተማምኖአልና። **19** ዕንጨቱን ንቃ!
ሕይወት የሌለውንም ድንጋይ ተነሣ ለሚል ወዮለት ለመሆኑ፣ እነዚህ ነገሮች ማስተማር ይችላሉን? በወርቅና በብር ተለብጦአል፤ እስትንፋስ ግን የለውም። **20**
ያህዌ ግን በተቀደሰ መቅደሱ አለ፤ ምድር ሁሉ በፊቱ ጸጥ ትበል!»

Habakkuk 2:1

በመጠበቂያ ላይ እቆማለሁ፤ በምሽጉ ቅጥር ላይ ወጥቼ እቆያለሁ
1) እነዚህ ሁለት ሐረጐች የሚያመለክቱት በመሠረቱ አንድ ዐይነት ስለሆኑ ነገሮች ነው። ይህም፣ ዕንባቆም ምሽጉ ቅጥር ላይ ወዳለ መጠበቂያ ወጥቶ ነበር ማለት ነው፤ ወይም 2) መጠበቂያው ላይ ወጥቶ የመልእክተኛውን መምጣት እንደሚጠብቅ ሰው የያህዌን ምላሽ በናፍቆት እንደሚጠብቅ ዕንባቆም በምሳሌ እየተናገረ ነው።

ምን እንደሚለኝ አያለሁ
‹‹ያህዌ ምን እንደሚናገረኝ አያለሁ››

ለክርክሬም የምሰጠውን መልስ ለማወቅ እጠባበቃለሁ
‹‹መልስ›› የሚለው መልስ መስጠትን ያመለክታል። ተናግሮ ስለ ነበረው ነገር፣ ዕንባቆም ምን መልስ እንደሚሰጥ እያሰበ ነው።

Habakkuk 2:2

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለዕንባቆም ይመልስለታል

ራእዩን ጻፈው፤ በሰሌዳም ላይ ቅረጸው
ሁለቱም ሐረጐች ስለ አንድ ዐይነት ጉዳይ በተለያዩ መንገዶች ይናገራሉ።

አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ይህን ራእይ በግልጽ ሰሌዳ ላይ ጻፈው››
ሰሌዳ

ይህ ለመጻፊያ የሚያገለግል ጠፍጣፋ ድንጋይ ወይም ሸክላ ነው።
የሚያነበው ሰው እንዲፈጥን ይህም፣ 1) መልእክቱን ለማድረስ መልእክተኛው ከቦታ ወደ ቦታ እየሮጠ እያለ በቀላሉ ማንበብ እንዲችል መልእክቱ በጣም ቀላል ነው ማለት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰሌዳውያን የሚያነበው ሰው እየሮጠ እያለ ማንበብ እንዲችል›› ወይም 2) የሚያነበው እየሮጠ ያለ ይመስል አንባቢው በፍጥነት ማንበብ እንዳለበት ያህዌ የሚናገረው ምሳሌ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰሌዳውን የሚያነብ በፍጥነት ማንበብ እንዲችል››

ራእዩ... ስለ መጨረሻው ይናገራል
ራእዩ መናገር የሚችል ሰው እንደ ሆነ አድርጐ ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ራእዩ... መጨረሻ ላይ ይፈጸማል›› ወይም፣ ‹‹ራእዩ... በመጨረሻ እውነት ይሆናል›› ቢዘገይም እንኳ ጠብቀው በእርግጥ ይመጣል፤ ከቶም አይዘገይም፤ ራእዩ ቶሎ የታሰበው ቦታ ከመድረስ የሚዘገይ ሰው ይመስል፣ ለመፈጸም ረጅም ጊዜ እንደሚወስድ ያህዌ ይናገራል።

አይዘገይም
ይህም፣ ‹‹ጊዜ አያልፍም›› ወይም 2) ‹‹ቶሎ ይመጣል›› ማለት ሊሆን ይችላል።

Habakkuk 2:4

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለዕንባቆም መመለሱን ቀጥሏል። እዚህ ላይ ከለዳውያን ትዕቢተኞች፣ ጠጥቶ የማይጠግብ ሰካራም መሆናቸውን ይናገራል።

ተመልከቱ
‹‹ተመልከቱ›› የሚለው ለሚከተለው ነገር አጽንዖት ይሰጣል።

ታብዮአል
ትዕቢተኛው ሰው፣ ‹‹መታበዩን›› ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በጣም ትዕቢተኛ ሆኖአል››

የወይን ጠጅ አታሎታል
ብዙ ወይን ጠጅ መጠጣት የሰውን ሚዛን እንዴት እንደሚያዛባ ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከወይን ጠጅ እርሱ የፈለገውን አያገኝም››

ከቶ አያርፍም
እዚህ ላይ፣ ‹‹ማረፍ›› የሚለው ቃል ቤት ውስጥ መኖርን የሚያመለክት ሲሆን፣ ማረፊያ ቦታ ማጣትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ምንም ዕረፍት እንዳይኖረው››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምኞቱን እንደ መቃብር ያሰፋል፤ እንደ ሞት ከቶ አይጠግብም
መቃብርና ሞት ፍጹም የማይጠግቡ ከመሆናቸው የተነሣ ሰዎች ሁሌም እንደሚሞቱ ሁሉ፣ እነዚህም በልተው አይጠግቡም። በተመሳሳይ መንገድ ሁልጊዜ የበለጠ ይፈልጋል፤ ግን በቃን አይልም።

ሕዝቦችን ለራሱ ይሰበስባል፤ ሰዎችንም ሁሉ ማርኮ ይወስዳል።
የእነዚህ ሁለት ሐረጐች ትርጉም ተመሳሳይ ነው። ሰዎችን ድል ማድረግና መቆጣጠር፣ ሰዎችን ለራስ መሰብሰብ እንደ ሆነ ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የየአገሩ ሰዎችን ድል እያደረገ ለራሱ ይሰበስባል››

Habakkuk 2:6

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለዕንባቆም መመለሱንና ከለዳውያን እንደ አንድ ሰው እንደ ሆኑ መናገሩን ቀጥሏል።

እንዲህ እያሉ ሁሉም አይሣለቁበትምን?
‹‹ሁሉም›› የሚለው ቃል ዕንባቆም 2፥5 ላይ የተጠቀሱትን መንግሥታትና ሕዝቦች ያመለክታል። በጥያቄ መልክ የቀረበው ዐረፍተ ነገር አዎንታዎ ምላሽ የሚጠብቅ በመሆኑ፣ እንደ ዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነዚህ መንግሥታትና ሕዝቦች ሁሉ ይሳለቁበታል››

የራሱ ያልሆነውን ለሚሰበስብ ወዮለት
የራሱ ያልሆኑ ነገሮችን በመሰብሰብ ንብረት ማከማቸቱ ተነግሮአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእርሱ ያልሆነውን በመሰብሰብ ሀብታም ለሚሆን ወዮለት››

ሰዎች ላይ ያለህን ዕዳ ሸክም የምታበዛው እስከ መቼ ነው?
‹‹ዕዳ›› የሚለው ቃል ዕዳቸውን እስኪከፍሉ ድረስ፣ ሰዎች ለተበደሩት ነገር የሚሰጡትን፣ ‹‹መያዣ›› ያመለክታል። አንድ ሰው እንዲህ ያሉ መያዣዎች እያበዛ ሲሄድ ሸክሙም ይጨምራል።

ሰዎች ላይ ያለህን ዕዳ ሸክም የምታበዛው እስከ መቼ ነው?
የሰዎችን ሀብት የሚዘርፉ ከለዳውያን የራሳቸው ባልሆነው ነገር ሰዎች መያዣ እንዲሰጧቸው ያስገድዳሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሌሎችን በመዝረፍ ራስህን ሀብታም የምታደርገው እስከ መቼ ነው?››

ድንገት አይነሡብህም? ነቅተውስ አያስደነግጡህምን?
በጥያቄ መልክ የቀረበው ዐረፍተ ነገር አዎንታዎ መልስ ይጠብቃል። እንደ ዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ድንገት ይነሡብሃል፤ ነቅተውም ያስደነግጡሃል››

‹‹ባለ ዕዳ ያደረግሃቸው››
ዕብራይስጡ፣ ‹‹ወለድ የምታስከፍላቸው›› ወይም፣ ‹‹ባለ ዕዳዎችህ›› ማለት ሊሆን ይችላል። በዚህ ዐውድ ውስጥ ሁለቱንም ትርጉሞች ይዞአል። ባለ ዕዳ የሆኑትና የተጨቆኑት መልሰው እርሱን እንደሚጨቁኑ የሚያመለክት ምሳሌያዊ አነጋገር ነው።

አያስደነግጡህምን?
ይህም የሚያመለክተው ስለ ባለ ዕዳዎቹ ነው። አስገድዶ እንዲከፍሉ ካደረገው መያዣ የተነሣ በቀል እንደሆን ከለዳውንን በማጥቃት ያስደነግጣቸዋል።

ነቅተው አይነሡብህምን?
ከለዳውያን ላይ የሚነሡ ሕዝቦች ድንገት፣ ‹‹ከእንቅልፍ›› — ‹‹ነቅተው›› እንደሚነሡ ተነግሮአል።

ዘረፋ
በጎይል መንጠቅ ወይም መውሰድ

የሰው ደም አፍሰሃልና
‹‹ደም ማፍሰስ›› — ‹‹መግደል›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎችን ገድለሃልና››

Habakkuk 2:9

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለዕንባቆም መመለሱንና ለከለዳውያን እንደ አንድ ሰው መናገሩን ቀጥሏል።

ክፉ ትርፍ የሚፈልግ
በዐመፅ ጥቅም የሚያገኝ ሰው፣ በዚያ ጥቅም መኖሪያውን እንደሚሠራ ተነግሯል››

በተጭበረበረ ትርፍ መኖሪያውን የሚገነባ
1) በተጭበረበረ ትርፍ መኖሪያውን... ሲል፣ 1) ‹‹መኖሪያ›› የሚለው በዐመፅ የተገነባውን የባቢሎን መንግሥት ለማመልከት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በዐመፅ ባገኘው ሀብት መኖሪያ ቤቱን የሠራ ወይም፣ 2) ‹‹መኖሪያ›› ሲል ‹‹ቤተ ሰብን›› ማለት በዐመፅ ቤተ ሰቡን ሀብታም ያደረገ ሰው ማለቱ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በግፍ በተገኘ ሀብት ቤተ ሰቡን ሀብታም ያደረገ››

ከጠላት እጅ ለማምለጥ፣ ቤቱን በከፍታ ላይ ለሚሠራ
ይህ ቤቱን የሠራ ሰው እንደ ወፍ ጐጆ በከፍታ ላይ ሠርቶአል። አጥቂ እንስሳ የወፍ ጐጆው ላይ መድረስ እንደማይችል ሰውየውም ቤቱ የተጠበቀና ምንም አደጋ የማይደርስበት እንደ ሆነ ያስባል።

ከጠላት እጅ ለማምለጥ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› የተባለው ኀይል ማለት ነው፤ ‹‹ጠላት›› የሚለውም ክፉ ነገር የሚያደርግ ሰው ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከጠላት ኀይል ለማምለጥ›› ወይም፣ ‹‹ጉዳት ከሚያደርሱ ሰዎች ለማምለጥ››

በገዛ ቤትህ ላይ ውርደትን... አምጥተሃል
እዚህ ላይ፣ ‹‹ውርደትን አምጥተሃል›› የሚለው ሐረግ ሰውየው ያቀደው ነገር እርሱ ላይ ውርደት እንዳመጣበት ያመለክታል። ‹‹ቤት›› ለሚለው ቃል አንድ አማራጭ ትርጉም፣ የባቢሎን መንግሥት ሰው በዐመፅ በተገኘ ገንዘብ የሠራው ቤት መሆኑን ማመልከት ሊሆን ይችላል። ‹‹ባቀድኸው ዕቅድ የሠራኸው ቤት ላይ ውርደትን አመጣህ›› — ‹‹ቤት›› የሚለው ሌላ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቤተ ሰብ›› ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ባቀድኸው ዕቅድ ቤተ ሰብህ ላይ ውርደትን አምጥተሃል››

ብዙ ሰዎችን ነጥለሃል
ብዙ ሰዎችን መግደል ቅርንጫፍ ከዛፍ ላይ እንደሚነጠል እነዚያን ሰዎች መቁረጥ ወይም መነጠል እንደ ሆነ ተነግሯል።

በገዛ ራስህ ላይ ኀጢአት ሠርተሃል
‹‹በገዛ ራስ ላይ ኀጢአት ማድረግ›› ሞትና ጥፋት የሚያስከትል ነገር ማድረግ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የራስህን መጥፊያ ሠርተሃል›› ወይም፣ ‹‹የገዛ ሞትህን አምጥተሃል››

ድንጋይ ከቅጥሩ ውስጥ ይጮኻል፤ ከእንጨት የተሠሩ ተሸካሚዎችም ይመልሱለታል።
እዚህ ላይ ሰውየው ቤቱን የሠራባቸው ነገሮች ያደረገውን ወንጀል እንደሚመሰክሩ ሰዎች ተመስለዋል። አንተ ባለህበት አገር ሰዎች ቤት ለመሥራት የሚጠቀሙት ከዚህ በተለየ ነገር ከሆነ እዚህ ላይ እነዚያን ነገሮች መጠቀም ትችላለህ።

ይጮኻል
‹‹አንተን በመቃወም ይጮኻል›› ወይም፣ ‹‹አንተን በመክሰስ ይጮኻል››

ይመልሱለታል
‹‹ከድንጋዩ ጋር ይስማማሉ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Habakkuk 2:12

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለዕንባቆም መመለሱንና ከለዳውያንን እንደ አንድ ሰው አድርጐ መናገሩን ቀጥሏል።

ከተማን ደም በማፍሰስ ለሚሠራ፣ በወንጀልም ለሚመሠርታት ወዮለት
ሁለቱም ሐረጐች በተለያየ መንገድ ስለ አንድ ዐይነት ነገር ይናገራሉ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከገደሉዋቸው ሰዎች በዘረፉት ከተሞቻቸውን ለሠሩ

ከለዳውያን የተሰጠ ማስጠንቀቂያ››
x

ከተማን ደም በማፍሰስ ለሚሠራ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ደም›› ግድያን ያመለክታል። ሰውየው ከተማን የሠራው እርሱ ከገደላቸው ሰዎች በተዘረፉ ነገሮች መሆኑ ተመልክቷል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰዎችን በመግደልና ያላቸውን ነገር በመዝረፍ ከተማን የሚሠራ››

በወንጀልም ለሚመሠርታት
ሰውየው ከተማ የሠራው ከገደላቸው ሰዎች በዘረፈው ነገር መሆኑን ያመለክታል። እዚህ ላይ፣ ‹‹መመሥረት›› የሚለው ቃል ‹‹መጀመር›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በክፉ ምግባር ባገኘው ትፍዖ ከተማ መሥራት የሚጀምር››

ሰዎች ለእሳት ማገዶ እንዲሆን እንዲለፉ፣ ሕዝቦችም በከንቱ እንዲደክሙ ያህዌ ጸባኦት ወስኖ የለምን?
ጥያቄው የቀረበ አዎንታዊ ምላሽ በመጠበቅ ነው። ሁለቱ ቁልፍ ቃሎች ተመሳሳይ ትርጒም ያላቸው ሲሆኑ፣ ሰዎች የሚሠሩት ሥራ ዘላቂነት እንደሌለው ያመለክታሉ። ጥያቄውን እንደ ዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰዎች በርትተው የሚሠሩዋቸው ነገሮች በእሳት ተቃጥለው እንዲጠፉ የወሰነ ያህዌ ነው››

ሰዎች ለእሳት ማገዶ እንዲሆን እንዲለፉ።
ይህ ማለት ሰዎች የሚለፉባቸው ነገሮች ለእሳት ማገዶ እንዲሆኑ ተወስኖአል ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰዎች የሚለፉባቸው ነገሮች ለእሳት ማገዶ ይሆናሉ››

ውሃ ባሕርን እንደሚሸፍን ሁሉ፣ ምድርም የያዌን ክብር በማወቅ ትሞላለች
ውሃ ባሕርን እንደሚሸፍን ሁሉ በየአገሩ ያሉ ሰዎችም፣ የያህዌን ክብር እንደሚያውቁ ንጽጽሩ ያመለክታል።

ውሃ ባሕርን እንደሚሸፍን ሁሉ፣ ምድር የያህዌን ክብር በማወቅ ትሞላለች
‹‹በማወቅ›› የሚለውን፣ ‹‹ያውቃሉ›› በማለት መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በምድሩ ሁሉ ያሉ ሰዎች የያህዌን ክብር ያውቃሉ››

Habakkuk 2:15

x
ያህዌ ለዕንባቆም መመለሱንና እንደ አንድ ሰው አድርጐ ለከለዳውያን መናገሩን ቀጥሏል።

ባልንጀሮቹን አስገድዶ ለሚያጠጣ... እስኪሰክሩም ድረስ...
ከለዳውያን ሌሎች ሕዝቦች ላይ ያደረጉት ጭካኔ ባልንጀሮቹን ለማዋረድ ሲል በግድ እንዲሰክሩ በሚያደርግ ሰው ተመሳስሎአል።ባልንጀሮቹን አስገድዶ ለሚያጠጣ

ኀፍረተ ሥጋቸውን ለማየት
ይህ በሌሎች ፊት እንዲዋረዱ ለማድረግ ሰዎችን በአደባባይ ዕርቃናቸውን እንዲሆኑ ከማድረግ ጋር ይመሳሰላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ዕርቃናቸውን በማድረግ ሕዝብ ፊት እንዲዋረዱ››

በክብር ፈንታ ዕፍረት ትሞላለህ
የከለዳውያን አጥብቆ ክብራቸውን መፈለግ በመስገብገብና በብዛት ከሚበሉትና ከሚጠጡት ምግብ ጋር ተመሳስሎአል። ክብር ከማግኘት ይልቅ፣ ዕፍረትን ይለብሳሉ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ስትፈልግ የነበረውን ክብር ሳይሆን፣ ራስህ ላይ ወርደት ታመጣለህ››

ጠጣ
ሌሎች ሰዎች ከለዳውያን ላይ የሚያደርጉት ነገር እነርሱ አስገድደው ሌሎችን እንዳጠጡ ሁሉ፣ እነርሱም ተገድደው ወይን ጠጅ እንዲጠጡ ከማድረግ ጋር ተመሳስሎአል›› አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከጽዋው ጠጣ›› ወይም፣ ‹‹ወይን ጠጁን ጠጣ››

ያልተገረዘ ኀፍረተ ሥጋህ ይገለጥ
ይህ ሐረግ ኀፍረተ ሥጋቸውን ለማየት ከለዳውያን በማስገደድ ሌሎች እንዲጠጡ ሲያስገድዱ ከነበረበት ሁኔታ ጋር ይመሳሰላል። እዚህ ላይ፣ ‹‹ያልተገረዘ ኀፍረተ ሥጋህ›› የሚለው ዕርቃናቸውን በመሆን መዋረዳቸውን ብቻ ሳይሆን፣ አለ መገረዛቸው የያህዌ ሕዝብ አለመሆናቸውን ጭምር በግልጽ ያሳያል።

በያህዌ ቀኝ እጅ ያለው ጽዋ ይመለስብሃል
ያህዌ ከለዳውያንን መቅጣቱ በእጁ ከያዘው ጽዋ ወይን ጠጅ ከመጠጣት ጋር ተመሳስሎአል። የያህዌ ቀን እጅ ጎይሉን ይወክላል።

በያህዌ ቀኝ እጅ ያለው ጽዋ
‹‹ያህዌ በቀኝ እጁ የያዘው ጽዋ›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ከያዘው ጽዋ››

ክብርህን ውርደት ይሸፍነዋል
ከለዳውያን ላይ የሚደርሰው ውርደት አለን ብለው ያስቡ የነበረውን ክብር እንደሚሸፍን አንዳች ነገር ተገልጾአል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ክብርህን ውርደት ይተካዋል›› ወይም፣ ‹‹ከማክበር ይልቅ ሰዎች ያዋርዱሃል››

Habakkuk 2:17

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለዕንባቆም መመለሱንና እንደ አንድ ሰው ለከለዳውያን መናገሩን ቀጥሏል።

በሊባኖስ ላይ የሠራኸው ግፍ ያጥለቀልቅሃል።
ሊባኖስ ላይ ለሠሩት ግፍ የሚደርስባቸው ቅጣት እነርሱን እንደሚያጥለቀልቅ አንዳች ነገር ተነግሮአል።

በሊባኖስ ላይ የሠራኸው ግፍ
‹‹ሊባኖስ›› የሚለው ቃል ተመሳሳይ ትርጉም፣ 1) የሊባኖስን ዱር ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በሊባኖስ ዛፎች ላይ የሠራኸው ግፍ›› ወይም 2) የሊባኖስን ሕዝብ ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በሊባኖስ ሕዝብ ላይ የሠራኸው ግፍ››

እንስሳቱን ማጥፋትህም ያስደነግጥሃል
ከለዳውያን የሊባኖስ እንስሶችን በማጥፋታቸው የሚደርስባቸው ቅጣት እነርሱን ከሚያስደነግጥ ሰው ጋር ተመሳስሎአል።

የሰውን ደም አፍስሰሃልና... በውስጣቸው የሚኖሩትንም ሁሉ
ዕንባቆም 2፥8 እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት

የሰውን ደም አፍስሰሃልና
‹‹የሰው ደም ማፍሰስ›› — ‹‹መግደል›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰዎችን ገድለሃልና››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Habakkuk 2:18

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለዕንባቆም መመለሱንና እንደ አንድ ሰው ለከለዳውያን መናገሩን ቀጥሏል።

የተቀረጹ ምስሎች ምን ጠቀሙህ?
ጥያቄው የቀረበው አሉታዊ መልስ በመጠበቅ ነው። ጥያቄው እንደ ዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የተቀረጹ ምስሎች ምንም አልጠቀሙህም›› ‹‹አንተ›› የሚለው የሚያመለክተው ከለዳውያንን ነው።

የቀለጠ ብረት
ይህ የሚያመለክተው በፈሳሽ መልክ ያለ ብረት ነው።

የሐሰት መምህር
ይህ የሚያመክተው ምስሎቹን የተቀረጸው ወይም ያበጀውን ሰው ነው። የሐሰት አምላክ መቅረጹ ሐሰት ማስተማሩ ነው።

ሕይወት የሌለውንም ድንጋይ
ግሡ ካለፈው ሐረግ ጋር ይያያዛል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሕይወት የሌለውንም ድንጋይ… ለሚል ወየለት››

በውኑ ማስተማር ይችላሉን?
ጥያቄው የቀረበው አሉታዊ መልስ በመጠበቅ ነው። ጥያቄው እንደ ዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እነዚህ ነገሮች ማስተማር አይችሉም›› ወይም፣‹‹እንጨትና ድንጋይ ማስተማር አይችሉም››

እነሆ… ተለብጦአል
‹‹ተመልከቱ፤ የተለበጠ መሆኑን ማየት ትችላላችሁ››

በወርቅና በብር ተለብጦአል
ይህን ድርጊትን በሚያመለክት ሁኔታ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንጨቱን ወይም ድንጋዩን ሰው በወርቅና በብር ለብጦታል››

እስትንፋስም የለውም
‹‹እስትንፋስ የለውም›› በሕይወት አይደለም፤ ሞቷል ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሕይወት የለውም›› ወይም፣ ‹‹በድን ነው››

ምድር ሁሉ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ምድር›› በምድሪቱ የሚኖሩ ሰዎች ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በምድሪቱ የሚኖር ሁሉ›› ወይም፣ ‹‹በምድር የሚኖር ሁሉ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 የነቢዩ ዕንባቆም ጸሎት **2** ያህዌ ሆይ፣ ስላደረግኸው ድንቅ ሥራ ሰዎች ፈራሁ፤ የቀድሞ ዘመን ሥራህን በዚህ ዘመንም አድርግ፤ በየዘመናቱም እንዲታወቅ
አድርግ። በቁጣህ ውስጥ እንኳ ምሕረት ርኅራኄህን አስብ። **3** እግዚአብሔር ከቴማን፣ ቅዱሱንም ከፋራን ተራራ መጣ! ሴላ። ክብሩ ሰማያትን ሸፈነ፤ ምድር
በምስጋናው ተሞላች። **4** ኃይሉ ከተሰወረበት እጁ የወጡ ሁለት ጨረሮች እንደ መብረቅ ደምቀዋል። **5** መቅሠፍት በፊቱ ሄደ፤ ቸነፈርም እግር በእግር
ተከተለው። **6** እርሱ ሲቆም ምድር ትናወጣለች፤ እርሱ ሲመለከት ሕዝቦች ይንቀጠቀጣሉ። የዘላለም ተራሮች እንኳ ተፈረካከሱ የጥንት ኮረብቶችም ዝቅ አሉ።
መንገዱ ዘላለማዊ ነው። **7** የኢትዮጵያ ድንኳኖች ሲጨነቁ፣ የምድያምም መኖሪያዎች ሲታወኩ አየሁ። **8** ያህዌ ወንዞች ላይ ተቆጥቷልን? መዓትህስ በምንጮች
ላይ ነበርን? ወይስ በፈረሶችህና በድል አድራጊ ሰረገሎችህ በጋለብህ ጊዜ ባሕር ላይ ተቆጥተህ ነበርን? **9** ቀስትህን ከሰገባው አወጣህ፤ ፍላጻህንም
ለመወርወር አዘጋጀህ። ሴላ። ምድርን በወንዞች ከፈልህ። **10** ተራሮች አዩህ፤ በፍርሃትም ተጨማደዱ የውሃ ወጀብ በላያቸው አለፈ፤ ጥልቁ ባሕር ድምፁን
አሰማ ማዕበሉም ወደ ላይ ከፍ ከፍ አለ። **11** ከሚወረወሩ ፍላጾች ብርሃን፣ ከሚያብረቀርቀው የጦርህ ነጸብራቅ የተነሣ ፀሐይና ጨረቃ በቦታቸው ቆሙ። **12**
በቁጣህ በምድር ላይ ተመላለስህ፤ በመዓትህ ሕዝቦችን አደቀቅህ። **13** ሕዝብህን ለማዳን፣ የቀባኸውንም ለመታደግ ወጣህ። ዕርቃኑን ታስቀረው ዘንድ
የዐመፃን ቤት ራስ ቀጠቀጥህ። ሴላ። **14** እንደ ዐውሎ ነፋስ ሊበታትን የመጣውን፣ ምስኪኑን በስውር ለመዋጥ የመጣውን ሰራዊት አለቃ ራስ በገዛ ፍላጻው
ወጋህ። **15** በፈረሶችህ ባሕሩ ላይ ተራመድህ፤ ታላላቅ ውሆችን ከመርህ። **16** እኔ ሰማሁ ውስጤም ተናወጠ፤ ከድምፁ የተነሣ ከንፈሮቼ ተንቀጠቀጡ።
አጥንቶቼ ይበሰብሳሉ፤ እግሮቼም ከታች ይርዳሉ ወራሪዎቻችን ላይ መከራ የሚመጣበትን ቀን በትዕግሥት እጠብቃለሁ። **17** ምንም እንኳ የበለስ ዛፍ ባያብብ፣
ወይን ዛፍ ላይ ፍሬ ባይገኝ፣ የወይራ ዛፍ ምንም ፍሬ ባይሰጥ፣ ከእርሻዎች ሰብል ቢጠፋ፣ የበግ መንጋዎች ሁሉ ቢያልቁ፣ በረት ውስጥ ምንም ከብት ባይገኝ፣
18 ይህም ሁሉ ቢሆን፣ እኔ በያህዌ ደስ ይለኛል በመድኃኒቴም አምላክ ሐሤት አደርጋለሁ። **19** ጌታ ያህዌ ኃይሌ ነው፤ እግሮቼን እንደ ዋሊያ እግሮች ያደርጋል፤
በከፍታዎቼም ላይ ይመራኛል። - ለመዘምራን አለቃ በባለ አውታር መሣሪያዎች የተዘመረ።

Habakkuk 3:1

የነቢዩ የዕንባቆም ጸሎት
እነዚህ ቃሎች የዚህን መጽሐፍ ሦስተኛ ምዕራፍ ያስተዋውቃሉ። ይህን በተሟላ ዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ይህ ነቢዩ ዕንባቆም ወደ እግዚአብሔር ያቀረበው ጸሎት ነው››

ዝናህን ሰምቻለሁ
የዚህ አማራጭ ትርጕም፣ 1) ቀድሞ ስላደረግኸው ሰዎች ሲናገሩ ሰምቻለሁ›› ወይም 2) ‹‹የተናገርኸውን ሰምቻለሁ››

ሥራህን አድስ
ቀድሞ ያደረገውን አሁንም እንዲያደርግ ዕንባቆም ያህዌን ይጠይቃል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ቀድሞ ያደረግኸውን ዛሬም አድርግ›› ወይም ‹‹ድሮ ያደረግኸውን አሁንም አድርግ››

በእነዚህ ዘመኖች መካከል
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሕዝቡን ለመታደግ ያህዌ ባለፈው ጊዜ ካደረገው ጋር በሚቃረን መልኩ ዕንባቆም ይህን ጸሎት ያቀረበበትን ዘመን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በዘመናችን››

እንዲታወቁ አድርግ
‹‹ሥራህ እንዲታወቅ አድርግ›› ወይም፣ ‹‹ሰዎች ሥራህን እንዲያውቁ አድርግ››

Habakkuk 3:3

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መጥቶ ጠላቶቹ ላይ እንደሚፈርድና ሕዝቡን እንደሚያድን የተቀበለውን ራእይ ዕንባቆም መግለጽ ጀምሮአል። ራእዩ እስከ ዕንባቆም 3፥15 ይቀጥላል። ንግግሩ ምሳሌያዊ አነጋገር የሞላው ሲሆን፣ የተለያዩ ተዛማጅ ሐሳቦችንም ያቀርባል።

እግዚአብሔር ከተማን፣ ቅዱሱም ከፋራን ተራራ መጣ።
ቴማንና የፋራን ተራራ የሚኙት ከይሁዳ በስተ ደቡብ ነው። ከሲና ተራራ በኩል እግዚአብሔር ወደ ይሁዳ እንደሚመጣ ዕንባቆም ይናገራል።

ክብሩ ሰማያትን ሸፈነ
‹‹ግርማው ሰማይን ሸፈነ›› እዚህ ላይ፣ ‹‹ክብር›› የሚለው ቃል የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ብዙውን ጊዜ ከእግዚአብሔር ሐልዎት ጋር የሚያያይዙትን ደማቅ ብርሃን ያመለክታል።

ውዳሴውም ምድርን ሞላ
‹‹ውዳሴ›› ሰዎች እርሱን እንዲያመሰግኑ የሚያደርገውን የእግዚአብሔር ባሕርያት ያመለክታል አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ምድርም ክብሩን ተሞልታ ነበር››

Habakkuk 3:4

አጠቃላይ መረጃ
ዕንባቆም የያህዌን ራእይ መግለጽን ቀጥሏል።

ጸዳሉ እንደ ፀሐይ ብርሃን ነው።
እዚህ ላይ፣ ‹‹ጸዳል›› ብዙውን ጊዜ ከያህዌ ክብር ጋር የሚያያዘውን ድምቀት የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። ይህም ማለት 1) የያህዌ ክብር ድምቀት እንደ መብረቅ ብርሃን ነው ወይም 2) የያህዌ ክብር ድምቀት እንደ ፀሐይ መውጣት ነው ማለት ሊሆን ይችላል።

ሁለት ጨረሮች ከእጁ ወጡ
የመብረቁ ድምቀት ያህዌ በእጁ የሚይዛቸው ሁለት የጨረር መሣሪያዎች እንደ ሆኑ ዕንባቆም ይናገራል

ኀይሉም በዚያ ተሰውሮአል
‹‹በዚያ›› የሚለው የሚያመለክተው የያህዌን እጅ ነው። ይህም ማለት፣ 1) ዕንባቆም ማየት የቻለው የመብረቅ ብልጭታዎች በያህዌ እጅ ውስጥ የተሰወረው ኀይል ሙላት አነስተኛ መገለጫ ነው፤ ወይም 2) ሊጠቀምበት ዝግጁ እስኪሆን ድረስ ያህዌ ኀይሉን እጁ ውስጥ ይሰውራል ማለት ሊሆን ይችላል።

Habakkuk 3:6

አጠቃላይ መረጃ
ዕንባቆም የያህዌን ራእይ መግለጽ ቀጥሏል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ቆመ
ይህ ማለት ያህዌ መራመዱን አቁሞ ቀጥ ብሎ ቆመ ማለት እንጂ፣ ከተቀመጠበት ተነሥቶ ቆመ ማለት አይደለም

ምድርን ለካ/መዘነ
ይህም ማለት 1) ‹‹ለካ/መዘነ›› የሚለው፣ ‹‹አናወጠ›› ተብሎ ሊተረጐም ይችላል ወይም 2) አንድ ድል አድራጊ ሰው ለባለ ሥልጣኖቹ ከማከፋፈሉ በፊት ምድሪቱን ተዘዋውሮ እንደሚያይ አሰሰ ማለት ሊሆን ይችላል።

የዘላለም ተራሮች... የጥንት ኮረብቶች
‹‹ዘመን ከመቆጠሩ በፊት የነበሩ ተራሮች... እስከ ዘመን ፍጻሜ ድረስ የሚዘልቁ ኮረብቶች›› የምትጠቀምበት ቋንቋ፣ ‹‹ኮረብቶች›› እና፣ ‹‹ተራሮች›› ወይም ‹‹ዘላለም›› እና ‹‹የጥንት›› ለተሰኙት የተለየ ቃሎች ከሌሉት UDB ላይ እንደ ተደረገው በአንድነት ልታያይዛቸው ትችላለህ።

የዘላለም ተራሮች ተፈረካከሱ
አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የዘላለም ተራሮች እንኳ ፈራረሱ›› ወይም፣ ‹‹የዘላለም ተራሮችን እንኳ ፈረካከሰ››

የጥንት ኮረብቶች ዝቅ አሉ
በያህዌ ፊት ዝቅ ብለው የሚሰግዱ ይመስል፣ የጥንት ኮረብቶችም እንደ ሌላው መሬት ደልዳላ ሆኑ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የጥንት ኮረብቶች ተናዱ››

መንገዱ ዘላለማዊ ነው
‹‹መንገድ›› ለሚለው አማራጭ ትርጉም፣ 1) ስለ ያህዌና ስለ ሥራው የሚናገር ምሳሌያዊ አገላለጽ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱ ዘላለማዊ ነው›› ወይም 2) ዕንባቆም በራእዩ ያህዌ ሲመላለስ ማየቱን አመልካች ሊሆን ይችላል፤ በጥንት ጊዜ ያህዌ በዚሁ መንገድ ሲመላለስ መኖሩንም ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጥንቱ መንገድ ተመላለስ››

Habakkuk 3:7

አጠቃላይ መረጃ
ዕንባቆም የያህዌን ራእይ መግለጹን ቀጥሏል።

የኢትዮጵያ ድንኳኖች ሲጨነቁ፣ የምድያምም መኖሪያዎች ሲታወኩ አየሁ
አማራጭ ትርጉሞቹ፣ 1) ‹‹ድንኳን›› እና፣ ‹‹መኖሪያ›› የተሰኙ ቃሎች በእነዚህ ድንኳኖች የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በኢትዮጵያ ድንኳኖች የሚኖሩ ሰዎች ሲጨነቁ፣ በምድያም ምድር በድንኳኖች የሚኖሩ ሰዎች ሲታወኩ አየሁ›› ወይም 2) ድንኳኖቹ በመከራ የሚናወጡ ሰዎች የሆኑ ይመስል፣ ምናልባት እዚህም ላይ ዕንባቆም በኢትዮጵያና በምድያም ያሉ ድንኳኖች በማዕበል መናወጣቸውን ማመልከቱ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መከራ ውስጥ እንዳሉ ሰዎች የኢትዮጵያ ድንኳኖች ሲጨነቁ፣ የምድያም ምድር ድንኳኖችም እንደ ሰዎች ሲታወኩ አየሁ።››

ኩሻዊ
ይህ ቃል፣ 1) በእርግጠኝነት የማይታወቅ ሕዝብ መጠሪያ ወይም 2) ኩሽ እንደ ማለት ይሆናል።

በፈረሶችህና በድል አድራጊ ሠረገሎችህ በጋለብህ ጊዜ
‹‹ፈረሶችህ›› እና፣ ‹‹ድል አድራጊ ሠረገሎችህ›› የሚሉት ሐረጐች ስለ ተመሳሳይ ነገር ያመለክታሉ። ይህም ያህዌ በፈረሶችህ በሚጐተት ሠረገላ ወደ ጦር ሜዳ እንደሚገባ ጦረኛ መሆኑን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በፈረሶች በሚጐተት ሠረገላህ ወደ ድል ጋለብህ››

Habakkuk 3:9

አጠቃላይ መመሪያ
ዕንባቆም የያህዌን ራእይ መግለጹን ቀጥሏል።

ቀስትህን ከማኖሪያው አወጣው
ይህ ማለት ያህዌ ቀስቱን ከማኅደሩ አወጥቶ ለማስፈንጠር መዘጋጀቱን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቀስትህን ለማስፈንጠር ተዘጋጅህ

ምድርን በወንዞች ከፈልህ
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹በሚያልፉበት ቦታ ምድርን የሚከፍሉ ወንዞች ፈጠርህ›› ወይም 2) ‹‹ምድርን ከፈልህ፤ ወንዞችም ፈሰሱ›› ማለት ሊሆን ይችላል።

ተራሮች አዩህ፤ ተጨነቁም
የያህዌ መገለጥ ተራሮቹ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ በስቃይ እንደ ተጨነቁ ሰዎች እንዳደረጋቸው ተነግሮአል። ይህ ተራሮቹ በምድር መንቀጥቀጥ መናወጣቸውን ወይም ከማዕበሉ የሚነሣው ውሃ ተራሮቹን መሸርሸሩን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።

የውሃ ሞገድ ዐልፎ ሄደ
ይህም ማለት፣ 1) የዝናብ ወጀብ ተራቶች ላይ ወረደ ወይም 2) ዝናቡ ተራሮች ላይ የሚፈሱ ታላላቅ ጅረቶች ፈጠረ›› ማለት ሊሆን ይችላል

ቀላዩ ደነፋ
ነፋሱና ማዕበሉ በላዩ ሲያልፉ ባሕሩ ያሰማው ታላቅ ድምፅ፣ በከፍተኛ ድምፅ እንደሚደነፋ ሰው ዐይነት ነበር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጥልቁ ባሕር ጮኸ››

ማዕበሉንም ወደ ላይ አነሣ
ባሕሩ ውስጥ ያለው ውሃ ወደ ላይ መነሣትና ነፋሱ ባሕሩ ላይ ያስነሣው ማዕበል፣ ነፋሱ እንደ ሰው ማዕበሉን ወደ ላይ ማንሣቱን ያመለክታል።

Habakkuk 3:11

አጠቃላይ መረጃ
ዕንባቆም የያህዌን ራእይ መግለጹን ቀጥሏል

ፀሐይና ጨረቃም በቦታቸው ቆሙ
ፀሐይና ጨረቃ ጉዞአቸውን እንዳቆሙ ሰዎች እነርሱም በሰማይ ላይ መጓዛቸውን እንዳቆሙ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ፀሐይና ጨረቃ መንቀሳቀሳቸውን አቆሙ››

በቦታቸው
‹‹በሰማይ››

ከሚወረወሩ ፍላጾችህ፣ ከሚያብረቀርቅ የጦርህ ነጸብራቅ
እነዚህ ሁለት ሐረጐች አንድ ዐይነት ትርጉም አላቸው፤ ፀሐይና ጨረቃ የቆሙት ለምን እንደ ነበረም ይናገራሉ። ሰማይ ላይ የሚታየው የመብረቅ ብልጭታ ያህዌ ከቀስቱ የሚያስፈነጥራቸው ፍላጻዎች ወይም ሰማይ ላይ እንደሚወረወር አብረቅራቂ ጦር እንደ ነበር ይናገራል።

ከሚወረወሩ ፍላጾችህ
‹‹የሚወረወሩ ፍላጾችህ ነጸብራቅ››

መዓት
ግፍ የደረሰበት ሰው ቁጣ

ሕዝቦችን ረገጥሃቸው
ያህዌ ሕዝቦችን መቅጣቱ እነርሱን መርገጥ ማለት እንደ ሆነ ተነግሮአል። ረገጥሃቸው የሚለው ገለባውን ከእህል ለመለየት በሬዎች ወይም ሌሎች እንስሶች እህል ላይ የሚረማመዱበትን ሁኔታ ያመለክታል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Habakkuk 3:13

አጠቃላይ መረጃ
ዕንባቆም የያህዌን ራእይ መግለጹን ቀጥሏል። በዚህ ቁጥር ያለውን የመጨረሻ ዐረፍተ ነገር ለመተርጐም ያስቸግራል። ይህን ለመተርጐም ከታች ባሉ ዐረፍተ ነገሮች ያሉትን እያንዳንዱን የትርጒም ማስታወሻዎች ተመልከት።

ሕዝብህን ለመታደግ... ወጣህ
‹‹ለመታደግ›› የሚለውን ግሥ ማድረግ ቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕዝብህን ለማዳን ወጣህ››

የቀባኸውንም ለማዳን
‹‹አንተ የቀባኸውን›› ይህ ሐረግ ያህዌ የመረጠውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉሙ፣ 1) ‹‹አንተ የመረጥኸውን ሕዝብ›› ወይም፣ ‹‹አንተ የመረጥኸውን መንግሥት›› ወይም 2) ‹‹አንተ የመረጥኸውን ንጉሥ››

የክፋትን ቤት ራስ ቀጠቀጥህ፤ ከራስ ጠጕሩ እስከ እግር ጥፍሩም ዕርቃኑን አስቀረኸው
ይህም ማለት 1) መሪን መግደልና ሕዝቡን ማጥፋት ቤትን እንደ ማፍረስ መሆኑን ያሳያል። እዚህ ላይ መሪው ራስ ማለትም የቤቱ ጣራ ሲሆን፣ ‹‹እግር ጥፍር›› እና፣ ‹‹አንገት›› የቀረው የቤቱ አካል ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የዐመፅን ቤት ጣራ አፈረስህ፤ የቀረውንም የቤቱን አካል አወደምህ›› ወይም፣ ‹‹የዐመፅ መንግሥትን መሪ ገደልህ፤ መንግሥቱንም ፈጽሞ ደመሰስህ›› ወይም 2) መሪውን መግደልና ከሕዝቡም ክብርንና ኀይልን ማስወገድ የሰውን ራስ እንደ ማፍረስና ልብሱን መግፈፍ ማለት እንደ ሆነ ተነግሯል። እዚህ ላይ መሪው፣ ‹‹ራስ ሲሆን፣ ‹‹ቤት›› ደግሞ አካል የሆኑ ሰዎች ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ክፉ ሕዝብና መሪያቸው ራሱን እንዳፈረስኸው፣ ከእግሩ እስከ አንገቱ ዕርቃኑን እንዳስቀረኸው ሰው ናቸው›› ወይም፣ ‹‹የዐመፀኛ ሕዝብን መሪ ገደልህ፤ የሕዝቦንም ኀይል ፈጽመህ አስወገድህ››

Habakkuk 3:14

አጠቃላይ መረጃ
ዕንባቆም የያህዌን ራእይ መግለጹን ቀጥሏል።

የሰራዊት አለቃ ራስ፣ በገዛ ጦሩ ወጋህ
ይህ የሚናገረው ስለ ከለዳውያን መሪ ነው። ይህም ማለት፣ 1) ጦረኞቹ አካል ሲሆኑ፣ መሪው ደግሞ ራስ መሆኑን የሚያሳይ ምሳሌ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጦረኞቹን የሚመራውን በገዛ ራሱ ጦር ወጋህ›› ወይም 2) ‹‹ራስ›› የሚለው ቃል የእያንዳንዱን ጦረኛ ራስ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በመሪው ጦር የእያንዳንዱን ጦረኛ ራስ ወጋህ››

እንደ ዐውሎ ነፋስ... የመጣውን
የእስራኤልን ሕዝብ ሲያጠቁ የከለዳውያን ኀይልና ፍጥነት በድንገት ከሚመጣ ዐውሎ ነፋስ ጋር ተነጻጽሮአል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እንደ ማዕበል ፈጥነው ይመጣሉ››

ምስኪኑን በስውር በመዋጥ የሚደሰተውን
እዚህ ላይ፣ ‹‹ደስታ›› የሚለው በክፉ ሥራ ደስ መሰኘት ሲሆን፣ ግሥ አድርጐ መተርጐም ይቻላል። ጦረኞቹ ሕዝቡ ላይ ጭካኔ መፈጸማቸውና መግደላቸው፣ በስውር በማድባት ንጥቂያቸውን እንደሚውጡ አራዊት ተመስሎአል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በስውር ሕዝብን እንደሚወጡ አራዊት ደስ ይላቸዋል›› ወይም፣ ‹‹ድኾችን ሲጨቆኑ ደስ ይላቸዋል፤ ንጥቂያውን ዋሻው ውስጥ እንደሚበላ አውሬም ይበሏቸዋል››

ታላላቅ ውሆችን ከመርህ
ያህዌ ውሆችን ማናወጡ ውሆችን ከመከመር ጋር ተመሳስሎአል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ታላላቅ ውሆችን ከመርህ››

Habakkuk 3:16

አጠቃላይ መረጃ
ዕንባቆም በያህዌ ራእይ የተሰማውን መግለጹን ቀጥሏል።

እኔ ሰማሁ
ምናልባትም ዕንባቆም የሰማውን መግለጽ ትችላለህ። ይህም ማለት፣ 1) ‹‹በዚያ ራእይ ማንኛውንም ነገር ሰማሁ›› ወይም 2) ‹‹ያህዌ እንደ ታላቅ ዐውሎ ነፋስ ሲመጣ ሰማሁ›› ማለት ሊሆን ይችላል።

ልቤም ደነገጠብኝ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ልቤ›› የሚለው፣ ‹‹ሆዴ›› ማለትም ይሆናል። የምትናገረው ቋንቋ ታላቅ ፍርሃትን ለመግለጽ የሚጠቀምበት ውስጠኛ የአካል ክፍል ካለው በዚያ መጠቀም ትችላለህ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የልቤ ምት ፈጠነ›› ወይም፣ ‹‹ሆድ ዕቃዬ ተገላበጠ››

ከንፈሬ ከድምፁ የተነሣ ተንቀጠቀጠ
የከንፈር መንቀጥቀጥ ከታላቅ ፍርሃት ጋር የሚመጣ ሌላው ድንገተኛ ምላሽ ነው።

ፍርሃት እስከ ዐጥንቴ ዘልቆ ገባ
ዕንባቆም የተሰማውን ደካማነት ፍርሃት ወደ ዐጥንቱ ዘልቆ ከመግባት ጋር አስመስሎታል። እዚህ ላይ በቋንቋህ ያለውን ፈሊጣዊ አነጋገር መጠቀም ትችላለህ

እግሬም ተብረከረከ
‹‹እግሬ›› የሚለው ከበታቹ ያለውን ነገር ያመለክታል። ይህም ማለት፣ 1) ‹‹እግሬ ተንቀጠቀጠ›› ወይም 2) ‹‹በቆምሁበት ተንቀጠቀጥሁ›› ማለት ሊሆን ይችላል።

Habakkuk 3:17

አጠቃላይ መረጃ
ዕንባቆም በያህዌ ራእይ የተሰማውን መግለጽ ቀጥሏል

የወይራ ዛፍ ፍሬ ባይሰጥ
‹‹የወይራ ዛፍ ባያፈራ›› ወይም፣ ‹‹የወይራ ዛፍ ፍሬ ቢነፍግም››

የበጎች ጕረኖ እንኳ ባዶውን ቢቀር
‹‹ጕረኖ›› የበጎችና የፍየሎች መኖሪያን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጎች ሁሉ ቢሞቱ፤ ጕረኖውም ባዶውን ቢቀር››

Habakkuk 3:18

አጠቃላይ መረጃ
ዕንባቆም በያህዌ ራእይ የተሰማውን መግለጽ ቀጥሏል፤ እርሱን ለማመስገንም ወስኖአል።

የድነቴ አምላክ
‹‹ድነት›› የሚለውን ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሚያድነኝ አምላክ››

እግሮቼን እንደ ዋላ እግሮች ያደርጋል፤ በከፍታዎችም ላይ ያስሄደኛል
ያህዌ እንደሚጠብቀውና በአስቸጋሪ ዘመን ውስጥ ማለፍ እንደሚስችለው ለማሳየት ዕንባቆም ድንጋያማና አደገኛውን ተራራ በቀላሉ መውጣት እንደሚችል የዋላ እግር እንደሚያደርገው ይናገራል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Zephaniah

Zephaniah

Chapter 1

1 ይህ በይሁዳ ንጉሥ በአሞን ልጅ በኢዮስያስ ዘመን፣ ወደ ሕዝቅያስ ልጅ፣ ወደ አማርያ ልጅ፣ ወደ ጐዶልያስ ልጅ፣ ወደ ኩሲ ልጅ፣ ወደ ሶፎንያስ የመጣ የያህዌ
ቃል ነው። 2 «ማንኛውንም ነገር ከምድር ገጽ ፈጽሜ አጠፋለሁ! ይላል ያህዌ 3 ሰውንና እንስሳን አጠፋለሁ፤ የሰማይን ወፎችና የባሕር ዓሦች አጠፋለሁ።
ሰውን ከምድር ገጽ በማስወግድበት ጊዜ ክፉዎች የፍርስራሽ ክምር ይሆናሉ ይላል ያህዌ። 4 እጄን በይሁዳና በኢየሩሳሌም በሚኖሩ ሁሉ ላይ እዘረጋለሁ።
የበአልን አምልኮ ርዝራዥ፣ የጣዖቶቹንና የአመንዝራ ካህናቱን ስም ከዚህ ቦታ አጠፋለሁ ስም ሁሉ ከዚህ ቦታ አጠፋለሁ፤ 5 በየቤቶቹ ጣራ የሰማይን ሰራዊት
የሚያመልኩትን፣ በያህዌ ስም እየማሉ ደግሞም በሜልኮም የሚምሉትን ሕዝብ አጠፋለሁ። 6 ያህዌን ከመከተል ወደ ኋላ የሚሉትን፣ ያህዌን የማይፈልጉትንም
ሆነ ከእርሱ ምሪት የማይፈልጉትን አጠፋለሁ።» 7 የያህዌ ቀን እየቀረበ ነውና በጌታ ያህዌ ፊት ጸጥ በሉ፤ ያህዌ መሥዋዕት አዘጋጅቷል፤ የጠራቸውንም
እንግዶች ቀድሷል። 8 በያህዌ የመሥዋዕት ቀን መኳንንቱንና የንጉሡን ልጆች፣ እንግዳ ልብስ የሚለብሱትንም ሁሉ እቀጣለሁ። 9 በዚያን ቀን፣ በመድረኩ ላይ
የሚዘልሉትን ሁሉ፣ የጌቶቻቸውን ቤት በዐመፅና በማጭበርበር የሚሞሉትንም ሁሉ እቀጣለሁ። 10 በዚያን ቀን ይላል ያህዌ፣ ከዓሣው በር ጩኸት፣ ከሁለተኛው
አደባባይ ዋይታ፣ ከኮረብቶችም ታላቅ የጥፋት ድምፅ ይሰማል። 11 እናንት በገበያው ቦታ የምትኖሩ ዋይ በሉ፤ ነጋዴዎች ሁሉ ይደመሰሳሉ፤ በብር
የሚነግዱትም ሁሉ ይጠፋሉ።› 12 በዚያ ዘመን፣ ኢየሩሳሌምን በመብራት እፈትሻለሁ፤ ወይን ጠጅ የሚያዘወትሩንና በልባቸው፣ «ክፉም ሆነ መልካም ያህዌ
ምንም አያደርግም» የሚሉትን ሰዎች እቀጣለሁ።» 13 ሀብታቸው ይዘረፋል፤ ቤቶቻቸውም ይፈርሳሉ፤ ቤት ይሠራሉ፤ ሆኖም፣ አይኖሩበትም፤ ወይን ይተክላሉ
የወይን ጠጁን ግን አይጠጡም። 14 ታላቁ የያህዌ ቀን ቀርቧል፤ እጅግ እየፈጠነ ነው፤ የያህዌ ቀን ድምፅ ጦረኞች አምርረው የሚያለቅሱበት ይሆናል፤ 15 ያ
ቀን የቁጣ፣ የመከራና የጭንቀት፣ የጥፋትና የመፍረስ፣ የጨለማና የጭጋግ፣ የደመናና የድቅድቅ ጨለማ ቀን ይሆናል። 16 በዚያ ቀን በተመሸጉት ከተሞችና
በረጃጅም ግንቦች ላይ የጦር መለከትና የማስጠንቀቂያ ድምፅ ይሰማል። 17 እንደ ዕውሮች እስኪደናበሩ ድረስ በሰዎች ላይ ታላቅ ጭንቀት አመጣለሁ፤ ያህዌ
ላይ ኃጢአት አድርገዋልና ደማቸው እንደ ውሃ ይፈስሳል፤ ሬሳቸውም እንደ ጉድፍ የትም ይጣላል። 18 ብራቸውም ሆነ ወርቃቸው ሊያድናቸው አይችልም፤ ያህዌ
ቁጣውን በሚገልጥበት ቀን የቁጣው እሳት ምድርን ሁሉ ይበላል፤ ይህም የሆነው በምድር በሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ላይ በድንገት ጥፋት ስለሚመጣ ነው።»

Zephaniah 1:1

አጠቃላይ መረጃ:- የመጣው የያህዌ ቃል
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ከእግዚአብሔር የመጣ ጠቃሚ መልእክት ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ መልእክት ሰጠ›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ይህን መልእክት ተናገረ››

ያህዌ
ይህ በብሉይ ኪዳን ዘመን ለሕዝቡ የገለጠው የእግዚብሔር ስም ነው። ይህን እንዴት እንደምትተረጉም፤ ስለ ያህዌ ከቃላት ትርጉም ገጽ ተመልከት።

የጐዶልያስ ልጅ፤ የአማርያ ልጅ፤ የሕዝቅያስ ልጅ
ይህ የሶፎንያስ ዘሮች ዝርዝር ነው። ይህ ‹‹የ... ልጅ›› የሚለው ሐረግ ሰፋ ባለ መልኩ፣ ‹‹...ትውልድ›› ማለት ነው። እዚህ ላይ፣ ‹‹ሕዝቅያስ›› የሚለው ንጉሥ ሕዝቅያስን ያመለክታል። ይህን በጣም ግልጽ ማድረግ ይቻላል፤ ‹‹ከሕዝቅያስ የተወለደው የአማርያ የልጅ ልጅ የጐዶልያስ ልጅ።››

ማንኛውንም ነገር ከምድር ላይ አጠፋለሁ... ሰውን ከምድር ገጽ በማስወግድበት ጊዜ
‹‹ማንኛውም ነገር›› እና ‹‹ሰውን ከምድር በማስወግድበት ጊዜ›› የተሰኙ ቃሎች ምን ያህል በሰዎች ኀጢአት መቆጣቱን ለማሳየት ሆን ብሎ ያህዌ የተጠቀመባቸው ናቸው። ያህዌ ንስሐ የማያደርጉ ኀጢአተኞችንና ሕይወት ያላቸው ነገሮችን ሁሉ ያጠፋል።

ከምድረ ገጽ ማንኛውንም ነገር ማጥፋት
‹‹በመላው ምድር ላይ ያለውን ማንኛውንም ነገር ማጥፋት››

ይህ የያህዌ ቃል ነው
የተናገረው በእርግጥ መሆኑን ለማመልከት ያህዌ ስሙን በማንሣት ስለ ራሱ ይናገራል። ‹‹ያህዌ እንዲህ አለ›› ወይም፣ ‹‹እኔ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ።››

ሰውንና እንስሳን
‹‹ሕዝብንና እንስሳን››

ማጥፋት
ተቃራራቢ ትርጉሙ 1) ከፍርዱ በኃላ የሚቀረውን የፍርስራሽ ክምር ወይም 2) ያህዌ የሚያጠፋቸው ጣዖቶችን ሊያመለክት ችላል።

መቁረጥ
ስለ ማጥፋት ሲናገር አንድ ነገር ከአካሉ ቆርጦ ስለ መጣል ይናገራል።
‹‹ማስወገድ››

Zephaniah 1:4

አጠቃላይ መረጃ
ቁጥር 1፥2-18 የያህዌን ፍርድ ያመለክታል። ቁጥር 1፥4-16 ያህዌ የይሁዳ ሕዝብ ላይ የሚያመጣውን ፍርድ ያመለክታል።

እጄን በይሁዳ ላይ... አነሣለሁ
ይህ እግዚአብሔር እንደሚቀጣ የሚያመለክት ፈሊጥ ነው። ‹‹ይሁዳን እቀጣለሁ››

የበአልን ትሩፍ፣ የጣዖታቱንና የአመንዝራ ካህናቱን ስም... በሰገነት ላይ ወጥተው የሚሰግዱትን... የሚሰግዱትንና የሚምሉትን... አጠፋለሁ
‹‹አጠፋለሁ›› የሚለው ግሥ የሚያመለክተው እነዚህን ሐረጐች ሁሉ ቢሆንም፣ ድግግሞሽን ለማስወገድ ሲባል ጥቅም ላይ የዋለው አንዴ ብቻ ነው። ‹‹የበአልን ትሩፍ፣ የጣዖታቱንና የአመንዝራ ካህናቱን ስም... በሰገንት ላይ ወጥተው የሚሰግዱትን... የሚሰግዱትንና የሚምሉትን... አጠፋለሁ››

መቁረጥ
ማጥፋት አንድን ነገር ከአካሉ ቆርጦ መጣል ማለት እንደ ሆነ ተነግሮአል። ሶፎንያስ 1፥3 ላይ ይህን እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። ‹‹ማስወገድ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የአመንዝራ ካህናቱን ስም ሁሉ ከዚህ ስፍራ አጠፋለሁ።
እዚህ ላይ ስማቸውን አጠፋለሁ ሲባል ሰዎች እንዲረሷቸው አደርጋለሁ ማለት ነው። ‹‹ጣዖት የሚያመልኩትን ካህናት ሰዎች ሁሉ እንዲረሷቸው አደርጋለሁ››

በንጉሣቸው
‹‹በሚልኮምም›› ለሚለው አማራጭ ትርጉም ለማግኘት የግርጌ ማስታወሻውን ተመልከት።

ያህዌን አልፈለጉም፤ እንዲመራቸውም አልጠየቁም
ያህዌን መፈለግ 1) ከእግዚአብሔር ርዳታ መለመን ወይም 2) ስለ እግዚአብሔር ማሰብና ለእርሱ መታዘዝን ያመለክታል። ስለ ያህዌ አላሰቡም ወይም እንዲመራቸው አልለመኑም።

Zephaniah 1:7

አጠቃላይ መረጃ
ቁጥር 1፥2-18 የያህዌን ፍርድ ያመለክታል። ቁጥር 1፥4-16 በይሁዳ ሕዝብ ላይ የያህዌን ፍርድ ያሳያል።

አጠቃላይ መረጃ
ቁጥር 1፥8-13 ላይ ያህዌ ሲናገር እንመለከታለን። ስለ ራሱ ሲናገር በመጀመሪያና በሦስተኛ ሰው ይጠቀማል።

ዝም በሉ
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። እዚህ ላይ ዝምታ የድንጋጤና የመደነቅ ምልክት ነው። ‹‹ደንግጡ››

ያህዌ መሥዋዕት አዘጋጅቶአል፤ እንግዶቹንም ቀድሶአል
የይሁዳ ሰዎች እንደ ያህዌ መሥዋዕት ጠላት የሆኑት ሕዝብ መሥዋዕቱን እንደሚበሉ የእርሱ እንግዶች ተገልጠዋል። በጣም ግልጽ በሆነ ሁኔታ ይህ፣ ‹‹ያህዌ የይሁዳን ሕዝብ እንደ መሥዋዕት አዘጋጅቶአል፤ ጠላት የሆኑትን ሕዝብ በእንግድነት ጠርቷል›› ሊባል ይችላል።

እንግዶቹንም ቀድሶአል
እዚህ ላይ፣ ‹‹ቀድሶአል›› ወደ ግብዣ ጠርቷል ለማለት ጥቅም ላይ የዋለ ፈሊጣዊ ንግግር ነው።

አዘጋጅቶአል
ይህ ቃል ይሁዳ ላይ የያህዌ ፍርድ የሚጀመርበትን ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል።

እንግዳ ልብስ የሚለብሱትን ሁሉ
ለባሕላቸው ያላቸውን ፍቅርና ባዕዳን ጣዖቶቻቸውን ማምለካቸውን ለማሳየት እስራኤላውያን ከባዕዳን ጋር የሚመሳሰል ልብስ መልበሳቸውን የሚያመለክት ሐረግ ነው። ‹‹ባዕዳን ጣዖታትን የሚያመልኩ ሁሉ››

በዚያን ቀን
‹‹በያህዌ ቀን››

በመድረኩ ላይ የሚዘሉትን ሁሉ
አማራጭ ትርጉሞቹ፣ 1) ይህ ዳጐን የሚባለውን ለማምለክ መድረኩ ላይ የዘለሉትን ሰዎች የሚያመለክት ነው፤ ወይም 2) የአረማውያንን አማልክት ለማምለክ መድረኩ ላይ የዘለሉትን ሰዎች ያመለክታል፤ ወይም 3) ወደ ዙፋን የወጡ ንጉሣውያን ባለ ሥልጣኖች ያመለክታል።

የአማልክቶቻቸውን ቤት በዐመፅና በማጭበርበር የሚሞሉትን እቀጣለሁ
‹‹ዐመፅ›› እና ‹‹ማጭበርበር›› የተሰኙት ድርጊትን ያመለክታሉ። ‹‹ዐመፅ የሚያደርጉና በአማልክቶቻቸው ቤተ መቅደስ ውስጥ የሚዋሹትን እቀጣለሁ።››

Zephaniah 1:10

አጠቃላይ መረጃ
ቁጥር 1፥2-18 የያህዌን ፍርድ ያመላክታሉ። ቁጥር 1፥4-16 በይሁዳ ላይ የያህዌን ፍርድ ያመለክታሉ።

አጠቃላይ መረጃ
ቁጥር 1፥8-13 ላይ ያህዌ ይናገራል። የሚናገረው የመጀመሪያ መጠሪያን በመጠቀምና ስለ ራሱ በሦስተኛ መጠሪያ በመናገር ነው።

በዚያን ቀን
‹‹የያህዌ ቀን›› ሶፎንያስ 1፥9 የተረጐምህበትን ሁኔታ ተመልከት።

የያህዌ አነጋገር
እየተናገረ ያለው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳየት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። ‹‹ያህዌ የተናገረው›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ በመሐላ የተናገረው››

የዓሣ በር
የዓሣ በር በኢየሩሳሌም ከተማ ግንብ ከነበሩ በሮች አንዱ ነው።

በሁለተኛው አደባባይ ዋይታ
‹‹በሁለተኛው አደባባይ... ዋይ በሉ።›› ‹‹ሁለተኛው በር›› አዲሱ የኢየሩሳሌም ክፍል ነው።

ታላቅ ሽብር ይሰማል
ይህ የሚያመለክተው ግንቡ ሲወድቅ የሚሰማውን ጩኸት ነው። ይህን፣ ‹‹ግንቡ ሲወድቅ የሚኖረው ታላቅ ድምፅ›› በማለት መተርጐም ይቻላል።

ከኮረብቶችም
ይህ የሚናገረው ኢየሩሳሌም ዙሪያ ስላሉት ኮረብቶች ነው።

ነጋዴዎቻችሁ ሁሉ ይደመሰሳሉ፤ በብር የሚነግዱትም ሁሉ ይሞታሉ።
እነዚህ ሁለት ሐረጐች የሚናገሩት ስለ አንድ ሕዝብ ሲሆን፣ ንግዳቸው እንደሚጠፋ አጽንዖት ለመስጠት ጥቅም ላይ ውለዋል። ‹‹ዕቃዎችን የሚገዙና የሚሸጡ ይገደላሉ።››

በብር የሚነግዱ
ይህ የሚመለከተው ነጋዴዎችን ነው። ሳንቲሞች ከመሠራታቸው በፊት ለገዙት ዕቃ ለመክፈል ሰዎች ብርና ወርቅ ይመዝኑ ነበር።

ይደመሰሳሉ
አንድን ነገር ከአካሉ ቆርጦ መጣልን በሚያመለክት ሁኔታ ይደመሰሳሉ በሚለው ቃል ተጠቅሞአል። ይህን ሶፎንያስ 1፥3 ላይ ከተረጐምህበት ሁኔታ ተመልከት። ‹‹አጠፋለሁ››

Zephaniah 1:12

አጠቃላይ መረጃ
ቁጥር 1፥2-18 ስለ ያህዌ ፍርድ ይናገራል። ቁጥር 1፥4-16 የይሁዳ ሕዝብ ላይ ስለሚመጣው የያህዌ ፍርድ ይናገራል።

አጠቃላይ መረጃ
ቁጥር 1፥8-13 ላይ ያህዌ ይናገራል። የሚናገረው የመጀመሪያ መጠሪያ በመጠቀምና ስለ ራሱ በሦስተኛ መጠሪያ በመጠቀም ነው።

በዚያ ዘመን ይሆናል
ይህ ሐረግ ጥቅም ላይ የዋለው ኢየሩሳሌም በጠላቶቿ የተደመሰሰችበትን ጊዜ ለማመልከት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ኢየሩሳሌምን በመብራት እፈትሻለሁ
መብራት አብርቶ የሚያያቸው ይመስል ያህዌ ስለ ኢየሩሳሌም ሰዎች ሁሉ እንደሚያውቅ ያህዌ ይናገራል።

በዝቃጭ ላይ እንደ ቀረ የወይን ጠጅ የሆኑትን
ከመከራ ሁሉ ያረፉ ይመስላቸዋል።

‹ክፉም ሆነ መልካም ያህዌ ምንም አያደርግም› ይላሉ
ይህን ቀጥተኛ ጥቅስ፣ ‹‹በልባቸውም ክፉም ሆነ መልካም ያህዌ ምንም አያደርግም›› በማለት ቀጥተኛ ባልሆነ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል።

በልባቸው… ይላሉ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር እንዲህ በማለት ያስባሉ ማለት ነው።

ክፉም ሆነ መልካም ያህዌ ምንም አያደርግም
እዚህ ላይ፣ ‹‹ክፉም ሆነ መልካም›› ሲል በመካከል ያሉትን ሁሉ ይጨምራል። ‹‹እግዚአብሔር ምንም አያደርግም››

ሙሉ በሙሉ ይደመሰሳል
‹‹ምንም የሚቀር የለም››

Zephaniah 1:14

አጠቃላይ መረጃ
ሶፎንያስ 1፥2-18 የያህዌን ፍርድ ያመለክታል። ቁጥር 1፥4-16 በይሁዳ ሕዝብ ላይ የሚመጣውን የያህዌ ፍርድ ያመለክታል።

ቅርብ ነው፤ ቅርብ ነው፤ ፈጥኖም ይመጣል
‹‹ቅርብ›› የሚለው ቃል መደጋገምና፣ ‹‹ፈጥኖም ይመጣል›› የሚለው ሐረግ ያህዌ ሕዝቡ ላይ የሚፈርደው በቅርቡ መሆኑን አጽንዖት ይሰጣል። ‹‹ሳይውል ሳያድር ቶሎ ይሆናል››

የያህዌ ቀን
ሶፎንያስ 1፥7 የተረጐምህበትን ሁኔታ ተመልከት።

ጦረኛው ምርር ብሎ ይጮኻል
አማራጭ ትርጉሙ 1) ተስፋ በመቁረጥ የሚጮኽ ወታደር፤ ወይም 2) የወታደር የጦርነት ጩኸት ሊሆን ይችላል።

ያ ቀን… ቀን
እነዚህ ቃሎች ቁጥር 14 ላይ ያለውን፣ ‹‹የያህዌ ቀን›› ያመለክታሉ።

ያ ቀን የመዓት ቀን የውጊያ ቀን
ቁጥር 15-16 በአንድነት ሆነው ስለዚህ የመጨረሻ የእግዚአብሔር ፍርድ የሚያስከትለው ከባድ ጥፋት አጽንዖት የሚሰጡ የተለያዩ የአነጋገር መንገዶች አሉት።

የመከራና የጭንቀት ቀን
‹‹መከራ›› እና ‹‹ጭንቀት›› የተሰኙት ቃሎች የሚያመለክቱት ስለ ተመሳሳይ ነገር ቢሆንም፣ ስለ ሕዝቡ ጭንቀት ከባድ መሆን አጽንዖት ይሰጣሉ። ‹‹ሰዎች ከባድ ጭንቀት ውስጥ የሚሆኑበት ቀን››

የሁከትና የጥፋት ቀን
እዚህ ላይ፣ ‹‹ሁከት›› የሚያመለክተው መለኮታዊ ፍርድን ነው። ‹‹ጥፋት›› የሚለው ቃል የዚያን ፍርድ ውጤት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አውዳሚ የሁከት ቀን›› ወይም፣ ‹‹አውዳሚ ፍርድ››

የጨለማና የጭጋግ ቀን
‹‹ጨለማ›› እና ‹‹ጭጋግ›› ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ የጨለማውን ከባድነት ያመለክታል። ሁለቱም የሚያመለክቱት የጥፋት ወይም የመለኮታዊ ፍርድን ጊዜ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጨለማ የዋጠው ቀን›› ወይም ‹‹አስፈሪ የፍርድ ቀን››

የደመናና የድቅድቅ ጨለማ ቀን
ይህኛውም የሚናገረው ስለ ተመሳሳይ ሁኔታ ሲሆን፣ ቀደም ሲል የነበረውን ሐረግ ሐሳብ ያጠናክራል። ‹‹ደመና›› እና፣ ‹‹ድቅድቅ ጨለማ›› የተሰኙትን የመሳሰሉ ሐረጐች መለኮታዊ ፍርድን ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጥቁር ደመና የሞላበት ቀን››

የመለከት ድምፅና የጦርነት ጩኸት የሚሰማበት ቀን
‹‹መለከት›› እና፣ ‹‹የጦርነት ጩኸት›› የተሰኙት ቃሎች እዚህ ላይ የሚያሳዩት ተመሳሳይ ነገርን ነው። ሁለቱም ወታደሮች ለጦርነት እንዲዘጋጁ መጥሪያ መንገዶች ናቸው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች የጦርነት ጥሪ የሚያሰሙበት ቀን››

በተመሸጉ ከተሞችና በረጃጅም ግንቦች ላይ
ሁለቱም ሐረጐች የሚያመለክቱት ወታደራዊ ምሽጐችን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሚገባ የተመሸጉ ከተሞች››

Zephaniah 1:17

አጠቃላይ መረጃ
1፥2-18 የያህዌን ፍርድ ያመለክታል። 1፥17-18 በእያንዳንዱ ጎጢአተኛ ላይ ወደ ፊት የሚመጣውን የመጨረሻ የያህዌ ፍርድ ያመለክታል።

እንደ ዕውር እንዲራመዱ
ከያህዌ ፍርድ የተነሣ ሰዎች ግራ ይጋባሉ፤ እነርሱ ሲራመዱ የሚመለከቱ ሰዎች ዕውር እንደ ሆኑ ያስባሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዐይናቸው እንደ ታወረ ሰዎች ግራ በመጋባት ይመላለሳሉ››

ደማቸው እንደ ትቢያ ይፈስሳል
የሚፈሰሰው ደማቸው እንደ ትቢያ ዋጋ ቢስ ነው። ይህን፣ ‹‹የሚፈስሰው ደማቸውን ጠላቶቻቸው እንደ ትቢያ ይቆጥሩታል›› በማለት መተርጐም ይቻላል።

ሥጋቸውም እንደ ጉድፍ ይጣላል
እዚህ ላይ፣ ‹‹ይፈስሳል›› የሚለው ግልጽ ሆኗል። ይህን፣ ‹‹ጠላቶቻቸው ሥጋቸውን ይቆርጣሉ፤ እንደ ጉድፍ እንዲበሰብስም ያደርጋሉ›› በማለት መተርጐም ይቻላል።

የቅንዓቱ እሳት
‹‹እሳት›› የያህዌን ቁጣ ከባድነት ያመለክታል። ይህን፣ ‹‹ቅንዓቱ እንደ ታላቅ እሳት ነው›› በማለት መተርጐም ይቻላል።

በምድር በሚኖሩ ሁሉ ላይ
ይህ የሚያመለክተው ዐመፀኞችን መሆኑ ግልጽ ነው። ይህንን፣ ‹‹በምድር የሚኖሩ ዐመፀኞች ሁሉ›› በማለት የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 እናንት ዕፍረት የሌላችሁ ሕዝብ ሆይ፣ በአንድነት ተሰብሰቡ ተከማቹም፤ **2** የወሰነው ጊዜ ሳይደርስ፣ ቀኑ እንደ ገለባ ሳይጠራርጋችሁ፣ የያህዌ ቁጣ በእናንተ ላይ ሳይመጣና የያህዌ መዓት ቀን ሳይደርስባችሁ ተሰብሰቡ። **3** እናንተ ትእዛዙን የምትፈጽሙ በምድር ያላችሁ ትሑታን ሁሉ ያህዌን ፈልጉ፤ ጽድቅንና ትሕትናንም ፈልጉ፤ በያህዌ ቀን ምናልባት ጥበቃ ታገኙ ይሆናል። **4** ጋዛ ባድማ ትሆናለች፤ አስቀሎናም ትፈራርሳለች፤ አሽዶድ በቀትር ባዶ ትሆናለች፤ አቃሮንም ትነቀላለች። **5** እናንተ በባሕር ዳርቻ የምትኖሩ የከሌታውያን ሰዎች ሆይ፣ የፍልስጥኤማውያን ምድር ከነዓን ሆይ፣ ያህዌ እናንተ ላይ ተናግሯልና ወዮላችሁ፤ ከእናንተ ማንም እስከማይተርፍ ድረስ አጠፋችኃለሁ። **6** የባሕሩ ዳርቻ የእረኞች መሰማርያና የበጎች በረት ይሆናል። **7** የባሕሩ ዳርቻ ከይሁዳ ቤት ለተረፉት ይሆናል፤ እነርሱም በዚያ መንጐቻቸውን ያሰማሩበታል። በአስቀሎና ቤቶች ውስጥ በምሽት ይተኛሉ፤ አምላካቸው ያህዌ ይጠብቃቸዋል፤ ሀብታቸውንም ይመልሳል። **8** በሕዝቤ ላይ የደረሰውን የሞዓብን ሕዝብ ፌዝና የአሞናውያንን ንቀት ሰምቻለሁ፤ ሕዝቤን ሰድበዋል፤ ርስታቸውን ለመውሰድም ዝተዋል። **9** ስለዚህ ይላል የሰራዊት ጌታ፣ የእስራኤል አምላክ ያህዌ፣ የሞዓብ ሕዝብ እንደ ሰዶም፣ አሞናውያንም እንደ ገሞራ ዐረም እንደ ዋጠው ቦታና እንደ ጨው ጉድጓድ ለዘላለም ጠፍ እንደሚሆኑ በሕያውነቴ እምላለሁ፤ ከሕዝቤ የተረፉት ይዘርፏቸዋል፤ ከወገኔ የተረፉትም ምድራቸውን ይወርሳሉ። **10** ከትዕቢታቸው የተነሣ፣ የሰራዊት ጌታ ያህዌ ሕዝብ ላይ በማፌዛቸውና እነርሱንም በመስደባቸው የሞዓብና የአሞን ሕዝብ ላይ ይህ ይሆናል። **11** እርሱ የምድሪቱን አማልክት በሚያጠፋበት ጊዜ፣ ያህዌ በእነርሱ ዘንድ የተፈራ ይሆናል። በባሕሩ ጠረፍና በየምድራቸው የሚኖሩ ሁሉ በያሉበት ያመልኩታል። **12** እናንተ ኢትዮጵያውያንም በሰይፌ ትገደላላችሁ፣ **13** የእግዚአብሔር እጅ ሰሜንን ይመታል፤ አሦርንም ያጠፋል፤ ነነዌን ባድማ ያደርጋል፤ እንደ ምድረ በዳም ትደርቃለች። **14** የአራዊት መንጋዎች፣ የአሕዛብ እንስሶች ሁሉ አሦር ውስጥ ያርፋሉ፤ ወፎችና ልዩ ልዩ ዐይነት ጉጉቶች በጉልላትዋ ላይ ይሰፍራሉ። ጩኸታቸው በየመስኮቱ ያስተጋባል፤ ከዝግባ የተሠሩ ተሸካሚዎች ተገልጠዋልና ቁራዎች በየደጃፎቻቸው ይጮኻሉ። **15** ይህች በልቧ «እኔ ብቻ ነኝ፤ ከእኔ በቀር ማንም የለም» ያለች ያለ አንዳች ፍርሃት ተደላድላ ትኖር የነበረች ከተማ ነች። ታዲያ፣ እንዴት የዱር አራዊት የሚኖሩባት ባድማ ሆና ቀረች? በአጠገቧ የሚያልፉ ሁሉ ያፌዙባታል፤ እጃቸውንም በንቀት ያወዛውዙባታል!

Zephaniah 2:1

አጠቃላይ መረጃ
2፥1-3 ላይ ያህዌ ለይሁዳ መናገሩን ቀጥሏል፤ ንስሐ እንዲገቡ ይነግራቸዋል።

በአንድነት ተሰብሰቡ
እነዚህ ሁለት ቃሎች ተመሳሳይ ናቸው። በጎጢአታቸው ንስሐ ለመግባት ሰዎች በአንድነት እንዲሰበሰቡ የተሰጠውን ትእዛዝ ያጠናክራሉ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሁላችሁም በአንድነት ተሰብሰቡ››

እፍረት የሌላችሁ ሕዝብ
ሕዝቡ በጎጢአታቸው አላዘኑም

የተወሰነው ጊዜ ሳይደርስ
ይህ ያህዌ በወሰነው ጊዜ የሚመጣውን ቅጣት ነው የሚያመለክተው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ እናንተን ከመቅጣቱ በፊት››

ያ ቀን... የያህዌ ጽኑ ቁጣ... የያህዌ የመዐት ቀን
እነዚህ ሐረጐች ሁሉም የሚያመለክቱት፣ ‹‹የያህዌ ቀን››ን ነው። እነዚህን ሐረጐች ሶፎንያስ 1፥7-9 ላይ ተመሳሳይ ሐረጐችን በተረጐምህበት ሁኔታ ተርጕማቸው።

ቀኑ እንደ ገለባ ሳይጠራርጋችሁ
ገለባ ነፋስ ጠርጐ የሚወስደው የማያስፈልግ የፍሬው አካል ነው። በተመሳሳይ መንገድ የፍርድ ቀን ቶሎ ይመጣል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ገለባ በነፋስ እንደሚጠረግ ያ ቀን በፍጥነት ይመጣል።

የያህዌ ጽኑ ቁጣ በእናንተ ላይ ሳይመጣ፤ የያህዌ የመዓት ቀን ሳይደርስባችሁ››
የያህዌ ፍርድ ምን ያህል ከባድ መሆኑን ለማመልከትና ሰዎች በአስቸኳይ ንስሐ እንዲገቡ አጽንዖት ለመስጠት ነቢዩ በጣም የሚመሳሰሉ ሐረጐች ተጠቅሟል።

የያህዌ ቁጣ
ይህ የእግዚአብሔርን ቅጣት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የያህዌ ቅጣት››

ያህዌን እሹ
ያህዌን መሻት፣ 1) የእግዚአብሔርን ርዳታ መለመንን ወይም 2) ስለ እግዚአብሔር ማሰብንና ለእርሱ መታዘዝን ይወክላል።

ጽድቅንና ትሕትናን ፈልጉ
‹‹ጽድቅ›› እና፣ ‹‹ትሕትና›› የተሰኙት ድርጊትን የሚያመለክቱ ናቸው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ትክክል የሆነውን ለማድረግና ትሑት ለመሆን ፈልጉ››

በያህዌ የቁጣ ቀን ትሰወሩ ይሆናል
ይህን፣ ‹‹በቁጣው ቀን ያህዌ ይሰውራችኃል›› በማለት መተርጐም ይቻላል።

Zephaniah 2:4

አጠቃላይ መረጃ
2፥4-15 ላይ ያህዌ በይሁዳ ዙሪያ ባሉ አገሮች ላይ ስለሚመጣው የእርሱ ፍርድ ይናገራል።

ጋዛ... አስቀሎና... አሽዶድ... አቃሮን
እነዚህ በዚያ ዘመን የነበሩ አራቱ የፍልስጥኤም ከተሞች ናቸው።

ባድማ ይሆናሉ... ይፈራርሳሉ
የእነዚህ ሁለት ሐረጐች ትርጉም ተመሳሳይ ሲሆን፣ እነዚህ ከተሞች ሙሉ በሙሉ እንደሚጠፉ አጽንዖት ይሰጣል።

አሽዶድ በቀትር ትባረራለች
እዚህ ላይ ‹‹እነርሱ›› የሚለው የፍልስጥኤማውያንን ጠላቶች ነው። ‹‹ቀትር›› ለሚለው አማራጭ ትርጕም፣ 1) ጠላቶች አሽዶድን ከቀትር በፊት ድል ያደርጓታል፤ ወይም 2) ሕዝቡ ዕረፍት ላይ እያሉና ምንም ሳያስቡ ጠላቶች አሽዶድን በቀትር ያጠቋታል የሚል ሊሆን ይችላል።

አቃሮንም ትነቀላለች
የአቃሮን መሸነፍ ከመሬት ተነቅሎ በሚጣል ዛፍ ተመስሎአል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የአቃሮንን ሰዎች ዛፍ ከሥሩ እንደሚነቀል ይነቅሏቸዋል›› ማለት ለሆን ይችላል።

በባሕር ዳርቻ የምትኖሩ የከሊታውያን ሰዎች
የመጀመሪያው ሐረግ ከሊታውያን የሚኖሩበትን ይመለክታል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የፍልስጥኤማውያን ምድር ከነዓን
ፍልስጥኤማውያን በከነዓን ከሚኖሩ ሕዝቦች አንዱ ነበሩ

ከነዋሪዎችሽም የሚተርፍ የለም
‹‹ምንም እስከማይተርፍ ድረስ›› - ይህ፣ ‹‹ነዋሪዎቿ ሁሉ ይሞታሉ›› ተብሎ ሊተረጐም ይችላል።

Zephaniah 2:6

አጠቃላይ መረጃ
2፥4-15 ላይ ያህዌ በይሁዳ ዙሪያ ባሉ አገሮች ላይ ስለሚመጣው ፍርድ ይናገራል።

በባሕሩ ዳር ያለው ምድር፣ የእረኞች መኖሪያና የበጎች በረት ይሆናል
ይህ የፍልስጥኤም ከተሞች ጠፍተዋል፣ አሁን ያለው ሜዳ ብቻ ነው ማለት ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ፣ የዕብራይስጡ ትርጉም ግልጽ ስላይደለ አንዳንድ የዘመኑ ትርጉሞች በተለያየ ሁኔታ ተርጉመውታል።

የበጎች በረት
የበጎች በረት በጐቹን በአንድነት ለማኖር የተከለለ ትንሽ ቦታ ነው።

ሕዝባቸው
‹‹የይሁዳ ሕዝብ››

ያርፋሉ
‹‹ለመተኛት ያርፋሉ››

Zephaniah 2:8

አጠቃላይ መረጃ
2፥4-15 ላይ ያህዌ በይሁዳ ዙሪያ ባሉ አገሮች ላይ ስለሚመጣው የእርሱ ፍርድ ይናገራል

ፌዝ… ስድብ
‹‹ፌዝ… ስድብ›› የተሰኙት ሁለት ሐረጐች የሚናገሩት ስለ አንድ ዐይነት ነገር ሲሆን፣ ሞዓብና አሞን ያህዌን መሳደባቸውን አጽንዖት ይሰጣሉ።

ድንበራቸውን አልፈዋል
ይህ የሚያመለክተው እነርሱን ለማጥቃት የይሁዳን ክልል መሻገራቸውን ሊሆን ይችላል

በሕያውነቴ
‹‹እኔ ሕያው እንደ መሆኔ›› ያህዌ በዚህ አገላለጽ የሚጠቀመው ቀጥሎ የሚናገረው ፍጹም እውነት መሆኑን ለማሳየት ነው።

ይህ የመሐላ ቃል ነው። ‹‹አጥብቄ እምላለሁ›› ይህ የሰራዊት ጌታ የእስራኤል አምላክ የያህዌ ቃል ነው
የሚናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳየት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሰራዊት ጌታ የእስራኤል አምላክ ያህዌ እንዲህ ይላል›› ወይም፣ ‹‹እኔ የሰራዊት ጌታ የእስራኤል አምላክ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ››

እንደ ሰዶም… እንደ ገሞራ
እነዚህን ሁለት ከተሞች በጣም ዐመፀኞች ስለ ነበሩ ከሰማይ በወረደ እሳት አጥፍቶአቸዋል። ይህ የሚያመለክተው ሙሉ በሙሉ መደምሰሳቸውን ነው። ይህን ግልጽ በሆነ ሁኔታ፣ ‹‹እንደ ሰዶም… እንደ ገሞራ ሙሉ በሙሉ አጥፍቶአቸዋል›› ብሎ መተርጐም ይቻላል።

ዐረም እንደ ዋጠው እንደ ጨው ጉድጓድ
‹‹እሾህ የሞላበት የጨው ጉድጓድ›› ይህ የሚያመለክተው ጠፍና ጥቅም የሌለውን ምድር ነው።

ከሕዝቤ የቀሩ… ከወገኔ የተረፉ
ሁለቱም ሐረጐች የሚናገሩት ስለ ተመሳሳይ ነገር ሲሆን፣ እስራኤላውያን ከያህዌ ቅጣት እንደሚተርፉ ያመለክታሉ።

Zephaniah 2:10

አጠቃላይ መረጃ
2፥4-15 ላይ ያህዌ በይሁዳ ዙሪያ ባሉ አገሮች ላይ ስለሚመጣው ፍርድ ይናገራል።

የያህዌን ሕዝብ ሰድበው ዝተውበታልና… እርሱም በምድሪቱ ያሉትን አማልክት ይዘልፋል።
ያህዌ በፈሊጣዊ መንገድ ይናገራል። እነዚህን አማልክት ሲያገለግሉ የነበሩ ሰዎች የያህዌን ሕዝብ እንደ ሰደቡና እንደ ዛቱ ያህዌም እነዚህን ከንቱ አማልክት ይዘልፋል።

Zephaniah 2:12

አጠቃላይ መረጃ
2፥14-15 ላይ ያህዌ በይሁዳ ዙሪያ ባሉ አገሮች ላይ ስለሚመጣው ፍርድ ይናገራል።

ኢትዮጵያውያን ሆይ፣ እናንተም በሰይፌ ትወጋላችሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹በሰይፌ ትወጋላችሁ›› ማለት በጦርነት ትገደላላችሁ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እናንተ የኢትዮጵያ ሰዎች በጦርነት እንድትገደሉ አደርጋለሁ››

የእግዚአብሔር እጅ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› ኀይልን፣ ‹‹የእግዚአብሔር ኀይል››ን ያመለክታል።

ፍጹም ባድማ
‹‹ባድማ›› ድርጊትን ያመለክታል፤ ‹‹የፈራረሰና የሚኖርበት የሌለ››

እንደ ምድረ በዳ ደረቅ
ይህ ማለት ምንም የማይበቅልበት ደረቅ ይሆናል ማለት ነው።

የበግና የፍየል መንጋዎች
‹‹ማንኛውም ዐይነት እንስሳ››

ጉጉትና ጃርት
ምን ማለት እንደ ሆነ ግልጽ አይደለም።

ከዝግባ የተሠሩ ተሸካሚዎች
ግንቡ ተንዶ ሲወድቅ ለጌጥና ድጋፍ እንዲሆኑ የተሠሩ ተሸካሚዎች ብዙውን ጊዜ ቆመው ይቀራሉ።

ጩኸታቸው በየመስኮቱ ያስተጋባል
‹‹ከየመስኮቱ ጩኸት ይሰማል››

ግንዶች
ግንዶች ረጃጅምና ወፍራም እንጨቶች ሲሆኑ፣ ሕንፃውን ደግፈው ያቆማሉ።

Zephaniah 2:15

አጠቃላይ መረጃ
2፥4-15 ላይ ያህል በይሁዳ ዙሪያ ባሉ አገሮች ላይ የሚመጣውን ፍርድ ይናገራል።

ደስተኛዪቱ ከተማ
‹‹በራስዋ የምትኮራ ከተማ›› ይህ የሚያመለክተው ሶፎንያስ 2፥13 ላይ ያህዌ ስለ እርሷ መናገር የጀመረውን የነነዌን ከተማ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በልቧ... ያለች
አባባሉ፣ ‹‹ለራስዋ አለች›› ወይም፣ ‹‹አሰበች›› ማለት ነው። ስለ ከተማዋ የሚናገረው መናገር እንደሚችል ሰው አድርጐ ነው። በዚያ ከተማ የሚኖሩ ሰዎችን ይወክላል።

እኔ ብቻ ነኝ ከእኔ በቀር ማንም የለም
እኔ ብቻ ነኝ ያለችበትን ምክንያት መግለጹ አስፈለጊ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ ታላቋ ከተማ ነኝ፤ ከእኔ የሚወዳደር የለም››

አስፈሪ
‹‹ለማየት የሚያስፈራ ቦታ››

ያፌዙባታል እጃቸውንም በንቀት ያወዛውዙባታል
ፌዝ ጮኽ ያለ ድምፅ ነው። ይህ ሐረግ የሚያመለክተው ሰዎች ነነዌ ላይ በጣም መቆጣታቸውን ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 ለዐመፀኛዋ፣ ለጨቋኛና ለረከሰች ከተማ ወዮላት። **2** እርሷ የእግዚአብሔርን ድምፅ አልሰማችም፤ የያህዌንም ተግሣጽ አልተቀበለችም፤ በያህዌ አትታመንም፤ ወደ አምላኳም አትቀርብም። **3** መሪዎቿ እንደሚያገሡ አንበሶች፣ ዳኞችዋም ለነገ ሳያስተርፉ ያገኙት ሁሉ በልተው እንደሚጨርሱ እንደ ተራቡ የማታ ተኩላዎች ናቸው። **4** ነቢያቶችዋ ትዕቢተኞችና ተንኰለኞች ናቸው። ካህናትዋ የተቀደሰውን አርክሰዋል፤ ሕጉንም ተላልፈዋል። **5** ጻድቁ ያህዌ በእርሷ ውስጥ አለ፤ እርሱ ፈጽሞ አይሳሳትም፤ በየማለዳው ፍርዱን ይሰጣል፤ በየቀኑም ይህን ከማድረግ አይቆጠብም፤ ዐመፀኞች ግን ዕፍረት አያውቁም። **6** ሕዝቦችን አጥፍቻለሁ፤ ምሽጐቻቸውንም ደምስሻለሁ። ማንም እንዳያልፍባቸው መንገዶቻቸውን አፈራርሻለሁ። ከተሞቻቸው ስለ ተደመሰሱ ከእንግዲህ የሚኖርባቸው አይኖርም። **7** እኔም፣ «በእርግጥ ትፈሪኛለሽ፣ እርምትም ተቀበዪ፤ ላደርግብሽ እንዳሰብኩት ከመኖሪያሽ አትነቀዪ አልኩ። እነርሱ ግን በሚያደርጉት ሁሉ ክፋትን እያበዙ ሄዱ። **8** ስለዚህ ያህዌ እንዲህ ይላል፣ «እስከምፈርድበት ቀን ድረስ ጠብቁኝ፤ ምድሪቱ ሁሉ በቁጣዬ እሳት እንድትጠፋ አሕዛብን ለመሰብሰብ፣ መንግሥታትን ለማከማቸት፤ ቁጣዬንና ጽኑ መዓቴን እነርሱ ላይ ለማፍሰስ ወስኛለሁ። **9** በዚያ ጊዜ ሰዎች የያህዌን ስም እንዲጠሩ፣ አንድ ልብ ሆነውም እንዲያገለግሉት ንጹሑን አንደበት እሰጣቸዋለሁ።› **10** ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ ያሉት እኔን የሚያመልኩ የተበተኑ ሕዝቤ ለእኔ የሚገባውን ቁርባን ያመጡልኛል። **11** በዚያ ቀን በእኔ ላይ ከፈጸማችሁት በደል ሁሉ የተነሣ አታፍሩም፤ በትዕቢታቸው የሚደሰቱትን ከመካከላችሁ ስለማስወግድ ከእንግዲህ ወዲያ በቅዱሱ ተራራዬ ላይ አትታበዩብኝም። **12** ሆኖም፣ የዋሃንንና ትሑታንን አስቀራለሁ፤ እናንተም በያህዌ ስም ትተማመናላችሁ። **13** የእስራኤል ትሩፋን ከእንግዲህ ፍርድ አያጐድሉም፤ ሐሰትንም አይናገሩም፤ በአንደበታቸው ሐሰት አይገኝም። ይበላሉ፤ በሰላምም ያርፋሉ፤ የሚያስፈራቸውም አይኖርም።» **14** የጽዮን ልጅ ሆይ፣ ዘምሪ፤ እስራኤል ሆይ፣ እልል በዪ፤ የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ፣ በፍጹም ልብሽ ደስ ይበልሽ ደስ ይበልሽ፤ ሐሤትም አድርጊ። **15** ያህዌ ቅጣትሽን አስወግዷል፤ ጠላቶችንም አስወጥቷል፤ የእስራኤል ንጉሥ ያህዌ በመካከልሽ ነው። ከእንግዲህ ክፉን አትፈሪም። **16** በዚያ ቀን ኢየሩሳሌምን እንዲህ ይሏታል፤ «ጽዮን ሆይ አትፍሪ፤ እጆችሽም አይዛሉ። **17** አንቺን ለማዳን ብርቱ የሆነው አምላክሽ ያህዌ በመካከልሽ ነው። በአንቺ እጅግ ደስ ይለዋል፤ በፍቅሩም ያሳርፍሻል። በዝማሬ በአንቺ ደስ ይለዋል። **18** ለታወቁ ክብረ በዓላት ሐዘንን ከአንቺ አርቃለሁ፤ በመካከልሽ ሸክምና ዕፍረት ሆነውብሻል። **19** በዚያ ቀን የበደሉሽን ሁሉ እቀጣለሁ፤ ያነከሱትን እታደጋለሁ፤ የተጣሉትንም እሰበስባለሁ። ዕፍረታቸውን አስወግጄ በምድር ሁሉ ላይ ለምስጋናና ለክብር አደርጋቸዋለሁ። **20** በዚያ ቀን እመራችኋለሁ፤ በዚያ ቀን በአንድነት እሰበስባችኋለሁ። እኔ እንደ ሰበሰብኋችሁ፣ ምርኮአችንም እንደ ሰበሰብሁ ስታዩ የምድር ሕዝቦች ሁሉ ያመሰግኗችኋል፤ ያከብራችኋል ይላል ያህዌ።

Zephaniah 3:1

አጠቃላይ መረጃ
3፥1-5 ላይ ሶፎንያስ ለነጢአተኞቹ የኢየሩሳሌም ሰዎች የያህዌን የፍርድ መልእክት ይናገራል። ከተማዋ ውስጧ የሚኖሩ ሰዎችን ትወክላለች። ይህን ግልጽ ለማድረግ፣ ‹‹እርሷ›› እና፣ ‹‹የእርሷ›› የሚለውን ነጠላ ቁጥር፣ ‹‹እነርሱ›› እና፣ ‹‹የእነርሱ›› በሚለው ብዙ ቁጥር መተካት ሊጠቅም ይችላል።

ዐመፀኛዪቱ ከተማ
የዐመፃቸውን ምንነት መዘርዘር ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በእግዚአብሔር ላይ ያመፁ የከተማዪቱ ሰዎች››

ጨቋኛ ከተማ ረከሰች
‹‹የከተማዋ ሰዎች ጨቋኞች ሆኑ፤ ስለዚህም በፊቴ ረከሱ››

የእግዚአብሔርን ድምፅ አልሰማችም
ድምፅ ተናጋሪው የሚናገረውን ይወክላል፤ መስማት መታዘዝን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔር ለነገራት ቃል አልታዘዘችም››

Zephaniah 3:3

አጠቃላይ መረጃ
3፥1-5 ላይ ሶፎንያስ ለነጢአተኞቹ የኢየሩሳሌም ሰዎች የያህዌን የፍርድ መልእክት ይናገራል። ከተማዋ ውስጧ የሚኖሩ ሰዎችን ትወክላለች። ይህን ግልጽ ለማድረግ፣ ‹‹እርሷ›› እና፣ ‹‹የእርሷ›› የተሰኙትን ነጠላ ቁጥሮች፣ ‹‹እነርሱ›› እና፣ ‹‹የእነርሱ›› በማለት መተካት ይቻላል።

ሹሞቿ የሚያገሡ አንበሶች
አንበሶች የሚያገሡት ከያዙት ንጥቂያ ሌሎች እንስሳትን ለማባረር ነው። የኢየሩሳሌም ሹሞች በእጃቸው ንጥቂያ እንደ ያዙ አንበሶች ተመስለዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የኢየሩሳሌም ሹመኞች እንደሚያገሡ አንበሶች ስግብግብ ናቸው››

ገዦቿ ለነገ የማይሉ የምሽት ተኩላዎች ናቸው
ሌሊት ከማደናቸው በፊት ተኩላዎች ይራባሉ። ገዦቹ በተራቡ ተኩላዎች ተመስለዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ገዦቿ ለሌሎች ምንም እንደማያስተርፉ የተራቡ ተኩላዎች ናቸው››

ነቢያቱ ትዕቢተኞች አታላዮችም ናቸው
‹‹ነቢያቷ ማንንም አይሰሙም፤ የሚታመኑም አይደሉም››

ቅዱስ የሆነውን ያረክሳሉ
‹‹ለተቀደሰው ነገር አክብሮት የላቸውም››

በሕግም ላይ ያምፃሉ››
‹‹ሕጉን ተላልፈዋል››

Zephaniah 3:5

አጠቃላይ መረጃ
3፥1-5 ላይ ሶፎንያስ ለነጢአተኞቹ የኢየሩሳሌም ሰዎች የያህዌን የፍርድ መልእክት ይናገራል።

ያህዌ ጻድቅ ነው፤ ፈጽሞ አይሳሳትም
ሁለቱም ሐረጐች የሚናገሩት ስለ ተመሳሳይ ነገር ሲሆን፣ በዐመፀኞቹ የኢየሩሳሌም ሰዎች መካከል እንኳ ያህዌ ጻድቅ መሆኑን አጽንዖት ይሰጣል።

በመካከልዋ
‹‹በእነርሱ መካከል››

‹‹በየማለዳው››
ይህ ፈሊጣዊ ቃል፣ ‹‹ሁልቀን›› ወይም፣ ‹‹በየቀኑ›› ማለት ነው።

ቅን ፍርድ ይሰጣል
ያህዌ ለሰው ሁሉ ያለው ቅን ፍርድ እንደ አንድ ስጦታ ተመስሎአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለሰዎች ቅን ፍርድ ያደርጋል››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ብርሃን ውስጥ አይሸሽግም
የያህዌ ፍርድ ሁሌም ግልጽ የመሆኑን እውነት አጽንዖት ለመስጠት አሉታዊ አነጋገርን ተጠቅሟል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእርሱ ቅን ፍርድ ለሰው ሁሉ በግልጽ ይታያል››

ዕፍረት አያውቁም
‹‹አያፍሩም››

Zephaniah 3:6

አጠቃላይ መረጃ
3፥6-7 ሌሎች ኀጢአተኞች ከተሞች ላይ እንዴት እንደ ፈረደ ባለ መማራቸው ያህዌ የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ይገሥጻል። ይህን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ ቁጥር 6 መጀመሪያ ላይ ያህዌ እንዲህ ይላል የሚል መጨመር ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

ማንም እንዳያልፍባቸው መንገዳቸውን ባድማ አደረግሁ፤ ከተሞቻቸው ተደምስሰዋል አንድም ሰው የለም።
እነዚህ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች የሚናገሩት ስለ አንድ ጉዳይ ሲሆን፣ የከተማዎቹ መደምሰስ እርግጥ መሆኑን አጽንዖት ይሰጣሉ።

ማንም እንዳያልፍባቸው
‹‹ማንም አያልፍባቸውም››

ነዋሪም ከቶ አይገኝባቸውም
‹‹እዚያ ማንም አይኖርም›› — ይህን የበለጠ ግልጽ ለማድረግ፣ ‹‹ሁሉም ይሞታሉ›› ማለት ይቻላል።

እኔም፣ ‹‹ትፈሪኛለሽ… ቅጣቴም በእርሷ ላይ አይደርስም ብዬ ነበር።››
እኔን ይፈሩኛል፤ አስቀድሞ እንዳልሁት ከቤቶቻችው እንዳይነቀሉ እርምት ይቀበላሉ ብዬ ነበር።››

ከቤታቸውም አይቆረጡም
እዚህ ላይ፣ ‹‹አይቆረጡም›› የሚለው መወገድን ያመለክታል። ይህንንም፣ ‹‹ከቤታቸው እንዳላስወግዳቸው›› ማለት ይቻላል።

ክፋትን በመፈጸም እየተጉ ሄዱ
‹‹ክፉ ነገሮችን በማድረግ››

Zephaniah 3:8

አጠቃላይ መረጃ
3፥8 ላይ ያህዌ በሕዝቦች ሁሉ ላይ እንደሚፈርድ ያስጠነቅቃል።

እስከምፈርድበት ቀን ድረስ ጠብቁኝ
ይህ ሐረግ ፍርዱን እየጠበቁ እንደ ነበር ያመለክታል።

ያህዌ እንዲህ ይላል
እየተናገረ ያለው እርግጥ መሆኑን ለማመልከት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ የተናገረው ይህን ነው›› ወይም፣ ‹‹ይህ እኔ ያህዌ የተናገርሁት ነው››

ሰለባ ለመያዝ እነሣለሁ
ያህዌ ሕዝቦች ላይ የሚያመጣው ፍርድ የተራበ እንስሳ ታናሹን እንስሳ በሚያጠቃበት ሁኔታ ተመስሎአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰላባውን እንደሚይዝ እንስሳ እኔም ተነሥቼ አጠፋቸዋለሁ››

አሕዛብን ልሰበስብ፤ መንግሥታትን ላከማች
እነዚህ ሁለት ሐረጐች የሚናገሩት ስለ አንድ ነገር ሲሆን፣ ያህዌ ሕዝቦች ሁሉ ላይ እንደሚፈርድ አጽንዖት ይሰጣል።

ቁጣዬ — የቁጣዬ እሳት
‹‹ቁጣ›› እና፣ ‹‹የቁጣ እሳት›› በመሠረቱ አንድ ናቸው፤ የሚያመለክቱት የያህዌ ቁጣ ምን ያህል ከባድ እንደሚሆን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ እሳት የሚነድ ቁጣዬ››

በቅናቴ ቁጣ እሳት አቃጥላቸዋለሁ!
እዚህ ላይ የያህዌ ቁጣ በሚያቃጥል እሳት ተመስሎአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቅናቴ መላውን ምድር እንደ እሳት ያቃጥላል››

Zephaniah 3:9

አጠቃላይ መረጃ
3፥9-10 ላይ ያህዌ ከፍርድ በኃላ ሕዝቦችን እንደሚያድስ ይናገራል።

አጠቃላይ መረጃ
3፥11-13 ላይ ያህዌ ከፍርድ የተረፉ ትሩፋንን ያጽናናል።

አንደበታቸውን አጠራለሁ
‹‹አንደበት›› የመናገር ችሎታን ያመለክታል። ‹‹ሕዝቡ እውነትን›› እንዲናገሩ አደርጋለሁ››

የያህዌን ስም እንዲጠሩ
ይህ ያህዌን ያመልካሉ ለማለት ጥቅም ላይ የዋለ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌን እንዲያመልኩ››

ተስማምተው እንዲያገለግሉ
‹‹ተስማምተው›› በአንድነት ሆነው ማለት ነው።

ከኩሽ ወንዞች ማዶ
ይህ የሚያመለክተው በዚህ ዘመን ሱዳን ያለችበትን ሊሆን ይችላል።

በዚያ ቀን… በዚያ ጊዜ
‹‹በዚያ ጊዜ… ያ ሲሆን›› ይህ የሚያመለክተው የያህዌን ቀን ወዲያውኑ ተክትሎ የሚኖረውን የሰላምና የመታደስ ጊዜ ነው።

በዚያ ቀን ባደረጋችሁት አታፍሩም።
ይህ ድርጊትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ባደረጋችሁ ነገር ከእንግዲህ በፍጹም አታፍሩም››

በትዕቢታቸው የሚደሰቱትን
‹‹በጣም የሚታበዩ ሰዎች ሁሉ››

Zephaniah 3:12

አጠቃላይ መረጃ
3፥11-13 ላይ ያህዌ ከፍርድ የተረፉ የእስራኤል ትሩፋንን ያጽናናል።

የዋሃንንና ትሑታንን በመካከላችሁ አስቀራለሁ… የእስራኤልን ትሩፋን
በመጀመሪያው ሐረግ፣ ‹‹ትሩፋኑን›› በሁለተኛው ሐረግ አስቀምጦአል።

የያህዌን ስም መጠጊያ ያደርጋሉ
ያህዌ ለእነዚህ ትሩፋን የሚያደርገው ጥበቃ እርሱ መጠጊያ ወይም መጠለያ ከመሆኑ ጋር ተመሳስሎአል። እዚህ ላይ፣ ‹‹የያህዌ ስም›› ማንነቱን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወደ ያህዌ ይመጣሉ፤ እርሱም ይረዳቸዋል››

ኀጢአት አይሠሩም
‹‹ክፉ ነገር አያደርጉም››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምላሳቸውም ሐሰት አይናገርም፤ በአንደበታቸውም ተንኰል አይገኝም
‹‹ምላስ… በአንደበታቸው›› የሚለው ምላስ አንደበት እንዲናገር የሚያደርገውን ነገር ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ማንኛቸውም ክፉ ነገር አይናገሩም›› ወይም፣ ‹‹ክፉ ነገር አያወሩም››

ይበላሉ ይተኛሉ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝቡ ስለሚያደርገው ቸርነት ሲናገር እነርሱ በሰላም ተመግበው የሚያርፉ በጐቹ መሆናቸውን ያመለክታል።

Zephaniah 3:14

አጠቃላይ መረጃ
3፥14-20 ላይ ሶፎንያስ ደስ እንዲላቸው ከፍርድ ለተረፉ ትሩፋን ይናገራል።

የጽዮን ልጅ… የኢየሩሳሌም ልጅ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ልጅ›› በከተማው የሚኖሩትን ሁሉ ይመለከታል።

ደስ ይበልሽ፤ ሐሤትም አድርጊ
ሁለቱም ሐረጐች አንድ ዐይነት ትርጕም ቢኖራቸውም፣ ምን ያህል ደስ ሊላቸው እንደሚገባ አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በጣም ደስ ይበላችሁ››

በፍጹም ልብሽ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ልብ›› የሰውን ውስጣዊ ሁለንተና ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በፍጹም ሁለንተናሽ››

ያህዌ ቅጣትሽን አስወግዶአል
ቅጣትን ማስወገድ ቅጣትን መተው ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ አንቺን መቅጣቱን ትቶአል››

ከእንግዲህ ወዲያ አንዳች ክፉ ነገር አትፈሪም
‹‹ክፉ›› የሚለው ድርጊትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከእንግዲህ ወዲህ ሰዎች ይጐዱኛል ብለሽ አትፈሪም››

በዚያ ቀን
‹‹በዚያ ቀን›› ወይም፣ ‹‹ያ በሚሆንበት ጊዜ›› ይህ የሚያመለክተው የያህዌን ቀን ወዲያውኑ ተከትሎ የሚመጣውን የሰላምና የመታደስ ጊዜ ነው።

ለኢየሩሳሌም… ለጽዮን እንዲህ ይሏታል
ስሞቹ የሚያመለክቱት እዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ነው። ‹‹ለኢየሩሳሌም ሕዝብ ለጽዮን ሕዝብ እንዲህ ይላል››

እጆችሽ አይዛሉ
ደካማና ዐቅም ቢስ መሆን በእጆች መዛል ተመስሎአል። እዚህ ላይ ‹‹እጆች›› የሰውን ሁለንተና ይወክላሉ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አትድከሚ››

Zephaniah 3:17

አጠቃላይ መረጃ
3፥14-20 ላይ ሶፎንያስ ከፍርድ የተረፉ ትሩፋን ደስ እንዲሰኙ ይናገራል።

የሚታደግ ኀያል ነው
‹‹እርሱ ኀያል ነው፤ ያድንሻል›› ያህዌ በብርቱ ጦረኛ ተመስሎአል። ‹‹እርሱ ብርቱ ጦረኛ ነው፤ ድል ይሰጣችኋል››

በአንቺ እጅግ ደስ ይለዋል… በዝማሬም በአንቺ ሐሤት ያደርጋል።
የእነዚህ ሁለት ሐረጐች ትርጉም ተመሳሳይ ሲሆን፣ የተደጋገመት ትሩፋኑ ወደ እርሱ በመመለሳቸው ያህዌ ምን ያህል ደስ መሰኘቱን አጽንዖት ለመስጠት ነው።

በፍቅሩ ያሳርፍሻል
አማራጭ ትርጕሞቹ፣ 1) ‹‹በፍቅሩ ጸጥ ያሰኝሻል›› ወይም 2) ‹‹እርሱ ስለሚወድሽ ያድስሻል›› ሊሆኑ ይችላሉ።

ከእንግዲህ ዕፍረት አትሸከሚም
ዕፍረት ሰዎች ላይ እንደ ሸክም መሆኑን ይናገራል። ‹‹ከእንግዲህ በዚያ ነገር አታፍሪም››

Zephaniah 3:19

አጠቃላይ መረጃ
3፥19-20 ላይ ሶፎንያስ በቀጥታ ከፍርድ የተረፉ የእስራኤል ትሩፋን ደስ እንዲሰኙ ይናገራል።

እነሆ
ይህ የሚያመለክተው አንባቢው ለሚከተለው ትኩረት እንዲሰጥ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ተመልከቱ›› ወይም፣ ‹‹ልብ በሉ››

ያስጨነቁሽን ሁሉ እቀጣለሁ
ይህም፣ ‹‹አንቺን ያስጨነቁትን በእርግጥ እቀጣቸዋለሁ›› ማለት ነው።

አንካሶችን እታደጋለሁ፤ የተበተኑትንም እሰበስባለሁ
በምርኮ የነበሩት እስራኤላውያን አንካሶችና የተበተኑ እንደ ነበሩ ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንደ አንካሶችና እንደ ተበተኑ ሰዎች የሆኑትን የእስራኤል ትሩፋን እታደጋለሁ››

አንካሳ
መራመድ የማይችል ሰው ወይም እንስሳ

ለውዳሴና ለክብር አደርጋቸዋለሁ
እዚህ ላይ የተሟላ ሐሳቡ፣ ‹‹የምስጋና ምክንያት አድርጋቸዋለሁ›› ማለትም፣ ‹‹ሌሎች ያመሰግናቸዋል››

ውርደታቸውን ወደ ዝና እለውጣለሁ
ውርደትና ዝና እንደ ድርጊት ሊነገሩ ይችላሉ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከእንግዲህ ሰዎች እንዲያከብሯቸው እንጂ፣ እንዲያፍሩ አላደርግም››

በዚያ ጊዜ እመራችኋለሁ፤ በዚያ ጊዜ በአንድነት እሰበስባችኋለሁ።
እነዚህ ሁለት ሐረጐች የሚናገሩት ስለ ተመሳሳይ ነገር ሲሆን፣ በምርኮ ያሉ ሰዎችን ያህዌ ወደ ትውልድ አገራቸው እንደሚያመጣ ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በዚያ ጊዜ በአንድነት ሰብስቤ ወደ ትውልድ አገራችሁ አመጣችኋለሁ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Haggai

Haggai

Chapter 1

1 ዳርዮስ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት በስድስተኛው ወር መጀመሪያ ቀን በነቢዩ በሐጌ በኩል ወደ ይሁዳ ገዢ ወደ ሰላትያል ልጅ ወደ ዘሩባቤልና ወደ ሊቀ ካህኑ ኢዮሴዴቅ ልጅ ወደ ኢያሱ የያህዌ ቃል መጣ። 2 የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል፤ ይህ ሕዝብ “እኛ የምንመጣበት ወይ የያህዌን ቤት የምንሠራበት ጊዜ ገና ነው” ይላል። 3 የያህዌ ቃል በነቢዩ በሐጌ በኩ መጣ፤ እንዲህም አሉ፣ 4 “ይህ ቤት ፈራርሶ እያለ፣ እናንተ ራሳችሁ ባማሩ ቤቶቻችሁ ለመኖር ጊዜው ነውን? 5 ስለዚህ የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል፣ እስቲ፣ የሠራችሁትን ቤት አስቡ! 6 ብዙ ዘራችሁ፤ ግን ጥቂት አጭዳችሁ፤ በላችሁ ግን አልጠገባችሁም፤ ጠጣችሁ ግን አልረካችሁም። ለበሳችሁ ግን አልሞቃችሁም፤ ደመወዝ ተቀበላችሁ ግን ብዙ ቀዳዶች በሞሉበት መያዣ የማስቀመጥ ያህል ሆነባችሁ! 7 የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል፤ እስቲ የሠራችሁትን አስቡ! 8 ወደ ተራራ ውጡ፤ እንጨትን አምጡና ቤቴን ሥሩ፤ ያኔ እኔ በእርሱ ደስ ይለኛል፣ እከብርበታለሁ! ይላል ያህዌ። 9 ብዙ ጠበቃችሁ፤ ግን እኔ እፍ ስላልሁበት ወደ ቤት ያመጣችሁት ግን ጥቂት ነው፤ እንዲህ ያደረግሁት ለምን ይመስላችኋል? የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል! ምክንያቱም የእኔ ቤት ፈርሶ እያለ፣ ሰው ሁሉ በገዛ ራሱ ቤት እጅግ ደስ በመሰኘቱ ነው። 10 ከዚህ የተነሣ ሰማያት ጠል ከለከሉ፤ ምድርም ፍሬዋን ነሣች። 11 እኔ በምድሪቱና በተራሮች፤ በእህሉና በአዲሱ ወይን ጠጅ፤ በዘይቱና ምድር በምትሰጠው ሁሉ ላይ፣ በሰዎችና በእንስሳት፣ በእጆቻችሁ ሥራ ሁሉ ላይ ድርቅ አመጣለሁ! 12 ከዚህ በኋላ የሰላትያል ልጅ ዘሩባቤልና ሊቀ ካህኑ የኢዮሴዴቅ ልጅ ኢያሱ፣ ከምርኮ ከተረፉት ሕዝብ ሁሉ ጋር የአምላካቸው የያህዌን ድምጽ ሰሙ፤ አምላካቸው ያህዌ ልኮታልና ለነቢዩ ሐጌ ቃል ታዘዙ። ሕዝቡም ያህዌን ፈሩ። 13 ከዚያም የያህዌ መልእክተኛ ሐጌ ለሕዝቡ የያህዌን መልእክት እንዲህ በማለት ተናገረ፤ “እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ! ይህ የያህዌ ቃል ነው! 14 ስለዚህ ሄደው የአምላካቸውን የሠራዊት ጌታ የያህዌን ቤት እንዲሠሩ የይሁዳን ገዢ የሰላትያል ልጅ የዘሩባቤልን መንፈስና የኢዮሴዴቅ ልጅ የካህኑ ኢያሱን መንፈስ፣ እንዲሁም ከምርኮ የተረፉትን ሰዎች ሁሉ መንፈስ ያህዌ አነሣሣ። 15 ይህ የሆነው በንጉሥ ዳርዮስ ሁለተኛ ዓመት በስድስተኛው ወር ሃያ አራተኛ ቀን ነው።

Haggai 1:1

ዳርዮስ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት
‹‹በንጉሥ ዳርዮስ ሁለተኛ ዓመት›› ወይም፣ ‹‹ዳርዮስ ንጉሥ በሆነ በሁለተኛው ዓመት››

ዳርዮስ... ሐጌ... ዘሩባቤል... ሰላትያል.. ኢያሱ... ኢዮሴዴቅ
የሰዎቹ ስም በሙሉ እነዚህ ናቸው

በስድስተኛው ወር የመጀመሪያ ቀን
‹‹በስድስተኛው ወር የመጀመሪያው ቀን::›› ስድስተኛ ወር የሆነው በአይሁድ ቀን አቆጣጠር ነው። የመጀመሪያ ቀን በምዕራባውያን ቀን መቁጠሪያ ነሐሴ አጋማሽ ላይ ነው።

የያህዌ ቃል መጣ
ይህ ፈሊጣዊ ቃል ከእግዚአብሔር ስለ መጣ ልዩ ቃል ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ መልእክት ሰጠ›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ይህን መልእክት ተናገረ››

ያህዌ
ይህ ብሉይ ኪዳን ውስጥ ለሕዝቡ የተገለጠ የእግዚአብሔር ስም ነው። ይህ እንዴት እንደሚተረጐም ከቃላት ትርጉም ገጽ ስለ ያህዌ የተጻፈውን ተመልከት።

በነቢዩ በሐጌ እጅ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› የሚለው ቃል የሚያመለክተው ራሱ ሐጌን ነው። መልእክቱን ለማስተላለፍ ያህዌ በሐጌ በኩል ተጠቀመ። ሐጌ 1፥1 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሐጌ በኩል››

የያህዌ ቤት
ቤተ መቅደሱ

Haggai 1:3

የያህዌ ቃል መጣ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ከእግዚአብሔር የመጣ ልዩ ቃል ያመለክታል። ሐጌ 1፥1 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ መልእክት ሰጠ›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ይህን መልእክት ተናገረ››

በሐጌ እጅ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› የሚለው ቃል የሚያመለክተው ራሱ ሐጌን ነው። ትእዛዙን ለሕዝቡ ለማድረስ ያህዌ በሐጌ በኩል ተጠቀመ። ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ከሐጌ 1፥1 ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣

ይህ ጊዜው ነውን?
ያህዌ ሕዝቡን እየገሠጸ ነው። ይህ መልስ የማያስፈልገው ጥያቄ እንደ ዐረፍተ ነገር መተርጐም ይችላል። ‹‹ይህ ጊዜው አይደለም››

ይህ ቤት
የያህዌ ቤተ መቅደስ

መስከር አልቻላችሁም
መስከር ቀርቶ ጥምን ለማስታገሥ እንኳ በቂ ወይን ጠጅ የለም። ይህ ዐረፍተ ነገር መስከር ጥሩ ነገር ነው ማለት አለመሆኑን አንባቢው መረዳት አለበት።

x
ደመወዝ ተቀበላችሁ ግን በቀዳዳ ኰረጆ የማስቀመጥ ያህል ነው የሆነባችሁ። አስፈላጊ ነገሮች ለመግዛት በቂ ገንዘብ አለማግኘት በቀዳዳ ኰረጆ ገንዘብ በማስቀመጥ ተመስሎአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሠራተኛው የተቀበለው ደመወዝ የሚያስፈልገውን ነገር ከመግዛቱ በፊት አለቀ››

Haggai 1:7

እንጨት አምጡ
ቤተ መቅደስ ለመሥራት ይህ አንድ አስፈላጊ ነገር ብቻ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እነሆ
‹‹ተመልከቱ›› ወይም፣ ‹‹አድምጡ›› ወይም፣ ‹‹የምነግራችሁን ልብ በሉ››

እፍ አልሁበት
ያህዌ እፍ ስላለበት እንደ ዐመድ በነነ፤ ስለዚህ ሰዎቹ የሚፈልጉትን አላገኙም። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የምታገኙት ነገር እንዳይኖር አደረግሁ››

ያህዌ ጸባኦት እንዲህ ይላል
እርሱ የሚናገረው እርግጥ መሆኑን ለማመልከት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ይህ ያህዌ የተናገረው ነው›› ወይም፣ ‹‹እኔ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ››

Haggai 1:10

ሰማያት ጠል ከለከሉ
ሌሊት የሚታየው ጠል ከሰማይ ደመና ሆኖ በሚወርድ ዝናብ ተመስሎአል። ሰማይ ስጦታ መስጠት እንዳልፈለገ ሰው ወይም ልጁን መመገብ እንደማይፈልግ ወላጅ ተመስሎአል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰማዩ ጠል እንዲዘንብ›› ወይም፣ ‹‹ጠል ዝናብ እንዲሆን አልፈለገም››

ምድር ላይ ድርቅ ጠራሁ
ለረጅም ጊዜ ዝናብ አለመዝነቡ ምድሪቱን ደረቅ እንዲያደርግ ያህዌ በነገረው ሰው ተመስሎአል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ምድር ላይ እንዳይዘንብ ከለከለሁ››

በአዲሱ ወይን ጠጅ በዘይቱ
ወይን ጠጅና ዘይት፣ የወይን ፍሬና የወይራ ፍሬ፣ ተተኪ ስም ነው።

በእጆቻችሁም ሥራ ላይ
ይህ ሐረግ፣ ‹‹ብዙ በደከማችሁበት›› ተብሎ ሊተረጐም ይችላል። እጅ የሚሠራው ሥራ የሰው ልፋት ውጤት ተተኪ መጠሪያ ነው። እጅ ሰውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በርትታችሁ የሠራችሁት››

Haggai 1:12

ዘሩባቤል... ሰላትያል... ኢያሱ... ኢዮሴዴቅ... ሐጌ
እነዚህን ስሞች እንዴት እንደተረጐምህ ከሐጌ 1፥1 ተመልከት።

ለያህዌ ድምፅ... ለሐጌ መልእክት ታዘዙ
ድምፅና መልእክት ሰዎችን ይወክላሉ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለያህዌና ለሐጌ ታዘዙ››

ሕዝቡ የያህዌን ፊት ፈሩ
የዚህ አማራጭ ትርጒም፣ 1) ፊት ያህዌን ይወክላል። ‹‹ሕዝቡ ያህዌን ፈሩ›› ወይም 2) ፊት የያህዌን ሓልዎት ይወክላል። ‹‹ሕዝቡ በያህዌ ሓልዎት ውስጥ መሆን ፈሩ››

ይህ የያህዌ ቃል ነው
‹‹ይህ ያህዌ የተናገረው ነው›› ወይም፣ ‹‹ይህን የተናገርሁ እኔ ያህዌ ነኝ››

Haggai 1:14

ያህዌ የይሁዳን ገዥ የሰላትያልን ልጅ የዘሩባቤልን መንፈስ፣ የሊቀ ካህናቱን የኢዮሴዴቅን ልጅ የኢያሱን መንፈስና ከምርኮ የተረፈውን ሕዝብ ሁሉ መንፈስ አነሣሣ
መንፈስን ማነሣሣት ለሥራ ማነሣሣት ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ የይሁዳን ገዥ የሰላትያልን ልጅ የዘሩባቤልን እንዲሁም የሊቀ ካህናቱን የኢዮሴዴቅን ልጅ የኢያሱን መንፈስና ከምርኮ የተረፈውን ሕዝብ ለሥራ አነሣሣ››

ትሩፋን
ባቢሎን ውስጥ በምርኮ የነበሩና በሕይወት ኖረው ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱ ሰዎች በስድስተኛው ወር ሃያ አራተኛው ቀን ይህ ማለት ራእዩ በመጣ በ23ኛው ቀን ማለት ነው። ይህ በአይሁድ አቆጣጠር ስድስተኛ ወር ነው። በምዕራውያን ቀን አቆጣጠር ሃያ አራተኛው ቀን የሚውለው መስከረም አጋማሽ ላይ ነው። በምዕራውያን ቀን አቆጣጠር ሃያ አራተኛው ቀን የሚውለው መስከረም አጋማሽ ላይ ነው።

ዳርዩስ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት
‹‹ንጉሥ ዳርዮስ በነገሠ ሁለተኛው ዓመት›› ወይም፣ ‹‹ዳርዮስ ንጉሥ በሆነ በሁለተኛው ዓመት››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 በሰባተኛው ወር፣ ከወሩም በሃያ አንደኛው ቀን የያህዌ ቃል በነቢዩ በሐጌ በኩል መጣ እንዲህም አለ፤ **2** “ለይሁዳ ገዢ ለሰላትያል ልጅ ለዘሩባቤልና ለኢዮሴዴቅ ልጅ ለካህኑ ኢያሱ፣ እንዲሁም ከምርኮ ለተረፉት ሰዎች ተናገሩ እንዲህም በሏቸው **3** የዚህን ቤት የቀድሞ ክብር ያየ በመካከላችሁ ማን አለ? አሁንስ እንዴት ሆኖ ይታያችኋል? በዓይኖቻችሁ ፊት እንደ ተራ ነገር ቀልሎ የለምን? **4** አሁንም ዘሩባቤል ሆይ፣ በርታ! ይህ የያህዌ ዐዋጅ ነው አንተም የኢዮሴዴቅ ልጅ ሊቀ ካህኑ ኢያሱ በርታ፤ በምድሪቱ ያላችሁ ሰዎች ሁሉ በርቱ! - ይህ የያህዌ ዐዋጅ ነው፤ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝና ተነሡ ሥሩ! ይህ የሠራዊት ጌታ የያህዌ ዐዋጅ ነው **5** ከግብፅ በወጣችሁ ጊዜ በገባሁላችሁ ኪዳን፣ በመካከላችሁም ባለው መንፈሴ አትፍሩ! **6** የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል፤ በቅርብ ጊዜ ሰማያትንና ምድርን፣ ባሕርንና ደረቁን ምድር አናውጣለሁ! **7** ሕዝቦችን ሁሉ አናውጣለሁ፤ ሕዝቦች የከበሩ ነገሮቻቸውን ወደ እኔ ያመጣሉ፤ ይህንንም ቤት በክብር እሞላዋለሁ! ይላል የሠራዊት ጌታ ያህዌ። **8** ብርና ወርቁ የእኔ ነው! ይህ የሠራዊት ጌታ የያህዌ ዐዋጅ ነው። **9** የወደፊቱ የዚህ ቤት ክብር ከመጀመሪያው ይበልጣል ይላል የሠራዊት ጌታ ያህዌ፤ በዚህ ቦታ ሰላም እሰጣለሁ - ይህ የሠራዊት ጌታ የያህዌ ዐዋጅ ነው።” **10** ዳርዮስ በነገሠ ሁለተኛው ዓመት፣ በዘጠነኛው ወር ሃያ አራተኛ ቀን የያህዌ ቃል በነቢዩ በሐጌ በኩል መጣ፤ እንዲህም አለ፣ **11** “የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል፤ ሕጉ ምን እንደሚል ካህናቱን ጠይቁ፤ **12** አንድ ሰው ለያህዌ የተቀደሰውን ሥጋ በልብሱ እጥፋት ቢይዝ፣ በልብሱ እጥፋት እንጀራ ወይም ወጥ፣ የወይን ጠጅ ወይም ዘይት ወይ ሌላ ምግብ ቢነካ፣ ያ ምግብ ይቀደሳልን?” ካህናቱም፣ “የለም፣ አይቀደስም” በማለት መለሱ። **13** ሐጌም፣ “ሬሳ በመንካቱ የረከሰ ሰው ከእነዚህ አንዱን ቢነካ ይረክሳሉን?” አለ። ካህናቱም፣ “አዎን፣ ይረክሳሉ” በማለት መለሱ። **14** ስለዚህ ሐጌ መልሶ፣ “ ይህም ሕዝብ በፊቴ እንዲሁ ነው! - ይህ የያህዌ ዐዋጅ ነው፤ የእጃቸው ሥራና ለእኔ የሚያቀርቡት ሁሉ የረከሰ ነው። **15** እንግዲህ ከዘሬ ጀምራችሁ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ከመነባበሩ በፊት የነበረውን ሁኔታ ልብ በሉ፤ **16** ለምሆኑ ያኔ እንዴት ነበር? አንድ ሰው ሃያ መስፈሪያ እህል ጠብቆ ወደ ክምሩ ሲሄድ አሥር ብቻ አገኘ። አምሳ ማድጋ ወይን ጠጅ ለመቅዳት ወደ መጭመቂያው ሲሄድ ሃያ ብቻ አገኘ። **17** እናንተንና የእጆቻችሁን ሥራ ሁሉ በዋግና በአረማሞ መታሁ፤ ያም ሆኖ ግን ወደ እኔ አልተመለሳችሁም - ይህ የያህዌ ዐዋጅ ነው። **18** ከዚህ ቀን ጀምሮ ማለትም የያህዌ ቤተመቅደስ መሠረት ከተጣለበት ከዘጠነኛው ወር ሃያ አራተኛው ቀን ጀምሮ ወደፊት ቁጠሩ፤ ልብ አድርጋችሁ አስቡት! **19** በጎተራው የቀረ ዘር ይኖራልን? የወይኑና የበለሱ፣ የሮማኑና የወይራው ዛፍ ፍሬ አላፈሩም! ከዚህ ቀን ጀምሮ እባርካችኋለሁ!” **20** በዘጠነኛው ወር በወሩም ሃያ አራተኛ ቀን የያህዌ ቃል በድጋሚ ወደ ሐጌ መጣ፤ እንዲህም አለ፣ **21** “ለይሁዳ ገዥ ለዘሩባቤል እንዲህ በለው፤ “ሰማያትንና ምድርን አናውጣለሁ። **22** የመንግሥታትን ዙፋን እገለብጣለሁ፤ የሕዝቦችን መንግሥት ብርታት አጠፋለሁ! ሰረገሎችንና በላያቸው ያሉትን እገለብጣለሁ፤ ፈረሶችና ጋላቢዎቻቸውን በገዛ ወንድሞቻቸው ሰይፍ ይወድቃሉ። **23** በዚያ ቀን - የሠራዊት ጌታ የያህዌ ዐዋጅ እንዲህ የሚል ይሆናል- የሰላትያል ልጅ ባርያዬ ዘሩባቤል ሆይ፣ እኔ እወስድሃለሁ፤ ይህ የያህዌ ዐዋጅ ነው። እኔ መርጬሃለሁና ቀለበቴ ላይ እንደ ማህተም አደርግሃለሁ፤ ይህ የሠራዊት ጌታ የያህዌ ዐዋጅ ነው።

Haggai 2:1

በሰባተኛው ወር በሃያ አንደኛው ቀን
ይህ የዕብራውያን ቀን አቆጣጠር ሰባተኛ ወር ነው። በምዕራባውያን ቀን መቁጠሪያ ሃያ አንደኛው ቀን የሚውለው ጥቅምት አጋማሽ ላይ ነው።

የያህዌ ቃል መጣ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ጥቅም ላይ የዋለው ከእግዚአብሔር የመጣውን ልዩ መልእክት ለማመልከት ነው። ሐጌ 1፥1 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ መልእክት ሰጠ›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ይህን መልእክት ተናገረ››

በሐጌ እጅ
‹‹እጅ›› የሚለው ቃል ሐጌ ራሱን ያመለክታል። ይህን መልእክት ለመስጠት ያህዌ በሐጌ ተጠቅሞአል። 1፥1 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሐጌ በኩል››

ሐጌ... ዘሩባቤል... ሰላትያል... ኢያሱ... ኢዮሴዴቅ
የእነዚህ ሰዎች ስም እንዴት እንደ ተረጐምህ ሐጌ 1፥1 ተመልከት።

Haggai 2:3

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ እየተሠራ ስለ ነበረው ቤተ መቅደስ ለሕዝቡ ይናገራል። ናቡከደነፆር ሙሉ በሙሉ ያወደመውን የድሮውን ቤተ መቅደስ አባቶቻቸው ሠርተው በነበረበት ቦታ ነበር እየሠሩት የነበረው ይህ ቤተ መቅደስ ከድሮው ቤተ መቅደስ በጣም ያነሰ ነበር።

ይህን ቤት በቀድሞ ክብሩ ሳለ ያየ በመካከላችሁ ማን አለ?
አዲሱ ቤተ መቅደስ ያው እንደ ቀድሞ እንደ ነበር አድርጐ ያህዌ ለሕዝቡ ይናገራል። ልብ እንዲሉ የቀድሞውን ቤተ መቅደስ አይተው ለነበሩ ሰዎች ይናገራል። ይህን መልስ የማያስፈልገው ጥያቄ እንደ ዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህን ቤተ መቅደስ በቀድሞ ክብሩ ያያችሁ ሰዎች ልብ እንድትሉ እፈልጋለሁ››

አሁንስ ምን መስሎ ይታያችኋል?
ስለ አዲሱ ቤተ መቅደስ የሚያስቡትን እንደሚያውቅ ያህዌ እየነገራቸው ነው። አዲሱ ቤተ መቅደስ እንደ ቀድሞው ቤተ መቅደስ እንደ ነበር ይናገራል። ይህን መልስ የማያስፈልገው ጥያቄ እንደ ዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለዚህ አዲስ ቤተ መቅደስ የምታስቡትን አውቃለሁ››

በፊታችሁ ምንም እንዳይደለ የሚቆጠር አይደለምን?
አዲሱ ቤተ መቅደስ በጣም ትንሽ ስለ ነበር ማዘናቸውን እንደሚያውቅ ያህዌ ለሕዝቡ ይነግራቸዋል። ይህን መልስ የማያስፈልገው ጥያቄ እንደ ዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህን ያህል ጠቃሚ እንዳይደለ የምታስቡትን አውቃለሁ››

አሁን በርታ
‹‹ከአሁን ጀምሮ ብርቱ ሁን››

ያህዌ እንዲህ ይላል
እርሱ የሚናገረው እርግጥ መሆኑን ለማመልከት ያህዌ ስሙን በመጥራት ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ይህን ተናግሮአል›› ወይም፣ ‹‹እኔ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ››

የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
እርሱ የሚናገረው እርግጥ መሆኑን ለማመልከት ያህዌ ስሙን በመጥራት ይናገራል። ከሐጌ 1፥9 ይህን እንዴ እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ትርጉም፣ ‹‹የሰራዊ ጌታ ያህዌ ይህን ተናግሮአል›› ወይም፣ ‹‹እኔ የሰራዊት ጌታ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ››

Haggai 2:6

ሰማያትን... ምድርን... ባሕርን... የብስን... ሕዝቦችን ሁሉ አናውጣለሁ
‹‹ምድርን አናውጣለሁ›› የሚለው፣ ‹‹የምድር መንቀጥቀጥ አመጣለሁ›› የምድር መንቀጥቀጡም፣ ‹‹ባሕርን›› እና፣ ‹‹የብሱን›› ያናውጣል ተብሎ ሊተረጐም ይችላል፤ ይህ መላውን ምድር የሚመለከት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ሰማያትና ሕዝቦች እንደ ግዑዝ ነገሮች እንደሚናወጡ ያህዌ ይናገራል።

አናውጣለሁ
ፍሬ ወይም ሌላ ነገር እንዲወድቅ ዛፍን ወደ ፊት ወደ ኃላ ለማነቃነቅ በምትጠቀምበት ግሥ መጠቀም ትችላለህ።

ይህንም ቤት በክብር እሞላዋለሁ
ክብር እንደ አንድ ጠጣር ወይም ፈሳሽ አንድን መያዣ ማለት ቤተ መቅደሱን እንደሚሞላ አድርጐ ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጉሞቹ፣ 1) ቤተ መቅደሱ በጣም ያማረ ይሆናል፤ ‹‹ይህን ቤተ መቅደስ በጣም ያማረ አደርገዋለሁ›› ወይም 2) ብርና ወርቁን እንዲሁም ሌላውን ሀብት ጨምሮ፣ ‹‹ሕዝቦች ሁሉ የሚያመጡትን ብርና ወርቅ›› ይመለከታል፤ ‹‹ሕዝቦች ወደዚህ ቤት ብዙ ያማሩ ነገሮች ያመጣሉ››

Haggai 2:8

ብሩ የእኔ ነው፤ ወርቁም የእኔ ነው
‹‹ብርና ወርቅ›› ሕዝቦች ወደ ቤተ መቅደሱ የሚያመጡትን ሀብት ሁሉ ይወክላል። (ሐጌ 2፥7)

የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
የሚናገረው እርግጥ መሆኑን ለማመልከት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ከሐጌ 1፥9 ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሰራዊት ጌታ ያህዌ ይህን ይላል›› ወይም፣ ‹‹እኔ የሰራዊት ጌታ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ››

Haggai 2:10

በዘጠነኛው ወር በሃያ አራተኛው ቀን
ይህ በዕብራውያን ቀን አቆጣጠር ዘጠነኛው ወር ነው። በምዕራባውያን አቆጣጠር ሃያ አራተኛውን ቀን የሚውለው ታህሳስ አጋማሽ ላይ ነው።

ዳርዮስ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት
‹‹ዳርዮስ ንጉሥ በሆነ በሁለተኛው ዓመት›› ወይም፣ ‹‹ዳርዮስ ከነገሠ ሁለት ዓመት ሲሆነው››

ዳርዮስ... ሐጌ
የእነዚህን ሰዎች ስም እንዴት እንደ ተረጐምህ ሐጌ 1፥1 ተመልከት።

የያህዌ ቃል መጣ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ጥቅም ላይ የዋለው ከእግዚአብሔር የመጣውን ልዩ መልእክት ለማመልከት ነው። ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ሐጌ 1፥1 ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ መልእክት ሰጠ›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ይህን መልእክት ተናገረ››

ለያህዌ የተለየ ምግብ... ቅዱስ
‹‹ለያህዌ የተለየ›› እና ‹‹ቅዱስ›› የተሰኙት ቃሎች የአንድ የዕብራይስጥ ቃል ትርጉም ናቸው። ‹‹የተቀደሰ ምግብ... ቅዱስ››

Haggai 2:13

በሞት ምክንያት
‹‹የሞተ ሰው ሥጋ ቢነካ››

ሐጌም እንዲህ አለ፣ ‹‹እንደዚሁ... የረከሰ ነው››
ሐጌ ለካህናቱ የሰጠው መልስ ለካህናቱ እንዲናገር ያህዌ የነገረውን ነበር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለዚህም ሐጌ መለሰላቸው፣ እንዲሁ... የረከሰ ነው በማለት የያህዌን ቃል ነገራቸው።››

ይህ ሕዝብና ይህ ወገንም በፊቴ እንደዚሁ ነው
‹‹ይህን ሕዝብና ይህን ወገን የምመለከተው እንደዚሁ ነው።›› አንድ ቅዱስ ነገር የረከሰውን ቢነካ ርኩሱ ነገር እንደሚቀደስ ያህዌ ለካህናቱ ያሳስባል። ከዚያም ጣዖትን ያመልኩ ስለ ነበር የረከሱ እንዲሆኑ እንደሚያስብና በዚህም ምክንያት እነርሱ የሚነኩት ሁሉ እንደሚረክስ ያሳስባቸዋል።

ይህ የያህዌ ቃል ነው
የሚናገረው በእርግጥ መሆኑን ለማመልከት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። ሐጌ 1፥9 እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ እንዲህ ይላል›› ወይም፣ ‹‹እኔ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ››

Haggai 2:15

በቤተ መቅደስ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ከመነባበሩ በፊት
ይህን ተግባርን በሚመለከት ሁኔታ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የቤተ መቅደሱን የመጀመሪያውን ድንጋይ ከማስቀመጣችሁ በፊት››

ሃያ መስፈሪያ
‹‹20 መስፈሪያ›› አንድ፣ ‹‹መስፈሪያ›› ልኩ ስንት እንደ ሆነ አይታወቅም

አምሳ ማድጋ
‹‹50 ማድጋ›› አንድ ‹‹ማድጋ›› ልኩ ስንት እንደ ሆነ አይታወቅም

የእጃችሁን ሥራ ሁሉ
‹‹የሠራችሁትን ሁሉ›› ወይም፣ ‹‹ሰብላችሁን››

ያህዌ እንዲህ ይላል
የሚናገረው በእርግጥ መሆኑን ለማመልከት ስሙን በመጥራት ያህዌ ስለ ራሱ ይናገራል። ሐጌ 1፥9 እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ይህን ተናግሮአል›› ወይም፣ ‹‹እኔ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ››

Haggai 2:18

በዘጠነኛው ወር ሃያ አራተኛ ቀን
ይህ በዕብራውያን አቆጣጠር ዘጠነኛ ወር ነው። በምዕራባውያን አቆጣጠር ሃያ አራተኛው ቀን የሚውለው ታህሳስ መሐል ነው። ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ሐጌ 2፥10 ላይ ተመልከት።

‹‹የያህዌ ቤተ መቅደስ መሠረት እስከ ተጣለበት ቀን ድረስ››
ይህን፣ ‹‹የያህዌን ቤተ መቅደስ መሠረት በጣላችሁበት›› በማለት መተርጐም ይቻላል።

በጐተራው የቀረ ዘር ይገኛልን?
ያህዌ ለሚሰጣቸው ተስፋ ቃል ሕዝቡን እያዘጋጀ ነው። ይህን ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጐተራ ውስጥ ምንም ዘር እንደ ሌላ ማየት ትችላላችሁ››

የወይኑ፣ የበለሱ ዛፍ፣ የሮማኑና የወይራው ዛፍ
‹‹የወይን፣ የበለስ፣ የሮማንና የወይራ ዛፎቻችሁ

ሮማኑ
ይህ አንድ ዐይነት ጣፍጭ ፍራፍሬ ነው። ስለዚህ ዛፍ እየተነገረ መሆኑን ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሮማን ዛፍ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Haggai 2:20

የያህዌ ቃል መጣ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ጥቅም ላይ የዋለው ከእግዚአብሔር የተለየ መልእክት መምጣቱን ለማመልከት ነው። ሐጌ 1፥1 ላይ ይህን እንዴ እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ መልእክት ሰጠ›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ይህን መልእክት ተናገረ››

ሐጌ... ዘሩባቤል
እነዚህ የሰዎች ስም ናቸው። ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ሐጌ 1፥1 ላይ ተመልከት።

በወሩ ሃያ አራተኛ ቀን
ይህ የሚናገረው ስለ የትኛው ወር እንደ ሆነ ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በዘጠነኛው ወር ሃያ አራተኛ ቀን››

ሰማያትንና ምድርን እንደማናወጥ
‹‹ምድርን አናውጣለሁ›› የሚለውን፣ ‹‹የምድር መናወጥ አመጣለሁ›› በማለት መተርጐም ይቻላል። ሰማያትም እንደሚናወጡ ነገሮች አድርጐ ያህዌ ይናገራል። ይህ ሐሳብ እንዴት እንደ ተተረጐመ ሐጌ 2፥6 ተመልከት።

አናወጠ
ይህን ግሥ ዛፍ ላይ ያለ ፍሬ ወይም ሌላ ነገር እንዲወድቅ ዛፉን ወዲያ ወዲህ ከመነቅነቅ ጋር ማመሳሰል ይቻላል። ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው 2፥6 ተመልከት።

ሰማያትንና ምድርን
ይህ፣ ‹‹መላውን ፍጥረት›› ወይም፣ ‹‹ማንኛውንም ነገር›› እንደ ማለት ነው።

የመንግሥታትን ዙፋን እገለብጣለሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ዙፋን›› የሚወክለው ላዩ ላይ የሚቀመጠውን ንጉሥ ነው። ‹‹በንጉሥ የሚገዛ አገር››

የመንግሥታትን ኀይል አጠፋለሁ
ምናልባትም እነዚህ፣ ‹‹መንግሥታት›› የእስራኤል ጠላቶች መሆናቸውን ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የእስራኤል ጠላት የሆኑ መንግሥታት ከእንግዲህ ወዲህ እንዳይበረቱ ይህን አደርጋለሁ››

እያንዳንዳቸው በገዛ ወንድሞቻቸው ሰይፍ ወድቃሉ።
እዚህ ላይ ሰይፍ አሰቃቂ አሟሟትን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እያንዳንዱ ሰው በገዛ ራሱ ወንድም ይገደላል››

Haggai 2:23

በዚያን ቀን
‹‹እኔ በምሠራበት ቀን››

የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
የሚናገረው በእርግጥ መሆኑን ለማመለክከት ስሙን በመጥራት ያህዌ ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ሐጌ 1፥9 ተመልከት። ‹‹ይህ የሰራዊት ጌታ ያህዌ የተናገረው ነው›› ወይም ‹‹እኔ የሰራዊት ጌታ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ››

ዘሩባቤል... ሰላትያል
የእነዚህን ሰዎች ስም እንዴት እንደ ተረጐምህ ሐጌ 1፥1 ተመልከት

ያህዌ እንዲህ ይላል
የሚናገረው በእርግጥ መሆኑን ለማመልከት ስሙን በመጥራት ያህዌ ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ሐጌ 1፥9 ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ ይህን ተናግሮአል›› ወይም፣ ‹‹እኔ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ››

እንደ ማተሚያ ቀለበቴ አደርግሃለሁ
ሥልጣን እንዳላቸው ለማሳየት ሰነዶች ላይ ለማተም ነገሥታት የቀለበት ማተሚያ ይጠቀማሉ። እርሱ የያህዌን ቃል ስለሚናገር ዘሩባቤል ይህን ሥልጣን ከያህዌ ተቀብሏል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Zechariah

Zechariah

Chapter 1

1 ዳርዮስ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት በስምንተኛው ወር ወደ አዶ ልጅ ወደ በራክዩ ልጅ ወደ ነቢዩ ዘካርያስ እንዲህ የሚል የያህዌ ቃል መጣ፤ 2 “ያህዌ
በአባቶቻችሁ እጅግ ተቆጥቶ ነበር! 3 ለሕዝቡ ተናገር፤ የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል፤ ወደ እኔ ተመለሱ! ይህ የሰራዊት ጌታ የያህዌ ዐዋጅ ነው፤ እኔም ወደ
እናንተ እመለሳለሁ፤ የሰራዊት ጌታ ያህዌ። 4 “የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል፤ “ከክፉ መንገዳችሁና ከክፉ ሥራችሁ ተመለሱ!” በማለት በቀድሞ ዘመን
ነቢያት እንደ ሰበኩላቸው አባቶቻችሁ አትሁኑ። እነርሱ ግን አልሰሙም፤ እኔንም አላደመጡም ይህ የያህዌ ዐዋጅ ነው። 5 ለመሆኑ፣ አባቶቻችሁ ወዴት አሉ?
ነቢያትስ ለዘላለም በሕይወት ይኖራሉን? 6 ለባሪያዎቼ ለነቢያት ያዘዝኋቸው ቃልና ሥርዐት በአባቶቻችሁ ላይ አልደረሰምን? እነርሱም ንስሐ በመግባት እንዲህ
አሉ፤ ‘የሰራዊት ጌታ ያህዌ በወሰነው መሠረት ለሥራችንና ለመንገዳችን የሚገባውን አድርጎብናል። 7 ዳርዮስ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት ሳባጥ በመባለው
በአሥራ አንደኛው ወር በሃያ አራተኛው ቀን ያይህዌ ቃል ወደ አዶ ልጅ ወደ በራክዩ ልጅ ወደ ነቢዩ ዘካርያስ መጣ። 8 እነሆም በሌሊት ራእይ አየሁ፤ አንድ ሰው
ቀይ ፈረስ ላይ ተቀምጦ ነበር፤ እርሱም በሸለቆው ውስጥ በባርሰነት ዛፎች መካከል ቆሞ ነበር፤ ከበስተ ኋላውም ቀይ፣ ቀይ ቡናማና ነጭ ፈረሶች ቆመው
ነበር። 9 እኔም፣ “ጌታ ሆይ፣ እነዚህ ምንድን ናቸው?” አልሁ። ከእኔ ጋር እየተነጋገረ የነበረው መልአክም፣ “እነዚህ፣ ምን እንደ ሆኑ፣ አሳይሃለሁ” አለኝ። 10
ዛፎች መካከል ቆሞየነበረውም ሰው “እነዚህ በምድር ሁሉእንዲመላለሱ ያህዌ የላካቸው ናቸው”በማለት መለሰ። 11 ከዚያም፣ በባርሰነትዛፎች መካከል ቆሞ
ለነበረው የያህዌመልአክ፣ “በምድር ሁሉ ተመላለስን፤እነሆ መላዋ ምድር አርፋ ተቀምጣለች”አሉት። 12 ያኔ የያህዌ መልአክ መልሶ፣ “የሰራዊት ጌታ ያህዌ
ሆይ፣ በእነዚህ ሰባ ዓመቶች ውስጥ የተቆጣሃቸውን ኢየሩሳላምንና የይሁዳን ከተሞች የማትራራላቸው እስከ መቼ ነው?” አለ። 13 ያህዌም ከእኔ ጋር
እየተነጋገረ ለነበረው መልአክ ደስ በሚያሰኝ የሚያጽናና ቃል መለሰለት። 14 ስለዚህ፣ ከእኔ ጋር እየተነጋገረ የነበረው መልአክ እንዲህ አለኝ፤ “እንዲህ ብለህ
ተናገር፣ የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል፣ ለኢየሩሳሌምና ለጽዮን እጅግ ቀንቻለሁ! 15 ተደላደለውና ተመቻችተው በተቀመጡ ሕዝቦች ላይ በጣም
ተቆጥቻለሁ። እኔ የተቆጣሁት በመጠኑ ቢሆንም፣ እነርሱ ግን ጥፋት እንዲባባስ አድርገዋል። 16 ስለዚህ የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል፣ በምሕረቴ ወደ
ኢየሩሳሌም ተመልሻለሁ። በውስጧ ቤቴ እንደ ገና ይሠራል፤ መለኪያ ገመድም በኢየሩሳሌም ላይ ይዘረጋል! ይህ የሰራዊት ጌታ የያህዌ ዐዋጅ ነው። 17
ደግሞም፣ እንዲህ በማለት ተናገር፣ ‘የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል፤ ከተሞቼ እንደ ገና በመልካም ነገሮች ይሞላሉ፤ ያህዌ እንደ ገና ጽዮንን ያጽናናል፤ እንደ
ገና ኢየሩሳሌምን ይመርጣታል። 18 ከዚያ ዐይኖቼን ወደ ላይ አንሥቼ አራት ቀንዶች ተመለከትሁ! 19 ከእኔ ጋር እየተነጋገረ ለነበረውም መልአክ፣ “እነዚህ
ምንድን ናቸው?” አልሁት። እርሱም፣ “እነዚህ ይሁዳን፣ እስራኤልንና ኢየሩሳሌምን የበተኑ ቀንዶች ናቸው” አለኝ። 20 ከዚያም ያህዌ አራት የእጅ ባለ ሙያዎች
አሳየኝ። 21 እኔም፣ “እነዚህ ይሁዳን፣ እስራኤልንና ኢየሩሳሌምን የበተኑ አራት ቀንዶች ናቸው፤ እነዚህ ሰዎች የመጡት ግን እነርሱን ለማስወጣትና ሕዝቡን
ለመበታተን በይሁዳ ምድር ላይ ቀንዳቸውን ያነሡትን ሕዝቦች ቀንዶች ሰባብሮ ለመጣል ነው” በማለት መለሰልኝ።

Zechariah 1:1

በስምንተኛው ወር
ይህ የዕብራይስጡ ስምንተኛው ወር ነው። በምዕራባውያኑ (ጎርጎሳውያኑ) የዘመን አቆጣጠር በጥቅምት ወር መጨረሻና በኅዳር ወር መጀመሪያ ግድም የሚውለው የዓመቱ ክፍል ነው። (‘የዕብራውያኑ ወራትና መደበኛ ቁጥሮች’ የሚለውን ይመልከቱ)

የዳርዮስ ዘመነ መንግሥት ሁለተኛው ዓመት
“የንጉሥ ዳርዮስ ዘመነ መንግሥት ሁለተኛው ዓመት” ወይም “ንጉሥ ዳርዮስ ንጉሥ ከሆነ በኋላ በሁለተኛው ዓመት” (‘መደበኛ ቁጥሮች’ የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል መጣ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ጥቅም ላይ የሚውለው ከእግዚአብሔር የመጣን የተለየ መልእክት ለማስተዋወቅ ነው። ትኩ. “እግዚአብሔር መልእክት ሰጠ (አስተላለፈ)” ወይም “ያህዌ ይህንን መልእክት ተናገረ” (‘ፈሊጣዊ አነጋገር’ የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ
ይህ በብሉይ ኪዳን ለነበሩት ሕዝቡ የገለጠው የእግዚአብሔር ስም ነው። ይህን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ በሚመለከት በትርጉም ቃል ገጽ ስለ ያህዌ የተጠቀሰውን ይመልከቱ።

በራክዮ ... አዶ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (‘ስሞችን እንዴት መተረጎም እንደሚገባ’ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር በአባቶቻችሁ ላይ እጅግ ተቆጥቶ ነበር
“በቀደሙት አባቶቻችሁ ላይ በጣም ተቆጥቶ ነበር”

ወደ እኔ ተመለሱ ... እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ
ለሚመለስ ወይም እንደገና ለሚመለስ አንድ ሌላ ሰው የአመለካከት ለውጥ እያደረገ እንደሆነ አድርጎ ያህዌ ይናገራል። ሕዝቡ ወደ ያህዌ ተመለሱ ማለት እንደገና ለእርሱ የተሰጡ ይሆናሉ እርሱንም ያመልኩታል ማለት ሲሆን ያህዌ ወደ ሕዝቡ ተመለሰ ማለት ደግሞ እንደገና ይባርካቸዋል፣ ይረዳቸዋልም ማለት ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 1:4

ከክፉ መንገዳችሁና ከክፉ ሥራችሁ ተመለሱ
አንዳንድ ድርጊቶችን ከማድረግ መቆጠብ እነዚያን ድርጊቶች ከማድረግ እንደመመለስ ሆኖ ይነገራል። ‘ክፉ መንገዳችሁ’ እና ‘ክፉ ሥራችሁ’ የሚሉት ሐረጎች በመሠረቱ ትርጉማቸው አንድ ነው። አት. “ክፉ ሥራዎቻችሁን ሁሉ መሥራት አቁሙ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ጥምር አገላለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እነርሱ ግን አልሰሙም እኔንም አላደመጡም
የእነዚህ የሁለቱም ሐረጎች ትርጉም የእስራኤል ሕዝብ ለያህዌ ሕግጋት አይታዘዙም ነበር ማለት ነው። ትኩ. “ነገር ግን ሕግጋቴን አያደምጡም” (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ ... እንዲህ ይላል
እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ ያህዌ ስለ ራሱ ስሙን በመጥቀስ ይናገራል። በዘካርያስ 1:3 ላይ ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንደዚህ ብሎ ተናግሯል” ወይም “እኔ የሠራዊት ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህንን ነው” (‘መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ሰው’ የሚለውን ይመልከቱ)

አባቶቻችሁ አሁን የት አሉ? ነቢያቱስ ወዴት አሉ? ለዘላለም በሕይወት ይኖራሉን?
ምላሽ የማይጠብቁት እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች ለቀደሙት አባቶቻቸው የእግዚአብሔርን መልእክት ያወጁላቸው ቀደምት አባቶችም ሆኑ ነቢያት የሞቱ ስለመሆናቸው አጽንዖት ይሰጣሉ። ጥያቄዎቹ በገለጻ መልክ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አት. “አባቶቻችሁም ሆኑ ነቢያቶቻችሁ እዚህ የሉም፣ ምክንያቱም ሁሉም ሞተዋል” (መልስ የማይጠብቁ ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ለባሪያዎቼ ለነቢያት ያዘዝኳቸው ቃልና ሥርዓት በአባቶቻችሁ ላይ አልደረሰምን
ይህ መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ አጽንዖት የሚሰጠው አዎንታዊ መልስ የሚጠብቅ መሆኑን ነው። ያህዌ የሚናገረው የሕዝቡ ቀደምት አባቶች እግዚአብሔርን ያለመታዘዛቸውን ውጤት እንደተቀበሉ ሲሆን ቃሉና ሥርዓቱ እነርሱን እንዳሳደዳቸውና እንደያዛቸው ሰው ሆኖ ቀርቧል። ጥያቄዎቹ በገለጻ መልክ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አት. “ነገር ግን ለባሪያዎቼ ለነቢያት ያዘዝኳቸው ቃሎቼና ሥርዓቶቼ አባቶቻችሁን ይዘዋቸዋል።” ወይም “ነገር ግን አባቶቻችሁ ባሪያዎቼ ነቢያት እንዲነግሯቸው ያዘዝኳቸውን ቃሎቼንና ሥርዓቶቼን ባለመታዘዛቸው ምክንያት ጉዳት ደርሶባቸዋል።” (መልስ የማይጠብቁ ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ቃሎቼና ሥርዓቶቼ
እነዚህ ቃላት ሁለቱም ነቢያት ለሕዝቡ ቀደምት አባቶች የያህዌን መልእክት ያወጁበትን መንገድ ለመግለጽ የዋሉ ናቸው። (ጥምር አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

መንገዶቻችንና ሥራዎቻችን
‘መንገዶች’ እና ‘ሥራዎች’ የሚሉት ቃላት ሁለቱም በመሠረቱ ትርጉማቸው አንድ ነው። ትኩ. ‘ባሕሪዎቻችን’ (ጥምር አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 1:7

በሁለተኛው ዓመት፣ ሳባጥ በሚባለው በዐሥራ አንደኛው ወር በሃያ አራተኛው ቀን
‘ሳባጥ’ የሚባለው በዕብራውያን ዘመን አቆጣጠር አሥራ አንደኛው ወር ነው። ሃያ አራተኛው ቀን በአውሮፓውያን (ግሪጎርያን) አቆጣጠር በየካቲት ወር አጋማሽ ላይ የሚውል ነው። (የዕብራውያን ወሮች፣ መደበኛ ቁጥሮች እና ስሞችን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ የሚሉትን ይመልከቱ)

ዳርዮስ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት
“የንጉሥ ዳርዮስ ዘመነ መንግሥት ሁለተኛው ዓመት” ወይም “ንጉሥ ዳርዮስ ንጉሥ ከሆነ በኋላ በሁለተኛው ዓመት” በዘካርያስ 1:1 ላይ ይህንን እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። (‘መደበኛ ቁጥሮች’ የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል መጣ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ጥቅም ላይ የሚውለው ከእግዚአብሔር የመጣን የተለየ መልእክት ለማስተዋወቅ ነው። በዘካርያስ 1:1 ላይ ይህንን እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “እግዚአብሔር መልእክት ሰጠ (አስተላለፈ)” ወይም “ያህዌ ይህንን መልእክት ተናገረ” (‘ፈሊጣዊ አነጋገር’ የሚለውን ይመልከቱ)

በራክዮ ... አዶ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (‘ስሞችን እንዴት መተረጎም እንደሚገባ’ የሚለውን ይመልከቱ)

ተመለከትሁ
እዚህ ላይ ‘መመልከት’ የሚለው ቃል ዘካርያስ ባየው ነገር እንደተደነቀ ያመለክታል።

ባርሰነት ዛፎች
ደማቅ አበቦች ያሉት አነስተኛ የዛፍ ዓይነት ነው። (የማይታወቁትን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

እኔም፣ “ጌታ ሆይ፣ እነዚህ ምንድን ናቸው?” አልሁ። ከእኔ ጋር ይነጋገር የነበረው መልአክም ...
እዚህ ላይ ዘካርያስ ማንነቱ ያልተገለጸውን መልአክ እያነጋገረ ነው። ይህ ‘በመጋላ (ቀይ) ፈረስ ላይ ከተቀመጠው ሰው’ ጋር ተመሳሳይ አይደለም።

ጌታ ሆይ፣ እነዚህ ምንድን ናቸው?
“ጌታው፣ እነዚህ ነገሮች ምንድን ናቸው?” እዚህ ላይ ‘ጌታ’ የሚለው የትሕትና አነጋገርን የሚያመለክት ነው።

Zechariah 1:10

በባርሰነት ዛፎች መካከል ቆሞ የነበረው ሰው ... በባርሰነት ዛፎች መካከል ቆሞ የነበረው የያህዌ መልአክ
እነዚህ ሐረጎች የሚያመለክቱት በዘካርያስ 1:8 ላይ ‘በአምባላይ (ቀይ) ፈረስ ላይ ተቀምጦ’ የነበረውን ሰው ነው። ትኩ. “በባርሰነት ዛፎች መካከል ቆሞ የነበረው ሰው ... በባርሰነት ዛፎች መካከል ቆሞ የነበረው የያህዌ መልአክ” (‘ፈሊጣዊ አነጋገር’ የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ እነዚያ ናቸው ... መለሱም ... እንደዚህም አሉ
‘እነዚህ’ እና ‘እነርሱ’ የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት በባርሰነት ዛፎች መካከል ከነበረው ሰው ጀርባ የነበሩትን መጋላ (ቀይ)፣ ሐመር (የቀይ ዳማ) እና አምባላይ (ነጭ) ፈረሶችን ነው። ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፡- 1) በውስጠ-ታዋቂነት በፈረሶቹ ላይ የሚቀመጡ ሌሎች ሰዎች አሉ፣ እነዚህ ቃላትም የሚያመለክቱት እነዚያን በፈረሶቹ ላይ የሚቀመጡትን ነው። 2) ፈረሶቹ መነጋገር እንደሚችሉ ተደርገው የሰውኛ ገጽታ ተሰጥቷቸዋል። (ግምታዊ እውቀት፣ ውስጠ-ታዋቂ መረጃ እና ሰውኛ የሚሉትን ይመልከቱ)

በምድር ሁሉ መመላለስ
እየተመላለሱ ምድርን እንዲቃኙ ያህዌ እነዚህን መላኩ ውስጠ-ታዋቂ ነው። ይህ የባዘኑ ወይም የጠፉ መሆናቸውን አያመለክትም። (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

Zechariah 1:12

ወደ ኢየሩሳሌምና ወደ ይሁዳ ከተሞች
እዚህ ላይ ‘ኢየሩሳሌም’ እና ‘ከተሞች’ የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት በእነዚያ ከተሞች የሚኖሩትን ሕዝቦች ነው። አት. “ለኢየሩሳሌም ሕዝቦችና ለይሁዳ ከተሞች ሕዝቦች” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

ደስ በሚያሰኝና በሚያጽናና
“በመልካም የሚያጽናና ቃል”

Zechariah 1:14

ለኢየሩሳሌም ቀንቻለሁ
እዚህ ላይ ‘ቀንቻለሁ’ የሚለው እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመጠበቅ የነበረውን ጠንካራ ፍላጎት ያመለክታል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሰላም አለ በሚሉ ሕዝቦች ላይ ግን በጣም ተቆጥቻለሁ
‘ሰላም አለ’ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሕዝቡ በሰላምና በዕርጋታ እንደሚኖሩ እያሰቡ መሆኑን ነው። አት. “ሰላማቸውንና ደህንነታቸውን እያጣጣሙ ባሉት ሕዝቦች በጣም ተቆጥቻለሁ” (‘ፈሊጣዊ አነጋገር’ የሚለውን ይመልከቱ)

በመጠኑ ብቻ ተቆጥቼባቸው ነበር
“በኢየሩሳሌም ሕዝብ ላይ የተቆጣሁት በመጠኑ ብቻ ነበር”

ጥፋቱ እንዲብስ አደረጉ
“ሰላም አለ የሚሉት” ሕዝቦች ጥፋቱ እንዲብስ አደረጉ። ይህ ማለት ምንም እንኳን ያህዌ ኢየሩሳሌምን ለመቅጣት እነዚህን ሕዝቦች ቢጠቀምባቸውም እነርሱ ግን ያህዌ እነርሱ እንዲያደርጉ ካቀደው በላይ በኢየሩሳሌም ላይ ጉዳት አደረሱ ማለት ነው። (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

Zechariah 1:16

በምሕረት ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሻለሁ
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፦ 1)ምንም እንኳን ሕዝቡ ወደ ምርኮ በሄዱበት ጊዜ ያህዌ ኢየሩሳሌምን የተዋት ቢሆንም፣ አሁን ግን ሕዝቡ ከምርኮ በተመለሱ ጊዜ እርሱም ወደ ኢየሩሳሌም ይመለሳል ወይም 2) ያህዌ ወደ ከተማይቱ እንደገና እየተመለሰ በሚመስል ሁኔታ ለኢየሩሳሌም በነበረው አመለካከት ላይ ለውጥ እንዳደረገና እንደገና እንደሚባርካቸው እንደሚረዳቸውም እየተናገረ ነው። አት. “ለኢየሩሳሌም እንደገና ምሕረቴን አሳያለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቤቴ በውስጥዋ ይሠራል
‘በውስጥዋ’ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢየሩሳሌምን ሲሆን ‘ቤቴ’ የሚለው ደግሞ ለቤተ መቅደሱ ስመ-ምስል ስያሜ ነው። ይህ በተናጋሪ አነጋገር መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት. “ሕዝቡ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደሴን ይገነባሉ” (ስመ-ምስል ስያሜ እና ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚሉትን ይመልከቱ)

ይህ የሠራዊት ጌታ የያህዌ አዋጅ ነው
እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ ያህዌ ስለ ራሱ ስሙን በመጥቀስ ይናገራል። በዘካርያስ 1:3 ላይ ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “የሠራዊት ጌታ ያህዌ ያወጀው ይህንን ነው” ወይም “እኔ የሠራዊት ጌታ ያህዌ ያወጅሁት ይህንን ነው” (መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ሰው የሚሉትን ይመልከቱ)

መለኪያ ገመድም በኢየሩሳሌም ላይ ይዘረጋል
ይህ የሚያመለክተው ገንቢዎች ከተማይቱን እንደገና ለመገንባት መሣሪያዎቻቸውን እንደሚጠቀሙ ነው። ይህ በአናጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት. “ገንቢዎች የመለኪያ ገመዳቸውን በኢየሩሳሌም ላይ ይዘረጋሉ” ወይም “ሕዝቡ ኢየሩሳሌምን እንደገና ይገነባሉ” (ግምታዊ እውቀት፣ ውስጠ-ታዋቂ መረጃ እና ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚሉትን ይመልከቱ)

በድጋሚ ተጣራና እንደዚህ በል
እነዚህን ቃላት የተናገረው ዘካርያስን ሲያነጋግር የነበረው መልአክ ነው።

ከተሞቼ እንደገና በበጎነት ይትረፈረፋሉ
‘ከተሞቼ’ የሚለው የሚያመለክተው የይሁዳን ከተሞች ሲሆን በእነዚያ ከተሞች የሚኖሩትንም ሕዝቦች ይወክላል። በውሃ መያዣ በርሜል የተመሰሉትን እነዚያን ከተሞች፣ በጎነት የሚያጥለቀልቅ ውሃ እንደሆነ ሁሉ የእነዚያን ከተሞች ነዋሪዎች በበጎነት እንደሚያጥለቀልቃቸውና እንደገና ባለጠጎች እንዲሆኑ እንደሚያደርጋቸው ያህዌ ይናገራል። አት. “ከተሞቼ እንደገና ባለጠጎች ይሆናሉ” ወይም “በይሁዳ ከተሞች ያሉት ሕዝቦች እንደገና ባለጠጎች ይሆናሉ” (ስመ-ምስል ስያሜ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ያህዌ ጽዮንን እንደገና ያጽናናል
እዚህ ላይ ‘ጽዮን’ የሚለው ቃል የሚያመለክተው በከተማ የሚኖሩትን ሰዎች ነው። አት. “ያህዌ በጽዮን የሚኖረውን ሕዝብ እንደገና ያጽናናል” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 1:18

ዓይኖቼን አነሳሁ
‘ዓይኖቼ’ የሚለው ቃል የሚመለከተውን ሰው ይወክላል። አት. “ወደ ላይ ተመለከትሁ” (በክፋይ የተወከለ አካል የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ ይሁዳን፣ እስራኤልንና ኢየሩሳሌምን የበታተኑ ቀንዶች ናቸው
ቀንዶች ብዙውን ጊዜ ወታደራዊ ኃይልን የሚወክሉ ተምሳሌቶች በመሆን ጥቅም ላይ ይውላሉ። እዚህ ላይ በተምሳሌትነተ የሚወክሉት የእስራኤልን መንግሥት ድል ያደረጉትን ኃያላን መንግሥታትን ነው። ‘ይሁዳ፣ እስራኤልና ኢየሩሳሌም’ የሚሉት ቃላት የሚወክሉት በእነዚያ ስፍራዎች የሚኖሩትን ሰዎች ነው። አት. “እነዚህ ቀንዶች የሚወክሉት ይሁዳን እስራኤልንና ኢየሩሳሌምን የበታተኑትን መንግሥታት ነው” (ተምሳሌታዊ ቋንቋ እና ስመ-ምስል ስያሜ የሚሉትን ይመልከቱ)

Zechariah 1:20

አራት ሙያተኞች
‘የብረት አንጥረኞች’ ወይም ‘የብረት-ሥራ ሠራተኞች’

እነዚህ ሰዎች
ይህ የሚያመለክተው አራቱን ሙያተኞች ነው።

እነዚህ ይሁዳን የበታተኑ ቀንዶች ናቸው
እነዚህ ቀንዶች የእስራኤልን መንግሥት ድል ያደረጉትን ኃይለኛ መንግሥታት በተምሳሌትነት ያመለክታሉ። ‘ይሁዳ’ የሚለው ቃል በይሁዳ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላል። በዘካርያስ 1:19 ላይ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “እነዚህ ቀንዶች የይሁዳን ሕዝብ የበታተኑትን መንግሥታት ይወክላሉ።” (ተምሳሌታዊ ቋንቋ እና ስመ-ምስል ስያሜ የሚሉትን ይመልከቱ)

ማንም ራሱን ቀና ማድረግ እንዳይችል
የይሁዳን ሕዝብ በአሰከፊ ሁኔታ ሲጨቁኑ የነበሩት መንግሥታት ማንም ሰው ራሱን ቀና ማድረግ እንዳይችል እንዳደረጉ ተነግሮላቸዋል። አት. “በጣም እንዲሰቃዩ አደረጓቸው።” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በይሁዳ ምድር ላይ ቀንዳቸውን መንግሥታት ቀንዶች ሰብሮ ለመጣል ነው
ወታደራዊ ኃይላቸውን በመጠቀም ይሁዳን ድል ለማድረግ የተነሱትን መንግሥታት ያህዌ መንግሥታቱ ቀንዳቸውን እንዳነሱ አድርጎ እየተናገረ ነው። የእነዚህን መንግሥታት ወታደራዊ ኃይል ሲደመስሱ የነበሩት አራቱ ሙያተኞች የመንግሥታቱን ቀንድ ሰብረው ወደ መሬት እንደጣሉ አድርጎ እየተናገረ ነው። አት. “በይሁዳ ምድር ላይ ወታደራዊ ኃይላቸውን የተጠቀሙትን የመንግሥታቱን ኃይል ለመደምሰስ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀንድ ያነሱትን የመንግሥታቱን ቀንዶች ለመስበር
“መንግሥታቱ ያነሷቸውን ቀንዶች ለመስበር”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 እንደ ገና ዐይኖቼን ወደ ላይ አንሥቼ በእጁ መለኪያገመድ የያዘ ሰው አየሁ። **2** እኔም፣ “የት ልትሄድ ነው?” አልሁት። እርሱም መልሶ፣ “የኢየሩሳሌም ስፋትና ርዝመት ምን ያህል እንደ ሆነ ለመለካት ነው” አለኝ። **3** ከዚያም ከእኔ ጋር እየተነጋገረ የነበረው መልአክ ሄደ፤ ሌላም መልአክ ሊገናኘው መጣ። **4** ሁለተኛው መልአክ፣ ሩጥና ለዚያ ወጣት እንዲህ ብለህ ንገረው፣ ‘በውስጧ ካለው ሕዝብና እንስሶች ባት የተነሣ ኢየሩሳሌም ቅጥር እንደሌላት ከተማ ትሆናለች። **5** ምክንያቱም እኔ ራሴ፣ በዙሪያዋ የእሳት ቅጥር በመካከልዋም ክብር እሆናለሁ ይህ የያህዌ ዐዋጅ ነው። **6** ኑ! ኑ! ከሰሜን ምድር አምልጡ፤ ይህ የያህዌ ዐዋጅ ነው። ወደ አራቱ የሰማይ ነፋሶች በትኛችኋለሁ! ይህ የያህዌ ዐዋጅ ነው። **7** እናንት ከባቢሎን ሴት ልጅ ጋር የምትኖሩ፣ ወደ ጽዮን አምልጡ!” **8** የሰራዊት ጌታ ያህዌ ካከበረኝና በዘረፉአችሁ ሕዝቦች ላይ ከላከኝ በኋላ፣ እናንተን የሚነካ የእግዚአብሔርን ዐይን ይነካል! ያህዌ ይህን ካደረገ በኋላ፣ **9** “እኔ ራሴ እጄን በእነርሱ ላይ አንሣለሁ፤ ባርያዎቻቸውም ይዘርፏቸዋል” ያኔ የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንደ ላከኝ ታውቃላችሁ። **10** እኔ ራሴ መጥቼ በመካከልሽ እኖራለሁና የጽዮን ልጅ ሆይ በደስታ ዘምሪ! ይህ የያህዌ ዐዋጅ ነው። **11** ከዚያም ቀን ብዙ ሕዝቦች ወደ እግዚአብሔር ይጠጋሉ፤ የእኔም ሕዝብ ይሆናሉ፤ በመካከልሽ እኖራለሁ” እናንተም ወደ እናንተ የላከኝ ያህዌ እንደ ሆነ ታውቃላችሁ። **12** ያህዌም በተቀደሰች ምድር ይሁዳን ርስቱ ያደርገዋል፤ ኢየሩሳሌምንም እንደ ገና ለራሱ ይመርጣታል። **13** ከተቀደሰ ማደሪያው ተነሥቷልና፤ ሥጋ ለባሽ ሁሉ በያህዌ ፊት ጸጥ በል!

Zechariah 2:1

ዓይኖቼን አነሳሁ
‘ዓይኖቼ’ የሚለው ቃል የሚመለከተውን ሰው ይወክላል። አት. “ወደ ላይ ተመለከትሁ” (በክፋይ የተወከለ አካል የሚለውን ይመልከቱ)

የመለኪያ ገመድ
አንድ ሰው ሕንፃዎችን ወይም ተለቅ ያለ የመሬት ይዞታን ለመለካት የሚጠቀምበት የተወሰነ ቁመት ያለው ገመድ

እርሱም እንደዚህ አለኝ
ስለሆነም የመለኪያውን ገመድ የያዘው ሰው እንደዚህ አለኝ

Zechariah 2:3

ሌላ መልአክ ለገናኘው መጣ
ይህ መልአክ ከዚህ በፊት ያልተከሰተ አዲስ ተሳታፊ ነው። (ቀደም ያሉና አዲስ ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

ሁለተኛውም መልአክ እንደዚህ አለው
ሁለተኛውም መልአክ እኔን ሲያነጋግረኝ የነበረውን መልአክ እንደዚህ አለው።

ኢየሩሳሌም በገላጣ ስፍራ ትቀመጣለች ... አውሬዎችም በውስጥዋ
‘በገላጣ ስፍራ ትቀመጣለች’ የሚለው ሐረግ ቅጠር የሌላትን ከተማ ለሚገልጸው ቃል ትርጉም ሆኖ ያገለግላል። በከተማይቱ እጅግ ብዙ ሰዎች ስለሚኖሩ በዙሪያዋ ቅጥር መሥራት እስከማይቻል ድረስ በጣም ሰፊ ትሆናለች። አት. “ኢየሩሳሌም በዙሪያዋ ቅጥር አይኖራትም ... አውሬዎችም በውስጥዋ ...” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

እኔ ለእርሷ በዙሪያዋ የእሳት ቅጥር እሆንላታለሁ
ሰዎች ለጥበቃ ዓላማ በከተሞቻቸው ዙሪያ ቅጥር ይገነባሉ። እዚህ ላይ ያህዌ እርሱ ራሱ በዙሪያዋ የእሳት ቅጥር እንደሆነላት ሁሉ ኢየሩሳሌምን እንደሚጠብቃት ነው የሚናገረው። አት. “የእሳት ቅጥር በዙሪያዋ እንደሚሆንላት እኔ ኢየሩሳሌምን እጠብቃታለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ ... እንዲህ ይላል
እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ ያህዌ ስለ ራሱ ስሙን በመጥቀስ ይናገራል። በዘካርያስ 1:4 ላይ ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንደዚህ ብሎ ተናግሯል” ወይም “እኔ የሠራዊት ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህንን ነው” (‘መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ሰው’ የሚለውን ይመልከቱ)

ዘካርያስ **2:6-7** የትርጉም ማስታወሻዎች ኑ፣ ኑ
እነዚህ ሁለት ቃላት ጥድፊያን ያመለክታሉ፣ ለሚከተለውም ትዕዛዝ አጽንዖት ይሰጣሉ። ቃላቱ በቋንቋችሁ ጥድፊያን በሚያመለክት ሐረግ ሊተረጎም ይችላል። አት. “ሩጡ፣ ሩጡ” ወይም “ቶሎ በሉ፣ ቶሎ በሉ” (ጣምራ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰሜን ምድር
ይህ የሚያመለክተው ባቢሎንን ነው።

እንደ አራቱ የሰማይ ነፋሳት በትኛችኋለሁ
‘አራቱ የሰማይ ነፋሳት’ የሚለው ሐረግ ‘በሁሉም አቅጣጫ’ ማለት ነው። ያህዌ ሕዝቡ በብዙ የተለያዩ አገሮች እንዲኖሩ ማድረጉን ነፍስ ከማንኛውም አቅጣጫ መንፈስ ከሚችልበት መንገደ ጋር ያነጻጽረዋል። አት. “በየአቅጣጫው በትኛችኋለሁ። (ንፅፅሮሽ የሚለውን ይመልከቱ)

ከባቢሎን ሴት ልጅ ጋር የምትኖሪ
‘ባቢሎን ሴት ልጅ’ የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው የባቢሎንን ከተማ ነው። ያህዌ ስለ ከተማዋ ሴት ልጅ እንደሆነች አድርጎ እየተናገረ ነው። አት. “እናንተ በባቢሎች የምትኖሩ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 2:8

አጠቃላይ መረጃ
ዘካርያስ አሁን መናገር ይጀምራል፣ ደግሞም ኢየሩሳሌምን በዘረፏት መንግሥታት ላይ ይፈርድ ዘንድ ያህዌ እንዴት እንደላከው ይናገራል።

በዘረፉአችሁ
በዘረፉአችሁ በሚለው በውስጠ-ታዋቂ ‘እናንተ’ የሚለው የሚያመለክተው ኢየሩሳሌምን ነው።

የሚነካችሁ
‘መንካት’ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ለመጉዳት የታሰበን መንካት ነው። አት. “የሚጎዳችሁ ማንም ቢሆን” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ዓይን ብሌን
የዓይን ብሌን በጣም ስስ (ለጉዳት የተጋለጠ) ከሆኑት የዓይን ክፍሎች አንዱ ነው። ‘የዓይን ብሌን’ የሚለው ፈሊጣዊ አባባል እጅግ ዋጋ ያለውን ነገር ያመለክታል። እዚህ ላይ እግዚአብሔር ለኢየሩሳሌም ታላቅ እሴት ሰጥቷታል ማለት ነው። አት. “ለእግዚአብሔር እጅግ ታላቅ ዋጋ ያለው” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እጄን በእነርሱ ላይ አነሳለሁ
እጅን በአንድ ሌላ ሰው ላይ ማንሳት የጠላትነት አዝማሚያ ነው። እዚህ እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን የሚጎዷትን ያጠቃል የሚል ተምሳሌታዊ ትርጉም አለው። አት. “እኔ ራሴ እዋጋቸዋለሁ” ወይም “እኔ ራሴ አጠቃቸዋለሁ” (ተምሳሌታዊ ተግባር የሚለውን ይመልከቱ)

ለባሪያዎቻቸው ዝርፊያዎች ይሆናሉ
‘ዝርፊያ’ የሚለው ቃል በግሥ መልኩ ሊተረጎም ይችላል። ትኩ. “ባሪያዎቻቸው ይዘርፏቸዋል”

Zechariah 2:10

የጽዮን ልጅ ሆይ፣ እልል በዪ
‘ጽዮን’ የሚለው ‘ከኢየሩሳሌም’ ጋር አንድ ነው። ነቢዩ ስለ ከተማይቱ ሴት ልጅ እንደሆነች አድርጎ ይናገራል። ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፡ - 1) ዘካርያስ ከተማይቱን መዘመር በሚችል ሰው በሰውኛ ይገልጻታል። ትኩ. “ጽዮን፣ እልል በዪ” ወይም 2) ‘የጽዮን ልጅ’ በከተማይቱ ለሚኖሩ ሕዝቦች ስመ-ምስል ስያሜ ነው። ትኩ. “የጽዮን ሕዝቦች፣ እልል በሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ፣ ሰውኛ እና ስመ-ምስል ስያሜ የሚሉትን ይመልከቱ)

እኔ ራሴ ልመጣና በመካከላችሁ ልሰፍር ነው
“እኔ ራሴ ልመጣና በመካከላችሁ ልኖር ነው” ‘መስፈር’ ማለት ድንኳን መትከልና በድንኳኑ ተጠቅሞ መኖር ማለት ነው።

ያህዌ ... እንዲህ ይላል
እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ ያህዌ ስለ ራሱ ስሙን በመጥቀስ ይናገራል። በዘካርያስ 1:4 ላይ ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንደዚህ ብሎ ተናግሯል” ወይም “እኔ የሠራዊት ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህንን ነው” (‘መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ሰው’ የሚለውን ይመልከቱ)

ታላላቅ ሕዝቦች ወደ ያህዌ ይጠጋሉ
ዘካርያስ የታላላቅ መንግሥታት ሕዝቦች የያህዌ ሕዝቦች እንደሚሆኑና ራሳቸውን ወደ ያህዌ እንዳስጠጉ ሁሉ እርሱን እንደሚያመልኩት አድርጎ ይናገራል። አት. “የታላላቅ መንግሥታት ሕዝቦች የያህዌ ሕዝቦች ይሆናሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ስመ-ምስል ስያሜ የሚሉትን ይመልከቱ)

በዚያ ቀን
‘በዚያን ጊዜ’

በመካከልሽም እሰፍራለሁ
‘በመካከልሽም እኖራለሁ’

Zechariah 2:12

ያህዌ ሕጋዊ ንብረቱ እንደሆነች አድርጎ ይሁዳን ይወርሳል
ዘካርያስ የሚወርሳት ቋሚ ንብረቱ እንደሆነች ሁሉ ያህዌ ይሁዳን እንደራሱ ምድር አድርጎ እንደሚናገር ይገልጻል። አት. “ያህዌ ይሁዳ ቋሚ ንብረቱ እንደሆነች አድርጎ ይናገራል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሥጋ ለባሽ ሁሉ
እዚህ ላይ ‘ሥጋ ለባሽ’ የሚለው ቃል የሰው ልጆችን ይወክላል። ትኩ. “ሕዝቦች ሁሉ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

ተነሥቶአል
ቸል ካለበት ሁኔታ አንድ ሰው ለሥራ እንዳንቀሳቀሰው ሁሉ ያህዌ ተግባሩን መፈጸም አድርጎ ዘካርያስ ይናገራል። ይህ እንቅስቃሴው ወደ ኢየሩሳሌም የመመለስ ተግባሩን እንደሚያመለክት ተደርጎ ተወስዷል። አት. “እየመጣ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ፣ ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከተቀደሰ ስፍራው
እዚህ ላይ ‘የተቀደሰ ስፍራ’ የሚለው የሚያመለክተው ሰማይን ነው እንጂ በኢየሩሳሌም ያለውን ቤተ መቅደስ አይደለም። (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 ከዚያም ሊቀ ካሁኑ ኢያሱ በያህዌ መልአክ ፊት ቆሞ ያህዌ አሳየኝ፤ እርሱን በኃጢአት ልመክሰሰ ሰይጣን በቀኙ በኩል ቆሞ ነበር። **2** የያህዌ መልአክ ሰይጣንን፣ “አንተ ሰይጣን ያህዌ ይገሥጽህ፣ ኢየሩሳሌምን የመረጠ ያህዌ ይገሥጽህ! ይህ ሰው ከእሳት የተነጠቀ ትንታግ አይደለምን?” አለው። **3** መልአኩ ፊት ቆሞ በነበረ ጊዜ ኢያሱ ያደፉ ልብሶች ለብሶ ነበር። **4** ስለዚህ መልአኩ በፊቱ ቆመው የነበሩትን፣ “ያደፉ ልብሶቹን አውልቁለት” አላቸው። ከዚያም ኢያሱን፣ “እነሆ፣ ርኩሰትህን ከአንተ አስወግጃለሁ፤ ጥሩ ልብስም አለብስሃለሁ” አለው። **5** መልአኩም፣ “ራሱ ላይ ንጹሕ መጠምጠሚያ ያድርጉለት! አለ። እነርሱም የያህዌ መልአክ አጠገቡ ቆሞ እያለ በኢያሱ ራስ ላይ ንጹሕ መጠምጠሚያ አደረጉለት፤ ንጹሕ ልብስም አለበሱት። **6** በመቀጠል የያህዌ መልአክ ለኢያሱ ይህን ማስጠንቀቂያ ሰጠው፤ **7** “የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል፣ በመንገዴ ብትሄድ፣ ትእዛዜንም ብትጠብቅ፣ ያኔ፣ ቤቴን ታስተዳድራለህ፤ በአደባባዮቼም ላይ ጎላፊ ትሆናለህ በእነዚህ በፊቴ በቆሙት መካከል እንድትገባና እንድትወጣ አደርግሃለሁ። **8** ሊቀ ካሁኑ ኢያሱ ሆይ ስማ፤ ከአንተ ጋር ያሉት ጓደኞችህም ፊት ለሚመጡት ምልክት የሚሆኑ ሰዎች ናቸውና ይስሙ፤ እነሆ፣ ባርያዬን ቁጥቋጡን አመጣለሁ። **9** ኢያሱ ፊት ያኖሩትን ድንጋይ ተመልከቱ። በዚያ አንድ ድንጋይ ላይ ሰባት ዐይኖች አሉ፤ በእርሱም ላይ ቅርጽ እቀርጻለሁ፤ የዚህችንም ምድር ኀጢአት በአንድ ቀን አስወግዳለሁ፤ ይህ የያህዌ ዐዋጅ ነው። **10** በዚያን ቀን እያንዳንዱ ሰው በገዛ ወይኑና በለስ ዛፉ ሥር እንዲቀመጥ ባልንጀራውን ይጋብዛል” ይላል ያህዌ።

Zechariah 3:1

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለዘካርያስ ስለ ካህኑ ስለ ኢያሱ ራዕይ ያሳየዋል።

ስለ ኃጢአት ሊከሰው በቀኙ በኩል ቆሞ ነበር
“ኢያሱን ስለ ኃጢአት ሊከሰው ዝግጁ ሆኖ ሰይጣን ከኢያሱ በስተቀኝ ቆሞ ነበር።”

ይህ ከእሳት የተነጠቀ ትግታግ አይደለምን?
የያህዌ መልአክ ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የጠየቀው ለሚጠበቀው አዎንታዊ ምላሽ አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህ አባባል በገለጻ መልክ ሊቀርብ ይችላል። አት. “ኢያሱ ከእሳት የተነጠቀ ትንታግ ነው።” (ምላሽ የማይጠብቅ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእሳት የተነጠቀ ትግታግ
ትንታግ እየተቃጠለ ያለ ጉርማጅ እንጨት ነው። የያህዌ መልአክ ኢያሱ ከባቢሎን ምርኮ ተርፎ መምጣቱን እንጨቱ ሙሉ በሙሉ ከመቃጠሉ በፊት አንድ ሰው ከእሳት ውስጥ መዞ እንዳወጣው እየተናገረ ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ኢያሱም ያደፈ ልብስ ለብሶ ነበር
በዚህ ራዕይ ‘ያደፉ ልብሶች’ የኃጢአተኛነት ተምሳሌት ናቸው። (ተምሳሌታዊ ቋንቋ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 3:4

ከፊቱ ቆመው የነበሩትን
በፊቱ በሚለው በውስጠ-ታዋቂ ‘ከእርሱ’ (ፊት) የሚለው ቃል የሚያመለክተው መልአኩን ነው። ቃሉ የሚያመለክተው በዚያ የነበሩትን ሌሎች መላእክትን ነው።

እነሆ **(አስተውል)**
“ልነግርህ ያለሁት እውነተኛና አስፈላጊም ስለሆነ ልብ አድርገው”

ኃጢአትህን ከአንተ አስወግጃለሁ
የኢያሱ ልብሶች የኃጢአተኛነት ተምሳሌት ስለነበሩ፣ ልብሱን በማስወገድ መልአኩ የኢያሱን ኃጢአተኛነት እያስወገደ ነበር። ኃጢአትን ማስወገድ የሚለው አገላለጽ ፈሊጣዊ አባባል ሲሆን ትርጉሙም የኢያሱን በደል ከእርሱ አርቆለታል ማለት ነው። አት. “ኃጢአትህን ከአንተ አርቄያለሁ” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ጥሩ ልብስም አለብስሃለሁ
እዚህ ላይ ‘ጥሩ ልብስ’ በተምሳሌትነት የሚወክለው ጽድቅን ነው። (ተምሳሌታዊ ቋንቋ የሚለውን ይመልከቱ)

አድርጉለት
እዚህ ላይ በውስጠ-ታዋቂ ‘እነርሱ’ (ያድርጉለት) የሚለው የሚያመለክተው በዚያ የነበሩትን ሌሎች መላእክት ነው።

ጥምጥም
በራስ ላይ የሚጠመጠም ረጅም የጨርቅ ቁራጭ

Zechariah 3:6

አበክሮ ኢያሱን አዘዘው
ጠበቅ ባለ ሁኔታ ኢያሱን አዘዘው።

በመንገዴ ብትሄድ ትዕዛዜንም ብትጠብቅ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ አንድ ናቸው። ያህዌ ስለ መታዘዝ የሚናገረው ሰውዬው በያህዌ መንገድ ላይ እንደሚራመድ አድርጎ ነው። አት. “የምትታዘዘኝ ከሆነና ትዕዛዜን የምትጠብቅ ከሆነ” (ትይዩነት እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ቤቴን ታስተዳድራለህ በአደባባዮቼም ላይ ጎላፊ ትሆናለህ
እዚህ ላይ ‘ቤቴ’ የሚለው ቃል ለቤተ መቅደሱ ምስለ-ምስል ስያሜ ሲሆን ‘አደባባዮቼ’ የሚለው ቃል ደግሞ የሚያመለክተው በቤተ መቅደሱ ዙሪያ የነበረውን ግቢ ነው። ቃላቱ በአንድነት ኢያሱ በአጠቃላይ በቤተ መቅደሱ ይዞታ ላይ ሥልጣነ ይኖረዋል የሚል ትርጉም አላቸው። አት. “በመቅደሴና በቅጥር ገቢው ላይ ሥልጣን ይኖርሃል” (ምስለ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

በፊቴ በሚቆሙት መካከል ትገባና ትወጣ ዘንድ
‘...መካከል ትገባና ትወጣ ዘንድ’ የሚለው ሐረግ ኢያሱ ወደ ያህዌ ዘንድ የመግባት መብት ያለው ቡድን አካል እንደሚሆንና ከእነርሱም እኩል መብት እንደሚኖረው የሚገልጽ ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ አባባል ነው። አት. “እነዚህ በፊቴ ያሉት እንደሚመጡ ሁሉ በፊቴ ትመጣ ዘንድ” (ፈሊጣዊ አባባል፣ ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

Zechariah 3:8

አጠቃላይ መረጃ
የያህዌ መልአክ ለኢያሱ መናገሩን ይቀጥላል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከአንተ ጋር የሚኖሩት ወዳጆችህ
ይህ ሐረግ የሚያመለክተው በኢያሱ መሪነት ሥር በቤተ መቅደስ የሚያገለግሉትን ሌሎች ካህናትን ነው። ትኩ. “ከአንተ ጋር የሚኖሩት ሌሎች ካህናት” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ምልክት የሚሆኑ ሰዎች ናቸው
እዚህ ላይ ‘ምልክት’ ለሚመለከቱት አንድ የተለየ ትርጉም የሚያስተላልፍ ነገርን የሚያመለክት ነው። ያህዌ በቤተ መቅደስ ውስጥ የሚያገለግሉት ካህናት ያህዌ ባሪያውን እንደሚያመጣ የሚያመለክቱ ምልክቶች እንደሆኑ አድርጎ እየተናገረ ነው።

ባሪያዬ ቁጥቋጡ
‘ቁጥቋጡ’ የሚለው ቃል እዚህ ላይ የሚያመለክተው በያህዌ ሕዝብ ላይ እንደ ንጉሥ የሚያገለግለውን መሲሐዊ ማንነት ነው። ያህዌ ስለዚህ ሰው ከዛፍ ላይ እንደበቀለ ቅርንጫፍ (ቁጥቋጥ) እንደሆነ አድርጎ ነው የሚናገረው። ‘ቁጥቋጥ’ የማዕረግ ስም ስለሆነ በእናንተም ቋንቋ ከዚህ ጋር በሚመጥን ቃል መተርጎም አለበት። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በኢያሱ ፊት ያስቀመጥሁት ድንጋይ
እዚህ ላይ ‘ድንጋይ’ የሚለው ቃል ምናልባት የከበረ ድንጋይን ወይም ዕንቁን የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም።

በአንዱ ድንጋይ ላይ ሰባት ዓይኖች አሉ
ብርሃን የሚያንፀባርቁት የድንጋይ ገጽታዎች ዓይኖች እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል። አት. “በዚህ አንድ ድንጋይ ሰባት ገጽታዎች አሉት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቅርጽ እቀርጻለሁ
ጽሑፉን በድንጋዩ ላይ እንደሚቀርጽ በውስጠ-ታዋቂ ግልጽ ነው። አት. “በ ድንጋዩ ላይ ጽሑፍ እቀርጻለሁ።” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

መቅረጽ
በሹል ብረት መጫር ወይም መቦርቦር

ያህዌ ... እንዲህ ይላል
እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ ያህዌ ስለ ራሱ ስሙን በመጥቀስ ይናገራል። በዘካርያስ 1:4 ላይ ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንደዚህ ብሎ ተናግሯል” ወይም “እኔ የሠራዊት ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህንን ነው” (‘መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ሰው’ የሚለውን ይመልከቱ)

የዚህችንም ምድር በደል በአንድ ቀን አስወግዳለሁ
እዚህ ላይ ‘ምድር’ የሚለው ቃል በምድሪቱ የሚኖሩትን ሕዝቦች ይወክላል። አት. “በዚህ ምድር የሚኖሩትን ሕዝቦች ኃጢአት በአንድ ቀን አስወግዳለሁ።” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 3:10

በዚያን ቀን
‘በዚያን ወቅት’

እያንዳንዱን በገዛ ወይኑን በለሱ ሥር ሆኖ ባልንጀራውን ይጋብዛል
‘ወይን’ እና ‘የበለስ ዛፍ’ ሁለቱም የብልጽግና ተምሳሌቶች ናቸው። ይህ ሐረግ ሕዝቡ በብልጽግናና በሰላም የሚኖሩበትን ተግባሮች ይገልጻል። አት. “በሰላም ስለሚኖሩ እያንዳንዱ ጎረቤቱን እንዲመጣና በወይኑና በበለሱ በታች እንዲያርፍ ይጋብዛል” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 ከእኔ ጋር ይነጋገር የነበረው መልአክም ተመልሶ፣ ከእንቅልፉ እንደሚነቃ ሰው አንቃኝ። **2** እርሱም፣ “ምን ይታይሃል?” አለኝ። እኔም፣ “በዐናቱ ላይ፣ የዘይት ማሰሮ ያለበት ሁለመናው ወርቅ የሆነ መቅረዝ አየሁ። መቅረዙም ላይ በእያንዳንዱ ጫፍ ሰባት ክሮች ያሏቸው ሰባት መብራቶች ነበር። **3** ደግሞም አንዱ ከዘይት ማሰሮው በስተ ቀኝ፣ ሌላውም በስተ ግራ ሁለት የወይራ ዛፎች አሉ።” **4** እኔም፣ ያነጋገረኝ የነበረውን መልአክ፣ “ጌታዬ እነዚህ ምንድን ናቸው?” አልሁት። **5** ከእኔ ጋር እየተነጋገረ የነበረው መልአክም መልሶ፣ “እነዚህ ምን እንደ ሆኑ አታውቅም?” አለኝ። እኔም፣ “ጌታዬ ሆይ፣ አላውቅም” አልሁት። **6** ከዚያም እንዲህ አለኝ፤ “ለዘሩባቤል የመጣው የያህዌ ቃል ይህ ነው፤ ‘በመንፈሴ እንጂ፣ በኀይልና በብርታት አይደለም፤ ይላል የሰራዊት ጌታ ያህዌ። **7** አንተ ታላቅ ተራራ ምንድነህ? በዘሩባቤል ፊት ደልዳላ ሜዳ ትሆናለህ፤ ሰዎች “ሞገስ! ሞገስ ይሁንለት!” ብለው እየጮኹ እርሱ መደምደሚያውን ድንጋይ ያወጣል። **8** የያህዌ ቃል ወደ እኔ መጣ፤ **9** “የዘሩባቤል እጆች የዚህን ቤት መሠረት እንደ ጣሉ ሁሉ፣ የእርሱ እጆች ይፈጽሙታል። ያኔ፣ የሰራዊት ጌታ ያህዌ ወደ እናንተ እንደ ላከኝ ታውቃላችሁ። **10** የጥቂቱን ቀን ነገሮች የናቀ ግን ነው? እነዚህ ሰዎች በዘሩባቤል እጅ ቱንቢውን ሲያዩ በጣም ደስ ይላቸዋል። እነዚህ ሰባት መብራቶች በምድር ሁሉ የሚመላለሱ የያህዌ ዐይኖች ናቸው። **11** ከዚያም መልአኩን፣ “ከመቅረዙ ግራና ቀኝ የቆሙት እነዚህ ሁለት የወይራ ዛፎች ምንድን ናቸው?” በማለት ጠየቅሁት። **12** እንደ ገናም፣ “በሁለት የወርቅ ቧንቧዎች አጠገብ የወርቅ ዘይት የሚያፈስሱት እነዚህ ሁለት የወይራ ቅንርንጫፎችስ ምንድን ናቸው?” አልሁት። **13** እርሱም፣ “እነዚህ ምን እንደ ሆኑ አታውቅም?” አለኝ፤ እኔም፣ “ጌታዬ ሆይ፣ አላውቅም” አልሁት። **14** እርሱም፣ “እነዚህ የምድርን ሁሉ ጌታ ለማገለል የሚቆሙ ሁለቱ የወይራ ዛፎች ናቸው” አለኝ።

Zechariah 4:1

አንድ ሰው ከእንቅልፉ እንደሚነቃ አነቃኝ
ዘካርያስ መልአኩ በነበረበት ጥልቅ ሃሳብ ጣልቃ የገባበትን መንገድ አንድ ሰው ሌላውን ሰው ከእንቅልፉ ከማንቃት ጋር አነፃፅሮታል። አት. “ከእንቅልፉ እንደሚነቃ ሰው ይበልጥ ንቁ እንድሆን አደረገኝ።” (ንፅፅሮሽ የሚለውን ይመልከቱ)

የመቅረዝ መኮስተሪያ
እሳት የሚለኮስበት የመቅረዙ ጫፍ

በስተግራ
በዚህ ሐረግ ላይ የተደረገው ግድፈት ቀደም ካለው ሐረግ ሊታከልበት ይችላል። (ግድፈት የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 4:4

እነዚህ ምን ማለት እንደሆኑ አታውቅምን?
መልአኩ ይህንን መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ የጠየቀው ዘካርያስ እነዚህ ምን ማለት እንደሆኑ ሊያውቅ እንደሚገባው አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ በገለጻ መልክ ሊተረጎምም ይችላል። አት. “በእርግጥ እነዚህ ምን ማለት እንደሆኑ ታውቃለህ።” (መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 4:6

አያያዥ መግለጫ
ከዘካርያስ ጋር የሚነጋገረው መልአክ ራዕዩን መግለጹን ይቀጥላል።

በኃይልና በብርታት አይደለም
በዚህ ሐረግ ውስጥ ግሥ ስለሌለበት በቋንቋችሁ ግሥ መጨመር አስፈላጊ ይሆናል። አት. “በኃይልና በብርታት አይሳካላችሁም።” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

በኃይልም ሆነ በብርታት አይሆንም
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፡ - 1) ‘ኃይል’ እና ‘ብርታት’ የሚሉት ቃላት በመሠረቱ ትርጉማቸው አንድ ሲሆን አጽንዖት የሚሰጡትም የዘሩባቤልን ኃይል ታላቅነት ነው ወይም 2) ‘ኃይል’ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ወታደራዊ ጥንካሬን ሲሆን ‘ብርታት’ የሚለው ቃል ደግሞ የዘሩባቤልን ሥጋዊ አቅም ወይም ጉልበት ነው። አት. “በእርግጥ በአንተ ጥንካሬ አይደለም” ወይም “በወታደራዊ ጥንካሬም ሆነ በራስህ ጉልበት አይደለም” (ጣምራ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ትልቅ ተራራ ምንድን ነህ? በዘሩባቤል ፊት ሜዳ ትሆናለህ
ይህ ያህዌ ዘሩባቤል የሚያጋጥሙት መሰናክሎች እንደ ትልቅ ተራራ እንደሆኑ አድርጎ የተናገረበት ተለዋጭ ዘይቤ ነው። ይህንን መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ የጠየቀው እነዚህ መሰናክሎች ለዘሩባቤል ስኬት ምንም ተግዳሮት እንደማይሆኑ አጽንዖት ለመስጠት ነው። ጥያቄው በገለጻ መልክ ሊተረጎምም ይችላል። አት. “ታላቅ ተራራ፣ አንተ ምንም አይደለህም፤ ዘሩባቤል ሜዳ ያደርግሃል” ወይም “መሰናክሎች እንደ ተራራ ታላላቅ መስለው ቢታዩም፣ አንድ ሰው በተስተካከለ ሜዳ ላይ እንደሚራምድ ያህል ዘሩባቤል ድል ይነሣቸዋል።” (ተለዋጭ ዘይቤ እና መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

መደምደሚያውን ድንጋይ ያወጣል
መደምደሚያ ድንጋይ አንድ ነገር በሚገነባበት ጊዜ በመጨረሻ የሚቀመጠው ድንጋይ ነው። ይህ የሚያመለክተው በቤተ መቅደሱ ድምድማት ላይ የሚቀመጠውን ድንጋይ ነው። አት. “በቤተ መቅደሱ አናት ላይ የሚቀመጠውን ድንጋይ ያወጣል” ወይም “የቤተ መቅደሱን ግንባታ ያጠናቅቃል” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ሞገስ ይሁንለት! ሞገስ ይሁንለት! እያሉ እየጮኹ
ለዚህ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት፡ - 1) ‘ሞገስ’ የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ሞገስ ሲሆን ሕዝቡም እግዚአብሔር የተጠናቀቀውን ቤተ መቅደስ እንዲባርክ እየጠየቁ ነው። አት. “’እግዚአብሔር ይባርከው! እግዚአብሔር ይባርከው!’ እያሉ ሕዝቡ እየጮኹ ሳሉ” ወይም 2) ‘ሞገስ’ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ውበትን ሕዝቡም የተጠናቀቀው ቤተ መቅደስ ምን ያህል ውብ እንደሆነ እየተናገሩ ነው። አት. “ሕዝቡ ’ውብ! ውብ እኮ ነው!’ ብለው እየጮኹ ሳለ” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

Zechariah 4:8

አያያዥ መግለጫ
ከዘካርያስ ጋር የሚነጋገረው መልአክ ራዕዩን መግለጹን ይቀጥላል።

የያህዌ ቃል ወደ እኔ መጣ እንዲህ ሲል፡ - “የዘሩባቤል እጆች ...”
ፈሊጣዊው አባባል ጥቅም ላየ የዋለው ከእግዚአብሔር የመጣን የተለየ መልእክት ለማስተዋወቅ ነው። አት. “እግዚአብሔር መልእክትን ሰጠኝ፣ እንዲህም አለኝ፡ - ‘የዘሩባቤል እጆች ...’” ወይም “ያህዌ ይህንን መልእክት ነገረኝ፡ - ‘የዘሩባቤል እጆች ...’” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የዘሩባቤል እጆች ... መሠረት ጣሉ ... የሚፈጽሙትም የእርሱ እጆች ናቸው
እዚህ ላይ ‘እጆች’ የሚለው ቃል የሚወክለው ዘሩባቤልን ነው። አት. “ዘሩባቤል መሠረቱን ጥሏል ... የሚፈጽመውም እርሱ ነው።” (በክፋይ የተወከለ አካል የሚለውን ይመልከቱ)

የዚህን ቤት መሠረት
እዚህ ላይ ‘ቤት’ የሚለው ቃል የሚወክለው ቤተ መቅደሱን ነው። አት. “የዚህ ቤተ መቅደስ መሠረት” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

የጥቂቱን ነገር ቀን የናቀ ማን ነው? ይህ ሕዝብ ይደሰታል
ዘካርያስ ይህንን መልስ የማይጠብቀውን ጥያቄ የተጠቀመበት በተለይ ‘የጥቂቱን ነገር ቀን’ ስለናቁት ለመናገር ነው። አባባሉ በገለጻ መልክ ሊተረጎም ይችላል። አት. “የጥቂቱን ነገር ቀን የናቁ ይደሰታሉ” (መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የጥቂት ነገሮች ቀን
‘የጥቂት ነገሮች ጊዜ’ ይህ ሐረግ የሚያመለክተው ሕዝቡ ቤተ መቅደሱን ሲገነቡ የነበሩበትንና ጥቂት እርምጃ እያሳዩ የመሰሉበትን ጊዜ ነው። አት. “የሥራው እርምጃ ዘገምተኛ የነበረበት ጊዜ” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ቱንቢው
ይህ የሚያመለክተው የሕንፃው ግድግዳዎች ትክክል መሆናቸውን ለማረጋገጥ ሕንፃውን የሚገነቡ የሚጠቀሙበት ከገመድ ጫፍ ከባድ ነገር የታሠረበት መሣሪያ ነው።

እነዚህ ሰባት መቅረዞች ... ሁለት የወይራ ዛፎች
እነዚህ የሚያመለክቱት ዘካርያስ በዘካ.4፡2-3 ላይ የተመለከታቸውን ሰባት መቅረዞችና ሁለት የወይራ ዛፎችን ነው።

እነዚህ ሰባቱ መቅረዞች በምድር ሁሉ የሚዘዋወሩ የያህዌ ዓይኖች ናቸው
እነዚህ ሰባት መቅረዞች በተምሳሌትነት የያህዌን ዓይኖች ይወክላሉ፣ ነገር ግን ቃል በቃል የያህዌ ዓይኖች አይደሉም። መልአኩ የይህዌ ዓይኖች በመላው ምድር እንደሚዘዋወሩ አድርጎ የያህዌ ዓይኖች በምድር የሚደረገውን ሁሉ እንደሚመለከቱ ይና ገራል። አት. “እነዚህ ሰባት መቅረዞች በመላው ምድር የሚደረገውን ማንኛውንም ነገር የሚመለከቱትን የያህዌን ዓይኖች ይወክላሉ።” (ተምሳሌታዊ ቋንቋ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

Zechariah 4:12

እነዚህ ሁለት የወይራ ቅርንጫፎች ምንድን ናቸው?
እዚህ ላይ ዘካርያስ ጥያቄውን በመቀየር ከሁለቱ የወይራ ዛፎች ጋር ስለተያያዙት ቅርንጫፎች ይጠይቃል።

ሁለቱ የወርቅ ቧንቧዎች
እነዚህ ቧንቧዎች ቀደም ባለው የዘካርያስ ራዕይ መግለጫ ላይ አልተጠቀሱም ነበር። ከመቅረዙ ዘንግ መቀመጫ ላይ ካለው ማሰሮ ጋር የተያያዙ እንደሚሆኑና ለሚነደው የመቅረዝ ዘንግ ዘይት የሚያቀብሉ ሳይሆኑ አይቀሩም።

ወርቃማው ዘይት
እዚህ ላይ ‘ወርቃማ’ የሚለው የሚያመለክተው የዘይቱን ቀለም እንጂ ዘይቱ ከወርቅ የተሠራ ነው ማለት አይደለም።

እነዚህ ምን እንደሆኑ አታውቅምን?
መልአኩ ይህንን መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ የጠየቀው ዘካርያስ እነዚህ ምን ማለት እንደሆኑ ሊያውቅ እንደሚገባው አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ በገለጻ መልክ ሊተረጎምም ይችላል። አት. “በእርግጥ እነዚህ ምን ማለት እንደሆኑ ታውቃለህ።” (መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 4:14

እነዚህ አዲስ የወይራ ዘይት ልጆች ናቸው
እነዚህ እነዚህን ሕዝቦች በተምሳሌትነት ይወክላሉ እንጂ ቃል በቃል ሕዝቡ አይደሉም። አት. “እነዚህ ሁለት ቅርንጫፎች የአዲስ የወይራ ዘይት ልጆችን ይወክላሉ” (ተምሳሌታዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

የአዲስ የወይራ ዘይት ልጆች
ይህ ፈሊጣዊ አባባል እነዚህ ሰዎች በአዲስ የወይራ ዘይት ተቀብተዋል ማለት ነው። የተቀባ ሰው በያህዌ የተመረጠ ወይም ለተለየ ተግባር የተሾመ ነው። አት. “የተቀቡ ሰዎች” ወይም “ያህዌ የሾማቸው ሰዎች” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

በጌታ ፊት የሚቆሙ
‘...ፊት መቆም’ እርሱን ለማገልገል በአንድ ሰው ሕላዌ ፊት መቆም ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 5

1 ከዚያም ዘወር ብዬ ዐይኖቼን አነሣሁ፤ እነሆም፣ የሚበር መጽሐፍ ተመለከትሁ! **2** መልአኩም፣ “ምን ይታይሃል?” አለኝ። እኔም፣ “ርዝመቱ ሃያ ክንድ፣ ወርዱ አሥር ክንድ የሆነ መጽሐፍ ሲበር ይታየኛል” በማለት መለስሁ። **3** እርሱም፣ “ይህ በምድር ሁሉ ላይ የሚመጣ መርገም ነው፤ የሚሰርቅ ሁሉ፣ በአንዱ በኩል በተጻፈው መሠረት ይጠፋል፤ በሐሰት የሚምል ሁሉ እንደ ተናገረው ቃል በሌላው ወገን በተጻፈው መሠረት ይጠፋል። **4** እኔ መርገሙን አመጣዋለሁ፤ ይህ የሰራዊት ጌታ የእግዚአብሔር ዐዋጅ ነው። ወደ ሌባው ቤትና በስሜ በሐሰት ወደሚምለው ሰው ቤት ይገባል፤ በዚያም ይቀመጣል፤ ቤቱን፣ እንጨቱንና ድንጋዩን ያጠፋል። **5** ከዚያም ከእኔ ጋር እየተነጋገረ የነበረው መልአክ መጥቶ፣ “ዐይንህን አንሥተህ እየመጣ ያለውን ተመልከት! አለኝ። **6** እኔም፣ “ምንድን ነው?” አልኩት። እርሱም፣ “ይህ እየመጣ ያለውን ኢፋ የያዘ መስፈሪያ ነው፤ ይህ የምድሪቱ ሁሉ በደል ነው” አለኝ። **7** ከዚያም ከእርሳስ የተሠራው ክዳን ተነሣ፤ የእፍ መስፈሪያው ውስጥ አንዲት ሴት ተቀምጣ ነበር! **8** መልአኩም፣ “ይህች ዐመፃ ናት!” ብሎ መልሶ ወደ መስፈሪያው አስገባትና የእርሳሱን ክዳን አጋው። **9** እነሆም፣ ዐይኔን አንሥቼ ሁለት ሴቶች ወደ እኔ ሲመጡ አየሁ፤ በክንፎቻቸውም ነፋስ ነበር፤ የሽመላ ክንፎችን የመሰሉ ክንፎች ነበሯቸው። መስፈሪያውን በምድርና በሰማይ መካከል አነሡት። **10** በእኔም ጋር እየተነጋገረ የነበረውን መልአክ፣ “መስፈሪያውን ወዴት እየወሰዱት ነው?” አልሁት። **11** እርሱም፣ “ቤተ መቅደስ ሊሠሩለት ወደ ባቢሎን ምድር ይወስዱታል፤ ቤተ መቅደሱ ዝግጁ ሲሆን፣ እዚያ በተዘጋጀለት ቦታ ይቀመጣል” አለኝ።

Zechariah 5:1

ከዚያ በኋላ ዘወር አልሁ
‘አልሁ’ በሚለው በውስጠ-ታዋቂ ‘እኔ’ የሚለው የሚያመለክተው ዘካርያስን ነው።

እነሆ
‘እነሆ’ የሚለው ቃል ዘካርያስ በተመለከተው ነገር እንደተገረመ ያሳያል።

ርዝመቱ ሃያ ክንድ ወርዱ አሥር ክንድ
አንድ ‘ክንድ’ 46 ሴንቲ ሜትር ነው። አት. “ርዝመቱ 9.2 ሜትር፣ ወርዱ 4.6 ሜትር” (መጽሐፍ ቅዱሳዊ ርቀት የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 5:3

አጠቃላይ መረጃ
ከዘካርያስ ጋር የሚነጋገረው መልአክ ራዕዩን መግለጹን ይቀጥላል።

ይህ ... እርግማን ነው
‘ይህ’ የሚለው ቃል የሚያመለክተው የመጽሐፉን ጥቅልል ነው። የመጽሐፉ ጥቅልል በጥቅልሉ ውስጥ ለተጻፈው ስመ-ምስል ስያሜ ነው። አት. “በዚህ መጽሐፍ ጥቅልል ውስጥ ያለው እርግማን ነው።” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ በምድር ሁሉ የሚወጣ
‘በምድር ሁሉ’ የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው በምድሩ ያለውን ማንኛውንም ስፍራ ነው። ርግማኑ በምድሪቱ ውስጥ በሚኖር በማንኛውም ሰው ላይ እንደሚደርስ ይጠቁማል። አት. “በመላ ምድሪቱ ባለ ማንኛውም ሰው ላይ ማለት ነው” (ፈሊጣዊ አባባል፣ ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

የሚሰርቅ ሁሉ ይጠፋል ... በሐሰት የሚምል ሁሉ ይጠፋል
እነዚህን ሕዝቦች ከምድሪቱ የሚያስወግደው ያህዌ አንድ ሰው ከዛፍ ላይ ቅርንጫፍ እንደሚቆርጥ ሲቆርጣቸው እንደነበረ ተደርጎ ተነግሯል። ይህ በተናጋሪ መልክ ሊቀርብ ይችላል። አት. “ያህዌ ማንኛውንም ሌባ ያስወግዳል ... ያህዌ በሐሰት መሐላ የሚምለውን ሁሉ ያስወግዳል” ወይም “ያህዌ ማንኛውንም ሌባ ከምድሪቱ ያስወግዳል ... ያህዌ ከምድሪቱ በሐሰት የሚምለውን ማንኛውንም ሰው ያስወግዳል።” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚሉትን ይመልከቱ)

በአንድ በኩል የሚለውን ... በሌላ በኩል የሚለውን
“የመጽሐፉ ጥቅልል በአንድ በኩል የሚለው ... የመጽሐፉ ጥቅልል በሌላ በኩል የሚለው”

አመጣዋለሁ
“እልከዋለሁ”

ያህዌ ... እንዲህ ይላል
እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ ያህዌ ስለ ራሱ ስሙን በመጥቀስ ይናገራል። በዘካርያስ 1:4 ላይ ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንደዚህ ብሎ ተናግሯል” ወይም “እኔ የሠራዊት ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህንን ነው” (‘መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ሰው’ የሚለውን ይመልከቱ)

እንጨቱንና ድንጋዩን ያጠፋል
የሌባውንና በሐሰት የሚምለውን ቤቶች የሚያጠፋው ርግማን ሰዎቹ የሚኖሩባቸው ቤቶች የተሠሩባቸውን የሕንፃ ቁሳቁሶች እንደሚያቃጥል ተደርጎ ተነግሯል። አት. “እንጨቱንና ድንጋዩን ያጠፋል” ወይም “ሙሉ በሙሉ ያጠፋዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና በክፋይ የተወከለ አካል የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 5:5

ዓይኖችህን አንሣ
‘ዓይኖች’ የሚለው ቃል የሚወከለው የሚመለከተውን ሰው ነው። አት. “ወደ ላይ ተመልከት” (በክፋይ የተወከለ አካል የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ሊመጣ ያለውን ኢፍ የያዘ ቅርጫት ነው
‘ኢፍ’ ደረቅ ነገሮች የሚለኩበት የልኬት መስፈሪያ ሲሆን መጠኑም 2.2 ሊትር ነው። እዚህ ላይ ቃሉ አንድ ኢፍ ደረቅ ነገሮች ለሚይዘው መስፈሪያ ስመ-ምስል ስያሜ ነው። አት. “ይህ ሊመጣ ያለው የመለኪያው ቅርጫት ነው” ወይም “ይህ ሊመጣ ያለው ትልቅ መስፈሪያ ነው” (መጽሐፍ ቅዱሳዊ የፍሳሽ መጠን እና ስመ-ምስል ስያሜ የሚሉትን ይመልከቱ)

በምድሪቱ ሁሉ ላይ ያለው የሕዝቡ በደል
ቅርጫቱ የሕዝቡን በደል በተምሳሌትነት ይወክላል ነገር ግን ቃል በቃል በደላቸው አይደለም። አት. “ይህ ቅርጫት በመላው ምድሪቱ ያሉትን ሰዎች በደል ይወክላል።” (ተምሳሌታዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ከእርሳስ የተሠራው ክዳን ተነሣ
ይህ በተናጋሪ መልኩ ሊቀርብ ይችላል። አት. “አንድ ሰው ከቅርጫቱ ላይ የእርሳሱን ክዳን አነሣ” (ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከበታቹም በውስጡ የተቀመጠች ሴት ነበረች
“ከእርሳሱ ክዳን በታች በቅርጫቱ ውስጥ የተቀመጠች ሴት ነበረች”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Zechariah 5:8

ይህች ርኩሰት ናት
ሴትዮዋ ርኩሰትን ትወክላለች። አት. “ይህች ሴት ርኩሰትን ትወክላለች” (ተምሳሌታዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

መልሶ አስገባት ... የእርሳሱንም ክዳን ...ገፍቶ
“መልሶ አስገባት ... የእርሳሱንም ክዳን ገፍቶ” ‘መልሶ አስገባት’ ወይም ‘ወረወራት’ የሚለው ቃል መልአኩ እነዚህን ነገሮች በእንዴት ያለ ኃይል እንዳከናወነ ያመለክታል። ሴቲቱንም ሆነ ክዳኑን ቃል በቃል አልወረወራቸውም።

ዓይኖችህን አንሣ
‘ዓይኖች’ የሚለው ቃል የሚወከለው የሚመለከተውን ሰው ነው። አት. “ወደ ላይ ተመልከት” (በክፋይ የተወከለ አካል የሚለውን ይመልከቱ)

በክንፎቻቸውም ንፋስ ነበረ
ይህ ፈሊጣዊ አባባል ይበሩ ነበር የሚል ትርጉም አለው። አት. “ይበሩ ነበር” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ክንፎቻቸውም እንደ ሽመላ ክንፎች ነበሩ
ሽመላ ከሁለት እስከ አራት ሜትር ርዝመት የሚሆን ክንፍ ያለው ትልቅ የወፍ ዘር ነው። ዘካርያስ የሴትዮዋን ክንፍ ስፋት መጠን ከሽመላ ክንፍ ጋር ያነጻጽረዋል።

ቅርጫቱንም በምድርና በሰማይ መካከል አነሡት
‘ምድር’ እና ‘ሰማይ’ የሚሉት ቃላት ሰማይን ለማመልከት ጥቅም ላይ የዋሉ የ... ዓይነት ናቸው። ሁለቱ ሴቶች ከቅርጫቱ ጋር መብረራቸው ውስጠ-ታዋቂ ነው። አት. “ቅርጫቱን ወደ ሰማይ አነሱትና በረሩ” (...ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

Zechariah 5:10

ቤተ መቅደስ ይሠሩለት ዘንድ ወደ ሲናር ምድር ይወስዱታል
የተደረገው ግድፈት ቀደም ካለው ቁጥር ሊወሰድ ይችላል። አት. “ቅርጫቱን የሚወስዱት በሲናር ምድር ቤተ መቅደስ ሊሠሩለት ነው።” (ግድፈት የሚለውን ይመልከቱ)

ቅርጫቱ እዚያ ይቀመጣል
ይህ በተናጋሪ መልክ ሊቀርብ ይችላል። አት. “ቅርጫቱን እዚያ ያስቀምጡታል” (ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚለውን ይመልከቱ)

በተዘጋጀለት ስፍራ
‘በተዘጋጀለት ስፍራ’ የሚሉት ቃላት አንድን መድረክ ወይም ቅርጫቱን የሚያስቀምጡበት አንድ ዓይነት የተዋቀረ ዝግጅትን ያመለክታል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 6

1 ከዚያም ዘወር ብዬ ዐይኖቼን ወደ ላይ ሳነሣ አራት ሰረገሎች ከሁለት ተራሮች መካከል ሲመጡ አየሁ፤ ሁለቱ ተራሮች የናስ ተራሮች ነበር። **2** የመጀመሪያው
ሰረገላ ቀይ ፈረሶች ነበሩት፤ ሁለተኛው ሰረገላ ጥቁር ፈረሶች ነበሩት። **3** ሦስተኛው ሰረገላ ነጭ ፈረሶች ነበሩት፤ አራተኛው ሰረገላ ዝንጉርጉር ፈረሶች ነበሩት።
4 እኔም ከእኔ ጋር እየተነጋገረ የነበረውን መልአክ፣ “ጌታዬ ሆይ፣ እነዚህ ምንድን ናቸው?” አልሁት። **5** መልአኩም እንዲህ አለኝ’ “እነዚህ በምድር ሁሉ ጌታ ፊት
ቆመው ከነበሩበት ቦታ የወጡ አራቱ የሰማይ ነፋሶች ናቸው!” አለኝ። **6** ጥቁር ፈረሶች ያሉት ወደ ሰሜን፣ ነጭ ፈረሶች ያሉት ወደ ምዕራብ፣ ዝንጉርጉር ፈረሶች
ያሉት ወደ ደቡብ ይሄዳሉ። **7** ጠንካሮች ፈረሶች ሲወጡ፣ በምድር ሁሉ ፊት ለመመላለስ አቆብቁበው ነበር፤ ስለዚህም መልአኩ፣ “ወደ ምድር ሁሉ ሂዱ!”
አላቸው። እነርሱም ወጥተው ወደ ምድር ሁሉ ሄዱ። **8** ከዚያም ወደ እኔ ጮኽ እንዲህ አለኝ፤ “ወደ ሰሜን እየሄዱ ያሉትን ተመልከት፣ መንፈሴን በሰሜን ምድር
አሳርፈውታል።” **9** የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ፤ **10** ከምርኮኞቹ ከሔልዳይና፣ ከጦቢያ፣ ከዮዳኤም ወርቅና ብር ወስደህ በዚያው ቀን ከምርኮ ወደ
መጣው ወደ ሶፎንያስ ልጅ ወደ ኢዮስያስ ቤት ሂድ። **11** ወርቁንና ብሩን ወስደህ አክሊል ሥራ በኢዮሴዴቅ ልጅ በሊቀ ካህኑ ኢያሱ ራስ ላይ አድርገው። **12**
እንዲህም በለው፤ የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል፣ እነሆ፣ ስሙ ቁጥቋጥ የተባለው ሰው ይህ ነው! እርሱም በቦታው ይንሰራፋል፤ የያህዌንም ቤተ መቅደስ
ይሠራል! **13** የያህዌን ቤተ መቅደስ የሚሠራው እርሱ ነው፤ ክብሩን ይጎናጸፋል፤ ከዚያም በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ይገዛል። በዙፋኑ ላይ ካህን ይሆናል፤ በሁለቱም
መካከል ስምምነት ይኖራል። **14** ለሔልዳይና፣ ለጦቢያና ለዮዳኤ ክብር አክሊል ቤተ መቅደሱ ውስጥ ይቀመጣል፤ ለሶፎንያስ ልጅ ቸርነት መታሰቢያ ይሆናል።
15 ያኔ በሩቅ ያሉት መጥተው የያህዌን ቤተ መቅደስ ይሠራሉ፤ ወደ እናንተ የላከኝ ያህዌ እንደ ሆነም ታውቃላችሁ፤ የአምላካችሁን የያህዌን ድምፅ ከልባችሁ
ብትሰሙ ይህ ይሆናል!”

Zechariah 6:1

ዓይኖችህን አንሣ
‘ዓይኖች’ የሚለው ቃል የሚወከለው የሚመለከተውን ሰው ነው። ትኩ. “ወደ ላይ ተመልከት” (በክፋይ የተወከለ አካል የሚለውን ይመልከቱ)

ከሁለቱ ተራሮች መካከል ... ተራሮቹም የናስ ተራሮች ነበሩ
ሁለተኛው ሐረግ በአንደኛው ሐረግ ያሉትን ተራራዎች ስለገለጻቸው ሁለቱ በአንድነት ሊጣመሩ ይችላሉ። ትኩ. “በሁለቱ የናስ ተራሮች መካከል”

የመጀመሪያው ሠረገላ ... መጋላ (ቀይ) ፈረሶች ነበሩት
ፈረሶቹ ሠረገሎቹን እንደሚስቡ ውስጠ-ታዋቂ ነው። አት. “የመጀመሪያውን ሠረገላ የሚስቡት ቀይ ፈረሶች ነበሩት” ወይም “የመጀመሪያውን ሠረገላ የሚስቡት ቀይ ፈረሶች ነበሩ” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

Zechariah 6:5

እነዚህ አራት የሰማይ ንፋሶች ናቸው
ሐረጉ የሚያመለክተው ንፋስ የሚነፍስባቸውን አራት አቅጣጫዎች ማለትም ሰሜንን፣ ምሥራቅን፣ ደቡብንና ምዕራብን ነው። ይሁን እንጂ አንዳንድ ዘመናዊ ትርጉሞች ይህንን ዕብራይስጣዊ አገላለጽ ‘አራቱ መናፍስት’ ማለት እንደሆነ አድርገው ይተረጉሙታል።

ከምድር ሁሉ ጌታ ፊት ቆመው ከነበሩት
‘...ፊት መቆም’ የሚለው ፈሊጣዊ አባባል እርሱን ለማገልገል በአንድ ሰው ሕላዌ ፊት መቆም ማለት ነው። ይህንን በዘካርያስ 4:14 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “የምድርን ሁሉ ጌታ ማገልገል” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

የባለ አምባላይ (ነጭ) ፈረሶች ወደ ምዕራብ አገር
አንዳንድ ዘመናዊ ትርጉሞች ይህንን የዕብራይስጥ ሐረግ “ነጫጮቹ ፈረሶች ከእነርሱ በኋላ ይሄዳሉ” የሚል ትርጉም ጥቁሮቹን ፈረሶች ተከትለው ወደ ሰሜን አገር እንደሚሉ አድርገው ያቀርባሉ።

የባለ አምባላይ (ነጭ) ፈረሶች ... የባለ ዝንጉርጉር ፈረሶች
እዚህ ላይ ፈረሶቹ የሚስቧቸውን ሠረገሎች ይወክላሉ። አት. “ነጫጭ ፈረሶች ያሉት ሠረገላ ... ነው፤ ዝንጉርጉር ፈረሶች ያሉት ሠረገላ ... ነው” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 6:7

ጮኽ እንዲህ አለኝ
“መልአኩ ጮክ ብሎ እንዲህ አለኝ”

እነሆ
“ወደ ጥቋቁሮቹ ተመልከተ”

መንፈሴን በሰሜን ምድር አሳርፈውታል
‘መንፈሴ’ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ያህዌን ነው፣ ስለሆነም ብዙ ትርጉሞች ‘የያህዌ መንፈስ’ በማለት ትርጉሙን ቀይረውታል። ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፡ 1) ‘መንፈሴ’ የሚለው ቃል የያህዌን ስሜት ይወክላል፣ እርሱንም ማሳረፍ ማለት ሠረገሎቹ ያህዌ በሰሜኑ ምድር ከእንግዲህ እንዳይቆጣ ያደርጉታል ማለት ነው። ትኩ. “የሰሜኑን ምድር በሚመለከት ያለኝን ቁጣ ያረጋጉታል” ወይም 2) ‘መንፈሴ’ የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ሕላዌ ይወክላል፣ ስለዚህ ሠረገሎቹ በሰሜን የሚኖሩት አይሁድ የእግዚአብሔርን በረከት እንዲያጣጥሙ ያደርጓቸዋል። ትኩ. “መንፈሴ በሰሜኑ ምድር እንዲያርፍ ያደርጉታል” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 6:9

የያህዌ ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ ... ውሰድ
ይህ ፈሊጣዊ አባባል አንድ የተለየ መልእክትን ለማሰተዋወቅ ጥቅም ላይ የዋለ ነው። አት. “ያህዌ እንዲህ የሚል መልእክት ሰጠኝ፡ ‘...ውሰድ’” ወይም “ያህዌ ይህንን መልእክት ነገረኝ፡ ‘...ውሰድ’” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ኤልዳይ፣ ጦብያ፣ ዮዳኤ፣ ... ኢዮሴዴቅ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚያው ቀን
‘ዛሬ’

Zechariah 6:12

እንዲህ ብለው ንገረው
“ለኢያሱ እንደዚህ ብለህ ንገረው”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ስሙ ቅርንጫፍ የተባለው
‘ቅርንጫፍ’ የሚለው ቃል በያህዌ ሕዝብ ላይ በንጉሥነት የሚያገለግለውን መሲሐዊ ግለሰብ ያመለክታል። ያህዌ ይህ ሰው በዛፍ ላይ እንደበቀለ ቅርንጫፍ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። ‘ቅርንጫፍ’ የሚለው ቃል ሹመትን የሚያመለክት በመሆኑ በእናንተም ቋንቋ ከዚሁ ጋር ተመጣጣኝ በሆነ ቃል መተርጎም አለበት። በዘካርያስ 3:8 ላይ ይህንን ቃል እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱም በቦታው ይንሰራፋል
‘ይንሰራፋል’ የሚለው ቃል የአንድን ተክል ዕድገት ያመለክታል፣ ስለሆነም ሰውዬው ‘ቅርንጫፍ’ ነው የሚለውን ተለዋጭ ዘይቤ ይቀጥላል። ይህ ሰውዬው የቤተ መቅደሱን እንደገና መታነጽ ለመቆጣጠር እንደሚገለጥ ወይም ወደ ሥልጣን እንደሚመጣ የሚያመለክት ይመስላል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በዙፋኑ የሚቀመጥ ካህን ይሆናል
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፡ 1) ‘ቅርንጫፉ’ ንጉሥም ካህንም እንደሚሆን፣ ወይም 2) ‘ቅርንጫፉ’ ንጉሥ ንጉሣዊ ሥልጣኑን የሚጋራ ሌላ ሰው ደግሞ ካህን እንደሚሆን ነው። አት. “በዙፋኑ ላይ ካህን ይኖራል”

በሁለቱም መካከል የሰላም ምክር እንዲኖር ያደርጋል
‘ሁለቱ’ የሚለው ቃል የንጉሥነትና የካህንነት ሚናዎችን ያመለክታል። የዚህ ሐረግ ትርጉም ቀደም ባለው ሐረግ ትርጉም ላይ የተመሠረተ ነው። ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፡ 1) ‘ቅርንጫፉ’ በታማኝነት የንጉሥነትና የካህንነት ተግባሩን ይወጣል እንጂ አንደኛውን ተግባር ለመፈጸም ብሎ ሌላኛውን አይተውም፣ ወይም 2) እንደ ንጉሥ የሚያገለግለውና እንደ ካህን የሚያገለግለው ሁለቱም በየግላቸው በታማኝነት ተግባራቸውን ያከናውናሉ፣ በአንድነትም በሰላም ሥራቸውን የሚያከናውኑ ይሆናሉ።

Zechariah 6:14

አክሊሉም ... ይሰጣል
ይህ በተናጋሪ መልኩ ሊቀርብ ይችላል። አት. “አክሊሉን ትሰጣለህ” (ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚሉትን ይመልከቱ)

ኤልዳይ፣ ጦብያ፣ ዮዳኤ፣ ... ሔን
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ የሚለውን ይመልከቱ)

ለሶፎንያስ ልጅ ለሔን እንደ መታሰቢያ
አንዳንድ ዘመናዊ ትርጉሞች ይህንን ሐረግ፣ “ለሶፎንያስ ልጅ ለጋስነት እንደ መታሰቢያ” ወይም “ለጋስ ለሆነው ለሶፎንያስ ልጅ እንደ መታሰቢያ” ብለው ይተረጉሙታል። በተጨማሪም አንዳንድ ዘመናዊ ትርጉሞች ‘ሔን’ የሚለውን ስም ‘ኢዮስያስ’ እንደሚል አድርገው ይተረጉሙታል።

በሩቅ ያሉት
ይህ በባቢሎን የቀሩትን ነው የሚያመለክተው። (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

እናንተም ታውቃላችሁ
በብዙ ቁጥር ‘እናንተም’ የሚለው የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። (አንተ እና እናንተ የሚሉት አቀራረብ የሚለውን ይመልከቱ)

በእውነት የአምላካችሁን የያህዌን ድምፅ ስሙ
እዚህ ላይ ‘መስማት’ ማለት መታዘዝ ማለት ነው፣ ‘ድምፅ’ የሚለውም የሚወክለው ያህዌ የሚናገረውን ቃል ነው። አት. “በእውነት አምላካችሁ ያህዌ የሚናገረውን ታዘዙ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 7

1 ንጉሥ ዳርዮስ በነገሠ በአራተኛው ዓመት ካሴሉ በተባለው በዘጠነኛው ወር የያህዌ ቃል ወደ ዘካርያስ መጣ። **2** የቤቴል ሰዎች እግዚአብሔርን ለመለመን
ሳራሳርንና ሬጌሜሌክን አብረዋቸው ከነበሩ ሰዎች ላኩ። **3** በሰራዊት ጌታ በያህዌ ቤት የነበሩትን ካህናትና ነቢያት፣ “ብዙ ዓመት እንዳደርግሁት በአምስተኛው
ወር ማዘንና መጾም ይገባኛልን?” አሏቸው። **4** ስለዚህ የሰራዊት ጌታ የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ፤ **5** “በምድሩ ላሉት ሕዝብ ሁሉ፣ ለካህናቱም
እንዲህ በላቸው፤ በእነዚህ ሰባ ዓመታት አምስተኛና ሰባተኛ ወሮች የጾማችሁትና ያዘናችሁት በእውነት ለእኔ ነውን? **6** የምትበሉትና የምትጠጡትስ ለራሳችሁ
አይደለምን? **7** በኢየሩሳሌምና በዙሪያዋ ባሉ ከተሞች በሰላምና በብልጽግና ትኖር በነበረ ጊዜ የኔጌቭና የምዕራብ ተራሮች ግርጌ የሰው መኖሪያ በነበሩ ዘመን
በቀደሙት ነቢያት የተነገረው የያህዌ ቃል ይኸው አልነበረምን?” **8** የያህዌ ቃል እንደ ገና ወደ ዘካርያስ እንዲህ ሲል መጣ፣ **9** “የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ
ይላል፤ ‘በእውነተኛ ፍትሕና የኪዳን ታማኝነት፣ በምሕረትም ፍረዱ። እያንዳንዱ ሰው ለወንድሙ እንዲህ ያድርግ። **10** መበለቶችንና ድኻ አደጎችን፣ መጻተኞችንና
ድኻውን አታስጨንቋቸው፤ በልባችሁም አንዳችሁ በሌላው ክፉ አታስቡ! **11** እነርሱ ግን መስማት አልፈለጉም፤ በእልኸኝነት ትከሻቸውን አሳበጡ። እንዳይሰሙ
ጆሮአቸውን ደፈኑ። **12** ሕጉንና የሰራዊት ጌታ የያህዌን ቃል ላለመስማት ልባቸውን እንደ ዐለት አጠነከሩ። በቀደሙት ዘመኖች በመንፈሱ፣ በነቢያትም አንደበት
እነዚህን መልእክቶች ወደ ሕዝቡ ላከ። ሕዝቡ ግን መስማት አልፈለጉም፤ ስለዚህ ያህዌ በእነርሱ ላይ በጣም ተቆጣ። **13** እርሱ ሲጠራቸው አልሰሙም።
በተመሳሳይ መንገድ፣ ይላል የሰራዊት ጌታ ያህዌ “ወደ እኔ ይጣራሉ፤ እኔ ግን አልሰማም።” **14** አይተዋቸው ወደማያውቁ ሕዝቦች ሁሉ በዐውሎ ነፋስ
እበትናቸዋለሁ፤ ምድሪቱም በኋላቸው ባድማ ትሆናለች። ሕዝቡ መልካሚቱ ምድራቸውን ባድማ አድርገዋልና ማንም በምድሪቱ አያልፍም ወደዚያም
አይመለስም።”

Zechariah 7:1

በአራተኛው ቀን
‘አራተኛው ቀን ሲሆን’ (መደበኛ ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ካሴሉ
‘ካሴሉ’ በዕብራውያን ዘመን አቆጣጠር ዘጠነኛው ወር ነው። የካሴሉ ወር በአውሮፓውያን (በጊሪጎርያን) ዘመን አቆጣጠር ወደ ኅዳር ወር መጨረሻ
አካባቢ ነው። (የዕብራውያን ወሮች እና ስሞችን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ የሚሉትን ይመልከቱ)

የያህዌ ቃል ወደ ዘካርያስ መጣ
ይህ ፈሊጣዊ አባባል አንድ የተለየ መልእክትን ለማሰተዋወቅ ጥቅም ላይ የዋለ ነው። አት. “ያህዌ ለዘካርያስ መልእክት ሰጠው’” ወይም “ያህዌ
ይህንን መልእክት ለዘካርያስ ነገረው” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ሳራሳርና ሬጌሜሌክ
እዚህ ላይ ‘መለመን’ ማለት መማፀን ወይም አጣዳፊ ጥያቄ ማቅረብ ማለት ነው።

በያህዌ ፊት
እዚህ ላይ ‘ፊት’ የሚለው ለያህዌ ሕላዌ ስመ-ምስል ስያሜ ነው። አት. “ያህዌ በተገኘበት” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

በአምስተኛው ወር ማዘን ... ይገባኛል
“5ተኛው ወር በሚሆንበት ጊዜ ማዘን ይገባኛል?” በግምታዊው እውቀት መሠረት በኢየሩሳሌም የነበረው ቤተ መቅደሱ በባቢሎናውያን የፈረሰው በዚህ
ወር ስለነበረ የአይሁድ ሕዝቦች በዕብራውያን ዘመን አቆጣጠር በአምስተኛው ወር በከፊል ይጾሙ ነበር። አምስተኛው ወር በአውሮፓውያን (ጊሪጎሪያን)
አቆጣጠር በሐምሌ ወር መጨረሻና በነሐሴ ወር መጀመሪያ ላይ ይውላል። (መደበኛ ቁጥሮች፣ ግምታዊ እውቀት፣ ውስጠ-ታዋቂ መረጃ እና የዕብራውያን
ወሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

በጾም አማካይነት
‘በመጾም’

Zechariah 7:4

የሠራዊት ጌታ የያህዌ ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ ... ተናገር
ይህ ፈሊጣዊ አባባል አንድ የተለየ መልእክትን ለማሰተዋወቅ ጥቅም ላይ የዋለ ነው። አት. “የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ የሚል መልእክት ሰጠኝ፡ ‘...
ተናገር’” ወይም “የሠራዊት ጌታ ያህዌ ይህንን መልእክት ነገረኝ፡ ‘...ተናገር’” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

በአምስተኛው ወርና በሰባተኛው ወር
‘5ተኛውና 7ተኛው ወሮች ሲሆኑ’ (መደበኛ ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በአምስተኛው
‘ወር’ የሚለው ቃል በመተርጎም ወቅት ሊጨመር ይችላል። አት. “በአምስተኛው ወር” (ግድፈት የሚለውን ይመልከቱ)

በሰባተኛው ወር
በግምታዊው እውቀት መሠረት የባቢሎን ንጉሥ በይሁዳ ላይ ገዢ አድርጎ ከሾመው ከጎዶልያስ መገደል በኋላ በኢየሩሳሌም ቀርተው የነበሩት አይሁድ ወደ ግብፅ የሸሹት በዚህ ወር ስለነበረ አይሁድ ያለቅሱ ነበር። ሰባተኛው ወር በአውሮፓውያን (ጊሪጎሪያን) አቆጣጠር በመስከረም ወር መጨረሻና በጥቅምት ወር መጀመሪያ ላይ ይውላል። (ግምታዊ እውቀት፣ ውስጠ-ታዋቂ መረጃ እና የዕብራውያን ወሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

ለእነዚህ ሰባ ዓመታት
በግምታዊው እውቀት መሠረት የእስራኤል ሕዝቦች በባቢሎን ለሰባ ዓመታት ባሪያዎች ሆነው ነበር። (ግምታዊ እውቀት፣ ውስጠ-ታዋቂ መረጃ እና ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

የጾማችሁት በእርግጥ ለእኔ ነበርን?
ጥያቄው የተጠየቀው ሕዝቡ የመጾማቸው እውነተኛ ምክንያት ምን እንደነበረ እንዲያስቡ ለማድረግ ነው። በገለጻ መልክ ሊተረጎም ይችላል፡ -አት. “በእርግጥ ትጾሙ የነበረው ለእኔ አልነበረም” (መልስ የማያጠብቅ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ትበሉና ትጠጡ የነበረው
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፡ 1) ሃይማኖታዊ በዓላትን ሲያከብሩ ፈንጠዝያ ያደርጉና ይጠጡ የነበሩት፣ ወይም 2) በማይጾሙበት ጊዜ ሁሉ ሲበሉና ሲጠጡ የነበሩት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ትበሉና ትጠጡ የነበረው ለራሳችሁ አልነበረምን?
ጥያቄው የተጠየቀው ሕዝቡ በሚበሉበትና በሚጠጡበት ጊዜ ያህዌ ያከብሩ እንደነበረ ወይም እንዳልነበረ እንዲያስቡ ለማድረግ ነው። አት. “ትበሉና ትጠጡ የነበራችሁት ለራሳችሁ ነበር” (መልስ የማያጠብቅ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የተናገረው ቃል ይህ አልነበረምን ... ለምዕራብ
ያህዌ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት ሕዝቡን ለመዝለፍ ነው። ይህ ጥያቄ በገለጻ መልክ ሊተረጎም ይችላል። አት. “እነዚህ ተመሳሳይ ቃላት ናቸው ... ለምዕራብ” (መልስ የማያጠብቅ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በቀደሙት ነቢያት አንደበት
እዚህ ላይ ‘አንደበት’ የሚለው በአንደበት ለተነገረው ቃል ስም-ምስል ስያሜ ነው። አት. “በቀደሙት ነቢያት ቃል” ወይም “በቀደሙት ነቢያት በኩል” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

አሁንም በኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ናችሁ
“አሁንም በኢየሩሳሌም እየኖራችሁ ነው”

ኮረብቶች ግርጌ
ከተራራው ወይም ከሰንሰለታማ ተራሮች በስተግርጌ ያሉ ኮረብቶች

Zechariah 7:8

የያህዌ ቃል ወደ ዘካርያስ መጣ ... እንዲህም አለው ‘ያህዌ ...’
ይህ ፈሊጣዊ አባባል አንድ የተለየ መልእክትን ለማሰተዋወቅ ጥቅም ላይ የዋለ ነው። አት. “ያህዌ ለዘካርያስ መልእክት ሰጠው፣ እንዲህም አለው ‘ያህዌ’” ወይም “ያህዌ ይህንን መልእክት ለዘካርያስ ነገረው፡ - ‘ያህዌ’” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

በእውነተኛ ፍትሕ ዳኙ፣ ታማኝነትንና ምሕረትን አድርጉ
የነገር ስም የሆኑት ‘ፍትሕ’፣ ‘ታማኝነት’ እና ‘ምሕረት’ በቅጽል መልክ ሊገለጹ ይችላሉ። አት. “በምትዳኙበት ጊዜ፣ ፍትሐዊ ሁኑ፣ ለኪዳኑ ታማኝ፣ መሐሪም ሁኑ” (የነገር ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እያንዳንዱ ሰው ይህንን ያድርግ
‘ይህንን’ የሚለው ቃል እያንዳንዱ ሰው እንዴት መዳኘት እንዳለበት የሚያመለክት ነው።

መበለት
ባሏ የሞተባት ሴት

ድኀ-አደግ (ወላጁን-ያጣ)
ወላጆቹ የሞቱበት ልጅ

መጻተኛ
ከራሱ አገር ወደ ሌላ አገር የሄደ ሰው

ከእናንተ ማንኛችሁም በሌላው ላይ በልባችሁ ክፉ ነገር አታስቡ
እዚህ ላይ ‘ልብ’ የሚለው የአንድን ሰው ሃሳብ ይወክላል። አት. “ክፋትን ለማድረግ ዕቅድ ማቀድ የለባችሁም” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 7:11

በእልኸኝነት ጀርባቸውን አዞሩ
ይህ ባለቤቱ በጫንቃው (ትከሻው) ላይ ቀንበር እንዳይጭንበት የሚከለክል በሬ ምስል ነው። አት. “እልኸኛ መሆን” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንዳይሰሙ ጆሮአቸውን ደፈኑ
ይህ ከያህዌ የሆነውን መልእክት እንዳይሰሙ የሆነ ነገር ጆሮአቸው ውስጥ የሚያደርጉ ሰዎች ምስል ነው። ይህ ተለዋጭ ዘይቤ ለመስማትና ለመታዘዝ ፈቃደኛ ያልሆኑ ሰዎችን ይወክላል። አት. “ለመስማት እምቢ አሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሠራዊት ጌታ የያህዌን ሕግ ወይም ቃሉን እንዳይሰሙ ልባቸውን እንደ ድንጋ አጠነከሩ
ያህዌን ለመስማትና ለመታዘዝ ፈቃደኛ ያልሆኑት ሕዝቦች ከማይበገር ድንጋይ ጋር ተነፃፅረዋል። እዚህ ላይ ልብ የሰውን ፈቃድ ወክሏል። አት. “የሠራዊት ጌታ የያህዌን ሕግ ወይም ቃሉን እንዳይሰሙ በእልኸኛነት እምቢ አሉ” (ምስስሎሽ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀደም ባሉት ጊዜያት
“ባለፉት ዘመናት”

በነቢያቱ አንደበት
እዚህ ላይ ‘የነቢያቱ አንደበት’ የሚለው ነቢያቱ በአንደበታቸው ለተነገሩት ቃል ስም-ምስል ስያሜ ነው። ትኩ. “በነቢያቱ ቃል አማካይነት” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 7:13

በዐውሎ ነፋስ እበትናቸዋለሁ
ያህዌ በመንገድ ላይ ያገኘውን ሁሉ እንደሚበታትን ዓውሎ ንፋስ ሕዝቡን እንዴት እንደሚበታትናቸው እየተናገረ ነው። አት. “ዓውሎ ንፋስ ነገሮችን (ዕቃዎችን) እንደሚበታትነ እበታትናቸዋለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዓውሎ ንፋስ
በሚጓዝበት ጊዜ እጅግ ፈጣን ሽክርክሪት የሚሠራና ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ጠንካራ ንፋስ

መልካሚቱን ምድር
‘ደስ የምትል ምድር’ ወይም ‘ፍሬያማ ምድር’

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 8

1 የሰራዊት ጌታ የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ፤ 2 የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል፤ “ስለ ጽዮን እጅግ ቀንቻለሁ፤ ስለ እርሷ በታላቅ ቁጣ ነድጃለሁ!
3 የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል ወደ ጽዮን እመለሳለሁ፤ በኢየሩሳሌምም መካከል እኖራለሁ፤ ኢየሩሳሌም የእውነት ከተማ ትባላለች፤ የሰራዊት ጌታ የያህዌ
ተራራም ቅዱሱ ተራራ ይባላል! 4 የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል ሽማግሌዎችና አሮጊቶች እንደ ገና በኢየሩሳሌም አደባባዮች ይሆናሉ፤ እያንዳንዱ ሰው
በጣም ስለሚያረጅ በእጁ ምርኩዝ ይይዛል። 5 የከተማዋ አደባባዮች በሚቦርቁ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ይሞላሉ። 6 የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል፣
በዚያን ጊዜ ይህ ከተቀሩት ሕዝብ የማይቻል መስሎ ቢታይ እንኳ፣ በእኔ ዐይን ፊት የማይቻል ይመስላልን? ይህ የያህዌ ዐዋጅ ነው። 7 የሰራዊት ጌታ ያህዌ
እንዲህ ይላል። እነሆ እኔ ሕዝቤን ከፀሐይ መውጫና ከፀሐይ መጥለቂያ ምድር አድናለሁ! 8 እንደ ገና አመጣቸዋለሁ፤ በኢየሩሳሌም መካከልም ይኖራሉ፤ እንደ
ገና ሕዝቤ ይሆናሉ እኔም በእውነትና በጽድቅ አምላካቸው እሆናለሁ! 9 የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል፤ እናንተ ከነቢያት አፍ የወጡ ቃሎችን አሁን
እየሰማችሁ ያላችሁ፣ የእኔ ቤት፣ የሰራውቲ ጌታ የእኔ የያህዌ ቤት መሠረት በተጣለ ጊዜ ቤተ መቅደሱ መሠራት እንዲችል እጆቻችሁን አበርቱ። 10 ከእነዚያ
ቀኖች በፊት ማንም እህል አልሰበሰበም ነበር፤ ለሰውም ሆነ ለእንስሳት የሚጠቅም ነገር አልነበረም፤ ከጠላት የተነሣ ለሚወጣም ሆነ ለሚገባ ሰው ሰላም
አልነበረም ምክንያቱም እያንዳንዱ ሰው በባልንጀራው ላይ እንዲነሣ አድርጌ ስለ ነበር ነው። 11 አሁን ግን እንደ ቀድሞው ዘመን አይሆንም፤ ከተረፈው ሕዝብ
ጋር እሆናለሁ፤ ይህ የሰራዊት ጌታ የያህዌ ዐዋጅ ነው። 12 የሰላም ዘር ይዘራል፤ ያንሰራራው ወይን ፍሬውን ይሰጣል፤ ምድሪቱም አዝመራዋን ታበረክታለች፤
ሰማያት ጠል ይሰጣሉ፤ የተፈረው ሕዝብ ይህን ሁሉ እንዲወርስ አድርጋለሁ። 13 የይሁዳና የእስራኤል ቤት ሆይ፣ ለሌሎች ሕዝቦች የመርገም ምሳሌ ሆናችሁ
ነበር። ስለዚህ አድናችኋለሁ፤ በረከትም ትሆናላችሁ። አትፍሩ፤ እጆችሁም ይበርታ! 14 የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል፤ አባቶቻችሁ ቁጣዬን ባነሳሡ ጊዜ
ያላንቻች ርኅራኄ ጥፋት ላመጣባቸው እንደ ወሰንሁ፣ ይላል የሰራዊት ጌታ ያህዌ 15 አሁን ደግሞ ለኢየሩሳሌምና ለይሁዳ እንደ ገና መልካም ለማድረግ
ወስኛለሁ፤ አትፍሩ! 16 እናንተ ማድረግ ያለባችሁ እነዚህን ነው፤ እርስ በርሳችሁ እውነትን ተነጋገሩ፤ በአደባባዮቻችሁም እውነትን፣ ፍትሕንና ሰላምን አስፍኑ። 17
በባልንጀራችሁ ላይ በልባችሁ ክፋትን አታውጠንጥኑ፤ የሐሰት መሓላን አትውደዱ፣ ምክንያቱም እኔ እነዚህን ሁሉ እጠላለሁ! ይህ የያህዌ ዐዋጅ ነው።” 18
እንደ ገናም የሰራዊት ጌታ የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ፤ 19 አሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል፤ የአራተኛው ወር፣ የአምስተኛው ወር፣ የሰባተኛውና
የአሥረኛው ወር ጾሞች ለይሁዳ ቤት የደስታ፣ የተድላና የሐሤት በዓሎች ይሆናሉ! ስለዚህ እውነትንና ሰላምን ውደዱ! 20 የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ያላል፤
በተለያዩ ብዙ ከተሞች ያሉት እንኳ ሳይቀሩ እንደ ገና ሰዎች ይመጣሉ። 21 የአንዱ ከተማ ነዋሪዎች ወደ ሌላው ከተማ እየሄዱ፣ “ያህዌን ለመለመንና የሰራዊት
ጌታ ያህዌን ለመፈለግ ኑ በፍጥነት እንሂድ፤ እኛ ራሳችንም ደግሞ እንሄዳለን” ይላሉ። 22 ብዙ ሕዝብና ኀያላይ መንግሥታት የሰራዊት ጌታ ያህዌን ለመፈለግ
ወደ ኢየሩሳሌም ይመጣሉ፤ የያህዌንም ሞገስ ይለምናሉ! 23 የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል በእነዚያ ቀኖች ከየወገኑና ከየቋንቋው አሥር ሰዎች የእናንተን
ልብስ ዘርፍ አጥብቀው በመያዝ፣ “እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር እንዳለ ሰምተናልና፤ ከእናንተ ጋር እንሂድ! ይላሉ።

Zechariah 8:1

የያህዌ ቃል ወደ እኔ መጣ ... እንዲህም አለኝ ‘ያህዌ ...’
ይህ ፈሊጣዊ አባባል አንድ የተለየ መልእክትን ለማሰተዋወቅ ጥቅም ላይ የዋለ ነው። በዘካርያስ 7:4 ላይ ይህንን እንዴት እንደተረጎማችሁት ዘር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “ያህዌ መልእክት ሰጠኝ፣ እንዲህም አለኝ ‘ያህዌ’ ” ወይም “ያህዌ ይህንን መልእክት ነገረኝ፣ እንዲህም አለኝ : -‘ያህዌ’” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ ጽዮን እጅግ ቀንቻለሁ
“ጽዮንን ለመከላከል ጠንካራ ፍላጎት አለኝ”

ለጽዮን
እዚህ ላይ ‘ጽዮን’ የጽዮንን ሕዝብ ይወክላል። አት. “ለጽዮን ሕዝብ” ወይም “ለኢየሩሳሌም ሕዝብ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

በታላቅ ቁጣ
በግንዛቤ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ይህ ቁጣ በጽዮን ጠላቶች ላይ ነው። አት. “በጠላቶቿ ላይ በታላቅ ቁጣ” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

የሠራዊት ጌታ የያህዌ ተራራ
በግንዛቤ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ይህ የኢየሩሳሌም ከተማ የተገነባችበት ስፍራ ያለበትን የጽዮን ተራራን ነው። (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

Zechariah 8:4

በኢየሩሳሌም መንገዶች ላይ
“በኢየሩሳሌም ይኖራሉ”

በጣም ስለሚያረጁ ... በእጆቻቸው ይይዛሉ
ሰዎች በጣም እስከሚያርጁ ድረስ በሕይወት መኖራቸው፣ ከተማይቱ ለረጅም ጊዜ በሰላምና በብልጽግና እንደምትቆይ ያመለክታል። (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

የከተማይቱ መንገዶች ... ይሞላሉ
የከተማይቱ አደባባይ ስፍራዎች መደበኛ ሥራቸውን በሚያከናውኑ ሰዎች ይሞላሉ።

Zechariah 8:6

... ዓይኖች ፊት የማይቻል መስሎ የሚታይ ነገር ቢኖር
ዓይኖች መመልከትን ያመለክታሉ፣ መመልከት ደግሞ ሃሳብንና ብያኔን ይወክላል። አት. “አንድ ነገር ለ... የማይቻል መስሎ የሚታይ ቢሆን እንኳ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የዚህ ሕዝብ ትሩፋን
“በሕይወት ያሉት የይሁዳ ሕዝቦች”

በዓይኖቼ ፊት የማይቻል መስሎ ሊታይ ይገባል
ሕዝቡ በተስፋ ቃሎቹ እንዲያምኑ ለማግባባት ጥያቄው አሉታዊ መልስ ይጠብቃል። በገለጻ መልክ ሊተረጎም ይችላል። ትኩ. “በእርግጥ ለእኔ ይቻለኛል!” (መልስ የማያጠብቅ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በዓይኖቼ
ዓይኖች መመልከትን ያመለክታሉ፣ መመልከት ደግሞ ሃሳብንና ብያኔን ይወክላል። አት. “ለእኔ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ያህዌ ... እንዲህ ይላል
እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ ያህዌ ስለ ራሱ ስሙን በመጥቀስ ይናገራል። በዘካርያስ 1:4 ላይ ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንደዚህ ብሎ ተናግሯል” ወይም “እኔ የሠራዊት ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህንን ነው” (‘መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ሰው’ የሚለውን ይመልከቱ)

ሕዝቤን ላድናቸው (ላወጣቸው) ነው
በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት ሕዝቡ ስደት ላይ ናቸው። አት. “ወደ ምርኮ የሄዱትን ሕዝቤን የይሁዳን ሰዎች ላድናቸው (ላወጣቸው) ነው” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ፀሐይ ከምትወጣበት ምድርና ፀሐይ ከምትጠልቅበት ምድር
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፡ - 1) ሕዝቡ ተሰደው የሄዱባቸውን የተለዩ አገሮች ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለ ቅኔያዊ የአገላለጽ መንገድ ነው። አት. “ከምሥራቅ በኩል ካለው ምድርና በምዕራብ በኩል ካለው ምድር” ወይም 2) ይህ ከሁሉም አቅጣጫ የሚል ትርጉም ያለው ... አባባል ነው። ትኩ. “በማንኛውም አቅጣጫዎች ካሉት ከሁሉም አገሮች” (... የሚለውን ይመልከቱ)

በእውነትና በጽድቅ አምላካቸው እሆናለሁ
የነገር ስሞች የሆኑትን ‘እውነት’ እና ‘ጽድቅ’ የሚሉትን በማስወገድ ይህ እንደገና ሊጻፍ ይችላል። አት. “አምላካቸው እሆናለሁ። ለእነርሱ ታማኝ እሆንላቸዋለሁ፣ ትክክለኛ በሆነ መንገድም አደርግላቸዋለሁ” (የነገር ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 8:9

የቤቱ መሠረት ሲጣል
ይህ በተናጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት. “የቤቴን መሠረት ባነጻችሁበት ጊዜ” (ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚለውን ይመልከቱ)

እጆቻችሁን አበርቱ
ይህ ለሥራው ድፍረት አገኙ የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ አባባል ነው። አት. “ጠንክሩ ደግሞም በርቱ” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ከእነዚህ ቀናት በፊት
እዚህ ላይ ‘እነዚያ ቀናት’ የሚለው የሚያመለክተው የይሁዳ ሕዝብ ቤተ መቅደሱን መገንባት የጀመሩበትን ጊዜ ነው።

ሰብልም አልተሰበሰበም ነበር
“የሚመረት ምንም ሰብል አልነበረም”

ሰውም ሆነ እንሰሳ የሚያተርፈው ነገር አልነበረም
ሰዎቹም ሆኑ እንሰሶቹ መሬታቸውን ማረሳቸው ጥቅም አልነበረውም፣ ምክንያቱም ምንም ምግብ አያገኙበትም ነበር።

ይመጣም ሆነ ይሄድ ለነበረው ለማንኛውም ሰው
ይህ ... ሰዎች ይሄዱባቸው የነበሩትን በማንኛውም ስፍራ የነበሩትን ሁሉንም የሕይወት ክንዋኔዎች የሚመለከት ነው። (... የሚለውን ይመልከቱ)

ማንኛውም ሰው በባልንጀራው ላይ እንዲነሳ አድርጌያለሁ
“ማንኛውም ሰው በሌላው ሰው ላይ እንዲነሳበት አድርጌያለሁ”

Zechariah 8:11

አሁን ግን እንደ ቀድሞው ዘመን አይሆንም፣ ከሕዝቤ ትሩፋን ጋር እሆናለሁ
“አሁን በእነዚህ የሕዝቡ ትሩፋን ላይ ቀድሞ እንዳደረግሁባቸው አላደርግባቸውም”

ቀደም ባሉት ዓመታት
‘ባለፈው ጊዜ’ ከግንዛቤ የተገኘው ይህ መረጃ የሚያመለክተው ሕዝቡ ቤተ መቅደሱን እንደገና መገንባት የጀመሩበትን ጊዜ ነው። (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

የዚህ ሕዝብ ትሩፋን
ከግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት ይህ ከምርኮ የተመለሱት የሕዝቡ ትሩፋን ናቸው። አት. “ከምርኮ የተመለሰው ሕዝብ” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

የሰላም ዘር ይዘራል
ይህ በተናጋሪ መልክ ሊገልጽ ይችላል። አት. “ሕዝቡ በሰላም ዘር ይዘራሉ” (ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ ... እንዲህ ይላል
እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ ያህዌ ስለ ራሱ ስሙን በመጥቀስ ይናገራል። በዘካርያስ 1:3 ላይ ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንደዚህ ብሎ ተናግሯል” ወይም “እኔ የሠራዊት ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህንን ነው” (‘መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ሰው’ የሚለውን ይመልከቱ)

ምድር ምርቷን ትሰጣለች፣ ሰማይም ጠሉን ይሰጣል
ምድርና ሰማያት የሚፈለገውን እንደሚሰጡ ሰዎች ተደርገው ተነግረዋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህን ነገሮች አወርሳለሁ
“እነዚህ ነገሮች ሁሉ እንዲኖሯቸው”

Zechariah 8:13

እናንተ ለሌሎች አገሮች የእርግማን ምሳሌ ሆናችሁ ነበር
በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት ያህዌ ቤተ መቅደሱ እንዲፈርስና ሕዝቡ እንዲማረክ የፈቀደበት መንገድ ሌሎች አገሮች በያህዌ መረገም ማለት ምን እንደሆነ እንደ ምሳሌ እንዲጠቀሙበት አድርጓል። አት. “በቀጣኋችሁ ጊዜ ሌሎች አገሮች እኔ አንድን ሕዝብ በረገምኩ ጊዜ ምን እንደሚሆን ትምህርት ተማሩ” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

የይሁዳ ቤትና የእስራኤል ቤት
‘ቤት’ የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩት ሰዎች ስመ-ምስል ስያሜ ነው። በዚህ ዓውድ በይሁዳና በእስራኤል መንግሥታት የሚኖሩትን ሕዝቦች ያመለክታል። አት. “የይሁዳና የእስራኤል ሕዝብ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

በረከት ትሆናላችሁ
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፡ -1) በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት የይሁዳና የእስራኤል ሕዝቦች በአካባቢያቸው ላሉት ሕዝቦች በረከት እንደሚሆኑ ነው። አት. “በአካባቢያችሁ ላሉት አገሮች በረከት ትሆናላችሁ” ወይም 2) በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት በአካባቢያቸው ያሉት ሕዝቦች በያህዌ መባረክ ምን ማለት እንደሆነ እንደሚመለከቱ ነው። ትኩ. በምባርካችሁ ጊዜ ሌሎች አገሮች አንድን ሕዝብ ስባርክ ምን እንደሚሆን ይማራሉ። 3) ያህዌ የይሁዳንና የእስራኤልን ሕዝብ ይባርካል። አት. “ብዙ መልካም ነገሮችን እሰጣችኋለሁ” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

እጆቻችሁን አበርቱ
ይህ ለሥራው ብርቱ መሆንን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አባባል ነው። አት. “ጠንክሩ ደግሞም በርቱ” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ጉዳት ላደርስባችሁ
‘ልቀጣችሁ’

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ቁጣዬን ባነሳሱት ጊዜ
‘ባስቆጡኝ ጊዜ’

ሐዘኔታ አላሳየሁም
‘ቅጣቴን ለማሳነስ አልወሰንኩም’

ኢየሩሳሌም
ይህ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ ስመ-ምስል ስያሜ ነው። አት. “የኢየሩሳሌም ሕዝብ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳ ቤትና የእስራኤል ቤት
‘ቤት’ የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩት ሰዎች ስመ-ምስል ስያሜ ነው። በዚህ ዓውድ በይሁዳና በእስራኤል መንግሥታት የሚኖሩትን ሕዝቦች ያመለክታል። አት. “የይሁዳና የእስራኤል ሕዝብ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 8:16

ልታደርጓቸው የሚገባችሁ
‘ልታደርጓቸው’ በሚለው በውስጠ-ታዋቂ ‘እናንተ’ የሚለው የሚያመለክተው የይሁዳን ሕዝብ ነው።

እያንዳንዱ ሰው ከጎረቤቱ ጋር እውነትን ይነጋገር
የነገር ስም የሆነው ‘እውነትን’ የሚለው እውነት የሚለውን ቅጽል በመጠቀም ሊተረጎም ይችላል። አት. “እያንዳንዱ ሰው ለጎረቤቱ እውነት የሆነውን መናገር አለበት።” (የነገር ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ለጎረቤቱ
እዚህ ላይ ጎረቤት የተባለው በአቅራቢያ የሚኖር ሰው ብቻ ሳይሆን ማንኛውንም ሰው ነው።

በአደባባያችሁም በእውነት፣ በፍትሐዊነትና ሰላምን በማስፈን ፍረዱ
የነገር ስም የሆኑትን ‘እውነት’፣ ‘ፍትሐዊነት’ እና ‘ሰላም’ በማስወገድ በድጋሚ ሊገለጽ ይችላል፡ - አት. “በአደባባዮቻችሁ ውሳኔ በምታደርጉበት ጊዜ እውነትና ትክክል በሆነ መንገድ እንዲሁም ሰዎች እርስ በርሳቸው በሰላም ሊኖሩ በሚችሉበት መንገድ ፍረዱ” (የነገር ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በአደባባዮቻችሁ
በግምታዊው እውቀት መሠረት ይህ የሚያመለክተው ፍርድ የሚሰጥባቸውን ስፍራዎች ነው። አት. “ፍርድ በምትሰጡባቸው ቦታዎች”

በሐሰት መማልን አትውደዱ
በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት ይህ የሚያመለክተው በፍርድ ሸንጎ የሚከናወነውን መሐላ ነው። አትአ. “በፍርድ ሸንጎ ጉዳዮች ላይ ሰዎች ሲዋሹ አትቀበሏቸው” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ያህዌ ... እንዲህ ይላል
እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ ያህዌ ስለ ራሱ ስሙን በመጥቀስ ይናገራል። በዘካርያስ 1:3 ላይ ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንደዚህ ብሎ ተናግሯል” ወይም “እኔ የሠራዊት ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህንን ነው” (‘መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ሰው’ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 8:18

የያህዌ ቃል ወደ እኔ መጣ ... እንዲህም አለኝ ‘ያህዌ ...’
ይህ ፈሊጣዊ አባባል አንድ የተለየ መልእክትን ለማሰተዋወቅ ጥቅም ላይ የዋለ ነው። በዘካርያስ 7:4 ላይ ይህንን እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “ያህዌ መልእክት ሰጠኝ፣ እንዲህም አለኝ ‘ያህዌ’” ወይም “ያህዌ ይህንን መልእክት ነገረኝ፣ እንዲህም አለኝ ፡ -‘ያህዌ’” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እኔ መጣ
እዚህ ላይ ‘እኔ’ የሚለው የሚያመለክተው ዘካርያስን ነው።

የአራተኛው፣ የአምስተኛው፣ የሰባተኛውና የአሥረኛው ወር ጾሞች
የ4ኛው፣የ5ኛው፣የ7ኛውና የ10ኛው ወር ጾሞች (መደበኛ ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

የአራተኛው ወር ጾሞች
በግምታዊ እውቀት መሠረት ባቢሎናውያን የኢየሩሳሌምን ጥሰው የገቡት በከፊል በአራተኛው ወር በዚህ ወቅት ስለነበረ አይሁዳውያን በዕብራውያን ዘመን አቆጣጠር በከፊል በአራተኛው ወር ያለቅሱ ነበር። አራተኛው ወር በአውሮፓውይን (ጊሪጎርያን) ዘመን አቆጣጠር በሰኔ ወር መጨረሻና በሐምሌ ወር መጀመሪያ ላይ ይውላል። (ግምታዊ እውቀት፣ ውስጠ-ታዋቂ መረጃ እና የዕብራውያን ወሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

አምስተኛው ወር
በግምታዊ እውቀት መሠረት ባቢሎናውያን ቤተ መቅደሱን ያፈረሱት በዚህ ወቅት ስለነበረ አይሁዳውያን በዕብራውያን ዘመን አቆጣጠር በከፊል በአምስተኛው ወር ይጾሙ ነበር። አምስተኛው ወር በአውሮፓውይን (ጊሪጎርያን) ዘመን አቆጣጠር በሐምሌ ወር መጨረሻና በነሐሴ ወር መጀመሪያ ላይ ይውላል። በዘካርያስ 7:3 ይህንን እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። (ግምታዊ እውቀት፣ ውስጠ-ታዋቂ መረጃ እና የዕብራውያን ወሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

ሰባተኛው ወር
በግምታዊው እውቀት መሠረት የባቢሎን ንጉሥ በይሁዳ ላይ ገዢ አድርጎ ከሾመው ከጎዶልያስ መገደል በኋላ በኢየሩሳሌም ቀርተው የነበሩት አይሁድ ወደ ግብፅ የሸሹት በዚህ ወር ስለነበረ አይሁድ ያለቅሱ ነበር። ሰባተኛው ወር በአውሮፓውያን (ጊሪጎሪያን) አቆጣጠር በመስከረም ወር መጨረሻና በጥቅምት ወር መጀመሪያ ላይ ይውላል። በዘካርያስ 7:5 ላይ ይህንን እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። (ግምታዊ እውቀት፣ ውስጠ-ታዋቂ መረጃ እና የዕብራውያን ወሮች የሚሉትን ይመልከቱ

አሥረኛው ወር
በግምታዊው እውቀት መሠረት ባቢሎናውያን ኢየሩሳሌምን መክበብ የጀመሩት በዚህ ወር ስለነበረ አይሁድ ያለቅሱ ነበር። አሥረኛው ወር በአውሮፓውያን (ጊሪጎሪያን) አቆጣጠር በታህሣሥ ወር መጨረሻና በጥር ወር መጀመሪያ ላይ ይውላል። (ግምታዊ እውቀት፣ ውስጠ-ታዋቂ መረጃ እና የዕብራውያን ወሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

የሐሴት፣ የተድላና የደስታ በዓላት
የነገር ስሞች የሆኑት ‘ሐሴት’ እና ‘ተድላ’ ቅጽልን በመጠቀም ሊተረጎም ይችላል። አት. “በሐሴትና በተድላ የተሞሉ የደስታ በዓላት” (የነገር ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳ ቤት
‘ቤት’ የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩት ሰዎች ስመ-ምስል ስያሜ ነው። በዚህ ዓውድ የይሁዳንና የቢንያምን ዝርያዎችን በሚያካትተው በይሁዳ መንግሥት የሚኖሩትን ሕዝቦች ያመለክታል። አት. “የይሁዳ ሕዝቦች” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

ፍቅር፣ እውነትና ሰላም
የነገር ስሞች የሆኑት ‘እውነት’ እና ‘ሰላም’ ቅጽልን በመጠቀም ሊተረጎም ይችላል። አት. “እውነትና ሰላም የሞላበትን ውደዱ” (የነገር ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Zechariah 8:20

ሕዝቦች እንደገና ይመጣሉ
በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት ሕዝቡ የሚመጡት ወደ ኢየሩሳሌም ነው። አት. “ሕዝቦች እንደገና ወደ ኢየሩሳሌም ይመጣሉ።” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ወደ ሌላ ከተማ ይሄዳሉ
ይህ በሌላይቱ ከተማ ለሚኖሩት ሕዝቦች ስመ-ምስል ስያሜ ነው። አት. “በሌላይቱ ከተማ ወዳሉት ሕዝቦች ይሄዳሉ።” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

መለመን
እዚህ ላይ ’መለመን’ የሚለው መማፀን ወይም በአጣዳፊ ሁኔታ መጠየቅ ማለት ነው።

በያህዌ ፊት
እዚህ ላይ ‘ፊት’ የሚለው ለያህዌ ሕላዌ ስመ-ምስል ስያሜ ነው። በዘካርያስ 7:2 ላይ ይህንን እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “ያህዌ በተገኘበት” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

የሠራዊት ጌታ ያህዌን ፈልጉ
ያህዌን ለማወቅና እርሱን ለማስደሰት የሚፈልጉ ቃል በቃል እርሱን ለማግኘት እንደሚፈልጉት ተደርገው ተጠቅሰዋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ኃያላን መንግሥታት
ይህ በኃያላን መንግሥታት ውስጥ ለሚኖሩ ሕዝቦች ስመ-ምስል ስያሜ ነው። አት. “የኃያላን መንግሥታት ሕዝቦች” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 8:23

የልብሳችሁን ዘርፍ አጥብቀው በመያዝ
በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት መጻተኞቹ ወይም እንግዶቹ ሰዎች የእነርሱን ትኩረት ለማግኘት የልብሳቸውን ዘርፍ እንደሚይዙ ነው። (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከእናንተ ጋር አብረን እንሂድ
በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚሄዱ ነው። አት. “ከእናንተ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም እንሂድ” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር አለ
“እግዚአብሔር ከእናንተ ከሕዝቦቹ ጋር አለ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 9

1 ይህ በሴድራክና በደማስቆ ላይ የተነገረ የያህዌ ቃል ዐዋጅ ነው። የያህዌ ዐይኖች በሰው ልጆች ሁሉ እና በእስራኤል ነገዶች ሁሉ ላይ ናቸው። **2** ይህ ዐዋጅ ደማስቆን የምታዋስናትን ሐማትንም ይመለከታል፤ በጣም ጥበበኞች ቢሆኑም ጢሮስንና ሲዶናንም ይመለከታል። **3** ጢሮስ ለራሷ ምሽግ ሠርታለች፤ ብሩን እንደ ዐፈር፣ ንጹሑን ወርቅ እንደ መንገድ ላይ ትቢያ ቆልላለች። **4** እነሆ፣ ጌታ ሀብቷን ይወስዳል፤ በባሕሩ ላይ ያላትንም ኀይል ይደመስሳል፤ እርሷም ፈጽማ በእሳት ትጸፋለች። **5** አስቀሎና አይታ ትፈራለች! ጋዛም እጅግ ትሸበራለች! የአቃሮና ተስፋ ይጨነግፋል! ንጉሥ ከጋዛ ይጠፋል፤ አስቀሎና ከእንግዲህ መኖሪያ አትሆንም! **6** ባዕዳን ቤታቸውን በአሽዶድ ያደርጋሉ፤ የፍልስጥኤማውያንን ትዕቢት አጠፋለሁ። **7** ደሙን ከአፋቸው፣ የተከለከለውንም ምግብ ከጥርሶቻቸው መካከል አወጣለሁ። ያኔ እንደ ይሁዳ ነገድ የአምላካችን ትሩፋን ይሆናሉ፤ አቃሮንም እንደ ኢያቡሳዊ ይሆናል። **8** እኔ ግን ቤቴን ከዘራፊዎች እጠብቃለሁ፤ ጨቋኝ እንግዲህ ምድሬን አይወርስም፤ አሁን ነቅቼ እጠብቃለሁና! **9** አንቺ የጽዮን ልጅ ሆይ፣ እጅግ ደስ ይበልሽ! አንቺ የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ፣ በደስታ ጩኺ! እነሆ ንጉሥሽ በጽድቅ ወደ አንቺ መጥቶ ያድንሻል። እርሱ ትሑት ነው፤ በአህያ ላይ ይቀመጣል፤ በአህያ ግልገል በውርንጫዋ ላይ ይቀመጣል። **10** ከዚያም ከኤፍሬም ሰረገላን፣ ከኢየሩሳሌም ፈረስን አጠፋለሁ፤ ቀስት ከጦርነት ይሰበራል፤ ሰላምን ለሕዝቦች ይናገራል፤ ግዛቱ ከባሕር እስከ ባሕር ይሆናል፤ ከወንዝም እስከ ምድር ዳርቻ ይሆናል! **11** ለአንቺ ደግሞ፣ ከአንቺ ጋር ካደረግሁት የደም ኪዳን የተነሣ እስረኞችሽን ውሃ ከሌለበት ጉድጓድ ነጻ እለቃቸዋለሁ። **12** እናንተ የተስፋ እስረኞች ወደ ምሽጋችሁ ተመለሱ! አሁንም ቢሆን ዕጥፍ አድርጌ እንደምመልስላችሁ እናገራለሁ፤ **13** እንደ እኔ ቀስት ይሁዳን አጉብጫለሁ። ኤፍሬምን በፍላጻ ሞልቻለሁ። ጽዮን ሆይ፣ ልጆችሽን አስነሣለሁ፤ ግሪክ ሆይ በአንቺ ልጆች ላይ ይነሣሉ፤ እንደ ተዋጊ ሰይፍም አደርግሻለሁ! **14** ያህዌ ለእነርሱ ይገለጣል፤ ፍላጻውም እንደ መብረቅ ይፈነጠራል! ጌታ ያህዌ መለከት ይነፋል፤ በቴማን ዐውሎ ነፋስ ይገሰግሣል። **15** የሰራዊት ጌታ ያህዌ ይከልላቸዋል፤ ጠላቶቻቸውን ይደመስሳሉ፣ በድንጋይ ወንጭፍም ያሸንፋሉ። ይጠጣሉ፤ በወይን ጠጅ እንደ ሰከረ ሰው ይጮኻሉ፤ መሠዊያው ላይ እንዳሉ ዕቃዎች፣ እንደ መሠዊያው ማእዘኖች በወይን ይሚላሉ። **16** በዚያ ቀን አምላካቸው ያህዌ ያድናቸዋል፤ ሕዝቡን የራሱ መንጋ ያደርጋቸዋል። አክሊል ላይ እንዳለ ዕንቁ፣ በገዛ ምድሩ ላይ ያብለጨልጫሉ። **17** ምንኛ መልካም፣ ምንኛ ቆንጆ ይሆናሉ! እህል ወጣቶችን፣ ጣፋጭ ወይን ጠጅ ቆነጃጅቱን ያሳምራል!

Zechariah 9:1

... በሚመለከት ይህ የያህዌ ቃል አዋጅ ነው
“ይህ ስለ ... የያህዌ መልእክት ነው”

የሴድራክና የደማስቆ ምድር
እዚህ ላይ ‘ሴድራክ’ እና ‘ደማስቆ’ በእነዚያ ስፍራዎች የሚኖሩትን ሕዝብ ያመለክታሉ። አት. “የሴድራክ ምድርና የደማስቆ ከተማ ሕዝቦች” (ስመ-ምስል ስያሜ እና ስሞችን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ የሚሉትን ይመልከቱ)

ሴድራክ
የሴድራክ አድራሻ አሁን የት እንደሆነ አይታወቅም።

ማረፊያ ቦታው
“የሴድራክ ሕዝብ ማረፊያ ቦታ”

የሰዎች ሁሉና የእስራኤል ነገዶች ሁሉ ዓይኖች ወደ እግዚአብሔር አቅንቷል
እዚህ ላይ ‘ዓይኖች’ የሚመለከቱትን ነገር ያመለክታል። አት. “የሰው ልጆች ሁሉና የእስራኤል ነገዶች ሁሉ ወደ ያህዌ ይመለከታሉ።” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

ሐማት
ይህ በዚያ ምድር የሚኖሩትን ሕዝቦች ያመለክታል። አት. “የሐማት ምድር ሰዎች” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

ጢሮስና ሲዶና
ይህ በዚያ ምድር የሚኖሩትን ሕዝቦች ያመለክታል። አት. “የጢሮስና የሲዶና ምድር ሰዎች” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

በጣም ጥበበኞች ስለሆኑ
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፡ - 1) ለዕርዳታ ወደ ያህዌ በመመልከታቸው ሕዝቡ ጠቢባን ናቸው ወይም 2) ዘካርያስ የሐማት ሰዎች በእርግጥ ጠቢባን ነበሩ ማለቱ ሳይሆን ሽሙጥ አነጋገር እየተጠቀመ ነበር። ትኩ. “ምንም እንኳን በጣም ጠቢባን ነን እያሉ የሚያስቡ ቢሆኑም” (ሽሙጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 9:3

ለራሷ ምሽግ ሠርታለች
እዚህ ላይ የጢሮስ ከተማ በሴት ተመስላለች። አት. “ጠንካራ ምሽግ ሠርታለች” ወይም “ከፍ ያለ ቅጥር ሠርታለች” (ሰውኛ የሚለውን ይመልከቱ)

ብርን እንደ አፈር የነጠረንም ወርቅ እንደ መንገድ ላይ ጭቃ ቆልላለች
ጢሮስ ምን ያህል ባለጠጋ እንደነበረች አጽንዖት ለመስጠት ያህዌ የግነት አነጋገር ይጠቀማል። አት. “በመንገድ ላይ እንዳለ ጭቃ ብርንና ወርቅን አከማችታለች” (ግነት እና ጥቅል አባባል የሚባሉትን ይመልከቱ)

እነሆ፣ ጌታ ይወስድባታል
እዚህ ላይ ‘እነሆ’ የሚለው ቃል ተአንባቢው ለሚቀጥለው አስፈላጊ ገለጻ ትኩረት እንዲሰጥ ያሳስበዋል። አት. “አስተውል! ጌታ የጢሮስን ሀብት ይወስድባታል።”

በባሕር ላይ ያላትን ኃይል ይደመስሳል
‘በባሕር ላይ ያላት ኃይል’ የሚያመለክተው ለንግድና ለወረራ የሚውሉትን መርከቦች ነው። አት. “ሰዎች በባሕር ላይ ውጊያ የሚያካሂዱባቸውን የጢሮስን መርከቦች ይደመስሳል” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

በእሳት ፈጽማ ትጠፋለች
ይህ በተናጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት. “ጠላቶች ከተማይቱን እስክትወድም በእሳት ያቃጥሏታል” (ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 9:5

አስቀሎና፣ ጋዛ፣ አቃሮንም ... ተስፋዋ
እነዚህ ከተሞች እያንዳንዳቸው በውስጣቸው የሚኖሩ ሕዝቦችን ያመለክታሉ። አት. “የአስቀሎና ሕዝቦች ... የጋዛ ሕዝቦች ... የአቃሮን ሕዝቦች ተስፋዎች” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

አይታ
ጢሮስ ስትወድም ታያለች

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንግዶች ቤታቸውን በአሽዶድ ያደርጋሉ
“እንግዶች አሽዶድን ወስደው በዚያ ይኖራሉ”

የፍልስጥኤማውያንንም ትምክህት እቆርጣለሁ
እዚህ ላይ ‘እቆርጣለሁ’ የሚለው ትምክህታቸውን አስቆማለሁ የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ አባባል ነው። አት. “ፍልስጥኤማውያን ከእንግዲህ በራሳቸው እንዳይመኩ አደርጋቸዋለሁ።” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ደሙን ከአፋቸው ነውራቸውንም ከጥርሳቸው መካከል አወጣለሁ
እዚህ ላይ ‘ደም’ ደም በውስጡ ላለበት ሥጋ፣ ‘ነውር’ ደግሞ ለጣዖት ለቀረበ ሥጋ ስመ-ምስል ስያሜዎች ናቸው። አት. “በውስጡ ደም ያለበትን ሥጋ ከእንግዲህ እንዲበሉ አልፈቅድላቸውም፣ ለጣዖት የሚያቀርቡትንም ምግብ እንዳይበሉ እከለክላቸዋለሁ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 9:8

በምድሬ ዙሪያ እሰፍራለሁ
እግዚአብሔር ምድሩን ለመጠበቅ በዙሪያው እንደሰፈረ ሠራዊት አድርጎ ስለ ራሱ ይናገራል። አት. “ምድሬን እጠብቃለሁ።” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አሁን
‘በዚያን ጊዜ’

በራሴ ዓይኖች እመለከታለሁ
‘በራሴ ዓይኖች’ የሚለው የያህዌን የግል ትኩረት ይወክላል። አት. “እኔ በግሌ ምድሬን እመለከታለሁ።” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 9:9

አጠቃላይ መረጃ
ከቁ.9-13 ባሉት ተናጋሪው ያህዌ ይመስላል።

የጽዮን ልጅ ሆይ፣ በታላቅ ሐሴት ድምፅሽን አሰሚ፣ የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ በደስታ እልል በዪ
የእነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ነው፣ ሁለቱም ደስ እንዲላቸው የተሰጠውን ትዕዛዝ ያጠናክራሉ። ያህዌ የኢየሩሳሌም ሕዝቦች እዚያ እንደነበሩ አድርጎ እየተናገረ ነው፣ እነርሱ ግን እዚያ አልነበሩም። (ትይዩነት እና የሌለን እንዳለ አድርጎ መናገር የሚሉትን ይመልከቱ)

የጽዮን ሴት ልጅ፣ የኢየሩሳሌም ሴት ልጅ
‘ጽዮን’ እና ‘ኢየሩሳሌም’ አንድ ናቸው። ነቢዩ ስለ ከተማይቱ ሴት ልጅ እንደሆነች አድርጎ እየተናገረ ነው። በዘካርያስ 2:10 ላይ የጽዮን ሴት ልጅ የሚለውን እንዴት እንደተረጎማችሁት ዘር ብላችሁ ተመልከቱ።

እነሆ
ይህ አንባቢው ለሚቀጥለው አስደናቂ ገለጻ የተለየ ትኩረት እንዲሰጥ ያሳስበዋል። አት. “ልብ በል” ወይም “እዚህ ላይ አስደናቂ እውነታ አለ”

ንጉሥሽ ወደ አንቺ በጽድቅ ይመጣል፣ያድንሽማል
“ንጉሥሽ ጻድቅ ነው፣ የሚመጣውም ሊያድንሽ ነው።”

በአህያ ላይ በአህያይቱም ውርንጫ ላይ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ አንድ ዓይነት ትርጉም ያላቸው ናቸው፣ የሚናገሩትም ስለ አንድ እንሰሳ ነው። ሁለተኛው ሐረግ ግልገል አህያ እንደሆነ መግለጫ ይሰጣል። አት. “በግልገል አህያ ላይ” (ጥምር አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ሠረገላውንም ከኤፍሬም እቆርጣለሁ
እዚህ ላይ ‘እቆርጣለሁ’ የሚለው እደመሰሳለሁ የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ አባባል ነው። አት. “በእስራኤል ያሉትን ለጦርነት የሚያገለግሉትን ሠረገሎች እደመሰሳለሁ”

ፈረሶችንም ከኢየሩሳሌም
ስለ ‘ሠረገላ’ እና ስለ ‘ቀስት’ መጠቀሱ ፈረሶቹ ለጦርነት የሚያገለግሉ እንደነበሩ ያመለክታል። ይህንን ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አት. “በኢየሩሳሌም ያሉት የውጊያ ፈረሶች” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ቀስቱ ከውጊያ ይቆረጣል
እዚህ ላይ ቀስት በጦርነት ጥቅም ላይ የሚውሉትን መሣሪያዎች ይወክላል። አት. “የጦር መሣሪያዎች ሁሉ ይደመሰሳሉ” (በከፊል የተወከለ አካል የሚለውን ይመልከቱ)

ሰላምን ለሕዝቦች ይናገራል
እዚህ ላይ ሰላምን የማወጅ ተግባር ሰላም የማድረግን ተግባር ይወክላል። አት. “ንጉሣችሁ ለሕዝቦች ሰላምን ያመጣላቸዋል” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

ግዛቱም ከባሕር እስከ ባሕር፣ ከወንዙ እስከ ምድር ዳርቻ ይሆናል
‘ከባሕር እስከ ባሕር’ እና ‘ከወንዙም እስከ ምድር ዳርቻ’ የሚሉት ሐረጎች ትርጉማቸው አንድ እንደመሆኑ በአንድ ላይ ሊጣመሩ ይችላሉ። አት. “መንግሥቱ በመላው ምድር ላይ ይሆናል” (ጥምር አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ወንዙ
ይህ ምናልባት የኤፍራጥስን ወንዝ ሳያመለክት አይቀርም።

Zechariah 9:11

አጠቃላይ መረጃ
ከቁ.9-13 ተናጋሪው ያህዌ ይመስላል።

አንቺ ጽዮን
እዚህ ላይ ‘አንቺ’ የሚለው ነጠላ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተውም ‘ጽዮን’ እየተባለችም የምትጠራውን የኢየሩሳሌምን ከተማ ነው።

ውሃ ከሌለበት ጉድጓድ
ይህ ደረቅ ጉድጓድ የባቢሎን ስደትን ይወክላል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ምሽጎቻችሁ ተመለሱ
ኢየሩሳሌም ደህንነት ያለባት ስፍራ እንደሆነች እየተነገረ ነው። አት. “ደህንነታችሁ ወደሚጠበቅበት ወደ አገራችሁ ተመለሱ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የተስፋ እስረኞች
አገላለጹ በምርኮ ላይ ሳሉ እግዚአብሔር ገና ያድነናል ብለው ሲያምኑ የነበሩትን እስራኤላውያንን ያመለክታል። ትኩ. “በያህዌ ላይ ገና ያምኑ የነበሩ እስረኞች”

ሁለት እጥፍ አድርጌ እመልስላችኋለሁ
“ከእናንተ የተወሰደው እጥፍ ሆኖ ይመለስላችኋል”

ይሁዳን እንደ ቀስቴ እንትረዋለሁ
የይሁዳ ሕዝብ እግዚአብሔር ወደ ጦርነት እንደወሰደው ቀስት እንደሆኑ ተደርገው ተጠቅሰዋል። እዚህ ላይ ‘ይሁዳ’ የዚያ አገር ሕዝቦችን ያመለክታል። አት. “የይሁዳ ሕዝቦች እንደ ቀስቴ እንዲሆኑ አደርጋቸዋለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ስመ-ምስል ስያሜ የሚሉትን ይመልከቱ)

በኤፍሬምም ኮረጆዎቼን እሞላለሁ
ያህዌ የሰሜኑን መንግሥት የእስራኤልን ሕዝብ በጠላቶቹ ላይ የሚወረውራቸው ቀስቶች እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። ኮርጆ አንድ ወታደር ቀስቶቹን የሚይዝበት ከረጢት ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ጽዮን ሆይ፣ ልጆችሽን አስነሣለሁ፣ ግሪክ ሆይ፣ በአንቺ ላይ
እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ ለሁለት የተለያዩ አገር ሕዝቦች እየተናገረ ነው። (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 9:14

አጠቃላይ መረጃ
ከቁ.14-16 ዘካርያስ እግዚአብሔር እስራኤልን ከጠላቶቿ እንዴት እንደሚያድናት ይገልጻል።

ለእነርሱ ይገለጣል
‘ለእነርሱ’ የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ሕዝብ ነው። አት. “በሰማይ ላይ በሕዝቡ ይታያል” ወይም “ወደ ሕዝቡ ይመጣል”

ፍላጻውም እንደ መብረቅ ይወጣል!
እስራኤላውያን አንዳንድ ጊዜ የመብረቅ ብልጭታ እግዚአብሔር የሚወረውረው ቀስት እንደሆነ አድርገው ያስባሉ። (ምስስሎሽ የሚለውን ይመልከቱ)

መለከትን ንፉ
መለከቶች የአውራ በግ ቀንዶች ናቸው። ሰዎች በጦርነት ጊዜ ምልክቶችን ለመስጠት በሌሎችም አጋጣሚዎች ይነፏቸዋል። እዚህ ላይ መለከቱ የተነፋው ለጦርነት ምልክት እንዲሆን ነው።

ከቴማንም ከዓውሎ ነፋስ ጋር ይጓዛል
ቴማን ከይሁዳ በስተደቡብ በኩል ያለ ስፍራ ነበር። እስራኤላውያን አንዳንድ ጊዜ ከደቡብ በሚነፍሰው ኃይለኛ ዓውሎ ነፋስ እንደሚጓዝ አድርገው ያስቡ ነበር። አት. “ከቴማን ከሚነፍሰው ዓውሎ ነፋስ ጋር ይጓዛል”

ይደመስሷቸዋል
“የይሁዳ ሕዝብ ጠላቶቻቸውን ይደመስሳሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በድንጋይ ወንጭፍም ያሸንፋሉ
ለድንጋይ መወርወሪያ የሚጠቅሙ ወንጭፎች በዘካርያስ ዘመን የተለመዱ ነበሩ። እዚህ ላይ ‘የወንጭፍ ድንጋይ’ እስራኤልን ለማጥቃት የሚጠቀሙባቸውን ወታደሮችን ያመለክታል። አት. “በወንጭፍና በድንጋይ የሚያጠቋቸውን ጠላቶች ድል ያደርጋል” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያ በኋላም ይጠጣሉ፣ ወይን ጠጅ ጠጥቶ እንደሰከረ ሰውም ይጮኻሉ
የይሁዳ ሕዝብ እንደ ጫኺ ሰካራሞች በጠላቶቻቸው ላይ ስላገኙት ድል ይጮኻሉ፣ ድላቸውንም ያከብራሉ። አት. “ከዚያ በኋላ ይጮኻሉ፣ እንደ ሰከሩ ሰዎችም ድላቸውን በጩኸት ያከብራሉ” (ምስስሎሽ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ወጭት በወይን ጠጅ ይሞላሉ
ይህ ምናልባት ካህናት የእንሰሶችን ደም ወደ መሠዊያ ለመውሰድ የሚጠቀሙበትን ወጭት ሳያመለክት አይቀርም። አት. “ካህናት ደሙን ወደ መሠዊያ እንደሚወስዱባቸው ወጭቶች በወይን ጠጅ የተሞሉ ይሆናሉ።” (ምስስሎሽ፣ ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

የመሠዊያውን ማዕዝኖች
መሠዊያዎች ወደ ውጭ ወጣ ወጣ ያሉ በእንሰሳ ደም የረሰረሱ ማዕዝኖች አሏቸው። አት. “የመሠዊያው ማዕዝኖች በደም የተነከሩ እንደሆኑ ሁሉ እነርሱም እንደዚሁ የረሰረሱ ይሆናሉ” (ምስስሎሽ፣ ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

Zechariah 9:16

አጠቃላይ መረጃ
ከቁ.14-16 ዘካርያስ እግዚአብሔር እስራኤልን ከጠላቶቿ እንዴት እንደሚያድናት ይገልጻል።

እንደ ሕዝቡ መንጋ እግዚአብሔር ያድናቸዋል
የእስራኤል ሕዝብ የሚንከባከባቸውና የሚጠብቃቸው የእግዚአብሔር በጎች እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል። (ምስስሎሽ የሚለውን ይመልከቱ)

የአክሊል ዕንቁዎች ናቸው
የእስራኤል ሕዝብ ምን ያህል የከበረ እንደሆነ በሚያመለክተው የንጉሡ አክሊል ላይ የተደረጉ ውድ ዕንቁዎች እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል። አት. “በአክሊል ላይ እንደተደረጉ ውብ የከበሩ ድንጋዮች ናቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ምን ያህል መልካምና ምን ያህል ውብ ይሆናሉ!
ይህ ቃለ-አጋኖ እንጂ ጥያቄ አይደለም። አት. “እጅግ መልካምና ውብ ይሆናሉ።” (ቃለ-አጋኖ የሚለውን ይመልከቱ)

እህል ጎልማሶችን፣ ጣፋጭ ወይንም ደናግሉን ያሳምራል
ማንኛውም ሰው የተትረፈረፈ ምግብና መጠጥ እንደሚኖረው ለማመልከት ይህ ዓረፍተ ነገር የትይዩነት አወቃቀር ይጠቀማል። አንባቢዎቻችሁ ወንዶቹ ብቻ እንደሚበሉ፣ ሴቶቹ ብቻ እንደሚጠጡ የሚያስቡ ከሆነ አባባሉን መለወጥ ሊያስፈልጋችሁ ይችላል። አት. “ሁሉም ሰዎች፣ ወንዶችም ሴቶችም የተትረፈረፈ የሚበላና የሚጠጣ ይኖራቸዋል” (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ጎልማሶቹ ... ደናግሉ
ሁለቱ ቃላት ትይዩዎች ናቸው፣ በአንድነትም መላውን የእስራኤል ሕዘብ ይወክላሉ። (በከፊል የተወከለ አካል የሚለውን ይመልከቱ)

እህል ... ጣፋጭ ወይን ጠጅ
ሁለቱ ቃላት ትይዩዎች ናቸው፣ በአንድነትም ሁሉንም የተለያዩ ምግቦችና መጠጦች ይወክላሉ። (ትይዩነት እና በከፊል የተወከለ አካል የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 10

1 የበልግ ወራት ዝናብ እንዲሰጣችሁ ጠይቁ፣ ዝናብ ያዘለ ደመናን የሚልክ ያህዌ ነው እርሱ ዝናብንና የመስክ አትክልትን ለሁሉም ይሰጣል። **2** የቤተ ሰብ ጣዖቶች ውሸት ይናገራሉ፤ ሟርተኞች የሐሰት ራእይ ያያሉ አሳሳች ሕልም ይናገራሉ፤ ባዶ መጽናኛ ይሰጣሉ ስለዚህ ሕዝቡ እንደ በጎች ይባዝናሉ፣ እረኛ በማጣጥም ይጨነቃሉ። **3** ጽኑ ቁጣዬ በእረኞች ላይ ነዶአል፤ መሪዎችንም እቀጣለሁ። የሰራዊት ጌታ ያህዌ ለመንጋው ለይሁዳ ቤት ይጠነቀቃል፤ በጦርነት ጊዜ እንደ ኩሩ የጦር ፈረሱ ያደርጋቸዋል! **4** ከይሁዳ ሕዝብ የማእዘን ድንጋይ ይወጣል፤ ከእነርሱ የድንኳን ካስማ ይገኛል፤ ከእነርሱ የጦር ቀስት ይመጣል፤ ከእነርሱ ገዥ ሁሉ ይወጣል። **5** በጦርነት ጊዜ ጠላቶቹን እንደ መንገድ ላይ ጭቃ እንደሚረግጥ ሰራዊት ይሆናሉ፤ ያህዌ ከእነርሱ ጋር ስለሆነ ተዋግተው የጦር ፈረሰኞችን ያሸንፋሉ። **6** የይሁዳን ቤት አበረታለሁ፤ የዮሴፍንም ቤት አድናለሁ፤ እምራቸዋለሁ፤ ወደ ቦታቸውም እመልሳቸዋለሁ። ከዚህ በፊት በፍጹም ጥዬአቸው እንደማላውቅ ይሆናሉ፤ እኔ አምላካቸው ያህዌ ነኝ፤ ጸሎታቸውንም እሰማለሁ። **7** በዚያ ጊዜ ኤፍሬም እንደ ብርቱ ጦረኛ ይሆናል፤ ወይን ጠጅ እንደ ጠጣ ሰው ልባቸውን ደስ ይለዋል፤ ልጆቻቸውም አይተው ሐሤት ያደርጋሉ። ልባቸው በእኔ ሐሤት ያደርጋል! **8** በፉጨት ጠርቼ እሰበስባቸዋለሁ፤ በእርግጥ እታደጋቸዋለሁ፤ እንደ ቀድሞው ዘመን ይበዛሉ! **9** በሕዝቦች መካከል ብበትናቸው እንኳ፣ በሚኖሩባቸው ሩቅ አገሮች ሆነው ያስታውሱኛል፤ እነርሱና ልጆቻቸው ተርፈው ይመለሳሉ። **10** ከግብፅ ምድር እመልሳቸዋለሁ፤ ከአሦርም እሰበስባቸዋልሁ። ቦታ እስኪጠባቸው ድረስ በገልዓድና በሊባኖስ አሰፍራቸዋለሁ። **11** በመከራቸው ባሕር ውስጥ አልፋለሁ፤ ምክንያቱም የባሕሩን ማዕበል እመታለሁ፤ የዐባይም ጥልቅ ሁሉ ይደርቃል። የአሦር ግርማ ይወገዳል፤ የግብፅ በትረ መንግሥት ከግብፃውያን ይወገዳል። **12** በእኔ በራሴ አበረታቸዋለሁ፤ በስሜ ይመላለሳሉ፤ ይህ የያህዌ ዐዋጅ ነው።

Zechariah 10:1

አጠቃላይ መረጃ
ዘካርያስ ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል።

ነገድጓዶችን ይፈጥራል
“ዝናብ እየጎረፈ የሚወጣባቸውን ደመናዎች ይፈጥራል”

በእርሻ ላይ ሰብል
“በእርሻ ላይ ሰብል እንዲበቅል ያደርጋል”

በቤት ውስጥ የተቀረጹ ጣዖቶች ሐሰት ይናገራሉ
“በቤት ውስጥ የተቀረጹ ጣዖቶች ሐሰተኛ መልእክት ይሰጣሉ” ዘካርያስ ጣዖቶች በእርግጥ ይናገራሉ የሚል ሃሳብ እየሰጠ አይደለም። ሰዎች ከጣዖቶች ሰማን እያሉ ስለሚናገሯቸው መልእክቶች እያመለከተ ነው። UDB ይህንን ግልጽ ያደርገዋል።

ሟርተኞች የውሸት ራዕይ ያያሉ
“ሟርተኞች ሐሰት የሆነ ራዕይ ይመለከታሉ”

አታላይ ሕልሞችን ይናገራሉ
በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት እነርሱ እነዚህ ሕልሞች ሐሰት እንደሆኑ ያውቃሉ። ይህንን በግልጽነት ማቅረብ ይቻላል። አት. “ሰዎችን ለማታለል ሲሉ ሟርተኞች ስለ ሕልማቸው ይዋሻሉ።” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከንቱ መጽናናት
ለጊዜው የሚያባብሉ እንጂ ዘላቂ ዕርዳታ የማይሰጡ ቃላትን የሚያመለክት ነው።

እንደ በጎች ይቅበዘበዛሉ
እውነቱን የሚናገሩ ነቢያት የሌላቸው ሕዝቦች ወዴት እንደሚሄዱ የሚነግራቸው እረኛ የሌላቸው በጎች እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል። አት. “ሐሰተኛ ነቢያትን የሚያዳምጡ ሕዝቦች በየት በኩል እንደሚሄዱ እንደማያውቁ በጎች ናቸው።” (ምስስሎሽ የሚለውን ይመልከቱ)

እረኛ ስለሌላቸው ይሰቃያሉ
እውነቱን የሚናገሩ ነቢያት የሌላቸው ሕዝቦች ወዴት እንደሚሄዱ የሚነግራቸው እረኛ ስለሌላቸው የሚሰቃዩ በጎች እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል። አት. “ሐሰተኛ ነቢያትን የሚያዳምጡ ሕዝቦች የሚመራቸው እረኛ ስለሌላቸው እንደሚሰቃዩ በጎች ናቸው።” (ምስስሎሽ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 10:3

አጠቃላይ መረጃ
ከቁ.3-5 የሚናገረው ያህዌ ይሁን ወይም ዘካርያስ በያህዌ ምትክ ሆኖ እየተናገረ እንደሆነ ግልጽ አይደለም።

ቁጣዬ በእረኞች ላይ ነዶአል
እዚህ ላይ “እረኞች” የእግዚአብሔርን ሕዝብ መሪዎች ይወክላል። የያህዌ የቁጣ ብርታት የሚነድ እሳት እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አት. “በሕዝቤ እረኞች ላይ ያለኝ ቁጣ እንደ እሳት ብርቱ ነው።” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የምቀጣው ተባዕት ፍየሎችን፣ መሪዎችን ነው
ተባዕት ፍየሎች ከእንስቶቹ ይልቅ በኃይለኝነታቸው በተለይ የታወቁ ናቸው። እዚህ ላይ ‘ተባዕት ፍየሎች’ ጨቋኝ የነበሩትን የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪዎች ይወክላሉ። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሠራዊት ጌታ ያህዌ ለመንጋው ለይሁዳ ቤትም ይጠነቀቃል
እዚህ ላይ ያህዌ ለሕዝቡ የሚያደርገው እንክብካቤ እረኛ ለበጎቹ እንደሚያደርገው እንክብካቤ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አት. “እረኛ ለበጎቹ እንክብካቤ እንደሚያደርግላቸው የሠራዊት ጌታ ያህዌ ለይሁዳ ቤት እንክብካቤ ያደርጋል”

የይሁዳ ቤት
‘ቤት’ የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ስመ-ምስል ስያሜ ነው። እዚህ ላይ የሚያመለክተው የይሁዳንና የቢንያምን ዝርያዎች የሚያካትተውን የይሁዳን ሕዝብ ነው። ትኩ. “ይሁዳ” ወይም “የይሁዳ ሕዝብ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ጦርነት ፈረሶቹ ያደርጋቸዋል
ያህዌ የሕዝቡን ተለዋጭ ዘይቤ ተካላካይ ከሌላቸው በጎች ወደ ጦርነት ፈረሶች ይለውጣል። አት. “በውጊያ ላይ ብርቱ እንደሆኑ የጦርነት ፈረሶች ያደርጋቸዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምስስሎሽ የሚሉትን ይመልከቱ)

Zechariah 10:4

አጠቃላይ መረጃ
ከቁ.3-5 የሚናገረው ያህዌ ይሁን ወይም ዘካርያስ በያህዌ ምትክ ሆኖ እየተናገረ እንደሆነ ግልጽ አይደለም።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከይሁዳ የማዕዘን ራስ ድንጋይ ይመጣል
“የማዕዘኑ ራስ ድንጋይ ከይሁዳ ይመጣል” በጣም አስፈላጊ የሆነው ገዢ የሕንፃው ዋና መሠረት እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አት. “ከይሁዳ ዝርያዎች አንዱ በጣም አስፈላጊ የሆነው ገዢ ይሆናል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የማዕዘን ራስ ድንጋይ ... የድንኳን ካስማ ... የውጊያ ቀስት
ለእነዚህ ሶስት ነገሮች ትርጉሞች ሊሆኑ የሚችሉት፡ - 1) ከይሁዳ ነገድ የሚመጣውን መሲሑን ለማመልከት ጥቅም ላይ የዋሉ ተምሳሌታዊ አባባሎች ሊሆኑ ይችላሉ፣ ወይም 2) ከይሁዳ የሚመጡ የተለያዩ መሪዎችን ሊያመለክት ይችላል። (ተምሳሌታዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ከእርሱም የድንኳን ካስማ
“ከእርሱ ዘንድ የድንኳን ካስማ ይመጣል” የድንኳን ካስማ ሰዎች የሚኖሩባቸውን ድንኳኖች የሚደግፉትን ገመዶች የሚይዘው ነው። እዚህ ላይ በጣም አስፈላጊ የሆነው ገዢ ድንኳኑን በስፍራው እንደሚይዘው የድንኳኑ ዋና ካስማ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አት. “አገሪቱን በአንድነት አስተባብሮ የሚይዘው መሪ ከይሁዳ ይመጣል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእርሱ ዘንድ የጦርነቱ ቀስት ይመጣል
“የጦርነቱ ቀስት ከእርሱ ዘንድ ይመጣል” እዚህ ላይ በጣም አስፈላጊ የሆነው ገዢ በጦርነት ጊዜ ጥቅም ላይ እንደሚውለው የጦርነት ቀስት እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አት. “ወታደራዊው መሪ ከይሁዳ ይመጣል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእርሱ ዘንድ ማናቸውም መሪዎች በአንድነት ይመጣሉ
“ማንኛውም መሪ ከይሁዳ ይመጣል”

እንደ ተዋጊዎች ይሆናሉ ... በውጊያ ወቅት ያሉ መንገዶች
ከይሁዳ የሚመጡት ገዢዎች ድል አድራጊ ተዋጊዎች እንደሆኑ ተደርገው ተነግሮዋል። አት. “በጦርነት ኃይለኞች ይሆናሉ፣ ጠላቶቻቸውንም እንደ መንገድ ጭቃ ይረግጣሉ” (ምስስሎሽ የሚለውን ይመልከቱ)

በጦርነት ጊዜ ጠላቶቻቸውን እንደ መንገድ ጭቃ ይረግጣሉ
እንደ ጭቃ መርገጥ ሙሉ በሙሉ ድል ነሷቸው ለማለት የዋለ ፈሊጣዊ አባባል ነው። አት. “ጠላቶቻቸውን ሙሉ በሙሉ ድል የሚያደርጉ” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ ከእነርሱ ጋር ነው
እዚህ ላይ ‘ከእነርሱ ጋር’ የሚለው ሊረዳቸው በዚያ እንደሚገኝ የሚገልጽ ፈሊጣዊ አባባል ነው። አት. “ያህዌ ይረዳቸዋል” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

የጦር ፈረሶችን የሚጋልቡትን ያሳፍራሉ
እዚህ ላይ ኃፍረት መሸነፍን የሚያጅብና የሚወክል ነው። አት. “የጦር ፈረሶችን የሚጋልቡትን ድል ያደርጋሉ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 10:6

አጠቃላይ መረጃ
ከቁ.6-12 ላይ ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ ይናገራል።

የይሁዳ ቤት
‘ቤት’ የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ስመ-ምስል ስያሜ ነው። እዚህ ላይ የሚያመለክተው የይሁዳንና የቢንያምን ዝርያዎች የሚያካትተውን የእስራኤልን መንግሥት ነው። አት. “ይሁዳ” ወይም “የይሁዳ መንግሥት” ወይም “የይሁዳ ሕዝብ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

የዮሴፍ ቤት
‘ቤት’ የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ስመ-ምስል ስያሜ ነው። እዚህ ላይ የሚያመለክተው የይሁዳንና የቢንያምን ዝርያዎች የሚያካትተውን የይሁዳን መንግሥት ነው። አት. “እስራኤል” ወይም “የእስራኤል መንግሥት” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

አልጣልኳቸውም
ይህ ስለ ሕዝቡ ያህዌ እንደሚያወልቀውና እንደሚጥለው እንደተቀዳደ ወይም እንደ ቆሸሸ ልብስ ይናገራል። ይህ መተውን ወይም መጣልን በተምሳሌትነት ይገልጻል። አት. “አልጣልኳቸውም” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ተምሳሌታዊ ተግባር የሚሉትን ይመልከቱ)

ኤፍሬም እንደ ተዋጊ ይሆናል
‘ኤፍሬም’ እዚህ ላይ ሰሜናዊውን የእስራኤል መንግሥት ያመለክታል። ተዋጊዎች ብርቱዎች ናቸው። አት. “ኤፍሬም እጅግ ብርቱ ይሆናል” (ምስስሎሽ የሚለውን ይመልከቱ)

የወይን ጠጅ የጠጡ ደስ እንደሚላቸው ልባቸው ሐሴት ያደርጋል
እዚህ ላይ ‘ልብ’ መላውን ሰው ያመለክታል። ወይን ጠጅ በመጠጣት ደስ እንደሚለው ሁሉ እነርሱም እንደዚሁ ደስ ይላቸዋል። አት. “በጣም ደስ ይላቸዋል” (በከፊል የተወከለ አካል እና ምስስሎሽ የሚሉትን ይመልከቱ)

ልጆቻቸው ይመለከታሉ ሐሴትም ያደርጋሉ ... በእኔም ደስ ይላቸዋል
“ለእነርሱ ያህዌ ስላደረገላቸው ነገር ልጆቻቸው የተደረገውን ተመልክተው ደስ ይላቸዋል!”

Zechariah 10:8

አጠቃላይ መረጃ
ከቁ.6-12 ላይ ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ ይናገራል።

አፏጫለሁ
ማፏጨት በተጋጠሙ ከንፈሮች መካከል በሚወጣ ትንፋሽ ከፍተኛ የሚያቃጭል ድምፅ ነው። እዚህ ላይ እንደተደረገው ብዙውን ጊዜ ለሌሎች ሰዎች ምልክት ለመሰጠት የሚደረግ ነው።

በሕዝቦች መካከል ዘራኋቸው
የሕዝቡ መማረክ ያህዌ በሩቅ አገር እንደተከላቸው ዘሮች እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በቂ ስፍራ እስከማይገኝላቸው ድረስ
ሕዝቡ ወደ ይሁዳ መመለሳቸውን ስለሚቀጥሉ እዚያ ለመኖር ምንም ተጨማሪ ሕዝብ ለመቀበል ቦታ እስከማይኖር ድረስ የተጨናነቀ ይሆናል። ይህ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለጽ ይችላል። አት. “ሙሉ በሙሉ ምድሪቱን ይሞሏታል”

Zechariah 10:11

አጠቃላይ መረጃ
ከቁ.6-12 ላይ ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ ይናገራል።

በእነርሱ የመከራ ባሕር ውስጥ አልፋለሁ
የእግዚአብሔር ቃል ብዙውን ጊዜ ባሕር የብዙ ችግሮችና ጭንቀቶች ምስል እንደሆነ ያመለክታል። እዚህ ላይ ያህዌ በእነዚህ ጭንቀቶች ውስጥ ሲያልፉ ሕዝቡን እንደሚያጅባቸው እየተናገረ ነው። አት. “እኔ ከእነርሱ ጋር እሄዳለሁ፣ በብዙ ጭንቀቶቻቸው ውስጥ በሚያልፉበትም ጊዜ እረዳቸዋለሁ።” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የዚያንም ባሕር ማዕበል እመታለሁ
እዚህ ላይ የባሕሩን ማዕበል ‘እመታለሁ’ የሚለው ማዕበሉ እንዳይከሰት አስቆመዋለሁ ለማለት የሚውል ፈሊጣዊ አባባል ነው። የሕዝቡን ጭንቀት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ማስቆም የዚያን ባሕር ማዕበል እንደማረጋጋት ሆኖ እየተነገረ ነው። አት. “ያንን የመከራ ባሕር ማዕበል እንዲቆም አደርገዋለሁ” (ፈሊጣዊ አባባል እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

የዓባይም ጥልቅ ሁሉ ይደርቃል
“የዓባይ ወንዝ ውሃውን ሁሉ እንዲያጣ አደርገዋለሁ”

የአሦርም ግርማ ይዋረዳል
እዚህ ላይ ‘የአሦር ግርማ’ የአሦርን ጦር ሠራዊት የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም። (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

የግብፅም በትረ መንግሥት ከግብፃውያን ይወገዳል
እዚህ ላይ ‘የግብፅ በትረ መንግሥት’ የግብፅን ፖለቲካዊ ኃይል የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም። አት. “ግብፅ ሌሎች አገሮችን የመግዛት ኃይሏ ያበቃል” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

በእኔ በራሴ አበረታቸዋለሁ
“ብርቱ እንዲሆኑና በእኔ እንዲያምኑ አደርጋቸዋለሁ”

በስሜም ይመላለሳሉ
እዚህ ላይ ‘በስሜ’ የሚለው ያህዌ የሚለውን ያደርጋሉ የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ አባባል ነው። አት. “እኔ እንዲያደርጉ እንደምፈልግባቸው ይታዘዙኛል ያከብሩኛልም።” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ ... እንዲህ ይላል
እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ ያህዌ ስለ ራሱ ስሙን በመጥቀስ ይናገራል። በዘካርያስ 1:4 ላይ ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንደዚህ ብሎ ተናግሯል” ወይም “እኔ የሠራዊት ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህንን ነው” (‘መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ሰው’ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 11

1 ሊባኖስ ሆይ፣ እሳት ዝግባሽን እንዲበላው በሮችሽን ክፈቺ! **2** የጥድ ዛፍ ሆይ፣ ዝግባ ውድቋልና አልቅስ! ግርማ የነበራቸው ዛፎች ጠፍተዋል! ጥቅጥቅ ያለው ደን ተመንጥሯልና እናንት የባሳን ወርካዎች ሆይ አልቅሱ። **3** ክብራቸው ጠፍቷልና እረኞች ሆይ ጩኹ! **4** አምላኬ ያህዌ እንዲህ ይላል፣ “ለእርስ የተለዩትን በጎች እንደ እረኛ አሰማራ! **5** የሚገዟቸው ያርዷቸዋል ሳይቀጡም ይቀራሉ፤ የሚሸጧቸውም፣ “ሀብታም ሆኛለሁና ያህዌ ይመስገን” ይላሉ። እረኞቻቸው እንኳ አይራሩላቸውም። **6** ከእንግዲህ እኔም በምድሪቱ ለሚኖረው ሕዝብ አልራራም! ይህ የያህዌ ዐዋጅ ነው። እኔ ራሴ ሰውን ሁሉ ለባልንጀራውና ለንጉሡ እጅ አሳልፌ እሰጣለሁ። እነርሱ ምድሪቱን ያስጨንቃሉ። ይሁዳንም ከእጃቸው አልታደገውም።” **7** ስለዚህ እኔ ለእርድ ለተለዩትና ለተጨቆኑት እረኛ ሆንሁ። ሁለት በትሮች ወስጄ እንዱን፣ “ሞገስ” ሌላውንም፣ “አንድነት” ብዬ ጠራኋቸው። መንጋውንም አሰማራሁ። **8** በአንድ ወር ውስጥ ሦስቱን እረኞች አስወገድሁ፤ ትዕግሥቴ አለቀ፤ እነርሱም እንዲሁ እኔን ጠሉኝ። **9** ከዚያም ለበጎቹ ባለቤቶች፣ “ከእንግዲህ እረኛችሁ አልሆንም፤ የሚሞቱ በጎች ይሙቱ፤ የሚጠፉት በጎች ይጥፉ። የቀሩትም አንዱ የሌላውን ሥጋ ይብላ” አልኋቸው። **10** ከዚያም፣ ከነገዶቼ ሁሉ ጋር ያደረግሁት ኪዳን መቋረጡን ለማመልከት፣ “ሞገስ” የተባለው በትሬን ሰበርሁ። **11** በዚያ ቀን ኪዳኑ ፈረሰ፣ ብጎቹን ያስጨነቁትና ሲመለከቱኝ የነበሩትም ያህዌ እንደ ተናገረ አወቁ። **12** እኔም፣ “መልካም መስሎ ከታያችሁ ደመወዜን ክፈሉኝ፤ ካልመሰላችሁም ተዉት” አልኋቸው። ስለዚህ ሰላሣ ብር ከፈሉኝ። **13** ያህዌም፣ “ሊከፍሉህ የተስማሙትን ጥሩ ዋጋ ሰላሣ ብሩን ግምጃ ቤት ውስጥ አኑረው” አለኝ። ስለዚህም ሰላሣውን ብር ወስጄ በሃህዌ ቤት ባለው ግምጃ ቤት ውስጥ አኖሩሁት። **14** ከዚያም በይሁዳና በእስራኤል መካከል የነበረው ወንድማማችነት መፍረሱን ለማመልከት፣ “አንድነት” የተባለው ሁለተኛውን በትሬን ሰበርሁት። **15** ያህዌም እንዲህ አለኝ፤ “እንደ ገና የሰነፍ እረኛ ዕቃ ውሰድ፣ **16** እነሆ እኔ በምድሪቱ ላይ እረኛ ላስነሣ ነው። እርሱም ለጠፋው በግ አያስብም፤ የባዘነውን በግ አይፈልግም፤ የተሰበረውን አይጠግንም፤ ጤነኛውን አይመግብም፤ ሆኖም፣ የሰባውን ሥጋ ይበላል፤ ሰኮናው እንኳ ሳይቀር ይቀለጣጥማል። **17** መንጋውን ለሚተው እረኛ ወዮለት! ሰይፍ ክንዱንና ቀኝ ዐይኑን ይውጋ! ክንዱ ፈጽማ ትሰልል፤ ቀኝ ዐይኑም ጨርሶ ትታወር!”

Zechariah 11:1

ሊባኖስ ሆይ፣ እሳት እንዲያወድማቸው በሮችሽን ክፈቺ
ሊሆን ያለውን መቋቋም አለመቻሉ ሊባኖስ በሮችዋን እንደምትከፍት ሆኖ እየተነገረ ነው። እዚህ ላይ ‘ሊባኖስ’ የሊባኖስን ሕዝብ የሚወክል ስመ-መስል ስያሜ ነው። አት. “የሊባኖስ ሕዝብ ሆይ፣ እሳት ሊያወድም ስለሆነ ተዘጋጁ” ወይም “የሊባኖስ ሕዝብ ሊያወድም ያለውን እሳት ለማስቆም አትሞክሩ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ስመ-ምስል ስያሜ የሚሉትን ይመልከቱ)

እሳት ዝግባዎችሽን እንዲያወድም
እሳት ዝግባዎችን ፈጽሞ ማቃጠሉ እሳት ዝግባዎቹን እንደሚያወድም ተደርጎ ተነግሯል። አት. “እሳት ሙሉ በሙሉ ዝግባዎችሽን እንዲያወድም” ወይም “እሳት ሙሉ በሙሉ ዝግባዎችሽን እንዲያቃጥል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የጥድ ዛፎች ሆይ፣ የዝግባ ዛፎች ወድቀዋልና አልቅሱ
የጥድ ዛፎች እንደ ሰው እንደሚያዝኑ ተደርገው ተነግረዋል። አት. “ዛፎች ሰዎች ቢሆኑ ኖሮ በኃዘን ያለቅሱ ነበር። ዝግባዎቹ ስለተቃጠሉና ስለወደቁ የጥድ ዛፎቹ ለብቻቸው ቆመዋል።” (ሰውኛ የሚለውን ይመልከቱ)

የከበሩትም ጠፍተዋል
ይህ በተናጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት. “ግርማ ያላቸው የዝግባ ዛፎች ከእንግዲህ የሉም” ወይም “የዝግባ ዛፎቹ በአንድ ወቅት ግርማ ያላቸው ነበሩ፣ አሁን ግን ጠፍተዋል።” (ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚለውን ይመልከቱ)

የባሳን ወርካዎች ሆይ፣ አልቅሱ፣ ጠንካራ የነበረው ደን ጠፍቶአልና
የባሳን ወርካዎች እንደ ሰው እንደሚያዝኑ ተደርገው ተነግረዋል። አት. “ጥቅጥቅ ያሉት ደኖቻቸው ስለተመነጠሩ፣ የባሳን ወርካዎች ሰዎች ቢሆኑ ኖሮ ያለቅሱ ነበር።” (ሰውኛ የሚለውን ይመልከቱ)

እረኞች ዋይ ይላሉ
“እረኞች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ያለቅሳሉ”

ክብራቸው ተገፎአልና
እዚህ ላይ ‘ክብራቸው’ የሚለው ምናልባት እረኞች በጎቻቸውን የሚያሰማሩባቸውን ለምለም ግጦሽ የሚወክል ሳይሆን አይቀርም። አት. “ለምለም ግጦሾቻቸው ጠፍተዋልና” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

የዮርዳኖስ ወንዝ ትዕቢት ወድሟል
እዚህ ላይ ‘ትዕቢት’ ምናልባት የሚለው በዮርዳኖስ ወንዝ አጠገብ የበቀሉትን ደኖች የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም። አት. “ይኖሩባቸው በነበሩት በዮርዳኖስ ወንዝ አጠገብ የነበሩት ዛፎችና ቁጥቋጦዎች ስለወደሙ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 11:4

አጠቃላይ መረጃ
በ11:4-17 የሁለት እረኞች ታሪክ ቀርቧል። ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፡ -1)ያህዌ ሕዝቡን እንዴት እንደሚይዝ ለመግለጽ በተምሳሌታዊ ተግባር ዘካርያስ የአንድ መንጋ እረኛ ይሆናል። 2)ያህዌ ሕዝቡን እንዴት እንደሚይዝ ለማስተማር ዘካርያስ ምሳሌ ይናገራል። ከእነዚህ ሁለት ትርጉሞች የትኛው ትክክል እንደሆነ እርግጠኛ ስላልሆነ፣ በትርጉም ወቅት ማንኛውንም ትርጉም አለመወሰን መልካም ይሆናል። (ተምሳሌታዊ ተግባር እና ምሳሌዎች የሚሉትን ይመልከቱ)

ለዕርድ የተለዩትን መንጋዎች ጠብቅ
“ባላቤቶቻቸው ለዕርድ ያቀዷቸውን በጎች ተንከባከብ”

አልተቀጡም
ይህ በተናጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት. “ማንም አይቀጣቸውም” (ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚለውን ይመልከቱ)

የምድሪቱ ነዋሪዎች
“የምድሩ ሕዝብ”

ያህዌ ... እንዲህ ይላል
እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ ያህዌ ስለ ራሱ ስሙን በመጥቀስ ይናገራል። በዘካርያስ 1:4 ላይ ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንደዚህ ብሎ ተናግሯል” ወይም “እኔ የሠራዊት ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህንን ነው” (‘መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ሰው’ የሚለውን ይመልከቱ)

ተመልከቱ
“አድምጡ” ወይም “ልብ አድርጉ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እኔ ራሴ
‘ራሴ’ የሚለው ቃል እነዚህን ነገሮች የሚያደርገው ይህዌ እንደሆነ አጽንዖት ለመስጠት ነው። (አጽንዖት የሚሰጡ ተወላጠ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰውን ሁሉ ለባልንጀራው እጅና ለንጉሡ እጅ አሳልፎ መስጠት
እዚህ ላይ ‘እጅ’ ኃይልን ወይም መቆጣጠርን ይወክላል። አት. “ሕዝቡ እርስ በርሳቸው እንዲጎዳዱ አደርጋለሁ፣ ንጉሡም ይጨቁናቸዋል።” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

ማናቸውንም ከእጃቸው አላድናቸውም
እዚህ ላይ ‘እጅ’ ኃይልን ወይም መቆጣጠርን ይወክላል። አት. “ከሚጎዷቸው አላድናቸውም” ወይም “አላድናቸውም” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 11:7

የበግ ንግድ የሚሠሩ
“በጎችን የሚገዙና የሚሸጡ”

ሞገስ
ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ይህንን ‘ፀጋ’፣ ‘ውበት’ እና ‘ደስ የሚል’ ብለው ይተረጉሙታል

በእነርሱ ምክንያት ትዕግሥት አጣሁ
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፡ - 1) ‘እነርሱ’ የሚለው ሶስቱን እረኞች ያመለክታል። ወይም 2) ‘እነርሱ’ የሚለው የበጎቹን ባለቤት ያመለክታል።

የሚጠፉት ይጥፉ
ይህ በተናጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል፡ - አት. “እያለቁ ያሉት በጎች ይለቁ” ወይም “የሚቅበዘበዙትና የሚጠፉት በጎች ይጥፉ” (ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 11:10

ኪዳኑ ፈርሶአል
ይህ በተናጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል፡ - አት. “ኪዳኑ አበቃ” (ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ እንደተናገረ አወቅሁ
በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት የሚመለከቱት በበትሩ መሰበር አማካይነት ያህዌ መልእክት እንደሰጣቸው አውቀው ነበር የሚል ነው። አት. “ያህዌ መልእክት እንደሰጣቸው አውቀዋል” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ሰላሳ የብር መክሊት
በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት ይህ ለእረኛ በጣም ዝቅተኛ ክፍያ ነው። አት. “ሰላሳ መክሊት ብር ብቻ” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ሰላሳ መክሊት
’30 መክሊቶች’ (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 11:13

አጠቃላይ መረጃ
ስለ እረኞችን ስለ በጎች የሚነገረው ምሳሌ ቀጥሏል።

ግምጃ ቤት
ይህ በያህዌ ቤተ መቅደስ ካህናቱ ገንዘብ የሚያስቀምጡበት ቦታ ነው። ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ይህንን ‘አንጥረኛ’ ብለው ይተረጉሙታል። ይሄ ሰው (አንጥረኛው) ዕቃዎችን (ድስቶችን፣ ማንቆርቆሪያዎችን) ለመሥራት ብረታ ብረትን የሚያቀልጥ ሰው ነው። እዚህ ላይ ያህዌ ክፍያው እጅግ ዝቅ ያለ በመሆኑ እረኛው ምን ያህል እንደተዋረደ ለመግለጽ ብሩን ያቀልጠዋል ማለት ፈልጎ ነው።

በጣም ጥሩ ዋጋ
የያህዌን ሥራ ለሚሠራ ይህ በጣም ዝቅተኛ ክፍያ ለመሆኑ እዚህ ላይ ያህዌ የሽሙጥ አነጋገር እየተጠቀመ ነው። አት. “ከሞኝነት የሚቆጠር እጅግ ዝቅ ያለ ገንዘብ” (ሽሙጥ የሚለውን ይመልከቱ)

በይሁዳና በእስራኤል መካከል
እዚህ ላይ ‘ይሁዳ’ በደቡባዊው መንግሥት የነበረው ሕዝብ፣ ‘እስራኤል’ ደግሞ በሰሜናዊው መንግሥት የነበረውን ሕዝብ ይወክላሉ። አት. “በይሁዳ ሕዝብና በእስራኤል ሕዝብ መካከል” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 11:15

አጠቃላይ መረጃ
ይህ በዘካርያስ 11፡4 ስለ ሁለቱ እረኞች የተጀመረውን ታሪክ ይቀጥላል። ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፡ - 1) ያህዌ ሕዝቡን እንዴት እንደሚይዝ ለመግለጽ በተምሳሌታዊ ተግባር ዘካርያስ የአንድ መንጋ እረኛ ይሆናል። 2)ያህዌ ሕዝቡን እንዴት እንደሚይዝ ለማስተማር ዘካርያስ ምሳሌ ይናገራል። ከእነዚህ ሁለት ትርጉሞች የትኛው ትክክል እንደሆነ እርግጠኛ ስላልሆነ፣ በትርጉም ወቅት ማንኛውንም ትርጉም አለመወሰን መልካም ይሆናል። (ተምሳሌታዊ ተግባር እና ምሳሌዎች የሚሉትን ይመልከቱ)

አንድን እረኛ በቦታው ላስቀምጥ ነው
እዚህ ላይ ‘በቦታው ማስቀመጥ’ ፈሊጣዊ አባባል ነው። አት. “በምድሪቱ እረኛን ልሾም ነው” ወይም “ኃላፊነት ያለውን እረኛ በምድሪቱ ላስቀምጥ ነው።” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

የሰባውን በግ
‘እጅግ የሰባውን በግ’ ወይም ‘ምርጥ የሆነውን በግ’

ሰኮናቸውን ይቀለጣጥማል
ይህ ምናልባት በክፋት የሚፈጸም ድርጊት ሳይሆን አይቀርም።

Zechariah 11:17

ሰይፍ
እዚህ ላይ ‘ሰይፍ’ ሕዝቡን የሚያጠቁትን ጠላቶች ይወክላል። አት. “ጠላቶች” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

በክንዱና በቀኝ ዓይኑ ላይ ይምጡበት
እዚህ ላይ ‘ይምጡበት’ የሚለው ፈሊጣዊ አባባል ነው። አት. “ቀኝ ክንዱን ያቁስሉት ደግሞም ቀኝ ዓይኑን ይውጉት” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ክንዱ
የእርሱ ‘ክንድ’ የመዋጋት ኃይሉን ይወክላል። (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀኝ ዓይኑ
አንድ ወታደር ቀኝ ዓይኑን በግራ እጁ በያዘው ጋሻ ዙሪያ ያለውን ለማየት ይጠቀምበታል። ቀኝ ዓይኑ ከቆሰለ በጦርነት ጊዜ ለመዋጋት መመልከት አይችልም። (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ክንዱ ትስለል
“ክንዱ ትበስብስ” ወይም “ክንዱ ፈጽማ ከጥቅም ውጪ ትሁን”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 12

1 ስለ እስራኤል የተነገረው የያህዌ ቃል ዐዋጅ ይህ ነው። ሰማያትን የዘረጋ፣ ምድርን የመሠረተ፣ የሰውን መንፈስ የሠራ ያህዌ እንዲህ ይላል፣ **2** “ኢየሩሳሌምን በዙሪያዋ ያሉትን ሕዝቦች ሁሉ የሚያንገዳግድ ጽዋ አደርጋታለሁ። ኢየሩሳሌም በምትከበብበት ጊዜ ይሁዳም ላይ እንደዚያው ይሆናል። **3** በዚያ ቀን ኢየሩሳሌምን አሕዛብ ሁሉ ላይ ከባድ ድንጋይ አደርጋታለሁ። ያንን ድንጋይ ማንቀሳቀስ የሚሞክር ሁሉ ክፉኛ ይጎዳል፤ የምድር ሕዝቦች ሁሉ በዚያች ከተማ ላይ ይሰበሰባሉ። **4** በዚያ ቀን፣ ፍረሱን ሁሉ በሽብር፣ የተቀመጠበትንም ሁሉ በእብደት እመታለሁ። የይሁዳን ቤት በምሕረት አያለሁ፤ የጠላትን ፈረስ ሁሉ አሳውራለሁ። **5** በዚያ ጊዜ የይሁዳ መሪዎች በልባቸው፣ የሰራዊት ጌታ ያህዌ አምላካቸው ስለ ሆነ የኢየሩሳሌም ሕዝቦች ብርታታችን ናቸው!” ይላሉ። **6** በዚያ ቀን የይሁዳን መሪዎች በእንጨት ክምር ውስጥ እንዳለ የእሳት ምድጃ በነዶም መካከል እንዳለ ችቦ ነበልባል አደርጋለሁ፤ በቀኝና በግራ ዙሪያውን ያሉትን ሕዝቦች ይበላሉ፤ ኢየሩሳሌምም እንደ ገና ከምድሯ ትኖራልች። **7** የዳዊት ቤትና የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ክብር ከይሁዳ ክብር እንዳይበልጥ፣ በዚያ ቀን ያህዌ በመጀመሪያ የይሁዳን መኖሪያዎች ያድናል። **8** በዚያ ቀን ያህዌ የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ከለላ ይሆናል፤ በዚያ ቀን በመካከላቸው ያለው ደካማው እንደ ዳዊት፣ የዳዊት ቤትም በፊታቸው እንደ አምላክ፣ እንደ ያህዌም መልአክ ይሆናል። **9** በዚያ ቀን ኢየሩሳሌም ላይ የሚነሡ ሕዝቦችን ሁሉ ማጥፋት እጀምራለሁ። **10** በዚያ ቀን በዳዊት ቤትና በኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ላይ የርኅራኄና የልመናን መንፈስ አፈስሳለሁ፣ ወደ ወጉኝ ወደ እኔ ይመለክታሉ፤ እነርሱም ለአንድ ልጁ እንደሚያለቅስ ሰው ያለቅሱልኛል፤ ለበኩር ልጁ ሞት እንደሚያለቅስ ሰው ምርር ብለው ያለቅሳሉ። **11** በዚያ ቀን ኢየሩሳሌም ውስጥ የሚሆነው ለቅስ በመጊዶ ሜዳ ለሐዳድ ሪሞን እንደ ተለቀሰው ታላቅ ለቅሶ ይሆናል። **12** ምድሪቱ ታለቅሳለች፤ የእያንዳንዱ ወገን ቤተ ሰብ ለየራሱ ያለቅሳል። የዳዊት ቤት ወገን ወንዶች ከነሚስቶቻቸው፣ የናታን ቤት ወገን ወንዶች ከነሚስቶቻቸው፣ **13** የሌዊ ቤት ወገን ወንዶች ከነሚስቶቻቸው፣ የሰማኢ ቤት ወገን ወንዶች ከነሚስቶቻቸው፣ **14** የቀሩትም ወገኖች ወንዶች ሁሉ ከነሚስቶቻቸው ያለቅሳሉ።

Zechariah 12:1

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ጥቅሶች በኢየሩሳሌም ላይ ሊመጣ ያለውን ጥቃትና እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያድናቸው የሚናገረውን ክፍል ይጀምራል።

ይህ እስራኤልን በሚመለከት የያህዌ ቃል እወጃ ነው
“ይህ እስራኤልን በሚመለከት ያህዌ ያወጀው መልእክት ነው”

ሰማያትን የዘረጋ
ይህ ሰማይ እንደ ብራና የተጠቀለለና መዘርጋት እንደሚያስፈልገው የሚናገር ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አት. “ሰማይን የፈጠረ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የምድርን መሠረት ያስቀመጠ
ይህ ምድርን መሠረት እንዳለው ሕንፃ አድርጎ የሚናገር ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አት. “ምድርን በሞላ በስፍራው የሚያስቀምጥ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰው ውስጥ የሰውን ልጅ መንፈስ የቀረጸ
ይህ መንፈስን ሸክላ ሠሪ እንደሚቀርጸው ሸክላ አድርጎ የሚናገር ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አት. “የሰውን ልጅ መንፈስ የሚፈጥር”

ኢየሩሳሌምን የሚያንገዳግድ ጽዋ አደርጋታለሁ
ያህዌ ኢየሩሳሌምን ለመቅጣት እንደሚጠብቃት ማድረጉን ኢየሩሳሌምን የአልኮል መጠጥ እንደሚያደርጋትና በአካባቢው ያሉት ሕዝቦች ጠጥተዋት እንደሚንገዳገዱ አድርጎ እየተናገረ ነው። አት. “በቅርቡ ኢየሩሳሌምን የምታንገዳግድ ጽዋ እንደማደርጋት ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ጽዋነት
እዚህ ላይ ‘ጽዋ’ ጽዋውንና በጽዋ ውስጥ ያለውን ይወክላል። አት. “በወይን ጠጅ ወደተሞላ ጽዋነት” ወይም “በአልኮል መጠጥ እንደተሞላ ጽዋ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሷን የከበቧት
እዚህ ላይ ‘እርሷን’ የሚለው የሚያመለክተው ኢየሩሳሌምን ነው። በዕብራውያን ዘንድ አንድ አገር ወይም አንድን ከተማ ሴት እንደሆነች አድርጎ መናገር የተለመደ ነው። (ሰውኛ የሚለውን ይመልከቱ)

ኢየሩሳሌምን ለሕዝቦች ሁሉ ከባድ ዐለት አደርጋታለሁ
ያህዌ ኢየሩሳሌምን የአካባቢውን ሕዝቦች ለመቅጫ መጠቀሙ ኢየሩሳሌምን ከባድ ዐለት እንደሚያደርጋት ተደርጎ ተነግሯል። አት. “ኢየሩሳሌምን ለሕዝቦች ከባድ ዐለት እንደማደርጋት ያለ ይሆናል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 12:4

የትርጉም ማስታወሻዎች
እነዚህ ጥቅሶች በኢየሩሳሌም ላይ ሊመጣ ያለውን ጥቃትና እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያድናቸው መናገር ይቃጥላሉ።

በዚያን ቀን
“ሠራዊቱ ኢየሩሳሌምን በሚያጠቁበት ጊዜ”

ያህዌ ... እንዲህ ይላል
እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ ያህዌ ስለ ራሱ ስሙን በመጥቀስ ይናገራል። በዘካርያስ 1:3 ላይ ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንደዚህ ብሎ ተናግሯል” ወይም “እኔ የሠራዊት ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህንን ነው” (‘መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ሰው’ የሚለውን ይመልከቱ)

በይሁዳ ቤት ላይ ዓይኖቼን እከፍታለሁ
እዚህ ላይ በአንድ ሰው ላይ ዓይንን መክፈት ለዚያ ሰው በጎ ለማድረግ መፈለግን የሚገልጽ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አት. “ለይሁዳ በጎ ነገርን አደርጋለሁ” ወይም “የይሁዳን ቤት እጠብቃለሁ” ([[rc://*/ta/vol.1/translate/fig/metaphor]] ይመልከቱ)

የይሁዳ ቤት
እዚህ ላይ ‘ቤት’ የሚወክለው ሕዝብን ነው። አት. “የይሁዳ ሕዝብ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

በልባቸው እንደዚህ የሚሉ
እዚህ ላይ ‘በልባቸው’ የሚለው የአንድን ሰው ሃሳብ ይወክላል። አት. “ለራሳቸው የሚያስቡ” ወይም “ለራሳቸው የሚሉ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ብርታታችን ናቸው
የነገር ስም የሆነው ‘ብርታት’ ‘ጠንካራ’ ወይም ‘ማደፋፈር’ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። አት. “ጠንካራ አድርገን” ወይም “አደፋፍረን” (የነገር ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የሠራዊት ጌታ ያህዌ፣ አምላካቸው
“የሠራዊት ጌታ ያህዌ፣ የሚያመልኩት አምላካቸው”

Zechariah 12:6

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ጥቅሶች በኢየሩሳሌም ላይ ሊመጣ ያለውን ጥቃትና እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያድናቸው መናገር ይቃጥላሉ።

በእንጨት መካከል እንዳለ የእሳት ምድጃ ... በነዶም መካከል
ይህ ምስስሎሽ ያህዌ የይሁዳን መሪዎች ጠንካሮች እንዲሆኑና ሕዝባቸውም ጠላቶቻቸውን ድል ወደ ማድረግ እንዲመሩ ያስችላቸዋል ማለት ነው። አት. “በተከመሪ እንጨት መካከል እንደ እሳት ምድጃ ... በእርሻ ውስጥ የቆመ ያልታጨደ ነዶ” (ምስስሎሽ የሚለውን ይመልከቱ)

የእሳት ምድጃ
የጥንት ሰዎች የሚነድ ከሰልን ይዘው የሚሄዱባቸው የሸክላ ማሰሮዎች

የፋና ነበልባል
በአንድ ጫፍ በኩል የሚነድና አንድ ሰው በሚጓዝበት ጊዜ ብርሃን የሚሰጥ ወይም እሳትን አንድ ሌላ ስፍራ የሚያደርስ

በዙሪያው ያሉትን ሰዎች ይበላል
ሰዎቹን ፈጽሞ መደምሰስ የይሁዳ ሰዎች ሰዎቹን እንደሚበሏቸው ተደርጎ ተነግሯል። አት. “የአካባቢውን ሕዝቦች ያጠፋሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በቀኛቸውና በግራቸው
እዚህ ላይ ‘ቀኝ’ እና ‘ግራ’ የሚለው በሁሉም አቅጣጫ የሚለውን ይወክላል። አት. “በሁሉም አቅጣጫ” (... የሚለውን ይመልከቱ)

ኢየሩሳሌም በድጋሚ በስፍራዋ ትቀመጣለች
እዚህ ላይ ‘ኢየሩሳሌም’ በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላል። አት. “የኢየሩሳሌም ሕዝቦች እንደገና በራሳቸው ከተማ ይኖራሉ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 12:7

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ጥቅሶች በኢየሩሳሌም ላይ ሊመጣ ያለውን ጥቃትና እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያድናቸው መናገር ይቃጥላሉ።

የይሁዳ ድንኳኖች
እዚህ ላይ ‘ድንኳኖች’ ቤቶችን ይወክላሉ፣ ቤቶች ደግሞ በውስጣቸው የሚኖሩ ሰዎችን ይወክላሉ። አት. “የይሁዳ ሕዝብ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

የዳዊት ቤት
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፡ - 1)የዳዊት ዝርያዎች ወይም 2)የሕዝቡ የገዢ መደብ (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእነርሱ መካከል ደካማው እንደ ዳዊት ይሆናል
ይህ ምስስሎሽ ደካሞች የሆኑት ጠንካሮች ይሆናሉ የሚል ትርጉም አለው። አት. “ደካሞች የሆኑት እንደ ዳዊት ብርቱዎች ይሆናሉ” (ምስስሎሽ የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌ መልአክ
ይህ ሕዝቡን እንዲጠብቅ በያህዌ የተላከ መልአክ ነው።

Zechariah 12:10

በዳዊት ቤትና በኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ላይ የርህራሄና የልመናን መንፈስ አፈሳለሁ
ሕዝቡ ርህሩህ እንዲሆኑና እንዲለምኑ መደረጋቸው መንፈሱ በእነርሱ ላይ የሚያፈሰው ፈሳሽ እንደሆነ ተደርጎ እየተነገረ ነው። አት. “የዳዊት ቤትና የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ለሌሎች ምሕረት የሚያደርጉ እንዲሆኑና ምሕረት እንዳደርግ ወደ እኔ የሚጸልዩ እንዲሆኑ አደርጋቸዋለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የርህራሄና የልመና መንፈስ
እዚህ ላይ ይህ የርህራሄና የልመና ባሕርይ ይኖራቸዋል ማለት ነው።

የዳዊት ቤት
እዚህ ላይ ‘ቤት’ ዝርያዎችን ይወክላል። አት. “የዳዊት ዝርያዎች” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

የወጉትን
“በስለት ወግተው የገደሉትን”

ለአንድያ ልጅ
‘ልጁ’ ሞቷል የሚል ግንዛቤ አለ። አት. “ለሞተው አንድያ ልጅ” (ግድፈት የሚለውን ይመልከቱ)

በኢየሩሳሌም የሚደረገው ልቅሶ ለሐዳድ ሪሞን እንደተደረገው ልቅሶ ይሆናል
ሐዳድ ሪሞን መልካሙ ንጉሥ ኢዮስያስ ከመጊዶ ጦርነት በኋላ በደረሰበት የጦርነት ቁስል የሞተበት ስፍራ ሊሆን ይችላል። በዚያ ስፍራ ስለ እርሱ ሞት በየተወሰኑ ወቅቶች የማልቀስ ልማድ የነበረ ይመስላል። ይሁን እንጂ፣ አንዳንድ ሰዎች ሐዳድ ሪሞን በየዓመቱ እንደሚሞት የሚታመን የሐሰት አምላክ ስም ነው ብለው የሚያስቡ ሲሆን፤ ይህም ኩነት አምላኪዎቹን እንዲያለቅሱ ያደርጋቸዋል። (ስሞችን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ፣ ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

መጊዶ
ይህ በእስራኤል የሚገኝ ሜዳ ስም ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 12:12

ምድሪቱ ታለቅሳለች
ይህ በይሁዳ ምድር የሚኖሩትን ሕዝቦች ሁሉ ይወክላል። አት. “በይሁዳ ምድር የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ያለቅሳሉ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

የዳዊት ቤት ነገድ ... የናታን ቤት ነገድ ... የሌዊ ቤት ነገድ
እዚህ ላይ ‘ቤት’ ዝርያዎችን ይወክላል። አት. “የዳዊት ዝርያዎች” ... “የናታን ዝርያዎች” ... “የሌዊ ዝርያዎች” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 13

1 በዚያ ቀን የዳዊትን ቤትና የኢየሩሳሌም ነዋሪዎችን ኀጢአትና ርኩሰት የሚያነጻ ምንጭ ይከፈታል። **2** በዚያ ቀን ከእንግዲህ አስታዋሽ እንዳይኖራቸው የጣዖቶችን ስሞች ከምድሪቱ አጠፋለሁ ይላል የሰራዊት ጌታ ያህዌ። ሐሰተኛ ነቢያትንና ርኩሳን መናፍስቶቻቸውም ከምድሪቱ ይወገዳሉ። **3** ማንም ትንቢት ቢናገር ወላጅ አባት እናቱ፣ “በያህዌ ስም ሐሰት ተናግረሃልና ትሞታለህ!” ይሉታል። ትንቢት ሲናገርም የገዛ ወላጆቹ ይወጉታል። **4** በዚያ ቀን እያንዳንዱ ነቢይ ስለሚናገረው ትንቢት ራእይ ያፍራል። እነዚህ ነቢያት ሕዝቡን ለማታለል ከእንግዲህ ጠጕራም ልብስ አይለብስም። **5** እያንዳንዱ፣ “እኔ ገበሬ እንጂ፣ ነቢይ አይደለሁም፤ ከልጅነቴ ጀምሮ ኑርዬ የተመሠረተውም በዚሁ ነበር!” ይላል። **6** ሌላውም መልሶ፣ “ታዲያ፣ ክንዶችህ” መካከል ያሉት እነዚህ ቁስሎች ምንድናቸው?” በማለት ቢጠይቀው፣ “በባልንጀሮቼ ቤት ሳለሁ ያቆሰልሁት ነው” በማለት ይመልሳል። **7** “ሰይፍ ሆይ፣ በእረኛ፣ ለእኔ ቅርብ በሆነው ላይ ተነሣ ይላል የሰራዊት ጌታ ያህዌ። እረኛውን ምታው በጎቹም ይበተናሉ! እኔም ክንዴን በታናናሾች ላይ አዘራለሁ። **8** የምድሩ ሁሉ ሁለት ሦስተኛው ተመትቶ ይጠፋል! ሰዎች ይሞታሉ አንድ ሦስተኛው ብቻ ይተርፋል ያላል ያህዌ። **9** እንደ ብር እንደነጹ፣ ያንን አንድ ሦስተኛ ሕዝብ በእሳት ውስጥ አሳልፋለሁ፤ ወርቅ እንደሚፈተን እፈትናቸዋለሁ። ስሜን ይጠራሉ፣ እኔም እመልስላቸዋለሁ ‘ይህ ሕዝቤ ነው’ እላለሁ፤ እነርሱም፣ “ያህዌ አምላኬ ነው!” ያላሉ።

Zechariah 13:1

ከኃጢአትና ከርኩሰተ የሚያነጻ ምንጭ ይከፈታል
የሕዝቡ ኃጢአት ይቅር መባሉ በተከፈተ የውሃ ምንጭ ኃጢአታቸው እንደሚታጠብላቸው ሆኖ ተነግሯል። ይህ በተናጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት. “ኃጢአታቸውንና ርኩስታቸውን የሚያነጻ ምንጭ እንደሚከፈት ያለ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚሉትን ይመልከቱ)

ምንጭ
ከመሬት ውሰጥ ውሃ በተፈጥሮ የሚፈልቅበት ቦታ

የይሁዳ ቤት
እዚህ ላይ ‘ቤት’ የሚወክለው ዝርያዎችን ነው። አት. “የይሁዳ ዝርያዎች” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ ... እንዲህ ይላል
እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ ያህዌ ስለ ራሱ ስሙን በመጥቀስ ይናገራል። በዘካርያስ 1:3 ላይ ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንደዚህ ብሎ ተናግሯል” ወይም “እኔ የሠራዊት ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህንን ነው” (‘መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ሰው’ የሚለውን ይመልከቱ)

የጣዖታቱን ስም ከምድሪቱ እቆርጣለሁ
ሕዝቡ ከእንግዲህ የጣዖታቱን ስም እንዳይጠሩ መደረጋቸው ያህዌ “የጣዖታቱን ስም ከምድሪቱ” እንደሚቆርጥ ተደርጎ ተነግሯል። አት. “ሕዝቡ ከእንግዲህ የጣዖታቱን ስም እንዳይጠሩ አደርጋቸዋለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህ አይታወሱም
ይህ በተናጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል፡ - አት. “ከእንግዲህ ስለ ጣዖታት እንዳያስቡ” (ፈሊጣዊ አባባል እና ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚሉትን ይመልከቱ)

ነቢያትንና የርኩሰት መንፈስን ከምድሪቱ አስወግዳለሁ
ነቢያት የሚለው ‘የሐሰት ነቢያት’ን ሊያመለክት ይችላል። የርኩሰት መንፈስ በአካላዊ ሁኔታ የቆሸሸ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አት. “ከምድሪቱ የሐሰት ነቢያትንና ርኩስ መንፈሳቸውን አስወግዳለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 13:3

መተንበይ
በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት ይህ የሐሰት ትንቢቶች ናቸው። አት. “በሐሰት ትንቢት መናገር” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

የወለዱት አባቱና እናቱ
የአንድ ሰው የራሱ ወላጆች ልጃቸውን እንደዚህ በማድረጋቸው የተሰማን አድናቆት ለመግለጽ ‘የወለዱት’ የሚለው ቃል ‘አባቱና እናቱ’ የሚለውን ይገልጻል። አት. “የራሱ አባትና እናት” (መለየት ከማስታወቅ ወይም ከማስታወስ ጋር ሲነጻጸር የሚለውን ይመልከቱ)

አትኖሩም
ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊገለጽ ይችላል፡ -አት. “መሞት ይገባችኋል”

በያህዌ ስም ሐሰት ተናግረሃል
በአንድ ሰው ስም መናገር በእርሱ ኃይልና ሥልጣን መናገር ወይም የእርሱ ወኪል ሆኖ መናገር ማለት ነው። አት. “በያህዌ ስም እንናገራለን ትላላችሁ፣ ነገር ግን ሐሰት ትናገራላችሁ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

ይወጉታል
“ወግተው ይገድሉታል”

Zechariah 13:4

እያንዳንዱ ነቢይ
ይህ ሐሰተኛ ነቢያትን ያስገነዝባል። አት. “ማንኛውም ሐሰተኛ ነቢይ” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ጠጕራም ልብስ አይለብስም
ነቢያት ብዙውን ጊዜ ከእንሰሳት ጠጕር የተሠራ ከበድ ያለ ልብስ በላያቸው ይደርቡ ነበር። (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከአፈር ጋር የተያያዘ ሥራ የምሠራ ነኝ “ገበሬ ነኝ” ገና ልጅ ሳለሁ ሥራዬ ከምድሩ ጋር የተያያዘ ነበር
ገበሬ የሆንኩት ገና ልጅ ሳለሁ ነበር። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ይህንን፡ -“ልጅ ሳለሁ አንድ ሰው ባሪያ እንድሆን ሸጠኝ” እንደሚል አድርገው ይተረጉሙታል።

በክንድህ መካከል ያሉት ቁስሎች ምንድን ናቸው?
“በደረትህ ላይ ያሉት እነዚያ ቁስሎች እንዴት ሊደርሱብህ ቻሉ?” ይህ ሐሰተኛ ነቢያት በሥርዓቶቻቸው ወቅት ራሳቸውን ሲያቆስሉ የነበሩበትን ግልጽ ልማድ ያመለክታል። (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

እንዲህ ብሎ ይመልሳል
በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት የሚሰጠው ምላሽ ውሸት ነው። አት. “እንዲህ በማለት ውሸት ይነግረዋል” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Zechariah 13:7

አጠቃላይ መረጃ
ዘካርያስ ብዙውን ጊዜ ትንቢትን በሥነ-ግጥም መልክ ጽፏል። የዕብራውያን ሥነ-ግጥም የተለያዩ ትይዩነቶችን ይጠቀማል። (ሥነ-ግጥም እን ትይዩነት የሚሉትን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ላይ ያህዌ መናገር ይጀምራል።

ሰይፍ ሆይ፣ በእረኛዬ ላይ ተነሥ
“አንተ ሰይፍ፣ ሂድና በእረኛዬ ላይ ጥቃት ፈጽም” እዚህ ላይ ያህዌ እንደ ሰው አድርጎ ለሰይፉ ይናገራል። እዚህ ላይ ጠላቶችን ይወክላል። አት. “እናንተ ጠላቶች፣ ሂዱና በእረኛዬ ላይ ጥቃት ፈጽሙ።” (ሰውኛ የሚለውን ይመልከቱ)

እረኛዬ
ይህ የእግዚአብሔር አገልጋይ እረኛ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አት. “እንደ እረኛ የሆነው አገልጋዬ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በአጠገቤ የቆመው ሰው
ይህ ፈሊጣዊ አባባል ነው። አት. “የቅርብ ወዳጄ የሆነው ሰው” ወይም “ባልንጀራዬ የሆነው ሰው” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ ... እንዲህ ይላል
እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ ያህዌ ስለ ራሱ ስሙን በመጥቀስ ይናገራል። በዘካርያስ 1:3 ላይ ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንደዚህ ብሎ ተናግሯል” ወይም “እኔ የሠራዊት ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህንን ነው” (‘መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ሰው’ የሚለውን ይመልከቱ)

መንጋው ይበተናል
የእግዚአብሔር ሕዝብ መንጋ እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል። አት. “ሕዝቤ እንደ በጎች ይሸሻሉ።” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በታናናሾች ላይ እጄን አዞራለሁ
“እጅን ማዞር” የሚለው ፈሊጣዊ አባባል በአንድ ሰው ላይ በጠላትነት መነሳት የሚል ትርጉም አለው። አት. “ታናናሾችን አጠቃለሁ።” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ታናናሾች
ይህ ምናልባት ደካማና የሚከላከልላቸው የሌላቸውን እስራኤላውያንን ሁሉ የሚመለከት ሳይሆን አይቀርም።

Zechariah 13:8

ያህዌ ... እንዲህ ይላል
እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ ያህዌ ስለ ራሱ ስሙን በመጥቀስ ይናገራል። በዘካርያስ 1:3 ላይ ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንደዚህ ብሎ ተናግሯል” ወይም “እኔ የሠራዊት ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህንን ነው” (‘መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ሰው’ የሚለውን ይመልከቱ)

ከሕዝቡ አንድ ሶስተኛው ተመትቶ ይጠፋል፣ አንድ ሶስተኛው ብቻ ይቀራል
እየተገደሉት ያሉት ሰዎች ከልብስ ላይ ጨርቅ እንደሚቀደድ ወይም ከዛፍ ላይ ቅርንጫፍ እንደሚሰበር ተደርገው ተነግረዋል። አት. “ከሶስት ሰዎች ሁለቱ ይሞታሉ። ከሶስት ሰዎች አንዱ ብቻ በምድሪቱ ይቀራል።” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ክፍልፋዮች የሚሉትን ይመልከቱ)

ያንን ሲሶ (አንድ ሶስተኛ) በእሳት ውስጥ አሳልፈዋለሁ
ብረታ ብረት እንዲጠራ ወይም እንዲጠነክር በእሳት ውስጥ ያልፋል። ይህ አገላለጽ እዚህ ላይ ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ይበልጥ ታማኞች ይሆኑ ዘንድ በመከራ ውስጥ ማለፋቸውን የሚገልጽ ተለዋጭ ዘይቤ በመሆን ያገለግላል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ብር እንደሚጠራ አጠራቸዋለሁ፣ ወርቅ እንደሚፈተን እፈትናቸዋለሁ
ማጥራት እንደ ብር ያሉ የከበሩ ብረታ ብረቶችን ይበልጥ የጠሩ ማድረግን ያመለክታል። እንደ ብርና እንደ ወርቅ ያሉት ምን ያህል የጠሩና ጠንካራ መሆናቸውን ለማወቅ ይፈተናሉ። እዚህ ላይ ማጥራትና መፈተን ሁለቱም ሕዝቡ ይበልጥ ለእግዚአብሔር ታማኞች እንዲሆኑ ተለዋጭ ዘይቤ አገላለጾች ናቸው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ስሜን ይጠራሉ
እዚህ ላይ ‘ስም’ የሚለው ያህዌን ይወክላል። ትኩ. “ወደ እኔ ይጣራሉ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 14

1 እነሆ፣ ብዝበዛሽን በውስጥሽ የሚከፋፈሉበት ቀን ይመጣል። 2 ሕዝብን ሁሉ ለጦርነት ኢየሩሳሌም ላይ አስነሣለሁ፤ ከተማዋም ትያዛለች። ቤቶች
ይበዘበዛሉ፣ ሴቶች ይነወራሉ። የከተማው ግማሽ ሕዝብ በምርኮ ይወሰዳል፤ የተቀረው ሕዝብ ግን ከከተማው አይጠፋም። 3 ነገር ግን በጦርነት ጊዜ
እንደሚዋጋ ያህዌ እነዚያን ሕዝቦች ይዋጋል። 4 በዚያ ጊዜ እግሮቹ ከኢየሩሳሌም በስተ ምሥራቅ ባለው ደብረ ዘይት ተራራ ይቆማሉ። የደብረ ዘይት ተራራ
በመካከሉ ባለው ታላቅ ሸለቆ ወደ ምሥራቅና ምዕራብ ለሁለት ይከፈልና እኩሌታው ወደ ሰሜን፣ እኩሌታው ወደ ደቡብ ይሄዳሉ። 5 እናንተም በያህዌ ተራሮች
መካከል ባለው ሸለቆ በኩል ታመልጣላችሁ፤ በእነዚህ ተራሮች መካከል ያለው ሸለቆ እስከ አጸል ይደርሳል። በይሁዳ ንጉሥ በዖዝያን ዘመን ከነበረው የመሬት
መንቀጥቀጥ እንደ ሸሻችሁ ትሸሻላችሁ። ያኔ አምላኬ ያህዌ ይመጣል፤ ከእርሱም ጋር ቅዱሳኑ ይመጣሉ። 6 በዚያ ቀን ብርሃን አይኖርም፣ ብርድና ውርጭም
አይኖርም። 7 በዚያ በእግዚአብሔር ብቻ በሚታወቅ ቀን ቀንም ሆነ ማታ ከኢየሩሳሌም ይፈስሳል። 8 ክረምትም ሆነ በጋ እኩሌታው ወደ ምሥራቅ ባሕር፣
እኩሌታው ወደ ምዕራብ ባሕር ይፈስሳል። 9 ያህዌ በመላው ምድር ይነግሣል። በዚያ ቀን አንድ አምላክ ያህዌ ብቻ ይሆናል፤ ስሙም አንድ ይሆናል። 10 ከጌባ
አንሥቶ በኢየሩሳሌም ደቡብ እስካለችው ሬሞን ድረስ ምድር ሁሉ እንደ አረባ ትሆናለች። ኢየሩሳሌም ከፍ እንዳለች ትዘልቃለች። ከብንያም በር አንሥቶ
የመጀመሪያው በር እስከ ነበረበት እስከ ማእዘኑ በር ድረስ፣ ከሐናንኤል ግንብ እስከ ንጉሡ ወይን መርገጫ ድረስ በቦታዋ ትኖራለች። 11 ሕዝቡም በኢየሩሳሌም
ይኖራል፤ ከእግዚአብሔር ዘንድ ከባድ ጥፋት አይመጣባቸውም፤ ኢየሩሳሌም በሰላም ትኖራለች። 12 ኢየሩሳሌምን በወጉ ሕዝቦች ሁሉ ላይ ያህዌ
የሚያመጣባቸው መቅሠፍቶች እነዚህ ናቸው፤ በእግራቸው ቆመው እያለ ሥጋቸው ይበሰብሳል። ዐይኖቻቸው ጉድጓዶቻቸው ውስጥ እያሉ ይበሰብሳሉ፤
ምላሳቸው አፋቸው ውስጥ ይበሰብሳል። 13 በዚያ ቀን ከያህዌ ዘንድ ታላቅ ፍርሃት ይመጣባቸዋል። እያንዳንዱ ሰው የባልንጀራውን እጅ ይይዛል፤ አንዱ ሌላውን
ይወጋል። 14 ይሁዳም ኢየሩሳሌምን ይወጋል። የአካባቢውን ሕዝቦች ሁሉ ሀብት ይሰበስባሉ፤ ወርቅ፣ ብርና ልብስ በብዛት ይኖራል። 15 ፈረሶችና በቅሎዎች
ላይ፣ ግመሎችና አይሆች ላይ መቅሠፍት ይወርዳል፤ ይኸው መቅሠፍት በየሰፈሩ ያሉ እንስሳትንም ሁሉ ይመታል። 16 ኢየሩሳሌምን ከወጓት ሕዝቦች ከሞት
የተረፉት ለንጉሡ ለሰራዊት ጌታ ለያህዌ ለመስገድና የዳስን በዓል ለማክበር በየዓመቱ ይወጣሉ። 17 በምድር ካሉ ሕዝቦች ሁሉ ለንጉሡ፣ ለሰራዊት ጌታ
ለያህዌ ለመስገድ ወደ ኢየሩሳሌም የማይወጣ ካለ፣ ያህዌ ደግሞ ዝናብ አያዘንብላቸውም። 18 የግብፅ ሕዝብ የማይወጣ ከሆነ ዝናብ አያገኝም። የዳስ በዓልን
ለማክበር በማይወጡ ሕዝቦች ላይ መቅሠፍት ከያህዌ ዘንድ ይመጣባቸዋል። 19 የዳስ በዓልን ለማክበር በማይወጣው ግብፅና ማንኛውም ሕዝብ ላይ
የሚመጣው ቅጣት ይህ ይሆናል። 20 በዚያ ቀን በፈረሶች ሻኩራ ላይ፣ “ለእግዚአብሔር የተቀደሰ” የሚል ጽሑፍ ይቀረጻል፤ በእግዚአብሔር ቤት ያሉት
መታጠቢያዎች መሠዊያው ፊት እንዳሉት ሳህኖች የተቀደሱ ይሆናሉ፤ 21 በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ያሉት ምንቸቶች ሁሉ ለሰራዊት ጌታ ለያህዌ ይቀደሳሉ፤
መሥዋዕት ለማቅረብ የሚመጡ ሁሉ በእነርሱ በማብሰል ይበሉባቸዋል። በዚያ ቀን በሰራዊት ጌታ በያህዌ ቤት ውስጥ ከእንግዲህ ነጋዴዎች አይኖሩም።

Zechariah 14:1

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ምዕራፍ ኢየሩሳሌምን ለመያዝ የሚደረገውን የመጨረሻ ጦርነትና እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያድናት ይገልጻል።

ብዝበዛችሁ በመካከላችሁ የሚከፋፈልበት የያህዌ ቀን ይመጣል
ወደፊት የሚመጣ ጊዜ ‘ቀን እንደሚመጣ’ ተደርጎ ተነግሯል። ‘የሚከፋፈልበት’ የሚለው ቃል በተናጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት. “ያህዌ ፈጥኖ ይፈርድባችኋል፣ ጠላቶቻችሁም ንብረቶቻችሁን ሁሉ እንዲወስዱና ዓይኖቻችሁ እያዩ ለራሳቸው እንዲከፋፈሉት ይፈቅድላቸዋል።” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚሉትን ይመልከቱ)

ሁሉንም መንግሥታት በኢየሩሳሌም ላይ ለጦርነት እሰበስባቸዋለሁ
እዚህ ላይ ‘ሁሉንም መንግሥታት’ የሚለው ብዙ መንግሥታት ለማለት የማጠቃለል አባባል ነው። አት. “ብዙ መንግሥታት ኢየሩሳሌምን እንዲያጠቋት አደርጋለሁ።” (ግነት እና የማጠቃለል አባባል የሚሉትን ይመልከቱ)

ከተማይቱ ትያዛለች
ይህ በተናጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት. “ጠላቶቻችሁ ከተማይቱን ይይዟታል።” (ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚለውን ይመልከቱ)

ቤቶች ይበዘበዛሉ፣ ሴቶችም ይደፈራሉ
ይህ በተናጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት. “ጠላቶች ቤቶችን ይበዘብዛሉ፣ ሴቶችንም ይደፍራሉ።” (ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚለውን ይመልከቱ)

የሚቀረው ሕዝብ ከከተማይቱ አይወገድም
ሕዝቡን ከከተማይቱ አለመውሰድ ሕዝቡ ‘እንደማይወገድ’ ተደርገ ተነግሯል። ይህ በተናጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት. “ጠላቶቻችሁ ቀሪው ሕዝብ በከተማይቱ እንዲቆይ ይፈቅዱለታል።” (ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 14:3

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ጥቅሶች ኢየሩሳሌምን ለመያዝ የሚደረገውን የመጨረሻ ጦርነትና እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያድናት መግለጽ ይቀጥላሉ። ያህዌ እንደሚመጣና እንደሚዋጋ ተዋጊ ተደርጎ ተገልጾአል።

በጦርነት ጊዜ እንደሚዋጋ
“በቀደሙት ጊዜያት በጦርነት ሲዋጋ እንደነበረ”

በዚያን ቀን
“በዚያን ወቅት”

እግሮቹ በኢየሩሳሌም ተራራ ላይ ይቆማሉ
እዚህ ላይ ‘እግሮቹ’ የሚለው ያህዌን ይወክላል። አት. “በኢየሩሳሌም ተራራ ላይ ይቆማል።” (በክፋይ የተወከለ አካል የሚለውን ይመልከቱ)

የኢየሩሳሌም ተራራም ተከፍሎ ... ታላቅ ሸለቆ ይሆናል
ይህ በተናጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት. “የያህዌ ሕላዌ የኢየሩሳሌምን ተራራ ሁለት ቦታ ከፍሎ ታላቅ ሸለቆ በዚያ እንዲፈጠር ያደርጋል።” (ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 14:5

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ጥቅሶች ኢየሩሳሌምን ለመያዝ የሚደረገውን የመጨረሻ ጦርነትና እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያድናት መግለጽ ይቀጥላሉ።

እናንተ ትሸሻላችሁ
እዚህ ላይ ‘እናንተ’ የሚለው የብዙ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተውም የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ነው። (አንተ እና እናንተ የሚገለጽባቸው መልኮች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በእግዚአብሔር ተራሮች መካከል
ይህ የኢየሩሳሌም ተራራ ለሁለት ከተከፈለ በኋላ የሚፈጠሩትን ተራራዎች ይመለከታል።

አጼል
ይህ ከኢየሩሳሌም በስተምሥራቅ የሚገኝ ከተማ ወይም መንደር ስም ነው። (ስምን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚህ ቀደም እንደሸሻችሁ ትሸሻላችሁ
እዚህ ላይ ‘ትሸሻላችሁ’ በሚለው በውስጠ ታዋቂ ‘እናንተ’ የሚለው የሚያመለክተው የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ነው። ነገር ግን ‘እንደሸሻችሁ’ የሚለው የሚያመለክተው ከብዙ ዓመታት በፊት የተፈጸመ ድርጊትን በመሆኑ የሸሹት ቀደምት አባታቶቻቸው ናቸው። አት. “ቀደምት አባቶቻችሁ እንደሸሹ ትሸሻላችሁ” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

በይሁዳ ንጉሥ በዖዝያን ዘመን
እዚህ ላይ ‘በ ... ዘመን’ የሚለው ፈሊጣዊ አባባል ሲሆን ዖዝያን ንጉሥ በነበረበት ጊዜ ማለት ነው። አት. “ዖዝያን ንጉሥ በነበረበት ጊዜ” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ቅዱሳኑም
ይህ ምናልባት የእግዚአብሔርን መላእክት የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም።

Zechariah 14:6

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ጥቅሶች ኢየሩሳሌምን ለመያዝ የሚደረገውን የመጨረሻ ጦርነትና እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያድናት መግለጽ ይቀጥላሉ።

በዚያን ቀን
“በዚያን ወቅት”

ብርሃን አይኖርም
በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት ከፀሐይ የሚገኝ ብርሃን አይኖርም። አት. “የፀሐይ ብርሃን አይኖርም” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ያህዌ ዘንድ ብቻ የታወቀ ቀን
ይህ በተናጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት. “ያ ቀን መቼ እንደሚጀምር የሚያውቀው ያህዌ ብቻ ነው።” ወይም “ያህዌ ብቻ ያ ቀን መቼ እንደሚጀምር ያውቃል።” (ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚለውን ይመልከቱ)

የሕይወት ውሃ
ይህ በመደበኛነት በአንድ ቦታ የረጋ ወይም ጮሮቃ ውሃ ሳይሆን ወረጅ ወይም ፈሳሽ ውሃ ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

የምሥራቅ ባሕር
ይህ ከኢየሩሳሌም በስተምሥራቅ ያለውን ሙት-ባሕርን ያመለክታል።

የምዕራብ ባሕር
ይህ ሜዴትራኒያን ባሕርን (ታላቁን ባሕር) ያመለክታል።

Zechariah 14:9

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ጥቅሶች ኢየሩሳሌምን ለመያዝ የሚደረገውን የመጨረሻ ጦርነትና እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያድናት መግለጽ ይቀጥላሉ።

ያህዌ አንዱ አምላክና ስሙም ብቻ ይኖራል
እዚህ ላይ ‘ስሙ’ የያህዌን ዝናና ባሕርዩን ይወክላል። ትኩ. “ሕዝቡ ያህዌ ብቸኛው እውነተኛ አምላክ እንደሆነ ያውቃሉ” ወይም “ሰዎች ብቻኛውንና እውነተኛ የሆነውን የሆነውን ያህዌን ብቻ ያመልካሉ።” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

ምድር ሁሉ
በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት ይህ የይሁዳ ምድር ነው። አት. “መላው የይሁዳ ምድር” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

አረባ
ይህ በዮርዳኖስ ወንዝ ሸለቆ ያለ ሜዳ ስም ነው። (ስምን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ የሚለውን ይመልከቱ)

ጌባ
ይህ በሰሜን ይሁዳ ዳርቻ ያለ ከተማ ስም ነው። (ስምን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ የሚለውን ይመልከቱ)

ሪሞን
ይህ በኢየሩሳሌም በስተደቡብ ያለ ከተማ ስም ነው። (ስምን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ የሚለውን ይመልከቱ)

ኢየሩሳሌም ከፍ ከፍ በማለት ትቀጥላለች
ይህ ከፍ በማለት የምትቀጥለውን ኢየሩሳሌምን ከባሕር ጠለል በላይ ከፍታቸው ዝቅ ካለው ከአካባቢው ቦታዎች ጋር ያለውን ቅራኔ ያሳያል። ቅራኔውን ‘ነገር ግን’ የሚለውን ቃል በመጨመር ማመልከት ይቻላል። ይህ በተናጋሪ መልክም ሊገለጽ ይችላል። አት. “ኢየሩሳሌም ከፍ እንዳለች ትቆያለች።” (አያያዥ ቃላት እና ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚሉትን መልከቱ)

የብንያም በር ... የመጀመሪያው በር ... የማዕዘን በር
እነዚህ በኢየሩሳሌም ከተማ ቅጥር በስተ ሰሜንምሥራቅ በኩል ያሉ የበሮች ስሞች ናቸው። ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች ፡ - 1)’የመጀመሪያው በር’ እና ‘የማዕዘን በር’ አንድ ዓይነት በሮች ናቸው ወይም 2) ’የመጀመሪያው በር’ እና ‘የማዕዘን በር’ የተለያዩ በሮች ናቸው። (ስምን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ፣ ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

የሐናንኤል ግንብ
ይህ በስተሰሜን ቅጥር ባለው የከተማይቱ መካላከያ ጠንካራውን ስፍራ ያመለክታል። ይህ ምናልባት ሐናንኤል በተባለ ሰው የተገነባ ሳይሆን አይቀርም። (ስምን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ የሚለውን ይመልከቱ)

የንጉሡ የወይን ጠጅ መጥመቂያ
ይህ ምናልባት ለንጉሣዊው ቤተ ሰብ የወይን ጠጅ የሚዘጋጅበት ሳይሆን አይቀርም። ከኢየሩሳሌም በስተ ደቡብምዕራብ በኩል የሚገኝ ስፍራ ነበር። (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ኢየሩሳሌም በሰላም ትኖራለች
እዚህ ላይ ‘ኢየሩሳሌም’ ሕዝቡን ትወክላለች። አት. “ሕዝቡ በሰላም በኢየሩሳሌም ይኖራሉ።” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 14:12

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ጥቅሶች ኢየሩሳሌምን ለመያዝ የሚደረገውን የመጨረሻ ጦርነትና እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያድናት መግለጽ ይቀጥላሉ።

ገና በእግሮቻቸው ቆመው ሳሉ
“ቆመው ሳሉ” ይህ ሥጋቸው ምን ያህል ፈጥኖ እንደሚበሰብስ አጽንዖት ይሰጣል። ለመተኛት እንኳን ጊዜ አይኖራቸውም።

በመካከላቸውም ከያህዌ ዘንድ ያ ታላቅ ፍርሃት ይመጣባቸዋል
‘ፍርሃት’ የሚለው የነገር ስም ‘ድንጋጤ’ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። አት. “ያህዌ ሕዝቡ በጣም እንዲደነግጡ ያደርጋቸዋል” (የነገር ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የአንዱ እጅ የሌላውን እጅ ይይዛል፣ የአንደኛውም እጅ በሌላው እጅ ላይ ይነሳል
እነዚህ ፈሊጣዊ አባባሎች በሌላው ሰው ላይ በጠላትነት መነሳትን የሚያመለክቱ ናቸው። አት. “እያንዳንዱ ሰው ሌላውን ሰው ይይዘዋል፣ እርስ በርሳቸውም ይጣላሉ።” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 14:14

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ጥቅሶች ኢየሩሳሌምን ለመያዝ የሚደረገውን የመጨረሻ ጦርነትና እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያድናት መግለጽ ይቀጥላሉ።

ይሁዳም ኢየሩሳሌምን ይወጋል
‘ይሁዳ’ እና ‘ኢየሩሳሌም’ በዚያ የሚኖሩትን ሕዝቦች ይወክላሉ። አት. “በይሁዳ ያሉት ሌሎች ሕዝቦች እንኳን ከኢየሩሳሌም ጋር ይዋጋሉ።” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

ይሁዳም ከኢየሩሳሌም ጋር ይዋጋል
በአንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች፡ - “ይሁዳም በኢየሩሳሌም ይዋጋል” ተብሎ ይነበባል።

ሀብቱን ይሰበስባሉ
ውድ የሆኑትን ንብረቶች ሁሉ ይይዛሉ።

በተትረፈረፈ መጠን
‘በከፍተኛ መጠን’

Zechariah 14:16

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ጥቅሶች ኢየሩሳሌምን ለመያዝ የሚደረገውን የመጨረሻ ጦርነትና እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያድናት መግለጽ ይቀጥላሉ።

በኢየሩሳሌም ላይ ከመጡት
“በ … ላይ መጡ” የሚለው ፈሊጣዊ አባባል ነው። አት. “ኢየሩሳሌምን ያጠቁት” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያ ይልቅ ከዓመት ወደ ዓመት ይወጣሉ
ከዚያ ይልቅ ወደ ኢየሩሳሌም በየዓመቱ ይወጣሉ።

የመጠለያዎች በዓል
‘የማረፊያ ቦታዎች በዓል’ ወይም ‘የዳሶች በዓል’ ወይም ‘የድንኳኖች በዓል’

ከያህዌ ዘንድ የሆነ ቸነፈር መንግሥታትን ያጠቃል
አንድን ሕዝብ በቸነፈር እንዲሰቃይ ማድረግ ቸነፈሩ እንደ ሠራዊት ሕዝቡን እንደሚያጠቃው ተደርጎ ተነግሯል። አት. “በመንግሥታት ሕዝቦች መካከል ያህዌ ቸነፈር እንዲመጣ ያደርጋል።” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 14:19

አቃላይ መረጃ
እነዚህ ጥቅሶች ኢየሩሳሌምን ለመያዝ የሚደረገውን የመጨረሻ ጦርነትና እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያድናት መግለጽ ይቀጥላሉ።

Zechariah 14:20

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ጥቅሶች ኢየሩሳሌምን ለመያዝ የሚደረገውን የመጨረሻ ጦርነትና እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያድናት መግለጽ ይቀጥላሉ።

በፈረሶቹ ላይ ያሉት ሻኩራዎች እንደዚህ ይላሉ
በፈረሶቹ ባሉት ሻኩራዎች ላይ ያሉት ጽሑፎች እንደዚህ ይላሉ።

በያህዌ ቤት ያሉት ምንቸቶች
ለእነዚህ ምንቸቶች በቤተ መቅደሱ አደባባይ ሥጋን ለመቀቀያ ጥቅም ላይ ይውሉ ነበር። አት. “ቤተ መቅደሱ አደባባይ የነበሩት የማብሰያ ምንቸቶች” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከመሠዊያው ፊት ለፊት እንዳሉት ሳህኖች
በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት ምንቸቶቹ የመሥዋዕቱን ደም ለመቀበል እንደሚያገለግሉት ሳህኖች የተቀደሱ ይሆናሉ የሚል ነው። አት. “በመሠዊያው እንዳሉት ሳህኖች የተቀደሱ ይሆናሉ።” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ያለ ማንኛውም ምንቸት ለሠራዊት ጌታ ለያህዌ የተለየ ይሆናል
ልዩ ልዩ ዓይነት ምንቸቶችና ቁሳቁሶች በተለይ ለያህዌ አምልኮና ለመሥዋዕቶቹ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ተሠርተው ነበር። እነዚህ ለምንም ሌላ ጥቅም እንዳይውሉ የተለዩ ተደርገው ይቆጠሩ ነበር።

ከእንግዲህ ወዲህ ነጋዴዎች በያህዌ ቤት አይኖሩም
ሕዝቡ በቤተ መቅደስ ለያህዌ ተገቢ መሥዋዕቶችን እንዲያቀርቡ የሚያስፈልጓቸውን ለሕዝቡ መሸጥ በነጋዴዎች ዘንድ የተለመደ ነበር። አት. “ከእንግዲህ ሰዎች በያህዌ ቤተ መቅደስ የሚሸጡም የሚገዙም አይሆኑም።” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ነጋዴዎች
አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ‘ነጋዴዎች’ የሚለውን ‘ከነዓናውያን’ ብለው ይተረጉሙታል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Malachi

Malachi

Chapter 1

1 በሚልክያስ በኩል ወደ እስራኤል የመጣው የያህዌ ቃል ዐዋጅ ይህ ነው። 2 “እኔ ወድጃችኋለሁ” ይላል ያህዌ። እናንተ ግን፣ “እንዴት ወደድኸን?” ብላችኋል? “ዔሳው የያዕቆብ ወንድም አልነበረምን? ያዕቆብን ወደድሁ 3 ዔሳውን ግን ጠላሁ። ተራራውን ባድማ አደረግሁ፤ ርስቱንም የምድረ በዳ ቀበሮዎች መኖሪያ አደረግሁ።” 4 ኤዶምያስ፣ “ብንደመሰስ እንኳ፣ የፈረሰውን መልስን እንሠራዋለን” ይል ይሆናል፤ የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል፤ “እነርሱ የሠሩ ይሆናል፤ እኔ ግን መልሼ አፈርሳለሁ።” ሌሎች ሰዎች፣ “የዐመፀኞች አገር፤ ያህዌ ለዘላለም የተቆጣው ሕዝብ” በማለት የጠሯቸዋል። 5 የገዛ ዓይኖቻችሁ ይህን ያያሉ። ከእስራኤል ዳርቻዎች ወዲያ እንኳ ያህዌ ትልቅ ነው ትላላችሁ” 6 ለእናንተ ስሜን ለታቃልሉ ካህናት “ልጅ አባቱን ያከብራል፤ አገልጋይም ጌታውን ያከብራል። እኔ አባት ከሆንሁ፣ ታዲያ፣ ክብሬ የታለ? ጌታስ ከሆንሁ፣ መፈራቴ የታለ? ይላል የሰራዊት ጌታ ያህዌ። እናንተ ግን፣ “ስምህን ያቃለልነው በመንድነው?” ብላችኋል። 7 መሠዊያዬ ላይ የረከሰ ምግብ በማቅረብ ነው። እናንተ፣ “ያረከስንህ በምንድነው” ብላችኋል። የእግዚአብሔር ገበታ የተናቀ ነው በማለታችሁ ነው። 8 የታወረውን እንስሳ መሥዋዕት ማቅረብ፣ በደል አይደለም? አንካሳውንና በሽተኛውን መሥዋዕት ማቅረብስ በደል አይደለም? እስቲ ያንኑ ለባለሥልጣን አቅርቡት፣ ይቀበላችኋልን? ወይስ በእናንተ ደስ ይለዋልን?” ይላል የሰራዊት ጌታ ያህዌ። 9 አሁን ግን እንዲራራልን የእግዚአብሔርን ፊት ፈልጉ። ለመሆኑ፣ እንዲህ ዓይነቱን መሥዋዕት ይዛችሁ ስትቀርቡ እርሱ ይቀበላችኋልን? ይላል የሰራዊት ጌታ ያህዌ። 10 መሠዊያዬ ላይ ከንቱ እሳት እንዳታነዱ፣ ምነው ከእናንተ አንዱ የቤተመቅደሱን ደጆች በዘጋ ኖሮ! በእናንተ ደስ አልሰኝም፤ ከእጃችሁም ማንኛውንም መሥዋዕት አልቀበልም ይላል የሠራዊት ጌታ ያህዌ። 11 ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያው ድረስ በሕዝቦች መካከል ስሜ ታላው ይሆናል፤ በየቦታው ሁሉ በስሜ ዕጣንና ንጹሕ መሥዋዕት ይቀርባል። በሕዝቦች መካከል ስሜ ታላቅ ይሆናል” የሠራዊት ጌታ ያህዌ። 12 እናንተ ግን “የእግዚአብሔር ማዕድ የረከሰ ነው በማለት ታረክሱታላችሁ፤ ምግቡም የተናቀ ነው” በማለት ታቃልሉታላችሁ። 13 ደግሞም፣ “ይህ ድካም ነው” በማለት ፣ “በንቀት ጢቅ አላችሁበት” ይላል የሠራዊት ጌታ ያህዌ። በዱር እንስሳ ተወስዶ የነበረውን ወይም አንካሳና በሽተኛውን መሥዋዕት ለማቅረብ ታመጣላችሁ። ታዲያ፣ ይህን ከእናንተ እጅ ልቀበል?” ይላል ያህዌ። 14 “መንጋው ውስጥ ያለውን ተባዕት በግ መሥዋዕት ለማቅረብ ተስሎ ሳለ ለእኔ ነውር ያለበትን እንስሳ የሚያቀርብ አታላይ ርጉም ይሁን! እኔ’ኮ ታላቅ ንጉሥ ነኝ፤ ስሜም በአሕዛብ መካከል ይከበራል” ይላል የሠራዊት ጌታ ያህዌ።

Malachi 1:4

ኤዶምያስ እንዲህ ቢል፤
“ኤዶምያስ” በዚህ ስፍራ የኤዶምን ህዝብ ይወክላል ‘የኤዶማዉያን እንዲህ ቢሉ ወይንም የኤዶም ህዝብ እንዲህ ቢል’

እኔ ወደታች እወረውራለሁ
በዚህ ስፍራ ‘ወደታች እወረውራለሁ’ የሚለው ‘አፈርሳለሁ’ ለማለት እንደሆነ ይለመታል።

የበደል አገር
‘በደለኛ’ የሚለው ቃል ‘የበደለኛ ህዝብ አገር’ ለማለት ነው።

በአይኖቻችሁ ይህንን ታያላችሁ
በዚህ ስፍራ “በአይኖቻችሁ” የሚለው ህዝቡን ይወክላል። ስለዚህ “እናንተ ራሳችሁ ይህንን ታያላችሁ” ይባል።

Malachi 1:6

ስሜን የምታቃልሉ
በዚህ ስፍራ “የኔ ስም” የሚለው እግዚአብሔርን የሚለውን ያመለክታል እን“ደጠላችሁኝ ያሳያል”

ስምህን እንዴት አቃለልን ?
በዚህ ስፍራ ካህናት የሚጠይቁት ጥያቄ እግዚአብሔርን በእርግጥ አላቃለልንም እያሉ ነበር።ስለሆነም እንዲህ ይባል፤ “እኛ ስምህን ያቃለልን ይመስለሀል?” ወይም “ስምህን እንዴት አድርገን እንዳቃለልን እስቲ ንገረን?”

እርኩስ እንጀራ (ምግብ)
“እርኩስ” የሚለው ቃል የሚገልጸው ለእግዚአብሔር መቅረብ የማይገባውን መሰዋዕት ማቅረብን ነው

እንዴት አረከስንህ?
በዚህ ስፍራ ካህናት የሚጠይቁት ጥያቄ እኛ ስምህን አላረከስንም የሚል ነበር። ይህም እንደዚህ ቢባል፤ “ እኛ አላረክስንህም” ወይም “እንዴት ነው ያረከስንህ?”

አረከስንህ
ይህ አገላለጽ ለእግዚአብሔር የማይገባውን መሰዋእት ማቅረብ እግዚአብሔር እንደመሳደብ ይቆጠራል የሚለውን ይገልጻል።

ገበታ
ይህ መሰዉያውን ያሳያል።

የእግዚአብሔር ገበታ የተነቀፈ ነው በማለታችሁ ነው።
እግዚአብሔር ለካህናቱ የሰጠው ምላሽ እንዲህ የሚል ነበር፤(ግልጽ ሲደረግ)፤”የእግዚአብሔር ገበታ የተናቀ ነው በማለት እኔን አርክሳችሁዋል”

የተነቀፈ / የተናቀ
ዋጋ እንደሌለው የተቆጠረ

Malachi 1:8

ዕውር መሥዋዕትንም ስታቀርቡ ይህ ክፉ አይደለምን?
በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር ጥያቄውን በመጠቀም ህዝቡን ይገስጻል።ስለዚህ እንዲህ ይባል “ለእግዚአብሔር ዕውር እንስሳን መሰዋእት ማቅረብ ክፉ እንደሆነ በደንብ ታውቃላችሁ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አንካሳውንና የታመመውን ስታቀርቡ ይህ ክፉ አይደለምን?
በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር ጥያቄውን በመጠቀም ህዝቡን ይገስጻል። ስለሆነም እንዲህ ይባል “ አንካሳና የታመመዉን እንስሳ ማቅረብ ክፉ እንደሆነ እያወቃችሁ መሰዋዕት ታቀርባላችሁ።

ያንን ለአለቃህ አቅርብ፥ በውኑ በአንተ ደስ ይለዋልን? ወይስ ፊትህን ይቀበላልን?
የመጀመሪያው አረፍተነገር በትእዛዝ መልክ ለመከራከሪያነት የቀረበ ስለሆነ እንደዚህ ይባል “ያንን ለአለቃህ ብታቀርብ ይቀበለሃል ወይ ወይንም ፊትህን ይቀበላል ወይ?”

ይቀበለሃል ወይንም ፊትህን ይቀበላል ወይ?”
በዚህ ስፍራ ማለት የተፈለገው እግዚአብሔር ህዝቡን ለማስታወስ ጥያቄ በመጠየቅ አለቃችሁ በፍጹም እንዲህ አይነቱን አካለ ስንኩል እንስሳ አይቀበልም ነው።

ፊትህን ወደ ላይ ከፍ ያደርጋል
ፊትን ወደ ላይ ከፍ ማድረግ የሚለው ፈሊጥ በሞገስ ግለሰቡን መቀበልን ያመለክታል። ስለሆነም “ በጥሩ ሁኔታ ይቀበለሃል” ወይም “ እንተን ለመርዳት ፈቃደኛ ነው” ማለት ይቻላል።

መስጠት (ስጦታን)
አክብሮትን ለማሳየት ስጦታን እንደመስጠት

አሁንም ጸጋን ይሰጠን ዘንድ እግዚአብሔርን ለምኑ፥
ሚልክያስ ለእግዚአብሔር በቀጥታ አይናገርም። ነገርግን እስራኤልን በቀጥታ እንዲህ በማለት ይናገራል፤ እነሱን በወቀሳ መልክ እግዚአብሔር ምህረት ያድርጋል እያላችሁ ታስባላችሁ ይላቸዋል።

ይእግዚአብሔርን ፊት እየጠየቁ መቀጠል
እዚህ ላይ “ፊት” የሚለው ቃል እግዚአብሔርንና የሱን መገኘት ነው። ስለሆነም “ እግዚአብሔር በሚገኝበት እሱን ፈልግ” ይባል።

ይህን ስጦታ ከእጃችሁ የተሰጠ ሲሆን ከቶ ፊታችሁን ይቀበላልን
በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር የሚጠይቀው በጥያቄ ዉስጥ ህዝቡን ለመገሰጽ ፈልጎ ነው። ስለሆነም “ለእግዚአብሔር የማይመጥን መሰዋዕት ብታቀርብ በእርሱ አንድ ተቀባይነት የለውም” ይባል።

በእጃችሁ ባለው በዚህ ስጦታ
ይህ አስቸጋሪ የሆነ የዕብራይስጥ ሐረግ በተለያየ መንገድ ሊተረጎም ይችላል።

በእጅህ ውስጥ
x

Malachi 1:10

ከሆነ ብቻ
የከፍተኛ ፍላጎት መግለጫ

በመሠዊያዬ ላይ እሳትን በከንቱ እንዳታቃጥሉ
በዚህ ስፍራ “በመሰውያየ ላይ እሳት ማቃጠል” የሚለው የሚያመለክተው ለእግዚአብሔር መሰዋእት በመሰውያው ላይ ማቅረብን ነው።ስለሆነም “ተቀባይነት የሌለውን ስጦታ ማቃጠል ተገቢ አይደለም” ይባል።

ከእጃችሁ
እዚህ ላይ “እጃችሁ” የሚለው “እናንተ” የሚለውን ይወክላል። ስለሆንም “ከእናንተ” ይባል።

ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያዋ ድረስ
ይህ አገላለጽ “በሁሉም ስፍራ” ለማለት ነው።

ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ይሆናልና
እዚህ ላይ “የኔ ስም” የሚለው አባባል የእግዚአብሔርን ዝናና ክብር ለማመልከት ነው። ስለሆነም “በሌሎች ህዝቦች ላይ እከብራለሁ” ይባል።

በሁሉም ስፍራ ዕጣንና ንጹህ ስጦታ በስሜ ይቀርባል
ይህ አገላለጽ እንደሚከተለው ሊቀርብ ይችላል፡ “ከእነዚህ አገሮች ሰዎች እኔን ለማምለክ እጣንና ንጹህ ስጦታን ያቀርባሉ”።

በኔ ስም
በዚህ ስፍራ “ስም” እግዚአብሔርን ይወክላል። ስለሆነም “ለኔ” ይባል።

ፍሬው፥ መብሉም
አማራጭ ትርጉሞች 1) “በመሰውያ ላይ የተሰዋ የእንስሳት ስጋ ሆኖ ከብልቱ ካህናት የሚበሉት” ወይም 2) በመሰውያ ላይ የተሰዋ ስጋ”

Malachi 1:13

ጣቅ አላችሁበት
እክብሮት በመንፈግ ድምጽ ማሰማት

በውኑ ከእጃችሁ ይህን ልቀበለውን?
በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር ሊገስጻቸው ጥያቄ ይጠይቃቸዋል። ስለሆነም “እኔ ይህንን በእርግጥ ከእናንተ አልቀበልም” ይባል።

ከእጃችሁ
በዚህ ስፍራ “እጃችሁ” የሚለው የሚወክለው “እናንተ” ነው።

ስሜም በአሕዛብ ዘንድ የተከበረ ነው ።
ይህ በቀጥታ ንግግር ሊገለጽ ይችላል። “ሌሎች ህዝቦች ስሜን ያከብራሉ” ይባል።

ስሜ ይከብራል
እዚህ ላይ “የኔ ስም” የሚለው እግዚአብሔርን ይወክላል። ስለሆነም “እኔ እከብራለሁ” ይባል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 2

1 አሁንም፣ እናንተ ካህናት ይህ ትእዛዝ ለእናንተ ነው። **2** “የማትሰሙና ለስሜ ክብር ለመስጠት በልባችሁም የማታኖኑት ከሆነ” ይላል የሠራዊት ጌታ ያህዌ፣ “መርገም እልክባችኋለሁ፤ በረከታችሁን እረግማለሁ። ትእዛዜን በልባችሁ አላኖራችሁምና በእርግጥ ረግሜአችኋለሁ። **3** ዘራችሁን እገሥጻለሁ፤ የመሥዋዕታችሁንም ፋንድያ ፊታችሁ ላይ እበትናለሁ፤ እናንተም ከእርሱ ጋር ትጠፋላችሁ። **4** ኪዳኔ ከሌዊ ጋር ይሆን ዘንድ ይህን ያዘዝሁ እኔ መሆኔንም ታውቃላችሁ” ይላል የሠራዊት ጌታ ያህዌ። **5** “ከእርሱ ጋር ያደረግሁት ኪዳን የሕይወትና የሰላም ኪዳን ነበር፤ እነዚህን ለእርሱ ሰጠሁት፤ አከበርኩት፤ እርሱ አከበረኝ፤ በስሜ ፊት በፍርሃት በመንቀጥቀጥ ቆመ። **6** እውነተኛ ትምህርት በአንደበቱ ነበር፤ በከንፈሮቹ ምንም ሐሰት አልተገኘም። በሰላምና በጽድቅ ከእኔ ጋር ተመላለሰ፤ ብዙዎችንም ከኀጢአት መለሰ። **7** የካህኑ ከንፈሮች ዕውቀትን ይጠብቃሉ፤ እርሱ የሠራዊት ጌታ የያህዌ መልዕክተኛ ስለሆነ ሰዎች ከአፉ ትምህርት መፈለግ ይኖርባቸዋል። **8** እናንተ ግን ከእውነተኛው መንገድ ወጥታችኋል። ሕጉን በተመለከተም ብዙዎችን አሰናክላችኋል፤ የሌዊን ኪዳን አፍርሳችኋል።” ይላል የሠራዊት ጌታ ያህዌ። **9** “መንገዴን አልጠበቃችሁም፤ ትምሕርቱን በተመለከተ አድልዎ አድርጋችኋል፤ ስለዚህ እኔም በሰዎች ሁሉ ፊት እንድትዋረዱና እንድትናቁ አደርጋለሁ።” **10** ለሁላችንም ያለን አንድ አባት አይደለምን? የፈጠረንስ አንድ አምላክ አይደለምን? ታዲያ፣ እያንዳንዱ ሰው ለወንድሙ ታማኝ ባለመሆን የአባቶቻችንን ኪዳን ያረከስነው ለምንድነው? **11** ይሁዳ አልታመነም። በእስራኤልና በኢየሩሳሌም አስጸያፊ ነገር ተፈጽሞአል። **12** እንዲህ የሚያደርገውን ሰው፣ ሌላው ቀርቶ ለሠራዊት ጌታ ለያህዌ መሥዋዕት የሚያመጣ እንኳ ቢሆን፣ ያህዌ ከያዕቆብ ድንኳኖች ያስወግደው። **13** እናንተ ይህንንም አድርጋችኋል፣ የያህዌን መሠዊያ በእንባ አጥለቅልቃችኋል፤ እርሱ ቁርባናችሁን ስለማይመለከት ወይ በደስታ ከእጃችሁ ስለማይቀበለው ትጮኻላችሁ ታለቅሳላችሁም። **14** እናንተም፣ “ይህ ለምን ሆነ?” በማለት ትጠይቃላችሁ። እንዲህ የሆነው ያህዌ በአንተና በወጣትነት ሚስትህ መካከል ምስክር ስለሆነ ነው፤ የቃል ኪዳን ጓደኝህና ሚስትህ ብትሆን እንኳ አንተ ለእርሷ ታማኝ አልነበርክም። **15** በመንፈሱ ክፋይ እግዚአብሔር አንድ አላደረጋቸውምን? እርሱ አንድ ያደረጋችሁ ለመንድነው? ምክንያቱም ለእግዚአብሔር የሚሆን መሥዋዕት ስለፈለገ ነው። ስለዚህ በመንፈሳችሁ ራሳችሁን ጠብቁ፤ ከወጣትነት ሚስታችሁ ጋር ያላችሁንም ታማኝነት አታጉድሉ። **16** “እኔ መፋታትን እጠላለሁ” ይላል የእስራኤል አምላክ ያህዌ፤ “ልብሱን በግፍ ሥራ የሚሸፍነውንውም ሰው እጠላለሁ” ይላል የሠራዊት ጌታ ያህዌ። “ስለዚህ በመንፈሳችሁ ራሳችሁን ጠብቁ፤ ታማኝነታችሁንም አታጉድሉ።” **17** በቃላችሁ ያህዌን አታክታችኋል። እናንተ ግን፣ “እርሱን ያታከትነው በምንድነው?” ብላችኋል። “ክፉ የሚያደርግ ሁሉ በያህዌ ፊት መልካም ነው፤ እርሱም በክፉዎች ደስ ይለዋል፤ ወይም፣ “የፍትህ አምላክ ወዴት ነው?” በመለታችሁ ነው።

Malachi 2:1

በልባችሁ አኑሩት
ይህ የሚያመለክተው አንድ ነገር በጣም አስፈላጊ/ ጠቃሚ መሆኑን ነው። ስለሆነም “በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ቁጠሩት ይባል።

ለስሜ ክብር ስጡት
‘ክብር” የሚለው ቃል እብደ ግስ (ድርጊት ገላጭ) ሊወሰድ ይችላል። ስለሆነም “የኔን ስም አክብሩ” ይባል።

የኔ ስም
ይህ በዚህ ስፍራ እግዚአብሔርን ያመለክታል።

እኔ በእናንተ ላይ እርግማን እልካለሁ
“እርግማን” ረቂቅ ስም ሲህን እንደ ግስ ያገለግላል። ስልሆነም “እኔ እረግማችሁዋለሁ” ይባል።

እናንተ አትእዛኤን በልባችሁ አላኖራችሁም
ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ትእዛዝ በጣም ጥቃሚ/አስፈላጊ መሆኑን ነው።

Malachi 2:3

ፋንድያ በፊታችሁ ላይ እበትናለሁ
እዚህ ላይ “ፋንድያ በፊታችሁ ላይ” የሚለው ሐረግ ማዋረድ/ ማሳፈር የሚለውን ለማመልከት ነው።

የመሥዋዕታችሁንም ፋንድያ
እዚህ ላይ “መሰዋዕት” የሚለው ቃል በእስራኤል በእላት ላይ ካህናት ለመሰዋእትን እንስሳት ይመለከታል። “ፋንዲያ/እበት” የሚለው ቃል እንስሳቱ ለመሰዋዕት ከመታረዳቸው የሚጥሉትን ቆሻሻ ወይንም ከታረዱ በሁዋላ ስጋቸው ሲበለት ከሰውነታቸው የሚወጣውን ለማመልከት ሊሆን ይችላል። የቤተመቅደስ ሰራተኞች እበቱን ከቤተመቅደሱ ዉጪ ወይንም ከእየሩሳሌም ዉጪ ይጥሉታል።

ከእርሱም ጋር በአንድ ላይ ይወሰዳችሁዋል
ይህ ለትርጉም የሚያስቸግር አገላለጽ ቢሆንም እንደዚህ ማለት ይቻላል “እግዚአብሄር ከእርሱ ጋር(ከእበቱ ጋር) ይወስዳችሁዋል። ስለሆነም “በእበት መጣያ ላይ ይወረውሩአችሁዋል፤እግዚአብሔር በእርግጥ ከእበት መጣያ ጋር እንድትወሰዱ ያደርጋል”።

ከእርሱም ጋር በአንድ ላይ ይወሰዳችሁዋል
ለዚህ አባባል ሁለት አማራጮች አሉ፤ 1) እግዚአብሔር ታማኝ ያልሆኑትን ካህናት በሞት በመቅጣት ሬሳቸው ከእንስሳት እበት መጣያ ላይ እንዲጣሉ ያደርጋል ወይንም 2) እግዚአብሔር ታማኝ ያልሆኑትን ካህናት በአሰቃቂ ሁኔታ በሞት በመቅጣት ሬሳቸዉን ከእንስሳት ፋንዲያ ጋር እንዲጣሉ ያደርጋል።

ሌዋዊ
በዚህ ስፍራ ሌዋዊ የሚለው ቃል የሌዊን ተወላጆችና ዘሮቹን ለማለት ነው። ስለዚህ “ ቃልኪዳኔ ከእናንተ ከሌዊ ዘሮች ጋር ነው” ይባል።

Malachi 2:5

ቃል ኪዳኔ ከእርሱ ጋር የሕይወትና የሰላም ቃል ኪዳን ነበረ
በዚህ ስፍራ ለማለት የተፈለገው ውጤት ቃልኪዳን በራሱ ቃልኪዳን መሆኑን ነው። ስለሆነም “ከሌዊ ጋር ያለው የቃልኪዳን ዐላማ ካህናቱ በብልጽግናና በሰላም መኖር ነበር” ይባል።

ይፈራ፥ እርሱም እኔን ፈራኝ፥
ይህ አባባል “ከእርሱ ጋር ያለኝ ቃልኪዳን እርሱ እንዲፈራኝና እሱ እንደፈራኝም ነበር” ይባል።

ከስሜም የተነሣ ደነገጠ
በዚህ ስፍራ “የኔ ስም” የሚለው ሐረግ እግዚአብሔርን ይወክላል።

ምንም ዉሸት አልተገኘበትም
ለማለት የተፈለገው “ ምንም ዉሸት የለበትም” ነው።

በእሱ ከንፈሮች
በዚህ ስፍራ “ከንፈሮች” የሚለው የሰውየውን የመናገር ችሎታን ይወክላል።

እሱ ከኔጋር ይሄዳል
በዚህ ስፍራ መሄድ የሚለው መኖርን እንዲሁም በተወሰነ የህይወት ምንገድ መኖርን ያሳያል።

በሰላምና በቅንነት
በዚህ ስፍራ ሐረጉ የሚያመለክተው የሌዋውያን የኖሩበትን የህይውት ስርዐት ነበር። ስለሆነም “ሰላማዊና ቅንነት” ይባል።

ብዙዎችን ከኃጢአት መለሰ
በዚህ ስፍራ ሰዎች ኃጢአት መስራት እንዲያቆሙና ከሀጢያት ፊታቸዉን እንዲመልሱ ለማለት ስለሆነ “ እሱ ብዙ ሰዎች ከህጢአት እንዲመልሱ አደረገ” ይባል።

የካህናቱ ከንፈሮቹ እውቀትን መጠበቅ ይገባቸዋል
በዚህ ስፍራ እዉቀት የተባለውን ነገር ካህናቱ መጠበቅ ይገባቸዋል። ስለሆነም “እውቀትን መጠበቅ” የሚለው ሃሳብ እዉነተኛ የሆነው ስለ እልዚአብሔር ያለ እዉቀት ለማለት ነው።

ከንፈሮች
በዚህ ስፍራ “ከንፈሮች” የሚለው የሰውየውን የመናገር ችሎታን ይወክላል።

መመሪያ መፈለግ
በዚህ ስፍራ መመሪያ የቀረበው ሊታይ የሚችል እንደ አንድ ነገር ነበር። ይህንን ዐረፍተነገር እንደሚከተለው ማስተካከል ይቻላል። “መመሪያ ለመቀበል መፈለግ” ወይም “ካህናቱ እውነቱን እንዲሩዋቸው መፈለግ”።

ከእርሱ አፍ
በዚህ ስፍራ “አፍ” ሰውየው የሚናገረውን ይወክላል።

Malachi 2:8

እናንተ ግን ከእውነት መንገድ ፈቀቅ ብላችኋል
ቀጥተኛና ትክክለኛ የሆነውን መንገድ መከተል ለማለት ነው።

ብዙዎች እንዲሰናከሉ አድርጋችሁዋል
ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ እንደማሰናከል ይቆጠራል።

በሕግም ብዙዎች እንዲሰናከሉ አድርጋችሁዋል
“በሕግም” የሚለው አገላለጽ “መሰናከል” የሚለውን አውድ ይሰጣል። ስለዚህ “እናንተ ብዙዎች ለሕጉ እንዳይታዘዙ አድርጋችሁዋል” ይባል።

በሕዝብ ሁሉ ፊት
ይህ ሃሳብ ሕዝቡ የካህናቱን ክፉ ባህሪይ ማወቃቸውን ያመለክታል።

መንገዴን እንዳልጠበቃችሁ
በዚህስፍራ “መንገድ” የሚለው “ፍላጎት” ወይም “ባህሪይ” የሚለዉን ያመለክታል።

በሕግም ለሰው ፊት አዳልታችሁዋል
“ለምትወዱአቸው ሰዎች ቀላል ምስፈርት ስታስቀምጡ፤ ለምትጠሉዋቸው ሰዎች ግን አስቸጋሪ መስፈርት ታስቀምጣላችሁ”።

አድልዖ ማሳየት
በዚህ ስፍራ አንድን ሰው ከሌላው አብልጦ መውደድን ያመለክታል፤ስለዚህ “አንዱን ከሌላው አስበልጣችሁ እንድምትወዱ እወቁ” ይባል።

Malachi 2:10

ለሁላችን አንድ አባት ያለን አይደለምን? አንድ አምላክስ የፈጠረን አይደለምን?
ሚልክያስ የሱ ወገን የሆኑትን እስራኤላውያንን ቀደም ሲል የሚያውቁትን ነገር ለማሳሰብ ጥያቄ ይጠይቃቸዋል፤ ስለሆነም መባል ያለበት “ሁላችንም አንድ አባት ያለን፤የእኛ አምላክም ከእኛ አንድ ህዝብ እንደፈጠረ ታውቃላችሁ” ወይም “ሁላችሁም እንደምታዉቁት እግዚአብሔር የእስራኤላውያን ሁሉ አባት ነው፥ ምክንያቱም እግዚአብሔር መንግስታችንን/ሕዝባችንን የመሰረተው እሱ ስለሆነ ነው”።

አንድ አምላክስ አልፈጠረምን?
ይህጥያቄ የሚገልጸው ቀጥሎ ያለዉን አረፍተነገር ነው፤ “በእርግጥ አንድ አምላክ ሁላችንንም ፈጥሮናል”።

ፈጥሮናል
ይህ አረፍተነገር የሚያሳየው እግዚአብሔር አይሁዳውያንን አንድ ህዝብ እንዲሆኑ ማድረጉ ነው።

የአባቶቻችንን ቃል ኪዳን ለማስነቀፍ እኛ እያንዳዳችን ወንድማችንን ስለ ምን አታለልን?
ሚልክያስ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው የራሱ ወገን የሆኑትን እስራኤላውያንን ለመገሰጽ ፈልጎ ነው። ስለዚህ ይህ ጥያቄ ቀጥሎ ባለው መንገድ ወደ አረፍትነገር ሊቀየር ይችላል። “አሁን እንደምታደርጉት እኛ በእርግጥ ወንድሞቻችንን በክፉ በማየትና ለእግዚአብሔር ትእዛዝ ባለመታዘዝ የእግዚአብሔርን ቃልኪዳን ማቃለል የለብንም”።

ይሁዳ አታልሎአል
በዚህስፍራ “ይሁዳ” የሚለው ቃል አይሁዳውያን የሚኖሩበት ስፍራ ያሉትን የአይሁድ ህዝብ ሲወክል ለእግዚአብሔር አለመታመናቸውን ለመግለጽ “ይሁዳ” ብሎዋል። ስለዚህ “የአይሁድ ህዝብ ለእግዚአብሔር አልታመነም” ይባል።

በእስራኤልና በኢየሩሳሌም ውስጥ ርኩሰት ተሠርቶአል
ይህንን አገላለጽ ቀጥሎ ባለው መንገድ ማቅረብ ይቻላል፤ “በእስራኤልና በእየሩሳሌም ያሉ ሰዎች አስጸያፊ ነገሮችን ሰርተዋል”።

እግዚአብሔር ቅዱስ ስፍራ ይሁዳ ስላረከሰ
በዚህ ስፍራ “ይሁዳ” የእስራኤልን ህዝብ ይወክላል።ስልዚህ “የይሁዳ ህዝብ/አይሁዳውያን የተቀደሰውን የእግዚአብሔርን ስፍራ ስላረከሱ” ሊባል ይችላል።

የእንግዳውንም አምላክ ልጅ ሚስት አድርጎ አግብቶአልና
በዚህ ስፍራ የይሁዳ ህዝብ እንደ አንድ ሰው ስም ”ይሁዳ” ተብለዋል። ስለሆነም ፤ “ይሁዳ ጣዖት አምላኪ የሆነች የሌላ አገር ህዝብ ሴት አግብቶአል” ይባል።

እንዲህ የሚያደርገውን ሰው እግዚአብሔር ከያዕቆብ ድንኳን ቆርጦ ያጥፋው
በዚህ ስፍራ አንድን ነገር ማጥፋት ማለት ከአንድ ነገር ላይ ቆርጦ መጣል ማለት ነው።ስለሆነም “እንደዚህ የሚያደርገውን ሰው እግዚአብሔር ያጥፋው” ወይም “ከእስራኤል ህዝብ መካከል እንደዚህ የሚያደርገውን ሰው እግዚአብሔር ይግደለው” ይባል።

የያዕቆብ ድንኩዋን
በዚህ ስፍራ “የያዕቆብ ድንኩዋን” የሚያመለክተው የእስራኤል ህዝብ ነው።

ያዕቆብ
በዚህ ስፍራ “ያዕቆብ” የሚያመለክተው እስራኤላውያንን ነው፥ ምክንያቱም እስራኤላውያን ሁሉ የከያዕቆብ ተወላጆች ስለሆኑ ነው።

እግዚአብሔር የሚጠራውንና የሚመልሰውን
ይህ አገላለጽ “አንድም ሳይቀር ሁሉንም” ለማለት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Malachi 2:13

መሠዊያውን በእንባ ትከድናላችሁ።
ይህ አባባል በፌዝ መልክ በማጋነን የሰዎቹን እንባና ለቅሶ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ሰዎቹ ምንም ሀዘን አይሰማቸውም ለማለት ነው።

በለቅሶና በሀዘን
“ለቅሶ” እና “ሀዘን” የሚሉ ቃላት በተመሳሰለ አገላለጽ ለቅሶ የሚለዉን ሃሳብ ለማጠንከር ነው። ስልዚህ “በከፍተኛ ለቅሶ” ይባል።

እግዚአብሔር ቍርባኑን ዳግመኛ እንዳይመለከት፥
እዚህ ላይ ቁርባኑን አይመለከትም የሚለው ስጦታውን በመቀበል ለሰጪው አድልዖ ማድረግን ያሳያል።

እግዚአብሔር ቍርባኑን ዳግመኛ እንዳይመለከት
ይህም የሚያመለክተው እነዚህ በእግዚአብሔር መሰውያ ላይ የሚያለቅሱ ሰዎች መሰዋዕት ለእሱ እንዳቀረቡ ነው።

ከእጃችሁ
በዚህ ስፍራ “እጅ” የሚለው የሚያመለክተው ሰጭው ስጦታ መስጠቱን ነው።

Malachi 2:14

ስለ ምንድር ነው?
የዚህ ጽሁፍ ሙሉ ሃሳብ “እግዚአብሔር ለምን ወደ ስጦታችን አይመለከትም?” ወይም “ከእጃችን ስጦታችንን ደስ ብሎት አይቀበልም” ነው።

የወጣትነት ሚስትህ
“ወጣት በነበርክ ጊዜ ያገባሃት ሚስትህ”

እግዚአብሔር በአንተና በልጅነት ሚስትህ መካከል ምስክር ስለ ሆነ ነው
በዚህ ዐረፍተነገር መሰረት ይህቺ ሴት በዚህ ጊዜ በህይወት አለች።

ባንተና በልጅነት ሚስትህ መካከል ምስክር
የዚህ አረፍተነገር ትርጉም፥ የጋብቻ ቃልኪዳኑን የሚያፈርሰውን ማንኛውን እስራኤላዊ እግዚአብሔር ይቀጠዋል ነው።

እግዚአብሔር የሕይወትን መንፈስ አንድ አድርጎ ጠብቆልን የለምን?
ይህ ዐረፍተነገር እንደሚከተለው ሊገለጽ ይችላል፥ “እግዚአብሔር በመንፈሱ አንድ አድርጋቸው
ይህ አገላለጽ ባልና ሚስት አንድ ስጋ ይሆንሉ የሚለውን ስለሚያመለክት “ ባልና ሚስት አንድ አካል/ስጋ አደረገ” ይባል።

ከእግዚአብሔር የሆነ ስጦታ
እግዝዚአብሔርን የሚያከብሩና ለሚታዘዙ ልጆች

ሚስትህ ባልንጀራህና የቃል ኪዳንህ ሚስት ናት
ይህ ዐረፍተነገር የሚያሳየው ብዙ እስራኤላውያን ሚስቶቻቸውን እንደ ፈቱ ነው።

በቃልኪዳን
“በጋብቻ ቃልኪዳን ተስማምታችሁዋል”፥

Malachi 2:17

እግዚአብሔርን በቃላችሁ አታክታችኋል
እግዚአብሔር እንደሚሰለች ተደርጎ ቢቀርብም እርሱ ግን በአካል የማይደክም ወይም ስሜታዊ የሆነ አምላክ አይደለም። ምናልባት እግዚአብሔር ተናዶአል ማልት ይቻላል። ስለሆነም “እግዚአብሔርን አናዳችሓል” ይባል።

ያታከትነው በምንድር ነው?
ይህ ጥያቄ የሚያሳየው ህዝቡ ምንም ስህተት እንዳልሰሩ ነው ። ስለዚህ በሚከተለው አገላለጽ ዐረፍተነገሩን መግለጽ ይቻላል።”በእርግጥ እኛ እሱን አላሰለቸንም”

በማለት
በዚህ ስፍራ አጠቃላይ መልዕክቱ “እንደዚህ በማለት አታክታችሁታል” ። የነብዩ ጥያቄ መልስ እንደዚህ መሆን አለበት።

በዓይናችሁ
አይኖች ማየት ሲወክሉ ፥ ማየት ደግሞ ሃሳባቸውን ይወክላል። ስለዚህ “በእናንተ ሃሳብ” ወይም “በውሳኔአችሁ” ይባል።

የፍርድ አምላክ ወዴት አለ?
ካህናቱ ይህንን ጥያቄ የጠየቁት ህዝቡ ሀጢያት ቢሰራም ባይሰራም እግዚአብሔር ስለ ህዝቡ ደንታ የለውም ወይም ክፉ አድራጊዎችን በፍጹም አይቀጣም፥ ስለዚህ “እግዚአብሔር በፍጹም ክፉሰዎችን አረሳም” ይባል።

የፍርድ አምላክ
ክፉሰዎችን በትክክል የሚቀጣ እግዚአብሔር

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 3

1 “እነሆ፣ መልእክተኛዬን እልካለሁ፤ እርሱም መንገዴን በፊቴ ያዘጋጃል። እናንተ የምትፈልጉትም ጌታ በድንገት ወደ መቅደሱ የመጣል። ደስ የምትሰኙበትን
የቃል ኪዳኑ መልእክተኛ ለመጣ ነው” ይላል የሠራዊት ጌታ ያህዌ። 2 እርሱ የሚመጠበትን ቀን ማን መቋቋም ይችላል? እርሱ ሲገለጥ ማን ፊቱ መቆም
ይችላል? ምክንቱም እርሱ እንደ አንጥረኛ እሳት፣ እንደ ለብስ አጠቢ ሳሙና ነው። 3 ብር እንደሚያጠራና እንደ እንደሚያነጻ ሰው ይቀመጣል፤ የሌዊንም ልጆች
ያጠራል እንደወርቅና እንደብር ያጠራቸዋል፤ እነርሱም የጽድቅን ቁርባን ለያህዌ ያመጣሉ። 4 ያኔ የይሁዳና የኢየሩሳሌም ቁርባን እንደ ቀድሞ ዘመን፣
እንደጥንቱም ዘመን ያህዌን ደስ ያሰኘዋል። 5 “በዚያ ጊዜ እኔ ለፍርድ ወደ እናንተ እቀርባለሁ። በመተተኞችና በአመንዝራዎች ላይ፣ በሐሰተኛ ምስክሮችና
የሠራተኞቻቸውን ደመወዝ በሚከለክሉ ላይ፣ መበለቶችንና ድኻ አደጉን በሚጨቁን ላይ፣ መጻተኞችን ፍትሕ በሚነፍጉ ላይ፣ እኔንም በማያከብሩ ላይ በፍጥነት
እመሰክርባቸዋለሁ” ይላል የሠራዊት ጌታ ያህዌ። 6 እኔ ያህዌ አልተለወጥሁም፤ ስለዚህ እናንተ የያዕቆብ ልጆች አልጠፋችሁም። 7 ከአባቶቻችሁ ዘመን ጀምሮ
ከትእዛዞቼ ፈቀቅ ብላችኋል፤ እነርሱንም አልጠበቃችሁም። ወደ እኔ ተመለሱ፤ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ ይላል የሠራዊት ጌታ ያህዌ። እናንተ ግን፣
“የምንመለሰው እንዴት ነው?” ብላችኋል። 8 ሰው ከእግዚአብሔር ይሰርቃልን? እናንተ ግን ከእኔ ሰርቃችኋል፤ ያም ሆኖ ግን፣ “ከአንተ የሰረቅነው እንዴት ነው?”
ብላችኋል። በዐሥራትና በበኩራት ነው። 9 እናንተም ሆናችሁ መላው ሕዝብ ከእኔ ሰርቃችኋልና የተረገማችሁ ናችሁ። 10 በቤቴ መብል እንዲኖር ሙሉ አስራት
ወደጎተራ አስገቡ። “በቂ ቦታ እስከማይኖራችሁ ድረስ የሰማይን መስኮት ከፍቼ በረከትን ባላፈስስላችሁ በዚህ አሁን ፈትኑኝ” ይላል የሠራዊት ጌታ ያህዌ። 11
የምድራችሁን ፍሬ እንዳያጠፋ እህላችሁን የሚያጠፉትን አገሥጻለሁ። እርሻ ላይ ያለው የወይን ተክላችሁም ፍሬ አልባ አይሆንም” ይላል የሠራዊት ጌታ ያህዌ።
12 የምድር ደስታ ስለምትሆኑ ሕዝቦች ሁሉ ቡሩካን ብለው ይጠሯችኋል” ይላል የሠራዊት ጌታ ያህዌ። 13 “እኔ ላይ የድፍረት ቃል ተናግራችኋል” ይላል
ያህዌ። እናንተ ግን፣ “በአንተ ላይ የተናገርነው ምንድነው?” ትላላችሁ። 14 “እግዚአብሔርን ማገልገል ከንቱ ነው ብላችኋል። የእርሱን ትእዛዞች መጠበቅ፣
ወይም በሠራዊት ጌታ በያህዌ ፊት ሐዘንተኞች ሆነን መመላለሳችን ጥቅሙ ምንድነው?” ብላችኋል። 15 ስለዚህም አሁን እብሪተኞችን ቡሩካን እንላቸዋለን።
ክፉ አድራጊዎችን መበልጸግ ብቻ ሳይሆን፣ እግዚአብሔርን የሚፈታተኑትም ያመልጣሉ። 16 ከዚያም ያህዌን የሚፈሩ እርስ በርሳቸው ተነጋገሩ። እግዚአብሔርም
ሰማ፤ አደመጠም፤ ያህዌን ስለሚፈሩትና ስሙንም ስለሚያከብሩት ሰዎች በፊቱ መታሰቢያ እንዲሆን ተጻፈ። 17 “እነርሱ የእኔ ይሆናሉ” ይላል የሠራዊት ጌታ
ያህዌ፣ “እኔ በምሠራበት ቀን ርስቴ ይሆናሉ። ለሚያገለግለው ልጁ እንደሚራራ ሰው እኔም እራራላቸዋለሁ። 18 በጻድቁና በዐመፀኛው መካከል፣ እግዚአብሔርን
በሚያመልኩና እርሱን በማያመልኩ መካከል እንደገና ትለያላችሁ።

Malachi 3:1

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለእስራኤል ህዝብ በቁጥር አንድ መናገር ሲጀምር፥ ሚልክያስ ደግሞ በቁጥር ሁለት መናገር ይጀምራል።

እይ
“ተመልከት” ወይም “አዳምጥ” ወይም “ስለምነግርህ ነገር አጽንዖት ስጥ”

መንገድንም በፊቴ ያስተካክላል
በዚህ ስፍራ ህዝቡ እግዚአብሔርን ለመቀበል መዘጋጀት ማለት እግዚአብሔር የሚሄድበትን መንገድ መጥረግ እንደማለት ነው።

እናንተም የምትፈልጉት ጌታ. . . የምትወዱትም የቃል ኪዳን መልእክተኛ፥
አንዳንድ የመጸሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ይሄንን ቁጥር የሚገልጹት ስለ አንድ ሰው እንደተነገረ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ ግልጽ እንዳልሆነ በመቀበል ግልጽ ለማድረግ ባለመፈለጋቸው እንድዚሁ ትተውታል።እኛም ግልጽ አይደለም እንላለን።

የቃልኪዳን መልእክተኛ
አብዛኛዎቹ ትርጉሞች ይህንን ክፍል ግልጽ ስላልሆነ እንዳለ አስቀምጠውታል። ሆኖም ግን ተርጉዋሚዎች “መልእክተኛ” በሚለውና “ቃልኪዳኑ” በሚለው መካከል ያለውን ግንኙነት “መልእክተኛው”እንደተሰጠው ተስፋና ቃልኪዳኑ ደግሞ እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር የገባውን ለማመልከት እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል። ሌላው አማራጭ ደግሞ መልዕክተኛ የተባለዉ ሰው ቃልኪዳኑን እንደሚያጸና ወይም አዲስ ቃልኪዳን እንደሚያውጅ መግለጽ ነው።

ነገር ግን እርሱ የሚመጣበትን ቀን መታገሥ የሚችል ማን ነው? እርሱስ በተገለጠ ጊዜ የሚቆም ማን ነው?
እነዚህ መልስ የማያስፈልጋቸው ጥያቄዎች የሚገልጹት ማንም ሰው በእግዚአብሔር ፊት መቆም እንደማይችል ነው።ሁለቱን ጥያቄዎች በማዋሃድ በአንድ አረፍተነገር እንደሚከተለው መግለጽ ይቻላል። “ማንም ቢሆን እግዚአብሔር ለፍርድ በሚመጣበት ጊዜ በፊቱ ሊቆም አይችልም”

እሱ በሚመጣበት ቀን
በዚህ ስፍራ “ቀን” የሚለው “ጊዜ” የሚለዉን ይወክላል፥ ስልሆነም “ በሚመጣበት ጊዜ” ይባል።

መታገስ የሚችል
በዚህ ስፍራ “መቆም” የሚለው የአንድን ሰው ጥቃት ወይም ተቃውሞን መቻቻምን ያሳያል።

እርሱ እንደ አንጥረኛ እሳትና እንደ አጣቢ ሳሙና ይሆናል
ይህ ዐረፍተነገር እግዚአብሔር በሚመጣበት ጊዜ ማንም ሰው ሊቆም አይችልም ለሚለው ምክንያት ለመስጠት ነው። ፍርድ ለመስጠት የእግዚአብሔር ሃይል ሰዎች ሓጢያት መስራታቸውን እንዲያቆሙ የተባለው ልብስ ለማንጻት ጠንካራ ሃይል እንዳለው ሳሙና ወይንም ብረታብረት ለማቅለጥ ሓይል እንዳለው እሳት ነው። የእነዚህ የአባባል መንገዶች የእግዚአብሔር ሃይል ማንኛውንም ነገር ለመስራት የሚከለክለው የለም ለማለት ነው።

የሌዊንም ልጆች ያጠራል፥
ለሌዊ ልጆች ይቅር ማለትና የሐጢአት መንገድ እንዳይከተሉ ማድረግ ብረታብረትን እንደማጥራት ይታያል። ስለዚህ “እሱ የሌዊን ልጆች ያስተካክላል፥ ሐጢያታቸውን ይቅር ይላል” ይባል።

የሌዊ ልጆች
በዚህ ስፍራ “ልጆች”የሚለው ዘሮቻቸውን ይወክላል።ወንድ የሌዊ ዘሮች ካህናት ወይም የቤተመቅደስ ሰራተኞች ናቸው።

እሱ ይቀመጣል
በዚህ ስፍራ መቀመጥ የብር አንጥረኛን ተግባር ያመለክታል።ይሄውም የብር አንጥረኛው ብር ወይም ወርቅ በሚያነጥርበት ጊዜ ቁጭ ብሎ እንደሚያነጥር ለማለት ነው። እንደዚሁም ደግሞ ንጉስ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ንጉስ ፍርድ እንደሚሰጥ ያለውን ተግባር ያመለክታል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እሱ እንደ ወርቅና ብር ያነጥራቸዋል
በዚህ ስፍራ ሰዎች ከእንግዲህ ሰዎች የሀጢያት መንገድ አይከተሉም፥ ነገርግን የወርቅና የብር አንጥረኛ የበለጠ እንደሚያጠራ የሚለዉን ያሳያል።

እነርሱም ለእግዚአብሔር በጽድቅ ቍርባንን የሚያቀርቡ ይሆናሉ
በዚህ ስፍራ “የጽድቅ” ማለት እግዚአብሄርን በጽድቅ ለማምለክ መሻት ማለት ስልሆነ፥ “እግዚአብሔርን ለማምለክ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ያለውን ቁርባን/ስጦታ ያመጣሉ” ለማለት ነው ።

Malachi 3:4

x
ሚልክያስ ንግግሩን በቁጥር 4 ሲቀጥል እግዚአብሔር ደግሞ እንደገና ንግግሩን በቁጥር 5 ይቀጥላል።

የይሁዳና የኢየሩሳሌም ቍርባን
“ይሁዳ” እና “ኢየሩሳሌም” የሚሉት ቃላት በእነዚያ ስፍራ የሚኖሩትን ህዝብ ይወክላሉ። ስለሆነም “በይሁዳና በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ህዝቦች የሚያመጡት ስጦታ/ቁርባን” ይባል።

እንደ ዱሮው ዘመንና እንደ ቀደሙት ዓመታት
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች አንድ ሲሆኑ ትኩረት የሚያደርጉት ግን ስጦታው/ቁርባኑ እግዚአብሔርን ያስደስት እንደነበር ነው። ስለዚህ “ባለፉት ዘመናት እንደነበረው” መባል አለበት።

ለፍርድ ወደ እናንተ እቀርባለሁ
በዚህ ስፍራ “ፍርድ” የመፍረድ ተግባርን ያመለክታል። ስለዚህ “ወደ እናንተ ቀርቤ እፈርድባችሁዋለሁ” መባል አለበት።

የምንደኛውን ደመመዝ በሚከለክሉ
“ተቀጥረው የሚሰሩትን ሰራተኞች ደመወዛቸውን በመከልከል ማሰቃየት”

የመጻተኛው ላይ ፊት ማዞር
የመጻተኛው የሚገባውን በመከልከል የሚጨቁኑ፥የአንድን ሰው መብት መከልከል ማለት ፊትን ከአንድ ሰው ላይ ማዞር እንደ ማለት ነው።ስለዚህ “በእስራኤል ውስጥ የሚኖሩትን ሰዎች መብት ትከለክላላችሁ” ማለት ይገባል።

Malachi 3:6

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩን ቀጠለ።

ወደፍጻሜ አልመጣችሁም
“ የጠፋችሁ አይደላችሁም”

ከአባቶቻችሁ ዘመን ጀምሮ ከሥርዓቴ ፈቀቅ ብላችኋል፥ እርስዋንም አልጠበቃችሁም ችሁ
እግዚአብሔርን አለመታዘዝ ማለት ፊትን ከእርሱ ላይ ማዞር ማለት ነው። ስለዚህ “ ከአባቶቻችሁ ዘመን ጀምሮ ስርአቴን አልጠበቃችሁም” ይባል።

ወደ እኔ ተመለሱ፥ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ
በዚህ ስፍራ እርስ በርስ መዋደድ ማለት ፊትን ወደእያንዳንዱ ማዞር ማለት ነው። ስለዚህ “ውደዱኝ አክብሩኝ እኔ ደግሞ እረዳችሁአለሁ” መባል አለበት።

የምንመለሰው እንዴት ነው?
ሰዎች ይህንን ጥያቄ የሚጠይቁት መቸነው ለእግዚአብሔር ያልታዘዝነው ለማለት ነው። ይሄንን ደግሞ በሚቀጥለው መንገድ መግለጥ ይቻላል፤ ከአንተ ወደየትም ስላልሄድን ወደአንተ እንዴት እንመለሳለን”።

Malachi 3:8

ሰው እግዚአብሔርን ይሰርቃልን?
ይህ ጥያቄ የሚያመለክተው ስርቆት/ ዘረፋ በጣም ክፉ መሆኑን ነው።እግዚአብሔር በዚህ ዐረፍተነገር ውስጥ እንደ ሶስተኛ ተናጋሪ ሆኖ ቀርቦአል። ስለሆነም እንደሚከተለው ይገለጽ “ሰው በእርግጥ እግዚአብሔርን መስረቅ የለበትም” ውይም “ማንም እኔን ምስረቅ የለበትም”

የሰረቅንህ በምንድር ነው?
ይህ ጥያቄ የሚያመለክተው ህዝቡ እግዚአብሄር እንደሚሰርቁ እድርገው ስለማይቆጥሩ ነው። ስለሆነም “እኛ አንተን አልሰረቅንህም” ይባል።

በአሥራትና በበኩራት
ይህ መልስ የተሰጠው ከእግዚአብሔር ስለ ሆን ሙሉ መልስ ነው። ስለዚህ “አስራትና በኩራቴን በመከልከል እኔን ሰርቃችሁኛላችሁ” ይባል።

በእርግማን ርጉሞች ናችሁ
በግልጽ “በእርግጥ ረግሜአችሁአልሁ” ማለት ይቻላል።

ሰርቃችሁኝል፥ ሕዝቡን ሁሉ
በዚህ ስፍራ “ሕዝብ” የሚለው የሚወክለው እግዚአብሄር እየተናገራቸው ያለውን ህዝብ ነው። ስለዚህ “በአገሩ ያላችሁ ህዝቦች ሁሉ” ማለት ይቻላል።

Malachi 3:10

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሄር ለእስራኤል ህዝብ መናግሩን ቀጥሎ

ሙሉ አስራት
“አሥራቱን ሁሉ”

የኔ ቤት
በዚህ ስፍራ “ቤት” የሚለው ቤተመቅደሱን ይወክላል።ስለሆነም “የኔ ቤተመቅደስ” ይባል።

እናም አሁን በዚህ ፈትኑኝ . . . የሰማይንም መስኮት ባልከፍትላችሁ፥
በዚህ ስፍራ “ፈትኑኝ” የሚያመለክተው ሰዎች የሚያደርጉትናማድረግ ያለባቸውን ነው። በዚህ ስፍራ “ብትፈትኑኝ” የሚለው በሁለት ዐረፍተነገሮች ሊከፈል ይችላል።ስለ ሆነም “እናም ብትፈትኑኝ. . . የሰማይ መስኮቶችን እከፍታለሁ” ወይም “ካደረጋችሁ . . . እናም ልትፈትኑኝ ትችላላችሁ፥የሰማይን መስኮት እከፍታለሁ” መባል አለበት።

አሕዛብ ሁሉ የተባረኩ ብለው ይጠሩአችኋል
በዚህ ስፍራ የተባረኩ የሚለው መባረክን ያመለክታል። ስለዚህ “አህዛብ ሁሉ እናንተ እንደተባረካችሁ ያውቃሉ” ይሁን።

አህዛብ ሁሉ
ይህ አገላለጽ በአገር ሁሉ ያሉትን ሕዝቦች ይመለከታል። ስለሆነም “በሁሉም አገር ያሉ ሕዝቦች” ይባል።

የተድላ ምድር
በዚህ ስፍራ “ተድላ” የሚወክለው የምድሪቱን ኑዋሪዎች የኑሮ ሲሆን በደስታ/ በተድላ መሆኑን ነው።

Malachi 3:13

አጠቃላይ መረጃ
ቁጥሮቹ አዲስ ሃሳብ ይጀምራሉ፥ እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ ይናገራል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ቃላችሁ በእኔ ላይ ጠንካራ ሆኖአል/በእኔ ላይ ጠንካራ ቃል ትናገራላችሁ።
በዚህ ስፍራ “ጠንካራ” ድፍረት የሚለውን ይወክላል፥ እንዲሁም ደግሞ “ቃላችሁ” የሚለው አባባል “እናንተ ያላችሁት” ማለት ስለሆነ “ ስለ እኔ እናንተ ያላችሁት ድፍረት ነው” መባል አለበት።

እኛ በአንተ ላይ ምን ክፉ ነገር ተናገርን?
ሰዎች እኛ ስለ እግዚአብሔር ምንም ክፉ ነገር አልተናገርንም ስለሚሉ ይህንን ጥያቄ ይጠይቃሉ። ይህ ደግሞ በሚክተለው ዐረፍተነገር ሊገለጽ ይችላል “እኛ እርስበርሳችን ስላንተ ምንም ክፉነገር አልተናገርንም”።

እናንተ ‘እግዚአብሔርን ማገልገል ከንቱ ነው፤ ትእዛዞቹን መጠበቅና እንደ ሐዘንተኞች በሠራዊት አምላክ ፊት መመላለስ ምን ይጠቅመናል?’
ሰዎቹ ይህንን ጥያቄ እርስ በርስ የሚጠያየቁት ቀጥሎ የተጠቀሰውን ለማለት ፈልገው ነው። “የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መጠበቅና በፊቱ በሐዘን ማገልገል አይጠቅምም”።

በሰራዊት ጌታ ፊት በሐዘን መሄድ
በዚህ ስፍራ “በሐዘን መሄድ” የሚለው ሐረግ “በሐዘን ስሜት” የሚለውን ይወክላል፤ምናልባትም ስለ ሀጢያታቸው ማዘንን ይጠቁማል።

በሠራዊት ጌታ ፊት
ይህ አገላለጽ ሰዎች የሚሰሩትን እግዚአብሔር ያውራል የሚለውን ይጠቁማል።

የተባረኩ ክፉዎች እንላለን
በዚህ ስፍራ “የተባረኩ የተባሉት” የሚለው ሐረግ መባረክን ያመለክታል። ስለዚህ “ክፉዎች ተባርከዋል” እንላለን።

የተባረኩ ክፉዎች እንላለን
ይህ አገላለጽ እንደሚከተለው ሊቀርብ ይችላል፥” ክፉዎች በብልጽግና ይኖራሉ እንላለን”።

ያመልጣሉ
“ከእግዚአብሔር ቁጣ ያመልታሉ” ለማለት ነው።

Malachi 3:16

እግዚአብሔርን የሚፈሩና ስሙንም የሚያከብሩ ሰዎች ለተግባራቸው መታሰቢያ በመጽሐፍ ተጻፈ።
ይህም ማለት 1)እስራኤላውያን መጸሐፍ የጻፉት ለእግዚአብሔር ቃል የገቡትና እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎችን ስም ዝርዝር ለማስታወስ ነበር፥ ወይም 2)እግዚአብሔር በመንግስተ ሰማይ አንድ ሰው እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎችን ስም እንዲጽፉ ያደርጋል ማለት ነው።

መታሰቢያ መጽሐፍ
ይህ አገላልጽ የሚያመለክተው ሕዝቡ ጠቃሚ የሆኑ ነገሮችን፤ ክስተቶችንና ባለፉት ዘመናት የኖሩትን ሰዎች ለማስታውስ የሚረዱ መጸሀፍትን ለማመልከት ነው።

ስሙን ማክበር
በዚህ ስፍራ “የሱን ስም” የሚለው እግዚአብሔርን ያመለክታል።

Malachi 3:17

እነሱ የኔ ይሆናሉ
“እነሱ የኔ ሕዝብ ይሆናሉ”

የእኔ የግሌ ገንዘብ ይሆናሉ
በዚህ ስፍራ “ንብረት” የሚለው የአንድን ሰው የግል ንብረት ያመለክታል። ይህን ሀሳብ በሚቀጥለው መንገድ መግለጥ እንችላለን፥”እነሱ ለኔ ሙሉ በሙሉ የተገቡ ይሆናሉ”።

እኔ በምሠራበት ቀን
የዚህ አገላለጽ የሚያመለክተው እግዚአብሔር በፍርድ ጊዜ አመጸኞቹን እስራኤላውያን በሚቀጣበትና ለታማኞቹ እስራኤላውያን ድል የሚሰጥበትን ነው።

በመካከል ልዩነት ይሆናል
“በመካከል ልዩነት ታያላችሁ” ወይም “በልዩነት ትታያላችሁ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Chapter 4

1 “እብሪተኞችና ክፉ አድራጊዎች በሙሉ ገለባ የሚሆኑበት እንደምድጃ እሳት የሚነድ ቀን ይመጣል። የሚመጣው ቀን ያነዳቸዋል” ይላል የሠራዊት ጌታ ያህዌ፤ “ሥርም ሆን ቅርንጫፍ አይተውላቸውም። **2** ስሜን ለምትፈሩ ለእናንተ ግን ፈውስ በክንፎቹ የያዘ የጽድቅ ፀሐይ ይወጣላቸዋል። እናንተም ከጋጥ እንደተለቀቁ እንቦሳ እየቦረቃችሁ ትወጣላችሁ። **3** እኔ በምሠራበት ቀን ዐመፀኛውን ትረግጣላችሁ፤ ከእግራችሁ ጫማ በታች ዐመድ ይሆናሉ” ይላል የሠራዊት ጌታ ያህዌ። **4** ለእስራኤል ሁሉ ሕጎችና ሥርዐቶች ይሆኑ ዘንድ ለአገልጋዬ ለሙሴ በኮሬብ የሰጠሁትን ትምህርቶች አስታውሱ። **5** ታላቁና አስፈሪው የያህዌ ቀን ከመምጣቱ በፊት ነቢዩ ኤልያስን እልክላችኋለሁ። **6** መጥቼ ምድርን ፈጽሜ እንዳላጠፋ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች የልጆችንም ልብ ውደ አባቶች ይመልሳል።

Malachi 4:1

እይ
“ተመልከት” ወይም “አድምጥ” ወይም “ለምነግርህ ነገር ትኩረት ስጥ”

ጊዜው እየመጣ ነው፥ እንደ ገለባ በእሳት የሚቃጠሉበት
ሊመጣ ያለው የጥፋት ቀን ራሱ እንደሚያቃጥል ይነገራል። የእግዚአብሔር የፍርድ ቀን ብዙውን ጊዜ እሳት እንደ ሆነ ይነገራል።

ትዕቢተኞች . . . ክፉ አድራጊዎች
x

ሁሉም ትዕቢተኞችና ክፉአድራጊዎች ገለባ ይሆናሉ
እነዚህ ህዝቦች ገለባ ስለሆኑ ዕድላቸው መቃጠል ነው። በመጸሐፍ ቅዱስ ስዎች በዕጽዋትና በዛፍ መመሰላቸው የተለመደ ነው። ስለዚህ “ሁሉም ትዕቢተኞች እንደ ደረቀ ገለባ ይቃጠላሉ” ይባል።

ቀኑ ሲመጣ ያቃጥላቸዋል
በዚህ ስፍራ “ቀኑ” የሚለው በዚያን ቀን የሚሆነውን ያመለክታል። ስለሆነም “በዚያን ቀን እኔ አቃጥላቸዋለሁ" ይባል።

ከእነርሱ ሥር፥ ወይም ቅርንጫፍ አይቀርም
ይህ አገላለጽ ሰዎችን በዕጽዋትና በዛፎች እየመሰለ ይቀጥላል። ስለዚህ ስርና ቅርንጫፍ አይኖራችሁም ሲል በእርግጥ ትሞታላችሁ ለማለት ነው። ስለሆነም “ምንም አይቀርም” ይባል።

እናንተ ስሜን የምትፈሩ
በዚህ ስፍራ “የኔ ስም” የሚለው እግዚአብሔርን ይተካል።

የጽድቅ ፀሐይ ይወጣላችኋል፤ ፈውስንም በክንፎችዋ ውስጥ ትሆናለች
ይህም ማለት 1) እግዚአብሔር በጽድቅ በሚሰራበት በዚያን ቀን ሕዝቡን ይፈውሳል ወይም 2) በዚያን ቀን እግዚአብሔር ሕዝቡን በጽድቅ ይገልጣል ይፈዉሳቸዋልም

ፈውስ በክንፎቹ ውስጥ
አማራጭ ትርጉሞች 1) የአንድ ሰው ፈውስ ጸሀይ በክንፎችዋ ተሸክማ እንደምታደርስ ነገር ይነገራል 2) ፈውስ የሚሰራው በክንፎች ስር እንደሆነ፥ ማለትም እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚያደርገው ጥበቃ ናቸው።

ክንፎች
በጥንታዊ የመካከለኛው ምስራቅ አገሮች ፀሐይ ክንፍ እንዳላትና ሰማይን እንደምታቁዋርጥ ይታሰብ ነበር። በዚህም መሰረት ሁለት አማራጭ ትርጉሞች እንደሚከተለው ነው። 1) የፀሀይ ህይወት ሰጪ ጨረሮች በክንፍዋ እንዳለ ይነገራል። ወይም 2) ክንፎቹዋ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ሰላምና ደህንነት በመስጠት እንደ እንደሚሸፍናቸው ነው።

ከጕረኖ እንደ ተለቀቀ ጥጃ ትቦርቃላችሁ
እንደተለቀቃችሁ የእግዚአብሔር ሕዝብ ፤ ተብሎ የተነገረው እንደ ተለቀቀ ጥጃ ወደመሰማሪያ መሄድን ያመለክታል።

ክፉዎች በእግራችሁ ጫማ ሥር እንደ ዐመድ ሆነው ይረገጣሉ
በዚህ ስፍራ የእግዚአብሔር ሕዝብ በተቃጠው በጠላት ሬሳ ላይ ይራመዳሉ ለማለት ነው።

ዐመድ ይሆናሉ
የእስራኤል ጠላቶች ተቃጥለው አመድ ይሆናሉ ለማለት ነው።

Malachi 4:4

በሲና ተራራ ላይ ለአገልጋዬ ለሙሴ የሰጠሁትን ትምህርት ሕግና ትእዛዝ አስታውሱ
“ትምህርት” የተባለው የተማሩትን ለማለት ነው። ስለዚህ “ አገልጋዬን ሙሴን ያስተማርኩትን” ይባል።

አስታውሱ
በዚህ ስፍራ “አስታውሱ” የተባለው “ ስለዚህ ነገር አስቡ” እንዲሁም “ታዘዙዝ” ለማለት ነው።

ሆሬብ
ይህ የሲና ሌላው ስም ነው።

እስራኤል ሁሉ
በዚህ ስፍራ “እስራኤል ሁሉ” የሚለው በእስራኤል አገር የሚኖሩትን ሕዝብ ለማለት ነው።

ሕጉን/ደንብ
ይህ ሕግ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ሁሉ የሰጠው ነው።

ትዕዛዞች
እነዚህ ሕጋዊ ዉሳኔዎች በየእለቱ በህይወታቸው በአጠቃላይ ሕጉ እንዴት ስራላይ ሊዉል እንደሚችል ግልጽ የሚያደርጉ ናቸው።

ታላቁና አስፈሪው የእግዚአብሔር ቀን መምጣት
የዚህ ቀን መምጣት የተገለጸው እየመጣ ነው በማለት ነው።ስለዚህ “ታላቁና አስፈሪው የእግዚአብሔር ቀን ከመምጣቱ በፊት” ይባል።

ታላቁና አስፈሪው የእግዚአብሔር ቀን
ይህ አገላለጽ የሚያመለክተው እግዚአብሔር የመከራ ቀን የሚያመጣበትን ጊዜ ነው።

እርሱ የወላጆችን ልብ ወደ ልጆች፥ የልጆችንም ልብ ወደ ወላጆች ይመልሳል
በዚህ ስፍራ ይመልሳል/ ይለዉጣል የተባለው ልባቸውን ይመልሳል ለማለት ነው።

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Matthew

Matthew

ምዕራፍ 1

1 የዳዊት ልጅ፣ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ መጽሐፍ። 2 አብርሃም ይስሐቅን ወለደ፤ ይስሐቅም ያዕቆብን ወለደ፤ ያዕቆብም ይሁዳንና
የይሁዳን ወንድሞች ወለደ፤ 3 ይሁዳም ከትዕማር ፋሬስንና ዛራን ወለደ፤ ፋሬስም ኤስሮምን ወለደ፤ ኤስሮምም አራምን ወለደ፤ 4 አራምም አሚናዳብን ወለደ፤
አሚናዳብም ነአሶንን ወለደ፤ ነአሶንም ሰልሞንን ወለደ፤ 5 ሰልሞንም ከረዓብ ቦዔዝን ወለደ፤ ቦዔዝም ከሩት ኢዮቤድን ወለደ፤ ኢዮቤድም እሴይን ወለደ፤
እሴይም ንጉሥ ዳዊትን ወለደ። 6 ንጉሥ ዳዊትም ከኦርዮ ሚስት ሰሎሞንን ወለደ፤ 7 ሰሎሞንም ሮብዓምን ወለደ፤ ሮብዓምም አብያን ወለደ፤ አብያም አሳፍን
ወለደ፤ 8 አሳፍም ኢዮሣፍጥን ወለደ፤ ኢዮሣፍጥም ኢዮራምን ወለደ፤ ኢዮራምም ዖዝያንን ወለደ፤ 9 ዖዝያንም ኢዮአታምን ወለደ፤ ኢዮአታምም አካዝን ወለደ፤
አካዝም ሕዝቅያስን ወለደ፤ 10 ሕዝቅያስም ምናሴን ወለደ፤ ምናሴም አሞጽን ወለደ፤ አሞጽም ኢዮስያስን ወለደ፤ 11 ኢዮስያስም በባቢሎን ምርኮ ጊዜ
ኢኮንያንንና ወንድሞቹን ወለደ። 12 ከባቢሎን ምርኮ በኋላም፣ ኢኮንያን ሰላትያልን ወለደ፤ ሰላትያልም ዘሩባቤልን ወለደ፤ 13 ዘሩባቤልም አብዩድን ወለደ፤
አብዩድም ኤልያቄምን ወለደ፤ ኤልያቄምም አዛርን ወለደ፤ 14 አዛርም ሳዶቅን ወለደ፤ ሳዶቅም አኪምን ወለደ፤ አኪምም ኤልዩድን ወለደ፤ 15 ኤልዩድም
አልዓዛርን ወለደ፤ አልዓዛርም ማታንን ወለደ፤ ማታንም ያዕቆብን ወለደ፤ 16 ያዕቆብም ክርስቶስ ተብሎ የሚጠራውን ኢያሱስን የወለደችውን፣ የማርያምን ባል
ዮሴፍን ወለደ። 17 ከአብርሃም እስከ ዳዊት፣ የነበሩት ትውልዶች ሁሉ ዐሥራ አራት፤ ከዳዊት እስከ ባቢሎን ምርኮ ድረስም እንደዚሁ ዐሥራ አራት፤ ከባቢሎን
ምርኮ እስከ ክርስቶስ ድረስ የነበሩትም ዐሥራ አራት ትውልዶች ናቸው። 18 የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በሚከተለው መንገድ ተፈጸመ፦ እናቱ ማርያም ዮሴፍን
ልታገባው ታጭታ ነበር፤ ነገር ግን ሳይጋቡ በመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች። 19 ዮሴፍ ጻድቅ ነበረ፤ በመሆኑም እርሷን በሕዝብ ፊት ሊያዋርዳት አልፈለገም።
ስለዚህ ከእርሷ ጋር የነበረውን የዕጮኛነቱን ግንኙነት በምስጢር ለማቋረጥ ወሰነ። 20 ዮሴፍ ስለ እነዚህ ነገሮች እያሰበ ሳለ፣ የጌታ መልአክ፣ "የዳዊት ልጅ
ዮሴፍ ሆይ፣ ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ፤ ምክንያቱም እርሷ የፀነሰችው በመንፈስ ቅዱስ ነው። 21 እርሷ ወንድ ልጅ ትወልዳለች፣ ሕዝቡንም ከኃጢአታቸው
ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ብለህ ትጠራዋለህ" በማለት ተገለጠለት። 22-23 ይህ ሁሉ የሆነው፣ "እነሆ ድንግል ትፀንሳለች፤ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤
ስሙንም ዐማኑኤል ብለው ይጠሩታል፤ ትርጓሜውም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው ማለት ነው" ብሎ ጌታ በነቢይ የተናገረው እንዲፈጸም ነው። 24 ዮሴፍ
ከእንቅልፉ ነቃ፣ የጌታ መልአክ አዝዞት እንደ ነበረውም አደረገ፦ ማርያምን እን ደሚስቱ ወሰዳት። 25 (ይሁን እንጂ፣ ልጅ እስከምትወልድ ድረስ ከእርሷ ጋር
ግንኙነት አላደረገም።) የሕፃኑንም ስም ኢየሱስ አለው።

Matthew 1:1

ማቴዎስ **1**:**1-3**
አጠቃላይ መረጃ ጸሐፊው ኢየሱስ ከዳዊት እና ከአብርሃም ዘር እንደመጣ ለማሳየት ጽሑፉን የጀመረው ከኢየሱስ የዘር ሀረግ ነው። ይህ የዘር ሀረግ ዝርዝር እስክ ዲረስ ይቀጥላል MAT 1:17 የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ መጽሐፍ ይህ የኢየሱስ ትውልድ ዝርዝር ነው። የዳዊት ልጅ፥ የአብርሃም ልጅ በኢየሱስ፥ በዳዊት እና በአብረሃም መካከል ብዙ ትውልዶች አሉ። በዚህ ሥፍራ "ልጅ" ማለት "ዘር' ማለት ነው። "የዳዊት ልጅ የሆነው እርሱ የአብርሃምም ልጅ ነው።" የዳዊት ልጅ አንዳንድ ጊዜ "የዳዊት ልጅ" የሚልው ሀረግ እንደ ስያሜ ሆኖ ያገልግላል ነገር ግን በዚህ ሥፍራ ላይ የኢየሱስን ቅድመ አያቶች ለማሳየት የገባ ቃል ነው። አብርሃም የይሳቅ አባት ነው። ይህንን በተለያዩ መንገዶች መተርጎም ይቻላል። በዬትኛውም መንገድ ተርጉሙት በዘር ሀርግ ዝርዝር ውስጥ ተመሳሳ በሆነ መልኩ መተርጎሙ ጥሩ ነው። ትርጉም፡ "አብርሃም የይሳቅ አባት ሆነ" ወይም "አብርሃም ይሳቅ የሚባል ልጅ ነበረው።" ፋሬስንና ዛራን . . . ኤስሮምን . . . አራም እነዚህ የሰዎች ስም ። ፋሬስን . . . አባት ነው ኤስሮም . . . ነው።

Matthew 1:4

ማቴዎስ **1**፥**4-6**
ሰልሞንም የቦኤዝ አባት ነው "ሰልሞን የቦኤዝ አባት ነው፤ የቦኤዝ እናት ደግሞ ረአብ ናት" ወይም "ሰልሞን እና ረአብ የቦኤዝ ወላጆች ናቸው።" ቦኤዝ የኢዮቤድ አባት ነው፤ የኢዮቤድም እናት ሩት ናቴ" ወይም "ቦኤዝ እና ሩት የኢዮቤድ ወላጆች ናቸው። ዳዊትን የኦርዮ ሚስት ከነበረችው ምስቱ ሰሎሞንን ወልዶ አባቱ ሆን ወይም "ዳዊት እና የኦርዮ ሚስት የነበረችው ምስቱ የሰለሞን ወላጆች ናቸው። የኦርዮ ሚስት የነበረችው ሰለሞን የተወለደው ኦርዩ ከሞተ በኃላ ነው።

Matthew 1:7

ማቴዎስ **1**፥ **7-8**
አሳ አንዳንድ ጊዜ "አሳፍ" ተብሎ ይተረጎማል። የዖዝያን ትክክለኛ ስሙ ሮብዓም፥ ስለዚህም "አባት" የሚለው ቃል "የዘር ሀረግ" ተብሎ መተርጎም ይችላል። ሰሎሞንም ሮብዓምን ወለደ፤ ሮብዓምም አቢያን ወለደ፤ (UDB).

Matthew 1:9

ማቴዎስ **1**፥ **9-11**
አሞን አሞን አንዳንድ ጊዜ "አሞፅ" ተብሎ ይተረጎማል። ኢዮስያስ የኢኮንያንን አባት ነው እውነታው ኢዮስያስ የኢኮንያንን አያት ነው። በባቢሎንም ምርኮ ጊዜ "ወደ ባቢሎን በምርኮ ተገደው እንዲሄዱ ሲድረግ" ወይም "ባቢሎናዊያን ቁጥጥር በሆኑ ጊዜና ወደ ባቢሎን እንዲሄዱ ስያስገድዷቸው።" በቋንቋችሁ ማን ወደ ባቢሎን እንደሄደ መግለጽ አስፈላጊ ከሆነ እንዲህ ማለት ትችላላችሁ "እስራኤላዊያን" ወይም "በይሁዳ ይኖሩ የነበሩ እስራኤላዊያን" ባቢሎን በዚህ ሥፍራ ላይ ባቢሎን የሚለው ቃል የሚያመለክተው ባቢሎን የተሰኘችውን ሀገር እንጂ የባቢሎን ከተማን ብቻ አይደለም።

Matthew 1:12

ማቴዎስ **1**፥ **12-14**
ከባቢሎንም ምርኮ በኋላ MAT 1:11. ላይ ከተጠቀምከው ቃል ጋር ተመሳሳይ ቃልን ተጠቀም። ሰላትያል የዘሩባቤል አባት ነው እውነታው ሰላትያል የዘሩባቤል አያት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Matthew 1:15

ማቴዎስ **1፥ 15-17**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ጸሐፊው በ MAT 1:1. ላይ የጀመረውን የኢየሱስን የትውልድ ሀርግ ያጠናቅቃል። ኢየሱስን የወለደችው ማሪያም ኤቲ፡ "ኢየሱስን የወለደችው ማሪያም" (ይመልከቱ) ክርስቶስ የተባለው ይህ እንዲህ ልተረጎም ይችላል፡ ኤቲ፡ "ሰዎች ክርስቶስ ብለው የሚጠሩት።" (ተመልከቱ) ዐሥራት አራት "14" (ተመልከቱ) የባቢሎን ምርኮ MAT 1:11. ላይ ከተጠቀምከው ቃል ጋር ተመሳሳይ ቃልን ተጠቀም።

Matthew 1:18

ማቴዎስ **1፥ 18-19**
አጠቃላይ መረጃ ይህ ክፍል ጸሐፊው ለኢየሱስ መወለድ ምክንያት የሆኑ ሁኔታዎችን የገለጸበት የታርኩ አዲሱ ጅማሬ ነው። እናቱ ማርያም ለዮሴፍ ታጭታ ነበር "እናቱ ማርያም ዮሴፍን ልታገባ ነበር።" ብዘመኑ ወላጆች ለልጆቻቸው ትዳር አጋር ያዘጋጁ ነበር። ኤቲ፡ "የኢየሱስ እናት የሆነችው ሪያም ወላጆቿ ለዮሴፍ እርሷን ለመዳር ተስማምተዋል።" (ተመልከት) እናቱ ማርያም ታጭታ ነበር ማርያም ለዮሴፍ ታጭታ በነበረበት ወቅት ኢየሱስ አለመወለዱን በሚያሳይ መንገድ ተርጉሙት። ኤቲ፡ "ኋላ ላይ ኢየሱስን የወለደችው ማሪያም ታጭታ ነበር" ሳይገናኙ "ከመጋባታቸው በፊት።" ይህ ዮሴፍ እና ማሪያም አብረው ከመተኛታቸው በፊት" የሚለውን የሚያመልክት ይሆናል። ኤቲ፡ "አብረው ከመተኛታቸው በፊት"። (ተመልከት) አርግዛ ተገኘች ይህ እንዲህ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “ልጅ ልትወልድ እንደሆነ አወቁ” ወይም “አረገዘች።” (ተመልከት) በመንፈስ ቅዱስ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ማሪያም ከሰው ጋር ሳትተኛ ማርገዝ እንድትችል አደረጋት። ባሏ ዮሴፍ ዮሴፍ ማሪያምን ገና አላገባትም ነበር ይሁን እንጂ አንድ ወንድ እና አንድ ሴት ትዳር ለመጋባት ቃል ከተገባቡ ምንም እንኳ አብረው መኖር ባይጀምሩም አይሁዶች ባል እና ምስት አድርገው ይቆጥሯቸው ነበር። ከእርሷ ጋር የተነበረውን እጮኝነት ለማቆም “ለመጋባት የነበራቸውን እቅድ ለመሰረዝ”

Matthew 1:20

ማቴዎስ **1፡ 2-22**
እንዳሰበው “ዳዊት እንዳሰበው” በሕልም ተገለጠለት “ለዮሴፍ በሕልም ተገልጦለት” የዳዊት ልጅ በዚህ ሥፍራ “ልጅ” ማለት “የልጅ ልጅ” ማለት ነው። በማሕጸኗ ውስጥ የተሸከመችው ልጅ የተጸነሰው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ነው ይህ እንዲህ ባለ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “መንፈስ ቅዱስ ማሪያም እንዲትጸንስ አደረገ።” (ተመልከት) ወንድ ልጅ ትወልዳለች እግዚአብሔር መልአክን ስላዘዘ መልአኩ የተወለደው ወንድ ልጅ እንደሆነ ያውቅ ነበር። እንዲህ ብለሽ ትጠሪዋለሽ ይህ ትዕዛዝ ነው። ኤቲ፡ “እንዲህ ብለሽ ጥሪው” ወይም “እንዲህ የሚል ስም ልትሰጪው ይገባል። ያድናልና በዚህ ሥፍራ ላይ ተርጓሚዎች እንዲህ የሚል የግሪጌ ማስታወሻ መጨመር ይችላሉ፡ “ኢየሱስ የሚለው ስም ጌታ ያድናል ማለት ነው። ሕዝቡን ይህ የሚያመለክተው አይሁዳዊያንን ነው

Matthew 1:22

ማቴዎስ **1፡22-23**
አጠቃላይ መረጃ ጸሐፊው የኢየሱስ አወላለድ በቅዱሳት መጽሐፍት አስቀድሞ በተነገረው መሠረት መሆኑን ለማሳየት ከነብይ ኢሳያስ መጽሐፍ ጠቅሶዋል። (ተመልከት) ይህ ሁሉ ሆነ መልአኩ መናገር አቁሟል። አሁን ማቴዎስ መልአኩ የተናገረው ነገር ምን ያኽል አስፈላጊ እንደሆነ እያብራራ ነው። ጌታ በመላዕክቱ አማካኝነት የተናገረው ነገር ይህ እንዲህ ባለ መንገድ ሊገለጽ ይችላል፡ ኤቲ፡ “ጌታ ለነብይ ኢሳያስ ከብዙ ዘመናት በፊት የተናገረው እንዲጽፍ የነገረው ነገር።” (ተመልከት) እነሆ . . . አማኑኤል በዚህ ሥፍራ ላይ ማቴዎስ ከነብዩ ኢሳያስ መጽሐፍ ጠቅሷል። እነሆ ይህ ቃል ሰዎች ከዚህ በኋላ ለሚነገረው ነገር አጽኖት እንዲሰጡ የሚጨመር ቃል ነው፡ ኤቲ፡ “ተመልከቱ” ወይም “አድምጡ” ወይም “አሁን ለምነግራችሁ ነገር ትኩረት ስጡ”:: አማኑኤል ይህ የወንድ ስም ነው። (ተመልከት) “እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው” ማለት ነው ይህ በኢሳያስ መጽሐፍ ውስጥ የለም። ማቴዎስ የስሙን ትርጉም እያብራራ ነው። ይህን ለብቻው በአንድ ዐረፍተ ነገር መተርጎም ትችላላችሁ። ኤቲ፡ “የዚህ ስም ትርጉም “እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው” ማለት ነው።

Matthew 1:24

ማቴዎስ **1፡24-25**
አያያዥ ዐረፍተ ነገር ጸሐፊው የኢየሱስ አወላለድን ምን ይመስል እንደነበር የሰጠውን ገለጻ አጠናቀቀ። የጌታ መልአክ ባዘዘው መሠረት መልአኩ ዮሴፍን ማሪያምን ምስቱ አድርጎ እንዲወስዳት እና የልጁንም ስም ኢየሱስ እንዲለው አዘዘው። እርሱም እርሷን ምስቱ አድርጎ ወሰዳት “አገባት” ለልጁ ዮሴፍ እውነተኛ አባቱ አለመሆኑን ግልጽ መሆኑን እርግጠኞች ሁኑ። ኤቲ፡ “ወንድ ልጅ” ወይም “ለልጁ” እና ኢየሱስ ብሎ ስም ጠራው “ዮሴፍ ሕጻኑን ኢየሱስ የሚል ስም አወጣለት”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 2

1 በንጉሥ ሄሮድስ ዘመን ኢየሱስ በቤተ ልሔም ይሁዳ ከተወለደ በኋላ፣ ጠቢባን ሰዎች ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጡ። እንደዚህም በማለት ጠየቁ፤ 2 ‹‹የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ የት ነው? የእርሱን ኮከብ በምሥራቅ አየን፣ ልንሰግድለትም መጥተናል።›› 3 ንጉሡ ሄሮድስ ይህን ሲሰማ ተረበሸ፤ መላው ኢየሩሳሌምም ከእርሱ ጋር ታወከ። 4 ሄሮድስ የካህናቱን አለቆችና የሕዝቡን የሕግ መምህራን ሰብስቦ፣ ‹‹ክርስቶስ የሚወለደው የት ነው?›› በማለት ጠየቀ። 5 ‹‹በቤተ ልሔም ይሁዳ›› አሉት፤ በነቢዩ የተጻፈው ይህ ነውና፡ 6 በይሁዳ ምድር የምትገኚ አንቺ ቤተ ልሔም፣ ከይሁዳ ገዦች በምንም አታንሺም፣ ሕዝቡን እስራኤልን የሚጠብቅ ገዥ፣ ከአንቺ ይወጣልና። 7 ከዚያም በኋላ ሄሮድስ ኮከቡ በትክክል በምን ሰዓት ታይቶ እንደ ነበር ሊጠይቃቸው ጠቢባኑን በምስጢር ጠራቸው። 8 ወደ ቤተ ልሔምም ላካቸው፤ ‹‹ሂዱና ሕፃኑን በጥንቃቄ ፈልጉ። ስታገኙት እኔም ደግሞ እንድመጣና እንድሰግድለት ንገሩኝ›› አላቸው። 9 ንጉሡ የተናገረውን ከሰሙ በኋላ ሄዱ፤ በምሥራቅ አይተውት የነበረውም ኮከብ ሕፃኑ በነበረበት ላይ እስኪደርስና እስኪቆም ድረስ በፊታቸው ይሄድ ነበር። 10 ጠቢባኑ ኮከቡን ባዩት ጊዜ፣ እጅግ በጣም ተደሰቱ። 11 ወደ ቤት ገብተው ሕፃኑንም ከእናቱ ከማርያም ጋር አዩት፤ ተንበርክከውም ሰገዱለት። ሣጥኖቻቸውንም ከፍተው የወርቅ፣ የዕጣንና የከርቤ ስጦታ አቀረቡለት። 12 እግዚአብሔር ጠቢባኑን ወደ ሄሮድስ ተመልሰው እንዳይሄዱ በሕልም አስጠነቀቃቸው፤ ስለዚህም በሌላ መንገድ ወደ አገራቸው ሄዱ። 13 ጠበባኑ ከሄዱ በኋላ፣ የጌታ መልአክ ለዮሴፍ በሕልም ተገለጠለትና፣ "ተነሥ፣ ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ ወደ ግብፅ ሽሽ። እኔ እስክነግርም ድረስ እዚያ ቈይ፤ ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው ይፈልጋልና" አለው። 14 በዚያ ሌሊት ዮሴፍ ተነሣ፣ ሕፃኑንና እናቱንም ይዞ ወደ ግብፅ ሄደ። 15 ሄሮድስ እስኪሞት ድረስ እዚያው ቈየ። በዚህም ጌታ፣ ‹‹ልጄን ከግብፅ ጠራሁት›› ብሎ በነቢዩ የተናገረው ቃል ተፈጸመ። 16 ከዚያም ሄሮድስ ጠቢባኑ እንደ ተሣለቁበት ሲገነዘብ በጣም ተናደደ። በቤተ ልሔምና በዚያ አውራጃ የነበሩ ወንድ ሕፃናትን፣ እንደዚሁም ሁለት ዓመትና ከዚያም በታች የሆኑትን ሁሉ ከጠቢባኑ በትክክል በተረዳው ጊዜ መሠረት ልኮ አስፈጀ። 17 በዚያም በነቢዩ ኤርምያስ ተነግሮ የነበረው፡- 18 ‹‹ድምፅ በራማ ተሰማ፣ ልቅሶና መሪር ዋይታ፣ ራሔል ስለ ልጆቿ በማልቀስ፣ ለመጽናናትም እምቢ አለች፣ በሕይወት የተረፈ የለምና›› የሚለው ተፈጸመ። 19 ሄሮድስ ሲሞት፣ እነሆ፣ የጌታ መልአክ በግብፅ ለዮሴፍ በሕልም ተገለጠለትና፣ 20 ‹‹ሕፃኑን ሊገድሉት የፈለጉት ስለ ሞቱ፣ ተነሣ፤ ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ ወደ እስራኤል አገር ሂድ›› አለው። 21 ዮሴፍ ተነሣ፣ ሕፃኑንና እናቱን ይዞ ወደ እስራኤል አገር ሄደ። 22 አርኬላዎስ በአባቱ በሄሮድስ ስፍራ ተተክቶ ይሁዳን ይገዛ እንደ ነበረ ሲሰማ ግን ወደዚያ ለመሄድ ፈራ። እግዚአብሔር በሕልም ካስጠነቀቀው በኋላ፣ ወደ ገሊላ አውራጃ ሄደ፤ 23 ናዝሬት በምትባል ከተማ ውስጥም ኖረ። ይህ በነቢዩ ተነግሮ የነበረውን፣ ናዝራዊ ተብሎ ይጠራል የሚለውን እንዲፈጸም አደረገ።

Matthew 2:1

ማቴዎስ 2:1-3
አጠቃላይ መረጃ የታሪኩ አዲስ ክፍል የሚጀምረው በዚህ ሥፍራ ላይ ነው። ከዚያም እስከ ምዕራፉ መጨረሻ ድረስ ይሄዳል። ጸሐፊው ሄሮዶስ አዲሱን የአይሁድ ንጉሥ ለመግደል ስላደረገው ሙከራ ይነግረናል። ቤተልሔም ይሁዳ “በይሁዳ ግዛት ውስጥ የሚትገኝ የቤተልሔም ከተማ” ሄሮዶስ ንጉሥ በነበረበት ዘመን “በዚያ ሄሮዶስ ንጉሥ ሆኖ ሳለ” ሄሮዶስ ሄሮዶስ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ታላቁን ሄሮዶስን ነው። የተማሩ ሰዎች “ክዋክብትን ያጠኑ ሰዎች” (UDB) ከምስራቅ የመጡ “ከይሁዳ በስተምስራቅ በኩል ከሚገኝ ሀገር የመጡ” የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ዬት አለ? ሰዎቹ ከክዋክብት ጥናታቸው የአይሁድ ንጉሥ ለመሆን የተወለደ ልጅ እንዳለ አውቀዋል። በዬት ሥፍራ እንዳለ ለማወቅ ፈልገዋል። ኤቲ፡ “የአይሁድ ንጉሥ ለመሆን አንድ ልጅ ተወልዷል። ዬት ነው ያለው?” የእርሱ ኮከብ ኮከቧ ትክክለኛ ባለቤት ልጁ ነው እያሉ አይደለም። ኤቲ፡ “ስለ እርሱ የሚትናገረው ኮከብ” ወይም “ከእርሱ መወለድ ጋር የተያያዘችው ኮከብ” በምስራቅ “በምስራቅ በወጣች ጊዜ” ወይም “በሀገራችን ሳለን” ማምለክ አማራጭ ትርጉሞች 1) ልጁ መለኮት እንደሆነ ተገንዝበው ለማምለክ ፈልገዋል ወይምመ 2) እንደ አንድ ንጉሥ ልያከብሩት ፈልገዋል። ቋንቋዋችሁ ሁለቱንም ትርጉሞች መያዝ የሚችል ቃል ካለው በዚህ ሥፍራ ላይ ይህንን ቃል መጠቀምንን ከግንዛቤ ውስጥ አስገቡ። ተጨነቀ “ፈራ”። ይህ ልጅ ንግሥናዬን ይቀማኛል ብሎ በመፍራት ተጨነቀ። ኢየሩሳሌም በሙሉ በዚህ ሥፍራ ላይ “ኢየሩሳሌም” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰዎችን ነው። እንዲሁም “ሁሉም” ማለት “ብዙ” ማለት ነው። ማቴዎስ በዚህ ሥፍራ ላይ ብዙ ሰዎች በዚህ ጉዳይ መጨነቃቸውን ለማመልከት ግነት ተጠቅሟል። ኤቲ፡ “በኢየሩሳሌም ያሉ ብዙ ሰዎች።” (UDB) (and ተመልከት)

Matthew 2:4

ማቴዎስ 2:4-6
አጠቃላይ መረጃ በቁጥር 6 ላይ ካህናት አለቆች እና ጸሐፊት ክርስቶስ በቤተልሔም ከተማ እንደሚወል ከሚልክያስ መጽሐፍ በመጥቀስ አሳይተዋል። በቤተልሔም ይሁዳ “በይሁዳ ግዛት የሚትገኘው ቤተልሔም ውስጥ” ይህ በነብያት የተነገረው ነገር ነው ይህ እንዲህ ባለ መንገድ ሊገለጽ ይችላል፡ ኤቲ፡ “ይህ ነቢያት ከብዙ ዘመናት በፊት የጻፉት ነገር ነው።” (፡ ተመልከት) እና አንች፣ ቤተልሔም . . . ኢስራኤል ከሚልክያስ መጽሐፍ ላይ እየጠቀሱ ነው። አንች፣ ቤተልሔም . . . ከይሁዳ መሪዎች መካከል መጨረሻ አይደለሽም ሚልክያስ በቤተልሔም ይኖሩ ለነበሩ ሰዎች ከእርሱ ጋር እንደሆኑ አድርጎ ይነግራቸው ነበር ነገር ግን እነርሱ ጋር ከእርሱ ጋር አልነበሩም። በተጨማሪም “የመጨረሻ አልነበሩም” ይህ አዎንታዊ በሆነ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። ኤቲ፡ “እናንተ የቤተልሔም ሰዎች . . . ከተማችሁ በይሁዳ ግዛት ውስጥ ከሚገኙ ከተሞች መካል ትልቁ ነው።” (እና ተመልከቱ) ሕዝቤን ኢስራኤል የሚጠብቅ ማን ነው ሚልክያስ እነዚህን ገዥዎችን እንደ እርኛ አድርጎ ይናገራቸዋል። ይህ ማለት ሕዝቡን የሚመሩ እና የሚንከባከቡ። ኤቲ፡ “እረኛ በጎቹን እንደሚመራ ሁሉ ሕዝቤን የሚመራ ማን ነው” (ተመልከት)

Matthew 2:7

ማቴዎስ 2:7-8
ሄሮዶስ በሚስጥር የተማሩ ሰዎችን ጠራቸው ይህ ማለት ሄሮዶስ የተማሩ ሰዎችን ሌሎች ሰዎች ሳያውቁ በድብቅ አስጠርቶ አናገራቸው ማለት ነው። ኮከቡ የታየው በትክክል መቼ እንደሆነ ጠያቃቸው ይህ እንዲህ ባለ መንገድ በቀጥታ ሊተረጎም ይችላል። ኤቲ፡ “ከዚያም እንዲህ ሲል ጠየቃቸው፣ “ኮከቡ በትክክል የታየው መቼ ነበር?” (ተመልከት) ኮከቡ የታየው መቼ ነበር ይህ የተማሩት ሰዎች ከኮቡን መቼ እንደተመለከቱት በተዘዋዋር መንገድ እንደነገሩት ያሳያል። የተማሩትም ሰዎች ለሄሮዶስ ኮከቡን መቼ እንደተመለከቱ ነገሩት። (ተመልከት) ጨቅላው ሕጻን ይህ ኢየሱስ የሚያመለክት ነው። ቃል አምጡልኝ ኤቲ፡ “አሳውቁኝ” ወይም “ንገሩኝ”(ተመልከት) እንዳመልከው ይህንን በ MAT 2:2 ላይ በተረጎምከው መሠረት ተርጉመው።

Matthew 2:9

ማቴዎስ 2:9-10
ከእነርሱ በኋላ “ከተማሩት ሰዎች በኋላ” በምስራቅ ተመለከቱ “በምስራቅ በኩል ስወጣ አዩት” ወይም “በሀገራቸው አዩት” ከፊት ፊታቸው ይሄድ ነበር “ይመራቸው ነበር” ወይም “መንገድ ያሳያቸው ነበር” ቀጥ ብሎ ቆመ “ቆመ” ጨቅላው ሕጻን ያለበት “ጨቅላው ሕጻን ያለበት ሥፍራ ስደረስ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Matthew 2:11

ማቴዎስ **2:11-12**
አያያዥ ዐረፍተ ነገር በዚህ ሥፍራ ላይ የታሪኩ ፍሰት ወደ ማሪያም፣ ዮሴፍ እና ትንሹ ኢየሱስ ወደ ሚኖሩበት ቦታ ተለውጧል። ሄዱ “የተማሩት ሰዎች ሄዱ” አምልኮ ይህንን በ MAT 1:2 ላይ በተረጎምከው መሠረት ተርጉመው። ንብረታቸው በዚህ ሥፍራ ላይ “ንብረታቸው” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ንብረታቸውን ብዙ ጊዜ የሚይዙበት ሳጥን ወይም ሻንጣን ነው። ኤቲ፡ “ንብረታቸውን የሚይዙበት ሻንጣ።” ." (ተመልከት) እግዚአብሔር አስጠነቀቃቸው “ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር አስጠነቀቃቸው። ሄሮዶስ ልጁን ሊገድለው እንደሚፈልግ እግዚአብሔር ያውቃል። ወደ ሄሮዶስ እንዳይመለሱ ይህ በትምህርተ ጥቅስ ውስጥ ተደርጎ መተርጎም ይችላል። ኤቲ፡ “እንዲህ በማለት “ወደ ንጉሥ ሄሮዶስ ተመልሳችሁ እንዳትሄዱ።” (ተመልከቱ)

Matthew 2:13

ማቴዎስ **2:13-15**
አጠቃላይ መረጃ በቁጥር 15 ላይ ጸሐፊው ክርስቶስ በግብጽ ምድር እንደሚቆይ ከነብዩ ሆሴን ይጠቅሳል። ሄዱ “የተማሩት ሰዎች ሄዱ” ለዮሴፍ በሕልም ተገለጠለት “ዮሴፍ ሕልም እያለመ ሳለ ወደ እርሱ መጣ” ተነስ፣ ያዝ . . . ሸሽ . . . ቆይ . . . አንተ እግዚአብሔር ለዮሴፍ ተናገረው። ስለዚህ ሁሉም በነጠላ ቁጥር ሊሆኑ ይገባቸዋል። . (ተመልከት) እስክነግርህ ድረስ የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም በግልጽ መቀመጥ ይኖርበታል። ኤቲ፡ “መመለስህ ሰላም እንደሆነ እኔ እስክነገር ድረስ” (ተመልከት) ቆየ ይህ ዮሴፍ፣ ማሪያም እና ኢየሱስ በግብጽ ምድር ውስጥ መቆየታቸውን ያሳያል:::: ኤቲ፡ “በዚያ ቆዩ” (ተመልከት) ሄሮዶስ እስኪሞት ድረስ ሄሮዶስ MAT 2:19. ድረስ አልመተም። ይህ ዓረፍተ ነገር በግብጽ ምድር ውስጥ ለምን ያክል ጊዜ እንደቆዩ ያሳያል እንዲሁም በእነዚህ ጊዜያት ሄሮዶስ እንደሞተ አይናገረም። ልጄን ከግብጽ ምድር ጠራሁት “ልሄን ከግብጽ ጠራት” ልጄ በሆሴ ውስጥ ይህ እስራኤላዊያንን የሚያመለክት ቃል ነው። ማቴዎስ ይህ እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ለመናገር ይህንን ክፍል ጠቅሶታል። ይህንን ብቸኛ ልጅ ወይም የመጀመሪያ ልጅን በሚያሳይ ቃል ተርጉሙት።

Matthew 2:16

ማቴዎስ **2:16-16**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር በዚህ ሥፍራ ላይ የታርኩ ፍሰት ወደ ሄሮዶስ ይመለሳልና የተማሩት ሰዎች እንዳታለሉት ሄሮዶስ ባወቀ ጊዜ ያደረገውን ይነግረናል። አጠቃላይ መረጃ ይህ ሁኔታ የተከሰተው ጸሐፊው MAT 2:15. ላይ የጠቀሰው እና ሄሮዶስ ከመሞቱ በፊት ነው። (ተመልከት) የተማሩት ሰዎች ቀለዱበት ይህ እንዲህ ባለ መልኩ ሊገለጽ ይችላል፡ ኤቲ፡ “የተማሩት ሰዎች ሸውደውት ሄደው አዋረዱት”። (ተመልከት) ሰዎችን ልኮ ሁሉንም ልጆች አስገደላቸው ሄሮዶስ ልጆቹን እርሱ ራሱ አልገደላቸውም። ኤቲ፡ “ሁሉንም ወንድ ልጆችን ይገድሉ ዘንድ ግን ትዕዛዝ ሰጣቸው” ወይም “ሁሉንም ወንድ ሕጻናትን ይገድሉ ዘንድ ወታደሮቹን ላካቸው።” (ተመልከት) ሁለት እና ከሁለት ዓመት በታች የሆኑትን “2 ዓመት እና ከዚያ በታች ያሉትን” (UDB) (ተመልከት) እንደግዜው “በጊዜው መሠረት”

Matthew 2:17

ማቴዎስ **2:17-18**
አጠቃላይ መረጃ በይሁዳ ግዛት ውስጥ የነበሩት ወንድ ልጆች ሁሉ መገደላቸው በቅዱሳት መጽሐፍት በተነገረው መሠረት መሆኑን ጸሐፊው ነብዩ ኤርሚያስን በመጥቀስ ጽፏል። ይህም ተፈጸመ ይህ እንዲህ ባለ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “ይህ ተፈጸመ” ወይም “የሄሮዶስ ተግባር ተፈጸመ።” (ተመልከት) የተፈጸመው ነገር በነብይ ኤርሚያስ አስቀድሞ ተነግሮ ነበር ይህ እንዲህ ባለ መንገድ ሊተረጎም ይችላል። ኤቲ፡ “ገታ በነብይ ኤርሚያስ አማካኝነት ከብዙ ዘመናት በፊት እንደተናገረው።” (ተመልከት) ድምፅ ተሰማ . . . ከእንግዲህ የሉም ማቴዎስ ነብዩን ኤርሚያስን እየጠቀሰ ነው ድምፅ ተሰማ ይህ እንዲህ ባለ መንገድ ሊገለጽ ይችላል፡ ኤቲ፡ “ሰዎች ድምፅ ሰሙ” ወይም “ከፍተኛ ድምፅ ነበር። (ተመልከት) ራሔል ስለልጆቿ አለቀሰች ራሔል ይህ ነገር ከመሆኑ ብዙ ዓመታት በፊት ነው የኖረችው። ይህ ትንቢት የሚያሳያው ከብዙ ዓመታት በፊት የሞተችው ራሔል ስለ ልጆቿ ማልቀሷን ነው። መጽናናትንም እንቢ አለች ይህ እንዲህ ባለ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “ማንም ሊያጽናናት አልቻለም።” (ተመልከት) የሉምና “ልጆቿ ጠፍተዋል እንዲሁም እንደገና ፈጽመው አይመለሱም። በዚህ ሥፍራ “የሉም” የሚለው ቃል ለዘብ ባለ ቃል መሞታቸውን የሚያሳይ ነው። ኤቲ፡ “ስለሞቱ”። (ተመልከት)

Matthew 2:19

ማቴዎስ **2:19-21**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር በዚህ ሥፍራ የታርኩ ፍሰት ዮሴፍ፣ ማሪያም እና ጨቅላው ኢየሱስ ወደሚኖሩበት ወደ ግብጽ ተቀይሯል። እነሆ ይህ በትልቁ ታርክ ውስጥ አንድ ሌላ ሁኔታ የመጀመሩ ምልክት ነው። ከዚህ ቀደም ካሉት ሁኔታዎች ውስጥ ከነበሩት ሰዎች ተጨማሪ ሰዎችን ሊጨምር ይችላል። በቋንቋችሁ ይህንን የሚትገልጹበት መንገድ ሊኖራችሁ ይችላል። የሕጻኑን ሕይወት የሚፈልጉት ሰዎች ኤቲ፡ “ሕጻኑን ለመግደል የሚፈልጉት ሰዎች”። (ተመልከት) የሚፈልጉት ሰዎች ይህ ንጉሥ ሄሮዶስን እና አማካሪዎቹን የሚያመለክት ነው።

Matthew 2:22

ማቴዎስ **2:22-23**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ይህ በ MAT 2:1 የተጀመረው ታርክ ሄሮዶስ የአይሁድ አዲሱን ንጉሥ ለመግደል ያደረገው ሙከራ የመጨረሻው ክፍል ነው። ይህንን በሰማ ጊዜ “ዮሴፍ ይህንን ስሰማ ግን” አርኬላዎስ ይህ የሄሮዶስ ልጅ ስም ነው። (ተመልከት) ፈራ “ዮሴፍ ፈራ” በነቢያቱ የተነገረው ነገር ይህ እንዲህ ባለ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “ከብዙ ዘመናት በፊት ጊዜ በነቢያቱ አማካኝት እንደተናገረው።” (ተመልከት) ናዝራዊ ተብሎ ይጠራል በዚህ ሥፍራ “እርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢየሱስን ነው። ከእርሱ በፊት ይኖሩ የነሩ ነቢያት ስለ እርሱ ስባገሩ መስሑ ወይም ክርስቶስ ብለው ይጠሩታል። ኤቲ፡ “ሰዎች ክርስቶስ ናዝራዊ ነው ይላሉ።” (ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 3

1 በእነዚያ ቀኖች መጥምቁ ዮሐንስ በይሁዳ ምድረ በዳ ፤ 2 "መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ" እያለ እየሰበከ መጣ። 3 በነቢዩ ኢሳይያስ፦ "ምድረ በዳ ውስጥ የሚጮኽ ሰው ድምፅ፣ የጌታን መንገድ አዘጋጁ፣ ጎዳናዎቹንም አስተካክሉ" ተብሎ የተነገረለት ይህ ነውና። 4 ዮሐንስ ይለብስ የነበረው የግመል ጠጕር፣ በወገቡ የሚታጠቀውም የቆዳ ጠፍር ነው፤ ምግቡም አንበጣና የዱር ማር ነበረ። 5 በዚያ ጊዜ ኢየሩሳሌም፣ መላው ይሁዳና በዮርዳኖስ ወንዝ ዙሪያ ያለ አገር ሁሉ ወደ እርሱ ይመጡ ነበር። 6 ሕዝቡ ኀጢአታቸውን እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ በእርሱ እጅ ተጠመቁ። 7 ነገር ግን ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን ብዙዎች ለመጠመቅ ወደ እርሱ ሲመጡ ባየ ጊዜ፣ "እናንተ የመርዛማ እባቦች ልጆች ከሚመጣው ቊጣ ለማምለጥ ማን አስጠነቀቃችሁ? 8 ለንስሐ የሚጠቅም ፍሬ ይኑራችሁ። 9 ለራሳችሁም አብርሃም አባታችን አለን" ብላችሁ አታስቡ። እግዚአብሔር ከእነዚህ ድንጋዮች እንኳ ለአብርሃም ልጆችን ማስነሣት እንደሚችል እነግራችኋለሁና። 10 አሁን መጥረቢያው በዛፎቹ ሥር ተቀምጦአል። ስለዚህ መልካም ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል በእሳት ውስጥም ይጣላል። 11 እኔ ለንስሐ የማጠምቃችሁ በውሃ ነው፤ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቃል፤ ጫማውን መሸከምም እንኳ አይገባኝም። እርሱ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል። 12 ዐውድማውን ፈጽሞ ለማጥራትና ስንዴውን በጎተራ ውስጥ ለመክተት መንሹ በእጁ ነው። ገለባውን ግን ፈጽሞ በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል። 13 ከዚያም ኢየሱስ በዮሐንስ እጅ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ መጣ። 14 ነገር ግን "እኔ አንተ እንድታጠምቀኝ ሲገባ፣ አንተ እንዴት ወደ እኔ ትመጣለህ?" በማለት ሊያስቆመው ሞከረ። 15 ኢየሱስም መልሶ፣ "አሁን ይህን ፍቀድ፤ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ለእኛ ተገቢ ነውና" አለው። ከዚያም በኋላ ዮሐንስ ፈቀደለት። 16 ኢየሱስ ከተጠመቀ በኋላ፣ ወዲያውኑ ከውሃ ውስጥ ወጣ፤ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ። የእግዚአብሔር መንፈስ በርግብ መልክ ሲወርድና በእርሱ ላይ ሲቀመጥ አየ። 17 እነሆ፣ የምወደው ልጄ ይህ ነው። "በእርሱ እጅግ ደስ ይለኛል" የሚል ድምፅ ከሰማያት መጣ።

Matthew 3:1

ማቴዎስ 3፡ 1-3
አጠቃላይ መረጃ፡ ይህ ጸሐፊው የመጥመቁ ዮሐንስን ታሪክ የተነናገረበት አዲስ የታሪኩ አካል መጀመሪያ ነው። በቁ. 3 ላይ ጸሐፊው የኢየሱስ አገልግሎት መንገድን ያዘጋጅ ዘንድ መጥመቁ ዮሐንስ በእግዚብሔር የተመረጠ መሆኑን ከነብዩ ኢሳያስ መጽሐፍ ጠቅሶ ጽፏል። በእነዚህ ቀናት ይህ ዮሴፍ እና የእርሱ ቤተሰብ ከግብጽ ምድር ወደ ናዝሬት ከተመለሱ ብዙ ዓመታት በኋላ የሆነ ነው። ይህ ምናልባትም ኢየሱስ አገልግሎቱን ለመጀመር በተቃረበበት ጊዜ የተፈጸመ ነገር ይሆናል። ኤቲ፡ “ከዚያ በኋላ” ወይም “ከጥቂት ዓመታት በኋላ” ንሰሓ ግቡ ይህ በቅርጹ ብዙ ቁጥር ነው። ዮሐንስ ይህንን ለሕዝቡ እየተናገረ ነው። (ተመልከት) የእግዚአብሔር መንግስት ቀርባለች “የእግዚአብሔር መንግስት ቀርባለች” የሚለው ሀረግ እግዚአብሔር ንጉሥ ሆነ መግዛቱን ያሳያል። ይህ ሀረግ በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ብቻ ይገኛል። ከተቻለ በትርጉምህ ውስጥ “ሰማይ” የሚል ቃልን ተጠቀም። ኤቲ፡ “በሰማይ የሚኖር አባታችን ራሱን እንደ ንጉሥ አድርጎ በቅርቡ ያሳያል።” (ተመልከት) በነብዩ ኢሳያስ አስቀድሞ ስለ እርሱ እንዲህ ተብሎ የተነገረው ይህ ስለሆነ ነው ይህ እንዲህ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ። “ነብዩ ኢሳያስ ስለ መጥመቁ ዮሐንስ እንዲህ ሲል ተናግሯል።” (ተመልከት) የአንድ ሰው ድምፅ በዚህ ሥፍራ ላይ “ድምፅ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሙሉ ሰውን ነው። ኤቲ፡ “አንድ ሰው አለ።” (ተመልከት) የጌታን መንገድ አዘጋጁ፣ መንገዱንም አቅኑ “የጌታን መንገድ አዘጋጁ፣ መንገዱንም አቅኑ”። ይህ በዮሐንስ ሰዎችን ለኢየሱስ መምጣት ሰዎችን በንሰሓ የሚያዘጋጅ ምሳሌያዊ መልዕክት ነው። (ተመልከት)

Matthew 3:4

ማቴዎስ 3፡4-6
አሁን . . . የበረሃ ማር “አሁን” የሚለው ቃል በታሪኩ ፍሰት ውስጥ በዚህ ሥፍራ ለአንባቢው ምልክት እንዲሰጥ ተብሎ ጥቅም ላይ የዋለ ነው። በዚህ ሥፍራ ማቴዎስ ስለ መጥመቁ ዮሐንስ የኋላ ታሪክ መረጃን ይሰጣል። (ተመልከት) የግመል ጠጕር ይለብስ ነበር እንዲሁም ጠፍርንም ይታጠቅ ነበር ይህ የዮሐንስ አለባበስ ከእርሱ በፊት ይኖሩ እንደነበሩ ነብያት በተለይም እንደ ለነብዩ ኤልሳ ትንብታዊ መልዕክት ነበረው። (እና ተመልከት) ኢየሩሳሌም፣ ይሁዳ ሁሉ እና በአከባቢው ያሉ ሁሉ ይህ በዚህ አከባቢ ይኖሩ የነበሩ ሰዎችን የሚያመለክት ነው። በዚህ ሥፍራ “ሁሉም” የሚለው ቃ “ብዙ” ማለት ነው። ማቴወዎስ ወደ መጥመቁ ዮሐንስ የመጡት ብዙ ሰዎች መሆናቸውን አጽኖት ይሰጠቃል። (እና ተመልከት) በእርሱ ተጠመቁ ይህ እንዲህ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “ዮሐንስ አጠመቃቸው።” (ተመልከቱ) እነርሱ ይህ ማለት ከኢየሩሳሌም፣ ከይዳ እና ከዮርዳኖስ ዙሪያ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች መምጣታቸውን ያመለክታል።

Matthew 3:7

ማቴዎስ 3፡7-9
አጠቃላይ መረጃ መጥመቁ ዮሐንስ ፈርሳዊያንን እና ሳዱቃዊያንን ይገስጻቸው ጀመረ። እናንተ የመርዛማ እባብ ልጆች ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው። መርዛማ እባቦች አደገኛ ናቸው እንደሁም ክፋትን ይወክላሉ። ኤቲ፡ “እናንተ መርዛማ እባቦች!” ወይም “ልክ እንደ መርዝማ እባቦች ክፉዎች ናችሁ።” (ተመልከት ከሚመጣው ቁጣ እንድታመልጡ ማን አስጠነቀቃችሁ ዮሐንስ ፈርሳዊያንን እና ሳዱቃዊያንን ለማስጠንቀቅ ምክንያቱም እግዚአብሔር እንዳይቀጣቸው ዮሐንስ ያጠምቃቸው ዘንድ ይጠይቁት ነበር። ይሁን እንጂ ኃጢአት ማድረጋቸውን ማቆም አይፈልጉም ነበር። ኤቲ፡ “በዚህ ዓይነት መንገድ ከእግዚአብሔር ፍርድ ማምለጥ አይቻልም።” ወይም “እኔ ስላጠመቅኳችሁ ከእግዚአብሔር ፍርድ የሚታመልጡ አይመስላችሁ።” (ተመልከት) ከሚመጣው ቁጣ እንድታመልጡ “ቁጣ” የሚለው ቃል በዚህ ሥፍራ ጥቅም ላይ የዋለው የእግዚአብሔርን ቁጣ ለማመለከት ሲሆን ምክንያቱ ደግሞ ይህ ከእግዚአብሔር ቅጣት ቀድሞ የሚመጣ ስለሆነ ነው። ኤቲ፡ “ከሚመጣው ቅጣት ለማምለጥ” ወይም “ከእግዚአብሔር ቅጣት ለማምለጥ።” (ተመልከት) የንሰሓን ፍሬ አፍሩ “አፍሩ” የሚለው ቃል ምሳሌያዊ አነጋገር ሲሆን የሰውዬውን ተግበባራት ያሳያል። ኤቲ፡ “ተግባራችሁ በእውነት ንሰሓ እንደገባችሁ ያሳይ።” (ተመልከት) አባታችን አብረሃም አለልን “አብረሃም አባታችን ነው” ወይም “እኛ የአብረሃም ዘሮች ነን።” የአይሁድ መሪዎች የአብረሃም ዘሮች በመሆናቸው ምክንያት እግዚአብሔር እንደማይቀጣቸው ያስቡ ነበር።” (ተመልከት) እኔ ግን እንዲህ እላችኋለሁ ይህ ዮሐንስ ቀጥሎ ስለሚናር ነገር አጽኖት እንድሰጠ ያሳያል። ከእነዚህ ድንጋዮች እግዚአብሔር ልጆችን ማስነሳት ይችላል “ከእነዚህ ድንጋዮች ሳይቅር እግዚአብሔር ለአብረሃም ለልጆችን አበጅቶ ለአብረሃም መስጠጥ ይችላል።”

Matthew 3:10

ማቴዎስ 3፡ 10-12
አያያዥ ዓረፍተ ነገር መጥመቁ ዮሐንስ ፈርሳዊያንን እና ሳዱቃዊያንን መገሰጹን ቀጥሏል። በዛፉ ሥር ላይ መሳሩ ተቀምጦዋል። መልካምን ፍሬ የማያፈራ ዘፍ ሁሉ ተቆርጦ ወደ እሳት ይጣላል። ይህ ምሳሌ እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ለመቅጣት ተዘጋጅቷል። ይህ በዚህ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “እግዚብሔር ምሳሩን አንስቷል። መጥፎ ፍሬ የሚያፈሩ ዛፎችን ለመቁረጥ እና ለማቃጠል ተዘጋጅቷል” ወይም “አንድ ሰው መጥፎ ፍሬ የሚያፈራን ዘፍ ለመቁረጥ እና ለማቃጠል ምሳሩን እንደሚያዘጋጅ ሁሉ እግዚአብሔርም ስለኃጢአታችሁ ሊቀጣችሁ ተዘጋጅቷል። (እና ተመልከት) ለንሰሓ “ንሰሓ

እንደገባችሁ የሚያሳይ ነገር” ነገር ግን ከእኔ በኋላ የሚመጣው ኢየሱስ ከዮሐንስ በኋላ የሚመጣው ነው። ከእኔ ይልቅ ኃይለኛ ነው “ከእኔ ይልቅ በጣም ጠቃሚ ነው።” በመንፈስ ቅዱስ እና በእሳት ያጠምቃችኋል ይህ ምሳሌ የዮሐንስን ጥምቀት ለወደፊት ከሚሆነው በእሳት መጠመቅ ጋር ያነጻጽራል። ይህ ማለት የዮሐንስ ጥምቀት ሰዎች ከኃጢአታቸው መንጻታቸው ውጫዊ ምሳሌ ሆኖ የሚያገለግል ብቻ ነው። በመንፈስ ቅዱስ እና በእሳት መጠመቅ ግን ሰዎችን በእውነት ከኃጢአታቸው ያነጻል። ከዮሐንስ ጥምቀት ጋር ለማነጻጸር ይረዳ ዘንድ በትርጉማችሁ ውስጥ ከተቻለ “መጠመቅ” የሚለውን ቃል ጥቅም ላይ አውሉት። (ተመልከት) ስንዴውን ከገለባው መለየት እንዲችል መንሹ በእጁ ላይ ነው ይህ ምሳሌ ስንዴ ከገለባ እንደሚለይ ሁሉ ክርስቶስ ጻድቅ የሆኑ ሰዎችን ኃጢአተኞች ከሆኑን ይለያል። ኤቲ፡ “ክርስቶስ በእጁ መንሽን እንደያዘ ሰው ነው።” (ተመልከት) መንሽ በእጁ ላይ ነው በዚህ ሥፍራ “በእጁ ላይ ነው” የሚለው ሀረግ ሰውየው ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን ያሳያል። ኤቲ፡ “ክርስቶስም መንሹን በእጁ ይዟል ምክንያቱም ዝግጁ ነው።” መንሽ ይህ የስንዴ ነዶን ወደ ሰማይ በመወርወር በንፋስ አማካኝነት ገለባውን ከፍሬው ለመለየት የሚረዳ መሣሪያ ነው። ክብደት ያለው ፍሬው መደመሬት ስወድቅ የማይፈለገው ገለባው ግን በንፋስ ይወሰዳል። ከሹካ ጋር ተመሳሳይ ቅርጽ ያለው ሲሆን መንሽ ግን የሚሠራው ከእንጨት ነው። (ተመልከት) አውድማ “እህል የሚወቃበት ሜዳ” ወይም “ፍሬው እና ገለባው የሚለይበት ሥፍራ” ምርቱንም ወደ ጎተራው ይከተዋል . . . ገለባውን ግን ወደ ማይጠፋ እሳት ውስጥ ይጨምረዋል።

ይህ እግዚአብሔር እንዴት ጻድቃንን ከኃጢአትን እንደሚለይ የሚያሳይ ምሳሌ ነው። ገበሬ ስንዴውን ወደ ጎተራው እንደሚያስገባ ሁሉ ጻድቃንም ወደ ሰማይ ይሄዳሉ እንዲሁም እንደ ገለባው ያሉትን ሰዎች እግዝአብሔር ወደ ማይጠፋ እሳት ውስጥ ይጨምራቸዋል። (ተመልከት) ወደማይጠፋ ይህ እንዲህ ባለ መንገድ ሊገለጽ ይችላለል። ኤቲ፡ “ነዶ ወደማያልቅ።” (ማይጠፋ እሳት ውስጥ ይጨምራቸዋል። (ተመልከት))

Matthew 3:13

ማቴዎስ **3:13-15**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር በዚህ ሥፍራ ጸሐፊው ታርኩ በኋላ ላይ ዮሐንስን ኢየሱስን ወደ አጠመቀበት ይቀይረዋል። በዮሐንስ እጅ ለመጠመቅ

ይህ እንዲህ ባለ መንገድ በቀጥታ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “ዮሐንስ ያጠምቀው ዘንድ።” (ተመልከት) አንተ ወደ እኔ ትመጣለህ? እኔ በአንተ እጅ መጠመቅ ያስፈልገኛል።

ኢየሱስ ለጠየቀው ጥያቄ ዮሐንስ በአግራሞት በጥያቄ መልክ ስመልስ እናያለን። ኤቲ፡ “አንተ ከእኔ ይልቅ አስፈላጊ ነህ። እኔ አንተን ማጥመቅ የለብኝም። አንተ እኔ ማጥመቅ አለብህ።” (ተመልከት) ለእኛ በዚህ ሥፍራ “እኛ” የሚለው ቃል ኢየሱስን እና ዮሐንስን የሚታመለክት ናት። (ተመልከት)

Matthew 3:16

ማቴዎስ **3:16-17**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ይህ ስለ መጥመቁ ዮሐንስ የተነገረው ታርክ መጨረሻ እና ኢየሱስን ካጠመቀ በኋላ ምን እንደሆነ የተገለጸበት ክፍል ነው። ከተጠመቀ በኋላ ይህ በቀጥታ እንዲህ ባለ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “ዮሐንስ ኢየሱስን ካጠመቀ በኋላ።” (ተመልከት) እነሆ “እነሆ” የሚለው ከዚህ ቀጥሎ ያለው ማስረጃ አስገራሚ ስለሆነ አጽኖት ለመስጠት ነው። ሰማያት ለእርሱ ተከፈቱ ይህ እንዲህ ባለ መንገድ በቀጥታ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “ኢየሱስ ሰማያት ተከፍቶ ተመለከተ” ወይም “እግዚአብሔር ሰማያትን ለኢየሱስ ከፈተ”። (ተመልከት) በእርግም አምሳሌ ወረደ አማራጭ ትርጉሞች እነዚህ ናቸው 1) መንፈስ በእርግም አምሳሌ መውረዱን የሚያመለክት ቀጥተኛ ትርጉም ወይም 2) እርግም በቀስታ እንደሚትወርድ ሁሉ ልክ እንደዚሁ መንፈስ ቅዱስ በቀስታ በኢየሱስ ላይ መውረዱን የሚያመለክት ምሳሌ ነው። (ተመልከት) እንዲህ የሚል ድምፅ ከሰማይ መጣ “ኢየሱስ ድምፅ ከሰማይ ሰማ።” (UDB) (ተመልከት) ልጅ ይህ የኢየሱስ በጣም አስፈላጉ የማዕረግ ስም ነው፣ የእግዚአብሔር ልጅ። (ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 4

1 ከዚያም በኋላ በዲያብሎስ ሊፈተን መንፈስ ኢየሱስን ወደ ምድረ በዳ መራው። 2 ኢየሱስ ዐርባ ቀንና ዐርባ ሌሊት ከጾመ በኋላ ተራበ። 3 ፈታኙ ወደ እርሱ መጣና፣ ‹‹የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ፣ እንጀራ እንዲሆኑ እነዚህን ድንጋዮች እዘዛቸው›› አለው። 4 ኢየሱስ ግን መለሰና፣ ‹‹ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል" አለው። 5 ከዚያም ዲያብሎስ ወደ ቅድስቲቱ ከተማ ወሰደው፤ በቤተ መቅደስ ሕንጻ ዐናት ላይም አቁሞ፣ 6 የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ፣ ራስህን ወደ ታች ወርውር፤ ‹እንዲጠብቁህ መላእክቱን ይልካል፣› እና ‹‹እግርህ ድንጋይ እንዳይመታው፣ በእጆቻቸው ያነሡሃል›› ተብሎ ተጽፎአል አለው። 7 ኢየሱስም፣ ‹‹‹ጌታ አምላክህን አትፈታተን› ተብሎም ተጽፎአል›› አለው። 8 እንደ ገናም ዲያብሎስ ወደ አንድ ተራራ ወሰደውና የዓለምን መንግሥታት ሁሉ ከሙሉ ክብራቸው ጋር አሳየው። 9 ‹‹ብትወድቅና ብትሰግድልኝ፣ እነዚህን ሁሉ እሰጥሃለሁ›› አለው። 10 ከዚያም ኢየሱስ፣ አንተ ሰይጣን ከዚህ ሂድ! ‹ለጌታ ለአምላክህ ስገድ፣ እርሱንም ብቻ አምልክ››› ተብሎ ተጽፎአልና አለው። 11 ከዚያ በኋላ ዲያብሎስ ተወው፤ እነሆም፣ መላእክት መጡና ኢየሱስን አገለገሉት። 12 ኢየሱስ የዮሐንስን መያዝ ሲሰማ፣ ወደ ገሊላ ሄደ። 13 ናዝሬትን ትቶ በመሄድ በዛብሎንና በንፍታሌም አገር በገሊላ ባሕር አጠገብ ባለው በቅፍርናሆም ኖረ። 14 ይህ የሆነው፣ በነቢዩ ኢሳይያስ ተነግሮ የነበረው እንዲፈጸም ነው፤ ይኸውም፦ 15 ‹‹የዛብሎን ምድርና የንፍታሌም ምድር፣ በባሕሩ አቅጣጫ፣ ከዮርዳኖስ ማዶ፣ የአሕዛብ ገሊላ! 16 በጨለማ ውስጥ የኖረ ሕዝብ ታላቅ ብርሃን አየ፣ በሞት ጥላና ምድር ውስጥ ለሚኖሩትም፣ ብርሃን ወጣላቸው›› የሚለው ነው። 17 ኢየሱስ ከዚያ ጊዜ አንሥቶ፣ ‹‹መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ›› እያለ መስበክ ጀመረ። 18 ኢየሱስ በገሊላ ባሕር አጠገብ እየሄደ ሳለ፣ ሁለት ወንድማማቾችን አየ፤ ጴጥሮስ ተብሎ የሚጠራው ስምዖንና ወንድሙ እንድርያስ ዓሣ አጥማጆች ስለ ነበሩ፣ ወደ ባሕሩ መረብ እየጣሉ ነበር። 19 ኢየሱስ፣ ‹‹ኑ፣ ተከተሉኝ፤ ሰዎችን የምታጠምዱ አደርጋችኋለሁ›› አላቸው። 20 እነርሱም ወዲያውኑ መረባቸውን ትተው ተከተሉት። 21 ኢየሱስ ከዚያ ዐለፍ እንዳለም ሁለት ሌሎች ወንድማማቾችን፣ የዘብዴዎስን ልጅ ያዕቆብንና ወንድሙን የሐንስን አየ፤ ከአባታቸው ከዘብዴዎስ ጋር በጀልባ ውስጥ መረቦቻቸውን ያበጃጁ ነበር። ኢየሱስም ጠራቸው። 22 ወዲያውኑ ጀልባዋንና አባታቸውን ትተው ተከተሉት። 23 ኢየሱስ በምኵራቦቻቸው ውስጥ እያስተማረ፣ የመንግሥትን ወንጌልም እየሰበከና በሕዝቡ መካከል ያሉ በሁሉም የደዌና የበሽታ ዐይነት የሚሠቃዩትን እየፈወሰ በመላው ገሊላ ተዘዋወረ። 24 ስለ እርሱ በሶርያ ምድር ሁሉ ተወራ፤ ሕዝቡም የታመሙትን ሁሉ፣ በልዩ ልዩ ደዌና ሕመም የሚሠቃዩትን፣ በአጋንንት የተያዙትንና የሚጥል በሽታ ያለባቸውን፣ ሽባዎችንም ወደ እርሱ አመጡ፤ እርሱም ፈወሳቸው። 25 ከገሊላ፣ ከዐሥሩ ከተሞች፣ ከኢየሩሳሌም፣ ከይሁዳና ከዮርዳኖስ ወንዝ ማዶ እጅግ ብዙ ሕዝብ ተከተሉት።

Matthew 4:1

ማቴዎስ **4**:**1**-**4**
አጠቃላይ መረጃ በዚህ ሥፍራ ላይ ጸሐፊው ኢየሱስ በምድረ በዳ 40 ቀናትን ያሳለፈበትን፣ በሴጣን የተፈተነበትን የታሪኩን አዲስ ክፍል ይጀምራል። በቁጥር 4 ላይ ኢየሱስ ከዘዳግም መጽሐፍ በተወሰዱ ጥቅሶች አማካኝነት ሴጣንን ስገስጸው እንመለከታለን። ኢየሱስ በመንፈስ ተመርቶ

ይህ በቀጥታ በዚህ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “መንፈስ ኢየሱስን መራው።” (ተመልከት) በዳብሎስ ይፈተን ዘንድ ይህ በቀጥታ በዚህ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “ዳብሎስ እርሱን መፈተን ይችል ዘንድ።” (ተመልከት) ዳቢሎስ . . . ፈታኙ እነዚህ ሁለት ቃላት የሚያመለክቱት አንድ ነው። እነዚህ ሁለቱን ለመተርጎም አንድ ቃል መጠቀም ትችላላችሁ። ጾመ . . . ተራበ ይህ ስለኢየሱስ የተባለ ነው። አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ እዘዝ የዚህ ሀረግ አማራጭ ትርጓሜዎች 1) ይህ ፈተና ኢየሱስ ለራሱ ጥቅም ተዓምራትን ይሠራ ዘንድ የቀረበ ፈተና ነው። ኤቲ፡ “አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ስለዚህ ማዘዝ ትችላለህ።” 2) ይህ የሚያመለክተው በኢየሱስ ላይ የቀረበውን ክስ ነው። ኤቲ፡ “የእግዚአብሔር ልጅ መሆንህ ትዕዛዝ በመስጠት አረጋግጥ።” ሴጣን ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እንደሚያውቅ ማሰቡ ይበልጥ ተመራጭ ነው።

የእግዚአብሔር ልጅ ይህ በኢየሱስ እና በእግዚአብሔር መካከሎ ያለውን ግንኙነት የሚገልጽ ስም ነው። (ተመልከት) ድንጋዩ ዳቦ እዲሆን እዘዝ ይህንን በቀጥጣ እንዲህ ባለ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “ለእነዚህ ድንጋዮች እንዲህ ብለህ ተናገር፣ ዳቦ ሁኑ!” (ተመልከት)

ዳቦ ኤቲ፡ “ምግብ” (ተመልከት)

እንዲህ ተብሎ ተጽፏል ይህ እንዲህ ባለ መንገድ በቀጥታ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “ሙሴ ከብዙ ዘመናት በፊት እንዲህ በማለት ጽፏል።” (ተመልከት)

የሰው ልጅ በዳቦ ብቻ አይኖርም ይህ በቀላሉ በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ከምግብ በላይ ሌላ በጣም አስፈላጊ ነገር አለ ማለት ነው።

ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ማንኛውም ቃ እንጂ በዚህ ሥፍራ “ቃል” እና “አፍ” የሚሉ ቃላት እግዚአብሔር የተናገራቸውን ነገሮችን ያመለክታሉ። ኤቲ፡ “እግዚአብሔር የተናገራቸውን ነገሮች በማድመጥ እንጂ።” (ተመልከት)

Matthew 4:5

ማቴዎስ **4**:**5**-**6**
አጠቃላይ መረጃ፡ በቁጥር 6 ላይ ሴጣን ከመዝሙረ ዳዊት መጽሐፍ ውስጥ ኢየሱስን ለመፈተን ሲል የሆነ ሀሳብ ስወስድ እናያለን።

አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ ራስህን ወደታች ወርውር የዚህ ሀረግ አማራጭ ትርጉሞች 1) 1) ይህ ፈተና ኢየሱስ ለራሱ ጥቅም ተዓምራትን ይሠራ ዘንድ የቀረበ ፈተና ነው። ኤቲ፡ “አንተ የእግዚአብሔር ልጅ በመሆንህ ራስህን ወደታች መወርወር ትችላለህ።” ወይም 2) ይህ የሚያመለክተው በኢየሱስ ላይ የቀረበውን ክስ ነው። ኤቲ፡ “አንተ በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ስለመሆንህ ራስህን ወደታች በመወርወር አረጋግጥ።” (UDB) ሴጣን ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እንደሚያውቅ ማሰቡ ይበልጥ ተመራጭ ነው።

የእግዚአብሔር ልጅ ይህ በኢየሱስ እና በእግዚአብሔር መካከሎ ያለውን ግንኙነት የሚገልጽ ስም ነው። (ተመልከት)

ራስህን ወደታች ወርውር “ወደታች ራስህን ወርውረህ ውደቅ” ወይም “ወደታች ዝለል”

እንዲህ ተብሎ ተጽፏልና ይህ በዚህ መንገድ በቀጥታ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “መዝሙረኛው በመመጽሐፉ ውስጥ እንዲህ ብሎ ጽፏልና” ወይም “በቅዱሳት መጽሐፍ ውስጥ እንዲህ ተብሏልና።” (ተመልከት)

ይጠብቁህ ዘንድ መልአክቱን ስለአንተ ያዛልና “አንተን እንዲጠብቁህ እግዚአብሔር መልአክቱን ስለአንተ ያዛል።” ይህ እንዲህ ተብሎ በትምህረተ ጥቅስ ውስጥ ሊተረጎም ይችላል። ኤቲ፡ “እግዚአብሔር ለመልአክቱ እንዲህ ይላቸዋል፣ “ጠብቁት።” (ተመልከት)

ያነሱሃል “መልአክቱ ይይዙሃል”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Matthew 4:7

ማቴዎስ **4**:**7**-**9**
አጠቃላይ መረጃ፡ በቁጥር 7 ላይ ኢየሱስ ሴጣንን የገሰጸው ከዘዳግም መጽሐፍ ውስጥ በተወሰደ ጥቅ አማካኝነት ነው።

እንደገና እንዲህ ተብሎ ተጽፏል ኢየሱስ እንዲህ ማለቱ እንደገና ከመጽሐፍ ቅዱስ መጥቀሱን የሚያመለክት ነው። ኤቲ፡ “እንደገና ሙሴ በቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ የጻፈውን ነገር እነግርሃለሁ።” (እና ተመልከት)

አትፈታተኑት በዚህ ሥፍራ ላይ “እናንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ማንኛውንም ሰው ነው። ኤቲ፡ “ማንም እርሱን መፈታተን የለበትም” ወይም “ማንኛውም ሰው እርሱን መፈታተን የለበትም።”

እንደገና ዳቢሎስ “በመቀጠልም ዳቢሎስ”

እንዲህ አለው “ዳቢሎስ ኢየሱስን እንዲህ አለው።”

እነዚህን ነገሮች ሁሉ እሰጥሃለሁ። “እነዚህ ነገሮች ሁሉ እሰጥሃለሁ።” ፈታኙ አንዳንዶቹን ሳይሆን “ሁሉንም ነገሮች” እንደሚሰጠው አጽኖት ሰጥቶዋል።”

Matthew 4:10

ማቴዎስ **4**:**10**-**11**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ይህ ሴጣን ኢየሱስን እንዴት እንደፈተነው የሚያወሳው ታሪክ የመጨረሻው ክፍል ነው።

አጠቃላይ መረጃ፡ በቁጥር 10 ላይ ኢየሱስ ከዘዳግም መጽሐፍ ውስጥ በመውሰድ ሴጣንን ገስጾታል።

እንዲህ ተብሎ ተጽፏልና ይህ በዚህ መንገድ በቀጥታ ለገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “መዝሙረኛው በመመጽሐፉ ውስጥ አንዲህ ብሎ ጽፏልና” ወይም “በቅዱሳት መጽሐፍ ውስጥ እንዲህ ተብሏልና።” (ተመልከት)

አንተ አለብህ በዚህ ሥፍራ “አንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ማንኛውንም ሰው ነው። (ተመልከት)

እነሆ “እነሆ” የሚለው ቃል ከዚህ በመቀጠል የሚሰጠው መረጃ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን የሚያመለክት ነው።

Matthew 4:12

ማቴዎስ **4**:**12**-**13**
አጠቃላይ መረጃዎች፡ ይህ ኢየሱስ በገሊላ አገልግሎቱን የጀመረበትን መንገድ ጸሐፊው የገለጸበት አዲሱ የታሪኩክፍል ጅማሬ ነው። እነዚህ ጥቅሶች ኢየሱስ እንዴት ወደ ገሊላ እንደመጣ ያብራራሉ። (ተመልከት)

አሁን ይህ ቃል በታሪኩ ፍሰት ውስጥ ያለውን ክፍተት ለማሳየት ጥቅም ላይ የዋሉ ናቸው። ማቴዎስ በዚህ ሥፍራ ላይ የታሪኩን አንዲስ ጅማሬ ክፍል ይናገራል። ዮሐንስ ተሠረ ይህ በቀጥታ እንዲህ ባለ መንገድ ለገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “ንጉሡ ዮሐንስን አሠረው።” (ተመልከት)

በዛብሎን እና ንፍታሌን አገር እነዚህ ከብዙ ዓመታት በፊት ከሌላ ሀገር የመጡ ሰዎች ቦታወን ከመቆጣጠራቸው በፊት በእነዚህ ሥፍራዎች ይኖሩ የነበሩ ጎሣዎች ስም ነው። (ተመልከት)

Matthew 4:14

ማቴዎስ **4**:**14**-**16**
አጠቃላይ መረጃ፡ በቁጥር 15 እና 16 ላይ ኢየሱስ በገሊላ የነበረው አገልግሎት ከዚህ በፊት ተነግሮ የነበረ ትንቢት ፍጻሜ መሆኑን ለማሳየት ጸሐፊው ከነብዩ ኢሳያስ መጽሐፍ ይጠቅሳል።

እንዲህም ሆነ ይህ ኢየሱስ ቅፍርናሆም ወደ ተሰኘው መንደር ለመኖር መምጣቱን ያመለክታል።

ከዚህ በፊት እንደተነገረው ይህ እንዲህ ባለ መንገድ በቀጥታ ለገለጽ ይችላል፡ ኤቲ፡ “እግዚአብሔር እንደተናገረው።” (ተመልከት)

የዛብሎን እና የንፍታሌን አገር . . . የአሕዛብ ገሊላ እነዚህ ሁሉ ስሞች አንድን አከባቢ የሚያመለክቱ ናቸው። ይህ በአንድ ዓረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። ኤቲ፡ “በዛብሎን እና ንፍታሌን አገር . . . ብዙ አሕዛብ የሚኖሩበት የገሊላ መንድ።”

በባሕር መንገድ ይህ የገሊላን ባሕርን ያመለክታል።

በጨለማ የተቀመጠ ሕዝብ ታላቅ ብርሃንን አየ በዚህ ሥፍራ “ብርሃን” የሚለው ቃል ግብረገባዊ ጨለማን ወይም ሰዎችን ከእግዚአብሔር የለየውን ኃጢአትን የሚያመለክት ነው። ይህ አሁን ከእግዚአብሔር ዘንድ ተስፋን ያገኙ ነገር ግን አስቀድሞ ምንም ተስፋ ያልነበራቸውን ሕዝቦች ያሳያል። (ተመልከት)

በዚያ አከባቢ የሚኖሩ እና በሞት ጥላ ሥር ላሉ ሕዝቦች ብርሃን ወጣላቸው ይህ ከመጀመሪያው የዓረፍተ ነገሩ ክፍል ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው። በዚህ ሥፍራ ላይ “አከባቢ እና በሞት ጥላ ሥር” የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው መንፈሳዊ ሞት ወይም ከእግዚአብሔር መለየት ነው። (እና ተመልከት)

Matthew 4:17

ማቴዎስ **4**: **17**-**17**
መንግስተ ሰማያት ቀርባለችና ንሰሓ ግቡ ይህን በ MAT 3:2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Matthew 4:18

ማቴዎስ **4**:**18**-**20**
አጠቃላይ መረጃ ይህ በታሪኩ ውስጥ ኢየሱስ በገሊላ ስለነበረው አገልግሎት አስመልክቶ አዲስ ታሪክ የተጀመረበት ነው። በዚህ ሥፍራ ሰዎች የእርሱ ደቀ መዛሙርት ይሆኑ ዘንድ መሰብሰብ ጀመረ።

መረባቸውን ወደ ባሕሩ ይጥሉ ነበር ኤቲ፡ “ዓሳ ለማጥመድ መረባቸውን ወደ ውሃው ውሰጥ ይጨምሩ” (ተመልከት)

ተከተሉኝ ኢየሱስ ጴጥሮስ እና እንድርያስን ይከተሉት፣ ከእርሱ ጋር ይኖሩ እና የእርሱ ደቀ መዛሙርት ይሆኑ ዘንድ ጠራቸው። ኤቲ፡ “ደቀ መዛሙርቴ ሁኑ።” ሰዎችን የሚታጠምዱ አደርጋችኋለሁ ይህ ምሳሌያዊ ንግግር ጴጥሮስ እና እንድርያስ እውነተኛውን መልዕክት ለእግዚአብሔርን ሕዝብ በማስተማሪ ሌሎችም ደግሞ ኢየሱስን እንዲከተሉ ያደርጋሉ። ኤቲ፡ “ዓሳ ታጠምዱ በነበረበት መንገድ እናንተም ሰዎችን እንዴት መሰብሰብ እንደሚትችል አስተምራችኋለሁ።” (ተመልከት)

Matthew 4:21

ማቴዎስ **4**:**21**-**22**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ይሆኑ ዘንድ ተጨማሪ ሰዎችን ጠራ።

ጠራቸው “ኢየሱስ ዮሐንስ እና ያዕቆብን ጠራቸው።” ይህ ሀረግም ኢየሱስ ይከተሉት፣ ከእርሱ ጋር ይኖሩ እና የእርሱ ደቀ መዛሙርት ይሆኑ ዘነድ ጠራቸው ማለት ነው።

ወዲያውኑ “በዚያኑ ጊዜ”

ታንኳቸውን ትተው . . እና ተከተሉት ይህ የሕይወት ዘይቤ ለውጥ መሆኑን መግለጽ በጣም አስፈላጊ ነው። እነዚህ ሰዎች ወደ ዓሳ አጥማጅነታቸው እና

የቤተሰባቸውን ሥራ ከዚያን ጊዜ ጀምረው በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ ኢየሱስን ለመከተል ትተዋለል።

Matthew 4:23

ማቴዎስ **4:23-25**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ይህ ኢየሱስ በገሊላ የጀመረው አገልግሎት ታሪክ የመጨረሻው ክፍል ነው። እነዚህ ቁጥሮች ምን እንዳደረገ እና ሰዎች የሰጡት ምላሽ ምን እንደሆነ ጠቅለል አድርጎ ያሳየናል። ([[End of Story]] ተመልከት)

በምኩራቦቻቸው እያስተማረ “በገሊላ ውስጥ በሚገኙ ምኩራቦች ውስጥ እያስተማረ” ወይም “በእነዚህ ሰዎች ምኩራብ ውስጥ እያስተማረ።”

የመንግስቱን ወንጌል እየሰበከ በዚህ ሥፍራ ላይ “መንግስት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚብሔር ንጉሥ ሆኖ መንገሡን ነው። ኤቲ፡ “ወንጌልን ማለትም እግዚአብሔር እንዴት ራሱን ንጉሥ አድርጎ እንደገለጠ እየሰበከ” (UDB) (ተመልከት)

ሁሉንም ዓይነት በሽታዎች እና ደዌዎች “ማንኛውንም በሽታ እና ደዌ።” “በሽታ” እና “ደዌ” የሚሉት ቃላት በጣም የተቀራረቡ ናቸው ነገር ግን ከተቻለ በሁለት የተያዩ ቃላት አማካኝነት ቢተረጎሙ መልካም ነው። “በሽታ” አንድ ሰው አንዲታመም የሚያደርገው ነገር ነው። “ደዌ” አካላዊ ድክመት ወይም በሽተኛ በመሆን በአካል ላይ የሚሆን ህመም ነው።

በዳቢሎስ የተያዙ ይህ እንዲህ ባለ መንገድ በቀጥታ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “በዳቢሎስ የተያዘ” ወይም “ዳቢሎስ የተቆጣጠራቸው።” (ተመልከት) የሚጥል በሽታ “የሚጥል በሽታ ያለባቸው” ወይም “ካለባቸው በሽታ የተነሳ የሚወድቁትን”

ሽባዎችን “መራመድ የማይችሉትን” ከዐሥሩም ከተሞች ይህ “ዐሥር ከተማዎች” ስም ነው። ." (UDB) ይህ ከገሊላ ባሕር በደቡብ ምስራቅ በኩሉ የሚገኘውን አከባቢ መጠሪያ ስም ነው። (ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 5

1 ኢየሱስ ሕዝቡን ሲያይ፣ ወደ ተራራ ወጣ፤ እዚያም ሲቀመጥ ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ መጡ። 2 እንደዚህ እያለም አስተማራቸው፤ 3 በመንፈስ የደኸዩ
የተባረኩ ናቸው፤ መንግሥተ ሰማይ የእነርሱ ናትና። 4 የሚያዝኑ የተባረኩ ናቸው፤ ይጽናናሉና። 5 የዋሆች የተባረኩ ናቸው፤ ምድርን ይወርሳሉና። 6 ለጽድቅ
የሚራቡና የሚጠሙ የተባረኩ ናቸው፤ ይጠግባሉና። 7 የሚምሩ የተባረኩ ናቸው፤ ይማራሉና። 8 ልበ ንጹሖች የተባረኩ ናቸው እግዚአብሔርን ያዩታልና። 9
የሚያስታርቁ የተባረኩ ናቸው፤ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና። 10 ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ የተባረኩ ናቸው፤ መንግሥተ ሰማይ የእነርሱ ናትና። 11 ሰዎች
ሲሰድቧችሁና ሲያሳድዷችሁ፣ ወይም በእኔ የተነሣ ክፉውን ሁሉ በእናንተ ላይ በሐሰት ሲናገሩ ብፁዓን ናችሁ። 12 በሰማይ ዋጋችሁ ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ፣
ሐሤትም አድርጉ። ሰዎች ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያት በዚህ መንገድ አሳድደዋቸዋልና። 13 እናንተ የምድር ጨው ናችሁ፤ ጨው ጣዕሙን ካጣ፣ እንደ ገና
ጨው እንዴት መሆን ይችላል? ወደ ውጭ ተጥሎ በእግር ከመረገጥ በቀር ፈጽሞ ለምንም አይጠቅምም። 14 እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ። በተራራ ላይ
የተመሠረተች ከተማ ልትሰወር አትችልም። 15 ሰዎች መብራት አብርተው ቤት ውስጥ ላሉት ሁሉ እንዲበራ በመቅረዝ ላይ ያስቀምጡታል እንጂ በቅርጫት ሥር
አያስቀምጡትም። 16 መልካሙን ሥራችሁን እንዲያዩና በሰማይ ያለ አባታችሁን እንዲያከብሩት መብራታችሁ እንዲሁ በሰዎች ፊት ይብራ። 17 ሕግንና ነቢያትን
ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ የመጣሁት ልሽራቸው ሳይሆን ልፈጽማቸው ነው። 18 ምክንያቱም፣ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ፣ ሁሉ እስኪፈጸምም ድረስ፣
ከሕግ እንዷ ፊደል ወይም ቅንጣት ከቶ አታልፍም ብዬ በእውነት እነግራችኋለሁ። 19 እንግዲህ ከእነዚህ ትእዛዞች ትንሿን የሚሽርና ለሌሎችም እንዲሁ
እንዲያደርጉ የሚያስተምር፣ በመንግሥተ ሰማይ ታናሽ ይባላል። የሚጠብቃቸውና የሚያስተምራቸው ግን በመንግሥተ ሰማይ ታላቅ ይባላል። 20 ምክንያቱም፣
ጽድቃችሁ ከሕግ መምህራንና ከፈሪሳውያን ጽድቅ ልቆ ካልተገኘ መንግሥተ ሰማይ ከቶ አትገቡም እላችኋለሁ። 21 ለቀደሙት፣ 'አትግደል፣ የገደለ
ይፈረድበታል' እንደ ተባለ ሰምታችኋል። 22 እኔ ግን፣ 'ወንድሙን የሚቆጣ ሁሉ ይፈረድበታል፣ ወንድሙን፣ 'አንተ የማትረባ!' የሚለው የሸንጎ ፍርድ፣ 'ቂል'
የሚለውም የገሃነመ እሳት ፍርድ ይፈረድበታል። 23 እንግዲህ መባህን በመሠዊያው ላይ ልታቀርብ ከሆነና ወንድምህ አንዳች ነገር በአንተ ላይ እንዳለው
ካስታወስህ፣ 24 መባህን በመሠዊያው ፊት ትተህ ሂድ፣ በቅድሚያ ከወንድምህ ጋር ታረቅ፣ ከዚያም ተመልሰህ መጥተህ መባህን አቅርብ። 25 ባላጋራህ
ለዳኛው፣ ዳኛውም ለአሳሪው አሳልፎ እንዳይሰጥህና በወህኒ ውስጥ እንዳትጣል፣ ወደ ፍርድ ቤት ዐብረኸው እየሄድህ ሳለ ከሚከስስህ ባላጋራህ ጋር
በፍጥነት ተስማማ። 26 እውነት እነግርሃለሁ፣ የመጨረሻዋን ሳንቲም እስክትከፍል ድረስ ከዚያ ፈጽሞ አትወጣም። 27 "አታመንዝር" እንደ ተባለ ሰምታችኋል፤
28 እኔ ግን፣ ሴትን ተመኝቷት የሚመለከት ሁሉ በልቡ አመንዝሯል እላችኋለሁ። 29 የቀኝ ዐይንህ ቢያሰናክልህ አውጥተህ ጣለው፤ መላ ሰውነትህ በገሃነም
ከሚቃጠል፣ ከሰውነትህ ክፍሎች አንዱ ቢጠፋ ይሻልሃልና። 30 የቀኝ እጅህም ቢያሰናክልህ ቆርጠህ ጣለው፤ መላ ሰውነትህ ገሃነም ውስጥ ከሚገባ
ከሰውነትህ ክፍሎች አንዱ ቢጠፋ ይሻልሃል። 31 'ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ የፍቺ ማረጋገጫ ይስጣት' ተብሎአል። 32 እኔ ግን፣ 'በዝሙት ምክንያት ካልሆነ በቀር
ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ፣ እንድታመንዝር ያደርጋታል፤ ከተፈታች በኋላ የሚያገባትም ምንዝርና ይፈጽማል። 33 ደግሞም ለቀደሙት፣ በሐሰት አትማል፣
መሐላዎችህንም ለጌታ ስጥ እንደ ተባለ ሰምታችኋል። 34 እኔ ግን ከቶ አትማሉ፤ በሰማይም፣ የእግዚአብሔር ዙፋን ነውና፤ 35 በምድርም፣ እግሩ የሚያርፍባት
ናትና፤ በኢየሩሳሌምም፣ የታላቁ ንጉሥ ከተማ ናትና። 36 በራሳችሁም አትማሉ፤ አንዷን ጠጕር ነጭ ወይም ጥቍር ማድረግ አትችሉምና። 37 ነገር ግን
ንግግራችሁ 'አዎ፣ አዎ'፣ ወይም 'አይደለም፣ አይደለም' ይሁን። ከዚህ የወጣ ሁሉ ከክፉው ነው። 38 ዐይን ስለ ዐይን፣ ጥርስ ስለ ጥርስ እንደ ተባለ
ሰምታችኋል፣ 39 እኔ ግን እላችኋለሁ፣ 'ክፉውን ሰው አትቃወሙት፣ ይልቁን የቀኝ ጕንጭህን ለሚመታህ ሌላውንም አዙርለት። 40 ማንም ሰው ሊከስስህና
ኮትህን ሊወስድ ቢመኝ፣ ካባህንም ይውሰድ። 41 አንድ ምዕራፍ እንድትሄድ ማንም ሰው ቢያስገድድህ፣ ዐብረኸው ሁለት ምዕራፍ ሂድ። 42 ለሚለምንህ ሁሉ
ስጥ፣ ከአንተ መበደር ከሚፈልገውም ፊትህን አታዙር። 43 ባልንጀራህን ውደድ፣ ጠላትህንም ጥላ እንደ ተባለ ሰምታችኋል። 44 እኔ ግን ጠላቶችህን ውደድ
ለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ ብዬ እነግራችኋለሁ። 45 ይኸውም በሰማያት ያለ አባታችሁ ልጆች እንድትሆኑ ነው። እርሱ ፀሐይን በክፉዎችና በደጎች ላይ ያወጣል፤
ዝናብም በጻድቃንና በኀጥኣን ላይ ያዘንባል። 46 የሚወድዷችሁን ብትወዱ፣ ምን ዋጋ ታገኛላችሁ? ቀራጮች እንኳ እንደዚህ ያደርጉ የለምን? 47
ለወንድሞቻችሁ ብቻ ሰላምታ ብታቀርቡ፣ ከሌሎች የበለጠ የምታደርጉት ምንድን ነው? አሕዛብስ እንኳ ይህንኑ ያደርጉ የለምን? 48 እንግዲህ የሰማይ
አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ።

Matthew 5:1

ማቴዎስ 5:1-4
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ይህ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ማስመተማር የጀመረበት አዲስ ታሪክ ጅማሬ ክፍል ነው። ይህ ክፍል እስከ ምዕራፍ 7 ድረስ ይቀጥላል እንዲሁም ብዙ ጊዜም የተራራው ስብከት ተብሎ ይጠራል።

አጠቃላይ መረጃ፡ በቁጥር 3 ላይ ኢየሱስ የተባረኩ ሰዎች ባሕርያት ምን ምን እንደሆኑ መግለጽ ይጀምራል።

አፉን ከፍቶ ኤቲ፡ “ኢየሱስ መናገር ጀመረ” (ተመልከት)

አስተማራቸው “እነርሱን” የሚለው ቃል ደቀ መዛሙርቱን የሚያመለክት ነው።

በመንፈሰስ ድሆች ይህ ማለት ትሁት የሆነ ማለት ነው። ኤቲ፡ “እግዚአብሔር እንደሚያስፈልጋቸው ያወቁ።” (ተመልከት)

መንግስተ ሰማያት የእነርሱ ናትና በዚህ ሥፍራ ላይ “መንግስተ ሰማየት” የሚያመለክተው እግዚአብሔር እንደ ንጉሥ መግዛቱን። ይህ ሀረግ በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ብቻ ነው የሚገኘው። ከተቻለ በትርጉማችሁ ውስጥ “ሰማይ” የሚለው ቃል እንዲኖር አድርጉ። ኤቲ፡ “በሰማይ ያለው እግዚአብሔር ንጉሣቸው ይሆናልና።” (ተመልከት)

የሚያለቅሱ ያዘኑበት ምክንያት ሊሆን የሚችለው 1) በዚህ ዓለም ኃጢአት ወይም 2) በራሳቸው ኃጢአት ወይም 3) በሌላ ሰው ሞት ምክንያት። ቋንቋችሁ ካላስገደዳችሁ በስቀተር ምክንያቱን አትግለጹ።

ይጽናናሉና ይህ እንዲህ በቀጥታ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “እግዚአብሔር ያጽናናቸዋል።” (ተመልከት)

Matthew 5:5

ማቴዎስ 5:5-8
የዋሆች “ትሁታን” ወይም “በራሳቸው ኃይል የማይታመኑት”

ምድርን ይወርሳሉ “እግዚአብሔር ምድርን ሁሉ ይሰጣቸዋል”

ጽድቅን የሚራቡ እና የሚጠሙ ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር ትክክለኛውን ነገር ለማድረግ ከልቡ የሚሻ ሰው ማለት ነው። ኤቲ፡ “ውሃ እና ምግብን ሰው እንደሚሻ ሁሉ በጽድቅ ለመኖር የሚሹ” (ተመልከት)

ይሞላሉ ይህ እንዲህ ተብሎ በቀጥታ ሊገለጽ ይችላል፡፡ ኤቲ፡ “እግዚአብሔር ይሞላቸዋ” ወይም “እግዚብሔር ያረካቸዋል፡፡” : (ተመልከት)

ልበ ንጹሖች

“ልባቸው ንጹሕ የሆኑ ሰዎች፡፡” በዚህ ሥፍራ “ልብ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የአንድ ሰውን ፍላጎት ነው፡፡ ኤቲ፡ “እግዚአብሔርን ለማገልገል የሚፈልጉ ሰዎች፡፡” (ተመልከት)

እግዚአብሔርን ያዩታል በዚህ ሥፍራ ላይ “ማየት” የሚለው ቃል በእግዚአብሔር መገኘት ውስጥ መኖር መቻልን የሚያመለክት ነው፡፡ ኤቲ፡ “እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር መኖር እንዲችሉ ይፈቅድላቸዋል፡፡”

Matthew 5:9

ማቴዎስ **5:9-10**
አስታራቂዎች እነዚህ ሌሎች ሰዎች እርስ በእርሳቸው ሰላም እንዲሆኑየሚያግዙ ሰዎችን ናቸው፡፡ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና ይህ በእንዲህ ዓይነት መንገድ በቀጥታ ሊገለጽ ይችላል፡፡ ኤቲ፡ “እግዚአብሔር ልጆቼ ብሎ ይጠራቸዋልና” ወይም “የእግዚአብሔር ልጆች ይሆናሉና፡፡” (: ተመልከት)

የእግዚአብሔር ልጅ “ልጆች” የሚለውን ቃል በእናንተ ቋንቋ ለሰው ልጅ ወይም ሕጻናት በተለምዶ የሚትጠቀምበትን ተመሳሳይ ቃላት መጠቀሙ ጥሩ ነው፡፡

የሚሰደዱ ይህ በቀጥታ በዚህ ዓይነት መልኩ ሊገለጽ ይችላል፡፡ ኤቲ፡ “ሌሎእ ሰዎች በተገቢው መንገድ ያልያዟቸው ሰዎች፡፡” (ተመልከት)

ስለጽድቅ “እግዚአብሔር እንዲያደርጉ የሚፈልገውን ነገር በማድረጋቸው ምክንያት”

መንግስተ ሰማያት የእነርሱ ናትና ይህንን በ MAT 5:3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት፡፡

Matthew 5:11

ማቴዎስ **5:11-12**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ኢየሱስ የተባረኩ ሰዎች ባሕርያትን ማብራሩትን ጨርሷል፡፡

የተባረካቹ ናቸሁ “እናንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ነው፡፡ (ተመልከት)

ስለ አንተ በውሸት ክፉ ነገሮችን ሁሉ ይናገራሉ፡፡ “ስለ አንተ ሁሉንም ዓይነት ክፉ ውሸትን ይናገራሉ” ወይም “እውነት ያልሆነ መጥፎ መጥፎ ነገሮችን ይናገራሉ”

ስለ እኔ ሲባል “እኔን በመከተልህ ምክንያት” ወይም “በእኔ በማመንህ ምክንያት”

ደስ ይበላችሁ እንዲሁም ሐሴትም አድርጉ “ደስ ይበላችሁ” እና “ሐሴት አድርጉ” የሚሉት ሁለቱ ቃላት ተመሳሳይ መልዕክቶችን የሚያስተልፉ ናቸው፡፡ ኢየሱስ አድማጮቹ ደስ ይበላችሁ ብቻ አላላቸው ነገር ግን ከተቻለ ከመደሰት በላይ እንዲያደርጉ ነግሮዋቸዋል፡፡ (ተመልከት)

Matthew 5:13

ማቴዎስ **5:13-14**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እንደ ጨው እና ብርሃን ይሆኑ ዘንድ ማስተማር ጀመረ፡፡

እናንተ የምድር ጨው ናቸው አማራጭ ትርጓሜዎች 1) ጨው ለምግብት ጣእም እንደሚሰጥ ሁሉ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት በዓለም ውስጥ ያሉ ሰዎች መልካም ይሆኑ ዘንድ ተጽእኖ ፈጣሪዎች መሆን ይኖርባቸዋል ወይም 2) ልክ ጨው ምግብ ለረጅም ጊዜ ሳይበላሽ እንዲቆይ እንደሚያደረግ ሁሉ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ሰዎች ሙሉ ለሙሉ እንዳይበላሹ የሚያደርጉ ሊሆኑ ይባል፡፡ ኤቲ፡ “ለዓለም ሕዝቦች እናንተ ልክ እንደ ጨው ናችሁ” ወይም “ጨው ለምግብ እንደሆነ ሁሉ እናንተም ለዓለም እንደዚሁ ናችሁ፡፡” (ተመልከት)

ጨው ጣእሙን ካጣ አማራጭ ትርጉሞች 1) “ጨው ጨው የሚሠራውን ነገር መሠርት የሚያስችለውን ኃይሉን ካጣ” ((UDB) ወይም 2) “ጨው ጣዕሙን ካጣ፡፡” (ተመልከት)

እንዴት ጨው የሚሰጠውን ጥቅም ሊሰጥ ይችላል? “እንደገና እንዴት ጠቃሚ ሊሆን ይችላል?” ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ለማስተማር ጥያቄን ይጠቀማል፡፡ ኤቲ፡ “እንደገና ጠቃሚ መሆን የሚችልበት ምንም ዓይነት መንገድ የለም፡፡” (እና ተመልከት)

ወደ ውጪ ከመጣል እና በሰዎች ከመረገጥ በስቀር ይህ እንዲህ ባለ መንገድ በቀጥታ ሊገለጽ ይችላል፡ ኤቲ፡ “በመንገድ ዳር ይጥሉታል፤ ሰዎችም ይረጋግጡታል፡፡” (See: ተመልከት)

እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ ይህም ማለት የኢየሱስ ተከታዮች የእግዚአበብሔር እውነት ያለበትን መልዕክት እግዚብሔርን ወደ ማያውቁት ሰዎች ሁሉ ድረስ የሚያደርሱ ናቸው፡፡ ኤቲ፡ “እናንተ በዓለም ውስጥ ላሉ ሰዎች ልክ እንደ ብርሃን ናችሁ፡፡” (See: ተመልከት)

በተራራ ላይ ያለች ከተማ ፈጽሞ ልትደበቅ አትችልም ይህ ሰዎች የከተማዋን ብርሃን በምሽት መመልከት ይችላሉ ማለት ነው፡፡ ይህ በቀጥታ እንዲህ ባለ መንገድ ሊገለጽ ይችላል፡፡ ኤቲ፡ “በምሽት በተራራ ላይ ያለች ከተማን ብርሃን ማንም ሰው ሊከልል አይችልም፡፡ (እና ተመልከት)

Matthew 5:15

ማቴዎስ **5:15-16**
መብራት የሚያበራ ሰውም እንዲሁ “ሰዎች መብራትን እንዲሁ አብርቶ

ከእንቅብ በታች አያኖረውም “መብራቱን ከቅርጫት በታች አያኖረውምለለ”፡፡ ይህ ማለት መብራን አብርቶ ሰዎች እንዳያዩት መደበቅ ሞኝነት ነው የሚል ነግግር ነው፡፡

ብርሃናችሁ በሰዎች ሁሉ ፊት ያብራ ይህ ማለት የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ሌሎች ሰዎች የእግዚአብሔር እውነት ከእነርሱ መማር በሚችሉበት መንገድ መኖር አለባቸው ማለት ነው፡፡ ኤቲ፡ “ሕይወታችሁ ልክ እንደ መብራት በሰዎች ፊት ይብራ፡፡” (ተመልከት)

በሰማይ የሚኖረው አባታችሁ “አባት” የሚለውን ቃል በጥሩ ሁኔታ ለመተርጎም በቋንቋችሁ ውስጥ አንድን አባት ለመጥራት የሚትጠቀሙትን ቃል ተጠቀሙ፡፡

Matthew 5:17

ማቴዎስ **5:17-18**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን መጽሕፍት ውስጥ የተጻፉትን ሕግጋት ለመፈጸም እንደመጣ ማስተማሪ ጀመረ፡፡ ነቢያት ይህ ነቢያት በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የጻፏቸውን መጽሐፍትን ያመለክታል፡፡ (ተመልከት) እውነት እላችኋለሁ “እውነት እላችኋለሁ፡፡” ይህ ሀረግ ኢየሱስ ቀጥሎሊናገረው ያለው ሀሳብ አጽኖት ልሰጥበት የሚገባ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ሰማይና ምድር ያልፋሉ ኤቲ፡ “እግዚአብሔር የፈጠራቸው ነገሮች ሁሉ ያልፋሉ፡፡” (ተመልከት) አንድት ነጥብ “ከፊደል ትንሸዋ እንኳ ሳትቀር፡፡ ይህ ከቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ በሰዎች ይህንን ያኽለ አስፈላጊ አይደሉም ተብሎ የሚቆጠሩት እንኳ ሳይቀሩ የሚለውን ለማሳየት የቀረበበ ምሳሌያዊ ንግግር ነው፡፡ ኤቲ፡ “አስፈላጊ የማይመስሉ ሕግጋት እንኳ ሳይቀሩ”፡፡ (ተመልከት) ሁሉ ነገር ይፈጸማል ይህ በግልጽ እንዲህ ሊገለጽ ይችላል፡፡ ኤቲ፡ “እግዚአብሔር በሕግ ውስጥ የተጻፉትን ነገሮች ሁሉ ፈጽሟል፡፡ (ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Matthew 5:19

ማቴዎስ 5:19-20
የተላለፈ ማንኛውም ሰው “የማይታዘዝ ማንኛውም ሰው” ወይም “ሳይታዘዝ የቀረ ማንኛውም ሰው” ከእነዚህ ትዕዛዛት መካከል ትንሹን “ከእነዝህ ትዕዛዛት መካከል፣ ጥቅሟ በጣም ትንሽ የሆነችውን ትዕዛዛ እንኳ ሳይቀር” ተብሎ ይጠራል ይህ እንዲህ በቀጥታ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “ያንን ሰው አግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ይጠራዋል።” (ተመልከት) በመንግስተ ሰማይ ውስጥ ትንሽ “መንግስተ ሰማይ” ሚለው ሀረግ የእግዚአብሔር አገዛዝ ያመለክታል። ይህ ሀረግ የሚገኘው በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ብቻ ነው። የሚቻል ከሆነ “በትርጉማችሁ ውሰጥ “ሰማይ” የሚለው ቃል ተጠቀሙ። ኤቲ፡ “በመንግስተ ሰማይ ውስጥ አስፈላጊነቱ ትንሽ ይሆናል” ወይም “በሰማይ የእግዚአብሔ አገዛዝ ውስጥ ያለው ጠቀሜታ በጣም ትንሽ ይሆናል።” (ተመልከት) ጠብቋቸው እንዲሁም አስተምሯቸው “እነዚህ ትዕዛዛት ሁሉ ታዘዙ እንዲሁም ሌሎችም ይህንኑ ያደርጉ ዘንድ አስተምሯቸው።” ታላቅ “በጣም አስፈላጊ” እንዲህ ብዬአችኋለሁ ይህ ኢየሱስ ከዚህ በመቀጠል ስለሚናገረው ነገር አጽኖት ይሰጣል። አንተ . . . እናንተ . . . አንተ ይህ ብዙ ቁጥርን ያመለክታል። (ጽድቃችሁ ካልበለጥ . . . ልትገቡ አትችሉም ይህ በአዎንታዊ መንገድ እንዲህ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “ጽድቃችሁ መብለጥ አለበት . . . ለመግባት። (ተመልከት)

Matthew 5:21

ማቴዎስ 5:21-22
አያያዥ ዓረፍ ነገር ኢሰየሱስ የብሉይ ኪዳን ሕግጋትን ለመፈጸም መምጣቱን ማስተማሩን ቀጥሏል። በዚህ ሥፍራ ስለ ነፍስ ማጥፋት እና ንዴት ተናግሯል። አጠቃላይ መረጃ ኢየሱስ ለተሰበሰቡት ሰዎች እንደ ግለሰብ እያንዳንዳቸው ምን ሊያጋጥማቸው እንደሚችል እየተናገረ ነው። “ሰምታችኋል” የሚለው ሀረግ ውስጥ ያለው “እናንተ” የሚለው ቃል እና “እላችኋለሁ” ሀረግ ብዙ ቁጥር ነው። “አትግደል” የሚለው ሀረግነጠላ ቁጥር ነው ይሁን እንጂ በብዙ ቁጥር ሊተረጎም ይችላል። በጥት ዘመን እንዲህ ተብሎ ተነግሯቸዋል ይህ በቀጥታ እንዲህ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “ከብዙ ዘመናት በፊት እግዚአብሔር ተናግሮ ነበር። (ተመልከት) ነፈስ ያጠፋ ማንኛውም ሰው ፍርድ አለበት በዚህ ሥፍራ “ፍርድ” የሚለው ቃል ይህ ሰው እንዲገደል የሚያዘውን ሕግ የሚያሳይ ነው። ኤቲ፡ “ሌላ ሰው የገደለ ማንኛው ሰው ላይ ዳኛው ይፈርዳል።” (ተመልከት) ግዲያ. . . ግድያዎች ይህ የሚያመለክተው ቃል ሆኖ ነፍስ ማጥፋት እንጂ ሁሉንም ዓይነት የግዲያ አይነቶችን አይደለም። ነገር ግን እኔ እንዲህ እላችኋለሁ “እኔ” የሚትለው ቃ አጽኖታዊ ናት። ይህ የሚያመለክተው ኢየሱስ የተናገረው ነገር እግዚአብሐየር በመጀመሪያ ከሰጠው ትዕዛዝ ጋር የሚስተካከል ነው። ስትተረጉም ይህንን አጽኖት በሚያሳይ ሀረግ ለመተርጎም ሞከር። ወንድም ይህ አማኝን እንጂ በሥጋ ወንድምን ወይም ጎረበትን የሚያመለክት አይደለም። ፍርድ ይገባዋል በዚህ ሥፍራ ላይ ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ስለ ሰው ፍርድ ሳይሆን በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሰውን እግዚአብሔር የሚያመጣውን ፍርድ ነው። (ተመልከት) እርባና የሌለው . . . ሞኝ ይህ በትክክል ማሰብ የማይችሉ ሰዎች የሚሰደቡትን ስድብ የሚያመለክት ነው። “እርባና ያሌለው” የሚለው ቃል “አእምሮ የሌለው” ከሚለው ቃል ጋር ተቀራራቢ ሲሆን “ሞኝ የሚለው ደግሞ እግዚአብሔርን አለመታዘዝ ጋር ተያያዥነት ያለው ሀሳብ ነው። ሸንጎ ይህ በኢየሩሳሌም የሚገኘው የሸንጎ ሳይሆን በአከባቢው ያለው ሸንጎ ነው።

Matthew 5:23

ማቴዎስ 5:23-24
እንተ ኢየሱስ በቡድን ላሉ ሰዎች እያንዳንዳቸው ምን እንደሚያጋጥማቸው እየተናገረ ነው። “አንተ” የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር ነው። እናንተ ግን በቋንቋች በብዙ ቁጥር ሊትተረጉሙት ትችላላችሁ። (ተመልከት) መባህን “ስጦታ ስትሰጥ” ወይም “ስጦታህ ስታቀርብ” በመሠዊያው ላይ ይህ በኢየሩሳሌሚ ቤተ መቅደስ ውስጥ የሚገኘውን የእግዚአብሄርን መሠዊያ የሚያመለክት ነው። ኤቲ፡ “በቤተ መቅዲስ ውስጥ በሚገኘው የእግዚአብሔር መሠዊያ ላይ።” (ተመልከት) በዚያ ሳለህ ቢታስታውስ “በመሠዊያው ፊት ቆመህ ሳለ ቢታስታውስ” ወንድምህ አንዳች ነገር ከአንተ ጋር እንዳለው “አንተ ባደረከው አንድ ነገር የተነሳ ወንድም በአንተ የተቆጣ መሆኑን ካስታወስክ” በመጀመሪያ ሂድና ከወንድምህ ጋር ታረቅ ይህ በቀጥታ እንዲህ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “ከሰውዬው ጋር ሰላምን ፍጠር።” (ተመልከት)

Matthew 5:25

ማቴዎስ 5:25-26
ከአንተ . . . ጋር ተስማማ ኢየሱስ በቡድን ላሉ ሰዎች እያንዳንዳቸው ምን እንደሚያጋጥማቸው እየተናገረ ነው። “አንተ” የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር ነው። እናንተ ግን በቋንቋች በብዙ ቁጥር ሊትተረጉሙት ትችላላችሁ። (ተመልከት) ከከሳሽ ጋር ይህ ሰው ሌላኛውን ሰው በደል እየነቀሰ የሚወቅስ ሰው ነው። በዳኛ ፊት ሆኖ ሌላኛው ሰው የበደለውን በደል በመናገር ይከሳል። ለዳኛ አሳልፎ ይሰጥሃል በዚህ ሥፍራ ላይ “አሳልፎ ይሰጥሃል” የሚለው ሀረግ ትርጉሙ አንድን ሰው በሌላ ሰው ቁጥጥር ሥር እንዲሆን መስጠትን ያመለክታል። ኤቲ፡ “ዳኛው በሕጉ መሠረት እንዲፈርድብህ ያደርጋል።” (ተመልከት) ዳኛውም ለወህኒ ጠባቂዎች አሳልፎ ይሰጥሃል በዚህ ሥፍራ ላይ “አሳልፎ ይሰጥሃል” የሚለው ሀረግ ትርጉሙ አንድን ሰው በሌላ ሰው ቁጥጥር ሥር እንዲሆን መስጠትን ያመለክታል። ኤቲ፡ “ዳኛውም ለወህኒ ጠበቂ አሳልፎ ይሰጥሃል።” (ተመልከት) የወህኒ ጠባቂ ይህ ሰው ሰው በዳኛው የተሰጠውን ውሳኔ የሚያስፈጽም ግለሰብ ነው። ወደ ወህኒ ትጣላለህ ይህ በቀጥታ እንዲህ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “የወህኒ ጠባቂው በወህኒ ቤት ውስጥ እንዲትታሠር ያደርጋል።” (ተመልከት) እውነት እውነት እላችኋለሁ “እውነት እውነት እላችኋለሁ”። ይህ ሀረግ ኢየሱስ ቀጥሎ ለሚናገረው ነገር አጽኖት እንዲንሰጥ ያደርገናል። ከዚያ ሥፍራም “ከወህኒ ቤት”

Matthew 5:27

ማቴዎስ 5:27-28
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን ሕግጋትን ለመፈጸም መምጣቱን ማስተማሩን ቀጥሏል። በዚህ ሥፍራ ስለዝሙት እና ምኞች ማስተማር ጀምሯል። አጠቃላይ መረጃ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። “ሰምታችኋል” በሚለው ሀረግ ውስጥ የሚገኘው “እናንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ነው። “አታመንዝር” የሚለው ትዕዛዝ “አንተ” የሚለውን ቃ በውስጡ ይዞዋል ይሁን እንጂ “አንተ” የሚለው ቃል በብዙ ቁጥር መተርጎም ትችላለህ። (ተመልከት) እንዲህ እንደተባለ ሰምታችኋል ይህ በቀጥታ እንዲህ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “እግዚአብሔር እንዲህ ብሏል።” (ተመልከት) መፈጸም ይህ ቃል አንድን ነገር ማድረግን ያመለክታል። እኔ ግን እንዲህ እላችኋለሁ ይህንን በ MAT 5:22 እንደ ተረጎማችሁት ተመልከቱ። ሴትን ተመልክቶ በልቡ የተመኛት ማንኛውም ሰው አመንዝሯል ይህ ምሳሌያዊ ንግግር ሴትን ተመልክቶ በልቡ የተመኛት ማንኛውም ሰው ካመነዘረ ሰው እኩሉ ጥፋተኛ መሆኑን ያሳያል። (ተመልከት) የተመኛት “እንዲሁም የተመኛት” ወይም “ከእርሷ ጋር ለመተኛት የተመኘ ሰው” በልቡ በዚህ ሥፍራ “ልብ” የሚያመለክተው የአንድን ሰው ሀሳብ ነው። ኤቲ፡ “በአእምሮው” ወይም “በሀሳቡ”። (ተመልከት)

Matthew 5:29

ማቴዎስ 5:29-30
የአንተ . . . ከ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። “አንተ” የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር ነው ይሁን እንጂ በብዙ ቁጥር መተርጎም የግድ ሊሆንብህ ይችላል። (ተመልከት) የቀኝ ዐይንህ ካሰናከለችህ በዚህ ሥፍራ “ዐይን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው አንድ ሰው የሚያየውን ነው። እንዲሁም “መሰናከል” ምሳሌያዊ ንግግር ሲሆን “ኃጢአት” ማለት ነው። ኤቲ፡ “የሚትመለከተው ነገር እንድትሰናከል የሚያደርግ ከሆነ” ወይም “ከሚታየው ነገር የተነሳ ኃጢአት ማድረግ የሚትሻ ከሆነ።” (እና ተመልከት) ቀኝ ዐይን . . . ቀኝ እጅ ከግራ ዐይን ወይም እጅ በተቃራኒው በጣም ጠቃሚው ዐይን ወይም እጅ። “ቀኝ” የሚለው ቃል “አስፈላጊ የሆነ” ወይም “ብቸኛ” በሚሉ ቃላት ለትተረጉማቸው ትችላለህ። (ተመልከት) አውጥተህ “በኃይል ማስወገድ” ወይም “ማጥፋት”። ቀኝ ዐይን የሚለው በቀጥታ ካልተጠቀሰ “ዐይንህ አጥፋ” ብለህ ልትተረጉም ትችላል። ዐይን የተጠቀሰ ከሆነ “አጥፋቸው”

ብለህ ልትተረጉም ትችላለህ። አውጣው . . . ቁረጠው ኢየሱስ የኃጢአትን አደገኝነት ላይ አጽኖት በመስጠት ለዚህ ሰዎች መስጠት ስላለባቸው ምላሽ ግነት የተሞላት መልኩ ተናግግሯል። (ተመልከት) አውጥተህ ጣለው “አስወግደው” ከሰውነት ክፍለህ አንዱ ይጥፋ “ከሰውነት ክፍልህ አንዱን ማጣት ይሻላል።” መላ አካልህ ወደ ሲኦል ከሚጣል ይልቅ ይህ በቀጥታ እንዲህ ሊገለጽ ይችላለል፡ ኤቲ፡ “እግዚአብሔር መላ አካልህን ወደ ሲኦል ከሚጨምረው ይልቅ።” (ተመልከት) ቀኝ እጅህ ካሰናከለችህ ይህ ምሳሌያዊ ንግግር የአንድ ሰው ሁለተናዊ ተግባርን ከእጁ ጋር ታያይዛለች። (ተመልከት)

Matthew 5:31

አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን ሕግጋትን እንዴት ለመፈጸም እንደመጣ ማስተማሩ ቀጥሏል። በዚህ ሥፍራ ላይ ስለፍች ማስተማር ጀምሯል። እንዲህም ተብሏል “የተናገረው” እግዚአብሔር ነው። ኢየሱስ የእርሱ ተቃርኖ ከእግዚብሔር ወይም ከእግዚብሔር ቃል ጋር አለመሆኑን ለመግለጽ ነው ይህን ዓይነት ንግግር የተናገረው። ይልቁንም ፍች የተፈቀደው ለትክክለኛ ምክንያት ብቻ ነው። ወንዱ ምንም እንኳ በትዕዛዛቱ መሠረት የፍች ወረቀቷን ለሚስቱ ቢሰጣትም እንኳ ፍትሓዊ አይደለም። (ተመልከት) ሚስቱን የሚሰዳት ይህ ፍችን የሚያመለክት ምሳሌያዊ አነጋገር ነው። (ተመልከት) ይስጣት “ልሰጣት ይገባል” እኔ ግን እንዲህ እላለሁ ይህንን በ MAT 5:22 በምን ዓይነት መንገድ እንደተረጎማችሁ ተመልከቱ። አመንዝራ ያደርጋታል ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ ሚስቱን የፈታት ሰው “እንድታመነዝር ያደርጋል”። በብዙ ባሕሎች ውስጥ እንደገና ማግባት ትችላለች ነገር ግን የተፋታችው ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ ከሆነ ግን እንዲህ አይነቱ ትዳር ዝሙት ነው። ከተፋታች በኋላ ይህ በቀጥታ እንዲህ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “ባሏ ከፈታት በኋላ” ወይም “ፍች የፈጸመችው ሴት”። (ተመልከት)

Matthew 5:33

አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን ሕግጋትን እንዴት ለመፈጸም እንደመጣ ማስተማሩ ቀጥሏል። በዚህ ሥፍራ ላይ ስለመሃላ ማስተማር ጀምሯል። አጠቃላይ መረጃ፡ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። “ሰምታችኋል በሚለው ሀረግ ውስጥ ያለው “እናንተ” የሚለው ቃል በብዙ ቁጥር የተገለጸ ነው። ይሁን እንጂ “አትማል” እና “ፈጽማቸው” በሚለው ውስጥ ያለው “አንተ” የሚለው ቃል በነጠላ ቁጥር የተገለጸ ነው። እንደገና አንተ “አንተም ደግሞ” ወይም “ሌላ ምሳሌ ይኼው። አንተ” እንዲህ ሲባል ሰምታችኋል . . . በውሸት አትማሉ በዚህ ሥፍራ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር እና ከቃሉ ጋር በግልጽ የሚስማማ ነገር ስናገር ትመለከታላችሁ። ይሁን እንጂ ሰዎችን ለማሳመን የእነርሱ ያልሆነ ነገር እንዳይናገሩ ያሳስባቸዋል። ኤቲ፡ “የሃይማኖት መሪዎቻችሁ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ብለው ነግረዋችኋል . . . አትማሉ።” (ተመልከት) በውሸት አትማሉ መኃላችሁን ፈጽሙ እንጂ አማራጭ ትርጉሞች 1) የማትፈጽሙትን ነገር አደርጋለሁ ብላችሁ በእግዚአብሔር ፊት አትማሉ ወይም 2) አንድ ነገር ውሸት መሆኑን እያወቃችሁ በእግዚአብሔር ፊት እውነት ነው ብላችሁ አትማሉ። እኔ ግን እንዲህ እላችኋለሁ በ MAT 5:22 የሚገኘውን በምን መንገድ እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ። ፈጽሞ አትማሉ . . . የታላቁ ንጉሥ ከተማ በዚህ ሥፍራ ላይ ኢየሱስ የተናገረው ማንም ሰው ፈጽሞ መማል እንዳሌለበት ነው። አንዳንዶች አንድ ሰው የማለው ከእግዚአብሔር ውጪ በሆነ ነገር ማለትም በሰማይ፣ በምድር ቄም በኢየሩሳም የማለ ከሆነ መሃላውን ሳይፈጽም ቢቀር ይህን ያክል ጉዳት የለውም ብለው ሳያስተምሩ አልቀሩም። ኢየሱስ ይህም ቢሆን እንደ ማንኛውም መሃላ መጥፎ ነው ምክንያቱም ሁሉ ነገር የእግዚአብሔር ስለሆነ ነው። ፈጽሞ አትማሉ ለዚህ ትዕዛዝ የሚሆን ቃል በቋንቋችሁ በብዙ ቁጥር የሚገኝ ከሆነ በዚህ ሥፍራ ይህንን ቃል ተጠቀሙ። “በውሸት አትማሉ” የሚለው ሀረግ አድማጮች መማል እንደሚቻል ነገር ግን በውሸት መማል የማይቻል እንደሆነ ያሳያል። “ፈጽሞ አትማሉ” የሚለው ሀረግ ግን ሁሉንም ዓይነት መሃላዎችን ይከለክላል። የእግዚአብሔር ዚፋን ነው በዚህ ሥፍራ ላይ “ዙፋን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔር እንደ ንጉሥ መግዛቱን ነው። ኤቲ፡ “የእግዚአብሔር አገዛዝ”። (ተመልከት) የእግሩ መረገጫ ናት ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር ምድርም ቢትሆን የእግዚአብሔር መሆኗን ያሳያል። ኤቲ፡ “ንጉሥ እግሩን የሚያሳርፍበት የእግሩ መርገጫ ሥፍራ ዓይነት ናት። (ተመልከት) የታላቁ ንጉሥ ከተማ ናትና “ይህች ከተማ የታላቁ ንጉሥ የእግዚአብሔር ከተማ ናትና።”

Matthew 5:36

አጠቃላይ መረጃ፡ ከዚህ በፊት በነበረው ክፍል ውስጥ ኢየሱስ ስለ እግዚአብሔር ዙፋን፣ የእግሩ መረገጫ እና ምድራዊ ቤተ ጭምር ሊምሉበት የሚገባ የእርሱ ንብረት አለመሆኑን ገልጾዋል። በዚህ ሥፍራ ላይ ደግሞ በራሳቸው ላይ ባለው ጸጉር እንኳ መማል እንደማይገባቸው ይናገራል። እናንተ . . . አንተ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። “አትማል” እና “አትችልም” በሚሉ ሀረጋት ውስጥ ያለው “አንተ” የሚለው ቃል በነጠላ ቁጥር የተገለጸ ነው። ይሁን እንጂ በምትተረጉሙበት ጊዜ በብዙ ቁጥር ልትተረጉሙ ትችላላችሁ። (ተመልከት) መሃላ በ MAT 5:34እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት። ንግግርህ “አዎ፣ አዎ ወይም አይ ፣ አይ” ይሁን” “አዎ ማለት ከፈለግህ “አዎ” በል እንዲሁም “አይ” ማለት ከፈለግህ “አይ” በል።

Matthew 5:38

አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን ሕግጋትን እንዴት ለመፈጸም እንደመጣ ማስተማሩ ቀጥሏል። በዚህ ሥፍራ ላይ ጠላትን ስለመበቀል ማስተማር ጀምሯል። አጠቃላይ መረጃ፡ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። “ሰምታችኋል” እና “እኔ እንዲህ እላችኋለሁ” በሚለው ሀረግ ውስጥ የሚገኘው “እናንተ” የሚለው ቃል የተገለጸው በብዙ ቁጥር ነው። “ማንም ቢመታህ” የሚለው ሀረግ ውስጥ የሚገኘው “አንተ” የሚለው ቃል ግን በብዙ ቁጥር መተርጎም ትችላላችሁ። (ተመልከት) እንዲህ መባሉን ሰምታችኋል ይህንን በ MAT 5:33 እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከት። ዐይን ለዐይን ጥርስ ለጥርስ የሙሴ ሕግ የጎዳንን ሰው በተመሳሳይ መንገድ እንዲጎዳ ያዛል ይሁን እንጂ ከዚያ በላይ እንዲጎዳ አያደርግም። እኔ ግን እንዲህ እላለሁ ይህንን በ MAT 5:22.እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከት። ክፉውን “ክፉ የሆነ ሰው” ወይም “የጎዳችሁ ሰው” (UDB) ቀኝ ጉንጫችሁን የመታችሁ ኢየሱስ በኖረበት ባሕል ውስጥ የአንድን ሰው ቀኝ ጉንጭ በጥፊ መምታት ስድብ ነው። ልክ እንደ ዐይን እና እጅ ሁሉ ቀኝ ጉንጭም በጣም ጠቃሚ ነገር ነው። ጉንጭን በጥፊ መምታት ትልቅ ስድብ ነው። መምታት “በጥፊ መምታት”። ይህ ማለት በቃሪያ ጥፉ አንድን ሰው መምታት ማለት ነው። ሌላኛውንም ፊት አዙሩለት “ሌላኛውን ፊታችሁን የሚታችሁ ዘንድ አዙሩለት”

Matthew 5:40

አጠቃላይ መረጃ፡ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። “ፍቀድ”፣ “ሂድ”፣ “ስጥ” እና “አትመለስ” በሚሉ ቃላት ውስጥ ያለው “አንተ” የሚለው ቃል በነጠላ ቁጥር የተገለጸ ነው። (ተመልከት) ኮትህ . . . መጎናጸፊያ “ኮት” በሰዉነት ላይ እንደ ቲሸረት የሚጠለቅ ነው። “መጎናጸፊያ” ከእነዚህ ይልቅ ውድ የሆነ “ከኮት” ላይ ለሙቀት የሚደረብ እንዲሁም በሸት ለሙቀት የሚለበስ ነገር ነው። ይወስድ ዘንድ ፍቀድለት “ለዚያ ሰው ስጠው” ማንምን ሰው “እንዲሁም ይህ ሰው”። በዚህ ሥፍራ ላይ በተዘዋዋር መንገድ የተጠቀሰው የሮማዊያን ወታደር ነው። (ተመልከት) አንድ ምዕራፍ አንድ የሮም ወታደር በዚያ ዘመን አንድን ሰው አንድ ዕቃ ተሸክሞ እንዲሄድ በሕግ ማስገደድ የሚችለው አንድ ሺህ እርምጃዎች ያክል ነው። “ማይል” የሚለው ቃል የሚያምታታ ከሆነ “አንድ ኪሎ ሜትር” ወይም “ረጅም ርቀት” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ከእርሱ ጋር አብረኸው እንዲትሄድ ያስገደደ ሰውን ያመለክታል። ከእርሱ ጋር እጥፍ መንገድ ሂደት “አስገድዶህ እንዲትሄድ ያደረግህን ምዕራፍ ያኽል ሂደት ከዚያም ሌላ አንድ ማዕራፍ ጨምርለት።” “ማይል” የሚለው ቃል የሚያምታታ ከሆነ “ሁለት ኪሎ ሜትር” ወይም “እጥፍ ርቀት” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። አትከልክል “እንዲሁም ሊበደርህ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የሚፈልግ ሰውን አትከልክል።” ይህ በአውንታዊ መንገድ ለገለጽ ይገባል። ኤቲ፡ “አበድር”።

Matthew 5:43

ማቴዎስ **5:43-45**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን ሕግጋትን እንዴት ለመፈጸም እንደመጣ ማስተማሩ ቀጥሏል። በዚህ ሥፍራ ላይ ጠላትን ስለመውደድ ማስተማር ጀምሯል። አጠቃላይ መረጃ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። “የሚወድሁን ውደድ . . . የሚጠሉህ ጥላ” የሚለው ብቻ በነጠላ ቁጥ የተጻፈ ሲሆን እነዚህም ቢሆን በብዙ ቁጥር መተርጎም ትችላህ። ለሌሎች “እናንተ” የሚል ቃል ባለባቸው ሥፍራዎች ሁሉ እና “ፍቅር”እና “ጸሎት” ቦታዎች በብዙ ቁጥር የተገለጹ ናቸው። (ተመልከት) እንዲህ እንደተባለ ሰምታችኋል ይህንን በ MAT 5:33. እንደተረጎማችሁት ተመልከት። ባለንጀራህን “ባለንጀራ” የሚለው ቃል አንድ ሰው በመልካም መንገድ ማስተናገድ የሚሻውን የተመሳሳይ ማህበረሰብ ወይም ቡድን አባላትን የሚያመለክት እንጂ በአከባቢያችን የሚኖሩ ሰዎችን ሁሉ አያመለክትም። ይህንን የብዙ ቁጥርን በሚያመለክት ቃል ልትተረጉሙት ትችላላችሁ። እኔ ግን እንዲህ እላችኋለሁ ይህንን በ MAT 5:22. እንደተረጎማችሁት ተመልከት። የአባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ “ልጆች” የሚለው ቃል በጥሩ ሁኔታ ለመተርጎም በቋንቋችሁ ለሰው ልጆችን ወይም ሕጻናት የሚትጠቀሙትን ቃል ተጠቀሙ። አባት ይህ የእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ የማዕረግ ስም ነው። (ተመልከት)

Matthew 5:46

ማቴዎስ **5:46-48**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን ሕግጋትን እንዴት ለመፈጸም እንደመጣ ያስተማረውን ትምህርት በዚህ ከፍል ውስጥ ያጠናቅቃል። ይህ ክፍል የሚጀምረው በ MAT 5:17 ላይ ነው። አጠቃላይ መረጃ፡ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። ለምሳሌ ያክል “እናንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር አመልካች ነው። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የሚገኘው ጥያቄ መጠይቃዊ ነው። (እና ተመልከት) ታላቅ ይህ አድማጮቹ መልካምነት ያለውን መሻት የሚያሳይ አጠቃላይ ቃል ነው።አባት ይህ የእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ የማዕረግ ስም ነው። (ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 6

1 ሰዎች እንዲያዩአችሁ የጽድቅ ተግባሮቻችሁን በፊታቸው ከማከናወን ተጠንቀቁ፤ አለበለዚያ ከሰማይ አባታችሁ ዋጋ አታገኙም። 2 ስለዚህ አንተ ምጽዋት ስትሰጥ ግብዞች የሰዎችን ከበሬታ ለማግኘት በምኵራቦችና በጐዳና ላይ እንደሚያደርጉት፣ በፊትህ ጥሩንባ አታስነፋ። በእውነት እነግራችኋለሁ፣ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። 3 አንተ ግን ምጽዋት ስትሰጥ፣ የቀኝ እጅህ የሚያደርገውን የግራ እጅህ እንዲያውቅ አታድርግ፤ 4 ይኸውም ምጽዋትህ በስውር የሚሰጥ እንዲሆንና ከዚያም በስውር የሚያይ አባትህ ዋጋህን እንዲከፍልህ ነው። 5 ስትጸልዩም እንደ ግብዞች አትሁኑ፤ ግብዞች ሕዝብ እንዲያያቸው በምኵራቦችና በጐዳና ማእዘኖች ላይ ቆመው መጸለይ ይወዳሉና። በእውነት እነግራችኋለሁ፤ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። 6 አንተ ግን ስትጸልይ ወደ ጓዳህ ገብተህ በር ዝጋና በስውር ወዳለው አባትህ ጸልይ፤ በስውር የሚያይ አባትህም ዋጋህን ይከፍልሃል። 7 ስትጸልይም አሕዛብ እንደሚያደርጉት ረብ የለሽ ድግግሞሽ አታድርግ፤ አሕዛብ በንግግራቸው ብዛት ምክንያት የሚሰሙ ይመስላቸዋልና። 8 ስለዚህ እንደ እነርሱ አትሁኑ፤ እናንተ ከመለመናችሁ በፊት ምን እንደሚያስፈልጋችሁ አባታችሁ ያውቃልና። 9 እንግዲህ እንደዚህ ጸልዩ፦ ‹በሰማይ የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ስምህ ይቀደስ፡ 10 መንግሥትህ ትምጣ። ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች፣ እንዲሁ በምድር ትሁን። 11 የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን። 12 በደላችንን ይቅር በለን፣ እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል። 13 ወደ ፈተና አታግባን፣ ከክፉው አድነን እንጂ።› [መንግሥት፣ ኀይል፣ ክብርም የአንተ ነውና፣ ለዘላለም፣ አሜን።] 14 የሰዎችን ኀጢአት ይቅር ብትሉ፣ የሰማይ አባታችሁ እናንተንም ይቅር ይላችኋል። 15 የሰዎችን ኀጢአት ይቅር ካላላችሁ ግን፣ የሰማይ አባታችሁ የእናንተን ኀጢአት ይቅር አይልም። 16 ስትጾሙም ግብዞች እንደሚያደርጉት ፊታችሁን አታጠውልጉ፤ እንደ ጾመኛ ለመታየት ግብዞች ፊታቸውን ያጠወልጋሉና። በእውነት እነግራችኋለሁ፣ዋጋቸውን ተቀብለዋል። 17 አንተ ግን ስትጾም ራስህን ተቀባ፣ ፊትህንም ታጠብ፣ 18 ይኸውም፣ በስውር ላለው የሰማይ አባትህ ብቻ እንጂ ለሰዎች ጾመኛ መስለህ እንዳትታይ ነው። በስውር የሚያይ የሰማይ አባትህም ዋጋህን ይከፍልሃል። 19 ብልና ዝገት በሚበላውና ሌቦችም ሰብረው በሚሰርቁበት በምድር ላይ ሀብትን ለራሳችሁ አታከማቹ። 20 ይልቁን ብልም ሆነ ዝገት በማያጠፋበት፣ ሌቦችም ሰብረው በማይሰርቁበት በሰማይ ሀብትን ለራሳችሁ አከማቹ። 21 ሀብታችሁ ባለበት ልባችሁም ይገኛልና። 22 ዐይን የሰውነት መብራት ነው። ስለሆነም ዐይንህ ጤናማ ከሆነ፣ መላ ሰውነትህ በብርሃን ይሞላል። 23 ዐይንህ ጤናማ ካልሆነ ግን፣ መላ ሰውነትህ ጨለማ ይሆናል። እንግዲህ በውስጥህ ያለው መብራት በእውነት ጨለማ ከሆነ፣ ጨለማው እንዴት ከባድ ይሆን 24 ! ሁለት ጌቶችን ማገልገል የሚችል ማንም የለም፤ አንዱን ይጠላል ሌላውንም ይወዳል፣ ወይም ለአንዱ ይታዘዛል ሌላውን ደግሞ ይንቃል። እግዚአብሔርንና ሀብትን ማገልገል አትችሉም። 25 ስለዚህ ስለ ሕይወታችሁ ምን እንደምትበሉ ወይም ምን እንደምትጠጡ፦ ወይም ስለ ሰውነታችሁ ምን እንደምትለብሱ አትጨነቁ፤ ሕይወት ከምግብ፣ ሰውነትስ ከልብስ አይበልጥምን? 26 አየር ላይ የሚበርሩ ወፎችን ተመልከቱ! እነርሱ እህል አይዘሩም ወይም አያጭዱም፣ በጐተራም አያከማቹም፤ ይሁን እንጂ፣ የሰማይ አባታችሁ ይመግባቸዋል። ከወፎች ይልቅ እናንተ እጅግ የሚበልጥ ዋጋ ያላችሁ አይደላችሁምን? 27 ከእናንተ መካከል ተጨንቆ በዕድሜው ላይ አንድ ቀን መጨመር የሚችል ይገኛልን? 28 ስለ ልብስስ የምትጨነቁት ለምንድን ነው? 29 ነገር ግን እነግራችኋለሁ፤ ሰሎሞን እንኳ በዚያ ክብሩ ሁሉ ከእነዚህ አበቦች እንደ አንዱ አልለበሰም። 30 እግዚአብሔር ዛሬ የሚታየውንና ነገ እሳት ውስጥ የሚጣለውን የሜዳ ሣር እንደዚህ ካለበሰ፣ እናንት እምነት የጐደላችሁ! እናንተንማ እንዴት እጅግ የበለጠ አያለብሳችሁም? 31 እንግዲህ ‹ምን እንበላለን?› ወይም ‹ምን እንጠጣለን?› ወይም ‹ምን እንለብሳለን?› ብላችሁ አትጨነቁ። 32 አሕዛብ እነዚህን ሁሉ ይፈልጋሉና፤ የሰማይ አባታችሁ እነዚህ ሁሉ እንደሚያስፈልጓችሁ ያውቃል። 33 ነገር ግን በመጀመሪያ መንግሥቱንና ጽድቁን ፈልጉ፤ ከዚያም እነዚህ ሁሉ ይጨመሩላችኋል። 34 ስለዚህ ለነገ አትጨነቁ፤ ነገ ለራሱ ይጨነቃልና። ለቀኑ ክፋቱ ይበቃዋል።

Matthew 6:1

ማቴዎስ 6:1-2
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ በ MAT 5:3ላይ የተጀመረውን የተራራው ስብከቱን ማስተማር ቀጥሏል። በዚህ ክፍል ውስጥ “የጽድቅን ተግባራት” የሆኑትን አስራት ማውጣት፣ ጸሎት እና ጾምን አስመልክቶ አስምሯል። አጠቃላይ መረጃ: ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። “እናንተ” የሚለው ቃል ሁሉም በብዙ ቁጥር የተገለጸ ነው። በሰዎች ለመታየት ለሰዎች ብለው የሚያደርጉ ሰዎች እርሱን እያከበሩት እንዳልሆነ በተዘዋዋሪ መልኩ ያመለክታል። ይህ እንዲህ ባለ መልኩ በቀጥታ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ: “ስላደጋችሁት ነገር ሰዎች ያመሰግናችሁ ዘንድ በሰዎች ፊት የሚታደርጉት ከሆነ።” (እና ተመልከት) አባት ይህ የእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ የማዕረግ ስም ነው። (ተመልከት) ለራስህ መለከት አታስነፋ ይህ ምሳሌ የሚያሳየው የሰዎችን ትኩረት ሆን ብለህ ለመሳብ የተለያዩ ነገሮችን ማድረግ ነው። ኤቲ: “በብዙ ሰዎች መካከል መለከት በታላቅ ድምፅ እንደሚነፋ ሰው ወደ ራስህ የሰዎችን ትኩረት ለመሳብ ጥረት አታድርግ።” (ተመልከት) እውነት እልሃለሁ “እውነቱን እነግርሃለሁ”። ይህ ሀረግ ኢየሱስ በመቀጠል ስለሚናገረው ነገር አጽኖት የሚሰጥ ሀረግ ነው።

Matthew 6:3

ማቴዎስ 6:3-4
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ኢየሱስ ስመ ስጦታ መስተማሩን ቀጥሏል። አጠቃላያ መረጃ: ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። “እናንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር አመልከች ነው። ግራ እጅህ ቀኝ እጅህ የሚሰጠውን አይወቅ ይህ የሚታደርገው ነገር ሁሉ ሙሉ ለሙሉ ምስጥር መሆን እንዳለበት የሚያሳይ ምሳሌ ነው። ምንም እንኳ ሁለቱም እጆች ብዙ ጊዜ ነገሮችን በጋራ የሚያከናውኑ ቢሆንም እንኳ፣ አንዱ የሚያደርገውን ሌላኛው “የሚያውቅ” ቢሆንም እንኳ ለድሆች በሚትሰጥበት ጊዜ እነዚህ በጣም የሚቀራረቡ እጆች እንኳ አንደኛው የሌላኛውን ማወቅ የለበትም። (ተመልከት) ስጦታችሁ በድብቅ ይሁን ይህ በቀጥታ እንዲህ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ: “ሌሎች ሰዎች መስጠትህ ሳያውቁ ለድሆች ልትሰጥ ትችላለህ።” (ተመልከት) ይሸልምሃል “ሽልማት ይሰጥሃል።” (UDB)

Matthew 6:5

ማቴዎስ 6:5-7
አያያዥ ዓረፍተ ነገሮች ኢየሱስ ስለ ጸሎት እንዲህ በማለት ማስተማር ጀመረ። ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። በቁጥር 5 እና 7 ላይ “እናንተ” የሚለው ቃል የብዙ ቁጥር አመልካች ቃል ሲሆን በቁጥር 6 ላይ ግን በነጠላ ቁጥር ተገልጸዋል። ይሁን እንጂ ይህንን በብዙ ቁጥር ልትተረጉመው ትችላለህ። (ተመልከት) ሌሎች ሰዎች የሚያደርጉትን ያዩላቸው ዘንድ በዚህ ሀረግ ውስጥ ተመልካቾቹ ድርጊቱን ተመልክተው ክብር እንደሚሰጧቸው በተዘዋዋሪ መንገድ ያሳያል። ይህ በቀጥታ እንዲህ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ: “ሰዎች ያዮዋቸው እና ክብር ይሰጧቸው ዘንድ።” (እና ተመልከት) እውነት እውነት እላችኋለሁ “እውነቱን እነግራቹሃለሁ”። ይህ ሀረግ ኢየሱስ በመቀጠል ለመናገረው ነገረ ትኩርት እንዲንሰጥ ያደርገናል። ወደ እልፍኝህ ግባ። በርህንም ዝጋ “ለብቻ ወደምትሆንበት ሥፍራ ግባ” ወይም “ለብቻ መሆን ወደምትችልበት ሥፍራ ሂድ” በውስር ያለው አባት ለዚህ አማራጭ ትርጉሞች 1) እግዚአብሔርን ማንም ሰው ማየት አይችልም ወይም 2) እግዚአብሔር

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በዚያ ለብቻው ከሚጸልየው ሰው ጋር አለ። አባት ይህ የእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ የማዕረግ ስም ነው። (ተመልከት) በስውር የሚታደርገውን የሚያይ አባት “አባትህ በስውር የሚታደርገውን ያያል” በከንቱ አትድገም “ትርጉም የሌሽ ቃላትን አትደጋግም” ይሰማል ይህ እንዲህ በቀላሉ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “የሐሰት አማልክቶች ይሰሟቸዋል።” (ተመልከት) ብዙ በመናገራቸው “በረጃጅም ጸሎቶቻቸው” ወይም “ በብዙ ቃሎቶቻቸው።”

Matthew 6:8

ማቴዎስ **6:8-10**
አጠቃላይ መረጃ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። “እንዲህ ጸልዩ” እስከሚለው ድረስ ለቡድን ተናግሯል። “እናንተ” ከሚለው ቀጥሎ ያለው “ሰማያዊ አባታችሁ” የሚለው ቃል በነጠላ ቁጥር ነው የተቀመጠው። (See: ተመልከት) አባት ይህ የእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ የማዕረግ ስም ነው። (ተመልከት) ስምህን ይቀደስ በዚህ ሥፍራ ላይ “ስም” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን የሚያመለክት ነው። ኤቲ፡ “ቅዱስ እንደሆንክ ሁሉም ሰው ይወቅት።” (ተመልከት) መንግስትህ ትምጣ በዚህ ሥፍራ “መንግስት” የሚለው ቃል እግዚአብሔር እንደ ንጉሥ ሆኖ የሚገዛበትን የሚያመለክት ቃል ነው። ኤቲ፡ “በሁሉም ላይ ገዥ ሁን እና ሙሉ ለሙሉ ሁሉን ግዛ።” (ተመልከት) ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እዲሁም በምድር ላይ ትሁን ይህ በቀጥታ እንዲህ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “በሰማይ ያሉት ሁሉም እንደሚታዘዙህ ሁሉ በምድር ላይ ያሉት ሁሉ ይታዘዙህ።” (ተመልከት)

Matthew 6:11

ማቴዎስ **6:11-13**
አጠቃላይ መረጃ “እኛ” እና “የእኛ” የሚሉት ቃላት ኢየሱስ እየተናገራቸው ያለውን የተሰበሰበውን ሕዝብ ያመለክታል። (ተመልከት) የእለት እንጀራችንን በዚህ ሥፍራ ይ “እንጀራ” የሚለው ቃል በአጠቃላይ ምግብን ያመለክታል። (ተመልከት) ብድር ብድር አንድ ሰው ያለበት ዕዳ ነው። ይህ ኃጢአትን በምሳሌ ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለ ቃል ነው። (ተመልከት) ባለዕዳ ባለዕዳለ ከሌላ ሰው የተበደረ ሰው ነው። ይህ ኃጢአትን በምሳሌ ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለ ቃል ነው። (ተመልከት) ወደ ፈተና አታግባን “ፈተና” የሚለው ቃል በግሥ ልገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “ምንም ነገር እንድፈትነን አትፍቀድለት” ወይም “ኃጢአትን እንድንመኝ የሚያደርግ ማንኛውንም ነገር ሕይወታችን ውስጥ አትፍቀድ።” (ተመልከት)

Matthew 6:14

ማቴዎስ **6:14-15**
አጠቃላይ መረጃ “እናንተ” የሚለው ቃል የሚገኝበት ሥፍራ ሁሉ በብዙ ቁጥር ነው። ይሁን እንጂ ኢየሱስ ሌሎች ሰዎችን ይቅር ካላሉ በግል ምን እንደሚደርስባቸው እየነገራቸው ነው። ተመልከት) መተላለፍ “ስህተት” ወይም “ኃጢአት” አባት ይህ የእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ የማዕረግ ስም ነው። (ተመልከት)

Matthew 6:16

ማቴዎስ **6:16-18**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ ስለ ጾም ማስተማር ጀመረ። አጠቃላይ መረጃ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። በቁጥር 17 እና 18 ላይ “አንተ” የሚለው ቃል በነጠላ ቁጥር የተገለጸ ሲሆን በቁጥር 16 ላይ ካለው ጋር ተመሳሳይ እንዲሆን በብዙ ቁጥር ልትተረጉመው ትፈልግ ይሆናል። (ተመልከት) በተጨማሪ “እንዲሁም” ፊታቸውን ያጎሳቁላሉ ግብዞች ፍታቸውን አይታጠቡም ወይም ጸጉራቸውን አያበጥሩም። ይህንን የሚያደርጉት ሆን ብለው እየጾሙ መሆናቸውን ለማሳየት የሰዎችን ትኩረት ለመሳብ እና ከእነርሱ ክብር ለማግኘት ሲሉ ይህንን ያደርጋሉ። እውነት እውነት እላችኋለሁ “እውነት እውነት እላችኋለሁ።” ይህ ሀረግ ኢየሱስ በመቀጠል ለሚናገረው ነገር ትኩረት መስጠቱን ያመለክታል። ራስህን ዘይት ተቀባ “ዘይት ተቀባ” ወይም “ጸጉርህን አበጥር”። ራስህን “ተቀባ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ለጸጉር የተለመደውን እንክብካቤ ማድረግ ነው። “ከክርስቶስ” “የተቀባው” መሆኑ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ኢየሱስ ማለት የፈለገው ሰዎች ጾም እየጾሙም ሆነ ሳይጾሙ ተመሳሳይ መሆን አለባቸው ነው። በስውር ያለው አባት . . . በስውር የሚያይ ይህንን እንዴት በ MAT 6:6. እንደተረጎምከው ተመልከት። አባት ይህ የእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ የማዕረግ ስም ነው። (ተመልከት)

Matthew 6:19

ማቴዎስ **6:19-21**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ ስለ ገንዘብ እና ንብረት ማስማር ጀመረ። አጠቃላይ መረጃ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ “አንተ” የሚል ቃል ጥቅም ላይ በዋለባቸው ሥፍራዎች ከቁር 21 በስተቀር ብዙ ቁጥርን ያመለክታል። ይሁን እንጂ በቁትር 21 ላይ ነጠላ ቁጥር ነው። (ተመልከት) ንብረት “ሀብት” ብል እና ዝገት የሚበሉት “ብል እና ዝገት የሚያበላሹት ሀብት” ብል ብል ልብስን የሚያበላሹ በራሪ ነፍሳት ናቸው። ዝገት ብረት ውሃ ሲነካው የሚፈጠር ቡናማ ቀለም ያለው ነገር ነው። store up for yourselves treasures in heaven This is a metaphor that means do good things on earth so God will bless you in heaven. በሰማይ ሀብትን አከማቹ ይህ ምሳሌ የሚያሳየው እግዚአብሔር በሰማይ ይበባርካችሁ ዘንድ በምድር ላይ ሳላቹ መልካምን ነገር አድርጉ። (ተመልከት) ልብህም ደግሞ በዚያ ይሆናል በዚህ ሥፍራ ላይ “ልብ1 ማለት አሳብ እና ፍላጎት ማለት ነው። (ተመልከት)

Matthew 6:22

ማቴዎስ **6:22-24**
አጠቃላይ መረጃ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ “አንተ” የሚል ቃል ጥቅም ላይ በዋለባቸው ሥፍራዎች ውስጥ በነጠላ ቁጥር የተጠቀሰ ሲሆን አንተ ግን በብዙ ቁጥር ለመተርጎም ታስብ ይሆናል። (ተመልከት) ዐይን የሰውነት ብርሃን ነች . . . ጨለማው ምን ያክል ታላቅ ይሆን ይህ ማየት የሚችል ጤናማ ዐይንን አንድን ሰው ዐይነ ሥውር ከሚያደረግ በሽታ ጋር ያነጻጸጽራል። ይህ ምሳሌ የሚያመለክተው መንፈሳዊ ጤንነትን ነው። ብዙ ጊዜ አይሁዳዊያን “መጥፎ ዐይንን” ከስስት ጋር ያይዙታል። ትርጉሙም አንድ ሰው ሁለተናውን ለእግዚአብሔር ከሰጠ እንዲሁም ሁሉንም ነገር ከእግዚአብሔር አንጻር መመልከት ከቻለ ትክክለኛውን ነገር ያደርጋል። ይሁን እንጂ አንድ ሰው ስስታም ከሆነ ክፋትን ያደርጋል። (ተመልከት) ዐይን የሰውነት ብርሃን ነው የዚህ ምሳሌያዊ ንግግር ትርጉም ልክ መብራት በጨለማ ውስጥ ሰው አጥርቶ እንዲያይ እንደሚያደርግ ሁሉ ዐይንም አንድ ሰው በደንብ ማየት እንዲችል ያደርገዋ። ኤቲ፡ “እንደ መብራት ዐይን ነገሮችን በግልጽ ማየት እንድትችል ያደርጋል።” (ተመልከት) ዐይን ይህንን በብዙ ቁጥር ልትተረጉመው ትችላለህ፤ “ዐይኖች”። ዐይንህ መጥፎ ቢሆን ይህ ምትሃትን አያመለክትም። አይሁዶች ብዙ ጊዜ ስስታምነትን በዚህ ምሳሌያዊ አነጋገር ይገልጹታል። (ተመልከት) አንዱን ይወዳል ሌላኛውን ይጠላል ወይም ለአንዱ ይገዛል ሌላኛውን ደግሞ ይንቃል ሁለቱም በመሠረታዊ ሀሳባቸው አንድ ናቸው። አጽኖት የሚሰጡት አንድ ሰው እግዚአብሔር መውደድ እና መገዛት እንዲሁም ገንዘብንም መውደድና ለእርሱ መገዛት በአንድ ጊዜ አይችልመም። (ተመልከት) ለሀብት እና ለእግዚአብሔር መገዛት አትችሉም። “በአንድ ጊዜ እግዚአብሔርን እና ገንዘብን መውደድ አትችሉም።”

Matthew 6:25

ማቴዎስ **6:25-26**
እላችኋለሁ ይህ ኢየሱስ ከዚህ በመቀጠል የሚናገረው ነገር አጽኖት ሊሰጠው የሚገባ መሆኑን ያሳያል። ለእናንተ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። “እናንተ” የሚለው ቃል በብዙ ቁጥር የተገለጸ ነው። (ተመልከት) ሕይወት ከመብል እንዲሁም ሰውነት ከልብስ አይበልጥምን? በዚህ ሥፍራ ላይ ኢየሱስ ሰዎችን ለማሰተማር ጥያቄን ተጠቅሟል። ኤቲ፡ “በእርግጥ ሕይወት ከምግብ እንዲሁም አካል ከምንለብሰው ልብስ ይበልጣል።” (ተመልከት) ጎተራ

እህል ማጠራቀሚያ ሥፍራ። አባት ይህ የእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ የማዕረግ ስም ነው። (ተመልከት) Are not you of much more value than they? Jesus uses a question to teach the people. AT: "Obviously you are more valuable than birds." አንተ ከእነርሱ ይልቅ በጣም ኩቡር አይደለህምን? ኢየሱስ ሰዎችን ለማስተማር ጥያቄን ይጠቀማል። ኤቲ፡ “ከሰማይ ወፎች ይልቅ አንተ ክቡር ነህ።” (ተመልከት)

Matthew 6:27

ማቴዎስ **6:27-29**
አጠቃላይ መረጃ፡ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። “እናንተ” የሚለው ቃል በብዙ ቁጥር የተገለጸ ነው። (ተመልከት) ከእናንተ መካከል በመጨነቅ በእድሜው ላይ ስንዝር ታክል የጨመረ ማን ነው? ኢየሱስ ሰዎችን ለማስተማር ጥያቄን ይጠቀማል። ይህ ማለት ማንም በጭንቀት ረጅም እድሜ መኖር የሚችል የለም። (ተመልከት) አንድ ክንድ “አንድ ክንድ” ከከግማሽ ሜትር ትንሽ የሚያንስ ነው።በዚህ ሥፍራ ላይ ጥቅም ላይ የዋለው አንድ ሰው በእድሜው ላይ ምንም መጨመር እንደማይችል በምሳሌ ለመግለጽ ነው። (እና ተመልከት) ስለምትለብሱት ነገር ስለምንት ትጨነቃላችሁ? ኢየሱስ ሰዎችን ለማስተማር ጥያቄን ይጠቀም ነበረው። ኤቲ፡ “ምን እለብሳለሁ ብላችሁ አትጨነቁ።” (ተመልከት) ስለአንድ ነገር ማሰብ “መጨነቅ” አበቦች የሜዳ አበቦች (ተመልከቱ) እላችኋለሁ ይህ ኢየሱስ ከዚህ በመቀጠል የሚናገረው ነገር አጽኖት ሊሰጠው የሚገባ መሆኑን ያሳያል። ማንም እንደነዚህ አግጦ አያውቅም ይህ በቀጥታ እንዲህ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “እንደነዚህ የሜዳ አበቦች ያጌጠ ልብስ ማንም ለብሶ አያውቅም።”

Matthew 6:30

ማቴዎስ **6:30-31**
አጠቃላይ መረጃ፡ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። “እናንተ” የሚለው ቃል በብዙ ቁጥር የተገለጸ ነው። እነዚህ ሣሮች እንደዚህ ካለበሳቸው ይህ ምሳሌ እግዚአብሔር አበቦችን እንዲህ ውብ ካደረጋቸው ማለት ነው። (ተመልከት) ሣር በቋንቋችሁ ሣር የሚለው ቃል የሚያካትት እና ከከዚህ በፊት የሜዳ አበባዎች ተብሎ የተተረጎመውን የሚያካትት ከተገኘ ያንን ቃል ተጠቀም። ወደ ማቃጠያ እቶን የሚጣለውን አይሁዳዊያን ምግባቸውን ለማብሰል ሣርን ይጠቀማሉ። ይህ በቀጥታ እንዲህ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “ወደ ማቃጠያ ይጥለዋል” ወይም “አንድ ሰው እንዲቀጣል ያደርገዋል።” (ተመልከት) እናንተ ምን አያለብሳችሁም . . . እምነት? ኢየሱስ ሰዎችን ለማስተማር ጥያቄን ይጠቀም ነበር። ኤቲ፡ “በእርግጠኝነት ያለብሳችኋል . . . እምነት።” (ተመልከት) እናንተ እምነት የጎደላችሁ “እናንተ ትንሽ እምነት ያላችሁ።” በእግዚአብሔር ላይ ያላቸው እምነት በጣም ትንሽ ከመሆኑ የተነሳ ኢየሱስ ሰዎችን ይገስጻቸዋል። ስለዚህ “እነዚህ ሁሉ ምክንቶች”

Matthew 6:32

ማቴዎስ **6:32-34**
አሕዛብም እነዚህ ነገሮች ሁሉ ይፈልጋሉ “አሕዛብም ነገ ምን እንደሚበሉ፣ እንደሚጠጡ እና እንደሚለብሱ ይጨነቃሉ።” በሰማይ ያለው አባታችሁ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ያውቃል ኢየሱስ በዚህ ንግግሩ ውስጥ በተዘዋዋር መልኩ የሚያስረግጠው ነገር መሠረታዊ ፍላጎቶቻችሁ በእግዚአብሔር በእርግጠኝነት ይሟላሉ። አባት ይህ የእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ የማዕረግ ስም ነው። (ተመልከት) በመጀመሪያ መግስቱን እና ጽድቁን ፈልጉ በዚህ ሥፍራ ላይ “መንግስቱ” የሚለው ቃል እግዚብሔር እንደ ንጉሥ መግዛቱን የሚያመለክት ነው። ኤቲ፡ “ንጉሥ የሆነውን እግዚአብሔርን አገልግል እንዲሁም መልካም የሆነውን ነገር አድርግ።” (ተመልከት) እነዚህ ሁሉ ነገሮች ይጨመሩልሃል ይህ በቀጥታ እንዲህ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “እግዚአብሔር እነዚህ ነገሮች ያዘጋጅልሃል።” (ተመልከት) ስለዚህ “በእነዚህ ሁሉ ምክንቶች” tomorrow will be anxious for itself Jesus is describing "tomorrow" as if it is a person that can worry. Jesus means that a person will have enough to worry about when the next day comes. ነገ ስለራሱ ይጨነቅ በዚህ ሥፍራ ላይ ኢየሱስ “ነገን” ልክ እንደ ሰው የሚጨነቅ አድርጎ ያቀርበዋል። ኢየሱስ አንድ ሰው ነገ ስመጣ በዚያ ቀን በቂ የሚጨነቅበት ነገር አለው ማለቱ ነው። (ተመልከት) ለዛሬ የራሱ ክፋት ይበቃዋል “እያንዳንዱ ቀን በውስጡ በቂ የሆነ ክፋትን ይዟል” ወይም “ሁሉም ቀናት በቂ ችግሮች አሏቸው”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 7

1 አትፍረዱ፥ እናንተም አይፈረድባችሁም። **2** በምትፈርዱበት ፍርድ፥ ይፈረድባችኋል፤በምትሰፍሩበትም መስፈሪያ፥ ለእናንተም ይሰፈርላችኋል። **3** በራስህ ዐይን ውስጥ ያለውን ግንድ ሳታስተውል፥ በወንድምህ ዐይን ውስጥ ያለውን ጉድፍ የምታየው ለምንድን ነው? **4** በአንተ ዐይንህ ውስጥ ግንድ እያለ፣ በወንድምህ ዐይን ውስጥ ያለውን ጉድፍ ላውጣልህ ማለት እንዴት ትችላለህ? **5** አንተ ግብዝ! በወንድምህ ዐይን ውስጥ ያለውን ጉድፍ በደንብ አይተህ ለማውጣት፣ በመጀመሪያ በራስህ ዐይን ውስጥ ያለውን ግንድ አስወግድ። **6** በእግራቸው እንዳይረግጡትና እናንተንም እንዳይቦጫጭቁዋችሁ፤ ቅዱስ የሆነውን ለውሾች አትስጡ፥ እንቁዎቻችሁንም ለዐሳማዎች አትጣሉ። **7** ለምኑ፣ ይሰጣችኋል፤ ፈልጉ፥ ታገኛላችሁ፤ አንኳኩ፣ ይከፈትላችኋል። **8** የሚለምን ሰው ሁሉ ይቀበላልና፣ የሚፈልግ ሰውም ያገኛል፥ ለሚያንኳኳም ሰው ይከፈትለታል። **9** ከእናንተ መካከል ልጁ እንጀራ ሲለምነው፣ ድንጋይ የሚሰጠው፣ **10** ዐሣ ሲለምነው፣ እባብ የሚሰጠው? ምን ዐይነት ሰው ነው? **11** እንግዲህ፥ እናንተ ክፉዎች የሆናችሁ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ፥ በሰማይ የሚኖር አባታችሁ ለሚለምኑት አብዝቶ መልካም ስጦታን እንዴት አይስጣቸውም? **12** ስለዚህ፣ ማንኛውንም ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትፈልጉትን ሁሉ፣ እናንተም ልታደርጉላቸው ይገባል፤ ምክንያቱም ሕጉም ነቢያቱም የሚያስተምሩት ይህንኑ ነው። **13** በጠባቡ በር ግቡ፣ ምክንያቱም ወደ ጥፋት የሚወስደው መንገድ ሰፊ፣ የሚሄዱበትም ብዙዎች ናቸው። **14** በሩ ጠባብ፣ ወደ ሕይወት የሚወስደውም መንገድ ቀጭን ስለ ሆነ፣ የሚያገኙት ጥቂቶች ናቸው። **15** የበግ ቆዳ ለብሰው ከሚመጡባችሁ፣ በትክክል ግን ነጣቂ ተኩላዎች ከሆኑ፣ ከሃሰተኛ ነቢያት ተጠንቀቁ። **16** በሚያፈሩት ፍሬ ታውቋቸዋላችሁ።ሰው ከእሾኽ የወይን ፍሬ፣ ወይም ከኩርንችት በለስ ሊሰበስብ ይችላልን? **17** እንደዚያው፥ መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬ ያፈራል፣ መጥፎ ዛፍ መጥፎ ፍሬ ያፈራል። **18** መልካም ዛፍ ሆኖ መጥፎ ፍሬ የሚያፈራ፣ ወይም መጥፎ ዛፍ ሆኖ መልካም ፍሬ የሚያፈራ ዛፍ የለም። **19** ማንኛውም መልካም ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል፣ ወደ እሳትም ይጣላል። **20** እንግዲህ በሚያፈሩት ፍሬ ታውቋቸዋላችሁ። **21** በሰማይ ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ እንጂ፣" ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ፣" እያለ የሚጠራኝ ሁሉ፣ ወደ መንግሥተ ሰማይ የሚገባ አይደለም። **22** በዚያ ቀን ብዙዎች፣ "ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ፣ በስምህ ትንቢት ተናግረን አልነበረም እንዴ፣ በስምህ አጋንንት አስወጥተን አልነበረም እንዴ፣ በስምህስ ብዙ ታላላቅ ነገሮችን አድርገን አልነበረም እንዴ?" ይሉኛል። **23** እኔም፣ “እናንት ክፉ አድራጊዎች፣ የት ዐውቃችሁና ነው? ከእኔ ራቁ ብዬ በግልጽ እነግራቸዋለሁ” **24** ስለዚህ፣ ቃሎቼን የሚሰማና የሚታዘዛቸው ልክ ቤቱን በድንጋይ ላይ የመሠረተ አስተዋይ ሰውን ይመስላል። **25** ዝናብ ዘነበ፣ ጎርፍም ጎረፈ፣ ነፋስም ነፈሰ ያንን ቤት መታው፤ ይሁን እንጂ ቤቱ በዐለት ላይ ስለ ተመሠረተ፣ አልወደቀም። **26** ሆኖም ቃሌን ሰምቶ የማይታዘዝ፣ ቤቱን በአሸዋ ላይ የመሠረተ ሞኝ ሰውን ይመስላል። **27** ዝናብ ዘነበ፣ ጎርፍ ጎረፈ፣ ነፋስም ነፈሰ፣ ያንንም ቤት መታው፤ ቤቱም ወደቀ፤ አወዳደቁም ከባድ ሆነ ። **28** ኢየሱስ እነዚህን ነገሮች ተናግሮ ሲጨርስ፣ ሕዝቡ በትምህርቱ ተገረሙ። **29** ያስተማረውም እንደ ባለስሥልጣን እንጂ ፣እንደ ጽሐፍት አልነበረም።

Matthew 7:1

ማቴዎስ 7:**1**-**2**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ በ in MAT 5:3 በተጀመረው የተራራው ስብከት ውስጥ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ማስተማሩን ቀጥሏል። አጠቃላይ መረጃ፡ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ “እናንተ” የሚለው ቃል እና የተሰጡት ትዕዛዛት በብዙ ቁጥር ተገልጸዋል። (ተመልትከት) አትፍረድ በዚህ ሥፍራ ላይ “አትፍረድ” የሚለው ቃል ጠንከር ያለ “ጠንከር ያለ ማውገዝን” ወይም “ጥፋተኛ አድርጎ መወሰንን” የሚያመለክት ቃል ነው። ኤቲ፡ “በሰዎችን ላይ አትፍረድ”። (ተመልከት) አይፈረድብህም ይህ በግልጽ እንዲህ ልገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “መጥፎ ፍርድ አይፈረድብህም።” (ተመልከት) Be sure the reader understands the statement in 7:2 is based on what Jesus said in 7:1. ምክንያቱም ኢየሱስ በ7:2 ላይ የተናገረው ንግግር መሠረቱ በ7:1ላይ የተናገረው መሆኑን እርግጠኞች ሁኑ። በፈረዳችሁት ፍርድ እናንተም ላይ እንዲሁ ይፈረዳል ይህ በዚህ መልኩ ልገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “በሌሎች ሰዎች ላይ በፈረዳችሁበት መጥን ልክ እናንተም ላይ እግዚአብሔር ይፈርዳል።” (ተመልከት) በዚያው ልክ ይፈረዳል ይህ እንዲህ በቀጥታ ልገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “እግዚአብሔር በዚያው ልክ ይፈርዳል።” (ተመልከት)

Matthew 7:3

ማቴዎስ 7:**3**-**5**
አጠቃላይ መረጃ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ “እንተ” የሚለው ቃል በነጠላ ቁጥር ተገልጸዋል ይን እንጂ በብዙ ቁጥር ልትተረጎማቸው ትችላለህ። ስለምን ታያለህ . . . እንዴትስ ትለዋለህ ኢየሱስ እነዚህን ሁሉት ጥያቄዎች የተጠቀመው ሰዎችን ለማስተማር እና አመለካከታቸውን እንደገና ይመለከቱት ዘንድ ነው። የሌሎች ሰዎች ኃጢአት ላይ ጣታቸውን ከመቀሰራቸው በፊት ለራሳቸውን ኃጢአት ትኩረት መስጠት ስለፈለገ ነው። (ተመልከት) በጣም ትንሽ ብናኝ “ቆሻሻ”(UDB) ወይም “ብናኝ” ወይም “አፈር”። ወደ ሰዎች ዐይን ውስጥ ብዙ ጊዜ የሚገባን ነገር ለመግለጽ የሚትጠቀሙትን ቃል ተጠቀም። ይህ በሰዎች ውስጥ የሚያጋጥምም በጣም ትንሹን ስህተትን ለማመልከት ጥቅም ላይ የዋ ምሳሌ ነው። (ተመልከት) ወንድም ይህ የሥጋ ወንድምን ወይም ጎረቤትን ሳይሆን አማኝን የሚያመለክት ነው። ምሰሶ አንድ ሰው በቆረጠው ዛፍ ውስጥ የሚገኘው ትልቁ ክፍል ምሰሶ ነው። ይህ ወደ ሰዎች ዐይን ለመግባት በጣም ትልቅ የሆነ ግንድ ነው። ይህ በሰው ሕይወት ውስጥ ያለ በጣም ትልቅ ስህተትን ያሳያል። እና ተመልከት)።

Matthew 7:6

ማቴዎስ 7:**6**-**6**
አጠቃላይ መረጃ፡ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ “እናንተ” የሚለው ቃል በብዙ ቁጥር ተገልጸዋል። ውሾች . . . እሪያዎች አይሁዶች እነዚህ እንስሳት ቆሻሾች አድርገው ይቆጥሯቸዋል እንዲሁም እግዚአብሔርም እነዚህን እንስሳት እንዳይበሉ አዞዋቸዋል። ይህ ቅዱስ ለሆነው ነገር ዋጋ የማይሰጡ ኃጢአተኛ ሰዎችን ለማመልከት የቀረበ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው። ይህንን ቃል በቁሙ መተርጎሙ ባጣም ጥሩ ነው። (ተመልከት)። እንቁዎች እነዚህ በጣም ትንንሽ፣ ውድ የሆኑ ድንጋዮች ናቸው። ይህ ስለእግዚአብሔር ወይም ስለውድ ነገሮች በአጠቃላይ ማወቅ ጋር ተያያዥነት ያለው ምሳሌያዊ ንግግር ነው። (ተመልከት) በእግሮቻቸው ልረጋግጡት ይችላሉ “እሪያዎቹ ይረጋግጡታል” እናም ወደ ትፋታቸው ይመለሳሉ “እናም ውሾች ወደ ትፋታቸው ይመለሳሉ”

Matthew 7:7

ማቴዎስ 7:**7**-**10**
አጠቃላይ መረጃ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ “እንተ”

የሚለው ቃል በብዙ ቁጥር ተገልጸዋል። (ተመልከት)። ጠይቁ . . . ፈልጉ . . . አንኳኩ ይህ ወደ እግዚአብሔር መጸለይን ለማመልከት ጥቅም ላይ የዋለ ምሳሌያዊ ንግግር ነው። በዚህ ሥፍራ ላይ ጥቅም ላይ የዋለው ግሥ እግዚአብሔር ምላሽ እስኪሰጠን ድረስ እንዲንጸለይ የሚያደርግ ነው። በቋንቋችሁ አንድን ነገር መልሳችሁ መልሳችሁ ማድረግ እንዳለባችሁ የሚገልጽ ቃል ካለ ይህንን ቃል ተጠቀሙ። (ተመልከት) ጠይቁ ይህ ከእግዚአብሔር የሆነ ነገርን ጠይቁ ማለት ነው። (UDB) ይሰጣችኋል ይህ እንዲህ ባለ መልኩ በቀጥታ ልገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “የሚያስፈልጋችሁን ነገር እግዚአብሔር ይሰጣችኋል። (ተመልከት) ፈልጉ “ስለምትፈልጉትን ነገር የእግዚአብሔርን ፊት ፈልጉ” አንኳኩ በር ማንኳኳት በቤት ውስጥ ያለ ሰው በሩን እንዲከፍትላችሁ በትህትና መጠየቅ ነው። በእናንት ባሕል ውስጥ በር ማንኳኳት ትህትና ካልሆነ ሰዎች በእናንተ ባሕል ውስጥ በር እንዲከፈትላቸው በትህትና የሚጠይቁ በምን ዓይነት መንገድ ነው፣ ይህንንም ቃል ተጠቀሙ። ኤቲ፡ “እግዚአብሔር በሩን እንዲከፍትላችሁ እንደሚትልጉ ንገሩት።” ወይም ከእናንተ መካከል ማን ነው . . . ድንጋይ? ኢየሱስ ሰዎችን ለማስተማር ጥያቄን ይጠቀማል። ኤቲ፡ “ከእናንተ መካከል ማንም የለም . . . ድንጋይ።” (ተመልከት) ቁራጭ ዳቦ ይህ በአጠቃላይ ምግብን ያመለክታል። ኤቲ፡ “የሆነ ምግብ።” (ተመልከት) ድንጋይ. . . ዓሳ . . . እባብ እነዚህ ስሞች በቁማቸው መተርጎም አለባቸው። ወይም ኣሳ ጠይቋችሁ እባብ የምትሰጡት? ኢየሱስ ለማስተማር ሌላ ጥያቄ ጠየቃቸው። በዚህ ሥፍራም ኢየሱስ ስለ ሰውዬው እና ልጁ እየተናገረ መሆኑን መረዳት አስፈላጊ ነው። ኤቲ፡ “ከእናንተ መካከል ልጁ ዓሳ ጠይቆት እባብ የሚሰጠው ማንንም የለም።” (እና ተመልከት)

Matthew 7:11

ማቴዎስ 7:**11-12**
አጠቃላይ መረጃ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ “እንተ” የሚለው ቃል በብዙ ቁጥር ተገልጸዋል። (ተመልከት)። በሰማይ ያለው አባታችሁ አስበልጦ ምን ያኽል አይሰጣችሁ . . . አርሱ? በዚህ ሥፍራ ኢየሱስ ሕዝቡን ለማስተማር ጥየቄን ተጠቀሟል። ኤቲ፡ “በሰማይ ያለው አባታችሁ በእርግጠኝነት ይሰጠዋል . . . እርሱ።” (ተመልከት) አባት ይህ የእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ የማዕረግ ስም ነው። (ተመልከት) ሰዎችን እንዲያደርጉላችሁ የሚትፈልጉትን ነገር ሁሉ “ሰዎች እንዲያደርጉላችሁ የሚትልጉትን ነገር ሁሉ” (UDB) ሕግ እና ነቢያት እነዚህ ናቸው በዚህ ሥፍራ ላይ “ሕግ” እና “ነቢያት” የሚለው ቃል ሙሴ እና ነቢያት የጻፏቸው መጽሐፍትን ያመለክታል። ኤቲ፡ “ይህ ሙሴ እና ነቢያት የጻፉጽ ስለዚህ ጉዳይ ነው። (ተመልከት)

Matthew 7:13

ማቴዎስ 7:**13-14**
አጠቃላይ መረጃ፡ ስለ ሁለቱ በሮች እና መንገዶች አጽኖት መስጠት ያስችለ ዘንድ ስትተረጉም “ሰፍ” የሚለው ቃል “ጠባብ” ከሚለው በተቻለ መጠን የሚለይ መሆኑን አሳይ። በጠባቢ በር ግቡ . . የሚገኙት ጥቂቶች ናቸው ይህ በመንገድ ላይ የሚሄድ እና ወደ መንግስቱ በበር የሚገባ ሰው ምስል ነው። ወደ አንደኛው መንግስት መግባት ቀላል ሲሆን ወደሌላኛው መንግስት መግባት ግን ከባድ ነው። ይህ ሰዎች የዘላለም ሕይወትን ለማግኘት ሰዎች ከባድ የሆነውን በሕይወታቸው እግዚአብሔርን መታዘዝ መቀበል እንደሚኖርባቸው ለማሳየት የቀረበ ምሳሌ ነው። እግዚአብሔር የተመታዘዝ ቀላሉን መንገድ ከመረጡ ወደ ስኦል ይገባሉ። (ተመልከት) በጠባቢ በር ግቡ ይህንን ወደ ቁጥር 14 መጨረሻ ልትወስዱት ትችላላችሁ፡ “ስለዚህ በጠባቡ በር ግቡ”። በር . . . መንገድ አማራጭ ትርጉሞች 1) ይህ ወደ መንግስቱ መግቢያ በር እና ወደ በሩ የሚወስድ መንገድን ያመለክታል። ይህ ከሆነ በUDB ላይ ያለውን ቅደም ተከተል ልታለዋውጠው ትችላለህ። ወይም 2) “በር” እና “መንገድ” ሁለቱም የመንግስቱ መግቢያነ ናቸው። ይህ ከሆነ ቅደም ተከተሉን ማለዋወጥ አይኖርብህም። (ተመልከት) ወደ ጥፋት . . . ወደ ሕይወት እነዚህ በግስ ልተረጎሙ ይችላሉ። ኤቲ፡ “ወደምትሞቱበት ሥፍራ . . . በሕይወት ወደሚትኖርቡት ሥፍራ” (ተመልከት)

Matthew 7:15

ማቴዎስ 7፡ **15-17**
ተጠንቀቁ “ራሳችሁን ጠብቁ” የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡ ነገር ግን ተኩላዎች ከሆኑ ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር መልካም እና መርዳት የሚፈልጉ መስለው የሚመጡ ነገር ግን ክፉ የሆኑ እና ከሚጎዷችሁ ሐሰተኛ ነቢያት ራሳችሁን ጠብቁ። (ተመልከት) በፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ ይህ ምሳሌዊ ንግግር የሰውን ተግባር የሚያመለክት ነው። ኤቲ፡ “ዘፍ በፍሬው እንደሚታወቅ ሁሉ ሐሰተኛ ነቢያት በሥራቸው ይታወቃሉ።” (ተመልከት) ሰዎች ከኩርንችት. . . ይለቅማሉን ኢየሱስ ጥየቄን ሰዎችን ለማስተማር ተጠቅሟል። ሰዎች ለዚህ ጥያቄ ምላሱ አይ መሆኑን ማወቅ አለባቸው። ኤቲ፡ “ሰዎች ከኩርንችት . . . አይለቅሙም።” (ተመልከት) መልካም ዛፉ ሁሉ መልካ ፍሬን ያፈራል ኢየሱስ የፍሬን ምሳሌ በመጠቀም ጥሩ ሥራ ወይም ቃል ስለሚያመጡ ስለጥሩ ነቢያት መናገሩን ቀጥሏል። (ተመልከት) የተበላሸ ዘፍ መጥፎ ፍሬ ያፈራል ኢየሱስ የፍሬን ምሳሌ በመጠቀም መጥፎ ሥራ ስለሚሠሩ መጥፎ ነቢያት መናገሩን ቀጥሏል። (ተመልከት)

Matthew 7:18

ማቴዎስ 7፡**18-20**
መልካምን ፍሬ የማያፈራውን ዘፍ ይቆረጣል እንዲሁም ወደ እሳት ይጣላል ኢየሱስ የፍሬውን ምሳሌ ሐሰተኛ ነቢያትን ለማመልከት ተጠቅሞዋል። በዚህ ሥፍራ ላይ በመጥፎ ዛፍ ላይ ምን እንደሚሆን ብቻ ተናግሯል። ይህ በተዘዋዋር መንገድ የሚያሳየው በሐሰተኛ ነቢያት ላይ ተመሳሳይ ነገር ነው። (እና ተመልከት) ይቆረጣል፣ ወደ እሳትም ይጣላል ይህ በዚህ መንገድ ልገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “ይቆርጡትና ያቃጥሉታል። “ (ተመልከት) በፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ “እነርሱን” የሚለው ቃል ነብያቱን ወይም ዛፎቹን ሊያመለክት ይችላል። የዛፉ ፍሬ እና የነቢያቱ ድርጊት የሁለቱም መልካ ወይም መጥፎ ሊሆን ይችላል። ከተቻለ ከሁለቱ አንዱን በሚያመለክት መልኩ ተርጉሙት። (ተመልከት)

Matthew 7:21

ማቴዎስ 7፡ **21-23**
ወደ መንግስተ ሰማያት ይገባል በዚህ ሥፍራ ላይ “መንግስት” የሚለው ቃ እግዚአብሔር እንደ ንጉሥ መግዛቱን ያመለክታል። “መንግስተ ሰማያት” በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ብቻ ጥቅም ላይ የዋለ ቃል ነው። ከተቻለ “ሰማይ” የሚለውን ቃል በትርጉማችሁ ውስጥ ለማኖር ጥረት አድርጉ። ኤቲ፡ “እግዚአብሔር ራሱን እንደ ንጉሥ በሚገልጥበት ጊዜ በሰማይ ከእግዚአብሔር ጋር ይኖራል።” (ተመልከት) የአባቴን ፈቃድ የሚያደረግ ማንኛውም ሰው “የአባቴን ፍላጎት የሚፈጽም ማንም ሰው” አባት ይህ የእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ የማዕረግ ስም ነው። (ተመልከት) በዚያ ቀን ኢየሱስ “በዚያ ቀን” በማለት የተናገረው አድማጮቹ በዚያ ቀን የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው የፍርድ ቀንን እንደሆነ እንደሚገባቸው ታሳቢ በማድረግ ነው። አንባቢዎቻችሁ በግልጽ በዚያ ቀን የሚለው ሀረግ ትንቢት አልተናገርንምን . . . ሴጣንን አላወጣንምን . . . ብዙ ተዓምራትን አላደረግንምን? ሰዎች እነዚህ ነገሮች ማድረጋቸው ላይ ትኩረት ያደርጋሉ። ኤቲ፡ “ትንቡትን ተናግረናል . . . ሴጣንን አስወጥተናል . . . ታላላቅ ተዓምራን አድርገናል።” (ተመልከት) እኛ ይህ “እኛ” የሚለው ቃ ኢየሱስን አያካትትም። (ተመልከት) በስምህ በዚህ ሥፍራ ላይ “በስምህ” የሚለው ቃል በኢየሱስ ስልጣን እና ስም” ማት ነው። (ተመልከት) ታላላቅ ነገሮችን “ተዓምራትን” አላውቃችሁም ይህ ማለት ይህ ሰው የኢየሱስ አይደለም ማለት ነው። ኤቲ፡ “አንተ የእኔ ተከታይ አይደለህም” ወይም “ከአንተ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለኝም።” (ተመልከት)

Matthew 7:24

ማቴዎስ 7፡**24-25**
ስለዚህ “በዚህ ምክንያት” ቃሎቼ በዚህ ሥፍራ ላይ “ቃሎቼ” የሚለው ቃል ኢየሱስ የተናገራውን ቃላት ያመለክታል። (ተመልከት) በዓለት ላይ ቤትን የሠራን ጠቢብ ሰው ይመስላሉ ኢየሱስ የእርሱን ቃል የሚጠብቁ ሰዎችን

ምንም ነገር ልጎዳው በማይችል መሠረት ላይ ቤታውን ከሠሩ ሰዎች ጋር ያነጻጽራል። (ተመልከት) ዓለት ይህ በመሬት የላይኛው ክፍል ላይ ከመገኘው አፈር እ አሸዋ ቀጥሎ የሚገኝ ነው። በዚህ ላይ ቤቱን የገነባ ይህ በቀጥታ እንዲህ ልገለጽ ይገባል። ኤቲ፡ “የገነባው” (ተመልከት)

Matthew 7:26

ማቴዎስ **7**:**26**-**27**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ይህ በ MAT 5:3. የተጀመረው የኢየሱስ የተራራው ስብከት መጨረሻ ነው። ሞኝ ሰው ቤቱን በአሸዋ ላይ ይሠራል ኢየሱስ ከዚህ በፊት ያቀረበውን ንጽጽር ቀጥሏል። ትዕዛዛቱን ያልታዘዙ ሰዎችን ቤታቸውን በአሸዋ ላይ ከሠሩ ሞኝ ሰዎች ጋር አነጻጽሯል። ቤቱን ዝናብ፣ ጎርፍ እና አውሎ ንፋስ ልያጠፋው በሚችል አሸዋማ መሬት ላይ የሚሠራ ሞኝ ሰው ብቻ ነው። (ተመልከት) ወደቀ በቋንቋችሁ አንድ ቤት መውደቁን ለመግለጽ የሚትጠቀሙትን የተለመደ ቃል በዚህ ሥፍራ ላይ ተጠቀሙ። ጥፋቱ እጅግ በጣም የከፋ ይሆናል ዝናቡ፣ ጎር እና አውሎ ንፋሱ ቤቱን ፈጽሞ ያጠፋዋል።

Matthew 7:28

ማቴዎስ **7**፡ **28**-**29**
አጠቃላይ መረጃ እነዚህ ቁጥሮች ኢየሱስ በተራራው ስብከት ውስጥ ስላስተማራቸው ትመህርቶች የሰጠውን ምላሽ ምን ይህንን ከፈጸመ በኋላ ይህ ሀረግ የተራራው ስብከት መጨረሻ ለመሆኑ ምልክት ነው። ኤቲ፡ በመጨረሻውም” በትምህርቱ እጅግ በጣም ተገረሙ በ7:29 ላይ ኢየሱስ ባስተማረው ትምህርት ብቻ ሳይሆን ባስተማረበት መንገድም እንደተገረሙ በግልጽ ማየት ይቻላል። ኤቲ፡ “በማስተማር ዘዴውም እጅግ በጣም ተገረሙ።”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 8

1 ኢየሱስ ከተራራው በወረደ ጊዜ፣ ብዙ ሕዝብ ተከተሉት። 2 እነሆ፣ አንድ ለምጻም ወደ እርሱ መጣ፣ “ጌታ ሆይ፣ ፈቃደኛ ከሆንህ፣ ልታነጻኝ ትችላለህ” በማለት በፊቱ ሰገደለት። 3 ኢየሱስም፣ “ፈቃደኛ ነኝ ንጻ” በማለት እጁን ዘርግቶ ዳሰሰው። ወዲያውኑ ከለምጹ ነጻ። 4 ኢየሱስ፣ “ተጠንቀቅ! ለማንም አትናገር። ዝም ብለህ ሂድና ራስህን ለካህን አሳይ፣ምስክር እንዲሆናቸውም ሙሴ ያዘዘውን ስጦታ አቅርብ”አለው። 5 ኢየሱስ ወደቅፍርናሆም በገባ ጊዜ፣ አንድ የመቶ አለቃ ወደ እርሱ መጥቶ፣ 6 ጌታ ሆይ፣ "አገልጋዬ በከባድ ሕመም ሸባ ሆኖ ቤቴ ተኝቷል" በማለት ለመነው። 7 ኢየሱስ፣ "መጥቼ እፈውሰዋለሁ” አለው። 8 የመቶ አለቃውም መልሶ፣“ጌታ ሆይ፣ አንተ ወደ ቤቴ ጣራ በታች ልትገባ አይገባኝም፣ ነገር ግን ቃል ብቻ ተናገር አገልጋዬም ይፈወሳል” አለው። 9 እኔ ደግሞ ከሌላው ሥልጣን ሥር ያለሁና በእኔም ሥልጣን ሥር ወታደሮች ያሉኝ ሰው ነኝ። አንዱን “ሂድ” ብለው ይሄዳል፤ ሌላውንም “ና” ብለው ይመጣል፣ አገልጋዬንም 'ይህን አድርግ' ብለው ያደርጋል"። 10 ኢየሱስም ይህን በሰማ ጊዜ በጣም ተደነቀ፣ ይከተሉት ለነበሩት ሰዎችም “እውነት ነው የምነግራችሁ፣ በእስራኤል እንኳ እንደዚህ ያለ ትልቅ እምነት አላገኘሁም” አላቸው። 11 እነግራችኋለሁ ብዙዎች ከምሥራቅና ከምዕራብ ይመጣሉ፣ በእግዚአብሔር መንግሥትም ከአብርሃም፣ ከይስሐቅና ከያዕቆብ ጋር በማዕድ ይቀመጣሉ። 12 የመንግሥት ልጆች ግን ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ወዳለበት ወደ ውጪው ጨለማ ይጣላሉ። 13 ኢየሱስም የመቶ አለቃውን፣ “ሂድ! እንደ እምነትህ ይሁንልህ" አለው። አገልጋዩም በዚያው ሰዓት ተፈወሰ ። 14 ኢየሱስ ወደ ጴጥሮስ ቤት በገባ ጊዜ የጴጥሮስን አማት በትኩሳት ታማ ተኝታ አገኛት። 15 ኢየሱስ እጅዋን ነካት፣ ትኩሳቱም ለቀቃት፣ ተነሥታም ታገለግለው ጀመር። 16 በመሸ ጊዜ፣ ሕዝቡ አጋንንት የያዙአቸውን ብዙዎችን ወደ ኢየሱስ አመጡ፣ እርሱም በቃሉ፣ መናፍስቱን አስወጣቸው፤ ታመው የነበሩትንም ሁሉ ፈወሳቸው። 17 በዚህ ዐይነት፣ በነቢዩ ኢሳይያስ፣ “እርሱ ሕመማችንን ተቀበለ ደዌዎቻችንን ተሸከመ” ተብሎ የተነገረው ተፈጸመ። 18 ኢየሱስም በዙሪያው ያሉትን ሕዝብ ባየ ጊዜ፣ ወደ ገሊላ ባሕር ማዶ እንዲሻገሩ አዘዘ። 19 ከዚያም አንድ ጸሐፊ ወደ እርሱ ቀርቦ፣ “መምህር ሆይ፣ ወደምትሄድበት ሁሉ እከተልሃለሁ” አለው። 20 ኢየሱስም "ቀበሮዎች ጉድጓድ የሰማይ ወፎችም ጎጆዎች አሏቸው። የሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያሳርፍበት ምንም ስፍራ የለውም"አለው። 21 ከደቀመዛሙርቱም ሌላው፣ "ጌታ ሆይ፣ በመጀመሪያ እንድሄድና አባቴን እንድቀብር ፍቀድልኝ አለው።" 22 ኢየሱስ ግን፣ “ተከተለኝ፣ ሙታናቸውን እንዲቀብሩ ሙታንን ተዋቸው” አለው። 23 ኢየሱስ ወደ ጀልባ በገባ ጊዜ፣ ደቀ መዛሙርቱም ተከትለውት ገቡ። 24 እነሆም፣ በባሕሩ ላይ ታላቅ ማዕበል ተነሥቶ ጀልባዋ በማዕበል ተሸፈነች። ኢየሱስ ግን ተኝቶ ነበር። 25 ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ መጥተው፣ "ጌታ ሆ፣ እድነን ልንጠፋ ነው" በማለት ቀሰቀሱት። 26 ኢየሱስ፣ "እናንተ እምነት የጐደላችሁ ስለምን ፈራችሁ?”አላቸው። ከዚያም ተነሥቶ ነፋሱንና ባሕሩን ገሠፀ፣ ከዚያ በኋላ ታላቅ ጸጥታ ሆነ። 27 ሰዎቹም ተገርመው፣ "ይህ ምን ዓይነት ሰው ነው? ነፋሳትና ባሕሩም እንኳ ይታዘዙለታል" አሉ። 28 ኢየሱስም ወደ ማዶ ወደ ጌርጌሴኖን አገር በመጣ ጊዜ፣ አጋንንት የተቆጣጠራቸው ሁለት ሰዎች ተገናኙት። የመጡትም ከመቃብር ነበርና በዚያ ማንም ማለፍ እስከማይችል ድረስ በጣም ጎይለኞች ነበሩ። 29 እነሆም፣ እየጮኹ፣ "አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ሆይ፣ እኛ ከአንተ ምን ጉዳይ አለን? ጊዜው ሳይደርስ ልታሠቃየን ወደዚህ መጣህን?" አሉ። 30 ከዚያ አካባቢ ብዙ ሳይርቅ በግጦሽ ላይ ያሉ ብዙ ዐሳማዎች ነበሩ። 31 አጋንንቱም ኢየሱስን፣ "የምታወጣን ከሆነ ወደዚያ የዐሳማዎች መንጋ ስደደን" ብለው መለመናቸውን ቀጠሉ። 32 ኢየሱስም፣ "ሂዱ!"አላቸው። አጋንንቱም ወጥተው ዐሳማዎቹ ውስጥ ገቡ፤ እነሆም፣ የዐሳማዎቹ መንጋ ሁሉ ወደ ታች ቁልቁለቱን እየተጣደፉ ወደ ባሕሩ ወርደው ውሃው ውስጥ ገብተው ጠፉ። 33 እነዚያም ዐሳማዎቹን ይጠብቁ የነበሩት ሰዎች ሸሽተው ወደ ከተማ ሄደው የሆነውን ሁሉ ፣ በአጋንንት ተይዘው ስለ ነበሩት ሰለ ሁሉቱ ሰዎችም አወሩ። 34 የከተማውም ሕዝብ ሁሉ ኢየሱስን ለማየት መጡ። ባዩትም ጊዜ አካባቢያቸውን ለቆ አንዲሄድ ለመኑት።

Matthew 8:1

ማቴዎስ **8:1-3**
አጠቃላይ መረጃ: ይህ በታሪክ ውስጥ ኢየሱስ ብዙ ሰዎችን የፈወሰበት የአዲሱ ክፍል ጅማሬ ነው። ይህ ጭብጥ በእነዚህ ውስጥ ይቀጥላል MAT 9:35. (ተመልከት) ኢየሱስ ከተራራ በወረደ ጊዜ ብዙ ሕዝብ ተከተለው “ኢየሱስ ከተራራ ከወረደ በኋላ ብዙ ሕዝብ ከተለው።” ይህ ሕዝብ በተራራው ከእርሱ ጋር የነበሩትን እንዲሁም ያልነበሩትንም ሊያካትት ይችላል። እነሆ “እነሆ” የሚለው ቃል በታሪክ ውስጥ አዲስ ሰውን ያስተዋውቀናል። በቋንቋችሁ ይህንን የሚታደርጉበት ቃል ሊኖራችሁ ይችላል። ለምጻም “ለምጽ ያለበት ሰው” ወይም “የቆዳ በሽታ ያለበት ሰው።” (UDB) በፊቱ ሰገደ ይህ በኢየሱስ ፊት ያሳየው ትህትና የሞላበት አቀራረብ ምልክት ነው። (ተመልከት) ፈቃደኛ ከሆንክ “ከፈለግህ” ወይም “ፍላጎት ካለህ”። ለምጻሙ ሰው ኢየሱስ እርሱን የመፈወስ ኃይል እንዳለው አውቋል ይሁን እንጂ ኢየሱስ እርሱን ለመንካት ፈቃደኛ ይሁን አይሁን ግን አላወቀም። ልታነጻኝ ትችላለህ በዚህ ሥፍራ ላይ “ልታነጻኝ” የሚለው ቃል መፈወስን እና በማህህበረሰቡ ውስጥ እንደገና ተቀላቅሎ መኖርን የሚያመለክት ቃል ነው። ኤቲ: “ልትፈውሰኝ ትችላለህ” ወይም 1እባክህ ፈውሰኝ”። (UDB) (ተመልከት) ወዲያው “በዚያን ጊዜ” ከለምጹ ነጻ “ንጻ” የሚለው የኢየሱስ ንግግር ውጤቱ የሰውዬው መፈወስ ነው። ይህ እንዲህ ባለ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ: “ጤነኛ ሆነ” ወይም “ለምጹ ለቀቀው” ወይም “ከለምጹ ነጻ”። (ተመልከት)

Matthew 8:4

ማቴዎስ **8:4-4**
ለእርሱ ይህ ኢየሱስ የፈወሰውን ሰው ያመለክታል። ለማንም አትናገር “ለማንም ምንም አትናገር” ወይም “እኔ እንደፈወስኩህ ለማንም አትናገር” ለካህናት ራስህን አሳይ የአይሁዳዊያን ሕግ የተፈወሰ ሰው ቆዳውን ለካህናት ማሳየት እንዳለበት ይጠይቃል። እነርሱም ቆዳውን ከተመለከቱ በኋላ ከሕዝቡ ጋር እንዲቀላቀል ይፈቅዱለታል። (ተመልከት) ለእርሱ ምስክር ይሆንህ ዘንድ በሙሴ ትዕዛዝ መሠረት መስዋዕትን አቅርብ በሙሴ ሕግ መሠረት ከለምጽ የተፈወሰ ሰው የምስጋና መስዋዕትን ለከካህናት ማቅረብ ይኖርበታል። ካህናቱ ስጦታውን ከተቀበሉ ሕዝቡ ይህ ሰው መፈወሱን ያውቃሉ። (ተመልከት) ለእነርሱ ይህ የሚያመለክተው 1) ካህናትን ወይም 2) ሌሎች ሰዎችን ወይም 3) ኢየሱስን የሚተቹ ሰዎችን ሊሆን ይችላል። ከተቻለ ከእነዚህ ቡድኖች መካከል ዬትኛውንም የሚያመለክትን ስም ተጠቀሙ። (ተመልከት)

Matthew 8:5

ማቴዎስ **8:5-7**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር በዚህ የታሪኩ ክፍል ውስጥ ጸሐፊው ወደሌላ ጊዜ እና ቦታ በመሄድ ኢየሱስ ሌላ ሰው የፈወሰበትን ሁኔታ ያሳያል። ወደ እርሱ መጥቶ ጠየቀው “በዚህ ሥፍራ “እርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢየሱስን ነው። ሸባ “ከበሽታው የተነሳ ከቦታ ቦታ መዘዋወር የማይችል” ኢየሱስም እንዲህ አለው። “ኢየሱስ ለመቶ አለቃው እንዲህ አለው” መጥቼ እፈውሰዋለሁ “ወደ ቤትህ መጥቼ ባርያህን አድነዋለሁ።”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Matthew 8:8

ማቴዎስ **8:8-10**
ወደ ቤቴ ጣሪያ ሥር ግባ ""የቤቴ ጣሪያ ሥር" የሚለው ሀረግ "ቤቴ" ማለት ነው። (ተመልከት) ቃል ተናገር በዚህ ሥፍራ "ቃል" የሚለው ቃል ትዕዛዝ ስጥ ማለት ነው። ኤቲ: "ትዕዛዝ ስጥ"። (ተመልከት) ይፈወሳል ይህ እንዲህ ልገለጽ ይችላል። ኤቲ: "ይድናል።" (ተመልከት) በስልጣን ሥር ያለ ይህ በዚህ መልኩ ልገለጽ ይችላል። ኤቲ: "በሌላ ሰው ሥልጣን ሥር ያለ ማንኛውም ሰው።" (ተመልከት) በሥልጣን ሥር . . . በእኔ ሥር በአንድ ሰው "ሥር" መሆን ማለት የሌላ ሰው ትዕዛዝ እንደሚበልጥ በማወቅ ትዕዛዙን መቀበል። (ተመልከት) ወታደሮች "የሰለጠኑ ተደባዳቢዎች" እውነት እልሃለሁ "እውነት እልሃለሁ።" ይህ ሀረግ ኢየሱስ በቀጣይነት የሚናገረው ነገር ላይ ትኩረት እንዲደረግ ይጋብዛል። እንዲህ ዓይነት እምነት በእስራኤል እንኳ አላገኘሁም የኢየሱስ አድማጮች የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆኑ የሚያስቡት በእስራኤል ያሉ አይሁዳዊያን ከማንም ይልቅ ታላቅ የሆነ እምነት እንደሚኖራቸው ያስቡ ነበር። ኢየሱስ ግን ተሳስተዋል በማለት ተናግሯል። የመቶ አለቃው እምነት ከሁሉ ታላቅ ነበር። (ተመልከት)

Matthew 8:11

ማቴዎስ **8:11-13**
አንተ በዚህ ሥፍራ ላይ "አንተ" የሚለው ቃል ብዙ ቁጥርን የሚያመለክት ሲሆን "እርሱን የሚከተሉትን ሰዎችን" ነው። MAT 8:10. (: ተመልከት) ከምስራቅ እና ከምዕራብ ተቃራኒ የሆኑትን "ምቅራቅ" እና "ምዕራብ"ን በመጠቀም "በሁሉም አከባቢ" የሚል መልዕክት አስተላልፏል። ኤቲ: "በሁሉም አከባቢ" ወይም "በሁሉም አቅጣጫ ከሩቅ ሥፍራ" (ተመልከት) በማዕድ ይቀመጣሉ በዚያ ባሕል ውስጥ ያሉ ሰዎች ምግብ በሚመገቡበት ወቅት በጠረጴዛ ዙሪያ ይቀመጣሉ። ይህ ሀረግ የሚያመለክተው በጠረጴዛው ዙሪያ የሚቀመጡት ቤተሰብ እና የቅርብ ጓደኞች ናቸው። ኤቲ: "እንደ ቤተሰብ ከዳኞች ጋር መኖር"። (ተመልከት) በመንግስተ ሰማያት በዚህ ሥፍራ "መንግስት" የሚለው ቃል እግዚአብሔር እንደ ንጉሥ የሚገዛበትን የሚያመለክት ነው። "መንግስ ሰማያት" የሚለው ሀረግ ጥቅም ላይ የዋለው በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ብቻ ነው። ከተቻለ "ሰማይ" የሚለውን ቃል በትርጉማችሁ ውስጥ ላማስቀመት ሞክሩ። ኤቲ: "በሰማይ ያለው አምላካችን ንጉሥ መሆኑን በሚሳይበት ጊዜ።" (ተመልከት) የመንግስቱ ለልጆች ይጣላሉ ይህ እንዲህ ልገለጽ ይችላል። ኤቲ: "እግዚአብሔር የመንግስቱን ልጆች አውጥቶ ይጥላቸዋል።" (ተመልከት) የመንግስ ልጆች "የ. . . ልጆች" የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው የእርሱ የሆኑት ፤ በዚህ ሁኔታ ውስጥ የእግዚአብሔር መንግስት የሆኑት ማለት ነው። ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ሥፍረ ምጸታዊ ንግግር አለ ምክንያቱም እንግዶች ወደ መንግስቱ እንዲገቡ ሲደረግ "ልጆች" ወደ ውጪ ይጣላሉ። ኤቲ: "እግዚአብሔር ይገዛቸው ዘንድ የፈቀዱለት"። (እና ተመልከት) ወደ ውጭ ጨለማ ይህ እግዚአብሔርን ያልተቀበሉት ዘላለማዊ መዳረሻቸው ምን እንደሆነ የሚያሳይ ነው። ኤቲ: "ከእግዚአብሔር የራቀ ጨለማ ሥፍራ" ወይም "ስኦል"። (ተመልከት) ለእናንተ ይሆን ዘንድ ይህ እንዲህ ልገለጽ ይችላል። ኤቲ: "ለእናንተ አደርገዋለሁ።" (ተመልከት) ባሪያው ተፈወሰ ይህ እንዲህ ልገለጽ ይችላል። ኤቲ: "ኢየሱስ ባሪያወን ፈወሰ።" (ተመልከት) በዚያው ሰዓት "ኢየሱስ ባሪያውን እፈውሰዋለሁ ብሎ በተናገረበት ቅጽበት"

Matthew 8:14

ማቴዎስ **8:14-15**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር በዚህ ሥፍራ ጸሐፊው ታሪኩን ወደ ሌላ ጊዜ እና ቦታ በመቀየር ኢየሱስ ሌላ ሰው የፈወሰበትን ሁኔታ ያሳየናል። ኢየሱስ መጥቶ ደቀ መዛሙርቱ ምናባት ከእርሱ ጋር ልሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን የታሪኩ ዋና ትኩረት ኢየሱስ ስላደረገው እና ሰስለተናገረው ነገር ነው። በዚህ ሥፍራ ደቀ መዛሙርቱን የጠቀሰበት ምክንት የተሳሳተ ትርጉም እንዳይኖር በማለት ነው። የጴጥሮስ አማች "የጴጥሮስ ምስት እናት" ንዳዱ ትቷት ሄደ በቋንቋችሄ እንዲህ ያለ ሰውኛ የአጻጻፍ ስልት ማለትም ንዳድ በራሱ አስቦ አንድን ነገር እንደሚፈጽ የሚሳይ ሰውኛ የአነጋገር ስልት ካለ "ተሸለት" ወይም "ኢየሱስ ፈወሳት" ተብሎ ልተረጎም ይችላል። (ተመልከት) ተነስታ "ከተኛችበት አልጋ ተነስታ"

Matthew 8:16

ማቴዎስ **8:16-17**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር› በዚህ ሥፍራ የታሪኩ ፍሰት በዚያው ቀን ምሽት ላይ ኢየሱስ ብዙ ሰዎችን ወደ ፈወሰበት እና ሴጣንን ከብዙ ሰዎች ወደአወጣበት ታርክ ይዞራል። አጠቃላይ መረጃ: በቁጥር 17 ላይ ጸሐፊው የኢየሱስ የፈውስ አገልግሎቱን በነብያት የተነገው ትንቢት ፍጻሜ መሆኑን ከነብዩ ኢሳያስ መጽሐፍ ውስጥ በመጥቀስ ጽፏል። በመሸም ጊዜ ይህ ከሰንበት በኋላ መሆኑን ያሳያል ምክንያቱም አይሁዳዊየን በሰንበት ቀን ሥራ አይሠሩም ወይም መንገድ አይሄዱም። እስኪመሸ ድረስ ጠብቀው ሰዎችን ወደ ኢየሱስ አመጡ። የተሳሳተ ትርጉምን ከማስወገድ አንጻር ካልሆነ በስተቀር ሰንበት የሚለው ቃል መጥቀሱ አስፈላጊ አይደለም። (ተመልከት) በዳብሎ የተያዙ ብዙ ሰዎችን ወደ እርሱ አመጡ ይህ እንዲህ ልገለጽ ይችላል። ኤቲ: "ብዙ በዳብሎስ የተያዙ" (UDB) ወይም "በዳብሎስ ቁጥር ሥር የሆኑ ብዙ ሰዎች" (ተመልከት) በቃሉ መናፍስቱን አስወጣ በዚህ ሥፍራ "ቃል" የሚለው ቃል ትርጉሙ ትዕዛዝ ነው። ኤቲ: "መንፈሱ እንዲወጣ አዘዘ።" (ተመልከት) በነብይ ኢሳያስ የተነገረው ትንቢትን ይፈጽም ነበር ይህ እንዲህ ልገለጽ ይችላል። ኤቲ: "ነብዩ ኢሳያስ ለእስራኤል ሕዝብ የተናገረው የትንቢት ቃልን ኢየሱስ ፈጸመው። () ተመልከት) ድካማችን ተቀበለ ደዊያችንንም ተሸከመ ማቴዎስ ከነብዩ ኢሳያስ መጽሐፍ በዚህ ሥፍራ ላይ ጠቅሷል። እነዚህ ሁለቱ ሀረጋት በመሠረታዊ መልዕክታቸው ተመሳሳይ ናቸው። ሁለቱም አጽኖት የሚሰጡት እርሱ ሁሉንም በሽታችንን ፈውሷል። ኤቲ: "የታመሙትን ፈውሷል እንዲሁም ደና አድርጓቸዋል። (ተመልከት)

Matthew 8:18

ማቴዎስ **8:18-20**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር በዚህ ሥፍራ ላይ ታሪኩ ኢየሱስ ልከተሉት ለሚፈልጉ ሰዎች የሰጠው ምላሽ ምን እንደሆነ ወደማሳየት ይሄዳል። አሁን በዚህ ሥፍራ ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው በዋናው ታርክ ውስጥ አዲስ ታሪክ መጀመሩን ለማሳየት ነው። ማቴዎስ በዚህ ሥፍራ ላይ የታሪኩን አዲስ ክፍል ይነግረናል። መመሪያዎች ሰጠ "ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አላቸው" ከዚያ ማለትም ኢየሰስ "መመሪያዎችን ከሰጠ በኋላ ነገር ግን ወደ ታንኳይቱ ከመግባቱ በፊት በዬትም ሥፍራ "በዬትኛውም ቦታ" ቀበሮዎች ጉድጓድ አላቸው እንዲሁም የሰማይ ወፎች ጎኛ አላቸው ቀበሮዎች ቀበሮዎች እንደ ውሻ ያሉ እንስሳት ናቸው። በጎጆዋቸው ውስጥ ያሉትን አእዋፋት እና ሌሎች ትንንሽ እንስሳትን ይበላሉ። ቀበሮዎች በእናንተ ዙሪያ የማይታወቁ ከሆነ እንደ ውሻ ያለ በማለት አጠቃላይ ቃልን ተጠቀሙ። (ተመልከቱ) ጉድጋዶች ቀበሮዎች ለመኖሪያቸው የሚሆን ጉድጓድን ይቆፍራሉ። ቀበሮወችን ለማመልከት የተጠቀማችኋቸው እንስሳት የሚኖሩበትን ሥፍራ ግለጹ። የሰው ልጅ ኢየሱስ ስለ ራሱ እየተናገረ ነው። (ተመልከት) ራሱን የሚያሳርፍበት ሥፍራ ይህ የመተኛ ሥፍራን ያመለክታል። ኤቲ: "የሚተኛበት የራሱ ሥፍራ የለውም።" (ተመልከት)

Matthew 8:21

ማቴዎስ **8:21-22**
በመጀመሪያ አባቴን እንድቀብረው ፍቀድልኝ የሰውዬው አባት መሞቱን እና ወዲያው መቅበር እንዳለበት በእርግጠኝነት ማወቅ አይቻልም ወይም አባቱ እስኪሞት እና እስኪቀበር ድረስ ለረጅም ጊዜ መቀየት ይኖርበት አይኖርበት የሚታወቅ ነገር የለም። ዋናውን ነጥብ ይህ ሰው ኢየሱስን ከመከተሉ በፊት ሌላ አዲስ ነገር ማድረግ ይፈለጋል ማለት ነው። ሙታን ሙታናቸውን ይቀብሩ ዘንድ ተዋቸው በዚህ ሥፍራ ላይ ኢየሱስ በቀጥታ የሞቲ ሰዎች ሌሎች የሞቱትን ይቅበሩ ማለቱ አይደለም። "ሙታን" የሚለው ቃል አማራጭ ትርጉሞች 1) በቅርብ ጊዜ ስለሚሞቱ ሰዎች የሚነገር ምሳሌያዊ አነጋገር ወይም 2) ኢየሱስን የማይከተሉ እና መንፈሳዊ ሞት የሞቱ ሰዎችን ለማመልከት የሚውል ሚሳሌያዊ አነጋገር። ዋናው ነጥብ ማንኛውም ኢየሱስን መከተል ለሚወድ ሰው ምንም ነገር ሊያዘገየው አይገባም። (ተመልከት)

Matthew 8:23

ማቴዎስ **8:23-25**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር በዚህ ሥፍራ ላይ የታሪኩ ፍሰት ኢየሱስ እና ደቀ መዛሙር የገሊላን ባሕር ሽሻገሩ የተነሳውን ማዕበል ኢየሱስ እንዴት ጸጥ እንዳደረገው ወደሚያሳይ ታሪክ ይለወጣል። ወደ ታንኳይቱ ገቡ “ወደ ተንኳ ገቡ” ደቀ መዛሙርቱ ተከተሉት ለ”ደቀ መዛሙር” እና “ተከተል” ለሚለው ቃል በ(MAT 8:21-22). ላይ የተጠቀምከውን ተመሳሳይ ቃላትን ተጠቀም። እነሆ ይህ በትልቁ ታሪክ ውስጥ የአንድ አዲስ ነገር ጅማሬ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ነው። በቋንቋችሁ ውስጥ ይህንን ማሳየት የሚቻልበት መንገድ ይራል። ኤቲ፡ “በድንገት”(UDB) ወይም “ያለምንም ማስጠንቀቂያ” ባሕሩም በታላቅ ማዕበል ተናወጠ ኤቲ፡ “ታላቅ ማዕበል ባሕሩን አናወጠው” በዚህም ምክንያት ታንኳይቱን ውሃ ሞላት ይህ እንዲህ ልገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “ስለዚህም ምክንያት ታንኳይቱን ውሃ ሞላት”። (ተመልከት) ተነስ አድነን አሉት የዚህ ሀረግ አማራጭ ትርጓሜዎች 1) በመጀመሪያ ኢየሱስን ከተኛት ቀስቅሰው “አድነን” አሉት ወይም 2)ኢየሱስን እየቀሰቀሱት “አድነን” አሉት። እኛ . . . እኛ ይህ ቃል ሁሉን የሚያጠቃልል ወይም የማያጠቃልል አድርገን የሚንተረጉመው ከሆነ ሁሉን የሚያጠቃልል ቃልን ብንጠቀም መልካም ይሆናል። ደቀ መዛሙርቱ ምናልባት ኢየሱስ እነርሱን እና ራሱን ከትንኳይቱ መስጠም እንዲታደግ ያቀረቡት ጥያቄ ሊሆን ይችላል። (ተመልከት) መሞታችን ነው “ልንሞት ነው”

Matthew 8:26

ማቴዎስ **8: 26-27**
ለእነርሱ “ለደቀ መዛሙርቱ” ለምን ፈራችሁ . . . እምነት? ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ጥያቄ በመጠየቅ ይገስጻቸዋል። ኤቲ፡ “ልትፈሩ አይገባም . . እምነት” ወይም “የምትፈሩበት አንዳች ምክንያት የለም . . . እምነት።” (ተመልከት) እናንተ ትንሽ እምነት ያላችሁ ይህንን በ MAT 6:30 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ። ንፋስን እና ባሕር የሚታዘዙለት ይህ ምን ዓይነት ሰው ነው? “ንፋስና ባሕር ይታዘዙታል! ምን ዓይነስ ሰው ነው? ይህ የደቀ መዛሙርቱን አግራሞት የሚያሳይ ጥያቄ ነው። ኤቲ፡ “ይህ ከሌሎች ሰዎች ሁሉ የተለየ ነው! ንፋስ እና ማዕበል ሳይቀር ይታዘዙታል!” (ተመልከት) ንፋስ እና ባሕር ሳይቀር ይታዘዙታል ሰዎች ወይም እንስሳት ቢታዘዙት ወይም ባይታዘዙት ብዙም አያስደንቅም ነገር ግን ንፋስ እና ውሃ እርሱን መታዘዛቸው በጣም አስደናቂ ነገር ነው። ይህ በሰውኛ የቀረበው ሀሳብ ተፈጥሮአዊ ነገሮች ልክ እንደ ሰው ሰምተው ምላሽ መስጠጥ ይችላሉ። (ተመልከት)

Matthew 8:28

ማቴዎስ **8:28-29**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር በዚህ ሥፍራ ላይ ጸሐፊው ከዚህ በፊት ወደ ጀመረው ኢየሱስ በሽተኞችን ወደሚፈውስበት አገልግሎት ታሪኩ ተመልሶ እናገኘዋለን። በዚህ ታሪክ ውስጥ መጀመሪያ ላይ ኢየሱስ ሁለት በዳብሎስ እስራት ተይዘው የነበሩትን ሰዎች ነጻ ሲያወጣ እንመለከታለን። በዚያኛው በኩል “ከገሊላ ባሕር ማዶ” የጌርጋሴኖን ሀገር ጌርጋሴኖን የጌርጋ ከተማ ስም ነው። (ተመልከት) እነርሱም ሰው በዚያ መንገድ ማለፍ እስኪሳነው ድረስ በጣም አስቸጋሪዎች ነበሩ እነዚህን ሁለት ሰዎችን የያዙት ዳብሎሶች በጣም አደገኞች ከመሆናቸው የተነሳ ማንም ሰው በዚያ በኩል ማለፍ አይችልም ነበር። እነሆ ይህ በትልቁ ታሪክ ውስጥ የአንድ አዲስ ነገር ጅማሬ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ነው። በቋንቋችሁ ውስጥ ይህንን ማሳየት የሚቻልበት መንገድ ይራል። የእግዚአብሔር ልጅ ከአንተ ጋር ምን አለን? ይህንን ጥያቄ የጠየቁት በቁጣ ነበር። (ተመልከት) የእግዚአብሔር ልጅ ይህ ኢየሱስ ከእግዚብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያሳይ የኢየሱስ ወሳኝ የሆነ መጠሪያ ስሙ ነው። (ተመልከት) ጊዜው ሳይደርስ ልትሣቅየን ወደዚህ መጣህን? ሁለተኛው ጥያቄም ሰላማዊ የሆነ ጥያቄ አልነበረም። ትረጉሙም “እግዚአብሔር እኛን ለመቅጣት የወሰነው ጊዜ ሳይደርስ መጥተህ እኛን በመቅጣት እግዚአብሔርን መታዘዝ መተው የለብህም።” (ተመልከት)

Matthew 8:30

ማቴዎስ **8:28-29**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር በዚህ ሥፍራ ላይ ጸሐፊው ከዚህ በፊት ወደ ጀመረው ኢየሱስ በሽተኞችን ወደሚፈውስበት አገልግሎት ታሪኩ ተመልሶ እናገኘዋለን። በዚህ ታሪክ ውስጥ መጀመሪያ ላይ ኢየሱስ ሁለት በዳብሎስ እስራት ተይዘው የነበሩትን ሰዎች ነጻ ሲያወጣ እንመለከታለን። በዚያኛው በኩል “ከገሊላ ባሕር ማዶ” የጌርጋሴኖን ሀገር ጌርጋሴኖን የጌርጋ ከተማ ስም ነው። (ተመልከት) እነርሱም ሰው በዚያ መንገድ ማለፍ እስኪሳነው ድረስ በጣም አስቸጋሪዎች ነበሩ እነዚህን ሁለት ሰዎችን የያዙት ዳብሎሶች በጣም አደገኞች ከመሆናቸው የተነሳ ማንም ሰው በዚያ በኩል ማለፍ አይችልም ነበር። እነሆ ይህ በትልቁ ታሪክ ውስጥ የአንድ አዲስ ነገር ጅማሬ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ነው። በቋንቋችሁ ውስጥ ይህንን ማሳየት የሚቻልበት መንገድ ይራል። የእግዚአብሔር ልጅ ከአንተ ጋር ምን አለን? ይህንን ጥያቄ የጠየቁት በቁጣ ነበር። (ተመልከት) የእግዚአብሔር ልጅ ይህ ኢየሱስ ከእግዚብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያሳይ የኢየሱስ ወሳኝ የሆነ መጠሪያ ስሙ ነው። (ተመልከት) ጊዜው ሳይደርስ ልትሣቅየን ወደዚህ መጣህን? ሁለተኛው ጥያቄም ሰላማዊ የሆነ ጥያቄ አልነበረም። ትረጉሙም “እግዚአብሔር እኛን ለመቅጣት የወሰነው ጊዜ ሳይደርስ መጥተህ እኛን በመቅጣት እግዚአብሔርን መታዘዝ መተው የለብህም።” (ተመልከት)

አሁን ይህ ቃል ጸሐፊው የታሪኩን ቀጣይ ክፍል ከመተረኩ በፊት አንባቢዎቹ ማወቅ ያለባቸውን አንድ መረጃ እንደሚሰጣቸው ያሳያል። ኢየሱስ ወደዚያ ሥፍራ ከመምጣቱ በፊት አሳማዎች በዚያ ሥፍራ ነበሩ። (ተመልከት) ካስወጣኸን ኤቲ፡ “ልታስወጣን ስለሆነ” እኛ ይህ ሁሉን አቀፍ ነው፤ ትርጉሙም ለአሳማዎች ብቻ ነው። (ተመልከት) እነርሱ በሰውዬው ውስጥ ያለው እርኩስ መንፈስ እርኩስ መንፈሱም ከሰውዬው ውስጥ ወጥቶ ወደ አሳማዎቹ ገባ ኤቲ፡ “እርኩስ መንፈሱም ከሰውዬው ውስጥ ወጥቶ ወደ አሳማዎቹ ገባ” እነሆ ይህ በትልቁ ታሪክ ውስጥ የአንድ አዲስ ነገር ጅማሬ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ነው። በቋንቋችሁ ውስጥ ይህንን ማሳየት የሚቻልበት መንገድ ይራል። ከተራራው አፋፍ ወደታች ሮጡ ኤቲ፡ “በፍጥነት ከተራራው አናት ወደታች ሮጡ” በውሃ ውስጥ ሞቱ ኤቲ፡ “በውሃ ውስጥ ወድቀው ሰመጡ”

Matthew 8:33

ማቴዎስ **8:33-34**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ይህ ኢየሱስ በእርኩስ መንፈስ የተያዙ ሁለት ሰዎችን ኢየሱስ የፈወሰበት ታሪክ ማጠቃለያ ነው። አሳማዎች የሚያሰማሩ “አሳማዎችን የሚጠብቁ” በእርኩስ መንፈስ የተያዙት ሰዎች ምን እንደሆኑ ኤቲ፡ “በእርኩስ መንፈስ የተያዙትን እነነዚህ ሰዎች ለማገዝ ኢየሱስ ያደረገው ነገር” እነሆ ይህ በትልቁ ታሪክ ውስጥ የአንድ አዲስ ነገር ጅማሬ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ነው። በቋንቋችሁ ውስጥ ይህንን ማሳየት የሚቻልበት መንገድ ይራል። በሁሉም ከተሞች ይህ ማለት ብዙ ወይም አብዛኞቹ ሰዎች ማለት እንጂ ሁሉም ሰዎች ማለት የግድ አይደለም። (ተመልከት) አከባቢ ኤቲ፡ “ከተማዋ እና በአካቢው ያሉት”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 9

1 ኢየሱስ ወደ ጀልባ ገባ፤ ባሕሩንም አቋርጦ ወደ ገዛ ከተማው መጣ። 2 እነሆ፣ በምንጣፍ የተኛ አንድ ሽባ ሰው ወደ እርሱ አመጡ። ኢየሱስም እምነታቸውን በማየት ሽባውን፣ “አንተ ልጅ፣ አይዞህ፤ ኀጢአትህ ይቅር ተብሎልሃል” አለው። 3 አንዳንድ ጸሐፍት ግን እርስ በርሳቸው፣ "ይህ ሰው እኮ እየተሳደበ ነው" ተባባሉ ። 4 ኢየሱስም ዐሳባቸውን ዐውቆ፣ “ስለ ምን በልባችሁ ክፉ ታስባላችሁ?” 5 ለመሆኑ የሚቀለው፣'ኃጢአትህ ይቅር ተብሎልሃል' ነው፣ ወይስ 'ተነሣና ሂድ ማለት ነው?' 6 ነገር ግን የሰው ልጅ በምድር ላይ ኃጢአትን ይቅር የማለት ሥልጣን እንዳለው ዕወቁ" አለ። ሽባውንም፣ "ተነሣና፣ምንጣፍህን ይዘህ ወደ ቤት ሂድ" አለው። 7 ከዚያም ሰውየው ተነሥቶ ወደ ቤቱ ሄደ። 8 ሕዝቡም ይህን ባዩ ጊዜ ተገርመው፣ ለሰው እንዲህ ያለ ሥልጣን የሰጠውን እግዚአብሔርን አመሰገኑ። 9 ኢየሱስም ከዚያ አለፍ እንዳለ፣ ማቴዎስ የሚባለውን ሰው በቀረጥ መሰብሰቢያ ቦታ ላይ ተቀምጦ አየውና "ተከተለኝ" አለው።እርሱም ተነሥቶ ተከተለው። 10 ኢየሱስም በቤቱ ውስጥ ለመመገብ በተቀመጠ ጊዜ፣ ቀረጥ የሚሰበስቡ ብዙ ሰዎችና ኃጢአተኞች መጥተው፣ ከኢየሱስና ከደቀ መዛሙርት ጋር አብረው ተመገቡ። 11 ፈሪሳውያንም ይህን ሲያዩ፣ደቀ መዛሙርቱን "ለምንድን ነው መምህራችሁ፣ ከግብር ሰብሳቢዎችና ከኃጢአተኞች ጋር የሚበላው?" አሏቸው። 12 ኢየሱስም ይህንን ሲሰማ ፣"ሕመምተኞች እንጂ ጤነኞች ሐኪም አያስፈልጋቸውም። 13 'ሂዱና' ምሕረት እንጂ መሥዋዕትን አልፈልግም' የሚለውን ተማሩ፣ እኔ የመጣሁት ጻድቃንን ሳይሆን ኀጥአንን ወደ ንስሓ ለመጥራት" ነው አለ። 14 ከዚያም የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት መጥተው፣" እኛና ፈሪሳውያን ብዙ ጊዜ እንጾማለን ፣የአንተ ደቀ መዛሙርት ግን የማይጾሙት ለምንድን ነው?" አሉት። 15 ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፣ “ሰርገኞች ሙሽራው ከእነርሱ ጋር እያለ እንዴት ሊያዝኑ ይችላሉ? ሆኖም ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ጊዜ ይመጣል፣በእነዚያ ቀናት ይጾማሉ። 16 ማንም ሰው በአሮጌ ልብስ ላይ ዐዲስ ቍራጭ ጨርቅ አይለጥፍም፤ ምክንያቱም አሮጌውን ልብስ ይቦጭቀዋል፣ ልብሱም የባሰ ይጐዳል። 17 ሰዎች ዐዲስ የወይን ጠጅ በአሮጌ አቁማዳ ውስጥ አያስቀምጡም፤ እንደዚያ ካደረጉ አቁማዳው ይፈነዳል፣ የወይን ጠጁ ይፈሳል፣ አቁማዳውም ይቀደዳል። ይልቁንም ዐዲሱን የወይን ጠጅ በአዲስ አቁማዳ ውስጥ ያስቀምጡታል፣ ሁለቱም ይጠበቃሉ።" 18 ኢየሱስ ይህን እየተናገራቸው እያለ፣ አንድ ሹም እየሰገደ ወደ እርሱ መጣ። “ልጄ አሁን ገና ሞተች፣ ነገር ግን ና ና እጅህን ጫንባት በሕይወትም ትኖራለች አለው”። 19 ኢየሱስም ተነሥቶ ተከትሎት ሄደ፤ ደቀ ዛሙርቱም ደግሞ አብረውት ሄዱ። 20 አንዲት ለዐሥራ ሁለት ዓመት ከባድ የደም መፍሰስ የነበረባት ሴት፣ ከኢየሱስ ኋላ መጥታ የልብሱን ጠርዝ ነካች፤ 21 "የልብሱን ጫፍ ብቻ ብነካ ደኅና እሆናለሁ" ብላ ነበርና። 22 ኢየሱስም ዞር ብሎ አያትና፣ “ልጄ ሆይ፣ አይዞሽ እምነትሽ አድኖሻል” አላት። ሴቲቱም ወዲያውኑ ደኅና ሆነች። 23 ኢየሱስም ወደ ሹሙ ቤት በገባ ጊዜ፣ዋሽንት የሚነፉትንና የሚንጫጩትን አይቶ፣ 24 "ወደዚያ ዞር በሉ፣ ልጅቷ ተኝታለች እንጂ አልሞተችም"አላቸው። እነርሱ ግን በማፌዝ ሳቁበት። 25 ሕዝቡን ወደ ውጭ ባስወጡ ጊዜ፥ ኢየሱስ ወደ ክፍሉ ገብቶ እጅዋን ያዘ፤ልጅቱም ተነሣች። 26 ወሬውም በዚያ አካባቢ ሁሉ ተዳረሰ። 27 ኢየሱስም በዚያ ሲያልፍ፣ ሁለት ዐይነ ስውሮች ተከተሉት፣ ያለ ማቋረጥም፣ "የዳዊት ልጅ ማረን!" እያሉ ይጮኹ ነበር። 28 ኢየሱስም ወደ ቤቱ በገባ ጊዜ፣ ዐይነ ስውሮቹ ወደ እርሱ መጡ። ኢየሱስም፣ "ይህን ለማድረግ እንደምችል ታምናላችሁ?" አላቸው። እነርሱም "አዎን፣ ጌታ ሆይ" አሉት። 29 ከዚያም ኢየሱስ ዐይኖቻቸውን ዳሰሶ፣ "እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ" አላቸው። 30 ዐይኖቻቸውም ተከፈቱ። ከዚያም ኢየሱስ፣"ይህንን ማንም እንዳያውቅ" ብሎ በጥብቅ አዘዛቸው። 31 ሁለቱ ሰዎች ግን ሄደው ወሬውን በየቦታው አዳረሱት። 32 ሁለቱ ሰዎች እየሄዱ እያሉ እነሆ፣ በጋኔን የተያዘ ዲዳ ወደ ኢየሱስ አመጡ። 33 ጋኔኑም ከወጣ በኋላ ዲዳው ተናገረ። ሕዝቡም ተገርመው፣ "እንዲህ ያለ ከዚህ በፊት በእስራኤል አልታየም" አሉ። 34 ፈሪሳውያን ግን "አጋንንትን የሚያወጣው በአጋንንት አለቃ ነው" ይሉ ነበር። 35 ኢየሱስ ወደ ከተሞችና መንደሮች ሁሉ ሄደ፣ በየምኩኩራቦቻቸውም ማስተማሩን፣ የመንግሥትን ወንጌል መስበኩንና፣ ማንኛውንም ዐይነት በሽታና ደዌ መፈወሱን ቀጠለ። 36 ሕዝቡንም ሲያይ፣ ጠባቂ እንደሌላቸው በጎች ተጨንቀውና ግራ ተጋብተው ነበርና ራራላቸው። 37 ለደቀ መዛሙርቱም፣ "መከሩ ብዙ ነው ሠራተኞች ግን ጥቂት ናቸው። 38 ስለዚህ፣ ሠራተኞችን ወደ መከሩ እንዲልክ፣ ወደ መከሩ ጌታ አጥብቃችሁ ጸልዩ" አላቸው።

Matthew 9:1

ማቴዎስ **9**:**1-2**
ማቴዎስ 9:1-2 አያያዥ ዓረፍተ ነገር ጸሐፊው በ MAT 8:1 የጀመረው ኢየሱስ ሰዎችን ከበሽታ የፈወሰበትን ታሪክ እንደገና ወደ መተረክ ተመልሷል። በዚህ ታሪክ ውስጥ ኢየሱስ ሽባውን ሰው እንዴት እንደፈወሰው ይተርካል። ኢየሱስ ወደ ታንኳይቱ ገባ ደቀ መዛሙርቱም ከእርሱ ጋር ሄደው ሊሆን ይችላል። ታንኳ ይህ ምናልባት በ MAT 8:23 ላይ የተገለጸው ታንኳ ሊሆን ይችላል። ግራ መጋባትን ለማስወገድ ከፈለግህ ብቻ ይህንን መግለጽ ትችላለህ። ወደ ገዛ ከተማው መጣ ኤቲ፡ “ወደመከኖርበት ከተማ” (UDB) እነሆ ይህ በትልቁ ታሪክ ውስጥ የአንድ አዲስ ነገር ጅማሬ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ነው። በቋንቋችሁ ውስጥ ይህንን ማሳየት የሚቻልበት መንገድ ይኖራል። እነርሱ . . . እነርሱ ይህ ሽባውን ሰው ወደኢየሱስ ያመጡትን ሰዎች ያመለክታል። ሽባውንም ሰው ሊያመለክት ይችላል። ልጅ ይህ ሰው በእርግጥ የኢየሱስ ልጅ አይደለም። ኢየሱስ በዚህ ሥፍራ ላይ በትህትና እያናገረው ነው። ይህ ሰዎችን ግራ የሚያጋባ ከሆነ እንዲህ በማለት ሊትተረጉመው ተትችላለህ “ወዳጄ ሆይ” ወይም “አንተ ጎበዝ” ወይም ከተውኑ ልትተው ትችላለህ። ኃጢአትህ ተሰረያልሃለች ኤቲ፡ “እግዚአብሔር ኃጢአትህን ሠሪዮልሃል” ወይም “ኃጢአትን ሠሪዬልሃለሁ” (ተመልከት)

Matthew 9:3

ማቴዎስ **9**:**3-6**
እነሆ ይህ በትልቁ ታሪክ ውስጥ የአንድ አዲስ ነገር ጅማሬ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ነው። በቋንቋችሁ ውስጥ ይህንን ማሳየት የሚቻልበት መንገድ ይኖራል። ከእነርሱ መካከል ይህ “ለእነርሱ ለራሳቸው” “በመካከላቸው” ወይም “እርስ በእርሳቸው”፣ “በራሳቸው አፍ” እግዚአብሔርን ይሳደባል እግዚአብሔር ብቻ ሊያደርጋቸው የሚችላቸው ነገሮች ኢየሱስ ማድረግ እችላለው እያለ ነው። የልባቸውን ሀሳብ አውቆ ኢየሱስ ሀሳባቸውን ያወቀው በልዕለ ተፈጥሮ ኃይል አማካኝነት ነው ወይም እርሱ በእርሳቸው ስነጋገሩ ተመልክቶ ነው። በልባችሁ ስለምን ክፋትን ታስባላችሁ? ኢየሱስ ይህንን የተናገረው ጸሐፊትን ለመገሰጽ ነው። (ተመልከት) አንናተ . . . እናንተ እነዚህ ቃላት ብዙ ቁጥር አመልካች ናቸው። (ተመልከት) ክፋት ይህ ግብረገባዊ ክፋት እንጂ ዝም ብሎ ስህተት አይደለም። ዬቱ ይቀላል . . . ተራመድ ኢየሱስ ጸሐፊዎችን ይህንን ጥያቄ በመጠየቅ ማስታወስ የፈለገው ነገር ሰውዬው ሽባ የሆነው በኃጢአቱ ምክንያት ነው። ስለዚህም ኃጢአቱ ይቅር ከተባለለት ሽባው ሰው መራመድ ይችላል ማለት ነው። ስለዚህም ኢየሱስ ኃጢአትን ይቅር ማለት እንደሚችል ጸሐፊት ያውቁ ዘንድ ይህን ጥያቄ ጠየቃቸው። ለመናገር ቀላሉ ዬቱ ነው፤ “ኃጢአትህ ተሠረየችልህ” ወይስ “ተነሳና ተራመድ?” ብሎ መናገር ነው ኤቲ፡ ለመናገር ቀላሉ ዬቱ ነው፤ “ኃጢአትህ ተሠረየችልህ” ወይስ “ተነሳና ተራመድ” ብሎ መናገር ነው? Your sins are forgiven This can mean 1) "I forgive your sins" ኃጢአትህ ተሠረየችልህ ይህ ማለት 1) “ኃጢአትን ይቅር ብዬሃለሁ” (UDB) ወይም

2) “እግዚአብሔር ኃጢአትህን ይቅር ብሎልሃል”። በዚህ ክፍል ውስጥ “አንተ” የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው በነጠላ ቁጥር ነው። (ተመልከት) ታውቁ ዘንድ ነው ኤቲ፡ “አረጋግጥላችኋለሁ”። በዚህ ሥፍራ ለእናንተ የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው የብዙ ቁጥርን በሚያመለክት መልኩ ነው። (ተመልከት) your...your These are singular. አንተ . . . አንተ ይህ ነጠላ ቁጥር ነው። (ተመልከት) ወደ ቤትህ ሂድ ኢየሱስ ሰውዬውን ወደ ሌላ ቦታ እንዳይሄድ አልከለከለውም። ለሰውዬው ወደ ቤቱ የሜድ ዕድል ሰጠው።

Matthew 9:7

ማቴዎስ 9:7-9
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ይህ ኢየሱስ ሽባውን ሰው የፈወሰበት ታሪክ ማጠቃለያ ነው። ከዚያም ኢየሱስ ከቀረጥ ሰብሳቢዎች መካከል አንድ ሰውን የእርሱ ደቀ መዝሙር ይሆን ዘንድ ጠራው። ምሳጋና በ MAT 5:16 ላይ የተጠቀምከውን ተመሳሳይ ቃል በዚህ ሥፍራም ተጠቀም። እንዲህ ያለ ስልጣን ኃጢአትን የማስተሰረይ ስልጣን ማቴዎስ . . . እርሱ . . እርሱ የቤተ ክርስቲያን አባቶች በዚህ ሥፍራ ላይ የተጠቀሰው የማቴዎስ ወንጌል ጸሐፊ ማቴዎስ እራሱ ነው ይላሉ። ይሁን እንጂ በክፍሉ ውስጥ ያለው “እርሱ” የሚለው ቃል “እኔ” ወደሚለው እንዲንለውጥ የሚያደርገን ምንም ምክንያት የለም። እርሱም እንዲህ አለው “ኢየሱስ ለማቴዎስ እንዲህ አለው” ኢየሱስም በዚያ ስያልፍ ሳለ ይህ ሀረግ እነሆ በሚል ቃል በ MAT 9:8 የተጀመረው ታሪክ መግቢያን የሚያሳይ ነው። በቋንቋችሁ እንዲህ ማሳየት ከቻላችሁ ተጠቀሙበት። በዚያ ስያልፍ “መሄድ” የሚለውን ቃል ተጠቀሙ። ኢየሱስ ወደ ተራራ መውጣቱን ወይም ወደ ሸለቆ መውረዱን ወይም ወደ ቅፍረናሆም መሄዱን ወይም ከዚያ ሪቆ ለመሄድ መነሳቱን የሚገለጽ ምንም ነገር የለም። ተነሥቶም ተከተለው “ማቴዎስ ተነሣና ኢየሱስን ተከተለው”። የተከተለው ኢየሱስን እስከሚቀጥለው ሥፍራ ድረስ እንደተከተሉት ሰዎች ሳይሆን እንደ ደቀ መዝሙር ነው።

Matthew 9:10

ማቴዎስ 9:10-11
አጠቃላይ መረጃ ይህ ታሪክ የተፈጸመው በቀራጩ ማቴዎስ ቤት ውስጥ ነው። ቤት ይህ ምናልባትም የማቴዎስ ቤት ይሆናል፤ ነገር ግን የኢየሱስም ቤት ሊሆን ይችላል (“ከኢየሱስ እና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አብረው በሉ”። ግራ መጋባትን የሚፈጥር ከሆነ ብቻ ምንነቱን በመግለጽ አስቀምጡት። ፈሪሳዊያን ይህንን በተመለከቱ ጊዜ “ፈሪሳዊያን ኢየሱስ ከቀረጥ ሰብሳቢዎች እና ከኃጢአተኛ ሰዎች ጋር እየበላ እንደሆነ በተመለከቱ ጊዜ”

Matthew 9:12

ማቴዎስ 9:12-13
አጠቃላይ መረጃ፡ ይህ ታሪክ የተፈጸመው በቀራጩ ማቴዎስ ቤት ውስጥ ነው። ኢየሱስም ይህንን በሰማ ጊዜ “ይህንን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ፈሪሳዊያን ኢየሱስ ስለምን ከቀራጮች እና ከኃጢአተኞች ጋር ይበላል ብለው የጠየቁትን ጥያቄን ያመለክታል። ጤነኞች ኤቲ፡ “ጤናማ የሆኑ ሰዎች” (ተመልከት) ሐኪም “ዶክተር”(UDB) ታማሚዎች “ዶክተር የሚያስፈልጋቸው ታማሚዎች ናቸው” ይህ ምን ማለት እንደሆነ ሄዳችሁ አጥኑ ኤቲ፡ “የዚህን ትርጉም ምንነት ሄዳችሁ አጥኑ፡” ሂዱ “እናንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥርን ያመለክታል።

Matthew 9:14

ማቴዎስ 9:14-15
አያያዥ ዓረፈተ ነገር የመጥቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ስለምን እንደማይጾሙ ጥያቄ አቀረቡ። አይጾሙም ጾም ማለት ምንም ነገር አለመብላት ማለት ነው። ምንም ዓይነት ጾም ባሌለባቸው አንዳንድ ባሕሎች ውስጥ “በቀጣይነት መብላት መቆም” ተብሎ ልገለጽ ይችላል። (ተመልከት) የሠረግ ታዳሚዎች ኃዘንተኞች መሆን ይችላሉ . . . እነርሱ? የሠረግ ታዳሚዎች ሠርገኞቹ ከእነርሱ ጋር እያሉ እንድጾሙ የሚጠብቅባቸው ማንም የለም። (ተመልከት) የሠርግ ታዳሚዎች ይህ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት የሚያመለክት ምሳሌያዊ ንግግር ነው። (ተመልከት) ሠርገኛው ገና ከእርሱ ጋር ነውና . . . ሠርገኛው ከእነርሱ ከተለየ በኋላ “ሠርገኛው” ኢየሱስ ነው፣ እርሱ ደግሙ አሁን ከእነርሱ ጋር ነው። (ተመልከት) ሠርገኛው ከእነርሱ የሚወሰደብት ጊዜ ይመጣል ኤቲ፡ “የሆነ ሰው ሠርገኛውን ይወስደዋል።” ይህ እንደሚገደል በምሰሌያዊ አነጋገር ስገለጽ ነው። (ተመልከት) ያዝናሉ “ያለቅሳሉ” ወይም “ያዝናሉ”(UDB)

Matthew 9:16

ማቴዎስ 9:16-16
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ላነሱት ጥያቄ መልስ መስጠቱን ቀጥሏል። ማንም በአረጀ ልብስ ላይ አዲስ እራፊ የሚሰፋ የለም የዚህ ምሳሌያዊ ንግግር ትርጉሙ አሮጌውን ባሕል የሚያው ሰዎች አዲሱን ለመቀበል አይጓጉም። (ተመልከት) ልብስ “ልብስ” እራፊ የተቀደደ ልብስን ለመስፋት የሚሆን “አዲስ ቁራጭ ጨርቅ”

Matthew 9:17

ማቴዎስ 9:17-17
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ለተየቁት ጥያቄ መልስ መስጠቱት ቀጥሏል። በአረጀ አቁማዳ አዲስ የወይን ጠጅ የሚያኖር ማንም የለም ኢየሱስ ይህንን ምሳሌያዊ አነጋገር የተጠቀመው ለዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ጥያቄ መልስ ለመስጠት ነው። ጥያቄያቸውም “እኛ እና ፈሪሳዊን እንጾማለን ነገር ነገር የአንተ ደቀ መዛሙርት ግን ስለምን አይጾሙም?” (ተመልከት) የሚያኖር ማንም የለም ኤቲ፡ “የሚያኖር ማንም የለም” (UDB) ወይም “ሰዎች በጭራሽ አያስቀምጡም” አዲስ ወይን ኤቲ፡ “የወይን ጁስ”። ይህ ያልፈለ ወይንን ያመለክታል። ወይን በእናንተ አከባቢ የማይታወቅ ከሆነ ለፍራፍሬ አጠቃላይ ስም የሚውል ቃል ተጠቀሙ። (ተመልከት) የአረጀ አቁማዳ ይህ ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለን አቁማዳ ያመለክታል። (ተመልከት) አቁማዳ ከእንስሳት ቆዳ የሚሠራ ከረጥት ነው። “የወይን መያዣ” ወይም “የቆዳ ከረጥት” ተብሎም ይጠራል። (UDB). (ተመልከት) አቁማዳው ይፈነዳል አዲሱ ወይን ስፈለ አቁማዳው ይፈነዳል ምክንያቱም ከዚህ በላይ መለጠጥ ስለማይችል ነው። (ተመልከት) ይጠፋል “ይበላሻል”(UDB) አዲስ አቁማዳ “አዲስ አቁማዳ” ወይም “አዲስ የወይን ከረጥት”። ይህ ከዚህ በፊት ጥቅም ላይ ውሎ የማያቅን አቆማዳ ያመለክታል። (ተመልከቱ)

Matthew 9:18

ማቴዎስ 9: 18-19
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ይህ ታሪክ የሚጀምረው ኢየሱስ የአይሁድ አለቃነ ሴት ልጅ ከሞት ካስነሳ በበኋላ ነው። እነዚህ ነገሮች ይህ ኢየሱስ ለዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ስለ ጾም የሰጠውን መልስ የሚያመለክት ነው። እነሆ ይህ በትልቁ ታሪክ ውስጥ የአንድ አዲስ ነገር ጅማሬ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ነው። በቋንቋችሁ ውስጥ ይህንን ማሳየት የሚቻልበት መንገድ ይኖራል። ወድቀው ሰገዱለት ይህ በአይሁድ ባሕል መሠረት ለሰዎች አክበሮትን ማሳያ መንገድ ነው። ና እና እጅህን በእርሷ ላይ ጫን፤ ከዚያም በሕይወት ትኖራለች ይህ የአይሁድ አለቃ ኢየሱስ ሴት ልጁን ከሞት ለማስነሳት የሚያስችለው ኃይል እንዳለው ያምናል ማለት ነው።

Matthew 9:20

ማቴዎስ 9: 20-22
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ይህ ኢየሱስ ወደ አይሁድ አለቃው ቤት በመሄድ ላይ ሳለ እንዴት አንዲትን ሴት እንደፈወሳት የሚገልጽ ታሪክ ነው። እነሆ ይህ በትልቁ ታሪክ ውስጥ የአንድ አዲስ ነገር ጅማሬ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ነው። በቋንቋችሁ ውስጥ ይህንን ማሳየት የሚቻልበት መንገድ ይኖራል። ከፍተኛ የደም መፍሰስ ኤቲ፡ “በከፍተኛ ሁኔታ ደም ይፈሳታል።” የወር አበባዋ መምጫው ጊዜ እንኳ ሳይሆን ከማሕጸኗ ውስጥ ድም ይፈሳት ነበር። ይህንን ሁኔታ ለመግለጽ የሚያስችል ቃል በአንዳንድ ባሕሎች ውስጥ አለ። (ተመልከት) ልብሶቹን መንካት ብችል እንኳ ደህና እሆናለሁ ኢየሱስ ብዙ ሰዎችን ፈውሷል፤ ከዚህች ሴት ይበልጥ ከፈተኛ በሽታ ውስጥ የሆኑትን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሰዎች እንኳ ፈውሷል። (ተመልከት) ጨርቅ “መቀነት” ነገር ግን “ይልቁንም” ሴትቱ ይሆናል ብላ የጠበቀችው ነገር አልሆነም። ሴት ልጅ ይህች ልጅ የኢየሱስ ልጅ አይደለችም። ኢየሱስ በትህትና አናገራት። ይህ በሰዎች አእምሮ ውስጥ ግራ መገጋባትን የሚፈጥር ከሆነ “አንድ ወጣት” ወይም ሳይተረጎም ሊታለፍ ይችላል።

Matthew 9:23

ማቴዎስ **9**:**23**-**24**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ይህ ኢየሱስ የአይሁድ አለቃውን ሴት ልጅ ወደ ሕይወት ወደመለሰበት ታሪክ ይመራናል። የአለቃው ቤት ይህ የአይሁድ አለቃው ቤት ነው። እምቢልታ ይህ ረጅም የሆነ በአንድ በኩል እስትፋንስ እየተሰጠው ጥቅም ላይ የሚውል የሙዚቃ መሣሪያ ነው። የእምቢልታ ጠቻዋቾች “እምቢልታ የሚጫወቱ ሰዎች” ሂዱ በዚህ ሥፍራ ላይ ኢየሱስ ለብዙ ሰዎች እየተናገረ ነው። ስለዚህ በቋንቋችሁ የብዙ ቁጥር አመልካች ቃልን ተጠቀም። ልጅቱ አልሞተችም አንቀላፍታለች እንጂ በዚህ ሥፍራ ላይ ኢየሱስ የያዘው የቃላት ጫወታ ነው። ኢየሱስ በኖረበት ዘመን የሞተ ሰው ተኝቷል ብሎ መጥራት የተለመደ ነው። ይሁን ዘንጂ በዚህ ሥፍራ ሞታ የነበረችው ልጅ ልክ ተኝቶ እንደነበር ሰው ከሞት ተነሳች። (ተመልከት)

Matthew 9:25

ማቴዎስ **9**: **25**-**26**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ይህ ኢየሱስ የአይሁድ አለቃውን ሴት ልጅ ወደ ሕይወት የመለሰት ታሪክ ማብቂያ ነው። አጠቃላይ መረጃ ቁጥር 26 ኢየሱስ ልጅቷን ከሞት የማስነሳቱ ውጤት ምን እንደሆነ ማጠቃለያ ሀሳብ ነው። ሕዝቡ ውጪ እንዲወጣ ካደረገ በኋላ “ኢየሱስ ሕዝቡን ወደ ውጪ ካስወጣ በኋላ” ወይም “የልጅቱ ቤተሰቦች ሕዝቡን ወደ ወጪ ካስወጣ በኋላ” ተነሽ “ከአልጋሽ ተነሽ”። በ MAT 8:15 ያለው ትርጉም ተመሳሳይ ነው። የዚህ ነገር ዜና በሀገሩ ሁሉ ተሰማ ይህ ሰውኛ አገላለጽ የዚህ ነገር ዜና መሰራጨቱን ያሳያል። ይህም የሆነበት ምክንተያት አንዱ ለሌላኛው ሰው በመንገሩ ነው። ኤቲ፡ “በአከባቢው የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ሰለተፈጠረው ነገር ሰሙ” (UDB) ወይም “የልጅቱን በሕይወት መኖር የተመለከቱ ሰዎች በዚያ አለባቢ ላሉ ሰዎች ሁሉ ማናገር ጀመሩ።” (ተመልከት)

Matthew 9:27

ማቴዎስ **9**:**27**-**28**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ይህ ስለ ሁለት ዐይነ ስውራን ታሪክ የሚጀመርበት ነው። ኢየሱስ በዚያ ስያልፍ ሳለ ኢየሱስ አከባቢውን ለቆ ሲሄድ ስያልፍ ኢየሱስ ወደ ተራራ እየወጣ ወይም እየወረደ እንደሆነ ምንም ፍንጭ የለም። ስለዚህ “ሄደ” የሚል ጠቅለል ያለ ቃል መጠቀሙ ጥሩ ነው። የዳዊት ልጅ ኢየሱስ በቀጥታ የዳዊት ልጅ አይደለም። ስለዚህም እንዲህ ልተረጎም ይችላል “ከዳዊት ዘር የሆነው” (UDB)። ይሁን እንጂ “የዳዊት ልጅ” የሚለው የመስሑ የማዕረግ ስም ነው። see MAT 21:9 ተመልከት) እና እነዚህ ሰዎችም ምናበት ኢየሱስን ይህንኑ የማዕረግ ስሙን ታሳቢ በማድረግ ጠርተውታል። ወደ ቤትም በገባ ጊዜ ይህ ኢየሱስ ወደ ገዛ ቤቱ መግባቱን (UDB) ወይም በ MAT 9:10 ላይ የተጠቀሰውን ቤት ልያመለክት ይችላል። አዎን፥ ጌታ ሆይ ኤቲ፡ “አዎን ጌታዬ አንተ መፈወስ እንደሚትችል እናምናለን።”

Matthew 9:29

ማቴዎስ **9**: **29**-**31**
ዓይኖቻቸውን ዳሰሰ። ኢየሱስ የሁለቱንም ሰዎች ዐይኖች እንዴት በአንድ ጊዜ መዳሰስ እንደቻለ ግልጽ አይደለም ወይም በቀኝ እጁ የአንዱን ዐይን በሌላኛው እጁ ደግሞ የሌላኛውን ዐይን ዳስሶ ይሆናል። የግራ እጅ ብዙ ጊዜ ንጹሕ ላልሆነ ነገር እንደመዋሉ መጠን ኢየሱስ እነዚህን ሰዎች የፈወሳቸው ቀኝ እጁን ተጠቅሞ ነው። ከዚህ በተጨማሪ እየዳሰሳቸው ሳለ ቃል መናገር አለመናገሩ ወይም በመጀመሪያ መዳሰሱን ከዚያመ ቃል መናገሩን የሚታወቅ ነገር የለም። ዐይኖቻቸው ተከፈቱ ኤቲ፡ “እግዚአብሔር ዐይኖቻቸውን ፈወሰ” ወይም “ሁለቱ ዐይነ ስውራን መመልከት ቻሉ” (ተመልከት) But "Instead." The men did not do what Jesus told them to do. ነገረ ግን “ይሁን እንጂ” እነዚህ ሰሰዎች ኢየሱስ እንዲያደርጉ የነገራውን ነገር አላደረጉም። ዜናውን አሰራጩት ኤቲ፡ “ምን እንደተደረገላቸው ለብዙ ሰዎች ተናገሩ”

Matthew 9:32

ማቴዎስ **9**:**32**-**34**
አያያዥ ዐረፍተ ነገር ይህ ኢየሱስ በእርኩስ መንፈስ በመያዙ ምክያት መናገር የማይችለውን ሰው የፈወሰበት ታሪክ እና ለዚህ ፈውስ ሰዎች የሰጡት ምላሽ ታሪክ ነው። እነሆ ይህ በትልቁ ታሪክ ውስጥ የአንድ አዲስ ነገር ጅማሬ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ነው። በቋንቋችሁ ውስጥ ይህንን ማሳየት የሚቻልበት መንገድ ይኖራል። ዲዳ መናገር የማይችል ዲዳ ሰው ተናገረ ኤቲ፡ “ዲዳው ሰው ማናገር ጀመረ” ወይም “መናገር የማይችለው ሰውዬ መናገር ቻለ” ወይም “ዲዳ የነበረው ሰው መናገር ቻለ” ሕዝቡም ተገረሙ ኤቲ፡ “ሕዝቡም ተደነቀ” እንዲህ ያለ ነገር ታይቶም አይታወቅም “እንዲህ ዓይነት ሀገር ተደርጎ አይታወቅም” ወይም “ይህን ዓይነት ነገር ከዚህ በፊት ማንም ሰው አድርጎ አያውቅም” ማለት ሊሆን ይችላል። እርኩሳን መናስፍስት አስወጣ በዚህ ሥፍራ ላጥ “እርሱ” የሚለው የሚያመለክተው ኢየሱስን ነው።

Matthew 9:35

ማቴዎስ **9**:**35**-**36**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ቁጥር 35 በ MAT 8:1 የተጀመረው ኢየሱስ በገሊላ የነረው የፈውስ አገልግሎት ታሪክ ማብቂያ ነው። (የታሪኩ ማብቂያ) አጠቃላይ መረጃ፡ ከቁጥር 36 ጀምሮ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን በማስተማር እርሱ እንዳደረገው ይስብኩና ይፈውሱ ዘንድ የላካቸው ታሪክ አዲስ የታሪኩ ክፍል ጅማሬ ነው። በሁሉም ከተሞች ኤቲ፡ “በብዙ ከተሞች” (ተመልከት) ከተሞች . . . መንደሮች ኤቲ፡ “ትልልቅ መንደሮች . . . ትንንሽ መንደሮች” ወይም “ትልልቅ ከተሞች . . . ትንንሽ ከተሞች” ሁሉንም ዓይነት በሽታዎች እና ሕመሞች ኤቲ፡ “ሁሉንም በሽታዎች እና ሕመሞች”። “በሽታ” እና “ሕመም” ተቀራራቢ የሆኑ ነገሮች ይሁን እንዲ ከተቻለ በሁለት የተለያዩ ቃላት ቢተረጎሙ የተሸለ ነው። “በሽታ” አንድ ሰው እንዲታመም የሚያደርጉት ነገሮች ሲሆኑ። “በሽታ” ደግሞ በዚህ በሽታ ከመያዛችን የተነሳ የሚሰማን አካላዊ ድካም ወይም ሕመም ነው። እረኞች እንደሌላቸው በጎች ተቅበዝብዘዋል ኤቲ፡ “ሰዎቹ መሪ አልበራቸውም” (ተመልከት)

Matthew 9:37

ማቴዎስ **9**:**37**-**38**
አጠቃላይ መረጃ፡ ኢየሱስ የመከርን ምሳሌ በመጠቀም ከዚህ በፊት ለነበረው የሕዝቡ ፍላጎት ደቀ መዛሙርቱ በምን ዓይነት መንገድ ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው ነገራቸው። መከሩ ብዙ ነው ሠራተኞቹ ግን ጥቂቶች ናቸው ይህ ምሰሌያዊ ንግግር በእግዚአብሔር የሚያምኑ እና ወደ መንግስቱ የሚጨመሩ ሰዎች ቁጥር በእርሻ ማሳ ውስጥ በለ ሰብል በመመሰል ስ እግዚአብሔር ለሰዎች የሚናገሩ ሰዎችን በሠራተኞች በመመሰል ያነጻጽራል። የዚህ ምሳሌያዊ ንግግር ዋናው ነጥብ ስለ እግዚአብሔር የሚናገሩ በጣም ጥቂት ሰዎች ናቸው ነው። መከር ኤቲ፡ “የደረሰ ሰብል” ሠራተኞች “ሠራተኞች” ለመከሩ ጌታ ጸልዩ ኤቲ፡ “የመከሩ ባለቤት ወደሆነው ጌታ ጸልዩ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **10**

1 ሁለቱን ደቀ መዛሙርት በአንድ ላይ ጠርቶ፣ ርኩሳን መናፍስትን እንዲያወጡ፣ ሁሉንም ዐይነት በሽታና ደዌ እንዲፈውሱ ሥልጣንን ሰጣቸው። **2** የዐስራ ሁለቱም ሐዋርያት ስም ይህ ነው፤ የመጀመሪያው ጴጥሮስ የተባለው ስምዖንና ወንድሙ እንድርያስ፣ የዘብዴዎስ ልጅ ያዕቆብና ወንድሙ የሐንስ፣ **3** ፊልጶስና በርተሎሜዎስ፣ ቶማስና ቀረጥ ሰብሳቢው ማቴዎስ፣ የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብና ታዴዎስ፣ **4** ቀነናዊው ስምዖን፣አሳልፎ የሚሰጠው የአስቆሮቱ ይሁዳ። **5** ኢየሱስ እነዚህን ዐሥራ ሁለቱን "አሕዛብ ወደሚኖሩበት የትኛውም ቦታ አትሂዱ፤ ወደ የትኛውም የሳምራውያን ከተማ አትግቡ። **6** ከዚያ ይልቅ ወደ ጠፉት የእስራኤል ቤት በጐች ሂዱ። **7** መንግሥተ ሰማይ ቀርባለች፣ ብላችሁ ስበኩ" ብሎ አስተምሮ ላካቸው። **8** ሕሙማንን ፈውሱ፣ ሙታንን አስነሡ፣ ለምጻሞችን አንጹ፣ አጋንንትንም አስወጡ፣ በነጻ ተቀብላችኋል በነጻ ስጡ። **9** በቦርሳችሁ ወርቅ ብር ወይም ናስ አትያዙ፤ **10** ለሠራተኛ ቀለቡ የሚገባው ስለ ሆነ፣ ለመንገዳችሁ ሻንጣ ወይም ትርፍ ልብስ፣ ወይም ጫማ፣ ወይም በትር አትያዙ። **11** ወደ የትኛውም ከተማ ወይም መንደር ስትገቡ፣ በዚያ ተገቢ የሆነው ሰው ማን እንደሆን እወቁ፤ ለቃችሁ እስከምትሄዱ ድረስ በዚያው ቆዩ። **12** ወደ ቤት ስትገቡ፣ ሰላምታ ስጡ። **13** ቤቱ የሚገባው ከሆነ ሰላማችሁ ይደርሰዋል፤ የማይገባው ከሆነ ግን ሰላማችሁ ይመለስላችኋል። **14** እናንተን የማይቀበላችሁን፣ ወይም ቃላችሁን የማይሰማውን በተመለከተ ግን፣ ከዚያ ቤት ወይም ከተማ ስትወጡ የእግራችሁን አቧራ አራግፉ። **15** እውነት እላችኋለሁ፣ በፍርድ ቀን ከዚያች ከተማ ይልቅ ለሰዶምና ለገሞራ ይቀልላቸዋል። **16** ተመልከቱ፣ እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ። ስለዚህ፣ እንደ እባብ ብልኆች እንደ ርግብም የዋሆች ሁኑ። **17** ከሰዎች ተጠበቁ፣ ወደ ፍርድ ሸንጎ ያቅርቧችኋል፣ በምኵራባቸውም ይገርፏችኋል። **18** ለእነርሱና ለአሕዛብ ምስክር እንዲሆን፣ በእኔም ምክንያት ወደ ገዥዎችና ነገሥታት ፊት ትቀርባላችሁ። **19** ለፍርድም ሲያቀርቧችሁ፣ በዚያች ሰዓት የምትናገሩት ስለሚሰጣችሁ፣ ምን ወይም እንዴት እንደምትናገሩ አትጨነቁ። **20** በእናንተ ውስጥ የሚናገረው የአባታችሁ መንፈስ ነው እንጂ የምትናገሩት እናንተ አይደላችሁም። **21** ወንድም ወንድሙን፣ አባትም ልጁን፣ ለሞት አሳልፎ ይሰጣል፤ ልጆችም በወላጆቻቸው ላይ ተነሥተው ያስገድሏቸዋል። **22** ከስሜ የተነሣ በሰው ሁሉ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ፤ ነገር ግን ማንም እስከ መጨረሻ የሚጸና እርሱ ይድናል። **23** በዚህች ከተማ በሚያሳድዷችሁ ጊዜ ወደሚቀጥለው ከተማ ሸሹ። እውነት እላችኋለሁ፣ የሰው ልጅ ከመምጣቱ በፊት፣ የእስራኤልን ከተሞች አታዳርሱም። **24** ደቀ መዝሙር ከመምህሩ አይበልጥም፤ ወይም አገልጋይ ከጌታው በላይ አይደለም። **25** ለደቀ መዝሙር ልክ እንደ መምህሩ፣ ለአገልጋይም ልክ እንደ ጌታው መሆን ይበቃዋል። **26** እንግዲህ አትፍሯቸው፤ የማይገለጥ የተሰወረ፣ የማይታወቅ የተደበቀ ምንም የለም። **27** በጨለማ የምነግራችሁን በብርሃን፣ በሹክሹክታ የምትሰሙትንም በአደባባይ ተናገሩት። **28** ሥጋን እንጂ ነፍስን መግደል የማይችሉትን አትፍሩ፤ ከዚያ ይልቅ ነፍስንም፣ ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፋ የሚችለውን ፍሩ። **29** ሁለት ድንቢጦች በትንሽ ሳንቲም ይሸጡ የለምን? ሆኖም አንዷም ብትሆን አባታችሁ ሳያውቅ በመሬት ላይ አትወድቅም። **30** የእናንተ ግን የራሳችሁ ጠጉር እንኳን ሳይቀር የተቈጠረ ነው። **31** አትፍሩ፤ ከብዙ ድንቢጦች የበለጠ ዋጋ አላችሁ። **32** ስለዚህ በሰዎች ፊት ለሚመሰክርልኝ፣ እኔም በሰማይ ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ። **33** በሰው ፊት የሚክደኝን ግን፣ እኔም ደግሞ በሰማይ ባለው በአባቴ ፊት እክደዋለሁ። **34** በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ሰይፍን እንጂ፣ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም። **35** ሰውን በአባቱ ላይ፣ ሴት ልጅን በእናቷ ላይ፣ ምራትን በአማቷ ላይ ለማነሣሣት መጥቻለሁ። **36** የሰውም ጠላቶቹ የገዛ ቤተ ሰቦቹ ይሆናሉ። **37** አባትን ወይም እናትን ከእኔ የበለጠ የሚወድ ለእኔ የተገባ አይደለም፤ እንዲሁም ወንድ ልጅን፣ ወይም ሴት ልጅን ከእኔ የበለጠ የሚወድ ለእኔ የተገባ አይደለም። **38** መስቀሉን ተሸክሞ፣ ከኋላዬ የማይከተለኝ የእኔ ሊሆን አይገባውም። **39** ሕይወቱን የሚያገኛት ያጣታል፤ ስለ እኔ ብሎ ሕይወቱን የሚያጣት ግን ያገኛታል። **40** እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤ እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል። **41** ነቢይ ስለ ሆነ ነቢይን የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ያገኛል፤ ጻድቅ ስለ ሆነ ጻድቅን የሚቀበል የጻድቅን ዋጋ ያገኛል። **42** እውነት እላችኋለሁ፣ ከእነዚህ ታናናሾች ለአንዱ፣ ደቀ መዝሙሬ ስለ ሆነ፣ አንድ ብርጭቆ ቀዝቃዛ ውሃ እንኳ የሚሰጥ ማንም፣ በምንም ዐይነት ዋጋውን አያጣም።

Matthew 10:1

ማቴዎስ **10**:**1**-**1**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ይህ ኢየሱስ ዐሥራ ሁለት ደቀ መዛሙርቱን የእርሱን ሥራ ይሠሩ ዘንድ የለከበት ታሪክ መጀመሪያ ነው። የእርሱ የሆኑትን ዐሥራ ሁለቱን በአንድነት ጠርቶ ኤቲ: “የእረሱን ዐሥራ ሁለት ደቀ መዛሙርት ጠርቶ” ሥልጣንን ሰጣቸው በዚህ ክፍል ውስጥ የተሰጣቸው ስልጣን 1) እርሰኩስ መንፈስን ማስወጣት እንዲችሉ 2) በሽታን እና ደዌን ይፈውሱ ዘንድ እንደሆነ ክፍሉ በግልጽ እንደሚናገር እርግጠኞች ሁኑ። ማስወጣት ኤቲ: “እርኩስ መንፈስ እንዲወጣ ማድረግ” ሁሉንም ዓይነት በሽታዎች እና ሕመሞች ኤቲ: “ሁሉንም በሽታዎች እና ሕመሞች”። “በሽታ” እና “ሕመም” ተቀራራቢ የሆኑ ነገሮች ይሁን እንዲ ከተቻለ በሁለት የተለያዩ ቃላት ቢተረጎሙ የተሸለ ነው። “በሽታ” አንድ ሰው እንዲታመም የሚያደርጉት ነገሮች ሲሆኑ። “በሽታ” ደግሞ በዚህ በሽታ ከመያዛችን የተነሳ የሚሰማን አካላዊ ድካም ወይም ሕመም ነው።

Matthew 10:2

ማቴዎስ **10**:**2**-**4**
አጠቃላይ መረጃዎች በዚህ ሥፍራ ላይ ጸሐፊው የዐሥራ ሁሉትን ሐዋሪያት ስም በመዘርዝር የኋላ ታሪክ መረጃ ይሰጣል። (ተመልከት) መጀመሪያ በቅደም ተከተል እንጂ በደረጃ አይደለም ቀናተኛው የዚህ ቃል አንዱ ትርጉም ሊሆን የሚችለው 1) “ቀናተኛ”። አይሁዳዊያንን ከሮማዊያን አገዛዝ ነጻ ለማውጣት የሚፈልጉ ቡድች ውስጥ ያለን ሰው ያመለክታል። ኤቲ: “ታጋይ” ወይም “የሀገር ፍቅር ያለው” ወይም “የነጻነት ታጋይ”። ሌላኛው የቃሉ ትርጉም ሊሆን የሚችለው 2 “ቀናተኛ የሆነው”። ይህ እግዚአብሔር ይከብር ዘንድ ይቀና የነበረው እንደ ማለት ነው። ማቴዎስ ቀረጥ ሰብሳቢው “ቀረጥ ይሰበስብ የነበረው ማቴዎስ” እርሱን የካደው “ኢየሱስን የካደው”

Matthew 10:5

ማቴዎስ **10**:**5**-**7**
ዓያያዥ ዓረፍተ ነገር በዚህ ሥፍራ ላይ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ለመስበክ ስሄድ ምን ማድረግ እንዳለባቸው እና ምን እንደሚያጋጥማቸው መመሪያ መስጠት መጀመሩን እንመለከታለን። አጠቃላይ መረጃ: ምንም እንኳ ቁጥር 5 የሚጀምረው ኢየሱስ ዐሥራ ሁለቱን ላካቸው በማለት ቢሆንም ኢየሱስ ይህንን መመሪያ የሰጣቸው እነርሱን ከመላኩ በፊት ነው። (ተመልከት) እነዚህን ዐሥራ ሁለቱን ላካቸው ኤቲ: “ኢየሱስ እነዚህ ዐሥራ ሁለት ሰዎች ላካቸው” ወይም “ኢየሱስ የላካቸው እነዚህን ዐሥራ ሁለት ሰዎችን ነው” የተላከ ኢየሱስ የላካቸው ለተወሰነ ዓላማ ነው። “የተላከ” የሚለው ቃል በ MAT 10:2 ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለው “አፖስትል” የሚለው ቃል የግሥ ቅርጹ ነው። አዘዛዘቸው ኤቲ: “ምን ማድረግ እንዳለባቸው ነገራው” ወይም “አዘዛቸው” የጠፉት የእስራኤል በጎች ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር አጠቀላይ የእስራኤልን ሕዝብ ከእረኛቸው ከጠፉት በጎች ጋር የሚያነጻጽር ነው። (UDB) (ተመልከት) የእስራኤል ቤት ይህ ገለጻ የእስራኤልን ሕዝብ የሚገልጽ ነው። ኤቲ: “የእስራኤል ሕዝብ” ወይም “የእስራኤል ዘር” (ተመልከት) እንዲሁም ስትሄዱ “እናንተ” የሚለው ተውላጠ ስም ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያትን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የሚያመለክት ነው። (: ተመልከት) የእግዚአብሔር መንግስ ቀርባለች ይህንን በ MAT 3:2 ውስጥ ያለውን ተመሳሳይ ሀሳብ በተረጎምክበት መንገድ መተርጎም ይኖርብሃል።

Matthew 10:8

ማቴዎስ **10:8-10**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ለመስበክ በሚወጡበት ወቅት ምን ማድረግ እንዳለባቸው እና ምን እንደሚጠብቃቸው ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ትዕዛዝ መስጠቱን ቀጥሏል። እናንተ ይህ ቃል የሚያመለክተው ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ነው። ወርቅ፣ ብር ወይም ናስ እነዚህ ሳንትሞች የሚሠሩባቸው ብረታ ብረቶች ናቸው። እነዚህ የገንዘብ ተለዋጭ ዝርዝሮች ናቸው። ብረታ ብረቶች በአካቢያችሁ የማዬታወቁ ከሆነ እነዚህ"ገንዘብ" ብለህ መተርጎም ትችላለህ። (ተመልከት) ቦርሳ ይህ "ቀበቶ" ወይም "የገንዘብ ቀበቶ" ማለት ነው ነገር ግን ማንኛውንም ገንዘብ ለመያዝ የሚያገለግል ነገርን ሊያመለክት ይችላል። ቀበቶ ረጅም የጨርቅ መቀነት ወይም በወገብ ዙሪያ ሰዎች የሚታጠቁት ከቆዳ የሚሠራ ነገር ነው። ብዙ ጊዜ ታጥፎ በውስጡ ሳንቲሞችን እና ገንዘብን ለመያዝ የሚያስችለው ስፋት አለው። የጉዞ ቦርሳ ይህ በጉዞ ወቅት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ለመያዝ የሚያገለግል ቦርሳ ወይም በሰዎች ምግብ ወይም ገንዘብ ለመሰበብሰብ የሚሆን ቦርሳን ያመለክታል። ተጨማሪ ነገሮችን በ MAT 5:40 ውስጥ ተጨማሪ ነገሮችን ብላችሁ የተረጎማችሁትን ቃል በዚህ ሥፍራ ተጠቀሙ። ሠራተኛ "ሠራተኛ" ምግቡ ኤቲ፡ "የሚያስፈልገው ነገር"

Matthew 10:11

ማቴዎስ **10:11-13**
አያያዥ ዓረፈተ ነገር ለመስበክ በሚወጡበት ወቅት ምን ማድረግ እንዳለባቸው እና ምን እንደሚጠብቃቸው ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ትዕዛዝ መስጠቱን ቀጥሏል። እናንተ እነዚህ ተውላጠ ስሞች ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያትን ያመለክታሉ። ወደዬትኛው ከተማ ወይም መንደር ስትገቡ ኤቲ፡ "ወደ አንድ ከተማ ወይም መንድር ስትገቡ" ወይም "ወደዬትኛውም መንደር ወይም ከተማ ስትገቡ" ከተማ ወይም መንደር "ትልቅ መንደር . . . ትንንሽ መንደር" ወይም "ታላላቅ ከተማ . . . ትንንሽ ከተማ።" በ MAT 9:35 ውስጥ የተጠቀምከውን ተመሳሳይ ቃል በዚህም ሥፍራ ተጠቀም። ከዚያ ከተማ ለቃችሁ እስክትወጡ ድረስ በዚያ ቆዩ ኤቲ፡ "ከተማውን ወይም መንደሩን ለቃችሁ እስኪትወጡ ድረስ በዚያ ሰው ቤት ውስጥ ቆዩ" As you enter into the house, greet it AT: "As you enter into the house, greet the people who live in it." A common greeting in those days was "Peace be to this house!" ወደቤትም ስትገቡ ሰላምታ ስጡ ኤቲ፡ "ወደቤት ስትገቡ በዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ሰላም በሏቸው።" በዚያ ዘመን የተለመደው የሠላምታ ዓይነት "ሰላም ለዚህ ቤት ይሁን" የሚል ነበር›› (ተመልከቱ) ቤቱም የሚገባው ቢሆን ኤቲ፡ "በዚያ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ከተቀበሏችሁ" (UDB) ወይም "በዚያ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች በሚገባ ከተንከባከቧችሁ" (ተመልከት) ሰላማችሁ ይሁንለት ኤቲ፡ "ሠላም ይሁንለት" ወይም "በዚያ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች በሠላም ይኑሩ" ሰላማችሁ ይህ ሐዋርያቱ በዚያ ቤት ውስጥ በሚኖሩ ሰዎች ዘንድ ይመጣ ዘንድ እግዚአብሔርን የሚጠይቁት ሰላም ነው። ባይገባው ግን ኤቲ፡ "በደንብ ካልተቀበሏችሁ" (UDB) ወይም "በደንብ ያላስተናገዷችሁ ከሆነ" ሰላማችሁ ይመለስ ይህ ሁለት አማራጭ ትርጓሜዎች ይሩታል፡ 1) ይህ ቤት ያልተገባው ከሆነ እግዚአብሔር ሰላሙን ወይም በረከቱን ከዚያ ቤት ላይ ይይዘዋል ወይም 2) ቤቱ ያልተገባው ከሆነ ሐዋርያቱ አንድ ነገር ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ይኸውም እግዚአብሔርን ያቀረቡላቸውን ሰላምታ እንዲያከብር መጠየቅ። ሰላምታችሁን መልሳችሁ መውሰድ ወይም የዚህ ውጤት አስመልክቶ በቋንቋችሁ ውስጥ ያሉት ቃላት ተመሳሳይ ከሆኑ በዚህ ሥፍራ መጠቀም ያለባችሁም እነዚህኑ ቃላት ነው።

Matthew 10:14

ማቴዎስ **10:14-15**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ለመስበክ በሚወጡበት ወቅት ምን ማድረግ እንዳለባቸው እና ምን እንደሚጠብቃቸው ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ትዕዛዝ መስጠቱን ቀጥሏል። ከማይቀበላችሁም ቃላችሁንም ከማይሰሙ ሁሉ ኤቲ፡ "በከተማው ውስጥ ከሚኖሩ ሰዎች መካከል ማንም ሳይበቀላች ቢቀር ወይም ያደመጣችሁ ሰው ባይኖር" እናንተ ይህ ዐሥራ ሁለት ደቀ መዛሙርት ያመለክታል። ቃላችሁን የማይሰሙ ቢሆን ኤቲ፡ "መልዕክታችሁን ማድመጥ" " (UDB) ወይም "ማለት የፈለጋችሁትን የሚያደምጥ" ከተማ ይህንን በ MAT 10:11 ከተጠቀምከው ቃል ጋር ተመሳሳይ የሆነ ቃልን በመጠቀም ለትተረጉመው ትችላለህ። የእግራችሁን ትቢያ አራግፉ ኤቲ፡ "ከእግራችሁ ላይ የዚያን ቤት ወይም ከተማ አቧራ አራግፉ።" ይህ እግዚአብሔር በዚያ ቤት ወይም ከተማ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን መተውን የሚያመለክት ምልክት ነው። ይበልጥ ይቀልላቸዋል ኤቲ፡ "መከራቸው ትንሽ ይሆናል።" የሶዶም እና ገሞራ ምድር ኤቲ፡ እግዚአብሔር ከሰማይ በመጣ እሳት ያጠፋቸው በ"ሰዶም እና ገሞራ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች። ይችህ ከተማ ይህ ሐዋርያትን ወይም መልዕክቶቻቸውን ያልተቀበሉ በከተማይቱ የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታል።

Matthew 10:16

ማቴዎስ **10:16-18**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ ደቀ መዛሙርን ማስተማሩን ቀጥሏል። በዚህም ሥፍራ ላይ ለመስበክ በሚሄዱበት ወቅት ስለሚያጋጥማቸው ስደት ይነግራቸው ጀምሯል። ተመልከቱ "ተመልከቱ" የሚለው ቃል በዚህ ሥፍራ ላይ ያለው ጠቀሜታ ከዚህ በታች የተጠቀሰው ሀሳብ ትኩረት እንዲሰጠው ማድረግ ነው። ኤቲ፡ "ተመልከቱ" ወይም "አዲምጡ" ወይም " ከዚህ በመቀጠል ለሚናረው ነገር ትኩረት ስጡ"። እልካችኋለሁ ለተወሰነ ዓላማ ኦየሱስ ልኳቸዋል። እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ራሳቸውን መከላከል በማይችሉ እንስሳት በመመሰል ሊያጠቋቸው በሚችሉ የዱር እንስሳት መካከል እንደሚልካቸው ይናገራል። (ተመልከት) እንደ በጎች በጎች ራሳቸውን መከላከል አይችሉም። (ተመልከት) በተኩላዎች መካከል ኤቲ፡ "እንደ ተኩላ አደገኛ በሆኑ ሰዎች መካከል" ወይም "አደገኛ እንስሳት ከሚያደርጓቸው ነገሮች ጋር የሚመሳሰል ተግባር በሚያደርጉ ሰዎች መካከል" ወይም "ሊያጠቋችሁ በሚችሉ ሰዎች መካከል" (ተመልከት) እንደ እባብ ብልጦች እና እንደ ርግብም የዋሆች ሁኑ ንጽጽሩን አለመግለጡ የተሻለ ነው። ኤቲ፡ "በመረዳት እና በጥንቃቄ እንዲሁም በንጹሕ ልብ እና ሥነ-ምግባርን በጠበቀ መልኩ ነገሮችን ፈጽሙ" (ተመልከቱ) ወደ ሸንጎ አሳልፈው ይሰጧችኋል ኤቲ፡ "ምክንያቱም ወደ ፍርድ ቤታቸው አሳልፈው ይሰጧኋል" ሸንጎዎች እነዚህ የማህረሰቡን ሰላም የሚጠብቁ የአከባቢው የሃይማኖት መሪዎችን ወይም ሸማግሌዎች ናቸው። ኤቲ፡ "ፍርድ ቤቶች" ይገርፏችኋል ኤቲ፡ "በመግረፊያ ይገርፏቸኋል" አሳልፈው ይሰጧኋል "ይወስዷችኋል" ወይም "ይጎትቷችኋል" (ተመልከት) ስለ እኔ ኤቲ፡ "የእኔ ስለሆናችሁ" (UDB) ወይም "እኔን በመከተላችሁ ምክንያት" ለእነርሱና ለአሕዛብም "ለእነርሱ" የሚለው ተውላጠ ስም የሚያመለክተው "ገዥዎች እና ነገሥታት" ነው ወይም አይሁዳዊያን ከሳሾችን ነው (10:17)

Matthew 10:19

ማቴዎስ **10:19-20**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ለመስበክ ስወጡ ስለሚጋጥማቸው ስደት ማስተማሩን ቀጥሏል። አሳልፈውም ሲሰጡአችሁ፥ "ሰዎች ወደ ሸንጎ ስወሰዷችሁ"። በዚህ ሥፍራ "ሰዎች" ተብሎ የተጠቀሱት በ MAT 10:17 ላይ ሰዎች ተብለው ከተጠቀሱት ጋር ተመሳሳይ ናቸው። እናንተ "እናንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ነው። አትፍሩ ኤቲ፡ "አትጨነቁ" እንዴት ወይስ ምን እንድትናገሩ "እንዴት መናገር እንዳለባችሁ ወይም ምን መናገር እንዳለባችሁ"። እነዚህ ሁለት ሀሳቦች በአንድነት ሊጣመሩ ይችላሉ። "ምን ማለት እንዳለባችሁ" (ተመልከት) በዚያች ሰዓት ኤቲ፡ "በዚያን ጊዜ" (: ተመልከት) የአባታችሁ መንፈስ አስፈላጊ ከሆነ ይህ "የሰማያዊ አበባተታችሁ የእግዚአብሔር መንፈስ" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል ወይም ይህ የእግዚአብሔርብ መንፈስ የሚያመለክት እንጂ ምድራዊ አባትን የማያመለከት እንደሆነ ለማሳየት የግርጌ ማስታወሻ መጨመረም ይቻላል። አባት ይህ የእግዚአብሔር ዋና መጠሪያ ነው (ተመልከት) በእናንተ ውስጥ ኤቲ፡ "በእናንተ በኩል"

Matthew 10:21

ማቴዎስ **10**:**21**-**23**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ለመስበክ ስወጡ ስለሚጋጥማቸው ስደት ማስተማሩን ቀጥሏል። ወንድምም ወንድሙን፥ አባትም ልጁን ለሞት አሳልፎ ይሰጣል፥ ኤቲ፡ “ወንድም ወንድሙን ለሞት አሳልፎ ይሰጣል እንዲሁም አባቶች ልጆቻቸውን ለሞት አሳልፈው ይሰጣሉ።” አሳልፎ መስጠት በ MAT 10:17 በተረጎምከው መሠረት ይህንን መተርጎም። ይነሣሉ ኤቲ፡ “ማመጽ”(UDB) ወይም “መቃወም” ይገድሉአቸውማል ኤቲ፡ “ያስገድሏቸል” ወይም “ ባለስልታናቱ እንዲገድሏቸው ደርጋሉ በሁሉም የተጠላችሁ ትሆናላችሁ ኤቲ፡ “በሁሉም የተጠላች ትሆናላችሁ” ወይም “ሁሉም ሰዎች ይጠሏችኋል”ተመልከቱ) እናንተ ... እናንተ . . . እናንተ ይህ ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያትን የሚያመለክት ነው። ስለስሜ ኤቲ፡ “በስሜ ምክንያት” ወይም “በእኔ በማመናችሁ ምክንያት” (UDB) እስከ መጨረሻ የሚጸና ኤቲ፡ “እስከ መጨረሻ በታማኝነት የሚቆይ” እርሱ ይድናል ኤቲ፡ “ያን ሰው እግዚአብሔር ያድነዋል” (ተመልከት) ወደ ቀጣዩ ሸሹ “ወደ ቀጣዩ ከተማ ሸሹ” እስኪመጣ ኤቲ፡ እስኪመጣ

Matthew 10:24

ማቴዎስ **10**:**24**-**25**
አያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ለመስበክ ስወጡ ስለሚጋጥማቸው ስደት ማስተማሩን ቀጥሏል። ደቀ መዝሙር ከመምህሩ አይበልጥም ይህ በአጠቃላይ እውነት የሆነ ነገር ነው። ይን አንጂ ይህንን ዓረፍተ ነገር ለሁሉም ደቀ መዝሙር እና መምህር ማዋል አንችል። ደቀ መዝሙር ከመምህሩ “በላይ ጠቃሚ” አይደለም። ይህ ምልባትም ከመመምህሩ “በላይ ስለማያውቅ” ወይም “ከፍተኛ ደረጃ ስለሌለው” ወይም “የተሸለ ስላልሆነ” ሊሆን ይችላል። ኤቲ፡ “የደቀ መዝሙሩ አስፈላጊነት ሁል ጊዜ ከመምህሩ ያነሰ ነው” ወይም “መምህሩ አስፈላጊነቱ ከደቀ መዝሙር ሁሉ ጊዜ የተሻለ ነው። ባሪያም ከጌታው አይበልጥም “ጌታው ከመምህሩ አይበልጥም”። ይህ አጠቃላይ መርህ እንጂ ማንኛውንም ባሪያን እና ጌታን አይወክልም። ባሪያው ከጌታው “አይበልጥም” ወይም “የተሻለ ጠቃሚ” አይደለም። ኤቲ፡ “ባሪያ ያለው ጠቂታ ሁል ጊዜ ከጌታው ያነሰ ነው።” ወይም “ጌታው ያለው ጠቀሜታ ከባሪያው ሁልጊዜ የበለጠ ነው።” አገልጋይ “ባሪያ” ጌታ “ባለቤት” ደቀ መዝሙር እንደ መምህሩ መሆኑ ይበቃዋል ኤቲ፡ “ደቀ መዝሙር እንደ መምህሩ መሆኑ በቂው ነው” እንደ መምህሩ ኤቲ፡ “መምህሩ የሚያውቀውን ያኽል ቢያውቅ” ወይም “እንደ መምህሩ ቢሆን” እንዲሁም ባሪያውም እንደ ጌታው ኤቲ፡ “ባሪያው እንደ መምህሩ ጠቃሚ መሆኑ ይበቃዋል” ባለቤቱን ብዔል ዜቡል ካሉት፥ ቤተሰዎቹንማ እንዴት አብዝተው አይሉአቸው ኢየሱስን አንገላተውታል ስለዚህም ደቀ መዛሙርቱም ተመሳሳይ ነገር እንደሚጠብቃቸው ማወቅ አለባቸው። ካሉት ኤቲ፡ “ሰዎች አንዲህ ብለው ከጠሩት” የቤቱን ባለቤት ኢየሱስ ይህንን ምሳሌያዊ ንግግር የተናገረው ስለራሱ ነው። (ተመልከት) ብዔል ዜቡል ይህ ስም 1) እንዳለ “ብዔል ዘቡል” ወይም 2) ጸሐፊው ማስተላለፍ የፈለገው ትርጉም “ሴጣን” በሚለው ሊተረጎም ይችላል። ቤተሰቦቹ ይህ ምሳሌያዊ ንግግር የሚያመለክተው የኢየሱስን ደቀ መዛሙርት ነው። (ተመልከት)

Matthew 10:26

ማቴዎስ **10**:**26**-**27**
አያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ለመስበክ ስወጡ ስለሚጋጥማቸው ስደት ማስተማሩን ቀጥሏል። አትፍሩአቸው በዚህ ሥፍራ ላይ “እነርሱን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የኢየሱ ደቀ መዛሙርትን የሚያንገላቱትን ሰዎች ነው። የማይገለጥ የተከደነ፥ የማይታወቅም የተሰወረ ምንም የለምና። ኤቲ፡ ሰዎች የደበቋቸውን ነገሮች እግዚአብሔር ይገልጣቸዋል። (ተመልከት) በጨለማ የምነግራችሁን በብርሃን ተናገሩ፤ በጆሮም የምትሰሙትን በሰገነት ላይ ስበኩ። ኤቲ፡ “በጨለማ የነገርኳችሁ ነገር በቀን ለሰዎች ተናገሩ እንዲሁም በጆሮዋችሁ የነገርኳችሁን ነገር ለሰዎች ንገሩ።” (ተመልከት) በጨለማ የምነግራችሁን ኤቲ፡ “በሚስጥር የሚነግራችሁን” ወይም “በግላችሁ የሚነግራችሁን ነገር” (ተመልከት) በብርሃን ተናገሩ፤ ኤቲ፡ “በግልጽ ተናገሩ” ወይም “በአደባባይ ተናገሩ” (ተመልከት) በጆሮም የምትሰሙትን ኤቲ፡ “በጆሮዋችሁ የነገርኳችሁን ነገር” በሰገነት ላይ ስበኩ። ኤቲ፡ “በሚሰማ ድምጽ ሁሉም እንዲሰማ አድርጋችሁ ተናገሩ”። ሰገነት ኢየሱስ በኖረበት ሥፍራ በከፍታ ላይ ያለ ሥፍራ ሲሆን በከፍተኛ ድምፅ ከዚህ ሥፍራ ሆኖ የሚደረግን ንግግር በሩቅ ሥፍራ ያሉ ሰዎች እንኳ ይሰሙታል።

Matthew 10:28

ማቴዎስ **10**: **28**-**31**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ለመስበክ ስወጡ ስለሚጋጥማቸው ስደት ማስተማሩን ቀጥሏል። አጠቃላይ መረጃ በተጨማሪም በዚህ ክፍል ውስጥ ኢየሱ ደቀ መዛሙርቱ የሚያጋጥማቸውን ስደት መፍራት ያሌለባቸው ለምን እንደሆነ መናገር የጀመረበት ክፍል ነው። ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ “ሰዎችን አትፍሩ። ሥጋን መግደል ይችላሉ ነገር ግ ነፍስን ግን መግደል አይችሉም።” ሥጋን መግደል አካላዊ ሞት ማስከተል። እነዚህ ቃላት ግራ የሚጋቡ ከሆኑ “ልገድሉአችሁ” ወይም “ሌሎች ሰዎችን መግደል” የሚለችሉ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ሥጋ በእጅ ልዳሰስ የሚችል የሰው ክፍል ነፍስ መግደል ሰዎች ከሞቱ በኋላ መጉደት ነፍስ በእጅ ልዳሰስ የማይችል የሰው ክፍል እና ከአካላዊ ሞት በኋላ የሚኖር ሁለት ድንቢጦች በአምስት ሳንቲም ይሸጡ የለምን? ይህ ጥያቄ እንነዲህ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል “ስለ ድንቢጦች አስቡ። ያላቸው ዋጋ በጣም ትንሽ ከመሆኑ የተነሳ በአምስት ሳንቲም ሁለቱን ልትገዟቸው ትችለላላችሁ” (UDB). (ተመልከት) ድንቢጦች እነዚህ በጣም ትንንሽ የሆኑ ጥራጥሬ የሚበሉ ወፎች ሲሆን በዚህ ምሌያዊ ንግግር ውስጥም ሰዎች ምንም ጥቅም የለቸው ብለው ከሚያስባቸው ነገሮች ጋር ተነጻጽሮ ቀርቧል። አምስት ሳንቲም ይህ ብዙ ጊዜ በሚተረጎምበት ቋንቋ ውስጥ ጥቅም ላይ በዋለው ገንዘብ ውስጥ በሚገኘው ሳንቲም ይተረጎማል። ይህ የመዳብ ሳንቲም ሲሆን አንድ ሰው በቀን ከሚገኘው ገቢ ውስጥ አንድ ዐሥራ ስድስተኛው ያኽል ነው። “በጣም ትንሽ ገንዘብ” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ከእነርሱም አንዲቱ ያለ አባታችሁ ፈቃድ በምድር ላይ አትወድቅም። ይህ ንግግር እንዲህ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል “ከእነዚህ መካከል አንዱ እንኳ ወደ ምድር የሚወድቀው አባታችሁ ካወቀው ብቻ ነው” ወይም “አባታችሁ ካወቀው ብቻ ነው ከእነዚህ መካከል አንዱ ወደ ምድር ሊወድቅ የሚችለው”። (: ተመልከት) አንዱም እንኳ “አንድ ድንቢጥ እንኳ” ወደ ምድረ አይወድቅም “አይሞትም” የእናንተስ የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ እንኳ ተቈጥሮአል “በራሳችሁ ላይ እንኳ ስንት ጸጉር እንዳለ እግዚአብሔር ያውቃል” (ተመልከት) ተቆጥሮአል “ተቆጥሮአል” በዋጋችሁ ከብዙ ድንቢጦች ትበልጣላችሁ “ከብዙ ድንቢጦች ይልቅ እግዚአብሔር ለእናንተ ዋጋ ይሰጣል”

Matthew 10:32

ማቴዎስ **10**:**32**-**33**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ለመስበክ ስወጡ ስለሚጋጥማቸው ስደት ማስተማሩን ቀጥሏል። በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ “ለሌሎች የእኔ ደቀ መዝሙር መሆኑን የሚናገር ማንኛውም ሰው” ወይም “ለእኔ ታማኝ መሆኑን ለማንም ሰው የሚናገር ማንም ሰው” መመስከር “መናገር” በሰዎች ፊት “በሰዎች ፊት” ወይም “በሌሎች ሰዎች ፊት” አባት ይህ የእግዚአብሔር ዋና መጠሪያ ነው (ተመልከት) በሰዎች ፊት የሚክደኝ ሁሉ “በሰዎች ፊት የሚክደኝ ሁሉ” ወይም “በሰዎች ፊት የማይቀበለኝ ሁሉ” ወይም “በሌሎች ሰዎች ፊት የእኔ ደቀ መዝሙር መሆኑን የማይናር ሁሉ” ወይም “ለእኔ ታማኝ መሆኑን የማይናገር ሁሉ”

Matthew 10:34

ማቴዎስ **10**:**34**-**36**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ሊያጋጥማቸው የሚችለውን ስደት መፍራት የሌለባቸው በምን ምክንያት እንደሆነ ማስተማሩን ቀጥሏል አይምሰላችሁ “እንደዚህ አታስቡ” ወይም “እንዲህ አይምሰላችሁ” ሰይፍ ይህ ምሳሌያዊ ንግግር 1)የአመጽ ሞት ("መስቀል" በ MAT 10:38(ተመልከት) ወይም 2) መከፋፈልን የሚያመጣ መከራ (

ተመልከት) ለማምጣት “መመለስ” ወይም "መከፋፈል" ወይም "መለያየት" ሰውን ከአባቱ “ልጅን በአባቱ ላይ” ለሰውም ጠላቶች “የሰው ጠላቶ” ወይም “የሰው መጥፎ ጠላቶቹ” ቤተ ሰዎቹ ናቸው “የራሱ ቤተሰብ አባላት ናቸው”

Matthew 10:37

ማቴዎስ **10**:**37**-**39**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ሊያጋጥማቸው የሚችለውን ስደት መፍራት የሌለባቸው በምን ምክንያት እንደሆነ ማስተማሩን ቀጥሏል። የሚወድ . . . ሊሆን አይገባውም፤ ኤቲ፡ “የሚወድ . . . ሊሆን አይገባውም፤” ወይም “የሚትወዱ ከሆነ . . . አትገቡም” የ ይህ “ማንም” ወይም “ይህንን የሚያደረግ” ወይም “ይህንን የሚያደረግ ማንን ሰው” ወይም “ይህንን የሚያደርጉ ሰዎች” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። መውደድ በዚህ ሥፍራ ላይ መውደድ የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው “ወንድማዊ መዋደድን” ወይም “ከጓደኛ የሚገኝ ፍቅርን” የሚያመለክት ነው። በተጨማሪም “መንከባከብ” ወይም “መሰጠት” ወይም “የሚገኝ” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ለእኔ ሊሆን አይገባውም፤ ይህ እንዲህ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል “የእኔ ሊሆን ፈጽሞ አይገባውም” ወይም “የእኔ ደቀ መዝሙር ሊሆን አይገባውም” ወይም “የእኔ መሆን አይገባውም” የማይዝ . . . አይሆንም አማራጭ ትርጉሞች፡ “የማይዙ . . አይደሉም” ወይም “የማትይዝ ከሆነ . . . አይደለህም” ወይም “የማትይዙ ከሆነ . . . አይደላችሁም።” አንሣ . . . መስቀሉን እና ተከተለኝ ይህ ምሳሌያዊ ንግግር ለመሞት ፈቃደኛ መሆን ማለት ነው። ማንሣትን እና ከሌላ ሰው ኋላ መከተልን የሚያመለክቱ የተለመዱ ቃላትን ተጠቀም። (ተመልከት) አንሣ “አንሣ” ወይም “አንሣና ተሸከም” የሚያገኝ . . . ያጠፋታል . . የሚያጠፋ . . . ያገኛታል። እነዚህ ቃላት በተቻለ መጠን በጣም ትንሽ ቃላት አማካኝነት ሊተረጎሙ ይገባል። አማራጩ ትርጓሜዎች፡ “የሚያገኟት. . . ያጠፏታል . . . የሚያጠፏት . . . ያገኟታል” ወይም “ካገኘሃት . . . ታጠፋታለህ . . . ካጠፋሃት . . . ታገኛታለህ” ማግኘት ይህ “መጠበቅ” ወይም “ደንነቱን መጠበቅ” ከሚለው ቃል ጋር ተቀራራቢ ትርጉም ያለው ነው። አማራጭ ትርጓሜዎቹ፡ “ለመጠበቅ የሚሞክር” ወይም “ለማዳን የሚሞክር” (ተመልከት) ያጠፋታል ይህ ሰውዬው ይሞታል ማለት አይደለም። “እውነተኛ ሕይወት አይኖረውም” ለሚለው ምሳሌያዊ ንግግር ነው። (ተመልከት) ነፍሱን የሚያጠፋ ይህ ማለት መሞት ማለት አይደለም። ይህ ማለት ከራሱ ሕይወት ይልቅ ኢየሱስን መታዘዝ አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ማለት ነው። ኤቲ፡ “የራሱን ሕይወት የካደ።” ለእኔ ሲል “በእኔ በማመኑ ምክንያት” ወይም “ለእኔ ሲል” ወይም “በእኔ ምክንያት”። ይህ በ MAT 10:18. ላይ ካለው “ለእኔ ሲል” ከሚለው ሀረግ ጋር ተመሳሳይ ሀሳብ ያለው ነው። ያገኛታል ይህ ምሳሌያዊ ንግግር ትርጉሙ “እውነተኛ ሕይወትን ያገኛል” ማለት ነው። (ተመልከት)

Matthew 10:40

ማቴዎስ **10**:**40**-**41**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ሊያጋጥማቸው የሚችለውን ስደት መፍራት የሌለባቸው በምን ምክንያት እንደሆነ ማስተማሩን ቀጥሏል። የሚ ይህ እንዲህ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል “ማንም” ወይም “ማንም ሰው” ወይም “ይህን ያደረገ ሰው” የሚቀበል ይህ በ MAT 10:14 ውስጥ “መቀበል” ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው። ትርጉሙም “እንደ እንግዳ መቀበል ማለት ነው።” እናንተ በዚህ ሥፍራ ላይ “እናንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢየሱስ እያስረማራቸው ያሉትን ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ነው። የላከኝን ይቀበላል። “የላከኝን እግዚአብሔር አብን ይቀበላል”

Matthew 10:42

ማቴዎስ **10**:**42**-**42**
አያያዥ ዓርፈተ ነገር ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ለመስበክ ሲወጡ ምን ማድረግ እንዳለባቸው እና ምን ምን ነገር እንደሚያጋጥማቸው ማስተማሩን አጠናቀቀ። የሚሰጥ ሁሉ “የሚሰጥ ማንኛውም ሰው” ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ፥ ይህ እንዲህ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል “የእኔ ደቀ መዝሙር ስለሆነ ከእነዚህ ከታነናናሺቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ውሃ የሚሰጥ ማንም ሰው” ወይም “ከእነዚህ ደቀ መዛሙርቶቼ መካከል ለአንዱ ቀዝቃዛ ውሃ እንዲጠጣ የሚሰጥ ማንኛውም ሰው” ዋጋው አይጠፋበትም። “ይህ ሰው በእርግጥ ሽልማቱን ይቀበላል” (ተመልከት) አያጣም “አይከለከልም”። ይህ በምንም ዓይነት መንገድ ንብረቱን ከመውሰድ ጋር አይገናኝም።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **11**

1 እንዲህም ሆነ፣ ኢየሱስ አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት አዝዞ ከጨረሰ በኋላ፣ በከተሞቻቸው ሊያስተምርና ሊሰብክ ከዚያ ሄደ። **2** ዮሐንስ በወህኒ ቤት ሆኖ የክርስቶስን ሥራዎች በሰማ ጊዜ፣ በደቀ መዛሙርቱ መልእክት ላከበት። **3** እንዲህም አለው፣ "የሚመጣው አንተ ነህ፣ ወይስ መጠበቅ ያለብን ሌላ ሰው አለ?" **4** ኢየሱስም መለሰ እንዲህም አላቸው፤ “ሂዱና፣ ለዮሐንስ የምታዩትንና የምትሰሙትን እንዲህ ብላችሁ ንገሩት፤ **5** ዕውሮች ብርሃናቸውን እያገኙ፣ አንካሶች እየተራመዱ፣ ለምጻሞች እየነጹ፣ መስማት የተሳናቸው እየሰሙ፣ ሙታን እየተነሡ፣ ድኾችም የምሥራች እየሰሙ ነው። **6** በማንኛውም ሁኔታ በእኔ የማይሰናከል ሁሉ የተባረከ ነው" ። **7** እነዚህ ሰዎች እንደ ሄዱ፣ ኢየሱስ ለሕዝቡ ስለ ዮሐንስ መናገር ጀመረ፣ እንዲህም አለ፣ "ምን ልታዩ ወደ በረሓ ወጣችሁ? ነፋስ የሚያወዛውዘውን ሸምበቆን? **8** ግን ምን ልታዩ ወጣችሁ? የሚያምር ልብስ የለበሰውን? በርግጥ፣ ጥሩ ልብስ የሚለብሱ የሚኖሩት በቤተ መንግሥት ነው። **9** ግን ምን ልታዩ ወጣችሁ? ነቢይን ነውን? አዎ፣ እላችኋለሁ፣ ከነቢይም የሚበልጠውን ነው። **10** እንዲህ ተብሎ የተጻፈው ስለ እርሱ ነው፦ 'መንገድህን የሚያዘጋጅ መልእክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ።' **11** እውነት እላችኋለሁ፣ ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከዮሐንስ የሚበልጥ ማንም የለም። በመንግሥተ ሰማይ ግን፣ ታናሹ ሰው ከእርሱ ይበልጣል። **12** ከመጥምቁ ዮሐንስ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት በዐመፅ ትቸገራለች፣ ዐመጸፀኞች ግን በኅይል ይወስዷታል። **13** እስከ ዮሐንስ ዘመን ድረስ ሕጉም፣ ነቢያቱም ሁሉ ትንቢት ሲናገሩ ነበርና። **14** እንግዲህ ልትቀበሉት ፈቃደኞች ከሆናችሁ፣ የሚመጣው ኤልያስ እርሱ ነው። **15** የሚሰማ ጆሮ ያለው፣ ይስማ። **16** ይህን ትውልድ ከምን ጋር ላነጻጽረው? በገበያ ተቀምጠው፣ እየተቀባበሉ እንደሚዘፍኑ ልጆች ነው። **17** 'ዋሽንት ነፋንላችሁ፣ አልጨፈራችሁም፤ ሙሾ አወጣንላችሁ እናንተም አላለቀሳችሁም' ይላሉ። **18** ዮሐንስ እንጀራ ሳይበላና የወይን ጠጅ ሳይጠጣ በመምጣቱ፣'ጋኔን አለበት' አሉት። **19** የሰው ልጅ እየበላና እየጠጣ በመምጣቱ፣ 'ተመልከቱ ይህ ሰው በላተኛና ጠጪ፣ የቀረጥ ሰብሳቢዎችና፣ የኃጢአተኞች ወዳጅ ነው!' አሉት ነገር ግን ጥበብ በሥራዋ ትክክል ሆነች። **20** ኢየሱስም ብዙ ታላላቅ ሥራዎች ያደረገባቸውን ከተማዎች፣ ንስሓ ባለመግባታቸው ይገሥጻቸው ጀመር። **21** ወዮልሽ ኮራዚን! ወዮልሽ ቤተሳይዳ! በእናንተ የተደረጉት ታላላቅ ሥራዎች በጢሮስና በሲዶና ተደርገው ቢሆን ኖሮ፣ ማቅ ለብሰውና፥ ዐመድ ነስንሰው ድሮ ንስሓ በገቡ ነበር። **22** ነገር ግን በፍርድ ቀን ከእናንተ ይልቅ፣ ለጢሮስና ለሲዶና ይቀልላቸዋል። **23** አንቺ ቅፍርናሆም፣ እስከ ሰማይ የወጣሽ ይመስልሻልን? በፍጹም፤ ወደ ሲኦል ትወርጂያለሽ። ለአንቺ እንደተደረጉት ትልልቅ ነገሮች በሰዶም ተደርገው ቢሆን ፣ እስከ አሁን በኖረች ነበር። **24** ነገር ግን እላችኋለሁ፣ በፍርድ ቀን፣ ከእናንተ ይልቅ ለሰዶም ይቀልላታል። **25** በዚያን ጊዜ ኢየሱስ መለሰ እንዲህም አለ፤ “የሰማይና የምድር ጌታ አባት ሆይ፣ ይህን ከዐዋቂዎችና ከአስተዋዮች ሰውረህ እንደ ሕፃናት ላልተማሩት ስለ ገለጥህላቸው አመሰግንሃለሁ።” **26** አዎ፣ አባት ሆይ፣ በፊትህ እጅግ ደስ የሚያሰኝህ ይህ ሆኖአልና። **27** ከአባቴ ሁሉ ተሰጥቶኛል፣ ከአባት በቀር ማንም ልጅን የሚያውቀው የለም፤ ከልጅም በቀር፣ ልጁም ሊገልጥለት ከሚፈልገው በቀር፣ አባትን የሚያውቅ ማንም የለም። **28** እናንተ ደካሞች፣ ሸክም የከበዳችሁ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፣ እኔም ዕረፍት እሰጣችኋለሁ። **29** ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ፣ ከእኔም ተማሩ፣ እኔ የዋህና በልቤ ትሁት ነኝ፣ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ። **30** ቀንበሬ ቀላል፣ ሸክሜም የማይከብድ ነው።

Matthew 11:1

ማቴዎስ **11**:**1**-**3**
አጠቃላይ መረጃ ይህ በታሪከው ውስጥ ጸሐፊው ኢየሱስ ለመጥመቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ጥያቄ ምን ዓይነት ምላሽ እንደሰጠ የሚተርከው ታሪክ ጅማሬ ነው። (ተመልከት) ከዚያ አለፈ ይህ ሀረግ የአዲስ ታሪክ ጅማሬ መሆኑን የሚያሳይ ነው። የአንድ ታሪክ ጅማሬን ማሳያ መንገድ በቋንቋችሁ ውስጥ ካለ ያንን መጠቀም ትችላላችሁ። “ከዚያ” ወየም “ከዚያ በኋላ” በሚሉ ቃላት ሊተረጎም ይችላል። ማዘዙን ይህ ቃል “ማስተማር” ወይም “ትዕዛዝ መስጠት” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ዐሥራ ሁለቱ የእርሱ ደቀ መዛሙርት ይህ በኢየሱስን የተመረጡን ዐሥራ ሁለቱን ያመለክታል። አሁን “በዚያን ጊዜ”። ይህንን ሳትተረጉሙት ማለፍ ትችላላችሁ። ዮሐንስ በእስር ቤት ሆኖ በሰማ ጊዜ አማራጭ ትርጓሜዎች፡ “በእርስ ቤት ያለው ዮሐንስ በሰማ ጊዜ” ወይም “ሌሎች ሰዎች በእርስ ላይ ላለው ለዮሐንስ በነገሩት ጊዜ” በደቀ መዛሙርቱ በኩል መልዕክትን ላከ መጥመቁ ዮሐንስ በራሱ ደቀ መዛሙርት በኩል ወደ ኢየሱስ መልዕክትን ላከ እንዲህም አለው “እርሱን” የሚለው ተውላጠ ስም የሚያመለክተው ኢየሱስ ነው። የሚትመጣው አንተ ነህን “የሚትመጣው” ወይም “ትመጣለህ ተብለህ የሚትጠበቀው” ተብሎ ይተርጎም ይህ የሚያመለክተው መስሑን ወይም ክርስቶስን ነው። (ተመልከት) ሌላ እንፈለግ “ሌላ እንጠብቅ”። “እኛ” የሚለው ተውላጠ ስም ሁሉንም አይሁዳዊንን የሚያመለክታል እንጂ የዮሐንስን ደቀ መዛሙርት ብቻ አይደለም።

Matthew 11:4

ማቴዎስ **11**:**4**-**6**
ለዮሐንስ መልሱ ነገሩት “ለዮሐንስ ነገሩት”

Matthew 11:7

ማቴዎስ **11**:**7**-**8**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ ለሕዝቡ ስለመጥመቁ ዮሐንስ መናገር ጀመረ። ምን ልታዩ ወጣችሁ . . . ንፋስ? ኢየሱስ ሕዝቡ ስለመጥመቁ ዮሐንስ እንዲያስቡ ለማድረግ እነዚህ ሦስት ደረጃዎች ያሉት ጥያቄ ጠየቃቸው። እንዲህ ሊተረጎም ይችላል “ንፋስ . . . ለማየት ነው የወጣችሁትን? በእርግጥ አይደለም!” ወይም “በእርግጠኝነት ንፋስን ለማየት አልወጣችሁም!” (ተመልከት) በንፋስ የሚወዛወዝ ሸንበቆ ይህ እንዲህ ሊሆን ይችላል 1) በዮርዳኖስ ወንዝ አጠገብ የሚበቅሉ ተክሎች ወይም 2) አንድን ሰው ለማመልከት የቀረበ ምሳሌያዊ ንግግር፡ “በንፋስ እንደሚዝዋዝው ሸንበቆ ያለ ሰው።” ይህ ምሳሌያዊ ንግግር ሁለት አማራጭ ትርጓሜዎች ይኖሩታል፡ እንዲህ ዓይነቱ ሰው 1) በቀላሉ በንፋስ አማካኝነት የሚንቀሳቀስ፣ ይህ ሀሳቡን በቀላሉ የሚለውጥ ሰውን ለማመልከት ጥቅም ላይ የዋለ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው። ወይም 2) ንፋሱ ስነፍስ ድምፅ የሚያሰማ። ይህ ምሳሌያዊ ገለጻ ብዙ ነገር ይናገራል ይሁን እንጂ ይህን ያኽል ጠቃሚ ነገር አይናገርም። (and ተመልከት) ሸንበቆ “ረጅም፣ ሳር መሰል ተክል” ለስላሳ ልብስ የለበሰ “ውድ ልብስ የለበሰ”። ሀብታሞች ይህንን ዓይነት ልብስ ይለብሱ ነበር። የምር ይህ ቃል ብዙ ጊዜ “እነሆ” በሚል ቀጥሎ ለሚመጣው ሀሳብ ትኩረት መስጠት እንደሚያስፈልግ በሚያሳስብ ቃል ተተርጉሟል። ተለዋጭ ትርጉሙለ “በእርግጥ”

Matthew 11:9

ማቴዎስ **11**:**9**-**10**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ ለሕዝቡ ስለ መጥመቁ ዮሐንስ መናገሩን ቀጥሏል። አጠቃላይ መረጃ፡ በቁጥር 10 ላይ ኢየሱስ ከነቢይ ሚልክያስ መጽሐፍ በመጥቀስ የመጥመቁ ዮሐንስ ሕይወት እና አገልግሎት በተነገረው ትንቢት መሠረት መሆኑን አሳይቷል። ነገር ግን ምን ልታዩ ወጣችሁ - ነብይ ይህ ስለመጥመቁ ዮሐንስ የተጠየቁ ተከታታይ ጥያቄዎች ቀጣዩ ክፍል ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

(ተመልከት) ነገር ግን ምን ልታዩ ወጣችሁ - ነብይ? አዎን እላችኋለሁ “እናንተ” የሚለው በብዙ ቁጥር የተገለጸው ተውላጠ ስም በሁለቱም ሁኔታዎች ውስጥ ሕዝቡን የሚያመለክት ነው። ከነቢይም የሚበልጥ “ተራ ነቢይ ያለሆነ” ወይም “ከተራ ነቢይ በጣም የሚበልጥ” ይህ እርሱ ነው “ይህ” መጥመቁ ዮሐንስ የሚያመለክት ነው። ስለ እርሱ የተጻፈው እርሱ ነው “እርሱ” የሚው ቃል “በቀጣዩ ሀረግ ውስጥ “መልዕክተኛዬ” የተባለው የሚያመለክት ነው። መልዕክተኛዬን እልካለሁ “እኔ” የሚለው ተውላጠ ስም የሚያመለክተው እግዚአብሔር ነው። የዚህ የብሉይ ኪዳን ትንቢት ጸሐፊ እግዚአብሔር የተናገረውን በቀጥታ ጽፏል። በፊትህ “ከፊትህ” ወይም “ከአንተ በፊት ይሄድ ዘንድ።” “አንተ” የሚለው ተውላጠ ስም የነጠላ ቁጥር ነው። ምክንያቱም በትምህርተ ጥቅስ ውስጥ እግዚአብሔር ስለ መስሑ የተነገረ ነው። (ተመልከት)

Matthew 11:11

ማቴዎስ **11**:**11**-**12**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ ለሕዝቡ ስለ መጥመቁ ዮሐንስ መናገሩን ቀጥሏል። ከሴቶች ከተወለዱ ሁሉ “ሴቶች ከወለዷቸው ሰዎች መካከል” ወይም “በምድር ላይ ከኖሩ ሰዎች መካከል” ከመጥመቁ ዮሐንስ የሚበልጥ ማንም የለም ኤቲ: “መጥመቁ ዮሐንስ ትልቁ ነው” በመንግስተ ሰማያት እግዚአብሔር በሚመሰርተው አገዛዝ ውስጥ። ኤቲ: “ወደ መንግስተ ሰማየት ከሚገቡ ሰዎች መካከል” ከእርሱ የሚበልጥ የለም “ከመጥመቁ ዮሐንስ በላይ ጠቃሚ የለም” ከመጥመቁ ዮሐንስ ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ““ከመጥምቁም ከዮሐንስ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ” መንግሥተ ሰማያት ትገፋለች፥ ግፈኞችም ይናጠቋታል። አማራጭ ትርጓሜዎቹ 1) ግፈኞች በግፍ ይናጠቁታል ወይም 2) “ሰዎች የመንግስተ ሰማይን ዋና ሀሳብ ያሳድዳሉ እንዲሁም ግፈኞች ልቆጣጠሩት ይሞክራሉ” ወይም 3) “መንግስተ ሰማያት በኃይል ወደፊት ትሄዳለች እንዲሁም ኃይለኛ የሆኑ ሰዎች የዚህ አካል ለመሆን ይፈልጋሉ።”

Matthew 11:13

ማቴዎስ **11**:**13**-**15**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ ለሕዝቡ ስለ መጥመቁ ዮሐንስ መናገሩን ቀጥሏል። ሕግ “የሙሴ ሕግ” ዮሐንስ “መጥመቁ ዮሐንስ” እና አናንተ ከሆነክ “አናንተ” የሚለው ተውላጠ ስም በሕዝቡ መካከል ያሉ ሰዎችን ነው። ይህ ኤልያስ ነው “ይህ” መጥመቁ ዮሐንስ የሚያመለክት ነው። ይህ ሀረግ መጥመቁ ዮሐንስ በብሉይ ኪዳን የተገለጸው የነብዩ ኤልያስ ጋር ተዛምዶ ያለው ነው ይሁን እንጂ መጥመቁ ዮሐንስ ኤልያስ ግን ማለት አይደለም። (ተመልከት) የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ ኤቲ: “የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ” የሚሰማ ጆሮ ያለው “መስማት የሚችል ጆሮ ያለው” ወይም “የሚሰማኝ ሁሉ” ይስማ በደንብ ይስማ” ወይም “ለተናገርኩት ነገር ትኩረት ይስጥ”

Matthew 11:16

ማቴዎስ **11**:**16**-**17**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ ለሕዝቡ ስለ መጥመቁ ዮሐንስ መናገሩን ቀጥሏል። ይህን በምን እመስለዋለሁ? ይህ የጥያቄ መጀመሪያ ነው።ይህንን ጥያቄ ኢየሱስ የተጠቀመው በዚያ ዘመን ይኖር የነበረውን ሕዝብ እና ሕጻናት በገቢያ ሥፍራ ከሚያደርት ነገር ጋር በማነጻጸር ነው። በጥያቄ ጀምሯል። “ (ተመልከት) በገበያ የሚቀመጡትን ልጆች ይመስላሉ፥ እነርሱም በዚያ ተቀምጠው እርስ በእርሳቸው ይጠራራሉ። ይህ ምሳሌያዊ ንግግር ትርጉም እንደዚህ ሊሆን ይችላል 1) ኢየሱስ “ዋሽንት ነፋላቸው” እንዲሁም ዮሐንስ “አለቀሰላቸው” ነገር ግን “ይህ ትውልድ” ለመደነስም ሆነ ለማልቀስ አሻፈረኝ አለ። ይህ የመታዘዝ ምሳሌ ነው። ወይም 2) ፈሪሳዊያን እና ሌለች ሃይማኖታዊ መሪዎች እነርሱ በሙሴ ሕግ ላይ የጨመሯቸውን ሕጎች አልታዘዝ አለ በማለት ሕዝቡን ይወቅሱታል። (ተመልከት) ይህ ተውልድ “በዚህ ዘመን የሚኖሩ ሰዎች” ወይም “እነዚህ ሰዎች” ወይም “እናንተ የዚህ ዘመን ሰዎች” የገቢያ ሥፍራ ይህ ትልቅ የሆነ ሰዎች የተለያዩ ነገሮችን የሚገዙበትን እና የሚሸጡበት ክፍት ሥፍራ ነው። ዋሽንት ተጫወትንላችሁ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በገቢያ ሥፍራ የተቀመጡትን ልጆች ነው። “እናንተ” የሚለው ቃ የሚያመለክተው “ይህንን ተውልድ” ነው ወይም ሙዝቃ ሰምቶ ምንም ምላሽ ያልሰጠውን ሕዝብ ነው። ዋሽንት የመሰለ የሙዚቃ መሣሪያ ይህ ረጅም የሆነ የትንፋሽ የሙዚቃ መሣሪያ ነው። እንዲሁም አልደነሳችሁም “ይሁን እንጂ በሙዚቃው አልተጫወታችሁም” ወይም አላለቀሳችሁም "ከእኛ ጋርም አላለቀሳችሁም"

Matthew 11:18

ማቴዎስ **11**:**18**-**19**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ ለሕዝቡ ስለ መጥመቁ ዮሐንስ መናገሩን አጠናቀቀ። ምግብ ሳይበላና ሳይጠጣ "ምግብ ሳይበላ" ይህ ዮሐንስ ምንም ዓይነት ምግብ በልቶ አያውቅም ማለት አይደለም። ኤቲ: “ብዙ ጊዜ ይጾም ነበር” ወይም “ጥሩ ምግብ አይበላም ነበር” (UDB) እንዲህ አሉት። “እርኩስ መንፈስ አለበት” ኢየሱስ ሰዎች ስለ ዮሐንስ የተናገሩትን በቀጥታ ጠቅሷል። ይህ በቀጥታ እንዲህ ሊጠቀስ ይችላል : “እነርሱም እርኩስ መንፈስ አለበት አሉት” ወይም “ዳብሎስ አለበት አሉት” ወይም “እርኩስ መንፈስ አለበት ብለው ከሰሱት”(ተመልከት) እነርሱ “እነርሱ” የሚለው ተውላጠ ስም በዚያ ዘመን ይኖሩ የነበረው ሰዎችን ያመለክታል። የሰው ልጅ በዚያ ዘመን ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ኢየሱስ የሰው ልጅ እንደሆነ መረዳት ይኖርባቸው ብሎ ይጠብቅ ስነበር እንዲህ ተብሎ መተርጎም ይችላል “እኔ የሰው ልጅ እነርሱ ግን እንዲህ አሉት፣ “እነሆ፥ በላተኛው ኢየሱስ እንደ የሰው ልጅነቱ ሰዎች ስለ እርሱ የተናገረውን ጠቅሷል። ይህንን በትምህርት ጥቅስ ውስጥ ሳናስቀምጥ እንዲህ ሊተረጎም ይችላል፡ “በታለተኛ ነው አሉት” ወይም “ብዙ ይበላል ብለው ከሰሱት”። የሰው ልጅ የሚለው ሀረግ 1እኔ የሰው ልጅ” ብለህ ከተጎምህ ይህንን ደግሞ “እኔን በታለተኛ ነው አሉኝ” ብለህ መተርም ትችላለህ። በታለተኛና ነው "እርሱ በላተኛ ነው” ወይም “ሁል ጊዜ ብዙ ምግብ ይበላል” ጠጭ "ጠጭ" ወይም "ብዙ አልኮል ሁል ጊዜ ይጠጠቃል" ይሁን እንጂ ጥበብም በሥራዋ ጸደቀች። ይህ ምናልባትም ኢየሱስ ከሁኔታው ጋር ተስማሚ የሆነ ምሳሌን የተናገረበት ነው። ምክንያቱም ሕዘቡም እርሱ እና ዮሐንስን ስለ ጥበባቸው አልተቀበሏቸውም። በ UDB ውስጥ ባለው መሠረት በቀጥታ ሊተረጎም ይችላል። (ተመልከት) ጥበብ ጸደቀች በዚህ ገለጻ መሠረት ኢየሱስ ጥበብን በሴት ይመስላታል። በዚህ ሥፍራ ላይ ጠበብ ከእግዚአብሔር ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት እንደሚያደረገን የሚናገር ሳይሆን ጥበብ ራሱ ትክክለኛ እንደሆነች የተገለጸበት ነው (ተመልከት) በሥራዎቿ “እርሷ” የሚለው ተውላጠ ስም የሚያመለክተው ““ኢየሱስ በሴት የመሰላትን ጥበብን ነው።

Matthew 11:20

ማቴዎስ **11**:**20**-**22**
አጠቃላይ መረጃ: ኢየሱስ ከዚህ በፊት የተለያዩ ተዓምራትን ባደረገባቸው ሥፍራዎች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን መገሰጽ ጀመረ። ከተማዎቹን ገሰጸ ኢየሱስ በዚህ ሥፍራ ላይ ምሌን በመጠቀም በከተማዎቹ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን ትክክለኛ ስላልሆነው ሥራቸው ገሰጸቻ (ተመልከት) ከተማዎች "ከተማዎች" ታላላቅ ተዓምራት የተደረጉባቸው ይህ እንዲህ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል: “ብዙዎቹን ታላላቅ ተዓራትን ያደረገባቸው ሥፍራዎች” (ተመልከት) ታላላቅ ተዓምራት ኤቲ: “ታላላቅ ሥራዎች” ወይም “ታላላቅ ኃይል” ወይም “ተዓምራት” ንሰሓ ስላልገቡ “እነርሱ” የሚለው ተውላጠ ስም በከተማዎቹ ውስጥ የሚኖሩ ንሰሓ ያልገቡትን ሰዎች ያመለክታል። ወየልሽ ኮራዚ፤ ወየልሽ ቤተ ሳይዳ! ኢየሱስ ኮራዚ እና ቤተ ሳይዳ የተባሉ ከተማዎች የሚደምጡ አድርጎ ነው የተናገረው። ይሁን እንጂ እነርሱ አይሰሙን። (ተመልከት) ኮራዚ . . . ቤተ ሳይዳ . . . ጢሮስ . . . ሲዶና በእነዚያ ከተሞች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን ለማመልከት የዋለ ምሳሌያዊ ንግግር ነው። (ተመልከት) እናንተ የተደረገው ተአምራት በጢሮስና በሲዶና ተደርጎ ቢሆን፥ ይህ እንዲህ ሊተረጎም ይችላል: "በእናንተ መካከል ያደረኩትን ተዓምራት በጢሮስና በሲሶና ባደረግ ኖሮ" (ተመልከት) ወየልሽ . . . በእናንተ መካከል የተደረገው “አንተ” የሚለው ተውላጠ ስም የተገለጸው በነጣ ቁጥር ነው። ከብዙ ጊዜ በፊት ንስሐ በገቡ ነበርና። በዚህ ሥፍራ “እነርሱ” ተብሎ የተገለጸው የጢሮስና ሲዶና ሰዎች ነው። ንሰሓ "ስለ ኃጢአታቸው ይቅርታን በጠየቁ ነበር" በፍርድ ቀን ከእናንተ ይልቅ ለጢሮስና ለሲዶና ይቀልላቸዋል። "በፍርድ ቀን ከእናንተ ይልቅ እግዚብሔር ለጢሮስ እና ለሲዶና የተሻለ መምህረት ያደርግላቸዋል" ወይም "እግዚብሔር ከጢሮስ እና ከሶዶና ሐህዝቦች ይልቅ እግዚአብሔር እናንተን ይቀጣል።” በተዘዋዋር የተገለጸው መረጃ “ምንም እንኳ ያደረኳቸውን

ተዓምራትን ቢትመለከቱም ንሰሓ ስላልገባቹ እና በእኔ ስላላመናችሁ።” (ተመልከት) ከአንተ ይልቅ በዚህ ሥፍራ “አንተ” የሚለው ተውላጠ ስም በነጠላ ቁጥር ሲሆን ኮራዚ ወይም ቤተ ሳይዳን ያመለክታል። (ተመልከት)

Matthew 11:23

ማቴዎስ **11**:**23**-**24**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ኢየሱስ ከዚህ በፊት ተዓምራት ያደረገባቸው ከተማዎች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን መገሰጹን ቀጥሏል። . እንች ቅፍርናሆም በዚህ ሥፍራ ላይ ኢየሱስ በቅርፍናሆን የሚኖሩ ሰዎች ልክ እንደሚያደምጡ አድርጎ ይናገራል ይሁን እንጂ እነርሱ እየሰዳመጡት አይደለም፡፤ “አንተ” የሚለው ተውላጠ ስም በነጠላ ቁጥር የተገለጸ ሲሆን በእነዚህ ሁለት ጥቅሶች ውስጥ ቅፍርናሆምን የሚያመለክት ነው። (and ተመልከት) ቅፍርናሆም . . . ሶዶም የእነዚህ ከተሞች ስም በቅፍርናሆም እና ሶዶም ውስጥ ለሞኖሩ ሰዎች ምሳሌ ሆኖ ጥቅም ላይ ውሏል። (ተመልከት) እስከ ሰማይ ከፍ አልኩ ብለስ ታስቢያለሽ? የቅፍርናሆም ሕዝቦች ስላላቸው ትምክት ለመገሰጽ ኢየሱስ የተጠቀመው ጥያቄ ነው። በዚህ ዓይነት መንገድ ሊተረጎም ይችላል “እስከ ሰማይ እሄዳለሁ?" ወይም “እግዚአብሔር ያከብረኛል ብለሽ ታስቢያለሽ?" (እና ተመልከት) ከፍ ከፍ እላለሁ "እከብራለሁ" (ተመልከት) ወደ ሲኦል ትወርጂያለሽ "እግዚአብሔር ወደ ሲኦል ያወርድሻ" (ተመልከት) በአንቺ የተደረገው ተአምራት በሰዶም ተደርጎ ቢሆን፥ "በእናንተ ያደረኳቸውን ተዓምራት በሶዶም አድርጌ ቢሆን ኖሮ" (ተመልከት) ታላላቅ ነገሮች "ታላላቅ ሥራዎች" ወይም "የኃይል ሥራ" ወይን "ተዓምራት" እስከ ዛሬ በኖረች ነበርና። “እርሷ” የሚለው ተውላጠ ስም የሶዶምን ከተማ ያመለክታል። በፍርድ ቀን ከአንቺ ይልቅ ለሰዶም አገር ይቀልላታል። ይህ እንዲህ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል “በፍርድ ቀን እግዚብሔር ከእናንተ ይልቅ ለሶዶም ምድር ይበልይ ምህረት ያደርግላታል” ወይም “በፍርድ ቀን እግገዚአብሔር እናንተ ከሶዶም ይልቅ ይቀጣችኋል”። ይህ በተዘወዘዋር መልኩ የሚሰጠው መረጃ “ምንም እንኳ እኔ የሠራኋቸውን ተዓምራትን ቢትመለከቱም ንሰሓ ስላልገባቹ እና በእኔ ስላለመናችሁ” (ተመልከት)

Matthew 11:25

ማቴዎስ **11**:**25**-**27**
አጠቃላይ መረጃ: በቁጥር 25 እና 26 ላይ በሕዝቡ መካከል ሆኖ በሰማይ ወደሚኖረው አባቱ ጸለየ። በቁጥር 27 እንደገና ለሕዝቡ መናገር ጀመረ። ኢየሱስ እንዲህ የሚል ምላሽ ሰጠ ከዚያም እንዲህ አለ ይህ እንዲህ ማለት ሊሆን ይችላል 1) በ MAT 10:5 የተላኩት የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ከሄዱበት ተመልሰዋል (MAT 12:1 ተመልከት) እንዲሁም አንድ ሰው ስላለው አንድ ነገር ኢየሱስ ምላሽ እየሰጠ ነው ወይም 2) ኢየሱስ ንሰሓ ስላልገቡት ከተሞች የተናገረውን የፍረድ ንግግር አጠቃሏል፡ “ከዚህ በተጨማሪ ኢየሱስ እንዲህ አለ።” አባት . . . ልጅ በእግዚአብሔር እና ኢየሱስ መካከል ያለውን የአባት እና ልጅ ግንኙነት የሚያሳይ የማዕረግ ስም ነው (የሰማይ እና የምድር ጌታ ይህንን እንደ ምሳሌ መረደት ይቻላል “በሰማይ እና በምደር ባሉት ነገሮች ሁሉ ላይ ጌታ የሆነ” ወይም “የዓለማት ሁሉ ጌታ” ይህን ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ሰውረህ ለሕፃናት ስለ ገለጥህላቸው “እነዚህን ነገሮች” የሚለው ሀረግ ምንን እንደሚያመለክት ግልጽ ነው። ይህ ምን ማለት እንደሆነ በግልጽ ቋንቋ ለመናገር አማራጭ ትርጉም ተመራጭ ይሆናል፡ “ጠብባን እና የተማሩ ሰዎች ለማወቅ ያልተፈቀደላቸውን እውነት ምንም ለማያውቁ ሰዎች ገለጥክላቸው።” ይህንን ነገር ከ . . . ሰወርክ “ይህንን ከ. . . ሰወርክ” ወይም “ይህንን ነገር ለ . . . አልገለጥክም”። አልገለጥም የሚለው ግሥ “የመገለጥ” ተቃራኒ ነው። ጠቢባን እና አዋቂዎች "ጠቢባን እናነአዋቂዎች የሆኑ ሰዎች" ለተርጓሚዎች ምክር፡ “ጠቢባን እና አዋቂዎች እንደሆኑ የሚያስቡ ሰዎች” (ተመልከት) ገለጥክላቸው “አስታወካቸው”። “ለእርሱ” የሚለው ተውላጠ ስም የሚያመለክተው በዚህ ቁጥር መጀመሪያ አከባቢ የተጠቀሰውን “እነዚህ ነገሮች” የሚለውን ነው። ላልተማሩ፣ እንደ ትንንሽ ሕጻናት ላሉት ይህ አጠቃላይ ሀረግ “ትንንሽ ልጆች1 እና “ያልተማሩ” ወይም “የማያውቁ” የሚለውን በውስጡ አጠቃሎ በመያዝ የተተረጎመ ነው። ለተርጓሚዎች ምክር: “ምንም የማያውቁ ትንንሽ ልጆች” ይህ በአንተ ፊት መልካም ፈቃድህ ሆነ በፊትህ መልካም ፈቃድ ሆነ - "ምክንያቱም ይህንን ማድረግ መልካም እንደሆነ ተመለከትህ"

እንደ ትንንሽ ሕጻናት ያሉ ጠብባን ያልሆኑ ወይም በጣም ያልተማሩ ሰዎችን ወይም ጠብባን እና በሚገባ የተማሩ እንዳልሆኑ ለሚያውቁ ሰዎች ለማመልከት ጥቅም ላይ የዋለ ምሳሌ ነው። (ተመለልከት) ይህ በአንተ ፊት መልካም ፈቃድህ ሆነ በፊትህ መልካም ፈቃድ ሆነ - "ምክንያቱም ይህንን ማድረግ መልካም እንደሆነ ተመለከትህ"

ሁሉ ከአባቴ ዘንድ ተሰጥቶኛል፤ ይህ እንዲህ ባለ መንገድ ሊተረጎም ይችላል፡ “አባቴ ሁሉን ነገር ሰጥቶኛል” ወይም “አባቴ ሁሉን ነገር ለእኔ ሰጥቶኛል”። እግዚአብሔር አብ ከእግዚአብሔር ወልድ፣ ከኢየሱስ ጋር ዘላለማዊ ግንኙነት ያለው ሲሆን ይም በእግዚአብሔየር አብ እና ወልድ መካከል ባለ የአባት እና ልጅ ግንኙነት ተገልጧል። “አባት” እና “ልጅ” የሚሉ ቃላት በመጀመሪያዎቹ ቅዱሳት መጽሐፍ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉት ይህንን ግንኙነት ለመግሌ ነው (እና ተመልከት ከአብ በቀር ልጅን የሚያውቅ የለም "ልጅን የሚያውቅ አብ ብቻ ነው።" አባት እና ልጅ በእርግጠኝነት እርስ በእርስ የእውነት የሚተዋወቁ ናቸው (ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ጋር)። ልጅን የሚያውቅ ካላቸው ግንኙነተ የተነሳ ልጅን ማወቅ ልጅ በዚህ ሥፍራ ላይ ኢየሱስ ራሱን በሦስተኛ መደብ ይጠራል። (ተመልከት) ከልጅ በስተቀር አባትን የሚያውቅ ማንም የለም “ከወልድም በቀር አብን የሚያውቅ የለም።” አብን የሚያውቅ ከግል ግንኙነታች የተነሳ ወልድም ሊገለጥለት ከሚፈቅድ በቀር ለተርጓሚዎች ምክር: "ሰዎች አብ ማን እንደሆነ ማወቅ የሚችሉት ልህ አብን ልገልጥላቸው ከወደደ ብቻ ነው።”

Matthew 11:28

ማቴዎስ **11**: **28**-**30**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ኢየሱስ ለለሕዝቡ ማናገሩን ጨረሰ። ደካች እና ሸክም የከበደባችሁ ይህ ምሳሌ የአይሁድ ሕግ “ቀንበር” የሚያመለክት ነው። (ተመልከት) እኔም አሳርፋችኋለሁ "ከድካማችሁ እና ሸክማችሁ አሳርፋችኋለሁ" (ተመልከት) ቀንበሬን ተሸከሙ “እናንተ” የሚለው ተውላጠ ስም “ደካሞች እና ሸክም የከበደበባችሁ ሁሉ” የሚለውን የሚያመለክት ነው። የዚህ ምሳሌ ትርጉሙ “የሰጠኋችሁን ሥራ ተቀበሉ” ወይም “ከእኔ ጋር ተባብራችሁ ሥሩ” (ተመልከት) ሸክሜ ቀሊል ነው “ቀላል” የሚለው ቃል የከባድ ተቃራኒ እንጂ የጨለማ ተቃራኒ አይደለም

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 12

1 በዚያን ጊዜ ኢየሱስ በሰንበት በእርሻ መካከል ሄደ። ደቀ መዛሙርቱም ተርበው ስለ ነበር፣ እሸቱን እየቀጠፉ ይበሉ ጀመር። 2 ፈሪሳውያንም ያንን ባዩ ጊዜ፣ “ኢየሱስን፣ ደቀ መዛሙርትህ በሰንበት የሚያደርጉትን የማይገባ ነገር ተመልከት” አሉት። 3 ኢየሱስ ግን፣ "ዳዊትና ከእርሱ ጋር የነበሩት ሰዎች በተራቡ ጊዜ ያደረገውን ከቶ አላነበባችሁምን? 4 ወደ እግዚአብሔር ቤት ገብቶ፣ ለካህናት ብቻ እንጂ ለእርሱና ከእርሱ ጋር ለነበሩት ያልተፈቀደውን የተቀደሰ እንጀራ እንዴት እንደበላ?" አላቸው። 5 በሰንበት ካህናት በቤተ በመቀደስ ሥራ እንድሚሠሩና፣ ሰንበትን እንደሚያረክሱ፣ በደልም እንደማይሆንባቸው ከሕጉ አላነበባችሁምን? 6 እኔ ግን እላችኋለሁ፣ ከቤተ መቅደስ የሚበልጠው እዚህ አለ። 7 “መሥዋዕትን ሳይሆን ምሕረትን እፈልጋለሁ” የሚለውን ብታውቁ ኖሮ፣ በደል የሌለባቸውን አትፈርዱባቸውም ነበር። 8 የሰው ልጅ የሰንበት ጌታ ነውና።" 9 ከዚያም ኢየሱስ ከዚያ ተነስቶ፣ ወደ ምኩራባቸው ገባ። 10 እነሆ፣ እጁ ሽባ የሆነ አንድ ሰው ነበረ። ፈሪሳውያንም ኢየሱስን በኀጢአት ለመክሰስ፣ "ሕጉ በሰንበት መፈወስን ይፈቅዳልን?" ብለው ጠየቁት። 11 ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፤ “ከእናንተ መካከል አንድ በግ ብቻ ብትኖረውና፣ ያቺም በግ ጉድጓድ ውስጥ ብትገባበት፣ በሰንበት የማያወጣት ማን ነው? 12 ታዲያ ሰውማ ፣ ከበግ ይልቅ ምን ያህል ዋጋ ይኖረዋል! ስለዚህ በሰንበት መልካም መሥራት ተፈቅዷል ።" 13 ከዚያም ኢየሱስ፣ ሰውየውን፣ “እጅህን ዘርጋ” አለው። እጁንም ዘረጋ፣ እንደ ሌላውም እጅ ጤነኛ ሆነ። 14 ነገር ግን ፈሪሳውያን ሄደው አሤሩበት፣ እርሱን የሚገድሉበትን መንገድ ይፈልጉ ነበር። 15 ኢየሱስ ይህን እንዳወቀ፣ ከዚያ ፈቀቅ አለ። ብዙ ሰዎች ተከተሉት፤ እርሱም ሁሉንም ፈወሳቸው። 16 ሰዎቹን ስለ እርሱ ለሌሎች እንዳይገልጹ አዘዛቸው፣ 17 ይህም የሆነው በነቢዩ በኢሳይያስ እንዲህ ተብሎ የተነገረው እንዲፈጸም ነው፤ 18 እነሆ፣ እኔ የመረጥኩት አገልጋዬ፤ የምወደው ነፍሴም ደስ የተሰኘችበት። መንፈሴን በእርሱ ላይ አኖራለሁ፤ እርሱም ፍትሕን ለአሕዛብ ያውጃል። 19 አይጨቃጨቅም ወይም አይጮህም፤ ወይም ማንም ድምፁን በጐዳናዎች ላይ አይሰማም። 20 ፍርድን ለድል እስኪያበቃ ድረስ፤ የተቀጠቀጠን ሸምበቆ አይሰብርም፣ የሚጤሰውንም የጧፍ ክር አያጠፋም፣ 21 አሕዛብም በስሙ ይታመናሉ።" 22 ከዚያም በአጋንንት የተያዘን ዐይነ ስውርና ዲዳ ሰው ወደ ኢየሱስ አመጡ፤ እርሱም ፈወሰው፤ ዲዳውም ተናገረ፣ አየም። 23 ሕዝቡም በመገረም፣ "ይህ ሰው የዳዊት ልጅ ይሆን እንዴ?" አሉ። 24 ነገር ግን ፈሪሳውያን ይህን ተአምር በሰሙ ጊዜ “ይህ ሰው በአጋንንት አለቃ በብዔልዜቡል ካልሆነ በቀር አጋንንቱን አያወጣም ነበር" አሉ። 25 ኢየሱስም ዐሳባቸውን ዐውቆ ፣“እርስ በርሱ የሚከፋፈል መንግሥት ይወድቃል፤ እርስ በርሱ የሚለያይ ከተማ ወይም ቤት ሁሉ አይጸናም። 26 ሰይጣን ሰይጣንን የሚያወጣ ከሆነ፣ እርስ በርሱ ተከፋፍሏል፣ መንግሥቱስ እንዴት ይቆማል? 27 እኔ አጋንንትን የማወጣው በብዔልዜቡል ከሆነ፣ ተከታዮቻችሁ በማን ሊያወጡ ነው? ከዚህ የተነሣ እነርሱው ይፈርዱባችኋል። 28 ነገር ግን በእግዚአብሔር መንፈስ አጋንንትን የማወጣ ከሆነ፣ እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ መጥታለች። 29 ማንም ኃይለኛውን ሳያስር ወደ ቤቱ ገብቶ ንብረቱን እንዴት መዝረፍ ይችላል? ካሰረው በኋላ ግን፣ ንብረቱን ይዘርፋል። 30 ከእኔ ጋር ያልሆነ ተቃዋሚዬ ነው፣ ከእኔም ጋር የማይሰበስብ ይበትናል። 31 ስለዚህ እላችኋለሁ፣ ማንኛውም ኀጢአትና ስድብ ለሰዎች ይቅር ይባልላቸዋል ፤መንፈስ ቅዱስን የሚሳደብ ግን ይቅር አይባልም። 32 በሰው ልጅ ላይ ማንኛውንም ቃል የሚናገር ይቅር ይባልለታል፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚናገር ግን፣ በዚህ ዓለምም ሆነ በሚመጣው ይቅር አይባልም። 33 እንግዲህ ዛፍ የሚታወቀው በፍሬው ስለ ሆነ ዛፉን መልካም አድርጉ፤ ፍሬውም መልካም ይሆናል፣ ወይም ዛፉን መጥፎ አድርጉ ፍሬውም መጥፎ ይሆናል። 34 እናንተ የእባብ ልጆች ክፉዎች ስለ ሆናችሁ፣ እንዴት መልካም ልትናገሩ ትችላላችሁ? ምክንያቱም በልብ ውስጥ የሞላውን አፍ ይናገረዋል። 35 . መልካም ሰው በልቡ ውስጥ ካለው መልካም መዝገብ፣ መልካሙን ያወጣል፤ ክፉ ሰውም ልቡ ውስጥ ካለው ክፉ መዝገብ ክፉውን ይወጣል። 36 ለእናንተም እላችኋለሁ፣ በፍርድ ቀን ሰዎች ስለ ተናገሯቸው ከንቱ ንግግሮች መልስ ይሰጣሉ። 37 ምትናገሩት ትጸድቃላችሁ፣ በምትናገሩትም ይፈረድባችኋልና። 38 አንዳንድ የሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን መልሰው ኢየሱስን፣ “መምህር ሆይ፣ ምልክት እንድታሳየን እንፈልጋለን" አሉት። 39 ኢየሱስ ግን መልሶ እንዲህ አላቸው፣ ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይፈልጋል፤ ነገር ግን ከነቢዩ ከዮናስ ምልክት በቀር ምንም አይሰጠውም። 40 ዮናስ በትልቅ ዐሣ ሆድ ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ነበረ፣ የሰው ልጅም ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት በምድር ልብ ውስጥ ይሆናል። 41 የነነዌ ሰዎች በዮናስ ስብከት ንስሓ በመግባታቸው፣ በፍርድ ቀን ከዚህ ትውልድ ሰዎች ጋር ተነሥተው ይፈርዱበታል። ደግሞም ከዮናስ የሚበልጥ እዚህ አለ። 42 የደቡብ ንግሥት፣ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ከምድር ዳርቻዎች መጥታለችና፣ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥታ ትፈርድበታለች።ደግሞም ከሰሎሞን የሚበልጥ እዚህ አለ። 43 ርኩስ መንፈስ ከሰው በወጣ ጊዜ፣ ዕረፍት ፍለጋ ውሃ በሌለባቸው ቦታዎች ያልፋል፣ ነገር ግን አያገኝም። 44 ከዚያም፣ 'ወደ ወጣሁበት ቤቴ እመለሳለሁ' ይላል። ሲመለስም ቤቱ ጸድቶ ተዘጋጅቶ ያገኘዋል። 45 ከዚያም ይሄድና ከእርሱ ይልቅ የከፉትን ሰባት ሌሎች መናፍስትን ይዞ ይመጣል፣ ሁሉም በዚያ ለመኖር ይመጣሉ። የዚያም ሰው የመጨረሻው ሁኔታ ከመጀመሪያው የከፋ ይሆናል። በዚህ ክፉ ትውልድ ላይ የሚሆነውም እንደዚሁ ነው። 46 ኢየሱስም ለሕዝቡ እየተናገረ እያለ፣ እናቱና ወንድሞቹ ሊያናግሩት ፈልገው፣ በውጭ ቆመው ነበር። 47 አንድ ሰውም፣ "እነሆ፣ እናትህና ወንድሞችህ ሊያነጋግሩህ በውጭ ቆመዋል" አለው። 48 ኢየሱስም መልሶ ለነገረው ሰው፣ "እናቴ ማን ናት? ወንድሞቼስ እነማን ናቸው?" አለው። 49 ከዚያም እጁን ወደ ደቀ መዛሙርቱ ዘርግቶ፣ "እናቴና ወንድሞቼ እነዚህ ናቸው! 50 በሰማይ ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ፣ ወንድሜ፣ እኅቴ እናቴም ነውና" አለ።

Matthew 12:1

ማቴዎስ 12፡1-2
አጠቃላይ መረጃ: ይህ አዲስ የታሪኩ አዲስ ክፍል ሲሆን ጸሐፊው በዚህ ክፍል ውስጥ በኢየሱስ አገልግሎት ላይ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ስለመጣው ተቃውሞ ይተርካል። በዚህ ክፍል ውስጥም ፈርሳዊያን የእርሱን ደቀ መዛሙርት በሰንበት አሸት መቅጠፋቸውን አስመልክቶ ያቀረቡትን ተቃውሞ እንመለከታለን። የእርሻ ማሳ ሰብል የተዘራበት መሬት። ስንዴ በአከባቢያችሁ የማይታወቅ ከሆነ “ሰብል”፣ “ዳቦ ለመጋገር የሚሆን እህል ማብቀያ ሥፍራ” በሚል አጠቃላይ መጠሪያን ተጠቀሙ። እሸት ይቀጥፉ ይበሉም ጀመር . . . በሰንበት ማድረግ ያልተፈቀደውን ያደርጋሉ በሰዎች ማሳ ውስጥ የሚገኝን እሸት ቀጥፈው መብላት ሌብነት አይደለም። ጥያቄው በበሰንበት ማድረግ ያልተፈቀደን ነገር ማድረግ ይቻላል ወይ የሚል ነው። ይህንን የእሼቱን ጫፍ ቀንጠበው እሸቱን ጫፍ ይህ ረጅም ሳሪ ከሚመስለው የስንዴ ተክል ጫፍ ላይ የሚገኝ ነው። ይህ ጫፍ የተክሉን ፍሬ በውስጡ ይይዛል። ተመልከት አማራጭ ትርጉሞች: “ተመልከት”ወይም “አድምጥ” ወይም “አሁን ለምናገረው ነገር ትኩረት ስጥ”

Matthew 12:3

ማቴዎስ 12፡1-2
አጠቃላይ መረጃ: ይህ አዲስ የታሪኩ አዲስ ክፍል ሲሆን ጸሐፊው በዚህ ክፍል ውስጥ በኢየሱስ አገልግሎት ላይ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ስለመጣው ተቃውሞ ይተርካል። በዚህ ክፍል ውስጥም ፈርሳዊያን የእርሱን ደቀ መዛሙርት በሰንበት አሸት መቅጠፋቸውን አስመልክቶ ያቀረቡትን ተቃውሞ እንመለከታለን። የእርሻ ማሳ ሰብል የተዘራበት መሬት። ስንዴ በአከባቢያችሁ የማይታወቅ ከሆነ “ሰብል”፣ “ዳቦ ለመጋገር የሚሆን እህል

ማብቀያ ሥፍራ” በሚል አጠቃላይ መጠሪያን ተጠቀሙ። እሸት ይቀጥፉ ይበሉም ጀመር . . . በሰንበት ማድረግ ያልተፈቀደውን ያደርጋሉ በሰዎች ማሳ ውስጥ የሚገኝን እሸት ቀጥፈው መብላት ሌብነት አይደለም። ጥያቄው በበሰንበት ማድረግ ያልተፈቀደን ነገር ማድረግ ይቻላል ወይ የሚል ነው። ይህንን የእሼቱን ጫፍ ቀንጠበው እሸቱን ጫፍ ይህ ረጅም ሳሪ ከሚመስለው የስንዴ ተክል ጫፍ ላይ የሚገኝ ነው። ይህ ጫፍ የተክሉን ፍሬ በውስጡ ይይዛል። ተመልከት አማራጭ ትርጉሞች: “ተመልከት”ወይም “አድምጥ” ወይም “አሁን ለምናገረው ነገር ትኩረት ስጥ”

Matthew 12:5

ማቴዎስ **12**:**5**-**6**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ኢየሱስ ለፈርሳዊያን ትችት ምላሽ መስጠቱን ቀጥሏል። አናንተ . . . አናንተ ፈርሳዊያን በ . . . ውስጥ እንዲህ የሚል ቃል አላነበባችሁምን “ሕግ ምን እንደሚል ታውቁ ዘንድ የሕግ መጽሐፍትን አላነበባችሁምን" (ተመልከት) ሰንበትን አያከብሩም "በሌሎች ቀናት የሚያደርጉትን ነገር በሰንበትም ያደርጋሉ" ጥፋት የለባቸውም "እግዚብሔር አይቀጣቸውም" ከመቅደስ የሚበልጥ በዚህ አለ "ከመቅደሱ ይበልጥ ጠቃሙ የሆነ”። ኢየሱስ የሚበልጠው ብሎ የተናገረው ስለ ራሱ ነው።

Matthew 12:7

ማቴዎስ **12**: **7**-**8**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ኢየሱስ ለፈሪሳዊያን ምላሽ መስጠቱን ቀጥሏል። አጠቃላይ መረጃ: በቁጠር 7 ላይ ኢየሱስ ፈሪሳዊያንን ለመገሰጽ ከነብዩ ሆሴ መጽሐፍ ጠቅሷል። ብታውቁ ኖሮ "አታውቁም" እናንተ . . . እናንተ ፈሪሳዊያን ምሕረትን እወዳለሁ መሥዋዕትንም አይደለም መሥዋዕት ጥሩ ነገር ነው ነገር ግን ምህረት ግን ይሻላል። (ተመልከት) ይህ ማለት ምን ማለት ነው "እግዚአብሔር በቅዱሳት መጽሐፍቱ አማካኝነት ምን አለ" እወዳለሁ “እኔ” የሚለው ተውላጠ ስም እግዚአብሔርን የሚያመለክት ነው።

Matthew 12:9

ማቴዎስ **12**:**9**-**10**
አጠቃላይ መረጃ: በዚህ ሥፍራ ፈሪሳዊያን ኢየሱስ በሰንበት አንድ ሰውን መፈወሱን ወደተቃወሙበት የታሪኩ አቅጣጫ ይለወጣል። ኢየሱስ ከዚያ አልፎ ሄደ "ኢየሱስ የእርሻ ማሳውን ለቆ ወጣ" የእነርሱ ኢየሱስ እየተናገራቸው ያሉት ፈሪሳዊያን ምኩራብ እነሆ “እነሆ” የሚለው ቃል በታሪክ ውስጥ አዲስ ሰውን ያስተዋውቀናል። በቋንቋችሁ እንዲህ ዓይነት ነገር ማድረግ ይቻል ይሆናል። እጁ የሰለለች ሰው ነበረ "የሰለለች" ወይም "ያጠረች"

Matthew 12:11

ማቴዎስ **12**: **11**-**12**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ኢየሱስ ለፈሪሳዊያን ትችት ምላሽ ሰጠ። ከእናንተ . . . ይዞ የማያወጣው ሰው ማን ነው? አማራጭ ትርጉም: “ሁላችሁም . . . ጎትታችሁ ታወጣላችሁ (ተመልከት) እናንተ . . . እናንተ ፈሪሳዊያን ያለው "ያለው ሰው" በዚያ የሚተወው "በጉን በጉድጓድ ውስጥ የሚተወው" መልካም ማድረግ በሕግ ተፈቅዷል "መልካም የሚያደርጉ ሰዎች ሕጉን እየተላለፉ አይደለም” ወይም “መልካም የሚያደርጉ ሰዎች ሕጉን እየታዘዙ ነው"

Matthew 12:13

ማቴዎስ **12**: **13**-**14**
ሰው የሰለለች እጅ ያለው ሰው እጅህን ዘርጋ "እጅህን አንሳ" ወይም እጅህን ዘርጋ" እርሱ ሰውዬው እጁ የሰውዬው እጅ ጤናው ተመለሰች "ሙሉ ለሙሉ ተፈወሰ" ወይም "ሙሉ ጤነኛ ሆነ" በእርሱ ላይ ተማከሩበት "እንዲያጠፉት ተማከሩ" እንዴት አድርገው "ዘዴ ፈለጉ" እርሱን ለመግደል ኢየሱስን ለመግደል h

Matthew 12:15

ማቴዎስ **12**: **15**-**17**
አጠቃላይ መረጃ: ይህ ታሪክ እንዴት የኢየሱስ ተግባር የነብዩ ኢሳያስን ፍጻሜ እንደሆነ ያሳያል። ይህ "ፈሪሳዊያን እርሱን ለመግደል አቀዱ" ትቷቸው ሄደ "ተዋቸው" እንዳይገልጡትም ነገራቸው "ስለ እርሱ ለሌላ ለማንም ሰው እንዳይናገሩ" በነቢዩ በኢሳይያስ የተባለው ይፈጸም ዘንድ እንዲህ ሲል:- "እግዚአብሔር በነብዩ ኢሳያስ አማካኝነት የተናገረው እና የተጻፈው"

Matthew 12:18

ማቴዎስ **12**:**18**-**18**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: በዚህ ክፍል ውስጥ ጸሐፊው የኢየሱስ አገልግሎት በነብዬ ኢሳያስ የተጻፈው የትንቢት ቃል ፍጻሜ መሆኑን ለማሳየት ጠቅሶታ።

Matthew 12:19

ማቴዎስ **12**: **19**-**21**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጸሐፊው ነብዩ ኢሳያስን መጥቀሱን ቀጥሏል። የተቀጠቀጠን ሸምበቆ አይሰብርም "ደካማ ሰዎችን አያጠቃም” (ተመልከት) የተቀጠቀጠ "በግማሽ የተሰበረ ወይም ጉዳት የደረሰበት” የሚጤስን የጥዋፍ ክርም የጥዋፍ ክር አንድ ጊዜ መብራት ከጀመረ በኋላ ጠንካራ አይደለም፤ ይህ ደግሞ ረዳት ያሌላቸው ሰዎችን ያመለክታል (ተመልከት) እስኪ. . . ይህ ከአዲስ ዓረፍተ ነገር ጋር እንዲህ ሊተረጎም ይችላል: “ይህን እስኪያመጣ ድረስ ይህንን ያደርጋል” ወደ ድል የሚያደርስ ፍርድን ያመጣል "እኔ ትክክል እንደሆንኩ ሰዎችን ያሳምናል" በእርሱ ስም ለተርጓሚዎች ምክር: "በእርሱ" (ተመልከት)

Matthew 12:22

ማቴዎስ **12**:**22**-**23**
አንድ ዕውር ዲዳም የሆነ ሰው "ማየት እና መናገር የማይችል አንድ ሰው" ሕብዙም ሁሉ ተገረሙ "ኢየሱስ ሰወዬውን እንደፈወሰው የተመለከቱ ሰዎች ሁሉ በጣም ተገረሙ"

Matthew 12:24

ማቴዎስ **12**:**24**-**25**
ይት ተዓምር የዐይነ ስውሩ፣ ደንቆሮው እና በእርኩስ መንፈስ የተያዘው ሰው የመፈወሱ ተዓምር ይህ ሰው በብዔል ዜቡል በአጋንንት አለቃ ካልሆነ በቀር አጋንንትን አያወጣም "ይህ ሰው አጋንንትን ማውጣት የቻለበት ብቸኛው ምክንያት የብዔል ዜቡል አገልጋይ በመሆኑ ነው" ይህ ሰው ፈሪሳዊያን ኢየሱስን ያለመቀበላቸውን ለማሳየጥ የእርሱን ስም አይጠሩም ነበር። እናንተ . . . እናንተ ፈሪሳዊያን

Matthew 12:26

ማቴዎስ **12**:**26**-**27**
ሰይጣንም ሰይጣንን የሚያወጣ ከሆነ "ሴጣን የራሱን መንግስት ተቃውሞ የሚሠራ ከሆነ" (ተመልከት) መንግስቱ እንዴት ጸንታ ትቆማለች? "የሴጣን መንግስት ጸንቶ ሊቆም አይችልም" ወይም "የሴጣን መንግስት ይፈራርሳል" (ተመልከት) ማስወጣት "አስገድዶ ማስወጣት" ወይም "ማበባረር" ወይም "አውጥቶ መወርወር" ወይም "ነቅሎ ማውጣት" ተከታዮቻችሁ በማን ያወጧቸዋል ለተርጓሚዎች ምክር: "የእናንተ ተከታዮች አጋንትን የሚያስወጡት በብዔል ዘቡል ኃይል አማካኝነት ነው" (ወይም UDB ተመልከት) (ተመልከት) እነርሱ ፈራጆች ይሆኑባችኋል ለተርጓሚዎች ምክር: "አጋንትን በእግዚአብሔር ኃይል የሚያስወጡት የእናንተ ተከታዮች እኔን በብዔል ዘቡል ኃይል አጋንት ያስወጣል በማለታችሁ በእናንተ ላይ ይፈርዳሉ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Matthew 12:28

ማቴዎስ **12**:**28**-**30**
ወደ እናንተ ደርሳለች በፈሪሳዊያን ላይ መጣለች በመጀመሪያ ኃይለኛውን ሳያስሩ "ኃይለኛውን በመጀመሪያ በቁጥጥር ሥር ሳያደርጉ" ከእኔ ጋር ያልሆነ "እኔን የማይደግፈኝ" ወይም “ከእኔ ጋር የማይሠራ" የእኔ ተቃዋሚ ነው "እኔን ተቃውሞ ይሠራል" ወይም "ሥራዬን ያፈርሳል" መሰብሰብ ይህ ሰብል መሰብሰብ የሚያመለክት የተለመደ ቃል ነው። (ተመልከት)

Matthew 12:31

ማቴዎስ **12**:**31**-**32**
ማንኛው ኃጢአት እና በእግዚአብሔር ላይ የሚደረግ ስድብ ለሰዎች ይሰረይላቸዋል "ሰዎች የፈጸሟቸው ኃጢአቶች እና ስድቦችን እግዚአብሔር ይቅር ይላቸዋል” ወይም “ኃጢአት የፈጸሙ ሰዎችን ሁሉ እግዚአብሔር ይቅር ይላቸዋል። ወይም “እግዚብሔር ኃጢአት ያደረጉ ወይም የተሳደቡ ሰዎችን ሁሉ ይቅር ይላቸዋል” (ተመልከት) በመንፈስ ቅዱስ ላይ ግን የሚናገር ሁሉ አይሰረይለትም። "መንፈስ ቅዱስን የሚሳደብን ግን እገግዚአብሔር ይቅር አይለውም" (ተመልከት) እንነዲሁም በሰው ልጅ ላይ የሚናገር ኃጢአቱ ይሰረይለታል "የሰው ልጅን በመቃወም የሚነገርን ንግግር እግዚአብሔር ይቅር ይለዋል" በዚህ ዓለም ቢሆን ወይም በሚመጣው ለተርጓሚዎች ምክር: "በዚህ ጊዜ . . . በመጪው ጊዜ"

Matthew 12:33

ማቴዎስ **12**:**33**-**35**
ዛፍዋን መልካም፥ ፍሬዋንም መልካም አድርጉ፥ ወይም ዛፍዋን ክፉ ፍሬዋንም ክፉ አድርጉ። "ፍሬዋ መልካም ከሆነ ዛፏ መልካም እንደሆነች እንዲሁም ፍሬዋ ክፉ ከሆነ ዛፏም ክፉ እንደሆነች ይታወቃል" መልካም . . . ክፉ ይህ ማለት 1) “ጤናማ . . . ጤናማ ያልሆነ” ወይም 2) "የሚበላ . . . የማይበላ" ዘፍ በፍሬው ይታወቃል ይህ እንዲህ ሊሆን ይችላል 1) "ሰዎች አንድ ዘፍ ጤናማ መሆን አለመሆኑን ፍሬውን ተመልክተው ያውቃሉ" ወይም 2) "ሰዎች የዛፉን ፍሬ በመመልከት የዛፉን ዝሪያ ያውቃሉ" (ተመልከት) እናንተ . . . እናንተ ፈሪሳዊያን በልብ ሞልቶ ከተረፈው አፍ ይናገራልና። "አንድ ሰው በአንደበቱ የሚናገረው በልቡ ውስጥ ካለው ብቻ ነው” (ተመልከት) መልካም መዝገብ . . . ክፉ መዝገብ "ትክክለኛ ሀሳቦች. . . ክፉ ሀሳቦች" (ተመልከት)

Matthew 12:36

ማቴዎስ **12**: **36**-**37**
እናንተ . . . እናንተ ፈሪሳዊያን ሰዎች ስለሚናገሩት ነገር . . .መልስ ይሰጡበታል፤ "እግዚአብሔር ይጠይቀቸዋል" ወይም "እግዚአብሔር ቃላቸውን ይመዝናል" እርባና የሌለው "ጥቅም የሌለው" ለተርጓሚዎች ምክር: "የሚጎዳ" እነርሱ "ሕዝቡ" ትጸድቃለህ . . . ትኰነናለህ "እግዚአብሔር ያጸድቅሃል . . . እግዚአብሔር ይፈርድብሃል" (ተመልከት)

Matthew 12:38

ማቴዎስ **12**:**38**-**40**
መሻት "ፍላጎት" ክፉና አመንዝራ ትውልድ በዚህ ዘመን የሚኖሩ ሰዎች ክፉ ማድረግ ይወዳሉ እንዲሁም ከእግዚአብሔር ታማኞች አይደሉም። ምንም ዓይነት ምልክት አይሰጣቸውም "ለዚህ ክፉ እና አመንዝራ ትውልድ እግዚአብሔር ምንም ዓይነት ምልክት አይሰጥም" (ተመልከት) የዮናስ ምልክት ለትርጓሚዎች ምክር: "ለዮናስ ምን ሆነ" ወይም "ለዮናስ እግዚአብሔር ያደረገው ተዓምር ምን ነበር” (ተመልከት) በመሬት ልብ ውስጥ በመቃብር ውስጥ (ተመልከት)

Matthew 12:41

ማቴዎስ **12**:**41**-**41**
የነነዌ ሰዎች በፍርድ ቀን ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥተው ይፈርዱበታል፤ ለተርጓሚዎች ምክር: "የነነዌ ሰዎች ይህንን ትውልድ ይከሳሉ . . . እንዲሁም እግዚአብሔር ክዳቸውን ይሰማል እና በእናንተ ላይም ይፈርዳል” "እግዚአብሔር የነነዌ ሰዎችን እና ይህንን ትውልድ በኃጢአተኛነታቸው ይፈርድባቸዋል ይሁን እንጂ እነርሱ ንሰሓ ገብተዋል፤ እናንተ ግን አልገባችሁም ስለዚህም በእናንተ ላይ ብቻ ይፈርዳል” (ተመልከት) ይህ ትውልድ ኢየሱስ በኖረበት እና ባገለገለበት ዘመን ይኖሩ የነበሩ ሰዎች (ተመልከት) የሚበልጥ "ይበልጥ አስፈላጊ የሆነ"

Matthew 12:42

ማቴዎስ **12**: **42**-**42**
የደቡድ ንግሥተ ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥታ ትፈርድበታለች፤ ለተርጓሚዎች ምክር: "የደቡድ ንግሥት በዚህ ትውልድ ላይ ትፈርዳለች . . . እግዚአብሔርም ፍርዷን ይሰማል በእናንተም ላይ ይፈርዳል” ወይም እግዚአብሔር በደቡቧ ንግሥት እና በዚህ ትውልድ ላይ በኃጢአታቸው ይፈርዳል ይሁን እንጂ እርሷ ንጉሥ ሰለሞንን ስለመጣች እናንተ ግን እኔን ስላልሰማችሁ የሚፈረደው በእናንተ ላይ ብቻ ይሆናል። (ተመልከት) የደቡቧ ንግሥት ይህ የአሕዛብ መንግስ ንግሥት ሳባን ያመለክታል (ተመልከት) ከምድር ዳርቻ መጥታለች "በጣም ሩቅ ከሆነ ሥፍራ መጥታለች” (ተመልከት) ይህ ትውልድ ኢየሱስ ባገለገለበት ዘመን ይኖሩ የነበሩ ሰዎች (ተመልከት) የሚበልጥ "ይበልጥ አስፈላጊ የሆነ"

Matthew 12:43

ማቴዎስ **12**:**43**-**45**
ውሃ የሌለበት ሥፍራ "ደረቅ ቦታ" ወይም "ሰዎች የማይኖሩበት ቦታ" አያገኝም "የሚያርፍበት ቦታ አያገኝም" እንዲህም ይላል "እርኩስ መንፈሱም እንዲህ ይላል" ቢመጣም ባዶ ሆኖ ተጠርጎና አጊጦ ያገኘዋል። ለተርጓሚዎች ምክር: "እርኩስ መንፈሱም ቤቱ ጸድቶ እና ሁሉ ነገር ተስተካክሎ ያገኘዋል" (ተመልከት)

Matthew 12:46

ማቴዎስ **12**:**46**-**47**
እናቱ የኢየሱስ እናት ወንድሞቹ ይህ እንዲህ ሊሆን ይችላል 1) የእናቱ እና የአባቱ ልጆች ወይም 2) የቅርብ ጓደኞቹ ወይም በእስራኤል ውስጥ ከእርሱ ጋር የሚቀራረቡ

ፍለጋውን "ፈለጉት"

Matthew 12:48

ማቴዎስ **12**:**48**-**50**
እርሱ ለነገረው "ለኢየሱስ እናቱ እና ወንድሞቹ ልያናግሩት እንደሚፈለጉ ለነገረው ሰው" እናቴ ማን ናት? ወንድሞቼስ እነማን ናቸው? ለተርጓሚዎች ምክር: “እናቴ እና ወንድሞቼ እነማን እንደሆኑ በእርግጥ እነግራችኋለሁ" (ተመልከት) ማንም "ማንም" አባት ይህ ለእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ የማዕረግ ስም ነው። (ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **13**

1 በዚያ ቀን ኢየሱስ ከቤት ወጥቶ በባሕር ዳርቻ ተቀመጠ። **2** በጣም ብዙ ሕዝብ በዙሪያው ተሰበሰቡ፣ ስለዚህ ጀልባ ውስጥ ገብቶ ተቀመጠ፤ ሕዝቡም ሁሉ በባሕሩ ዳርቻ ቆመው ነበር። **3** ከዚያም ኢየሱስ በምሳሌ ብዙ ነገር ነገራቸው። እንዲህም አለ፤ "ዘሪ ለመዘራት ወጣ። **4** ሲዘራም፣ አንዳንዱ ዘር በመንገድ አጠገብ ወድቆ፣ ወፎች መጥተው በሉት። **5** ሌላውም ዘር በቂ አፈር በሌለበት በዐለታማ መሬት ላይ ወደቀ። አፈሩም ጥልቀት ስላልነበረው ወዲያው በቀለ። **6** ፀሐይ ሲወጣ ግን፣ሥር ስላልነበረው ጠውልጎ ደረቀ። **7** ሌላው ዘር ደግሞ በእሾኽማ ቊጥቋጦ መካከል ወደቀ፣ እሾኹም አድጎ አነቀው። **8** ሌላው ዘር በመልካም መሬት ላይ ወድቆ ፍሬ አፈራ፤ አንዳንዱ መቶ፣ አንዳንዱ ሥልሳ፣ አንዳንዱም ሠላሳ ፍሬ አፈራ። **9** ጆሮ ያለው ይሰማ።" **10** ደቀ መዛሙርቱም መጡና ኢየሱስን፣ “ለምንድን ነው ለሕዝቡ በምሳሌ የምትናገረው?" አሉት። **11** ኢየሱስም መልሶ፣ "ለእናንተ የመንግሥተ ሰማይን ምስጢር ማወቅ ተሰጥቷችኋል፣ ለእነርሱ ግን አልተሰጣቸውም" አላቸው። **12** ምክንያቱም ላለው ሁሉ የበለጠ ይሰጠዋል፤ ይበዛለትማል። የሌለው ግን ያለው እንኳ ይወሰድበታል። **13** ስለዚህ ለእነርሱ በምሳሌ እነግራቸዋለሁ፤ ምክንያቱም ቢያዩ እንኳ እያዩ አይደለም፣ ቢሰሙም እየሰሙ አይደለም፣ ወይም አያስተውሉም። **14** በእነርሱ ላይ እንዲህ የሚለው የኢሳይያስ ትንቢት ተፈጸመ ፦ መስማትን ትሰማላችሁ፣ ነገር ግን በምንም መንገድ አታስተውሉም፣ ማየትን ታያላችሁ፣ ግን ምንም አትገነዘቡትም። **15** በዐይናቸውም እንዳይመለከቱ፣ በጆሮአቸውም እንዳይሰሙ፣ በልባቸውም እንዳያስተውሉ ጆሯቸው ለመስማት ተደፍኗል፣ ዐይናቸውም ተጨፍኗል። እንዳይመለሱና እኔም እንዳልፈውሳቸው የዚህ ሕዝብ ልብ ደንድኗል። **16** የእናንተ ዐይኖች ግን ስለሚያዩ፣ ጆሮቻችሁም ስለሚሰሙ የተባረኩ ናቸው። **17** እውነት እላችኋለሁ፣ ብዙ ነቢያትና ጻድቃን የምታዩትን ለማየት ተመኝተው አላዩም፤ የምትሰሙትን ለመስማት ተመኝተው አልሰሙም። **18** እንግዲህ የዘሪውን ምሳሌ ስሙ። **19** ማንም የመንግሥትን ቃል ሰምቶ ባያስተውል፣ ክፉው ይመጣል በልቡም የተዘራውን ይነጥቃል። ይህም በመንገድ ዳር የተዘራውን ይመስላል። **20** በዐለት ላይ የተዘራው ፣ቃሉን የሚሰማና ወዲያውኑ በደስታ የሚቀበለው ነው፤ **21** ሆኖም በራሱ ሥር ስለሌለው፣ የሚቆየው ለአጭር ጊዜ ነው። በቃሉ ምክንያት መከራ ወይም ስደት በሚነሣበት ጊዜ፣ ወዲያውኑ ይሰናከላል። **22** በእሾኽ ተክሎች መካከል የተዘራው፣ ቃሉን የሚሰማ ሆኖ የዓለም ዐሳብ፣ የብልጥግናም አሳሳችነት ቃሉን ያንቁታል፣ ፍሬ ቢስም ይሆናል። **23** በመልካም መሬት ላይ የተዘራው፣ ቃሉን የሚሰማና የሚረዳ ነው፤ በርግጥ የሚያድገውና ፍሬ የሚሰጠውም ይህኛው ነው፤ አንዱ መቶ፣ አንዱም ሥልሳ፣ አንዱም ሠላሣ እጥፍ ያፈራል። **24** ኢየሱስ ሌላ ምሳሌ ነገራቸው፤ እንዲህ አለ፤ “መንግሥተ ሰማይ በዕርሻው ላይ መልካም ዘር የዘራ ሰው ትመስላለች። **25** ሰዎቹ በተኙ ጊዜ ግን፣ ጠላቱ መጥቶ በስንዴው መካከል እንክርዳድ ዘርቶ ሄደ። **26** ቅጠሉም በለመለመና ፍሬ ማፍራት በጀመረ ጊዜ፣ እንክርዳዱ ደግሞ አለ። **27** የዕርሻው ባለቤት አገልጋዮች መጥተው፣ "ጌታ ሆይ፣ በዕርሻው ላይ መልካም ዘር ዘርተህ አልነበረምን? ታዲያ እንክርዳድ የበቀለው እንዴት ነው?"አሉት። **28** እርሱም፣ “ጠላት ይህን አደረገ" አላቸው። አገልጋዮቹም መልሰው፣"ስለዚህ ሄደን እንድንነቅለው ትፈልጋለህን?" አሉት። **29** የዕርሻውም ባለቤት፣ 'አይሆንም፣ እንክርዳዱን በምትነቅሉበት ጊዜ ስንዴውንም አብራችሁ ልትነቅሉት ትችላላችሁ 'አላቸው። **30** እስከ መከር ድረስ አብረው ይደጉ። በመከሩ ጊዜ ለኣጫጆቹ፣ "መጀመሪያ እንክርዳዱን ነቅላችሁ እንዲቃጠል አንድ ላይ ሰብስቡ። ስንዴውን ግን ሰብስባችሁ ወደ ጎተራዬ አስገቡት እላቸዋለሁ" አላቸው። **31** ኢየሱስም ሌላ ምሳሌ ነገራቸው። እንዲህም አለ፤ “መንግሥተ ሰማይ ሰው ወስዶ በዕርሻው ላይ የዘራትን የሰናፍጭ ዘር ትመስላለች። **32** በርግጥ ይህች ዘር ከሌሎች ዘሮች ሁሉ ታንሳለች። በምታድግበት ጊዜ ግን የሰማይ ወፎች በቅርንጫፎቿ እስኪሰፍሩባት ድረስ፣ ከሌሎች ዛፎች ትበልጣለች። **33** ከዚያም ኢየሱስ ሌላ ምሳሌ ነገራቸው፤ “መንግሥተ ሰማይ ሴት ወስዳ ኩፍ እስኪል ድረስ ከሦስት እጅ ዱቄት ጋር የደባለቀችውን እርሾ ትመስላለች።” **34** ኢየሱስም ለሕዝቡ እነዚህን ነገሮች ሁሉ በምሳሌ ተናገረ፣ ያለ ምሳሌም ምንም አልነገራቸውም። **35** ይህም ፦ "አፌን በምሳሌ እከፍታለሁ፣ ከዓለም መጀመሪያ ጀምሮ የተሰወረውን አገልጣለሁ" ተብሎ በነቢዩ የተነገረው እንዲፈጸም ነው። **36** ኢየሱስ ሕዝቡን ትቶ ወደ ቤት ገባ። ደቀ መዛሙርቱም ወደ እርሱ መጥተው "በዕርሻው የነበረውን የእንክርዳዱን ምሳሌ አስረዳን" አሉት። **37** ኢየሱስ መለሰ እንዲህም አለ፤ “መልካሙን ዘር የዘራው የሰው ልጅ ነው። **38** ዕርሻው ይህ ዓለም ነው፣ መልካሙ ዘር የመንግሥቱ ልጆች ናቸው። እንክርዳዱ የክፉው ልጆች ናቸው፤ **39** ዘሩን የዘራው ጠላት ዲያብሎስ ነው። መከሩ የዓለም መጨረሻ ሲሆን፣ አጫጆቹም መላእክት ናቸው። **40** ስለዚህ እንክርዳዱ ተሰብስቦ በእሳት እንደሚቃጠል፣ በዓለም መጨረሻም እንዲሁ ይሆናል። **41** የሰው ልጅ መላእክቱን ይልካል፣ ከመንግሥቱ ለኀጢአት ምክንያት የሆኑ ነገሮችን ሁሉና፣ ክፉ አድራጊዎችን ይሰበስቧቸዋል፣ **42** ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ወዳለበት፣ ወደ እቶን እሳትም ይጥሏቸዋል። **43** ከዚያም ፃድቃን በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ያበራሉ። ጆሮ ያለው ይስማ። **44** መንግሥተ ሰማይ በዕርሻ ውስጥ የተደበቀ ሀብት ትመስላለች፣ አንድ ሰውም አግኝቶ ደበቃት፤ ከደስታውም የተነሳ ያለውን ንብረት ሁሉ ሸጦ ያንን ዕርሻ ገዛው። **45** ደግሞም፣ መንግሥተ ሰማይ የከበሩ ዕንቈች የሚፈልግ ነጋዴን ትመስላለች። **46** በጣም ትልቅ ዋጋ ያለው ዕንቊ ባገኘ ጊዜ፣ ሄዶ ያለውን ንበረት ሁሉ ሸጠና ገዛው። **47** እንዲሁም፣መንግሥተ ሰማይ ወደ ባሕር የተጣለችና ሁሉም ዓይነት ፍጥረታት የሰበሰበች መረብን ትመስላለች። **48** መረቡዋ ስትሞላ፣ ዓሣ አጥማጆቹ ወደ ዳር አወጡት። ተቀምጠውም መልካም መልካሙን ሰብስበው በዕቃ አደረጉ፣ የማይጠቅመውን ግን አውጥተው ጣሉት። **49** በዓለም መጨረሻ እንዲሁ ይሆናል፣ መላእክት መጥተው ከጻድቃን መካከል ክፉዎችን ይለያሉ። **50** ከዚያም ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ወዳለበት፣ ወደሚነደው እቶን እሳት ይጥሏቸዋል። **51** ይህን ሁሉ ተረድታችኋል?" አላቸው። ደቀ መዛሙርቱም፣ “አዎን” አሉት። **52** ከዚያም ኢየሱስ፣ “ስለዚህ የመንግሥተ ሰማይ ደቀ መዝሙር የሆነ ጸሐፊ ሁሉ፣ ከሀብቱ መካከል አሮጌውንና ዐዲሱን ያወጣ የቤት ጌታን ይመስላል አላቸው"። **53** ከዚያም ኢየሱስ እነዚህን ምሳሌዎች በጨረሰ ጊዜ፣ ከዚያ ስፍራ ሄደ። **54** ኢየሱስ ወደ ራሱ አገር መጥቶ፣ በምኩራቦቻቸው ሕዝቡን አስተማረ፣ ከዚህም የተነሣ ተገርመው፣ "ይህ ሰው ይህን ጥበቡንና እነዚህን ተአምራት ከየት አገኘ? **55** ይህ ሰው የአናጢው ልጅ አይደለምን? እናቱስ ማርያም አይደለችም ወይ? ያዕቆብ፣ ዮሴፍ፣ ስምዖንና ይሁዳስ ወንድሞቹ አይደሉም ወይ? **56** እኅቶቹስ ከእኛው ጋር አይደሉም ወይ? ታዲያ ይህ ሰው እነዚህን ነገሮች ሁሉ ከየት አገኛቸው?" አሉ። **57** በእርሱም ተሰናከሉበት። ኢየሱስ ግን፣ "ነቢይ ከገዛ አገሩና ከገዛ ቤተ ሰቡ በቀር መከበሩ አይቀርም" አላቸው። **58** በአለማናቸውም ምክንያት ፣በዚያ ብዙ ተአምራት አላደረገም።

Matthew 13:1

ማቴዎስ **13**:**1-2**
በዚያ ቀን ይህ ነገር የፈጸመው ከዚህ በፊት ባለው ምዕራፍ ውስጥ የተገለጸው ታሪክ በተፈመበት ዕለት ነው። ከቤት ውጪ ኢየሱስ በማን ቤት ውስጥ በእንግድነት እንደተቀመጠ አልተገለጸም። ወደ ተንኳይቱ ገብቶ ይህ ምናልባትም ከእንጨት የተሠራ የዓሳ ማጥመጃ ጀልባ ሊሆን ይችላል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Matthew 13:3

ማቴዎስ **13**:**3**-**6**
ኢየሱስ በምሳሌም ብዙ ነገራቸው "ኢየሱስ በምሳሌም ብዙ ነገራቸው " ለእነርሱ ለሕዝቡ to the people in the crowd እነሆ ለተርጓሚዎች ምክር፡ "ተመልከቱ" ወይም “አድምጡ” ወይም “እሁን ለምነግራችሁ ነገር ትኩረት ስጡ” ዘሪ ሊዘራ ወጣ "አንድ ገበሬ በማሳው ላይ ዘርን ለመዝራት ወጣ" እርሱም ሲዘራ "ገበሬው ስዘራ ሳለ" መንገድ ዳር ከማሳው አጠገብ ባለ “መንገድ” ላይ። ብዙ ሰዎች በዚያ መንገድ ላይ ከመራመዳቸው የተነሳ መንገዱ ጠንክሯል። ለቀሟቸው "የተዘሩትን ዘሮች ለቀሟቸው" ዓለታማ መሬት በድንጋይ ላይ ብዙ አፈር ያሌለበት ወዲያው በቀለ "የተዘረዘው ዘር ወዲያው በቀለ” ጠወለገ "ፀሐይ በወጣ ጊዜ ግን ጠወለገ፤ በጣም ይሞቅ ነበር" (ተመልከት) ደረቀ "ተክሉ ደረቀና ሞተ"

Matthew 13:7

ማቴዎስ **13**:**7**-**9**
በእሾህ መካከል ወደቀ "የእሾህ ተክል ባለበት ሥፍራ ወደቀ" አነቀው "አዲሱን ተክል አነቀው።" የተለመዱ አረሞች ሌሎች ተክሎች እንዳያድጉ የሚገልጽን ቃል ተጠቀሙ። ፍሬ ሰጠ "ፍሬ አፈራ" ወይም "ብዙ ፍሬ አፈራ” የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ። ለተርጓሚዎች ምክር፡ "ለመስማት ጆሮ ያላችሁ ስሙ" ጆሮ ያለው "ማስማት የሚችሉ ሁሉ” ወይም “የሚሰማኝ ሁሉ" ያድምጠኝ “በሚገባ ያድምጠኝ" ወይም "አሁን ለሚናገረው ነገር ትኩረት ይስጥ"

Matthew 13:10

ማቴዎስ **13**:**10**-**12**
ለእነርሱ ለደቀ መዛሙርቱ ለእናንተ የመንግሥተ ሰማያትን ምሥጢር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል፥ ለእነርሱ ግን አልተሰጣቸውም። ይህ በቀጥታ በተዘዋዋሪ መንገድ የተሰጡ መረጃዎችን በማካተት እንዲህ ሊገለጽ ይችላል ፡ እግዚአብሔር የመንግስተ ሰማያትን ምስጢር መረዳት የሚትችሉበትን ዕድል ሰጥቶዋችኋ ይሁን እንጂ ይህ እድል ለሌሎች ሰዎች አልተሰጠም።” ወይም እግዚአብሔር የመንግስተ ሰማያትን ምስጢር መረዳት እንዲትችሉ አድርጓል ይሁን እንጂ ለሌሎች ግን ይህ ችሎታ አልተሰጣቸውም።” (en:ta:vol2:translate: and ተመልከት) አናንተ ደቀ መዛሙርት ምስጢር ለብዙ ጊዜ ተደብቆ የነበረው እውነት አሁን በኢየሱስ ተገጦዋል። ለተርጓሚዎች ምክር፡ “ምስጢር” ወይም “የተደበቀ እውነት”። ይህ የተሰጠው "ይህንን መረዳት የተሰጠው" ወይም "የማስተምረው ነገርን የተቀበለ ማንም ነው" ለእርሱ ተጨማሪ ይሰጠዋል ይህ እንዲህ ባለ መንገድ በቀጥታ ሊተረጎም ይችላል፡ “እግዚአብሐየር ተጨማሪ መረዳትን ይሰጠዋ።” (ተመልከት) ይህንን መረዳት ላለው "በግልጽ መረዳት ይችላል" ይህንን መረዳት ላሌለው "ይህንን መረዳት ላሌለው ሁሉ” ወይም "የማስተምረውን ነገር ያልተቀበለ ሰው ሁሉ" ያለው እንኳ ይወሰድበታል ይህ እንዲህ ባለ መንገድ ሊተረጎም ይችላል፡ "ያለውን እንኳ እግዚአብሔር ይወስድበታል።” (ተመልከት)

Matthew 13:13

ማቴዎስ **13**:**13**-**14**
እነግራቸዋለሁ በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ “እነርሱ” የሚለው ተውላጠ ስም የሚያመለክተው ሕዝቡን ነው። ስለዚህ እያዩ ስለማያዩ እየሰሙም ስለማይሰሙ ስለማያስተውሉም በምሳሌ እነግራቸዋለሁ። ኢየሱስ ይህንን ትይዩዋዊ ንጽትር የጠጠቀመው ሕዝቡ ለመስማት አሻፈረኝ ማለቱን ለደቀ መዛሙርቱ ለመናገር ነው። (ተመልከት) ማየትም ታያላችሁና አትመለከቱም። "ምንም እንኳ በዐይናቸው ቢመለከቱም አይረዱትም”። “መምለከት “ የሚለው ሁለተኛው ቃል ትርጉም መረዳት ነው። መስማት ትሰማላችሁና አታስተውሉም፥ የተሰማው ነገር ምን እንደሆነ በግልጽ እንዲህ ሊገለጽ ይችላል፡ ለተርጓሚዎች ምክር፡ “ምንም እንኳ ትምህርቱን ቢሰሙም እውነቱን ግን አይረዱተም።” (ተመልከት) መስማትን ትሰማላችሁ ነገር ግን አትረዱትም፤ ማየትን ታያላችሁ ነገር ግን አታስተውሉም ይህ ከነብዩ ኢሳያስ የተወሰደው በኢሳያስ ዘመን ይኖሩ ስለነበሩ የማያምኑ ሰዎች የተነገረው ክፍል የሚጀምርበት ነው። ኢየሱስ ይህንን ክፍል በመውሰድ እያዳመጡ ያሉት ሰዎችን ለመግለጽ ተጠቅሞበታል። ይህ ሌላኛው ትይዩዋዊ ንጽጽር ነው (ተመልከት) መስማትን ትሰማላችሁ ነገር ግን በጭራሽ አታስተውሉም "ነገሮችን ተሰማላችሁ ነገር ግን አትረዷቸውም"። የተሰማው ነገር ምን እንደሆነ በግልጽ እንዲህ ሊገለጽ ይችላል። ለተርጓሚዎች ምክር: “ትምህርቱን ትሰማላችሁ ነገር ግን እውነቱን ግን አትረዱም” (ተመልቱ) ማየትን ታያላችሁ ነገር ግን በጭራሽ አታስተውሉም "ነገሮችን ትመለከታላችሁ ነገር ግን አትረዷቸውም"

Matthew 13:15

ማቴዎስ **13**: **15**-**15**
የዚህ ሕዝብ ልብ ደንድኖአልና "ይህ ሕዝብ ከእንግዲህ በኋላ አይማርም" ለመስማት አስቸጋሪዎች ሆነዋል "ለመስማት ምንም ፍላጎት የላቸውም" ዐይኖቻቸውን ጨፍነዋል "ለመስማት አሻፈረኝ ብለዋል" በዓይናቸው እንዳያዩ፥ ወይም በጆሮአቸውም እንዳይሰሙ፥ ወይም በልባቸውም እንዳያስተውሉ፥ እንዳይመሰሉ "በዐይኖቻው እንዳያዩ፣ በጆሮአቸውም እንዳይሰሙ፣ በልባቸውም እንዳያስተውሉ እና በዚህም ምክንያት እንዳይመለሱ" እንዳይመለሱ “ወደኋላ እንዳይመሰሉ” ወይም "ንሰሓ እንዳይገቡ” እንድፈውሳቸው "እኔ እንዳድናቸው" ለተርጓሚዎች ምክር፤ "እንደገና እንድቀበላቸው" (ተመልከት)

Matthew 13:16

ማቴዎስ **13**:**16**-**17**
እናንተ . . . እናንተ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርት እየተናገር ነው። እናንተ ስለሚታዩ "ማየት ስለሚችሉ” ወይም “እናንተ ማየት ስለሚችሉ" እናንተ ስለሙትሰሙ "እናንተ መስማት ስለሚትችሉ” ወይም “እናንተ መስማት ስለሚትችሉ” ያያችሁትን ነገር "ሳደረግ ያያችሁኝን ነገሮች" የሰማችሁኝ ነገሮች "ስናገር የሰማችሁኝን ነገሮች

Matthew 13:18

ማቴዎስ **13**:**18**-**19**
ክፉው ይመጣል፥ በልቡ የተዘራውንም ይነጥቃል፤ "ሴጣን የሰማውን የእግዚአብሔርን ቃል እንዲረሣ ያደርገዋል” ይነጥቃል የአንድ ሰውን ንብረት በጉልበት መቀማትን ለመግለጥ የሚያገለግል ቃልን ተጠቀሙ። በልቡ የተዘራውንም ይህ እንዲህ ባለ መንገድ በቀጥታ ሊተረጎም ይችላል፡ “የእግዚአብሔር ቃል በልብቡ ውስጥ ተዘርቷል” (ተመልከት) በልቡም ውስጥ በአድማጩ ልብ ውስጥ በመንገድ ዳር የተዘራው ይህ ነው። የቁም ትርጉሙ ምንም ትርጉም የማይሰጥ ከሆነ አንባቢዎቹ ዘሪው ኢየሱስ፣ ዘሩ መልዕክቱ እና በመንገድ ዳር ያለው አፈር ደግሞ አድማጮቹ መሆናቸው መረዳት በሚችሉበት መንገድ ለመተርጎም ጥረት አድርጉ (and ተመልከት) በመንገድ ዳር "መንገድ” ወይም "መተላለፊያ" ይህንን በ MAT 13:4 ላይ በተረጎማችሁት መንገድ ተርጉሙት።

Matthew 13:20

ማቴዎስ **13**:**20**-**21**
በጭንጫ ላይ የተዘራውም የቁም ትርጉሙ ምንም ትርጉም የማይሰጥ ከሆነ አንባቢዎቹ ዘሪው ኢየሱስ፣ ዘሩ መልዕክቱ እና በመንገድ ዳር ያለው አፈር ደግሞ አድማጮቹ መሆናቸው መረዳት በሚችሉበት መንገድ ለመተርጎም ጥረት አድርጉ (and ተመልከት) ሥር የለውም "ረጅም ሥር የለውም” ወይም “አዲሱ ተክል ለሥሩ የሚሆን ሥፍራን አያገኝም”(እና ተመልከት) ከቃሉ የተነሣ "ከመልዕክቱ የተነሣ" ወዲያውኑ ይሰናከላል "ወዲያውኑ ወድቃል" ወይም "ወዲያውኑ እምነቱን ይተዋል" (ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Matthew 13:22

ማቴዎስ **13:22-23**
በእሾህ መካከል የተዘራው . . . በመልካም መሬት የተዘራው የቁም ትርጉሙ ምንም ትርጉም የማይሰጥ ከሆነ አንባቢዎቹ ዘሪው ኢየሱስ፣ ዘሩ መልዕክቱ እና እሾሃማ መሬት ደግሞ አድማጮቹ መሆናቸው መረዳት በሚችሉበት መንገድ ለመተርጎም ጥረት አድርጉ። አማራጭ ትርጉም: “በእሾህ መካከል የተዘረው ዘር እንዲህ ሆነ . . . በመልካም መሬት ላይ የተዘራው ዘር እንዲህ ሆነ (እና ተመልከት) ቃል "መልዕክት" የዚህም ዓለም አሳብና የባለጠግነት መታለል ቃሉን ያንቃል፥ የማያፈራም ይሆናል። ለተርጓሚዎች ምክር: "አረሞች መልካም ተክል እንዳያድግ እንደሚያደርጉት ሁሉ የዓለም አሳብና የባለጠግነት መታለልም ይህ ሰው ፍሬያማ እንዳይሆን ያደርጉታል (ተመልከት) የዓለም አሳብ "በዚህ ዓለም ውስጥ ያሉና ሰዎችን የሚያሳስቡ ነገሮች" ፍሬያማ እንዳይሆኑ ያደርጋል "ውጤታማ እንዳይሆኑ ያደርጋል" ይህ በእውነት ፍሬ የሚያፈራ ነውና ተንከባከቡት "እነዚህ ፈፍሬ የሚያፈሩ እና ውጤታማ የሚሆኑት ናቸው" ወይም "መልካም ፍሬን እንደሚያፈሩት ጤናማ አትክልቶች እነዚህ ሰዎች ውጤታማ ናቸው" (እና ተመልከት)

Matthew 13:24

ማቴዎስ **13:24-26**
ኢየሱስ ሌላ ምሳሌ ነገራቸው ኢየሱስ ለሕዝቡ ሌላ ምሳሌ ነገራው። (ተመልከት) መንግስተ ሰማይት . . . ሰው ትመስላለች ትርጉም መነንግስተ ሰማይን ከሰውዬው ጋር እኩል ማድረግ የለበትም ይልቁንም መንግስተ ሰማያት በምሳሌ ውስጥ ከተገለጸው ሁኔታ ጋር ይመሳሰላል። *ተመልከት: መልካም ዘር "መልካም ዘሮች" ወይም "መልካም የሰብል ዘሮች”። ኢየሱስን የሚያደምጡት ሰዎች ኢየሱስ ስለ ስንዴት እየተናገረ እንደሆነ ተገንዝበዋል። (ተመልከት) ጠላቱ መጥቶ "ጠላቱ ወደ ማሳው መጥቶ" አረሞች እነዚህ አረሞች ገና በለጋነታቸው የምግብ አትክሎቶችን የሚመስል ቢሆንም ፍሬያቸው ግን መርዛማ ነው። ለተርጓሚዎች ምክር: “መጥፎ ዘሮች” ወይም “የአረም ፍሬዎች” (UDB) ስንዴው በበቀለ ጊዜ "የስንዴው ዘር በበቀለ ጊዜ” ወይም “ፍሬው በበቀለ ጊዜ” ፍሬያቸውን ባፈሩ ጊዜ "ፍሬያቸውን ስያፈሩ" ወይም "የስንዴ ፍሬ ባፈራ ጊዜ" አረሞችም አብረው በቀሉ ለተርጓማች ምክር: "ከዚያም ሰዎች በማሳው ውስጥ አረሞችም መኖራቸውን ተመለከቱ"

Matthew 13:27

ማቴዎስ **13: 27-28**
የእርሻው ባለቤት ይህ በእርሻ ማሳው ላይ መልካም ዘርን ከዘራው ሰው ጋር ተመሳሳይ ነው። መልካምን ዘር በእርሻህ ዘርተህ አልነበርህምን? "መልካም ዘርን በእርሻህ ዘርተህ ነበር”። የመሬቱ ባለቤት ባሮቹ እንዲዘሩ አድርጋቸው ይሆናል። (እና ተመልከት) አንዲህም አላቸው "የመሬቱ ባለቤት ለሎሌዎቹ እንዲህ አላቸው" እኛ . . . ትፈልጋለህን “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሎሌዎቹን ነው።

Matthew 13:29

ማቴዎስ **13:29-30**
የመሬቱ ባለቤት እንዲህ አለ "የመሬቱ ባለቤት ለሎሌዎቹ እንዲህ አለ" አጫጆችን:- “እንክርዳዱን አስቀድማችሁ ልቀሙ በእሳትም ለማቃጠል በየነዶው እሰሩ፥ ስንዴውን ግን በጎተራዬ ክተቱ” እላለሁ አለ። ይህንን በትምህርተ ጥቅስ ውስጥ ሳትከቱ መተርጎም ትችላላችሁ: “ለአጫጆቹ እንዲህ እላቸዋለሁ፤ በመጀመሪያ በእሳት እዲቃጠል እንክርዳዱን ሰብስቡና በአንድ ላይ እሰሩ ከዚያም ስዴውን ሰብስባችሁ ወደ ጎተራዬ አስገቡ (ተመልከት) ጎተራዬ ጎተራ በእርሻ ቦታ የሚሠራ የሰብል ምርት ማከማቻ ነው።

Matthew 13:31

ማቴዎስ **13:31-32**
ኢየሱስ እንዲህ ሲል ሌላ ምሳሌ አቀረበላቸው "ኢየሱስ ለሕዝቡ ሌላ ምሳሌ ነገራቸው" (ተመልከት) መንግስተ ሰማያት . . . ትመስላለች ይህንን በ MAT 13:24 ላይ እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። የሰናፍጭ ፍሬ ትልቅ ዛፍ የሚትሆን በጣም ትን ሽ ዘር (ተመልከት) ይህ ዘር ከሌሎች ዘሮች ሁሉ ይልቅ በጣም ትንሽ ናት የምሳሌው የመጀመሪያ አድማጮች ከሚያውቋቸው ዘሮ መካከል በጣም ትንሸዋ የሰናፍጭ ፍሬ ናት (ተመልከት) ይሁን እንጂ ካደገች በኋላ "ይሁን እንጂ ተክሏ ካደገች በኋላ" ዛፍ ይሆናል "በጣም ትልቅ ዛፍ ይሆናል" (እና እና ተመልከት) የሰማይ ወፎች "ወፎች" (ተመልከት)

Matthew 13:33

ማቴዎስ **13:33-33**
ከዚያም ኢየሱስ ሌላ ምሳሌ ነገራቸው "ከዚያም ኢየሱስ ለሕዝቡ ሌላ ምሳሌ ነገራቸው" (ተመልከት) መንግስተ ሰማየት . . . ትመስላለች በ MAT 13:24 ላይ እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። መንግስቱ እንደ እርሾ አይደለም ይሆኑ እንጂ የመንግስቱ መስፋፋት እንደ እርሾ ነው ተመልከት) ሦስት መሥፈሪያ ዱቄት "ብዙ ዱቄት" ወይም በባሕላችሁ ውስጥ ብዙ መጠን ያለው የዱቄት መሥፈሪያን መጠቀም ትችላላችሁ። እስኪቦካ ድረስ እስኪቦካ ድረስ። በዚህ ሥፍራ በተዘዋዋር የተሰጠው መረጃ ዳቦ ለመጋገር በሦስት መሥፈሪያ ዱቄቱ ላይ እርሾ ተጨምሮ መቦካቱ ነው። (ተመልከት)

Matthew 13:34

ማቴዎስ **13:34-35**
ኢየሱስም ለሕዝቡ ይህን ሁሉ በምሳሌ ተናገረ፤ ያለ ምሳሌ አልተናገራቸውም። ቅደም ተከተሉ “ተናገረ . . . በምሳሌዎች . . . በምሳሌዎች . . . ተናገረ”። ይህንን ቅደም ተከተል የተከተለው በምሳሌ እንደተናገራቸው አጽኖት ለመስጠት ነው። (ተመልከት) እነዚህን ሁሉ ነገሮች ይህ ኢየሱስ በ MAT 13:1 መጀመሪያ ላይ ያስተማረውን ያመለክታል። ያለ ምሳሌ ምንም አልተናገራቸውም "ከምሳሌ ውጪ ምንም አልነገራቸውም" ለተርጓሚዎች መክር: "የነገራውን ሁሉ በምሳሌ ነገራቸው" (እና ተመልከት) በነቢዩምየተባለው ይፈጸም ዘንድ፣ እኔ ስናገር ይህ እንዲህ ባለ መንገድ በቀጥታ ልገለጽ ይችላል: “ከብዙ ዘመናት በፊት እግዚአብሔር ለአንድ ነቢይ እንዲጽፍ ያደረገው ነገር እውን እንዲሆን አደረገ” (UDB). (ተመልከት) የተሰወረ ነገር ይህ እንዲህ ባለ መንገድ ልገለጽ ይችላል: “ለብዙ ጊዜያት ተሰውሮ የነበረው ነገር" (ተመልከት) ዓለም ከተፈጠረ ጊዜ ጀምሮ "ከፍጠትረታት ጅማሬ አንስቶ" ወይም "እግዚብሔር ዓለምን ከፈጠረበት ጊዜ አንስቶ"

Matthew 13:36

ማቴዎስ **13:36-39**
ወደ ቤት ገባ "ወደ ቤት ውስጥ ገባ" ወይም "ወደሚያርፍበት ቤት ገባ" ዘር የዘራው "ዘሪው" የሰው ልጅ በዚህ ሥፍራ ኢየሱስ ራስን እያመለከተ ነው። የመንግስቱ ልጆች "የመንግስቱ አካል የሆኑ ሰዎች” የክፉ ልጆች "የክፉ የሆኑት ሰዎች" ጠላት የዘራቸው እንክርዳዱን የዘረው ጠላት የዓለም መጨረሻ "የዘመን መጨረሻ"

Matthew 13:40

ማቴዎስ **13: 40-43**
ስለዚህ እንክርዳዱ ተሰብስቦ እንዲቃጠል ሲደረግ ይህ እንዲህ ባለ መንገድ በቀጥታ ሊተረጎም ይችላል: “ስለዚህም ሰዎቹ እንክርዳዱን ሰብስበው ስያቃጥሉ" (ተመልከት) የዓለም መጨረሻ "የዘመን መጨረሻ" የሰው ልጅ መላእክቱን ይልካል በዚህ ሥፍራ ኢየሱስ ስለ ራሱ እየተናገረ ነው። ለተርጓሚዎች ምክር: “እኔ፣ የሰው ልጅ መላእክት እልካቸዋለሁ”። ዓመፃን የሚያደርጉት "ክፋትን የሚያደርጉ" ወይም "ክፉ ሰዎች" እቶን እሳት ለተርጓሚዎች ምክር: "እቶን እሳት”። “ማቃጠያ ሥፍራ” የሚለው ቃል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በእናንተ አከባቢ የማይታወቅ ከሆነ “እሳት ማንደጃ ሥፍራ” የሚለውን ቃል መውሰድ ይቻላል። እንደ ጸሐይ ይበራል "ልክ እንደ ፀሐይ የሚትታዩ ሁኑ” (ተመልከት) የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ። ለተርጓሚዎች ምክር: "ጆሮ ያለው ይስማ” ወይም “ጆሮዎች ያሉት እንገግዲህ ያድምጥ"።

Matthew 13:44

ማቴዎስ **13**:**44**-**46**
መንግስተ ሰማያት . . . ትመስላለች በ MAT 13:24 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ተመልከት) በእርሻ ውስጥ የተሰወረን መዝገብ ትመስላለች መዝገብ በጣም ጠቃ፣ እና ውድ የሆኑ ነገሮች ስብስብ ነው። ይህ እንዲህ ባለ መንገድ ሊተረጎም ይችላል: “የሆነ ሰው በእርሻ ውስጥ የደበቀው መዝገብ” (እና ተመልከት) ደበቀው "covered it up" ያለውን ሁሉ ሸጠና ያን እርሻ ገዛ በዚህ ሥፍራ ላይ በተዘዋዋሪ መንገድ የተገለጸው መረጃ የተሰወረ መዝገብ በውስጡ የያዘው የእርሻ ቦት ሰውዬው መግዛቱ ነው። (ተመልከት ነጋዴ ነጋዴ የተለያዩ ነገሮችን የሚሸጥ፣ ብዙ ጊዜም የሚሸጡ ነገሮችን ከሩቅ ሥፍራ የሚያመጣ ነው። መልካምን ዕንቁ የሚሻ ነጋዴን ትመስላለች፤ በዚህ ሥፍራ ላይ በተዘዋዋር መንድ የተገለጸው መረጃ መሠረት ይህ ሰው መልካም ዕንቁን ለመግዛት ይፈልጋል። ውድ ዕንቁ “ዕንቁ” ለስላሳ፣ ጠንካራ፣ የሚያንጸባርቅ፣ ነጭ ወይም ቀለል ያለ ቀለም ያለው ከውሃ ውስጥ የሚገኝ እና ውድ የሆኑ ጌጣ ጌጦችን ለማዘጋጀት የሚውል ውስድ ነገር ነው። ለተርጓሚዎች ምክር: “መልካም ዕንቆዎች” ወይም “የሚያምሩ ዕንቁዎች”።

Matthew 13:47

ማቴዎስ **13**:**47**-**48**
መንግስተ ሰማያት . . . ትመስላለች በ MAT 13:24 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። የእግዚአብሔር መንግስት እንደ መረብ አይደለችም ይሁን እንጂ መንግስተ ሰማያት ልክ መረብ የተለያዩ ዓሳዎችን እንደሚይዝ እንዲሁ መንግስተ ሰማይም ሁሉንም ዓይነት ሰዎችን ወደራሱ ይሰበስባል። (ተመልከት) ወደ ባሕር እንደሚጣል መረብ ይህ በዚህ ዓይነት መንገድ ሊተረጎም ይችላል: “አንዳንድ ዓሳ አጥማጆች ዓሳ ለማጥመድ ወደ ባሕር ውስጥ እንደሚጥሉት መረብ።” (ተመልከት) ወደ ባሕር ውስጥ የሚጣል ባሕር "ወደ ባሕር ውስጥ የሚጣል መረብ" ሁሉንም ዓይነት ፍጥረታትን እንደሚሰበስብ "ሁሉንም ዓይነት ዓሳዎች እንደሚይዝ" ወደ ወደቡ አወጦአት "መረቡን ወደ ባሕሩ ዳርቻ አወጡት” ወይም “መረቡን ወደ ባሕሩ ዳርቻ ጎትተው አወጡት" መልካም የሆኑ ነገሮችን "ጥሩ ጥሩውን ነገር" ጥቅም ያሌለውን "መጥፎዎቹን ዓሳዎች" ወይም "የማይበሉ የዓሳ ዓይነቶችን ግን" አውጥተው ይጥሉአቸዋል "አያስቀምጡትም"

Matthew 13:49

x
ማቴዎስ 13:49-50

የዓለም መጨረሻ "የዘመን መጨረሻ" መጣ "ከሌላ ቦታ የመጣ" ወይም "የሚሄድ" ወይም "ከሰማይ የመጣ" ወረወራቸው "ክፉዎቹን ወረወራቸው" ቆሻሻ ማቃጠያ እሳት ይህ የገሃነም እሳት ምሳሌ ነው። “ቆሻሻ ማቃጠያ” የሚለው የማይታወቅ ከሆነ “ማቃጠያ” የሚል ቃል ልንጠቀም እንችላለን። ለተርጓማች ምክር: "የማቃጠያ ሥፍራ" (ተመልከት) በዚያ ለቅሶ እና የጥርስ ማፋጨት ይሆናል "ክፉዎች የሚያለቅሱበት እና ጥርሳቸውን የሚያፋጩበት ሥፍራ"

Matthew 13:51

x
ማቴዎስ 13:51-53

ይህን ሁሉ አስተዋላችሁን? ደቀ መዛሙርቱ “አዎን” አሉት። አስፈለጊ ሆኖ ከተገኘ ይህን በቀጥታ በመጥቀስ ሳይጠቀስ ማስቀመጥ ይቻላል። “ይህንን ሁሉ በደንብ መረዳታቸውን ኢየሱስ ጠየቃቸው፣ እነርሱን አዎን ተረድተነዋል (ተመልከት) ደቀ መዝሙር የሆነ "ስለሆነ ነገር ተማረ" መዝገብ መዝገብ በጣም ውድ እና ዋጋ ያላቸው ነገሮች ስብስብ ነው። በዚህ ሥፍራ እነዚህ ነገሮች የተከማቹበት ሥፍራን፣ “መጋዝን” ማለት ነው።:

Matthew 13:54

ማቴዎስ **1**:**54**-**56**
ወደ ገዛ አገሩ "የእርሱ ሀገር" ወደ ምኩራቦች በዚህ ሥፍራ ላይ “የእነርሱ” የተጠቀሰው ተውላጠ ስም በዚያ አከባቢ ያሉ ሰዎችን ያመለክታል። በጣም ተገረሙ "ተደነቁ" በእነዚህ ተዓምራቶች "እነዚህን ተዓምራት ያደረገበትን ኃይል ከዬት አገኘ” (ተመልከት) የአናጥዉ ስም አናጢ ከእንጨት ወይም ከድንጋይ የተለያዩ ነገሮችን የሚያበጅ ሰው ነው። “አናጢ” የሚለው ቃል በእናንተ ዘንድ የማይታወቅ ከሆነ “ግንበኛ” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል።

Matthew 13:57

ማቴዎስ **13**: **57**-**58**
ተሰናከሉበት "ኢየሱስ በሚኖርበት መንደር ውስጥ የሚኖሩት ሰዎች በእርሱ ተሰናከሉበት” ወይም “. . . እርሱን አይቀበሉትም” ነብይ አይከበርም "ነብይ በሁሉም ሥፍራ ይከበራል" “ነብይ ክብርን በሁሉም ሥፍራ ያገኛል” ወይ “በሁሉም ሥፍራ ያሉ ሰዎች ነብያትን ያከብራሉ” (ተመልከት) በገዛ ሀገሩ "በአከባቢው" ወይም "በመንደሩ" የገዛ ቤተሰቦቹ "በራሱ ቤት" በዚያም ብዙ ተዓምራትን አላደረገም “ኢየሱስ በገዛ ሀገሩ ብዙ ተዓምራትን አላደረገም”።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **14**

1 በዚያን ጊዜ፣ የአራተኛው ክፍል ገዢ የነበረው ሄሮድስ ስለ ኢየሱስ ሰማ። **2** አገልጋዮቹንም፣ "ይህ መጥምቁ ዮሐንስ ነው። ስለዚህ ይህ ሁሉ ኀይል በእርሱ የሚሠራው ከሞት ስለ ተነሣ ነው" አላቸው። **3** ሄሮድስ፣ በወንድሙ በፊልጶስ ሚስት በሄሮድያዳ ምክንያት፣ ይዞ አሳስሮት ነበርና። **4** ምክንያቱም ዮሐንስ፣ "እርሷን ማግባትህ ተገቢ አይደለም" ይለው ነበር። **5** ሄሮድስ ሊያስገድለው ፈልጎ፣ ሕዝቡን ፈራ፣ ምክንያቱም ሕዝቡ ዮሐንስን እንደ ነቢይ ያዩት ነበር። **6** ነገር ግን በሄሮድስ የልደት ቀን፣ የሄሮድያዳ ልጅ በመካከል ስትጨፍር፣ ሄሮድስን ደስ አሰኘችው። **7** በዚህም ምክንያት፣ የምትጠይቀውን ሁሉ እንደሚሰጣት በመሓላ ቃል ገባላት። **8** በእናቷም ተመክራ፣ “የመጥምቁ ዮሐንስን ራስ እዚሁ፣ በሳሕን አድርገህ ስጠኝ” አለችው። **9** ንጉሡ በጥያቄዋ በጣም ዐዘነ፣ ነገር ግን በመሓላውና ከእርሱ ጋር እራት ላይ በነበሩት ምክንያት፣ የተናገረው እንዲፈጸም አዘዘ። **10** ሰው ልኮ፣ በወህኒ ቤት የዮሐንስን ራስ አስቈረጠ። **11** ከዚያም ራሱ በሳሕን ተደርጎ ለልጅቱ ተሰጣት፣ እርሷም ለእናቷ ወሰዳ ሰጠች። **12** ከዚያም የእርሱ ደቀ መዛሙርት መጥተው፣ በድኑን ወስደው ቀበሩት። ከዚህ በኋላ ሄደው ለኢየሱስ ነገሩት። **13** ኢየሱስም ይህን በሰማ ጊዜ፣ በጀልባ ገለል ወዳለ ቦታ ሄደ። ሕዝቡም ይህን በሰሙ ጊዜ ፣ ከየከተሞቹ በእግር ተከተሉት። **14** ከዚያም ኢየሱስ ቀድሞአቸው መጥቶ ብዙ ሕዝብ አየና ራራላቸው፣ ሕመምተኞቻቸውንም ፈወሰ። **15** በመሸም ጊዜ፣ ደቀ መዛሙርቱ መጡና፣ “ቀኑ መሸቷል ይህም ስፍራ ምድረ በዳ ነው ። ሕዝቡን ወደ መንደሮች እንዲሄዱና፣ ለራሳቸው ምግብ እንዲገዙ አሰናብት" አሉት። **16** ኢየሱስ ግን፣ "መሄድ አያስፈልጋቸውም፤ እናንተው የሚበሉትን ስጧቸው" አላቸው። **17** እነርሱም፣ “ እኛ ያለን አምስት እንጀራና ሁለት ዐሣ ብቻ ነው" አሉት። **18** ኢየሱስም፣ "እነርሱኑ ወደ እኔ አምጡአቸው" አለ። **19** ከዚያም ኢየሱስ ሣሩ ላይ እንዲቀምጡ ሕዝቡን አዘዘ። ዐምስቱን እንጀራና ሁለቱን ዐሣ ወሰደ፣ ወደ ሰማይ አሻቅቦ እያየ፣ አመሰገነ፤ እንጀራውንም ቈርሶ፣ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸው፤ ደቀ መዛሙርቱም ለሕዝቡ ሰጡ። **20** ሁሉም በልተው ጠገቡ። ከዚያም የተረፈውን ዐሥራ ሁለት መሶብ ሙሉ ቍርስራሽ ሰበሰቡ። **21** የበሉትም፣ ከሴቶችና ከልጆች ሌላ፣ ዐምስት ሺ ያህል ወንዶች ነበሩ። **22** እርሱም ሕዝቡን እያሰናበተ እያለ፣ ደቀ መዛሙርቱን ወዲያው ወደ ጀልባ ገብተው፣ ከእርሱ በፊት ወደ ማዶ እንዲሄዱ አዘዛቸው። **23** ሕዝቡን ካሰናበተ በኋላ፣ ብቻውን ለመጸለይ ወደ ተራራ ወጣ። በመሸ ጊዜ፣ በዚያ እርሱ ብቻውን ነበር። **24** ጀልባዋ በባሕሩ መካከል እያለች፤ ከተቃራኒ አቅጣጫ ይነፍስ ስለ ነበር፣ በማዕበሉ ክፉኛ ትንገላታ ነበር። **25** ከምሽቱ በአራተኛው ክፍል፣ ኢየሱስ በባሕሩ ላይ እየተራመደ ወደ እነርሱ እየመጣ ነበር። **26** ደቀ መዛሙርቱም በባሕር ላይ እየተራመደ ሲያዩት፣ እጅግ ደንግጠው፣ “መንፈስ ነው”ብለው በፍርሀት ጮኹ። **27** ኢየሱስ ግን ወዲያውኑ፣ “አይዟችሁ! እኔ ነኝ! አትፍሩ” ብሎ ተናገራቸው። **28** ጴጥሮስም መልሶ፣ “ጌታ ሆይ፣ አንተስ ከሆንህ፣ በውሃው ላይ ወደ አንተ እንድመጣ እዘዘኝ" አለው። **29** ኢየሱስም፣ “ና" አለው። ስለዚህ ጴጥሮስ ከጀልባው ወጥቶ ወደ ኢየሱስ ለመሄድ፣ በውሃው ላይ ተራመደ። **30** ነገር ግን ጴጥሮስ ነፋሱን አይቶ በመፍራት፣ መስጠም በጀመረ ጊዜ ፣ “ጌታ ሆይ፣ አድነኝ” ብሎ ጮኸ። **31** ኢየሱስም ያኔውኑ እጁን ዘርግቶ ጴጥሮስን ያዘውና፣ “አንተ እምነት የጎደለህ፣ ለምን ትጠራጠራለህ?” አለው። **32** ከዚያም ኢየሱስና ጴጥሮስ ወደ ጀልባው በገቡ ጊዜ፣ ነፋሱ መንፈሱን አቆመ። **33** በጀልባው ውስጥ የነበሩት ደቀ መዛሙርትም ኢየሱስን፣ “አንተ በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነህ” ብለው ሰገዱለት። **34** ከተሻገሩም በኋላ፣ ጌንሳሬጥ ወደ ተባለ አገር መጡ። **35** በዚያም ስፍራ የነበሩ ሰዎች ኢየሱስ መሆኑን ባወቁ ጊዜ፣ በአካባቢው ወዳለ ስፍራ ሁሉ መልእክት ላኩና፣ የታመመውን ሁሉ ወደ እርሱ አመጡ። **36** የልብሱን ጫፍ ብቻ ለመንካት ለመኑት፣ የነኩትም ሁሉ ተፈወሱ።

Matthew 14:1

ማቴዎስ **14**:**1**-**2**
በዚያ ጊዜ "በዚያ ዘመን" ወይም “ኢየሱስ በገሊላ እያገለገለ ሳለ" የአራተኛው ክፍል ገዥ የሆነው ሄሮዶስ ሄሮድ አንቲፓስ የእስራኤልን አንድ አረተኛ ግዛት ይገዛ ነበር (ተመልከት) ስለኢየሱስ ዝና ሰማ "ሰዎች ስኢየሱስ የሚሉትን ሰማ" ወይም "ስለ ኢየሱስ ዝና ሰማ" እንዲህም አለ "ሄሮዶስ እንዲህ አለ"

Matthew 14:3

ማቴዎስ **14**:**3**-**5**
ሄሮዶስ ዮሐንስን አስይዞ አሳስሮት በወህኒ አኑሮት ነበር ይህ የሚሆነው ሄሮዶስ ሌሎች ሰዎችን በእርሱ ፈንታ ሄደው ዮሐንስን እንዲይዙት በማዘዝ ነው (ተመልከት) ሄሮዶስ የሐንስን አስያዘው "ሄሮዶስ የሐንስ እንድታሠሰር አደረገ" ዮሐንስ፦ እርስዋ ለአንተ ትሆን ዘንድ አልተፈቀደም ይለው ነበርና። “እርሷን ምስትህ አድርገህ መውሰድ ለአንድ አልተፈቀደም ስላለው ነው (ተመልከት) ዮሐንስ ስላለው ነው "ዮሐንስ ይህንን ደጋግሞ ለሄሮዶስ ይለው ነበር" በሕግ አክተፈቀደም ሄሮዶስ ሄሮዲያስን ስያገባ ፊልፕ በሕይወት ነበር።

Matthew 14:6

ማቴዎስ **14**:**6**-**7**
በዚህ መካከል የልደት ክብረ በዓል ለማክበር የመጡ እንግዶች መካከል (ተመልከት)

Matthew 14:8

ማቴዎስ **14**:**8**-**9**
የእናቷን ምክር ተከትላ ለተርጓሚዎች ምክር፡ “እናትየው ከመከረቻት በኋላ" (ተመልከት) ተምክራ "መመሪያ መሠረት" እንዲህ አለች “እርሷ” የሚለው ተውላጠ ስም የሚያመለክተው የሄሮዲስን ሴት ልጅ ነው። ሳህን ትልቅ ሳህን ንጉሡ በጥያቄዋ እጅግ በጣም ተበሳጨ "ጥያቄዋ ንጉሡን አበሳጨው" (ተመልከት) ንጉሥ የአራተኛ ክፍል ገዥው ሄሮዶስ አንቲፓስ (MAT 14:1).

Matthew 14:10

ማቴዎስ **14**: **10**-**12**
ጭንቅላቱን በሳህን አድርገው ለልጅቷ ሰጧት "የሆነ ሰው ጭንቅላቱን በሳህን አድርጎ ለልጅቷ ሰጣት" (ተመልከት) ሳህን ትልቅ ሳህን ሴት ልጅ ያላገባች ልጅን የሚያመለክት ቃልን ተጠቀም። ደቀ መዛሙርቱ "የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት" ሬሳውን "በድኑን" ወደ ኢየሱስ ሄደው ነገሩት "የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ወደ ኢየሱስ ዘንድ ሄደው መጥመቁ ዮሐንስ ላይ ምን እንዳደረጉበት ለኢየሱስ ነገሩት (ተመልከት

Matthew 14:13

ማቴዎስ **14**: **13**-**14**
ይህንን ስሰማ "በዮሐንስ ላይ የሆነውን ነገር ስሰማ" ወይም "ስለ ዮሐንስ የተነገረውን ነገር ስሰማ” (ተመልከት) ፈቀቅ አለ ከሕዝቡ ተለይቶ ሄደ ከዚያ "ከዚያ ሥፍራ" ሕዝቡን ይህንን ሰሰሙ “ሕዝቡን ወዴት እንደሄደ በሰሙ ጊዜ” ወይም “እንደሄደ ሕዝቡ በሰሙ ጊዜ” ሕዝቡ "ሕዝቡ" ወይም “የተሰበሰበው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሕዝብ” ኢየሱስ ወደ እነርሱ መጥቶ የተሰበሰበውን ብዙ ሕዝብ ተመለከተ "ኢየሱስ ወደ ባሕሩ ዳርጃ በመጣ ጊዜ ብዙ ሕዝብ ተሰብስቦ ተመለከተ”

Matthew 14:15

ማቴዎስ **14**፡**15**-**15**
ደቀ መዛሙርቱም ወደ እርሱ መጥተው "የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ወደ እርሱ መጥተው"

Matthew 14:16

ማቴዎስ **14**፡ **16**-**18**
አያስፈልጋቸውም "ሕዝቡ . . . አያስፈልጋቸውም" እናንተ ስጧቸው “አናንተ” የሚለው ቃል የብዙ ቁጥር አመልካች ሲሆን የሚያመለክተውም ደቀ መዛሙርቱን ነው። (en:ta:vol1:translate: ተመልከት) እነርሱም እንዲህ አሉት "ደቀ መዛርቱ ለኢየሱስ እንዲህ አሉት" አምስት ዳቦ እና ሁለት ዓሣ "5 ዳቦዎች እና 2 ዓሣዎች (ተመልከት) እነርሱን ወደ እኔ አምጧቸው "ዳቦዎቹን እና ዓሣዎቹን ወደ እኔ አምጧቸው"

Matthew 14:19

ማቴዎስ **14**፡ **19**-**21**
ተቀመጡ ወይም “ይረፉ”። በዚህ ሥፍራ ላይ በእናንተ ባሕል ውስጥ ሰዎች ምግብ ለመመገብ የሚቀመጡበትን መንገድ የሚገልጽ ቃልን ተጠቀሙ። ወሰደ "በእጆቹ ይዞ።" ሰርቋቸው አይደለም። (en:ta:vol1:translate: ተመልከት) ዳቦዎች "ዳቦዎች” ወይም “ያላቸውን ሁሉ ዳቦ" ወደ ሰማይ ተመለከተ ይህ ማለት 1) “ወደላይ እየተመለከተ” ወይም 2) “ወደላይ ከተመለከተ በኋላ”። እነርሱም ወደ ላይ ተመለከቱ "ደቀ መዛሙርቱም ደወ እርሱ ተሰበሰቡ " የበሉትም ሰዎች ዳቦውን እና ዓሣውን የበሉት ሰዎች" (ተመልከት)

Matthew 14:22

ማቴዎስ **14**፡ **22**-**24**
ወዲያውም "ኢየሱስ አምስት ሺህ ሰዎችን ከመገበ በኋላ" በመሸም ጊዜ "ወደ ምሸት ላይ” ወይም “በጨለመ ጊዜ”" ከማዕበሉ የተነሳ ልቆጣጠሯት አልቻሉም "ማዕበሉ ታንኳይቱን ያናውጣት ነበር"

Matthew 14:25

ማቴዎስ **14**፡ **25**-**27**
በባሕሩ ላይ እየተራመደ "በውሃው ላይ እየተራመደ" በጣም ፈሩ "ደቀ መዛሙርቱ በጣም ፈሩthe disciples were very afraid" ምትሃት የሞተ ሰውን ትቶ የሄደ መንፈስ መሰላቸው

Matthew 14:28

ማቴዎስ **14**፡**28**-**30**
ጴጥሮስ እንዲህ ሲል መለሰ "ጴጥሮስ ለኢየሱስ እንዲህ ሲል መለሰ"

Matthew 14:31

ማቴዎስ **14**፡ **31**-**33**
አንተ እምነት የጎደለህ በ MAT 6:30 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ስለምን ትጠራጠራለህ? "ልትጠራጠር አይገባህም" (ተመልከት) የእግዚአብሔር ልጅ የይህ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት የሚገልጽ በጣም አስፈላጊ የሆነ የማዕረግ ስም ነው። (ተመልከት)

Matthew 14:34

ማቴዎስ **14**፡**34**-**36**
በተሻገሩም ጊዜ "ኢየሱስ እና ደቀ መዛሙርቱ ባሕሩን ከተሸገሩ በኋላ" ጌንሴሬጥ ከገሊላ ባሕር ማዶ በሰሜን ደቡብ በኩል የሚትገኝ ትንሽ መንደር ናት (ተመልከት) መልዕከት ላኩ "በዚያ አከባቢ የሚኖሩ ሰዎች መልዕክት ላኩ” ለመኑት "የታመሙት ሰዎች ለመኑት" ልብስ "የለበሰው ልብስ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 15

1 ከዚያም አንዳንድ ፈሪሳውያንና የአይሁድ የሕግ መምህራን ከኢየሩሳሌም ኢየሱስን ለማነጋገር መጥተው እንዲህ አሉ፤ 2 "ደቀ መዛሙርትህ የሽማግሌዎችን
ወግ የሚጥሱት ለምንድነው? ምግብ ከመብላታቸው በፊት እንደ ወጉ እጃቸውን አይታጠቡምና።" 3 ኢየሱስም መለሰና፣ "እናንተስ ስለ ወጋችሁ ስትሉ ለምን
የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትተላለፋላችሁ?" አላቸው። 4 እግዚአብሔር፣ ‹አባትህንና እናትህን አክብር፣› ‹ስለ አባቱ ወይም ስለ እናቱ ክፉ የሚናገር በርግጥ
ይሞታል› ብሏልና። 5 እናንተ ግን፣ "አባቱን ወይም እናቱን፣ 'ከእኔ የተቀበላችሁት ማንኛውም እርዳታ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ስጦታ ነው ትላላችሁ።' 6 ያ ሰው
አባቱን ማክበር አያስፈልገውም። ስለ ወጋችሁ ስትሉ የእግዚአብሔርን ቃል ትሽራላችሁ። 7 እናንተ ግብዞች፣ ኢሳይያስ ስለ እናንተ፣ 8 'ይህ ሕዝብ በከንፈሩ
ያከብረኛል፤ ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነው፤ 9 የሰዎችን ትእዛዝ እንደ ሕግ በመቊጠር የራሳቸውን ትምህርት ስለሚያስተምሩ፣ እኔን በከንቱ ያመልኩኛል›› ብሎ
ትንቢት በመናገሩ መልካም አድርጓል። 10 ከዚያ ሕዝቡን ወደ ራሱ ጠርቶ፣ "አድምጡ አስተውሉም፦ 11 ወደ አፍ የሚገባ ሰውን ምንም አያረክስም። ይልቁንም
ከአፍ የሚወጣው ሰውን የሚያረክስ ነው" አላቸው። 12 ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ መጥተው ኢየሱስን፣ ‹‹ፈሪሳውያን ይህን ቃል ሲሰሙ እንደ ተሰናከሉ
ዐወቀሃል?›› አሉት። 13 ኢየሱስም መለሰና፣ ‹‹አባቴ ያልተከለው ተክል ሁሉ ይነቀላል፤ 14 እነርሱን ተዉአቸው፤ ዕይነ ስውር መሪዎች ናቸው። አንድ ዕይነ ስውር
ሌላውን ዕይነ ስውር ቢመራው ሁለቱም ተያይዘው ጕድጓድ ውስጥ ይወድቃሉ።›› 15 ጴጥሮስ መልሶ ኢየሱስን፣ ‹‹ይህን ምሳሌ አብራራልን›› አለው። 16
ኢየሱስ፣ ‹‹እናንተ ደግሞ አሁንም አታስተውሉምን? 17 ወደ አፍ የሚገባው ሁሉ ወደ ሆድ እንደሚሄድና ከዚያም ዕይነ ምድር ሆኖ ወደ ውጭ እንደሚጣል
አታስተውሉምን? 18 ዳሩ ግን ከአፍ የሚወጣ ከልብ ይወጣል። እነዚህ ነገሮች ሰውን ያረክሳሉ። 19 ከልብ ክፉ ዐሳብ፣ ነፍስ መግደል፣ ምንዝርና፣ ዝሙት፣
ስርቆት፣ የሐሰት ምስክርነትና ስድብ ይወጣሉ፤ 20 ሰውን የሚያረክሱት እነዚህ ናቸው። ነገር ግን ባልታጠበ እጅ መብላት ሰውን አያረክስም።" 21 ቀጥሎም
ኢየሱስ ከዚያ ወደ ጢሮስና ወደ ሲዶና ከተሞች አካባቢ ሄደ። 22 እነሆም፣ አንዲት ከነዓናዊት ሴት ከዚያ አካባቢ ወጣችና ጮኽ ብላ እንዲህ አለች፣ ‹‹የዳዊት
ልጅ፣ ጌታ ሆይ፣ ማረኝ። ልጄ በጋኔን ተይዛ በጣም እየተሠቃየች ነው።›› 23 ኢየሱስ ግን አንድም ቃል አልመለሰላትም። ደቀ መዛሙርቱ መጥተው፣ ‹‹ይህች
ሴት ትጮኽብናለችና ሸኛት›› ብለው ለመኑት። 24 ነገር ግን ኢየሱስ መልሶ፣ ‹‹እንደ በግ ወደ ጠፉት የእስራኤል ቤት ሰዎች ካልሆነ በቀር ወደ ማንም
አልተላክሁም›› አለ። 25 ነገር ግን ሴቲቱ "ጌታ ሆይ፣ እርዳኝ" በማለት መጥታ በፊቱ ሰገደች። 26 ኢየሱስ መልሶ፣ "የልጆችን እንጀራ ወስዶ ለቡችሎች
መጣል ትክክል አይደለም" አለ። 27 ሴቲቱ፣ "አዎን፣ ጌታ ሆይ፣ ቡችሎችም እኮ ከጌቶቻቸው ማዕድ ከሚወድቀው የተወሰነውን ትርፍራፊ ይበላሉ" አለች። 28
ከዚያም ኢየሱስ መልሶ፣ "አንቺ ሴት እምነትሽ ታላቅ ነው፤ ልክ እንደ ተመኘሽው ይሁንልሽ" አላት። ልጂም በዚያች ሰዓት ተፈወሰች። 29 ኢየሱስ ከዚያ ቦታ ወደ
ገሊላ ባሕር አቅራቢያ ሄደ። ከዚያም ወደ አንድ ኮረብታ ወጥቶ በዚያ ተቀመጠ። 30 ብዙ ሕዝብም ወደ እርሱ መጡ፤ አንካሶችን፣ ዕይነ ስውሮችን፣ ዲዳዎችንና
ጕንድሾችን፣ እንዲሁም ሌሎች ታመው የነበሩ ብዙዎችን ይዘው መጡ። በኢየሱስ እግር አጠገብም አስቀመጧቸው፤ እርሱም ፈወሳቸው። 31 ስለዚህ ሕዝቡ
ዲዳዎች ሲናገሩ፣ ጕንድሾች ሲፈወሱ፣ አንካሶች ሲራመዱ፣ ዕይነ ስውሮችም ሲያዩ አይተው ተደነቁ። የእስራኤልንም አምላክ አመሰገኑ። 32 ኢየሱስ ደቀ
መዛሙርቱን ወደ ራሱ ጠርቶ፣ "ለሕዝቡ አዝንላቸዋለሁ፤ ምክንያቱም ከእኔ ጋር ሦስት ቀን ቈይተዋል፣ የሚበሉትም የላቸውም። በመንገድ ላይ ዝለው
እንዳይወድቁ ሳይበሉ ዝም ብዬ አላሰናብታቸውም" አለ። 33 ደቀ መዛሙርቱ፣ "በዚህ በረሓ ይህን የሚያህል ብዙ ሕዝብ የሚያጠግብ እንጀራ ከየት
እናገኛለን?" አሉት። 34 ኢየሱስ፣ "ስንት እንጀራ አላችሁ?" አላቸው። "ሰባት እንጀራና ጥቂት ትናንሽ ዐሣ አለ" አሉት። 35 ከዚያም ኢየሱስ ሕዝቡን መሬት ላይ
እንዲቀመጡ አዘዛቸው። 36 ኢየሱስ ሰባቱን እንጀራና ዐሣዎቹን ይዞ ካመሰገነ በኋላ እንጀራውን ቈርሶ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸው። ደቀ መዛሙርቱም ለሕዝቡ
ሰጧቸው። 37 ሕዝቡ ሁሉ በሉና ጠገቡ። ትርፍራፊውንም ሰበሰቡ፤ ትርፍራፊውም ሰባት ቅርጫት ሙሉ ነበር። 38 የበሉትም ከሴቶችና ከልጆች በቀር አራት
ሺህ ወንዶች ነበሩ። 39 ከዚያም ኢየሱስ ሕዝቡን አሰናበተና በጀልባም ገብቶ መጌዶን ወደ ተባለ ክፍለ አገር ሄደ።

Matthew 15:1

ማቴዎስ **15**:**1**-**3**
የሽማግሌዎችን ወግ ይተላለፋሉ "በትልልቅ የሃይማኖት መሪዎች የተሰጡትን ደንቦች አይጠብቁም" እጃቸውን አይጣጠቡም "በሕጉ መሠረት የተሰጠውን የእጅ መታጠብ ስርዓትን በመከተል እጃቸውን አይታጠቡም (ተመልከት)

Matthew 15:4

ማቴዎስ **15**:**4**-**6**
ማንም "ዬትኛውም ሰው" ወይም "ማንም ቢሆን" አባቱን ሊያከብር የማይወድ አባቱን በመንከባከብ ለእርሱ ያለውን አክብሮት ለማሳየት የማይፈልግ ሰው ለወጋችሁ ስትሉ የእግዚአብሔርን ቃል አፍርሳችሁታል ለተርጓሚዎች ምክር: “ስለ ወጋችሁም የእግዚአብሔርን ቃል ሻራችሁ።”

Matthew 15:7

ማቴዎስ **15**: **7**-**9**
ኢሳያስ ስለ እናንተ ምን አለ ለተርጓሚዎች ምክር: "ኢሳያስ በዚህ ትንቢት ላይ የተናገረው እውነት ነው” እንዲህ ሲል ለተርጓሚዎች ምክር: “እግዚአብሔር የተናገረውን ስናገር" ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል ኤቲ: “ይህ ሕዝብ ስለእኔ ትክክል የሆኑ ነገሮችን ይናገራል” ልቡ ግን ከእኔ ርቋል ለተርጓሚዎች ምክር: “ይሁን እንጂ በእርግጥ አይወዱኝ” (en:ta:vol1:translate: ተመልከት) እንዲሁ በከንቱ ያመልኩኛል ለተርጓሚዎች ምክር: “አምልኮአቸው ለእኔ ምንም አይደለም” ወይም “እኔን ያመለኩ ያስመስላሉ” የሰው ስርዓት "ሰዎች በሰሩት ስርዓት"

Matthew 15:10

ማቴዎስ **15**:**10**-**11**
ሰሙ አስተዋሉም ኢየሱስ ከዚህ ቀጥሎ ላለው ዓረፍተ ነገር አጽኖት በመስጠት ተናግሯል

Matthew 15:12

ማቴዎስ **15**:**12**-**14**
ይህን ቃል የሰሙ ፈሪሳዊያን እንደ ተሰናከሉብህ አወቅህን? ለተሯሚዎች ምክር: “ይህ ዓረፍተ ነገር ፈሪሳዊያንን አበሳጭቷቸዋል?" ወይም "ይህ ዓረፍተ ነገር ፈሪሳዊያንን አሰናክለሏልን?" (ተመልከት)

Matthew 15:15

ማቴዎስ **15**:**15**-**17**
ለእኛ "ለእኛ ለደቀ መዛሙርትህ" ያለፋል "ይወጣል" እዳሪ ሰዎች የሆድ እዳሪያቸውን የሚያስወግዱበት ሥፍራን በጨዋ ቋንቋ ለመግለጽ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Matthew 15:18

ማቴዎስ **15**:**18**-**20**
ከአፍ የሚወጣ "አንድ ሰው የሚናገረው ቃል" ከልብ ይወጣል "ከሰውዬው እውነተኛ ስሜት እና ሀሳቦች ውጤት ናቸው” መግደል ንጹሕ ሰውን መግደል ስድብ "ሌላ ሰውን የሚያሰናክል ነገር ማነገር" ያልታጠበ እጅ ሥርዓቱን በጠበቀ መልኩ ያልታጠበ እጅ

Matthew 15:21

ማቴዎስ **15**: **21**-**23**
ከነናዊት ሴት ከዚያ አገር ሴትቱ ሀገሯን ትታ ወደ እስራኤል በመምጣት ኢየሱስን አገኘችው ከነናዊት ሴት ከነዓን የሚባል ሀገር አሁን የለም። “ከነዓን ተባለ ሀገር ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች መካከል የሆነች አንዲት ሴት" ሴት ልጄን ጋኔን ክፉኛ ይዞአታል "ሴት ልጄን ጋኔን በጣም እያሰቃያት ነው” (ተመልከት) ምንም ቃል አልመለሰላትም "ዝም አላት"

Matthew 15:24

ማቴዎስ **15**: **24**-**26**
ወደ እርሱ መጣች "ከነዓናዊቷ ሴት ወደ እርሱ መጣች" የልጆችን እንጀራ ...ለቡችሎች "በትክክለኛው መንገድ ለአይሁዶች የሆነውን ነገር . . . ለአሕዛብ" (ተመልከት)

Matthew 15:27

ማቴዎስ **15**:**27**-**28**
ቡችሎች እንኳ ከጌቶቻቸው ማዕድ የተራረፈውን ይበላሉ አሕዛብ ከአይሁዳዊያን የተራረፈው መልካም ነገር ልያገኙ ይገባል። (ተመልከት) ሴት ልጇ ተፈወሰች "ኢየሱስ ሴት ልጇን ፈወሰላት” ወይም "ኢየሱስ የሴት ልጇን ጤና መለሰላት” (ተመልከት) በዚያን ጊዜ "በተመሳሳይ ሰዓት" ወይም "ወዲያው"

Matthew 15:29

ማቴዎስ **15**: **29**- **31**
ሸባ፣ ዐይነ ስውር፣ ዲዳ እና መሄድ የማይችል "መራመድ የማይችሉ ሰዎች፣ ማየት የማይችሉ አንዳንዶች፣ መናገር የማይችሉ፣ እግራው እና እጃቸው የማይሰራ ሰዎች”። አንዳንድ ጥንታዊያን ቅጅዎች እነዚህን ቃላት በተለያየ ቅደም ተከተል አስቀምጠውታል። በኢየሱስ እግሪ ፊት አስቀመጡ "ሕዝቡ የታመመውን ሰው በኢየሱስ ፊት አስቀመጡ"

Matthew 15:32

ማቴዎስ **15**:**32**-**35**
ዝለው እንዳይወድቁ አማራጭ ትርጉሞች 1) “ራሳቸነውን እንዳይስቱ በመፍራት” ወይም 2) “ሊደክማቸው ይችላል ከሚል ስጋት” (ተመልከት) ተቀመጡ ጠረጴሳ ባሌለበት ሁኔታ ሰዎች ምግብ ለመመገብ በባሕላችሁ የሚቀመጡበትን መንገድ የሚገልጽ ቃልን ተጠቀም።

Matthew 15:36

ማቴዎስ **15**:**36**-**39**
ወሰደ "ኢየሱስ ወስዶ” ። ይህንን በ MAT 14:19 በተረጎምከው መሠረት ተርጉመው። ስጧቸው "ዳቦዎቹን እና ዓሳዎቹን ስጧቸው" ለቀሟአቸው "ደቀ መዛሙርቱ ለቀሙ" የተመገቡት "የበሉት ሰዎች" አከባቢ "የአንድ ሀገር አንዱ ክፍል" መጌዶል አንዳንድ ጊዜ “ማጌዳላ” ተብሎ ይጠራል (ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 16

1 ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያንም መጥተው ከሰማይ ምልክት እንዲያሳያቸው በመጠየቅ ኢየሱስን ፈተኑት። 2 ነገር ግን ኢየሱስ መልሶ እንዲህ አላቸው፣ "በመሸ
ጊዜ ሰማዩ ቀልቷልና ዝናብ አይኖርም ትላላችሁ 3 በነጋ ጊዜም፣ ‹ዛሬ ሰማዩ ስለ ጠቈረ ይዘንባል› ትላላችሁ፤ የዘመኑን ምልክት ግን መለየት አትችሉም። 4
ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻልኔ፤ ነገር ግን ከነቢዩ ከዮናስ ምልክት በቀር ሌላ ምልክት አይሰጠውም።" ከዚያም ኢየሱስ ትቶአቸው ሄደ። 5 ደቀ
መዛሙርቱ ወደ ማዶ ተሻገሩ፤ እንጀራ መያዝን ግን ረሱ። 6 ኢየሱስ፣ "ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን እርሾ ተጠንቀቁ፣ ተጠበቁም" አላቸው። 7 ደቀ መዛሙርቱ፣
"እንጀራ ስላልያዝን ነው" ብለው እርስ በርሳቸው ተነጋገሩ። 8 ኢየሱስ ይህን ዐውቆ፣ "እናንተ እምነተ ጎደሎዎች፣ እንጀራ ስላልያዝን ነው ብላችሁ ስለ ምን እርስ
በርሳችሁ ትነጋገራላችሁ?" 9 ዐምስት እንጀራ ለዐምስቱ ሺህ እንደ በቃና ስንት ቅርጫት እንደ ሰበሰባችሁ አሁንም አታስተውሉም ወይም አታስታውሱም? 10
ወይም ደግሞ ሰባቱ እንጀራ ለአራቱ ሺህ እንደ በቃና ስንት ቅርጫት እንዳነሣችሁስ አታስታውሱምን? 11 እኔ የነገርኋችሁ ስለ እንጀራ እንዳልነበረ እንዴት ነው
የማታስተውሉት? ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያ እርሾ ተጠንቀቁ፣ ተጠበቁም።" 12 ከዚያም እርሱ ሲነግራቸው የነበረው ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን ትምህርት
እንዲጠበቁ እንጂ፣ ስለ እንጀራ እርሾ እንዳልነበረ ተረዱ። 13 ኢየሱስም ወደ ቂሣርያ ፊልጶስ ክልል በመጣ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን፣ "ሰዎች የሰውን ልጅ ማን
ነው ይላሉ?" በማለት ጠየቃቸው። 14 እነርሱ፣ እንዲህ አሉ፤ "አንዳንዶች መጥምቁ ዮሐንስ፣ ሌሎች ኤልያስ፣ የቀሩትም ኤርምያስ፣ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው
ይላሉ።" 15 "እናንተስ እኔን ማን ትሉኛላችሁ?" አላቸው። 16 ስምዖን ጴጥሮስ፣ "አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ" በማለት መልስ ሰጠ። 17
ኢየሱስ መልሶ እንዲህ አለው፣ "የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፣ አንተ የተባረክህ ነህ፤ ይህን የገለጠልህ የሰማዩ አባቴ ነው እንጂ፣ ሥጋና ደም አይደለም። 18 ደግሞም
አንተ ጴጥሮስ ነህም እላለሁ፤ በዚህም አለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፤ የገሃነም ደጆችም አያሸንፏትም። 19 እኔ የመንግሥተ ሰማያትን መክፈቻዎች
እሰጥሃለሁ። በምድር የምታስረው ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድር የምትፈታውም ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል።›› 20 ከዚያም ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ
መሆኑን ለማንም እንዳይናገሩ ደቀ መዛሙርቱን አዘዛቸው። 21 ከዚያን ጊዜ አንሥቶ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ፣ በሽማግሌዎችና በካህናት አለቆች፣
በፈሪሳውያንና በሕግ መምህራንም እጅ ብዙ መከራ መቀበልና መገደል፣ በሦስተኛውም ቀን መነሣት እንዳለበት ለደቀ መዛሙርቱ ይነግራቸው ጀመር። 22
ከዚያም ጴጥሮስ ኢየሱስን ለብቻው ገለል አድርጎ፣ "ጌታ ሆይ፣ ይህ ከአንተ ይራቅ፤ ይህም ከቶ አይሁንብህ" በማለት ገሠጸው። 23 ኢየሱስ ግን ዞር ብሎ
ጴጥሮስን፣ "ከፊቴ ዞር በል፣ ሰይጣን! ስለ ሰው እንጂ ስለ እግዚአብሔር ነገር ደንታ የለህምና አንተ ለእኔ እንቅፋት ነህ" አለው። 24 ከዚያም በኋላ ኢየሱስ ደቀ
መዛሙርቱን እንዲህ አላቸው፤ "ሊከተለኝ የሚፈልግ ማንም ቢኖር፣ ራሱን መካድ፣ የራሱን መስቀል መሸከምና እኔን መከተል አለበት። 25 ሕይወቱን ለማዳን
የሚፈልግ ሁሉ ያጣዋል፤ ስለ እኔ ሕይወቱን የሚያጣ ግን ያገኘዋል። 26 ሰው ሙሉውን ዓለም የራሱ ቢያደርግ ሕይወቱን ግን ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል?
ሰው በሕይወቱ ፈንታ ምን መስጠት ይችላል? 27 የሰው ልጅ በአባቱ ክብር ከመላእክቱ ጋር ይመጣልና። ከዚያም ለእያንዳንዱ ሰው እንደ ሥራው ይከፍለዋል።
28 እውነት እላችኋለሁ፤ እዚህ ከቆማችሁት መካከል የሰው ልጅ በመንግሥቱ ሲመጣ እስኪያዩ ድረስ ሞትን የማይቀምሱ አንዳንዶች አሉ።"

Matthew 16:1

ማቴዎስ **16**፡**1**-**2**
ሰማይ . . . ሰማይ የአይሁድ መሪዎች ከእግዚአብሔር ዘንድ ምልክትን ይሹ ነበር ይሁን እንጂ ኢየሱስ ማየት ወደሚችሉት ሰማይ ይመለከቱ ዘንድ ነገራቸው። አንባቢዎቹ የትርጉም ልዩነቱን መረዳት የሚችሉ ከሆነ ብቻ ለእግዚአብሔር ማደሪያም እንዲሁም ለሰማይ ከተቻለ አንድ ቃል ተጠቀም። (ተመልከት) በመሸም ጊዜ ፀሐጥ በጠለቀች ጊዜ ጥሩ የአየር ሁኔታ ግልጽ እና ጥርት ያለ ሰማይ ነው ሰማዩ ቀልቷል ሰማዩ ብርሃማ እና ከፀሐይ መትለቅ ጋር ተያይዞ ቀላልቷል

Matthew 16:3

ማቴዎስ **16**፡**3**-**4**
የአየር ጸባዩ ጥሩ አይደለም "ዳመናማ እና ጭጋጋማ ነው" ጨልሟል "ጨለማ እና የሚያስፈራ ነው" ምንም ዓይነት ምልክት አይሰጣችሁም ለተርጓሚዎች ምክር፡ “ለእናነት ምንም ምልክት እግዚአብሔር አይሰጣችሁም (en:ta:vol2:translate: እና ተመልከት)

Matthew 16:5

ማቴዎስ **16**፡**5**-**8**
እርሾ ክፉ ሀሳቦች እና ስህተት ትምህርት (ተመልከት) ምክንያት "መከራከር" ወይም “መጣላት"

Matthew 16:9

ማቴዎስ **16**፡**9**-**10**
ለአምስቱ ሺህ አምስቱ እንጀራ፥ ስንት መሶብም እንዳነሣችሁ ትዝ አይላችሁምን? ወይስ ለአራቱ ሺህ ሰባቱ እንጀራ፥ ስንት ቅርጫትም እንዳነሣችሁ ትዝ አይላችሁምን? ኢየሱስ እየገሰጻቸው ነው። ለተርጓሚዎች ምክር: “በአምስት ዳቦ 5000 ሰዎች የተመገቡበት እና ምን ያህል ቅርጫት እንደሰበሰባችሁ መረዳት እና ማስታወስ ነበረባችሁ! ከዚህ በተጨማሪ በ7 ዳቦዎችን 4000 ሰዎች ስትመግቡ ምን ያህል ሰበሰባችሁ! (and ተመልከት)

Matthew 16:11

ማቴዎስ **16**፡**11**-**12**
ስለ እንጀራ እንዳልተናገርኋችሁ እንዴት አታስተውሉምን? "በእርግጥ ስለ እንጀራ እያወራሁ እንዳልሆነ መረዳት ነበረባችሁ።” (UDB) (ተመልከት) እርሾ ክፉ ሀሳቦች እና የተሳሳቱ ትምህርቶች (ተመልከት) እነርሱ . . . እነርሱ “ደቀ መዛሙርቱ”

Matthew 16:13

ማቴዎስ **16**፡**13**-**16**
ነገር ግን እናንተ እኔ ማን እንደሆኑ ትለላላችሁ? "እናንተን ግል ልጠይቃች፡ እኔ ማን እንደሆኑን ትላላችሁ?"

Matthew 16:17

ማቴዎስ **16**፡**17**-**18**
የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ "የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ " (UDB) ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህም "ይህንን ዬትኛው የሰው ልጅ አልገለጠልህም” (ተመልከት)። “አንተ ክርስቶስ ፣ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ” የሚለው የጴጥሮስ ንግግር ወደ ጴጥሮስ የመጣው በማንም ሳይሆን በእግዚአብሔር በራሱ ነው፡ አባት ይህ በኢየሱስ እና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ግንኙነት በሚገባ የሚገልጽ በጣም ጠቃሚ የሆነ የማዕረግ ስም ነው። (ተመልከት) የገሃነም ደጆች አይችሏትም አማራጭ ትርጉሞች: 1) "የሞት ኃይል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ልቋቋማት አይችልም " ወይም 2) የጦር ሠራዊት አንድን ከተማ ሰብሮ እንደሚገባው ሁሉ የሞትን ኃይል ይሠባብራል። (ተመልከት)

Matthew 16:19

ማቴዎስ **16:19-20**
የመንግስተ ሰማያት ቁልፍ አገልጋይ ሰዎች ወደቤት ስገቡ ተቀበሎ እንደሚያገልግል ሁሉ ሰዎች የእግዚአብሔር ሕዝብ መሆን የሚችሉበትን መንገድ የመክፈት ክህሎት (ተመልከት) በምድር ያሠራችሁት . . . በሰማይ የተፈራ ይሆናል በሰማይ እንደሚሆነው ሁሉ ለሰዎች ይቅርታን መስጠት ወይም በእነርሱ ላይ መፍረድ (ተመልከት)

Matthew 16:21

ማቴዎስ **16:21-23**
ከዚያ ቀን ጀምሮ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እርሱ ክርስቶስ መሆኑን ለሌላ ለማንም እንዳይናገሩ ካዘዛቸው በኋላ እግዚአብሔር ለእርሱ ያለው እቅዱን ያካፍላቸው ጀመረ። anded his disciples not to tell anyone that he was the Christ, he began sharing God's plan for himself. እንደሚሞት ለተርጓሚዎች ምክር: “እንደሚገድሉት” (ተመልከት) በሦስተኛው ቀን በሕይወት እንደሚነሳ "በሦስተኛው ቀን እግዚአብሔር እንደገና ሕያው እንደሚያደርገው"

Matthew 16:24

ማቴዎስ **16:24-26**
ተከተለኝ "ደቀ መዝሙሬ ሁን" ራስህን ካድ "በራስህ ምኞች አትወሰድ" ወይም "የራስህን መሻት ተው" መስቀሉን ተሸከምና ተከተለኝ "መስቀሉን አንሳ፣ ተሸከም እና ከእኔ በኋላ ተከተል”፣ መከራን ለመቀበል እና ለክርስቶስ ለመሞት ፈቃደኛ ሁን (ተመልከት) የሚወድ ማንም ቢኖር "የሚፈልግ ማንም ቢኖር" ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ "በዓለም ያለውን ሁሉ ቢያተርፍ" ነፍሱን ግን ቢያጎድል "እርሱን ግን ቢጠፋ”

Matthew 16:27

ማቴዎስ **16: 27-28**
የሰው ልጅ . . . አባቱ ኢየሱስ እንደ “ሰው ልጅነቱ” እና “የእርሱ” ልጅ መሆኑን ስገልጽ በሥላሴ ውስጥ እንዳለ ሦስተኛ አካል ያሳያል ። ለተሯሚዎች ምክር: "እኔ፣ የሰው ልጅ . . . አባቴ” (ተመልከት) አባቱ ይህ በኢየሱስ እና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ግንኙነት በሚገባ የሚገልጽ በጣም ጠቃሚ የሆነ የማዕረግ ስም ነው። (ተመልከት) የሰው ልጅ በመንግስቱ እስኪመጣ ድረስ ሞትን አይቀምሱም "ከመሞታቸው በፊት የሰው ልጅ በመንግስቱ ስመጣ ያዩታል” ሞትን አይቀምሱም "ሞትን አያዩም" ወይም “አይሞቱም" የሰው ልጅ በመንግስቱ ሲመጣ ኢየሱስ ራሱን እንደ ሥላሴ ሦተኛ አካል እየጠራ ነው። ለተርጓሚዎች ምክር: “በመንግስቴ ሲመጣ እስኪያዩኝ ድረስ” (ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 17

1 ከስድስት ቀን በኋላ ኢየሱስ ጴጥሮስን፣ ዮሐንስን፣ ያዕቆብንና ወንድሙን ይዞ ብቻቸውን ወደ ረጅም ተራራ አወጣቸው። 2 በፊታቸውም መልኩ ተለወጠ፤ ፊቱ
እንደ ፀሐይ አበራ፤ ልብሱም እንደ ብርሃን አንጸባረቀ። 3 እነሆ፣ ሙሴና ኤልያስ ከእርሱ ጋር ሲነጋገሩ ታዩአቸው። 4 ጴጥሮስ መልሶ ኢየሱስን፣ "ጌታ ሆይ፣ እዚህ
መሆን ለእኛ መልካም ነው። ብትፈልግ እኔ እዚህ ሦስት ዳሶችን፦ አንድ ለአንተ፣ አንድ ለሙሴ፣ አንድ ለኤልያስ እሠራለሁ" አለው። 5 እርሱ ገና እየተናገረ እያለ፣
እነሆ፣ ብሩህ ደመና ጋረዳቸው። ከደመናውም፣ "በእርሱ እጅግ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት" የሚል ድምፅ ነበረ። 6 ደቀ መዛሙርቱ
ድምፁን በሰሙ ጊዜ ፈሩ፣ በግንባራቸውም ወደቁ። 7 ከዚያም ኢየሱስ መጥቶ ዳሰሳቸውና፣ ‹‹ተነሡ አትፍሩ›› አላቸው። 8 ከዚያም እነርሱ ቀና ብለው
ተመለከቱ፣ ነገር ግን ከኢየሱስ ብቻ በቀር ማንንም አላዩም። 9 ከተራራ ሲወርዱም ኢየሱስ፣ "የሰው ልጅ ከሙታን እስኪነሣ ድረስ ይህን ያያችሁትን ለማንም
አትንገሩ" ብሎ አዘዛቸው። 10 ደቀ መዛሙርቱ፣ "እንግዲያው የአይሁድ ሕግ መምህራን መጀመሪያ ኤልያስ መምጣት አለበት ለምን ይላሉ?" በማለት
ጠየቁት። 11 ኢየሱስ መልሶ እንዲህ አለ፤ "ኤልያስ በርግጥ ይመጣል፣ ሁሉንም ነገር ያስተካክላል። 12 ነገር ግን እላችኋለሁ፤ ኤልያስ አስቀድሞ መጥቷል፤
ነገር ግን አላወቁትም። በዚህ ፈንታ የፈለጉትን ነገር ሁሉ አደረጉበት። በተመሳሳይ መንገድ የሰው ልጅ በእነርሱ እጅ መከራ ይቀበላል።›› 13 በዚያን ጊዜ ደቀ
መዛሙርቱ የተናገራቸው ስለ መጥምቁ ዮሐንስ እንደ ነበረ ተረዱ። 14 ወደ ሕዝቡ በመጡ ጊዜ አንድ ሰው መጥቶ በፊቱ ተንበረከከ፤ እንዲህም አለው፤ 15
"ጌታ ሆይ፣ ልጄን ማረው፣ የሚጥል በሽታ ይዞት በጎይል ይሠቃያል፤ ብዙ ጊዜ በእሳት ወይም በውሃ ውስጥ ይጥለዋልና። 16 ወደ ደቀ መዛሙርትህ
አመጣሁት፤ ነገር ግን እነርሱ ሊፈውሱት አልቻሉም።› 17 ኢየሱስ መልሶ፣ "የማታምኑና ምግባረ ብልሹ ትውልድ፣ እስከ መቼ ድረስ ከእናንተ ጋር እቆያለሁ?
እስከ መቼስ እናንተን መታገሥ አለብኝ? እስቲ ወደ እኔ አምጡት" አለ። 18 ኢየሱስ ገሠጸው፤ ጋኔኑም ከእርሱ ወጣ፤ ልጁም ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ተፈወሰ። 19
ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ ኢየሱስ መጥተው፣ "እኛ ልናወጣው ያልቻልነው ለምንድን ነው?" አሉ። 20 ኢየሱስ፣ ‹‹በእምነታችሁ ማነስ ምክንያት፤
እውነት እላችኋለሁና፣ የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት እንኳ ቢኖራችሁ ይህን ተራራ ከዚህ ተነሥተህ ወደ ማዶ ሂድ ብትሉት ይሄዳል። ማድረግ የሚሳናችሁ
ምንም ነገር አይኖርም። 21[1]22 በገሊላ እያሉ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን፣ "የሰው ልጅ በሰዎች እጅ ተላልፎ ይሰጣል፤ 23 እነርሱም ይገድሉታል፤
በሦስተኛውም ቀን ይነሣል" አላቸው። ደቀ መዛሙርቱ በጣም ዐዘኑ። 24 ወደ ቅፍርናሆም በመጡ ጊዜ ግማሽ ሰቅል ቀረጥ የሰበሰቡ ሰዎች ወደ ጴጥሮስ
መጥተው፣ "መምህራችሁ ግማሽ ሰቅሉን ቀረጥ አይከፍልምን?" አሉ። 25 እርሱ፣ "አዎ" አለ። ጴጥሮስ ወደ ቤት በገባ ጊዜ ግን ኢየሱስ መጀመሪያ እርሱን
ተናገረው፤ "ስምዖን ሆይ፣ ምን ይመስልሃል? የምድር ነገሥታት ቀረጥ ወይም ግብር የሚሰበስቡት ከማን ነው? ከዜጎቻቸው ወይስ ከውጭ አገር ሰዎች?"
አለው። 26 ጴጥሮስ፣ "ከውጭ አገር ሰዎች" ባለ ጊዜ፣ ኢየሱስ እንዲህ አለው፤ "እንግዲያስ ዜጎቹ ከክፍያ ነጻ ናቸው። 27 ነገር ግን ቀረጥ ሰብሳቢዎቹን
ኃጢአት እንዲሠሩ እንዳናደርጋቸው ወደ ባሕር ሄደህ መንጠቆ ጣል፤ በመጀመሪያ የምታጠምደውን ዐሣ አፍ ስትከፍት አንድ ሰቅል ታገኛለህ፤ ያንን ወስደህ ስለ
እኔና ስለ አንተ ክፈል።››

Footnotes

17:21 [1]አንዳንድ የጥንት ቅጂዎች ቊጥር 21ን ያስቀሩታል። ነገር ግን የዚህ ዓይነቱ ጋኔን በጸምና በጸሎት ካልሆነ በቀር አይወጣም።

Matthew 17:1

ማቴዎስ **17**፡ **1**-**2**
ማቴዎስ 17፡ 1-2

ጴጥሮስ እና ያዕቆብ እንዲሁም ወንድሙ ዮሐንስ "ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ እና የያዕቆብ ወንድም ዮሐንስ” ተለወጠ "እግዚአብሔር የኢየሱስ መልክ ሙሉ ለሙሉ ለወጠው” ወይም (ተመልከት) ልብሶች "ልብስ" እንደ ብርሃን ያበሩ ነበር "እንደ ብርሃን ያንጸባርቁ ነበር" (ተመልከት)

Matthew 17:3

x
ማቴዎስ 17፡3-4

እነሆ ይህ ቃል ሰዎች ከዚህ በኋላ ለሚነገረው ነገር አጽኖት እንዲሰጡ የሚጨመር ቃል ነው። ለእነረሱ ከኢየሱስ ጋር ለነበሩት ደቀ መዛሙርት እንዲህ ሲል መለሰላቸው "አላቸው” ጴጥሮስ ለተጠየቀው ጥያቄ መልስ እየሰጠ አይደለም። በዚህ መሆን ለእኛ ይሻላል አማራጭ ትርጉሞች: 1) "እኛ ደቀ መዛሙርት በዚህ ከአንተ፣ ከሙሴ እና ከኤልያስ ጋር መሆናችን መልካም ነው” ወይም “አንተ፣ ሙሴ፣ ኤልያስ እና እኛ ደቀ መዛሙርትህ በአንድነት መሆናችን መልካም ነው።” (ተመልከት) መጠለያዎች አማራጭ ትርጉሞች 1) ሰዎች ለአምልኮ የሚመጧቸው ሥፍራዎች ወይም 2) ሰዎች በጊዜያዊነት ለመተኛ የሚዘጋጁቸው

Matthew 17:5

ማቴዎስ **17**፡ **5**-**8**
እነሆ ይህ ቃል ሰዎች ከዚህ በኋላ ለሚነገረው ነገር አጽኖት እንዲሰጡ የሚጨመር ቃል ነው። በግንባራቸው መሬት ላይ ተደፍተው "ደቀ መዛሙርተ በግንባራቸው በመሬት ላይ ተደፍተው”

Matthew 17:9

ማቴዎስ **17**፡**9**-**10**
እነርሱ . . . ሳለ "ኢየሱስ እና ደቀ መዛሙርቱ . . . ሰለ"

Matthew 17:11

ማቴዎስ **17**፡**11**-**13**
ሁሉን ነገር ያድሳል "ሁሉን ነገር በሥርዓት ያደርጋል" እነርሱ . . . እነርሱ . . . እነርሱ አማራጭ ትርጉሞች: 1) የአይሁድ መሪች ወይም 2) ሁሉም የአይሁድ ሕዝቦች

Matthew 17:14

x
የሚጥል በሽታ ያለበት ራሱን ስቶ የሚያደርገው ነገር የማያውቅ ሰው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Matthew 17:17

ማቴዎስ **17**:**17**-**18**
ከእናንተ ጋር እስከ መቼ እቆያለሁ? እስከ መቼስ እታገሣችኋለሁ? ኢየሱስ በሕዝቡ ደስተኛ አልነበረም። የተርጓሚዎች ምክር፡ ከእናንተ ጋር መሆን ደከመኝ! አለማመናችሁ እና ክፋታችሁ ሰለቸኝ!” (,ተመልከት)

Matthew 17:19

ማቴዎስ **17**:**19**-**21**
እኛ ተናጋሪው እንጂ ሰሚዎቹ አይደሉም (ተመልከት) እኛ ማውጣት ያቃተን ለምንድ ነው "ጋኔኑ እንዲወጣ ማድረግ ያቃጠን ለምንድ ነው” ማድረግ የማትችሉት ነገር የለለምNothing will be impossible for you to do "ምንም ነገር ማድረግ ትችላላችሁ” (ተመልከት)

Matthew 17:22

ማቴዎስ **17**:**22**-**23**
በዚያም ቆዩ "ደቀ መዛሙር እና ኢየሱስ በዚያ ቆዩ" የሰው ልጅ አሳልፎ ይሰጣል ለተርጓሚዎች ምክር: "የሆኑ ሰዎች የሰው ልጅን አሳልፈው ይሰጡታል” (ተመልከት) ይገድሉታ "ባለስልጣናት የሰወ ልጅን ይገድሉታል” ከሞት ይነሣል "እግዚብሔር ከሞት ያሥነሣዋል” ወይም “እንደገና ወደ ህይወት ይመላሳለር” (ተመልትከት)

Matthew 17:24

ማቴዎስ **17**:**24**-**25**
በ . . . ጊዜ እነርሱ ኢየሱስ እና ደቀ መዛሙርቱ በ . . ጊዜ

Matthew 17:26

ማቴዎስ **17**:**26**-**27**
ሥር ያሉ በአጋዘዙ ውስጥ ወይም በንጉሥ ሥር ያሉ አፉ "የዓሣ አፍ" ውሰዱ "አስታተር ውሰድና"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **18**

1 በዚያው ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየሱስ መጥተው፣ "በእግዚአብሔር መንግሥት ከሁሉ የሚበልጥ ማን ነው?" አሉ **2** ኢየሱስ አንድ ትንሽ ልጅ ጠርቶ በመካከላቸው አቆመው፤ **3** እንዲህም አለ፦ "እውነት እላችኋለሁ፤ ንስሐ ካልገባችሁና እንደ ልጆች ካልሆናችሁ በምንም መንገድ ወደ መንግሥተ ሰማያት አትገቡም። **4** ስለዚህ እንደዚህ ልጅ ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ሰው ሁሉ፣ እንዲሁ በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ ይበልጣል። **5** እንደዚህ ያለውን ልጅ በስሜ የሚቀበል ሁሉ እኔን ይቀበላል። **6** ነገር ግን በእኔ ከሚያምነው ከእነዚህ ልጆች አንዱን ኀጢአት እንዲሠራ የሚያደርግ ማንም፣ ትልቅ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቁ ባሕር ቢሰጥም ይሻለዋል። **7** የመሰናክል ምክንያት በመሆኗ ለዓለም ወዮላት! መሰናክል መምጣቱ ግድ ነው፤ ነገር ግን መሰናክሉን ለሚያመጣ ሰው ወዮለት! **8** እጅህ ወይም እግርህ ቢያሰናክልህ፣ ቈርጠህ ከአንተ ጣለው። ሁለት እጆች ወይም እግሮች ኖረውህ ወደ ዘላለም እሳት ከምትጣል የአካል ጉዳተኛ ወይም አንካሳ ሆነህ ወደ ሕይወት ብትገባ ይሻልሃል። **9** ዐይንህ እንድትሰናከል ቢያደርግህ፣ አውጥተህ ከአንተ ጣለው። ሁለት ዐይኖች ኖረውህ ወደ ዘላለም እሳት ከምትጣል፣ አንድ ዐይን ኖሮህ ወደ ሕይወት ብትገባ ይሻላል። **10** ከእነዚህ ከታናናሾች ማንኛውንም እንዳትንቁ ተጠንቀቁ። በሰማይ ያሉ መላእክታቸው በሰማይ ያለውን የአባቴን ፊት ሁልጊዜ ያያሉና። 11 (2) ብዙ ምንጮች፣ አንዳንድ የጥንት የሆኑ ቊ. 11ን ያስገባሉ። **11**[1]**12** ምን ይመስላችኋል? አንድ ሰው መቶ በጎች ቢኖሩት፣ ከእነርሱም አንዱ ቢጠፋ፣ ዘጠና ዘጠኙን በኮረብታው ጥግ ትቶ የጠፋውን ሊፈልግ አይሄድምን? **13** በሚያገኘውም ጊዜ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ካልጠፉት ከዘጠና ዘጠኙ ይልቅ በእርሱ ደስ ይለዋል። **14** በተመሳሳይ መንገድ ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱ እንዲጠፋ የሰማዩ አባታችሁ ፈቃድ አይደለም። **15** ወንድምህ ቢበድልህ፣ ሂድና አንተና እርሱ ብቻ ሆናችሁም ጥፋቱን አሳየው። ቢሰማህ፣ ወንድምህን የራስህ ታደርገዋለህ። **16** ባይሰማህ ግን፣ ቃል ሁሉ በሁለት ወይም በሦስት ምስክሮች ይጸናልና፣ ከአንተ ጋር አንድ ወይም ሁለት ተጨማሪ ወንድሞችን ይዘህ ሂድ። **17** እነርሱንም አልሰማም ቢል፣ ጉዳዩን ለቤተ ክርስቲያን ንገር። ቤተ ክርስቲያንን ደግሞ አልሰማም ቢል፣ እንደ አረመኔና እንደ ቀራጭ ቊጠረው። **18** እውነት እላችኋለሁ፣ በምድር የምታስሩት ነገር ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድር የምትፈቱትም ነገር ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል። **19** በተጨማሪም እላችኋለሁ፣ ከእናንተ ሁለቱ በምድር ስለሚለምኑት ስለ ማንኛውም ነገር ቢስማሙ፣ በሰማይ ያለው አባቴ ያደርግላቸዋል። **20** ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት ቦታ እዚያ በመካከላቸው እገኛለሁና። **21** ከዚያም ጴጥሮስ መጥቶ ኢየሱስን፣ ‹‹ጌታ ሆይ፣ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ይቅር ልበለው? እስከ ሰባት ጊዜ ነውን?›› አለው። **22** ኢየሱስም፣ ‹‹ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ፣ ሰባት ጊዜ አልልህም›› አለው። **23** ስለዚህ መንግሥተ ሰማያት ከአገልጋዮቹ ጋር ሒሳብ ሊተሳሰብ የፈለገ ንጉሥን ትመስላለች። **24** መተሳሰቡን እንደ ጀመረ፣ የዐሥር ሺህ መክሊት ዕዳ ያለበትን አገልጋይ ወደ እርሱ አመጡ። **25** ነገር ግን የሚከፍልበት መንገድ ስላልነበረው፣ ጌታው ከሚስቱና ከልጆቹ ጋር ያለውም ሁሉ ተሸጦ ክፍያው እንዲፈጸም አዘዘው። **26** ስለዚህ አገልጋዩ ወድቆ በፊቱ ተንበረከከ እንዲህም አለ፤ ‹ጌታዬ ሆይ፣ ታገሠኝ፣ ሁሉንም እከፍልሃለሁ።› **27** ስለዚህ የዚያ አገልጋይ ጌታ ስለ ራራለት፣ ተወው፤ ዕዳውንም ሠረዘለት። **28** ነገር ግን ያ አገልጋይ ወጥቶ አብረውት ከሚሠሩት አገልጋዮች መቶ ዲናር ያበደረውን አንዱን አገልጋይ አግኝቶ ያዘው፤ ጕሮሮውን አነቀውና፣ ‹‹ያለብህን ዕዳ ክፈለኝ›› አለው። **29** ነገር ግን የሥራ ባልደረባው፣ ‹‹ታገሠኝ፣ እከፍልሃለሁ›› በማለት ወድቆ ለመነው። **30** የመጀመሪያው አገልጋይ ግን አሻፈረኝ አለ፤ በዚህ ፈንታ ያለበትን ዕዳ እስኪከፍለው ድረስ በእስር ቤት ጣለው። **31** የሥራ ጓደኞቹ የሆኑት አገልጋዮች የሆነውን ነገር ባዩ ጊዜ፣ በጣም ተበሳጩ፤ መጥተውም ለጌታቸው የሆነውን ሁሉ ነገሩት። **32** ከዚያም የዚያ አገልጋይ ጌታ ጠራው፣ እንዲህም አለው፤ 'አንተ ክፉ አገልጋይ፣ ስለ ለመንኸኝ ያን ሁሉ ዕዳ ተውሁልህ። **33** እኔ አንተን እንደማርሁህ፣ የሥራ ባልደረባህ የሆነውን አገልጋይ ልትምረው አይገባህም ነበርን?' **34** ጌታው ተቈጥቶ ዕዳውን ሁሉ እስኪከፍል ድረስ ለሚያሠቃዩት አሳልፎ ሰጠው። **35** ስለዚህም ከእናንተ እያንዳንዱ ወንድሙን ከልብ ይቅር ባይል የሰማዩ አባቴ እንዲሁ ያደርግበታል።"

Footnotes

18:11 [1]አንዳንዶቹ ጥንታዊ የሆኑ፣ ብዙ ቅጂዎች ቊ.11ን የሰው ልጅ የጠፋውን ለማዳን መጥቷልና።

Matthew 18:1

ማቴዎስ **18**፡ **1**-**3**
እንደ ሕጻን መሆን "ሕጻናት እነደሚያስቡት ማሰብ።" (MAT 18:4 እና ተመልከት)

Matthew 18:4

ማቴዎስ **18**:**4**-**6**
እንደዚህ ሕጻን ራሱን የሚያዋርድ "ይህ ሕጻን ራሱን በሚያዋርድበት መንገድ ራሱን የሚያዋርድ ማንኛውም ሰው" (ተመልከት) የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባሕር መስጠም ይሻለው ነበር። "የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ አስረው ወደ ጥልቅ ባሕር መስጠም ከተሻለው"(ተመልከት የወፍጮ ድንጋይ ትልቅ፣ ክብ ቅርጽ ያለው ከባድ ድንጋይ ሆኖ እህል ለመፍጨት የሚያገለግል ነው። ለተርጓሚዎች ምክር፡ "ከባድ ድንጋይ"

Matthew 18:7

ማቴዎስ **18**፡ **7**-**8**
እጅህ ኢየሱስ አድማጮቹ እንደ አንድ ሰው አድርጎ በነጠላ ቁጥር እየተናገራቸው ነው።

Matthew 18:9

ማቴዎስ **18**:**9**-**9**
አውጥተህ ጣለው ይህ ሀረግ የሚያሳየው ተከታታይነት ያለው አለማመንን እና የሚያስከፍለውን ማንኛውንም ዋጋ መሸሸን ነው። ወደ ሕይወት መግባት "ወደ ዘላለም ሕይወት መግባት"

Matthew 18:10

ማቴዎስ **18**:**10**-**11**
አትናቁ "አትናቁ" ወይም "ጠቃሚ አይደሉም ብላችሁ አታስቡ" ለተርጓሚዎች ምክር፡ "አክብሩ" ሁል ጊዜ . . . ፊት ያያሉ "ሁል ጊዜ ቅርብ ናቸው "

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Matthew 18:12

ማቴዎስ **18:12-14**
ምን ይመስላችኋል? “ሰዎች ምን እንደሚያደርጉ አስቡ" (ተመልከት) ትቶ ሄዶም የባዘነውን አይፈልግምን? "ሁልጊዜ ትቶ ሄዶ የባዘነውን ይፈልጋል።” ዘጠና ዘጠኝ “99” ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱ እንዲጠፋ በሰማያት ያለው አባታችሁ ፈቃድ አይደለም። "በሰማይ ያለው አባታችሁ እነዚህ ትንንሾቹም ሁሉ እንዲኖሩ ፈቃዱ ነው" (ተመልከት)

Matthew 18:15

ማቴዎስ **18:15-16**
ወንድምህን ገንዘብ አደረግኸው "ከወንድምህ ጋር ያለህን ግንኙነት እንደገና መልካም ታደርጋለህ” አፍ ለምስክሮችህ “አፍ” በሚወጣው ቃል (ተመልከት)

Matthew 18:17

ማቴዎስ **18:17-17**
እነርሱ መስማት ምስክሮቹን መስማት (MAT 18:16) ለአንተ ልክ እንደ አሕዛብ እና ቀራጭ ይሁንልህ "አሕዛብን እና ቀራጭን እንደሚትመለከተው እንደዚያው ይሁንልህ"

Matthew 18:18

ማቴዎስ **18:18-20**
ያሰራችሁት ... የታሰረ . . . -ፈታችሁት . . . የተፈታ ይህህ በ MAT 16:19 ላይ እንዴት እንደተረጎምከተው ተመልከት። ይታሰራል . . . ይፈታል "እግዚአብሔር ያስረዋል . . . እግዚአብሔር ይፈተዋል" (ተመልከት) እነርሱ . . . እነርሱ "ሁለት ሆናችሄ" ሁለት ወይም ሦስት "ሁለት ወይም ከዚያ በላይ" ወይም "ቢያንስ ሁለት" ተሰብሰባችሁ "ስበሰባ" አባት ይህ የእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ የማዕረግ ስም ነው። (ተመልከት)

Matthew 18:21

ማቴዎስ **18:21-22**
ሰባት እጥፍ "7 እጥፍ" (ተመልከት ሰባ ጊዜ ሰባት አማራጭ ትርጉሞች: 1) "70 ጊዜ 7" (ULB) ወይም 2) "77 ጊዜ"። ቁጥርን መጠቀም ግራ የሚያጋባ ከሆነ እንዲህ ማለት ትችላለህ “መቁጠር ከማትችለው ቁጥር በላይ" (ተመልከት)

Matthew 18:23

ማቴዎስ **18:23-25**
አንድ አገልጋይ አመጡ "አንድ ሰው ከንጉሡ አገልጋዮች መካከል አንድ ሰው አመጣ" (ተመልከት) ዐስር ሺህ መክልት "10,000 መክልቶች" ወይም "አገልጋዩ መክፍለል ከሚችለው በላይ" (ተመልከት) አለቃው ተሸጦ ክፍያው እንዲፈጸም አዘዘ "ንጉሡ ይህ ሰው እንዲሸጥና ከሸያጩ ላይ እዳው እንዲከፈል አዘዘ"

Matthew 18:26

ማቴዎስ **18: 26-27**
በፊቱ ወድቆ በመስገድ "በጉልበቱ ወድቆ አንገቱን ወደ ታች ደፍቶ" በእርሱ ፊት "በንጉሡ ፊት" ለቀቀው "እንዲሄድ ፈቀለትet him"

Matthew 18:28

ማቴዎስ **18:28-29**
አንድ መቶ ዲናር "100 ዲናር" ወይም "የመቶ ቀን የሥራ ክፍያ (ተመልከት) ያዘው "አሰረው" ወይም “ያዘው" (UDB) በፊቱ ወደቀ . . . ታገሰኝ እና እከፍልሃለሁ ይህንን በ MAT 18:26 ላይ “በፊቱ ወደቀ . . . ታገሰኝ እና እከፍልሃለሁ” በተረጎምከው መሠረት ትርጉመው። (ተመልከት)

Matthew 18:30

ማቴዎስ **18:30-31**

Matthew 18:32

ማቴዎስ **18:32-33**
ከዚያም የአገልጋዩ ጌታ ጠራው "ከዚያ ንጉሡ የመጀመሪያውን አገልጋይ ጠርቶት" አይገባህምን "አይገባህምን” (ተመልከት)

Matthew 18:34

x
ማቴዎስ 18፡ 34-35

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **19**

1 እንዲህም ሆነ፤ ኢየሱስ ንግግሩን በጨረሰ ጊዜ ገሊላን ትቶ፣ በዮርዳኖስ ወንዝ ማዶ ወዳለው ወደ ይሁዳ ጠረፍ መጣ። **2** ብዙ ሕዝብ ተከተሉት፤ እዚያም ፈወሳቸው። **3** ፈሪሳውያን እንዲህ በማለት ሊፈትኑት ወደ እርሱ መጡ፤ "በማንኛውም ምክንያት ሰው ሚስቱን ቢፈታ ሕጋዊ ነውን?" **4** ኢየሱስ መልሶ እንዲህ አለ፣ "ከመጀመሪያው የፈጠራቸው እግዚአብሔር ወንድና ሴት አድርጎ እንደ ፈጠራቸውና **5** ደግሞም፣ 'በዚህ ምክንያት ሰው አባቱንና እናቱን ትቶ ከሚስቱ ጋር ይጣመራል፤ አንድ ሥጋም ይሆናሉ' የተባለውን አላነበባችሁምን? **6** ስለዚህ እነርሱ ከእንግዲህ አንድ ሥጋ እንጂ ሁለት አይደሉም። ስለዚህ እግዚአብሔር አንድ ላይ ያጣመረውን፣ ማንም አይለየው።›› **7** እነርሱ፣ "ታዲያ የፍቺ የምስክር ወረቀት ሰጥተን ከዚያ በኋላ እንድናባርራት ሙሴ ለምን አዘዘን?" አሉት። **8** ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፣ "ከልባችሁ ድንዳኔ የተነሣ ሚስቶቻችሁን እንድትፈቱ ሙሴ ፈቀደላችሁ፤ ነገር ግን ከመጀመሪያው እንደዚያ አልነበረም። **9** እኔ እላችኋለሁ፣ ከዝሙት በቀር ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ፣ ሌላይቱንም የሚያገባ ያመነዝራል፤ የተፈታችውንም የሚያገባ ያመነዝራል።" **10** ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስን፣ "የባልና የሚስት ጉዳይ እንዲህ ከሆነ ማግባት ጥሩ አይደለም" አሉት። **11** ኢየሱስ ግን እንዲህ አላቸው፤ "እንዲቀበሉት የተፈቀደላቸው እንጂ፣ ሁሉም ሰው ይህን ትምህርት አይቀበለውም። **12** በተፈጥሮ ከእናታቸው ማኅፀን ስልብ ሆነው የተወለዱ አሉና። ሰዎች የሰለቧቸውም ይገኛሉ። ስለ መንግሥተ ሰማያት ሲሉም ራሳቸውን ስልብ ያደረጉ አሉ። ይህን ትምህርት መቀበል የሚችል፣ ይቀበለው።›› **13** በዚያን ጊዜ እጁን ጭኖ እንዲጸልይላቸው ሰዎች ልጆችን ወደ እርሱ አመጡ፤ ደቀ መዛሙርቱ ግን ገሠጿቸው። **14** ኢየሱስ ግን፣ "ልጆቹን ተዉአቸው፤ ወደ እኔም እንዲመጡ አትከልክሏቸው፤ መንግሥተ ሰማያት እንደነዚህ ላሉት ናትና" አለ። **15** 15 እጁንም በልጆቹ ላይ ጫነባቸው፤ ከዚያም ያን ቦታ ትቶ ሄደ። **16** እነሆ፣ አንድ ሰው ወደ ኢየሱስ መጥቶ፣ ‹‹መምህር ሆይ፣ የዘላለም ሕይወት እንዳገኝ ምን መልካም ነገር ማድረግ አለብኝ?›› አለ። **17** ኢየሱስ፣ ‹‹ስለ መልካም ነገር ለምን ትጠይቀኛለህ? መልካም አንድ ብቻ ነው፤ ነገር ግን ወደ ሕይወት ለመግባት ብትፈልግ ትእዛዛትን ጠብቅ›› አለው። **18** ሰውዬው፣ ‹‹የትኞቹን ትእዛዛት? አለ። ኢየሱስ እንዲህ አለው፤ "አትግደል፤" "አታመንዝር" "አትስረቅ፤" "በሐሰት አትመስክር፤" **19** "አባትህንና እናትህን አክብር፤" እንዲሁም፣ "ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ።" **20** ወጣቱ፣ "እነዚህን ነገሮች ሁሉ ፈጽሜአለሁ፣ ሌላስ ምን ያስፈልገኛል?" አለው። **21** ኢየሱስ እንዲህ አለው፤ "ፍጹም ለመሆን ብትፈልግ፣ ሂድና ያለህን ሸጠህ ለድኾችም ስጠው፤ በሰማይም ሀብት ይኖርሃል። ከዚያም መጥተህ ተከተለኝ።›› **22** ነገር ግን ወጣቱ ኢየሱስ የተናገረውን በሰማ ጊዜ፣ ብዙ ንብረት ነበረውና ዐዝኖ ሄደ። **23** ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ አላቸው፤ "እውነት እላችኋለሁ፤ ለባለ ጠጋ ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት ከባድ ነው። **24** ደግሜ እላችኋለሁ፤ ለባለ ጠጋ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከመግባት፣ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ይቀላል።" **25** ደቀ መዛሙርቱ ይህን በሰሙ ጊዜ በጣም ተደነቁና፣ "ታዲያ ማን ሊድን ይችላል?" አሉ። **26** ኢየሱስ ወደ እነርሱ ተመልክቶ፣ "ይህ ለሰዎች የማይቻል ነው፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ሁሉ ይቻላል" አለ። **27** ከዚያም ጴጥሮስ መልሶ፣ "ተመልከት፣ እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ፤ ታዲያ ምን እናገኛለን?" አለ። **28** ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፤ "እውነት እላችኋለሁ፣ እናንተ እኔን የተከተላችሁኝ፣ በዐዲሱ ልደት የሰው ልጅ በክብሩ ዙፋን ላይ በሚቀመጥበት ጊዜ፣ እናንተም በዐሥራ ሁለት ዙፋኖች ላይ ትቀመጣላችሁ፤ በዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶችም ላይ ትፈርዳላችሁ። **29** ስለ ስሜ ቤቶችን፣ ወንድሞችን፣ እኅቶችን፣ አባትን፣ እናትን፣ ልጆችን፣ ወይም ርስትን የተወ ሁሉ፣ መቶ እጥፍ ይቀበላል፣ የዘላለምንም ሕይወት ይወርሳል። **30** ነገር ግን አሁን ፊተኞች የሆኑ ብዙዎች ኋለኞች ይሆናሉ፤ ኋለኞች የሆኑ ብዙዎችም ፊተኞች ይሆናሉ።

Matthew 19:1

ማቴዎስ **19**:**1**-**2**
ከዚያ በኋላ በቋንቋችሁ የአንድን ታሪክ አዲስ ክፍል ለመጀመር የሚያገለግል ቃል ካለ ይህንን ቃል ተጠቀሙ። እነዚህ ቃላት የ . . . ቃላት MAT 18:1-35 ተለየ "ከእነርሱ ራቀ” ወይም "ተዋቸው" በዚያው ክልል ውስጥ "በዚያው አከባቢ"

Matthew 19:3

ማቴዎስ **19**:**3**-**4**
ወደ እርሱ መጣ "ወደ ኢየሱስ መጣ" አላነበባችሁምን . . . ሴት? ኢየሱስ ፈሪሳዊያኑን ሊያሳፍራቸው ፈልጎል። (ተመልከት)

Matthew 19:5

ማቴዎስ **19**:**5**-**6**
እንዲሁም እንዲህ አለ .. . ሥጋ? በ MAT 19:3 ላይ የተጀመረው ጥያቄ የቀጠለ ነው፡ "በተጨማሪም እንዲህ የሚል ነገር አላነባችሁምን . . . ሥጋ?" (እና ተመልከት) ከምስቱ ጋር ይጣበቃል "ከምስቱ ጋር ይቀራረባል" አንድ ሥጋ "አንድ ሰው"

Matthew 19:7

ማቴዎስ **19**:**7**-**9**
እንዲህ አሉት "ፈሪሳዊያኑ ለኢየሱስ አንዲህ አሉት" አዞናል "አይሁዳዊ እንደመሆናችን እንዲህ ታዘናል" የፊች ወረቀት ጋብቻው ሕጋዊ በሆነ መንገድ መቆሙን የሚሳይ ወረቀት ከመጀመሪያው ግን እንዲህ አልነበረም "እግዚብሔር ወንድን እና ሴትን ሲፈጥር መቼም ቢሆን እንድፋቱ አልነበረም" የተፈታቸችሁንም የሚያገባ ማንኛውም ሰው ያመነዝራል ብዙዎቹ የጥንት ቅጂዎች እነዚህንን ቃላት አይጨምሩትም።

Matthew 19:10

ማቴዎስ **9**:**10**-**12**
ራሱን ጃንደረባ ያደረገ አማራጭ ትርጉሞች 1) "የግል አካሉን ቆርጦ የጣለ” ወይም 2) "ላለማግባት እና ምንም ዓይነት ግብረስጋ ግንኙነት ላለማድረግ የወሰነ ሰው” (ተመልከት) ለመንግስተ ሰማያት ሲል "እግዚአብሔርን ይበልጥ ለማገልገል ይችል ዘንድ" ይህንን ትምህርት ተቀበል . . . ተቀበል “ይህንን ትምህርት ተቀበል . . . ተቀበል” የሚለው በ19:11 ላይ እንዴት እንደተረጎምከተው ተመልከት።

Matthew 19:13

ማቴዎስ **19**: **13**-**15**
ሕጻናትን ወደ እርሱ አመጡ ለተርጓሚዎች ምክት፡ “አንዳንድ ሰዎች ሕጻናትን ወደ ኢየሱስ አመጡ።” (ተመልከት) ፈቃድ "ፍቀዱ" ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሏቸው "ወደ እኔ እንዳይመጡ አትከልክሏቸው" የመንግስተ ሰማያት እንደነዚህ ላሉት ናትና "መንግስተ ሰማየት እንደነዚህ ላሉ ሰዎች ናትና” ወይም “ልክ እንደነዚህ ሕጻናት የሆኑ ሰዎች ብቻ ናቸው ወደ መንግስተ ሰማያት መግባት የሚችሉት"

Matthew 19:16

ማቴዎስ **19**: **16**-**17**
እነሆ ይህ ቃል ሰዎች ከዚህ በኋላ ለሚነገረው ነገር አጽኖት እንዲሰጡ የሚጨመር ቃል ነው፡ ለተርጓሚዎች ምክር፡ “ተመልከቱ” ወይም “አድምጡ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወይም “አሁን ለምነግራችሁ ነገር ትኩረት ስጡ”:: መልካም ነገር እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ነገር

Matthew 19:18

ማቴዎስ **19:18-19**

Matthew 19:20

ማቴዎስ **19:20-22**
ምኞት "ፍላጎት"

Matthew 19:23

ማቴዎስ **19:23-24**
ሀብታም ወደ እግዚአብሔር መንግስት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ብትሾልክ ይቀላል ለሀብታም ወደ እግዚአብሔር መንግስር መግባት በጣም ከባድ ነው (ተመልከት) የመርፌ ቀዳዳ ለክር ማስገቢያ የሚሆን በመርፌ አናት ላይ የሚገኝ ቀዳዳ

Matthew 19:25

ማቴዎስ **19:25-27**
በጣም ተገረሙ "ደቀ መዛሙርቱ ተደነቁ" ማን ልድን ይችላል? አማራጭ ትርጉሞች: 1) መልስ እየፈለጉ ነው ወይም 2) ለተርጓሚዎች ምክር: “ማንም ሊድን አይችልም!” (ተመልከት) እኛ ሁሉን ነገር ተውን "ሀብታችንን ሁሉ ተውን" ወይም "ያለንን ነገር ሁሉ ተውን" ታዲያ ምን እናገኛለን? "እግዚአብሔር ለእኛ ምን መልካም ነገር ይሰጠናል?"

Matthew 19:28

ማቴዎስ **19:28-28**
አዲስ ልደት "ሁሉ ነገር አዲስ በሚሆንበት ጊዜ” ወይም "በአዲሱ ዘመን" በዐሥራ ሁለቱ ዙፋናት ላይ ትቀመጣላችሁ፣ ትርዳላችሁ "ነገሥታት እና ፈራጆች ትሆናላችሁ"

Matthew 19:29

ማቴዎስ **19: 29-30**
መቶ እጥፍ ትቀበላላችሁ "የተዋቿቸውን መልካም ነገሮች ሁሉ በመቶ እጥፍ ትቀበላላችሁ" አሁን መጀመሪያ የነበሩ ብዙዎች መጨረሻ ሆነዋል በሰዎች ዐይን መጀመሪያ የነበሩት ማለትም ሀብታሞች እና ሌሎችን የሚዙ ሰዎች በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ አንድ ቀን መጨረሻ ይናሉ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **20**

1 መንግሥተ ሰማይ ለወይኑ አትክልት ሠራተኞችን ሊቀጥር ማልዶ የወጣ ባለቤትን ትመስላለች። **2** በቀን አንዳንድ ዲናር ሊከፍላቸው ከሠራተኞቹ ጋር
ከተስማማ በኋላ፣ ወደ ወይኑ አትክልት ስፍራ ላካቸው። **3** ደግሞም በሦስት ሰዓት ገደማ ወጥቶ በገበያ ቦታ ሥራ ፈትተው የቆሙ ሌሎች ሠራተኞችን አየና፣ **4**
'እናንተ ደግሞ ወደ ወይኑ አትክልት ስፍራ ሂዱ፤ የሚገባችሁንም እከፍላችኋለሁ' አላቸው። ስለዚህ እነርሱም ሊሠሩ ሄዱ። **5** ደግሞ በስድስት ሰዓትና በዘጠኝ
ሰዓት ገደማ ወጥቶ እንደዚሁ አደረገ። **6** አሁንም በዐሥራ አንደኛው ሰዓት ገደማ ወጥቶ ሥራ ፈትተው የቆሙ ሌሎችን አገኘ። እነርሱንም፣ 'ቀኑን ሙሉ ሥራ
ፈትታችሁ እዚህ ለምን ቆማችኋል?' አላቸው። **7** 'ማንም ስላልቀጠረን ነው' አሉት። 'እናንተም ደግሞ ወደ ወይኑ አትክልት ስፍራ ሂዱ' አላቸው። **8** ቀኑ በመሸ
ጊዜ፣ የወይኑ አትክልት ባለቤት ሥራ አስኪያጁን፣ 'ሠራተኞቹን ጥራ ከኋለኞቹ አንሥተህ እስከ ፊተኞቹ የሠሩበትን ገንዘብ ክፈላቸው' አለው። **9** በዐሥራ
አንደኛው ሰዓት የተቀጠሩት ሠራተኞች በመጡ ጊዜ፣ እያንዳንዳቸው አንዳንድ ዲናር ተቀበሉ። **10** ፊተኞቹ ሠራተኞች በመጡ ጊዜ፣ የበለጠ የሚቀበሉ
መሰላቸው፤ ነገር ግን እነርሱም ደግም እያንዳንዳቸው አንዳንድ ዲናር ተቀበሉ። **11** ገንዘባቸውን በተቀበሉ ጊዜ፣ በወይኑ አትክልት ባለቤት ላይ አጒረመረሙ።
12 እንዲህም አሉ፤ 'እነዚህ በመጨረሻ የመጡ ሠራተኞች በሥራ ላይ አንድ ሰዓት ብቻ አሳልፈዋል፤ ነገር ግን አንተ የዕለቱን ሸክምና የሚለበልበውን ሙቀት
ከተሸከምነው ከእኛ ጋር እኩል አድርገሃቸዋል።' **13** ባለቤቱ ግን መልሶ ከእነርሱ አንዱን እንዲህ አለው፤ "ወዳጄ ሆይ፣ አልበደልኩህም። ከእኔ ጋር በአንድ ዲናር
አልተስማማህምን? **14** የሚገባህን ተቀብለህ መንገድህን ሂድ፤ ለእነዚህ በመጨረሻ ለተቀጠሩት ሠራተኞች ልክ እንደ አንተው ልሰጣቸው ደስ ይለኛል። **15**
በገዛ ንብረቴ የፈለግሁትን ማድረግ አይገባኝምን? ወይስ እኔ ደግ ስለ ሆንሁ ትመቀኛለህን? **16** ስለዚህ ኋለኞች ፊተኞች፣ ፊተኞችም ኋለኞች ይሆናሉ።" **17**
ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ይወጣ ስለ ነበር፣ ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ለብቻቸው ወሰደ፤ በመንገድ ላይም እንዲህ አላቸው፡- **18** እነሆ ወደ ኢየሩሳሌም
እንወጣለን፤ የሰው ልጅም ለካህናት አለቆችና ለሕግ መምህራን ተላልፎ ይሰጣል። ሞትም ይፈርዱበታል፤ **19** እንዲዘብቱበት፣ እንዲገርፉት፣ እንዲሰቅሉትም
ለአሕዛብ ይሰጡታል። ነገር ግን በሦስተኛው ቀን ይነሣል።" **20** በዚያን ጊዜ የዘብዴዎስ ልጆች እናት ከልጆቿ ጋር ወደ ኢየሱስ መጣች፤ በፊቱ ተንበርክካም
ከእርሱ አንድ ነገር ለመነች። **21** ኢየሱስ፣ "ምን ትፈልጊያለሽ?" አላት። እርሷም፣ "በመንግሥትህ እነዚህ ሁለት ልጆቼ አንዱ በቀኝህ፣ አንዱም በግራህ
እንዲቀመጡ እዘዝ" አለችው። **22** ኢየሱስ ግን መልሶ፣ "የምትለምኑትን አታውቁም። እኔ የምጠጣውን ጽዋ መጠጣት ትችላላችሁን?" አለ። እነርሱ፣
"እንችላለን" አሉት። **23** ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፤ "በርግጥ ጽዋዬን ትጠጣላችሁ። በቀኜና በግራዬ መቀመጥን የምሰጥ ግን እኔ አይደለሁም፤ ነገር ግን
በአባቴ ለተዘጋጀላቸው ለእነርሱ ነው።" **24** ሌሎቹ ዐሥሩ ደቀ መዛሙርት ይህን በሰሙ ጊዜ፣ በሁለቱ ወንድማማች ላይ ተቈጡ። **25** ነገር ግን ኢየሱስ ወደ ራሱ
ጠርቶ እንዲህ አላቸው፣ "የአሕዛብ አለቆች ሕዝባቸውን ጨቊነው ይገዛሉ፤ የበላዮቻቸውም ይሠለጥኑባቸዋል። **26** በእናንተ መካከል ግን እንዲህ መደረግ
የለበትም። ይልቁንም፣ ከእናንተ መካከል ታላቅ ሊሆን የሚፈልግ ሁሉ አገልጋያችሁ ይሁን፤ **27** ከእናንተም ፊተኛ ሊሆን የሚፈልግ ሁሉ አገልጋያችሁ ይሁን። **28**
የሰው ልጅ ሊያገለግል፣ ሕይወቱንም ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ሊሰጥ እንጂ፣ እንዲያገለግሉት አልመጣም።" **29** ከኢያሪኮ እንደ ወጡ፣ ብዙ ሕዝብ ኢየሱስን
ተከተሉት። **30** እነሆ፣ ሁለት ዐይነ ስውሮች በመንገድ ዳር ተቀምጠው ነበር፤ ኢየሱስ ሲያልፍ በሰሙ ጊዜ ጮኽ ብለው፣ "ጌታ ሆይ፣ የዳዊት ልጅ፣ ማረን" አሉ።
31 ሕዝቡ ግን ዝም እንዲሉ በመንገር ገሠጿቸው። ይሁን እንጂ፣ እነርሱ አብዝተው በመጮኽ፣ "ጌታ ሆይ፣ የዳዊት ልጅ ማረን" አሉ። **32** በዚያን ጊዜ ኢየሱስ
ቆም ብሎ ጠራቸውና፣ "ምን እንዳደርግላችሁ ትፈልጋላችሁ?" አለ። **33** እነርሱም፣ "ጌታ ሆይ፣ ዐይኖቻችን እንዲከፈቱ ነው" አሉት። **34** ከዚያም ኢየሱስ
ራርቶ፣ ዐይኖቻቸውን ዳሰሰ። እነርሱም ወዲያውኑ አይተው ተከተሉት።

Matthew 20:1

ማቴዎስ **20**:**1-2**
መንግስ ሰማያት የመሬት ባለቤትን ትመስላለች እግዚአብሔር በሁሉም ነገር ላይ ያለው አገዛዝ አንድ ባለመሬት መሬቱን የሚያስተዳድርበትን መንገድ ይመስላል (ተመልከት) መንግስተ ሰማይ ትመስላለች በ MAT 13:24 ላይ በምን መልኩ እንደተረጎምከው ተመልከት። ከተስማማ በኋላ "የመሬቱ ባለቤት ከተስማማ በኋላ" በአንድ ዲናር "የአንድ ቀን ገቢ" (ተመልከት)

Matthew 20:3

ማቴዎስ **20**:**3-4**
እንደ ገና ወጣና "የመሬቱ ባለቤት እንደገና ወጣና" ያለሥራ የቆሙተን "ምንመ የማይሠሩትን” ወይም “ሥራ ያሌላቸውን"

Matthew 20:5

ማቴዎስ **20**:**5-6**
እንደ ገና ወጣና "የመሬቱ ባለቤት እንደገና ወጣና" ያለሥራ የቆሙተን "ምንመ የማይሠሩትን” ወይም “ሥራ ያሌላቸውን"

Matthew 20:8

ማቴዎስ **20**: **8-10**
ለእያንዳንዱ "በዐሥራ አንድ ሰዓት መሥራት ለጀመረውም ለእያንዳንዱ" አንድ ዲናር "የአንድ ቀን ገቢ" (ተመልከት) እነርሱ እነንዲህ አሰቡ "ረጅም ሰዓት የሠሩት ሠራተኞች እንዲህ አሰቡ"

Matthew 20:11

ማቴዎስ **20**:**11-12**
በተቀበሉ ጊዜ "ረጀም ሰዓት ስሰሩ የነበሩት ሠራተኞች ስቀበሉ" ባለቤቱ "የመሬቱ ባለቤት" ወይም "የወይን እርሻው ባለቤት" የቀኑንም ድካምና ትኩሳት ከተሸከምን "በጠራራ ፀሐይ ቀኑን ሙሉ ሥንሠራ የነበርን"

Matthew 20:13

ማቴዎስ **20**:**13-14**
ከመካከላቸው አንዱ "ረጅሙን ሰዓት ከሠሩት ሠራተኞች መካከል አንዱ" ወዳጆቼ በዚህ ሥፍራ ላይ አንድ ሰው ሌላኛውን ሰው በትህትና ለመገሰጽ የሚጠቀምበትን ቃል ተጠቀም። በአንድ ዲናር ለመሥራት ከእኔ ጋር አልተስማማችሁምን? ለተርጓሚዎች ምክር: “ለሥራችሁ ዋጋ አንድ ዲናር ለመክፈል ተስማሚቼያለሁ። (en:ta:vol1:translate: ተመልከት) አንድ ዲናር "የአንድ ቀን ገቢ" (ተመልከት) መስጠት እወዳለሁ "መስጠት ያስደስተኛል” ወይም “መስጠት እወዳለሁ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Matthew 20:15

ማቴዎስ **20: 15-16**
በራሴ ሀብት የፈለኩትን የማድረግ መብት የለኝምን? ለተርጓሚዎች ምክር: "በራሴ ሀብት የፈለኩትን ማድረግ እችላለሁ” መብት "ሕጋዊ" ወይም "ፍትሐዊ" ወይም "ትክክል" ወይም እኔ መልካም ስለሆንኩ ቀናችሁን? "ለማይገባቸው ሰዎች መልካም በማድረጌ አልተደሰታችሁምን"

Matthew 20:17

ማቴዎስ **20:17-19**
እንሄዳለን ኢየሱስ እና ደቀ መዛሙርቱ የሰው ልጅን አሳልፈው ይሰጡታል "አንድ ሰው የሰው ልጅን አሳልፎ ይሰጠዋል" ይፈርዱበታል. . . እና አሕዛብ ይዘባበቱበት ዘንድ አሳልፎ ይሰጣል የካህናት አለቆች እና ፀሐፍት ይፈርዱበታል እንዲሁም ለአሕዛብ አሳልፈው ይሰጡታል፤ አሕዛብም ይዘባበቱበታል ይነሳል "እግዚብሔር ያስነሳዋል”

Matthew 20:20

ማቴዎስ **20:20-21**
በቀኝህ በኩል . . . በግራህ በኩል ሥልጣን ያለው ቦታ

Matthew 20:22

ማቴዎስ **20:22-24**
አናንተ እናት እና ልጆች ትችላለህን...ለመጠጣት? "ለመጠጣት . . . ትችላለህን?" ኢየሱስ ይህን የተናረው ለልጆች ብቻ ነው። አሁን ልጠጣው ያለሂትን ጽዋ ጠጣ "አሁን ልቀበለው ያለሁትን መከራ ውስጥ እለፍ" እነርሱ ልጆች በአባቴ ለተዘጋጀላቸው ነው "ከአጠገቤ በክብር መቀመጥ ይህንን ክብር አባቴ ላዘጋጀላቸው ነው" መዘጋጀት የተዘጋጀላቸው

Matthew 20:25

ማቴዎስ **20:25-28**
የአሕዛብ ገዥዎች ይገዟቸዋል "የአሕዛብ ገዥዎች ገዥው የፈለገውን ነገር እንዲያደር ሕዝቡን ያዛሉ" እርሱ በጣም አስፈላጊ ሰው ናቸው በገዥዎች ስልጣን የተሰጣቸው ሰዎች በእነርሱ ላይ ስልጣን አላቸው "ይቆጣጠሯቸዋል" ፍላጎት "ፍላጎት" ወይም "መሻት" ሕይወት መስጠት "ለመሞት መፈለግ"

Matthew 20:29

ማቴዎስ **20:29-31**
እንደፈለጉ ለደቀ መዛሙርቱ እና ኢየሱስ ተከተሉት "ኢየሱስን ተከተሉ" እናም ተመለከቱ አንዳንድ ጊዜ “እነሆነ” ተብሎ ተተርጉሟል። ጸሐፊው ከዚህ በመቀጠል ለሚመጣው ነገር ትኩርት እንዲሰጠው ይፈልጋል። ይህንን ለማድረግ የሚያስችል ነገር በቋንቋችሁ ውስጥ ይኖራል። በዚያ ስያልፉ "በዚያ ሥያልፉ" ይበልጥ ድምጻቸው አሰመተው ጮኹ "ዐይነ ሥውራኑ ከበፊቱ ይልቅ አብዝተው ጮኹ” ወይም “ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ጮኹ"

Matthew 20:32

ማቴዎስ **20:32-34**
ጠራቸው ዐይነ ሥውራኑን ጠራቸው ፍላጎት "ፍላጎት" እናይ ዘንድ እንወዳለን ለተርጓማች ምክር: “ማየት እንችል ዘንድ ታደርግ ዘንድ እንወዳለን" ወይም "ማየት እንችል ዘንድ እንወዳለን ራራላቸው "ራራላቸው” ወይም "ለእነርሱ ራራ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 21

1 ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየሩሳሌም እንደቀረቡ፣ በደብረ ዘይት ወዳለው ወደ ቤተ ፋጌ መጡ፤ 2 ከዚያም ኢየሱስ እንዲህ በማለት ሁለት ደቀ መዛሙርት
ላከ፤ “ወደሚቀጥለው መንደር ሂዱ፤ አህያም ከነውርንጫዋ ታስራ ታገኛላችሁ። ፈትታችሁ ወደ እኔ አምጧቸው፤ 3 ማንም ስለዚያ አንዳች ቢናገራችሁ፣ እርሱም
ከእናንተ ጋር ፈጥኖ ይሰዳቸዋል።” 4-5 ይህ የሆነው፣ “እነሆ፣ ንጉሥሽ ትሑት ሆኖ በአህያና በውርንጫዋ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል ብላችሁ ለጽዮን
ልጅ ንገሯት” ተብሎ በነቢዩ የተተነበየው ይፈጸም ዘንድ ነው። 6 ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ ሄደው ልክ ኢየሱስ እንዳዘዛቸው አደረጉ። 7 አህያይቱንና ውርንጫዋን
አመጡ፤ ልብሳቸውንም አደረጉባቸውና ኢየሱስ ተቀመጠባቸው። 8 ከሕዝቡ አብዛኞቹ ልብሳቸውን በመንገድ ላይ አነጠፉ፣ ሌሎችም የዘንባባ ዝንጣፊ
እየቈረጡ በመንገድ ላይ አደረጉ። 9 ከኢየሱስ ፊት ይሄዱ የነበሩትና የተከተሉትም ሕዝብ፣ “ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ በጌታ ስም የሚመጣ እርሱ የተባረከ ነው።
ሆሣዕና በአርያም ይሁን!” በማለት ጮኹ። 10 ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በመጣ ጊዜ ከተማይቱ በሞላ ታወከችና፣ “ይህ ማን ነው?” አለች። 11 ሕዝቡ፣ “ይህ
ከገሊላ ናዝሬት የሆነው ነቢዩ ኢየሱስ ነው” ብለው መለሱ። 12 ከዚያም ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ሄደ። በቤተ መቅደስ የሚሸጡትንና የሚገዙትን
አስወጣ። የገንዘብ ለዋጮችን ጠረጴዛዎችና ወንበሮች ገለበጠ። 13 እንዲህም አላቸው፤ ‘ቤቴ የጸሎት ቤት ይባላል’ ተብሎ ተጽፏል። እናንተ ግን የወንበዴዎች
ዋሻ አደረጋችሁት።" 14 ከዚያም ዕይነ ስውሮችና ሽባዎች ወደ እርሱ ወደ ቤተ መቅደስ መጡ፤ እርሱም ፈወሳቸው። 15 ነገር ግን የካህናት አለቆችና የሕግ
መምህራን እርሱ ያደረጋቸውን ድንቅ ነገሮች ባዩና በቤተ መቅደስ ልጆች፣ “ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ” በማለት ሲጮኹ በሰሙ ጊዜ፣ ተቈጡ። 16 “ሕዝቡ
የሚሉትን ትሰማለህን?” አሉት። ኢየሱስ፣ “አዎ! ነገር ግን ‘ከሕፃናትና ከሚጠቡት አፍ ምስጋናን አዘጋጀህ’ የሚለውን ከቶ አላነበባችሁምን?” አላቸው። 17
ከዚያም ኢየሱስ ትቷቸው ከከተማው ወጣና ወደ ቢታንያ ሄዶ በዚያ ዐደረ። 18 ኢየሱስ ጠዋት ወደ ከተማው እንደተመለሰ፣ ተራበ። 19 በመንገድ ዳር አንዲት
የበለስ ተክል አየና ወደ እርሷ ሄደ፤ ነገር ግን ከቅጠል በቀር ምንም አላገኘባትም። “ሁለተኛ ከቶ ፍሬ አይገኝብሽ” አላት። የበለስ ተክሊቱም ወዲያውኑ ደረቀች።
20 ደቀ መዛሙርቱ ባዩአት ጊዜ ተደንቀው፣ “የበለስ ተክሊቱ እንዴት ወዲያውኑ ደረቀች?” አሉ። 21 ኢየሱስ መልሶ እንዲህ አላቸው፤ "እውነት እላችኋለሁ፣
እምነት ቢኖራችሁና ባትጠራጠሩ፣ በዚች የበለስ ተክል የሆነባትን ብቻ ሳይሆን፣ ይህን ኮረብታ ከዚህ ተነሥተህ ወደ ባሕር ተወርወር ብትሉት እንኳ ይሆናል። 22
አምናችሁ በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ ትቀበላላችሁ።” 23 ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ ሲያስተምር የካህናት አለቆችና የሕዝቡ ሽማግሌዎች ወደ እርሱ
መጥተው፣ “በምን ሥልጣን እነዚህን ነገሮች ታደርጋለህ? ይህንስ ሥልጣን ማን ሰጠህ?” አሉ። 24 ኢየሱስ መልሶ እንዲህ አላቸው፤ “እኔ ደግሞ አንድ ጥያቄ
እጠይቃችኋለሁ። ያንን ከነገራችሁኝ እኔ ደግሞ በማን ሥልጣን እነዚህን ነገሮች እንደማደርግ እነግራችኋለሁ። 25 የዮሐንስ ጥምቀት ከየት መጣ ከሰማይ ነውን
ወይስ ከሰዎች?” እርስ በርሳቸው እንዲህ በማለት ተነጋገሩ፤ “ከሰማይ ነው ብንለው፣ ‘ለምን አታምኑትም?’ ይለናል። 26 ነገር ግን ‘ከሰው ነው ብንል፣ ዮሐንስን
እንደ ነቢይ ስለሚያዩት ሕዝቡን እንፈራለን።” 27 ከዚያም መልሰው ኢየሱስን፣ “አናውቅም” አሉት። እርሱ ደግሞ፣ “እኔም በምን ሥልጣን እነዚህን ነገሮች
እንደማደርግ አልነግራችሁም” አላቸው። 28 ነገር ግን ምን ይመስላችኋል? አንድ ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት፣ ወደ መጀመሪያው ሄዶ፣ ልጄ ሆይ፣ ዛሬ ወደ ወይኑ
አትክልት ስፍራ ሄደህ ሥራ’ አለው። 29 ልጁ መልሶ፣ ‘አልሄድም’ አለ፤ በኋላ ግን ዐሳቡን ለውጦ ሄደ። 30 ሰውዬውም ወደ ሁለተኛው ልጅ ሄዶ ይህንኑ
ነገረው። ይህኛው ልጅ መልሶ፣ ‘እሄዳለሁ፣ አባዬ’ አለ። ነገር ግን አልሄደም። 31 ከሁለቱ ልጆች የአባቱን ትእዛዝ የፈጸመው የትኛው ነው? እነርሱ፣
"የመጀመሪያው” አሉ። ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፦ “እውነት እላችኋለሁ፣ ቀረጥ ሰብሳቢዎችና አመንዝራዎች ቀድመዋችሁ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት
ይገባሉ። 32 ዮሐንስ በጽድቅ መንገድ ወደ እናንተ መጥቶ ነበርና፤ እናንተ ግን አላመናችሁትም፤ ቀረጥ ሰብሳቢዎችና አመንዝራዎች ግን አመኑት። እናንተም ይህ
ሲሆን አይታችሁ ታምኑት ዘንድ በኋላ እንኳ ንሰሐ አልገባችሁም። 33 ሌላም ምሳሌ ስሙ። ሰፊ መሬት ያለው አንድ ሰው ነበር። የወይን አትክልት ተከለ፤ ዐጥር
አጠረለት፤ የወይን መጥመቂያ ማሰለት፤ መጠበቂያ ማማ ሠራለት፤ ለወይን ገበሬዎችም አከራይቶ ወደ ሌላ አገር ሄደ። 34 የወይን ፍሬ የሚሰበሰብበት ጊዜ
እንደ ደረሰ፣ ፍሬውን እንዲቀበሉ ጥቂት አገልጋዮችን ላከ። 35 የወይኑ ገበሬዎች ግን አገልጋዮቹን ያዙ፤ አንዱን ደበደቡት፣ ሌላውን ገደሉት፤ ሌላውንም በድንጋይ
ወገሩት። 36 ባለቤቱ እንደ ገና ከፊተኞቹ የበዙ ሌሎች አገልጋዮችን ላከ፤ ነገር ግን የወይን ገበሬዎቹ ያንኑ አደረጉባቸው። 37 ከዚያ በኋላ ባለቤቱ፣ ‘ልጄንስ
ያከብሩታል’ በማለት የገዛ ልጁን ላከ። 38 የወይን ገበሬዎቹ ግን ልጁን ባዩ ጊዜ፣ እርስ በርሳቸው፣ 'ይህ ወራሹ ነው፤ ኑ፣ እንግደለውና ርስቱን እንውረስ’
ተባባሉ። 39 ስለዚህ ያዙትና ከወይኑ አትክልት ስፍራ ወደ ውጭ ጣሉት፤ ገደሉትም። 40 እንግዲህ የወይኑ አትክልት ባለቤት በሚመጣበት ጊዜ እነዚያን የወይን
ገበሬዎች ምን ያደርጋቸዋል?” 41 ሕዝቡ እንዲህ አሉት፤ “እነዚያን ክፉ ሰዎች እጅግ በጣም አሰቃቂ በሆነ መንገድ ያጠፋቸዋል፤ ከዚያም የወይኑን አትክልት
ስፍራ ወይኑ በሚያፈራበት ጊዜ ገንዘቡን ለሚከፍሉ ለሌሎች የወይን ገበሬዎች ያከራየዋል።” 42 ኢየሱስ እነርሱን፣ “ 'ግንበኞች የናቁት ድንጋይ የማዕዘን ራስ
ሆነ። ይህ ከጌታ ዘንድ ሆነ፤ ለዐይኖቻችንም ድንቅ ነው ተብሎ የተጻፈውን ፈጽሞ አላነበባችሁም?’ 43 ስለዚህ እላችኋለሁ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ከእናንተ
ትወሰድና ፍሬዋን ለሚያፈራ ሕዝብ ትሰጣለች። 44 በዚህ ድንጋይ ላይ የሚወድቅ ሁሉ ይሰባበራል። ድንጋዩ የሚወድቅበትን ሁሉ ግን ይፈጨዋል።” 45
የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ምሳሌዎቹን በሰሙ ጊዜ፣ የተናገረው ስለ እነርሱ እንደ ሆነ ተረዱ። 46 ነገር ግን ሊይዙት በፈለጉ ጊዜ ሁሉ፣ ሰዎቹ እንደ ነቢይ
ይቈጥሩት ስለ ነበር ሕዝቡን ፈሩ።

Matthew 21:1

ማቴዎስ **21**:**1-3**
ቤተ ፋጌ መንደር
ውርንጭላ "ትንሽ ወንድ አህያ"

Matthew 21:4

ማቴዎስ **21**:**4-5**
ይህ በነቢያት የተነገረው ይፈጸም ዘንድ ነው "እግዚአብሔር ስለዚህ ጉዳይ
ከብዙ ዘመናት በፊት በነቢያ አማካኝነት ምን እንደሚሆን ተናግሮ ነበር”
በነቢያት የተነገረው ነገር "ነገሩ ከመፈጸሙ በፊት ነቢያት አስቀድመው
የተናገሩት ነገር” የጽዮን ሴት ልጅ እስራኤል አህያ ድሆች የሚጋልቡት እንስሳ
ውርንጭላ ትንሽ ወንድ አህያ

Matthew 21:6

ማቴዎስ **21**:**6-8**
ጨርቅ ከውጪ የሚደረብ ወይም ረጅም ኮት ኢየሱስ በዚያ ተቀመጠ
"አህያይቱን ጨርቅ አልብሰው ኢየሱስ በዚያ ላይ እንዲቀመጥ አደረጉ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Matthew 21:9

ማቴዎስ **21**:**9**-**11**
ሆሣዕና ይህ የዕብራይስጥ ቃል ሲሂን ትርጉሙም “አድነን” ማለት ነው ይሁን እንጂ “እግዚአብሔር ይመስገንም” መሆን ይችላል። ከተማው ሁሉ ተናወጠ "በከተማይቱ ውስጥ ያሉ ሁሌ እርሱን ለማየት ጓግተው ነበር" ከተማው ሁሉ "በከተማይቱ ውስጥ ያሉ ብዙ ሰዎች"

Matthew 21:12

ማቴዎስ **21**:**12**-**14**
እንዲህ አላቸው "ገንዘብ ለዋጮቹን እና የተለያዩ ነገሮችን የሚገዙትን እና የሚሸጡትን ሰዎች" የጸሎት ቤት "ሰዎች የሚጸልዩበት ሥፍራ" የወንበዴዎች ዋሻ "እንደ ወንበዴዎች መሸሸጊያ ዋሻ” አንካሳ በጣም ከመጎዳታቸው የተነሳ መራመድ የማይችሉ ሰዎች

Matthew 21:15

ማቴዎስ **21**:**15**-**17**
ሆሣዕና በ MAT 21:09 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምው ተመልከት። የዳዊት ልጅ በ MAT 21:09 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ተቆጡ "ኢየሱስን ጠሉት እንዲሁም በጣም ተበሳጩበት" እነዚህ ሰዎች የሚሉትን አትሰማምን? "ሰዎች ስለአንተ እንዲህ ዓይነት ንግግር እንዲያደርጉ ልትፈቅድላቸው አይገባም!" ይሁን እንጂ ፈጽሞ አላነበባችሁምን . . . ምስጋና'? "አዎ አየሰማኋቸው ነው ይሁን እንጂ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ያነበባችሁት ማስታወስ ይገባችሁ ነበር . . . ምሳጋና" ኢየሱስ ትቷቸው ሄደ "ኢየሱስ የካህናት አለቆችንና ጸሐፊትን ትቶ ሄደ"

Matthew 21:18

ማቴዎስ **21**:**18**-**19**
ደረቀ "ሞተ" ማቴዎስ 21:20-21

እምነት ካላችሁና የማትጠራጠሩ ከሆነ እነዚህ ሁለት ሀረጎች የሚስተላልፉት ተመሳሳይ ሀሳብ ነው። ሁለት ጊዜ የተጻፈው አጽኖት ለመስጠት ነው። በአንዳንድ ቋንቋዎች ውስጥ አጽኖት መስጫ ሌላ መንገድ አለ። ለተርጓሚዎች ምክር፡ “በእርግጥ ካመናችሁ” ወዲያው ደረቀ "ደርቆ ሞተ"

Matthew 21:20

ማቴዎስ **21**:**20**-**21**
እምነት ካላችሁና የማትጠራጠሩ ከሆነ እነዚህ ሁለት ሀረጎች የሚስተላልፉት ተመሳሳይ ሀሳብ ነው። ሁለት ጊዜ የተጻፈው አጽኖት ለመስጠት ነው። በአንዳንድ ቋንቋዎች ውስጥ አጽኖት መስጫ ሌላ መንገድ አለ። ለተርጓሚዎች ምክር፡ “በእርግጥ ካመናችሁ” ወዲያው ደረቀ "ደርቆ ሞተ"

Matthew 21:23

ማቴዎስ **21**:**23**-**24**

Matthew 21:25

ማቴዎስ **21**:**28**-**30**
ማቴዎስ 21:25-27

ከሰማይ "በሰማይ ካለው እግዚአብሔር” እንዲህ ይለናል "ኢየሱስ እንዲህ ይለናል" ሕዝቡን ፈራን "ሕዝቡ ምን እንደሚያስብ ፈራን ወይም ምን እንደሚያደርግብን ፈራን" ዮሐንስን ነብይ አድርገው ይቆጥሩት ነበር "ዮሐንስ ነብይ እንደሆነ ያምኑ ነበር"

Matthew 21:28

ማቴዎስ **21**:**28**-**30**

Matthew 21:31

ማቴዎስ **21**:**31**-**32**
እንዲህ አሉ "የካህናት አለቆችና ሽምግሌዎች እንዲህ አሉ" ኢየሱስ እንዲህ አላቸው "ኢየሱስ ለካህናት አለቆችና ለሽማግሌዎች እንዲህ አላቸው" ዮሐንስ ወደ እናንተ መጣ ዮሐንስ ወደ ሃይማኖት መሪዎች እና ሕዘቡ መጥቶ ሰበከ። በጽድቅን መንገድ ዮሐንስ ሰዎች እንዴት ለእግዚአብሔት ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው እና መኖር እንዳለባቸው አሳየ

Matthew 21:33

ማቴዎስ **21**:**33**-**34**
ትልቅ መሬት ያለው አንድ ሰው "ብዙ ሀብት ያለው አንድ ሰው" ለወይን ተካዮች መሬቱን አከራየ "ወይን የሚያመርቱ ሰዎችን በቦታው ላይ ሾመ” የወይን እርሻው ባለቤት ግን አሁንም ቢሆን የመሬቱ ባለቤት ነው። የወይን ተክል የሚተክሉ ሰዎች ወይንን እንዴት መትከል እና ማሳደግ እንደሚቻል የሚያውቁ ሰዎች

Matthew 21:35

ማቴዎስ **21**:**35**-**37**
ሠራተኞችን የመሬቱ ባለቤት ሠራተኞች (MAT 21:33)

Matthew 21:38

ማቴዎስ **21**: **38**-**39**

Matthew 21:40

ማቴዎስ **21**:**40**-**41**
ሰዎች እንዲህ አሉት "ሕዝቡ ለኢየሱስ እንዲህ አሉት"

Matthew 21:42

ማቴዎስ **21**:**42**-**42**
ኢየሱስ እንዲህ አላቸው "ኢየሱስ ለሕዝቡ እንዲህ ብሎ ተናገረ" (MAT 21:41) ግንበኞች የናቁት ድንጋጥ የማዕዘን ራስ ሆነ። ለተርጓሚዎች ምክር: "በአናጽዋች የናቁት ድንጋይ በጣም አስፈላጊው ድንጋይ ሆነ።” ባለስልጣናቱ ኢየሱስን ባይቀበሉትም ነገር ግን እግዚአብሔር የመንግስቱ ራስ ያደርገዋል። “ ይህ ከጌታ ነው "ይህንን ታላቅ ለውጥ ያመጣው ጌታ ነው"

Matthew 21:43

ማቴዎስ **21**:**43**-**44**
እላችኋለሁ ኢየሱስ ለካህናት አለቆች እና ሽማግሌዎች እንዲህ አላቸው። ፍሬውን ተንከባቡ "ትክክለኛውን ነገር አድርጉ ፍሬውን "የእግዚአብሔር መንግስ ፍሬ" በዚህ ድንጋይ ላይ የሚወድቅ ማንም ሰው "በዚህ ድንጋይ የሚሰናከል ማንም ቢኖር የሚወድቅበት ማንም ሰው "ፍርዱ የሚመጣበት ማንም ሰው

Matthew 21:45

ማቴዎስ **21**:**45**-**46**
የእርሱ ምሳሌዎች "የኢየሱስ ምሳሌዎች" እጃቸውን በእርሱ ላይ አኖሩ "አሰሩት"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 22

1 ኢየሱስም ደግሞ እንዲህ በማለት በምሳሌ መለሰላቸው፤ 2 "መንግሥተ ሰማይ ለልጁ የሰርግ ድግስ የደገሰ ንጉሥን ትመስላለች። 3 ወደ ሰርጉ እንዲመጡ
ወደ ጋበዛቸው ሰዎች አገልጋዮቹን ላከ፤ እነርሱ ግን መምጣት አልፈለጉም። 4 እንደ ገና ንጉሡ ሌሎች አገልጋዮችን እንዲህ በማለት ላከ፤ "እነሆ፣ እራት
አዘጋጅቻለሁ፤ በሬዎቼንና የሰቡ ወይፈኖቼን አርጀለሁ፤ ሁሉም ተዘጋጅቶአልና ወደ ሰርግ ግብዣው ኑ በሏቸው።' " 5 ሰዎቹ ግን ግብዣውን ከልብ
አልተቀበሉትም። አንዳንዶቹ ወደ እርሻዎቻቸው፣ ሌሎች ደግሞ ወደ ሥራ ቦታቸው ሄዱ። 6 አንዳንዶቹ የንጉሡን አገልጋዮች ደበደቡአቸው፤ አዋረዱአቸው፤
ገደሉአቸው። 7 ንጉሡ ግን ተቈጣ፤ ወታደሮቹን ላከ፤ እነዚያን ነፍሰ ገዳዮች ገደለ፤ ከተማቸውንም አቃጠለ። 8 ከዚያም ለአገልጋዮቹ እንዲህ አለ፤ 'ሰርጉ
ተዘጋጅቶአል፤ ጥሪ የተደረገላቸው ሰዎች ግን የሚገባቸው ሆነው አልተገኙም። 9 ስለዚህ ወደ ዐውራ መንገድ ማቋረጫ ሄዳችሁ የምታገኙአቸውን ያህል ሰዎች
ወደ ሰርጉ ግብዣ ጥሩ። 10 ሰዎቹም ወደ ዐውራው መንገድ ሄደው መልካምም ሆኑ መጥፎዎች ያገኙአቸውን ሁሉ አንድ ላይ ሰበሰቡ። ስለዚህ የግብዣው
አዳራሽ በተጋባዦች ተሞላ። 11 ንጉሡ ተጋባዦቹን ለማየት ሲመጣ ግን፣ የሰርግ ልብስ ያልለበሰ ሰው አየ። 12 ንጉሡ እንዲህ አለው፤ ‹ወዳጄ፣' የሰርግ ልብስ
ሳትለብስ እንዴት ወደዚህ ገባህ?› ሰውየውም ዝም አለ። 13 ከዚያም ንጉሡ ለአገልጋዮቹ እንዲህ አላቸው፤ እጅና እግሩን አስራችሁ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት
ወዳለበት በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጥታችሁ ጣሉት።' 14 የተጠሩ ብዙዎች የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸው።" 15 ከዚያም ፈሪሳውያን ሄደው ኢየሱስን
እንዴት በንግግሩ ማጥመድ እንደሚችሉ ዕቅድ አወጡ። 16 ከዚያም ከሄሮድስ ሰዎች ጋር ደቀ መዛሙርታቸውን ወደ እርሱ ላኩ። ኢየሱስንም እንዲህ አሉት፤
"መምህር ሆይ፣ አንተ በእውነት የእግዚአብሔርን መንገድ የምታስተምር እውነተኛ ሰው መሆንህን እናውቃለን፤ ሰውን በመፍራት ዐሳብህን አትለውጥም፤ በሰዎች
መካከል አድልዎ አታደርግም። 17 እስቲ ንገረን ምን ይመስልሃል? ለቄሳር ግብር መስጠት ተገቢ ነው ወይስ አይደለም?" 18 ኢየሱስ ግን ተንኰላቸውን ዐውቆ
እንዲህ አላቸው፤ "እናንት ግብዞች የምትፈትኑኝ ለምንድን ነው? 19 እስቲ የግብሩን ገንዘብ አሳዩኝ" አላቸው። እነርሱም ዲናሩን አመጡለት። 20 ኢየሱስም፣
"ይህ የማን መልክና ስም ነው?›› አላቸው። 21 እነርሱም፣ "የቄሣር፣" አሉት። ከዚያም ኢየሱስ፣ "እንግዲያስ የቄሣር የሆነውን ለቄሣር ስጡ፤ የእግዚአብሔር
የሆነውን ለእግዚአብሔር ስጡ" አላቸው። 22 ያንን ሲሰሙ ተገረሙ። ትተውትም ሄዱ። 23 በዚያው ቀን ትንሣኤ ሙታን የለም የሚሉ ጥቂት ሰዱቃውያን ወደ
እርሱ መጡ። 24 "መምህር ሆይ፣ ‹አንድ ሰው ልጅ ሳይወልድ ከሞተ ሚስቱን ወንድሙ እንዲያገባና ለወንድሙ ልጅ እንዲወልድለት ሙሴ ተናግሮአል› 25
ሰባት ወንድማማች ነበሩ። የመጀመሪያው አግብቶ ልጅ ሳይወልድ ሞተ። ሚስቱ የወንድምየው ሆነች። 26 ሁለተኛውና ሦስተኛውም እስከ ሰባተኛው ድረስ ያንኑ
አደረጉ። 27 ከሁሉም በኋላ ደግሞ ሴትየዋ ሞተች። 28 እንግዲህ ሰባቱም ወንድማማች አግብተዋት ነበርና በትንሣኤ ቀን የማንኛው ሚስት ልትሆን ነው?"
በማለት ጠየቁት። 29 ኢየሱስ ግን እንዲህ በማለት መለሰላቸው፤ "መጻሕፍትንም ሆነ የእግዚአብሔርን ኀይል ስለማታወቁ ተሳስታችኋል። 30 ምክንያቱም
በትንሣኤ ቀን እንደ ሰማይ መላእክት ይሆናሉ እንጂ፣ አያገቡም፣ ደግሞም አይጋቡም። 31 ትንሣኤ ሙታንን በተመለከተ፣ እግዚአብሔር 32 "እኔ የአብርሃም
አምላክ፣ የይስሐቅ አምላክ፣ የያዕቆብም አምላክ ነኝ" በማለት ለእናንተ የተናገረውን አላነበባችሁምን? እግዚአብሔር የሕያዋን አምላክ እንጂ፣ የሙታን አምላክ
አይደለም።" 33 ሕዝቡ ይህን ሲሰሙ በትምህርቱ ተገረሙ። 34 ኢየሱስ ሰዱቃውያንን ዝም እንዳሰኛቸው ፈሪሳውያን ሲሰሙ፣ በአንድነት ተሰበሰቡ። 35
ከእነርሱ መካከል ሕግ ዐዋቂ የሆነ አንዱ እርሱን ለመፈተን፣ 36 "መምህር ሆይ፣ ከሕጉ ሁሉ የሚበልጠው ትእዛዝ የትኛው ነው" ብሎ ጠየቀው። 37 ኢየሱስም
እንዲህ አለው፤ "እግዚአብሔር አምላክህን በሙሉ ልብህ፣ በሙሉ ነፍስህና በሙሉ ዐሳብህ ውደድ።" 38 ከሁሉም የሚበልጠው የመጀመሪያው ትእዛዝ ይህ
ነው። 39 ሁለተኛውም ትእዛዝ ያንኑ ይመስላል፤ 'ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ።' 40 ሕግና ነቢያት ሁሉ የትመሠረቱት በእነዚህ ሁለት ትእዛዛት ላይ ነው። 41
ፈሪሳውያን በአንድነት ተሰብስበው እያለ ኢየሱስ አንድ ጥያቄ አቀረበላቸው። 42 "ስለ ክርስቶስ ምን ታስባላችሁ? ለመሆኑ የማን ልጅ ነው?" አላቸው።
"የዳዊት ልጅ ነው" አሉት። 43 ኢየሱስም፣ "ታዲያ፣ ዳዊት፣ በመንፈስ፣ 44 ጌታ ጌታዬን ‹ጠላቶችህን በእግርህ ሥር እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ'
በማለት እንዴት ጌታ ብሎ ይጠራዋል? 45 ዳዊት ክርስቶስን 'ጌታ' በማለት ከጠራው እንዴት የዳዊት ልጅ ሊሆን ይችላል?" 46 ማንም አንዲት ቃል ሊመልስለት
አልቻለም፤ ከዚያ ቀን ጀምሮ ጥያቄ ሊያቀርብለት የደፈረ አልነበረም።

Matthew 22:1

ማቴዎስ 22:1-3
መንግሰተ ሰማያት . . . ትመስላለችThe kingdom of heaven is like በ MAT 13:24 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምህ ተመልከት
የተጋበዙት ለተርጓሚዎች ምክር: “ንጉሡ የጋበዛቸው ሰዎች

Matthew 22:4

ማቴዎስ 22:4-4

Matthew 22:5

ማቴዎስ 22:5-7
እነዚህ ሰዎች "የተጋበዙት እንግዶች" (MAT 22:4) ግብዣውን ከቁም ነገር አልቆጠሩትም "የእርሱን ግብዣ ቸል አሉት"

Matthew 22:8

ማቴዎስ 22:8-10
የማቋረጫ መንገድ "መንገዶች የሚገናኙበት ቦታ" አደራሽ ትልቅ ክፍል

Matthew 22:11

ማቴዎስ 22:11-12

Matthew 22:13

ማቴዎስ 22:13-14

Matthew 22:15

ማቴዎስ 22:15-17
ኢየሱስ በሚናገርበት ወቅት እንዴት ያቋርጡት ነበር "ኢየሱስ አንድ ነገር ስናገር በየመኃሉ እያቋረጡት ለክስ የሚሆናቸውን ነገር ለማግኘት ጥረት ያደርጉ ነበር።” ከሄሮዶስ ወገን ከሮማዊያን አገዛዝ ጋር ጓድኛ የሆነው የአይሁድ ንጉሥ የሆነው የሄሮዶስ ተወካዮች እና ተከታዮች በሰዎች መካከል ልዩነት አታደረግም "ለሰዎች የተለየ አክብሮት አትሰጥም " ወይም "በጣም ጠቃሚ ለሚባሉ ሰዎች ትኩርት አትሰጥም"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Matthew 22:18

ማቴዎስ **22:18-19**
ዲናር የአንድ ቀን ደሞዝ የሆነ የሮማዊን ገንዘብ ነው

Matthew 22:20

ማቴዎስ **22:20-22**
የቄሳርን "የቄሳር የሆነው ነገር የእግዚአብሔርን "የእግዚአብሔር የሆነውን ነገር"

Matthew 22:23

ማቴዎስ **22:23- 24**
መምህር ሙሰተ እንዲህ ብሏል “አንድ ሰው ከሞተ ሙሴ በቅዱሳት መጽሕፍት ውስጥ ስለጻፈው ነገር ጠየቁት። በቋንቋችሁ ውስጥ በትቅስ ውስጥ ሌላ ትቅስ መጻፍን የማይፈቅድላችሁ ከሆነ በተዘዋዋር መንገድ ሀሳቡን መግለጽ ትችላላችሁለ “ሙሴ አንድ ሰው ከሞት” (ተመልከት ወንድሙ . . . ምስቱ . . ወንድሙ የሞተው ሰው

Matthew 22:25

ማቴዎስ **22:25-28**
ሁሉም አንዱ ከሌላኛው በኋላ "የሰውዬው ወንድሞች ሁሉ እርሷን ካገቡ በኋላ ሞቱ” ወይም “ሁሉም ወንድሞቹ ከሞቱ በኋላ”

Matthew 22:29

x
ማቴዎስ 22:29-30 የእግዚአብሔርን ኃይል "እግዚአብሔር ምን ማድረግ እንደሚችል"

Matthew 22:31

ማቴዎስ **22:31-33**
እንዲህ የሚል ነገር አላነበባችሁምን . . . ያዕቆብ? "እንዳነበባችሁ አውቃለሁ ነገር ግን ያዕቆብ . . . የሚለውን የተረዳችሁት ግን አይመስልም”

በ . . . ለእናንተ የተነገረው "እገዚአብሔር ለእናንተ የተናገረው እግዚአብሔር እንዲህ ይላል “እኔ . . . ያዕቆብ”? ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ ነው። “እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ አለው። እኔ እግዚአብሔር የአብረሃም አምላ፣ የይሳቅ አምላክ እና የያዕቆብ አምላክ ነኝ።”

Matthew 22:34

ማቴዎስ **22:34-36**
የሕግ ባለሞያዎች የሙሴን ሕግ ጠንቅቀው የሚያውቁት ፈሪሳዊያን

Matthew 22:37

ማቴዎስ **22:37-38**

Matthew 22:39

ማቴዎስ **22:39-40**
ወደዱት ሕግጋቱን ወደዱት MAT 22:37.

Matthew 22:41

x
ማቴዎስ 22:41-42

Matthew 22:43

ማቴዎስ **22:43-44**
ጠላቶችህን የእግር መረገጫ እስካደረግ ድረስ "ጠላቶችን እስካጠፋቸው ድረስ”

Matthew 22:45

ማቴዎስ **22:45-46**
ዳዊት ክርስቶስን “ጌታዬ” ብሎ ከጠራው እንዴት እርሱ የዳዊት ልጅ ሊሆን ይችላል? ለተርጓሚዎች ምክር: “ዳዊት ጌታዬ ብሎ ጠርቶታል ስለዚህ ክርስቶስ ከዳዊት ዘር በላይ ነው ማለት ነው።” ዳዊት ክርስቶስን እንዲህ ብሎ ከጠራው ዳዊት ክርስቶስን “ጌታዬ” ብሎ ከጠራው። ይህ ሊሆን የሚችለው ክርስቶስ የዳዊት ዘር የሆነ ብቻ ሳይን ከዚያም በላይ የሆነ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 23

1 ከዚያም ኢየሱስ ለሕዝቡና ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ ሲል ተናገረ፤ 2 "የአይሁድ የሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን በሙሴ ወንበር ተቀምጠዋል። 3 ስለዚህ
የሚያዝዙአችሁን ሁሉ አድርጉ፤ አክብሩትም። እነርሱ የሚያደርጉትን ግን አታደርጉ፤ ምክንያቱም እነርሱ ራሳቸው የሚናገሩትን አያደርጉትም። 4 ለመሸከም
የሚያስቸግር ከባድ ሸክም አንሥተው በሰዎች ትከሻ ላይ ይጭናሉ። እነርሱ ራሳቸው ግን መሸከም ቀርቶ በጣታቸው ሊያነሡት እንኳ አይፈልጉም። 5 ሥራቸውን
ሁሉ የሚያደርጉት በሰዎች ለመታየት ነው፤ አሸንክታባቸውን ያሰፋሉ፤ የልብሳቸውንም ዘርፍ ያስረዝማሉ። 6 ግብዣ ላይ የከበሬታ ቦታዎችንና በምኵራብ ውስጥ
የተለየ መቀመጫ እንዲሰጣቸው ይፈልጋሉ፤ 7 በገበያ ቦታ ሰዎች የተለየ ክብር እንዲሰጧቸውና፣ 'መምህር ሆይ› በማለት እንዲጠሩአቸው ይፈልጋሉ። 8
እናንተ ግን ያላችሁ አንድ መምህር ብቻ ስለሆነና ሁላችሁም ወንድማማች ስለሆናችሁ ‹መምህር› ተብላችሁ አትጠሩ። 9 በምድር ላይ ማንንም አባት ብላችሁ
አትጥሩ፤ ምክንያቱም በሰማይ የሚኖር አንድ አባት ብቻ አላችሁ። 10 ‹ሊቅም› ተብላችሁ አትጠሩ፤ ምክንያቱም ያላችሁ አንድ ሊቅ ብቻ ነው፤ እርሱም ክርስቶስ
ነው። 11 ከእናንተ መካከል ታላቅ የሆነው አገልጋያችሁ ይሁን። 12 ራሱን ከፍ የሚያደርግ ዝቅ ይላል፤ ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ከፍ ይላል። 13 እናንተ፣ ግብዞች
የአይሁድ የሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን ግን ወዮላችሁ! በሰዎች ፊት መንግሥተ ሰማይን ትዘጋላችሁ። እናንተ ራሳችሁ አትገቡበትም፤ የሚገቡትንም እንዳይገቡ
ትከለክላላችሁ። 14[1] እናንተ ግብዞች የአይሁድ የሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን ለታይታ ረጅም ጸሎታችሁን በማድረግ የመበለቶችን ቤት ስለምትበሉ
ወዮላችሁ! ስለዚህ የበለጠውን ፍርድ ትቀበላላችሁ። እናንተ ግብዞች የአይሁድ ሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን ወዮላችሁ! 15 አንድን ሰው ተከታያችሁ ለማድረግ
በባሕርና በምድር ትሄዳላችሁ፤ ተከታያችሁ ካደረጋችሁት በኋላ፣ ከእናንተ እጥፍ የሚከፋ የገሃነም ልጅ ታደርጉታላችሁ። 16 እናንተ ዕይነ ስውራን መሪዎች
ወዮላችሁ፤ አንድ ሰው 'በቤተ መቅደሱ ቢምል ምንም ማለት አይደለም፤ ቤተ መቅደሱ ውስጥ ባለው ወርቅ ቢምል ግን፣ በመሐላው ይጠመዳል' ትላላችሁ። 17
እናንተ የታወራችሁ ሞኞች፣ ለመሆኑ የትኛው ይበልጣል ወርቁ ወይስ ወርቁን የሚቀድሰው ቤተ መቅደሱ? 18 አንድ ሰው በመሠዊያው ቢምል ምንም ማለት
አይደለም፤ መሠዊያው ላይ ባለው ስጦታ ቢምል ግን በመሐላው ይጠመዳል ትላላችሁ። 19 እናንተ ዕውሮች፤ ለመሆኑ የትኛው ይበልጣል ስጦታው ወይስ
ስጦታውን የሚቀድሰው መሠዊያ? 20 ስለዚህ በመሠዊያው የሚምል በመሠዊያውና እርሱ ላይ ባሉ ነገሮች ሁሉ ይምላል። 21 በቤተ መቅደሱ የሚምል በቤተ
መቅደስና እርሱ ውስጥ በሚኖረው ይምላል። 22 በሰማይ የሚምል በእግዚአብሔር ዙፋንና በእርሱ ላይ በተቀመጠው ይምላል። 23 እናንተ ግብዞች የአይሁድ
የሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን ወዮላችሁ፣ ከአዝሙድ፣ ከእንስላልና ከከሙን ዐሥራት ብታወጡም፣ የሕጉን ዋና ዋና ነገሮች ማለትም ፍትሕን፣ ምሕረትንና
እምነትን ሥራ ላይ አታውሉም። ሌላውን ችላ ሳትሉ እነዚህን መፈጸም ነበረባችሁ። 24 እናንተ ዕይነ ስውራን መሪዎች፣ ትንኝን አውጥታችሁ ትጥላላችሁ፤
ግመልን ግን ትውጣላችሁ! 25 እናንተ ግብዞች የአይሁድ የሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን ወዮላችሁ! የጽዋውንና የሳሕኑን ውጫዊ ክፍል ታጠራላችህ፤ ውስጡ
ግን ቅሚያና ስስት ሞልቶበታል። 26 አንተ ዕውር ፈሪሳዊ፣ ውጫዊ አካሉም ንጹሕ እንዲሆን በመጀመሪያ የጽዋውንና የሳሕኑን ውስጥ አጽዳ። 27 እናንተ
ግብዞች የአይሁድ የሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን ወዮላችሁ! ከውጭ ሲያዩት እንደሚያምር፣ ውስጡ ግን የሞቱ ሰዎች አጥንትና ርኩሰት እንደ ሞላበት መቃብር
ናችሁ። 28 በተመሳሳይ መንገድ እናንተም ከውጭ ለሰዎች ጻድቃን ትመስላላችሁ፤ ውስጣችሁ ግን ግብዝነትና ርኩሰት ሞልቶበታል። 29 እናንተ ግብዞች
የአይሁድ የሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን ወዮላችሁ! የነቢያትን መቃብር ስለምትሠሩ፣ የጻድቃንን መቃብር ስለምታስጌጡ፣ 30 በአባቶቻችን ዘመን ኖረን ቢሆን
ኖሮ፣ የነቢያትን ደም በማፍሰስ አንተባበራቸውም ነበር ትላላችሁ። 31 ስለሆነም የነቢያት ገዳይ ልጆች መሆናችሁን እናንተ ራሳችሁ ትመሰክራላችሁ። 32
እናንተ ራሳችሁም አባቶቻችሁ የጀመሩትን ኃጢአት ትፈጽማላችሁ። 33 እናንተ እባቦች፣ እናንተ የእፉኝት ልጆች፣ ከገሃነም ፍርድ እንዴት ታመልጣላችሁ? 34
ስለዚህ ነቢያትን፣ አስተዋይ ሰዎችንና የአይሁድ ሕግ መምህራንን ወደ እናንተ እልካለሁ። አንዳንዶቹን ትገድላላችሁ፣ ትሰቅላላችሁ፤ ሌሎቹን በምኵራቦቻችሁ
ትገርፋላችሁ፣ ከከተማ ወደ ከተማ ታሳድዳላችሁ። 35 ከጻድቁ ከአቤል አንሥቶ በቤተ መቅደሱና በመሠዊያው መካካል እስከ ገደላችሁት የበራክዩ ልጅ
ዘካርያስ ደም ድረስ፣ በምድር ላይ በፈሰሰው ጻድቃን ደም ሁሉ ትጠየቃላችሁ። 36 እውነት እላችኋለሁ፤ እነዚህ ነገሮች ሁሉ በዚህ ትውልድ ላይ ይሆናሉ። 37
ኢየሩሳሌም፣ ኢየሩሳሌም ሆይ፣ አንቺ ነቢያትን የምትገድዪ ወደ አንቺ የተላኩትን በድንጋይ የምትወግሪ! ዶሮ ጫጩቶችዋን በክንፎቿ ሥር እንደምትሰበስብ
እኔም ልጆችሽን መሰብሰብ ብዙ ጊዜ ፈልጌ ነበር፤ እናንተ ግን አልፈለጋችሁም! 38 ስለሆነም ቤታችሁ ወና ሆኖ ይቀራል። 39 'በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ
ነው' እስክትሉ ድረስ ከአሁን ጀምሮ አታዩኝም እላችኋለሁ።

Footnotes

23:14 [1]በጣም የታወቁ የጥንት ቅጂዎች ቊጥር 14 የላቸውም። (አንዳንድ ቅጂዎች ይህን እዚህና ከቊጥር 12 በኋላ አስገብተውታል)።

Matthew 23:1

ማቴዎስ **23**፡ **1-3**

Matthew 23:4

ማቴዎስ **23**፡**4-5**
ከባድና አስቸጋሪ ሸክም ተብትበው በሰው ትከሻ ይጭናሉ፥ "ተግባራዊ ለማድረግ በጣም አስቸጋሪ የሆኑ ደንቦችን በእናንተ ላይ ይጭናሉ" እነርሱ ግን በጣታቸው ስንኳ ሊነኩት አይወዱም። "ምንም ዓይነት እገዛ ለማድረግ ግን ፈቃደኞች አይደሉም" አሸንክታብ ቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፉበት ወረቀት መያዣው ትንሽ የቆዳ ሳጥን

Matthew 23:6

ማቴዎስ **23**፡**6-7**

Matthew 23:8

ማቴዎስ **23**፡**8-10**
በምድር ላይ ማንንም አባት ብላችሁ አትጥሩ "በምድር ላይ ማንንም አባት ብላችሁ አትጥሩ" ወይም “በምድር ላይ ያለን ማንንም ሰው አባቴ ብላችሁ አትጥሩ" በሰማይ ያለ አንድ አባት አላችሁና እግዚአብሔር አባር የአማኞች ሁሉ “አባት” ነው። አንድ መምህር አለችሁ እርሱም ክርስቶስ ነው ኢየሱስ “ክርስቶስ” ብሎ ስናገር በሦስተኛ መደብ ስለራሱ መናገሩ ነው። ለተርጓሚዎች ምክርለ “እኔ ክርስቶስ፣ እኔ ብቻ የእናንተ መምህር ነኝ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Matthew 23:11

ማቴዎስ **23**፡ **11-12**
ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደረግ "ራሱን በጣም አስፈላጊ የሚያደረግ" ከፍ ከፍ ያለ "ራሱን በጣም አስፈላጊ ያደረገ"

Matthew 23:13

ማቴዎስ **23**፡ **13-15**
አትገባም "እግዚአብሔር በአንተ ላይ እንዲገዛ አትፈቅድ" የመበልቶችን ቤት መበዝበዝ "የሚጠብቃቸው ወንድ ያሌላቸው ሴቶች ትዘርፋለህ” የገሃነም ልጅ "ለገሃነም የተገባህ ሰው" ወይም "ወደ ገሃነም መግባት ያለበት ሰው

Matthew 23:16

ማቴዎስ **23**፡**16-17**
የእውር ምሪት . . . ሞኞች ምንም እንኳ መሪዎቹ ዐይነ ሥውራን ባይሆንም እንደ ተሳቱ ማወቅ አይችሉም ነበር በመጋላ ታሥሯል "ለማድረግ በመጋላ የገባውን ቃል መፈጸም አለበት” ወርቁ ነውን? ወይስ ወርቁን የቀደሰው ቤተ መቅደስ? ኢየሱስ ይህንን ጥቅስ ፈሪሳዊያንን ለመገሰጽ ተጠቅሞበታል።

Matthew 23:18

ማቴዎስ **23**፡**18-19**
ዐይነ ሥውራን መንፈሳዊ ዐይነ ሥውርነት ያለባቸው ሰዎች መባው ነውን? ወይስ መባውን የሚቀድሰው መሠዊያው? ኢየሱስ ይህንን ጥቅስ እንሱ እሰቀድመው የሚያውቁትን ነገር ለማስታወስ ተጠቅሞበታል ስጦታ/መባ በመሰዊያው ላይ በእግዚአብሔር ፊት የሚቀርብ የእንስሳት መስዋዕት ወይም እህል መስዋዕት ነው። አንድ ጊዜ መሰዊያው ላይ ከሆነ ቧላ መስዋእት ይሆናል።

Matthew 23:20

ማቴዎስ **23**፡**20-22**

Matthew 23:23

ማቴዎስ **23**፡**23-24**
ወዮላችሁ በ MAT 23:13 በምን መንገድ እንተረጎምከው ተመልከት መባው ነውን? ወይስ መባውን የሚቀድሰው መሠዊያው? ለምግብ ጥሩ ጣዕም ለመስጠጥ የሚውሉ ቅጠላ ቅጠሎች እና ፍሬዎች ዐይነ ሥውራነት መሪዎች እነዚህ ሰዎች አካላዊ ዐይናቸው አልጠፋም። ኢየሱስ አካላዊ ዐይነ ሥውርነትን ከመንፈሳዊ ዐይነ ሥውርነት ጋር ያነጻጽራል። ትንኝን የምታጠሩ ግመልንም የምትውጡ። በጣም ትንንሽ የሆኑ ንጹሕ እንስሳትን ላለመዋጥ በመጠንቀቅ የትልቁን ንጹሕ ያልሆነ እንስሳ ሥጋ ግን ሆን ብላችሁ ወይም ሳታውቁ ትበላላችሁ ልክ እንደዚሁ በጣም ትንነሽ የሆኑ ሕግጋትን ለመጠበቅ ጥረት ታደርላችሁ ይሂን እንጂ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ሕግጋትን ግን ቸል ትላላችሁ። ለተርጓሚዎች ምክር: "ልክ ትንኝ በምጠጣው ነገር ውስጥ የሚያወጣ ነገር ግን ግመል እንደሚውጥ ሰው ሞኞች ናችሁ።” ትንኝን እንዳይገባ ትንንኝ ወደ አፋቸው እንዳይገባ በጨርቅ አጥልለው ይጠጣሉ ትንኝ ትንንሽ በራሪ ነፍሳት

Matthew 23:25

ማቴዎስ **23**፡**25-26**
ወዮላችሁ በ MAT 23:13 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። የብርጭቆ እና የሣህኑን ውጪ ታጠራላችሁ “ጸሐፍ” እና “ፈርሳዊያን” ከውጪ በሰዎች ፊት “ንጹሕ መስለው” መታየት ይፈልጋሉ። በውስጡ ግን የሙታን አጥንት ርኩሰትም ሁሉ የተሞሉ "ከሚያስፈልጋቸው በላይ እንዲኖራው በጉልበት የሌላ ሰውን ነገር ይወስዳሉ “ ዐይነ ሥውራን ፈሪሳዊያን ፈሪሳዊያን እውነቱን አይረዱትም። አካላዊ ዐይነሥውነት ግን የለባቸውም። ውጭው ደግሞ ጥሩ እንዲሆን አስቀድመህ የጽዋውንና የወጭቱን ውስጡን አጥራ። ልባቸው ከእግዚአብሔር ጋር ትክክል ከሆነ ሕይወታቸውም ይህንኑ ያሳያል።

Matthew 23:27

ማቴዎስ **23**፡**27-28**

Matthew 23:29

ማቴዎስ **23**፡**29-31**

Matthew 23:32

ማቴዎስ **23**፡**32-33**
የአባቶቻችሁን መስፈሪያ ኃጢአት ሙሉ። "አባቶቻችሁ የጀመሩትን ኃጢአት ፈጽሙ" እናንተ እባቦች፥ የእፉኝት ልጆች "ልክ እንደ አደገኛ እና መርዛማ እባቦች ናችሁ" ከገሃነም ፍርድ እንዴት ታመልጣላችሁ? "የገሃነም ፍርድን የሚታመልጡበት ምንም ዓይነት መንገድ የለም!" (ተመልከት:

Matthew 23:34

ማቴዎስ **23**፡**34-36**
ከአቤል . . እስከ ዘካሪያስ አቤል የመጀመሪያው የተገደለ ሰው ነው እንዲሁም ምናልባትም በአይሁዳዊያን ዘንድ በቤተ መቅደስ ውስጥ የተገደለው የመጨረሻው ሰው ነው። ዘካሪያስ ይህ የመጥመቁ ዮሐንስ አባት አይደለም

Matthew 23:37

ማቴዎስ **23**፡ **37-39**
እየሩሳሌም፣ እየሩሳሌም ኢየሱስ በእየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎችን ልክ ከተማዋን እንደሚናገር ሰው ይናገራቸዋል። ልጆቻችሁ የሁሉም እስራኤላዊያን ቤታችሁ የተፈታ ሆኖ ይቀርላችኋል። ለተርጓሚዎች ምክር: “እግዚአብሔር ቤታችሁን ትቶ ይሄዳል ባዶም ይሆናል” ቤታችሁ አማራጭ ትርጉሞች: 1) የኢየሩሳሌም ከተማ ወይም 2) ቤተ መቅደሱ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 24

1 ኢየሱስ ከቤተ መቅደስ ወጥቶ እየሄደ ሳለ፤ ደቀ መዛሙርቱ የቤተ መቅደሱን ሕንጻ ሊያሳዩት ወደ እርሱ መጡ። 2 እርሱ ግን፣ "እነዚህን ሁሉ ነገሮች
ታያላችሁ? እውነት እላችኋለሁ፣ ይፈርሳል እንጂ፣ አንድ ድንጋይ እንኳ በሌላ ድንጋይ ላይ እንደ ተነባበረ አይቀርም" በማለት መለሰላቸው። 3 በደብረ ዘይት ተራራ
ላይ ተቀምጦ እያለ፣ ደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ እርሱ መጥተው፣ "እስቲ ንገረን፤ ይህ ሁሉ የሚሆነው መቼ ነው? የአንተ መምጣትና የዓለም መጨረሻስ
ምልክቱ ምንድን ነው?" አሉት። 4 ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፣ "ማንም እንዳያሳስታችሁ ተጠንቀቁ። 5 ምክንያቱም ብዙዎች በስሜ ይመጣሉ፤ 'እኔ
ክርስቶስ ነኝ' እያሉ ብዙዎችን ያሳስታሉ 6 ጦርነትንና የጦርነትን ዜና ትሰማላችሁ፤ በፍጹም እንዳትታወኩ፤ ምክንያቱም እነዚህ ነገሮች እንዲሆኑ ግድ ነው፤
ቢሆንም፣ መጨረሻው ገና ነው። 7 ሕዝብ በሕዝብ ላይ፣ መንግሥት በመንግሥት ላይ ይነሣል። በተለያየ ቦታ ራብና የምድር መናወጥ ይሆናል። 8 እነዚህ ሁሉ
ግን የምጥ ጣር መጀመሪያ ብቻ ናቸው። 9 ከዚያም ለመከራ አሳልፈው ይሰጧችኋል ይገድሏችኋልም። ስለ ስሜ ሕዝቦች ሁሉ ይጠሏችኋል። 10 ብዙዎች
ይሰናከላሉ፤ እርስ በርስ ይካካዳሉ፤ እርስ በርስ ይጠላላሉ። 11 ብዙ ሐሰተኛ ነቢያት ተነሥተው፣ ብዙዎችን ያሳስታሉ። 12 ዐመፅ ስለሚበዛ የብዙዎች ፍቅር
ይቀዘቅዛል። 13 እስከ መጨረሻ የሚታገሥ ግን ይድናል። 14 ለሕዝቦች ሁሉ ምስክር እንዲሆን የመንግሥቱ ወንጌል ለመላው ዓለም ይሰበካል፤ ከዚያም
መጨረሻው ይመጣል። 15 ስለዚህ በነቢዩ ዳንኤል የተነገረለት የጥፋት ርኩሰት በተቀደሰው ቦታ ቆሞ ስታዩ፣ (ያኔ አንባቢው ያስተውል) 16 በይሁዳ ያሉ ወደ
ተራሮች ይሸሹ፣ 17 ጣራ ላይ ያለ ሰው በቤቱ ያለውን ምንም ነገር ከቤቱ ለመውሰድ አይመለስ፣ 18 በእርሻ ያለ ልብሱን ለመውሰድ አይመለስ። 19 ልጆች
ላሉአቸውና ለሚያጠቡ እናቶች ግን ወዮላቸው! 20 ሸሽታችሁ በክረምት ወይም በሰንበት እንዳይሆን ጸልዩ። 21 ምክንያቱም ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ
አሁን ድረስና ከዚያም በኋላ ፈጽሞ የማይሆን ታላቅ መከራ ይሆናል። 22 እነዚያ ቀኖች ባያጥሩ ኖሮ፣ ማንም ሥጋ ለባሽ አይድንም ነበር፤ ለተመረጡት ሲባል
ግን እነዚያ ቀኖች ያጥራሉ። 23 ስለዚህ ማንም "እነሆ ክርስቶስ፣ እዚህ ነው" ወይም፣ 'ክርስቶስ እዚያ ነው' ቢላችሁ አትመኑ። 24 ምክንያቱም ብዙዎችን
ለማሳሳት ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት መጥተው ታላላቅ ምልክቶችንና ድንቆችን ያደርጋሉ፤ ከተቻለም የተመረጡትን እንኳ ያሳስታሉ። 25 ይህ
ከመሆኑ በፊት አስቀድሜ ነግሬአችኋለሁ። 26 ስለዚህ፣ ‹ክርስቶስ በምድረ በዳ ነው› ቢሏችሁ ወደ ምድረ በዳ አትሂዱ ወይም ቤት ውስጥ ነው ቢሏችሁ
አትመኑ። 27 መብረቅ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ በአንዴ እንደሚታይ የሰው ልጅ ሲመጣ እንደዚያው ይሆናል። 28 የሞተ እንስሳ ባለበት ሁሉ፣ በዚያ አሞሮች
ይሰበሰባሉ። 29 ከእነዚህ የመከራ ቀኖች በኋላ ወዲያውኑ ፀሐይ ትጨልማለች፣ ጨረቃም ብርሃኗን አትሰጥም፤ ከዋክብት ከሰማይ ይወድቃሉ፤ የሰማያት
ኀይላት ይናወጣሉ። 30 ከዚያም የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል፤ የምድር ነገዶች ሁሉ አምርረው ያለቅሳሉ። የሰው ልጅንም በኀይልና በታላቅ ክብር
ሲመጣ ያዩታል። 31 መላእክቱንም ከታላቅ መለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋል፤ እነርሱም፣ ከአንድ የሰማይ ጫፍ እስከ ሌላው ጫፍ ድረስ ከአራቱም ነፋሳት
ምርጦቹን ይሰበስቧቸዋል። 32 ከበለስ ዛፍ ተማሩ። ቅርንጫፎቿ ሲለመልሙና ቅጠሎች ብቅ ብቅ ሲሉ በጋ መቅረቡን ታውቃላችሁ። 33 እናንተም እነዚህን ሁሉ
ስታዩ እርሱ መቅረቡን፣ እንዲያውም በደጅ መሆኑን ዕወቁ። 34 እውነት እላችኋለሁ፣ እነዚህ ሁሉ እስኪፈጸሙ ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም። 35 ሰማይና ምድር
ያልፋሉ ቃሌ ግን ፈጽሞ አያልፍም። 36 ስለዚያች ቀንና ሰዓት ግን ማንም አያውቅም፤ የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ አያወቁም፤ አብ ብቻ እንጂ ወልድ እንኳ ቢሆን
አያውቅም። 37 በኖኅ ዘመን እንደ ነበረው፣ የሰው ልጅ መምጣትም እንዲሁ ይሆናል። 38 ከጥፋት ውሃ በፊት እንደ ነበረው ዘመን፣ ኖኅ ወደ መርከብ እስከ ገባ
ድረስ ይበሉና ይጠጡ፣ ያገቡና ይጋቡ ነበር። 39 ጐርፉ መጥቶ እስኪያጠፋቸው ድረስ ምንም አላወቁም፣ የሰው ልጅ ሲመጣም እንዲሁ ይሆናል። 40 በዚያን
ጊዜ ሁለት ሰዎች በዕርሻ ይሆናሉ፤ አንዱ ይወሰዳል ሌላው ይቀራል። 41 ሁለት ሴቶች በወፍጮ ይፈጫሉ፤ አንዷ ትወሰዳለች ሌላዋ ትቀራለች። 42 ስለዚህ
ጌታችሁ በምን ቀን እንደሚመጣ አታውቁምና ተጠንቀቁ። 43 ይህን ግን ዕወቁ፤ ሌባው በየትኛው ሰዓት እንደሚመጣ የቤቱ ባለቤት ቢያውቅ ኖሮ ይጠነቀቅ
ነበር፤ ቤቱ አይዘረፍም ነበር። 44 የሰው ልጅ ባልጠበቃችሁት ሰዓት ስለሚመጣ እናንተም ብትሆኑ ተዘጋጅታችሁ መጠበቅ አለባችሁ። 45 በተገቢው ጊዜ
ለቤተ ሰቦቹ ምግባቸውን ለመስጠት ጌታው በቤቱ ላይ ጎላፊነት የሰጠው ታማኝና አስተዋይ አገልጋይ ማን ነው? 46 ጌታው ሲመጣ ያንን እያደረገ የሚያገኘው
አገልጋይ የተባረከ ነው። 47 እውነት እላችኋለሁ የምላችሁ፣ ጌታው ባለው ነገር ሁሉ ላይ ጎላፊ አድርጎ ይሾመዋል። 48 ይሁን እንጂ፣ አንድ ክፉ አገልጋይ በልቡ፣
‹‹ጌታዬ ከመምጣት ዘግይቶአል ብሎ ቢያስብ፣ 49 አገልጋይ ጓደኞቹን መደብደብና ከሰካራሞች ጋር መብላት መጠጣት ቢጀምር 50 የዚያ አገልጋይ ጌታ
አገልጋዩ ባልጠበቀው ቀንና በማያውቀው ሰዓት ይመጣበታል። 51 ጌታው ለሁለት ይሰነጥቀዋል፤ ዕጣ ፈንታውን ከግብዞች ጋር ያደርግበታል፣ በዚያም ልቅሶና
ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።

Matthew 24:1

ማቴዎስ **24**:**1**-**2**
ይህን ሁሉ ታያላችሁን? አማራጭ ትርጉሞች: ኢየሱስ እየተናገረ ያው 1) ስለ ቤተ መቅደሱ ግንባታ

Matthew 24:3

ማቴዎስ **24**:**3**-**5**
ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ "ማንም ስለዚህ ጉዳይ እንዳይዋሻችሁ ተጠንቀቁ"

Matthew 24:6

ማቴዎስ **24**:**6**-**8**
አትደናገጡ "እነዚህ ነገሮች አያናውጧችሁ"

Matthew 24:9

ማቴዎስ **24**:**9**-**11**
አሳልፈው ይሰጢ,ጡአችዋል

"የእናንተን መሰደድ የሚወዱ ሰዎች አሳልፈው ይሰጡአችዋል" አሳልፎ መሰጠት በ MAT 10:17 ላይ ምን ብለህ እንዴተረጎምከው ተመልከት።

Matthew 24:12

ማቴዎስ **24**:**12**-**14**
የብዙዎች ፍቅር እየቀዘቀዘ ይመጣል አማራጭ ትርጉሞች: 1) "ብዙ ሰዎች ሌሎች ሰዎችን መውደድ ይተዋሉ" ወይም 2) "ብዙ ሰዎች እግዚአብሔርን መውደዳቸውን ይተዋሉ" በዓለም ሁሉ ለተርጓሚዎች ምክር: “በሁሉም ሥፍራ ያሉ ሁሉም ሰዎች"

Matthew 24:15

ማቴዎስ **24**:**15**-**18**
በነብዩ ዳንኤል የተነገረው ትንቢት ለተርጓሚዎች ምክር: “ነብዩ ዳንኤል በጻፈው ትንቢት መሠረት”

Matthew 24:19

ማቴዎስ **24**: **19**-**22**
ነፍሰ ጡር ያረገዘች ሴት ክረምት "ቀዝቃዛ ወራት" ሥጋ ለባሽ ሰዎች

Matthew 24:23

ማቴዎስ **24**:**23**-**25**
አትመኑ "የሚነግሯችሁን ውሸት አትመኑ"

Matthew 24:26

ማቴዎስ **24**:**26**-**28**
መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ እስከ ምዕራብ እንደሚታይ፥ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናልና፤ አመጣጡ በፍጥነት እና በቀላሉ ለታይ በሚችል መልኩ ነው። የሞተ እንስሳ ባለበት በዚያ ጥንብ አንሳዎች ይሰበሰባሉ አማራጭ ትርጉሞች 1) የሰው ልጅ በመጣ ጊዜ ሁሉም ሰዎች ያዩታል እንዲሁም የእርሱን መምጣት ያውቃሉ ወይም 2) በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የሞቱ ሰዎች ባሉበት ሥፍራ ውሸትን የሚነግሯቸው ሐሰተኛ ነብያት በዚያ አሉ። ጥንብ አንሳ የሞቱ ወይም ሊሞቱ ያሉ እንስሳትን ሥጋ የሚበሉ አእዋፋት

Matthew 24:29

ማቴዎስ **24**:**29**-**29**
ወዲያው "በዚያ ቅጽበት" በእነዚያ ቀናት በ MAT 24:23-28 ላይ የተገለጹት ቀናት አራት ንፈሳት ለተርጓሚዎች ምክር: “ከሰሜን፣ ከደቡብ፣ ከምስራቅ እና ከምዕራብ” ወይም “ከሁሉም አቅጣጫ" የሰማይ ኃይላት ሁሉ ይናወጣሉ ለተርጓሚዎች ምክር: “እግዚአብሔር በሰማይ ያሉትን ነገሮች ሁሉ እና ከሰማይ በላይ ያሉትን ነገሮች ያናውጣል

Matthew 24:30

ማቴዎስ **24**:**30**-**31**
ደረታቸውን ይደቃሉ የሚመጣውን ፍርድ በመፍራት ደረታቸውን ይመታሉ ይሰበሰባሉ "መላዕክቶቹ ይሰበስባሉ" ምርጦቹን የሰው ልጅ የመረጣቸውን ሰዎች ከአራቱም ንፋሳት ለተርጓሚዎች ምክር: “ከሰሜን፣ ከደቡብ፣ ከምስራቅ እና ከምዕራብ” ወይም “ከሁሉም አቅጣጫ"

Matthew 24:32

ማቴዎስ **24**:**32**-**33**
በደጅ እንደቀረበ እወቁ ወራሪ ሠራዊት ከተማዋን ሰብሮ ለመግባት ዝግጁ እንደሆነ

Matthew 24:34

ማቴዎስ **24**:**34**-**35**
ይህ ተውልድ አያልፍም "ዛሬ የሚኖሩ ሰዎች አይሞቱም" ይህ ሁሉ እስኪሆን ድረስ ለተርጓሚዎች ምክር: “እነዚህ ነገሮች እግዚአብሔር እንዲሆኑ እስኪደረግ ድረስ" ሰማይ እና ምድር ያልፋሉ "ሰማይ እና ምድር ሕልውናቸው ያበቃል"

Matthew 24:36

ማቴዎስ **24**:**36**-**36**
የሰው ልጅም ቢሆን "የሰው ልጅ እንኳ"

Matthew 24:37

ማቴዎስ **24**: **37**-**39**
በኖህ ዘመን እንደሆነው የሰው ልጅ መምጣትም እንዲሁ ይሆናል "የሰው ልጅ የሚመጣበት ቀን ልክ በኖህ ዘመን እንደሆነው ነው” ምክንያቱም ማንም መጥፎ ነገር ይሆንብና ብሎ አላሰበም። በዚያ ዘመን እንደሆነው ከጥፋት ውሃ በፊት ይበሉ እና ይጠጡ . . . ጠራርቆ ወሰዳቸው- የሰው ልጅ መምጣትም እንዲሁ ይሆናል "ከሰው ልጅ መምጣት በፊት ያለው ጊዜ ልክ የጥፋት ውሃ ሊመጣ ሲል ያለውን ይመስላል፣ ሁሉም ስበሉና ስጠጡ ሳለ - - - ጠራትቆ ወሰዳቸው”

Matthew 24:40

ማቴዎስ **24**: **40**-**42**
ከዚያ የሰው ልጅ ሲመጣ አንዱ ይወሰዳል ሌላኛው ይቀራል አማራጭ ትርጉሞች: 1) እግዚአብሔር ወደ ሰማይ ይወስደዋል ሌሎቹን ደግሞ ለፍርድ በምድር ላይ ይተዋቸዋ። ወይም 2) መላእክት አንዱ ልፍርድ ይወስዱታል ሌላኛውን ለበረከት ይተውታል ወይም (ተመልከት), MAT 13:40-43). የድንጋይ ወፍጮ እህል ለመከካት የሚሆን እቃ ስለዚህ "ከነገርኳችሁ ነገር የተነሳ" ጸንታችሁ ቁሙ "በንቃት ተከታተሉ"

Matthew 24:43

ማቴዎስ **24**: **43**-**44**
ሌባ ኢየሱስ ልክ እንደ ሌባ ሰዎች ባላሰቡት ሰዓት እንደሚመጣ ተናግሯል፤ ይሁን እንጂ ሊሰርቅ አይደለም የሚመጣው። ነቅቶ ይጠብቅ ነበር ቤቱ እንዳይዘረፍ “ነቅቶ በጠበቀ ነበር” ቤቱም ሊቄፈር ባልተወም ነበር። "ማንም ቤቱ ገብቶ ንረቱን አንድሰርቅ ባላደረገ ነበር"

Matthew 24:45

ማቴዎስ **24**: **45**-**47**
እንኪያስ በጊዜው ይሰጣቸው ዘንድ . . . ታማኝና ልባም ባሪያ ማን ነው? "ታማኝ፣ ልባም ባሪያ ማን ነው? ጌታው በጊዜው . . . እርሱን ነው።” ምግባቸውን ይሰጣቸው ዘንድ "በጌታው ቤት ላሉት ሰዎች ምግባቸውን ይሰጥ ዘንድ"

Matthew 24:48

ማቴዎስ **24**: **48**-**51**
በለልቡ እንዲህ አለ "በአእምሮው እንዲህ አሰበ" እድል ፈንታወን ለመወሰን "ይቀበሉት ዘንድ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 25

1 መንግሥተ ሰማይ መብራታቸውን ይዘው ሙሽራውን ለመቀበል የወጡ ዐሥር ድንግሎችን ትመስላለች። 2 ዐምስቱ ሞኞች፣ ዐምስቱ ልባሞች ነበሩ። 3 ሞኞቹ
ድንግሎች መብራታቸውን ይዘው ሲሄዱ ምንም ዘይት አልያዙም ነበር። 4 ልባሞቹ ግን ከመብራታቸው ጋር ዘይትም ይዘው ነበር። 5 ሙሽራው በዘገየ ጊዜ
እንቅልፍ እንቅልፍ አላቸውና ሁሉም ተኙ። 6 ዕኩለ ሌሊት ላይ ግን፣ “ሙሽራው መጥቶአልና ወጥታችሁ ተቀበሉት!” የሚል ሁካታ ሆነ። 7 ያኔ እነዚያ
ድንግሎች ሁሉ ተነሥተው መብራታቸውን አዘጋጁ። 8 ሞኞቹም ልባሞቹን፣ “መብራታችን እየጠፋ ስለ ሆነ፣ ከዘይታችሁ ጥቂት ስጡን” አሏቸው። 9 ልባሞቹ
ግን፣ “ለእኛና ለእናንተ የሚበቃ ስለሌለን፣ ወደ ሻጮች ሄዳችሁ ለራሳችሁ ግዙ” በማለት መለሱአቸው። 10 ለመግዛት ሲሄዱ፣ ሙሽራው መጣ፤ ተዘጋጅተው
የነበሩት ግብዣው ላይ ለመገኘት ከእርሱ ጋር ሄዱ፤ በሩም ተዘጋ። 11 በኋላ ሌሎቹ ድንግሎች መጥተው፣ “ጌታው፣ በሩን ክፈትልን” አሉ። 12 እርሱ ግን
መልሶ፣ “እውነት እላችኋለሁ፣ አላውቃችሁም” አላቸው። 13 ስለዚህ ቀኑን ወይም ሰዓቱን አታውቁምና ነቅታችሁ ጠብቁ። 14 ነገሩ ወደ ሌላ አገር ለመሄድ ያሰበ
ሰውን ይመስላልና፤ አገልጋዮቹን ጠርቶ በሀብት በንብረቱ ሁሉ ላይ ጎላፊነት ሰጣቸው። 15 እንደ ዐቅማቸው መጠን ለአንዱ ዐምስት መክሊት፣ ለሌላው ሁለት፣
ለሌላው ደግሞ አንድ መክሊት ሰጣቸውና ሄደ። 16 ዐምስት መክሊት የተቀበለው ወዲያውኑ ሄዶ ነገደበት፤ ሌላ ዐምስት አተረፈ። 17 ሁለት መክሊት
የተቀበለውም እንደዚያው ሌላ ሁለት መክሊት አተረፈ። 18 አንድ መክሊት የተቀበለው አገልጋይ ግን ሄዶ ጉድጓድ ቈፈረና የጌታውን ገንዘብ ቀበረ። 19 ከብዙ
ጊዜ በኋላ የእነዚያ አገልጋዮች ጌታ ተመልሶ መጣና ተሳሰባቸው። 20 ዐምስት መክሊት የተቀበለው አገልጋይ ሌላ ዐምስት መክሊት ጨምሮ አመጣና፣ “ጌታ
ሆይ፣ ዐምስት መክሊት ሰጥተኸኝ ነበር፤ እኔ ግን ሌላ ዐምስት መክሊት አተረፍሁ” አለ። 21 ጌታውም፣ 'አንተ መልካምና ታማኝ አገልጋይ ደግ አደረግህ!
በጥቂት ነገሮች ታምነሃል፤ በብዙ ነገሮች ላይ እሾምሃለሁ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ።' አለው። 22 ሁለት መክሊት ተቀብሎ የነበረው አገልጋይም መጥቶ፣ ‘ጌታ
ሆይ፣ ሁለት መክሊት ሰጥተኸኝ ነበር። ሌላ ሁለት መክሊት አትርፌአለሁ’ አለ። 23 ጌታውም፣ 'አንተ መልካምና ታማኝ አገልጋይ ደግ አደረግህ! በጥቂት
ነገሮች ታምነሃል፤ በብዙ ነገሮች ላይ እሾምሃለሁ። ወደ ጌታህ ደስታ ግባ’ አለው። 24 ከዚያም አንድ መክሊት የተቀበለው አገልጋይ መጥቶ፣ 'ጌታ ሆይ፣
ካልዘራህበት የምታጭድ፣ ካልበተንህበት የምትሰበስብ ጨካኝ ሰው መሆንህን አውቃለሁ። 25 ስለዚህ ፈራሁ፤ መክሊትህን መሬት ውስጥ ቀበርሁት።
መክሊትህ ይኸውልህ' አለው። 26 ጌታው ግን መልሶ፣ 'አንተ ዐመፀኛና ሰነፍ አገልጋይ፤ ካልዘራሁበት የማጭድ፣ ካልበተንሁበት የምሰበስብ መሆኔን
ታውቃለህ። 27 ስለዚህ ገንዘቤን በባንክ ማስቀመጥ ይገባህ ነበር፤ እኔ ስመጣ ከነወለዱ እወስደው ነበር' አለው። 28 ስለዚህ መክሊቱን ከእርሱ ወስዳችሁ
ዐሥር መክሊት ላለው ስጡት። 29 ላለው የበለጠ እንዲያውም የተትረፈረፈ ይሰጠዋል። ምንም ከሌለው ግን፣ ያው ያለው ነገር እንኳ ይወሰድበታል። 30 ይህን
የማይረባ አገልጋይ አውጡና ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ወዳለበት በውጭ ወዳለው ጨለማ ጣሉት” አለ። 31 የሰው ልጅ በክብሩ ከመላእክቱ ሁሉ ጋር ሲመጣ፣
በክብር ዙፋኑ ላይ ይቀመጣል። 32 አሕዛብ ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፤ እረኛ በጎችን ከፍየሎች እንደሚለይ ሕዝቡን ይለያቸዋል። 33 በጎቹን በቀኙ፣ ፍየሎቹን
በግራው ያደርጋቸዋል። 34 ከዚያም ንጉሡ በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል፤ 'እናንተ አባቴ የባረካችሁ ኑ፤ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት የተዘጋጀላችሁን መንግሥት
ውረሱ። 35 ተርቤ ነበር ምግብ ሰጣችሁኝ፤ ተጠምቼ ነበር የምጠጣው ሰጣችሁኝ፤ እንግዳ ሆኜ ነበር አስተናገዳችሁኝ፤ 36 ተራቊቼ ነበር አለበሳችሁኝ፤
ታምሜ ነበር ተንከባከባችሁኝ፤ ታስሬ ነበር ጠየቃችሁኝ' ይላቸዋል። 37 ከዚያም ጻድቃን እንዲህ ብለው ይመልሱለታል፣ ‘ጌታ ሆይ፣ ተርበህ ያገኘንህና ያበላንህ
ወይስ ተጠምተህ ያጠጣንህ መቼ ነው? 38 38 እንግዳ ሆነህ ያየንህና ያስተናገድንህ መቼ ነው? ወይም ተራቊተህ ያለበስንህ መቼ ነው? 39 ታምመህ
የተንከባከብንህ ወይስ ታስረህ የጠየቅንህ መቼ ነው?’ 40 ንጉሡም መልሶ እንዲህ ይላቸዋል፤ ‘እውነት እላችኋለሁ፤ ለእነዚህ ታናናሽ ወንድሞቼ ያደረጋችሁትን
ለእኔ አድርጋችሁታል።’ 41 ከዚያም በግራው ያሉትን፣ ‘እናንተ ርጉማን ከእኔ ራቁ፤ ለዲያብሎስና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀው ገሃነም እሳት ሂዱ። 42 ምክንያቱም
‘ተርቤ ነበር አላበላችሁኝም፤ ተጠምቼ ነበር አላጠጣችሁኝም፤ 43 እንግዳ ሆኜ ነበር አልተቀበላችሁኝም፤ ተራቊቼ ነበር አላለበሳችሁኝም፤ ታምሜ፣ ታስሬ ነበር፣
እናንተ ግን አልተንከባከባችሁኝም’ ይላቸዋል። 44 እነርሱም መልሰው እንዲህ ይሉታል፤ ‘ጌታ ሆይ፣ ተርበህ ወይም ተጠምተህ ወይም እንግዳ ሆነህ ወይም
ተራቊተህ ወይም ታምመህ ወይም ታስረህ ያላገለገልንህ መቼ ነው?’ 45 እርሱም መልሶ፣ ‘እውነት እላችኋለሁ፣ ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ አለማድረጋችሁ
ለእኔ አለማድረጋችሁ ነው’ ይላቸዋል። 46 እነዚህ ወደ ዘላለም ቅጣት፣ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ።"

Matthew 25:1

ማቴዎስ 25፡ 1-4
መብራት ይህ እንዲህ ሊሆን ይችላል 1) መብራት ወይም 2) በእንጨት ጫፍ ላይ ጨርቅ በመጠምጠም ጨርቁን በዘይት በመንከር የሚዘጋጅ ችቦ አምስት ሴቶች "አምስት ልጃገረዶች" ትርፍ ዘይት አልያዙም "በመብራታቸው ውስጥ እንጂ ተጠባባቂ ዘይት አልያዙም"

Matthew 25:5

ማቴዎስ 25:5-6
እንቅልፍ ወሰዳቸው "ዐሥሩም ልጃገረዶች ተኙ"

Matthew 25:7

ማቴዎስ 25:7-9
መብራታቸውን አዘጋጁ "በደንብ እንድበራ መብራቸውን አስተካከሉ " ሞኞቹ ለጠቢባኑ እንዲህ አሏቸው "ሞኞቹ ልጃገረዶች ለጠቢባኑ ልጃገረዶች እንዲህ አሏቸው" ዘይታችን ሊያልቅ ነው "በመብራታችን ውስጥ ያለው ዘይት ደምቆ መብረቱን አቁሟል”

Matthew 25:10

ማቴዎስ 25:10-13
ሄዱ "አምስቱ ሞኝ ልጃገረዶች ሄዱ" ዝግጁዎች የሆኑት ተጠባባቂ ዘይት የነበራቸው ልጃገረዶች በሩ ተዘጋ ለተርጓሚዎች ምክር፡ “ብሩን ተዘጋ" ክፈቱልን "ወደ ውስጥ መግባት እንችል ዘንድ በሩን ክፈቱልን" አላውቃችሁም "ማን እንደሆናችሁ አላውቅም”

Matthew 25:14

ማቴዎስ 25፡ 14-16
ይህንን ይመስላል "መንግስ ሰማያት ይህንን ይመስላል" (ተመልከት MAT 25:1) ለሄድ ስነሳ "ለመሄድ ዝግጁ በሆነ ጊዜ” ወይም “ለመሄድ በተነሳ ጊዜ” ሀብቱን አስረከበ "ሀብቱን ይቆጣጠሩለት ዘንድ ስልጣን ሰጣቸው" ሀብቱ "የእርሱ ሀብት" የእርሱ ሀብት መክሊት “አንድ መክሊት” የሃያ ዓመት ደሞዝ ያክላል። ይህንን በዘመናዊ የገንዘብ መጠን አትለውጡት። ምሳሌው በማነጻጸር ላይ ያለው አምስት፣ ሁለት እና አንድ እንዲሁም በጣም ትልቅ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሀብትን ነው። ለተርጓማች ምክር፡ “አምስት ሻንጣ ሙሉ ወርቅ “ ከዚያም አምስት ጠጨማሪ መክሊቶችን አተረፈ “በመክሊቱ ነግዶ አምስት መክሊቶችን አተረፈ”

Matthew 25:17

ማቴዎስ **25**፡ **17**-**18**
ሌላ ሁለት አተረፈ "ሌላ ሁለት መክሊቶችን አተረፈ"

Matthew 25:19

ማቴዎስ **25**፡ **19**-**21**
አምስት ተጨማሪ መክሊቶችን አተረፈ "አምስት ተጨማሪ መክሊቶችን አተረፍኩ" መክሊቶች በ MAT 25:15 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት፡፤ ጥሩ አድርገሃል "ጥሩ አድርገሃል” ወይም “መልካም አድርገሃል”። ባሕላቹ ምናልባት የጌታውን ንግግር ይበልጥ መግለጽ የሚያስችል ቃል ይኖረው ይሆናል።

Matthew 25:22

ማቴዎስ **25**፡ **22**-**23**
ተጨማር መክሊቶችን አተረፍኩ በ MAT 25:20 ላይ እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት። ጥሩ አድርገሃል . . . የጌታው ሰላም በ MAT 25:21 ላይ እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት።

Matthew 25:24

ማቴዎስ **25**፡ **24**-**25**
ካልዘራህባት የምታጭድ ካልበተንህባትም የምትሰበስብ ጨካኝ ሰው መሆንህን አውቃለሁ፤ r እነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ሀሳብን የሚያስተላልፉ ናቸው። አገልጋዩ ጌታውን የእርሱ ያልሆነ ምርትን ይሰበስባል በማለት ይከሰዋል። ለተርጓሚዎች ምክር፡ “ምግብን የአንተ ካልሆነ ማሳ ውሰጥ ትሰበስባለህ” " መዝራት በዚያ ዘመን በመሥመር ከመዝራት ይልቅ በጥቂት በጥቂቱ ይበትኑት ነበር። ተመልከት የአንተ የሆነውን ይኸው ይዜ መጥቻለሁ "ይኼው፣ የአንተን ይዜ መጥቻለሁ"

Matthew 25:26

ማቴዎስ **25**፡**26**-**27**
አንተ ክፉና ሃኬተኛ ባሪያ "አንተ መስራት የማትፈልግ ክፉ ባሪያ ነህ" ካልዘራሁባት እንዳጭድ ካልበተንሁባትም እንድሰበስብ ይህንን ሀሳብ በ MAT 25:24 ላይ እንዴት እንተረጎምክ ተመልከት። ጠራሴን እወሰዳለሁ “የራሴን ወርቅ እወስዳለሁ" ትርፍ ከባንክ በብድር የሚወሰድ ብር ላይ የሚደመር ትርፍ

Matthew 25:28

ማቴዎስ **25**፡ **28**-**30**
ከዚያም የሚበልጥ "የሚበዛ" በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል። "ሰዎች የሚያለቅሱበት እና ጥርሳቸውን የሚያፋጩበት ቦታ"

Matthew 25:31

x
ማቴዎስ 25፡31-33

አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ ለተርጓሚዎች ምክር: "በፊቱ ሕዝቦችን ሁሉ ይሰበስባል" በፊቱ "ከእርሱ ፊት" አሕዛብን ሁሉ "ከሁሉም ሀገራት የተውጣጡ ሕዝቦች" ፍየሎች ፍየሎች መካከለኛ መጠን ያላቸው በአራት እግሮቻቸው የሚራመዱ ከበግ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ አጥቢ እንስሳት ናቸው። ያስቀምጣቸዋል "የሰው ልጅ ያስቀምጣቸዋል"

Matthew 25:34

ማቴዎስ **24**፡ **34**-**36**
ንጉሥ ይህ ኢየሱስ በ MAT 25:31 ላይ ስለ ሰው ልጅ የተናገረው ሌላኛው ሥፍራ ነው። ንጉሥ . . . በቀኙ ኢየሱስ ስለ ራሱ በሦስተኛ መደብ እየጠናገረ ነው። ለተርጓሚዎች ምክር: “እኔ፣ ንጉሡ . . . በቀኜ” ኑ፣ የአባቴ ብሩካን ለተርጓሚዎች ምክር: "ኑ አባቴ የባረካችሁ" አባት ይህ ለእግዚአብሔር የማዕረግ ስም ነው ለእናንተ የተዘጋጀውን መንግስት ውረሱ ለተርጓሚዎች ምክር: “እግዚአብሔር ያዘጋጀላችሁን መንግስት ውረሱ"

Matthew 25:37

ማቴዎስ **25**፡ **37**-**40**
ንጉሥ "የሰው ልጅ" (MAT 25:31) እንዲህ አላቸው "በቀኙ ላሉት እንዲህ አላቸው" ወንድሞች በቋንቋችሁ ወንዶችን እና ሴቶችን የሚካትት ቃል ቃለ ያንን ቃል ተጠቀሙ። ለእኔ አድርጋችኋል "ለእኔ እንዳደረጋችሁት እቆጥረዋለሁ"

Matthew 25:41

ማቴዎስ **25**፡ **41**-**43**
እናንተ ርጉማን "እናንተ እግዚአብሔር የረገማችሁ" ወደ ተዘጋጀላቸው ዘላለማው እሳት ለተርጓሚዎች ምክር: "እግዚብሔር ያዘጋቸው ዘላለማዊ እሳት" መላእክቱ የእርሱ አጋዦች ታርዜ አላለበሳችሁኝም "ታርዜ አላለበሳችሁኝምን” ታምሜ እና ታስሬ "ታምሜ እነ ታስሬ"

Matthew 25:44

ማቴዎስ **25**፡ **44**-**46**
እነርሱም እንዲህ ብለው ይመልሱለታል "በግራው ያሉት" (MAT 25:41) ይመልሱለታል ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ለአንዱ "ከእነዚህ የእኔ ሕዝብ ከሆኑን ለአንዱም” ስላላደረጋችሁ "ለእኔ እንዳላደረጋችሁት አስባለሁ" ወይም "በእርግጥ ያልረዳችሁት እኔን ነው" ዘላለማዊ ቅጣት "ማብቂያ ያሌለው ቅጣት" ጻድቃን ወደ ዘላለም ሕይወት ይገባሉ "ጻድቅ የሆኑ ሰዎች ወደ ዘላለም ሕይወት ይገባሉ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 26

1 ኢየሱስ እነዚህን ቃሎች ተናግሮ በጨረሰ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ አላቸው፤ 2 "ከሁለት ቀን በኋላ ፋሲካ እንደሚሆን ታውቃላችሁ፣ የሰው ልጅም ተሰቅሎ
እንዲገደል ተላልፎ ይሰጣል።" 3 ከዚያ የካህናት አለቆቹና የሕዝቡ ሽማግሌዎች ቀያፋ በሚሉት ሊቀ ካህናት ግቢ ውስጥ ተሰበሰቡ፤ 4 ኢየሱስን በረቀቀ ዘዴ
ለማሰርና ለመግደል ተማከሩ። 5 ምክንያቱም፣ በሕዝቡ መሓል ረብሻ እንዳይነሣ በበዓሉ ሰሞን መሆን የለበትም እያሉ ነበር። 6 ኢየሱስ በቢታንያ በለምጻሙ
ስምዖን ቤት 7 ማዕድ ላይ ተቀምጦ እያለ፣ አንዲት ሴት ዋጋው ውድ የሆነ ሽቱ ያለበት የአልባስጥሮስ ብልቃጥ ይዛ መጣችና ራሱ ላይ አፈሰሰች። 8 ደቀ
መዛሙርቱ ይህን ሲያዩ በጣም ተቈጥተው፣ "ይህ ብክነት ምንድን ነው? 9 ይህ እኮ ከፍ ባለ ዋጋ ተሸጦ ገንዘቡን ለድኾች መስጠት ይቻል ነበር" አሉ። 10
ኢየሱስም ይህን ዐውቆ እንዲህ አላቸው፣ "ይህችን ሴት ለምን ታስቸግሯታላችሁ? ለእኔ መልካም ነገር አድርጋለች። 11 ድኾች ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ናቸው፤ እኔ
ግን ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር አልሆንም። 12 ይህን ሽቱ እኔ ላይ ባፈሰሰች ጊዜ ለቀብሬ አድርጋዋለች። 13 እውነት እላችኋለሁ፣ ይህ ወንጌል በመላው ዓለም
ሲሰበክ ለእርሷ መታሰቢያ እንዲሆን ይህች ሴት ያደረገችውም ይነገርላታል።" 14 ከዚያም የአስቆሮቱ ይሁዳ የሚባለው ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ ወደ ካህናት
አለቆቹ ሄዶ፣ 15 "እርሱን አሳልፌ ብሰጣችሁ ለእኔ ምን ትሰጡኛላችሁ?" አላቸው። እነርሱም ሠላሳ ጥሬ ብር ተመኑለት። 16 ከዚያ ጊዜ ወዲህ እርሱን አሳልፎ
የሚሰጥበትን ምቹ ጊዜ ይጠባበቅ ጀመር። 17 በቂጣ በዓል በመጀመሪያው ግን ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየሱስ መጥተው፣ "የፋሲካን እራት እንድትበላ የት
እንድናዘጋጅልህ ትፈልጋለህ?" አሉት። 18 እርሱም፣ "ከተማው ውስጥ ወዳለ አንድ ሰው ሂዱና፣ 'መምህሩ "ጊዜዬ ደርሷል፤ ከደቀ መዛሙርቴ ጋር ፋሲካን
በአንተ ቤት ማክበር እፈልጋለሁ' ይልሃል በሉት'" አላቸው። 19 ደቀ መዛሙርቱም ኢየሱስ እንደ ነገራቸው አደረጉ፤ የፋሲካንም እራት አዘጋጁለት፡ 20 ምሽት
ላይ ከዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ጋር ለመብላት ተቀመጠ። 21 በመብላት ላይ እያሉ፣ "እውነት እላችኋለሁ፣ ከእናንተ አንዱ አሳልፎ ይሰጠኛል" አላቸው። 22
እነርሱ በጣም ዐዘኑ፤ እያንዳንዱም፣ "እኔ እሆንን?" በማለት ይጠያየቁ ጀመር። 23 እርሱም፣ "አሳልፎ የሚሰጠኝ ከእኔ ጋር እጁን ወደ ሳሕኑ የሚሰደው ነው።
24 የሰው ልጅ ስለ እርሱ እንደ ተጻፈው ይሄዳል፤ የሰውን ልጅ አሳልፎ ለሚሰጠው ግን ወዮለት! ያ ሰው ባይወለድ ይሻለው ነበር" በማለት መለሰላቸው። 25
አሳልፎ የሚሰጠው ይሁዳ፣ "መምህር ሆይ፣ እኔ ነኝ እንዴ?" አለው፤ እርሱም፣ "አንተው ራስህ ብለኸዋል" አለው። 26 በመብላት ላይ እያሉ፣ ኢየሱስ እንጀራ
አንሥቶ ባርኮ ቈረሰ። "እንካችሁ ውሰዱ፣ ብሉት፤ ይህ ሥጋዬ ነው" ብሎ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸው። 27 ጽዋውንም አንሥቶ አመሰገነና ሰጣቸው፤ እንዲህም
አላቸው፤ "ሁላችሁም ጠጡት 28 ይህ ለብዙዎች ኀጢአት ይቅርታ የሚፈስ የኪዳኑ ደሜ ነው። 29 እንደ ገና በአባቴ መንግሥት ከእናንተ ጋር እስክጠጣው
ድረስ ከእንግዲህ ከዚህ ወይን ፍሬ እንደማልጠጣ ግን እነግራችኋለሁ።" 30 መዝሙር ከዘመሩ በኋላ ወደ ደብረ ዘይት ተራራ ወጡ። 31 ያኔ ኢየሱስ፣ "በዚህ
ሌሊት ሁላችሁም በእኔ ምክንያት ትሰናከላላችሁ፤ ምክንያቱም፣ 'እረኛውን እመታለሁ በጎቹም ይበተናሉ' ተብሎ ተጽፎአል። 32 ከተነሣሁ በኋላ ግን ቀድሜአችሁ
ወደ ገሊላ እሄዳለሁ" አላቸው። 33 ጴጥሮስ ግን፣ "ሁሉም በአንተ ቢሰናከሉ እንኳ እኔ አልሰናከልም" አለው። 34 ኢየሱስም፣ "እውነት እልሃለሁ ፣ በዚህች
ሌሊት ዶሮ ከመጮኹ በፊት ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ" አለው። 35 ጴጥሮስም፣ "ከአንተ ጋር መሞት ቢኖርብኝ እንኳ አልክድህም" አለ። ሌሎችም ደቀ
መዛሙርት ሁሉ እንደዚያው አሉ። 36 ከዚያም ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር ጌቴሴማኒ ወደሚሉት ቦታ ሄደ፤ ደቀ መዛሙርቱንም፣ "ወደዚያ ሄጄ እስክጸልይ ድረስ እዚህ
ሁኑ" አላቸው። 37 ጴጥሮስንና ሁለቱን የዘብዴዎስ ልጆች ይዞ ሄደ፤ ያዝንና ይጨነቅም ጀመር። ከዚያም፣ 38 "ነፍሴ፣ እስከ ሞት ድረስ በጣም ዐዝናለች። እዚህ
ሆናችሁ ከእኔ ጋር ትጉ" አላቸው። 39 ጥቂት ራቅ ብሎ በመሄድ በግንባሩ ወድቆ ጸለየ፤ "አባት ሆይ፣ የሚቻል ከሆነ ይህ ጽዋ ከእኔ ይለፍ፤ ይሁን እንጂ፣ የእኔ
ፈቃድ ሳይሆን የአንተ ፈቃድ ይሁን" አለ። 40 ወደ ደቀ መዛሙርቱ ሲመጣ ተኝተው አገኛቸው፤ ጴጥሮስንም፣ "ከእኔ ጋር አንድ ሰዓት ያህል እንኳ መትጋት
አልቻላችሁምን? 41 ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ። መንፈስ በእርግጥ ፈቃደኛ ነው፤ ሥጋ ግን ደካማ ነው" አለው። 42 ለሁለተኛ ጊዜ ጥቂት ፈቀቅ ብሎ
ጸለየ፤ "አባት ሆይ፣ እኔ ካልጠጣሁት በቀር ይህ የማያልፍ ከሆነ፣ ፈቃድህ ይሁን" አለ። 43 እንደ ገና ሲመጣ ዐይኖቻቸው ከብደው ነበርና ተኝተው አገኛቸው።
44 እንደ ገና ትቶአቸው ሄዶ ለሦስተኛ ጊዜ ያንኑ ቃል ጸለየ። 45 ከዚያም ኢየሱስ ወደ ደቀ መዛሙርቱ መጥቶ፣ "አሁንም ዐርፋችሁ ተኝታችኋል? ጊዜው ደርሷል፤
የሰው ልጅ በኀጢአተኞች እጅ ተላልፎ ይሰጣል። 46 እንግዲህ ተነሡ እንሂድ አሳልፎ የሚሰጠኝ ቀርቧል" አላቸው። 47 ገና እየተናገረ እያለ፣ ከዐሥራ ሁለቱ
አንዱ የሆነው ይሁዳ መጣ፣ ከእርሱም ጋር ከካህናት አለቆችና ከሕዝቡ ሽማግሌዎች የመጡ ሰይፍና ዱላ የያዙ ብዙ ሰዎች ነበሩ። 48 በዚህ ጊዜ አሳልፎ
የሚሰጠው፣ "እኔ የምስመው እርሱ ነው፤ ያዙት" የሚል ምልክት ሰጣቸው። 49 ወዲያውኑ ወደ ኢየሱስ መጥቶ፣ "መምህር ሆይ፣ ሰላም ለአንተ ይሁን!" ብሎ
ሳመው። 50 ኢየሱስም፣ "ወዳጄ፣ የመጣህበትን ጉዳይ ፈጽም" አለው። ከዚያም መጡ ኢየሱስ ላይ እጆቸውን ጫኑ፣ ያዙትም። 51 ከኢየሱስ ጋር ከነበሩት
አንዱ እጁን ዘርግቶ ሰይፍ አወጣ፤ የሊቀ ካህናቱን አገልጋይ ጆሮ መትቶ ቈረጠ። 52 ያኔ ኢየሱስ፣ "ሰይፍህን ወደ ቦታው መልስ፤ ሰይፍ የሚያነሡ በሰይፍ
ይጠፋሉ። 53 አባቴን ብጠይቅ በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ መላእክት የማይልክልኝ ይመስልሃል? 54 እንደዚያ ከሆነ ይህ እንደሚሆን የሚናገረው መጽሐፉ ቃል
እንዴት ይፈጸማል?" አለው። 55 በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ለሕዝቡ፣ "ወንበዴን እንደምትይዙ ሰይፍና ዱላ ይዛችሁ መጣችሁ? በየቀኑ በቤተ መቅደስ ተቀምጬ
እያስተማርሁ ነበርሁ። እናንተም አልያዛችሁኝም ነበር። 56 የነቢያት መጽሐፍ እንዲፈጸም ይህ ሆኗል" አላቸው። ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ትተውት ሸሹ።
57 ኢየሱስን የያዙ ሰዎች የአይሁድ የሕግ መምህራንና ሽማግሌዎቹ ተሰብስበው ወደ ነበሩበት ወደ ሊቀ ካህናቱ ወደ ቀያፋ ቤት ወሰዱት። 58 ጴጥሮስ ግን
ከሩቅ ሆኖ እስከ ሊቀ ካህናቱ ግቢ ድረስ ተከተለው፤ ወደ ውስጥ ገብቶም የሚሆነውን ለማየት ከጠባቂዎቹ ጋር ተቀመጠ። 59 እርሱን ለማስገደል የካህናት
አለቆቹና ሸንጎው ሁሉ በኢየሱስ ላይ በሐሰት የሚመሰክሩበትን ሰዎች እየፈለጉ ነበር። 60 ምንም እንኳ ብዙ የሐሰት ምስክሮች ቢመጡም፤ በቂ ማስረጃ
አላገኙም። በኋላ ግን ሁለት ሰዎች ወደ ፊት መጥተው፣ 61 "ይህ ሰው፣ 'የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ አፍርሼ በሦስት ቀን ውስጥ እንደ ገና ልሠራው
እችላለሁ' ብሏል" አሉ። 62 ሊቀ ካህናቱ ተነሥቶ፣ "መልስ የለህም? በአንተ ላይ እየመሰከሩብህ ያለው ምንድን ነው?" አለው። 63 ኢየሱስ ግን ዝም አለ። ሊቀ
ካህናቱም፣ "በሕያው እግዚአብሔር አዝሃለሁ፤ አንተ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆን አለመሆንህን ንገረን" አለው። 64 ኢየሱስም፣ "አንተው ራስህ አልህ፤
ግን ልንገርህ፣ ከአሁን ጀምሮ የሰው ልጅ በኀይል ቀኝ በሰማይ ደመና ሲመጣ ታያለህ" በማለት መለሰለት። 65 ከዚያም ሊቀ ካህናቱ ልብሱን ቀደደና፣
"እግዚአብሔርን ተሳድቧል፤ ታዲያ፣ ምስክር የምንፈልገው ለምንድን ነው? አሁን ስድቡን ሰምታችኋል 66 ለመሆኑ፣ ምን ታስባላችሁ?" አለ። እነርሱም
መልሰው፣ "ሞት ይገባዋል" አሉ። 67 ከዚያም ፊቱ ላይ ተፉበት፣ በጡጫና በጥፊ መቱት፤ 68 "አንተ ክርስቶስ እስቲ ትንቢት ተናገር። ለመሆኑ፣ በጥፊ
የመታህ ማን ነው?" አሉት። 69 በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ እደጅ ግቢው ውስጥ ተቀምጦ ነበር፤ አንዲት አገልጋይ ልጅ ወደ እርሱ መጥታ፣ "አንተም ደግሞ
ከገሊላው ኢየሱስ ጋር ነበርህ" አለችው። 70 እርሱ ግን፣ "ምን እየተናገርሽ እንደ ሆነ አላውቅም" በማለት በሁሉም ፊት ካደ። 71 ከግቢው ወደሚያስወጣው
በር እየሄደ እያለ፣ ሌላ አገልጋይ ልጅ አየችውና እዚያ ለነበሩት፣ "ይህኛውም ሰውየ ከናዝሬቱ ኢየሱስ ጋር ነበረ" አለች። 72 እርሱም፣ "ሰውየውን አላውቀውም"
በማለት በመሐላ ጭምር በድጋሚ ካደ። 73 ጥቂት ቆየት ብሎ እዚያ ቆመው የነበሩት መጥተው ጴጥሮስን፣ "በርግጥ አንተም ብትሆን ከእነርሱ አንዱ ነህ፤

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አነጋገርህ ራሱ ያጋልጥሃል" አሉት። [74] ከዚያም፣ "ሰውየውን ጨርሶ አላውቀውም" በማለት ይራገምና ይምል ጀመር፤ ወዲያውኑ ዶሮ ጮኸ። [75] ጴጥሮስ "ዶሮ ሳይጮኽ ሦስቴ ትክደኛለህ" በማለት ኢየሱስ የተናገረውን አስታወሰ። ከዚያ ወደ ውጭ ወጥቶ ምርር ብሎ አለቀሰ።

Matthew 26:1

ማቴዎስ **26**:**1**-**2**
በፈጸመ ጊዜ፥ በቋንቋችሁ አዲስ ታሪክ መጀመሪያን ማሳያ መንገድ ካለ ያንን ተጠቀሙ። እነዚህ ቃላትን በ MAT 24:4-25:46 ውስጥ ያሉትን ቃላት የሰው ልጅ እንዲሰቀል አሳልፈው ይሰጡታል "አንዳንድ ሰዎች የሰው ልጅን ለሚሰቅሉት አሳልፈው ይሰጡታል"

Matthew 26:3

ማቴዎስ **26**:**3**-**5**
ተሰበሰቡ "በምስጥር" በበዓል ቀን ግን አይደለም ለተርጓሚዎች ምክር: “በበዓል ቀን ኢየሱን መግደል የለብንም” በዓል ዓመታዊ የፈስካ በዓል

Matthew 26:6

ማቴዎስ **26**:**6**-**9**
ምግብ ለመብላት ተቀምጠው ሳለ በጎናቸው ጋደም ብለው። ሰዎች ምግብ ለመመገብ የሚቀመጡበትን መንገድ የሚገልጽን ቃል መጠቀም ትችላለህ። አንድት ሴት ወደ እርሱ መጥታ አንድደት ሴት ወደ ኢየሱስ መጥታ የአልባስጥሮስ ጠርሙስ ከለስላሳ ድንጋይ የሚሰራ በጣም ውድ መያዥያ ነው ሽቶ ጥሩ መዓዛ ያለው ዘይት የዚህ ብክነት ምክንያቱ ምንድ ነው? "ይህች ሴት ይህንን ሽቶ በማባከኗ መጥፎ ነገር አድርጋለች!"

Matthew 26:10

ማቴዎስ **26**: **10**-**11**
ይህችን ሴት ስለምን ታስጨንቋታላችሁ? "ይህችን ሴት ልታስጨንቋት አይገባም!" እናንተ . . . እናንተ . . . አናንተ ደቀ መዛሙርቱ

Matthew 26:12

ማቴዎስ **26**: **12**-**13**

Matthew 26:14

ማቴዎስ **26**: **14**-**16**
ለእነርሱ አሳልፎ ይሰጣቸው ዘንድ “አሳልፌ እንድሰጣችሁ” ወይም "ኢየሱስን መያዝ ትችሉ ዘንድ" ሠላሣ ብር ይህ ቃል በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከሚገኘው የትንቢት መልዕክት ጋር ተመሳሳይ ቃል በመሆኑ የገንዘቡን መጠን በዘመናዊ የገንዘብ መጠን ከመጻፍ ይልቅ እንዳለ ማስቀመጡ ተመራጭ ነው። ለእነርሱ አሳልፎ ለመስጠት "የካህናት አለቆች ኢየሱስን ይዙት ዘንድ ለማገዝ”

Matthew 26:17

ማቴዎስ **26**: **17**-**19**
እርሱም፦ ወደ ከተማ ከእገሌ ዘንድ ሄዳችሁ፦ መምህር፦ ጊዜዬ ቀርቦአል፤ ከደቀ መዛሙርቴ ጋር ከአንተ ዘንድ ፋሲካን አደርጋለሁ ይላል በሉት አለ።" ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ለሌላ ሰው ሄደው የኢየሱስን መልክት እንድነገሩት ነገራቸው። ለተርጓሚዎች ምክር: “ለደቀ መዛሙርቱ ወደ ከተማ እንዲሄዱ፣ ወደ አንድ ሰው ቤትም እንዲሄዱና መምህር እንዲህ ይልሃል ብለው እንድነግሩት ነገራቸው። “ጊዜዬ ቀርቦአል። ከደቀ መዛሙርቴ ጋር ፋስካን በአንተ ቤት ማሳለፍ እፈልጋለሁ” ብሏል ብላችሁ ንገሩት። ወይም “ ደቀ መዛሙርቱ ወደ አንድ ሰው ዘንድ እንዲሄዱና መምህራቸው ጊዜዬ ቀርቧል፤ ፋስካን በአንተ ቤት ከደቀ መዛሙርተቼ ጋር ማሳለፍ እፈልጋለሁ ብለው ይነግሩት ዘንድ ላካቸው።” ጊዜዬ አማራጭ ትርጉሞች: 1) "የነገርኳችሁ ጊዜ" (UDB) or 2) "እግዚአብሔር ለእኔ አስቀድሞ ያዘጋጀው ጊዜ" ቀርቧል አማራጩ ትርጉሞች: 1) "ቅርብ ነው" ፋስካን ማክበር "የፋስካን መብል መብላት" ወይም "ልዩ የሆነ ምግብ በመብላት ፋስካን ማክበር"

Matthew 26:20

ማቴዎስ **26**: **20**-**22**
ምግብ ልመገብ ተቀመጠ በባሕላችሁ ሰዎች ምግብ ለመመገብ የሚቀመጡበትን መንግድ የሚገለጽ ቃልን ተጠቀሙ። ጌታዬ እኔ በእርግጠኝነት አይደለሁም? "በእርግጠኝነት እኔ አይደለሁም፣ ነኝ እንዴ ጌታዬ?"

Matthew 26:23

ማቴዎስ **26**: **23**-**25**
የሰው ልጅን አሳልፎ የሚሰጥ ሰው "የሰው ልጅን የሚከዳ ሰው" አንተ ራስህ አልክ "አንተ ራስህ እንዳልከው አንተ ነህ" ወይም "አንተ ራስህ አሁን አመንክ"

Matthew 26:26

ማቴዎስ **26**: **26**-**26**
ወሰደ . . . ባረከው . . . ሰበረው ይህንን በ MAT 14:19 ላይ በተረጎምከው መሠረት ተርጉመው።

Matthew 26:27

ማቴዎስ **26**: **27**-**29**
ወሰደ ይህንን በ MAT 14:19. ላይ በተረጎምከው መሠረት ተርጉመው። ሰጣቸው "ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸው" ስለቃል ኪዳኑ የሚፈሰው ደሜ ነው "ኪዳኑ የጸና መሆኑን የሚያሳይ ደም ነው”ወይም “ኪዳን እንዲቻል ደረገ ደም ነው" የሚፈሰው "በሞቱ ጊዜ የሚፈሰው” ወይም “በቅርቡ ከአካሌ የሚፈሰው” ወይም ስሞት ከአካሌ የሚፈስ ደም ነው” የወይንን ፍሬ "ወይን" በአባቴ መንግስት ውስጥ አዲሱን ከእናንተ ጋር እስከሚጠጣት ጊዜ ድረስ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው፣ ደሙ በእርሱ ለሚያምኑት ከአባት ዘንድ የዘላለም የኃጢአት ይቅርታን ያስገኘው ኢየሱስ አባቱ በመስቀል ላይ የቀረበውን መስዋእት መርካቱን የሚያከብርበት ነው። “አባት” እና “ልጅ” የሚለው ቃል በሥላሴ አካላት መካከል መቀራረብ እና ቤተሰባዊ ህብረት ያለ መሆኑን የሚያሳይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል በመሆኑን እንዳለ በቁሙ መቀመጥ ይኖርበታል።

Matthew 26:30

ማቴዎስ **26**: **30**-**32**
መዝሙር ለእግዚአብሔር የሚቀርብ የሚስጋና መዝሙር ይወድቃሉ "ትተውኝ ይሄዳሉ" የመንጋውም በጎች ይበተናሉ ለተርጓሚዎች ምክር: 1) "ሁሉን የበጎች መንጋዎች ይበተናሉ " (UDB) ወይም 2) "የበጎች መንጋዎቹ በሁሉም አቅጣጫ ይበተናሉ" የበጎች መንጋ ደቀ መዛሙርቱ ከተነሳሁ በኋላ ለተርጓሚዎች ምክር: "እግዚአብሔር ካስነሳኝ በኋላ"

Matthew 26:33

ማቴዎስ **26**: **33**-**35**
ይበተናሉ ይህንን በ MAT 26:31 ላይ በተረጎምከው መሠረት ትረጉም ዶሮ ሳይጮኽ ለተርጓሚዎች ምክር: "ፀሐይ ከመውጣቱ በፊት" ዶሮ ከመጮኹ rooster ልነጋጋ ሲል ዶሮ የሚያሰማቸው ከፍተኛ ጩኸት የዶሮ ጩኸት ዶሮ የሚያሰማው ጩኸት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Matthew 26:36

ማቴዎስ **26**፡ **36**-**38**
ኃዘን በጣም አዘነ

Matthew 26:39

ማቴዎስ **26**፡ **39**-**41**
በፊቱ ወድቆ ለመጸለይ ሆን ብሎ ፊቱን በመሬት ላይ መድፋት አባቴ ይህ በእግዚአብሔር እና በኢየሱስ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያሳይ የእግዚአብሔር የማዕረግ ስም ነው ይህ ጽዋ ከእኔ ይለፍ ከ “ይህ ጽዋ” የሚለው ቃል ኢየሱስ ሊያልፈበት ያለውን መከራ የሚያመለክት ነው። ይሁን እንጂ የእኔ ፈቃድ ሳይሆን የአንተ ፈቃድ ይሁን ይህ በሙሉ ዐዓረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። ለተርጓሚዎች ምክር፡ “እኔ የሚፈልገው አታደርግ ነገር ግን አንተ የሚትፈልገውን አድርግ”"

Matthew 26:42

x
ማቴዎስ 26፡ 42-44

ሄደ "ኢየሱስ ሄደ" እኔ ካልጠጣሁት "የዚህ የመከራ ጽዋ የማልጠጣ ከሆነ" አባቴ ይህ በእግዚአብሔር እና በኢየሱስ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያሳይ የእግዚአብሔር የማዕረግ ስም ነው ዓይኖቻቸው በእንቅልፍ ከብደው ነበር "እንቅልፍ ይዞዋቸው ነበር"

Matthew 26:45

ማቴዎስ **26**፡ **45**-**46**
ሰዓቲቱ ቀርባለች "ጊዜው ቀርቧል" በኃጢአተኞች እጅ "ኃጢአተኞች" ተመልከቱ "አሁን ለምናገረው ነገር ትኩረት ስጡ"

Matthew 26:47

ማቴዎስ **26**፡ **47**-**48**
በመናገር ላይ ሳለ "ኢየሱስ እየተናገረ ሳለ" እንዲህ አለ “የሚስመው እርሱ ነውና ያዙት” "እርሱ የሚስመው እርሱ ነውና ያዙት” የሚስመው "አሁን የሚስመው" ወይም "እኔ የሚስመው ሰው" (UDB) መሳም ለአንድ ታላቅ መምህር የሚቀርብ አክብሮት

Matthew 26:49

ማቴዎስ **26**፡ **49**-**50**
ወደ ኢየሱስ መጥቶ "ይሁዳ ወደ ኢየሱስ መጥቶ" ሳመው "በመሳም ሰላም አለው" ኢየሱስን ያዙት ኢየሱስን ልጎዱት ያዙት ያዙት እስረኛ አደረጉት

Matthew 26:51

ማቴዎስ **26**፡ **51**-**54**
እነሆ ጸሐፊው አዲስ ሰውን በታሪኩ ውስጥ አካቷል። በቋንቋችሁ ይህንን ለማደረግ የሚያስችል መንገድ ሊኖር ይችላል። አባቴን እንድለምን እርሱም አሁን ከአሥራ ሁለት ጭፍሮች የሚበዙ መላእክት እንዲሰድልኝ የማይቻል ይመስልሃልን? ለተርጓሚዎች ምክር: "አባቴን መጥራት እንደሚችል፣ እርሱ ደግሞ ከዐሥራ ሁለት ጭፍሮች በላይ መላእክትን ልልክልኝ እንደሚችል ማወቅ ነበረባችሁ።” አባቴ ይህ በእግዚአብሔር እና በኢየሱስ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያሳይ የእግዚአብሔር የማዕረግ ስም ነው ከዐሥራ ሁለት ጭፍሮች በላይ መላእክት የመላእክቱ ትክክለኛ ቁጥት ይህን ያኽል አስፈላጊ አይደለም ጭፍሮች የሮማዊያን ሠራዊት አከፋፈል ሆኒ አንዱ ስድት ሺህ ወታደሮችን ይይዛል

Matthew 26:55

ማቴዎስ **26**፡ **55**-**56**
ወንበዴን እንደምትይዙ ሰይፍና ጐመድ ይዛችሁ ልትይዙኝ ወጣችሁን? ለተርጓማች ምክር: “እኔ ወንበዴ እንዳልሆንኩ ታውቃላችሁ ስለዚህ እኔት ለመያዝ ሰይፍ እና ጎመድ ይዛችሁ መምጣታችሁ ስህተት ነው።” ጎመድ ሰዎችን ለመምታት የሚሆን ጠንካራ ደረቅ ዱላ ተውት በቋንቋችሁ ከእርሱ ጋር መሆን ስገባቸው ትተውት መሄዳቸውን ለማመልከት የሚሆን ቃል ካለ ይህንን ቃል ተጠቀሙ።

Matthew 26:57

ማቴዎስ **26**፡ **57**-**58**

Matthew 26:59

ማቴዎስ **26**፡ **59**-**61**
ሁለት ሰዎች ወደፊት መጥተው "ሁለት ሰዎች ቀርበው” (UDB) ወይም "ሁለት ምስክሮች ቀርበው" “እነዚህ ሰዎች እንዲህ አሉ፣ እኔ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ አፍርሼ በሦስት ቀን ውስጥ እንደገና እገነባለሁ” ለተርጓሚዎች ምክር: "የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ አፍርሶ በሦስት ቀናት ውስጥ መልሶ እንደሚገነባ ስናገር ሰምተናል ብለው መሰከሩበት” ይህ ሰው እንዲህ አለ "ይህ ሰው ኢየሱስ እንዲህ አለ"

Matthew 26:62

ማቴዎስ **26**፡ **62**-**64**
በእርሱ ላይ መሰከሩበት "ምስክሮቹ በኢየሱስ ላይ መሰከሩ" የእግዚብሔር ልጅ ይህ በክርስቶስ እና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያሳይ በጣም አስፈላጊ የሆነ ስም ነው። አንተ ራስህ አልህ ኢየሱስ ራሱ እርሱ “ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ” አረጋግጧል። ለተርጓሚዎች ምክር: “አንተው ራስህ እንዳልከው ነኝ” ወይም “አንተ ራስህ አሁን አመንክ” ነገር ግን እላችኋለሁ፥ እንግዲህ ወዲህ ኢየሱስ ለሊቀ ካህኑ እና በዚያ ላሉት ሰዎች በመመናር ላይ ነው። እንግዲህ ወዲህ የሰው ልጅ በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ አማራጭ ትርጉሞች ›: 1) የሰው ልጅን ወደፊት የሆነ ጊዜ ያዩታል ወይም 2) “አሁን” የሚለው ቃ የሚያመለክተው የሰው ልጅ የሞተበትን፣ ከሞቱ የተነሳበትን እና ወደ ሰማይ ያረገዘበት ጊዜ ነው። በኃይል ቀኝ "ሁሉን ቻይ በሆነው በእግዚአብሔር ቀኝ” በሰማይም ደመና ሲመጣ "በሰማይ ዳመና ሆኖ ወደ መሬት ሲመጣ"

Matthew 26:65

ማቴዎስ **26**፡ **65**-**66**
ሊቀ ካህኑ ልብሱን ቀደደ ልብስ መቅደድ የሚያሳዝን ነገር በመሆኑ የተከሰተ ንዴት ምልክት ማሳያ ነው። እንዲህ ሲሉ መለሱለት "የአይሁድ መሪዎች እንዲህ ሲሉ መለሱለት"

Matthew 26:67

ማቴዎስ **26**፡ **67**-**68**
ከዚያ እነርሱ አማራጭ ትርጉሞች፡ “ከዚያም ከእነርሱ መካከል አንዳንዶቹ” ወይም “ከዚያ ወታደሮቹ” ፊቱ ላይ ተፉበት ይህ ስድብ ነው ትንቢት ንገረን በዚህ ሥፍራ “ትንቢት ንገረን” ማለት “በእግዚአብሔር ኃይል ንገረን” ማለታቸው እንጂ “ወደፊት የሚሆነውን ነገር ንገረን ማለታቸው አይደልም”

Matthew 26:69

ማቴዎስ **26**፡ **69**-**70**
እናንተ ስለምትሉት ነገር የማውቀው ነገር የለኝም ጴጥሮስ ይህች ገረድ እያለች ያለው ነገር ገብቶታል። ከኢየሱስ ጋር የነበረ መሆኑን ለመካድ ይህንን ቃል ተጠቀሟል።

Matthew 26:71

ማቴዎስ **26**፡ **71**-**72**
እንዲህ ሲል "ጴጥሮስ እንዲህ ባለ ጊዜ" መግቢያ በግቢው አጥር መግቢያ በር

Matthew 26:73

ማቴዎስ **26**፡ **73**-**75**
ከእነርሱ አንዱ "ከኢየሱስ ጋር ከነበሩት አንዱ ነው" የንግግር ቅላጼህ ያስታውቃል "ከገሊላ እንደሆንክ ከንግግርህ ቅላጼ ማወቅ እንችላለን ምክንያቱም የሚትናገረው እንደ ገሊላ ሰዎች ነው።" እምላለሁ “ይህን ሰው ፈጽሞ አላውቀውም” ለተርጓሚዎች ምክር: “ይህን ሰው አላውቀውም”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 27

1 ጠዋት በማለዳ የካህናት አለቆቹና የሕዝቡ ሽማግሌዎች ሁሉ ኢየሱስን ለመግደል ተማከሩ። 2 አስረው ወሰዱትና ለአገሩ ገዢው ለጲላጦስ አስረከቡት። 3 አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ ኢየሱስ እንደ ተፈረደበት ባየ ጊዜ ተጸጸተ፣ ሠላሣውን ጥሬ ብር ለካህናት አለቆቹና ለሽማግሌዎቹ መልሶ፣ 4 "ንጹሕ ሰው አሳልፌ በመስጠት በድያለሁ" አለ። እነርሱ ግን፣ "ታዲያ፣ እኛን ምን አገባን? የራስህ ጉዳይ ነው” አሉት። 5 ከዚያም ጥሬ ብሩን በቤተ መቅደሱ ውስጥ ወረወረና ወጥቶ ራሱን ሰቀለ። 6 የካህናት አለቆቹ ጥሬ ብሩን ወስደው፣ “ይህ የደም ዋጋ ስለ ሆነ፣ ከቤተ መቅደሱ ገንዘብ ጋር መቀላቀል ተገቢ አይደለም” አሉ። 7 እርስ በርሳቸው ተነጋግረው የእንግዶች መቀበሪያ እንዲሆን የሸክላ ሠሪውን መሬት ገዙበት። 8 ከዚህ የተነሣ ያ መሬት እስከዚህ ጊዜ ድረስ፣ “የደም መሬት” ተባለ። 9 በነቢዩ ኤርምያስ፣ “የእርሱ ዋጋ እንዲሆን የእስራኤል ልጆች የተመኑለትን ሠላሣ ጥሬ ብር ወሰዱ፣ 10 እግዚአብሔር እንደ አዘዘኝ ለሸክላ ሠሪው መሬት ከፈሉት” ተብሎ የተነገረው ተፈጸመ። 11 ኢየሱስ በአገረ ገዢው ፊት ቆመ፤ አገረ ገዢውም፣ “አንተ የአይሁድ ንጉሥ ነህ እንዴ?” በማለት ጠየቀው። ኢየሱስም፣ “አንተ እንዳልኸው ነው” በማለት መለሰለት። 12 የካህናት አለቆችና፣ ሽማግሌዎቹ፣ ሲከሱት ምንም አልመለሰም። 13 በዚህ ጊዜ ጲላጦስ፣ “በአንተ ላይ የሚያቀርቡትን ክስ ሁሉ አትሰማምን?” አለው። 14 እርሱ ግን አንድ ቃል እንኳ ስላልመለሰለት አገረ ገዡ በጣም ተደነቀ። 15 በዓል ሲመጣ አገረ ገዢው ሕዝቡ የሚፈልጉትን አንድ እስረኛ የመፍታት ልማድ ነበረው። 16 በዚያን ጊዜ በርባን የሚሉት ከባድ ወንጀለኛ በእስር ቤት ውስጥ ነበር። 17 ተሰብስበው እያለ ጲላጦስ፣ “ማንን እንድፈታላችሁ ትፈልጋላችሁ፣ በርባንን ወይስ ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን?” አላቸው። 18 ምክንያቱም አሳልፈው የሰጡት በቅናት መሆኑን ያውቅ ነበር። 19 በፍርድ ወንበር ላይ ተቀምጦ እያለ ሚስቱ፣ “በዚያ ንጹሕ ሰው ላይ ምንም እንዳታደርግ፤ እርሱን በተመለከተ በዚህ ሌሊት በሕልሜ ብዙ መከራ ተቀብያለሁ” የሚል ቃል ላከችበት። 20 የካህናት አለቆቹና ሽማግሌዎቹ በርባን እንዲፈታና ኢየሱስ እንዲገደል እንዲጠይቁ ሕዝቡን ቀሰቀሱ። 21 አገረ ገዢው፣ “ከሁለቱ የትኛውን እንድፈታላችሁ ትፈልጋላችሁ?” በማለት ጠየቃቸው። እነርሱም፣”በርባንን” አሉ። 22 ጲላጦስም፣ “ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስንስ ምን ላድርገው?” አላቸው። ሁሉም፣ “ስቀለው” በማለት መለሱ። 23 እርሱም፣ “ለምን፣ የሠራው ወንጀል ምንድንነው?” አላቸው። እነርሱ ግን፣ “ስቀለው” እያሉ የበለጠ ጮኹ። 24 ስለዚህ ምንም ማድረግ እንዳልቻለና እንዲያውም ዐመፅ እየተነሣ መሆኑን ጲላጦስ ባየ ጊዜ፣ በሕዝቡ ፊት እጁን በውሃ ታጥቦ፣ “እኔ ከዚህ ንጹሕ ሰው ደም ነጻ ነኝ፤ ከእንግዲህ ኀላፊነቱ የእናንተው ነው” አለ። 25 ሕዝቡ ሁሉ፣ “ደሙ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይሁን” አሉ። 26 ከዚያም በርባንን ፈታላቸው፤ ኢየሱስን ግን ገርፎ እንዲሰቅሉት ሰጣቸው። 27 የአገረ ገዢው ወታደሮች ኢየሱስን ወደ ገዢው ግቢ ወሰዱትና ወታደሮቹን ሁሉ ሰበሰቡ። 28 ልብሱን ገፍፈው ቀይ ልብስ አለበሱት። 29 ከዚያም የእሾኽ አክሊል ሠርተው በራሱ ላይ ደፉ፣ በቀኝ እጁ በትር አስያዙት፤ በፊቱ ተንበርክከውም፣ “የአይሁድ ንጉሥ ሆይ፣ ሰላም ለአንተ ይሁን!” እያሉ አሾፉበት። 30 ፊቱ ላይም ተፉበት፤ በትሩን ወስደው ራሱን መቱት። 31 ካፌዙበትም በኋላ ልብሱን አውልቀው የራሱን ልብስ አለበሱትና እንዲሰቀል ወሰዱት። 32 እንደወጡ ስምዖን የሚሉት የቀሬና ሰው አገኙ፤ መስቀሉን እንዲሸከም አስገደዱት። 33 ጎልጎታ ወደሚባል ቦታ መጡ፤ ትርጕሙም “የራስ ቅል” ማለት ነው። 34 ከሐሞት ጋር የተቀላቀለ የወይን ጠጅ ሰጡት፤ እርሱ ግን ቀምሶ ሊጠጣው አልፈለገም። 35 በሰቀሉት ጊዜ ዕጣ በመጣጣል ልብሶቹን ተከፋፈሉ፤ 36 ተቀምጠው ይጠብቁትም ጀመር። 37 ከራሱ በላይ፣ “ይህ የአይሁድ ንጉሥ ኢየሱስ ነው” የሚል የክስ ጽሕፈት አኖሩ። 38 ሁለት ወንበዴዎች አንዱ በቀኙ ሌላው በግራው በኩል ከእርሱ ጋር ተሰቅለው ነበር። 39 የሚያልፉ ሰዎችም ሰደቡት፤ ራሳቸውን እየነቀነቁም 40 “ቤተ መቅደሱን የምታፈርስና በሦስት ቀን የምትሠራ ራስህን አድን። የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ ከመስቀል ውረድ” ይሉት ነበር። 41 በተመሳሳይ መንገድ የካህናት አለቆች፣ ከአይሁድ የሕግ መምህራንና ከሽማግሌዎቹ ጋር አብረው፣ 42 “ሌሎችን አዳነ፤ ራሱን ግን ማዳን አልቻለም። እርሱ የእስራኤል ንጉሥ ነው፣ ከመስቀል ይውረድ፣ ከዚያም እኛ እናምንበታለን። 43 በእግዚአብሔር ተማምኖአል፤ እርሱ ከወደደ ያድነው፤ ምክንያቱም፣ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ብሏል" እያሉ ያፌዙበት ነበር። 44 ከእርሱ ጋር የተሰቀሉት ወንበዴዎችም እንዲሁ ይሰድቡት ነበር። 45 ከስድስት ሰዓት ጀምሮ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ ምድሩን ሁሉ የሚሸፍን ጨለማ ሆነ። 46 በዘጠኝ ሰዓት ኢየሱስ፣ “ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰባቅታኒ” በማለት በታላቅ ድምፅ ጮኸ፤ ትርጕሙም፣ “አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ” ማለት ነው። 47 እዚያ ቆመው ከነበሩት አንዳንዶቹ ይህን ሲሰሙ፣ “ኤልያስን እየተጣራ ነው” አሉ። 48 ወዲያውኑ ከእነርሱ አንዱ ሮጦ ሄደና ስፖንጁን የኮመጠጠ ወይን ጠጅ ውስጥ ነክሮ በሸንበቆ በትር አድርጎ እንዲጠጣ ሰጠው። 49 የተቀሩትም፣ "እስቲ ተዉት፤ ኤልያስ መጥቶ ሲያድነው እናያለን” አሉ። 50 ከዚያም ኢየሱስ በድጋሚ በታላቅ ድምፅ ጮኾ መንፈሱን ሰጠ። 51 የቤተ መቅደሱ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ለሁለት ተከፈለ፤ ምድር ተናወጠ፤ ዐለቶችም ተሰነጠቁ፤ 52 መቃብሮች ተከፈቱ፤ አንቀላፍተው የነበሩ ብዙ ቅዱሳን ተነሡ። 53 ከትንሣኤው በኋላ ከመቃብር ወጡ፤ ወደ ቅድስት ከተማ ገብተው ለብዙዎች ታዩ። 54 የመቶ አለቃውና ኢየሱስን ይጠብቁ የነበሩ ሰዎች የምድር መናወጡንና የሆኑትን ነገሮች ሲያዩ በጣም ፈርተው፣ "በእውነት ይህ የእግዚአብሔር ልጅ ነው" አሉ። 55 እርሱን ለመርዳት ከገሊላ ጀምሮ ኢየሱስን ተከትለው የነበሩ ብዙ ሴቶች በሩቅ ሆነው ይመለከቱ ነበር። 56 ማርያም መግደላዊት፣ የያዕቆብና የዮሴፍ እናት ማርያም፣ እንዲሁም የዘብዲዎስ ልጆች እናት ከእነርሱ ጋር ነበሩ። 57 ምሽት ላይ ዮሴፍ የሚሉት አንድ ሀብታም ሰው ከአርማትያስ መጣ፤ እርሱ ራሱ የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ነበር። 58 ወደ ጲላጦስ መጥቶ የኢየሱስን አስከሬን እንዲሰጠው ጠየቀ። ጲላጦስም እንዲሰጠው አዘዘ። 59 ዮሴፍ አስከሬኑን ወስዶ፤ በንጹሕ ናይለን ጨርቅ ጠቀለለውና 60 ለራሱ ከዐለት በሠራው መቃብር ውስጥ አኖረው። ከዚያም ትልቅ ድንጋይ አንከባልሎ መቃብሩ ደጃፍ ላይ አድርጎ ሄደ። 61 ማርያም መግደላዊትና ሌላዋ ማርያም መቃብሩ ፊት ለፊት ተቀምጠው በዚያ ነበሩ። 62 በሚቀጥለው ቀን ከዝግጅት በኋላ የካህናት አለቆቹና ፈሪሳውያን በአንድነት ከጲላጦስ ጋር ተሰበሰቡ። 63 እንዲህም አሉ፣ "ጌታ ሆይ፣ ያ አሳሳች በሕይወት በነበረ ጊዜ፣ 'ከሦስት ቀን በኋላ እነሣለሁ' ብሎ እንደ ነበር ትዝ አለን። 64 ስለሆነም፣ እስከ ሦስተኛው ቀን ድረስ መቃብሩ በጥንቃቄ እንዲጠበቅ እዘዝ፤ አለበለዚያ ግን፣ ደቀ መዛሙርቱ መጥተው ሥጋውን ይሰርቁና ለሕዝቡ፣ ‘ከሞት ተነሣ’ ይላሉ፤ የኋላው ስሕተት ከመጀመሪያው የከፋ ይሆናል” አሉት። 65 ጲላጦስም፣ “ጠባቂ ወስዳችሁ፣ የሚቻላችሁን ያህል በጥንቃቄ እንዲጠበቅ አድርጉ” አላቸው። 66 ስለዚህ ሄደው መቃብሩ በጥንቃቄ እንዲጠበቅ አደረጉ፤ ድንጋዩን አተሙ፤ ጠባቂ አኖሩ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Matthew 27:1

ማቴዎስ 27፡ 1-2

Matthew 27:3

ማቴዎስ 27፡ 3-5
ከዚያም ይሁዳ ይንን ባደረገ ጊዜ በቋንቋችሁ የተጀመረን አንድ ታሪክ አቋርጦ ሌላ ታሪክ መጀመሩን የሚያመለክት ቃል ካለ ይህንን ቃል በዚህ ሥፍራ ላይ ተጠቀም። ሠላሳ ብር የካህናት አለቆች ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ ይሰጣቸው ዘንድ ለይዳ የሰጤት ብር ነው (MAT 26:15) ንጹሕ ደም "መሞት የማይገባው ሰው"

Matthew 27:6

ማቴዎስ 27፡6-8
ይህንን ማድረግ ሕጋዊ አይደለም "ሕጋችን ይህንን እዲናደረግ አይፈቅድልንም" እንድናስቀመጥ "ይህንን ብር እንድናስቀመጥ" የደም ዋጋ አንድ ሰው እንዲሞት የሚከፈል ገንዘብ የሸክላ መሬት ይህ መሬት በኢየሩሳሌም ከተማ ውስጥ ምጻተኛ የሆነ ሰው ቢሞት የሚቀበርበት ቦታ ነው። እስከዛሬ ድረስ ጸሐፊው መጽሐፉን እስከ ጻፈበት ጊዜ ድረስ

Matthew 27:9

ማቴዎስ 27፡ 9-10
ነብዩ ኤርሚያስ እንዲህ በማለት የተናገረው የትንቢት ቃል ተፈተመ "ነብዩ ኤርሚያስ ይህንን የትንቢት ቃል ተናገረ፤ እንደተናገውም ሆነ። ነብዩ ያለው እንዲህ ነው" የእስራኤል ሕዝቦች የእስራኤል የሃይማኖት መሪዎች እንደገመተኝ ነብዩ ኤርሚያስ እንደገመተው

Matthew 27:11

ማቴዎስ 27፡ 11-14
አሁን በቋንቋችሁ ውስጥ የተቋረጠው ታሪክ መቀጠሉን የሚያሳይ ቃል ካለ ይህንን ቃል መጠቀሙ መልካም ይሆናል። ሀገረ ገዥው ጵላጦስ (MAT 27:1) አንተ አልክ "አንተ ራሰህ ተቀበልከው" ይሁን እንጂ በካህናት ለቆች እና ሽማግሌዎች ክስ በቀረበበት ጊዜ ለተርጓሚዎች ምክር፡ “ነገር ግን የካህናት አለቆች እና ሽምግሌዎች በከሰሰቱት ጊዜ” በእንተ ላይ የሚያቀርቡትን ክስት አትሰማምን? "መጥፎ ነገር አድርጓል ብለው ለሚከሱህ ሰዎች ምንም ምላሽ አለመስጠትህ አስገርሞኛል!” አንዲት ቃል፣ በዚህም ገዥው በጣም ተገረመ። ለተርጓሚዎች ምክር፡ "አንዲት ቃል፤ ይህ ነገር ገዥውን እጅግ አስገረመው።"

Matthew 27:15

ማቴዎስ 27፡ 15-16
አሁን ይህ ቃል በታሪኩ ፍሰት ውስጥ የእረፈት ጊዜ መኖሩ የሚያሳይ ነው። በዚህም ጸሐፊው በ [MAT 27:17] ክብረ በዓል ፋስካ በዓል የሚከበርበት ጊዜ (MAT 26:2) በሕዝቡ የተመረጠው እስረኛ ለተርጓሚዎች ምክር፡ “ሕዝቡ የመረጠው እስረኛ” ነውጠኛ መጥፎ ነገር በማድረግ በጣም የሚታወቅ ሰው

Matthew 27:17

ማቴዎስ 27፡ 17-19
አሳልፈው ሰጡት ጵላጦስ ይፈርድበት ዘንድ "ኢየሱስን ወደ እርሱ አመጡ” በዚያም ተቀምጦ ሳለ "ጵላጦስ በዚያ ተቀምጦ ሳለ" በፍርድ ወንበር ላይ ተቀምጦ ሳለ ፍርድን እንደሚሰጥ ሰው በስራው ላይ ሳለ መልዕክት ላከ "መልዕክት ላከ"

Matthew 27:20

ማቴዎስ 27፡ 20-22
ጠየቃቸው "ሕዝቡን ጠየቀ"

Matthew 27:23

ማቴዎስ 27፡ 23-24
ምን አድርጎ ነው "ኢየሱስ ምን አደረገ" በታላቅ ድምፅ ጮኹ "ሕዝቡም በታላቅ ድምፅ ጮኹ" ደሙ "ሞቱ"

Matthew 27:25

ማቴዎስ 27፡ 25-26
ደሙ በእኛ እና በልጆቻችን ላይ ይሁን። "አዎ! እኛ እና የእኛ ልጆች በደስታ እርሱን እንዲሞት የማድረግ ኃላፊነቱን እንወስዳን!"

Matthew 27:27

ማቴዎስ 27፡ 27-29
የገዥው ግቢ አማራጭ ትርጉሞች: 1) ወታደሮቹ የሚኖሩበት ሥፍራ ወይም 2) የገዥዎቹ መኖሪያ ልብሱን ገፈፉት "ልብሱን ገፈፉት" (UDB) ቀይ ልብስ ደማቅ ቀይ ልብስ ተዘባበቱበት "እናከብርሃን" ወይም "ረጅም እድሜ ኑር"

Matthew 27:30

ማቴዎስ 27፡ 30-31
እነርሱ . . . እነርሱ . . . እነርሱ የጵላጦስ ወታደሮች እርሱ . . . እርሱ . . . እርሱ . . . እርሱ . . . እርሱ ኢየሱስ

Matthew 27:32

ማቴዎስ 27፡ 32-34
ከዚያ በወጡ ጊዜ "ከእየሩሳሌም እየወጡ ሳለ" የእርሱን መስቀል ይሸከም ዘንድ አስገደዱት "ወታደሮቹ የኢየሱስን መስቀል ይሸከም ዘንድ አስገደዱት" ጎልጎታ ወደ ተባለ ሥፍራ "ሰዎች ጎልጎታ ብለው ወደሚጠሩት ሥፍራ" ሐሞት ሰውነታችን ምግብን ለመፍጨት የሚጠቀምበት ብጫ ፈሳሽ ነገር

Matthew 27:35

ማቴዎስ 27፡ 35-37
ልብስ ኢየሱስ ይለብሰው የነበረውን ልብስ

Matthew 27:38

x
ማቴዎስ 27፡ 38-40

ከእርሱ ጋር ሁለት ወንበዴዎች ተሰቅለው ነበር ለተርጓሚዎች ምክር፡ “ወታደሮቹ ሁለት ወንበዴዎችን ከኢየሱስ ጋር ሰቀሉ”። ራሳቸውን እየነቀነቁ ይህንን ያደረጉት በኢየሱስ ላይ ለመሳለቅ ነው። አንተ በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ ከመስቀል ውረድ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ በመሆኑ ስለማያምኑ ይህን እንዲያረጋግጥላቸው ጠየቁት። ለተርጓሚዎች ምክር፡ “አንተ በእርግጥ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ ከመስቀል በመውረድ ይህንን አረጋግጥልን አሉት” የእግዚብሔር ልጅ ይህ በክርስቶስ እና በእግዚአብሔር ልጅ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያስረዳ በጣም አስፈላጊ የሆነ ስም ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Matthew 27:41

ማቴዎስ **27**፡ **41**-**42**
ሌሎቹን አዳነ ነገር ግን ራሱን ማዳን አልቻለም አማራጭ ትርጓሜዎች፡ 1) የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስ ሌሎችን እንዳዳነ አያምኑም ወይም ራሱንም ማዳን እንደሚችል አያምኑም ወይም 2) ሌሎችን እንዳዳነ ያምናሉ ነገር ግን ራሱን ማዳን ስላልቻለ ሳቁበት። እርሱ የእስራኤል ንጉሥ ነው መሪዎቹ የእስራኤል ንጉሥ እንደሆነ አያምኑም ነበር

Matthew 27:43

ማቴዎስ **27**፡ **43**-**44**
የእግዚብሔር ልጅ ይህ በክርስቶስ እና በእግዚአብሔር ልጅ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያስረዳ በጣም አስፈላጊ የሆነ ስም ነው። ከእርሱ ጋር የተሰቀሉት ወንበዴዎችም "ወታደሮቹ ከኢየሱስ ጋር የሰቀሏቸው ወንበዴዎችም

Matthew 27:45

ማቴዎስ **27**፡ **45**-**47**
ጮኸ "ተጣራ" ወይም "በታላቅ ድምፅ ጮኸ" ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ? ተርጓሚዎች ብዙ ጊዜ እነዚህ ቃላት እንዳሉ በዕብራይስጥ ቋንቋዎች ይተዋቸዋል።

Matthew 27:48

ማቴዎስ **27**፡ **48**-**50**
ከእነርሱ መካከል አንዱ አማራጭ ትርጉሞች፡ 1) ከወታደሮቹ መካከል አንዱ ወይም 2) ቆመው ከሚመለከቱት መካከል አንዱ እስፖንጅ ከባሕር እንስሳት መካከል የሚሰበሰብ ውሃ ለመያዣነት የሚገለግል። ለእርሱ ሰጠው "ለኢየሱስ ሰጠው

Matthew 27:51

ማቴዎስ **27**፡ **51**-**53**
እነሆ ይህ ቃል ሰዎች ከዚህ በኋላ ለሚነገረው ነገር አጽኖት እንዲሰጡ የሚጨመር ቃል ነው፡ ለተርጓሚዎች ምክር፡ “ተመልከቱ” ወይም “አድምጡ” ወይም “አሁን ለምነግራችሁ ነገር ትኩረት ስጡ”:: መቃብሮችም ተከፈቱ፥ ተኝተው ከነበሩትም ከቅዱሳን ብዙ ሥጋዎች ተነሡ፤ "እግዚብሔር መቃብሮችን ከፍቶ ከሞቱት መካል ብዙ ቅዱሳንን ከሞት አስነሣ ተኝተው የነበሩ "የሞቱ" መቃብሮችም ተከፍተው . . . ለብዙዎች ታዩ። ሁኔታዎቹ የተፈጸሙበት የጊዜ ቅደም ተከተል ግልጽ አይደለም። ሊሆነ የሚችሉት የጊዜ ቅደም ተከተሎች፡ ኢየሱስ ሲሞት በተነሳው ከተነሳው የምድር መንቀጥቀጥ በኋላ መቃብሮች ተከፈቱ 1) ቅዱሳን ተነሱ፣ ኢየሱስ ከሞት ተነሣ እና ቅዱሳን ወደ ከተማው ገቡ እና ለብዙዎች ታዩ ወይም 2) ኢየሱስ ከሞት ተነሣ እና ቅዱሳን ከሞት ተነሡ፣ ወደ ከተማ ገቡ እና ለብዙዎች ታዩ።

Matthew 27:54

ማቴዎስ **27**፡ **54**-**56**
የእግዚብሔር ልጅ ይህ በክርስቶስ እና በእግዚአብሔር ልጅ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያስረዳ በጣም አስፈላጊ የሆነ ስም ነው።

Matthew 27:57

ማቴዎስ **27**፡ **57**-**58**
ከዚያም ጵላጦስ ይሰጠው ዘንድ አዘዘ "ከዚያም ጵላጦስ ወታደሮቹን የኢየሱስ በድን ለዮሴፍ ይሰጠው ዘንድ አዘዘ።”

Matthew 27:59

ማቴዎስ **27**፡ **59**-**61**
ለስላሳ ጨርቅ ብዙ ብር የሚያወጣ ጨርቅ ከመቃብሩ ተቃራኒ "ከመቃብሩ ማዶ"

Matthew 27:62

ማቴዎስ **27**፡ **62**-**64**
ዝግጅት ለፋሲካ በዓል የሚዘጋጁበት ጊዜ ነበር ይህ አሳች በሕይወት እያለ "አሳቹ ኢየሱስ በሕይወት እያለ"

Matthew 27:65

ማቴዎስ **27**፡ **65**-**66**
ጠባቂ 4 እስከ 16 የሮማዊያን ወታደሮች ድንጋዩን በማሕተም አትመው አማራጭ ትርጓሜዎች፡ 1) በድንጋዩ ዙሪያ ገመድ በማድረግ ወደ መቃብሩ ሌላኛው መግቢያ ጋር በማያያዝ አሠሩት ወይም 2) በድንጋዩ ና በግድግዳው መካከል ማሕተም አኖሩ። ጠባቂዎች በዚያ አኖሩ "ወታደሮቹ ሰዎች መቃብሩን መንካት የማይችሉበት ቦታ እንዲቆሙ ትዕዛዝ ሰጡ።"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **28**

1 ሰንበት እንዳለፈ፣ በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ማለዳ፣ ማርያም መግደላዊትና ሌላዋ ማርያም ወደ መቃብሩ መጡ። **2** የጌታ መልአክ ከሰማይ ወርዶ ነበርና ታላቅ የምድር መንቀጥቀጥ ሆነ፤ መጥቶም ድንጋዩን አንከባልሎ በላዩ ተቀመጠ። **3** መልኩ እንደ መብረቅ፣ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ነበር። **4** ጠባቂዎቹ በፍርሃት ተንቀጠቀጡ፤ እንደ ሞተ ሰውም ሆኑ። **5** መልአኩም እንዲህ በማለት ተናገረ፤ "አትፍሩ፤ ተሰቅሎ የነበረውን ክርስቶስን እንደምትፈልጉ አውቃለሁ። **6** እንደ ተናገረ ተነሥቷል እንጂ፣ እዚህ የለም፤ ኑና የነበረበትን ቦታ እዩ። **7** በፍጥነት ሄዳችሁ፣ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ በማለት ንገሩ፤ 'እርሱ ከሞት ተነሥቷል፤ ቀድሟችሁ ወደ ገሊላ ይሄዳል። እዚያ ታዩታላችሁ።' እንግዲህ ነግሬአችኋለሁ።" **8** ሴቶቹ ፈጥነው በፍርሃትና በታላቅ ደስታ ለደቀ መዛሙርቱ ለመንገር ከመቃብሩ እየሮጡ ሄዱ። **9** እነሆ ኢየሱስ አገኛቸውና፣ "ሰላም ለእናንተ ይሁን" አላቸው። ሴቶቹም እግሮቹን ይዘው ሰገዱለት። **10** ከዚያም ኢየሱስ፣ "አትፍሩ፤ ሄዳችሁ ወደ ገሊላ እንዲሄዱ ለወንድሞቼ ንገሩ፤ እዚያ ያዩኛል" አላቸው። **11** ሴቶቹ እየሄዱ እያሉ፣ ከጠባቂዎች ጥቂቱ ወደ ከተማ ሄደው የሆነውን ሁሉ ለካህናት አለቆቹ ነገሩ። **12** ካህናቱ ከሽማግሌዎቹ ጋር ተገናኝተው የሆነውን ሁሉ ሲናገሩ፣ ለወታደሮቹ ብዙ ገንዘብ በመስጠት፣ **13** "እኛ ተኝተን እያለ ፣ ሌሊት የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት መጥተው አስክሬኑን ሰረቁ" ብለው እንዲናገሩ ነገሩዋቸው። **14** ይህ ወሬ ወደ አገረ ገዢው ከደረሰ፤ እኛ እናሳምነዋለን፣ እናንተም ከሥጋት ነጻ ትሆናላችሁ" አሏቸው። **15** ወታደሮቹ ገንዘቡን ተቀብለው ፣ እንደ ተነገራቸው አደረጉ። ይህ ወሬ እስከ ዛሬ ድረስ በአይሁድ መሐል በሰፊው ተሰራጭቷል። **16** ዐሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ግን ወደ ገሊላ ኢየሱስ ወደ ነገራቸው ተራራ ሄዱ። **17** ባዩት ጊዜ ሰገዱለት፤ አንዳንዶቹ ግን ተጠራጥረው ነበር። **18** ኢየሱስ ወደ እነርሱ መጥቶ፣ "በሰማይና በምድር ሁሉ ላይ ሥልጣን ተሰጠኝ። **19** ስለዚህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ፣ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስም ስም እያጠመቃችኋቸው፤ **20** እኔ ያዘዝኋችሁን ሁሉ እንዲያደርጉ እያስተማራችኋቸው፤ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው። እኔም እስከ ዓለም ፍጻሜ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።"

Matthew 28:1

ማቴዎስ **28**፡ **1**-**2**
በሰንበትም በሳምንቱ መጀመሪያው ቀን መጨረሻ "ሰንበት ካለቀ በኋላ የእሁድ ማለዳ ጸሐይ መውጣት ሲጀምር" ሌላኛዋ ማሪያም "ማሪያም ተብላ የሚትጠራዋ ሌላኛዋ ሴት" የያዕቆብ እና የዮሴፍ እናት የሆነችው ማሪያም (MAT 27:56) እነሆ ይህ ቃል ሰዎች ከዚህ በኋላ ለሚነገረው ነገር አጽኖት እንዲሰጡ የሚጨመር ቃል ነው፡ ለተርጓሚዎች ምክር፡ “ተመልከቱ” ወይም “አድምጡ” ወይም “አሁን ለምነግራችሁ ነገር ትኩረት ስጡ”:: የጌታ መላእክት በመውረዳቸው . . . እና ድንጋዩን በማንከባለላቸው ምክንያት ታላቅ የመሬት መናወጥ ሆነ አማራጭ ትርጉሞች: 1) የመሬት መናወጡ የተከሰተበት ምክንያት መላእክት በመውረዳቸው እና ድንጋዩን በማንከባለላቸው ነው (ULB) ወይም 2) እነዚህ ሁሉም ነገሮች የሆኑት በተመሳሳይ ጊዜ ነው (UDB). የመሬት መናወጥ (መንቀጥቀጥ) ድንገተኛ እና አስደንጋጭ የመሬት መንቀጥቀጥ

Matthew 28:3

ማቴዎስ **28**፡ **3**-**4**
የእርሱ መልክ "የመልአክ መልክ" መብረቅ ይመስል ነበር "እንደ መብረቅ ያበራ ነበር" እንደ በረዶ ነጭ ነበር "በከፍተኛ ሁኔታ ያንጸባርቅ ነበር" እንደ ሞተ ሰው "መንቀሳቀስ ያቃተው"

Matthew 28:5

ማቴዎስ **28**፡ **5**-**7**
ሴቶቹ "መግደላዊት ማሪያም እና ማሪያም ተብላ የተጠራው ሌላኛዋ ሴት" የተሰቀለው "ሕዝቡ እና ወታደሮቹ የሰቀሉት" ነገር ግን ተነሣ " ገር ግን እግዚአብሔር አስነሣው"

Matthew 28:8

ማቴዎስ **28**፡ **8**-**10**
ሴቶቹ "መግደላዊት ማሪያም እና ማሪያም ተብላ የሚትጠራው ሌላኛይቱ ሴት" እነሆ ጸሐፊው አንድ አስደናቂ ነገር ልሆን እንዳለ ለአንባቢዮቹ ያስታውቃቸዋል። በቋንቋችሁ ይህን ዓይነቱን ነገር ማድረግ የሚችትችሉበት መንገድ ሊኖር ይችላል:: እግሩን ያዙት "በጉልበታቸው ተንበርክከው እግሩን ያዙት" ወንድሞቼ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት

Matthew 28:11

ማቴዎስ **28**፡ **11**-**13**
ሴቶቹ መግደላዊት ማሪያም እና ሌላኛዋ ማሪያም ከእነርሱ ጋር ስለሁኔታው ተወያዩ "ስለ አቀዱት እቅድም በጋራ ወሰኑ::” ካህናቱ እና ሽማግሌዎቹ ለወታደሮቹ ብር ለመስጠት ወሰኑ። ለሌሎች እንዲህ ብላችሁ ንገሩ “በተኛንበት ሰዓት የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት መጥተው . . .” "ለጠየቃችሁ ሁሉ እንዲህ ብላችሁ ንገሩ፣ ተኝተን ሳለ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት መጥተው"

Matthew 28:14

ማቴዎስ **28**፡**14**-**15**
ገዥው ጵላጦስ (MAT 27:2) እንደተነገራቸው እንደዚያው አደረጉ "ካህናቱ እንዲያደርጉ እንደ ነገሯቸው እንደዚያው አደረጉ" ዛሬ ማቴዎስ መጽሐፉን በጻፈበት ወቅት

Matthew 28:16

ማቴዎስ **28**፡ **16**-**17**

Matthew 28:18

ማቴዎስ **28**፡ **18**-**19**
በስሜ "በእኔ ስልጣን" አብ . . . ወልድ ይህ በእግዚአብሔር አብ እና በኢየሱስ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያብራራ ጠቃሚ ስም ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Mark

Mark

ምዕራፍ 1

1 ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መጀመሪያ። 2 በነብዩ በኢሳይያስ እንደተጻፈው እነሆ! መንገድን የሚያዘጋጅላችሁን መልዕክተኛዬን በፊታችሁ እልካለሁ፤ 3 መንገድን አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ ብሎ በምድረበዳ የሚጮህ ሰው ድምፅ። 4 በምድረበዳ እያጠመቀና ለኃጢአት ይቅርታ የንሰሐን ጥምቀት እየሰበከ መጣ። 5 ሁሉና በኢየሩሳሌም ያሉ ሁሉ ወደ እርሱ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ እየመጡ ኃጢአታቸውን በመናዘዝ ይጠመቁ ነበር። 6 የግመል ጠጉር ይለብስና ወገቡን በቆዳ መታጠቂያ ይታጠቅ፣ አንበጣና የበረሃ ማርም ይበላ ነበር። 7 የጫማውን ማሰሪያ ለመፍታት የማልበቃ ከእኔ ይልቅ ታላቅ የሆነ እርሱ ከበስተኋላዬ ይመጣል። 8 በውሃ አጥምቄአችኋለሁ፤ እርሱ ግን በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል እያለ ይሰብክ ነበር። 9 ቀናት ኢየሱስ ከገሊላ ናዝሬት በመምጣት በዮርዳኖስ ውስጥ በዮሐንስ ተጠመቀ። 10 እንደወጣም ሰማይ ሲከፈት፣ መንፈስ ቅዱስም እንደ እርግብ በእርሱ ላይ ሲወርድ አየ፤ 11 ልጄ አንተ ነህ፤ በአንተ ደስ ይለኛል የሚል ድምጽም ከሰማያት መጣ። 12 መንፈስ ቅዱስ ወደ ምድረበዳ መራው። 13 በሰይጣን እየተፈተነም በምድረበዳ ለአርባ ቀን ቆየ። ከዱር አራዊትም ጋር ነበረ፤ መላዕክትም አገለገሉት። 14 ታልፎ ከተሰጠ በኋላ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን የምሥራች ቃል እየሰበከ ወደ ገሊላ መጣ። 15 ተፈጸመ፤የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና ንሰሐ ግቡ፤ በወንጌልም እመኑ ይል ነበር። 16 ባህር ዳር ሲያልፍ ሳለ ስምዖን ጴጥሮስንና ወንድሙን እንድርያስን መረባቸውን ወደ ባህር ሲጥሉ አያቸው፤ አሳ አጥማጆች ነበሩና። 17 በኋላዬ ኑና ሰዎችን የምታጠምዱ አደርጋችኋለሁ አላቸው። 18 መረቦቻቸውን ትተው ተከተሉት። 19 እልፍ እንዳለም የዘብዴዎስን ልጅ ያዕቆብንና ወንድሙን ዮሐንስን እነርሱም በጀልባቸው ውስጥ መረቦቻቸውን ሲጠግኑ አያቸው። 20 ጠራቸው፤ እነርሱም ዘብዴዎስ አባታቸውን ከተቀጣሪ ሰራተኞቻቸው ጋር በጀልባው ውስጥ ትተው ተከተሉት። 21 ቅፍርናሆም ሔዱ። ወዲያው በሰንበት ቀን ወደ ምኩራብ ገብቶ አስተማራቸው። 22 ጸሐፍት ሳይሆን ትምህርቱ እንደ ባለሥልጣን ስለነበረ በትምህርቱ ተገረሙ። 23 ርኩስ መንፈስ ያለበት አንድ ሰው በምኩራባቸው ነበረ። 24 የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ! ከአንተ ጋር ምን አለን? ልታጠፋን መጣህን? ማን እንደሆንክ አውቄሃለሁ፤ አንተ የእግዚአብሔር ቅዱስ ብሎ ጮኸ። 25 ዝም በል! ከእርሱም ውጣ ብሎ ገሰጸው። 26 መንፈስ መሬት ላይ ጥሎ ካንፈራገጠው በኋላ በታላቅ ድምጽ ጮኾ ወጣ። 27 ሁሉ በጣም ተገረሙና ይህ አዲስ ትምህርት ምንድነው? ርኩሳን መናፍስትን እንኳን በሥልጣን ያዛቸዋልና እነርሱም ይታዘዙለታል በማለት እርስ በርሳቸው ተጠያየቁ። 28 እርሱም በገሊላ አውራጃና በዙሪያው ባሉ ሀገራት ሁሉ ዝናው ወጣ። 29 እንደወጡ ወዲያው ከዮሐንስና ከያዕቆብ ጋር ወደ ስምዖንና እንድርያስ ቤት መጡ። 30 ጊዜ የስምዖን አማት አተኩሷት ተኝታ ነበርና ወዲያው ስለ እርስዋ ነገሩት። 31 እጇን ይዞ አስነሳት፤ ወዲያውኑ ትኩሳቱ ለቀቃትና አገለገለቻቸው። 32 ጠልቃ በመሸ ጊዜም ብዙ በሽተኞችንና በአጋንንት የተያዙትን ወደ እርሱ አመጧቸው። 33 ሰው ሁሉ በአንድነት በቤቱ ደጃፍ ተከማችቶ ነበር። 34 በተለያየ በሽታ የታመሙትን ፈወሳቸው፤ ብዙ አጋንንትንም አወጣ። አጋንንቱ ማን መሆኑን አውቀውት ነበርና እንዳይገልጡት አዘዛቸው። 35 እጅግ በማለዳ ተነስቶ ለብቻው ወደ ምድረበዳ ሔደና ጸለየ። 36 ከእርሱ ጋር የነበሩትም ተከተሉት። 37 ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ ይፈልጉሃል አሉት። 38 የምሥራቹን ቃል እንድሰብክ ወደ ሌሎቹ ከተሞች ደግሞ እንሂድ፣ ስለዚህ ጉዳይ መጥቻለሁና አላቸው። 39 ወዳሉ ምኩራቦቻቸው ሁሉ እየገባ ሰበከላቸው፣ አጋንንትንም አወጣ። 40 ለምጻም ወደ እርሱ መጥቶ ሰገደለትና ብትፈቅድስ ልታነጻኝ ትችላለህ ብሎ ለመነው። 41 አዘነለት፤ እጁን ዘርግቶ ዳሰሰውና እፈቅዳለሁ፣ ንጻ! አለው። 42 ለምጹ ለቀቀውና ንጹህ ሆነ። 43 ለማንም እንዳይናገር አጥብቆ አዘዘውና ወዲያው ሲያሰናብተው ሳለ 44 ግን ራስህን ለካህን አሳይ፤ ስለመንጻትህ ምሥክር እንዲሆንባቸው ሙሴ ያዘዘውን መስዋዕት አቅርብ አለው። 45 ግን ሄደና ኢየሱስ በግልጽ ወደ ከተማ ለመግባት እስኪሳነው ድረስ ስለዚህ ነገር አብዝቶ ሊያወራና ሊያሰራጭ ጀመረ። በመሆኑም በምድረበዳ አካባቢዎች እንዲቆይ ሆነ፤ ሰዎችም ከየአቅጣጫው ወደ እርሱ ይመጡ ነበር።

Mark 1:1

ማርቆስ **1**:**1**-**3**
የእግዚአብሔር ልጅ ይህ የኢየሱስ አስፈላጊ የሆነ ስም ነው። አንተ . . . አንተ ነጠላ ቁጥር መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ “መንገድ” እና “ጥርጊያ” የሚሉት ሁለት ቃላት የኢየሱስን ሕይወት ከመንገድ ጋር የሚያነጻጽሩ ናቸው። የእነዚህ ሁለት ትዕዛዞች ትርጉም ተመሳሳይ ነው። በእናንተም ቋንቋ ተመሳሳይ ከሆኑ UDB እንዳደረገው ሁለተኛውን ዐረፍተ ነገር መተው ትችላላችሁ። አማራጭ ትርጓሜ: በጣም ወሳኝ የሆነ ሰውን ለመገናኘት ተዘጋጁ

Mark 1:4

ማርቆስ **1**:**1**-**3**
የእግዚአብሔር ልጅ ይህ የኢየሱስ አስፈላጊ የሆነ ስም ነው። አንተ . . . አንተ ነጠላ ቁጥር መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ “መንገድ” እና “ጥርጊያ” የሚሉት ሁለት ቃላት የኢየሱስን ሕይወት ከመንገድ ጋር የሚያነጻጽሩ ናቸው። የእነዚህ ሁለት ትዕዛዞች ትርጉም ተመሳሳይ ነው። በእናንተም ቋንቋ ተመሳሳይ ከሆኑ UDB እንዳደረገው ሁለተኛውን ዐረፍተ ነገር መተው ትችላላችሁ። አማራጭ ትርጓሜ: በጣም ወሳኝ የሆነ ሰውን ለመገናኘት ተዘጋጁ

Mark 1:7

ማርቆስ **1**:**7**-**8**
ሰበከ "የሐንስ ሰበከ" (ተመልከት (MRK 1:2-3))። ተጎንብሼ የጫማውን ጠፍር መፍታት የማይገባኝ የሐንስ ኢየሱስ ከእርሱ ምን ያኽል እንደሚበልጥ ለማሳየት ራሱን ከአገልጋይ ጋር ያነጻጽራል። አማራጭ ትርጓሜ: “እኔ አስደሳች ያልሆነውን የአገልጋይነት ሥራን ለመሥራት እንኳ ብቁ አይደለሁም።” ማጎንበስ "ወደ ታች ገንበስ ማለት" በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል በዚህ ሥፍራ ላይ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከውሃ ጥምቀት ጋር ተነጻጽሮ ቅርቧል። የውሃ ጥምቀት ሰዎች ከውሃ ጋር ግንኙነት እንዲኖራቸው እንደሚያደርጉ ሁሉ የመንፈስ ጥምቀት ሰዎች ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ግንኙነት እንዲያደርጉ ያደርጋል። አማራጭ ትርጓሜ: “ከመንፈስ ቅዱስ ወግኖ መገኘት።”

Mark 1:9

ማርቆስ **1**: **9**-**11**
የምወድህ ልጄ እንተ ነህ እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሐየር ወልድ፣ እና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በአንድነት፣ በተመሳሳይ ጊዜ በመገለጥ። የምወድህ ልጄ ይህ የኢየሱስ ወሳኝ ስም ነው። እግዚብሔር አባር እርሱን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

“የምወድህ ልጄ” ብሎ ጠርቶታል። ይህ የሆነው ደግሞ እርሱ ለእርሱ ካለው ዘላለማዊ ፍቅሩ የተነሳ ነው።

Mark 1:12

ማርቆስ **1**፡**12**-**13**
ይሄድ ዘንድ አስገደደው "ኢየሱስን በግድ አስኬደው" በምድረ በዳ ውስጥ ነበር "በምድረ በዳ ውስጥ ቆየ አርባ ቀን እና ሌልት "40 ቀናት" ከ . . . ጋር ነበር "በ . . . መካከል ነበር"

Mark 1:14

ማርቆስ **1**፡ **14**-**15**
ዮሐንስ አልፎ ከተሰጠ በኋላ "ዮሐንስ ወደ ወህኒ ቤት ከተወሰደ በኋላ." አማራጭ ትርጓሜ: "ዮሐንስን ካሠሩት በኋላ." የእግዚብሔርን ወንጌል ሰበከ "ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣውን መልካሙን ዜና ሰበከ" ዘመኑ ተፈጸመ "ጊዜው አሁን ነው"

Mark 1:16

ማርቆስ **1**፡ **16**-**18**
ስምኦንና አንድሪውን ተመለከተ "ኢየሱስ ስምኦንና አንድሪውን ተመለከተ" መረብ መጣል "መረብ መወርወር" ዓሣ አጥማጆች ነበሩ "እነርሱ ዓሣ አጥማጆ ስለነበሩ" ተከተሉኝ "እኔን ተከተሉኝ" ሰዎችን የሚታጠምዱ አድርጋችኋለሁ በዚህ ሥፍራ ላይ ኢየሱስ ዓሣ ማጥመድን ከሰው ማጥመድ ጋር እያነጻጸረ ነው። አማራጭ ትርጓሜ: "እንዴት ሰውን ማጥመድ እንደሚትችሉ አስትምራችኋለሁ" እነርሱም መረባቸውን ትተው ተከተሉት "የኢየሱስ ተከታዮች ለመሆን የዓሣ ማጥመድ ሥራቸውን ተው"

Mark 1:19

ማርቆስ **1**:**19**-**20**
በታንኳይቱ ውስጥ "በተንኳቸው ውስጥ" መረባቸውን ሲያበጁ "መረባቸውን ስያበጃጁ አየ" ተቀጣሪ ሠራተኞች "ለእነርሱ ተቀጥረው የሚሠሩ ሠራተኞች" ተከተሉት "ያዕቆብ እና ዮሐንስ ከኢየሱስ ጋር ሄዱ"

Mark 1:21

ማርቆስ **1**:**21**-**22**

Mark 1:23

ማርቆስ **1**:**23**-**26**
ምኩራባቸው ይህ ኢየሱስ እና የእርሱ ደቀ መዛሙርት የገቡበት የአምልኮ ሥፍራ ከዚህም በተጨማሪ ኢየሱስ ትምህርት ማስተማር የጀመረበት ሥፍራ ነው። የመጣኸው እኛል ለማፍታት ነውን? እርኩሳን መናፍሱ ኢየሱስን ይህንን ጥያቄ የጠየቁት ኢየሱስ እንዳይጎዳቸው ለመለመን ነው። አማራጭ ትርጓሜ: "እባክህ ፈጽመህ አታጥፋን!"

Mark 1:27

ማርቆስ **1**:**27**-**28**

Mark 1:29

ማርቆስ **1**:**29**-**31**
ከወጡ በኋላ ኢየሱስ፣ ስምኦን እና እንድሪያስ ከዚያ ከወጡ በኋላ ንዳዱ ተዋት "የስምኦን ምስት እናት ከነበረባት ንዳድ በሽታ ተፈወሰች" እርሱንም ታገለግላቸው ጀመረች በዚህ ሥፍራ ላይ በተዘዋዋር መንገድ ታገለግላቸው ጀመረች በሚል ሀረግ የተገለጸው ምግብ ማቅረብ ነው። አማራጭ ትርጓሜ: “ምግብ እና የሚጠጣ ነገር ሰጠቻቸው።”

Mark 1:32

ማርቆስ **1**:**32**-**34**
እርሱ . . . እርሱ . . . እርሱ . . . እርሱ እነዚህ ተውላጠ ስሞች የሚመለክቱት ኢየሱስ ነው። አጠቃላይ ከተማው በበር ላይ ተሰበሰበ በዚህ ሥፍራ ላይ “በአጠቃላይ” የሚለው ቃል ኢየሱስን ፍለጋ የመጠው ሰው ብዙ መሆኑን ለማሳየት የቀረበ በግነታዊ የሥነ-ጽሑፍ ዘይቤ የተገለፀ ነው። አማራጭ ትርጓሜ: “ከዚያ ከተማ በጣመ ብዙ ሕዝብ በበሩ አከባቢ ተሰበሰቡ።”

Mark 1:35

ማርቆስ **1**:**35**-**37**
ጸጥ ያለ ሥፍራ "እርሱ ብቻውን መሆን የሚያስችለው ሥፍራ" ሁሉም ሰው እርሱን ይፈልገው ነበር በዚህ ሥፍራ ላይ “ሁሉም” የሚለው ቃል ኢየሱስን ፍለጋ የመጡት ሰዎች ብዙ መሆናቸውን ለማሳየት በግነታዊ የሥነ-ጽሑፍ ዘይቤ በመጠቀም ነው። ለተሯሚዎች ምክር: በጣም ብዙ ሰዎች እየፈለጉህ ነው።”

Mark 1:38

ማርቆስ **1**:**38**-**39**
እርሱ . . . እርሱ . . . እርሱ . . . እርሱ እነዚህ ቃላት የሚያመለክቱት ኢየሱስ ነው። ወደ ሌላ ሥፍራ እንሂደት "ወደ ሌላ ሥፍራ መሄድ ያስፈልገናል" በገሊላ በኩል አልፎ ሄደ በዚህ ሥፍራ ላይ ጥቅም ላይ የዋለው “አልፎ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢየሱስ በአገልግሎቱ ወቅት ወደ ተለያዩ ሥፍራዎች ይሄድ እንደነበረ አጽኖት ለመስጠጥ ነው። አማራጭ ትርጓሜ: “በገሊላ ውስጥ ወደ ተለያዩ ሥፍራዎች ሄዷል።”

Mark 1:40

ማርቆስ **1**:**40**-**42**
አንድ ለምጻምም ሰው ወደ እርሱ መጣ፤ በፊቱም በጉልበቱ ተንበርክኮ ለመነው። እንድህም አለው "አንድ ለምጻምም ሰው ወደ ኢየሱስ መጣ፤ ለምጻሙም ሰው ኢየሱስን በጉልበቶቹ ተንበርክኮ ይለምነው ነበር። ለምጻሙ ሰው ኢየሱስን እንዲህ አለው” ፈቃድህስ ቢሆን "እኔን ንጹህ ልታደርገኝ ከፈለግህ" ልታነጻኝ ትችላለህ በዚህ ሥፍራ ላይ “ንጹሕ” የሚለው ቃል የሚወክለው ጤናማ መሆንን ነው። አማራጭ ትርጓሜ: “እኔን ማዳነት ትችላለህ።” እኔ ፈቃደኛ ነኝ "አንተን ንጹሕ ማድረግ እፈልጋለሁ"

Mark 1:43

ማርቆስ **1**፡ **43**-**44**
እርሱ . . . እርሱ . . . እርሱ . . . እነዚህ ቃላት የሚያመለክቱት ከለምጹ የተነጻውን ሰው ነው። ራስህን አሳይ በዚህ ሥፍራ ላይ “ራስህን “ የሚለው ቃል የሚያመለክተው የለምጻሙን ሰው ቆዳ ነው። ለተርጓሚወች ምክር: “ሄደህ ቆዳህን አሳይ።"

Mark 1:45

ማርቆስ **1**:**45**-**45**
ለሁሉም ሰው ተናገር . . . ወሬውም ተዳረሰ እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉሞች የሚጋሩ ሲሆን ይህ ሰው ለብዙ ሰዎች መናገሩ ላይ አጽኖት ይሰጣል። ሁለም ሰዎች በዚህ ሥፍራ ጥቅም ላይ የዋለው “ሁሉም ሰዎች” የሚለው ቃል ግነታዊ የስነ ጽሑፍ ዘይቤን በመጠቀም አጽኖት ለመስጠት ነው።” ለትርጓሚዎች ምክር: “ከብዙ ሰዎች ጋር ተገናኘ”። ኢየሱስ በነጻነት ወደዬትኛው ከተማ ለመግባት አልቻለም ነበር። "ኢየሱስ በከተማዎቹ ውስጥ በነጻነት እንዳይንቀሳቀስ ሕዝቡ ከለከሉት።” ከሁሉም ቦታ የመጡ በዚህ ሥፍራ ጥቅም ላይ የዋለው “ከሁሉም ቦታ የመጡ” የሚለው ሀረግ አጽኖት ለመስጠት የገባ ቃል ነው። አማራጭ ትርጓሜ: “በአከባቢው የመጡ ሰዎች ሁሉ።፤”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 2

1 ቀናት በኋላ ኢየሱስ ወደ ቅፍርናሆም ተመልሶ በመጣ ጊዜ፣ በቤት እንዳለ ወሬው ተሰማ። 2 ሰዎችም ተሰበሰቡ፤ከዚህ የተነሣ በበሩ መግቢያም እንኳ በቂ
ቦታ አልነበራቸውም። ኢየሱስም የእግዚአብሔርን ቃል ነገራቸው። 3 ሰዎችም አንድ ሽባ ሰው ወደ እርሱ አመጡ። 4 ብዛት ምክንያት ወደ እርሱ መቅረብ
ስላልቻሉ፣ኢየሱስ ባለበት አቅጣጫ ጣሪያውን ነደሉት። በቀዳዳውም ሽባው ያለበትን ዐልጋ ወደ ታች አወረዱት። 5 እምነታቸውን አይቶ ሽባውን ሰው፣ "አንተ
ልጅ ኀጢአትህ ተሰርዮልሃል" አለው። 6 ግን አንዳንድ ጸሓፍት በዚያ ተቀምጠው ነበር። ይህ ሰው እንዲህ ብሎ የሚናገረው ለምንድን ነው? እርሱ
እግዚአብሔርን ይሳደባል፤ 7 ከእግዚአብሔር በቀር ኀጢአትን ይቅር ማለት የሚችል ማን ነው? እያሉ በልባቸው ያጉረመርሙ ነበር። 8 ኢየሱስ በውስጣቸው
እያጉረመረሙ እንደሆነ በመንፈሱ ዐውቆ፣ "በልባችሁ የምታጉረመርሙት ለምንድን ነው? አላቸው። 9 ለሽባው ሰው የትኛውን ማለት ይቀላል? ኀጢአትህ
ተሰርዮልሃል ወይስ ተነሣ ዐልጋህን ተሸክመህ ሂድ ማለት? 10 እንጂ የሰው ልጅ በምድር ላይ ኀጢአትን የማስተሰረይ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ፣ 11
እልሃለሁ፤ ተነሣ! ዐልጋህን ተሸከምና ወደ ቤትህ ሂድ" አለው። 12 እርሱም ተነሣ፤ ወዲያውኑም ዐልጋውን ተሸክሞ በሁሉም ፊት ወጥቶ ሄደ።በዚያ የነበሩትም
ሁሉም ተገርመው ስለ ነበር እንዲህ ያለ ነገር ፈጽሞ አይተን አናውቅም በማለት እግዚአብሔርን አከበሩ። 13 ወደ ባሕሩ ዳርቻ ሄደ።ሕዝቡም በሙሉ ወደ እርሱ
ተሰበሰቡ፤ አስተማራቸውም። 14 ሲያልፍም የእልፍዮስን ልጅ ሌዊን ቀረጥ በመሰብሰቢያ ቦታው ተቀምጦ አየውና "ተከተለኝ" አለው። ተነሥቶም ተከተለው።
15 በእርሱ(በሌዊ) ቤት ተቀምጦ እየበላ ነበር። ብዙ ቀራጮችና ኀጢአተኞችም ከኢየሱስና ከደቀመዛሙርቱ ጋር ተቀመጡ፤ ብዙዎቹም ተከትለውት ነበርና። 16
ጸሓፍትም ከኀጢአተኞችና ከቀራጮች ጋር ሲበላ ሲያዩት ደቀመዛሙርቱን፣ "እርሱ ከቀራጮችና ከኀጢአተኞች ጋር የሚበላውና የሚጠጣው እንዴት ነው"
አሏቸው። 17 ይህን ሲሰማ፣ "ሕሙማን እንጅ ጤናሞች ሐኪም አያስፈልጋቸውም" ፤ እኔ ኀጢአተኞችን እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም አላቸው። 18
ደቀመዛሙርትና ፈሪሳውያን ይጾሙ ነበር። ወደ እርሱም መጥተው የዮሐንስ ደቀመዛሙርትና የፈሪሳውያን ደቀመዛሙርት የሚጾሙት ነገር ግን የአንተ
ደቀመዛሙርት የማይጾሙት ለምንድን ነው? አሉት። 19 እንዲህ አላቸው።ሙሽራው አብሮአቸው ሳለ ሚዜዎቹ ይጾማሉ? ሙሽራው ከእነርሱ ጋር እስካለ ሊጾሙ
አይችሉም። 20 ግን ሙሽራው የሚወሰድበት ቀን ይመጣል። በዚያን ጊዜ በዚያ ቀን ይጾማሉ። 21 አዲስ እራፊ ጨርቅ በዐሮጌ ልብስ ላይ አየይጥፍም፤
ያለበለዚያ የተጣፈው እራፊ ይቀደዳል። ቀዳዳውም የባሰ ይሆናል። 22 የወይን ጠጅ በዐሮጌ ዐቁማዳ ውስጥ የሚያስቀምጥ ማንም ለም። አለበለዚያ የወይን
ጠጁ ዐቁማዳውን ያፈነዳዋል፤የወይን ጠጁና ዐቁማዳውም ይበላሻሉ። ነገር ግን አዲስ የወይን ጠጅ በአዲስ ዐቁማዳ ውስጥ ያስቀምጣሉ። 23 በሰንበት ቀን
በእህል ማሳ መካከል ያልፍ ነበር። ደቀመዛሙርቱም ሲያልፉ እሸት መቅጠፍ ጀመሩ። 24 ፈሪሳውያንም እነሆ በሕግ ያልተፈቀደውን በሰንበት የሚያደርጉት
ለምንድን ነው? አሉት። 25 እንዲህ አላቸው። ዳዊት በተራበና በተቸገረ ጊዜ ለራሱና አብረውት ለነበሩት ምን እንዳደረገ፣ አብያታር ሊቀ ካህናት በነበረ ጊዜ ወደ
እግዚአብሔር ቤት እንደገባ፤ 26 ብቻ የተፈቀደውን ገጸ ኅብስት እንደ በላ፣ ከእርሱም ጋር ለነበሩት እንደሰጣቸው ፈጽሞ አላነበባችሁምን? እንዲህም አላቸው።
27 የተፈጠረው ለሰው ነው እንጂ ሰው ለሰንበት አልተፈጠረም። 28 የሰው ልጅ የሰንበትም እንኳ ጌታ ነው።

Mark 2:1

ማርቆስ 2:1-2
በዚያ የነበሩት ሰዎች እርሱ በቤት ውስጥ እንዳሉ ሰምተው "በዚያ የነበሩት ሰዎች በተመሳሳይ ቤት ውስጥ እንዳሉ ሰምተው" በቤት ውስጥ ለእነርሱ የሚሆን በቂ ቦታ አልነበረም "በቤቱ ውስጥ ለእነርሱ የሚሆን በቂ ቦታ አልነበረም”።

Mark 2:3

ማርቆስ 2:3-4
አንድ ሽባ ሰው ይዘው ወደ እርሱ መጡ "መራመድ የማይችል ወይም እጁን ማንቀሳቀስ የማይችል አንድ ሰውን ወደ እርሱ አመጡ" አራት ሰዎች "4 ሰዎች" ወደ እርሱ መቅረብ ፈጽመው አልቻሉም "ኢየሱስ ወደአለበት ሥፍራ መቅረብ ፈጽመው አልቻሉም"

Mark 2:5

ማርቆስ 2:5-7
እምነታቸውን አይቶ "እነዚህ ሰዎች እምነት እንዳላቸው አውቆ።" ይህ የተለያዩ ትርጉሞች ልኖሩት ይችላል 1) ሽባውን ሰው ተሸክመው የመጡት ሰዎች ብቻ እምነት ነበራቸው ወይም 2) ሽባው ሰው እና ተሸክመውት የመጡ ሰዎች እምነት ነበራቸው። ሽባወ ሰው "መራመድ የማይችለው ሰው" ልጅ በዚህ ሥፍራ ላይ “ልጅ” የሚለው ቃል የሚያሳየው አባት ልጁን እንደሚንከባከብ ሁሉ ኢየሱስም ለዚህ ሰው ግድ እንደሚለው ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጓሜ: “ልጄ” ኃጢአትህ ተሰረየለችልህ አማራጭ ትርጓሚዎች 1) "እግዚብሔር ኃጢአትህን ይቅር ብሎሃል" (ተመልከት 2:7) ወይም 2) "ኃጢአትህን ይቅት ብዬልሃለሁ።" (ተመልከት MRK 2:10) በልባቸው እንዲህ ብለው አሰቡ "ለራሳቸው እንዲህ በማለለት አሰቡ" ይህ ሰው እንዴት እንዲህ ሊናገር ቻለ? ይህ ጥያቄ የተጠየቀው ጸሐፍት ኢየሱስ ኃጢአትን የማስተሰረይ ኃይል እንዳለው ስለተጠራጠሩ ነው። አማራጭ ትርጓሜ: "ይህ ሰው እንዲህ ባለ መንገድ እንዴት ይናገራል!" ኃጢአትን ማስተሰይ ኃይል ከእግዚአብሔር ውጪ ያለው ማን ነው? ይህ ጥያቄ የተጠየቀው ጸሐፍት ኢየሱስ አምላክ መሆኑን ለሚጠራጠሩት ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጓሜ: “ኃጢአት ማስተሰረይ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።”

Mark 2:8

ማርቆስ 2:8-9
ለራሳቸው እንዲህ ብለው አሰቡ እያንዳንዱ ጸሐፍት ለራሳቸው እንዲህ ብለው አሰቡ፤ ይሁን እንጂ እርስ በእርሳቸው አልተነጋገሩም። በልባችሁ ስለምን እንዲህ ታስባለህ? ኢየሱስ ይህንን ጥያቄ የጠየቀበት ምክንያት ጸሐፍት የእርሱን ሥልጣን በመጠራጠራው ነው። አማራጭ ትርጓሜ: "ሥልጣኔን መጠራጠር የለባችሁም!" ልባቸውም ይህ "ልብ" የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ የሰዎችን አመለካከት፣ ስሜት፣ ፍላጎት ወይም ፈቃድ ለማመልከት ነው። ዬትኛው ይቀላል . . . . ሂድ? ኢየሱስ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው ጸሐፍት ሰውዬው ሽባ የሆነው በኃጢአቱ ምክንያት ነው የሚል እምነት ነበራቸው። ሰውዬው ኃጢአቱ ይቅር ከተባለለት መራመድ ይችላሉ። ኢየሱስ ሽባውን ሰው ከፈወሰው ጸሐፍት ኢየሱስ ኃጢአትን የማስተሰረይ እንደሚችል ልቀበሉ ይገባቸዋል ማለት ነው። አማራጭ ትርጓሜ: “ሽባውነን ሰው ኃጠአትህ ተሰረየችልህ ማለት ቀላል ነው!”

Mark 2:10

ማርቆስ 2:10-12
ይህንን ታውቁ ዘንድ "ይህንን አረጋግጥላችኋለሁ" የሰው ልጅ በዚህ ሥፍራ ላይ ራሱን “የሰው ልጅ” በማለት ይጠራል። እናንተ ጸሐፍት እና ሕዝቡ ለሽባው ሰው እንዲህ አለው "መራመድ ለማይችለው ሰው እንዲህ አለው" በሁሉም ሰዎች ፊት "በዚያ ሥፍራ በተሰበሰቱ ሰዎች ዐይን ፊት”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Mark 2:13

ማርቆስ 2፡ 13-14
ሕዝቡም ወደ እርሱ መጥተው "ሕዝቡም እርሱ ወደአለበት ሥፍራ መጥተው"

Mark 2:15

ማርቆስ 2:15-16
የሌዊ ቤት "የሌዊ ቤት" በጣም ብዙ ሰዎች የከተሉት ስለነበር ከብዙ ቀራጮች እና ኃጢአተኞች ጋር ኢየሱስ እና የእርሱ ደቀ መዛሙርት ጋር ምግብ ይበሉ ነበር። "ኢየሱስን ይከተሉት የነበሩት ብዙ ቀራጮች እና ኃጢአተኛ ከእየሱስ እና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ምግብ ይበሉ ነበር።" ከቀራጮች እና ከኃጢአተኞች ጋር ስለምን ይበላል? ጸሐፍት እና ፈሪሳዊያን ይህንን ጥያቄ የጠየቁት የኢየሱስን ከሁሉም ጋር መሆንን ትክክል አለመሆን ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጓሜ: ቀረጥ ከሚሰበስቡ ኃጢአተኛ ሰዎች ጋር መብላት እና መጠጣት የለበትን!"

Mark 2:17

ማርቆስ 2:17-17
እንዲህ አላቸው "ለፈሪሳዊያን እንዲህ አላቸው" ጤነኛ የሆኑ ሰዎች ሐኪም አያስፈልጋቸውም፤ ሐኪም የሚያስፈልጋቸው በሽተኞች ብቻ ናቸው ኢየሱስ በዚህ ሥፍራ ላይ ኃጢአተኛ መሆናቸውን የሚያውቁ ሰዎችን መታመማቸውን ከሚያውቁ ሰዎች ጋር ያነጻጽራል። አማራጭ ትርጓሜ: "ጻድቃን እንደሆኑ የሚያስቡ ሰዎች እገዛ አይፈልጉም፤ መታመማቸውን የሚያውቁ ሰዎች ብቻ ናቸው ከሌሎች እገዛ የሚፈልጉት! እኔ ጻድቅ የሆኑትን ሰዎች ለመጥራት አልመጣሁም። ይልቁንም ኃጢአተኛ የሆኑ ሰዎችን ለመጥራት ነው የመጣሁት። ኢየሱስ የመጣው እገዛን ለሚሹ ሰዎች መሆኑን አድማጮቹ እንዲገነዘቡ ይፈልጋል። ለትርጓሚዎች ምክር: "የመጣሁት ኃጢአተኞች መሆናቸውን ለተገዘነቡ ሰዎች እንጂ ራሳቸውን ጻድቅ አድረገው ለሚቆጥሩ ሰዎች አይደለም።"

Mark 2:18

ማርቆስ 2፡ 18-19
ነገር ግን ደቀ መዛሙርቱ አይጾሙም መጾም ማለት ምግብ አለመብላት ማለት ነው። ጾም በማይጾምበት አከበቢ ባለ ቋንቋ ውስጥ አውንታዊ ዓረፍተ ነገሮችን መጠቀም የተሻለ ነው። አማራጭ ትርጓሜ: “ይሁን እንጂ ደቀ መዛሙርትህ ያለማቋረጥ ይበለላሉ።” ሠርገኞች ሙሽራው ከእነርሱ ጋር እያለ ይጾናሉን? ኢየሱስ ይህንን ጥየቄ እርሱን እና ደቀ መዛሙርቱን ከሙሽራ እና የእርሱ ጓደኛ ጋር ለማነጻጸር ተጠቅሞበታል። አማራጭ ትርጓሜ: “እኔ ከእነርሱ ጋር እስካለሁ ድረስ ደቀ መዛሙርቴ በአዚህ ደስ ይላቸዋል።

Mark 2:20

ማርቆስ 2:20-21
ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ዘመን ይመጣል ኢየሱስ ስለሞቱ፣ ትንሳዔው እና እርገቱ ስናገር ራሱን ከሙሽራ ጋር ያነጻጽራል። ቋንቋችሁ ዋነ ገጸባህርው ማን እንደሆነ መግለጽ የሚፈልገው ከሆነ በተቻለ መጠን ጠቅላል ባለ ቋንቋ ግለጸው።ለተርጓሚዎች ምክር: "ሙሽራውን ይወስዱታል” ወይም “ሙሽራው ከእነርሱ ይሄዳል።" እነርሱ . . . እነርሱ በሠርጉ ላይ የታደሙት ሰዎች ማንም አዲስ እራፍ ጨርቅን በአሮጌ ልብስ ላይ የሚጥፍ የለም አዲስ እራፍ ጨርቅን በአሮጌ ልብስ ላይ መጣፍ በአሮጌው ጨርቅ ላይ ያለውን ቀዳዳ ይበልጥ ያሰፋዋል ምክንያቱም አዲሱ ጨርቅ በቀላሉ አይተጣጠፍምና ነው። አዲሱ ጨርቅ እና አሮጌው ልብስ፣ ሁለቱም ይበላሻሉ።

Mark 2:22

ማርቆስ 2፡ 22 -22
ማንም አዲስን የወይን ጠጅ በአሮጌ አቆማዳ ውስጥ የሚያስቀምጥ የለም ኢየሱስ በዚህ ሥፍራ ላይ የእርሱ ትምህረት እነና የደቀ መዛሙርቱን ከአዲስ የወይን ጠጅ እና አቆማዳ ጋር አነጻጽረዋል።ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር “የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት እና የፈርሳዊያን ደቀ መዛሙረት ለምን እንደሚጾሙ ነገር ግን የአንተ ደቀ መዛሙርት ግን ለምን አይጾሙም” ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ ምላሽ ይሰጣል። አማራጭ ትርጓሜ: “ማንም አዲስ ትምህርት ሌላ ልምምድ ውስጥ ውስጥ ላሉ ሰዎች አደራ ብሎ አይሰጥም።" አዲስ የወይን ጠጅ "የወይን ፍሬ ጁስ"። ይህ ገና ያልፈለ፣ አልኮል ያሌለው ወይንን ያሳያል። በአከባያችቹ የወይን ፍሬ የማይታወቅ ከሆነ ለፍራፍሬ መጠሪያ የሚሆን አጠቃላይ ቃልን ተጠቀሙ። አሮጌ አቆማዳ ይህ ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለን አቆማዳ ያመለክታል። አቆማዳ ይህ ከእንስሳት ቆዳ የሚሠራ ከረጥት ነው። “አቆማዳ” ወይም “የቆዳ ከረጥት” ተብሎ ይጠራል "skin (UDB)። ወይኑ የቆዳውን ከረጥት ይቀደዋል አዲሱ ወይን ስፈለ እና ስገላበጥ ከዚያ በላይ መለጠጥ ስለማይችል ይቀደዋ። ይጠፋል "ይበላሻል" (UDB) አዲስ የወይን አቆማዳ "አዲስ የወይን አቆማዳ” ወይም “አዲስ የወይን መያዥያ”። ይህ ከዚህ በፊት ወይን ተይዞበት የማያውቅን የወይን አቆማዳን ያመለክታል።

Mark 2:23

ማርቆስ 2:23-24
እነሆ፥ በሰንበት ያልተፈቀደውን ስለ ምን ያደርጋሉ? አሉት። ፈርሳዊያኑ ይህንን ጥያቄ የጠየቁት ኢየሱን ለመውቀስ ነው። አማራጭ ትርጓሜ: “ተመልከት! የአይሁድ ሕግ ስለ ስንበት የሚናገረውን ሕግ ይሸራሉ።" እሸት እየቀጠፉ ይበላሉ . . . በሰሰንት ያልተፈቀደውን ነገር ያደርጋሉ። በሌሎች ሰዎች ማሳ ውስጥ ያለን እሸት ቀጥፎ መብላት ስርቆት አይባልም ። ጥያቄው ይህንን በሰንበት ማድረጋቸው ተገቢ ነው ወይም አይደለም የሚል ነው። ይህንን ነገር እሼት እሸት ይህ የስንዴ ዘላላ ገና ሳይደርቅ ያለውን ያመለክታል። በዚህ የስንዴ ተክል አናት ላይ ፍሬዎቹ ይገኛሉ። ተመልከት "አሁን ለምነገር ነገር ትኩረት ስጥ"

Mark 2:25

ማርቆስ 2፡ 25-26
ዳዊት ባስፈለገውና በተራበ ጊዜ፥ እርሱ አብረውት ከነበሩት ጋር ያደረገውን፥ . . . አላነበባችሁምን? አላቸው። ኢየሱስ ጸሐፍት እና ፈርሳዊያን ታሪኩን ከዚህ በፊት ማንበባቸውን ያውቃል። ይሁን እንጂ ሆን ብለው ታሪኩ ማስተላለፍ የፈለገውን መልዕክት በትክክል አልተረዳችሁትም በማለት ኢየሱስ ይከሳቸዋል። አማራጭ ትርጉሞች: “ዳዊት እና ከእርሱ ጋር የተነበሩት ሰዎች ያደረገጉትን አስታውሱ . . . ይህንን እንዳደረገ ታውቃላችሁ" አብያተር በአይሁድ ታሪክ ውስጥ ዳዊት በኖረበት ዘመን ከነበሩት ሊቀ ካህናት መካከል አንዱ ነው። እርሱ እንዴት ወደ እግዚብሔር ቤት እንደገባ "ዳዊት ወደ እግዚአብሔር ቤር ገብቶ" (UDB)

Mark 2:27

ማርቆስ 2፡ 27-28
ሰንበት ስለ ሰው ተፈጥሮአል አማራጭ ትርጓሜ: "እግዚአብሔር ሰንበትን የፈጠረው ለሰው ልጆች መልካምነት ነው" እንጂ ሰው ስለ ሰንበት አልተፈጠረም፤ አማራጭ ትርጓሜ: "እግዚአብሔር ሰውን ለሰንበት መልካምነት አልፈጠረውም"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 3

1 ምኩራብም ደግሞ ገባ፤ በዚያም እጁ የሰለለችበት ሰው ነበረ። 2 ሰውየውን በሰንበት ቀን ይፈውሰው እንደሆነ ተመለከቱት። 3 የሰለለችበትን ሰውየም ተነሥ
አለው። 4 ሕዝቡንም በሰንበት ቀን የተፈቀደው መልካም ማድረግ ነው ወይስ ክፉ ማድረግ? ሕይወትን ማዳን ወይስ ማጥፋት? አላቸው። ነገር ግን ሕዝቡ ዝም
አሉ። 5 በቁጣ ሲመለከት፣ በልባቸው ድንዳኔ ዐዝኖ፣ ሰውየውን እጅህን ዘርጋ አለው፤ ዘረጋውም፤ ዳነም። 6 ወጡ፤ ወዲውም እንዴት ሊያጠፉት እንደሚችሉ
ከሄሮድስ ወገኖች ጋር በእርሱ ላይ ተማከሩ። 7 ከደቀ ዛሙርቱ ጋር ወደ ባሕሩ ሄደ፤ ከገሊላም እጅግ ብዙ ሕዝብ ተከትለው፤ ከይሁዳና 8 ከኤዶምያስና
ከዮርዳኖስ ማዶ፣ ከጢሮስና ከሲዶና ምን ታላላቅ ነገሮችን እንዳደረገ በመስማት እጅግ ብዙ ሕዝብ ወደ እርሱ መጣ። 9 የተነሣ እንዳያጨናንቁት ትንሽ ጀልባ
እንዲያቆዩለት ለደቀ መዛሙርቱ ተናገረ፤ 10 ፈውሶ ነበርና። በብዙ ደዌ የሚሠቃዩ ሁሉ ሊዳስሱት ይጋፉት ነበር። 11 መናፍስትም ባዩት ጊዜ በፊቱ ወደቁ፤ አንተ
የእግዚአብሔር ልጅ ነህ እያሉም ጮኹ። 12 ግን ማንነቱን እንዳይገልጡት አጥብቆ አዘዛቸው። 13 ወደ ተራራውም ወጣ፤ የሚፈልጋቸውንም ወደ እርሱ ጠራ፤
እነርሱም ወደ እርሱ ሄዱ። 14 ጋር እንዲሆኑ፣ ለመስበክ እንዲልካቸውና 15 ለማስወጣት ሥልጣን እንዲኖራቸው 16 ሁለት ሾመ፤ ጴጥሮስ ብሎ የሰየመው
ስምዖን፣ 17 ልጅ ያዕቆብና የያዕቆብ ወንድም ዮሐንስ፤ እነርሱንም ቦአኔርጌስ ብሎ ጠራቸው፤ የነጎድጓድ ልጆች ማለት ነው፤ 18 እንድርያስና ፊልጶስ፣
በርተሎሜዎስና ማቴያስ፣ ቶማስና የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ፣ ታዴዎስ፣ ቀናተኛው ስምኦንና 19 የሰጠው የአስቆሮቱ ይሁዳ። 20 ኢየሱስ ወደ አንድ ቤት ውስጥ
ገባ። መብላት እንኳ እስከማይችሉ ድረስ እንደ ገና ብዙ ሕዝብ መጥቶ ተሰበሰበ። 21 ዘመዶቹም በሰሙ ጊዜ ይዘውት ሊሄዱ ወደ እርሱ መጡ፤ ዐብዶአል
ብለው ነበርና። 22 የወረዱ ጻፎችም ብዔልዜቡል አለበት፤ አጋንንንትን የሚያስወጣውም በአጋንንት አለቃ ነው አሉ። 23 እርሱ ጠርቶአቸውም በምሳሌ
ነገራቸው፤ ሰይጣን እንዴት ሰይጣንንን ማስወጣት ይችላል? 24 መንግሥትም እርስ በርሱ ቢከፋፈል፣ ያ መንግሥት መቆም አይችልም፤ 25 ቤትም እርስ በርሱ
ቢለያይ፣ ያ ቤት ጸንቶ ሊቆም አይችልም። 26 ሰይጣንም እርስ በርሱ ቢቀዋወምና ቢለያይ፣ ፍጻሜው ይሆናል እንጂ መቆም አይችልም። በመጀመሪያ ኀይለኛውን
ሰው ካላሰረና ከዚያም ንብረቱን ካልዘረፈ በቀር፣ 27 ወደ ኀይለኛው ቤት መግባትና ንብረቱን መዝረፍ የሚችል የለም። 28 እላችኋለሁ፤ ለሰው ልጆች
ኀጢአታቸው ሁሉ፣ የሚሳደቡትም ስድብ ሁሉ ይቅር ይባላል፤ 29 ቅዱስን የሚሳደብ ግን ፈጽሞ ይቅርታ አያገኝም፤ ይልቁንም የየዘለዓለም ኀጢአት ዕዳ
አለበት፤ 30 ርኩስ መንፈስ አለበት ብለዋል። 31 ወንድሞቹም መጡ፤ ውጭ ቆመውም እንዲጠሩት ወደ እርሱ ላኩ። 32 ብዙ ሰው ተቀምጦ ነበር፤ ሰዎችም
እነሆ፣ እናትህና ወንድሞችህ ውጭ ይፈልጉሃል አሉት። 33 መለሰላቸው፤ አላቸውም፣ እናቴና ወንድሞቼ ማን ናቸው? 34 ዙሪያ የተቀመጡትን ተመልክቶም፣
እነሆ እናቴና ወንድሞቼ! ምክንያቱም 35 ፈቃድ የሚፈጽም ሁሉ ወንድሜ፣ እኅቴና እናቴ ነው።

Mark 3:1

ማርቆስ 3:1-2
ኢየሱስ ወደ ምኩራብ ገባ "ኢየሱስ ወደ ምኩራብ ገባ " እጁ የሰለለች ሰው "እጁ ሽባ የሆነችበት ሰው ነበር" ይህንን ሰው ይፈውሰው እንደሆነ ለማየት ይከታተሉት ነበር "ፈርሳዊያን ኢየሱስ ይህንን ሰው ይፈውሰው እንደሆነ ለማየት ይከታተሉት ነበር"

Mark 3:3

ማርቆስ 3:3-4
ተነሣና በሁሉም መካከል ቁም "ተነሣና በዚህ ሕዝብ መካከል ቁም።" ለመግደል . . . ተፈቅዷልን? ጸሐፊው “ሁሉም ዝም ማለታቸውን” ስለገለጸልን ኢየሱስ እነርሱን መጠየቁን እና መልስ እንዲሰጡት እየተጠበቀ እንደሆነ እንመለከታለን። ለተርጓሚዎች: "በሰንበት መልካም ነገርን ማድረግ ወይም መጉዳት ነው የተፈቀደው፤ ነፍስ ማዳን ወይስ መግደል።” በሕግ የተፈቀደው በሙሴ ሕግ መሠረት

Mark 3:5

ማርቆስ 3:5-6
እጅህን ዘርጋ "እጅህን ዘርጋ" ኢየሱስ የሰውዬውን እጅ ፈወሰ "ኢየሱስ እጁን አዳነ" ወይም "ኢየሱስ የሰውዬውን እጅ ከዚህ በፊት እንደነበረው ደህና አደረገለት" ከሄሮድስ ወገን ጋር ተማከሩበት። አማራጭ ትርጓሜ: "ከሄሮዶስ ወገን ከሆኑት ጋር ተሰበሰቡ" ወይም "ከሄሮዶስ ወገን ከሆኑት ጋር ተሰብስበው እቅድ አወጡ"

Mark 3:7

ማርቆስ 3:7-8
ማደረገውን ነገር ሁሉ ሰማ "ኢየሱስ ስላደረገው ታላላቅ ተአምራት ሁሉ ሰማ" ወደ እርሱም መጥተው "ሕዝቡም ወደ ኢየሱስ ወደአለበት መጥተው"

Mark 3:9

ማርቆስ 3:9-10
ለደቀ መዛሙርቱ ጀልባ ያዘጋጁለት ዘንድ ጠየቃቸው "ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አላቸው: ጀልባ አዘጋጁልኝ።" የሕዝቡ ተጽእኖ እጅግ በጣም ከባድ ነበር። "ሕዝቡ እርሱን ለመንካት ወደፊት ይጋፉ ነበር" (UDB) ችግር ያለባቸው ሁሉ እርሱን ለመንካት ይጋፉ ነበር "የታመሙ ሁሉ እርሱን ለመንካት ከፍተኛ ጥረት ያደርጉ ስለነበር እርስ በእርሳቸው ይገፋፉሉ"

Mark 3:11

ማርቆስ 3:11-12
እነርሱ . . . እነርሱ . . . እነርሱ በእርኩሳን መናስፍት ቁጥጥር የሆኑት ሰዎች አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ኢየሱስ በእርኩሳን መናስፍት ላይ ያለው ስልጣን ተያያዥነቱ “የእግዚአብሔር ልጅ1,” ከሚለው የእርሱ የማዕረግ ስም ጋር ነው። የእግዚአብሔር ልጅ ይህ ወሳኝ የሆነ የኢየሱስ የማዕረግ ስም ነው።

Mark 3:13

ማርቆስ 3:13-16
ከእርሱ ጋር ይሆኑ ዘንድ እንዲሁም ወንጌልን እንዲሰብኩ ይልካቸው ዘንድ ነው “ከእርሱ ጋር ይሆኑ ዘንድ እንዲሁም ወንጌልን እንዲሰብኩ ይልካቸው ዘንድ ነው” ወይም ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ እና ወንጌልን እንዲሰብኩ እንዲልካቸው" (UDB)

Mark 3:17

ማርቆስ 3:17-19
ታዴዎስ "ታዴዎስ" የኢየሱስ 12 ሐዋርያት ይሆኑ ዘንድ ከተመረጡት ሰዎች መካከል አንዱ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Mark 3:20

ማርቆስ **3:20-22**
እንደገናም ብዙ በጣም ብዙ ሰዎች ከመሰብሰባቸው የተነሳ ምግብ እንኳ ለመብላት አልቻሉም ነበር። "በጣም ብዙ ሕዝብ እንደገና ከመሰብሰቡ የተነሳ ምግብ ለመብላት እንኳ ጊዜ አላገኙም ነበር ወይም" ወይም "እርሱ በሚቆይበት ሥፍራ ላይ እንደገና ብዙ ሰዎች ተሰበሰቡ። በእርሱ ዙሪያም በጣም ብዙ ሰዎች ነበሩ። እርሱ እና የእርሱ ደቀ መዛሙርት ምግብ ለመብላት በቂ ጊዜ እንኳ ማግኘት አልቻሉም።" (UDB) እርሱን ለመያዝ መጡ የእርሱ ቤተሰብ አባላት ወደ ቤት መጥተው ለመያዝ እና እነርሱ ጋር ወደ ቤት በጉልበት እንዲሄድ መጡ።

Mark 3:23

ማርቆስ **3: 23-25**
ሴጣን እንዴት ሴጣንን ልያስወጣ ይችላል? "ሴጣን ራሱን ማስወጣት አይችልም" ወይም "ሴጣን የራሱ በሆኑት እርኩሳን መናስፍት ተቃራኒ አይሆንም"

Mark 3:26

ማርቆስ **3: 26-27**

Mark 3:28

ማርቆስ **3: 28-30**

Mark 3:31

ማርቆስ **3: 31-32**
መልዕክተኛ ወደእርሱ ዘንድ ሰደዱና አስጠሩት። "የኢየሱስ እናት እና ታናሽ ወንድሙ አንድ ሰው ወደ ቤቱ ውስጥ ልከው እነርሱ በውጪ እንደሚገኙ ለኢየሱስ ይናገርውና ውጪ ወጥቶ እንዲያናግራቸው ይነግረው ዘንድ መልዕክተኛ ላኩበት።"

Mark 3:33

ማርቆስ **3:33-35**
በውስጧ ተቀመጠ "ወደ ተንኳይቱ ገብቶ ተቀመጠ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 4

1 በባህር አጠገብ ማስተማር ጀመረ። ከህዝቡ መብዛት የተነሳ በባህር ላይ ባለ ጀልባ ገብቶ ተቀመጠ። ህዝቡም ሁሉ በባህሩ ዳርቻ ላይ ተሰብስበው ነበር። 2 ነገርም በምሳሌ አስተማራቸው። በትምህርቱም እንዲህ አላቸው። 3 ስሙ ዘሪ ሊዘራ ወጣ፤ 4 በሚዘራበትም ጊዜ አንዳንዱ በመንገድ ዳር ወደቀ ወፎችም መጥተው ለቀሙት። 5 ደግሞ ብዙ አፈር በሌለው በድንጋያማ መሬት ላይ ወደቀ። መሬቱ ጥልቀት ስላልነበረው ወዲያው በቀለ፤ 6 በወጣ ጊዜም ጠወለገ ሥርም ስላልነበረው ደረቀ። 7 ደግሞም አንዳንዱ በእሾህ መካከል ወደቀ እሾሁም አድጎ አነቀው ፍሬም አላፈራም። 8 አንዳንዱ በመልካም መሬት ላይ ወደቀ አደገ እየበዛ ሄደ ፍሬም አፈራ ሶስት እጥፍ ስልሳ እጥፍ እና መቶ እጥፍ ፍሬ ሰጠ። 9 እንዲህም አለ ጆሮ ያለው ይስማ። 10 በሆነ ጊዜ ከደቀመዛሙርቱ ጋር አብረው የነበሩት ስለ ምሳሌዎቹ ጠየቁት። 11 አላቸው ለእናንተ የእግዚአብሔር መንግሥት ምስጢር ተሰጥቷችኋል። በውጭ ላሉት ግን እንዲህ አይደለም 12 እንዳያዩ ሰምተውም እንዳያስተውሉ እንደገና ተመልሰው ይቅር እንዳይባሉ ሁሉም ነገር በምሳሌ ይሆንባቸዋል። 13 አላቸው እናንተ ይህ ምሳሌ አልገባችሁምን? ሌሎቹን ምሳሌዎች ሁሉ እንዴት ትረዳላችሁ? 14 ዘሪው ቃሉን ዘራ። 15 በመንገድ ዳር የወደቁት እነዚህ ናቸው ቃሉ በሚዘራበት ጊዜና ቃሉን እንደሰሙ ወዲያውኑ ሰይጣን መጥቶ በውስጣቸው የተዘራውን ቃል ይወስዳል። 16 በድንጋያማ መሬት ላይ የወደቁት እነዚህ ቃሉን በሰሙ ጊዜ ወዲያውኑ በደስታ ይቀበሉታል 17 ሥር የላቸውምና ለጊዜው ይቀበሉታል ከዚያም በቃሉ ምክንያት መከራ ወይም ስደት በሚነሳበት ጊዜ ወዲያውኑ በቃሉ ይሰናከሉበታል፤ 18 ቦታ የወደቁት እነዚህ ቃሉን የሰሙ ናቸው 19 አለም ሀሳብና የባለጠግነት ማታለል የሌሎች ነገሮች ምኞት ይገቡና ዘሩን ያንቁታል ፍሬ የማያፈራም ይሆናል። 20 መሬት የወደቁት እነዚህ ቃሉን ሰምተው የሚቀበሉት ናቸው ሰላሳ እጥፍ ስልሳ እጥፍ እና መቶ እጥፍ የሚያፈሩ ናቸው። 21 አላቸው፦ መብራትን ከፍ ባለ ማስመጫ ላይ እንጂ ከእንቅብ በታች ወይም አልጋ ሥር ያስቀምጡታልን? 22 ሳይገለጥ የሚቀር ነገር የለም በሚስጢር የተደረገ ወደ ብርሃንም የማይወጣ የለም። 23 ያለው ይስማ እንዲህም አላቸው 24-25 አስተውሉ መስፈሪያ ይሰፈርላችኋል ለእናንተም የበለጠ ይሰጣችኋል። ላለው የበለጠ ይጨመርለታል ከሌለው ግን ያ ያለው እንኳ ይወሰድበታል። 26 አለ የእግዚአብሔር መንግሥት በመሬት ላይ ዘርን የዘራን ሰው ትመስላለች። 27 ሲመሽ ይተኛል ሲነጋም ይነቃል። እንዴት እንደሆነ ባላወቀው መልኩ ዘሩ አቆትቁጦ በቀለ፤ 28 ምድር የራሷን ሰብል ፍሬ አፈራች መጀመሪያ ቅጠሉ ቀጥሎም ዛላው በመጨረሻም በዛላው ውስጥ ሙሉ ፍሬ አፈራች። 29 ግን ፍሬው በደረሰ ጊዜ መከር ነውና ወዲያውኑ ማጭድ አዘጋጀ። 30 እንዲህ አለ የእግዚአብሔርን መንግሥት በምን እንመስላታለን? ወይም በምን ምሳሌ እንገልጻታለን? 31 ቅንጣት ትመስላለች። በምድር ላይ በተዘራ ጊዜ ሲዘራ ምንም እንኳ በምድር ካሉ ዘሮች ሁሉ ያነሰ ቢሆንም 32 ጊዜ ያድጋል ቅርንጫፍም ያወጣል የሰማይ ወፎች ከጥላው ሥር እስኪጠለልቡበት ድረስ ከተክሎች ሁሉ ይልቅ ታላቅ ይሆናል። 33 ሊሰሙ በሚችሉት መጠን ቃሉን በብዙ ምሳሌዎች ተናገራቸው 34 ምሳሌ ምንም አልተናገራቸውም። ለደቀመዛሙርቱ ግን ለብቻቸው ሁሉንም ነገር ገለጸላቸው። 35 ቀን በመሸ ጊዜ ወደ ማዶ እንሻገር አላቸው። 36 ህዝቡንም ትተው በጀልባ ወሰዱት። ሌሎችም ጀልባዎች ከእርሱ ጋር ነበሩ። 37 የነፋስ ማዕበልም ተነሳ ጀልባው እስኪጥለቀለቅ ድረስ ማዕበል ጀልባውን መታው። 38 ከጀልባው በስተኋለኛው ክፍል ትራስ ተንተርሶ ተኝቶ ነበር። ቀስቅሰውም መምህር ሆይ ስንጠፋ አይገድህምን አሉት። 39 እርሱም ተነሳ ነፋሱንም ገሰጸው ባህሩንም ዝም በል ጸጥ በል አለው። ነፋሱም ተወ ታላቅ ጸጥታም ሆነ። 40 ስለምን ፈራችሁ? እምነት የላችሁምን እምነታችሁስ ወዴት አለ አላቸው። 41 ፈርተው እርስ በእርሳቸው ነፋሱና ባህሩ እንኳ የሚታዘዙለት እንግዲህ ይህ ማነው? ተባባሉ።

Mark 4:1

ማርቆስ 4:1-2
እናም ወደ ባሕሩ ውስጥ ገፏት “እናም ተንኳይቱን ወደ ባሕሩ ውስጥ ገፏት

Mark 4:3

ማርቆስ 4:3-5
አደጉ "በፍጥነት ማደግ ጀመሩ"

Mark 4:6

ማርቆስ 4:6-7
ጠቀለጉ "ተቃጠሉ"

Mark 4:8

ማርቆስ 4፡ 8-9
የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ "በጥሞና የሚሰማ ሰው የዚህን ነገር ትርጉም በሚገባ ይረዳል”።

Mark 4:10

ማርቆስ 4፡ 10-12
ለእናንተ ተሰጥቶዋችኋል "እግዚአብሔር ሰጥቶዋችኋል" ወይም "እኔ ሰጥቼአችኋዋለሁ" ያያሉ ግን አያስተውሉም "ይመለከታሉ ነገር ግን ለማስተዋል አይፈልጉም" ወይም "ይመለከታሉ ግን አይረዱም"

Mark 4:13

ማርቆስ 4፡ 13-15
ይህንን ምሳሌ ተረድታችሁታልን? እንዲህ ከሆነ እንዴት ሌሎችን ምሳሌው መረዳት ትችላላችሁ? "የዚህን ምሳሌ ትርጉም መረዳት የማትችሉ ከሆነ የተቀሩትን ምሳሌዎችንም መረዳት አትችሉም።"

Mark 4:16

ማርቆስ 4፡ 16-17

Mark 4:18

ማርቆስ 4፡ 18-20
የዚህ ዓለም ሀሰብ አማራጭ ትርጉም: "አሁን ስላለው ሕይወት ግድ የሚላቸው" የባለጠግነት ምኞት አማራጭ ትርጉም: "እርካታ የማይሰጡት በሀብት የሚገኘው ደስታ" የሌሎች ነገሮች ምኞች "ከሀብት ውጪ ያሉት ሌሎች መሻቶች"

Mark 4:21

ማርቆስ 4፡ 21-23
መብራትን ከእንቅብ ወይም ከአልጋ በታች ለማኖር ወደ ቤት ውስጥ ያመጡታልን? "መብራትክ ከእንቅብ ወይምከአልጋ በታች ለማኖር በእርግጠኝነት ወደ ቤት ውስጥ አታመጡም።" የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ ይህንን በ MRK 4:9 ላይ በተረጎማችሁት መሠረት ትርጉሙት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Mark 4:24

ማርቆስ **4**፡ **24-25**
በሠፈራችሁት መሥፈሪያ ልክ ትቀበላላችሁ፤ እንዲያው ከዚያ በላይ ታገኛላችሁ "የበለጠ ባደመጣችሁ ቁጥር እግዚብሔር የለልጥ መረዳትን ይሰጣችኋል።" ማንም . . . "ቃሌን የተረዳ ማንም ሰው ቢሆኖር።"

Mark 4:26

ማርቆስ **4**፡ **26-29**
ዘርን እንደሚዘራ ሰው "ዘሩን እንደሚዘራ ገበሬ" ማጭድ የእርሻ ምርት ለማጨድ የሚገለግል መሣሪያ

Mark 4:30

ማርቆስ **4**፡ **30-32**
"የእግዚብሔርን መንግስት ከምን ጋር እናነጻጽራታለን እንዲሁም በምን ምሳሌ እንገልጻታለን? "በዚህ ምሳሌ አማካኝነት የእግዚአብሔር መንግሰት ምን እንደሚትመስል ማስረዳት ይቻላል።

Mark 4:33

ማርቆስ **4**፡ **33-34**
ማድመጥ እስከቻሉ ድረስ "መረዳት እስከቻሉ ድረስ"

Mark 4:35

ማርቆስ **4**፡ **35-37**

Mark 4:38

ማርቆስ **4**፡ **38-39**
ስንጠፋ ግድ አይልህምን? "ለሁኔታው ትኩረት እንድትሰጠው እንፈልጋለን፤ ልንሞት ነው!" - ልንሞት ነው በዚህ ሥፍራ ላይ "እኛ" የሚለው ቃል ደቀ መዛሙርቱን እና ኢየሱስን የሚያካትት ነው። ገሰጸው "በቁጣ አስተካከለው" ወይም "መገሰጽ" ሠላም፣ ጸጥ በል። "ሠላም" እና "ጸጥ በል" ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ቃላት ናቸው።

Mark 4:40

ማርቆስ **4**፡ **40-41**
እንዲህ የምትፈሩ ስለ ምን ነው? "በጣም በመፍራታችሁ በጣም አፍሬባችኋለሁ።" ይህ ማን ሊሆን ይችላል "ይህ ሰው ማን እንደሆነ በጥንቃቄ ልናሰብ ይገባናል!"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 5

1 ባሕሩ ሌላ ዳርቻ፣ ወደ ጌርጌሴኖን አገር መጡ። 2 ከጀልባዋ ውስጥ ሲወጣም ወዲያውኑ ርኩስ መንፈስ ያለበት አንድ ሰው ከመቃብር ሥፍራ ወጥቶ
ተገናኘው፤ 3 በመቃብር ስፍራ አድርጎ ነበር፤ እርሱን በሰንሰለት ሊያስረው የሚችል ሰው አልነበረም፤ 4 ጊዜ በእግር ብረትና በሰንሰለት ይታሰር ስለ ነበር፣
ሰንሰለቶቹን ይበጣጥሳቸው፣ እግር ብረቶቹንም ይሰባብራቸው ነበር፤ እርሱን ለመያዝ የሚያስችል ጥንካሬ ያለው ሰውም አልነበረም። 5 ቀንና ሌሊት
በመቃብሮቹና በተራራዎቹ ዘንድ ሰውነቱን በድንጋይ እየቈረጠ ይጮኽ ነበር። 6 ከሩቅ ሲያየው፣ ሮጠና ሰገደለት፤ 7 በመጮኽም፣ የልዑል እግዚአብሔር ልጅ
ኢየሱስ ከአንተ ጋር ምን አለኝ? በእግዚአብሔር አምልሃለሁ፣ አታሠቃየኝ አለ። 8 ርኩስ መንፈስ ከሰውየው ውጣ ብሎት ነበርና። 9 ማን ነው ብሎም ጠየቀው፤
ብዙ ነንና ስሜ ሌጌዎን ነው አለው። 10 እንዳያባርራቸውም አጥብቆ ለመነው። 11 በተራራው ጥግ ትልቅ የእሪያ መንጋ ይሰማራ ነበር። 12 በእነርሱ ውስጥ
እንድንገባ ወደ እሪያዎቹ ስደደን በማለትም ለመኑት። 13 እዲሄዱ ፈቀደላቸው። ርኩሳን መናፍስቱም ወጡ፣ በእሪያዎቹም ውስጥ ገቡ፤ ሁለት ሺ ያህል እሪያ
ያለበት መንጋም በቁልቁለቱ ላይ ወደ ባሕሩ እየተንጋጋ ሄደ፤ በባሕሩም ውስጥ ሰመጠ። 14 የሚጠብቁትም ሸሹ፤ በከተማውና በአገሩ ውስጥም አወሩት።
የሆነውንም እንዴት እንደ ነበረ ለማየትም ሰዎች መጡ። 15 ኢየሱስም መጥተው አጋንንት ያደሩበትን፣ ሌጌዎንም እንኳ የነበረበትን ሰው ተቀምጦ፣ ልብስ
ለብሶና ልቡም ተመልሶለት አይተው ፈሩ። 16 ሰዎችም አጋንንት ባደሩበት ሰውየ ላይ የታየው እንዴት እንደ ሆነና በእሪያዎቹ የሆነውም እንዴት እንደ ነበረ
ነገሯቸው። 17 ኢየሱስንም ከአገራቸው እንዲወጣ ይለምኑት ጀመር። 18 ጀልባዋ ውስጥ እየገባ ሳለ፣ በአጋንንት ተይዞ የነበረው ሰው ከአንተ ጋር ልኑር ብሎ
ለመነው። 19 አልፈቀደለትም፤ ይልቁንም ወደ ቤትህ፣ ወደ ዘመዶችህ ሂድ፣ ጌታ ለአንተ እንዴት ታላላቅ ነገሮችን እንዳደረገልህ፣ እንዴትም ምሕረቱን ባንተ ላይ
እንዳሳየ ንገራቸው አለው። 20 ሄደና ኢየሱስ እንዴት ታላላቅ ነገሮችን እንዳደረገለት ዐሥር ከተማ በሚባለው ውስጥ ማሠራጨት ጀመረ፤ ሰዎችም ሁሉ ተደነቁ።
21 በጀልባዋ ወደ ሌላ አቅጣጫ ይሄድ በነበረ ጊዜም ደግሞ፣ እጅግ ብዙ ሕዝብ ወደ እርሱ ተሰበሰበ፤ እርሱም በባሕሩ አቅራቢያ ነበረ። 22 ከምኵራብ
ኀላፊዎች አንዱ፣ ኢያኢሮስ የሚባል መጣ፣ እርሱንም አይቶ በእግሩ ሥር ወደቀ፤ 23 ልጄ ልትሞት ነው፤ እንድትድንና በሕይወት እንድትኖር መጥተህ እጅህን
ትጭንባት ዘንድ እለምንሃለሁ በማለትም አጥብቆ ለመነው። 24 ዐብሮት ሄደ፤ እጅግ ብዙ ሰዎችም ተከተሉት፤ ይጋፉትም ነበር። 25 ሁለት ዓመት ደም ይፈስባት
የነበረ፣ 26 ብዙ ችግር የደረሰባት ብትሆንና ያላትን ሁሉ ብትከፍልም፣ ምንም ያልተሻላት፣ ይልቁንም የባሰባት 27 ሴት ስለ ኢየሱስ ሰምታ ከሕዝቡ በስተኋላ
መጣች፣ የኢየሱስንም ልብስ ነካች። 28 ላት፣ ይልቁንም የባሰባት 27አንድ ሴት ስለ ኢየሱስ ሰምታ ከሕዝቡ በስተኋላ መጣች፣ የኢየሱስንም ልብስ ነካች።
28ልብሱን ብቻ ከነካሁ እድናለሁ ብላለችና። 29 የሚፈስሰው ደሟ ቆመ፤ ከሕማሟ እንደ ተፈወሰችም በሰውነቷ ታወቃት። 30 ኢየሱስ ኀይል ከእርሱ
መውጣቱን በራሱ በመረዳት፣ ዙሪያውን ወደ ሕዝቡ ተመለከተ፤ ልብሴን የነካው ማን ነው? ብሎም ተናገረ። 31 መዛሙርቱም ሕዝቡ ሲጋፉህ ታያለህ፣ የነካኝ
ማን ነውም? ትላለህ። 32 ይህን ያደረገችውንም ለማየት ዙሪያውን ተመለከተ። 33 ሴትዮዋ ግን በመፍራትና በመንቀጥቀጥ፣ ለእርሷ የተደረገውንም በማወቅ
መጣችና በፊቱ ወደቀች፤ እውነቱንም ሁሉ ነገረችው። 34 እርሱም፡- ልጄ ሆይ! እምነትሽ አድኖሻል፤ በሰላም ሂጂ፣ ከሕማምሽም ተፈወሺ አላት። 35 ኢየሱስ
ገና እየተናገረ ሳለ ከምኵራቡ ኀላፊ ቤት ሰዎች መጡ፤ ልጅህ ሞታለች፤ መምህሩን ለምን ታስቸግረዋለህ ብለውም ተናገሩ። 36 ኢየሱስ የተናገሩትን ሰምቶ
የምኵራቡን ኀላፊ “አትፍራ፤ እመን ብቻ” አለው። 37 ኢየሱስ ከጴጥሮስ፣ ከያዕቆብና ከያዕቆብ ወንድም ከዮሐንስ በቀር ማንም እንዲከተለው አልፈቀደም። 38
ወደ ምኵራቡ ኀላፊ ቤት መጡ፤ ኢየሱስ ያዘኑ፣ የሚያለቅሱና የዋይታ ጩኸት የሚያሰሙ ሰዎችን ተመለከተ። 39 ወደ ውስጥ ገባና “ለምን ታዝናላችሁ?
ለምንስ ታለቅሳላችሁ? ልጅቱ ተኝታለች እንጂ አልሞተችም” አላቸው። 40 ሰዎቹ በኢየሱስ ሣቁበት፤ እርሱ ግን ሁሉንም ወደ ውጭ አስወጣቸው። የልጅቱን
አባትና እናት፣ ከእርሱም ጋር የነበሩትን ይዞ ልጅቱ ወደ ነበረችበት ክፍል ገባ። 41 ከዚያም ልጅቱን በእጁ ይዞ “ታሊታ ኩም!” ትርጉሙ “ትንሿ ልጅ ተነሺ
እልሻለሁ” ማለት ነው። 42 ወዲያው ልጅቱ ተነሣች፤ መራመድም ጀመረች። (ዐሥራ ሁለት ዓመቷ ነበርና) በዚህ ሰዎቹ በጣም ተገረሙ። 43 ከዚያም ኢየሱስ
ስለዚህ ጕዳይ ማንም ማወቅ እንደሌለበት ለሰዎቹ ጥብቅ ትእዛዛትን ሰጣቸው፤ የምትበላውንም ስጧት አለ።

Mark 5:1

ማርቆስ 5፡ 1-2

Mark 5:3

ማርቆስ 5፡ 3-4
እግሮቹ በሰንሰለት የታሠሩ "በሰንሰለት እግሮቹ የታሠሩ" እርሱን መያዝ "እርሱን መቆጣጠር"

Mark 5:5

ማርቆስ 5፡ 5-6

Mark 5:7

ማርቆስ 5፡ 7-8
ይጮኽ ነበር "እርኩስ መንፈሱ ይጮኽ ነበር" ከአንተ ጋር ምን አለኝ? አማራጭ ትርጉም: "ከአንተ ጋር ምንም ጉዳይ የለኝ" አታሰቃየኝ "አታዘቃየኝ" (UDB) የልዑል የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ? በእግዚአብሔር በራሱ አምልሃለሁ እባክህ አታሰቃየኝ። “የልዑል የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ” እርኩሳን መናፍስትን የማሰቃየት ኃይል አለው። የልዑል የእግዚአብሔር ልጅ ይህ የኢየሱስ ወሳኝ የሆነ የማዕረግ ስሙ ነው።

Mark 5:9

ማርቆስ 5፡ 9-10
እርሱም እንዲህ አለው፣ "ስሜ ሠሰራዊት ነው፣ ምክንያቱም ብዙዎች ነን።" በሰውዬው ውስጥ ያሉት እርኩሳን መናፍስት ለኢየሱስ እንዲህ አሉት፤ በዚህ ሰው ውስጥ ያለው አንድ እርኩስ መንፈስ ብቻ ሳይሆን ብዙ እርኩሳን መናፍስት ናቸው።

Mark 5:11

ማርቆስ 5፡ 11-13
እርሱም ፈቀደላቸው "ኢየሱስ ለእርኩሳን መናፍስቱ ፈቀደላቸው" ወደ ሁለት ሺህ አከባቢ የሚጠጉ አሳማዎች "ወደ 2000 አከባቢ የሚጠጉ አሳማዎች"

Mark 5:14

ማርቆስ 5፡ 14-15
ወደ አእምሮውም ተመለሰ "ወደ አእምሮው ተመለሰ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Mark 5:16

ማርቆስ 5፡ 16-17
በእርኩስ መናፈስት ተይዞ የነበረውም ሰው "በእርኩሳን መናፍስት ቁጥጥር ሥር የነበረው ሰው"

Mark 5:18

ማርቆስ 5፡ 18-20
ዐሥር ከተሞች ከገሊላ በባሕር በደቡብ ምሥራቅ አከባቢ

Mark 5:21

ማርቆስ 5፡ 21-24

Mark 5:25

ማርቆስ 5:25-27
ለዐሥራ ሁለት ዓመታት "ለ 12 ዓመታት"

Mark 5:28

ማርቆስ 5፡ 28-29

Mark 5:30

ማርቆስ 5፡ 30-32
“አሁን የነካኝ ማን ነው?” ትላለህን አማራጭ ትርጉም፡ “በዚህ ግርግር ውስጥ ሆነህ ማን እንደነካህ መጠየቅህ በጣም አስገርሞናል”

Mark 5:33

ማርቆስ 5፡ 33-34
ሴት ልጅ ኢየሱስ ይህንን ቃል የተጠቀመው በምሳሌያዊ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ማሳየት የፈለገውም ይህች ሴት በእርሱ ማመኗን ነው።

Mark 5:35

ማርቆስ 5፡ 35-35
መምህሩን ከዚህ በላይ ለምን ታስቸግሪዋለህ? አማራጭ ትርጉም፡ "መምህሩን ከዚህ በላይ አታስቸግረው።"

Mark 5:36

ማርቆስ 5፡ 36-38
ሲንጫጩና ሲያለቅሱ በዚህ ሥፍራ ላይ “ሲንጫጩ” እና “ሲያለቅሱ” የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጓሜዎች አሏቸው። አማራጩ ትርጉም፡ "ሲያለቅሱ በታላቅ ድምፅ ይጮኹ ነበር"

Mark 5:39

ማርቆስ 5፡ 39-40
ስለምን ተቆጣችሁ፣ ሰለምንስ ታለቅሳላችሁ? አማራጭ ትርጉም፡ "መንጫጫትም ሆነ ማልቀስ የለባችሁም።"

Mark 5:41

ማርቆስ 5፡ 41-43
የዐሥራ ሁለት ዓመት ዕድሜ ነበራት "ዐሥራ ሁለት ዓመቷ ነበር" በጣም አስጠነቀቃቸው "አጥብቆ ነገራቸው"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 6

1 ከዚያ ወጥቶ ወደ ገዛ ምድሩ መጣ፤ ደቀመዛሙርቱም ተከተሉት። 2 ሰንበት በሆነ ጊዜም በምኩራብ ውስጥ ሊያስተምር ጀመረ። የሰሙትም ሁሉ ይህ ሰው እነዚህን ነገሮች ከወዴት አገኛቸው? ለዚህ ሰው የተሰጠችውስ ጥበብ እንደምን ያለች ናት፤ በእጆቹ የሚደረጉት እነዚህ ታላላቅ ነገሮችስ ምን ትርጉም ይኖራቸው ይሆን? 3 ይህ አናጺው የማርያም ልጅ፤ የያዕቆብና የዮሳ፣ የይሁዳና የስምዖን ወንድም አይደለምን? እህቶቹስ ቢሆኑ እዚህ ከእኛ ጋር አይደሉምን? በማለት ተደነቁ፤ ተሰናከሉበትም። 4 ኢየሱስም ነብይ በሀገሩ፣ በወገኑና በገዛ ቤተሰቡ ካልሆነ በስተቀር ሳይከበር አይቀርም አላቸው። 5 ላይ እጆቹን ጭኖ ከመፈወስ በስተቀር በዚያ ታላቅ ተአምራት አላደረገም። 6 ምክንያት ተደነቀ። በየመንደሮቹም እያስተማረ ዞረ። 7 አሥራ ሁለቱን ወደ ራሱ ጠራና ሁለት ሁለት አድርጎ ይልካቸው ጀመር፤ በእርኩሳን መናፍስት ላይም ሥልጣንን ሰጣቸው። 8 ለጉዞአቸውም ከበትራቸው በቀር ምግብ፣ የመንገድ ሻንጣም ሆነ በገንዘብ ቦርሳቸው ውስጥ ገንዘብ እንዳይዙ አዘዛቸው። 9 በስተቀር ቅያሪ ልብስ አትያዙ አላቸው። 10 ከዚያ እስክትወጡ ድረስ በምትገቡበት ቤት በዚያ ቆዩ አላቸው። 11 ቦታ ሁሉ ከማይቀበሏችሁና ከማይሰሟችሁ ሰዎች ምሥክር ይሆንባቸው ዘንድ በጫማችሁ ሥር ያለውን አቧራ አራግፉ። 12 ደቀ መዛሙርቱም ወጥተው ሰዎች ንሰሐ እንዲገቡ ሰበኩላቸው። 13 ብዙ አጋንንትን አስወጡ፤ ታመው የነበሩ ብዙዎችንም ዘይት ቀብተው ፈወሱአቸው። 14 ዝናው ወጥቶ ነበርና ንጉሡ ሔሮድስ በሰማ ጊዜ አጥማቂው ዮሐንስ ከሙታን ተነሥቶአል፤ ስለዚህ እነዚህ ታላላቅ ነገሮች የሚደረጉትም በእርሱ ነው አለ። 15 ግን ሌሎች ኤልያስ ነው አሉ። ሌሎቹም ነብይ ወይም ከነብያት አንዱ ነው አሉ። 16 ነገር ግን ሔሮድስ ይህንን ሁሉ በሰማ ጊዜ እኔ አንገቱን ያስቆረጥኩት ዮሐንስ ተነሥቶአል አለ። 17 ባገባት በወንድሙ በፊሊጶስ ሚስት በሄሮድያስ ምክንያት ራሱ ልኮ ዮሐንስን በመያዝ በወህኒ አኑሮት ነበርና። 18 ዮሐንስም ሔሮድስን የወንድምህ ሚስት ለአንተ ልትሆን አይገባም ይለው ነበር። 19 ሔሮድያዳ ዮሐንስን ትቃወምና ልትገድለው ትፈልግ ነበር፣አልቻለችምም። 20 ሔሮድስ ዮሐንስን ይፈራው ነበር። ቅዱስና ጻድቅ እንደሆነ በማወቁም ይጠነቀቅለት ነበር። በሚሰማው ጊዜ ግራ እየተጋባም ቢሆን በደስታ ይሰማው ነበር። 21 ምቹ ቀን በመጣ ጊዜም ልደቱን አስመልክቶ ሔሮድስ ለመኳንንቱ፣ ለሹማምንቱና ለገሊላ ታላላቅ ሰዎች የእራት ግብዣ አዘጋጀላቸው። 22 የሄሮድያዳ ልጅ ራሷ ገብታ በዘፈነች ጊዜም ሔሮድስንና ከእርሱ ጋር በማዕድ የተቀመጡትን አስደሰተቻቸው። ንጉሱም ልጃገረዲቱን የምትፈልጊውን ሁሉ ጠይቂኝ እሰጥሻለሁ አላት። 23 ማናቸውንም የምትፈልጊውን ጠይቂኝ፣ የመንግሥቴን ግማሽም ቢሆን እሰጥሻለሁ ብሎ ማለላት። 24 እርስዋም ወጥታ ወደ እናቷ በመሄድ ምን ልጠይቀው? ብትላት የአጥማቂው የዮሐንስን ራስ አለቻት። 25 እርስዋም ወደ ንጉሱ ፈጥና በመምጣት የአጥማቂውን የዮሐንስን ራስ በሳህን እንድትሰጠኝ እፈልጋለሁ አለችው። 26 ንጉሡም እጅግ አዘነ። ነገር ግን በመሐላዎቹና በማዕድ በተቀመጡት ምክንያት አልተቃወማትም። 27 ንጉሡም ወዲያውኑ ከጠባቂዎቹ አንደኛውን ወታደር ልኮ ራሱን እንዲያመጣ አዘዘው። እርሱም ሔደና በወህኒ የዮሐንስን ራስ ቆረጠው፤ 28 በሳህን አምጥቶም ለልጃገረዲቱ ሰጣት፣ ልጃገረዲቱም ለእናቷ ሰጠቻት። 29 ደቀመዛሙርቱም ይህንን በሰሙ ጊዜ መጡና አስከሬኑን ወስደው በመቃብር አኖሩት። 30 ሐዋርያቱም ወደ ኢየሱስ ተመልሰው ያደረጉትንና ያስተማሩትን ነገር ሁሉ ነገሩት። 31 እርሱም እናንተ ራሳችሁ ወደ ምድረበዳ ኑና ጥቂት ጊዜ ዕረፉ አላቸው። ወደ እነርሱ የሚመጡና የሚሔዱ ብዙዎች ነበሩና ለመብላት እንኳን ጊዜ አጥተው ነበር። 32 በጀልባ ገብተው ወደ ምድረበዳው ፈቀቅ ብለው ሔዱ። 33 ሲሔዱም ሕዝቡ አዩአቸውና ብዙዎቹ አወቁአቸው፤ እነርሱም ከየከተሞቹ ሁሉ በአንድነት በሩጫ ቀደሟቸው። 34 ወደዚያ በመጣም ጊዜ ብዙ ሕዝብ አይቶ እረኛ እንደሌላቸው በጎች ይመስሉ ነበርና አዘነላቸው። ብዙ ነገሮችንም ያስተምራቸው ጀመር። 35 ቀኑ በመሸ ጊዜም ደቀመዛሙርቱ ወደ እርሱ ቀርበው ሥፍራው ምድረበዳ ነው፣ ቀኑም መሸቶአል፤ 36 በአቅራቢያው ወደሚገኙ ከተሞችና መንደሮች ሔደው ለራሳቸው አንዳች የሚበሉትን እንዲገዙ ሕዝቡን አሰናብታቸው አሉት። 37 እርሱ ግን መልሶ እናንተ የሚበሉትን ስጧቸው አላቸው። እነርሱም እንሂድና ይበሉ ዘንድ የአንድን ሰው የስድስት ወር ገቢ በሚያህል ገንዘብ እንጀራ ገዝተን እንስጣቸውን? አሉት። 38 እርሱም ምን ያህል እንጀራ እንዳላችሁ ሂዱና እዩ አላቸው። ባወቁ ጊዜም ያለው አምስት እንጀራና ሁለት ዓሳ ነው አሉት። 39 እርሱም ሁሉን በአረንጓዴው ሣር ላይ በቡድን በቡድን እንዲያስቀምጡ አዘዛቸው። 40 እነርሱም በመቶዎችና በሃምሳዎች እየሆኑ በረድፍ ተቀመጡ። 41 እርሱም አምስቱን እንጀራና ሁለቱን ዓሳ ተቀብሎ ወደ ሰማይ በመመልከት ባረከውና ቆርሶ ለሕዝቡ እንዲያቀርቡት ለደቀመዛሙርቱ ሰጣቸው። ሁለቱን ዓሳም ለሁሉም አካፈላቸው። 42 ሁሉም በልተው ጠገቡ። 43 አሥራ ሁለት ትላልቅ መሶብ ሙሉ ቁርስራሽ፣ እንዲሁም ከዓሳው ሰበሰቡ። 44 እንጀራውን የበሉት እነዚያ 5000 ወንዶች ነበሩ። 45 ወዲያውኑ እርሱ ራሱ ሕዝቡን ሲያሰናብት ሳለ ደቀመዛሙርቱ በጀልባ ገብተው ወደ ማዶ ወደ ቤተሳይዳ ቀድመውት እንዲሻገሩ ግድ አላቸው። 46 ከተለያቸው በኋላም ሊጸልይ ወደ ተራራ ፈቀቅ አለ። 47 በመሸም ጊዜ ጀልባዋ በባህር ላይ ነበረች፤ እርሱም ብቻውን በምድር ላይ ነበር። 48 ነፋሱ ከፊት ለፊታቸው እየተቃወማቸው ሳለ ለመቅዘፍ ሲጨነቁ አያቸውና ከሌሊቱ በአራተኛው ክፍል በባህሩ ላይ እየተራመደ ወደ እነርሱ መጣ፤ ሊያልፋቸውም ይፈልግ ነበር። 49 ነገር ግን በባህሩ ላይ ሲራመድ ባዩት ጊዜ ምትሃት ነው ብለው ስላሰቡ ጮኹ። 50 ሁሉም አይተውት ስለነበረ ታወኩ። እርሱ ግን ወዲያው ተናገራቸውና አይዞአችሁ! እኔ ነኝ አትፍሩ! አላቸው። 51 ወደ እነርሱ ወጥቶም ወደ ጀልባይቱ ገባ፤ ነፋሱም ተወ። 52 እነርሱም በራሳቸው ያለመጠን ተገረሙ፤ ልባቸው ደንዝዞ ነበርና ስለ እንጀራው አላስተዋሉም። 53 በተሻገሩ ጊዜም ወደ ጌንሳሬጥ አገር ወደ ባህሩ ዳርቻ መጡ። 54 ከጀልባዋ በወጡ ጊዜም ሕዝቡ ወዲያው አወቁትና 55 በዙሪያው ወዳሉ መንደሮች በሞላ በመሮጥ ህሙማንን በአልጋ ተሸክመው እርሱ እንዳለ ወደሰሙበት ወደዚያ አመጧቸው። 56 በየትኛውም እርሱ በገባባቸው መንደሮች ወይም ከተማዎች ወይም ሀገሮች ህሙማንን በገበያ ሥፍራዎች ያስቀምጧቸው፣ ቢቻላቸው ሊዳስሱት ካልሆነም የልብሱን ጫፍ ለመንካት ይለምኑት ነበር፤ የዳሰሱትም ሁሉ ይድኑ ነበር።

Mark 6:1

ማርቆስ 6፡ 1-3
ይህስ ጸራቢው የማርያም ልጅ የያቆብም የዮሳም የይሁዳም የስምዖንም ወንድም አይደለምን? እኅቶቹስ በዚህ በእኛ ዘንድ አይደሉምን? አሉ፤ "እርሱ ተራ ጸራቢ ነው! እርሱ እና የእርሱን ቤተሰቦች እናውቃቸዋለን! እናቱ ማሪያምንም እናውቃታለን! ታናናሽ ወንድሞቹን እና ያዕቆን፣ የዩሳም፣ ይሁዳ እና ስምኦን እናውቃቸዋለን! እንዲሁም ታናሽ እህቱ ከእኛ ጋር በዚህ ትኖራለች!"

Mark 6:4

ማርቆስ 6፡ 4-6
ነቢይ ከ . . . ይከበራል "ሰዎች በእርግጠኝነት ሰዎች እኔን እንዲሁም ሌሎች ነቢያትን በሌሎች ሥፍራዎች ያከብራሉ ይሁን እንጂ በገዛ ሀገራችን ግን አይደለም! ዘመዶቻችን እና በገዛ ቤታችን ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች እንኳ ሳይቀሩ እኛን አያከብሩንም!"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Mark 6:7

ማርቆስ 6፡ 7-9
ሁለት ሁለት "2 በ 2" ወይም "በጥንድ" ሁለት እጀ ጠባቢ አትልበሱ "ተጨማሪ ከነቴራ አትያዙ።"

Mark 6:10

ማርቆስ 6፡ 10-11
ለቃችሁ እስኪትሄዱ ድረስ በዚያ ቆዩ "ከተማውን ለቃችሁ እስኪትሄዱ ድረስ በዚያው ቤት ውስጥ ቆዩ።"

Mark 6:12

ማርቆስ 6፡ 12-13

Mark 6:14

ማርቆስ 6፡ 14-15
መጥመቁ ዮሐንስ ከሞት ተንስቷል "እግዚአብሔር መጥመቁ ዮሐንስን ከሞት አስነስቶታል"

Mark 6:16

ማርቆስ 6፡ 16-17
የወንድሙን የፊልጶስን ሚስት "የወንድሙን የፊልጶስን ሚስት"

Mark 6:18

ማርቆስ 6፡ 18-20
ትጠላው ነበር "ትቃወመው"

Mark 6:21

ማርቆስ 6፡ 21-22

Mark 6:23

ማርቆስ 6፡ 23-25
በሣህን "በትሪ"

Mark 6:26

ማርቆስ 6፡ 26-29
ስለማለላት እና ለእንግዶቹ ሲል "ቃል ሲገባላት እንግዶቹ ስለሰሙት፣" በሣህን "በትሪ ላይ"

Mark 6:30

ማርቆስ 6፡ 30-32

Mark 6:33

ማርቆስ 6፡ 33-34

Mark 6:35

ማርቆስ 6፡ 35-36

Mark 6:37

ማርቆስ 6፡ 37-38
ሁለት መቶ ዲናር "200 ዲናር።" ዲናር የሮማዊያን ከመዳብ የተሠራ የመገበያያ ገንዘብ ነበር። አምስት እንጀራ እና ሁለት ዓሣዎች "5 እንጀራ እና 2 ዓሣዎች።" .

Mark 6:39

ማርቆስ 6፡ 39-41
በመቶ መቶዎች እና በሃምሳ ሃምሳዎች "100 የሚቆጠሩ እና 50 የሚቆጠሩ።" አምስት እንጀራ እና ሁለት ዓሣዎች "5 እንጀራ እና 2 ዓሣዎች።" .

Mark 6:42

ማርቆስ 6፡ 42-44
ዐሥራ ሁለት ቅርጫቶች "12 ቅርጫቶች" አምት ሺህ ወንዶች አማራጭ ትርጉም: "5,000 ወንዶች እና የእነርሱ ቤተሰቦች"

Mark 6:45

ማርቆስ 6፡ 45-47
ቤተሳይዳ ይህ ከገሊላ ባሕር በስተሰሜን በኩል የሚትገኝ ከተማ ናት።

Mark 6:48

ማርቆስ 6፡ 48-50
ከሌሊቱ አራተኛው ክፍል ይህ ከንጋቱ 9 ሰዓት እስከ ፀሐይ መውጫ ያለውን ጊዜ ያመለክታል። በርቱ!...አትፍሩ እነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ጥቅም ላይ የዋሉትም “እኔን አትፍሩ!” የሚል መልዕክት ለማስተላለፍ ነው”

Mark 6:51

ማርቆስ 6፡ 51-52
ይህንን አልተረዱም ነበር "መረዳት የነበራቸው ያኽል እርሱ ምን ያኽል ኃይለኛ እንደነበር አልተገነዘቡም ነበር።"

Mark 6:53

ማርቆስ 6፡ 53-55
ቃሬዛ "ሰዎችን ለመሸከም የሚሆን አልጋ"

Mark 6:56

ማርቆስ 6፡ 53-55
ቃሬዛ "ሰዎችን ለመሸከም የሚሆን አልጋ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 7

1 ፈሪሳውያንና ከኢየሩሳሌም የመጡ አንዳንድ ጸሓፍት በአንድ ላይ ተሰብስበው ወደ ኢየሱስ መጡ። 2 ከደቀመዛሙርቱ አንዳንዶቹ በረከሰ እጅ ማለትም
ባልታጠበ እጅ እንጀራ ሲበሉ አዩ። 3 (ፈሪሳውያንና ሁሉም አይሁድ የአባቶችን ወግ ስለሚጠብቁ እጆቻቸውን ካልታጠቡ በቀር አይበሉም ነበር) 4 ከገበያ
ስፍራ ሲመጡ እጃቸውን ካልታጠቡ በቀር አይበሉም ነበር ፤እንዲሁም ዋንጫዎችን፣ ማሰሮዎችንና የናስ እቃዎችን ማጠብን የመሳሰሉ ሌሎች በርካታ ወጎችን
ይጠብቁ ነበር። 5 ፈሪሳውያንና ጸሓፍት "ደቀመዛሙርትህ በአባቶች ወግ መሰረት የማይጓዙት፣ ነገር ግን ባልታጠበ እጅ የሚበሉት ለምንድን ነው?" ብለው
ጠየቁት ። 6 እርሱም እንዲህ ሲል መለሰላቸው። ኢሳይያስ ስለ እናንተ ስለ ግብዞች በተናገረው ትንቢት፣ ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ብቻ ያከብረኛል፤ ልቡ ግን ከእኔ
በጣም የራቀ ነው፤ 7 ሰው ሠራሽ ሥርዐት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል ″ ተብሎ የተጻፈው ትክክል ነው። 8 እናንተ የእግዚአብሔርን ሕግ ትታችሁ የሰዎችን
ወግ ታጠብቃላችሁ። 9 እንዲህም አላቸው። ወጋችሁን ለመጠበቅ ስትሉ የእግዚአብሔርን ሕግ ትሽራላችሁ። 10 ሙሴ፣ «አባትህንና እናትህን አክብር፤ አባቱን
ወይም እናቱን የሚሳደብ ሞትን ይሙት» ብሏልና። 11 እናንተ ግን አንድ ሰው እናቱን ወይም አባቱን፣ «ከእኔ ልታገኙ የሚገባችሁን እርዳታ ቁርባን አድርጌዋለሁ፤
ማለትም ለእግዚአብሔር ሰጥቼዋለሁ» ቢለቸው፣ 12 ከዚህ በኋላ ለአባቱና ለእናቱ ምንም ነገር እንዲያደርግ አትፈቅዱለትም። ለሌሎች በምታስተላልፉት ወግ
የእግዚአብሔርን ቃል ትሽራላችሁ። 13 ይህን የመሳሰሉ ብዙ ነገሮችንም ታደርጋላችሁ። 14 ደግሞም ሕዝቡን ወደ እርሱ ጠርቶ እንዲህ አላቸው፣ ሁላችሁም
ስሙኝ ፤ አስተውሉም። 15 ከውጭ ወደ ውስጡ ገብቶ ሰውን የሚያረክስ ምንም ነገር የለም። 16 ነገር ግን ከውስጡ የሚወጡ ነገሮች እነርሱ ሰውን
ያረክሱታል። 17 ከሕዝቡ ተለይቶ ወደ ቤት እንደ ገባም ደቀመዛሙርቱ ስለ ምሳሌው ጠየቁት። 18 እርሱም፣ «እናንተም አልተረዳችሁምን? ከውጭ ወደ
ውስጡ ገብቶ ሰውን የሚያረክሰው ምንም ነገር እንደሌለ አታስተውሉምን?» አላቸው። 19 ምክንያቱም ፣ወደ ውስጡ (ዐፉ) የሚገባው ነገር ወደ ሆዱ እንጂ
ወደ ልቡ የሚገባ ስላልሆነ ከሰውነቱ የሚወጣ አይደለምን? ይህን በማለቱ ምግብ ሁሉ ንጹሕ መሆኑን ተናገረ። 20 20እንዲህም አለ፤ ከሰው የሚወጣ ያ
ሰውን ያረክሰዋል። 21 ከውስጥ ከሰው ልብ ክፉ ሐሳብ፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ መግደል፣ 22 ምንዝር፣ ስግብግብነት፣ ክፋት፣ ማታለል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣ ስም
ማጥፋት፣ ትእቢት፣ ስንፍና ይወጣሉ። 23 እነዚህ ክፉ ነገሮች ሁሉ ከውስጥ ይወጣሉ፡ ሰውንም ያረክሱታል። 24 ከዚያም ተነሥቶ ወደ ጢሮስና ሲዶና አካባቢ
ሄደ። ያለበትን ማንም እንዳያውቅም ወደ አንድ ቤት ገባ ፤ሆኖም ሊደበቅ አልቻለም። 25 ወዲያውኑም ስለ እርሱ የሰማችና ትንሽ ልጅዋ በእርኩስ መንፈስ
የተያዘችባት አንዲት ሴት ወደ እርሱ መጥታ በእግሩ ሥር ተደፋች። 26 ሴቲቱ ዝርያዋ ከሲሮፊኒቃዊት ወገን የሆነ ግሪካዊት ነበረች። እርስዋም ኢየሱስ በልጅዋ
ውስጥ ያለውን ጋኔን እንዲያወጣላት ለመነቸው። 27 እርሱም «በመጀመሪያ ልጆች ይጥገቡ፤ የልጆችን እንጀራ ወስዶ ለውሾች መስጠት ተገቢ አይደለምና»
አላት። 28 እርስዋ ግን «አዎን ጌታ ሆይ፤ ውሾችም እኮ ከገበታ ሥር የሚወዳድቀውን የልጆችን ፍርፋሪ ይበላሉ።» ብላ መለሰችለት። 29 ኢየሱስም ፣ እንዲህ
በማለትሽ ወደ ቤትሽ ሂጂ ጋኔኑ ከልጅሽ ወጥቷል አላት። 30 ወደ ቤትዋም ሄደች፤ልጅዋም አጋንንቱ ለቅቋት ዐልጋው ላይ ተኝታ አገኘቻት። 31 ደግሞም
ከጢሮስ አካባቢ ተነሥቶ በሲዶና በኩል አድርጎ በዐሥሩ ከተሞች ዐልፎ ወደ ገሊላ ባሕር መጣ። 32 እጁን እንዲጭንበትና እንዲፈውሰው አንድ መስማት
የተሳነውና ኮልታፋ ሰው ወደ እርሱ አመጡ። 33 እርሱም ከሕዝቡ ለይቶ ወደ ገለልተኛ ስፍራ ወሰደው፤ጣቶቹን በጆሮዎቹ ውስጥ አስገብቶ እንትፍ
አለበት፤ምላሱንም ነካው። 34 ወደ ሰማይ ቀና ብሎ ተመለከተና በረጅሙ ተንፍሶ «ኤፍታህ» አለው። ይህም ተከፈት ማለት ነው። 35 ጆሮዎቹ ተከፈቱ፤
የታሰረውም ምላሱ ተፈታ። ጥርት አድርጎም ተናገረ። 36 ኢየሱስም ይህን ለማንም እንዳይናገሩ አዘዛቸው፤ ሆኖም አጥብቆ ባዘዛቸው መጠን አብልጠው
አሰራጩት ። 37 እነርሱም ከልክ በላይ ተደንቀው ፣ ሁሉንም ነገር ደኅና አድርጓል፤እርሱ መስማት የተሣነው እንዲሰማ ኮልታፋውም እንኳ እንዲናገር ያደርጋል
አሉ።

Mark 7:1

ማርቆስ 7:1-1

Mark 7:2

ማርቆስ 7: 2-4
የናስ ዕቃዎች፣ እና የመመገቢያ ፍረሽን እንኳ ሳይቀር በዚያ ዘመን ይኖሩ የነበሩ አይሁዳዊያን ምግብ የሚመገቡት በፍራሽ ላይ ተቀምጠው ነበር። አማራጭ ትርጉሞች፡ “መያዥያዎች እንዲሁም የመመገቢያ መቀመጫዎች”

Mark 7:5

ማርቆስ 7: 5-5
ደቀ መዛሙርትህ ለምን እንደ ሽማግሌዎች ወግ አይኖሩም፣ ስለምንስ እጃቸውን ሳይታጠቡ ይበላሉ? "የአንተ ደቀ መዛሙርት የሽማግሌዎችን ወግ ይተላለፋሉ! የእኛን ሥርዓት በመጠቀም እጆቻቸውን መታጠብ አለባቸው!" ዳቦ ምግብ

Mark 7:6

ማርቆስ 7: 6-7
ስለእናንተ ግብዝነት ኢሳያስ በደንብ ትንቢትን ተናግሯል፡ እንዲህ ብሎም ጽፈዋል፡ ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ቃላት ኢሳያስ ከተናገራቸው የተወሰዱ ናቸው ISA 29:13-14።

Mark 7:8

ማርቆስ 7: 8-10
ማጥበቅ ጠንከር አድርጎ ክፋትን የሚናገሩ "የሚረግሙ"

Mark 7:11

ማርቆስ 7: 11-13
ከእኔ ታገኝ የነበረው እርዳታ ሁሉ ቁርባን ነው ለቤተ መቅዱስ ቃል የተገባ ማንኛውም ገንዝብ ወይም ሌሎች ማንኛውም ነገሮች ለሌላ ዓላማ መዋል እንደሌለባቸው የጸሐፍት ትውፍት ይናገራል። ቁርባን ጸሐፍው በዚህ ቃል አማካኝነት ማስተላለፍ የፈለገው ነገር የዚህ ቃል ንባብ ከሚሰጠው ድምጽ ጋር ተያያዥነት ስላለው በተቸለ መጠን በቋንቋችሁ ከዚህ ቃል ጋር ተቀራረቢ ድምጽ ያለውን ቃል ተጠቀሙ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Mark 7:14

ማርቆስ 7፡ **14-16**
ሁላችሁም አድምጡኝ እንዲሁም የሚናገረውን ነገር ተረዱ በዚህ ክፍል ውስጥ “ማድመጥ” እና “መረዳት” የሚሉት ሁለት ቃላት እርስ በእርሳቸው የተገናኙ ናቸው። ኢየሱስ እነዚህ ቃላት በአንድነት በንግግሩ ውስጥ የተጠቀመበት ምክንያት አድመወጮቹ እርሱ እየተናገረ ላለው ነገር ትኩረት ይሰጤ ዘንድ ነው። ከሰው የሚወጣው ያ ነው "የሰው ውስጡ ነው” ወይም “ሰው የሚያስበው ወይም የሚያደርገው ያ ነው"

Mark 7:17

ማርቆስ 7፡ **17-19**
እናንተ ደግሞ እንደዚህ የማታስተውሉ ናችሁን? አማራጭ ትርጉም: "ይህንን ሁሉ ከተናገርኩ እና ካደረኩ በኋላ በትክክል ትገነዘባላቸሁ ብዬ አስቤ ነበር።"

Mark 7:20

ማርቆስ 7፡ **20-23**

Mark 7:24

ማርቆስ 7፡ **24-26**
በፊቱ ወደቀ "ተንበረከከ" ትውልድዋም ሲሮፊኒቃዊት በሦሪያ ሀገር ውስጥ በሚትገኝ ፊኒቃ በተባለች ከተማ ውስጥ ነው የተወለደችው።

Mark 7:27

ማርቆስ 7፡ **27-28**
ልጆቹ በፊት ይጠግቡ "ልጆች መጀመሪያ መብላት ይኖርባቸዋል" ወይም "በመጀመሪያ ልጆች መመገብ ይገባቸዋል።" ልጆች አይሁዳዊያን። አማራጭ ትርጉሞች፡ "በመጀመሪያ አይሁዶችን ማገልገል ይገባኛል።" ዳቦ ምግብ ውሾች አሕዛብ። በጠረጴዛ ሥር ያሉት ውሾች እንኳ ከልጆች እጅ የወዳደቀውን ፍርፋሪ ይበላሉ። "እኔን ከአሕዛብ ወገን የሆንኩትንም በተመሳሳይ መንገድ ልታገለግለኝ ትችላለህ።" ፍርፋሪዎች የዳቦ ፍርፋሪዎች

Mark 7:29

ማርቆስ 7፡ **29-30**

Mark 7:31

ማርቆስ 7፡ **31-32**
አልፎ መጣ "በውስጡ አልፎ ሄደ" ዐሥር ከተሞች "ዐሥሩ ከተሞች፣" ከገሊላ ሀይቅ በደቡብ ምስራቅ በኩል የሚገኝ አከባቢ። ደንቆሮ "መስማት የማይችል ሰው" መናገር የማይችል፣ አንደበተ ኰልታፋ "ግልጽ በሆነ መንገድ መናገር የማይችል"

Mark 7:33

ማርቆስ 7፡ **33-35**
ኤፍታህ ጸሐፊው አይህ ቃል ሲነበብ የሚያስማውን ድምጽ አንባቢያኑ እንዲሰሙት ስለሚፈለግ በተቻለ መጠን በቋንቋቹ ፍደላት አማካኝነት ይህንን ቃል ለመጻፍ ጥረት አድርጉ። ቃተተ ደስተኛ አለመሆኑን ለማሳየት ወደ ውስጥ ሳብ አድርጎ ወደ ውጪ ተነፈሰ ምላሱን ያሠረው ነገር ተፈታ "ምላሱን ያሠረው ነገርን ኢየሱስ አስለቀቀው" ወይም "ግልጽ በሆነ መንገድ እንዳይናገር ካደረገው ነገር ኢየሱስ ፈወሰው"

Mark 7:36

ማርቆስ 7፡ **36-37**

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 8

1 በእነዚያ ቀናት እንደገና ብዙ ህዝብ በተሰበሰበና የሚበሉት ባጡ ጊዜ 2 ኢየሱስም ደቀመዛሙርቱን ወደእርሱ ጠርቶ ህዝቡ ከኔ ጋር ሶስት ቀናት ቆይተዋል
የሚበሉትም የላቸውምና እራራላቸዋለሁ 3 ሳይበሉ ብሰዳቸውም በመንገድ ላይ ይደክማሉ አንዳንዶቹም ከሩቅ ሥፍራ ነው የመጡት አላቸው። 4
ደቀመዛሙርቱም በዚህ ምድረበዳ እነዚህን ሁሉ የሚያጠግብ እንጀራ እንዴት ይገኛል ብለው መለሱለት። 5 ስንት እንጀራ አላችሁ ብሎ ጠየቃቸው። ሰባት አሉት ፤
6 ህዝቡን በምድር ላይ እንዲቀመጡ አዘዘ ሰባቱንም እንጀራ ተቀብሎ እግዚአብሔርን ካመሰገነ በኋላ ቆርሶ እንዲያቀርቡላቸው ለደቀመዛሙርቱ ሰጣቸው
እነርሱም ለህዝቡ አቀረቡላቸው።፤ 7 ጥቂትም ትናንሽ አሦች ነበሯቸው ባርኮም ያንንም አንዲያቀርቡላቸው አዘዘ። 8 ሕዝቡም በልተውም ጠገቡ፡
ደቀመዛሙርቱም የተረፈውን ቁርስራሽ ሰባት ታላላቅ መሶብ አነሱ። 9 የህዝቡም ቁጥር ቁጥራቸውም አራት ሺ ያህል ነበር። ከዚያም ኢየሱስ ህዝቡን
አሰናበታቸው ። 10 ወዲያውም ከደቀመዛሙርቱ ጋር ወደ ጀልባ ገብተው ወደ ዳልማኑታ አውራጃ አካባቢ ሄዱ። 11 ፈሪሳውያንም ወደ ኢየሱስ እርሱ መጥተው
ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነ ምልክትን እንዲያሳያቸው በመፈለግ ሊፈትኑት ይጠይቁት ጀምር። 12 ኢየሱስም እርሱም በመንፈሱ እጅግ ተበሳጭቶ በዚህ ዘመን
ያለ ህዝብ ለምን ምልክት ይፈልጋል እዉነት እላችኋለሁ እናንተ ሰዎች አይሰጣችሁም አላቸው። 13 ትቶአቸው እንደገና ወደ ጀልባ ገብቶ ወደ ባህሩ ማዶ
ተሻገረ። 14 ደቀመዛሙርቱም እንጀራ መያዝን ረሱ። 15 በጀልባ ውስጥም ከአንድ እንጀራ በቀር ምንም አልያዙም ነበር። 16 ኢየሱስ ከፈሪሳዊያንና ከንጉሥ
ሄሮድስ እርሾ ተጠንቀቁ ብሎ አሳሰባቸው። እንጀራ ስላልያዝን ነው ብለው እርስ በእርሳቸው ተነጋገሩ ። 17 ኢየሱስም ይህን አውቆ እንጀራ ስለሌላችሁ ለምን
ትነጋገራላችሁ። እስከአሁን አልገባችሁምን ወይም እስከአሁን አታስተውሉምን ልባችሁ ደንዝዞአልን 18 አይን እያላችሁ አታዩምን ጆሮ እያላችሁ አትሰሙምን
አታስታውሱምን 19 አምስቱን እንጀራ ለአምስት ሺ ባካፈልኩ ጊዜ ስንት መሶብ ቁርስራሽ ሰበሰባችሁ ብሎ ጠየቃቸው እነርሱም አሥራ ሁለት ብለው መለሱለት።
20 ሰባቱን ለአራት ሺ ባካፈልኩ ጊዜስ ስንት ቅርጫት ቁርስራሽ አነሳችሁ አላቸው ሰባት አሉት ። 21 ገና አታስተውሉምን አላቸው። 22 ወደ ቤተ ሳይዳም
መጡ። የአካባቢው ሰዎችም አይነ ስውር የሆነን ሰው ወደ እርሱ አምጥተው እንዲዳስሰው ለመኑት። 23 የአይነስውሩንም ሰው እጅ ይዞ ከመንደሩ ውጭ
ወሰደው። በአይኖቹም ላይ እንትፍ ብሎና እጁን ጭኖ አሁን ይታይሀልን ብሎ ጠየቀው። 24 ቀና ብሎ ተመለከተና ሰዎች ሲራመዱ እንደዛፍ ሆነው ይታየኛል
አለው። 25 እንደገናም እጁን በአይኑ ላይ በጫነበት ጊዜ በሚገባ ተመለከተ የአይኑም ብርሀን ተመለሰለት ሁሉንም ነገር አጥርቶ አየ። 26 ኢየሱስም ወደ
መንደሩ እንኳ እንዳትገባ ብሎ ወደ ቤቱ አሰናበተው። 27 ኢየሱስም ከደቀመዛሙርቱ ጋር ወደ ፊሊጶስዩ ቂሳሪያ ዙሪያ ወዳሉ መንደርሮች ሄዱ፡ በመንገድም ላይ
ሳሉ ሰዎች እኔን ማነው ይላሉ ብሎ ጠየቃቸው 28 እነርሱም መጥምቁ ዮሐንስ ሌሎች ደግሞ ኤልያስ አንዳንች ግን ከነቢያት አንዱ ብለው መለሱለት። 29
እንደገናም እናንተስ እኔ ማን እንደሆንኩ ትላለችሁ ብሎ ጠየቃቸው። ጴጥሮስም አንተ መሲሁ ነህ በማለት መለሰለት። 30 ስለእርሱ ለማንም እንዳይናገሩ
አስጠነቀቃቸው። 31 የሰው ልጅ ብዙ መከራ እንደሚቀበል በሽማግሌዎች፣ በካህናት አለቆችና በጻፎች እንደሚነቀፍና እንደሚገደል በሦስተኛውም ቀን እንደገና
እንደሚነሳ እንዳለው ያስተምራቸው ጀመር። 32 ይህንንም በግልጽ ተናገረ። ጴጥሮስም ወስዶ ሊገስጸው ጀመረ። 33 ኢየሱስም ዞር ብሎ ደቀመዛሙርቱን አየና
ወደ ኋላዬ ሂድ አንተ ሰይጣን የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን ነገር አታስብምና ብሎ ጴጥሮስን ገሰጸው። 34 ህዝቡንና ደቀመዛሙርቱንም ወደ እርሱ ጠርቶ
ሊከተለኝ የሚወድ ማንም ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ። 35 ህይወቱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠጣፋታልና ነፍሱን ግን ስለኔ ወይም
ስለወንጌል የሚያጣ ያገኛታልና። 36 ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ግን ቢያጣ ምን ይጠቅመዋል። 37 ወይስ ሰው ስለነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል። 38 በዚህ
አመንዝራ ኃጢአተኛ ህዝብ ፊት በእኔና በቃሌ የሚያፍርብኝ ማንም ቢኖር የሰው ልጅም ከቅዱሳን መላዕክቱ ጋር በአባቱ ክብር በሚመጣበት ጊዜ ያፍርበታል።

Mark 8:1

ማርቆስ 8፡ 1-4
ሦስት ቀናት "3 ቀናት" ራሳቸውን ሊስቱ ይችላሉ አማራጭ ትርጉሞች፡ 1) "ለአጭር ጊዜ ራሳቸውን ሊስቱ ይችላሉ" ወይም 2) "ደካማ ሊሆኑ ይችላሉ" እነዚህን ሁሉ ሰዎች መመገብ የሚችል በቂ ምግብ ከዬት ማግኘት ይቻላል? ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ ይህንን ሁሉ ሰው መመገብ የሚያችል ምግብ እንዲፈልጉ መጠየቁ በጣም አስገርሟቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡ "ያሉበት ቦት በቂ ለዚህ ሁሉ ሕዝብ የሚሆን ምግብ የማይቻልበት ሥፍራ አይደለም!"

Mark 8:5

ማርቆስ 8፡ 5-6
ተቀመጡ ሰዎች ምግብ ለመመገብ ጠረጴዛ በማይኖርበት ሥፍራ ላይ ሰዎች ምግብ የሚመገቡበትን መንገድ የሚትገልጽበትን መንገድ የሚገልጽ ቃልን ተጠቀም።

Mark 8:7

ማርቆስ 8፡ 7-10
ዳልማኑታ ከገሊላ ባሕር በሰሜን ምዕራብ በኩሉ የሚገኝ አከባቢ ነው።

Mark 8:11

ማርቆስ 8፡ 11-13
ፈለጉት "ለማግኘት ጥረት አደረጉ" በጥብቅ ይህንን በ MRK 7:34 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። ይህ ትውልድ ለምን ምልክትን ይሻል በዚህ ሥፍራ ኢየሱስ ኢየገሰጻቸው ነው። አማራጭ ትርጉም፡ “ይህ ትውልድ ምልክትን መሻት አልነበረበተም።” ይህ ትውልድ ይህንን ያደርጋል "ሁላችሁም ይህንን ታደርጋላችሁ"

Mark 8:14

ማርቆስ 8፡ 14-15
ተጠንቀቁ እንዲሁ ራሳችሁን ጠብቁ በዚህ ሥፍራ ጥቅም ላይ የዋሉት እነዚህ ሁለት ቃላት የጋራ ፍች ሲኖራው ሁለቱም ጥቅም ላይ የዋሉበት ምክንያት አጽኖት ለመስጠት ነው። ከፈርሳዊያን እና ከሄሮዶስ ወገን እርሾ አማራጭ ትርጉም፡ "ከፈርሳዊያን የሐሰት ትምህርት እና ከሄሮዶስ ወገን የሐሰት ትምህርት"

Mark 8:16

ማርቆስ 8፡ 16-17
እንጀራ ስለሌለ ስለምን በመካከላችሁ ትከራከራላችሁ? ኢየሱስ እርሱ እየነገራቸው እና እያደረገ ያለውን ነገር መረዳት ባለመቻላቸው ተስፋ ቆረጠ። አማራጭ ትርጉም፡ "እኔ እየተናገርኩ ያለሁት ስለ ግዑዝ እንጀራ ነው ብላችሁ ማሰብ የለባችሁም።"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Mark 8:18

ማርቆስ **8**: **18**-**19**
ዓይን ሳላችሁ አታዩምን? ጆሮስ ሳላችሁ አትሰሙምን? ትዝስ አይላችሁምን? ኢየሱስ ምንም ልገነዘቡ ባለመቻላቸው ተስፋ ቆርጦዋል። አማራጭ ትርጉም: “የሚያይ ዐይን አላችሁ ይሁን እንጂ የሚትመለከቱትን ነገር አትረዱም! የሚሰማ ጆሮ አላችሁ ይሁን እንጂ የሚትሰሙትን ነገር አትረዱም! እነዚህ ሁሉ ልታስታውሱ ይገባ ነበር!"

Mark 8:20

ማርቆስ **8**: **20**-**21**
ትስዝ አይላችሁምን? አማራጭ ትርጉም: "ስለቁሳዊ እንጀራ እያወራሁ እንዳልሆነ በዚህ ጊዜ መገንዘብ ነበረባችሁ።"

Mark 8:22

ማርቆስ **8**: **22**-**23**
ቤተ ሳይዳ ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምስራቅ የሚትገኝ ከተማ

Mark 8:24

ማርቆስ **8**: **24**-**26**

Mark 8:27

ማርቆስ **8**: **27**-**28**

Mark 8:29

ማርቆስ **8**: **29**-**30**

Mark 8:31

ማርቆስ **8**: **31**-**32**
የሰው ልጅ ብዙ መከራ ሊቀበል፥ ከሽማግሌዎችም ከካህናት አለቆችም ከጻፎችም ሊጣል፥ ሊገደልም ወደ ሕይወት ሊነሣ እንዲገባው አማራጭ ትርጉም: "ሽማግሌች እና የካህናት አለቆች እንዲሁም ጻፎችም የሰው ልጅነን አይቀበሉመም እንዲሁም ይገድሉታል። ይሁን እነንጂ እግዚአብሔር ወደ ሕይወት መልሶ ያመጣዋል።" ሦስት ቀናት "3 ቀናት"

Mark 8:33

ማርቆስ **8**: **33**-**34**

Mark 8:35

ማርቆስ **8**: **35**-**37**
ስለዚህ ኢየሱስ የመሞታቸው ምክንያት ወንጀለኞች ስለሆኑ እንዳልሆነ እና በምንም ምክንያት እንደሆነ ለደቀ መዛሙርቱ ይህንን እንዲያስታውሱ ይነግራቸዋ።(MRK 8:34).

Mark 8:38

ማርቆስ **8**: **38**-**38**
የሰው ልጅ ... በአባቱ ክብር ከቅዱሳን መላእክት ጋር በመጣ ጊዜ የሰው ልጅ እንዲሁም የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ አባቱ ባለው ክብር እርሱም ተመልሶ ይመጣል። የሰው ልጅ ይህ የኢየሱስ ወሳኝ የሆነ የማዕረግ ስም ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 9

1 ኢየሱስም እውነት እላችኋለሁ፣ በዚህ ከቆሙት አንዳንዶቹ የእግዚአብሔር መንግሥት በኃይል መምጣቷን ሳያዩ የማይሞቱ አሉ አላቸው። 2 ከስድስት ቀን
በኋላም ኢየሱስ ጴጥሮስን፣ ያዕቆብንና ዮሐንስን ለብቻቸው ይዞ ወደ ረጅም ተራራ ላይ አመጣቸው። 3 በፊታቸውም ተለወጠባቸው፤ ልብሱም አጣቢ በምድር
ላይ ሊያነጻው እስከማይችል ድረስ ተብለጭልጮ ነጭ ሆነ። 4 ሙሴና ኤልያስ ታዩአቸው፤ ከኢየሱስ ጋርም ይነጋገሩ ነበር። 5 ጴጥሮስም መልሶ ኢየሱስን ረቡኒ!
በዚህ መሆን ለእኛ መልካም ነው፤ አንድ ለአንተ፣ አንድ ለሙሴና አንድ ለኤልያስ ሦስት ዳሶችን እንሥራ አለው። 6 እጅግ ፈርተው ስለነበረ የሚመልሰውን
አያውቅም ነበር። 7 ከዚያም ደመና መጥቶ ጋረዳቸው፤ ከደመናውም ውስጥ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፣ እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ
መጣ። 8 ድንገት ዙሪያቸውን ሲመለከቱ ከኢየሱስ በቀር ከእነርሱ ጋር ሌላ ማንንም አላዩም። 9 ከተራራው ሲወርዱ ሳሉም ይህንን ያዩትን ነገር ሁሉ የሰው ልጅ
ከሙታን እስኪነሳ ድረስ ለማንም እንዳይናገሩ አዘዛቸው። 10 እነርሱም ቃሉን ይዘው ከሙታን መነሳት ማለት ምን ማለት ነው ተባባሉ። 11 እነርሱም ጸሐፍት
አስቀድሞ ኤልያስ መምጣት አለበት የሚሉት ለምንድነው ብለው ጠየቁት። 12 ኢየሱስም ኤልያስማ በርግጥ አስቀድሞ ይመጣል፤ ሁሉንም ነገር
ያስተካክላል። ስለ ሰው ልጅ ብዙ መከራ እንዲቀበልና እንዲጣል የተጻፈው ታዲያ እንዴት ይሆናል? 13 እኔ ግን እላችኋለሁ! ኤልያስ መጥቷል፤ ስለ እርሱም
እንደተጻፈው የወደዱትን አደረጉበት። 14 ወደ ደቀመዛሙርቱ በመጡ ጊዜ ብዙ ሕዝብ ከበዋቸው ጸሓፍትም ሲጠይቋቸው ተመለከቱ። 15 ወዲያው ሕዝቡ ሁሉ
ኢየሱስን ባዩት ጊዜ እጅግ ተገርመው ወደ እርሱ በመሮጥ ሰላምታ ሰጡት። 16 እርሱም ስለምንድነው የምትጠይቋቸው? ብሎ ጠየቃቸው። 17 ከሕዝቡም
መሐል አንዱ መምህር ሆይ! ዲዳ መንፈስ ያደረበትን ልጄን ወዳንተ አመጣሁት። 18 በሚወስደው ቦታ ሁሉ ይጥለውና አረፋ ያስደፍቀዋል፣ ጥርሱን
ያንቀጫቅጭና ያደርቀዋል። እንዲያወጡት ደቀመዛሙርትህን ጠየቅኳቸው፣ እነርሱም አልቻሉም። 19 ኢየሱስም መልሶ እናንተ የማታምኑ ትውልዶች እስከ መቼ
ከእናንተ ጋር እኖራለሁ? እስከ መቼስ እታገሳችኋለሁ? ወደ እኔ አምጡት አላቸው። 20 ወደ እርሱም አመጡለት፤ ባየውም ጊዜ ወዲያው መንፈሱ በምድር ላይ
በኃይል ጥሎ እያንፈራገጠ አረፋ አስደፈቀው። 21 ኢየሱስም የልጁን አባት ይህ ከያዘው ምን ያህል ጊዜ ሆነው? ሲል ጠየቀው። እርሱም ከሕጻንነቱ ጀምሮ
ነው። 22 ብዙ ጊዜ ሊያጠፋው በውሃና በእሳት ላይ ይጥለዋል፤ የሚቻልህ ከሆነ እዘንልንና እርዳን አለው። 23 ኢየሱስም የሚቻልህ ከሆነ አልክን ለሚያምን
ሁሉም ነገር ይቻላል አለው። 24 ወዲያው የልጁ አባት ጮኸና አምናለሁ፣ እንዳምንም እርዳኝ አለው። 25 ኢየሱስ ሕዝቡ እየሮጠ ሲመጣ ተመልክቶ እርኩሱን
መንፈስ አንተ ዲዳ ደንቆሮም መንፈስ ከእርሱ እንድትወጣ ተመልሰህም እንዳትገባበት አዝሃለሁ ብሎ ገሰጸው። 26 መንፈሱም ካንፈራገጠው በኋላ ጮኾ
ወጣ። ብዙዎች ሞተ እስኪሉ ድረስም እንደ ሞተ ሰው ሆነ። 27 ኢየሱስ ግን እጁን ይዞ አስነሳው፤ እርሱም ተነሣ። 28 ወደ ቤት በገቡ ጊዜም ደቀመዛሙርቱ
እኛ ልናስወጣው ያልቻልነው ለምንድነው? ብለው ለብቻው ጠየቁት። 29 ኢየሱስም እንዲህ ዓይነቱ ወገን በጸሎት ካልሆነ በስተቀር አይወጣም አላቸው። 30
ከዚያም ወጥተው በገሊላ በኩል አለፉ፤ በዚያ መሆኑን ማንም እንዲያውቅ አይፈልግም ነበር። 31 ደቀመዛሙርቱንም እንዲህ ሲል አስተማራቸው፤ የሰው ልጅ
በሰዎች እጅ ታልፎ ይሰጣል፣ ይገድሉታልም፣ ከተገደለ ከሶስት ቀን በኋላም ይነሣል አላቸው። 32 ነገር ግን የተናገራቸውን አላስተዋሉም፤ እንዳይጠይቁትም
ፈርተው ነበር። 33 ወደ ቅፍርናሆም መጡ፤ በቤት ሳሉም መንገድ ላይ ስለምን ጉዳይ ነበር የምትነጋገሩት ብሎ ደቀመዛሙርቱን ጠየቃቸው። 34 ከእነርሱ ማን
ይበልጥ እንደሆነ ተከራክረው ነበርና ዝም አሉ። 35 ተቀምጦም አሥራ ሁለቱን ጠራቸው፣ እንዲህም አላቸው፣ ከእናንተ የመጀመሪያ ሊሆን የሚወድ የሁሉ
መጨረሻና አገልጋይ ይሁን፤ 36 ትንሽ ልጅ በመካከላቸው አቁሞና አቅፎት እንዲህ አላቸው፤ 37 ማንም እንደዚህ ካሉት ታናናሽ ልጆች አንዱን በስሜ የሚቀበል
እኔን ይቀበላል፣ እኔንም የሚቀበል የሚቀበለው የላከኝን ነው እንጂ እኔን አይደለም። 38 ዮሐንስም መምህር ሆይ! አንድ ሰው በስምህ አጋንንትን ሲያስወጣ
አየነው፤ ስለማይከተለንም ከለከልነው አለው። 39 ኢየሱስ ግን በስሜ ተአምራትን አድርጎ ፈጥኖ በእኔ ላይ ክፉ ሊናገር የሚችል የለምና አትከልክሉት፤ 40
የማይቃወመን ሁሉ ከእኛ ጋር ነው አለው። 41 እውነት እላችኋለሁ የክርስቶስ በመሆናችሁ ምክንያት አንድ ብርጭቆ ውሃ እንድትጠጡ የሚሰጣችሁ ዋጋውን
አያጣም። 42 በእኔ ከሚያምኑ ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን ከእምነቱ የሚያስት ሰው ትልቅ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ላይ ታሥሮ በጥልቅ ባህር ላይ ቢጣል
ይሻለው ነበር። 43 እጅህ ለመሰናከልህ ምክንያት የምትሆን ከሆነ ቆርጠህ ጣላት፤ ሁለት እጅ ኖሮህ እሳቱ ወደማይጠፋበት ወደ ሲዖል ከምትሔድ አካልህ
ጎሎ ወደ ሕይወት ብትገባ ይሻልሃልና። 4445 እግርህ ለመሰናከልህ ምክንያት የሚሆን ከሆነ ቆርጠህ ጣለው፤ ሁለት እግር ኖሮህ ወደ ሲዖል ወደ እሳቱ
ከምትጣል አንድ እግር ኖሮህ ወደ ሕይወት ብትገባ ይሻልሃል። 4647 ዐይንህ ለመሰናከልህ ምክንያት የምትሆን ከሆነ አውጥተህ ጣላት፤ 48 ሁለት ዐይን
ኖሮህ ትሉ ወደማይሞትበት፣ እሳቱ ወደማይጠፋበት ከምትገባ አንድ ዐይና ሆነህ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ብትገባ ይሻልሃል። 49 እያንዳንዱ ሰው በእሳት
ይቀመማል። 50 ጨው መልካም ነው፤ የጨውነት ጣዕሙን ቢያጣ ግን ምን ታደርጉታላችሁ? በእያንዳንዳችሁ ሕይወት የጨውነት ጣዕም ይኑርባችሁ! እርስ
በርሳችሁም በሰላም ኑሩ።

Mark 9:1

ማርቆስ 9፡ 1-3
ተለወጠ "ወደ ሌላ ቅርጽ ተለወጠ" ወይም "የበለጠ የተለመ ሆኖ ታያቸው" (UDB) እንደ ብርሃን አንጸባራቂ "በጣም ነጭ" አጣቢም በምድር ላይ እንደዚያ ሊያነጣው "ማንጽያ" የሚባለው ከልብስ ላይ ቆሻሻን ለማንጻት እና ነጭ ለማድረግ የሚያገለግል ኬሚካል ነው። “የሚያነጻ” ቆሻሻን የሚያነጻ ሰው።

Mark 9:4

ማርቆስ 9፡ 4-6
ፈሩ "በጣም ፈሩ"

Mark 9:7

ማርቆስ 9፡ 7-8
ማርቆስ 9፡ 7-8

ይህ የሚወደው ልጄ ነው። እርሱን ስሙት። እግዚአብሔር “ስለሚወደው ልጁ”፣ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነው ስለ ልጁ ያለውን ፍቅር የገለጸበት መንገድ ነው። የሚወደው ልጄ ይህ የእግዚአብሔር ልጅ የሚለው የኢየሱስ ወሳኝ የሆነ የማዕረግ ስም ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Mark 9:9

ማርቆስ 9: 9-10
ስለዚህም ይህንን ነገር በልባቸው ይጠበቅት ነበር "ይህ ነገር ሲሆን ላልተመለከተ ለማንም ሰው ሳይናገሩ፣ ስለዚህ ነገር ከማንም ጋር አይነጋገሩም ነበር።" ከሞት መነሳት "ከሞተ በኋላ ተመልሶ እንደገና በሕይወት መኖር"

Mark 9:11

ማርቆስ 9: 11-13
ኤልያስማ ይህንን በእርግጥ አድርጓል . . . ሰዎችም ጠልተውታል? ኤልያስ ከሰማይ እንደሚመጣ፣ ከዚያም መስሑ የሆነው የሰው ልጅ መጥቶ ይነግሣል እንዲሁም ይገዛል ተብሎ አስቀድሞ ትንቢት ተነግሯል። ሌሎች ትንቢታዊ መልዕክቶችም የሰው ልጅ መከራን እንዲቀበል እና በሰዎች እንዲጠላ የትንቢት መልዕክት ተናግረዋል። ደቀ መዛሙርቱ እነዚህ ሁለት ትንቢታዊ መልዕክቶች እንዴት አንድ ሊሆኑ እንደሚችሉ አልገባቸው ስለዚህም ግራ ገብቷቸዋል። ኤልያስ ይመጣል በትንቢት መልዕክቶች ብዙ ጊዜ ሁለትዮሽ ፍጻሜ አላቸው።

Mark 9:14

ማርቆስ 9: 14-16
ስከራከሩ "ስወያዩ" ወይም "ስጨቃጨቁ" ወይም "ስጠያየቁ"

Mark 9:17

ማርቆስ 9: 17-19
ከእርሱ ውስጥ ለማውጣት "ከልጁ ውስጥ ለማስወጣት" ወይም "እርኩስ መንፈሱን ለመማባረር" እታገሳችኋለሁ "እችላችኋለሁ" ወይም "አልፋችኋለሁ"

Mark 9:20

ማርቆስ 9: 20-22
አዘነላቸው "አሳዘኑት" ወይም "ራራላቸው"

Mark 9:23

ማርቆስ 9: 23-25
ኢየሱስም እንዲህ አለው፣ “ቢቻልህስ”? ለሚያምን ሁሉ ይቻለዋል”። ኢየሱስ የሰውዬውን ጥርጣሬ ገሰጸው። አማራጭ ትርጉም: “ኢየሱስ ሰውዬውን እንዲህ አለው፣ “ስለምን ከቻልክ ትላለህ”? ለምያምንስ ሁሉ ይቻለዋል።” ወይም "ኢየሱስ ሰውዬውን እንዲህ አለው፣ “ከቻልክስ” ማለት የለብህም!” ለምያምንስ ሁሉ ይቻለዋል።”

Mark 9:26

ማርቆስ 9: 26-27
ልጁ የሞተ ይመስል ነበር "ልጁ የሞተ ይመስል ነበር" ወይም "ልጁ የሞተ ሰው ይመስል ነበር"

Mark 9:28

ማርቆስ 9: 28-29
እንዲህ ዓይነቱን በጸሎት ካልሆነ ማስወጣት አይቻልም ቃ“አይቻልም” እና “ካልሆነ በስተቀር” የሚሉት ቃላት ሁለቱም አሉታዊ ቃላት ናቸው። በአንዳንድ ቋንቋዎች ውስጥ አዎንታዊ ቃላትን መጠቀሙ አግባብ ነው። አማራጭ ትርጉም: “እንዲህ ዓይነቱን ማስወጣት የሚቻው በጸሎት ብቻ ነው።”

Mark 9:30

ማርቆስ 9: 30-32
በዚያ አልፎ ሄደ "በዚያ አለፈ" ወይም "በዚያ አለፈ" ሦስት ቀናት "3 ቀናት"

Mark 9:33

ማርቆስ 9: 33-35

Mark 9:36

ማርቆስ 9: 36-37

Mark 9:38

ማርቆስ 9: 38-39
እርኩስ መናፈስትን ማስወጣት "ዳቢሎስን ማስወጣት"

Mark 9:40

ማርቆስ 9: 40-41
እንዳይጠፋ "እንዳይጠፋ" የሚለው ቃል አሉታዊ ነው። በአንዳንድ ቋንቋዎች ውስጥ አዎናታዊ ዓረፍተ ነገሮችን መጠቀም የተለመደ ነው። አማራጭ ትርጉም: "ይቀበላል" (ተመልከት:

Mark 9:42

ማርቆስ 9: 42-44
የወፍጮ ድንጋይ እህል ለመፍጨት የሚያገለግል ትልቅ ድንጋይ የማይጠፋ እሳት "የማጥፋ እሳት"

Mark 9:45

ማርቆስ 9: 45-46
እንዲሁም ወደ ሲኦል ይወረወራል "እንዲሁም እግዚአብሔር ወደ ሲኦል ይወረውረዋል"

Mark 9:47

ማርቆስ 9: 47-48
ትላቸው "የሞተውን አካላቸውን የሚበላ ትል"

Mark 9:49

ማርቆስ 9: 49-50

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **10**

1 ኢየሱስም ከዚያ ተነስቶ ከዮርዳኖስ ወንዝ ማዶ ወደ ይሁዳ አውራጃዎች መጣ። ብዙ ህዝብም በአንድ ላይ ሆነው እንደገና ወደ እርሱ መጡ። እንደልማዱም ያስተምራቸው ጀመር። **2** ፊሪሳውያንም ወደ ኢየሱስ መጥተው ሊፈትኑት አንድ ሰው ሚስቱን መፍታት ተፈቅዶለታል ሲሉ ጠየቁት። **3** እርሱም መልሶ ሙሴ ምን ብሎ አዘዛችሁ አላቸው። **4** እነርሱም የፍቺውን ጽፈት ሰጥቶ ይፍታት ብሎ ደንግጓል አሉት። **5** ኢየሱስ ግን ሙሴ ስለልባችሁ ድንዛዜ ይህን ትዕዛዝ ሰጣችሁ እንጂ **6** ከፍጥረት መጀመሪያ ግን እግዚአብሔር ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። **7** በዚህም ምክንያት ሰው እናቱንና አባቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይጣበቃል **8** ሁለቱም አንድ ስጋ ይሆናሉ ስለዚህም አንድ ሥጋ እንጂ ከእንግዲህ ሁለት አይደሉም **9** እንግዲህ እግዚአብሔር ያጣመረውን ሰው አይለየው አላቸው። **10** በቤትም ሳሉ ደቀመዛሙርቱ ስለጉዳዩ እንደገና ጠየቁት። **11** ኢየሱስም ማንም ሚስቱን ፈቶ ሌላይቱን ቢያገባ በሚስቱ ላይ ያመነዝራል። **12** እንዲሁም እርሷም ራሷ ባሉዋን ትታ ሌላ ሰው ካገባች ታመነዝራለች አላቸው ። **13** ህዝቡም እንዲዳስሳቸው ህጻናትን ወደ ኢየሱስ ያመጡ ነበር። ደቀመዛሙርትም ገሰጹዋቸው። **14** ኢየሱስ ግን ባየ ጊዜ በቁጣ ተሞልቶ ህጻናትን ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተው አትከልክሏቸው። የእግዚአብሔር መንግሥት እንደነዚህ ላሉት ናትና አላቸው። **15** እውነት እላችኋለሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደ ህጻን ሆኖ የማይቀበላት ሊገባባት አይችልም። **16** ህጻናቱንም አቅፎ እጁን ጭኖ ባረካቸው። **17** በመንገድም ሳሉ አንድ ሰው ወደእርሱ ሮጠና በፊቱ ተንበርክኮ ቸር መመህር ሆይ የዘላለምን ህይወት እንድወርስ ምን ማድረግ ይገባኛል? ብሎ ጠየቀው ። **18** ኢየሱስም ለምን ቸር ትለኛለህ ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር የለም አለው። **19** ትዕዛዛትን ታውቃለህ አትግደል አትስረቅ አታመንዝር በሀሰት አትመስክር አታታልል አባትህንና እናትህን አክብር አለው። **20** እርሱም መምህር ሆይ እነኚህን ሁሉ ከልጅነቴ ጀምሮ ጠብቄአለሁ አለው። **21** ኢየሱስም አይቶ ወደደውና አንዲት ነገር ቀርታሀለች ሂድ ያለህን ሁሉ ሸጥና ለድሆች ስጥ መዝገብም በሰማይ ይቆይሀል መጥተህም ተከተለኝ አለው። **22** እርሱም ብዙ ሀብት ነበረውና በሰማው ነገር ፊቱ ተቁሮ እያዘነ ሄደ። **23** ኢየሱስም ዙሪያውን ተመለከተና ደቀመዛሙርቱን ለሀብታሞች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት እንዴት ጭንቅ ነው አላቸው። **24** ደቀመዛሙርቱም በንግግሩ እጅግ ተገረሙ። ኢየሱስ እርሱ ግን መልሶ ልጆች ሆይ በሀብታቸው ለሚታመኑ ወደ እግዚአብሔር መንግስት መግባት እንዴት ከባድ ነው አላቸው። **25** ሀብታም ሰው ወደ መንግስተ ሰማያት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢሾልክ ይቀላል አላቸው። **26** ደቀመዛሙርቱም እጅግ ተገርመው እንግዲያውስ ማን ሊድን ይችላል አሉት። **27** ኢየሱስም ወደ እነርሱ ተመከተና ለሰዎች ይህ አይቻልም ነገር ግን ለእግዚአብሔር ይቻላል ለእግዚአብሔር ሁሉ ይቻላልና አላቸው። **28** ጴጥሮስም ጌታ ሆይ እኛ ሁሉን ትተን ተከልንህ ይለው ጀመር። **29** ኢየሱስም እውነት እላችኋለሁ ስለኔና ስለ ወንጌል ቤቱን ወንዳሞቹን ወይም እህቶቹንወይም እናቱን ወይም አባቱን ወይም ልጆቹን ወይም መሬቱን የሚተው **30** በዚህ ዓለም መቶ እጥፍ ቤቶችን ወንድሞችን እህቶችን እናቶችን ልጆችንና መሬት ከስደት ጋር በሚመጣውም አለም የዘላለምን ህይወት የማይቀበል የለም **31** ነገር ግን ብዙዎች ፊተኞች ኋለኞች ኋለኞችም ፊተኞች ይሆናሉ አላቸው። **32** ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ ሳለ ኢየሱስ ከፊት ከፊታቸው ይሄድ ነበር። እጅግም ተገርመው ነበር የሚከተሉትም በጣም ፈርተው ነበር። አስራሁለቱን እንደገና ወስዶ ሊደርስበት ያለውን ነገር ይነግራቸው ጀመር። **33** እነሆ ወደ ኢየሩሳሌም እንሄዳለን የሰው ልጅም ለካህናት አለቆችና ለጻፎች አልፎ ይሰጣል እነርሱም ሞትን ይፈርዱበታል ለአህዛብም አሳልፈው ይሰጡታል። **34** አህዛብም/ፈሪሳዊያን ይቀልዱበታል ይተፉበታል ይገርፉታል ይገድሉታልም ከሶስት ቀን በኋላም ይነሳል እያለ ይነግራቸው ጀመር። **35** የዘብድዮስ ልጆች ያዕቆብና ዮሀንስ ወደ ኢየሱስ ቀርበው መምህር ሆይ የምንጠይቅህን ሁሉ እንድታደርግልን እንለምንሀለን አሉት። **36** እርሱም ምን እንዳደርግላችሁ ትፈልጋለችሁ አላቸው። **37** እነርሱም በክብርህ በምትሆንበት ጊዜ አንዳችን በቀኝህ አንዳችን በግራህ እንድንቀመጥ ፍቀድ አሉት። **38** ኢየሱስ ግን የምትለምኑትን አታውቁም እኔ የምጠጣውን ጽዋ ልትጠጡ እኔ የምጠመቀውን ጥምቀት ልትጠመቁ ትችላላችሁን አላቸው፤ **39** እነርሱም እንችላለን አሉት። ኢየሱስም እኔ የምጠጣውን ጽዋ ትጠጣላችሁ እኔ የምጠመቀውን ጥምቀት ትጠመቃላችሁ **40** ነገር ግን በግራዬና በቀኜ መሆን ለተዘጋጀላቸው ነው እንጂ እኔ የምሰጠው አይደለም አላቸው። **41** አሥሩ ደቀማዘሙርትም ይህን በሰሙ ጊዜ በያዕቆብና በዮሀንስ ላይ ተቆጡ። **42** ኢየሱስም ወደ እርሱ ጠርቶ የአህዛብ አለቆች በሚመሩዋቸው ላይ እንደሚሠለጥኑባቸው ታላላቆቻቸውም እንደሚገዙዋቸው ታውቃላችሁ። **43** በእናንተ ዘንድ ግን እንዲህ አይደለም ነገር ግን ከእናንተ ማንም የበላይ(ታላቅ) ለመሆን የሚፈልግ የሁሉ አገልጋይ ይሁን **44** ፊተኛ ለመሆን የሚፈልግም የሁሉ ባሪያ ይሁን **45** የሰው ልጅም ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊያደርግ እንጂ እንዲያገልግሉት አልመጣም አላቸው። **46** ኢየሱስና ደቀመዛሙርቱም ወደ ኢያሪኮ መጡ። ከደቀመዛሙርቱና ከብዙ ህዝብ ጋር ከኢያሪኮ በመውጣት ላይ ሳለ የጤሚዮስ ልጅ ዓይነ ስወሩ ለማኝ በርጠሚዮስ በመንገድ ዳር ተቀምጦ ይለምን ነበር። **47** የናዝሬቱ ኢየሱስ እያለፈ መሆኑን ሲሰማ የዳዊተ ልጅ ኢየሱስ ሆይ እራራልኝ እያለ ጮኸ። **48** ብዙዎችም ዝም እንዲል ገሰፁት። እርሱ ግን አብዝቶ የዳዊት ልጅ ሆይ እራራልኝ ብሎ ጮኸ። **49** ኢየሱስም ቆመና ጥሩት አለ። እነርሱም አይዞህ መምህሩ ይጠራሀልና ተነሳ አሉት። **50** በርጠሚዮስም ልብሱን ጥሎ እየዘለለ ወደ ኢየሱስ መጣ። **51** ኢየሱስም ምን እንዳደርግልህ ትወዳለህ አለው። ዓይነ ስውሩም ሰው መምህር ሆይ ማየት እንድችል አለው። **52** ኢየሱስም መንገድህን ሂድ እምነትህ አድኖሀል አለው። ወዲያውም አየ ኢየሱስንም ተከትሎ ሄደ።

Mark 10:1

ማርቆስ **10**: **1-4**

Mark 10:5

ማርቆስ **10**: **5-6**
እናንተ ልበ ደንዳኖች "እናንተ እልከኞች"

Mark 10:7

ማርቆስ **10**: **7-9**
ከእንግዲህ ሁለት አይደሉም ግን አንድ ሥጋ ይሆናሉ ይህ እንደ ባል እና ምስት ያላቸውን አካላዊ ትሥሥር የሚያሳይ ምሳሌያዊ ንግግር ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Mark 10:10

ማርቆስ **10**፡ **10-12**

Mark 10:13

ማርቆስ **10**፡ **13-14**
ሕጻናት ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ፍቀዱላቸውለ ፈጽሞ አትከልክሏቸው። እነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው በድጋሜ የተጻፈውም አጽኖት ለመስጠት ሲባል ነው። አማራጭ ትርጉም: “ሕጻናት ወደ እኔ እንዲመጡ አድርጓቸው።” አትከልክሏው ይህ በላሁት አሉታዊ ንግግር ነው። በአንዳንድ ቋንቋዎች ውስጥ አዎንታዊ ቃላትን መጠቀም የተለመደ ነው። አማራጭ ትርጉም: “ፍቀዱላቸው።”

Mark 10:15

ማርቆስ **10**፡ **15-16**

Mark 10:17

ማርቆስ **10**፡ **17-19**
መልካም ብለህ ለምን ትረጠራኛለህ? አማራጭ ትርጉም: "በዚህ ንግግር ውስጥ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚታስተፈለልፈው መልዕክት በጥንቃቄ ማወቅ ይኖርብሃል)

Mark 10:20

ማርቆስ **10**፡ **20-22**

Mark 10:23

ማርቆስ **10**፡ **23-25**
ሀብታም ወደ እግዚአብሔር መንግስት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ውስጥ በትሾልክ ይቀላል። ለግመል በመርፌ ቀዳዳ ውስጥ ማለፍ ፈጽሞ የማይቻላት ነገር ነው። እንደዚሁም ሀብታም ሰዎች እግዚአብሔርን የሕይወታቸውን ንጉሥ አድርጎ መቀበል በጣም አስቸጋር ነው። የመርፌ ዐይን/ቀዳዳ “የመርፌ ዐይን” በመርፌ አናት ላይ የሚገኝ ቀዳዳ ነው።

Mark 10:26

ማርቆስ **10**:**26-28**
ታዲያ ማን ሊድን ይችላል? "ስለዚህ ማንም ሊድን አይችልም።"

Mark 10:29

ማርቆስ **10**፡ **29-31**
ከተውቱ መካል . . . የማይቀበል አይኖርም "ከተውት መካከል . . . የማይቀበል አይኖርም።" ለእኔ ሲል "ለእኔ ጥቅም" ወይም "ለእኔ ጥቅም ሲል" ይህንን ዓለም "ይህን ሕይወት" ወይም "በአሁኑ ዘመን" በሚመጣው ዘመን "በሚመጣው ሕይወት" ወይም "በሚመጣው ጊዜ"

Mark 10:32

ማርቆስ **10**፡ **32-34**
የሰው ልጅን አሳልፈው ይሰጡታል "ሰዎች የሰው ልጅ አሳልፈው ይሰጡታል" ወይም "ሰዎች የሰው ልጅን አሳለፈው ይሰጡታል"

Mark 10:35

ማርቆስ **10**፡ **35-37**

Mark 10:38

ማርቆስ **10**፡ **38-40**
የሚጠጣው ጽዋ ኢየሱስ ይህንን ሀረግ የተጠቀመው ስለሚቀበለው መከራ ለመግለጽ ነው። የሚጠመቀውን ጥምቀት ኢየሱስ ይህንን ሀረግ የተጠቀመው ስለሚቀበለው መከራ ለመግለጽ ነው።

Mark 10:41

ማርቆስ **10**፡ **41-42**
ገዥዎች ተብለው በሚጠሩት "ገዥዎች ተብለው በሌሎች በሚቆጠሩት" ተቆጣጣሪዎች "የሚቆጣጠሩ" ወይም "ኃይል ያላቸው" መለማመድ "የሚጠቀሙ"

Mark 10:43

ማርቆስ **10**፡ **43-45**
ትልቅ የሚሆን "የሚከበር" ወይም "የሚሞገስ" ማንም "ዬትኛውም ሰው" የሰው ልጅ ሊገለገል ሳይሆን "የሰው ልጅ ሰዎች እንዲገለግሉት አልመጣም"

Mark 10:46

ማርቆስ **10**፡ **46-48**
በርጤሜዎስ የአንድ ሰው ስም ጤሜዎስ ይህ በመንገድ ላይ ስለለምን የነበረው ለማኝ አባት ነው።

Mark 10:49

ማርቆስ **10**፡ **29-50**
እንዲጠሩት አዘዘ "ሰውዬውን ይጠሩት ዘንድ አዘዛቸው" ጠንከር በል "አትፍራ"

Mark 10:51

ማርቆስ **10**፡ **51-52**
መመልከት "የማየት ክህሎት" ወዲያው "በዚያን ጊዜ" ወይም "ያለምንም መዘግየት"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **11**

1 ከደብረ ዘይት ተራራ ወደ ኢየሩሳሌም፣ ወደ ቤተ ፋጌና ወደ ቢታንያ በቀረቡ ጊዜ ኢየሱስ ከደቀመዛሙርቱ ሁለቱን ላካቸው። **2** እንዲህም አላቸው፣ ፊት ለፊታችን ወዳለው መንደር ሂዱ፤ወዲያው እንደ ገባችሁም ማንም ሰው ተቀምጦበት የማያውቅ ውርንጫ መንገድ ዳር ታስሮ ታገኛላችሁ። ፍቱትና አምጡልኝ፤ **3** ማንም ለምን ይህን ታደርጋላችሁ ቢለችሁ ለጌታ ያስፈልገዋል በሉት፤ እርሱም ይለቅቀዋል አላቸው። **4** እነርሱም ሄዱ፤ አንድ ውርንጫ ከቤት ውጭ በመንገድ ዳር ታስሮ አገኙ፤ ፈቱትም። **5** በአካባቢው ከቆሙት አንዳንዶቹ ሰዎች ለምን ፈታችሁት? አሏቸው። **6** እነርሱም ልክ ኢየሱስ እንዳላቸው ነገሯቸው፤ ለቀቋቸውም። **7** ደቀመዛሙርቱም ውርንጫውን ወደ ኢየሱስ አመጡት፤ ልብሳቸውንም አለበሱት፤ ኢየሱስም ተቀመጠበት። **8** ብዙ ሰዎችም ልብሳቸውን ፣ሌሎችም ከየቦታው ቅርንጫፎችን ቆርጠው በሚሄድበት መንገድ ላይ አነጠፉ። **9** ከፊት የቀደሙት ከኋላውም የተከተሉት ሆሳእና! በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው፤ **10** የሚመጣው የአባታችን የንጉሥ ዳዊት መንግስት የተባረከ ነው፤ ሆሳእና በአርያም እያሉ ጮኹ። **11** ኢየሩሳሌም እንደ ደረሰ ወደ ቤተመቅደስ ገባ። በአካባቢው ያለውን ሁሉ ተመለከተ፤መሸቶም ነበርና ከዐሥራ ሁለቱ ጋር ወደ ቢታንያ ሄደ። **12** በማግስቱም ከቢታንያ እንደ ወጡ ተራበ፤ **13** አንዲት ቅጠሏ ያቆጠቆጠ በለስ ከርቀት አየ። ምናልባት አንዳች አገኝባት ይሆናል በማለት ወደ እርሷ መጣ። ሲደርስ ግን በለስ የሚያፈራበት ጊዜ ስላልነበረ ከቅጠል በቀር ምንም አላገኘባትም። **14** ስለዚህም ማንም ሰው ለዘላለም ምንም ፍሬ አያግኝብሽ ብሎ ረገማት። ደቀመዛሙርቱም ሰሙት። **15** ወደ ኢየሩሳሌምም እንደ መጡ ወደ ቤተመቅደስ ገባ፤ በዚያም የሚሸጡትንና የሚገዙትን አባረረ፤የገንዘብ ለዋጮችን ጠረጴዛ የርግብ ሻጮችንም መቀመጫቸውን ገለበጠባቸው። **16** ማንም ሰው በቤተ መቅደስ ውስጥ ዕቃ ይዞ እንዳይመላለስ ከለከለ። **17** አስተማራቸውም፤ ቤቴ የአሕዛብ ሁሉ የጸሎት ቤት ይባላል ተብሎ አልተጻፈምን? እናንተ ግን የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችሁት አላቸው። **18** ሊቀ ካህናቱና ጸሓፍትም፣ይህን ሲናገር ሲሰሙ ሕዝቡ ሁሉ በትምህርቱ ተደንቀው ስለ ተከተሉት ፈርተው ነበርና እንዴት እንደሚገድሉት ማሰብ ጀመሩ። **19** ኢየሱስም በየምሽቱ ከከተማ ይወጣ ነበር። **20** በማለዳ ሲያልፉም በለሲቱ ከሥሯ ደርቃ አገኟት። **21** ጴጥሮስም አስታውሶ መምህር ሆይ! እነሆ፤የረገምሃት በለስ ደርቃለች አለው። **22** ኢየሱስም እንዲህ አለው። በእግዚአብሔር እመን፤ **23** እውነት እላችኋለሁ፣ ማንም በልቡ ሳይጠራጠር ይህን ተራራ ከዚህ ተነቅለህ ወደ ባሕር ውስጥ ተወርወር ቢልና የተናገረው እንደሚፈጸም በልቡ ቢያምን ይሆንለታል። **24** ስለዚህ እላችኋለሁ፤የጸለያችሁትንና የለመናችሁትን ነገር ሁሉ እንደምትቀበሉ ብታምኑ ይሆንላችሁማል። **25** ለጸሎት ስትቆሙ፣ በማንም ላይ ቅርታ ቢኖራችሁ፣ የሰማዩ አባታችሁ ኀጢአታችሁን ይቅር እንዲላችሁ ይቅር በሉ። **26** እናንተ ግን ይቅር ባትሉ በሰማያት ያለው አባታችሁ ደግሞ የቅር አይላችሁም። **27** በድጋሚም ወደ ኢየሩሳሌም መጡ። ኢየሱስ ወደ ቤተመቅደስ ሲገባም ሊቀ ካህናት፣ጸሓፍትና ሽማግሌዎችም ወደ ኢየሱስ መጥተው፣ **28** እነዚህን ነገሮች የምታደርገው በምን ሥልጣን ነው? ወይም እነዚህን ነገሮች እንድታደርግ ሥልጣን የሰጠህ ማን ነው? አሉት። **29** ኢየሱስም አንድ ጥያቄ ጠይቃችኋለሁ እናንተም መልሱልኝ፤ እኔም እነዚህን ነገሮች በምን ሥልጣን እንደማደርግ እነግራችኋለሁ አላቸው። **30** መልሱልኝ፤ የዮሐንስ ጥምቀት ከሰማይ ነው? ወይስ ከሰው? አላቸው ። **31** እነርሱም እርስ በርሳቸው ተመካከሩ፤ ከሰማይ ነው ብንል ታዲያ ለምን አላመናችሁበትም? ይለናል፤ **32** ነገር ግን ከሰው ነው ብንል ደግሞ ሰዉ ሁሉ ዮሐንስ ነቢይ ነው ብሎ አምኖበታል ብለው ሕዝቡን ፈሩ። **33** ለኢየሱስም አናውቅም ብለው መለሱለት። ኢየሱስም እኔም እነዚህን ነገሮች በምን ሥልጣን እንደማደርግ አልነግራችሁም አላቸው።

Mark 11:1

ማርቆስ **11**:**1**-**3**
ቤተ ፋጌ የመንደሯ ስም

Mark 11:4

ማርቆስ **11**:**4**-**6**

Mark 11:7

ማርቆስ **11**:**7**-**10**
ሆሣዕና የዚህ ቃል ትርጉም ምን እንደሆነ ግልጽ አይደለም ይሁን እንጂ እንኳ ደህና መጡ እና ምስጋና ጋር ተያያዥነት ባለው መልኩ ቢተረጎም መልካም ነው፤ ማለትም “እግዚአብሔር ይመስገን” (UDB)።

Mark 11:11

ማርቆስ **11**:**11**-**12**

Mark 11:13

ማርቆስ **11**: **13**-**14**

Mark 11:15

ማርቆስ **11**: **15**-**16**

Mark 11:17

ማርቆስ **11**: **17**-**19**
“ቤተ ለአሕዛቡ ሁሉ የጸሎት ቤት ይባልል” ተብሎ አልተጻፈምን? "በቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ እግዚአብሔር “ቤቴ ከሁሉም ሕዝቦች የመጡ ሰዎች የሚጸልዩበት ቤት ይሆናል” በማለት የተናገረው ተጽፏል፤ ነገር ግን እናንት ወሮበላዎች ለእናንተ መደበቂያ ዋሻ አደረጋችሁት!"

Mark 11:20

ማርቆስ **11**: **17**-**19**
“ቤተ ለአሕዛቡ ሁሉ የጸሎት ቤት ይባልል” ተብሎ አልተጻፈምን? "በቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ እግዚአብሔር “ቤቴ ከሁሉም ሕዝቦች የመጡ ሰዎች የሚጸልዩበት ቤት ይሆናል” በማለት የተናገረው ተጽፏል፤ ነገር ግን እናንት ወሮበላዎች ለእናንተ መደበቂያ ዋሻ አደረጋችሁት!"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Mark 11:22

ማርቆስ **11**፡ **22**-**23**
በልቡ ሳይጠራጠር ቢያምን "ሳይጠራጠር" የሚለው ቃል ባለሁት አሉታዊ ቃል ነው። ትርጉሙም “በእውነት ቢያምን” ማለት ነው። እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው አጽኖት ለመስጠት ሲባል ብቻ ጥቅም ላይ የዋሉ ናቸው። አንዳንድ ቋንቋዎች አጽኖት የሚቀጠሙት ሌላ መንገድ ነው። አማርጭ ትርጉም፡ “በእውነት ቢያምን”

Mark 11:24

ማርቆስ **11**፡ **24**-**26**
ቆማችሁ ስትጸልዩ በዕብራዊን ባሕል መሠረት ወደ እግዚብሔር የሚደረግ ጸሎት የሚደረገው ተቁሞ ነው።

Mark 11:27

ማርቆስ **11**፡ **27**-**28**
እነዚህ ነገሮች የሚታደርገው በምን ሥልጣን ነው “እነዚህ ነገሮች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢየሱስ በቤተ መቅደሱ ውስጥ የነበሩት የሸያጮችን ጠረጴዛዎች መገለባበጡን እና የሚያድርጉትን እና የሚያስተምሩትን ነገር በመቃወም መነናገሩን የሚያመለክት ቃል ነው። እነዚህ ነገሮች የሚታደርገው በምን ሥልጣን ነው እንዲሁም እነዚህ ነገሮች እንዲታደረግ ሥልጣን ማን ሰጠህ አማራጭ ትርጉም፡ "እነዚህን ነገሮች ለማድረግ ሥልጣን የለህም ምክንያቱም እኛ ይህንን ሥልጣን አልሰጠንህም"

Mark 11:29

ማርቆስ **11**፡ **29**-**30**
የዮሐንስ ጥምቀት ከሰማይ ወይም ከሰዎች ናት? ምንም እንኳ ኢየሱስ ለዚህ ጥያቄ ምላሹ ምን እንደሆነ ቢያውቅም ይህን ጥያቄ የጠየቃቸው የሃይማኖት መሪዎቹ ለእርሱ ሥልጣን የጠየቁት ጥያቄ መሠረቱ ምን አመክኒዬ እንደሆነ ለመፈተን ነው።

Mark 11:31

ማርቆስ **11**፡ **31**-**33**

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 12

1 ኢየሱስም በምሳሌ ይነግራቸው ጀመር። አንድ ሰው የወይን ተክል ተከለ፤በዙሪያው ዐጥር ሠራ፤ለወይን መጭመቂያ የሚሆን ጕድጓድ ቈፈረ፤ማማም ሠራ። ለገበሬዎችም አከራይቶ ወደ ሌላ አገር ሄደ። 2 በወቅቱ የወይኑን ፍሬ እንዲቀበል አንድ አገልጋይ ወደ ገበሬዎቹ ላከ። 3 እነርሱም አገልጋዩን ያዙት፤ ደብድበውም ባዶ እጁን ሰደዱት። 4 በድጋሚም ሌላ አገልጋይ ላከ፤እነርሱም ፈነከቱት፤ አሳፈሩትም። 5 ሌላም አገልጋይ ወደ እነርሱ ላከ፤ እርሱንም ገደሉት። ብዙዎች ሌሎችንም ላከ፤ አንዳንዶቹን ደበደቡ፤ ሌሎቹንም ገደሉ። 6 የወይኑ ተክል ባለቤት አንድ ተወዳጅ ልጅ ነበረው፤ልጁን ያከብሩታል በማለት በመጨረሻ እርሱን ላከው። 7 ገበሬዎቹ ግን እርስበርሳቸው እንዲህ አሉ። ይህ ወራሹ ነው ኑ እንግደለው ሀብቱ ሁሉ የእኛ ይሆናል ተባባሉ። 8 ልጁንም ያዙት፤ ገደሉት፤ከወይኑ ቦታ ውጭም ጣሉት። 9 የወይኑ ተክል ባለቤት በዚህ ጊዜ ምን ያደርጋል? ይመጣና ገበሬዎቹን ያጠፋቸዋል፤የወይን ቦታውንም ለሌሎች ይሰጣቸዋል። 10 ይህን የመጽሓፍ ቃል አላነበባችሁምን? እነሆ ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማእዘን ድንጋይ ሆነ፤ 11 ይህ ከጌታ ነው፤ ለዐይኖቻችንም ድንቅ ነው። 12 ኢየሱስ ምሳሌውን የተናገረው ስለ እነርሱ እንደ ሆነ ስለ ተገነዘቡ እጃቸውን ሊጭኑበት ፈለጉ፤ነገር ግን ሕዝቡን ስለ ፈሩ፤ትተውት ሄዱ። 13 እነርሱም በንግግር እንዲያጠምዱት አንዳንድ ፈሪሳውያንና ከሄሮድስ ወገን የሆኑ ሰዎችን ላኩ። 14 ወደ እርሱ በመጡ ጊዜ እንዲህ አሉት፤መምህር ሆይ፣ አንተ እውነተኛ እንደ ሆንህ ለማንም በይሉኝታ እንደማታደርግ፣ለሰው ፊትም እንደማታዳላ ነገር ግን የእግዚአብሔርን መንገድ በእውነት እንደምታስተምር እናውቃለን። ለቄሳር ግብር መክፈል ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? 15 እንክፈል ወይስ አንክፈል? አሉት። ኢየሱስ ግን ግብዝነታቸውን ዐውቆ ለምን ትፈትኑኛላችሁ? አላቸው። እንዳየው አንደ ዲናር አምጡልኝ አላቸው። 16 እነርሱም አመጡለት። ኢየሱስም ይህ ምስል ቅርጹም የማን ነው? አላቸው። እነርሱም የቄሳር ነው አሉት። 17 ኢየሱስም እንግዲህ የቄሳርን ለቄሳር የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር ስጡ አላቸው። እጅግም ተገረሙበት። 18 ትንሣኤ ሙታን የለም የሚሉ ሰዱቃውያን ወደ እርሱ መጥተው እንዲህ ብለው ጠየቁት። 19 መምህር ሆይ፣ ሙሴ፣ አንድ ሰው ልጅ ሳይወልድ ሚስቱን ትቶ ቢሞት፣ ወንድሙ እርስዋን አግብቶ ለወንድሙ ዘር ይተካለት ብሎ ጽፎልናል። 20 ሰባት ወንድማማቾች ነበሩ። የመጀመሪያው ሚስት አገባ፤ ዘር ሳይተካም ሞተ። 21 ሁለተኛውም አገባት፤ እርሱም ዘር ሳይተካለት ሞተ። ሦስተኛውም እንዲሁ። 22 ሰባቱም ለወንድማቸው ዘር አልተኩም። ከሁሉም በኋላ ሴቲቱም ደግሞ ሞተች። 23 ታዲያ ይህች ሴት በትንሣኤ የየትኛው ሚስት ትሆናለች? አሉት። ሰባቱም አግብተዋት ነበርና። 24 ኢየሱስም የምትስቱት መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኀይል ስለማታውቁ አይደለምን? 25 በትንሳኤ ጊዜ ሰዎች አያገቡም፤ አይጋቡም፤ ነገር ግን በሰማይ እንደ መላእክት ይሆናሉ እንጂ። 26 ነገር ግን ሙታን እንደሚነሡ በሚነድደው ቁጥቋጦ ውስጥ እኔ የአብርሃም፣ የይስሐቅ፣ የያእቆብ አምላክ ነኝ ሲል እግዚአብሔር ለሙሴ የተናገረውን አላነበባችሁምን? እጅግ ትስታላችሁ። 27 እርሱ የሕያዋን አምላክ እንጂ የሙታን አምላክ አይደለም። 28 ከጸሓፍት አንዱ መጣና በአንድነት ሆነው ሲጠይቁት እንዴት በጥሩ ሁኔታ እንደ መላሰላቸው አይቶ፣ ከሕግ ፊተኛው የትኛው ነው? ብሎ ኢየሱስን ጠየቀው። 29 ኢየሱስም ፊተኛው፣ እስራኤል ሆይ ስማ! አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው፤ 30 አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህ፣በፍጹም አሳብህ፣ በፍጹምም ኀይልህ ውደድ የምትለዋ ናት። 31 ሁለተኛዋም ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ የምትለዋ ናት። ከእነዚህ የሚበልጥ ምንም ሌላ ትእዛዝ የለም አለው። 32 ሰውዬውም መምህር ሆይ፣በእውነት መልካም ብለሃል፤ እርሱ አንድ ነው፤ከእርሱም በቀር ሌላ የለም፤ እርሱን በፍጹም ልብ፣ በፍጹም ማስተዋል፣ 33 በፍጹም ኀይል መውደድና ባልንጀራን እንደ ራስ መውደድ ሁሉንም ዓይነት መስዋእትና የሚቃጠል መሥዋእት ከማቅረብ ይበልጣል አለ። 34 ኢየሱስም ሰውዬው በማስተዋል እንደ መለሰለት ባየ ጊዜ አንተ ከእግዚአብሔር መንግስት የራቅህ አይደለህም አለው። ከዚያ በኋላ ማንም ሰው ምንም ጥያቄ ሊጠይቀው አልደፈረም። 35 ኢየሱስም መለሰላቸው፤ በቤተ መቅደስ ውስጥ ሲያስተምር፣ ጸሓፍት ክርስቶስ የዳዊት ልጅ ነው የሚሉት እንዴት ነው? አለ። 36 ዳዊት ራሱ በመንፈስ ቅዱስ ጌታ ጌታዬን ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው። 37 ዳዊት ራሱ ጌታዬ ብሎ ይጠራዋል፤ ታዲያ እንዴት ልጁ ይሆናል? ሕዝቡም በደስታ ይሰማው ነበር። 38 ኢየሱስም እንዲህ አለ። ከጸሓፍት ተጠንቀቁ፤ የተንዘረፈፈ ልብስ ለብሰው መሄድን ይወድዳሉ፤ እነርሱ በገበያ ቦታ ሰላምታን፣ 39 በምኩራብም የክብር ወንበር፣ በግብዣም የክብር ቦታ ላይ መቀመጥ ይወድዳሉ። 40 ለይምሰል ጸሎት በማስረዘም የመበለቶችን ቤት ይበዘብዛሉ። እነዚህ የባሰ ፍርድ ይቀበላሉ። 41 ኢየሱስም በመባ መቀበያው ፊት ለፊት ተቀመጠ። ብዙ ሰዎች በመባ መቀበያው ውስጥ ገንዘብ ሲጨምሩ ተመለከተ። ብዙ ሃብታሞች ብዙ ገንዘብ ይጨምሩ ነበር። 42 ከዚያም አንዲት ድኻ መበለት መጥታ ሁለት ናስ ጨመረች፤ይህም የብር ሩብ ነው። 43 እርሱም ደቀመዛሙርቱን ወደ ራሱ ጠርቶ እንዲህ አላቸው። እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ይህች መበለት በመባ መቀበያው ውስጥ ገንዘባቸውን ከጨመሩት ሁሉ አብልጣ ሰጠች። 44 እነርሱ ከትርፋቸው ሰጥተዋልና። እርስዋ ግን ከጉድለቷ ሰጠች፤ ያላትን ሁሉ ሰጠች፤ ኑሮዋን እንኳ ሳይቀር ሁሉንም ሰጠች።

Mark 12:1

ማርቆስ 12፡ 1-3
የወይን እርሻውን አከራይቶ ሄደ የእርሻው ባለቤት ወይኑን ይንከባከቡለት ለሌሎች ሰዎች ሰጠ።

Mark 12:4

ማርቆስ 12፡ 4-5

Mark 12:6

ማርቆስ 12፡ 6-7
ገበሬዎቹ ከባለቤቱ የወይን እርሻውን ለመንከባከብ የተረከቡት ገበሬዎች

Mark 12:8

ማርቆስ 12፡ 8-9
ማርቆስ 12፡ 8-9 ስለዚህ የወይን እርሻው ባለቤት ምን ያድረጋል? አማራጭ ትርጉም: "የወይን እርሻው ባለቤት ምን እንደሚያደርግ እነግራችኋለሁ።

Mark 12:10

ማርቆስ 12፡ 10-12
ማርቆስ 12፡ 10-12 ይህን የቅዱስ መጽሐፍ ክፍል አላነበባችሁምን? አማራጭ ትርጉም፡ "በእነዚህ የቅዱስ መጽሐፍ ክፍል ውስጥ የሚገኙትን እነዚህን ቃላት በጥንቃቄ አስቡ።"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Mark 12:13

ማርቆስ **12**፡ **13-15**
ስለምን ትፈትኑኛላችሁ? "እኔን መከሰስ ያስችላችሁ ዘንድ ትክክል ያልሆነ ነገር እስኪናገር ድረስ እየፈለጋችሁ መሆኑን አውቃለሁ።" ዲናር ይህ ገንዘብ የአንድ ቀን የሥራ ደሞዝን ያክላል።

Mark 12:16

ማርቆስ **12**፡ **16-17**
አንድ አመጡለት "ፈርሳዊያን እና ሄሮዶሳዊያን የሮም መንግስት ፍራንክ አመጡለት" የቄሣርን ለቄሣር ስጡ አማራጭ ትርጉም፡ "የሮም መንግስት የሆነውን ነገር ለሮም መንግስት ስጡ፣" .

Mark 12:18

ማርቆስ **12**፡ **18-19**
ሙሴ እንዲህ ብሎ ጽፎልናል፣ 'የእንድ ሰው ወንድም . . . ለወንድሙ ልጅ ይውለድለት።' አማራጭ ትርጉም: "ሙሴ እንዲህ ሲል ጽፏል የአንድ ሰው ወንድም ከሞተ . . ለወንድሙ ልጅ ይውለድለት።

Mark 12:20

ማርቆስ **12**፡ **20-23**
በትንሳዔ ጊዜ፣ ከሞት ሲነሳ የማን ምስት ትሆናለች? አማራጭ ትርጉም፡ "በትንሳዔ ጊዜ፣ ከሞት ሲነሳ የእነዚህ ሰባት ወንድመማማቾች ምስት መሆን እትችልም!"

Mark 12:24

ማርቆስ **12**፡ **24-25**
ስህተታሁ ይህ አይደለምን . . . የእግዚአብሔር ኃይል? "የተሳሳታችሁት በዚህ ምክንያት ነው . . . የእግዚአብሔር ኃይል።"

Mark 12:26

ማርቆስ **12**፡ **26-27**
ከሞት ይነሳሉ "እግዚአብሔር ያስነሳቸዋል፣"

Mark 12:28

ማርቆስ **12**፡ **28-31**

Mark 12:32

ማርቆስ **12**፡ **32-34**

Mark 12:35

ማርቆስ **12**፡ **35-37**
ታዲያ ጸሐፍት እንዴት ክርስቶስ የዳዊት ልጅ ነው ይላሉ? አማራጭ ትርጉም: "የአይሁድ ሕግ ክርስቶስ የዳዊት ልጅ ነው ብለው የሚያስተምሩት እነዚህ ሰዎች ተሳተዋል!" የዳዊተ ልጅ “ልጅ” የሚለው ቃል በዚህ ሥፍራ ጥቅም ላይ የዋለው ዘር የሚለውን ለማመለከት ነው። ታዲያ እንዴት የዳዊት ልጅ ሊሆን ይችላል? አማራጭ ትርጉም፡ "የዳዊት ልጅ መሆን አይችም!"

Mark 12:38

ማርቆስ **12**፡ **38-40**

Mark 12:41

ማርቆስ **12**፡ **38-40**

Mark 12:43

ማርቆስ **12**፡ **43-44**
እውነት እውነት እላችኋለሁ ይህንን በ MRK 11:23 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ። የመባ ሳጥን ይህ ሳጥን በቤተ መቅደሱ ውስጥ መባ ለመሰብሰብ የሚው ሳጥን ነው። የተትረፈረፈ "በጣም ብዙ" ድህነት "እጥረት" ወይም "ድህነት"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 13

1 ኢየሱስ ከቤተመቅደስ ሲወጣ ሳለ ከደቀመዛሙርቱ አንዱ መምህር ሆይ፤ እንዴት ያሉ ድንጋዮችና እንዴት ያሉ ሕንጻዎቹ እንደሆኑ ተመልከት! አለው። 2 እርሱም እነዚህን ታላላቅ ሕንጻዎች ታያለህን? ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ እንደዚህ አይቀርም አለው። 3 ኢየሱስ በደብረዘይት ተራራ ላይ በቤተመቅደሱ ትይዩ ተቀምጦ ሳለ ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ፣ ዮሐንስና እንድርያስ 4 ንገረን፣ እነዚህ ነገሮች የሚሆኑት መቼ ነው? እነዚህ ነገሮች ሁሉ የሚፈጸሙበት ምልክቱስ ምንድነው? ብለው ለብቻው ጠየቁት፤ 5 ኢየሱስም ማንም እንዳያስታችሁ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ አላቸው። 6 ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ! እያሉ በስሜ ይመጣሉና ብዙዎችንም ያስታሉ። 7 ጦርነትንና የጦርነትን ወሬ በምትሰሙበት ጊዜ አትታወኩ፤ እነዚህ ነገሮች የግድ መፈጸም አለባቸው፤ ነገር ግን መጨረሻው ገና ነው። 8 ሕዝብ በሕዝብ ላይ፣ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣልና። በተለያዩ ቦታዎች የምድር መንቀጥቀጥ፣ ረሃብም ይሆናል። እነዚህ የምጥ ጣር መጀመሪያ ናቸው። 9 እናንተ ግን ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። ወደ ሸንጎዎቻቸው ያቀርቧችኋል፣ በምኩራቦች ውስጥ ትደበደባላችሁ። ለእነርሱ ምስክር እንዲሆን በእኔ ምክንያት በገዢዎችና በነገሥታት ፊት ትቆማላችሁ። 10 አስቀድሞ ወንጌል ለሕዝቦች ሁሉ ይሰበካል። 11 ወደ ፍርድ በሚያቀርቧችሁና አሳልፈው በሚሰጧችሁ ጊዜ አስቀድማችሁ ምን እንደምትናገሩ አትጨነቁ፤ ነገር ግን በዚያች ሰዓት የምትናገሩት ይሰጣችኋልና፤ የሚናገረውም መንፈስ ቅዱስ ነው እንጂ እናንተ አይደላችሁም። 12 ወንድም ወንድሙን ለሞት አሳልፎ ይሰጣል፣ አባትም ልጁን፤ ልጆችም ወላጆቻቸውን በመቃወም ተነስተው ይገድሏቸዋል። 13 ስለስሜም በሰዎች ሁሉ ትጠላላችሁ። ነገር ግን እስከ መጨረሻው የሚጸና እርሱ ይድናል። 14 የጥፋትን እርኩሰት በማይገባው ቦታ ቆሙ ስታዩት (አንባቢው ያስተውል) በይሁዳ ያሉ ወደ ተራሮች ይሸሹ፤ 15 በቤቱ ጣሪያ ላይ ያለም አንዳች ይወስድ ዘንድ አይውረድ፣ ወደ ቤትም አይግባ፤ 16 በእርሻም ያለ ልብሱን ይወስድ ዘንድ ወደ ኋላው አይመልከት። 17 ነገር ግን በእነዚያ ወራት ለእርጉዞችና ለሚያጠቡ ወዮላቸው! 18 በክረምት እንዳይሆን ጸልዩ። 19 እግዚአብሔር ከፈጠረው ከፍጥረት መጀመሪያ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ያልሆነ ወደፊትም የማይሆን ታላቅ መከራ በእነዚያ ቀናት ይሆናልና። 20 ጌታ ቀኖቹን ባያሳጥር ኖሮ ሥጋን የለበሰ ሁሉ አይድንም ነበር። ነገር ግን ስለመረጣቸው ስለ ምርጦቹ ሲል ቀኖቹን አሳጠረ። 21 አንድ ሰው እነሆ ክርስቶስ በዚህ ነው ወይም እነሆ በዚያ ነው ቢላችሁ አትመኑት። 22 ሐሰተኛ ክርስቶሶችና ሐሰተኛ ነብያት ይነሣሉና፤ ቢቻላቸው የተመረጡትን ለማሳት ድንቆችንና ምልክቶችን ያሳያሉ። 23 ነገር ግን አስተውሉ፤ እነሆ አስቀድሜ ሁሉንም ነገር ነግሬአችኋለሁ። 24 ከመከራው በኋላ በእነዚያ ቀናት ፀሐይ ትጨልማለች፣ ጨረቃም ብርሃንዋን አትሰጥም፣ 25 ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ፣ በሰማያት ውስጥ ያሉ ኃይላትም ይናወጣሉ። 26 እነርሱም የሰው ልጅ በደመና ውስጥ በታላቅ ኃይልና ክብር ሲመጣ ያዩታል። 27 ከምድር ጫፍ እስከ ጫፍ ለእርሱ የተመረጡትን ከአራቱም ነፋሳት በአንድ ላይ እንዲሰበስቡለት መላዕክትን ይልካቸዋል። 28 ምሳሌውን ከበለስ ዛፍ ተማሩ፤ ቅርንጫፏ ሲለሰልስ፣ ቅጠሏም ሲያቆጠቁጥ ያን ጊዜ በጋ መቃረቡን ታውቃላችሁ። 29 እናንተም ደግሞ እነዚህ ነገሮች ሲፈጸሙ በምታዩበት ጊዜ የሰው ልጅ በበር ላይ መሆኑን ታውቃላችሁ። 30 እውነት እላችኋለሁ፣ እነዚህ ነገሮች እስኪፈጸሙ ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም። 31 ሰማይና ምድር ያልፋል፣ ቃሌ ግን አያልፍም። 32 ስለዚያች ቀን ወይም ስለዚያች ሰዓት ግን ከአባት በስተቀር የሰማይ መላዕክትም ቢሆኑ፣ ልጅም ቢሆን ማንም አያውቅም። 33 ጊዜው መቼ እንደሆነ አታውቁምና አስተውሉ፣ ንቁና ጸልዩ። 34 ነገሩ ለአገልጋዮቹ ሥልጣን፣ ለእያንዳንዳቸውም የሥራ ድርሻ በመስጠት ዘበኛውም ደግሞ እንዲጠብቅ አዝዞት ቤቱን ትቶ ወደ ሩቅ ሀገር የሚሔድን ሰው ይመስላል። 35 35የቤቱ ጌታ በምሽት፣ ወይም በእኩለ ሌሊት፣ ወይም ዶሮ ሲጮህ፣ ወይም ጠዋት ላይ ምን ጊዜ እንደሚመጣ አታውቁምና እንግዲህ ንቁ! 36 በድንገት ሲመጣ እንቅልፍ ላይ ሆናችሁ እንዳያገኛችሁ። 37 ለእናንተ የምነግራችሁን ለሁሉም እናገራለሁ፣ንቁ!

Mark 13:1

ማርቆስ 13፡ 1-2
ይህንን ትልቅ ሕንጻ ትመለከታለህን? አማራጭ ትርጉም፡ “እነዚህ ሕንጻዎች እንዴት እንደሚያምሩ ተመልከት።

Mark 13:3

ማርቆስ 13፡ 3-4
እነዚህ ነገሮች "አሁን የነገርከኝ ነገሮች"

Mark 13:5

ማርቆስ 13፡ 5-6
በእኔ ስም ብዙ ሰዎች ይመጣሉ “ስም” የሚለው ቃል የኢየሱስን ስልጣን የሚያሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም፡ ብዙዎች የእኔ ስልጣን እና ከእኔ ፈቃድ እንደጋኙ በመናገር ይመጣሉ፣"

Mark 13:7

ማርቆስ 13፡ 7-8
ወሬ "የስህተት ትምህርት" ወይም "ወሬ"

Mark 13:9

ማርቆስ 13፡ 9-10
ለእነርሱ ምስክር ይሆናቸው ዘንድ “ለእነርሱ ምስክር ይሆናቸው ዘንድ” የሚለው ሀረግ “እውነት እንደሆነ ለማሳየት” ወይም “እውነቱ ዬቱ እንደሆነ ለማረጋገጥ” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል።

Mark 13:11

ማርቆስ 13፡ 11-13
አባት ልጁን "አባት ልጁን ለሞት አሳልፎ ይሰጣል።" እስከመጨረሻ የሚጸና ሰው እርሱ ይድናል አማራጭ ትርጉም፡ "እስከመጨረሻ የሚጸናውን እግዚአብሔር ያድነዋል።"

Mark 13:14

ማርቆስ 13፡ 14-16
የጥፋት እርኩሰት "ክፉ የሆነ የጣኦት አምልኮ" ወይም "እርባና ያሌለው ክፋት"

Mark 13:17

ማርቆስ 13፡ 17-20
the elect, those he chose “እርሱ የመረጣቸው” የሚለው ሀረግ “የተመረጡት” ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው። እነዚህ ሁለቱ በአንድነት እግዚአብሔር እነዚህ ሕዝቡን መምረጡን አጽኖት በመስጠት ይናገራሉ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Mark 13:21

ማርቆስ **13:21-23**
የተመረጠ ሰዎች እንዲቀደሱ እግዚአብሔር ይመርጣል፣ ጥሩ መንፈሳዊ ፍሬን እንዲያፈሩ እርሱ ራሱ ሰዎችን ይለያል። ለዚህም ነው “የተመረጡት” ተብለው የሚጠሩት።

Mark 13:24

ማርቆስ **13: 24-27**
ፀሐይ ይጨልማል "እግዚአብሔር ፀሐይ እንዲትጨልም ያደርጋል።" በሰማይ ያሉት ኃይላት ሁሉ ይናወጣሉ "እግዚአብሔር በሰማይ ያሉት ኃይላት ሁሉ ያናውጣልይናወጣሉ"

Mark 13:28

ማርቆስ **13: 28-29**

Mark 13:30

ማርቆስ **13: 30-32**
እውነት እውነት እላችኋለሁ ኢየሱስ ያስተማራቸው ነገር ሁሉ እርሱ በተናገረው መንገድ እየተፈጸመ መሆኑን አጽኖት በመስጠት በመናገር ላይ ነው። ያልፋሉ "ያበቃሉ" Father “አባት” የሚለው ቃል በቋንቋችሁ በተለምዶ ለሰው አባት መጠሪያነት የሚትጠቀሙበትን ቃል ተጠቀሙ።

Mark 13:33

ማርቆስ **13: 33-34**
አስተውሉ “አስተውሉ” ወይም “እያስተዋላችሁ” የሚለው ቃል ኃጢአትን እና ክፋትን ሁል ጊዜ መጠንቀቅ እና በንቃት መጠበቅን ያመለክታል። ከዚህ በተጨማሪ “ሁል ጊዜ ዝግጁ መሆንን” ማለትም ሊሆን ይችላል።

Mark 13:35

ማርቆስ **13: 35-37**
የአውራ ዶሮ ጩኸት አውራ ዶሮ ጥዋት በማለዳ የሚያሰማው ጩኸት ነው። የአውራ ዶሮ በጥዋት የሚያሰማው ጩኸት የአውራ ዶሮ በጥዋት የሚያሰማው ጩኸት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **14**

1 ከሁለት ቀን በኋላ የፋሲካና የቂጣ በዓል ነበር። የካህናት አለቆችና ጸሓፍት እንዴት አድርገው በተንኮል ይዘው ሊገድሉት እንደሚችሉ ያስቡ ነበር። **2** ነገር ግን የህዝብ ሁከት እንዳይሆን በበዓል ቀን አይሁን ተባብለው ነበር። **3** እርሱም በቢታኒያ በለምጻሙ በስምዖን ቤት በማዕድ ተቀምጦ ሳለ አንዲት ሴት ዋጋው እጅግ የከበረ ሽቱ የያዘ የአልባስጥሮስ ጠርሙስ ይዛ መጣች። ጠርሙሱንም ሰብራ ሽቱውን በኢየሱስ በራሱ ላይ አፈሰሰች ። **4** ነገር ግን ከመካከላቸው አንዳንዶቹ እንዲህ ያለው የሽቱ ማባከን ያስፈለገው ለምንድነው በማለት የተበሳጩ አንዳንድ ሰዎች ነበሩ **5** ይህ ቅባት ከሦስተ መቶ ሽልንግ በላይ ተሸጦ ለድሆች ሊሰጥ ይቻል ነበር እያሉ በእርሷ ላይ አጉረመረሙ። **6** ኢየሱስ ግን ተዋት ለምን ታስቸግሯታላችሁ እርሷ መልካምን ነገር አድርጋልኛለች። **7** ድሆች ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ናቸው በፈለጋችሁም ጊዜ መልካም ልታድጉላቸው ትችላላችሁ እኔን ግን ሁልጊዜ አታገኙኝም። **8** እርሷ ከመቃብር በፊት ሰውነቴን ሽቱ በመቀባት የምትችለውን አድርጋለች። **9** ደግሞም እውነት እላችኋለሁ ይህ ወንጌል በዓለም ዙሪያ በሚሰበክበት ጊዜ ሁሉ ይህች ሴት ያደረገችው ነገር ለመታሰቢያዋ ይነገራል አላቸው። **10** ከአስራ ሁለቱ አንዱ የሆነው የአስቆሮቱ ይሁዳ እንዴት አሳልፎ ይሰጠው ዘንድ ወደ ካህናት አለቆች ሄደ **11** እነርሱም በሰሙ ጊዜ ደስ አላቸው ገንዘብም ሊሰጡት ቃል ገቡለት።እርሱም አሳልፎ ሊሰጠው አመቺ ጊዜ ይጠብቅ ነበር። **12** የፋሲካን መስዋዕት በሚያቀርቡበት በቂጣ በዓል የመጀመሪው ቀን ደቀመዛሙርቱ ፋሲካን ትበላ ዘንድ የት እናዛገጅልህ ብለው ጠየቁት። **13** እርሱም ከደቀመዛሙርቱ ሁለቱን ልኮ ወደ ከተማ ሂዱ ወዲያውም አንድ ሰው ውሃ ተሸክሞ ታገኛላችሁ ተከትላችሁትም ሂዱና **14** ወደሚገባበት ቤት ገብታችሁ የቤቱን ባለቤት መምህሩ ከደቀመዛሙርቴ ጋር ፋሲካን እበላ ዘንድ የእንግዳ ክፍሌ የትኛው ነው ብሎሀል ብላችሁ ጠይቁት **15** እርሱ ራሱ በሰገነት ላይ ያለ በቤት ዕቃ የተደራጀና የተዘጋጀ ሰፊ አዳራሽ ያሳያችኋል በዚያም አዘጋጁልን ። **16** ደቀመዛሙርቱም ወጥተው ወደ ከተማ መጡ ልክ እንዳላቸውም አገኙ ፋሲካንም አዘጋጁ። **17** በመሸም ጊዜ ከአስራ ሁለቱ ጋር መጣ። **18** ተቀምጠውም በመመገብ ላይ ኢየሱስ አውነት እላችኋለሁ በማዕድ ከኔ ጋር ያለ ከእናንተ አንዱ አሳልፎ ይሰጠኛል አላቸው። **19** እነርሱም እጅግ አዝነው በየተራ እኔ እሆንን ይሉት ጀምር። **20** ኢየሱስም ከእኔ ጋር ወደ ወጥ ሳህኑ የሚነክረውና ከአስራሁለቱ አንዱ ነው አላቸው። **21** የሰው ልጅስ ስለ እርሱ እንደተጻፈው ይሄዳል የሰው ልጅ አሳልፎ ለሚሰጠው ለዚያ ሰው ግን ወዮለት ባይወለድ ይሻለው ነበር አላቸው። **22** እየተመገቡም ሳለ እንጀራን አንስቶ ከባረከ በኋላ ቆርሶ ሰጣቸውና ውሰዱና ብሉ ይህ ስጋዬ ነው አላቸው። **23** እንዲሁም ጽዋውን አንስቶ አመስግኖ ለደቀመዛሙርቱ ሰጣቸው ሁሉም ጠጡ። **24** እርሱም ይህ ለብዙዎች የሚፈስ የቃል ኪዳን ደሜ ነው ። **25** እውነት እላችኋለሁ በእግዚአብሔር መንግስት እንደገና እንደ አዲስ እስከምጠጣበት ቀን ድረስ ከዚህ ወይን ከዚህ በኋላ አልጠጣም። **26** መዝሙርም ከዘመሩም በኋላ ወደ ደብረ ዘይት ተራራ ሄዱ። **27** ኢየሱስም እረኛውን እመታለው በጎቹም ይበታተናሉ ተብሎ እንደተጻፈ ሁላችሁ ትሰናከላላችሁ **28** ከተነሳሁ በኋላ ግን ወደ ገሊላ እቀድማችኋለሁ አላቸው። **29** ጴጥሮስም ሁሉ ቢሰናከሉ እኔ ግን አልሰናከልም አለው። **30** ኢየሱስም አውነት እልሃለሁ ዛሬ ሌሊት ዶሮ ሁለት ጊዜ ሳይጮህ ሶስት ጊዜ ትክደኛለህ አለው። **31** እርሱ ግን እጅግ እየጮኸ እስከሞት እንኳ ቢሆን አልክድህም አለው። ሌሎቹም እንደዚያው አሉ። **32** ጌቴ ሴማኒ ወደሚባል ሥፍራም መጡ። ደቀመዛሙርቱንም እስክ ጸልይ ድረስ በዚህ ተቀመጡ አላቸው። **33** ኢየሱስም ጴጥሮስን ያዕቆብንና ዮሐንስን ይዞ ሄደ እጅግ ሊያዝንና ሊተክዝ ጀመረ። **34** ነፍሴ እስከሞት ድረስ እጅግ አዝናለች በዚህ ሆናችሁ ትጉ ንቁም አላቸው። **35** ጥቂትም ፈቀቅ ብሎ ሄደ፤ በግንባሩም ተደፍቶ የሚቻል ከሆነ ይህች ሰዓት ሰዓቲቱ እንድታልፍ መጸለይ ጀመረ። **36** አባት ሆይ ለአንተ ሁሉ ይቻላል ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ ነገር ግን የእኔ ሳይሆን የአንተ ፈቃድ ይሁን አለ። **37** ወደ እነርሱም መጣ ተኝተውም አገኛቸው ጴጥሮስንም ስምዖን ተኝተሀልን ለአንድ ሰዓት እንኳ ልትተጋ አልቻልክምን። **38** ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ። መንፈስ ዝግጁ ነው ሥጋ ግን ደካማ ነው አለው። **39** ተመልሶም ሄደና ያንኑ ቃል ደግሞ ጸለየ። **40** እንደገና ወደ ደቀመዛሙርቱ በመጣ ጊዜ አሁንም ተኝው አገኛቸው አይናቸው በእንቀልፍ ከብዶ ስለነበር የሚመልሱለትንም አያውቁም ነበር። **41** ለሦስተኛም ጊዜ ወደ እነርሱ መጣና እንግዲህስ ይበቃል ተኙ እረፉም የሰው ልጅ ለኃጢአተኞች አልፎ ይሰጥ ዘንድ ሰዓቲቱ ደርሳለች ። **42** ተነሱ እንሂድ እነሆ አሳልፎ የሚሰጠኝ በደጅ ነው አላቸው። **43** ወዲያውም ገና በመናገር ላይ ሳለ ከአስራ ሁለቱ አንዱ የነበረው የአስቆሮቱ ይሁዳ መጣ ። ከእርሱም ጋር ከካህናት አለቆች፣ ከጸሓፍትና ከሽማግሌዎች ዘንድ የተላኩ ብዙ ህዝብ ሠይፍና ቆመጥ ይዘው መጡ። **44** አሳልፎ የሚሰጠውም የምስመው እርሱ ነውና ያዙት በጥንቃቄ ውሰዱት ብሎ ምልክት ሰጥቷቸው ነበር። **45** በመጣም ጊዜ በቀጥታ ወደ ኢየሱስ ቀርቦ መምህር ሆይ ብሎ ሳመው። **46** እነርሱም ይዘው ወሰዱት። **47** ነገር ግን በዚያ ከቆሙት መካከል አንዱ ሰይፉን መዘዘ፤ የሊቀ ካህናቱን አገልጋይ ጆሮም ቆረጠው። **48** ኢየሱስም መልሶ ወንበዴ እንደምትይዙ ሰይፍና ቆመጥ ይዛችሁ ልትይዙኝ መጣችሁን **49** በየዕለቱ በቤተ መቅደስ እያስተማርከ ከእናንተ ጋር በነበርኩ ጊዘ አልያዛችሁኝም። ነገር ግን የተጻፈው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሆኗል አላቸው። **50** ሁሉም ትተውት ሸሹ። **51** እርቃኑን ከበፍታ በተሰራ ጨርቅ የሸፈነ አንድ ወጣት ይከተለው ነበር ሊይዙትም ባሉ ጊዜ **52** የበፍታ ጨርቁን ነጠላውን ትቶ ራቁቱን አመለጠ። **53** ኢየሱስንም ወደ ሊቀ ካህናቱ ይዘውት መጡ። የካህናት አለቆች፣ ሽማግሌዎችና ጸሓፍትም አብረውት መጡ። **54** ጴጥሮስም እስከ ሊቀካህናቱ ግቢ ድረስ በሩቅ ሆኖ ይከተለው ነበር። ከዚያም ከጠበቃዊዎች ጋር እሳት እየሞቀ ተቀመጠ። **55** ሊቀ ካህናቱና ጉባኤው ሁሉ በኢየሱስ ላይ ሞት የሚያስፈርድበት ምክንያት ይፈልጉ ነበር ነገር ግን ሊያገኙ አልቻሉም። **56** ብዙዎች በሀሰት ቢመሰክሩበትም ምስክርነታቸው እርስ በእርሱ የሚጣረስ ነበር። **57** ሦስት ሰዎችም ተነስተው በሀሰት መሰከሩበት እንዲህም አሉ **58** ይህንን በእጅ የተሰራ ቤተመቅደስ በሶስት ቀን አፍርሼ እንደገና በሶስት ቀን ውስጥ በእጅ ያልተሰራ ሌላ ቤተመቅደስ እሰራለሁ ሲል ሰምተነዋል ። **59** የእነርሱም ምስክርነት ቢሆን እርስ በእርሱ የሚጣረስ ነበረ። **60** ሊቀ ካህናቱም ተነስቶ በመካከል ቆመና ለሚመሰክሩብህ መልስ አትሰጥምን ብሎ ጠየቀው። **61** ኢየሱስ ግን ዝም አለ መልስም አልሰጠም። ሊቀ ካህናቱም በድጋሚ የቡሩኩ ልጅ መሲሁ አንተ ነህን ብሎ ጠየቀው **62** ኢየሱሰም አዎ ነኝ የሰው ልጅ በኃይሉ ቀኝ ተቀምጦ በሰማይ ደመና ሲመጣ ታዩታላችሁ አለው። **63** ሊቀካህናቱም ልብሱን ቀደደና ከእንግዲህ ምን ሌላ ምስክር ያስፈልጋል **64** እግዚአብሔርን ሲሳደብ ሰምታችኋል ታዲያ ምን ታስባላችሁ ። ሁሉም ሞት ይገባዋል አሉ። **65** አንዳነዶቹም ይተፉበት ፊቱንም ሸፍነው ትንቢት ተናገር እያሉ ያሾፉበት ጀመር። መኮንኖችም በእጃቸው እየጎሰሙ ወሰዱት። **66** ጴጥሮስም በሊቀ ካህናቱ ግቢ እሳት በመሞቅ ላይ ሳለ **67** አንዲት የሊቀ ክህናቱ የቤት ውስጥ ሠራተኛ አየችውና አንተ በትክክል ከናዝሬቱ ኢየሱስ ጋር ነበርክ አለችው። **68** እርሱ ግን የምትይውን አላውቀውም ምን እንደምታወሪም አልገባኝም ብሎ ካደ። ወደ ዋናው በር መግቢያ በሄደ ጊዜ ዶሮ ጮኸ **69** ሠራተኛይቱም አይታው በዚያ ላሉት ወታደሮች ይህ ከእነርሱ አንዱ ነው አለቻቸው። **70** እርሱ ግን እንደገና ካደ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ በዚያ ከቆሙት መካከል አንዳንዶቹ ጴጥሮስን አንተ የገሊላ ሰው ስለሆንክ በትክክል ከእነርሱ አንዱ ነህ አሉት። **71** እርሱም የምትሉትን ሰው አላውቀውም ብሎ መማልና መራገም ጀመረ። **72** ወዲያውም ለሁለተኛ ጊዜ ዶሮ ጮኸ ጴጥሮስም ኢየሱስ ዛሬ ሌሊት ዶሮ ሁለት ጊዜ ሳይጮህ ሶስት ጊዜ ትክደኛለህ ያለውን ቃል አስታወሰ ነገሩንም ባሰበ ጊዜ አለቀሰ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Mark 14:1

ማርቆስ **14**:**1**-**2**

Mark 14:3

ማርቆስ **14**: **3**-**5**
ለምጻሙ ስምዖን ይህ ሰው ከከዚህ በፊት ለምጽ ያለበት ቢሆንም አሁን ግን ታሞ አይደለም። አልባስጥሮስ ይህ ለስላሳ “ነጭ ድንጋይ” ነው። የዚህ ሁሉ ብክነት ምክንያቱ ምንድ ነው? አማራጭ ትርጉም: "እንዲህ ዓይነቱን ውድ ሽቶ ለማባከን የሚሆን ምንም በቂ ምክንያት የለም።” ይህ ሽቶ ልሸጥ ይችላል "ይህንን ሽቶ ሸጠን” ወይም “ይህንን ሽቶ ሸጣ” ሦስት መቶ ዲናር "300 ዲናር።" ዲናር የሮማዊያን የብር ሳንቲም ነው።

Mark 14:6

ማርቆስ **14**: **6**-**9**
ስለምን ታደክሙአታላችሁ? አማራጭ ትርጉም: “ልታስቸግሯት አይገባም።"

Mark 14:10

ማርቆስ **14**:**10**-**11**
ማርቆስ 14:10-11 የአስቆሮቱ ይሁዳ ይህንን በ [MRK 3:17]

Mark 14:12

ማርቆስ **14**: **12**-**14**
የእንግዳ ማረፍያ ክፍል an extra room for visitors ለእንግዶች ማረፊያነት የሚዘጋጅ ትርፍ ክፍል

Mark 14:15

ማርቆስ **14**: **15**-**16**

Mark 14:17

ማርቆስ **14**: **17**-**19**
በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጦ ሳለ በምግብ የጠረጴዛ ዙሪያ እንግዶች ተቀምጠው ሳለ። አንድ በአንድ ይህ ማለት “ተራ በተራ” እያንዳንዱ ደቀ መዝሙር እንዲህ ሲል ጠየቀው። እኔ አይደለሁም "በእርግጠኝነት ጠላቶችህ እንዲይዙህ የማግዛቸው እኔ አይደለሁም!"

Mark 14:20

ማርቆስ **14**: **20**-**21**

Mark 14:22

ማርቆስ **14**: **22**-**25**
ማርቆስ 14: 22-25

Mark 14:26

ማርቆስ **14**: **26**-**27**
መዝሙር። የመዝሙር ዓይነት ነው። በዚህ ወቅት የብሉይ ኪዳን መዝሙር መዘመር ባሕል ነበር።

Mark 14:28

ማርቆስ **14**: **26**-**27**
መዝሙር። የመዝሙር ዓይነት ነው። በዚህ ወቅት የብሉይ ኪዳን መዝሙር መዘመር ባሕል ነበር።

Mark 14:30

ማርቆስ **14**: **30**-**31**
እውነት እውነት አልሃለሁ ይህንን በ MRK 11:22 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ትክደኛለህ "አላውቀውም ትላለህ”

Mark 14:32

ማርቆስ **14**: **32**-**34**
ነፍስ “ነፍስ” የሚለው ቃል አንዳንድ ጊዜ ሙሉ ሰውን ለማመልከት በምሳሌያዊ መልኩ ጥቅም ላይ ይውላል።

Mark 14:35

ማርቆስ **14**: **35**-**36**
ይህ ጽዋ ከእኔ ይለፍ "እያለፈበት ያለውን መከራ መቋቋም የሚያስችለው ጥንካሬ ያስፈልገዋ።” አባ "አባ" የግሪክ ቃል ሲሆን ልጆች አባታቸውን ለመጥራት የሚጠቀሙበት ቃል ነው። ይህ ቅርብ የሆነ ግነንኙነት መኖሩን ያሳያል። ይህ ቃል ኢየሱስ አባቱን የጠራበትን መንገድ የሚሳይ በመሆኑ ይህንን የግሪክ ቃል በትርጉማችሁ ውስጥ እንዳለ መስቀመጡ አስፈላጊ ነው። ይህ ጽዋ ከእኔ ይለፍ ጽዋ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢየሱስ ለሸከመው ያለውን የእግዚአብሔር ቁጣን ነው። ኢየሱስ . . .. አንዲህ አለ፣ "አባ አባት . . . ይህን ጽዋ ከእነተ አሳልፍ። ይሁን እንጂ የኔ ፈቃድ ሳይሆን የአንተ ፈቃድ ይሁን።" ኢየሱስ አባቱን ለሰው ልጆች ኃጢአት ሲል የሚቀበለውን መከራ ይተውለት ዘነድ አባቱን ይጠይቃል። ነገር ግን አባቱ የእርሱን ብቸኛ፣ ፍጹም ልጅ መስዋእትነት ለእርሱ የማይቆጠር ቅድስና ይፈልጋል። ስለዚህ ኢየሱስ የመስቀልን መከራ ተቀበለ። አባት ይህ የእግዚአብሔር አባት ወሳኝ የማዕረግ ስሙ ነው።

Mark 14:37

ማርቆስ **14**: **37**-**39**
ተኝተው አገኛቸው "ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ እና ዮሐንስ ተንኝተው አገኛቸው" ስምኦን ተኝተሃልን "አትተኙ ንቁ ቢዬአችሁ ሳለ አንተ ስምኦን ተኝታችኋልን ነቅታቹ ለአንድ ሰዓት እንኳ መጠበቅ አቃታችሁን? "ነቅታችሁ መቆየት ፈጽሞ አቃታችሁን" መንፈስስ ተዘጋጅታለች፥ ሥጋ ግን ደካማ ነው "አእምሮዋችሁ ማድረግ የሚፈልገውን ነገር አካላችሁ ማድረግ አይችልም።" ሥጋ "አካል"

Mark 14:40

ማርቆስ **14**: **40**-**42**
ተኝተው አገኛቸው "ጴጥሮስ፣ ዮሐንስ እና ያዕቆብ ተኝተው ነበር" አሁንም ተኝታችኋልን? አማራጭ ትርጉም: "አሁንም ተኘንታችኋልን1 እረፍት እያደረጋችሁ ነውን!"

Mark 14:43

ማርቆስ **14**: **43**-**46**
እጃቸውን ጫኑበት "ያዙት"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Mark 14:47

ማርቆስ **14**፡ **47-50**
ወንበዴ እንደምትይዙ ሰይፍና ጐመድ ይዛችሁ ልትይዙኝ መጣችሁን? "ወንበዴ ለመያዝ እንደሚመጣ ሰው ሰይፍ እና ጎመድ ይዛችሁ እኔን ለመያዝ መጣችሁ።”

Mark 14:51

ማርቆስ **14**፡ **51-52**
ነጠላ ከጥጥ ፈትል የሚሠራ ልብስ

Mark 14:53

ማርቆስ **14**፡ **53-54**

Mark 14:55

ማርቆስ **14**፡ **55-56**

Mark 14:57

ማርቆስ **14**፡ **57- 59**
ሰምተነዋል “እኛ” የሚለው ቃል በኢያሱስ ላይ በሐሰት የመሰከሩበትን ሰዎችን ያመለክታል።

Mark 14:60

ማርቆስ **14**፡ **60--62**
ከእርሱ መካከል ቆሞ ነበር "ከካህናት አለቆች፣ ጸሐፍት እና ሽማግሌዎች መካከል ቆሞ" እኔ ነኝ ይህ ቃል በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ እግዚአብሔር ራሱን የጠራበት ቃል ነው።

Mark 14:63

ማርቆስ **14**፡ **63-65**
ልብሱን ቀደደ ኢየሱስ በተናገረው ቃል መቆጣጡት የሚያሳይ ምልክት ነው ሁሉም ፈረዱበት "ሽንጎው ሙሉ ለሙሉ በኢየሱስ ላይ ፈረደ"

Mark 14:66

ማርቆስ **14**፡ **66-68**

Mark 14:69

ማርቆስ **14**፡ **69-70**
ከእነርሱ መካከል አንዱ "ከደቀ መዛሙርቱ መካከል አንዱ"

Mark 14:71

ማርቆስ **14**፡ **71-72**
ተሰበረ “ተሰበረ” የሚለው ቃል በጣም መደንገጡን ወይም በጣም ማዘኑን የሚያሳይ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 15

1 ወዲያውኑም በማለዳ የካህናት አለቆች ከሽማግሌዎች፣ ከጸሓፍት፣ ከሸንጎም አባሎችም ሁሉ ጋር ተማከሩ፤ ኢየሱስን አስረው ወሰዱትና ለጲላጦስ አሳልፈው
ሰጡት። 2 ጲላጦስም፣ አንተ የአይሁድ ንጉሥ ነህን? ብሎ ጠየቀው። ኢየሱስም ሲመልስ አንተ እንዳልከው ነኝ አለው። 3 የካህናት አለቆችም ብዙ ክስ
አቀረቡበት። 4 ጲላጦስም ስንት ክስ እንዳቀረቡብህ ተመልከት! ምንም አትመልስምን? ብሎ እንደገና ጠየቀው። 5 ኢየሱስ ግን ጲላጦስ እስኪደነቅ ድረስ
ምንም መልስ አልሰጠም። 6 በየበዓሉ ሕዝቡ ጲላጦስ እንዲፈታላቸው የጠየቁትን አንድ እስረኛ የመፍታት ልማድ ነበረው። 7 በዚያም ዅከት ቀስቅሰው ግድያ
ከፈጸሙ ሰዎች ጋር የታሰረ አንድ በርባን የሚባል ሰው ነበር። 8 ሕዝቡም ወደ ጲላጦስ ቀርበው የተለመደውን እንዲያደርግላቸው ጠየቁት። 9 ጲላጦስም
"የአይሁድን ንጉሥ" እንድፈታላችሁ ትፈልጋላቸሁን? አላቸው። 10 እንዲህ ያለው የካህናት አለቆች ኢየሱስን አሳልፈው የሰጡት በቅናት መሆኑን ያውቅ ስለ ነበር
ነው። 11 የካህናት አለቆች ግን በእርሱ ፈንታ በርባን እንዲፈታላቸው ጲላጦስን እንዲጠይቁ ሕዝቡን ቀሰቀሱ። 12 ጲላጦስም መልሶ ታዲያ በዚህ የአይሁድ
ንጉሥ ብላችሁ በምትጠሩት ሰው ላይ ምን ላድርግበት? አላቸው። 13 እነርሱም "ስቀለው!" እያሉ እንደገና ጮኹ። 14 ጲላጦስም "ለምን? ምን በደል
ፈጽሟል?" አላቸው። እነርሱም "ስቀለው!" እያሉ አብዝተው ጮኹ። 15 ጲላጦስም ሰዎቹን ደስ ለማሰኘት ብሎ በርባንን ፈቶ ለቀቀላቸው፤ኢየሱስን ግን አስገርፎ
እንዲሰቀል አሳልፎ ሰጠው። 16 ወታደሮቹም ኢየሱስን ፕራይቶሪዮን ወደሚባለው ግቢ ወሰዱት፤ወታደሮቹንም ሁሉ ጠሩ፤ 17 ሐምራዊ ልብስ አለበሱት፤ የእሾኽ
አክሊልም በራሱ ላይ ደፉበት። 18 "የአይሁድ ንጉሥ ሆይ! ሰላም ለአንተ ይሁን!" እያሉ ሰላምታ ይሰጡት ነበር። 19 በመቃ ዐናቱን እየመቱ፤ ምራቃቸውን
ተፉበት፤ በፊቱም ተንበርክከው ሰገዱለት። 20 አላግጠውበትም ሐምራዊውን ልብስ አወለቁበት፤ የራሱንም ልብስ አልብሰው፤ሊሰቅሉ ወሰዱት። 21 በመንገድ
ሳሉም የቀሬና ሰው የሆነውን የእስክንድርንና የሩፎስን አባት ስምዖንን ከገጠር ሲመጣ አግኝተው፤ የኢየሱስን መስቀል ተሸክሞ ከእነርሱ ጋር እንዲሄድ
አስገደዱት። 22 ከዚያም በኋላ ኢየሱስን ጎልጎታ ተብሎ ወደሚጠራው ቦታ ወሰዱት፤ ትርጉሙም፦ "የራስ ቅል ስፍራ" ማለት ነው። 23 ከከርቤ ጋር የተቀላቀለ
የወይን ጠጅም ሰጡት፤ እርሱ ግን አልጠጣውም። 24 ከዚያም ሰቀሉት፤ ልብሶቹንም ማን ምን እንደሚወስድ ዕጣ ተጣጥለው ተከፋፈሉ። 25 ከጧቱ ሦስት
ሰዓት ሲሆን ሰቀሉት። 26 "የአይሁድ ንጉሥ" የሚል የክስ ጽሑፍ በመስቀሉ ዐናት ተጽፎ ነበር። 27 ከኢየሱስም ጋር ሁለት ወንበዴዎችን አንዱን
በቀኙ፣አንዱንም በግራው ሰቀሉ። 28 መጽሓፍ "ከዐመፀኞች ጋር ተቈጠረ፤" የሚለው ቃል ተፈጸመ። 29 በአጠገቡ ያልፉ የነበሩትም ሰዎች ራሳቸውን በንቀት
እየነቀነቁ እንዲህ በማለት ይሰድቡት ነበር፣ "አንተ ቤተ መቅደስን አፍርሰህ በሦስት ቀን የምትሠራ ሆይ! 30 እስቲ አሁን ራስህን አድን፤ከመስቀልም ውረድ!"
31 እንደዚሁም የካህናት አለቆች ከጸሓፍት ጋር ሆነው እርስበርሳቸው እንዲህ እያሉ ያፌዙበት ነበር፤ "ሌሎችን አድኖአል፤ ራሱን ማዳን ግን አይችልም" አሉ። 32
"አይተን እንድናምንበት መሲሑ የእስራኤል ንጉሥ እስቲ አሁን ከመስቀል ይውረድ" ከእርሱ ጋር የተሰቀሉት ወንበዴዎችም ይሰድቡት ነበር። 33 ከቀኑም
ስድስት ሰዓት ጀምሮ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ በምድሪቱ ሁሉ ላይ ጨለማ ሆነ። 34 ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን ኢየሱስ፣ "ኤሎሄ፣ ኤሎሄ፣ ላማሰበቅታኒ፤" ብሎ በታላቅ
ድምፅ ጮኸ። ትርጓሜውም "አምላኬ፣ አምላኬ ለምን ተውከኝ?" ማለት ነው። 35 በዚያም ቆመው ከነበሩት ሰዎች አንዳንዶቹ ሰምተው "እነሆ! ኤልያስን
ይጣራል፤" አሉ። 36 ከእነርሱም አንዱ ሮጠና ሆምጣጤ በሰፍነግ ሞላ፤ "ኤልያስ መጥቶ ያወርደው እንደ ሆነ እንይ" አለ።እንዲጠጣውም በመቃ ላይ አድርጎ
ለኢየሱስ ሰጠው። 37 ከዚያም ኢየሱስ በታላቅ ድምፅ ጮኸ፤ መንፈሱንም ሰጠ። 38 የቤተ መቅደሱም መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ተቀደ ከሁለት ተከፈለ። 39
በመስቀሉ ፊት ለፊት ቆሞ የነበረ የመቶ አለቃ ኢየሱስ እንዴት መንፈሱን እንደ ሰጠ ባየ ጊዜ፣ "ይህ ሰው በእርግጥ የእግዚአብሔር ልጅ ነበር፤" አለ። 40 በሩቅ
ሆነው የሚመለከቱ ሴቶችም በዚያ ነበሩ። ከእነርሱም መካከል መግደላዊት ማርያም፣ የታናሹ ያዕቆብና የዮሳ እናት ማርያም፣ሰሎሜም ነበሩ። 41 እነርሱ ኢየሱስ
በገሊላ በነበረበት ጊዜ ይከተሉትና ያገለግሉት ነበር። እንዲሁም ከኢየሱስ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም የመጡ ሌሎች ብዙ ሴቶችም ነበሩ። 42 መሸቶ ስለ ነበርና
የሰንበት ዋዜማና ለሰንበት የመዘጋጃ ጊዜ ስለ ነበር፡፡ 43 የተከበረ የሸንጎ አባል የነበረ ዮሴፍ የሚባል የአርማትያስ ሰው መጣ። እርሱም የእግዚአብሔርን
መንግሥት የሚጠባበቅ ሰው ነበር። በድፍረትም ወደ ጲላጦስ ፊት ቀርቦ የኢየሱስን አስከሬን እንዲሰጠው ለመነው። 44 ጲላጦስም "እንዴት እንዲህ በቶሎ
ሞተ?" ብሎ ተደነቀ። የመቶ አለቃውንም ጠርቶ፣ "ከሞተ ቈይቶአልን?" ሲል ጠየቀው። 45 የኢየሱስን መሞት ከመቶ አለቃው ከሰማ በኋላ አስከሬኑን
እንዲወስድ ለዮሴፍ ፈቀደለት። 46 ዮሴፍም የከፈን ልብስ ገዛ፤ የኢየሱስን አስከሬን ከመስቀል አውርዶ ገነዘው፤ ከዐለት ተወቅሮ በተዘጋጀ መቃብር ውስጥ
አስቀመጠው። ትልቅ ድንጋይም አንከባሎ የመቃብሩን መግቢያ ዘጋ። 47 መግደላዊት ማርያምና የዮሳ እናት ማርያምምሰ ኢየሱስን የት እንዳኖሩት አዩ።

Mark 15:1

ማርቆስ **15**፡ **1-3**
አንተ አልክ "አንተ ራስህ መሰከርክ።"

Mark 15:4

ማርቆስ **15**፡ **4-5**

Mark 15:6

ማርቆስ **15**፡ **6-8**

Mark 15:9

ማርቆስ **15**፡ **9-11**
ማርቆስ 15፡ 9-11 ለቀቁት "እንዲሄድ ፈቀዱለት" ወይም "ፈቱት"

Mark 15:12

ማርቆስ **15**፡ **12-13**
ማርቆስ 15፡ 12-13

Mark 15:14

ማርቆስ **15**፡ **14-15**
ኢየሱስን ገረፉት በልዩ መግረፊያ ኢየሱስን እንዲያመው አድርገው ገረፉት
አሳልፈው ሰጡት ይህንን በ MRK 15:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው
ተመልከት።

Mark 15:16

ማርቆስ **15**፡ **16-18**
የወታደሮች ካንፕ ይህ ወታደሮች የሞቆዩበት ሥፍራ ነው። ጭፍራ "በጣም
ብዙ" ወይም " ብዙ" ቀይ ልብስም አለበሱት፥ ይህ የመሳለቅ ምልክት ነው።
እንዲህ ዓይነት ቀለም ያለው ልብስ የነገስታት ልብስ ሲሆን ይህንን ዓይነት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ልብስ እርሱን በማልበስ “የአይሁድ ንጉሥ” በሚለው የኢየሱስ የማዕረግ ስሙ ላይ እየጠሳለቁ ነበር።" እንዲህ እያሉ ይሰግዱለትም ጀመር፣ “የአይሁድ ንጉሥ ሆይ፥ ሰላም ለአንተ ይሁን እያሉ እጅ ይነሱት ጀመር፤” እንደገና ወታደሮቹ ኢየሱስ የአይሁድ ንጉሥ መሆኑን ስላላመኑበት በኢየሱስ ላይ ይሳለለቁ ነበር።

Mark 15:19

ማርቆስ **15**፡ **19-21**

Mark 15:22

ማርቆስ **15**፡ **22-24**

Mark 15:25

ማርቆስ **15**፡ **25-28**
ወንበዴዎች "የታጠቁ ዘራፊዎች"

Mark 15:29

ማርቆስ **15**፡ **29-30**

Mark 15:31

ማርቆስ **15**፡ **31-32**

Mark 15:33

ማርቆስ **15**፡ **33-35**

Mark 15:36

ማርቆስ **15**፡ **36-38**
የሚቆመጥት ወይን "ኮምጣጤ" የቤተ መቅደሱ መጋረጃ ለሁለት ተቀደደ የቤተ መቅደሱን መጋረጃ እግዚአብሔር ሁለት ቦታ ቀደደው።

Mark 15:39

ማርቆስ **15**፡ **39-41**
የእግዚአብሔር ልጅ ይህ የኢየሱስ ወሳኝ የሆነ የማዕረግ ስም ነው። ሰሎሜ

Mark 15:42

ማርቆስ **15**፡ **42-44**

Mark 15:45

ማርቆስ **15**፡ **45-47**
መከፈኛ ጨርቅ ከጥጥ ተክል የተሠራ ልብስ (ይህንን በ14፡ 51-52 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት።) ኢየሱስ የተቀበረበት ሥፍራ "ዮሴፍ እና ሌሎች የኢየሱስን በድን የቀበሩበት ሥፍራ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **16**

1 ሰንበት ካለፈ በኋላም መጥተው ይቀቡት ዘንድ መግደላዊት ማርያም፣ የያዕቆብ እናት ማርያምና ሰሎሜ ሽቶ ገዙ። **2** ከሳምንቱም በመጀመሪያው ቀን ጎህ በቀደደ ጊዜ ወደ መቃብሩ መጡ። **3** እርስ በርሳቸውም ድንጋዩን ከመቃብሩ መግቢያ ማን ያንከባልልናል ይባባሉ ነበር። **4** አሻግረው ሲመለከቱም ድንጋዩ እጅግ ትልቅ ነበርና ተንከባሎ አዩት። **5** ወደ መቃብሩም ገብተው የሚያንጸባርቅ ነጭ ልብስ የለበሰ አንድ ወጣት በስተቀኝ ተቀምጦ አዩና ተገረሙ። **6** እርሱም አትገረሙ፣ የምትፈልጉት ተሰቅሎ የነበረውን የናዝሬቱን ኢየሱስን ነው። ያኖሩበትን ቦታ ተመልከቱ፤ እርሱ በዚህ የለም፣ ተነሥቷልና። **7** ነገር ግን ሂዱ፣ ለጴጥሮስና ለደቀመዛሙርቱም እንደነገራችሁ ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል፣ በዚያም ታዩታላችሁ ብላችሁ ንገሯቸው አላቸው። **8** እነርሱም መገረምና ፍርሃት ወድቆባቸው ነበርና ከዚያ ወጥተው ከመቃብሩ ሸሹ። ፈርተውም ነበርና ለማንም አንዳች አልተናገሩም። **9** ከሳምንቱም በመጀመሪያው ቀን በማለዳ በተነሳ ጊዜ ሰባት አጋንንት አውጥቶላት ለነበረችው ለመግደላዊት ማርያም አስቀድሞ ታያት። **10** እርሷም ከኢየሱስ ጋር የነበሩት እያዘኑና እያለቀሱ ሳሉ ሄዳ ነገረቻቸው። **11** እነርሱም ሕያው እንደሆነና ለእርሷም እንደታያት በሰሙ ጊዜ አላመኑም። **12** ከእነዚህ ነገሮች በኋላም ከእነርሱ ሁለቱ ወደ ገጠር በመሄድ ላይ ሳሉ ኢየሱስ በሌላ ሰው መልክ ተገለጠላቸው። **13** እነርሱም ሄደው ለተቀሩት ነገሯቸው፤ እነርሱንም አላመኗቸውም። **14** ከዚያም በማዕድ ተቀምጠው ሳሉ ለአሥራ አንዱ ለራሳቸው ኢየሱስ ተገለጠላቸውና ስለ ልባቸው ጥንካሬና ከትንሳኤው በኋላ ያዩትን ስላላመኗቸው ወቀሳቸው። **15** እንዲህም አላቸው፣ ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፣ ወንጌልንም ለፍጥረት በሙሉ ስበኩ አላቸው። **16** ያመነና የተጠመቀም ይድናል፣ ያላመነ ግን ይፈረድበታል። **17** ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፣ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፣ **18** እባቦችን ይይዛሉ፣ የሚገድል ነገር እንኳን ቢጠጡ አይጎዳቸውም፣ እጆቻቸውን በህሙማን ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይፈወሳሉ። **19** ጌታ ኢየሱስ ይህንን ካላቸው በኋላ ወደ ሰማይ ወጥቶም በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ። **20** እነርሱም ወጥተው በየቦታው ሰበኩ። ጌታም ቃሉን ተከትለው በሚመጡ ምልክቶች እያጸና ከእነርሱ ጋር ይሠራ ነበር። አሜን።

Mark 16:1

ማርቆስ **16**፡ **1-2**
ቆንጆ ሽታ የሚሸት "ጥሩ መዓዛ ያለው"

Mark 16:3

ማርቆስ **16**፡ **3-4**

Mark 16:5

ማርቆስ **16**፡ **5-7**
ተነስቷል! "እርሱ ተነስቷል" ወይም "እግዚአብሔር ከሞት አስነስቶታል!" ወይም "ከሞት በራሱ ተነስቷል!"

Mark 16:8

ማርቆስ **16**፡ **8-8**

Mark 16:9

ማርቆስ **16**:**9-11**
በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን "በሰንበት"

Mark 16:12

ማርቆስ **16**፡ **12-13**

Mark 16:14

ማርቆስ **16**፡ **14-16**
የልብ ድንዳኔ አማራጭ ትርጉም፡ "ለማመን አለመፈለግ"

Mark 16:17

ማርቆስ **16**፡ **17-18**
ማርቆስ 16፡ 17-18

Mark 16:19

ማርቆስ **16**፡ **19-20**
No text

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Luke

Luke

ምዕራፍ 1

1 ብዙዎች በእኛ ዘንድ ስለተፈጸሙት ጉዳዮች ታሪኩን በቅደም ተከተል ለማስቀመጥ ሞክረዋል፣ 2 ይህም የዓይን ምስክሮችና የቃሉ አገልጋዮች የሆኑት
በመጀመሪያ ለእኛ ባስተላለፉልን መሠረት ነበር። 3 ስለሆነም፣ እጅግ የተከበርክ ቴዎፍሎስ ሆይ፣ እኔም የእነዚህን ነገሮች ሂደት ከመጀመሪያው በትክክል
ከመረመርኩ በኋላ፣ በቅደም ተከተላቸው መጻፍ መልካም መስሎ ታየኝ። 4 ይህንንም ያደረግሁት ስለ ተማርኸው ነገር እውነቱን ታውቅ ዘንድ ነው። 5 በይሁዳ
ገዢ፣ በሄሮድስ ዘመን ከአብያ ክፍል የሆነ ዘካርያስ የሚባል አንድ ካህን ነበረ። ሚስቱም ከአሮን ልጆች የነበረችና ስሟም ኤልሳቤጥ የሚባል ነበር። 6 ሁለቱም
በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ፣ የእግዚአብሔርን ሕግጋትና ትእዛዛት ሁሉ ያለ ነቀፋ እየጠበቁ ይኖሩ ነበር። 7 ነገር ግን ኤልሳቤጥ መካን ስለነበረች ልጅ
አልነበራቸውም፣ በዚህ ጊዜ ደግሞ ሁለቱም አርጅተው ነበር። 8 በዚህን ጊዜ፣ ዘካርያስ በክፍሉ ተራ የክህነት አገልግሎቱን እየፈጸመ በእግዚአብሔር ፊት
የሚሆንበት ጊዜ ደረሰ። 9 የትኛው ካህን እንደሚያገለግል ለመምረጥ በሚፈጸመው ልምድ መሠረት፣ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ገብቶ ዕጣን ዕጣ ደረሰው።
10 እርሱ ዕጣን በሚያጥንበት ወቅት፣ ሕዝቡ ሁሉ በውጭ ይጸልይ ነበር። 11 በዚህን ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ ተገለጠለትና በዕጣኑ መሠዊያ በስተቀኝ
ቆመ። 12 ዘካርያስ በተመለከተው ጊዜ ደነገጠ፣ ፍርሃትም በእርሱ ላይ ወደቀ። 13 ነገር ግን መልአኩ፣ “ጸሎትህ ተሰምቶአልና ዘካርያስ ሆይ፣ አትፍራ።
ሚስትህ ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች፤ ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ። 14 ሐሴትና ደስታ ይሆንልሃል፣ ብዙዎችም በእርሱ መወለድ ሐሴት ያደርጋሉ። 15
በእግዚአብሔር ፊት ታላቅ ይሆናልና፣ ወይን ጠጅ ወይም የሚያሰክር መጠጥ አይጠጣም፤ ከእናቱ ማሕፀን ጀምሮም በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ይሆናል። 16
ከእስራኤል ሕዝብም ብዙዎቹ ወደ ጌታ ወደ አምላካቸው ይመለሳሉ። 17 በእግዚአብሔርም ፊት በኤልያስ መንፈስና ኃይል ይመላለሳል። ይህንንም
የሚያደርገው የማይታዘዙት በጻድቃን ጥበብ ይሄዱ ዘንድ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች ለመመለስና የተዘጋጁትን ሕዝብ ለእግዚአብሔር ያዘጋጅ ዘንድ ነው”
አለው። 18 ዘካርያስም፣ “እኔ ያረጀሁ በመሆኔና ሚስቴም ዕድሜዋ የገፋ በመሆኑ፣ ይህንን እንዴት ማወቅ እችላለሁ?” አለ፤ 19 መልአኩም፣ “እኔ
በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ፤ ይህንን የምሥራች እነግርህ ዘንድ ተልኬያለሁ። 20 እነሆ፣ እነዚህ ነገሮች እስኪፈጸሙ ድረስ ጸጥ ትላለህ፣
መናገርም አትችልም። ይህም የሚሆነው በትክክለኛው ጊዜ የሚፈጸመውን ቃሌን ስላላመንክ ነው።” 21 በዚህን ጊዜ ሕዝቡ ዘካርያስን እየተጠባበቁ ነበር፣
ለረጅም ጊዜ በቤተ መቅደስ በመቆየቱም ተደነቁ። 22 በወጣ ጊዜ ግን ሊያነጋግራቸው አልቻለም፤ እነርሱም በቤተ መቅደስ በነበረበት ጊዜ ራእይ እንደ
ተገለጠለት ተገነዘቡ። ለእነርሱ ምልክት ብቻ እየሰጣቸው ጸጥ ብሎ ቆየ። 23 የአገልግሎቱም ወቅት እንዳበቃ ወደ ቤቱ ለመመለስ ተነሣ። 24 ከዚህም ወቅት
በኋላ ሚስቱ ኤልሳቤጥ ፀነሰች፤ ለአምስት ወራትም ራሷን ሰወረች፣ እንደዚህም አለች፣ 25 “በሕዝብ ዘንድ የነበረብኝን ነቀፌታ ለማስወገድ ብሎ በሞገስ
ተመልክቶኝ እግዚአብሔር ለእኔ ያደረገልኝ ይህንን ነው።” 26 ስድስት ወሯ በነበረ ጊዜ መልአኩ ገብርኤል ናዝሬት ወደተባለች የገሊላ ከተማ ተላከ። 27
የተላከውም ዮሴፍ ለተባለ ከዳዊት ነገድ ለሆነ ሰው ወደ ታጨች አንዲት ድንግል ነበር። የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበር። 28 ወደ እርሷም መጣና እንደዚህ
አላት፣ “እጅግ የተከበርሽ ሆይ፣ ሰላም ለአንቺ ይሁን! እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው።” 29 እርሷ ግን በንግግሩ በጣም ግራ ተጋባች፣ ምን ዓይነት ሰላምታ
ሊሆን እንደሚችልም በማሰብ ተደነቀች። 30 መልአኩም፣ “ማርያም ሆይ፤ አትፍሪ፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ አግኝተሻል፤ 31 እነሆ፣ ፅንስ በማሕፀንሽ
ውስጥ ይፀነሳል፣ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ። ስሙንም ‘ኢየሱስ’ ትይዋለሽ። 32 እርሱም ታላቅ ይሆናል፣ የልዑልም ልጅ ይባላል። እግዚአብሔር አምላክም
የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል። 33 በያዕቆብም ቤት ላይ ለዘላለም ይነግሣል፣ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም።" 34 ማርያምም ለመልአኩ፣ “ከማንም
ወንድ ጋር ተኝቼ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል?” አለችው። 35 መልአኩም እንደዚህ በማለት መለሰላት፣ “መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፣ የልዑል
ኃይልም በአንቺ ላይ ያርፋል፤ ከዚህ የተነሣም የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል። 36 እነሆ፣ ዘመድሽም ኤልሳቤጥ በእርጅናዋ ወንድ ልጅ
ፀንሳለች፤ መካን ትባል ለነበረችው ለእርሷ ይህ ስድስተኛ ወሯ ነው። 37 ለእግዚአብሔር የሚሳነው ምንም ነገር የለምና።” 38 ማርያምም፣ “እነሆ፣
የእግዚአብሔር ባሪያው ነኝ፤ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ።” ከዚያ በኋላም መልአኩ ትቷት ሄደ። 39 ከዚያ በኋላ፣ ማርያም ተነሥታ በእነዚያ ቀናት በኮረብታማው አገር
በይሁዳ ወዳለች ወደ አንዲት ከተማ በፍጥነት ሄደች። 40 ወደ ዘካርያስም ቤት ሄደችና ለኤልሳቤጥ ሰላምታ አቀረበችላት። 41 ኤልሳቤጥም የማርያምን
ሰላምታ በሰማች ጊዜ፣ እንደዚህ ሆነ፣ በማሕፀኗ ያለው ፅንስ ዘለለ፣ ኤልሳቤጥም በመንፈስ ቅዱስ ተሞላች። 42 ድምፅዋን ከፍ በማድረግ ጮክ ብላ፣
“ከሴቶች መካከል አንቺ የተባረክሽ ነሽ፣ የማሕፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው። 43 የጌታዬ እናት ወደ እኔ እንድትመጣ ይህ ለምን ሆነ? 44 እነሆ፣ የሰላምታሽ
ድምፅ ወደ ጆሮዬ በመጣ ጊዜ በማሕፀኔ ውስጥ ያለው ሕፃን በደስታ ዘለለ። 45 ከጌታ የተነገሩላት ነገሮች እንደሚፈጸሙ የምታምን እነሆ እርሷ የተባረከች
ናት።” 46 ከጌታ የተነገሩላት ነገሮች እንደሚፈጸሙ የምታምን እነሆ እርሷ የተባረከች ናት።” 46. ማርያምም፣ “ነፍሴ እግዚአብሔርን ታመሰግናለች፣ 47
መንፈሴም በመድኃኒቴ በእግዚአብሔር ሐሴት ታደርጋለች። 48 የሴት ባሪያውን ውርደት ተመልክቶአልና። እነሆ፣ ከዚህ በኋላ ትውልድ ሁሉ የተባረከች ይሉኛል።
49 ብርቱ የሆነ እርሱ ለእኔ ታላቅ ነገር አድርጎልኛልና፣ ስሙም ቅዱስ ነው። 50 ለሚያከብሩት ምሕረቱ ከትውልድ እስከ ትውልድ ነው። 51 በክንዱ ብርታትን
ገልጾአል፣ ስለ ልባቸው ሐሳብ የሚታበዩትን በትኖአቸዋል። 52 ገዢዎችን ከዙፋናቸው አውርዷቸዋል፣ ዝቅ ያሉትንም ከፍ አድርጓቸዋል። 53 የተራቡትን
በመልካም ነገር አጥግቧቸዋል፣ ባለጠጎችን ግን ባዶአቸውን ሰድዷቸዋል። 54 ምሕረት ማድረጉን ያስታውስ ዘንድ ለባሪያው ለእስራኤል ረድኤቱን ልኮለታል፣ 55
ይህንንም ያደረገው (ለአባቶቻችን እንደተናገረው) ለአብርሃምና ለዘሩ ለዘላለም።” 56 ማርያም ከኤልሳቤጥ ጋር ሦስት ወራት ያህል ተቀመጠች፣ ከዚያ በኋላም
ወደ ቤቷ ተመለሰች። 57 በዚያን ጊዜ ኤልሳቤጥ የምትወልድበት ወቅት ደረሰ፣ ወንድ ልጅም ወለደች። 58 ጎረቤቶቿና ዘመዶቿ እግዚአብሔር ምሕረቱን
እንዳበዛላት ሰሙ፣ ከእርሷም ጋር ደስ አላቸው። 59 ልጁን የሚገርዙበት ስምንተኛው ቀን በመጣ ጊዜ፣ በአባቱ ስም ዘካርያስ ብለው ሊሰይሙት ፈልገው ነበር።
60 እናትዬዋ ግን መልስ ሰጠቻቸው፣ “አይሆንም፣ ስሙ ዮሐንስ ይሆናል” አለች። 61 እነርሱም ለእርሷ፣ “ከዘመዶችሽ መካከል በዚህ ስም የተጠራ የለም”
አሏት። 62 በምን ስም እንዲጠራ እንደሚፈልግ አባቱን በምልክት ጠየቁት። 63 አባቱም ሰሌዳ እንዲያቀርቡለት ጠየቀና፣ “ስሙ ዮሐንስ ነው” ብሎ ጻፈ።
በዚህም ሁሉም ተደነቁ፡ 64 ወዲያውኑም አንደበቱ ተከፈተ፣ ምላሱም ተፈትቶ ተናገረ፣ እግዚአብሔርንም አመሰገነ። 65 በዙሪያቸውም በሚኖሩት ሰዎች ዘንድ
ፍርሃት መጣባቸው፣ የእነዚህም ነገሮች ዜና በኮረብታማው በይሁዳ አገር ሁሉ ተሠራጨ። 66 ዜናውን የሰሙትም ሁሉ፣ የእግዚአብሔር እጅ ከእርሱ ጋር ነበርና
“እንግዲህ ይህ ልጅ ምን ሊሆን ይሆን?” እያሉ ነገሩን በልባቸው ጠበቁት። 67 አባቱም ዘካርያስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ፣ 68 “የእስራኤል አምላክ፣

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን፣ የመቤዠት ሥራ በመሥራት ሕዝቡን ረድቶታልና። **69** ከባሪያው ከዳዊት ዝርያዎች መካከል ለባሪያው ለዳዊት ቤት የድነት ቀንድ አስነሥቶልናል። **70** ይህም በጥንት ዘመን በነበሩት በቅዱሳን ነቢያቱ እንደ ተናገረው ነው። **71** ከጠላቶቻችንና ከሚጠሉን ሁሉ ያድነናል። **72** ይህንን የሚያደርገው ለአባቶቻችን ምሕረቱን ለማሳየትና ቅዱስ ኪዳኑን፣ **73** ማለትም ለአባታችን ለአብርሃም የማለውን መሐላ ለማስታወስ ነው። **74** መሐላውን የማለውም እኛ ከጠላቶቻችን ድነን በዘመኖቻችን ሁሉ በእርሱ ፊት በመሆን ያለ ፍርሃት፣ **75** በቅድስናና በጽድቅ እርሱን እንድናገለግለው ነው። **76** አዎን፣ አንተም ሕፃን የእርሱን መንገድን ለማዘጋጀት በጌታ ፊት ስለምትሄድና ሕዝብንም ለመምጣቱ ስለምታሰናዳ የልዑል ነቢይ ትባላለህ። **77** ለኃጢአቶቻቸው ይቅርታ የሚያገኙትን የድነት ዕውቀት ለሕዝቡ ትሰጣለህ። **78** ይህም ከእግዚአብሔር አምላካችን መልካም ምሕረት የተነሣ ከእርሱ የተነሣ የፀሐይ ብርሃን በእኛ ላይ እንዲያርፍብንና **79** በጨለማና በሞት ጥላ ላሉት እናበራላቸው ዘንድ ነው። ይህንንም እግሮቻችንን በሰላም መንገድ ይመራው ዘንድ ያደርገዋል።” **80** ልጁም አደገ፣ በመንፈሱም ጠነከረ፣ ለእስራኤልም እስኪገለጥ ድረስ በምድረ በዳ ኖረ።

Luke 1:1

አጠቃላይ መረጃ፦
ሉቃስ ለምን ወደ ቴዎፍሎስ እንደሚጽፍ ያብራራል።

በእኛ ዘንድ ስለተፈጸሙት ነገሮች
“በእኛ መካከል ስለተፈጸሙት ነገሮች” ወይም “በእኛ መካከል ተከስተው ሰለነበሩት ነገሮች”

በእኛ ዘንድ
ቴዎፍሎስ ማን እንደነበር በእርግጠኝነት የሚያውቅ ሰው የለም። ቴዎፍሎስ ክርስቲያን የነበረ ከሆነ ግን “እኛ” የሚለው ገላጭ እርሱንም ያካትት የነበረ ይሆናል፣ ካልሆነ ግን እርሱን የሚያካትት አይሆንም። (አካታች “እኛ” እና አግላይ እና አካታች “እኛ” የሚለውን ይመልከቱ)

የቃሉ አገልጋዮችና የዓይን እማኞች የነበሩ
“የዓይን እማኝ” ማለት አንድ ነገር ሲከሰት በዓይኑ የተመለከተ ማለት ነው፣ አገልጋይ ማለት ደግሞ የእግዚአብሔርን መልዕክት ለሰዎች በመናገር እግዚአብሔርን የሚያገለግል ሰው ነው። እንዴት የቃሉ አገልጋዮች እንደተባሉ ግልጽ አድርጎ መናገር ያስፈልጋል። አማራጭ ትርጉም፦ “የተከሰተውን የተመለከቱና መልዕክቱን በመናገር እግዚአብሔርን ያገለገሉ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የቃሉ አገልጋዮች
“ቃሉ” የሚለው ቃል የሚወክለው ከብዙ ቃላት የተገነባ አንድን መልዕክት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የመልዕክቱ አገልጋዮች” ወይም “የእግዚአብሔር መልዕክት አገልጋዮች” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

በትክክል አጥንቼ
“ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ የተመረመረ።” ሉቃስ በትክክል ምን እንደተከሰተ ለማወቅ በጥንቃቄ ምርምር አድርጓል። እርሱ ሰለተከሰቱት ነገሮች የጻፋቸው ነገሮች ትክክል መሆናቸውን ለማረጋገጥ ድርጊቱን በዓይናቸው ከተመለከቱ ከተለያዩ ሰዎች ጋር በመነጋገር የድርጊቶቹን እርግጠኝነት እንዳረጋገጠ ይገመታል።

የከበርክ ቴዎፍሎስ
ሉቃስ ይህንን ያለው ለቴዎፍሎስ የነበረውን ክብርና አክብሮት ለማሳየት ፈልጎ ነው። ይህ ክፍል በባህላችሁ የተከበሩ ሰዎች የሚሰጣቸውን ስያሜ በመቀየር መጻፍ ይቻላል። አንዳንድ ሰዎች ሰላምታን በመጠቀም “ለቴዎፍሎስ” ወይም “የተወደድክ ቴዎፍሎስ” ብለው መጻፍን ይመርጣሉ።

የከበርክ
“የተከበርክ” ወይም “ክቡር”

ቴዎፍሎስ
የዚህ ሥም ትርጉም “የእግዚአብሔር ወዳጅ” ማለት ነው። ይህ ስም የዚህን ሰው ባሕርይ የሚገልጽ ስያሜ ሊሆን ይችላል፣ ወይም ትክክለኛው የዚህ ሰው መጠሪያም ሊሆን ይችላል። በርካታ ትርጉሞች እንደ መጠርያ ስም አድርገው ተርጉመውታል። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 1:5

አያያዥ ሀሳብ፦
መልዓኩ የዮሐንስን ውልደት ተነበየ

አጠቃላይ መረጃ፦
ዘካርያስ እና ኤልሳቤጥን ለመጀመርያ ጊዜ እናያቸዋለን። ቀጥሎ ያሉት ጥቅሶች ሰለ እነርሱ የጀርባ ታሪክ የበለጠ መረጃ ይነግሩናል። (የጀርባ ታሪክ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 1:8

እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ በታሪኩ ውስጥ ከተሰጠው የጀርባ ታሪክ መረጃ ወደ ሌላ ታሪክ ትኩረት እንደተቀየረ የሚያሳይ ሐረግ ነው።

ዘካርያስ በእግዚአብሔር ፊት የክህነት ስራውን እየሰራ ነበር
ይህ ዘካርያስ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውስጥ መሆኑን፣ የክህነት ስራዎቹም እግዚአብሔርን የማምለክ ስርዓት አካላት መሆናቸውን ያሳያል። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በክፍሉ ተራ
“የእርሱ ቡድን ተራ ሲሆን” ወይም “የእርሱ ቡድን የማገልገል ጊዜያቸው በደረሰ ጊዜ”

እንደ ካህናት ሥርዓት ... ዕጣን ለማጠን እጣ ደረሰበት
ይህ ዓረፍተ ነገር ስለ ካህናት ስራዎች መረጃን ይሰጣል። (የጀርባ ታሪክ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ስርዓት
“ባሕላዊው መንገድ” ወይም “ሁልጊዜ እንደሚያደርጉት”

እጣ ደረሰበት
ምልክት ያለበትን ድንጋይ ወደ መሬት በመጣል እንደ እጣ በማውጣት አንድን ነገር ለመወሰን እንዲረዳቸው ይጠቀሙ ነበር። ካህናቱ በሚያወጡት እጣ ውስጥ የትኛው ካህንን ለተለያዩ ስራዎች መምረጥ እንዳለባቸው እግዚአብሔር ምሪትን እንደሚሰጣቸው ያምኑ ነበር።

እጣን ለማጠን
ካህናቱ በየጠዋቱና በየማታው ጣፋጭ ሽታ ያለውን እጣን በመቅደሱ ውስጥ በሚገኝ መሰዊያ ላይ በማቃጠል ለእግዚአብሔር እንደ መስዋዕት ያቀርቡ ነበር።

ሕዝቡ ሁሉ
“ብዙ ቁጥር ያለው ሕዝብ” ወይም “ብዙ ሰዎች”

በውጪ
ቅጥር ግቢው ቤተ መቅደሱ ዙሪያ የሚገኝ የተከለለ ቦታ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ከቤተ መቅደሱ ሕንጻ ውጪ” ወይም “ከቤተ መቅደሱ ውጪ

ባለው ቅጥር ግቢ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 1:11

አያያዥ ሀሳብ፦
ዘካርያስ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ስራውን እያከናወነ እያለ የእግዚአብሔር መልዓክ መልዕክትን ሊሰጠው ይመጣል።

አሁን
ይህ ቃል በታሪክ ውስጥ ለሚከሰት ክስተት መጀመርያን ያሳያል።

ታየው
“በድንገት ወደ እርሱ መጣ” ወይም “በድንገት ከዘካርያስ ጋር ነበር” ይህ መልዓኩ በእርግጥም ከዘጋርያስ ጋር እንደነበርና ራዕይ እንዳልነበር ያሳያል።

ዘካርያስም ... ደነገጠ ... ፍርሃትም ወደቀበት
እነዚህ ሁለት ሐረጎች አንድ ዓይነት ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ፣ ዘካርያስ ምን ያህል እንደፈራ ያሳያሉ።

ዘካርያስ ባየው ጊዜ
“ዘካርያስ መልዓኩን ባየው ጊዜ” ዘካርያስ የፈራው የመልዓኩ መልክ አስፈሪ ስለነበር ነው። ዘካርያስ ክፉ የሆነ ነገር አልሰራም፣ ስለዚህ መልዓኩ ቅጣት ይጥልብኛል ብሎ አልፈራም።

ፍርሃት ወደቀበት
x

Luke 1:14

ታላቅ ይሆናል
“የዚህም ምክንያት ታላቅ ስለሚሆን ነው” ዘካርያስና “ብዙዎች” ደስ የሚላቸው ዮሐንስ “በእግዚአብሔር ፊት ታላቅ” ስለሚሆን ነው። ተከትሎ ያለው የቁጥር 15 ክፍል እግዚአብሔር ዮሐንስ እንዴት እንዲኖር እንደሚፈልግ ይናገራል።

ደስታና ተድላ ይሆንልሃል
“ደስታ” እና “ተድላ” የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ይህም ምን ያህል ደስታ እንደሚሆን ትኩረት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ታላቅ ደስታ ይሆንልሃል” ወይም “እጅግ ደስተኛ ትሆናለህ” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

በመወለዱም
“በመወለዱ ምክንያትም”

በእግዚአብሔር ፊት ታላቅ ይሆናል
“ለጌታ እጅግ ጠቃሚ ሰው ይሆናል” ወይም “እግዚአብሔር እርሱን እጅግ ጠቃሚ ሰው አድርጎ ያየዋል”

በመንፈስ ቅዱስ ይሞላል
ይህ በአድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “መንፈስ ቅዱስ ኃይልን ይሰጠዋል” ወይም “መንፈስ ቅዱስ ምሪትን ይሰጠዋል።” ይህ አርፍተ ነገር ክፉ መንፈስ ሰውን እንደሚያረገው አይነት እንዳይመስል ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በእናቱ ማሕጸን
“ገና በእናቱ ማሕጸን ውስጥ ሳለ” ወይም “ገና ሳይወለድ”

Luke 1:16

ብዙዎቹ የእስራኤል ሕዝቦች ወደ አምላካቸው እግዚአብሔር ይመለሳሉ
እዚህ ላይ “ይመለሳሉ” የሚለው ቃል አንድ ሰው ንስሃ ገብቶ እግዚአብሔርን ማምለክ መጀመርን የሚያመለክት ዘይቤ ነው። ይህም በአድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እርሱም ብዙዎች የእስራኤል ሕዝቦችን ንስሐ እንዲገቡና አምላካቸው እግዚአብሔርን እንዲያመለኩ ያደርጋል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በአምላክ ፊት ይሄዳል
ጌታ ከመምጣቱ በፊት፣ ጌታ እንደሚመጣ ለሰዎች ይሰብካል።

በጌታ ፊት
እዚህ ላይ “ፊት” የሚለው ቃል የአንድን ሰው ሕልውና የሚያሳይ ፈሊጥ ነው። በአንዳንድ ትርጉሞች ላይ ተጽፎ ላይገኝ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ጌታ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

በኤልያስ መንፈስና ኃይል
“ኤልያስ በነበረው መንፈስና ኃይል።” “መንፈስ“ የሚለው የእግዚአብሔርን መንፈስ ወይም ኤልያስ የነበረውን አስተሳሰብ ሊያሳይ ይችላል። “መንፈስ” የሚለው ቃል የሞትን ወይም የክፉን መንፈስ በሚለው እንዳይተረጎም ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች ይመልስ ዘንድ
“አባቶች ስለ ልጆቻቸው እንዲያስቡ ደግሞ ጠየቃቸው” ወይም “አባቶች ከልጆቻቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት ያድሱ ዘንድ”

ልባቸውን ይመልሳል
እዚህ ላይ ልብ አቅጣጫውን እንደሚቀይር ነገር ተደርጎ ተቀምጧል። ይህ የአንድ ሰው አስተሳሰብን ስለመቀየር ያመለክታል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የማይታዘዙትንም ወደ ጻድቃን ጥበብ
“የማይታዘዙትን ወደ ጻድቃን ጥበብ ለመመለስ” ወይም “የማይታዘዙት ጠቢብ እንዲሆኑና የጻድቅ ሰዎችን ተግባር እንዲፈጽሙ ለማሳመን”

የማይታዘዙት
ይህ የሚያሳየው ጌታን የማይታዘዙትን ሰዎች ነው።

ለጌታ የተዘጋጁትን ሕዝብ እንዲያሰናዳ
ሕዝቡ ምን ለማድረግ እንደሚዘጋጁ በግልጽ ማሳየት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “መልዕክቱን ለማመን የተዘጋጁ ሕዝቦችን ለጌታ ማሰናዳት” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 1:18

ይህን በምን አውቃለሁ?
“የተናገርኸው ነገር እንደሚፈጸም በእርግጠኝነት ማወቅ የምችለው እንዴት ነው?” እዚህ ላይ “ማወቅ” የሚለው ቃል በልምድ መማር ማለት ነው፣ ይህን ሃሳብ ያነሳው ዘካርያስ እንደ ማረጋገጫ ምልክት ጠይቆ ስለነበር ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ይህ ነገር እንደሚፈጸም ለእኔ ለማረጋገጥ ምን ልታደርግ ትችላለህ”

እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ
ይህ ለዘካርያስ እንደ ተግሳጽ ተደርጎ ተጽፏል። ከእግዚአብሔር ቀጥታ የመጣው የገብርኤል መገኘት ብቻ ለዘካርያስ በቂ ማረጋገጫ መሆን ነበረበት።

የምቆመው
x

Luke 1:21

አሁን
ይህ በታሪኩ ውስጥ ቤተ መቅደስ ውስጥ ከተከሰተው ነገር ከቤተ መቅደስ ውጪ ወደተከሰተው ነገር ትኩረቱ መቀየሩን ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይህ እየተከሰተ በነበረ ጊዜ” ወይም “መልዓኩና ዘካርያስ እየተነጋገሩ በነበረ ጊዜ”

በቤተ መቅደስ ውስጥ ራዕይ እንዳየ ተገነዘቡ። እርሱም ምልክቶችን ያሳያቸው ነበር፣ ዲዳም ሆኖ ቆየ
እነዚህ ነገሮች በተመሳሳይ ሰዓት የተከሰቱ እንደሆን ይገመታል፣ የዘካርያስ ምልክቶችም ሕዝቡ እርሱ ራዕይን እንዳይ እንዲገነዘቡ አድርገዋቸዋል። የነዚህን ቅደም ተከተል መቀየር አድማጩ የበለጠ መረዳት እንዲኖረው ሊያደርግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ዘካርያስ ምልክቶችን ያሳያቸው ነበር ዲዳም ሆኖ ኖረ። ስለዚህ በቤተ መቅደስ ውስጥ ሳለ ራዕይን እንደተመለከተ ሕዝቡ ተገነዘበ”

ራዕይ
ቀድሞ የተሰጠው መግለጫ ገብርኤል በእርግጥም ወደ ዘካርያስ ወደ ቤተ መቅደሱ እንደመጣ ያሳያል። ሕዝቡ ይህንን ባለማወቅ ዘካርያስ ራዕይ እንደተመለከተ አሰቡ።

Luke 1:24

ከነዚህም ቀናት በኋላ
“እነዚህ ቀናት” የሚለው ሐረግ ዘካርያስ በቤተመቅደስ ውስጥ ያገለገለባቸውን ቀናት ያመለክታል። ይህ ምንን እንደሚያመለክት የበለጠ ግልጽ አድርጎ ማስረዳት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ዘካርያስ በቤተመቅደስ ካገለገለበት ጊዜ በኋላ” (የአዲስ ሁነት መግቢያ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሚስቱ
“የዘካርያስ ሚስት”

ራሷን ደበቀች
“ከቤት አልወጣችም” ወይም “ ብቻዋን ቆየች”

ጌታ እንዲህ አድርጎልኛል
ይህ ጌታ ልጅ ማርገዝ እንድትችል እንዳስቻላት ያሳያል።

እንዲህ አድርጎልኛል
ይህ አዎንታዊ የሆነ ግነት ነው። ጌታ ባደረገላት ነገር በጣም ደስተኛ ናት።

በቸርነቱ ተመልክቶኛል
እዚህ ላይ “መመልከት” የሚለው ፈሊጥ ፈሊጥ ሲሆን ትርጉሙም “መንከባከብ” ወይም “በሚገባ መያዝ“ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በርህራሄ ተመለከተኝ” ወይም “አዘነልኝ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ነቀፌታዬን
ይህ እርሷ ልጆች ባለመውለዷ ይሰማት የነበረውን ነቀፋ ያሳያል።

Luke 1:30

ማርያም ሆይ አትፍሪ
መልዓኩ ማርያም እርሱን አይታ እንድትፈራ አይፈልግም ምክንያቱም እግዚአብሔር መልካም መልዕክትን እንዲያደርስ ስለላከው ነው።

በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን አግኝተሻል
“ሞገስን ማግኘት” የሚለው ፈሊጥ በአንድ ሰው ዘንድ መልካም ተቀባይነትን ማግኘት ነው። የአርፍተ ነገሩን ቅደም ተከተል በመቀየር እግዚአብሔርን የድርጊቱ ባለቤት አድርጎ ማሳየት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ጸጋውን ሊሰጥሽ ወስኗል” ወይም “እግዚአብሔር ቸርነቱን ላንቺ እያሳየ ነው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ትጸንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ... ኢየሱስ ... የልዑል ልጅ
ማርያም “ወንድ ልጅን” ትወልዳልች ስሙም “የልዑል ልጅ” ይባላል። ስለዚህ ኢየሱስ ከሰው እናት የተወለደ የሰው ልጅ ነው፣ እርሱ የእግዚአብሔርም ልጅ ነው። እነዚህ ቃላት በጥንቃቄ መተርጎም አለባቸው።

ይባላል
የዚህ ትርጉሞች ሊሆኑ የሚችሉት 1) “ሰዎች ... ብለው ይጠሩታል” 2) “እግዚአብሔር ... ይጠራዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የልዑል ልጅ
ይህ የእግዚአብሔር ልጅ ለሆነው ለኢየሱስ እጅግ ወሳኝ የሆነ ስያሜ ነው። (ልጅ እና አባትን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል
ዙፋን የሚየያሳየው የንጉስን የመግዛት ስልጣን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አባቱ ዳዊት ይገዛ እንደነበር እርሱም እንዲገዛ ስልጣንን ይሰጠዋል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ለመንግሥቱም መጨረሻ አይኖርም
“መጨረሻ አይኖርም” የሚለው አሉታዊ መግለጫ ለዘላለም የሚቀጥል መሆኑን አጽንኦት ይሰጣል። አርፍተ ነገሩ በአዎንታዊ ሐረግ መገለጽ ይችላል። “መንግስቱ እስከመጨረሻ አያበቃም” አማራጭ ትርጉም፡- (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 1:34

ይህ እንዴት ይሆናል
ምንም እንኳ ማርያም ነገሩ እንዴት እንደሚከሰት ባይገባትም፣ መከሰቱን ግን አልተጠራጠረችም።

ከማንም ጋር ተኝቼ አላውቅም
ማርያም ይህንን ትህትና የተሞላበት አገላለጽ የተጠቀመችው እርሷ ከማንም ጋር ወሲባዊ ግንኙነት ፈጽማ እንደማታውቅ ለመግለጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ድንግል ነኝ” (ለስላሴ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይሆናል
የማርያም እርግዝና የሚጀምረው መንፈስ ቅዱስ ወደ እርሷ በመምጣት ነው።

በአንቺ ላይ ይሆናል
“ይቆጣጠርሻል”

የልዑልም ኃይል
ማርያም ድንግል እያለች ከተፈጥሮ በላይ በሆነ ሁኔታ እንድታረግዝ የሚያደርጋት የእግዚአብሔር “ኃይል” ነበር።ይህ አካላዊ ወይም ወሲባዊ ትርጉም ያለው እንዳይመስል ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፣ ይህ ተዓምር ነበር።

በአንቺ ላይ ይሆናል
“እንደ ጥላ ይከልልሻል”

የሚወለደውም ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል
ይህ በአድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሚወለደውንም ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ብለው ይጠሩታል” ወይም “የሚወለደውም ሕጻን ቅዱስ ይሆናል፣ ሰዎችም የእግዚአብሔር ልጅ ብለው ይጠሩታል። (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ቅዱሱ
“ቅዱሱ ልጅ” ወይም “ቅዱሱ ሕጻን”

የእግዚአብሔር ልጅ
ይህ ለኢየሱስ የተሰጠ ልዩ መጠርያ ማዕረግ ነው። (ልጅ እና አባትን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 1:36

ዘመድሽን ተመልከች
“ትኩረት ስጪ፣ ምክንያቱም አሁን የምነገርሽ ነገር እውነትና እጅግ ጠቃሚ ነው፣ ዘመድሽ”

Luke 1:39

አያያዥ ሀሳብ፦
ማርያም የሐንስን ልትወልድ የነበረችውን ዘመዷን ኤልሳቤጥን ለመጎብኘት ወደ እርሷ ሄደች። (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

ተነሳች
ይህ ፈሊጥ ከተቀመጠችበት ተነሳች የሚለውን ትርጉም ብቻ ሳይሆን፣ “ተዘጋጀች” የሚለውንም ትርጉም ይይዛል። አማራጭ ትርጉም፦ “ጀመረች” ወይም “ተዘጋጀች” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ተራራማው ሀገር
“በተራራ የተሞላው አካባቢ” ወይም “የእስራኤል ተራራማው ክፍል”

ሄደች
x

Luke 1:42

ድምጿን ከፍ አድርጋ ... በጩኸት ተናገረች
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ሲይዙ ኤልሳቤጥ ምን ያህል ደስተኛ እንደነበረች አጽንኦት ይሰጣሉ።ሁለቱን አደባልቆ አንድ ሐረግ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በአድናቆት ጮኸች” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ድምጿን ከፍ አደረገች
ይህ ፈሊጥ “ድምፁዋን አጩሃ ተናገረች” የሚለውን ትርጉም የያዘ ነው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ
“ከሴቶች መካከል” የሚለው ፈሊጥ “ከሌላ ሴት በሙሉ የተሻለች” የሚለውን ትርጉም ይይዛል። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

የማሕጸንሽ ፍሬ
የማርያም ልጅ እዚህ ላይ አንድ ተክል እንደሚያፈራው ፍሬ ተደርጎ ተጽፏል። አማራጭ ትርጉም፦ “በማሕጸንሽ ውስጥ ያለው ሕጻን” ወይም “የምታረግዥው ሕጻን” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ሆነልኝ?
ኤልሳቤጥ መልስ ፈልጋ ጥያቄን እየጠየቀች አይደለም። የጌታ እናት ወደ እርሷ በመምጣቷ ምን ያህል እንደተደነቀችና ደስተኛ እንደነበረች እያሳየች ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የጌታዬ እናት ወደ እኔ መምጣቷ እንዴት የሚደንቅ ነው!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የጌታዬ እናት
ኤልሳቤጥ ማርያምን “የጌታዬ እናት” ብላ እንደጠራቻት “አንቺ” የሚለውን መግለጫ በመጨመር የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አንቺ የጌታዬ እናት” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ
ይህ ኤልሳቤጥ ቀጥላ ለምትናገረው አስገራሚ ነገር ማርያም ትኩረት እንድትሰጥ የሚናገር ቃል ነው።

የሰላምታሽ ድምጽ ወደ ጆሮዬ በደረሰ ጊዜ
የአንድን ነገር ድምጽ መስማትን “ድምጹ ወደ ጆሮ ደረሰ” በማለት ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የሰላምታሽን ድምጽ በሰማሁ ጊዜ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በደስታ ዘለለ
“በድንገት በደስታ ተንቀሳቀሰ” ወይም “በጣም ከመደሰቱ የተነሳ በኃይል ዞረ”

ከጌታ የተነገራትን የምታምን የተባረከች ናት
ኤልሳቤጥ ለማርያም ስለ ራሷ ስለ ማርያም ነበር የምትነግራት። አማራጭ ትርጉም፦“ከጌታ የተነገረሽን የምታምኚ አንቺ የተባረክሽ ነሽ” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ወይም ሶስተኛ መደብ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የምታምን ... የተባረከች ናት
በተደራጊ ቅርጽ የተቀመጠው ግስ በአድራጊ ቅርጽ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ስላመነች እግዚአብሔር ይባርካታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የእነዚህ ነገሮች ፍጻሜ ይሆናልና
“እነዚህ ነገሮች በእርግጠኝነት ይፈጸማሉ” ወይም “እነዚህ ነገሮች እውን ይሆናሉ”

ከጌታ ለእርሷ የተነገሯት ነገሮች
መልእክቱን ሲናገር የሰማችው መልአኩ ገብርኤልን ነው (ሉቃስ 1:26 ይመልከቱ)፣ ነገር ግን መልእክቱ (“እነዚህ ነገሮች”) በዋነኛነት የመጣው ከጌታ ነበር። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ከጌታ የሰማችው መልእክት” ወይም “መልአኩ የነገራት የጌታ መልእክት” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 1:46

አጠቃላይ መረጃ፦
ማርያም ለአምላኳና ለአዳኟ የምስጋናን መዝሙር መዘመር ትጀምራለች።

ነፍሴ ታመሰግነዋለች ... መንፈሴም ሐሴት ታደርጋለች
ሁለቱም “ነፍስ” እና “መንፈስ” የአንድ ሰው መንፈሳዊ ማንነት አካላት ናቸው። ማርያም አምልኮዋ ከውስጥ የመነጨ እንደሆነ ለማሳየት እንደዚህ ብላለች። አማራጭ ትርጉም፦ “የውስጥ ማንነቴ ያምሰግናል ... ልቤም እጅግ ሐሴትን አድርጓል” ወይም “አመሰግናለሁ ... ሐሴትም አደርጋለሁ” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

በ ... ሐሴትን አድርጋለች
“በ ... እጅግ ደስታ ተሰምቷታል” ወይም “በ ... እጅግ ተደስታለች”

አዳኜ እግዚአብሔር
“እኔን ያዳነኝ እግዚአብሔር” ወይም “የሚያደነኝ እግዚአብሔር”

Luke 1:48

እርሱም
“ምክንያቱም እርሱ”

ተመልክቷል
“በእንክብካቤ ተመለከተ” ወይም “በጥንቃቄ”

በዝቅተኛ የኑሮ ሁኔታ
“ድህነት።” የማርያም ቤተሰብ ሃብታም አልነበረም።

እነሆም
ይህ ሐረግ ተከትሎ ለሚመጣው ንግግር ትኩረት እንዲሰጥ ያደርጋል።

ከአሁን በኋላ
“አሁንና ለወደፊቱ”

ትውልድ ሁሉ
“በእያንዳንዱ ትውልድ ያሉ ሕዝቦች በሙሉ”

ብርቱ የሆነው
“ኃይለኛው እግዚአብሔር”

ስሙም
እዚህ ላይ “ሰሙ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሙሉ የእግዚአብሔር ማንነትን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 1:50

ምህረቱ
“የእግዚአብሔር ምህረት”

ከትውልድ እስከ ትውልድ
“ከአንድ ትውልድ እስከ ቀጣይ ትውልድ” ወይም “በእያንዳንዱ ትውልድ ውስጥ” ወይም “በማንኛውም ጊዜ ላይ ለሚኖሩ ሕዝቦች”

በክንዱ ኃይልን አሳይቷል
x

Luke 1:52

ገዢዎችን ከዙፋናቸው አውርዷል
ዙፋን ማለት ገዢ የሚቀመጥበት ወንበር ነው፣ ወንበሩ የስልጣኑም ምልክት ነው። ገዢ ከዙፋኑ ከወረደ በኋላ ለገዛበት የሚችል ስልጣን የለውም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የገዢዎችን ስልጣን ወስዷል” ወይም “ገዢዎች መግዛትን እንዲያቆሙ አድርጓቸዋል” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

ዝቅ ያሉትንም ከፍ አደረጋቸው
በዚህ የቃላት መግለጫ መሰረት፣ ከፍተኛ ስፍራ ያላቸው ሰዎች ዝቅተኛ ስፍራ ካላቸው ይልቅ እጅግ ከፍ ያሉ እንደሆኑ ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፡- “ትሁት ሰዎችን ታላቅ አደረጋቸው” ወይም “ሌሎች ሰዎች ያላከበሯቸውን ሰዎች እርሱ አከበራቸው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዝቅ ያሉትን
“በድህነት ውስጥ ያሉትን።” ይህ በሉቃስ 1:48 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።

የተራቡትን መግቧል ... ባለጠጎችንም ባዶ እጃቸውን ልኳቸዋል
በእነዚህ ተቃራኒ ድርጊቶች መካከል ያለው ልዩነት ከተቻለ በትርጉሙ ላይ ግልጽ ይደረግ።

የተራቡትን በመልካም ነገር አጠገበ
የዚህ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት 1) “ለተራቡት ጥሩ የሚበላ ምግብ ሰጣቸው” ወይም 2) “ለተቸገሩት መልካምን ነገር ሰጣቸው”

Luke 1:54

አጠቃላይ መረጃ፡-
ዩዲቢ የሚባለው ትርጉም ስለ እስራኤል የተቀመጠው መረጃ ሳይቀየር እንዲተላለፍ የእነዚህን ቁጥሮች ቅደም ተከተል በመቀያየር አንድ የመሸጋገርያ ቁጥር አድርጓቸዋል። (የጥቅስ ድልድዮች የሚለውን ይመልከቱ)

ረድቷል
x

Luke 1:56

አያያዥ ሀሳብ፡-
ኤልሳቤጥ ልጇን ትወልደዋለች ከዛም ዘካርያስ ለሕጻኑ ስም ያወጣለታል።

ወደ ቤቷ ተመለሰች
“ማርያም ወደ ቤቷ (ወደ ማርያም) ቤት ተመለሰች” ወይም “ማርያም ወደ ራሷ ቤት ተመለሰች”

አሁን
ይህ ቃል በታሪኩ ውስጥ ቀጣይ ክስተት መጀመሩን ይናገራል።

ልጇን ተገላገለች
“ልጇን ወለደች”

ጎረቤቶቿና እና ዘመዶቿ
“የኤልሳቤጥ ጎረቤቶችና ዘመዶች”

ታላቅ ምህረቱን እንዳሳያት
x

Luke 1:59

እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ እዚህ ላይ ዋናው የታሪክ መስመር ተቆርጦ ሌላ ታሪክ ሊነገር መጀመሩን ለማሳየት ጥቅም ላይ ውሏል። እዚህ ላይ ሉቃስ አዲስ ታሪክ መናገር ይጀምራል። (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

በስምንተኛው ቀን
እዚህ ላይ “ስምንተኛው ቀን” የሚለው ቃል ከሕጻኑ ውልደት በኋላ ያለውን ቀን ያሳያል ይህም ከመጀመርያው ቀን ጀምሮ ወይም ሕጻኑ ከተወለደበት ጀምሮ ተቆጥሮ ያለውን ቀን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በሕጻኑ ሕይወት በስምንተኛው ቀን” (ደረጃ የሚያሳይ ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

ሕጻኑን ሊገርዙት መጡ
ይህ ብዙ ጊዜ አንድ ሰው ልጁን በሚገርዝበት ጊዜ ወዳጆቹ በዚያ ተገኝተው ከቤተሰቡ ጋር ሆነው የሚያከብሩበት ስነ ስርዓት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ለሕጻኑ የግርዘት ሥርዓት መጡ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

... ብለው ሊጠሩት ነበር
“... ብለው ስም ሊያወጡለት ነበር” ወይም “... የሚል ስም ሊሰጡት ፈልገው ነበር”

በአባቱ ስም
“የአባቱን ስም”

በዚህ ስም
“በዚያ ስም” ወይም “በተመሳሳይ ስም”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Luke 1:64

አፉ ተከፈተ ... ምላሱም ተፈታ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ዘካርያስ በድንገት መናገር መቻሉን አጽንኦት ይሰጣሉ። (ፈሊጥ እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

አፉ ተከፈተ እና ምላሱም ተፈታ
እነዚህ ሐረጎች በአድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር አፉን ከፈተለት ምላሱንም ፈታለት” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ አካባቢ ይኖሩ በነበሩ ላይ ሁሉ ፍርሃት ሆነ
“ከዘካርያስ እና ኤልሳቤጥ አካባቢ ይኖሩ በነበሩ ላይ ሁሉ” ለምን ፈርተው እንደነበር ግልጽ ማድረግ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከእነርሱ አካባቢ ይኖሩ የነበሩት ሁሉ እግዚአብሔር ለዘካርያስ እንዲህ በማድረጉ በእግዚአብሔር እጅግ ተደነቁ“ (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ አካባቢ ይኖሩ በነበሩ ላይ
“ሁሉ” የሚለው ቃል ጅምላ ፍረጃ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ አካባቢ ይኖሩ የነበሩ” ወይም “በዚያ አካባቢ ይኖሩ የነበሩ ብዙ ሰዎች” (ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ ነገሮች መከሰታቸው በይሁዳ ተራራማው ከተማ ሁሉ ተዳረሰ
“እነዚህ ነገሮች መከሰታቸው ... ተዳረሰ” የሚለው ሐረግ ሰዎች ስለ እነርሱ ማውራታቸውን የሚያሳይ ዘይቤ ነው። ጥቅም ላይ የዋለው ተደራጊ ቅርጽ በአድራጊ ቅርጽ መቀየር ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህ ነገሮች በሙሉ በይሁዳ ተራራማው ከተማ ይኖሩ በነበሩ ሰዎች ይወሩ ነበር” ወይም “በይሁዳ ተራራማው ከተማ የሚገኙ ሕዝቦች ስለ እነዚህ ነገሮች ያወሩ ነበር” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰሟቸው ሁሉ
“ስለተከሰቱት ነገሮች የሰሙ በሙሉ”

በልባቸው አኖሯቸው
ስለ ተከሰቱ ነገሮች ነገር ደጋግሞ ማሰላሰልና ማሰብ ነገሮቹን በልብ ውስጥ በጥንቃቄ እንደማኖር ተደርጎ ይታሰባል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለ እነዚህ ነገሮች በጥንቃቄ ያስቡና ያሰላስሉ ነበር” ወይም “ስለ እነዚህ ክስተቶች ደጋግመው ያስቡ ነበር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እያሉ በልባቸው አኖሯቸው
“እየጠየቁ በልባቸው አኖሯቸው”

ይሄ ሕጻን ምን ይሆን ይሆን?
“ይህ ሕጻን አድጎ ምን ዓይነት ልዩ ሰው ይሆን ይሆን?” ይህ ጥያቄ ሰዎቹ ስለ ሕጻኑ በሰሙት ነገሮች ያደረባቸውን መገረም ለመግለጽ የተጠቀሙበት መንገድ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ይሄ ልጅ አድጎ ምን ዓይነት ልዩ ሰው ይሆን ይሆን?” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የጌታ እጅ ከእርሱ ጋር ነበር
“የአምላክ እጅ” የሚለው ሐረግ የአምላክን ኃይል ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “የአምላክ ኃይል ከእርሱ ጋር ነበር” ወይም “አምላክ በእርሱ ውስጥ በኃይል ይሰራ ነበር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 1:67

አያያዥ ሀሳብ፡-
ዘካርያስ በልጁ በዮሐንስ ላይ ምን እንደሚሆን ተናገረ።

አባቱ ዘካርያስ መንፈስ ቅዱስን ተሞለቶ ትነቢት ተናረ
ይህ በአድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “መንፈስ ቅዱስ አባቱን ዘካርያስን ሞላው፣ ዘካርያስም ትንቢት ተናገረ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

አባቱ
የዮሐንስ አባት

.... እያለ ትንቢትን ተናገረ
በራሳችሁ ቋንቋ ውስጥ ቀጥተኛ ጥቅሶቸን የማስተዋወቂያ የተለመዱ መንገዶችን አስብ። አማራጭ ትርጉም፡- “ትንቢትን ተናገረ እንዲህም አለ” ወይም “ትንቢትን ተናገረ፣ የተናገረውም እንዲህ ነው ... “ (ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ጥቅሶች የሚለውን ይመልከቱ)

.... እያለ ትንቢትን ተናገረ
በራሳችሁ ቋንቋ ውስጥ ቀጥተኛ ጥቅሶቸን የማስተዋወቂያ የተለመዱ መንገዶችን አስብ። አማራጭ ትርጉም፡- “ትንቢትን ተናገረ እንዲህም አለ” ወይም “ትንቢትን ተናገረ፣ የተናገረውም እንዲህ ነው ... “ (ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ጥቅሶች የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር
እዚህ ላይ “እስራኤል” የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። በእግዚአብሔር እና በእስራኤል መካከል ያለው ግንኙነት የበለጠ ቀጥተኝነት ባለው መልኩ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በእስራኤልን ላይ የሚገዛው አምላክ እግዚአብሔር” ወይም “እስራኤል የምታመልከው አምላክ እግዚአብሔር” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሕዝቡ
“የእግዚአብሔር ሕዝብ”

Luke 1:69

የመዳንን ቀንድ አስነስቶልናል
የአንድ እንስሳ ቀንድ ራስን የመከላከል አቅሙን የሚያመለክት ምሳሌ ነው። ማስነሳት ማለት ደግሞ ያልነበረን ማኖር ወይም አንድን ድርጊት መጀመርን ያሳይል። እዚህ ላይ መሲሑ እስራኤልን የማዳን ኃይል እንዳለው እንደ ቀንድ ምሳሌ ተደርጎ ተመስሏል። አማራጭ ትርጉም፡- “(እግዚአብሔር) እኛን የማዳን ኃይል ያለውን ሰው ሰጥቶናል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በአገልጋዩ በዳዊት ቤት
“የዳዊት ቤት” የሚወክለው ቤተሰቡን ነው በተለይም ደግሞ ዘሮቹን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በአገልጋዩ በዳዊት ቤተሰብ” ወይም “የአገልጋዩ ዳዊት ዘር የሆነ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እንደተናገረ
“እግዚአብሔር እንዳለው”

ድሮ በነበሩት በነብያቱ አፍ እንደተናገረው
እግዚአብሔር በነብያቱ አፍ ተናገረ የሚለው የሚያመለክተው እግዚአብሔር ነብያቱን እርሱ እንዲላቸው የፈለገውን እንዲናገሩ ማድረጉን ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፡- “ድሮ የኖሩትን ቅዱሳን ነብያቱን እንዲናገሩ ያደረጋቸውን” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ድሮ የኖሩትን ... ማዳኑ ከጠላቶቻችን ነው
“ማዳን” የሚለው ረቂቅ ቃል “መታደግ” እና “ማትረፍ” በሚሉት ግሶች ተለውጦ መገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ድሮ የኖሩትን .... እርሱም ከጠላቶቻችን ይታደገናል።” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ከሚጠሉን ... ከጠላቶቻችን
እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ይይዛሉ፣ የተደጋገሙትም ጠላቶቻቸው ምን ያህል ይቃወሟቸው እንደነበረ አጽንኦት ለመስጠት ነው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

እጅ
እጅ የሚለው ቃል አንድ ሰው ኃይሉን የሚለማመድበትን እጅ የሚወክል ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ኃይል” ወይም “ቁጥጥር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 1:72

ለ .... ምህረትን ማሳየት ...
“ለ ... መሃሪ መሆን” ወይም “ለ ... እንደ ምህረቱ ማድረግ”

አስታወሰ
እዚህ ላይ “አስታወሰ” የሚለው ቃል ቃለኪዳንን መጠበቅ ወይም አንድን ነገር መፈጸምን ያሳያል።

ቅዱስ ኪዳኑን፣ የተናገረውንም መሃላ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉምን ይይዛሉ። መደጋገማቸው እግዚብሔር ለአብርሃም የገባው ቃልኪዳን ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ያሳያል። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ሰጠን
“እኛ ... ማድረግ እንድንችል አደረገ”

ከጠላቶቻችን እጅም ነጻ ወጥተን እርሱን ያለ ፍርሃት እንድናገለግለው
ይህ በአድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ከጠላቶቻችን እጅ ካስመለጠን በኋላ ያለ ፍርሃት እርሱን እንድናገለግለው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ከጠላቶቻችን እጅ ወጥተን
x

Luke 1:76

አዎ፣ አንተ ደግሞ
ዘካርያስ ይህንን ሐረግ ቀጥታ ለልጁ መናገር መጀመሩን ለማሳየት ይጠቀማል። በራሳችሁ ቋንቋ ይህንን ንግግር ለመጀመር የሚሆን መንገድ መጠቀም ይቻላል።

አንተ ሕጻን ሆይ ነብይ ትባላለህ
ሰዎች እርሱ ነብይ እንደሆነ ይረዳሉ። ይህ በአድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰዎች አንተ ነብይ መሆንህን ያውቃሉ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የበላይ የሆነው
እነዚህ ቃላት እግዚአብሔርን ለመግለጽ የምንጠምባቸው ለስላሴ ዘይቤያዊ ቃላት ናቸው። አማራጭ ትርጉም፦ “የበላይ የሆነውን የሚያገለግል” ወይም “የበላይ ለሆነው ለእግዚአብሔር የሚናገር” (ለስላሴ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከጌታ ፊት ትሄዳለህ
ጌታ ከመምጣቱ በፊት እርሱ ሄዶ ጌታ ወደ እነርሱ እንደሚመጣ ይነግራቸዋል። ይህንን በሉቃስ 1:17.

በጌታ ፊት
የአንድ ሰው “ፊት” የዛን ሰው መገኘት ይወክላል። ብዙ ጊዜ በትርጉሞች ላይ ተጽፎ አይገኝም። አማራጭ ትርጉም፦ “ጌታ” ይህን በሉቃስ 1:17 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።. (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

መንገዱን ለማዘጋጀት
ይህ ዮሐንስ ሰዎች የጌታን መልዕክት እንዲሰሙና እንዲያምኑ ያዘጋጃቸዋል የሚለውን መልዕክት የያዘ ዘይቤ ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በኃጢአታቸው ምህረት ማግኘት ... የድነትን እውቀት ትሰጣለህ
“እውቀት ትሰጣለህ” የሚለው ሐረግ ማስተማር የሚለውን ትርጉም የያዘ ዘይቤ ነው። “ድነት” እና “ምህረት” የሚሉት ረቂቅ ቃላት “ማዳን” እና “ይቅር ማለት“ በሚሉት ቃላት ሊገለጹ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ለሰዎች በኃጢአታቸው ይቅር መባል መዳናቸውን ያስተምራል” ወይም “ለሰዎች እንዴት እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን ይቅር በማለት እንዳዳናቸው ያስተምራል” (ምትክ ስም እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 1:78

በአምላካችን ርህራሄና ምህረት
የእግዚአብሔር ምህረት ሰዎችን እንደሚረዳ መግለጽ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ምክንያቱም እግዚአብሔር ለእኛ ሩህሩህና መሃሪ ስለሆነ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከላይ የመጣ የጸሐይ ብርሃን .... እንዲያበራ
ብርሃን ብዙ ጊዜ የእውነት ምሳሌ ነው። እዚህ ላይ አዳኙ ለእኛ የሚሰጠው መንፈሳዊ እውነት ዓለምን ሁሉ በብርሃን የሚሞላ የጸሐይ ብርሃን ተደርጎ ተመስሏል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ማብራት
“እውቀት መስጠት” ወይም “መንፈሳዊ ብርሃንን መስጠት”

በጨለማ ለተቀመጡ
ጨለማ እዚህ ላይ የመንፈሳዊ እውነት እጦትን ወይም አለመገኘትን ይወክላል። እዚህ ላይ መንፈሳዊ እውነት የሌላቸው ሰዎች በጨለማ ውስጥ እንደተቀመጡ ተደርገው ተመስለዋል። አማራጭ ትርጉም፦ “እውነትን የማያውቁ ሕዝቦች” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጨለማ ... የሞት ጥላ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች አንድ ላይ በመሆን እግዚአብሔር ምህረቱን ለእነርሱ ከማድረጉ በፊት ሰዎች ላይ የነበረውን ጥልቅ ጨለማ አስከፊነት ይገልጻሉ። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

በሞት ጥላ
ጥላ ብዙ ጊዜ ሊመጣ ያለውን ነገር ይገልጻል። እዚህ ላይ እየመጣ ያለን ሞትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሊሞቱ ያሉ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

እግሮቻችንም በሰላም መንገድ ይመራል
እዚህ ላይ “መምራት” የሚለው ቃል ማስተማር ለሚለው ቃል ዘይቤ ነው፣ “የሰላም መንገድ” የሚለው ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር በሰላም መኖርን የሚወክል ዘይቤ ነው። “እግሮቻችንን” የሚለው ቃል የአንድን ሰው ሙሉ ማንነት የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ከእግዚአብሔር ጋር በሰላም መኖርን ያስተምረናል”(ተለዋጭ ዘይቤ እና ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 1:80

አጠቃላይ መረጃ፦
ይህ ዮሐንስ እያደገ ስለመጣባቸው አመታት ይናገራል።

አሁን
ይህ ቃል ዋናው የታሪክ መስመር መቋረጡን ያመለክታል። ሉቃስ ስለ ዮሐንስ ውልደት ከመናገር በፍጥነት ወጥቶ ዮሐንስ አድጎ ያደርግ ስለነበረው አገልግሎት ይናገራል።

በመንፈስ ጠነከረ
“በመንፈስ እየበሰለ መጣ” ወይም “ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት አጠነከረ”

በምድረ በዳ ነበር
“በምድረ በዳ ኖረ” ሉቃስ የሐንስ በምን እድሜ ላይ በምድረ በዳ መኖር እንደጀመረ አይናገርም።

እስከ ታየበት ቀን ድረስ
ይህ ከጊዜ ጋር በተያያዘ ያቆመበትን ነጥብ የግድ አያመለክትም። የሐንስ በአደባባይ መስበክ ከጀመረ በኋላም እንኳ ቢሆን በምድረ በዳ ይኖር ነበር።

በአደባባይ መታይ እስኪጀምር
“በአደባባይ መስበክ እስከሚጀምር ድረስ”

እስከጀመረበት ቀን
ይህ በጠቅላላው “ጊዜውን” እና “ሁኔታውን” ለመናገር ጥቅም ላይ ነው የዋለው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 2

1 በዚያን ጊዜ አውግስጦስ ቄሣር በዓለም የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ይቆጠሩ ዘንድ ዐዋጅ አወጣ። 2 ይህም ቄሬኔዎስ የሶርያ ገዥ በነበረበት ጊዜ የተደረገ
የመጀመሪያው የሕዝብ ቆጠራ ነበር። 3 ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው ለሕዝብ ቆጠራው ወደየራሱ ከተማ ሄደ። 4 ዮሴፍም የዳዊት ቤተሰብ ዝርያ ስለነበረ በገሊላ
ከነበረችው ከናዝሬት ተነሥቶ የዳዊት ከተማ ወደምትባለው የይሁዳ ከተማ ወደ ነበረችው ወደ ቤተ ልሔም ተጓዘ። 5 ይመዘገብ ዘንድ ለእርሱ ታጭታ
ከነበረችውና የመውለጃዋን ቀን እየተጠባበቀች ከነበረችው ከማርያም ጋር ወደዚያ ስፍራ ሄደ። 6 እዚያም በነበሩበት ጊዜ የምትወልድበት ወቅት ደረሰ። 7
የበኩር ልጅዋ የሆነውን ወንድ ልጅ ወለደች፣ በመታቀፊያ ጨርቅም በሚገባ ጠቀለለችው። በእንግዳ መቀበያውም ስፍራ ስላልነበረ በእንስሳት መመገቢያ
ግርግም ውስጥ አስተኛቸው። 8 በዚያው አካባቢ በሌሊት የበግ መንጎቻቸውን እየጠበቁ በመስክ የነበሩ እረኞች ነበሩ። 9 በድንገትም የእግዚአብሔር መልአክ
ለእነርሱ ተገለጠላቸው፣ የእግዚአብሔርም ክብር በእነርሱ ዙሪያ አበራላቸው፤ እነርሱም በጣም ፈሩ። 10 ከዚያ በኋላ መልአኩ፣ “ለሕዝብ ሁሉ ታላቅ ደስታ
የሚሆን የምሥራች ይዤላችሁ መጥቻለሁና አትፍሩ። 11 ዛሬ በዳዊት ከተማ፣ አዳኝ ተወልዶላችኋል፤ እርሱም ክርስቶስ ጌታ ነው። 12 ለእናንተም ይህ ምልክት
ይሰጣችኋል፣ ሕፃን በመታቀፊያ ጨርቅ ተጠቅልሎ፣ በግርግም ተኝቶ ታገኛላችሁ።” 13 በድንገትም ከመልአኩ ጋር ብዙ የሰማይ ሠራዊት እግዚአብሔርን
እያመሰገኑ፣ 14 “ከፍ ባለ ስፍራ ለሚኖረው ለእግዚአብሔር ክብር፣ በምድርም እርሱ ደስ በሚሰኝባቸው ሕዝቦች መካከል ሰላም ይሁን።” ይሉ ነበር። 15
መላእክቱም ከእነርሱ ተለይተው ወደ ሰማይ በሄዱ ጊዜ፣ እረኞቹ እርስ በርሳቸው፣ “ወደ ቤተልሔም እንሂድና፣ እግዚአብሔር ለእኛ የገለጠልንን ይህንን የሆነውን
ነገር እንመልከት።” ተባባሉ። 16 በችኮላ ወደዚያ ሄደው ማርያምንና ዮሴፍን አገኝዋቸው፣ ሕፃኑንም በግርግም ተኝቶ ተመለከቱት። 17 ይህንን ከተመለከቱ
በኋላ ስለዚህ ልጅ የተባለውን ለሕዝቡ አስታወቁ። 18 ያዳመጡአቸውም ከእረኞቹ በተነገራቸው ነገር ተደነቁ። 19 ስለሰማችው ነገር ሁሉ ማርያም እያሰላሰለች
በልብዋ ትጠብቀው ነበር። 20 ልክ እንደ ተነገራቸው ስለ ሰሙትና ስላዩት ስለ ማንኛውም ነገር እረኞቹ እግዚአብሔርን እያከበሩና እያመሰገኑ ተመለሱ። 21
ሕፃኑ የሚገረዝበት ስምንተኛው ቀን በደረሰ ጊዜ በማሕፀን ከመፀነሱ በፊት በመልአኩ በተሰጠው ስም ኢየሱስ ብለው ጠሩት። 22 በሙሴ ሕግ መሠረት
የመንጻታቸው ወራት በተፈጸመ ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ያቀርቡት ዘንድ በኢየሩሳሌም ወዳለው ወደ ቤተ መቅደሱ 23 ይህም፣ “ማሕፀንን የሚከፍት ማንኛውም
ወንድ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ይሆናል” ተብሎ በሕጉ እንደ ተጻፈው ነው። 24 በእግዚአብሔር ሕግም በተነገረው መሠረት መሥዋዕት ማለትም ‘ሁለት ዋኖሶች
ወይም ሁለት የርግብ ጫጩቶች’ ያቀርቡ ዘንድ መጡ። 25 በኢየሩሳሌምም የሚኖር ስሙ ስምዖን የተባለ ሰው ነበር። ይህ ሰው ጻድቅና የእግዚአብሔርን
ትዕዛዝ የሚያከብር ነበር፤ ለእስራኤል መጽናኛም የሚሆነውን ይጠባበቅ ነበር፣ መንፈስ ቅዱስም በእርሱ ላይ ነበር። 26 እግዚአብሔር የቀባውን ሳያይ
እንደማይሞት በመንፈስ ቅዱስ ተገልጦለት ነበር። 27 የሕጉ ሥርዓት የሚጠይቀውን ሊያደርጉለት ወላጆቹ ሕፃኑ ኢየሱስን ይዘው በመጡበት ቀን በመንፈስ
ቅዱስ ተመርቶ ወደ ቤተ መቅደስ መጣ። 28 ከዚያም ስምዖን በእጆቹ አቅፎት፣ እግዚአብሔርን እያመሰገነ፣ 29 “ጌታ ሆይ፣ እንግዲህ፣ ባሪያህን እንደ ቃልህ
በሰላም አሰናብተው፣ 30 ዓይኖቼ ማዳንህን አይተዋልና 31 ይህም ድነት አንተ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸው ነው። 32 እርሱም ለአሕዛብ መገለጥ ብርሃን፣
ለሕዝብህም ለእስራኤል ክብር ነው።” 33 የልጁም አባትና እናት ስለ እርሱ እየተነገረ ባለው ነገር ተደነቁ። 34 ከዚያ በኋላ ስምዖን ባረካቸውና እናቱን
ማርያምን፣ “በጥንቃቄ አድምጪ! ይህ ልጅ በእስራኤል ለብዙዎች ለመውደቃቸውና ለመነሣታቸው ምክንያት፣ ክፉም ለተናገሩበት ምልክት የሚሆን ነው። 35
የብዙዎች የልባቸው ሐሳብ ይገለጥ ዘንድ የአንቺም የራስሽ ልብ በሰይፍ የሚወጋ ይሆናል።” 36 ሐና የተባለች ነቢይትም በዚያ ነበረች፤ እርሷም ከአሴር ነገድ
የሆነ የፋኑኤል ልጅ ነበረች። ዕድሜዋ እጅግ የገፋ ሲሆን ከጋብቻዋ በኋላ ከባልዋ ጋር ለሰባት ዓመታት ቆይታለች። 37 ከዚያ በኋላ ለሰማንያ አራት ዓመታት
መበለት ሆና ኖራለች። ከቤተ መቅደስ በፍጹም ሳትለይ ቀንና ሌሊት በጾምና በጸሎት እግዚአብሔርን ታመልክ ነበር። 38 ልክ በዚያን ሰዓት ወደ እነርሱ መጥታ
እግዚአብሔርን ማመስገን ጀመረች። የኢየሩሳሌምን መቤዠት ለሚጠባበቁ ለማንኛዎቹም ሰዎች ስለ ልጁ ትናገር ነበር። 39 እንደ እግዚአብሔር ሕግ
እንዲያደርጉ የሚፈለግባቸውን ማንኛውንም ነገር ካጠናቀቁ በኋላ ወደ ገሊላ ወደ ራሳቸው ከተማ ወደ ናዝሬት ተመለሱ። 40 ልጁ አደገ፣ ጠነከረ፣ በጥበብም
ጨመረ፤ የእግዚአብሔር ጸጋም በ እርሱ ላይ ነበረ። 41 ወላጆቹም ለፋሲካ በዓል በየዓመቱ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄዱ ነበር። 42 አሥራ ሁለት ዓመት በሆነው ጊዜ
በተለመደው ጊዜ እንደገና በዓሉን ለማክበር ሄዱ። 43 ለበዓሉ መቆየት ያለባቸውን ሁሉንም ቀናት ከቆዩ በኋላ ወደ ቤታቸው መመለስ ጀመሩ። ልጁ ኢየሱስ ግን
በኢየሩሳሌም ቀረ፣ ወላጆቹም ይህንን አላወቁም ነበር። 44 ከእነርሱ ጋር ይጓዙ ከነበሩት መንገደኞች ጋር የነበረ መስሏቸው ስለነበረ የአንድ ቀን መንገድ ተጓዙ።
ከዚያ በኋላም በዘመዶቻቸውና በወዳጆቻቸው ዘንድ ፈለጉት። 45 ባላገኙትም ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው በዚያ ሊፈልጉት ጀመሩ። 46 ከሦስት ቀን በኋላ
እያዳመጣቸውና ጥያቄዎችን እየጠየቃቸው በመምህራን መካከል ተቀምጦ በቤተ መቅደስ ውስጥ አገኙት። 47 ያዳመጡት ሁሉ በማስተዋሉና በሚሰጣቸው
መልሶች ተገረሙ። 48 ባዩትም ጊዜ ተደነቁ። እናቱም እርሱን፣ “ልጄ ሆይ፣ ለምን እንደዚህ አደረግኸን? አድምጠኝ፣ እኔና አባትህ ተጨንቀን አንተን ስንፈልግህ
ነበርን” አለችው። 49 እርሱም፣ “ለምን ነበር የፈለጋችሁኝ? በአባቴ ቤት እሆን ዘንድ እንደሚገባኝ አታውቁምን?” 50 ነገር ግን እንደዚያ ሲል ምን ማለቱ
እንደነበረ አልገባቸውም። 51 ከዚያ በኋላ ከእነርሱ ጋር ወደ ናዝሬት ተመለሰ፣ ይታዘዝላቸውም ነበር። እናቱም ይህንን ሁሉ ነገር በልቧ ትጠብቀው ነበር። 52
ኢየሱስ ግን በጥበብና በሰውነት ቁመና ማደጉን ቀጠለ፣ በእግዚአብሔርና በሰዎችም ፊት ያለው ሞገስ እየጨመረ ሄደ።

Luke 2:1

አጠቃላይ መረጃ፦
ይህ ማርያምና ዮሴፍ በኢየሱስ ውልደት ወቅት ለምን በጉዞ ላይ እንደነበሩ ጠቅላላ የጀርባ መረጃን ይሰጣል።

አሁን
ይህ ቃል የታሪኩ አዲስ ክፍል መጀመሩን ይናገራል። (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህ ሆነ
ይህ ሐረግ ቦታው የአዲስ ታሪክ ጅማሬ እንደሆነ ያሳያል። ቋንቋችሁ ለታሪክ መጀመርያ የተለየ መግለጫ ካለው እሱን መጠቀም ይቻላል። አንዳንድ ትርጉሞች ይህንነ ሐረግ አያካትቱትም።

አውግስጦስ ቄሣር
“ንጉሥ አውግስጦስ” ወይም “አጼ አውግስጦስ” አውግስጦስ የሮም ግዛት የመጀመርያው ንጉሥ ነበር። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል እና የአዲስና የቀድሞ ተሳታፊዎች መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

ትዕዛዝ ያለበት ጽሑፍ ላከ
ይህ ትዕዛዝ በተለያዩ መልዕክተኞች አማካኝነት በግዛቱ ውስጥ እንደተሰራጨ ይገመታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ትዕዛዝ ያለበትን ጽሑፍ በመልዕክተኞች ላከ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

በዓለም ላይ ያሉ ሰዎች ሁሉ ቆጠራ እንዲደረግ
ይህ በአድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በዓለም ላይ የሚኖሩትን ሕዝቦች በሙሉ እንዲመዘግቡ” ወይም “በዓለም ላይ የሚገኙ ሕዝቦችን በሙሉ እንዲቆጥሩና ስማቸውን እንዲመዘግቡ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ዓለም
እዚህ ላይ “ዓለም” የሚለው ቃል አውግስጦስ ቄሣር ይገዛ የነበረውን የዓለም ክፍል ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በግዛቱ ውስጥ” ወይም “የሮም ዓለም” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

ቄሬኔዎስ
ቄሬኔዎስ የሦርያ ክፍለ ሐገርን እንዲገዛ የተሾመ ሰው ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉም ... ሄደ
“ሁሉም ጉዞ ጀመሩ” ወይም “ሁሉም እየሄዱ ነበር”

ወደ ከተማው
ይህ የሰዎች አባቶችና አያቶች ይኖሩበት የነበረውን ከተማ ይወክላል። ሰዎች በተለያየ ከተሞች ሊኖሩ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “አባትና አያቶቻቸው ይኖሩበት ወደነበረው ከተማ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለቆጠራው ለመመዝገብ
“በመዝገብ ውስጥ ስማቸውን ለማስመዝገብ” ወይም “መንግስት እያደረገ ባለው ቆጠራ ውስጥ ለመካተት”

Luke 2:4

አጠቃላይ መረጃ፦
ዩዲቢ የሚባለው ትርጉም አርፍተ ነገሮቹን ለማሳጠር እነዚህን ሁለት ቁጥሮች አንድ ላይ በማድረግ አንድ የመሸጋገርያ ቁጥር አድርገዋቸዋል። (የጥቅስ ድልድዮች የሚለውን ይመልከቱ)

ዮሴፍም
ይህ ዮሴፍን በታሪኩ ውስጥ እንደ አንድ ተሳታፊ አድርጎ ያስተዋውቀዋል። (የአዲስና የቀድሞ ተሳታፊዎች መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

ቤተልሔም ወደተባለችው የዳዊት ከተማ
“የዳዊት ከተማ” የሚለው ሐረግ ቤተልሔም ምን አይነት ወሳኝ ከተማ እንደሆነች የሚያሳይ የቤተልሔም ከተማ ስም ነው። ምንም እንኳ ትንሽ ከተማ ብትሆንም ንጉሥ ዳዊት የተወለደው በዚች ከተማ ነው፣ መሲሑም በዚው ከተማ እንደሚወለድ የሚናገር ትንቢት ነበር። አማራጭ ትርጉም፦ “የንጉሥ ዳዊት ከተማ ወደነበረችው ወደ ቤተልሔም” ወይም “ንጉሥ ዳዊት ወደተወለደበት ከተማ ወደ ቤተልሔም” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የዳዊት ወገንና ቤት ስለነበር
“ምክንያቱም ዮሴፍ የዳዊት ዘር ስለነበር”

ለመጻፍ
ይህ ማለት በሕዝብ ቆጠራው ውስጥ እንዲያካትቱት ለመንግስቱ ሹማምንት ለማሳወቅ ማለት ነው። የሚቻል ከሆነ የመንግስት የሕዝብ ቆጠራን የሚገልጽ ቃል ተጠቀም።

ከማርያም ጋር
ማርያም ከዮሴፍ ጋር ከናዝሬት ተነስታ ተጉዛ ነበር። ሴቶችም እንደወንዶች ቀረጥ ይጣልባቸው ስለነበረ እርሷም አብራ ተጉዛ መመዝገብ ነበረባት። (የአዲስና የቀድሞ ተሳታፊዎች መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእርሱ ታጭታ የነበረችው
“እጮኛው” ወይም “ለእርሱ ቃል ገብታለት የነበረች” እጮኛ የነበሩ ጥንዶች በሕግ እንደተጋቡ ተደርገው ይታሰባሉ ነገር ግን በመካከላቸው ምንም አይነት አካላዊ ግንኙነት አይኖርም ነበር።

Luke 2:6

አያያዥ ሀሳብ፦
ይህ የኢየሱስን ውልደትን እና ለበግ ጠባቂዎች የመላዕክቱን ብስራት ይናገራል።

አጠቃላይ መረጃ፦
ዩዲቢ የሚባለው ትርጉም (እነ ዮሴፍ) የቆዩበትን ቦታ ዝርዝር መረጃ ለመጠበቅ ሲባል እነዚህን ቁጥሮች ቅደም ተከተላቸውን በመቀያየር አንድ መሸጋገርያ ቁጥር አድርጓቸዋል። (የጥቅስ ድልድዮች የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ በታሪኩ ውስጥ ቀጣዩ ክስተት መጀመሩን ያሳያል። (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚያም ሳሉ
“ማርያምና ዮሴፍ በቤተልሔም እያሉ”

ልጇን የመውለጃዋ ጊዜ ደረሰ
“ልጇን የምትገላገልበት ጊዜ ደረሰ”

በረዥም የጨርቅ ብጣሽ ጠቀለለችው
በአንዳንድ ባህሎች እናቶች ልጆቻቸውን በጨርቅ ወይም በብርድ ልብስ በመጠቅለል እንዲመቻቸው ያደርጋሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ሙሉ ሰውነቱን በጨርቅ ጠቀለለችው” ወይም “በብርድ ልብስ አጥብቃ ጠቀለለችው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በግርግም አስቀመጠችው
ይህ በተለየ ሁኔታ የሚሰራ እንስሶች እንዲበሉ መኖ ወይም ሌላ የከብት ምግብ የሚቀመጥበት የምግብ ማስቀመጫ ሳጥን ነገር ነው። ንጹህ እንደነበረና ለስላሳና ጠንከር ያለ ለሕጻኑ የሚመች መተኛ የሚሆን የሳር ድርቆሽ ክምር እንደነበረው ይገመታል። ከብቶች ከዋናው ቤት ሳይርቅ ቅርብ የሆነ ቦታ ላይ መኖርያ ይሰራላቸዋል፣ ይህም እነርሱን ለመመገብና ለመጠበቅ እንዲመች ነው። ማርያምና ዮሴፍ በእንስሳት መኖርያ ውስጥ ነበር ይቆዩ የነበረው።

በእንግዶች ማረፍያ ውስጥ ለእነርሱ ቦታ አልነበረም
“በእንግዶ ማረፍያ ክፍል ውስጥ እነርሱ ሊያርፉ የሚችሉበት ቦታ አልነበረም” ቦታ ያለመኖሩ ምክንያት ብዙ ሰዎች ለመመዝገብ ወደ ቤተልሔም መጓዛቸው እንደሆነ ይገመታል። ሉቃስ ይህንን እንደ ተጨማሪ የጀርባ መረጃ ይናገራል። (የጀርባ ታሪክ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 2:8

የጌታ መልዓክ
“ከጌታ የተላከ መልዓክ” ወይም “ጌታን ያገለግል የነበረ መልዓክ”

ታያቸው
“ወደ እረኞቹ መጣ”

የጌታ ክብር
የብርሃኑ ምንጭ ከመልዓኩ መታየት ጋር በተመሳሳይ ሰዓት መጥቶ የነበረው የጌታ ክብር ነው።.

Luke 2:10

አትፍሩ
“መፍራት አቁሙ”

Luke 2:13

ብዙ የሰማይ ሰራዊት
“የሰማይ ሰራዊት” የሚለው ሐረግ ቃል በቃል የመላዕክትን ሰራዊትን፣ ወይም የተቀናጀ የመላዕክትን ስብስብ ሊወክል ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከሰማይ ብዙ መላዕክት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን እያመሰገኑ
“ለእግዚአብሔር ምስጋናን በመስጠት”

ክብር በከፍታ ለሚኖረው ለእግዚአብሔር ይሁን
የዚህ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት 1) ”በከፍታ ለሚኖረው ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን ወይም” 2) “ከፍ ያለ ክብር ለእግዚአብሔርን ይሁን”

እርሱ የሚደሰትባቸው ሰዎች ባሉበት በምድርም ሰላም ይሁን
“በምድር ያሉ እግዚአብሔር የሚደሰትባቸው ሰዎች ሰላምን ያግኙ”

Luke 2:15

እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ መልዓክቶቹ ከሄዱ በኋላ እረኞቹ ወዳደረጉት ነገር የታሪኩን ትኩረት ይቀይራል።

ከእነርሱ
“ከእረኞቹ”

እርስ በርሳቸው
“አንዱ ለሌላው”

“እናድርግ (እንይ፣ እንሂድ) ... ለእኛ (የተገለጠልን)”
እረኞቹ እርስ በርሳቸው እየተነጋገሩ ስለነበር፣ “እኛ” የሚል መደብ ያላቸው ቃላት በአካታች ቅርጻቸው ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው። (አካታች “እኛ” የሚለውን ይመልከቱ)

እናድርግ (እንይ፣ እንሂድ)
“ማድረግ አለብን”

የተከሰተውን ይሄን ነገር
ይህ የሚወክለው የሕጻኑን ውልደት እንጂ የመላዕክቱን መታየት አይደለም።

በግርግም ተቀምጦ
ይህ ሰዎች እንስሶች የሚበሉትን እንደ ሳር ድርቆሽ አይነት ምግብ እንዲበሉ የሚያስቀምጡበት የተለየ ሳጥን ነገር ነው። ይህ በሉቃስ 2:7 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።

Luke 2:17

የተነገራቸውን
ይህ በአድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “መላዕክቱ ለእረኞቹ የነገሯቸውን” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

(ስለዚህ) ሕጻን
“ሕጻኑ”

በእረኞቹ የተነገራቸውን
ይህ በአድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እረኞቹ የነገሯቸውን” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በልቧ ውስጥ ትጠብቀው ነበር
አንድ ሰው አንድ ነገር ዋጋ እንዳለው ወይም የከበረ እንደሆነ ካሰበ ልቡ ውስጥ “ይጠብቀዋል።” ማርያም ስለ ልጇ የተነገሩትን ነገሮች በሙሉ እጅግ የከበሩና ትልቅ ዋጋ እንዳላቸው ታስብ ነበር። አማራጭ ትርጉም፡- “በጥንቃቄ ታሰላስል ነበር” ወይም “በደስታ ታስበው ነበር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 2:21

አጠቃላይ መረጃ፡-
እግዚአብሔር ለአይሁዳውያን የሰጠው ሕግ ወንድ ሕጻናትን መቼ መገረዝ እንዳለባቸውና ወላጆቹ ደግሞ ምን ዓይነት መስዋዕት ማምጣት እንዳለባቸው ይነግሯቸዋል።

በስምንተኛው ቀን ማለቂያ
ይህ ሐረግ አዲስ ክስተት ከመከሰቱ በፊት ያለፈውን ጊዜ ይናገራል። (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

በስምንተኛው ቀን ማለቂያ
“በሕጻኑ ሕይወት በስምንተኛው ቀን ማለቂያ።” ልጁ የተወለደበት ቀን እንደ አንደኛ ቀን ይቆጠራል።

Luke 2:22

የታዘዘው ቀን ብዛት ባለፈ ጊዜ
ይህ ከዚህ አዲስ ክስተት በፊት ያለፈውን ጊዜ ያሳያል። (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

የታዘዘው ቀን ብዛት
ይህ በአድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ያዘዘው የቀን ብዛት” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ለመንጻታቸው
“እነርሱ በስርዓቱ መሰረት ንጹሕ እንዲሆኑ።” እዚህ ላይ የእግዚአብሔርን ድርሻም ማብራራት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር እንደገና ንጹሃን እንደሆኑ እስኪቆጥራቸው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለጌታ ሊያቀርቡት
x

Luke 2:25

አያያዥ ሀሳብ፡-
ማርያምና ዮሴፍ በቤተ መቅደስ ውስጥ እያሉ ሁለት ሰዎች ያገኛሉ፣ እነዚህም ሰዎች እግዚአብሔርን የሚያመሰግነውና ስለሕጻኑ ትንቢትን የተናገረው ስምኦንና ነብይቷ ሃና ናቸው።

እነሆ
“እነሆ” የሚለው ቃል በታሪኩ ውስጥ አዲስ ውስጥ አዲስ ሰውን ያስተዋውቃል። ቋንቋችሁ ይህንን ማሳያ የራሱ መንገድ ሊኖረው ይችላል። (የአዲስና የቀድሞ ተሳታፊዎች መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

ጻድቅና ትጉ ነበር
እነዚህ ረቂቅ ቃላት እንደ ድርጊት ተደርገው መገለጽ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ጽድቅን ይፈጽም ነበር፣ እግዚአብሔርንም ይፈራ ነበር” ወይም “የእግዚአብሔርን ሕግ ይታዘዝ ነበር እግዚአብሔርንም ይፈራ ነበር።

የእስራኤል መጽናናት
“እስራኤል” የሚለው ቃል የእስራኤልን ሕዝብ የሚወክል ምትክ ስም ነው። “ማጽናናት” ማለት አንድን ሰው “ማበረታታት” ነው። “የእስራኤል መጽናናት” ማለት ክርስቶስ ወይም መሲሑ ለእስራኤል ሕዝብ የሚያመጣውን መጽናናት የሚወክል ሐረግ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የእስራኤል ሕዝብን የሚያጽናናው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ላይ ነበር
“መንፈስ ቅዱስ ከእርሱ ጋር ነበር” እግዚአብሔር በተለየ መንገድ ከእርሱ ጋር ነበር፣ በሕይወትም ጥበብና ምሪትን ይሰጠው ነበር።

በመንፈስ ቅዱስ ተገልጦለት ነበር
ይህ በአድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “መንፈስ ቅዱስ አሳይቶት ነበር” ወይም “መንፈስ ቅዱስ ነግሮት ነበር” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በጌታ የተቀባውን ሳያይ ሞትን እንደማያይ
“ሳይሞት በፊት በጌታ የተቀባውን መሲህ ያየዋል”

Luke 2:27

በመንፈስ ተመርቶ
ይህ በአድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “መንፈስ ቅዱስ እንደመራው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

መጣ
አንዳንድ ቋንቋዎች “ሄደ” ሊሉ ይችላሉ።

ወደ ቤተ መቅደስ ውስጥ
“ወደ ቤተ መቅደስ ቅጥር ግቢ ውስጥ” ወደ ቤተ መቅደስ ሕንጻ ውስጥ መግባት የሚችሉት ካህናት ብቻ ናቸው። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ወላጆቹ
“የኢየሱስ ወላጆች”

እንደ ሕጉ ልማድ
“እንደ እግዚአብሔር ሕግ ልማድ”

ወደ እጆቹ ውስጥ አስገባው
“ስምኦን ሕጻኑን ኢየሱስን ወደ እጆቹ አስገባው” ወይም “ስምኦን ኢየሱስን በእጆቹ ያዘው”

አሁን ባርያህን በሰላም አሰናብተው
“እኔ አገልጋይህ ነኝ፣ በሰላም አሰናብተኝ” ስምኦን ስለራሱ ነበር የሚያወራው።

መሰናበት
ይህ “መሞት” ለሚለው ቃል ለስላሴ ዘይቤ ነው። (ለስላሴ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ቃልህ
“ቃል” የሚለው “ቃልኪዳን” ለሚለው ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እንደገባኸው ቃልኪዳን” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 2:30

ዓይኖቼ አይተዋል
ይህ አገላለጽ “በግሌ አይቻለሁ” ወይም “እኔ እራሴ አይቻለሁ” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

ማዳንህን
ይህ አገላለጽ ድነትን የሚያመጣውን ሰው ስምኦን በእጁ ይዞት የነበረውን ሕጻኑን ኢየሱን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የላክከውን አዳኝ” ወይም “እንዲያድን የላክከውን” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ የላክኸው
የቀደመው ሐረግ እንደተተረጎመት አተረጓጎም፣ ይህ “አንተ የላክኸውን” ወደሚለው ሊለወጥ ይችላል።

ያዘጋጀኸውን
“ያሰብከውን” ወይም “እንዲከሰት ያደረግከውን”

ለአህዛብ የሚገልጥ ብርሃን
ይህ ዘይቤ ሕጻኑ ሰዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅና መረዳት እንዲችሉ ይረዳቸዋል የሚለውን ይገልጻል። እዚህ ላይ የአሕዛብ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መረዳት ሰዎች አንድን ቁስ ለማየት ብርሃንን እንደሚጠቀሙት ተደርጎ ተመስሎ ቀርቧል። አሕዛብ የሚመለከቱት ምን እንደሆነ በግልጽ ማሳየት አለብህ። አማራጭ ትርጉም፡- “ይህ ሕጻን ብርሃን ሰዎች አጥርተው መመልከት እንዲችሉ እንደሚያደርግ፣ ልክ እንደዛ እርሱም አሕዛብ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲሁ እንዲያውቁ ይረዳቸዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የሚገልጥ
የሚገለጠው ነገር ምን እንደሆነ በግልጽ ማስቀመጥ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእግዚአብሔርን እውነት የሚገልጥ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለሕዝብህ ለእስራኤል ክብር
“እርሱ ለሕዝብህ ለእስራኤል ክብር መምጣት ምክንያት ይሆናል”

Luke 2:33

ስለ እርሱ በተባሉት ነገሮች
ይህ በአድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስምኦን ስለ እርሱ በተናገራቸው ነገሮች” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእናቱ ለማርያም እንዲህ አላት
“ለሕጻኑ እናት ለማርያም እንዲህ አላት።“ ማርያም የስምኦን እናት የሆነች መስሎ እንዳይታይ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠይቃል።

እነሆ
ስምኦን ይሄን አገላለጽ የሚጠቀመው ለማርያም ቀጥሎ የሚነግራት ነገር እጅግ ጠቃሚ እንደሆነ ለማሳየት ነው።

ይህ ሕጻን በእስራኤል ለብዙዎች መውደቅና መነሳት ተሸሟል
“መውደቅ” እና “መነሳት” የሚሉት ቃላት ከእግዚአብሔር መራቅ እና ወደ እግዚአብሔር መጠጋት የሚሉትን ትርጉም ይዘዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይህ ሕጻን በእስራኤል ለብዙዎች ከእግዚአብሔር የመራቅና ለብዙዎችም ወደ እግዚአብሔር የመቅረብ ምክንያት ይሆናል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ለሚቃወሙትም ምልክት
“ብዙ ሰዎች ስለሚቃወሙት ስለ እግዚአብሔር መልዕክት ምልክት”

በነፍስሽ ውስጥ ሰይፍ ያልፋል
ይህ ዘይቤ ማርያም ወደፊት የሚሰማትን ጥልቅ የሆነ ሀዘን ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሐዘንሽ ልብሽ በሰይፍ እንደተወጋ ያህል እጅግ ጥልቅ ይሆናል“ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የብዙ ልቦች አሳብ ይገለጥ ዘንድ
እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል የሰዎችን ውስጣዊ ማንነት ይወክላል። ይህ በአድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የብዙ ሰዎችን ሃሳብ ይገልጥ ዘንድ” ወይም “ብዙ ሰዎች በድብቅ የሚያስቡን ይገልጥ ዘንድ” (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 2:39

አያያዥ ሀሳብ፡-
ማርያም ዮሴፍና ኢየሱስ ቤተልሔም ከተማን ለቅቀው ኢየሱስ ልጅነቱን ወደሚያሳልፍባት ወደ ናዝሬት ከተማ ይመለሳሉ።

በጌታ ሕግ መሰረት እንዲያደርጉ የሚጠበቅባቸውን
ይህ በአድራጊ ቅርጽ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእግዚአብሔር ሕግ እንዲያደርጉ የሚያዝዘውን” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 2:41

አያያዥ ሀሳብ፡-
ኢየሱስ 12 ዓመት ሲሞላው ከቤተሰቡ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ። በዚያም እያለ የቤተ መቅደስ መምህሮችን ጥያቄዎች ይጠይቃቸው ነበር፣ እርሱም የእነርሱን ጥያቄዎች ይመልስላቸው ነበር።

ለፋሲካ በዓል ... ወላጆቹ ሄዱ
ይህ ተጨማሪ የጀርባ መረጃ ነው። (የጀርባ ታሪክ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ወላጆቹ
“የኢየሱስ ወላጆች”

ደግመው ወጡ
ኢየሩሳሌም በእስራኤል ከሚገኙ ከሌሎች ቦታዎች በመሬት ከፍታ ከፍ ብላ የምትገኝ ከተማ ነበረች፣ ስለዚህ ወደ ኢየሩሳሌም ስለመሄድ ሲወራ “መውጣት” ተብሎ ሊገለጽ ይችላል።

በሥርዓቱ ሰዓት
“በተለመደው ሰዓት” ወይም “በየዓመቱ ያደርጉ እንደነበረው”

የክብረ በዓሉንም ሙሉ ቀናት ቆይተው ከጨረሱ በኋላ
“ክብረ በዓሉ የሚከበርባቸው ቀናት ካለፉ በኋላ” ወይም “ክብረ በዓሉ መከበር ላለበት ቀናት አክብረው ከጨረሱ በኋላ”

ግብዣ
x

Luke 2:45

እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ በታሪኩ ውስጥ የተከሰተን ወሳኝ ክስተት ያሳያል። ቋንቋችሁ እንደዚህ ዓይነትን ነገር ማሳያ መንገድ ካለው እሱን መጠቀም ይቻላል።

በቤተ መቅደስ
ይህ የመቅደሱ ቅጥር ግቢን ያሳያል። ወደ ቤተ መቅደስ ውስጥ መግባት የሚችሉት ካህናት ብቻ ነበሩ። አማራጭ ትርጉም፡- “በመቅደሱ ቅጥር ግቢ ውስጥ” ወይም “በቤተ መቅደስ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በመካከል
ይህ ቃለ በቃል መሃል ላይ ማለት አይደለም። ይልቁንም “አብሮ ሆኖ” ፣ “በእነርሱ መካከል” ወይም “በእነርሱ ተከብቦ” የሚለውን ትርጉም ይይዛል።

አስተማሪዎቹ
“የኃይማኖት መምህሮች” ወይም “ስለ እግዚአብሔር ለሰዎች ያስተምሩ የነበሩ”

የሰሙት ሁሉ ይገረሙ ነበር
12 ዓመቱ የሆነና፣ የኃይማኖት ትምህርት ያልተማረ አንድ ልጅ በጥሩ ሁኔታ ጥያቄዎችን መመለስ መቻሉ እንዴት እንደሆነ አልገባቸውም።

በማስተዋሉ
“ምን ያህል ማስተዋል በመቻሉ” ወይም “ስለ እግዚአብሔር ብዙ ማስተዋል በመቻሉ”

መልሶቹ
“እንዴት በጥሩ ሁኔታ እንደመለሰላቸው” ወይም “ጥያቄዎቻቸውን በጥሩ ሁኔታ በመመለሱ”

Luke 2:48

ሲያዩት
“ማርያምና ዮሴፍ ኢየሱስን ሲያገኙት”

ለምን እንዲህ ታደርገናለህ?
ይህ ቀጥተኛ ያልሆነ ተግሳጽ ነው ይህም እነርሱ ወደ ቤት ሲሄዱ አብሯቸው ስላልነበረ ነው። ይህ ስለ እርሱ እንዲጨነቁ አድርጓቸው ነበር። አማራጭ ትርጉም፡- “እኛን እንዲህ እንድንሆን ማድረግ አልነበረብህም!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ስሙ
ይህ ቃል ብዙ ጊዜ አንድ አዲስ ወይም ወሳኝ የሆነ ሁነት ሊጀምር መሆኑን ለማሳየት ጥቅም ላይ የሚውል ነው። ከዚህ በተጨማሪ ይህ አዲስ ድርጊት የት እንደሚጀምር ለማሳየት ሊጠቅም ይችላል። በቋንቋችሁ ውስጥ በእንዲህ ዓይነት መንገድ ጥቅም ላይ የሚውል ሀረግ ካለው እዚህ ላይ ለመጠቀም አግባብነት ያለው መሆኑን አስብ።

ለምን ፈለጋችሁኝ?
ኢየሱስ ወላጆቹን በለስላሴው ለመገሰጽ ሁለት ጥያቄዎችን ይጠቀማል፣ እነርሱ ያልተረዱት በሰማይ ያለው አባቱ የሰጠው ዓላማ እንዳለም ይነግራቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለ እኔ መጨነቅ የለባችሁም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

(... ማድረግ**)** እንዳለብኝ **....** አታውቁም?
ኢየሱስ ወላጆቹ አባቱ ሊያደርገው የሰጠው ዓላማ እንዳለ ማወቅ እንዳለባቸው ለመንገር ሁለተኛውን ጥያቄ ይጠቀማል። “(ማድረግ) እንዳለብኝ ማወቅ ነበረባችሁ” አማራጭ (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ አባቴ ስራ
የዚህ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉ 1) ኢየሱስ እነዚህን ቃላት በጥንቃቄ መርጦ የተናገረው አባቱ የሰጠውን ስራ እየሰራ እንደሆነ ለማሳየት ነው፣ ወይም 2) እነዚህ ቃላት ኢየሱስ የነበረበትን ቦታ፣ “የአባቴ ቤት” የሚያስረዳ ፈሊጥ ነው። ቀጣዩ ቁጥር የኢየሱስ ወላጆች ኢየሱስ የሚነግራቸውን ነገሮች አልተረዱትም ስለሚል ይህን ከዚህ በላይ ለማብራራት ባይሞከር ጥሩ ነው።

የአባቴን ስራ
የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ፣ በ12 አመቱ የእውነት አባቱ የማርያም ባል የነበረው ዮሴፍ ሳይሆን እግዚአብሔር እንደነበር አስተውሎ ነበር። (ልጅ እና አባትን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 2:51

ከእነርሱ ጋር ወደ ቤት ተመለሰ
“ኢየሱስ ከማርያምና ከዮሴፍ ጋር ወደ ቤት ተመለሰ”

ይታዘዛቸው ነበር
“ለእነርሱ ይታዘዝ ነበር” ወይም “ሁልጊዜ ለእነርሱ ይታዘዝ ነበር”

እነዚህን ነገሮች በልቧ ትጠብቃቸው ነበር
እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል የአንድን ሰው ውስጣዊ ማንነት ወይም አእምሮ የሚያሳይ ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በጥንቃቄ እነዚህን ሁሉ ነገሮች ታስብ ነበር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በጥበብና በቁመት አደገ
“ጠቢብና ጠንካራ ሆነ” እነዚህ አእምሮአዊና አካላዊ እድገትን ያመለክታሉ።

በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት አደገ
ይህ መንፈሳዊና ማሕበራዊ እድገትን ያሳያል። እነዚህ ተነጣጥለው መጻፍ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር አብዝቶ ባረከው፣ በሰዎችም ዘንድ የበለጠ የተወደደ ሆነ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 3

1 ጢባርዮስ ቄሣር በነገሠ በአሥራ አምስተኛው ዓመት፣ ጴንጤናዊው ጲላጦስ የይሁዳ ገዥ፣ ሄሮድስ የገሊላ አራተኛው ክፍል ገዥ፣ ወንድሙ ፊልጶስ
የኢጡርያስና የጥራኮኒዶስ የአራተኛው ክፍል ገዥ፣ ሊሳኒዮስም የሳቢላኒስ አራተኛው ክፈል ገዥ 2 እንደዚሁም ሐናና ቀያፋ ሊቃነ ካህናት በነበሩበት ጊዜ
የእግዚአብሔር ቃል ለዘካርያስ ልጅ ለዮሐንስ በምድረ-በዳ መጣ። 3 ለኃጢአት ይቅርታ የንስሓን ጥምቀት እየሰበከ በዮርዳኖስ ወንዝ አውራጃ ሁሉ ተመላለሰ።
4 ይህም በነቢዩ በኢሳይያስ መጽሐፍ፣ “በምድረ-በዳ የሚጣራ ሰው ድምፅ፣ ‘የእግዚአብሔርን መንገድ አዘጋጁ፣ ጎዳናውንም አቅኑ። 5 ሸለቆ ሁሉ ይሞላል፣
ተራራውና ኮረብታው ደልዳላ ይሆናል፣ ጠማማው መንገድ ቀና ይሆናል፣ ሸካራውም መንገድ የተመቸ ይሆናል። 6 ሰዎችም ሁሉ የእግዚአብሔርን ማዳን
ያያሉ።’” 7 ስለዚህ በእርሱ ለመጠመቅ ይመጣ ለነበረው ከፍተኛ ቁጥር ላለው ሕዝብ ዮሐንስ እንደዚህ አላቸው፣ “እናንተ የመርዘኛ እባብ ልጆች፣ ሊመጣ
ካለው ቁጣ እንድትሸሹ ማን አስጠነቀቃችሁ? 8 ለንስሓ የሚሆን ፍሬ አፍሩ፣ እርስ በርሳችሁም፣ ‘አባታችን አብርሃም አለን’ አትበሉ፣ ምክንያቱም ከእነዚህ
ድንጋዮች እንኳን እግዚአብሔር ለአብርሃም ልጆችን ሊያስነሣለት ይችላል። 9 መጥረቢያ በዛፎች ግንድ ሥር ተቀምጦአል፤ ስለዚህ መልካም ፍሬ የማያፈራ ዛፍ
ሁሉ ተቆርጦ ወደ እሳት ውስጥ ያጣላል።” 10 ከዚያ በኋላ ተሰብስበው የነበሩት ሰዎች እንደዚህ ብለው ጠየቁት፣ “እንግዲህ ምን እናድርግ?” 11 እርሱም
እንደዚህ ብሎ መለሰላቸው፣ “አንድ ሰው ሁለት ልብስ ካለው ምንም ለሌለው ለሌላ ሰው ይስጠው፤ ትርፍ ምግብ ያለውም እንደዚሁ ያድርግ።” 12 ከዚያ
በኋላም አንዳንድ ቀረጥ ሰብሳቢዎች ለመጠመቅ መጡና እንደዚህ አሉት፣ “መምህር ሆይ፣ እኛስ ምን ማድረግ ይገባናል?” 13 እርሱም እንደዚህ አላቸው፣
“መሰብሰብ ከሚገባችሁ ገንዘብ በላይ አትሰብስቡ።” 14 አንዳንድ ወታደሮችም እንደዚህ ብለው ጠየቁት፣ “እኛስ፣ ምን ማድረግ ይገባናል?” እርሱም
እንደዚህ አላቸው፣ “ከማንም ላይ አስገድዳችሁ ገንዘብ አትውሰዱ፣ ማንንም በሐሰት አትክሰሱ። የምታገኙትም ደመወዝ ይብቃችሁ።” 15 ሕዝቡ የክርስቶስን
መምጣት እየተጠባበቁ ሳሉ፣ ሰዎች ሁሉ በልባቸው እርሱ ክርስቶስ ይሆን እያሉ ስለ ዮሐንስ ይደነቁ ነበር። 16 እንደዚህ በማለት ዮሐንስ ለሁሉም መልስ
ሰጣቸው፣ “እኔ በበኩሌ በውሃ አጠምቃችኋለሁ፣ የጫማውን ማሠሪያ መፍታት እንኳን የማይገባኝ ከእኔ ይልቅ ብርቱ የሆነ ይመጣል። እርሱ በመንፈስ ቅዱስና
በእሳት ያጠምቃችኋል። 17 አውድማውን ፈጽሞ ያጠራውና ስንዴውን ወደ ጎተራ ያስገባ ዘንድ የሚያበራይበት መንሽ በእጁ ነው። ገለባውን ግን በማይጠፋ
እሳት ያቃጥለዋል።” 18 ሌሎች ብዙ ምክሮችንም በመምከር፣ የምሥራቹን ቃል ለሕዝቡ ሰበከላቸው። 19 የወንድሙን ሚስት ሄሮዳይዳን ስላገባና
ስላደረጋቸውም ሌሎች ክፉ ሥራዎች የአራተኛው ክፍል ገዥ የነበረውን ሄሮድስንም ገሰጸው። 20 ሄሮድስ ግን ከዚህም የባሰ ክፉ ሥራ ሠራ፣ ዮሐንስን ወህኒ ቤት
አስገብቶ ቆለፈበት። 21 ሰዎች ሁሉ በዮሐንስ እየተጠመቁ ሳሉ፣ ኢያሱስም ደግሞ ተጠመቀ። እየጸለየም ሳለ ሰማያት ተከፈቱ። 22 መንፈስ ቅዱስም በርግብ
አምሳል በአካል በእርሱ ላይ አረፈ፣ በዚህም ጊዜ ከሰማይ፣ “አንተ፣ ውድ ልጄ ነህ፤ በአንተ እጅግ ደስ ይለኛል።” የሚል ድምፅ መጣ። 23 በዚህን ጊዜ ኢያሱስ
ራሱ ማስተማር ሲጀምር ዕድሜው ሰላሳ ዓመት ገደማ ነበር። (ይገመት እንደነበረው) እርሱ የኤሊ ልጅ የነበረው የዮሴፍ ልጅ 24 ኤሊም የማቲ ልጅ፣ የሌዊ
ልጅ፣ የሚልኪ ልጅ፣ የዮና ልጅ፣ የዮሴፍ ልጅ፣ 25 የማታትዩ ልጅ፣ የአሞጽ ልጅ፣ የናሆም ልጅ፣ የኤሲሊም ልጅ፣ የናጌ ልጅ፣ 26 የማኦት ልጅ፣ የማታትዩ ልጅ፣
የሰሜይ ልጅ፣ የዮሴፍ ልጅ፣ የዮዳ ልጅ፣ 27 የዮናን ልጅ፣ የሬስ ልጅ፣ የዘሩባቤል ልጅ፣ የሰላትያል ልጅ፣ የኔር ልጅ፣ 28 የሚልኪ ልጅ፣ የሐዲ ልጅ፣ የዮሳስ ልጅ፣
የቆሳም ልጅ፣ የኤልሞዳም ልጅ፣ የኤር ልጅ፣ 29 የዮሴዕ ልጅ፣ የአልዓዛር ልጅ፣ የዮራም ልጅ፣ የማጣት ልጅ፣ የሌዊ ልጅ፣ 30 የስምዖን ልጅ፣ የይሁዳ ልጅ፣
የዮሴፍ ልጅ፣ የዮናም ልጅ፣ የኤልያቄም ልጅ፣ 31 የሜልያ ልጅ፣ የማይናን ልጅ፣ የማጣት ልጅ፣ የናታን ልጅ፣ የዳዊት ልጅ፣ 32 የእሴይ ልጅ፣ የኢዮቤድ ልጅ፣
የቦዔዝ ልጅ፣ የሰልሞን ልጅ፣ የነአሶን ልጅ፣ 33 የአሚናዳብ ልጅ፣ የአራም ልጅ፣ የአሮኒ ልጅ፣ የኤስሮም ልጅ፣ የፋሬስ ልጅ፣ የይሁዳ ልጅ፣ 34 የያዕቆብ ልጅ፣
የይስሐቅ ልጅ፣ የአብርሃም ልጅ፣ የታራ ልጅ፣ የናኮር ልጅ፣ 35 የሴሮህ ልጅ፣ የራጋው ልጅ፣ የፋሌቅ ልጅ፣ የአቤር ልጅ፣ የሳላ ልጅ፣ 36 የቃይንም ልጅ፣
የአርፋክስድ ልጅ፣ የሴም ልጅ፣ የኖኅ ልጅ፣ የላሜህ ልጅ፣ 37 የማቱሳላ ልጅ፣ የሄኖክ ልጅ፣ የያሬድ ልጅ፣ የመላልኤል ልጅ፣ የቃይናን ልጅ፣ 38 የሄኖስ ልጅ፣ የሴት
ልጅ፣ የአዳም ልጅ፣ የእግዚአብሔር ልጅ።

Luke 3:1

አያያዥ ሀሳብ፦
ነቢዩ ኢሳይያስ እንደ ተነበየው፣ ዮሐንስ መልካም ዜናን ለህዝቡ መስበክ ጀመረ።

አጠቃላይ መረጃ፦
እነዚህ ጥቅሶች የኢየሱስ የአክስት ልጅ ዮሐንስ አገልግሎቱን ሲጀምር ምን እየተደረገ እንደሆነ ለመናገር የጀርባ ታሪክ መረጃን ይሰጣሉ።

ጢባርዮስ ቄሳር በነገሰ በአስራ አምስተኛው አመት
“ጢባርዮስ ቄሳር ለአስራ አምስት አመታት በመራ በዚያ ጊዜ” (ደረጃ የሚያሳይ ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

ፊሊጶስ... ሊሳንዮስ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ኢጡሪያስ እና ጥራኮኒዶስ... ሳቢላኒስ
እነዚህ የግዛት ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ሐና እና ቀያፋ ሊቃነ ካህናት በነበሩ ጊዜ
“ሐና እና ቀያፋ እንደ ሊቀ ካህናት ባንድነት በሚያገለግሉበት ጊዜ።” ሐና ሊቀ ካህን ነበር፣ ሮማውያን አማቹን ቀያፋን እንደ ሊቀ ካህን እንዲተካው ከሾሙት በኋላ እንኳን ሳይቀር አይሁዶችም ለእርሱ እውቅና መስጠታቸውን ቀጥለዋል።”

የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ጸሐፊው የእግዚአብሔር መልእክት እርሱን ወደሚያዳምጡት ሰዎች የሚንቀሳቀስ ሰው እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር መልእክቱን ተናገረ”

Luke 3:3

የንስሀን ጥምቀት መስበክ
“ጥምቀት” እና “ንስሀ” የሚሉት ስሞች እንደ ድርጊት ሊገለፁ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “እርሱም ሰዎች ንስሀ እየገቡ እንደሆነ ለማሳየት መጠመቅ እንዳለባቸው ሰበከ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ለኃጢአት ስርየት
እነርሱ እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን ይቅር እንዲል ንስሀ ይገባሉ። “ይቅርታ” የሚለው ስም እንደ ድርጊት ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦

“ኃጢአታቸው ይቅር እንዲባል” ወይም “እግዚአብሔር ኀጢአታቸውን ይቅር እንዲል” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 3:4

አጠቃላይ መረጃ፦
ጸሐፊው ሉቃስ መጥምቁ ዮሐንስን የሚመለከት ምንባብ ከነቢዩ ኢሳይያስ ጠቀሰ።

በነቢዩ ኢሳይያስ መጽሐፍ እንደ ተፃፈ
እነዚህ ቃላቶች ከነቢዩ ኢሳይያስ የተወሰደ ጥቅስ ያቀርባሉ። እነርሱ በገቢር/አድርጊ ቅርፅ ሊገለፁ ይችላሉ፣ የትዘለሉት ቃላቶችም መቅረብ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ይህ ነቢዩ ኢሳይያስ የእርሱን ቃላት በያዘውን መጽሐፍ እንደፃፈው እንደዚያው ሆነ” ወይም “ዮሐንስ ነቢዩ ኢሳይያስ በመፅሀፉ የፃፈውን መልእክት ፈፀመ” (ገቢር/አድርጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

በበረሃ ውስጥ የሚጮኽ የአንድ ሰው ድምፅ
ይህ እንደ አረፍተ ሀሳብ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በበረሃ ውስጥ የሚጮኽ የአንድ ሰው ድምፅ ተሰማ” ወይም “እነርሱ በበረሃ ውስጥ የሚጮኽ የአንድ ሰው ድምፅ ሰሙ”

የጌታን መንገድ አዘጋጁ፣ ጎዳናውንም አቅኑ
ሁለተኛው ትእዚያዝ ለመጀመሪያው በይበልጥ ዝርዝር ይጨምርለታል ወይም ያብራራዋል።

የጌታን መንገድ አዘጋጁ
“ለጌታ መንገዱን አዘጋጁ።” ይህን ማድረግ የጌታ መልእክት ሲመጣ ለመስማት መዘጋጀትን ይወክላል። ሰዎች ከኀጢአታቸው ንስሀ በመግባት ይህን ያደርጉታል። አማራጭ ትርጉም፦ “እርሱ ሲመጣ የጌታን መልእክት ለመስማት ተዘጋጅ” ወይም “ንስሀ ግባ፣ ለሚመጣው ጌታ የተዘጋጀህ ሁን” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መንገድ
“መተላለፊያ” ወይም “ጎዳና”

Luke 3:5

ሸለቆው ሁሉ ይሞላል... ተራራው እና ኮረብታው ሁሉ ዝቅ ይላል
ሰዎች በጣም ወደ እነርሱ እየመጣ ላለ ከፍተኛ ስልጣን ያለው ሰው መንገድ ሲያዘጋጁ፣ ከፍተኛ ቦታዎችን ይቆርጡና መንገዱ ደልዳላ እንዲሆን ዝቅተኛ ቦታዎችን ይሞላሉ። ይህ በፊተኛው ጥቅስ ውስጥ የተጀመረው ተለዋጭ ዘይቤ አካል ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሸለቆው ሁሉ ይሞላል
ይህ በገቢር/አድርጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በመንገዱ ውስጥ ዝቅተኛ ቦታውን ሁሉ ይሞላሉ” (ገቢር/አድርጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ተራራው እና ኮረብታው ሁሉ ዝቅ ይላል
ይህ በገቢር/አድርጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ተራራውን እና ኮረብታውን ሁሉ ደልዳላ ያደርጋሉ” ወይም “በመንገዱ ውስጥ ከፍተኛ ቦታውን ሁሉ ያስወግዳሉ” (ገቢር/አድርጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔርን ማዳን ማየት
ይህ እንደ ድርጊት ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር እንዴት ሰዎችን ከኃጢአት እንደሚያድን ማወቅ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 3:7

በእርሱ ለመጠመቅ
ይህ በገቢር/አድርጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ዮሐንስ እነርሱን እንዲያጠምቃቸው” (ገቢር/አድርጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ የእፉኝት ልጆች
ይህ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። እዚህ ላይ “ልጆች” “የወላጆቹ ባህርይ ያለው” ማለት ነው። እፉኝቶች ክፋትን የሚወክሉ እና አደገኛ የሆኑ መርዛማ እባቦች ናቸው። አማራጭ ትርጉም፦ “እናንተ ክፉ መርዛማ እባቦች” ወይም “እናንተ እንደ መርዛማ እባብ ክፉ ናችሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ማን አስጠነቀቃችሁ... ከሚመጣው?
እርሱ በእርግጥ መልስ እንዲሰጡ እየጠበቀ አልነበረም። ዮሐንስ ህዝቡን እየገሰፀ ነበር ምክንያቱም እግዚአብሔር እንዳይቀጣቸው እነርሱን እንዲያጠምቅ እየጠየቁት ነበር ነገር ግን ኃጢአት መስራታቸውን ማቆም አልፈለጉም። አማራጭ ትርጉም፦ “ከእግዚአብሔር ቁጣ በእንዲህ ዓይነት መንገድ መሸሸ አትችሉም!” ወይም “ከእግዚአብሔር ቁጣ በመጠመቅ ብቻ ማምለጥ አትችሉም!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ከሚመጣው ቁጣ
“ቁጣ” የሚለው ቃል እዚህ ላይ የእግዚአብሔርን ቅጣት ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል ምክንያቱም የእርሱ ቁጣ ይቀድመዋል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር እየላከ ካለው ቅጣት” ወይም “እርሱ ሊተገብረው ካለው ከእግዚአብሔር ቁጣ” (ምትክ ስም እና ገቢር/አድርጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 3:8

ለንስሀ የሚገባ ፍሬ አፍሩ
በዚህ ተለዋጭ ዘይቤ ውስጥ፣ የሰው ባህርይ ከፍሬ ጋር ተነፃፅሯል። ልክ ተክል ለተክሉ አይነት ተገቢ የሆነ ፍሬ እንዲያፈራ እንደሚጠበቅ ሁሉ እርሱ ንስሀ እንደገባ የሚናገር ሰው በፅድቅ እንዲኖር ይጠበቃል።. አማራጭ ትርጉም፦ “ንስሀ እንደገባህ የሚያሳይ የፍሬ አይነት አፍራ“ ወይም “ከኃጢአትህ መመለሰስህን የሚያሳዩ መልካም ነገሮችን አድርግ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በልባችሁ መናገር
“ለራሳችሁ መናገር” ወይም “ማሰብ”

አብርሀም አባታችን አለን
“አብርሀም የእኛ የዘር ግንድ ነው” ወይም “እኛ የአብርሀም ተወላጅ ነን።” ይህንን ለምን እንደሚሉ ግልፅ ካልሆነ፣ የተጠቀሰውን መረጃ ደግሞ መጨመር ትችላለህ፦ “እግዚአብሔር እኛን እንዳይቀጣን” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለአብርሃም ልጆች ማስነሳት
“ለአብርሃም ልጆች መፍጠር”

ከእነዚህ ድንጋዮች
ዮሐንስ ምናልባትም በዮርዳኖስ ባህር ያሉትን ትክክለኛ ድንጋዮች እያመለከተ ነበር።

Luke 3:9

ምሳር በዛፎች ስር ተቀምጧል
የዛፎችን ስር መቁረጥ እንዲችል ቦታው ላይ ያለ ምሳር ሊጀምር ስላለው ቅጣት ተለዋጭ ዘይቤ ነው። በገቢር/አድርጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ምሳሩን በዛፎች ስር እንዳስቀመጠ ሰው እንደዛው

ነው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ማንኛውም ዛፍ... ይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል
እዚህ ላይ “እሳት” ለቅጣት ተለዋጭ ዘይቤ ነው። ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እርሱ ማንኛውንም ዛፍ ይቆርጣል... እናም ወደ እሳት ውስጥ ይጥለዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 3:10

አያያዥ ሀሳብ፦
ዮሐንስ ሰዎች ከህዝቡ ውስጥ ለሚጠይቁት ጥያቄዎች መልስ መስጠት ጀመረ።

እርሱን ጠየቁት፣ እንዲህ እያሉ
x

Luke 3:12

ለመጠመቅ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ዮሐንስ እነርሱን እንዲያጠምቃቸው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ተጨማሪ ገንዘብ አትሰብስቡ
“ተጨማሪ ገንዘብ አትጠይቁ” ወይም “ተጨማሪ ገንዘብ አትውሰዱ።” ቀረጥ ሰብሳቢዎች መሰብሰብ ከነበረባቸው ገንዘብ ተጨማሪ እየሰበሰቡ ነበር። ዮሐንስ ያንን ማድረግ እንዲያቆሙ ነገራቸው።

እንድትሰበስቡ ከታዘዛችሁት
ይህ የቀረጥ ሰብሳቢዎቹ ስልጣን ከሮም እንደመጣ ለማሳየት ተገብሮ/ተሳቢ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ሮማውያን እንድትወስዱ ስልጣን ከሰጧችሁ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 3:14

እኛስ? እኛ ምን ማድረግ አለብን?
“እኛ ወታደሮችስ፣ ምን ማድረግ አለብን?” “እኛ” እና “ለኛ” የሚሉት ቃላት ውስጥ ዮሐንስ አልተካተተም። ወታደሮቹ ዮሐንስ ለሰተበሰበው ህዝብ እና ለቀረጥ ሰብሳቢዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንደተናገረ አመልክተዋል እነርሱም እንደ ወታደሮች ምን እንደሚያደርጉ ማወቅ ይፈልጋሉ። (አግላይ እና አካታች “እኛ” የሚለውን ይመልከቱ)

ማንንም በሐሰት አትክሰሱ
ወታደሮቹ ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ በሰዎች ላይ ሐሰተኛ ክስ እያዘጋጁ የነበረ ይመስላል። ይህ በትክክል ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በተመሳሳይ መንገድ፣ ከእነርሱ ገንዘብ ለማግኘት ማንንም ሰው በሀሰት አትክሰሱ” ወይም “ንፁሁን ሰው ህገወጥ ነገር ሰርቷል ብላችሁ አትናገሩ”

ደመወዛችሁ ይብቃችሁ
“በክፍያችሁ የረካችሁ ሁኑ”

Luke 3:15

ሕዝቡም
“ምክንያቱም ሕዝቡ።” ይህ ወደ ዮሐንስ መጥተው የነበሩትን ሰዎች ያመለክታል።

ሁሉም ሰዎች በልባቸው ስለ ዮሐንስ፣ ይህ ክርስቶስ ይሆንን ብለው ሲያስቡ ነበር
“ሁሉም ሰው ስለ ዮሐንስ ምን ማሰብ እንዳለበት እርግጠኛ አልነበረም፤ ራሳቸውንም “እርሱ ክርስቶስ ይሆንን?” ብለው ጠየቁ” ወይም “ማንም ሰው ስለ ዮሐንስ ምን ማሰብ እንዳለበት እርግጠኛ አልበነረም ምክንያቱም እርሱ ምናልባት ክርስቶስ ይሆናል ብለው እያሰቡ ነበር።”

የሐንስ ለሁሉም እንዲህ ሲል መለሰላቸው
ታላቅ ሰው ስለ መምጣቱ ዮሐንስ የሰጠው መልስ ዮሐንስ ክርስቶስ እንዳልሆነ በግልፅ ያመለክታል። ይህንን ለአንባቢው በትክክል መግለፅ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ዮሐንስ ለሁሉም እንዲህ በማለት እርሱ ክርስቶስ እንዳልሆነ ያብራራል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ በውሀ አጠምቃችኋለሁ
“እኔ ውሀን በመጠቀም አጠምቃለሁ” ወይም “እኔ በውሀ አማካኝነት አጠምቃለሁ”

የእርሱን ጫማ ጠፍር እንኳ ለመፍታት የማይገባኝ
“የእርሱን ጫማ ጠፍር እንኳን ለማላላት በቂ ያልሆንሁ።” የጫማን ጠፍር መፍታት የባሪያ ተግባር ነበር። የሚመጣው እርሱ በጣም ታላቅ ስለሆነ ዮሐንስ የእርሱ ባሪያ ለመሆን እንኳን የሚገባ እንዳልሆነ እየተናገረ ነበር።

እርሱ በመንፈስ ቅዱስ እና በእሳት ያጠምቃችኋል
ይህ ተለዋጭ ዘይቤ ሰውን ከውሀ ጋር የሚያገናኘውን የውሀ ጥምቀት እነርሱን ከመንፈስ ቅዱስ እና ከእሳት ጋር ከሚያገናኘው መንፈሳዊ ጥምቀት ጋር ያወዳድራል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እሳት
እዚህ ላይ “እሳት” የሚለው ቃል ሊያመለክት የሚችለው 1) ፍርድ ወይም 2) ማንጻት። “እሳት” የሚልወን እንዳለ መተው ይመረጣል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 3:17

መንሹም በእጁ ነው
“መንሽ ይዟል ምክንያቱም እርሱ ዝግጁ ነው።” ዮሐንስ ክርስቶስ በህዝብ ላይ ለመፍረድ ስለመምጣቱ ሲናገር እርሱ የስንዴውን ፍሬ ከገለባው ለመለየት የተዘጋጀ ገበሬ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “እርሱ ዝግጁ እንደሆነ ገበሬ በህዝብ ላይ ለመፍረድ ዝግጁ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መንሽ
ይህ የስንዴውን ፍሬ ከገለባው ለመለየት ስንዴውን ወደ አየር የሚበትን መሳሪያ ነው። ከባድ ፍሬዎች ወደ ታች ይወድቃሉ የማይፈለገው ገለባ ደግሞ በንፋስ ይወሰዳል። ከሹካ መሰል ማበጠርያ ጋር ተመሳሳይ ነው።

አውድማውንም ፈፅሞ ያጠራል
አውድማ የመውቃት ዝግጅት ላይ ስንዴው የሚከመርበት ቦታ ነበር። አውድማውን “ማጥራት” ፍሬዎቹን ወቅቶ መጨረስ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የእርሱን ፍሬዎች ወቅቶ መጨረስ”

ስንዴውን ይሰበስባል
ስንዴው የሚጠበቅ እና የሚከማች ተቀባይነት ያለው አዝመራ ነው።

ገለባውን ያቃጥለዋል
ገለባው ለምንም ጠቃሚ አይደለም፣ ስለዚህ ሰዎች ያቃጥሉታል።

Luke 3:18

አጠቃላይ መረጃ፦
x

Luke 3:21

አያያዥ ሀሳብ፦
ኢየሱስ አገልግሎቱን የጀመረው በጥምቀቱ ነው።

አጠቃላይ መረጃ፦
የቀደመው ጥቅስ ሄሮድስ ዮሐንስን ወህኒ ቤት አስገባው ይላል። በቁጥር 21 ላይ የጀመረው መግለጫ ዮሐንስ ከመታሰሩ በፊት የተከሰተ እንደሆነ ግልፅ ማድረግ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ዩዲቢ የሚባለው ትርጉም ቁጥር 21ን “ነገር ግን ዮሐንስ ወህኒ ቤት ከመግባቱ በፊት” ብሎ በመጀመር ግልጽ ያደርገዋል። (የሁነቶች ቅደም ተከተል የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ሆነ
ይህ ሀረግ በታሪኩ ውስጥ የአዲስ ክስተት ጅማሬን ያመላክታል። የአንተ ቋንቋ ይህንን ለማድረግ መንገድ ካለው፣ እርሱን እዚህ ላይ ለመጠቀም ማሰብ ትችላለህ። (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

ህዝቡም ሁሉ ከተጠመቁ በኋላ
“ዮሐንስ ህዝቡን ሁሉ ባጠመቀበት ጊዜ።” “ህዝቡ ሁሉ” የሚለው ሀረግ ከዮሐንስ ጋር የነበሩትን ህዝብ ያመለክታል። (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ኢየሱስ ደግሞ ተጠመቀ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ዮሐንስ ደግሞ ኢየሱስን አጠመቀው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰማይ ተከፈተ
“ሰማይ ክፍት ሆነ።” ይህ ከተራ የደመና መጥራት የበለጠ ነው፣ ነገር ግን ምን ማለት እንደሆነ ግልፅ አይደለም። ምናልባትም በሰማይ ውስጥ ቀዳዳ ታየ ማለት ነው።

መንፈስ ቅዱስም በአካል መልክ እንደ ርግብ በእርሱ ላይ ወረደ
“መንፈስ ቅዱስ በሰውነት ቅርፅ በኢየሱስ ላይ እንደ ርግብ ወረደ”

ድምፅ ከሰማይ መጣ
እዚህ ላይ “ድምፅ ከሰማይ መጣ” የሚለው ሰዎች በምድር ላይ ሆነው እግዚአብሔር ከሰማይ ሲናገር መስማታቸውን ይወክላል። እግዚአብሔር ለኢየሱስ ተናገሮ እንደነበረ ግልፅ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ድምፅ ከሰማይ ተናገረ” ወይም “እግዚአብሔር ከሰማይ ኢየሱስን እንዲህ በማለት ተናገረ” (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ልጄ
ይህ ለኢየሱስ አስፈላጊ ስም ነው፣ የእግዚአብሔር ልጅ። (ልጅ እና አባትን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 3:23

አጠቃላይ መረጃ፦
ሉቃስ የኢየሱስን የዘር ግንድ አባቱ ነው ተብሎ በሚታሰበው በዮሴፍ መስመር በኩል ይዘረዝራል።

በጀመረበት ጊዜ
እዚህ ላይ ይህ ሀረግ ጥቅም ላይ የዋለው መረጃው ከታሪክ ወደ ኢየሱስ እድሜ እና የዘር ግንድ የጀርባ ታሪክ መለወጡን ለማመልከት ነው። (የጀርባ ታሪክ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰላሳ አመታት እድሜ
“30 አመት” (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ የዮሴፍ ልጅ ነበር (እንደመሰላቸው)
“እርሱ የዮሴፍ ልጅ እንደሆነ ይታሰብ ነበር” ወይም “ሰዎች እርሱ የዮሴፍ ልጅ ነው ብለው ያምኑ ነበር”

የኤሊ ልጅ፣ የማቲ ልጅ፣ የሌዊ ልጅ
በአንተ ቋንቋ ሰዎች በብዛት የዘር ግንድ እንዴት እንደሚዘረዝሩ አስብ። በሙሉ ዝርዝሩ ውስጥ አንድ አይነት አፃፃፍ መጠቀም አለብህ። ሊሆኑ የሚችሉ አቀራረቦች 1) “የኤሊ ልጅ ማን ነበር፣ የማቲ ልጅ ማን ነበር፣ የሌዊ ልጅ ማን ነበር” ወይም 2) “ዮሴፍ የኤሊ ልጅ ነበር፣ ኤሊ የማቲ ልጅ ነበር፣ ማቲ የሌዊ ልጅ ነበር” ወይም 3) “የኤሊ አባት ማቲ ነበር፣ የማቲ አባት ሌዊ ነበር” (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 3:25

የማታትዩ ልጅ፣ የአሞፅ ልጅ... ዮዳ
ይህ የኢየሱስ የዘር ግንድ ዝርዝር ቀጣይ ነው። የፊተኛው ቁጥር ላይ የተጠቀምክበትን አንድ አይነት አቀራራብ ተጠቀም። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 3:27

የዮናን ልጅ፣ የሬስ ልጅ... ሌዊ
ይህ የኢየሱስ የዘር ግንድ ዝርዝር ቀጣይ ነው። የፊተኛው ቁጥር ላይ የተጠቀምክበትን አንድ አይነት አቀራራብ ተጠቀም። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

የሰላትያል ልጅ
ሰላትያል የሚለው ስም ሺያልትያል ለሚለው ስም ሌላ የቃላት አፃፃፍ ሊሆን ይችላል (አንዳንድ የእንግሊዘኛ ትርጉሞች እንደሚጠቀሙት)፣ ነገር ግን በሚገባ መለየት አስቸጋሪ ነው።

Luke 3:30

የስምኦን ልጅ፣ የይሁዳ ልጅ... ነአሶን
ይህ የኢየሱስ የዘር ግንድ ዝርዝር ቀጣይ ነው። የፊተኛው ቁጥር ላይ የተጠቀምክበትን አንድ አይነት አቀራራብ ተጠቀም። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 3:33

የአሚናዳብ ልጅ፣ የአድሚን ልጅ... ሳላ
ይህ የኢየሱስ የዘር ግንድ ዝርዝር ቀጣይ ነው። የፊተኛው ቁጥር ላይ የተጠቀምክበትን አንድ አይነት አቀራራብ ተጠቀም። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 3:36

የቃይንም ልጅ፣ የአርፋክስድ ልጅ... አዳም
ይህ የኢየሱስ የዘር ግንድ ዝርዝር ቀጣይ ነው። የፊተኛው ቁጥር ላይ የተጠቀምክበትን አንድ አይነት አቀራራብ ተጠቀም። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

አዳም፣ የእግዚአብሔር ልጅ
“አዳም፣ በእግዚአብሔር የተፈጠረ” ወይም “አዳም፣ ከእግዚአብሔር የነበረ” ወይም “አዳም፣ የእግዚአብሔር ልጅ፣ ማለት የምንችለው”

ምዕራፍ 4

1 ከዚያ በኋላ፣ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ከዮርዳኖስ ወንዝ ተመለሰ፤ መንፈስም ወደ ምድረ-በዳ መራው። 2 በዚያም ለአርባ ቀናት በዲያብሎስ
ተፈተነ። በእነዚያም ቀናት ምንም አልበላም፣ ያም ወቅት በተጠናቀቀ ጊዜ ተራበ። 3 ዲያብሎስም፣ “የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ ይህ ድንጋይ እንጀራ እንዲሆን
እዘዝ” አለው። 4 ኢየሱስም፣ “’ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም’ ተብሎ ተጽፎአል።” ብሎ መለሰለት። 5 ከዚያ በኋላም ዲያብሎስ ከፍ ወዳለ ስፍራ ወሰደውና፣
በቅጽበት የዓለም መንግሥታትን ሁሉ አሳየው። 6 ዲያብሎስም ለእርሱ፣ “እነዚህን ሁሉ መንግሥታት ከክብራቸው ሁሉ ጋር እንድትገዛ እኔ ሥልጣን እሰጥሃለሁ፤
ይህንን ማድረግ የምችለው እገዛቸው ዘንድ ለእኔ ስለተሰጠኝ ነው፣ እኔም ለምፈልገው ለማንኛውም ሰው ልሰጣቸው እችላለሁ። 7 ስለዚህ በፊቴ ብትሰግድልኝና
ብታመልከኝ፣ ይሄ ሁሉ የአንተ ይሆናል አለው። 8 ኢየሱስ ግን እንደዚህ ብሎ መለሰለት፣ “’እግዚአብሔር አምላክህን አምልክ፣ እርሱንም ብቻ አገልግል’ ተብሎ
ተጽፎአል።” 9 ከዚህ በኋላ ዲያብሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ወስዶ በቤተ መቅደሱ ሕንፃ እጅግ ከፍተኛ ስፍራ አቆመውና፣ 10 “’ይጠብቁህና ይንከባከቡህ ዘንድ
መላእክቱን ስለ አንተ ያዛቸዋል’ 11 ደግሞም፣ ‘እግርህም ከድንጋይ ጋር እንዳይጋጭ በእጆቻቸው ወደ ላይ ይይዙሃል’ ተብሎ ተጽፎአልና፣ የእግዚአብሔር ልጅ
ከሆንክ ራስህን ከዚህ ላይ ወርውር።” አለው። 12 ኢየሱስም፣ “’እግዚአብሔር አምላክህን መፈታተን የለብህም’ ተብሎአል።” ብሎ መለሰለት። 13
ዲያብሎስም ኢየሱስን መፈተኑን ባበቃ ጊዜ፣ እስከ ሌላ ጊዜ ድረስ ትቶት ሄደ። 14 ከዚያ በኋላ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተሞልቶ ወደ ገሊላ ተመለሰ፤
በዚያ አካባቢ በነበሩት ስፍራዎች ሁሉ የእርሱ ዝና ተሰራጨ። 15 በምኩራቦቻቸው አስተማረ፣ ሰዎችም ሁሉ ያመሰግኑት ነበር። 16 አንድ ቀንም ወዳደገበት
ከተማ ወደ ናዝሬት መጣ። እንደ ልማዱም በሰንበት ቀን ወደ ምኩራብ ገባ፣ የእግዚአብሔርንም ቃል ያነብ ዘንድ ቆመ። 17 የነቢዩ የኢሳይያስ የመጽሐፍ ጥቅልል
ተሰጥቶት ስለነበረ፣ ጥቅልሉን ሲከፍተው፣ 18 “ለድሆች የምሥራቹን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤ ለምርኮኞች ነፃነትን፣
ለዕውሮች ብርሃናቸው እንደሚመለስላቸው ፣ የተጨቆኑትም መፈታትን እንደሚያገኙ 19 የእግዚአብሔርን የሞገስ ዓመት ዐውጅ ዘንድ ልኮኛል።” የሚለውን
ስፍራ አገኘ። 20 ከዚያ በኋላ የመጽሐፉን ጥቅልል ዘጋና ለምኩራቡ አገልጋይ ሰጥቶ ተቀመጠ። 21 “እናንተ እየሰማችሁ ይህ የእግዚአብሔር ቃል ተፈጸመ።”
እያለ ሊነግራቸው ጀመረ። 22 በዚያ የነበሩ ሰዎች ሁሉ የተናገረውን አስተዋሉ፣ ከአንደበቱም በሚወጣው የጸጋ ቃል ሁሉም ተገረሙ። እነርሱም፣ “ይህ የዮሴፍ
ልጅ ነው፣ አይደለም እንዴ?” ይሉ ነበር። 23 ኢየሱስም፣ “በእርግጥ ‘ሐኪም ሆይ፣ ራስህን አድን፤ በቅፍርናሆም እንደምታደርግ የሰማነውን በዚህም በትውልድ
ከተማህ አድርግ’ የሚለውን ይህንን ምሳሌ ትመስሉብኛላችሁ።” 24 ደግሞም እንደዚህ አላቸው፣ “እውነት እላችኋለሁ፣ ማንኛውም ነቢይ በገዛ አገሩ ተቀባይነት
የለውም። 25 ነገር ግን እኔ እውነት እላችኋለሁ፣ ለሦስት ዓመታት ተኩል ሰማይ ተዘግቶ ዝናብ ባልነበረበትና በምድሪቱም ሁሉ ረሃብ በነበረበት በኤልያስ ዘመን
በእስራኤል ብዙ መበለቶች ነበሩ። 26 ነገር ግን ኤልያስ በሲዶና አጠገብ በሰራፕታ ትኖር ወደነበረችው መበለት ብቻ እንጂ ከእነርሱ ወደ አንዲቱም
አልተላከም። 27 በነቢዩ በኤልሳዕ ዘመንም በእስራኤል ብዙ ለምጻሞች ነበሩ፣ ነገር ግን ከሶርያዊው ከንዕማን በቀር ከእነርሱ አንዳቸውም አልተፈወሱም።” 28
በምኩራብ የነበሩት ሰዎች ሁሉ እነዚህን ነገሮች በሰሙ ጊዜ በቁጣ ተሞሉ። 29 ተነሥተው ከከተማይቱ እንዲወጣ አስገደዱት፣ ከገደል ጫፍም ገፍትረው
ይጥሉት ዘንድ ከተማይቱ ወደ ተመሠረተችበት ወደ ኮረብታው ጫፍ ገፍተው ወሰዱት። 30 ነገር ግን በመካከላቸው አልፎ ጉዞውን ቀጠለ። 31 ከዚያ በኋላም
በገሊላ ወደምትገኝ ወደ ቅፍርናሆም ከተማ ሄደ። 32 በሥልጣን ይናገር ስለነበረ፣ በትምህርቱ ተገረሙ። 33 በዚያን ቀን በምኩራብ ውስጥ ርኩስ መንፈስ
የነበረበት ሰው ነበረ፤ እርሱም በታላቅ ድምፅ ጮኸ። 34 “የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ፣ ከአንተ ጋር ምን አለን? ልታጠፋን መጣህን? ማን እንደሆንክ አውቄሃለሁ፣
አንተ የእግዚአብሔር ቅዱስ ነህ።” 35 ኢየሱስም ጋኔኑን፣ “ፀጥ ብለህ ከእርሱ ውጣ!” ብሎ ገሠጸው። ጋኔኑ በሰዎቹ መካከል በጣለው ጊዜ፣ ምንም ጉዳት
ሳያደርስበት ከእርሱ ወጣ። 36 ሰዎች ሁሉ በጣም ተደነቁ፣ እርስ በርሳቸውም ስለሆነው ነገር መነጋገር ቀጠሉ። እነርሱም፣ “እነዚህ እንዴት ያሉ ቃላት ናቸው?
ርኩሳን መናፍስትን በሥልጣንና በኃይል ያዛቸዋል፣ እነርሱም ይወጣሉ።” 37 የእርሱም ዝና በአካባቢው ባሉት አውራጃዎች በማንኛውም ስፍራ ወጣ። 38
ከዚያ በኋላ ኢየሱስ ከምኩራብ ወጥቶ ወደ ስምዖን ቤት ገባ። በዚያን ጊዜ የስምዖን አማት በከፍተኛ ትኩሳት ታማ ነበር፣ እነርሱም ስለ እርሷ ተማፀኑት። 39
ስለዚህ በአጠገብዋ ቆሞ ትኩሳቱን ገሠጸው፣ ትኩሳቱም ቆመ። ወዲያውኑም ተነሥታ ልታገለግላቸው ጀመረች። 40 ፀሐይም በጠለቀች ጊዜ ሰዎች በተለያዩ
ደዌዎች የተያዙትን በሽተኞች ወደ እርሱ አመጡ። እርሱም እጆቹን በእያንዳንዳቸው ላይ ጭኖ ፈወሳቸው። 41 አጋንንትም፣ “አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ”
እያሉ በመጮኽ ከብዙዎች ወጡ። ኢየሱስ አጋንንትን ገሠጻቸው፣ እንዲናገሩም አልፈቀደላቸውም፣ ምክንያቱም እርሱ ክርስቶስ መሆኑን አውቀው ነበርና። 42
ንጋትም በሆነ ጊዜ ወደ ገለልተኛ ስፍራ ሄደ። ብዙ የሕዝብ አጀብ እየፈለጉት ነበርና፣ እርሱ ወደነበረበት ስፍራ መጡ። እነርሱንም ትቷቸው እንዳይሄድ ሊያስቀሩት
ሞከሩ። 43 እርሱ ግን እንደዚህ አላቸው፣ “የእግዚአብሔርን መንግሥት የምሥራች ለብዙ ከተሞች መስበክ ይገባኛል፣ ምክንያቱም ወደዚህ የተላክሁት ለዚህ
ነው።” 44 ከዚያ በኋላ በመላው ይሁዳ ባሉት ምኩራቦች መስበኩን ቀጠለ።

Luke 4:1

አያያዥ ሀሳብ፦
ኢየሱስ ለ40 ቀን ፆመ፣ ዲያቢሎስም ኃጢአት እንዲያደርግ እርሱን ማሳመን ለመሞከር ተገናኘው።

ከዚያም ኢየሱስ
የሐንስ ኢየሱስን ካጠመቀው በኋላ። (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

በመንፈስ ተመርቶ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “መንፈስ እርሱን መራው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ለ**40** ቀን ተፈተነ
ብዙ እትሞች የተፈተነው 40 ቀኑን በሙሉ ነው ይላሉ። ይህንን ግልፅ ለማድረግ ዩዲቢ የሚባለው ትርጉም “እርሱ እዚያ በነበረበት ጊዜ፣ ዲያቢሎስ እርሱን መፈተን ቀጥሏል” ብሎ ገልፆታል።

አርባ ቀን
“40 ቀን” (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 4:3

የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ
ዲያቢሎስ ኢየሱስ “የእግዚአብሔር ልጅ” እንደሆነ ለማረጋገጥ ይህንን ተአምራት እንዲያደርግ ተገዳደረው። (ልጅ እና አባትን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይህ ድንጋይ
ዲያቢሎስ በእጁ ድንጋይ ይዟል ወይም በአቅራቢያው ወዳለ ድንጋይ ጠቁሟል።

ኢየሱስ መለሰለት፣ “. . . ብቻ . . . ተብሎ ተፅፏል።”
ኢየሱስ የዲያቢሎስን ተግዳሮት አለመቀበሉ በመልሱ ላይ በግልፅ ይታያል። ዩዲቢ የሚባለው ትርጉም እንዳደረገው፣ ለአንባቢዎችህ ይህንን በትክክል መግለፅ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ኢየሱስ ‘አይሆንም፣ ይህንን አላደርግም ምክንያቱም . . . ብቻ . . . ተብሎ ተፅፏል’ ብሎ መለሰ።” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ተፅፏል
የተጠቀሰው በብሉይ ኪዳን ከሙሴ ፅሁፎች ውስጥ ነው። ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሙሴ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ፅፏል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም
“እንጀራ” የሚለው ቃል በአጠቃላይ ምግብን ያመለክታል። ምግብ ከእግዚአብሔር ጋር ሲወዳደር፣ ብቻውን፣ ሰውን በህይወት ለማቆየት በቂ አይደለም። ኢየሱስ ለምን ድንጋዩን ወደ እንጀራ እንደማይቀይር ለመናገር መጽሐፍ ቅዱስን ጠቀሰ። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች በእንጀራ ብቻ መኖር አይችሉም” ወይም “ሰውን እንዲኖር የሚያደርገው እንጀራ ብቻ አይደለም” ወይም “እግዚአብሔር ከእንጀራ ይበልጥ ጠቃሚ የሆኑ ነገሮች አሉ ብሏል” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 4:5

ኢየሱስን መራው
እርሱ በተራራ ላይ ኢየሱስን መራው። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በቅፅበታዊ ጊዜ
“በቅፅበት” ወይም “ባንዳፍታ”

እነርሱ ለእኔ ተሰጥተዋል
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች “እነርሱ” የሚለው የሚያመለክተው 1) የግዛቶቹ ስልጣን እና ውበት ወይም 2) ግዛቶቹ። አማራጭ ትርጉም፡- “ እግዚአብሔር እነርሱን ለእኔ ሰጥቶኛል “ (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የምትሰግድ ከሆነ... የምታመልከኝ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በጣም ተመሳሳይ ናቸው። መጣመር ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔን ለማምለክ የምትሰግድ ከሆነ” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ ይሆናል
“እነዚህን ሁሉ ግዛቶች ከነ ውበታቸው ለአንተ እሰጥሀለሁ”

Luke 4:9

በጣም ከፍተኛ ቦታ
ይህ የቤተ መቅደስ ጣሪያ ጠርዝ ነበር። አንድ ሰው ከዚህ ከወደቀ፣ በጠና ይጎዳል ወይም ይሞታል።

የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ
ዲያቢሎስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እንዲያረጋግጥ እየተገዳደረው ነው።

የእግዚአብሔር ልጅ
ይህ ለኢየሱስ ጠቃሚ ስም ነው። (ልጅ እና አባትን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

ራስህን ወርውር
“ወደ መሬት ዝለል”

ተብሎ ተፅፏልና
ከመዝሙረ ዳዊት የጠቀሰው ጥቅስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆነ እርሱ አይጎዳም ማለት እንደሆነ ዲያቢሎስ ያመለክታል። ዩዲቢ የሚባለው ትርጉም እንዳደረገው፣ ይህ በትክክል ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ አትጎዳም፣ ምክንያቱም ተብሎ ተፅፏል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ተፅፏል
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጸሐፊው ፅፏል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ትእዛዝ ይሰጣል
“እርሱ” እግዚአብሔርን ያመለክታል። ዲያቢሎስ ኢየሱስ ከህንፃው እንዲዘል ለማሳመን በመጣር ከመዝሙረ ዳዊት ጥቅስ በከፊል ጠቅሷል።

Luke 4:12

ተብሎአል
ኢየሱስ ለምን ዲያቢሎስ እርሱ እንዲያደርግ የነገረውን እንደማያደርግ ለዲያቢሎስ ተናገረ። የእርሱ ለማድረግ ፈቃደኛ አለመሆን በትክክል ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አይሆንም፣ ይህን አላደርግም፣ ምክንያቱም ተብሎአል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ተብሎአል
ኢየሱስ ከኦሪት ዘዳግም ውስጥ የሙሴን ፅሁፍ ጠቀሰ። ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሙሴ ብሏል” ወይም “ሙሴ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብሏል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ጌታን አምላክህን አትፈታተነው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ኢየሱስ ከቤተ መቅደሱ በመዝለል እግዚአብሔርን መፈታተን የለበትም፣ ወይም 2) ዲያቢሎስ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ለማየት ኢየሱስን መፈታተን የለበትም። ይህንን ጥቅስ ትርጉሙን ለማብራራት ከመሞከር ይልቅ እንደ ተገለፀው መተርጎም የተሻለ ነው።

ሌላ ጊዜ እስከሚመጣ
“ሌላ አመቺ ጊዜ እስከሚገኝ”

ኢየሱስን መፈተን ጨረሰ
ይህ ዲያቢሎስ በፈተናው ስኬታማ ነበር የሚል መልእክት አያስተላልፍም። ኢየሱስ እያንዳንዱ ሙከራውን ተቋቁሟል። ይህ በትክክል ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ኢየሱስ ኃጢአት እንዲያደርግ ለማሳመን መሞከሩን ጨረሰ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 4:14

አያያዥ ሀሳብ፡-
ኢየሱስ ወደ ገሊላ ተመለሰ፣ በምኩራብ አስተማረ፣ እዚያ ላሉ ሰዎችም እርሱ የነቢዩ ኢሳይያስን ትንቢት እየፈፀመ እንደሆነ ነገራቸው።

ከዛም ኢየሱስ ተመለሰ
ይህ በታሪኩ ውስጥ አዲስ ሁነትን ይጀምራል። (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

በመንፈስ ኃይል
“መንፈስም ኃይል እየሰጠው ነበር።” የሰው ልጆች በተለምዶ ማድረግ የማይችሉትን ነገር እንዲያደርግ እያስቻለው፣ እግዚአብሔር በልዩ መንገድ ከኢየሱስ ጋር ነበር።

የእርሱ ዝና ተስፋፋ
“ስለ ኢየሱስ ሰዎች ዝናውን አስፋፉ” ወይም “ሰዎች ለሌሎች ሰዎች ስለ ኢየሱስ ተናገሩ” ወይም “ስለ እርሱ ያለ እውቀት ከሰው ወደ ሰው ተላለፈ።” ኢየሱስን የሰሙ ሰዎች ለሌላ ሰዎች ስለ እርሱ ተናገሩ፣ ከዚያም እነዚህ ሌላ ሰዎች ለበለጡ ሌላ ሰዎች ስለ እርሱ ተናገሩ።

በዙሪያው ላለው ሀገር በሙሉ
ይህ በገሊላ ዙሪያ ያሉ ቦታዎችን እና አካባቢዎችን ያመለክታል።

እርሱ በሁሉም ተመሰገነ
“እያንዳንዱ ሰው ስለ እርሱ ታላቅ ነገርን ተናገረ” ወይም “ሁሉም ሰው ስለ እርሱ በመልካም መንገድ ተናገረ”

Luke 4:16

እርሱ ያደገበት
“ቤተሰቦቹ እርሱን ያሳደጉበት” ወይም “ልጅ እያለ የኖረበት”

ልማዱ እንደነበረው
“በእያንዳንዱ ሰንበት እንደሚያደርገው።” በሰንበት ቀን ወደ ምኩራብ መሄድ የእርሱ የአብዛኛውን ጊዜ ልምምድ ነበር።

የነቢዩ ኢሳይያስ መጽሐፍ ተሰጠው
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አንድ ሰው የነቢዩ ኢሳይያስን መጽሐፍ ሰጠው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የነቢዩ ኢሳይያስ መጽሐፍ
ይህ በብራና ላይ የተፃፈውን የኢሳይያስን መጽሐፍ ያመለክታል። ኢሳይያስ መልእክቱን ከብዙ አመት በፊት ፅፎታል፣ እናም ሌላ ሰው ፅሁፎቹን ወደ ብራና ገልብጧል።

የተፃፈበት ስፍራ
“እነኚህ ቃላቶች ያሉበት የብራናው ስፍራ።” ይህ አረፍተ ነገር ወደ ቀጣዩ ቁጥር ይቀጥላል።

Luke 4:18

የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው
“መንፈስ ቅዱስ በልዩ መንገድ ከእኔ ጋር ነው።” አንድ ሰው ይህንን ሲል፣ የእግዚአብሔርን ቃል ነው የምናገረው እያለ ነው።

እርሱ ቀብቶኛል
በብሉይ ኪዳን፣ ሰው ልዩ ተግባር ለማድረግ ስልጣን እና ሀይል ሲሰጠው የስርአት መፈጸሚያ ዘይት በሰውየው ላይ ይፈስ ነበር። ኢየሱስ ይህንን ተለዋጭ ዘይቤ መንፈስ ቅዱስ እርሱን ለዚህ ስራ ለማዘጋጀት በእርሱ ላይ እንደነበር ለማመላከት ተጠቀመበት። አማራጭ ትርጉም፦ “መንፈስ ቅዱስ በኃይል ሊሞላኝ በእኔ ላይ ነው” ወይም “መንፈስ ቅዱስ ስልጣን እና ሀይልን ሰጠኝ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ድሆች
“ድሀ ሰዎች”

ለታሰሩት ነፃነትን ማወጅ
“ምርኮኛ ሆነው ለተያዙ ህዝቦች በነፃ መሄድ አንደሚችሉ መንገር” ወይም “የጦርነት ታሳሪዎችን ነፃ ማውጣት”

ለታወሩት መልሶ ማየት
“ለታወሩት ማየትን መስጠት” ወይም “የታወሩት እንደገና ማየት እንዲችሉ ማድረግ”

የተጨቆኑትን ነፃ ማውጣት
“በግፍ የሚሰቃዩትን ነፃ ማውጣት”

የተወደደውን የጌታን አመት ለማወጅ
“እግዚአብሔር ህዝቡን ለመባረክ ዝግጁ እንደሆነ ለእያንዳንዱ ሰው መናገር” ወይም “ይህ እግዚአብሔር ቸርነቱን የሚያሳይበት አመት እንደሆነ ማስታወቅ”

Luke 4:20

ብራናውን ጠቀለለው
ብራና ውስጡ ያለውን ፅሁፍ ለመጠበቅ እንደ ቱቦ በመጠቅለል ነበር የሚዘጋው።

ጠባቂ
ይህ መጽሐፍ ቅዱስ የያዙትን ብራናዎች በተገቢው ጥንቃቄ እና ክብር የሚያወጣ እና የሚያስቀምጥ የምኩራብ ሰራተኛን ያመለክታል።

Luke 4:23

አጠቃላይ መረጃ፦
ናዝሬት ኢየሱስ ያደገበት ከተማ ነው።

Luke 4:25

አጠቃላይ መረጃ፦
ኢየሱስ በምኩራብ ውስጥ ለሚያዳምጡት ህዝብ እነርሱ ስለሚያውቋቸው ነቢያት፣ ስለ ኤልያስ እና ኤልሳዕ አስታወሳቸው። (የጀርባ ታሪክ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን እውነት እላችኋለሁ
“በእውነት እነግራችኋለሁ።” ኢየሱስ ይህንን ሀረግ የተከታዩን አረፍተ ሀሳብ ጥቅም፣ እውነት እና ትክክለኛነት አፅንኦት ለመስጠት ይጠቀመዋል።

መበለቶች
መበለቶች ባሎቻቸው የሞተባቸው ሴቶች ናቸው።

በኤልያስ ዘመን
ኢየሱስ እየተናገራቸው ያሉት ህዝብ ኤልያስ ከእግዚአብሔር ነቢያት አንዱ እንደሆነ ያውቁ ነበር። አንባቢዎችህ ያንን ካላወቁ፣ ይህንን ያልተገለፀ መረጃ እንደ ዩዲቢ የሚባለው ትርጉም ግልፅ ማድረግ ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፦ “ኤልያስ በእስራኤል ውስጥ እየተነበየ በነበረበት ጊዜ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰማይ ተዘግቶ ሳለ
ይህ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። ሰማይ ከእርሱ ምንም ዝናብ እንዳይወርድ የተዘጋ ጣሪያ እንደሆነ ተደርጎ ተስሏል። አማራጭ ትርጉም፦ “ከሰማይ ምንም ዝናብ ባልወረደ ጊዜ” ወይም “ከቶ ምንም ዝናብ በሌለ ጊዜ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ታላቅ ራብ
“አሳሳቢ የምግብ እጥረት።” ራብ ሰብሎች ለህዝቡ በቂ ምግብ የማያፈሩበት ረጅም ጊዜ ነው።

ወደ ሰራፕታ… እዚያ ወደ ምትኖር መበለት
በሰራፕታ ከተማ የሚኖሩ ህዝቦች አህዛብ ነበሩ፣ አይሁድ አልነበሩም። ኢየሱስን እያዳመጡ ያሉት ሰዎች የሰራፕታ ህዝብ አህዛብ እንደሆኑ ይገባቸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰራፕታ ውስጥ ለምትኖር ከአህዛብ ወገን

የሆነች መበለት” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ እና ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ሶርያዊው ንዕማን
ሶርያዊ ከሶርያ አገር የሆነ ሰው ነው። የሶርያ ህዝቦች አህዛብ ነበሩ፣ አይሁድ አልነበሩም። አማራጭ ትርጉም፡- “ከሶሪያ የሆነው አህዛቡ ንዕማን” (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 4:28

በምኩራቡ ውስጥ የነበሩ ሰዎች ሁሉ እነዚህን ነገሮች ሲሰሙ ቁጣ ሞላባቸው
የናዝሬት ህዝብ እግዚአብሔር በአይሁድ ፋንታ አህዛብ የረዳበትን መጽሐፍ ኢየሱስ ስለጠቀሰ በእጅጉ ተናደው ነበር።

በግድ ከከተማው ወደ ውጪ አስወጡት
“ከተማውን እንዲለቅ አስገደዱት” ወይም “ከከተማው ወደ ውጪ በሀይል ገፉት”

ወደ ገደል አፋፍ
“የገደል ጠርዝ”

በመካከላቸው አልፎ ሄደ
“በተሰበሰው ህዝብ መካከል” ወይም “ እርሱን ለመግደል በሚሞክሩት ህዝብ መካከል”

ወደ ሌላ ቦታ ሄደ
“እርሱ ሄደ” ወይም “በራሱ መንገድ ሄደ” ኢየሱስ ህዝቡ እርሱ እንዲሄድ ለማስገደድ ከሚሞክሩበት ቦታ ይልቅ እርሱ ለመሄድ ያቀደበት ቦታ ሄደ።

Luke 4:31

አያያዥ ሀሳብ፦
ከዚያም ኢየሱስ ወደ ቅፍርናሆም ሄደ፣ እዚያ ምኩራብ ውስጥ ላሉ ሰዎች አስተማረ፣ ርኩስ ጋኔንም ግለሰቡን ለቆ እንዲወጣ አዘዘ።

ከዚያም እርሱ
“ከዚያም ኢየሱስ።” ይህ አዲስ ሁነትን ያመለክታል። (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ቅፍርናሆም ወረደ
“ወረደ” የሚለው ሀረግ እዚህ ላይ ጥቅም ላይ የዋለው ቅፍርናሆም ከናዝሬት በከፍታው ዝቅ ያለ ስለሆነ ነው።

ቅፍርናሆም፣ የገሊላ ከተማ
“ቅፍርናሆም፣ በገሊላ ውስጥ ሌላ ከተማ”

መገረም
በእጅጉ መደነቅ

እርሱ በሥልጣን ተናገረ
“ሥልጣን እንዳለው ሰው ተናገረ” ወይም “የእርሱ ቃላት ትልቅ ኃይል ነበራቸው”

Luke 4:33

አሁን... ሰው ነበር
ይህ ሀረግ በታሪኩ ውስጥ የአዲስ ገፀ ባህርይ መግባትን ለማመላከት ይጠቅማል፤ በዚህ ጊዜ፣ ርኩስ መንፈስ የተቆጣጠረውን ሰው። (የአዲስና የቀድሞ ተሳታፊዎች መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

ግልፅ ያልሆነ የርኩስ መንፈስ ያለበት
“ግልፅ ያልሆነ ርኩስ መንፈስ የተቆጣጠረው” ወይም “በክፉ መንፈስ ቁጥጥር ስር ያለ”

በጉልህ ድምፅ ጮኸ
“በሀይል ጮኸ”

እኛ ከአንተ ጋር ምን አለን
ይህ ጠብ አጫሪ መልስ “እኛ ምን የጋራ ነገር አለን?” ወይም “እኛን ለማስቸገር አንተ ምን መብት አለህ?” የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጥ ነው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

የናዝሬቱ ኢየሱስ፣ እኛ ከአንተ ጋር ምን አለን
ይህ ጥያቄ እንደ አረፍተ ሀሳብ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የናዝሬቱ ኢየሱስ፣ አንተ ከእኛ ጋር ምን አለህ!” ወይም “እኛ ከአንተ ጋር ምንም የለንም፣ የናዝሬቱ ኢየሱስ!” ወይም “አንተ እኛን ለማስቸገር ምንም መብት የለህም፣ የናዝሬቱ ኢየሱስ!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 4:35

ኢየሱስ ርኩስ መንፈሱን ገሰፀው፣ እንዲህ በማለት
“ኢየሱስ ርኩስ መንፈሱን ተቆጣው፣ እንዲህ በማለት” ወይም “ኢየሱስ በሀይል ርኩስ መንፈሱን ተናገረው”

ከእርሱ ወጣ
ርኩስ መንፈሱ ግለሰቡን መቆጣጠር እንዲያቆም አዘዘው። አማራጭ ትርጉም፡- “ብቻውን ተወው” ወይም “በዚህ ሰው ውስጥ ከዚህ በኋላ አትኑር”

እነዚህ ምን አይነት ቃላት ናቸው
ኢየሱስ ርኩስ መንፈስ ሰውን ትቶ እንዲወጣ ለማዘዝ ስልጣን ስላለው ህዝቡ እንዴት ተደንቀው እንደነበር እየገለፁ ነበር። ይህ እንደ አረፍተ ሀሳብ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህ ቃላት ድንቅ ናቸው!” ወይም “የእርሱ ቃላት ድንቅ ናቸው!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ግልፅ ያልሆነውን መንፈስ በስልጣን እና በሀይል አዘዘ
“እርሱ ግልፅ ያልሆነውን መንፈስ ለማዘዝ ስልጣን እና ሀይል አለው”

እንደዚሁ ስለ እርሱ ዝና መስፋፋት ጀመረ... በዙሪያ ባለ ክልል
ይህ በታሪኩ ውስጥ በተከሰቱ ክስተቶች አማካኝነት ስለተፈጠረው ነገር የሚናገር መግለጫ ነው። (የታሪክ መጨረሻ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ እርሱ ዝና መስፋፋት ጀመረ
“ስለ ኢየሱስ ወሬዎች መስፋፋት ጀመሩ” ወይም “ህዝቡ ስለ ኢየሱስ ዝና ማስፋፋት ጀመሩ”

Luke 4:38

አያያዥ ሀሳብ፦
ኢየሱስ አሁንም ቅፍርናሆም ውስጥ ነው፣ ነገር ግን አሁን የስምዖንን አማት እና ብዙ ሰዎችን በፈወሰበት በስምኦን ቤት ውስጥ ነው።

ከዚያም ኢየሱስ ሄደ
ይህ አዲስ ሁነትን ይገልፃል። (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

የስምዖን አማት
“የስምዖን ሚስት እናት”

እየተሰቃየች ነበር
ይህ “በጣም ታማ ነበር” የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጥ ነው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ኃይለኛ ትኩሳት... ትኩሳቱን ገሰፀው
x

Luke 4:40

እጆቹን ጫነ
“እጆቹን አስቀመጠ” ወይም “ነካ”

አጋንንትም ደግሞ ወጡ
ኢየሱስ አጋንንት ከተቆጣጠራቸው ሰዎች አጋንንቶች እንዲለቁ እንዳደረገ ያመለክታል። ይህ በትክክል ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ኢየሱስ ደግሞ አጋንንቶች እንዲወጡ አስገደዳቸው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መጮህ እና መናገር
እነዚህ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ምናልባትም የፍርሀት ወይም የንዴትን ጩኸትን ያመለክታሉ። አንዳንድ ትርጉሞች አንድ ስያሜን ብቻ ይጠቀማሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “መጮህ” ወይም “መንጫጫት” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 4:42

አያያዥ ሀሳብ፡-
ሕዝቡ ኢየሱስ በቅፍርናሆም እንዲቆይ ቢፈልጉም፣ በሌላ የአይሁድ ምኩራቦች ለመስበክ ሄደ።

በነጋ ጊዜ
“ፀሐይ ስትወጣ”

ጭር ያለ ቦታ
“ሰው ለቅቆ የሄደበት ቦታ” ወይም “ምንም ሰው የሌለበት ቦታ”

ለሌላ ብዙ ከተሞች
“በሌላ ብዙ ከተማ ላሉ ሰዎች”

ይህ እዚህ የተላኩበት ምክንያት ነው
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይህ እግዚአብሔር እኔን እዚህ የላከበት ምክንያት ነው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ይሁዳ
ኢየሱስ ገሊላ ውስጥ ስለነበር፣ “ይሁዳ” የሚለው ስም እዚህ ላይ ምናልባትም በዚያን ጊዜ አይሁዶች የኖሩበትን ክልል በሙሉ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “አይሁዶች የኖሩበት”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 5

1 ሕዝቡ ከበውት የእግዚአብሔርን ቃል እያዳመጡ ሳሉ፣ ኢየሱስ በጌንሳሬጥ ሐይቅ ዳር ቆሞ ነበር። 2 ሁለት ጀልባዎች በሐይቁ ጥግ በኩል ሲጎተቱ
ተመለከተ። ዓሣ አጥማጆቹ ከጀልባዎቹ ወርደው መረቦቻቸውን እያጠቡ ነበር። 3 ኢየሱስ የስምዖን ወደ ነበረችው ከጀልባዎቹ ወደ አንዲቱ ገባና ከምድር ጥቂት
ፈቀቅ አድርጎ ወደ ውሃ ውስጥ እንዲያስገባት ጠየቀው። ከዚያ በኋላም በጀልባዋ ውስጥ ተቀምጦ ሕዝቡን ማስተማር ጀመረ። 4 ንግግሩንም በጨረሰ ጊዜ
ለስምዖን፣ “ጀልባይቱን ወደ ጥልቁ ውሃ ፈቀቅ አድርጋትና ዓሣ ለማጥመድ መረቦቻችሁን ጣሉ።” አለው። 5 ስምዖንም፣ “ጌታ ሆይ፣ ሌሊቱን ሁሉ ስንሠራ
አደርን ምንም አላጠመድንም፣ ነገር ግን በቃልህ መረቡን እጥላለሁ።” ብሎ መለሰለት። 6 ይህንን ባደረጉ ጊዜ እጅግ ብዙ ዓሣ ያዙ፣ መረቦቻቸውም ሊቀደዱ
ደረሱ። 7 ስለዚህ እንዲመጡና እንዲረዷቸው በሌላ ጀልባ የነበሩትን ጓደኞቻቸውን በጥቅሻ ጠሩ። እነርሱም መጥተው ሁለቱንም ጀልባዎች እስኪሰጥሙ ድረስ
ሞሉአቸው። 8 ስምዖን ጴጥሮስ ግን ይህንን በተመለከተ ጊዜ በኢየሱስ ጉልበት ሥር ዝቅ ብሎ በመንበርከክ፣ “ጌታ ሆይ፣ እኔ ኃጢአተኛ ሰው ነኝና ከእኔ ተለይ”
አለው። 9 እንደዚህም ያለው ስላጠመዷቸው ዓሣዎች እርሱና ከእርሱ ጋር የነበሩት ሁሉ ተደንቀው ስለነበረ ነው። 10 በዚያም ከነበሩት መካከል የዘብዴዎስ
ልጆች ዮሐንስና ያዕቆብ አብረውት ነበሩ። ኢየሱስም ለስምዖን፣ “ከእንግዲህ ሰውን የምታጠምድ ትሆናለህና፣ አትፍራ።” አለው። 11 ጀልባቸውን ወደ ምድር
ባመጧት ጊዜ ሁሉንም ትተው ተከተሉት። 12 ከከተማዎቹ በአንዲቱ በነበረ ጊዜ፣ መላ ሰውነቱ በለምጽ የተመታ ሰው በዚያ ነበረ። ኢየሱስንም ባየ ጊዜ በፊቱ
ወድቆ፣ “ብትፈቅድስ፣ ልታነጻኝ ትችላለህ።” ብሎ ለመነው። 13 በዚያን ጊዜ ኢየሱስ እጁን ዘርግቶ ዳሰሰውና፣ “እፈቅዳለሁ፣ ንጻ” አለው። ወዲያውኑም ለምጹ
ከእርሱ ተወገደ። 14 ለማንም እንዳይነግር አስጠነቀቀው፣ ነገር ግን፣ “ሂድና ራስህን ለካህን አሳይ፣ ሙሴ ባዘዘውም መሠረት ለእነርሱ ምስክር ይሆን ዘንድ
ለመንጻትህ መሥዋዕት አቅርብ።” አለው፡ 15 ነገር ግን ስለ እርሱ ያለው ዝና ከዚያም ርቆ ወጣ፤ ብዙም የሕዝብ አጀብ ሲያስተምር ለመስማትና ከሕመሞቻቸው
ለመፈወስ በአንድነት ወደ እርሱ መጡ። 16 እርሱ ግን ወደ ገለልተኛ ስፍራዎች ሄዶ በዚያ ይጸልይ ነበር። 17 ያስተምር ከነበረባቸውም ከእነዚያ በአንዱ ቀን
ከገሊላና ከይሁዳ መንደሮችና አውራጃዎች እንዲሁም ከኢየሩሳሌም ከተማ መጥተው በዚያ የተቀመጡ ፈሪሳውያንና የሕግ መምህራን ነበሩ። ይፈውስም ዘንድ
የእግዚአብሔር ኃይል በእርሱ ላይ ነበረ። 18 በዚያን ጊዜ ጥቂት ሰዎች ሰውነቱ የደነዘዘ ሰው በቃሬዛ ይዘው መጡ፤ በኢየሱስ ፊትም ያደርጉት ዘንድ ወደ
ውስጥ የሚያስገቡበትን መንገድ ይፈልጉ ነበር። 19 ከሕዝቡም ብዛት የተነሣ ሊያስገቡ የሚችሉበትን መንገድ አላገኙም፤ ስለዚህ ወደ ቤቱ ጣሪያ ላይ
ወጥተው፣ ሰውዬውን በቃሬዛው ላይ እንዳለ በጣሪያው አሳልፈው በሰዎቹ መካከል ከኢየሱስ ፊት አወረዱት። 20 ኢየሱስ እምነታቸውን ተመልክቶ፣ “አንተ ሰው፣
ኃጢአትህ ተሰርዮልሃል” አለው። 21 ፈሪሳውያንና ጸሐፍት፣ “የስድብ ቃል የሚናገር ይህ ማን ነው? እግዚአብሔር ብቻ ካልሆነ በስተቀር፣ ኃጢአትን ይቅር
ማለት የሚችል ማን ነው?” በማለት መጠየቅ ጀመሩ። 22 ነገር ግን ኢየሱስ ምን እንዳሰቡ አውቆ፣ “በልባችሁ ይህንን ለምን ትጠይቃላችሁ? 23 የትኛውን
ማለት ይቀላል፦ ‘ኃጢአትህ ተሰረየችልህ’ ማለት ወይስ ‘ተነሣና ሂድ’ ማለት? 24 ነገር ግን ለሰው ልጅ በምድር ላይ ኃጢአትን ይቅር ለማለት ሥልጣን
እንዳለው እንድታውቁ፣ ለአንተ፣ ‘ተነሣና ቃሬዛህን ተሸክመህ ወደ ቤትህ ሂድ’ ብዬ እናገራለሁ።" 25 ከዚያ በኋላ በእነርሱ ፊት ተነሣ፣ ተኝቶበት የነበረውንም
ቃሬዛ ተሸክሞ እግዚአብሔርን እያከበረ ወደ ቤቱ ተመለሰ። 26 ሰዎች ሁሉ ተገረሙ፣ እግዚአብሔርንም አከበሩ። “በዛሬው ዕለት ያልተለመደ ነገር አየን” እያሉ
በፍርሃት ተሞሉ። 27 እነዚህ ነገሮች ከሆኑ በኋላ፣ ኢየሱስ ከዚያ ወጥቶ በቀረጥ መሰብሰቢያው ስፍራ ተቀምጦ የነበረውን ሌዊ የተባለውን ቀረጥ ሰብሳቢ
ተመለከተ። እርሱንም፣ “ተከተለኝ” አለው። 28 ስለዚህ ሌዊ ሁሉንም ትቶ ተነሥቶ ተከተለው። 29 ከዚያ በኋላ፣ ሌዊ በቤቱ ለኢየሱስ ታላቅ ግብዣ አደረገለት፣
በዚያም ብዙ ቀረጥ ሰብሳቢዎችና በማዕድ ቀርበው ከእነርሱ ጋር የሚመገቡ ሌሎች ሰዎችም ነበሩ። 30 ነገር ግን ፈሪሳውያንና ጻሐፍት በደቀመዛሙርቱ ላይ፣
“ከቀረጥ ሰብሳቢዎችና ከሌሎች ኃጢአተኛ ሰዎች ጋር ለምን ትበላላችሁ ትጠጣላችሁም?” እያሉ ያጉረመርሙባቸው ነበር። 31 ኢየሱስም እንደዚህ በማለት
መለሰላቸው፣ “በመልካም ጤንነት ላይ ያሉ ሐኪም አያስፈልጋቸውም፣ ሐኪም የሚያስፈልጋቸው የታመሙ ብቻ ናቸው። 32 እኔ የመጣሁት ጻድቃንን ለንስሐ
ለመጥራት ሳይሆን ኃጢአተኞችን ወደ ንስሐ ለመጥራት ነው።” 33 እነርሱም ፣ “የዮሐንስ ደቀመዛሙርት ይጾማሉ ይጸልያሉም፣ የፈሪሳውያን ደቀመዛሙርትም
እንደዚሁ ያደርጋሉ። የአንተ ደቀመዛሙርት ግን ይበላሉ፣ ይጠጣሉም።” አሉት። 34 ኢየሱስም ፣ “ሙሽራው ከእነርሱ ጋር ሳለ ሚዜዎቹን እንዲጾሙ
ሊያደርጋቸው የሚችል አለን? 35 ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ወቅት ይመጣል በእነዚያ ቀናት ይጾማሉ።” 36 ከዚያ በኋላ ኢየሱስ በምሳሌ
ተናገራቸው፣ “ማንም ሰው ከአዲስ ልብስ ላይ እራፊ ቀዶ አሮጌ ልብስ አይጥፍም። እንደዚህ የሚያደርግ ከሆነ፣ ከአዲሱ ልብስ ላይ እራፊ ይቀዳል፣ ነገር ግን
ከአዲሱ ልብስ ላይ የተቀደደው እራፊ ከአሮጌው ልብስ ጋር አብሮ አይሄድም። 37 እንደዚሁም፣ ማንም ሰው በአሮጌው አቁማዳ አዲስ የወይን ጠጅ
አያስቀምጥም። እንደዚህ ቢያደርግ፣ አዲሱ ወይን ጠጅ አቁማዳውን ያፈነዳዋል፣ ወይን ጠጁም ይፈሳል፣ አቁማዳውም ይበላሻል። 38 ነገር ግን አዲስ ወይን
ጠጅ በአዲስ አቁማዳ ይቀመጣል። 39 ማንም ሰው አሮጌውን ወይን ጠጅ ከጠጣ በኋላ አዲሱን የወይን ጠጅ አይፈልግም፣ ‘አሮጌው ይሻላል’ ይላልና።”

Luke 5:1

አያያዥ ሀሳብ፦
ኢየሱስ በስምዖን ጴጥሮስ ጀልባ በጌንሳሬጥ ሀይቅ ላይ አስተማረ።

አሁን ይህ ሆነ
ይህ ሀረግ የታሪኩ አዲስ ክፍል መጀመሩን ለማመላከት እዚህ ላይ ጥቅም ላይ ውሏል። የአንተ ቋንቋ ይህንን የማድረግ መንገድ ካለው፣ እዚህ ላይ እርሱን ለመጠቀም ማሰብ ትችላለህ። (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔርን ቃል ማዳመጥ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “እግዚአብሔር እነርሱ እንዲሰሙ የሚፈልገውን መልእክት ማዳመጥ” ወይም 2) “ስለ እግዚአብሔር የሆነውን የኢየሱስ መልእክት ማዳመጥ”

የጌንሳሬጥ ሀይቅ
እነዚህ ቃላት የገሊላን ባህር ይወክላሉ። ገሊላ በሀይቁ ምዕራብ ጎን ነው፣ የጌንሳሬጥ መሬት በምስራቅ ጎን ነበር፣ ስለዚህ በሁለቱም ስሞች ይጠራ ነበር። አንዳንድ የእንግሊዘኛ እትሞች ይህንን እንደ ትክክለኛ የውሀው አካል ስም “የጌንሳሬጥ ሀይቅ” ብለው ይተረጉሙታል።

መረባቸውን እያጠቡ
አሳ ማጥመጃ መረባቸውን እንደገና ለአሳ መያዣነት ለመጠቀም እያፀዱ ነበር።

ከጀልባዎቹ አንዱ፣ የስምዖን የነበረው
“የስምዖን ንብረት የነበረው ጀልባ”

ከመሬት ጥቂት አርቆ በውሀው ውስጥ እንዲያስቀምጥ እርሱን ጠየቀ
“ስምዖንን ጀልባውን ከባህር ዳርቻው ራቅ እንዲያደርገው ጠየቀ”

ተቀመጠ እና ሕዝቡን አስተማረ
መቀመጥ ለአስተማሪ የተለመደ ሁኔታ ነበር።

ከጀልባው ውስጥ ህዝቡን አስተማረ
“ጀልባው ውስጥ እንደተቀመጠ ሆኖ ህዝቡን አስተማረ።” ኢየሱስ ከባህር ዳርቻው አጭር ርቀት ላይ በሚገኘው ጀልባው ውስጥ ነበር እናም በባህር ዳርቻው ላይ ለነበሩ ሰዎች እየተናገረ ነበር።

Luke 5:4

መናገሩን ሲጨርስ
“ኢየሱስ ሕዝቡን ማስተማር ሲጨርስ”

በቃልህ
“ምክንያቱም አንተ ይህንን እንዳደርግ ስለነገርከኝ”

ማንቀሳቀስ
ከባህር ዳርቻው ለመጣራት በጣም ሩቅ ነበሩ፣ ስለዚህ ምናልባትም እጃቸውን በማውለብለብ፣ የሰውነት እንቅስቃሴን አደረጉ።

መስጠም ጀመሩ
“ጀልባዎቹ መስጠም ጀመሩ።” ምክንያቱ በትክክል ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አሳው በጣም ከባድ ስለነበር ጀልባዎቹ መስጠም ጀመሩ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 5:8

በኢየሱስ ጉልበት ላይ ወደቀ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “በኢየሱስ ፊት ተንበረከከ” ወይም 2) “በኢየሱስ እግር ስር ሰገደ” ወይም 3) “የኢየሱስ እግር ስር ባለው መሬት ላይ ተኛ።” ጴጥርስ በአጋጣሚ አልወደቀም። ይህንን የክብር እና የትህትና ምልክት እንዲሆን ለኢየሱስ አድርጎታል። (ምሳሌያዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ኀጢአተኛ ሰው
እዚህ ላይ “ሰው” የሚለው ቃል “ጎልማሳ ወንድ” ለማለት እንጂ በይበልጥ አጠቃላይ ለሆነው “የሰው ልጅ” አይደለም።

የተያዘ ብዙ አሳ
“ብዙ ቁጥር ያለው አሳ”

የስምዖን ባልንጀሮች
“አሳ በማጥመድ ንግዱ ውስጥ የስምዖን ባልንጀሮች”

ሰውን ትይዛለህ
አሳን የማጥመድ ምስል ክርስቶስን እንዲከተል ሕዝብን ለመሰብሰብ እንደ ተለዋጭ ዘይቤ ጥቅም ላይ እየዋለ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎችን ታጠምዳለህ” ወይም “ለእኔ ሰውን ትሰበስባለህ” ወይም “ሰዎች የእኔ ደቀ መዝሙር እንዲሆኑ ታመጣለህ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 5:12

አያያዥ ሀሳብ፡-
ኢየሱስ ሌላ ስሙ ባልተጠቀሰ ከተማ ለምፃም ፈወሰ።

እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ በታሪኩ ውስጥ አዲስ ክስተት መከሰቱን ያሳያል።

በለምጽ የተሸፈነ ሰው
“ቆዳው በለምጽ የተሸፈነ ሰው።” ይህ በታሪኩ ውስጥ አዲስ ገጸ ባሕርይን ያስተዋውቃል። (የአዲስና የቀድሞ ተሳታፊዎች መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

በፊቱ ተደፋ
እዚህ ላይ “በፊቱ ተደፋ” የሚለው ሰገደ የሚለውን ትርጉም የያዘ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ተንበርክኮ በፊቱ መሬቱን ነካ” ወይም “በመሬት ላይ ሰገደ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ፈቃድህ ከሆነ
“የምትፈልግ ከሆነ”

ልታነጻኝ ትችላለህ
እዚህ ላይ ሰውየው ኢየሱስ እንዲፈውሰው እየጠየቀው እንደሆነ መረዳት ይቻላል። ይህ በግልጽ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ማንጻት ስለምትችል እባክህ አንጻኝ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አንጻኝ ... ንጻ
ይህ ሥርዓታዊ ንጽህናን ያመለክታል፣ ሰውየው በለምጹ ምክንያት ንጹህ እንዳልነበረ መረዳት ይቻላል። ካለበት በሽታም ኢየሱስ እንዲፈውሰው እየጠየቀው ነበር። ይህ ግልጽ በሆነ መንገድ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ካለብኝ ለምጽ ፈውሰኝ ... የተፈወስክ ሁን” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለምጹ ለቀቀው
“ከዚያ ጊዜ ኋላ ለምጽ አልነበረበትም”

Luke 5:14

¬ለማንም እንዳይነግር
ይህ በቀጥታ በጥቅስ መልክ መተርጎም ይቻላል። “ለማንም እንዳትናገር።” በግልጽ መቀመጥ የሚችል ሌላም ያልተገለጸ መረጃ አለ። አማራጭ ትርጉም፡- “መፈወስህን ለማንም እንዳትናገር” (ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ጥቅሶች እና አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ መንጻትህ መስዋዕትን
x

Luke 5:15

ስለ እርሱ ወሬ
“ስለ ኢየሱስ ይወራ የነበረ ወሬ።” ይህ “ኢየሱስ ለምጽ ያለበትን ሰው የመፈወሱ ወሬ” ወይም “ኢየሱስ በሽተኞችን ስለመፈወሱ ወሬ” ሊሆን ይችላል።

ስለ እርሱ የነበረው ወሬ ግን በርቀት አብዝቶ ተስፋፋ
“ስለ እርሱ የነበረው ወሬ እስከ ሩቅ ቦታዎች ድረስ ተዳረሰ” ይህ በገቢር ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች በሌሎች ቦታዎች ለሚገኙ ሰዎች ስለ እርሱ ያወሩ ነበር” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ምድረ በዳ
“ባዶ ቦታዎች” ወይም “ሌሎች ሰዎች የማይገኙባቸው ቦታዎች” “

Luke 5:17

አያያዥ ሀሳብ፡-
ኢየሱስ አንድ ህንጻ ላይ ያስተምር በነበረበት በአንድ ቀን ሰዎች አንድ ሽባ የነበረ ሰውን ኢየሱስ እንዲፈውሰው አመጡለት።

እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ በታሪኩ ውስጥ አዲስ ክፍል መጀመሩን ያሳያል። (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 5:18

አንዳንድ ሰዎች መጡ
እነዚህ በታሪኩ ውስጥ አዲስ ሰዎች ናቸው። ቋንቋችሁ አዲስ ሰዎች መሆናቸውን የሚናገር አገላለጽ ሊኖረው ይችላል። (የአዲስና የቀድሞ ተሳታፊዎች መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

ምንጣፍ
መተኛ ምንጣፍ ወይም አልጋ ወይም ቃሬዛ

ሽባ የነበረ
“ራሱን ማንቀሳቀስ የማይችል የነበረ”

የሰው ጭንቅንቅ ብዙ ስለነበር እርሱን ይዘው ሊያስገቡት አልቻሉም ስለዚህ ...
በአንዳንድ ቋንቋዎች የዚህን ቅደም ተከተል መቀየር የተለመደ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰውየውን ወደ ውስጥ ማስገባት አልቻሉም ምክንያቱም የሰው ጭንቅንቁ ከባድ ስለነበር ነው፣ ስለዚህ”

በሰዉ መጨናነቅ ምክንያት
ሰዎቹ መግባት ያልቻሉበት ምክንያት ክፍሉ በሰዎች ተጨናንቆ ስለነበርና ለእነርሱ የሚሆን ቦታ ስላልነበር እንደሆነ ግልጽ ነው። (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ሰገነቱ ወጡ
ቤቶች ጠፍጣፋ የሆነ ጣርያ ነበራቸው፣ አንዳንድ ቤቶች ደግሞ ወደ እነዚህ ጣርያዎች መውጫነት የሚያገለግሉ መሰላሎች ወይም ደረጃዎች ነበሯቸው። ይህን በግልጽ ማሳየት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ወደ ጠፍጣፋው የቤት ጣርያ ወጡ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከኢየሱስ ፊት
“ከኢየሱስ ፊት ለፊት” ወይም “ኢየሱስ ከነበረበት ቀጥታ ፊትለፊት”

Luke 5:20

ኢየሱስም እምነታቸውን አይቶ ... አለ
ኢየሱስ ሽባውን ሰው መፈወስ እንደሚችል ሰዎቹ እንደሚያምኑ ግልጽ ነው። ይህን በግልጽ ማሳየት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ኢየሱስም ሰዎቹ እርሱ ሰውየውን ሊፈውሰው እንደሚችል እንዳመኑ ሲረዳ እንዲህ አለው” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ሰው
ይህ ስሙን ከማያውቁት ሰው ጋር ሲነጋገሩ ሰዎች የሚጠቀሙት የተለመደ ቃል ነው። አግባብ የሌለው አነጋገር አልነበረም፣ ግን የተለየ አክብሮትም አያሳይም። አንዳንድ ቋንቋዎች ይህን ለማሳየት “ወዳጄ” እና “ጌታዬ” የመሰሉ ቃላትን ሊጠቀሙ ይችላሉ።

ኃጢአትህ ተሰረየችልህ
ይህ በገቢር ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ይቅር ተብለሃል” ወይም “ኃጢአትህን ይቅር ብዬሃለሁ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህ ጥያቄ ማቅረብ ጀመሩ
“ስለዚህ ነገር ተወያዩ” ወይም “ስለዚህ ነገር ምክንያቶችን ሰጡ።” የጠየቁትን ጥያቄ በግልጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ኢየሱስ ኃጢአትን ይቅር ለማለት ስልጣን ያለው መሆኑንና አለመሆኑን መወያያት ጀመሩ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 5:22

ያስቡ የነበሩትን ተረድቶ
ይህ ሐረግ የሚያሳየው እነርሱ ድምጽ ሳያወጡ እያሰላሰሉ እንደነበር ኢየሱስ ግን ይናገሩ የነበረውን ሳይሆን ያስቡ የነበረውን እንደተረዳ ያሳያል።

በልባችሁ ይህን ለምን ትጠይቃላችሁ?
ይህ በአረፍተ ሃሳብ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በልባችሁ ውስጥ ስለዚህ ነገር ምንም አይነት ሙግት ውስጥ መግባት የለባችሁም” ወይም “ኃጢአትን ይቅር የማለት ስልጣን እንዳለኝ መጠራጠር የለባችሁም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በልባችሁ ውስጥ
እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል የሰውን አእምሮ ወይም የውስጥ ማንነት የሚወክል ምትክ ስም ነው። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የትኛው ይቀላል ... ተነሳና ተመለለስ
ጻፎቹ እርሱ ኃጢአትን ይቅር የማለት ስልጣን እንዳለው ወይም እንደሌለው የሚያረጋግጥላቸው ነገር ምን እንደሆነ እንዲያስቡ ይህን ጥያቄ ይጠይቃቸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔ 'ኃጢአትህ ተሰረየችልህ' አልኩ፣ እናንተ 'ተነስና ተመላለስ' ማለት ይከብዳል ብላችሁ ታስቡ ይሆናል ምክንያቱም ሰውየውን መፈወስ መቻሌና አለመቻሌ በሰውየው ተነስቶ መሄድና አለመሄድ ይታወቅ ነበር።” ወይም “እናንተ 'ተነስና ሂድ' ከማለት 'ኃጢአትህ ተሰረየችልህ' ማለት ይቀላል ብላችሁ ታስቡ ይሆናል። (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ማለት ይቀላል
እዚህ ላይ በንግግር ያልተገለጸው እንድምታ አንድ ነገር “መናገር ይቀላል ምክንያቱም ምን እንደተከናወነ ማንም ማወቅ አይችልም” ነገር ግን ሌላውን ነገር “መናገር ይከብዳል ምክንያቱም ሁሉም ሰው ምን እንደተከናወነ ያውቃል።” ሰዎች የሰውየው ኃጢአት ተሰርዮለት እንደሆነ ሰዎች ማየት አይችሉም፣ ነገር ግን ሰውየው ከተነሳና ከተራመደ እንደተፈወሰ ሁሉም ያውቃሉ። (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

እንድታውቁ
ኢየሱስ ለጻፎቹና ለፈሪሳውያኑ ነበር ሲያወራ የነበረው። “እናንተ” የሚለው የባለቤት መግለጫ ብዙ ቁጥርን ያመለክታል። (የሁለተኛ መደብ ቅርጾች የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ
ኢየሱስ ስለራሱ ነበር የሚያወራው።

እልሃለሁ
ኢየሱስ ይህን የተናገረው ለሽባው ሰው ነው። “አንተ” የሚለው የድርጊት ተቀባይ ገላጭ ነጠላ ቁጥር ነው።

Luke 5:25

ወዲያውኑም ተነሳ
“በፍጥነት ተነሳ” ወይም “ቶሎ ተነሳ”

ተነሳ
እዚህ ላይ ሰውየው መፈወሱን መናገር አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰውየውም ተፈወሰ! ተነሳም”

በፍርሃት ተሞሉ
x

Luke 5:27

አያያዥ ሀሳብ፦
ኢየሱስ ቤቱን ለቅቆ በወጣ ጊዜ ሌዊ የሚባል አንድ አይሁዳዊ ቀረጥ ቀራጭን እንዲከተለው ጥሪ ያቀርብለታል። ሌዊ ባዘጋጀው ትልቅ ድግስ ላይ የኢየሱስ መታደም ጻፎችና ፈሪሳውያንን እጅግ ያናድዳቸዋል።

እነዚህ ነገሮች ከተከሰቱ በኋላም
“እነዚህ ነገሮች” የሚለው ሐረግ ቀደም ባሉ ቁጥሮች ላይ የተከሰቱትን ነገሮች ይወክላል። ይህ አዲስ ክስተት መጀመሩን ያሳያል። (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

የቀረጥ ቀራጭ ተመለከተ
“አንድ ቀራጭን በትኩረት ተመለከተ” ወይም “አንድ ቀራጭን አጥብቆ ተመለከተ”

ተከተለኝ
አንድን ሰው “መከተል” ማለት የዚያ ሰው ደቀ መዝሙር መሆን ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ደቀ መዝሙሬ ሁን” ወይም “እንደ አስተማሪ ተከተለኝ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉንም ነገር ትቶ
“የቀራጭነት ስራውን ትቶ”

Luke 5:29

አያያዥ ሀሳብ፦
በድግሱ ላይ ኢየሱስ ከጻፎችና ከፈሪሳውያን ጋር ያወራ ጀመር።

በቤቱ
“በሌዊ ቤት”

በማዕድ አብረው ተቀምጠው
በግብዣ ላይ የግሪክ የአመጋገብ ዘይቤ መደገፊያ ባለው መቀመጫ ላይ ተጋድመውና በመቀመጫቸው በግራ በኩል ባለው ድጋፍ ላይ ትራስ አስቀምጠው እዚያ ላይ በመደገፍ ነበር። አማራጭ ትርጉም፦ “በአንድ ላይ ምመብላት” ወይም “በማዕድ መብላት” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለደቀ መዛሙርቱ
“ለኢየሱስ ደቀ መዛሙርት”

ከኃጢአተኞች ጋር ለምን ትበላላችሁ
ጻፎችና ፈሪሳውያን የኢየሱስ ደቀመዛሙርት ከኃጢአተኞች ጋር አብረው መብላታቸውን ለመቃወም ይህንን ጥያቄ ይጠይቃሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ከኃጢአተኞች ጋር አብራችሁ መብላት የለባችሁም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

... ከኃጢአተኞች ጋር አብራችሁ ትበላላችሁ ትጠጣላችሁም
ፈሪሳውያንና ጻፎች ኃይማኖተኛ ሰዎች ኃጢአተኛ ብለው ከሚያስቧቸው ሰዎች ጋር አብረው መሆን እንደሌለባቸው ያምኑ ነበር። “እናንተ” የሚለው ገላጭ ብዙ ቁጥር አመልካች ነው። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ባለጤናዎች ... ሕመምተኞች
x

Luke 5:33

አሉት
“የኃይማኖት መሪዎቹ ለኢየሱስ ... አሉት”

ከእነርሱ ጋር .... ሊያደርግ ይችላል?
ኢየሱስ ሰዎቹ ከዚህ ቀደም የሚያውቁትን ነገር ደግመው እንዲያስቡ በማለት ይሄንን ጥያቄ ይጠይቃቸዋል። ይህ በአረፍተ ሃሳብ መልክ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሙሽራው ከእነርሱ ጋር እያለ ዕድምተኞቹ ጹሙ የሚላቸው ማንም የለም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የሰርጉ ታዳሚዎች
“እንግዶቹ” ወይም “ወዳጆች” እነዚህ ከሚያገባ ወንድ ጋር ሆነው አብረው ደስታውን የሚጋሩ ሰዎች ናቸው።

የሙሽራው ዕድምተኞች እንዲጾሙ ማድረግ
መጾም ሐዘንን ማሳያ ነው። የኃይማኖት መሪዎቹ ሙሽራው አብሯቸው እያለ ዕድምተኞቹ ሊጾሙ እንደማይችሉ ገብቷቸዋል። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀን ይመጣል
“በቅርብ” ወይም “አንድ ቀን”

ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት
ኢየሱስ ራሱን ከአንድ ሙሽራ ጋር ደቀ መዛሙርቱን ደግሞ ከሚዜዎች ጋር በንጽጽር ያቀርባል። ዘይቤውን አያብራራውም ስለዚህ ትርጉም ላይ እጅግ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ብቻ ዘይቤው ይብራራ። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 5:36

አጠቃላይ መረጃ፦
ኢየሱስ በሌዊ ቤት ተገኝተው ለነበሩት ጻፎችና ፈሪሳውያን አንድ ታሪክ ይነግራቸዋል። (ተምሳሌቶች የሚለውን ይመልከቱ)

ማንም ቀድዶ ... አይጠቀምም ... እርሱ . . . እርሱ
ማንም ቦጭቆ . . . አይጠቀምም . . . እርሱ . . . እርሱ” ወይም “ሰዎች ቀድደው . . . አይጠቀሙበትም . . . እነርሱ . . . እነርሱ

የተቀደደውን መስፋት
ማደስ

እንደዚያ ቢያደርግ
ይህ ግምታዊ አርፍተ ነገር ለምን አንድ ሰው በዚያ መንገድ አንድን ልብስ እንደማያድስ ምክንያትን ይሰጣል። (ግምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ልኩ አይሆንም
“አይገጥምም” ወይም “ተመሳሳይ አይሆንም”

Luke 5:37

አዲስ ወይን
“የወይን ፍሬ ጭማቂ።” ይህ ያልፈለ የወይን ጠጅን ይወክላል።

አቁማዳ
እነዚህ ከእንስሳ ቆዳ የተሰሩ መያዣ ከረጢቶች ናቸው። “የወይን ከረጢቶች” ወይም “ከቆዳ የተሰሩ ከረጢቶች” ተብለው መጠራትም ይችላሉ።

አዲሱ ወይን ቆዳውን ያፈነዳዋል
አዲሱ ወይን ሲፈላና ቆዳውን ሲወጥረው ያረጀውን ቆዳ ያፈነዳዋል ምክንያቱም መለጠጥ ስለማይችል ነው። ኢየሱስ ይናገር የነበረውን ያዳምጡ የነበሩ ሰዎች ስለ ወይን መፍላትና ይዞታ መጨመር የሚረዱ ሰዎች ነበሩ። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ወይኑ ይፈስሳል
ይህ በአድራጊ ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ወይኑ ከከረጢቶቹ ውስጥ ወጥቶ ይፈስሳል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

አዲስ አቁማዳ
“አዲስ አቁማዳዎች” ወይም “አዲስ የወይን ከረጢቶች” ይህ ጥቅም ላይ ያልዋለ አቁማዳን ይወክላል።

አሮጌ የወይን ጠጅ የሚጠጣ ... አዲሱን የሚፈልግ
ይህ ዘይቤ የኃይማኖት መምህሮችን አሮጌ ትምህርት ከኢየሱስ አዲስ ትምህርት ጋር አነጻጽሮ ያቀርባል። የዚህ ንግግር ዋና ነጥብ የድሮ ትምህርትን መስማት የለመዱ ሰዎች ኢየሱስ የሚያስተምረውን አዲስ ትምህርት ለመስማት ፈቃደኛ አለመሆናቸው ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አሮጌ ወይን ጠጅ
“የፈለ ወይን ጠጅ”

'አሮጌው ይሻላል' ይላልና
“ስለዚህም አዲሱን ወይን ለመሞከር ፈቃደኛ አይሆንም” የሚለውን መጨመር አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 6

1 በሰንበት ቀን በእህል እርሻ መካከል በሚያልፍበት ጊዜ ደቀመዛሙርቱ እሸት እየቀጠፉና በእጆቻቸው እያሹ እህሉን ይቅሙ ነበር። 2 ገር ግን ከፈሪሳውያን
አንዳንዶቹ፣ “በሰንበት ቀን ማድረግ ያልተፈቀደውን የምታደርጉት ለምንድን ነው?” አሏቸው። 3 ኢየሱስም ለእነርሱ፣ “ዳዊት በተራበ ጊዜ እርሱና ከእርሱ ጋር
የነበሩት ያደረጉትን እንኳ አላነበባችሁምን? 4 ወደ እግዚአብሔር ቤት ገብቶ ከተቀደሰው ኅብስት ጥቂት ወሰደ፤ ካህናትም ብቻ ይበሉ ዘንድ የተፈቀደላቸውን
ለራሱ በላ። አብረውት ከነበሩትም ለአንዳንዶቹ ይበሉ ዘንድ ሰጣቸው” አላቸው። 5 ከዚያ በኋላም፣ “የሰው ልጅ የሰንበት ጌታ ነው” አላቸው። 6 በሌላም ሰንበት
ቀን ወደ ምኩራብ ገብቶ በዚያ የነበሩትን ሰዎች አስተማራቸው። በዚያም የቀኝ እጁ የሰለለች አንድ ሰው ነበረ። 7 አንድ የተሳሳተ ነገር ሲያደርግ ተመልክተው
ለመክሰስ ምክንያት ያገኙ ዘንድ በሰንበት ቀን አንድን ሰው ይፈውስ እንደሆነ ፈሪሳውያንና ጸሐፍት በትኩረት ይመለከቱት ነበር። 8 እርሱ ግን ምን እንደሚያስቡ
አውቆ፣ እጁ የሰለለችበትን ሰውዬ፣ “ተነሣና በሰዎች ሁሉ መካከል ቁም” አለው። ስለዚህም ሰውዬው ተነሣና በዚያ ስፍራ ቆመ። 9 ኢየሱስም፣ “ እኔም
እናንተን እጠይቃችኋለሁ፦ በሰንበት ሕጋዊ የሚሆነው መልካም ማድረግ ነው ክፉ፣ ሕይወት ማድን ነው ወይስ ማጥፋት?” 10 ከዚያም ዞር ብሎ ሁሉንም
ተመለከታቸውና ለሰውዬው፣ “እጅህን ዘርጋ” አለው፤ ዘረጋውም፣ እጁም ዳነለት። 11 ከዚያ በኋላም በቁጣ ተሞልተው፣ በኢየሱስ ላይ ምን እንደሚያደርጉበት
እርስ በርሳቸው ተነጋገሩ። 12 በዚያም ወቅት ኢየሱስ ለመጸለይ ወደ ተራራ ወጣ፣ ሌሊቱንም ሁሉ ወደ እግዚአብሔር መጸለዩን ቀጠለ። 13 በነጋም ጊዜ
ደቀመዛሙርቱን ወደ እርሱ ጠራ፣ ከእነርሱም ‘ሐዋርያት’ ብሎ የሰየማቸውን አሥራ ሁለቱን መረጠ። 14 የሐዋርያቱም ስም፣ ስምዖን (ጴጥሮስ ብሎ የሰየመው)
ወንድሙ እንድርያስ፣ ያዕቆብ፣ ዮሐንስ፣ ፊልጶስ፣ በርተሎሚዎስ፣ 15 ማቴዎስ፣ ቶማስ፣ ያዕቆብ የእልፍዮስ ልጅ፣ ቀናተኛ የተባለው ስምዖን፣ 16 የያዕቆብ ልጅ
ይሁዳና ከዳተኛ የሆነው ይሁዳ አስቆሮቱ ናቸው። 17 ከዚያ በኋላም ኢየሱስ ከተራራው ወረደና በደልዳላ ቦታ ላይ ቆመ። ከደቀመዛሙርቱ በርከት ያሉት፣
ከይሁዳና ከኢየሩሳሌም እንዲሁም ከጢሮስና ከሲዶና ባሕር ዳርቻ ብዙ ሰዎች በዚያ ነበሩ። 18 ወደዚያ የመጡት እርሱን ሊያዳምጡትና ከበሽታዎቻቸው
ሊፈወሱ ነበር። በርኩሳን መናፍስት ሲጨነቁ የነበሩም ሰዎች ተፈወሱ። 19 የሚፈውስ ኃይል ከእርሱ ይወጣ ስለነበረ፣ በሕዝቡ መካከል ያለ እያንዳንዱ ሰው
እርሱን ለመንካት ጥረት ያደርግ ነበር፤ እርሱም ሁሉንም ፈወሳቸ. 20 ከዚያ በኋላም ወደ ደቀመዛሙርቱ ተመለከተና፣ እንደዚህ አላቸው፣ “የእግዚአብሔር
መንግሥት ለእናንተ ናትና፣ እናንተ ድሆች የተባረካችሁ ናችሁ። 21 አሁን የምትራቡ የተባረካችሁ ናችሁ፣ ትጠግባላችሁና። አሁን የምታለቅሱ የተባረካችሁ
ናችሁ፣ ትስቃላችሁና። 22 ሰዎች በሚጠሏችሁና በሚያገሏችሁ ጊዜ እንደዚሁም በሰው ልጅ ምክንያት ስማችሁን በክፉ ሲያነሱ የተባረካችሁ ናችሁ። 23
አባቶቻቸው ነቢያትን እንደዚሁ አድርገውባቸው ነበርና ፣ በዚያን ቀን ሐሴት አድርጉ፣ በደስታም ዝለሉ፣ ምክንያቱም በሰማይ በእርግጥ ታላቅ ብድራት
ይኖራችኋል። 24 እናንተ አሁኑኑ መጽናናትን ተቀብላችኋልና፣ ነገር ግን እናንተ ባለጠጎች ወዮላችሁ! 25 በኋላ ትራባላችሁና፣ እናንተ አሁን የጠገባችሁ
ወዮላችሁ! በኋላ ስለምታለቅሱና ዋይ፣ ዋይ ስለምትሉ፣ እናንተ አሁን የምትስቁ ወዮላችሁ! 26 ሰዎች ሁሉ ስለ እናንተ መልካም በሚናገሩላችሁ ጊዜ ወዮላችሁ!
ምክንያቱም አባቶቻቸው ለሐሰተኛ ነቢያት እንደዚያ ያደርጉላቸው ነበርና። 27 ለእናንተ ለምታደምጡ ግን እላችኋለሁ፣ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፣ ለሚጠሏችሁም
መልካም አድርጉላቸው። 28 የሚረግሟችሁን መርቁ፣ ለሚያንገላቷችሁም ጸልዩላቸው። 29 አንድ ጉንጭህን ለሚመታህ ሌላውንም ጉንጭህን አዙርለት። አንድ
ሰው ነጠላህን የሚወስድብህ ከሆነ፣ እጀ ጠባብህን አትከልክለው። 30 ለሚለምንህ ሁሉ ስጥ፣ አንድ ሰው የአንተ የሆነውን የሚወስድብህ ከሆነ፣
እንዲመልስልህ አትጠይቀው። 31 ሰዎች እንዲያደርጉልህ የምትፈልገውን ሁሉ አንተም ለእነርሱ ልታደርግላቸው ይገባሃል። 32 ኃጢአተኞችም እንኳን
የሚወዷቸውን ይወዳሉና የሚወዷችሁን የምትወዱ ከሆነ፣ ምን ምስጋና ትቀበላላችሁ? 33 ኃጢአተኞችም እንደዚያው ያደርጋሉና መልካም ለሚያደርጉላችሁ ብቻ
መልካም የምታደርጉ ከሆናችሁ፣ ምን ምስጋና ትቀበላላችሁ? 34 እንደሚመልሱላችሁ ለምትጠብቋቸው ብቻ የምታበድሩ ከሆናችሁ፣ ምን ምስጋና አላችሁ?
የሰጡትን ያንኑ ያህል ለመቀበል ተስፋ አድርገው፣ ኃጢአተኞችም እንኳን ለኃጢአተኞች ያበድራሉ። 35 ነገር ግን ጠላቶቻችሁን ውደዱ፣ መልካምም
አድርጉላቸው፤ ምንም ነገር ስለመቀበል ሳትጨነቁ አበድሯቸው፣ ዋጋችሁም ታላቅ ይሆናል። እርሱ ራሱ ለማያመሰግኑና ለክፉ ሰዎች ቸር ነውና፣ እናንተም የልዑል
ልጆች ትባላላችሁ። 36 አባታችሁ መሐሪ እንደሆነ ሁሉ እናንተም መሐሪዎች ሁኑ። 37 አትፍረዱ አይፈርድባችሁም፤ አትኮንኑ አትኮነኑምም፤ ሌሎችን ይቅር
በሉ፣ እናንተም ይቅር ትባላላችሁ። 38 ለሌሎች ስጡ፣ ለእናንተም የተጠቀጠቀ፣ የተነቀነቀ፣ በእቅፎቻችሁም ተርፎ የሚፈስ መልካም መስፈሪያ ተሰፍሮ
ይሰጣችኋል። ለሌሎች ለመስፈር በምትጠቀሙበት በዚያው መስፈሪያ ለእናንተም ይሰፈርላችኋል።" 39 ከዚያም ይህን ምሳሌ ነገራቸው፣ በኋላም፣ “አንድ
ዕውር ሌላውን ዕውር ሊመራው ይችላልን? እንደዚያ ቢያደርግ፣ ሁለቱም ጉድጓድ ውስጥ ይገቡ የለምን? 40 ደቀመዝሙር ከመምህሩ አይበልጥም፤ ነገር ግን
አንድ ሰው ፈጽሞ ከተማረ እንደ መምህሩ ይሆናል። 41 በወንድምህ ዓይን ያለውን ትንሽ ጉድፍ ለምን ትመለከታለህ? ለምንስ በራስህ ዓይን ያለውን ግንድ
አትመለከትም? በራስህ ዓይን ውስጥ ያለውን ግንድ ሳትመለከት፣ 42 ለወንድምህ፣ ‘ወንድሜ ሆይ፣ ዓይንህ ውስጥ ያለውን ጉድፍ ላውጣልህ’ እንዴት
ትለዋለህ? አንተ ግብዝ! በመጀመሪያ በዓይንህ ውስጥ ያለውን ግንድ አውጣ፣ ከዚያም በወንድምህ ዓይን ውስጥ ያለውን ጉድፍ ለማውጣት አጥርተህ ታያለህ።
43 የተበላሸ ፍሬ የሚያፈራ መልካም ዛፍ የለምና፣ መልካም ፍሬም የሚያፈራ የተበላሸ ዛፍ የለም። 44 እያንዳንዱ ዛፍ የሚታወቀው በሚያፈራው ፍሬ ነውና፤
ከእሾህ የበለስ ፍሬ አይለቀምም፣ ከቀጋ ቁጥቋጦም የወይን ፍሬ አይቆረጥም። 45 መልካሙ ሰው በልቡ ካከማቸው መልካም ሀብት መልካም የሆነውን ነገር
ያወጣል፤ ክፉም ሰው በልቡ ካከማቸው ክፉ ክምችት ክፉ የሆነውን ያወጣል። በልቡ ሞልቶ ከተረፈው በአፉ ይናገራልና። 46 ለምንስ ‘ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ’
ትሉኛላችሁ? ለምናገራቸውስ ነገሮች ለምን አትታዘዙም? 47 ወደ እኔ የሚመጣና ለቃሌ የሚታዘዝ ምን እንደሚመስል እነግራችኋለሁ እነግራችኋለሁ፣ 48
መሬቱን በጥልቁ ከቆፈረ በኋላ መሠረቱን በዓለት ላይ በማድረግ ቤቱን እንደሚገነባ ሰው ነው። ጎርፍ በመጣ ጊዜ የውሃው ሙላት ያን ቤት ገፋው፣ ሆኖም
በሚገባ ተገንብቶ ነበርና አልነቀነቀውም። 49 ነገር ግን ቃሌን ሰምቶ የማይታዘዘው ሰው ቤቱን ያለ መሠረት በመሬቱ አፈር ላይ እንደ ሠራው ሰው ነው፤ ጎርፉ
በመጣ ጊዜ ቤቱን መታው፣ ወዲያውኑም ፈረሰ፣ ውድም ብሎም ጠፋ።”

Luke 6:1

አጠቃላይ መረጃ፦
“እናንተ” የሚለው የድርጊት ባለቤት መግለጫ ባለ ብዙ ቁጥር ሲሆን ደቀ መዛሙርቱን ይወክላል። (የሁለተኛ መደብ ቅርጾች የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ በታሪኩ ውስጥ አዲስ ክስተት መጀመሩን ያሳያል። ቋንቋችሁ ይህን ማሳያ መንገድ ካለው እሱን መጠቀም ይመከራል። (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እርሻ
እነዚህ ሰዎች የበለጠ ስንዴ ለማብቀል ስንዴ ዘርተውባቸው የሚገኙ ሰፋፊ የመሬት ክፍልፋዮች ናቸው።

የጥራጥሬ እሸት
ይህ ረዥም ሳር የሚመስል የአንድ ጥራጥሬ ተክል ጫፍ ላይ የሚገኝ የተክሉ ክፍል ነው። ሊበሉ የሚችሉና የበሰሉ የተክሉ ፍሬዎችን ይይዛል።

ፍሬዎቹን በእጃቸው መሃል እያሹ
ይህን የሚያደርጉት የጥሬውን ፍሬዎች ለመለየት ነው። ይህ ግልጽ ተደርጎ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በእጃቸው መሃል አድርገው ያሹአቸው ገለባውን ከፍሬው ለመለየት ነው (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰንበት ቀን ሕጉ የሚከለክለውን ነገር ለምን ታደርጋላችሁ?
ይህን ጥያቄ የጠየቁት ደቀ መዛሙርቱን ሕግን በመጣስ ሊከሷቸው ፈልገው ነው። ይህ በአረፍተ ሃሳብ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በሰንበት ቀን ጥራጥሬ መቅጠፍ ከእግዚአብሔር ሕግ ጋር ይቃረናል” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ነገር ትሰራላችሁ
ፈሪሳውያን አንድ እፍኝ ጥራጥሬን አሽቶ መብላትን የሚያክል ትንሽ ድርጊትን ራሱ ስራ እንደመስራት ይቆጥሩ ነበር። ይህ በግልጽ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስራን እየሰራችሁ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 6:3

ከቶ አላነበባችሁምን? ... እርሱ ራሱ
ኢየሱስ ፈሪሳውያን ከቅዱስ መጻሕፍት ባለመማራቸው ይገስጻቸዋል። ይህ በአረፍተ ሃሳብ መልክ ሊጻፍ ይችላል።. አማራጭ ትርጉም፡- “ካነበባችሁት ነገር መማር ነበረባችሁ .... እርሱ ራሱ” ወይም “በእርግጠኝነት አንብባችኋል ... እርሱ ራሱ” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 6:6

አያያዥ ሀሳብ፦
ጻፎችና ፈሪሳውያን ኢየሱስ በሰንበት ቀን አንድ ሰውን ሲፈውስ ይመለከታሉ።

አጠቃላይ መረጃ፦
ይህ ሌላ የሰንበት ቀን ሲሆን ኢየሱስም በምኩራብ ነበር።

እንዲህ ሆነ
ይህ ሐረግ በታሪኩ ውስጥ አዲስ ክስተት መጀመሩን ያሳያል። (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

... ሰው በዚያ ነበር
ይህ በታሪኩ ውስጥ አዲስ ገጸ ባህሪይን ያስተዋውቃል። (የአዲስና የቀድሞ ተሳታፊዎች መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

እጁ የደከመ
የሰውየው እጅ መዘርጋት እንዳይችል ሆኖ ተጎድቶ ነበር። የሰውየው እጅ ቡጢ በሚመስል ሁኔታ ታጥፎ የነበረ እንደነበርና መታጠፉም ትንሽና የተሸበሸበ እንዳስመሰለው ይገመታል።

እያዩ ይከታተሉት ነበር
“በትኩረት ኢየሱስን እየተመለከቱት ነበር”

ሊያገኙበት
“ማግኘት ፈልገው”

በሁሉም መካከል
“ከሁሉም ፊት።” ኢየሱስ ሰውየው ሁሉም ሰው ሊያየው በሚችልበት ቦታ ላይ እንዲቆም ፈልጎ ነበር።

Luke 6:9

ለእነርሱ አላቸው
“ለፈሪሳውያኑ አላቸው”

እጠይቃችኋለሁ በሰንበት ቀን ሕጉ የሚከለክለው በጎ ማድረግን ነው ወይስ ክፋትን፣ ነፍስን ማጥፋት ነው ወይስ ነፍስን ማዳን?
ኢየሱስ ይህንን ጥያቄ ለፈሪሳውያን የሚጠይቃቸው በሰንበት ቀን ሰው መፈወሱ ትክክል እንደነበረ ፈሪሳውያን እንዲያምኑ ለማድረግ ነው። ስለዚህ የዚህ ጥያቄ ዓላማ መልስ ፍለጋ አይደለም፣ ይልቁንም እውነት እንደሆነ የሚያውቁትን ነገር እንዲያምኑ ለማድረግ ነው። ይሁን እንጂ ኢየሱስ “እጠይቃችኋለሁ” ይላል፣ ስለዚህ ይህ ጥያቄ እንደሌሎች መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች በአረፍተ ሃሳብ ቅርጽ ተቀይሮ መጻፍ የሚችል አይደለም። ይህ ጥያቄ የጥያቄነት ቅርጹን ጠብቆ መተርጎም አለበት። (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 6:12

አጠቃላይ መረጃ፦
ኢየሱስ ለሊቱን ሙሉ ከጨረሰ በኋላ አስራ ሁለት ሐዋርያትን ይመርጣል።

በነዚያም ቀናት እንዲህ ሆነ
ይህ ሐረግ የታሪኩ አዲስ ክፍል መጀመሩን ያሳያል። (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

በነዚያም ቀናት
“በዚያን ጊዜ” ወይም “ይህ ከሆነ ብዙም ሳይቆይ” ወይም “በዚያን ጊዜ አካባቢ አንድ ቀን”

ወጣ
“ኢየሱስ ወጣ”

ቀን በሆነ ጊዜ
“ጠዋት በሆነ ጊዜ” ወይም “በቀጣዩ ቀን”

አስራ ሁለቱን መረጠ
“አስራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት መረጠ”

ደግሞም ሐዋርያት ብሎ ጠራቸው
“ደግሞም ሐዋርያት አድረጋቸው” ወይም “እናም ሐዋርያት አድርጎ ሾማቸው”

Luke 6:14

የሐዋርያቱም ስም
ሉቃስ የሐዋርያቱን የስም ዝርዝር ጻፈ። ዩኤልቢ የሚባለው ትርጉም የስም ዝርዝሩን ለመጀመር እነዚህን ቃላት ይጠቀማል። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ወንድሙ እንድርያስ
“የስምኦን ወንድም እንድርያስ”

ቀናተኛው
x

Luke 6:17

አያያዥ ሀሳብ፦
ምንም እንኳ ኢየሱስ በተለየ ሁኔታ በቀጥታ የተናገረው ለደቀ መዛሙርቱ ቢሆንም በአካባቢው ሆነው ሲሰሙ የነበሩ ብዙ ሰዎች ነበሩ።

ከእነርሱ ጋር
“ከመረጣቸው ከአስራ ሁለቱ ጋር” ወይም “ከአስራ ሁለቱ ሐዋርያት ጋር”

ሊፈወሱ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ኢየሱስ እንዲፈውሳቸው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በእርኩስ መናፍስት ይሰቃዩ የነበሩ ሰዎችም ተፈወሱ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ኢየሱስ በእርኩስ መንፈስ ይሰቃዩ የነበሩ ሰዎችንም ፈወሰ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በእርኩስ መናፍስት ይሰቃዩ የነበሩ
“በእርኩስ መናፍስት ይቸገሩ የነበሩ” ወይም “በክፉ መናፍስት ቁጥጥር ስር የነበሩ”

የመፈወስ ኃይል ከእርሱ ይወጣ ነበር
“ሰዎችን ለመፈወስ ኃይል ነበረው” ወይም “ኃይሉን ሰዎችን ለመፈወስ ይጠቀም ነበር”

Luke 6:20

ብፁዓን
ይህ ቃል ሶስት ጊዜ ይደገማል። በእያንዳንዱ ጊዜም እግዚአብሔር ለተወሰኑ ሰዎች የሚያደርገውን ቸርነት ወይም እነዚያ ሰዎች ያሉበት ሁኔታ አዎንታዊ ወይም ጥሩ እንደሆነ ይናገራል።

ድሆች ብፁዓን ናችሁ
“ድሃ የሆናችሁ እናንተ የእግዚአብሔርን ቸርነት ትቀበላላችሁ” ወይም “ድሃ የሆናችሁ እናንተ ትጠቀማላችሁ”

የእግዚአብሔር መንግስት የእናንተ ናትና
መንግስት የሚለው ቃል መግለጫ የሌላቸው ቋንቋዎች “እግዚአብሔር ንጉሳችሁ ነውና” ወይም “እግዚአብሔር ገዢያችሁ ነውና” ሊሉ ይችላሉ።

የእግዚአብሔር መንግስት የእናንተ ናት
x

Luke 6:22

ብፁዓን ናችሁ
“የእግዚአብሔርን ቸርነት ትቀበላላችሁ” ወይም “ትጠቀማላችሁ” ወይም “እንደዛ መሆን ለእናንተ ምንኛ መልካም ነው”

ሲለዩአችሁ
“ሲቃወሟችሁ”

በሰው ልጅ ምክንያት
“ከሰው ልጅ ጋር የተያያዛችሁ ስለሆናችሁ” ወይም “የሰው ልጅንም ስለሚቃወሙት”

በዚያን ቀን
“እነዚህን ነገሮች ሲያደርጓችሁ” ወይም “ያ ነገር በተከሰተ ጊዜ”

በደስታ ዝለሉ
ይህ ፈሊጥ “እጅግ ደስተኛ ሁኑ” ማለት ነው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ትልቅ ዋጋ
“ትልቅ ክፍያ” ወይም “መልካም ስጦታዎች”

Luke 6:26

ወየላችሁ
“ምንኛ ክፉ ነገር ይጠብቃችኋል!” ወይም “ምንኛ የከፋ ሐዘን ውስጥ ትገቡ ይሆን”

ሰዎች ሁሉ ... ሲናገሩላችሁ
እዚህ ላይ “ሰዎች” የሚለው ቃል ሁሉንም የሕዝብ ክፍል ያካትታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሕዝብ ሁሉ ሲናገሩላችሁ” ወይም “ሁሉም ሰው ሲናገሩላችሁ” (ተባዕታይ ቃላቶች ሴቶችን ሲጨምር የሚለውን ይመልከቱ)

አባቶቻቸው ለሐሰት ነቢያት እንደዚያ አድርገው ነበር
“አባቶቻቸውም ለሐሰት ነቢያት መልካምን ነገር ይናገሩላቸው ነበር”

Luke 6:27

አያያዥ ሀሳብ፦
ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱና አብረው ሆነው ይሰሙ ለነበሩት ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል።

ለእናንተ ለምትሰሙ
ኢየሱስ አሁን ለደቀመዛሙርት ብቻ ሳይሆን በዚያ ለነበሩት ሰዎች ለሁሉም መናገር ይጀምራል። (የአዲስና የቀድሞ ተሳታፊዎች መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

ውደዱ ... መልካም አድርጉ ... ባርኩ ... ጸልዩ
እዚህ ላይ ያሉት እያንዳንዱ ትዕዛዛት በቀጣይነት መደረግ ያለባቸው ናቸው፣ አንድ ጊዜ ብቻ የሚደረጉ አይደሉም።

ጠላቶቻችሁን ውደዱ
ይህ መውደድ ያለባቸው ጠላቶቻቸውን ብቻና ወዳጆቻቸውን መውደድ የለባቸውም ለማለት አይደለም። ይህ በግልጽ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ወዳጆቻችሁን ብቻ ሳይሆን ጠላቶቻችሁንም ውደዱ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ውደዱ ... መልካም አድርጉ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ዋናው ነጥብ ላይም አጽንኦት ይሰጣሉ። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ባርኩ
የሚባርከው እግዚአብሔር ነው። ይህ ግልጽ ተደርጎ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር እንዲባርካቸው ጠይቁ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የሚረግሟችሁን
x

Luke 6:29

ቢመታህ
“ማንም ሰው ቢመታህ”

አንድ ጉንጭህን
“አንደኛውን ጉንጭህን”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሌላኛውን ስጠው
የሚያጠቃው ሰውዬ በሰውየው ላይ ምን እንደሚያደርስ ግልጽ አድርጎ መጻፍ ሊያስፈልግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ፊትህን አዙረህ ሌላኛውን ጉንጭህንም እንዲመታህ ስጠው” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

አትከልክለው
“ከመውሰድ አታግደው”

ለሚጠይቅህ ሁሉ ስጥ
“ማንም ሰሰው አንድን ነገር ቢጠይቅህ ስጠው”

እንዲመልስልህ አትጠይቀው
“መልሶ እንዲሰጥህ አትጠብቅ” ወይም “መልሶ እንዲሰጥህ አትጠይቀው”

Luke 6:31

ሰዎች ለእናንተ እንዲያደርጉ እንደምትፈልጉት፣ እናንተም ለእነርሱ እንደዛው አድርጉላቸው
በአንዳንድ ቋንቋዎች ቅደም ተከተሉን መለወጥ የተለመደ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ለሰዎች ማድረግ ያለባችሁ እናንተ እነርሱ እንዲያደርጉባችሁ እንደምትፈልጉት ነው” ወይም “ለሰዎች ማሰብ ያለባችሁ እነርሱ ለእናንተ እንዲያስቡ በምትፈልጉት መንገድ ነው”

ምን የተለየ ዋጋ ታገኛላችሁ?
“ምን ዋጋ ታገኛላችሁ?” ወይም “ያንን በማድረጋችሁ ምን አይነት ምስጋናን ታተርፋላችሁ” ይህ በአረፍተ ሃሳብ ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል።. አማራጭ ትርጉም፦ “ያንን በማድረጋችሁ ምንም ሽልማትን አታገኙም” ወይም “ያንን በማድረጋችሁ እግዚአብሔር ምንም ሽልማትን አይሰጣችሁም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ተመሳሳይ መጠን ያለውን መልሳችሁ ብትቀበሉ
የሙሴ ሕግ አይሁዳውያን እርስ በርስ በተበዳደሩት ገንዘብ ላይ ወለድን እንዳይቀበሉ ያዝዛል። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 6:35

በምላሹ ምንም ሳትጠብቁ
“የሰጣችሁት ሰው የሰጣችሁትን ነገር እንዲመልስላችሁ ሳትጠብቁ” ወይም “የሰጣችሁት ሰው ምንም ነገር እንዲመልስላችሁ ሳትጠብቁ”

ሽልማታችሁ ታላቅ ይሆናል
“ታላቅን ሽልማት ትቀበላላችሁ” ወይም “መልካም ክፍያን ታገኛላችሁ” ወይም “ባደረጋችሁት ነገር ምክንያት ጥሩ ስጦታን ታገኛላችሁ”

የልዑልም ልጆች ትሆናላችሁ
“ልጆች” የሚለውን ቃል በቋንቋችሁ ውስጥ የተለመደ የአንድ ሰውን ልጅ ለመግለጽ ጥቅም ላይ በሚውለው ቃል ተርጉሞ ማቅረብ ተመራጭ ነው።

የልዑል ልጆች
ልጆች የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል ምክንያቱም “የልዑል ልጅ” ከሚለው ከኢየሱስ ማዕረግ ጋር መመሳሰል ስለሌለበት ነው።

ምስጋና ቢስና ክፉ ሰዎች
“እርሱን የማያመሰግኑና ሰዎችና ክፉዎች የሆኑ”

አባታችሁ
ይህ እግዚአብሔርን ይወክላል። ይህን በቋንቋችሁ ውስጥ ስጋዊ አባትን በሚወክለው ቃል መተርጎም ቢቻል ይመረጣል።

Luke 6:37

አትፍረዱ
“ሰው ላይ አትፍረዱ” ወይም “የመረረ ነቀፋ በሰው ላይ አታድርሱ”

እናንተም
“ስለዚህም እናንተ”

አይፈረድባችሁም
x

Luke 6:38

ይሰጣችኋል
ኢየሱስ የሚሰጠው ማን እንደሆነ ግልጽ አድርጎ አይናገርም። ሊሆን የሚችለው፡ 1) “የሆነ ሰው ይሰጣችኋል” ወይም 2) “እግዚአብሔር ይሰጣችኋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እጅግ ብዙ መጠን ያለው .. የተጨቆነ፣ የተነቀነቀና ሞልቶም የተረፈ . . . በጭናችሁ ላይ ይፈስሳል
እዚህ ላይ ኢየሱስ እግዚአብሔርን ወይም በቸርነት የሚሰጡትን ሰዎችን እንደ አንድ ቸር ነጋዴ አድርጎ ያቀርባቸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር የተጨቆነ የተነቀነቀና የተትረፈረፈ መጠን ያለውን ሞልቶ በጭናችሁ ላይ ያፈስሳል” ወይም “ቸር የጥራጥሬ ነጋዴ ጥራጥሬን ጨቁኖና ነቅንቆ መጠኑም ሞልቶ እስኪፈስ ድረስ ብዙ አድርጎ እንደሚሰጥ፣ ለእናንተም በቸርነት እንዲሁ ይሰጧችኋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ብዙ መጠን ያለው
“ትልቅ መጠን ያለው”

ይሰፈርላችኋል
ኢየሱስ ማን እንደሚሰፍርላቸው በግልጽ አይናገርም። ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት፡ 1) “እነርሱ ይሰፍሩላችኋል” ወይም “እግዚአብሔር ይሰፍራችኋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 6:39

አያያዥ ሀሳብ፦
ኢየሱስ የንግግሩን ዋና ሃሳብ ለማጠንከር አንዳንድ ምሳሌዎችን ይጨምራል። (ተምሳሌቶች የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ዕውር ሰው ሌላ ዕውር ሰውን ሊመራ ይችላል?
ኢየሱስ ሰዎቹ ኪዚህ በፊት ያውቁ የነበረውን ነገር ደግመው እንዲያስ ለማድረግ ይህን ጥያቄ ይጠይቃቸዋል። ይህ በአረፍተ ነገር ቅርጽ ደግሞ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሁላችንም አንድ ዕውር ሰው ሌላ ዕውር ሰውን መንገድ ሊመራ እንደማይችል እናውቃለን” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 6:41

በወንድምህ አይን ላይ ያለውን .... ለምን ታያለህ? በራስህ አይን ውስጥ ያለውን ግንድ ለምን አትመለከትም?
ኢየሱስ ይሄን ጥያቄ የጠየቀው ሰዎቹ የሌላን ሰው ኃጢአት ከመመልከታቸው በፊት የራሳቸውን ኃጢአት መመልከት እንዳለባቸው ለመሞገት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በራስህ አይን ውስጥ ያለውን ምሰሶ ትተህ በወንድምህ አይን ያለውን ... አትመልከት” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በወንድምህ አይን ያለውን ጉድፍ
ይህ ዘይቤ ሌላ አማኝ የሚያደርጋቸውን ጥቃቅን ስህተቶችን ይወክላል።። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጉድፍ
“ጠብታ” ወይም “ጉድፍ” ወይም “የአቧራ ብናኝ”። የሰው አይን ውስጥ ሊገባ የሚችል በጣም ትንሽ ነገርን የሚወክል ቃል ካለ እሱን መጠቀም ይቻላል።

በወንድምህ
እዚህ ላይ “ወንድም” የሚለው ሌላ አይሁዊን ወይም በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ሌላ ሰውን ይወክላል።

በራስህ አይን የሚገኘውን ግንድ
ይህ ዘይቤ የአንድ ሰውን ትልልቅ የሚባሉ ጥፋቶችን የሚወክል ነው። ግንድ በአንድ ሰው አይን ውስጥ ቃል በቃል ሊገባ አይችልም። ኢየሱስ አጋንኖ የሚያወራው አንድ ሰው የሰውን ጥቃቅን ጥፋቶች ከማየቱ በፊቱ የራሱን ትልልቅ ጥፋቶች መመልከት እንዳለበት አጽንኦት ለመስጠት ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ እና ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ግንድ
“ምሰሶ” ወይም “ሳንቃ”

በአይንህ .... ልትል ትችላለህ?
ኢየሱስ ይሄን ጥያቄ የሚጠይቀው ሰዎቹ የሰው ኃጢአት ላይ ትኩረት ከማድረግ ይልቅ በራሳቸው ኃጢአቶች ላይ ትኩረት ማድረግ እንዳለባቸው ለመሞገት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በአይንህ ... ማለት የለብህም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 6:43

አጠቃላይ መረጃ፦
ሰዎች አንድን ዛፍ መልካም ወይ ክፉ መሆኑንና ምን ዓይነት ዛፍ መሆኑን ከሚያፈራው ፍሬ ማወቅ ይችላሉ። ኢየሱስ አንድን ሰው ከሚያደርገው ድርጊት ምን ዓይነት ሰው እንደሆነ ማወቅ እንደምንችል ለማሳየት ይሄንን ንግግር እንደ ዘይቤ ይጠቀመዋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አለና
“ምክንያቱም ስላለ” ይህ የሚያሳየው ቀጥሎ የሚናገረው ነገር ወንድሞች ላይ ለምን መፍረድ እንደማይገባ ምክንያቱን እንደሚያመለክት ነው።

መልካም ዛፍ
“ጤናማ ዛፍ”

የተበላሸ ፍሬ
እየበሰበሰ ያለ ፍሬ ወይም መጥፎ ወይም ዋጋ የሌለው ፍሬ

Luke 6:45

አጠቃላይ መረጃ፦
እዚህ ላይ ኢየሱስ የአንድ ሰውን ሃሳብ ሰውየው ካለው ከመልካም ወይም ከክፉ መዝገብ ጋር አነጻጽሮ ያቀርባል። መልካም ሰው መልካም ሃሳቦችን ሲያስብ መልካም ድርጊቶችን በመፈጸም ይጠመዳል። ክፉ ሰው ክፉ ሃሳቦችን ሲያስብ ክፋት ያለባቸውን ድርጊቶች በመስራት ይጠመዳል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መልካም ሰው
እዚህ ላይ “መልካም” የሚለው ቃል ጻድቅ ወይም መልካም ሥነ ምግባር ያለው የሚለውን ይወክላል።

መልካም ሰው
እዚህ ላይ “ሰው” የሚለው ወንድ ወይም ሴት የሆነን ሰው ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡-“መልካም ሰው” (ተባዕታይ ቃላቶች ሴቶችን ሲጨምር የሚለውን ይመልከቱ)

ከልቡ መልካም መዝገብ
እዚህ ላይ የአንድ ሰው መልካም ሃሳቦች በዚያ ሰው ልብ ውስጥ እንደሚቀመጥ እንደ መዝገብ ተደርጎ ተመስሏል። “ልብ” የሚለው ደግሞ የአንድን ሰው ውስጣዊ ማንነት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በውስጡ ከሚያኖረው ከመልካም ነገር” ወይም “እርሱ ዋጋ የሚሰጣቸው መልካም ነገሮች” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

መልካም የሆነውን ያፈራል
መልካም የሆነውን ያፈራል ማለት መልካም ስራዎችን ይሰራል የሚለውን የሚያሳይ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “መልካም የሆነውን ይሰራል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በልቡ ካለው ከክፉ መዝገብ
x

Luke 6:46

አጠቃላይ መረጃ፦
ኢየሱስ እርሱ የሚያስተምረውን የሚቀበልን ሰው በድንጋይ መሰረት ላይ ቤቱን ሰርቶ ጎርፍ ቤቱን ከማያፈርስበት ሰው ጋር አነጻጽሮ ያቀርባል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 6:49

አጠቃላይ መረጃ፦
ኢየሱስ እርሱ የሚናገረውን ሰምቶ የማይታዘዘውን ሰው ቤቱን ያለመሰረት ሰርቶ ጎርፍ በመጣ ጊዜ ቤቱ ከሚፈርስበት ሰው ጋር አነጻጽሮ ያቀርባል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰውየው ግን
“ግን” የሚለው ቃል ቀድሞ ከተነገረው ቤቱን መሰረት ላይ ከሰራው ሰው ጋር ጠንካራ የተቃራኒ ንጽጽር መኖሩን ያሳያል።

ያለ መሰረት በመሬት ላይ
አንዳንድ ሰዎች መሰረት ያለው ቤት ጠንካራ እንደሆነ ላያውቁ ይችላሉ። ተጨማሪ መረጃ መስጠት አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን ቤቱን ከመስራት በፊት መሬትን ቆፍሮ መሰረትን አልገነባም ነበር” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መሰረት
ቤቱን ከመሬት ጋር የሚያገናኘው የሕንጻው ክፍል። ኢየሱስ በኖረበት ጊዜ የነበሩ ሰዎች መሬቱን አለት ድንጋይ እስከሚያገኙ ድረስ ቆፍረው በአለቱ ላይ ነበር ቤቱን ይገነቡ የነበረው። አለቱ የቤቱ መሰረት ነበር።

ምዕራፍ 7

1 ኢየሱስ ለሕዝቡ የሚናገረውን ሁሉ ከጨረሰ በኋላ፣ ወደ ቅፍርናሆም ገባ። 2 እጅግ የሚወደውና ሞት አፋፍ ላይ የደረሰ አገልጋይ የነበረው አንድ የመቶ አለቃ
ነበረ። 3 ስለ ኢየሱስ በሰማ ጊዜ መጥቶ አገልጋዩን ከመሞት እንዲያድንለት እንዲለምኑት የአይሁድ ሽማግሌዎችን ወደ እርሱ ላካቸው። 4 እነርሱ ወደ ኢየሱስ
በቀረቡ ጊዜ፣ "ለእርሱ ይህን ልታደርግለት የተገባ ነው፣ 5 ምክንያቱም ሕዝባችንን ይወዳል፣ ምኩራብ የሠራልንም እርሱ ነው" በማለት አጥብቀው ለመኑት። 6
ስለዚህ ኢየሱስ ዐብሮአቸው መንገዱን ቀጠለ። ነገር ግን ወደ ቤቱ ለመድረስ ጥቂት በቀረው ጊዜ፣ የመቶ አለቃው፣ እንዲህ ብለው እንዲነግሩት ወዳጆቹን ወደ
ኢየሱስ ላካቸው፤ “ጌታ ሆይ፣ አትድከም፣ ምክንያቱም አንተ ወደ ቤቴ ልትገባ የተገባሁ አይደለሁም፤ 7 ከዚህ የተነሣ እኔም ራሴ ወደ አንተ ለመምጣት የምገባ
አድርጌ እንኳ ራሴን አልቈጥረውም። ነገር ግን ቃል ብቻ ተናገር አገልጋዬ ይፈወሳል፤ 8 እኔም ደግሞ ባለ ሥልጣን ነኝና፤ በእኔ ሥር ወታደሮች አሉኝ፤ አንዱን
'ሂድ' ስለው ይሄዳል፤ ሌላውን 'ና' ስለው ይመጣል። 9 ኢየሱስ ይህን በሰማ ጊዜ፣ በመቶ አለቃው ተደንቀ፣ ይከተሉት ወደነበሩት ሰዎችም ዞር ብሎ፣
“በእስራኤልም እንኳ እንዲህ ያለ እምነት ያለው ሰው አላገኘሁም” አላቸው። 10 ከዚያም የተላኩት ሰዎች ወደ መቶ አለቃው ቤት ተመልሰው፣ አገልጋዩን ጤናማ
ሆኖ አገኙት። 11 ከጥቂት ጊዜ በኋላ ኢየሱስ ናይን ወደ ምትባል ከተማ እየተጓዘ ነበር። ከእርሱም ጋር ደቀ መዛሙርቱና ብዙ ሕዝብ ዐብረውት ይሄዱ ነበር። 12
ወደ ከተማይቱም በቀረበ ጊዜ፣ እነሆ፣ ለእናቱ ብቸኛ ልጅ የነበረ ሰው ሞቶ አስከሬኑን ሰዎች ተሸክመው እየሄዱ ነበር። የልጁ እናት መበለት ነበረች፤ በርከት ያሉ
ለቀስተኞችም ተከትለዋት ነበር። 13 ጌታም ተመልክቷት እጅግ ዐዘነላትና፣ “አታልቅሺ” አላት። 14 ከዚያም ወደ ቃሬዛው ተጠግቶ ነካው ቃሬዛውን
የተሸከሙትም ቆሙ። ኢየሱስ፣ “አንተ ወጣት ተነሥ እልሃለሁ” አለ። 15 ወጣቱም ተነሥቶ መናገር ጀመረ፤ ከዚያም ኢየሱስ ልጁን ለእናትዮዋ ሰጣት። 16
ከዚያም ሁሉንም ፍርሀት ያዛቸው። “ታላቅ ነቢይ በመካከላችን ተነሥቶአል" "ደግሞ እግዚአብሔር ሕዝቡን ጎበኝቶአል” በማለት እግዚአብሔርን አመሰገኑ። 17
ይህ የኢየሱስ ዝና በመላው ይሁዳና በዙሪያው ባለው አገር ሁሉ ተሰማ። 18 የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ስለ እነዚህ ነገሮች ሁሉ አወሩለት። 19 ከዚያም ዮሐንስ፣
“የምትመጣው አንተ ነህን ወይስ ሌላ እንጠብቅ?” ብለው እንዲጠይቁት ከእነርሱ ሁለቱን ወደ ኢየሱስ ላካቸው። 20 ሰዎቹም ወደ ኢየሱስ ቀርበው፣
"'የምትመጣው አንተ ነህን ወይስ ሌ እንጠብቅ?' ብለን እንድንጠይቅህ መጥምቁ ዮሐንስ ልኮናል" አሉ። 21 በዚያኑ ሰዓት ኢየሱስ ብዙ ሰዎችን ከተለያየ ደዌና
በሽታ ፈወሰ። በአጋንንት የተያዙትን ነጻ አወጣ፣ ዐይነ ስውራንም ማየት እንዲችሉ አደረገ። 22 ኢየሱስ መልእክተኞቹን፣ “ወደ ዮሐንስ ተመልሳችሁ ሂዱና
ያያችሁትንና የሰማችሁትን እንዲህ ብላችሁ ንገሩት፣ ዐይነ ስውራን ያያሉ፣ ሽባዎች ይራመዳሉ፣ ለምጻሞች ይነጻሉ፣ መስማት የተሳናቸው ይሰማሉ፣ ሙታን
ይነሣሉ፣ ለድኾችም ወንጌል እየተሰበከ ነው። 23 በማደርጋቸው ነገሮች በእኔ ሳይሰናከል በእምነቱ የሚጸና ሰው የተመሰገነ ነው” አላቸው። 24 የዮሐንስ
መልእክተኞች ከሄዱ በኋላ ኢየሱስ ስለ ዮሐንስ ለሕዝቡ እንዲህ ይላቸው ጀመር፣ “ምን ልታዩ ወደ በረሐ ወጣችሁ በነፋስ የሚወዛወዘውን ሸንበቆ ለማየት
ነውን? 25 ወይስ የወጣችሁት የሚያማምሩ ልብሶች የለበሱትን ለማየት ነውን? እነሆ፣ የሚያማምሩ ልብሶችን ለብሰው በድሎት የሚኖሩ ሰዎች የሚገኙት
በአብያተ መንግሥታት ነው። 26 ልታዩ የወጣችሁት ግን ነቢይን ከሆነ፣ እንግዲያውስ ያያችሁት ነቢይን ብቻ ሳይሆን ከነቢያትም የበለጠውን ነው። 27 ስለ
እርሱ፣ ‘እነሆ፣ በፊታችሁ መንገድን የሚጠርግ መልእክተኛዬን እልካለሁ’ ተብሎ ተጽፏል። 28 እላችኋለሁ፣ ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከዮሐንስ የሚበልጥ
ማንም የለም፤ ቢሆንም በእግዚአብሔር መንግሥት ከሁሉም የሚያንሰው ይበልጠዋል። 29 ይህን በሰሙ ጊዜ ቀራጮች እንኳ ሳይቀሩ ሕዝቡ ሁሉ እግዚአብሔር
ጻድቅ እንደ ሆነ ተናገሩ፤ ምክንያቱም እነርሱን ያጠመቃቸው ዮሐንስ ነበር። 30 በዮሐንስ ያልተጠመቁት ፈሪሳውያንና የአይሁድ የሕግ ዐዋቂዎች ግን በራሳቸው
ፈቃድ የእግዚአብሔርን ጥበብ ተቃወሙ። 31 እንግዲያውስ የዚህን ትውልድ ሰዎች ከምን ጋር አመሳስላቸዋለሁ? ምንስ ይመስላሉ? 32 እርስ በርሳቸው
በገበያ እየተጠራሩ፥ ‘እንቢልታ ነፋንላችሁ እናንተም አልዘፈናችሁም፣ ሙሾ አወጣንላችሁ እናንተም አላለቀሳችሁም’ እንደሚባባሉ ልጆች ናቸው። 33 መጥምቁ
ዮሐንስ እንጀራ ሳይበላና ወይን ጠጅ ሳይጠጣ ቢመጣ፣ ‘ጋኔን አለበት’ አላችሁት፣ 34 የሰው ልጅ እየበላና እየጠጣ ቢመጣ፡- ‘በላተኛና ጠጪ፣ የቀራጮችና
የኃጢአተኞች ወዳጅ!’ አላችሁት። 35 ጥበብ ግን በልጆቿ ሁሉ ትክክል እንደ ሆነች ታወቀች። 36 አንድ ፈሪሳዊም በቤቱ ዐብሮት እንዲመገብ ኢየሱስን
ጋበዘው ኢየሱስ ግብዣውን ተቀብሎ ወደ ማዕዱ ቀረበ። 37 እነሆ፣ በዚያ ከተማ በመጥፎ ምግባሯ የታወቀች እንዲት ሴት ኢየሱስ በፈሪሳዊው ቤት ተጋብዞ
በማዕድ እንደ ተቀመጠ ተረድታ የአልባስጥሮስ ሽቱ ብልቃጥ ይዛ ወደ ቤቱ ገባችና 38 ከኢየሱስ በስተኋላ ከእግሩ አጠገብ ቆማ ማልቀስ ጀመረች። ከዚያም
በእንባዋ እግሩን ማራስና በፀጉሯም ማበስ ቀጠለች፣ እግሩንም ትስመው በሽቱም ትቀባው ነበር። 39 ኢየሱስን የጋበዘው ፈሪሳዊ ይህንን ባየ ጊዜ፣ "ይህ ሰው
በእርግጥ ነቢይ ቢሆን ኖሮ እየነካችው ያለችው ሴት ምን ዓይነት ሴት እንደ ሆነች ባወቀም ነበር" ብሎ በልቡ ዐሰበ። 40 ኢየሱስም መልሶ ፈሪሳዊውን፣ “አንድ
የምነግርህ ነገር አለኝ” አለው። ፈሪሳዊውም፣ “መምህር ሆይ፣ ተናገር” አለው። 41 ኢየሱስ፣ “ከአንድ አበዳሪ ገንዘብ የተበደሩ ሁለት ሰዎች ነበሩ፣ አንደኛው
የአምስት መቶ ዲናር ሌላኛው ደግሞ የሃምሳ ዲናር ዕዳ ነበረባቸው፤ 42 የሚከፍሉት ስላልነበራቸው ሁለቱንም ዕዳቸውን ማራቸው። ስለዚህ ዕዳቸው
ከተማረላቸው ከእነዚህ ከሁለቱ ማንኛቸው አብዳሪውን የበለጠ የሚወደው ይመስልሃል? አለው። 43 ስምዖንም መልሶ፣ “ብዙ የተተወለቱ ይመስለኛል” አለው።
ኢየሱስ፣ “በትክክል መልሰሃል” አለው። 44 ኢየሱስም ወደ ሴትዮይቱ ዞር ብሎ ስምዖንን እንዲህ አለው፣ “ይህችን ሴት ትመለከታታለህ? እኔ ወደ ቤትህ ገብቼ
ለእግሬ ውሃ እንኳን አላቀረብህልኝም፣ እርሷ ግን በእንባዋ እግሬን አራሰች፣ በፀጉሯም አበሰችው፤ 45 አንተ አልሳምኸኝም፣ እርሷ ግን ከመጣሁበት ጊዜ ጀምሮ
እግሬን ከመሳም አላቋረጠችም። 46 አንተ ራሴን ዘይት አልቀባኸኝም፣ እርሷ ግን እግሬን ሽቱ ቀባች፣ 47 ስለዚህ ለበዛው ኃጢአቷ ብዙ ምሕረትን አግኝታለችና
አብዝታ ወዳለች። ጥቂት ኃጢአቱ ይቅር የተባለለት ግን ጥቂት ይወዳል” አለው። 48 ከዚያም ወደ ሴቱቱ ዞር ብሎ፣ “ኃጢአትሽ ተሰርዮልሻል” አላት። 49
በዚያም ተቀምጠው የነበሩት እርስ በርሳቸው፣ “ኃጢአትን ይቅር የሚል ይህ ማን ነው?” አሉ። 50 ከዚያም ኢየሱስ ሴቲቱን፣ “እምነትሽ አድኖሻል። በስላም
ሂጂ” አላት።

Luke 7:1

አጠቃላይ መረጃ
ኢየሱስ የመቶ አለቃውን አገልጋይ ወደፈወሰበት ወደ ቅፍርናሆም ይገባል።

ሕዝቡ እየሰሙት
የአነጋገር ዘይቤ የሆነው “እየሰሙት”፣ እርሱ የተናገረውን እንዲሰሙት ስለመፈለጉ አጽንዖት ይሰጣል። እ.ት፡ “ይሰሙት ለነበሩት ሰዎች” ወይም “ለተገኘው ሕዝብ” ወይም “ሕዝቡ እንዲሰሙ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ወደ ቅፍርናሆም ገባ
ይህ በታሪኩ ውስጥ አዲስ ሁነትን ይጀምራል። (አዲስ ሁነትን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Luke 7:2

በጣም ይወደው የነበረ
“የመቶ አለቃው ከፍ ያለ ቦታ የሚሰጠው” ወይም “ያከብረው የነበረ”

Luke 7:6

ጉዞውን ቀጠለ
“አብሮት ሄደ”

ከቤቱ ሳይርቅ
ድርብ አሉታው ሊቀየር ይችላል። አ.ት፡ “ወደ ቤቱ ሲቃረብ” (ድርብ አሉታ የሚለውን ተመልከት)

ራስህን አታድክም
የመቶ አለቃው ኢየሱስን በትህትና እያነጋገረው ነበር። አ.ት፡ “ወደ ቤቴ ለመምጣት ራስህን አታድክም” ወይም “ላስቸግርህ አልፈልግም”

ከጣሪያዬ በታች ልትመጣ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ትርጉሙ “ወደ ቤቴ መምጣት” ማለት ነው። የአንተ ቋንቋ “ወደ ቤቴ መምጣት” የሚል ትርጉም ያለው የአነጋገር ዘይቤ ካለው እዚህ ጋ ልትጠቀምበት ያስፈልግህ እንደሆነ አስብበት። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

አንድ ቃል ብቻ ተናገር
ኢየሱስ በመናገር ብቻ አገልጋዩን ሊፈውሰው እንደሚችል የመቶ አለቃው ተረድቷል። እዚህ ጋ “ቃል” የሚያመለክተው ትዕዛዝን ነው። አ.ት፡ “ትዕዛዝ ብቻ ስጥ”

አገልጋዬ ይፈወሳል
እዚህ ጋ “አገልጋይ” ተብሎ የተተረጎመው ቃል አብዛኛውን ጊዜ የሚተረጎመው “ወንድ ልጅ” ተብሎ ነው። ይህ ምናልባት አገልጋዩ ታዳጊ ወጣት እንደ ነበረ ወይም የመቶ አለቃው ለእርሱ ያለውን ፍቅር ይጠቁም ይሆናል።

እኔም ደግሞ ከሥልጣን በታች ያለሁ ሰው ነኝ
“እኔም ደግሞ የምታዘዘው የበላይ አለኝ”

በእኔ ሥር
“በሥልጣኔ ሥር”

ለአገልጋዬ
እዚህ ጋ “አገልጋይ” ተብሎ የተተረጎመው ቃል ለአገልጋይ የተለመደ ቃል ነው።

Luke 7:9

በእርሱ ተደነቀ
“በመቶ አለቃው ተደነቀ”

እላችኋሃለሁ
ኢየሱስ ይህንን ያለው ሊነግራቸው ስላለው አስገራሚ ነገር አጽንዖት ለመስጠት ነው።

እንዲህ ያለውን እምነት በእስራኤል እንኳን አላገኘሁም
ይህ የሚያመለክተው፣ ኢየሱስ የአይሁድ ሕዝብ እንዲህ ያለ እምነት እንዲኖራቸው መጠበቁን፣ እነርሱ ግን እንዳልነበራቸው ነው። አሕዛብ እንዲህ ያለ እምነት እንዲኖራቸው አልጠበቀም፣ ሆኖም ይህ ሰው ነበረው። ይህንን ጠቋሚ መረጃ መጨመር ይኖርብህ ይሆናል። አ.ት፡ “እንደዚህ አሕዛብ የሚታመንብኝን አንድም እስራኤላዊ አላገኘሁም!”

እነዚያ ተልከው የነበሩት
እነዚህ የመቶ አለቃው የላካቸው ሰዎች መሆናቸው ግልጽ ነው። ይህ በአ.ት፡ “ሮማዊው ባለሥልጣን ወደ ኢየሱስ ልኳቸው የነበሩ ሰዎች”

Luke 7:11

አያያዥ መግለጫ፡
ኢየሱስ የሞተውን ሰው ወደ ፈወሰበት ወደ ናይን ከተማ በመሄድ ላይ ነው።

ናይን
የከተማይቱ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

እነሆ፣ አንድ የሞተ ሰው
“እነሆ” የሚለው ቃል በታሪኩ ውስጥ ስላለው የሞተ ሰው ሊያስተዋውቀን ያነቃናል። የአንተ ቋንቋ ይህንን አሳብ መግለጫ መንገድ ይኖረው ይሆናል። አ.ት፡ “አንድ የሞተ ሰው ነበር፣ እርሱም” (አዲስና ነባር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)

የሞተ ሰው ተሸክመው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ሰዎች የሞተውን ሰው ተሸክመው ከከተማይቱ ይወጡ ነበር” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ብዙ ሕዝብም መበለት ለነበረች ለእናቱ ብቸኛ ልጁ የነበረውን ተሸክመው ወጡ
“ብዙ ሕዝብ ነበሩ፤ ተሸክመውት ወጡ፤ እርሱም ለእናቱ ብቸኛ ልጁ ነበር፣ እርሷም መበለት ነበረች”። ይህ ስለ ሟቹ ሰውና ስለ እናቱ ዳራዊ መረጃ ነበር። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

መበለት
ባሏ የሞተባትና ሁለተኛ ያላገባች ሴት

እጅግ ራራላት
“በጣም አዘነላት”

ቀርቦ
x

Luke 7:16

አያያዥ መግለጫ፡
ይህ ኢየሱስ ሞቶ የነበረውን ሰው በመፈወሱ ምክንያት የሆነውን ነገር ይነግረናል።

በሁሉም ላይ ፍርሐት ወደቀባቸው
“ሁሉም ፍርሐት ሞላባቸው”። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሁሉም በጣም ፈሩ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በመካከላችን ታላቅ ነቢይ ተነሥቷል
ያመለክቱ የነበሩት ወደ አንድ ማንነቱ ወዳልታወቀ ነቢይ ሳይሆን ወደ ኢየሱስ ነበር። እዚህ ጋ “ተነሥቷል” የሚለው ቃል “እንዲሆን ተደርጓል” ለሚለው የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ከእኛ አንዱን ታላቅ ነቢይ አድርጎታል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ እና የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ጎብኝቷል
የዚህ የአነጋገር ዘይቤ ትርጉም “አስቧቸዋል” የሚል ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ስለ ኢየሱስ የሆነው ይህ ወሬ ተስፋፋ
“ይህ ወሬ” የሚያመለክተው ሕዝቡ በቁጥር 16 ላይ ይናገሩት የነበሩትን ነገር ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሕዝቡ ይህንን የኢየሱስን ዝና አሰራጩት” ወይም “ሕዝቡ የኢየሱስን ዝና ለሌሎች ነገሯቸው”

ይህ ወሬ
“ይህ ዝና” ወይም “ይህ መልዕክት”

Luke 7:18

አያያዥ መግለጫ፡
የሐንስ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን ኢየሱስን እንዲጠይቁት ይልካቸዋል።

የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ስለእነዚህ ነገሮች ሁሉ ነገሩት
ይህ በታሪኩ ውስጥ ስላለው አዲስ ሁነት ያስተዋውቃል። (አዲስ ሁነትን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)

ነገሩት
“ለዮሐንስ ነገሩት”

እነዚህን ነገሮች ሁሉ
“ኢየሱስ ሲያደርጋቸው የነበሩትን ነገሮች ሁሉ”

ሰዎቹ፣ “አጥማቂው ዮሐንስ ‘. . . አንተ ነህ ወይስ ሌላውን እንጠብቅ?’ ብለን እንድንጠይቅህ ወደ አንተ ልኮናል” አሉት።
ይህ ዐረፍተ ነገር፣ አንድ ግልጽ የሆነ ትዕምርተ ጥቅስ እንዲኖረው እንደገና ሊጻፍ ይችላል። አ.ት፡ “ሰዎቹ ‘እየመጣህ ያለኸው አንተ ነህ? ወይስ ሌላ እንጠብቅ’ ብለው እንዲጠይቁት አጥማቂው ዮሐንስ የላካቸው መሆኑን ተናገሩ” ወይም “ሰዎቹ፣ ‘እየመጣህ ያለኸው አንተ ትሆን እንደሆን ወይም ሌላ መጠበቅ ይኖርብን እንደሆን እንድንጠይቅህ አጥማቂው ዮሐንስ ወደ አንተ ልኮናል’ አሉት”። (ግልጽ የሆነና ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ተመልከት)

ሌላ መጠበቅ ይኖርብን ይሆን?
“ሌላ እንጠብቅ?” ወይም “ሌላን ሰው እንጠባበቅ?”

Luke 7:21

በዚያን ሰዓት
“በዚያን ጊዜ”

ከክፉ መናፍስት
ፈውሱን እንደገና መናገር ይጠቅም ይሆናል። አ.ት: “ከክፉ መናፍስት ፈወሳቸው” ወይም “ሰዎችን ከክፉ መናፍስት ነጻ አወጣቸው” (See: Ellipsis)

እንዲህ አላቸው
“ለዮሐንስ መልዕክተኞች እንዲህ አላቸው” ወይም “ዮሐንስ ለላካቸው መልዕክተኞች እንዲህ አላቸው”

ለዮሐንስ አስታውቁት
“ለዮሐንስ ንገሩት”

የሞቱ ሰዎች ተነሥተዋል
“የሞቱ ሰዎች እንደገና በሕይወት እንዲኖሩ ተደርገዋል”

የተቸገሩ ሰዎች
“ድኾች ሰዎች”

በሥራዎቼ ምክንያት በእኔ ማመኑን የማያቋርጥ ሰው የተባረከ ነው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት: “በሥራዎቼ ምክንያት በእኔ ማመኑን የማያቋርጠውን ሰው እግዚአብሔር ይባርከዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የማያቋርጥ ሰው የተባረከ ነው
“የማያቋርጡ ሰዎች የተባረኩ ናቸው” ወይም “ማንም የማያቋርጥ ሰው የተባረከ ነው” ወይም “የ . . . ማንም ቢሆን የተባረከ ነው”። ይህ አንድ ተለይቶ የታወቀ ሰው አይደለም።

በ. . . ምክንያት በእኔ ማመኑን የማያቋርጥ
የዚህ ድርብ አሉታ ትርጉም “በእኔ ማመኑን የሚቀጥል” (ድርብ አሉታ የሚለውን ተመልከት)

በእኔ የሚያምን
“ሙሉ በሙሉ በእኔ የሚታመን”

Luke 7:24

አያያዥ መግለጫ፡
x

Luke 7:27

ስለ እርሱ የተጻፈለት ይህ ነው
“ነቢያት ስለ እርሱ የጻፉለት ነቢይ እርሱ ነው” ወይም “ከረጅም ዓመታት በፊት ነቢያት የጻፉለት ሰው ዮሐንስ ነው”

እነሆ፣ እልካለሁ
በዚህ ቁጥር ኢየሱስ ከትንቢተ ሚልክያስን በመጥቀስ፣ ሚልክያስ የተናገረለት መልዕክተኛ ዮሐንስ መሆኑን ይናገራል።

በፊትህ
የዚህ የአነጋገር ዘይቤ ትርጉም፣ “በፊት ለፊትህ” ወይም “ከአንተ ቀድሞ እንዲሄድ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የአንተ
በትዕምርተ ጥቅሱ ውስጥ እግዚአብሔር የሚናገረው ለመሲሑ ስለ ነበረ “የአንተ” የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር ነው።

እልሃለሁ
ኢየሱስ የሚናገረው ለሕዝቡ ስለሆነ “አንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥርን አመልካች ነው። ኢየሱስ ይህንን የሚለው ቀጥሎ ለሚናገረው አስገራሚ እውነት አጽንዖት ለመስጠት ነው።

ከሴቶች በተወለዱት መካከል
“ሴቶች ከወለዷቸው መካከል”። ይህ ሰዎችን ሁሉ የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት: “በሕይወት ከነበሩት ሰዎች ሁሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከዮሐንስ የሚበልጥ የለም
“የሚበልጠው ዮሐንስ ነው”

በእግዚአብሔር መንግሥት ታናሽ የሆነው
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር በሚመሠርተው መንግሥት ውስጥ አባል የሚሆነውን ማንኛውንም ሰው ነው።

እርሱን የሚበልጠው ይሆናል
በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የሰዎች መንፈሳዊ ሁኔታ መንግሥቱ ከመመሥረቱ በፊት ከነበራቸው የሚበልጥ ይሆናል። አ.ት: “የመንፈሳዊ ሕይወታቸው ደረጃ ከዮሐንስ ይልቅ ከፍ ያለ ይሆናል”

Luke 7:29

አጠቃላይ መረጃ
የዚህ መጽሐፍ ደራሲ የሆነው ሉቃስ ሰዎች ለዮሐንስና ለኢየሱስ ስላሳዩት ምላሽ አስተያየቱን ይሰጣል።

ሕዝቡ ሁሉ ... ጊዜ የዮሐንስ ጥምቀት
ለበለጠ ግልጽነት የዚህ ቁጥር ቅደም ተከተል ሊስተካከል ይችላል። አ.ት፡ “ቀረጥ ሰብሳቢዎቹን ጨምሮ በዮሐንስ የተጠመቁ ሰዎች ሁሉ ይህንን በሰሙ ጊዜ እግዚአብሔር ጻድቅ መሆኑን መሰከሩ”

እግዚአብሔር ጻድቅ መሆኑን መሰከሩ
“እግዚአብሔር ጻድቅ መሆኑን አሳይቷል አሉ” ወይም “እግዚአብሔር በጽድቅ አድርጓል ብለው መሰከሩ”

በዮሐንስ ጥምቀት ተጠምቀው ነበርና
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ዮሐንስ እንዲያጠምቃቸው ፈቅደው ነበርና” ወይም “ዮሐንስ አጥምቋቸው ነበርና” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር ለእነርሱ ያለውን ዓላማ አልተቀበሉም
“እግዚአብሔር እንዲያደርጉ የፈለገባቸውን አልተቀበሉም” ወይም “እግዚአብሔር የነገራቸውን ላለመታዘዝ መረጡ”

በዮሐንስ አልተጠመቁም ነበር
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ዮሐንስ እንዲያጠምቃቸው አልፈቀዱም ነበር” ወይም “የዮሐንስን ጥምቀት አልተቀበሉም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Luke 7:31

አያያዥ መግለጫ፡
ኢየሱስ ስለ አጥማቂው ዮሐንስ ለሕዝቡ መናገሩን ይቀጥላል።

እንግዲህ ከምን ጋር ላነጻጽራቸው እችላለሁ ... በምን ልመስላቸው?
ኢየሱስ ንጽጽርን ለማስተዋወቅ እነዚህን ጥያቄዎች ይጠይቃል። እነዚህ እንደ መግለጫ ሊጻፉ ይችላሉ። አ.ት፡ “ይህንን ትውልድ የማነጻጽረውና ምን እንደሚመስሉ የምገልጸው እንደዚህ ነው” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

አነጻጽራቸዋለሁ ... ምን እንደሚመስሉ
እነዚህ ንጽጽር መሆኑ የተነገረባቸው ሁለት መንገዶች ናቸው።

የዚህ ትውልድ ሰዎች
ኢየሱስ በሚናገርበት ጊዜ በሕይወት የነበሩ ሰዎች ማለት ነው።

እነርሱ እንደዚህ ናቸው
እነዚህ ቃላት የኢየሱስ ንጽጽር ጅማሬዎች ናቸው። ሕዝቡ፣ በሌሎች ልጆች ሥራ በፍጹም እንደማይረኩ ልጆች መሆናቸውን ኢየሱስ ይናገራል። (ተነጻጻሪ የሚለውን ተመልከት)

በገበያ ስፍራ
ሰዎች ሸቀጦቻቸውን ለመሸጥ የሚመጡበት ሰፊ ሜዳ

አልዘፈናችሁም
“እናንተ ግን ከሙዚቃው ጋር አልዘፈናችሁም”

አላለቀሳችሁም
“እናንተ ግን ከእኛ ጋር አላለቀሳችሁም”

Luke 7:33

እንጀራ አልበላም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “አዘውትሮ መጾም” ወይም 2) “የተለመደውን ምግብ አለመብላት” የሚሉት ናቸው።

‘አጋንንት አለበት’ ትላላችሁ
ኢየሱስ የሚጠቅሰው ሕዝቡ ስለ ዮሐንስ ይናገሩ የነበሩትን ነው። ይህ ያለ ቀጥተኛ ትዕምርተ ጥቅስ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አጋንንት አለበት ትላላችሁ” ወይም “አጋንንት እንዳለበት አድርጋችሁ ትከሱታላችሁ” (ግልጽ የሆነና ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ተመልከት)

የሰው ልጅ
ኢየሱስ ወደ ራሱ ማመልከቱን ሕዝቡ እንደሚረዱ ጠብቋል። አ.ት፡ “የሰው ልጅ የሆንኩ እኔ” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

‘እነሆ፣ ከኃጢአተኞች ... ሆዳምና ሰካራም ሰው ነው!’ ትላላችሁ
ይህ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ተደርጎ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እርሱ ከኃጢአተኞች ... ሆዳምና ሰካራም ሰው ነው ትላላችሁ” ወይም “ከኃጢአተኞች... በመብላቱና ብዙ በመጠጣቱ ምክንያት ትከሱታላችሁ” (ግልጽ የሆነና ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ተመልከት)

‘ተመልከቱ፣ ከኃጢአተኞች ... ሆዳምና ሰካራም ሰው ነው!’ ትላላችሁ
“የሰው ልጅ” የሚለውን “የሰው ልጅ የሆንኩ እኔ” ብለህ ተርጉመህ ከሆነ አንደኛ መደብን በመጠቀም ቀጥተኛ እንዳልሆነ መግለጫ አድርገህ መናገር ትችላለህ። አ.ት፡ “ከኃጢአተኞች... ሆዳምና ሰካራም እንደሆንኩ ትናገራላችሁ” (ቀጥተኛ የሆነና ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ እና አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

ሆዳም ሰው ነው
“ንፉግ በላተኛ ነው” ወይም “ባለማቋረጥ ብዙ ምግብ ይበላል”

ሰካራም
“ጠጪ” ወይም “ባለማቋረጥ የሚያሰክር መጠጥ አብዝቶ ይጠጣል”

ጥበብ በልጆቿ ሁሉ ጸድቃለች
ይህ ምናልባት ጥበበኞች ሰዎች ሕዝቡ ኢየሱስንና ዮሐንስን መቃወም እንዳልነበረባቸው የሚገነዘቡ መሆናቸውን ለማስተማር ኢየሱስ ከሁኔታው ጋር ያዛመደው ምሳሌአዊ አነጋገር ይሆናል።

Luke 7:36

አያያዥ መግለጫ፡
ፈሪሳዊው በቤቱ እንዲበላ ኢየሱስን ይጋብዘዋል።

አጠቃላይ መረጃ፡
አንድ ፈሪሳዊ በቤቱ ምግብ እንዲበላ ኢየሱስን ይጋብዘዋል።

ከፈሪሳውያኑ አንዱ
ይህ የታሪኩ አዲስ ክፍል መጀመሩን፣ በታሪኩ ውስጥም ፈሪሳዊውን ማስተዋወቁን ያመለክታል። (አዲስ ሁነትን ማስተዋወቅ፣ አዲስና ነባር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)

ለመብላት በገበታው አጠገብ ጋደም አለ
“ገበታው ጋ ለመብላት ተቀመጠ”። ወንዶች በምግቡ ዙሪያ በምቾት ጋደም ማለታቸውና እንዲህ ያለውን እራት ዘና ብለው መብላታቸው የተለመደ ነበር።

እነሆ፣ አንዲት ሴት ነበረች
“እነሆ” የሚለው ቃል በታሪኩ ውስጥ ስላለ አዲስ ሰው ያነቃናል። የአንተ ቋንቋ ይህንን የሚገልጽበት መንገድ ይኖረው ይሆናል። (አዲስ ሁነትን ማስተዋወቅ፣ አዲስና ነባር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)

ኃጢአተኛ የነበረች
“በኃጢአት የተሞላ የኑሮ ዘይቤ የነበራት” ወይም “በኃጢአት ስለመኗሯ መጥፎ ምስክርነት የነበራት”። ምናልባት በሴተኛ አዳሪነት ትተዳደር የነበረች ሴት ትሆን ይሆናል።

የአልባስጥሮስ ብልቃጥ
“ከለስላሳ ድንጋይ የተሠራ ብልቃጥ”። አልባስጥሮስ ለስላሳና ነጭ የሆነ ድንጋይ ነው። ሰዎች ዋጋቸው ውድ የሆኑ ነገሮችን በአልባስጥሮስ ብልቃጦች ውስጥ ያስቀምጡ ነበር።

ሽቶ ያለበት ዘይት
“ከሽቶ ጋር የተዋሐደ”። ዘይቱ ጥሩ መዓዛ እንዲኖረው ያስደረገው አንዳች ነገር ነበረበት። ሰዎች ጥሩ መዓዛ እንዲኖራቸው በራሳቸው ላይ ያስነኩት ወይም በልብሳቸው ላይ ይረጩት ነበር።

በራሷ ጸጉር
“በጸጉሯ”

ሽቶ ባለው ዘይት ቀባቻቸው
“ሽቶ ቀባቻቸው”

Luke 7:39

እንዲህ ሲል ለራሱ አሰበ
“ለራሱ እንዲህ አለ”

ይህ ሰው ነቢይ ቢሆን ኖሮ ኃጢአተኛ ... ባወቀ ነበር
ኢየሱስ ኃጢአተኛ የሆነች ሴት እንድትነካው በመፍቀዱ ነቢይ እንዳልሆነ ፈሪሳዊው አሰበ። አ.ት፡ “ኢየሱስ ነቢይ አለመሆኑ ግልጽ ነው፣ ምክንያቱም ነቢይ ቢሆን ኖሮ እየነካችው ያለችው ሴት ኃጢአተኛ መሆኗን ያውቅ ነበር”

እርሷ ኃጢአተኛ ናትና
ስምዖን፣ ኃጢአተኛ የሆነ ሰው እርሱን እንዲነካው አንድ ነቢይ በፍጹም መፍቀድ አይኖርበትም ብሎ ገምቷል። ይህ የግምቱ አካል በግልጽ መነገር ይችላል። አ.ት፡ “እርሷ ኃጢአተኛ ናት፣ እርሱ እንድትነካው መፍቀድ አይኖርበትም”

ስምዖን
ይህ ኢየሱስን ወደ ቤቱ የጋበዘው ፈሪሳዊ ስም ነበር። ይህ ስምዖን ጴጥሮስ አይደለም።

Luke 7:41

አጠቃላይ መረጃ፡
ኢየሱስ ለፈሪሳዊው ስምዖን ለሚነግረው ነገር አጽንዖት ለመስጠት ታሪክ ይነግረዋል። (ምሳሌዎች የሚለውን ተመልከት)

ለአንድ ገንዘብ አበዳሪ ሁለት ተበዳሪዎች ነበሩት
“ሁለት ሰዎች ከአንድ የገንዘብ አበዳሪ ገንዘብ ተበደሩት”

አምስት መቶ ዲናር
“የ ‘500 ቀናት’ ደሞዝ”። “ዲናር” የዲናሪየስ ብዙ ቁጥር ነው። “ዲናሪየስ” ከብር ማዕድን የሚሠራ ሳንቲም ነበር። (መጽሐፍ ቅዱሳዊው ገንዘብ እና ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ሌላኛው ሃምሳ
“ሌላኛው ተበዳሪ ሃምሳ ዲናር ተበደረ” ወይም “የ ’50 ቀን’ ደሞዝ”

Luke 7:46

አንተ ... አላደረግህም፣ እርሷ ግን
ኢየሱስ የስምዖንን ደካማ እንግዳ አቀባበል ከሴቲቱ ተግባር ጋር ማነጻጸሩን ይቀጥላል።

Luke 7:48

ከዚያም እንዲህ አላት
“ከዚያም ሴቲቱን እንዲህ አላት”

ኃጢአትሽ ይቅር ተብሎልሻል
“ይቅር ተብለሻል”። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ኃጢአትሽን ይቅር ብዬሻለሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በአንድነት ጋደም ብለው
“በማዕዱ ዙሪያ በአንድነት ጋደም ብለው” ወይም “በአንድነት ሲመገቡ”

ኃጢአትን እንኳን ይቅር የሚል ይህ ማነው?
የሃይማኖት መሪዎች ኃጢአትን ይቅር ማለት የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ያውቃሉ፣ ኢየሱስ እግዚአብሔር እንደነበረ ግን አላመኑም። ይህ ጥያቄ ምናልባት ወቀሳ እንዲሆን ሳይታሰብ አልቀረም። አ.ት፡ “ይህ ሰው ማን እንደሆነ ነው የሚያስበው? ኃጢአትን ይቅር ማለት የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው!” ወይም “ይህ ሰው እርሱ ብቻ ኃጢአትን ይቅር ለማለት የሚችለውን እግዚአብሔርን ለመሆን የሚሞክረው ለምንድነው?”

እምነትሽ አድኖሻል
“በእምነትሽ ምክንያት ድነሻል”። የነገር ስም የሆነው “እምነት” እንደ ድርጊት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ስላመንሽ ድነሻል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 8

1 ከዚያ በኋላ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት የምሥራች ወንጌል እየሰበከና እያወጀ ወደ ልዩ ልዩ ከተሞችና መደሮች መጓዝ ጀመረ። በጒዞውም ወቅት
ዐሥራ ሁለቱ፣ 2 እንዲሁም ከርኩሳን መናፍስትና ከሕመማቸው የተፈወሱ አንዳንድ ሴቶች ዐብረውት ሄዱ፤ እነርሱም ሰባት አጋንንት የወጡላት መግደላዊት
ማርያም፣ 3 እንደ የሄሮድስ ቤተ መንግሥት አዛዥ የነበረው የኩዛ ሚስት የነበረችው ዮሐና፣ ሶስና ሌሎችም ብዙ ሴቶች ነበሩ፤ እነዚህ ኢየሱስንና ደቀ
መዛሙርቱን በገንዘባቸው ያገለግሉ ነበር። 4 ከብዙ የተለያዩ ከተሞች የመጡትን ጨምሮ ብዙ ሕዝብ በተሰበሰቡ ጊዜ፣ በምሳሌ ተጠቅሞ እንዲህ ብሎ
ነገራቸው፤ 5 “አንድ ዘሪ ዘሩን ሊዘራ ወጣ።እንደ ዘራም አንዳንዱ ዘር በመንገድ ዳር ወደቀና ተረገጠ፣ የሰማይ ወፎችም መጥተው በሉት። 6 ሌላው ዘርም
በጭንጫ መሬት ላይ ወደቀ፤ በበቀለም ጊዜ እርጥብ አፈር ስላልነበረው ወዲያው ደረቀ። 7 ሌላውም ዘር በእሾህ መካከል ወደቀ እሾሁም ከዘሩ ጋር ዐብሮት
አደገና አነቀው። 8 ከዘሩ አንዳንዱ ግን በመልካም ዐፈር ላይ ወደቀ መቶ እጥፍ ፍሬም አፈራ።" ኢየሱስ ይህንን ከተናገረ በኋላ ጮኽ ብሎ፣ "ጆሮ ያለው
ይስማ” አለ። 9 ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ ይህ ምሳሌ ምን ማለት እንደ ሆነ ጠየቁት፤ 10 ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፤ "ለእናንተ የእግዚአብሔርን መንግሥት
ምሥጢር የማወቅ ዕድል ተሰጥቷችኋል፣ ለተቀሩት ሕዝብ ግን 'እያዩ ስለማያዩ፣ እየሰሙም ስለማያስተውሉ' የሚማሩት በምሳሌ ነው። 11 ትርጒም እንደዚህ
ነው፣ ዘሩ የእግዚአብሔር ቃል ነው። 12 በመንገድ ዳር የወደቁት ሰምተው እንዳይድኑ ዲያብሎስ መጥቶ የሰሙትን ቃል ከልባቸው የሚወሰድባቸው ናቸው። 13
በድንጋይ መካከል የወደቁትም ቃሉን በሰሙ ጊዜ በደስታ የሚቀበሉትና መስማት እንጂ፣ በቃሉ ሥር ስላልሰደዱ ለጊዜው አምነው ፈተና በመጣባቸው ጊዜ፣
እምነታቸውን የሚክዱ ናቸው። 14 በእሾኽ መካከል የወደቀው ዘር ቃሉን የሰሙ ሰዎች ሲሆኑ፣ በኑሮ ሂደታቸው ወቅት በምድራዊ ሕይወት ዐሳብና በባለጠግነት
ምኞት የሚታነቁ በመሆናቸው ፍሬ ወደ ማፍራት የማይመጡ ናቸው። 15 ነገር ግን በመልካሙ ዐፈር ላይ የወደቁት በመልካምና በቅን ልብ ካደመጡ በኋላ
ቃሉን አጥብቀው የሚይዙ በመጽናት ፍሬ የሚያፈሩ ናቸው። 16 እንግዲህ፣ አንድ ሰው መብራት ካበራ በኋላ ጎድጓዳ ነገር ውስጥ ወይም ከአልጋ ሥር
አያደርገውም። ከዚያ ይልቅ ሁሉም ሰው ብርሃኑን ማየት ይችል ዘንድ ከፍ ባለ ስፍራ ላይ ያስቀምጠዋል። 17 ምክንያቱም የሚታወቅ እንጂ የሚደበቅ፣ ታውቆ
ወደ ብርሃን የሚወጣ እንጂ ምሥጢር የሚሆን ነገር የለም። 18 ስለዚህ እንዴት እንደምትሰሙ ተጠንቀቁ፣ ምክንያቱም ላለው ሁሉ የበለጠ ይሰጠዋል፣ ከሌለው
ደግሞ እንዳለው የሚመስለው እንኳ ይወሰድበታል።" 19 ከዚያም የኢየሱስ እናትና ወንድሞቹ ወደ እርሱ መጡ፣ ነገር ግን ከሕዝቡ ብዛት የተነሣ ወደ እርሱ
መቅረብ አልቻሉም። 20 ስለሆነም፣ ‘እናትህና ወንድሞችህ ሊያነጋግሩህ ፈልገው እየጠበቁህ ናቸው’ የሚል መልእክት አመጡለት። 21 ነገር ግን ኢየሱስ
መልሶ፣ “እናቴና ወንድሞቼ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚያደርጉት ናቸው” አላቸው። 22 ከዕለታት አንድ ቀን ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ በጀልባ ሲሳፈሩ
ኢየሱስ፣ "ሐይቁ ማዶ እንሻገር" አላቸው። ከዚያም እነርሱ መቅዘፍ ጀመሩ። 23 ነገር ግን እየቀዘፉ ሳሉ ኢየሱስ እንቅልፍ ወሰደውና በታላቅ ነፋስ የታጀበ ማዕበል
በሐይቁ ላይ ስለተነሣ ጀልባቸው ውስጥ ውሃ መግባት ጀመረ'፤ታላቅ አደጋም በፊታቸው ተደቀነ። 24 ከዚያም የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ወደ እርሱ መጥተው፣
"መምህር ሆይ፣ መምህር ሆይ፣ መሞታችን ነው" በማለት ቀሰቀሱት። እርሱም ከእንቅልፉ ነቅቶ ነፋሱንና የሚናወጠውን ማዕበል ገሰጸ ጸጥ አደረጋቸው። 25
ከዚያም ኢየሱስ፣ “እምነታችሁ የት አለ?” አላቸው። ፍርሃት ይዟቸውና በጣም ተደንቀው እርስ በርሳቸው፣ “ነፋሳትንና ባሕርን የሚያዝ እነርሱም የሚታዘዙለት
ይህ ማን ነው?" ተባባሉ። 26 ከገሊላ ባሕር በስተ ማዶ በሌላው አንጻር ወደ ነበረው ወደ ጌርጌሴኖን ክልል ደረሱ። 27 ኢየሱስ ከጀልባው ወርዶ ወደ ምድር
በተሻገረ ጊዜ፣ አጋንንት የነበሩበት አንድ ሰው አገኘው። ይህ ሰው ለረጅም ጊዜ ልብስ ለብሶ አያውቅም፤ በመቃብር ስፍራ እንጂ፣ በቤትም ውስጥ አልኖረም።
28 ኢየሱስን ባየው ጊዜ ጮኾ በፊቱ ተደፋ፤ በታላቅም ድምፅ፣ “የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሆይ! እኔ ከአንተ ምን ጉዳይ አለኝ? እንዳታሠቃየኝ
እለምንሃለሁ” አለው። 29 እንደዚህም ያለበት ምክንያት ብዙ ጊዜ ይይዘውና ያሠቃየው የነበረውን ርኩስ መንፈስ ከእርሱ እንዲወጣ ኢየሱስ አዞት ስለነበር ነው።
ምንም እንኳ በብረት ሰንሰለት የታሰረና በቁጥጥር ስር እንዲውል የተደረገ ቢሆንም፣ እስራቱን ይበጥስ፣ በአጋንንቱም ግፊት ወደ በረሐ እየሄደ ይንከራተት
ነበር። 30 ከዚያም ጊዜም ኢየሱስ፣ “ስምህ ማን ነው?” ብሎ ጠየቀው፤ እርሱም ብዙ አጋንንት ገብተውበት ነበርና ስሜ፣ "ጭፍራ" ነው ብሎ መለሰ። 31
በውስጡ የነበሩት አጋንንት ወደ ጥልቁ እንዲሄዱ እንዳያዛቸው መለመናቸውን ቀጠሉ። 32 በዚያም ብዙ ዐሳማዎች በኮረብታው ላይ ለግጦሽ ተሰማርተው
ነበር፤ አጋንንቱም ወደ ዐሳማዎቹ ይገቡ ዘንድ እንዲፈቅድላቸው ለመኑት። ኢየሱስ የለመኑትን እንዲያደርጉ ፈቀደላቸው። 33 ስለዚህ አጋንንቱ ከሰውዬው
ወጥተው ዐሳማዎቹ ውስጥ ገቡ። ዐሣማዎቹን ከኮረብታው ተጣድፈው ቁልቁል ወረዱ፣ ወደ ሐይቁም ውስጥ ገብተው ሰጠሙ። 34 ዐሳማዎቹን ሲያሰማሩ
የነበሩት ሰዎች ይህን በተመለከቱ ጊዜ ወደ ከተማውና ወደ ገጠሮች ሁሉ ሸሽተው በመሄድ ዜናውን አሠራጩ። 35 ስለዚህ ይህንን የሰሙት ሰዎች የሆነውን
ለማየት ወጡ፤ ወደ ኢየሱስም በመጡ ጊዜ አጋንንት የወጡለትን ሰው አገኙት። ሰውዬውም ልብስ ለብሶ ወደ አእምሮውም ተመልሶ በኢየሱስ እግር ሥር
ተቀምጦ ሲያዩት፣ ፍርሃት ያዛቸው። 36 ከዚያም የሆነውን ነገር ያዩ ሰዎች በአጋንንት ቁጥጥር ሥር የነበረው ሰው እንዴት እንደ ዳነ ለሌሎች ተናገሩ። 37
የጌርጌሴኖን ክልልና የዚያ አካባቢ ሰዎች ሁሉ ታላቅ ፍርሃት ይዟቸው ስለ ነበረ፣ ኢየሱስ ከእነርሱ እንዲሄድ ለመኑት፤ እርሱም ከዚያ ስፍራ ወደ መጣበት
ለመመለስ ወደ ጀልባይቱ ገባ። 38 አጋንንት የወጡለት ሰው ዐብሮት ለመሄድ ኢየሱስን ለመነው። 39 ኢየሱስ ግን፣ “ወደ ቤተ ሰብህ ተመልሰህ እግዚአብሔር
ያደረገልህን ታላላቅ ነገሮች ሁሉ ተርክላቸው” ብሎ አሰናበተው። ሰውየውም ኢየሱስ ያደረገለትን ታላላቅ ነገሮች በከተማው ሁሉ እየመሰከረ ጒዞውን ቀጠለ። 40
ሁሉም ይጠብቁት ነበርና ኢየሱስ ሲመለስ ሕዝቡ ተቀበሉት። 41 እነሆም ከምኩራብ መሪዎች አንዱ ኢያኢሮስ የተባለ ሰው መጣ፤ እርሱም በኢየሱስ እግር ላይ
ወድቆ ወደ ቤቱ ይመጣ ዘንድ ለመነው። 42 ወደ ቤቱ እንዲመጣ የፈለገው ዐሥራ ሁለት ዓመት የሆናት እንድያ ልጁ በሞት አፋፍ ላይ ስለነበርች ነው። ነገር ግን
ወደዚያ እየሄደ በነበረበት ጊዜ፣ ብዙ ሕዝብ በመጨናነቅ ይጋፉት ነበር። 43 በዚያም ለዐሥራ ሁለት ዓመት ደም ሲፈሳት የነበረች፣ ገንዘቧን ሁሉ ለሐኪሞች
ብትከፍልም አንዳቸውም ያልፈወሷት አንዲት ሴት ነበረች። 44 እርሷ ከኢየሱስ በስተኋላ መጥታ የልብሱን ጫፍ ነካች፤ የፈሳት የነበረው ደምም ወዲያው ቆመ።
45 ኢየሱስ፣ “የነካኝ ማን ነው?” አለ። ሁሉም አልነካንህም ብለው በተናገሩ ጊዜ፣ ጴጥሮስ፣ “ጌታ ሆይ፣ ሕዝቡ እኮ እየገፋፉህና እያጨናነቁህ ነው” አለው።
46 ኢየሱስ ግን፣ “ከእኔ ኀይል እንደ ወጣ ዐውቄአለሁና አንድ ሰው ነክቶኛል” አለ። 47 ሴቲቱ ያደረገችውን መደበቅ እንዳልቻለች ባስተዋለች ጊዜ፣ ሴቲቱ
እየተንቀጠቀጠች መጣችና በኢየሱስ እግር ሥር ወድቃ በሰዎች ሁሉ ፊት እርሱን ለምን እንደነካችውና እንዴት ወዲያው እንደ ተፈወሰች ተናገረች። ከዚያም
ኢየሱስ ሴቲቱን፥ 48 “ልጄ ሆይ እምነትሽ አድኖሻል በሰላም ሂጂ” አላት። 49 እርሱም ገና እየተናገረ ሳለ ከምኩራብ አለቃው ቤት አንድ ሰው መጥቶ፣ “ልጅህ
ሞታለች። መምህሩን አታድክመው” አለ። 50 ኢየሱስ ግን ይህን በሰማ ጊዜ፣ “እመን ብቻ እንጂ አትፍራ፣ እርሷም ትድናለች” አለው። 51 ከዚያም እርሱ ወደዚያ
ቤት በመጣ ጊዜ፣ ከጴጥሮስ፣ ከዮሐንስ፣ ከያዕቆብ እንዲሁም ከልጅቱ አባትና ከእናትዋ በስተቀር ማንም ዐብሮት እንዲገባ አልፈቀደም። 52 በዚያ ስፍራ
የነበሩት ሰዎች ሁሉ ያለቅሱ ዋይ ዋይም ይሉ ነበር። እርሱ ግን፣ “አታልቅሱ ልጅትዋ ተኝታለች እንጂ አልሞተችም” አለ። 53 እነርሱ ግን መሞቷን ዐውቀው ስለ
ነበር፣ በንቀት ሳቁበት። 54 እርሱ ግን የልጅቱን እጅ ይዞ፣ “አንቺ ልጅ ተነሽ” አላት። 55 ነፍስዋም ተመለሰች፣ ወዲያውኑም ብድግ አለች። እርሱም የምትበላው
እንዲሰጧት አዘዘ። 56 ወላጆቿም ተደነቁ፤ እርሱ ግን ስለሆነው ነገር ለማንም እንዳይናገሩ አዘዛቸው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Luke 8:1

አጠቃላይ መረጃ፡
እነዚህ ቁጥሮች ኢየሱስ በጉዞ ላይ እያለ ስለ ሰበከው ስብከት ዳራዊ መረጃ ይሰጣሉ።

እንዲህ ሆነ
ይህ ሐረግ እዚህ ጋ ጥቅም ላይ የዋለው የታሪኩን አዲስ ክፍል ለማመልከት ነው። (አዲስ ሁነትን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)

ከክፉ መናፍስትና ከበሽታ ተፈውሰው የነበሩት
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ኢየሱስ ከክፉ መናፍስት ነጻ ያወጣቸውና ከበሽታ ፈውሷቸው የነበሩ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ማርያም ... ሶስና
ሦስቱ ሴቶች ተጠቅሰዋል፡ ማርያም፣ ዮሐና፣ እና ሶስና (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ሰባት አጋንንት የወጡላት መግደላዊት የተባለችው ማርያም
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሰዎች መግደላዊት ብለው የሚጠሯት ማርያም ... ኢየሱስ ሰባት አጋንንት አስወጥቶላት የነበረች” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የሔሮድስ ቤት ኃላፊ የሆነው የኩዛ ሚስት ዮሐና
ዮሐና የኩዛ ሚስት ስትሆን ኩዛ ደግሞ የሔሮድስ ቤት ኃላፊ ነበር። “የሔሮድስ ቤት ኃላፊ የሆነው የኩዛ ሚስት ዮሐና” (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የሚያስፈልጋቸውን ያቀርቡ ነበር
“ኢየሱስንና ደቀ መዛሙርቱን በገንዘብ ይደግፉ ነበር”

Luke 8:4

አጠቃላይ መረጃ፡
ኢየሱስ ስለ መሬቱ ምሳሌ ለሕዝቡ ይነግራቸዋል። የምሳሌውን ትርጉም ለደቀ መዛሙርቱ ያብራራላቸዋል። (ምሳሌዎች የሚለውን ተመልከት)

ወደ እርሱ ይመጡ ነበር
“ወደ ኢየሱስ ይመጡ ነበር”

አንድ ገበሬ ዘሩን ለመዝራት ሄደ
“አንድ ገበሬ እርሻ ላይ ዘር ለመዝራት ሄደ” ወይም “አንድ ገበሬ ጥቂት ዘር እርሻ ላይ ለመዝራት ሄደ”

ጥቂቱ ወደቀ
“ከዘሩ ጥቂቱ ወደቀ” ወይም “ጥቂት ዘሮች ወደቁ”

በእግር ተረገጠ
x

Luke 8:7

አያያዥ መግለጫ፡
ኢየሱስ ለሕዝቡ ምሳሌዎቹን መናገሩን ያበቃል።

አነቀው
የገበሬው ዘር መብቀል እንዳይችል ማዕድናቱን ሁሉ፣ ውሃውንና የፀሐይ ብርሃኑን የእሾኹ ተክል ወሰደው።

ፍሬ አፈራ
“ምርት አበቀለ” ወይም “ብዙ ዘር አበቀለ”

ከመቶ ዕጥፍ የበለጠ
ይህ ማለት ከተዘራው ዘር ከመቶ ዕጥፍ በላይ የሆነ ማለት ነው።

የሚሰማ ጆሮ ያለው ማንም ቢሆን ይስማ
በአንዳንድ ቋንቋዎች በሁለተኛ መደብ መጠቀም በይበልጥ የተለመደ ይሆናል። “የሚሰማ ጆሮ ያላችሁ እናንተ፣ ስሙ” (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

Luke 8:9

አያያዥ መግለጫ፡
ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ መናገር ይጀምራል።

የ ... እውቀት እግዚአብሔር የሰጣችሁን
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የ... እውቀት እግዚአብሔር ሰጥቷችኋል” ወይም “የእግዚአብሔርን ... መረዳት እንድትችሉ እግዚአብሔር አድርጓችኋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የእግዚአብሔርን መንግሥት ምስጢር
እነዚህ የተደበቁ እውነቶች ናቸው፣ አሁን ግን ኢየሱስ ገልጧቸዋል።

ለሌሎች
“ለሌሎች ሰዎች”። ይህ የሚያመለክተው የኢየሱስን ትምህርት ያልተቀበሉትንና እርሱን ያልተከተሉትን ሰዎች ነው።

እያዩ እንዳያዩ
“ቢያዩም አይገነዘቡም”። ይህ ከነቢዩ ከኢሳይያስ የተጠቀሰ ጥቅስ ነው። አንዳንድ ቋንቋዎች የግሱን ባለቤት ማስታወቅ ያስፈልጋቸው ይሆናል። አ.ት፡ “ነገሮችን ቢያዩም አያስተውሏቸውም” ወይም “የሚሆኑትን ነገሮች ቢያዩም ምን ትርጉም እንዳላቸው አያስተውሉም”

እየሰሙ አያስተውሉም
“ቢሰሙም አያስተውሉም”። ይህ ከነቢዩ ከኢሳይያስ የተጠቀሰ ጥቅስ ነው። አንዳንድ ቋንቋዎች የግሱን ባለቤት ማስታወቅ ያስፈልጋቸው ይሆናል። አ.ት፡ “ትምህርትን ቢሰሙም እውነቱን አያስተውሉም”

Luke 8:11

አያያዥ መግለጫ፡
ኢየሱስ ስለ መሬት የተናገረውን ምሳሌ ትርጉም ለደቀ መዛሙርቱ ማብራራት ይጀምራል።

ዘሩ የእግዚአብሔር ቃል ነው
“ዘሩ ከእግዚአብሔር የመጣው መልዕክት ነው”

በመንገድ ዳር የሆኑት እነዚያ
“በመንገድ ዳር የወደቀው ዘር እርሱ”። ኢየሱስ ከሰዎች ጋር በማገናኘት ዘሩ ምን እንደሚሆን ይናገራል። አ.ት፡ “በመንገድ ዳር የወደቀው ዘር ሰዎችን ይወክላል” ወይም “በምሳሌው ውስጥ በመንገድ ዳር የወደቀው ዘር ሰዎችን ይወክላል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እነዚያ ናቸው
ዘሩ ሰው የሆነ ይመስል ኢየሱስ ስለ ሰዎች አንድ ነገር ለማሳየት በመፈለግ ስለ ዘር ይናገራል። አ.ት፡ “ሰዎች ላይ የሚሆነውን ያሳያል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ዲያብሎስ ይመጣና ከልባቸው ቃሉን ይወስደዋል
እዚህ ጋ “ልባቸው” የሰዎችን አዕምሮ ወይም ውስጣዊ ማንነት የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ዲያብሎስ ይመጣና የእግዚአብሔርን መልዕክት ከውስጠኛው አስተሳሰባቸው ይወስደዋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ይወስደዋል
ይህ ዘሩን የሚለቅም ወፍ በምሳሌው ውስጥ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ይህንን ስዕል ማሳየት የሚችልን ቃል በቋንቋህ ለመጠቀም ሞክር። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አምነው እንዳይድኑ
ይህ የዲያብሎስ ዓላማ እስከ ሆነ ድረስ እንደሚከተለው ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ዲያብሎስ፣ ‘አምነው መዳን የለባቸውም’ ብሎ ስለሚያስብ” ወይም “እንዳያምኑና እግዚአብሔር እንዳያድናቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በዐለት ላይ የወደቁት እነዚያ
“በዐለታማ አፈር ላይ የወደቁት እነዚያ”። ኢየሱስ ከሰዎች ጋር በማገናኘት ዘሩ ምን እንደሚሆን ይናገራል። አ.ት፡ “በዐለታማው መሬት ላይ የወደቀው ዘር ሰዎችን ይወክላል” ወይም “በምሳሌው ውስጥ በዐለታማው መሬት ላይ የወደቀው ዘር ሰዎችን ይወክላል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ዐለቱ
“ዐለታማው መሬት”

በፈተና ጊዜ
“መከራ በሚገጥማቸው ጊዜ”

ይወድቃሉ
የአነጋገር ዘይቤው ትርጉም “ማመናቸውን ያቆማሉ” ወይም “ኢየሱስን መከተላቸውን ያቆማሉ” የሚል ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Luke 8:14

በእሾህ መካከል የወደቀው ዘር ሰዎች ናቸው
“በእሾህ መካከል የወደቀው ዘር ሰዎችን ይወክላል” ወይም “በምሳሌው ውስጥ በእሾህ መካከል የወደቀው ዘር ሰዎችን ይወካላል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የዚህ ሕይወት ምኞት ... ታንቀዋል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የዚህ ሕይወት ፍላጎት፣ ባለጸግነትና ደስታ ያንቃቸዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ፍላጎት
ሰዎች የሚጨነቁላቸው ነገሮች

የዚህ ሕይወት ደስታ
“በዚህ ሕይወት ሰዎች የሚደሰቱባቸው ነገሮች”

በዚህ ሕይወት ፍላጎት፣ ባለጸግነትና ደስታ ስለ ታነቁ በተገቢው ሁኔታ አያፈሩም
ይህ ዘይቤአዊ አነጋገር የሚያመለክተው አረሙ የቡቃያውን ብርሃንና ማዕድናት በማቋረጥ ከዕድገት እንደሚገታቸው ነው። አ.ት፡ “አረም መልካሙን ቡቃያ ከማደግ እንደሚገታው የዚህ ሕይወት ፍላጎት፣ ብልጽግና እና ደስታም እነዚህን ሰዎች ፍሬአማ ከመሆን ይገታቸዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ፍሬአቸው አይበስልም
“የደረሰ ፍሬ አያፈሩም”። ብስል ፍሬ የመልካም ሥራ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “የበሰለ ፍሬ እንደማያፈራ ተክል እነርሱም መልካም ሥራ አይሠሩም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በመልካሙ መሬት ላይ የወደቀው ዘር እነዚህ ናቸው
“በመልካም መሬት ላይ የወደቀው ዘር ሰዎችን ይወክላል” ወይም “በምሳሌው ውስጥ በመልካም መሬት ላይ የወደቀው ዘር ሰዎችን ይወክላል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ቃሉን ሰምተው
“መልዕክቱን ሰምተው”

በመልካምና ቅን ልብ
እዚህ ጋ “ልብ” የሰውን አሳብ ወይም ፍላጎት የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “በመልካምና ቅን ምኞት”

በትዕግስት በመጽናት ፍሬ የሚያፈራ
“በትዕግስት በመጽናት ፍሬ የሚሰጡ” ወይም “በማያቋርጥ ጥረት ፍሬ የሚሰጡ”። ፍሬ የመልካም ሥራ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “መልካም ፍሬ እንደሚያፈራ ጤነኛ ተክል በመጽናት መልካም ሥራን ይሠራሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Luke 8:16

አያያዥ መግለጫ፡
ኢየሱስ በሌላ ምሳሌ መናገሩን ይቀጥላል፣ ከዚያም ቤተሰቦቹ በእርሱ ሥራ ውስጥ ስለሚኖራቸው ሚና አጽንዖት በመስጠት ለደቀ መዛሙርቱ መናገሩን ያበቃል።

ማንም የለም
ይህ ሌላ ምሳሌ የመጀመሩ ምልክት ነው። (ምሳሌዎች የሚለውን ተመልከት)

ተደብቆ ሳይታወቅ የሚቀር ምንም ነገር የለም
ይህ ድርብ አሉታ እንደ አዎንታዊ ንግግር ሊጻፍ ይችላል። አ.ት፡ “የተደበቀ ነገር ሁሉ እንዲታወቅ ይደረጋል” (ድርብ አሉታ የሚለውን ተመልከት)

የማይታወቅና ወደ ብርሃን የማይመጣ ምስጢር ሆኖ የሚቀር ምንም ነገር የለም
ይህ ድርብ አሉታ እንደ አዎንታዊ ንግግር ሊጻፍ ይችላል። አ.ት፡ “ምስጢር የሆነው ነገር ሁሉ ወደ ብርሃን ይመጣል፣ እንዲታወቅም ይደረጋል” (ድርብ አሉታ የሚለውን ተመልከት)

ላለው የበለጠ ይሰጠዋል
ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ስለ ማስተዋልና ስለ ማመን መሆኑን ከዐውዱ በግልጽ መረዳት ይቻላል። ይህ በግልጽ ሊነገርና ወደ አድራጊ ድምፅ ሊቀየር ይችላል። አ.ት፡ “ማስተዋል ላለው ለማንም ቢሆን የበለጠ ማስተዋል ይሰጠዋል” ወይም “እግዚአብሔር እውነትን የሚያምኑትን እነዚያን የበለጠ እንዲያስተውሉ ደግሞ ያስችላቸዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ከሌለው ... ከእርሱ ይወሰድበታል
ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ስለ ማስተዋልና ስለ ማመን መሆኑን ከዐውዱ በግልጽ መረዳት ይቻላል። ይህ በግልጽ ሊነገርና ወደ አድራጊ ድምፅ ሊቀየር ይችላል። አ.ት፡ “ማንም ማስተዋል የሌለው ሰው አለኝ የሚለውን ማስተዋል እንኳን ያጣዋል” ወይም “ነገር ግን እውነትን የማያምኑትን እነዚያን ተረድተነዋል የሚሉትን ጥቂቱን ማስተዋል እንኳን እንዳያስተውሉ ያደርጋቸዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Luke 8:19

ወንድሞች
እነዚህ ከኢየሱስ በኋላ ከማርያምና ከዮሴፍ የተወለዱ፣ የኢየሱስ ታናናሽ ወንድሞች የነበሩ ሌሎች ወንዶች ልጆች ናቸው። የኢየሱስ አባት እግዚአብሔር፣ የእነርሱ አባት ደግሞ ዮሴፍ እስከ ሆነ ድረስ በሙያዊ አገላለጽ በእናቱ በኩል ወንድሞቹ ናቸው። ይህ ዝርዝር በአግባቡ አልተተረጎመም።

ተነገረው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሰዎች ነገሩት” ወይም “አንድ ሰው ነገረው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ሊያዩህ ፈልገው
“ሊያዩህ ይፈልጋሉ”

እናትና ወንድሞቼ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚያደርጉት እነርሱ ናቸው
ይህ ዘይቤአዊ አነጋገር የሚገልጸው ከኢየሱስ ለመስማት የሚመጡ ሰዎች ለእርሱ የቤተሰቡን ያህል አስፈላጊዎች መሆናቸውን ነው። አ.ት፡ “የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚታዘዙት እነርሱ ለእኔ እንደ እናቴና ወንድሞቼ ናቸው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የእግዚአብሔር ቃል
“እግዚአብሔር የተናገረው መልዕክት”

Luke 8:22

አያያዥ መግለጫ፡
ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ የጌንሳሬጥን ሐይቅ ለመሻገር በጀልባ ይጠቀማሉ። ደቀ መዛሙርቱ በሚነሣው ማዕበል አማካይነት ስለ ኢየሱስ ኃይል በይበልጥ ይማራሉ።

ሐይቁ
ይህ የጌንሳሬጥ ሐይቅ ነው፣ የገሊላ ባህር ተብሎም ይጠራል።

መጓዝ ጀመሩ
የዚህ አገላለጽ ትርጉም፣ ሐይቁን ለመሻገር በጀልባቸው መጓዝ ጀመሩ የሚል ነው።

በመጓዝ ላይ እያሉ
“ሲሄዱ ሳሉ”

አንቀላፋ
“ማንቀላፋት ጀመረ”

ከባድ ዐውሎ ንፋስ ወረደ
“በጣም ታላቅ የሆነ ዐውሎ ንፋስ ጀመረ” ወይም “በጣም ኃይለኛ ንፋስ በድንገት መንፈስ ጀመረ”

ጀልባቸው በውሃ ይሞላ ነበር
ኃይለኛው ንፋስ ብርቱ ሞገድ በማስነሣት የጀልባዋን ጎንና ጎን በውሃ እንዲገፋት አደረገ። ይህ በግልጽ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ንፋሱ ከፍተኛ ሞገድ በመፍጠር ጀልባቸውን በውሃ መሙላት ጀመረ”

Luke 8:24

ገሰጸው
በቀጥታ ተናገረው

የውሃው ቁጣ
“አስፈሪው ሞገድ”

ተዉ
“ንፋሱና ማዕበሉ ቆመ” ወይም “ጸጥ አሉ”

እምነታችሁ የት አለ?
ኢየሱስ ለእነርሱ ስለሚያደርግላቸው ጥበቃ ስላልታመኑት በእርጋታ ይገስጻቸዋል። ይህ እንደ መግለጫ ሊጻፍ ይችላል። አ.ት፡ “እምነት ሊኖራችሁ ይገባል!” ወይም “ልትታመኑብኝ ይገባል!” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

... የሚታዘዙለት እንግዲያው ይህ ማን ይሆን?
“... የሚታዘዙለት ይህ ምን ዓይነት ሰው ነው?” ይህ ጥያቄ ኢየሱስ ማዕበሉን መቆጣጠር መቻሉ የፈጠረባቸውን ድንጋጤና ግራ መጋባት ይገልጻል። (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

የሚያዝ ... የሚታዘዙለት እንግዲያው ይህ ማን ይሆን?
ይህ ወደ ሁለት ዐረፍተ ነገር ሊቀየር ይችላል። “እንግዲህ ይህ ማነው? እርሱ ያዛቸዋል ... ይታዘዙታል!”

Luke 8:26

አያያዥ መግለጫ፡
ኢየሱስ ከአንድ ሰው ብዙ አጋንንት ወዳወጣበት ወደ ጌርጌሴኖን ባህር ዳርቻ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር መጣ።

ጌርጌሴኖን ወደሚባል ሀገር
ጌርጌሶናዊያን ጌርጌሴኖን የምትባል ከተማ ሰዎች ነበሩ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ከገሊላ ሐይቅ ማዶ
“ከገሊላ ሐይቅ በወዲያኛው ማዶ”

አንድ ሰው ከከተማው
“አንድ ሰው ከጌርጌሴኖን ከተማ”

አጋንንት የነበሩበት አንድ ሰው ከከተማ
ሰውየው አጋንንት ነበሩበት፤ አጋንንት የኖሩት በከተማው ላይ አልነበረም። አ.ት፡ “አንድ ሰው ከከተማ. . . ይህ ሰው አጋንንት ነበሩበት”

አጋንንት የነበሩበት
“አጋንንት ተቆጣጥረውት የነበረ” ወይም “አጋንንት የተቆጣጠሩት”

ለረጅም ጊዜ ራቁቱን ይኖር ነበር ... ነገር ግን በመቃብር መካከል
ይህ አጋንንት ስለነበሩበት ሰው ዳራዊ መረጃ ነው። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ራቁቱን ይኖር ነበር
“ልብስ አይለብስም ነበር”

መቃብር
ይህ ሰዎች ሬሳ የሚያኖሩበት፣ ምናልባት አንድ ሰው ለመጠለያነት የሚጠቀምበት ዋሻ ወይም አነስተኛ ግንብ ሊሆን ይችላል።

Luke 8:28

ኢየሱስን ባየው ጊዜ
“አጋንንት የነበሩበት ሰው ኢየሱስን ባየው ጊዜ”

ጮኸ
“በታላቅ ድምፅ ጮኸ” ወይም “በስቃይ ጮኸ”

በፊቱ ወደቀ
“በኢየሱስ ፊት በምድር ላይ ወደቀ”። የወደቀው በድንገት አይደለም።

በታላቅ ድምፅ ተናገረ
“በጩኸት ተናገረ” ወይም “ከፍ ባለ ድምፅ ጮኸ”

ከእኔ ጋር ምን ጉዳይ አለህ
የዚህ የአነጋገር ዘይቤ ትርጉም “ለምን ታስቸግረኛለህ?” ማለት ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የልዑል እግዚአብሔር ልጅ
ይህ ለኢየሱስ አስፈላጊ ማዕረግ ነው። (አባትን እና ልጅን መተርጎም የሚለውን ተመልከት)

ከያዘው ብዙ ጊዜ ሆኖት ነበር
“ሰውየውን ከተቆጣጠረው ብዙ ጊዜ ሆኖት ነበር” ወይም “ወደ እርሱ ከገባበት ብዙ ጊዜ ሆኖት ነበር”። ይህ የሚናገረው ኢየሱስ ከሰውዬው ጋር ከመገናኘቱ በፊት አጋንንቱ ብዙ ጊዜ ያደርገው የነበረውን ነው።

ቢታሰርም እንኳን ... ይጠብቁት ነበር
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሰዎች በሰንሰለትና በእግር ብረት ቢያስሩትና ቢጠብቁትም እንኳን” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Luke 8:30

ሌጌዎን
ይህንን ብዙ ቁጥር ያላቸውን ወታደሮች ወይም ሰዎች በሚያመለክት ቃል ተርጉመው። አንዳንድ ትርጉሞች “ሰራዊት” ይሉታል። አ.ት፡ “የሻለቃ ጦር” ወይም “ብርጌድ”

እርሱን ይለምነው ጀመር
“ኢየሱስን ይለምነው ጀመር”

Luke 8:32

በዚህ ጊዜ በኮረብታው ወገብ ላይ ብዙ የአሳማ መንጋ ይመገቡ ነበር
ይህ ስለ አሳማዎቹ ለማስተዋወቅ የተጨመረ ዳራዊ መረጃ ነው። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

በኮረብታው ወገብ ይመገቡ ነበር
“ኮረብታው ላይ ሣር እየተመገቡ በአቅራቢያው ነበሩ”

ስለዚህ አጋንንቱ ወጡ
እዚህ ጋ፣ “ስለዚህ” የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው አጋንንቱ ከሰውየው የወጡት ኢየሱስ ወደ አሳማዎቹ እንዲገቡ ስለነገራቸው መሆኑን ለማብራራት ነው።

ተጣደፉ
በጣም በፍጥነት ሮጡ

መንጋው ... ሰመጡ
“መንጋው... ሰመጡ”። አሳማዎቹ ራሳቸው ውሃው ውስጥ ስለ ነበሩ ማንም እንዲሰምጡ አላደረጋቸውም።

Luke 8:34

አጋንንት የወጡለትን ሰው አገኙት
“አጋንንት የለቀቁትን ሰው አዩት”

በአዕምሮው ሆኖ
“ጤነኛ” ወይም “ትክክለኛ ጠባይ ሲያሳይ”

በኢየሱስ እግሮች አጠገብ ተቀምጦ
እዚህ ጋ፣ “እግሮች አጠገብ ተቀምጦ” የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ትርጉሙ “በአጠገቡ በትህትና ተቀምጦ” ወይም “በፊት ለፊቱ ተቀምጦ”። አ.ት፡ “በኢየሱስ ፊት ለፊት መሬት ላይ ተቀምጦ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ፈርተው ነበር
ኢየሱስን ፈርተውት እንደነበረ በግልጽ መናገር ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። አ.ት፡ “ኢየሱስን ፈርተውት ነበር”

Luke 8:36

አይተውት የነበሩት
“እነዚያ የሆነውን ነገር ያዩት”

በአጋንንት ተይዞ የነበረውና የተፈወሰው ሰው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አጋንንት ይዞት የነበረውን ሰው ኢየሱስ ፈውሶት ነበር” ወይም “አጋንንት ተቆጣጥሮት የነበረውን ሰው ኢየሱስ ፈውሶት ነበር” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የጌርጌሴኖን ሀገር
“ያ የጌርጌሴናውያን አካባቢ” ወይም “ጌርጌሴናውያን ሰዎች ይኖሩበት የነበረ አካባቢ”

ታላቅ ፍርሃት ያዛቸው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በጣም ፈሩ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ተመለስ
መዳረሻው ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ወደ ሐይቁ ማዶ ተመልሰህ ሂድ”

Luke 8:38

ሰውዬው
በእነዚህ ቁጥሮች የተፈጸሙት ሁነቶች ኢየሱስ በጀልባ ከመሄዱ በፊት ነው። ይህንን መነሻው ላይ ግልጽ አድርጎ መናገር ሊጠቅም ይችላል። አ.ት፡ “ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ከመሄዳቸው በፊት ሰውዬው” ወይም “ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ የጀልባ ጉዞአቸውን ከመጀመራቸው በፊት ሰውዬው”

ቤትህ
“ቤተሰቦችህ” ወይም “ዘመዶችህ”

እግዚአብሔር ያደረገልህን ሁሉ መስክር
“እግዚአብሔር ስላደረገልህ ነገር ሁሉ ንገራቸው”

Luke 8:40

አያያዥ መግለጫ፡
ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ከሐይቁ በሌላኛው በኩል ከገሊላ በተመለሱ ጊዜ 12 ዓመት የሆናትን የምኩራብ አለቃውን ልጅ፣ እንዲሁም 12 ዓመት ደም ሲፈሳት የነበረችውን ሴት ፈወሳቸው።

አጠቃላይ መረጃ፡
እነዚህ ቁጥሮች ስለ ኢያኢሮስ ዳራዊ መረጃ ይሰጣሉ። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ሕዝቡ ተቀበለው
“ሕዝቡ በደስታ ሰላምታ ሰጡት”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከምኩራብ አለቆች አንዱ
“በአካባቢው በነበረ ምኩራብ አለቆች ከሆኑት አንዱ” ወይም “በዚያች ከተማ በምኩራብ የተገናኘው የሕዝቡ መሪ”

በኢየሱስ እግር ላይ ተደፋ
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፣ 1) “በኢየሱስ እግር ስር ሰገደ” ወይም 2) “በኢየሱስ እግር አጠገብ በምድር ላይ ወደቀ”። ኢያኢሮስ የወደቀው በድንገት አይደለም። ይህንን ያደረገው ለኢየሱስ ስላለው ትህትና እና አክብሮት ምልክት እንዲሆን ነው የሚሉት ናቸው።

እየሞተች ነው
“ልትሞት ነው”

ኢየሱስ በመንገድ ላይ እያለ
አንዳንድ ተርጓሚዎች ኢየሱስ ከኢያኢሮስ ጋር ለመሄድ መስማማቱን በቅድሚያ መናገር ይኖርባቸዋል። አ.ት፡ “ስለዚህ ኢየሱስ ከእርሱ ጋር ለመሄድ ተስማማ። በመንገድ ላይ እያለ”

ብዙ ሕዝብ በዙሪያው ሆነው አጋፉት
“ሰዎቹ በኢየሱስ ዙሪያ ተጠጋግተው ከበውት ነበር”

Luke 8:43

በዚያ አንዲት ሴት ነበረች
ይህ በታሪኩ ውስጥ አንድ አዲስ ገጸ ባህርይ ያስተዋውቃል። (አዲስና ነባር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)

ትደማ የነበረች
“ደም ይፈሳት የነበረች”። ተገቢው ጊዜ ባይሆንም እንኳን ምናልባት በማህፀን እያለች ጀምሮ ሳትደማ አልቀረችም። አንዳንድ ባህሎች እንደዚህ ያለውን ሁኔታ በትህትና የሚያመላክቱበት መንገድ ይኖራቸዋል።

በማንም ልትፈወስ አልቻለችም
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ነገር ግን ማንም ሊፈውሳት አልቻለም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የልብሱን ጫፍ ነካች
“የመጎናጸፊያውን ዘርፍ ነካች”። አይሁዳውያን ወንዶች በእግዚአብሔር ሕግ እንደታዘዘው የክብረ በዓል ልብሶቻቸው አካል በማድረግ በመጎናጸፊያዎቻቸው ላይ መነሳንስ ይደርቡ ነበር። እርሷ የነካችው ይህንን ሊሆን ይችላል።

Luke 8:45

ብዙ ሕዝብ ... እያጋፉህ ነው
ጴጥሮስ ይህንን ሲል የትኛውም ሰው ኢየሱስን ሊነካው ይችል እንደነበር ማመልከቱ ነው። አስፈላጊ ከሆነ ይህ ግልጽ ያልሆነ መረጃ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አ.ት፡ “በዙሪያህ ብዙ ሕዝብ ከቦ እያጋፋህ ነው፣ ስለዚህ ከእነርሱ አንዱ ነክቶህ ይሆናል”

አንድ ሰው ነክቶኛል
ይህንን ሆነ ተብሎ የተደረገውን “መንካት” ከሕዝቡ ድንገተኛ መንካት መለየት ሊጠቅም ይችላል። አ.ት፡ “አንድ ሰው ሥራዬ ብሎ ነክቶኛል”

ከእኔ ኃይል እንደ ወጣ አውቃለሁ
ኢየሱስ ኃይል አላጣም ወይም አልደከመም፣ ነገር ግን የእርሱ ኃይል ሴቲቱን ፈውሷታል። አ.ት፡ “የሚፈውስ ኃይል ከእኔ እንደወጣ አውቃለሁ” ወይም “ኃይሌ አንድ ሰው እንደ ፈወሰ ተሰምቶኛል”

Luke 8:47

ከዕይታ ማምለጥ እንደማትችል
“ያደረገችውን በምስጢር መያዝ እንደማትችል”። ምን እንዳደረገች መናገር ሊጠቅም ይችላል። አ.ት፡ “ኢየሱስን የነካችው እርሷ የመሆኗን ምስጢር መያዝ እንደማትችል”

እየተንቀጠቀጠች መጣች
“በፍርሐት እየተንቀጠቀጠች መጣች”

በፊቱ ወደቀች
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፣ 1) “በኢየሱስ ፊት ሰገደች” ወይም 2) “በኢየሱስ እግር ላይ በምድር ላይ ተደፋች”። የወደቀችው በድንገት አይደለም። ይህ ለኢየሱስ የቀረበ የትህትና እና የአክብሮት ምልክት ነው የሚሉት ናቸው።

በሕዝቡ ሁሉ ፊት
“ሕዝቡ ሁሉ እያዩ”

ሴት ልጅ
ይህ አንዲትን ሴት በደግነት የመናገሪያ መንገድ ነበር። የአንተ ቋንቋ ይህንን ደግነት የሚያሳይበት ሌላ መንገድ ይኖረው ይሆናል።

እምነትሽ ጤነኛ አድርጎሻል
“በእምነትሽ ምክንያት ጤነኛ ሆነሻል”። የነገር ስም የሆነው “እምነት” እንደ ድርጊት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ስላመንሽ ተፈውሰሻል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

በሰላም ሂጂ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ “ደህና ሁኚ” የማለትና በዚያው ጊዜ ቡራኬን የመስጠት መንገድ ነው። አ.ት፡ “ስትሄጂም ከእንግዲህ አትጨነቂ” ወይም “እየሄድሽ እያለሽ እግዚአብሔር ሰላምን ይስጥሽ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Luke 8:49

ገና እየተናገረ እያለ
“ኢየሱስ ገና ለሴቲቱ እየተናገረ እያለ”

የምኩራብ አለቃ
ይህ ኢያኢሮስን ያመለክታል (ሉቃስ 8:41 ን ተመልከት)።

መምህሩን አታስቸግረው
ይህ መግለጫ ልጅቱ ስለሞተች ኢየሱስ ከአሁን በኋላ ምንም ነገር ለማድረግ እንደማይችል ያመለክታል።

መምህሩ
ይህ ኢየሱስን ያመለክታል።

ትፈወሳለች
“ደህና ትሆናለች” ወይም “እንደገና በሕይወት ትኖራለች”

Luke 8:51

ወደ ቤት በመጣ ጊዜ
“ወደ ቤት በመጡ ጊዜ”። ኢየሱስ ከኢያኢሮስ ጋር ወደዚያ ሄደ። ደግሞም አንዳንድ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ከእነርሱ ጋር ሄዱ።

ከጴጥሮስ፣ ዮሐንስ፣ ያዕቆብ፣ ከልጅቱ አባትና እናት በስተቀር ... ለማንም አልፈቀደም
ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ኢየሱስ ለጴጥሮስ፣ ለዮሐንስ፣ ለያዕቆብ፣ ለልጅቱ አባትና እናት ብቻ ከእርሱ ጋር ወደ ውስጥ እንዲገቡ ፈቀደላቸው”

የልጅቱ አባት
ይህ የሚያመለክተው ኢያኢሮስን ነው።

ሁሉም ያለቅሱና ሙሾ ያወጡላት ነበር
ይህ በዚያ ባህል የተለመደ የሐዘን መግለጫ መንገድ ነበር። አ.ት፡ “በዚያ የነበሩት ሰዎች ሁሉ ልጅቱ ሞታ ስለነበር ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በማልቀስ ምን ያህል እንዳዘኑ በመግለጽ ላይ ነበሩ”

መሞቷን ስላወቁ ሳቁበት
“ልጅቱ መሞቷን ስላወቁ ሳቁበት”

Luke 8:54

እጇን ያዘ
“ኢየሱስ የልጅቱን እጅ ያዘ”

መንፈሷ ተመለሰ
“መንፈሷ ወደ አካሏ ተመለሰ”። አይሁድ ሕይወት ማለት የመንፈስ ወደ ሰው ውስጥ መምጣት እንደነበር ተረድተዋል። አ.ት፡ “እንደገና መተንፈስ ጀመረች” ወይም “ወደ ሕይወት ተመለሰች” ወይም “እንደገና ሕያው ሆነች”

ለአንድም ሰው እንዳይነግሩ
ይህ በተለየ ሁኔታ መነገር ይችል ነበር። አ.ት፡ “ለማንም እንዳይነግሩ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 9

1 ኢየሱስም ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ወደ እርሱ ጠርቶ በአጋንንት ሁሉ ላይና በሽታዎችን የመፈወስ ሥልጣን ሰጣቸው። 2 የእግዚአብሔርን መንግሥት
እንዲሰብኩና በሽተኞችን እንዲፈውሱ ላካቸው። 3 እንዲህም አላቸው፤ “ለጕዞአችሁ በትርም ቢሆን፣ የገንዘብም ቦርሳ ቢሆን፣ ስንቅም ቢሆን፣ ገንዘብ ወይም
ቅያሬ ልብስ፣ ምንም ነገር አትያዙ። 4 ከዚያ ስፍራ እስከምትወጡ በገባችሁበት ቤት በዚያ ቆዩ። 5 “የማይቀበሏችሁ ቢኖሩ ከዚያ ከተማ ስትወጡ ምስክር
እንዲሆንባቸው ከእግሮቻችሁ ጫማ ላይ አቧራውን አራግፉ።” 6 ከዚያም እነርሱ ከዚያ ተነሥተው የምሥራቹን ወንጌል እየሰበኩ፣ በሄዱባቸውም ስፍራዎች ሁሉ
በሽተኞችን እየፈወሱ ያልፉ ነበር። 7 የአራተኛው ክፍል ገዢ ሄሮድስ እየተደረገ የነበረውን ሁሉ በሰማ ጊዜ፣ በጣም ተሸበረ፣ ምክንያቱም ‘አንዳንዶቹ መጥምቁ
ዮሐንስ ከሞት ተነሥቷል፤ 8 በሌሎች ዘንድ ደግሞ ኤልያስ ተገልጧል፤ እንደ ገና ሌሎች ከጥንት ነቢያት አንዱ ሕያው ሆኖ ተነሥቷል’ ይሉ ነበር። 9 ሄሮድስም
“የዮሐንስን ራስ እኔ አስቈርጬዋለሁ፣ እንዲህ ያለ ነገር የምሰማበት ይህ ማን ነው?” አለ። ሄሮድስም ኢየሱስን ለማየት ጥረት ያደርግ ነበር። 10 የተላኩት
በተመለሱ ጊዜ፣ ያደረጉትን ሁሉ ነገሩት። ኢየሱስ ራሱ ሐዋርያቱን አስከትሎ ቤተ ሳይዳ ወደምትባል ከተማ ሄደ። 11 ነገር ግን፣ ሕዝቡ ስለዚህ ጉዳይ ሰሙና
ተከተሉት፣ እርሱም ተቀብሏቸው ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ነገራቸው፣ መፈወስ የሚያስፈልጋቸውንም ፈወሳቸው። 12 ቀኑ ወደ መገባደድ ተቃረበ፣ ዐሥራ
ሁለቱም ወደ እርሱ መጡና “ያለንበት ቦታ ምንም የሌለበት ምድረ በዳ በመሆኑ ሕዝቡ በአካባቢው ወዳሉት መንደሮችና ገጠሮች ሄደው ማረፊያ ቦታና ምግብ
እንዲያገኙ አሰናብታቸው” አሉት። 13 እርሱ ግን፣ “የሚበሉትን እናንተ ስጧቸው” አላቸው። እነርሱም፣ “ወጣ ብለን ለዚህ ሁሉ ሕዝብ ምግብ ካልገዛን በስተቀር
አሁን ያለን ከአምስት እንጀራና ከሁለት ዐሣ የበለጠ አይደለም” አሉት። 14 በዚያ አምስት ሺህ ያህል ሰዎች ነበሩ። እርሱም ደቀ መዛሙርቱን፣ “ሃምሳ ሃምሳ
ሆነው በቡድን እንዲቀመጡ አድርጓቸው” አላቸው። 15 ስለዚህ እርሱ እንዳላቸው አደረጉ፣ ሕዝቡም ሁሉ ተቀመጡ። 16 እርሱም አምስቱን እንጀራና ሁለቱን
ዐሣ ይዞ ወደ ሰማይ አሻቅቦ ከተመለከተ በኋላ ባርኮ፣ ቈርሶም ለሕዝቡ እንዲያቀርቡላቸው ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸው። 17 ሁሉም በልተው ጠገቡ፣
የተራረፈውም የምግብ ፍርፋሪ ተሰበሰበና ዐሥራ ሁለት ቅርጫት ሙሉ ሆነ። 18 ኢየሱስ ብቻውን ይጸልይ በነበረበት አንድ ወቅት ደቀ መዛሙርቱ ከእርሱ ጋር
ነበሩና፣ “ሕዝቡ እኔ ማን እንደሆንሁ ነው የሚናገሩት?” ብሎ ጠየቃቸው። 19 እነርሱም፣ “አጥማቂው ዮሐንስ ፣ ሌሎች ደግሞ ኤልያስ፣ እንደ ገና ሌሎች ጥንት
ከነበሩት ነቢያት አንዱ ከሙታን ተነሥቶ ነው ይላሉ” አሉት። 20 “እናንተ ግን እኔን ማን ትሉኛላችሁ?” አላቸው። ጴጥሮስ፣ “አንተ ከእግዚአብሔር የመጣህ
ክርስቶስ ነህ” ብሎ መለሰ። 21 ነገር ግን ኢየሱስ ይህን ለማንም እንዳይነግሩ በማስጠንቀቅ አዘዛቸው። 22 በተጨማሪም የሰው ልጅ ብዙ መከራ መቀበል
እንደሚገባው በሽማግሌዎች፣ በካህናት አለቆችና በሕግ መምሕራን ተቀባይነት እንደማያገኝ፣ እንደሚሞትና በሦስተኛው ቀን ከሙታን እንደሚነሣ በቅድሚያ
አስታወቃቸው። 23 ለሁሉም እንዲህ አላቸው፤ "እኔን መከተል የሚፈልግ ራሱን ይካድ ዕለት ዕለትም መስቀሉን ተሸክሞ ይከተለኝ። 24 ሕይወቱን ሊያድን ጥረት
የሚያደርግ ሰው ካለ ያጠፋታል፣ ስለ እኔ ብሎ ሕይወቱን የሚጥል ደግሞ ያድናታል። 25 አንድ ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ የራሱን ሕይወት ግን ቢያጣ ምን
ይጠቅመዋል? 26 በእኔና በቃሌ የሚያፍር ሁሉ የሰው ልጅ በራሱ፣ በአባቱ፣ እንዲሁም በቅዱሳን መላእክት ክብር በሚመጣበት ጊዜ ያፍርበታል። 27 እኔ ግን
በእውነት እላችኋለሁ፣ እዚህ ከቆማችሁት መካከል አንዳንዶቻችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት እስከምታዩ ድረስ ሞትን አትቀምሱም። 28 ኢየሱስ ይህን
ከተናገረ ከስምንት ቀን ገደማ በኋላ ጴጥሮስን፣ ዮሐንስን፣ እንዲሁም ያዕቆብን ይዞ ለመጸለይ ወደ ተራራ ወጣ። 29 እየጸለየም ሳለ የፊቱ መልክ ተለወጠ
ልብሱም በጣም ከመንጣቱ የተነሣ አንፀባረቀ። 30 እነሆ፣ ሁለት ሰዎች ከእርሱ ጋር ይነጋገሩ ነበር! 31 እነርሱም በክብር የተገለጡት ሙሴና ኤልያስ ነበሩ።
በኢየሩሳሌም ሊፈጽም ስላለው ከዚህ ሕይወት ስለ መለየቱ ይነጋገሩ ነበር። 32 ጴጥሮስና ዐብረውት የነበሩት እንቅልፍ ከብዶባቸው ነበር። ሙሉ በሙሉ በነቁ
ጊዜ ግን የኢየሱስን ክብርና ዐብረውት የነበሩትን ሁለቱን ሰዎች አዩ። 33 እነርሱ ከኢየሱስ ተለይተው ሲሄዱ፣ ጴጥሮስ፣ “ጌታ ሆይ፣ ለእኛ በዚህ መሆን መልካም
ነው፣ አንድ ለአንተ፣ አንድ ለሙሴ፣ አንድ ደግሞ ለኤልያስ ሦስት ዳሶችን ልንሠራ ይገባናል” አለው። ስለ ምን እየተናገረ እንደ ነበረ አላስተዋለም። 34 ከዚያም
እርሱ ይህን እየተናገረ ሳለ ደመና መጥቶ ጋረዳቸው፤ በዙሪያቸው ከነበረው ደመና የተነሣ ፈሩ። 35 ከደመናው ውስጥ፣ “የመረጥሁት ልጄ ይህ ነው፣ እርሱን
ስሙት” የሚል ድምፅ መጣ። 36 የድምፁ መሰማት ባበቃ ጊዜ፣ ኢየሱስ ብቻውን ነበረ። እነርሱም ዝም አሉ፤ በነዚያ ቀናት ስላዩአቸው ስለ እነዚያ ነገሮች
ምንም ነገር ለማንም አልተናገሩም። 37 ከተራራው በወረዱ ማግስት ብዙ ሕዝብ ተሰብስበው ወደ እርሱ መጡ። 38 እነሆም፣ ከሕዝቡ መካከል አንድ ሰው፣
“መምህር ሆይ፣ ብቸኛ የሆነውን አንድ ልጄን ትመለከትልኝ ዘንድ እለምንሃለሁ። 39 ክፉ መንፈስ በላዩ ሲመጣበት በድንገት ይጮኻል፣ እየጣለ
ያንፈራግጠዋል፤ አረፋም በአፉ ይደፍቃል። በጭንቅ ለቅቆት ይሄዳል፣ በሚሄድበት ጊዜ ክፉኛ ያቈስለዋል። 40 ክፉውን መንፈስ እንዲያወጡለት ደቀ
መዛሙርትህን ለመንኋቸው፣ እነርሱ ግን አልቻሉም” በማለት ጮኸ። 41 ኢየሱስ እንደዚህ በማለት መልስ ሰጠ፣ “ክፉና ጠማማ ትውልድ፣ ከእናንተ ጋር
የምኖረውና የምታገሣችሁ እስክ መቼ ነው? ልጅህን ወደዚህ አምጣው።” 42 ልጁ እየመጣ ሳለ ጋኔኑ ጣለው፣ እጅግም አንፈራገጠው። ኢየሱስ ግን ርኩሱን
መንፈስ ገሠጸውና ልጁን ፈወሰው፣ ለአባቱም መልሶ ሰጠው። 43 ሁሉም በእግዚአብሔር ታላቅነት ተደነቁ። ነገር ግን ሁሉም እርሱ ባደረጋቸው ነገሮች ሁሉ
እየተደነቁ ሳሉ፣ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን፣ 44 "የነገርኋችሁን እነዚህን ነገሮች በጥልቀት አስተውሉ፤ ምክንያቱም የሰውን ልጅ በሰዎች እጅ አሳልፈው
ይሰጡታል" አላቸው። 45 ነገር ግን ተሰውሮባቸው ስለ ነበረ፣ ይህ አባባሉ ምን እንደ ሆነ ስላልተረዱት ሊገባቸው አልቻለም። ስለዚያ አባባል እርሱን መጠየቅ
ፈሩ። 46 ከዚያም ከእነርሱ መካከል ከሁሉም እጅግ ታላቅ የሆነው ማን ነው የሚለውን ጥያቄ በሚመለከት ክርክር ተነሣ። 47 ኢየሱስ ግን በልባቸው ምን
እያሰላሰሉ እንደ ነበሩ ባወቀ ጊዜ፣ አንድ ትንሽ ልጅ ይዞ በአጠገቡ አቆመው፣ እንዲህም አላቸው፤ 48 "እንደዚህ ያለውን ሕፃን በስሜ የሚቀበል፣ እኔን
ይቀበላል። እኔን የሚቀበል ከሆነ ደግሞ የላከኝን ይቀበላል። ስለሆነም፣ በመካከላችሁ ከሁላችሁም የሚያንስ እርሱ ታላቅ ነውና።" 49 ዮሐንስ መልሶ እንዲህ
አለ፤ “ጌታ ሆይ፣ አንድ ሰው በስምህ አጋንንት ሲያወጣ አየነው፣ ከእኛ ጋር ስላልሆነ ከለከልነው።" 50 ኢየሱስ ግን፣ “አትከልክሉት፣ ምክንያቱም
የማይቃወማችሁ ከእናንተ ጋር ነው” አላቸው። 51 ወደ ሰማይ የሚሄድበት ጊዜ እየተቃረበ ሲመጣ፣ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ቈርጦ ተነሣ። 52 ከእርሱ ቀደም
ብለው እንዲሄዱ መልእክተኞች ላከ፤ እነርሱም ሊያዘጋጁለት ዘንድ ወደ ሳምራውያን መንደር ገቡ። 53 ነገር ግን ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ፊቱን አንቅቶ ስለ
ነበር፣ በዚያ የነበሩት ሕዝብ አልተቀበሉትም። 54 ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ ያዕቆብና ዮሐንስ ይህን ባዩ ጊዜ፣ “ጌታ ሆይ፣ እሳት ከሰማይ ወርዶ እንዲያጠፋቸው
እንድናዝ ትወዳለህን?” አሉት። 55 እርሱ ግን ዘወር ብሎ ገሰጻቸው። 56 ከዚያም ወደ ሌላ መንደር ሄዱ። 57 እየሄዱ ሳሉም አንድ ሰው፣ “ወደምትሄድበት ሁሉ
እከተልሃለሁ” አለው። 58 ኢየሱስ፣ “ቀበሮዎች ጕድጓድ አላቸው፣ የሰማይ ወፎችም ጎጆ አላቸው፤ የሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት መጠለያ የለውም”
አለው። 59 ከዚያም ለሌላውን ሰው፣ “ተከተለኝ” አለው። ሰውዬው ግን፣ “ጌታ ሆይ፣ በቅድሚያ እንድሄድና አባቴን እንድቀብር ፍቀድልኝ” አለው። 60 እርሱ
ግን፣ ሙታናቸውን እንዲቀብሩ ሙታንን ተዋቸው፣ አንተ ግን በየስፍራው ሁሉ ሄደህ የእግዚአብሔርን መንግሥት አውጅ” አለው። 61 ሌላ ሰው ደግሞ፣ “ጌታ
ሆይ፣ እከተልሃለሁ ነገር ግን በቅድሚያ የቤተ ሰቤን አባላት እንድሰናበት ፍቀድልኝ” አለው። 62 ኢየሱስ ግን፣ “ዕርፍ በእጁ ይዞ ወደ ኋላ የሚመለከት
ለእግዚአብሔር መንግሥት የተገባ አይደለም” አለው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Luke 9:1

አያያዥ መግለጫ፡
ኃይል እንዲሰጣቸው በገንዘብና ባላቸው ነገር እንዳይታመኑ ኢየሱስ ያስታውሳቸዋል፣ ከዚያም ወደ ተለያየ ስፍራ ይልካቸዋል።

ኃይልና ሥልጣን
እነዚህ ሁለት ቃላት በአንድ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት፣ አሥራ ሁለቱ ሰዎች ለመፈወስ ችሎታና መብት እንደነበራቸው ለማሳየት ነው። ይህንን ሐረግ እነዚህን ሁለቱንም አሳቦች በሚይዙ ውሁድ ቃላት ተርጉማቸው።

አጋንንትን ሁሉ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “እያንዳንዱን አጋንንት” 2) “ሁሉንም ዓይነት አጋንንት” የሚሉት ናቸው።

በሽታ
ሕመም

ላካቸው
“ወደተለያየ ስፍራ ላካቸው” ወይም “እንዲሄዱ ነገራቸው”

Luke 9:3

እንዲህ አላቸው
“ኢየሱስ ለአሥራ ሁለቱ እንዲህ አላቸው”። ይህ የሆነው ከመሄዳቸው በፊት መሆኑን መናገር ሊጠቅም ይችላል። አ.ት፡ “ከመሄዳቸው በፊት ኢየሱስ እንዲህ አላቸው”

ምንም ነገር አትውሰዱ
“ምንም ነገር ይዛችሁ አትሂዱ” ወይም “ምንም ነገር አታምጡ”

ለጉዞአችሁ
“ለመንገዳችሁ” ወይም “በምትጓዙበት ጊዜ”። ወደ ኢየሱስ እስኪመለሱ ድረስ ከመንደር ወደ መንደር በሚዘዋወሩበት ጊዜ ለጉዞአቸው ምንም ነገር መውሰድ አይኖርባቸውም።

በትር
ሰዎች ተራራ ሲወጡ ወይም ጎርበጥባጣ መንገድ ላይ ሲሄዱ ሚዛናቸውን ለመጠበቅ እንዲሁም አጥቂዎችን ለመከላከል የሚጠቀሙበት ረዘም ያለ ዘንግ ነው።

ሻንጣ
መንገደኛ ለጉዞው የሚፈልጋቸውን ነገሮች ለመያዣነት የሚጠቀምበት ቦርሳ

እንጀራ
እዚህ ጋ፣ ይህ ጥቅም ላይ የዋለው በጥቅሉ “ምግብ”ን ለማመልከት ነው።

ወደ የትኛውም ወደምትገቡበት ቤት
“ወደምትገቡበት ወደ ማናቸውም ቤት”

በዚያ ቆዩ
“በዚያ ሰንብቱ” ወይም “በዚያ ቤት ውስጥ ለጊዜው በአንግድነት ኑሩ”

ከዚያ እስክትሄዱ ድረስ
“ያንን ከተማ ለቃችሁ እስክትሄዱ ድረስ” ወይም “ያንን ስፍራ እስክትለቁ ድረስ”

Luke 9:5

ከማይቀበሏችሁ ከየትኛውም ስፍራ በምትለቁበት ጊዜ
“ሰዎች በማይቀበሏችሁ በየትኛውም ከተማ ማድረግ የሚኖርባችሁ ይህንን ነው፡ በምትለቁበት ጊዜ”

በእነርሱ ላይ ምስክር እንዲሆንባቸው የእግሮቻችሁን አቧራ አራግፉ
“የእግሮቻችሁን አቧራ አራግፉ” በዚያ ባህል ውስጥ ተቀባይነት የማጣት ብርቱ መግለጫ ነው። የዚያ ከተማ አቧራ እንኳን በእነርሱ ላይ እንዲቆይ እንደማይፈልጉ ማሳያ ነው። (See: Symbolic Action)

ወጥተው ሄዱ
“ኢየሱስ የነበረበትን ስፍራ ትተው ሄዱ”

በየስፍራው እየፈወሳችሁ
“በሚሄዱበት ሁሉ እየፈወሱ”

Luke 9:7

አጠቃላይ መረጃ፡
እነዚህ ቁጥሮች ስለ ሔሮድስ መረጃ ለመስጠት ጣልቃ ይገባሉ።

በዚህ ጊዜ ሔሮድስ
ይህ ሐረግ በዋናው የታሪክ መስመር ላይ ቆም እንዲባል ምልክት ይሰጣል። እዚህ ጋ ሉቃስ ስለ ሔሮድስ ዳራዊ መረጃ ይናገራል። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

የአራተኛው ክፍል ገዢ
ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን አንድ አራተኛ ይገዛ የነበረውን ሔሮድስ አንቲጳስን ነው።

ግራ ተጋባ
ተደናገረ፣ መረዳት አቃተው

በአንዳንዶች ተነግሮ ነበር
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አንዳንድ ሰዎች ተናግረዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ሌሎች ደግሞ ከጥንት ነቢያቶች አንዱ ተነሥቷል
“ተናግረዋል” የሚለውን ቃል ቀደም ብሎ ካለው ሐረግ መገንዘብ ይቻላል። አ.ት፡ “ሌሎች ደግሞ ከጥንት ነቢያቶች አንዱ ተነሥቷል አሉ”

የዮሐንስን ራስ ቆረጥሁት። ይህ ማነው?
ዮሐንስ ከሙታን ሊነሣ አይችልም ብሎ ገምቷል። ይህ በግልጽ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ራሱን ስለቆረጥኩት ዮሐንስ ሊሆን አይችልም። ስለዚህ፣ ይህ ሰው ማነው?”

የዮሐንስን ራስ ቆረጥሁት
x

Luke 9:10

አያያዥ መግለጫ፡
ደቀ መዛሙርት ወደ ኢየሱስ ቢመለሱና የጋራ ጊዜ ለማሳለፍ ወደ ቤተሳይዳ ቢሄዱም እንኳን ሕዝቡ ለመፈወስና ትምህርቱን ለመስማት ኢየሱስን ይከተላል። ወደ ቤታቸው በመመለስ ላይ እያሉ ኢየሱስ እንጀራና ዓሣ ሊያቀርብላቸው ተአምራት ያደርጋል።

ሐዋርያት ተመለሱ
“ሐዋርያት ኢየሱስ ወደነበረበት ተመልሰው መጡ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ያደረጉትን ሁሉ
ይህ የሚያመለክተው ወደ ሌሎች ከተሞች በሄዱ ጊዜ የሰጡትን ትምህርትና ፈውስ ነው።

ቤተሳይዳ
ይህ የአንድ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Luke 9:12

ቀኑ ሊመሽ ሲል
“ቀኑ ሊያልቅ ሲል” ወይም “በቀኑ ማለቂያ አቅራቢያ”

አምስት እንጀራ
እንጀራ፣ በተቦካ ዱቄት ቅርጽ ወጥቶለት የሚጋገር ነው።

ሁለት ዓሣ - ለዚህ ሁሉ ሕዝብ ሄደን ምግብ ካልገዛን በስተቀር
በአንተ ቋንቋ “በስተቀር”ን ለመረዳት አስቸጋሪ የሚሆን ከሆነ አዲስ ዐረፍተ ነገር ማድረግ ትችላለህ። “ሁለት ዓሣ። ይህን ሁሉ ሕዝብ ለመመገብ ሄደን ምግብ መግዛት ይኖርብናል”

አምስት ሺ ያህል ወንዶች
“5000 ያህል ወንዶች” ይህ ቁጥር በዚያ ሊገኙ የሚችሉትን ሴቶችና ሕፃናት አያካትትም። (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

አስቀምጧቸው
“እንዲቀመጡ ንገሯቸው”

ለእያንዳንዱ ሃምሳ
“ለእያንዳንዱ 50” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

Luke 9:15

እነርሱም ይህንኑ አደረጉ
“ይህንኑ” የሚያመለክተው በሉቃስ 9:4 ኢየሱስ እንዲያደርጉት የነገራቸውን ነው። ሕዝቡ ሃምሳ ሃምሳ ሆነው በቡድን እንዲቀመጡ ነገሯቸው።

አምስቱን እንጀራ ይዞ
“ኢየሱስ አምስቱን እንጀራ ይዞ”

ወደ ሰማይ
ይህ የሚያመለክተው ወደ ላይ፣ ወደ ጠፈር መመልከቱን ነው። አይሁድ ሰማይ ከጠፈር በላይ እንደሆነ ያምኑ ነበር።

Luke 9:18

አያያዥ መግለጫ፡
ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ብቻ በአጠገቡ ሆነው እየጸለየ ነው፣ ኢየሱስ ማን እንደሆነ መነጋገር ይጀምራሉ። ኢየሱስ በቅርቡ እንደሚሞትና እንደሚነሣ ይነግራቸዋል፣ ሊያደርጉት በጣም ከባድ ቢሆንም እንኳን እንዲከተሉት አጥብቆ ያሳስባቸዋል።

ከዚህ በኋላ
ይህ ሐረግ እዚህ ጋ ጥቅም ላይ የዋለው የአዲስ ሁነት ጅማሬን ለማመልከት ነው። (አዲስ ሁነትን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)

በግሉ ሲጸልይ
“ብቻውን ሲጸልይ”። ደቀ መዛሙርቱ ከኢየሱስ ጋር ነበሩ፣ ነገር ግን እርሱ በግሉና ለብቻው ይጸልይ ነበር።

አጥማቂው የሐንስ
እዚህ ጋ የጥያቄውን አካል እንደገና መናገር ሊጠቅም ይችላል። አ.ት፡ “አንዳንዶች አጥማቂው የሐንስ ነህ ይላሉ”

ጥንት ከነበሩት ነቢያት አንዱ ተነሥቷል
ይህ ምላሽ ከኢየሱስ ጥያቄ ጋር እንዴት እንደሚገናኝ ማብራራት ሊጠቅም ይችላል። አ.ት፡ “ጥንት ከነበሩት ነቢያት አንዱ ሆነህ ተነሥተሃል”

ተነሥቷል
“ወደ ሕይወት ተመልሷል”

Luke 9:20

ከዚያም እርሱ እንዲህ አላቸው
“ከዚያም ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አላቸው”

ለአንድም ሰው እንዳትናገሩ አላቸው
“ለማንም እንዳይናገሩ” ወይም “ለማንም መናገር እንደሌለባቸው”። ይህ እንደ ቀጥተኛ ትዕምርተ ጥቅስ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ለማንም አትንገሩ” አላቸው። (ግልጽ የሆነና ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ተመልከት)

የሰው ልጅ ብዙ መከራ መቀበል አለበት
“ሰዎች የሰውን ልጅ ታላቅ መከራ እንዲቀበል ያደርጉታል”

የሰው ልጅ ... እርሱ ይነሣል
ኢየሱስ ወደ ራሱ እያመለከተ ነው። አ.ት፡ “የሰው ልጅ የሆንኩ እኔ ... እኔ እነሣለሁ” (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

በሽማግሌዎች፣ በካህናት አለቆችና በጸሐፊዎች ይጣላል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሽማግሌዎቹ፣ የካህናት አለቆችና ጸሐፊዎች ይጥሉታል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ይገደላል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ይገድሉታል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በሦስተኛው ቀን
“ከሞተ ከሦስት ቀን በኋላ” ወይም “በሞተ በሦስተኛው ቀን”

ይነሣል
“እንደገና በሕይወት እንዲኖር ይደረጋል”። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር እንደገና በሕይወት እንዲኖር ያደርገዋል” ወይም “እንደገና በሕይወት ይኖራል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Luke 9:26

ቃሎቼ
x

Luke 9:28

አያያዥ መግለጫ፡
አንዳንዶቻቸው የእግዚአብሔርን መንግሥት ከማየታቸው በፊት እንደማይሞቱ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ከነገራቸው ከስምንት ቀን በኋላ ኢየሱስ ከጴጥሮስ፣ ያዕቆብና ዮሐንስ ጋር ለመጸለይ ወደ ተራራ ይወጣል፣ ኢየሱስ ወደ አንጸባራቂ መልክ በሚለወጥበት ጊዜ ሁሉም አንቀላፍተዋል።

እነዚህ ቃላት
ይህ የሚያመለክተው በሚቀጥሉት ቁጥሮች ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቶቹ የሚነግራቸውን ነው።

Luke 9:30

እነሆ
እዚህ ጋ፣ “እነሆ” የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚነገረው አስገራሚ መረጃ ትኩረት እንድንሰጥ ያነቃናል። አ.ት፡ “በድንገት”

በደማቅ ክብር ተገልጠው
ይህ ሐረግ ሙሴና ኤልያስ ምን ይመስሉ እንደነበሩ መረጃ ይሰጣል። አንዳንድ ቋንቋዎች እንደ ተናጠል አንቀጽ ሊተረጉሙት ይችላሉ። አ.ት፡ “በደማቅ ክብር ተገለጡ” ወይም “እጅግ ያንጸባርቁ ነበር”

ስለ እርሱ መሄድ
“ስለ እርሱ መለየት” ወይም “ኢየሱስ ይህንን ዓለም እንዴት እንደሚተው”። ይህ ስለ ሞቱ በትህትና የተነገረበት መንገድ ነበር። አ.ት፡ “ስለ ሞቱ”

Luke 9:32

በዚህ ጊዜ
እዚህ ጋ፣ ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው በዋናው የታሪክ መስመር ላይ የተደረገውን ቆምታ ለማመልከት ነው። እዚህ ጋ ሉቃስ ስለ ጴጥሮስ፣ ያዕቆብና ዮሐንስ መረጃ ይሰጣል። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

በእንቅልፍ ከብዶ
የዚህ የአነጋገር ዘይቤ ትርጉም “በጣም አንቀላፍተው” የሚል ነው።

ክብሩን አዩ
ይህ የሚያመለክተው የከበባቸውን አንጸባራቂ ብርሃን ነው። አ.ት፡ “አንጸባራቂ ብርሃን ከኢየሱስ ሲመጣ አዩ” ወይም “በጣም ብሩኅ የሆነ ብርሃን ከኢየሱስ ወጥቶ ሲመጣ አዩ”

ከእርሱ ጋር ቆመው የነበሩት ሁለቱ ሰዎች
ይህ ሙሴንና ኤልያስን ያመለክታል።

በመሄድ ላይ እያሉ
“ሙሴና ኤልያስ በመሄድ ላይ እያሉ”

መጠለያዎች
የሚቀመጡበት ወይም የሚተኙበት ቀለል ያለ፣ ጊዜያዊ ስፍራ

Luke 9:34

እርሱ ይህንን እየተናገረ እያለ
“እነዚህን ነገሮች ጴጥሮስ በመናገር ላይ እያለ”

ፈርተው ነበር
እነዚህ ጎልማሳ ደቀ መዛሙርት የፈሩት ደመናውን አልነበረም። ይህ ሐረግ የሚጠቁመው ከደመናው ጋር አንድ ያልተለመደ ዓይነት ፍርሃት እንደመጣባቸው ነው። አ.ት፡ “ደንግጠው ነበር”

ወደ ደመናው ውስጥ ገቡ
ደመናው ያደረገው ነገር ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ደመናው ከበባቸው”

ከደመናው ውስጥ ድምፅ መጣ
ድምፁ የእግዚአብሔር ብቻ እንደሚሆን ግልጽ ነው። አ.ት፡ “ከደመናው ውስጥ እግዚአብሔር ተናገራቸው”

ልጅ
ይህ ለእግዚአብሔር ልጅ፣ ለኢየሱስ አስፈላጊ የሆነ ማዕረግ ነው። (አባትና ልጅን መተርጎም የሚለውን ተመልከት)

የተመረጠው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እኔ የመረጥኩት” ወይም “እኔ መርጬዋለሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ያዩትን ... ዝም አሉ
ይህ ከሁነቱ የተነሣ በራሱ በታሪኩ ውስጥ ከታሪኩ በኋላ ስለሆነው ነገር የሚናገር መረጃ ነው (የታሪኩ መጨረሻ የሚለውን ተመልከት)።

ዝም አሉ ... ለማንም አልተናገሩም
የመጀመሪያው ሐረግ ወዲያው የሰጡትን ምላሻቸውን ሲያመለክት ሁለተኛው በቀጣዮቹ ቀናት ያደረጉትን ያመለክታል።

Luke 9:37

አያያዥ መግለጫ፡
ከኢየሱስ አንጸባራቂ መገለጥ በኋላ በቀጣዩ ቀን ደቀ መዛሙርት ሊፈውሱት ያልቻሉትን በአጋንን ተይዞ የነበረውን ልጅ ይፈውሰዋል።

እነሆ፣ ከሕዝቡ መካከል አንድ ሰው
“እነሆ” የሚለው ቃል በታሪኩ ውስጥ ለተነገረው አዲስ ሰው ያነቃናል። የአንተ ቋንቋ ይህንን መግለጽ የሚያስችል መንገድ ይኖረው ይሆናል። እንግሊዝኛው “በሕዝቡ መካከል አንድ ሰው ነበረ” የሚለውን ይጠቀማል። (አዲስና ነባር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)

አየኸው፣ መንፈስ
“አየኸው” የሚለው ቃል በሰውዬው ታሪክ ውስጥ ክፉዉን መንፈስ ያስተዋውቀናል። የአንተ ቋንቋ ይህንን መግለጽ የሚያስችል መንገድ ይኖረው ይሆናል። አ.ት፡ “ክፉ መንፈስ አለ” (አዲስና ነባር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)

አረፋ ይደፍቃል
x

Luke 9:41

ኢየሱስ መልሶ እንዲህ አለ
“ኢየሱስ እንዲህ በማለት መለሰለት”

እናንተ እምነት የለሾችና ብልሹ ትውልድ
ኢየሱስ ይህንን የተናገረው ለደቀ መዛሙርቱ ሳይሆን ተሰብስቦ ለነበረው ሕዝብ ነው።

ብልሹ ትውልድ
“ምግባረ ብልሹ ትውልድ”

ከእናንተ ጋር የምሆነውና የምታገሳችሁ እስከ መቼ ነው?
እዚህ ጋ በእንግሊዝኛ “ዩ” የተባለው ብዙ ቁጥር ነው። ሰዎች ባለማመናቸው ኢየሱስ ሐዘኑን ለመግለጽ እነዚህን ጥያቄዎች ይጠይቃል። እንደ መግለጫ ሊጻፉ ይችላሉ። አ.ት፡ “ለረጅም ጊዜ ከእናንተ ጋር ነበርኩ፣ እናንተ ግን አታምኑም። እስከ መቼ ልታገሳችሁ ያስፈልገኝ እንደሆነ እደነቃለሁ” (Forms of You እና ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ልጅህን ወደዚህ አምጣው
እዚህ ጋ የእንግሊዝኛው “የአንተን” የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር ነው። ኢየሱስ እየተናገረ ያለው በቀጥታ አስታውቆት ለነበረው ለአባትየው ነው።

Luke 9:43

ሁሉም በእግዚአብሔር ታላቅነት ተገረሙ
ኢየሱስ ተአምራትን አደረገ፣ ሆኖም ከፈውሱ ጀርባ የነበረው ኃይል እግዚአብሔር እንደሆነ ሕዝቡ ተገንዝቧል።

ሲያደርግ የነበረው ነገር ሁሉ
“ኢየሱስ ሲያደርግ የነበረው ነገር ሁሉ”

እነዚህ ቃላት በጆሮአችሁ ጠልቀው ይግቡ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ትኩረት መስጠት አለባቸው ማለት ነው። አ.ት፡ “በጥንቃቄ ስሙ፣ አስታውሱም” ወይም “ይህንን አትርሱ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የሰው ልጅ በሰዎች እጅ ተክዶ ይሰጣል
ይህ ከአድራጊ አንቀጽ ጋር ሊነገር ይችላል። እዚህ ጋ “እጅ” የሚያመለክተው ኃይልን ወይም መቆጣጠርን ነው። አ.ት፡ “የሰውን ልጅ ይክዱታል፣ በሰዎች ቁጥጥር ስር እንዲሆንም ያደርጉታል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የሰው ልጅ በሰዎች እጅ ተክዶ ይሰጣል
ኢየሱስ በሦስተኛ መደብ የሚናገረው ስለ ራሱ ነው። “እጅ” የሚለው ቃል እጅ ያላቸውን ሰዎች ወይም በፈሊጣዊ አነጋገር እነዚያን እጆች የሚጠቀመውን ኃይል ገላጭ ነው። እነዚህ ሰዎች ማን እንደሆኑ ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። አ.ት፡ “የሰው ልጅ የሆንኩ እኔ በሰዎች እጅ እካዳለሁ” ወይም “የሰው ልጅ ተክዶ ለጠላቶቹ ኃይል ይሰጣል” ወይም “የሰው ልጅ የሆንኩ እኔ ተክጄ ለጠላቶቼ ታልፌ እሰጣለሁ”

ከእነርሱ ተሰውሮ ነበር
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ትርጉሙን ከእነርሱ ሰወረው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Luke 9:46

አጠቃላይ መረጃ፡
ደቀ መዛሙርት ከመካከላቸው ማን እጅግ ታላቅ እንደሚሆን መከራከር ይጀምራሉ።

በመካከላቸው
“በደቀ መዛሙርት መካከል”

በልባቸው የሚያስቡትን አውቆ
እዚህ ጋ “ልባቸው” አዕምሮአቸውን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “በአዕምሮአቸው የሚያስቡትን አውቆ” ወይም “ሲያስቡት የነበረውን አውቆ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በስሜ
ይህ የሚያመለክተው ኢየሱስን ወክሎ አንድ ነገር የሚያደርገውን ሰው ነው። አ.ት፡ “በእኔ ምክንያት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በስሜ፣ የሚቀበለኝ
ይህ ዘይቤአዊ አነጋገርም እንደ ንጽጽር ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በስሜ፣ እኔን የሚቀበለኝ ያህል ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የላከኝ እርሱ
“የላከኝ እግዚአብሔር”

ታላቅ የሆነ እርሱ
“እግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ አድርጎ የሚቆጥረው እርሱ”

Luke 9:49

ዮሐንስ መለሰ
“ዮሐንስ እንዲህ ሲል መለሰ” ወይም “ዮሐንስ ለኢየሱስ መለሰለት”። ኢየሱስ የሁሉ ታላቅ ስለ መሆን ለተናገረው ለዮሐንስ ምላሽ እየሰጠ ነበር። እርሱ የሰጠው ለጥያቄ መልስ አይደለም።

አይተናል
ኢየሱስ ሳይሆን ዮሐንስ ስለ ራሱ ይናገራል፣ ስለዚህ እዚህ ጋ “እኛ” አግላይ ነው። (አግላይና አካታች “እኛ” የሚለውን ተመልከት)

በስምህ
ይህ ማለት ሰውዬው በኢየሱስ ኃይልና ሥልጣን ሲናገር ነበር። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አታስቁሙት
ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እንዲቀጥል ፍቀዱለት”

የማይቃወማችሁ ሁሉ የእናንተ ወገን ነው
አንዳንድ የዘመናችን ቋንቋዎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው አባባሎች አሏቸው። አ.ት፡ “እንድ ሰው እናንተን ከመሥራት ካላገዳችሁ እየረዳችሁ እንዳለ ያህል ነው” ወይም “አንድ ሰው እናንተን በመቃወም ካልሠራ ከእናንተ ጋር እየሠራ ነው”

Luke 9:51

አጠቃላይ መረጃ፡
በዚህ ጊዜ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ መወሰኑ ግልጽ ሆነ።

የሚያርግበት ቀን በቀረበ ጊዜ
“የሚያርግበት ሰዓት በመጣ ጊዜ” ወይም “የሚያርግበት ሰዓት በደረሰ ጊዜ”

ፊቱን አቀና
የዚህ የአነጋገር ዘይቤ ትርጉም “ቁርጥ ውሳኔ አደረገ” የሚል ነው። አ.ት፡ “አዕምሮውን አሠራው” ወይም “ወሰነ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ሁሉንም ነገር እንዲያዘጋጁለት
ይህ ማለት እርሱ ወደዚያ እንዲደርስ የመናገሪያ ስፍራን፣ ማደሪያ ቦታንና ምግብን ጨምሮ ዝግጅት ማድረግን ያካትታል።

አልተቀበሉትም
“በዚያ እንዲቆይ አልፈለጉም”

ፊቱን በኢየሩሳሌም አቅጣጫ አቅንቶ ስለነበረ
ሳምራውያንና አይሁድ እርስ በእርሳቸው ይጠላሉ ነበር። በመሆኑም ኢየሱስ ወደ አይሁድ ዋና ከተማ ወደ ኢየሩሳሌም በሚያደርገው ጉዞ ሳምራውያን አልረዱትም።

Luke 9:54

ይህንን አዩ
“ሳምራውያን ኢየሱስን እንዳልተቀበሉት አዩ”

እሳት ከሰማይ ወርዶ እንዲያጠፋቸው እዘዝ
እንደ ኤልያስ ያሉ ነቢያት እግዚአብሔርን በሚቃወሙ ሰዎች ላይ የፈረዱት እንደዚህ እንደነበር ስለሚያውቁ ያዕቆብና ዮሐንስ ይህንን የፍርድ አማራጭ አቀረቡ።

ዘወር አለና ገሰጻቸው
“ኢየሱስ ዘወር አለና ያዕቆብንና ዮሐንስን ገሰጻቸው”። ደቀ መዛሙርት እንደ ጠበቁት ኢየሱስ በሳምራውያን ላይ አልፈረደባቸውም።

Luke 9:59

አያያዥ መግለጫ፡
ኢየሱስ ከሰዎች ጋር መንገድ እየሄደ መናገሩን ቀጥሏል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ተከተለኝ
ኢየሱስ ይህንን በማለት ሰውዬው የእርሱ ደቀ መዝሙር እንዲሆንና ከእርሱ ጋር እንዲሄድ እየጠየቀው ነው።

መጀመሪያ ሄጄ አባቴን እንድቀብረው ፍቀድልኝ
የሰውዬው አባት ስለ ሞተ ወዲያው ሊቀብር ወይስ አባቱ እስኪሞት ለረጅም ጊዜ ቆይቶ ከዚያ በኋላ ሊቀብረው እንዲችል ፈልጎ ይሆን ግልጽ አይደለም። ዋናው ነጥብ ሰውየው ኢየሱስን ከመከተሉ በፊት አስቀድሞ አንድ ነገር ማድረግ ይፈልጋል።

በመጀመሪያ እንድሄድ ፍቀድልኝ
“ያንን ከማድረጌ በፊት እንድሄድ ፍቀድልኝ”

ሙታን የራሳቸውን ሙታን እንዲቀብሩ ተዋቸው
ኢየሱስ በቀጥታ የሞቱ ሰዎች ሌሎች የሞቱ ሰዎችን ይቀብራሉ ማለቱ አይደለም። ሊሆኑ የሚችሉ “የሙታን” ትርጉሞች፣ 1) በቅርቡ የሚሞቱትን የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው፣ ወይም 2) ኢየሱስን የማይከተሉትንና በመንፈስ የሞቱትን የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው የሚሉት ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሙታን
ይህ በጥቅሉ የሞቱትን ሰዎች ያመለክታል። አ.ት፡ “የሞቱ ሰዎች” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

Luke 9:61

እከተልሃለሁ
“ደቀ መዝሙር እሆናለሁ” ወይም “አንተን ለመከተል ዝግጁ ነኝ”

በመጀመሪያ በቤቴ ያሉትን እንድሰናበታቸው ፍቀድልኝ
“ያንን ከማድረጌ በፊት በቤቴ ላሉት ሰዎቼ ልሄድ መሆኔን እንድነግራቸው ፍቀድልኝ”

ማንም ... ለእግዚአብሔር መንግሥት ብቁ
ኢየሱስ የእርሱ ደቀ መዝሙር ስለ መሆን ለሰውዬው ለማስተማር በምሳሌ ይመልስለታል። ኢየሱስን ከመከተል ይልቅ ትኩረቱን ከእርሱ በፊት በነበሩ ሰዎች ላይ የሚያደርግ ሰው ለእግዚአብሔር መንግሥት ተስማሚ አይደለም ማለቱ ነው።

ማንም እጁን በማረሻ ላይ የሚያደርግ
እዚህ ጋ፣ “እጁን በ - የሚያደርግ” የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ሰውዬው አንድ ነገር ለማድረግ ይጀምራል ማለት ነው። አ.ት፡ “ማንም እርሻውን ለማረስ ጀምሮ” (የአነጋገር ዘይቤ እና የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)

ወደ ኋላው የሚመለከት
ማንም እያረሰ ወደ ኋላው የሚመለከት ማረሻውን መሄድ በሚገባው አቅጣጫ መምራት አይችልም። ያ ሰው በአግባቡ ለማረስ ወደ ፊት መመልከቱ ላይ ማተኮር አለበት።

ለእግዚአብሔር መንግሥት ብቁ
“ለእግዚአብሔር መንግሥት ጠቃሚ” ወይም “ለእግዚአብሔር መንግሥት ተስማሚ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **10**

1 ከዚህ በኋላ ጌታ፣ ሌሎች ሰባ ሰዎችን ሾመ፤ እርሱ ራሱ ሊሄድባቸው ወዳሰባቸው ከተማዎችና ስፍራዎች ሁሉ ቀድመውት እንዲሄዱ ሁለት ሁለት አድርጎ
ላካቸው፤ **2** እንዲህም አላቸው፣ "መከሩ ብዙ ነው፣ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው። ስለዚህ ወደ መከሩ ሠራተኞችን እንዲክ የመከሩን ጌታ በአስቸኳይ
ለምኑት። **3** እንግዲህ ሂዱ፣ እነሆ፣ በተኩላዎች መካከል እንደ በጎች እልካችኋለሁ። **4** ለመንገዳችሁ ምንም አትያዙ፤ የገንዘብ ቦርሳም ቢሆን የመንገደኛ
ሻንጣም ቢሆን፣ ጫማም ቢሆን አትያዙ፣ በመንገድም ላይ ለማንም ሰላምታ አትስጡ። **5** ወደ ማንኛውም ሰው ቤት ስትገቡ፣ በቅድሚያ 'ሰላም ለዚህ ቤት
ይሁን' በሉ። **6** በዚያ ቤት ያለው ሰው የሰላም ሰው ከሆነ ሰላማችሁ ያርፍበታል፣ የሰላም ሰው ካልሆነ ደግሞ ሰላማችሁ ይመለስላችኋል። **7** ያቀረቡላችሁን
እየበላችሁና እየጠጣችሁ በገባችሁበት በዚያው ቤት ቆዩ፣ ምክንያቱም ሠራተኛ ደመወዙን ማግኘት ይገባዋል። ከቤት ወደ ቤት ግን አትዘዋወሩ። **8** ወደ
ማንኛውም ከተማ ስትገቡና እነርሱም ሲቀበሏችሁ፣ ያቀረቡላችሁን ብሉ። **9** በዚያም ያሉትን ሕመምተኞች ፈውሱ፣ 'የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ
ቀርባለች' ብላችሁም ንገሩአቸው። **10** ነገር ግን ወደ ማንኛውም ከተማ ስትገቡ እነርሱ ባይቀበሏችሁ፣ ወደ ጐዳናዎቻቸው ውጡና፣ **11** 'በጫማችን ላይ
የተጣበቀውን የከተማችሁን አቧራ እንኳ በእናንተ ላይ ምስክር ይሆንባችሁ ዘንድ እናራግፈዋለን! የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ እንደ ቀረበ ግን ይህንን
እወቁ' በሏቸው። **12** እላችኋለሁ፣ በፍርድ ቀን ከዚያች ከተማ ይልቅ ለሰዶምና ለገሞራ ይቀልላቸዋል። **13** ወዮልሽ ኮራዚን! ወዮልሽ ቤተ ሳይዳ! በእናንተ ዘንድ
የተደረጉት ታላላቅ ታምራት በጢሮስና በሲዶና ተደርገው ቢሆን ኖሮ፣ የሐዘን ልብስ ለብሰውና ራሳቸውን አዋርደው ከረጅም ጊዜ በፊት ንስሐ በገቡ ነበር። **14**
ነገር ግን በፍርድ ወቅት ከእናንተ ይልቅ ለጢሮስና ለሲዶና ይቀልላቸዋል። **15** አንቺስ ቅፍርናሆም፣ እስከ ሰማይ ከፍ እንዳልሽ ታስቢ ይሆን? እንደዚያ አታስቢ፣
እስከ ሲዖል ድረስ ትወርጃለሽ። **16** እናንተን የሚሰማችሁ እኔን ይሰማኛል፣ እናንተንም የማይቀበል እኔን አይቀበለኝም፣ እኔን የማይቀበል ደግሞ የላከኝን
አይቀበልም። **17** ሰባዎቹም ደስ እያላቸው ተመለሱና፣ ጌታ ሆይ፣ አጋንንት እንኳ በስምህ ታዘዙልን" አሉት። **18** ኢየሱስ፣ "ሰይጣን እንደ መብረቅ ከሰማይ
ሲወድቅ አየሁ **19** እነሆ፣ እባቦችንና ጊንጦችን እንድትረግጡ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፣ በምንም ዓይነት መንገድ ምንም
አይጐዳችሁም። **20** የሆነ ሆኖ መናፍስት ስለተገዙላችሁ በዚህ ብቻ ደስ አይበላችሁ፤ ነገር ግን ስማችሁ በሰማይ ስለ ተጻፈ የላቀ ደስታ ይሰማችሁ።" **21**
በዚያን ጊዜ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ እጅግ ሐሤት አደረገና፣ "የሰማይና የምድር ጌታ፣ አባት ሆይ፣ እነዚህን ነገሮች ከጥበበኞችና ከሚያስተውሉ ሰውረህ እንደ
ሕፃናት ለሆኑት ላልተማሩት ለእነዚህ ስለ ገለጽህላቸው አመሰግንሃለሁ። አዎ፣ አባት ሆይ፣ ይህ በፊትህ ዘንድ መልካም ሆኖአልና። **22** ሁሉም ነገር ከአባቴ ዘንድ
ተሰጥቶኛል፣ ከአባትም በቀር ልጁ ማን እንደ ሆነ የሚያውቅ የለም፣ አባትም ማን እንደ ሆነ ከልጁ ወይም ልጁ ሊገልጥለት ከፈለገው ሰው በቀር ማንም
የሚያውቅ የለም።" **23** ኢየሱስ ወደ ደቀ መዛሙርቱ መለስ ብሎ፣ ለእነርሱ ብቻ፣ "እናንተ የምታዩትን የሚያዩ የተባረኩ ናቸው። **24** ብዙ ነቢያትና ነገሥታት
እናንተ ያያችሁትን ለማየት ፈልገው ሳያዩ፣ እናንተም የሰማችሁትን ሊሰሙ ፈልገው ሳይሰሙ ቀርተዋል" አለ። **25** እነሆ፣ አንድ የአይሁድ የሕግ መምህር
ሊፈትነው ፈልጎ ብድግ አለና፣ "መምህር ሆይ፣ የዘላለምን ሕይወት ለመውረስ ምን ማድረግ ይገባኛል?" በማለት ጠየቀው። **26** ኢየሱስ፣ "በሕጉ የተጻፈው
ምንድን ነው? የተረዳኸው እንዴት ነው?" አለው። **27** እርሱም፣ "ጌታ አምላክህን በሙሉ ልብህ፣ በሙሉ ነፍስህ፣ በሙሉ ኃይልህ፣ በሙሉ ዐሳብህም ውደድ፤
ባልንጀራህንም እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ" ብሎ መለሰ። **28** ኢየሱስም፣ "በትክክል መልሰሃል። ይህን አድርግ በሕይወትም ትኖራለህ" አለው። **29** መምህሩ
ግን ራሱን ሊያጸድቅ ወዶ፣ ኢየሱስን፣ "ባልንጀራዬ ማን ነው?" ብሎ ጠየቀው። **30** ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፤ "አንድ ሰው ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ
እየሄደ ሳለ ወንበዴዎች አግኝተውት ንብረቱን ዘረፉት፣ ደበደቡት፣ በሞት አፋፍ ላይ እያለም ጥለውት ሄዱ። **31** እንደ አጋጣሚ አንድ ካህን በዚያ መንገድ ሲሄድ
ሰውዬውን ተመለከተውና በሌላ በኩል አድርጎ አልፎት ሄደ። **32** በተመሳሳይ ሁኔታ አንድ ሌዋዊም ወደዚያ ስፍራ መጥቶ በሌላ በኩል አድርጎ አልፎ ሄደ። **33**
አንድ ሳምራዊ ግን እየተጓዘ ሳለ ሰውዬው ወደነበረበት መጣ። ባየውም ጊዜ በርኅራኄ ልቡ ተነካ። **34** ወደ እርሱም ጠጋ ብሎ መድኃኒት ካደረገለት በኋላ
ቍስሉን በጨርቅ አሰረለት። እርሱ ይጓዝበት በነበረበትም አህያ ላይ አስቀምጦት ወደ አንድ የእንግዶች ማረፊያ አመጣው፣ እንክብካቤም አደረገለት። **35**
በማግስቱ ሁለት ዲናር ከኪሱ አውጥቶ ለእንግዳ ማረፊያው ጎላፊ ሰጠውና፣ "ተንከባከበው፣ ከዚህ በላይ ወጪ የሚያስወጣህ ከሆነ በምመለስበት ጊዜ
ያወጣኸውን ትርፍ ወጪ እመልስልሃለሁ" አለው። **36** "ከእነዚህ ከሦስቱ በወንበዴዎች እጅ ለወደቀው ባልንጀራ የሆነለት የትኛው ይመስልሃል?" አለው። **37**
መምህሩም፣ "የራራለቱ ነው" አለ። ኢየሱስም፣ "አንተም ሂድና ይህንኑ አድርግ" አለው። **38** እየተጓዙ ሳሉም ወደ አንድ መንደር ገባ፤ ማርታ የምትባልም አንዲት
ሴት በቤትዋ ተቀበለችው" **39** እርሷም ማርያም የተባለች በኢየሱስ እግር ሥር ተቀምጣ ቃሉን የምትሰማ እኅት ነበረቻት" **40** ማርታ ግን ምግብ ለማዘጋጀት
ባደረገችው ጥረት በጣም ውጥረት በዛባት። ወደ ኢየሱስም ዘንድ መጥታ፣ "ጌታ ሆይ፣ እኔ ብቻዬን ሥራ ስሠራ፣ እኅቴ እኔን ሳትረዳኝና ስትተወኝ አንተ ዝም
ትላለህን? እንግዲያውስ እንድታግዘኝ ንገራት" አለችው። **41** ጌታ ግን፣ "ማርታ፣ ማርታ ስለ ብዙ ነገር ትጨነቂያለሽ፣ **42** የሚያስፈልገው ግን አንድ ነገር ነው።
ማርያም በጣም ትክክል የሆነውን ምርጫ መርጣለች፣ ይህም ደግሞ ከእርሷ አይወሰድባትም›› ብሎ መለሰላት።

Luke 10:1

አጠቃላይ መረጃ፡
ኢየሱስ ተጨማሪ 70 ሰዎችን በፊቱ አስቀድሞ ይልካቸዋል። እነዚያ 70ዎቹ በደስታ ይመለሳሉ፣ ኢየሱስም ለሰማይ አባቱ የምስጋናን ምላሽ ያቀርባል።

በዚህ ጊዜ
እዚህ ጋ ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው በታሪኩ ውስጥ አዲስ ሁነትን ለማመልከት ነው። (አዲስ ሁነትን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)

ሰባ
“70”። አንዳንድ ትርጉሞች “ሰባ ሁለት” ወይም “72” ይላሉ። ይህንን የሚናገር የግርጌ ማስታወሻ መጨመር ያስፈልግህ ይሆናል። (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ሁለት ሁለት አድርጎ ላካቸው
“ሁለት ሰዎችን የያዘ ቡድን አድርጎ ላካቸው” ወይም “በእያንዳንዱ ቡድን ሁለት ሰዎችን አድርጎ ላካቸው”

እንዲህ አላቸው
በእውነቱ ይህ የተነገረው ሰዎቹ ከመሄዳቸው በፊት ነው። አ.ት: “እንዲህ ብሏቸው ነበር” ወይም “ከመሄዳቸው በፊት ነገራቸው” (የሁነቶች ቅደም ተከተል የሚለውን ተመልከት)

መከሩ ብዙ ነው፣ ሠራተኞቹ ግን ጥቂቶች ናቸው
“ሰብሉ ብዙ ነው፣ የሚያስገቡት ሠራተኞች ግን በቂዎች አይደሉም”። ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት የተዘጋጁ ሰዎች ብዙዎች ናቸው፣ ሕዝቡን ለማስተማርና ለመርዳት የሚሄዱ ደቀ መዛሙርት ግን በቂዎች አይደሉም” ማለቱ ነበር። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Luke 10:3

መንገዳችሁን ሂዱ
“ወደ ከተሞቹ ሂዱ” ወይም “ወደ ሕዝቡ ሂዱ”

እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ
ተኩላዎች በጎችን ያጠቃሉ፣ ይገድላሉም። በመሆኑም የዚህ ዘይቤአዊ አነጋገር ትርጉም ኢየሱስ በሚልካቸው ደቀ መዛሙርት ላይ ጉዳት ለማድረስ የሚሞክሩ ሰዎች ይኖራሉ የሚል ነው። የሌላ የዱር አውሬ ስም ሊተካ ይችላል። አ.ት፡ “በምልካችሁ ጊዜ ተኩላዎች በጎችን እንደሚያጠቁ ሰዎች ሊጎዱአችሁ ይፈልጋሉ”

የገንዘብ መያዣ ወይም የመንገደኛ ሻንጣ ወይም ጫማ አትሸከሙ
“ቦርሳ፣ የመንገደኛ ሻንጣ፣ ወይም ጫማ ከእናንተ ጋር አትውሰዱ”

በመንገድ ላይ ለማንም ሰላምታ አትስጡ
“በመንገድ ላይ ማንንም ሰላም አትበሉ”። ኢየሱስ በፍጥነት ወደ መንደሮች እንዲሄዱና ይህንን ሥራ እንዲሠሩ አጽንዖት እየሰጠ ነበር። እርሱ ባለጌ እንዲሆኑ እየነገራቸው አልነበረም።

Luke 10:5

በዚህ ቤት ላይ ሰላም ይሁን
ይህ ሰላምታና ባርኮት ነበር። እዚህ ጋ “ቤት” የሚያመለክተው በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ነው። አ.ት፡ “በዚህ ቤተሰብ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ሰላምን ይቀበሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የሰላም ሰው
“ሰላማዊ ሰው”። ይህ ከእግዚአብሔርና ከሰዎች ጋር ሰላም እንዲኖረው የሚፈልግ ሰው ነው።

ሰላማችሁ በእርሱ ላይ ያርፍበታል
እዚህ ጋ፣ “ሰላም” የሚቆይበትን እንደሚመርጥ ሕያው ነገር ተደርጎ ተገልጿል። አ.ት፡ “የባረካችሁበት ሰላም ይኖረዋል” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

ካልሆነ
ሙሉዉን ሐረግ እንደገና መናገር ሊጠቅም ይችላል። አ.ት፡ “በዚያ የሰላም ሰው ከሌለ” ወይም “የቤቱ ባለቤት ሰላማዊ ሰው ካልሆነ”

ወደ እናንተ ይመለሳል
እዚህ ጋ፣ “ሰላም” ትቶ መሄድ እንደሚመርጥ ሕያው ነገር ተደርጎ ተገልጿል። አ.ት፡ “ያ ሰላም ይኖራችኋል” ወይም “የባረካችሁበትን ሰላም አይቀበልም” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

በዚያው ቤት ቆዩ
ኢየሱስ በዚያ በሚቆዩበት ጊዜ ሁሉ አዳራቸውን በዚያው ቤት እንዲያደርጉ እንጂ ቀኑን ሙሉ እቤት ውስጥ ቆዩ ማለቱ አልነበረም። አ.ት፡ “በዚያው ቤት ማደራችሁን ቀጥሉ”

ለሠራተኛው ደሞዙ ይገባዋልና
ይህ ኢየሱስ በሚልካቸው ሰዎች ላይ ሲተገብረው የነበረ ጥቅል መርህ ነው። ሕዝቡን እስካስተማሩና እስከ ፈወሱ ድረስ ሕዝቡ ማደሪያና ምግብ ሊያቀርቡላቸው ይገባል።

ከቤት ወደ ቤት አትዘዋወሩ
ከቤት ወደ ቤት መዘዋወር ማለት ወደ ተለያዩ ቤቶች መሄድ ማለት ነው። እርሱ ይናገር የነበረው በተለያየ ቤት ስለ ማደር መሆኑን ግልጽ ማድረግ ይቻላል። “በየምሽቱ በተለያየ ቤት አትደሩ”

Luke 10:8

ይቀበሏችኋል
“ከተቀበሏችሁ”

በፊታችሁ የቀረበውን ብሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “የትኛውንም የሚሰጧችሁን ምግብ ብሉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የታመመውን
ይህ በጥቅሉ የታመሙትን ሰዎች ያመለክታል። አ.ት፡ “የታመሙትን ሰዎች” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

Luke 10:10

ካልተቀበሏችሁ
“የከተማዪቱ ሰዎች ከተቃወሟችሁ”

በእግሮቻችን ላይ የተጣበቀውን የከተማችሁን አቧራ እንኳን በእናንተ ላይ እናራግፈዋለን
ይህ የከተማዪቱን ሰዎች እንደማይቀበሏቸው የሚያሳይ ምልክታዊ ድርጊት ነው። አ.ት፡ “ልክ እናንተ እንዳልተቀበላችሁን እኛም በጥንቃቄ አንቀበላችሁም። እግሮቻችን ላይ የሚጣበቀውን የከተማችሁን አቧራ እንኳን እንተውላችኋለን” (ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ተመልከት)

እናራግፍላችኋለን
ኢየሱስ እነዚህን ሰዎች ሁለት ሁለት አድርጎ በቡድን እስከ ላካቸው ድረስ ይህንን የሚናገሩት ሁለት ሰዎች መሆን አለባቸው። ስለዚህ ሁለትነትን ገላጭ “እኛ” የሚል ቃል ያለው ቋንቋ ሊጠቀምበት ይችላል። (አግላይ እና አካታች “እኛ” የሚለውን ተመልከት)

ይህንን ግን እወቁ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርቧል
“ይህንን ግን እወቁ” የሚለው ሐረግ ማስጠንቀቂያን ያስተዋውቃል። “እናንተ ባትቀበሉንም የእግዚአብሔር መንግሥት የመቅረቡን ሐቅ አይቀይረውም!”

የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርቧል
የነገር ስም የሆነው “መንግሥት” ከግሥ ጋር “ንግሥና” ወይም “አገዛዝ” ተብሎ መገለጽ ይችላል። ተመሳሳዩን ዐረፍተ ነገር በሉቃስ 10:8 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “በቅርቡ በሁሉም ስፍራ እግዚአብሔር እንደ ንጉሥ ይገዛል” ወይም “እግዚአብሔር በዙሪያችሁ ሁሉ በመግዛት ላይ ስለመሆኑ ማረጋገጫ አለ” የሚሉት ናቸው (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)።

እላችኋለሁ
ኢየሱስ ይህንን ይናገራቸው የነበሩት ይልካቸው ለነበሩት ለ70ዎቹ ሰዎች ነው። ይህንን ያለው አንድ በጣም አስፈላጊ የሆነ ነገር ሊነግራቸው እንዳለ ለማሳየት ነበር።

የፍርድ ቀን
ደቀ መዛሙርት ይህ የሚያመለክተው በኃጢአተኞች ስለሚፈረድበት የመጨረሻው ጊዜ መሆኑን ሳይረዱ አይቀሩም።

ከዚያች ከተማ ይልቅ ሰዶምን መታገስ ይቀላል
“እግዚአብሔር በዚያች ከተማ ላይ የሚፈርደውን ያህል በሰዶም ላይ አይፈርድም”። አ.ት፡ “እግዚአብሔር በሰዶም ሕዝብ ላይ ከሚፈርድበት በበለጠ በዚያች ከተማ ሕዝብ ላይ ይፈርዳል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Luke 10:13

ወዮልሽ ኮራዚን! ወዮልሽ ቤተሳይዳ
ኢየሱስ የኮራዚንና የቤተሳይዳ ከተማ ሰዎች በዚያ ሆነው ይሰሙት ይመስል ይናገራቸዋል፣ እነርሱ ግን በዚያ የሉም። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእናንተ የተደረጉት ታላላቅ ሥራዎች በጢሮስና በሲዶና ተደርገው ቢሆን ኖሮ
ኢየሱስ እየገለጸ ያለው ባለፈ ጊዜ ሊሆን ስለሚችል ነገር ግን ስላልሆነ ሁኔታ ነው። አ.ት፡ “እኔ ለእናንተ ያደረግሁትን ተአምራት አንድ ሰው ለጢሮስና ለሲዶና ሰዎች አድርጎ ቢሆን ኖሮ”

ከብዙ ጊዜ በፊት ተቀምጠው ንሰሐ ይገቡ ነበር
“በዚያ ይኖሩ የነበሩ ክፉዎች ሰዎች በመቀመጥ ስለ ኃጢአታቸው መጸጸታቸውን ያሳዩ ነበር”

ማቅና አመድ ላይ ተቀምጠው
“ማቅ ለብሰው፣ አመድ ላይም ተቀምጠው”

ነገር ግን ከእናንተ ይልቅ በፍርድ ጢሮስንና ሲዶናን መታገስ ይቀላል
ለምን እንደሚፈረድባቸው በግልጽ መናገር ሊጠቅም ይችላል። አ.ት፡ “ምንም እንኳን ተአምራትን ሳደርግ ብታዩም ንሰሐ ስላልገባችሁና በእኔ ስላላመናችሁ እግዚአብሔር በጢሮስና በሲዶና ሕዝብ ላይ ከሚፈርድባቸው እጅግ በሚበልጥ ሁኔታ ይፈርድባችኋል”

በፍርድ
“እግዚአብሔር በእያንዳንዱ ላይ በሚፈርድበት በመጨረሻው ቀን”

አንቺ ቅፍርናሆም
በዚህ ጊዜ ኢየሱስ ይሰሙት ይመስል በቅፍርናሆም ከተማ ለሚኖሩ ሰዎች ይናገራል፣ እነርሱ ግን አይሰሙትም። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ወደ ሰማይ ከፍ እንደምትይ ታስቢያለሽ?
ኢየሱስ ስለ ትዕቢታቸው የቅፍርናሆምን ሰዎች ለመገሰጽ ጥያቄ ይጠይቃቸዋል። አ.ት፡ “በእርግጥ ወደ ሰማይ አታርጊም!” ወይም “እግዚአብሔር አያከብርሽም!” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ አልሽ
ይህ አገላለጽ “እጅግ ከፍ አልሽ” ማለት ነው።

ወደ ሲዖል ያወርዱሻል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ወደ ሲዖል ትወርጃለሽ” ወይም “እግዚአብሔር ወደ ሲዖል ይልክሻል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Luke 10:17

ሰባዎቹ ተመልሰው
አንዳንድ ቋንቋዎች የተከፈተው ተለዋዋጭ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም እንደሚያደርገው ሰባዎቹ በእውነቱ አስቀድመው ሄደው እንደነበር መናገር ይኖርባቸዋል። ይህ ግልጽ መደረግ የሚችል የተሰወረ መረጃ ነው።

Luke 10:21

አባት
ይህ ለእግዚአብሔር አስፈላጊ የሆነ ማዕረግ ነው። (አባት እና ልጅን መተርጎም የሚለውን ተመልከት)

የሰማይና የምድር ጌታ
“ሰማይ” እና “ምድር” ያለውን ነገር ሁሉ ይወክላል። አ.ት፡ “በሰማይና በምድር ባለው ሁሉ ላይ እና ሁሉ ነገር ላይ የበላይ”

እነዚህ ነገሮች
ይህ የሚያመለክተው ስለ ደቀ መዛሙርቱ ሥልጣን ቀደም ሲል ኢየሱስ ያስተማረውን ነው። “እነዚህ ነገሮች” በማለት ብቻ አንባቢው ትርጉሙን እንዲወስን መተው በጣም የተሻለ ሊሆን ይችላል።

ጥበበኛና አስተዋይ
“ጥበበኛ” እና “አስተዋይ” የሚሉት ቃላት ስማዊ ቅጽሎች ሲሆኑ እንዲህ ያለ ስብዕና ያላቸውን ሰዎች የሚያመለክቱ ናቸው። እነዚህ ሰዎች፣ እግዚአብሔር እውነትን ስለ ሰወረባቸው እነርሱ ነን ቢሉም እንኳን በእውነቱ ጥበበኞችና አስተዋዮች አልነበሩም። አ.ት፡ “ጥበበኞችና አስተዋዮች እንደሆኑ ከሚያስቡ ሰዎች” (ቅኔ እና ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

እነዚያ እንደ ትንንሽ ልጆች ያልተማሩ
ይህ የሚያመለክተው ብዙ ባይማሩም እንኳን ትንንሽ ልጆች የሚያምኗቸውን ሰዎች በፈቃዳቸው በሚሰሟቸው መልኩ የኢየሱስን ትምህርቶች ለመቀበል ፈቃደኞች የሚሆኑትን ሰዎች ነው። አ.ት፡ “በጥቂቱ የተማሩ፣ ነገር ግን ትንንሽ ልጆች እንደሚያደርጉት እግዚአብሔርን የሚሰሙ ሰዎች”

ይህ በፊትህ ደስ የሚያሰኝህ ሆኗልና
“ይህንን ማድረግ አስደስቶሃል”

Luke 10:22

ሁሉም ነገር ከአባቴ ተሰጥቶኛል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አባቴ ሁሉንም ነገር አሳልፎ ሰጥቶኛል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

አባት ... ልጅ
እነዚህ በእግዚአብሔርና በኢየሱስ መካከል ያለውን ዝምድና የሚገልጹ አስፈላጊ ማዕረጎች ናቸው። (አባት እና ልጅን መተርጎም የሚለውን ተመልከት)

ልጅ ማን መሆኑን ያውቃል
x

Luke 10:23

ከዚያም ወደ ደቀ መዛሙርቱ ዘወር ብሎ ለብቻቸው እንዲህ አላቸው
“ለብቻቸው” የሚለው ቃል እርሱ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ብቻ እንደነበረ ያመላክታል። አ.ት፡ “ከዚያ በኋላ፣ ብቻውን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በሆነ ጊዜ፣ ወደ እነርሱ ዘወር ብሎ እንዲህ አላቸው”

እናንተ የምታዩአቸውን ነገሮች የሚያዩ እነርሱ የተባረኩ ናቸው
ይህ ምናልባት ኢየሱስ ያደርጋቸው የነበሩትን መልካም ሥራዎችና ተአምራቶች ያመለክት ይሆናል። አ.ት፡ “እኔ ሳደርግ የምታዩትን ለሚያዩ ለእነዚያ እንዴት መልካም ነ

እነርሱ አላዩአቸውም
ይህ የሚያመለክተው ኢየሱስ እነዚያን ነገሮች ገና እንዳላደረጋቸው ነው። አ.ት፡ “ሆኖም፣ ገና ስላላደረግኋቸው ሊያዩአቸው አልቻ

እናንተ የምትሰሟቸውን ነገሮች
ይህ ምናልባት የኢየሱስን ትምህርት ያመለክት ይሆናል። አ.ት፡ “እኔ ስናገር የሰማችኋቸውን ነገሮች”

እነርሱ አልሰሟቸውም
ይህ ኢየሱስ ገና እንዳላስተማረ ያመለክታል። አ.ት፡ “ሆኖም፣ ማስተማር ባለመጀመሬ ሊሰሟቸው አልቻሉም”

Luke 10:25

አያያዥ መግለጫ፡
ኢየሱስ ሊፈትነው ለሞከረው አይሁዳዊ መምህር በምሳሌ ይመልስለታል። (ምሳሌዎች የሚለውን ተመልከት)

እነሆ፣ አንድ መምህር
ይህ በታሪኩ ውስጥ ለአዲስ ሁነትና ለአዲስ ሰው ትኩረት እንድንሰጥ ያነቃናል። (አዲስ ሁነትን ማስተዋወቅ፣ አዲስና ነባር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)

ሊፈትነው
“ኢየሱስን ለመገዳደር”

በሕጉ የተጻፈው ምንድነው? እንዴትስ ታነበዋለህ?
ኢየሱስ መረጃ እየፈለገ አይደለም። እርሱ እነዚህን ጥያቄዎች ያቀረበው የአይሁዳዊ መምህሩን እውቀት ለመፈተን ነው። አ.ት፡ “ሙሴ በሕጉ ላይ ምን እንደጻፈና ትርጉሙ ምን ይሆናል ብለህ እንደምታስብ ንገረኝ” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

በሕጉ የተጻፈው ምንድነው?
ይህ በአድርጊ ድምፅ ሊጠየቅ ይችላል። አ.ት፡ “ሙሴ በሕጉ ላይ የጻፈው ምን ነበር?” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እንዴት ታነበዋለህ?
“በእርሱ ውስጥ ምን አነበብክ?” ወይም “ምን እንደሚል ተረዳህ?”

ባልንጀራህን እንደ ራስህ ... ውደደው
ሰውዬው ሙሴ በሕጉ የጻፈውን እየጠቀሰ ነው።

በሙሉ ልብህ፣ በሙሉ ነፍስህ፣ በሙሉ ኃይልህና በሙሉ አሳብህ
እዚህ ጋ፣ “ልብ” እና “ነፍስ” የአንድን ሰው ውስጣዊ ማንነት የሚያመለክቱ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ናቸው። እነዚህ አራት ሐረጎች በአንድ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት “ሙሉ በሙሉ” ወይም “በቅንነት” ለማለት ነው።

ባልንጀራህን እንደ ራስህ
ይህ ተነጻጻሪ በበለጠ ግልጽነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ራስህን የምትወደውን ያህል ባልንጀራህን ውደደው” (ተነጻጻሪ የሚለውን ተመልከት)

Luke 10:29

ሆኖም፣ መምህሩ ራሱን ለማጽደቅ በመፈለግ እንዲህ አለ
“ሆኖም መምህሩ ራሱን የሚያጸድቅበትን መንገድ ለማሰብ ፈለገ፣ ስለዚህ እንዲህ አለ” ወይም “ሆኖም፣ መምህሩ ጻድቅ ሆኖ መታየት በመፈለግ እንዲህ አለ”

Luke 10:31

በአጋጣሚ
ይህ የትኛውም ሰው ያቀደው ነገር አልነበረም።

አንድ ካህን
ይህ አገላለጽ በታሪኩ ውስጥ አንድ አዲስ ሰው ያስተዋውቃል፣ ሆኖም ማንነቱን በስም አይገልጸውም። (አዲስና ነባር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)

ባየው ጊዜ
“ካህኑ የቆሰለውን ሰው ባየው ጊዜ”። ካህን በጣም ሃይማኖተኛ ሰው ነው፣ በመሆኑም የቆሰለውን ሰው እንደሚረዳው አድማጮች ይገምታሉ። እርሱ እንደተገመተው ስላላደረገ፣ ትኩረታቸውን ወደዚህ ያልተጠበቀ ውጤት ለመሳብ ይህ ሐረግ “ነገር ግን ባየው ጊዜ” ተብሎ ሊነገር ይችላል።

በሌላኛው በኩል ተሻገረ
ሰውዬውን እንዳልረዳው ያመለክታል። አ.ት፡ “የቆሰለውን ሰው አልረዳውም፣ ነገር ግን በመንገዱ በወዲያኛው በኩል ተሻግሮ ሄደ”

ሌዋዊ ... በሌላኛው በኩል
ሌዋዊው በቤተ መቅደስ ያገለግል ነበር። ባልንጀራው የሆነውን አይሁዳዊ ሰው መርዳት ይጠበቅበት ነበር። ይህንን አላደረገምና ሁኔታው ቢነገር ሊጠቅም ይችላል። አ.ት፡ “ሌዋዊ በሌላ በኩል ... አልረዳውምም”

Luke 10:33

ነገር ግን አንድ ሳምራዊ
ይህ በታሪኩ ውስጥ ስሙን ሳይጠቅስ አንድን አዲስ ሰው ያስተዋውቃል። ከሰማርያ መሆኑን ብቻ እናውቃለን። (አዲስና ነባር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)

አንድ ሳምራዊ
አይሁዶች ሳምራውያንን ይንቋቸው ስለነበር የቆሰለውን አይሁዳዊ ሰው አይረዳውም ብለው ገምተዋል።

እርሱ ባየው ጊዜ
“ሳምራዊው የቆሰለውን ሰው ባየው ጊዜ”

ራራለት
“አዘነለት”

ዘይትና ወይን አፍስሶባቸው ቁስሎቹን አሰረለት
በመጀመሪያ ዘይቱንና ወይኑን በቁስሎቹ ላይ ማድረግ ነበረበት። አ.ት፡ “ወይንና ዘይት በቁስሎቹ ላይ ጨምሮ በጨርቅ ጠቀለላቸው” (የሁነቶች ቅደም ተከተል የሚለውን ተመልከት)

ዘይትና ወይን አፍስሶባቸው
ወይን የተጠቀመው ቁስሉን ለማጽዳት ሲሆን ዘይቱ ምናልባት ማመርቀዝን ለመከላከል ሳይሆን አይቀርም። ይህ እንደሚከተለው ሊነገር ይችላል፤ አ.ት፡ “ቁስሉ እንዲፈወስ ዘይትና ወይን በላዩ ላይ ማፍሰስ”

የራሱን እንስሳ
“የራሱ የጭነት እንስሳ”። ይህ ከባድ ጭነት እንዲሸከም የተጠቀመበት እንስሳ ነበር። ምናልባት አህያ ሳይሆን አይቀርም።

ሁለት ዲናር
“የሁለት ቀን ደሞዝ”። “ዲናር” የ”ዲናሪየስ” ብዙ ቁጥር ነው። (በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰ ገንዘብ የሚለውን ተመልከት)

አስተናጋጁ
“የሆቴሉ ጠባቂ” ወይም “የሆቴሉን ኃላፊነት የወሰደው ሰው”

የትኛውንም የምታወጣውን ተጨማሪ ወጪ ስመለስ እከፍልሃለሁ
ይህ ቅደም ተከተል እንደገና ሊስተካከል ይችላል። አ.ት፡ “በምመለስበት ጊዜ የምታወጣውን የትኛውንም ተጨማሪ ወጪ እኔ እከፍልሃለሁ”

Luke 10:38

አጠቃላይ መረጃ፡
ኢየሱስ እህቷ ማርያም እርሱን በጥሞና ወደምታዳምጥበት ወደ ማርታ ቤት ይመጣል።

Luke 10:40

በጣም ባተለች
“በጣም ሥራ በዛባት” ወይም “እጅግ ሥራ በዛባት”

ብቻዬን ... አይገድህም?
ማርያም ብዙ የሚሠራ ሥራ ባለበት ጊዜ ጌታ እርሱን እንድትሰማው በመፍቀዱ ማርታ ቅሬታ እያቀረበች ነው። እርሷ ጌታን ታከብረዋለች፣ በመሆኑም ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ በመጠቀም ቅሬታዋን በበለጠ ትህትና ታቀርባለች። (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ማርታ፣ ማርታ
ኢየሱስ አጽንዖት ለመስጠት የማርታን ስም ይደግመዋል። አ.ት፡ “የተወደድሽ ማርታ” ወይም “አንቺ ማርታ”

የሚያስፈልገው አንድ ነገር ብቻ ነው
ኢየሱስ ማርያም የምታደርገውን ማርታ ከምታደርገው ጋር እያነጻጸረ ነው። ይህንን ግልጽ ማድረግ ሊጠቅም ይችላል። አ.ት፡ “በእርግጠኝነት አስፈላጊ የሆነው ብቸኛው ነገር የእኔን ትምህርት መስማት ነው” ወይም “ምግብ ከማዘጋጀት ይልቅ የእኔን ትምህርት መስማት በይበልጥ አስፈላጊ ነው”

ከእርሷ አይወሰድባትም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “ይህንን ዕድል ከእርሷ አልወስድባትም” ወይም 2) “እኔን ስትሰማኝ የምታገኘውን አትጥለውም” የሚሉት ናቸው (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **11**

1 ኢየሱስ በአንድ ስፍራ መጸለዩን በፈጸመ ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ እንዲህ አለው፣ “ጌታ ሆይ፣ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርቱን እንዳስተማረ እኛን መጸለይ አስተምረን” አለ። **2** ኢየሱስም፣ “በምትጸልዩበት ጊዜ፣ 'በሰማይ የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ስምህ ይቀደስ መንግሥትህ ትምጣ **3** የዕለት እንጀራችን በየዕለቱ ስጠን። **4** እኛን የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን። ወደ ፈተናም አታግባን በሉ'" አላቸው። **5** ኢየሱስም፣ “ከእናንተ ወዳጅ ያለው በእኩለ ሌሊት ውድ ወዳጁ ዘንድ በመሄድ **6** ‘አንድ ወዳጄ ከሌላ ስፍራ ወደ እኔ መጥቶ የማስተናግድበት ምንም ስለሌለኝ፣ ሦስት እንጀራ አበድረኝ የማይለው ማነው’? **7** በቤት ውስጥ ያለው ወዳጁ ‘አታስቸግረኝ፤ በሩ ተዘግቶአል ልጆቼም ከእኔ ጋር በአልጋ ላይ ተኝተዋል። ለመነሣትና ለአንተ እንጀራ ለመስጠት አልችልም’ ይለዋልን? **8** ምንም እንኳን ወዳጁ ስለሆናችሁ ተነሥቶ እንጀራ ባይሰጣችሁም ያለ ዕረፍት ስለነዘነዛችሁት ብቻ ተነስቶ የምትፈልጉትን ያህል እንጀራ ይሰጣችኋል፤ **9** ለምኑ ይሰጣችኋል፣ ፈልጉ ታገኛላችሁ፣ አንኳኩ ይከፈትላችኋል፤ **10** የሚለምን ሰው ሁሉ ይቀበላልና የሚፈልግም ሰው ያገኛል፣ ለሚያንኳኳም ይከፈትለታል። **11** አባት ከሆናችሁት ከእናንተ ዓሣ ሲለምነው በዓሣ ፈንታ እባብ ወይም **12** ዕንቁላል ሲለምነው በዕንቁላሉ ፈንታ ጊንጥ የሚሰጠው ማን ነው? **13** ስለዚህ፣ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ፣ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠትን የምታውቁ ከሆነ፣ በሰማይ የሚኖረው አባታችሁማ ለሚለምኑት መንፈስ ቅዱስን እንዴት አብልጦ አይሰጣቸውም?” **14** በኋላ ኢየሱስ ጋኔን እያወጣ ነበር፤ እርሱም ድዳ ነበር። ጋኔኑም በወጣ ጊዜ ድዳው ሰውዬ ተናገረ፤ ሕዝቡም ተደነቁ። **15** ነገር ግን ከሕዝቡ አንዳንዶቹ፣ “አጋንንትን የሚያወጣው የአጋንንት አለቃ በሆነው በብዔል ዜቡል ነው” አሉ። **16** ሌሎች ሊፈትኑት ፈልገው ከሰማይ ምልክት እንዲያሳያቸው ጠየቁት። **17** ኢየሱስ ግን ዐሳባቸውን አውቆ፣ “እርስ በርሱ የሚከፋፈል መንግሥት ይፈርሳል፤ እርስ በርሱ የሚለያይ ቤተ ሰብም ይወድቃል። **18** ሰይጣን ራሱን በራሱ የሚቃረን ከሆነ መንግሥቱ እንዴት ይጸናል? እናንተ ግን እኔን አጋንንትን የሚያወጣው በብዔል ዜቡል ነው ትሉኛላችሁ። **19** እኔ በቡዔል ዜቡል አጋንንትን የማወጣ ከሆንሁ የእናንተ ተከታዮች የሚያወጧቸው በማን ነው? ከዚህም የተነሣ እነርሱ ፈራጆች ይሆኑባችኋል። **20** እኔ ግን በእግዚአብሔር ኃይል አጋንንትን የማወጣ ከሆንሁ፣ እንግዲያውስ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ መጥቷል። **21** 21 በሚገባ የታጠቀ ብርቱ ሰው ቤቱን በሚጠብቅበት ጊዜ የቤቱ ንብረት ያለ ስጋት ይሆናል፤ **22** ከእርሱ የበረታ ሰው ሲያሸንፈው ግን ያ ከእርሱ የበረታው ሰው መሣሪያውን ይቀማዋል፣ የቤቱንም ሀብት ይበዘብዛል። **23** ከእኔ ጋር ያልሆነ ይቃወመኛል፣ ከእኔ ጋርም የማይሰበስብ ይበትናል። **24** ርኩስ መንፈስ ከሰው በሚወጣበት ጊዜ ውሃ በሌለባቸው ስፍራዎች እየተዘዋወረ ማረፊያ ይፈልጋል። ምንም ማረፊያ ሲያጣ ‘ወደ ወጣሁበት ቤት እመለሳለሁ’ ይላል። **25** በሚመለስበት ጊዜ ያንን ቤት ተጠርጎና ጸድቶ ያገኘዋል። **26** ከዚያም ከእርሱ ይልቅ የከፉ ሰባት ሌሎችን ከእርሱ ጋር ይዞ ይሄድና ሁሉም በዚያ ሰው ውስጥ ገብተው ይኖራሉ። ከዚያም ያ ሰው በመጨረሻ የሚገጥመው ሁኔታ ከመጀመሪያው ይልቅ የከፋ ይሆናል። **27** ኢየሱስ እነዚህን ነገሮች በሚናገርበት ጊዜ፣ ከሕዝቡ መካከል አንዲት ሴት ድምጿን ከፍ አድርጋ፣ “አንተን የተሸከመችህ ማኅፀንና የጠባሃቸው ጡቶች የተባረኩ ናቸው” አለችው። **28** እርሱ ግን፣ “የተባረኩትስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚጠብቁት ናቸው” አለ። **29** የሕዝቡም ቍጥር እየጨመረ ሲሄድ፣ እንዲህ ማለት ጀመረ፣ “ይህ ትውልድ ክፉ ትውልድ ነው። ምልክት ይፈልጋል፤ ሆኖም ከዮናስ ምልክት በቀር ሌላ ምልክት አይሰጠውም። **30** ልክ ዮናስ ለነነዌ ሰዎች ምልክት እንደ ሆነላቸው፣ የሰው ልጅም ለዚህ ትውልድ ምልክት ይሆናልና። **31** የደቡብ ንግሥት በፍርድ ወቅት ከዚህ ትውልድ ጋር ትነሣና ትፈርድበታለች፣ ምክንያቱም የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ከምድር ዳርቻ መጥታለችና፤ እነሆም ከሰሎሞን የሚበልጥ በዚህ አለ። **32** 32 የነነዌ ሰዎች በፍርድ ቀን ከዚህ ትውልድ ጋር ይነሡና ይፈርዱበታል፣ ምክንያቱም በዮናስ ስብከት ንስሐ ገብተዋል፤ እነሆም ከዮናስ የሚበልጥ ከዚህ አለ። **33** አንድ ሰው መብራት ካበራ በኋላ ብርሃኑ በማይታይበት ሰዋራ ስፍራ አያስቀምጠውም ወይም እንቅብ በላዩ ላይ አይደፋበትም። ነገር ግን ወደዚያ ቤት የሚገቡ እንዲታያቸው ከፍ ባለ ስፍራ ላይ ያስቀምጠዋል። **34** ዓይን የሰውነት መብራት ነው። ዓይንህ ጤናማ ከሆነ፣ መላ ሰውነትህ በብርሃን የተሞላ ይሆናል። ዓይንህ ሕመምተኛ ከሆነ ግን መላ ሰውነትህ ጨለማ ይሆናል። **35** ስለዚህ በአንተ ውስጥ ያለው ብርሃን ጨለማ እንዳይሆን ተጠንቀቅ። **36** እንግዲህ መላ ሰውነትህ ምንም ጨለማ የሌለበትና በብርሃን የተሞላ ከሆነ፣ በዚያን ጊዜ በሙሉ ብርሃኑ መብራት በአንተ ላይ እንደሚያበራ ያህል ይሆናል። **37** ንግግሩንም ሲያበቃ አንድ ፈሪሳዊ በቤቱ ምግብ ይመገብ ዘንድ ጋበዘው፤ ኢየሱስም ከፈሪሳዊው ቤት ሄዶ ለማዕድ ቀረበ። **38** ኢየሱስ ወደ ማዕድ ከመቅረቡ በፊት እጁን ባለመታጠቡ ፈሪሳዊው ተደነቀ። **39** ጌታ ግን እንዲህ አለው፤ “እንግዲህ፣ እናንተ ፈሪሳውያን የጽዋውንና የወጭቱን ውጭ ታጸዳላችሁ፣ ውስጣችሁ ግን በስስትና በክፋት የተሞላ ነው። **40** እናንተ ማስተዋል የሌላችሁ ሰዎች፣ ውጪውን የፈጠረ የውስጡንስ አልፈጠረምን? **41** በውስጥ ያለውን ለድኾች ስጡ፣ ከዚያም ሁሉም ነገር ንጹሕ ይሆንላችኋል። **42** ነገር ግን እናንተ ፈሪሳውያን ወዮላችሁ! ምክንያቱም ካመረታችሁት አዝሙድና ጤና አዳም ዐሥራት እያወጣችሁ ፍትሕንና የእግዚአብሔርን ፍቅር ንቃችሁ ትተዋላችሁ። ሌላውን ነገር ማድረግ ሳትተዉ ፍትሕ ማድረግንና የእግዚአብሔርን ፍቅር መጠበቅ ያስፈልጋችኋል። **43** እናንተ ፈሪሳውያን ወዮላችሁ! በምኩራቦች የክብር መቀመጫዎችንና በገበያ ስፍራም የከበሬታ ሰላምታን ትወዳላችሁና። **44** ሰዎች የማን እንደሆኑ ሳያውቁ የሚረማመዱባቸው መቃብሮችን ትመስላላችሁና ወዮላችሁ!" **45** የአይሁድ የሕግ መምህር የነበረ አንድ ሰው፣ “መምህር ሆይ፣ በምትናገረው ነገር እኛንም እየሰደብኸን ነው” ብሎ መለሰለት። **46** ኢየሱስም እንዲህ አለ፣ “እናንተም የሕግ መምህራን፣ ለመሸከም የሚከብድ ሸክም በሰዎች ላይ ትጭናላችሁና፣ እናንተ ግን እነዚያን ሸክሞች በአንድ ጣታችሁ እንኳ አትነኳቸውምና ወዮላችሁ! **47** የገደሏቸው የእናንተ አባቶች ሆነው ሳለ እናንተ ግን የቀደሙ ነቢያትን መቃብር የምታንጹ ናችሁና ወዮላችሁ!። **48** ከዚህም የተነሣ አባቶቻችሁ በሠሩት ሥራ ምስክሮችና ከእነርሱም ጋር የምትስማሙ ናችሁና፣ ምክንያቱም እናንተ የመታሰቢያ መቃብራቸውን የምታንጹላቸው ነቢያት በእርግጥም በአባቶቻችሁ የተገደሉ ነበር። **49** በዚህ ምክንያት በእግዚአብሔር ጥበብ እንዲህ ተብሏል፣ ‘ነቢያትንና ሐዋርያትን ወደ እነርሱ እልካለሁ፣ እነርሱም አንዳንዶችን ያሳድዳሉ ይገድሉማል። **50** ስለሆነም ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ለፈሰሰው የነቢያት ሁሉ ደም ይህ ትውልድ ተጠያቂ ነው’። **51** ተጠያቂ የሚሆነውም ከአቤል ጀምሮ በመሠዊያውና በቤተ መቅደሱ መካከል እስከ ተገደለው እስከ ዘካርያስ ድረስ ለፈሰሰው የነቢያት ደም ነው። አዎን፣ ይህ ትውልድ ተጠያቂ ነው እላችኋለሁ። **52** 52 እናንተ የአይሁድ የሕግ መምህራንም የዕውቀትን ቍልፍ ጨብጣችሁ ሳላችሁ እናንተ ራሳችሁ የማትገቡ፣ ለገቡ ያሉትን እንዳይገቡ የምትከለክሉ ናችሁና ወዮላችሁ! **53** ኢየሱስ ከዚያ ለመሄድ እንደተነሣ፣ የአይሁድ የሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን ተቃወሙት፣ ብዙ ጉዳዮችን አስመልክተው ከእርሱ ጋር ተከራረኩ። **54** ይህንም ያደረጉት ራሱ በተናገረው ቃል ሊያጠምዱት ፈልገው ስለነበረ ነው።

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Luke 11:1

አጠቃላይ መረጃ፡
ይህ የቀጣዩ ታሪክ ክፍል ጅማሬ ነው። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እንዲጸልዩ ያስተምራቸዋል።

እንዲህ ሆነ
ይህ ሐረግ ጥቅም ላይ የዋለው የታሪኩን አዲስ ክፍል እንደተጀመረ ለማመልከት ነው። የአንተ ቋንቋ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ ጋ ልትጠቀምበት እንደምትችል አስብ። (አዲስ ሁነትን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)

ኢየሱስ በሚጸልይበት ጊዜ ከ ... አንዱ
ደቀ መዛሙርት ጥያቄ ከመጠየቃቸው በፊት ኢየሱስ ጸሎቱን መጨረሱን መናገር የበለጠ አግባብነት ሊኖረው ይችላል። አ.ት፡ “በአንድ ቦታ ኢየሱስ ይጸልይ ነበር። ጸሎቱን በጨረሰ ጊዜ ከ ... አንዱ

Luke 11:2

ኢየሱስ እንዲህ አላቸው
“ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አላቸው”

አባት
ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ በሚጸልዩበት ጊዜ “አባት” በማለት የእግዚአብሔር አብን ስም እንዲያከብሩ ኢየሱስ አዘዛቸው። (አባት እና ልጅን መተርጎም የሚለውን ተመልከት)

ስምህ ቅዱስ ይሁን
“ሁሉም ስምህን እንዲያከብሩት አድርግ”። “ስም” ብዙ ጊዜ የሚያመለክተው ሙሉውን ሰው ነው። አ.ት፡ “ሰዎች ሁሉ ያክብሩህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መንግሥትህ ትምጣ
እግዚአብሔር በሁሉም ላይ የመግዛቱ አሠራር እርሱ ራሱ እግዚአብሔር እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ናና በሁሉም ላይ ግዛ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Luke 11:3

አያያዥ መግለጫ፡
ኢየሱስ እንዴት መጸለይ እንዳለባቸው ለደቀ መዛሙርቱ ማስተማሩን ቀጥሏል።

ስጠን ... ይቅር በለን ... አትምራን
እነዚህ ትዕዛዛዊ አንቀጾች ናቸው፣ ሆኖም ከትዕዛዝ ይልቅ እንደ ልመና ተደርገው መተርጎም አለባቸው። ይህንን ግልጽ ለማድረግ “እባክህን” የመሳሰለ ቃል መጨመር ሊጠቅም ይችላል። አ.ት፡ “... እባክህን ስጠን፣ እባክህን ... ይቅር በለን ... እባክህን አትምራን”

የዕለት እንጀራችንን
እንጀራ ውድ ያልሆነ፣ ሰዎች በየዕለቱ የሚበሉት ምግብ ነበር። እዚህ ጋ ጥቅም ላይ የዋለው በጥቅሉ ምግብን ለማመልከት ነው። አ.ት፡ “በየዕለቱ የምንፈልገውን ምግብ”

ኃጢአታችንን ይቅር በለን
“በአንተ ላይ ኃጢአት ስለማድረጋችን ይቅር በለን” ወይም “የእኛን ኃጢአት ይቅር በል”

እኛ ይቅር እንደምንል
“እኛም ደግሞ ይቅር እንላለንና”

እኛን የበደለንን
“በእኛ ላይ ኃጢአት ያደረገውን” ወይም “የማይገባውን ነገር ያደረገብንን”

ወደ ፈተና አትምራን
ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ከፈተና አርቀን”

Luke 11:5

አያያዥ መግለጫ፡
ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ስለ ጸሎት ማስተማሩን ቀጥሏል።

በፊቱ የሚያቀርብለት ከእናንተ ... ያለው?
ኢየሱስ ደቀ መዛሙርትን ለማስተማር ጥያቄ ይጠይቃል። አ.ት፡ “አስቡ፣ ከእናንተ አንዱ ... በፊቱ ሊያቀርብለት” ወይም “እንዳላችሁ አስቡ ... በፊቱ ሊያቀርብለት” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ሦስት እንጀራ አበድረኝ
“ሦስት እንጀራ እንድበደር ፍቀድልኝ” ወይም “ሦስት እንጀራ ስጠኝና በኋላ እከፍልሃለሁ”። እንግዳ ተቀባዩ ለእንግዳው የሚያቀርብለት ምንም የተዘጋጀ ምግብ የለውም።

ሦስት እንጀራ
እንጀራ አብዛኛውን ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለው በጥቅሉ ምግብን እንዲወክል ሆኖ ነው። አ.ት፡ “የሚበላ የበሰለ በቂ ምግብ” ወይም “አንድ ሰው የሚበላው የተዘጋጀ በቂ ምግብ”

አሁን ከመንገድ መጥቷል
ጎብኚው ሩቅ ከሆነ ቤቱ መምጣቱ ታውቋል። አ.ት፡ “ሲጓዝ ውሎ አሁን ወደ ቤቴ መጥቷል”

ምንም በፊቱ የማቀርብለት
“የምሰጠው ምንም የተዘጋጀ ምግብ”

ለመነሣት አልችልም
x

Luke 11:9

ለምኑ ... ፈልጉ ... አንኳኩ
ኢየሱስ የእርሱ ደቀ መዛሙርት ባለማቋረጥ እንዲጸልዩ ለማበረታታት እነዚህን ትዕዛዞች ይሰጣቸዋል። አንዳንድ ቋንቋዎች ከእነዚህ ግሦች ጋር ተጨማሪ መረጃ ደግሞ ይፈልጉ ይሆናል። በዚህ ዐውድ በይበልጥ ተስማሚ የሚሆነውን “እናንተ” የሚለውን ቃል ተጠቀሙ። አ.ት፡ “የሚያስፈልጋችሁን መለመናችሁን ቀጥሉበት ... ከእግዚአብሔር የምትፈልጉትን መፈለጋችሁን ቀጥሉ ... አግኙት ... በሩን ማንኳኳታችሁን ቀጥሉ”

ይሰጣችኋል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር እርሱን ይሰጣችኋል” ወይም “ትቀበሉታላችሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

አንኳኩ
በር ማንኳኳት በቤቱ ውስጥ ያለው ሰው እናንተ በውጪ መቆማችሁን እንዲያውቅ ለጥቂት ጊዜ በሩን መምታት ነው። ደግሞም በባህልህ ሰዎች ወደ ቤት መድረሳቸውን ለማሳየት በሚጠቀሙበት ለምሳሌ “መጠራት” ወይም “መሳል” ወይም “ማጨብጨብ” የመሳሰሉትን መንገዶች በመጠቀም መተርጎም ይቻላል። እዚህ ጋ፣ ትርጉሙ አንድ ሰው እግዚአብሔር መልስ እስኪሰጠው ድረስ ጸሎቱን መቀጠል አለበት የሚል ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ይከፈትላችኋል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር በሩን ይከፍትላችኋል” ወይም “እግዚአብሔር ወደ ውስጥ ያስገባችኋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Luke 11:11

አያያዥ መግለጫ፡
ኢየሱስ ስለ ጸሎት ለደቀ መዛሙርቱ ማስተማሩን ይጨርሳል።

ከእናንተ የትኛው አባት ... ዓሣ?
ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ለማስተማር በጥያቄ ይጠቀማል። ይህ እንደ መግለጫ ደግሞ ሊጻፍ ይችላል። አ.ት፡ “አባቶች ከሆናችሁት ከእናንተ ማንም ... ዓሣ” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ወይስ ... ቢለምነው ጊንጥ ይሰጠዋል?
ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ለማስተማር በጥያቄ ይጠቀማል። ይህ እንደ መግለጫ ደግሞ ሊጻፍ ይችላል። አ.ት፡ “እንቁላል ቢለምናችሁ በፍጹም ጊንጥ አትሰጡትም” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ጊንጥ
ጊንጥ ከሸረሪት ጋር ይመሳሰላል፣ ነገር ግን እርሱ መርዛማ መናደፊያ ጭራ አለው። አንተ ባለህበት አካባቢ ጊንጥ የማይታወቅ ከሆነ “መርዛማ ሸረሪት” ወይም “የሚናደፍ ሸረሪት” ብለህ ልትተረጉመው ትችላለህ። (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)

ክፉ የሆናችሁ እናንተ . . . ካወቃችሁ
“እናንተ ክፉ የሆናችሁት . . . ካወቃችሁ” ወይም “ኃጢአተኞችም እንኳን ብትሆኑ፣ እናንተ . . . ታውቃላችሁ”

Luke 11:14

አጠቃላይ መረጃ፡
ኢየሱስ ከዲዳው ሰው አጋንንትን ካወጣ በኋላ ጥያቄ ይቀርብለታል።

በዚህ ጊዜ
ደራሲው የአዲስ ሁነት ጅማሬን ለማመልከት ይህንን ቃል ይጠቀማል። (አዲስ ሁነትን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)

ኢየሱስ አጋንንትን ያስወጣ ነበር
ልዩ መረጃ መጨመር ሊረዳ ይችል ይሆናል። አ.ት፡ “ኢየሱስ ከአንድ ሰው አጋንንትን ያወጣ ነበር” ወይም “ኢየሱስ፣ አጋንንት ሰውየውን እንዲለቀው ያደርግ ነበር”

ዲዳ የሆነ አጋንንት ነበር
አጋንንቱ ሰዎችን ከመናገር የሚከለክልበት ኃይል ነበረው። አ.ት፡ “ሰውየው መናገር እንዳይችል አድርጎት የነበረው አጋንንት”

በዚህ ጊዜ
ድርጊቱ የቱ ጋ እንደሚጀምር ለማመልከት ይህ ቃል እዚህ ጋ ጥቅም ላይ ውሏል። የአንተ ቋንቋ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው ያንን እዚህ ጋ ስለመጠቀም ማሰብ ይኖርብሃል። አጋንንቱ ከሰውዬው በወጣ ጊዜ ከሕዝቡ አንዳንዶቹ ኢየሱስን ነቀፉት፣ ይህም ኢየሱስ ስለ ክፉ መናፍስት ወዳስተማረው ትምህርት የሚመራ ሆነ።

አጋንንቱ በወጣ ጊዜ
ልዩ መረጃ መጨመር ሊረዳ ይችል ይሆናል። አ.ት፡ “አጋንንቱ ከሰውዬው በወጣ ጊዜ” ወይም “አጋንንቱ ሰውዬውን በለቀቀው ጊዜ”

ዲዳ የነበረው ሰው ተናገረ
“መናገር የማይችል የነበረው ሰው በዚህ ጊዜ ተናገረ”

በብኤልዜቡል በአጋንንት አለቃ አጋንንትን ያወጣል
“አጋንንትን የሚያወጣው የአጋንንት አለቃ በሆነው በብኤልዜቡል ኃይል ነው”

Luke 11:16

አጠቃላይ መረጃ፡
ኢየሱስ ለሕዝቡ ምላሽ መስጠት ይጀምራል።

ሌሎች ፈተኑት
“ሌሎች ሰዎች ኢየሱስን ፈተኑት”። ሥልጣኑ ከእግዚአብሔር መሆኑን እንዲያረጋግጥላቸው ፈለጉበት።

ከሰማይ ምልክት እንዲያሳያቸው ጠየቁት
“ከሰማይ ምልክት እንዲሰጣቸው ለመኑት” ወይም “ከሰማይ ምልክት እንዲሰጣቸው በመጠየቅ”። ሥልጣኑ ከእግዚአብሔር መሆኑን እንዲያረጋግጥላቸው የፈለጉት እንዲህ ባለ መንገድ ነበር።

እርስ በእርሱ የሚከፋፈል መንግሥት ሁሉ ይጠፋል
እዚህ ጋ፣ “መንግሥት” የሚያመለክተው በውስጡ የሚኖረውን ሕዝብ ነው። ይህም ደግሞ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በአንድ መንግሥት ውስጥ የሚኖሩ ሕዝቦች እርስ በእርሳቸው ከተዋጉ መንግሥታቸውን ያጠፋሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እርስ በእርሱ የሚከፋፈል ቤት ይወድቃል
እዚህ ጋ “ቤት” የሚያመለክተው ቤተሰብን ነው። አ.ት፡ “የቤተሰብ አባላት እርስ በእርስ ከተጣሉ ቤተሰባቸውን ይበታትኑታል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ይወድቃል
“ተሰባብሮ ይወድቅና ይጠፋል”። ይህ የሚደረመስ ቤት ስዕል የሚያመለክተው የቤተሰብ አባላት እርስ በእርስ በሚጣሉበት ጊዜ ቤተሰቡ የሚጠፋ መሆኑን ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Luke 11:18

ሰይጣን እርስ በእርሱ ከተከፋፈለ
እዚህ ጋ፣ “ሰይጣን” የሚያመለክተው እርሱን የሚከተሉትን አጋንንትን እንዲሁም ራሱን ሰይጣንን ነው። አ.ት፡ “ሰይጣንና በመንግሥቱ ያሉ አባላቱ እርስ በእርሳቸው ከተዋጉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሰይጣን ... ከሆነ መንግሥቱ እንዴት ይጸናል?
ኢየሱስ ሕዝቡን ለማስተማር ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ሰይጣን . . . ከሆነ መንግሥቱ አይጸናም” ወይም “ሰይጣን . . . መንግሥቱ ይፈራርሳል”። (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

አጋንንትን የማወጣው በብኤልዜቡል እንደሆነ ትላላችሁና
“አጋንንትን ከሰዎች የማወጣው በብኤልዜቡል ኃይል እንደሆነ ትናገራላችሁና”። የክርክሩ ቀጣይ ክፍል በግልጽ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አጋንንትን ከሰዎች የማወጣው በብኤልዜቡል ኃይል እንደሆነ ትናገራላችሁና። ያ ደግሞ ሰይጣን እርስ በእርሱ ተከፋፍሏል ማለት ነው”

ነገር ግን እኔ ... ተከታዮቻችሁ በማን ያወጧቸዋል?
“ነገር ግን እኔ . . . ተከታዮቻችሁ አጋንንት ከሰዎች እንዲወጡ በማን ኃይል ያስገድዷቸዋል?” ኢየሱስ ሕዝቡን ለማስተማር ጥያቄዎችን ይጠይቃል። ኢየሱስ የሚጠይቀው ጥያቄ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አ.ት፡ “ነገር ግን እኔ . . . እንግዲያውስ ተከታዮቻችሁም ደግሞ አጋንንትን የሚያወጡት በብኤልዜቡል ኃይል ነው ብለን መስማማት አለብን። ይሁን እንጂ ይህ እውነት እንደሆነ አታምኑም”።

እነርሱ ፈራጆቻችሁ ይሆናሉ
“እኔ በብኤልዜቡል ኃይል አጋንንትን እንደማወጣ ስለማለታችሁ በእግዚአብሔር ኃይል አጋንንትን የሚያወጡ ተከታዮቻችሁ ይፈርዱባችኋል”

በእግዚአብሔር ጣት
“የእግዚአብሔር ጣት” የእግዚአብሔርን ኃይል ያመለክታል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እንግዲያው የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ መጥታለች
“ይህ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ መምጣቷን ያሳያል”

Luke 11:21

ብርቱ ሰው ... ጊዜ የሰውዬው ንብረት
ይህ ኢየሱስ ብርቱ ሰው ሆኖ የሌላውን ብርቱ ሰው ንብረት ይወስድ ይመስል እርሱ ሰይጣንን እና አጋንንቶቹን ስለ ማሸነፉ የሚናገር ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የጦር መሣሪያውን ከሰውዬው ይወስድበታል
“የሰውዬውን የጦር መሣሪያና መከላከያ ያስወግዳል”

ንብረቱ ይጠበቅለታል
“ማንም የእርሱን ነገር ሊሰርቅበት አይችልም”

የሰውዬውን ሀብት ይበዘብዛል
“ሀብቱን ይሰርቀዋል” ወይም “የሚፈልገውን ነገር ሁሉ ይወስዳል”

ከእኔ ጋር ያልሆነ ይቃወመኛል፣ ከእኔ ጋር የማይሰበስብም ይበትናል
ይህ የሚያመለክተው የትኛውንም ሰው ወይም የሰዎች ቡድን ነው። “ከእኔ ጋር ያልሆነ ማንም ቢሆን ይቃወመኛል፣ ከእኔ ጋር የማይሰበስብ ማንም ቢሆን ይበትናል” ወይም “ከእኔ ጋር ያልሆኑት እነርሱ ይቃወሙኛል፣ ከእኔ ጋር የማይሰበስቡ እነዚያም ይበትናሉ”

ከእኔ ጋር ያልሆነ
“እኔን የማይደግፈኝ” ወይም “ከእኔ ጋር የማይሠራ”

ይቃወመኛል
“እኔን በመቃወም ይሠራል”

ከእኔ ጋር የማይሰበስብ ይበትናል
ከእኔ ጋር የማይሰበስብ ይበትናል ኢየሱስ የሚያመለክተው እርሱን የሚከተሉ ደቀ መዛሙርትን መሰብሰብን ነው። ይህ በግልጽ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሰዎች መጥተው እንዲከተሉኝ የማያደርግ ማንም ቢኖር ከእኔ እንዲርቁ ያደርጋቸዋል”

Luke 11:24

ውሃ በሌለበት ሥፍራ
ይህ ክፉ መናፍስት የሚቅበዘበዙበትን “ኦና ሥፍራ” ያመለክታል።

ምንም አያገኝም
“መንፈስ በዚያ ምንም ዓይነት እረፍት በሚያጣበት ጊዜ”

ትቼው ወደ መጣሁበት ቤቴ
ይህ ለመኖሪያነት የተጠቀመበትን ሰውዬ ያመለክታል። አ.ት፡ “ወደ ኖርኩበት ሰው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ያ ቤት ተጠርጎና ተስተካክሎ ያገኘዋል
ይህ ዘይቤአዊ አነጋገር ተጠርጎ በጸዳውና ነገሮች ተስተካክለው በተቀመጡበት ቤት ስለተመሰለው ሰው ይናገራል። ቤቱ እስካሁን ድረስ ባዶ እንደሆነ ያመላክታል። ይህ ግልጽ ካደረገው መረጃ ጋር በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሰውዬው ልክ አንድ ሰው ጠርጎ ያጸዳውና ሁሉንም ነገር በተገቢው ቦታ አድራጅቶ በማስቀመጥ የተወውን ቤት መስሎ ያገኘዋል” ወይም “ሰውዬው የጸዳና የተደራጀ፣ ነገር ግን የተተወ ቤት መስሎ ያገኘዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከመጀመሪያው ይልቅ የከፋ
“መጀመሪያ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እርኩሱ መንፈስ ሳይለቀው በፊት የነበረውን የሰውዬውን ሁኔታ ነው። አ.ት፡ “መንፈሱ ሳይለቀው በፊት ከነበረው ሁኔታ ይልቅ የከፋ”

Luke 11:27

አጠቃላይ መረጃ፡
x

Luke 11:29

አያያዥ መግለጫ፡
ኢየሱስ ሕዝቡን ማስተማሩን ይቀጥላል።

የሕዝቡ ብዛት ሲጨምር
“ብዙ ሰዎች ሕዝቡ ላይ ሲጨመሩ” ወይም “ሕዝቡ እየበዛ ሲሄድ”

ይህ ትውልድ ክፉ ትውልድ ነው። ... ይፈልጋል
እዚህ ጋ፣ “ትውልድ” በውስጡ ያለውን ሕዝብ ያመለክታል። አ.ት፡ “በዚህ ዘመን ያሉ ሰዎች ክፉዎች ናቸው። ለራሳቸው ... ይፈልጋሉ” ወይም “በዚህ ዘመን የምትኖሩ ሰዎች ክፉዎች ናችሁ። ለእናንተ ... ትፈልጋላችሁ”

ምልክትን ይፈልጋል
ስለሚፈልገው የምልክት ዓይነት መረጃው ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አ.ት፡ “ከእግዚአብሔር መምጣቴን ለማረጋገጥ ተአምራት እንዳደርግ ይፈልግብኛል”

ምንም ምልክት አይሰጠውም
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር አንድም ምልክት አይሰጠውም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የዮናስን ምልክት
“በዮናስ የሆነው” ወይም “እግዚአብሔር ለዮናስ ያደረገለት ተአምር”

ልክ ዮናስ ምልክት እንደሆነ ... እንዲሁ ደግሞ ... ይህ ትውልድ
ይህ ማለት ዮናስ ለነነዌ ሕዝብ ከእግዚአብሔር ዘንድ ምልክት ሆኖ እንዳገለገለ ኢየሱስም በተመሳሳይ መንገድ በዚያ ዘመን ለነበሩት አይሁድ ከእግዚአብሔር ዘንድ ምልክት ሆኖ ያገለግላል።

የሰው ልጅ
ኢየሱስ ወደ ራሱ እያመለከተ ነው።

ይህ ትውልድ
“ዛሬ በሕይወት ያሉ ሰዎች”

Luke 11:31

የደቡብ ንግሥት
ይህ የሳባን ንግሥት ያመለክታል። ሳባ ከእስራኤል በስተደቡብ የነበረ መንግሥት ነው።

ከዚህ ትውልድ ሰዎች ጋር በፍርድ ትነሣለች
“ተነሥታ በዚህ ዘመን ሰዎች ላይ ትፈርዳለች”

ከምድር ጫፍ መጥታለች
ይህ የአነጋገር ዘይቤ በጣም ሩቅ ከሆነ ቦታ መጥታለች የሚል ትርጉም አለው። አ.ት፡ “በጣም ረጅም ርቀት ተጉዛ መጥታለች” ወይም “በጣም ሩቅ ከሆነ ቦታ መጥታለች” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ከሰለሞን የሚበልጥ እዚህ አለ
ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ስለ ራሱ ነው። አ.ት፡ “ከሰለሞን የምበልጠው እኔ እዚህ አለሁ”

ከሰለሞን የሚበልጥ
ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ስለ ራሱ ነው። አ.ት፡ “እኔ ከሰለሞን እበልጣለሁ”

Luke 11:32

የነነዌ ሰዎች
ይህ ጥንታዊቷን የነነዌ ከተማ የሚያመለክት መሆኑን በግልጽ መንገር ያግዝ ይሆናል። አ.ት፡ “በጥንታዊቷ የነነዌ ከተማ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች”

ሰዎች
ይህ ወንዶችንና ሴቶችን ያካትታል። አ.ት፡ “ሕዝብ” (ተባዕታዊ ቃል በምታገኝበት ጊዜ እንስታዊንም ጨምርበት የሚለውን ተመልከት)

የዚህ ትውልድ ሕዝብ
“የዚህ ዘመን ሕዝብ”

ንሰሐ ገብተዋልና
“የነነዌ ሕዝብ ንሰሐ ገብተዋልና”

ከዮናስ የሚበልጥ እዚህ አለ
ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ስለ ራሱ ነው። እርሱን እንዳልሰሙት በግልጽ መንገሩ ሊጠቅም ይችላል። አ.ት፡ “ከዮናስ የምበልጥ ብሆንም እንኳን እናንተ ገና ንሰሐ አልገባችሁም”

Luke 11:33

አያያዥ መግለጫ፡
ኢየሱስ ሕዝቡን ማስተማሩን ይጨርሳል።

አጠቃላይ መረጃ፡
ከቁጥር 33 – 36 ያሉት ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ እንዲታዘዙትና ከሌሎች ጋር እንዲካፈሉት ስለሚፈልገው “ብርሃን” ስለሆነው ትምህርቱ የተናገረባቸው ዘይቤአዊ አነጋገሮች ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በድብቅ ቦታ ወይም ከቅርጫት በታች ያስቀምጠዋል
“ይደብቀዋል ወይም ከቅርጫት በታች ያስቀምጠዋል”

ነገር ግን በመብራት ማስቀመጫ ላይ
በዚህ አንቀጽ ውስጥ መገንዘብ በሚቻለው ባለቤትና ግሥ ላይ መጨመር ይቻላል። አ.ት፡ “ነገር ግን አንድ ሰው በመብራት ማስቀመጫው ላይ ያስቀምጠዋል” ወይም “ነገር ግን አንድ ሰው በጠረጴዛ ላይ ያስቀምጠዋል”

ዐይንህ የሰውነትህ መብራት ነው
በዚህ የዘይቤአዊ አነጋገር ክፍል ውስጥ ልክ ዐይን ለሰውነት ብርሃንን እንደሚያቀርብ ኢየሱስ ሲያደርግ የሚያዩአቸው ነገሮች ማስተዋልን ያቀርቡላቸዋል። አ.ት፡ “ዐይንህ ልክ እንደ ሰውነት መብራት ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ዐይንህ
ዐይን የማየት ችሎታ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሰውነት
ሰውነት ለሰው ሕይወት ነው።

ዐይንህ ጤነኛ በሚሆንበት ጊዜ
እዚህ ጋ፣ “ዐይን” የማየት ችሎታ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “የማየት ችሎታህ ጤነኛ በሚሆንበት ጊዜ” ወይም “በሚገባ በምታይበት ጊዜ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሰውነትህ በሙሉ በብርሃን ይሞላል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሰውነትህን በሙሉ ብርሃን ይሞላዋል” ወይም “ሁሉንም ነገር አጥርተህ ለማየት ትችላለህ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ዐይንህ በሚታመምበት ጊዜ
እዚህ ጋ፣ “ዐይን” የማየት ችሎታ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “የማየት ችሎታህ በሚታወክበት ጊዜ” ወይም “በሚገባ ማየት በማትችልበት ጊዜ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሰውነትህ በጨለማ የተሞላ ነው
“ምንም ነገር ለማየት አትችልም”

በአንተ ውስጥ ያለው ብርሃን ጨለማ እንዳይሆን ተጠንቀቅ
“ብርሃን ነው ብለህ የምታስበው ጨለማ ሆኖ እንዳይገኝ አረጋግጥ” ወይም “የትኛው ብርሃን፣ የትኛው ደግሞ ጨለማ መሆኑን ስለ ማወቅህ እርግጠኛ ሁን”

ከዚያም ሙሉ ሰውነትህ ብርሃን ድምቀቱን በላይህ ላይ በሚያንጸባርቅበት ጊዜ የሚመስለውን ዓይነት ይሆናል
ኢየሱስ ተመሳሳዩን እውነት በተነጻጻሪ ይናገራል። እርሱ እውነትን ሰለ ተሞሉ ሰዎች በድምቀት እንደሚያበሩ መብራቶች አድርጎ ይናገርለቸዋል። (ተነጻጻሪ የሚለውን ተመልከት)

Luke 11:37

አጠቃላይ መረጃ፡
ኢየሱስ በፈሪሳዊ ቤት እንዲበላ ተጋበዘ።

ንግግሩን በጨረሰ ጊዜ
ደራሲው የአዲስ ሁነት ጅማሬን ለማመልከት እነዚህን ቃላት ይጠቀማል። (አዲስ ሁነትን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)

በቤቱ
ይህ የፈሪሳዊውን ቤት ያመለክታል።

ጋደም አለ
ወንዶች በምግቡ ዙሪያ በምቾት ጋደም ማለታቸውና እንዲህ ያለውን እራት ዘና ብለው መብላታቸው የተለመደ ነበር። በአንተ ቋንቋ ሰዎች በሚበሉበት ጊዜ ሰውነታቸውን እንዴት ባለ ሁኔታ እንደሚያሳርፉት ገላጭ ቃል ካለው ያንን ቃል በመጠቀም መተርጎም ያስፈልግህ ይሆናል። አ.ት፡ “ለመብላት ተቀመጡ”

መታጠብ
በሥርዓቱ መሠረት ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት ንጹሕ ለመሆን እጆቻቸውን መታጠብ እንዳለባቸው የሚናገር መመሪያ ፈሪሳውያን ነበራቸው። አ.ት፡ “እጆቹን መታጠብ” ወይም “በሃይማኖታዊው ሥርዓት ንጹህ ለመሆን እጆቹን መታጠብ”

Luke 11:39

አጠቃላይ መረጃ:
ኢየሱስ ዘይቤአዊ አነጋገርን በመጠቀም ለፈሪሳዊው መናገር ይጀምራል። እርሱ ሲኒና ጎድጓድ ሳህኖችን የሚያነጹበትን መንገድ ራሳቸውን ከሚያነጹበት ጋር ያነጻጽራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የሲኒውንና የጎድጓድ ሳህኑን ውጫዊ ገጽ
የዕቃ መያዣዎቹን ውጫዊ ገጽ ማጠብ የፈሪሳውያን የሃማኖታዊ ሥርዓታቸው አካል ነበር።

ነገር ግን ውስጣችሁ በስስትና በክፋት የተሞላ ነው
ይህ የዘይቤአዊ አነጋገር ክፍል የሳህኑን ውጫዊ ገጽታ ለማጽዳት የሚያደርጉትን ጥንቃቄ ቸል ከሚሉት ውስጣዊ ሁኔታቸው ጋር ያነጻጽራል።

እናንተ ሞኞች
እዚህ ጋ ኢየሱስ የሚናገራቸው ሁሉ ወንዶች ፈሪሳውያን ቢሆኑም እንኳን ይህ አገላለጽ ወንዶችን ወይም ሴቶችን ሊያመለክት ይችላል።

ውጪውን የሠራው እርሱ ውስጡን ደግሞ አይሠራውም?
እግዚአብሔር በውስጣቸው ስላለው ነገር እንደሚገደው ባለማስተዋላቸው ኢየሱስ ፈሪሳውያንን በጥያቄ ይገስጻቸዋል። ይህ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ውጪውን የሠራው እርሱ ውስጡንም ደግሞ ሠርቶታል!” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

በውስጥ ያለውን ለድኾች ስጡ
ይህ በሲኒዎቻቸውና በጎድጓዳ ሳህኖቻቸው ሊያደርጉት የሚገባቸውን ያመለክታል። አ.ት፡ “በሲኒዎቻችሁና በጎድጓዳ ሳህኖቻችሁ ውስጥ ያለውን ለድኾች ስጡ” ወይም “ለድኾች ለጋሾች ሁኑ”

ሁሉም ነገር ንጹሕ ይሆንላችኋል
“ሙሉ በሙሉ ንጹሕ ትሆናላችሁ” ወይም “በውስጣችሁና በውጪአችሁ ሁሉ ንጹሕ ትሆናላችሁ”

Luke 11:42

ከአዝሙድ፣ ጤና አዳምና ከሌሎችም የጓሮ ዕጽች አሥራት ታወጣላችሁ
“ከአዝሙድ፣ ከጤና አዳምና ከሌሎች የጓሮ ዕጽቻችሁ አንድ አሥረኛውን ለእግዚአብሔር ትሰጣላችሁ”። ከገቢያቸው ላይ አሥረኛውን ከመስጠት አንጻር ፈሪሳውያን እንዴት ያለ ጽንፍ እንደነበራቸው ኢየሱስ ምሳሌ እየሰጠ ነበር።

አዝሙድና ጤና አዳም
እነዚህ ዕጽች ናቸው። ሰዎች ከእነዚህ ቅጠላ ቅጠሎች ቀንጥሰው ጣዕም እንዲሰጥ ምግባቸው ላይ ይጨምራሉ። ሰዎች አዝሙድና ጤና አዳም ምን እንደሆኑ ካላወቁ እነርሱ የሚያውቁትን የዕጽ ስም ወይም “ዕጽች” የሚል ጥቅል አገላለጽ መጠቀም ትችላለህ። (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)

ከሌላ የጓሮ ዕጽ ሁሉ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “ከሌላ ከእያንዳንዱ አትክልት” 2) “ከሌላ የጓሮ ዕጽ ሁሉ” ወይም 3) “ከሌላ የጓሮ ተክል ሁሉ” የሚሉት ናቸው።

የእግዚአብሔር ፍቅር
“እግዚአብሔርን ለመውደድ” ወይም “ለእግዚአብሔር የሆነ ፍቅር”። የሚወደደው እግዚአብሔር ነው።

ሌሎቹን ነገሮች ማድረግን ደግሞ ሳትተዉ
“ሳትተዉ” ይህ ሁልጊዜ መደረግ እንዳለበት አጽንዖት ይሰጣል። ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሌሎቹንም መልካም ነገሮች እንዲሁ አዘውትራችሁ ለማድረግ” (ምጸት የሚለውን ተመልከት)

Luke 11:43

አያያዥ መግለጫ:
ኢየሱስ ፈሪሳውያንን መናገሩን ያበቃል።

ከፊት ያሉ መቀመጫዎች
“ምርጥ መቀመጫዎች”

የአክብሮት ሰላምታ
“ሰዎች በልዩ አክብሮት ሰላምታ እንዲሰጧችሁ ትወዳላችሁ”

ሰዎች ሳያውቁት በላዩ ላይ እንደሚሄዱበት ምልክት የሌለበት መቃብር ናችሁ
ፈሪሳውያን ምልክት እንደሌለበት መቃብር ናቸው፣ ምክንያቱም በሃይማኖት ሥርዓት ንጹሕ ይመስላሉ፣ ነገር ግን በዙሪያቸው ያሉት እንዲረክሱ ያደርጋሉ። (ተነጻጻሪ የሚለውን ተመልከት)

ምልክት የሌለበት መቃብር
እነዚህ መቃብሮች አስክሬን የሚቀበርባቸው የተቆፈሩ ጉድጓዶች ናችው። እነዚህ ሌሎች ሰዎች ያዩአቸው ዘንድ እንደተለመደው ሰዎች በመቃብር ሥፍራ የሚያስቀምጧቸው ነጭ ድንጋዮች የሏቸውም።

ሳያውቁት
አይሁድ በመቃብር ላይ በሚሄዱበት ጊዜ በሃይማኖታዊው ሥርዓት ይረክሳሉ። እነዚህ ምልክት የሌለባቸው መቃብሮች በድንገት እንዲረክሱ ያደርጓቸዋል። ይህ በግልጽ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሳያስተውሉት እና በሃይማኖታዊ ሥርዓት እርኩስ ይሆናሉ”

Luke 11:45

አጠቃላይ መረጃ:
ኢየሱስ ለአይሁዳዊው መምህር ምላሽ መስጠት ይጀምራል።

ከሕግ መምህራን አንዱ
ይህ በታሪኩ ውስጥ አዲስ ገጸ ባህርይን ያስተዋውቃል። (አዲስና ነባር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)

በምትናገረው እኛንም መሳደብህ ነው
ኢየሱስ በፈሪሳውያን ላይ የሰጠው አስተያየት የአይሁድ የሕግ መምህራንንም የሚመለከት መስሏል።

ወዮላችሁ እናንተ የሕግ መምህራን!
ኢየሱስ ከፈሪሳውያን ጋር የሕግ መምህራኑንም ተግባር ለመኮነን መፈለጉን ግልጽ ያደርጋል።

ለመሸከም የሚከብድ ሸክም በሕዝብ ላይ ትጭናላችሁ
“ሊሸከሙት የማይችሉትን ከባድ ሸክም በሕዝብ ላይ ትጭናላችሁ”። ኢየሱስ የሚናገረው አንድ ሰው ከባድ ነገሮችን እንዲሸከሙት ለሕዝብ ይሰጣቸው ይመስል ብዙ መመሪያዎችን ስለሚሰጣቸው ሰው ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሸክሙን ከጣቶቻችሁ በአንዱ መንካት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “ሕዝቡ እነዚያን ከባድ ሸክሞች እንዲሸከም ለመርዳት ምንም ነገር አታደርጉም” ወይም 2) “እነዚያን ሸክሞች ራሳችሁ ለመሸከም ምንም ጥረት አታደርጉም”

Luke 11:47

እናንተ ደግሞ ምስክሮች ስለሆናችሁ ትስማማላችሁ
ኢየሱስ ፈሪሳውያንን እና የሕግ መምህራንን እየገሰጻቸው ነው። ስለ ነቢያት መገደል ያውቃሉ፣ ነገር ግን እነርሱን ስለመግደላቸው አባቶቻቸውን

አይኮንኑም። አ.ት፡ “ስለዚህ፣ እነርሱን ከማውገዝ ይልቅ ታጸናላችሁ፣ ትስማማላችሁም”

Luke 11:49

በዚህ ምክንያት
ይህ ቀደም ሲል የሕግ መምህራን መመሪያዎችን በሕዝቡ ላይ ስለመጫናቸው የተነገረውን መግለጫ ወደ ኋላ ያመለክታል።

የእግዚአብሔር ጥበብ እንዲህ አለች
“ጥበብ” ስለ እግዚአብሔር ሆና መናገር እንደቻለች ተደርጋ ተወስዳለች። አ.ት፡ “እግዚአብሔር በጥበቡ እንዲህ አለ” ወይም “እግዚአብሔር በጥበብ ተናገረ” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

ነቢያትንና ሐዋርያትን እልክላቸዋለሁ
“ለሕዝቤ ነቢያትንና ሐዋርያትን እልክላቸዋለሁ”። ኢየሱስ ይናገራቸው ለነበሩ አይሁድ አድማጮች፣ እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው ነቢያትንና ሐዋርያትን እንደሚልክ አስቀድሞ አስታውቋቸው ነበር።

ከእነርሱ አንዳንዶቹን ያሳድዳሉ፣ ይገድላሉም
“ሕዝቤ ከነቢያትና ከሐዋርያት አንዳንዶቹን ያሳድዳሉ፣ ይገድላሉም”። ኢየሱስ ይናገራቸው ለነበሩ አይሁድ አድማጮች እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው ነቢያትንና ሐዋርያትን እንደሚያሳድዱና እንደሚገድሉ አስቀድሞ አስታውቋቸው ነበር።

እንግዲህ ለፈሰሰው የነቢያት ሁሉ ደም ይህ ትውልድ ተጠያቂ ይሆናል
ኢየሱስ ይናገራቸው የነበሩ ሰዎች በአባቶቻቸው ስለ ተገደሉት ነቢያት ተጠያቂዎች ይሆናሉ። አ.ት፡ “ስለዚህ ሰዎች ስለ ገደሏቸው ነቢያት ሞት በሙሉ እግዚአብሔር ይህንን ትውልድ ተጠያቂ ያደርገዋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የፈሰሰው የነቢያት ደም
“ደም… ፈሰሰ” በተገደሉ ጊዜ የተረጨውን ደም ያመለክታል። አ.ት፡ “የነቢያትን መገደል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ዘካርያስ
ይህ ምናልባት በብሉይ ኪዳን ስለ ጣዖት አምልኮአቸው የእስራኤልን ሕዝብ የገሰጻቸው ካህን ይሆን ይሆናል። ይህ የአጥማቂው ዮሐንስ አባት አይደለም።

የተገደለው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሕዝቡ የገደሉት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Luke 11:52

አያያዥ መግለጫ፡
ኢየሱስ ለአይሁዳዊው መምህር የሚሰጠውን ምላሽ ያበቃል።

የእውቀትን ቁልፍ ወስዳችኋል ... የሚገቡትን ታደናቅፋላችሁ
ኢየሱስ የእግዚአብሔር እውነት በቤት ውስጥ እንዳለ፣ መምህራን ለመግባት እምቢ እንዳሉና ሌሎች ደግሞ ቁልፉን አግኝተው እንዳይገቡ እንዳልፈቀዱላቸው ይናገራል። ይህ ማለት መምህራኑ እግዚአብሔርን በእውነት አያውቁትም፣ ሌሎችንም ደግሞ እርሱን ከማወቅ ይከለክላቸዋል ማለት ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ቁልፉን
ይህ ወደ ቤት ወይም ወደ ዕቃ ማስቀመጫ ክፍል የመግቢያውን መንገድ ይወክላል።

ራሳችሁ አትገቡም
“እናንተ ራሳችሁ እውቀት ለማግኘት አትገቡም”

Luke 11:53

አጠቃላይ መረጃ፡
ይህ ኢየሱስ በፈሪሳዊው ቤት የሚበላበት የታሪኩ የመጨረሻ ክፍል ነው። የታሪኩ ዋነኛው ክፍል ካለቀ በኋላ ስለሆነው ነገር እነዚህ ቁጥሮች ለአንባቢው ይናገራሉ።

ኢየሱስ ከዚያ ከሄደ በኋላ
“ኢየሱስ ከፈሪሳዊው ቤት ወጥቶ ከሄደ በኋላ”

ለማጥመድ በመሞከር ... ከእርሱ ጋር ተከራከሩ
ጸሐፊዎችና ፈሪሳውያን ከኢየሱስ ጋር የተከራከሩት የእግዚአብሔርን ሕግ ስለ ማፍረሱ ሊከሱት እንዲችሉ ለማጥመድ በመሞከር እንጂ አመለካከታቸውን ለማስከበር አልነበረም።

በራሱ ቃል ሊያጠምዱት በመሞከር
ይህ ማለት ሊከሱት ይችሉ ዘንድ ኢየሱስ አንድ የተሳሳተ ነገር እንዲናገር ፈልገዋል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 12

1 ይህ እየሆነ ሳለ እርስ በርሳቸው እስኪረጋገጡ ድረስ በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ ሰዎች ተሰብስበው ባሉበት ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ ይላቸው ጀመር። "ግብዝነት
ከሆነው የፈሪሳውያን እርሾ ተጠንቀቁ።" 2 ነገር ግን የሚገለጥ እንጂ ምንም የተሰወረ፣ የሚታወቅ እንጂ ምንም የተደበቀ ነገር የለም። 3 በጨለማ
የተናገራችሁት ማንኛውም ነገር በብርሃን የሚሰማ፣ በጓዳ በጆሮ የተናገራችሁትም በከፍተኛ መድረኮች ላይ የሚታወጅ ይሆናል። 4 ለእናንተ ለወዳጆቼ፣ እንዲህ
እላችኋለሁ፤ ሥጋን የሚገድሉትን ከዚያ በኋላ ግን ምንም ማድረግ የማይችሉትን አትፍሩ። 5 ማንን መፍራት እንደሚገባችሁ እኔ እነግራችኋለሁ። ከገደለ በኋላ
ወደ ገሃነም እሳት የመጣል ሥልጣን ያለውን እርሱን ፍሩት። አዎን፣ እርሱን ፍሩት ብዬ እላችኋለሁ። 6 ሁለት ድንቢጦች ዝቅተኛ ዋጋ ባላቸው ሳንቲሞች ይሸጡ
የለምን? ሆኖም ከእነርሱ አንዷም እንኳ በእግዚአብሔር ፊት የተዘነጋች አይደለችም። 7 ነገር ግን የእናንተ የራሳችሁ ፀጉሮች እንኳ የተቈጠሩ ናቸው። አትፍሩ፣
እናንተ ከብዙ ድንቢጦች የላቀ ዋጋ አላችሁ። 8 በሰዎች ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ የሰው ልጅ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ይመሰክርለታል፤ 9 በሰዎች ፊት
የሚክደኝ ግን በእግዚአብሔር መላእክት ፊት የሚካድ ይሆናል ብዬ እነግራችኋለሁ። 10 በሰው ልጅ ላይ የተቃውሞ ንግግር የተናገረ ማንኛውም ሰው ይቅርታ
ያገኛል፣ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ግን ይቅርታ አያገኝም። 11 በምኩራቦች፣ በገዢዎችና በባለ ሥልጣኖች ፊት በሚያቀርቧችሁ ጊዜ
ለቀረበባችሁ ክስ እንዴት መልስ መስጠት እንደሚገባችሁ ወይም ምን ማለት እንዳለባችሁ አትጨነቁ፤ 12 መንፈስ ቅዱስ በዚያ ወቅት ምን መናገር
እንደሚገባችሁ ይነግራችኋልና" 13 ከሕዝቡም መካከል አንድ ሰው፣ "መምህር ሆይ፣ ወንድሜ ርስት እንዲያካፍለኝ ንገረው" አለ። 14 ኢየሱስም፣ "አንተ ሰው፣
በእናንተ ላይ ዳኛ ወይም አደራዳሪ አድርጎ የሾመኝ ማን ነው?" አለው። 15 ለእነርሱም እንዲህ አላቸው፣ "ስግብግብነት ከሞላባቸው ምኞቶች ራሳችሁን
ጠብቁ፣ ምክንያቱም የአንድ ሰው ሕይወት በሀብቱ ብዛት ላይ የተመሠረተ አይደለም" 16 ከዚያም ኢየሱስ እንዲህ በማለት ምሳሌ ነገራቸው፤ "የአንድ ሰው
ዕርሻ ከፍተኛ ምርት አስገኘለት፤ 17 እርሱም፣ 'የተመረተውን እህል የማከማችበት የለኝምና ምን ማድረግ ይገባኛል?' ብሎ በልቡ ዐሰበ። 18 እንዲህም አለ፤
'እንግዲያውስ እንደዚህ አደርጋለሁ፣ ጐተራዎቼን አፍርሼ በምትኩ ትልልቅ ጐተራዎችን እሠራለሁ፣ የተመረተውን እህልና ሌሎች ንብረቶቼንም ሁሉ
አከማችባቸዋለሁ። 19 ነፍሴንም፣ "ነፍሴ ሆይ፣ ለብዙ ዘመን የሚበቃ ብዙ ሀብት ተከማችቶልሻልና አትጨነቂ ብዪ፣ ጠጪ ደስም ይበልሽ እላታለሁ'" አለ። 20
እግዚአብሔር ግን እንዲህ አለው፤ "አንተ ሞኝ ሰው፣ ዛሬ ማታ ከአንተ ልትወሰድ ነፍስህ ትፈለጋለች፣ ያዘጋጀሃቸው ነገሮች ታዲያ ለማን ይሆናሉ?" 21
በእግዚአብሔር ፊት ባለ ጠጋ ያልሆነ ለራሱ ግን ሀብትን የሚያከማች ሰው ይህን ይመስላል። 22 ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ አላቸው፤ "ስለዚህ
እላችኋለሁ፣ ምን እንበላለን ብላችሁ ስለ ሕይወታችሁ ወይም ምን እንለብሳለን ብላችሁ ስለ ሰውነታችሁ አትጨነቁ። 23 ምክንያቱም ሕይወት ከምግብ
ሰውነትም ከልብስ ይበልጣልና። 24 የማይዘሩትን ወይም የማያጭዱትን ቁራዎችን ተመልከቱ። መጋዘን ወይም ጐተራ የላቸውም፤ እግዚአብሔር ግን
ይመግባቸዋል። ከወፎች ይልቅ እናንተ ምን ያህል የላቀ ግምት ያላችሁ ናችሁ? 25 ከእናንተስ ተጨንቆ በዕድሜው ላይ አንዲት ቀን መጨመር የሚችል ማን
ነው? 26 ታዲያ፣ ታናሽ የሆነውን ነገር እንኳ ማድረግ የማትችሉ ከሆነ ስለ ሌላው ጉዳይ ለምን ትጨነቃላችሁ? 27 እንዴት እንደሚያድጉ አበቦችን ተመልከቱ።
አይሠሩም ወይም አይፈትሉም። ሆኖም፣ ሰሎሞን እንኳ በዚያ ሁሉ ክብሩ ከእነዚህ እንደ አንዱ እንዳልለበሰ እኔ እነግራችኋለሁ። 28 ዛሬ ታይቶ ነገ ወደ ቆሻሻ
ማከማቻ እንደሚጣለው ሣር በሜዳ ላይ ያለውን እግዚአብሔር እንደዚህ የሚያለብሰው ከሆነ፣ እምነታችሁ ትንሽ የሆነውን እናንተንማ ምን ያህል የበለጠ
አያለብሳችሁም? 29 የምትበሉትንና የምትጠጡትን በመፈለግ አትጨነቁ። 30 በዓለም ውስጥ ባሉት አገሮች የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ እነዚህን ይፈልጋሉና፣
እናንተም እነዚህን እንደምትፈልጉ አባታችሁ ያውቃል። 31 ነገር ግን የእርሱን መንግሥት ፈልጉ፣ እነዚህም ነገሮች ይጨመሩላችኋል። 32 አንተ ታናሽ መንጋ፣
መንግሥትን ሊሰጥህ አባትህ እጅግ ደስ ይለዋልና አትፍራ። 33 ንብረቶቻችሁን ሸጡና ለድኾች ስጡ። በማያረጅ ከረጢት ሌቦች ሊቀርቡትና ብል ሊያጠፋው
የማይቻለውን የማያልቀውን ሀብት በሰማይ አከማቹ። 34 ንብረታችሁ ባለበት ልባችሁም በዚያ ይሆናልና። 35 የሥራ ልብሳችሁን በአጭር ታጥቃችሁ
በተጠንቀቅ ቁሙ፣ መብራታችሁም የበራ ይሁን፤ 36 በሚመጣበትና በሩን በሚያንኳኳበት ጊዜ ፈጥነው በሩን እንደሚከፍቱለት ጌታቸው ከሠርግ ሲመለስ
እንደሚጠባበቁ ሰዎች ሁኑ። 37 በሚመጣበት ጊዜ ነቅተው ሲጠብቁ ጌታቸው የሚያገኛቸው እነዚያ አገልጋዮች የተመሰገኑ ናቸው። በእርግጥ እላችኋለሁ፣
እርሱም የሥራ ልብሱን ለብሶ ምግብ ለመመገብ እንዲቀመጡ ያደርጋቸውና ወደ እነርሱ መጥቶ ያገለግላቸዋል። 38 ከሌሊቱ በስድስት ሰዓት ወይም በዘጠኝ
ሰዓትም እንኳ ቢሆን ሲመጣ ተዘጋጅተው የሚያገኛቸው እነዚያ አገልጋዮች የተመሰገኑ ናቸው። 39 በተጨማሪ ይህን እወቁ፤ የአንድ ቤት ጌታ ሌባ የሚመጣበትን
ሰዓት የሚያውቅ ቢሆን ኖሮ የቤቱ በር እንዲሰበር ባልፈቀደም ነበር። 40 እናንተም እንደዚሁ ዝግጁ ሁኑ፣ ምክንያቱም የሰው ልጅ የሚመጣበትን ሰዓት
አታውቁምና።" 41 ጴጥሮስ፣ "ጌታ ሆይ፣ ይህንን ምሳሌ የተናገርኸው ለእኛ ብቻ ነው ወይስ ለሌሎችም ሰዎች ሁሉ ነው?" አለ። 42 ጌታም እንዲህ አለ፣
"ታዲያ ለሌሎቹ አገልጋዮቹ የተመደበላቸውን ምግብ በትክክለኛው ጊዜ ይሰጣቸው ዘንድ ጌታው የሾመው ታማኝና ብልህ አስተዳዳሪ ማን ነው? 43 ጌታው
በሚመጣበት ጊዜ ይህን ሲያደርግ የሚያገኘው ያ አገልጋይ የተመሰገነ ነው" 44 እውነት እላችኋለሁ፣ ባለው ንብረት ሁሉ ላይ ይሾመዋል። 45 ያ አገልጋይ ግን
በልቡ፣ 'የጌታዬ የመመለሻ ወቅት ይዘገያል' ቢልና ወንድና ሴት አገልጋዮችን መደብደብ፣ መብላትና መጠጣት እንዲሁም መስከር ቢጀምር፣ 46 የዚያ አገልጋይ
ጌታ ባልጠበቀው ቀንና ባላወቀው ሰዓት ይመጣል፣ ይቆራርጠዋል፣ ካልታመኑት ጋርም ይደባልቀዋል። 47 የጌታውን ፈቃድ ያወቀውና እንደ ፈቃዱ ሆኖ
ለመገኘት ያልተዘጋጀውና ፈቃዱን ያልፈጸመው ያ አገልጋይ ከፍተኛ ቅጣት ይቀጣል። 48 ነገር ግን ያላወቀና ቅጣት የሚያስከትልበትን ተግባር የፈጸመ ጥቂት
ይቀጣል። ብዙ ከተሰጠው ከማንኛውም ሰው ብዙ ይጠበቅበታል፣ ከፍ ያለ አደራ ከተሰጠውም፣ ከእርሱ ብዙ ይፈለግበታል። 49 የመጣሁት በምድር ላይ እሳት
ለመለኰስ ነው፣ ሆኖም አሁኑኑ ተቀጣጥሎ ባገኘው ደስ ባለኝ ነበር። 50 ነገር ግን የምጠመቀው ጥምቀት አለኝ፣ ያንንም ጥምቀት እስከምፈጽመው ምን
ያህል በጭንቀት እጠባበቀዋለሁ! 51 በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት እንደ መጣሁ ታስባላችሁን? እንደዚያ አታስቡ፣ እነግራችኋለሁ፣ የመጣሁት ይልቁኑ
መለያየትን ለመጣ ነው። 52 ከእንግዲህ ወዲህ በአንድ ቤት ውስጥ አምስት ሰዎች ቢኖሩ ሦስቱ በሁለቱ ላይ፣ ሁለቱም በሦስቱ ላይ የሚነሡና የሚለያዩ
ይሆናሉ። 53 አባት በልጅ ላይ ልጅም በአባት ላይ፤ አማት በምራት ላይ፣ ምራትም በአማት ላይ ይነሡና ይለያያሉ። 54 ደግሞም ኢየሱስ ለሕዝቡ እንዲህ
አላቸው፤ "በምዕራብ በኩል ደመና ሲያንጃብብ በምትመለከቱበት ጊዜ ወዲያውኑ፣ 'ሊያካፋ ነው' ትላላችሁ፣ እንዳላችሁትም ይሆናል። 55 የደቡብ ነፋስም
ሲነፍስ፣ 'የሚያቃጥል ሙቀት ሊመጣ ነው' ትላላችሁ፣ እንዳላችሁትም ይሆናል። 56 እናንተ ግብዞች፣ የምድርንና የሰማይን መልክ እንዴት እንደምትተረጕሙ
ታውቃላችሁ፣ ታዲያ የአሁኑን ወቅት እንዴት እንደምትተረጕሙ እንዴት አታውቁም? 57 እናንተ ራሳችሁ ትክክል የሆነውን ለምን አትፈርዱም? 58 ከባላጋራህ ጋር
ወደ ከተማው አስተዳዳሪ በምትሄድበት ጊዜ፣ በመንገድ ላይ ቅራኔህን ለመፍታት ጥረት ማድረግ አለብህና፣ ይህን ባታደርግ ዳኛው ለዕለቱ ተረኛ መኰንን
አሳልፎ ይሰጥሃል፣ ተረኛው መኰንንም ወደ ወንጀለኛ ማረፊያ ክፍል ያስገባሃል። 59 ዕዳህን ሙሉ በሙሉ እስካልከፈልህ ድረስ ከዚያ በፍጹም እንደማትወጣ
እኔ እነግርሃለሁ።"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Luke 12:1

አጠቃላይ መረጃ፡
ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን በሺህ በሚቆጠሩ ሰዎች ፊት ማስተማር ጀመረ

በዚያን ጊዜ
ይህ ምናልባት ጸሐፍት እና ፈሪሳውያን እርሱን ለማጥመድ መንገድ በሚፈልጉበት ጊዜ ሊሆን ይችላል። ጸሐፊው እነዚህን ቃላት የተጠቀመው አዲስ የሚጀምረውን ትዕይንት ለመግለጽ ነው። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ...እርስ በእርሳቸው በሚገፋፉበት/በሚረጋገጡበት ጊዜ
ይህ የታሪኩን መቼት የሚያሳይ ዳራ የመረጃ ዳራ ነው። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 12:2

ነገር ግን በዚያ አለ
"ነገር ግን" የሚለው ቃል ስለ ፈሪሳውያን ግብዝነት ለመግለጽ ይህንን ሀረግ ከቀደመው ሀረግ ጋር ያያይዛል። (አያያዥ ቃላት የሚለውን ይመልከቱ)

ሳይገለጥ ተሸፍኖ የሚቀር ምንም ነገር የለም
"ማናቸውም የተደበቀ ነገር ይገለጣል።" ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች በሌሎች ሰዎች በድብቅ የተደረገን ማናቸውንም ነገር ይደርሱበታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ሳይታወቅ ተደብቆ የሚቀር ምንም ነገር የለም
ይህ ከዐረፍተ ነገሩ የመጀመሪያ ክፍል ጋር ተመሳሳይ ትርጉም ያለው እውነቱን ላይ ትኩረት የሚሰጥ አገላለጽ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች ሌሎች ሰዎች ሊደብቁ ስለሚሞክሩት ነገር በሙሉ ማወቅ ይችላሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በጨለማ ውስጥ የተናገራችሁት ነገር ሁሉ በብርሃን ይሰማል
እዚህ ስፍራ "ጨለማ" የሚለው "ምሽት" ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሲሆን ይህም "በግል" ለሚለው ሜቶኖሚ ነው። እንደዚሁም "ብርሃን" የሚለው "ቀን" ለሚለው ሜቶኖሚ ሲሆን ይህም "ሕዝብ" ለሚለው ሜቶኖሚ ነው። "ይሰማል" የሚለው ሀረግ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በምሽት ብቻችሁን ሆናችሁ የተናገራችሁትን፣ ሰዎች በቀን ብርሃን ይሰሙታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

በጆሮ የተነገረ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ለሌላ ሰው ማንሾካሾክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/የነገሩን ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በውስጠኛው ክፍሎች/በጓዳ
"በተዘጋ ክፍል።" ይህ የግል ንግግርን ያመለክታል። "በግል" ወይም "በድብቅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ይሰማል
"ከፍ ባለ ድምጽ ይነገራል።" ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች ያሰሙታል/ይናገሩታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በቤቶች ሰገነት ላይ
በእሥራኤል ቤቶች ጠፍጣፋ ጣራ/ሰገነት አላቸው፤ ስለዚህም ሰዎች ወደዚያ ላይ ወጥተው ሊቆሙ ይችላሉ። ሰዎች እንዴት በቤት ጫፍ ላይ እንደሚወጡ ለመገመት አንባቢው ግር የሚለው ከሆነ፤ ይህ አጠቃላይ በሆነ መንገድ፣ "ሁሉም ሰው ሊሰማው በሚችለው ከፍ ባለ ስፍራ" በሚል ሊተረጎም ይችላል።

Luke 12:4

እኔ ግን ለወዳጆቼ ለእናንተ እንዲህ እላችኋለሁ
ኢየሱስ በዚህ ሁኔታ ደቀ መዛሙርቱ እንዳይፈሩ ዳግም ንግግሩን በአዲስ መልክ ለማቅረብ

ከዚያ ያለፈ ሊያደርጉት የሚችሉት ነገር የለም
"ከዚህ በላይ ጉዳት ሊያደርሱ አይችሉም"

ከ.... በኋላ... ስልጣን ያለውን ፣ እርሱን ፍሩ
x

Luke 12:6

አምስት ድንቢጦች በሁለት ሳንቲም ይሸጡ የለምን?
ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ለማስተማር ጥያቄ ይጠቀማል። "አምስት ድንቢጦች በሁለት ሳንቲም ብቻ እንደሚሸጥ ታውቃላችሁ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ድንቢጦች
ጥራጥሬ የሚመገቡ፣ በጣም ትንንሽ ወፎች

በእግዚአብሔር ዐይኖች አንዳቸውም እንኳን አልተረሱም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር እና በአዎንታዊ መልክ ሊገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር ከእነርሱ አንዲቱን አንኳን በፍጹም አይረሳም" ወይም "እግዚአብሔር በእርግጥ እያንዳንዷን ድንቢጥ እንኳን አይረሳም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እን ምፀት የሚሉትን ይመልከቱ)

እያንዳንዱ የራሳችሁ ፀጉር እንኳን የተቆጠረች ናት
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር በራሳችሁ ላይ ስንት ፀጉር እንዳለ እንኳን ያውቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አትፍሩ
ለፍርሃቱ ምክንያት የሚሆነው ነገር አልተገለጸም። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "በሚደርስባችሁ ነገር አትፍሩ" ወይም 2) "ስለዚህ ለጎዷችሁ የሚችሉ ሰዎችን እትፍሩ።"

እናንተ ከብዙ ድንቢጦች ይልቅ ይበልጥ ዋጋ አላችሁ
"እናንተ ለእግዚአብሔር ከብዙ ድንቢጦች ይልቅ ዋጋ አላችሁ"

Luke 12:8

እኔ ግን እንዲህ እላችኋለሁ
ኢየሱስ ወደ አዲስ ርዕስ ለመግባት፣ በዚህ ሁኔታ ስለ ንስሃ ለማስተማር አድማጮቹን ዳግም እንዲህ ይላቸዋል።

በሰዎች ፊት ስለ እኔ ለሚመሰክረው ሁሉ
የሚመሰከረው ነገር በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "ስለ እኔ ለሌሎች የሚመሰክር እርሱ የእኔ ደቀ መዝሙር ነው" ወይም "ለእኔ ታዛዥ መሆኑን ለመናገር አሻፈረኝ የሚል፣ እርሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ
ኢየሱስ የሚናገረው ስለ ራሱ ነው። "እኔ፣ የሰው ልጅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

በሰዎች ፊት የሚክደኝ እርሱ
"በሰዎች ፊት የሚክደኝ እርሱ።" የተደረገው ክህደት ምን እንደሆነ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "የእኔ ደቀ መዝሙር መሆኑን በሌሎች ፊት እውቅና ለምጠት ያልፈቀደ" ወይም "ለእኔ ታዛዥ መሆኑን ለመናገር ያልፈቀደ እርሱ" (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እክደዋለሁ
"ተቀባይነት አያገኝም።" ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የሰው ልጅ እርሱን ይክደዋል" ወይም "የእኔ ደቀ መዝሙር አይደለም እላለሁ/እክደዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰው ልጅ ላይ የሚናገር ሁሉ
"ስለ ሰው ልጅ ክፉ ነገር የሚናገር ሁሉ"

ይቅር ይባላል
"ይቅርታ ይቀበላል።" ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር ይምረዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

መንፈስ ቅዱስን የሚሰድብ
"በመንፈስ ቅዱስ ላይ ክፉ የሚናገር"

ነገር ግን እርሱ... ይቅር አይባልለትም
ይህ በአድራጊ ግስ ሊገለጽ ይችላል። "ነገር ግን እርሱ... እርሱን እግዚአብሔር ይቅር አይለውም" ወይም "ነገር ግን እርሱ... እግዚአብሔር እርሱን ለዘለዓለም ጥፋተኛ ያደርገዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ምፀት የሚሉትን ይመልከቱ)

Luke 12:11

እናንተን በሚያቀርቧችሁ ጊዜ
እነርሱን ወደ ፍርድ ማን እንደሚያቀርባቸው አልተገለጸም

በሸንጎ ፊት
"በሀይማኖት መሪዎች ፊት ለጥያቄ ወደ ሸንጎ ሲያቀርቧችሁ"

መሪዎች...ባለስልጣናት
ይህንን በአንድ ዐረፍተ ነገር ማጣመር አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። "በአገሪቱ አቅም/ሀይል ያላቸው ሌሎች ሰዎች"

በዚያ ሰዓት
"በዚያን ጊዜ" ወይም "ከዚያም"

Luke 12:13

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ በኢየሱስ ትምህርት መሃል ጣልቃ የገባ ድርጊት ነው። አንድ ሰው ኢየሱስን አንድ ነገር እንዲያደርግ ይጠይቀውል እርሱም ለሰውየው መልስ ይሰጠዋል።

ከእኔ ጋር ውርስ አካፍለን
በዚያ ባህል ውስጥ፣ ብዙውን ጊዜ አባት ከሞተ በኋላ ውርስ ይተላለፋል። የተናጋሪው ሰው አባት መሞቱን ማረጋገጥ ሊያስፈልግ ይችላል። "አሁን አባታችን ስለ ሞተ ድርሻዬን ከሀብቱ አካፍለኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰው
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ እንግዳ የሆነን ለማመልከት የሚውል ነው፤ ወይም 2) ኢየሱስ ሰውየውን እየገሰጸው ነው። የእናንተ ቋንቋ ከእነዚህ በአንዱ መንገዶች በአንዱ ሰዎችን ሊገልጽ የሚችልበት መንገድ ሊኖረው ይችላል። አንዳንዶች ይህን ቃል ከነጭርሱ ሳይተረጉሙት ይቀራሉ።

ማን በእናንተ መሃል ዳኛ ወይም አካፋ አደረገኝ?
ኢየሱስ ጥያቄውን የተጠቀመበት ሰውየውን ለመገሰጽ ነው። አንዳንድ ቋንቋዎች "አንተ" ወይም "የአንተ" ለሚለው ብዙ ቁጥርን ይጠቀማሉ። "እኔ የእናንተ ዳኛ ወይም ፈራጅ አይደለሁም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእነርሱ እንደዚህ አላቸው
እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው ቃል ምናልባት በዚያ የተሰበሰበውን ሕዝብ ሁሉ ሊያመለክት ይችላል። "ኢየሱስ በዚያ ለተሰበሰቡት እንዲህ አላቸው"

ከስግብግብነት ምኞት ሁሉ ራሳችሁን ጠብቁ
"ከማናቸውም አይነት ራስ ወዳድነት ተጠበቁ።" "ከአፍቅሮተ ንዋይ ራሳችሁን አርቁ" ወይም "የንዋይ ፍቅር እንዳይገዛችሁ ራሳችሁን ጠብቁ"

የሰው ሕይወት
ይህ እውነታን የሚያንጸባርቅ አጠቃለይ ሀሳብ ነው። አንደን ሰው ለይቶ አያመለክትም። አንዳንድ ቋንቋዎች ይህን የሚገልጹበት መንገድ አላቸው።

የሀብቱ ብዛት
"ምንም ያህል ሀብት ያለው መሆኑ" ወይም "የቱንም ያህል ንብረት ይኑረው"

Luke 12:16

አያያዥ ሃሳብ:
ኢየሱስ በምሳሌ ትምህርቱን ማስተማሩን ቀጠለ። (ግብረ ገባዊ ምሳሌ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያም ኢየሱስ እንዲህ ሲል ነገራቸው
ምናልባት ኢየሱስ እሰከዚህም ድረስ ለተሰበሰበው ሕዝብ በሙሉ እየተናገረ ነበር።

አብዝቶ አፈራ
"በጣም ጥሩ አዝነራ ሰጠ"

ሰብሌን ለማከማቸት በቂ ስፍራ የለኝምና ምን ላደርግ እችላለሁ?
ይህ ጥያቄ የሚያንጸባርቀው ሰውየው ምን ማድረግ እንዳለበት በውስጡ ያስብ የነበረውን ነው። "ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም፣ ምክንያቱም ሰብሌን ሁሉ የማከማችበት በቂ ስፍራ የለኝም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ጎተራ
ገበሬዎች የሰበሰቡትን አዝመራ የሚያከማቹበት

ንብረት
ሀብት

ነፍሴን እንዲህ እላታለሁ፣ "ነፍሴ ሆይ፣ ለአመታት የሚሆነ... አለሽ። እረፊ...ደስ ይበልሽ።" ለራሴ እንዲህ እላለሁ፣ 'ለአመታት የሚበቃ...አለኝ። እርፍ ልበል... ደስ ይበለኝ።'" ወይም "ለራሴ እንዲህ እላለሁ ለአመታት የሚበቃ አለኝ... ስለዚህ ማረፍ እችላለሁ...ደስ ይበለኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/የነገሩን ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 12:20

አያያዥ ሃሳብ:
ኢየሱስ በምሳሌ ማስተማሩን ሲጨርስ እግዚአብሔር እንዴት ለባለጸጋው ሰው ምላሽ እንደጠቀሰ ይጠቅሳል።

ዛሬ ምሽት ነፍስህ ከአንተ ትፈለጋለች
"ነፍስ" የአንድን ሰው ሕይወት ያመለክታል። "ዛሬ ምሽት ትሞታለህ" ወይም "ዛሬ ምሽት ነፍስህን ከአንተ እወስዳታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ያከማቸሃቸው ነገሮች ለማን ይሆናሉ?
"አንተ ያከማቸኸው ለማን ይሆናል?" ወይም "አንተ የሰበሰብከው ለማን ይሆናል?" እግዚአብሔር ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት ሰውየው የሰበሰባቸው ነገሮች የእርሱ እንደማይሆኑ እንዲረዳ ለማድረግ ነው። "አንተ የሰበሰብካቸው ነገሮች የሌላ ሰው ይሆናሉ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ሀብት መሰብሰብ
"ዋጋ ያላቸውን ነገሮች ማከማቸት"

በእግዚአብሔር ዘንድ ባለጸጋ ያልሆነ
ጊዜውን እና ሃብቱን እግዚአብሔር ዋጋ ለሚሰጣቸው ነገሮች አልተጠቀመበትም

Luke 12:22

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢየሱስ በተሰበሰበው ሕዝብ ፊት ደቀ መዛሙርቱን ማስተማሩን ቀጠለ።

ስለዚህም
"በዚህም ምክንያት" ወይም "ይህ ታሪክ ከሚያስተምረው የተነሳ"

እኔ እንዲህ እላችኋለሁ
"እኔ አስፋላጊ የሆነ ነገር ልነግራችሁ እፈልጋለሁ" ወይም "ይህንን የምነግራችሁን ነገር በጥንቃቄ ልትሰሙ ይገባል"

ስለ ሕይወታችሁ ምን እንደምትመገቡ
"ስለ ሕይወታችሁ እና ስለምትበሉት" ወይም "ለሰውነታችሁ ስለምትለብሱት ልብስ"

ሕይወት ከመብል ስለሚበልጥ
ይህ በአጠቃላይ ስለ እሴት የሚነገር ሀሳብ ነው። "ሕይወት ከምትመገቡት ምግብ ይልቅ ይበልጥ ጠቃሚ ነው"

ሰውነት ከልብስ ይበልጣል
"ሰውነታችሁ ከምትለብሱት ልብስ ይልቅ ይበልጥ ጠቃሚ ነው"

Luke 12:27

ሊሊ አበቦች እንዴት እንደሚያድጉ ተመልከቱ
"አበቦች እንዴት እንደሚያድጉ አስተውሉ"

ሊሊ አበቦች
ሊሊ አበቦች በሜዳ የሚያድጉ ውብ ተክሎች ናቸው። በቋንቋችሁ እነዚህን የአበባ አይነቶች የምትገልጹበት መንገድ ከሌለ እነዚህን አበቦች የሚመስሉ የሌሎችን አበቦች ስያሜ መጠቀም ትችላላችሁ ወይም "አበቦች" ብላችሁ መተርጎም ትችላላችሁ። (የማይታወቁትን መተረጎም የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ አይፈትሉም
ክርን ወይም ፈትልን ለልብስነት ማዘጋጀት "መፍተል" ይባላል። ይህንን ይበልጥ ግልጽ ማድረግ ሊያስፈልግ ይችላል። "እነርሱ ልብስ ለማበጀት አይፈትሉም" ወይም "እነርሱ የስፍ ክር አያዘጋጁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰሎሞን በክብሩ ሁሉ
"ታላቅ ሀብት የነበረው፣ ሰሎሞን" ወይም "ውብ ልብሶችን የለበሰው፣ ሰሎሞን"

Luke 12:29

ስለምትበሉት እና ስለምትተጡት አትጨነቁ
"ምን እንበላለን ምን እንጠጣለን ብላችሁ አትጨነቁ" ወይም "ብዙ ስለ መብላት እና መጠጣት አትጨነቁ

የዓለም ሕዝብ በሙሉ
እዚህ ስፍራ "ሕዝብ/አገር" የሚለው የሚያመለክተው "የማያምኑትን" ነው። "የሌሎች አገራት ሰዎች ሁሉ" ወይም "በዓለም የሚገኙ የማያምኑ ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የእናንተ አባት/አባታችሁ
ይህ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ዋና ማዕረግ ነው።(ልጅ እና አባት የሚሉትን መተረረጎም የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 12:31

የእርሱን መንግሥት ፈልጉ
x

Luke 12:33

ለድሆች ስጡ
እነርሱ የተቀበሉትን መግለጹ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። "ከሸያጭ ካገኛችሁት ለደሆች ስጡ" (ኢሊፕሲስ- የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

ለራሳችሁ በሰማያት ...ለራሳችሁ የገንዘብ ቦርሳ/ከረጢት አዘጋጁ
በሰማያት ከረጢት/የገንዘብ ቦርሳ እና ሀብት የሚሉት ተመሳሳይ ነገሮች ናቸው። እነዚህ ሁለቱም ነገሮች በሰማያት የእግዚአብሔርን በረከት ይወክላሉ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለራሳችሁ አዘጋጁ
ይህ ለድሆች በመስጠት የሚገኝ ነው። "በዚህ መንገድ ለራሳችሁ በሰማይ ታዘጋጃላችሁ"

የማይደበዝዘውን ግዙ
"ቀዳዳ የማይኖረው/የማይቀደድ የገንዘብ ቦርሳ/ ከረጢት"

ጊዜ የማያልፍበት/የማያረጅ
"የማይጠፋ" ወይም "እየመነመነ/ እያደር እያነሰ የማይሄድ"

የትኛውም ሌባ የማይቀርበው
"ሌቦች የማይደርሱበት"

የቱም ብል የማያጠፋው
"ብል የማይበላው"

ብል
"ብል" ጨርቅን እየቀደደ የሚበላ ትንሽ ነፍሳት ነው። ምናልባት እንደ ጉንዳን ወይም ምስጥ የመሰሉ ሌሎች ነፍሳትን መጠቀም ሊያስፈልጋችሁ ይችላል።

ሃብታችሁ ባለበት፣ ልባችሁ በዚያ ይሆናል
"ልባችሁ ሃብታችሁ በተጠራቀመበት በዚያ ላይ ያተኩራል"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ልባችሁ
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚያመለክተው የሰውን አሳተሳሰብ ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 12:35

አጠቃላይ መረጃ:
ኢየሱስ ግብረገባዊ ምሳሌ መናገር ጀመረ። (ግብረገባዊ ምሳሌ የሚለውን ይመልከቱ)

ረጅም ልብሳችሁን በቀበቶአችሁ ታጥቃችሁ
ሰዎች ረጅም ልብስ ይለብሱ ነበር። በሚሰሩበት ወቅት እንዳያስቸግራቸው በቀበትዋቸው ያሥራሉ። "ልብሳችሁን በአጭር ታጥቃችሁ ለማገልገል ተዘጋጁ" ወይም "ለብሳችሁ ለማገልገል ተዘጋጁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

መብራታችሁ የበራ ይሁን
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "መብራታችሁ ይብራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ጌታቸውን እንደሚጠብቁ ሰዎች ሁኑ
ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን አገልጋዮች የጌታቸውን መመለስ በሚጠባበቁበት መንገድ የእርሱን መመለስ እንዲጠብቁ ያዛቸዋል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 12:37

የተባረኩ ናቸው
"እንዴት ለእነርሱ መልካም ይሆናል"

ጌታቸው ሲመጣ እርሱን ሲጠብቁት የሚያገኛቸው
"እርሱ በሚመለስበት ጊዜ ጌታቸውን ሲጠበቁት የሚያገኛቸው" ወይም "ጌታቸው በሚመለስበት ጊዜ ዝግጁ የሆኑ"

እነርሱ ይቀመጣሉ፣ እርሱ ታጥቆ ቆሞ ያገለግላቸዋል
አገላጋዮቹ ታማኞች ስለነበሩ እና ጌታቸውን ለማገልገል ዝግጁ ስለነበሩ፣ አሁን ጌታቸው እነርሱን በማገልጋል ዋጋቸውን ይከፍላቸዋል/ይሸልማቸዋል።

በምሽቱ ሁለተኛ ክፍለ ጊዜ
ሁለተኛው ሰዓት ከምሽቱ ሶስት ሰዓት እስከ እኩለ ሌሊት ያለው ነው። "በውድቅት ሌሊት" ወይም "ከእኩለ ለሊት አስቀድሞ"

ወይም ደግሞ በሶስተኛው ሰዓት እንኳን
ሶስተኛው ሰዓት ከእኩለሌሊት እስከ ሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ያለው ነው። "ወይም ሌሊት ዘግይቶ ቢመጣም እንኳን"

Luke 12:39

ሰዓቱን አውቆ ቢሆን
"መቼ እንደሆነ ቢያውቅ"

ቤቱ እንዲቆፈር ባልተወ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሌባ ቆፍሮ ወደ ቤቱ እንዲገባ ባልተወም/ዝም ብሎ ባላየ/ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ የሚመጣበትን ሰዓት ስለማታውቁ
በሰው ልጅ እና በሌባ መሃል ያለው ብቸኛው መመሳሰል የትኛቸውም መቼ እንደሚመጡ ሰዎች አለማወቃቸው በመሆኑ ሁሌም ዝግጁ መሆን ይገባቸዋል።

ሰዓቲቱ መቼ እንደሆነች አታውቁም
"ምን ጊዜ እንደሆነ ጊዜውን አታውቁም"

መች የሰው ልጅ እንደሚመጣ
ኢየሱስ ስለ ራሱ እየተናገረ ነው። "እኔ፣ የሰው ልጅ መቼ እንደምመጣ"

Luke 12:41

አያያዥ ሃሳብ:
በቁጥር 42 ኢየሱስ ሌላ ግብረገባዊ ምሳሌ መናገር ይጀምራል።

አጠቃላይ መረጃ:
በቁጥር 41፣ ጴጥሮስ ስለ ቀደመው ምሳሌ ሲጠይቅ በታሪኩ ፍሰት መቆሚያ ይፈጠራል።

እንዲህ ከሆነ ትክክለኛውን ጊዜ...ማን ነው?
ኢየሱስ የጴጥሮስን ጥያቄ በተዘዋዋሪ ለመመለስ ጥያቄ ይጠቀማል። ታማኝ አስተዳዳሪ መሆን የሚፈልጉ ምሳሌው ስለ እነርሱ እንደሆነ እንዲረዱ ይጠብቃል ። "ትክክለኛው ጊዜ...ለሆኑ ሁሉ ይህን ተናግሪያለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ብልህ እና ታማኝ አስተዳዳሪ
ኢየሱስ አገልጋዮች እንዴት በታማኝነት የጌታቸውን መመለስ መጠበቅ እንዳለባቸው ሌላ ምሳሌ ይናገራል። (ግብረገባዊ ምሳሌዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 12:45

ያ አገልጋይ
ይህ የሚያመለክተው ጌታው በሌሎች አገልጋዮች ላይ ሀላፊ ያደረገውን አገላጋይ ነው

በልቡ እንዲህ ይላል
እዚህ ስፍራ "ልብ" ለአንድ ሰው አስተሳሰብ ወይም ውስጣዊ ማንነት ሜቶኖሚ/ ነው። "በውስጡ እንዲህ ብሎ ቢያስብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የጌታዬ መመለስ ይዘገያል
"አለቃዬ በቶሎ አይመለስም"

ወንድ እና ሴቶች አገልጋዮች
እዚህ ስፍራ "ወንድ እና ሴቶች አገልጋዮች" ተብለው የተተረጎሙት ቃላት "ወንድ ልጆች" እና "ልጃገረዶች" ተብለው ተተርጉመዋል። ይህ አገልጋዮቹ ወጣቶች እንደነበሩ ወይም በጌታቸው ዘንድ ተወዳጆች እንደነበሩ ሊያመለክት ይችላል።

እርሱ ባልጠበቃት ቀን፣ ደግሞም እርሱ በማያውቃት ሰዓት
"ቀን" እና "ሰዓት" ከእስከ ያለውን ማናቸውንም ጊዜ ሲያመለክት፣ "በስተቀር" እና "ያውቃል" የሚሉት ቃላትም ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ ስለዚህም እዚህ ስፍራ ሁለቱ ሀረጎች፣ ለአገላጋዮቹ የጌታቸው መምጣት ፍጹም በድንገት እንደሚሆን ትኩረት ለመስጠት በንጽጽር የቀረቡ ናቸው። ሆኖም፣ የእናተ ቋንቋ "ማወቅ" እና "መጠባበቅ" ወይም "ቀን" እና "ሰዓት" ለሚሉት ቃላት ልዩነት የሌለው ካልሆነ በስተቀር ሀረጋቱ በአንድነት ተጣምረው መቅረብ የለባቸውም። "አገልያዩ እርሱን በማይጠባበቅበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ከጽንፍ ጽንፍ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ይቆራርጠዋል ስፍራውንም ታማኝ ካልሆኑት ጋር ያደርጋል
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ ጌታው በአገልጋዩ ላይ የሚያደርሰው ከባድ ቅጣት ተጋኖ የተገለጸበት ነው፣ ወይም 2) ይህ አገልጋዩ የሚደርስበት

የቅጣት ሁኔታ የሚገደል እና የሚቀበር መሆኑን ይገልጻል። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉት ይመልከቱ)

Luke 12:47

አያያዥ ሀሳብ፡
x

Luke 12:49

አያያዥ ሀሳብ፡
ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ማስተማር ቀጥሏል።

በምድር ላይ እሳት ለማድረግ መጥቻለሁ
"በምድር ላይ እሳት ለመጣል መጥቻለሁ" ወይም "በምድር ላይ እሳት ለመለኮስ መጥቻለሁ።" ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ኢየሱስ የመጣው ሰዎችን ለመዳኘት ነው ወይም 2) ኢየሱስ የመጣው ሰዎችን ለማንጻት ነው፣ ወይም 3) ኢየሱስ የመጣው በሰዎች መሃል ልዩነትን ለማምጣት ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከነደደ ምን እፈልጋለሁ
ይህ አጋኖ የሚያጎላው፣ እርሱ ምን ያህል ይህ ሊሆን እንደፈለገ ነው። "አስቀድሞ ነድዶ ቢሆን በጣም በወደድኩ" ወይም "አስቀድሞ ጀምሮ ቢሆን ኖሮ እወድ ነበር" (ቃለ አጋኖዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የምጠመቃት ጥምቀት አለች
እዚህ ስፍራ "ጥምቀት" የሚያመለክተው ኢየሱስ ሊቀበል ያለውን መከራ ነው። በጥምቀት ውሃ የሰውን ሁለመና እንደሚሸፍን፣ መከራ ኢየሱስን ያጥለቀልቀዋል። "በክፍተኛ የመከራ ጥምቀት ውስጥ ማለፍ ይኖርብኛል" ወይም "ሰው ሲጠመቅ በውሃ ውስጥ እንደሚሸፈን በመከራ መጥለቅለቅ ይኖርብኛል" (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ነገር ግን
"ነገር ግን" የሚለው ቃል የዋለው እርሱ በመከራ ውስጥ ከማለፉ አስቀድሞ በምድር ላይ እሳት ሊጥል አለመቻሉን ለማሳየት ነው።

እስኪፈጸም ድረስ እንዴት እጨነቃለሁ
ይህ አጋኖ የሚያጎላው እርሱ ምን ያህል ተጨንቆ እንደነበረ ነው። "እጅግ ተጨንቄያለሁ፣ ይህን የመከራ ጥምቀት እስክፈጽም ድረስ ይኸው ይሆናል" (ቃለ አጋኖዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 12:51

በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ ይመስላችኋልን? አይደለም፣ እላችኋለሁ፣ ይልቁንም መከፋፈልን ለማምጣት እንጂ
ኢየሱስ የተሳሳተ መረዳታቸውን እንዲያርሙ እንደሚያደርግ ሊያሳውቃቸው ጥያቄ ያነሳል። በሁለተኛው ዐረፍተ ነገር የተተወውን "እኔ የመጣሁት" የሚሉ ቃላት መጨመር ሊያስፈልጋችሁ ይችላል። "በምድር ላይ ሰላም ለማምጣት የመጣሁ ይመስላችኋል፣ ነገር ግን እላችኋለሁ ለዚህ አልመጣሁም። ይልቁንም፣ መለያየትን ለማምጣት መጥቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

መለያየት
"ጠላትነት" ወይም "አለመስማማት"

በአንድ ቤት ውስጥ የተከፋፈሉ አምስት ይኖራሉ
ይህ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ እንኳን ለሚኖረው የመከፋፈል አይነት ምሳሌ ነው

በአንድ ቤት ውስጥ አምስት ይኖራሉ
ይህ ሰዎችን እንደሚያመለክት መግለጽ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። "በአንድ ቤት ውስጥ አምስት ሰዎች ይኖራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

አንዱ በአንዱ ላይ....አንዱ በአንዱ ላይ....አንዱ በአንዱ ላይ....አንዱ በአንዱ ላይ....አንዱ በአንዱ ላይ....አንዱ በአንዱ ላይ....አንዱ በአንዱ ላይ....አንዱ በአንዱ ላይ....
"ይቀዋወማል...ይቀዋወማል...ይቀዋወማል...ይቀዋወማል... ይቀዋወማል...ይቀዋወማል..ይቀዋወማል...ይቀዋወማል"

Luke 12:54

አጠቃላይ መረጃ፡
ኢየሱስ ለተሰበሰበው ሕዝብ መናገር ይጀምራል።

ደመና ሲወጣ ስትመለከቱ...ይሆናል
ይህ ሁኔታ በተለምዶ በእሥራኤል ዝናብ ይመጣል ማለት ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ዝናብ እመጣ ነው
"ዝናብ ይመጣል" ወይም "ሊዘንብ ነው"

የደቡብ ነፋስ ሲነፍስ
ይህ ሁኔታ በተለምዶ በእሥራኤል ሞቃታማ የአየር ንብረት ይመጣል ማለት ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ምድር እና ሰማያት
"ምድር እና ሰማይ"

ታዲያ እንዴት የአሁኑን ጊዜ መረዳት አትችሉም?
ኢየሱስ ይህንን ጥያቄ ያነሳው የተሰበሰበውን ሕዝብ ለመገሰጽ ነው። ኢየሱስ ይህን ጥያቄ የተጠቀመው እነርሱን ለማሳመን ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ወቅቱን መተረጎም መቻል ይኖርባችኋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 12:57

ራሳችሁ ለምን ትክክል የሆነውን አትፈርዱም?
ኢየሱስ ጥያቄውን ያነሳው የተሰበሰበውን ሕዝብ ለመገሰጽ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "እናንተ ራሳችሁ ትክክለኛ የሆነውን መለየት ይኖርባችኋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እራሳችሁ
"በራሳችሁ ተነሳሽነት"

በምትሄዱበት ጊዜ...የመጨረሻዋን ገንዘብ
ኢየሱስ የተሰበሰበውን ሕዝብ ለማስተማር መላምታዊ ሁኔታ ይጠቀማል። የእርሱ ትምህርት፣ ማቃለል የሚችሉትን ነገር ዳኛ ፊት ሳይቀርቡ ችግራቸውን እንዲያቃልሉ ማስተማር ነው። ይህን ግልጽ ለማድረግ መሆን የማይገባውን መሆን እንደማይገባው በግለጽ ደግሞ መጻፍ ይቻላል። "ማድረግ የሚገባችሁ ከሆነ...የመጨረሻዋን ገንዘብ

በምትሄድበት ጊዜ
x

ምዕራፍ **13**

1 በዚያን ጊዜ አንዳንድ ሰዎች ወደ ኢየሱስ መጥተው፣ የገሊላ ሰዎች ለእግዚአብሔር መሥዋዕት በሚያቀርቡበት ጊዜ፣ ጲላጦስ ስለ ገደላቸውና ደማቸውንም
ከመሥዋዕታቸው ጋር ስላደባለቀባቸው ሰዎች ነገሩት። **2** ኢየሱስ እንዲህ ብሎ መለሰላቸው፤ "እነዚያ የገሊላ ሰዎች ይህ ሁሉ የደረሰባቸው በዙሪያቸው ካሉት
ከሌሎች የገሊላ ሰዎች ይልቅ ኀጢአተኞች ስለ ነበሩ ነውን? **3** አይደለም፤ እናንተም ንስሓ ካልገባችሁ እንዲሁ ትጠፋላችሁ ። **4** ወይም በሰሊሆም ግንብ
ተደርምሶባቸው የሞቱ ዐሥራ ስምንት ሰዎች በኢየሩሳሌም ዙሪያ ካሉ ሰዎች ይልቅ ኃጢአተኞች ስለ ነበሩ ነውን? **5** አይደለም፤ ሁላችሁም ንስሓ ባትገቡ
ትጠፋላችሁ።" **6** ኢየሱስ ይህን ምሳሌ ተናገረ፤ "አንድ ሰው በወይን አትክልት ቦታው የበለስ ዛፍ ተከለ፤ ፍሬዋንም ፈልጎ ወደ በለሲቱ መጣ፤ ነገር ግን ምንም
ፍሬ አላገኘባትም። **7** እርሱም ለአትክልተኛው እንዲህ አለው፤ "ተመልከት! ሦስት ዓመት ሙሉ ፍሬ ፈልጌ ወደ በለሲቱ መጣሁ፤ ግን ምንም ፍሬ
አላገኘሁባትም። ቍረጣት ስለምን መሬትን ታበላሻለች።" **8** አትክልተኛውም መልሰና እንዲህ አለ፣ "ለዚህ ዓመት ተዋት ዙሪያዋን ኮትኩቼ ማዳበሪያ አደርግላትና
9 በሚቀጥለው ዓመት ታፈራ ይሆናል፤ ባታፈራ ግን ቍረጣት።" **10** ኢየሱስም በሰንበት ቀን በአንዱ ምኵራብ እያስተማረ ነበር። **11** ለዐሥራ ስምንት ዓመት
ርኩስ መንፈስ ያጐበጣት አንዲት ሴት በዚያ ነበረች። እርስዋም ከመጕበጧ የተነሣ ቀና ብላ መቆም አትችልም ነበር። **12** ኢየሱስም ባያት ጊዜ ጠራትና፣
"ተነሺና ከበሽታሽ ተፈወሺ" አላት። **13** በእጁ ዳሰሳት፣ ወዲያውኑም ቀጥ ብላ ቆመች፤ እግዚአብሔርንም **14** አመሰገነች። የምኵራቡ አለቃ ግን በሰንበት
በመፈወሷ ተቈጣና ለሕዝቡ እንዲህ አለ፤ "ከሳምንቱ ቀኖች ሥራ የሚሠራባቸው ስድስት ቀኖች አሉ፤ ሄዳችሁ በእነዚያ ቀኖች ተፈወሱ እንጂ በሰንበት ቀን
አይሆንም አላቸው።" **15** ጌታ እንዲህ ብሎ መለሰለት፤ "እናንት ግብዞች! በሰንበት ቀን ከእናንተ መካከል በሬውን ወይም አህያውን ከታሰረበት በረት አወጥቶ
ውኃ የማያጠጣው ማን ነው? **16** ይህች የአብርሃም ዘር የሆነች ለዐሥራ ስምንት ዓመት በሰይጣን ታስራ የኖረች ሴት በሰንበት ቀን ከበሽታዋ መፈታት
አይገባትምን?" **17** ኢየሱስ እነዚህን ነገሮች በተናገረ ጊዜ፣ ይቃወሙት የነበሩ ሁሉ አፈሩ፣ ሕዝቡ ግን በተደረገው ድንቅ ነገር ሁሉ ደስ አላቸው። **18** ከዚያም
ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ "የእግዚአብሔር መንግሥት በምን ትመሰላለች? ከምንስ ጋር አነጻጽራታለሁ? **19** አንድ ሰው የሰናፍጭ ዘር በአትክልት ቦታው እንደተከላት
ዛፍዋም አድጋ፣ ወፎች በቅርንጫፎችዋ ላይ ጎጆአቸውን ሠርተው ማረፊያ ያደረጉባት ዛፍ ትመሰላለች።" **20** እንደ ገናም እንዲህ አለ፤ "የእግዚአብሔርን
መንግሥት በምን ላነጻጽራት እችላለሁ? **21** የእግዚአብሔር መንግሥት አንዲት ሴት ሊጡን ሁሉ እስኪያቦካ ድረስ በሶሦስት መስፈሪያ ዱቄት ውስጥ
የሰወረችውን እርሾ ትመስላለች።" **22** ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ ሳለ በየከተማውና በየገጠሩ እያስተማረ ያልፍ ነበር። **23** አንድ ሰው፣ "ጌታ ሆይ፤
የሚድኑት ጥቂት ሰዎች ብቻ ናቸውን?" ብሎ ጠየቀው። ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፤ **24** "በጠባብዋ በር ለመግባት ታገሉ፣ ብዙዎች በዚህች በር ሊገቡ ይሞክራሉ
ነገር ግን ሊገቡባት አይችሉም። **25** የቤቱ ጌታ በሩን ይዘጋል፤ እናንተም በደጅ ቆማችሁ፤ አንኳኩታችሁ፣ 'ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤ እንድንገባ ክፈትልን' ትላላችሁ።
እርሱ መልሶ 'ከየት ነው የመጣችሁት? እኔ አላውቃችሁም' ይላችኋል። **26** ከዚያም እናንተ፣ 'ጌታ ሆይ፣ ከአንተ ጋር አብረን በልተናል፤ አብረንም ጠጥተናል፤
በአደባባዮቻችንም አስተምረሃል' ትላላችሁ። **27** እርሱ ግን እንዲህ ይመልሳል፤ 'ከየት እንደ መጣችሁ አላውቅም ፤ እናንተ ዐመፀኞች ከእኔ ራቁ እላችኋለሁ።'
28 በእግዚአብሔር መንግሥት አብርሃምን፤ይስሐቅን፤ ያዕቆብን፤ ነቢያትንም በምታዩበት ጊዜ፤ እናንተ ግን በውጪ ትጣላላችሁ ከዚያም ልቅሶና ጥርስ
ማፋጨት ይሆናል። **29** ብዙ ሰዎች ከምሥራቅና ከምዕራብ፤ ከሰሜንና ከደቡብ መጥተው በእግዚአብሔር መንግሥት በማዕድ ተቀምጠው ይደሰታሉ። **30**
ይህንም እወቁ ኋለኞች ፊተኞች፤ ፊተኞችም ኋለኞች ይሆናሉ።" **31** ከዚያ በኋላ፣ አንዳንድ ፈሪሳውያን ወደ እርሱ ቀርበው፣ "ሄሮድስ ሊገድልህ ይፈልጋልና ከዚህ
ወጥተህ ወደ ሌላ ስፍራ ሂድ" አሉት። **32** ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፤ "ሂዱና ለዚያ ቀበሮ፣ 'ዛሬና ነገ አጋንንትን አወጣለሁ፤ በሽታኞችን እፈውሳለሁ፤ በሦስተኛም
ቀን ሥራዬን እፈጽማለሁ' ይላል በሉት" **33** ይሁን እንጂ ዛሬና ነገ ከዚያም በኋላ ነቢይ ከኢየሩሳሌም በቀር በሌላ ስፍራ መሞት ስለሌበት ወደ ኢየሩሳሌም
መንገዴን መቀጠል አለብኝ" አለ። **34** አንቺ ኢየሩሳሌም! ኢየሩሳሌም ሆይ! ነቢያትን የምትገድዪ፤ መልእክተኞችሽንም የምትወግሪ ነሽ። ዶሮ ጫጩቶችዋን
ከክንፎችዋ ሥር እንደምትሰበስብ እኔም ልጆችሽን ለመሰብሰብ ስንት ጊዜ ፈለግሁ። እናንተ ግን አልፈለጋችሁም። **35** እነሆ፣ ቤታችሁ ባዶ ሆኖ ቀርቶአል።
እላችኋለሁ፣ እናንተ 'በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የተባረከ ነው' እስከምትሉ ድረስ አታዩኝም።"

Luke 13:1

አያያዥ ሀሳብ፡
ኢየሱስ እስከ አሁን ድረስ ለተሰበሰበው ሕዝብ እየተናገረ ነው። ከተሰበሰበው ህስብ መሃል አንዳንዱ እርሱን ስጠይቀው እርሱም ምላሽ መስጠት ጀመረ። ይህ በሉቃስ 12፡1 ላይ የጀመረውን ታሪክ ይቀጥላል።

በዚያን ጊዜ
ይህ ሀረግ፣ ኢየሱስ የተሰበሰበውን ሕዝብ በሚያስተምርበት ወቅት እሰከ ምዕራፍ 12 መጨረሻ ድረስ ያለውን ትዕይንት ያያይዛል።

ጲላጦስ መስዋዕታቸውን ከደም ጋር የቀላቀላባቸው
እዚህ ስፍራ "ደም" የሚያመለክተው የገሊላ ሰዎችን ሞት ነው። ምናልባት እነርሱ የተገደሉት መስዋዕታቸውን በሚያቀርቡበት ጊዜ ሊሆን ይችላል። በዩዲቢ ውስጥ እንደቀረበው ብልጽ ሊደረግ ይችላል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ጲላጦስ መስዋዕታቸውን ከደም ጋር የቀላቀላባቸው
ምናልባት ጲላጦስ ህዝቡን የገደለው ራሱ ሳይሆን ወታደሮችን ልኮ ሊሆን ይችላል። "እንስሳትን መስዋዕት በማቅረብ ላይ እያሉ የጲላጦስ ወታደሮች የገደሏቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ የገሊላ ሰዎች በ...መንገድ ይበልጥ ኃጢአተኞች ስለሆኑ ይመስላችኋል? አይደለም፣ እኔ እላችኋለሁ
"እነዚህ ገሊላውያን ይበልጥ በ...መንገድ ኃጢአተኞች ነበሩን? አይደለም፣ እኔ እላችኋለሁ" ወይም "ይህ እነዚህ ገሊላውያን ይበልጥ በ...መንገድ ኃጢአተኞች እንደሆኑ ያረጋግጣልን? አይደለም፣ እኔ እላችኋለሁ" ኢየሱስ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት የህዝቡን መረዳት ለመገዳደር ነው። "እናንተ እነዚህ ገሊላውያን በ...መንገድ ይበልጥ ኃጢአተኞች እንደሆኑ ታስባላችሁ ነገር ግን አልነበሩም" ወይም "እነዚህ ገሊላውያን በ...መንገድ ይበልጥ ኃጢአተኞች እንደሆኑ አታስቡ" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

አይደለም፣ እኔ እላችኋለሁ
እዚህ ስፍራ "እኔ እላችኋለሁ" የሚለው ትኩረት የሚሰጠው "አይደለም" የሚለውን ነው። "በእርግጥ እነርሱ ይበልጥ ኃጢአተኞች አልነበሩም" ወይም "መከራ ስለደረሰባቸው ይህ ይበልጥ ኃጢአተኛ መሆናቸው ያረጋግጣል ብላችሁ ማሰባችሁ ስህተት ነው"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሁላችሁም በተመሳሳይ መንገድ ትጠፋላችሁ
"ሁላችሁም ደግሞ ትሞታላችሁ::" "በተመሳሳይ መንገድ" የሚለው ሀረግ ተመሳሳይ ነገር ይደርስባቸዋል ማለት እንጂ በተመሳሳይ መልክ ይሞታሉ ማለት አይደለም::

መጥፋት
መሞት

Luke 13:4

ወይም እነርሱ
ይህ ኢየሱስ መከራ ስለ ደረሰባቸው ሰዎች የሰጠው ሁለተኛ ምሳሌ ነው:: "ወይም እነዚያን ተመልከቱ" ወይም "ስለ እነዚያ አስቡ"

አሥራ ስምንት ሰዎች
"18 ሰዎች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰሊሆም
ይህ በኢየሩሳሌም ውስጥ የሚገኝ ስፍራ ስም ነው:: (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በኢየሩሳሌም...እነርሱ የከፉ ኃጢአተኞች ነበሩ ብላችሁ ታስባላችሁ? እኔ እላችኋለሁ፣ አይደለም
"ይህ እነርሱ በኢየሩሳሌም... ይበልጥ ኃጢአተኞች እንደሆኑ ያረጋግጣልን? እኔ እላችኋለሁ፣ አይደለም::" ኢየሱስ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት የህዝቡን መረዳት ለመገዳደር ነው:: "እነርሱ በኢየሩሳሌም...ይበልጥ ኃጢአተኛ እንደሆኑ ታስባላችሁ፣ እኔ ግን አልነበሩም እላለሁ" ወይም "እነርሱ በኢየሩሳሌም... ይበልጥ ኃጢአተኞች ነበሩ ብላችሁ ማሰብ የለባችሁም እላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ የከፉ ኃጢአተኞች ነበሩ
x

Luke 13:6

አጠቃላይ መረጃ:
ኢየሱስ ለተሰበሰበው ሕዝብ የመጨረሻ ሃሳቡን ለማብራራት ግብረገባዊ ምሳሌ መናገር ጀመረ፣ "ነገር ግን ንስሃ ባትገቡ፣ እናንተ ሁላችሁም ደግሞ ትጠፋላችሁ::" (ግብረገባዊ ምሳሌ የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ሰው በወይን ተክሉ ስፍራ የበለስ ዛፍ ነበረው
የወይን ተክሉ ባለቤት በወይን እርሻው ውስጥ ሌላ ሰው የበለስ ዛፍ ተከለበት::

ለምን መሬቱን እንድታጠፋ ትፈቅድላታለህ?
ሰውየው ጥያቄውን የተጠቀመበት ዛፏ ጥቅም እንደማትሰጥ እና አትክልተኛው ሊቆርጣት እንደሚገባ ትኩረት ለመስጠት ነው:: "መሬቱን እንድታበላሽ አትፍቀድ/ መሬቱን ታበላሽ ዘንድ አትተዋት::" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 13:8

አያያዥ ሀሳብ:
ኢየሱስ ግብረገባዊ ምሳሌውን መናገሩን ጨረሰ:: ይህ በሉቃስ 12:1 የተጀመረው ታሪክ መጨረሻ ነው::

ተዋት
"በዛፊቱ ላይ አንዳች አታድርግ" ወይም "አትቁረጣት"

ፍግ አድርግላት
"በአፈሩ ላይ ማዳበሪያ ጨምር::" ማዳበሪያ/ፍግ የእንስሳ ኩበት ነው:: አፈሩ ለተክሎች እና ለዛፍ መልካም እንዲሆን ሰዎች ይህን በመሬት ላይ ይጨምራሉ:: "በላዩ ማዳበሪያ መጨመር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በቀጣዩ አመት ፍሬ ከሰጠች መልካም
x

Luke 13:10

አጠቃላይ መረጃ:
እነዚህ ቁጥሮች ለዚህኛው የታሪኩ ክፍል መቼት እና ወደ ታሪኩ ለምትገባው ሸባ ሴት የመረጃ ዳራ ይሰጣሉ:: (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

አሁን
ጸሐፊው ይህንን ቃል የተጠቀመበት የአዱሱን ትዕይንት ጅማሬ ለማመልከት ነው:: (የአዲስ ትዕይንት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰንበት
"በሰንበት ዕለት::" አንዳንድ ቋንቋዎች "ሰንበት" ይላሉ፤ ምክንያቱም የትኛው የተለየ የሰንበት ዕለት እንደነበር አናውቅም::

Luke 13:12

አንቺ ሴት፣ ከድካምሽ ተፈውሰሻል
"አንቺ ሴት፣ ከድካምሽ ተፈውሰሻል::" ይህ "አንቺ ሴት፣ ከድካምሽ ፈውሼሻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው በአድራጊ ግስ ሊገለጽ ይችላል:: (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አንቺ ሴት፣ ከድካምሽ ተፈውሰሻል
ይህን በመናገር፣ ኢየሱስ እርሷን ፈወሳት:: ይህ ነገር እንዲሆን ማድረጉን፣ ወይም ማዘዙን በሚያሳይ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል:: "አንቺ ሴት፣ አሁን እኔ ከድካምሽ ፈውሼሻለሁ" ወይም "አንቺ ሴት፣ ከድካምሽ ነጻ ሁኚ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (ሃሳቦች- ሌላ ጥቅሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እጁን በላይዋ ጫነ
"እርሱ ነካት"

እርሷ ቀጥ ብላ ቆመች
ይህ አድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል:: "ቀና ብላ ቆመች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው:: (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰንበት ዕለት
"በአንድ የሰንበት ዕለት::" አንዳንድ ቋንቋዎች "በሰንበት" ይላሉ፤ ምክንያቱም የትኛው የተለየ የሰንበት ዕለት እንደ ነበር አናውቅም::

Luke 13:15

ጌታ ለእርሱ መልስ ሰጠው
"ጌታ ለሸንጎ መሪው ምላሽ ሰጠ"

ግብዞች
ኢየሱስ በቀጥታ ከምኩራብ መሪው ጋር ተናገረ፣ ነገርግን የብዙ ቁጥሩ ሌሎችንም የሃይማኖት መሪዎች ጭምር ያጠቃልላል:: ይህ ይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: "አንተ እና እንንተ የሃይማኖት መሪዎቻችሁ ግብዞች ናችሁ" (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእናንተ እያንዳንዱ በሬውን ወይም አህያውን ከማደሪያው ፈትቶ በሰንበት ሊያጠጣ ይወስደው የለምን?
ኢየሱስ ጥያቄውን የተጠቀመበት አስቀድሞ ስለሚያውቁት ነገር እንዲያስቡበት ለማድረግ ነው። "ከእናንተ እያንዳንዱ በሬውን ወይም አህያውን በሰንበት ከታሰረበት ፈትቶ ወደ ሚጠጣበት ስፍራ ይወስደዋል።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በሬ...አህያ
እነዚህ ሰዎች ውሃ በመስጠት የሚንከባከቧቸው እንስሳት ናቸው

በሰንበት ዕለት
x

Luke 13:17

እርሱ እነዚህን ነገሮች እየተናገረ ሳለ
"ኢየሱስ እነዚህን ነገሮች በሚናገርበት ጊዜ"

እርሱ ያደረጋቸው አስደናቂ ነገሮች
"ኢየሱስ ያደርጋቸው የነበሩ አስደናቂ ነገሮች"

Luke 13:18

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢየሱስ በምኩራብ ለነበሩ ሰዎች ግብረገባዊ ምሳሌ መናገር ጀመረ። (ግብረገባዊ ምሳሌ የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር መንግሥት ምን ትመስላለች...ከምንስ ጋር አወዳድራታለሁ?
ኢየሱስ ሁለትን ጥያቄዎች የተጠቀመባቸው ሊያስተምር ያለውን ነገር ለማስተዋወቅ ነው። "የእግዚአብሔር መንግሥት ምን እንደምትመስል እነግራችኋለሁ...ከምን ጋር ላነጻጽራት እችላለሁ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ከምን ጋር ላነጻጽራት እችላለሁ?
ይህ ከቀደመው ጥያቄ ጋር በመሰረቱ ተመሳሳይ ነው። አንዳንድ ቋንቋዎች ሁለቱንም ጥያቄዎች ሊጠቀሙ ይችላሉ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ አንዱን ጥያቄ ብቻ ይጠቀማሉ።(ትይዩ ንጽጽራዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ልክ እንደ ሰናፍጭ ፍሬ ናት
ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ከሰነፍጭ ጋር ያነጻጽራል። "የእግዚአብሔር መንግሥት የሰናፍጭን ፍሬ ትመስላለች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 13:20

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢየሱስ በምኩራብ ለነበሩ ሰዎች መናገሩን ጨረሰ። ይህ የዚህ ታሪክ ክፍል መጨረሻ ነው።

የእግዚአብሔርን መንግሥት ከምን ጋር ላነጻጽራት እችላለሁ?
ኢየሱስ ቀጥሎ ሊያስተምር ያለውን ለማስተዋወቅ ሌላ ጥያቄ ያነሳል። "ከእግዚአብሔር መንግሥት ጋር ላነጻጽር የምችለውን ሌላ ነገር እነግራችኋለሁ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ እርሾ ናት
ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት በዳቦ ሊጥ ውስጥ ከሚገኝ እርሾ ጋር ያነጻጽራል። "የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደ እርሾ ናት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ እርሾ
ብዙ ሊጥ ለማቡካት በጣም ትንሽ እርሾ ብቻ ያስፈልጋል። ይህ በዩዲቢ ውስጥ እንደሚገኘው ግልጽ ሊደረግ ይችላል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሦስት እጅ/ልኬት ዱቄት
አንድ እጅ/ልኬታ የሚባለው ወደ 13 ኪሎ ግራም የሚጠጋ በመሆኑ፣ይህ ብዙ መጠን ያለው ዱቄት ነው። የእናንተ ባህል ዱቄትን ለመለካት የሚጠቀምበትን መለኪያ መጠቀም ትችላላችሁ። "ብዙ መጠን ያለው ዱቄት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

Luke 13:22

አጠቃላይ መረጃ፡
ኢየሱስ ለጥያቄው ምላሽ የሰጠው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ስለ መግባት ዘይቤያዊ አገላለጽ በመጠቀም ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሚድኑ ጥቂት ሰዎች ብቻ ናቸውን?
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር የሚያድነው ጥቂት ሰዎችን ብቻ ነውን?" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በጠባቡ በር ለመግባት ታገሉ
"በጠባቡ በር ለመግባት ትጉ።" ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ስለ መግባት የሚናገረው፣ ወደ ቤት እንደሚያስገባ ትንሽ በር አድርጎ ነው። ኢየሱስ ለሰዎች ስብስብ እንደመናገሩ በዚህ ትእዛዝ ውስጥ "እናንተ" የሚለው ተውላጠ ስም ብዙ ቁጥር ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አንተ የሚለው ተውላተ ስም መልኮች የሚለውን ይመልከቱ)

ጠባቢቱ በር
በሩ ጠባብ መሆኑ የሚያመለክተው በውስጡ ማለፍ አስቸጋሪ መሆኑን ነው። ይህን ውስንነት በሚያሳይ መንገድ ተርጉሙት። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ብዙዎች ሊገቡባት ይፈልጋሉ፣ ነገር ግን ሊገቡ አይችሉም
ለመግባት ከባድ ከመሆኑ የተነሳ፣ መግባት እንደማይችሉ ተጠቁሟል። ቀጣዩ ሀረግ ከባድነቱን ያብራራል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 13:25

አጠቃላይ መረጃ፡
ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ስለ መግባት መናገሩን ቀጥሏል።

አንድ ጊዜ ባለቤቱ
"ባለቤቱ ከ...በኋላ"

የቤቱ ባለቤት
ይህ በቀደመው ቁጥር ላይ ጠባብ በር ያለውን ቤት ባለቤት ያመለክታል። ይህ እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔር መንግሥት ገዢ የሚያቀርብ ዘይቤ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ በውጭ ትቆማላችሁ/ትቀራላችሁ
ኢየሱስ ለተሰበሰበው ሕዝብ እየተናገረ ነበር። "እናንተ" የሚለው ተውላጠ ስም ብዙ ቁጥር ነው። እነርሱ በጠባቡ በር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንደማይገቡ እየተናገረ ነው። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)

በሩን ትደበድባላችሁ
"በሩን ትመታላችሁ።" ይህ የባለቤቱን ትኩረት ለማግኘት የሚደረግ ጥረት ነው።

ከዚህ ሂዱ
"ከእኔ ራቁ"

Luke 13:28

አያያዥ ሀሳብ፡
ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ስለ መግባት መናገሩን ቀጥሏል። ይህ የዚህ ንግግር መጨረሻ ነው።

ለቅሶ እና ጥርስ ማፋጨት
እነዚህ ድርጊቶች ታላቅ ጸጸትን እና ሀዘንን የሚያመለክቱ ትዕምርታዊ ድርጊቶች ናቸው። "ከታላቅ ጸጸታቸው የተነሳ የተከተለ ለቅሶ እና ጥርስ ማፋጨት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

በምትመለከቱበት ጊዜ
ኢየሱስ ለተሰበሰበው ሕዝብ ወደ ሰማዩ መንግስት እንደማይገቡ አድርጎ መናገሩን ቀጥሏል።

ነገር ግን ወደ ውጭ ትጣላላችሁ
"ነገር ግን እናንተ ራሳችሁ ወደ ውጭ ትጣላላችሁ።" ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ነገር ግን እግዚአብሔር ወደ ውጭ ይጥላችኋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ከምሥራቅ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን እና ደቡብ
ይህ ማለት "ከሁሉም አቅጣጫ።" ማለት ነው።

በእግዚአብሔር መንግሥት በማዕድ ይቀመጣሉ
የእግዚአብሔርን መንግሥት ደስታ እንደ ግብዣ መግለጽ የተለመደ ነበር። "በእግዚአብሔር መንግሥት ይጋበዛሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የመጀመሪያ ይሆናሉ...የመጨረሻ ይሆናሉ
የመጀመሪያ መሆን የሚወክለው አስፈላጊ ወይም የተከበረ መሆንን ነው። "እጅግ አስፈላጊ ይሆናሉ...የመጨረሻዎቹ ይሆናሉ" ወይም "እግዚአብሔር ያከብራቸዋል...እግዚአብሔር ያሳፍራቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 13:31

አያያዥ ሀሳብ፡
ይህ በዚህ የታሪክ ክፍል ቀጣዩ ትዕይንት ነው። አንዳንድ ፈሪሳውያን ስለ ሄሮድስ ቢነግሩትም ኢየሱስ ግን ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ ላይ ነው።

ከዚያም ብዙ ሳይቆይ
"ኢየሱስ ንግግሩን እንደጨረሰ ወዲያውኑ"

ከዚህ በቶሎ ሂድ ምክንየቱም ሄሮድስ ሊገድልህ ይፈልጋል
ይህንን ለኢየሱስ እንደ ተሰጠ ማስጠንቀቅያ ተርጉሙት። ወደ አንድ ስፍራ እንዲሄድ እና ራሱን እንዲያድን እየመከሩት ነበር።

ሄሮድስ ሊገድልህ ይፈልጋል
ሄሮድስ ሰዎች ኢየሱስን እንዲገድሉት ያዛል። "ሄሮድስ አንተን እንዲገድሉ ወታደሮቹን መላክ ይፈልጋል"

ያ ቀበሮ
ኢየሱስ ሄሮድስን ቀበሮ ብሎ እየጠራው ነበር። ቀበሮ ትንሽ የሆነ የዱር ውሻ ነው። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሄሮድስ በፍጹም የሚያስፈራው አልነበረም 2) ሄሮድስ አሳሳች ነበር። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በማናቸውም ሁኔታ
"የሆነ ሆኖ" ወይም "ሆኖም" ወይም "የሆነው ቢሆንም"

ነቢይን ከኢየሩሳሌም ውጭ መግደል ተቀባይነት የለውም
የአይሁድ መሪዎች እግዚአብሔርን እንደሚያገለግሉ ይናገራሉ። ሆኖም ግን አባቶቻቸው ብዙ የእግዚአብሔርን ነቢያት በኢየሩሳሌም ውስጥ ገድለዋል፣ እናም ኢየሱስ እርሱንም በዚህ እንደሚገድሉት ያውቃል። "የአይሁድ መሪዎች የእግዚአብሔርን መልዕክተኞች የገደሉት እዚህ ኢየሩሳሌም ውስጥ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምጸት የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 13:34

አያያዥ ሀሳብ፡
ኢየሱስ ለፈሪሳውያን ምላሽ መስጠቱን አበቃ። ይህ የዚህኛው ታረክ ክፍል መጨረሻ ነው።

ኢየሩሳሌም፣ ኢየሩሳሌም
ኢየሱስ የኢየሩሳሌም ሰዎች በዚያ ሆነው እንደሚሰደሙት አድርጎ ይናገራል። ኢየሱስ ይህን ሁለት ጊዜ የደገመው ለእነርሱ ምን ያህል እንዳዘነ ለማሳየት ነው። (ቃለ አጋኖ የሚለውን ይመልከቱ)

ነቢያትን የገደልሽ ወደ አንቺ የተላኩትን በድንጋይ የወገርሽ
ከተማን መናገር እንግዳ ነገር ከሆነ፣ ኢየሱስ በከተማይቱ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን እየተናገረ እንደሆነ ገልጽ ማድረግ ትችላላችሁ፡ "እናንተ ነቢያትን የገደላችሁ እና ወደ እናንተ የተላኩትን በድንጋይ የወገራችሁ ህዝቦች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እናንተ የተላኩትን
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር ወደ እናንተ የላካቸውን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ምን ያህል አብዝቼ ፈለግሁ
"እኔ እጅግ አብዝቼ ፈለግሁ።" ይህ ጉልህ ማድረግ እንጂ ጥያቄ አይደለም።

ልጆችሽን ለመሰብሰብ
የኢየሩሳሌም ሰዎች የተገለጹት የእርሷ "ልጆች" ተደርገው ነው። "የአንቺን ሕዝብ ለመሰብሰብ" ወይም "የእየሩሳሌምን ሰዎች ለመሰብሰብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ዶሮ ጫጩቶቿን ከክንፎቿ ስር እንደምትሰበስብ
ይህ የሚገልጸው ዶሮ እንዴት ጫጩቶቿን በክንፎችዋ ሸፍና ከጥፋት እንደምትጠብቅ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ቤታችሁ ወና ሆኖል
ይህ ወደፊት በቶሎ ለሚሆን ነገር ትንቢት ነው። ይህ ማለት እግዚአብሔር የኢየሩሳሌምን ሰዎች መጠበቁን አቁሟል፣ ስለዚህም ጠላት ሊያጠቃቸው እና ሊያባርራቸው ይችላል ማለት ነው። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እግዚአብሔር እነርሱን ይበትናቸዋል። "እግዚአብሔር ይተዋችኋል" ወይም 2) ከተማቸው ባዶ ትሆናለች። "ቤታችሁ ወና ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህ እስክትሉ ድረስ እኔን አታዩኝም
"እንዲህ የምትሉበት ጊዜ እስኪመጣ ድረስ እኔን አታዩኝም" ወይም "በሚቀጥለው ጊዜ እኔን ስታዩ፣ እንዲህ ትላላችሁ"

የጌታ ስም
እዚህ ስፍራ "ስም" የሚለው የሚያመለክተው የጌታን ሀይል እና ስልጣን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **14**

1 በሰንበት ቀን ኢየሱስ ከፈሪሳዊያን አለቆች ወደ እንዱ ቤት እንጀራ ሊበላ በገባ ጊዜ፣ የሚያደርገውን ለማየት በቅርበት ይጠባበቁት ነበር። **2** በዚያም በእጅና በእግር ዕብጠት የሚሠቃይ አንድ ሰው በኢየሱስ ፊት ነበር። **3** ኢየሱስ የአይሁድ ሕግ ዐዋቂዎችንና ፈሪሳውያንን፣ "በሰንበት ቀን መፈወስ በሕግ ይፈቀዳል ወይስ አይፈቀድም? "ብሎ ጠየቃቸው። **4** እነርሱ ግን ዝም አሉ። ኢየሱስ የታመመውን ሰው ይዞ ፈወሰውና አሰናበተው። **5** ቀጥሎም ኢየሱስ፣ "ከእናንተ ልጅ ወይም በሬ በሰንበት ቀን በጕድጓድ ውስጥ ቢወድቁ ወዲያውኑ የማያወጣቸው ማን ነው?" አላቸው። **6** እነርሱ ለእነዚህ ነገሮች መልስ መስጠት አልቻሉም። **7** ኢየሱስ በግብዣ ቦታ የከበሬታ ወንበር ለመያዝ ሲሽቀዳደሙ በተመለከት ጊዜ እንዲህ በማለት አንድ ምሳሌ **8** ነገራቸው፤ "አንድ ሰው ወደ ሰርግ ግብዣ ቢጠራህ በመጀመሪያ በከበሬታ ቦታ አትቀመጥ፣ ምናልባት በዚያ ቦታ የሚቀመጥ ከአንተ ይልቅ ክብር የሚሰጠው ሰው ተጋብዞ ይሆናል። **9** ሁለታችሁንም የጋበዛችሁ ሰው መጥቶ፣ 'ይህን ቦታ ለሌላ ሰው ልቀቅለት' ይልሃል፣ ከዚያም አንተ በሃፍረት ወደ ዝቅተኛ ቦታ ትሄዳለህ። **10** ነገር ግን ወደ ግብዣ ስትጠራ በዝቅተኛ ቦታ ተቀመጥ፤ አንተን የጋበዘህ ሰው መጥቶ፤ ወዳጄ ሆይ፣ 'ወደ ከፍተኛ ስፍራ መጥተህ ተቀመጥ' ይልሃል። ከዚያም በተጋባዦቹ ፊት ሁሉ የተከበርህ ትሆናለህ። **11** ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ዝቅ ዝቅ ይላል። ራሱንም ዝቅ ዝቅ የሚያደርግ ደግሞ ከፍ ከፍ ይላል። **12** ኢየሱስ ደግሞ ጋባዡን ሰው ደግሞ እንዲህ አለው፤ "የምሳ ወይም የራት ግብዣ በምታደርግበት ጊዜ መልሰው ይጋብዙኛል በማለት ብድራትን በመፈለግ ወዳጆችህን ወይም ወንድሞችህን ወይም ዘመዶችህን ወይም ሀብታም ጎረቤቶችህን አትጋብዝ። **13** ነገር ግን ግብዣ በምታደርግበት ጊዜ ድሆችን፣ የአካል ጕዳተኞችን፣ ሽባዎችንና ዐይነ ስውራንን ጥራ። **14** ይህን በማድረግህ እነርሱ መልሰው ሊከፍሉህ ስለማይችሉ፣ የተባረክህ ትሆናለህ። በጻድቃን ትንሣኤ ቀንም እግዚአብሔር ብድራትህን ይከፍልሃል። **15** በማዕድ ተቀምጠው ከነበሩት አንዱ ኢየሱስ የተናገራውን ሰምቶ፣ "በእግዚአብሔር መንግሥት ማዕድ ተቀምጦ እንጀራ የሚበላ ሰው የተባረከ ነው" አለው። **16** ኢየሱስ ግን እንዲህ አለው፤ "አንድ ሰው ትልቅ የእራት ግብዣ አዘጋጅቶ ብዙ ሰዎችን ጋበዘ። **17** የግበዣውም ዝግጅት በተጠናቀቀ ጊዜ ወደ እራት ግብዣው ወደ ተጋበዙት ሰዎች፣ 'ሁሉ ተዘጋጅቶአልና ወደ ግብዣው ኑ' ብሎ መልእክተኞችን ላከ። **18** ነገር ግን እያንዳንዱ ተጋባዥ ከግብዣው ለመቅረት ምክንያት መደርደር ጀመረ። የመጀመሪያው፤ "መሬት ስለ ገዛሁ ሄጄ ማየት አለብኝባ ይቅርታ አድርግልኝ አለው። **19** ሌላው፣ 'አምስት ጥማድ በሬዎችን ገዝቻለሁ፣ እነርሱን ልፈትናቸው ስለምሄድ፤ ይቅርታ አድርግልኝ' አለው። **20** ሌላኛውም ሰው፣ 'ሚስት አግብቼ ሙሽራ ስልሆንሁ፣ ልመጣ አልችልም' አለ።" **21** አገልጋዩ ለጌታው እነዚህን ነገሮች ነገረው። ከዚያም የቤቱ ጌታ ተቈጥቶ አገልጋዩን 'ቶሎ ሄደህ በከተማው አውራ ጐዳናዎች ስላች መንገዶች ሁሉ ያሉ ድኾችን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ ዐይነ ስውራንን፣ ሽባዎችን ሁሉ ወደዚህ እንዲገቡ ጥራቸው' አለው። **22** አገልጋዩም አለው፤ 'ጌታ ሆይ፤ ያዘዝኸኝን ሁሉ አድርጌአለሁ፤ አሁንም ትርፍ ቦታ አለ።' **23** ጌታውም አገልጋዩን፣ 'ወደ ጎዳናዎችና ወደ ገጠር መንገዶች ውጣ፤ ቤቴም እንዲሞላ ያገኘሃቸውን ሁሉ እንዲገቡ ግድ በላቸው። **24** "እላችኋለሁ፣ በመጀመሪያ ከተጋበዙት ከእነዚያ ሰዎች መካከል አንድ ሰው እንኳ ከእራቴ አይቀምስም' አለው። **25** ሕዝብም ከኢየሱስ ጋር አብረው እየሄዱ ሳለ፣ እርሱ ዞር ብሎ እንዲህ አላቸው፤ **26** "ማንም ወደ እኔ ሊመጣ የሚወድ አባቱንና እናቱን፣ ሚስቱንና ልጆቹን፣ ወንድሞቹንና እኅቶቹን፣ እንዲያውም የራሱንም ሕይወት ስንኳ ስለ እኔ ብሎ ካልተወ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም። **27** የራሱንም መስቀል ተሸክሞ የማይከተለኝ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።" **28** ከእናንተ አንድ ሰው ሕንጻ መሥራት ቢፈልግ ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገውን ገንዘብ በመጀመሪያ ተቀምጦ የማይተምን ማን ነው? **29** መሠረቱን ሠርቶ መደመደም ቢያቅተው በዚያ የሚያልፉት ሁሉ ፣ **30** 'ይህ ሰው መገንባት ጀምሮ መደምደም አቃተው እያሉ ይዘብቱበታል' ። **31** ወይም አንድ ንጉሥ ከሌላ ንጉሥ ጋር ለዋጋ በሚነሣበት ጊዜ ሃያ ሺህ ሰራዊት አስከትቶ የሚመጣበትን በአሥር ሺህ ሰራዊት ለመመከት ተቀምጦ የማይመክር ማን አለ? **32** መመከት የማይችል ከሆነ የሌላው ሰራዊት ገና ከሩቅ ሳለ መልእክተኛ ልኮ ዕርቅ ይጠይቃል። **33** እንዲሁም ከእናንተ ማንም ያለውን ሁሉ የማይተው ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም። **34** ጨው መልካም ነው፤ ነገር ግን ጨው ጣዕም ካጣ እንዴት ተመልሶ እንደ ገና የጨውነት ጣዕም ሊኖረው ይችላል? **35** ለመሬትም ሆነ ለማዳበሪያነት የማይጠቅም በመሆኑ ወደ ውጪ ይጣላል። የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ!"

Luke 14:1

አጠቃላይ መረጃ፡
ይህ የሆነው በሰንበት ሲሆን፣ ኢየሱስ በፈሪሳዊው ቤት ውስጥ ነው። ቁጥር 1 ቀጥሎ ለሚከናወነው ትእይነት የመረጃ ዳራ ይሰጣል። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

በአንድ ሰንበት እንዲህ ሆነ
ይህ አዲስ ትዕይንትን ያመለክታል። (የአዲስ ትዕይንት ትውውቅ የሚለውን ይመልከቱ)

እንጀራ ለመብላት
"ለመብላት" ወይም "ለምሳ/ለምግብ።" እንጀራ የምግቡ ዋና ክፍል ነበር፣ እናም በዚህ ዐረፍተ ነገር ውስጥ ገበታውን ለማመልከት ውሏል። (ስኔክቲክ/የነገሩን ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በቅርበት እርሱን ይመለከቱ
ይከሱት ዘንድ አንዳች ስህተት ይሰራ ይሆናል ብለው ይጠባበቁ

እነሆ፣ ከእርሱ ፊት አንድ ሰው ነበር
"እነሆ" የሚለው ቃል በታሪኩ ውስጥ አዲስ ሰው እንደሚተዋወቅ ያነቃናል። ቋንቋችሁ ይህንን የሚገልጽበት መንገድ ሊኖረው ይችላል። እንግሊዝኛው "በዚያ በእርሱ ፊትለፊት አንድ ሰው ነበር" የሚለውን ይጠቀማል። (አዲስ እና ነባር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

በእብጠት የሚሰቃይ
x

Luke 14:4

ነገር ግን እነርሱ ዝም አሉ
የሃይማኖት መሪዎቹ የኢየሱስኝ ጥያቄ መመለስ አልፈቀዱም።

ስለዚህ ኢየሱስ ሰውየውን ያዘው
"ስለዚህ ኢየሱስ በእብጠት በሽታ የሚሰቃየውን ሰው ይዞ ፈወሰው"

ከእናንተ ማናችሁ ልጅ ወይም በሬ ያለው... ፈጥኖ አያወጣውም?
ኢየሱስ ጥያቄውን የተጠቀመበት እነርሱ በሰንበት ቀንም ቢሆን እንኳን ልጆቸውን ወይም በሬያቸውን እንደሚረዱ እንዲያምኑ ስለፈለገ ነው። ስለዚህ፣ ለእርሱ ሰዎችን በሰንበትም ቢሆን መፈወስ ትክክል ነበር። "ከእናንተ መሃል ልጅ ወይም በሬ ቢኖረው...በእርግጥ ፈጥናችሁ ታወጡታላችሁ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Luke 14:7

አጠቃላይ መረጃ፡
ኢየሱስ ምሳ በጋበዘው ፈሪሳዊው ቤት ከነበሩ እንግዶች ጋር መናገሩን ቀጠለ።

ተጋብዘው የነበሩ
እነዚህ ሰዎች እነማን እንደሆኑ እና ይህን በአድራጊ ዐረፍተ ነገር መግለጹ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። "ከፈሪሳዊያን አለቆች አንዱ ወደ ግብዣ የጠራቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የክብር ወንበር
"ለተከበሩ ሰዎች የተዘጋጀ ወንበር" ወይም "ከፍ ላሉ ሰዎች የተዘጋጁ ወንበሮች"

አንድ ሰው በሚጋብዝህ ወቅት
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንድ ሰው በሚጋብዝህ ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ በ...ጊዜ....ከዚያ አንተ...አንተን ይልሃል....አንተን ልቀቅ
በእነዚህ ስፍራዎች "አንተ" የሚሉት ተውላጠ ስሞች ነጠላ ቁጥር ናቸው። ኢየሱስ በዚያ የተሰበሰቡትን የሚያናግራቸው እያንዳንዳቸውን በግለሰብ ደረጃ እንደሚናገር አድርጎ ነው። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)

ምናልባት ከአንተ ይልቅ የከበረ ሰው ተጠርቶ ይሆናል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ምናልባት ደጋሹ ከአንተ ይልቅ የተከበረ ሰው ጋብዞ ሊሆን ይችላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ሁለታችሁም
በዚህ ስፍራ "እናንተ" የሚለው የሚያመለክተው አንድን የክብር ስፍራ የሚፈልጉ ሁለት ሰዎችን ነው።

በፍርሃት
"ታፍራለህ ደግሞም"

Luke 14:10

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢየሱስ በፈሪሳዊው ቤት ለሚገኙ ሰዎች መናገሩን ቀጥሏል።

በምትጋበዝበት ወቅት
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። " አንድ ሰው በሚጋብዝህ ወቀት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ዝቅተኛ የሆነ ስፍራ
"ዝቅ ያለ ደረጃ ላለው ሰው የተዘጋጀ ስፍራ/መቀመጫ"

ወደ ላይ ከፍ በል
"የከበሩ ሰዎች/ታላላቆች ወደተቀመጡበት ወንበር ሂድ"

በዚህን ጊዜ ትከበራለህ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በዚይን ጊዜ የጋበዘህ ሰው ያከብርሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ራሱን የሚያከብር
"ራሱን ከፍ የሚያደርግ" ወይም "ከፍ ባለ ስፍራ የሚያስቀምጥ"

ትሁት የሚያደርግ
"ራሱን ትሁት የሚያደርግ" ወይም "ከፍ ከፍ ይደረጋል።" ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር ያከብረዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ራሱን ዝቅ የሚያደርግ
"ራሱን ዝቅ ለማድረግ የሚፈቅድ" ወይም "ራሱን ዝቅ ባለ ስፍራ የሚያስቀምጥ"

ከፍ ይደረጋል
"ይከብራል" ወይም "ከፍ ያለ ስፍራ ይሰጠዋል።" ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር ከፍ ያደርገዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 14:12

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢየሱስ በፈሪሳዊው ቤት መናገሩን ቀጥሏል፤ ነገር ግን የሚናገረው በቀጥታ ለጋባዡ ነበር።

እርሱ የጋበዘው ሰው
"ቤቱ ግብዣ የጠራውን ፈሪሳዊ"

አንተ ስትሰጥ
"አንተ" የሚለው ነጠላ ቁጥር ነው፤ ምክንያቱም ኢየሱስ በቀጥታ የሚናገረው ለጋበዘው ፈሪሳዊ ነው። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)

አትጥራ/አተጋብዝ
ይህ ምናልባት እነዚህን ሰዎች ፈጽሞ መጋበዝ አይችሉም ማለት ላይሆን ይችላል። ሌሎችንም/ድሆችንም ደግሞ መጋበዝ ነበረባቸው ማለት ይመስላል። "...ብቻ አትጋብዝ" ወይም "ሁሌም...ብቻ አትጋብዝ"

ምናልባት እነርሱ
"ምክንያቱም እነርሱ"

በተራቸው ይጋብዙሃል
"ወደ እራት ወይም ግብዣ ይጠሩሃል"

መልሶ ይከፍልሃል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በዚህ መንገድ መልሰው ይከፍሉሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 14:13

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢየሱስ እርሱን ቤቱ ለጋበዘው ፈሪሳዊ መናገሩን ይቀጥላል

Luke 14:15

አጠቃላይ መረጃ፡
በማዕድ ከተቀመጡት መሃል አንዱ ከኢየሱስ ጋር ተነጋገረ እናም ኢየሱስ ለእርሱ በግብረገባዊ ምሳሌ ምላሽ ሰጠው። (ግብረገባዊ ምሳሌ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእነርሱ መሃል በማዕድ ከተቀመጡት አንዱ
ይህ አዲስ የሆነ አንድ ሰውን ያስተዋውቃል። (አዲስ እና ነበር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ የተባረከ ነው
ሰውየው ስለ አንድ የተለየ ሰው እየተናገረ አይደለም። "እርሱ የተባረከ ነው" ወይም "ይህ ለእያንዳንዱ እንዴት መልካም ነው"

ከዚህ እንጀራ የሚበላ እርሱ
"እንጀራ" የሚለው ቃል የዋለው በአጠቃሌ መዕዱን ለማመልከተ ነው። "ከዚህ ማዕድ የሚበላ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/የነገሩን ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን ኢየሱስ እንዲህ አለው
ኢየሱስ ግብረ ገባዊ ምሳሌ መናገር ጀመረ። (ግብረ ገባዊ ምሳሌ የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ሰው ትልቅ እራት አዘጋጅቶ ብዙዎችን ጋበዘ
አንባቢው ምናልባት የዚያ ሰው አገልጋዮች መዕደስ እንዳዘጋጁ እና እንግዶችን እንደጋበዙ መገመት መቻል ይኖርበታል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ሰው
ይህ ሀረግ ስለማንነቱ ምንም መረጃ ስላልሰጠ ሰው ማጣቀሻ መንገድ ነው።

ብዙዎችን ግብዣ ጠራ
"ብዙ ሰዎች ጋበዘ" ወይም "ብዙ እንግዶች ጠራ"

Luke 14:18

አያያዥ ሀሳብ፡
ኢየሱስ ግብረገባዊ ምሳሌውን መናገሩን ቀጠለ።

አጠቃላይ መረጃ፡
የተጋበዙት ሰዎች ሁሉ ለአገልጋዩ ወደ ግብዣው ሊመጡ የማይችሉባቸውን ምክንጠቶች ሰጡ።

ምክንያት መስጠት/ማቅረብ
"ወደ እራት መምጣት ያልቻሉበትን መናገር"

የመጀመሪያው እንዲህ አለው... ሌላው እንዲህ አለ... ሌላው ሰው እንዲህ አለ
አንባቢያን፣ እነዚህ ሰዎች በቀጥታ ጌታቸው ለላከው አገልጋይ እንደተናገሩ መገንዘብ መቻል ይኖርባቸዋል (ሉቃስ 14፡17) ። "የመጀመሪያው እንዲህ ሲል መልዕክት ላከ...ሌላው እንዲህ ሲል መልዕክት ላከ... ሌላውም ሰው እንዲህ ሲል መልዕክት ላከ" ወይም "የመጀመሪያው አገላጋዩ እንዲህ እንዲል ነገረው...ሌላኛው አገልጋዩ እንዲህ እንዲል ነገረው... ሌላው ሰው አገልጋዩ እንዲህ እንዲል ነገረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እባክህ ይቅር በለኝ
"እባክህ ይቅርታ አድርግልኝ" ወይም "እባክህን ይቅርታዬን ተቀበል"

አምስት ጥማድ በሬ
በሬዎች የእርሻ መሳሪያ ለመሳብ/ለማረስ በጥንድ ይጠመዳሉ። "10 በሬዎች በእርሻዬ ላይ ተጠምደዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሙሽራ ነኝ
በቋንቋችሁ የተለመደውን አገላለጽ ተጠቀሙ። አንዳንድ ቋንቋዎች "አግብቻለሁ" ወይም "ሚስት ወስጃለሁ" ሊሉ ይችላሉ።

Luke 14:21

ተቆጣ
"ግብዣ በጠራቸው ሰዎች ተቆጣ"

ወደዚህ አምጧቸው
"እራት እንዲበሉ ወደዚህ ጥሯቸው"

አገልጋዩ እንዲህ አለ
በውስጠ ታዋቂነት ያለውን አገልጋዩ ጌታው ያዘዘውን ማድረጉን የሚያሳየውን በግልጽ መጻፍ አስፈለዘጊ ሊሆን ይችላል። "አገልጋዩ ወደ ውጭ ሄዶ ያን አድርጎ ተመልሶ መጥቶ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ያዘዝከው ተደርጓል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንተ ያዘዝከውን አድርጌያለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 14:23

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢየሱስ ግብረ ገባዊ ምሳሌውም መናገር ጨረሰ።

አውራ መንገዶች እና መተላለፊያዎች
ይህ የሚያመለክተው መንገዶችን እና ከከተማ ውጭ ያሉ መተላለፊያዎችን ነው። "አውራ መንገዶች እና ከከተማ ውጭ የሚገኙ መተላለፊያ መንገዶች"

ወደ ውስጥ እንዲመጡ ግድ በሏቸው
"እንዲመጡ ግድ በሏቸው"

እነርሱን ግድ በሏቸው
"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ማናቸውንም አገልጋዮቹ የሚያገኟቸውን ሰዎች ነው። "ያገኟችኋቸውን ሁሉ ግድ በሏቸው"

ቤቴ ይሞላ ዘንድ
"ሰዎች ቤቴን ይሞሉ ዘንደ"

እኔ እናንተን እላችኋለሁ
"እናንተ" የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ነው፤ ስለዙህ ይህ ማንን እንደሚያመለክት ግልጽ አይደለም። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)

እነዚያ ወንዶች/ሰዎች
እዚህ ስፍራ "ወንዶች" የሚለው "አዋቂ ወንዶች" ማለት እንጂ በአጠቃላይ ሰዎችን ማለት አይደለም።

የተጋበዙ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እኔ የጋበዝኳቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እራቴን ይበላሉ
"ያዘጋጀሁትን እራት ይበላሉ"

Luke 14:25

አጠቃላይ መረጃ፡
ኢየሱስ ከእርሱ ጋር ይጓዝ የነበረውን የተሰበሰበውን ሕዝብ ማስተማር ጀምሯል።

ማንም ወደ እኔ መጥቶ የራሱን አባት ባይጠላ ... የእኔ ደቀመዝሙር ሊሆን አይችልም
እዚህ ስፍራ "መጥላት" የሚለው ሰዎች ሌለውን አስበልጠው ለኢየሱስ ለሚያሳዩት አነስ ያለ ፍቅር በግነት የቀረበ አገላለጽ ነው። "ማንም ወደ እኔ መጥቶ አባቱን ከሚወደው በላይ እኔን ካልወደደ...እርሱ የእኔ ደቀመዝሙር መሆን አይችልም" ወይም "አንድ ሰው አባቱን ከሚወደው በላይ እኔን መውደድ ከቻለ ብቻ ...እርሱ የእኔ ደቀመዝሙር መሆን ይችላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት እንደዚሁም ጥንድ አሉታ የሚሉትን ይመልከቱ)

የራሱን መስቀል የማይችል እና ከእኔ ኋላ የማይመጣ ደቀመዝሙሬ ሊሆን አይችልም
ይህ በአዎንታዊ ግሶች ሊገለጽ ይችላል። "ማንም የእኔ ደቀመዝሙር መሆን ቢፈልግ፣ የራሱን መስቀል ሊሸከም እና ሊከተለኝ ይገባል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ አሉታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የራሱን መስቀል ተሸክሞ
ኢየሱስ እያንዳንዱ ክርስቲያን መሰቀል አለበት ማለቱ አይደለም። ሮማውያን ብዙውን ጊዜ ለሮም ያላቸውን ታማኝነት እንዲያሳዩ ወንጀለኛ ሰዎች ራሳቸው የሚሰቀሉበትን መስቀል እንዲሸከሙ ያደርጉ ነበር። የዚህ ዘይቤ ትርጉም እነርሱም ለእግዚአብሔር መገዛት እና የኢየሱስ ደቀመዝሙር ለመሆን መከራ ለመቀበል ፈቃደኛ መሆን እንደሚገባቸው ያሳያል። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

Luke 14:28

አጠቃላይ መረጃ:
ኢየሱስ ለተሰበሰበው ሕዝብ ደቀመዝሙር ለመሆን የሚጠይቀውን ዋጋ ማወቅ እንደሚያስፈልግ ማብራሩቱን ቀጥሏል።

ከእናንተ መሃል ህንጻ ለመሥራት የሚፈልግ አስቀድሞ ቁጭ ብሎ ለመደምደም የሚያስፈልገውን ዋጋ የማያሰላ ማን ነው?
ኢየሱስ ይህን ጥያቄ የተጠቀመበት ሰዎች አንድን ሥራ ለመሥራት ለሥራው የሚያስፈልገውን እንደሚያሰሉ ለማሳየት ነው። "አንድ ሰው ህንጻ ማነጽ ቢፈልግ፣ በመጀመሪያ ተቀምጦ ህንጻውን ሊደመደምበት የሚያበቃው ገንዘብ እንዳለው ይወስናል።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ህንጻ
ይህ ትልቅ ህንጻ ሊሆን ይችላል። "ትልቅ ህንጻ" ወይም "ጎላ ብሎ የሚያይ ግንብ"

ካልሆነ
ተጨማሪ መረጃ መስጠት ሊረዳ ይችላል። "አስቀድሞ ዋጋውን ካላወቀ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

መሰረቱን ሲጥል
"መሰረቱን ሲገነባ" ወይም "የህንጻውን የመጀመሪያ ክፈል ሲያጠናቅቅ"

መጨረስ/ማጠናቀቅ አልቻለም
መጨረስ ያልቻለው በቂ ገንዘብ ስለሌለው መሆኑ ይታወቃል። እንዲህ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "ለመጨረስ በቂ ገንዘብ አልነበረውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 14:31

አጠቃላይ መረጃ:
ኢየሱስ ለተሰበሰበው ሕዝብ ደቀመዝሙር ለመሆን የሚጠይቀውን ዋጋ ማወቅ አስፈላጊ እንደሆነ ማብራራቱን ቀጥሏል።

ወይም
ኢየሱስ ይህን ቃል የተጠቀመው ሰዎች አንድ ውሳኔ ከማድረጋቸው አስቀድሞ ውሳኔው የሚጠይቀውን ዋጋ ሌላ ሁኔታ ለማስተዋወቅ ነው።

አስቀድሞ የማይቀመጥ እና... ከሰዎቹ/አማካሪዎቹ ምክር የማይቀበል... የቱ ንጉሥ ነው?
ኢየሱስ የተሰበሰበውብ ሕዝብ ዋጋ ስለመተመን ለማስተማር ሌላ ጥያቄ ያነሳል። " አንድ ንጉሥ... በመጀመሪያ ተቀምጦ... ከአማካሪዎቹ ምክር እንደሚቀበል ታውቃላችሁ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ምክር ይቀበላል
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1)"በጥንቃቄ ማሰብ" ወይም 2) "አማካሪዎቹን መስማት"

አስር ሺህ...ሃያ ሺህ
"10,000...20,000" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ካልሆነ
ተጨማሪ መረጃዎችን መግለጽ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። "ሌላውን ንጉሥ ለማሸነፍ እንደማይችል ከተገነዘበ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰላም ሁኔታዎች
"ጦርነቱን ለማጠናቀቅ የሚያስፈልጉ" ወይም "ጦርነቱን ለማጠናቀቅ ሌላው ንጉሥ እርሱ እንዲያደርግ የሚፈልገው"

ከእናንተ መሃል ማንም ያለውን ሁሉ የማይተው የእኔ ደቀመዝሙር መሆን አይችልም
ይህ በአዎንታዊ ግሶች ሊገለጽ ይችላል። "ያላችሁን ሁሉ የምትተዉ ብቻ ደቀመዝሙሬ መሆን ትችላላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ አሉታ የሚለውን ይመልከቱ)

ያለውን ሁሉ የሚተው
"ያለውን ሁሉ ከኋላው የሚጥል"

Luke 14:34

አያያዥ ሀሳብ:
ኢየሱስ የተሰበሰበውን ህዘውብ ማስተማሩን አጠናቀቀ።

ጨው መልካም ነው
"ጨው ጠቃሚ ነው።" ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ሊሆኑ ለሚፈልጉ ትምህርት እየሰጠ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንዴት ዳግም ጣዕሙን ሊያገኝ ይችላል?
ኢየሱስ ይህን ጥያቄ የተጠቀመው የተሰበሰበውን ሕዝብ ለማስተማር ነው። "ዳግም ጣዕም ሊሰጠው አይችልም።" ወይም "ማንም ዳግም ጣዕም ሊሰጠው አይችልም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

የፍግ ክምር
ሰዎች አትክልት ስፍራዎችን እና እርሻን ለማልማት ማዳበሪያ ይጠቀማሉ። ጣዕም የሌለው ጨው አንዳች ጥቅም የለውም፤ ከፍግ ጋር ለመደባለቅ እንኳን አይጠቅምም። "የማዳበሪያ ቁልል" ወይም "ማዳበሪያ/ፍግ"

ወደ ውጭ ይጣላል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገል ሊጻፍ ይችላል። "ወደ ውጭ ይጥሉታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የሚሰማ ጆሮ ያለው እርሱ ይስማ
በአንዳንድ ቋንቋዎች ሁለተኛ መደብን መጠቀም ይበልጥ ተፈጥሯዊ ሊሆን ይችላል። "እናንተ መስሚያ ጆሮ ያላችሁ ስሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

የሚሰማ ጆሮ ያለው እርሱ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "እያንዳንዱ" ጤናማ ጆሮ እስካላቸው ድረስ፣ ወይም 2) "የመረዳት ችሎታ ያለው ሁሉ፣" እግዚአብሔርን ለመስማት ፈቃደኛ የሆኑትን ያሚያመለክት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ይስማ
"እርሱ በሚገባ መስማት አለበት" ወይም "እርሱ እኔ ለምናገረው ትኩረት መስጠት አለበት"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 15

1 አንድ ቀንም ቀረጥ ሰብሳቢዎችና ሌሎች ኀጢአተኞች ሁሉ ኢየሱስን ለመስማት መጡ። 2 ፈሪሳውያንና የሕግ መምህራን፣ "ይህ ሰው ኀጢአተኞችን
ይቀበላል፤ ከእነርሱም ጋር ይበላል" በማለት እርስ በርሳቸው አጒረመረሙ። 3 ኢየሱስ እንዲህ በማለት ይህን ምሳሌ ነገራቸው፤ 4 "ከእናንተ መካከል መቶ በጎች
ያሉት ከዚያም ከእነርሱ አንዱ ቢጠፋበት ዘጠና ዘጠኙን በዱር ትቶ የጠፋበትን እስኪያገኘው ድረስ ሊፈልግ የማይሄድ ማንነው? 5 ባገኘውም ጊዜ ከመደሰቱ
የተነሣ በጫንቃው ይሸከመዋል። 6 ወደ ቤቱም ሲመለስ ወዳጆቹንና ጎረቤቶቹን በአንድነት ጠርቶ፣ 'የጠፋብኝን በጌን አግኝቻለሁና ከእኔ ጋር ደስ ይበላችሁ'
ይላቸዋል። 7 እንዲሁም ንስሓ ከማያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ ንስሓ በሚገባ በአንድ ኀጢአተኛ በሰማይ ታላቅ ደስታ እንደሚሆን
እነግራችኋለሁ። 8 ወይስ ዐሥር የብር ሳንቲሞች ያላት ሴት ከዐሥሩ አንዱ ቢጠፋበት፣ እስከምታገኛው ድረስ መብራት አብርታ፣ ቤቷንም ሁሉ ጠርጋ በትጋት
የማትፈልግ ሴት ማን ናት? 9 ባገኘችም ጊዜ ወዳጆቿንና ጎረቤቶቿን ሁሉ በአንድነት ጠርታ፣ 'የጠፋብኝን የብር ሳንቲሜን አግኝቻለሁና ኑ ከእኔ ጋር ደስ
ይበላችሁ' ትላቸዋለች። 10 "እንደዚሁም ንስሓ በሚገባ በአንድ ኀጢአተኛ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ታላቅ ደስታ እንደሚሆን እነግራችኋለሁ።" 11
ከዚያም ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ "አንድ ሰው ሁለት ወንዶች ልጆች ነበሩት፤ 12 ታናሹ ልጅም አባቱን፣ 'አባቴ ሆይ፣ በኋላ ከሀብትህ ከሚደርሰኝ ድርሻዬን ስጠኝ'
አለው። አባቱም ሀብቱን ለሁለቱም ልጆቹ አካፈለቸው። 13 ከጥቂት ቀናትም በኋላ ታናሹ ልጅ ድርሻውን ይዞ ወደ ሩቅ አገር ሄደ። እዚያም ገንዘቡን ሁሉ
አላግባብ እየጨፈረ አባከነ። 14 እርሱም ያለውን ሁሉ ከጨረሰ በኋላ በዚያ አገር ጽኑ ራብ ሆነ። ከዚህም የተነሳ ችግር ላይ ወደቀ። 15 በዚያም አገር ዐሳማ
ያረባ ወደ ነበረ ወደ አንዱ ሰው ዘንድ ሄዶ ተቀጠረ። ሰውዬው ዐሳማዎችን እንዲጠብቅለት አሰማራው። 16 እርሱም የሚበላውን ምግብ የሚሰጠው ስላልነበረ፣
ዐሳማዎቹ ከሚመገቡት መኖ ለመብላት ይፈልግ ነበር። 17 እርሱም አንድ ቀን ወደ ልቡ ተመልሶ እንዲህ አለ፤ 'ምግብ የሚተርፋቸው የአባቴ ቤት ሠራተኞች
ስንት ናቸው? 18 እኔ ግን እዚህ የምበላውን አጥቼ በራብ እሞታለሁ! ተነሥቼ ወደ አባቴ ቤት ልሂድና እንዲህ ልበለው፤ "አባቴ ሆይ፣ በእግዚአብሔርና በአንተ
ፊት ኀጢአት አድርጌአለሁ። 19 ከእንግዲህ ልጅህ ተብዬ መጠራት አይገባኝም፤ ከአገልጋዮችህ እንደ አንዱ ቊጠረኝ።" 20 ስለዚህ ታናሹ ልጅ ተነሥቶ ወደ
አባቱ መጣ። ልጁ ገና ከሩቅ እየመጣ ሳለ፤ አባቱ አይቶ በርኅራኄ ሮጦ ተቀበለውና ዐቅፎ ሳመው። 21 ልጁ፣ 'አባቴ ሆይ፣ በእግዚአብሔርና በአንተ ፊት ኀጢአት
አድርጌአለሁ። ከእንግዲህ ልጅህ ተብዬ ልጠራ አይገባኝም' አለ። 22 አባቱም አገልጋዮቹን እንዲህ አላቸው፤ "ፈጥናችሁ ምርጡን ልብስ አምጡና አልብሱት፣
በጣቱ ቀለበት፣ በእግሩም ጫማ አድርጉለት። 23 ከዚያም የሰባውን ወይፈን አምጡና ዕረዱት። እንብላ፤ እንደሰት። 24 ይህ ልጄ ሞቶ ነበረ አሁን በሕይወት
አለ፤ ጠፍቶም ነበረ ተገኝቶአል።" ይደሰቱም ጀመር። 25 ታላቁ ልጅ በዕርሻ ቦታ ነበረ። ወደ ቤትም በተቃረበ ጊዜ፣ ሙዚቃና ጭፈራ ሰማ። 26 ከአገልጋዮቹ
አንዱን ጠርቶ፤ ምን እየሆነ እንዳለ ጠየቀው። አገልጋዩም፣ 'ወንድምህ መጥቶአል። 27 በደኅና ስለተመለሰም አባትህ የሰባውን ወይፈን አርዶለታል' አለው። 28
ታላቁ ልጅ ይህን ሰምቶ ተቈጣ፤ ወደ ቤትም ሊገባ አልፈለገም። አባቱም ወጥቶ እንዲገባ ለመነው። 29 እርሱ ግን አባቱን እንዲህ አለው፤ 'እነሆ፣ ይህን ሁሉ
ዘመን እንደ ባሪያ አገለገልሁህ፤ ከትእዛዝህ አንዱንም ሳላጎድል ከአንተ ጋር ኖርሁ፤ ከባልንጀሮቼ ጋር እንድደሰት አንዲት የፍየል ግልገል እንኳ አልሰጠኸኝም፤ 30
ነገር ግን ይህ ልጅህ ገንዘብህን ሁሉ ከሴተኛ አዳሪዎች ጋር አባክኖ ሲመጣ፣ የሰባውን ወይፈን አረድህለት።' 31 አባቱ እንዲህ አለው፤ "ልጄ ሆይ፣ አንተ
ሁልጊዜ ከእኔ ጋር ነህ፤ ያለኝ ሁሉ የአንተ ነው። 32 ነገር ግን ይህ ወንድምህ ሞቶ ነበር፤ አሁን በሕይወት አለ፤ ጠፍቶም ነበር ተገኝቶአል። ስለዚህ ልንበላና
ልንደሰት ይገባናል።'

Luke 15:1

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ መቼ እንደተፈጸመ አናውቅም፤ ይህ የሆነው አንድ ዕለት ኢየሱስ እያስተማረ ሳለ ነው።

አሁን
የአዲስ ተዕይንት ጅማሬ ምልክቶችን ያሳያል። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

ግበር ሰብሳቢዎች በሙሉ
በርካታ ግብር ሰብሳቢዎች እንደነበሩ በግነት የተገለጸ ነው። "ብዙ ግብር ሰብሳቢዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

ይህ ሰው ኃጢአተኞችን ይቀበላል
"ይህ ሰው ኃጢአተኞች እንዲቀርቡት ይፈቅዳል" ወይም "ይህ ሰው ከጢአተኞች ጋር ህብረት ያደርጋል"

ይህ ሰው
ስለ ኢየሱስ እየተናገሩ ነበር።

ከእነርሱ ጋር እንኳን ይበላል
እንኳን/ጭምር የሚለው ኢየሱስ ኃጢአተኞች ወደ እርሱ እንዲቀርቡ መፍቀዱ እጅግ መጥፎ ነገር ነው ብለው ማሰባቸውን ያሳያል፤ ይልቁንም ከእነርሱ ጋር መመገቡ ከዚያም የከፋ ነገር እንደሆነ ያስቡ ነበር።

Luke 15:3

አጠቃላይ መረጃ:
ኢየሱስ ብዙ ምሳሌዎችን መናገር ጀመረ። እነዚህ ማንም ሰው ሊገጥመው የሚችላቸው ግብረገባዊ ምሳሌዎች መላምታዊ ሁኔታዎች ናቸው። እነዚህ ስለተለያዩ ሰዎች የሚናገሩ አይደለም። የመጀመሪያው ግብረገባዊ ምሳሌ አንድ ሰው ከበጎቹ አንዱ ቢጠፋ ያ ሰው ምን እንደሚያደርግ የሚገልጽ ነው። (ግብረገባዊ ምሳሌዎች እና መላምታዊ ሁኔታዎች የሚሉትን ይመልከቱ)

ለእነርሱ
እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው የሚያመለክተው የሃይማኖት መሪዎችን ነው።

ከእናንተ መሃል ...እስኪያገኘው ድረስ ...የማይፈልገው ማን ነው?
ኢየሱስ ጥያቄውን የተጠቀመበት፣ ሰዎቹ ከበጎቻቸው መሃል አንዱ ቢጠፋ ፍለጋ እንደሚሄዱ ሊያሳስባቸው ነው። "እናንተ እያንዳንዳችሁ ... እስክታገኙት ድረስ...በእርግጥ ፍለጋ ታደርጋላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

መቶ በጎች ቢኖሩት፣ ከእናንተ መሃል ማን
ምሳሌያዊ አነጋገሩ "ከእናንተ መሃል ማን" በሚል እንደመጀመሩ፣ አንዳንድ ቋንቋዎች ምሳሌያዊ አነጋገሩን በሁለተኛ መደብ ይቀጥላል። "መቶ በጎች ቢኖራችሁ፣ ከእናንተ መሃል ማን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

መቶ...ዘጠና ዘጠኝ
"100... 99" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Luke 15:6

ወደ ቤቱ ስመለስ
"የበጉ ባለቤት ወደ ቤቱ ስመለስ" ወይም "ወደ ቤት ሲመለስ።" የበጉን ባለቤት በቀደመው ቁጥር እንዳደረጋችሁት አመልክቱ።

ምንም እንኳን
"በተመሳሳይ መንገድ" ወይም "እረኛው እና ወዳጆቹ እንደዚሁም ጎረቤቶቹ ደስ እንደሚሰኙ"

በሰማይ ደስታ ይሆናል
"በሰማይ ያሉት ሁሉ ደስ ይላቸዋል"

ንስሃ የማያስፈልጋቸውን ዘጠና ዘጠኙን ጻድቃን ሰዎች
ኢየሱስ ፈሪሳውያኑ ንስሃ እንደማያስፈልጋቸው ማሰባቸው ስህተት መሆኑን በምጸት ይናገራል። የእናንተ ቋንቋ ይህን ሃሳብ ለመግለጽ የተለያ መንገድ ሊኖረው ይችላል። "እንደ እናንተ የመሰሉ ጻድቃን ነን ብለው የሚያስቡ ንስሃ መግባት የማይፈልጉ ዘጠና ዘጠኝ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚለውን ይመልከቱ)

ዘጠና ዘጠኝ
"99" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 15:8

አያያዥ ሀሳብ፡
ኢየሱስ ሌላ ግብረገባዊ ምሳሌ መናገር ይጀምራል። ይህኛው 10 የብር ሳንቲሞች ስላላት ሴት ነው።

ወይም የትኛዋ ሴት...ሻማ ለኩሳ... እስክታገኘው ደረስ ተግታ አትፈልግም?
ኢየሱስ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት ሰዎቹ የብር ሳንቲም ቢጠፋባቸው፣ ያንን በእርግጥ በትጋት እንደሚፈልጉ ለማስታወስ ነው። "የትኛዋም ሴት... በእርግጥ ፋኖስ ትለኩሳለች... እናም እስክታገኘው ድረስ በትጋት የጠፋባትን ትፈልጋለች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ባታገኘው
ይህ መላምታዊ ሁኔታ እንጂ በዕውን ስላለች አንዲት ሴት የሚናገር ታሪክ አይደለም። አንዳንድ ቋንቋዎች ይህን የሚያሳዩበት መንገድ አላቸው። (መላምታዊ ሁኔታ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደዚሁም
"በተመሳሳይ መንገድ" ወይም "ሰዎች ከሴቲቱ ጋር ደስ እንደሚላቸው" ንስሃ በሚገባ አንድ ኃጢአተኛ "አንድ ኃጢአተኛ ንስሃ በሚገባበት ጊዜ"

Luke 15:11

አያያዥ ሀሳብ፡
ኢየሱስ ሌላ ግብረገባዊ ምሳሌ መናገር ጀመረ። ይህም አባቱን ከሚደርሰው ውርስ ድርሻውን ስለጠየቀው ወጣት ነው። (ግብረገባዊ ምሳሌ የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ሰው
ይህ አዲስ ገጸባህሪን በግብረገባዊ ምዋሌው ውስጥ ያስተዋውቃል። አንዳንድ ቋንቋዎች "አንድ ሰው ነበረ" ብለው ይጀምራሉ። (አዲስ እና ነባር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

ስጠኝ/አምጣ
ልጁ አባቱ ወዲያውኑ ድርሻውን እንዲሰጠው ፈልጓል። ወዲያውኒ ሊደረግ የሚፈልገውን በትዕዛዝ መልክ መግለጽ የሚችል ቃል በቋንቋ ካለ ያንን መልክ መጠቀም አለባችሁ።

ለእኔ የሚደርሰኝን የሀብት መጠን
"በምትሞትበት ጊዜ ልታወርሰኝ ያቀድከውን የሀብት መጠን"

በእነርሱ መሃል
"በሁለቱ ልጆቹ መሃል"

Luke 15:13

እርሱ ያለውን ሁሉ/ድርሻው ሸከፈ
"ያሉትን ነገሮች ጠቀለለ" ወይም "ያሉትን ነገሮች በቦርሳው ውስጥ አደረገ"

በንዝህላልነት መኖር
"ድርጊቶች ስለሚያስከትሉት ውጤት ባለማሰብ መኖር" ወይም "ልቅ አኗኗር"

አሁን
x

Luke 15:15

እርሱ ሄደ
"እርሱ" የሚለው ቃል ታናሹን ልጅ ያመለክታል።

ለ...ራሱን ተቀጣሪ አደረገ
"ከ...ዘንድ ሥራ ያዘ" ወይም "ለ...መሥራት/ማገልግል ጀመረ"

ከዚያ አገር ነዋሪዎች መሃል አንዱ
"የዚያ አገር ሰው"

አሳሞችን ለመመገብ
"ለሰውየው አሳሞች ምግብ ለመስጠት"

ደስ ብሎት በተመገበ ነበር/ሊያገኝ ተመኘ
"አግኝቶ ሊበላ በጣም ይፈልግ ነበር።" ይህ የሆነው በመራቡ ምክንያት እንደሆነ ግልጽ ነው። እንዲህ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "ቢያገኝ በደስታ እስኪመገብ ድረስ በጣም ተርቦ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰብል ግልፋፊ
እነዚህ ዐሰር ናቸው። "የባቄላ ግልፋፊ" ወይም "የባቄላ/በቆሎ ልባስ" በሚለው ወስጥ እንደሚገኘው። (ያልታወቀውን መተረጎም የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 15:17

ወደ ልቡ ተመለሰ
የዚህ ፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉም፣ ከፍ ያለ ስህተት እንደፈጸመ እና እውነታው ምን እንደነበረ አስተዋለ። "በግልጽ ሁኔታውን ተረዳ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ምን ያህሉ የአባቴ ተቀጣሪ ሰራተኞች ከሚያስፈልጋቸው በላይ ምግብ ያገኛሉ
ይህ የማጋነኑ አንዱ ክፍል ነው፤ እናም ጥያቄ አልነበረም። "የአባቴ አጋልጋዮች ሁሉ ከሚያስፈልጋቸው በላይ ምግብ አላቸው"

ከረሃብ የተነሳ መሞት
ይህ ምናልባት ማጋነን አይደለም። ወጣቱ ሰው በእርግጥም ተረቧል።

በሰማይ ፊት በደልኩ
የአይሁድ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ "እግዚአብሔር" የሚለውን ቃል "ሰማይ" በሚል ተክተው ይጠቀማሉ። "በእግዚአብሔር ፊት በደልኩ" በሚለው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህ ልጅህ ተብዬ ልጠራ አይገባኝም
"ልጅህ ተብዬ ልጠራ አይገባኝም።" ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ልጄ ብለህ ልትጠራኝ አይገባኝም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ከተቀጣሪ ሰራተኞችህ አንዱ አድርገኝ
"እንደ አንድ አገልጋይህ ቅጠረኝ" ወይም "ቅጠረኝ እኔም ከሰራተኞችህ እንደ አንዱ እሆናለሁ።" ይህ ጥያቄ ነው፤ ትዕዛዝ አይደለም። በዩቢዲ ውስጥ እንደሚገኘው "እባክህ" የሚለው ቢጨመር ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

Luke 15:20

ስለዚህም ታናሹ ልጅ ወደ አባቱ ተመለሰ
"ስለዚህ ከሄደበት አገር ወደ አባቱ ተመለሰ።" "ስለዚህ" የሚለው ቃል የሆነውን ድርጊት አስቀድሞ በሆነው ሌላ ነገር ምክንየት እንደሆነ ያመለክታል። በዚህ ሁኔታ፣ ወጣቱ ሰው ሲቸግረው ወደ ቤት ለመመለስ ወሰነ።

ገና ከሩቅ ስፍራ ሳለ
"ገና ከቤቱ ሩቅ ስፍራ ሳለ" ወይም "ገና ከአባቱ ቤት ሩቅ ስፍራ ሳለ"

በርህራሄ ቀረበው
"ለእርሱ ርህራሄ ነበረው" ወይም "እጅግ ከልቡ ይወደው ነበር"

አቅፎ ሳመው
አባቱ ይህን ያደረገው እንደሚወደው ለልጁ ለማሳየት እና ልጁ ተመልሶ ቤት በመምጣቱ ስለተደሰተ ነበር። ሰዎች አባት ወንድ ልጁን ማቀፉ ወይም መሳሙ እንግዳ ነገር ወይም ስህተት ነው ብለው የሚያስቡ ከሆነ፣ በባህላችሁ አባቶች ለወንድ ልጆቸው ያላቸውን ፍቅር የሚገልጹበትን መንገድ ተክታችሁ መተርጎም ትችላላችሁ። "እርሱን በፍቅር ተቀበለው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

በሰማይ ፊት መበደል
የአይሁድ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ "እግዚአብሔር" የሚለውን ቃል "ሰማይ" በሚል ተክተው ይጠቀማሉ። ይህ በሉቃስ 15:18 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ። "እግዚአብሔርን በደልኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህ ልጅህ ተብዬ ልጠራ አይገባኝም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። ተመሳሳይ የሆነው ሀረግ በሉቃስ 15:18 ላ እንዴት እንደ ተተረጎም ይመልከቱ።"ልጄ ብለህ ልትጠራኝ አይገባኝም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 15:22

ምርጥ ካባ/ልብስ
"በቤት ካለው ምርጡን ልብስ።" "ምርጡን ኮት" ወይም "ምርጡን ጨርቅ"

ለጣቱ ቀለበት አድርጉለት
ቀለበት ወንዶች ከጣታቸው መሃል በአንዱ የሚያጠልቁት የስልጣን ምልክት ነበር።

ነጠላ ጫማ
በዘመኑ ባለጸጋ ሰዎች ነጠላ ጫማ ያደርጉ ነበር። ሆኖም፣ በብዙ ባህሎች የዚህ ዘመናዊ አቻ የሆነው "ጫማ" ነው።

የሰባ ጥጃ
ጥጃ ገና በሬ ያለሆነ ነው። ሰዎች ጥጃዎች በሚገባ እንያድጉ ጥሩ አድረገው ይቀለቀቧቸዋል፤ ከዚያም የተለየ ድግስ ሲኖርባቸው ይመገቧቸዋል/አርደው ይበሏቸዋል። "የሰባውን ፍሪዳ" ወይም "በሚገባ ያባነውን ወይፈን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እረዱ
ለምን ፍሪዳው እንደታረደ በውስጠታዋቂነት ያለው መረጃ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "አርዳችሁ ስሩት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ልጄ ሞቶ ነበር፣ አሁን በሕይወት አለ
ይህ ዘይቤ የሚናገረው የኮበለለውን ልጅ እንደሞተ አድርጎ ነው። "ልጄ ከሞተ በኋላ ዳግም ህያው እንደሆነ ይቆጠራል" ወይም "ልጄ ሞቶ እንደነበረ እና አሁን ዳግም ህያው እንደሆነ ይሰማኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጠፍቶ ነበር፣ አሁን ተገኘ
ይህ ዘይቤ የሚናገረው የልጁን መኮብለል/መሄድ እንደጠፋ አድርጎ ነው። "ልጄ ጠፍቶ ነበር አሁን ግን አገኘሁት" ወይም "ልጄ ጠፍቶ ነበር አሁን ቤት ተመለሰ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 15:25

አሁን
እዚህ ስፍራ ይህ ቃለ የዋለው በዋናው የታሪክ መስመር ማቆሚያ ለማበጀት ነው። እዚህ ስፍራ ኢየሱስ ስለ ታላቁ ልጅ አዲሱን የታሪኩን ክፍል መናገር ይጀምራል።

ውጭ በመስክ/በእርሻ
እርሱ ውጭ በመስክ ላይ እንደነበረ ተጠቅሷል፣ ምክንያቱም በዚያ በሥራ ላይ ነበር። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከአገልጋዮቹ አንዱ
እዚህ ስፍራ "አገልጋይ" ተብሎ የተተረጎመው ቃል በቀጥታ "ልጅ" በሚል ተተርጉሟል። ይህ አገልጋዩ በጣም ወጣት እንደሆነ ያመለክታል።

እነዚህ ነገሮች ምን ይሆናሉ
"ምን እየሆነ ነበር"

የሰባ ጥጃ
ጥጃ ገና በሬ ያለሆነ ነው። ሰዎች ጥጃዎች በሚገባ እንያድጉ ጥሩ አድረገው ይቀለቀቧቸዋል፤ ከዚያም የተለየ ድግስ ሲኖርባቸው ይመገቧቸዋል/አርደው ይበሏቸዋል።ይህ ሀረግ በሉቃስ 15:23 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "የሰባው/ምርጡ ጥጃ" "ያሰባነው ወይፈን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 15:28

እነዚህ ብዙ አመታት
"ለብዙ አመታት"

ለአንተ ባሪያ ሆንኩ
"ለአንተ እጅግ በከባዱ ሰራሁ" ወይም "ለአንተ እንደ ባሪያ በከባዱ ሰራሁ"

በፍጹም የአንተን አንዲት ህግ አልጣስኩም
"በፍጹም ከትእዛዝህ አልወጣሁም" ወይም "ሁልጊዜም አድርግ ያልከኝን ሁሉ አድርጌያለሁ"

አንዲት ትንሽ ፍየል
ትንሽ ፍየል ከሰባ ጥጃ ያነሰች እና ዋጋዋም ዝቅተኛ ነበረች። "ትንሽ ፍየል እንኳን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ ልጅ
"ያ የአንተ ልጅ።" ትልቁ ልጅ ወንድሙን በዚህ መንገድ የሚገልጸው ምን ያህል እንደተናደደ ለማሳየት ነው።

ሀብትህን/ኑሮህን በላ
ምግብ ለገንዘብ ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። አንድ ሰው ምግብን ከተመገበው በኋላ፣ ምግቡ ዳግመኛ አይበላም። ወንድሙ ከወሰደው ገንዘብ አንዳች አልተረፈም፤ ምንም ነገር አልቀረም። "ሀብትህን ሁሉ አባከነ" ወይም "ገንዘብህን ሁሉ በተነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከጋለሞቶች ጋር
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ወንድሙ ገንዘቡን ያባከነው እንደዚህ ነው ብሎ ገምቷል፣ ወይም 2) ስለ ጋለሞቶች የተናገረው "በሄደበት ሩቅ አገር" ወንድሙ የሰራቸውን የኃጢአተኝነት ድርጊቶች ለማጋነን ነው (ሉቃስ 15፡13)። (ኩሸት እና አጠቃላ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

የሰባ ጥጃ
ጥጃ ገና በሬ ያለሆነ ነው። ሰዎች ጥጃዎች በሚገባ እንያድጉ ጥሩ አድረገው ይቀለቀቧቸዋል፤ ከዚያም የተለየ ድግስ ሲኖርባቸው ይመገቧቸዋል/አርደው ይበሏቸዋል።ይህ ሀረግ በሉቃስ 15:23 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "የሰባው/ምርጡ ጥጃ" "ያሰባነው ወይፈን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **16**

1 ደግሞም ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ፤ "አንድ ሀብታም ሰው ነበረ፤ እርሱም በንብረቱ ሁሉ ላይ የሾመው አስተዳዳሪ ነበረው። ይህ አስተዳዳሪ ሀብቱ
ያባክናል ተብሎ ለሀብታሙ ተነገረው። **2** ስለዚህ ሀብታሙ ሰው አስተዳዳሪውን ጠርቶ፣ 'ይህ ስለ አንተ የምሰማው ነገር ምንድን ነው? ከዚህ በኋላ ለእኔ
አስተዳዳሪ ልትሆን ስለማትችል ንብረቴን አስረክበኝ' አለው። **3** አስተዳዳሪው እንዲህ ብሎ አሰበ፤ 'እንግዲህ ጌታዬ ከአስተዳደር ሥራዬ ስለሚያሰናብተኝ፣ ምን
ባደርግ ይሻለኛል? ዓቅም ስለሌለኝ፣ ከእንግዲህ መሬት በመቈፈር ለመተዳደር አልችልም፤ መለመንም ያሳፍረኛል። **4** ከአስተዳዳሪነት ሥራዬ ስሰናበት፣ ሰዎች
በቤታቸው እንዲቀበሉኝ ካሁኑ ምን እንደማደርግ ዐውቃለሁ።' **5** ከዚያም አስተዳዳሪው የጌታውን ተበዳሪዎች አንድ በአንድ ጠርቶ፣ የመጀመሪያውን ሰው 'ያለብህ
ዕዳ ምን ያህል ነው?' ብሎ ጠየቀው። **6** እርሱም፣ 'አንድ መቶ ማድጋ ዘይት አለብኝ' አለ። አስተዳዳሪውም፣ 'በፈረምኸው ውል ላይ ዐምሳ ማድጋ ብለህ ጻፍ'
አለው። **7** ሌላውንም፣ 'አንተስ ስንት ዕዳ አለብህ?' ብሎ ጠየቀው። እርሱም፣ 'መቶ ኩንታል ስንዴ አለብኝ' አለ፤ በፈረምኸው ውል ላይ ሰማንያ ኩንታል ብለህ
ጻፍ' አለው። **8** ጌታውም እምነት ያጎደው አስተዳዳሪ ያደረገውን ሰምቶ፤ በብልኅነቱ በመደነቅ እንዲህ አለ፤ 'በዚህ ዓለም እግዚአብሔርን የማያውቁ ሰዎች
እግዚአብሔርን ከሚያውቁ ሰዎች ይልቅ በዓለማዊ ሥራቸው ብልኆች ናቸው። **9** ስለዚህ እላችኋለሁ፣ በዓለም ባላችሁ ሀብት ለራሳችሁ ወዳጆችን አፍሩበት፤
ምክንያቱም ሀብታችሁ ባለቀ ጊዜ በዘላለም ቤቶች ይቀበሉአችኋል። **10** በጥቂቱ የታመነ ሰው በብዙ ላይ የታመነ ይሆናል፤ በጥቂቱ የሚያምፅ በብዙም
ዐመፀኛ ይሆናል። **11** ስለዚህ በዚህ ዓለም ሀብት ካልታመናችሁ እውነተኛውን ሀብትማ ማን አምኖ ይሰጣችኋል? **12** እንደዚሁም በሌላ ሰው ሀብት
ካልታመናችሁ የራሳችሁን ማን ይሰጣችኋል? **13** ሁለት ጌቶችን ማገልገል የሚችል ማንም የለም፤ አንዱን ይተዋል፤ ሌላውን ይወዳል፤ አለበለዚያም ለአንዱ
ራሱን የሰጠ ይሆናል፤ሌላውን ደግሞ ይንቃል። ስለሆነም ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም። **14** ገንዘብን የሚወዱ ፈሪሳውያን ይህን ሁሉ ሰምተው፣
በኢየሱስ ላይ አፌዙበት። **15** እርሱም እንዲህ አላቸው፤ "እናንተ በሰው ፊት ራሳችሁን እንደ ጻድቃን ትቈጥራላችሁ፣ እግዚአብሔር ግን ልባችሁን ያውቃል።
በሰዎች ፊት የከበረ በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ነው።" **16** ሕግና ነቢያት እስከ መጥምቁ ዮሐንስ ድረስ ሲሠራባቸው ኖረዋል። ከዚያ በኋላ ግን
የእግዚአብሔር መንግሥት ወንጌል ተሰብኳል። ሰው ሁሉ ወደዚህ ለመግባት ይጋፋል። **17** ነገር ግን ከሕግ አንድ ነጥብ ዋጋ ከሚያጣ ሰማይና ምድር ቢያልፍ
ይቀላል። **18** ማንም ሚስቱን ፈትቶ ሌላይቱን የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል፤ ከባሏ የተፋታችውንም የሚያገባ ያመነዝራል። **19** ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ "ሐምራዊና
ቀጭን የሐር ልብስ የለበሰ በየቀኑም በምኞትና በደስታ የሚኖር ሀብታም ሰው ነበረ። **20** ሰውነቱ በቊስል የተወረረ አልዓዛር የሚባል ለማኝም በሀብታሙ ሰው
ደጅ ይተኛ ነበር። **21** አልዓዛርም ከሀብታሙ ማዕድ የተረፈውን ፍርፋሪ ሊመገብ ይመኝ ነበር። ውሾች እንኳ እየመጡ ቍስሉን ይልሱ ነበር። **22** ከጊዜ በኋላ
ለማኙ ሞተ፤መላእክትም መጥተው ወደ አብርሃም አጠገብ ወሰዱት። ሀብታሙም ሞተ፤ ተቀበረም። **23** ሀብታሙ በሲኦል እየተሠቃየ ሳለ፣ ቀና ብሎ አብርሃም
አልዓዛርን በዕቅፉ ይዞት አየ። **24** እርሱም፣ 'አብርሃም አባት ሆይ፣ ራራልኝ በዚህ ነበልባል እየተሠቃየሁ ስለ ሆነ፣ አልዓዛር የጣቱን ጫፍ በውሃ ነክሮ ምላሴን
እንዲያቀዘቅዝልኝ እባክህ አልዓዛርን' ላክልኝ ብሎ ጮኸ። **25** አብርሃም ግን እንዲህ አለው፤ "ልጄ ሆይ፣ አንተ በምድር የሕይወት ዘመንህ መልካም ነገሮችን
እንደተቀበልህና በደስታ እንደ ኖርህ፤ አልዓዛርም ክፉ ነገሮችን ሲቀበል እንደ ኖረ አስታውስ። አሁን ግን አልዓዛር እዚህ በምቾት ሲኖር፣ አንተ በሥቃይ ላይ
ትገኛለህ። **26** ከሁሉ በላይ ከዚህ ወደ እናንተ ለማለፍ የሚፈልጉ እንዳይሻገሩ እዚያ ያሉትም ወደ እኛ እንዳይመጡ በእኛና በእናንተ መካከል ትልቅ ገደል አለ።'
27 ሀብታሙ ሰው እንዲህ አለ፤ 'አባት ሆይ፣ እንግዲያውስ አልዓዛርን ወደ አባቴ ቤተ ሰብ እንድትሰደው እለምንሃለሁ፤ **28** ምክንያቱም አምስት ወንድሞች
አሉኝና እነርሱ ወደዚህ ሥቃይ ቦታ እንዳይመጡ ያስጠንቅቃቸው።' **29** አብርሃም ግን፣ 'ወንድሞችህ ሙሴና ነቢያት አሏቸው፤ እነርሱንም ይስሙአቸው' ብሎ
መለሰለት። ነገር ግን **30** ሀብታሙ ሰው፣ 'አብርሃም አባት ሆይ፣ እንደዚህ አይደለም፤ አንድ ሰው ከሙታን ተነሥቶ ሄዶ ቢነግራቸው ንስሓ ይገባሉ' አለ። **31**
አብርሃም ግን ሙሴንና ነቢያትን የማይሰሙ ከሆነ፣ አንድ ሰው ከሙታን ተነሥቶ ቢነግራቸው እንኳ አያምኑም' አለው።

Luke 16:1

አያያዥ ሀሳብ፡
ኢየሱስ ሌላ ግብረገባዊ ምሳሌ መናገር ጀመረ። ይህም ስለ አንድ ጌታ እና ገንዘቡን ስለሚያበድርለት አስተዳዳሪ ነበር። ይህም ቢሆን በሉቃስ 15:3 ውስጥ የጀምረው ተመሳሳይ ታሪክ ክፍል እና በተመሳሳይ ቀን የተናገረው ነው። (ግብረገባዊ ምሳሌ የሚለውን ይመልከቱ)

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ
ምንም እንኳን የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ተሰብስቦ ከሚያደምጠው ሕዝብ ውስጥ ቢሆኑም፣ የመጨረሻው ክፍል ፈሪሳውያንን እና ጸሐፍትን ያመለክታል።

አንድ ባለጸጋ ሰው ነበር
ይህ በግብረገባዊ ምሳሌው ውስጥ አዲስ ገጸባህሪን ያስተዋውቃል። (አዲስ እና ነበር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእርሱ ተነገረው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች ለባለጸጋው ሰው ነገሩት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ሃብቱን እያባከነ እንደሆነ
"የባለጸጋውን ሰው ንብረት በንዝህላልነት እያስተዳደረ እንደሆነ"

ይህ ስለ አንተ የምሰማው ነገር ምንድን ነው?
ባለጸጋው ሰው ጥያቄውን ያነሳው የሃብቱን አስተዳዳሪ ለመገሰጽ ነው። "እያደረግህ የምትገኘውን ሰምቻለሁ።" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 16:3

ምን ላድርግ...ምን ማድረግ ይገባኛል?
አስተዳዳሪው፣ ያሉትን አማራጮች ለመመልከት ሲል ይህንን ጥያቄ ያነሳው ለራሱ ነው። "ስለዚህ ሥራ...ማድረግ ያለብኝን ማሰብ ያስፈልገኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይልከቱ)

አለቃዬ/ጌታዬ
ይህ የሚያመለክተው ባለጸጋውን ሰው ነው። አስተዳዳሪው ባሪያ አልነበረም። "ቀጣሪዬ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ለመቆፈር አቅም የለኝም
"መሬት ለመቆፈር አቅም የለኝም" ወይም "መቆፈር/ማረስ አልችልም"

ከአስተዳዳሪነት ሥራዬ ስወገድ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የማስተዳደር ሥራዬን ሳጣ" ወይም "ጌታዬ የአስተዳዳሪነት ሥራዬን ሲወስድብኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሰዎች በቤታቸው ይቀበሉኛል
ይህ እነዚያ ሰዎች ሥራ፣ ወይም ለኑሮ የሚያስፈልገውን ሌሎች ነገሮች እንደሚሰጡት ያመለክታል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 16:5

ከእርሱ አለቃ ተበዳሪዎች/ባለዕዳዎች
"የአለቃው ንብረት ብድር የነበረባቸው ሰዎች" ወይም "የእርሱ አለቃ ሀብት በእጃቸው የነበረ ሰዎች።" በዚህ ታሪክ ውስጥ ተበዳሪዎች/ባለዕዳዎቹ የነበረባቸው የወይራ ዘይት እና ስንዴ ነበር።

እርሱ አለ...እርሱ እንዲህ አለው
"ተበዳሪው/ባለዕዳው አለ... አስተዳዳሪው ለባለዕዳው እንዲህ አለው"

አንድ መቶ ማድጋ የወይራ ዘይት
ይህ ወደ 3,000 ሊትር የወይራ ዘይት ነው። (መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት ዘመን የነበረ የመጠን መለኪያ)

መቶ...ሀምሳ...ሰማንያ
"100...50...80" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

የውል ወረቀትህን ውሰድ
"የውል ወረቀት" አንድ ሰው ምን ያህል እንዳለበት የሚያሳይ ወረቀት ነው።

አስተዳዳሪው ሌላውንም ሰው... እንዲህ አለው...ለእርሱ እንዲህ አለ
"አስተዳዳሪው ለሌላው ተበዳሪ እንዲህ አለ...ተበዳሪው/ባለዕዳው እንዲህ አለ...አስተዳዳሪው ባለእዳውን አለው

መቶ ዳውላ ስንዴ
ይህን ወደ ዘመናዊ መለኪያ መለወጥ ትችላላችሁ። "ሃያ ሺህ ኪሎ ስንዴ" ወይም "አንድ ሺህ ቅርጫት ስንዴ" (መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት ዘመን የነበረ የመጠን መለኪያ)

ሰማንያ ብለህ ጻፍ
"ሰማንያ ዳውላ ስንዴ ብለህ ጻፍ።" ይህን ወደ ዘመናዊ መለኪያ መለወጥ ትችላላችሁ። "አሥራ ስድስት ሺህ ኪሎ ስንዴ" ወይም "ስምንት መቶ ቅርጫት ብለህ ጻፍ"

Luke 16:8

አያያዥ ሀሳብ፡
ኢየሱስ ስለ ባለሃብቱ እና ሃብቱን ያበድርለት ስለነበረው አስተዳዳሪ የሚናገረውን ምሳሌ ጨረሰ። በቁጥር 9 ላይ፣ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ማስተማሩን ቀጠለ።

ከዚያም ጌታው አመሰገነው
ጽሁፉ ጌታው እንዴት የአሰተዳዳሪውን ድርጊት እንዳወቀ አይናገርም

አመሰገነ
"አወደሰ" ወይም "በመነልካም አየው" ወይም "ተቀበለው/አጸደቀለት"

በብልሃት አደረገ
"በዘዴ አደረገ" ወይም "ምክንያታዊ በሆነ መንገድ አደረገ"

የዚህ ዓለም ልጆች
ይህ የሚያመለክተው ስለ እግዚአብሔር ስለማያውቁ ወይም ግድ ስለማይላቸው ትክክለኛ እንዳልሆነው አስተዳዳሪ ያሉትን ነው። "የዚህ ዓለም ሰዎች" ወይም "ዓለማውያን ሰዎች"

የብርሃን ልጆች
እዚህ ስፍራ "ብርሃን" እግዚአብሔራዊ/ቅዱስ ለሆኑ ነገሮች ሁሉ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "የእግዚአብሔር ሰዎች" ወይም "ቅዱሳን ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ግን እላችኋለሁ
"እኔ" የሚለው የሚያመለክተው ኢየሱስን ነው። "እኔ ግን እላችኋለሁ" የሚለው ሀረግ የታሪኩን ማጠቃላያ ያሳያል፤ አሁን ኢየሱስ ሰዎቹ እንዴት ታሪኩን በህይወታቸው ተግባራዊ እንደሚያደርጉት ይነግራቸዋል።

ጻድቅ ባልሆነው ሃብት/በዚህ ዓለም ገንዘብ ለራሳችሁ ባልንጀሮችን አፍሩ
እዚህ ስፍራ ትኩረት የተሰጠው ገንዘብን ሌሎችን ለመርዳት ስለመጠቀም ነው። "በዓለማዊ ሃብት እነርሱን በመርዳት ሰዎችን ወዳጆቻችሁ አድርጓቸው"

ጻድቅ ባልሆነ ሀብት አማካይነት
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ኢየሱስ ገንዘብን "ጻድቅ ያልሆነ" ብሎ ሲጠራው ግነት እየተጠቀመ ነው፤ ምክንያቱም ዘላለማዊ ዋጋ የለውም። "ዘላለማዊ ዋጋ የሌለውን ገንዘብን በመጠቀም" ወይም "ምድራዊ ገንዘብን በመጠቀም" ወይም 2) ኢየሱስ ገንዘብን "ጻድቅ ያልሆነ" ብሎ በመጥራት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ይጠቀማል፤ ምክንያቱም ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ገንዘብን ትክክል ባልሆነ መንገድ ያገኙታል ወይም ጠቀሙበታል። "ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ ያገኛችሁትን ገንዘብ በመጠቀም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ኩሸት እንደዚሁም አጠቃላ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

እነርሱ ይቀበሏችኋል
ይህ የሚያመለክተው 1) ገንዘባቸውን ሌሎችን ለመርዳት ባዋሉት ደስ የሚሰኝ በሰማይ ያለ እግዚአብሔር፣ ወይም 2) በገንዘባችሁ የረዳችኋቸው ወዳጆቻችሁ።

ዘላለማዊ መኖሪያዎች
ይህ የእግዚአብሔር መኖሪያን፣ ሰማይን ያመለክታል።

Luke 16:13

የትኛውም አገልጋይ አይችልም
"አንድ አገልጋይ አይችልም"

ሁለት ጌቶች ማገልግል
"ሁለት የተለያዩ ጌቶችን በአንድ ጊዜ ማገልግል እንደማይችል" በውስጠ ታዋቂነት ተጠቁሟል

እርሱ አንዱን ...አሊያም ደግሞ እርሱ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ናቸው። ብቸኛው እና ዋናው ልዩነታቸው በመጀሪያው ሀረግ የመጀመሪያው ጌታ ይጠላል፣ ሁለተኛው ጌታ በሁለተኛው ሀረግ ይጠላል።

Luke 16:14

አጠቃላይ መረጃ፡
በቁጥር 14 ላይ ፈሪሳውያን በኢየሱስ ላይ እንዳፉዙበት የመረጃ ዳራ እንደሚጥ ይህ በኢየሱስ ትምህርት ማቆሚያ/ማረፊያ ነው። በቁጥር 15 ኢየሱስ ትምህርቱን ይቀጣላል ደግሞም ለፈሪሳውያን ምላሽ ይሰጣል፡፤ (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

አሁን
ይህ ቃል ወደ መረጃ ዳራው ያመለክታል

ገንዘብ ወዳጅ የነበሩት
"ገንዘብ እንዲኖራቸው የሚወዱ" ወይም "ለገንዘብ በጣም ስስታም የነበሩ"

አፌዙበት
"ፈሪሳውያን በኢየሱስ ላይ አፌዙ"

እንዲህ አላቸው
"ኢየሱስ ለፈሪሳውያን እንዲህ አላቸው"

በሰዎች ፊት ራሳችሁን ትክክለኛ አድርጋችሁ ታቀርባላችሁ
"ራሳችሁን በሰዎች ፊት መልካም አድርጋችሁ ለማሳየት ትሞክራላችሁ"

እግዚአብሔር ልቦቻችሁን ያውቃል
እዚህ ስፍራ "ልቦች" የሚለው የሚያመለክተው የሰዎችን ፍላጎት ነው። "እግዚአብሔር እውነተኛ ፍላጎቶቻችሁን ያውቃል" ወይም "እግዚአብሔር ለምን እንደምታደርጉ አንቀሳቃሽ ምክንያታችሁን/ሰበበ ነገራችሁን ያውቃል" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በሰዎች መሃል ራሱን ከፍ የሚያደርግ በእግዚአብሔር ዐይኖች የተጣላ ነው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች በጣም ጠቃሚ ናቸው ብለው የሚያስቧቸው ነገሮች እግዚአብሔር የሚጠላቸው ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 16:16

ህጉ እና ነቢያቱ
ይህ እስከዚያ ጊዜ ድረስ የተጻፈውን የእግዚአብሔርን ቃል ሁሉ በአጠቃላይ ያመለክታል

የሐንስ መጣ
x

Luke 16:18

ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ
"ማንም ሚስቱን የሚፈታ" ወይም "ማንም ሚስቱን የሚፈታ ሰው"

ዝሙት መፈጸም
"በዝሙት ምክንያት ጥፋተኛ መሆን"

አንዲቱን ያገባ
"አንዲት ሴት ያገባ ወንድ"

Luke 16:19

አያያዥ ሀሳብ፡
ኢየሱስ ህዝቡን ማስተማሩን እየቀጠለ ሳለ፤ አንድ ታሪክ መናገር ጀመረ። ይህም ስለ አልዓዛር እና ስለ አንድ ሀብታም ነው።

አጠቃላይ መረጃ፡
እነዚህ ቁጥሮች ኢየሱስ ስለ ሀብታሙ ሰው እና አልዓዛር የሚናገረውን ታሪክ የመረጃ ዳራ ይሰጣሉ። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

አሁን/እነሆ
ይህ ኢየሱስ ታሪኩን መናገር ሲጀምር የሚያስተምራቸውን መረዳት እንዲችሉ ለታሪኩ ጅማሬ ምልከት ይሰጣል

አንድ ባለጸጋ ሰው
ይህ ሀረግ በኢየሱስ ታሪክ ውስጥ አንድን ሰው ያስተዋውቃል። ይህ ሰው በእውን የነበረ ይሁን ወይስ ኢየሱስ ሊያስተምር የፈለገውን ነጥብ ግልጽ ለማድረግ በዚህ ታሪክ ውስጥ ብቻ የሚገኝ ስለመሆኑ ግልጽ አይደለም። (አዲስ እና ነበር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

ሐምራዊ እና ያማረ ሊኖ የለበሰ
x

Luke 16:22

እንዲህም ሆነ
እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ውስጥ መሸጋገሪያ ሆኖ ነው። የእናንተ ቋንቋ ይህን ለማድረግ መንገድ ካለው እዚህ ላይ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

መላዕክት ይዘውት ሄዱ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "መላዕክት ወሰዱት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 16:25

ልጄ
ባለጸጋው ከአብርሃም ዘር አንዱ ነበር

Luke 16:27

ወደ አባቴ ቤት እርሱን ላከው
"አልዓዛር ወደ አባቴ ቤት እንዲሄድ ንገረው" ወይም "እባክህ፣ ወደ አባቴ ቤት እርሱን ላከው"

የአባቴ ቤት
ይህ በቤት ውስጥ የሚገኙ ሰዎችን ያመለክታል። "ቤተሰቤ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ያስጠነቅቃቸው ዘንድ
"አልዓዛር እንዲያስጠነቅቃቸው"

ይህ የከፍተኛ ጭንቅ ስፍራ
"በስቃይ የምንጨነቅበት ይህ ስፍራ" ወይም "በአስጨናቂ ስቃይ ውስጥ የምንገኝበት ይህ ስፍራ"

Luke 16:29

አያያዥ ሀሳብ፡
ኢየሱስ ስለ ባለጸጋው ሰው እና አልዓዛር የሚናገረውን ታሪክ ጨረሰ።

ሙሴ እና ነቢያት
ይህ ጽሁፋቸውን ያመለክታል። "ሙሴ እና ነቢያት የጻፉት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱን ይስሟቸው
"ወንድሞችህ ለሙሴ እና ነቢያት ትኩረት መስጠት አለባቸው"

አንድ ሰው ከሙታን መሃል ወደ እነርሱ ቢሄድ
ይህ ያልተፈጸመ ሁኔታን ይገልጻል፣ ነገር ግን ያባለጸጋ ሰው ይህ ቢሆን ይወዳል። "አንድ ሰው ከሙታን መሃል ወደ እነርሱ ቢሄድ" ወይም "አንድ የሞተ ሰው ተነስቶ ሄዶ ቢያስጠነቅቃቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ከሙታን መሃል
አስቀድሞ ከሞቱት ሁሉ ውስጥ። ይህ ሁኔታ የሚገልጸው በዓለም ከርሰ ምድር የተቀበሩ ሙታንን ሁሉ ነው።

ሙሴን እና ነቢቱን ካልሰሙ
እዚህ ስፍራ "ሙሴ እና ነቢያቱ" የሚለው የሚወክለው እነርሱ የጻፏቸውን ነገሮች ነው። "ሙሴ እና ነቢያት ለጻፉት ትኩረት የማይሰጡ ከሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ሰው ከሙታን ቢነሳም እነርሱ አይሰሙም
አብርሃም መላምታዊው ሁኔታ ቢሆን/ቢፈጸምም የሚገሆነውን ይገልጻል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ከሙታን ተመልሶ የመጣም ሰው ቢሆን እነርሱን ማሳመን አይችልም" ወይም "አንድ ሰው ከሞት ተመልሶ ቢመጣም እነርሱ አያምኑም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መላምታዊ ሁኔታዎች እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከሙታን ተነስቶ
x

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 17

1 ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አላቸው፤ "ወደ ኅጢአት የሚያመሩ ነገሮች መምጣታቸው የማይቀር ነው። ነገር ግን ለኅጢአት ምክንያት ለሚሆነው ሰው
ወዮለት። 2 በእምነት ደካማ ከሆኑት ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን ከማስናከል ይልቅ ትልቅ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ባሕር ቢጣል ይሻለዋል። 3 ለራሳችሁ
ተጠንቀቁ። ወንድምህ ቢበድልህ ገሥጸው፤ ተመልሶ ከተጸጸተ ይቅር በለው፤ 4 በቀንም ሰባት ጊዜ እንኳ ቢበድልህና ሰባት ጊዜ ተመላልሶ፤ 'ስለ ሠራሁት
ኅጢአት ተጸጸትሁ' እያለ ወደ አንተ ቢመለስ ይቅር ልትለው ይገባል።" 5 ሐዋርያት ጌታን፣ "እምነት ጨምርልን" አሉት። 6 ጌታም እንዲህ ብሎ መለሰላቸው፣
"የሰናፍጭን ዘር ያህል እምነት ቢኖራችሁ፤ ይህን የሾላ ዛፍ፣ 'ከመሬት ተነቅለህ ወደ ባሕር ተተከል' ብትሉት ይታዘዝላችኋል። 7 "በዕርሻ ወይም በበጎች እረኝነት
የተሰማራ አገልጋይ ካላችሁ፣ አገልጋዩ ከሥራ ደክሞ ሲመለስ፣ ወዲያውኑ "ና ተቀመጥና እራትህን ብላ የሚለው ከእናንተ ማን ነው?" 8 "እራቴን አዘጋጅልኝ፤
እስክበላና እስክጠጣም ወገብህን ታጥቀህ ቆመህ አስተናግደኝ፤ ከዚያ በኋላ አንተ ደግሞ ትበላለህ ትጠጣለህም አይለውምን?" 9 ታዲያ አገልጋዩ
የታዘዘውን ስለ ፈጸመ ጌታው ያመሰግነዋልን? 10 እንዲሁም እናንተም የታዘዛችሁትን ሁሉ ከፈጸማችሁ በኋላ የማንጠቅም አገልጋዮች ነን፤ 'የፈጸምነውም
የታዘዝንውን ግዳጃችንን ብቻ ነው' ማለት አለባችሁ።" 11 ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ ሳለ፣ ሰማርያንና ገሊላን በሚያዋስነው መንገድ
ያልፉ ነበር። 12 ኢየሱስም ወደ አንዲት መንደር በገባ ጊዜ ዐሥር ለምጻሞች አገኙት። እነርሱም ከእርሱ ርቀው ቆሙና 13 ድምፃቸውን ከፍ አድርገው፣ "ኢየሱስ
ሆይ፣ መምህር ሆይ፣ እባክህ ማረን" እያሉ ጮኹ። 14 ኢየሱስ ባያቸው ጊዜ፣ "ሂዱና ራሳችሁን ለካህናት አሳዩ" አላቸው። እነርሱም እየሄዱ ሳሉ፣ ከለምጻቸው
ነጹ። 15 ከእነርሱ አንዱ ከለምጹ መፈወሱን ባየ ጊዜ፣ ጮክ ብሎ እግዚአብሔርን እያከበረ ተመለሰ። 16 በኢየሱስ እግር ሥር በግንባሩ ተደፍቶ አመሰገነው።
እርሱም የሰማርያ ሰው ነበር። 17 ኢየሱስ መልሶ እንዲህ አለ፣ "ዐሥሩም ለምጻሞች ተፈውሰው አልነበረምን? ታዲያ ዘጠኙ የት አሉ? 18 ከዚህ ከባዕድ ሰው
በቀር እግዚአብርሔን ለማመስገን ተመልሶ የመጣ ሌላ የለምን?" 19 ኢየሱስ ሰውየውን፣ "ተነሥና ሂድ እምነትህ አድኖሃል" አለው። 20 ፈሪሳውያን ኢየሱስን፣
"የእግዚአብሔር መንግሥት መቼ ትመጣለች?" ብለው ለጠየቁት ጥያቄ እንዲህ ብሎ መለሰላቸው፤ "የእግዚአብሔር መንግሥት የምትታይ አይደለችም።"
ወይም'እነሆ፣ እዚህ ናት' 21 ወይም 'እነሆ፣እዚያ ናት' የምትባል አይደለችም። ምክንያቱም የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ ናት።" 22 ኢየሱስ ለደቀ
መዛሙርቱ እንዲህ አላቸው፤" ከሰው ልጅ ቀኖች አንዱን ለማየት የምትናፍቁበት ቀን ይመጣል። ነገር ግን አታዩትም። 23 ሰዎች፣ 'እነሆ፣ ክርስቶስ እዚህ ነው!
ወይም እዚያ ነው!' ይሉአችኋል። ነገር ግን እነርሱን ሰምታችሁ አትፈልጉ፤ አትከተሉአቸውም። 24 መብረቅ በሰማይ ላይ ሲበርቅ ከዳር እስከ ዳር እንደሚያበራ፣
የሰው ልጅም በሚመጣበት ቀን እንዲሁ ይሆናል። 25 ነገር ግን ይህ ከመሆኑ በፊት የሰው ልጅ ብዙ መከራ ሊቀበል ይገባል። በዚህ ዘመን ሰዎችም ሊናቅና
ሊነቀፍ ግድ ነው። 26 በኖኅ ዘመን እንደሆነው፣ በሰው ልጅ ዘመንም እንዲሁ ይሆናል። 27 ኖኅ ወደ መርከብ እስከገባበት ቀን ድረስ ሰዎች ሲበሉና ሲጠጡ፣
ሲያገቡና ሲጋቡና ነበር። ነገር ግን በዚያን ጊዜ የጥፋት ውሃ መጥቶ ሁሉንም አጠፋቸው። 28 እንደዚሁም በሎጥ ዘመን ሰዎች ይበሉ፣ ይጠጡ፣ ይሸጡ
ይገዙ፣ አትክልት ይተክሉና ቤትም ይሠሩ እንደ ነበረ ይሆናል። 29 ሎጥ ከሰዶም በወጣበት ቀን ግን እሳትና ዲን ከሰማይ ዘንቦ ሁሉንም አጠፋ። 30 የሰው ልጅ
በሚገለጥበት ቀንም እንዲሁ ይሆናል። 31 በዚያ ቀን በቤቱ ጣሪያ ላይ ያለ ሰው በቤቱ ውስጥ ያለውን ዕቃ ለመውሰድ አይውረድ። በዕርሻም ቦታ ያለ ሰው ወደ
ቤቱ አይመለስ። 32 የሎጥን ሚስት አስታውሱአት። ሕይወቱን ሊያድን በራሱ መንገድ ለመሄድ የሚፈልግ ሁሉ ያጣታል። 33 ነገር ግን ሕይወቱን ለጌታ አሳልፎ
የሚሰጥ ሁሉ ያድናታል። 34 ይህን እላችኋለሁ፣ "በዚያች ሌሊት ሁለት ሰዎች በአንድ ዐልጋ ላይ ይተኛሉ። 35 ከእነርሱም አንዱ ይወሰዳል፤ ሌላው ይቀራል።
እንዲሁም ሁለት ሴቶች በአንድ ቦታ አብረው ይፈጫሉ፤ 36 አንድዋ ትወሰዳለች ሌላዋ ትቀራለች። ሁለት ሰዎች በአንድ ዕርሻ ቦታ ያርሳሉ፤አንዱ ይወሰዳል፤
ሌላው ይቀራል።" 37 ደቀ መዛሙርቱም ኢየሱስን፦ 'ጌታ ሆይ፤ ወዴት?' ብለው ጠየቁት። እርሱም፦ "በድን ባለበት አሞራዎች ይሰበባሉ።" ሲል መለሰላቸው።

Luke 17:1

አያያዥ ሀሳብ፡
ኢየሱስ ማስተማሩን ቀጥሏል፣ ነገር ግን ንግግሩን ወደ ደቀ መዛሙርቱ መልሷል። ይህ አሁንም የታሪኩ ተመሳሳይ ክፍል ሲሆን በሉቃስ 15:3 ላይ የጀመረውን ታሪክ በዚያው ቀን ማስተማሩን ቀጥሏል።

ኃጢአት እንድንሰራ የሚያደርጉ ነገሮች መኖራቸው የተረጋገጠ ነው
"ሰዎች ኃጢአት እንዲሰሩ የሚፈታተኑ ነገሮች በእርግጥ ይፈጠራሉ"

በእርሱ በኩል እነርሱ ለሚመጡበት ለዚያ ሰው
"ፈተናዎች እንዲመጡ ምክንያት ለሚሆን ሰው" ወይም "ሰዎች እንዲፈተኑ ምክንያት ለሚሆን ሰው"

ለእርሱ...ይሻለዋል
ይህ መላምታዊ ሁኔታን ያስተዋውቃል። ይህ ማለት ይህ ሰው ሰዎች ኃጢአት እንዲሰሩ ምክንያት በመሆኑ የሚደርስበት ቅጣት ባህር ውስጥ ከመስመጥ የከፋ ይሆናል። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ቢወረወር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ዙሪያ አስረው ቢወረውሩት" ወይም "በአንድ ሰው አንገት ዙሪያ ከባድ ድንጋይ ተደርጎ ቢወረወር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእርሱ...በአንገቱ...እርሱ ይሻለው
እነዚህ ቃላት ሴቶችን እና ወንዶችንም ያመለክታሉ። (ጠንቃቃነት የሚገልጹ ቃላት ሴቶችን ሲያካትት የሚለውን ይመልከቱ)

የወፍጮ ድንጋይ
ይህ በጣም ትልቅ፣ ከባድ ክብ ድንጋይ ሲሆን እህል ለመፍጨት የሚያገለግል ነው። "ከባድ ድንጋይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እነዚህ ትንንሾች
ይህ እዚህ ስፍራ የሚያመለክተው እምነታቸው ገና ደካማ የሆነውን ነው። "እነዚህ እምነታቸው ትንሽ የሆነ ሰዎች"

መሰናከል
ይህ ይሁን ሳይባል የሚፈጸምን ኃጢአት የማመልከቻ መንገድ ነው። "ኃጢአት መፈጸም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

Luke 17:3

ወንድምህ ቢበድል
ይህ ምናልባት ወደፊት ሊሆን ስለሚችል ድርጊት የሚናገር ሁኔታዊ ዐረፍተ ነገር ነው።

ወንድምህ
እዚህ ስፍራ "ወንድም" የሚለው ቃል የዋለው ተመሳሳይ እምነት ያለው ሰው በሚለው ስሜት ነው። "መሰል አማኝ"

እርሱን ገስጸው
"የሰራው ስህተት እንደሆነ በብርቱ ንገረው" ወይም "እርሱን አርመው"

ሰባት ጊዜ ቢበድልህ
ይህ መላምታዊ ሁኔታ ነው። ይህ ፈጽሞ ላያጋጥም ይችላል፣ ነገር ግን ቢያጋጥም እንኳን ኢየሱስ ሰዎች ይቅር እንዲሉ ይናገራል።(መላምታዊ ሁኔታ የሚለውን ይመልከቱ)

በቀን ውስጥ ሰባት ጊዜ፣ ደግሞም ሰባት ጊዜ
በመጽሐፍ ቅዱስ ውስት ሰባት ቁጥር ለሙሉነት ምሳሌ/ምልክት ነው። "በቀን ውስጥ ብዙ ጊዜ፣ ደግሞም በእያንዳንዱ ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 17:5

አጠቃላይ መረጃ፡
ደቀ መዛሙርቱ ከእርሱ ጋር በሚናገሩበት ወቅት የተፈጠረ አጭር ጊዜ በኢየሱስ ትምህርተ መሃል አለ። ከዚያም ኢየሱስ ማስተማሩን ቀጠለ።

እምነታችንን አሳድግ/ጨምርልን
"እባክህ የበለጠ እምነት ስጠን" ወይም "በእምነታችን ላይ ተጨማሪ እምነት ስጠን"

የሰናፍጭ ፍሬ የሚያክል እምነት ቢኖራችሁ
የሰናፍጭ ፍሬ በጣም ትንሽ ፍሬ ነው። ኢየሱስ ትንሽ እምነት እንኳን እንደሌላቸው እያመለከተ ነው። "የሰናፍጭ ፍሬ የሚያክል ትንሽ እምነት እንኳን ቢኖራችሁ፣ እናንተ" ወይም "እምነታችሁ የሰናፍጭ ፍሬ ያህል አይደለም- ነገር ግን ቢሆን ኖሮ፣ እናንተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

የእንጆሪ ዛፍ
የዚህ አይነት ዛፍ የሚታወቅ ካልሆነ፣ ሌላ አይነት ዛፍ መተካት ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። "የሾላ ዛፍ" ወይም "ዛፍ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የማይታወቀውን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

ተነቅሎ፣ በባህር ይተከል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ራሳችሁ ነቅላችሁ ራሳችሁ በባህር ትከሉት" ወይም "ከመሬት ነቅላችሁ በውቅያኖስ ወለል ትከሉት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ይሆንላችኋል/ይታዘዛችኋል
"ዛፉ ይታዘዛችኋል።" ይህ ውጤት ቅድመ ሁኔታዊ ነው። ይህ የሚሆነው እምነት ካላቸው ብቻ ነው።

Luke 17:9

አያያዥ ሀሳብ፡
ኢየሱስ ማስተማሩን ጨረሰ። ይህ የዚህ ታሪክ የመጨረሻው ክፍል ነው።

Luke 17:11

አጠቃላይ መረጃ፡
ኢየሱስ 10 ለምጽ ያለባቸውን ሰዎች ፈወሰ። ቁጥር 11 እና 12 የመረጃ ዳራ እና የሁኔታዎችን መቼ እና የት ይሰጣል። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህም ሆነ
እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ የዋለው የአዲስ ትዕንት ጅማሬን ለማመልከት ነው። የእናንተ ቋንቋ ይህን ለማድረግ መንገድ ካለው እዚህ ስፍራ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ኢየሩሳሌም በመጓዝ ላይ ሳለ
"ኢየሱስ እና ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየሩሳሌም እተጓዙ ሳለ"

አንዲት መንደር
ይህ ሀረግ መንደሯን ለይቶ አይናገርም።

በዚያ ለምጽ ያለባቸውን አስር ሰዎች አገኙት
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ለምጽ ያለባቸው አስር ሰዎች አገኙት" ወይም "አስር ለምጽ ያለባቸው ሰዎች አገኙት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ከእርሱ ርቀው ቆሙ
ይህ የክብር ምልክት ነው፣ ምክንያቱም ለምጽ ያለባቸው ወደ ሌሎች መቅረብ አይፈቀድላቸውም ነበር። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ድምጻቸውን ከፍ አድረገው
x

Luke 17:14

ራሳችሁን ለካህን አሳዩ
ለምጽ ያለባቸው ከለምጻቸው ስለ መፈወሳቸው ከካህናትን ማረጋገጫ ማግኘት ነበረባቸው። "ይመረምሯችሁ ዘንድ ራሳችሁን ለካህናት አሳዩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ነጽተው ነበር
ሰዎች ሲፈወሱ፣ ከዚያ ወዲያ የመንጻት ስርዓት አያደርጉም። ይህ ይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "እነርሱ ከለምጻቸው ነጽ ተፈውሰው እና ንጹህ ሆነው ነበር" ወይም "እነርሱ ከለምጻቸው ተፈውሰው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ተፈወሰ አየ
"እንደ ተፈወሰ አወቀ" ወይም "ኢየሱስ እንደፈወሰው አወቀ"

ተመልሶ መጣ
"ወደ ኢየሱስ ተመልሶ መጣ"

ከፍ ባለ ድምጽ እግዚአብሔርን እያመሰገነ
"እግዚአብሔርን ጮሆ አመሰገነ"

በኢየሱስ እግር ስር ወደቀ
"ተንበርክኮ በኢየሱስ እግር ስር በፊቱ ወደቀ።" ይህንን ያደረገው ኢየሱስን ለማክበር ነው። (ምልክታዊ/ትዕምርታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 17:17

አያያዥ ሀሳብ፡
ይህ ኢየሱስ አስሩን ለምጻሞች ስለ ፈወሰበት ታሪክ የመጨረሻው ክፈል ነው።

ከዚያም ኢየሱስ እንዲህ አለ
ኢየሱስ አንዱ ሰው ስላደረገው ምላሽ ሰጠ፣ የተናገረው ግን በዙሪያው ለነበሩ ሰዎች ነበር። "ስለዚህም ኢየሱስ ለተሰበሰበው ሕዝብ እንዲህ አለ" በሚለው

ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አስሩ አልነጹም ነበርን?
ይህ ከሶስቱ ቃለምልልሳዊ ጥያቄዎች የመጀመሪያው ነው። ኢየሱስ እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመባቸው ከተፈወሱት መሃል እግዚአብሔርን ለማክበር የመጣው አንዱ ብቻ በመሆኑ ምን ያህል እንደተደነቀ እና እንዳዘነ በዙሪያው ለነበሩ ሰዎች ለማሳየትነው። "አስር ሰዎች ተፈውሰው ነበር።" ወይም "እግዚአብሔር አስር ሰዎችን ፈወሰ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚህ ባዕድ በስተቀር፣ ለእግዚአብሔር ክብር ለመስጠት የተመለሱ የሉምን?
ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጽ ይችላል። "ከዚህ ባዕድ በስተቀር ለእግዚአብሔር ክብር ለመስጠት ማንም ተመልሶ አልመጣም!" ወይም "እግዚአብሔር አስር ሰዎች ፈወሰ፣ ሆኖም ይህ ባዕድ ብቻ ለእግዚአብሔር ክብር ለመስጠት ተመልሶ መጣ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ባዕድ
ሳምራውያን አይሁድ ያለሆነ ዝርያ አላቸው፤ እናም እነርሱ እግዚአብሔርን አይሁዶች በሚያመልኩበት ተመሳሳይ መንገድ አያመልኩም።

እምነትህ አድኖሃል/ደህና አድርጎሃል
"በእምነትህ ምክንያት ድነሃል/እምነትህ አድኖሃል።" "እምነት" የሚለው ሀሳብ "እምነት" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "በማመንህ ምክንያት፣ ዳግም ደህና ሆነሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 17:20

አጠቃላይ መረጃ:
ይህ የት እንደሆነ እንኳን አናውቅም፤ ይህ የሆነው አንድ ቀን ኢየሱስ ከፈሪሳውያን ጋር በሚነጋገርበት ጊዜ ነው።

የእግዚአብሔር መንግሥት መቼ እንደሚመጣ ፈሪሳውያን በጠየቁት ጊዜ፣
ይህ የአዲሱ ትዕይንት መጀመሪያ ነው። አንዳንድ ትርጉሞች "አንድ ቀን" ወይም "አንድ ወቅት" በማለት ይጀምራሉ። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንድ ዕለት ፈሪሳውያን ኢየሱስን እንዲህ ሲሉ ጠየቁት፣ ‘የእግዚአብሔር መንግሥት መቼ ትመጣለች?’" (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ እንደዚሁም ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ጥቅሶች የሚሉትን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር መንግስት በውስጣችሁ/በመካከላችሁ ናት
"መንግሥት" የሚለው ስም ጽንሰ ሀሳብ "መግዛት" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር በውስጣችሁ ይገዛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይምለከቱ)

የእግዚአብሔር መንግሥት በእናንተ ውስጥ ናት
ኢየሱስ እርሱን ከሚጠሉ የሃይማኖት መሪዎች ጋር ይነጋገር ነበር። ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "እናንተ" የሚለው ቃል ሰዎችን በአጠቃላይ ያመለክታል። "የእግዚአብሔር መንግሥት በሰዎች ውስጥ ናት" ወይም 2) "በውስጣችሁ" የሚለው ቃል የተተረጎመው "በመሃላችሁ" በሚል ነው። "የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ ናት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

Luke 17:25

ነገር ግን በመጀመሪያ እርሱ መከራ መቀበል ይኖርበታል
"ነገር ግን በመጀመሪያ የሰው ልጅ መከራ መቀበል ይኖርበታል።" ኢየሱስ ስለ ራሱ በሶስተኛ መደብ እየተናገረ ነው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚሉትን ይመልከቱ)

በትውልዱ መናቅ/መወገድ ይኖርበታል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር መገለጽ ይኖርበታል። "የዚህ ትውልድ ሰዎች እርሱን መቃወም/ ማስወገድ ይኖርባቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ በሚሆንበት ጊዜ...እንዲህ ቢሆንም እንኳን
"ሰዎች ነገሮችን በማከናወን ላይ ሳሉ...ሰዎች ተመሳሳይ ነገሮችን እያደረጉ ሳሉ"

በኖህ ዘመን
"የኖህ ዘመን" ይህ እግዚአብሔር የዓለምን ሕዝብ ከመቅጣቱ አስቀድሞ ኖህ በኖረበት ዘመን ያለውን ወቅት ያመለክታል። "ኖህ ይኖር በነበረበት ዘመን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

በሰው ልጅ ቀናት
"የሰው ልጅ ቀናት" የሚለው የሚያመለክተው ልክ የሰው ልጅ ከመምጣቱ አስቀድሞ ያለውን ወቅት ነው። "የሰው ልጅ ሊመጣ ባለበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው"

ይበላሉ፣ ይጠጣሉ፣ ይጋባሉ፣ ደግሞም ልጆቻቸውን ይድራሉ
ሰዎች መደበኛ ነገሮችን ያደርጋሉ። እግዚአብሔር ሊፈርድባቸው እንደሆነ አያውቁም ወይም ለዚህ ግድ አይላቸውም።

ልጆቻቸውን ይድራሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ወላጆች ሴት ልጆቻቸውን እንዲያገቡ ለወንዶች ይፈቅዳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

መርከቡ/የኖህ መርከብ
"ታንኳ" ወይም "ጀልባ"

ሁሉንም አጠፋቸው
ይህ ኖህን እና በመርከቧ ውስጥ የነበሩ ቤተሰቦቹን አያጠቃልልም። "በጀልባዋ ውስጥ ያልገቡትን ሁሉ አጠፋ"

Luke 17:28

እንደዚሁ ሁሉ፣ በሎጥ ዘመን እንደሆነው
"የሎጥ ዘመን" የሚለው የሚያመለክተው እግዚአብሔር የሰዶም እና ገሞራን ከተሞች ከመቅጣቱ አስቀድሞ ያለውን ጊዜ ነው። "ሌላው ምሳሌ በሎጥ ዘመን እንዴት እንደሆነ የሚያሳይ ነው" ወይም "ሎጥ በኖረበት ዘመን ሰዎች ያደርጉት እንደነበረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ይበሉ እና ይጠጡ ነበር
"የሰዶም ሰዎች ይበሉ እና ይጠጡ ነበር"

ከሰማይ እሳት እና ሲን ዘነበ
"እሳት እና የሚነድ ዲን እንደ ዝናብ ከሰማይ ወረደ"

ሁሉንም አጠፋቸው
ይህ ሎጥን እና ቤተሰቡን አይጨምርም። "በከተማይቱ የነበሩትን ሁሉ አጠፋ"

Luke 17:30

ልክ እንደዚያው ይሆናል
"እንደዚያው ይሆናል።" በተመሳሳይ መንገድ እንደዚያው ሰዎች የተዘጋጁ አይሆኑም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ በሚገለጽበት ቀን
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የሰው ልጅ በሚገለጽበት ጊዜ" ወይም "የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ ይገለጻል
ኢየሱስ ስለ ራሱ እየተናገረ ነው። "እኔ፣ የሰው ልጅ፣ እገለጻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

በቤት ጫፍ ጣራ ላይ የሚገኝ ወደ ታች አይውረድ
"ማንም በቤት ጣራ ላይ የሚገኝ ወደ ታች አይውረድ" ወይም "ማንም ሰው በቤቱ ጣራ ላይ ቢሆን ወደ ታች መውረድ የለበትም"

በቤት ጣራ
የቤቶቻቸው ጣራ ጠፍጣፋ ነበር በዚያ ላይ መራመድ ወይም መቀመጥ ይችሉ ነበር።

ንብረቶቹን
"ሃብቱን" ወይም "ያሉትን ነገሮች"

Luke 17:32

የሎጥን ሚስት አስታውሷት
ተመካከሩ። 3 ሰይጣን ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ በሆነው በአስቆሮቱ ይሁዳ ገባበት። 4 አርሱም ኢየሱስን እንዴት አድርጎ አሳልፎ እንደሚሰጣቸው ከካህናት
አለቆችና ከሕዝብ መሪዎች ጋር ተነጋገረ። 5 እነርሱም ደስ አላቸው፣ ገንዘብም ሊሰጡት ተስማሙ። 6 እርሱም ኢየሱስን ለእነርሱ አሳልፎ ለመስጠት ሕዝብ
የሌሉበትን ምቹ ጊዜ ይፈልግ ነበር። 7 የፋሲካ በግ መሥዋዕት የሚደረግበት የቂጣ በዓል ደረሰ። 8 ኢየሱስም ጴጥሮስንና ዮሐንስን፣ “ሂዱና የፋሲካ ምግብ
እንድንበላ አዘጋጁልን” ብሎ ላካቸው። 9 እነርሱም፣ “የት እንድናዘጋጅልህ ትፈልጋለህ?” ብለው ጠየቁት። 10 እንዲህም ብሎ መለሰላቸው፣ “እድምጡ፣ ወደ
ከተማው በገባችሁ ጊዜ የውሃ እንስራ ተሸክሞ የሚመጣ ሰው ያገኛችኋል። ይህን ሰው ወደሚገባበት ቤት ተከትላችሁ ግቡ። 11 ከዚያም ለቤቱ ባለቤት፣
'መምህሩ እንዲህ ይልሃል፤" የፋሲካን እራት ከደቀ መዛሙርቴ ጋር የምበላበት የእንግዳ ክፍል የት ነው?' በሉት።” 12 እርሱም በፎቁ ላይ ሰፊና በሚገባ
የተሰናዳ ክፍል ያሳያችኋል። ዝግጅቱንም በዚያ አድርጉ። 13 ስለዚህ ወጥተው ሲሄዱ፣ ሁሉም ነገር እርሱ እንደተናገረው ሆኖ አገኙት። ከዚያም የፋሲካውን
ምግብ አዘጋጁ። 14 ሰዓቱ ሲደርስ፣ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ዐብሮ ተቀመጠ። 15 ከዚያም እንዲህ አላቸው፤ “መከራ ከመቀበሌ በፊት ይህን የፋሲካ እራት
ከእናንተ ጋር ለመብላት በእጅጉ እጓጓ ነበር። 16 በእግዚአብሔር መንግሥት እስከሚፈጸም ድረስ ከዚህ ምግብ ዳግመኛ እንደማልበላ እነግራችኋለሁና።" 17
ከዚያም ኢየሱስ ጽዋውን አንሥቶ አመሰገነና እንዲህ አላቸው፤ “ይህን ውሰዱና ተካፈሉት። 18 እላችኋለሁ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት እስክትመጣ ድረስ ከዚህ
ወይን ፍሬ ዳግመኛ አልጠጣም።” 19 እንጀራውን ወሰደ፣ ካመሰገነ በኋላ እንዲህ በማለት ቈርሶ ሰጣቸው፣ “ይህ ለእናንተ የተሰጠው ሥጋዬ ነው። እኔን
እያሰባችሁ ተመገቡት።” 20 በተመሳሳይ ሁኔታም፣ ከእራት በኋላ ጽዋውን አነሣና እንዲህ አለ፣ “ይህ ጽዋ ስለ እናንተ የፈሰሰ በደሜ የሚሆን ዐዲስ ኪዳን ነው።
21 ነገር ግን እኔን አሳልፎ የሚሰጠኝ ከእኔ ጋር በማዕድ እየበላ መሆኑን ልብ በሉ። 22 የሰው ልጅስ እንደተወሰነለት ይሆናል። ነገር ግን አሳልፎ ለሚሰጠው
ለዚያ ሰው ወዮለት!" 23 በዚህ ጊዜ እርስ በርሳቸው ይህን ነገር የሚያደርግ ማን እንደ ሆነ ተጠያየቁ። 24 ከዚያም ከሁሉም የሚበልጥ ማን ሊሆን
እንደሚገባው በመካከላቸው ጠብ ተነሣ። እርሱ እንዲህ አላቸው፣ 25 “የአሕዛብ ነገሥታት በሕዝብ ላይ ይገዛሉ፣ በእነርሱ ላይ ሥልጣን ያላቸውንም የተከበሩ
ገዦች ይሏቸዋል። 26 ነገር ግን በእናንተ ዘንድ እንዲህ አይሁን። ይልቅ ከእናንተ ታላቅ የሆነ እንደ ታናሽ ይሁን። እጅግ ተፈላጊ የሆነ እንደሚያገለግል ሰው ይሁን።
27 በማዕድ ከተቀመጠውና ከሚያገለግለው የትኛው ታላቅ ነው? በማዕድ የተቀመጠ አይደለምን? እኔ ግን በእናንተ መካከል እንደሚያገለግል ሰው ነኝ። 28
ነገር ግን እናንተ በፈተናዬ ከእኔ ጋር ጸንታችኋል። አብ ለእኔ መንግሥትን እንደ ሰጠኝ፣ 29 በመንግሥቴ በእኔ ማዕድ እንድትበሉና እንድትጠጡ መንግሥትን
እሰጣችኋለሁ። 30 ደግሞም በዙፋን ተቀምጣችሁ በዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች ላይ ትፈርዳላችሁ። 31 ስምዖን ሆይ፣ ስምዖን ሆይ፣ ተጠንቀቅ፤ ሰይጣን
እንደ ስንዴ ሊያበጥርህ ፈልጎ ጠይቋል። 32 ነገር ግን እኔ እምነትህ እንዳይጠፋ ጸለይሁልህ። ዳግመኛ ከተመለስህ በኋላ ወንድሞችህን አበርታቸው።” 33
ጴጥሮስ፣ “ጌታ ሆይ፣ ወደ እስር ቤትም ይሁን ወደ ሞት ከአንተ ጋር ለመሄድ ዝግጁ ነኝ” አለው። 34 ኢየሱስ፣ “ዛሬ ዶሮ ሳይጮኽ አላውቀውም ብለህ ሦስት
ጊዜ እንደምትክደኝ እነግርሃለሁ” ብሎ መለሰለት። 35 ከዚያም ኢየሱስ፣ “ያለ ገንዘብ ቦርሣ፣ ወይም ያለ ስንቅ ወይም ያለ ጫማ በላክኋችሁ ጊዜ ያጣችሁት
ነገር ነበርን?” አላቸው። እነርሱ፣ “ምንም አላጣንም" ብለው መለሱለት። 36 ከዚያም እንዲህ አላቸው፣ “አሁን ግን የገንዘብ ቦርሣ ያለው ቦርሣውን፣ ደግሞም
ስንቁን ይያዝ። ጎራዴ የሌለው ልብሱን ሸጦ ጎራዴ ይግዛ። 37 እላችኋለሁ፣ 'ከወንበዴዎች እንደ አንዱ ተቈጠረ' ተብሎ ስለ እኔ የተጻፈው መፈጸም አለበት። ይህ
ስለ እኔ የተነገረው አሁን እየተፈጸመ ነው።" 38 ከዚያም እነርሱ፣ “ጌታ ሆይ፣ ተመልከት፣ እዚህ ሁለት ጎራዴዎች አሉ” አሉት። እርሱም “ይበቃል” አላቸው። 39
ከእራት በኋላ ኢየሱስ ብዙ ጊዜ እንደሚያደርገው ወደ ደብረ ዘይት ተራራ ሄደ፣ ደቀ መዛሙርቱም ተከተሉት። 40 እዚያ በደረሱ ጊዜ፣ “ወደ ፈተና እንዳትገቡ
ጸልዩ” አላቸው። 41 ከእነርሱ የድንጋይ ውርወራ ያህል ራቅ ብሎ ሄደና ተንበርክኮ፣ 42 “አባት ሆይ፣ ብትወድ ይህን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፣ ነገር ግን የአንተ ፈቃድ
እንጂ የእኔ ፈቃድ አይሁን” በማለት ጸለየ። 43 የሚያበረታታው መልአክም ከሰማይ መጣለት። 44 በጣር ውስጥ ሆኖ በጣም እየቃተተ ጸለየ፣ ላቡም እንደ
ትልልቅ የደም ጠብታዎች ወደ መሬት ይንጠባጠብ ነበር። 45 ከጸሎቱ ተነሥቶ ወደ ደቀ መዛሙርቱ በመጣ ጊዜ ከሐዘን የተነሣ ተኝተው አገኛቸውና፣ 46
“ለምን ትተኛላችሁ? ወደ ፈተና እንዳትገቡ ተነሡና ጸልዩ” አላቸው። 47 ገና እየተናገረ እያለ ብዙ ሰዎች ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ የሆነው ይሁዳ እየመራቸው
መጡ። ይሁዳም ሊስመው ወደ ኢየሱስ ቀረበ፤ 48 ነገር ግን ኢየሱስ፣ “ይሁዳ ሆይ፣ የሰውን ልጅ በመሳም አሳልፈህ ትሰጣለህን?” አለው። 49 በኢየሱስ ዙሪያ
የነበሩት እየሆነ ያለውን ነገር ባዩ ጊዜ፣ 50 “በጎራዴ እንምታቸውን?” አሉ። ከዚያም ከመካከላቸው አንዱ በጎራዴ የሊቀ ካህኑን አገልጋይ ቀኝ ጆሮ መታና
ቈረጠው። 51 ኢየሱስ፣ “ይህ ይብቃ” አለ። የአገልጋዩንም ጆሮ ዳሰሰ፣ ፈወሰውም። 52 ኢየሱስ ሊያጠቁት ለመጡ የካህናት አለቆችና የቤተ መቅደስ መሪዎች
እንዲሁም ሽማግሌዎች እንዲህ አላቸው፤ “ወንበዴን እንደሚይዝ ሰው ጐራዴና ዱላ ይዛችሁ ትመጡብኛላችሁን? 53 በየዕለቱ በቤተ መቅደስ ከእናንተ ጋር
ሳለሁ አልያዛችሁኝም። ነገር ግን ይህ የእናንተና የጨለማው ሥልጣን ጊዜ ነው።” 54 ያዙትና ወሰዱት፣ ወደ ሊቀ ካህናቱ ቤትም አመጡት። ጴጥሮስ ግን
ከርቀት ተከተለው። 55 በግቢው መሓል እሳት ካቀጣጠሉና ዐብረው ከተቀመጡ ጴጥሮስ መጥቶ በመካከላቸው ተቀመጠ። 56 በእሳቱ ብርሃን
እንደተቀመጠም አንዲት ገረድ አየችውና በቀጥታ ተመልክታው፣ “ይህ ሰው ደግሞ ከእርሱ ጋር ነበር” አለች። 57 ጴጥሮስ ግን፣ “ሴትዮ፣ የምትዪውን ሰው
አላውቀውም” ብሎ ካደ። 58 ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ፣ ሌላ ሰው አየውና፣ “አንተም ከእነርሱ አንዱ ነህ” አለው። ነገር ግን ጴጥሮስ፣ “አንተ ሰው፣ እኔ
አይደለሁም” አለ። 59 ከአንድ ሰዓት ያህል ጊዜ በኋላ፣ ሌላ ሰው፣ “በእውነት ይህ ሰው ደግሞ ገሊላዊ ስለ ሆነ ከእርሱ ጋር ነበረ” በማለት በጥብቅ ተናገረ።
60 ነገር ግን ጴጥሮስ፣ “አንተ ሰው የምትለውን አላውቅም” አለ። ይህን እየተናገረ እያለ ወዲያው ዶሮ ጮኸ። 61 ጌታም ዞር አለና ጴጥሮስን ተመለከተው።
ጴጥሮስም፣ ጌታ “ዛሬ ዶሮ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ” ያለውን ቃል አስታወሰ። 62 ጴጥሮስ ወደ ውጭ ወጣና መራራ ልቅሶ አለቀሰ። 63 ከዚያም
ኢየሱስን ይጠብቁ የነበሩት ሰዎች እያላገጡበት ደበደቡት። 64 ዐይኖቹን ከሸፈኑ በኋላ፣ “እስቲ ትንቢት ተናገር። አሁን የመታህ ሰው ማን ነው?” በማለት
ጠየቁት። 65 እየተሳደቡ፣ ሌሎች ብዙ ነገሮችን በኢየሱስ ላይ ተናገሩ። 66 እንደነጋም የሕዝቡ ሽማግሌዎች፣ ከካህናት አለቆችና ከሕግ መምህራን ጋር ዐብረው
ተሰበሰቡ። ከዚያም ኢየሱስን ወደ ሸንጎው ፊት አቀረቡትና፣ 67 “ክርስቶስ ከሆንህ ንገረን” አሉት። እርሱ ግን፣ “እኔ ብነግራችሁ አታምኑም፣ 68 ደግሞም
ብጠይቃችሁ አትመልሱም። 69 ነገር ግን ከአሁን ጀምሮ የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ኀይል ቀኝ ይቀመጣል” አላቸው። 70 ሁሉም በአንድነት፣ “እንግዲህ አንተ
የእግዚአብሔር ልጅ ነሃ?” አሉት። ኢየሱስም፣ “እኔ እንደ ሆንሁ እናንተ ትናገራላችሁ” አላቸው። እነርሱ፣ 71 “እንግዲህ ለምን ምስክር እንፈልጋለን? ሲናገር እኛ
ራሳችን ከአፉ ሰምተነዋል” አሉ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Luke 22:1

አጠቃላይ መረጃ
ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ ለመስጠት ተስማማ። እነዚህ ቁጥሮች ስለዚህ ሁኔታ ዳራ የሚሆን መረጃ ይሰጣሉ።

አሁን
ቃሉ እዚህ ጥቅም ላይ የዋለው አዲስ ሁኔታን ለማስተዋወቅ ነው።

የቂጣ በዓል
ይህ በዓል በዚህ ስም የተጠራው በዚህ ጊዜ አይሁድ እርሾ የገባበት እንጀራ ስለማይበሉ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያልቦካ እንጀራ የሚበሉበት በዓል››

ተቃርቦ ነበር
‹‹ለመጀመር ዝግጁ ነበር››

ኢየሱስን እንዴት እንደሚያስገድሉት
ካህናትና ጸሐፍት ኢየሱስን ለመግደል ሥልጣን አልነበራቸውም፣ ሌሎች እንዲገድሉት ግን ተስፋ አድርገዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኢየሱስን እንዴት እንደሚያስገድሉት›› ወይም፣ ‹‹ሌሎች ኢየሱስን እንዲገድሉ ለማድረግ››

ሕዝቡን ስለ ፈሩ
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ሕዝቡ የሚያደርገው ስላስደነገጣቸው›› ወይም 2) ‹‹ሕዝቡ ኢየሱስን ንጉሥ ያደርጉታል ብለው ስለ ፈሩ››

Luke 22:3

አጠቃላይ መረጃ
ይህ የዚህ ታሪክ ክፍል ጅማሬ ነው።

ሰይጣን በአስቆሮቱ ይሁዳ ገባበት
ይህ በጋኔን ከመያዝ ጋር ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል።

የካህናት አለቆች
‹‹የካህናት መሪዎች››

ሹሞች
የቤተ መቅደሱ ጥበቃ ጎላፊዎች

ኢየሱስን እንዴት አሳልፎ እንደሚሰጣቸው
‹‹ኢየሱስን ለማሰር እንዴት እንደሚረዳቸው››

Luke 22:5

ደስ አላቸው
‹‹የካህናት አለቆችና ሹሞቹ ደስ አላቸው››

ገንዘብ ሊሰጡት
‹‹ለይሁዳ ገንዘብ ሊሰጡት››

ተስማማ
‹‹በሐሳቡ ተስማማ››

አሳልፎ ሊሰጣቸው ሕዝብ የማይገኝበትን ምቹ ጊዜ ይጠባበቅ ነበር።
ይህ የታሪኩ ክፍል ካበቃ በኃላ ቀጣይ ሂደት ነበር።

አሳልፎ ሊሰጠው
‹‹ሊወስደው››

ሕዝብ የማይገኝበት
‹‹በድብቅ›› ወይም፣ ‹‹በዙሪያው ሰዎች ሳይኖሩ››

Luke 22:10

እርሱም መለሰላቸው
‹‹ኢየሱስ ለጴጥሮስ ለዮሐንስ መለሰላቸው››

ስሙ
ኢየሱስ ይህን ቃል የተጠቀመው ልብ ብለው እንዲያደምጡና እርሱ የነገራቸውንም ሁሉ እንዲያደርጉ ሊነግራቸው ነው።

እንስራ የተሸከመ ሰው ያገኛችኋል
‹‹ውሃ በእንስራ የተሸከመ›› እንስራውን የተሸከመው በትከሻው ሊሆን ይችላል።

ወደ ቤት ተከተሉት
‹‹ተከተሉትና ወደ ቤት ግቡ››

መምህሩ የእንግዳ ክፍል ወዴት ነው? ይልሃል... ከደቀ መዛሙርቴ
‹‹የእንግዳ ክፍል ወዴት ነው?›› በማለት የሚጀምረው ጥቅስ መምህሩ ኢየሱስ ለቤቱ ባለቤት መናገር የፈለገው ቀጥተኛ ጥቅስ ነው። ቀጥተኛ ባልሆነ ጥቅስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱና ደቀመዛሙቱ ፋሲካን እንዲበሉ መምህራችን የእንግዳ ክፍል ወዴት ነው? ይልሃል›› ወይም፣ ‹‹ከእኛና ከተቀሩት ደቀ መዛሙርት ጋር ፋሲካን የሚበላበትን የእንግዳ ክፍል እንድታሳየን መምህራችን ጠይቆሃል››

መምህሩ
ይህ የሚያመለክተው ኢየሱስን ነው

ፋሲካን እንድበላ
‹‹የፋሲካን ምግብ እንድበላ››

Luke 22:12

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ኢየሱስ ለጴጥሮስና ለዮሐንስ መመሪያ መስጠት ቀጥሏል።

ያሳያችኋል
‹‹የቤቱ ባለቤት ያሳያችኋል››

በሰገነቱ ላይ
‹‹ፎቅ ቤት›› ማኅበረ ሰብህ ሌሎች ክፍሎች ላይ የሚሠራ ቤት ከሌለው ከተማ ውስጥ ያሉት ሕንፃዎች የሚጠሩበትን ቃል ማሰብ ትችላለህ።

ስለዚህ ሄዱ
x

Luke 22:14

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ይህ ስለ ፋሲካው ታሪክ ቀጣዩ ሁኔታ ነው። ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ የፋሲካን ምግብ ለመብላት ተቀምጠዋል።

ጊዜው ሲደርስ
‹‹ምግብ የሚበላበት ጊዜ ሲደርስ››

እርሱ ተቀመጠ
‹‹ኢየሱስ ተቀመጠ››

በጣም ስመኝ ነበር
‹‹በጣም እፈልግ ነበር››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መከራ ከመቀበሌ በፊት
ኢየሱስ ስለ ሞቱ እያመለከተ ነው። እዚህ ላይ፣ ‹‹መከራ›› የሚለው ቃል ያልተለመደ አስቸጋሪ ወይም የስቃይ ሁኔታ ማለት ነው።

እላችኋለሁና
ኢየሱስ ይህን ሐረግ የተጠቀመው ቀጥሎ የሚነግራቸው ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ አጽንዎች ለመስጠት ነው።

Luke 22:17

የትርጒም ማስታወሻዎች ጽዋውን አነሣ
‹‹ወይን ጠጅ የነበረበትን ጽዋ አነሣ››

ምስጋና ከሰጠ በኋላ
‹‹ለእግዚአብሔር ምስጋና ከሰጠ በኋላ››

እንዲህ አለ
‹‹ለሐዋርያት እንዲህ አለ››

እርስ በርሳችሁ ተከፋፈሉት
ጽዋውን ሳይሆን ጽዋው ውስጥ የነበረውን ነው መከፋፈል ያለባቸው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እርስ በርሳችሁ ጽዋው ውስጥ ያለውን ወይን ጠጅ ተከፋፈሉ›› ወይም፣ ‹‹እያንዳንዳችሁ ጽዋ ውስጥ ካለው የወይን ጠጅ ጠጡ።››

እላችኋለሁና
ይህን ሐረግ የተጠቀመው ቀጥሎ ኢየሱስ ለሚናገረው አስፈላጊ ነገር አጽንዖት ለመስጠት ነው።

የወይን ፍሬ
ይህ የሚያመለክተው የወይኑ ፍሬ ተጨምቆ የሚወጣውን ጭማቂ ነው። ወይን ጠጅ የሚሠራው ከተብላላው የወይን ፍሬ ጭማቂ ነው።

የእግዚአብሔር መንግሥት እስከምትመጣ
‹‹እግዚአብሔር መንግሥቱን እስኪመሠርት›› ወይም፣ ‹‹እግዚአብሔር መንግሥቱ ውስጥ እስኪገዛ››

Luke 22:19

እንጀራ
ይህ እንጀራ እርሾ የለውም፤ ጠፍጣፋ ነው።

ሰበረው
‹‹ቆረሰው›› ወይም፣ ‹‹ከፋፈለው›› ብዙ ቁርጥራጮች እንዲኖሩት ከፋፍሎት ይሆናል፤ ወይም ሐዋርያቱ እርስ በርሳቸው እንዲከፋፈሉት ለሁለት ከፍሎ ሰጥቷቸው ይሆናል። የሚቻል ከሆነ ሁለቱንም የሚያመለክት አገላለጽ ተጠቀም።

ይህ ሥጋዬ ነው
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ይህ እንጀራ ሥጋዬ ነው›› ወይም 2) ‹‹ይህ እንጀራ የእኔን ሥጋ ይወክላል››

ለእናንተ የተሰጠ ሥጋዬ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለእናንተ የምሰጠው ሥጋዬ›› ወይም፣ ‹‹ለእናንተ መሥዋዕት የምሰጠው ሥጋዬ››

ይህን አድርጉ
‹‹ይህን እንጀራ ብሉ››

ለእኔ መታሰቢያ
x

Luke 22:21

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ኢየሱስ ለሐዋርያቱ መናገር ቀጥሏል

አሳልፎ የሚሰጠኝ
‹‹አሳልፎ የሚሰጠኝ ሰው››

የሰው ልጅ ግን በእርግጥ ይሄዳልና
‹‹በእግጥ የሰው ልጅ ይሄዳል›› ወይም፣ ‹‹የሰው ልጅ ይሞታል››

የሰው ልጅ በእርግጥ ይሄዳል
ኢየሱስ ስለ ራሱ በሦስተኛ ሰው ደረጃ እየተናገረ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እኔ የሰው ልጅ በእርግጥ እሄዳለሁ››

በተወሰነው መሠረት
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እግዚአብሔር እንደ ወሰነው›› ወይም፣ ‹‹እግዚአብሔር እንዳቀደው››

አሳልፎ ለሚሰጠው ለዚያ ሰው ግን ወዮለት
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሰውን ልጅ አሳልፎ ለሚሰጠው ሰው ወዮለት›› ወይም፣ ‹‹የሰው ልጅን አሳልፎ ለሚሰጠው ሰው ምንኛ ከባድ ይሆንበታል››

Luke 22:24

ከዚያም በመካከላቸው ፀብ ተነሣ
‹‹ከዚያ ሐዋርያት እርስ በርስ ይከራከሩ ጀመር››

ማን ታላቅ ሊሆን እንደሚችል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በጣም አስፈላጊ ማን እንደሆነ›› ወይም፣ ‹‹ሰዎች በጣም አስፈላጊ ብለው የሚያስቡት››

እንዲህ አላቸው
‹‹ኢየሱስ ለሐዋርያት እንዲህ አላቸው››

በላያቸው ጌታ ይሆኑባቸዋል
‹‹አሕዛብ ላይ በጎይል ይገዛሉ››

ተብለው ይጠራሉ
ምናልባትም ሕዝቡ ገዦዎቹ ለሕዝቡ መልካም እያደረጉ ነው ብለው አያስቡም። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹መጠራት ይወዳሉ›› ወይም፣ ‹‹ራሳቸውን ይጠራሉ››

Luke 22:26

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ኢየሱስ ሐዋርያትን ማስተማር ቀጥሏል

በእናንተ ዘንድ ግን እንዲህ አይሁን
‹‹እንዲህ ማድረግ የለባችሁም››

ታናሹ
በዚያ ባሕል ትልልቅ ሰዎች ይከበሩ ነበር። ብዙ ጊዜ መሪዎቹ ትልልቅ ሰዎች ስለ ነበሩ፣ ‹‹ሽማግሌዎች›› ይባሉ ነበር። ታናሹ ሰው መሪ የመሆን ዕድሉ ዝቅ ያለ ነው፤ አስፈላጊነቱም ዝቅ ያለ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ዝቅ ያለ አስፈላጊ››

የሚያገለግል
‹‹አገልጋይ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ነውና
ይህ ቁጥር 26 ላይ ኢየሱስ የሰጠውን ትእዛዝ ከቁጥር 27 ሙሉ ጋር ያያይዛል። ኢየሱስ አገልጋይ በመሆኑ በጣም ትልቅ የተባለው ማገልገል አለበት ማለት ነው።

ታላቅ የሆነው የትኛው ነው፤... ያገልግል?
‹‹ታላቅ የተባለው የትኛው ነው... ያገልግል›› ኢየሱስ ይህን ጥያቄ ያነሣው በእውነት ታላቅ የሆነው የትኛው እንደሆነ ለሐዋርያት ለመግለጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ታላቁ ማን እንደሆነ እንድታስቡ እፈልጋለሁ... ያገልግል››

በማእድ የተቀመጠው
‹‹የሚመገበው››

በማእድ የተቀመጠው አይደለምን?
ደቀ መዛሙርቱን ለማስተማር ኢየሱስ ሌላ ጥያቄ አነሣ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርግጥ ነው፤ በማእድ የተቀመጠው ከአገልጋዩ ይበልጣል!››

ያም ሆኖ በመካከላችሁ እኔ እንደ አገልጋይ ነኝ
‹‹እኔ ከእናንተ ጋር ያለሁት አገልጋይ ለመሆን ነው›› ወይም፣ ‹‹እኔ ከእናንተ ጋር ያለሁ አገልጋይ እንዴት መሆን እንዳለበት ላሳያችሁ ነው›› እዚህ ላይ፣ ‹‹ያም ሆኖ›› የሚለው ቃል ሰዎች ኢየሱስ ነው ብለው በሚያስቡትና እርሱ በእርግጥ በሆነው መካከል ንጽጽር ስላለ ነው።

Luke 22:28

በመከራዬ ከእኔ ጋር ቆማችኋል
‹‹በመከራዬ ከእኔ ጋር ቆይታችኋል››

እኔ መንግሥት እሰጣችኋለሁ፤ አባቴ ለእኔ መንግሥት እንደ ሰጠኝ
አንዳንድ ቋንቋዎች የቅደም ተከተል ለውጥ ያስፈልጋቸው ይሆናል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አባቴ ለእኔ መንግሥት እንደ ሰጠኝ እኔም መንግሥት እሰጣችኋለሁ››

መንግሥት እሰጣችኋለሁ
‹‹በእግዚአብሔር መንግሥት መሪዎች አደርጋችኋለሁ›› ወይም፣ ‹‹በመንግሥቴ ውስጥ እንድትገዙ ሥልጣን እሰጣችኋለሁ›› ወይም፣ ‹‹ነገሥታት አደርጋችኋለሁ››

አባቴ ለእኔ መንግሥት እንደ ሰጠኝ
‹‹የእርሱ መንግሥት ውስጥ እንድገዛ አባቴ ለእኔ ሥልጣን እንደ ሰጠኝ››

ዙፋኖች ላይ ትቀመጣላችሁ
ንጉሦች ዙፋን ላይ ይቀመጣሉ። ዙፋን ላይ መቀመጥ የመግዛት ምሳሌ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ነገሥታት ትሠራላችሁ›› ወይም፣ ‹‹የነገሥታትን ሥራ ትሠራላችሁ››

Luke 22:31

አጠቃላይ መረጃ
ኢየሱስ በቀጥታ ለስምዖን እየተናገረ ነው።

ስምዖን፣ ስምዖን
ኢየሱስ ስሙን ሁለቴ የጠራው ሊነግረው የፈለገው ነገር በጣም አስፈላጊ መሆኑን ለማሳየት ነው።

ሊያበጥራችሁ ፈለገ
‹‹እናንተ›› ሐዋርያቱን ሁሉ ይመለከታል። ‹‹እናንተ›› ለሚለው የተለየ አጠራር ያላቸው ቋንቋዎች ብዙ ቁጥርን መጠቀም አለባቸው።

እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ
ይህ ማለት አንዳች ጥፋት ለማግኘት ሰይጣን ደቀ መዛሙትን መፈተን ፈለገ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስንዴ በወንፊት እንደሚያበጠር ሰው ሊያበጥራችሁ››

እኔ ግን ለአንተ ጸለይሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹አንተ›› በተለይ ስምዖንን ነው። ‹‹አንተ›› ለሚለው የተለየ አጠራር ያላቸው ቋንቋዎች ነጠላ ቁጥርን መጠቀም አለባቸው።

እምነትህ እንዳይወድቅ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በእምነት እንድትዘልቅ›› ወይም፣ ‹‹በእኔ በማመን እንድትዘልቅ››

ወደ ኋላ ከተመለስህ በኋላ
እዚህ ላይ ‹‹ወደ ኋላ መመለስ›› እንደ ገና ማመንን የሚያመለክት ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ገና በእኔ ማመን ስትጀምር›› ወይም፣ ‹‹እንደ ገና እኔን ማገልገል ስትጀምር››

ወንድሞችህን አበርታ
ይህ ሌሎቹ ደቀ መዛሙርትን ይመለከታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አማኝ ወገኖችህን›› ወይም፣ ‹‹ሌሎች ደቀ መዛሙትን››

Luke 22:33

ዛሬ ዶሮ ሳይጮኽ አላውቀውም ብለህ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ
የዐረፍተ ነገሩን ክፍሎች መገልበጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አላውቀውም ብለህ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ ዶሮ ሳይጮኽ››

አንተ ከመካድህ በፊት ዶሮ በዚህ ቀን አይጮኽም
x

Luke 22:35

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ኢየሱስ ትኩረቱን ለሁሉም ደቀ መዛሙርት ወደ መናገር መልሷል።

ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፤ በላክኋችሁ ጊዜ... የጐደለባችሁ ነበርን? እነርሱም፣ ‹‹ምንም አልጐደለብንም›› አሉ።
ኢየሱስ ጥያቄውን ያነሣው በጉዞ ላይ በነበሩ ጊዜ ሕዝቡ የሚያስፈልጋቸውን ይሰጧቸው እንደ ነበር እንዲያስታወሱ ሐዋርያቱን ለመርዳት ነበር። ኢየሱስ ይህን የጠየቀው መረጃ በመጠበቅ ባይሆንም፣ ደቀ መዛሙርቱ ምንም እንዳልጐደለባቸው የሚያደርጋቸው ዐረፍተ ነገር ብቻ እስካልሆነ ድረስ በጥያቄ መልኩ ተርጉመው።

እኔ በላክኋችሁ ጊዜ
ኢየሱስ ለሐዋርያቱ እየተናገረ ነው። ስለዚህ፣ ‹‹እናንተ›› ለሚለው የተለየ አገላለጽ ያላቸው ቋንቋዎች በብዙ ቁጥር መጠቀም አለባቸው።

ኩሮጆ
ኩሮጆ ገንዘብ መያዣ ቦርሳ ነው። እዚህ ላይ ጥቅም የዋለው፣ ‹‹ገንዘብን›› ለማመልከት ነው።

መያዣ ቦርሳ
‹‹የተጓዥ ቦርሳ›› ወይም፣ ‹‹የምግብ መያዣ››

ምንም
ለአንዳንድ ሰሚዎች ለውይይቱ ተጨማሪ ገለጻ መስጠት አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምንም አልጐደለብንም›› ወይም፣ ‹‹የሚያስፈልገን ሁሉ ነበረን››

ሰይፍ የሌለው መጐናጸፊያውን ይሸጥ
ኢየሱስ ሰይፍ ስለሌለው አንድ ሰው እየተናገረ አይደለም። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሰይፍ የሌለው ማንኛውም መጐናጸፊያውን መሸጥ አለበት››

መጐናጸፊያ
‹‹ኮት›› ወይም፣ ‹‹ከላይ የሚለበስ››

Luke 22:37

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር መነጋገር አበቃ

ስለ እኔ የተጻፈው
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ነቢይ ስለ እኔ የጻፈው››

መፈጸም አለበት
የሚሆነውን ሁሉ እግዚአብሔር ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እንዲጻፍ ማድረጉን ሐዋርያት ይረዳሉ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እግዚአብሔር ይፈጽማል›› ወይም፣ ‹‹እግዚአብሔር እንዲጻፍ ያደርጋል››

ከዐመፀኞች ጋር ተቆጠረ
እዚህ ላይ ኢየሱስ ከቅዱሳት መጻሕፍት ጠቀሰ። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሰዎች ከዐመፀኖች ጋር እንደሆነ ቆጠሩት››

ዐመፀኞች
‹‹ሕግ የሚተላለፉ›› ወይም፣ ‹‹ወንጀለኞች››

ስለ እኔ አስቀድሞ የተነገረው መፈጸም አለበት
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ነቢይ ስለ እኔ አስቀድሞ የተናገረው መሆን አለበት። ወይም፣ 2) ‹‹ሕይወቴ ለፍጻሜ ቀርቧል››

እነርሱ አሉ
ይህ ቢያንስ ሁለቱን የኢየሱስ ሐዋርያት ይመለከታል።

ይበቃል
x

Luke 22:39

አጠቃላይ መረጃ
ኢየሱስ ለመጸለይ ወደ ደብረ ዘይት ተራራ ሄደ

ወደ ፈተና እንዳትገቡ
‹‹እንዳትፈተኑ›› ወይም፣ ‹‹ኀጢአት ለማድረግ ምንም ነገር እንዳይፈትናችሁ››

Luke 22:41

የድንጋይ ውርወራ ያህል
‹‹አንድ ሰው ድንጋይ መወርወር የሚችልበት ርቀት ያህል›› አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አጭር ርቀት›› ወይም በግምት፣ ‹‹ሰላሣ ሜትር ያህል›› ርቀት።

አባት ሆይ፣ ከፈቀድህ
ኢየሱስ የእያንዳንዱን ሰው ኀጢአት መስቀል ላይ ሊሸከም ነው። ሌላ መንገድ ይኖር እንደሁ በመጠየቅ ወደ አባቱ እየጸለየ ነው።

አባት
ይህ በጣም አስፈላጊ የእግዚአብሔር መጠሪያ ነው።

ይህን ጽዋ ከእኔ ውሰድ
አሁን እርሱ ላይ የሚደርሰው መራራ ነገር ያለበት ጽዋ መጠጣት እንደ ሆነ ኢየሱስ ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ይህን ጽዋ እንዳልጠጣ ፍቀድልኝ›› ወይም፣ ‹‹የሚሆነው ነገር እኔ ላይ እንዳይደርስ››

ነገር ግን የእኔ ሳይሆን የአንተ ፈቃድ ይፈጸም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንደ እኔ ፈቃድ ሳይሆን፣ እንደ አንተ ፈቃድ የሆነውን አድርግ››

Luke 22:43

ተገለጠለት
‹‹ለኢየሱስ ታየው››

አበረታታው
‹‹አደፋፈረው››

እጅግ ተጨንቆ ጸለየ
‹‹በጣም እየተሰቃየ ሳለ ጸለየ››

አጥብቆ ጸለየ
‹‹የበለጠ ጸለየ››

ላቡ እንደ ደም ነጠብጣብ ወደ ምድር ይፈስስ ነበር
‹‹ላቡ እንደ ብዙ የደም ነጠብጣብ መሬት ላይ ፈሰሰ››

Luke 22:45

ከጸሎት ሲነሣ፣ እርሱ
‹‹ኢየሱስ ከጸሎት ሲነሣ እርሱ›› ወይም፣ ከጸሎት በኋላ ኢየሱስ ተነሣ፣ እርሱ››

ከሐዘን የተነሣ ተኝተው አገኛቸው
‹‹በሐዘን ደክመው ስለ ነበር እንደ ተኙ አየ››

ለምን ትተኛላችሁ?
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹በዚህ ጊዜ መተኛታችሁ ገርሞኛል›› ወይም 2) ‹‹በዚህ ጊዜ መተኛት አልነበረባችሁም››

ወደ ፈተና እንዳትገቡ
‹‹እንዳትፈተኑ›› ወይም፣ ‹‹ኀጢአት ለማድረግ ምንም ነገር እንዳይፈትናችሁ››

Luke 22:47

እነሆ፣ ብዙ ሰዎች
‹‹እነሆ›› የሚለው ቃል ለታሪኩ አዲስ ሰዎች ያነቃናል። ቋንቋህ ይህን ማድረግ የሚችልበት መንገድ ይኖረዋል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ብዙ ሰዎች ሲመጡ ታየ››

እየመራቸው
ይሁዳ ኢየሱስ የነበረበትን ለሰዎች እያሳየ ነው። ለሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለባቸው አልተናገረም። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ወደ ኢየሱስ እየመራቸው››

ሊስመው
‹‹እየሳመ ሰላም አለው›› ወይም፣ ‹‹በመሳም ሰላም አለው›› ሰዎች ቤተ ሰባቸው ወይም ጓደኞቸው የሆነውን ሰው ሰላም ሲሉ አንድ ጉንጫቸውን ወይም ሁለቱንም ጉንጮቻቸውን ይስሟቸዋል። አንባቢዎችህ ወንድ ሌላውን ወንድ መሳሙ እንደ ነውር የሚቆጥሩ ከሆነ፣ ‹‹የጓደኝነት ሰላምታ ሰጠው›› በሚል አጠቃላይ መንገድ መተርጐም ትችላለህ።

በመሳም የሰውን ልጅ አሳልፈህ ትሰጣለህን?
በመሳም እርሱን አሳልፎ በመስጠቱ ይሁዳን ለመገሠጽ ኢየሱስ በጥያቄ ተጠቀመ። በተለምዶ መሳም የፍቅር ምልክት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሰው ልጅን አሳልፈህ የምትሰጠው በመሳም ነውን?››

የሰውን ልጅ በ...
ኢየሱስ በዚህ አገላለጽ የተጠቀመው ስለ ራሱ ለመናገር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ፣ የሰው ልጅን››

Luke 22:49

በኢየሱስ ዙሪያ የነበሩት
ይህ የሚያመለክተው የኢየሱስን ደቀ መዛሙርት ነው።

እየሆነ የነበረው
ይህ የሚያመለክተው ኢየሱስን ለመያዝ እየመጡ የነበሩትን ካህናትና ወታደሮቹን ነው።

በሰይፍ መታ
ጥያቄው እያደረጉ የነበረው ውጊያ አይደለም፤ (የሰይፍ ውጊያ) በምን ዐይነት መሣሪያ መጠቀማቸውም አይደለም (ይዘው የመጡት ሰይፍ፤ ሉቃስ 22፥38) ይሁን እንጂ፣ ትርጉምህ ይዘው ስለ መጡት መሣሪያ መናገር አለበት።

ከእነርሱ አንዱ
‹‹ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ››

የሊቀ ካህናቱን አገልጋይ መትቶ
‹‹የሊቀ ካህናቱን አገልጋይ በሰይፍ መታ››

ያ ይበቃል
‹‹ከዚህ የበለጠ አታድርግ››

ጆሮውን ዳሰሰ
‹‹ጆሮው የተቆረጠውን አገልጋይ ዳሰሰ››

Luke 22:52

ወንበዴ እንደሚይዝ ሰው፣ ሰይፍና ቆመጥ ይዛችሁ ወጣችሁን?
‹‹እኔ ወንበዴ እንደሆንሁ በማሰብ ሰይፍና ቆመጥ ይዛችሁ ወጣችሁን? ‹‹ኢየሱስ ይህን ጥያቄ ያቀረበው የአይሁድ መሪዎችን ለመገሠጽ ነበር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ ወንበዴ እንዳይደለሁ ታውቃላችሁ፤ ግን ሰይፍና ቆመጥ ይዛችሁ መጣችሁብኝ››

በየዕለቱ ከእናንተ ጋር ነበርሁ
‹‹በየቀኑ በመካከላችሁ ነበርሁ››

ቤተ መቅደስ ውስጥ
ቤተ መቅደስ ውስጥ የሚገቡ ካህናት ብቻ ናቸው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በቤተ መቅደስ አደባባይ›› ወይም፣ ‹‹በቤተ መቅደስ››

እጃችሁን እኔ ላይ ጫናችሁ
በዚህ ቁጥር እጆችን መጫን ሰውየውን ማሰር ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ልታሰሩኝ››

የእናንተ ሰዓት
‹‹የእናንተ ጊዜ›› ወይም፣ ‹‹የምትሠሩበት ጊዜ››

የጨለማ ሥልጣን
ዐረፍተ ነገሩን ሁለት ጊዜ መድገም ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የጨለማ ሥልጣን ጊዜ››

የጨለማ ሥልጣን
ይህ የሚናገረው ስለ ሰይጣን አገዛዝ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የጨለማ ግዛት ጊዜ›› ወይም፣ ‹‹ሰይጣን የሚሠራበት ጊዜ››

Luke 22:54

ወሰዱት
‹‹እርሱን ከያዙበት አትክልት ቦታ ኢየሱስን ወሰዱት››

ወደ ሊቀ ካህናቱ ቤት
‹‹ወደ ሊቀ ካህናቱ ቤት ግቢ››

እሳት አነደዱ
‹‹አንዳንድ ሰዎች እሳት አነደዱ›› እሳቱ በቀዝቃዛው ሌሊት ሕዝቡ ሙቀት እንዲያገኙ ነበር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንዳንድ ሰዎች ሙቀት ለማግኘት እሳት አነደዱ››

ግቢው መካከል
ይህ የሊቀ ካህናቱ ቤት ግቢ ነው። ዙሪያውን አጥር ቢኖረውም ጣራ አልነበረውም።

ከእነርሱ መካከል
‹‹ከእነርሱ ጋር››

Luke 22:56

በእሳቱ ብርሃን አጠገብ ተቀመጠ
እሳቱ አጠገብ ተቀመጠ፤ ብርሃኑ ፊቱ ላይ አበራ

ትኩር ብላ በመመልከት እንዲህ አለች
‹‹ጴጥሮስን ትኩር ብላ በመመልከት ግቢው ውስጥ ለነበሩት ሰዎች እንዲህ አለች››

ይህም ሰውዬ ከእርሱ ጋር ነበረ
ሴትዮዋ ጴጥሮስ ከኢየሱስ ጋር እንደ ነበር ለሰዎቹ እየነገረች ነው። ምናልባትም የጴጥሮስን ስም አታውቅም።

ጴጥሮስ ግን ካደ
‹‹ጴጥሮስ ግን እውነት አይደለም አለ››

ሴትዮ አላወቀውም
ጴጥሮስ የሴትዮዋን ስም አያውቅም። ‹‹ሴትዮ›› ሲል እየሰደባት አልነበረም። ሰዎች እየሰደባት እንደሆነ የሚያስቡ ከሆነ፣ አንድ ሰው የማያውቃትን ሴት ሲጠራ ተቀባይነት ያለው ባሕል መጠቀም ትችላለህ፤ ወይም ቃሉን ተወው።

አንተም ከእነርሱ አንዱ ነህ
‹‹አንተም ከኢየሱስ ጋር ከነበሩት አንዱ ነህ››

አንተ ሰው አይደለሁም
ጴጥሮስ የሰውየውን ስም አያውቅም። ‹‹አንተ ሰው›› ሲለው እየሰደበው አልነበረም። ሰዎች እየሰደበው እንደሆነ የሚያስቡ ከሆነ፣ አንድ ሰው የማያውቀውን ሰው ሲጠራ ተቀባይነት ያለው ባሕል መጠቀም ትችላለህ፤ ወይም ቃሉን ተወው።

Luke 22:59

አጥብቆ አለ
‹‹በጥብቅ አለ›› ወይም፣ ‹‹ጮኽ ብሎ አለ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በእውነት ይህ ሰው
እዚህ ላይ፣ ‹‹ይህ ሰው›› የሚያመለክተው ጴጥሮስን ነው። ተናጋሪው ምናልባት የጴጥሮስን ስም አያውቅም።

ገሊላዊ ነው
ሰውየው ጴጥሮስን ገሊላዊ ያለው በአነጋገሩ ሊሆን ይችላል።

ሰውዬ
ጴጥሮስ የሰውየውን ስም አያውቅም። ‹‹ሰውዬ›› ብሎ ሲጠራው እየሰደበው አልነበረም። ሰዎች እየሰደበው እንደሆነ የሚያስቡ ከሆነ ሰዎች የሚያውቁን ሰው ሲጠራ ተቀባይነት ባለው ባሕል ተጠቀም። ወይም ቃሉን ተወው። ሉቃስ 22፥58 እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

የምትናገረውን አላውቅም
‹‹ምን እያልህ እንደሆነ አላውቅም›› ይህም ማለት ጴጥሮስ ከሰውየው ጋር በፍጹም አልተስማማም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የምትለው በፍጹም እውነት አይደለም›› ወይም፣ ‹‹የምትለው በፍጹም ውሸት ነው››

እየተናገረ ሳለ
‹‹ጴጥሮስ እየተናገረ ሳለ››

ዶሮ ጮኸ
ብዙ ጊዜ ዶሮ የሚጮኸው ጠዋት ፀሐይ ከመውጣቷ በፊት ነው። ሉቃስ 22፥34 ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

Luke 22:61

ጌታም መለስ ብሎ ጰጥሮስን አየው
‹‹ጌታም ዘወር ብሎ ጴጥሮስን ተመለከተው››

የጌታ ቃል
ጴጥሮስ አሳልፎ እንደሚሰጠው ሲናገር፣ ‹‹ኢየሱስ ያለው››

ዶሮ ጮኸ
x

Luke 22:63

ፊቱ ላይ መሸፈኛ አኖሩ
‹‹ማየት እንዳይችል ዐይኖቹን ሸፈኑ››

ትንቢት ተናገር! የመታህ ማን ነው?
ጠባቂዎቹ ኢየሱስ ነቢይ መሆኑን አያምኑም በዐይኑ ባያይም፣ እውነተኛ ነቢይ ማን እንደ መታው እንደሚያውቅ ያምናሉ። ኢየሱስን ነቢይ በማለት ቢጠሩትም እያፌዙበትና ነቢይ ነው ብለው እንደማያምኑ እያሳዩ ነበር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ነቢይነትህን አሳይ፤ ማን እንደ መታህ ንገረን!›› ወይም፣ ‹‹እ ነቢይ፣ ማን ነው የመታህ?››

ትንቢት ተናገር!
‹‹ከእግዚአብሔር ቃል ተናገር!›› እነርሱ ማለት የፈለጉት ኢየሱስ ዐይኖቹ በመሸፈናቸው ማየት ስለማይችል የመታው ማን እንደሆነ እግዚአብሔር ለኢየሱስ እንዲነግረው ነው።

Luke 22:66

አጠቃላይ መረጃ
አሁን ቀጣዩ ቀን ነው፤ ኢየሱስን በሸንጐው ፊት አቀረቡት

ቀን ሲሆን ወዲያው
‹‹በሚቀጥለው ጠዋት ሲነጋ››

ኢየሱስን በሸንጐው ፊት አቀረቡት
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ሽማግሌዎቹ ኢየሱስን ሸንጐው ፊት አቀረቡት›› ወይም 2) ‹‹ጠባቂዎቹ ኢየሱስን ወደ ሽማግሌዎቹ ሸንጐ ወሰዱት›› አንዳንድ ቋንቋዎች ‹‹እነርሱ›› የሚለውን ተውላጠ ስም በመጠቀም ወይም፣ ‹‹እንዲሁ፣ ‹‹ኢየሱስን ወደ ሸንጐው ወሰዱት›› በማለት የወሰደው ማን እንደ ነበር አይናገሩም።

Luke 22:69

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ኢየሱስ ለሸንጐው መናገር ቀጥሏል

ከአሁን ጀምሮ
‹‹ከዚህ ቀን›› ወይም፣ ‹‹ከዛሬ ጀምሮ››

የሰው ልጅ
ኢየሱስ በዚህ አባባል የሚጠቀመው ስለ ራሱ ለመናገር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሰው ልጅ፣ እኔ››

በእግዚአብሔር ኀይል ቀኝ ይቀመጣል
‹‹በእግዚአብሔር ቀኝ›› መቀመጥ ከእግዚአብሔር ታላቅ ሥልጣንና ክብር የመቀበል ምሳሌ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በእግዚአብሔር ኀይል ጐን፣ በክብር ስፍራ ይቀመጣል››

የእግዚአብሔር ኀይል
‹‹ኀያል እግዚአብሔር›› እዚህ ላይ፣ ‹‹ኀይል›› የላቀ ሥልጣን ያመለክታል።

ታዲያ፣ አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህን?
ሸንጐው ይህን የጠየቀው የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ማለቱን በትክክል ኢየሱስ እንዲያረጋግጥ ስለ ፈለጉ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ታዲያ፣ እንደዚያ ስትል የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ማለትህ ነውን?››

የእግዚአብሔር ልጅ
ይህ የኢየሱስ አስፈላጊ መጠሪያ ነው።

እኔ እንደሆንሁ ትናገራላችሁ
‹‹አዎን፣ እናንተ እንዳላችሁት ነው?››

ምን ምስክር ያስፈልገናል?
ጥያቄ ያቀረቡት ለአጽንዖት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእንግዲህ ሌላ ምስክር አያስፈልገንም››

ከአፉ ሰምተናል
‹‹ከአፉ›› የሚለው ከአነጋገሩ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን እንደሚያምን ሲናገር ሰምተነዋል››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 23

1 ሕዝቡ በጠቅላላ ተነሥተው ቆሙ፣ ኢየሱስንም በጲላጦስ ፊት አቀረቡት። 2 “ይህ ሰው ራሱን ክርስቶስ፣ ንጉሥ ነኝ ሲልና ለቄሣር ግብር እንዳይከፈል
በመከልከል አገር ሲበጠብጥ አግኝተነዋል” በማለት ይከሱት ጀመር። 3 ጲላጦስ፣ “አንተ የአይሁድ ንጉሥ ነህን?” በማለት ጠየቀው። ኢየሱስም፣ “አንተ
አልህ” ብሎ መለሰለት። 4 ጲላጦስ የካህናት አለቆችንና የተሰበሰቡትን ሕዝብ፣ “በዚህ ሰው ምንም ስሕተት አላገኘሁበትም” አላቸው። 5 እነርሱ ግን፣ “ከገሊላ
ጀምሮ በመላው ይሁዳ፣ እስከዚህ ስፍራም እንኳ እያስተማረ ሕዝቡን ያነሣሣል” በማለት አጥብቀው ተናገሩ። 6 ስለዚህ ጲላጦስ ይህን በሰማ ጊዜ ሰውየው
ገሊላዊ እንደ ሆነ አጠያየቀ። 7 ከሄሮድስ ሥልጣን በታች እንደ ሆነ ተረድቶ በዚያው ሰሞን ኢየሱስን በኢየሩሳሌም ወደ ነበረው ሄሮድስ ላከው። 8 ሄሮድስ
ኢየሱስን ባየው ጊዜ በጣም ደስ አለው፣ ምክንያቱም ለረጅም ጊዜ ሊያየው ሲፈልግ ነበር። ስለ እርሱ ሰምቶ የነበረ ሲሆን፣ አንዳንድ ተአምራት ሲያደርግ
ለማየትም ተስፋ ነበረው። 9 ሄሮድስ ኢየሱስን በብዙ ቃሎች ቢጠይቅም፣ ኢየሱስ ግን ምንም መልስ አልሰጠውም። 10 በዚህ ጊዜ የካህናት አለቆችና የሕግ
መምህራን ተነሥተው ቆሙና በኀይለ ቃል ከሰሱት። 11 ሄሮድስ ከወታደሮቹ ጋር በመሆን ኢየሱስን ሰደበው፣ አላገጠበትም፤ ጥሩ ልብስ ካለበሰው በኋላ መልሶ
ወደ ሄሮድስ ላከው። 12 ከዚያን ቀን ጀምሮ ሄሮድስና ጲላጦስ ወዳጆች ሆኑ (ከዚያ በፊት አንዱ የአንዱ ጠበኞች ነበሩ)። 13 ከዚያም ጲላጦስ የካህናት
አለቆችን፣ ገዢዎችንና ሕዝቡን አንድ ላይ ጠራ፤ 14 እንዲህም አላቸው፤ “ ይህን ሰው ሰዎችን ለክፉ ድርጊት የሚያነሣሣ አድርጋችሁ ወደ እኔ አመጣችሁት፣
እኔም በፊታችሁ ከጠየቅሁት በኋላ ፣ እነሆ፣ እርሱን በምትከሱባቸው ነገሮች ምንም ጥፋት አላገኘሁበትም። 15 ሄሮድስም ቢሆን ምንም ነገር አላገኘበትም፤
ምክንያቱም መልሶ ወደ እኛ ልኮታልና፤ እነሆ፣ እርሱን ለሞት የሚያደርስ በዚህ ሰው የተፈጸመ ምንም ጥፋት አላገኘሁበትም። 16 ስለዚህ ቀጥቼው
እለቀዋለሁ።" ጲላጦስም በበዓሉ ለአይሁድ አንድ እስረኛ የመፍታት ግዴታ ነበረበት። 1718 ነገር ግን እነርሱ በአንድነት፣ “ይህን ሰው አስወግደው፣ በርናባስን
ለእኛ ፍታልን!" በማለት ጮኹ። 19 በርናባስ በከተማይቱ ውስጥ አንድ ዐይነት ዐመፅና ግድያ በመፈጸም የታሰረ ሰው ነበር። 20 ጲላጦስ ኢየሱስን ሊፈታ ፈልጎ
እንደ ገና ሕዝቡን አነጋገራቸው። 21 ነገር ግን ሕዝቡ፣ “ስቀለው፣ ስቀለው” እያሉ ጮኹ። 22 ለሦስተኛ ጊዜም እንዲህ አላቸው፤ “ለምን? ይህ ሰው የሠራው
ክፋት ምንድን ነው? ለሞት ቅጣት የሚያበቃ ነገር አላገኘሁበትም። ስለዚህ ቀጥቼው እለቀዋለሁ።” 23 እነርሱ ግን ኢየሱስ እንዲሰቀል በመጠየቅ ሳያቋርጡ
አብዝተው ጮኹ። ጩኸታቸውም ጲላጦስን አሳመነው። 24 ስለዚህ ጲላጦስ ፍላጎታቸውን ለማሟለት ወሰነ። 25 እንዲፈታላቸው የጠየቁትን፣ በዐመፅና በግድያ
ምክንያት የታሰረውን ሰው ለቀቀላቸው። ኢየሱስን ግን ለፈቃዳቸው አሳልፎ ሰጠው። 26 እየወሰዱት ሳሉ፣ ከገጠር ይመጣ የነበረ ስምዖን የተባለ የቀሬናን ሰው
ያዙና ኢየሱስ ይሸከመው የነበረውን መስቀል አሸከሙት። 27 እጅግ ብዙ ሕዝብና ለእርሱ የሚያዝኑና የሚያለቅሱ ሴቶች ይከተሉት ነበር። 28 ኢየሱስም ወደ
እነርሱ ዞር ብሎ፣ “የኢየሩሳሌም ሴቶች ሆይ፣ ለእኔ ሳይሆን ለራሳችሁና ለልጆቻችሁ አልቅሱ” አለ። 29 እነሆ፣ 'መካን የሆኑና ያልወለዱ ማኅፀኖች እንዲሁም
ያላጠቡ ጡቶች የተባረኩ ናቸው' የሚሉባቸው ቀኖች ይመጣሉና። 30 ከዚያም ተራሮችን፣ 'በላያችን ውደቁ፣ ኮረብቶችንም ክደኑን ማለትይጀምራሉ።' 31 ዛፉ
እርጥብ እያለ ይህን ነገር ካደረጉ፣ በሚደርቅበት ጊዜ ምን ይሆናል?" 32 ሌሎች ሁለት ወንጀለኞችም ከእርሱ ጋር ለገደሉ ተወሰዱ። 33 የራስ ቅል ወደሚባል
ቦታ በደረሱ ጊዜ፣ እርሱን ከሌሎች ሁለት ወንጀለኞች ጋር ሰቀሉት፥ አንደኛው በቀኙ ሌላኛው በግራው ነበሩ። 34 ኢየሱስ፣”አባት ሆይ፣ የሚያደርጉትን
አያውቁምና ይቅር በላቸው” አለ። ዕጣ ተጣጥለውም ልብሱን ተከፋፈሉ። 35 “ሌሎችን አዳነ፣ እርሱ በእግዚአብሔር የተመረጠ ክርስቶስ ከሆነ አስኪ ራሱን
ያድን” በማለት ገዢዎቹ እየዘበቱበት ሳለ ሕዝቡ ቆመው ያዩ ነበር። 36 ወታደሮቹም ወደ እርሱ ቀርበው፣ 37 “አንተ ንጉሥ ከሆንህ ራስህን አድን” በማለት
እያሾፉበት ኮምጣጤ ሰጡት። 38 “የአይሁድ ንጉሥ” የሚል ምልክትም ከበላዩ ተደርጎ ነበር። 39 ከተሰቀሉት ወንጀለኞች አንዱ፣ "አንተ ክርስቶስ ነህን?
ራስህንም እኛንም አድን” በማለት ሰደበው። 40 ሌላኛው ግን እየገሠጸው፣ “ከፍርድ በታች ሆነህ እግዚአብሔርን አትፈራምን? እኛ በዚህ ያለነው እንደ ሥራችን
ስለ ሆነ፣ ትክክል ነው፣ 41 ነገር ግን ይህ ሰው ምንም ጥፋት አላደረገም” ብሎ መለሰለት። 42 ቀጥሎም፣ “ኢየሱስ ሆይ፣ በመንግሥትህ ስትመጣ
አስታውሰኝ” አለ። 43 ኢየሱስ፣ “እውነት እልሃለሁ፣ ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትሆናለህ” አለው። 44 ጊዜው ስድስት ሰዓት ገደማ ነበር፣ የፀሐይ ብርሃን በመቋረጡ
እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ በምድር ላይ ጨለማ ሆነ። 45 ከዚያም የቤተ መቅደሱ መጋረጃ ከመሐል ተቀደደ። 46 ኢየሱስ፣ “አባት ሆይ፣ ነፍሴን በእጅህ
አኖራለሁ” በማለት በታላቅ ድምፅ ጮኸ። ይህን ከተናገረ በኋላ ሞተ። 47 መቶ አለቃው የተደረገውን ነገር ባየ ጊዜ፣ “ይህ ሰው በእውነት ጻድቅ ነበር” በማለት
እግዚአብሔርን አከበረ። 48 ሁኔታውን ለማየት እጅግ ብዙ ሰዎች በመጡ ጊዜ፣ የተደረጉትን ነገሮች አይተው ደረታቸውን እየደቁ ተመለሱ። 49 ነገር ግን ከገሊላ
ጀምሮ የተከተሉት አንዳንድ ወንዶችና ሴቶች ከርቀት ቆመው ይህን ድርጊት ይከታተሉ ነበር። 50 እነሆ፣ የአግዚአብሔርን መንግሥት መምጣት የሚጠባበቅ፣
ከአይሁድ ከተማ፣ ከአርማቲያ የሆነ ዮሴፍ የሚባል 51 (በውሳኔያቸውና በድርጊታቸው ያልተስማማ) አንድ መልካምና ጻድቅ ሰው ነበረ። 52 ይህ ሰው ወደ
ጲላጦስ በመቅረብ የኢየሱስን አስከሬን እንዲሰጠው ጠየቀው። 53 አስክሬኑን አውርዶ በጥሩ የተልባ እግር ጨርቅ ከፈነውና ማንም ባልተቀበረበት ከድንጋይ
በተወቀረ መቃብር ውስጥ አኖረው። 54 ጊዜው የዝግጅት ቀን የነበረ ሲሆን፣ ሰንበትም እየገባ ነበር። 55 ከእርሱ ጋር ከገሊላ የመጡ ሴቶች ተከትለውት
በመሄድ መቃብሩንና አስከሬኑ እንዴት እንዳረፈ አዩ። 56 ከዚያም ተመልሰው ቅመማ ቅመምና ቅባቶችን አዘጋጁ። ሰንበት ስለ ነበር በሕጉ መሠረት ዐረፉ።

Luke 23:1

አጠቃላይ መረጃ
ኢየሱስ ጲላጦስ ፊት ቀረበ

የተሰበሰቡት በሙሉ
‹‹የአይሁድ መሪዎች ሁሉ›› ወይም፣ ‹‹የሸንጎው አባሎች ሁሉ››

ተነሡ
‹‹ቆሙ›› ወይም፣ ‹‹በእግራቸው ቆሙ››

ጲላጦስ ፊት
አንድ ሰው ፊት መቅረብ እርሱ ሥልጣን ውስጥ መግባት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የጲላጦስን ፍርድ ለማግኘት››

አገኘነው
‹‹እኛ›› የሚያመለክተው ጲላጦስን ወይም እዚያ የነበሩትን ሳይሆን የሸንጎውን አባሎች ነው።

ሕዝባችንን ሲያጣምም
‹‹ሕዝባችንን ሲያሳስት›› ወይም፣ ‹‹ሐሰት በመናገር ሕዝባችንን ሲያውክ››

ግብር እንዳይከፈል ሲከላከል
‹‹ግብር እንዳይከፍል ሲናገር››

ለቄሳር
ቄሳር የሮምን ንጉሥ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለንጉሥ››

Luke 23:3

ጲላጦስ ጠየቀው
‹‹ጲላጦስ ኢየሱስን ጠየቀው››

እንደዚያ ትላለህ
ይህም ማለት፣ 1) እንዲህ ሲል ኢየሱስ እርሱ የአይሁድ ንጉሥ መሆኑን እያመለከተ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አዎን፣ አንተ እንዳልኸው ነኝ›› ወይም፣ ‹‹አዎን፣ አንተ እንዳልኸው ነው›› ወይም 2) ኢየሱስ ይህን ሲል፣ የአይሁድ ንጉሥ በማለት የጠራው ጲላጦስ እንጂ፣ እርሱ አለመሆኑን እያመለከተ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያንን ያልኸው አንተ ራስህ ነህ››

መላው ሕዝብ
ብዙ ሕዝብ

በዚህ ሰው ላይ ምንም በደል አላገኘሁበትም
‹‹ይህን ሰው በምንም ዐይነት በደለኛ ሆኖ አላገኘሁትም››

ሲያውክ
‹‹በመካከል ሲረብሽ››

ከገሊላ ጀምሮ፣ መላው ይሁዳ ሳይቀር እዚህ ድረስ
ይህን እንደ አዲስ ዐረፍተ ነገር መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በይሁዳ ሁሉ፤ በገሊላ አሁን ደግሞ እዚህ ያውካል››

Luke 23:6

ይህን ሰምተናል
‹‹ኢየሱስ በገሊላ ማስተማር መጀመሩን ሰምተናል››

ሰውየው ገሊላዊ መሆኑን ጠየቀ
ጲላጦስ ኢየሱስ የመጣበትን ማወቅ የፈለገው ኢየሱስ ዝቅ ወዳለ ባለሥልጣን እንዲቀርብ ስለ ፈለገ ነው። ከገሊላ ከሆነ በገሊላ ላይ ሥልጣን ያለው ሄሮድስ ስለሆነ ሄሮድስ ኢየሱስ ላይ መፍረድ ነበረበት።

ሰውየው
x

Luke 23:8

በጣም ደስ አለው
‹‹ሄሮድስ በጣም ደስ አለው››

ሊያየው ይመኝ ነበር
‹‹ሄሮድስ ኢየሱስን ለማየት ይመኝ ነበር››

ስለ እርሱ ሰምቶ ነበር
‹‹ሄሮድስ ስለ ኢየሱስ ሰምቶ ነበር››

ተስፋ ያደርግ ነበር
‹‹ሄሮድስ ተስፋ ያደርግ ነበር››

እርሱ ተአምር ሲያደርግ ለማየት
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንዳንድ ተአምራት ሲያደርግ ለማየት››

ሄሮድስ ኢየሱስን በብዙ ቃላት ጠየቀው
‹‹ሄሮድስ ኢየሱስን ብዙ ጥያቄዎች ጠየቀው››

ምንም አልመለሰለትም
‹‹መልስ አልሰጠውም›› ወይም፣ ‹‹ለሄሮድስ መልስ አልሰጠውም››

ጸሐፍት ቆሙ
‹‹ጸሐፍት እዚያ ቆመው ነበር››

በብዙ ይወነጅሉት ነበር
‹‹አጥብቀው ኢየሱስን ከሰሱት›› ወይም፣ ‹‹ኢየሱስን በብዙ ዐይነት ወንጀል ከሰሱት››

Luke 23:11

ሄሮድስ ከሰራዊቱ ጋር
‹‹ሄሮድስና ሰራዊቱ››

የክብር ልብስ አለበሰው
‹‹ያማረ ልብስ አለበሰው›› ትርጉሙ ይህ ለኢየሱስ ክብርን ወይም ማሰብን እንደማያሳይ ማመልከት አለበት። ይህን ያደረጉት ኢየሱስ ላይ ለማፌዝና በእርሱ ለመቀለድ ነበር።

በዚያ ቀን ሄሮድስና ጲላጦስ ተወዳጁ
ከዚህ የምናገኘው መረጃ የተወዳጁት ኢየሱስ ላይ እንዲፈርድ ጲላጦስ ማድረጉን ሄሮድስ በማድነቁ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በእርሱ ላይ እንዲፈርድ ጲላጦስ ኢየሱስን ወደ ሄሮድስ ስለላከው በዚያ ቀን ሄሮድስና ጲላጦስ ተወዳጁ››

ከዚያ በፊት በመካከላቸው ጥል ነበር
x

Luke 23:13

የካህናት አለቆችን፣ ገዦችንና ሕዝቡን ሰበሰበ
‹‹የካህናት አለቆችንና ገዦችን፣ የሕዝቡንም ጉባኤ ስብሰባ ጠራ››

የሕዝብ ብዛት
ጲላጦስ ብዙ ሕዝብ አልጠራም። ኢየሱስ ላይ የሚሆነውን ለማየት ሕዝቡ እዚያው ነበሩ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እዚያ የነበረውን ሕዝብ››

ይህ ሰው
ይህ የሚያመለክተው ኢየሱስን ነው።

በፊታችሁ መረመርሁት
‹‹በፊታችሁ ኢየሱስን መረመርሁ›› ይህ ማለት የሚሆነውን ሁሉ እያዩ ነበር ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እዚሁ እናንተው ፊት ኢየሱስን መረመርሁት››

በዚህ ሰው ምንም በደል አላገኘሁም
‹‹በደለኛ ነው ብዬ አላስብም››

Luke 23:15

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ጲላጦስ ለአይሁድ መሪዎችና ለሕዝቡ መናገር ቀጥሏል።

ሄሮድስም እንዲሁ
እዚህ አጭር ዐረፍተ ነገር ውስጥ ያልተካተተ መረጃ መጨመር ሊጠቅም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሄሮድስም ቢሆን በደለኛ ነው ብሎ አያስብም›› ወይም፣ ‹‹ሄሮድስም ቢሆን ንጹሕ ነው ብሎ ያስባል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሄሮድስም ቢሆን
‹‹ሄሮድስም ቢሆን ምክንያቱም›› ወይም፣ ‹‹ሄሮድስም እንዲሁ፤ ምክንያቱም እኛ እናውቃለን››

ወደ እኛ መልሶታል
‹‹ሄሮድስ ኢየሱስን ወደ እኛ መለሰው›› — ‹‹እኛ›› የሚለው ጲላጦስን፣ ወታደሮቹን፣ ካህናትና ጸሐፍትንና እንጂ፣ ጲላጦስንና እየሰሙ የነበሩን ሰዎች አያመለክትም።

ለሞት የሚያበቃው ምንም ነገር አላደረገም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለሞት ፍርድ የሚያደርስ ምንም አላደረገም››

ስለዚህ እቀጣዋለሁ
ጲላጦስ ኢየሱስ ላይ ጥፋት ባለማግኘቱ ሳይቀጣው ሊፈታው ይገባ ነበር። ይህ ዐረፍተ ነገር ትርጒሙ ውስጥ ምክንያታዊ እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ አይደለም። ሕዝቡን በመፍራቱ ብቻ ንጹሕ መሆኑን የሚያውቀውን ኢየሱስን ጲላጦስ ቀጣው።

Luke 23:18

አጠቃላይ መረጃ
ቁጥር 19 በርባን ማን እንደ ነበር መረጃ ይሰጠናል።

ሁሉም በአንድነት ጮኹ
‹‹ሕዝቡ ሁሉ በአንድነት ጮኹ››

ይህን ሰው አስወግደውና ፍታው
‹‹ይህን ሰው ወዲያ በለው፤ ፍታልን!›› ወታደሮቹ ኢየሱስን እንዲገድሉ እየጠየቁት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ይህን ሰው ወዲያ ብለህ ግደለው፤ ፍታው››

ፍታልን
‹‹እኛ›› የሚለው የሚያመለክተው ሕዝቡን ብቻ እንጂ፣ ጲላጦስንና ወታደሮቹን አይደለም።

በርባን... ግድያ ሰው ነበር
ይህ ስለ በርባን ማንነት ሉቃስ የሚሰጠን ማስረጃ ነው።

ታስሮ ነበር
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሮማውያን አስረውት ነበር››

በከተማው በማመፅ
‹‹የከተማው ሰዎች የሮም መንግሥት ላይ እንዲያምፁ ለማነሣሣት በመሞከር››

Luke 23:20

እንደ ገና ነገራቸው
‹‹በድጋሚ ተናገራቸው›› ወይም፣ ‹‹ለሕዝቡና ለሃይማኖት መሪዎች እንደ ገና ነገራቸው››

ኢየሱስን ሊፈታው ፈልጐ
‹‹ኢየሱስን ነጻ ማድረግ ስለ ፈለገ››

ለሦስተኛ ጊዜ አላቸው
‹‹ጲላጦስ ለሦስተኛ ጊዜ እንደ ገና ለሕዝቡ አላቸው››

ይህ ሰው ምን ያደረገው አለ?
ጲላጦስ ይህን ጥያቄ ያቀረበው ኢየሱስ ንጹሕ መሆኑን ሕዝቡ እንዲረዱ ለማስቻል ነበር። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ይህ ሰው ምንም ያደረገው በደል የለም››

ለሞት ፍርድ የሚያበቃ ምንም አላገኘሁበትም
‹‹ለሞት የሚያበቃው ምንም አላደረገም››

ከገረፍሁ በኋላ እፈተዋለሁ
እርሱ ንጹ በመሆኑ ሉቃስ 23፥16 ላይ ጲላጦስ ያለ ምንም ቅጣት ሊፈታው ይገባ ነበር። ይሁን እንጂ፣ የሕዝቡን ቁጣ ለማብረድ ኢየሱስን መቅጣት ፈለገ።

እፈታዋለሁ
‹‹ነጻ እለቀዋለሁ››

Luke 23:23

አጥብቀው ለመኑት
‹‹ሕዝቡ አጥብቀው ለመኑት››

በታላቅ ድምፅ
‹‹በጩኸት››

እርሱ እንዲሰቀል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የጲላጦስ ወታደሮች ኢየሱስን እንዲሰቅሉ››

ጩኸታቸው እሺ አሰኘው
‹‹ጲላጦስ እሺ እስኪል ድረስ ሕዝቡ ጩኹ››

የጠየቁትን ለማድረግ
‹‹ሕዝቡ የጠየቁትን ለማድረግ››

የለመኑትን ፈታላቸው
ጲላጦስ በርባንን ከእስር ፈተው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጲላጦስ ሕዝቡ የለመኑትን በርባንን ፈታው››

በግድያ እስር ቤት... የነበረውን
ይህ በዚያ ጊዜ በርባን የት እንደ ነበር ዳራ መረጃ ነው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሮማውያን በግድያ አስረውት... የነበረውን››

ኢየሱስን ለፈቃዳቸው አሳልፎ ሰጠው
‹‹ሕዝቡ የፈለጉትን እንዲያደርጉበት ጲላጦስ ወታደሮቹ ኢየሱስን እንዲያመጣላቸው አዘዘ።

Luke 23:26

እየወሰዱ ሳለ
‹‹ወታደሮቹ ጲላጦስ ከነበረበት ኢየሱስን እየወሰዱ ሳለ››

ያዙት
ሮማውያን ወታደሮች ሰዎች ሸክም እንዲሸከሙ የማስገደድ ሥልጣን ነበራቸው። ይህን ስምዖን እንደ ታሰረ ወይም አንዳች በደል መፈጸሙን በሚያሳይ መልኩ አትተርጉም።

ስምዖን የተባለ የቀሬና ሰው
‹‹ከቀሬና ከተማ የሆነ ስምዖን የሚባል ሰው››

ከገጠር ሲመጣ
‹‹ከገጠር ወደ ኢየሩሳሌም እየመጣ የነበረ››

መስቀሉን አሸከሙት
‹‹መስቀሉን ትከሻው ላይ አኖሩ››

ኢየሱስን እንዲከተል
‹‹ከኢየሱስ ኋላ ተከተለ››

Luke 23:27

ብዙ ሕዝብ
‹‹በጣም ብዙ ሰዎች››

ብዙ ወንዶችና ሴቶች
ሴቶቹ የብዙ ሕዝብ አካል እንጂ፣ በራሳቸው ብዙ ሕዝብ አልነበሩም።

አለቀሱለት
‹‹ለኢየሱስ አለቀሱ››

ይከተሉት ነበር
ይህ ማለት የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ነበሩ ማለት አይደለም። ከእርሱ ኋላ ኋላ ይሄዱ ነበር ማለት ብቻ ነው።

ወደ እነርሱ ዘወር ብሎ
ይህ የሚያመለክተው ኢየሱስ ወደ ሴቶቹ ዘወር ማለቱንና በቀጥታ ለእነርሱ መናገሩን ነው።

የኢየሩሳሌም ሴቶች
‹‹የከተማው ሴቶች›› ማለት ከተማው ውስጥ የሚኖሩ ሴቶች ማለት ነው። ይህ ነውር ሳይሆን ከሌላው አካባቢ ሴቶች ለይቶ ለማመልከት የሚያገለግል አባባል ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እናንተ ከኢየሩሳሌም የሆናችሁ ሴቶች››

ለእኔ አታልቅሱ፤ ነገር ግን ለራሳችሁና ለልጆቻችሁ አልቅሱ
አንድ ሰው አንዳች ነገር እየሆነ ያለበትን ሰው ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ ላይ እየደረሰ ስላለው መከራ አታልቅሱ፤ ይልቁን፣ በእናንተና በልጆቻችሁ ላይ ስለሚደርሰው መከራ አልቅሱ›› ወይም፣ ‹‹እኔ ላይ በደረሰው መከራ እያለቀሳችሁ ነው፤ እናንተና ልጆቻችሁ ላይ በሚደርሰው የከፋ ነገር ይበልጥ ታለቅሳላችሁ››

Luke 23:29

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ኢየሱስ ለሕዝቡ መናገሩን አበቃ

እነሆ
ይህ የኢየሩሳሌም ሴቶች ለራሳቸው የሚያለቅሱበትን ምክንያት ያቀርባል።

ጊዜ ይመጣል
‹‹በቅርቡ ጊዜ ይመጣል››

እንዲህ የምትሉበት
‹‹ሰዎች እንዲህ የሚሉበት››

መካኖች
‹‹ልጆች የሌሉዋቸው ሴቶች››

ያልተሸከሙ ማሕፀኖች… ያላጠቡ ጡቶች
ገለጻዎቹ የተሰጡት፣ ‹‹መካኖችን›› የበለጠ ለመግለጽ ነው። እነዚህ ሴቶች አልወለዱም፤ ልጆች ጡት አላጠቡም። ሁለቱንም ከመካንነት ጋር ማያያዙ ይጠቅማል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ልጆች ያልወለዱ፣ ወይም ጡት ያላጠቡ መካኖች››

ከዚያም
በዚያ ጊዜ

ተራሮችን
ሐረጉን አጭር ለማድረግ ቃላት ተትተዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ተራሮችን ይሉዋቸዋል››

በእርጥብ እንጨት እንዲህ የሚያደርጉ ከሆነ፣ በደረቁ ምን ያደርጉ ይሆን?
ኢየሱስ ይህን ጥያቄ ያቀረበው በመልካሙ ጊዜ ይህን ያህል መጥፎ ነገር ካደረጉ፣ ወደ ፊት በሚመጣው ክፉ ጊዜ ደግሞ ከዚህ የከፋ ነገር እንደሚያደርጉ ሕዝቡ መገንዘብ እንዲችሉ ለመርዳት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዛፉ ደረቅ በሚሆንበት ጊዜ የበለጠ መጥፎ ነገር እንደሚያደርጉ እርግጠኛ መሆን ትችላላችሁ››

እርጥብ ዛፍ
እርጥብ ዛፍ የመልካም ነገር ምሳሌ ነው። ቋንቋህ ተመሳሳይ ምሳሌ ካለው እዚህ ተጠቀምበት።

በደረቁ
ደረቅ ዛፍ ለመቃጠል ብቻ የሚጠቅም ነገርን የሚያመለክት ምሳሌ ነው።

እነርሱ
ይህ የሚያመለክተው ሮማውያንን ወይም የአይሁድ መሪዎችን ሊሆን ይችላል። ከሁለት አንዱን ብቻ አይደለም።

Luke 23:32

ሌሎች ሰዎች፣ ሁለት ወንጀለኞች ለመገደል ከእርሱ ጋር ተወሰዱ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወታደሮቹ ሁለት ወንጀለኞች እንዲገደሉ ከኢየሱስ ጋር ወሰዱ››

ሌሎች ሰዎች፣ ሁለት ወንጀለኞች
‹‹ወንጀለኞች የነበሩ ሁለት ሌሎች ሰዎች›› ወይም፣ ‹‹ሁለት ወንጀለኞች›› ሉቃስ ‹‹ሌሎች ወንጀለኞች›› ማለት አልፈለጉም፤ ምክንያቱም ምንም እንኳ እንደ ወንጀለኛ ቢቆጠርም፣ ኢየሱስ ንጹሕ ሰው ነበር። ሉቃስ ሌሎቹን ሁለት ሰዎች እንጂ፣ ኢየሱስን ወንጀለኛ አላለም።

Luke 23:33

ሲመጡ
‹‹እነርሱ›› የሚያመለክተው ወታደሮቹን፣ ወንጀለኞቹንና ኢየሱስን ነው።

ሰቀሉት
‹‹የሮም ወታደሮች ኢየሱስን ሰቀሉት››

አንዱን በቀኙ፣ ሌላውን በግራው
‹‹አንዱን ወንጀለኛ በኢየሱስ ቀኝ ሌላውን ወንጀለኛ በኢየሱስ ግራ ጐን ሰቀሉ››

አባት ሆይ፣ ይቅር በላቸው
‹‹እነርሱ›› የሚያመለክተው ኢየሱስን የሰቀሉ ሰዎች ነው። ኢየሱስ ወደ አባቱ የጸለየው ለሰቀሉት ሰዎች በመራራት ነበር።

አባት
ይህ ጠቃሚ የእግዚአብሔር መጠሪያ ነው።

የሚያደርጉን አያውቁምና
‹‹ምክንያቱም ምን እያደረጉ እንደሆነ አያስተውሉም›› የሮም ወታደሮች የእግዚአብሔርን ልጅ እየሰቀሉ እንደ ነበር አይረዱም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እየሰቀሉ ያለው ማን እንደሆነ በእርግጥ አይረዱም።

ዕጣ ጣሉ
ወታደሮቹ ቁማር በሚመስል አሠራር ተሳተፉ። ‹‹ቁማር ተጫወቱ››

ዕጣ ጥለው ልብሶቹን ተከፋፈሉ
‹‹እያንዳንዱን የኢየሱስ ልብስ ቁራጭ ማን መውሰድ እንዳለበት ለመወሰን ወታደሮቹ ዕጣ ጣሉ››

Luke 23:35

ሕዝቡ ቆሙ
‹‹ሕዝቡ እዚያ ቆመው ነበር››

እርሱ
ይህ የሚያመለክተው ኢየሱስን ነው።

ሌሎቹን አዳነ፤ ራሱን ያድን
ሉቃስ የመሪዎቹን ስላቅ ቃሎች አስፍሮአል። ኢየሱስ ሌሎቹን የሚያድንበት ብቸኛ መንገድ በመሞት እንጂ፣ ራሱን በማዳን አይደለም።

ራሱን ያድን
‹‹ኢየሱስ ራሱን ማዳን መቻል አለበት›› ይህን ያሉት በኢየሱስ ለማፌዝ ነው። ራሱን ማዳን እንደሚችል አያምኑም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ራሱን ከመስቀል በማዳን ማንነቱን ሲያረጋግጥ ማየት እንፈልጋለን››

የተመረጠው
‹‹እግዚአብሔር የመረጠው እርሱ››

Luke 23:36

እርሱ
ኢየሱስ

ወደ እርሱ ቀርቦ
‹‹ወደ ኢየሱስ ተጠግቶ››

የኮመጠጠ ወይን ጠጅ ሰጠው
‹‹ኢየሱስ እንዲጠጣ የኮመጠጠ ወይን ጠጅ ቀረበለት›› ኮምጣጣ ወይን ጠጅ ማንኛውም ሰው የሚጠጣው ተራ መጠጥ ነው። ንጉሥ ነኝ ይል ለነበረው ርካሽ መጠጥ በመስጠት ወታደሮቹ በኢየሱስ እያፌዙ ነበር።

የአይሁድ ንጉሥ ከሆንህ ራስህን አድን
ወታደሮቹ በኢየሱስ እያፌዙ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአይሁድ ንጉሥ ነህ ብለን አናምንም፤ ግን ከሆንህ ራስህን በማዳን ስህተታችንን አሳየን››

ከእርሱ በላይ ምልክት
‹‹ኢየሱስ መስቀል ዐናት ላይ የነበረ ጽሑፍ››

ይህ የአይሁድ ንጉሥ ነው
ምልክቱን ከእርሱ በላይ በማድረግ ሰዎቹ ኢየሱስ ላይ እያፌዙ ነበር። ንጉሥ ነው ብለው አያስቡም።

Luke 23:39

ሰደቡት
‹‹ኢየሱስን ሰደቡት››

አንተ ክርስቶስ አይደለህንም? ራስህን አድን
ወንጀለኛው ጥያቄውን ያቀረበው በኢየሱስ ለማፌዝ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ክርስቶስ ነኝ ብለሃል፤ ራስህን አድን›› ወይም፣ ‹‹አንተ በእርግጥ ክርስቶ ከሆንህ ራስህን ማዳን ነበረብህ››

ራስህንና እኛን አድን
ወንጀለኛው ኢየሱስ ከመስቀል እንደሚያድናቸው በእርግጥ አያስብም።

ሌላው ገሠጸው
‹‹ሌላው ወንጀለኛ ገሠጸው››

ተመሳሳይ ፍርድ እየተቀበልህ ሳለህ ከቶ እግዚአብሔርን አትፈራምን?
ወንጀለኛው ጥያቄውን ያቀረበው ሌላውን ወንጀለኛ ለመገሠጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔርን መፍራት አለብህ ምክንያቱም እርሱን በቀጡበት መንገድ አንተንም እየቀጡህ ነው። ወይም፣ ‹‹እንደ እርሱ ሁሉ አንተም መስቀል ላይ ተሰቅለህ ሳለ እርሱ ላይ በማፌዝህ እግዚአብሔርን አትፈራም ማለት ነው››

እኛ ላደረግነው... ቅጣት... ይገባናል
‹‹እኛ›› የሚያመለክተው ሁለቱን ወንጀለኞች እንጂ፣ ኢየሱስን ወይም ሌሎችን ሰዎች አይደለም።

እኛ እዚህ መሆናችን ተገቢ ነው
‹‹በእውነት እኛ ይህ ቅጣት ይገባናል››

ይህ ሰው
ይህ የሚያመለክተው ኢየሱስን ነው

Luke 23:42

ከዚያም አለ
‹‹ወንጀለኛውም አለ››

አስበኝ
‹‹እኔንም አስበኝ፤ በመልካም እየኝ››

ወደ መንግሥትህ ስትመጣ
‹‹ወደ መንግሥትህ ስትመጣ›› ማለት መግዛት ስትጀምር ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ንጉሥ መግዛት ስትጀምር››

ዛሬ በእውነት እልሃለሁ
‹‹በእውነት›› የተጨመረው ኢየሱስ ለተናገረው አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዛሬ ያንን እንድታውቅ እፈልጋለሁ››

Luke 23:44

ስድስት ሰዓት ያህል
‹‹ቀትር አካባቢ›› ይህ ቀኑ በ12 ሰዓት መቆጠር በሚጀምርበት ባሕል ያለውን ያመለክታል።

በምድር ሁሉ ላይ ጨለማ መጣ
‹‹ምድሩ ሁሉ ጨለማ ሆነ››

እስከ ዘጠኝ ሰዓት
እስከ 3 ሰዓት ‹‹ይህ የሚያመለክተው ቀኑ 12 ሰዓት ላይ መቆጠር የሚጀምርበትን ባሕል ነው።

የፀሐይ ብርሃን ጠፋ
ይህ ፀሐይ ጠለቀች ማለት አይደለም። ይልቁን ቀኑ አጋማሽ ላይ የፀሐይ ብርሃን ጨለመ ማለት ነው። ፀሐይ ጠለቀች የሚል ሳይሆን ፀሐይ ጨለመች የሚል አገላለጽ ተጠቀም።

የቤተ መቅደስ መጋረጃ
‹‹ቤተ መቅደስ ውስጥ ያለው መጋረጃ›› ይህ ቅዱሳት ቅዱሳኑን ከተቀረው መቅደስ የሚለይ መጋረጃ ነው።

የቤተ መቅደስ መጋረጃ ተከፈለ
x

Luke 23:46

በከፍተኛ ድምፅ ማልቀስ
‹‹በጣም ጮኸ›› ይህን ቀደም ሲል ከነበረው ቁጥር ሁኔታ ጋር ማያያዙ መልካም ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያ በሚሆንበት ጊዜ ኢየሱስ በጣም ጮኸ››

አባት ሆይ
ይህ በጣም አስፈላጊ የእግዚአብሔር መጠሪያ ነው።

መንፈሴን በእጅህ እሰጣለሁ
‹‹በእጅህ›› የሚለው የእግዚአብሔርን ጥበቃ ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹መንፈሴን ለአንተ ጥበቃ እሰጣለሁ›› ወይም፣ ‹‹አንተ እንድትጠብቀው በማወቅ፣ መንፈሴን ለአንተ እሰጣለሁ››

ይህንም ብሎ
‹‹ኢየሱስ ይህን ካለ በኋላ››

ሞተ
‹‹ኢየሱስ ሞተ››

መቶ አለቃው
ይህ በሌሎች ሮማውያን ወታደሮች ላይ ኀላፊነት ላለው ሮማዊ ባለ ሥልጣን የሚሰጥ መጠሪያ ነው። ስቅለቱን ይከታተል ነበር።

የተደረገውን
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሆነውን ነገር ሁሉ››

ይህ ጻድቅ ሰው ነው
‹‹ይህ ሰው ምንም በደል አልፈጸመም›› ወይም፣ ‹‹ይህ ሰው ያደረገው መጥፎ ነገር የለም››

Luke 23:48

ብዙዎች
በጣም ብዙ ሰዎች

መጥተው የነበሩ
‹‹ተሰብስበው የነበሩ››

ይህን ያዩ
‹‹ይህን ሁኔታ ያዩ›› ወይም፣ ‹‹እየሆነ ያለውን የተመለከቱ››

የተደረገውን ነገር
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሆነውን››

እየደቁ ተመለሱ
‹‹እየመቱ ወደ ቤታቸው ተመለሱ››

ደረታቸውን እየደቁ
ይህ የሐዘንና የፀፀት ምልክት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ማዘናቸውን ለማሳየት የገዛ ራሳቸውን ደረት እየመቱ››

ተከተሉት
‹‹ከኢየሱስ ጋር ተጓዙ››

ከሩቅ
‹‹ከኢየሱስ ጥቂት ራቅ ብሎ››

እነዚህ ነገሮች
‹‹የሆነው››

Luke 23:50

አጠቃላይ መረጃ
ዮሴፍ ጲላጦስን የኢየሱስን ሥጋ ለመነው። ይህ ስለ ዮሴፍ ታሪክ መረጃ ይሰጠናል። ምናልባትም ዩዲቢ እንዳደረገው ይህን መረጃ ከመሸጋገሪያ ጥቅስ ጋር መጻፍ ይጠቅም ይሆናል።

እነሆ አንድ ሰው ነበረ
‹‹እነሆ›› የሚለው ቃል የአዲስ ሰው ታሪክ እንድንሰማ ያዘጋጀናል። ቋንቋህ ይህን የሚያደርግበት መንገድ ይኖረዋል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹… የሆነ ሰው ነበር››

ሸንጎ
‹‹የአይሁድ ሸንጎ››

በሸንጎው ውሳኔና ድርጊት
ውሳኔው ምን እንደ ነበር መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ኢየሱስን ለመግደል ባደረጉ ውሳኔም ሆነ እርሱን በመግደል ድርጊታቸው››

አርማትያስ የምትባል የይሁዳ ከተማ
‹‹የይሁዳ ከተማ›› ማለት ይሁዳ ውስጥ ነበረች ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ይሁዳ ውስጥ ያለች አርማትያስ የምትባል ከተማ››

Luke 23:52

ይህ ሰው ወደ ጲላጦስ መጥቶ የኢየሱስን ሥጋ ለመነው
‹‹ይህ ሰው ወደ ጲላጦስ ሄዶ የኢየሱስን ሥጋ ለመቅበር እንዲሰጠው ጠየቀ››

አወረደው
‹‹ዮሴፍ የኢየሱስን ሥጋ ከመስቀል አወረደ››

በበፍታ ጠቀለለው
‹‹ሥጋውን በንጹሕ በፍታ ልብስ ጠቀለለው›› በዚያ ዘመን ይህ የተለመደ አቀባበር ሥርዐት ነበር።

ከድንጋይ ተፈልፍሎ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አንድ ሰው ገደል ላይ ካለ ዐለት የፈለፈለው››

ማንም ባልተቀበረበት
ይህን በአዲስ ዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከዚያ በፊት የማንም ሰው ሥጋ ባልተቀመጠበት››

Luke 23:54

የመዘጋጀት ቀን
‹‹ሰንበት ለሚባለው ዕረፍት አይሁድ የሚዘጋጁበት ቀን››

ሰንበት ሊገባ ነበር
ለአይሁድ ቀኑ የሚጀምረው ፀሐይ ስትጠልቅ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ፀሐይ ጠልቃ ሰንበት የሚጀምርበት ጊዜ ቀርቦ ነበር››

ከገሊላ ከኢየሱስ ጋር የመጡ
‹‹ከገሊላ አውራጃ ከኢየሱስ ጋር የተጓዙ››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ተከትለው መቃብሩንና ሥጋውን እንዴት እንዳኖሩት አዩ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከዮሴፍና አብረውት ከነበሩ ሰዎች ኋላ በመሄድ፣ ሴቶቹ መቃብሩንና ሰዎቹ የኢየሱስን ሥጋ መቃብሩ ውስጥ እንዴት እንዳኖሩት አዩ››

ተመለሱ
‹‹ሴቶቹ ወደ ቤት ተመለሱ››

ሽቱና ቅባት አዘጋጁ
እርሱ በሞተበት ቀን ሴቶቹ መዓዛ ያለው ሽቱና ቅባት በማድረግ ኢየሱስን ለማክበር ጊዜ ስላልነበራቸው በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን ጠዋት ያንን ለማድረግ ሄዱ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የኢየሱስ ሥጋ ላይ ለማኖር ሽቱና ቅባት አዘጋጁ››

ዐረፉ
‹‹ሴቶቹ ምንም አልሠሩም››

በትእዛዙ መሠረት
‹‹እንደ አይሁድ ሕግ›› ወይም፣ ‹‹የአይሁድ ሕግ እንደሚያዝዘው›› በሕጉ መሠረት በሰንበት ሥጋን ለማዘጋጀት አይፈቀድላቸውም።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **24**

1 በሳምንቱ በመጀመሪያው ቀን ሴቶች ያዘጋጁትን ሽቱ ይዘው በጣም ማልደው ወደ መቃብሩ መጡ። **2** ድንጋዩ ከመቃብሩ ተንከባሎ አገኙት። **3** ወደ ውስጥ ገቡ፣ ነገር ግን የጌታ ኢየሱስን ሥጋ አላገኙም። **4** ስለዚህ ነገር ግራ ተጋብተው ሳሉ፣ የሚያብረቀርቅ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች በድንገት ከአጠገባቸው ቆመው አገኙ። **5** ሴቶቹ በፍርሃት ተሞልተውና ወደ መሬት አቀርቅረው ሳሉ፣ ሰዎቹ ፣“ስለምን ሕያውን ከሙታን መካከል ትፈልጋላችሁ? **6** እርሱ በዚህ የለም፣ ተነሥቷል! ገና በገሊላ ሳለ፣ **7** እንዴት በኃጢአተኞች ሰዎች እጅ ተላልፎ እንደሚሰጥ፣ እንደሚሰቀልና በሦስተኛው ቀን እንደሚነሣ የነገራችሁን አስታውሱ" አሏቸው። **8** ሴቶቹ ቃሎቹን አስታወሱ፣ **9** ከመቃብሩም ተመለሱና እነዚህን ነገሮች ሁሉ ለዐሥራ አንዱና ለተቀሩትም ነገሩ። **10** መግደላዊት ማርያም፣ ዮሐናና የያዕቆብ እናት ማርያም እንዲሁም ሌሎች ሴቶች ሁኔታውን ለሐዋርያት ነገሯቸው። **11** ነገር ግን ይህ ንግግር ለሐዋርያቱ ቀልድ ስለ መሰላቸው፣ ሴቶቹን አላመኗቸውም፣ **12** ሆኖም ግን ጴጥሮስ ተነሣና እየሮጠ ወደ መቃብሩ ሄደ፣ ከዚያም አጎንብሶ ወደ ውስጥ ሲመለከት፣ የተልባው እግር ጨርቅ ለብቻው ተቀምጦ አየ። ከዚያ በኋላ ጴጥሮስ ምን ተፈጥሮ ይሆን ብሎ እያሰበ ወደ ቤቱ ተመለሰ። **13** እነሆ፣ ከእነርሱ ሁለቱ በዚያው ቀን ከኢየሩሳሌም ስድሳ ምዕራፍ ርቆ ወደሚገኝ ኤማሁስ ወደሚባል መንደር እየተጓዙ ነበር። **14** ስለሆኑት ነገሮች ሁሉ በመንገዳቸው ላይ እርስ በርስ ይነጋገሩ ነበር። **15** እየተነጋገሩና እየተጠያየቁ በመሄድ ላይ ሳሉ፣ ኢየሱስ ወደ እነርሱ ተጠግቶ ይሄድ ነበር። **16** ነገር ግን እርሱን እንዳያውቁት ዐይኖቻቸው ተይዘው ነበር። **17** ኢየሱስ፣ “እናንተ ሁለታችሁ እየተጓዛችሁ የምትነጋገሩት ስለምንድን ነው?” አላቸው። ያዘኑ መስለው ቆም አሉ። **18** ስሙ ቀለዮጳ የተባለ ከሁለቱ አንዱ፣ “በኢየሩሳሌም ሰሞኑን የተደረጉትን ነገሮች የማታውቅ አንተ ብቻ ነህን?" ብሎ መለሰለት። **19** ኢየሱስም፣ “ነገሮቹ ምንድን ናቸው?” አላቸው። **20** እነርሱም እንዲህ ብለው መለሱለት፣ “የካህናት አለቆችና ገዢዎቻችን ኢየሱስ የተባለውን ናዝራዊና ነቢይ እንዴት አድርገው እንደ ፈረዱበትና ለሞትና ለስቅላት አሳልፈው እንደ ሰጡት ነዋ። **21** እስራኤልን ነጻ ያወጣል ብለን ተስፋ ያደረግነው እርሱን ነበር። አዎን፣ ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ ይህ ነገር ከሆነ አሁን ሦስተኛ ቀኑ ነው” **22** ነገር ግን ጠዋት ወደ መቃብሩ የሄዱ ከእኛ ጋር የሆኑ አንዳንድ ሴቶች አስገረሙን። **23** ሥጋውን ባላገኙ ጊዜ፣ በመቃብሩ ውስጥ ሥጋውን እንዳላገኙና እርሱ ሕያው ሆኗል ብለው የነገሯቸውን የመላእክት ራእይ አይተናል አሉ። **24** ከእኛ ጋር ካሉት ወንዶችም አንዳንዶች ወደ መቃብሩ ሄደው ልክ ሴቶቹ እንዳሉት ሆኖ አገኙት። ነገር ግን እርሱን አላዩትም”። **25** ኢየሱስም፣ “ነቢያት የተናገሩትን ሁሉ ለማመን የዘገያችሁ እናንተ ሞኞች! **26** ክርስቶስ በእነዚህ ነገሮች መሠቃየቱና ወደ ክብሩ መግባቱ ግድ መሆኑን አታውቁምን?" አላቸው። **27** ከዚያም ከሙሴ ጀምሮ እስከ ነቢያት መጻሕፍት፣ በመጻሕፍት ሁሉ ስለ እርሱ የተነገረውን ተረጐመላቸው። **28** ወደሚሄዱበት መንደር በተቃረቡ ጊዜ፣ ኢየሱስ ቀደም ቀደም እያለ መሄድ ጀመረ። **29** ነገር ግን እነርሱ፣ “ቀኑ እየመሸ ጊዜውም እያለፈ ስለ ሆነ ከእኛ ጋር እደር” ብለው ጎተጎቱት። ስለዚህ ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር ሊያድር ሄደ። **30** ለመብላት ከእነርሱ ጋር በማዕድ በተቀመጠ ጊዜ፣ እንጀራውን ወሰደና ከባረከው በኋላ ቈርሶ ሰጣቸው። **31** በዚህ ጊዜ ዐይኖቻቸው ተከፈቱና አወቁት። እርሱ ግን ከዐይናቸው ተሰወረባቸው። **32** እርስ በርሳቸው፣ “በመንገድ ላይ አብረን ሳለን ሲያናግረንና መጻሕፍትን ሲከፍት ልባችን በውስጣችን ይቃጠልብን አልነበርምን?” ተባባሉ። **33** በዚያው ሰዓት ተነሥተው ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ። ዐሥራ አንዱና ከእነርሱ ጋር የነበሩትም ተሰብስበው እንዲህ እያሉ አገኟቸው፤ **34** “ጌታ በእርግጥ ተነሥቷል፣ ለስምዖንም ታይቷል።” **35** ከዚያም በመንገድ ላይ የሆነውን ነገርና ኢየሱስ በማዕድ እንጀራን በሚቈርስበት ጊዜ እንዴት እንደ ታያቸው ተናገሩ። **36** እነዚህን ነገሮች እየተናገሩ እያሉ ኢየሱስ ራሱ በመካከላቸው ቆሞ፣ “ሰላም ለእናንተ ይሁን" አላቸው። **37** እነርሱም ስለ ተሸበሩና በፍርሃት ስለ ተዋጡ መንፈስ ያዩ መሰላቸው። **38** ኢየሱስ፣ “ለምን ትጨነቃላችሁ? ለምንስ በልባችሁ ጥያቄዎች ይነሣሉ? **39** እኔው ራሴ ስለ መሆኔ እጆቼንና እግሮቼን እዩ። ዳሳችሁም እዩኝ። በእኔ እንደምታዩት መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውም" አላቸው። **40** ይህን ተናግሮ እጆቹንና እግሮቹን አሳያቸው። **41** ከደስታ የተነሣ ማመን ተስኗቸው ግራ ተጋብተው ሳሉ፣ ኢየሱስ፣ “የሚበላ ጥቂት ነገር ይኖራችኋል?” አላቸው። **42** የተጠበሰ ዐሣ ሰጡት። **43** ኢየሱስም ወስዶ በፊታቸው በላው። **44** እንዲህም አላቸው፤ “ከእናንተ ጋር በነበርሁ ጊዜ በሙሴ ሕግ፣ በነቢያትና በመዝሙራት የተጻፈው ሁሉ መፈጸም እንደሚገባው ነግሬአችሁ ነበር።” **45** ከዚያም መጻሕፍትን ይረዱ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው። **46** እንዲህ አላቸው፤ “እንግዲህ ክርስቶስ መሠቃየት፣ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን መካከል መነሣት እንደሚገባው በመጻሕፍት ተጽፏል። **47** ደግሞም ንስሐና የኃጢአት ይቅርታ ከኢየሩሳሌም ጀምሮ ለአሕዛብ ሁሉ በስሙ መሰበክ አለበት። **48** እናንተ የእነዚህ ነገሮች ምስክሮች ናችሁ። **49** እነሆ፣ የአባቴን ተስፋ በእናንተ ላይ እልካለሁ። ኀይልን ከላይ እስከምትቀበሉ ድረስ በዚህ ከተማ ሆናችሁ ተጠባበቁ።" **50** ከዚያም ኢየሱስ ወደ ቢታንያ እስከሚቃረቡ ድረስ ይዟቸው ሄደ። እጆቹንም አነሣና ባረካቸው፤ **51** እየባረካቸውም ሳለ ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ አለ። **52** ስለዚህ እነርሱ ሰገዱለት፣ እጅግ ደስ እያላቸውም ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ። **53** በቤተ መቅደስም ያለ ማቋረጥ እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር።

Luke 24:1

አጠቃላይ መረጃ
ሴቶቹ የኢየሱስ ሥጋ ላይ ለማድረግ ሽቱ ይዘው ወደ መቃብሩ ተመለሱ።

በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን በጣም ጠዋት ሳለ
‹‹ከእሑድ ጠዋት በፊት››

ወደ መቃብሩ መጡ
‹‹ሴቶቹ ወደ መቃብሩ ደረሱ››

መቃብሩ
ከገደል ዐለት ተፈልፍሎ የተሠራ መቃብር።

ሽቱ ይዘው
ይህ ሉቃስ 23፥56 ላይ ያዘጋጁት ሽቱ ነው።

ድንጋዩን አገኙ
‹‹ድንጋዩን አዩ››

ድንጋዩ ተንከባልሎ ነበር
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሰው ድንጋዩን አንከባልሎት››

ድንጋዩ
ይህ የመቃብሩን መግቢያ በር መዝጋት የሚችል ትልቅ፣ የተጠረበና ክብ ትልቅ ድንጋይ ነው። ያንን ለማንከባለል ብዙ ሰው ይጠይቃል።

የጌታ ኢየሱስን ሥጋ አላገኙም
ያላገኙት እዚያ ስላልነበረ መሆኑን በግልጽ ማመልከት ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የጌታ ኢየሱስ ሥጋ እዚያ አልነበረም››

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Luke 24:4

አጠቃላይ መረጃ
መላእክት ተገልጠው ለሴቶቹ መናገር ጀመሩ

እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ ጥቅም ላይ የዋለው ታሪኩ ውስጥ አዲስ ሁኔታ መጀመሩን ለማመልከት ነው። ቋንቋህ ይህን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ ላይ ተጠቀምበት።

በፍርሃት ተሞሉ
‹‹በጣም ፈሩ››

ፊታቸውን ወደ መሬት ዝቅ አደረጉ
‹‹ወደ መሬት በጣም ዝቅ›› ይህ የሚያመለክተው ለሰዎቹ ያላቸውን አክብሮት ነው።

ሕያው የሆነውን ከሙታን መካከል ለምን ትፈልጋላችሁ?
x

Luke 24:6

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
መላእክቱ ለሴቶቹ መናገር አበቁ

ግን፣ ተነሥቷል
‹‹ግን እርሱ እንደ ገና ሕያው ሆኖአል›› እዚህ ላይ፣ ‹‹ተነሣ›› የሚለው፣ ‹‹እንደ ገና ሕያው መሆንን›› ያመለክታል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምክንያቱም እግዚአብሔር እንደ ገና ሕያው አድርጐታል››

እንዳላችሁ አስታውሱ
‹‹የነገራችሁን አስታውሱ››

ለእናንተ
‹‹እናንተ›› ብዙ ቁጥር ሲሆን ሴቶቹንና በተጨማሪም ሌሎቹን ደቀ መዛሙርት ሊያመለክት ይችላል።

የሰው ልጅ
ይህ ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅስ መጀመሪያ ነው። ዩዲቢ ላይ እንዳለው በቀጥተኛ ጥቅስ ሊተረጐም ይችላል።

የሰው ልጅ ለኀጢአተኞች እጅ ተላልፎ ሊሰጥና ሊሰቀል ይገባዋል
‹‹ይገባዋል›› የሚለው እንደዚያ እንዲሆን እግዚአብሔር በመወሰኑ በእርግጥ መሆኑ የማይቀር ነገር ማለት ነው። ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱን ለሚሰቅሉ ክፉ ሰዎች የሰውን ልጅ አሳልፈው መስጠታቸው አስፈላጊ ነበር››

እጅ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› ኀይል ወይም ቁጥጥርን ያመለክታል።

በሦስተኛው ቀን
አይሁድ ማንኛውንም የቀኑን ክፍል እንደ ቀን ይቆጥራሉ። ስለዚህም የተቀበረበትንና የሰንበትን ቀን በማስከተሉ ኢየሱስ የተነሣበት ቀን ‹‹ሦስተኛ ቀን›› ተብሏል።

Luke 24:8

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ሴቶቹ መቃብሩ ውስጥ ያዩትን ለሐዋርያት ለመናገር ሄዱ።

ቃሉን አስታውሱ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ቃል›› ኢየሱስ የተናገረውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኢየሱስ የተናገረውን አስታውሱ››

ዐሥራ አንዱና የተቀሩት ሁሉ
‹‹ዐሥራ አንዱ ሐዋርያትና ከእነርሱ ጋር የነበሩ ደቀ መዛሙርት››

ዐሥራ አንዱ
ይሁዳ ከዐሥራ ሁለቱ ተለይቶ ኢየሱስን አሳልፎ በመስጠቱ ሉቃስ ዐሥራ አንዱን ሲያመለክት ይህ የመጀመሪያ ጊዜ ነው።

አሁን
ቃሉ እዚህ ጥቅም ላይ የዋለው በዋናው ታሪክ መስመር የገባ መኖሩን ለማመልከት ነው። እዚህ ላይ ሉቃስ ከመቃብር መጥተው እዚያ የሆነውን ለሐዋርያት የተናገሩ የአንዳንድ ሴቶችን ስም ይሰጣል።

Luke 24:11

ለሐዋርያቱ ይህ መልእክት መቀባዠር መሰላቸው
‹‹ሐዋርያቱ ሴቶቹ ጅል ነገር እየተናገሩ እንደሆነ አሰቡ››

ጴጥሮስ ግን
ይህ ሐረግ ጴጥሮስን ከሌሎቹ ሐዋርያት ያነጻጽራል። ሴቶቹ የተናገሩትን አላቃለለውም፤ ግን ለራሱ ለማየት ወደ መቃብሩ ሮጠ።

ተነሣ
ይህ አነጋገር፣ ‹‹ማድረግ ጀመረ›› ማለት ነው። ማድረግ በጀመረ ጊዜ ጴጥሮስ ተቀምጦ ይህን ወይም ቆሞ የነበረ መሆኑ አስፈላጊ አይደለም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጀመረ››

ጐንበስ ብሎ
ከዐለት የተፈለፈለው መቃብር በጣም ዝቅ ያለ ስለ ነበር ውስጡ ያለውን ለማየት ጴጥሮስ ዝቅ ማለት ነበረበት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከወገቡ ጐንበስ ብሎ››

በፍታው እንዳለ ለብቻው
‹‹በፍታው ብቻ›› ይህ የሚያመለክተው ሉቃስ 23፥53 ላይ ሲቀበር ኢየሱስ ላይ ተጠቅልሎ የነበረውን ጨርቅ ነው። የኢየሱስ ሥጋ እዚያ አለመኖሩን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኢየሱስ ተጠቅልሎበት የነበረው ጨረቅ፣ ኢየሱስ ግን እዚያ አልነበረም››

ወደ ቤቱ ሄደ
‹‹ወደ ቤቱ ተመለሰ››

Luke 24:13

አጠቃላይ መረጃ
ሁለት ደቀ መዛሙርት በኤማሁስ መንገድ ላይ ናቸው።

እነሆ
ጸሐፊው ይህን ቃል የተጠቀመው አዲስ ሁኔታ መጀመሩን ለማመልከት ነው።

ከእነርሱ ሁለቱ
‹‹ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱ››

በዚያው ቀን
‹‹በዚያው ዕለት›› ይህ የሚያመለክተው ሴቶች መቃብሩ ባዶ ሆኖ ያገኙበትን ቀን ነው።

ኤማሁስ
ይህ የከተማ ስም ነው።

ስድሳ ስታዲያ
‹‹ዐሥራ አንድ ኪሎ ሜትር›› አንድ፣ ‹‹ስታዲያ›› 185 ሜትር ነው።

Luke 24:15

እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ እዚህ ጥቅም ላይ የዋለው ድርጊቱ የተጀመረበትን ለማመልከት ነው። የጀመረው ኢየሱስ ወደ እነርሱ የቀረበ ጊዜ ነበር። ቋንቋህ ይህን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ ተጠቀምበት።

ኢየሱስ ራሱ
‹‹ራሱ›› የሚለው ቃል ለእነርሱ የተገለጠው፣ ስለ እርሱ እየተናገሩ የነበረው ኢየሱስ እንደ ነበር አጽንዖት ይሰጣል። እስከዚህ ጊዜ ድረስ ሴቶቹ መላእክቱን ቢያዩም ኢየሱስ ያየ ሰው አልነበረም።

እንዳያውቁት ዐይናቸው ተይዞ ነበር
‹‹እንዳያውቁት ዐይናቸው ተጋርዶ ነበር›› የሰዎቹ ኢየሱስን የማወቅ ችሎታ እንደ መጋረጃ ተጋርዶ እንደ ነበር ተነግሯል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። ኢየሱስን እንዳያውቁ ዐይናቸውን የያዘው እግዚአብሔር እንደሆነ ግልጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱን እንዳያውቁት አንዳች ነገር ሆኖ ነበር›› ወይም፣ ‹‹እግዚአብሔር እንዳያውቁት አድርጓቸው ነበር››

Luke 24:17

ኢየሱስ አላቸው
‹‹ለሁለቱ ሰዎች ኢየሱስ አላቸው››

ቀለዮጳ
ይህ የሰው ስም ነው።

አንተ ብቻ ነህን... ቀኖች?
ቀለዮጳ ይህን ጥያቄ ያቀረበው ይህ ሰው በኢየሩሳሌም የተደረገውን ባለማወቁ መገረሙን ለመግለጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተ ብቻ መሆን አለብህ... በቀኖች››

Luke 24:21

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ሁለቱ ሰዎች ለኢየሱስ መናገር ቀጥለዋል።

እስራኤልን ይቤዣል
ሮማውያን አይሁድን ይገዙ ነገር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከጠላቶቻችን ከሮማውያን እስራኤልን ነጻ የሚያደርግ››

አዎን፣ ከዚያም በላይ
ይህ ለምን እስራኤልን ነጻ ያደርጋል ብለው እንደማያምኑ ተጨማሪ ምክንያት ያቀርባል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያ የሚቻል አይመስልም ምክንያቱም››

Luke 24:22

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ሁለቱ ሰዎች ለኢየሱስ መናገር አብቅተዋል።

ደግሞም እንዲሁ
ይህ ኢየሱስን በተመለከተ የሆኑ ነገሮችን ሰዎቹ መረዳት ላለመቻላቸው ሌላ ምክንያት ያቀርባል።

ከእኛ መካከል
‹‹የእኛ ወገን የሆኑ››

በመቃብሩ የነበሩ
በመቃብሩ የነበሩት ሴቶች ናቸው

የመላእክት ራእይ
‹‹በራእይ መላእክት››

Luke 24:25

ኢየሱስ እንዲህ አላቸው
ኢየሱስ ለሁለቱ ደቀ መዛሙርት እየተናገረ ነው።

ለማመን ልባችሁ የዘገዬ
‹‹ልብ›› የሰውን አእምሮ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አእምሮአችሁ ለማመን የዘገዬ›› ወይም፣ ‹‹ለማመን የዘገያችሁ››

አይገባውምን... ክብር?
x

Luke 24:28

ኢየሱስ አልፎ የሚሄድ መሰለ
ከሁኔታው ሁለቱ ሰዎች ኢየሱስ ወደ ሌላ ቦታ የሚሄድ መስሏቸው ነበር። ምናልባትም እነርሱ ወደ መንደር ለመግባት ሲታጠፉ ኢየሱስ መንገዱን ቀጥሎ ይሆናል። ኢየሱስ በንግግሩ እንዳሳሳታቸው የሚያመለክት ፍንጭ የለም።

ግድ አሉት
ግድ ያሉት ለምን እንደሆነ መግለጽ ያስፈልግ ይሆናል። ምናልባትም ይህ ሐሳቡን ከመለወጡ በፊት ከእርሱ ጋር ረጅም ጊዜ መነጋገር መፈለጋቸውን የሚያመለክት ግነት ይሆናል። ‹‹ግድ አሉት›› ጉልበትንም የሚጨምር ቢሆንም፣ በቃላቸው ብቻ አጥብቀው ለመኑት ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእነርሱ ጋር እንዲያድር አጥብቀው ለመኑት››

ቀኑ እየመሸ፤ ምሽቱ እየተቃረበ ነው
የአይሁድ ቀን የሚያበቃው ፀሐይ ስትጠልቅ ነው

ኢየሱስ ገባ
‹‹ኢየሱስ ወደ ቤት ገባ››

ከእነርሱ ጋር አደረ
‹‹ከሁለቱ ደቀ መዛሙርት ጋር አደረ››

Luke 24:30

እንዲህ ሆነ
ይህ ሐረግ እዚህ ጥቅም ላይ የዋለው ታሪኩ ውስጥ አስፈላጊ ሁኔታ መጀመሩን ለማመልከት ነው። ቋንቋህ ይህን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ ተጠቀምበት።

እንጀራው
ይህ እርሾ የገባበት እንጀራ ነው። በአጠቃላይ ምግብን የሚያመለክት አይደለም።

ባረከው
‹‹ስለ እርሱ አመሰገነ›› ወይም፣ ‹‹ስለ እርሱ እግዚአብሔርን አመሰገነ።

ዐይናቸው ተከፈተ
‹‹ዐይናቸው›› ማስተዋላቸውን ይወክላል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከዚያም አስተዋሉ›› ወይም፣ ‹‹ከዚያም ተረዱ››

ዐወቁት
‹‹ለይተው ዐወቁት›› እነዚህ ደቀ መዛሙርት ከሞቱም በፊት ያወቁት ነበር።

ከዐይናቸው ተሰወረ
ይህም ማለት በድንገት ከዚያ ጠፋ ማለት ነው። የማይታይ ሆነ ማለት አይደለም።

ልባችን ይቃጠልብን አልነበረምን... ቅዱሳት መጻሕፍት?
በጥያቄ የተጠቀሙት ከኢየሱስ ጋር በተገኙ ጊዜ ምን ያህል ተገርመው እንደ ነበር አጽንዖት ለመስጠት ነው። ከኢየሱስ ጋር ይነጋገሩ በነበረ ጊዜ የተሰማቸውን ሲገልጡ ውስጣቸው እሳት ይቀጣጠል እንደ ነበር ተናግረዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ልባችን ይቃጠል ነበር... ቅዱሳት መጻሕፍት››

በውስጣችን
ሁለቱ ሰዎች እርስ በርስ ይነጋገሩ ነበር። ‹‹እኛ›› የሚለው ቃል ሁለትን ያመለክታል፤ ይህን ልዩነት የሚቀበሉ ቋንቋዎችን ያካትታል።

ቅዱሳት መጻሕፍትን ሲከፍትልን
ኢየሱስ መጽሐፍ ወይም ጥቅልል ጽሑፍ አልከፈተም። ‹‹ከፈተ›› የሚለው የሚያመለክተው የእነርሱን መረዳት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቅዱሳት መጻሕፍትን ሲገልጥልን›› ወይም፣ ‹‹ቅዱሳት መጻሕፍትን ለማስተዋል ሲያስችለን››

Luke 24:33

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ሁለቱ ሰዎች ስለ ኢየሱስ ለመናገር ኢየሩሳሌም ወደ ነበሩት ዐሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ሄዱ።

ተነሡ
‹‹እነርሱ›› የሚለው ሁለቱን ሰዎች ያመለክታል።

ተነሡ
‹‹ብድግ አሉ›› ወይም፣ ቆሙ››

ዐሥራ አንዱ ... ከእነርሱ ጋር የነበሩት አሉ
‹‹ዐሥራ አንዱ... ከእነርሱ ጋር የነበሩት ሁለቱን ሰዎች አሉአቸው››

ዐሥራ አንዱ
ይህ የኢየሱስን ሐዋርያት ያመለክታል። ይሁዳ ከእንግዲህ ከእነርሱ ጋር አልተቆጠረም

ስለዚህ ተናገሩ
‹‹ስለዚህ ሁለቱ ሰዎች ነገሩአቸው››

መንገድ ላይ የሆነውን
ይህ የሚያመለክተው ወደ ኤማሁስ እየሄዱ በነበረ ጊዜ ኢየሱስ ሲገለጥላቸው የሆነውን ነው።

ኢየሱስ እንዴት እንደ ታያቸው
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኢየሱስን እንዴት እንዳወቁት››

እንጀራው ሲቆርስ
‹‹ኢየሱስ እንጀራውን ሲቆርስ›› ወይም፣ ‹‹ኢየሱስ እንጀራውን ሲባርክ››

Luke 24:36

አጠቃላይ መረጃ
ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ታየ። ቀደም ሲል ሁለቱ ሰዎች ሥራ አንዱ ወደ ነበሩበት ቤት ሲደርሱ ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር አልነበረም።

ኢየሱስ ራሱ
‹‹ራሱ›› የሚለው ቃል ኢየሱስና ኢየሱስ በተገለጠ ጊዜ የነበረው መገረም ላይ ያተኩራል። ብዙዎቻቸው ከትንሣኤው በኋላ አላዩትም ነበር።

በመካከላቸው
‹‹በእነርሱ መካከል››

ሰላም ለእናንተ ይሁን
‹‹ሰላም ይሁንላችሁ›› ወይም፣ ‹‹እግዚአብሔር ሰላም ይስጣችሁ›› ‹‹እናንተ›› የሚለው ብዙ ቁጥር ነው።

እነርሱ ግን ደነገጡ
‹‹ግን›› ጠንካራ ንጽጽር ያመለክታል። ኢየሱስ በሰላም እንዲሆኑ ነግሮአቸው ነበር፤ እነርሱ ግን በጣም ፈርተዋል።

ደንግጠው በፍርሃት ተዋጡ
‹‹ተሸበሩ፤ ፈሩ›› ሁለቱ ሐረጐች ተመሳሳይ ቢሆኑም በአንድነት የቀረቡት ምን ያህል እንደ ፈሩ አጽንዖት ለመስጠት ነው።

መንፈስ ያዩ መሰላቸው
‹‹መንፈስ እንዳዩ አሰቡ›› ኢየሱስ በእርግጥ ሕያው መሆኑን ገና አልተረዱም።

መንፈስ
እዚህ ላይ የሚያመለክተው የሞተ ሰው መንፈስን ነው።

Luke 24:38

ለምን ትጨነቃላችሁ?
ኢየሱስ በጥያቄ የተጠቀመው ሊያጽናናቸው ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አትፍሩ››

ለምንስ በልባችሁ ጥያቄዎች ይነሣሉ?
ኢየሱስ በጥያቄ የተጠቀመው በመጠኑ ሊገሥጻቸው ነው። እርሱ ሕያው መሆኑን እንዳይጠራጠሩ ኢየሱስ ነገራቸው። ‹‹ልብ›› የሰውን አእምሮ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በአእምሮአችሁ አትጠራጠሩ›› ወይም፣ ‹‹መጠራጠራችሁን አቁሙ››

ዳሰሱኝና እዩ... እንዳለኝ እዩ
እርሱን በመዳሰስ መንፈስ እንዳይደለ እንዲያረጋግጡ ኢየሱስ ጠየቃቸው። እነዚህን ሁለት ዐረፍተ ነገሮች ማጣመርና ቅደም ተከተላቸውን መለወጥ ይጠቅም ይሆናል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዳሰሱኝና ሥጋና አጥንት እንዳለኝ እዩ፣ መንፈስ ግን ያ የለውም››

ሥጋና አጥንት
ይህ አካልን ለማመልከት የተለመደ መንገድ ነው።

እጆቹንና እግሮቹን
እጆቹና እግሮቹ በተሰቀለ ጊዜ የሚስማር ምልክት ስለሚኖራቸው በእርግጥ ኢየሱስ መሆኑን ያረጋግጣሉ። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በእጆቹና በእግሮቹ ላይ የነበሩ ቁስሎች››

Luke 24:41

ከደስታ የተነሣ ገና አላመኑም ነበር
‹‹በጣም ደስ ብሎአቸው ስለ ነበር በእርግጥ እውነት መሆኑን ገና አላመኑም ነበር››

በፊታቸው በላ
ኢየሱስ ይህን ያደረገው አካል እንዳለው ለማሳየት ነበር። መንፈሶች ምግብ አይበሉም።

በፊታቸው
‹‹በእነርሱ ፊት›› ወይም፣ ‹‹እነርሱ እያዩ››

Luke 24:44

ከእናንተ ጋር በነበርሁ ጊዜ
‹‹በፊት ከእናንተ ጋር እያለሁ››

የተጻፈው ሁሉ... መዝሙሮች መፈጸም አለበት
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እግዚአብሔር የተጻፈውን ሁሉ ይፈጽመዋል... መዝሙሮች›› ወይም፣ ‹‹እግዚአብሔር የተጻፈውን ሁሉ ያደርገዋል... መዝሙሮች እንዲፈጸሙ››

በሙሴ ሕግ በነቢያትና በመዝሙር መጻሕፍት የተጻፈው ሁሉ
‹‹በሙሴ ሕግ›› ‹‹በነቢያት›› እና፣ ‹‹በመዝሙር መጻሕፍት›› የዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የተለመዱ ስሞች ናቸው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽና የተለመዱ መጠሪያዎች መጠቀም ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሙሴ በሕግ የጻፈው ሁሉ፣ ነቢያት የጻፉት ሁሉ፣ በመዝሙር መጻሕፍት ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ››

Luke 24:45

ከዚያም ቅዱሳት መጻሕፍትን መረዳት እንዲችሉ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው።
‹‹አእምሮአቸውን ከፈተላቸው›› ቅዱሳት መጻሕፍትን መረዳት አስቻላቸው ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከዚያም ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዲረዱ አስቻላቸው››

እንዲህ ተጽፎአል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ይህ ከብዙ ጊዜ በፊት ሰዎች የጻፉት ነው››

እንደ ገና ከሙታን እንደሚነሣ
በዚህ ቁጥር፣ ‹‹መነሣት›› እንደ ገና ሕያው መሆን ማለት ነው። ‹‹ከሙታን›› የሚለው ከምድር በታች ያሉ የሞቱ ሰዎችን ሁሉ ያመለክታል።

በሦስተኛው ቀን
አይሁድ ማንኛውንም የቀን ክፍል እንደ ቀን ይቆጥራሉ። ስለዚህም የተቀበረበትንና የሰንበትን ቀን ቀድሞ በመምጣቱ ኢየሱስ የሞተበት ቀን፣ ‹‹ሦስተኛ ቀን›› ተብሏል። ሉቃስ 24፥7 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

በስሙ ለሕዝቦች ሁሉ ንስሐና የኀጢአት ይቅርታ መሰበክ አለበት
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የክርስቶስ ተከታዮች ንስሐ መግባትና ለኃጢአታቸው በኢየሱስ ስም የእግዚአብሔር ይቅርታ እንደሚያስፈልጋቸው በየአገሩ ላሉ ሕዝብ ሁሉ መስበክ አለባቸው››

በስሙ
‹‹ስሙ›› የእርሱን ሥልጣን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በክርስቶስ ሥልጣን››

ለሕዝቦች ሁሉ
‹‹ለየአገሩ ሁሉ›› ወይም፣ ‹‹ለሰው ዘር ሁሉ››

ከኢየሩሳሌም ጀምሮ
‹‹ከኢየሩሳሌም አንሥቶ››

Luke 24:48

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ኢየሱስ ለደቀመዛሙርት መናገር ቀጥሏል።

እናንተ ምስክሮች ናችሁ
‹‹ስለ እኔ ያያችሁት እውነት መሆኑን ለሌሎች መናገር አለባችሁ›› ደቀመዛሙርት የኢየሱስን ሕይወት፣ ሞትና ትንሣኤ ተመልክተዋል፤ ስለዚህ እርሱ ያደረገውን ለሌሎች መናገር ይችላሉ።

አባቴ ቃል የገባውን እልክላችኋለሁ
‹‹አባቴ እሰጣችኋለሁ ያለውን እሰጣችኋለሁ›› እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን እንደሚሰጥ ቃል ገብቷል። ዩዲቢ ይህን የበለጠ ግልጽ ያደርገዋል።

አባት
ይህ አስፈላጊ የእግዚአብሔር መጠሪያ ነው።

ከላይ ኀይል ለብሳችኋል
ሰው ልብስ እንደሚለብስ የእግዚአብሔር ኀይል ይሸፍናቸዋል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ኀይል ትቀበላላችሁ››

ከላይ
‹‹ከሰማይ›› ወይም፣ ‹‹ከእግዚአብሔር››

Luke 24:50

ኢየሱስ ወሰዳቸው
‹‹ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ከከተማ ውጪ ወሰዳቸው››

እጁን አነሣ
ይህ ካህናት ሕዝብን ሲባርኩ የሚያደርጉ ነው።

እንዲህ ሆነ
‹‹እንዲህ ተደረገ›› ይህ ታሪኩ ውስጥ አዲስ ሁኔታ ያስተዋውቃል።

እየባረካቸው ሳለ
‹‹እግዚአብሔር ለእነርሱ መልካም እንዲያደርግ እየጠየቀ ሳለ››

ተሸከመ
x

Luke 24:52

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ቁጥሮች ታሪኩ ፍጻሜ ላይ ደቀ መዛሙርቱ ያደረጉትን ቀጣይ ድርጊት ይነግሩናል።

ሰገዱለት
‹‹ደቀ መዛሙርቱ ለኢየሱስ ሰገዱ››

ተመለሱ
‹‹ከዚያም ተመለሱ››

ዘወትር በቤተ መቅደስ ነበሩ
ይህ ሁልጊዜ ወደ ቤተ መቅደሱ ግቢ ይሄዱ እንደ ነበር ለመግለጽ ግነት ነው።

ቤተ መቅደስ ውስጥ
ወደ ቤተ ቅደስ መግባት የሚፈቀድላቸው ካህናት ብቻ ነበሩ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ቤተ መቅደሱ ግቢ ውስጥ››

እግዚአብሔርን ባረኩ
‹‹እግዚአብሔርን አመሰገኑ››

Book: John

John

ምዕራፍ 1

1 በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ቃልም ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ፤ 2 ይህም ቃል ከመጀመሪያው ከእግዚአብሔር ጋር ነበር። 3 ሁሉም ነገር
የተሠራው በእርሱ አማካይነት ነው፤ ከተሠሩት ነገሮች ሁሉ ያለ እርሱ የተሠራ አንድም ነገር አልነበረም። 4 በእርሱ ሕይወት ነበረ፤ያም ሕይወት የሰው ሁሉ
ብርሃን ነበር። 5 ብርሃኑ በጨለማ ይበራል፤ ጨለማም ሊያጠፋው አልቻለም። 6 ከእግዚአብሔር የተላከ ስሙ ዮሐንስ የሚባል አንድ ሰው ነበር። 7 ሁሉም
በእርሱ እንዲያምኑ እርሱ ስለ ብርሃን ሊመሰክር መጣ። 8 ስለ ብርሃን ሊመሰክር መጣ እንጂ ዮሐንስ ራሱ ብርሃን አልነበረም። 9 ወደ ዓለም የሚመጣውና
ለሰው ሁሉ ብርሃን ሰጭ የሆነው እውነተኛ ብርሃን እየመጣ ነበር። 10 እርሱ በዓለም ውስጥ ነበር፤ ዓለሙም የተሠራው በእርሱ ነው፤ ዓለም ግን አላወቀውም፤
11 የራሱ ወደ ሆኑት መጣ፤ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም። 12 ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች የመሆንን መብት
ሰጣቸው። 13 እነርሱም ከደምና ከሥጋ ወይም ከሰው ፈቃድ አልተወለዱም፤ ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ። 14 ቃል ሥጋ ሆነ፤ በመካከላችንም ዐደረ፤ እኛም
ጸጋና እውነት የተሞላውን ከአብ ዘንድ ያለውን የአንድያ ልጁን ክብር አየን። 15 ዮሐንስ ስለ እርሱ መሰከረ፤ ድምፁንም ከፍ አድርጎ፣ «ከእኔ በኋላ የሚመጣው
እርሱ ከእኔ ይበልጣል፤ 'ከእኔ በፊት ነበርና' ያልኋችሁ ይህ ነው» ይል ነበር። 16 ከእርሱ ሙላት ሁላችንም በጸጋ ላይ ጸጋ ተቀበልን፤ 17 ሕግ በሙሴ በኩል
ተሰጥቶ ነበር፤ ጸጋና እውነት ግን በኢየሱስ በኩል መጣ። 18 በየትኛውም ጊዜ እግዚአብሔርን ያየው አንድም ሰው የለም፤ ነገር ግን በአባቱ ዕቅፍ ያለውና እርሱ
ራሱ እግዚአብሔር የሆነው አንድያ ልጁ እርሱ እግዚአብሔርን እንዲታወቅ አደረገው። 19 አይሁድ ከኢየሩሳሌም ካህናትንና ሌዋውያንን ልከው፣ «አንተ ማን
ነህ?» ብለው በጠየቁት ጊዜ፣ የዮሐንስ ምስክርነት ይህ ነው። 20 እርሱ በግልጽ ተናገረ አልካደምም፤ ነገር ግን፣ «እኔ ክርስቶስ አይደለሁም» ብሎ
መለሰላቸው። 21 ስለዚህ እነርሱም፣ «ታዲያ ማን ነህ? ኤልያስ ነህን?» ብለው ጠየቁት፤ እርሱ፣ «አይደለሁም» አላቸው። እነርሱ፣ «ነቢዩ ነህን?» አሉት፤
እርሱ፣ «አይደለሁም» አለ። 22 ከዚያም እነርሱ፣ «ለላኩን መልስ መስጠት እንድንችል፣ አንተ ማን ነህ? ስለ ራስህስ ምን ትላለህ?» አሉት። 23 እርሱ፣ «ልክ
ነቢዩ ኢሳይያስ እንዳለው፦ 'የጌታን መንገድ አስተካክሉ' እያለ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ እኔ ነኝ» አላቸው። 24 ከፈሪሳውያን የተላኩ ሰዎችም ነበሩ።
25 እነርሱ፣ «ክርስቶስ፣ ኤልያስ ወይም ነቢዩ ካልሆንህ፣ ታዲያ ለምን ታጠምቃለህ?» ብለው ጠየቁት። 26 ዮሐንስ፣ «እኔ በውሃ አጠምቃለሁ፤ ይሁን እንጂ
እናንተ የማታውቁት በመካከላችሁ ቆሟል፤ 27 ከእኔ በኋላ የሚመጣው እርሱ ነው፤ እኔ የጫማውን ማሰሪያ ለመፍታት እንኳ የማልበቃ ነኝ» በማለት
መለሰላቸው፤ 28 ይህ ሁሉ የሆነው ዮሐንስ ሲያጠምቅ በነበረበት በዮርዳኖስ ማዶ በምትገኘው በቢታንያ ነበር። 29 በማግስቱ ዮሐንስ ኢየሱስ ወደ እርሱ
ሲመጣ ተመልክቶ እንዲህ አለ፤ «እነሆ፣ የዓለምን ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ይኸውና! 30 'ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ በፊት ስለ ነበረ
ከእኔ ይበልጣል' ብዬ ስለ እርሱ የነገርኋችሁ እርሱ ነው። 31 እኔ አላወቅሁትም ነበር፤ ነገር ግን እርሱ ለእስራኤል ይገለጥ ዘንድ እኔ በውሃ እያጠመቅሁ
መጣሁ።» 32 ዮሐንስ እንዲህ ሲል መሰከረ፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ከሰማይ እንደ ርግብ ሲወርድና በእርሱ ላይ ሲያርፍ አየሁ። 33 እኔ አላወቅሁትም ነበር፤
ነገር ግን በውሃ እንዳጠምቅ የላከኝ እርሱ፣ 'መንፈስ ሲወርድበትና ሲያርፍበት የምታየው፣ በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቀው እርሱ ነው' አለኝ። 34 እኔ ይህን
አይቻለሁ፤ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነም መስክሬአለሁ።» 35 ደግሞም በማግስቱ፣ ዮሐንስ ከሁለት ደቀ መዛሙርቱ ጋር ቆሞ ሳለ፣ 36 ኢየሱስን
በአጠገባቸው ሲያልፍ አዩት፤ ዮሐንስም፣ «እነሆ፣ የእግዚአብሔር በግ» አለ። 37 ሁለቱ ደቀ መዛሙርት፣ ዮሐንስ ይህን ሲናገር ሰምተው ኢየሱስን ተከተሉት፤
38 ከዚያም ኢየሱስ መለስ ብሎ ሲከተሉት አየና፣ «ምን ትፈልጋላችሁ?» አላቸው። እነርሱ፣ «ረቢ የት ነው የምትኖረው?» አሉት። ረቢ ማለት 'መምህር' ማለት
ነው። 39 እርሱ፣ «ኑና እዩ» አላቸው። ከዚያም እነርሱ መጥተው የሚኖርበትን አዩ፤ በዚያም ቀን ዐብረውት ዋሉ፤ ሰዓቱም ዐሥረኛው ሰዓት ያህል ሆኖ ነበርና። 40
የሐንስ ሲናገር ሰምተው ኢየሱስን ከተከተሉት ከሁለቱ አንዱ የስምዖን ጴጥሮስ ወንድም እንድርያስ ነበረ። 41 እርሱ በመጀመሪያ የራሱን ወንድም ጴጥሮስን
አገኘውና፣ «መሲሑን አግኝተነዋል» አለው። መሲሕ 'ክርስቶስ ማለት ነው'። 42 ወደ ኢየሱስም አመጣው። ኢየሱስ ጴጥሮስን ተመለከተውና፣ «አንተ የዮና ልጅ
ስምዖን ነህ፤ ኬፋ ትባላለህ» አለው። ኬፋ 'ጴጥሮስ ማለት ነው'። 43 በማግስቱ፣ ኢየሱስ ወደ ገሊላ ሊሄድ በፈለገ ጊዜ፣ ፊልጶስን አግኝቶ፣ «ተከተለኝ»
አለው። 44 ፊልጶስም ጴጥሮስና እንድርያስ ከሚኖሩበት ከተማ ከቤተ ሳይዳ ነበር። 45 ፊልጶስ ናትናኤልን አገኘውና፣ «ሙሴ በሕግ፣ ነቢያትም በትንቢት
የጻፉለትን የዮሴፍን ልጅ የናዝሬቱን ኢየሱስ አግኝተነዋል» አለው። 46 ናትናኤል፣ «ከናዝሬት መልካም ነገር ይወጣልን?» አለው። ፊልጶስም መጥተህ እይ
አለው። 47 ኢየሱስ፣ ናትናኤል ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ ስለ እርሱ፣ «እነሆ፣ ተንኰል የሌለበት እውነተኛ እስራኤላዊ!» አለ። 48 ናትናኤል፣ «እንዴት
ታውቀኛለህ?» አለው።ኢየሱስም፣ «ገና ፊልጶስ ሳይጠራህ ከበለስ ዛፍ ሥር ሳለህ አየሁህ» ብሎ መለሰለት። 49 ናትናኤል፣ «አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ፤
አንተ የእስራኤል ንጉሥ ነህ!» ብሎ መለሰለት። 50 ኢየሱስ፣ «ከበለስ ዛፍ ሥር ሳለህ አየሁህ ስላልሁህ አመንህን? ገና ከዚህ የሚበልጡ ነገሮችን ታያለህ»
ብሎ መለሰለት። 51 ኢየሱስ፣ «እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ሰማያት ሲከፈቱ መላእክትም በሰው ልጅ ላይ ሲወጡና ሲወርዱ ታያላችሁ» አለ።

John 1:1

በመጀመሪያ
ይህ እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን ከመፈጠሩ በፊት የነበረውን በጣም የመጀመሪያ ጊዜን ያመለክታል።

ቃል
ይህ ኢየሱስን ያመለክታል ። ከተቻለ እንደ “ቃሉ” ይተርጉሙ። በቃሉዎ ውስጥ “ቃል” አንስታይ ከሆነ ፣ “ቃል ተብሎ የተጠራው” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል ።

ሁሉ በእርሱ ሆነ
ይህ ከነቃ ግስ ጋር ሊተረጎም ይችላል። አት: - “እግዚአብሔር ሁሉንም ነገሮች በእርሱ አድርጎ ሠራው” (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር / ገባሪ ወይም አንቀፅ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ያለ እርሱ አንድም ነገር አልተፈጠረም ከተፈጠረው
ይህ ከነቃ ግስ ጋር ሊተረጎም ይችላል። አት: - “እግዚአብሔር ያለ እሱ ምንም ነገር አልሠራም” ወይም “እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ከሱ ጋር አደረገ” (ይመልከቱ።

John 1:4

በእርሱ ሕይወት ነበረች
1 ኢየሱስ ወደ ደብረ ዘይት ሄደ። 2 ጠዋት በማለዳ ተመልሶ ወደ ቤተ መቅደስ መጣ፤ ሕዝቡም ሁሉ ወደ እርሱ መጡ፤ እርሱም ተቀምጦ አስተማራቸው። 3 የሕግ መምህራንና ፈሪሳውያንም ስታመነዝር የተያዘችን ሴት አምጥተው፤ በመካከላቸው አቆሟት። 4 ከዚያም ኢየሱስን እንዲህ አሉት፤ «መምህር ሆይ፣ ይህች ሴት ስታመነዝር እጅ ከፍንጅ የተያዘች ናት፤ 5 ሙሴ በሕጉ እንዲህ ያሉትን በድንጋይ እንድንወግር አዞናል፤ አንተስ ስለ እርሷ ምን ትላለህ?» 6 ይህን ያሉት እርሱን ወጥመድ ውስጥ ለማስገባትና ለመክሰስ ፈልገው ነው፤ ኢየሱስ ግን ጎንበስ ብሎ በጣቱ መሬት ላይ ጻፈ። 7 ጥያቄ ማቅረባቸውን በቀጠሉ ጊዜም፣ ተነሥቶ ቆመና፣ “ከእናንተ መካከል ኃጢአት የሌለበት ሰው በመጀመሪያ ይውገራት” አላቸው። 8 ዳግመኛም ጐንበስ ብሎ፣ በጣቱ መሬት ላይ ጻፈ። 9 ይህንም በሰሙ ጊዜ፣ ከታላቅ ጀምረው አንድ ባንድ ወጥተው ሄዱ። በመጨረሻ ኢየሱስ በመካከላቸው ቆማ ከነበረችው ሴት ጋር ለብቻው ቀረ። 10 ኢየሱስ ተነሥቶ በመቆም፣ “አንቺ ሴት፤ የከሰሱሽ ሰዎች የት ናቸው? አንድም የፈረደብሽ የለም?” አላት። 11 እርሷም፣ “ጌታ ሆይ፣ አንድም የለም” አለች። ኢየሱስ፣ “እኔም አልፈርድብሽም፤ ሂጂ ከአሁን በኋላ ግን ደግመሽ ኀጢአት አትሥሪ” አላት። 12 ደግሞም ኢየሱስ ሕዝቡን፣ “እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝ ቢኖር የሕይወት ብርሃን ያገኛል እንጂ፣ በጨለማ አይመላለስም” አላቸው። 13 ፈሪሳውያንም፣ “አንተው ስለ ራስህ ስለምትመሰክር፤ ምስክርነትህ እውነት አይደለም” አሉት። 14 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ “እኔ ስለ ራሴ ብመሰክር እንኳ ምስክርነቴ እውነት ነው። ከየት እንደ መጣሁ፣ ወዴትም እንደምሄድ ዐውቃለሁ፤ እናንተ ግን እኔ ከየት እንደ መጣሁ ወይም ወዴት እንደምሄድ አታውቁም። 15 እናንተ በሥጋዊ ዐይን ትፈርዳላችሁ፤ እኔ በማንም አልፈርድም። 16 ብፈርድም እንኳ፣ ብቻዬን አይደለሁም፤ ከላከኝ አብ ጋር ስለ ሆንሁ፣ ፍርዴ እውነት ነው። 17 አዎን፤ በሕጋችሁ የሁለት ሰዎች ምስክርነት እውነት እንደ ሆነ ተጽፎአል። 18 እኔ ስለ ራሴ እመሰክራለሁ፤ የላከኝም አብ ስለ እኔ ይመሰክራል።” 19 እነርሱም፣ “አባትህ የት ነው ያለው?” አሉት። ኢየሱስም፣ “እናንተ እኔንም ሆነ አባቴን አታውቁንም፤ እኔን ብታውቁኝ ኖሮ አባቴንም ባወቃችሁት ነበር” አላቸው። 20 ይህንም የተናገረው በቤተ መቅደሱ ግምጃ ቤት አጠገብ ሆኖ ሲያስተምር ነበር፤ ሆኖም ሰዓቱ ገና ስላልደረሰ፣ ማንም አልያዘውም። 21 ደግሞም፣ “እኔ ተለይቻችሁ እሄዳለሁ፤ እናንተም ትፈልጉኛላችሁ፤ ግን በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ። እኔ ወደምሄድበት መምጣት አትችሉም” አላቸው። 22 አይሁድም፣ “ይህ 'እኔ ወደምሄድበት መምጣት አትችሉም' የሚለው ራሱን ሊገድል ዐስቦ ይሆን?” አሉ። 23 ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፤ “እናንተ ከታች ናችሁ፤ እኔ ግን ከላይ ነኝ። እናንተ ከዚህ ዓለም ናችሁ፤ እኔ ግን ከዚህ ዓለም አይደለሁም። 24 በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ ያልኋችሁ ለዚህ ነው። ምክንያቱም እኔ ነኝ ስላችሁ ካላመናችሁ፣ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ።” 25 እነርሱም፣ “ለመሆኑ፣ አንተ ማን ነህ?” አሉት። ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤”ከመጀመሪያው እንደ ነገርኋችሁ ነኝ። 26 ብዙ የምናገረውና ስለ እናንተም የምፈርደው አለኝ። ይሁን እንጂ የላከኝ እርሱ እውነተኛ ነው፤ እኔም ከእርሱ የሰማሁትን፣ ያንኑ ለዓለም እናገራለሁ።” 27 እነርሱ ግን ስለ አብ እየነገራቸው እንደ ነበር አልተረዱም። 28 ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ “የሰውን ልጅ ወደ ላይ ከፍ ስታደርጉት፣ በዚያን ጊዜ እኔው እንደ ሆንሁና ከራሴ አንድም ነገር እንደማላደርግ ታውቃላችሁ። አብ እንዳስተማረኝ ይህን እናገራለሁ። 29 የላከኝ እርሱ ከእኔ ጋር ነው፤ ብቻዬንም አልተወኝም፤ እኔ ሁልጊዜ እርሱን ደስ የሚያሰኘውን ነገር አደርጋለሁና።” 30 ኢየሱስ እነዚህን ነገሮች በተናገረ ጊዜ ብዙ ሰዎች በእርሱ አመኑ። 31 ኢየሱስ በእርሱ ያመኑትን አይሁድ፣ “እናንተ በቃሌ ብትኖሩ፣ በርግጥ ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ፤ 32 እውነትን ታውቃላችሁ፤ እውነትም ነጻ ያወጣችኋል” አላቸው። 33 እነርሱም፣ “እኛ የአብርሃም ዘሮች ነን፤ የማንም ባሪያ ሆነን አናውቅም፤ ታዲያ እንዴት ‘ነጻ ትወጣላችሁ’ ትለናለህ?” አሉት። 34 ኢየሱስ እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ “እውነት እላችኋለሁ፤ ኃጢአት የሚሠራ ሁሉ የኃጢአት ባሪያ ነው። 35 ባሪያ ለዘለቄታ በቤት አይኖርም፤ ልጅ ግን ለዘለቄታ ይኖራል። 36 ስለዚህ ልጁ ነጻ ካወጣችሁ፣ በርግጥ ነጻ ትወጣላችሁ። 37 የአብርሃም ዘር መሆናችሁን ዐውቃለሁ፤ ቃሌን ስላልተቀበላችሁ፣ ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ። 38 አባቴ ጋ ያየሁትን እናገራለሁ፤ እናንተም ደግሞ ከአባታችሁ የሰማችሁትን ታደርጋላችሁ።” 39 እነርሱም መልሰው፣ “አባታችንስ አብርሃም ነው” አሉት። ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፤ “የአብርሃም ልጆችስ ብትሆኑ ኖሮ፣ የአብርሃምን ሥራ በሠራችሁ ነበር። 40 አሁን ግን ከእግዚአብሔር የሰማሁትን እውነት የነገርኋችሁን ሰው ለመግደል ትፈልጋላችሁ። አብርሃምኮ ይህን አላደረገም። 41 እናንተ ግን የአባታችሁን ሥራ ትሠራላችሁ።” እነርሱም፣ “እኛ በዝሙት የተወለድን አይደለንም፤ አንድ አባት እግዚአብሔር አለን” አሉት። 42 ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ “እግዚአብሔር አባታችሁ ቢሆን ኖሮ፣ እኔ ከእግዚአብሔር ወጥቼ ስለ መጣሁ፣ በወደዳችሁኝ ነበር፤ በራሴም ፈቃድ አልመጣሁም፤ ነገር ግን እርሱ ላከኝ። 43 ቃሌን የማትረዱት ለምንድን ነው? ምክንያቱም ቃሌን መስማት ስለማትችሉ ነው። 44 እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ፤ የአባታችሁንም ፍላጎት ለማድረግ ትመኛላችሁ። እርሱ ከመጀመሪያውም ነፍሰ ገዳይ ነበር፤ እውነት በእርሱ ዘንድ ስለሌለም፣ በእውነት አይጸናም። ሐሰትንም ሲናገር ከራሱ አፍልቆ ይናገራል፤ ምክንያቱም እርሱ ሐሰተኛ፣ የሐሰትም አባት ነው። 45 እኔ ግን እውነትን ስለምናገር አታምኑኝም። 46 ከእናንተ ስለ ኃጢአት የሚወቅሰኝ ሰው ማን ነው? እውነትን የምናገር ከሆነስ፣ ታዲያ ለምን አታምኑኝም? 47 ከእግዚአብሔር ስላልሆናችሁ፣ ቃሉን አትሰሙም።” 48 አይሁድም፣ “እንግዲህ ጋኔን ያደረብህ ሳምራዊ ነህ በማለታችን እውነት አልተናገርንምን?” በማለት መለሱለት። 49 ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰላቸው፤ “እኔ ጋኔን የለብኝም፤ እኔ አባቴን አከብረዋለሁ እንጂ፣ እናንተ ግን ታዋርዱኛላችሁ። 50 እኔ የራሴን ክብር አልሻም፤ የሚሻና የሚፈርድ አንድ አለ። 51 እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፤ ቃሌን የሚጠብቅ ማንም ቢኖር፣ እርሱ ሞትን በፍጹም አያይም።” 52 አይሁድም፣ “አሁን ጋኔን እንዳለብህ ዐወቅን። አብርሃምም ነቢያትም ሞተዋል፤ አንተ ግን 'ማንም ቃሌን ቢጠብቅ ሞትን አይቀምስም' ትላለህ። 53 አንተ ከሞተው ከአባታችን፣ ከአብርሃም ትበልጣለህን? ነቢያትም ሞተዋል። ለመሆኑ፣ አንተ ማን ነኝ ልትል ነው?” አሉት። 54 ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ “እኔ ራሴን ባከብር፣ ክብሬ ከንቱ ነው፤ እኔን የሚያከብረኝ እናንተ አምላካችን ነው የምትሉት አባቴ ነው። 55 እናንተ እርሱን አላወቃችሁትም፤ እኔ ግን ዐውቀዋለሁ። እኔ ‘አላውቀውም’ ብል እንደ እናንተው ሐሰተኛ እሆናለሁ። ነገር ግን እኔ ዐውቀዋለሁ፤ ቃሉንም እጠብቃለሁ። 56 አባታችሁ አብርሃም ቀኔን በማየቱ ደስ አለው፤ አይቶም ሐሤት አደረገ።” 57 አይሁድም፣ “ገና ዐምሳ ዓመት ያልሞላህ፣ አንተ አብርሃምን አይተሃልን?” አሉት። 58 ኢየሱስም፣ “እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ አብርሃም ከመወለዱ በፊት እኔ አለሁ” አላቸው። 59 እነርሱም፣ ሊወግሩት ድንጋይ አነሡ፤ ኢየሱስ ግን ራሱን ሰውሮ ከቤተ መቅደስ ወጥቶ ሄደ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 9

1 ኢየሱስ በመንገድ ሲያልፍ ፣ ከተወለደ ጀምሮ ዐይነ ስውር የነበረ አንድ ሰው አየ። 2 ደቀ መዛሙርቱ፣ “መምህር ሆይ፤ ይህ ሰው ዐይነ ስውር ሆኖ እንዲወለድ
ያደረገው የራሱ ኀጢአት ነው ወይስ የወላጆቹ?” አሉት። 3 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ “የእግዚአብሔር ሥራ በእርሱ እንዲገለጥ ነው እንጂ፣ እርሱ
ወይም ወላጆቹ ኀጢአት አልሠሩም። 4 የላከኝን ሥራ ቀን ሳለ መሥራት ይገባናል። ማንም ሊሠራ የማይችልበት ሌሊት እየመጣ ነው። 5 በዓለም እስካለሁ፣
የዓለም ብርሃን እኔ ነኝ።” 6 ኢየሱስ ይህን ካለ በኋላ፣ መሬት ላይ እንትፍ ብሎ፣ በምራቁ ጭቃ ሠራ፤ በጭቃውም የሰውየውን ዐይን ቀባ። 7 ሰውየውንም፣ “ሂድና
በሰሊሆም መጠመቂያ ታጠበ” አለው፣ ‘ሰሊሆም’ የተላከ ማለት ነው። ሰውየውም ወደዚያው ሄዶ ታጠበ፤ ዐይኑም እያየለት ተመልሶ መጣ። 8 የሰውየው
ጐረቤቶችና ቀድሞ ለማኝ ሆኖ ያዩት ሰዎችም፣ “ይህ ሰው ተቀምጦ ሲለምን የነበረው ሰው አይደለምን?” አሉ። 9 አንዳንዶቹ፣ “እርሱ ነው” አሉ፤ ሌሎችም፣
“ይመስለዋል እንጂ እርሱ አይደለም” አሉ። እርሱ ግን፣ “እኔው ነኝ” አለ። 10 እነርሱም፣ “ታዲያ፣ ዐይኖችህ እንዴት ተከፈቱልህ?” አሉት። 11 እርሱም እንዲህ
ብሎ መለሰላቸው፤ “ኢየሱስ የሚባለው ሰው ጭቃ ሠርቶ ዐይኔን ቀባ፤ ከዚያም፣ ‘ወደ ሰሊሆም ሄደህ ታጠብ’ አለኝ። እኔም ሄጄ ታጠብሁ፤ ዐይኖቼም በሩ።”
12 እነርሱም፣ “ታዲያ፣ እርሱ የት ነው?” አሉ። እርሱም፣ “እኔ አላውቅም” ብሎ መለሰላቸው። 13 እነርሱም ዐይነ ስውር የነበረውን ሰው ወደ ፈሪሳውያን
ወሰዱት። 14 ኢየሱስ ጭቃ ሠርቶ የሰውየውን ዐይን የከፈተው በሰንበት ቀን ነበረ። 15 ፈሪሳውያንም ዐይኑ እንዴት እንደ ተከፈተለት እንደ ገና ሰውየውን
ጠየቁት። እርሱም፣ “ዐይኖቼን ጭቃ ቀባ፤ ታጠብሁና ማየት ቻልሁ” አላቸው። 16 ከፈሪሳውያን አንዳንዶቹ፣ “ይህ ሰው ሰንበትን ስለማያከብር፣ ከእግዚአብሔር
አይደለም” አሉ። ሌሎቹም፣ “ኀጢአተኛ የሆነ ሰው እንዴት እንደዚህ ያለ ተአምር ይሠራል?” አሉ። ስለዚህ በመካከላቸው መከፋፈል ተፈጠረ። 17 እንደ ገናም
ዐይነ ስውሩን ሰው፣ “ዐይንህን ስለ ከፈተው ሰው ምን ትላለህ?” አሉት። ዐይነ ስውሩም፣ “ነቢይ ነው” አለ። 18 ፈሪሳውያንም ዐይነ ስውር የነበረው ሰው
ዐይኖች መከፈታቸውን አሁንም ስላላመኑ፣ ዐይኑ የበራለትን ሰው ወላጆች አስጠሩ። 19 ወላጆቹንም፣ “ይህ ዐይነ ስውር ሆኖ የተወለደ ነው የምትሉት ሰው
ልጃችሁ ነውን? ከሆነስ፣ አሁን እንዴት ማየት ቻለ?” ብለው ጠየቋቸው። 20 ወላጆቹም እንዲህ ሲሉ መለሱላቸው፤ “ይህ ልጃችን መሆኑንና ዐይነ ስውር ሆኖ
መወለዱን እናውቃለን። 21 አሁን እንዴት ማየት እንደ ቻለ ግን አናውቅም፤ ዐይኑን የከፈተለት ማን እንደ ሆነም አናውቅም። እርሱን ጠይቁት፤ ጕልማሳ ነው፤ ስለ
ራሱ መናገር ይችላል።” 22 ወላጆቹ እንዲህ ያሉት አይሁድን ስለ ፈሩ ነበር። ምክንያቱም አይሁድ፣ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ ነው የሚል ሰው ካገኙ፣ ከምኵራብ
ሊያስወግዱት ቀደም ብለው ተስማምተው ነበር። 23 ወላጆቹ፣ “እርሱ ጕልማሳ ነው፤ ራሱን ጠይቁት” ያሉትም በዚህ ምክንያት ነበር። 24 ዐይነ ስውር
የነበረውን ሰው እንደ ገና አስጠርተው፣ “ለእግዚአብሔር ክብር ስጥ፤ እኛ ይህ ሰው ኀጢአተኛ እንደ ሆነ እናውቃለን” አሉት። 25 ሰውየውም፣ “እኔ እርሱ
ኀጢአተኛ መሆኑን አላውቅም። ነገር ግን አንድ ነገር ዐውቃለሁ፤ ዐይነ ስውር ነበርሁ፤ አሁን ግን እያየሁ ነው” አላቸው። 26 እነርሱም፣ “ያደረገልህ ምንድን ነው?
ዐይኖችህንስ የከፈተው እንዴት ነው?” አሉት። 27 እርሱም፣ “አስቀድሜ ነግሬአችሁ ነበር! እናንተ ግን አትሰሙም። እንደ ገና መስማትስ ለምን ፈለጋችሁ?
እናንተም የእርሱ ደቀ መዛሙርት ለመሆን ትፈልጋላችሁን?” ብሎ መለሰ። 28 ሰደቡትና እንዲህ አሉ፤ “አንተ የእርሱ ደቀ መዝሙር ነህ፣ እኛ ግን የሙሴ ደቀ
መዛሙርት ነን። 29 እግዚአብሔር ሙሴን እንደ ተናገረው እናውቃለን፤ ይህ ሰው ግን ከየት እንደ መጣ አናውቅም።” 30 ሰውየውም፣ “ይህ ሰው ከየት እንደ
መጣ አለማወቃችሁ የሚገርም ነው፤ ይሁን እንጂ፣ ዐይኔን የከፈተው እርሱ ነው። 31 እግዚአብሔር ኀጢአተኞችን እንደማይሰማ እናውቃለን፤ ነገር ግን
እግዚአብሔርን የሚያመልክና ፈቃዱን የሚያደርግ ሰው ሁሉ እግዚአብሔር ይሰማዋል። 32 ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ፣ ዐይነ ስውር ሆኖ የተወለደን ሰው ዐይን
የከፈተ ሰው ከቶ አልተሰማም። 33 ይህ ሰው ከእግዚአብሔር ባይሆን ኖሮ፣ አንድም ነገር ማድረግ ባልቻለ ነበር።” 34 እነርሱም፣ መልሰው “አንተ ሁለንተናህ
በኀጢአት የተወለደ፣ አሁን አንተ እኛን ታስተምረናለህን?” አሉት። ከዚያም ከምኵራብ አስወጡት። 35 ኢየሱስም ሰውየውን ከምኵራብ እንዳስወጡት ሰማ።
ሰውየውንም አግኝቶ፣ “በሰው ልጅ ታምናለህን?” አለው። 36 እርሱም፣ “ጌታ ሆይ፣ አምንበት ዘንድ እርሱ ማን ነው?” አለው። 37 ኢየሱስም፣ “አይተኸዋል፤
አሁን እንኳ ከአንተ ጋር እየተነጋገረ ያለው እርሱ ነው” አለው። 38 ሰውየውም፣ “ጌታ ሆይ፣ አምናለሁ” አለ። ከዚያም ሰገደለት። 39 ኢየሱስም፣ “የማያዩ
እንዲያዩ፣ የሚያዩም እንዳያዩ፣ ለፍርድ ወደዚህ ዓለም መጣሁ” አለ። 40 ከእነርሱም ጋር ከነበሩት አንዳንድ ፈሪሳውያን ይህን ሰምተው፣ “እኛም ደግሞ ዐይነ
ስውራን ነን ወይ?” አሉት። 41 ኢየሱስም ፣ “ዐይነ ስውራን ብትሆኑማ፣ ኀጢአት ባልሆነባችሁ ነበር። ነገር ግን፣ ‘እናያለን’ ስለምትሉ፣ ኀጢአታችሁ እንዳለ
ይኖራል።”

John 9:1

አጠቃላይ መረጃ
ይህ የታሪኩ ቀጣይ ክፍል ነው ። ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ እየተጓዙ ሳሉ አንድ ዓይነ ስውር አገኘ።

ኢየሱስ ሲያልፍ
እዚህ “ኢየሱስ” ለኢየሱስ እና ለደቀመዛሙርቱ የማይነገር ምሳሌ ነው ። አት: - “ኢየሱስ እና ደቀመዛሙርቱ ሲያልፉ”

ይህ ኃጢአት የሠራው ይህ ሰው ነው ወይስ ወላጆቹ ... ዕውር?
ይህ ጥያቄ ኃጢአት ሁሉንም በሽታዎች እና ሌሎች የአካል ጉድለቶችን ያስከተለ የጥንት የአይሁድን እምነት ያንፀባርቃል ። ራቢዎች በተጨማሪም ሕፃን ገና በማህፀን ውስጥ እያለ ኃጢአት መሥራቱን አስተምረዋል ። AT: - “መምህር ፣ ኃጢአት አንድን ሰው ዕውር እንዲለው እንደሚያደርገው እናውቃለን። ይህ ሰው ዕውር ሆኖ እንዲወለድ ያደረገው ይህ ኃጢአት ነው? ይህ ሰው ራሱ ኃጢአት ሠርቷል ወይንስ ወላጆቹ ኃጢአት ሠሩ?”

John 9:3

እኛ
ይህ “እኛ” ኢየሱስን እና የሚናገራቸውን ደቀመዛሙርትን ያካትታል ።

ቀን. . . ማታ
እዚህ “ቀን” እና “ሌሊት” ዘይቤዎች ናቸው ። ኢየሱስ ሰዎች የእግዚአብሔርን ሥራ የቀን ጊዜን ፣ ሰዎች በተለምዶ የሚሰሩበትን ጊዜ እና የሌሊት ጊዜን የእግዚአብሔርን ሥራ ማከናወን ለማይችሉበት ጊዜ እያወዳደረ ነው ።

በዚህ አለም
እዚህ “ዓለም” በዓለም ለሚኖሩት ሰዎች የሚያገለግል ዘይቤ ነው ። አት: - “በዚህ ዓለም ሰዎች መካከል”

John 9:6

በምራቁ ጭቃ አደረገ
ኢየሱስ ጣቶቹን አፈር እና ምራቅ ለማደባለቅ ተጠቅሞበታል። አት: - “ጣቶቹን ጭቃ እና ምራቅ ለመደባለቅ ጣቶቹን ተጠቅሞ ነበር

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሲተረጎም፦ የተላከ ማለት ነው
ዮሐንስ በግሪክኛ ተናጋሪ ታዳሚዎችን የሚጠቅሙ አንዳንድ ተጨማሪ መረጃዎችን እንዲያቀርብ በታሪክ መስመሩ ውስጥ አጭር እረፍቱ እዚህ ይገኛል ።

አጠበው
"አይኖቹን ገንዳ ውስጥ አጠባቸው"

John 9:8

ተቀምጠው የሚለምን ሰው ይህ አይደለምን?
ይህ አስተያየት የሰዎችን አስገራሚነት ለመግለጽ በጥያቄ መልክ ይታያል። AT: - “ይህ ሰው ቁጭ ብሎ ይለምን የነበረው እርሱ ነው!”

John 9:10

አጠቃላይ መረጃ
ቁጥር 14 ኢየሱስ ሰውየውን መቼ እንደፈወሰ ዳራውን ይነግረናል ።

አይኖእህ እንዴት ተከፈቱ
ታዲያ ለምን ማየት ቻልክ? ወይም “አሁን እንዴት ታያለህ?”

አይኔ ላይ ቀባው
ጣቶቼን በጭቃ ይሸፍኑ ነበር ። በ 9: 6 ውስጥ ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጉሙ ይመልከቱ ።

John 9:13

አጠቃላይ መረጃ
ቁጥር 14 ኢየሱስ ሰውየውን መቼ እንደፈወሰ ዳራውን ይነግረናል ።

በፊት ዕውር የነበረውን ሰው ወደ ፈሪሳውያን ወሰዱት
ሰዎቹም ሰውዬው ወደ ፈሪሳውያን እንዲሄድ ጠየቁት ። እነሱ እንዲሄድ በአካል አላስገደዱትም ።

ሰንበት ቀን
“የአይሁድ የእረፍት ቀን”

እንግዲህ ፈሪሳውያን ደግሞ
ፈሪሳውያንም ደግሞ ጠየቁት።

John 9:16

አጠቃላይ መረጃ
በቁጥር 18 ውስጥ ዮሐንስ ስለ አይሁዶች ክህደት የበስተጀርባ መረጃን ሲያቀርብ ፣ ከዋናው የታሪክ መስመር ዕረፍት አለ ።

ሰንበትን አይጠብቅም
ይህ ማለት ኢየሱስ በአይሁድ የእረፍት ቀን ምንም ሥራ ስለሌለ ህጉን አይታዘዝም ማለት ነው ።

ኃጢአተኛ የሆነ አው እነዚህን ምልክቶች እንዴት ሊያደርግ ይችላል?
ይህ አስተያየት የኢየሱስ ምልክቶች ምልክቶች ኃጢአተኛ አለመሆኑን ለማጉላት በጥያቄ መልክ ይታያል ። AT: "አንድ ኃጢአተኛ እንደዚህ ያሉትን ምልክቶች ማድረግ አይችልም!"

John 9:19

እነሱ ወላጆቹን ጠየቁ
"እነሱ" የሚያመለክተው የአይሁድ መሪዎችን ነው

እሱ አዋቂ ነው
"እሱ አዋቂ ሰው ነው" ወይም "አሁንም ልጅ አይደለም"

John 9:22

አጠቃላይ መረጃ
በቁጥር 22 ውስጥ ዮሐንስ የሰውየውን ወላጆች አይሁዶች ስለሚፈሩ የበስተጀርባ መረጃ ሲያቀርብ ዮሐንስ ከዋናው የታሪክ መስመር ዕረፍት አለ ።

አይሁድን ፈርተዋልና
እዚህ ላይ “አይሁዶች” ኢየሱስን ለተቃወሙት “የአይሁድ መሪዎች” አንድ ማሳያ ነው ። አት: - "የአይሁድ መሪዎች ምን ሊያደርግባቸው ፈሩ?"

ፍርሃት
ይህ በእራሱ ወይም በሌሎች ላይ የመጉዳት አደጋ ሲኖር አንድ ሰው የሚሰማውን ደስ የማይል ስሜት ያመለክታል ።

እሱ አዋቂ ነው
"እሱ ሰው ነው" ወይም "እሱ ከእንግዲህ ልጅ አይደለም።" ይህንን በ 9 19 ውስጥ እንዴት እንደተረጉሙ ይመልከቱ ።

John 9:24

ሰውየውን ጠሩት
እዚህ “እነሱ” የሚያመለክተው አይሁዶችን ነው ። (9 16)

ለእግዚአብሔር ክብር ስጥ
ይህ ሰዎች መሐላ በሚፈጽሙበት ጊዜ ይጠቀሙበት የነበረው ፈሊጥ ነው ። አት: - “በእግዚአብሔር ፊት እውነቱን ይናገሩ!” በእግዚአብሔር ፊት እውነቱን ተናገሩ!

ይህ ሰው
ኢየሱስን ነው የሚያመለክተው

ይህ ሰው
እውሩን ነው የሚያመለክተው

John 9:26

አያያዝ መግለጫ
አይሁዶች ዕውር የነበረውን ሰው ማናገራቸውን ቀጠሉ ።

እንደገና ለመስማት ለምን ትፈልጋላችሁ
ይህ አስተያየት የአይሁድ መሪዎች የተከሰተውን እንደገና እንዲነግራቸው የጠየቁት ሰው ያስገረመውን ለመግለጽ በጥያቄ መልክ ይታያል ። አት: - "እኔ ምን እንዳደረብኝ እንደገና ለመስማት መፈለግህ አስደንቆኛል!"

John 9:30

ከወዴት እንደሆነ አለማወቃችሁ
የአይሁድ መሪዎች የመፈወስ ኃይል እንዳለው ሲገነዘቡ የኢየሱስን ሥልጣን ሲጠራጠሩ ሰውየው ተገረመ ። አት: - “ሥልጣኑን የት እንዳገኘ አታውቅም”

ኃጢአተኞችን አያደምጥም. . . ያዳምጠዋል
"የኃጢአተኞች ጸሎትን አይመልስም ... እግዚአብሔር ጸሎቱን ይሰማል"

John 9:32

አያያዝ መግለጫ
ዓይነ ስውር የነበረው ሰው ለአይሁድ መናገሩን ቀጠለ ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ማንም እንደተከፈተ አይሰማም
ይህ ቀጥተኛ መግለጫ ነው። በገባ ቅርጸት ሊተረጉሙት ይችላሉ። አት: - “ከተወለደበት ጊዜ ዕውር የነበረውን ዕውር የፈውስ ማንም ሰው ከቶ አይሰማም”

ይህ አው ከእግዚአብሔር ባይሆን ኖሮ ምንም ማድረግ አይችልም ነበር
ይህ ዓረፍተ ነገር ድርብ አሉታዊ ንድፍን ይጠቀማል። እንደዚህ ያለ ነገር ሊያከናውን የሚችለው ከእግዚአብሔር አንድ ሰው ብቻ ነው! ”

በኃጢያት ሙሉ በሙሉ ተወልደናል ፣ እናም እያስተማርክ ነው?
ይህ ማስታወሻ አፅን .ትን ለመጨመር በጥያቄ መልክ ይታያል ። ደግሞም የሚያመለክተው ሰውየው በወላጆቹ ኃጢአት ምክንያት ዕውር ሆኖ መወለዱን ነው ። አት: - "የተወለዱት በወላጆችዎ ኃጢአት ምክንያት ነው። እኛን ለማስተማር ብቃት የላችሁም!"

ወደ ውጭ አባረሩት
ከሙኩራባቸው አስወጡት

John 9:35

አጠቃላይ መረጃ
ይህ የታሪኩ ቀጣይ ክፍል ነው ። ኢየሱስ የፈወሰውን ሰው አገኘና እሱንና ሕዝቡን አነጋገረው ።

እመኑ
ይህ የታሪኩ ቀጣይ ክፍል ነው ። ኢየሱስ የፈወሰውን ሰው አገኘና እሱንና ሕዝቡን አነጋገረው ።

John 9:39

ወደዚህ ዓለም መጣ
“ዓለም” የሚለው ቃል “በዓለም ለሚኖሩት ሰዎች” የሚለው አገላለጽ ነው ። አት: - “በዚህ ዓለም ሰዎች መካከል ለመኖር መጣ”

እንዲያዩ እንዲያዩ የሚያዩም እንዲታወሩ እኔ የማያውቁ ዕውሮች እንዲሆኑ ታዩአቸው
እዚህ “ማየት” እና “ዕውርነት” ዘይቤዎች ናቸው ። ኢየሱስ በመንፈሳዊ ዓይነ ስውር በሆኑና በአካላዊ ዓይነ ስውር በሆኑት ሰዎች መካከል ይለያል ። AT: “ስለሆነም በመንፈሳዊ ዕውሮች የሆኑ ግን እግዚአብሔርን ማየት የሚፈልጉት እሱን ሊያዩ ይችላሉ ፣ እናም ቀድሞውንም እግዚአብሔርን ያታልላሉ ብለው በሐሰተኛነት ላይ ይቆያሉ” (ይመልከቱ ። የበለስ_ቁጥር) ።

እኛ ደግሞ ዕውሮች ነንን?
እኛ በመንፈሳዊ ዕውራን የሆንን ይመስልሃል?

ዕውሮች ብትሆኑ ኖሮ ኃጢአት የለብህም
እዚህ “ዕውር” የእግዚአብሔርን እውነት አለማወቅ ምሳሌ ነው ። አት: - "የእግዚአብሔርን እውነት ማወቅ ከፈለግክ ፣ ዓይንህን ማየት ይችል ነበር ።"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **10**

1 “እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፤ ወደ በጎች በረት በበር ሳይሆን፣ በሌላ መንገድ ተንጠላጥሎ የሚገባ እርሱ ሌባና ወንበዴ ነው። **2** በበር የሚገባ ግን የበጎች እረኛ ነው። **3** በር ጠባቂውም ለእርሱ ይከፍትለታል። በጎቹም ድምፁን ይሰማሉ፤ እርሱም የራሱን በጎች በስማቸው ጠርቶ፣ ወደ ውጭ ይመራቸዋል። **4** የራሱን ሁሉ ካወጣቸው በኋላ፣ ፊት ፊታቸው ይሄዳል፤ በጎቹም ድምፁን ስለሚያውቁ ይከተሉታል። **5** ባዕድ የሆነውን አይከተሉትም፤ ይልቁንም የባዕዱን ድምፅ ስለማያውቁት ይሸሹታል።” **6** ኢየሱስ ይህን ምሳሌ ነገራቸው፤ እነርሱ ግን የነገራቸው ስለ ምን እንደ ሆነ አልገባቸውም። **7** ኢየሱስም እንደ ገና እንዲህ አላቸው፤ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፤ የበጎች በር እኔ ነኝ። **8** ከእኔ በፊት የመጡ ሁሉ ሌቦችና ወንበዴዎች ናቸው፤ በጎቹ ግን አላዳመጡአቸውም። **9** በሩ እኔ ነኝ። ማንም በእኔ በኩል ቢገባ፣ ይድናል፤ ይገባል፣ ይወጣልም፤ መሰማሪያም ያገኛል። **10** ሌባው የሚመጣው ሊሰርቅ፣ ሊገድልና ሊያጠፋ ብቻ ነው። እኔ ግን ሕይወት እንዲኖራቸውና እንዲትረፈረፍላቸው መጥቻለሁ። **11** መልካም እረኛ እኔ ነኝ። መልካም እረኛ ለበጎቹ ሲል ነፍሱን ይሰጣል። **12** እረኛ ያልሆነው ተቀጣሪ በጎቹም የእርሱ ያልሆኑት፣ ቀበሮ መምጣቱን ሲያይ በጎቹን ጥሎ ይሸሻል ። ቀበሮም ነጥቆአቸው ይሄዳል፤ ይበታትናቸውማል። **13** የሚሸሸውም ተቀጣሪ ስለ ሆነና ለበጎቹ ደንታ ስለሌለው ነው። **14** መልካም እረኛ እኔ ነኝ፤ የእኔ የሆኑትን ዐውቃቸዋለው፤ የእኔ የሆኑትም ያውቁኛል። **15** አብ እንደሚያውቀኝ፤ እኔም አብን ዐውቀዋለው፤ ነፍሴንም ስለ በጎች እሰጣለሁ። **16** ከዚህ በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ። እነዚያን ደግሞ ማምጣት አለብኝ፤ እነርሱ ድምፄን ይሰማሉ። አንድ መንጋ ይሆናሉ፤ እረኛቸውም አንድ ይሆናል። **17** አባቴ የሚወደኝ ለዚህ ነው፤ መልሼ ልወስደው እንድችል ነፍሴን እሰጣለሁ ። **18** ነፍሴን ማንም ከእኔ አይወሰድም፤ ግን እኔው ራሴ እሰጣለሁ ። ለመስጠት ሥልጣን አለኝ፤ መልሼ ለመውሰድም ሥልጣን አለኝ። ይህን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀብያለሁ።” **19** ከዚህ አባባል የተነሣም በአይሁድ መካከል እንደ ገና መከፋፈል ተፈጠረ። **20** ብዙዎች፣ “ጋኔን ስላለበት ዐብዶአል፤ ለምን ታዳምጡታላችሁ?” አሉ። **21** ሌሎችም፣ “ንግግሩ ጋኔን ያለበት ሰው ንግግር አይደለም። ጋኔን ያለበት ሰው የዐይነ ስውርን ዐይን መክፈት ይችላልን?” አሉ። **22** በኢየሩሳሌምም የቤተ መቅደስ መታደስ በዓል ደርሶ ነበር። **23** ጊዜው ክረምት ነበረ፤ ኢየሱስም በቤተ መቅደስ በሰሎሞን መተላለፊያ ይመላለስ ነበር። **24** ከዚያም አይሁድ ወደ እርሱ ተሰብስበው፣ «እስከ መቼ ድረስ ልባችንን ታንጠለጥላለህ? አንተ ክርስቶስ ከሆንህ፣ በግልጽ ንገረን» አሉት። **25** ኢየሱስ መልሶ እንዲህ አላቸው፤ “ነገርኋችሁኮ፤ እናንተ ግን አታምኑም፤ በአባቴ ስም የማደርጋቸው ሥራዎች እነዚህ ስለ እኔ ይመሰክራሉ። **26** እናንተ ግን በጎቼ ስላልሆናችሁ አታምኑም። **27** በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ፤ እኔ ዐውቃቸዋለሁ፤ እነርሱም ይከተሉኛል። **28** የዘላለም ሕይወት እሰጣቸዋለው፤ ፈጽሞም አይጠፉም፤ ነጥቆ ከእጄ የሚያወጣቸው ማንም የለም። **29** እነርሱን ለእኔ የሰጠ አባቴ ከሌሎች ሁሉ ይበልጣል፤ ስለዚህ ከአብ እጅ ነጥቆ ሊያወጣቸው የሚችል ማንም የለም። **30** እኔና አብ አንድ ነን።” **31** አይሁድ ሊወግሩት እንደ ገና ድንጋይ አነሡ። **32** ኢየሱስም መልሶ፣ «ከአብ የሆነ ብዙ መልካም ሥራ አሳይቻችኋለሁ፤ ከእነዚህ ሥራዎች ውስጥ በየትኛው ምክንያት ትወግሩኛላችሁ?” አላቸው። **33** አይሁድም መልሰው፣ «የምንወግርህ በየትኛውም መልካም ሥራ ምክንያት አይደለም፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ላይ በምትሰነዝረው የስድብ ቃል ምክንያት ነው፤ አንተ ሰው ሆነህ ሳለህ፣ ራስህን አምላክ እያደረግህ ስለ ሆነ ነው» አሉት። **34** ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ «በሕጋችሁ፣ ‘አማልክት ናችሁ አልሁ’ ተብሎ አልተጻፈምን? **35** የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸውን አማልክት ናችሁ ካላቸው፣ የመጻሕፍት ቃል አይሻርምና፣ **36** እኔ ‘የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ’ ስላልሁ፣ አብ ቀድሶ ወደ ዓለም የላከውን እንዴት የስድብ ቃል ሰነዘረ ትሉታላችሁ? **37** እኔ የአባቴን ሥራዎች የማላደርግ ከሆንሁ አትመኑኝ። **38** ነገር ግን የማደርጋቸው ከሆንሁ፣ በእኔ ባታምኑ እንኳ፣ አብ በእኔ እንዳለ፣ እኔም በአብ እንዳለሁ እንድታውቁና እንድትረዱ፣ በሥራዎቹ እመኑ።» **39** እነርሱም ኢያሱስን እንደ ገና ለመያዝ ሞከሩ፣ እርሱ ግን ከእጃቸው አምልጦ ሄደ። **40** ኢየሱስ ዮርዳኖስን ተሻግሮ፣ ዮሐንስ በመጀመሪያ ሲያጠምቅበት ወደ ነበረው ቦታ እንደ ገና ሄደ፤ በዚያም ቆየ ። **41** ብዙ ሰዎች ወደ ኢየሱስ መጡ። እነርሱም፣ «በርግጥ ዮሐንስ ምንም ተአምር አልሠራም፤ ነገር ግን ዮሐንስ ስለዚህ ሰው የተናገረው ሁሉ እውነት ነው» ይሉ ነበር። **42** በዚያም ብዙ ሰዎች በኢያሱስ አመኑ።

John 10:1

አጠቃላይ መረጃ
እየሱሰ ምሳሌያዊ አነጋገር መናገር ጀመረ

አያያዥ መገለጫ
እየሱስመ ፈሪሳውያንን ማነገር ቀጠለ። ይህ ታሪክ በ9:35 ጋር አንድ ነው።

እውነት አውነት
እንደ 1:49 ይተርጎም

የበግ
እረኛው በጎቹን የሚያኖሩበት አጥር

ሌባና ቀማኛ
ሁለት አንድ አይነት ትረጉም ያለው ቃል ክብደት ለመጨመር መጠቀም

John 10:3

በር ጠባቂው
እረኛው ሳይኖር በማታ በር እንዲጠብቅ የተቀጠረ

በጎቹ ድምጹን ይሰማሉ
በጎቹ ድምጹን ለይተው ይሰማሉ

ከፊታቸው ይቀድማቸዋል
ከፊታቸው ይራመዳል

ድምጹን ስለሚያውቁት
ድምጹተን ይለዩታል

John 10:5

አልገባቸውም
ሊሆን የሚችለው 1) ደቀመዛሙርቱ አልገባቸውም 2) የተሰበሰቡትም አልገባቸውም

ይህ ምሳሌ
ይህ መግለጫ የእረኛው ነው ዘይቤዎችን በመጠቀም። እረኛው የእየሱስ ምሳሌ ነው። በጉ የእየሱስ ተከታዮችን ሲወክል፥ እንግዶች ደግሞ የአይሁድ መሪዎች እና ፈሪሳውያን፤ ሰዎቹን ለማታለል የሞከሩት

John 10:7

አያያዝ መግለጫ
ኢየሱስ የተናገራቸውን ምሳሌዎች ትርጉም ማብራራት ይጀምራል ።

እኔ የበጎች በር ነኝ
እዚህ “በር” ይህ የእግዚአብሔር ህዝብ በእርሱ ፊት በሚኖርባቸው በጎች ወደ ስፍራው ለመድረስ የሚያስችል ኢየሱስ ነው ። አት: - “በጎቹ ወደ በግ በጎች ለመግባት እንደሚጠቀሙበት በር ነኝ”

ከእኔ በፊት የመጡት በሙሉ
ይህ ፈሪሳውያንንና ሌሎች የአይሁድ መሪዎችን ጨምሮ ሕዝቡን ያስተማሩ ሌሎች አስተማሪዎች ናቸው ። አት: - “ከኔ ስልጣን ውጭ የመጡ አስተማሪዎች ሁሉ” (የበለስ_ቁጥር ይመልከቱ)

John 10:9

እኔ በር ነኝ
በር ምሳሌያዊ ነው።

ለምለም
ለምለም ማለት በጎች የሚበሉት ሳር ያለበት

ሊሰርቅ ካልሆነ አይመጣም
ይህ ድርብ አሉታዊ ነው። በአንዳንድ ቋንቋዎች አወንታዊ መግለጫን መጠቀም የበለጠ ተፈጥሮአዊ ነው። አት: “የሚመጣው ለመስረቅ ብቻ ነው”

ሊሰርቅ ሊገል እና ሊያጠፋ
እዚህ በምሳሌ የተገለጸው በጉ ነው፤ የእግዚአብሄርን ሕዝብ ይወክላል። በጎቹን ሊሰርቅ ሊገል እነ ሊያተፋ

ሕይወት እአንዲኖራቸው
እነሱ የሚለው ቃል የሚያመለክተው በጉን ነው። ሕይወት ደግሞ የዘላለም ሕይወትነ ያመለክታል።

John 10:11

አያያዥ መግለጫ
እየሱስ ስለ መልካሙ እረኛ ምሳሌያዊ ነግግሩን ቀጠለ

መልካም እረኛ እኔ ነኝ
መልካም እረኛ በምሳሌ የሚወክለው እየሱስን ነው።

ሕይወቱን ሰጠ
አንድነ ነገር መተው ማለት መቆጣጠር አለመቻልን ተስፋ መቁረጥን ያሳያል። መለስተኛ የሞት መንገድ

የተቀጠረ አገልጋይ
የተቀጠረ አገልጋይ የአይሁድ መሪዎችና አስተማሪዎች ዘይቤ

በጎቹን ይተዋል ስለ በጎቹም ግድ የለውም
እዚህ ላይ በግ የሚለው የእግዚአብሔርን ሕዝብ ይወክላል። እየሱስም አለ እንደ ተቀጠረ እረኛ በጎቹን እንደሚተው፤ የአይሁድ መሪዎችና አስተማሪዎች ለእግዚአብሄር ሕዝቦች ግድ የላቸውም

John 10:14

መልካም እረኛ እኔ ነኝ
ለእየሱሰ መልካም እረኛ ነኝ የሚለው ምሳሌያዊ ነው

አባቴም ያውቀኛል እኔም አውቀዋለሁ
አብም እንደሚያውቀኝ አኔም አብን እንደማውቅ እናንተም ታውቁኛላችሁ። አባት የሚለው ለእግዚአብሔር አስፈላጊ ርዕስ ነው

ሕይወቴን ለበጎቼ አሳልፌ ሰጣለሁ
ይህ ለየሱስ ስለ በጎቹ ራሱን ኣሳልፎ እንደሚሰጥ

ሌላ በግ አለኝ
ሌላ በግ ማለት አይሁድ ያልሆኑ ተከታዮች እንዳሉት ለመግለጽ

አንድ መንጋና አንድ እረኛ
እዜህ መንጋና በግ ምሳሌያዊ ናቸው። አይሁድ እና አይሁድ ያይደሉት አንድ መንጋ ይሆናሉ። አርሱም በጎቹን እንደሚንከባከብ እረኛ ይሆናል።

John 10:17

አያያዥ መቻለጫ
እየሱስም ለሕዝቡ መናገሩን ጨረሰ።

አባቴም የሚወደኝ ለዚህ ነው፥ ሕይወቴን ስለምሰጥ
የእግዚአብሔር ዘላለማዊ እቅድ ልጁ ስለሰው ለጆች ሐጢአት ሲል ሕይወቱን አሳልፎ እንዲሰጥ ነው። የእየሱስ የመስቀል ሞት የሚያሳየን የአባትና የልጁን ፍቅር ነው

አባት
ይህ ለእግዚአብሔር አስፈላጊ ርእስ ነው።

ፍቅር
ይህ አይነት ፍቅር የሚገኘው ከእግዚአብሔር ሲሆን የሚያተኩረውም ለሌሎች መልካመን በማድረግ፤ለርሱ ምንም ትርፍ ባይኖረውም። ይህ አይነት ፍቅር የሚጨነቀው የፈለጉትንም ቢሰሩ ስለሌሎች ነው።

ሕይወቴን ኣኖራታለሁ እነደገናም መልሼ ወስዳታለሁ
እየሱስ በመለስተኛ አባባል እንደሚሞትና እንደገናም በሕይወት እንደሚኖር

እራሴ ኣኖራታለሁ
እራሴ የሚለው የሚገልጸው እየሱስ እራሱ ሕይወቱን እንደሚያኖር ነው። ከሱ ማንም አይወስድበትም።

ይህንን ትዕዛዝ ከአባቴ ነው የተቀበልኩት
አባተ እንድሰራው ያዘዘኝ ይህንን ነው። አባት የሚለው ለእግዚአብሄር አስፈላጊ ነው።

John 10:19

አያያዥ መግለጫ
ይህ ጥቅስ የሚነግረን አይሁዶች ለኢየሱስ የመለሱለትን ነው።

ስለምን ትሰሙታላችሁ?
ይህ አስተያየት በጥያቄ መለክ የሚያመለክተው ሕዝቡ ትኩረት ሰጥተው ዕርሱን ዕነዳይሰሙት ነው።

ሰይጣን የእውርነ አይን መክፈት ይችላልን?
ይህ አስተያተ በጥያቄ መልክ የቀረበው ለጉዳዩ ትኩረት ለመስጠት ነው።

John 10:22

አጠቃላይ መግለጫ
ይህ የሚቀጥለው ከፍል ታሪክ ነው። የመታደስም በአል ስለነበር አይሁዶቹ ኢየሱስን መጠየቅ ጀመሩ። ቁጥር 22 እና 23 ስለታሪኩ አመጣጥ መነሻ ይሰጣሉ።

የመታደስ በዓል
ይህ ለ8 ቀን የሚቆይ በክረምት ጊዜ የሚከበር በኣል እግዚአብሄር ያደረገውነ ተአምራት ትንሽ የቀረችውን ዘይት በመቅረዝ ለ8 ቀን ስለበራ። መቅረዙን የሚያበሩት የአይሁድን ቤተ መቅደስ ለእግዚአብሄር ለመለየት ነው። አንድ ነገር ሲለይ ለተለየ ነገር ቢቻ ለመጠቀም ቃል መግባት ነው።

እየሱሰ በቤተመቅደሱ ውስጥ ይራመድ ነበር
እየሱስ ይራመድ የነበረው ከቤተመቅደሱ ውጪ ባለው ግቢ ነበር

በረንዳ
ይህ ቅርጽ በሕነጻ መግቢያ ጋር የተያያዘ ሶሆን ጣራ ሲኖረው ግርግዳ ግን የለውም

አይሁዶችም ከበቡት
እዚህ ላይ “አይሁዶች” ኢያሱስን ለተቃወሙት የአይሁድ መሪዎች ምሳሌ ነው ። AT: “የአይሁድ መሪዎችም ከበቡት”

መጠራጠር
ይህ ፈሊጥ ነው ። አት: - "እንድንደነቅ ያደርገናል" (UDB) ወይም "በእርግጠኝነት እንዳናውቅ ያድርገንን?"

John 10:25

ማያያዣ መግለጫ
እየሱስመ ለአይሁዶች መመለስ ጀመረ

በአባቴ ስም
ስም የሚለው የእግዚአብሔር ሐይል ነው። አበት የሚለው ቃል ለእግዚአብሄር ኣስፈላጊ ነው። ዔሱስ ያደረጋቸው ተአምራት በአባቱ ሀይልና ስልጣን ነው።

እኔን ይህ ይገልጸኛል
ልክ በፍርድቤት ቀርቦ እንደሚመሰከር ሰው ተአምራቶቹ ስለእርሱ ይመሰክራሉ

በጎቼ አይደሉም
በጎቼ የሚለው ቃል የኢየሱስ ተከታዮችን ይገልጻል

John 10:27

በጎቼ ድምጼን ይሰማሉ
በግ የሚለው ቃል ለእየሱሰ ተከታዮች የሚጠቀሙበት ዘይቤ ነው። ዘይቤውም እየሱስ እረኛ እንደሆን ይገልጻል።

ከእጄ ማንም አይነጥቃቸውም
እጅ የሚለው የእየሱስን ተከላካይነት እና ጥበቃ

John 10:29

አባቴም ለእኔ ሰጠኝ
አባት የሚለው ቃል ለእግዚአብሄር አስፈላጊ ነው

የአባቴ እጅ
እጅ የሚለው የእግዚአብሄርን ይዞታ እና ጥበቃ

እኔና አባቴ አንድ ነን
እየሱስ የእግዚአብሄር ልጅ እና እግዚአብሄር አባት አንድ ናቸው። አባት የሚለው ቃል ለእግዚአብሄር አስፈላጊ ነው

አይሁዶችም ድንጋይ አነሱ
“አይሁዶች” የሚለው ቃል ኢየሱስን ለሚቃወሙት የአይሁድ መሪዎች መፈክር ነው ። አትቲ: - “የአይሁድ መሪዎች እንደገና ድንጋይ መከሩን ጀመሩ”

John 10:32

እየሱስመ መለሰ፤ ከአባቴ የሆነውን ጥሩ ስራ አሳየሁዋችሁ
እየሱስም ተአምራቶችን በእግዚአብሄር ያሳይ ነበር። አባት የሚለው ቃል ለእግዚአብሄር አስፈላጊ ነው

ስለየትኛው ስራዱ ነው በድንጋይ የምትወግሩኝ?
ይህ ጥያቄ ጠንካራ ነው። እየሱስ የአይሁድ መሪዎች መልካም ስራ ስለሰራ በድንጋይ ሊወግሩት እንዳልሆነ ያውቃል።

አይሁዶችም መለሱለት
“አይሁዶች” የሚለው ቃል ኢየሱስን የሚቃወሙትን የአይሁድ መሪዎች የሚወክል የመከራከሪያ መግለጫ ነው ። AT: - “የአይሁድ ተቃዋሚዎች መለሱ” ወይም “የአይሁድ መሪዎች መለሱለት”

ራስህን እግዚአብሄር ኣደረክ
እግዚአብሄር ነኝ ኣልክ

John 10:34

አልተጻፈምን አማለክት
በጥያቄ ምልክት የቀረበው አጽንኦት ለመስጠት ነው።

እናንተ አማልክት ናችሁ
እዚህ ላይ ኢየሱስ ተከታዮቹን “አማልክት” ብሎ የሚጠራውን ጥቅስ ይጠቅሳል ፣ ምናልባትም በምድር ላይ እሱን እንዲወክሉ ስለመረጣቸው ።

የእግዚአብሄር ቃል መጣ
እግዚአብሄርም ቃሉን ተናገረ

ቃሉ አይለወጥም አይሰበርም
ትርጉሙ ሊሆን የሚችለው፡ 1) ቃሉን ማን መለወ አይችልም 2) ቃሉ ሁሌም እውነት ነው

አባት የእግዚአብሄር ልጅ
ይህ የእግዚአብሄርነና የእየሱስን ግኑኝነት የሚገልጽ አስፈላጊ ርእስ ነው

John 10:37

አያያዥ መግለጫ
እየሱስም ለአይሁዶች መልስ መስጠቱን ጨረሰ

አባት
አባት የሚለው ቃል ለእግዚአብሄር አስፈላጊ ነው

እመኑኝ
እመኑኝ የሚለው ቃል እየሱስ ያለው እውነት እንደሆን መቀበል ወይም ማመን

በስራ እመኑ
እመኑ የሚለው እየሱስ እየሰራ ያለው ከአባቱ እንደሆነ እንዲያወቁ

አባቴም በእኔ አለ እኔም በአባቴ
በእግዚአብሄርና በእየሱስ መካከል ያለውነ ግንኙነት የሚገልጽ

ከእጆቸውም ወቶ ሄደ
እጅ የሚለው የአይሁድ መሪዎችን

John 10:40

ከጆርዳን በኃላ
እየሱሰ በምእራብ ጆርዳን ወንዝ ነበረ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በዚያም ቆየ
እየሱስመ ለጥቂት ጊዜ በምስራቅ ጆረዳነ ቆየ

ምልክት
ተአምራቶቹ አንድ ነገር እውነት እነደሆነና ለዛ ሰውም ምስጋና መስጠት

ዮሀንስ ምንመ ምልክት አልሰራም ግን ዮሀንስ ስለዚህ ሰው ያለው ሁሉ እውነት ነበር
ዮሀንስ ምልክት አለማድረጉ እውነት ቢሆንም ስለዚህ ሰው የተናገረው ምልክት እነደሚያደርግመ እውነት ነው

አመኑ
አመኑ የሚለው እየሱስ ያለውን ማመንና መቀበል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **11**

1 አልዓዛር የተባለ አንድ ሰውም ታሞ ነበር። እርሱም ማርያምና እኅትዋ ማርታ በሚኖሩበት መንደር በቢታንያ ይኖር ነበር። **2** ወንድምዋ የታመመባትም የጌታ
ኢየሱስን እግር ሽቱ የቀባችውና በጠጒርዋ ያበሰችው ናት። **3** ከዚያም እኅትማማቹ፣ ‹‹እነሆ፣ የምትወደው ታሞአልና በፍጥነት ድረስ›› በማለት ወደ ኢየሱስ
ላኩበት። **4** ኢየሱስ መልእክቱን በሰማ ጊዜ፣ ‹‹ይህ የእግዚአብሔር ልጅ እንዲከብርበት ለእግዚአብሔር ክብር የሚሆን ነው›› አለ። **5** ኢየሱስ ማርታንና እኅቷን
እንዲሁም አልዓዛርን ይወድ ነበር። **6** ስለሆነም አልዓዛር መታመሙን በሰማ ጊዜ፣ ኢየሱስ በነበረበት ቦታ ሁለት ተጨማሪ ቀናት ቆየ። **7** ከዚህ በኋላም ደቀ
መዛሙርቱን፣ “ወደ ይሁዳ ዳግመኛ እንሂድ” አላቸው። **8** ደቀ መዛሙርቱ፣ “መምህር ሆይ፣ አይሁድ አሁን ሊወግሩህ ነበር፣ እንደ ገና ወደዚያ ተመልሰህ
ትሄዳለህን?” አሉት። **9** ኢየሱስም፣ “በአንድ ቀን ውስጥ አሥራ ሁለት የብርሃን ሰዓታት አሉ አይደለምን? አንድ ሰው በቀን የሚራመድ ከሆነ የቀኑን ብርሃን
ስለሚመለከት፣ አይደናቀፍም። **10** በሌሊት የሚራመድ ከሆነ ግን ብርሃኑ በእርሱ ውስጥ ስለሌለ፣ ይደናቀፋል።” **11** ኢየሱስ እነዚህን ነገሮች ተናገረ፣
ከእነዚህም ነገሮች በኋላ፣ “ወዳጃችን አልዓዛር አንቀላፍቷል፣ እኔ ግን ከእንቅልፉ ላነቃው እሄዳለሁ” አላቸው። **12** ስለዚህ ደቀ መዛሙርቱ፣ “ጌታ ሆይ፣ ተኝቶስ
ከሆነ ይድናል” አሉት። **13** ኢየሱስም የተናገረው አልዓዛር ስለ መሞቱ ነበር፣ እነርሱ ግን ዕረፍት ለማድረግ ስለ መተኛቱ የተናገረ መስሎአቸው ነበር። **14**
ከዚያም ኢየሱስ በግልጽ፣ “አልዓዛር ሞቷል **15** እናንተ ታምኑ ዘንድ እኔ እዚያ ባለመኖሬ ስለ እናንተ ደስ ብሎኛል” አላቸው። **16** ዲዲሞስ የተባለው ቶማስ
ባልደረቦቹ ደቀ መዛሙርትን፣ “ከኢየሱስ ጋር እንሞት ዘንድ እኛም ከእርሱ ጋር እንሂድ” አላቸው። **17** ኢየሱስ በመጣ ጊዜ፣ አልዓዛር በመቃብር ውስጥ አራት
ቀን መቆየቱን ተረዳ። **18** ቢታንያ አሥራ አምስት ኪሎ ሜትር ብቻ የምትርቅ ለኢየሩሳሌም ቅርብ ስፍራ ነበረች። **19** ስለ ወንድማቸው ሞት ሊያጽናኗቸው
ከአይሁድ ብዙዎቹ መጥተው ነበር። **20** ከዚያም ማርታ ኢየሱስ እንደ መጣ በሰማች ጊዜ፣ ልትቀበለው ወጣች፣ ማርያም ግን በቤት ተቀምጣ ነበር። **21**
ከዚያም ማርታ ኢየሱስን፣ “ጌታ ሆይ፣ አንተ እዚህ ብትኖር ኖሮ ወንድሜ ባልሞተም ነበር። **22** አሁንም ቢሆን የምትለምነውን ሁሉ እግዚአብሔር እንደሚሰጥህ
ዐውቃለሁ” አለችው። **23** ኢየሱስ፣ “ወንድምሽ ይነሣል” አላት። **24** ማርታ፣ “በመጨረሻው ቀን በሚሆነው በትንሣኤ ከሞት እንደሚነሣ ዐውቃለሁ” አለችው።
25 ኢየሱስ፣ “እኔ ትንሣኤና ሕይወት ነኝ፣ በእኔ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል። **26** በእኔ የሚኖርና የሚያምንብኝ ሁሉ ፈጽሞ አይሞትም፤ ይህን
ታምኛለሽን?” አላት። **27** እርሷም፣ “አዎን፣ ጌታ ሆይ፣ አንተ ወደ ዓለም ልትመጣ ያለኸው ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆንህ አምናለሁ” አለችው። **28**
ማርታ ይህን ከተናገረች በኋላ እኅቷን ማርያምን በግል ለማነጋገር ትጠራት ዘንድ ሄደችና፣ “መምህሩ እዚህ ነው፣ ሊያነጋግርሽ ይፈልጋል” አለቻት። **29** ማርያም
ይህን እንደ ሰማች በፍጥነት ተነሥታ ወደ ኢየሱስ ሄደች። **30** ኢየሱስም ማርታን ባገኘበት ስፍራ ነበር እንጂ ገና ወደ መንደሩ አልገባም ነበር። **31** ከዚያም
በቤት ውስጥ ሆነው ማርያምን ሲያጽናኗት የነበሩት አይሁድ ፈጥና ስትወጣ ባዩአት ጊዜ፣ ወደ መቃብር ሄዳ በዚያ ልታለቅስ መስሏቸው ተከተሏት። **32** ከዚያም
ማርያም ኢየሱስ ወደ ነበረበት መጥታ ስታየው በእግሩ ሥር ወድቃ፣ “ጌታ ሆይ፣ አንተ እዚህ ብትሆን ኖሮ፣ ወንድሜ ባልሞተም ነበር” አለችው። **33** ኢየሱስ
እርሷና ዐብረዋት የነበሩት አይሁድ ሲያለቅሱ ተመልክቶ በመንፈሱ ቃትቶና ተጨንቆ፣ **34** “ወዴት አኖራችሁት?” አላቸው። እነርሱም፣ “ጌታ ሆይ፣ መጥተህ
እይ” አሉት። **35** ኢየሱስ አለቀሰ። **36** ከዚያም አይሁድ፣ “አልዓዛርን ምን ያህል ይወደው እንደ ነበረ ተመልከቱ!” አሉ። **37** ከእነርሱ አንዳንዶቹ ግን፣ “ዓይነ
ስውር የነበረውን ሰውዬ ዓይን የከፈተ ይህ ሰው የሞተውን ይህን ሰው እንዳይሞት ማድረግ አይችልም ነበር?” አሉ። **38** ከዚያም ኢየሱስ አሁንም በውስጡ
እየቃተተ ወደ መቃብሩ ሄደ። መቃብሩ ዋሻ ነበረ፣ ድንጋይም ተገጥሞበት ነበር። **39** ኢየሱስ፣ “ድንጋዩን አንሡት” አለ። የሟቹ የአልዓዛር እኅት ማርታም
ኢየሱስን፣ “ከሞተ አራት ቀን ስለሆነው፣ በአሁኑ ጊዜ ገላው ይበሰብሳል” አለችው። **40** ኢየሱስ ማርታን፣ “ብታምኚስ፣ የእግዚአብሔርን ክብር እንደምታዪ
አልነገርሁሽምን” አላት። **41** ስለዚህ ድንጋዩን አነሡት። ኢየሱስም ሸቅብ እየተመለከተ፣ “አባት ሆይ፣ ስለ ሰማኸኝ አመሰግንሃለሁ፤ **42** ሁልጊዜም
እንደምትሰማኝ ዐውቃለሁ፣ ነገር ግን ይህን ያልሁት አንተ እንደላክኸኝ ያምኑ ዘንድ እዚህ በዙሪያዬ ስለቆመው ሕዝብ ነው” አለ። **43** ይህን ካለ በኋላ ድምፁን
ከፍ አድርጎ፣ “አልዓዛር ሆይ፣ ውጣ!” አለ። **44** የሞተው ሰው እጁና እግሩ በመገነዣ ጨርቅ እንደ ተጠቀለለ፣ ፊቱም በጨርቅ እንደ ተሸፈነ ወጣ። ኢየሱስ፣
“ፍቱትና ይሂድ” አላቸው። **45** ከዚያም ወደ ማርያም ከመጡትና ይህን ከተመለከቱት አይሁድ አብዛኛዎቹ በእርሱ አመኑ፤ **46** ነገር ግን ከእነርሱ አንዳንዶቹ ወደ
ፈሪሳውያን ሄደው ኢየሱስ ያደረገውን ነገሯቸው። **47** ከዚያም ሊቀ ካህናቱና ፈሪሳውያን ጉባዔ ጠርተው፣ “ምን እናድርግ? ይህ ሰው ብዙ ምልክቶችን እያደረገ
ነው። **48** እንደዚሁ የምንተወው ከሆነ፣ ሮማውያን መጥተው ስፍራችንና አገራችንንም ይወስዳሉ” አሉ። **49** ሆኖም በዚያ ዓመት ሊቀ ካህን የነበረ ከእነርሱ
መካከል ቀያፋ የተባለው አንዱ፣ “እናንተ ምንም አታውቁም፤ **50** አገሪቱ በመላ ከምትጠፋ አንድ ሰው ስለ ሕዝቡ ቢሞት የተሻለ እንደሆነ ከግምት ውስጥ
አላስገባችሁም” አላቸው። **51** እርሱ ይህን የተናገረው ከራሱ አልነበረም፣ ይልቁንም በዚያ ዓመት ሊቀ ካህን ስለ ነበረ፣ ኢየሱስ ስለ ሕዝቡ፣ **52** ደግሞም ስለ
ሕዝቡ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን በልዩ ልዩ ስፍራ የተበታተኑትን የእግዚአብሔርን ልጆች ይሰበስብ ዘንድ መሞት እንደሚገባው ትንቢት ተናገረ። **53** ስለዚህ ከዚያ
ቀን ጀምሮ ኢየሱስን እንዴት መግደል እንዳለባቸው ዕቅድ አወጡ። **54** ከዚያ ወዲያ ኢየሱስ በአይሁድ መካከል በግልጽ መውጣትና መግባቱን ትቶ ኤፍሬም
ወደ ተባለው በበረሓው አጠገብ ወዳለው ከተማ ሄደ። እዚያ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ቈየ። **55** የአይሁድ የፋሲካ በዓልም ቀርቦ ነበረና ብዙዎች ራሳቸውን ያነጹ
ዘንድ ከፋሲካው በፊት ከየገጠሩ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄዱ ነበር። **56** ኢየሱስን እየፈለጉት፣ በቤተ መቅደስ ቆመው ሳሉ፣ “ምን ይመስላችኋል? ወደ በዓሉ
አይመጣ ይሆን?” እያሉ እርስ በርሳቸው ይነጋገሩ ነበር። **57** ሊቀ ካህናቱና ፈሪሳውያኑም ኢየሱስን ይይዙት ዘንድ እርሱ የት እንዳለ ያወቀ ማንኛውም ሰው
ጥቆማ እንዲያቀርብ ትእዛዝ አስተላለፉ።

John 11:1

ጠቅላላ መግለጫ
ይህ የሚቀጥለው ክፍል ታሪክ ስለ አልአዛር ነው። ይህ ጥቅሰ እሱን ሲያስተዋውቅ ስለእህቱ ሜሪእና ስለአልአዛር የኃላ መግለጫ ኣስተዋውቃል

ሜሪ ነበረች የጌታን እግር የቀባች በጸጉሯ
የማርታን እህት ሜሪን ዮሀንስ እያስተዋወቀ ቀጥሎ ምን እንደሚሆን መግለጫ ያጋራ ነበር

John 11:3

ለእየሱሰ ተላከ
እየሱሰስ እንዲመጣ ጠየቁት

ፍቅር
እዚህ ፍቀር የሚያመለክተው ወንድማዊ ፍቅር ተፈጠሮአዊ የሰው ፍቅር በጓደኞች እና በዘመድ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ይህ ህመም ለሞት አይደለም
እየሱስም ያመለከተው በአልአዛር ምን እንደሚሆንና ስለበሽታው ነው።

ሞት
የስጋ ሞትን ያመለክታል

ለእግዚአብሄር ክብር ነው እንዲሁም የእግዚአብሄር ሊጅ እንዲከብር
እየሱሰ ውጤቱ ምን እንደሚሆን ያውቅ ነበር

የእግዚአብሄር ልጅ
የእግዚአብሄር ልጅ የሚለው ለእየሱስ አስፈላጊ ነው

John 11:5

እየሱስ ማርታንና እህቷን እና አልአዛርን ይወዳቸዋል
የኃላ ታረክ መግለጫ

John 11:8

መምህር ሆይ አይሁዶች በድንጋይ ሊወግሩህ ነው ተመልሰህ መሄድ ትፈልጋለህን?
ይህ ነጥብ በጥያቄ መልክ የሆነው ደቀመዛሙርቱ አጽንኦት ሰተው እየሱስ ወደ እንዳይሄድ ስለፈለጉ ነው።

አይሁዶች
እየሱስን የሚቃወሙ የአይሁድ መረዎች ማደንዘዣ ነበር

ቀኑ አስራ ሁለት ሰአት አይደለምን?
በጥያቄ መልክ የሆነው አጽንኦት ለመስጠት ነው።

በቀን የሚመላስ ቢኖር አይሰናከልም የዚህን ዓለም ብርሀን ያያልና
በቀን ብርሀን የሚመላሱ በደንብ ስለሚያዩ አይሰናከሉም። ብርሀን የእውነት መግለጫ ነው።እየሱሰ ዕያለ ያለው እውነትን መሰረት አድረገው የሚኖሩ እግዚአብሄር ያዘዛቸውን መፈጸም ይችላሉ

John 11:10

አያያዥ መገለጫ
እየሱስ ለደቀመዛሙርቱ መናገሩን ቀጠለ

በለሌት የሚመላለስ
ጭለማ የሚያመለክተው ከዕግዚአብሄር ብርሀን ውጪ መመላለስን ነው

ብርሀን በርሱ የለም
ትርጉሙ ሊሆን የሚችለው 1) አያይም ወይም የእግዚአብሄር ብርሀን የለውም

ወዳጃችን አልአዛር ተኝቶአል
ተኝቷል የሚለው ፈሊጠእ አልአዛር ሞቶአል። በናንተ ቋነቋ አባባል ካለ መጠቀም ትችላላችሁ

ከእንቅልፉ ላስነሳው ወደዛ ሄዳለሁ
ከእንቅልፉ ላስነሳው እየሱሰ አልአዛርን ወደህይወት እንደሚመልሰው እቅዱን እያሳየ ነው። ናንተ ቋነቋ አባባል ካለ መጠቀም ትችላላችሁ

John 11:12

አጠቃላይ መግለጫ
በቁጥር 13 ላየ ዮሃንስ ለደቀመዛሙርቱ እየሱስ ስለ አላዛር ማንቀላፋት የተናገረውነ እንዳልገባቸው

አንቀላፍቶ እንደሆነ
ደቀመዛሙርቱ እየሱስ ያለው አልገባቸውምና የመሰላቸው አልአዛር እርፍተ እያረገ ነው ይሻለዋልም

ቀጥሎም እያሱሰ በግልጽ እንዲህ አላቸው
እንዲገባቸው እየሱሰ ቃል በቃል ነገራቸው

John 11:15

አያያዥ መግለጫ
እየሱስም ደቀመዛሙርቱን ማናገር ቀጠለ

ስለ እናንተ
ለጥቅማችሁ

እንድታምኑም በዛ አልነበርኩም
በዚያ አልነበርኩም። ስለዚህም ምክንያት በኔ ታምናላችሁ

ዲዲሞስ የሚባለውም
ይህንን በገባ መልኩ መተርጎም ይችላሉ። አት: - "ዲዲሞስ ብለው የጠሩት"

ዲዲሞስ
የወንድ ስም መንታ ማለት ነው

John 11:17

አጠቃላይ መግለጫ
ኤየሱስም በቢታንያ ነው። ይህ ቁጥር ከኃላ ያለውነ መረጃና እየሱስ ከመምጣቱ በፊት ያለውን ይገለጻል

አልአዛርም በመቃብር አራት ቀን ቆይቷል
ይህንን ኣሁን እንደሆነ መተርጎም ትችላላችሁ። የአልኣዘርን አስክሬን ከ4 ቀን በፈት በመቃብር እነዳኖሩት አወቀ፡

አስራ አምስት ምእራፍ ያህል
ሶስት ኪሊሜትር ይርቃል። ስታዲየም 185 ሜትር ነው

ስለ ወንድማቸው።
አልአዛር ታናሽ ወንድማቸው ነው። ሶስተኛ ወንድማቸው።

John 11:21

ወንድሜ ባልሞተም ነበር
አልአዛር ታናሽ ወንድም ነው። የኔ ታናሽ ወንድም በህይወት ይኖር ነበር

ወንድምሽ ይነሳል
አልአዛር ታናሽ ወንድም ነው። ያንቺ ታናሽ ወንድምሽ አሁን ይነሳል።

John 11:24

እንደገና ይነሳል
እንደገና በሕይወት ይኖራል

ቢሞትም እንኳን
ሞት የሚያመለክተው ስጋ ሞትን ነው

ይኖራል
ይኖራል የሚለው መንፈሳዊ ሕይወትን ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በእኔ ብታምኑ ሞትን አትሞቱም በህይወት ትኖራላችሁ
በእኔ የሚያምኑ ሁሉ በመንፈስ ከእግዚአብሄር አይለያዩም ወይም በእኔ የሚያምኑ በመንፈስ ከእግዚአብሄር ጋር ለዘላለም ይኖራሉ

አይሞቱም
ሞት የሚያመለክተው መንፈሳዊ ሞትን ነው

John 11:27

እሷም ለሱ አለች
ማርታ ለእየሱስ አለች

አዎን፤ ጌታ ሆይ አንተ ክርስቶስ ወደ አለም የሚመጣው ክርስቶስ የዐግዚአብሄር ልጅ እንደሆንክ አምናለሁ
ማርታም እየሱስ ጌታ የእግዚአብሄር ልጅ መሲሁ እንደሆነ ኣመነች

የእግዚአብሄር ልጅ
ይህ ለእየሱስ አሰፈላጊ ርዕስ ነው

እህቷን ሜሪን ለመጥራት ሄደች
ሜሪ የማርታ ታናሽ እህት ናት። ሄዳም ታናሽ እህቷን ሜሪን ጠራቻት።

መምህር
ይህ ርእሰ እየሱሰስን ያመለክታል

ይጠራሽ ነበር
እንቺ እንድትመጪ ጠየቀ

John 11:30

እየሱስ በመንደሩ ገና አልደረሰም ነበር
ዮሀንስ በዚህ ክፍል ታሪኩን ኣቋርጦ እየሱስ ያለበትን አካባቢ መግለጫ ሰጠ

በእግሩ ላይ ወደቀች
ሜሪ ክብር ለመስጠት በእየሱሰ እግር ላይ ወደቀች

ወንድሜ ባልሞተም ነበር
አልአዛር የሜሪ ታናሽ ወንድሟ ነበር። ታናሽ ወንድሜ በህይወት ይኖረ ነበር።

John 11:33

በመንፈሱ ኣዘነ በራሱም ታወከ
ዮሀንስ በዚህ ክፍል የእየሱስነን መታወክ መረበሽ ማዘን ይገልጻል። በጣም ተረብሾ ነበር።

እየሱስ አለቀሰ
እየሱስ ማለቀስ ጀመረ ወይም እየሱስ አለቀሰ።

ወዴት አኖራችሁት
ይህ የተለሳለሰ ጥያቄ ነው። የት ቀበራችሁት?

John 11:36

ፍቅር
ይህ ወንድማዊ ፍቅር ወይም የስ ው ፍቅር ለጓደኛ ወይም ለቤተሰብ አባል

ይህ የእውሩን ዓይን የከፈተ አይደለምን ይንንም እንዳይሞት ባደረገ ነበር
ይህ ኣስተያየት እንደጥያቄ ያቀረቡት አይሁዶች እንዴት እየሱሰ አለአዛርን አለዳነውም ለማለት ነው። እውርን ያድናል ያበራል አልአዛርንም እነዳይሞት ሊያድነው በቻለ ነበር። ይህንን ሰው ከሞት ስላላዳለነው እውር ሆኖ የተወለደውንም አላዳነወም አዳነው ኣሉተ እንጂ

አይኑን ከፈተ
ይህ አባባል ነው። ዐይኑን አዳነው።

John 11:38

ዋሻ ነበር ድንጋይም ተገጥሞበት ነበር
ዮሀንስ ትንሽ ታሪኩን ኣቋርጦ አልኣዛርን የት እንደ ቀበሩት አስረዳ

ማርታ የአልአዛር እህት
ማርታና ሜሪ የ አልአዛር ታላቀ እህቶች ናቸው። ማርታ የ አልአዛር ታለቅ እህት

በዚህ ግዜ አስከሬኑ ይሸታል
በዚህ ግዜ መጥፎ ሽታ ይኖራል ወይም አስከሬኑ መሸተት ጀምሮአል።

ብታምኚስ የእግዚአብሄርን ክብር እንድታዪ አልነገርኩሽምን
ይህ አባባል በጥያቄ መልክ የሆነው እግዚአብሄር ቀጥሎ አስደናቂ ስራ ሊሰራ ስለሆን አጽንኦት ለመስጠት ነው። በኔ ብታምኚ የእግዚአብሄርን ስራ እንድታዪ ነግሪሽ ነበር

John 11:41

እየሱስም አይኖቹን ወደ ላይ ኣነሳ
ይህ ወደላይ ማየትን ያመለክታል።እየሱስ ወደ መንግሰተሰማያት ተመለከተ

አባ ስለሰማኀኝ ኣመሰግንሀለሁ
እየሱሰ ቀጥታ ወደአባቱ መጸለዩ በአጠገቡ የነበሩት ጸሎቱን እንዲሰሙ ነው። አባ ስለሰማኀኝ ኣመሰግንሀለሁ። ወይም አባ ጸሎቴን ስለሰማህ አመሰግንሀሉ።

አባ
ይህ ለእግዚአብሄር አስፈላጊ ርእሰ ነው።

አንተ እንደላከኝ ያምኑ ዘንድ
አንተ እንደላከኝ እንዲያምኑ ጸለግሁ።

John 11:43

ይህን ከለ በሁዋላ
ዕየሱስ ከጸለየም በሁዋላ

በትልቅ ድመጽ ጮኀ
ጮኀ

እጅና እግሮቹ ተገንዘው ነበር ፊቱም በጨርቅ ተሸፍኖ ነበር
በዚያን ግዜ ባህሉ የሞተን ሰው በረዥም ጨርቅ ይጠቀለል ነበር።

እየሱስም ለእነሱ አላቸው
እነሱ የሚለው በዚያ ተሰብስበው ለነበሩና ታምራቱን ላዩት

John 11:45

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ቁጥሮች ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት ካስነሳ በኋላ ምን እንደ ሆነ ይነግሩናል።

John 11:47

ጠቅላላ መግለጫ
ይህ የሚቀጥለው ክፍል ታሪክ ነው። የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን በአይሁድ ሸነጎ ተሰበሰቡ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የካህናት አለቆቻም
ከቀሳወስቱ መካከል መሪዎቹም

ምን እናድርግ?
የሸንጎው መሪዎችም ስለ እየሱስ እንደሚያወሩ የሳያል። ስለ እየሱስ ምን ማድረግ እንችላለን።

ሁሉም በርሱ ያምናሉ
የአይሁድ መሪዎችም ህዝቡ እየሱስነ ንጉሳቸው ያደርጉታል በለው ፈሩ። ሁሉም በርሱ ካመኑ በሮም ላይ ያምጻሉ።

ሮማዊያንም ይመጣሉ
የሮም ጦር ሰራዊት የሮም ጦር ሰራዊት ይመጣሉ

ቦታችንን እና ህዝባችንን ይወስዳሉ
ቤተ መቅደሳችንን እና ህእባችንን ያፈረሳሉ

John 11:49

ከነሱ መካከል አንዱ
አዲስ ሀሳብን ለማስተዋወቅ መንገዱ ይህ ነው። በራስህ ቋነቋ መግለጽ መንገድ ካለህ መጠቀም ትችላለህ።

ምንም አታውቁም
ቀያፋም እያጋነነ ለመናገር ነው እንደዛ ያለው። እየሆነ ያለውን ነገር አልገባችሁም። የምትናገሩት ምንም እንደማያውቅ ሆናችሁ ነው።

ህዝቡ ሁሉ ከሚጠፋ
ቀያፋ ማለት የፈለገው እየሱስ እንዲኖር ከተፈቀደ የሮም ጦር ሰራዊት የእስራኤልን ህዝብ ይገላሉ። ህዝብ የሚለው የሚያመለክተው እስራኤልን ህዝብ ነው።ሮማውያን ህዝባችንን ሁሉ ከሚገሉ

John 11:51

ጠቅላላ መግለጫ
በቁጥር 51 እና 52 ኬፋ ባያውቀውም ትንቢትን እየተናገረ ነበር። ይህ ለሚቀጥለው መግለጫ ነው።

ለህዝቡ ይሞታል
ህዝብ የሚለው የሚያመለክተው የእስራኤልን ህዝብ ነው

ሁሉም በአንድነት ይሰበሰባሉ
ይህ ኤሊፕሲስ ነው። “ሰዎች” የሚለው ቃል በጥቅሱ አውድ ተተክቷል ። አት: - “ወደ አንድ ህዝብ ይሰበሰባሉ”

የእግዚአብሄር ልጆች
ይህ የእግዚአብሄር የሆኑ ህዝቦችን በክርስቶስ ያመኑት በመንፈስ የዕግዚአብሄር ልጆች የሆኑ

John 11:54

ጠቅላላ መግለጫ
እየሱስም ከቢጣንያ ኤፍሪም ወደ ምትባል መንደር ሄደ። በቁጥር 55 ላይ የፋሲካ በዓል ደርሶ ስለነበር አይሁዶች ምን እንደሚሰሩ ይነግረናል።

በአይሁዶች መካከልም በግልጽ ይመላለሰል
አይሁድ የሚለው የአይሁድ መሪዎችን ነው። በሚቃወሙተ አይሁዶች መካከል በግልጽ ይመላለሳል

ሀገሩ
ከከተማ ወጣ ያለ ጥቂት ህዝብ የሚኖሩበት

በዚያ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ቆየ
እየሱሰስና ደቀመዛሙርቱ ለጥቂት ጊዝ በኤፍሬም ቆዩ። በዚያ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ለጥቂት ጊዜ ቆየ

ወደ እየሩሳሌም ወጣ
ወጣ የሚለው ኢየሩሳለምን ከአካባቢው ካሉ ከተሞች ከፍታ ላይ መሆኗን ለማመልከት ነው

John 11:56

ጠቅላላ መግለጫ
በቁጥር 57 ላይ የሆነው የተጻፈው ከቁጥር 56 በፊት ነው። ቅደም ተከተሉ አንባቢዎችን የሚያደናግር ከሆነ ቁጥሮቹን ማዋሀድ እና የ 57 ጽሁፍ ከ 56 በፊት ማድረግ ተችላለህ።

እየሱስንም ይፈለጉ ነበር
እነዱ የሚለው ቃል ወደ የሩሳሌም የተጓዙትን አይሁዶች ለማመልከት ነው

ምን ታስባለህ? ወደ በዓሉ አየመጣምን?
ይህ የተሀድሶ ጥያቄ የሚገልጸው እየሱሰ ወደ ፋሲካ በዓል መምጣቱን በመጠራጠር ነበር። ሁለተኛው ጥያቄ ታስባለህን ተናጋሪው እየሱሰ ወደ በአሉ ቢመጣ የመታሰር እድሉ ከፍተኛ ስለሆን ይገረም ነበር። እየሱስ ምናልባት ወደ በዓሉ አይመጣም። እታሰራለሁ ብሎ ይፈራል።

መረ ካህኑም
ይህ መግለጫ የሚያስረዳው የአይሁደ አምላኪዎች እየሱስ በበዓሉ ለመገኛት ይመጣ ይሆን ብለው መገረም ነበረባቸው። በቋነቋህ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 12

1 የፋሲካ በዓል ሊከበር ስድስት ቀናት ሲቀሩት ኢየሱስ ከሞት ያስነሣው አልዓዛር ወደ ነበረበት ወደ ቢታንያ መጣ። 2 ስለዚህ በዚያ እራት አዘጋጁለት፣ አልዓዛር
ከኢየሱስ ጋር በማዕድ ከተቀመጡት ጋር ሲሆን ማርታ ደግሞ ታገለግላቸው ነበር። 3 ማርያም ከንጹሕ ናርዶስ የተሠራ በጣም ውድ የሽቱ ብልቃጥ ወስዳ
የኢየሱስን እግር ትቀባ፣ በፀጉሩዋም ታብስ ስለነበር፣ ቤቱ በሽቱው መዓዛ ታወደ። 4 ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ ኢየሱስን አሳልፎ የሚሰጠው የአስቆሮቱ ይሁዳ፣ 5
“ይህ ሽቱ በሦስት መቶ ዲናር ተሸጦ ለድሆች ያልተሰጠው ለምንድን ነው?” አለ። 6 ይህን ያለው ለድሆች ተገዶላቸው ሳይሆን ሌባ ስለነበረ ነው፤ የገንዘብ
ከረጢቱን የሚይዘው እርሱ ስለነበረ፣ ከዚያ ውስጥ ለራሱ ጥቂት ይወስድ ነበር። 7 ኢየሱስ፣ “የያዘችውን ለቀብሬ ቀን እንድታቆየው ፍቀዱላት፤ 8 ድሆች
ምንጊዜም ከእናንተ ጋር ይሆናሉ፣ እኔን ግን ሁልጊዜ አታገኙኝም” አላቸው። 9 ብዙ የአይሁድ ሕዝብም ኢየሱስ በዚያ እንደነበረ ተረድተው ነበርና ወደዚያ መጡ፣
የመጡትም ለኢየሱስ ብቻ ብለው ሳይሆን ኢየሱስ ከሞት ያስነሣውን አልዓዛርንም ለማየት ጭምር ነበር። 10 የካህናት አለቆች አልዓዛርን ደግሞ ለመግደል
በአንድነት የተንኮል ስምምነት አደረጉ፣ 11 ምክንያቱም ብዙ አይሁድ የሄዱትና በኢየሱስ ያመኑት ከእርሱ የተነሣ ነበር። 12 በማግስቱ ብዙ ሕዝብ ወደ በዓሉ
መጡ። ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም መምጣቱን በሰሙ ጊዜ፣ 13 የዘንባባ ዛፍ ዝንጣፊ ይዘው፣ “ሆሣዕና! በጌታ ስም የሚመጣ የእስራኤል ንጉሥ የተባረከ ነው”
እያሉ ሊቀበሉት ወጡ። 14 ኢየሱስ የአህያ ውርንጫ አገኘና ተቀመጠባት፣ ይህንን ያደረገው፣ 15 “የጽዮን ልጅ ሆይ፣ አትፍሪ፣ እነሆ፣ ንጉሥሽ በአህያ ውርንጫ
ላይ ተቀምጦ ይመጣል” ተብሎ በተጻፈው መሠረት ነው። 16 ደቀ መዛሙርቱ በመጀመሪያ ይህን አልተረዱም ነበር፣ ኢየሱስ በከበረ ጊዜ ግን እነዚህ ነገሮች
ስለ እርሱ ተጽፈው እንደነበረና እነርሱም እነዚህን ነገሮች ለእርሱ እንዳደረጉለት ተገነዘቡ። 17 ኢየሱስ አልዓዛርን ከመቃብር በጠራውና ከሞት ባስነሣው ጊዜ
በዚያ የነበሩት ሕዝብም ለሌሎች መሰከሩላቸው። 18 ይህን ምልክት እንዳደረገ ሰምተው ነበርና ሊቀበሉት የወጡትም በዚህ ምክንያት ነበር። 19 ስለዚህ
ፈሪሳውያን እርስ በርሳቸው፣ “ምንም ማድረግ እንደማትችሉ ተመልከቱ፣ ዓለሙ ተከትሎታል” ተባባሉ። 20 በበዓሉ ሊያመልኩ ከሄዱት መካከል አንዳንድ
የግሪክ ሰዎችም ነበሩ። 21 እነዚህ በገሊላ ካለችው ከቤተሳይዳ ወደ ሆነው ወደ ፊልጶስ ዘንድ ሄደው፣ “ጌታ ሆይ፣ ኢየሱስን ማየት እንፈልጋለን” አሉት። 22
ፊልጶስ ሄዶ ለእንድርያስ ነገረው፣ እንድርያስና ፊልጶስም ዐብረው ሄዱና ለኢየሱስ ነገሩት። 23 ኢየሱስም፣ “የሰው ልጅ የሚከብርበት ሰዓት ደርሷል፤ 24 እውነት፣
እውነት እላችኋለሁ፣ የስንዴ ዘር ወደ ምድር ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች፤ ከሞተች ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች።” ብሎ መለሰላቸው። 25 ሕይወቱን የሚወድ
ያጠፋታል፤ ነገር ግን በዚህ ዓለም እያለ ሕይወቱን የሚጠላ ለዘላለም ሕይወት እንድትጠበቅ ያደርጋታል። 26 ማንም ሊያገለግለኝ የሚወድ ይከተለኝ፤ እኔ
ባለሁበት አገልጋዬም በዚያ ይሆናል። ማንም ቢያገለግለኝ አብ ያከብረዋል። 27 አሁን ነፍሴ ታውካለች ምን እላለሁ? 'አባት ሆይ፣ ከዚህ ሰዓት አድነኝ' ነገር ግን
ስለዚህ ጉዳይ ወደዚህ ሰዓት መጥቻለሁ። 28 አባት ሆይ፣ ስምህን አክብረው።» ከዚያም ከሰማይ፣ «አክብሬዋለሁ ደግሞም አከብረዋለሁ» የሚል ድምፅ
መጣ።። 29 ባጠገቡ ቆመው የነበሩትና ድምፁን የሰሙት ብዙ ሕዝብ ነጐድጓድ መሰላቸው። ሌሎች ደግሞ «መልአክ ተናግሮታል» አሉ። 30 ኢየሱስ መልሶ፣
«ይህ ድምፅ የመጣው ስለ እኔ ሳይሆን ስለ እናንተ ነው» አለ። 31 በዚህ ዓለም ላይ የሚፈረድበት ጊዜ አሁን ነው፤ አሁን የዚህ ዓለም ገዢ ወደ ውጭ
ይጣላል። 32 እኔ ከምድር ከፍ ከፍ በምልበት ጊዜ፣ ሰውን ሁሉ ወደ ራሴ እስባለሁ።» 33 ይህን የተናገረው በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሚሞት ለማመልከት
ነበር። 34 ሕዝቡ፣ «ክርስቶስ ለዘላለም እንደሚኖር ከሕጉ ሰምተናል። ታዲያ 'የሰው ልጅ ከፍ ከፍ ማለት አለበት እንዴት ትላለህ?' ይህስ የሰው ልጅ ማን ነው?»
ብለው መለሱለት። 35 ከዚያም ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፤ «አሁን ለጥቂት ጊዜ ብርሃን በመካከላችሁ አለ፤ ጨለማ እንዳይውጣችሁ በዚህ ብርሃን ተመላለሱ።
በጨለማ የሚመላለስም ወዴት እንደሚሄድ አያውቅም። 36 የብርሃን ልጆች እንድትሆኑ ብርሃኑ እያለላችሁ በብርሃኑ እመኑ።» ኢየሱስ ይህን ከተናገረ በኋላ
ከእነርሱ ተለየ፤ ተሰወረባቸውም። 37 ምንም እንኳ ኢየሱስ በሕዝቡ ፊት ብዙ ምልክቶችን ቢያደርግም በእርሱ አላመኑም። 38 ይህም ነቢዩ ኢሳይያስ፣ «ጌታ ሆይ
የተናገርነውን ማን አመነ? የጌታስ ክንድ ለማን ተገለጠ?» በማለት የተናገረው ቃል እንዲፈጸም ነው። 39 በዚህም ምክንያት ማመን አልቻሉም፤ ኢሳይያስ እንደ
ገና እንዲህ ብሏልና፤ 40 «ዐይኖቻቸውን አሳውሯል፤ ልባቸውንም አደንድኗል፤ ይህም የሆነው በዐይናቸው ዐይተው በልባቸው አስተውለውና ተመልሰው
እንዳልፈውሳቸው ነው።» 41 ኢሳይያስ እነዚህን ነገሮች የተናገረው የኢየሱስን ክብር ስላየና ስለ እርሱም ስለ ተናገረ ነው፤ 42 የሆነ ሆኖ ከገዢዎች እንኳ
ብዙዎች በኢየሱስ አምነዋል፤ ነገር ግን ፈሪሳውያን ከምኩራብ እንዳያግዷቸው በመፍራት ማመናቸውን አልገለጹም። 43 በእግዚአብሔር ከመመስገን ይልቅ
በሰዎች ለመመስገን ወደዱ። 44 ኢየሱስ ድምፁን ከፍ አድርጎ እንዲህ አለ፤ «በእኔ የሚያምን በእኔ ብቻ የሚያምን ሳይሆን በላከኝም ያምናል፤ 45 እንደዚሁም
እኔን የሚያይ የላከኝንም ያያል። 46 በእኔ የሚያምን በጨለማ ውስጥ እንዳይኖር ብርሃን ሆኜ ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤ 47 ማንም ቃሌን ሰምቶ ባያደርገው
የምፈርድበት እኔ አይደለሁም፤ ዓለምን ለማዳን እንጂ በዓለም ላይ ልፈርድ አልመጣሁምና። 48 እኔን የሚቃወምና ቃሌንም የማይቀበል የሚፈርድበት አለ፤
በመጨረሻው ቀን የሚፈርድበት እኔ የተናገርሁት ቃል ነው። 49 ምክንያቱም ይህ ቃል ከራሴ የተናገርሁት አይደለም፤ ይልቁን ምን እንደምልና እንደምናገር ትእዛዝ
የሰጠኝ የላከኝ አብ ነው። 50 ትእዛዙም የዘላለም ሕይወት እንደሚያስገኝ አውቃለሁ፤ ስለዚህ የምናገረው ቃል አብ እንደ ነገረኝ የምናገረው ነው።»

John 12:1

አጠቃላይ መግለጫ
ይህ የሚቀጥለው ታሪ ክፍል ነው። እየሱስ በቢታንያ በእራት ላይ ሳለ ሜሪ እግሮቹን በዘይት ቀባችው

ለትራ
የክብደት መለኪያ ነው። የአንድ ኪሎ ግራም አንድ ሶሰተኛ ነው።

ሽቶ
ጥሩ መአዛ ያለው ፈሰሽ ሲሆን ትሩ ሽታ ካላቸው አትክልቶች ዘይት የሚሰራ ነው።

ናርድ
የደወል ቅርጽ ካለው አበባ የሚሰራ ሽቶ ሲሆን የሚገኘውም ኔፓል ቻይና ህንድ ተራራዎች ላይ ነው

ቤቱ በሽቶው መአዛ ተሞላ
ይህ ኣሁን እነደተደረገ መተርጎም ይቻላል። የሽቶው መአዛ ወይም ሽታወ ቤቱን ሞላው።

John 12:4

አሳልፎ የሚሰጠው
የእየሱሰ ጠላቶች እንዲይዙት ያደረገው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለሶስት መተ ዲናር ተሸጦ ለድሆች ያልተሰጠ ለምን ነው?
ጥያቄያዊ አነጋገር ነው። እንደ ከባድ አረፍተነገር መተርጎም ተችላለህ። ይህ ሽቶ ለሶስተ ሞተ ዲናር ተሸጦ ገንዘቡን ለድሆች መስጠት ይቻል ነበር።

ሶስተ መቶ ዲናር
በቁጥርም መተርጎም ትችላለህ። 300 ዲናር

እንዲህም አለ ወደ ውስጥ ከሚጣለው ይሰርቅ ስለነበር ነው
ዮሀንስ ይሁዳ ስለምን ስለድሆች እንደጠየቀ ያስረደዳል። በቋንቋህ በተሻለ ማስረዳት ከቻልክ መጠቀም ትችላለህ።

ይህን ያለው ለድሆች ስለሚያዝነ አይደለም ግነ ሌባ ስለነበረ ነው
ይህነ ያለው ሌባ ስለነበረ ነው። ስለድሆች ግድ አልነበረውም።

John 12:7

ያላትን ለምቀበርበት እንድታስቀምጠው ተዉአት
እሷ ያረገችው ለሞቱ እና ለቀብሩ ምን ያህል እንዳደነቀችኝ እንድታሳይ ተዉአት! በዚህ መንገድ ሰውነቴን ለቀብር አዘጋጅታለች

ድሆች ሁሌም ከናንተ ጋር ናቸው
ዕየሱስ ይህንን ማለቱ ድሆችን ለመርዳት ብዙ ኣጋጣሚዎች አሉ። ድሆች ሁሌም በመካከላቸሁ አሉ፤ በፈለጋችሁ ግዜ ልትረዱአቸው ተችላላችሁ

እኔን ግነ ሁሌ አታገኙኝም
ይህን ማለቱም እንደሚሞት ለመንገር ነው። እኔ ግን ሁሌም ከናንተ ጋር እዚህ የለሁም።

John 12:9

አሁን
ይህን ቃል የተጠቀመው ከዋናው ታሪክ ለማረፍ ነው ዮሃነስ አዲስ ሰዎች ከቢታኒያ ወደ እየሩሳለም አንድ መጡ ለመንገር ነው።

በሱ ምክንያት
የአላአዛር ከሞት መነሳት ብዙ አይሁዶች እንዲያምኑ ሆነ

በእየሱስ ኣመኑ
ይህ የሚያመለክተው ብዙ አይሁዶች እየሱስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ኣመኑ። እምነታቸውነ በእየሱስ ላይ ጣሉ።

John 12:12

ጠቅላላ መግለጫ
ይህ የሚቀጥለው ታረክ ክፍለ ነው። እየሱስ ወደ እየሩሳለም ገበ ህዝቡም እንደ ንጉስ አከበሩት

ብዙ ህዝብ
ብዙ ህዝብ ሰብስብ

ሆሳእና
ይህ ማለት እግዚአብሄር አሁን ያድነን

የተባረኩ
ይህ የእግዚአብሄርን መልካም ፍላጎት ለሰው ያለውነ ያሳያል

በእግዚአብሄር ስም የሚመጣ
እዘህ ስም የሚለው የሚያመለክተው በስልጣንና በኃይል ነው። በእግዚአብሄር የተወከለ ወይም በእግዚአብሄር ኃይል የመጣ

John 12:14

እየሱስም የአህያ ውርንጫ ኣግኝቶ ተቀመጠባት
ዮሃነሰ እየሱስ አህያዋን እንዴት እንዳገኘ ያስረዳል። በአህያ ውርንጫ ተቀምጦ ወደ እየሩሳሌም እንደሚገባ ያስረዳል። የአህያ ውርነጫ አገኘ ተቀመጠባትም ወደ ከተማውም ገባ

እንደተጻፈው
አሁን እንደተደረገ ኣድርገህ መተርጎም ተችላለህ። ነቢዩ እንደጻፈው

የጽዮን ልጅ
የጽዮን ልጅ የሚያመለክተው የእስራኤልን ህዝብ ነው

John 12:16

ጠቅላላ መግለጫ
ዮሀንስ ጸሀፊው እዚህ ላእ ኣቋርጦ ደቀመዛሙርቱ ቆይተው የገባቸውን ነገር መግለጫ ይሰጣል

ደቀመዛሙርቱ ይህ ነገር አልገባቸውም
ይህን ነገር የሚለው ነቢያቶች ስለ እየሱስ የጻፉትን ለማለት ነው

ኢየሱስም ሲከብር
አሁን እንደተደረገ መተርጎም ቲችላለህ። ዕግዚአብሄር እየሱስነ ሲያከብረው

ይህንንም ኣደረጉለት
ይህንን ነገር የሚለው የሚያመለክተው እየሱስ በአህያ ውርንጫ ተቀምጦ ወደ እየሩሳለምነ ሲገባ እያወደሱት ዘንባባ ዝንጣፊ ያወዛውዜ ነበር

John 12:17

አሁን
ይህ ቃል ትረካውን ቆም ለማድረግ ነው። ዮሃንስ እዚህ የሚያስረዳወው ብዙ ህዘብ የመጣው አልአዛርነ ከሞት እንዳስነሳው ስለሰሙ ነው።

ምልክቶችንም ያደርግ እንደነበር ሰሙ
ለሎች ብዙ ምልክቶችን እንዳደረገ ሲያወሩ ሰሙ

ተመልከቱ ምንም ማድረግ አትችሉም
ፈሪሳውያኑም ኢየሱስን ማቆም እንደማይቻል አሰቡ። እሱን ለማቆም ምንም ማድረግ አንችልም እንደማለት ይመስላል

ተመልከቱ አለም በሙሉ ተከትሎታል
ፈሪሳውያኑ እየሱስን ብዙ ሰው እነደተከተሉት ባዩ ግዜ ፍርሀት ውስጥ ስለነበሩ ዕያጋነኑ ገለጹ። ሁሉም የርሱ ደቀመዝሙር የሆነ ይመስላል።

አለም
አለም የሚለው ለማጋነን የተጠቀሙበት የዓለም ህዝብ ሁሉ

John 12:20

የተወሰኑ ግሪኮች
የተወሰኑ የሚለው አዲሰ ገጸ ባህሪን ለማስተዋወቀ ነው

በበዓሉ ለማምለክ
ዮሀንስ ግሪኮች በፋሲካ በዓል እግዚአብሄርን ለማምለክ ይሄዱ ነበር።እግዚአብሄርነ በፋሲካ በዓል ለማክበር።

በተሳይዳ
በገሊላ ውስጥ ያለች ከተማ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለዕየሱስም ነገሩት
ፊሊፖስና እንድርያስ የግሪክ ሰዎች ሊያዩት እንደሚፈልጉ ነገሩት። ግሪኮችም ምን እነዳሉት ነገሩት።

John 12:23

ጠቅላላ መግለጫ
እየሱስም ለፊሊፖስና እንድርያስ መለሰላቸው

የሰው ልጅ ይከብር ዘንድ ሰዓቱ ደርሶዓል
እየሱስ ይህን ያለው እግዚአብሄር ልጁን በስቃይ በሞት እና ከሞት በማስነሳት የሚከብርበት ሰዓት ትክክለኛው ሰዓት እንደደረሰ ለማስረዳት ነው

እውነት አውነት እላችኃለሁ
የሚከተለው የሚከተለው አስፈላጊ እና እውነት መሆኑን በቋንቋዎ አፅን emphasiት በመስጠት ይህንን ይተረጉሙ ። በ 1 49 ውስጥ “በእውነት ፣ በእውነት” እንዴት እንደተረጉሙ ይመልከቱ ።

የስንዴ ቅንጣት በምድር ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች
እዚህ “የስንዴ እህል” ወይም “ዘር” ለኢየሱስ ሞት ፣ የቀብር እና የትንሳኤ ምሳሌ ነው። አንድ ዘር እንደተተከለ እና ብዙ ፍሬ ወደሚያፈራ ተክል እንደገና እንደሚበቅል ፣ እንዲሁ ከሞተ ፣ ከተቀበረ እና ከሞት ከተነሳ በኋላ ብዙ ሰዎች በኢየሱስ ያምናሉ።

John 12:25

ነፍሱን የሚወድ ያጠፋታል
ህይወቱን የሚወድ የሚያመለክተው የራስን ህይወት ከሌላው ህይወት አስበልጦ ማየት። የራሱን ህይወት ከሌላው አስበልጦ የሚያየእ የዘላለም ህይወት አይቀበልም

ነፍሱን በዚህ ዓለም የሚጠላ ለዘላለም ሕይወት ይጠብቃታል
እዚህ ላይ “ሕይወቱን የሚጠላ” የሚያመለክተው የሌሎችን ሕይወት ከሚወድደው በታች የሆነውን የራሱን ሕይወት የሚወድ ነው ። አት: - “የሌሎችን ሕይወት ከራሱ የበለጠ አስፈላጊ እንደሆነ አድርጎ የሚቆጥር ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ለዘላለም ይኖራል” (ይመልከቱ። የበለስ_ቁጥር)

እኔ ባለሁበት አገልጋዬ በዚያ ይኖራል
እየሱስ እኔን የሚያገለግል ሁሉ ከርሱ ጋር በገነት ይኖራሉ ማለቱ ነው። እኔ በገነት ስሆን አገልጋዮቹ=ቼም በገነት ከኔ ጋር ይሆናሉ

አባቱም ያከብረዋል
አባት የሚለው ለእግዚአብሄር አስፈላጊ ነው

John 12:27

ምንስ እላለሁ? አባት ሆ ከዚህ ሰዓት ኣድነኝ
ይህ አስተያየት እንደ ንግግራዊ ጥያቄ ነው። እየሱሰ ስቅለቱ እንዲያልፍለት ቢመኝም ለአባቱ ታዛዥ መሆንን መርጦ ለመሞት ወሰነ ከዚህ ሰዓት ኣድነኝ ብዬ አልጸልይም

አባት
ይህ ለእግዚአብሄር አስፈላጊ ርእሰ ነው

ሰዓቱ
ሰዓቱ የሚለው እየሱሰ በመስቀል ተሰቃይቶ የሚሞትበትነ ነው የሚያመለክተው

ሰምህን አክብረው
ስም የሚለው እግዚአብሄርን ነው የሚገልጸው። ክብርህ ይታይ ወይም ክብርህ ይገለጽ

ድምጽ ከሰማይ መጣ
የእግዚአብሄርን ነግግር ይወክላል። አንዳንድ ግዜ ሰዎች ወደ እግዚአብሄር ማመለክት ይፈራሉ ስለሚያከብሩት። እግዚአብሄር ከሰማይ ተናገረ

John 12:30

ጠቅላላ መግለጫ
ድምጽ ከሰማይ ለምን እንደመጣ እየሱስ ኣስረዳ

አሁን የዚህ አለም ፍርደ ደደርሶአል
ዐለም የሚለው በጠቅላላ የአለምን ሕዝብን ያመለክታል እግዚአብሄር በሰው ልጆች ላይ ሊፈርድ ሰዓቱ ኣሁን ነው

የዚህ አለም ገዥ ወደ ውጭ ይጣላል
ገዢ የሚለው ሰይጣንን ያመለክታል። የዘህን አለም ገዢ ሰይጣንን የማፈርስበት ጊዜው ኣሁን ነው።

John 12:32

ጠቀላላ መግለጫ
በቁጥር 33 ላይ ዮሃነስ ወደ ላይ ከፍ ስለ ማለት እየሱስ የተናገረውን ይገልጻል

እኔም ከምድር ከፍ ያልሁ እነደሆነ
ስለ ስቅላቱ ነበር የሚለው። ሰዎች ወደ መስቀሉ ከፍ ሲያረጉኘ

ሁሉን ወደእኔ እስባለሁ
በስቅላቱ እየሱስ ለሁሉም እንዲያምኑተ መንገድን ያዘጋጃል

ይህንን ያለውም በምን ዓይነት ለሞት እነዳለ ሲያመለክት ነው
ዮሀንስ የእየሱስን ቃል ሲያብራራ ሰዎች እንደሚሰቅሉት ገለጸ። ይህንንም ያለው እንዴት እንደሚሞት ሰዎች እንዲያዊቁት ነው።

John 12:34

የሰው ልጅ ከፍ ሊል ይገባዋል
ከፍ ማለት መሰቀልን ያመለክታል። የሰው ልጅ በመስቀል ላይ ከፍ ሊል ወይም ለሰቀል ይገባዋል

ይህ የሰው ልጅ ማነው?
ትርጉሙ ሊሆን የሚችለው 1) ይህ የሰው ልጅ ማን ነው? 2) ስለ የትኛው የሰው ልጅ ነው የምታወሩት?

ለጥቂት ጊዜ ብርሀን ከናንተ ጋር ነው። ብርሃን ሳለ ተመላለሱ በጭለማም እንዳትዋጡ። በጭለማ የሚመላለስ ወዴት እንደሚሄድ አያውቅምና።
እዚህ “ብርሃን” የእግዚአብሔርን እውነት የሚገልጥ የኢየሱስ ትምህርቶች ዘይቤ ነው ። “በጨለማ ውስጥ መሄድ” ያለ እግዚአብሔር እውነት መኖርን የሚያሳይ ዘይቤ ነው። አት: - ቃሌ እግዚአብሔር እንደሚፈልግህ እንዴት እንደምኖር እንድትረዳ ቃሌ እንደ ብርሃንህ ብርሃን ነው ። እኔ ከአንተ ጋር ገና አልሆንም ። አሁንም እኔ ከአንተ ጋር እያለሁ መመሪያዎቼን መከተል አለብህ ። ቃሌን ፣ በጨለማ ውስጥ እንደ መጓዝ ይሆናል ፣ ወዴት እንደምትሄድም አታይም ። ”(ይመልከቱ ።

የብርሀን ልጆች እንድትሆኑ ብርሀን ሳለላችሁ በብርሀን እመኑ
“ብርሃን” የእግዚአብሔርን እውነት የሚገልጥ የኢየሱስ ትምህርቶች ዘይቤ ነው ። “የብርሃን ልጆች” የኢየሱስን መልእክት የሚቀበሉ እና በእግዚአብሔር እውነት ለሚኖሩ ሰዎች ምሳሌ ነው። AT: - “እኔ ከእናንተ ጋር ሳለሁ የእግዚአብሔር እውነት በእናንተ ውስጥ እንዲኖር ቃሌን ተቀበል” (የበለስ_ማይታፎርን ይመልከቱ)

John 12:37

ጠቅላላ መግለጫ
የሆንስ ታረኩን አቋርጦ በነቢዩ ኢሳያስ የተነገረውን ትንቢቱ እንደተፈጸመ ኣስረዳት ጀመረ

የነቢዩ የኢሳያስ ትንቢት የፈጸም ዘንድ
የነቢዩ የኢሳያስ ትንቢት የፈጸም ዘንደ

ጌታ ሆይ ምስክርነታችንን ማን ኣመነ? የእግዚአብሄርስ ክንድ ለማን ተገለጠ?
ይህ በጥያቄ መለክ የተጻፈው የነቢዩ ኢሳያስን መልእክት እንዳላመኑ ለመግለጽ ነው።

የእግዚአብሄር ክንድ
የእግዚአብሄርን የማዳን ክንድ ኃይል ለመግለጽ

John 12:39

ልባቸውንም ኣደነደነ
እግዚአብሄርም ልባቸውን ኣደነደነ። ግትር ኣደረጋቸው።

በልባቸውም ገባቸው
አይሁዶች ልብ እንዲገባን የሚያደርግ የሰውነት ክፍል ነው ብለው ያምናሉ

John 12:41

ማምለኪያ ቦታ እንዳይገቡ ዕንዳይከለከሉ
ሰዎች ወደ አይሁድ ማምለኪያ ቦታ እንዳይገቡ እነዳያደርጓቸው

ከእግዚአብሄር ከሚመጣው ክብር ይልቅ ከሰው የሚመጣውን ከብር ይወዱ ነበር
ዕግዚአብሄር ከሚያከብራቸው በይላ ሰዎች እንዲያከብሩዋቸው ይፈልጉ ነበር

John 12:44

ጠቅላላ መግለጫ
ዮሀናእስ ወደዋናው ትረካ ይመለሳል። ይህ በሌላ ግዜ እየሱስ ለህዘቡ ሲናገር ነው።

እየሱስም ጮሆ አለ
ብዙ ህዝበ ተሰብሰቦ እየሱስ ሲናገር ይሰሙ ነበር። እየሱስም ለተሰበሰበው ህዝብ ጮኸ

እኔን የሚያይ የላከኝንም ያያል
እሱ የሚለው እግዚአብሄርን ያመለክታል። እኔን ያየ የላከኝን እግዚአብሄርን ያያል።

John 12:46

አያያዥ መግለጫ
እየሱስም ለተሰበሰበው ህዝብ መናገሩን ቀጠለ

እንደ ብርሀን መጥቻለሁ
ብርሀን የሚለው የእየሱሰ ምሳሌ ነው። እውነትን ለማሳየት መጥቻለሁ።

በጭለማ ውስጥ አየኖርም
ጭለማ የዕግዚአብሄርን አውነት ኣቶ በድንቁርና መኖር። መንፈሳዊ እውር ሆኖ ላይቀጥል ይችላል።

ቃሌን ሰምቶ የማይጠብቅ ቢኖር አልፈርድበትም በአለም ልፈርድ ስላልመጣሁ ግን አለምነ ላድነ እንጂ
እዚህ “በዓለም ላይ መፍረድ” ማለት ኩነኔ ማለት ነው ። ኢየሱስ የመጣው ሰዎችን ለመኮነን አይደለም ። አት: - "ማንም ትምህርቴን ቢሰማና ቢቃወም አላውቀውም ፣ እኔ አላውቅም ። ሰዎችን ለመፍረድ አልመጣም ። ይልቁን በእኔ የሚታመኑትን ለማዳን ነው ።"

ዓለም
እዚህ “ዓለም” በዓለም ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ህዝብ የሚወክል ቃል ነው ። (ይመልከቱ: የበለስ_ጥበብ)

John 12:48

በመጨረሻውም ቀን
እግዚአብሄር በኃጢአተኞች ላይ ሲፈርድ

ተእዛዜ የዘላለም ሕይወት እንደሆነች
እንደናገር የሰጠኝ ትዕዛዛት ሁሉ የዘላለምን ሕይወት ይሰጣል።

አባት
ይህ የእግዚአብሔር አስፈላጊ መጠሪያ ነው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 13

1 በዚህ ጊዜ ኢየሱስ ከፋሲካ በዓል በፊት ከዚህ ዓለም ተለይቶ ወደ አብ የሚሄድበት ሰዓት እንደ ደረሰ ስላወቀ፣ ቀድሞውኑ የሚወዳቸውን በዓለም ይኖሩ
የነበሩትን የራሱን ወገኖች እስከ መጨረሻው ወደዳቸው። 2 ዲያብሎስም ኢየሱስን አሳልፎ እንዲሰጥ በስምዖን ልጅ በአስቆሮቱ ይሁዳ ልብ ክፉ ዐሳብ አስገባ።
3 ኢየሱስ አብ ሁሉን ነገር በእጁ አሳልፎ እንደ ሰጠው፣ ከእግዚአብሔር እንደ መጣ ወደ እግዚአብሔርም ተመልሶ እንደሚሄድ ዐወቀ፤ 4 ከእራት ላይ ተነሣ፤
መጎናጸፊያውንም አስቀመጠ፤ ከዚያም ፎጣ ወስዶ ወገቡ ላይ ከታጠቀ በኋላ 5 በሳሕን ውስጥ ውሃ ጨምሮ የደቀ መዛሙርቱን እግር ማጠብና በያዘውም
ፎጣ ማበስ ጀመረ። 6 ወደ ስምዖን ጴጥሮስ መጣ፤ ጴጥሮስም «ጌታ ሆይ የእኔን እግር ልታጥብ ነውን?» አለው 7 ኢየሱስም «የማደርገውን አሁን
አይገባህም፤ወደፊት ግን ትረዳዋለህ» በማለት መለሰለት 8 ጴጥሮስም «ፈጽሞ የእኔን እግር አታጥብም» አለው ኢየሱስም «እግርህን ካላጠብሁህ ከእኔ ጋር
ዕድል ፈንታ አይኖርህም» ሲል መለሰለት 9 ስምዖን ጴጥሮስም «ጌታ ሆይ እንግዲያስ እግሬን ብቻ ሳይሆን እጄንና ራሴንም እጠበኝ» አለው 10 ኢየሱስም
«ገላውን የታጠበ እግሩን ብቻ ከመታጠብ በስተቀር ሌላ ሰውነቱ ንጹህ ነው፤ እናንተ ንጹሓን ናችሁ ነገር ግን ይህን ስል ሁላችሁንም ማለቴ አይደለም» 11
ኢየሱስ «ሁላችሁም ንጹህ አይደላችሁም» ያለው ኣሳልፎ የሚሰጠው ማን እንደሆነ ያውቅ ስለነበረ ነው 12 ኢየሱስ እግራቸውን አጥቦ ከጨረሰ በኋላ ልብሱን
ለብሶ ተቀመጠ፤ እነርሱንም፣ «ያደረግሁላችሁን ልብ ብላችኋል? 13 'መምህር' እና 'ጌታ' ትሉኛላችሁ። እንደዚያም ስለሆንሁ አባባላችሁ ትክክል ነው። 14 እኔ
ጌታና መምህር ሆኜ እግራችሁን ካጠብሁ፣ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ልትተጣጠቡ ይገባል። 15 እኔ እንዳደረግሁላችሁ እንደዚያው ታደርጉ ዘንድ
ምሳሌ ትቼላችኋለሁ። 16 እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ አገልጋይ ከጌታው አይበልጥም ወይም የተላከ ሰው ከላኪው አይበልጥም። 17 እነዚህን ነገሮች
ብታውቁና ብታደርጓቸው የተባረካችሁ ናችሁ። 18 የምናገረው ሁላችሁን በሚመለከት አይደለም፤ የመረጥኋቸውን አውቃለሁና፣ ነገር ግን እንደዚህ የምናገረው
እንጀራዬን የበላ በእኔ ላይ ተረከዙን አነሣ የሚለው የመጽሐፉ ቃል እንዲፈጸም ነው። 19 ከመሆኑ በፊት አስቀድሜ የምነግራችሁ በሚፈጸምበት ጊዜ እኔ
እንደሆንሁ እንድታምኑ ነው። 20 እውነት እውነት እላችኋለሁ እኔን የሚቀበል የላክሁትን ይቀበላል፤ እኔን የተቀበለ ደግሞ የላክኝን ይቀባላል» 21 ኢየሱስ ይህን
በሚናገርበት ጊዜ በመንፈሱ ታወከ፤ «እውነት እውነት እላችኋለሁ ከእናንተ መካከል አንዱ አሳልፎ ይሰጠኛል» ብሎ በግልጽ ነገራቸው 22 ደቀ መዛሙርቱም
ስለማን እየተናገረ እንደሆነ ስላልገባቸው እርስ በርስ ተያዩ። 23 ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ የሆነው ኢየሱስ ይወደው የነበረው ደቀ መዝሙር ወደ ደረቱ ተጠግቶ
ተቀምጦ ነበር። 24 ስለዚህ ስምዖን ጴጥሮስ ወደዚህ ደቀ መዝሙር ጠጋ ብሎ «ንገረን ለመሆኑ ስለ ማን ነው እየተናገረ ያለው?» በማለት ጠየቀው። 25 ወደ
ኢየሱስ ደረት ተጠግቶ የተቀመጠው ደቀ መዝሙርም፣ «ጌታ ሆይ፣ ይህ የምትለው ሰው ማን ነው?» ብሎ ጠየቀው። 26 ከዚያም ኢየሱስ፣ «ይህን ቍራሽ
እንጀራ ከወጭቱ አጥቅሼ የምሰጠው ያ ሰው እርሱ ነው» በማለት መለሰለት። ስለዚህ ቍራሹን እንጀራ አጥቅሶ ለአስቆሮቱ ይሁዳ ሰጠው። 27 ቍራሹንም
እንጀራ ከተቀበለ በኋላ፣ ሰይጣን ገባበት። ከዚያም ኢየሱስ፣ «ለማድረግ ያሰብኸውን ፈጥነህ አድርግ» አለው። 28 ኢየሱስ ለይሁዳ እንደዚያ ለምን እንዳለው
በማዕድ ላይ ከተቀመጡት ማንም ያወቀ የለም። 29 አንዳንዶቹ ይሁዳ ገንዝብ ያዥ ስለ ነበር፣ ኢየሱስ «ለበዓሉ የሚያስፈልጉንን ነገሮች ግዛ» ወይም ለድኾች
ገንዘብ ስጥ ብሎ ነግሮታል ብለው ዐሰቡ። 30 ይሁዳ ቍራሹን እንጀራ ከተቀበለ በኋላ፣ ፈጥኖ ወጣ ምሽትም ነበረ። 31 ይሁዳ በሄደ ጊዜ፣ ኢየሱስ እንዲህ
በማለት ተናገረ፤ «አሁን የሰው ልጅ ከብሯል፣ እግዚአብሔርም በእርሱ ከብሯል። 32 እግዚአብሔር በራሱ ያከብረዋል፣ ደግሞም ፈጥኖ ያከብረዋል። 33 ልጆች
ሆይ፣ ከእንግዲህ ከእናንተ ጋር የምቆየው ለጥቂት ጊዜ ነው። እናንተ ትፈልጉኛላችሁ፣ ይሁን እንጂ፣ ለአይሁድ፣ 'እኔ ወደምሄድበት እናንተ ልትመጡ አትችሉም'
እንዳልኋቸው፣ ለእናንተም የምናገረው እንደዚያ ነው። 34 እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ ዐዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ፤ እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ
ተዋደዱ። 35 እርስ በርሳችሁም ብትዋደዱ የእኔ ደቀ መዛሙርት እንደ ሆናችሁ ሰዎች በዚህ ያውቃሉ።» 36 ስምዖን ጴጥሮስ «ጌታ ሆይ፣ ወዴት ልትሄድ
ነው?» ሲል ጠየቀው። ኢየሱስ፣ «ወደምሄድበት አሁን ልትከተለኝ አትችልም፣ በኋላ ግን ትከተለኛለህ» በማለት መለሰለት። 37 ጴጥሮስ፣ «ጌታ ሆይ፣ አሁን
ልከተልህ የማልችለው ለምንድን ነው? ስላንተ ሕይወቴን እንኳ አሳልፌ ለመስጠት ቈርጫለሁ» አለው። 38 ኢየሱስ፣ «ስለ እኔ ሕይወትህን አሳልፈህ
ትሰጣለህን? እውነት፣ እውነት እልሃለሁ፣ ዶሮ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ» ብሎ መለሰለት።

John 13:1

ጠቅላላ መግለጫ
ገና የፋሲካ በዓል አልሆነምና እየሱሰ ከደቀመዛሙርቱ ጋር በራት ላይ ነበር። ይህ ታሪክ የሚያስረዳው የእየሱስንና የይሁዳን

አባት
ይህ ርዕሰ ለእግዚአብሔር አስፈለጊ ነው።

ተፈቀረ
ይህ ዓየነት ፍቅር ከእግዚአብሄር የሚመጣ በሰዎች ምለካምነት ላይ ያተኮረ ራስን የማይጠቅም ቢሆን እንኳን። የፈለጉትን ስራ ቢሰሩ እንደዚህ ዓይነት ፍቅር ለሌሎች ይጨነቃል

ሰይጣን በአስቆሮቱ ይሁዳ በስምኦን ልጅ እየሱስን አሳለፎ እንዲሰጥ በልቡ ሀሳብ አገና
በልቡ ኣኖረ የሚለው አንድ ሰው ስለአንደ ነገር እንዲያስብ ማድረግ። ሰይጣን ቀድሞዉኑ በስምኦን ልጅ በአስቆሮቱ ይሁዳ እየሱስን አሳለፎ እንዲሰጥ ኣሳስቦታል

John 13:3

አያያዥ መግለጫ
ቁጥር ሶስት እየሱስ ስለሚያውቀው ነገር የገልጣል። ድርጊቱ በቁጥር አራት ላይ ይጀምራል

አባት
ይህ ርእስ ለእግዚአብሄር አስፈለጊ ነው

ሁሉንም አሳለፎ በእጁ ሰጣቸው
እጁ የሚለው ኃይልና ስልጣንን ያመለክታል

ከእግዚአብሄር መጣ ወደ እግዚአብሄርም ይመለሳል
እየሱሰ ሁሌም ከአባቱ ጋር ነበር እናም በምድር ስራውን ሲጨርስ ወደ አባቱ ይመለሳል

ከእራቱም ተነሳና ውጭ ልብሱን አወለቀ የደቀመዛሙርቱንም እግር ማጠብ ጀመረ
ሀገሩ አቧራ ስለነበር በባህሉ እራቱን የጋበዘው ሰው የእንግዶቹን እግር የሚጣጥብ አገልጋይ ያዘጋጃል

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

John 13:6

ጌታ ሆይ እግሬን ልታጥብ ነው እንዴ?
የፒተር ጥያቄ የሚያመለክተው እየሱስ እግሩን እንዲያጥብ ፈቃደኛ አልነበረም። ጌታ ሆይ የኔን የሀጢአተኛውን እግር ማጠብ አግባብ አይደለም።

ካለጠብሁህ ከኔ ጋር ድርሻ የለህም
እየሱስ ፒተርን ለማግባባት ሁለት ኣፍራሾችን ተናገረ። ፒተር የእየሱስ ደቀመዝሙር ሆኖ መቀጠል ከፈለገ እግሩን ማሳጠብ አለበት። ካጠብኩህ ሁሌም የኔ ትሆናለህ።

John 13:10

አያያዥ መግለጫ
እየሱስም ስምኦን ጴጥሮስን ማናገር ቀጠለ

ጠቅላላ መግለጫ
እየሱስ አንተ የሚለውን ቃል ሉሁለም ደቀ መዝሙር ይጠቀማል

የታጠበ እግሩን ከመታጠብ ውጪ ሌላ መታጠብ አያስፈልገውም
መታጠብ ያሚለው እግዚአብሄር ሰውን በመንፈሳዊ ህይወት ሲያጥብ ለማመልከት ነው። የእግዚአብሄርን ምህረት ከተቀበልን አሁን የሚያስፈለገን ከእለት ኃጢአት መንጻት ነው

ሁላችሁም ንጹህ አይደላችሁም
እየሱስ አሳልፎ የሚሰጠው ይሁዳ በሱ እንዳላመነ ለማሳየት ነው። ስለዚህም እግዚአብሄር ኃጢአቱን ይቀር አላለውም። ሁላችሁም የእግዚአብሄርን ይቅርታ አልተቀበላችሁም

John 13:12

ያደረኩላችሁን ታስተውላላችሁ?
ይህ አባባል በጥያቄ መልክ የሆነው እየሱስ ለደቀመዛሙረቱ ያደረገውን ያስተማረውን አጽንኦት ለመስጠት ነው። ለናንተ ያደረኩትን እንዲገባችሁ ነው።

መምህር እና ጌታ ትሉኛላችሁ
እየሱስ ደቀመዛሙረቱ ለርሱ ምን ያህል ከብር እንደሰጡት ለመግለጽ ነው። መምህር እና ጌታ ብለችሁ ሰትጠሩኝ ትልቅ ክብር አሳያችሁኝ

እኔ ለናንተ እንዳረኩላችሁ እናንተም እንዲሁ ኣድርጉ
እየሱስ ለማለት የፈለገው ደቀመዛሙርቱ የሱን ምሳሌ እንዲከተሉና እርስ በርሳቸው እንዲገለገሉ ነው።

John 13:16

አያያዥ መገለጫ
እየሱስ ለደቀመዛሙርቱ መናገሩን ቀጠለ

እውነት እውነት እላችኃለሁ
በ1:49 ላይ እንደተረጎማችሁት ተረጉሙት

ታላቅ
በጣም እሰፈላጊ

ተባርካችሁዋል
መባረክ ማለት ጥሩ እና ጠቃሚ ነገር ለሰው እንዲሆን። እግዚአብሄር ይባርክሀል

ይህ የሚሆነው ቃሉ እንዲፈጸም ነው
ቃሉ ሊፈጸም ግድ ነው

እንጀራዬን የበላ ተረከዙን በኔ ላይ አነሳ
እንጀራዬን የበላ የሚለው ጓደኛ መስሎ የነበረውነ ለመግለጽ ነው። ተረከዙን አነሳ የሚለውም አንድ ሰው ጠላት እንደሆነ ለማሳየት ነው። ጓደኛ መስሎ ይታይ የነበረው ጠላት ሆነ

John 13:19

ሳይሆን በፊት ነግሬአችኃለሁ
እኔ ምነግራችሁ ምን ሊሆን እንደሚችል ነገሩ ከመሆኑ በፊት ነው

እኔ እነደሆኑ ታምኑ ዘንድ
እኔ እኔ ነኝ ብዬ የነገርኃችሁን እንድታምኑ ወይም መሳያ እንደሆንኩ እንድታምኑ

እውነት እውነት
እኔ እንደ ሆንሁ አምናለሁ ፣ ወይንም “እኔ ክርስቶስ እንደሆንኩ ታምኑ ይሆናል”

John 13:21

ታወከ
ተጨነቀ ተረበሸ

እውነት እውነት
በ1:49 ላይ እንደተረጎማችሁት ተርጉሙት

ደቀመዛሙርቱ እርስ በርስ በመገረም ተያዩ ስለማን እነደሚናገር ግራ ገብቶአቸው
ደቀመዛሙርቱ እርስ በርስ በመገረም ተያዩ። እየሱስን ማን አሳልፎ የሰጣል?

John 13:23

እየሱስ ይወደው የነበረው ደቀመዝሙር
ዮሀንስን ያመለክታል

ጠረጴዛ
በእየሱስ ጊዜ አይሁድ እንደ ግሪኮች

እየሱስም አለ
በእራት ጠረጴዛ ዙሪያ ጭንቅላትን

ተፈቀረ
ይህ አይነት ፍቅር የሚመጣውከእግዚአብሄርና ስለሌላው መልካም ባማሰብ ለራስ እንኩዋን ጥቅም ባይኖር። ይህ አይነት ፍቅር ስለሌላው ይጨነቃል ምንም አይነት ነግረ ቢሰሩ

John 13:26

አስቆረቱ
ይሁዳ ከ ኬሪዮት ከምትባል መንደር ነው

ከእንጀራም በሁዋላ
ይህ ቃል ጁዳ እንጀራውን እንደተቀበለ ወዲያውኑ

ሰይጣን በውስጡ ገባ
ይህ ማለት ሰይጣን ሙሉ በሙሉ ይሁዳን ተቆጣጠረ። ሰይጣን ተቆጣጠረው ወይም ሰይጠን ያዛወው ጀመር

እየሱስም አለው
ይሁዳን እያናገረ ነው

የምታደርገውን በፍጥነት አድርግ
ልትሰራ ያሰብከውን በፍጥነት ስራው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

John 13:28

ለድሆች ምጽዋት እንዲሰጥ
ሂድና ለድሆች ገንዘብ ስጥ

በፍጥነት ወጣ። ማታም ነበ
ዮሃንስ ትኩረት ለመሳብ ይሁዳ ኃጢአቱን ወይም ጭለማ ነገሩን በጭለማ ውስጥ ለመስራት እንደወጣ ያሳያል። በድቅድቅ ጭለማ ወዲያውኑ ወጣ

John 13:31

የሰው ልጅ ከበር እግዚአብሄርም ስለእሱ ከበረ
አሁን ሕዝቡም የሰው ልጅ ክብር ከእግዚአብሔር ሲቀበልና እግዚአብሔርም ከሰው ልጅ ክብር ሲቀበል ያያሉ

እግዚአብሄር ስለርሱ ከበረ ወዲያውኑም ያከብረዋል
እሱ የሚለው የሰው ልጅን ነው የሚያመለክተው። እራሱ የሚለው የእግዚአብሔር አንጸባራቂ ነው። እግዚአብሔር ራሱ የሰውን ለጅ ያከብርዋል።

ሕጻናት ልጆች
ሕጻናት ልጆች ብሎ ደቀመዛሙርቱን መጥራት ይወዳል ልክ እንደራሱ ልጆች

ለአይሁዶች እንዳልኩዋቸው
አይሁድ የሚለው እየሱስነ የሚቃወሙትን የአይሁድ መሪዎቹን ነው። ለአይሁድ መሪዎች እንዳልኳቸው

John 13:34

አያያዥ መገለጫ
እየሱስም ደቀመዛሙርቱን ማናገር ቀጠለ

ፍቅር
ከእግዚአብሄር የሚመጣ ፍቅር ሲሆን ጥሩ የሚሰሩትን ይመለከታል ምንም እንኩዋን ለራስ ባይጠቅምም። ይህ ዓይነት ፍቅር ስለሌላው ይጨነቃል ምን ነግረ ቢሰሩ

ሁሉም
እየሱስ በተናገረው አረፍተነገር ላይ ክብደት ለመጨመር ነው። ደቀመዛሙርቱ ለእያንዳንዳቸው ያላቸውን ፍቅር ለሚያዩ ሰዎች ነው። እያንዳነዱ ለእያነዳንዱ ያለውን ፍቅር ማወቅ

John 13:36

ሕይወቴን ልሰጥ
ሕይወቴን ልሰጥ ወይም ልሞት

ሕይወትህን ስለኔ ትሰጣለህን?
እየሱስ በተናገረው አረፍተነገር ላይ አጽንኦት ለመስጠት ነው። ስለ አንተ እሞታለሁ አልክ እወነቱ ግን አታደርገውም

ሶስት ግዜ እስክትክደኝ ዶሮ አይጮህም
ዶሮከመጮሁ በፈት አላውቀውም ብለህ ሶስት ግዜ ትክደኛለህ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **14**

1 «ልባችሁ አይታወክ በእግዚአብሔር እመኑ፤ በእኔ ደግሞ እመኑ። **2** በአባቴ ቤት ብዙ የመኖሪያ ስፍራ አለ፤ እንደዚያ ባይሆን ኖሮ፣ ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁ ብዬ አልነግራችሁም ነበር። **3** ሄጄም ስፍራ ካዘጋጀሁላችሁ በኋላ፣ እኔ ባለሁበት እናንተም እንድትሆኑ ዳግመኛ እመጣለሁ፣ ወደ ራሴም እወስዳችኋለሁ።` **4** ወዴት እንደምሄድ መንገዱን ታውቃላችሁ።» **5** ቶማስ ኢየሱስን፣ «ጌታ ሆይ፣ ወዴት እንደምትሄድ አናውቅም፣ መንገዱን እንዴት ማወቅ እንችላለን?» በማለት ጠየቀው። **6** ኢየሱስ እንዲህ አለው፤ «እኔ መንገድ፣ እውነትና ሕይወት ነኝ፤ በእኔ ካልሆነ በቀር ማንም ሰው ወደ አብ ሊመጣ አይችልም። **7** እኔን ብታውቁኝ ኖሮ አባቴንም ባወቃችሁት ነበር። ከአሁን ጀምሮ ታውቁታላችሁ አይታችሁትማል።» **8** ፊልጶስ ጌታ ኢየሱስን፣ «ጌታ ሆይ፣ አብን አሳየን ያ ለእኛ በቂያችን ነው» አለው። **9** ኢየሱስ፣ «ፊልጶስ ሆይ፣ ይህን ያህል ጊዜ ከእናንተ ጋር ኖሬ ገና ኣላወቅኸኝምን? እኔን ያየ አብን አይቷል፤ 'እንዴትስ አብን አሳየን' ትላለህ? **10** እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን? እየነገርኋችሁ ያለው ቃል ከራሴ የምናገረው አይደለም፤ ይልቁንስ ይህን ሥራ የሚሠራው በእኔ ውስጥ የሚኖረው አብ ነው። **11** እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ፤ ሌላው ቢቀር ከምሠራው ሥራ የተነሣ እመኑኝ። **12** እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ በእኔ የሚያምን እኔ የምሠራውን ሥራ እርሱም ይሠራል፤ እንዲያውም እኔ ወደ አብ ስለምሄድ፣ እኔ ከሠራሁት የሚበልጥ ሥራ ይሠራል። **13** አብ በልጁ ይከብር ዘንድ ማንኛውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ። **14** ማንኛውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ፣ እኔ አደርገዋለሁ። **15** የምትወዱኝ ከሆነ ትእዛዜን ትጠብቃላችሁ። **16** እኔም ለዘላለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ እንዲሰጣችሁ አብን እለምናለሁ። **17** እርሱም የእውነት መንፈስ ነው፤ ዓለም ስለማያየው ወይም ስለማያውቀው አይቀበለውም። ይሁን እንጂ፣ ከእናንተ ጋር ስለሚኖርና በውስጣችሁም ስለሚሆን፣ እናንተ ታውቁታላችሁ። **18** ወላጅ እንደሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም፣ ዳግመኛ ወደ እናንተ እመጣለሁ። **19** ከጥቂት ጊዜ በኋላ ዓለም አያየኝም፤ እናንተ ግን ታዩኛላችሁ፤ እኔ ሕያው ነኝና እናንተም ሕያዋን ትሆናላችሁ። **20** በዚያን ቀን እኔ በአብ እንዳለሁ፣ እናንተ በእኔ እንዳላችሁ እኔም በእናንተ እንዳለሁ ታውቃላችሁ። **21** ትእዛዜ በውስጡ ያለ የሚያደርገውም የሚወደኝ እርሱ ነው፤ የሚወደኝንም አባቴ ይወደዋል፤ እኔም እወደዋለሁ፤ ራሴንም እገልጥለታለሁ። **22** የአስቆሮቱ ያልሆነው ይሁዳም ኢየሱስን፣ «ጌታ ሆይ፣ ለዓለም ሳይሆን ለእኛ ራስህን የምትገልጠው እንዴት ነው?» ብሎ ጠየቀው። **23** ኢየሱስ እንዲህ ብሎ መለሰለት፤ «ማንም ሰው ቢወደኝ ቃሌን ይጠብቃል። አባቴም ይወደዋል፣ ወደ እርሱ እንመጣለን፣ መኖሪያችንንም በእርሱ እናደርጋለን። **24** የማይወደኝ ማንኛውም ሰው ቃሌን አይጠብቅም። የምትሰሙት ቃል የእኔ ሳይሆን፣ የላከኝ የአብ ቃል ነው። **25** በመካከላችሁ ሳለሁ እነዚህን ነገሮች ልብ እንድትሉ ነግሬአችኋለሁ። **26** የሆነ ሆኖ፣ አብ በስሜ የሚልከው አጽናኙ መንፈስ ቅዱስ ሁሉንም ነገር ያስተምራችኋል፤ እኔ የነገርኋችሁንም ነገር ሁሉ እንድታስታውሱ ያስችላችኋል። **27** ሰላምን እተውላችኋለሁ፤ ሰላሜንም እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጠው ሰላም ዓለም እንደሚሰጠው ዓይነት አይደለም። ልባችሁ አይጨነቅ፣ አይፍራም። **28** 'እሄዳለሁ፣ ዳግመኛም ወደ እናንተ እመጣለሁ' ብዬ የነገርኋችሁን ቃል ሰምታችኋል። ከወደዳችሁኝስ ወደ አብ በመሄዴ ደስ ሊላችሁ ይገባ ነበር፤ ምክንያቱም አብ ከእኔ ይበልጣል። **29** ይህ ነገር በሚፈጸምበት ጊዜ ታምኑ ዘንድ አሁን ከመሆኑ በፊት አስቀድሜ ነገርኋችሁ። **30** የዚህ ዓለም ገዥ እየመጣ ስለሆነ ከዚህ በላይ ከእናንተ ጋር መነጋገር አልችልም።እርሱ በእኔ ላይ ምንም ሥልጣን የለውም፡ **31** ነገር ግን አብን እንደምወድ ዓለም ሁሉ ያውቅ ዘንድ በሰጠኝ ትዕዛዝ መሠረት አብ ያዘዝኝን አደርጋለሁ። ተነሱ ከዚህ እንሂድ»

John 14:1

አያያዝ መግለጫ
ታሪኩ ከቀደመው ምዕራፍ ይቀጥላል። እየሱስም በጠረጴዛ ላይ ተቀምጦ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ማውራቱን ቀጠለ

ልባችሁ አይታወክ
ይህ አባባል ነው። የታወከ ልብ ማለት መጨነቅ መረበሽ ማለት ነው። መጨነቅና መረበሻችሁን አቁሙ።

ባባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ
ባባቴ ቤት ለመኖር ብዙ መኖሪያ አለ

ባባቴ ቤት
ይህ የሚያመለክተው መንግሰተ ሰማይን ነው፤ እግዚአብሄር የሚኖርበት

አባቴ
ይህ ለእግዚአብሄር አስፈላጊ ርዕስ ነው

ብዙ ክፍሎች ወይም ቦታዎች
ክፍል የሚለው ቃል ለነጠላ ክፍልም ወይም ለብዙ መኖሪያ ነው

ቦታ ላዘጋጅላችሁ እሄዳለሁ
እየሱስ በርሱ ለሚያምኑ ሁሉ በመንግስተ ሰማይ ቦታ ያዘጋጃል። አንተ የሚለው ቃል ለብዙ ነው ለሁሉም ደቀመዛሙርት

John 14:4

መንገዱን እንዴት እናውቃለን?
ወደዛ ለመድረስ እንዴት እናወቃለን?

መንገዱ
ይህ አባባል የሚከተሉት ትርጉሞች ሊኖሩት ይችላል 1)የእግዚአብሄር መንገድ 2) ሰዎችን ወደ እግዚአበሔር የሚወስድ

እውነቱ
ይህ አባባል የሚከተሉት ትርጉሞች ሊኖሩት ይችላል 1) እውነተኛ ሰው ወይም 2) ስለ እግዚአብሔር እውነትን የሚናገር ሰው

ሕይወት
ይህ ኣባባል እየሱስ ለሰዎች ሕይወትን ይሰጣል ማለት ነው። ሰውን ሕያው የሚያደርግ

በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም
ሰዎች በእየሱስ በማመን ብቻ ከእግዚአብሔር ጋር መኖር ይችላሉ። በኔ ካልሆነ በስተቀር ማንም ከአባቴ ጋር መኖር አይችልም

አባት
ይህ በንቃት ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “ግን አንድ ሰው ከታጠቀው በፍታ ጨርቆቹ ላይ አነጥፈው ከዚያ አውጥተውትታል” (የበለስ_ቁጥር / ይመልከቱ)

John 20:8

ሁለተኛው ደቀ መዝሙር ነው
የሐንስ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስሙን ከማካተት ይልቅ እራሱን “ሌላኛው ደቀመዝሙር” ብሎ በመጥራት ትህትናውን ገል expressል ።

አይቶ አመነ
መቃብሩ ባዶ እንደ ሆነ ባየ ጊዜ ኢየሱስ ከሙታን መነሳቱን ያምናል ። በዚህ ጊዜ “እነዚህን ነገሮች አይቶ ኢየሱስ ከሙታን መነሳቱን ማመን ጀመረ” (ዩ.አር.ቢ.)

አሁንም መጽሐፉን አላወቁም
እዚህ “እነሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢየሱስ እንደገና ይነሳል የሚለውን የቅዱሳት መጻሕፍቱን ያልተገነዘቡ ደቀመዛሙርትን ነው ። አት: - - “አሁንም ደቀ መዛሙርቱ መጽሐፍ ቅዱስን አልተረዱም” (የበለስ_ቁጥር ይመልከቱ)

ተነስቶ ከሙታን ይነሣ ዘንድ አለው
ኢየሱስ ከሞት መነሳት አለበት አለ

እንደገና ወደ ቤት ተመለስኩ
ደቀመዛሙርቱ በኢየሩሳሌም መኖራቸውን ቀጠሉ ። አት: - “በኢየሩሳሌም ወደሚኖሩበት ተመልሰዋል” (የበለስ_ቁጥር ይመልከቱ)

John 20:11

ሁለት መላእክትን በነጭ አየች
መላእክቱ ነጭ ልብስ ለብሰው ነበር ። አት: - “ሁለት መላእክት ነጭ ልብስ ለብሰው አየች” (UDB) (ይመልከቱ ። የበለስ_ቁጥር)

እነርሱም
“ጠየቋት”

ምክንያቱም ጌታዬን ወሰዱ
“የጌታዬን ሥጋ ወስደዋል”

የት እንዳኖሩት አላውቅም
"የት እንዳስቀመጡ አላውቅም"

John 20:14

ኢየሱስም
ኢየሱስም ጠየቃት።

ጌታ ሆይ ፣ ወስደኸው ከሆነ
እዚህ “እሱ” የሚለው ቃል ኢየሱስን ያመለክታል ። አት: - “የኢየሱስን አስከሬን ከወሰዱ” (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር ይመልከቱ)

የት እንዳኖራችሁ ንገሩኝ
የት እንዳስቀመጥክ ንገረኝ ”

እሱን እወስደዋለሁ ፤
መግደላዊት ማርያም የኢየሱስን አስከሬን ልትወስድና እንደገና ልትቀበር ትፈልጋለች ። አት: - እናም አስከሬን አገኛለሁ እንደገና እቀብራለሁ (ይመልከቱ ። የበለስ_ቁጥር)

John 20:16

ረቢኒ
“ራቢኒ” የሚለው ቃል ኢየሱስ እና ደቀመዛሙርቱ የተናገሩበት ቋንቋ ረቢዎች ወይም መምህር በአረማይክ ቋንቋ ማለት ነው ።

ወንድሞች
ኢየሱስ “ወንድሞች” የሚለውን ቃል ደቀመዛሙርቱን ለማመልከት ተጠቀመ ።

እኔ ወደ አባቴ ፣ ወደ አባታችሁ ፣ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ እወጣለሁ
ኢየሱስ ከሙታን ተነስቶ ወደ እግዚአብሔር ወደ አባቱ ወደ ሰማይ እንደሚሄድ ተንብዮ ነበር ። አትቲን: - “እኔ ከአባቴና ከአባትህ ፣ አምላኬና አምላካችሁ ወደ ሆነኝ ወደ ሰማይ እመለሳለሁ (ኦ.ሲ.ቢ. ይመልከቱ)

እኔ አባቴና አባታችሁ ነኝ
እነዚህ በኢየሱስ እና በእግዚአብሔር ፣ እንዲሁም በአማኞች እና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን ግንኙነት የሚገልፁ አስፈላጊ አርዕስት ናቸው ። (መመሪያዎችን ይመልከቱ) መመሪያዎች_ሶፍትዌር መመሪያዎች

መግደላዊት ማርያም መጥታ ለደቀ መዛሙርቱ ነገረቻቸው
መግደላዊት ማርያም ደቀ መዛሙርቱ ወደሚኖሩበት ቦታ ሄደች ያየችውንና የሰማችውን ነገር ነገረቻቸው ። በዚህ ጊዜ-መግደላዊት ማርያም ደቀመዛሙርቱ ወደነበሩበት ሄዳ ትነግራቸው ነበር (ይመልከቱ ።

John 20:19

አጠቃላይ መረጃ
ጊዜው አሁን ምሽት ሲሆን ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ተገለጠላቸው።

ያ ቀን ፣ የሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን
ይህ እሑድን ያመለክታል።

ደቀመዛሙርቱ ያሉባቸው በሮች ተዘጉ
ይህንን በገባ መልኩ መተርጎም ይችላሉ። አት: - “ደቀመዛሙርቱ ያሉበትን በሮች ዘግተው ነበር” (ይመልከቱ ። የበለስ_ቁጥር / ይመልከቱ)

አይሁድን ስለ ፈሩ
እዚህ “አይሁዶች” ደቀመዛሙርቱን ሊይዝ ለሚችል የአይሁድ መሪዎች ምሳሌ ነው ። AT: - “የአይሁድ መሪዎች ይያ mightቸው ዘንድ ፈርተው ነበር” (ይመልከቱ ። የበለስ_ቁጥር)

ሰላም ለአንተ ይሁን
ይህ ‹እግዚአብሔር ሰላም ይሰጣችኋል› ማለት ነው ።

እሱ እጆቹን እና ጎኑን አሳያቸው
ኢየሱስ ቁስሎቹን ለደቀ መዛሙርቱ አሳያቸው ። አት: - በእጁና ከጎኑ ያሉትን ቁስሎች አሳየባቸው

John 20:21

ሰላም ለአንተ ይሁን
ይህ ‹እግዚአብሔር ሰላም ይሰጣችኋል› ማለት ነው ።

አብ እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ ... እርሱ ... መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ
እግዚአብሔር አብ እግዚአብሔር አማኞችን አሁን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማኞችን የሚልክ ልጁን እግዚአብሔር ልኮታል ።

አባት
ይህ ለእግዚአብሔር አስፈላጊ ርዕስ ነው ። (መመሪያዎችን ይመልከቱ) መመሪያዎች_ሶፍትዌር መመሪያዎች

ይቅር ተባባሉ
ይህንን በገባ መልኩ መተርጎም ይችላሉ። አት: - “እግዚአብሔር ይቅር ይላል” (የበለስ_ቁጥር / ተመልከት)

ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ ያጠፋል
"የሌላውን ኃጢአት ይቅር ካላለዎት" (ዩ.አር.ቢ.)

እነሱ ተጠብቀዋል
ይህንን በገባ መልኩ መተርጎም ይችላሉ። አት: - “እግዚአብሔር ይቅር አይላቸውም” (የበለስ_ቁጥርን ይመልከቱ)

John 20:24

መንትያ
ይህ ወንድ ‹ስም› ማለት ‹መንትዮች› ማለት ነው ። ይህ ስም በ 11 15 ውስጥ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ ። (ይመልከቱ: መተርጎም_ቁጥር)

ከዚህ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ
“እሱ” የሚለው ቃል ቶማስን ያመለክታል ።

እኔ ካላየሁ በስተቀር ... የእርሱ ወገን ፣ አላምንም
ይህንን ድርብ አሉታዊ በአዎንታዊ መልኩ መተርጎም ይችላሉ። አት: - “አምናለሁ... የእርሱን ጎን ካየሁ ብቻ” አምናለሁ (የበለስ_ቁጥር ችግሮች)

በእጆቹ ... ወደ ጎኑ
“የእርሱ” የሚለው ቃል ኢየሱስን ያመለክታል ።

John 20:26

ደቀመዛሙርቱ
“የእርሱ” የሚለው ቃል ኢየሱስን ያመለክታል ።

በሮቹ ተዘግተው ሳሉ
ይህንን በገባ መልኩ መተርጎም ይችላሉ። አት: - "በሮቹን በቆለፉ ጊዜ" (የበለስ_ቁጥር / ይመልከቱ)

ሰላም ለአንተ ይሁን
ይህ ‹እግዚአብሔር ሰላም ይሰጣችኋል› ማለት ነው ።

የማያምን
“ያለ እምነት” ወይም “ያለ እምነት”

ግን አምናለሁ
እዚህ “ማመን” ማለት በኢየሱስ ማመን ማለት ነው ። አት: - "በእኔ ታመኑ" (UDB) (ይመልከቱ ። የበለስ_ቁጥር)

John 20:28

አምናለሁ
ቶማስ ኢየሱስ ስላየው ስላየ ህያው ነው ብሎ ያምናል ። አት: - “በሕይወት መኖሬ ታምናላችሁ” (የበለስ_ቁጥር ይመልከቱ)

የተባረኩ የተባረኩ ናቸው
ይህ ማለት “እግዚአብሔር ለእነዚያ ታላቅ ደስታን ይሰጣል” (ዩ.ቢ.ቢ.) ።

የማያውቁት
ይህ ማለት ኢየሱስን ያላዩ ናቸው ። አት: - "በህይወቴ ያላየኝ" (የበለስ_ቁጥር ይመልከቱ)

John 20:30

አጠቃላይ መረጃ
ታሪኩ ወደ መጨረሻው እየተቃረበ ሲመጣ ደራሲው ኢየሱስ ስላከናወናቸው በርካታ ነገሮች አስተያየት ሰጡ ። (ይመልከቱ: Writ_endofstory)

ምልክቶች
የሚለው ቃል እግዚአብሔር በአጽናፈ ዓለም ሁሉ ላይ ሙሉ ኃይል ያለው መሆኑን የሚያሳዩ ተዓምራቶችን ይመለከታል ።

በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፉ ምልክቶች
ይህንን በገባ መልኩ መተርጎም ይችላሉ። አት: - “ደራሲው በዚህ መጽሐፍ ላይ የፃፋቸው ምልክቶች” (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር / ይመልከቱ)

ነገር ግን ይህ ተጽፎአል
ይህንን በገባ መልኩ መተርጎም ይችላሉ። አት: - "ደራሲው ግን ስለ እነዚህ ምልክቶች ጽ "ል" (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር / ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ልጅ
ይህ ለኢየሱስ አስፈላጊ ርዕስ ነው ። (መመሪያዎችን ይመልከቱ) መመሪያዎች_ሶፍትዌር መመሪያዎች

በስሙ ሕይወት
እዚህ “ሕይወት” ማለት ኢየሱስ ሕይወትን ይሰጣል ማለት ነው ። አት: - “ከኢየሱስ የተነሳ ሕይወት ሊኖርህ ይችላል” (ይመልከቱ ። የበለስ.

ሕይወት
ይህ መንፈሳዊ ሕይወትን ያመለክታል ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 21

1 እነዚህ ነገሮች ከተፈጸሙ በኋላ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንደ ገና በጥብርያዶስ ባሕር አጠገብ ተገለጠላቸው፤ ሁኔታውም እንደዚህ ነበር፦ 2 ስምዖን
ጴጥሮስ ዲዲሞስ ከተባለው ከቶማስ፣ ከገሊላ አውራጃ ከቃና መንደር ከሆነው ከናትናኤል፣ ከዘብዴዎስ ልጆችና ከሌሎች ሁለት የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ጋር
ዐብረው ነበሩ። 3 ስምዖን ጴጥሮስ፣ «ዓሣ ለማጥመድ መሄዴ ነው» አላቸው። እነርሱም፣ «እኛም ከአንተ ጋር እንሄዳለን» አሉት። በጀልባ ተሳፍረው ሄዱ፤ ነገር
ግን በዚያች ሌሊት ምንም ዐሣ አላጠመዱም። 4 ቀኑ እየነጋ ሳለ ኢየሱስ መጥቶ በባሕሩ ዳር ቆመ፤ እነርሱ ግን ኢየሱስ እንደ ሆነ አላወቁም ነበር። 5 ከዚያም
ኢየሱስ «ልጆች ሆይ፣ የሚበላ ዐሣ አላችሁን?» አላቸው። «የለንም» ብለው መለሱለት። 6 ኢየሱስ፣ «መረባችሁን ከጀልባው በቀኝ በኩል ጣሉት
ታገኙማላችሁ» አላቸው። እነርሱም እንደተባሉት መረባቸውን ጣሉ፤ ነገር ግን ከዐሣው ብዛት የተነሣ መረቡን ወደ ጀልባው ውስጥ መጐተት አቃታቸው። 7
ከዚያም ኢየሱስ ይወደው የነበረው ደቀ መዝሙር ስምዖን ጴጥሮስን፣ «ጌታ እኮ ነው» አለው። ጴጥሮስ ጌታ እኮ ነው የሚለውን ቃል በሰማ ጊዜ፣
መደረቢያውን ልብስ ታጥቆ ወደ ውሃው ውስጥ ዘሎ ገባ። 8 ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ግን ከምድር የነበራቸው ርቀት ሁለት መቶ ክንድ ያህል ብቻ ስለ ነበር ዐሣ
የሞላውን መረብ እየጐተቱ በጀልባ ወደ ዳር መጡ። 9 ወደ መሬትም በደረሱ ጊዜ፣ በላዩ ላይ ዐሣ የተቀመጠበት ፍምና እንጀራ ተዘጋጅቶ አዩ። 10 ኢየሱስ፣
«እስኪ ካጠመዳችሁት ዐሣ ጥቂት ወደዚህ አምጡ» አላቸው። 11 ስምዖን ጴጥሮስም ሄዶ 153 ዐሣ የሞላውን መረብ ወደ ምድር ጐተተ፤ ምንም እንኳ
የዐሣው ብዛት ከፍተኛ ቢሆንም፣ መረቡ ግን አልተቀደደም ነበር። 12 ኢየሱስ፣ «ኑ ቍርስ ብሉ» አላቸው። ኢየሱስ እንደ ሆነ አውቀው ነበርና ከደቀ መዛሙርቱ
ማንም፣ «አንተ ማነህ?» ብሎ ሊጠይቀው የደፈረ አልነበረም። 13 ኢየሱስ እንጀራውን አንሥቶ ሰጣቸው፤ ዐሣውንም እንደዚያው አደረገ። 14 ከሞት ከተነሣ
በኋላ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ሲገለጥላቸው ይህ ለሦስተኛ ጊዜ ነበር። 15 ቍርስ ከበሉ በኋላ፣ ኢየሱስ ስምዖን ጴጥሮስን፣ «የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፣
ከእነዚህ የበለጠ ትወደኛለህን?» አለው። ጴጥሮስ፣ «አዎን፣ ጌታ ሆይ፣ እንደምወድህማ አንተም ታውቃለህ» አለው። ኢየሱ፣ «ጠቦቶቼን መግብ» አለው። 16
እንደ ገና ለሁለተኛ ጊዜ፣ «የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ ትወደኛለህን?» አለው። ጴጥሮስ፣ «አዎን፣ ጌታ ሆይ፣ እንደምወድህማ አንተም ታውቃለህ» አለው። ኢየሱስ፣
«በጎቼን ጠብቅ» አለው። 17 ለሦስተኛ ጊዜ፣ «የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፣ ትወደኛለህ?» አለው። ለሦስተኛ ጊዜ «ትወደኛለህ ወይ?» ብሎ ስለ ጠየቀው
ጴጥሮስ በጣም ዐዘነ። ቀጥሎም፣ «ጌታ ሆይ፣ አንተ ሁሉን ታውቃለህ፤ እንደምወድህም ታውቃለህ» አለው። ኢየሱስም «በጎቼን መግብ። 18 እውነት፣ እውነት
እልሃለሁ፣ ወጣት እያለህ ልብስህን ራስህ ለብሰህ ወደምትፈልገው ቦታ ትሄድ ነበር፤ ስታረጅ ግን ሌላ ሰው ልብስህን አልብሶህ ወደማትፈልገው ቦታ
ይወስድሃል፣ በዚያን ጊዜ አንተ እጅህን ከመዘርጋት ውጪ ሌላ ማድረግ የምትችለው ነገር አይኖርም» አለው። 19 ኢየሱስ ይህን የተናገረው ጴጥሮስ በምን
ዓይነት አሟሟት እግዚአብሔርን እንደሚያከብር ለማመልከት ነው። ከዚያም ኢየሱስ ጴጥሮስን፣ «ተከተለኝ» አለው። 20 ጴጥሮስም ዞር ብሎ በፋሲካ እራት
ላይ እያሉ ወደ ኢየሱስ ደረት ጠጋ ብሎ፣ «አሳልፎ የሚስጥህ ማን ነው?» ብሎ የጠየቀውንና ኢየሱስ ይወደው የነበረውን ደቀ መዝሙር ሲከተላቸው አየው። 21
ጴጥሮስ ኢየሱስን፣ «ጌታ ሆይ፣ ይህ ሰውስ ምን ይሆናል?» አለው። 22 ኢየሱስ፣ «እኔ እስክመጣ እንዲቆይ ብፈልግስ አንተን ምን ይመለከትሃል? ዝም ብለህ
ተከተለኝ» አለው። 23 በዚህ ምክንያት «ያ ደቀ መዝሙር አይሞትም» የሚል ወሬ በየ ስፍራው ተሠራጨ። ኢየሱስ ግን ለጴጥሮስ፣ «እኔ እስክመጣ እንዲቆይ
ብፈልግስ አንተን ምን ይመለከትሃል?» አለው እንጂ ያ ደቀ መዝሙር አይሞትም አላለውም። 24 ስለ እነዚህ ነገሮች የመሰከረውና የጻፈው ይህ ደቀ መዝሙር
ነው፣ ምስክርነቱም እውነት እንደ ሆነ እናውቃለን። 25 ከእነዚህ ሌላ ኢየሱስ ያደረጋቸው ብዙ ነገሮች አሉ። እያንዳንዱ ነገር ቢጻፍ ኖሮ ለሚጻፉት መጻሕፍት
ማስቀመጫ ዓለም እንኳ የሚበቃ አይመስለኝም።

John 21:1

አጠቃላይ መረጃ
ኢየሱስ በጥብርያስ ባሕር አጠገብ ለደቀ መዛሙርቱ እንደገና ተገለጠ ። ቁጥር 2 እና 3 ኢየሱስ ከመገለጡ በፊት በታሪኩ ውስጥ ምን እንደ ሆነ ይነግሩናል ። (ይመልከቱ: የአፃፃፍ_ኋላ)

ከእነዚህ ነገሮች በኋላ
"ከተወሰነ ጊዜ በኋላ"

ዲዲሞስ የሚሉት ቶማስ
ይህንን በገባ መልኩ መተርጎም ይችላሉ። አት: - “ዲዲሞስ ብለን ከጠራነው ቶማስ ጋር (የበለስ_ቁጥር / ተመልከት)

መንትያ
ይህ ወንድ ‹ስም› ማለት ‹መንትዮች› ማለት ነው ። ይህ ስም በ 11 15 ውስጥ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ ። (ይመልከቱ: መተርጎም_ቁጥር)

John 21:4

ወጣት ወንዶች
ይህ ‹ውድ ጓደኞቼ› ማለት የፍቅር መግለጫ ነው ።

ጥቂት ታገኛለህ
እዚህ “የተወሰኑት” ዓሦችን ያመለክታል ። አት: - “መረብህ ውስጥ አንዳንድ ዓሳ ትይዛለህ” (የበለስ_ቁጥር ተመልከት)

ይሳቡት
መረቡን ጎትት "

John 21:7

የተወደደ
ይህ ፍቅር ከእግዚአብሄር የሚመጣ እና ለሌሎች ጥቅም ላይ ያተኮረ ፍቅር ነው ፣ ምንም እንኳን በእራሱ የማይጠቅም ቢሆንም። ምንም ይሁን ምን እንዲህ ዓይነቱ ፍቅር ለሌሎች ይንከባከባል ።

ወደ ባሕሩ ወረወረ
ጴጥሮስም ወደ ውሃው ዘልሎ ወደ ባሕሩ ዳርቻ ገባ ። አት: - “ወደ ባሕሩ ውስጥ ዘለለ ፤ እስከ ባሕሩ ዳርቻ ድረስ ጠመጠመ” (ይመልከቱ። የበለስ_ቁጥር)

ራሱን ወረወረ
ይህ ፈሊጥ ነው ጴጥሮስ ማለት በፍጥነት ወደ ውሃው ውስጥ ዘለለ ማለት ነው ። (ይመልከቱ: የበለስ_ ቪዲዮም)

ከምድርም ርቀው ሄዱ ፤ ሁለት መቶ ክንድ ያህል ርቀት ላይ ነበሩ
ይህ የዳራ መረጃ ነው ። (ይመልከቱ: የአፃፃፍ_ኋላ)

ሁለት መቶ ክንድ
"90 ሜትር." አንድ ክንድ ከግማሽ ሜትር ያነሰ ነበር ። (ይመልከቱ: translation_bdistance)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

John 21:10

ስም **Simon**ን ጴጥሮስም ወደ ውጭ ወጣ
እዚህ “ወጣ” ማለት ስም Simonን ጴጥሮስ ወደ ጀልባው መመለስ ነበረበት ። አት: - "ስም Simonን ጴጥሮስ ወደ ጀልባው ተመለሰ" (የበለስ_ቁጥር ተመልከት)

መረቡም ወደ ምድር መሳብ ጀመረ
መረቡን ወደ ባሕሩ ዳርቻ ጎትተው ”

መረቡ አልተቀደደም
ይህንን እንደ ገባሪ ቅጽ መተርጎም ይችላሉ። አት: - “መረቡ አልተሰበረም” (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)

John 21:12

ቁርስ
ጠዋት ላይ ምግብ

ለሦስተኛ ጊዜ
ይህንን የስምምነት ቃል “ሶስተኛ” ን እንደ “የጊዜ ቁጥር 3” መተርጎም ይችላሉ ። (ይመልከቱ: ተርጉም_ordinal)

John 21:15

አጠቃላይ መረጃ
ኢየሱስ ከስም Simonን ጴጥሮስ ጋር ውይይት ይጀምራል ።

ትወደኛለህ ... ትወደኛለህ? እዚህ "ፍቅር"
እዚህ ላይ “ፍቅር” ሌሎችን የሚጠቅመው እንኳን ባይሆንም በሌሎች መልካም ላይ የሚያተኩር ከእግዚአብሔር የሚመጣውን የፍቅር ዓይነት ነው ።

እንደምወድህ ታውቃለህ
ጴጥሮስ መልስ ሲሰጥ ፣ “ፍቅር” የሚለውን ቃል የሚጠቀመው የወንድማማችነት ፍቅርን ወይም ለጓደኛ ወይም ለቤተሰብ አባል ፍቅርን ነው ።

ግልገሎቼን አሰማራ
እዚህ “ጠቦቶች” ኢየሱስን ለሚወዱ እና ለሚከተሉት ሰዎች ዘይቤ ነው ። አት: - "እኔ የምወዳቸውን ሰዎች መመገብ" (የበለስ_ቁጥር ን ይመልከቱ)

በጎቼን ጠብቅ
እዚህ “በጎች” ኢየሱስን ለሚወዱ እና ለሚከተሉት ሰዎች ዘይቤ ነው ። አት: - "እኔ ለምከባከባቸው ሰዎች ይንከባከቡ" (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)

John 21:17

ሦስተኛ ጊዜ
“እሱ” የሚለው ተውላጠ ስም የሚያመለክተው ኢየሱስን ነው ። እዚህ “ሶስተኛ ጊዜ” ማለት “የጊዜ ቁጥር 3” ማለት ነው ። አት: - “ኢየሱስ ለሦስተኛ ጊዜ።” (ተመልከት: መተርጎም

ትፈቅርኛለህ
በዚህ ጊዜ ኢየሱስ ይህንን ጥያቄ በጠየቀ ጊዜ “ፍቅርን” ለሚለው ቃል የሚያመለክተው የወንድማማች ፍቅርን ወይም ለጓደኛ ወይም ለቤተሰብ አባል ፍቅርን ለመግለጽ ነው ።

በጎቼን አሰማራ
የእኔን በጎቼን መመገብ የኢየሱስን የሚወክሉ እና እሱን የሚከተሉ ዘይቤ ነው ። አት: - "እኔ ለመንከባከባቸው ሰዎች እንክብካቤ" (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር) ክፍል

በእውነት በእውነት
በ 1 48 ውስጥ እንዳደረገው ይህንን ይተረጉሙ ።

John 21:19

አሁን
ታሪኩን ከመቀጠል በፊት ዮሐንስ ዳራውን መረጃ እየሰጠ መሆኑን ለማሳየት ይህንን ቃል ይጠቀማል ። (ይመልከቱ: የአፃፃፍ_ኋላ)

ጴጥሮስ በምን ዓይነት ሞት እግዚአብሔርን እንደሚያከብር ለማመልከት ነው
እዚህ ላይ ዮሐንስ የሚያመለክተው ጴጥሮስ በመስቀል ላይ እንደሚሞት ነው ። አት-“ጴጥሮስ እግዚአብሔርን ለማክበር በመስቀል ላይ መሞቱን ለማመልከት” (የበለስ_ቁጥር ይመልከቱ)

ተከተለኝ
እዚህ “ተከተል” የሚለው ቃል “ደቀ መዝሙር መሆን” ማለት ነው ። አት: - “የእኔ ደቀ መዝሙር መሆንህን ቀጥል” (የበለስ_ቁጥር ተመልከት)

John 21:20

ኢየሱስ ይወደው የነበረው ደቀመዝሙር
ዮሐንስ ስሙን ከመጥቀስ ይልቅ ራሱን በመጽሐፉ ውስጥ ሁሉ በዚህ መንገድ ይጠቅሳል ።

የተወደደ
ይህ ዓይነቱ ፍቅር ከእግዚአብሔር የሚመጣ እና ሁል ጊዜም የሌሎችን መልካም ነገር የሚሻ ቢሆንም ፣ በራሱ የማይጠቅም ቢሆንም ። ምንም እንኳን ምንም ቢያደርጉ ይህ ዓይነቱ ፍቅር ለሌሎች ይንከባከባል ።

እራት ላይ
ይህ ለመጨረሻው እራት ማጣቀሻ ነው ። (ተመልከት: 13: 1)

ጴጥሮስ አየው
እዚህ “እሱ” የሚያመለክተው “ኢየሱስ ይወደው የነበረውን ደቀመዝሙር” ነው ።

ጌታ ሆይ ፣ ይህ ሰው ምን ያደርጋል?
ጴጥሮስ በዮሐንስ ላይ የሚሆነውን ማወቅ ፈለገ ። AT: - “ጌታ ሆይ ፣ ይህ ሰው ምን ይሆናል?” (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)

John 21:22

ኢየሱስም
"ኢየሱስም ጴጥሮስን"

እሱ እንዲቆይ ከፈለግኩ
እዚህ “እሱ” የሚያመለክተው በ 21 20 ውስጥ ‹ኢየሱስ የወደደውን ደቀመዝሙር› ነው ።

እመጣለሁ
ይህ የሚያመለክተው የኢየሱስን ዳግም ምጽዓት ፣ ከሰማይ ወደ ምድር መመለሱን ነው ።

ምንድነው ለእርስዎ?
ይህ አስተያየት መለስተኛ ገጸ-ባህሪን ለመግለጽ በጥያቄ መልክ ይታያል። አት: - ያ ያንተ ጉዳይ አይደለም (UDB) ወይም “ስለዚህ ጉዳይ አትጨነቅ” (ተመልከት: የበለስ_ቁጥር)

በወንድሞች መካከል
እዚህ “ወንድሞች” ሁሉንም የኢየሱስ ተከታዮች የሚያመለክቱ ናቸው ።

John 21:24

አጠቃላይ መረጃ
ይህ የዮሐንስ ወንጌል መጨረሻ ነው ። እዚህ ደራሲው ሐዋርያው ዮሐንስ ስለራሱ እና በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስለ ጻፈው ለመዝጋት አስተያየት ይሰጣል ። (ይመልከቱ: Writ_endofstory)

ደቀመዝሙሩ
“ደቀ መዝሙሩ ዮሐንስ”

ስለ እነዚህም የመሰከረ
እዚህ “መሰከረ” ማለት እሱ ራሱ የሆነ ነገር ያያል ማለት ነው ። አት: - “እነዚህን ሁሉ ያየ ማን ነው” (የበለስ_ቁጥር ይመልከቱ)

እናውቃለን
እዚህ “እኛ” የሚያመለክተው በኢየሱስ የሚያምኑትን ነው ። አት: - "እኛ በኢየሱስ የምናምነው እናውቃለን" (የበለስ_ቁጥር ይመልከቱ)

እያንዳንዳቸው ቢፃፉ ኖሮ
ይህንን በገባ መልኩ መተርጎም ይችላሉ። አት: - “አንድ ሰው ሁሉንም ቢጽፍላቸው” (የበለስ_ቁጥር / ይመልከቱ)

ዓለም ራሱ እንኳ መጽሐፎቹን መያዝ አልቻለም
ሰዎች ኢየሱስ በብዙ መጽሐፍት ከሚጽፉት የበለጠ ብዙ ተአምራትን ሠራ ። እዚህ ላይ ዮሐንስ የተጋነነ መጠቀምን ለማጉላት ጥቅም ላይ ውሏል ። (ይመልከቱ: የበለስ_ፀሐይ መከላከያ) ld ራሱ መጽሐፎቹን መያዝ አልቻለም

የሚፃፉ መጻሕፍት
ይህንን በገባ መልኩ መተርጎም ይችላሉ። አት: - “ሰዎች ስላደረጋቸው ነገሮች ሊጽ thatቸው የሚችሏቸው መጽሐፍት”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Acts

Acts

ምዕራፍ 1

1 ቴዎፍሎስ ሆይ፣ ኢየሱስ እስካረገበት ቀን ድረስ ለማድረግና ለማስተማር የጀመረውን ሁሉ የሚናገረውን የመጀመሪያውን መጽሐፍ ጻፍሁ፤ 2 ይህም የሆነው ጌታ
ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት እርሱ የመረጣቸውን ሐዋርያትን ካዘዘቸው በኋላ ነበር፤ 3 ለምርጦቹ ከመከራው በኋላ ሕያው ሆኖ ተገልጦላቸዋል። አርባ
ቀን እየታያቸው፣ ስለ እግዚአብሔር መንግሥትም እየተናገረ ቆየ። 4 ከእነርሱም ጋር ዐብሮ ሳለ ከኢየሩሳሌም እንዳይወጡ አዘዛቸው፤ ነገር ግን "ከእኔ
የሰማችሁትን አብ የሰጠውን ተስፋ ጠብቁ፤ 5 በእርግጥ ዮሐንስ በውሃ አጥምቆ ነበር፤ እናንተ ግን በጥቂት ቀናት ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ"
አለ። 6 ሐዋርያት በአንድነት ተሰብስበው ሳለ፣ “ጌታ ሆይ፣ ይህ የእስራኤልን መንግሥት የምትመልስበት ጊዜ ነውን?” ብለው ጠየቁት። 7 እርሱም እንደዚህ
አላቸው፤ “አብ በገዛ ሥልጣኑ የወሰነውን ጊዜ ወይም ወቅት ማወቅ እናንተን አይመለከትም። 8 ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ ሲመጣ፣ ኀይልን
ትቀበላላችሁ፤ በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ሁሉ፣ በሰማርያና እስከ ምድር ዳርቻ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ።” 9 ጌታ ኢየሱስ እነዚህን ነገሮች ከተናገረ በኋላ፣ ሐዋርያቱ
እያዩት ወደ ላይ ዐረገ፤ ደመናም ከዐይናቸው ሰወረው። 10 ትኵር አድርገው ወደ ሰማይ እየተመለከቱ ሳለ፣ ድንገት ነጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች
በአጠገባቸው ቆሙ። 11 እነርሱም፣ “እናንተ የገሊላ ሰዎች፣ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ለምን እዚህ ትቆማላችሁ? ወደ ሰማይ የወጣው ይህ ኢየሱስ ወደ
ሰማይ ሲሄድ ባያችሁበት ሁኔታ ተመልሶ ይመጣል” አሏቸው። 12 ከዚያም በኋላ፣ የሰንበት ቀን ጉዞ ያህል ከሚያስሄደው፣ በኢየሩሳሌም አቅራቢያ ካለው
ከደብረ ዘይት ተራራ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው ሄዱ። 13 ሐዋርያት እዚያ ሲደርሱ፣ ወደሚቈዩበት፣ ወደ ላይኛው ሰገነት ወጡ። እነርሱም ጴጥሮስ፣ ዮሐንስ፣
ያዕቆብ፣ እንድርያስ፣ ፊልጶስ፣ ቶማስ፣ በርተሎሜዎስ፣ ማቴዎስ፣ የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ፣ ቀናተኛው ስምዖንና የያዕቆብ ልጅ ይሁዳ ነበሩ። 14 ሁሉም በአንድነት
ሆነው፣ ሴቶቹ፣ የኢየሱስ እናት ማርያምና ወንድሞቹም ጭምር በጸሎት ይተጉ ነበር። 15 በዚያ ጊዜ ጴጥሮስ 120 ያህል በሚሆኑት ወንድሞች መካከል ቆመ፤
እንደዚህም አለ፤ 16 “ወንድሞች ሆይ፣ ኢየሱስን የያዙትንና መርቶ ያመጣውን ይሁዳን በሚመለከት መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ በዳዊት አፍ የተናገረው የመጽሐፍ
ቃል ይፈጸም ዘንድ አስፈላጊ ነበር። 17 ይሁዳ ከእኛ እንደ አንዱ ተቈጥሮና የዚህን አገልግሎት ድርሻም ተቀብሎ ነበርና። 18 “ይሁዳም ለክፉ ሥራው
በተከፈለው ዋጋ መሬት ገዛ። ከዚያም በግንባሩ ተደፋ፤ አካሉ ተሰነጠቀ፤ አንጀቱም ተዘረገፈ። 19 በኢየሩሳሌም ለሚኖሩ ሁሉ መሬቱ በቋንቋቸው አኬልዳማ
[የደም መሬት] ተብሎ እንደሚጠራ ታወቀ። 20 በመዝሙር መጽሐፍ፦ መኖሪያው ወና ይሁን፤ የሚኖርበት አንድ ሰውም እንኳ አይገኝ፤ ሹመቱንም ሌላ ሰው
ይውሰደው፤ ተብሎ ተጽፎአልና። 21 ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ በመካከላችን በገባባትና በወጣበት ጊዜ ሁሉ ዐብረውን ከቈዩ ሰዎች፣ 22 ይኸውም ዮሐንስ
ካጠመቀው ጥምቀት ጀምሮ ኢየሱስ ከእኛ እስካረገበት ቀን ድረስ፣ ከነበሩት ከእነዚህ አንዱ ከእኛ ጋር የትንሣኤው ምስክር ሊሆን ይገባል።” 23 ኢዮስጦስም
የሚባለውን፣ በርስያን ተብሎ የሚጠራውን ዮሴፍንና ማትያስን፣ ሁለት ሰዎችን እንዲቀርቡ አደረጉ። 24 እንደዚህ ብለውም ጸለዩ፤ “ጌታ ሆይ፣ የሰዎችን ሁሉ ልብ
አንተ ታውቃለህ፤ ስለዚህ ከእነዚህ ከሁለቱ የትኛውን እንደ መረጥኸው ግለጥ፤ 25 ይኸውም ይሁዳ ወደገዛ ስፍራው ትቶት በሄደው በዚህ አገልግሎትና
ሐዋርያነት ውስጥ ስፍራ እንዲያገኝ ነው።” 26 ሐዋርያት ዕጣዎችን ለእነርሱ ጣሉ፤ ዕጣውም ለማትያስ ወደቀ፤ እርሱም ከዐሥራ አንዱ ሐዋርያት ጋር አንድ ሆኖ
ተቈጠረ።

Acts 1:1

የሐዋርያት ሥራ 1፡ 1-3
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ሉቃስ ለቴዎፍሎስ ይህንን መጽሐፍ መጻፍ ለምን እንዳስፈለገው ያብራራል። ከዚህ መጽሐፍ በፊት በጻፈው መጽሐፉ ከዚህ መጽሐፍ በፊት የጻፈው መጽሐፍ የሉቃስ ወንጌልን ነው። ቴፍሎስ ሉቃስ ይህንን መጽሐፍ የጻፈው ቴዎፍሎስ ተብሎ ለሚጠራ ሰው ነው። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች በባሕላቸው ደብዳቤ በሚጻፍበት ወቅት መግቢያው ላይ የሚጻፈውን ነገር በመከተል “ውድ ቴዎፍሎስ ሆሕ” በማለት ተርጉመውታል። ቴዎፍሎስ ማለት “የእግዚአብሔር ወዳጅ” ማለት ነው። እስከ አረገበት ቀን ድረስ ያለውን ይህ የሚያመለክተው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ያረገበት ወቅት ነው። በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የሰጠውን ትዕዛዝ መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ በተወሰኑ ነገሮች ዙሪያ የተለያዩ መመሪያዎችን በመስጠት ሂደት ውስጥ መሪቶታል። ከመከራው በኋላ ይህ ኢየሱስ የተቀበለውን መከራን እና በመስቀል ላይ የሞተውን ሞት ያመለክታል። ሕያው ሆኖ እንደገና ለእነርሱ ታያቸው ኢየሱስ ከመጀመሪያዎቹ ዐሥራ ሁለት ደቀ መዛሙርት በተጨማሪ ለብዙ ሰዎች ከሞት ከተነሣ በኋላ ታይቷቸዋል።

Acts 1:4

የሐዋርያት ሥራ 1፡ 4-5
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ይህ ሁኔታ የተፈጸመው ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ ለዐርባ ቀናት ለደቀ መዛሙርቱ በተያየበት ጊዜያት ነው። . . . ሳለ "እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢየሱስ ነው። ከእነርሱ ጋር "እነርሱ" የሚያመለክተው ዐሥራ አንዱ ሐዋርያት ነው። የአባትን የተስፋ ቃል ይህ መንፈስ ቅዱስን የሚያመለክት ቃል ነው። በውሃ ያጠምቃችኋል . . . በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ ኢየሱስ መጠምቁ ዮሐንስ በውሃ ያጠመቀበት መንገድ እግዚብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ከሚጠምቅበት መንገድ ጋር ያነጻጽራል። መጥመቁ ዮሐንስ በእርግጥ በውሃ አጥምቋል "ዮሐንስ በእርግጥ ሰዎችን በውሃ አጥምቋል" ትጠመቃላችሁ አመራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር ያጠምቃችኋል"

Acts 1:6

የሐዋርያት ሥራ 1፡ 6-8
ለእስራኤል መንግስትን የሚትመልስበት ወራት ይህ ነውን "እስራኤልን እንደገና ጠንካራ ሀገር የሚታደርግበት ጊዜ አሁን ነውን?" ጊዜው ወይም ዘመኑን "ጊዜውን ወይም ቀናቱን" ኃይል ትቀበላላችሁ "በመነንፈሳዊነት ትጠነክራላችሁ" እናም ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አማራጭ ትርጉም: “የእኔ ምስክሮች ትሆኑ ዘንድ" እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ "በዓለም ዙሪያ" ወይም "እስከ ምድር ጥግ ድረስ"

Acts 1:9

የሐዋርያት ሥራ 1:9-11
እየተመለከቱት ሳለ "ሐዋርያቱ ወደ ሰማይ እየተመለከቱ ሳለ" ዳመናው ከዐይናቸው ጋረደው "ወደ ሰማይ አረገ እና ዳመናውም ከዐይናቸው ጋረደው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ስለዚህም ከሊያዩት አልቻሉም" ወደ ሰማይ አተኩረው ሲያዩ ሳለ "ወደ ሰማይ እየተመለከቱ" ወይም “ሰማይ ሰማዩን ሲያዩ ሳለ” እናንተ የገሊላ ሰዎች ሆይ "እናንተ ሐዋርያት"

Acts 1:12

የሐዋርያት ሥር **1**: **12**-**14**
ከዚያም ተመለሱ "ሐዋርያቱ ተመለሱ" የሰንበት ጉዞ ያኽል ርቀት ይህ በፈርሳዊያን ደንብ መሰረት ሰዎች በሰንበት ማድረግ የተፈቀደላቸው ነገር ነበር። እዚያ በደረሱ ጊዜበ "በኢየሩሳሌም ውስጥ ወደሚገኘው ለሄዱ ወደአሰቡት ስፍራ በደረሱ ጊዜ" ሰገነት "በቤት ውስጥ በከፍታ ላይ የሚገኝ ክፍል" ቀናተኛው ስምኦን "ለሀገሩ ይዋጋ የነበረው ስምኦን።" ብዙ ቀናተኞች ነበሩ ነገር ግን ከእርሱ መካከል ሐዋርያ የሆነው ስምኦን ብቻ ነው። ቀናተኞች ሮማዊያን እስራኤልን መግዛት እንዲያቆሙ የሚታገሉ ሰዎች ናቸው። ሁልም በአንድ ልብ ሆነው ሳሉ ቡድኑ በአንድ ልብ ነበር፤ በመካከላቸው መከፋፍል አልነበረም። በትጋት እየጸለዩ ሳሉ "በአንድ ላይ ሆነው በትጋት ስጸልዩ ሳለ"

Acts 1:15

የሐዋርያት ሥራ **1**: **15**-**16**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ይህ ነገር ጴጥሮስ እና ሌሎች አማኞች በእንድነት በሰገነት ላይ ሳሉ የተፈጸመ ነገር ነው። በእነዚያ ቀን "ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከተመለሰ በኋላ ባሉት እነዚያ ቀናት" በወንድሞች መካከል በዚህ ክፍል ውስጥ “ወንድሞች” የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ የሚያመለክተው አማኞችን ሆኖ ወንዶችን እና ሴቶችን ያካትታል። በቅዱሳት መጻሕፍት የተነገረው ነገር ይፈጸም ዘንድ አስፈላጊ ነው ጴጥሮስ በዚህ ሥፍራ ላይ በተለይ ከይሁዳ ጋር ተያያዥነት ስላለውን ትንቢት እየተናገረ ነው። በዳዊት አፍ "የዳዊት ቃል።" በዚህ ሥፍራ ላይ ጥቅም ላይ የዋለው “አፍ” የሚለው ቃል “ቃል” የሚያመልክት ሲሆን ዳዊት የተናገራቸውን ቃል ያመለክታል።

Acts 1:17

የሐዋርያት ሥራ **1**: **17**-**19**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጴጥሮስ በ ACT 1:16 ላይ ለአማኞች መናገር የጀመረውን ንግግር የቀጠለበት ክፍል ነው። አጠቃላይ መረጃ: በቁጥር 18-19 ውስጥ ይሁዳ ስላደረገው ነገር የኋላ ታሪክ የተሰጠበት እና እንዴት እንደሚተ የተገለጸበት ክፍል ነው። አሁን ይህ ሰው "አሁን ይሁዳ" ባደረገው ክፉ ነገር የተከፈለው ክፍያ በዚህ ክፍል “ክፍያ” የሚለው ነገር እና “ተግባር”። አማራጭ ትርጉም: “ስላደረገው ክፉ ነገር የተከፈለው ክፍያ።” በክፉ ተግባሩ "የኢየሱስን ጠላቶች ወደ እርሱ የመራበት ክፉ ተግባሩ።" ይህ “ክፉ ተግባሩ” የሚለው ቃል በግልጽ ምንን እንደሚያመለክት ያሳያል።

በግንባሩም ተደፍቶ ከመካከሉ ተሰነጠቀ አንጀቱም ሁሉ ተዘረገፈ። ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎ ይሁዳ ራሱን አንቆ ሞተ ይላሉ። የደም መሬት . . . ተብሎ ይታወቅ ነበር። በሞት ምክንያት ሰዎች መሬቱን በአዲስ ስም ይጠሩት ጀምሯል።

Acts 1:20

የሐዋርያት ሥራ **1**: **20**-**20**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጴጥሮስ በ ACT 1:16 ላይ ለአማኞች መናገር የጀመረውን ንግግር የቀጠለበት ክፍል ነው። አጠቃላይ መረጃ: ከዚህ በፊት በተነገረው የይሁዳ ታሪክ መሠረት ጴጥሮስ ከመዝሙር መጽሐፍ ውስጥ ያልን ምንባብ በማስታወስ አሁን ላሉበት ሁኔታ ተስማሚ እንደሆነ አምኗል። ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተወሰደው ክፍል ማብቂያ ይህ ክፍል ነው። በመዝሙር መጽሐፍ ውስጥ እንዲህ ተብሎ ተጽፈዋል ጴጥሮስ ይህንን ሀረግ በመናገሩ ሰዎች ይህንን የተናገረው ከመዝሙር መጽሐፍ ላይ ወስዶ እንደሆነ ያውቃሉ። የመዝሙር መጽሐፍ ይህ መጽሐፍ የቅዱስ መጽሐፍ አንዱ ክፍል ነው። አማራጭ ትርጉም: "የመዝሙር መጽሐፍ" ወይም "የመዝሙሮች መጽሐፍ።" መሬቱ ወና እና ምድረ በዳ ከመሆኑ የተነሳ ሰዎች የመሬቱ ባለቤት ሞቷል ብለው ያስባሉ። እንዲሁም የሚኖርባት አይኑር መሬቱ የተረገመ ወይም ለሰዎች መኖሪያ የሚሆን አይሁን። የእርሱን የመሪነት ሥፍራ ሌላ ሰው ይውሰደው "በእርሱን የመሪነት ሥፍራ በሌላ ሰው ይተካ"

Acts 1:21

የሐዋርያት ሥራ **1**: **21**-**23**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጴጥሮስ በ ACT 1:16 ላይ ለአማኞች መናገር የጀመረውን ንግግር የቀጠለበት ክፍል ነው። ስለዚህ . . . አስፈላጊ ነው ጴጥሮስ ከመዝሙር መጽሐፍ የወሰደውን ክፍል ለምን በዚህ ሥፍራ መናገር እንዳለበት ማብራሪቱን እንዳስፈለገው እና በዚህም መሠረት ምን ማድረግ እንዳለባቸው ገልጸዋል። ከእኛ ጋር የነበረ . . . ለእርሱ ትንሳዔ ከእኛ ጋር ምስክር ሊሆን የሚችል ሰው ጴጥሮስ ይሁዳን እንደ ሐዋርያ ሊተካው የሚችለው ሰው ማሟላት የሚገባው መሥፈርት ምን እንደሆነ እየገለጸ ነው። ሁለት ሰዎችን ለምርጫ አቀረቡ ይሁዳን በሌላ ሰው ለመተካት በመሞከር ሂደታቸው ውስጥ ሁለት ለምርጫው ብቁ የሆኑ ሰዎችን አቀረቡ። ኢዮስጦስም የሚሉትን በርስያን የተባለውን ዮሴፍን ዮሴፍ በርስያን እና ኢዮስጦስ በተባሉ ሁለት ስሞች ይታወቃል።

Acts 1:24

የሐዋርያት ሥራ **1**: **24**-**26**
ጸለዩ "ከዚያም አማኞች ጸሎት አደረጉ" ጌታ ሆይ አንተ የሰዎችን ሁሉ ልብ ታውቃለህ "ጌታ ሆይ የሁሉንም ሰው የውስጥ መነሻ ምክንያን እና ሀሳብን ታውቃለህ" ይህንን አገልግሎት እና ሐዋርያነት እንዲተካ ከእነዚህ ሁለት ሰዎች መካከል ዬትኛውን አንተ እንደሚትመረጥ ግለጥልን "ስለዚህም ከሐዋርያቱ ጋር እንዲሆን ባዶ የሆነውን ቦታ እንዲተካ ከእነዚህ ሰዎች መካከል ማንን አንደመረጥክ እግዚአብሔር ሆይ አሳየን" ይሁዳ ወደ ገዛ ራሱ ስፍራ ይሄድ ዘንድ በተዋት ይሁዳ ኢየሱስን በመካዱ እና በበሞቱ ምክንያት ኃላፊነቱን ትቶ ሄዷል። ዕጣም ተጣጣሉላቸው፥ በዮሴፍ እና በማቴያስ መካከል ዕጣ ጣሉ ዕጣውም ለማትያስ ወደቀ የተጣለውም ዕጣ ማትያስ መመረጡን አመለከተ። ከአሥራ አንዱ ሐዋርያት ጋር ተቈጠረ። "ደቀ መዛሙርቱም እረሱን ከሐዋርያት መካከል እንዱ እንደሆነ ቆጠሩት"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 2

1 በበዓለ ኀምሳ ቀን ሁሉም በአንድነት አንድ ስፍራ ላይ ነበሩ። 2 ድንገት እንደ ኀይለኛ ዐውሎ ነፋስ ያለ ድምፅ ከሰማይ መጣ፤ ተቀምጠውበት የነበረውን
ቤትም ሞላው። 3 እንደ እሳት የተከፋፈሉ ልሳናት ታዩአቸው፤ በእያንዳንዳቸው ላይም ተቀመጡባቸው። 4 ሁሉም መንፈስ ቅዱስን ተሞሉ፤ መንፈስ ቅዱስ
እንዲናገሩ እንደ ሰጣቸውም በሌሎች ቋንቋዎች መናገር ጀመሩ። 5 በዚያን ጊዜ ከሰማይ በታች ካለው ሕዝብ ሁሉ የመጡ፣ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች፣
በኢየሩሳሌም የሚኖሩ አይሁድ ነበሩ። 6 ይህ ድምፅ ሲሰማ፣ ብዙ ሕዝብ በአንድነት ተሰበሰበ፣ እያንዳንዱ ሰውም በገዛ ራሱ ቋንቋ ሲናገሩ በመስማቱ ግራ
ተጋባ። 7 ሕዝቡ ተደነቁ፤ ተገረሙም፤ “እነዚህ የሚናገሩ ሰዎች ሁሉ በእውነት የገሊላ ሰዎች አይደሉምን? ብለውም ተናገሩ። 8 እያንዳንዳቸው በተወለድንበት
ቋንቋ ሲናገሩ የምንሰማቸው ለምንድን ነው? 9 የጳርቴና፣ የሜድና የኢላሜጥ ሰዎች፣ በመስጴጦምያም፣ በይሁዳም፣ በቀጶዶቅያም፣ በጳንጦስም፣ በእስያም፣
10 በፍርግያም፣ በጵንፍልያም፣ በግብፅም፣ በቀሬና በኩል በሚገኙት የሊቢያ ክፍሎች የምንኖርም፣ ከሮም የመጣን፣ 11 አይሁድና ወደ ይሁዲነት የገባን
ቀርጤሳውያንና ዐረባውያን የሆንን እኛም፣ እነዚህ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ታላላቅ ሥራዎች በራሳችን ቋንቋዎች ሲናገሩ እንሰማቸዋለን።" 12 ሁሉም ተደነቁ፣
ግራ ተጋቡም፤ እርስ በርሳቸውም፣ “ይህ ነገር ምን ይሆን?” ተባባሉ። 13 ሌሎች ግን፣ “ዐዲስ ወይን ጠጅ ጠጥተው ጠግበው ነው” ብለውም በማፌዝ
ተናገሩ። 14 ነገር ግን ጴጥሮስ ከዐሥራ አንዱ ጋር ቆሞ፣ ድምፁን ከፍ በማድረግ እንደዚህ አላቸው፤ “የይሁዳ ሰዎችና በኢየሩሳሌም የምትኖሩ ሁሉ፣ ይህ
ለእናንተ የታወቀ ይሁን፤ የምናገረውንም አድምጡ። 15 እነዚህ ሰዎች እናንተ እንደምታስቡት አልሰከሩም፤ ምክንያቱም ገና ከቀኑ ሦስተኛ ሰዓት ነው። 16 ነገር
ግን በነቢዩ በኢዩኤል ይህ ተነግሯል፦ 17 ‘በመጨረሻዎቹ ቀናት ይህ ይሆናል፣’ እግዚአብሔር እንደዚህ ይላል፤ ‘መንፈሴን ሥጋ በለበሱ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ፣
ወንዶች ልጆቻችሁና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ። ወጣቶቻችሁ ራእይ ያያሉ፤ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልም ያልማሉ። 18 በአገልጋዮቼና በሴት አገልጋዮቼ
ላይም በእነዚያ ቀናት መንፈሴን አፈስሳለሁ፤ እነርሱም ትንቢት ይናገራሉ። 19 በላይ በሰማይ ድንቆችን፣ ምልክቶችንም በታች በምድር ላይ፣ ደምን፣ እሳትንና
የጢስ ደመናን አሳያለሁ። 20 ታላቁና ገናናው የጌታ ቀን ከመምጣቱ በፊት፣ ፀሓይ ወደ ጨለማነት፣ ጨረቃም ወደ ደምነት ይለወጣሉ። 21 የጌታን ስም
የሚጠራ ሁሉ ይድናል።' 22 የእስራኤል ሰዎች ሆይ፣ እነዚህን ቃሎች ስሙ፦ ራሳችሁ እንደምታውቁት የናዝሬቱ ኢየሱስ፣ በመካከላችሁ እግዚአብሔር በእርሱ
በኩል ባደረጋቸው ታላላቅ ተግባራት፣ በተኣምራትና በምልክቶች፣ ከእግዚአብሔር ለእናንተ መገለጡ የተረጋገጠ ሰው ነው። 23 አስቀድሞ በተወሰነው
የእግዚአብሔር ዕቅድና በቀዳሚ ዕውቀቱ መሠረት፣ ዐልፎ ተሰጥቶአል፤ እናንተም በዐመፀኞች እጅ ሰቀላችሁት፤ ገደላችሁትም፤ 24 እግዚአብሔርም የሞትን
ጣር ከእርሱ አጥፍቶ አስነሣው፤ ምክንያቱም ሞት እርሱን ይይዘው ዘንድ አልቻለም። 25 ዳዊት ስለ እርሱ እንዲህ ብሎ ይናገራልና፦ ‘ጌታን ሁልጊዜ በፊቴ
አየሁት፤ በቀኜ ነውና አልናወጥም። 26 ስለዚህ ልቤ ተደሰተ፤ አንደበቴም ሐሤት አደረገ። ሥጋዬም በተስፋ ያድራል። 27 ነፍሴን በሲኦል አትተዋትም፤
ቅዱስህም መበስበስን እንዲያይ አትፈቅድም። 28 የሕይወትን መንገድ ገለጥህልኝ፤ በፊትህም ደስታን ታጠግበኛለህ።’ 29 ወንድሞች ሆይ፣ ስለ አባቶች አለቃ
ስለ ዳዊት በግልጽ ልነግራችሁ እችላለሁ፤ እርሱ ሞቶአል፤ ተቀብሮአልም፤ መቃብሩም እስከ ዛሬ ድረስ በእኛ ዘንድ ነው። 30 ስለዚህ ዳዊት ነቢይ ነበረና ከዘሩ
በዙፋኑ ላይ አንድን ሰው እንደሚያስቀምጥ እግዚአብሔር በመሐላ ለእርሱ ቃል ገብቶለት ነበር። 31 ዳዊት ይህን አስቀድሞ አየ፤ ስለ ክርስቶስ ትንሣኤም
ተናገረ፦ ክርስቶስ በሲኦል አልቀረም፤ ሥጋውም መበስበስን አላየም። 32 ይህን ኢየሱስን እግዚአብሔር አስነሣው፤ ለዚህም እኛ ሁላችን ምስክሮች ነን። 33
ስለዚህ ከሙታን በመነሣትና በእግዚአብሔር ቀኝ በመቀመጥ፣ ከአብ ቃል የተገባውን መንፈስ ቅዱስን ተቀብሎ፣ እናንተ የምታዩትንና የምትሰሙትን ይህን
አፈሰሰው። 34-35 ዳዊት ወደ ሰማይ አልወጣም፤ ነገር ግን እንዲህ ይላል፦ “ጌታ ለጌታዬ፣ ጠላቶችህን ለእግርህ መርገጫ እስከማደርጋቸው ድረስ በቀኜ
ተቀመጥ አለው።” 36 ስለዚህ፣ እናንተ የሰቀላችሁትን ይህን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ በእርግጥ
ይወቅ።" 37 ሕዝቡ ይህን ሲሰሙ ልባቸው ተነካና ለጴጥሮስና ለቀሩት ሐዋርያት፣ “ወንድሞች ሆይ፣ ምን እናድርግ?” አሉ። 38 ጴጥሮስም እንዲህ አላቸው፤
“ንስሓ ግቡ፤ እያንዳንዳችሁም ለኀጢአታችሁ ይቅርታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ መንፈስ ቅዱስንም በስጦታነት ትቀበላላችሁ። 39 የተስፋው ቃል
ለእናንተና ለልጆቻችሁ፣ ጌታ አምላካችን ለሚጠራቸው ሩቅ ላሉት ሁሉም ነውና።” 40 ጴጥሮስ በሌሎች ብዙ ቃላት መሰከረ፤ “ከዚህ ክፉ ትውልድ ራሳችሁን
አድኑ” በማለትም አስጠነቀቃቸው። 41 ከዚያም ሕዝቡ ቃሉን ተቀብለው ተጠመቁ፤ በዚያም ቀን ሦስት ሺሕ ያህል ሰዎች ተጨመሩ። 42 እነርሱም ሐዋርያት
በሚያስተምሩት ትምህርትና በኅብረት፣ እንጀራውን በመቍረስና በጸሎትም ይተጉ ነበር። 43 በሰው ሁሉ ላይ ፍርሀት መጣ፤ ብዙ ድንቆችና ምልክቶችም
በሐዋርያት እጅ ተደረጉ። 44 ያመኑት ሁሉ በአንድነት ነበሩ፤ ሁሉም ነገር የጋራ ነበር፤ 45 መሬታቸውንና ንብረታቸውን እየሸጡም ለሁሉም እንደሚያስፈልገው
አካፈሉ። 46 በየቀኑም በአንድ ዐላማ በመቅደስ እየተጉ፣ በቤት ውስጥ እንጀራ እየቈረሱም ምግብን ልባዊ በሆነ ደስታና ትሕትና ዐብረው ይመገቡ ነበር፤ 47
እግዚአብሔርን አመሰገኑ፤ በሕዝቡም ሁሉ ዘንድ ከበሬታ ነበራቸው። ጌታም የሚድኑትን በየቀኑ በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር።

Acts 2:1

ሐዋርያት ሥር 2፡ 1-4
አጠቃላይ መረጃ: ይህ አዲስ ክንውን ነው፤ አሁን የጴንጤ ቆስጤ ቀን ነው። ሁሉም በአንድነት ተሰብስበው ነበር “እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በሉቃስ 1፡ 15-16 ላይ በአንድነት የነበሩትን 120 አማኞችን ምናልባት የሚያመለክት ነው። ይህ ቁጥር ዐሥራ ሁለቱንም ሐዋርያትን ያካትታል። ድንገት ይህ ቃል በድንገር የተፈጸመን ነገር የሚያመለክት ነው። ከሰማይ ድምፅ መጣ "ድምፅ ከሰማይ መጣ" ድንገት እንደሚነጥቅ አውሎንፋሽ ያለ "ከባድ ንፋስ እንደሚነፍስ" ወይም "በጣም ጠንካር ንፋስ እንደሚነፍስ" ቤቱን ሙሉ ለሙሉ ይህ ምናልባት ቤት ወይም ትልቅ ሕንጻ ሊሆን ይችላል። እሳት የሚመስል ልሳን አማራጭ ትርጉሞች 1) ከእሳት የተሠሩ ምሳላሶች የሚመስሉ ልሳኖች ወይም 2) ልሳን የሚመስሌ ትንንሽ የእሳት ነበልባሎች። ክራዝ ስነድ የምላስ ቅርጽ ይዞ እንደሚነድ ሁሉ። በሌሎች ቋንቋ ተናገሩ ከዚህ በፊት በማያውቋቸው ቋንቋዎች።

Acts 2:5

የሐዋርያት ሥራ 2፡ 5-7
አጠቃላይ መረጃ: ቁጥር 5 በዚያ ዘመን በኢየሩሳሌም ይኖሩ ስለነበሩት አይሁዶች የኋላ ታሪክ የሚነግረን ሲሆን ከእነዚህም ሰዎች መካከል አብዛኞቹ ይህ ሁኔታ በተፈረ ጊዜ በቦታው ነበሩ። አሁን ይህ ቃል ከታሪኩ ታሪኩን ለመረዳት የሚያስችል የኋላ ታሪክ መረጃ ወደ መስጠጥ መሻገሩን የሚያሳይ ነው። ፈርሃ እግዚአብሔር ያላቸው ሰዎች እግዚአብሔርን ማክበር እና ማምለክ የሚፈልጉ ሰዎች ከሰማይ በታች ያሉ ሕዝቦች ሁሉ "በዓለም ውስጥ ያሉ ሕዝቦች ሁሉ" ይህ ድምፅ በተሰማ ጊዜ ይህ ድምፅ የትልቅ አውሎንፋስ ድምፅ ይመስል ነበር። አማራጭ ትርጉም፡ "ይህንን ድምፅ በሰሙ ጊዜ፡፡" ብዙ ሕዝብም "በጣ ብዙ ሕዝብም" ገሊላዊያን አማራጭ ትርጉም፡ "ከገሊላ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Acts 2:8

የሐዋርያት ሥራ **2**፡ **8**-**11**
ይህንን ስናገሩ የሚንሰማው ለምንድ ነው አማራጭ ትርጉሞች 1) ሰዎች መልስ ማግኘት የሚፈልጓቸው እውነኛ ጥያቄዎች ሊሆኑ ይችላሉ ወይም 2) በሁኔታው ምን ያኸል እንዳስገረማቸው የሚያሳይ ሊሆን ይችላል። UDB ይህንን የተረጎመው አስገራሚ የሆነ ነገርን እንደተመለከቱ አድርጎ ነው። የጳርቴ . . . የኢላሜጤም ሰዎች፥ "ከጳርቴ፣ ከሜድ እና ከኢላሜጤም የመጡ ሰዎች" ይሁዲነት "በዘር አይሁዳዊያን ያልሆኑ ነገር ግን ወደይሁዲነት የገቡ ሰዎች" ወይም "የአይሁድ ሃይማኖት መከተል የጀመሩ ሰዎች"

Acts 2:12

የሐዋርያት ሥራ **2**፡ **12**-**13**
ተገረሙ እና ግራ ገባቸው ሰዎች እየሆነ ስላለው ነገር ምን ማለት እንዳለባቸው ግራ መጋባታቸውን ያሳያል (UDB). አማራጭ ትርጉም: "ተደነቁ እና ግራ ተጋቡ።" ይህ ምን ማለት ነው በሆነው ነገር ሰዎች ተገረሙ። ሌሎች ግን ያፌዙ ነበር። "ሌሎች ግን ይሳደቡ" ወይም "ይዘባበቱ ነበር" ወይን ጠጥተው ሰክረዋል አማራጭ ትርጉም: "ሰክረዋ።" አንዳንዶች በሐዋርያቱ ላይ ይቀልዱባቸዋል ምክንያቱም በተዓምራት ለማመን ፍላጎት ስላሌላቸው ነው። አዲስ ወይን ከመደበኛው ወይን ይልቅ ጠንከር ያለ ወይን

Acts 2:14

የሐዋርያት ሥራ **2**፡ **14**-**15**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ጴጥሮስ በጴንጤቆስጤ ቀን ለነበሩት አይሁዳዊያን መስበክ ጀመረ። ከዐሥራ አንዱ ጋር በመሆን ሁሉም ሐዋርያት የጴጥሮስን ንግግር በመደገፍ ተነሱ። ገና ከቀኑ ሦስት ሰዓት ነው "ገና ከጥቃቱ ዘጠኝ ሰዓት ነው" በቀኑ ሦስት ሰዓት "ከጥቃት ዘጠኝ ሰዓት" (UDB)

Acts 2:16

የሐዋርያት ሥራ **2**፡ **16**-**17**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጴጥሮስ ለአይዳዊን መስበኩን ቀጥሏል። አጠቃላይ መረጃ: በዚህ ወቅት ጴጥሮስ ከዚህ ሁኔታ ጋር ተስማሚ የሆነ በነብይ ኢዮኤል አማካኝነት አስቀድሞ የተነገረ ትንቢትን አስታወሰ። በነቢዩ ኢዮኤል አማካኝነት የተነገረው ትንቢት ይህ ነው አማራጭ ትርጉም: "ይህ እግዚአብሔር የተናገረው እና ነብዩ ኢዮኤልን እንዲጽፈው ያደረገው ነገር ነው" ወይም "ነብዩ ኢዮኤል እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር እንዲህ ጽፎታል" ከአስቀድሞ የተነገረው አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር የተናገረው" ወይም "እግዚአብሔር ስለዚህ ነገር የተናረው" በመጨረሻው ዘመን አሁን ሊናገረው ያለው ነገር በመጨረሻው ዘመን እንደሚሆን የተነገረ ነው። ይህ እግዚአብሔር ከተናገረው ነገር የመጀመሪያው ክፍል ነው። “እግዚአብሔር እንዲህ ይላል” የሚለው ቃል በ UDB ውስጥ መጀመሪያ ላይ ሊመጣ ይችላል። አማራጭ ትርጉም: “በመጨረሻው ዘመን።” በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ መንፈሴን አፈሳለሁ ይህ ምሳሌያዊ ንግግር እግዚአብሔር መንፈሱን በሕዝቡ ላይ እንዴት በተተረፈረፈ መንገድ እንደሚሰጥ የሚያሳይ ነው። በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ “ሥጋ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰዎች ሁሉ ሥጋ ለባሽ መሆናቸውን ነው። አማራጭ ትርጉም: “ሁሉም ሰዎች።”

Acts 2:18

የሐዋርያት ሥራ **2**፡ **18**-**19**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጴጥሮስ የነብይ ኢዮኤል መጽሐፍ ውስጥ መውሰዱን ቀጥሏል። አገልጋይ . . . ሴት አገልጋዮች በብሉይ ኪዳን ውስጥ የእግዚአብሔር ነቢያት እና ሌሎች እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ሰዎች ብዙ ጊዜ የእርሱ “አገልጋዮች” ተብለው ይጠራሉ። መንፈሴን አፈሳለሁ እግዚአብሔርን መንፈሱን በልግስና ሰጥቷል። ትንቢት የእግዚአብሔርን እውነት ለመናገር እግዚአብሔር አነሳስተዋቸዋል። ትነት "ጤዛ" ወይም "ጭጋግ"

Acts 2:20

የሐዋርያት ሥራ **2**፡ **20**-**21**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጴጥሮስ ከነብዩ ኢዮኤል ትንቢት ወስዶ የተናገረውን ነገር የሚያበቃበት ጊዜ ነው። ፀሐይ ወደ ጨለማ ጨረቃም ወደ ደም ይለወጣሉ። የዚህ ሀረግ ቀጥተኛ ትርጉም አይታወቅም። በተቻላችሁ መጠን ወደ ቋንቋችሁ ስትተረጉሙ ቀጥተኛ ትርጉምን ለመከተል ሞክሩ። የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል አማራጭ ትርጉም: "የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል" የሚጠራ ጸሎት ወይም ልመና

Acts 2:22

የሐዋርያት ሥራ **2**፡ **22**-**24**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጴጥሮስ በ ACT 1:16 ላይ የጀመረውን ለአይሁዳዊያን መናገሩን የቀጠለበት ክፍል ነው። አስቀድሞ የታቀደ ዕቅድ እና የእግዚአብሔር ቅድመ እውቀት የክርስቶስ ሞት እንደ እግዚአብሔር ዕቅድ እና እውቀት መሠረት የተፈጸመ ነው። እናንተ “እናንተ” የሚለው የብዙ ቁጥር የተገለጸ ነው።” አሳልፎ ተሰጠ "ሰዎች አሳልፎ ሰጡት" ወይም "ሰዎች አሳልፈው ሰጡት" ከእርሱ ላይ የሞትን ጣር አንስቷል "ከሞት ጣር ነጻ አውጥቶታል" ነጻ መውጣት ይህ ማለት አንድ ሰው በገመድ ከታሠረበት እንደሚፈታው መፈታት ማለት ነው። መያዝ ሞት ኃይል ኢየሱስን ይዞ መቆየት አልቻለም።

Acts 2:25

የሐዋርያት ሥራ **2**፡ **25**-**26**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጴጥሮስ ለአይሁዳዊያን መናገሩን ቀጥሏል። አጠቃላይ መረጃ: በዚህ ሥፍራ ላይ ጴጥሮስ በዳዊት የተነገረውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በማስታወስ ከኢየሱስ ክርስቶስ መሰቀል እና መቃብርን ፈንቅሎ ከመነሳቱ ጋር ያያይዘዋል። አየሁት ነገሮች ከመከናወናቸው በፊት እግዚአብሔር በእርሱ ሕይወት ውስጥ እየሠራ መሆኑን ዳዊት ተመልክቷል። በፊቴ "በእኔ መገኘት ውስጥ" ወይም "ከእኔ ጋር" በቀኜ ቀኝ እጅ ጠንካራ ተደርጎ ይወሰዳል። በቀኝ እጅ እንደሆነ የሚታሰብ ሰው ጠንካራ አገልጋይ ወይም ጠንካር አጋዥ ተደርጎ ይወሰዳል። ልቤ ደስ አለው እዲሁም አንደበቴም ሐሴት አደረገ አማራጭ ትርጉም: "በጣም ደስ አለኝ እንዲሁም ሐሴት አደረኩኝ" ከዚህ በተጨናሪ ሥጋዬ በመተማመን ይኖራል አማራጭ ትርጉም: "ምንም እንኳ እኔ ሟች ቢሆንም በእግዚአብሔር ብቻ እተማመናለለሁ"

Acts 2:27

የሐዋርያት ሥራ **2**። **27**-**28**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጴጥሮስ ከዳዊት ንግግር ውስጥ መውሰዱን ያጠነናቀቀበት ሥፍራ ነው። ቅዱስህንም "ቅዱስህን" ወይም "ምርጥህን" መበስበስን ያይ ዘንድ የሞተው አካሉ ይበሰብስ ዘንድ በዚያ ለረጅም ጊዜ አትተወውመም። አማራጭ ትርጉም: "ይበሰብስ ዘንድ።" የአኗኗር ዘይቤ "ሕይወት ሰጭ እውነት"

Acts 2:29

የሐዋርያት ሥራ **2**፡ **29**-**31**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጴጥሮስ በ ACT 1:16. ላይ ለአይዳዊያን ማደረግ የጀመረውን ንግግር ቀጥሏል። አባቶች ይህ ከብዙ ዘመናት በፊት ይኖሩ የነበሩትን አባቶችን ያመለክታል። ብዙ ጊዜ አባቶ ከአጠቃላይ ሕዝቡ በመጀመሪው ረድፍ ላይ የሚገኙትን ያመለክታል። መማል አንድ ሰው ስሚል መኃላው እውነት መሆኑን እያረጋገጠ ነው። መኃላ “መኃላ” አንድ ነገር ልክ ለመሆኑ ማረጋገጫ ዓረፍተ ነገር ነው። አስቀድሞ ተመለከተ ዳዊት አስቀድሞ ተመልክቶ ስለ መስሑ ተናገረ።

Acts 2:32

የሐዋርያት ሥራ **2**፡ **32**-**33**
የእግዚአብሔር ቀኝ እጅ ይህ የመተማመን፣ የክብር፣ የሞገስ፣ መታመን፣ ኃይል እና ጥቅም የማግኛ ሥፍራ ነው።

Acts 2:34

የሐዋርያት ሥራ **2**፡ **34**-**36**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ይህ ጴጥሮስ በ ACT 1:16 ላይ ለአይዳዊያን ማደረግ የጀመረውን ንግግር የሚቋጭበት ክፍል ነው። ጌታ ጌታዬን እንዲህ አለው "ጌታ እግዚአብሔር ለጌታዬ (ለክርስቶስ) እንዲህ አለው" በቀኜ ተቀመጥ "የክብር፣ የተለየ ጥቅም፣ መታመን እና ኃይል የሚታገኝበት ሥፍራ ሥፍራ፣ ከእኔ አጠገብ ተቀመጥ።" ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደረግ ድረስ "ጠላቶችህ ተሸናፊዎች እስካደረግ ድረስ"

Acts 2:37

የሐዋርያት ሥራ **2**፡ **37**-**39**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: አይሁዳዊያን ለጴጥሮስ ንግግር ምላሽ ሰጡ ጴጥሮስም መለሰላቸው። ልባቸው ተነካ ሉቃስ ይህንን ምሳሌያዊ ንግግር በመጠቀም አጽኖት በመስጠት ማስተላለፍ የፈለገው መልዕክት ይህንን ዓረፍተ ነገር መሰስማታቸው ምን ይኽል የሚያሳዝን መሆኑን ነው። ተስፋውም ለእናንተ ነው "ተስፋው ለእናንተ ነው

Acts 2:40

የሐዋርያት ሥራ **2**፡ **40**-**42**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ይህ በጴንጤ ቅስጤ ቀን የተፈጸመው ታርክ ክፍል ፍጻሜ ነው። አጠቃላይ መረጃ: ቁጥር 42 አማኞች ከጴኝጤ ቆስጤ ቀን በኋላ እንዴት ይኖሩ እንደነበር ማብራራት ይጀምራል። (ተመልከት: [[End of Story]]) መሰከረ በአዲስ ኪዳን መጽሐፍት ውስጥ “ምስክር” የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለው የኢየሱስ ተከታዬች የኢየሱስን ሕይወት፣ ሞት እና ትንሳዔ እንዴት ይናገሩ እንደነበር ለመግለጽ ነው። ጠማማ ትውልድ "በጣም ክፉ የሆነ ትውልድ" ተቀበለ "አምኗል" ወይም "ተቀብሏል" ተጠመቀ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት አጠመቋቸው። ወደ ሦስት ሺህ ይጠጋሉ አማራጭ ትርጉም: "ወደ 3,000 ሰዎች"

Acts 2:43

የሐዋርያት ሥራ **2**፡ **40**-**42**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ይህ በጴንጤ ቅስጤ ቀን የተፈጸመው ታርክ ክፍል ፍጻሜ ነው። አጠቃላይ መረጃ: ቁጥር 42 አማኞች ከጴኝጤ ቆስጤ ቀን በኋላ እንዴት ይኖሩ እንደነበር ማብራራት ይጀምራል። (ተመልከት: [[End of Story]]) መሰከረ በአዲስ ኪዳን መጽሐፍት ውስጥ “ምስክር” የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለው የኢየሱስ ተከታዬች የኢየሱስን ሕይወት፣ ሞት እና ትንሳዔ እንዴት ይናገሩ እንደነበር ለመግለጽ ነው። ጠማማ ትውልድ "በጣም ክፉ የሆነ ትውልድ" ተቀበለ "አምኗል" ወይም "ተቀብሏል" ተጠመቀ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት አጠመቋቸው። ወደ ሦስት ሺህ ይጠጋሉ አማራጭ ትርጉም: "ወደ 3,000 ሰዎች"

Acts 2:46

የሐዋርያት ሥራ **2**፡ **46**-**47**
ቀጠሉበት "አማኞች ቀጠሉ" በአንድ ዓላማ "በአንድ ልብ" እንጀራ መቁረስ ምግባቸውን በጋራ መመገብ። የልብ ትህትና ይህ ማለት ያለምንም ቅድመ እሳቤ፣ በግልጽ፣ ያለምንም የአካሄድ ስርዓት፣ ያለ ደረጃ ማለት ነው። ሞገስ ነበራቸው "በሰዎች ዘንድ ይከበሩ ነበር"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 3

1 ጴጥሮስና ዮሐንስ በጸሎት ጊዜ፣ በዘጠኝ ሰዓት ወደ ቤተ መቅደስ ይወጡ ነበር። 2 ወደ ቤተ መቅደሱ ከሚገቡ ሰዎች ምጽዋት መለመን እንዲችል፣ ውብ
ተብሎ በሚጠራው በቤተ መቅደሱ በር ላይ ሰዎች በየቀኑ በሸክም አምጥተው የሚያስቀምጡት፣ ከተወለደበት ጊዜ ጀምሮ ዐንካሳ የሆነ አንድ ሰው ነበረ። 3
ጴጥሮስንና ዮሐንስን ወደ ቤተ መቅደሱ ሊገቡ ሲሉ ባያቸው ጊዜ፣ ምጽዋት ለመነ። 4 ጴጥሮስ ዐይኖቹን ምጽዋት በሚለምነው ሰውዬ ላይ በማድረግ፣ ከዮሐንስ
ጋር “ወደ እኛ ተመልከት” አለው። 5 ዐንካሳውም፣ ከእነርሱ አንድ ነገር ለመቀበል በመጠበቅ ወደ እነርሱ ተመለከተ። 6 ጴጥሮስ ግን፣ “ብርና ወርቅ የለኝም፤
ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ። በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተራመድ” አለው። 7 ጴጥሮስ ቀኝ እጁን ያዘውና ወደ ላይ አነሣው፤ ወዲያውም እግሮቹና
የቍርጭምጭሚቱ ዐጥንቶች ጥንካሬ አገኙ። 8 ዐንካሳው ሰውዬ ወደ ላይ ዘልሎ ቆመ፤ መራመድም ጀመረ፤ ከጴጥሮስና ከዮሐንስ ጋርም እየተራመደ፣
እየዘለለና እግዚአብሔርን እያመሰገነ ወደ ቤተ መቅደስ ገባ። 9 ሰዎች ሁሉ ዐንካሳው እየተራመደ ሲሄድና እግዚአብሔርን ሲያመሰግን አዩት። 10 ምጽዋት
ለመቀበል ውብ በሚባለው የቤተ መቅደሱ በር ላይ ይቀመጥ የነበረው ሰውዬ እንደ ሆነም ዐወቁ፤ በእርሱ ላይ ከሆነው የተነሣም በመደነቅና በመገረም ተሞሉ።
11 ሰውየው የጴጥሮስንና የዮሐንስን እጅ ይዞ ሳለ፣ የሰሎሞን መመላለሻ በሚባለው ደጅ ሰዎች ሁሉ በኀይል እየተደነቁ በአንድነት ወደ እነርሱ ሮጡ። 12
ጴጥሮስ ይህን ሲያይ ለሕዝቡ፣ “እናንተ የእስራኤል ሰዎች ሆይ፣ ለምን ትደነቃላችሁ? ይህን ሰው በገዛ ኀይላችን ወይም በመንፈሳዊነታችን እኛ እንዲራመድ
እንዳደረግን ሁሉ፣ ለምን ዐይናችሁን አፍጥጣችሁ ትመለከታላችሁ? በማለት መልስ ሰጠ። 13 የአብርሃም፣ የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ፣ የአባቶቻችን አምላክ
አገልጋዩን ኢየሱስን አክብሮታል። እርሱ አሳልፋችሁ የሰጣችሁትና ጲላጦስ ሊፈታው ወስኖ ሳለ፣ በፊቱ የካዳችሁት ነው። 14 ቅዱሱንና ጻድቁን ካዳችሁት፤
በእርሱም ፈንታ ነፍሰ ገዳይ እንዲፈታላችሁ ለመናችሁ። 15 እግዚአብሔር ከሙታን ያስነሣውን፣ የሕይወትን ጌታ ገደላችሁት፤ እኛም የዚህ ምስክሮች ነን። 16
በእርሱ ስም ማመን አሁን የምታዩትንና የምታውቁትን ይህን ሰው ብርቱ አድርጎታል። አዎ፣ በኢየሱስ ያለው እምነቱ በሁላችሁ ፊት ይህን ፍጹም ጤንነት ሰጠው።
17 አሁን ወንድሞች ሆይ፣ አለቆቻችሁም እንዳደረጉት ባለማወቅ ያደረጋችሁት እንደ ሆነ ዐውቃለሁ። 18 ነገር ግን እግዚአብሔር በነቢያቱ ሁሉ አፍ የእርሱ
ክርስቶስ መከራ መቀበል እንዳለበት አስቀድሞ የተናገረውን አሁን ፈጸመው። 19 እንግዲህ ኀጢአታችሁ እንዲደመሰስ፣ ከጌታ ዘንድም የመታደስ ዘመን
እንዲመጣ ንስሓ ግቡ፤ ተመለሱም፤ 20 ይኸውም ለእናንተ የመረጠውን ክርስቶስ የሆነውን ኢየሱስን እንዲልከው ነው። 21 እርሱ ሰማያት ሊቀበሉትና ነገሮች
ሁሉ እስከሚታደሱበት ዘመን ድረስ ጠብቀው ሊያቈዩት የሚገባ፣ ከጥንት ጀምሮ በነበሩ ቅዱሳን ነቢያቱ አፍ የተነገረለት ነው። 22 ሙሴ በእርግጥ፣ ‘ጌታ
እግዚአብሔር ከወንድሞቻችሁ መካከል እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣል። የሚነግራችሁንም ሁሉ ስሙ’ አለ። 23 ያን ነቢይ የማይሰማ ሰው ሁሉ ከሕዝቡ መካከል
ተለይቶ ይጠፋል። 24 አዎ፣ ከሳሙኤል ጀምሮና ከእርሱም በኋላ የተናገሩ ነቢያት ሁሉ ስለ እነዚህ ቀኖች ተናግረዋል። 25 እናንተ የነቢያትና ‘በዘርህ የምድር
ሕዝቦች ሁሉ ይባረካሉ’ ብሎ ለአብርሃም እንደ ተናገረው፣ ከአባቶቻችሁ ጋር እግዚአብሔር ያደረገው ኪዳን ልጆች ናችሁ። 26 እግዚአብሔር አገልጋዩን ካስነሣ
በኋላ በመጀመሪያ ወደ እናንተ ላከው፤ ይኸውም እያንዳንዳችሁን ከክፋታችሁ መልሶ ሊባርካችሁ ነው።

Acts 3:1

የሐዋርያት ሥራ 3: 1-3
አያያዥ ዓረፍ ነገር: ይህ አዲስ ቀን ነው፤ ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ወደ ቤተ መቅደሱ እየሄዱ ነው። ቁጥር 2 ላይ ስለ ሽባው ሰው የኋላ ታሪክ የተሰጠበት ነው። ወደ ቤተ መቅደሱ "በቤተ መቅደሱ አከባቢ" ወይም "ቤተ መቅደሱ።" ካህናቱ ወደሚያገለግሉበት የውስጠኛው የሕንጻው ክፍል ገና አልገቡም። በዘጠኝ ሰዓት "ከሰዓት በኋላ ወደ ዘጠኝ ሰዓት ገደማ" (UDB) ምጽዋት “ምጽዋት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰዎች ለድሆች የሚሰጡትን ገንዘብ ነው።

Acts 3:4

የሐዋርያት ሥራ 3: 4-6
እርሱን አተኩሮ እያየው "አተኩሮ እያየው" ወይም "ወደ እርሱ አተኩሮ እየተመለከተ" ሽባው ሰው ወደ እነርሱ እየተመለከ "ሽባው ሰው እነርሱን አተኩሮ እየተመለከተ" ብር እና ወርቅ ብር እና ወርቅ ገንዘብን የሚሉት ሀረጋት ለመወከል ጥቅም ላይ ይውላሉ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም "በኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል"

Acts 3:7

የሐዋርያት ሥራ 3: 7-8
ወደ ቤተ መቅደሱ ገቡ ሰዎቹ ወደ ቤተ መቅደሱ ቅጥር ውስጥ ገቡ። ወደ ቤተ መቅደሱ ውስጥ መግባት የሚችሉት ካህናት ብቻ ነው።

Acts 3:9

የሐዋርያት ሥራ 3: 9-10
አስተዋሉ "ተመለከቱ" ወይም "አዩ" መልካም መግቢያ "መልካም ተብሎ የሚጠራ መግቢያ"

Acts 3:11

የሐዋርያት ሥራ 3: 11-12
ሳለ "እያለ" የሰለሞን መመላለሻ ደጅ ተብሎ ከሚጠራው "የሰለሞን መመላለሻ ደጅ።" ሰለሞን ከብዙ ዘመናት በፊት ይኖር የነበረ የእስራኤል ልንጉሥ ነው። መመላለሻ ደጅ በአንድ በኩል ክፍት የሆነ ራቅ ራቅ ተደርገው በተተከሉ ምሰሶዎች በተደገፉ ላይ በተመታ ጣሪያ ያለው ነው። እየተደነቁ "በጣም በመገረም" ወይም "በአድናቆት" ጴጥሮስ ይህንን ባየ ጊዜ "ጴጥሮስ የተሰበሰቡት ሰዎች ቁጥጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደረገ መሄዱን ስመለከት" ወይም "ጴጥሮስ ሕዝቡን ሲያይ" (UDB)

እናንተ የእስራኤል ሰዎች ሆይ "እናንተ እስራኤላዊያን" (UDB)። ይህን በማለት ጴጥሮስ ለሕዝቡ እየተናገረ መሆኑኑ መመልከት ይቻላል። በዚህ አውድ ውስጥ “ሰዎች” የሚለው ቃል በዚያ ሥፍራ ላይ የተገኙትን ሰዎች ሁሉ ይወክላል። ስለምን ተደነቃችሁ? አማራጭ ትርጉም: "በዚህ ልትደነቁ አያስፈልግም" ዐይኖቻችሁ ስለምን በእኛ ላይ ሆነ አማራጭ ትርጉም: "ትኩረታችሁን በእኛ ላይ ማድረግ አያስፈልጋችሁም" ወይም "የትኩረት አቅጣጫችሁን በእኛ ላይ ለማድረግ ምንም ምክንያት የላችሁም" እኛ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጴጥሮስን እና ዮሐንስን ነው። እኛ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጴጥሮስን እና ዮሐንስ ነው። በእኛ ኃይል ወይም መለኮትነት ይህን ሰው በእግሩ ቆሞ እንዲሄድ ያደረግን ይመስል? አማራጭ ትርጉም: "በራሳችን ኃይል ወይም መለኮታዊ ጥበብ ይህንን አላደረግም"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Acts 3:13

የሐዋርያት ሥራ **3: 13-14**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጴጥሮስ በ ACT 3:12 ላይ የመጀመረውን ለአይሁዊያን ማናገሩን ቀጥሏል። እናንተ አሳልፋችሁ የሰጣችሁት "እናንተ ለጵላጦስ አሳልፋችሁ የሰጣችሁት" በጵላጦስ ፊት የከዳችሁት "ጵላጦስ ባለበት የከዳችሁት" እርሱ ሊፈታው በወደደ ጊዜ "ጵላጦስ ሊፈታው በፈለገ ጊዜ" ነፍሰ ገዳዩ እንዲፈታላችሁ ጠየቃችሁ አማራጭ ትርጉም: "ጵላጦስ ነፍሰ ገዳን እንዲፈታላችሁ ጠየቃችሁ"

Acts 3:15

የሐዋርያት ሥራ **3:15-16**
የሕይወት ራስ "የሕይወትን ምንጭ" (UDB) ወይም "የሕይወት ገዥ" አሁን ይህ ቃል የተደራሲያኑን የትኩረት አቅጣጫ ወደ ሽባው ሰው ለመመለስ የሚያገለግል ነው። ይህ ሰው እንዲጠነክር ያደረገው "ይህ ሰው ደኽና እንዲሆን ያደረገው"

Acts 3:17

የሐዋርያት ሥራ **3: 17-18**
አሁን ጴጥሮስ የተደራሲያኑን የትኩረት አቅጣጫ ከሽባው ሰው ላይ በማንሰሳት እነርሱን በቀጥታ ወደመናገር እንደዞረ የሚያሳይ ነው።

Acts 3:19

የሐዋርያት ሥራ **3: 19-20**
ተመለሱ "ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ" ይሰረዝ "ይደመሰስ ዘንድ" ወይም "ይፋቅ ዘንድ" እንግዲህ ከጌታ ፊት የመጽናናት ዘመን እንድትመጣላችሁ "ጌታ መልሶ ያበረታችሁ ዘንድ"

Acts 3:21

የሐዋርያት ሥራ **3: 21-23**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጴጥሮስ በ ACT 3:13 ላይ የመጀመረውን ለአይሁዊያን ማናገሩን ቀጥሏል። አጠቃላይ መረጃ: በቁጥር 22-23 ላይ ጴጥሮስ ሙሴ ስለመስሐ አስቀድሞ የተናገረውን ነገር በማንሳት ተናግሯል። ሰማይ ይቀበለው ዘንድ ከዚህ በፊት አደርገዋለሁ ብሎ እንደተናገረው ኢየሱስ ያለው በሰማይ ነው። ነገር ሁሉ እስከሚታደስበት ዘመን ድረስ "እግዚአብሔር ሁሉን ነገት እስከሚያድስበት ጊዜ ድረስ" ከጥንት ጀምሮ በቅዱሳን ነቢያቱ አፍ የተናገረው፥ "እግዚአብሔር ለቅዱስ ነቢያቱ ሁሉን ነገር እንደሚያድስ ተናግሯል" ከጥንት ጀምሮ በቅዱሳን ነቢያቱ "ከብዙ ዘመናት በፊት የኖሩት ቅዱስ ነቢያቱ" ነቢያ ያስነሣላችኋለ "አንድ ሰው ነቢይ እንዲሆን ይመርጣል" ትጠፋለች "ትወገዳለች" ወይም "ትወሰዳለች"

Acts 3:24

የሐዋርያት ሥራ **3: 24-26**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጴጥሮስ በ ACT 3:13 ላይ የመጀመረውን ለአይሁዊያን ማናገሩን ቀጥሏል። እርሱን የተከተሉት ሰዎች "ከሳሙኤል በኋላ የኖሩት ነቢያት" ስለእነዚህ ቀናት "ስለእነዚህ ጊዜያት" ወይም "አሁን እየሆኑ ስላሉት ነገሮች" እናንተ የነቢያቱ ልጆች ናችሁ "እናንተ የነቢያቱ ወራሾች ናችሁ።" አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካኝነት የገባውን ቃል ትቀበላላችሁ።" እንዲሁም የኪዳኑን "እንዲሁም የኪዳኑ ልጆች ናችሁ።" አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር በኪዳኑ አማከካኝነት የገባውን ቃል ትቀበላላችሁ።" በዘርህ "ከአንተ ልጆች የተነሣ" እግዚአብሔር ባሪያውን ካስነሣ በኋላ "እግዚአብሔር ባሪያውን ከመረጠ በኋላ" ወይም "እግዚአብሔር ሥልጣንን ለባሪያው ከሰጠ በኋላ" ባያሪው ይህ የእግዚአብሔርን መስሕ የሚያመለክት ቃል ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 4

1 ጴጥሮስና ዮሐንስ ለሕዝቡ እየተናገሩ ሳሉ፣ ካህናቱና የቤተ መቅደሱ ሹም፣ ሰዱቃውያንም ወደ እነርሱ መጡ። 2 እነርሱም፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ
ሕዝቡን ያስተምሩና ከሙታን መነሣቱንም ያውጁ ስለ ነበረ፣ እጅግ ተበሳጩ። 3 ያዟቸውና በዚያ ጊዜ ምሽት ስለ ነበረ እስከሚቀጥለው ጧት ድረስ በወኅኒ
አቈዩአቸው። 4 ነገር ግን መልእክቱን ከሰሙት ብዙ ሰዎች አመኑ፤ ያመኑት ሰዎች ቍጥርም ዐምስት ሺሕ ያህል ነበረ። 5 በሚቀጥለው ቀን እንደዚህ ሆነ፤
አለቆቻቸው፣ ሽማግሌዎቻቸውና የሕግ መምህራናቸው በኢየሩሳሌም ውስጥ በአንድነት ተሰበሰቡ። 6 ሊቀ ካህናቱ ሐና እዚያ ነበረ፤ ቀያፋም፣ ዮሐንስም፣
እስክንድሮስና የሊቀ ካህናቱ ዘመዶች ሁሉ ነበሩ። 7 ጴጥሮስንና ዮሐንስን በመካከላቸው አቁመውም፣ "በማን ሥልጣን ወይም በማንስ ስም ይህን አደረጋችሁ?"
ብለው ጠየቋቸው። 8 ከዚያም ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ እንዲህ አላቸው፤ “እናንተ የሕዝቡ አለቆች፣ ሽማግሌዎችም፣ 9 ለታመመ ሰው የተደረገ
መልካም ነገርን በሚመለከት በዚህ ቀን እየተጠየቅን ከሆንን፣ ይህ ሰው በምን ዳነ? 10 ይህ ለእናንተ ለሁላችሁ፣ ለእስራኤልም ሕዝብ ሁሉ የታወቀ ይሁን፤ ይህ
ሰው በፊታችሁ እዚህ በጤንነት የቆመው እናንተ በሰቀላችሁት፣ እግዚአብሔር ከሞት ባስነሣው በናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው። 11 ኢየሱስ ክርስቶስ
እናንተ ግንበኞች የናቃችሁት፣ ነገር ግን የማእዘን ራስ የሆነ ድንጋይ ነው። 12 በሌላ በማንም ድነት የለም፤ ልንድንበት የሚገባ በሰዎች መካከል የተሰጠ ሌላ
ስም ከሰማይ በታች የለምና።” 13 የጴጥሮስንና የዮሐንስን ድፍረት ሲያዩ፣ ያልተማሩና ተራ ሰዎች እንደ ሆኑ ሲያውቁም፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ ከኢየሱስ ጋር እንደ
ነበሩ በማወቅ ተደነቁ። 14 የተፈወሰው ሰውዬ ዐብሯቸው ቆሞ ስላዩት፣ የአይሁድ መሪዎች በእነርሱ ላይ ምንም መናገር አልቻሉም። 15 ሐዋርያቱ ከሸንጎው
ወጥተው እንዲሄዱ ካዘዙ በኋላ፣ እርስ በርሳቸው ተነጋገሩ። 16 እንደዚህም አሉ፤ “በእነዚህ ሰዎች ላይ ምን እናድርግ? በእነርሱ አማካይነት የታወቀ ተአምር
የመፈጸሙ እውነታ በኢየሩሳሌም ለሚኖር ሁሉ ታውቆአልና፤ ልንክደው አንችልም። 17 ሆኖም ይህ በሕዝቡ መካከል የበለጠ እንዳይሠራጭ፣ በዚህ ስም
ከእንግዲህ ለማንም እንዳይናገሩ እናስጠንቅቃቸው።” 18 ጴጥሮስንና ዮሐንስን ወደ ውስጥ ጠርተው በኢየሱስ ስም ፈጽሞ እንዳይናገሩም፣ እንዳያስተምሩም
አዘዟቸው። 19 ነገር ግን ጴጥሮስና ዮሐንስ መልሰው እንዲህ አሏቸው፤ “ለእግዚአብሔር ከመታዘዝ ይልቅ እናንተን መታዘዝ በእግዚአብሔር ፊት ትክክል እንደ
ሆነ እናንተ ፍረዱ። 20 እኛ ስላየናቸውና ስለ ሰማናቸው ነገሮች ለመናገር ዝም ማለት አንችልም።” 21 እንደ ገናም ጴጥሮስንና ዮሐንስን ካስጠነቀቋቸው በኋላ፣
ለቀቋቸው። እነርሱን ለመቅጣት ምንም ምክንያት ለማግኘት አልቻሉም፤ ምክንያቱም ሰዎቹ ሁሉ ለተደረገው እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር። 22 ይህ በተአምር
የተፈወሰው ሰውዬ ከዐርባ ዓመት በላይ ዕድሜ ነበረው። 23 ከተለቀቁ በኋላ፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደ ራሳቸው ሰዎች መጡና የካህናት አለቆችና ሽማግሌዎች
ያሏቸውን ሁሉ ነገሯቸው። 24 ሰዎቹ የነገሯቸውን ሲሰሙም፣ ድምፃቸውን በአንድነት ወደ እግዚአብሔር ከፍ አድርገው እንዲህ አሉ፤ “ጌታ ሆይ፣ አንተ ሰማያትን፣
ምድርንና ባሕርን፣ በውስጣቸው የሚገኘውንም ሁሉ የፈጠርህ ነህ፤ 25 በመንፈስ ቅዱስም በአገልጋይህ በአባታችን በዳዊት አፍ እንዲህ ብለሃል፦ ‘አሕዛብ
ለምን አኵረመረሙ፣ ሕዝቡስ ከንቱ ነገርን ለምን ዐሰቡ? 26 በጌታ፣ በእርሱ መሲሕም ላይ የምድር ነገሥታት ተነሡ፣ አለቆችም በአንድነት ተሰበሰቡ።’ 27
በእውነት ሄሮድስና ጴንጤናዊው ጲላጦስ፣ ከአሕዛብና ከእስራኤል ሕዝብ ጋር በቀባኸው በቅዱሱ አገልጋይህ በኢየሱስ ላይ በዚህ ከተማ ውስጥ በአንድነት
ተሰብስበዋል። 28 የተሰበሰቡትም እጅህና ዐሳብህ አስቀድመው የወሰኑት እንዲፈጸም ነው። 29 ጌታ ሆይ፣ አሁን ወደ ዛቻዎቻቸው ተመልከት፤ ለባሪያዎችህም
ቃልህን በሙሉ ድፍረት እንዲናገሩ ስጥ። 30 ለመፈወስ እጅህን ስትዘረጋው፣ ምልክቶችና ድንቆች በቅዱሱ አገልጋይህ በኢየሱስ ስም ይደረጋሉ።" 31 ጸሎት
ሲጨርሱ፣ ተሰብስበውበት የነበረው ስፍራ ተናወጠ፤ ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፤ የእግዚአብሔርን ቃልም በድፍረት ተናገሩ። 32 ካመኑት እጅግ ብዙዎች
አንድ ልብና አንድ ነፍስ ነበራቸው፤ ከእነርሱ አንድም ሰው፣ ያለው ማንኛውም ነገር የራሱ እንደ ሆነ አልተናገረም፤ ይልቁን ሁሉም ነገሮች የጋራ ነበሩ። 33
ሐዋርያቱም በታላቅ ኀይል ስለ ጌታ ኢየሱስ ትንሣኤ ምስክርነታቸውን ያውጁ ነበር፤ በሁሉም ላይ ታላቅ ጸጋ ነበረባቸው። 34 በመካከላቸው ችግረኛ ሰው
አልነበረም፤ መሬት ወይም ቤት ያላቸው ሁሉ ሸጠው የሸያጩን ገንዘብ ያመጡትና፣ 35 በሐዋርያት እግር አጠገብ ያስቀምጡት ነበርና። አከፋፈሉም ይደረግ
የነበረው እያንዳንዱ አማኝ በሚያስፈልገው መሠረት ነው። 36 ሌዋዊ የሆነው፣ ቆጵሮሳዊው ዮሴፍ ሐዋርያት በርናባስ የሚባል ስም ያወጡለት ሰው ነበር
(ትርጕሙ የመጽናናት ልጅ ማለት ነው)። 37 እርሱ የነበረውን መሬት ሸጠው፤ ገንዘቡንም አምጥቶ በሐዋርያት እግር አጠገብ አስቀመጠው።

Acts 4:1

Acts 4:1-4
የሐዋርያት ሥራ 4፡ 1-3 የቤተ መቅደሱ ጠባቂዎች አለቃ የቤተ መቅዱስ ጠባቂዎች ኃላፊ ወደ እነርሱ መጣ "ቀረባቸው" ወይም "ወደ እርሱ መጣ" በጣም ፈሩ ጴጥሮስ ስለኢየሱስ እና ስለእርሱ ከሞት መነሳት አስተማረ። ይህ ሳዱቃዎያንንን አስጨነቃቸው ምክንያቱም ኢየሱስ ከሞት መነሳቱን አያምኑም ነበርና። የወንዶች ቁጥር ይህ የወንዶችን ቁጥር ብቻ የሚያመለክት ነው። ሴቶች እና ሕጻና በቁጥሩ ውስጥ አልተካተቱም። ጥዋት እንደሆነም ሰዎች መርማሪ ጥያቄ የሚጠየቁት ጥዋት ነው፤ ይህ የተለመደ ተግባር ነው። ወደ አምስት ሺህ ዓመት ገደማ "ወደ አምስት ሺህ ዓመታት ገደማ" ወይም “ወደ አምስት ሺህ ዓመታት አድገዋል”

Acts 4:5

የሐዋርያት ሥራ 4፡ 5-7
በምን ኃይል "ሥልጣን ማን ሰጠህUr" (UDB) ወይም "ስልጣን ማን ሰጠህ።" ጴጥሮስ እና ዮሐንስ በራሳቸው ሰዎችን መፈወስ እንደማይችሉ ያውቃሉ። በማን ስም "ስልጣን የሰጠህ ማን ነው"

Acts 4:8

የሐዋርያት ሥራ 4፡ 8-10
የእስራኤል ሰዎች ሆይ "እናንተ እስራኤላዊያን"

Acts 4:11

የሐዋርያት ሥራ 4፡ 11-12
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ጴጥሮስ ለአይሁድ የሃይማኖር መሪዎች በ ACT 4:8 ላይ መናገር የጀመረው ሀሳብ ይቋጫል። ኢየሱስ ክርስቶስ ድንጋይ ነው ይህ ምሳሌያዊ ንግግር ነው። አንድ የማዕዘን ድንጋይ መሠረት ለመጣል እና በሕንጻ ግንባታ ወቅት ለማነጻጸሪያ እንደሚያገለግል ሁሉ ኢየሱስም ለድነት ብቸኛው መሠረት ነው።

Acts 4:13

የሐዋርያት ሥራ 4፡ 13-14
የእነዚህ ሰዎች ደፈረት በተመለከቱ ጊዜ በዚህ ሥፍራ “እነዚህ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የመሪዎችን ቡድን ነው። እነርሱ . . . እንደሆኑ አወቁ "ተገነዘቡ" ወይም "አወቁ" ተራ ሰዎች መሆናቸው። they were ordinary በዚህ ሥፍራ "እነርሱ" የሚለው ቃ የሚያመለክተው ጴጥሮስን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እና ዮሐንስን ነው። ያልተማሩ ሰዎች "ምንም ዓይነት ስልጠና ያልወሰዱ ሰዎች" ወይም "መደበኛ ትምህርት ያልተከታተሉ ሰዎች"

Acts 4:15

የሐዋርያት ሥራ 4፡ 15-18
ሸንጎ በየሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ሸንጎ የሚለው ቃል አዘውትሮ ጥቅም ላይ ይውላል። ከየሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ከምዕራፍ 25፡12 በስተቀር ይህ ቃል የሚያመለክተው የአይሁን ሳንሄድረንን ነው። እነርሱ ይህ ቃል የሚያመለክተው ጴጥሮስን እና ዮሐንስን ነው።

Acts 4:19

የሐዋርያት ሥራ 4፡ 19-20
ትክክል ይሁን አይሁን "ጻድቅ እና እግዚአብሔርን የሚያከብር" ምንም ልናደረግ አንችልም "ለመናገር እንገዳደለን"

Acts 4:21

የሐዋርያት ሥራ 4፡ 21-22
አጠቃላይ መረጃ: ቁጠር 22 ፈውስን ያገኘው ስለሸባው ሰው ዕድሜ የኃላ ታሪክ ይሰጠናል ከብዙ ማስጠንቀቂያ በኋላ መሪዎቹ ይህንን ማድረግ የሚቀጥሉ ከሆነ ተጨማሪ ቅጣት እንደሚጠብቃቸው በመናር አስፈራሯው። እነርሱን ለመቅጣት የሚበቃ በዚ ምክንያት ማግኘት አላቻሉም የሰውዬውን መፈወስ የተመለኮቱ ሰዎች ረበሻ ሳያስነሱ መሪዎች ጴጥሮስ እና ዮሐንስን መቅጣት የሚችሉበት መንገድ ማግኘት አልቻሉም።

Acts 4:23

የሐዋርያት ሥራ 4፡ 23-25
የራሳቸው ወደ ሆኑ ሰዎች መጡ ወደ ሌሎች አማኞች ዘንድ ሄዱ። ድምጻቸውን በአንድነት ከፍ በማድግ በሀሳብ እና ልብ ሆነው። በአባታችን በዳዊት በእናንተ አገልጋይ አፍ በተነገረው መሠረት "በዳዊት አባታችን በእናተ አገልጋይ አማካኝነት በተነገረው መሠረት" አገልጋይ በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ነቢያት እና እግዚአብሔርን የሚያመልከቱ ሌሎች ሰዎች ብዙ ጊዜ የእርሱ “አገልጋዮች” ተብለው ይጠራሉ።

Acts 4:26

የሐዋርያት ሥራ 4፡ 26-26
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: አማኞች በ ACT 4:25 ላይ የጀመሩትን ከንጉሥ ዳዊት የመዝሙር መጽሐፍ ውስጥ የወሰዱትን ሀሳብ ያጠናቅቃሉ። አብረው ተከማቹ "ኃይላቸውን በአንድነት አጣመሩ" ክርስቶስ ይህ ከመዝሙርት 2፡ 1-2 ክፍል የተወሰደ ነው። “መስሕ” የሚለው ቃል በዕብራይስጥ ቋንቋ ሲሆን ትርጓሜውም “ክረስቶስ” ማለት ነው። ይህም “የተቀባውም” ማለት ነው።

Acts 4:27

የሐዋርያት ሥር 4፡ 27-28
ሄሮዶስ እና ጵላጦስ ከአሕዛቦች እና ከእስራኤል ሕዝብ ጋር በአንድነት በመሆኑን በመዝሙር መጽሐፍ ውስጥ ዳዊት ያካተተው አሕዛብን ብቻ ሲሆን ጴጥሮስ ግን መስሑን የተቃወሙትን እስራኤልን እና የእርሷ መሪዎች ከአሕዛብ ጋር በአንድነተን በዚህ ከተማ ውስጥ "በእየሩሳሌም ውስጥ" በእጅህ እና ውሳኔህ "ትወስናለህ"

Acts 4:29

የሐዋርያት ሥራ 4፡ 29-31
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: አማኞቹ በ ACT 4:24 ላይ የተመሩትን ጸሎት ያጠናቅቃል። የእግዚአብሔርን ቃል በድፍረት ይናገሩ ነበር ይህ ደቀ መዛሙርቱ በመንፈስ ቅዱስ ከመሞላታቸው የተነሳ የሆኑ ነገሮች ናቸው።

Acts 4:32

የሐዋርያት ሥራ 4፡ 32-33
ምስክርነት በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይህ ቃል ብዙ ጊዜ የኢየሱስን ተከታዮች ሕይወቱን፣ ሞቱን እና ትንሣኤውን ለማመልከት ይውላል። ታላቅ ጸጋ በእነርሱ ላይ ነበር አማራጭ ትርጉሞች: 1) እግዚአብሔር ብዙ ስጦታዎችን ያፈስ ነበር እና አማኞቹም ሁሉ ትልቅ ድፍረት ነበራው። ወይም 2) አማኞች ሁሉ በእየሩሳሌም ውስጥ ባሉ አማኞቹ ሁሉ ዘንድ ትልቅ አክብሮት ነበራቸው።

Acts 4:34

የሐዋርያት ሥራ 4፡ 34-35
በሐዋርያቱ እግር ሥር ያኖሩ ነበር ይህ አማኞቹ . . መግለጫ ነበር: 1) በአደባባይ ልባቸው መለወጡን የሚያሳዩበት መንገድ ነው እና 2) ስጦታዎቹ በአግባቡ ጥቅም ላይ በማዋል ማስተዳደር እንዲችሉ ለሐዋርያቱ ስልጣን መስጠትን የሚያመለክት ነው።

Acts 4:36

የሐዋርያት ሥራ 4፡ 34-35
በሐዋርያቱ እግር ሥር ያኖሩ ነበር ይህ አማኞቹ . . መግለጫ ነበር: 1) በአደባባይ ልባቸው መለወጡን የሚያሳዩበት መንገድ ነው እና 2) ስጦታዎቹ በአግባቡ ጥቅም ላይ በማዋል ማስተዳደር እንዲችሉ ለሐዋርያቱ ስልጣን መስጠትን የሚያመለክት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 5

1 ሐናንያ የሚባል አንድ ሰውም ከሚስቱ ከሰጲራ ጋራ መሬት ሸጠ፤ 2 የሸያጩን ገንዘብ ከፊል መጠን አስቀረው (ሚስቱም ታውቅ ነበር)፤ ሌላውን የገንዘብ
መጠን ግን አምጥቶ በሐዋርያት እግር አጠገብ አስቀመጠው። 3 ጴጥሮስ ግን ሐናንያን እንዲህ አለው፤ “ሐናንያ ሆይ፣ ለመንፈስ ቅዱስ እንድትዋሸና የመሬቱን
ዋጋ ከፊል መጠን እንድታስቀር ሰይጣን ልብህን ለምን ሞላው? 4 መሬቱ ሳይሸጥ የአንተ እንደ ሆነ አይዘልቅም ነበርን? ከተሸጠ በኋላስ በአንተ ቍጥጥር
ሥር አልነበረምን? በልብህ ይህን ነገር እንዴት ዐሰብህ? የዋሸኸው ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰዎች አይደለም። 5 እነዚህን ቃሎች ሰምቶ፣ ሐናንያ ወደቀ፤
ሞተም። በሰሙት ሁሉ ላይም ታላቅ ፍርሀት መጣ። 6 ጐበዛዝቱ ወደ ፊት መጡና ከፈኑት፤ ወደ ውጭ አውጥተውም ቀበሩት። 7 ከሦስት ሰዓት ያህል በኋላ፣
ሚስቱ ምን እንደ ሆነ ሳታውቅ ወደ ውስጥ ገባች። 8 ጴጥሮስ፣ “መሬቱን ይህን ለሚያህል ዋጋ ሸጣችሁት ከሆነ ንገሪኝ” አላት። እርሷም፣ "አዎ፣ ይህን
ለሚያህል ነው” አለችው። 9 ከዚያም ጴጥሮስ፣ “የጌታን መንፈስ ለመፈታተን እንዴት ተስማማችሁ? ተመልከቺ፣ ባልሸን የቀበሩት ሰዎች እግር በር ላይ ነው፤
አንቺንም ወደ ውጭ ያወጡሻል።” 10 እርሷም ወዲያው በጴጥሮስ እግር ሥር ወደቀች፤ ሞተችም፤ ጐበዛዝቱም ወደ ውስጥ ሲገቡ ሞታ አገኟት፤ ወደ ውጭ
አወጧትና በባሏ አጠገብ ቀበሯት። 11 በቤተ ክርስቲያን ሁሉና እነዚህን ነገሮች በሰሙት ላይ ታላቅ ፍርሀት መጣ። 12 በሕዝቡ መካከል ብዙ ምልክቶችና
ድንቆች በሐዋርያት እጅ ይደረጉ ነበር። ሁሉም በሰሎሞን ደጅ መመላለሻ በአንድነት ነበሩ። 13 ነገር ግን አንድም ሌላ ሰው እንኳ ከእነርሱ ጋር ለመተባበር
ድፍረት አልነበረውም፤ ሆኖም ከሕዝቡ ከፍተኛ አክብሮት ነበራቸው። 14 አሁንም የበለጡ አማኞች፣ እጅግ ብዙ ወንዶችና ሴቶች ለጌታ ይጨመሩ ነበር፤ 15
በሽተኞችንም እንኳ ተሸክመው ወደ መንገድ እያመጡ በዐልጋና በቃሬዛ ላይ ያስቀምጧቸው ነበር፤ ይኸውም ጴጥሮስ ሲያልፍ በተወሰኑት ላይ ጥላው
እንዲያርፍባቸውነው። 16 በሽተኞችንና በርኩሳን መናፍስት የሚሠቃዩትን በማምጣት በኢየሩሳሌም ዙሪያ ካሉ ከተሞች አያሌ ሰዎችም በአንድነት ተሰበሰቡ፤
በሽተኞችም ሁሉ ተፈወሱ። 17 ነገር ግን ሊቀ ካህናቱና ዐብረውት የነበሩትም ሁሉ ተነሡ (የሰዱቃውያን ወገን የሆነው ማለት ነው)፤ እነርሱም በቅናት ተሞልተው
ነበር፤ 18 እጃቸውንም በሐዋርያት ላይ ጫኑ፤ በሕዝብ ወኅኒ ውስጥም አስገብተው አሰሯቸው። 19 ይሁን እንጂ፣ የጌታ መልአክ በሌሊት የወኅኒውን በሮች
ከፈተ፤ ወደ ውጭ አውጥቶአቸውም እንዲህ አላቸው፤ 20 “ሂዱ፤ በቤተ መቅደስ ውስጥ ቁሙና የዚህን ሕይወት ቃሎች ሁሉ ለሕዝቡ ተናገሩ።” 21 ይህን
ሲሰሙም፣ ንጋት ላይ ወደ ቤተ መቅደስ ገቡና አስተማሩ። ነገር ግን ሊቀ ካህናቱና ከእርሱ ጋር የነበሩት መጡ፤ ሸንጎውንም በአንድነት፣ የእስራኤል ሕዝብ
ሸማግሌዎችንም ጠሩ፤ ሐዋርያቱን እንዲያመጧቸውም ወደ ወኅኒው ላኩ። 22 ነገር ግን የተላኩት መኰንኖች በወኅኒው ውስጥ አላገኟቸውም፤ ተመልሰው
በመሄድም እንዲህ ብለው ተናገሩ፣ 23 “ወኅኒው በደኅና እንደ ተቈለፈና ጠባቂዎችም በር ላይ እንደ ቆሙ አግኝተናል፤ በከፈትነው ጊዜ ግን በውስጡ ማንንም
አላገኘንም።” 24 የመቅደሱ ጥበቃ ሹምና ሊቃነ ካህናቱ እነዚህን ቃላት ሲሰሙ፣ እስረኞችን በሚመለከት ምን እንደሚሆን እጅግ ግራ ተጋቡ። 25 ከዚያም
አንድ ሰው መጣና፣ “ወኅኒ ውስጥ ያስገባችኋቸው ሰዎች ቤተ መቅደስ ውስጥ ቆመው ሕዝቡን እያስተማሩ ናቸው” ብሎ ነገራቸው። 26 ስለዚህ ሹሙ
ከመኰንኖች ጋር ሄደ፤ መልሶም አመጣቸው፤ ያመጧቸው ግን በኀይል አልነበረም፤ ሕዝቡ በድንጋይ ይወግሯቸዋል ብለው ፈርተው ነበርና። 27 አምጥተዋቸው
በነበረ ጊዜ፣ በሸንጎው ፊት አቆሟቸው። ሊቀ ካህናቱም ጠየቃቸው፤ 28 እንዲህም አላቸው፤ “በዚህ ስም እንዳታስተምሩ በጥብቅ አስጠንቅቀናችሁ ነበር፤
እናንተ ግን ኢየሩሳሌምን በትምህርታችሁ ሞልታችኋታል፤ የዚህን ሰው ደም በእኛ ላይ ለማምጣትም ትፈልጋላችሁ።” 29 ጴጥሮስና ሐዋርያቱ ግን መልሰው፣
“ለሰው ከመታዘዝ ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል። 30 የአባቶቻችን አምላክ በዕንጨት ላይ በመስቀል የገደላችሁትን፣ ኢየሱስን አስነሣው። 31 አዳኝና
የሁሉ የበላይ እንዲሆን፣ ለእስራኤል ንስሓንና የኀጢአት ይቅርታን ለመስጠት እግዚአብሔር በቀኙ ከፍ ከፍ አደረገው። 32 እኛና እግዚአብሔር ለሚታዘዙት
የሰጠው መንፈስ ቅዱስ የእነዚህ ነገሮች ምስክሮች ነን።” 33 የሸንጎው አባሎች ይህን ሲሰሙ፣ በጣም ተናደዱ፤ ሐዋርያቱንም ለመግደል ፈለጉ። 34 ነገር ግን
የሕግ መምህር የነበረና ሕዝቡም ሁሉ የሚያከብረው ገማልያል የሚባል አንድ ፈሪሳዊ ተነሥቶ፣ ሐዋርያት ለተወሰነ ጊዜ ውጭ እንዲቈዩ አዘዘ። 35 ከዚያም
እንዲህ አላቸው፤ “የእስራኤል ሰዎች ሆይ፣ በእነዚህ ሰዎች ልታደርጉ ያሰባችሁትን በጥንቃቄ ተመልከቱት። 36 ከጥቂት ጊዜ በፊት ቴዎዳስ ትልቅ ሰው ነኝ
በማለት ተነሥቶ ነበርና፤ አራት መቶ ያህል ወንዶችም ተከተሉት። እርሱ ተገደለ፤ ይታዘዙለት የነበሩትም ሁሉ ተበታትነው እንዳልነበሩ ሆኑ። 37 ከዚህም ሰው
በኋላ፣ የገሊላው ይሁዳ በቈጠራው ቀናት ዐምፆ የተወሰኑ ሰዎችን አስከትሎ ሄደ። እርሱም ሞተ፤ እርሱን ይታዘዙት የነበሩትም ተበታተኑ። 38 አሁንም
እነግራችኋለሁ፤ ከእነዚህ ሰዎች ተለዩ፤ እነርሱንም ተዉአቸው፤ ይህ ዐሳብ ወይም ሥራ የሰዎች ከሆነ፣ ይጠፋል። 39 የእግዚአብሔር ከሆነ ግን፣ ልታጠፏቸው
አትችሉም፤ ከእግዚአብሔር ጋር ስትጋጩም እንኳ እንዳትገኙ።” እነርሱም በዐሳቡ ተስማሙ። 40 ከዚያም በኋላ፣ ሐዋርያቱን ወደ ውስጥ ጠርተው ገረፏቸው፤
በኢየሱስ ስም እንዳይናገሩም አዘዟቸውና ለቀቋቸው። 41 እነርሱም ስለ ስሙ ይዋረዱ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ስለ ተቈጠሩ፣ ደስ እያላቸው ከሸንጎው ወጡ።
42 ከዚያ በኋላ በየቀኑ፣ በቤተ መቅደስና ከቤት ወደ ቤት፣ በተከታታይ ኢየሱስ፣ ክርስቶስ እንደ ሆነ ያስተምሩና ይሰብኩ ነበር።

Acts 5:1

የሐዋርያት ሥራ 5: 1-2
አጠቃላይ መረጃ: ይህ የታሪኩ አዲስ ጅማሬ ክፍል ነው። ይህ ታሪክ የአናኒያ እና ሳጵራ ስለተባሉ ሁለት ሰዎች የኃላ ታርክ ይሰጠናል። አሁን "አሁን ግን።" ይህ የታሪኩ አንዲስ ክፍል መጀመሩን ያሳያል። ይህ በቋንቋችሁ በንጽጽር ሊቀመጡ የሚችሉ ታሪክች መግቢያን በሚያሳዩ ቃላት ተተርጉሚ ሊቀመጥ ይችላል። የሆነ ሰው ይህንን ቃል በቋንቋችሁ አንድን ሰው ለማስተዋወቅ በሚትጠቀሙበት ቃል ለመተርጎም ጥረት አድርጉ። ከሽያጩ የጠወሰነ ገንዘብ ወስዶ ሸሸገ የሸጠበትን ገንዘብ ሙሉውን ለሐዋርያት ባለመናገሩ ታማኝ አልነበረም። አማራጭ ትርጉም: “ከሰጣ ገንዘብ ውስጥ የተወሰነው በምስጥር አስቀመጠ።" ይህንን ነገር ምስቱም ታውቅ ነበር አማራጭ ትርጉም: "ምስቱን ታውቅ ነበር እንዲሁም ይህንን በማድረጉ ተስማምታ ነበር" በሐዋርያቱ እግር ፉት አስቀመጡ ይህንን በ ACT 4:35 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት።

Acts 5:3

የሐዋርያት ሥራ 5: 3-6
ሴጣን ስለምን ልባችሁን ሞላው . . . መሬቱን? ጴጥሮስ አናኒያስን ለመገሰጽ ይህንን ጥያቄ ጠይቆታል። አማራጭ ትርጉም: "ሴጣን እንድትዋሹ የሰጣችሁን ሽንገላ ልጽቀበለጽ ባልጸገባ ነበር።" የእናንት አልነበረምን . . . በእናንተ ቁጥጥር ሥር አልነበረምን? ጴጥሮስ አናናይስን በገንዘቡ የፈለገውን የማድረግ መብት እንደነበረው ለማስታወስ ይህንን ጥያቄ ጠይቆታል። አማራጭ ትርጉም: “የገዛ ገንዘብህን ኃላፊነት በተሞለው መልኩ የማስተዳደር ኃለፊነት አለብህ።” እንዲህ ዓይነቱ ነገር በልብህ እንዴት ልታስብ ቻልክ? ጴጥሮስ ይህንንነ ጥያቄ የተጠቀመው አናናስን ለመገሰጽ ነው። አማራጭ ትርጉም: “ገንዘብህን በመደበቅ ለማታለል መወሰን አልነበረብህም።” ወጣቶቹ ወደ ፊት መጡ። "ወጣቶቹ ተነሱ።" ይህ ተግባራዊ እርምጃ የመውሰድ መገለጫ ነው። ተሸክመው አወጡት እና ቀበሩት። አንድ ሰው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሲሞት በድኑን ለመቅበር የሚፈጸም ሂደት አለ። ይሁን እንጂ ይህ ሥርዓት የተፈጸመለት አይመስልም።

Acts 5:7

የሐዋርያት ሥራ **5**: **7**-**8**
የተከሠተው ነገር ምንድ ነው "ባሏ ሞተ"

Acts 5:9

የሐዋርያት ሥራ **5**: **9**-**11**
አያያዥ ዓረፈት ነገር: ይህ የአናኒስ እና ሰጵራ ታሪክ የመጨረሻው ክፍል ነው። እንዴት አንች ሰጵራ የጌታን መንፈስ ለመፈተን ከእርሱ ጋር ትተባበሪያለሽ? ጴጥሮስ ይህንን ጥያቄ የጠየቃት ሁለቱ ኃጢአት ለማድረግ መስማማታቸውን ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም: "መንፈስን ለመፈትን የጋራ ስምምነት ላይ ደርሳችኋል!" ባልሽን የቀበሩት ሰዎች እግር በደጅ ነው በዚህ ሥፍራ ላይ “እግር” የሚለው ቃል የሚያመለክተው አናኒያስን የቀበሩትን ሰዎች ነው። የመጨረሻ እስትንፋሷን ተነፈሰች ይህ በሌላ አገላለጽ “ሞተች” ለማለት ነው።

Acts 5:12

የሐዋርያት ሥራ **5**: **12**-**13**
የሰለሞን ደጅ መመላለሻ ይህ በቤተ መቅደሱ አጥር ግቢ ውስጥ ያለ ሥፍራ ነው። ማንም "የቤተ ክርስቲያን አካል ያልሆነ ማንም ሰው ማለት ነው" ይሯቸው ነበር "ለእነርሱ ታላቅ አክብሮት እና ፍርሃት ነበራቸው"

Acts 5:14

የሐዋርያት ሥራ **5**: **14**-**16**
ጥላው በእነርሱ ላይ ያርፍ ዘንድ ይህ በተዘዋዋር መልኩ የሚያመለክተው የጴጥሮስ ጥላ ከነካቸው እንደሚፈወሱ ነው።

Acts 5:17

የሐዋርያት ሥራ **5**: **17**-**18**
ይሁን እንጂ በዚህ ሥፍራ ላይ ሌላ ለንጽጽር የቀረበ ታሪክ እንዳለ እንመለከታን። ይህንን በቋንቋችሁ ሌላ ለንጽጽር የቀረበ ታሪክን ለማስተዋወቅ በሚቻልበት መንገድ ልትተረጉሙት ትችላላችሁ። ቅንዓት "ቅንዓት" በሐዋርያት ላይ እጅቻቸውን ለመጫን "ሐዋርያቱን ለማሠር"

Acts 5:19

የሐዋርያት ሥራ **5**: **19**-**21**
እየመራ አወጣቸው "ሐዋርያቱን ከእስር ቤት መርቶ አወጣቸው" በማለዳ ቤተ መቅዱስ በምሽት ተዘግቶ ነበር። ሐዋርያቱ በተቻለው መጠን መለአኩን ተከተሉት።

Acts 5:22

የሐዋርያት ሥራ **5**: **22**-**23**

Acts 5:24

የሐዋርያት ሥራ **5**: **24**-**25**
በጣም ፈሩ "ግራ ተጋቡ" ወይም "ተምታታባቸው" ስለእነርሱ "አሁን ስለሰሙት ነገር" (ሐዋርያቱ በእስር ቤት ውስጥ እንደሌሉ ስለተነገራቸው ሪፖርት) እንድታሠሩ ያደረጋችኋቸው ሰዎች “እናንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር የሚያሳይ ነው።

Acts 5:26

የሐዋርያት ሥራ **5**: **26**-**28**
ሥልጣን የሰጣችሁ በዚህ ሥፍራ “እናንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥርን የሚያመለክት ነው። ሙላችሁ በዚህ ሥፍራ “እናንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥርን የሚያመለክት ነው። የዚህ ሰው ደም በእኛ ላይ ለማድረግ ትጥራላችሁ "የዚህ ሰው መሞት ምክንያት እኛ እንደሆንን ታደርጋላችሁ"

Acts 5:29

የሐዋርያት ሥራ **5**: **29**-**32**
ለእስራኤል ንሰሓን እና የኃጢአት ይቅርታ አማራጭ ትርጉመም: "እስራኤል ከኃጢአቷ ትመለስ ዘንድ እና የኃጢአት ይቅርታን የመቀበል እድል ታገኝ ዘንድ" እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ በዚህ ሥፍራ ላይ መንፈስ ቅዱስ የተጠቀሰው የኢየሱስ ተዓምራታዊ ሥራዎች የሚያረጋግጥ አካል ሆኖ ነው።

Acts 5:33

የሐዋርያት ሥራ **5**: **33**-**34**
ተቆጡ ሐዋርያቱ ስለገሰጸዋቸው የሸንጎው አባላት በሐዋርያቱ ላይ በጣም ተቆጡ። በሰዎች ሁሉ ዘንድ የተከበረ አንድ የሕግ መምህር፣ ይህ ስለገማሊያ የኃላ ታሪክ ነው፤ ይህ መረጃ የተሰጠው አንባቢያን ይህ ሰው ማን እንደሆነ ያውቁ ዘንድ ነው።

Acts 5:35

የሐዋርያት ሥራ **5**: **35**-**37**
አጠቃላይ መረጃ: ገማሊያ የሸንጎ አባላትን እንዲህ አላቸው። በጥንቃቄ በቅርበት ተከታተሉ "ስለዚህ ነገር በጥንቃቄ አስቡ" (UDB)፣ ወይም "ስለዚህ ነገር ከፍተኛ ጥንቄ አድርጉ"

Acts 5:38

የሐዋርያት ሥራ **5**: **38**-**39**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ገማሊያ ለሸንጎ አባላት ያደረገውን ንግግር አጠናቋል።

Acts 5:40

የሐዋርያት ሥራ **5**: **40**-**42**
ከዚህማ አስጠሩአቸዋው በዚህ ሥፍራ ላይ “እነርሱ” የሚለው ቃል የሸንጎ አባላትን ነው። እንደ ክብር እንቆጥረዋለን ለኢየሱስ መከራን መቀበል ክብር ነው። ከዚህያን ጊዜ አንስቶ በየዕለቱ "ከዚያ ቀን በኋላ፣ በየዕለቱ።" ይህ ሐዋርያቱ ከዚያን ዕለት በኋላ ባሉት ቀናት ውስጥ በየዕለቱ የሚያደርጓቸውን ነገሮች የሚያመለክት ነው። ሐዋርያቱ ይህንን ነገር ለማድረግ የተበረታቱት በዚህ ክፍል ውስጥ በተከሰተው ታርክ አማካኝነት ነው። በቀጣይነት ያስተምሩ ነበር አማራጭ ትርጉም: "ማስተማራቸውን ፈጽመው አላቆሙም"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 6

1 በእነዚህ ወራት፣ የደቀ መዛሙርት ቍጥር እየበዛ በሄደ ጊዜ፣ ከግሪክ የመጡት አይሁድ በዕብራውያን ላይ ማጕረምረም ጀመሩ፤ ምክንያቱም መበለቶቻቸው
በየዕለቱ የምግብ ዕደላ ላይ ቸል ተብለውባቸው ነበር። 2 ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ደቀ መዛሙርቱን ሁሉ ጠርተው እንዲህ አሏቸው፤ “የምግብ አገልግሎትን
ለመስጠት ብለን የእግዚአብሔርን ቃል መተው ለእኛ ተገቢ አይደለም። 3 ስለዚህ ወንድሞች ሆይ፣ በዚህ ኀላፊነት ላይ ልንሾማቸው የምንችል መልካም
አርአያነት ያላቸውን፣ መንፈስና ጥበብ የሞላባቸውን ሰባት ሰዎች ከእናንተ መካከል ምረጡ። 4 እኛ ግን፣ ሁልጊዜ በጸሎትና በቃሉ አገልግሎት እንቀጥላለን።” 5
ንግግራቸው ሕዝቡን ሁሉ ደስ አሰኘ። ስለዚህ እምነትና መንፈስ ቅዱስ የሞላበትን እስጢፋኖስን፣ ፊልጶስን፣ ጵሮኮሮስን፣ ኒቃሮናን፣ ጢሞናን፣ ጳርሜናንና ወደ
ይሁዲነት ገብቶ የነበረውን አንጾኪያዊውን ኒቆላዎስን መረጡ። 6 አማኞቹ እነዚህን ሰዎች፣ በጸለዩላቸውና ከዚያም እጆቸውን በላያቸው በጫኑት በሐዋርያት ፊት
አቀረቧቸው። 7 ስለዚህም የእግዚአብሔር ቃል አደገ፤ የደቀ መዛሙርት ቍጥርም በኢየሩሳሌም ውስጥ በብዛት ጨመረ፤ ከካህናትም ብዙዎቹ ለእምነት
ታዛዦች ሆኑ። 8 እስጢፋኖስ ጸጋንና ኀይልን ተሞልቶ፣ በሕዝቡ መካከል ታላላቅ ድንቆችንና ምልክቶችን ያደርግ ነበር። 9 ነገር ግን ነጻ የወጡት ሰዎች ምኵራብ
ከሚባለው ምኵራብ፣ ከቀሬናና ከእስክንድርያ፣ ከኪልቅያና ከእስያም የሆኑ ጥቂት ሰዎች ተነሡ። እነዚህ ሰዎች ከእስጢፋኖስ ጋር ይከራከሩ ነበር። 10 ነገር ግን
ሰዎቹ እስጢፋኖስ የተናረገረበትን ጥበብና መንፈስ መቋቋም አልቻሉም። 11 ከዚያም፣ “እስጢፋኖስ በሙሴና በእግዚአብሔር ላይ የስድብ ቃል ሲናገር
ሰምተናል” እንዲሉ አንዳንድ ሰዎችን በምስጢር አሳመኑ። 12 ሰዎቹን፣ ሽማግሌዎቹን፣ የሕግ መምህራኖቹንም አነሣሡ፤ እስጢፋኖስንም ይዘው ወደ ሸንጎው
አቀረቡት። 13 እንዲህ ብለው የሚናገሩ ሐሰተኛ ምስክሮችንም አመጡ፤ “ይህ ሰው ይህን ቅዱስ ስፍራና ሕጉን ተቃውሞ መናገርን አያቆምም። 14 ምክንያቱም
ይህ የናዝሬቱ ኢየሱስ ይህን ስፍራ ያፈርሰዋል፤ ሙሴም ያስተላለፈልንን ሥርዐትም ይለውጠዋል ሲል ሰምተነዋል።” 15 በሸንጎው ውስጥ የተቀመጡት ሁሉ
አተኵረው ተመለከቱት፤ ፊቱም እንደ መልአክ ፊት ሆኖ አዩት።

Acts 6:1

የሐዋርያት ሥራ 6: 1-1
አጠቃላይ መረጃ: ይህ የአዲስ ታሪክ መጀመሪያ ክፍል ነው። በዚህ ሥፍራ ታሪኩን ለመረዳት የሚያስችሉ የኃላ ታሪክ መመረጃዎች ተሰጥተዋል። አሁን በእነዚያ ቀናት ይህ የአዲስ ታሪክ መጀመሩን የሚያመለክት ነው። በእናንተ ቋንቋ አዲስ ታሪክ እንዴት እንደሚጀመር ከግንዛቤ ውስጥ አስገባ። ማብዛት "በብዛት መጨመር" ግሪካዊያን አይዶች ይህ አብዛኛውን ሕይወታውን ከእስራኤል ውጪ በሚገኙ የሮም ግዛቶች ውስጥ የኖሩትን እና የግሪክ ቋንቋ በመናገር ያደጉት አይሁዶችን ያመለክታል። ቋንቋቸው እና ባሕላቸው በእስራኤል ውስጥ ካደጉት ሰዎች በተወሰነ መልኩም ቢሆን ይለያል። ዕብራዊያን ይህ በእስራኤል ውስጥ የአራማይክ ቋንቋ እየተናገሩ ያደጉ አይሁዳዊያንን ያመለክታል። እስካሁን ድረስ ቤተ ክርስቲያን በውስጧ ያቀፈቻቸው አይሁዳዊያንን እና ወደ አይሁድ ሃይማኖት የተለወጡ ሰዎችን ብቻ ነው። ባል የሞተበት ሴት እውነተኛ ባል የሞተበት ሴት እንደገና ለማግባት በጣም ያረጀች እና ልደግፋት የሚችል የቅርብ ዘመድ ያሌላት ናት። ችላ መባል "ቸል መባል" ወይም "መተው።" እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ነገር ግን የተረሱ ሰዎች በተለያዩ ሠስፍራ ነበሩ። የዕለት ምግብ ማደል ለሐዋርያቱ ከሚሰጠው ገንዘብ ከፊሉ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ላሉ ባሎቻቸው ለሞቱባቸው መበልቶች ምግብ ለመግዛት ይውል ነበር።

Acts 6:2

የሐዋርያት ሥራ 6: 2-4
ማዕድ ማገልገል ይህ ለሰዎች መግብ ማደለን ለማመልከት የዋለ ምሳሌያዊ ንግግር ነው። ጥሩ ምግባር ያላቸው፣ በመንፈስ እና በጥበብ የተሞሉትን አማራጭ ትርጉሞቹ እነዚህ ናቸው 1) እነዚህ ሦሰዎች ሦስት ልዩ ባሕርያት አሏቸው - መልካ ምግባ፣ መንፈስ የሞላባቸው እና ጥበብ የሞላባቸው ናቸው ወይም 2) እነዚህ ሰዎች ሁለት መልካም ባሕርያት አላቸው - መንፈስ የሞላባቸው እና ጥበብ የሞላባቸው ናቸው (UDB)። መልካም ምግባር "ሰዎች መልካምነታቸውን የሚያውቁላቸው ሰዎች" ወይም "ሰዎች የሚያምኗቸው ሰዎች" እናንተ ተግባራዊ ማድረግ በሚቻልበት ሥፍራ በቋንቋችሁ ብዙ ቁጥር አመልካች ቃን ተጠቀሙ። እኛ . . . እኛ ተግራዊ ማድረግ በሚቻልበት ሥፍራ የጠወሰኑ ሰዎችን ብቻ የሚያመለክትን ቃልን ተጠቀሙ።

Acts 6:5

የሐዋርያት ሥራ 6: 5-6
ንግግራቸው ሰዎችን አስደሰተ የተናሩት ነገር ተቀባይነት አገኘ እስጥፋኖስ . . . እና ኒቃሮናን እነዚህ የግሪክ ስሞች ናቸው። እነዚህ ስሞች የተመረጡት ሰዎች ብዙዎቹ ወይም ሙሉ ለሙሉ ከግሪካዊያን አይሁድ አማኞች ቡድን ውስጥ መሆኑን አመላካች ነው። ወደ አይሁድ ሃይማኖት የተለወጠ “ወደ አይሁድ ሃይማኖት የተለወጠ አሕዛብ” እጆቻቸውን ጫኑባቸው ባረኳቸው እንዲሁም ለሰባቱም ሥራውን መሥራት እንዲችሉ ኃላፊነት እና ስልጣን አካፈሏቸው።

Acts 6:7

የሐዋርያት ሥራ 6: 7-7
አጠቃላይ መረጃ: ይህ ዓረፍተ ነገር የቤተ ክርስቲያንን እድገት አስመልክቶ የተሰጠ የጊዜው መረጃ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ያድግ ነበር ተጽእኖው እየተስፋፋ መጠ። ለእምነት መታዘዝ "አዲሱን የእምነት መንገድ መከተል"

Acts 6:8

የሐዋርያት ሥራ 6: 8-9
አጠቃላይ መረጃ: ይህ የአዲስ ታሪክ ጅማሬ ነው። እነዚህ ቁጥሮች ታሪኩን ለመረዳት ያስችሉ ዘንድ ስለእስጥፋኖስ እና ስለሌሎች ሰዎች የኃላ ታሪክ መረጃዎችን ይሰጣሉ። የነጻ ወጪዎች "ነጻ የወጡ ሰዎች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከተለያዩ በታዎች ከባርነት ነጻ የወጡ ሰዎችን ለማመልከት ነው። በዚያ ስፍራ ስማቸው የተጠቀሱት ሌሎች ሰዎች የምኩራቡ አባላት ይሁኑ አይሁኑ ወይም ከእስጥፋኖስ ጋር በነበረው ክርክር ውስጥ ተሳታፉዎች ብቻ ይሁኑ ምንም የሚታወቅ ነገር የለም። ከእስጥፋኖስ ጋር ይከራከሩ ነበር "ከእስጥፋኖስ ጋር ይከራከሩ ነበር" (UDB) ወይም "ከእስጥፋኖስ ጋር ይወያዩ ነበር"

Acts 6:10

የሐዋርያት ሥራ 6: 10-11
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: በ ACT 6:8 ላይ የተጀመረው የኃላ ታሪክ መረጃ የመስጠቱ ነገር እስከ ቁጥር 10 ድረስ ቀጥሏል። ከዚያም ይህ በታሪኩ ውስጥ የድርግቱ ጅማሬን የሚያሳይ ምልክት ነው። ልቋቋሙት "ለመግት ሀሳቡ ምላሽ መስጠት አልተቻላቸውም" መንፈስ "መንፈስ ቅዱስ" በድብቅ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በማሳመን "በምስጥር በማሳመን" የስድብ ቃላት አማራጭ ትርገጉሞች: "በእግዚአብሔር እና የሙሴ ሕግጋት ተቃውሞ መናገር"

“ስለማንጻባረቁ” ባይናገረም ማነጻጸሪያ። አማራጭ ትርጉም፡ "እንደ መላእክ ፊት ያበራ ነበር"

Acts 6:12

የሐዋርያት ሥራ **6**፡ **12**-**15**
ሕዝቡን ማነሳሳት "ሕዝቡ እንዲቆጣ ማነሳሳት" ያዙት "ያዙት" ፊቱ የመላእክት ፊት ይመስላል ይህ ምሳሌያዊ ንግግር ምንም እንኳ በግልጽ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 7

1 ሊቀ ካህናቱም፣ “እነዚህ ነገሮች እውነት ናቸውን?” አለ። 2 እስጢፋኖስ እንዲህ ብሎ መለሰ፦ “ወንድሞችና አባቶች ሆይ፣ አድምጡኝ፤ የክብር አምላክ
ለአባታችን ለአብርሃም በካራን ከመኖሩ በፊት በመስጴጦምያ ሳለ ተገለጠለት፤ 3 እግዚአብሔርም፣ 'አገርህንና ዘመዶችህን ተውና እኔ ወደማሳይህ ምድር ሂድ'
አለው። 4 ከዚያም በኋላ፣ ጊዜ አብርሃም ከከለዳውያን ምድር ወጥቶ በካራን ኖረ፤ ከዚያም፣ አባቱ ከሞተ በኋላ፣ እግዚአብሔር አሁን እናንተ ወደምትኖሩበት፣
ወደዚህ ምድር አመጣው። 5 ከዚህ ምድር ምንም ርስት፣ የእግር ጫማ ለማሳረፍ የሚበቃ እንኳ አልሰጠውም። ነገር ግን አብርሃም ገና ልጅ ያልነበረው ቢሆንም
እንኳ፣ እግዚአብሔር ምድሪቱን ርስት አድርጎ ለእርሱና ከእርሱ በኋላ ለዘሮቹ እንደሚሰጥ ቃል ገባ። 6 እግዚአብሔር ለአብርሃም እንደዚህ እየተናገረው ነበር፤
ይኸውም ዘሮቹ ለተወሰነ ጊዜ በባዕድ ምድር እንደሚኖሩ፣ እዚያ ያሉ ፈሪዎችም በባርነት ውስጥ እንደሚያስገቧቸውና ለአራት መቶ ዓመታት
እንደሚያስጨንቋቸው ነው። 7 ‘በባርነት የሚኖሩበትን ሕዝብም እፈርድበታለሁ፤ ከዚያም በኋላ ይወጣሉ፤ በዚህም ስፍራ ያመልኩኛል’ አለ እግዚአብሔር። 8
እግዚአብሔር ለአብርሃም የግዝረትን ኪዳን ሰጠው፤ አብርሃምም የይስሐቅ አባት ሆነ ይስሐቅንም በስምንተኛው ቀን ገረዘው፤ ይስሐቅ የያዕቆብ አባት ሆነ፤
ያዕቆብም የዐሥራ ሁለቱ አለቆች አባት። 9 አለቆች በዮሴፍ ላይ በቅናት ተነሣሥተው ወደ ግብፅ ሸጡት፤ እግዚአብሔር ግን ከእርሱ ጋር ነበረ፤ 10 ከመከራውም
ሁሉ አዳነው፤ በግብፅ ንጉሥ በፈርዖን ፊትም ሞገስና ጥበብ ሰጠው። ፈርዖንም ዮሴፍን በግብፅና በቤቱ ባለው ሁሉ ላይ ገዥ አደረገው። 11 በመላው ግብፅና
በከነዓን ራብና ትልቅ ጭንቀት መጣ፤ አባቶቻችንም ምንም ምግብ አላገኙም። 12 ነገር ግን ያዕቆብ እህል በግብፅ ውስጥ እንደ ነበረ ሲሰማ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ
አባቶቻችንን ላካቸው። 13 በሁለተኛው ጊዜ ዮሴፍ ለወንድሞቹ ራሱን ገለጠ፤ የዮሴፍ ቤተ ሰብም ከፈርዖን ጋር ተዋወቀ። 14 ከዘመዶቹ ሁሉ ጋር፣ ሰባ ዐምስት
ሰዎች ሆኖ ወደ ግብፅ እንዲመጣ፣ ለአባቱ ለያዕቆብ እንዲነግሩ ዮሴፍ ወንድሞቹን መልሶ ላካቸው። 15 ስለዚህ ያዕቆብ ወደ ግብፅ ወረደ፤ ከጊዜ በኋላም፣
እርሱና አባቶቻችን በዚያ ሞቱ። 16 ወደ ሴኬም ተወስደውም አብርሃም በሴኬም ከኤሞር ልጆች በብር ገዝቶት በነበረው መቃብር ተቀበሩ። 17 እግዚአብሔር
ለአብርሃም ገብቶት የነበረው የተስፋ ቃል ጊዜ ሲቃረብ፣ ሕዝቡ በግብፅ ውስጥ በቍጥር እያደጉና እየበዙ ሄዱ፤ 18 በግብፅ ሌላ ንጉሥ፣ ስለ ዮሴፍ ያላወቀ
ንጉሥ እስከ ተነሣ ድረስ። 19 ይኸው ንጉሥ ሕዝባችንን አታለለ፤ አባቶቻችንንም አስጨነቀ፤ ሕጻናቶቻቸውን በሕይወት እንዳይኖሩ ወደ ውጭ መጣል
ነበረባቸው። 20 በዚያ ጊዜ ሙሴ ተወለደ፤ እርሱ በእግዚአብሔር ፊት በጣም ያማረ ነበር፤ በአባቱ ቤትም ሦስት ወር አደገ። 21 ሙሴ ወንዝ ውስጥ ሲጣል፣
የፈርዖን ሴት ልጅ ወስዳ እንደ ልጇ አሳደገችው። 22 ሙሴ በግብፃውያን ትምህርት ሁሉ የሠለጠነ፣ በንግግሩና በሥራውም ታላቅ ሰው ነበር። 23 አርባ ዓመት
ሲሆነው ግን ወንድሞቹን፣ የእስራኤልን ልጆች የመጐብኘት ዐሳብ ወደ ልቡ መጣ። 24 አንድ እስራኤላዊ ሲጠቃ አይቶ፣ ሙሴ ተከላከለለት፤ ያጠቃውንም
ግብፃዊ ተበቀለው፤ 25 ሙሴ በእርሱ እጅ እግዚአብሔር እያዳናቸው መሆኑን ወንድሞቹ ያስተውላሉ ብሎ ዐሰበ፤ እነርሱ ግን አላስተዋሉም። 26 በሚቀጥለው
ቀን ሙሴ እየተጣሉ ወደ ነበሩ እስራኤላውያን መጣ፤ እርስ በርስ ሊያስታርቃቸውም ሞከረ፤ ‘እናንተ ሰዎች ሆይ፣ ወንድማማቾች ናችሁ፤ እርስ በርስ ለምን
ትጐዳዳላችሁ?’ አለ። 27 ባልንጀራውን የጐዳው ግን ሙሴን ገፈተረው፤ እንደዚህም አለው፤ 'በእኛ ላይ ገዥና ዳኛ ያደረገህ ማን ነው? 28 ግብፃዊውን ትናንት
እንደ ገደልኸው እኔንም ልትገድለኝ ትፈልጋለህን?' 29 ሙሴ ይህን ከሰማ በኋላ ሸሽቶ ሄደ፤ የሁለት ልጆች አባት በሆነበት በምድያም ምድር መጻተኛ ሆነ። 30
አርባ ዓመት ሲያልፍ፣ በሲና ተራራ ምድረ በዳ፣ በቍጥቋጦ ውስጥ በእሳት ነበልባል መልአክ ታየው። 31 ሙሴ እሳቱን ሲያይ፣ በሚታየው ተደነቀ፤ ሊመለከተው
ሲቀርብም፣ እንዲህ የሚል የጌታ ድምፅ መጣ፤ 32 ‘እኔ የአባቶችህ አምላክ፣ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅም አምላክ፣ የያዕቆብም አምላክ ነኝ።’ ሙሴ
ተንቀጠቀጠ፣ መመልከትም አልቻለም። 33 ጌታም ለሙሴ እንዲህ አለው፤ ‘የቆምህበት ስፍራ ቅዱስ ነውና ጫማህን አውልቅ። 34 በግብፅ ውስጥ ያሉትን
የሕዝቤን ሥቃይ በእርግጥ አይቻለሁ፤ የሥቃይ ጩኸታቸውን ሰምቻለሁ፤ ላድናቸውም ወርጃለሁና አሁን ና፤ ወደ ግብፅ እልክሃለሁ።’ 35 “በእኛ ላይ ገዥና ዳኛ
ያደረገህ ማን ነው?” ባሉት ጊዜ ተቀባይነትን ያሳጡት ይህ ሙሴ፦ እግዚአብሔር ገዥም ታዳጊም አድርጎ የላከው ነው። እግዚአብሔር ሙሴን በቍጥቋጦው
ውስጥ በታየው መልአክ እጅ ላከው። 36 በግብፅና በቀይ ባሕር፣ በአርባ ዓመታቱ ወቅትም በምድረ በዳ ተአምራትንና ምልክቶችን ካደረገ በኋላ፣ ሙሴ ሕዝቡን
ከግብፅ አወጣቸው። 37 ‘እግዚአብሔር ከወንድሞቻችሁ መካከል እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣላችኋል’ ብሎ ለእስራኤል ሕዝብ የተናገረው ያው ሙሴ ነው። 38
ይህ ሰው ሲና ተራራ ላይ ያናግረው ከነበረው መልአክ ጋር በምድረ በዳው በጉባኤ ውስጥ የነበረ ሰው ነው። ሰው ከአባቶችችን ጋር ነበረ፤ ለእኛ ሊሰጥ ሕያው
ቃልን የተቀበለ ሰውም ነው። 39 ይህ አባቶቻችን ለመታዘዝ እንቢ ያሉት ሰው ነው፤ እነርሱም ገፉት፤ በልባቸውም ወደ ግብፅ ተመለሱ። 40 በዚያ ጊዜ አሮንን
እንዲህ አሉት፤ ‘የሚመሩንን አማልክት ሥራልን። ከግብፅ ምድር መርቶ ያወጣን ይህ ሙሴ፣ ምን እንዳጋጠመው አናውቅም።' 41 ስለዚህ እስራኤላውያን
በእነዚያ ቀኖች ጥጃ ሠርተው ለጣዖቱ መሥዋዕት አቀረቡ፤ ከእጆቻቸው ሥራ የተነሣም ደስ አላቸው። 42 እግዚአብሔር ግን ዘወር አለ፤ የሰማይ ከዋክብትን
እንዲያመልኩም አሳልፎ ሰጣቸው፤ በነቢያት መጽሐፍ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፦ የእስራኤል ቤት ሆይ፣ አርባ ዓመት በምድረ በዳ፣ የታረዱ እንስሳትንና
መሥዋዕቶችን አቀረባችሁልኝን? 43 የሞሎክን ድንኳን፣ ሬምፉም የሚባለውን አምላክ ኮከብም፣ ልታመልኳቸው የሠራችኋቸውን ምስሎችም ተቀበላችሁ፤ እኔም
ከባቢሎን ወዲያ እሰድዳችኋለሁ።’ 44 አባቶቻችን የምስክሩ ድንኳን በምድረ በዳ ነበራቸው፤ ይኸውም ባየው ምሳሌ መሠረት መሥራት እንዳለበት
እግዚአብሔር ሙሴን ሲያናግረው እንዳዘዘው ያለ ነው። 45 ይህ አባቶቻችን በተራቸው ከኢያሱ ጋር ወደ ምድሪቱ ያመጡት ድንኳን ነው። እግዚአብሔር
በአባቶቻችን ፊት ባስወጣቸው አሕዛብ አገር ውስጥ ሲገቡ፣ ይህ ሆነ። እስከ ዳዊት ዘመን ድረስ እንደዚህ ነበር፤ 46 ዳዊት በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ አገኘ፤
ለያዕቆብ አምላክም ማደሪያ ስፍራን ለማግኘት ለመነ። 47 ነገር ግን ሰሎሞን ለእግዚአብሔር ቤት ሠራለት። 48 ይሁን እንጂ፣ ልዑሉ በእጅ በተሠሩ ቤቶች
ውስጥ አይኖርም፤ ይህም ነቢዩ እንዲህ ብሎ እንደሚናገረው ነው፦ 49 ሰማይ ዙፋኔ፣ ምድርም የእግሬ መርገጫ ነው። ምን ዐይነት ቤት ልትሠሩልኝ
ትችላላችሁ? ይላል ጌታ፤ ወይስ የማርፍበት ስፍራ የት ነው? 50 እጄ እነዚህን ሁሉ አልሠራችምን? 51 እናንተ ዐንገተ ደንዳኖች፣ ልባችሁንና ጆሮዎቻችሁን
ያልተገረዛችሁ፣ ሁልጊዜ መንፈስ ቅዱስን ትቃወማላችሁ፤ አባቶቻችሁ እንዳደረጉትም ታደርጋላችሁ። 52 ከነቢያት የእናንተ አባቶች ያላሳደዱት የትኛው ነው?
እነርሱ ከጻድቁ መምጣት ቀድመው የተናገሩ ነቢያትን ገድለዋል፤ እናንተም አሁን ጻድቁን የምትክዱና የምትገድሉ ሆናችኋል፤ 53 መላእክት ያጸኑትን ሕግ
ብትቀበሉም አልጠበቃችሁትም።” 54 አሁን የሸንጎው አባላት እነዚህን ነገሮች ሲሰሙ፣ በልባቸው እጅግ ተቈጡ፣ ጥርሳቸውንም በእስጢፋኖስ ላይ አፋጩ።
55 እስጢፋኖስ ግን በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ፣ ወደ ሰማይ አተኵሮ ተመለከተ፣ የእግዚአብሔርንም ክብር አየ፤ ኢየሱስንም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየው። 56
እስጢፋኖስ፣ “እነሆ፣ ሰማያት ተከፍተው፣ የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየሁ” አለ። 57 የሸንጎው አባላት ግን በታላቅ ድምፅ ጮኹ፤ ጆሮአቸውንም
በመድፈን በአንድነት እየሮጡ ወደ እስጢፋኖስ ሄዱ፤ 58 ከከተማው አውጥተውም በድንጋይ ወገሩት፤ ምስክሮችም ልብሳቸውን ሳውል በሚባል አንድ ወጣት
እግር አጠገብ አኖሩ። 59 እስጢፋኖስን ሲወግሩት፣ ወደ እግዚአብሔር ይጣራ፣ “ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ ነፍሴን ተቀበል” እያለ ይናገርም ነበር። 60 ተንበረከከና
በታላቅ ድምፅ፣ “ጌታ ሆይ፣ ይህን ኀጢአት አትቊጠርባቸው” ብሎ ጮኸ። ይህን ተናግሮም፣ አንቀላፋ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Acts 7:1

የሐዋርያት ሥራ 7፡ **1-3**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: በ ACT 6:8 ላይ የተጀመረው ስለእስጥፋኖስ የተነገረው ታሪክ ይቀጥላል። አጠቃላይ መረጃ: በቁጥር 2 ላይ እስጥፋኖስ ለሊቀ ካህኑ እና ሸንጎው ምላሽ መስጠቱን ይጀምራል። ንግግሩንም የጀመረው በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ስለተፈጸሙ ነገሮች በመናገር ነው። ወንድሞች እና አባቶች አድምጡኝ እስጥፋኖስ ንግግሩን የጀመረው ለእነርሱ አክብሮት እንዳለው በሚያሳይ መልኩ እንደዘመዶቹ ሰላምታ በማቅረብ ነው። አባታችን እስጥፋኖስ አድማጮቹን “አባታችን አብረሃም” በሚለው ንግግሩ ውስጥ አካቷቸዋል። ምድርህንና ዘመዶችህን ተው "የአንተን" የሚለው ቃል የሚያመለክተው አብረሃምን ነው (ነጠላ ቁጥር)።

Acts 7:4

የሐዋርያት ሥራ 7፡ **4-5**
አሁን የምትኖርባት በዚህ ሥፍራ ላይ “እናንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የአይሁድ ሸንጎን እና በሥፍራው ላይ ያሉትን የሚያደምጡትን ሰዎችን ነው። ርስቱ ይሆን ዘንድ መሬቱ ለዘላለም የአብረሃም ይሆን ዘንድ።

Acts 7:6

የሐዋርያት ሥራ 7፡ **6-8**
ለእርሱ ባሮች ይሆናሉ "የአንተ ዘሮች ባሮች ይሆናሉ" ስለዚህም አብረሃም የይሳቅ አባት ሆነ ታሪኩ የአብረሃ ዘሮች ታሪክ መሸጋገሪያ ነው።

Acts 7:9

የሐዋርያት ሥራ 7፡**9-10**
አባቶች "የያዕቆብ ወንድ ልጆች" or "Joseph's older brothers"

Acts 7:11

የሐዋርያት ሥራ 7፡ **11-13**
ረሃብ ሆነ "ረሃብ መጣ።" ምድርቷ ፍሬ መስጠት አቆመች። አባቶቻችን "የዮሴፍ ታላለቅ ወንድሞች" ስንዴ አማራጭ ትረጉም: "ምግብ" ራሱን ገለጠላቸው ዮሴፍ ለወንድሞቹ ማንነቱን ገለጠላቸው።

Acts 7:14

የሐዋርያት ሥራ 7፡ **14-16**
እርሱ ራሱ እና አባቶቻችን "ያዕቆብ እና የእርሱ ልጆች፣ አባቶቻችን" ተሸክመው ወሰዱት "የያዕቆብ ልች የያዕቆብን እና የወንድ ልጆቹን አጽም ተሸክመው ወሰዱ" በብር "ገንዝብ"

Acts 7:17

የሐዋርያት ሥራ 7፡ **17-19**
የተስፋው ሰዓት እግዚአብሔር ለአብረሃም የገባው ቃል መፈጸሚያ ሰዓት በተቃረበ ጊዜ። ስለዮሴፍ የማያውቅ "ዮሴፍ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የዮሴፍን መልካም ሥራ የማያውቅ የሚለውን ነው። አማራጭ ትርጉም: "ዮሴፍ በግብጽ ምድር ውስጥ የነበረውን ስልጣን የማያውቅ።" ሕዝባችንን "የእኛን" የሚለው ቃል እስጥፋኖስን እና ንግግሩን በማድመጥ ላይ ያሉትን ሰዎች የሚያካትት ነው። አባቶቻችን ጨቆናቸው "አባቶቻችንን አሰቃያቸው" ወይም "አባቶቻችንን በዘበዛቸው" ልጆቻችን አውጥተው ይጥሉ ነበር ልጆቻቸው ይሞቱ ዘንድ አውጥተው ይጥሉ ነበር

Acts 7:20

የሐዋርያት ሥራ 7፡ **20-21**
በዚያን ጊዜ ይህ አዲስ ሰውን (ሙሴን) ለማስተዋወቅ ጥቅም ላይ የዋለ ቃል ነው። በእግዚአብሔር ፊት ያማረ ነው "በእግዚብሔር ፊት" የሚለው ቃል የሙሴን ቁንጅና ለማሳየት የገባ ቃል ነው። When he was thrown out ሙሴ “የተጣለው” ከፈርኦን ትዕዛዝ የተነሣ ነው። ወሰዱት "ለማሳደግ ወሰዱት" (መምናልባም ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ሊሆን ይችላል) እንደ ገዛ ልጁ "የገዛ ልጁ እስኪመስል ድረስ"

Acts 7:22

የሐዋርያት ሥራ 7፡ **22-25**
ሙሴ ተማረ "ግብጻዊያን ሙሴን አስተማሩት" የግብጻዊያንን ጥበብ ሁሉ ይህ “ግብጻዊያን የሚያውቋቸውን ብዙ ነገሮች” ለማሳየት የቀረበ ግነት የሞላበት ንግግር ነው። በቃሉ እና በሥራው የበረታ "በተግባሩ እና በንግግሩ ውጤታማ የሆነ" ወይም "በቃሉ እና በተግባሩ" ኃይለኛ የሆነ (UDB) ወይም "በሚያደርቸው እና በሚናገራው ነገሮች ተጽእኖ ፈጣሪ የሆነ" ወንድሞቹን ጎበኛቸው የአኗኗር ሁኔታቸውን ለመመልከት ግብጻዊውን መታው ሙሴ ግብጻዊውን ሰው በኃይል መታው ስለዚህም ሰውዬው ሞተ። አሰበ "አሰላሰለ" በእጁ "በእርሱ በኩል" ሊያድናቸው አማራጭ ትርጉም: "ወዲያውም ልታደጋቸው"

Acts 7:26

የሐዋርያት ሥራ 7፡ **26-28**
እናነተ፣ ወንድማማቾች ናችሁ ይህ እርስ በእርሳቸው ስጣሉ የነበሩትን እስራኤላዊንን የሚያመለክት ነው። መጎዳት መጉዳት የሚለው ቃል አንድን ሰው ላይ ፍትሐዊ ያልሆነ ነገር ማድረግ ወይም ታማኝነት ማጉደል ማለት ነው። አንተን በእኛ ላይ ገዥ እና ፈራጅ ያደረገህ ማን ነው? ይህ ጥያቄ ጥቅም ላይ የዋለው ሙሴን ለመገሰጽ ነው። አማራጭ ትርጉም: "በእኛ ላይ ምንም ዓይነት ስልጣን የለህም!" በእኛ ላይ ፈራጅ ያደረግ? እስራኤላዊያን ሙሴ የእነርሱ እንደሆነ አያስቡም ነበር።

Acts 7:29

የሐዋርያት ሥራ 7፡**29-30**
ይህንን ከሰማ በኋላ በዚህ ሥፍራ ላይ በተዘዋዋር መልኩ የተገለጸው መረጃ "ከዚያ አንድ ቀን በፊት ሙሴ ግብጻዊውን ሰው መግደሉን እስራኤላዊያን ሰምተዋል ማለት ነው።" አርባ ዓመታት ካለፉ በኋላ "ሙሴ ከግብጽ ምድር ከሸሸ በኋላ አርባ ዓመታት ካለፉ በኋላ"

Acts 7:31

የሐዋርያት ሥራ 7፡ **31-32**
በተመለከተው ነገር ተደነቀ ሙሴ ቁጥቋጦው በእሳት አለመንደዱን በመመልከቱ በጣም ተደነቀ። ይህ የእስጥፋኖስን ንግግር በማድመጥ ላይ በነበሩት ሰዎች ዘንድ አስቀድሞ የታወቀ ነበር። ተጠግቶ ስመለከት . . . ሙሴ እጅግ ከመፍራቱ የተነሣ ወደ ቁጥቋጦው ለመመልከት አልደፈረም ይህ ምናልባት ሙሴ በመጀመሪያ ወደ ቁትቋጦው ምን እንደሆነ ለማየት መጠጋቱን ነገር ግን ከፍርሃቱ የተነሣ ወደ ኋላ መመለሱን የሚያሳይ ሊሆን ይችላል። በጣም ፈራ ሙሴ ከፍርሃቱ የተነሣ ተንቀጠቀጠ።

Acts 7:33

የሐዋርያት ሥራ 7፡ **33-34**
የቆምክበት ሥፍራ የተቀደሰ ነው በዚህ ንግግር ውስጥ በተዘዋዋር መንገድ የተገለጠው መረጃ ሥፍራው የእግዚአብሔር መገኘት ያለበት፣ የእግዚአብሔር ሕልውና ያለበት ወይም በእግዚአብሔር የተቀደሰ ሥፍራ ነው። በእርግጠኝነት ተመለከተ "በእርግጠኝነት" “የመመልከቱን” ዓይነት በመግለጽ አጽኖት

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የሚሰጥ ነው። ሕዝቤን "የአብረሃም፣ የይሳቅ እና የያዕቆብ የልጅ ልጆች" እኔ ራሴ መጥቻለሁ "በግሌ ነጻ እንደወጡ ለማየት"

Acts 7:35

የሐዋርያት ሥራ 7፡ **35-37**
አጠቃላይ መረጃ: ቁጥር 35-38 ላይ ከሙሴ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የተለያዩ ተከታታይ ሀረጎች ይገኛሉ። በእያንዳንዱ ሀረጎች መጀመሪያ ላይ “ይህ ሙሴ” ወይም “ይኼው ሙሴ” የሚለው ነገር እናገኛን። ከተቻለ ተመሳሳይ አጽኖት መስጠት ያስችል ዘንድ ተመሳሳይ ቃላትን እናንተ ተጠቀሙ። እነረሱ ያልተቀበሉት ይህ ሙሴ ይህ በ ACT 7:26-28 ላይ የተጠቀሰውን ያመለክታል። ገዥ እና ፈራጅ ያደረገህ ማን ነው? ይህንን በ ACT 7:26 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። ገዥ እና ነጻ አውጪ "በእርሱ ላይ የሚገዛ እና ከባርነት ነጻ የሚያወጣ" በመለአክት እጅ "በመለአክት አማካኝነት" በአራባ ዓመታት ውስጥ "እስራኤላዊያን በምድረ በዳ ውስጥ በኖሩባቸው አርባ ዓመታት" (UDB) ከወንድሞቻችሁ መካከል "ከእናንተው ወንድሞች መካከል" (UDB)

Acts 7:38

የሐዋርያት ሥራ 7፡ **38-40**
አጠቃላይ መረጃ: ቁጥር 35-38 ላይ ከሙሴ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የተለያዩ ተከታታይ ሀረጎች ይገኛሉ። በእያንዳንዱ ሀረጎች መጀመሪያ ላይ “ይህ ሙሴ” ወይም “ይኼው ሙሴ” የሚለው ነገር እናገኛን። ከተቻለ ተመሳሳይ አጽኖት መስጠት ያስችል ዘንድ ተመሳሳይ ቃላትን እናንተ ተጠቀሙ። ይህ በጉባኤው መካከል ያለ ሰው ነው። "ይህ ከእስራኤላዊን መካከል የነበረው ሙሴ ነው።" (UDB) ይህ ለእኛ ለመስጠት ሕያው የሆነውን ቃል የተቀበለው ሰው ነው አማራጭ ትርጉም: "ይህ ለእኛ እንዲሰጥ እግዚብሔር ሕያው ቃልን የተናገረው ሰው ነው" ሕያው ቃላትን አማራጭ ትርጉሞች 1) "ጸንቶ የሚቆም ቃል" ወይም 2) "ሕይወት የሚሰጥ ቃላት።" ከራሳቸው ገፍተው አራቁት ይህ ምሳሌያዊ ንግግር ሙሴን አለመቀበላቸውን አጽኖት የሚሰጥ ነው። አማራጭ ትርጉም: "ሙሴን መሪያቸው አድርው አልተቀበሉትም" በዚያ ጊዜ "ወደ ግብጽ ለመመለስ በወሰኑ ጊዜ"

Acts 7:41

የሐዋርያት ሥራ 7፡ **41-42**
አጠቃላይ መረጃ: በቁጥር 42 ላይ እስጥፋስ ከነቢያት መጽሐፍ፣ በተለይም ከአሞጽ መጽሐፍት መጥቀስ ጀመረ። የወርቅ ጥጃ ሠሩ "ጥጃ የሚመስል ሐውልት ሠሩ" በሰማይ የሚገኙ ክዋክብትን አመለኩ "ክዋክብትን እንደ አማልክት አድርገው ማምለክ ጀመሩ" የታደውን ከብት እና መስዋእትን አቀረባችሁልጅ . . . እስራኤል? እግዚአብሔር በዚህ ጥያቄ አማካኝነት ያቀረበው ሀሳብ እስራኤላዊያን በመሰዋእትን እርሱ አለማመለካቸውን ነው። አማራጭ ትርጉም: "እናንተ እስራኤላዊያን. . . የሚታድ መስዋእትን አላቀረባችሁልኝም።" የእስራኤል ቤት ይህ አጠቃላይ እስራኤላዊንን የሚያመለክት ምሳሌያዊ ንግግር ነው።

Acts 7:43

የሐዋርያት ሥራ 7፡**43-43**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: እስጥፋኖስ በ ACT 7:2 ላይ የጀመረውም ለሊቀ ካህኑ እና ሸንጎው ምላሽ የሰጠበትን ንግግሩን ቀጥሏል። እንዲሁም እስጥፋኖስ ከነቢያት መጽሐፍ በመውሰድ በ ACT 7:42 ላይ የጀመረውን ንግግር በዚህ ክፍል ውስጥ አጠናቋል። የሞልኮን ድንኳን ሞልኮን የተሰኘው የሐሰት አምላክ ድንኳን። ሬምፉም የሚሉትን የአምላካችሁን ኮከብ ይህ ኮከብ ሬምፋም የተሰኘው የሐሰት አምላክ ነው ይላሉ የሠራችኋቸውን ምስሎች የሞልኮን እና ሬምፋም አማልክት ምስሎችን ለማምለክ በእጆቻቸው አበጅተዋቸው ነበር። እኔም ከባቢሎን ወዲያ እሰዳችኋለሁ "ወደባቢሎን መድር እሰዳችኋለሁ"

Acts 7:44

የሐዋርያት ሥራ 7፡ **44-46**
የምስክር ድንኳን ዐሥርቱ ትዕዛዛትን በላዩ ላይ የያዘው ድንጋይ የሚቀመጥበት ድንኳን ቤት። የሀገርቱ ንብረቶች ይህ ምድርቷን፣ ሕንተጻዎቿን፣ ሰብሏን፣ እንስሳቶቿ እንዲሁም እስራኤላዊያን የያዝዋቸውን ሥፍራዎች ውስጥ ያሉትን ሀብቶች ያካትታል። ታቦቱ እስከ የእስራኤል ንጉሥ ዳዊት ዘመን ድረስ፣ የዳዊትን ዘመን ጨምሮ በድንኳን ውስጥ ነበር። የያዕቆብ አምላጅ ማደሪያ ሥፍራ ዳዊት ታቦቱ በእስራኤል ውስጥ ከቦታ ቦታ ከሚዘዋወር ይልቅ በእየሩሳሌም እንዲሆን ፈልጎ ነበር።

Acts 7:47

የሐዋርያት ሥራ 7፡ **47-50**
አጠቃላይ መረጃ: በቁጥር 49 እና 50 ላይ እስጥፋኖስ ከነቢዩ እሳያስ መጽሐፍ በመጥቀስ ተናግሯል። በዚህ ጥቅስ ውስጥም እግዚአብሔር ስለራሱ ይናገራል። በእጅ የተሠራ ቤት ውስጥ "በሰዎች በተሠራ" ሰማይ ዙፋኔ ነው . . . ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት ነብዩ የእግዚአብሔር መገኘት ትልቅነት በማሳየት ምድርና ሞላዋ የእግዚአብሔር የእግሩ መረገጫ መሆኗ በማሳየት የሰው ልጅ በምድር ላይ ለእግዚአብሔር ማደሪያ ሥፍራ ማዘጋጀት እንደማይችል አሳይቷል። ለእኔ ምን ዓይነት ቤት ትሠሩልኛላችሁ? እግዚአብሔር በዚህ ጥያቄ መሠረት ያሳየው ዬትኛውም የሰው ልጅ ጥሬ የእግዚአብሔርን ባሕርይ ማሟላት እንደማይችል ነው!" ለእኔ ማረፊያ ሥፍራ ከየዬት ይገኛል? እግዚአብሔር ይህንን ጥያቄ የጠየቀው የሰው ልጅ ለእግዚአብሔር ማረፊያ ማዘጋጀት እንደማይችል ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም: "ለእኔ በቂ ማረፊያ የሚሆን ሥፍራ የለም!" እነዚህ ሁሉ ነገሮች የፈጠርኳቸው እኔ አይደለሁምን? እግዚአብሔር ይህንን ጥያቄ የጠየቀው የሰው ልጅ የፈጠረው አንዳችም ነገር አለመኖሩን ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም: "እጆቼ ይህንን ሁሉ ነገር ፈጥራለች!"

Acts 7:51

የሐዋርያት ሥራ 7፡ **51-53**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: እስጥፋኖስ ለካህናት አለቃው እና ለሸንጎው በ ACT 7:2 ላይ ምላሽ መስጠት የጀመረበትን ንግግር የሚበቃበት ነው። እናንተ አንገተ ደንዳኖች አንገተደ ደንዳኖች - እስጥፋኖስ ራሱን ከእርሱ እንደ አንዱ ማድረጉን ትቶ የአይሁድ መሪዎችን ወደ መገሰጽ ዞሯል።

ልባችሁ ያልተገረዘ "የማይታዘዝ ልብ ያላችሁ።" በዚህ ንግግር እስጥፋኖስ ምናልባት እነርሱ ከአሕዛብ ጋር እያነጻጸረ ሊሆን ይችላል። ይህንን ንግግሩን ምናልባት እንደ ስድብ ልቆጥሩት ይችላሉ። ከነቢያት መካከል አባቶቻችሁ ያላሳደዷቸው ነቢያት ዬትኞቹ ናቸው? እስጥፋኖስ ይህንን ጥያቄ የጠየቀበት ምክንያት ከአባቶቻቸው ስህተት አለመማራቸውን ለማሳየት ነው።፤ አማራጭ ትርጉም: "ቀደምት አባቶቻችሁ ሁሉንም ነቢያት ያሳድዱ ነበር!" ቅዱሱን ይህ ክርስቶስን፣ መስሐን ያመለክታል። የእርሱ ገዳዮች "የቅዱሱ ገዳዮች" ወይም "የክርስቶስ ገዳዮች"

Acts 7:54

የሐዋርያት ሥራ 7፡ **54-56**
እነዚህን ነገሮች ሰሙ ይህ ነገሩ የተለወጠበት ሥፍራ ነው፤ ስብከቱ ያበቃበት እንዲሁም ሸንጎም አጸፋዊ ምላሽ የሰጡበት ነው። በልባቸው ቆረጡ ይህ “ሁሉም በንግግሩ መበሳጨታቸውን” የሚያሳይ ምሳሌያዊ ንግግር ነው። ጥርሳቸውን አፋጨበት ይህ ከፍተኛ ንዴት ወይም ጥላቻ ማሳያ መንገድ ነው። አማራጭ ትርጉም: "በጣም ከመናደዳቸው የተነሣ ጥርሳቸውን አፋጨበት።" ወደ ሰማይ ትኩር ብሎ እየተመለከ "ወደ ሰማይ እያየ።" ይህንን ራዕይ የተመለከተው እስጥፋኖስ ብቻ ይመስላል። ከሕዝቡ መካከል ይህንን ያየ ሰው ያለ አይመስልም። የእግዚአብሔር ክብር "የእግዚአብሔር ክብር እንደ ብርሃን።" አማራጭ ትርጉም: "ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነ ደማቅ ብርሃን።" ኢያሱስ ቆሞ ተመለከተ ኢያሱስ በእግዚአብሔር ቀኝ “ሞ” እንደነበር

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አስተውሉ። ይህ ንጉሥ እንግዳ ሰው ሲመጣ በክብር ለመቀበል የሚደርገው ነገር ነው። የሰው ልጅ እስጥፋኖስ ኢየሱስን “የሰው ልጅ” ብሎ ይጠራዋል።

Acts 7:57

የሐዋርያት ሥራ 7፡ **57**-**58**
ጆሮዋቸው ቆመ ከዚያ በኋላ እስጥፋኖስ የሚናገረውን ነገር ላለመስማት ጆሮዋቸውን ያዙ። ከከተማው ውጪ አወጡት "የሸንጎ አባላቱም እስጥፋኖስን በመያዝ ከከተማው ውጪ በጉልበት ይዘውት ወጡ" መደረቢያቸውን ይህ ከውጪ እንደ ጃኬት ወይም ኮት ከውጪ ተደርቦ የሚለበስ ልብስ ነው። በእግር ሥር "ፊት ለፊት" ለመጠበቅ ይመቻቸው ዘንድ

Acts 7:59

የሐዋርያት ሥራ 7፡ **59**-**60**
መንፈሴን ተቀበል "መንፈሴን ውሰድ" አንቀላፋ ይህ በጨዋ ደንብ “መሞቱን” ለመግለጽ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 8

1 ሳውል በእስጢፋኖስ ሞት ተስማምቶ ነበር። በዚያም ጊዜ በኢየሩሳሌም በነበረችዋ ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ተነሣ፤ አማኞችም ሁሉ ከሐዋርያት በቀር
በይሁዳና በሰማርያ ተበታተኑ። 2 በመንፈሳዊ ነገር የተጉ ሰዎች እስጢፋኖስን ቀበሩት፤ መሪር ልቅሶም አለቀሱለት። 3 ሳውል ግን ቤተ ክርስቲያንን በጣም ጐዳ፤
ከቤት ወደ ቤት በመሄድም ክርስቲያን ወንዶችንና ሴቶችን ጐትቶ አወጣቸው፤ ወኅኒ ቤት ውስጥም አስገባቸው። 4 የተበታተኑት አማኞች ግን ቃሉን እየሰበኩ
በየቦታው ዞሩ። 5 ፊልጶስ ወደ ሰማርያ ከተማ ወረደ፣ ለሕዝቡም ክርስቶስን ሰበከላቸው። 6 እጅግ ብዙ ሰዎች ፊልጶስን ሲሰሙትና ያደረጋቸውንም ምልክቶች
ሲያዩ፣ በአንድነት እርሱ ለተናገረው ትኵረት ሰጡ። 7 ምክንያቱም ከብዙ ሰዎች ርኩሳን መናፍስት እየጮኹ ወጥተው፣ አያሌ ሽባዎችና ዐንካሶችም ተፈውሰው
ነበር። 8 ስለዚህ በዚያች ከተማ ውስጥ ብዙ ደስታ ነበር። 9 ነገር ግን በዚያች ከተማ ውስጥ ቀደም ሲል የጥንቈላ ሥራ ይሠራ የነበረ ሲሞን የሚባል ሰው
ነበረ፤ ተፈላጊ ሰው እንደ ሆነ እየተናገረ የሰማርያን ሰዎች ያስደንቅ ነበር። 10 ሳምራውያን በሙሉ ከትንሹ እስከ ትልቁ፣ “ይህ ሰው ታላቅ የሚባለው
የእግዚአብሔር ኀይል ነው” እያሉ በሚገባ ያደምጡት ነበር። 11 በጥንቈላ ሥራው ለረጅም ጊዜ ያስገርማቸው ስለ ነበር አደመጡት። 12 ስለ እግዚአብሔር
መንግሥትና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ፊልጶስ የሰበከውን ወንጌል ሲያምኑ ግን ወንዶችም ሴቶችም ተጠመቁ። 13 ሲሞንም ደግሞ አመነ፤ ከተጠመቀም
በኋላ ከፊልጶስ ጋር መሆንን ቀጠለ፤ የተደረጉ ምልክቶችንና ታላላቅ ተኣምራትን ባየ ጊዜም ተደነቀ። 14 በኢየሩሳሌም የነበሩ ሐዋርያት ሰማርያ የእግዚአብሔርን
ቃል የተቀበለች መሆኗን ሲሰሙ፣ ጴጥሮስንና ዮሐንስን ላኩላቸው። 15 እነርሱም እዚያ ወርደው መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ ጸለዩላቸው። 16 መንፈስ ቅዱስ
እስከዚያ ጊዜ ድረስ በማንኛቸውም ላይ አልወረደም ነበርና፣ እነርሱ በጌታ ኢየሱስ ስም ብቻ ተጠምቀው ነበር። 17 ከዚያም ጴጥሮስና ዮሐንስ እጃቸውን
ጫኑባቸው፣ መንፈስ ቅዱስንም ተቀበሉ። 18 በሐዋርያት እጅ መጫን መንፈስ ቅዱስ እንደሚሰጥ ሲያይ፣ ሲሞን ገንዘብ አቀረበላቸው። 19 “እኔም እጁን
የምጭንበት ሰው ሁሉ መንፈስ ቅዱስን መቀበል እንዲችል ይህን ሥልጣን ስጡኝ” አላቸው። 20 ነገር ግን ጴጥሮስ እንዲህ አለው፤ “የእግዚአብሔርን ስጦታ
በገንዘብ ለማግኘት አስበሃልና ብርህ ከአንተ ጋር ይጥፋ። 21 ልብህ ለእግዚአብሔር የቀና አይደለምና በዚህ ጕዳይ ውስጥ ዕድል ወይም ድርሻ የለህም። 22
እንግዲህ ለዚህ ክፋትህ ንስሓ ግባ፤ ምናልባትም ለልብህ ዐሳብ ይቅር ይልህ እንደ ሆነ ጌታን ለምን። 23 በኀጢአት እስራትና በመራርነት መርዝ ውስጥ
እንዳለህ አያለሁና።” 24 ሲሞንም መልሶ፣ “ከተናገራችኋቸው አንዱም በእኔ ላይ እንዳይፈጸም ወደ ጌታ ጸልዩልኝ” አላቸው። 25 ጴጥሮስና ዮሐንስ ከመሰከሩና
የጌታን ቃል ከተናገሩ በኋላ፣ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፤ በመንገድም ለብዙ የሰማርያ መንደሮች ወንጌልን ሰበኩ። 26 የጌታ መልአክ ፊልጶስን፣ “ከኢየሩሳሌም
ወደ ጋዛ በሚወስደው መንገድ ወደ ደቡብ አቅጣጫ ተነሥና ሂድ” አለው። (ይህ መንገድ በበረሓ ውስጥ ነው።) 27 እርሱም ተነሣና ሄደ። እነሆ፣
በኢትዮጵያውያን ንግሥት በሕንደኬ ሥር ትልቅ ሥልጣን የነበረው አንድ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ ነበረ። ሰውዬው በንግሥቲቱ ንብረት ሁሉ ላይ ጎላፊነት ነበረው።
ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ነበር። 28 ከኢየሩሳሌም በመመለስ ላይ ሳለ፣ በሠረገላው ላይ ተቀምጦ ትንቢተ ኢሳይያስን እያነበበ ነበር። 29 መንፈስ
ፊልጶስን፣ “ሂድ ወደዚህ ሠረገላ ቅረብ” አለው። 30 ፊልጶስ ወደ ጃንደረባው ሮጠ፣ ትንቢተ ኢሳይያስንም ሲያነብ ሰማው፤ “የምታነበውን ትረዳዋለህ?” አለው።
31 ኢትዮጵያዊውም፣ “የሚመራኝ ከሌለ እንዴት ልረዳው እችላለሁ?” አለው። ወደ ሠረገላው እንዲወጣና ዐብሮት እንዲቀመጥ ፊልጶስን ለመነው። 32
ኢትዮጵያዊው ያነበው የነበረ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ይህ ነው፦ “እንደ በግ ለመታረድ ተነዳ፤ በሸለቾቹ ፊት ዝም እንደሚል ጠቦት፣ አፉን አልከፈተም፤ 33
በውርደቱ ፍርዱ ተወገደ፤ ትውልዱን ማን ይናገራል? ሕይወቱ ከምድር ተወግዶአልና።” 34 ጃንደረባው ፊልጶስን፣ “እባክህ ነቢዩ ስለ ማን ነው የሚናገረው?
ስለ ራሱ ወይስ ስለ ሌላ ነው?” አለው። 35 ፊልጶስም መናገር ጀመረ፤ ከዚህም ከኢሳይያስ መጽሐፍ ጀምሮ ስለ ኢየሱስ ሰበከው። 36 እየሄዱ ሳሉ ውሃ አለበት
ዘንድ ደረሱ፤ ጃንደረባው፣ “ተመልከት፣ እዚህ ውሃ አለ፤ እንዳልጠመቅ ምን ይከለክለኛል?” አለ። 37 ፊልጶስም፣ “በፍጹም ልብህ ካመንህ፣ መጠመቅ
ትችላለህ” አለ። ኢትዮጵያዊውም መልሶ፣ “ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ አምናለሁ” አለ። 38 ኢትዮጵያዊው ሠረገላው እንዲቆም አዘዘና፣
ፊልጶስም ጃንደረባውም ወደ ውሃው ወረዱ፤ ፊልጶስም አጠመቀው። 39 ከውሃው ውስጥ ሲወጡ፣ የጌታ መንፈስ ፊልጶስን ወሰደው፤ ጃንደረባውም ከዚያ
ወዲያ አላየውም፤ ደስ ብሎትም ጕዞውን ቀጠለ። 40 ነገር ግን ፊልጶስ በአዛጦን ታየ። በዚያ አገር ውስጥ በማለፍ ቂሣርያ እስኪደርስ ድረስ፣ ለከተሞች ሁሉ
ወንጌልን ሰበከ።

Acts 8:1

የሐዋርያት ሥራ **8**: **1**-**3**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ከቁጥር 1 ጀምሮ ስለ እስጥፋኖስ እየተነገረ ያለ ታሪክ ክፍል ነው። ሉቃስ በዚህ ሥፍራ ላይ የታሪኩን አቅጣጫ ከእስጥፋኖስ ወደ ሳኦል ይለውጣል። ስለዚህም በዚህ ሥፍራ ጀመሩ “ስለዚህም” የሚለው ቃል በታሪኩ ውስጥ ዋና ለውጥ መካሄዱን ያሳያል። እስጥፋኖስ በድንጋይ በመወገሩ ምክንያት ስደት እና ሐዋርያቱን ማሠር ተጀመረ። አማራጭ ትርጉም: "በዚያ ሥፍራ ከተፈጸመው ነገር የተነሳ ይህ ነገር መሆን ጀመረ" በዚያ ቀን ይህ ቃል የሚያመለክተው እስጥፋኖስ የሞተበትን ቀን ነው። አማኞች በየሥፍራው ተበተኑ ይህ በስደቱ ምክንያት ከእየሩሳሌም ወደ ተለያዩ ሥፍራዎች የተሰደዱትን ብዙ ወይም አብዛኞቹን አማኞች ለማመለክት ነው። ከሐዋርያት በስተቀር በዚህ መረጃ ውስጥ በተዘዋዋር መልኩ የተገለጸው ሀሳብ ሐዋርያቱ በእየሩሳሌም መቆየታቸውን እና ይህ ዓይነቱ ስደት በእነርሱ ላይ አለመድረሱን ነው። የተሰጡ ሰዎች "ፈረሃ እግዚአብሔር ያላቸው ሰዎች" ወይም "እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች" ታላቅ ኃዘን ሆነ "ስለእርሱ ታላቅ ለቅሶ አለቀሱ" (UDB) ወንዶችን እና ሴቶችን እየጎተቱ ሳኦል አይሁዳዊያን አማኞችን ከመኖሪያ ቤታው በጉልበት እየወሰደ በእስርቤት ውስጥ ያጉራው ነበር። እየጎተቱ "በኃይል እየወሰዱ"

Acts 8:4

የሐዋርያት ሥራ **8**: **4**-**5**
የተበተኑት "ከታላቁ ስደት የተነሣ በየሥፍራው የተበተኑት።" በየሥፍራው የመበተናቸው ምክንያት ከዚህ በፊት የተጠቀሰው ስድት ነው። የሰማሪያ ከተማ ሰዎች ሰማሪያ የሚለው ቃል የሚያመለክተው “ከተማዋን” (ULB) ወይም “ከተማ” (UDB) እንደሆ ግልጽ አይደለም።

Acts 8:6

የሐዋርያት ሥራ **8**: **6**-**8**
ብዙ ሰዎች "ከሰማሪያ ከተማ ብዙ ሰዎች በመጡ ጊዜ።" ይህ ሥፍራ ከዚህ በፊት ተገልጾ ነበር። ትኩረት ሰጡት ሰዎች ትኩረት የሰጡበት ዋነኛ ምክንያት ከዚህ በፊት ፊልጶስ ባደረገው ፈውስ ነው። ይህ እንደሆነ ግንዛቤ ውስጥ ለገባ ይገባዋል። እንዲሁም ሌሎች ብዙ ነበሩ ፊልጶስ ካደረገው ፈውስ የተነሳ ብዙ ሰዎች ደስ ይላቸው ነበር።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Acts 8:9

የሐዋርያት ሥራ **8: 9-11**
አጠቃላይ መረጃ: ሲሞን በታሪኩ ውስጥ የተዋወቀበት ሥፍራ ነው። እንዲሁም በቁጥር 9 እስከ 11 ላይ የሲሞን የኃላ ታሪክ መረጃዎች ተሰጥተዋ። እርሱም ከሰማሪያዊን ወገን ነበር። ይሁን እንጂ አንድ ሰው ነበር . . . ስሙም ሲሞን ይባላል። ይህ በታሪኩ ውስጥ አዲስ ሰውን የማስተዋወቂያ መንገድ ነው። በቋንቋችሁ እንዲህ አዲስ ሰውን በታሪክ ውስጥ የሚታስተዋውቁበት መንገድ ይኖራልና ያንን መንገድ ተጠቀሙ። ከተማ "በሰማሪያ ከተማ ውስጥ" ሰማሪያዊያን ሁሉ ይህ ግነት ነው። አማራጭ ትርጉም: "በከተማው ውስጥ የሚኖሩ ብዙ ሰማሪያዊያን።" ይህ ሰው ታላቅ ተብሎ የሚጠራ የአምላክ ኃይል እንዳለው ይሳተባል። ሰዎች ሲሞን ታላቅ ኃይል ተብሎ የሚታወቀው የመለኮት ኃይል ነው ብለው ይናገራሉ።

Acts 8:12

የሐዋርያት ሥራ **8: 12-13**
አጠቃላይ መረጃ: ቁጥር 12 እና 13 ስሲሞን እና በኢየሱስ ስላመኑት አንዳንድ የሰማሪያ ሰዎች የኃላ ታሪክ መረጃን በውስጡ ይዟል። ተጠመቁ ፊልጶስ አዳዲስ አማኞችን አጠመቀ። ምልክቶች እና ታላላቅ ነገሮች መደረጋቸውን በተመለከተ ጊዜ እጅግ በጣም ተገረመ "በፊልጶስ እጅ ምልክቶች እና ታላላቅ ተዓምራት መደረጋቸውን ሲሞን በተመለከተ ጊዜ በጣም ተገረመ"

Acts 8:14

የሐዋርያት ሥራ **8: 14-17**
አሁን ይህ ቃል በታሪክ ውስጥ አዲስ ታክ ለመጀመሩ ምልክት ነው። ሰማሪያዊያን ይህ በሰማሪያ ግዛት ውስጥ የሚኖሩ ብዙ ሰዎች መታወቂያ ስም ነው እነርሱ ወደዚያ በመጡ ጊዜ "ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ወደዚያ በመጡ ጊዜ" ጸለዩላቸው "ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ለሰማሪያ አማኞች ጸለዩላቸው" መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ። "በሰማሪያ የሚገኙ አማኞች መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ" ብቻ ተጠምቀዋል "ፊልጶስ በሰማሪያ የሚገኙ አማኒችን በ . . . ብቻ አጥምቆዋቸዋል" ከዚያ ጴጥሮስ እና ዮሐንስ እጆቻቸውን ጫኑባቸው "እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእስጥፋኖስን የወንጌል መልዕክ ያመኑ የሰማሪያ ሰዎችን ነው።

Acts 8:18

የሐዋርያት ሥራ **8: 18-19**
መንፈስ ቅዱስ የተሰጣቸው በሐዋርያቱ የእጅ መጫን ነው "ሐዋርያቱ በሕዝቡ ላይ እጆቻቸውን በመጫን መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ አድርገዋል" እጄን የሚጭንት ሰው ሁሉ መንፈስ ቅዱስን ይቀበል ዘንድ። "በሰዎች ላይ እጄን ስጭን መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ።"

Acts 8:20

የሐዋርያት ሥራ **8: 20-23**
እርሱ . . . አንተ . . . እንተ እነዚህ ተውላጠ ስሞች ሁሉም የሚያመለክቱት ሲሞንን ነው። የእግዚአብሔር ስጦታ እጅ በመጫን ሰዎች መንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ የማድረግ ስጦታ ልብህ ትክክል አይደለ "አስተሳሰብህ ልክ አይደለም" ምክንያቱም መሻትህ "ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስን ለሌሎች የመስጠትን ስጦታ ለመግዛት ትፈልጋለህና" በመራራነት ተበክለሃል ይህ “ከፍተኛ ቅናትን” የሚያለክት ምሳሌያዊ አገላለጽ ነው (UDB). ከኃጢአት ጋር የተቆራኘ "የኃጢአት እስረኛ" ወይም "ኃጢአት ማድረግ ብቻ የሚችል"

Acts 8:24

የሐዋርያት ሥራ **8: 24-24**
ከተናገርካቸው ውስጥ ዬትኛውም ይህ የሚያመለክተው የጴጥሮስን ተግሳጻዊ ንግግር ነው፣ “ብርህ ከአንተ ጋር ይጥፋ።" የተናገራችሁት ነገር በዚህ ሥፍራ ላይ “እናንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጴጥሮስን እና ዮሐንስን ነው።

Acts 8:25

የሐዋርያት ሥራ **8: 25-25**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ይህ ስለ ሲሞን እና ሰማሪያዊያን ታሪክ ክፍል የመጨረሻው ነው። ሕያው ምስክሮች ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ለሰማሪያዊያን ኢየሱስን በግላቸው እንደሚያውቁት ነገሯቸው። የጌታን ቃል ተናገሩ ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ለሰማሪያ ሰዎች ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ኢየሱስ ምን እንደሚሉ አብራሩላቸው። በሰማሪያ ውስጥ የሚገኙ ብዙ መንደሮች "በብዙ የሰማሪያ መንደሮች ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች"

Acts 8:26

የሐዋርያት ሥራ **8: 26-28**
አጠቃላይ መረጃ: ይህ ስለ ፊልጶስ እና ከኢትዮጵያ የመጣው ሰው ታሪክ ክፍል ነው። ቁጥር 27 ከኢትዮጵያ የመጣው ሰው የኃላ ታሪክ መረጃን ይሰጣል። አሁን ይህ በታሪኩ ውስጥ ሽግግር መኖሩን ያሳያል። እነሆ “እነሆ” የሚለው ቃል በታሪኩ ውስጥ አዲስ ሰው መጨመሩን ያሳየናል። በቋንቋችሁ እንዲህ ያለውን ነገር ማድረጊያ መንገድ ይኖራል። ጃንደረባ በዚህ ክፍል ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው “ጃንደረባው” ከኢትዮጵያ የመጣ ክፈተኛ የመንግስት ባለስልጣን መሁን ለማሳየት እንጂ የሰውነት ክፍሉ መጉደሉን ለማሳየት አይደለም። ህንደኬ ይህ ከኢትዮጵያ የሆነችው ንግሥት የማዕረግ ስም ነው። ይህ ልክ የግብጽ ነገሥታት መጠሪያ ስም “ፈርኦን” እንደሆነው ሁሉ ማለት ነው። ሠረገላ "ሠረገላ" ወይም “ጋሪ” ሲሆን በዚህ አውድ ውስጥ ሠረገላ የሚለው ቃል ተስማሚ ይሆናል። ሠረገላ ብዙ ጊዜ ረጅም ጉዞ ለመጓዝ የሚያገለግል ነው። የነቢዩ ኢሳያስን መጽሐፍ እያነበበ ይህ በብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ውስጥ የሚገኘው የኢሳያስ መጽሐፍ ነው: አማራጭ ትርጉም: “ከነቢዩ ኢሳያስ መጽሐፍ ውስጥ እያነበበ።"

Acts 8:29

የሐዋርያት ሥራ **8: 29-31**
የምታበውን ነገር ትረዳዋለህን? ኢትዮጵያዊው ሰው የተማረ እና ማንበብ የሚችል ነው ነገር ግን መንፈሳዊ መረዳት የሚጎድለው ነው። አማራጭ ትርጉም: “የሚታነበው ነገር ትርጉሙ ምን እንደሆነ ትረዳዋለህን?" አንድ ሌላ ሰው ካልመራኝ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ይህ በጥዬቄ መልክ የቀረበበት ምክንያት ከሰው አገዛ ውጪ መረዳት እንደማይችል አጽኖት ለመስጠጥ ነው። አማራጭ ትርጉም: "የሰው እገዛ ካላገኘሁ በስተቀር ይህ ሊሆን አይችልም" ፊልጶስ ወደ ሠረገላው ወጥቶ ከእርሱ ጋር እድቀመጥ ለመነው በዚህ ሥፍራ ላይ በተዘዋዋር መልኩ የተገለጸው መረጃ ፊልጶስ የተወሰነ መንገድ ከእርሱ ጋር ለመሄድ መስማማቱን ነው።

Acts 8:32

የሐዋርያት ሥራ **8: 32-33**
አጠቃላይ መረጃ: ይህ ክፍል ከኢሳያስ መጽሐፍ ውስጥ ነው። በሸላቶቹ ፊት ዝም እንደሚል በግ ሸላት ለተለያዩ አገልግሎቶች ይውል ዘንድ የበጎችን ጸጉር ከበጎች ላይ የሚሸልት ሰው ነው። በውርደቱ ጊዜ ፍትኃዊ እርምጃ አልወሰዱበትም "አዋረዱት እንዱም ፍትኃዊ በሆነ መልኩ አልዳኙትም"

Acts 8:34

የሐዋርያት ሥራ **8: 34-35**
ለእርሱ ስለ ኢየሱስ ይሰብከው ጀመር "ለጃንደረባ ስለ ኢየሱስ መልካሙን ዜና ያስተምረው ጀመር"

Acts 8:36

የሐዋርያት ሥራ **8**: **36**-**38**
ከመጠመቅ የሚከለክለኝ ምን ነገር አለ? ጃንደረባው ይህንን ንግግር የተናገረው መጠመቅ መፈለጉን ለመግለጽ ነው። አማራጭ ትርጉም: "እንዳትጠመቅ የሚከለክል ምንም ነገር የለም።" and

Acts 8:39

የሐዋርያት ሥራ **8**: **39**-**40**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ይህ ስለ ፊልጶስ እና ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ታሪክ የመጨረሻው ክፍል ነው። ጃንደረባውም ከዚያን ጊዜ አንስቶ አላየውም "ጃንደረባው ከዚያን ጊዜ አንስቶ ፊልጶስን አላየውም" ፊልጶስ በአዛጦን ተገኘ። ፊልጶስ ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ከተገናኘበት ሥፍራ ወደ አዛጦን እንዴት እንደተጓዘ ምንም ፍንጭ የለም። በድንጋ በጋዛ መንገድ ላይ ተሰወረና በአዛጢን ተገኘ። ወደቄሳሪያ እስኪመጣ ድረስ የፊልጶስ ታሪክ የሚያበቃው በቄሳሪያ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 9

1 ሳውል ግን በጌታ ደቀ መዛሙርት ላይ ለግድያም እንኳ እየዛተ ወደ ሊቀ ካህናቱ ሄደ፤ 2 የጌታን መንገድ ከሚከተሉት ወንዶችም ሆነ ሴቶች ቢያገኝ፣ ወደ
ኢየሩሳሌም አስሮ እንዲያመጣቸው፣ ለምኩራቦች ደብዳቤ እንዲሰጠውም ሊቀ ካህናቱን ጠየቀ። 3 እየሄደ ሳለ ደማስቆ አጠገብ ሲደርስ፣ በድንገት ከሰማይ
ብርሃን በዙሪያው በራበት፤ 4 በምድር ላይ ወደቀ፤ “ሳውል፣ ሳውል ለምን ታሳድደኛለህ” የሚል ድምፅ ሰማ። 5 ሳውልም፣ "ጌታ ሆይ፣ ማን ነህ?" ብሎ መለሰ፤
ጌታም፣ “አንተ የምታሳድደኝ ኢየሱስ ነኝ፤ 6 ነገር ግን ተነሥተህ ወደ ከተማው ግባ፤ ማድረግ ያለብህም ይነገርሃል” አለ። 7 ከዚያም ከሳውል ጋር የተጓዙት
ሰዎች ድምፁን እየሰሙ፣ ማንንም ግን ሳያዩና ሳይነጋገሩ ቆሙ። 8 ሳውል ከወደቀበት ተነሣ፤ ዐይኑን ሲከፍትም ምንም ማየት አልቻለም፤ ስለዚህም በእጅ
እየመሩ ወደ ደማስቆ አስገቡት። 9 ሦስት ቀን ዕውር ሆኖ ቆየ፤ አልበላም አልጠጣምም። 10 በዚያ ጊዜ ሐናንያ የሚባል አንድ ደቀ መዝሙር በደማስቆ ነበር፤
ጌታም ለእርሱ በራእይ፣ “ሐናንያ” አለው። እርሱም፣ “ጌታ ሆይ፣ እነሆኝ” አለ። 11 ጌታም መልሶ እንዲህ አለው፤ “ተነሥና ቀጥተኛ ወደሚባለው ጎዳና ሂድ፤
በይሁዳ ቤትም ሳውል የሚባል የጠርሴስ ሰውን ፈልግ፤ እርሱ እዚያ እየጸለየ ነውና፤ 12 እርሱ እንዲያይ ሐናንያ የሚባል ሰው ሲገባና በእርሱ ላይ እጁን
ሲጭንበት በራእይ አይቶአል።” 13 ሐናንያም መልሶ እንዲህ አለ፤ “ጌታ ሆይ፣ ስለዚህ ሰው በኢየሩሳሌም ባሉት ሕዝብህ ላይ ምን ያህል ክፋት እንደ
ፈጸመባቸው ከብዙዎች ሰምቻለሁ። 14 ስምህን የሚጠሩትን ሁሉ ለማሰር ከሊቀ ካህናቱ ሥልጣን ተቀብሎአል።” 15 ጌታ ግን መልሶ እንዲህ አለው፤ “ሂድ፤
እርሱ በአሕዛብ፣ በነገሥታትና በእስራኤል ልጆች ፊት ስሜን ለመሸከም የተመረጠ ዕቃየ ነውና፤ 16 ስለ ስሜ ሲል ምን ያህል መከራ መቀበል እንዳለበትም
አሳየዋለሁና። 17 ስለዚህ ሐናንያ ሄደ፤ ወደ ቤትም ገባ፤ እጁን በሳውል ላይ በመጫንም፣ “ወንድሜ ሳውል ሆይ፣ ስትመጣ በመንገድ ላይ የተገለጠልህ ጌታ
ኢየሱስ እንድታይና መንፈስ ቅዱስን እንድትሞላ ወዳንተ ልኮኛል።” 18 ወዲያው እንደ ቅርፊት ያለ ነገር ከሳውል ዐይን ወደቀ፤ ማየትም ጀመረ፤ ተነሥቶም
ተጠመቀ፤ 19 በላ፣ በረታም። ሳውል በደማስቆ ውስጥ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ብዙ ቀን ቆየ። 20 ወዲያውም ኢየሱስን የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ በምኩራብ
ውስጥ ዐወጀ። 21 የሰሙትም ሁሉ በመደነቅ እንዲህ አሉ፤ “ይህ ሰው በኢየሩሳሌም ይህን ስም የሚጠሩትን ያጠፋው አይደለምን? የመጣውም አስሮ ወደ
ሊቀ ካህናቱ ሊያቀርባቸው ነው።” 22 ሳውል ግን ለመስበክ በረታ፣ በደማስቆ ይኖሩ የነበሩ አይሁድንም ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን በማረጋገጥ ግራ አጋባቸው።
23 ከብዙ ቀን በኋላ፣ አይሁድ ሊገድሉት ዐሰቡ። 24 ሳውል ግን ዐሳባቸውን ዐወቀባቸው። ሊገድሉት የከተማይቱን በሮች ቀንም ሌሊትም ይጠብቁ ነበር። 25
ደቀ መዛሙርቱ ግን በግድግዳው በኩል በቅርጫት አወረዱት። 26 ሳውል ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶ በመጣ ጊዜ፣ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ለመገናኘት ሞከረ፤
ነገር ግን ደቀ መዝሙር መሆኑን በመጠራጠር ሁሉም ፈሩት። 27 ይሁን እንጂ፣ በርናባስ ወስዶ ወደ ደቀ መዛሙርቱ አቀረበው። ሳውል ጌታን በመንገድ ላይ
እንዴት እንዳየው፣ ጌታም እንደ ተናገረው፣ በኢየሱስ ስም ደማስቆ ውስጥ በድፍረት እንዴት እንደ ሰበከም ነገራቸው። 28 ሳውል ኢየሩሳሌም ውስጥ ሲገባና
ከዚያም ሲወጣ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተገናኘ። በጌታ ኢየሱስ ስም በድፍረት ተናገረ፤ 29 ከግሪክ አይሁድ ጋርም ተከራከረ፤ ሊገድሉት ሙከራ ማድረጋቸውን ግን
አላቋረጡም። 30 ወንድሞች ስለዚህ ባወቁ ጊዜ፣ ወደ ቂሣርያ አውርደው ወደ ጠርሴስ ላኩት። 31 ከዚያም በኋላ የይሁዳ ሁሉ፣ የገሊላና የሰማርያ ቤተ
ክርስቲያን ሰላም ነበራት፣ ታነጸችም፤ እግዚአብሔርን በመፍራትና በመንፈስ ቅዱስ መጽናናት ቤተ ክርስቲያን በቍጥር አደገች። 32 ጴጥሮስም በየቦታው
ሲዘዋወር፣ በልዳ ከተማ ወደሚኖሩ ቅዱሳንም ወረደ። 33 እዚያም፣ ሸባ በመሆኑ ስምንት ዓመት የአልጋ ቍራኛ የነበረን ኤንያ የሚባለውን አንድ ሰው አገኘ። 34
ጴጥሮስ፣ “ኤንያ ሆይ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈውስሃል፤ ተነሥና ዐልጋህን አንጥፍ” አለው። ወዲያውም ተነሣ። 35 በልዳና በሰሮና የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ሰውየውን
አዩትና ወደ ጌታ ተመለሱ። 36 በኢዮጴም ጣቢታ የምትባል አንድ ደቀ መዝሙር ነበረች፤ የስሟ ትርጒም “ዶርቃ” ማለት ነው። ይች ሴት በመልካም ምግባርና
ለድኾች በምታደርጋቸው የርኅራኄ ሥራዎች የተሞላች ነበረች። 37 በዚያም ወቅት ታመመችና ሞተች፤ ዐጥበውም ሰገነት ላይ አስቀመጧት። 38 ልዳ በኢዮጴ
አጠገብ በመሆኑና ደቀ መዛሙርቱም የጴጥሮስን በዚያ መኖር ስለ ሰሙ፣ “ሳትዘገይ ወደ እኛ ና” ብለው በመለመን ሁለት ሰዎችን ወደ እርሱ ላኩ። 39
ጴጥሮስም ተነሣና ከተላኩት ጋር ሄደ። እዚያ ሲደርስ፣ ወደ ሰገነቱ አወጡት። መበለታቱም ሁሉ ዶርቃ ከእነርሱ ጋር ሳለች ትለብሳቸው የነበሩትን ቀሚሶችና
ልብሶች እያሳዩትና እያለቀሱ በአጠገቡ ቆሙ። 40 ጴጥሮስ ሁሉንም ከክፍሉ አስወጣቸውና ተንበርክኮ ጸለየ፤ ከዚያም ወደ አስከሬኑ በመዞር፣ “ጣቢታ ሆይ፣
ተነሺ” አለ። ዐይኖቿን ከፈተች፤ ጴጥሮስንም ስታየው ተነሥታ ተቀመጠች። 41 ጴጥሮስም እጁን ይዞ አነሣት፤ አማኞችንና መበለታቱን ጠርቶም በሕይወት
እንዳለች ሰጣቸው። 42 ይህ ጉዳይ በመላው ኢዮጴ የታወቀ ሆነ፤ ብዙ ሰዎችም በጌታ አመኑ። 43 ጴጥሮስ በኢዮጴ ቍርበት ፋቂ ከነበረ ስምዖን ከሚባል ሰው
ጋር ብዙ ቀን ቆየ።

Acts 9:1

የሐዋርያት ሥራ 9: 1-2
አጠቃላይ መረጃ: የታሪኩ ትኩረት ተመልሶ ወደ ሳኦል መሆን ይጀምራል። እነዚህ ቁጥሮ ሳኦል ከእስጥፋኖስ በድንጋይ ተወግሮ መሞት በኋላ ምን ስያደርግ እንደነበር የኃላ ታሪክ መረጃ ይሰጠናል። ደቀ መዛሙርቱን በመቃወም ያስፈራራቸው ነበር፣ እንዲሁም እንደሚገድላቸው ይናገር ነበር “ገዳይ” የሚለው ቃል ስም ቢሆንም እንደ ግሥ ግን ለተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም: “ደቀ መዛሙርቱን ያስፈራራቸው እንዲሁም እንደሚገድላቸው ይዝት ነበር።” ደብዳቤ ይሰጠው ዘንድ ጠየቀ "ሊቀ ካህኑን የድጋፍ ደብዳቤ እንዲሰጠው ጠየቀው" ካገኘ . . . ለማምጣረት “እርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሳኦልን ነው። በዚያ መንገድ የሚሄዱትን "የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርት የሚከተሉትን" አሥሮ ወደ ኢየሩሳሌም ያመጣቸው ዘንድ "እሰረኛ አድርጎ ወደ ኢየሩሳሌም ማምጣት ይችል ዘንድ።" እነዚህ ቃላት በመጨመር ለጳውሎስ የተሰጠው ኃላፊነትን ይበልጥ ግልጽ ማድረግ ይቻላል “የአይሁድ መሪዎች ፍርድ መስጠጥ እና ይቀጧቸው ዘንድ”

Acts 9:3

የሐዋርያት ሥራ 9: 3-4
እየተጓዘ እያለ ሳኦል ከእየሩሳሌም ወጥቶ ወደ ደማስቆ ተጓዘ። እንዲህ ሆነ ይህ በታሪኩ ውስጥ ለውጥ መሆኑን በማሳየት ከዚህ በፊት ያለሆነ አዲስ ነገር መፈጠሩን የሚያሳይ ነው። ከሰማይ ብርሃን በእርሱ ዙሪያ አበራ "በእርሱ ዙሪያ ብርሃን ከሰማይ በእርሱ ዙሪያ አበራ" በምድር ላይ ወደቀአማራጭ አማራጭ ትርጉሞች እኝህ ናቸው 1) "ሳኦል ራሱን ወደ ምድር ወረወረ" ወይም 2) "ብርሃኑ ሳኦልን በምድር ላይ እዲወድቅ አደረገው" ወይም 3) "ሳኦል ራሱን እንደ ሳተ ሰው ሆኖ በምድ ላይ ወደቀ።" ሳኦል አወዳደቁ ድንገተኛ አልነበረም። ለምን ታሳድደኛለህ? ጌታ ሳኦልን በጥያቄ መልክ አድርጎ እየገሰጸው ነው። አማራጭ ትርጉም: "እያሳደድከኝ ነው!"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Acts 9:5

የሐዋርያት ሥራ **9**: **5**-**7**
አንተ ማን ነህ ጌታዬ! ዚህ ሥፍራ ላይ ሳኦል ኢየሱስን እንደ ጌታ አድርጎ ገና አላወቀውም። ይህ በአንድ ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል ሥር መሆኑን እውቅና የሚሰጥ ንግግር ነው። ነገር ግን ተነሣና ወደ ከተማይቱ ግባ "ተነስና ወደ ደማስቆ ከተማ ግባ" ለአንተ ይነገርሃል አንድ ሰው ይነግርሃል አንተ በዚህ ሥፍራ ውስጥ “አንተ” የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር አመልካች ነው። ነገር ግን ማንንም አላየም ብርሃኑን ማየት የቻለው ሳኦል ብቻ ነበር። -

Acts 9:8

የሐዋርያት ሥራ **9**: **8**-**9**
ሌላ ነገር ማየት አልቻለም የሳኦል ዐይች ታወሩ። መብላትም ሆነ መጠጣት አልቻለም እንደ “ሚጸም ሰው” "ለመብላትም ሆነ ለመጠጣት አልፈለገም" ወይም “እንዳልራበው ሰው” መብላትም ሀፐነ መጠጣት አልቻለም”

Acts 9:10

የሐዋርያት ሥራ **9**: **10**-**12**
አጠቃላይ መረጃ: የታሪኩ አቅጣጫ አናኒያስ ተብሎ ወደሚጠራ ሰው ታሪክ ዞሯል። ይህ በየሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ቅስጥ ከዚህ በፊት ከተጠቀሰው ሰው ጋር ተመሳሳይ ነው። አሁን . . . አንድ ሰው ነበር ይህ በታሪክ ውስጥ አዲስ ገጸ ባሕርን ያስተዋውቃል። ደቀ መዛሙርት በኢየሱስ የሚያምን እና እርሱ የሚታዘዝ ማንኛውም ሰው የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ይባላል። አናናስ የኢየሱስ ደቀ መዝሙር የሆነው ሰው እግዚአብሔር በመታዘዝ ወደ ሳኦል በመሄድ በሳኦል ላይ እጁን በመጫን ፈወሰው። እናም እንዲህ አለ "እናም ሐናኒያ እንዲህ አለ" የይሁዳ ቤት ይሁዳ በደማስቆስ ውስጥ ሐናኒያ በእንግድነት የተቀመጠበት ቤት ባለቤት ነው። ምንም እንኳ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተለያዩ ሰዎች ይሁዳ በሚል ስም ቢጠሩም ይህ ሰው ግን የተጠቀሰው በዚህ ሥፍራ ላይ ብቻ ነው። የጤርሰስ ሰው "ከጤትሰስ ከተማ የመጣ ሰው"

Acts 9:13

የሐዋርያት ሥራ **9**: **13**-**16**
ከካህናት አለቃ ዘንድ ስልጣን የተሰጠው ሰው በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ በተዘዋዋር መልኩ የተገለጸሰው ሀሳብ ሳኦል የተሰጠው ስልጣን በዚያ ዘመን በአይዶች ላይ ብቻ መሆኑን ያሳያል። እርሱ የእኔ የተመረጠ መሣሪያ ነው "የተመረጠ መሣሪያ" የሚለው ቃል ለአገልግሎት መለየትን የሚያሳይ ነው። አማርጭ ትርጉም: "ያገለገልኝ ዘንድ መርጬዋለሁ።" ስሜን ይሸከም ዘንድ ይህ ከእየሱስ ጋር መወገንን ወይም ስለኢየሱስ መናገርን የሚገልጽ ነው። አማራጭ ትርጉም: "ስለእኔ ይናገር ዘንድ" ስለእኔ ስም ይህ የአገላለት መንገድ ሲሆን ትርጉሙም "ለሰዎች ስለ እኔ ለመናገር።"

Acts 9:17

የሐዋርያት ሥራ **9**: **17**-**19**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ሐናኒያ ሳኦል ወደአረፈበት ቤት ሄደ። ሳኦል ከተፈወሰ በኋላ የታሪኩ አቅጣጫ ከሐናኒያ ወደ ሳኦል ተቀየረ። እጁን ጫነበት ሐናኒያ እጆቹን በሳኦል ላይ ጫነበት። የተገለጠለህ "አንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሳኦልን ነው (ነጠላ ቁጥር)፣ ምንም እንኳ በጉዞው ላይ ከሳኦል ጋር የነበሩ ሌሎች ሰዎች የነበሩ ቢሆንም ማለት ነው። ማየት ትችል ዘንድ እና በመንፈስ ቅዱስ ትሞላ ዘንድ ወደ አንተ ዘንድ ልኮኛል አማራጭ ትርጉም: "እንደገና ማየት ትችል ዘንድ እና በመንፈስ ቅዱስ ትሞላ ዘንድ ወደ አንተ ልኮኛል" ቅርፍት የሚመስል ነገር ከዐይኖቹ ላይ ወደቀ "የዓሣ ቅርፍት የሚመስል ነገር ከዐይኖቹ ላይ ወደቀ" ተነሣ እና ተጠመቀ አማራጭ ትርጉም: "ተነሣና ሐናኒያ አጠመቀው"

Acts 9:20

የሐዋርያት ሥራ **9**: **20**-**22**
ወዲያውም ስለኢየሱስ መናገር ጀመረ በዚህ ሥፍራ ላይ "እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሳኦል ነው። እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ነው እያለ በዚህ ሥፍራ ላይ "እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢየሱስን ነው። ሰኦል በኢየሱስ ካመነ በኋላ ኢየሱስ “የእግዚአብሔር ልጅ” መሆኑን ተናገረ። የእግዚአብሔር ልጅ ይህ የኢየሱስ ወሳኝ የማዕረግ ስም ነው። ይህንን ስናገር የሰሙ ሰዎች ሁሉ ይህ ግነት የሞላበት ንግግር “ንግግሩን የሰሙ ሰዎች ብዙዎቹ” የሚል ትርጉም አለው። በቋንቋችሁ ግነትን የሚትልጹበት መንገድ ከዚህ የሚለይ ከሆነ የእናንተ መንገድ ተጠቀሙ። ይህ ሰው በዚህ ስም የተጠሩትንና በእየሩሳሌም የሚኖሩትን ሰዎች የሚገድል አይደለምን? ይህ አሉታዊ እና ጥያቄያዊ ንግግር ሳኦል በእርግጥም አማኞችን ያሳድድ እንደነበረ አጽኖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም: “ይህ ሰው ይህንን ኢየሱስ የሚለውን ስም የሚጠሩ ሰዎችን የሚያሳድድ ሰው ነው።”

Acts 9:23

የሐዋርያት ሥራ **9**: **23**-**25**
እርሱንም ለመግደል አይሁዶች በጋራ ተማከሩ በዚህ ሥፍራ ላይ "እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሳኦልን ነው። ይሁን እንጂ ዕቅዳቸውን ሳኦል አስቀድሞ ደረሰበት። አማራጭ ትርጉም: "አንድ ሰው ለሳኦል እቅዳቸውን ገለጸለት" የከተማይቱን መግቢያ መውጫዎች ይጠብቁ ነበር ይህች ከተማ በቅጥር የታጠረች ነበረች። ሰዎች ወደ ከተማይቱ የሚገቡት እንዲሁም ከከተማይቱ የሚወጡት በቅጥሩ በር በኩል ብቻ ነበር። የእርሱ ደቀ መዛሙርት ሳኦል ስለኢየሱስ የተናረውን መልዕክት ያመኑት ሰዎች የእርሱን ትምህርት ይከተሉ ነበር።

Acts 9:26

የሐዋርያት ሥራ **9**: **26**-**27**
ይሁን እንደጂ ሁሉም እርሱን ይፈሩት ነበር በዚህ ሥፍራ ላይ "ሁሉም" የሚለው ቃል ግነት የተሞላበት ቃል ሆኒ ብዙዎች ወይም አብዛኞቹ ሰዎች ለማለት ነው። አማራጭ ትርጉም: "አብዛኞቹ ሰዎች" ነገር ግን ባርናባስ ወስዶት "ነገር ግን ባርናባስ ሳኦልን ወስዶት" ሳኦል በድፍረት የኢየሱስን ስም ይሰብክ ነበር ይህ ሳኦል ስለኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ያስተምር ወይም ይሰበክ እንደነበር የሚያሳይ ምሳሌያዊ ንግግር ነው።

Acts 9:28

የሐዋርያት ሥራ **9**: **28**-**30**
ከእነርሱ ጋር ተገናኘ "ሳኦል ከሐዋርያቱ ጋር ተገናኘ" በጌታችን በኢየሰሱስ ስም ይህ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ትምህርትን የሚያሳይ ነው። ከግሪካዊን አይሁዶች ጋር ይከራከር ነበር ሳኦል ከግሪክ አይሁዳዊን ጋር ይከራከር ነበር። ወደታች ወደ ቄሳሪያ ከእየሩሳሌም ወደ ቄሳሪያ የቦታ ከፈት ልዩት አለ። ይሁን እንጂ ወደ እየሩሳሌም እና ወደ ቤተ መቅዱሱ ወጣ እንዲሁም ከእየሩሳሌም ወረደ ማለት በዘመኑ የተለመደ ንግግር ነው።

Acts 9:31

የሐዋርያት ሥራ **9**: **31**-**32**
አጠቃላይ መረጃ: ቁጥር 31 ስለ ቤተ ክርስቲያን እድገት አጠቃላይ መረጃ ይሰጣል። በቁጥር 32 ላይ የታሪኩ አቅጣጫ ከሳኦል ወደ አዲስ የታሪኩ ክፍል ወደ ሆነው ወደ ጴጥሮስ ይዞራል። ከዚም እንዲህ ሆነ ይህ ሀረግ አዲስ የታሪኩ ክፍል መጀመሩን የሚበስር ነው። አደገ እግዚአብሔር እንዲያድግ አደረገው በጌታ ፍርሃት እየሄዱ "ጌታን ማክበራቸውን ቀጠሉ" በመንፈስ ቅዱስ መጽናናት "መንፈስ ቅዱስ ያበረታቸው እና ያበረታታቸው ነበር" በአጠቃላይ አከባቢው ይህ ጴጥሮስ በይሁዳ፣ ገሊላ እና ሰማሪያ አከባቢ ያሉ ብዙ አማኞቹን መጎብኘቱን ለማመልከት የቀረበ ግነት የሞላበት ገለጻ ነው። ልዳ ልዳ ከጆባ 18 ኪሜ በስተምስራቅ የሚትገኝ ከተማ ናት። በብሉይ ኪዳን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መጽሐፍ ውስጥ እና በአሁኗ እስራኤል ውስጥ ይህች ከተማ ሎድ ተብላ ትታወቅ ነበር።

Acts 9:33

የሐዋርያት ሥራ **9**: **33**-**35**
በዚያ አንድ ሰው አገኘ ጴጥሮስ ሆን ብሎ ሽባ የሆነ ሰውን እየፈለገ ሳይሆን ድንገት ከዚህ ሰው ጋር ተገናኘ። አማራጭ ትርጉም: “በዚያም ጴጥሮስ አንድ ሰው አገኘ።” በአልጋው ላይ ነበር . . . ሽባ ነበር ይህ ስለኤንያ የኃላ ታሪክ መረጃ ነው። የማይንቀሳቀስ መራመድ የማይችል፣ ምናልባትም ከወገቡ በታች መንቀሳቀስ የማይችል ሰው አልጋህን ያዝ "ምንጣፍህን ጠቅልል" (UDB) የኖረ ሰው ሁሉ ይህ “የኖሩ ብዙ ሰዎችን” ለማመልከት የዋለ ግነት የሞላበት ንግግር ነው።

Acts 9:36

የሐዋርያት ሥራ **9**: **36**-**37**
አጠቃላይ መረጃ: ይህ ስለጴጥሮስ የተነገረው ታሪክ ክፍል ውስጥ ያለ አዲስ ነገር ነው። ይህ ጠብታ ተብላ ስለምትጠራ አንዲት ሴት የኃላ ታሪክ መረጃ ነው። አሁን ይህ በታሪኩ ውስጥ አዲስ ጅማሬን ያስተዋውቃል። ደቀ መዝሙር ኢያሱስን ያመነ እና የእርሱን ትምህርት የሚታዘዝ ማንኛውም ሰው የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ተብሎ ይጠራል። ጠቢታ፣ “ዶርቃስ” ተብሎ ይተረጎማል። ጠቢታ የሚለው ስሟ በአረማይክ ቋንቋ ሲሆን ዶርቃስ የሚለው ስሟ ደግሞ በግሪክ ቋንቋ ነው። የሁለቱም ስሞች ትርጉም “ጋዜል” ነው። መልካም ሥራ የሞላበት "በጣም ብዙ መልካም ሥራዎችን መሥራት" በእነዚህ ቀናት እንዲህ ሆነ "ጴጥሮስ በልዳ እያለ እንዲህ ሆነ።” ይህ በተዘዋዋር መልኩ የተገለጸ መረጃ ነው።

Acts 9:38

የሐዋርያት ሥራ **9**: **38**-**39**
ወደ እርሱ ሁለት ሰዎችን ላኩ "ደቀ መዛሙርቱ ሁለት ሰዎችን ወደ ጴጥሮስ ዘንድ ላኩ" ባልቴቶች ባል የሞተባቸው ሴቶች ከእነርሱ ጋር በነበረችበት ወቅት "ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በሕይወት ሳለች" (UDB)

Acts 9:40

የሐዋርያት ሥራ **9**: **40**-**43**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ስለጠብታ የተነገረው ታሪክ የሚያበቃው በቁጥር 42 እና 43 ላይ ነው። ቁጥር 43 ታሪኩ ካለቀ በኋላ ጴጥሮስ ላይ ምን እንደደረሰበት ታሪኩ ይነግረናል። (ተመልከት: talink End of Story) ሁሉንም አስወጣቸው በዚህ ሁኔታ ውስጥ ጴጥሮስ ለጠብታ መጸለይ ይችል ዘንድ ሁሉንም ሰዎች ከቤት እንዲወጡ አደረገ። ይህ ነገር ታወቀ ጴጥሮስ ጠብታን ከሞት በተዓምራት የማስነሳቱ ነገር በጌታ አመኑ ይህ “በጌታ ኢየሱስ ወንጌል ማመናቸውን” የሚያሳይ ገለጻ ነው። ጴጥሮስም በዚያ ቆየ "ጴጥሮስም በዚያ እንዲቆይ ተደረገ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **10**

1 በቂሣርያ ከተማ ውስጥ የኢጣሊቄ ክፍለ ሰራዊት በሚባል የመቶ አለቃ የሆነ ቆርኔሌዎስ የሚባል ሰው ነበረ። **2** እርሱም መንፈሳዊ፣ ከቤተ ሰቡ ጋር እግዚአብሔርን የሚያመልክ፣ ለአይሁድ ብዙ ገንዘብ የሚሰጥና ሁልጊዜ ወደ እግዚአብሔር የሚጸልይ ሰው ነበረ። **3** ከቀኑ በዘጠኝ ሰዓት የእግዚአብሔር መልአክ ወደ እርሱ ሲመጣ በራእይ በግልጽ ታየው። መልአኩ፣ “ቆርኔሌዎስ!” አለው። **4** ቆርኔሌዎስ መልአኩን አተኵሮ ተመለከተውና ፈርቶ እንዲህ አለ፤ “ጌታዬ ሆይ፣ ይህ ምንድን ነው?” መልአኩም መልሶ፣ “ጸሎትህና ምጽዋትህ በመታሰቢያነት ወደ እግዚአብሔር ደርሶአል። **5** ጴጥሮስም ተብሎ የሚጠራውን ስምዖን የሚባለውን ሰውየ ለማስመጣት አሁን ወደ ኢዮጴ ከተማ ሁለት ሰዎችን ላክ። **6** ሰውየው ቤቱ በባሕሩ አጠገብ ከሚገኝ ስምዖን ከሚባለው ከቆዳ ፋቂው ጋር አለ” አለው። **7** ያነጋግረው የነበረው መልአክ እንደ ሄደ፣ ቆርኔሌዎስ ከሚያገለግሉት ወታደሮች መካከል እግዚአብሔርን ያመልክ የነበረ አንድ ወታደርንና ከቤት አሽከሮቹ ሁለቱን ጠራ። **8** ቆርኔሌዎስ የሆነውን ሁሉ ነግሮአቸው ወደ ኢዮጴ ላካቸው። **9** በሚቀጥለው ቀን ስድስት ሰዓት አካባቢ፣ በጉዞ ላይ ሳሉና ወደ ከተማዋ ሲቃረቡ፣ ጴጥሮስ ሊጸልይ ወደ ሰገነቱ ወጣ። **10** ራበውና አንዳች ነገር ለመብላት ፈለገ፤ ነገር ግን ሰዎች ምግብ በማዘጋጀት ላይ ሳሉ፣ በተመስጦ ውስጥ ገባ፤ **11** ሰማይ ተከፍቶ፣ ትልቅ ሸማ የሚመስል አንድ መያዣ በአራቱ ጠርዘኞቹ ተይዞ ወደ ምድር ሲወርድም አየ። **12** በውስጡም አራት እግር ያላቸው እንስሳት ሁሉና በምድር ላይ የሚሳቡ ፍጡራን፣ የሰማይ ወፎችም ነበሩበት። **13** “ጴጥሮስ ሆይ፣ ተነሥና ዐርደህ ብላ” የሚል ድምፅ ለጴጥሮስ መጣ። **14** ጴጥሮስም፣ “ጌታ ሆይ፣ አይሆንም፤ ምክንያቱም እኔ ርኩስና አስጸያፊ የሆነ ምንም ነገር ፈጽሞ በልቼ አላውቅም” አለ። **15** እንደገናም ድምፅ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ጴጥሮስ መጣ፤ “እግዚአብሔር ቅዱስ ያደረገውን ርኩስ ብለህ አትጥራው” የሚል ድምፅ። **16** ይህም ሦስት ጊዜ ሆነ፤ ከዚያም መያዣው ወዲያው ወደ ሰማይ ተመልሶ ተወሰደ። **17** ጴጥሮስ ያየው ራእይ ምን ትርጉም ሊኖረው እንደሚችል በጣም ግራ ገብቶት ሳለ፣ ወደ ቤት የሚያስሄደውን መንገድ ጠይቀው ካገኙ በኋላ እነሆ፣ ቆርኔሌዎስ የላካቸው ሰዎች በበሩ ፊት ለፊት ቆሙ። **18** ድምፃቸውን ከፍ በማድረግም ጴጥሮስ የሚባለው ስምዖን በዚያ መኖሩንና አለመኖሩን ጠየቁ። **19** ጴጥሮስ ስለ ራእዩ በማሰብ ላይ ሳለ፣ መንፈስ ቅዱስ ጴጥሮስን እንዲህ አለው፤ “እነሆ፣ ሦስት ሰዎች ይፈልጉሃል። **20** ተነሥና ውረድ፤ ከእነርሱም ጋር ሂድ። ዐብረሃቸው ለመሄድ አትፍራ፤ ምክንያቱም የላክኋቸው እኔ ነኝ።” **21** ስለዚህም ጴጥሮስ ወደ ሰዎቹ ወርዶ፣ “የምትፈልጉት ሰው እኔ ነኝ። የመጣችሁት ለምንድን ነው?” አላቸው። **22** እነርሱም እንዲህ አሉት፤ "እግዚአብሔርን የሚያመልክ፣ በአይሁድ ሕዝብ ሁሉ ዘንድም የተመሰገነ ቆርኔሌዎስ የሚባል ጻድቅ ሰው፣ ወደ ቤቱ ሰው ልኮ እንዲያስመጣህ የእግዚአብሔር መልአክ ነገረው፤ እንዲህ ያደረገውም ከአንተ መልእክትን መስማት እንዲችል ነው።” **23** ጴጥሮስም እንዲገቡና ከእርሱና ዐብረውት ከነበሩ ሰዎች ጋር እንዲቈዩ በእንግድነት ተቀበላቸው። በማግስቱ ጧት ጴጥሮስ ተነሣና ከእነርሱ ጋር ሄደ፤ በኢዮጴ ከነበሩት ወንድሞችም አንዳንዶቹ ዐብረውት ሄዱ። **24** በሚቀጥለው ቀን ቂሣርያ ደረሱ። ቆርኔሌዎስ እየጠበቃቸው ነበር፤ ዘመዶቹንና የቅርብ ወዳጆቹንም ጠርቶ እንዲሰበሰቡ አደረገ። **25** ጴጥሮስ ሲገባ፣ ቆርኔሌዎስ አግኝቶት እግሩ ላይ ወድቆ ሰገደለት። **26** ነገር ግን ጴጥሮስ አነሣውና፣ “ተነሥ ቁም፤ እኔ ራሴም ሰው ነኝ” አለው። **27** ጴጥሮስ ከቆርኔሌዎስ ጋር እየተነጋገረ ወደ ውስጥ ሲገባ፣ የተሰበሰቡ ብዙ ሰዎችን አገኘ። **28** እንዲህም አላቸው፤ "አይሁዳዊ የሆነ ሰው ከሌላ ሕዝብ ከሆነ ጋር መገናኘት ወይም እርሱን መጎብኘት በሕግ እንደማይፈቀድለት እናንተ ራሳችሁ ታውቃላችሁ። ነገር ግን እግዚአብሔር ማንንም ሰው ርኩስ ወይም አስጸያፊ ብዬ መጥራት እንደማይገባኝ ለእኔ አሳይቶኛል። **29** ሲላክብኝ ሳልከራከር የመጣሁት ከዚህ የተነሣ ነው። ስለዚህ ለምን እንደ ላካችሁብኝ እጠይቃችኋለሁ።" **30** ቆርኔሌዎስም እንዲህ አለ፤ “ከአራት ቀን በፊት ልክ በዚህ ሰዓት በዘጠኝ ሰዓት በቤቴ ውስጥ እጸልይ ነበር፤ እነሆም ነጭ ልብስ ለብሶ ፊት ለፊቴ ቆመና፣ **31** ‘ቆርኔሌዎስ ሆይ፣ ጸሎትህ በእግዚአብሔር ዘንድ ተሰምቶአል፤ ምጽዋትህም መታሰቢያ ሆኖልሃል። **32** ስለዚህ ወደ ኢዮጴ ሰው ላክና ጴጥሮስም የሚባለውን ስምዖንን ወደ አንተ ጠርተህ አስመጣ። እርሱ በቆዳ ፋቂው በስምዖን ቤት በባሕር አጠገብ ተቀምጦአል’ አለኝ። **33** ስለዚህ ወዲያው ላክሁብህ። አሁን መምጣትህ መልካም አደረግህ። አሁን እንግዲህ እኛ ሁላችን እግዚአብሔር እንድትናገር ያዘዘህን ሁሉ ለመስማት በእግዚአብሔር ፊት እንገኛለን።" **34** ጴጥሮስም እንዲህ ብሎ ተናገረ፦ “እግዚአብሔር ለማንም እንደማያዳላ በእውነት ተገንዝቤአለሁ። **35** ይልቁን በማንኛውም ሕዝብ ውስጥ እግዚአብሔርን የሚፈራ፣ የጽድቅ ተግባራትንም የሚፈጽም ሁሉ በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት አለው። **36** እግዚአብሔር በሁሉ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሰላምን የምሥራች ባወጀበት ጊዜ፣ ወደ እስራኤል ሕዝብ የላከውን መልእክት ታውቃላችሁ፦ **37** ዮሐንስ ካወጀው ጥምቀት በኋላ፣ በገሊላ በመጀመር በይሁዳ ሁሉ የታዩትን የተፈጸሙ ሁነቶችን እናንተ ራሳችሁ ታውቃላችሁ፤ **38** ሁነቶቹም እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስና በኀይል እንዴት እንደ ቀባው የናዝሬቱን ኢየሱስን የሚመለከቱ ናቸው። ኢየሱስ መልካም እያደረገና ለዲያብሎስ የተገዙትን እየፈወሰ ዞረ፤ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበረና። **39** በዕንጨት ላይ ሰቅለው የገደሉት ይህ ኢየሱስ ከአይሁድ አገርም በኢየሩሳሌምም ለፈጸማቸው ተግባራት ሁሉ እኛ ምስክሮች ነን። **40** ይህን ሰው እግዚአብሔር በሦስተኛው ቀን አስነሣው፤ እንዲገለጥም አደረገው፤ **41** ይኸውም እግዚአብሔር አስቀድሞ መርጦአቸው ለነበሩ ምስክሮች እንጂ፣ ለሕዝቡ ሁሉ አይደለም፦ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ዐብረነው የበላንና የጠጣን እኛው ራሳችን ነን። **42** ለሕዝቡ እንድንሰብክና በሕያዋንና በሙታን ላይ እንዲፈርድ፣ እግዚአብሔር የመረጠው ይህ እንደ ሆነ እንድንመሰክር አዘዘን። **43** በእርሱ የሚያምን ሁሉ በስሙ የኀጢአትን ይቅርታ እንዲቀበል ነቢያት ሁሉ የሚመሰክሩት ስለ እርሱ ነው።” **44** ጴጥሮስ እነዚህን ነገሮች ገና እየተናገረ ሳለ፣ መልእክቱን በሚሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው። **45** ከተገረዙት ወገን የሆኑ አማኞች፦ ከጴጥሮስ ጋር የመጡትም ሁሉ ተደነቁ፤ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ በአሕዛብም ላይ ወርዶ ነበር። **46** እነዚህ አሕዛብ በሌሎች ቋንቋዎች ሲናገሩና እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ ሰምተዋቸዋልና። ከዚያም በኋላ ጴጥሮስ መልሶ፣ **47** “እንደ እኛ መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉ እነዚህ ሰዎች እንዳይጠመቁ ማን ውሃ ሊከለክላቸው ይችላል?” አለ። **48** በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንዲጠመቁም አዘዛቸው። ከዚያ በኋላ ከእነርሱ ጋር ጥቂት ቀን እንዲቈይ ጴጥሮስን ለመኑት።

Acts 10:1

የሐዋርያት ሥራ **10**: **1-2**
አጠቃላይ መረጃ: ይህ ስለቆርኖሊዮስ ቲክ ጅማሬ ነው። ይህ ስለእርሱ የኃላ ታሪክ መረጃ ይሰጠናል። የሆነ ሰው ነበር ይህ በታሪኩ ውስጥ አዲስን ሰው የማስዋወቂያ መንገድ ነው። ስሙም ቆርኖሊዮስ ይባላል፣ የመቶ አለቃ ነበር "ስሙ ቆርኔሊዮስ ይባላል። በእጣልያን ሀገር ውስጥ በሚገኘው የሮማዊያን ግዛት ውስጥ የመቶ ወታደሮችን አለቀ ነበር።" እግዚአብሔርን የሚያመልክና የሚፈራ ሰው ነበር "በእግዚአብሔር የሚያምን እና በሕይወቱ እርሱን ለማክበር እና ለማምለክ የሚፈልግ ሰው ነበር" ከቤተሰቡ ሁሉ ጋር "ከእርሱ የቤተሰብ አባለላት ሁሉ ጋር"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Acts 10:3

የሐዋርያት ሥራ **10**: **3-6**
ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ይህ ለአይሁዳዊን የተለመደ የጸሎት ሰዓት ነው። በግልጽ ተመለከተ "ቆርኔሊዮስ በግልጽ አየ" ቆዳ ሠሪ ከእንስሳት ቆዳ የቆዳ ውጤቶችን የሚያዘጋጅ ሰው።

Acts 10:7

የሐዋርያት ሥራ **10**: **7-8**
የተናገረው መለአክ ከሄደ በኋላ "ቆርኔሊዮስ የተመለከተው ራዕይ ካለቀ በኋላ" የሆነውን ነገር ሁሉ ነገራቸው ቆርኔሊዮስ ለሁለቱ ሎሌዎቹ እና ወታደሩ ነገራቸው። ወደ ጆባ ላካቸው "ሁለቱን ሎሌዎቹን እና አንዱን ወታደር ወደ ጆባ ላካቸው"

Acts 10:9

የሐዋርያት ሥራ **10**: **9-12**
የሐዋርያት ሥራ 10፡ 9-12 አጠቃላይ መረጃ: ታሪኩ ከቆርኔሊዮስ ጴጥሮስ የሆነውን ነገር ወደ መዘገብ ተለወጠ። በጉዞ ላይ እያሉ "በቆርኔሊዮስ ትዕዛዝ መሠረት ሁለት ሎሌዎች እና ወታደሩ ወደ ጆባ እየተጓዙ ሳለ" ሰማይ ተከፍቶ ተመለከተ ይህ የጴጥሮ ራዕይ ጅማሬ ነበር። ትልቅ ጨርቅ የሚመስል ነገር እንስሶችን የያዘው ዕቃ ትልቅ ጨርቅ ይመስል ነበር።

Acts 10:13

የሐዋርያት ሥራ **10**: **13-16**
ድምፅ ሰማ የተናገረው ማን እንሆነ አልተገለጸም። ይሁን እንጂ የድምፁ ምንጭ እግዚአብሔር እንጂ ሴጣን አለመሆኑን ማወቅ ይቻላል። ጌታ ጴጥሮስ በዚህ ሥፍራ ላይ የተጠቀው ቃል የአክብሮት ቃል የሆነውን “ጌታ” የሚል ነው። እርኩስ የሆነ እና ንጹሕ ያለሆነ ነገር በልቼ አላውቅም። በዚህ ሥፍራ በተዘዋዋር መልኩ መረዳት የሚቻለው የቀረቡት እንስሳት በሙሴ ሕግ መሠረት እርኩስ የተባሌ እና ለመብልነት የማይሆኑ ናቸው።

Acts 10:17

የሐዋርያት ሥራ **10**: **17-18**
እነሆ “እነሆ” የሚለው ቃል በታሪኩ ውስጥ አዲስ አስገራሚ ነገር መኖሩን ያሳየናል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሁለት ሰዎች በሩ ጋር መቆማቸው ነው። ከበሩ ፊት "ከቤቱ ፊት ለፉት ቆመዋል።" በዚህ ሥፍራ ላይ ይህ ቤት ግድግዳ እና ትክክለኛ በር እንዳለው በተዘዋዋር መልኩ ተጠቅሷ። እንዲሁም ይጣራሉ በቆርኔሊዮስ የተላኩት ሰዎች ከቤቱ ውጭ ሆነው እነ ጴጥሮስ ዬት እንዳሉ ይጠይቃሉ።

Acts 10:19

የሐዋርያት ሥራ **10**: **19-21**
ጴጥሮስ ገና ስለተመለከተው ራዕይ እያሰላሰለ ሳለ "ጴጥሮስ ስላየው ራዕይ እያሰላሰለ ሳለ" መንፈስ "መንፈስ ቅዱስ" ተመልከት "ተጠንቀቅ" ወይም "ተነሥ"

Acts 10:22

የሐዋርያት ሥራ **10**: **22-23**
እንዲህ አሉት "ከቆርኔሊዎስ ዘንድ ተልዕከው የመጡት ሦስቱ ሰዎች ለጴጥሮስ እንዲህ አሉት" ቆርኔሊዎስ በአይሁዊያን ሁሉ ዘንድ የታወቀ ሰው ነበር ብዙ የአይሁድ ሰዎች ስለ ቆርኖሌዎስ መልካም ነገር ይናገራሉ። የአይሁድ ሕዝብ ሁሉ ይህ በግነት መልኩ የቀረበው የቆርኖሌዊስ ባሕርይ በብዙ አይሁዳዊያን ዘንድ በጣም የሚታወቅ ነበር።

Acts 10:24

የሐዋርያት ሥራ **10**: **24-24**
የሐዋርያት ሥራ 10፡ 24-24 መጡ "ጴጥሮስ፣ ጴጥሮስን ከጆባ አጅበው የመጡት ሰዎች እና የቆርኖሊዎስ ሌሎዎች ሆነው" ዘመዶቹን እና ሁሉም ጓደኞቹን ጠራው። "እርሴ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ቆርኖሊዎስን ነው።

Acts 10:25

የሐዋርያት ሥራ **10**: **25-26**
የሐዋርያት ሥራ 10፡ 25-26 በእግሩ ፊት ተደፉ ቆርኖሊዎስ በጴጥሮስ እግር ፊት ስወድቅ (ይህ የስግደት ተግባር ነው (UDB) እንጂ እንዲሁ የአክብሮት ተግባር አይደለም። ተነስ፤ እኔ እራሴ እንደ አንተው ሰው ነኝ ይህ ለቆርኖሊዎስ ጳውሎስን እንዳያመልክት የተነገረው መካከለኛ የሆነ ተግሳሳጽ ወይም ማስተካከያ ነው።

Acts 10:27

የሐዋርያት ሥራ **10**: **27-29**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጴጥሮስ በቆርኖሊዎስ ቤት ውስጥ ለተሰበሰቡት ሰዎች እንዲህ ሲል ንግግር አደረገ። ከእርሱ ጋር ተነጋገረ "ቆርኖሊዎስን አናገረው" ብዙ ሰዎች ተሰብስበው አገኘ "ብዙ አሕዛብ በዚያ ተሰብስቦ አገኘ።" ከዚህ በተዘዋዋሪ መንገድ መረዳት የሚቻለው ቆርኖሊዎስ የጋበዛቸው ሰዎች አሕዛብ መሆናቸውን ነው። ለአይሁዳዊ ሰው ይህ በሕግ የተፈቀደ አይደለም "ይህ ለአይሁዳዊ ሰው በሕግ የተከለከለ ነው" ይህንን አንተ ራስህ ታውቃለህ ጴጥሮስ ለቆርኖሊዎስ እና እርሱ ለጋበዛቸው እንግዶች በመናገር ላይ ነው። “ስለዚህ ለምን እንደ አስጠራኸኝ ማወቅ እፈልጋለሁ።” ምንም እንኳ ቆርኖሊዎስ ጥያቄውን ያቀረበው በቀጥታ ለቆርኖሊዎስ ቢሆንም “እናንተ” የሚለው ቃል በዚያ ሥፍራ ያሉትን አሕዛቦችን ሁሉ ያካትታል (ብዙ ቁጥር ነው)።

Acts 10:30

የሐዋርያት ሥራ **10**: **30-33**
የሐዋርያት ሥራ 10፡ 30-33 አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ቆርኖሊዎስ ለጴጥሮስ ጥያቄ እንዲህ ሲል ምላሽ ሰጠ። አጠቃላይ መረጃ: በቁጥር 31 እና 32 ላይ ቆርኖሊዎስ መልአኩ በዘጠኝ ሰዓት በተገለጠለት ጊዜ የተናገረውን ነገር ቃል በቃል በመጥቀስ ምላሽ ሰጠ። ከአራት ቀናት በፊት በመጽሐፍ ቅዱስ ባሕል መሠረት ይህ የነበሩበትን ቀንንም ያካትታል። በዘመናችን የምዕራባዊያን ባሕል መሰረት ይህ እንዲህ ሊሆን ይችላል “ከሦስት ቀናት በፊት” እየጸለይኩ ሳለ አንዳንድ ጥንታዊያን ቅጂዎች “ከእየጾምኩ” ይልቅ “እየጾምኩና እየጸለይኩ ሳለ”S ይላሉ። በዘጠን ሰዓት ላይ አይሁዊያን ወደ እግዚአብሔር የሚጸልዩበት የከሰዓቱ የተለመደው ሰዓት። እግዚብሔር አስቦሃል "እግዛብሔር ተመልክቶሃል" ስምኦን እንዲሁም በሌላ ስሙ ጴጥሮስ ተብሎ የሚጠራ ሰውን አስጠራ "ጴጥሮስ ተብሎ የሚታወቀውን ስምኦንን አስጠራ" እኔ ወደ አንተ እልከዋለሁ "እርሱን" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጴጥሮስን ብቻ ነው፤ እኛ ሁላችን በዚህ አለን "እኛ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጴጥሮስ ስናገር ይሰሙ ዘንድ ወደቆርኖሊዎስ ቤት የተጠሩትን ሰዎች ሁሉ ነው። “እኛ” የሚለው ቃል ጴጥሮስን አያካትትም።

Acts 10:34

የሐዋርያት ሥራ **10**: **34-35**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጴጥሮስም በቆርኖሊዎስ ቤት ውስጥ ለሚገኙት ሰዎች ሁሉ መናገር ጀመረ። ከዚያም ጴጥሮስ አፉን ከፍቶ እንዲህ አለ "ጴጥሮስም ልናገራቸው ጀመር" ማንም እርሱን የሚያመልክ እና ትክክለኛውን ነገር የሚያደርግ ሰው በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት አለው "እርሱ የሚያመልኩትን እና ትክክለኛውን ነገር የሚያደርጉ ሰዎችን ሁሉ ይቀበላል።"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Acts 10:36

የሐዋርያት ሥራ **10**: **36**-**38**
መልዕክቱን ታውቃላችሁ "ቃሉን ታውቃላችሁ እርሱ የሁሉ ጌታ ነውl "ሁሉም' የሚለው ቃል ሁሉን ሰው ይወክላል" እናንተ እረራሳችሁ ይህ ቆርኖሊዎስን እና የእርሱን እንግዶች ይወክላል።

Acts 10:39

የሐዋርያት ሥራ **10**: **39**-**41**
እኛ ምስክሮች ነን "ሐዋሪያቱ ምስክር ናቸው።" ጴጥሮስ “እኛ” የሚለውን ቃል በመጠቀም አድማጮቹን ከዚህ ክልል ውጪ አድርጎዋቸዋል። ስለዚህ እርሱ "ስለዚህ ኢየሱስ እንዳደረገው" እነርሱ የገደሉት "የአይሁድ መሪዎች የገደሉት" ይህ ሰው "ይህ ሰው ኢየሱስ" እግዚአብሔር ከሞት አስነሳው "እግዚአብሔር እንደገና በሕይወት እንዲኖር አደረገው" እደገና እንዲታወቅ አደረገ "እንገና እንድገለጥ አድረገው"

Acts 10:42

የሐዋርያት ሥራ **10**: **42**-**43**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጴጥሮስ በ ACT 10:34 ላይ በቆርኖሊዎስ ቤት ውስጥ ላሉ ሰዎች የጀመረውን ንግግር ጨርሷል። አዞናል "እግዚአብሔር ምስክር እንድንሆን ወይም ሐዋርያት እንሆን ዘንድ አዝዞናል። ይህ የጴጥሮስን አድማጮችን የማያካትት ነው። ይህ በእግዚአብሔር የተመረጠውን ነው “እግዚአብሔር ኢየሱስን መርጧል" ሕያዋን እና ሙታን ይህ አሁን በሕይወት ያሉ ሰዎችን እና የሞቱ ሰዎችን ያካትታል። ሰዎች ሁሉ ምስክር የሚሆኑ ለእርሱ ነው። "ነቢያት ሁሉ ለኢየሱስ ምስክር ይሆናሉ።"

Acts 10:44

የሐዋርያት ሥራ **10**: **44**-**45**
ያደምጡ በነበሩት ሰዎች ሁሉ ላይ ወረደ "ሁሉ" ጴጥሮስ የተናገረውን ነገር ያመኑትን በቤቱ ውስጥ የነበሩትን አይሁዊን ያልሆኑ ሰዎችን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። መንፈስ ቅዱስ ወረደ አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን አፈሰሰ" ስጦታ "ነጻ ስጦታ"

Acts 10:46

የሐዋርያት ሥራ **10**: **46**-**48**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ይህ ስለቆርኖሊዎስ የተነገረው ታሪክ ፍጻሜ ነው። አሕዛብ በሌላ ቋንቋ ይናገሩ እና እግዚአብሔርን ያመልኩ ነበር እነዚህ አይሁዳዊን በእርግጥም አሕዛብ እግዚአብሔርን እያመለኩ እንደሆነ እንዲያውቁ ያደረጋቸው የሚታወቅ ቋንቋ ነበር። እነዚህ ሰዎች ማለትም . . . የተቀበሉ ሰዎች እንዳይጠመቁ የሚከለክል ሰው ይኖራንል? አማራጭ ትርጉም: "እነዚህ ሰዎች እንዳይጠመቁ የሚከለክል ማንም ሰው ሊኖር አይችልም። እነዚህ ሰዎች እኛ . . . እነርሱ ተቀብለዋልና ልጠመቁ ይገባቸዋል። ይጠመቁ ዘንድ አዘዘ አመራጭ ትርጉም: "ጴጥሮስ አሕዛብ አማኞችን ያጠምቁ ዘንድ አይሁዳዊያን አማኞችን አዘዘ።" ጠየቁት "አሕዛብ ጴጥሮስን ጠየቁት"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 11

1 ሐዋርያትና በይሁዳ የነበሩት ወንድሞች አሕዛብ ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል ተቀብለው እንደ ነበር ሰሙ። 2 ጴጥሮስም ወደ ኢየሩሳሌም ወጥቶ በነበረ
ጊዜ፣ ከመገረዝ ወገን የነበሩት ነቀፉት፤ 3 “ካልተገረዙ ወንዶች ጋር ተባብረሃል፣ አብረሃቸውም በልተሃል!” አሉት። 4 ጴጥሮስ ግን እንዲህ ብሎ ጉዳዩን
በዝርዝር ያብራራላቸው ጀመር፤ 5 እኔ በኢዮጴ ከተማ እጸልይ ነበር፤ በተመስጦም አራት ማዕዘን ያለው ታላቅ ሸማ የመሰለ ዕቃ መያዣ ከሰማይ ሲወርድ ራእይ
ዐየሁ፤ ወደ እኔ ወረደ፣ 6 ትኵር ብዬ ተመለክትሁትና ስለ እርሱ ዐሰብሁ። አራት እግር ያላቸው የምድር እንስሳትን፣ አራዊትን፣ የሚሳቡ ፍጥረታትን፣ የሰማይ
አዕዋፍንም ዐየሁ። 7 በዚያን ጊዜ አንድ ድምፅ፣ “ጴጥሮስ ሆይ፣ ተነሣ፣ አርደህም ብላ!” ሲለኝ ሰማሁ። 8 “ጌታ ሆይ፣ አይሆንም፣ ምክንያቱም ጸያፍ ወይም
ርኩስ የሆነ ምንም ነገር ከቶ ወደ አፌ ገብቶ አያውቅም” አልሁ። 9 ነገር ግን ድምፁ ዳግመኛ ከሰማይ፣ “እግዚአብሔር ንጹሕ ነው ያለውን አንተ ርኩስ ብለህ
አትጥራው” ብሎ መለሰ። 10 ይህም ሦስት ጊዜ ሆነ፤ ከዚያም ሁሉም ነገር እንደ ገና ወደ ሰማይ ተወሰደ። 11 እነሆ፣ ወዲያውኑ እኛ በነበርንበት ቤት ፊት
ለፊት ሦስት ሰዎች ቆመው ነበር፤ እነርሱም ከቂሣርያ ወደ እኔ የተላኩ ናቸው። 12 መንፈስም ከእነርሱ ጋር እንድሄድ፣ ስለ እነርሱም ልዩነት እንዳላደርግ አዘዘኝ።
እነዚህ ስድስት ወንድሞች አብረውኝ ሄዱ፤ ወደ ሰውዬውም ቤት ገባን። 13 እርሱም መልአክ በቤቱ ቆሞ እንዳየና እንዲህ እንዳለውም ነገረን፤ “ወደ ኢዮጴ
ሰዎችን ላክና ሌላው ስሙ ጴጥሮስ የሆነውን፣ ስምዖንን አስመጣ። 14 አንተና ቤተ ሰቦችህ ሁሉ የምትድኑበትን መልእክት ይነግርሃል።” 15 ለእነርሱ መናገር
እንደ ጀመረና ልክ በመጀመሪያ በእኛ ላይ እንደ ሆነው፣ መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ ወረደ። 16 “ዮሐንስ በእርግጥ በውሃ አጥምቆ ነበር፤ እናንተ ግን
በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ” ብሎ እንደ ተናገረ፣ የጌታን ቃሎች አስታወስሁ። 17 እኛ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ባመንን ጊዜ እንደ ሰጠን ያለ ስጦታ
እግዚአብሔር ለእነርሱ ከሰጣቸው እንግዲያ፣ እግዚአብሔርን እቃወም ዘንድ እኔ ማን ነበርሁ?” 18 እነርሱ እነዚህን ነገሮች በሰሙ ጊዜ፣ መልስ አልሰጡም፤
ነገር ግን እግዚአብሔርን አመስግነው፣ “እግዚአብሔር ለአሕዛብ ለሕይወት የሚሆን ንስሓን ደግሞ ሰጥቷቸዋል” አሉ። 19 ስለዚህ በእስጢፋኖስ መሞት
የተጀመረው ሥቃይ ከኢየሩሳሌም የበተናቸው እነዚህ አማኞች እስከ ፊንቄ፣ ቆጵሮስና አንጾኪያ ድረስ ሄዱ። ስለ ኢየሱስ የሚናገረውን መልእክት ለአይሁድ ብቻ
እንጂ ለሌላ ለማንም አልተናገሩም። 20 ነገር ግን ከቆጵሮስና ከቀሬና የነበሩ ሰዎች አንዳንዶቹ ወደ አንጾኪያ መጥተው ለግሪኮች ተናገሩ፤ ጌታ ኢየሱስንም
ሰበኩላቸው። 21 የጌታም እጅ ከእነርሱ ጋር ነበረ፤ በቍጥር ብዛት ያላቸው ሰዎች አምነው ወደ ጌታ ዘወር አሉ። 22 ስለ እነርሱ ወሬ በኢየሩሳሌም ባለችው ጉባኤ
ተሰማ፤ በርናባስንም እስከ አንጾኪያ ላኩት። 23 እርሱም መጥቶ የእግዚአብሔርን ስጦታ ባየ ጊዜ፣ ደስ አለው። ከሙሉ ልባቸው ከጌታ ጋር እንዲኖሩ
ሁላቸውንም አበረታታቸው። 24 ምክንያቱም እርሱ መንፈስ ቅዱስና እምነት የሞላበት በጎ ሰው ነበር፤ ብዙ ሕዝብም ወደ ጌታ ተጨመሩ። 25 ከዚያም በርናባስ
ሳውልን ሊፈልግ ወደ ጠርሴስ ወጣ። 26 ባገኘውም ጊዜ፣ ወደ አንጾኪያ አመጣው። እንዲህም ሆነ፣ አንድ ዓመት ሙሉ በቤተ ክርስቲያን አብረው ተሰበሰቡ፣
ብዙ ሕዝብንም አስተማሩ። ደቀ መዛሙርቱ በመጀመሪያ በአንጾኪያ ክርስቲያን ተባሉ። 27 በእነዚያ ቀናትም አንዳንድ ነቢያት ከኢየሩሳሌም ወደ አንጾኪያ ወረዱ።
28 ከእነርሱ አንዱ አጋቦስ የተባለው፣ ተነሥቶ ቆመና በመላው ዓለም ላይ ታላቅ ራብ እንደሚሆን በመንፈስ አመለከተ። ይህም በቀላውዴዎስ ዘመን ሆነ። 29
ስለ ሆነም፣ ደቀ መዛሙርቱ እያንዳንዳቸው እንደ ዐቅማቸው በይሁዳ ላሉት ወንድሞች እርዳታ ለመላክ ወሰኑ። 30 ይህንም አደረጉ፤ በበርናባስና በሳውል እጅ
ለሽማግሌዎቹ ገንዘብ ላኩ።

Acts 11:1

የሐዋርያት ሥራ **11**: **1-3**
አጠቃላይ መረጃ: ይህ በታሪክ ውስጥ አዲስ ታሪክ የሚጀመርበት ሥፍራ ነው። ጴጥሮስ ወደ እየሩሳሌም በመሄድ በዚያ ካሉ አይሁዳዊን ጋር ንግግር ይጀምራል። አሁን ይህ የአዲስ ነገር ጅማሬን ያሳያል። በይሁዳ የነበሩት "በይሁዳ ከተማ ይኖሩ የነበሩ" የእግዚአብሔርን ቃል ተቀበሉ ይህ አሕዛብ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል መቀበላቸውን፣ መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ መውረዱን እና አሕዛብ መጠመቃቸውን የሚያሳይ ነው። ጴጥሮስ ወደ ኢየሩሳሌም በመጣ ጊዜ እየሩሳሌም የሚትገኘው በተራራማ ሥፍራ ነው። የተገረዙት ወገኖች እነዚህ ቡድኖች የክርስቶስ ተከታዮች የሆኑ ሰዎች ሁሉ መገረዝ እናየሙሴን ሕግ መጠበቅ አለባቸው የሚለው አይሁዊንን ናቸው። ገሰጹት "ከእርሱ ጋር ተነጋገሩ" ከእነርሱ ጋር በመብላቱ የተገረዙ ሰዎች ካልተገረዙ ሰዎች ጋር መብላታቸው ከሕግ ውጪ ስለሆነ ነው።

Acts 11:4

የሐዋርያት ሥራ **11**: **4-6**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጴጥሮስ ለዚህ ተቋቃውሞ ስለተመለከተው ራዕዮ እና በቆርኖሊዎስ ቤት ውስጥ የሆነውን ነገር መሠረት በማድረግ ምላሽ ሰጠ። ጴጥሮስ ማስረዳት ጀመረ ጴጥሮስ የአይሁድ አማኞችን አልተቻቸውም ልቁንም እንደጓደኛ በመሆን የሆነውን ነገር አብራራላቸው። በምድር ላይ ያሉ አራት እግራ ያላቸው እንስሳት በምድር ላይ ያሉ አራት እግር ያላቸው እንስሳት - ይህ ምንአልባት የሚያመለክተው ሰዎች ሊገሯቸው የሚችሉ እንስሳትን ነው።

የዱር እንስሳት ይህ ሰዎች ልቆጣጠሯቸው ወይም ሊገሯቸው የማይችሉትን እንስሳትን ነው። ተሳቢ እንስሳትን እነዚህ በምድር ላይ የሚሳቡ እንስሳትን ያመለክታሉ።

Acts 11:7

የሐዋርያት ሥራ **11**: **7-10**
ያልተቀደሰ ወይም ንጹሕ ያለሆነ ነገር ወደ አፌ ገብቶ አያውቅም በቅርጫቱ ውስጥ የነበሩት እንስሳት አይሁዳዊን በብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ውስጥ በአይሁድ ሕግ መሠረት እንዳይበሏቸው የተከለከሉት እንስሳት ናቸው። አማራጭ ትርጉሞች: "እኔ ቅዱስ እና ንጹሕ የሆኑ ነገሮችን ብቻ ነው የሚበላው።" እግዚአብሔር ንጹሕ ያደረገውን እርኩስ ብለህ አትጥራ ይህ “እግዚአብሔር ንጹሕ ብሎ የጠራውን ነገር ንጹሕ አትበል” ለማለት ነው።” ንጹሕ ያልሆነ በብሉይ ኪዳን የአይሁድ ሕግ አንድ ሰው በሥርዓቱ “ንጹሕ አይደለም” የሚባለው በተለያዩ መንገዶች ነው። ከእነርሱ መካከል አንዱ የተከለከሉ እንስሳትን በመብላት ነው።

Acts 11:11

የሐዋርያት ሥራ **11**: **11-14**
እነሆ "ወዲያው" ወይም "በዚያው ወቅት" (UDB)። እነሆነ - ይህ ቃል በታኩ ውስጥ አዲስ ሰው መግባቱን ያመለክተናል። በቋንቋችሁ እንዲህ ዓይቱን ነገር ማድረግ የሚቻልበት መንገድ ይኖራል። ተልከዋል አማራጭ ትርጉም: “የሆነ ሰው ልኳቸዋል።” በእነርሱ መካከል ምን ዓይነት ልዩነት እንዳላደረግ "አሕዛብ ወይም አይሁዳዊያን ናቸው ብዬ በመካከላቸው ልዩነት እንዳላደረግ" እነዚህ ስድስት ወንድሞች "እነዚህ ስድስት አይሁዳዊያን አማኞች" ጴጥሮስ ተብሎ የሚጠራውን ስሞኦንን ይዘውት መጡ "ጴጥሮስ ተብሎ የሚጠራውን ስምኦፕን ይዘውት መጡ" ትድናላችሁ አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር ያድናችኋል"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Acts 11:15

የሐዋርያት ሥራ **11**: **15-16**
በመጀመሪያ በእኛ ላይ እንደሆነው ሁሉ በእርሱ ላይም መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው "በጴንጤቆስጤ ቀን መንፈስ ቅዱስ በአይሁዳዊያን አማኞች ላይ እንደወረደ ሁሉ እንዲሁም በአሕዛብ አማኞች ላይም ወረደ" በመጀመሪያ በእኛ ላይ እንደወረደ "እኛ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጴጥሮስን እና ከመጀመሪያ ጊዜ ጀምሮ በዚያ የነበሩተን አይሁዳዊያን አማኞችን ሲሆን እነዚህ በክፍሉ ውስጥ ያሉት ሁሉ ከመጀመሪያው ጊዜ አንስቶ ነበሩ። በቋንቋችሁ ሌሎችን የሚለይ ቃል ካለ ተጠቀሙ። በመጀመሪያ በዚህ ሥፍራ ጴጥሮስ በዚህ ቃል አማካይነት ማመልከት የፈለገው ነገር የጴንጤቆስጤ ቀንን ነው። በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል"

Acts 11:17

የሐዋርያት ሥራ **11**: **17-18**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጴጥሮስ በ ACT 11:4 ላይ የጀመረውን ስለተመለከተው ራዕይ እና በቆርኖሊዎስ ቤት ውስጥ ስለተከሰተው ነገር ለአይሁዳዊያን ማብራራቱን ጨርሷል። እግዚአብሔር ሰጥቶዋቸዋል "እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ቆርኖሊዎን እና እርሱ የጠራቸውን አሕዛብን ነው። ጴጥሮስ እነዚህ ሰዎች በእየሩሳሌም ባሉ አይሁዳዊያን አማኞች ፊት ባደረገው ንግግሩ ውስጥ አሕዛብ ብሎ አልጠራቸውም። ተመሳሳይ ስጦታ ጴጥሮስ የመንፍስ ቅዱስ ስጦታ በማለት ይጠራዋል. እግዚአብሔርን እቃወም ዘንድ እኔ ማን ነኝ? ግልጽ የሆነውን ነገር ለማብራራት ጴጥሮስ ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔርን መቃወም አልችልም።" እነዚህ ነገሮች በሰሙ ጊዜ "እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጴጥሮስን በመቃወም ላይ የነበሩትን የተገረዙት ወገኖችን ነው። ለሕይወት የሚሆን ንሰሓን ሰጣቸው "ወደ ሕይወት የሚወስድ ንሰሓን ሰጣቸው"

Acts 11:19

የሐዋርያት ሥራ **11**: **19-21**
አጠቃላይ መረጃ: ይህ የታሪኩ አዲስ ክፍል ነው፤ እስጥፋኖስ በድንጋይ ተወግሮ ከሞተ በኋላ አማኞች ላይ ምን እንደደረሰባቸው ይናገራል። ስለዚህ ይህ የታሪኩን አዲስ ክፍል መግቢያ ሆኖ ያገለግላል። ከእስጥፋኖስ ሞት በኋላ የጀመረው የአማኞች ሞት ከእየሩሳሌም እንዲበተኑ አደረገ "የአይሁድ መሪዎች እስጥፋኖስን ከገደሉት በኋላ ብዙ አማኞች መከራ ይገጥማቸው ጀመረ። እነዚህ አማኞች ከእየሩሳሌም ወጥተው ወደ ተለያዩ ሥፍራዎች ሄዱ።" ለአይሁዳዊያን ብቻ እንጂ ለሌሎች አማኞች የእግዚአብሔር መልዕክት ለአይሁዳዊያን እንጂ ለአሕዛብም ጭምር ነው ብለው አያስቡም ነበር። የእግዚአብሔር እጅ የእግዚአብሔር እጅ የሚለው ሀረግ የሚያሳየው ኃይልን ነው። አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር በኃይል እንዲቻል አደረገ"

Acts 11:22

የሐዋርያት ሥራ **11**: **22-24**
አጠቃላይ መረጃ: በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ “እርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ባርናባስን ነው። ስለእነርሱ የተነገረው ዜና "እነርሱ" በአንጾኪያ ያለው አዳዲስ አማኞች። የቤተ ክርስቲያን ጆሮዎች "ጆሮዎች" የሚያመለክተው የተለያዩ ነገሮችን መስማትን ነው። አማራጭ ትርጉም: "በእየሩሳሌም ያት አማኞች ስለእነርሱ ሰሙ።" ላኩ "በእየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት አማኞች ላኩ" የእግዚአብሔርን ስጦታ አዩ "የእግዚአብሔርን ጸጋ አዩ" ወይም "እግዚአብሔርን አማኞችን አስመልክቶ ቸርነቱን እንዳደረገ" (UDB) አበረታታቸው "ማበረታታቱን ቀጠለ" ከጌታ ጋር መሆኑን ቀጠለ "ለጌታ ታማኝ ሆኖ ቀጠለ።" በልባቸው ሁሉ "ለጌታ የተሰጡ መሆን" ወይም "በጌታ ፈጽሞ መታመን" (UDB) በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ባርናባስ መንፈስ ቅዱስን መታዘዙን በቀጠለ ቁጥር መንፈስ ቅዱስ ባርናባስን ይቆጣጠረው ነበር። ብዙ ሰዎች ወደ ጌታ ተጨመሩ። "ተጨመሩ" ማለት አመኑ። አማራጭ ትርጉም: "ብዙ ሰዎች በጌታ አመኑ።"

Acts 11:25

የሐዋርያት ሥራ **11**: **25-26**
ከጠርሴስ "ከጠርሴስ ከተማ ውጪ" ባገኘው ጊዜ ይዞት መጣ "ባርናባስ ሳኦልን ስያገኘው ይዞት መጣ" ከእነርሱ ጋር በአንድነት ተሰበሰቡ "ባርናባስ እና ሳኦል ከእነርሱ ጋር ተሰበሰቡ" ወይም "ባርናባስ እና ሳኦል ሁል ጊዜ ከእነርሱ ጋር ይሰበሰቡ ነበር" ደቀ መዛሙርቱ ክርስቲየን ተብለው ተጠሩ አማራጭ ትርጉም: "የአንጾኪያ ሰዎች ደቀ መዛሙርቱን ክርስቲያኖች ብለው ይጠሯቸው ነበር።"

Acts 11:27

የሐዋርያት ሥራ **11**: **27-28**
አሁን በዚህ ሥፍራ ጥቅም ላይ የዋለው ይህ ቃል በታሪኩ መሥመር ላይ ለውጥ መደረጉን ያሳያል። በዚህ ስፍራ ሉቃስ ስለ በአንጾኪያ ስለሆነውን ትንቢት የኃላ ታሪክ መረጃ ይሰጣል። ከእየሩሳሌም ወደ አንጾኪያ ወረዱ ከእየሩሳሌም ወደ አንጾኪያ የከፍታ ለውጥ አለ። ከዚህ በተጨማሪ በእየሩሳሌም ያለው ቤተ መቅደስ ከፍተኛ ሚና እንዳውም ብዙ ሰዎች ይናገራሉ። ምንም አቀበታማ ቢሆንም ሰዎች ወደ እየሩሳሌም እና ቤተ መቅደሱ ይሄዳሉ እንዲሁም ከዚያም ይወርዳሉ። ታላቅ ረሃብም ሆነ "ከፍተኛ የምግብ እጥረት ተከሰተ" በዓለም ሁሉ ላይ ይህ የሮምን አገዛዝ ለማሳየት የዋለ ግነት የሞላበት ንግግር ነው። አማራጭ ትርጉም: "በአጠቃላይ ሮም አገዛዝ ውስጥ።"

Acts 11:29

የሐዋርያት ሥራ **11**: **29-30**
ስለዚህ ይህ የሆነው ነገር በመጀመሪያ ሌላ ነገር በመሆኑ ምክንያት እንደሆነ የሚያመለክት ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ገንዘብ የላኩ ከአጋቦስ ትንቢት የተነሣ ነው። ሁሉም ሰው የቻለውን ያኽል ሀብታሞች ብዙ ሲልኩ ድሆች ግን ጥቂት ሊከዋል። ይህንን አደረጉ፤ ገንዘብ ላኩ "በአንጾኪያ የሚገኙ አማኞች ገንዘብ አወጥተው ላኩ" በባርናባስ እና በሳኦል እጂ አድርገው "እጅ" ማለት በእነርሱ በኩል አድርገው። አማራጭ ትርጉም: "ባርናባስ እና ሳኦል ገንዘቡን ራሳቸው በኢየሩሳሌም በሚትገኛው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወደአሉት ሽማግሌዎች ዘንድ ይዘው መጡ።"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 12

1 በዚያን ጊዜ ንጉሡ ሄሮድስ ሊያሠቃያቸው ከቤተ ክርስቲያን አንዳንዶቹን ያዛቸው። 2 የዮሐንስን ወንድም ያዕቆብን በሰይፍ ገደለው። 3 ይህ አይሁድን ደስ
እንዳሰኛቸው ካየ በኋላ፣ ጴጥሮስንም ያዘው። ይህ የሆነው በቂጣ በዓል ጊዜ ነበር። 4 ከያዘውም በኋላ ወደ ወኅኒ አገባው፤ እንዲጠብቁትም እያንዳንዳቸው
አራት ወታደሮች ያሏቸው ቡድኖችን መደበ፤ ከፋሲካ በኋላ ወደ ሕዝቡ ሊያቀርበው ዐስቦ ነበር። 5 ጴጥሮስም በወኅኒው ይጠበቅ ነበር፤ ነገር ግን ስለ እርሱ
ጉባኤው ወደ እግዚአብሔር አጥብቆ ይጸልይ ነበር። 6 ሄሮድስ ሊያወጣው ባሰበበት በዚያ ሌሊት፣ ጴጥሮስ በሁለት ሰንሰለቶች ታስሮ በሩን በሚጠብቁ ሁለት
ወታደሮች መካከል ተኝቶ ነበር። 7 እነሆም የጌታ መልአክ በድንገት በአጠገቡ ታየ፣ በክፍሉም ብርሃን በራ። መልአኩ የጴጥሮስን ጎን መትቶ ቀሰቀሰውና፣
“ፈጥነህ ተነሥ” አለው። በዚያን ጊዜ ሰንሰለቶቹ ከእጆቹ ወደቁ። 8 መልአኩ ጴጥሮስን፣ “ልብስህን ልበስ ጫማህንም አድርግ” አለው። ጴጥሮስም እንዲሁ
አደረገ። መልአኩ፣ “መደረቢያህን ልበስና ተከተለኝ” አለው። 9 ጴጥሮስም መልአኩን ተከትሎ ወደ ውጭ ወጣ። መልአኩ ያደረገው ነገር በእውን እንደ ሆነ
ጴጥሮስ አላወቀም። ራእይ ያየ መሰለው። 10 የመጀመሪያውንና ሁለተኛውን ዘብ እንዳለፉ፣ ወደ ከተማይቱ ወደሚያወጣው የብረት በር ደረሱ፤ እርሱም ዐውቆ
ተከፈተላቸው። እነርሱም ወጥተው በአንድ መንገድ በኩል ወረዱ፤ መልአኩም ወዲያውኑ ተለየው። 11 ጴጥሮስም ራሱን ሲያውቅ፣ “ጌታ መልአኩን ልኮ
ከሄሮድስ እጅ፣ የአይሁድ ሕዝብም ይጠብቁት ከነበረው ሁሉ እንዳዳነኝ አሁን ዐወቅሁ” አለ። 12 ጴጥሮስ ይህን ከተገነዘበ በኋላ፣ ማርቆስ ተብሎ
ወደሚጠራው ወደ ዮሐንስ እናት ቤት መጣ፤ በዚያ ብዙ ምእመናን ተሰብስበው እየጸለዩ ነበር። 13 የደጁን በር ባንኳኳ ጊዜ፣ ሮዴ የሚሏት የቤት ሠራተኛ
ልትከፍትለት መጣች። 14 የጴጥሮስን ድምፅ ባወቀች ጊዜ ከደስታዋ የተነሣ በሩን መክፈት አቃታት፤ ይልቁን ሮጣ ወደ ቤት ገባች፤ ጴጥሮስ ከበሩ ውጭ
መቆሙን ተናገረች። 15 ምእመናኑም፣ “ዐብደሻል” አሏት። እርሷ ግን እንዲሁ ነው ብላ በዐሳብዋ ጸናች። እነርሱም፣ “የእርሱ መልአክ ነው” አሉ። 16 ጴጥሮስ
ግን ማንኳኳቱን ቀጠለ፤ በሩን በከፈቱ ጊዜ፣ ዐይተውት ተደነቁ። 17 ጴጥሮስ ዝም እንዲሉ በእጁ ምልክት ሰጣቸው፤ ጌታ ከወኅኒ እንዴት እንዳወጣውም
ነገራቸው። “እነዚህን ነገሮች ለያዕቆብና ለወንድሞች ንገሩ” አላቸው። ከዚያም ቤት ወጥቶ ወደ ሌላ ስፍራ ሄደ። 18 በማግስቱም፣ ጴጥሮስን በሚመለከት ስለ
ተከሠተው ነገር በወታደሮች መካከል መደናገጥ ሆነ። 19 ሄሮድስ ጴጥሮስን ፈልጎ ሊያገኘው አልቻለም፤ ጠባቂዎችን መርምሮ እንዲገደሉ አዘዘ። ከዚያም
ጴጥሮስ ከይሁዳ ወደ ቂሣርያ ወርዶ በዚያ ተቀመጠ። 20 ሄሮድስም በጢሮስና በሲዶና ሰዎች ላይ እጅግ ተቈጥሮ ነበር። የጢሮስና የሲዶና ሰዎች
ተሰብስበው ወደ እርሱ ሄዱ። እንዲረዳቸው የንጉሡን ረዳት ብላስጦስን እሺ አሰኙት። ከዚያም ዕርቅ ሰላም እንዲወርድ ጠየቁ፤ ምክንያቱም አገራቸው ከንጉሡ
አገር ምግብ ያገኝ ነበር። 21 በቀጠሮ ቀን ሄሮድስ ልብሰ መንግሥት ለብሶ በዙፋን ላይ ተቀመጠና ንግግር አደረገላቸው። 22 ሕዝቡም፣ “ይህ የአምላክ ድምፅ
ነው እንጂ፣ የሰው አይደለም!” ብለው ጮኹ። 23 ሄሮድስ ለእግዚአብሔር ክብር ስላልሰጠ፣ ወዲያውኑ የጌታ መልአክ ቀሠፈው፤ በትል ተበልቶም ሞተ። 24
የእግዚአብሔር ቃል ግን እያደገና እየሰፋ ሄደ። 25 በርናባስና ሳውል ለኢየሩሳሌም የነበራቸውን ተልእኮ ከፈጸሙ በኋላ፣ ተመለሱ፤ ማርቆስ የተባለውንም ዮሐንስን
ይዘው ሄዱ።

Acts 12:1

የሐዋርያት ሥራ **12**: **1**-**2**
አጠቃላይ መረጃ: ይህ ስለጴጥሮስ መታሠር የሚያወራ አዲስ የታሪኩ ክፍል ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ ሄሮዶስ ያዕቆብን እንደገደለው መረጃ ይሰጠናል። አሁን ይህ በታሪኩ ውስጥ አዲስ ከፍል መጀመሩን ያበስራል። በዚያን ጊዜ ይህ በአንጾኪያ የነበሩት ደቀ መዛሙርት በይሁዳ ለነበሩት ወንድሞች ገንዘብ የላኩበትን ጊዜ ያመለክታል። እጆቻቸውን ጫኑባቸው ይህ ሄሮዶስ አማኞችን ይጨቁን እንደነበረ የሚያሳይ ነው። አማራጭር ትርጉም: “ለማሠር ወታደሮችን ላከ።" ከተሰብሳቢዎቹ መካከል አንዳንዶቹ ከአውዱ የስብሰባው መሪዎች መሆናቸውን መረዳት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም: "የስብሰባው መሪዎች።" አሰቃዮዋቸው "አማኞች እንዲሰቃዩ አደረጉ" ያዕቆብ በስለት እንዲሞት አደረገ ይህ ሀረግ ያዕቆብ የተገደለበትን መንገድ በግልጽ ይናገራ። ገደለው "ንጉስ ሄሮዶስ ገደለው" ወይም "ንጉሥ ሄሮድ እንዲገደል ትዕዛዝ ሰጠ"

Acts 12:3

የሐዋርያት ሥራ **12**: **3**-**4**
የሐዋርያት ሥራ **17**: **16-17**
አጠቃላይ መረጃ: ይህ ስለጳውሎስ እና ሲላስ ጉዞ ታሪክ ሌላኛው ክፍል ነው። ጳውሎስ አሁን የሚገኘው በአቴንስ ነው። በዚህም ሆኖ ሲላስና ጢሞቴዎስ ወደ እርሱ ዘንድ እንዲመጡ ይጠብቃል። መንፈሱ ታወከ "ተጨነቀ" ወይም "በጣም ታወከ" ወይም "በጣም ተጨነቀ" (UDB) ተከራከረ ይህ ግሥ ከሰባኪው አንጻር ሳይሆን ከአድማጮቹ ዘንድ ብዙ ክርክር እንደነበረ ያሳያል። አማራጭ ትርጉም: "ተከራከረ" ወይም "ተወያየ።" በገቢያ ሥፍራ ይህ የተለያዩ ቢዝነሶች፣ የተለያዩ ነገሮች እንስሳት ግዥ እና ሽያጭ ወይም የተለያዩ ግልጋሎቶች የሚሰጡበት ሥፍራ ነው። አማራጭ ትርጉም: "በመስቀል አደባባይ" (UDB).

Acts 17:18

የሐዋርያት ሥራ **17**: **18-18**
ኤፊቆሮስ . . . ፈላስፎች እነዚህ ሰዎች ሁሉ ነገር በእድል የሆነ ነው በማለት ያምናሉ። አማልክት ራሳቸውን በማስደስት የተጠመዱ በመሆናቸው ምድርን ለማስተዳደር ግድ አይላቸውም። ትንሳኤ አካልን አይቀበሉም። እስቶይክ ፈላስፋዎች እነዚህ ሰዎች ነጻነት የሚገኘው ራሰን ከእድል በማላቀቅ ነው ብለው ያምናሉ። ሰዎችን የሚወድን አምላክ አይቀበሉም እንዲሁም በትንሳኤ ሙታን አያምኑም። ተሟገቱት "ከጳውሎስ ጋር ተከራከሩ" አንዳንዶቹም እንዲህ አሉ "አንዳዶቹ ፈላስፎች አንዲህ አሉ" ይህ ለፍላፊ ከዬት ነው የመጣው "ለፍላፊ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጥራጥሬ የሚለቃቅም ወፍን ነው። ይህ ቃል አሉታዊ በሆነ መልኩ ሀሜት የሚያወራን ሰው ለማመልከት ይውላል። ፈላስፎቹ ስለጳውሎስ ስናገሩ ለመስማት እንኳ ይህንን ያኽል ግድ የሚያሰኝ መረጃ የለውም ብለው ተናግረዋል። አንዳንዶቹ ደግሞ እንዲህ ብለዋል "ሌሎች ፈላስፎች እንዲህ ብለዋል" ሰባኪ ይመስላ "አዋጅ የሚነግር ሰው ይመስላል" ወይም "መልዕክቱን ለማሰራጨት የተላከ ሰው ይመስላል" ስለእንግዳ አማልክት ይናገራል ይህ “የማይገባ ማለት ሳይሆን” “አዲስ” ማለትም የግሪክ እና የሮማዊያን አማልክት ውጪ የሆነ አምላክ ማለት ነው። .

Acts 17:19

የሐዋርያት ሥራ **17**: **19-21**
ጳውሎስን ወስደው "ኤፊቆሮስ እና የስቶይክ ፈላስፎች ጳውሎን ወስደው" ወደ አርዮስፋጎስ በአቴንስ ከተማ ውስጥ የሚገኝ ተራራማ ስፍራ ሲሆን የአቴን ከፍተኛው ፍድ ቤት ይገኝ የነበረው በዚያ ነበር እነዚህ ነገሮች ምን እንደሆነ ልናውቅ እንወዳለን አሉት በዚህ ሥፍራ "እኛ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ፈላስፎቹን ብቻ ነው። አማራጭ ትርጉም: "እየተናገርካቸው ያሉትን ነገሮች ሰምተን የራሳችንን ቢያኔ ልንወስድ እንወዳለን።" የአቴና ሰዎች ሁሉ ሆይ "የአቴና" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከቴና ከተማ የመጡ ሰዎችን ነው። ይህች ከተማ ከመቂዶኒያ (ከአሁኗ ግሪክ) አቅራባ ያለች ከተማ ናት። እንዲሁም እንግዶች የሆናችሁ እንግዶች" ወይም “ለአቴና ማህበረሰብ አዲስ የሆኑትንም” ጊዜያቸውን ያሳለፉ "ጊዜያቸውን ይቀጠሙ " ወይም "ከእርሱ ጋር አሳለፉ" አዲስ ነገርን በመናገር ወይም በማድመጥ "አዳዲስ የፍልስፍና ሀሳቦችን" ወይም "ለእነርሱ አዲስ የሆነውን ነገር በመናገር" (UDB)

Acts 17:22

የሐዋርያት ሥራ **17**: **22-23**
አጠቃላይ መረጃ: ጳውሎስ በአርዮስፋጎስ ለነበሩት ፈላስፎች ንግግሩን እንዲህ በማለት ነው የጀመረው። በሁሉም ነገር ሃይማኖተኞች ናችሁ ጳውሎስ ኤናዊያን በአደባባይ አማልክቶቻቸውን በጸሎት፣ መሰዊያዎችን በመሥራት እና መስዋእትን በመሰዋት እንደሚያከብሩ በመናገር። ስዘዋወር "ምክንያቱም ከቦታ ቦታ ስዘዋወር" ለማይታወቅ አምላክ አማራጭ ትርጉሞች 1) "የሆነ የማይታወቅ አምላክ" ወይም 2) "ለማያውቁት ማንኛውም አምላክ።"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Acts 17:24

የሐዋርያት ሥራ **17**፡ **24**-**25**
ዓለም በአጠቃላይ ትርጉሙ “ዓለም” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰማይን እና ምድርን እንዲሁም በውጡ ያሉትን ነገሮች ሁሉ ነው። እርሱ ጌታ በመሆኑ ምክንያት በዚህ ሥፍራ ላይ "እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስ እያብራራ ያለውን የማይታወቅ አምላክን ሲሆን ይህንን ጳውሎ ጌታ እግዚአብሔርን ነው ይላቸዋል። አማራጭ ትርጉም: "እርሱ ጌታ ስለሆነ።" በእጆች የተሠራ "በሰዎች ጥረት የተሠራ" የሚገለገለው በዚህ ሥፍራ ላይ "የሚገለገለው" የሚለው ቃል የሚያመለክተው አንድ ዶክተር በሽተኛው ጤናማ እንዲሆን የሚያደርገውን ነገር ነው። አማራጭ ትርጉም: “ይጠነቀቅለታል።" በሰዎች እጅ "በሰው ልጆች እጅ" ምክንያቱም እርሱ ራሱ "ምክንያቱም እርሱ ራሱ"

Acts 17:26

የሐዋርያት ሥራ **17**፡ **26**-**27**
አንድ ሰው አማራጭ ትርጉሞች 1) "አንድ ሰው የሚለው የሚያመለክተው እግዚአብሔር የፈጠረውን አዳምን ነው" ወይም 2) "እግዚአብሔር የፈጠራቸውን አዳምን እና ሔዋንን ልያካትት ይችላል።" እርሱ ሁሉንም ነገዶች ፈጥሯል "እግዚአብሔር ሁሉንም ነገዶች ፈጥሯል" እነርሱ . . . እነርሱ ይህ ተውላጠ ስም በምድር ላይ የሚኖሩ ነገዶችን ሁሉ የሚያመለክት ነው። ስለዚህ ይህ ቃል ከዚህ በፊት የተነገረብ አንዲ ዓረፍተ ነገር የሚያመለክት ሲሆን ከዚህ በፊት ከተነገረው ዓረፈተ ነገር የተነሣ። እግዚአብሔርን ይፈልጉታል "እግዚአብሔርን ይፈልጉታል" ወደ እርሱ ለመድረስ ይፈልጋሉ "እርሱን ለማግኘት ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው" እርሱም ከእርሱ የራቀ አይደለም ጳውሎስ ያነሰውን ነጥብ ለማጎላት ሲል ማለት ከሚፈልገው ነገር ታቃራኒ የሆነ ነገር ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም: "እርሱ ለእነርሱ በጣም ቅርብ ነው።" ከእያንዳዳችን በዚህ ሥፍራ ላይ ጳውሎስ ራሱን፣ አድማጮቹን እና ሁሉንም ነገዶች በዚህ “እኛ” በሚለው ቃል ውስጥ አካቷል።

Acts 17:28

የሐዋርያት ሥራ **17**፡ **28**-**29**
ምክንያቱም በእርሱ "ምክንያቱም በእግዚአብሔር" እንኖራለን እንቀሳቀስማለን በዚህ ሥፍራ ላይ ጳውሎ አድማጮቹን ከራሱ ጋር ቀላቅሎ ይናገራል። እኛም የእርሱ ልጆች ነን በዚህ ሥፍራ ላይ “ልጆች” የሚለው ቃል የቅርብ ልጆች የሆኑትን የሚያመለክት አይደለም። ከቅድመ አያቶቻቸው ጋር የሚያመሳስላቸው ነገር አለ ማለት ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ “የእርሱ” የሚለው ቃል ማንን እንደሚያመለክት ግልጽ አይደለም። መለኮትነቱ በዚህ ሥፍራ ላይ “መለኮት” የሚለው ቃል የእግዚእሔር ባሕርይ የሚያመለክት ነው።

Acts 17:30

የሐዋርያት ሥራ **17**፡ **30**-**31**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ACT 17:22 ላይ የጀመረውን በአርዮስፋጎስ ለነበሩት ፈላስፎች ያደረገውን ንግግር ያጠናቅቃል። ስለዚህም ይህ ቃል ከዚህ በፊት በተነገረው ቃል ምክንያት የሚሆን ነገር የሚያሳይ ነው። ያለማወቅ አማራጭ ትርጉሞች 1) "ስለ አንድ ነገር እንዲሁ አለማወቅ" ወይም 2) "ሆን ብሎ አለመቀብል።" ዓለም በዚህ ሥፍራ ላይ “ዓለም” የሚለው ቃል በዓለም ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታል። በሰው አማካኝነት መረጦአል "በሰው አማካኝነት እግዚአብሔር መርጦዋአል" እግዚአብሔር በዚህ ሰው አማካኝነት አረጋግጧል "እግዚአብሔር ይህንን ሰው እንደመረጠው አሳይቷል"

Acts 17:32

የሐዋርያት ሥራ **17**፡ **32**-**34**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ይህ ጳውሎስ በአቴና ስለነበረው ቆይታ የሚተሪከው ክፍል ማብቂያ ነው። (ተመልከት: [[End of Story]]) የአቴና ሰዎች በአርዮስፋጎስ የነበሩትን እና ጳውሎስን እስከ አሁን ስሰሙት የቆዩት ሰዎች አንዳዶቹ ቀለዱበትl እነዚህ ሰዎች ሰው ከሞተ በኋላ ተመልሶ ወደ ሕይወት ይመጣል የሚለውን የማያምኑት ናቸው። አማራጭ ትርጉም: “አንዳንዶቹ በጳውሎስ ላይ ተሳለቁበት” ወይም “አንዳንዶቹ በጳውሎስ ላይ ሳቁበት።” እንሰማሃለን በዚህ ክፍል ውስጥ "እኛ" የሚለው ቃል ጳውሎስ የሚናገረውን ነገር ለመስማት ፍላጎት ያላቸውን የአቴና ሰዎችን ያመለክታል። እነዚህ ሰዎች በቀጥታ ለጳውሎስ ይናገሩት ነበር። ነገር ግን ጳውሎስን የእነርሱ ቡድን አድርገው አልተቀበሉትም ነበር። በአርዮስፋጎስ ያለው የፍርድ ቤት ፈራጅ ዲዮናስዮስ ደማሪስ የሚሉአትም አንዲት ሴት ዲያናስዮስ የአንድ ወንድ ስም ነው። Dionysius is a man's name. አርዮፓጌት የሚለው ቃል የሚያሳየው ዲዮናስዮስ በአርዮፋጎስ ፈራጅ የሆነውን ሰው ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **18**

1 ከዚህ በኋላ፣ ጳውሎስ ከአቴና ወደ ቆሮንቶስ ሄደ። **2** እዚያም ከጳንጦስ ወገን የሆነ አቂላ የሚባል አይሁዳዊ አገኘ። እርሱም አይሁድ ሁሉ ከሮም እንዲወጡ ቀላውዴዎስ ባዘዘው መሠረት፣ ከሚስቱ ከጵርቅላ ጋር በቅርብ ከኢጣሊያ የመጣ ሰው ነበር። ጳውሎስም ከእነርሱ ጋር ተቀራረበ። **3** ሥራቸው አንድ ዓይነት ስለ ሆነም፣ በእነርሱ ዘንድ እየኖረ ዐብሮአቸው ይሠራ ነበር። ሥራቸውም ድንኳን መስፋት ነበር። **4** በየሰንበቱም በምኵራብ ውስጥ በመገኘት እየተከራከረ፣ አይሁድንም ግሪኮችንም ያሳምን ነበር። **5** ሲላስና ጢሞቴዎስ ከመቄዶንያ እርሱ ወዳለበት በወረዱ ጊዜ ግን፣ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ ለአይሁድ እንዲመሰክር መንፈስ ቅዱስ ጳውሎስን ገፋፋው። **6** አይሁድ በተቃወሙትና በተሳደቡ ጊዜ፣ ጳውሎስ ልብሱን እያራገፈባቸው፣ «ደማችሁ በራሳችሁ ላይ ይሁን፤ እኔ ንጹሕ ነኝ፤ ከአሁን ጀምሮ ወደ አሕዛብ እሄዳለሁ» አላቸው። **7** ከዚያም ወጥቶ ቲቶ ኢዮስጦስ ወደሚባል፣ እግዚአብሔርን ወደሚያመልክ ሰው ቤት ሄደ። ቤቱም በምኵራብ አጠገብ ነበር። **8** ቀርስጶስ የተባለም የምኵራብ አለቃ ከቤተ ሰዎቹ ሁሉ ጋር በጌታ አመነ። ጳውሎስ ሲናገር ከሰሙት ከቆሮንቶስ ሰዎች መካከልም ብዙዎቹ አምነው ተጠመቁ። **9** ጌታም ሌሊት በራእይ ጳውሎስን እንዲህ አለው፤ "አትፍራ ተናገር፣ ዝምም አትበል። **10** ምክንያቱም እኔ ከአንተ ጋር አለሁ፤ ሊጎዳህ የሚነሣብህ ማንም የለም፤ እንዲያውም በዚህ ከተማ ብዙ ሰዎች አሉኝ።" **11** ጳውሎስም በመካከላቸው የእግዚአብሔርን ቃል እያስተማረ አንድ ዓመት ከስድስት ወር እዚያ ተቀመጠ። **12** ነገር ግን ጋልዮስ የአካይያ አገረ ገዢ በሆነ ጊዜ፣ አይሁድ በጳውሎስ ላይ በአንድነት ተነሡ፤ ይዘውም ፍርድ ፊት አቀረቡት። **13** ከዚያም፣ “ሕዝቡ እግዚአብሔርን እንዲያመልክ ይህ ሰው ከሕግ ውጪ እየቀሰቀሰ ነው” አሉ። **14** ጳውሎስ ሊናገር ሲልም፣ ጋልዮስ አይሁድን፣ “አይሁድ ሆይ፣ ጉዳዩ በርግጥ የበደል ወይም የወንጀል ቢሆን ኖሮ፣ ልታገሣችሁ በተገባኝ ነበር። **15** ነገር ግን ክርክሩ ስለ ቃላትና ስለ ስሞች፣ ደግሞም ስለ ገዛ ሕጋችሁ ስለ ሆነ፣ እናንተው ራሳችሁ ተነጋገሩበት። እኔ ስለ እንደዚህ ዐይነት ጉዳይ ፈራጅ መሆን አልፈልግም” አለ። **16** ከዚያም ጋልዮስም ከችሎቱ አስወጣቸው። **17** እነርሱ ሁሉ ግን የምኵራቡን አለቃ ሶስቴንስን በጉልበት ይዘው በፍርድ ወንበሩ ፊት ደበደቡት። ይሁን እንጂ፣ ይህ ድርጊታቸው ለጋልዮስ ደንታም አልሰጠውም። **18** ጳውሎስም ብዙ ቀናት ከተቀመጠ በኋላ፣ ወንድሞችን ተሰናብቶ ከጵርስቅላና ከአቂላ ጋር በመርከብ ወደ ሶርያ ሄደ። ስእለት ስለ ነበረበትም፣ ከወደቡ ከክንክራኦስ ከመነሣቱ በፊት ራሱን ተላጨ። **19** ኤፌሶን በደረሱ ጊዜ፣ ጳውሎስ ጵርስቅላንና አቂላን ትቶአቸው ወደ ምኵራብ ሄዶ ከአይሁድ ጋር ይነጋገር ነበር። **20** እነርሱም ረዘም ላለ ጊዜ ዐብሮአቸው እንዲቆይ ሲለምኑት፣ ጳውሎስ እንቢ አለ። **21** ከዚያም፣ “እግዚአብሔር ቢፈቅድ እንደ ገና ተመልሼ እመጣለሁ” ብሎ ተሰናበታቸው። ከኤፌሶንም ተነሥቶ በመርከብ ሄደ። **22** ጳውሎስ ቂሣርያ በደረሰ ጊዜ፣ በኢየሩሳሌም ወደ ነበረችው ቤተ ክርስቲያን ወጥቶ ሰላምታ አቀረበላቸውና ወደ አንጾኪያ ወረደ። **23** በዚያም ጥቂት ጊዜ ከተቀመጠ በኋላ፣ ጳውሎስ ተለያቸው፤ በገላትያና በፍርግያ አካባቢ በማለፍም ደቀ መዛሙርቱን ሁሉ አበረታታ። **24** ትውልዱ እስክንድርያዊ የሆነ፣ አጵሎስ የሚባል አንድ አይሁዳዊ ወደ ኤፌሶን መጣ፤ እርሱም የንግግር ችሎታና በቂ የቅዱሳት መጻሕፍት ዕውቀት ያለው ሰው ነበር። **25** አጵሎስ የጌታን ትምህርት በሚገባ የተማረ በመሆኑ፣ በመንፈሱ ተነቃቅቶ ስለ ኢየሱስ በትክክል ይናገርና ያስተምር ነበር፤ የሚያውቀው ግን ስለ ዮሐንስ ጥምቀት ብቻ ነበር። **26** አጵሎስ ምኵራብ ውስጥ በድፍረት መናገር ጀመረ። ነገር ግን ጵርስቅላና አቂላ በሰሙት ጊዜ፣ ወደ እርሱ ቀርበው የእግዚአብሔር መንገድ ይበልጥ በትክክል አብራሩለት። **27** እርሱም ወደ አካይያ ማለፍ በፈለገ ጊዜ፣ ወንድሞች አበረታቱት፤ በአካይያ የነበሩ ደቀ መዛሙርት እንዲቀበሉትም ጻፉላቸው። እዚያ በደረሰ ጊዜም፣ በጸጋ ያመኑትን እጅግ ረዳቸው። **28** አጵሎስ ከቅዱሳት መጻሕፍት እያስደገፈ፣ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ በማሳየት በኀይሉና በችሎታው አይሁድን ተከራክሮ ረታቸው።

Acts 18:1

የሐዋሪያት ሥራ **18**:**1**-**3**
አጠቃላይ መረጃ ይህ ከጳውሎስ የጉዞ ታሪኮች መካከል አንዱ ነው ፤በዚህ ጊዜ ጳውሎስ በቆሮንጦስ ከተማ ነው ያለው።በዚህ ታሪክ ውስጥ አቂላ እና ጵርስቅላ የተካተቱ ሲሆን ቁጥር 2 እና 3 ላይ ስለ እነርሱ የጀርባ ታሪክ መረጃ ተካቷል። ከዚህ በኋላ በአቴና ከተከናወነው ድርጊት (ሁኔታ) በኋላ በዚያ አገኘው ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉ አማራጮች:-1)በዚያ ጳውሎስ በድንገት አገኘው 2)በዚያ ጳውሎስ ሆነ ብሎ ፈልጎ አገኘው የጳንጦስ ተወላጅ ጳንጦስ በጥቁር ባህር ደቡባዊ ዳርቻ የምትገኝ አውራጃ ናት በቅርብ ጊዜ የመጣ ይህ ምን አልባት ባለፈው አመት ውስጥ ሊሆን ይችላል ቀላውዲዮስ አዘዘ ቀላውዲዮስ የሮም ንጉሰ ነገስት ነበር አይሁድን ሁሉ አዘዘ ትዕዛዝ ሰጠ ወይም መመሪያ አስተላለፈ።

Acts 18:4

የሐዋርያት ሥራ **18**:**4**-**6**
አጠቃላይ መረጃ ሲላስና ጢሞቲዎስ ከጳውሎስ ጋር እንደገና ተገናኙ ጳውሎስ አስረዳ (መሰከረ) በዚህ ቦታ አስረዳ (መሰከረ) የሚለው ቃል ጳውሎስ ሁለት አይነት ንግግሮችን እንዳዳረገ ያሳያል:: አማራጭ ትርጉም ጳውሎስ ተከራከረ ወይም ጳውሎስ ተወያየ አሳመነ አማራጭ ትርጉም:- ለማሳመን ጥረት አደረገ በመንፈስ ተገደደ አማራጭ ትርጉም:- መንፈስ ግድ አለው:: ልብሱን አራገፈ ይህ ድርጊት ጳውሎስ ከማያምኑ አይሁዳዊያን ጋር ያለውን ግንኙነት ያቋረጠበትን እና እነርሱን ለ እግዚያብሄር ፍርድ የተወበትን ሁኔታ የሚያሳይ ድርጊት ነው:: ደማችሁ በራሳችሁ ላይ ይሁን በዚህ ቦታ ደም የሚለው በሃጢት ምክንያት ከሚመጣ ቅጣት ጋር ይነፃፀራል:: ጳውሎስ አይሁዳዊያንን ንስሃ ካልገቡ በግትርነታቸው ምክንያት ለሚመጣባቸው የእግዚአብሄር ፍርድ ሃላፊነቱ የራሳቸው እንደሆነ ነገራቸው:: አማራጭ ትርጉም:- በሀጢያታችሁ ምክንያት የሚመጣውን ቅጣት የምትቀበሉት እናንተ ናችሁ::

Acts 18:7

ሐዋሪያት ሥራ **18**:**7**-**8**
ከዚያም ሄደ ከዚያም ጳውሎስ ሄደ

ቲቶስ ኢዩስጦስ- - - ቀርስጦስ አይሁዳዊያን አማኞች የምኩራቡ አለቃ ይህ ሰው ምንም ያልተማረ ሲሆን ስራው የምኩራቡን ወጪዎች መሸፈንና ምኩራቡን ማስተዳደር እንጂ የግድ አስተማሪ አይደለም:: ቤተሰቡ ሁሉ ዘመድ አዝማዱን ጨምሮ ከእርሱ ጋር የሚኖሩ ሁሉ ብዙ የቆሮንጦስ ሰዎች አይሁዳዊ ያልነበሩ የቆሮንጦስ ሰዎች

Acts 18:9

የሐዋርያት ሥራ **18**:**9**-**11**
አትፍራ ተናገር ዝምም አትበል ጌታ ቃሎቹ የበለጠ ሀይል ያላቸው እንዲሆኑ አንድን ትዕዛዝ በተለያየ መንገድ ተናገር ዝምም አትበል ጌታ ጳውሎስን እንዲናገር በሃይል እያዘዘው ነው:: አማራጭ ትርጉም:- መናገር አለብህ:: ዝም አትበል ስለ ወንጌል መናገር እንዳታቆም እኔ ነኝ እኔ የሚለው የሚወክለው (የሚያሳየው) ለጳውሎስ እየተናገረው ያለውን ጌታን ነው ከአንተ ጋር አንተ የሚለው የሚወክለው ጌታ በራዕይ እየተናገረው ያለውን ጳውሎስን ነው በዚህ ከተማ ብዙ ሰዎች አሉኝ በዚህ ከተማ እምነታቸውን በእኔ ላይ ያደረጉ ብዙ ሰዎች አሉኝ ጳውሎስ በዚያ ኖረ- - - የእግዚያብሄርን ቃ በመካከላቸው እያስተማረ (ተመልከት: [[End of Story]])

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Acts 18:12

የሐዋርያት ሥራ **18:12-13**
አጠቃላይ መረጃ ይህ በታሪኩ ውስጥ አዲስ ድርጊት ነው ፤ ጳውሎስን በጋልዮስ የፍርድ ወንበር ፊት አቀረቡት ጋልዩስ የአካይያ ገዥ ነበር አካይያ ቆሮንጦስን የምታካትት የሮምያውያን አውራጃ ስትሆን የአሁኑ ጊዜ ደቡባዊ ግሪክ ናት። በፍርድ ወንበር ፊት አቀረቡት አይሁዳዊያን ጳውሎስን በሃይል(ሃይልተጠቅመው) ፍርድ ቤት አቀረቡት።አማራጭ ትርጉም:- በአገረ ገዥው እንዲፈረድበት ወሰዱት ህጉ በማይፈቅደው መንገድ አይሁዳዊያን ሆነ ብለው የሚከሱት ያደረገው ነገር (የተናገረው ነገር) ከህጋቸው እና ከልምዳቸው የተፃረረ በመሆኑ ከሮም ህግ አንፃር ወንጀል ነው ብለው ነው።

Acts 18:14

የሐዋርያት ሥራ **18:14-15**
ጋልዮስ እንዲህ አለ ጋልዮስ በአውራጃው ላይ የተሾመ የሮም ገዢ ነው ህጋችሁ(የእናንተ ህግ) እነዚህ የሙሴን ህግና በጳውሎስ ዘመን የነበሩ የአይሁዳዊያን ልማዶችን ያካትታሉ እኔ በእንዲህ አይነት ነገር ፈራጅ መሆን አልሻም እኔ እንዲህ ባሉ ጉዳዩች ላይ መፍረድ አልፈልግም።

Acts 18:16

የሐዋርያት ሥራ **18:16-17**
ሁሉም ያዙት ይህ የግነት አገላለፅ የሕዝቡን ሃይለኛ ስሜት ለመግለፅ የገባ ነው።።አማራጭ ትርጉም:- ብዙ ሰዎች በጉጉት ያዙት ወይም አብዛኞቹ ያዙት። ሶስቴን የምኩራብ አለቃ ሶስቴን በቆሮንጦስ ያለው የአይሁድ ምኩራብ አለቃ ነበረ። መቱት (ደበደቡት) ሶስቴን አካላዊ ድብደባ ደርሶበታል። አማራጭ ትርጉም:- መቱት ወይም በቡጢ መቱት።

Acts 18:18

የሐዋርያት ሥራ **18:18-19**
አጠቃላይ መረጃ ጳውሎስ ከጵርስቅላና አቂላ ጋር ቆሮንጦስን ለቆ በመውጠት ጉዞውን ቀጠለ ወንድሞች ወንድሞች የሚለው ቃል አማኝ የሆኑ ሴቶችን እና ወንዶችን የሚገልፅ ነው ከጵርስቅላ እና አቂላ ጋር ወደ ሶሪያ በመርከብ ሄዱ ጳውሎስ በመርከብ ወደ ሶሪያ ሄደ።።ጵርስቅላ እና አቂላም ከእርሱ ጋር ነበሩ ክንክራኦስ የባህር ወደብ ክንክራኦስ የታላቋ ቆሮንጦስ ከተማ አካል የሆነች የባህር ወደብ ናት። ስዕለት ይህ በሙሴ ህግ ላይ የተገለፀ እና ለእግዚያብሄር አንድ ነገር ለማድረግ ቃል መግባትን ወይም መሃላን የሚያሳይ ነው።።ይህም ከሌዊ ነገድ ውጪ የሆኑ ሰዎች እግዚያብሄርን እንዲያገለግሉ መንገድ ይከፍታል። ወደ ኤፌሶን ሲደርሱ ጳውሎስ፣ጵርስቅላ እና አቂላ ኤፌሶን ሲደርሱ። አስረዳ ተወያየ ወይም ተከራከረ

Acts 18:20

የሐዋርያት ሥራ **18:20-21**
ጠየቁት አይሁዳዊያን ጠየቁት ሲለያቸው ሲሰናበታቸው

Acts 18:22

የሐዋሪያት ሥራ **18:22-23**
ቂሳሪያ በደረሰ ጊዜ ቂሳሪያ ደረሰ ወጥቶ ሄደ (ወደ ላይ ሄደ) ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ ተጓዘ በኢየሩሳሌም ለምትገኘው ቤተክርስቲያን ሰላምታ አቀረበ በኢየሩሳሌም ባለችው ቤተክርስቲያን ላሉ ምዕመናን ሰላምታ አቀረበ ወደታች ወረደ አይሁዳዊያን ወደ እየሩሳሌም መሄድን ወደ ላይ እንደመሄድ ሲቆጥሩት ከእየሩሳሌም መራቅን ወደታች እንደመሄድ (እንደመውረድ) ይቆጥሩታል። ጳውሎስ ተለያቸው ጳውሎስ ወደ ሌላ ቦታ ሄደ ገላቲያ እና ፍርጊያ በእሲያ የሚገኙ አውራጃዎች የነበሩ ሲሆን በአሁኔ ጊዜ ቱርክ የምትባለው አገር ናት።

Acts 18:24

የሐዋርያት ሥራ **15:27-29**
የሐዋርያት ሥራ 15:27-29 አጠቃላይ መረጃ አጵሎስ በታሪኩ ውስጥ የተካተተ ሲሆን ቁጥር 24 እና 25 ላይ ስለ እርሱ የጀርባ ታሪክ የእስክንድሪያ ተወላጅ የሆነ አማራጭ ከተሞች 1, በሰሜናዊ ዳርቻ በግብጽ የምትገኘው እስክንድርያ 2, በምዕራብ ዳርቻ በእሲያ የምትገኘው እስክንድሪያ። አማራጭ ትርጉም:- በእስክንድሪያ ከተማ የተወለደ ሰው ነው። አንደበተ ርዕቱ ጎበዝ ተናጋሪ በመንፈስ የተቃጠለ በሙሉ ልቡ የሚቀናና የሚያስተምር ነበር የዮሐንስ ጥምቀት መጥምቁ ዮሐንስ የሚያጠምቀው ጥምቀት ይበልጥ በተስተካከለ ሁኔታ በተሟላ ሁኔታ

Acts 18:27

የሐዋርያት ሥራ **18 : 27-28**
በፈለገ ጊዜ አጵሎስ በፈለገ ጊዜ አካይያ በደረሰ ጊዜ አካይያ የሮሜ አውራጃ ስትሆን በአሁኑ ጊዜ የደቡባዊ ግሪክ ክልል ናት። አማራጭ ትርጉም:- ወደ አካይያ ክልል በሄደ ጊዜ ወንድሞች እዚህ ቦታ ወንድሞች የሚለው ቃል አማኝ የሆኑ ወንዶችና ሴቶችን ነው ለደቀመዛሙርት ጻፉለት አካይያ ለሚገኙ ክርስትያኖች ደብዳቤ ጻፉለት በደረሰ ጊዜ አጵሎስ በደረሰ ጊዜ አጵሎስ በህዝብ ፊት ረታ አጵሎስ በሕዝብ ፊት አይሁዳዊያዊያንን በክርክሩ ረታቸው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 19

1 አጵሎስ በቆሮንቶስ በነበረ ጊዜ፣ ጳውሎስ በላይኛው አገር አድርጎ ወደ ኤፌሶን ከተማ መጣ፤ በዚያም አንዳንድ ደቀ መዛሙርትን አገኘ። 2 ጳውሎስም፣
“ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀብላችኋል?” አላቸው። እነርሱም፣ “አልተቀበልንም፤ እንዲያውም መንፈስ ቅዱስ መኖሩን አልሰማንም” አሉት። 3
ጳውሎስም፣ “ታዲያ፣ በምን ተጠመቃችሁ?” አላቸው። እነርሱም፣ “የተጠመቅነው በዮሐንስ ጥምቀት ነው” አሉት። 4 ጳውሎስም መልሶ፣ “ዮሐንስ
ያጠመቀው በንስሓ ጥምቀት ነው። ሰዎች ከእርሱ በኋላ በሚመጣው፣ በኢየሱስ ማመን እንደሚገባቸውም ነገራቸው” አለ። 5 ሕዝቡ ይህን ሲሰሙ፣ በጌታ
ኢየሱስ ስም ተጠመቁ። 6 ጳውሎስም እጆቹን በሰዎቹ ላይ በጫነ ጊዜ፣ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው፤ እነርሱም በልዩ ቋንቋ መናገርና መተንበይ ጀመሩ። 7
ቊጥራቸውም ዐሥራ ሁለት ያህል ነበረ። 8 ጳውሎስ ከዚህ በኋላ ወደ ምኵራብ እየገባ ሦስት ወር ያህል በድፍረት ይናገር ነበር፤ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት
እየገለጠ ሰዎችን ያስረዳ ነበር። 9 አንዳንድ አይሁድ ግን ልባቸውን አደንድነው በመቃወም፣ በሕዝቡ ፊት የክርስቶስን መንገድ ተሳደቡ፤ ስለዚህ ጳውሎስ
ትቶአቸው ሄደ፤ ያመኑትንም ከእነርሱ አራቀ። ጢራኖስ በሚባል የትምህርት አዳራሽም በየዕለቱ ንግግር ያደርግ ጀመር። 10 ይህም፣ በእስያ የሚኖሩ አይሁድና
ግሪኮችም ሁሉ የጌታን ቃል እስኪሰሙ ድረስ፣ ሁለት ዓመት ቀጠለ። 11 እግዚአብሔር በጳውሎስ እጅ ታላላቅ ተአምራትን ያደርግ ነበር፤ 12 ስለዚህ የጳውሎስ
አካል የነካው ጨርቅ ወይም መሐረብ ሲወሰድ፣ የታመሙት ይፈወሱ፣ አጋንንትም ከሰዎች ይወጡ ነበር። 13 አጋንንት እናስወጣለን እያሉ ከቦታ ቦታ የሚዞሩ
አይሁድ ነበሩ፤ እነርሱም የኢየሱስን ስም ለገዛ ጥቅማቸው ለማዋል፣ በክፉ መናፍስት ላይ እየጠሩ፣ “እንድትወጡ ጳውሎስ በሚሰብከው በኢየሱስ
እናዛችኋለን” ይሉ ነበር። 14 ይህን ያደረጉትም የአይሁድ የካህናት አለቃ የነበረው የአስቄዋ ሰባት ወንድ ልጆች ነበሩ። 15 ክፉው መንፈስም፣ “ኢየሱስን
ዐውቀዋለሁ፤ ጳውሎስንም ዐውቃለሁ፤ ለመሆኑ እናንተ እነማን ናችሁ?” ብለው መለሱላቸው። 16 ክፉ መንፈስ ያለበትም ሰው ዘሎ ያዛቸው፤ አሸንፏቸውም
ደበደባቸው። ከዚያም ቤት ቄስለው ዕራቁታቸውን ሸሹ። 17 ይህም በኤፌሶን ይኖሩ በነበሩ አይሁድና ግሪኮችም ዘንድ ሁሉ ታወቀ። እነርሱም ሁሉ በፍርሀት
ተዋጡ፤ የጌታ ኢየሱስም ስም ተከበረ። 18 ደግሞም ካመኑት ብዙዎቹ መጥተው ቀደም ሲል ያደረጉትን ክፉ ነገር ሳይሸሽጉ ይናዘዙ ነበር። 19 አስማተኞችም
የጥንቈላ መጻሕፍታቸውን ሰብስበው እያመጡ በሰው ሁሉ ፊት አቃጠሉ፤ ዋጋቸውም ሲተመን ሃምሳ ሺህ ብር ሆነ። 20 በዚህም መሠረት የጌታ ቃል በስፋትና
በኀይል ተሠራጨ። 21 ጳውሎስ በኤፌሶን የነበረውን አገልግሎቱን ከፈጸመ በኋላ፣ በመቄዶንያና በአካይያ አድርጎ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ በመንፈስ ቅዱስ
ሆኖ ወሰነ፤ ደግሞም፣ “እዚያ ከደረስሁ በኋላም፣ ሮሜን ማየት ይገባኛል” አለ። 22 ሲረዱት ከነበሩት ደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን፣ ጢሞቴዎስንና ኤርስጦንን ወደ
መቄዶንያ ላካቸው። እርሱ ራሱ ግን ጥቂት ጊዜ በእስያ ቆየ። 23 በዚህ ጊዜ የጌታን መንገድ በተመለከተ በኤፌሶን ትልቅ ሁከት ተነሣ። 24 ድሜጥሮስ
የሚባል አንድ ብር ሠሪም የዲያናን ምስል ከብር እያበጀ ለአንጥረኞች ትልቅ ገቢ ያስገኝላቸው ነበር። 25 ስለዚህ በዚህ ሙያ ላይ የተሰማሩትን ብዙ ሠራተኞች
አንድ ላይ ሰብስቦ፣ “ሰዎች ሆይ፤ በዚህ ሙያችን ብዙ ገንዘብ እንደምናገኝ ታውቃላችሁ። 26 ይህ ጳውሎስ በኤፌሶን ብቻ ሳይሆን፣ ከብዙ በጥቂቱ በእስያ ሁሉ
አብዛኛውን ሕዝብ በቃላት እያባበለ ከእኛ ማራቁን እያያችሁና እየሰማችሁ ነው። በእጅ የሚሠሩ አማልክት የሉም እያላቸው ነው። 27 የእኛ ሞያዊ ጥበብ
አላስፈለጊ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ የታላቅዋ አምላክ የዲያና ቤተ መቅደስም እንደ ከንቱ ነገር የመቍጠር አደጋ ያሠጋል፤ እስያ ሁሉና ዓለሙ የሚያመልካት ይህች
አምላክም ዝናዋን ታጣለች።” 28 ሕዝቡም ይህን በሰሙ ጊዜ፣ በቊጣ ተሞልተው፣ “የኤፌሶንዋ ዲያና ታላቅ ናት” እያሉ ጮኹ። 29 ከተማው ሁሉ ድብልቅልቁ
ወጣ፤ ሕዝቡም በአንድ ላይ ገንፍለው ወደ ቲያትር ማሳያው ቦታ ገቡ። ከመቄዶንያ የመጡትንም የጳውሎስን የጒዞ ባልደረቦች፣ ጋይዮስንና አርስጥሮኮስን
ያዙአቸው። 30 ጳውሎስ ወደ ሕዝቡ ሊደባለቅ ፈልጎ ነበር፤ ደቀ መዛሙርቱ ግን ከለከሉት። 31 ደግሞም፣ የጳውሎስ ወዳጆች የነበሩ አንዳንድ የአካባቢ ሹሞች
ጳውሎስ ወደ ቲያትር ማሳያ ቦታ እንዳይገባ መልእክት ላኩበት። 32 ሕዝቡ ሁሉ ግራ ተጋብቶ ነበርና፣ አንዳንዶቹ ስለ አንድ ነገር ሲጮኹ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ስለ
ሌላ ነገር ይጮኹ ነበር። አብዛኛዎቹ ደግሞ ለምን ተሰብስበው እንደ ወጡ እንኳ አያውቁም ነበር። 33 አይሁድም እስክንድሮስን ገፋፍተው ወደ ሕዝቡ ፊት
አወጡት። እስክንድሮስ ለሕዝቡ በእጅ ምልክት እያሳየ ሊያስረዳቸው ሞከረ። 34 ሕዝቡም አይሁዳዊ መሆኑን በተረዱ ጊዜ ሁሉም በአንድ ድምፅ፣ “የኤፌሶንዋ
ዲያና ታላቅ ናት” እያሉ ለሁለት ሰዓት ያህል ጮኹ። 35 የከተማዋ ጸሓፊ ሕዝቡን ዝም ካሰኘ በኋላ፣ እንዲህ አለ፤ “እናንተ የኤፌሶን ሰዎች ሆይ፣ የኤፌሶን
ከተማ የታላቅዋ ዲያና ቤት መቅደስና ከሰማይ የወረደው ምስል ጠባቂ መሆንዋን የማያውቅ የትኛው ሰው ነው? 36 እንግዲህ ይህ የማይካድ ነገር መሆኑ
ከታያችሁ፣ ጸጥ ልትሉ፣ አንዳች ነገርም በችኰላ ልታደርጉ አይገባም፤ 37 ምክንያቱም አብያተ መቅደስን ያልሰረቁ፣ አማልክታችንንም ያልሰደቡ እነዚህን ሰዎች
ወደዚህ ፍርድ ቤት አምጥታችኋል። 38 ስለዚህ ድሜጥሮስና ከእርሱ ጋር ያሉ አንጥረኞች የሚከሱት ሰው ካለ፣ ፍርድ ቤቱ ክፍት ነው፤ ዳኞችም አሉ፤ እዚያ
እርስ በርስ ይካሰሱ። 39 ስለ ሌላ ጒዳይ የምትፈልጉት ነገር ካለ ግን፣ ችግሩ በመደበኛው ጉባኤ ይፈታል፤ 40 ምክንያቱም በዛሬው ቀን የነበረው ዐመፅ
ሳያስጠይቀን አይቀርም። የነበረው ግርግር መንሥኢ የለውም፤ እንዲህ ነው ብለን ልንገልጸውም አንችልም።” 41 ጸሓፊው ይህን ተናግሮ ጉባኤውን አሰናበተው።

Acts 19:1

የሐዋርያት ሥራ **19**:**1-2**
አጠቃላይ መረጃ ይህ የጳውሎስ የጉዞ ታሪክ ሌላኛው ክፍል ነው፤ ጳውሎስ በዚህ ጉዞ ያለው በኤፌሶን ነው። እንዲህም ሆነ “ተከሰተ” በዚያ አለፈ በዚያ ተጓዘ የላኛው አገር ይህ የእስያ አካባቢና የአሁኑ ጊዜ ቱርክ ሲሆን የኤፌሶን እና የእስክንድርያ… መንፈስቅዱስን መቀበል መንፈስቅዱስን ማግኘት ስለ መንፈስቅዱስ ምንም አልሰማንም ስለ መንፈስቅዱስ የሰማነው ነገር የለም

Acts 19:3

የሐዋርያት ሥራ **19**:**3-4**
አያያዥ ዓረፍ ነገር ጳውሎስ በኤፌሶን ከሚገኙ አዲስ አማኞች ጋር ውይይቱን(ንግግሩን) ቀጠለ ታዲያ በምን ተጠመቃችሁ? በማን ጥምቀት ተጠመቃችሁ? ወይም በማን ስም ተጠመቃችሁ? እንዲህ አሉ ደቀመዛሙርት እንዲህ አሉ በመጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት በመጥምቁ ዮሓንስ የውሃ ጥምቀት የንስሐ ጥምቀት ይህ ጥምቀት ሰዎች ከሃጢያታቸው መመለስ ሲፈልጉ የሚጠመቁት ጥምቀት ነው ከእርሱ በኋላ በሚመጣው ይህ ማለት ከጊዜ አንጻር ከመጥምቁ ዮሐንስ በኋላ የሚመጣ ነገር ግን በአካል እርሱን የማይከተል ነው።

Acts 19:5

የሐዋርያት ሥራ **19**:**5-7**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር) ይህ በኤፌሶን ስላሉት አዳዲስ አማኞች የነበረው ታሪክ መጨረሻ ነው ሰዎቹ ሰዎቹ የሚገልጸው ከጳውሎስ ጋር በመነጋገር ላይ የነበሩትን አማኞች ነው እጁን ጫነነባቸው እየጸለየላቸው እጆቹን በጭንቅላታቸው ላይ ጫነባቸው በሌሎች ቋንቋዎች ተናገሩ ፤ ትንቢትም ተናገሩ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ በ ACT 2:3-4 ላይ ደጸገለጸው ሳይሆን በዚህ ሥፍራ ላይ የተናገሩትንም መልዕክት ትርጉም ማን እንደሰማ (

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንደተረዳ) በግልጽ የተጻፈ የለም በአጠቃላይ ሰዎቹ 12 ያክሉ ነበር ይህ የተጠመቁ ሰዎች አጠቃላይ መረጃ ነው።

Acts 19:8

የሐዋርያት ሥራ **19**: **8-10**
ጳውሎስ ወደ ምኩራብ ገብቶ ለሶስት ወራት ያህል በግልጥ አስተማረ አማራጭ ትርጉም: ጳውሎስ ለሶስት ወራት በየቀኑ (በየጊዜው) በምኩራብ የሚደረጉ ጉባኤዎችን በመካፈል በዚያ ቦታ በድፍረት ይናገር ነበር ሰዎችን እያሳመነ እየተናገረ ስለነበርው እውነት ሰዎችን ለማሳመን ሞከረ ክፉ ነገርን መናገር መጥፎ ንግግሮችን (ነገሮችን) መናገር የክርስቶስ መንገድ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ያለ ደኅንነት በእሲያ የሚኖሩ ሁሉ ሰሙ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉ አማራጮች 1 ጳውሎስ በመላው እሲያ ለሚኖሩ ብዙ ሰዎች ወንጌልን መሰከረ ወይም 2 የጳውሎስ መልዕክት ከመላው እሲያ ወደ ኤፌሶን በሚመጡ ሰዎች አማካኝነት ወደ ሁሉም የእሲያ አካባቢዎች ተዳረሰ።

Acts 19:11

የሐዋሪያት ሥራ **19**: **11-12**
በጳውሎስ እጅ በጳውሎስ በኩል ከጳውሎስ ልብስ ዘርፍና ከመጠምጠሚያው ጫፍ ሲወስዱ አማራጭ ትርጉም : በጳውሎስ የተነኩ የልብስ ዘርፎችና የመጠምጠሚያ ጫፎች በድዊያን ወይም በታመሙ ሰዎች ላይ ሲደረጉ።

Acts 19:13

የሐዋሪያት ሥራ **19**: **13-14**
አጠቃላይ መረጃ ይህ ክፍል ጳውሎስ በኤፌሶን ሳለ ርኩስ መንፈስን በሚያስወጡ አይሁዳዊያን ሰዎች ላይ የተከሰተ ሁኔታ ነው ርኩስ መንፈስ የሚያስወጡ ከሰዎች ወይም ከአካባቢያቸው ርኩስ መንፈስን የሚያባርሩ የኢየሱስን ስም ለግል ጥቅማቸው አዋሉት ወይም ተጠቀሙት ምንም እንኳን በኢየሱስ ባይምኑም የኢየሱስን ስም አስማት በመስራት ከሚጠቀሙባቸው ቃላት እንደ አንዱ ለመጠቀም ሞከሩ እርኩስ መንፈስ ያለባቸው በርኩስ መንፈስ ተጽዕኖ ሰር የነበሩ።

Acts 19:15

የሐዋርያት ሥራ **19**: **15-17**
ኢየሱስን አውቀዋለሁ፤ ጳውሎስን አውቀዋለሁ ኢየሱስንና ጳውሎስን አውቃቸዋለሁ ወይም ስለ ኢያሱስን ስለ ጳውሎስ ሰምቻለሁ

እነማን ከመንፈሱ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው አስማተኞቹ በርኩስ መንፈስ ላይ ስልጣን እንዳላቸው ለማረጋጋጥ ነው።
አማራጭ ትርጉም: ምን ስልጣን አላቹ ወይም ምንም አይነት ስልጣን ያላቹም አስማተኞች በ ACT 19:13 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምክ ተመልከት።
ራቁታቸውን ሸሹ አስማተኞቹ በክፈል ወይም በአጠቃላይ ተራቁተው ሸሹ እነርሱ በጣም ፈሩ በኤፌሶን የሚኖሩ አይሁዳዊያንና ግሪካዊያን በጣም ፈሩ።

Acts 19:18

የሐዋርያት ሥራ **19**: **18-20**
አያያዥ ዓረፍ ነገር ይህ አይሁዳዊያኑ አስማተኞች ታሪክ የመጨረሻ ክፍል ነው። (ተመልከት: [[End of Story]]) መጽሐፍቶቻቸውን ሰበሰቡ መጽሐፍት አስማታዎ ድግምቶችና መመሪያዎች የተጻፈባቸው ጥቅልሎች ናቸው ሁሉም እያዩ በሰው ሁሉ ፊት የብር ሳንቲሞች አንድ የብር ሳንቲም ለአንድ የጉልበት ሰራተኛ ቀን ደሞዙ ነበር የጌታ ቃል በሐይልና በስፋት ተሰራጨ ስለ ጌታ የሚነገረው መልዕክት በጣም በተሳካ ሁኔታ መሰራጨትና ተጽዕኖ ማምጣት ጀመረ።

Acts 19:21

የሐዋርያት ሥራ **19**: **21-22**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ጳውሎስ ወደ እየሩሳሌም ለመሄድ መወሰኑን ተናገረ ነገር ግን ከኤፌሶን ገና አልወጣም ጳውሎስ አገልግሎቱን ፈጸመ (ጨረሰ) ጳውሎስ እግዚአብሔር በኤፌሶን እንዲሰራ የሰጠውን ስራ ጨረሰ በመንፈስ ሆኖ ወሰነ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉ አማራጮች 1 ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ወሰነ ወይም 2 መንፈስ ጳውሎስን ወደ ውሳኔ መራው ሜቄዶኒያ እና አካያ እነዚህ አውራጃዎች የአሁኑ ጊዜ ግሪክ የሚባላው ቦታ ናቸው ሮሜን አይ ዘንድ ይገባኛል ወደ ሮሜ መሄድ አለብኝ ነገር ግን ራሱ ለጥቂት ጊዜ በእሲያ ቆየ በቀጣዮቹ ጥቂት ቁጥሮች ውስጥ ጳውሎስ በኤፌሶን እንደቆየ

Acts 19:23

የሐዋርያት ሥራ **19**: **23-25**
አጠቃላይ መረጃ ይህ ታሪክ ጳውሎስ በኤፌሶን እያለ ስለተከሰተው የህዝብ አመጽ ጅማሬ ነው :: ድሜጥሮስ በዚህ ታሪክ ውስጥ ተካቷል ታላቅ ሁከት የህዝብ አመጽ ሊቀሰቀስ ያለበት ሁኔታ መንገዱ ይህ ቃል ክርስትናን ለመግለጽ ጥቅም ላይ ይውል ነበር አንጥረኛ አንጥረኛ የእጅ ሙያ ያለው ብርን በማቅለጥ የሀውልት ቅርጽና ጌጣጌጥ የሚሰራ ሰው ነው ድሜጥሮስ የሚባል ድሜጥሮስ በኤፌሶን የሚኖር አንጥረኛ ሲሆን ጳውሎስንና በኤፌሶን የምትገኘውን አጥቢያ ቤተክርስቲያንን ይቃወም ነበር። በብር ሀውልቶችን የሚሰራ...ለአንጥረኞችም ብዙ ትርፍ የሚያስገኝ ይህ ስለ ድሜጥሮስ የጀርባ ታሪክ ነው። አርጤምስ ምስል ትልቁ የአርጤምስ ቤተመቅደስ በኤፌሶን ይገኝ ነበር። ብዙ ትርፍ አስገኘ በአርጤምስ ምስል የተሰሩ ብዙ ሐውልቶችን ሸጠ።

Acts 19:26

የሐዋርያት ሥራ **19**: **26-27**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ድሜጥሮስ ለአንጥረኞች መናገሩን ቀጠለ አይታችኋል ሰምታችሁማል አውቃችኋል ተረድታችሁማል ብዙ ሰዎችን አስቷል ብዙ ሰዎችን ጣኦትን እንዳያመልኩ እና ወደ ክርስቶስ እንዲመለሱ አሳምኗቿል ታላቅነቷንም ልታጣ ትችላለች የአርጤምስ ታላቅነት ሰዎች ስለሷ ከሚያስቡት የሚመነጭ ነው መላው እሲያና አለሙም ሁሉ የሚያመልካት ይህ የአርጤምስን ታዋቂነት ለማሳየት ጥቅም ላይ የዋለ ግነት ነው። አማራጭ ትርጉም:- በእሲያና በመላ አለም ብዙ ህዝብ የሚያመልካት ናት።

Acts 19:28

የሐዋርያት ሥራ **19** : **28-29**
ሲሰሙ አንጥረኞቹ ሲሰሙ ቁጣ ሞላባቸው በጣም ተቆጡ ጮሁ በታላቅ ድምጽ እየጮሁ ተናገሩ ህዝቡም በአንድነት ተጣደፉ ይህ የህዝብ አመጽ የሚያሳይ ሁኔታ ነው ወደ ጫወታ ቦታ (የቲያትር ቦታ) የኤፌሶን የጫዎታ ቦታ ለህዝብ ስብሰባና ለመዝናኛ የሚሆኑ ድራማዎችንና ሙዚቃዎችን ለማቅረብ ጥቅም ላይ ይውላል እነርሱም የጳውሎስን ጓደኞች ያዙዋቸው ህዝቡም የጳውሎስን ጓደኖች ያዙዋቸው ጋይዮስ እና አርስጥሮኮስ እነዚህ የሰዎች ሰሞች ናቸው ከሜቄዶኒያ የመጡ ጋይዮስ እና አርስጥሮኮስ ከሜቄዶኒያ ቢመጡም በዚህ ሰዓት ከጳውሎስ ጋር በኤፌሶን እየሰሩ ነበር።

Acts 19:30

የሐዋርያት ሥራ **19**: **30-32**
የጫዎታ ቦታ በግማሽ ክብ ቅርጽ የተሰራና በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን መያዝ (ማስቀመጥ) የሚችሉ መቀመጫዎች ያሉት ቦታ ነው።

Acts 19:33

የሐዋርያት ሥራ **19**: **33-34**
አይሁዳዊያን እስክንድሮስን አመጡት ጳውሎስ ጢሞቲዎስን የመዳብ ሰራተኛ ስለነበረው ስለ እስክንድሮስ አስጠንቅቆት ነበር (2 ጢሞቲዎስ 2TI 4:14)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በእጁ ጠቀሰ ወይም ገለጸ ለህዝቡ ምልክት አሳየ ማብራሪያ ሰጠ ለሟገትላቸው ፈልጎ ነበር ነገር ግን ምን ማለት እንደፈለገ ግልጽ አይደለም

Acts 19:35

የሐዋርያት ሥራ **19**፡ **35**-**37**
አጠቃላይ መረጃ የከተማይቱ ጸሐፊ ህዝቡን ተናገረ እናንተ የኤፌሶን ሰዎች እናንተ የሚለው የሚያመለክተው በዚያ ቦታ የተገኙትን የኤፌሶን ሰዎችን ነው። የኤፌሶን ከተማ ለታላቂቷ አርጤምስ ከሰማይም ለወረደው ጣኦቷ የመቅደስ ጠባቂ መሆኗን የማያውቅ ሰው ማነው? ጸሃፊው ይህንን ጥያቄ የጠየቀው ህዝቡ ትክክል እንደሆኑ ለማረጋገጥና ሊያረጋጋቸው ፈልጎ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- የኤፌሶን ከተማ ለታላቂቷ አርጤምስ ከሰማይም ለወረደው ጣኦቷ የመቅደስ ጠባቂ እንደሆነች ሁሉም ሰው ያውቃል። መቅደስ ጠባቂ የኤፌሶን ሰዎች የአርጤምስን መቅደስ ጠብቀው አቆይተዋል ከሰማይ የወረደው ምስሏ በአርጤንስ ቤተመቅድስ ውስጥ በቀጥታ ከዛስ በጣ ተብሎ በሚታመን ድንጋይ የተሰራ የጣኦት ምስል ይገኛል;;

Acts 19:38

የሐዋርያት ሥራ **19**:**38**-**41**
አያያዥ ጽሁፍ የከተማው ጸሃፊ ለህዝቡ ሚያደርገውን ንግግግር ጨረሰ ስለዚህ ይህ ቃል የሚያገለግለው ቀደሞ በተባለ ነገር ምክንያት የሚባልን ሌላ ነገር ለመግለፅ ነው;; በዚህ ጊዜ ይህ ቃል የሚያመለክተው ድሜጥሮስ ጋይዬስና አርስጥሮኮስ ሌቦችና ተሳዳቢዎች አይደሉም ብሎ የተናገረውን ACT 19:37 ነው። አገረ ገዢ ይህ በሮሜ አውራጃ ላይ የተሸመ አስተዳዳሪ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **20**

1 ሁከቱ ካበቃ በኋላ፣ ጳውሎስ ደቀ መዛሙርቱን አስጠርቶ አበረታታቸው። ከዚያም ተሰናበታቸውና ወደ መቄዶንያ ለመሄድ ተነሣ። **2** በእነዚያም አካባቢዎች እያለፈ ያመኑትን እጅግ ካበረታታ በኋላ፣ ወደ ግሪክ ገባ። **3** በዚያም ሦስት ወር ከቈየ በኋላ፣ ወደ ሶርያ በመርከብ ለመሄድ እያሰበ ሳለ፣ አይሁድ አሤሩበት፤ ስለዚህ በመቄዶንያ አድርጎ ለመመለስ ወሰነ። **4** እስከ እስያ የሸኙትም የቤርያው ሱሲጳጥሮስ፣ ከተሰሎንቄ የመጡት አርስጥሮኮስና ሲኮንዱስ፣ የደርቤኑ ጋይዮስ፣ ጢሞቴዎስ፣ እንዲሁም ከእስያ የመጡት ቲኪቆስና ጥሮፊሞስ ነበሩ። **5** እነዚህ ሰዎች ግን ቀድመውን በጢሮአዳ ጠበቁን። **6** እኛም ከቂጣ በዓል ቀን በኋላ፣ ከፊልጵስዩስ በመርከብ ተነሥተን በዐምስት ቀን ውስጥ ጢሮአዳ ደረስንባቸው፤ እዚያም ሰባት ቀን ተቀመጥን። **7** በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን እንጀራ ለመቍረስ በተሰበሰብን ጊዜ፣ ጳውሎስ ለምእመናኑ ንግግር አደረገ። በሚቀጥሉት ቀናት ለመሄድ ዐቅዶ ስለ ነበረ፣ እስከ እኩለ ሌሊት መናገሩን ቀጠለ። **8** በተሰበሰብንበትም ሰገነት ላይ ብዙ መብራቶች ነበሩ። **9** አውጤኪስ የሚባል ወጣትም በመስኮት ተቀምጦ ሳለ፣ እንቅልፍ ጭልጥ አድርጎ ወሰደው። ጳውሎስ ንግግሩን ባስረዘመ ጊዜ፣ ይህ ወጣት ገና ተኝቶ እንዳለ ከሦስተኛው ፎቅ ወደቀ፤ ሲያነሡትም ሞቶ ነበር። **10** ጳውሎስ ግን ወርዶ በላዩ ተዘረጋበት፣ ዐቀፈውም። ከዚያም፣ “በሕይወት ስላለ ከዚህ በኋላ አትታወኩ” አለ። **11** እንደ ገናም በደረጃ ወደ ላይ ወጣ፤ እንጀራ ቈርሶም በላ። እስኪነጋ ድረስም ለረዥም ጊዜ ከእነርሱ ጋር ከተነጋገረ በኋላ፣ ተለይቶአቸው ሄደ። **12** ወጣቱንም በሕይወት እያለ አመጡት፤ በዚህም እጅግ ተጽናኑ። **13** እኛም ራሳችን ጳውሎስን በመርከብ ለማሳፈር ወዳሰብንበት ወደ አሶን ቀድመን በመርከብ ሄድን። እርሱም ያሰበው ይህንኑ ነበር፤ በመርከብ ለመሄድ ዐቅዶ ነበርና። **14** በአሶን ሲያገኘንም፣ ወዳለንበት መርከብ አስገብተነው ወደ ሚሊጢን ጕዞአችንን ቀጠልን። **15** ከዚያም በመርከብ ተነሣንና በማግስቱ ኪዩ በምትባለዋ ደሴት ትይዩ ደረስን። በሚቀጥለውም ቀን ወደ ሳሞን ደሴት ጎራ ብለን፣ በማግስቱ ወደ ሚሊጢን ከተማ ገባን፤ **16** ጳውሎስም በእስያ ውስጥ ጊዜ ሳያባክን፣ ኤፌሶንን ዐልፎ በመርከብ ለመሄድ ወስኖ ነበርና፤ ምክንያቱም በተቻለው መጠን ሁሉ ለበዓለ ኀምሳ በኢየሩሳሌም ለመገኘት ቸኵሎ ነበር። **17** ሰዎችንም ከሚሊጢን ወደ ኤፌሶን ልኮ፣ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን ወደ ራሱ አስጠራቸው። **18** ወደ እርሱ በመጡም ጊዜ፣ እንዲህ አላቸው፤ “ወደ እስያ ከገባሁበት ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ፣ ዘወትር እንዴት ከእናንተ ጋር እንደ ኖርሁ እናንተ ራሳችሁ ታውቃላችሁ። **19** ራሴን እጅግ ዝቅ በማድረግና በእንባ፣ ከአይሁድ ሤራ የተነሣ በገጠመኝ መከራም ውስጥ ጌታን ማገልገል አላቋረጥሁም። **20** ጠቃሚ የሆነውን ነገር ሁሉ ለእናንተ ከመግለጽና በአደባባይም ሆነ ቤት ለቤት በመዞር እናንተን ከማስተማር ወደ ኋላ እንዳላልሁ ታውቃላችሁ። **21** በንስሓ ወደ እግዚአብሔር ስለ መመለስና በጌታችን በኢየሱስ ስለ ማመን አይሁድንና ግሪኮችን እንዴት ሳስጠነቅቃቸው እንደ ነበር ታውቃላችሁ። **22** እንግዲህ ተመልከቱ፤ እዚያ ምን እንደሚጠብቀኝ ሳላውቅ፣ በመንፈስ ቅዱስ ታስሬ ወደ ኢየሩሳሌም እሄዳለሁ፤ **23** ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ እስራትና መከራ እንደሚቆየኝ በየከተማው ይመሰክርልኛል። **24** ነገር ግን ሩጫዬንና ከጌታ ኢየሱስ የተቀበልሁትን የእግዚአብሔርን ጸጋ ወንጌል የመመስከር አገልግሎት እስከምጨርስ ድረስ፣ እንደ ውድ ነገር በመቍጠር፣ ለሕይወቴ አልሳሳላትም። **25** እንግዲህ ተመልከቱ፤ የእግዚአብሔርን መንግሥት እየሰበክሁ በመካከላችሁ የዞርሁትን የእኔን ፊት ሁላችሁ ዳግመኛ እንደማታዩ ዐውቃለሁ። **26** ስለዚህ ከማንም ሰው ደም ንጹሕ እንደ ሆንሁ ዛሬ እመሰክርላችኋለሁ፤ **27** ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሁሉ ለእናንተ ከመግለጽ ወደ ኋላ ብዬ አላውቅም። **28** ስለዚህ በገዛ ራሱ ደም የገዛትን የጌታን ጉባኤ ትጠብቁ ዘንድ፣ ስለ ራሳችሁና መንፈስ ቅዱስ ጠባቂ አድርጎ እናንተን ለሾመበት፣ ለመንጋው ሁሉ ተጠንቀቁ። **29** እኔ ከሄድሁ በኋላ፣ ለመንጋው ርኅራኄ የሌላቸው አጥፊ ተኵላዎች በመካከላችሁ እንደሚገቡ ዐውቃለሁ። **30** ከእናንተ መካከልም እንኳ ደቀ መዛሙርትን የራሳቸው ተከታዮች ለማድረግ አንዳንድ ሰዎች መጥተው ጠማማ ነገሮችን እንደሚናገሩ ዐውቃለሁ። **31** ስለዚህ ተጠንቀቁ። ሳላቋርጥ ቀንና ሌሊት፣ ሁላችሁንም ሦስት ዓመት በእንባ እንዳገለገልኋችሁም አስታውሱ። **32** አሁንም ለእግዚአብሔርና ሊያንጻችሁ፣ እንዲሁም በቅዱሳን ሁሉ መካከል ርስትን ሊሰጣችሁ ለሚችለው ለጸጋው ቃል ዐደራ እሰጣችኋለሁ። **33** የማንንም ብር፣ ወርቅ ወይም ልብስ አልተመኘሁም። **34** እነዚህ እጆቼ የእኔንም፣ ከእኔ ጋር የነበሩትንም ሰዎች ፍላጎት ሲያሟሉ እንደ ነበር እናንተ ራሳችሁ ታውቃላችሁ። **35** ደካሞችን በሥራ እንዴት እንደምትረዱ፣ “ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ የተባረከ ነው” የሚለውንም የጌታ ኢየሱስን ቃል እንዴት እንደምታስታውሱ በሁሉም ረገድ አርኣያ ሆንኋችሁ። **36** ጳውሎስ ይህን ሁሉ ካለ በኋላ፣ ተንበርክኮ ከሁሉም ጋር ጸለየ። **37** ሁሉም እጅግ በማልቀስ ዐንገቱ ላይ ተጠምጥመው ሳሙት። **38** ፊቱን ዳግመኛ እንደማያዩ መናገሩም ከሁሉ በላይ አሳዘናቸው። ከዚያም እስከ መርከቡ ድረስ ሸኙት።

Acts 20:1

የሐዋርያት ሥራ **20**:**1**-**3**
አጠቃላይ መረጃ ጳውሎስ ጉዞውን ቀጠለ ከሁከቱ በኃላ ከረብሻው በኃላ ውይም ከህዘቡ ዘመጽ ቀጥሎ ተሰናበታቸው ሰዎች ብዙ ጊዜ ሲለያዩ ይሰነባበታሉ። አማረጭ ትረጉም፦- ደህና ሁኑ አላቸው። አማኞችን በጣም አበረታታተቸው። አመኞችን ለማበረታታት ብዙ ነግረ ተናገረ በዚያም ሶስት ወር አሳለፈ በዚያም ሶስት ወር ተቀመጠ በጳውሎስ ላይ አይሁዳውያን አሴሩበት አማረጭ ትርጉም፦ አይሁዳውያን አሴሩበት። ሴራ ጠነሰሰ(ተሴረ) የድብቅ እቅድ ተዘጋጀ ወደሶሪያ በመርከብ ሊሄድ ነበር ወደ ሶሪያ በመርከብ ለመሄድ ዝግጁ ነበር።

Acts 20:4

የሐዋርያት ሥራ **20**:**4**-**6**
ያጅቡታል ከጳውሎስ ጋር ይጓዛሉ ሱሲጳጥሮስ ….ጥሮፊሞስ እነኚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። ቤሪያ….. በርቤን…..ጢሮአዳ እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። አርስጥሮኮስና . . . ጋይዮስ እነዚህ ስሞች በ ACT 19:29 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምህ ተመልክት። See how you translated these names in እነዚህም ሰዎቸ ቀድመውን ሄዱ የየሐዋርያት ሥራ ጸሀፊ የሆነው ሉቃስ እነዚህን ሰዎች እንደገና ተቀላቀላቸው። አማራጭ ትርጉም እነዚህ ሰዎች ከፊታችን ቀድመውን ተጓዙ።

Acts 20:7

የሐዋርያት ሥራ **20**:**7**-**8**
አጠቃላይ መረጃ ይህ ክፍል ስለ ጳውሎስ የጢሮአዳ ስብከትና ስለ አውጤኪስ የሚናገረው ታሪክ ጅማሬ ነው። በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን አሁድ እለት እንጀራ መቁረስ በጌታ እራት ጊዜ እንጀራ እየተቆረሰ ይበላል። ንግግሩን ቀጠለ ንግግሩን አላቋረጠም የላይኛው ክፍል ይህ ምንአልባት ሶስተኛ ፎቅ ላይ ሊሀን ይችላል።

Acts 20:9

የሐዋርያት ሥራ **20**: **9**-**10**
ጥልቅ የሆነ እንቅልፍ ወድቆ ነበር በጣም ከመተኛቱ የተነሳ ቢቀሰቅሱት እንኳ አይሰማም። ሦስተኛው ፎቅ "ከምድር ቤቱ በተጨማሪ ሁለት ፎቆች ያሉት ቤት" ከመሬት ስያነሱት ሞቶ ነበር ያለበትን ሁኔታ ለማጣራት ወደታች ሄደው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ስመለከቱት ሞቶ አገኙት። ከዚያም እንዲህ አለ "ከዚያም ጳውሎስ እንዲህ አለ" አልሞተም በሕይወት አለ "አውጤኪስ በሕይወት አለ"

Acts 20:11

የሐዋርያት ሥራ **20**: **11-12**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ይህ ጳወልስ በተርሴት ያደረገው ስብከት እና አውጤኪስ በተመለከተ የተዘገበው ታሪክ ክፍል ማብቂያ ነው። ደረጃውን ይዞ ወደላይ ወጣ "ጳውሎስ ወደ ደረጃው ወጣ" ማዕድ ቆረሰ ይህ አንድን ዳቦ ለሁሉም ሰዎች እንዲከፋፈል ተደረጎ መከፋፈል። አማራጭ ትርጉም: "በጋራ መብላት።" ከዚያ ተነሥቶ ሄደ "ከዚያ ወጥቶ ሄደ" ወንዱ ልጅ አማራጭ ትርጉሞች 1) ከ14 ዓመት በላይ የሆነ ወጣት ወንድ ልጅ ወይም 2) አገልጋይ ወይንም ባሪያ ወይም 3) በ9 እና 14 ዓመት መካከል ያለ ወንድ ልጅ።

Acts 20:13

የሐዋርያት ሥራ **20**: **13-14**
አጠቃላይ መረጃ: ጳውሎስ እና የአገልግሎት ባልደረቦቹ ጉዞዋቸውን ቀጥለዋል። እኛ ራሳችን ሄድን በዚህ ሥፍራ ላይ “ራሳችን” የሚለው ቃ የገባው አጽኖት ለመስጠት ሲሆን ይህ ሉቃስን እና የጳውሎስ የአገልግሎት አጋሮች የሆኑትን እና ከእርሱ ጋር በመርከብ የተጓዙትን እና ያልተጓዙት የሚለይ ነው።
ወደ አሶን በመርከብ ጉዞ ጀመረን አሶን በአሁኗ ባህሬን፣ የቱርክ የወደብ ከተማ ከሆነች ከአጌን ሀይቅ አከባቢ የሚትገኝ ከተማ ናት። እርሱ ራሱ ይፈልግ ነበር "ጳውሎስ ፍላጎት ነበረው" እርሱ እኛ ወሰድነው በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሉቃስን እና ከእርሱ ጋር የተጓዙትን እንጂ ጳውሎስን አይደለም። ወደ ሚጢሊኒ መጣን፤ ሚጢኒሊ በቱሪክ ሀገር ውስጥ በሚገኘው የኤአን ሐይቅ ዙሪያ የሚትገኝ የዘመኗ ሚጢሊኒ ናት።

Acts 20:15

የሐዋርያት ሥራ **20**: **15-16**
ከዚያ ተነሥተን ሄድን በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል ጳውሎን፣ ሉቃስን እና ከእነርሱ ጋር በመጓዝ ላይ ያሉትን ሰዎች ያመለክታል። የኪዩ ደሴት ኪዩ በአሁኗ ቱሪክ ሀገር ውስጥ በሚገኘው የአጌን ሐይቅ ላይ የሚገኝ ደሴት ነው። ሳሞን የተባለው ደሴት ተሻግረን ሄድን ሳሞን በአጋን ሐይቅ ውስጥ በዘመኑ ትሪክ ከሚገኘው ከኪዮስ ደሴት በስተደቡብ ላይ ይገኛል። አማራጭ ትርጉም: "የሳሞንን ደሴት ተሻግረን ሄድን።" የሚሊጢን ከተማ ሚሊጢን በምዕራብ ኢስያ አከባቢ በሜንዴር ወንዝ ጫፍ ላይ የሚትገኝ የወደብ ከተማ ናት። ጳውሎስ በኤፌሶን በኩል ለመሄድ ወስኖ ነበር ጳውሎስ በመርከብ በደቡብ በኩል አድርጎ የኤፌሶንን ወደብ አልፎ ሄደ። ይህንንም ያደረገው ወደሚሊጢስ ምድር ለመድረስ ፈልጎ ነበር።

Acts 20:17

የሐዋርያት ሥራ **20**: **17-21**
ከሚሊጢስ ተነስቶ ይህንን በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ በ ACT 20:15 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። በኢስያ መረት ረገጡ "ወደ እስያ አከባቢ ገቡ" በትህትና "ራሴን ዝቅ አድርጌ" ወይም "በትህትና" በእንባ "አንዳንድ ጊዜ ጌታን እያገለገልኩ እንኳ አለቅሳለሁ" አንዳችን ነገር አላስቀረሁባችሁም "ምንም ነገር አልሸሸኳችሁም" ወይም "ከእናንተ የደበኩት ነገር የለም" ከቤት ነቤት ጉብኘንት አንስቶ ጳውሎስ በተለያዩ የግለሰቦች ቤት ውስጥ ያስተምር ነበር። በእግዚአብሔር ፊት የሚሆን ንሰሓ "ከኃጢአት ፍታቸውን መልሰው ወደ እግዚአብሔር ይዙሩ ዘንድ"

Acts 20:22

የሐዋርያት ሥራ **20**: **22-24**
ከእየሩሳሌም ጋር በመንፈስ ቅዱስ አማካኘነት ይተሳሰሩ ዘንድ "ወደ እየሩሳሌም እሄድ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ስላስገደደኝ" መንፈስ ቅዱስ ለእኔ መስክሯል "መንፈስ ቅዱስ ይህንን ነገር አስቀድሞ በማሳወቅ አስጠንቅቆኛል።" እስራት እና መከራ ይጠብቀኛል "በሰንሰለት ገና እታሠራለሁ እንዲሁመም አካላዊ መከራም ገና ደርስበኛል። " ሩጫዬን ጨርሻለሁ "እግዚአብሔር እንድሠራው የላከኝ ሥራ አጠናቅቄያለሁ" ምስክር ይሆናሉ "ምስክርነት መስጠት" ወይም "መመስከር"

Acts 20:25

የሐዋርያት ሥራ **20**: **25-27**
እናንተን ሁላችሁንም አወቃለሁ1 "እናንተ ሁላችሁ" የእግዚብሔርን መንግስት ለመስበክ አብሬያች የወጣሁት እናንተ "ስለ እግዚአብሔር መንግስት የሰበኩላችሁ እናንተ" ከእንግዲህ ፊቴን አታዩም በዚህ ሥፍራ ላይ “ፊት” የሚለው የፓውሎስ አካል የሚያሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም: “ከእንግዲህ በምድር ላይ እኔን በሥጋ አተታዩኘንም።" እኔ የማንም ሰው ደም የለብኝም "ማንም ሰው በእግዚአብሔር በደለኛ ተደርጎ ቢፈረድበት በእኔ ምክክንያት ግን አይሆንም።"

Acts 20:28

የሐዋርያት ሥራ **20**: **28-30**
ስለዚህ በዚህ ሥፍራ ላይ “ስለዚህ” የሚለው ቃል ከዚህ በፊት በተነገረ አንድ ነገር ምክንያት ይህ እንደሆነ ያሳያል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ጳውሎስ እስካሁን የተናገረውን ነገር የሚያመለክት ነው። መንፈስ ቅዱስ ኤጴስ ቆጶስ አድርጎ በሾማችሁ መንጋዎች ላይ አማኞች የተመሰሉት በበግ መንጋ ነው። ልክ በጉችን የመጠበቅ ኃላፊነት የእረኞቹ እንነደሆነ ሁሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የእግዚአብሔርን መንጋ ይጠብቁ ዘንድ አደራ ተሰጥቶዋቸዋል። ስለዚህም ከተኩላዎች የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው። አማራጭ ትርጉም: "መንፈስ ቅዱስ አደራ የሰጣችሁ የአማኞች ቡድን።" በደሙ የገዛቸው የጌታ ጉባኤ የኢየሱስ ክርስቶስ “ደም” መፍሰስ ለእግዚአብሔር ስለኃጢአት የተከፈለ ዋጋ ሆኖ ቀርቧል። አመማራጭ ትርጉም: “ክርስቶስ ደሙን በመስቀል ላይ አፍስሶ የገዛቸው ሕዝቡ።” ለራሳቸው ደቀ መዛሙርትን ያፈራሉ "የክርስቶስ ተከታይ የሆኑ ሰዎችን የእርሱ ተከታዩች ይሆኑ ዘንድ በራሳቸው፣ በተሳሳተ ትምህር ያሳምኗቸዋል።"

Acts 20:31

የሐዋርያት ሥራ **20**: **31-32**
ተጠንቀቁ፣ አስታውሱ አማራጭ ትርጉም: "ተጠንቀቁ እንዲሁም አስታውሱ" ወይም "እያስታወሳችሁ ተጠንቀቁ" ወይም "በማስታወስ ተጠንቀቁ" ተጠንቀቁ "ንቁና ጠብቁ" ወይም “ነቅታችሁ ጠብቁt" (UDB) ወይም "ንቁዎች ሁኑ" አስታውሱ "ማስታወሳችሁን ቀጥሉ" ወይም "እንዳትዘነጉ" ለሦስት ዓመታት ማስተማር አላቋረጥኩም ጳውሎስ ለሦስት ዓመታት ያኽል በተከታታይ አላስተማራቸው ይሁን እንጂ በእነዚህ ሦስት ዓመታት ውስጥ አልፎ አልፎ ያስተምራቸው ነበር። ማስተማር አላቋረጥኩም አማራጭ ትርጉሞች 1) "ማስጠንቀቅ አላቆምኩም" ወይም 2) "ማሰተካከያዎችን በመስጠጥ ማበረታታቴን አላቆምኩም ነበር።"

Acts 20:33

የሐዋርያት ሥራ **20**: **33-35**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: በ ACT 20:18 ላይ የጀመረውን ጳውሎስ በኤፌሶን ላሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያደረገውን ንግግር በበዚህ ክፍል ውስጥ አጠናቋል። የማናችሁንም ብር አልቀማሁም "የማናችሁንም ሀብት አልተመኘሁም" ወይም "ለራሴ ምን ብር ከእናንተ አልፈለኩም" የሰውን ብር፣ ወርቅ ወይም ልብስ በዚያ ዘመን ልብስ እንደ ሀብት ይታይ ነበር፤ ብዙ ልብስ ባለህ ቁጥር ሀብታም ነህ ማለት ነው። እናንተ ራሳቸችሁ በዚህ ሥፍራ ላይ “ራሳችሁ” የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው አጽኖት ለመስጠት ነው። በእነዚህ እጆቼ እየሠራሁ የሚያስፈልገኝ ነገር አድርግ ነበር በዚህ ሥፍራ ላይ “እጅ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የጳውሎስን አጠቃላይ መንፈስ እና አካልን ነው። አማራጭ ትርጉም: “በገዛ እጆቼ እየሠራሁ ገንዘብ አገኛለሁ እንደሁም ወጪዬን ሁሉ በዚህ እሸፍን ነበር።" ደካሞችን ሥራ እየሠራችሁ አግዟቸው "ደካሞችን ማገዝ ያስችላችሁ ዘንድ ገንዘብ ለማግኘት ሥራ ሥሩ"

ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብጹዕ ነው ሰው ከእግዚአብሔር ሞገዝን እና ሀሴት ማደረግን መቀበል የሚችለው ይበልጥ ሲሰጥ ነው።

Acts 20:36

የሐዋርያት ሥራ **20**፡ **36**-**38**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ይህ ጳውሎስ በኤፌሶን ካሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር ያደረገውን ጸሎት የተዘገበበት ታሪክ ማብቂያ ነው። በጳውሎስ አንገት ላይ ተጠመጠመ "አጥብቆ አቀፈው" ወይም "እጆቻውን በእርሱ ዙሪያ አኖሩ" ሳሙት በመካከለኛው ምስራቅ አንድን ሰው ጉንጩን መሳም ወንድማማችነትን ወይም ጓደኝነት የሚያሳይ ነው። እንደገና ፊቱን አያዩትም በዚህ ሥፍራ “ፊት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የጳውሎስን ሙሉ አካልን ነው። አማራጭ ትርጉም፡ በዚህ መድር ላጥ እንደገና በሥጋ አታዩኝም።"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 21

1 ከእነርሱም ተለይተን የባሕር ላይ ጕዞአችንን በቀጠልን ጊዜ፣ ቀጥታ ወደ ቆስ ከተማ አመራን፤ በማግስቱም ወደ ሩድ ከተማ፣ ከዚያም ወደ ጳጥራ ከተማ
ሄድን። 2 ወደ ፊንቄ የሚሻገር መርከብ ባገኘን ጊዜም ተሳፍረን መጓዝ ጀመርን። 3 የቆጵሮስን ደሴት ከሩቅ ባየን ጊዜ፣ ወደ ግራ ትተናት በባሕር ወደ ሶርያ
ተጓዝን፤ መርከብዋ ጭነቷን የምታራግፈው በዚያ ስለ ነበር፣ ጢሮስ ወደብ ላይ ደረስን። 4 ደቀ መዛሙርቱን ካገኘን በኋላም፣ በዚያ ሰባት ቀን ተቀመጥን።
እነዚህም ደቀ መዛሙርት ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይገባ በመንፈስ ቅዱስ ተናገሩት። 5 የምንቈይበት ጊዜ ሲገባደድ፣ ተነሥተን ጕዞአችንን ቀጠልን።
ሁሉም፣ ከሚስቶቻቸውና ከልጆቻቸው ጋር ከከተማ እስክንወጣ ድረስ በመንገዳችን ሸኙን። ከዚያም እወደቡ ላይ ተንበርክከን ጸለይን፤ እርስ በርስም
ተሰነባበትን። 6 እኛ በመርከቡ ተሳፈርን፤ እነርሱም ወደ ቤታቸው ተመልሰው ሄዱ። 7 ከጢሮስ የተነሣንበትን ጕዞ በጨረስን ጊዜ፣ አካ ደረስን። በዚያም
ወንድሞችን አገኘንና አንድ ቀን ከእነርሱ ጋር ቈየን። 8 በሚቀጥለው ቀን ከዚያ ተነሥተን ወደ ቂሣርያ ሄድን። ከዚያም ከሰባቱ አንዱ ወደ ሆነው፣ ወደ ወንጌል
ሰባኪው ወደ ፊልጶስ ቤት ገብተን ከእርሱ ጋር ሰነበትን። 9 ይህም ሰው ትንቢት የሚናገሩ አራት ደናግል ሴቶች ልጆች ነበሩት። 10 የተወሰኑ ቀናት እንደ
ተቀመጥንም፣ አጋቦስ የሚሉት ነቢይ ከይሁዳ ወደ ነበርንበት ወረደ። 11 ወደ እኛም መጥቶ፣ የጳውሎስን መታጠቂያ ወሰደ፤ የገዛ ራሱን እጆችና እግሮችም
አስሮ፣ «መንፈስ ቅዱስ እንዲህ ይላል፤ ‘በኢየሩሳሌም ያሉ አይሁድ የዚህን መታጠቂያ ባለቤት እንደዚህ አድርገው ያስሩታል፤ አሳልፈውም ለአሕዛብ እጅ
ይሰጡታል’” አለ። 12 እነዚህን ነገሮች በሰማን ጊዜ፣ እኛና በዚያ ስፍራ የሚኖሩ ሰዎችም ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይወጣ ለመንነው። 13 ጳውሎስም፣
“እያለቀሳችሁ ልቤን የምትሰብሩት ምን ማድረጋችሁ ነው? እኔኮ መታሰር ብቻ ሳይሆን፣ ለጌታችን ለኢየሱስ ስም በኢየሩሳሌም ለመሞት ዝግጁ ነኝ” ብሎ
መለሰ። 14 ጳውሎስ ምክር ለመቀበል እንዳልፈለገ በተረዳን ጊዜ፣ “የጌታ ፈቃድ ይሁን” ብለን መለመኑን አቆምን። 15 ከእነዚህ ቀናት በኋላ፣ እኛም የጕዞ
ዕቃዎቻችንን ይዘን ወደ ኢየሩሳሌም ወጣን። 16 ደግሞም ከቂሣርያ የነበሩ አንዳንድ ደቀ መዛሙርት ከእኛ ጋራ መጡ። ምናሶን የሚባለውንም ሰው ይዘውት
መጡ፤ እርሱም የቆጵሮስ ሰው፣ ወደ ፊት ከእርሱ ጋር እንድንቀመጥ የታሰበ የቀድሞ ደቀ መዝሙር ነበረ። 17 ኢየሩሳሌም በደረስን ጊዜ፣ ወንድሞች በደስታ
ተቀበሉን። 18 በማግስቱም ጳውሎስ ከእኛ ጋር ወደ ያዕቆብ ሄደ፤ ሽማግሌዎችም ሁሉ በዚያ ነበሩ። 19 ሰላምታ ካቀረበላቸው በኋላ፣ እግዚአብሔር በእርሱ
አገልግሎት አማካይነት በአሕዛብ መካከል የሠራቸውን ነገሮች አንድ በአንድ ዘርዝሮ ነገራቸው። 20 እነርሱም ስለ ሰሙት ነገር እግዚአብሔርን አመሰገኑ፤
እንዲህም አሉት፤ “ወንድም ሆይ፣ ከአይሁድ ያመኑት ስንትና ስንት ሺህ እንደ ሆኑ ታያለህ። ሁላቸውም ሕግን ለመጠበቅ የወሰኑ ናቸው። 21 በአሕዛብ መካከል
የሚኖሩት አይሁድ ሁሉ ሙሴን እንዲተዉ እንደምታስተምራቸው፣ ልጆቻቸውንም እንዳይገርዙ እንደምትነግራቸውና በቀድሞው ልማድ እንዳይሄዱ እንደምታደርግ፣
ስለ አንተ ተነግሮአቸዋል። 22 እንግዲህ ምን እናድርግ? መምጣትህን እንደሚሰሙ ርግጠኞች ነን። 23 ስለዚህ አሁን እኛ የምንልህን አድርግ፤ ስለት ያለባቸው
አራት ሰዎች እዚህ አሉን። 24 እነዚህን ሰዎች ይዘህ ከእነርሱ ጋር ራስህን አንጻ፤ ጠጕራቸውን ለመላጨት የሚያስፈልጋቸውንም ገንዘብ ክፈልላቸው። በዚህም
ስለ አንተ የተነገራቸው ሁሉ ውሸት እንደ ሆነ ያውቃሉ፤ አንተም ልማዱን ጠብቀህ እንደምትኖር ይረዳሉ። 25 ስላመኑ አሕዛብ ግን ለጣዖት ከተሠዋ፣ ከደም፣
ከታነቀ፣ እንዲሁም ከዝሙት ራሳቸውን እንዲጠብቁ ጽፈን ትእዛዝ ሰጥተናል።” 26 ጳውሎስም ሰዎቹን ይዞ በሚቀጥለው ቀን ራሱን ከእነርሱ ጋር እያነጻ ወደ
መቅደሱ ገባ፤ ይኸውም መሥዋዕቱ ስለ እያንዳንዳቸው እስከሚቀርብ ድረስ መንጻቱ የሚወስደውን ጊዜ በመንገር ነው። 27 ሰባቱ ቀናት ወደ መገባደዱ
ሲቃረቡ፣ ከእስያ የመጡ አንዳንድ አይሁድ ጳውሎስን በቤተ መቅደስ ውስጥ አዩት፤ ሕዝቡንም ሁሉ በእርሱ ላይ አነሣሡ፤ ያዙትም። 28 እንዲህም እያሉ ይጮኹ
ነበር፤ “የእስራኤል ሰዎች ሆይ፣ ርዱን። ሰዎችን ሁሉ ከሕዝቡ፣ ከሕጉና ከዚህ ስፍራ ጋር የማይስማሙ ነገሮችን የሚያስተምር ይህ ሰው ነው። ከዚህም በላይ
የግሪክን ሰዎች ወደ ቤተ መቅደሱ በማስገባት፣ ይህን ቅዱስ ስፍራ የሚያረክሰውም እርሱ ነው።” 29 ምክንያቱም ቀደም ሲል የኤፌሶኑን ሰው ጥሮፊሞስን
ከእርሱ ጋር በከተማ ስላዩት፣ ጳውሎስ ወደ ቤተ መቅደስ ያስገባው መሰላቸው። 30 ከተማውም ሁሉ ታወከ፤ ሕዝቡም በአንድነት ተሰባስበው ጳውሎስን ያዙት፤
ጐትተውም ከቤተ መቅደስ አስወጡት፤ በሮቹም ወዲያው ተዘጉ። 31 ሊገድሉት ሲሞክሩም፣ መላዋ ኢየሩሳሌም እጅግ ታውካለች የሚል ወሬ ወደ ጭፍሮቹ
አለቃ ደረሰ። 32 እርሱም ወዲያው ወታደሮችንና የመቶ አለቆችን ይዞ ሕዝቡ ወዳሉበት በሩጫ ወረደ። ሰዎቹም ሻለቃውንና ወታደሮችን ሲያዩ፣ ጳውሎስን
መደብደብ አቆሙ። 33 ከዚያም ሻለቃው ወደ ጳውሎስ ሄዶ ያዘው፤ በሁለት ሰንሰለቶች እንዲታሰርም አዘዘ። ስለ ማንነቱና ስለ ፈጸመው ድርጊትም ጠየቀው።
34 ከሕዝቡም ግማሾቹ ስለ አንድ ነገር ሲጮኹ፣ የቀሩት ደግሞ ስለ ሌላ ነገር ይንጫጩ ነበር። ሻለቃውም ከጫጫታው ሁሉ የተነሣ፣ ስለ ምን እንደሚጮኹ
እንኳ መለየት አልቻለም፤ ስለዚህ ጳውሎስን ወደ ወታደሮች ምሽግ እንዲያገቡት አዘዘ። 35 ጳውሎስ ወደ መወጣጫው ደረጃ በደረሰ ጊዜ፣ ከሕዝቡ ረብሻ
የተነሣ፣ ወታደሮቹ ተሸክመውት ሄዱ። 36 ሕዝቡ “አስወግደው!” እያሉና እየጮኹ ከኋላ ይከተሉ ነበር። 37 ጳውሎስም ወደ ምሽጉ ሊገባ ጥቂት ሲቀረው፣
ሻለቃውን፣ “አንድ ነገር እንድናገርህ ትፈቅድልኛለህ?” አለው። ሻለቃውም፣ “የግሪክ ቋንቋ መናገር ትችላለህ ወይ? 38 አንተ ከዚህ በፊት ዐመፅ አስነሥተህ፣
አራት ሺህ ሰዎችን በማስሸፈት፣ ወደ ምድረ በዳ የገባህ ግብፃዊ አይደለህምን?” አለው። 39 ጳውሎስም፣ “እኔስ በኪልቅያ ከምትገኘው ከጠርሴስ ከተማ
የመጣሁ አይሁዳዊ ነኝ፤ የታዋቂዋ ከተማ ዜጋ ነኝ። አንድ ነገር እለምንሃለሁ፤ ለሰዎቹ እንድናገር ፍቀድልኝ” አለው። 40 ሻለቃው በፈቀደለት ጊዜም፣ ጳውሎስ
መወጣጫ ደረጃው ላይ ቆሞ፣ በእጁ ወደ ሕዝቡ አመለከተ። ሕዝቡ ጸጥ እረጭ ሲልም፣ በዕብራይስጥ ቋንቋ እንዲህ ብሎ ተናገረ፦

Acts 21:1

የሐዋርያት ሥራ **21**: **1-2**
አጠቃላይ መረጃ: ጳውሎስ እና ባልደረባዎቹ ጉዞዋቸውን ቀጥለዋል። ተከፋፈለን በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሉቃስን፣ ጳውሎስን እና ከእነርሱ ጋር ይጓዙ የነበሩትን ሌሎችን ሰዎች ነው። ቆስ ተብላ ወደምትጠራዋ ከተማ የሚወስደውን መንገድ ይዘን መጓዝ ጀመርን "እኛ በቀጥታ ወደ ቆስ ከተማ የሚትሄደውን መንገድ ይዘን ተጓዝን" ወይም "እኛ በቀጥታ ወደ ቆስ ከተማ አመራን" ቆስ ከተማ ቆስ የግሪክ ደሴት ስትሆን በዘመኗ ቱሪክ በደቡብ ከአጌን ሐይቅ አከባቢ የሚትገኝ ከተማ ናት። የሩድ ከተማ ሩድ የግሪክ ደሴት ስትሆን በዘመኗ ቱሪክ በደቡብ ከአጌን ሐይቅ አከባቢከቆስ በደቡብ በኩል እና ከቄርጤስ በሰሜን ምስራቅ በኩል የሚትዋሰን ከተማ ናት። የጳጥራ ከተማ ጳጥራ በዘመናዊዋ ቱርክ ውስጥ ከሚገኘው ከአጌን ሐይቅ በደቡብ ምዕራብ በሜድትራኒያን ባህር አከባቢ የሚትገኝ ከተማ ናት።

Acts 21:3

የሐዋርያት ሥራ **21**: **3-4**
መጣን በዚህ ክፍል ውስጥ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሉቃስን፣ ጳውሎስን እና ከእነርሱ ጋር ይጓዙ የነበሩትን ሌሎች ሰዎችን ነው። ወደ ግራ ትተው ሄድን "ደሴቱን በግራ በኩል ትተን ሄድን" ደቀ መዛሙርቱ በመንፈስ አማካኝነት ለጳውሎስ እንዲህ አሉት "እነዚህ አማኞች ለጳውሎስ እግዚአብሔር የገለጠላቸውን ነገር ነገሩት"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Acts 21:5

የሐዋርያት ሥራ **21**: **5-6**
ከእነርሱ ጋር ያሳለፈው ቃናት "ከእነርሱ ተለይቶ የሚሄድበት ጊዜ በደረሰ ጊዜ" እነርሱ ሁሉ በዚህ ሥፍራ “እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በጠርሴስ ውስጥ ያሉትን አማኞችን ነው። እርስ በእርሳቸው ተሰነባበቱ "እርስ በእርሳቸው ተሰነባበቱ"

Acts 21:7

የሐዋርያት ሥራ **21**: **7-9**
በጀልባ መጓዛችን ስናጠናቅቅ በዚህ ክፍል ውስጥ “እኛ” የሚለው ቃል ሉቃስን፣ ጳውሎስን እና ከእነርሱ ጋር ይጓዙ የነበሩ ሌሎች ሰዎችን ያጠቃልላል። ወደ ፓቶሌሚያስ ደረሰን ፓቶሌሚያስ ከጥሮስ በስተደቡብ በሊባኖስ ውስጥ የሚትገኝ ከተማ ናት። ፓቶሌሚያስ በዘመኑ እስራኤል ውስጥ አካ አከባቢ የሚትገኝ ከተማ ናት። ከሰባቱ አንዱ በዚህ ሥፍራ ላይ “ሰባት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ምግብ ለማከፋፈል እና ለመበልቶች እገዛ ለማድረግ በ ACT 6:5 ላይ የተመረጡት ሰዎች ይህ ሰው "ፊልጶስ" ይህ ሰው ትንቢት የሚናገሩ አራት ደናግል ሴት ልጆች ነበሩት "አራቱ ደናግላን ሴት ልጆቹ ከእግዚአብሔር መልዕክት ተቀብለው በማስተላለፍ የታወቁ ነበሩ።" ይህ ስለ ፊልጶስ የኃላ ታሪክ ማስረጃ ነው።

Acts 21:10

የሐዋርያት ሥራ **21**: **10-11**
አጠቃላይ መረጃ: ይህ በጳውሎስ ታሪክ ውስጥ ከተከናወኑት ነገሮች መካከል ሌላኛው ታሪክ መጀመሪያ ነው፤ ይህ አጋቦስ በተባለ ነቢይ አማካኝነት ስለ የተነገረ ትንቢት ነው። አንድ ነቢይ ይህ ሰው ብዙ ጊዜ ከእግዚአብሔት መልዕክ እየተቀበለ የሚያስተላልፍ ሰው ተደርጎ ይቆጠራል። አጋቦስ ተብሎ የሚጠራ አጋቦስ ከይሁዳ የመጣ ሰው ነው። የጳውሎስን መታጠቂያ ወስዶ "የጳውሎስን መታጠቂያ ከወገቡ ላይ ፈትቶ" በዚያ አሠረው "የጳውሎስን ቀበቶ ወስዶ አሠረው" አሳልፈው ይሰጡታል "ያሣስሩታል" ወይም "ያስዙታል" ወደ . . . እጅ በዚህ ሥፍራ ላይ “እጅ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ቁጥጥር ነው። አማራጭ ትርጉም: “በሕግ ቁጥጥር ሥር።”

Acts 21:12

የሐዋርያት ሥራ **21**: **12-14**
ምን እያደረጋችሁ ነው፣ እያለቀሳችሁ ስለምን ልቤን ትሰብሩታላችሁ? “ጳውሎስ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው በዚያ የነበሩት አማኞች እርሱን መጎትጎታቸውን እንዲተው ለማድረግ ነው።” የጌታ ፈቃድ ይሁን "አሁን በእየሩሳሌም እግዚአብሔር ለጳውሎስ ያለው ፈቃድ ይሁን ብለን ተቀበልን" ወይም "ጌታ ለጳውሎስ በኢየሩሳሌም ያለው እቅድን ለመቀበል አሁን የተዘጋጀን ሆንን"

=

Acts 21:15

የሐዋርያት ሥራ **21**: **15-16**
ሻንጣዎቻችንን አንስተን በዚህ ሥፍራ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሉቃስን፣ ጳውሎስን እና ሌሎች ከእነርሱ ጋር እየተጓዙ ያሉ ሰዎችን ነው። ከእነርሱ ጋር ይዘው መጡ በዚህ ስፍራ ላይ “እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከቄሳሪያ የመጡትን ደቀ መዛሙርት ነው። ምናሶን፣ የቆጵሮስ ሰው ነውson, a man from Cyprus ምናሶን ከቆጵሮስ ደሰት የመጣ ሰው ነው።

Acts 21:17

የሐዋርያት ሥራ **21**: **17-19**
አጠቃላይ መረጃ: ጳውሎስ እና ከእርሱ ጋር ይጓዙ የነበሩት ሰዎች ወደ እየሩሳሌም ደረሱ። ወንድሞች መልካም አቀባበል አደረጉላቸው ታላቁ ስደት ከተነሣ በኋላ በኢየሩሳሌም የቆዩ ወንዶች እና ሴቶች አይሁድ አማኞች ነበሩ። ሠላምታ ከተለዋወጠ በኋላ ሰለሆነው ነገር ይነግራቸው ጀመር "ጳውሎስ ሸማግሌዎቹን ሠላም ካለ በኋላ ስለሆነው ነገር ይነግራቸው ጀመር" ወይም "ሸማግሌዎቹን ሰሰላም ካለ በኋላ ስለሆነው ነገር ይነግራቸው ጀመር" እግዚአብሔር ስላደረገው ነገር አንድ በአንድ ነገራቸው አማራጭ ትርጉም: "ጳውሎስ እግዚአብሔር ስላደረጋቸው ነገሮች በጥልቀት ነገራቸው" አገልሎቱን "የጳውሎስን አገልግሎት"

Acts 21:20

የሐዋርያት ሥራ **21**: **20-21**
አጠቃላይ መረጃ: በኢየሩሳለሉም ያሉ ሸማግሌዎች ለጳውሎስ ምላሽ መስጠት ጀመሩ። ይህንን በሰሙ ጊዜ እግዚአብሔርን አመሰገኑ እና እንዲህ አሉት "ሸማግሌዎቹ ከሰሙት በኋላ እግዚአብሔርን አመሰገኑ እንዲሁም ለጳውሎስ እንዲህ አሉት፣" ሁሉም እንዲህ ብለው ወሰኑ "አይሁድ አማኞች ሁሉ ወሰኑ" እንዲህ ተብሎ ተነግሯቸዋል አማራጭ ትርጉም: "ሰዎች ለአይሁዳዊያን አማኞች እንዲህ ብለው ነግረዋቸዋል" እንዲህ ብለህ ንገራቸው "ለአይሁዶች እንዲህ ብለህ ንገራቸው"

Acts 21:22

የሐዋርያት ሥራ **21**: **22-24**
ምን ማድረግ አለብን? በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሸማግላቹን ና። የተማማሉ አራት ወንዶች ይህ ለተወሰነ ጊዜ ድረስ አልኮል መጠጥ ላለመጠጣት ወይም ጸጉራቸውን ለመላጨት የሚደረግ መሃላ ና። አማራጭ ትርጉም: ለእግዚአብሔር የተሳሉ አራት ወንዶች።" ለእነርሱ ወጪ አስፈላጊውን ነገር መክፍል ክፍያ የሚፈጸመው ወንድ እና ሴት ጠቦቶችን፣ ጥራጥሬዎችን እና የመጠጥ መስዋእት ለመግዛት ነው። አማራጭ ትርጉም: "የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ ለመክፈል።" ሕግን መከተል "ከሙሴን ሕግ እና ከሌሎች አይሁዳዊያን ሕግጋት ጋር የሚስማማ ሕይወትን መምራት"

Acts 21:25

የሐዋርያት ሥራ **21**: **25-26**
አያያዥ ዓረፍ ነገር: በኢየሩሳሌም የነበሩት ሸማግሌዎች ለጳውሎስ ምላሽ መስጠትን ጨረሱ። እንዲህ ብለን ጻፍን በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሸማግሌዎችን ነው። ታንቆ ከሞተ "ሳይታረደ የሞተን እንስሳ ለምግበት ከመጠመቀም" ራሱን ከእነርሱ ጋር ያንጻ ወደ ቤተ መቅዱስ አከባቢ አይሁዳዊያን የመነጻት ሥርዓትን ይፈጽማሉ።ይህ የመንጻት ሥርዓት አይሁዳዊያን ከአሕዛብ ጋር ከመገናኘት ጋር የተገናኘ ነው። የመንጻት ቀን ይህ የመንጻት ሥርዓት ወደ መቅደሱ አከባቢ ከሚደረገው የመንጻር ሥርዓት የተለየ ነው። መስዋእት እስኪሰጥ ድረስ "እንስሳትን ለመስዋእትነት ከማቅረባቸው በፊት"

Acts 21:27

የሐዋርያት ሥራ **21**: **27-29**
አጠቃላይ መረጃ: ይህ የጳውሎስን እስራት አስመልክቶ ያለው ታሪክ ጅማሬ ነው። በቁጥር 29 ከኢስያ ስለመጡት አይሁዳዊያን የኃላ ታሪክ መረጃ ይሰጠናል። ሕዝቡ ሁሉ ደስ ተሰኘ "ብዙ ሕዝብ እንዲያምጽ አደረገ" እጃቸውን ጫኑበት "ያዙት" ከዚህ በተጨማሪ ግሪኮችን ወደ ቤተ መቅዱስ አመጣቸው ወደ ኢየሩሳሌም ቤተ መቅዱስ የውስጠኛው ክፍል መግባት የሚችለው አይሁዳዊይ ወንዶች ብቻ ናቸው። ጥሮፊሞስ ይህ ጳውሎስ ለአይሁዳዊያን ብቻ ወደ ተከለከለው የመቅደሱ ውስጠኛው ክፍል ይዞት ገብቷል የተባለው የግሪክ ሰው ነው።

Acts 21:30

የሐዋርያት ሥራ **21**: **30**-**31**
ከተማይቱ በአጠቃላይ ታወከች በዚህ ሥፍራ ላይ “ሁሉ” የሚለው ቃል ግነት ሲሆን አለማውም አጽኖት ለመስጠት ነው። “ከተማ” የሚለው ቃል በከተማይ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡ “በከተማይቱ ውስጥ የነበሩ ብዙ ሰዎች በጳውሎስ ላይ ተቆጡ።" የመዝጊያው በር ወዲያ ተዘጋ ሕዝቡ ጳውሎስን ጎትተው ካስወጡት በኋላ ጳውሎስን በእንግድነት የተቀበለው ሰው በሩን በፍጥነት ከኋላው ዘጋው። አማራጭ ትርጉም: "አይሁዳዊያን የቤተ መቅደሱን በር በፍጥነት ዘጉት።" ዋናው አለቃ የወታደሮች አለቃ ወይም የስድስት መቶ ወታደሮች አለቃ ኢየሩሳሌም በአጠቃላይ ታወከች በዚህ ሥፍራ ላይ “ኢየሩሳሌም” የሚለው ቃቃ በኢየሩሳሌም ውሰጥ የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታል። “ሁሉም” የሚለው ቃል ግነት የሞላበት ሲሆን ብዙ ሕዝብ በሁኔታውን እንደ ተበሳጨ ለማሳየት የዋለ ነው። አማራጭ ትርጉም፡ "በኢየሩሳሌም ውስጥ ያሉት ብዙ ሰዎች ከተማይቱን አወኩ።"

Acts 21:32

የሐዋርያት ሥራ **21**: **32**-**33**
ወዲያው ወሰዱት "ወዲያው አለቃው ወሰደው" በፍጥነት በፍጥነት ወደ ችሎት ወሰዱት። ዋናው አለቃ የወታደሮች አለቃ ወይም የ600 ወታደሮች መሪ ጳውሎስን ይዞ "ጳውሎስን ይዞ" ወይም "ጳውሎስን አሠረው"

Acts 21:34

የሐዋርያት ሥራ **21**: **34**-**36**
አለቃው የወታደሮች አለቃ ወይም የ600 ወታደሮች መሪ የወታደር ካምፕ ለወታደራዊ ግልጋሎት የሚውል እና በወታደሮች ከፍተኛ ጥበቃ የሚደረግለት ሕንጻ ነው። ወደ ደረጃው በደረሰ ጊዜ ተሸከሙት አማራጭ ትርጉም: "ጳውሎስ ወደ ደረጃዎቹ በደረሰ ጊዜ ወታደሮቹ ተሸከሙት" አስወግዱት ሕዝቡም በጩኸት እና ግልጽ ባልሆነ ቋንቋ ጳውሎስ እንዲገደል ይወተውቱ ነበር። አማራጭ ትርጉም: "እንዲሞት።"

Acts 21:37

የሐዋርያት ሥራ **21**: **37**-**38**
ጳውሎስ ሊቀርብ ሲል አማራጭ ትርጉም: "ወታደሮቹ ጳውሎስን ለማቅረብ ዝግጅታቸው ስያጠናቅቁ" የወታደሮች ካምፕ ይህንን በ ACT 21:34 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ዋናው አለቃ የወታደሮች አለቃ ወይም የስድስት መቶ ወታደሮች አለቃ የግሪክ ቋንቋ ትናገራለህን? አንተ በእኛ ላይ አምጾ አራት ሺህ አሸባሪዎችን ይዞ ወደ በረሃው የገባው ግብጻዊው ሰው አይደለህምን? የወታደሮች አለቃ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው ጳውሎስ ነው ብሎ ያሰበው ሰው አለመሆኑን በተረዳ ጊዜ መገረሙን ለመግለጽ ነው። አማራጭ ትርጉም: "የግሪክ ቋንቋ መናገር ትችላለህ እንዲያውም አራት ሺህ አሸባሪዎችን ይዞ ወደ በረሃ የገባው ሰው ነህ።" አንተ ግብጻዊው ሰው አይደለህምን ጳውሎስ ወደዚያ አከባቢ ከመሄዱ ጥቂት ጊዜ በፊት ከግብጽ ምድር የመጣ አንድ ስሙ የማይታወቅ ሰው በኢየሩሰሌም ውስጥ በሮማዊያን ላይ ሰዎች እንዲያምጹ አድርጓል። ከዚያም “ወደ ምድረበዳ አምልጦ ሄዷል”። ስለዚህም ይህ የወታደሮች አለቃ ጳውሎስ ይህ ሰው ይሆን እንደሆነ አስቧል። አራት ሺህ አሸባሪዎችን "ከእነርሱ ጋር የማይስማሙ ሰዎችን ሁሉ የሚገድሉ አራት ሺህ ወንዶች"

Acts 21:39

የሐዋርያት ሥራ **21**: **39**-**40**
እጠይቅሃለሁ "እለምንሃለሁ" ወይም "እኔ አንተን እጠይቃለሁ" ፍቀድልኝ "እባክህ ፍቀድልኝ" ወይም “እባክህ ፈቃድ ስጠኝ" አለቃ “የወታደሮች አለቃ ወይም የስድስት መቶ ወታደሮች አለቃ” ጳውሎስ በደረጃዎቹ ላይ ቆሞ በዚህ ሥፍራ ላይ “ደረጃ” የሚለው ቃል ወደ ወታደሮች ካንፕ መውጫ ደረጃዎችን የሚያመለክት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 22

1 “ወንድሞችና አባቶች ሆይ፣ አሁን ስለ ራሴ ለእናንተ የማቀርበውን መከላከያ አድምጡኝ።” 2 ሕዝቡም ጳውሎስ በዕብራይስጥ ቋንቋ ሲያናግራቸው በሰሙ ጊዜ፣ ጸጥ አሉ። ጳውሎስም ንግግሩን በመቀጠል እንዲህ አለ፤ 3 “እኔ በኪልቅያዋ ጠርሴስ የተወለድሁ አይሁዳዊ ነኝ፤ የተማርሁትም በዚሁ ከተማ በገማልያል እግር ሥር ተቀምጬ ነው። የአባቶቻችንንም ጥብቅ የሕግ መንገድ በሚገባ ተምሬአለሁ። ዛሬ እናንተ ሁላችሁ እንደ ሆናችሁት፣ እኔም ለእግዚአብሔር ቀናተኛ ነኝ። 4 ይህን መንገድ እስከ ሞት አሳድጄዋለሁ፤ ሴቶችንና ወንዶችን አስሬ ለወኅኒ አሳልፌ ሰጠኋቸው። 5 ደግሞም ከእነርሱ ደብዳቤ ተቀብዬ፣ በደማስቆ ስለሚገኙ ወንድሞች ወደዚያ ለመጓዝ እንደ ተነሣሁ፣ ሊቀ ካህናቱና ሸማግሌዎች ሁሉ መመስከር ይችላሉ። ከዚያ መንገድ የሆኑትን አስሬ ወደ ኢየሩሳሌም ለመምጣትና ለማስቀጣት ስንቀሳቀስም ነበር። 6 እየተጓዝሁ ወደ ደማስቆ ስቃረብ፣ ቀትር ላይ ድንገት ታላቅ ብርሃን ከሰማይ በዙሪያዬ በራ፤ 7 እኔም መሬት ላይ ወደቅሁ፤ ከዚያም፣ 'ሳውል፣ ሳውል፣ ለምን ታሳድደኛለህ?' የሚለኝን ድምፅ ሰማሁ። 8 እኔም፣ 'ጌታ ሆይ፣ አንተ ማን ነህ?' ብዬ መለስሁለት። እርሱም፣ 'አንተ የምታሳድደኝ፣ የናዝሬቱ ኢየሱስ ነኝ' አለኝ። 9 ከእኔ ጋር የነበሩትም ብርሃኑን አዩ፤ ነገር ግን የተናገረኝን ድምፅ አልሰሙም። 10 እኔም፣ ‘ጌታ ሆይ፣ ምን ላድርግ?’ አልሁ። ጌታም፣ ‘ተነሥና ወደ ደማስቆ ሂድ፤ ማድረግ የሚገባህን ሁሉ እዚያ ይነግሩሃል’ አለኝ። 11 ከዚያ ብርሃን ድምቀት የተነሣም አንዳች ማየት አልቻልሁም፤ ስለዚህ ከእኔ ጋር በነበሩት ሰዎች እጅ እየተመራሁ ወደ ደማስቆ ገባሁ። 12 ለሕጉ በትጋት የሚታዘዝና በዚያ የሚኖሩ አይሁድ ሁሉ መልካምነቱን የመሰከሩለት፣ ሐናንያ የሚባል አንድ ሰው አገኘሁ። 13 እርሱም ወደ እኔ መጥቶ አጠገቤ በመቆም፣ ‘ወንድሜ ሳውል፣ ዐይንህን ገልጠህ እይ’ አለኝ። እኔም በዚያው ቅጽበት አየሁት። 14 እርሱም እንዲህ አለኝ፤ ‘ቅዱሱን እንድታይና ከገዛ አፉ የሚወጣውን ድምፅ እንድትሰማ፣ የአባቶቻችን አምላክ ፈቃዱን እንድታውቅ መርጦሃል፤ 15 ምክንያቱም ስለ አየኸውና ስለ ሰማኸው ነገር ለሰዎች ሁሉ ምስክር ትሆንለታለህ። 16 ስለዚህ አሁን ለምን ታመነታለህ? ተነሥ፤ ስሙን እየጠራህ ተጠመቅና ከኃጢአትህ ታጠብ።’ 17 ወደ ኢየሩሳሌም ከተመለስሁ በኋላም፣ በቤተ መቅደስ እየጸለይሁ ሳለሁ፣ ሸለብ አድርጎኝ ሰመመን ውስጥ ገባሁ። 18 እርሱም፣ ‘ከኢየሩሳሌም ቶሎ ብለህ ውጣ፤ ምክንያቱም ስለ እኔ የምትናገረውን ምስክርነትህን አይቀበሉህም’ ሲለኝ አየሁ። 19 እኔም እንዲህ አልሁ፤ ‘ጌታ ሆይ፣ በምኵራብ ሁሉ በአንተ ያመኑትን ሳስርና ስደበድብ እንደ ነበርሁ እነርሱ ራሳቸው ያውቃሉ። 20 የሰማዕትህን የእስጢፋኖስንም ደም በሚያፈሱበት ጊዜ፣ በመስማማት እዚያው ቆሜ ነበር፤ የገዳዮቹንም ልብሶች እጠብቅ ነበር።’ 21 እርሱ ግን፣ ‘ተነሥተህ ሂድ፤ ምክንያቱም ወደ አሕዛብ እልክሃለሁ’ አለኝ።” 22 ሕዝቡም እስከዚህ ድረስ እንዲናገር ፈቀዱለት፤ ከዚህ በኋላ ግን፣ “እንደዚህ ያለ ሰው ከምድር ይወገድ፤ በሕይወትም ይኖር ዘንድ አይገባውም” እያሉ ይጮኹ ጀመር። 23 እየጮኹም ሳለ፣ ልብሳቸውን እያወለቁና አቧራም ወደ ላይ ይበትኑ ነበር፤ 24 ሻለቃውም ጳውሎስን ወደ ወታደራዊው ምሽግ እንዲወስዱት አዘዘ። እርሱ ራሱ ሕዝቡ ለምን እንደዚያ እንደ ጮኹበት ለማወቅ ስለ ፈለገ፣ እየገረፉ ጳውሎስን እንዲመረምሩት ትእዛዝ ሰጠ። 25 ሰዎቹ በጠፍር ወጥረው ባሰሩት ጊዜ፣ ጳውሎስ በአጠገቡ የቆመውን መቶ አለቃ፣ “ሮማዊ የሆነን ሰው፣ ገና ሳይፈረድበት እንዲህ መግረፍህ ሕጋዊ ነው ወይ?” አለው። 26 መቶ አለቃውም ይህን ሲሰማ፣ ወደ ሻለቃው ሄዶ፣ “ምን ማድረግህ ነው? ሰውየውኮ የሮማ ዜጋ ነው” በማለት ነገረው። 27 ሻለቃውም መጥቶ፣ “አንተ የሮማ ዜጋ ነህን? እስቲ ንገረኝ” አለው። ጳውሎስም፣ “አዎ፣ ነኝ” አለ። 28 ሻለቃውም፣ “እኔኮ ይህን ዜግነት ያገኘሁት በብዙ ገንዘብ ነው” ብሎ መለሰለት። ጳውሎስም፣ “እኔ ግን ከመወለዴ ጀምሮ ሮማዊ ነኝ” አለ። 29 ሊመረምሩት የመጡ ሰዎችም ወዲያው ትተውት ሄዱ። ሻለቃውም ጳውሎስ የሮም ዜጋ መሆኑን ባወቀ ጊዜ ፈራ፤ ምክንያቱም ጳውሎስን አሳስሮት ነበር። 30 በማግስቱም ሻለቃው፣ አይሁድ ጳውሎስን የከሰሱበትን ትክክለኛ ምክንያት ለማወቅ ፈለገ። ስለዚህ ጳውሎስን ከእስራት አስፈታውና የካህናት አለቆችና ሸንጎው በሙሉ እንዲሰበሰቡ አዘዘ። ከዚያም ጳውሎስን አስመጥቶ በመካከላቸው አቆመው።

Acts 22:1

የሐዋርያት ሥራ 22: 1-2
አጠቃላይ መረጃ: ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ውስጥ ለተሰበሰበው ሕዝብ መናገር ጀመረ። በቁጥር 2 ላይ ጳውሎስ እየጠናገረ ሳይሆን የኃላ ታሪክ መረጃ እየተሰጠ ነው። ወንድሞች እና አባቶች ይህ በጳውሎስ እድሜ ላይ ላሉ ሰዎች እንዲሁም ከእርሱ እድሜ በላይ የሆኑ ሰዎችን በትህትና መናገር ነው። የመከራከሪያ ሀሳቤን አድምጡኝ "እባካቸሁ የመከራከሪያ ሀሳቤን አድምጡ" ይህንንም አሁን አቀርብላችኋለሁ "አሁን እኔ ለእናንተ አቀረባለሁ" በዕብራይስጥ ቋንቋ "በእነርሱ የዕብራይስጥ ቋንቋ"

Acts 22:3

የሐዋርያት ሥራ 22: 3-5
በዚህች ከተማ በገማሊያ እግር ሥር ሆኜ ተምሬያለሁ "በዚሁ በኢየሩሳሌም ውስጥ ገማሊያ በተባለው መምህር ተማሪ ነበርኩኝ" የቀደምት አባቶቻችን ሕግ በደንብ እከተል ዘንድ በደንብ ተምሬያለሁ አማራጭ ትርጉም: "እነርሱ የአባቶቻችን ሕግ መከተል እችል ዘንድ በሚገባ አስተምረውኛል" ወይም "የተማሪኩት ትምህርትም የአባቶቻችን ሕግጋት በትክክል መከተል እንዲችል ነው" ለእግዚአብሔር የቀናው ነኝ "የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ የማምነውን ነገር የማደርገው ከልቤ ነው" ወይም "እኔ ለእግዚአብሔር የማደርገውን አገልግሎት የማደርገው በሙሉ ልቤ ነው" ዛሬ እናንተ ሁላችሁ እንደሚታደረጉት ጳውሎስ ራሱን ከሕዝቡ ጋር በማነጻጸር: አማራጭ ትርጉም: "እናንተ ሁላችሁ ዛሬ እንደሚታደርጉት" ወይም "ዛሬ እንደሚታደረጉት ሁሉ::" በዚህ መልኩ በዚህ ሥፍራ ላይ “መልኩ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በኢየሩሳሌው ውስጥ በአንድ ሥፍራ የተሰበሰቡትን አማኞችን ነው። ይህንን በ ACT 9:2 ምን ብለህ እንደተረጎምህ ተመልከት። ለመግደል ይህንን መንገድ የሚከተሉ ሰዎች ለመግደል ጳውሎስ ፈቃደኛ ነበር። ምስክር በመሆን "በመመስከር" ወይም "ምስክር በመሆን" ከእርሱ ደብዳቤ ተቀብዬ ነበር "ከሊቀ ካህናት እና ሽማግሌዎች ደብዳቤ ተቀብዬ ነበር" አሥሬ አመጣቸው ዘንድ ትዕዛዝን ተቀብዬለሁ አመራጭ ትርጉም: "በሠንሰለት አስሬ አመጣቸው ዘንድ ትዕዛዝ ሰጥተውኝ ነበር"

Acts 22:6

የሐዋርያት ሥራ 22: 6-8
እንዲህ ሆነ ጳውሎስ ይህንን መንገድ መከተል ከመጀመሩ በፊት የሆነውን ነገር ነከመናገር በደማስቆስ መንገድ ላይ ጌታ እንዴት እንደጠራው ወደ መናገር ያደረገውን ሽግግር ያሳይለት ዘንድ ይህንን ሀረግ ተጠቅሟል።

Acts 22:9

የሐዋርያት ሥራ 22: 9-11
የእርሱ ድምፅ "የኢየሱስ ድምፅ" ከብርሃኑ ድምቀት የተነሳ ማየት እንኳ አልቻልኩም "ከብርሃኑ ድምቀት የተነሣ ከሌሎች ሁሉ ወደኋላ ቀረው"

Acts 22:12

የሐዋርያት ሥራ 22: 12-13
እንደ ሕጉ ከሆነ እኔ ከሌሎች ሁሉ ይልቅ የተሰጠሁ ነበርኩ አናኒያስ የእግዚአብሔር ሕግ በመጠበቅ ረገድ በጣም ጥንቁቅ ነበር። የተመሠከረለት

ነበር "በሌሎች ዘንድ ጥሩ ስም ነበረው" በተመሳሳይ ሰዓት ይህ ወዲያው የሆነን ነገር ለመግለጽ ጥቅም ላይ የሚለው የተለመደ መንገድ ነው። አማራጭ ትርጉም: "በዚያው ወቅት" ወይም "ወዲያውም።"

Acts 22:14

የሐዋርያት ሥራ **22**: **14**-**16**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ የገዛ ታሪኩን እየተናገረ አናንያስ የተናረወን ነገር መናገሩን ቀጥሏል። ይህ ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ለነበሩተ ሰዎች ያደረገው ንግግር ነው። ከዚያም እንዲህ አለ "ከዚያም አናናስ እንዲህ አለ" የእርሱ ፈቃድ "እግዚአብሔር ያቀደው እና እንዲሆን ያደረገውን ነገር" ምን ትጠብቃለህ? ይህ ጥያቄ ጳውሎስ እንዲጠመቅ ለማበረታታት የቀረበ ነው። አማራጭ ትርጉም: "ብዙ አትጠብቅ!" ወይም "ብዙ አትዘገይ!" ኃጢአትን ታጠብ ልክ ሰውነትን በመታጠብ በሰውነት ላይ ያለን ቆሻሻ እንደሚናስወግድ ሁሉ የኃጢአት ይቅርታን ለማግኘት የኢየሱስን ስም መጥራት የሰውን ውስጥ ከኃጢአት ያነጻል። አማራጭ ትርጉም: "የኃጢአት ይቅርታን ለማግኘት መጠየቅ።"

Acts 22:17

የሐዋርያት ሥራ **22**: **17**-**18**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ለተሰበሰበው ሕዝብ ስለተመለከተው የኢየሱስ ራዕይ መናገር ጀመረ። ራዕይ ተሰጠኝ "ራዕይ ተገለጠልኝ" ወይም "እግዚአብሔር ለእኔ ራዕይ ሰጠኝ" እንዲህ ሲለኝ አየሁት "እንዲህ ስለኝ ኢየሱስን አየሁት" አልተቀበሉትም "በኢየሩሳሌም ያሉት አልተቀበሉትም"

Acts 22:19

የሐዋርያት ሥራ **22**: **19**-**21**
አያያዥ ዓረፈተ ነገር: በዚህ ክፍል ውስጥ ጳውሎስ ኢየሱስን በራዕይ መመልከቱን መተረኩን ያበቃል። ከዚህ በተጨማሪ ይህ ንግግሩ በኢየሩሳሌም ለነበሩት የእርሱን ንግግር ተሰብስበው ያደምጡ ለነበሩት ሰዎች ያደረገው ንግግር ማብቂያም ነው። እነርሱ ራሳቸው ያውቁታል ይህ የሚያመለክተው በኢየሩሳሌም የነበሩትን የማያምኑ አይሁዳዊያንን ነው። "በግርፋት ቀጥተው ሊለቁት አሰቡ" በሁሉም ምኩራቦች ውስጥ ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ዙሪያ ባሉ ምኩራቦች ውስጥ የሚሳተፍ ማንኛውንም የአይሁድ አማኝ ይፈልግ ነበር። የእስጥፋኖስ ደም . . . በእርሱ ላይ ተረጭቶ ነበር ይህ የአነጋገር ዘይቤ ጥቅም ላይ የሚውለው አንድ ሰው ተገደለ ብሎ ለመግለጽ ነው። አማራጭ ትርጉም: "እስጥፋኖስን ገደሉት።"

Acts 22:22

የሐዋርያት ሥራ **22**: **22**-**24**
እንደዚህ ያለውን ሰው ከምድር አስወግደው፥ "ግደለው" ይህንን ስያደርጉ ሳሉ "ይህንን ስያደርጉ ሳሉ" (UDB.) ይህ ቃል በተመሰሳይ ሰዓት የሆኑ ሁለት ነገሮችን የሚያሳይ ነው። ጳውሎስን ይዘው እንዲመጡ አዘዙ አማራጭ ትርጉም: "ጳውሎስን ይዘውት ይመጡ ዘንድ ወታደሮቹን አዘዘ" የወታደሮች ካምፕ ይህንን በ ACT 21:34 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። "አዛዡ እራሱ"

Acts 22:25

የሐዋርያት ሥራ **22**: **25**-**26**
መግረፊያ አለንጋ። ሮማዊ እና በሕግ ቅጣት ያልተጣለበትን ሰው መግረፍ በሕግ ተፈቅዷልን? ይህ ጥያቄ ጥቅም ላይ የዋለው የመቶ አለቃው ጳውሎስን ለመግረፍ ምን ስልጣን እንዳለው ለመጠየቅ ነው። አማራጭ ትርጉም: "ሮማዊ የሆነን እና ያልተፈረደበትን ሰው ለመግረፍ ምንም ስልጣን የለህም!" ምን ለማድረግ አስበሃል? አዛዡ ጳውሎስን ለመግረፍ የነበረውን እቅድ እደገና እንዲያስብበት የቀረበ ጥያቄ ነው። "ይህንን ማድረግ የለብህም!"

Acts 22:27

የሐዋርያት ሥራ **22**: **27**-**29**
እንዲህ አለው "ለጳውሎስ ሂድ አለው" የተገኘ ዜግነት "ዜግነት ያገኘሁ" ወይም "ዜጋ የሆንኩ" የተወለድኩት ሮማዊ ሆኜ ነው "የተወለድኩት የሮም ዜግነት ካላቸው ቤተሰብ ነው፤ ስለዚህም የሮም ዜግነት ያገኘኹት በውልደት ነው።" ይህንን ሊያደረግ የነበረው ሰው "ይህንን ለማድረግ ያቀደው ሰው" ወይም "ይህንን ለማድረግ እየተዘጋጀ ያለው ሰው"

Acts 22:30

የሐዋርያት ሥራ **22**: **30**-**30**
ዋናው አዛዥ የስድስት መቶ ወታደሮች አለቃ ጳውሎስን ይዞት ወረደ ከወታደሮች ካምፕ ወደ ቤተ መቅደሱ የፍርድ አደባባይ ወደ ታች የሚወርድ ቀጥተኛ የሆነ መንገድ አለ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 23

1 ጳውሎስም ትኵር አድርጎ ወደ ሸንጎው በመመልከት፣ “ወንድሞች ሆይ፣ እኔ እስካሁን ድረስ፣ በእግዚአብሔር ፊት በንጹሕ ኅሊና ሁሉ ኖሬአለሁ” አለ። 2 ሊቀ
ካህናቱ ሐናንያም ጳውሎስ አጠገብ የነበሩትን ሰዎች አፉን እንዲመቱት አዘዛቸው። 3 በዚህ ጊዜ ጳውሎስ፣ “አንተ ነጭ ቀለም የተቀባህ ግድግዳ፣ እግዚአብሔር
ይመታሃል። በሕጉ መሠረት ልትፈርድብኝ የተቀመጥህ፣ ሕጉን ጥሰህ እኔ እንድመታ ታዛለህን?” አለው። 4 በአጠገቡ ቆመው የነበሩትም፣ “የእግዚአብሔርን
ሊቀ ካህናት እንዴት ትሰድባለህ?” አሉ። 5 ጳውሎስም፣ “ወንድሞች ሆይ፣ ሊቀ ካህናት መሆኑን አላወቅሁም፤ ምክንያቱም፣ በሕዝብህ አለቃ ላይ ክፉ ቃል
ከአፍህ አይውጣ ተብሎ ተጽፎአል።” 6 ጳውሎስም ከሸንጎው አባላት ከፊሉ ሰዱቃውያን፣ ሌሎቹም ፈሪሳውያን መሆናቸውን ሲያይ፣ በሸንጎ መካከል ሆኖ
በከፍተኛ ድምፅ፣ “ወንድሞች ሆይ፣ እኔ የፈሪሳዊ ልጅ የሆንሁ፣ ፈሪሳዊ ነኝ። ፍርድ ፊት የቀረብሁትም የሙታን ትንሣኤ እንዳለ ስለማምን ነው” አላቸው። 7
ይህን በተናገረ ጊዜ፣ በፈሪሳውያንና በሰዱቃውያን መካከል ክርክር ተነሣ፤ ጉባኤውም ተከፋፈለ። 8 ምክንያቱም ሰዱቃውያን ትንሣኤ ሙታን የለም፤
መላእክትም የሉም፤ መናፍስትም የሉም ስለሚሉና፣ ፈሪሳውያን ግን እነዚህ ሁሉ አሉ ስለሚሉ ነው። 9 በዚህ ጊዜ፣ ታላቅ ውካታ ሆነ፤ ከፈሪሳውያን ወገን የሆኑ
አንዳንድ ጸሐፍትም ተነሥተው፣ “በዚህ ሰው ላይ አንድም ጥፋት አላገኘንም፤ መንፈስ ወይም መልአክ ተናግሮት እንደ ሆነስ ማን ያውቃል?” በማለት ተከራከሩ።
10 ክርክሩም እየጋለ ሲሄድ፣ ጳውሎስን ይዘው እንዳይቦጫጭቁት ሻለቃው ፈራ፤ ስለዚህ ወታደሮቹ ወርደው ጳውሎስን በኀይል ይዘው ከሸንጎ አባላት መካከል
እንዲወስዱትና ወደ ምሽጉ አምጥተው እንዲያስገቡት አዘዘ። 11 በሚቀጥለውም ሌሊት ጌታ በጳውሎስ አጠገብ ቆሞ፣ “አትፍራ፤ በኢየሩሳሌም ስለ እኔ እንደ
መሰከርኸው፣ በሮምም ደግሞ ልትመሰክር ይገባሃል” አለው። 12 በነጋም ጊዜ፣ አንዳንድ አይሁድ ጳውሎስን ሳንገድል እኽል ውሃ አንቀምስም በማለት
በመሐላ ተስማሙ። 13 ይህን የዶለቱትም ሰዎች ቍጥር ከአርባ በላይ ነበር። 14 ወደ ካህናት አለቆችና ወደ ሽማግሌዎችም ሄደው እንዲህ አሉ፤ “ጳውሎስን
እስከምንገድል ድረስ፣ እኽል እንዳንቀምስ በታላቅ ርግማን ተማምለናል። 15 ስለዚህ አሁን ሻለቃው ጳውሎስን ወደ እናንተ እንዲያወርደውና እናንተ የእርሱን
ጕዳይ ይበልጥ በትክክል እንደምታዩለት አስመስላችሁ፣ ሸንጎው ለሻለቃው ያመልክት። በእኛ በኩል ግን እዚህ ከመምጣቱ በፊትም ቢሆን ልንገድለው ዝግጁ
ነን።” 16 የጳውሎስ እኅት ወንድ ልጅም ጳውሎስን አድፍጠው እንደሚጠብቁት ዐወቀ፤ ሄዶም ወደ ምሽጉ ገብቶ ለጳውሎስ ነገረው። 17 ጳውሎስም አንዱን
መቶ አለቃ ጠራና፣ “ይህን ወጣት ወደ ሻለቃው ውሰደው፤ የሚናገረው ነገር አለውና” አለ። 18 መቶ አለቃውም ወጣቱን ይዞ ወደ ሻለቃው አመጣውና እንዲህ
አለ፤ “ጳውሎስ የተባለው እስረኛ ወደ ራሱ ጠርቶኝ፣ ይህን ወጣት ወደ አንተ እንዳቀርበው ለመነኝ፤ ወጣቱ ለአንተ የሚነግርህ ነገር አለው።” 19 ሻለቃውም
እጁን ይዞ ወደ አንድ ገለልተኛ ስፍራ ወስዶት፣ “ልትነግረኝ የፈለግኸው ነገር ምንድን ነው?” ብሎ ጠየቀው። 20 ወጣቱም እንዲህ አለ፤ “አይሁድ ስለ ጕዳዩ
ትክክለኛነት ይበልጥ ለመረዳት የፈለጉ አስመስለው፣ ነገ ጳውሎስን ወደ ሸንጎው እንድታወርደው አንተን ለመለመን ተስማምተዋል። 21 ነገር ግን እሺ
አትበላቸው፤ ምክንያቱም ከአርባ በላይ የሚሆኑ ሰዎች አድፍጠው እየጠበቁት ነው። ጳውሎስን ካልገደሉም እኽል ውሃ እንደማይቀምሱ ተማምለዋል። አሁንም
እንኳ የአንተን መስማማት እየጠበቁ ነው እንጂ ዝግጁ ናቸው።” 22 ስለዚህ ሻለቃው ወጣቱን ልጅ፣ “ስለ እነዚህ ነገሮች ለእኔ መግለጥህን ለማንም
እንዳትናገር” ብሎ ካስጠነቀቀው በኋላ፣ አሰናበተው። 23 ከመቶ አለቆቹም ሁለቱን ወደ ራሱ ጠርቶ፣ “እስከ ቄሣርያ ለመሄድ የሚችሉ ሁለት መቶ ወታደሮችን፣
ሰባ ፈረሰኞችንና ሁለት መቶ ባለ ጦሮችን አዘጋጁ፤ ከሌሊቱም በሦስተኛው ሰዓት ትንቀሳቀሳላችሁ” አላቸው። 24 ጳውሎስ ወደ ሀገረ ገዡ፣ ወደ ፊልክስ
የሚሄድበትንም ከብት እንዲያዘጋጁና በሰላም እንዲያደርሱት አዘዛቸው። 25 ከዚያም እንዲህ የሚል ደብዳቤ ጻፈ፤ 26 “ከቀላውዴዎስ ሉስዮስ፣ ወደ ተከበረው
ሀገረ ገዢ ፊልክስ፤ ሰላም ለአንተ ይሁን። 27 ይህን ሰው አይሁድ ይዘው ሊገድሉት ሲሉ፣ ከወታደሮች ጋር ደርሼባቸው አዳንሁት፤ ይህን ያደረግሁትም ሮማዊ ዜጋ
መሆኑን ስለ ተረዳሁ ነው። 28 ለምን እንደ ከሰሱት ለማወቅ ስለ ፈለግሁም፣ ወደ ሸንጎአቸው ይዤው ወረድሁ። 29 የገዛ ራሳቸውን ሕግ በሚመለከት በተነሣ
ጥያቄ ምክንያት ተከሶ እንጂ፣ ሞት ወይም እስራት የሚገባው ክስ እንደሌለበት ዐውቄአለሁ። 30 በዚህ ሰው ላይ ሤራ እንደ ተካሄደበትም ደርሼበታለሁ፤
ስለዚህም ፈጥኜ ወደ አንተ ላክሁት፤ ከሳሾቹም በእርሱ ላይ ያላቸውን ክስ አንተ ባለህበት እንዲያቀርቡ መመሪያ ሰጥቻቸዋለሁ። በደኅና ሰንብት።” 31 ስለዚህ
ወታደሮቹ በታዘዙት መሠረት፣ ጳውሎስን ይዘው በሌሊት ወደ አንቲጳጥሪስ ወሰዱት። 32 በሚቀጥለውም ቀን፣ አብዛኞቹ ወታደሮች ፈረሰኞቹን ከእርሱ ጋር
እንዲሄዱ ትተው፣ ወደ ምሽግ ተመለሱ። 33 ፈረሰኞቹም ቂሣርያ በደረሱና ደብዳቤውን ለሀገር ገዡ ሲሰጡ፣ ጳውሎስንም ለእርሱ አስረከቡት። 34 ሀገረ ገዡም
ደብዳቤውን ካነበበ በኋላ፣ ጳውሎስ ከየትኛው አውራጃ እንደ መጣ ጠየቀ፤ ከኪልቅያ እንደ መጣ ባወቀ ጊዜም፣ 35 “ከሳሾችህ ወደዚህ ሲመጡ፣ በሚገባ
እሰማሃለሁ” አለው። ከዚያም በኋላ፣ በሄሮድስ ቅጥር ግቢ እንዲጠብቁት አዘዘ።

Acts 23:1

የሐዋርያት ሥራ 23: 1-3
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ከሸንጎው እና በሊቀ ካህኑ ፊት ይቆም ዘንድ ይዘውት መጡ። ACT 22:30. አናኒያስ ይህ የዚህ ሰው ስም ነው። ነጭ ቀለም የተቀባ ግድግዳ ይህ ግድግዳ ንጹሕ ይመስል ዘንድ ቀለም መቀባቱን ለማመልከት ነው። ጳውሎስ ለአናኒያስ እንዲህ ሲል ነገረው። ግድግዳ ንጹሕ ይመስል ዘንድ ቀለም እንደሚቀባው ሁሉ እንዲሁም አናኒያስም በውጪ መልካም ይመስላል ነገር ግን ውስጡ ግን በክፋት የተሞላ ነው። አማራጭ ትርጉም: "ነጭ ቀለም የተቀባ ግድግዳ።" እንድገረፍ አዘዘ "ሰዎች ይገርፉኝ ዘንድ አዘዘ" ወይም "እነዚህ ሰዎች ይደበድቡኝ ዘንድ አዘዘ"

Acts 23:4

የሐዋርያት ሥራ 23: 4-5
የእግዚአብሔርን ሊቀ ካህን እንደዚህ እንዴት ትሰድባለህ? ሰዎቹ ይህንን ጥያቄ በመጠቀም ጳውሎስ የተናገረው ነገር አግባብነት እንዳሌለው ለማሳየት ጥረት አድረገዋል። አማራጭ ትርጉም: "የእግዚአብሔር ሊቀ ካህን አትሳደብ!" ወንድም እኔ ይህ ሰው ሊቀ ካህን መሆኑን አላወኩም ነበር አማራጭ ትርጉሞች 1) "ጳውሎስ አላወቀም ነበር ምክንያቱ የዚህ ሰው ሁኔታው ሁሉ እንደ ሊቀ ካህን አይደለም" ወይም 2) "ጳውሎስ ከኢየሩሳሌ ለብዙ ጊዜያት ርቆ ስለነበር አዲስ ሊቀ ካህን መሾሙን አያውቅም ነበር።"

Acts 23:6

የሐዋርያት ሥራ 23: 6-8
ተፈርዶብኛል "አንተ በእኔ ላይ ፈርደሃል" ሸንጎው እርስ በእርሱ ተከፋፈለ "የሸነንጎው አባላት መስማማት አልቻሉም" ትንሰዔ የለም፣ መላእክት እና መናፈስት የሉም አማራጭ ትርጉሞች 1) በትንሳዔ፣ በመለአክት ወይም በመናፍስ አያምኑም ወይም 2) እግዚአብሔር ሰዎች እን መለአክት ወይም መናፍስት አድርጎ ሰዎችን ከሞት አያስነሳም።

Acts 23:9

የሐዋርያት ሥራ 23: 9-10
ከዚህም የተነሣ ከፍተኛ ኹከት ተነሣ “ስለዚህም” የሚለው ቃል አሁን የሆነው ነገር የሆነበት ምክንያት ከዚህ በፊት ከሆነው ነገር የተነሣ ነው። በዚህ

ሁኔታ ውስጥ ከዚህ በፊት የተከናወወነው ነገር ጳውሎስ ስለ ትንሳዔ ያለውን እምነት መግለጹ ነበር። መናፍስት ወይን መለአክት ቢያናግሩትስ? ፈርሳዊያን መላእክት እና መናስፍት እንዳሉና ከሰዎች ጋር እንደሚነጋገሩ በመግለጽ ሳዱቃዊያንን ገሰጸዋቸው። አማራጭ ትርጉም: "መላእክት ወይም መናፈስት ተናግረውት ይሆናል" ጳውሎስን እንደ ጨርቅ ልበጣጥሱ ፈለጉ "አካለዊ ጉዳት ባደረሱበት ነበር" በጉልበት ወሰዱት "ጳውሎስን በጉልበት ወሰዱት" ወደ ወታደሮች ካምፕ ወሰዱት ይህንን በ ACT 21:34 ላይ ምን ብለህ እንደ ተረጎምከው ተመልከት።

Acts 23:11

የሐዋርያት ሥራ **23**: **11**-**11**
መሰሰከረ አማራጭ ትርጉም 1) የግል ድነትን እንዴት እንደገኘ "መናገር" ወይም "መመሰከር" ወይም 2) የድነት መልዕክት መናገር።

Acts 23:12

የሐዋርያት ሥራ **23**: **12**-**13**
አጠቃላይ መረጃ: አጠቃላይ መረጃ: ይህ በጳውሎስ ታሪክ ውስጥ አዲስ ስለተፈጠረ ነገር ነው። አይሁዳዊያን ጳውሎስን ለመግደል ተማከሩ። ተማማሉ "አንድ ነገር ለማድረግ በመደበኛ ሁኔታ መስማማት" አርባ ወንዶች "40 ወንዶች"

Acts 23:14

የሐዋርያት ሥራ **23**: **14**-**15**
ሄዱ "አርባ አይሁዶች ሄዱ" ስለዚህም ይህ ቃል ከዚህ በፊት በተነገረ አንድ ነገር ምክንያት ይህ እንደሆነ ያሳያል። በዚህ ክፍል ውስጥ አይሁዳዊያኑ ለሸንጎው የደረሱበትን ስምምነት በመናገራቸው ምክንያት ነው። ወደ እናንት እናመጣው ዘንድ "ጳውሎስን ከወታደሮች ካምፕ ይዘውት በቤተ መቅደሱ ውስጥ ወደሚገኙት ሸንጎዎች ዘንድ ለማምጣት"

Acts 23:16

የሐዋርያት ሥራ **23**: **16**-**17**
ተኝተው ይጠባበቁ ነበር ጳውሎስን ለመግደል ቃል የተገባቡት ሰዎች በጳውሎስ በጉልበት ነጥቀው ለመውሰድ ተዘጋጅተው ነበር። የወታደሮች ካምፕ በ ACT 21:34 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። አንድ ነገር ሊነግረው ይፈልግ ነበር "ወጣቱ ለወታደሮች አለቃ የሆነ ነገር ሊነግረው ፈልጎ ነበር"

Acts 23:18

የሐዋርያት ሥራ **23**: **18**-**19**
እስረኛው ጳውሎስ ወደ እርሱ ዘንድ አስጠራኝ "እስረኛው ጳውሎስ እንድመጣ እና ከእርሱ ጋር እንዳወራ ጠየቀኝ" ይህ ወጣት የወታደር አለቃው ወጣቱን በእጆቹ ይዞት ስለነበር ይህ የጳውሎስ የአጎት ልጅ እድሜው ከ12 እስከ 15 ይሆናል።

Acts 23:20

የሐዋርያት ሥራ **23**: **20**-**21**
አጠቃላይ መረጃ: የጳውሎስ የአጎቱ ልጅ ለወታደሮቹ አለቃ ጥያቄ መልስ ይሰጥ ነበር። አርባ ወንዶች "40 ወንዶች" ተኝተው ይጠብቁት ነበር "ጳውሎስን በጉልበት ለመንጠቅ ዝግጁዎች ነበሩ"

Acts 23:22

የሐዋርያት ሥራ **23**: **22**-**24**
ሁለት መቶ አለቆች "2 መቶ አለቆች" ሰባ ፈረሰኞች "70 ፈረሰኞች" ሁለት መቶ ጦረኞች "200 ጦር የታጠቁ ወታደሮች" ከሌሊቱ ሦስተኛው ሰዓት ላይ ከሌልቱ ሰጠኝ ሰዓት ላይ። ፊሌክስ አገረገዥው የዚያ አከባቢ ገዥ የሆነው ፍልክስ በቄሳሪያ ይኖር ነበር።

Acts 23:25

የሐዋርያት ሥራ **23**: **25**-**27**
አጠቃላይ መረጃ: የወታደሮቹ አለቃ ለዘገረ ገዥው ፍልክስ የላከው ደብዳቤ የጀመረው እንዲህ ነው። ከቀላውዴዎስ ሉስዮስ ወደ ክቡር አገረ ገዡ ወደ ፊልክስ፤ ሰላም ለአንተ ይህ መደበኛ የደብዳቤ መግቢያ ነው። ቀላውዴዎስ ሉስዮስ የወታደሮቹ አለቃ ስም ነው። ፍልክስ አገረገዥው ፍሌክስ ለዚያ አከባቢ በአጠቃላይ በሮም የተሸመ አገረ ገዥ ነው። ልገድሉት ነበር አማራጭ ትርጉም: "አይሁዳዊያን ጳውሎስን ለመግደል ዝግጁዎች ነበሩ" መጡ "ደረሱ" ወይም "ወደፈለጉበት ቦታ ደረሱ"

Acts 23:28

የሐዋርያት ሥራ **23**: **28**-**30**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ይህ የወታደሮቹ አለቃ ለሀገረ ገዥው ፍልክስ የጻፈው ደብዳቤ ማብቂያ ነው። ማወቅ እፈልጋለሁ በዚህ ስፍራ ላይ “እኔ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ቀላውዴዎስ ሉስዮስ ነው። ከሰሱት "አይሁዳዊያን ጳውሎስን ከሰሱት" ከዚያ ነገሩ ምን እንደሆነ ተገነዘብኩ አማራጭ ትርጉም: "በኋላ ላይ ገባኝ"

Acts 23:31

የሐዋርያት ሥራ **23**: **31**-**33**
ስለዚህም ወታደሮቹ የተሰጣቸውን ትዕዛዝ ተግባራዊ አደረጉ በዚህ ሥፍራ ላይ “ስለዚህ” የሚለው ቃል ከዚህ በፊት በተነገረ አንድ ነገር ምክንያት ይህ እንደሆነ ያሳያል። በዚህ ክፍል ውስጥ የወታደሮቹ አለቃ ለወታደሮቹ የሰጣቸው ትዕዛዝ ጳውሎስን እንዲጠብቁት ነው። አንቲጳጥሪስ ይህች ሄሮዶስ ለአባቱ አንቶጳጥሪ ክብር ሲል የገነባት ከተማ ናት። በዘመናችን እስራኤል ውስጥ ትገኛለች።

Acts 23:34

የሐዋርያት ሥራ **23**: **34**-**35**
የኪልቅያ ሰው እንነደሆነ በተረዳ ጊዜ "አገረ ገዥው ጳውሎስ የኪልቅያ ሰው እንደሆነ ባወቀ ጊዜ" ይጠብቁት ዘንድ አዘዘ "ወታደሮቹ ጳውሎስን ይጠብቁት ዘንድ አዘዘ" ወይም "ወታደሮቹ ጳውሎስን ያስሩት ዘንድ አዘዘ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 24

1 ከዐምስት ቀናት በኋላ፣ ሊቀ ካህናቱ ሐናንያ፣ አንዳንድ ሽማግሌዎችና ጠርጡሉስ የተባለ አንድ የሕግ ባለ ሙያ ወደዚያ ሄዱ። እነዚህ ሰዎች ለገዡ አመልክተው
ጳውሎስን ከሰሱት። 2 ጳውሎስ በገዡ ፊት በቆመ ጊዜ፣ ጠርጡሉስ ይከሰው ጀመር፤ ገዡንም እንዲህ አለው፤ «ክቡር ፊልክስ ሆይ፣ በአንተ ምክንያት ብዙ
ሰላም አግኝተናል፤ የአንተ ማስተዋልም ለሕዝባችን ጥሩ መሻሻልን ያመጣለታል፤ 3 ስለ ሆነም አንተ የምታደርገውን ሁሉ በፍጹም ምስጋና እንቀበለዋለን። 4 ብዙ
እንዳላቄይህ፣ በቸርነትህ በዐጭሩ እንድትሰማኝ እለምንሃለሁ። 5 ይህ ሰው ቅንቅን ሆነና በመላው ዓለም ላይ ያሉትን አይሁዶች ሲያሳምፅ አግኝተነዋልና።
የናዝራውያን ወገን መሪ ነው። 6 ቤተ መቅደሱንም እንኳ ሊያረክስ ሞክሯል፤ ስለዚህ ያዝነው። 7 ነገር ግን ወታደራዊው መኰንን ሉስዮስ መጥቶ፣ ጳውሎስን
በኀይል ከእጃችን ወሰደው። 8 አንተም ስለ እነዚህ ነገሮች ሁሉ ጳውሎስን በምትጠይቀው ጊዜ ለምን እንደምንከሰው ልታውቅ ትችላለህ።» 9 አይሁድም አንድ
ላይ ሆነው ጳውሎስን ከሰሱት፤ ነገሮቹም ሁሉ እውነት መሆናቸውን ተናገሩ። 10 ገዡ ግን እንዲናገር ሲጠይቀው፣ ጳውሎስ እንዲህ ብሎ መልስ ሰጠ፤ «አንተ
ለብዙ ዓመታት ለዚህ ሕዝብ ፈራጅ መሆንህን ዐውቃለሁ፤ ስለ ሆነም ደስ እያለኝ ስለ ራሴ እገልጽልሃለሁ። 11 ለማምለክ ወደ ኢየሩሳሌም ከወጣሁ ከዐሥራ
ሁለት ቀን እንደማይበልጥ አንተ መርምረህ ልትደርስበት ትችላለህ፤ 12 እነርሱ በቤተ መቅደስ ባገኙኝ ጊዜም፣ ከማንም ጋር አልተከራከርሁም፤ በምኵራቦችም
ሆነ በከተማው ሕዝብን አልቀሰቀስሁም፤ 13 አሁን በእኔ ላይ የሚያቀርቡት ክስ እውነተኛ ለመሆኑ ማስረጃ የላቸውም። 14 ነገር ግን ለአንተ ይህን እነግርሃለሁ፤
እነርሱ የእምነት ክፍል ብለው እንደሚጠሩት እኔም በዚያ ተመሳሳይ መንገድ የአባቶቻችንን አምላክ አገለግላለሁ። በሕግና በነቢያት ለተጻፈው ሁሉ የታመንሁ
ነኝ። 15 ልክ እነዚህ ሰዎች ደግሞ እንደሚጠብቁት፣ ስለሚመጣው የሙታን ማለትም የጻድቃንና የኀጥአን ትንሣኤ በእግዚአብሔር ላይ እምነት አለኝ። 16
በዚህም በሁሉም ነገር በእግዚአብሔርና በሰዎች ፊት ነቀፋ የሌለበት ኅሊና እንዲኖረኝ እሠራለሁ። 17 ከብዙ ዓመታትም በኋላ ለሕዝቤ ርዳታና የገንዘብ ስጦታ
ለመስጠት መጣሁ። 18 ይህንም ባደረግሁ ጊዜ ከእስያ የሆኑ አንዳንድ አይሁድ፣ ሕዝብም ጩኸትም ሳይኖር በቤተ መቅደስ የመንጻት ሥርዓት ላይ አገኙኝ። 19
እነዚህ ሰዎች በእኔ ላይ አንዳች ነገር ካላቸው፣ በፊትህ መጥተው ክሱን ሊያቀርቡብኝ ይገባቸዋል። 20 አለበለዚያም፣ እነዚሁ ሰዎች በአይሁድ ሸንጎ ፊት
በቆምሁ ጊዜ፣ ምን እንዳጠፋሁ መናገር ነበረባቸው፤ 21 «ዛሬ አንተ የምትፈርድብኝ ስለ ሙታን ትንሣኤ ነው» ብዬ በመካከላቸው ቆሜ ድምፄን ከፍ
በማድረግ ከተናገርሁት ከዚህ አንድ ነገር በቀር፣ ምንም የተናገርሁት የለም። 22 ፊልክስ ግን ስለ መንገዱ በሚገባ ያውቅ ነበር፤ ስለ ሆነም፣ «አዛዡ ሉስዮስ
ከኢየሩሳሌም በሚወርድበት ጊዜ ለክሳችሁ ውሳኔ እሰጣለሁ» ብሎ አይሁድን እንዲጠብቁ አደረጋቸው። 23 ከዚያም ጳውሎስን እንዲጠብቀው፣ ነገር ግን
እንዲያደላለት፣ እርሱንም ከመርዳት ወይም ከመጎብኘት ማንም ወዳጆቹን እንዳይከለክል የመቶ አለቃውን አዘዘው። 24 ከጥቂት ቀናት በኋላ፣ ፊልክስ ድሩሲላ
ከምትባል አይሁዳዊት ሚስቱ ጋር ተመልሶ መጣ፤ ጳውሎስንም በማስጠራት በክርስቶስ ኢየሱስ ስላለው እምነት ከእርሱ ሰማ። 25 ነገር ግን ጳውሎስ ስለ
ጽድቅ፣ ራስን ስለ መግዛት፣ ስለሚመጣውም ፍርድ ከእርሱ ጋር በተነጋገረ ጊዜ፣ ፊልክስ ፈራ፤ «ለአሁኑ ሂድ፤ እንደ ገና ጊዜ ሲኖረኝ ግን፣ አስጠራሃለሁ»
አለው። 26 በዚሁ ጊዜ፣ ጳውሎስ ገንዘብ ይሰጠኛል ብሎ ፊልክስ ተስፋ ያደርግ ነበር፤ ስለዚህ ብዙ ጊዜ እያስጠራ ያነጋግረው ነበር። 27 ከሁለት ዓመት በኋላ
ግን፣ ከፊልክስ ቀጥሎ ጶርቅዮስ ፌስጦስ ገዢ ሆነ፤ ፊልክስ ግን አይሁድን ለማስደሰት ፈልጎ ጳውሎስን በጥበቃ ሥር እንዲቆይ አደረገ።

Acts 24:1

የሐዋርያት ሥራ **24**: **1-3**
አጠቃላይ መረጃ: ጳውሎስ በቄሳሪያ የፍርድ ሂደቱን በመከታተል ላይ ይገኛል። ጠርጡሉስ የተባለ ሰው ለአገረ ገዥው ፍልክስ በጳውሎስ ላይ የቀረበው ክስ ምን እንደሆነ አቀረበ። ከአምስት ቀናት በኋላ "የሮም ወታደሮች ጳውሎስን ወደ ቄሳሪያ ከወሰዱት በኋላ ባሉት አምስት ቀናት ውስጥ" አናኒያስ በ ACT 23:1 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምክ ተመልከት። ተናጋር "ጠበቃ" ወይም "በፍርድ ቤት አንድን ሰው ከሶ የሚቆም ሰው" ወደዚያ ሄደ "went to Caesarea where Paul was" ጠርጢላሰስ ይህ የሰው ስም ነው። ጳውሎስ በአገረ ገዥው ፊት ሲቆም "ጳውሎስ በፍርድ ቤቱ ውስጥ ፈራጅ በሆነው በሀገረ ገዥው ፊት ሲቆም" እርሱን መክሰስ ጀመረ "እርሱን ተቃውሞ መናገር ጀመረ" ወይም "የሮምን ሕግ መተላለፉን በማሳየት ጳውሎስን መክሰስ ጀመረ" በአንተ ምክንያት በዚህ ሥፍራ ላይ “አንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሀገረ ገዥውን ነው። ሠላም አለን "አንተ የሚታስተዳድራቸው ሕዝቦች ሠላም አላቸው" ፍልክስ ይህንን በ ACT 23:25 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት።

Acts 24:4

የሐዋርያት ሥራ **24**: **4-6**
ስለዚህም ብዙ ላቆይህ አልፈልግም አማራጭ ትርጉሞች 1) ስለዚህም ጊዜህን መሻማት አልፈልግም (UDB) ወይም 2) ስለዚህም ላደክምህ አልፈልግም። በአጭሩ የሚናገረውን አድምጠኝ "አጭር ንግግሬን አድምጥልኝ" ይህ ሰው እንዲህ ያለ ነገር ስያደርግ አግኝተነዋል “እኛ” የሚለው ቃል አናኒያስ፣ የተወሰኑ ሽማግሌዎች እና ጠርጡሊየስን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም: “ጳውሎስን ተመልክተነዋል” ወይም “ጳውሎስ ይህንን እንዳደረገ አውቀናል" በዓለም ያሉ አይሁዶች ሁሉ በዚህ ሥፍራ ላይ “ሁሉም” የሚለው ቃ በጳውሎስ ላይ የቀረበው ክስ ግነት ተሞልቶበት ነው። አማራጭ ትርጉም: "በዓለም ያሉ አይሁዳዊያን ሁሉ”።

Acts 24:7

የሐዋርያት ሥራ **24**: **7-9**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጠርጡሉስ ለአገረ ገዥው ፍልክስ በጳውሎስ ላይ ያቀረበው ክስ አጠናቀቀ። ጳውሎስን በጠየቁት ጊዜ "ጳውሎስን ባወጣጡት ጊዜ" ወይም "በችሎት ፊት እንደሚደረገው ጥያቄ በተጠየቀ ጊዜ" እኛ የምከሰው ስለ … ነው "ጳውሎስ ይህንን በማድረጉ ነው የሚንከሰው" ወይም "ጳውሎስ ይህንን በማድረጉ ጥፋተኛ በመሆኑ ነው የሚንከሰው"

Acts 24:10

የሐዋርያት ሥራ **24**: **10-13**
አጠቃላይ መረጃ: ጳውሎስ ለቀረበበት ክስ በሀገረ ገዥው ፍልክስ ፊት እንዲህ በማለት ምላሽ ሰጠ። አገረ ገዥው ተቁነጠነጠ "ሀገረ ገዥው ምልክት አሳየ" ሀሳቤን ላብራራ "ያለሁበትን ሁኔታ ላብራራ" አንተ ራስህ ልታረጋግጥ ትችላለህ "ማረጋገጥ ትችላለህ" እስካሁን ዐሥራ ሁለት ቀን ሆኖኛል "12 ቀናት ሆኖኛል" ኹከት አላስነሳሁም "አላወኩኝም" ወይም "ማንንም ለኹከት አልቀሰቀስኩም" የተከሰስኩበት ክስ "ጠፋተኛ ተደርጌ የተከሰስኩበት" ወይም 'ወንጀለኛ የተደረግኹት"

Acts 24:14

የሐዋርያት ሥራ **24**: **14-16**
ይህን ለአንተ አምናለሁ "ይህንን በአንተ ፍት እቀበላሉ" ወይም "ይህንን ለአንተ እናገራለሁ" የስህተት ትምህርት ብለው ይጠሩታል "የስህተት ትምህርት ቡድኖች ብለው ይጠራሉ" የአባቶቻን አምላክ ይህ የሚያሳየው ጳውሎስ የሚከተለው የትንቱን ሃይማኖት መሆኑን ነው። ይህ ደግሞ አዲስ አይደለም.

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የስህተት ትምህርት ተብሎም መጠራት አይችልም።" የተቀደሱት "ቅዱስ ሕዝብe" ይህንን ለማግኘት እሠራለሁ "ይህንን ለማግኘት እለማመዳለሁ" ወይም "ይህንን ለማግኘት እጥራለሁ" በእግዚአብሔር ፊት "በእግዚብሔር መገኘት ውስጥ"

Acts 24:17

የሐዋርያት ሥራ **24: 17-19**
ሀገሬን በመርዳት የገንዘብ ስጦታ። "ለመርዳት የሚሆን የገንዘብ ስጦታ" ከሕዝቡ ጋር አይደለም "ሕዝቡን የሰበሰብኩት ትክክለኛ ያልሆነ ነገር ለማድረግ አይደለም" እነዚህ ሰዎች "ከኢስያ የመጡ አይሁዳዊያን" የሚሉት ነገር አንዳች ካላቸው "የሚሉት ነገር ካላቸው"

Acts 24:20

የሐዋርያት ሥራ **24: 20-21**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ስለተከሰሰበት ነገር በሀገረ ገዥው ፍልክስ ፊት መለስ መስጠቱን አጠናቋል። እነዚሁ ተመሳሳይ ሰዎች በቄሳሪያ ጳውሎስ በችሎት በቀረበ ጊዜ የነበሩት እነዚሁ የሸንጎው አባላት የሆኑት ሰዎች።

Acts 24:22

የሐዋርያት ሥራ **24: 22-23**
የወታደሮች አዛዡ ሉስዮስ በወረደ ጊዜ "የወታደሮች አለቃ የሆነው ሉስዮስ በወረደ ጊዜ" ወይም "የወታደሮች አለቃ የሆነው ሉስዮስ በወረደ ጊዜ"

የአንተን ነገር ውሳኔ እሰጣለሁ "በአንተ ላይ የቀረበውን ክስ አስመልክቶ ውሳኔ እሰጣለሁ" ወይም "ጥፋተኛ መሆን አለመሆንን እወስናለሁ" በጥቂቱም ነጻነት ሰጠው "ለጳውሎስ በእስር ላይ እያለ በመጠኑም ቢሆን ነጻነት ሰጠው"

Acts 24:24

የሐዋርያት ሥራ **24: 24-25**
ከጥቂት ቀናት በኋላ "ከብዙ ቀናት በኋላ" ፍልክሽ ይህንን በ ACT 23:24 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። ድሩሲላ የእርሱ ምስት ናት ድሩሲላ የሴት ስም ነው። ፍልክስ በፍራት ተሞላ ፍልክስ ስለኃጢአቱ ጸጸት ተሰምቶት ልሆን ይችላል። ለአሁኑ "ለአሁኑ" ወይም "እስከ በኋላ ድረስ"

Acts 24:26

የሐዋርያት ሥራ **24: 26-27**
ጳውሎስ ገንዘብ ልሰጠው ይችል ነበር ፍልክስ ጳውሎስ ነጻ ለመውጣት ጉቦ ልሰጥ ይችላል ብሎ አስቦ ነበር። አማራጭ ትርጉም፡ "ጳውሎስ ለፍልክስ ገንዘብ መስጠት ይችል ነበር።" ስለዚህም ብዙ ጊዜ ሰዎችን ልኮ ያስጠራው እንዲሁም ያወራው ነበር "ስለዚህም ፊስጦስክስ ብዙ ጊዜ ጳውሎስን አስጠርቶ ያወራው ነበር" ጶርቅዮስ ፊስጦስ ይህ ፍልክስን ተክቶ የሀገረ ገዥ የሆነው ሰው ስም ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 25

1 ፊስጦስም ወደ ክፍለ ሀገሩ ገባ፤ ከሦስት ቀንም በኋላ ከቄሣርያ ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ። 2 የካህናት አለቃውና ታዋቂ የሆኑት አይሁድ ጳውሎስን ፊስጦስ ላይ
ከሰሱት፤ ለፊስጦስም በጎይል ተናገሩ። 3 በመንገድም ላይ ሊገድሉት ጳውሎስን ወደ ኢየሩሳሌም እንዲያስጠራው ፊስጦስን ለመኑት። 4 ፊስጦስ ግን መልሶ
ጳውሎስ በቄሣርያ እስረኛ እንደ ሆነ፣ እርሱ ራሱም ወደዚያ እንደሚመለስ ተናገረ። 5 “ስለዚህ፣ የሚችሉ ከእኛ ጋር ወደዚያ መሄድ አለባቸው። ሰውየው ያጠፋው
ነገር ካለ፣ ክሰሱት” አለ። 6 ፊስጦስም ስምንት ወይም ዐሥር ቀን ከቆየ በኋላ፣ ወደ ቄሣርያ ወረደ። በማግስቱም በፍርድ ወንበር ተቀምጦ ጳውሎስን ወደ እርሱ
እንዲያመጡት አዘዘ። 7 ጳውሎስም በደረሰ ጊዜ፣ ከኢየሩሳሌም የመጡት አይሁድ በአጠገቡ ቆሙ፤ በማስረጃ ማረጋገጥ ያልቻሉትን ብዙ ከባድ ክስም
አቀረቡ። 8 ጳውሎስ፣ “በአይሁድ ስምም ላይ፣ በቤተ መቅደሱም ላይ፣ በቄሣርም ላይ በደል አልፈጸምሁም” ብሎ ራሱን ተከላከለ። 9 ፊስጦስ ግን አይሁድን
ለማስደሰት ፈለገ፤ ስለሆነም፣ “እስከ ኢየሩሳሌም መውጣትና ስለ እነዚህ ነገሮች በዚያ ፍርድ እንድሰጥህ ትፈልጋለህን?” ብሎ ጳውሎስን ጠየቀው። 10
ጳውሎስም እንዲህ አለ፤ “ፍርድ ሊሰጠኝ በሚገባኝ በቄሣር የፍርድ ወንበር ፊት እቆማለሁ። አንተም ደግሞ በሚገባ እንደምታውቀው፣ አንድንም አይሁዳዊ
አልበደልሁም። 11 ብበድልና ሞት የሚገባውን ነገር አድርጌ ቢሆን እንኳ፣ አልሞትም አልልም። እነርሱ በእኔ ላይ የሚያቀርቡት ክስ ከንቱ ከሆነ ግን፣ ማንም
ለእነርሱ አሳልፎ ሊሰጠኝ አይችልም። ለቄሣር ይግባኝ ብያለሁ።” 12 ከዚያም ፊስጦስ ከሸንጎው ጋር ተነጋግሮ፣ “ለቄሣር ይግባኝ ብለሃልና ወደ ቄሣር
ትሄዳለህ” ብሎ መለሰ። 13 ከጥቂት ቀናትም በኋላ ንጉሥ አግሪጳና በርኒቄ ፊስጦስን ለመጐብኘት ቂሣርያ ደረሱ። 14 ንጉሥ አግሪጳ በዚያ ብዙ ቀን
ከተቀመጠ በኋላ፣ ፊስጦስ የጳውሎስን ጉዳይ ለንጉሡ አቀረበ፤ እንዲህም አለ፤ “ፊልክ አስሮ የተወው አንድ ሰው በዚህ አለ። 15 እኔ በኢየሩሳሌም በነበርሁ
ጊዜ የካህናት አለቆችና የአይሁድ ሽማግሌዎች ክስ መሥርተውበት ለእኔ አመለከቱ፤ እንድፈርድበትም ለመኑኝ። 16 ለዚህም፣ የተከሰሰው ሰው በከሳሾቹ ፊት
ቀርቦ ለተከሰሰበት ነገር እንዲከላከል ዕድል ሳይሰጠው አንድን ሰው አሳልፎ መስጠት የሮማውያን ልማድ አይደለም ብዬ መልስ ሰጠሁ።” 17 ስለዚህ፣ እነርሱ
በአንድ ላይ ወደዚህ በመጡ ጊዜ፣ አልዘገየሁም፤ ነገር ግን በማግስቱ በፍርድ ወንበር ተቀምጬ ሰውዬውን እንዲያመጡት አዘዝሁ። 18 ከሳሾቹ ቆመው
በከሰሱት ጊዜ፣ ካቀረቡበት ክሶች ማንኛቸውም ከባድ አይደሉም ብዬ ዐሰብሁ። 19 ይልቁንም ስለ ገዛ ራሳቸው ሃይማኖትና ጳውሎስ ሕያው ነው ስለሚለው
ሞቶ ስለ ነበረው ኢየሱስ ከእርሱ ጋር ይከራከሩ ነበር። 20 ይህን ጉዳይ እንዴት እንደምመረምር ግራ ገብቶኝ ነበር፤ ስለ እነዚህ ነገሮችም በዚያ ለመፋረድ ወደ
ኢየሩሳሌም ይሄድ እንደ ሆነ ጳውሎስን ጠየቅሁት። 21 ጳውሎስ ግን የንጉሠ ነገሥቱን ውሳኔ እስኪያገኝ፣ በዘብ እንዲጠበቅ ይግባኝ ባለ ጊዜ፣ ወደ ቄሣር
እስክሰደው ድረስ በጥበቃ ሥር እንዲሆን አዘዝሁት።” 22 አግሪጳ፣ “እኔ ደግሞ ይህን ሰው ልሰማው እፈልጋለሁ” ብሎ ፊስጦስን አነጋገረው። ፊስጦስም፣
“ነገ ትሰማዋለህ” አለው። 23 ስለ ሆነም፣ በማግስቱ፣ አግሪጳና በርኒቄ በታላቅ ሥነ ሥርዓት ከወታደራዊ መኮንኖችና ከከተማዋ ታዋቂ ሰዎች ጋር ወደ አዳራሹ
ገቡ። በፊስጦስ ትእዛዝም ጊዜ ጳውሎስን ወደ እነርሱ አመጡት። 24 ፊስጦስም እንዲህ አለ፤ “ንጉሥ አግሪጳ ሆይ፣ እዚህ ከእኛ ጋር ያላችሁትም ሰዎች ሁሉ፣
ይህን ሰው ተመልከቱት፤ በኢየሩሳሌምና እዚህም ያሉት የአይሁድ ሕዝብ ሁሉ ከእኔ ጋር ተማከሩ፤ ይህ ሰው ከእንግዲህ ወዲያ በሕይወት መኖር የለበትም
ብለውም ጮኹብኝ። 25 እኔ ግን ለሞት የሚያበቃው ምንም በደል አለመፍጸሙን ዐወቅሁ፤ ነገር ግን ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ይግባኝ በማለቱ ልሰደው ወሰንሁ። 26
ሆኖም ለንጉሠ ነገሥቱ ለመጻፍ አሳማኝ ነገር የለኝም። በዚህ ምክንያት ስለ ጉዳዩ የምጽፈው ነገር እንዲኖረኝ፣ በተለይ ንጉሥ አግሪጳ ሆይ፣ ወደ አንተ
አምጥቼዋለሁ። 27 አንድን እስረኛ መስደድና የቀረበበትን ክስም አለመግለጽ ለእኔ ምክንያታዊ ያልሆነ ይመስለኛልና።”

Acts 25:1

የሐዋርያት ሥራ 25፡ 1-3
አጠቃላይ መረጃ: አሁን ፊስጦስ የቄሳሪያ አገረ ገዥ ሆኗል። አሁን ይህ በታኩ ውስጥ የተከናወነው ቀጣዩ ነገር ምን እንደሆነ ምልክት ሆኖ ያሳየናል። ፊስጦስ ወደ መንደሩ ገባ አማራጭ ትርጉሞች 1) በቀላሉ ፊስጦስ ወደ አከባቢው መጣ ወይም 2) ፊስጦስ አከባቢውን ማስተዳደር ጀመረ። (UDB). ከቄሣሪያ አንስቶ እስከ ኢየሩሳሌም ድረስ ሄደ አማራጭ ትርጉሞች 1) ኢየሩሳሌም ወደ ላይ አድርጎ ማቀመጡ ኢየሩሳሌም ጠቃሚ መሆኗን የሚያሳይ ነው ወይም 2) ኢየሩሳሌም በተራራ ላይ ያለች ከተማ በመሆኗ ወደ ከፍታ መውጣቱን የሚያሳይ ነው። ጳውሎስ ላይ ክስ አቀረቡበት ይህ በፍርድቤት መደበኛ ክስ ማቅረባቸውን ያሳያል። አማራጭ ትርጉም: "ጳውሎስ ሕግጋትን መተላለፉን የሚያሳይ ክስ አቀረቡበት።" በፊስጦስ ፊት አጥብቀው ከሰሱት "ፊስጦስን ለመኑት" ወይም "ፊስጦስን ጠየቁት" ይጠራው ዘንድ . . . እነርሱም እርሱን መግደል ይችሉ ዘንድ "ፊስጦስ ጳውሎስን ይጠራው ዘንድ . . . አይሁዳዊያንም ጳውሎስን መግደል ይችሉ ዘንድ" ይጠራው ዘንድ "ይልከው ዘንድ" በመንገድ ላይም እነርሱ መግደል ይችሉ ዘንድ ጳውሎስን በመንገድ ላይ ተደብቀው ልገድሉት ይፈልጉ ነበር።

Acts 25:4

የሐዋርያት ሥራ 25፡ 4-5
ጳውሎስ በቄሣሪያ እስረኛ ነበር አማራጭ ትርጉም: "ጳውሎስ በቄሣሪያ እስረኛ ከመሆኑ የተነሣ እኔ እራሴ ወደዚያ በፍጥነት እመለሳለሁ።" ይህ ሰው ላይ አንዳች ነገር አድርጎ ከሆነ "ጳውሎስ ላይ ጥፋት የተገኘ እንደሆነ" ልትከሱት ትችላላችሁ "ክስ ልታቀርቡበት ትችላላችሁ" ወይም "የተላለፈውን ሕግ በማንሳት ልትከሱት ትችላላችሁ"

Acts 25:6

የሐዋርያት ሥራ 25፡ 6-8
በዚያ ከቆየ በኋላ "ፊስጦስ በዚያ ቆየ" በፍርድ ወንበር ላይ ተቀመጠ "እንደ ዳኛ ሆኖ በሚፈርድበት ወንበር ላይ ተቀመጠ" ጳውሎስም በፊቱ እንዲቆም ተደረገ አማራጭ ትርጉም: "ጳውሎስንም በፊቱ አቀረቡ" በመጣ ጊዜም "ጳውሎስ በመጣና በፊስጦስ ፊት በቆመ ጊዜ" የአይሁዳዊያን ስም "የአይሁዳዊያን ሕግ" (UDB) የቤተ መቅደሱን ሐህግ አለመተላለፉን ጳውሎስ ወደ ቤተ መቅደሱ ማን መግባት ይችላል የሚለውን ሐህግ አለመተላለፉን ተናገረ። አማራጭ ትርጉም: "ወደ ቤተ መቅደሱ መግባት የሚችሉሰዎች ሕግን አልመተላለፉን"

Acts 25:9

የሐዋርያት ሥራ 25፡ 9-10
በአይሁዳዊያን ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት ስለፈለገ "አይሁዳዊያንን ማስደሰት ስለፈለገ" እነዚህን ነገሮች ለመዳኘት እኔ አልችልም አማራጭ ትርጉም: "እነዚህን ነገሮች አስመልክቶ እኔ ምንም ቢያኔ መስጠት አልችልም" እነኔ ፍርድ መስጠት የሚችለው አማራጭ ትርጉም: "በእኔ ላይ ፍርድ መስጠት የሚችልበት ሥፍራ"

Acts 25:11

የሐዋርያት ሥራ 25፡ 11-12
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ከፊስጦስ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል። እኔ ያደረኩት ነገር ለሞት የሚያበቃ ከሆነ "ለሞት ቅጣት የሚያበቃ ጥፋት ፈጽሜ ከሆነ" ክሳቸው ትክክል ካልሆነ "የከሰሰኝ ክስ ትክክል ካልሆነ" ማንም

ለእነርሱ አሳልፎ ልሰጠኝ አይችልም አማራጭ ትርጉሞች 1) ፊስጦስ ለእነዚህ በሐሰት ለከሰሱት ሰዎች አሳልፎ ልሰጠው የሚስችል ምን ሕጋዊ ሥልጣን የለውም ወይም 2) ጳውሎስ እያለ ያለው ያቀረቡት ክስ መሠረት ያሌለው ከሆነ ሀገረ ገዥው በአይሁዳዊያን ጥያቄ መሠረት ለእነርሱ አሳልፎ ልሰጠው አይገባም። ወደ ቄሣር ይግባኝ አለ "ቄሣር ይዳኘኝ ዘንድ በእርሱ ፊት መቅረብ እፈልጋለሁ" ፊስጦስ ከሸንጎዎቹ ጋር ተመካከረ በዚህ ሥፍራ ላይ “ሸንጎ” ተበሎ የተጠቀሰው በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ በአጠቃላይ የተጠቀሰው የአይሁድ ሸንጎ አይደለም። ይህ በሮም አገዛዝ ውስጥ ያለ ፖለቲካዊ ሸብጎ ነው። አማራጭ ትርጉም: "ፊስጦስ ከራሱ የአስተዳደር አማካሪዎች ጋር ተነጋገረ።"

Acts 25:13

የሐዋርያት ሥራ **25: 13-16**
አጠቃላይ መረጃ: ፊስጦስ የጳውሎስን ጉዳይ ለንጉሥ አግሪጳ ማስረዳት ጀመረ። አሁን ይህ ቃል በታሪኩ ውስጥ አዲስ ነገር መጀመሩን የሚያሳይ ነው። ንጉሥ አግሪጳ በርኒቄ አግሪጳ በዚያ ዘመን የነገሠ ንጉሥ ሲሆን በርኒቄ ደግሞ እህቱ ናት። ለፊስጢስ ኦፍሳሌያዊ ክፍያ ለመፈጸም "ፊስጢስን በኦፍሴላዊ ጉዳይ ለመጎብኘት" አንድ ሰው ፊስጦስእስረኛ ሆኖ ወደኋላ ቀርቶ ነበር አማራጭ ትርጉም: "ፊስጦስ ቢሮን ትቶ ሲሄድ ሰውዬውን በዚህ በእስር ትቶት ሄዶ ነበር።"

Acts 25:17

የሐዋርያት ሥራ **25: 17-20**
ስለዚህ በዚህ ሥፍራ ላይ “ስለዚህ” የሚለው ቃል ከዚህ በፊት በተነገረ አንድ ነገር ምክንያት ይህ እንደሆነ ያሳያል። በዚህ ሁኔታ ውስጥም ፊስጦስ የተከሰሰው ሰው ከከሳሾቹ ጋር መገናኘት እና መከላከያ ሀሳቡን ማቅረብ አለበት ብሏል። ሁሉም ስገናኙ "የአይሁድ መሪዎች በዚህ ከእኔ ጋር ለመገናኘት በመጡ ጊዜ" በፍርድ ወንበር ላይ እቀመጣለሁ "እንደ ዳኛ ሆኜ በምፈርድበት ወንበር ላይ እቀመጣለሁ" (ተመልከት: ACT 25:6) ሰውዬው እንዲመጣ አዝኩ አማራጭ ትርጉም: ወታደሮቹ ጳውሎስን ወደፊት ይዘውት ይመጡ ዘንድ አዘዝኩኝ" ስለራሳቸው ሃይማኖት “ሃይማኖት” የሚለው ቃል ሰዎች ስለ ሕይወት እና ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል ያላቸው እምነት ነው። ስለእነዚህ ነገሮች በዚያ ቤታ ፍርድ ይሰጣቸው ዘንድ አማራጭ ትርጉም: "የአይሁድ ሸንጎ በእነዚህ ጉዳዮች በተለከ ይህ ሰው ጥፋተኛ አድረገው ወሰኑበት"

Acts 25:21

የሐዋርያት ሥራ **25: 21-22**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ፊስጦስ ጉዳዩን ለንጉሥ አግሪጳ ማብራራቱን አጠናቀቀ። እንድጠብቁት አዘዝኳቸው አማራጭ ትርጉም: "ወታደሮች በእስር ቤት ውስጥ እንዲጠብቁት አዘዝኳቸሁ" "ነገ፣" ፊስጦስ እንዲህ አለ፣ "ትሰሙታላችሁ።" "ፊስጦስ እንዲህ አለ፣ 'ነገ ጳውሎስ ስናገር መስማት ትችሉ ዘንድ አመቻቻለሁ።'"

Acts 25:23

የሐዋርያት ሥራ **25: 23-24**
አግሪጳ እና በርኒቄ እነዚህ ስሞች በ ACT 25:13 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምካቸው ተመልከት። ጳውሎስ ወደ እነርሱ ዘንድ ቀረበ አማራጭ ትርጉም: "ጳውሎስን በእነርሱ ፊት ይቀር ዘንድ ይዘውት መጡ። ወደ እኔ ጮኹ "አይሁዳዊያን በእኔ ላይ ተቆጥተው ተናገሩ" ከእንግዲህ ወዲህ በሕይወት ልኖር ፈጽሞ አይገባውም ይህ ዓረፍተ ነገር አጽኖት ሰጥቶ የሚያስተላልፈው ከተባለው በተቃራኒ የሆነውን ነገር ነው። አማራጭ ትርጉም: "በአፋጣኝ መሞት ይኖርበታል።"

Acts 25:25

የሐዋርያት ሥራ **25: 25-27**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ፊስጦስ ለንጉሥ አግሪጳ መናገሩን ቀጥሏል። እርሱን ወደ እናንተ ዘንድ ይዤው መጣሁ፣ በተለይም ወደ አንተ ወደ ንጉሥ አግሪጳ ዘንድ "ጳውሎስን ወደ እናንተ ሁሉ ዘንድ ይዤው መጣሁ ነገር ግን በተለይም አንተ ንጉሥ አግሪጳ ስለዚህ ተጨማሪ መጻሐፍ የሚችለው ነገር ይኖረኝ ዘንድ "ስለዚህ ሌላ መጻፍ እችል ዘንድ" ወይም "ስለዚህ ምን መጻፍ እንዳለብኝ አውቅ ዘንድ" አንድን እስረኛን የታሰረበት ምክንያት ምን እንደሆ በግልጽ ሳይጠቀስ ዝም ብሎ መላክ ምክንያታዊ አልመስል ብሎኛል "አንድን እስረኛ የታሠረበት ምክንያት ምን እንደሆነ በግልጽ ጽፎ መላክ ምክንያታዊ መስሎ ታይቶኛል" በእርሱ ላይ ያላቸው ክስ አማራጭ ትርጉሞች 1) የአይሁድ መሪዎች በእርሱ ላይ ያቀረቡት ክስ ወይም 2) በሮማዊያን ሕግ መሠረት ጳውሎስ ሊከሰስበት የሚችለው አንቀጽ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 26

1 አግሪጳም ጳውሎስን፣ «አንተ ለራስህ ተናገር» አለው። ከዚያም በኋላ፣ ጳውሎስ እጁን ዘርግቶ መከላከያውን አቀረበ። 2 «ንጉሥ አግሪጳ ሆይ፣ ዛሬ በፊትህ
አይሁድ ስለ ከፈቱብኝ ክስ ሁሉ መከላከያዬን ሳቀርብ ራሴን ደስተኛ አድርጌ እቈጥረዋለሁ፤ 3 ምክንያቱም በተለይ አንተ የአይሁድን ልማድና ጥያቄ ሁሉ
ጠንቅቀህ ታውቃለህ። ስለዚህ በትግዕሥት እንድታደምጠኝ እለምንሃለሁ። 4 በእውነት ከልጅነቴ ጀምሮ በሕዝቤ መካከልና በኢየሩሳሌም እንዴት እንደ ኖርሁ
አይሁድ ሁሉ ያውቃሉ። 5 ከመጀመሪያው አንሥቶ እኔን ያውቁኛል፤ የሃይማኖታችን በጣም ወግ አጥባቂ ክፍል ፈሪሳዊ ሆኜ እንደ ኖርሁም ሊያምኑ ይገባል። 6
አሁን እዚህ ለፍርድ የቆምሁት እግዚአብሔር ለአባቶቻችን የሰጠውን ተስፋ የምፈልግ በመሆኔ ነው። 7 በዚህ ምክንያት ዐሥራ ሁለቱ ነገዶቻችን ቀንና ሌሊት
በቅንነት እግዚአብሔርን ያገለግላሉ፤ እኛም ወደ እርሱ ለመድረስ ተስፋ እናደርጋለን። ንጉሥ ሆይ፣ አይሁድ እኔን የሚከሱኝ ስለዚህ ተስፋ ነው! 8 እግዚአብሔር
ሙታንን እንደሚያስነሣ አይታመንም ብላችሁ ለምን ታስባላችሁ? 9 አንድ ጊዜ እኔ የናዝሬቱ ኢየሱስን ስም በመቃወም ብዙ ነገር ማድረግ አለብኝ ብዬ ዐሰብሁ።
10 በኢየሩሳሌምም ይህንኑ አደረግሁ፤ ከምእመናን ብዙዎችን ወኅኒ እንዲገቡ አደረግሁ፤ ለዚህም ከካህናት አለቆች ሥልጣን ተቀብዬ ነበር፤ በሚገደሉበት
ጊዜም፣ ተስማምቻለው። 11 ብዙ ጊዜም በምኵራቦች ሁሉ እንዲቀጡ አድርጌአለሁ፤ የስድብ ቃል እንዲናገሩም ጥረት አድርጌአለሁ። ምእመናኑን እጅግ
እቈጣቸውና ሌሎች ከተሞች እንኳ አሳድዳቸው ነበር። 12 ይህን እያደረግሁ፣ ከካህናት አለቆች ሥልጣንና ትእዛዝ ተቀብዬ ወደ ደማስቆ ሄድሁ፤ 13 ወደዚያ
በመጓዝ ላይ እያለሁም ንጉሥ ሆይ፣ እኩለ ቀን ላይ ከፀሐይ ይልቅ የሚያበራ ብርሃን ከሰማይ አየሁ፤ በእኔና አብረውኝ ይጓዙ በነበሩት ሰዎች ዙሪያም አበራ። 14
ሁላችንም በመሬት ላይ በወደቅን ጊዜ፣ በዕብራይስጥ ቋንቋ፣ «ሳውል፣ ሳውል፣ ስለ ምን ታሳድደኛለህ? የመውጊያውን ብረት ብትረግጥ ለአንተ ይከፋብሃል»
የሚል ድምፅ ሲናገረኝ ሰማሁ። 15 እኔም፣ 'ጌታ ሆይ፣ አንተ ማን ነህ?' አልሁ። ጌታም እንዲህ ብሎ መለሰልኝ፤ 'አንተ የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ። 16
ተነሣና በእግርህ ቁም፤ እኔ የተገለጥሁልህ አሁን ስለ እኔ ስለምታውቃቸውና ኋላ ላይ ስለማሳይህ ነገሮች አገልጋዬና ምስክር እንድትሆን ልሾምህ ነው፤ 17 ወደ
እነርሱ ከምልክህ ሕዝብና ከአሕዛብም አድንሃለሁ ፤ 18 ዐይናቸውን እንድትከፍትላቸውና ከጨለማ ወደ ብርሃን፣ ከሰይጣን ኃይልም ወደ እግዚአብሔር
እንድትመልሳቸው አደርግሃለሁ፤ ይኸውም በእኔ በማመናቸው ለራሴ የለየኋቸው እነርሱ፣ ከእግዚአብሔር የኃጢአትን ይቅርታና ርስትን እንዲቀበሉ ነው።' 19
ስለዚህ፣ ንጉሥ አግሪጳ ሆይ፣ ለሰማያዊው ራእይ አልታዘዝም አላልሁም፤ 20 ነገር ግን መጀመሪያ በደማስቆ ላሉት፣ ከዚያም በኢየሩሳሌም፣ በመላው ይሁዳ፣
ደግሞም ለአሕዛብ ንስሓ እንዲገቡ፣ ወደ እግዚአብሔር ዘወር እንዲሉና ለንስሓ የሚገባ ሥራ እንዲሠሩ ሰበክሁ። 21 በዚህ ምክንያት አይሁድ በቤተ መቅደስ
ያዙኝና ሊገድሉኝ ሞከሩ። 22 እስካሁን ድረስ እግዚአብሔር ረድቶኛል፤ ስለዚህ ለታናናሾችና ለታላላቆች ለመመስከር እዚህ ቆሜአለሁ፤ ምስክርነቴም ሙሴና
ነቢያት ይሆናል ብለው ከተናገሩት የሚያልፍ አይደለም፤ 23 ይኸውም ክርስቶስ መከራ ይቀበላል፤ ከሙታን ለመነሣትና ለአይሁድ ሕዝብ፣ ለአሕዛብም ብርሃንን
ለመስበክ የመጀመሪያው ይሆናል የሚል ነው። 24 ጳውሎስም መከላከያውን እንደ ጨረሰ ፊስጦስ፣ «ጳውሎስ፣ አንተ ዕብድ ነህ፤ ብዙ መማርህ አሳብዶሃል»
ሲል ጮኾ ተናገረ። 25 ጳውሎስ ግን እንዲህ አለ፤ «እጅግ የተከበርህ ፊስጦስ ሆይ፣ እኔ ዕብድ አይደለሁም፤ ነገር ግን እውነተኛውንና ትክክለኛውን ቃል
በድፍረት እናገራለሁ። 26 ንጉሡ ስለ እነዚህ ነገሮች ያውቃልና እንደ ልብ እነግረዋለሁ፤ በመሆኑም ከእነዚህ ነገሮች አንዱም ከእርሱ የተሰወረ እንዳልሆነ
እርግጠኛ ነኝ። 27 ንጉሥ አግሪጳ ሆይ፣ በነቢያት ታምናለህን? እንደምታምን ዐውቃለሁ።» 28 አግሪጳም ጳውሎስን፣ «በአጭር ጊዜ ልታሳምነኝና ክርስቲያን
ልታደርገኝ ትፈልጋለህን?» አለው። 29 ጳውሎስም፣ «በአጭር ይሁን ወይም በረዥም ጊዜ፣ አንተ ብቻ ሳትሆን፣ ዛሬ የሚሰሙኝ ሁሉ፣ ከእነዚህ የወኅኒ
ሰንሰለቶች በቀር እንደ እኔ እንድትሆኑ ወደ እግዚአብሔር እጸልያለሁ» አለ። 30 ከዚያም ንጉሡ፣ ገዥውም፣ በርኒቄም ደግሞ፣ ከእነርሱ ጋር ተቀምጠው
የነበሩትም ተነሡ፤ 31 ከአዳራሹም በወጡ ጊዜ፣ እርስ በርስ ተነጋግረው ፣«ይህ ሰው ለሞት ወይም ለእስራት የሚያበቃ ምንም አላደረገም» አሉ። 32 አግሪጳ
ፊስጦስን፣ «ይህ ሰው ወደ ቄሣር ይግባኝ ባይል ኖሮ በነጻ ሊለቀቅ ይችል ነበር» አለው።

Acts 26:1

የሐዋርያት ሥራ 26፡ 1-3
አያያዥ ዓረፈተ ነገር : ፊስጦስ ጳውሎስን በንግሥ አግሪጳ ፊት አቀረበው። በቁጥር 2 ላይ ለንግሥ አግሪጳ ለተከሰሰበት ክስ ምላሽ መስጠት ጀመረ። እጆቹን ዘርግቶ "የሕዝቡን ትኩረት ማግኘት ይችል ዘንድ ወደሕዝቡ እጆቹን ዘርግቶ" ለተከሰሰበት ክስ መልስ ሰጠ "ለተከሰሰበት ክስ መልስ መስጠት ጀመረ" ራሴን ደስተኛ ሰው አድርጌ እቆጥረዋለሁ ጳውሎስ ደስተኛ ነበር ምክንያቱም በንጉሥ አግሪጳ ፊት መቆሙ ወንጌልን ለመናገር እድል ስለምሰጠው ነው።

Acts 26:4

የሐዋርያት ሥራ 26፡ 4-5
አይሁዳዊያን ሁሉ አማራጭ ትርጉሞች 1) ከጳውሎስ ጋር ያደጉት እና ፈርሳዊ ሆኖ የሚያውቁት አይሁዳዊያን ወይም 2) "ጳውሎስ በፈሪሳዊነቱ ከነበረው ቅናት የተነሣ በአይሁዳዊያን ዘንድ የታወቀ ነበር እንዲሁመም በአማኝነቱም የታወቀ ነው።" በራሴ ሀገር አማራጭ ትርጉም 1) በራሱ ሕዝብ መካከል፣ ይህ ማለት የግድ በእስራኤል መልከአምድር ውስጥ ማለት ላይሆን ይችላል ወይም 2) በእስራኤል ምድር ውስጥ።

Acts 26:6

የሐዋርያት ሥራ 26፡ 6-8
አሁን ጳውሎስ ይህንን ቃል የተጠቀመው ለተከሰሰበት ክስ መልስ በመስጠት ሂደት ውስጥ ወደሌላኛው መከራከሪያ ነጥቡ መሰጋገሩን ለማሳየት ነው። ዛሬ ፍርድ ለመቀበል በዚህ እገኛለሁ አማራጭ ትርጉም: "እነርሱ ከሰውኝ ዘሬ በዚህ አለሁ" እግዚብሔር ለአባቶቻችን የገባውን ቃል እጠባበቃለሁ ጳውሎስ የመስሑን መምጣት ይጠብቃል። ወደዚያ እንደሚንደርስ ተስፋ እናደርጋለን። "እግዚአብሔር የገባውን ተስፋ እንደሚንቀበል ተስፋ እናደርጋለን" እግዚአብሔር የሞተ ሰውን ማስነሳቱ ይህንን ያኽል የማይታመን ነው ብላችሁ ስለምን አሰባችሁ? ጳውሎስ ይህንን ንግግር የተናገረው አግሪጳ ጳውሎስ የተናገረው ነገር አግሪጳ ከዚህ በፊት እግዚአብሔር ሰዎችን ከሞት ማስነሳት እንደሚችል በማመኑ ምክንያት ከዚያ ጋር ለማያያዝ ነው። አማራጭ ትርጉም: "አንተ ራሰህ እግዚአብሔር ሰውን ከሞት ልያስነሣ ይችላል ብለሃል!"

Acts 26:9

ሐዋርያት ሠስራ 26፡ 9-11
በአንድ ጊዜ ጳውሎስ ይህንን ሀረግ የተጠቀመው ለክሱ የመከራከሪያ ሀሳቡን በማቅረብ ሂደት ውስጥ ለውጥ መኖሩን ለማሳየት ነው። ዘሂን ደግሞ እንዴት ቅዱሳንን ያሳድድ እንደነበር መናገር ጀመረ። የኢየሱስን ስም በመቃወም በዚህ ሥፍራ ላይ “ስም” የሚለው ቃል የኢየሱስን መልዕክ የሚውክል ነው። አማራጭ ትርጉም: "የኢየሱስን መልዕክት በመቃወም።" እነርሱን በመቃወም

ድምፄን ሰጥቻለሁ "እነርሱን ለመቅጣት ደምፅ ሰጥቻለሁ" ብዙ ጊዜ እቀጣቸው ነበር አማራጭ ትርጉሞች 1) ጳውሎስ የተወሰኑ አማኞችን ብዙ ጊዜ ቀጥቶዋቸዋል ወይም 2) ጳውሎስ ብዙና የተለያዩ አማኞችን ቀጥቶዋል።

Acts 26:12

የሐዋርያት ሥራ **26**: **12**-**14**
ይህንን በማድረግ ላይ ሳለሁ ጳውሎስ ይህንን ሀረግ የተጠቀመው በክርክር ሀሳኑ ላይ ሌላ ለውጥ መኖሩን ለማሳየት ነው። አሁን ኢዩስን ከማሳደድ እርሱን ወደ መከተል ኢያሱስ እንዴት እደለወጠው መናገር ጀመረ። እያለe ይህ ቃል በሆነ ጊዜ የተጀመሩ ሁለት ነገሮችን ያመለክታል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ጳውሎስ ቅዱሳንን በማሳደድ ላይ ሳለ ወደ ደማስቆ ሄዶ ነበር። ስልጣን ተሰጥቶ እንዲሁም ማዘዣ ወረቀት ይዞ ጳውሎስ ከአይሁድ መሪዎች ዘንድ የተሰጠው አይሁዳዊያን አማኞች ለማሳደድ የሚያስችለው ስልጣን የተሰጠበት ደብዳቤ በእጁ ይዞ ነበር። . እግዚአብሔር መቃወም በጣም ከባድ ነው ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ዕቅድ መቃወምን በሬ የአራሹን በተር ከመቃወም ጋር እግዚአብሔር እንዳነጻጸረ ተናገረ።

Acts 26:15

የሐዋርያት ሥራ **26**: **15**-**18**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ለንጉሥ አግሪጳ የመከራከሪያ ሀሳቡን ማቅረቡን ቀጥሏል። በእነዚህ ቁጥሮ ከጌታ ጋር ያደረገውን ነግግር በቀጥታ እያጣቀሰ ይናገራል። ለእኔ ለራሴ ለይቼሃለሁ "የራሴ አድርጌሃለሁ" (UDB) ወይም "ለራሴ ለይቼሃለሁ" በእኔ ላይ ባለህ እምነት ይህ በእግዚአብሔር ማመን እግዚብሔር ለራሱ የለያቸው ሰዎች መሆኑን ያሳያል። በእኔ ላይ ካላቸው እምነት የተነሣ ለራሴ የለየኋቸው ጳውሎስ የጌታን ንግግር በቀጥታ መጥቀሱን ጨርሶዋል።

Acts 26:19

የሐዋርያት ሥራ **26**: **19**-**21**
ስለዚህ በዚህ ሥፍራ ላይ “ስለዚህ” የሚለው ቃል ከዚህ በፊት በተነገረ አንድ ነገር ምክንያት ይህ እንደሆነ ያሳያል። በዚህ ሁኔታ ውሰጥም ጳውሎስ ጌታ በራዕይ ምን እንዳሳየው ከዚህ በፊት አብራርቶ ጨርሷል። ሰማያዊውን ራዕይ ለመታዘዝ አሻፈረኝ አላልኩም "በዚህ ራዕይ ከሰማይ መጥቶ ለተሰጠኝን መልዕክት ታዝዤያለሁ"

Acts 26:22

የሐዋርያት ሥራ **26**: **22**-**23**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ለንጉሥ አግሪጳ ያቀረበውን የመከራከሪያ ሀሳብ አጠናቀቀ።. ነቢያት ያሉት ነገር ጳውሎስ የብሉይ ኪዳን ነቢያት ጽሑፎች ስብስብን እያመለከተ ነው። ክርስስ መከራን እነንዲቀበል "ክርስቶስ መከራን ይቀበል ዘንድ እና እንዲሞት" ብርሃንን ያውጅ ዘንድ "የድነትን መልዕክት ይናገር ዘንድ"

Acts 26:24

የሐዋርያት ሥራ **26**: **24**-**26**
አንተ አብደሃል "ትርጉም ያሌለው ነገር መናገር ጀምረሃል" ወይም "አብደሃል" አላበድኩም "ጤነኛ ነኝ" ወይም "የማስበውም በትክክል ነው" በጥንቃቄ ልታሰብበት የሚገባ ነገር ነው "ጥንቃቄ ያስፈልገዋል" ወይም "ጥንቃ የሚያስፈልገው ጉዳይ" ለእርሱ በግልጽ ነገርኩት "ለንጉስ አግሪጳ በግልጽ ነገርኩት" ይህ በድብቅ የተደረገ ነገር አይደለም "በምስጥር የተደረገ ነገር አይደለም"

Acts 26:27

የሐዋርያት ሥራ **26**: **27**-**29**
ንጉሥ አግሪጳ ሆይ በነቢያት ታምናለህን? ጳውሎስ ይህንን ጥያቄ ለንጉሥ አግሪጳ የጠየቀው ንጉሥ አግሪጳ ነቢያት ስለ ኢየሱስ የተናገሩትን ነገር ያምን ስለነበረ ለማስታወስ ነው። አማራጭ ትርጉም: "የአይሁድ ነቢያት የተናገሩትን ነገር አንተ ታምናለህ!" በዚህ አጭር ጊዜ ልታሳምነኝ እና ክርስትያን ልታደረገኝ ትፈልጋለህን? አግሪጳ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው ጳውሎስ ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎችን ሳያቀርብ አግሪጳን እንዲሁ በቀላሉ ማሳመን እንደማይችል ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም: "እኔን እንዲሁ በቀላሉ ማሳመን እችላለሁ ብለህ አስበሃል!"

Acts 26:30

የሐዋርያት ሥራ **26**: **30**-**32**
ከዚያም ንጉሡ እና አገረ ገዥው ከመቀመጫቸው ተነሡ "ከዚያም ንጉሥ አግሪጳ እና አገረ ገዥው ፊስጦስ ከመቀመጫቸው ተነሡ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 27

1 ወደ ኢጣሊያ በመርከብ እንድንሄድ በተወሰነ ጊዜ፣ ጳውሎስንና ሌሎችን እስረኞች የአውግስጦስ ክፍለ ጦር አባል ለሆነ ዩልዮስ ለተባለ የመቶ አለቃ አስረከቡአቸው። 2 እኛም ከአድራሚጥዮን ተነሥተን በእስያ ጠረፍ ሊሄድ በተዘጋጀ መርከብ ላይ ተሳፍረን ወደ ባሕር ተጓዝን። በመቄዶንያ ካለችው ተሰሎንቄ የሆነው አርስጥሮኮስም ከእኛ ጋር ሄደ። 3 በማግስቱ ወደ ሲዶን ከተማ ደርሰን፣ ከመርከብ ወረድን፤ እዚያም ዩልዮስ ለጳውሎስ ቸርነት አደረገለት፤ ወደ ወዳጆቹ እንዲሄድና እንክብካቤ እንዲያደርጉለትም ፈቀደለት። 4 ከዚያም ተነሥተን ወደ ባሕር ሄድን፤ ነፋስ ይነፍስብን ስለ ነበር፣ በመርከብ ሆነን ነፋሱ በማያገኛት በቆጵሮስ ደሴት ዙሪያ ተጓዝን። 5 በኪልቅያና በጵንፍልያ አጠገብ ያለውን ባሕር ከተሻገርን በኋላም፣ የሉቅያ ከተማ ወደ ሆነው ወደ ሙራ ደረስን። 6 በዚያም፣ የመቶ አለቃው ከእስክንድርያ ወደ ኢጣሊያ የሚሄድ መርከብ አግኝቶ አሳፈረን። 7 ብዙ ቀንም በዝግታ ተጓዝንና በመጨረሻ በችግር ወደ ቀኒዶስ ደረስን፤ ነፋሱም በዚያ መንገድ እንዳንሄድ ስለከለከለን፣ በሰልሙና አንጻር ያለችውን ቀርጤስን ተገን አድርገን ተጓዝን። 8 በላሲያ ከተማ አጠገብ ወዳለው መልካም ወደብ ወደ ተባለው ስፍራ እስከምንደርስ ድረስ በችግር በጠረፉ በኩል ተጓዝን። 9 ብዙ ጊዜም አሳለፍን፤ የአይሁድ የጾም ወራት ደግሞ ዐልፎ ነበር፤ ጕዞውን መቀጠልም አደጋ የሚያስከትል ነበር። ስለዚህ ጳውሎስ አስጠነቀቃቸው፤ 10 እንዲህም አለ፤ “እናንተ ሰዎች፣ አሁን የምናደርገው ጕዞ አደጋና ብዙ ጉዳት እንደሚኖርበት ይታየኛል፤ አደጋውም በመርከቡና በጭነቱ ብቻ ሳይሆን፣ በእኛም ሕይወት ላይ የሚደርስ ነው።” 11 የመቶ አለቃው የሰማው ግን ጳውሎስ የተናገረውን ሳይሆን፣ በይበልጥ የመርከቡ አዛዥና ባለቤት ያሉትን ነው። 12 ክረምቱን ለማሳለፍ ወደቡ ተስማሚ ስላልነበረ፣ አብዛኛዎቹ ተጓዦች የሚቻል ከሆነ ከዚያ ተነሥተን ፊንቄ ወደ ተባለችው ከተማ እንድንሄድና ክረምቱን እዚያ እንድናሳልፍ ምክር ሰጡን። ፊንቄ በሰሜን ምሥራቅና በደቡብ ምሥራቅ አንጻር የምትገኝ የቀርጤስ ወደብ ነች። 13 የደቡቡ ነፋስ በቀስታ መንፈስ በጀመረ ጊዜ፣ መርከበኞቹ የፈለጉት እንደተከናወነላቸው ዐሰቡ። ስለዚህ ሸራውን አውርደው በባሕሩ ዳርቻ አቅራቢያ፣ በቀርጤስ በኩል አለፉ። 14 ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን፣ የሰሜን ምሥራቅ ዐውሎ ነፋስ የተባለ ኃይለኛ ነፋስ ደሴቲቱን አቋርጦ በመምጣት ይነፍስብን ጀመረ፤ 15 መርከቡም ወደ ፊት በተገፋና ነፋሱን መቋቋም ባልቻለ ጊዜ፣ ዝም ብለነው በነፋሱ እየተነዳን ሄድን። 16 ቄዳ የተባለችውን ትንሽ ደሴት ተተግነን ተጓዝን፤ በትልቅ ችግርም ሕይወት አድን ጀልባው ላይ መውጣት ቻልን። 17 መርከበኞቹ ጀልባውን ወደ መርከቡ ጎትተው አወጡት፤ ገመዱንም የመርከቡን ዙሪያ ለማሰር ተጠቀሙበት። ስርቲስ በምትባል አሸዋማ ስፍራ እንዳንወድቅ ፈርተው ነበር፤ ስለዚህ የባሕር ሸራውን አውርደው እየተነዱ ሄዱ። 18 ዐውሎ ነፋሱ በጣም ስላየለብን፣ በማግስቱ መርከበኞቹ የመርከቡን ጭነት ወደ ባሕር መጣል ጀመሩ። 19 በሦስተኛው ቀን መርከበኞቹ በመርከቡ የሚያገለግሉ ዕቃዎችን እያነሡ ጣሉ። 20 ለብዙ ቀንም ፀሐይና ከዋክብት ብርሃናቸውን ባልሰጡንና ትልቁ ማዕበልም በወረደብን ጊዜ፣ አንድንም ብለን ተስፋ ቈረጥን። 21 ተጓዦቹ ምግብ ሳይበሉ ብዙ ቀን ቈይተው ነበር፤ በዚያን ጊዜ ጳውሎስ በተጓዦቹ መካከል ቆሞ እንዲህ አለ፤ “እናንተ ሰዎች፣ ይህ አደጋና ጉዳት እንዳይደርስባችሁ፣ ከቀርጤስ አትነሡ ብዬ የነገርኋችሁን መስማት ነበረባችሁ፤ 22 አሁንም መርከቡ ብቻ ይጎዳል እንጂ ከመካከላችሁ የሚሞት አይኖርምና አይዞአችሁ ብዬ እመክራችኋለሁ። 23 ምክንያቱም ባለፈው ሌሊት የእርሱ የሆንሁትና ደግሞም የማመልከው የእግዚአብሔር መልአክ በአጠገቤ ቆሞ እንዲህ ብሏል፤ 24 “ጳውሎስ ሆይ፣ አትፍራ። በቄሣር ፊት ልትቆም ይገባሃል፤ ተመልከት፤ እግዚአብሔር በቸርነቱ ዐብረውህ የሚጓዙትን ሁሉ ሰጥቶሃል። 25 ስለዚህ እናንተ ሰዎች፣ አይዞአችሁ፤ ልክ እንደ ተናገረኝ እንደሚሆን እግዚአብሔርን አምነዋለሁ። 26 ነገር ግን ወደ አንዲት ደሴት ደርሰን ልናርፍ ይገባል።” 27 በዐሥራ አራተኛውም ሌሊት፣ በአድርያቲክ ባሕር ወዲያና ወዲህ እየተንገላታን እያለን፣ እኩለ ሌሊት ገደማ፣ መርከበኞቹ ወደ መሬት የቀረቡ መሰላቸው። 28 የባሕር ጥልቀት መለኪያ ገመድ ጣሉና ጥልቀቱን አርባ ሜትር ሆኖ አገኙት፤ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ መለኪያውን ሲጥሉም ሠላሳ ሜትር ሆኖ አገኙት። 29 ከዐለቶቹ ጋር እንጋጫለን ብለውም ፈሩ፤ ስለዚህ ከኋላ አራት መልሕቆችን አውርደው ቶሎ እንዲነጋ ጸለዩ። 30 መርከበኞቹ መርከቡን ትተው ለመሄድ መንገድ ይፈልጉና ሕይወት አድን ጀልባውን ወደ ባሕሩ ውስጥ ያወርዱ ነበር፤ መልሕቆቹንም ከቀስቱ የሚወረውሩ መሰሉ። 31 ጳውሎስ ግን መቶ አለቃውንና ወታደሮቹን፣ “እነዚህ ሰዎች በመርከቡ ካልቆዩ በቀር፣ እናንተ መዳን አትችሉም” አላቸው። 32 ከዚያም ወታደሮቹ የጀልባውን ገመዶች ቈረጡት፤ እንዲንሳፈፍም አደረጉት። 33 ቀኑ ሊነጋ ሲልም፣ ምግብ እንዲበሉ ጳውሎስ ሁሉንም መከራቸው። እንዲህም አላቸው፤ “ምንም ሳትበሉ ከቈያችሁ ይህ ዐሥራ አራተኛ ቀናችሁ ነው። 34 ስለዚህ በሕይወት እንድትኖሩ፣ ጥቂት ምግብ እንድትበሉ እለምናችኋለሁ፤ ከራሳችሁ ላይ አንዲቱም ጠጕር አትጠፋም።” 35 ይህን ተናግሮ፣ እንጀራ አነሣና በሁሉም ፊት እግዚአብሔርን አመሰገነ። ከዚያም እንጀራውን ቈርሶ መብላት ጀመረ። 36 በዚያን ጊዜ ሁሉም ተጽናንተው ምግብ በሉ። 37 በመርከቡ ውስጥ 276 ሰዎች ነበርን። 38 በልተው በጠገቡ ጊዜም፣ ስንዴውን ወደ ባሕሩ በመጣል የመርከቡን ጭነት አቃለሉ። 39 በነጋታውም፣ የነበሩበትን ምድር አላወቁትም፤ ነገር ግን በዳርቻ ያለውን የባሕር ሰርጥ አዩ፤ መርከቡን ወደ ሰርጡ መግፋት ይችሉ እንደሆነም ተነጋገሩ። 40 ስለዚህ መልሕቆቹን ቈርጠው ባሕሩ ላይ ተዉአቸው። በዚሁ ጊዜም የመቅዘፊያዎቹን ገመዶች ፈትተው ሸራውን ወደ ነፋሱ ከፍ አደረጉና ወደ ባሕሩ ዳርቻ ለመውጣት ሄዱ። 41 ነገር ግን ሁለት ማዕበሎች ወደ ተገናኙበት ስፍራ መጡ፤ መርከቡም ወደ መሬት ገባ፤ የመርከቡ ቅስትም በዚያ ተተከለና የማይነቃነቅ ሆነ፤ የኋላ ክፍሉ ግን ከማዕበሉ ነውጥ የተነሣ ይሰባበር ጀመር። 42 የወታደሮቹ ዕቅድ ከመካከላቸው ማንም ዋኝቶ እንዳያመልጥ እስረኞቹን ለመግደል ነበር። 43 የመቶ አለቃው ግን ጳውሎስን ለማዳን ፈለገ፤ ስለዚህ ዕቅዳቸውን አልተቀበለም፤ መዋኘት የሚችሉትም በመጀመሪያ ከመርከቡ ላይ እየዘለሉ ወደ የብስ እንዲወጡ አዘዘ። 44 ከዚያም የቀሩት ሰዎች በሳንቃዎችና ከመርከቡ በተገኙ ስብርባሪዎች ላይ ሆነው ተከትለው እንዲወጡ አደረገ። በዚህ ዐይነት ሁላችንም በደኅና ወደ የብስ ወጣን።

Acts 27:1

የሐዋርያት ሥራ 27፡ 1-2
አጠቃላይ መረጃ: ጳውሎስ ወደ ሮም ጉዞ ጀመረ። ይህ በተወሰነ ጊዜ አማራጭ ትርጉም: "ሀገረ ገዥው ይህንን በወሰነ ጊዜ" በመርከብ መሄድ ጀመርን በዚህ ክፍል ውስጥ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጸሐፊውን ሉቃስን እና ጳውሎስን ነው። እርሱ ጳውሎስ ወደ ሮም ስጓዝ አብሮት ተጉዞ ነበር። ወደ ጣሊያን በመርከብ ሄዱ ጣሊያን በሮም ውስጥ ያለች የአንድ አከባቢ ስም ነው። ዩልዩስ የተባለ መቶ አለቃ ዩልዩስ የወንድ ስም ነው። የአውጉስጦስ ጭፍራ ይህ የብዙ ሠራዊት መጠሪያ ስም ነው ወይም መቶ አለቃው ያለበት የወታደር ቡድን ስም ነው። በአድራሚጢስ መርከብ አማራጭ ትርጉም 1) ከአድራሚጢስ የሚመጣ መርከብ ወይም 2) በአድራሚጢስ ስም የተመዘገበ ወይም ፈቃድ ያወጣ መርከብ። ይህ ምናልባት በዘሟ ቱርክ በምዕራብ አከባቢ የሚገኝ ሥፍራ ሊሆን ይችላል። በመርከብ ለመጓዝ ጸዘጋጅታ ሻሉ "ለመገዋዝ ተዘጋጅተው" ወይም "ዝግጅታቸውን አጠናቀው" በባሕሩ ላይ መሄድ ጀመርን "በባሕሩ ላይ ጉዞዋችንንን ጀመርን" አርስጥሮኮስ ይህን በ ACT 19:29 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Acts 27:3

የሐዋርያት ሥራ 27፡ 3-6
ዩልዩስ ጳውሎስን በመልካም መንገድ አስተናገደው "ዩልዩስ ጳውሎስን በመልካም መንገድ አስተናገደው።" “ዩልዩስ” የሚወለውን ስም በምን ዓይነት መንገድ አንተረጎምከው በ ACT 27:1 ተመልከት። እንክብካቤ ያደርጉለት ዘንድ ወደ ጓደኞቹ ዘንድ ሄደ "አስፈላጊውን እንክብካቤ ለማግኘት ወደ ጓደኞቹ ዘንድ ሄደ" ወይም "አስፈላጊውን እገዛ ለማግኘት ሲል ወደ ጓደኞቹ ዘንድ ሄደ" በቆጵሮስ ደሴት አድርገን አውሎ ንፋሱን ተከልለን ሄድን "ከአውሎ ንፋሱ ለመከለክ ስንል በቆጵሮስ ደስት ደሴት በኩል አድረገን ተጓዝን" (UDB) ጵንፍልያም ይህንን በ ACT 2:10 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። በሉቅያ ወዳለ ወደ ሙራ ደረስን። ሙራ በሉቅያ ውስጥ የሚትገኝ ከተማ ናት። ይህች ከተማ በዘመኗ ቱርክ ውስጥ በደቡብ ምዕራብ አከባቢ ተገኛለች። የሉቅያ ከተማ ሉቅያ የሮም ግዛት ስትሆን በዘመኗ ቱርክ ውስጥ በደቡብ ምዕራብ አከባቢ ትገኛለች። አሌክሳንደሪያa ይህ የአንድ ከተማ ስም ነው። ጣሊያን ይህንን በ ACT 27:1 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት።

Acts 27:7

የሐዋርያት ሥራ 27፡ 7-8
ቀኒዶስ አቅራቢያ ይህ በዘመኗ ቱርክ ውስጥ የሚገኝ በጥንት ጊዜ ሰዎች ሠፍረውበት የነበረ ሥፍራ ነው። ሰልሙና ተቃራኒ ይህች የቀርጤስ ወደብ ከተማ ናት። መልካም ወደብ ይህ በልሳ አቅራቢያ የሚገኝ ከቀርጤስ ወደብ በስተደበቡ የሚገኝ ሥፍራ ነው። ለላሲያ ከተማ አቅራቢያ ይህች በቀርጤስ ውስጥ የሚትገኝ ወደብ ናት።

Acts 27:9

የሐዋርያት ሥራ 27፡ 9-11
አሁን ብዙ ጊዜ ወሰድን በንፋሱ አቅጣጫ ምክንያት ከቄሳሪያ ወደ መልካም ወደብ ያደረግነው ጉዞ ከታሰበው ቀን በላይ ፈጅቷል። የአይሁዳዊያን የጾምራጽም አልፏል ይህ ጾም ከመስከርም ወር ውስጥ ካለው የመስዋእት ዕለት አንስቶ እስከ ጥቅም ድረስ የሚቆይ በየዓቱ የሚደረግ ነው። ከዚህ ጊዜ በኋላ ከፍተኛ ማዕበል የመነሣት ዕድሉ ከፍተኛ ነው።

Acts 27:12

የሐዋርያት ሥራ 27፡ 12-13
መርከብቱ ይህንን ንፋስ የመቋቋም አቅም አይኖራትም "ይህንን ወጀብ ለመቋቋም የሚያስችል አቅም አይኖራትም" የፍንቄ ከተማ ፍንቄ በቀርጡስ ደሴት ውስጥ የሚትገኝ አንድ ወዳብ ናት። ከባድ መጎልቅ “ከባድ” የሚለው ቃል የሚመለክተው ከውሃ ውስጥ ለማውጣት ነው። መጎልቅ ከመርከብቱ ጋር በገመድ የሚታሠር መርከብቱ እንዳትቀሳቀስ የሚያደረግ ከባድ ዕቃ ነው። መጎልቁ በውሃ ውስጥ ከተጨመረ በኋላ ወደ ውሃው ውስጥ ይጣላልና መርከብቱ እንዳትሄድ ያደርጋል።

Acts 27:14

የሐዋርያት ሥራ 27፡ 14-16
ከባድ አውሎንፋሰስ "በጣም ጠንካራ እና አደገኛ የሆነ ንፋስ" ሸራ "ከንፋሹ ተከለሉ" ቄዳ ወደሚባል ትንሽ ደሴት ይህች ደሴት ከቀርጤስ ደሴት በስተደቡብ የሚትገኝ ናት።

Acts 27:17

የሐዋርያት ሥራ 27፡ 17-18
ወደላይ አወጧት "ተሸክመው አወጧት" ስርቲስም ወደ ተባለ አሸዋማ ሥፍራ ይህ ጥልቅ ያልሆነ አሸዋማ የሐይቁ ክፍል ሲሆን መርከቦችም በዚያ ተቀርቅረው ይቀራሉ። "ስርቲስ" በሰሜን አፍርካ ሊቢያ አከባቢ የሚገኝ ሥፍራ ነው። በንፋሱ እየተመራን ሄድን አማራጭ ትርጉም፡ "ንፋሱ በሚወስደን አቅጣጫ መጓዝ ግድ ሆነብን"

Acts 27:19

የሐዋርያት ሥራ 27፡ 19-20
የመትረፈስ ተስፋችን ሁሉ ተሟጠጠ አማራጭ ትርጉም፡ "ሁሉም ሰው እንተርፋለን የሚለው ተስፋው ተሟጠጠ"

Acts 27:21

የሐዋርያት ሥራ 27፡ 21-22
ከተጓዦቹ መካከል ከሰዎቹ መካከል" ጉዳት የሚደርስበት እና የሚጠፋ "በዚህ ምክንያት የሚጎዳ እና የሚጠፋ"

Acts 27:23

የሐዋርያት ሥራ 27፡ 23-26
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ በመርከብቱ ለሚጓዙ ሰዎች መናገሩን ቀጠሏል። ከአንተ ጋር በመርከብቷ የሚጓዙ ሰዎችን ሁሉንም ሰጥቼሃለሁ "ከአንተ ጋር በመርከብቷ የሚጓዙ ሰዎች በሕይወት ይኖሩ ዘንድ ወስኛለሁ" አንድ ደሴት ፈልገን ወደዚያ መጠጋት ይኖርብናል "መርከቧ በአንድ ደሴት ላይ መቆም ይኖርባታል"

Acts 27:27

የሐዋርያት ሥራ 27፡ 27-29
በአድርያ ባሕር ይህ በጣሊያን እና በግሪክ መካል ያለ ባሕር ነው። ለኩት የሐይቁን ውሃ መጠን ለኩት (UDB)። ሃያ የሰው ቁመት አገኙ "20 የሰው ቁመት አገኙ" ወይም "40 ሜትር አገኙ።" ይህ የመለኪያ መንገድ ነው። ዐሥራ አምት የሰው ቁመት አገኙ "15 የሰው ቁመት አገኙ" ወይም "30 ሜትር" ከመርከብቱ በስተኋላ "በከመርከብቱ በስተዋኋላ"

Acts 27:30

የሐዋርያት ሥራ 27፡ 30-32

Acts 27:33

የሐዋርያት ሥራ 27፡ 33-35
ከጸጉርህ አንድ ዘለላ እንኳ አትጠፋም ይህ በአንተ ላይ ምንም ጉዳት አይደርስም ለማለት የተለመደ ንግግር ነው። አማራጭ ትርጉም፡ "ይህንን አስቸጋሪ ሁኔታ ያለምንም ጉዳ ሁላችሁም ታልፋላችሁ።" መዕድ ቆረሰ "ዳቦ ሁለት ወይም ከዚያ በላ ቆርሶ" ወይም ዳቦውን ቆራርሶ"

Acts 27:36

የሐዋርያት ሥራ 27፡ 36-38
በመርከብቱ ውስጥ የነበርነው ወደ 276 ሰዎች ነን "በመርከብቷ ውስጥ ወደሁለት መቶ ሰባ ስድተስ ሰዎች ነበርን።" ይህ የኋላ ታርክ መረጃ ነው።

Acts 27:39

የሐዋርያት ሥራ 27፡ 39-41
ዬት ቦታ እንደሆነ አላወቁም "አንድ ሥፍራ ተመለከቱ ነገር ግን ይህ እነርሱ የሚያውቁት ሥፍራ አልነበረም" መጎልቁን ፈተው በውሃ ውስጥ ተውት "ገመዱን ቆርጠው መጎልቁን በዚያ ተውት" ወደባሕሩ ዳርቻ አመሩ "steered the ship toward the beach"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Acts 27:42

የሐዋርያት ሥራ **27፡ 42-44**
የወታደሮቹ እቅድ የነበረው "የወታደሮቹ እቅድ" ወደ ውሃ ውስጥ መዝለል
"ከመርከብቱ ወደ ውሃው ውስጥ መዝለል"

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **28**

1 ወደ መሬት በደኅና በደረስን ጊዜም፣ ደሴቲቱ ማልታ የምትባል መሆንዋን ዐወቅን። **2** የዚያች ደሴት ሰዎችም የተለመደውን ደግነት እንኳ አላሳዩንም፤ ሆኖም፣ በማያቋርጠው ዝናብና ብርድ ምክንያት እሳት አንድደው ሁላችንንም ተቀበሉን። **3** ነገር ግን ጳውሎስ ጭራሮ ሰብስቦ እሳቱ ላይ በጨመረው ጊዜ፣ ከሙቀቱ የተነሣ አንድ እፉኝት ወጣና በእጁ ላይ ተጣበቀ። **4** የደሴቲቱ ሰዎችም እፉኝቱ ከእጁ ላይ ተንጠልጥሎ ባዩ ጊዜ፣ እርስ በርሳቸው፣ “ይህ ሰው በእርግጥ ከባሕር ያመለጠ ነፍሰ ገዳይ ስለ ሆነ፣ ፍትሕ በሕይወት እንዲኖር አልፈቀደለትም” ተባባሉ። **5** ጳውሎስ ግን እፉኝቱን በእሳቱ ላይ አራገፈው፤ አልተጐዳምም። **6** ሰዎቹም ሰውነቱ በትኩሳት ያብጣል ወይም በድንገት ይሞታል ብለው ይጠባበቁ ነበር። ነገር ግን ረዘም ላለ ጊዜ ተጠባብቀውት ምንም እንዳልደረሰበት ካዩ በኋላ፣ ዐሳባቸውን ለውጠው አምላክ ነው አሉ። **7** በአቅራቢያው ባለ አንድ ስፍራም ፑብልዮስ የተባለ የደሴቲቱ ገዢ መሬት ነበር፤ እርሱም ተቀብሎን ሦስት ቀን በደግነት አስተናገደን። **8** የፑብልዮስ አባት ትኵሳትና ተቅማጥ ይዞት ታሞ ነበር። ጳውሎስ ወደ እርሱ ሄዶ ጸለየ፤ እጆቹን ጫነበት፤ ፈወሰውም። **9** ይህ ከሆነ በኋላ፣ በደሴቲቱ የሚኖሩ ታመው የነበሩ ሌሎች ደግሞ መጡና ተፈወሱ። **10** ሰዎቹም እጅግ አከበሩን። ለመሄድ በምንዘጋጅበት ጊዜም፣ የሚያስፈልገንን ሰጡን። **11** ከሦስት ወር በኋላ፣ አፍንጫው ላይ የመንታ ወንድማማች ዓርማ በነበረበት፣ ክረምቱን በደሴቲቱ ባሳለፈ የእስክንድርያ መርከብ ላይ ተሳፍረን ጕዞ ጀመርን። **12** ወደ ሲራኩስ ከተማ ከደረስን በኋላም፣ እዚያ ሦስት ቀን ቈየን። **13** ከዚያም ተጕዘን ወደ ሬጊዩም ከተማ ደረስን። ከአንድ ቀን በኋላ የደቡብ ነፋስ ተነሣ፤ በሁለት ቀንም ወደ ፑቲዮሉስ ከተማ መጣን። **14** እዚያም አንዳንድ ወንድሞችን አገኘንና ከእነርሱ ጋር ሰባት ቀን እንድንቈይ ተጋበዝን። በዚህ ዐይነት ወደ ሮም መጣን። **15** ከዚያም ወንድሞች ስለ እኛ ከሰሙ በኋላ፣ ሊቀበሉን አፍዩስ ገበያና ሦስቱ ማደሪያዎች ድረስ መጡ። ጳውሎስ ወንድሞችን ባየ ጊዜ፣ እግዚአብሔርን አመሰገነ፤ ተጽናናም። **16** ወደ ሮም በገባን ጊዜ፣ ጳውሎስ ከሚጠብቀው ወታደር ጋር ብቻውን እንዲኖር ተፈቀደለት። **17** ቀን በኋላ፣ ጳውሎስ በአይሁድ መካከል መሪዎች የነበሩትን ሰዎች አንድ ላይ ጠራ። በተሰበሰቡ ጊዜም፣ እንዲህ አላቸው፤ “ወንድሞች ሆይ፣ በሕዝቡ ወይም በአባቶች ሥርዓት ላይ የፈጸምሁት ስሕተት ባይኖርም እንኳ፣ ከኢየሩሳሌም በእስረኝነት ለሮማውያን እጅ ተላልፌ ተሰጠሁ። **18** እነርሱ ከመረመሩኝ በኋላ ለሞት የሚያበቃኝ ምክንያት ስላልነበረብኝ፣ በነጻ ሊለቁኝ ፈልገው ነበር። **19** ነገር ግን አይሁድ የሮማውያንን ፍላጎት ተቃውመው በተናገሩ ጊዜ፣ በሕዝቤ ላይ የማቀርበው ክስ ባይኖረኝም እንኳ፣ ወደ ቄሣር ይግባኝ ለማለት ተገደድሁ። **20** በዚህ ምክንያት፣ ላያችሁና ላነጋግራችሁ ልመና አቅርቤአለሁ፤ ምክንያቱም እኔ በዚህ ሰንሰለት የታሰርሁት ለእስራኤል ስለ ተሰጠው እምነት ነው።” **21** ከዚያም እነርሱ እንዲህ አሉት፤ “ከይሁዳ ስለ አንተ ደብዳቤ አልደረሰንም፤ ከወንድሞች መካከልም ስለ አንተ ያወራ ወይም ክፉ የተናገረ የለም። **22** ነገር ግን በሁሉም ስፍራ ተቃውሞ እየተወራበት መሆኑን እኛ ስለምናውቅ፣ ስለዚህ የሃይማኖት ወገን ምን እንደምታስብ ከአንተ መስማት እንፈልጋለን።” **23** ለጳውሎስ ቀን በቀጠሩለት ጊዜም፣ ብዙ ሰዎች ወደ መኖሪያ ቤቱ መጡ። እርሱም ጉዳዩን ገለጠላቸው፤ ስለ እግዚአብሔር መንግሥትም መሰከረላቸው። ከጠዋት እስከ ማታም ከሙሴ ሕግና ከነቢያት እየጠቀሰ፣ ስለ ኢየሱስ ሊያሳምናቸው ጥረት አደረገ። **24** አንዳንዶች የተናገረውን ቃል ሲያምኑ፣ ሌሎች ግን አላመኑም። **25** እርስ በርሳቸው ሳይስማሙ ሲቀሩ፣ ጳውሎስ ይህን አንድ ቃል ከተናገረ በኋላ ሄዱ፤ “መንፈስ ቅዱስ በነቢዩ ኢሳይያስ አማካይነት ለአባቶቻችሁ በትክክል ተናገረ። **26** እንዲህም አለ፤ ‘ወደዚህ ሕዝብ ሂድና እንደዚህ በላቸው፤ ‘መስማትስ ትሰማላችሁ፤ ነገር ግን አታስተውሉም፤ ማየትስ ታያላችሁ፤ ነገር ግን ልብ አታደርጉም። **27** በዐይናቸው እንዳያዩ፣ በጆሮአቸው እንዳይሰሙ፣ በልባቸው እንዳያስተውሉ፣ ተመልሰውም እንዳልፈውሳቸው፣ የዚህ ሕዝብ ልብ ደንድኖአል፤ ዐይናቸውም ተጨፍኖአል።’ **28-29** ስለዚህ፣ ይህ የእግዚአብሔር ድነት ወደ አሕዛብ እንደ ተላከ፣ እነርሱም እንደሚቀበሉት ዕወቁ። **30** ጳውሎስ በተከራየው በራሱ ቤት ሁለት ዓመት ሙሉ ኖረ፤ ወደ እርሱ የሚመጡትንም ሁሉ ይቀበል ነበር። **31** የእግዚአብሔርን መንግሥት ይሰብክ፣ ያስተምርም ነበር። ይህንም ሲያደርግ ማንም አልከለከለውም።

Acts 28:1

የሐዋርያት ሥራ **28**፡ **1-2**
አወቅን በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን እናበዘዚህ ጉዞ ላይ ከጳውሎስ ጋር አብሮ የተጓዘውን የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ጸሐፊ የሆነውን ሉቃስን ነው። አማራጭ ትርጉም "ከሰዎቹ አወቅን" ወይም "ከነዋሪዎቹ ጠይቀን ተረዳን።" ደሴትቱ መላጥያ ትባላለች መላጥያ በአሁኗ ሲስል ደቡብ አከባቢ የሚትገኝ ደሴት ናት። የሀገሩ ሰዎች “የሀገሩ ሰዎች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የግሪክ ቋንቋ መናገር የሚችሉ ሰዎች የግሪክ ባሕልን የተቀበሉ ሰዎች ናቸው። የሚያስገርም ቸርነት ይህ ሀረግ ከሚቀጠበው ተቃራኒ የሆነ ነገርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም: "ታላቅ ቸርነት።" እሳት አቀጣጥለው "እንጨት ሰብስበው እሳት አቀጣጠሉልን" ሁላችንንም በደስታ ተቀበሉን አማራጭ ትርጉሞች 1) "በመርከብቷ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ሁሉ በደስታ ተቀበሉ" ወይም 2) "ጳውሎስን እና ከእርሱ ጋር የነበረሩትን ሁሉ በደስታ ተቀበሏቸው።"

Acts 28:3

የሐዋርያት ሥራ **28**፡ **3-4**
እፉኝት ወጣች "ከሚነደው እሳት ውስጥ መርዛማ የሆነች እባብ ወጣች" ከእጁ ጋር ተጣበቀች "የጳውሎስን እጅ ይዛ አለቀም አለች" ይህ ሰው በእርግጥም ነፍስ አጥፍ ነው አሉ "በእርግጠኝነት ይህ ሰው ነፍሰ ገዳይ ነው አሉ" ወይም "ይህ ሰው በእርግጥም ነፍሰ ገዳይ ነው" ይሁን እንጂ ፍትሕ በሕይወት እንዲቆይ አልፈቀደለትም "ፍትሕ ተብላ የሚትጠራ አምላክ ከሞት እንዲያመልጥ አልፈቀደችለተም"

Acts 28:5

የሐዋርያት ሥራ **28**፡ **5-6**
እባቧን ወደ እሳት ውስጥ አራግፎ ጣላት "እባብቱን ከእጁ ላይ አራግፎ ወደ እሳቱ ውስጥ ጣላት" ተመርዞ ወዲያው ይወድቃል አማራጭ ትርጉሞች 1) ከፍተኛ ትኩሰሳት ይይዘዋል ወይም 2) ያብጣል። በእርሱ ላይ የታየ ለውጥ አልነበረም አማራጭ ትርጉም: "ሁሉን ነገር እንደቀድሞው ነበር" አምላክ ነው አሉ በመርዛማ እባብ ከተነደፈ በኋላ በሕይወት የሚኖር ሰው መለኮት ወይም አምላክ ነው የሚል እምነት አለ።

Acts 28:7

የሐዋርያት ሥራ **28**፡ **7-10**
በዚያም ስፍራ አጠገብ "በዚያ" የሚለው ቃል በታሪኩ ውስጥ አዲስ ሰው ወይም ነገር እንደተካተተ አመለካች ነው። የደሴትቱ አለቃ አማራጭ ትርጉሞች 1) የሕዝቡ ዋና መሪ ወይም 2) በደሴትቱ ለላይ ዋና ሰው ተደርጎ የሚወሰደው ምናልባትም በጣም ሀብታሙ ሰው ሊሆን ይችላል። ፑፕልዮስ ተብሎ የሚጠራ ሰው ፑፕልዮስ በደሴትቱ ላይ ዋና አለቃ ነው። መልካም አቀባበል አደረግልን "ጳውሎስን እና ከእርሱ ጋር የተጓዙትን ሰዎች" የሚያስፈልገንን ነገር ሁሉ በልግስና ሰጡን "ለእኛ እንግዶች ለሆነው ቸርነታቸውን አሳዩን" የፑፕልዮስም አባት በንዳድና በተቅማጥ ታሞ ተኝቶ ነበር፤ ይህ ስለ ፑፐፕልዮስ አባት አጠቃላይ የኃላ ታሪክ መረጃ የሚሰጥ ሆኖ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አጠቃላይ ታኩን ለመረዳ ወሳኝ ነው። ታሞ ነበር "ታሟል" በንዳድና በተቅማጥ ታሞ ነበር ይህ የአንጀት በሽታ ነው። እኮቹን በእርሱ ላይ ጫነ "በእጆቹ ዳሰሰው" ተፈወሰ አማራጭ ትርጉም: "እነርሱንም ፈወሳቸው" (UDB)

Acts 28:11

የሐዋርያት ሥራ **28**: **11**-**12**
አጠቃላይ መረጃ: ጳውሎስ ወደ ሮም የሚያደርገውን ጉዞ ቀጥሏል። በእስክንድሪያው መርከብ አማራጭ ትርጉሞች 1) "ከእስክንድሪያ በመጣው መርከብ አማካኝነት" ወይም 2) "በእስክንድሪያ የተመዘገበው ወይም ፈቃድ ያገኘው መርከብ።" በ ACT 6:9 ላይ “እስክንድሪያ” የሚለውን ቃል ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። መንቲያ ወንድማማቾች ይህ ካስቶር እና ፖሉእክስ የተባሉትን ያመለክታል፤ እነዚህ የግሪክ አምላክ የሆነው ዙስ መንቲያ ወንድ ልጆች ናቸው። እነዚህ የመርከቦችን ደንነት የሚጠብቁ ናቸው ተብሎ ስለሚታሰብ ይፈራሉ። የሰራኩስ ከተማ ሰርኩስ በአሁን ዘመን ከጣሊያን ደቡብ ምዕራብ በኩል፣ ከሲስል ከተማ ደቡብ ምስራቅ በኩል የሚትገኝ የወደብ ከተማ ናት።

Acts 28:13

የሐዋርያት ሥረ **28**: **13**-**15**
የሬጊዩም ከተማ ይህ ከጣሊያን ጫፍ በደቡብ ምዕራብ በኩል የሚገኝ የወደብ ከተማ ነው። የደቡብ ንፋስ ተነስቶ "ከደቡብ የሚነሳ ንፋስ መንፈስ ጀመረ" የፑቲዮሉስ ከተማ "ፑቲዮሉስ" በዘመኗ ኔፓል ከጣሊያን በምዕራብ በኩል የሚትገኝ ከተማ ናት። ወንድሞች እነዚህ የኢየሱስ ተከታዮች ሲሆን ወንዶችን እና ሴቶችን ያካትታል። በዚህ መንገድ ወደ ሮም መጣን አንድ ጊዜ ጳውሎስ ወደ ፑቲዮሉስ ከደረሰ በኋላ የተቀረው ወደ ሮም የሚደረገው ጉዞ በየብስ ላይ የሚደረግ ነው። አማራጭ ትርጉም: : "ከእነርሱ ጋር ለሰባት ቀናት ከቆየን በኋላ ወደ ሮም ሄድን።" ሦስት ማደሪያ s ይህ በመንገድ ላይ ማረፊያ ቦታ ሲሆን ከሮም ከተማ 50 ኪሜ ርቀት ላይ የሚገኝ አፋን የተባለ ስፍራ ነው።

Acts 28:16

የሐዋርያት ሥራ **28**: **16**-**18**
ወደ ሮም በደረስን ጊዜ ጳውሎስ ተፈቀደለት አማራጭ ትርጉም: "ወደሮም ከደረስን በኋላ መንግስት ፈቃድ ሰጠው" በአይሁዳዊያን መካከል ያሉት መሪዎች አይሁዳዊያን ማህበረሰባዊ ወይም ሃይማኖታዊ መሪዎች በሮም ተገኝተው ነበር የሞት ቅጣት የሚያስቀጣ አንዳች ጥፋት አልተገኘብኝም "የሞት ቅጣት የሚያስቀጣ አንዳች ነገር አላደረኩም"

Acts 28:19

የሐዋርያት ሥራ **28**: **19**-**20**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ በሮም ላሉት የአይሁድ መሪዎች መናገሩን ቀጥሏል። አይሁዳዊያን ተናገሩ "በኢየሩሳሌም ያሉት የአይሁድ መሪዎች ተናገሩ" ከእነርሱ ፍላጎት ውጪ "ከሮማዊያን መሪዎች መሻት ውጪ" እኔም ይግባኝ ለመጠየቅ ተገደድኩኝ አማራጭ ትርጉም: "ይግባኝ ከመጠየቅ ውጪ ሌላ አማራጭ አልነበረኝም" እስራኤል እርግጠኛ በሆነችበት ጉዳይ ላይ አማራጭ ትርጉም 1) "እግዚአብሔር መስሐን ወደ እስራኤል እንደሚልክ እስራኤል እርግጠኛ ናት" ወይም 2) የሞተውን ነገር ከሞት እግዚአብሔር እንደሚያስነሳ።

Acts 28:21

የሐዋርያት ሥራ **28**: **21**-**22**
አማራጭ ትርጉም: የአይሁድ መሪዎች ለጳውሎስ ምላሽ ሰጡ። ስለዚህ የስህተት ትምህርት ታስባለህን "ስለነዚህ ራሳቸውን ስለመረጡት ቡድኖች ታስባለህን" በሁሉም ሥፍራዎች በእነርሱ ላይ ተቃውሞ እየተነሣ ነው የወንጌል መልዕክትን ለመቀበል ፈቃደኛ ያልሆኑት በሮም አጠቃላይ ግዛት ውስጥ የሚኖሩት አይሁዊያን ስለ መንገዱ እና ይህንን መልዕክት አስመልክቶ መጥፎ ነገር መናገራውን በሮም የሚገኙ አይሁዳዊያን ሰምተዋል። .

Acts 28:23

የሐዋርያት ሥራ **28**: **23**-**24**
አጠቃላይ መረጃ: በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ “እርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን ነው። በተቀመጡ ጊዜ በዚህ ሥፍራ ላይ “እርሱ” የሚለው ቃ የሚያመለክተው የኤሁድ መሪዎችን ነው። አንዳንዶቹን አሳመናቸው አማራጭ ትርጉም: "ጳውሎስ አንዳንዶቹን አሳመናቸው"

Acts 28:25

የሐዋርያት ሥራ **28**: **25**-**26**
አጠቃላይ መረጃ: በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ “እነርሱ” የሚለው ቃል ጳውሎስ እየተናገራቸው ያሉትን ሰዎችን ነው። በቁጥር 26 ላይ ጳውሎስ ከነብዩ ኢሳያስ መጽሐፍ ወስዶ ተናግሯል።

Acts 28:27

የሐዋርያት ሥራ **28**: **27**-**27**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ከነቢይ ኢሳያስ መጽሐፍ ወስዶ መናገሩን አጠናቋል።

Acts 28:28

የሐዋርያት ሥራ **28**: **28**-**29**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ በሮም ላሉት የአይሁድ መሪዎች ያደረገውን ንግግር አጠናቀቀ። ያደምጡት ነበር "ከእነርሱ መካከል አንዳንዶቹ ያደምጡት ነበር"

Acts 28:30

የሐዋርያት ሥራ **28**: **30**-**31**
No Note

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Romans

Romans

ምዕራፍ 1

1 የእግዚአብሔርን ወንጌል በሐዋርያነት እንዲያገለግል ተለይቶ ከተጠራው ከኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ ከጳውሎስ። 2 ወንጌሉም በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ
በነቢያቱ አስቀድሞ ተስፋ የሰጠው ነው። 3 ይህም ወንጌል በስጋ ከዳዊት ዘር ስለተወለደው ስለ ልጁ ነው። 4 እርሱም በቅድስና መንፈስ ኃይል ከሙታን
በመነሳት የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ የተነገረለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነበር። 5 በስሙ ምክንያት ከእምነት የሚገኝ መታዘዝ በሕዝቦች ሁሉ መካከል
እንዲሆን በእርሱ በኩል ጸጋንና ሐዋርያነትን ተቀበልን። 6 እናንተም በእነዚህ ሕዝቦች መካከል የኢየሱስ ክርስቶስ ለመሆን ተጠራችሁ። 7 ይህ መልዕክት
የተጻፈው በእግዚአብሔር ለተወደዳችሁና ቅዱስ ሕዝብ ለመሆን ለተጠራችሁ በሮም ላላችሁት ሁሉ ነው። ከእግዚአብሔር ከአባታችንና ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ
ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን። 8 ስለ እምነታችሁ በመላው ዓለም በመነገሩ ምክንያት አስቀድሜ ስለሁላችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል አምላኬን አመሰግናለሁ።
9 ባለማቋረጥ እንደማስባችሁ የልጁን ወንጌል በመንፈሴ የማገለግለው እግዚአብሔር ምስክሬ ነው። 10 አሁን በተቻለኝ መጠን በእግዚአብሔር ፈቃድ
ተሳክቶልኝ ወደ እናንተ እንድመጣ ሁልጊዜ በጸሎቴ እለምናለሁ። 11 የሚያበረታችሁን ጥቂት መንፈሳዊ ስጦታ እንዳካፍላችሁ ላያችሁ እናፍቃለሁ፥ 12
ይኸውም የእኔና የእናንተ በሆነ የእርስ በርሳችን እምነት አማካይነት እንድንበረታታ ስለምጓጓ ነው። 13 ወንድሞች ሆይ፥ ብዙ ጊዜ ወደ እናንተ ለመምጣት እንደ
ሞከርኩኝና እስካሁን እንደተስተጓጎልኩኝ ሳታውቁ እንድትቀሩ አልፈልግም። ወደ እናንተ መምጣት የፈለግሁበት ምክንያት ከተቀሩት አሕዛብ እንዳገኘሁት ሁሉ
ከእናንተ ደግሞ ጥቂት ፍሬ እንዳገኝ ነው። 14 ለግሪኮችና ግሪኮች ላልሆኑት፥ ለጥበበኞችና ለማያስተውሉ ዕዳ አለብኝ። 15 ስለዚህ፥ በበኩሌ በሮም
ለምትገኙት ለእናንተ ደግሞ ወንጌልን ለመስበክ ተዘጋጅቻለሁ። 16 በወንጌል አላፍርም! ምክንያቱም እርሱ አስቀድሞ ለአይሁድ ደግሞም ለግሪኮች
የሚያምኑትን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ኃይል ስለሆነ ነው። 17 "ጻድቅ በእምነት ይኖራል" ተብሎ እንደተጻፈ የእግዚአብሔር ጽድቅ በወንጌል ከእምነት
ወደ እምነት ተገልጧልና። 18 በአመጻቸው እውነትን በሚያፍኑ አመጸኞችና ክፉዎች ሰዎች ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ከሰማይ ተገልጧል። 19 ይኸውም
እግዚአብሔር ስላስታወቃቸው ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚገባው ነገር ለእነርሱ ግልጥ ነው። 20 የማይታዩት ገጽታዎቹ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ
ግልጥ ሆነው ይታያሉ። እነዚህም በተፈጠሩት ነገሮች አማካይነት ይታወቃሉ። ገጽታዎቹም የዘላለም ኃይሉና የመለኮት ባህርዩ ናቸው። በመሆኑም እነዚህ ሰዎች
የሚያመካኙት አይኖራቸውም። 21 ምክንያቱም ስለ እግዚአብሔር ቢያውቁም እንደ እግዚአብሔርነቱ ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት ነው። ይልቁንም በሀሳባቸው
ሞኞች ሆኑ፥ የማያስተውለው ልባቸውም ጨለመ። 22 ጥበበኞች ነን ቢሉም የማያስተውሉ ሆኑ። 23 የማይጠፋውን የእግዚአብሔር ክብር በሚጠፋ ሰው
አምሳል፥በወፎች፥ አራት እግር ባላቸው አራዊትና በደረታቸው በሚሳቡ ፍጥረታት መልክ ለወጡ። 24 ስለዚህ እርስ በርሳቸው ሰውነታቸውን እንዲያዋርዱ
እግዚአብሔር ለልባቸው የክፋት ምኞት ለእርኩሰት አሳልፎ ሰጣቸው። 25 እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን እውነት በውሸት የለወጡና በፈጣሪ ፈንታ ፍጥረትን
ያመለኩና ያገለገሉ ናቸው፤ እርሱ ግን ለዘላለም የተመሰገነ ነው።አሜን። 26 ከዚህም የተነሳ እግዚአብሔር ለአስነዋሪ ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው፥ ሴቶቻቸውም
ለተፈጥሮአቸው የሚገባውን ተግባር ተገቢ ባልሆነው ለወጡ። 27 እንዲሁም ወንዶች ደግሞ ለተፈጥሮአቸው የሚገባውን ሴቶችን መገናኘት ትተው እርስ
በርሳቸው በፍትወተ-ሥጋ ምኞት ተቃጠሉ። እነዚህ ወንዶች የማይገባውን ነገር ከወንድ ጋር በማድረጋቸው ስለ ነውራቸው ቅጣትን የተቀበሉ ናቸው። 28
እግዚአብሔርን ለማወቅ ስላልፈቀዱ እነዚያን ተገቢ ያልሆኑ ነገሮች እንዲያደርጉ ለማይረባ አዕምሮ አሳልፎ ሰጣቸው። 29 እነርሱ በአመጻ ሁሉ፥ በጨካኝነት፥
በክፉ ምኞትና በምቀኝነት፥ በቅናት፥ በነፍስ መግደል፥ በጸብ፥ በማታለልና በክፉ ሃሳብ የተሞሉ ናቸው። 30 ሐሜተኞች፥ የሰው ስም አጥፊዎችና እግዚአብሔርን
የሚጠሉ፥ ቁጡዎች፥ ዕብሪተኞችና ትዕቢተኞች ናቸው። ክፉ ነገሮችን የሚያመነጩና ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፥ 31 ማስተዋል የሌላቸው፤ እምነት
የማይጣልባቸው፥ ፍቅር የሌላቸውና የማይምሩ ናቸው። 32 እንደዚህ ያሉትን ነገሮች የሚያደርጉ ሞት እንደሚገባቸው የሚናገረውን የእግዚአብሔር ትዕዛዝ
ያውቃሉ፥እነርሱ ግን እነዚህኑ ነገሮች ራሳቸው የሚያደርጉ ብቻ ሳይሆኑ የሚያደርጉትን ሌሎችን የሚያበረታቱ ናቸው።

Romans 1:1

ጳውሎስ
ቋንቋህ የዚህን መልእክት ጸሓፊ የሚያስተዋውቅበት የተለየ መንገድ ሊኖረው ይችላል። በዚሁ ተመሳሳይ ጥቅስ ጳውሎስ ደብዳቤውን የጻፈለቸው ሰዎእ እነማን እንደሆኑ መናገር ያስፈልግህ ይሆናል (ሮሜ 1:7) ። ‹‹እኔ ጳውሎስ ይህንን መልእክት ጽፌአለሁ (የተገመተ እውቀት እና ያልተገለጠ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ ለእግዚአብሔር ወንጌል ተለየ
ይህንን በአድራጊ ቅርጽ ልትተረጉመው ትችላለህ። “እግዚአብሔር ሐዋርያ እንድሆን ጠራኝ እንዲሁም ለሰዎች ስለ ወንጌል እናገር ዘንድ መረጠኝ።

የተጠራ
ይህ ማለት እግዚአብሔር ሰዎችን የእርሱ ልጆች ይሆኑ ዘንድ፣ አገልጋዮቹም ይሆኑ ዘንድ እና በኢየሱስ በኩል ያዘጋጀውን የመዳን መልእክት እንዲነግሩ ይመርጣቸዋል ወይም ይወስናቸዋል ማለት ነው።

በቅዱሱ የእግዚአብሔር ቃል እንደተገለጸው በነቢያቱ አስቀድሞ ቃል የገባውን
እግዚአብሔር ለሕዝቡ መንግሥቱን እንደሚያቋቁምቃል ገብቷል። ለነቢያቱም ይህንን ቃል ኪዳን በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ እንዲጽፉ ነግሮአቸዋል።

ልጁን በተመለከተ
ይህ የሚያመለክተው ‹‹የእግዚአብሔርን ወንጌል››፣ እግዚአብሔር ልጁን ወደዚህ ዓለም እንደሚልከው የገባውን ቃል ኪዳን የሚገልጽ የምሥራች ነው።

ልጅ
የእግዚአብሔር ልጅ፣ ይህ ለኢየሱስ አስፈላጊ ማዕረግ ነው። (ልጅ እና አባት እንዴት እንደተተረጎሙ ተመልከት)

በሥጋ የዳዊት ዘር የሆነው ማን ነበር?
እዚህ ላይ ‹‹ሥጋ›› የሚለው ቃል የሚያመለክተው ተጨባጭ የሆነውን አካል ነው። ‹‹ ተፈጥሮአዊ በሆነው አካል የዳዊት ዘር የሆነው ማን ነው›› ወይም ‹‹ከዳዊት ቤተ ሰብ የተወለደው ማን ነው›› (የተገመተ እውቀትና ያልተገለጠ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Romans 1:4

አያያዥ መግለጫ
ጳውሎስ እዚህ ላይ የሚናገረው ለመስበክ ስላለበት ግዴታ ነው።

Romans 1:8

ዓለሙ ሁሉ
ጳውሎስና የመልእክቱ አባቢዎች የሚያውቁትና የሚጓዙበት ዓለም የሮም ግዛት ነበር

እግዚአብሔር ምስክሬ ነው
ጳወሎሰ ከልቡ እንደሚጸልይላቸው እና ይህንንም ሲያደርግ እግዚአብሔር እንደሚያየው ትኩረት በመስጠት ይናገራል። ‹‹ስለ›› የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ ሳይተረጎም ይቀራል።

በመንፈሴ
የሰው መንፈስ የሰውአንድ ክፍል ሲሆን እግዚአብሔርን የሚያውቅና የሚያምን ነው።

የልጁ ወንጌል
የመጽሐፍ ቅዱስ የምሥራቹ ቃል (ወንጌሉ) የእግዚአብሔር ልጅ ዓለምን ለማዳን ራሱን አሳልፎ የሰጠበት ነው።

ልጅ
ይህ የእግዚአብሔር ልጅ ለሆነው ለኢየሱስ አስፈላጊ ማዕረግ ነው።

ስለ እናንተ አንስቼአለሁ
‹‹ስለ እናንተ ለእግዚአብሔር ተናግሬአለሁ››

በጸሎቴ ጊዜ ሁሉ ሁልጊዜ የምጠይቀው--- ወደ እናንተ በመምጣቴ ---በመጨረሻ ውጤታማ እንድሆን
‹‹በምጸልይበት ጊዜ ሁሉ፣ ወደ እናንተ መጥቼ --- በመጨረሻ ውጤታማ እንድሆን --- እግዚአብሔርን እጠይቃለሁ።

በሆነ መንገድ
‹‹እግዚአብሔር በሚፈቅደው በየትኛውም መመንገድ››

በመጨረሻ
‹‹ውሎ አድሮ›› ወይም ‹‹በመጨረሻ

በእግዚአብሔር ፈቃድ
‹‹እግዚአብሔር ስለፈለገው››

Romans 1:11

አያያዥ መግለጫ
ጳውሎስ የመክፈቻ መግለጫውን በሮም ላሉ ሰዎች በመቀጠል ሊያያቸው እንደሚመኝ ይነግራቸዋል

ላያችሁ እናፍቃለሁ
‹‹ምክንያቱም በእርግጥ ላያችሁ ስለምፈልግ ነው››

እንዲያጠነክራቸህ፣ መንፈሳዊ ስጦታን
ጳውሎስ የሮሜ ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲጠነክሩ ይፈልጋል። ‹‹በምንፈሳዊ ሕይወታችሁ እንድታድጉ አንዳንድ ስጦታዎች ይረዱአችኋል››

ይህም ማለቴ በመካከላችን ባለች በእናንተና በእኔ እምነት አብረን በእናነተ እንድንጽናና ነው።
ይህንን በአድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። ‹‹በኢየሱስ ባለን እምነታችን እርስ በእርስ ልንዳችንን እንድንከፋፈል ማለቴ ነው››

Romans 1:13

መረጃ የሌላችሁ እንድትሆኑ አልፈልግም
ጳውሎስ ይህ መረጃ እንዲኖራቸው አጥብቆ ይፈልጋል። ይህንን በእጥፍ አሉታዊ በሆነ መንገድ የተገለጸውን በአዎንታዊ ቅርጹ ልትተረጉመው ትችላለህ። ‹‹እንድታውቁ እፈልጋለሁ››

ወንድሞች
ይህ ማለት ክርስቲያን ወገኖች ማለት ሲሆን፣ ሁቱንም ወንዶችንና ሴቶችን ያጠቃልላል።

እስካሁን ድረስ እንድተከለከልኩ ነው
ይህንን በአድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። ‹‹ሁልጊዜ የሆነ ነገር ይከለክለኛል››

Romans 1:16

በወንጌል አላፍርምና
ይህንን በአዎንታዊ ቅርጹ መተርጎም ትችላለህ። ‹‹በወንጌል ሙሉ ለሙሉ አምናለሁ››

ለሚያምን በሙሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነው
እዚህ ላይ ‹‹ማመን›› ማለት እምነትን በክርሰቶስ ላይ ማድረግ ማለት ነው››

አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው
‹‹ለአይሁድ ሕዝቦች እና ለግሪክ ሰዎችም››

መጀመሪያ
መጀመሪያ ማለት በጊዜ ውስጥ ከሁሉ ቀድሞ የሚመጣ ማለት ነው

በእርሱ
‹‹በእርሱ›› የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስ ሙሉ ለሙሉ የሚታመንበትን ወንጌልን ነው።

የእግዚአብሔር ጽድቅ ከእምነት ወደ እምነት ይገለጣልና
ጳውሎስ ስለ ወንጌል መልእክት እንደ አንድ ተጨባጭ ነገር ነገር

እንደ ተጻፈው
ይህንን በአድራጊ ቅርጹ ልትተረጉመው ትችላለህ። ‹‹አንድ ሰው በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ እንደ ጻፈው››

ጻድቅ በእምነት ይኖራል
እዚህ ላይ ‹‹ጻድቅ›› የሚለው የሚያመለክተው በእግዚአብሔር የሚታመኑትን ነው። ‹‹በእግዚአብሔር የሚታመኑትን ሰዎች ከእርሱ ጋር የሆኑና ለዘላለም የሚኖሩ አድርጎ ይቆጥራቸዋል››

Romans 1:20

የሚታየው ማንነቱ --- በግልጽ የሚታይ ነው
ጳውሎስ ሰዎች የእግዚአብሔርን ያለመታየት ባሕርይውን መረዳታቸውን ሰዎች እነዚያን የእግዚአብሔር ባሕሪያት እንዳዩ ይናገራል። ይህ እንደ አድራጊ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። ‹‹ እግዚአብሔር ስለገለጠላቸው ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ በእነርሱ ዘንድ ግልጽ ነው።››

መለኮታዊ ባሕርይ
‹‹የእግዚአብሔር ጠቅላላ ባሕርይ እና ችሎታው›› ወይም ‹‹እግዚአብሔርን አምላክ የሚያደርጉት ስለ እርሱ ያሉ ነገሮች››

ዓለም
ይህ የሚያመለክተው ሰማይንና ምድርን በውስጣቸው ያለውን ሁሉ ነው።

በተፈጠሩት ፍጥረታት ውስጥ
x

Romans 1:22

ጥበበኞች ነን ሲሉ ደንቆሮዎች ሆኑ
‹‹ጥበበኛች እንደሆኑ ስለራሳቸው ሲናገሩ ነገር ግን ሞኞች ሆኑ››

እነርሱ . . . እነርሱ
በሮሜ 1፡18 የተጠቀሱት ሰዎች

የማይጠፋውን የእግዚአብሔርን ክብር ለወጡ
‹‹ እግዚአብሔር ክቡር እና ፈጽሞ የማይሞት የመሆኑን እውነት ለወጡ›› ወይም ‹‹እግዚአብሔር ክቡር እና ፈጽሞ የማይሞት መሆኑን ማመናቸውን አቆሙ››

የአንድ ነገር ምስል አስመስለው
‹‹ጣዖታት የሚመስሉ ነገሮችን ማምለክ መረጡ››

የሚጠፋ ሰውን
‹‹የሚሞት ሰውን ››

ወፎችን፣ አራት እግር ያላቸውን እንስሶችን፣ እና የሚሳቡ ፍጥረቶችን
‹‹ወይም ወሮችን የሚመስሉ አራት እግት ያላቸውን እንስሶች፣ ወይም የሚሳቡ ነገሮች››

Romans 1:24

ስለዚህ
‹‹ስለዚህ አሁን የተናገርኩት እውነት ነው››

እግዚአብሔር ለ--አሳልፎ ሰጣቸው
‹‹እግዚአብሔር ለልባቸው ፍትወት እንዲሰጡ ፈቀደላቸው››

እነርሱ---የእነርሱ---እነርሱ ራሰቸው --- እነርሱ
x

Romans 1:26

በዚህ ምክንያት
‹‹በምንዝርና እና በወሲብ ኃጢአት ምክንያት››

እግዚአብሔር አሳልፎ ሰጣቸው
‹‹እግዚአብሔር ለርኩሰታቸው አሳልፎ ሰጣቸው››

በሚያስነውር ሁኔታ
‹‹የሚያሳፍር የወሲብ ፍላጎት››

ለሴቶቻቸው
‹‹በሴቶቻቸው ምክንያት››

ለባሕርያቸው የሚገባውን ሥራ ለባሕርያቸው በማይገባው ለወጡ።
‹‹ተፈጥሮአዊ ያልሆነ›› የግንኙነት አሳብ ለመጥራት እንኳ የማይገባ ጸያፍ የሆነ የወሲብ ግንኙነት ነው። ‹‹እግዚአብሔር ባልፈጠረው መንገድ ወሲብን መለማመድ ጀመሩ››

ወንዶች ለባሕርያቸው የሚገባውን ሴቶችን መገናኘት ተዉ
እዚህ ላይ ‹‹ተፈጥሮአዊ ግንኙነት›› የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በማያሳፍር ሁኔታ የሚገለጽበት አባባል ነው። ‹‹ ብዙ ወንዶች ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ ሴቶችን መገናኘት አቆሙ።››

እርስ በርሳቸው በፍትዎታቸው ተቃጠሉ
‹‹ወንዶች ለወንዶች ጠንካራ የፍትወት ፍላጎት አሳዩ››

የሚያሳፍር ነገር አደረጉ
‹‹ሊያፍሩበት የሚገባውን ተግባር፣ ያለምንም እፍረት አደረጉ››

ወንዶችም በወንዶች ላይ ነውር አድርገው በስህተታችው የሚገባውን ብድራት በራሳቸው ተቀበሉ
“ወንዶች ባደረጉት ስህተት ምክንያት እግዚአብሔር በፍትሐዊነት ቀጣቸው”

ስህተት
የግብረገብ ስህተት፣ ስለ አንድ እውነት መሳት አይደለም

Romans 1:28

በኃሳባቸው ስለ እግዚአብሔር ማወቅ ስላልፈለጉ
“እግዚአብሔርን ማወቅ አስፈለጊ እንደሆነ እንደነበር አላሰቡም

እነርሱ . . . የእነርሱ . . . እነርሱ
በሮሜ 1፡18 የተጠቀሱት እነዚህ ቃሎች የሚያመለክቱት ስለ “ሰው ልጆች” ነው።

ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው
እዚህ ላይ ‹‹የማይረባ አእምሮ›› ማለት ስለ አስጸያፊ ነገሮች ብቻ የሚያስብ ማለት ነው። “እግዚአብሔር ይህ የሚያስቡት የማይጠቅምና አስጸያፊ ሃሳብ አእምሮአቸውን ሙሉ ለሙሉ እንዲቆጣጠራቸው ፈቀደ።

Romans 1:29

የተሞሉ ነበሩ
ይህንን በአድራጊ ቅርጽ ልትተረጉመው ትችላለህ። ‹‹ በውስጣቸው እጅግ ጠንካራ ፍላጎት አላቸው›› ወይም ‹‹ ይህንን ለማድረግ በጣም ጠንካራ ፍላጎት አላቸው።››

ዓመፃ ሁሉ፣ ግፍ፣ መመኘት፣ ክፋት ሁሉ መፐላባቸው
ይህንን በአድራጊ ቅርጽ ልትተረጉመው ትችላለህ። ‹‹ብዙዎች በሌሎች ሰዎች ላይ ዓመፃን ያደርጋሉ---ሰው ሰዎችን መግደልን በተከታታይ ይመኛል--- ክርክርና ኘልን በሰዎች መካከል ያነሳሳሉ--- ሌሎችን ያታልላሉ--- በሌሎች ላይ የጥላቻ ንግግርን የደርጋሉ››

ተሳዳቢዎች
ተሳዳቢዎች የተሳሳቱ ነገሮችን በሌላ ሰው ላይ በመናገር ሰውየውን ለአደጋ ያጋልጡታል።

ክፉ ነገሮችን ለማድረግ ዘዴ ይፈጥራሉ
‹‹በሌሎች ላይ ክፉ ነገሮችን ለማድረግ አዳዲስ መንገዶችን ያስባሉ››

ምዕራፍ 2

1 ስለዚህ አንተ ሰው፥ አንተው ፈራጁ እነዚያኑ ነገሮች ስለምታደርግ በሌላው በምትፈርድበት ራስህን ትኮንናለህና የምታመካኘው የለህም። **2** ነገር ግን እነዚያን
ነገሮች በሚያደርጉት ላይ ቁጣው በሚወርድባቸው ጊዜ የእግዚአብሔር ፍርድ እውነተኛ እንደሆነ እናውቃለን። **3** ነገር ግን አንተው ራስህ ያንኑ እያደረግህ
እንደነዚያ ያሉትን በሚያደርጉት ላይ የምትፈርድ አንተ ሰው፥ይህንን አስተውል። ከእግዚአብሔር ፍርድ ታመልጣለህን? **4** ወይስ የቸርነቱን ባለጠግነት፥የቅጣቱን
መዘግየትና ትዕግስቱን ታቃልላለህን? ቸርነቱ ወደ ንስሐ ሊመራህ እንደሆነ አታውቅምን? **5** ነገር ግን በፍርድ ቀን ያም የእግዚአብሔር የጽድቅ ፍርድ
በሚገለጥበት ጊዜ በድንዳኔህና ንስሐ በማይገባው ልብህ መጠን ለራስህ ቁጣን ታከማቻለህ። **6** እርሱ ለእያንዳንዱ ሰው እንደ ሥራው መጠን ዋጋውን
ይከፍለዋል፤ **7** በበጎ ተግባር በመጽናት ምስጋናን፥ክብርንና የማይጠፋውን ሕይወት ለሚፈልጉ የዘላለምን ሕይወት ይሰጣቸዋል። **8** የራሳቸውን ጥቅም
በሚፈልጉት፥ለአመጻ እንጂ ለእውነት በማይታዘዙት ላይ ግን መቅሰፍትና ብርቱ ቁጣ ይመጣባቸዋል። **9** አስቀድሞ በአይሁዳዊ ቀጥሎም በግሪክ ሰው፥ክፋትን
ባደረገ ነፍስ ሁሉ ላይ እግዚአብሔር መከራና ጭንቀትን ያመጣባቸዋል። **10** አስቀድሞ ለአይሁድ ቀጥሎም ለግሪክ መልካም ላደርጉ ሁሉ ግን ምስጋና፥ክብርና
ሰላም ይሆንላቸዋል። **11** እግዚአብሔር ስለማያዳላ **12** ሕግ እያላቸው ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ በሕግ ይፈረድባቸዋል፥ሕግ ሳይኖራቸው ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ
ደግሞ ያለ ሕግ ይጠፋሉ። **13** በእግዚአብሔር ፊት የሚጸድቁት ሕጉን የሚሰሙት ሳይሆኑ ሕጉን የሚያደርጉት ናቸው። **14** ሕግ የሌላቸው አሕዛብ
በተፈጥሮአቸው የሕጉን ነገሮች በሚፈጽሙበት ጊዜ ሕግ ባይኖራቸውም እንኳ ለእነርሱ ለራሳቸው ሕግ ናቸው። **15** በዚህም ሕጉ የሚጠይቃቸው ድርጊቶች
በልቦናቸው መጻፋቸውን ያሳያሉ። ሃሳባቸው ሲከሳቸው ወይም ሲደግፋቸው ኅሊናቸው ደግሞ ለራሳቸውና **16** ለእግዚአብሔር ይመሰክራል። ይህም እኔ ስለ
ኢየሱስ ክርስቶስ እንደምሰብከው ወንጌል ሰዎች ሁሉ በስውር ስላደረጉት ነገር እግዚአብሔር በሚፈርድበት ቀን በዚያን ጊዜ ይሆናል። **17** በሕጉ በመመራትህ
አይሁዳዊ ነኝ ትላለህ፥ በሕጉ ትደገፋለህ፥ በእግዚአብሔር በመመካት ደስ ትሰኛለህ፥ **18** ፈቃዱን ታውቃለህ፥ ከእርሱ ውጪ የሆኑትን ነገሮች መርምረህ ትረዳ
ይሆናል። **19** አንተ ራስህ የዕውሩ መሪ፥ በጨለማ ላሉት ብርሃን፥ **20** የሰነፎች አስተማሪ፥ የሕጻናትም መምህር በመሆንህ በሕግ የእውቀትና የእውነት መልክ
እንዳለህ ትታመን ይሆናል። **21** እንግዲህ አንተ ሌላውን የምታስተምር ራስህን አታስተምርምን? አትስረቅ ብለህ የምትሰብክ ትሰርቃለህን? **22** አታመንዝር
የምትል አንተ ታመነዝራለህን? ጣዖታትን የምትጸየፍ ቤተመቅደሶችን ትዘርፋለህን? **23** አንተ በሕጉ በመመካት የምትደሰተው ሰው ሕጉን በመተላለፍ
እግዚአብሔርን ትንቃለህን? ይህ ልክ "በእናንተ **24** ምክንያት በአሕዛብ መካከል የእግዚአብሔር ስም ይናቃል" ተብሎ እንደተጻፈው ነው። **25** ሕጉን ብትፈጽም
በርግጥ መገረዝ ይጠቅማል፥ የሕጉ ተላላፊ ብትሆን ግን መገረዝህ እንደ አለመገረዝ ይሆናል። **26** እንግዲህ ያልተገረዘው ሰው የሕጉን ትዕዛዛት ቢጠብቅ
አለመገረዙ እንደ መገረዝ አይቆጠርለትምን? **27** በፍጥረቱ ያልተገረዘው ሰው ሕጉን ቢፈጽም አይፈርድባችሁምን? ይህም እናንተ ቅዱሳት መጻሕፍትና መገረዝ
እያላችሁ ሕጉን ተላላፊ ስለሆናችሁ ነው። **28** በውጫዊ ማንነቱ ብቻ አይሁዳዊ የሆነ እርሱ አይሁዳዊ አይደለም፥ የሥጋ ውጫዊ መገረዝ ብቻም መገረዝ
አይደለም። **29** ነገር ግን በውስጣዊ ማንነቱ አይሁዳዊ የሆነ እርሱ አይሁዳዊ ነው፥ መገረዝም በፊደል ሳይሆን በመንፈስ በልብ የተደረገው ነው። እንዲህ ላለ
ሰው ከሰዎች ሳይሆን ከእግዚአብሔር ምስጋና ይሆንለታል።

Romans 2:1

አያያዥ መግለጫዎች
ጳውሎስ ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኞች እንደሆኑና ክፉዎች ስለመሆናቸው ማሳሰቡን ያረጋግጣል።

ስለዚህ የምታመካኝበት የለህም
‹‹ስለዚህ›› የሚለው ቃል የጽሑፉ አዲስ መስመር መጀመሪያ ነው። እንዲሁም ጳውሎስ በሮሜ 1፡1-32 ለተናገረው መደምደሚያ ይሆናል። “እግዚአብሔር ኃጢአትን በተደጋጋሚ የሚያደርጉትን የሚቀጣ ከሆነ፣ በእርግጥ ለኃጢአታችሁ ይቅርታ አያደርግም።”

አንተ ነህ
ጳውሎስ እዚህ ላይ ሲጽፍ ልክ ከእርሱ ጋር ለሚከራከር አንድ አይሁዳዊ እንደሚጽፍ አድርጎ ነው። ጳውሎስ ይህን የሚያደርገው እግዚአብሔር ኃጢአትን በማድረግ የሚጸኑትን እንደሚቀጣ የሚጽፍላቸውን አይሁዶች ቢሆኑ አሕዛብ+ ለማስገንዘብ ነው።

አንተ
ይህ ‹‹አንተ›› የሚለው ተውላጠ ስም የተናጠል ስም ነው።

ራስህ አንተ፣ ፈራጅ የሆንከው
ጳውሎስ ‹‹አንተ›› የሚለውን ቃል የሚጠቀመው ማንኛውም ራሱን እንደ አምላክ የሚቆጥርና በሌሎች ላይ የሚፈርደውን ለመገሰጽ ነው። ‹‹አንተ ራስህ ሰብኤ ፍጥረት ሆነህ እያለ የእግዚአብሔር ቅጣት ይገባቸዋል በማለት በሌሎች ላይ ትፈርዳለህ››

በሌላው ላይ በምትፈርድበት ነገር ሁሉ ራስህን ትኮንናለህ
‹‹እነርሱ እንደሚያደርጉት አንተም ታደርጋለህና በራስህ ላይ ትፈርዳለህ››

ነገር ግን እኛ እናውቃለን
እዚህ ላይ ‹‹እኛ›› የሚለው ተውላጠ ስም ክርስቲያን አማኞችንና ክርስቲያን ያልሆኑ አይሁዶችን የሚያጠቃልል ነው።

እንደዚህ በሚያደርጉትም ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ ትክክለኛ መሆኑን እናውቃለን
እዚህ ላይ ጳውሎስ ስለ ‹‹እግዚአብሔር ፍርድ›› ሲናገር ሕያው እንደሆነ በሰዎች ላይ ‹‹ሊወድቅ›› እንደሚችል አድርጎ ነው። ‹‹እግዚአብሔር እነዚያን ሰዎች በእውነትና በተገቢው ሁኔታ ይፈርድባቸዋል››

እነዚያን ነገሮች የሚለማመዱ
‹‹እነዚያን ክፉ ነገሮች የሚያደርጉ ሰዎች››

Romans 2:3

ነገር ግን ይህን አስብ
‹‹ስለዚህ ይህንን አስብ›› ወይም ‹‹ስለሆነም፣ ይህንን አስብ››

ይህን አስብ
‹‹እኔ ልነግርህ ያለሁትን አስብ››

ግለሰብ
ለሰው ዘሮች ሁሉ የምትጠቀምበት አጠቃላይ ቃል ነው ‹‹አንተ ማንም ብትሆን›

እነዚህን በሚያደርጉት ላይ የምትፈርድ አንተው ራስህ ያንኑ ነገር ታደርጋለህ
‹‹አንድን ሰው የእግዚአብሔር ቅጣት ይገባዋል ብለህ የምትፈርድ አንተው ያንኑ ክፉ ነገር ታደርጋለህ››

ከእግዚአብሔር ፍርድ ታመልጣለህን?
ይህ ማስገንዘቢያ በጥያቄ መልክ የቀረበው አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህንን ጥያቄ እንደ አንድ ጠንካራ አሉታዊ መግለጫ አድርገህ ልትተረጉመው ትችላለህ። ‹‹አንተ በእርግጥ የእግዚአብሔርን ፍርድ አታመልጥም››

የእርሱን መልካም ባለጠግነት፣ ቅጣቱን ማዘግየቱን፣ እና ታጋሽነቱን ... ወደ ንስሐ እንደሚመራህ ሳታውቅ ትንቃለህን?
ይህ ማስገንዘቢያ ትኩረት እንዲያገኝ በጥያቄ መልክ ቀርቦአል። ይህንን እንደ ጠንካራ መግለጫ አድርገህ መተርጎም ትችላለህ። ‹‹እግዚአብሔር መልካም ስለሆነ ሰዎችን ለብዙ ጊዜ ይታገሳቸዋል ስለዚህ ይህ መልካመነቱ ንስሓ እንዲገቡ ያደርጋቸዋልና ምንም አይደለም የሚል ሁኔታ ሊኖርህ አይገባም››

የትእግስቱን---ባለጠግነት ትንሽ እንደሆነ ታስባለህ
‹‹ባለጠግነቱንና --- ትእግስቱን እንደማያስፈልግ›› ወይም ‹‹መልካም እንዳልሆነ --- ትቆጥራለህ››

የእርሱ መልካምነት ወደ ንስሓ የሚመራህ መሆኑን አታውቅምን?
ይህ ማስገንዘቢያ ትኩረት እንዲያገኝ በጥያቄ መልክ ቀርቦአል። ይህንን እንደ ጠንካራ መግለጫ አድርገህ መተርጎም ትችላለህ። ‹‹እግዚአብሔር መልካም እንደሆነ የሚያሳይህ አንተ ንስሓ እንድትገባ እንደሆነ ማወቅ አለብሕ››

Romans 2:5

አያያዥ መግለጫ
ጳውሎስ ሕዝቡ ሁሉ ኃጢአተኛ መሆኑን ሕዝቡን ማስታወሱን ቀጥሎአል።

ነገር ግን በደንዳናውና ንስሐ የማይገባው ልብህ ልክ
ጳውሎስ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ የማይፈልገውን ሰው ለመግለጽ ልቡን ከጠንካራ ድንጋይ ጋር በማነጻጸር ገልጾታል። እንዲሁም የግለሰቡን አእምሮ ወይም ውስጣዊ ማንነት ለመግለጽ “ልብ” የሚለውን ዘይቤ ይጠቀማል። “ለማዳመጥና ንስሐ ለመግባት አሻፈረኝ በማለቱ ምክንያት ነው”

ደንዳና እና ንስሐ የማይገባ ልብ
ይህን “ንስሐ የማይገባ ልብ” በማለት ማጣመር ይቻላል።

በራስህ ላይ ቁጣን አከማችተሃል
“ማከማቸት” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ብዙውን ጊዜ ሀብቱን የሚሰበስብ እና በአስተማማኝ ቦታ የሚያኖርን ሰው ነው። ጳውሎስ በሀብት ፋንታ ግለሰቡ የእግዚአብሔርን ቅጣት እየሰበሰበ ነው ብሏል። ንስሐ ሳይገቡ በቆዩበት መጠን ቅጣታቸውም ከባድ ይሆናል። “ቅጣታችሁን የከፋ ታደርጋላችሁ”

በቁጣ ቀን . . . የእግዚአብሔር የጽድቅ ፍርድ የሚገለጥበት ቀን
እነዚህ ሁለቱም ሐረጎች የሚያመለክቱት ያንኑ ቀን ነው። “እግዚአብሔር ቁጣውን ለሁሉም ሲያሳይ፣ ለሰው ሁሉ በትክክል ይፈርዳል”

ይከፍላል
“ትክክለኛ ዋጋ ወይም ቅጣት ይሰጣል”

ለእያንዳንዱ ሰው እንደ ሥራው
“እያንዳንዱ ሰው በሠራው ሥራ መጠን”

ፈለጉ
x

Romans 2:8

አያያዥ መግለጫ
ይህ ክፍል ምንም እንኳን ሃይማኖተኛ ስላልሆነ ኃጢአተኛ ሰው የሚናገር ቢሆንም፣ ጳውሎስ አይሁድ ያልሆኑትም ሆኑ አይሁዶች በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአተኞች መሆናቸውን በመግለጽ ጠቅለል አድርጎ ገልጾታል።

በራስ መፈለግ
“ራስ ወዳድ” ወይም “ራሳቸው ስለሚደሰቱበት ብቻ ግድ የሚላቸው”

እውነትን የማይታዘዙ ነገር ግን ጽድቅ ያልሆነውን የሚታዘዙ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ አንድ ዓይነት ናቸው። ሁለተኛው የመጀመሪያውን ያጠናክራል።

ቁጣ እና የመረረ ንዴት ይመጣል
“ቁጣ” እና “የመረረ ንዴት” የሚሉት ቃላት በመሠረቱ አንድ ዓይነት ናቸው፤ የእግዚአብሔርን ቁጣ አፅንኦት ይሰጣሉ። “እግዚአብሔር እጅግ መቆጣቱን ያሳያል”

ቁጣ
እዚህ ላይ “ቁጣ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔር በኃጢአተኛ ሰዎች ላይ የሚመጣውን ከባድ ቅጣት የሚገልጽ ነው።

መከራና ጭንቀት
“መከራ” እና “ጭንቀት” የሚሉት ቃላት በመሠረቱ አንድ አይነት ትርጉም ያላቸው ሲሆን፣ እዚህ ላይ አፅንኦት የሚሰጡት የእግዚአብሔር ቅጣት ምን ያህል መጥፎ እንደሆነ ነው። “አሰቃቂ ቅጣት ይሆናል”)

በእያንዳንዱ የሰው ነፍስ ላይ
እዚህ ላይ፣ ጳውሎስ “ነፍስ” የሚለውን ቃል መላውን ሰው ለማመልከት እንደ መነጋገሪያ ዘዴ ይጠቀማል። “በእያንዳንዱ ሰው ላይ”

ክፉ ነገሮችን የተለማመደ
“ሁልጊዜም መጥፎ ነገሮችን የሚሠራ”

አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው
“እግዚአብሔር አስቀድሞ በአይሁድ ሕዝብ ላይ፣ ከዚያም አይሁድ ባልሆኑት ሕዝቦች ላይ ይፈርዳል”

አስቀድሞ
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) “መጀመሪያ ከጊዜ አንጻር” ወይም 2) “በእርግጠኝነት”

Romans 2:10

ነገር ግን ምስጋና፣ ክብር እና ሰላም ይመጣሉ
x

Romans 2:13

አያያዥ መግለጫ
ጳውሎስ ለእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም መታዘዝ፣ ሕጉ የሌላቸውም ሰዎች ብቻ ሳይሆን ሕጉ ያላቸውንም እንደሚጨምር አንባቢው እንዲያውቅ መግለጹን ቀጠለ።

ለ
ቁጥር 14 እና 15 ጳውሎስ ለአንባቢው የሚሰጠውን ተጨማሪ መረጃ ያቋርጣሉ። እንደዚህ ዓይነቱን ማቋረጥ በቋንቋህ ምልክት የምታደርግበት መንገድ ካለህ፣ እዚህ ላይ መጠቀም ትችላለህ።

የሕጉ አዳማጮች አይደሉም
እዚህ ላይ “ሕጉ” የሙሴን ሕግ ያመለክታል። “የሙሴን ሕግ የሚሰሙ ብቻ አይደሉም”

በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን የሆኑ ማን ናቸው
“እግዚአብሔር እንደ ጻድቃን የሚቆጥራቸው”

ነገር ግን ሕግን የሚያደርጉ
“ነገር ግን እነርሱ የሙሴን ሕግ የሚታዘዙ ናቸው”

የሚጸድቀው ማን ነው?
ይህንን በአድራጊ ቅርፅ መተርጎም ትችላለህ። “እግዚአብሔር የሚቀበለው እርሱ”

ሕግ የሌላቸው አሕዛብ . . . ለራሳቸው ሕግ ናቸው
“ለራሳቸው ሕግ” የሚለው ሐረግ ማለት እነዚህ ሰዎች በተፈጥሮአቸው የእግዚአብሔርን ሕጎች ይታዘዛሉ ማለት ነው። “የእግዚአብሔር ሕጎች ቀድሞውኑ በውስጣቸው ነበራቸው”

ሕጉ የላቸውም
እዚህ ላይ “ሕጉ” የሙሴን ሕግ ያመለክታል። “በመሠረቱ እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጣቸው ሕጎች የላቸውም”

Romans 2:15

በዚህ ያሳያሉ
“በተፈጥሮ ሕጉን በመታዘዛቸው ያሳያሉ”

በሕጉ የሚፈለጉት ድርጊቶች በልባቸው ውስጥ የተጻፉ ናቸው
እዚህ ላይ “ልቦች” የግለሰቡን ሀሳቦች ወይም ውስጣዊ ማንነትን የሚገልጽ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። “በልባቸው የተጻፈ” የሚለው ሐረግ በአዕምሯቸው ውስጥ የሆነ ነገር የማወቅ ምሳሌ ነው። ይህንን በአድራጊ ቅርፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። “ሕጉ ምን እንዲያደርጉ የሚጠበቅባቸውን እግዚአብሔር በልባቸው ላይ ጽፎታል” ወይም “እግዚአብሔር በሕጉ መሠረት እንዲያደርጉ የሚፈልገውን ያውቃሉ።

የራሳቸው አሳቦች እራሳቸውን ሲከሳቸው፣ ወይም ለእነርሱ ሲከላከል፣ ለእነርሱ ይመሠክርላቸዋል
እዚህ ላይ “ይመሰክራል” የሚያመለክተው እግዚአብሔር በልባቸው ውስጥ ከጻፈው ሕግ ያገኙትን እውቀት ነው። “የእግዚአብሔርን ሕግ የማይታዘዙ ወይም እየታዘዙ መሆናቸውን ይነግራቸዋል”

እግዚአብሔር በሚፈርድበት ቀን
ይህ በሮሜ 2:13 ላይ የተገለጸውን የጳውሎስን ኃሳብ ያጠቃልላል። “እግዚአብሔር በሚፈርድበት ጊዜ ይህ ይሆናል”

Romans 2:17

አያያዥ መግለጫ
እዚህ ላይ ጳውሎስ ንግግሩን በመቀጠል አይሁድ ያላቸው ሕግ በመሠረቱ እነርሱ ስላልታዘዙት ይፈርድባቸዋል ይላል።

አንተ እራስህን አይሁድ ብለህ ብትጠራ
“አንተ እራስህን አይሁዳዊ ብለህ ከጠራህ”

በሕጉ ላይ እረፍ
ይህ አባባል ሁለት ትርጉሞች ሊኖሩት ይችላል፣ 1) አንድ ሰው በመንፈስ ሕያው ይሆናል ምክንያቱም ትክክል የሆነውን ነገር እንዲሠራ እግዚአብሔር ኃይል ይሰጣዋል 2) አንድ ከሞተ በኋላ እግዚአብሔር ያንን ሰው በሕይወት ወደ መኖር ይመልሰዋል ምክንያቱም እግዚአብሔር ጻድቅ በመሆኑ ለአማኝ ክርስቲያኖች የዘላለም ሕይወት ይሰጣቸዋል።

Romans 8:11

መንፈሱ. . . በእናንተ የሚኖር ከሆነ
ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ በአንባቢዎቹ ውስጥ እንደሚኖር ያስባል። በሌላ አባባል፣ "ምክንያቱም መንፈሱ. . .በእናንተ ስለሚኖር".

ከሞት ያስነሣው የእርሱ
"ከሞት ያስነሣው የእግዚአብሔር"

ኢየሱስን ከሞት አስነሣ
እዚህ ላይ ከሞት አስነሣ ማለት የሞተን ሰው እንደገና መልሶ ሕያው ማድረግ ማለት ነው። በሌላ አባባል፣ “ኢየሱስን መልሶ በሕይወት እንዲኖር አደረገ”

ሟች የሆኑ አካላት
"ውጫዊ አካላት" ወይም "የሆነ ቀን ሊሞቱ ያሉ አካላት"

Romans 8:12

እንዲህ ከሆነ
"የነገር'ኳችሁ ነገር እውነት ስለሆነ"

ወንድሞች
እዚህ ላይ ወንድሞች ሲል ክርስቲያን ወገኖች ለማለት ነው፣ ወንዶችንም ሴቶችንም ያጠቃልላል።

Romans 8:14

በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ብዙዎች
በሌላ አተረጓጎም፣"የእግዚአብሔር መንፈስ የሚመራቸው ሰዎች ሁሉ"

የእግዚአብሔር ልጆች
እዚህ ላይ 'በኢየሱስ ያመኑ አማኞች ሁሉ' ማለት ነው። ብዙ ጊዜም "የእግዚአብሔር ልጆች" ተብሎ ይተረጎማል።

የምንጮኽበት
“እንድንጮህ የሚያደርገን”

አብ፣ አባት
አብ የሚለው አባ ከሚለው የአረሜይክ ቋንቋ የመጣ ሲሆን አባት ማለት ነው።

Romans 8:16

የእግዚአብሔር ወራሾች
x

Romans 8:18

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ሰውነታችን በሚበዥበት ጊዜ እንደሚለወጥ ጳውሎስ እኛ አማኞችን እስከ 8፡25 ባለው በዚህ ክፍል ያስታውሰናል።

ለዚህ
እዚህ ላይ 'አስባለሁ' የሚለውን ሐሳብ ለማጽናት ነው። 'ምክንያቱም' ለማለት አይደለም።

ከ. . . ጋር ለማወዳደር የሚገባቸው እንዳልሆኑ አስባለሁ
በሌላ አተረጓጎም፣ “የአሁኑን መከራ ከዚያ ጋር ማወዳደር አልችልም”.

ሊገለጥ ያለው
በሌላ አተረጓጎም፣ "እግዚአብሔር ሊገልጠው ያለው" ወይም "እግዚአብሔር ሊያሳውቅ ያለው"

የፍጥረት በጉጉት መጠባበቅን እየጠበቀ
ጳውሎስ እዚህ ላይ እግዚአብሔር የፈጠራቸውን ነገሮች ሁሉ በጉጉት የሆነ ነገር የሚጠብቁ አካላት እንደሆኑ ይናገራል።

ለእግዚአብሔር ልጆች መገለጥ
በሌላ አተረጓጎም፣ "እግዚአብሔር ልጆቹን የሚገልጥባቸውን ጊዜ"

የእግዚአብሔር ወንዶች ልጆች
ይህ ማለት በኢየሱስ ያመኑት ሁሉ፤ "የእግዚአብሔር ልጆች" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል።

Romans 8:23

እኛ የመጀመርያ መንፈሳዊ ፍሬ አፍርተናል
ጳውሎስ የክርስቲያን አማኞችን መንፈስ ቅዱስ መቀበል ተተክሎና ወቅቱን ጠብቆ ከደረሰው የመጀመርያ ፍሬና አትክልት ጋር ያነጻጽራል። መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ለክርስቲያን አማኞች ከሚሰጣቸው ነገሮች የመጀመርያ መሆኑን በአጽንኦት ለመናገር ነው። በሌላ አባባል፣ “እኛ የመጀመርያውን የእግዚአብሔር ስጦታ ያለን ነን፤ እሱም መንፈስ ቅዱስ ነው”

የእግዚአብሔር ልጅነታችንን መሟላት እየተጠባበቅን፤ እሱም የአካላችን መበዥት
እዚህ ላይ "የእግዚአብሔር ልጅነታችን መሟላት" ማለት የእግዚአብሔር ቤተሰብ ሙሉ አባል ስንሆን ማለት ነው። "መበዥት" የሚለው ቃል እግዚአብሔር ሲያድነን ማለት ነው። በሌላ አባባል፣ "የእግዚአብሔር ቤተሰብ ሙሉ አባል መሆናችንን እየተጠባበቅን ይኸውም እሱ ኣካላችንን ከመበስበስና ከሞት ሲያድን"

እኛ በዚህ የታመነ ተስፋ የዳንን ነን
በሌላ አተረጓጎም፣ “በእርሱ ተስፋ ስላደረግን እግዚአብሔር አዳነን”

ነገር ግን ተስፋ የምናደርገውን ነገር እያየን ከሆነ ተስፋ አይደለም ምክንያቱም የሚያየውን ነገር የሚጠብቅ ማን አለ?
ጳውሎስ የሚጽፍላቸውን ሰዎች "ተስፋ" የሚለው ቃል ምን ማለት እንደሆነ እንዲገነዘቡ በጥያቄ መልክ ተናገራቸው። በሌላ አባባል፣ "ነገር ግን በመታመን እየተጠባበቅን ከሆነ የምንፈልገው ነገር ገና አልሆነልንም ማለት ነው። የሚፈልገውን ካገኘማ ማንም በመታመን አይጠብቅም"

Romans 8:26

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ምንም እንኳ ጳውሎስ በሥጋዊ ምኞት እና በመንፈሳዊ እውነታ መካከል በክርስቲያን አማኞች ሕይወት የሚካሄድ ትግል መኖሩን አጽንኦት ሰጥቶ የሚናገር ቢሆንም የእግዚአብሔር መንፈስ እንደሚያግዘን ደግሞ ያረጋግጥልናል።

ልገለጽ የማይችል መቃተት
x

Romans 8:28

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ጳውሎስ ክርስቲያን አማኞችን ከእግዚአብሔር ፍቅር ማንም ሊለያቸው እንደማይችል ያስታውሳቸዋል።

ለተጠሩት
በሌላ አተረጓጎም፣ "እግዚአብሔር ለመረጣቸው"

አስቀድሞ ላወቃቸው
"ገና ሳይፈጥራቸው እንኳ ላወቃቸው”

መጨረሻቸውንም ደግሞ አስቀድሞ ወሰነ
"መዳረሻቸውን ደግሞ ወሰነ" ወይም "ደግሞም አስቀድሞ አቀደ"

የልጁን መልክ እንዲኖራቸው
እግዚአብሔር ከፍጥረት ጅማረ አስቀድሞ በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ የሚያምኑት ኢየሱስን ወደ መምሰል እንዲያድጉ አቀደ። በሌላ አባባል፣ "ልጁን እንዲመስሉ ልለውጣቸው"

ልጅ
ይህ ለኢየሱስ ለእግዚአብሔር ልጅ አስፈላጊ ማዕረግ ነው።

እሱ የመጀመርያ ልጅ እንዲሆን
“ልጁ የመጀመርያ ልጅ እንዲሆን”

ከብዙ ወንድሞች መካከል
እዚህ ላይ "ወንድሞች" የሚለው ሁሉንም አማኞች ወንድንም ሆነ ሴት ያመለክታል። በሌላ አባባል፣ "የእግዚአብሔር ቤተሰብ ከሆኑት ከብዙ ወንድሞችና እህቶች መካከል"

መጨረሻቸውን አስቀድሞ ለወሰነላቸው
"እግዚአብሔር አስቀድሞ ዕቅድ ላወጣላቸው"

እነዚህን ደግሞ ከጥፋተኝነት አወጣቸው
እዚህ ላይ "ከጥፋተኝነት አወጣቸው" የሚለው ያለፈውን ጊዜ አመልካች መሆኑ ይህ በእርግጠኝነት እንደሚሆን አስረግጦ ለመግለጽ ነው። በሌላ አባባል፣ "እነዚህን ደግሞ በፊቱ ከጥፋተኝነት ነፃ አደረጋቸው"

እነዚህን ደግሞ አከበራቸው
x

Romans 8:31

እንግድህ ስለ እነዚህ ነገሮች ምን እንላለን? እግዚአብሔር እኛን የሚደግፈን ከሆነ ማን ሊቃወመን ይችላል?
ጳውሎስ ከላይ ለተናገረው ነገር አጽንኦት ለመስጠት ዐረፍተ ነገሩን በጥያቄ መልክ ያስቀምጣል። በሌላ አባባል፣ "ከዚህ ሁሉ መረዳት ያለብን ነገር ይህ ነው፣ እግዚአብሔር እየረዳን ከሆነ ማንም ሊያሸንፈን አይችልም"

የራሱን ልጅ እንኳ ከሞት ያላተረፈው
ገደብ የለሽና ቅዱስ የሆነውን የእግዚአብሔርን ባሕርይ ኃጥአተኛ ከሆነው የሰው ባሕርይ ጋር ለማቀራረብ ቅዱስና ገደብ የለሽ መስዋዕት እንዲሆን እግዚአብሔር አብ የእግዚአብሔርን ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ መስቀል ላከ። እዚህ ላይ "ልጅ" የሚለው ለኢየሱስ ለእግዚአብሔር ልጅ አስፈላጊ ማዕረግ ነው።

ነገር ግን አሳልፎ ሰጠው
"ነገር ግን በጠላቶቹ እጅ ኣሳልፎ ሰጠው"

ታዲያ ከእርሱ ጋር እንዴት ሁሉን ነገር በነፃ አይሰጠንም?
ጳውሎስ ለተናገረው ነገር አጽንኦት ለመስጠት ዐረፍተ ነገሩን በጥያቄ መልክ ያስቀምጣል። በሌላ አባባል፣ "እርሱ በእርግጠኝነት ሁሉን ነገር በነፃ ይሰጠናል"

ሁሉን ነገር በነፃ ይሰጠናል
“በቸርነቱ ሁሉን ነገር ይሰጠናል"

Romans 8:33

እግዚአብሔር የመረጣቸውን ሰዎች የሚከስሳቸው ማን ነው? ከጥፋተኝነት የሚያወጣው እግዚአብሔር ነው።
ጳውሎስ ለተናገረው ነገር አጽንኦት ለመስጠት ዐረፍተ ነገሩን በጥያቄ መልክ ያስቀምጣል። በሌላ አባባል፣ "በእግዚአብሔር ፊት ማንም ልከሰን አይችልም ምክንያቱም በፊቱ ትክክለኛ ሕይወት እንዲኖረን ሊያደርገን የሚችል እርሱ ነው።

የሚወቅሰን ማነው?
ጳውሎስ ለተናገረው ነገር አጽንኦት ለመስጠት ዐረፍተ ነገሩን በጥያቄ መልክ ያስቀምጣል። መልስ እንዲሰጥ ጠብቆ አይደለም። "ማንም ልወቅሰን አይችልም"

ከዚህ ሁሉ በላይ እርሱ ከሞት እንዲነሣ የተደረገ
እዚህ ላይ ከሞት እንዲነሣ የተደረገ የሚለው አባባል የሞተን ሰው ተመልሶ በሕይወት እንዲኖር ማድረግ ለማለት ነው። በሌላ አተረጓጎም፣ "ክሁሉ ይልቅ እግዚአብሔር ከሙታን ያስነሣው እርሱ" ወይም "ከሁሉ ይልቅ እንዲያሁም ከሞት ወደ ሕይወት የተመለሰ እርሱ"

በእግዚአብሔር ቀኝ ያለ
“በእግዚአብሔር ቀኝ” መሆን ከእግዚአብሔር ከፍ ያለ ክብር እና ሥልጣን የመቀበል ተግባር ምልክት ነው። በሌላ አባባል፣ “በእግዚአብሔር አጠገብ በክብር ቦታ ያለ”

Romans 8:35

ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል?
ጳውሎስ ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ከክርስቶስ ፍቅር ምንም ነገር ሊለየን እንደማይችል ለማስተማር ነው። በሌላ አባባል፣ “መቼም ቢሆን ማንም ከክርስቶስ ፍቅር ሊለየን አይችልም”

መከራ ወይስ ሥቃይ ወይስ ስደት ወይስ ረሃብ ወይስ እርዛት ወይስ አደጋ ወይስ ሰይፍ?
“ከክርስቶስ ፍቅር ሊለየን” የሚሉትን ቃላት ከቀደመው ጥያቄ መረዳት ይቻላል። በሌላ አባባል፣ “መከራ ወይም ሥቃይ ወይም ስደት ወይም ረሃብ ወይም እርዛት ወይም አደጋ ወይም ሰይፍ ከክርስቶስ ፍቅር ሊለዩን ይችላሉ ወይ?

መከራ ወይስ ሥቃይ ወይስ ስደት ወይስ ረሃብ ወይስ እርዛት ወይስ አደጋ ወይስ ሰይፍ?
ጳውሎስ ይህን ጥያቄ የተጠቀመው እነዚህ ነገሮች እንኳ ከክርስቶስ ፍቅር ሊለዩን እንደማይችሉ በአጽንኦት ለመናገር ነው። በሌላ አባባል፣ “መከራ፣ ሥቃይ፣ ስደት፣ ረሃብ፣ እርዛት፣ አደጋ እናአሰይፍ ከክርስቶስ ፍቅር ሊለዩን አይችሉም”

መከራ ወይስ ሥቃይ ወይስ ስደት ወይስ ረሃብ ወይስ እርዛት ወይስ አደጋ ወይስ ሰይፍ?
በንድፈ ሐሳብ ደረጃ የተቀመጡ ስሞች በቃላት ሐረጎች ሊገለጹ ይችላሉ። እዚህ ላይ “ሰይፍ” የሚለው አነጋገር በጭካኔ መገደልን ይተካል። በሌላ አባባል፣ “ምንም እንኳ ሰዎች ቢያሰቃዩን፣ ቢጎዱን፣ ልብሳችንንና ምግባችንን ቢወስዱብን ወይም ቢገድሉን ከክርስቶስ ፍቅር ሊለዩን አይችሉም”

መከራ ወይም ሥቃይ
ሁለቱም ቃላት አንድ ትርጉም አላቸው።

ላንተ ጥቅም
እዚህ ላይ "ላንተ" የሚለው ቃል ነጠላ ሆኖ እግዚአብሔርን የሚያመለክት ነው

እኛ ቀኑን ሙሉ እንገደላለን
እዚህ ላይ "እኛ" የሚለው ቃል ይህን የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍል የጻፈውን ሰው ሰው ሲያመለክት የመልዕክቱን ተቀባይ አያመለክትም፣ እሱም እግዚአብሔር ነበር። "ቀኑን ሙሉ" የሚለው ሐረግ ምን ያህል አደገኛ ሁኔታ ውስጥ እንዳሉ በአጽንኦት አጋንኖ ለማሳየት ነው። ጳውሎስ ይህን የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍል የተጠቀመው የእግዚአብሔር የሆኑ ሰዎች ሁሉ በሕይወታቸው ከባድ ጊዜ ሊገጥማቸው እንደሚችል መጠበቅ እንደሚገባቸው ለማሳየት ነው። በሌላ አተረጓጎም፣ “ጠላቶቻችን ሁሌም ሊገድሉን ይፈልጋሉ”

Romans 8:37

እኛ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን
"እኛ ሙሉ የድል አድራጊነት ብቃት አለን"

በወደደን በእርሱ አማካይነት
ኢየሱስ እንዴት ያለ ፍቅር እንዳሳየ በግልጽ ማስቀመጥ እንችላለን። በሌላ አባባል፣ "በብዙ ፍቅር እኛን ከመውደዱ የተነሣ ኢየሱስ በእኛ ፈንታ ለመሞት ፍቃደኛ ነበር"

አምነት አደረብኝ
"አመንኩኝ" ወይም "እርግጠኛ ሆንኩኝ"

መንግሥታት
x

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 9

1 በክርስቶስ እውነትን እናገራለሁ እንጂ አልዋሸም፣ ህሊናዬ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ሆኖ ይመሰክርልኛል፣ 2 ከፍተኛ ሀዘንና የማያቋርጥ ህመም በልቤ ውስጥ አለ። 3 በሥጋ ዘሮቼ ስለሆኑት ወንድሞቼ ሲባል እኔ እራሴ በተረገምኩና ከክርስቶስ በተለየሁ ብዬ እመኛለሁ። 4 እነርሱ እስራኤላውያን ናቸው። የልጅነት መብት ፣ክብሩ፣ቃል ኪዳኑ፣የህግ ስጦታው፣የአምልኮ ሥርዓቱ፣ የተስፋው ቃል አላቸው። 5 ከሁሉ በላይና ለዘላለም የእግዚአብሔር ብሩክ የሆነው ክርስቶስ በሥጋ የመጣው ከአባቶቻቸው ነው። ለእርሱ ለዘላለም ምስጋና ይሁን። አሜን! 6 ነገር ግን የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ተሻረ ማለት አይደለም። ምክንያቱም በእስራኤል የሚኖር ሁሉ እስራኤላዊ አይደለም። 7 ወይም የአብርሀም ዘር ሁሉ የአብርሀም ልጆች አይደሉም። ነገር ግን «ዘርህ በይስሀቅ ይጠራልሀል» ተባለ። 8 ይህም ማለት የሥጋ ልጆች የሆኑ የእግዚአብሔር ልጆች አይደሉም። የተስፋው ቃል ልጆች ግን ዘሮቹ ሆነው ተቆጠሩ። 9 የተስፋው ቃል «በዚህ ጊዜ ተመልሼ እመጣለሁ ለሳራም ልጅ ይሰጣታል» የሚል ነው። 10 ይህ ብቻ አይደለም፣ ርብቃ ከአባታችን ከይስሀቅ 11 ከጸነሰች በኋላ በምርጫ የሆነው የእግዚአብሔር ዓላማ ከሥራ የተነሳ ሳይሆን ከእርሱ ጥሪ የተነሳ ይጸና ዘንድ ልጆቹ ገና ሳይወለዱና ክፉም ሆነ ደግ ሳያደርጉ 12 «ታላቁ ለታናሹ ይገዛል» ተብሎ ተነግሯት ነበር። 13 ልክ «ያዕቆብን ወደድኩ ኤሳውን ጠላሁ» ተብሎ እንደተጻፈው ማለት ነው። 14 እንግዲህ ምን እንላለን? በእግዚአብሔር ዘንድ የጽድቅ መጓደል አለ ማለት ነው? በጭራሽ አይደለም። 15 ምክንያቱም ለሙሴ «የምምረውን እምራለሁ ለምራራለትም እራራለሁ» ብሎታል። 16 ስለዚህም ምህረት ለፈለገ ወይም ለሮጠ ሳይሆን ምህረትን ከሚያሳይ ከእግዚአብሔር ነው። 17 ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ስለፈርዖን ሲናገር «ኃይሌን በአንተ ላይ አሳይ ዘንድ ስሜም በምድር ሁሉ ይታወቅ ዘንድ ለዚህ ዋና ዓላማ አስነሳሁህ» ይላል። 18 ስለዚህም ከፈለገ ለአንዱ ምህረትን ይሰጠዋል ሌላውን ደግሞ ግትር ያደርገዋል። 19 «ታዲያ ሁልጊዜ ፈቃዱን የሚያደርግ ከሆነ ለምን ስህተትን ይፈልግብናል?» ትሉኝ ይሆናል። 20 በአንጻሩ ለእግዚአሔር መልስ የምትስጥ አንተ ማን ነህ? የሸክላ ጭቃ ቅርጽ ያወጣለትን ሰው ለምን እንደዚህ አድርገህ ሰራኽኝ ሊለው ይችላልን? ። 21 ሸክላ ሰሪው ከዚያው ጭቃ አንዱን ለየት ባለ ቀን አገልግሎት ላይ የሚውል ዕቃ ሌላውን ደግሞ በየቀኑ አገልግሎት የሚሰጥ ዕቃ አድርጎ ሊሰራው በሸክላ ጭቃው ላይ ሥልጣን የለውም እንዴ? 22 ቁጣውን ሊያሳይና ኃይሉ እንዲታወቅ የሚፈልገው እግዚአብሔር ለጥፋት የተዘጋጁትን የቁጣ ዕቃዎችአብዝቶ ሊታገሳቸው ቢፈልገስ? 23 ይህን ያደረገው አስቀድሞ ለክብር ባዘጋጃቸው የምህረት ዕቃዎቹ ላይ ክብሩን ሊያሳይ ቢሆንስ? 24 ይህንን ለአይሁድ ብቻ ሳይሆን ከአህዛብ ለተጠራን ለእኛም ቢያደርገውስ? 25 በትንቢት ሆሴዕም ላይ «ህዝቤ ያልሆነውን ህዝቤ ብዬ ያልተወደደችውንም የተወደደች ብዬ እጠራለሁ። 26 'ህዝቤ አይደላችሁም በተባሉበት በዚያው ቦታ 'የህያው እግዚአብሔር ልጆች' ይባላሉ» እንደሚለው ነው። 27 ኢሳያስ ስለእስራኤል «የእስራኤል ልጆች ብዛት እንደ ባህር አሸዋ ቢሆን እንኳ የሚድኑት ግን ትሩፋን ናቸው» ብሎ ይጮኽል። 28 ምክንያቱም እግዚአብሔር ቃሉን በምድር ላይ ሙሉ በሙሉ ፈጥኖ ይፈጽማል። 29 ይህም ኢሳያስ ቀደም ሲል «የሠራዊት ጌታ ዘር ባያስቀርልን ኖሮ እንድ ሰዶም በሆንን እንደ ገሞራም በሆነብን ነበር» እንዳለው ነው። 30 እንግዲህ ምን እንላለን? ለጽድቅ ያልሮጡት አህዛብ በእምነት የሆነውን ጽድቅ አገኙ። 31 ለጽድቅ ህግ የተጉት እስራኤል ግን ወደዚያ ሊደርሱ አልቻሉም። 32 ለምን አልደረሱም? ምክንያቱም ጽድቅን የፈለጉት በእምነት ሳይሆን በሥራ ስለሆነ ነው። በማሰናከያው ድንጋይ ተሰናከሉበት። 33 «በጽዮን የማሰናከያ ድንጋይና የዕንቅፋት ዐለት አስቀምጣለሁ በእርሱ የሚያምን አያፍርም» ተብሎ እንደተጻፈው ነው።

Romans 9:1

አያያዥ ዐረፍተ ነገር፣
ጳውሎስ የእስራል ሕዝብ ይድናሉ ብሎ ምኞቱን ይገልፃል። ከዚያም እነሱ እንዲያምኑ እግዚአብሔር በተለያየ መንገድ ሲያዘጋጃቸው እንደነበር በአጽንኦት ይናገራል።

እኔ በክርስቶስ ያለውን እውነት እናገራለሁ። አልዋሸም።
እነዚህ ሁለት አገላለጾች አንድ ዓይነት ትርጉም የሚሰጡ ናቸው። ጳውሎስ እነዚህን ተጠቅሞ እውነት እንደሚናገር በአጽንኦት ለማስገንዘብ ነው።

ሕልናዬም ይህንን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ይመሰክርልኛል።
"መንፈስ ቅዱስ ሕልናዬን ይቆጣጠራል፤ እኔ የሚለውንም ነገር ያረጋግጣል"

በጣም አሳዛኝና የማያቋርጥ ሕመም በውስጤ አለ።
እዚህ ላይ “የማያቋርጥ ሕመም በውስጤ” የሚለው አነጋገር ጳውሎስ የራሱን የጭንቀት ስሜት ለመግለጽ የተጠቀመበት ነው። በሌላ አባባል፥ “እኔ ከፍተኛና ጥልቅ የሐዘን ስሜት እንዳለኝ እነግራችኋለሁ”

በጣም አሳዛኝና የማያቋርጥ ሕመም
እነዚህ ሁለቱ አገላለፆች ከመሠረታቸው አንድ ዓይነት ትርጉም አላቸው። ጳውሎስ የተጠቀመባቸው ስሜቱ ከፍተኛ መሆኑን በደንብ ለመግለጽ ነው።

Romans 9:3

እኔ በዘር ከእኔ ጋር አንድ ለሆኑት ወንድሞቼ ስል የተረገምኩ ሆኜ ከክርስቶስ መለየት ብችል እወድ ነበር።
በሌላ አባባል፥ “እኔ በግሌ ይህን ማድረጌ ከእኔ ቡድን የሆነውን ሕዝብ እስራኤላውያን ወገኖቼን በክርስቶስ ለማመን የሚረዳቸው ቢሆን ኖሮ በእግዚአብሔር ተረግሜ ከክርስቶስ ለዘላለም ለመለየት ፍቃደኛ ነበርኩ።

ወንድሞቼ
እንዲህ ማለት ክርስቲያን ወገኖች ለማለት ነው፤ይህም ወንዶችንም ሴቶችንም ይጨምራል።

እስራኤላውያን ናቸው
እነርሱ እንደ እኔ እስራኤላውያን ናቸው። እነርሱ የያዕቆብ ዘር እንዲሆኑ እግዚአብሔር መርጦአቸዋል።

እንደ ልጆቹ ተቆጥረዋል
እዚህ ላይ ጳውሎስ “እንደ ልጆቹ” የሚለውን ዘይበኤአዊ አነጋገር የተጠቀመው እስራኤላውያን እንደ እግዚአብሔር ልጆች ይታያሉ የሚለውን ለማመልከት ነው። በሌላ አባባል “ለእነርሱ እግዚአብሔር አባታቸው ነው”

ክርስቶስ የመጣበት የዘር ግንድ ውስጥ የቀድሙ ዘመዶች አሉ
እዚህ ላይ “ክርስቶስ የመጣበት የዘር ግንድ” ሲባል ክርስቶስ ሰብአዊ የደም ዝምድናን በተመለከተ ከእስራኤላውያን ዘር ነው።በሌላ አባባል፥ “ክርስቶስ ሰብአዊ የዘር ግንዱን በተመለከተ የመጣው ከእነርሱ ዘር ነው”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Romans 9:6

አያያዥ ዐረፍተ ነገር፥
ጳውሎስ በቤተ እስራኤል ውስጥ የተወለዱ ሰዎች ብቻ ከእምነት አንፃር እውነተኛ የእስራኤል ወገን ሊሆኑ ይችላሉ የሚለውን ሐሳብ ጠንከር አድርጎ ለማስረዳት ነው።

ነገር ግን የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ሳይከናወን እንደ ቀረ ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም
“ነገር ግን እግዚአብሔር የሰጠውን የተስፋ ቃል መጠበቅ አላቃተውም” ወይም “እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን ጠብቆአል”

በእስራኤል ውስጥ ያሉ ሰዎች ሁሉ እውነተኛ የእስራኤል ወገን አይደሉምና።
እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን የሰጠው ከእስራኤል (ወይም ያዕቆብ) የዘር ግንድ ለተወለዱ ሁሉ አይደለም ነገር ግን በመንፈስ ከያዕቆብ ለተወለዱት ነው ማለትም በኢያሱስ የታመኑት ናቸው።

Romans 9:8

ሰብአዊ ልጆቹ ግን አይደሉም
እዚህ ላይ “ሰብአዊ ልጆች” የሚለው ዘይበአዊ አነጋገር በሥጋ ከአብርሃም የተወለዱትን ያመለክታል። በሌላ አነጋገር “ከአብርሃም የዘር ግንድ የተወለዱ ሁሉ አይደሉም”

የእግዚአብሔር ልጆች
ይህ መንፈሳዊ ልጆቹ የሆኑ ሰዎችን የሚያመለክት ተለዋጭ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው፥ በኢያሱስ ያመኑትን።

የተስፋ ቃሉ ልጆች
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን የተስፋ ቃል የሚወርሱ ሰዎችን ነው።

ይህ የተነገረው የተስፋ ቃሉ ነው
“እነዚህ እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን ሲናገር የተጠቀመባቸው ቃላት ናቸው”

ለሳራ ወንድ ልጅ ይሰጣል
በሌላ አነጋገር ‘እግዚአብሔር ለሳራ ወንድ ልጅ ይሰጣል’ ማለት ይቻላል። “እኔ ለሳራ ወንድ ልጅ እሰጣለው”

Romans 9:14

ስለዚህ ምን እንበል?
ጳውሎስ ይኸንን በጥያቄ መልክ ሲያቀርብ የአንባቢዎቹን ትኩረት ለማግኘት ነው።

ይህ ፈጽሞ ሊሆን አይገባም
“ይህ ነገር አይቻልም” ወይም “ፈጽሞ አይሆንም” ይህ አገላለጽ ይህ ነገር እንደ ተባለው እንዳይሆን አጥብቆ ይከለክላል። በእናንተ ቋንቋ ሊትጠቀሙበት የሚትችሉት ተመሳሳይ አገላለጽ ይኖር ይሆናል።

ለሙሴ እንዲህ ይለዋል
ጳውሎስ እዚህ ላይ እግዚአብሔር ለሙሴ በአሁኑ ጊዜ እየሆነ እንዳለ ዓይነት አገላለጽ ተጠቅሞ መናገሩን ይገልጻል።

ይህ የሚሆነው ሰው ስለፈለገው ወይም ስለሮጠ አይደለም
“ይህ የሚሆነው ሰው ከሚፈልገው ነገር የተነሣ ወይም ሰው ከሚያደርገው ጥረት የተነሣ አይደለም”

ስለሚሮጠው ሰው ተብሎ አይደለም
ጳውሎስ እዚህ ላይ የእግዚአብሔርን ቸርነት ለማግኘት መልካም ነገር ስለሚያደርግ ሰው ሲናገር ለውድድር የሚሮጥ ሰው ምሳሌን ተጠቅሞ ይገልጸዋል።

Romans 9:17

በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ እንዲህ ይላል
እዚህ ላይ ቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የተነገረውን እግዚአብሔር ለፈረኦን እንደሚናገር ተደርጎ ተቀምጦአል። በሌላ አባባል፥ “ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚናገረው እግዚአብሔር እንዲህ ይላል”

እኔ. . .የኔ
እግዚአብሔር ራሱን ለማመልከት ነው።

አንተ
ነጠላ ቁጥር አመልካች

ጠበቅኩህ
x

Romans 9:19

ከዚያም እንዲህ ትለኛለህ
ጳውሎስ ለትምህርቱ ተቃዋሚዎች ልክ ለአንድ ሰው እንደሚናገር ዓይነት አድርጎ ይናገራቸዋል።ብዙ ቁጥር አመልካችንም ልትጠቀሙ ትችላላችሁ።

እስከዚህ ጊዜም ቢሆን ለምን ወቀሳ ይሰነዝራል? ፍቃዱንስ የተቋቋመ ሰው ማን ነው?
እነዚህ የማሳመኛ ነጥቦች ጳውሎስ ለነገሩ አጽንኦት ለመስጠት የተጠቀመባቸው ናቸው።ሁሉንም ጠበቅ ያሉ ዐረፍተ ነገሮች አድርገን መተርጎም እንችላለን።

እርሱ. . .የርሱ
እነዚህ ቃላት እግዚአብሔርን የሚያመለክቱ ናቸው።

የተሠራ ነገር እንዲህ ብሎ ይናገራል. . .ለዕለታዊ ግልጋሎት?
ጳውሎስ አንድ ሸክላ ሠሪ ከሸክላ የፈለገውን ዕቃ የመሥራት መብት አለው የሚለውን ዘይቤ ተጠቅሞ ፈጣሪ በፍጥረቱ የፈለገውን ነገር ለመሥራት መብት እንዳለው ይገልጻል። ጳውሎስ በጥያቄ መልክ ያቀረበው ነጥቡን ጠንከር አድርጎ ለማስቀመጥ ነው።

ለምን እንደዚህ አድርገህ ሠራኸኝ?
አንተ የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ያመለክታል።በጥያቄ መልክ ሲናገር ደግሞ ለነገሩ አጽንኦት ለመስጠት ነው።ይኸንን እንደ አንድ ጥብቅ ዐረፍተ ነገር መተረጎምም ትችላላችሁ። በሌላ አባባል፥ “እግዚአብሔር ሆይ፥ እንደዚህ አድርገህ ሊታበጀኝ አይገባም ነበር!”

Romans 9:22

እርሱ. . .የርሱ
እነዚህ ቃላት እግዚአብሔርን የሚያመለክቱ ናቸው።

የቁጣ ዕቃዎች. . . የምህረት ዕቃዎች
ጳውሎስ ሰዎችን እንደ ዕቃዎች በመውሰድ ይገልጻቸዋል። በሌላ አባባል፥ ቁጣ የሚገባቸው ሰዎች. . .ምህረት የሚገባቸው ሰዎች

የክብሩ ባለጠግነት
ጳውሎስ የእግዚአብሔርን አስገራሚ ሥራዎች ከትልቅ ባለጠግነት ጋር ያነፃፅራል። በሌላ አባባል፥ “ትልቅ ዋጋ ያለው ክብሩ”

አስቀድሞ ለክብር ያዘጋጃቸውን
እዚህ ላይ “ክብር” የሚያመለክተው በሰማይ ከእግዚአብሔር ጋር የምንኖረው ሕይወት ነው።በሌላ አባባል፥ “ከእርሱ ጋር እንዲኖሩ ቀደም ብሎ ያዘጋጃቸውን”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Romans 9:25

አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ጳውሎስ በዚህ ክፍል የእስራኤል ሕዝብን አለማመን አስቀድሞ በነብዮ ሆሴዕ እንደተነገረ ይገልጻል።

እርሱ በሆሴዕም ላይ እንደተናገረው
እዚህ ላይ “እርሱ” የሚለው እግዚአብሔርን ያመለክታል። በሌላ አባባል፥ “ሆሴዕ በጻፈው መጽሐፍም ላይ እግዚአብሔር እንደተናገረው”

ሆሴዕ
ሆሴዕ ነብይ ነበር።

እኔ በዚያን ጊዜ ሕዝቤ ያልሆነውን ሕዝቤ ብዬ እጠራዋለው
እኔ በዚያን ጊዜ የእኔ ያልነበረውን ሕዝብ ሕዝቤ እንዲሆን እመርጠዋለሁ

የተወደደ ያልነበረውን የእሷን ውድ
እዚህ ላይ “እሷ” የሚለው የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ የሚትወክለውን ጎመር የሚትባለውን የሆሴዕ ሚስት ነው። በሌላ አባባል፥ “በእኔ የማትወደድ የነበረችውን በእኔ የሚትወደድ እንዲትሆን እመርጣለሁ”
የሕያው እግዚአብሔር ልጆች

የሕያው እግዚአብሔር ልጆች
“ሕያው” የሚለው ቃል እግዚአብሔር ብቸኛው እውነተኛ አምላክ መሆኑን እንደ ሐሰተኛ ጣኦቶችም አለመሆኑን ያመለክታል።

Romans 9:27

ይጮሃል
“ይጣራል”

እንደ ባሕር አሸዋ
እዚህ ላይ ጳውሎስ የእስራኤል ሕዝብ ብዛትን ከባሕር አሸዋ ደቃቆች ብዛት ጋር ያነፃፅራል። በሌላ አባባል፣ “ከብዛቱ የተነሣ ለመቁጠር የሚከብድ”

ይድናሉ
ጳውሎስ “ይድናሉ” የሚለውን ቃል በመንፈሳዊ ትርጉሙ ይጠቀምበታል። እግዚአብሔር አንድን ሰው ካዳነ በኢያሱስ መስቀልና ሞት ባለው እምነት አማካይነት እግዚአብሔር ምህረት አድርጎለት በኃጢአቱ ምክንያት ከሚመጣበት ቅጣት ነፃ አደረገው።

ጌታ በምድር ፍርዱን ይፈጽማል
እዚህ ላይ “ፍርድ” የሚለው ቃል ሰዎች ለመቅጣት የወሰነውን ውሳኔ ያመለክታል። በሌላ አባባል፣ “ጌታ በምድር ያለውን ሕዝብ በውሳኔው መሠረት ይቀጣዋል”

እኛ
ይህ የሚያመለክተው ኢሳያስንና እርሱ ቃል የተናገራቸውን ሰዎች ነው።

እኛ እንደ ሰዶም እንሆናለን፤ እንደ ገሞራም ልንሆን እንችል ነበር
x

Romans 9:30

ስለዚህ ምን እንበል?
ጳውሎስ ይህን ጥያቄ የተጠቀመው የአንባቢዎቹን ትኩረት ለማግኘት ሲል ነው። በሌላ አባባል፥ “ስለዚህ እንዲህ ማለት አለብን”

እንግዲህ አይሁድ ያልሆኑ ሕዝቦች
“እንዲህ እንላለን፣ አይሁድ ያልሆኑ ሕዝቦች”

በእግዚአብሔር ሐሳብ ያልሄዱ
“እግዚአብሔርን ለማስደሰት ጥረት ያላደረጉ”

በእምነት የእግዚአብሔርን ሐሳብ መከተል
እዚህ ላይ “በእምነት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በክርስቶስ መታመን ነው። ይህንን በትርጉማችን ገልጦ ማሳየትይቻላል፥ “እነርሱ በክርስቶስ በታመኑ ጊዜ እግዚአብሔር በፊቱ ትክክለኞች አድርጎ ተቀበላቸው”

ሊደርሱበት አልቻሉም
ይህ ማለት እስራኤላውያን ሕግን ለመጠበቅ በመሞከር እግዚአብሔርን ሊያስደስቱ አልቻሉም። ይኸንን በትርጉማችን ገልጦ ማሳየትይቻላል፥ “ሕግን በመጠበቅ እግዚአብሔርን ማስደሰት አልቻሉም ምክንያቱም ሕግን መጠበቅ አልቻሉም”

Romans 9:32

ለምን አልሆነም?
ይህ በአጭሩ የተቀመጠ አባባል ነው። ለማለት የተፈለጉትን ቃላት ጨምረን መግለጽ እንችላለን። ጳውሎስ ይህን ጥያቄ የጠየቀው የአንባቢዎቹን ትኩረት ለማግኘት ነው። በሌላ አባባል ስናስቀምጠው፥ “እነርሱ በእግዝአብሔር ሐሳብ መሄድ ያልቻሉት ለምንድነው?”

በሥራ
ይህ የሚያመለክተው ሰዎች እግዚአብሔርን ለማስደሰት ሲሞክሩ የሚያደርጉትን ነገር ነው። ይህንን ሐሳብ በትርጉማችን ገልጦ ማሳየት ይቻላል፥ “እግዚአብሔርን የሚያስደስት ነገር ለመሥራት ጥረት ማድረግ” ወይም “ሕጉን በመጠበቅ”

እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል
ኢሳይያስ እንዲህ ብሎ ጽፎአል ማለት ይቻላል። በሌላ አባባል፣ “ነብዩ ኢሳይያስ እንደ ጻፈው”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **10**

1 ወንድሞች ሆይ፥ እኔ ስለእነርሱ ለእግዚአብሔር የማቀርበው ልመና እንዲድኑ ነው። **2** በእውቀት የሆነ ባይሆንም ለእግዚአብሔር እንደሚቀኑ እኔ ራሴ ስለእነርሱ እመሰክራለሁ። **3** የእግዚአብሔርን ጽድቅ አያውቁምና የራሳቸውን ጽድቅ ሊመሰርቱ ይጥራሉ፤ለእግዚአብሔርም ጽድቅ ራሳቸውን አያስገዙም። **4** ምክንያቱም ክርስቶስ ለሚያምን ሁሉ ለጽድቅ የሚሆን የህግ ፍጻሜ ነው። **5** ሙሴ ከህግ ስለሚመጣ ጽድቅ ሲናገር «ከህጉ የሆነውን ጽድቅ የሚያደርግ በዚያው ጽድቅ ይኖራል።» ይላልና። **6** በእምነት ስለሚሆን ጽድቅ ግን «በልብህ ማን ወደ ሰማይ ይወጣል አትበል (ይህ ክርስቶስን ማውረድ ነውና) **7** ወይም ወደ ሲዖል ማን ይወርዳል አትበል (ይህ ክርስቶስን ከሙታን መካከል ማውጣት ነውና)።» ይላል። **8** ነገር ግን ቃሉ ምን ይላል? «ቃሉ ለአፍህና ለልብህ ቅርብ ነው።» ይላል። የምንሰብከው የእምነት ቃል ይህ ነው። **9** ስለዚህም ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሳው በልብህ ብታምን ትድናለህ። **10** ምክንያቱም ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃል በአፉ መስክሮ ደግሞ ይድናል። **11** ምክንያቱም መጽሀፍ እንደሚል «በእርሱ የሚያምን አያፍርም» ። **12** በዚህ ጉዳይ በአይሁድና በግሪክ ልዩነት የለም። ያው አንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና ለሚጠሩትም ሁሉ ባለጠጋ ነው። **13** የጌታን ስም የሚጠራም ሁሉ ይድናል። **14** ታዲያ ያላመኑበትን እንዴት ይጠሩታል? ስለእርሱ ሳይሰሙስ እንዴት ያምኑበታል? **15** ያለ ሰባኪስ ከየት ይሰማሉ? «በመልካም ነገር የተሞላ ደስታን የሚሰብኩ እግሮች እንዴት ያማሩ ናቸው» ተብሎ እንድተጻፈ፣ ሳይላኩስ እንዴት ይሰብካሉ? **16** ነገር ግን ኢሳያስ «ጌታ ሆይ መልዕክታችንን ማን አምኗል» እንዳለው ሁሉም ወንጌልን አልተቀበሉም። **17** ስለዚህ እምነት የሚመጣው ከመስማት ሲሆን መሰማት ያለበትም የክርስቶስ ቃል ነው። **18** ነገር ግን «አልሰሙ ይሆንን?» እላለሁ። በሙሉ እርግጠኝነት ሰምተዋል።«ድምጻቸው በምድር ሁሉ ላይ ቃላቸውም እስከ ዓለም ዳርቻ ደርሷል።» **19** በተጨማሪም «እስራኤል አያውቁምን?» እላለሁ። ሙሴ አስቀድሞ «ህዝብ ባልሆነ በእሱ በቅናት አነሳሳችኋለሁ። በማያስተውልም ህዝብ በቁጣ አናውጣችኋለሁ» ይላል። **20** ደግሞም ኢሳያስ በድፍረት «ላልፈለጉኝ ተገኘሁ ላልጠየቁኝም ተገለጥኩ» ይላል። **21** ስለእስራኤል ግን «ለዚህ የማይታዘዝና ደንዳና ህዝብ ቀኑን ሙሉ እጄን ዘረጋሁ» ይላል።

Romans 10:1

አያያዥ ዐረፍተ ነገር፥
ጳውሎስ እስራኤል በክርስቶስ እንዲያምን ምኞቱን እየገለጸ ግን ደግሞ አይሁድም ሆነ ሌሎች ሕዝቦች ሁሉም ሊድኑ የሚችሉት በኢየሱስ ባላቸው እምነት ብቻ መሆኑን አጥብቆ ያስገነዝባል።

ወንድሞች
እዚህ ላይ እንዲህ ማለት ወንዶችንም ሴቶችንም ጨምሮ ክርስቲያን ወገኞች ለማለት ነው።

የልቤ ምኞት
እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል የሰውን ውስጣዊ ስሜት ለማለት ነው። በሌላ አባባል፣ “ከሁሉም የሚበልጥ ፍላጎቴ”

ለእነርሱ ነው፤ ለድነታቸው
“እግዚአብሔር አይሁዶችን ያድናቸዋል”

እኔ ስለ እነርሱ እመሰክራለሁ
“እኔ ስለ እነርሱ እውነቱን እናገራለሁ”

እነርሱ የእግዚአብሔርን መመዘኛ ሐሳብ አላወቁም
እዚህ ላይ “የእግዚአብሔር መመዘኛ ሐሳብ” የሚለው እግዚአብሔር ሰዎችን በፊቱ ሐሳቡን የሚያሟሉ የሚያደርግበት መንገድን ያመለክታል።

Romans 10:4

ክርስቶስ የእግዚአብሔር ሕግ ሙላት ነው
“ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ሕግ ሙሉ በሙሉ ፈጽሞአል።

የእግዚአብሔርን ሐሳብ የፈጸመ ለመሆን ላመነ ሁሉ
እዚህ ላይ “የሚያምን” ማለት “የተማመነ” ማለት ነው። በሌላ አባባል፥ “በሱ የተማመኑትን በፊቱ ሐሳቡን የፈጸሙ አድርጎ እንዲቀበላቸው”

ሕግን በመፈጸም የእግዚአብሔር ሐሳብ የፈጸመ ሆኖ መገኘት
ጳውሎስ “የእግዚአብሔርን ሐሳብ መፈጸም” የሚለውን ሕይወት እንዳለውና እንደሚንቀሳቀስ አድርጎ ይናገራል። በሌላ አባባል፥ “ሕግ አንድን ሰው ከእግዚአብሔር ሐሳብ አንጻር እንዴት የተስተካከለ እንደሚያደርግ”

ሕግን በመፈጸም የእግዚአብሔርን ሐሳብ የሚፈጽም ሰው በዚሁ ይኖራል
ሕግን በመፈጸም በእግዚአብሔር ፊት የእግዚአብሔርን ሐሳብ የፈጸመ ለመሆን ሕጉን ሙሉ በሙሉ መፈጸም አለበት፤ ይህ ደግሞ የሚቻል አይደለም። በሌላ አባባል፥ “ሕጉን ሙሉ በሙሉ የሚፈጽም ሰው በሕይወት ይኖራል ምክንያቱም ሕጉ የእግዚአብሔርን ሐሳብ የፈጸመ ያደርገዋል”

በሕይወት ይኖራል
ይህ አባባል የሚያመለክተው 1) ዘላለማዊ ሕይወት 2) ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ያለው የሚሞት ሕይወት

Romans 10:6

ነገር ግን ከእምነት የሚመጣው የእግዚአብሔርን ሐሳብ መፈጸም እንዲህ ይላል
እዚህ ላይ “የእግዚአብሔርን ሐሳብ መፈጸም” የሚለው አባባል መናገር እንደሚችል ሰው ተደርጎ የቀረበ ነው።በሌላ አባባል፥ “ነገር ግን ሙሴ እምነት እንዴት አንድን ሰው በእግዚአብሔር ፊት ሐሳቡን የፈጸመ እንደሚያደርገው ሲጽፍ እንዲህ ብሏል።

በልባችሁ እንዲህ አትበሉ
ሙሴ ለሕዝቡ ሲናገር ለአንድ ሰው እንደሚናገር አድርጎ ያቀርበዋል።እዚህ ላይ “ልብ” የአንድን ሰው አእምሮ ወይም ውስጣዊ ስሜት የሚተካ ነው። በሌላ አባባል፥ “ራሳችሁን እንዲህ አትበሉ”

ወደ ሰማይ የሚወጣ ማነው?
ሙሴ የሚናገራቸውን ሰዎች ለማስተማር በጥያቄ መልክ አቀረበ። ያለፈው ትምህርቱ ላይ “አትበሉ” ሲል ለዚህኛው ጥያቄ አሉታዊ መልስ እንደሚያስፈልገው ያሳያል። ይህን ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ማስቀመጥ ይቻላል፥ “ወደ ሰማይ ሊወጣ የቻለ ማንም የለም”

ይህም ማለት ክርስቶስን ለማውረድ
“ክርስቶስ ወደ ምድር እንዲመጣ ለማድረግ”

ወደ ጥልቅም የሚወርድ ማነው?
ሙሴ የሚናገራቸውን ሰዎች ለማስተማር በጥያቄ መልክ አቀረበ።ያለፈው ትምህርቱ ላይ “አትበሉ” ሲል ለዚህኛው ጥያቄ አሉታዊ መልስ እንደሚያስፈልገው ያሳያል። ይህን ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ማስቀመጥ ይቻላል፥ “ወደ ጥልቁ በመውረድ የሞቱ ሰዎች መናፍስት ያሉበት ቦታ ሊገባ የቻለ ማንም የለም”

ከሙታን
ከሞቱት ሰዎች ሁሉ መካከል ማለት ነው።ይህ አባባል በታችኛው ዓለም የሚገኙትን የሞቱ ሰዎች በአንድ ላይ የሚገልጽ ነው።

ሙት
ይህ ቃል ስለ አካላዊ ሞት ይናገራል።

Romans 10:11

ቅዱሳት መጻሕፍት ላይ እንደተጻፈው
ጳውሎስ ቅዱሳት መጻሕፍትን ሕይወትና ድምፅ እንዳለው አድርጎ ይናገራል። እዚህ ላይ ጳውሎስ የተጠቀመውን የቅዱሳት መጻሕፍት ቃል ጸሐፊውን በግልጽ መጥቀስ ትችላላችሁ። በሌላ አነጋገር፥ “ኢሳያስ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደጻፈው”

በእርሱ የሚያምን ሁሉ አያፍርም
ይህ “የማያምን ሁሉ ያፍራል” ከማለት ጋር ተመጣጣኝ ትርጉም አለው። እዚህ ላይ በአሉታዊ መልኩ የተቀመጠው ለነገሩ አጽንኦት ለመስጠት ነው። በሌላ አባባል፥ “እግዚአብሔር በእርሱ የሚያምኑትን ሁሉ ያከብራል”

በአይሁድና እና በግሪክ መካከል ልዮነት የለም
የጳውሎስ ሐሳብ እግዚአብሔር ለሁሉም ሕዝቦች እኩል ያስብላቸዋል።ይህንን ሐሳብ በትርጉማችን ገልጠን ማሳየት እንችላለን። በሌላ አባባል፥ “በዚህ መልኩ እግዚአብሔር ለአይሁድም አይሁድ ላልሆኑትም እኩል ያስብላቸዋል”

ስሙን ለሚጠሩት ሁሉ እርሱ ሁሉን ነገር አለው
እዚህ ላይ “ሁሉን ነገር አለው” ተብሎ የተተረጎመው አባባል እግዚአብሔር በብዙ በረከት ይባርካል ለማለት ነው።ይህን ሐሳብ በትርጉማችን ገልጠን ማሳየት እንችላለን። በሌላ አባባል፥ “እርሱ በእርሱ የሚተማመኑትን በብዙ በረከት ይባርካቸዋል”

የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል
እዚህ ላይ “ስም” የሚለው ቃል ኢየሱስን የሚተካ ነው። በሌላ አባባል፥ “ጌታ በእርሱ የሚተማመኑትን ሁሉ ያድናል”

Romans 10:14

ታዲያ እነርሱ ያላመኑበትን እርሱን እንዴት ሊጠሩት ይችላሉ?
ጳውሎስ ይኸንን ጥያቄ የተጠቀመው የክርስቶስን የምሥራች ቃል ወዳልሰሙት ሰዎች የማድረስን አስፈላጊነት አጥብቆ ለማስገንዘብ ነው። “እነርሱ” የሚለው ቃል ገና የእግዚአብሔር ሕዝብ ያልሆኑትን ያመለክታል።በሌላ አባባል፥ “በእግዚአብሔር የማያምኑት የእርሱን ስም ሊጠሩ አይችሉም”

ስለ እርሱ ባልሰሙት በእርሱ እንዴት ሊያምኑ ይችላሉ?
ጳውሎስ ለተመሳሳይ ምክንያት ሌላ ጥያቄ ይጠቀማል። በሌላ አባባል፥ “የእርሱን መልዕክት ያልሰሙ ከሆነ በእርሱ ሊያምኑ አይችሉም”

ማመን
ይህ ማለት ያ ሰው ያለው እውነት መሆኑን መመስከር ማለት ነው።

የሚሰብክ ሳይኖር እንዴት ሊሰሙ ይችላሉ?
ጳውሎስ ለተመሳሳይ ምክንያት ሌላ ጥያቄ ይጠቀማል።በሌላ አባባል፥ “ሰው ካልነገራቸው የእርሱን መልዕክት ሊሰሙ አይችሉም”

ታዲያ ካልተላኩ እንዴት ልሰብኩ ይችላሉ?
ጳውሎስ ለተመሳሳይ ምክንያት ሌላ ጥያቄ ይጠቀማል። “እነርሱ” የሚለው ቃል የእግዚአብሔር የሆኑትን ያመለክታል። በሌላ አባባል፥ “የሆነ ሰው ካልላካቸው መልዕክቱን ለሌሎች መንገር አይችሉም”

አስደሳች የሆነውን መልካም ዜና ከቦታ ቦታ ሄደው የሚያበሥሩ እግሮች በጣም ያማሩ ናቸው።
ጳውሎስ “እግር” የሚለውን አባባል የተጠቀመው መልዕክቱ ወዳልደረሳቸው ለማድረስ የሚጓዙትን ሰዎች ለማመልከት ነው። በሌላ አባባል።
“መልዕክተኞች መጥተው የምሥራቹን ዜና ሲነግሩን በጣም አስገራሚ ነው”

Romans 10:16

ነገር ግን ሁላቸውም አላዳምጡም።
እዚህ ላይ “እነርሱ” የሚለው ሐሳብ አይሁዶችን ያመለክታል። “ነገ ግን ያዳመጡት ሁሉም አይሁዶች አይደሉም”

ጌታ ሆይ የተናገርነውን መልዕክት ማን አመነ?
ጳውሎስ ይህንን በጥያቄ መልክ ያቀረበው በቅዱሳት መጻሕፍት ኢሳያስ ስለ አይሁዶች በኢየሱስ አለማመን የተነበየውን አጽንኦት ሰጥቶ ለማስገንዘብ ነው።

መልእክታችን
እዚህ ላይ “እኛ” የሚያመለክተው እግዚአብሔር እና ኢሳይያስን ነው።

እምነት ከመስማት ይመጣል፤
እዚህ ላይ “እምነት” የሚያመለክተው “በክርስቶስ ማመንን ነው።

መስማት የክርስቶስን ቃል ነው።
መስማት ስለ ክርስቶስ የሚነገረውን መልዕክት በማዳመጥ ነው።

Romans 10:18

ነገር ግን እኔ እላለው፥ “እነርሱ ሰምተው የለም ወይ?” አዎ፤ በእርግጥ ሰምተዋል።
ጳውሎስ በጥያቄ መልክ ያቀረበው ለነገሩ አጽንኦት በመስጠት ነው።ጥያቄውን ወደ ዐረፍተ ነገር መልሳችሁ መተርጎም ትችላላችሁ። በሌላ አባባል፥ “ነገር ግን እኔ እላለሁኝ፥ አይሁዶች በእርግጥ ስለ ክርስቶስ የሚነገረውን መልዕክት ሰምተዋል።

ድምጻቸው በምድር ሁሉ ቃላቸውም በምድር ዳርቻ ሁሉ ተሰራጨ
ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች መሠረታዊ ትርጉማቸው አንድ ነው፤ ጳውሎስ ሁለቱን የተጠቀመው ነገሩን አጥብቆ ለመንገር ነው። “እነርሱ” የሚለው ሐሳብ የሚያመለክተው ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ እና ኮከቦችን ነው።እዚህ ላይ እነዚህ ስለ እግዚአብሔር ለሕዝቦች እንደሚናገሩ መልዕክተኞች ሰዎች ተደርገው ተገልጸዋል።ይህም የሚያመለክተው የነዚህ መኖር ራሱ ምን ያህል የእግዚአብሔርን ኃይልና ክብር የሚያሳይ እንደሆነ ነው።እዚህ ላይ ጳውሎስ ከቅዱሳት መጻሕፍት እየጠቀሰ መሆኑን ገልጣችሁ ማሳየት ትችላላችሁ። በሌላ አባባል፥ “ቅዱሳት መጻሕፍት ላይ እንደተጻፈው ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ እና ኮከቦች የእግዚአብሔር ኃይልና ክብር ማረጋገጫ ናቸው፤በዓለም ላይ ያሉት ሰዎች ሁሉ እነርሱን አይተው ስለ እግዚአብሔር እውነቱን ያውቃሉ”

Romans 10:19

በተጨማሪም እላለሁ “እስራኤል አላወቀም ወይ?”
ጳውሎስ በጥያቄ መልክ ያቀረበው ለነገሩ አጽንኦት ለመስጠት ነው። “እስራኤል” የሚለው ቃል በእስራል አገር የኖሩ ሕዝቦችን ለማመልከት ነው። በሌላ አባባል። “አሁንም እነግራቸዋለሁ፥ የእስራኤል ሕዝብ መልዕክቱን አውቀዋል”

ሙሴ አስቀድሞ እንዲህ አለ፥ “አስቆጣችኋለሁ. .እንዲትበሳጩም አደርጋለሁ”
ይህ ማለት ሙሴ እግዚአብሔር ያለውን ነው የተናገረው። “እኔ” የሚለው የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው፤ “እናንተ” የሚለው ሐሳብ ደግሞ እስራኤላውያንን ነው። በሌላ አባባል፥ “ሙሴ አስቀድሞ እንዲህ አለ፥ “እግዚአብሔር ያስቆጣችኋል. . .እግዚአብሔር እንዲትበሳጩ ያደርጋል”

ሕዝብ ባልሆነው
“እናንተ እንደ ሕዝብ በማትቆጥሯቸው” ወይም “ከየትኛውም ሕዝብ በማይመደቡ ሰዎች”

ማስተዋል በሌለው ሕዝብ
እዚህ ላይ “ማስተዋል የሌለው” ማለት እግዚአብሔርን የማያውቅ ሕዝብ ማለት ነው። በሌላ አባባል፥ “እኔን ወይም ትዕዛዞቼን የማያውቁ ሰዎች በሚኖሩበት ሕዝብ”

ንዴታችሁን እቀሳቅስባችኋለሁ
“እንድትበሳጩ አደርጋለሁ” ወይም “እንዲትበሳጩ የሚያደርግ ነገር አደርጋለሁ”

እናንተ
ይህ የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል።

Romans 10:20

አጠቃላይ መረጃ፥
እዚህ ላይ “እኔ” እና “የእኔ” የሚሉ ቃላት የሚያመለክቱት እግዚአብሔርን ነው።

ከዚያም ኢሳይያስ በድፍረት እንዲህ ብሎ ተናገረ
ይህ ማለት ነብዩ ኢሳይያስ የጻፈው እግዚአብሔር የተናገረውን ነው።

ለማይፈልገኝ ሕዝብ ተገኘሁ
ነቢያት ብዙውን ጊዜ ለወደ ፊት ሊከሰቱ ያሉትን ነገሮች እንደተፈጸመ አድርገው ይናገራሉ። ይህ አጥብቆ የሚያስረዳው ትንቢቱ በእርግጠኝነት እንደሚፈጸም ነው። በሌላ አባባል፥ “የእግዚአብሔር ያልሆኑ ሕዝቦች ምንም እንኳ ባይፈልጉኝ ያገኙኛል”

ተገለጥኩ
“ራሴን አሳወቅኩ”

እርሱ እንዲህ ይላል
“እርሱ” የሚለው የሚያመለክተው በኢሳይያስ በኩል የተናገረውን እግዚአብሔርን ነው።

ቀኑን ሙሉ
ይህ ሐረግ አጥብቆ የሚገልጸው የእግዚአብሔርን ተከታታይ ጥረት ነው። “በተከታታይ”

እጆቼን ለማይታዘዝና ለልበ ደንዳና ሕዝብ ዘረጋው
“እናንተን ለመቀበልና ለመርዳት ሞከርኩ ነገር ግን እርዳታዬን እምቢ ብላችሁ በአለመታዘዝ ሕይወት ቀጠላችሁ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **11**

1 ታዲያ እግዚአብሄር ህዝቡን ጣላቸውን? ፥በጭራሽ። ምክንያቱም እኔ ራሴ ከቢንያም ወገን የሆንኩ የአብርሀም ዘር እስራኤላዊ ነኝ። **2** እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን ህዝቡን አልጣላቸውም። ኤልያስ እስራኤልን በመቃወም ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት እንደተከራከረ መጽሀፍ የሚለውን አታውቁምን? **3** «ጌታ ሆይ ነቢያትህን ገድለዋል፣ መሰዊያዎችህንም አፍርሰዋል፣ እኔም ብቻዬን ቀርቻለሁ ሊገድሉኝም እየፈለጉኝ ነው።» **4** ነገር ግን እግዚአብሔር ምን ብሎ መለሰለት? «ለበዓል ያልሰገዱ ሰባት ሺ ሰዎችን ለራሴ ጠብቄ አቆይቻለሁ።» **5** በዚህም በአሁኑ ዘመንም ከጸጋ ምርጫ የተነሳ ትሩፋን አሉ። **6** ነገር ግን በጸጋ ከሆነ ከእንግዲህ በሥራ አይደለም።አለዚያ ጸጋ ከእንግዲህ ጸጋ መሆኑ ቀርቷል። **7** እንግዲህ ምን ይሁን፣ እስራኤል ይፈልገው የነበረውን ነገር አላገኘም ፥ የተመረጡት ግን አግኝተውታል፥ የቀሩት ግን ደንዳኖች ሆነዋል። **8** ይህም ልክ «እያዩ እንዳያዩ እየሰሙ እንዳይሰሙ እስከ አሁን እግዚአብሔር ያለማስተዋልን መንፈስ ሰጣቸው» ተብሎ እንደተጻፈው ነው። **9** ዳዊትም «ገበታቸው መረብ፥ወጥመድ፥የእንቅፋት ድንጋይና የበቀል ይሁንባቸው» ይላል። **10** እንዳያዩ አይናቸው ይጨልም፥ ሁልጊዜ ጀርባቸው እንደጎበጠ ይቅር።» ይላል። **11** «እስኪወድቁ ድረስ ተሰናከሉ» እላለሁን? ፈጽሞ አይሁን። በቅናት ሊያነሳሳቸው በእነርሱ ውድቀት ለአህዛብ ድነት ሆነ። **12** እንግዲህ ውድቀታቸው ለዓለም ሙላት ከሆነ ጉድለታችው ለአህዛብም ሙላት ከሆነ ሙላታቸው እንዴት ታላቅ ይሆን? **13** አሁን ለእናንተ ለአህዛብ እናገራለሁ። የአህዛብ ሀዋሪያ እንደመሆኔ በአገልግሎቴ እመካለሁ። **14** ምናልባት የገዛ ሥጋዬ የሆኑትን አስቀናና አንዳንዶቹን እናድን ይሆናል። **15** የእነሂያ መጣል ለዓለም የመታረቅ ምክንያት ከሆነ ተቀባይነት ማግኘታቸው ከሞት ወደ ህይወት ማምለጥ ካልሆን ምን ሊሆን ይችላል? **16** በኩሩ ቅዱስ ከሆነ ሊጡም ቅዱስ ነው። ሥሩ ቅዱስ ከሆነ ቅርንጫፉ ቅዱስ ነው። **17** ነገር ግን አንዳንዶቹ ቅርንጫፎች በመሰበራቸው ምክንያት አንተ የበረሀ ወይራ ዛፍ ቅርንጫፍ ባልወደቁት ቅርንጫፎች መካከል ብትጣበቅና የወይራ ዛፉን ሥር ብልጽግና ተካፋይ ብትሆን **18** በቅርንጫፎቹ ላይ አትኩራራ። ብትኩራራ ግን ሥሩ አንተን ተሸከምህ እንጂ አንተ ሥሩን አልተሸከመከውም። **19** «ቅርንጫፎቹ ስለተሰበሩ እኔ ተተካሁ» ትላለህ። **20** እውነት ነው ባለማመናቸው ምክንያት እነርሱ ተቆርጠው ወድቀዋል አንተ ደግሞ በእምነት ቆመሀል። ፍራ እንጂ ራስህ ከፍ አድርገህ አታስብ። **21** እግዚአብሔር ለመጀመሪያዎቹ ቅርንጫፎች ካልራራ ለአንተም አይራራልህም። **22** እንግዲህ የእግዚአብሔርን የምህረት ሥራና ጭካኔ አስተውል። በአንድ በኩል ጭካኔው በወደቁት በአይሁድ ላይ መጣ፥በሌላ በኩል ደግሞ ጸንታችሁ ከቆያችሁ ምህረቱ ወደ እናንተ መጥቷል። አለበለዚያ ግን እናንተም ተቆርጣችሁ ትጣላላችሁ። **23** ደግሞም እነርሱ ባለማመናቸው ካልጸኑ እንደገና በዛፉ ላይ ሊተከሉ ይችላሉ። እግዚአብሔር እንደገና በዛፉ ላይ ሊተክላቸው ይችላልና። **24** እናንተ መነሻችሁ የበረሀ የወይራ ዛፍ የሆነና ተቆርጣችሁ የነበራችሁ ቅርንጫፎች ከተፈጥሮ ህግ ውጪ በመልካሙ የወይራ ዛፍ ላይ እንደገና ከተተከላችሁ የመጀመሪያዎቹ ቅርንጫፎች እነኝህ አይሁድ ወደገዛ ዛፋቸው እንዴት እንደግና አይጣበቁም? **25** ወንድሞች ሆይ በራሳችሁ አስተሳሰብ ጥበበኞች የሆናችሁ እንዳይመስላችሁ ስለዚህ ምስጢር እንግዳ እንድትሆኑ አልፈልግም፡ የአህዛብ ሙላት እስኪፈጸም ድረስ ከፊል ድንዛዜ በእስራኤል ላይ ወድቋል። **26** ስለዚህም እስራኤል በሙሉ እንደተጻፈው ይድናሉ። «ከጽዮን ነጻ አውጪ ይነሳል ከያዕቆብም የማይገባ አካሄድን ያስወግዳል። **27** ኃጢአታቸውን በማስወግድላቸው ጊዜ ከእነርሱ ጋር የምገባው ኪዳን ይህ ነው።» **28** በአንድ በኩል ወንጌልን በተመለከተ ስለእናንተ የተጠሉ ናቸው፣ በሌላ በኩል ደግሞ በእግዚአብሔር ምርጫ ምክንያት ስለአባቶቻቸው የተወደዱ ናቸው። **29** ምክንያቱም የእግዚአብሔር ስጦታና ጥሪ አይለወጥም። **30** እናንተ ቀድሞ ለእግዚአብሔር የማትታዘዙ የነበራችሁ አሁን ግን በእነርሱ አለመታዘዝ ምክንያት ምህረትን አግኝታችኋል። **31** ልክ እንደዚያው ዘንድ እነዚህ አይሁድ አሁን የማይታዘዙ ሆነዋል። በውጤቱም ለእናንት በተሰጠው ምህረት እነርሱ ደግሞ እንዲቀበሉ ነበር። **32** ምህረቱን ለሁሉ ያሳይ ዘንድ እግዚአብሔር ሁሉን ባለመታዘዝ ዘግቶታልና። **33** ኦ የእግዚአብሔር ጥበብና እውቀት ባለጠግነት ምን ያህል ጥልቅ ነው! ፍርዱ እንዴት የማይመረመር መንገዱም እንዴት ከመታወቅ ያለፈ ነው! **34** «የጌታን ልብ የሚያውቅ ማነው? አማካሪውስ የሆነ ማነው? **35** ወይስ መልሶ ይከፍለው ዘንድ ለእግዚአብሔር ያበደረ ማነው?» **36** ሁሉም ነገር ከእርሱ በእርሱና ለእርሱ ነው። ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን። አሜን።

Romans 11:1

አያያዥ መግለጫ፡
እስራኤል እንደ ሕዝብ እግዚአብሔርን ቢተዉትም ድነት ያለ ሥራ በጸጋ እንደሆነ ይረዱ ዘንድ እግዚአብሔር ይፈልግባቸዋል።

እንግዲህ እላለሁ
“እንግዲህ እኔ ጳውሎስ እላለሁ”

እግዚአብሔር ሕዝቡን ጥሎአቸዋል?
‘የእይሁድ ሕዝብ ልባቸው በመደንደኑ እግዚአብሔር አህዛብን በሕዝቡ ውስጥ አካተታቸው’ በማለት የሚበሳጩ የሌሎች አይሁዶችን ጥያቄ ለመመለስ እንዲያስችለው ጳውሎስ ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

እንዲህ አይደለም
“ይህ ሊሆን የማይችል ነው!” ወይም “ያለጥርጥር አልጣላቸውም!” ይህ አገላለጽ ሊሆን እንደማይችል አጥብቆ ይቃወማል። በአንተ ቋንቋ እዚህ ጋ መጠቀም የምትችልበት ተመሳሳይ አገላለጽ ይኖርህ ይሆናል። ይህንን በሮሜ 9፡14 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የብንያም ጎሳ
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር በ12 ጎሳ ከከፋፈላቸው ከእስራኤል ሕዝብ አንዱ ከሆነው ከብንያም ጎሳ የተገኙትን ነው።

አስቀድሞ ያወቃቸውን
“ከረጅም ጊዜ በፊት ያወቃቸውን”

ኤልያስ እስራኤልን በእግዚአብሔር ፊት እንዴት እንደከሰሳቸው መጽሐፍ የሚናገረውን አታውቁም?
ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “ኤልያስ እስራኤልን በእግዚአብሔር ፊት በከሰሳቸው ጊዜ ምን ተብሎ በመጽሐፍ እንደ ተጻፈ በእርግጥ ታውቃላችሁ” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

Romans 11:4

ነገር ግን የእግዚአብሔር መልስ ምን አለው?
ጳውሎስ አንባቢን ወደ ቀጣይ ማብራሪያው ለማምጣት ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር የመለሰለት እንዴት ነበር?” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

Romans 11:6

በጸጋ ከሆነ ግን
ጳውሎስ የእግዚአብሔር ምህረት እንዴት እንደሚሠራ ማብራራቱን ይቀጣላል። አ.ት “የእግዚአብሔር ምህረት በጸጋ የሚሠራ ከሆነ ግን”

እንግዲህ ምንድነው?
“ምን ብለን እንደምድምን?” ጳውሎስ አንባቢውን ወደ ቀጣዩ ማብራሪያ ለመውሰድ ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። ይህንን እንደ መግለጫ አድርገህ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “ማስታወስ የሚኖርብን ይህንን ነው” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር ዐይኖቻቸው እንዳያዩ፣ ጆሮዎቻቸው እንዳይሰሙ የድንዛዜን መንፈስ ሰጣቸው
ይህ ሕዝቡ በመንፈስ የመደንዘዙን ሐቅ የሚያሳይ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። መንፈሳዊ እውነትን ለመስማት ወይም ለመቀበል አይችሉም። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የ -- መንፈስ
እዚህ ጋ፣ ይህ ማለት እንደ “የጥበብ መንፈስ” ሁሉ “የአንዳች ዓይነት ጠባይ” ማለት ነው።

ዐይኖቻቸው እንዳያዩ፣
አንድ ሰው በዐይኑ የማየቱ አስተሳሰብ ዕውቀትን ከማግኘት ጋር እኩል እንደሆነ ተቆጥሯል።

ጆሮዎቻቸው እንዳይሰሙ
በጆሮ የመስማት አስተሳሰብ ከመታዘዝ ጋር እኩል እንደሆነ ተቆጥሯል።

Romans 11:9

ማዕዳቸው መረብና ወጥመድ ይሁንባቸው
እዚህ ጋ “ማዕድ” ግብዣን የሚወክል ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን “መረብ” እና “ወጥመድ” ቅጣትን የሚወክሉ ዘይቤአዊ አነጋገሮች ናቸው። ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ሆይ፣ እባክህን ግብዣዎቻቸውን እነርሱን እንደሚይዝ ወጥመድ አድርግ” (ፈሊጣዊ አነጋገር፣ ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እንቅፋት
“እንቅፋት” አንድ ሰው ተደናቅፎ እንዲወድቅ የሚያስደርገው ማንኛውም ነገር ነው። እዚህ ጋ፣ አንድ ሰው ኃጢአትን እንዲያደርግ የሚፈታተነውን አንድ ነገር ይወክላል። አ.ት፡ “ኃጢአት እንዲሠሩ የሚፈታተናቸው ነገር” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ለእነርሱ ቅጣት
“እንድትበቀላቸው የሚያስደርግህ ነገር”

ዘወትር ወገባቸውን አጉብጥ
እዚህ ጋ፣ “ወገባቸውን አጉብጥ” ባሮች በጀርባቸው ከባድ ሸክሞችን እንዲሸከሙ የሚገደዱበት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። እንዲሰቃዩ የማድረግ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ከባድ ሸክም እንደሚሸከሙ ሰዎች አሰቃያቸው” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Romans 11:11

አያያዥ መግለጫ፡
እስራኤል እንደ ሕዝብ እግዚአብሔርን እንደተዉት ተመሳሳይ ስሕተት ከመፈጸም እንዲጠነቀቁ ጳውሎስ አሕዛብን ያሳስባቸዋል።

የተደናቀፉት እስኪወድቁ ድረስ ነው?
ጳውሎስ አጽንዖት ለመጨመር ሲል ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። አ.ት፡ “ኃጢአትን ስለ ሠሩ እግዚአብሔር ለዘላለም ትቷቸዋል? (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

እንዲህ አይደለም
“ይህ ሊሆን አይችልም!” ወይም “ያለጥርጥር አይደለም!” ይህ አገላለጽ ነገሩ እንዲህ እንደማይሆን አጥብቆ ይቃወማል። በአንተ ቋንቋ እዚህ ጋ ልትጠቀምበት የምትችለው ተመሳሳይ አገላለጽ ይኖርህ ይሆናል። ይህንን በሮሜ 9፡14 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ቅናታቸውን ለማነሣሣት
x

Romans 11:13

ቅናታቸውን ለማነሣሣት
ይህንን ሐረግ በሮሜ 10፡19 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

እነዚያን ሥጋዬ የሆኑትን
ይህ የሚያመለክተው “እንደ እኔው አይሁዳዊ የሆኑ” የሚለውን ነው።

ምናልባት ከእነርሱ አንዳንዶቹን እናድን ይሆናል
የሚያምኑትን እነዚያን እግዚአብሔር ያድናቸዋል። አ.ት፡ “ምናልባት አንዳንዶቹ ያምናሉ፣ እግዚአብሔርም ያድናቸዋል”

Romans 11:15

የእነርሱ መተው የዓለም ዕርቅ ከሆነ
“እግዚአብሔር እነርሱን ትቷቸው ከሆነ የቀረውን ዓለም ከራሱ ጋር ያስታርቃል”

የእነርሱ መተው
“የእነርሱ” የሚለው ተውላጸ ስም የማያምኑትን አይሁድ ያመለክታል።

ዓለም
እዚህ ጋ፣ “ዓለም” በዓለም የሚኖሩትን ሰዎች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “በዓለም ያሉ ሰዎች” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ተቀባይነት ማግኘታቸው ከሞት መነሣት ካልሆነ በስተቀር ምን ይሆናል?
እግዚአብሔር አይሁዶችን መቀበሉ አስደናቂ ነገር መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት ጳውሎስ ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። አንተ በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ሲቀበላቸው ምን ይሆን ይሆን? ነገሩ ልክ ከሙታን መካከል የተነሡ ያህል ይሆናል!” ወይም “እግዚአብሔር እነርሱን በሚቀበልበት ጊዜ ከሞቱ በኋላ እንደገና በሕይወት የኖሩ ያህል ይሆናል!” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ሙታን
ይህ ቃል የሚናገረው በመቃብር ስላሉ፣ የሞቱ ሰዎች ሁሉ ነው።

በኩራቱ ከተጠበቀ ቡኮውም እንደዚያው ነው
ጳውሎስ የመጀመሪያው ሰብል ወይም “በኩራት” ሆነው እንደሚታጨዱ የሚናገረው የእስራኤላውያን አባቶች ስለሆኑት ስለ አብርሃም፣ ይስሐቅና ያዕቆብ ነው። ደግሞም ከእነዚያ ሰዎች ስለተወለዱት እስራኤላውያን ሲናገር ከሰብሉ እንደተዘጋጀ “ቡኮ” አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “አብርሃም ለእግዚአብሔር ከቀረበው የመጀመሪያ ሆኖ ከተቆጠረ፣ የተከተሉት አባቶቻችን ሁሉ ደግሞ እንደ እግዚአብሔር ንብረት መቆጠር አለባቸው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Romans 11:17

አንተ የበረሃ ወይራ ቅርንጫፍ
ተውላጸ ስም የሆነው “አንተ” እና “የበረሃ ወይራ ቅርንጫፍ” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው በኢየሱስ ድነትን የተቀበሉትን አሕዛብ ነው።

ከቅርንጫፎቹ አንዳንዶቹ ቢሰበሩ
እዚህ ጋ፣ ጳውሎስ “የተሰበሩ ቅርንጫፎች” በማለት የሚያመለክተው ኢየሱስን የተቃወሙትን አይሁዶች ነው። ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “አንዱ ጥቂት ቅርንጫፎችን ቢሰብራቸው” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በመካከላቸው ብትጣበቅ
እዚህ ጋ ጳውሎስ “እንደተጣበቁ ቅርንጫፎች” አድርጎ የሚናገረው ስለ አሕዛብ ክርስቲያኖች ነው። ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “በቀሩት ቅርንጫፎች መካከል እግዚአብሔር በዛፉ ላይ አጣብቆሃል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የበለጸገው የወይራው ዛፍ ሥር
እዚህ ጋ፣ “የበለጸገው ሥር” የእግዚአብሔርን ተስፋ የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በቅርንጫፎቹ አትመካ
እዚህ ጋ፣ “ቅርንጫፎቹ” የእስራኤልን ሕዝብ የሚወክል ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ከጣላቸው የአይሁድ ሕዝብ አንተ እንደምትሻል አትናገር” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሥሩ አንተን ይሸከምሃል እንጂ አንተ ሥሩን አትሸከመውም
ጳውሎስ አሕዛብ አማኞች ቅርንጫፎች መሆናቸውን እንደገና ያመለክታል። እግዚአብሔር ለአይሁድ በገባው የኪዳን ተስፋ ምክንያት ብቻ ያድናቸዋል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Romans 11:19

ቅርንጫፎች ተሰብረዋል
እዚህ ጋ፣ “ቅርንጫፎች” የሚያመለክተው ኢየሱስን የተቃወሙትንና አሁን እግዚአብሔር የተዋቸውን አይሁዶችን ነው። ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ቅርንጫፎቹን ሰበራቸው” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እኔ ገብቼ እንድጣበቅ
ጳውሎስ ይህንን ሐረግ የሚጠቀመው እግዚአብሔር የተቀበላቸውን አሕዛብ አማኞች ለማመልከት ነው። ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “እኔን አስገብቶ ሊያጣብቀኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የእነርሱ ... እነርሱ
ተውላጸ ስም የሆኑት “የእነርሱ” እና “እነርሱ” የሚያመለክቱት ያላመኑትን አይሁዶች ነው።

ነገር ግን በእምነትህ ምክንያት ጸንተህ ቆመሃል
ጳውሎስ የሚናገረው ማንም ሊያንቀሳቅሳቸው እስከማይቻለው ድረስ በታማኝነት ጸንተው ስለቆሙት አሕዛብ አማኞች ነው። አ.ት፡ “ነገር ግን በእምነታችሁ ምክንያት ቆማችኋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር በተፈጥሮአቸው ቅርንጫፍ ለሆኑት ካልራራላቸው ለአንተም አይራራልህም
እዚህ ጋ፣ “በተፈጥሮአቸው ቅርንጫፍ የሆኑት” የሚያመለክተው ኢየሱስን የተቃወሙትን አይሁዶች ነው። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ከሥር ጀምሮ ላደገው፣ የተፈጥሮ ዛፍ ቅርንጫፍ ለሆነው፣ ላላመኑት አይሁድ ካልራራላቸው፣ እንግዲህ ባታምን ለአንተም እንደማይራራልህ ዕወቅ። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Romans 11:22

የእግዚአብሔርን የደግነት ሥራና ጭካኔውን
ምንም እንኳን እግዚአብሔር በታላቅ ደግነት ቢያደርግላቸውም ሊፈርድባቸውና ለቀጣቸው እንደማያመነታ ጳውሎስ አሕዛብ አማኞችን ያስታውሳቸዋል።

ጭካኔው በወደቁት አይሁድ ላይ መጣ ... የእግዚአብሔር ደግነት በአንተ ላይ ይመጣል
የነገር ስም የሆኑትን “ጭካኔ” እና “ደግነት” ለማስቀረት ይህንን እንደገና መጻፍ ይቻላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር በወደቁት አይሁድ ላይ ክፉን አድርጎባቸዋል ... በአንተ ላይ ግን በደግነት ያደርጋል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

በወደቁት አይሁድ ላይ
የማይገባውን ማድረግ መውደቅ እንደሆነ ተነግሯል። አ.ት፡ “የማይገባውን ያደረጉ አይሁድ” ወይም “በክርስቶስ ለመታመን ፈቃደኛ ያልሆኑት አይሁድ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በደግነቱ ውስጥ ብትቀጥል
የነገር ስም የሆነውን “ደግነት” ለማስቀረት ይህ እንደገና ሊጻፍ ይችላል። አ.ት፡ “ትክክል የሆነውን ማድረግህን ብትቀጥል እርሱም ለአንተ ደግ መሆኑን ይቀጥላል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ካልሆነ አንተም ደግሞ ትቆረጣለህ
እግዚአብሔር ከፈለገ “ሊቆርጠው” ስለሚችለው ቅርንጫፍ ለመናገር ጳውሎስ እንደገና በዘይቤአዊ አነጋገር ይጠቀማል። እዚህ ጋ “መቆረጥ” አንድን ሰው የመጣል ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “ካልሆነ እግዚአብሔር አንተን ይቆርጥሃል” ወይም “ካልሆነ እግዚአብሔር አንተን ይጥልሃል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Romans 11:23

እነርሱ ባለማመናቸው ካልቀጠሉ
“ባለማመናቸው ካልቀጠሉ” የሚለው ሐረግ ድርብ አሉታ ነው። ይህንን በአዎንታ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “አይሁድ በክርስቶስ ማመን ከጀመሩ” (ድርብ አሉታ የሚለውን ተመልከት)

ገብተው ይጣበቃሉ
አይሁድ በኢየሱስ ማመን ከጀመሩ እንደ ቅርንጫፎች ተመልሰው በዛፉ ላይ ሊጣበቁ እንደሚችሉ ጳውሎስ ይናገራል። ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “እግዚአብሔር መልሶ አስገብቶ ያጣብቃቸዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ማጣበቅ
ከአንድ ተክል ላይ ሕያው የሆነውን ቅርንጫፍ በሌላው ተክል ላይ በማስገባት አዲሱ ቅርንጫፍ በዚያ ተክል ላይ ማደጉን እንዲቀጥል ማድረግ የተለመደ ሂደት ነው።

በተፈጥሮህ የበረሃ የወይራ ዛፍ የሆንከው አንተ ተቆርጠህ ተፈጥሮህ ባልሆነው መልካም የወይራ ዛፍ ላይ እንድትጣበቅ ከተደረግህ የተፈጥሮ ቅርንጫፎች የሆኑት እነዚህ አይሁዶች ወደ ራሳቸው የወይራ ዛፍ እንዴት አብልጠው አይጣበቁም?
ጳውሎስ የአሕዛብ አማኞችና አይሁድ የዛፍ ቅርንጫፎች እንደሆኑ አድርጎ መናገሩን ይቀጥላል። ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “እግዚአብሔር በተፈጥሮህ የበረሃ ወይራ ዛፍ የሆንከውን ቆርጦ ለተፈጥሮ ተቃራኒ በሆነው መልካም የወይራ ዛፍ ላይ ካጣበቀህ የተፈጥሮ ቅርንጫፎች የሆኑትን እነዚህን አይሁዶች በገዛ የወይራ ዛፋቸው ላይ እንዴት አብዝቶ አያጣብቃቸውም?” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ቅርንጫፎች
ጳውሎስ፣ አይሁድና አሕዛብ ቅርንጫፎች እንደሆኑ በመቁጠር ይናገራል። “የተፈጥሮ ቅርንጫፎች” የሚወክሉት አይሁዶችን ሲሆን “የተጣበቁት ቅርንጫፎች” የሚወክሉት ደግሞ አሕዛብ አማኞችን ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እነርሱ ... እነርሱን
“እነርሱ” ወይም “እነርሱን” የሚሉት አገባቦች በሙሉ የሚያመለክቱት አይሁዶችን ነው።

Romans 11:25

ሳታውቁ እንድትቀሩ አልፈልግም
እዚህ ጋ ጳውሎስ ድርብ አሉታን ይጠቀማል። ይህንን በአዎንታ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “እንድትገነዘቡ በጣም እፈልጋለሁ” (ድርብ አሉታ የሚለውን ተመልከት)

ወንድሞች
እዚህ ጋ “ወንድሞች” ማለት ወንዶችንና ሴቶችን ጨምሮ እንደ እርሱ ክርስቲያን የሆኑትን ነው።

እኔ
ተውላጸ ስም የሆነው “እኔ” የሚያመለክተው ጳውሎስን ነው።

አንተ ... አንተ ... የአንተ
ተውላጸ ስም የሆኑት “አንተ” እና “የአንተ” የሚያመለክቱት አሕዛብ አማኞችን ነው።

በራሳችሁ አሳብ ጥበበኞች የሆናችሁ እንዳይመስላችሁ
አሕዛብ አማኞች ካላመኑት አይሁዶች ይልቅ ጥበበኞች እንደሆኑ እንዲያስቡ ጳውሎስ አይፈልግም። አ.ት፡ “ከእነርሱ ይልቅ ጥበበኞች እንደሆናችሁ እንዳታስቡ”

በእስራኤል ከፊል ድንዳኔ ሆነባቸው
ጳውሎስ ስለ “ድንዳኔ” ወይም እልኸኝነት በሰውነት ውስጥ እንዳለ ጠጣር ብልት አድርጎ ይናገራል። አንዳንድ አይሁዶች በኢየሱስ አማካይነት ድነትን ለመቀበል እምቢ ብለዋል። አ.ት፡ “ብዙ እስራኤላውያን እልኸኞች ሆነው ቀጥለዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የአሕዛብ ሙሉነት እስኪመጣ ድረስ
“እስኪመጣ ድረስ” የሚለው ቃል እግዚአብሔር አሕዛብን ወደ ቤተክርስቲያን ማምጣቱን ከጨረሰ በኋላ ጥቂት አይሁዶች እንደሚያምኑ ያመለክታል።

Romans 11:26

አያያዥ መግለጫ፡
ጳውሎስ ለእግዚአብሔር ክብር ከእስራኤል ነጻ አውጪ እንደሚመጣ ይናገራል።

እንዲሁም እስራኤል ሁሉ ይድናሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እንዲሁም እግዚአብሔር እስራኤልን ሁሉ ያድናል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ልክ እንደተጻፈው
ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “ልክ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ዘገቡት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ከጽዮን
እዚህ ጋ “ጽዮን” እግዚአብሔር ለሚኖርበት ስፍራ በፈሊጣዊ አነጋገር ጥቅም ላይ ውሏል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር በአይሁዶች መካከል ከሚገኝበት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ነጻ አውጪው
“ሕዝቡን ወደ አስተማማኝ ስፍራ የሚያመጣቸው”

ኃጢአተኝነታቸውን ያስወግዳል
ጳውሎስ ኃጢአተኝነትን አንድ ሰው እንደሚያስወግደው ቁስ፣ ምናልባትም እንደሚገፈፍ ልብስ አድርጎ ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከያዕቆብ
እዚህ ጋ “ያዕቆብ” በፈሊጣዊ አነጋገር እስራኤልን ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል። አ.ት፡ “ከእስራኤል ሕዝብ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ኃጢአታቸውን አስወግድላቸዋለሁ
እዚህ ጋ ጳውሎስ ኃጢአትን አንድ ሰው ሊያስወግደው እንደሚችለው ቁስ አድርጎ ይናገርለታል። አ.ት፡ “የኃጢአታቸውን ሸክም አስወግዳለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Romans 11:28

ስለ የምሥራቹ ከሆነ
ጳውሎስ የምሥራቹን የሚጠቅስበትን ምክንያት ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። አ.ት፡ “አይሁዶች የምሥራቹን ቃል ስለ ተቃወሙ”

በእናንተ ምክንያት ጠላቶች ናቸው
የማን ጠላቶች እንደሆኑና ይህም እንዴት በአሕዛብ ምክንያት ሊሆን እንደቻለ ግልጽ ልታደርገው ትችላለህ። አ.ት፡ “ስለ እናንተ የእግዚአብሔር ጠላቶች ናቸው” ወይም “እናንተ ደግሞ የምሥራቹን እንድትሰሙ እግዚአብሔር እንደ ጠላት ቆጠራቸው”

ስለ ምርጫ ከሆነ
ጳውሎስ ስለ ምርጫ የሚያነሣበትን ምክንያት ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። አ.ት፡ “እግዚአብሔር አይሁዶችን መርጦአቸዋልና” ወይም “ምክንያቱም እግዚአብሔር አይሁዶችን ስለ መረጣቸው ነው”

በአባቶቻቸው ምክንያት የተወደዱ ናቸው
አይሁዶችን ማን እንደሚወዳቸውና ጳውሎስ ለምን አባቶቻቸውን እንደሚጠቅስ ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። ደግሞም ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው ሊያደርግላቸው ተስፋ በመስጠቱ ምክንያት አሁንም ይወዳቸዋል”

የእግዚአብሔር ስጦታና ጥሪው የማይለወጥ ነውና
እግዚአብሔር ለሕዝቡ ሊሰጣቸው ቃል ስለገባላቸው መንፈሳዊና ቁሳዊ በረከቶች ጳውሎስ እንደ ስጦታዎች በመቁጠር ይናገራል። የእግዚአብሔር ጥሪ አይሁዶች የእርሱ ሕዝብ እንዲሆኑ እግዚአብሔር የመጥራቱን ሐቅ ያመለክታል። አ.ት፡ “ሊሰጣቸው ቃል ስለገባላቸው ነገርና የእርሱ ሕዝብ እንዲሆኑ እንዴት እንደጠራቸው እግዚአብሔር በፍጹም አሳቡን አልለወጠም”

Romans 11:30

ቀድሞ የማትታዘዙ ነበራችሁ
“ባለፈው ጊዜ አልታዘዛችሁም ነበር”

በእነርሱ አለመታዘዝ ምክንያት እናንተ ምህረትን ተቀበላችሁ
እዚህ ጋ ምህረት ማለት የማይገቡ የእግዚአብሔር በረከቶች ማለት ነው። አ.ት፡ “አይሁዶች ኢየሱስን ስለ ተቃወሙት እናንተ የማይገባችሁን በረከቶች ተቀበላችሁ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እናንተ
x

Romans 11:33

ኦ! የእግዚአብሔር ጥበብና ዕውቀት ባለጠግነት እንዴት ጥልቅ ነው!
እዚህ ጋ የ “ጥበብ” እና “ዕውቀት” መሠረታዊ ትርጉማቸው አንድ ነው። አ.ት፡ “ከእግዚአብሔር ጥበብና ዕውቀት የሚገኙት ብዙ ጥቅሞች እንዴት የሚያስደንቁ ናቸው!”

ፍርዶቹ እንዴት የማይመረመሩ ናቸው፣ መንገዶቹም ከመታወቅ በላይ ናቸው
“እርሱ የወሰናቸውን ነገሮችና በእኛ ላይ የሚፈጽምባቸውን መንገዶቹን ለመረዳት በፍጹም አንችልም”

የጌታን አሳብ ያወቀ ወይም አማካሪው የሆነ ማነው?
እንደ ጌታ ጥበበኛ የሆነ ማንም እንደሌለ አጽንዖት ለመስጠት ጳውሎስ ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። ይህንን እንደ መግለጫ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “የጌታን አሳብ ያወቀ ማንም የለም፣ አማካሪው የሆነም ማንም የለም” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

የጌታን አሳብ
እዚህ ጋ “አሳብ” ነገሮችን ማወቅ ወይም ስለ ነገሮች ማሰብ የሚለውን ገላጭ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ጌታ የሚያውቀውን ሁሉ” ወይም “ጌታ ስለሚያስብለት ጉዳይ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Romans 11:35

ወይስ እግዚአብሔር ይመልስለት ዘንድ አስቀድሞ ለእርሱ አንዳች የሰጠው አለ?
ጳውሎስ ለማብራሪያው አጽንዖት ለመስጠት ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። አ.ት፡ “በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር ሳይቀበል ለእግዚአብሔር አንዳች ነገር የሰጠ ማንም የለም” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)* ከእርሱ … በእርሱ … ለእርሱ - እዚህ ጋ፣ “እርሱ” የሚሉት አገባቦች ሁሉ የሚያመለክቱት እግዚአብሔርን ነው።

ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን
ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔርን እንዲያከብሩት ጳውሎስ ያለውን ምኞት ይህ ይገልጻል። በትርጉምህ ይህንን ግልጽ ልታደርገው ትችላለህ። አ.ት፡ “ሰዎች ሁሉ እርሱን ለዘላለም ያክብሩት”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 12

1 ስለዚህም ወንድሞች ሆይ ሥጋችሁን ህያው መስዋዕት፥ቅዱስ፥ ለእግዚአብሔር የሚገባ አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ምህረት እለምናችኋለሁ፥ ያም ተገቢ የሆነ አገልግሎታችሁ ነው። **2** መልካም፥ተቀባይነት ያለውና ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንድታውቁ በታደስ አዕምሮ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትከትሉ። **3** ከእናንተ ማንም ስለራሱ ሊያስብ ከሚገባው በላይ እንዳያስብ በተሰጠኝ ጸጋ አሳስብለሁ። ይልቁኑም ለእያንዳንዱ ከእግዚአብሔር በተሰጠው እምነት ልክ በጥበብ ሊያስብ ይገባል። **4** ልክ እኛ በአንድ አካል ላይ ብዙ የአካል ክፍሎች ቢኖሩንም ተግባራቸው ግን ተመሳሳይ አይደለም። **5** እንዲሁ እኛም ብዙዎች ሳለን በክርስቶስ አንድ አካል ነን እያንዳንዳችንም አንዳችን የሌላችን የአካል ክፍል ነን። **6** በተሰጠን ጸጋ በኩል ልዩ ልዩ ስጦታዎች አሉን። የአንድ ሰው ስጦታ ትንቢት መናገር ከሆነ ባመነው መጠን ያድርገው። **7** የአንዱ ስጦታ ደግሞ ቸርነት ማድረግ ከሆነ ቸርነት ያድርግ። የማስተማር ስጦታ ያለው ያስተምር። **8** የማጽናናት ስጦታ ያለው ያጽናና፤ የመስጠት ስጦታ ያለው በልግስና ያድርገው፤ የመምራት ስጦታ ያለው በጥንቃቄ ይፈጽመው፤ምህረት የማድረግ ስጦታ ያለው በደስታ ያድርገው። **9** ፍቅራችሁ ያለግብዝነት ይሁን። ክፉ የሆነን ነገር ተጸየፉ፤መልካም የሆነውን ያዙ። **10** እውነተኛ የወንድማማች ፍቅር ይኑራችሁ፤ እርስ በእርሳችሁ ተከባበሩ። **11** ልግምተኞች አትሁኑ፤በመንፈሳችሁ ንቁ ሁኑ ፥ ጌታንም አገልግሉ። **12** ስላላችሁ የወደፊት ተስፋ ደስ ይበላችሁ፤ በመከራ ጊዜ ትዕግስተኞች ሁኑ፥ጸሎታችሁ የማያቋርጥ ይሁን፤ **13** ቅዱሳንን በችግራቸው እርዱ፤ መልካም ለማድረግ የሚያስችላቹሁን መንገዶች ፈልጉ። **14** የሚያሳድዷችሁን ባርኳቸው፥ባርኩ እንጂ አትርገሙ። **15** ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ ይበላችሁ ከሚያለቅሱም ጋር አልቅሱ። **16** አንድ ልብ ይኑራችሁ፥ትሁት ሰዎችን ተቀበሉዋቸው እንጂ በትዕቢት አታስቡ። በራሳችሁ አመለካከት ጥበበኞች እንደሆናችሁ አታስቡ። **17** ክፉ ላደረገባችሁ ለማንም ክፉ አትመልሱ። በሰዎች ሁሉ ፊት መልካምን ነገር አድርጉ። **18** በተቻላችሁ መጠን በእናንተ በኩል ከሰዎች ሁሉ ጋር በሠላም ኑሩ። **19** የተወደዳችሁ ሆይ ስለራሳችሁ አትበቀሉ ይልቁኑ ለእግዚአብሔር ቁጣ ዕድል ስጡ።ምክንያቱም እንዲህ ተብሎ ተጽፏል፦ «ጌታ 'በቀል የኔ ነው ብድራትን የምከፍለው እኔ ነኝ' ይላል»። **20** «ነገር ግን ጠላትህ ከተራበ መግበው። ከተጠማ ደግሞ የሚጠጣ ስጠው። ይህን ስታደርግ የእሳት ፍም በአናቱ ላይ ትከምራለህ። **21** ክፉን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ።»

Romans 12:1

አያያዥ መግለጫ፡
ጳውሎስ የአማኝ ሕይወት ምን መሆን እንዳለበትና እንዴት ማገልገል እንዳለበት ይናገራል።

ወንድሞች ሆይ፣ ስለዚህ በእግዚአብሔር ምህረት እለምናችኋለሁ
እዚህ ጋ፣ “ወንድሞች” የሚያመለክተው ወንዶችንና ሴቶች አማኞችን ነው። አ.ት፡ “አማኞች ሆይ፣ እግዚአብሔር በሰጣችሁ ታላቅ ምህረት ምክንያት አጥብቄ እለምናችኋለሁ”

ሰውነታችሁን ሕያው መስዋዕት አድርጋችሁ እንድታቀርቡ
ጳውሎስ እዚህ ጋ “ሰውነት” የሚለውን ቃል የሚጠቀመው ሙሉውን ሰው ለማመልከት ነው። ጳውሎስ በክርስቶስ ሆኖ እግዚአብሔርን በፍጹምነት የሚታዘዘውን አማኝ አይሁዶች አርደው ለእግዚአብሔር ከሚሰዉት እንስሳ ጋር እያነጻጸረ ነው። አ.ት፡ “በቤተ መቅደሱ መሰዊያ ላይ ታርዳችሁ በምትሰዉበት መልኩ ሕያው ሆናችሁ ሳላችሁ ራሳችሁን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር እንድታቀርቡ”

እግዚአብሔር የሚቀበለው፣ ቅዱስ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ለእግዚአብሔር ብቻ የምታቀርቡትና እርሱን ደስ የሚያሰኘው መስዋዕት” ወይም 2) “ንጹህ ሥነ ምግባር ስለሆነ እግዚአብሔር የሚቀበለው” የሚሉት ናቸው።

ይህ ምክንያታዊ አገልግሎታችሁ ነው
“ይህ እግዚአብሔርን የማምለክ ትክክለኛው መንገድ ነው”

ይህንን ዓለም አትምሰሉ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ዓለም እንደሚያደርገው አታድርጉ” ወይም 2) “ዓለም በሚያደርገው መልኩ አታስቡ” የሚሉት ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Romans 12:3

ለእኔ በተሰጠኝ ጸጋ ምክንያት
እዚህ ጋ “ጸጋ” የሚያመለክተው ሐዋርያና የቤተ ክርስቲያን መሪ እንዲሆን እግዚአብሔር ጳውሎስን ስለመምረጡ ነው። ይህንን በትርጉምህ ግልጽ ልታደርገው ትችላለህ። ደግሞም ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “ምክንያቱም ሐዋርያ እንድሆን እግዚአብሔር በነጻ መርጦኛል”

በመካከላችሁ ያሉ እያንዳንዳቸው ማሰብ ከሚገባቸው በላይ ስለ ራሳቸው እንዳያስቡ
“ከመካከላችሁ ማናቸውም ቢሆኑ ከሌሎች ሰዎች እንደሚሻሉ እንዳያስቡ”

ይልቁንም በጥበብ እንዲያስቡ
“ነገር ግን ስለ ራሳችሁ በምታስቡት ጥበበኞች እንድትሆኑ”

እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ በሰጠው የእምነት መጠን
እዚህ ጋ ጳውሎስ የሚያመለክተው፣ በእግዚአብሔር ላይ ካላቸው እምነት ጋር ተያይዞ አማኞች ስለሚኖራቸው የተለያዩ ችሎታዎች ነው። አ.ት፡ “በእርሱ ላይ ባላችሁ እምነት ምክንያት እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችሁ የተለያዩ ችሎታዎችን ስለሰጣችሁ”

Romans 12:4

ስለ
ጳውሎስ ይህንን ቃል የሚጠቀመው አንዳንድ ክርስቲያኖች ከሌላው እንደሚሻሉ ለምን ማሰብ እንደሌለባቸው የሚሰጠውን ማብራሪያ ለማሳየት ነው።

በአንድ አካል ላይ ብዙ ብልቶች አሉን
ጳውሎስ የሰው አካል ልዩ ልዩ ክፍሎች እንደሆኑ አድርጎ በክርስቶስ የሆኑትን አማኞች ሁሉ ያመለክታል። ይህንን የሚያደርገው አማኞች ክርስቶስን በተለያዩ መንገዶች የሚያገለግሉ ቢሆኑም እያንዳንዱ ሰው የክርስቶስ እንደሆነና ጠቃሚ በሆነ መንገድ እንደሚያገለግል ለማስረዳት ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Romans 12:6

እንደተሰጠን ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን
ጳውሎስ አማኞች ያሏቸው ልዩ ልዩ ችሎታዎች ከእግዚአብሔር በነጻ የተሰጡ ስጦታዎች መሆናቸውን ይናገራል። ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ልዩ ልዩ ነገሮችን ለእርሱ እንድናደርግለት ለእያንዳንዳችን ችሎታዎችን በነጻ ሰጥቶናል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንደተሰጠው የእምነት መጠን ያድርግ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “እግዚአብሔር ከሰጠን የእምነት መጠን ያላለፈ ትንቢትን ይናገር” ወይም 2) “ከእምነታችን አስተምህሮ ጋር የሚስማማ ትንቢት ይናገር” የሚሉት ናቸው።

የአንዱ ስጦታ መስጠት ከሆነ
እዚህ ጋ “መስጠት” የሚያመለክተው ገንዘብንና ሌሎችንም ነገሮች ለሰዎች መስጠትን ነው። ይህንን ፍቺ በትርጉምህ ውስጥ ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። አ.ት፡ “አንድ ሰው ገንዘብን ወይም ሌሎች መገልገያዎችን ለተቸገሩ ሰዎች የመስጠት ስጦታ ከተሰጠው”

Romans 12:9

ፍቅር ያለ ግብዝነት ይሁን
ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “ሰዎችን በቅንነትና በእውነተኝነት መውደድ ይኖርባችኋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ፍቅር
እዚህ ጋ ጳውሎስ የሚጠቀምበት ቃል የሚያመለክተው ከእግዚአብሔር በሚመጣውና ራስን በማይጠቅምበት ጊዜም እንኳን ለሌሎች በሚደረግ መልካም ነገር ላይ የሚያተኩረውን የፍቅር ዓይነት ነው።

የወንድማማች ፍቅር ቢሆን አጥብቃችሁ ተዋደዱ
እዚህ ጋ ጳውሎስ አማኞች ምን ዓይነት ሰዎች መሆን እንዳለባቸው ለመንገር እያንዳንዳቸው “. . . ሁኑ” የሚል ቅርጽ ያላቸው ዘጠኝ ዓይነቶችን መዘርዘር ይጀምራል። አንዳንዶቹን ዝርዝሮች “. . . አድርጉ” ብለህ መተርጎም ይኖርብህ ይሆናል። ዝርዝሩ እስከ ሮሜ 12፡13 ይቀጥላል።

የወንድማማች ፍቅር ቢሆን
“እንደ እናንተው አማኞች የሆኑትን መውደድን አስመልክቶ”

ፍቅር
ይህ የወንድማማች ፍቅር ወይም የጓደኛ ወይም የቤተሰብ ፍቅር የሚል ትርጉም ያለው ሌላ ቃል ነው። ይህ በጓደኛሞች ወይም በዘመዳሞች መካከል ያለ ተፈጥሮአዊና ሰብአዊ ፍቅር ነው።

አጥብቃችሁ ተዋደዱ
ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “ፍቅርን አሳዩ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

አክብሮትን በሚመለከት እርስ በእርሳችሁ ተከባበሩ
“እርስ በእርሳችሁ ተከባበሩ፣ አክብሮትንም አሳዩ” ወይም “አማኝ ባልንጀሮቻችሁን በማክበር ክብርን ስጧቸው”

Romans 12:11

ትጋትን በሚመለከት አታወላውሉ። መንፈስን በሚመለከት የምትጓጉ ሁኑ። ጌታን በሚመለከት አገልግሉት።
“በሥራችሁ ሰነፎች አትሁኑ፣ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን ለመከተልና ጌታን ለማገልገል የምትጓጉ ሁኑ”

በመከራ ታገሱ
“መከራ በሚደርስባችሁ ጊዜ ሁሉ በትዕግስት ቆዩ”

ለቅዱሳን የሚያስፈልጋቸውን አካፍሏቸው
ይህ በሮሜ 12:9 የጀመረው ዝርዝር የመጨረሻው ጉዳይ ነው። “እንደእናንተው ክርስቲያን የሆኑ በሚቸገሩበት ጊዜ በሚያስፈልጋቸው ነገር እርዷቸው”

እንግዳ ተቀባይነታችሁን የምታሳዩባቸውን አጋጣሚዎች ፈልጉ
“ማረፊያ በሚፈልጉበት ጊዜ ሁሉ በቤታችሁ ተቀበሏቸው”

Romans 12:14

እርስ በእርስ የምትስማሙ ሁኑ
ይህ በአንድነት መኖር የሚል ትርጉም ያለው የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “እርስ በእርሳችሁ ተስማሙ” ወይም “እርስ በእርሳችሁ በአንድነት ኑሩ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በትዕቢት መንገድ አታስቡ
“ከሌሎች በበለጠ የምታስፈልጉ እንደሆናችሁ አታስቡ”

ዝቅተኛ ኑሮ የሚኖሩትን ተቀበሏቸው
“የሚጠቅሙ የማይመስሉ ሰዎችን ተቀበሏቸው”

በራሳችሁ አሳብ ጥበበኞች አትሁኑ
x

Romans 12:17

ለማንም በክፉ ፈንታ ክፉ አትመልሱ
“ክፉ ባደረገባችሁ ሰው ላይ ክፉ አታድርጉ”

በሰዎች ሁሉ ፊት መልካም ነገሮችን አድርጉ
“ሁሉም መልካም እንደሆኑ የሚቆጥሯቸውን ነገሮች አድርጉ”

እናንተን በሚመለከት ከሰዎች ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ
“ከሁሉ ጋር በሰላም ለመኖር የምትችለውን ሁሉ አድርግ”

Romans 12:19

ለእግዚአብሔር ቁጣ ዕድል ስጠው
ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “እግዚአብሔር እንዲቀጣቸው ፍቀድለት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ተጽፏልና
ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “አንድ ሰው ጽፎታልና” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በቀል የእኔ ነው፤ እኔ እመልሳለሁ
እነዚህ ሁለቱም ሐረጎች መሠረታዊ ትርጉማቸው አንድ ሲሆን እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚበቀል አጽንዖት ይሰጣሉ። አ.ት፡ “በርግጥ እኔ እበቀላችኋለሁ”

ጠላትህን ... አብላው ... የሚጠጣውን ስጠው ... ይህንን ብታደርግ ... ትከምራለህ፣ ክፉን አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ
“አንተ” እና “የአንተ” የሚሉ አገባቦች ሁሉ ለአንድ ሰው እንደሚነገሩ ሆነው ቀርበዋል።

ነገር ግን ጠላትህ ከተራበ ... በራሱ ላይ
ጳውሎስ በ12፡20 ላይ ከሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ይጠቅሳል። አ.ት፡ “ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ፣ ‘ጠላትህ ከተራበ ... በራሱ ላይ ...’ ይላል”

አብላው
“ጥቂት ምግብ ስጠው”

በራሱ ላይ የእሳት ፍም ትከምራለህ
ጳውሎስ አንድ ሰው በራሳቸው ላይ የእሳት ፍም የሚያፈስባቸው በሚመስልበት ሁኔታ ጠላቶች ስለሚቀበሏቸው በረከቶች ይናገራል። ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፣ 1) “የጎዳችሁ ሰው የማይገባ ነገር እንዳደረገባችሁ

እጅግ ተሰምቶት እንዲጸጸት አድርጉት” ወይም 2) “እግዚአብሔር በጠላትህ ላይ የከፋ ፍርድ የሚሰጥበትን ምክንያት እንዲያገኝ አድርገው” የሚሉት ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ክፉን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ

ጳውሎስ “ክፉ”ን እንደ ሰው በመቁጠር ይገልጸዋል። ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉም ትችላለህ። አ.ት፡ “ክፉዎች እንዲያሸንፉህ አትፍቀድላቸው፣ ነገር ግን መልካም የሆነውን በማድረግ ክፉ የሆኑትን አሸንፋቸው” (ሰውኛ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 13

1 ከእግዚአብሔር ካልተሰጠ በቀር ሥልጣን የለምና ሰው ሁሉ ለመንግስት ባለሥልጣናት ይገዛ። አሁን በሥልጣን ላይ ያለውም የተሾመው በእግዚአብሔር ነው። 2 ስለዚህም ይህን ሥልጣን የሚቃወም የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ይቃወማል፥ የሚቃወሙትም ሁሉ በራሳቸው ላይ ፍርድን ያመጣሉ። 3 ምክንያቱም ገዢዎች ክፉ ለሚያደርጉ እንጂ መልካም ለሚያደርጉ የሚያስፈሩ አይደሉም። ባለሥልጣንን አለመፍራት ትፈልጋለህ? መልካምን አድርግ ከእርሱ ሽልማትን ታገኛለህ። 4 ለመልካም ለአንተ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና። ክፉ የምታደርግ ከሆነ ግን ያለምክንያት ሠይፍ አልታጠቀምና ልትፈራ ይገባሀል። ምክንያቱም ክፉ የሚያደርገውን በቁጣ የሚበቀል የእግዚአብሔር አገልጋይ ነው። 5 ስለዚህ ስለ ቁጣው ብለህ ብቻ ሳይሆን ስለህሊናህ ብለህ ልትገዛ ይገባሀል። 6 በዚህ ምክንያት ግብርም ትከፍላላችሁ። ምክንያቱም ባለሥልጣናት ይህንን ጉዳይ ያለመታከት የሚቆጣጠሩ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው። 7 ለእያንዳንዱ የሚገባውን ስጡ፥ ግብር ለሚገባው ግብርን፥ ቀረጥ ለሚገባው ቀረጥን፥ መፈራት ለሚገባው መፈራትን፣ አክብሮት ለሚገባው አክብሮትን ስጡ። 8 እርስ በእርስ ከመዋደድ በቀር የማንም ዕዳ አይኑርባችሁ። ምክንያቱም ባልንጀራውን የሚወድ ህግን ፈጽሟል። 9 ምክንያቱም «አታመንዝር፥ አትግደል፥ አትስረቅ፥ አትመኝ» የሚሉትና ሌሎቹም ትዕዛዛት «ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ» በሚለው ትዕዛዝ ተጠቃለዋል። 10 ፍቅር ያለው ባልንጀራውን አይጎዳም። ስለዚህ ፍቅር የህጉ ፍጻሜ ነው። 11 በዚህም ምክንያት ከእንቅልፍ የምትነቁበት እንደደረስ ታውቃላችሁ። መዳናችን መጀመሪያ ካመንበት ጊዜ ይልቅ ቅርብ ነው። 12 ሌሊቱ እያለፈ ቀኑም እየቀረበ ነው። ስለዚህ የጨለማን ሥራ ጥለን የብርሀንን የጦር ዕቃ እንልበስ። 13 ቅጥ ባጣ ፈንጠዝያና በስካር ሳይሆን በቀን እንደሚመላለስ ሰው በተገቢው ሁኔታ እንመላለስ። በዝሙት ወይም በማይገታ ክፉ ምኞት፥ በጭቅጭቅና በቅናት አንመላለስ ። 14 ይልቁኑ ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት ለሥጋችሁና ለክፉ ምኞቱም ዕድል አትስጡ።

Romans 13:1

አያያዥ መግለጫ:
አማኞች በገዢዎቻቸው ሥር እንዴት መኖር እንዳለባቸው ጳውሎስ ይነግራቸዋል።

ነፍስ ሁሉ ለ . . . ታዛዥ ትሁን
እዚህ ጋ “ነፍስ” ሙሉዉን ሰው በከፊል የሚገልጽ ነው። “ክርስቲያን ሁሉ መታዘዝ አለበት” ወይም “ሁሉም መታዘዝ አለበት”

ከፍተኛ ባለሥልጣናት
“የመንግሥት ኃላፊዎች”

ስለ
ምክንያቱም

ከእግዚአብሔር ካልመጣ በስተቀር ሥልጣን የለም
“ሥልጣን ሁሉ የሚመጣው ከእግዚአብሔር ነው”

አሁን ያሉት ባለሥልጣናት በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው
ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “በሥልጣን ላይ ያሉ ሰዎች በዚያ ያሉት እግዚአብሔር እዚያ ላይ ስላስቀመጣቸው ነው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ያ ሥልጣን
“ያ የመንግሥት ሥልጣን” ወይም “እግዚአብሔር በኃላፊነት ላይ ያስቀመጠው ሰው ሥልጣን”

ይህንን የሚቃወሙ በራሳቸው ላይ ፍርድን ይቀበላሉ
ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “የመንግሥትን ሥልጣን በሚቃወሙት ላይ እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Romans 13:3

ስለ
ጳውሎስ የሮሜ 13፡2 ማብራሪያውን ለመጀመርና መንግሥት በአንድ ሰው ላይ ቢፈርድበት ምን እንደሚከተለው ለመንገር ይህንን ቃል ይጠቀማል።

ገዢዎች አስፈሪዎች አይደሉም
መልካም ሰዎችን ገዢዎች እንዲፈሩ አያደርጓቸውም።

ለመልካም ሥራ ... ለክፉ ሥራ
ሰዎች በ”መልካም ሥራቸው” ወይም በ”ክፉ” ሥራቸው ተለይተዋል”።

በሥልጣን ላይ ያለን ሰው የማትፈራው መሆን ትፈልጋለህ?
ሰዎች ገዢዎችን ላለመፍራት ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንዲያስቡ ለማድረግ ጳውሎስ ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። አ.ት፡ “ገዢዎችን እንዴት መፍራት እንደማይኖርባችሁ እንድነግራችሁ ፍቀዱልኝ”። (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

አድናቆቱን ትቀበላለህ
መንግሥት መልካም የሆነውን ስለሚያደርጉ ሰዎች መልካም ነገር ይናገራል።

እርሱ ያለምክንያት ሰይፍ አይታጠቅም
ይህንን በአዎንታ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “እርሱ ሰይፍ የሚታጠቀው በጣም ጥሩ በሆነ ምክንያት ነው” ወይም “እርሱ ሰዎችን የሚቀጣበት መብት አለው፣ ስለዚህ ሰዎችን ይቀጣቸዋል” (ምጸት የሚለውን ተመልከት)

ሰይፍ መታጠቅ
ሮማውያን ገዢዎች የሥልጣናቸው ምልክት የሚሆን አጭር ሰይፍ ይታጠቁ ነበር። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የቁጣ ተበቃይ
እዚህ ጋ “ቁጣ” የሚወክለው ሰዎች ክፉ ነገር በሚያደርጉበት ጊዜ የሚቀበሉትን ቅጣት ነው። አ.ት፡ “በክፉ ላይ የመንግሥትን ቁጣ ለመግለጽ ሰዎችን የሚቀጣ ሰው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ስለ ሕሊና ደግሞ እንጂ በቁጣው ምክንያት ብቻ አይደለም
“መንግሥት እንዳይቀጣህ ብለህ ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር ፊት ንጹህ ሕሊና እንዲኖርህ ደግሞ ነው”

Romans 13:6

በዚህ ምክንያት
“መንግሥት ክፉ አድራጊዎችን ስለሚቀጣ”

እናንተ ... ለእያንዳንዱ ስጡ
እዚህ ጋ ጳውሎስ የሚናገረው ለአማኞች ነው።

ለባለሥልጣናት
“ለባለሥልጣናት ግብር መክፈል የሚኖርባችሁ ለዚህ ነው”

የሚተጉ
“የሚያስተዳድሩ” ወይም “የሚሠሩ”

ግብር ለሚገባው ግብርን፣ ቀረጥ ለሚገባው ቀረጥን፤ መፈራት ለሚገባው መፈራትን፣ ክብር ለሚገባው ክብርን።
“ስጡ” የሚለውን ቃል ቀደም ሲል ከነበረው ዐረፍተ ነገር መገንዘብ ይቻላል። አ.ት፡ “ግብር ለሚገባው ግብርን፣ ቀረጥ ለሚገባውም ቀረጥን ስጡ። መፈራት ለሚገባው መፈራትን፣ ክብር ለሚገባውም ክብርን ስጡ”

መፈራት ለሚገባው መፈራትን፣ ክብር ለሚገባው ክብርን
እዚህ ጋ፣ መፈራትንና ክብርን መስጠት መፈራትና መከበር የሚገባቸውን እነርሱን የመፍራትና የማክበር ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “መፈራት የሚገባቸውን እነርሱን ፍሩ፣ መከበር የሚገባቸውን እነርሱን ደግሞ አክብሩ” ወይም “ልታከብሯቸው የሚገባችሁን አክብሯቸው፣ አክብሮት ልታሳዩአቸው የሚገባችሁንም አክብሮትን አሳዩአቸው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ቀረጥ
ይህ የቀረጥ ዓይነት ነው።

Romans 13:8

አያያዥ መግለጫ፡
ባልንጀሮቻቸውን በሚመለከት ምን ማድረግ እንዳለባቸው ጳውሎስ ለአማኞች ይነግራቸዋል።

እርስ በእርስ ከመዋደድ በቀር ምንም ዓይነት ዕዳ አይኑርባችሁ
ይህ ድርብ አሉታ ነው። ይህንን በአዎንታ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “በእያንዳንዱ ላይ ያለባችሁን ዕዳ ክፈሉ፣ እርስ በእርሳችሁም ተዋደዱ” (ድርብ አሉታ የሚለውን ተመልከት)

ባለዕዳ
ይህ ግሥ ብዙ ቁጥር ሲሆን በሮም የሚኖሩትን ክርስቲያኖች ሁሉ የሚመለከት ነው።

እርስ በእርስ ከመዋደድ በቀር
ከላይ በተጠቀሰው ማስታወሻ እንደተመለከተው ሊኖርባቸው የሚችለው ዕዳ ይህ ነው።

ፍቅር
ይህ የሚያመለክተው ከእግዚአብሔር በሚመጣውና ራስን በማይጠቅምበት ጊዜም እንኳን ለሌሎች በሚደረግ መልካም ነገር ላይ የሚያተኩረውን የፍቅር ዓይነት ነው።

መመኘት
ለሌላው ሰው ያለው ነገር የራስ እንዲሆን ወይም እንዲኖር መፈለግ።

ፍቅር የአንድን ሰው ባልንጀራ አይጎዳም
ይህ ሐረግ ፍቅርን ለሌሎች ሰዎች ደግ እንደሚሆን ሰው አድርጎ ይገልጸዋል። አ.ት፡ “ባልንጀሮቻቸውን የሚወዱ ሰዎች አይጎዷቸውም” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

Romans 13:11

ከእንቅልፍ የምትነቁበት ሰዓት አሁን መሆኑን ጊዜውን ታውቃላችሁ
ከእንቅልፍ መንቃት በሚያስፈልጋቸው መልኩ የሮም አማኞች የባህርይ ለውጥ ማድረግ እንደሚያስፈልጋቸው ጳውሎስ ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Romans 13:13

እናድርግ
ጳውሎስ አንባቢዎቹንና ሌሎች አማኞችን ከራሱ ጋር ያካትታል። (አካታች “እኛ” የሚለውን ተመልከት)

በቀን እንደሚሆን በአግባብ እንመላለስ
ጳውሎስ እንደ እውነተኞች አማኞች መኖርን ለማስረዳት አንድ ሰው በቀን እንደሚመላለስ አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “ሁሉ ሊያየን እንደሚችል እያወቅን በግልጽነት እንመላለስ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በዝሙት ወይም በማይቆጣጠሩት የፍትወት ምኞት
እነዚህ አሳቦች መሠረታዊ ትርጉማቸው አንድ ነው። በትርጉምህ ውስጥ ልታጣምራቸው ትችላለህ። አ.ት፡ “አስጸያፊ የዝሙት ተግባር”

ሁከት
ይህ በሌሎች ላይ ማሴርንና ከሌሎች ሰዎች ጋር መከራከርን ያመለክታል።

ቅናት
ይህ በሌላው ሰው ስኬት ወይም ሌሎች በሚገጥሟቸው ዕድሎች የሚሰማውን አሉታዊ ስሜት ያመለክታል።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት
ጳውሎስ የክርስቶስን የሥነ ምግባር ባህርይ መቀበልን ሰዎች ሊያዩት እንደሚችሉት ውጫዊ ልብሳችን አድርጎ ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ልበሱት
የአንተ ቋንቋ ትዕዛዝን በብዙ ቁጥር የሚገልጽበት አግባብ ካለ እዚህ ጋ ተጠቀምበት።

ለሥጋ አትመቻቹለት
እዚህ ጋ “ሥጋ” የሚያመለክተው እግዚአብሔርን የሚቃወመውን የሰዎችን ራስ - መር ተፈጥሮ ነው። ይህ የሰው ልጆች ኃጢአታዊ ተፈጥሮ ነው። አ.ት፡ “ክፉ ነገሮችን እንዲያደርግ ለአሮጌው ክፉ ልብ አንዳችም ዕድል ከቶ አትስጡት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 14

1 በእምነት ደካማ የሆነውን በጥያቄዎቹ ላይ በመፍረድ ሳይሆን በፍቅር ተቀበሉት። 2 አንዳንዱ ማንኛውንም ነገር በእምነት ይበላል፥በእምነቱ ደካማ የሆነው
ደግሞ አትክልት ብቻ ይበላል። 3 ስለዚህ ማንኛውንም ዓይነት ምግብ የሚበላው የማይበላውን አይናቀው። የማይበላውም በሚበላው ላይ አይፍረድ።
ምክንያቱም እግዚአብሔር ተቀብሎታል። 4 በሌላው አገልጋይ ላይ የምትፈርድ አንተ ማን ነህ? በገዛ ጌታው ፊት ወይ ይቆማል አሊያም ይወድቃል። ነገር ግን
ጌታ ሊያቆመው ይችላልና ይቆማል። 5 አንደኛው አንዱን ቀን ከሌላው ቀን የሚበልጥ አድርጎ ይቆጥራል። ሌላው ደግሞ ሁሉም ቀናት አንድ ናቸው ብሎ
ያምናል። እያንዳንዱ ሰው የራሱ መረዳት ይኑረው። 6 ቀንን የሚያከብር ለእግዚአብሔር ብሎ ያከብራል፥ የሚበላውም እግዚአብሔርን ያመሰግናልና
ለእግዚአብሔር ብሎ ይበላል። የማይበላውም ራሱን ከመብላት ያቅባል። እርሱም እግዚአብሔርን ያመሰግናል። 7 ምክንያቱም ከእኛ ማንም ለራሱ የሚኖር
ወይም የሚሞት የለም። 8 ብንኖር ለጌታ እንኖራልንና ብንሞትም ለጌታ እንሞታለንና። እንግዲያውስ ብንኖርም ብንሞትም የጌታ ነን። 9 ምክንያቱም በሙታንና
በህያዋን ላይ ጌታ ይሆን ዘንድ ለዚህ ዓላማ ክርስቶስ ሞቷል ደግሞም ህያው ሆኗል። 10 ግን አንተ በወንድምህ ላይ ለምን ትፈርዳለህ? አንተስ ወንድምህን
ለምን ትንቃለህ? ሁላችንም በእግዚአብሔር የፍርድ ዙፋን ፊት እንቆማለን። 11 ምክንያቱም «እኔ ህያው ነኝና ጉልበት ሁሉ በፊቴ ይንበረከካል ምላስም ሁሉ
እግዚአብሔርን ያመሰግናል» ይላል ጌታ ተብሎ ተጽፏልና። 12 ስለዚህም እያንዳንዳችን ስለ ስራችን በእግዚአብሔር ፊት መልስ እንሰጣለን። 13 ስለዚህ
ከእንግዲህ ወዲያ አንዳችን በሌላችን ላይ አንፍረድ በዚያ ፋንታ ማንም በወንድሙ ፊት መሰናክል ወይም ወጥመድ እንዳያስቀምጥ እንወስን። 14 ምንም ነገር
በራሱ ርኩስ እንዳልሆነ በጌታ በኢየሱስ አውቃለሁ ተረድቻለሁም። ማንኛውም ነገር ርኩስ ነው ብሎ ለሚያስብ ለእርሱ ብቻ ያ ነገር እርኩስ ነው። 15 በምግብ
ጉዳይ ወንድምህን የምታሰናክል ከሆነ አንተ በፍቅር እየተመላለስክ አይደለም። ስለምግብህ ብለህ ክርስቶስ የሞተለትን ሰው አታጥፋ። 16 ስለዚህ መልካም
ስራዎቻችሁን ለሰዎች መቀለጃ አታድርጉ። 17 ምክንያቱም የእግዚአብሔር መንግሥት በመንፈስ ቅዱስ የሚሆን ጽድቅ፥ ሠላምና ደስታ እንጂ የመብልና
የመጠጥ ጉዳይ አይደለም። 18 ክርስቶስ እንዲህ ባል ሁኔታ የሚያገለግለውን እግዚአብሔር ይቀበለዋል በሰዎችም ይመሰገናል። 19 ስለዚህ ሠላም
የሚገኝበትንና እርስበእርሳችን የምንተናነጽባቸውን ነገሮች እንፈልግ። 20 በምግብ ምክንያት የእግዚአብሔርን ሥራ አታበላሹ። በእርግጥም ሁሉ ነገር ንጹህ
ነው፥ ነገር ግን እየተጠራጠረ ለሚበላ ለዚያ ሰው ክፉ ነው፣ እንዲሰናከልም ያደርገዋል። 21 ወንድምህን የሚጎዳ ከሆነ ሥጋ ባትበላም ወይን ባትጠጣም
ወይም ምንም ባታደርግ መልካም ነው። 22 አንተ በግልህ ያለህ መረዳት ባንተና በእግዚአብሔር መሀል ይቅር። አምኖ የተቀበለውን ነገር በማድረጉ ራሱን
የማይወቅስ የተባረከ ነው። 23 እየተጠራጠረ የሚበላ ግን በእምነት ስላልሆነ ይፈረድበታል። ምክንያቱም ያለ እምነት የሆነ ነገር ሁሉ ኃጢአት ነው።

Romans 14:1

አያያዥ ሀሳብ
ጳውሎስ አማኞች በእግዚአብሔር ዘንድ ተጠያቂ አንደሆኑ እንዲያስታውሱ ያበረታታቸዋል።

በእምነት ደካማ
ይህ የሚወክለው አንዳንድ ነገሮችን በመብላታቸው የወቀሳ ስሜት የሚሰማቸውን ሰዎች ነው።

በክርክራቸው ሳትፈርዱባቸው
“እናም በአስተሳሰባቸው ምክንያት አትክሰሷቸው”

አንድ ሰው ማንኛውንም ነገር ለመብላት እምነት አለው
እዚህ ላይ “እምነት” የሚለው ቃል አንድ ሰው እግዚአብሔር አድርግ ብሎኛል ብሎ የሚያምነውን ነገር ማድረግን ያመለክታል።

ሌላው ደካማ የሆነው ደግሞ አትክልትን ብቻ ይበላል
ይህ እርሱ ስጋን እንዲበላ እግዚአብሔር እንደማይፈልግ የሚያምንን ሰው ይገልጻል።

Romans 14:3

እናንተ የሌላ ሰው አገልጋይ ላይ የምትፈርዱ፣ እናንተ ማን ናችሁ?
ጳውሎስ ይህን ጥያቄ በሌሎች ላይ የሚፈርዱ ሰዎችን ለመገሰጽ ይጠቀምበታል። ይህ በአረፍተ ሃሳብ መልክ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እናንተ እግዚአብሔር አይደላችሁም፣ እናም የእርሱ አገልጋዮች ላይ ለመፍረድ አልተፈቀደላችሁም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ፣ አንተ
ይህ “አንተ” የሚለው ቃል በነጠላ ቁጥር የተገለጸ ነው። (የሁለተኛ መደብ ቅርጾች የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ የሚቆመውም የሚወድቀውም በገዛ ራሱ ጌታ ፊት ነው
እዚህ ላይ ጳውሎስ ስለ እግዚአብሔር ሲናገር አገልጋዮች እንዳሉት ጌታ አድርጎ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አገልጋዩን ለመቀበልም ሆነ ላለመቀበል መወሰን የሚችለው ጌታው ብቻ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን እንዲቆም ይደረጋል፣ ምክንያቱም ጌታ እርሱ እንዲቆም ያደርገዋልና
ጳውሎስ እዚህ ላይ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያገኘው አገልጋይ ከመውደቅ ይልቅ “እንዲቆም ይደረጋል” ሲል ይናገራል። ይህንን በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፡- “ጌታ ግን ይቀበለዋል ምክንያቱም እርሱ አገልጋዮች ተቀባይነት እንዲኖራቸው ማድረግ ይችላል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 14:5

አንድ ሰው አንድን ቀን ከሌላው ቀን አብልጦ ዋጋ ይሰጣል። ሌላው ግን ለሁሉም ቀኖች እኩል ዋጋ ይሰጣል
“አንድ ሰው አንድ ቀን ከሌላው ቀን የበለጠ እንደሆነ ያስባል፣ ሌላው ግን ሁሉም ቀናት እኩል እንደሆኑ ያስባል።

እያንዳንዱ ሰው በራሱ አእምሮ የሚያስበውን ይመን
የዚህን ትርጉም በግልጽ መናገር ይቻላል። ይህንን በገቢር/አድራጊ ቅርጽም መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እያንዳንዱ ሰው የሚያደርገው ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን ለማክበር እንደሆነ እርግጠኛ ይሁን” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀንን የሚያከብር፣ ለጌታ ብሎ ያከብራል
እዚህ ላይ “ማክበር” የሚለው ማምለክን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በአንድ በተወሰነ ቀን የሚያመልክ ሰው ይህን የሚያደርገው እግዚአብሔርን ለማክበር ነው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የሚበላ
“ሁሉንም” የሚለው ቃል ሮሜ 14:03 ላይ ባለው አገባብ መረዳት ይቻላል። እዚህ ላይ ተደግሞ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሁሉንም አይነት ምግብ የሚበላ ሰው” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ለጌታ ብሎ ይበላል
“እግዚአብሔርን ለማክበር ይበላል” ወይም “በዚያ መንገድ የሚበላው እግዚአብሔርን ለማክበር ነው”

የማይበላ
“ሁሉንም” የሚለው ቃል በሮሜ ሮሜ 14:03 ላይ ባለው አገባብ መሰረት መረዳት ይቻላል። እዚህ ላይ ተደግሞ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሁሉንም የማይበላ” ወይም “አንዳንድ የምግብ ዓይነቶችን የማይበላ ሰው” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ለጌታ ብሎ ከመብላት ይቆጠባል
“እነዚያን የምግብ ዓይነቶች ጌታን ለማክበር ሲል ከመብላት ይቆጠባል” ወይም “በዚያ መንገድ የሚበላው ጌታን ለማክበር ነው”

Romans 14:7

ከእኛ ውስጥ ማንም ለራሱ የሚኖር የለም
እዚህ ላይ “ለራሱ የሚኖር” ማለት ራሱን ለማስደሰት ብቻ የሚኖር ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ማናችንም ራሳችንን ለማስደሰት ብቻ ብለን መኖር የለብንም” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለራሱ የሚሞት ማንም የለም
ይህ ማለት የአንድ ሰው ሞት ሌሎች ሰዎችንም ይነካል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ማናችንም እኛ ብቻ ስንሞት እኛን ብቻ እንደሚጎዳ ማሰብ የለብንም። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ ... እኛ
ጳውሎስ አንባቢዎቹንም በዚህ ንግግር ውስጥ እያካተተ ነው። (አካታች “እኛ” የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 14:10

አንተ በወንድምህ ላይ ለምን ትፈርዳለህ? አንተስ ወንድምህን ለምን ትንቃለህ?
እነዚህን ጥያቄዎች በመጠቀም ጳውሎስ ከአንባቢዎቹ ውስጥ አንዳንድ ግለሰቦችን መገሰጽ እንደሚገባው ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፡- “በወንድምህ ላይ መፍረድህ ትክክል አይደለም፣ ወንድምህንም መናቅ ትክክል አይደለም” ወይም “በወንድምህ ላይ መፍረድ፣ ወንድምህንም መናቅ አቁም!” (የሁለተኛ መደብ ቅርጾች የሚለውን ይመልከቱ)

ወንድም
ይህ ሌላ ክርስቲያን፣ ሴት ወይም ወንድ የሆነን ይወክላል።

ሁላችን በእግዚአብሔር የፍርድ ዙፋን ፊት እንቆማለንና
“የፍርድ ዙፋን” የእግዚአብሔርን የመፍረድ ስልጣንን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር በሁላችን ላይ ይፈርዳልና” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

...” ተብሎ ተጽፏልና
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አንድ ሰው እንዲህ ብሎ ጽፎ ነበርና’ ... ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ሕያው ነኝና
ይህ ሐረግ አንድን መሃላ ወይም ቃልኪዳንን ለመጀመር ጥቅም ላይ ይውላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይህ እውነት እንደሆነ እርግጠኛ መሆን ትችላላችሁ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእኔ ሁሉም ጉልበት ይንበረከካል፣ ሁሉም ምላስ ለእግዚአብሔር ምስጋናን ይሰጣል
ጳውሎስ “ጉልበት” እና “ምላስ” የመሳሰሉትን ቃላት የሚጠቀመው የአንድን ሰው ሙሉ ማንነት ለመወከል ነው። በተጨማሪም ጌታ “እግዚአብሔር” የሚለውን ቃል ራሱን ለመወከል ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሁሉም ሰው ይሰግዳል፣ ምስጋናንም ለእኔ ይሰጣል” (ወካይ እና አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 14:12

ስለ ራሱ ለእግዚአብሔር መልስ ይሰጣል
“ለሰራናቸው ስራዎች ለእግዚአብሔር ማብራርያን እንሰጣለን”

ነገር ግን ይልቁንም ማንም ለወንድሙ የማሰናከያ እንቅፋት ወይም ወጥመድ እንዳያደርግበት ይህን ወስኑ
እዚህ ላይ “የማሰናከያ እንቅፋት” ወይም “ወጥመድ” የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ነገርን ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን ይልቁንም ሌላውን አማኝ ወደ ኃጢአት ሊወስድ የሚችል ነገርን አለማድረግንና አለመናገርን ግባችሁ አድርጉት” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ወንድም
ይህ ሌላ ክርስቲያንን ይወክላል፣ ሴት ወይም ወንድ ሊሆን ይችላል።

Romans 14:14

... ክርስቶስ ኢየሱስን አውቄያለሁ አምኛለሁም
እዚህ ላይ “አውቄያለሁ” እና “አምኛለሁ” የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉምን የያዙ ናቸው፡ ጳውሎስ እርግጠኛ መሆኑን አጽንኦት ለመስጠት ይጠቀምባቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከጌታ ኢየሱስ ጋር ባለኝ ግንኙነት ምክንያት እርግጠኛ ነኝ” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ምንም ነገር በራሱ ርኩስ አይደለም
ይህን በአዎንታዊ መልኩ መተርጎም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሁሉም ነገር በራሱ ንጹህ ነው” (መንትያ አሉታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በራሱ
“በተፈጥሮው” ወይም “በይዘቱ”

ምንም ነገር ርኩስ ነው ብሎ ለሚያስብ ፣ ለእርሱ ርኩስ ነው
ጳውሎስ እዚህ ላይ ለመናገር የፈለገው አንድ ሰው ርኩስ ነው ብሎ ከሚያስበው ነገር መራቅ እንዳለበት ነው። ይህን በትርጉምህ ግልጽ አድርገህ ማስቀመጥ ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን አንድ ሰው አንድን ነገር ርኩስ ነው ብሎ የሚያስብ ከሆነ፣ ለዚያ ሰው ያ ነገር ርኩስ ነውና ከእርሱ ሊርቅ ይገባዋል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በመብልህ ምክንያት ወንድምህ ቢጎዳ
“የሌላውን ክርስቲያን እምነት በመብል ምክንያት የምትጎዳ ከሆነ” እዚህ ላይ “በመብልህ” ውስጥ ያለው የባለቤት አመልካች የሚያመለክተው በእምነቱ ጠንካራ የሆነን አማኝ ነው፣ “ወንድም” የሚለው ደግሞ በእምነታቸው ደካማ የሆኑትን ያመለክታል።

ወንድም
ይህ ሌሎች ክርስቲያኖችን ይወክላል፣ ወንዶችንም ሴቶችንም ይወክላል

እንግዲያው በፍቅር እየተመላለስክ አይደለም
ጳውሎስ የአማኞችን ባሕርይ ጉዞ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከእንግዲህ ፍቅርን እያሳየህ አይደለም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 14:16

ስለዚህ አንተ መልካም ብለህ የቆጠርከውን ነገር ክፉ እንደሆነ ተደርጎ እንዲነገር አትፍቀድ
“ሌላ ሰው አንድ ነገር ክፉ ነው ብሎ ካሰበ፣ ያንን ነገር አንተ አታድርገው፣ ምንም እንኳ አንተ መልካም ነው ብለህ የምታስብ ቢሆንም አታድርገው”

የእግዚአብሔር መንግስት ጽድቅ፣ ሰላምና በመንፈስ ቅዱስ የሚሆን ደስታ እንጂ ምግብና መጠጥ አይደለምና
ጳውሎስ እግዚአብሔር መንግስቱን ያዘጋጀው ከራሱ ጋር ትክክለኛ የሆነ ግንኙነት እንዲኖረን ለማድረግ፣ እንዲሁም ሰላምንና ደስታን ሊሰጠን እንደሆነ በመናገር ይሞግታቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር መንግስቱን ያዘጋጀው የምንበላውንና የምንጠጣውን ለማስተዳደር አይደለም። መንግስቱን ያዘጋጀው ከእርሱ ጋር ትክክለኛ ግንኙነት እንዲኖረን፣ እንዲሁም ሰላምና ደስታን ሊሰጠን ነው። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 14:18

በሰው ዘንድ ተቀባይነት ያለው
ይህን በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች እርሱን ይቀበሉታል” ወይም “ሰዎች እርሱን ያከብሩታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰላም ያለባቸውንና እርስ በርሳችን የምንታነጽባቸውን ነገሮች እንከተል
እዚህ ላይ “የምንታነጽባቸውን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እርስ በርስ በእምነት የሚያሳድጉ ነገሮችን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አብረን በሰላም ለመኖርና በእምነታችን ለመበርታት እንፈልግ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 14:20

ለመብል ብለህ የእግዚአብሔርን ሥራ አታፍርስ
የዚህን አርፍተ ነገር ትርጉም ግልጽ አድርጎ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ የሆነ የምግብ ዓይነት መብላት ስለፈለግህ ብቻ እግዚአብሔር ለአንድ አማኝ የሰራውን ስራ አታፍርሰው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን ለሚበላና ሌላው እንዲሰናከል ለሚያደርግ ለዚያ ሰው ክፉ ነው
እዚህ ላይ “ሌላውን እንዲሰናከል የሚያደርግ” ማለት ደካማ የሆነው ወንድም ከሕሊናው ጋር የማይጣጣም ነገር እንዲያደርግ የሚገፋው ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን አንድ ወንድም ሌላው ወንድም መብላት ትክክል አይደለም ብሎ የሚያስበውን ምግብ ቢበላ፣ ለዚያ ሰው ኃጢአት ይሆንበታል፣ እርሱ በመብላቱ ምክንያት ደካማውን ወንድም ከሕሊናው ጋር የማይጣጣም ነገር እንዲያደርግ ምክንያት ከሆነበት ኃጢአት ይሆንበታል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ስጋ መብላት፣ ወይንንም አለመጠጣት፣ እንደዚሁም ወንድምህን ያሰናክላል ብለህ የምታስበውን ነገር አለማድረግ መልካም ነው
“ስጋ መብላት፣ ወይን መጠጣት እንዲሁም ወንድምህ ኃጢአት እንዲያደርግ ምክንያት የሚሆን ነገርን አለማድረግ ይመረጣል”

ወንድም
ይህ ሌሎች አማኝ ክርስቲያኖችን ይወክላል፣ ወንድ ወይም ሴት ሊሆኑ ይችላሉ

የአንተ
“የአንተ” የሚለው በእምነቱ ጠንካራ የሆነውን ይወክላል፣ “ወንድም” የሚለው ደግሞ በእምነቱ ደካማ የሆነውን ይወክላል።

Romans 14:22

ያለህ እምነት
ይህ የሚያመለክተው ስለ መብልና መጠጥ ያላቸውን እምነት ነው።

አንተ ... ራስህ
ነጠላ ቁጥር ነው። ጳውሎስ መልዕክቱን የሚያስተላልፈው ለአማኞቹ ነው ስለዚህ ይህንን በብዙ ቁጥር መተርጎም ይቻላል። (የሁለተኛ መደብ ቅርጾች የሚለውን ይመልከቱ)

ራሱ አምኖ በተቀበለው ነገር በራሱ ላይ የማይፈርድ ሰው እርሱ የተባረከ ነው
“ለማድረግ ወስነው በሚያደርጉት ነገር ወንጀለኝነት የማይሰማቸው ሰዎች የተባረኩ ናቸው”

የሚጠራጠር ግን ቢበላ እርሱ ይኮነናል
ይህን በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ሰው የሆነ ምግብ መብላት ትክክል መሆኑን እርግጠኛ ሳይሆን ያንን ምግብ ቢበላ እግዚአብሔር ያ ሰው ስህትተ ፈጽሟል ይለዋል” ወይም “አንድን ምግብ መብላት ትክክል ይሁን አይሁን እርግጠኛ ያልሆነ ሰው፣ ነገር ግን ምግቡን ቢበላው ያ ምግቡን የበላው ሰው መጥፎ ሕሊና ይኖረዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ምክንያቱም በእምነት አይደለምና
“በእምነት ያልሆነ” ማንኛውም ነገር እግዚአብሔር እንድናደርገው የማይፈልገው ነገር ነው። ሙሉ ትርጉሙን በግልጽ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር እንዲበላ የማይፈልገው ነገር መሆኑን አውቆ ያመነበትን ነገር በልቷልና እግዚአብሔር ስህተት ነህ ይለዋል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእምነት ያልሆነ ነገር ሁሉ ኃጢአት ነው
“ከእምነት ያልሆነ” ነገር ሁሉ ማለት እግዚአብሔር እንድታደርጉት የማይፈልገው ነገር ማለት ነው። እዚህ ላይ ሙሉ ትርጉሙን በግልጽ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር እንዳደርገው አይፈልግም ብላችሁ የምታምኑትን ነገር ብታደርጉ ኃጢአትን እየሰራችሁ ነው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 15

1 እንግዲህ ብርቱዎች የሆንን እኛ የደካሞቹን ድካም ልንሸከም እንጂ ራሳችንን ብቻ ልናስደስት አይገባም። 2 መልካም ነውና እንድናንጸው እያንዳንዳችን
ባልንጀራችንን ደስ እናሰኝ። 3 ምክንያቱም ክርስቶስ እንኳን እራሱን ደስ አላሰኘም። ይልቁንም «አንተን የሰደቡበት ስድብ በኔም ላይ ደረሰ» ተብሎ እንደተጻፈው
ነው። 4 አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ በትዕግስትና በቅዱሳት መጽሀፍት እየተበረታታን ድፍረት እንድናገኝ ለትምህርታችን ተጽፎአል። 5 እንግዲህ የትዕግስትና
የመጽናናት አምላክ ለእርስ በእርሳችሁ በክርስቶስ አንድ ልብ ይስጣችሁ። 6 በአንድ ልብና በአንድ አፍ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክና አባት
እንድታመሰግኑ ይህን ያድርግ። 7 ልክ ክርስቶስ እንደተቀበላችሁ ለእግዚአብሔር ክብር እርስ በእርሳችሁ ተቀባበሉ። 8 ስለ እግዚአብሔር እውነት ክርስቶስ
የመገረዝ አገልጋይ ሆነ እላለሁ። ይህን ያደረገው ለአባቶች የተሰጠውን ተስፋ ሊያጸና 9 አህዛብ ደግሞ ስለምህረቱ እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ ነው። ይህም
«በአህዛብ መካከል አመሰግንሀለሁ፣ለስምህም እዘምራለሁ» ተብሎ በተጻፈው መሰረት ነው። 10 እንደገናም ደግሞ «እናንተ አህዛብ ከህዝቡ ጋር ደስ
ይበላችሁ» ይላል። 11 ደግሞም እንደገና «አህዛብ ሁላችሁ እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔርን ያመስግኑት» ይላል። 12 ኢሳያስ ደግሞ
«አህዛብን ሊገዛ የሚነሳ የእሴይ ሥር ይወጣል፥ አህዛብም በእርሱ ይመካሉ።» ይላል። 13 በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በተስፋ ትሞሉ ዘንድ የተስፋ አምላክ
በማመናችሁ ምክንያት በደስታና በሰላም ሁሉ ይሙላችሁ። 14 ወንድሞቼ ሆይ እናንተ ራሳችሁ በመልካምነትና በእውቀት እንደተሞላችሁ እርስ በእርሳችሁም
ልትማማሩ እንደምትችሉ ስለእናንተ ተረድቻለሁ። 15 ነገር ግን ከእግዚአብሔር በተሰጠኝ ስጦታ ስለአንድ ጉዳይ ላሳስባችሁ በድፍረት ጽፌላችኋለሁ። 16
ይኸም ስጦታ የእግዚአብሔርን ወንጌልን እንደ ካህን እንዳቀርብላቸው ወደ አህዛብ የተላክሁ የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ መሆኔ ነው። ይህን ማድረግ ያለብኝ
የአህዛብ መስዋዕት ተቀባይነት እንዲያገኝና በመንፈስ ቅዱስ ለእግዚአብሔር እንዲቀርብ ነው። 17 እንግዲህ ደስታዬ በክርስቶስ ኢየሱስና ከእግዚአብሔር
በሚሆኑ ነገሮች ነው። 18 አህዛብ ወደ መታዘዝ እንዲመጡ ክርስቶስ በእኔ ካከናወነው ነገር በቀር ስለምንም ነገር ለመናገር አልደፍርም። እነዚህም ነገሮች
በቃልና በሥራ 19 በምልክትና በድንቆች ኃይል በመንፈስ ቅዱስም ኃይል የተከናወኑ ናቸው። ይህም በኢየሩሳሌምና በዙሪያዋ እስከ አልዋሪቆን ድርስ የክርስቶስን
ወንጌል በሙላት እንዳደርስ ነበር። 20 በዚህ መንገድ ፍላጎቴ ወንጌልን መስበክ ነው፥ ነግር ግን የምሰብከው በሌላው ሰው መሠረት ላይ እንዳልገነባ የክርስቶስ
ስም በሚታወቅበት አካባቢ አይደለም። 21 ይህም «ስለእርሱ ያልተነገራቸው ያዩታል፥ ያልሰሙም ያስተውላሉ» ተብሎ የተጻፈው እንዲፈጸም ነው። 22
ስለዚህም ወደ እናንተ እንዳልመጣ ብዙ ጊዜ እንቅፋት ገጠመኝ። 23 አሁን ግን በዚህ ባሉ ክልሎች እንብዛም የምሰራው ነገር የለኝም ወደ እናንተም ለመምጣት
ለበርካታ ዓመታት ስናፍቅ ነበር። 24 ስለሆነም ወደ እስፔን በምሄድበት ጊዜ ከእናንተ ጋር ደስ የሚያሰኝ ጥቂት ጊዜ አሳልፌ በጉዞዬ እንድትረዱኝ ወደናንተ ጎራ
ብዬ እንደማያችሁ ተስፋ አደርጋለሁ። 25 አሁን ግን በጌታ ያመኑትን ለማገልገል ወደ ኢየሩሳሌም እሄዳለሁ። 26 ምክንያቱም በመቄዶኒያና በአካይያ ያሉ
አማኞች በኢየሩሳሌም ባሉ አማኞች መካከል ለሚገኙ ድሆች የተወሰነ ድጋፍ ለማድረግ በደስታ ፈቅደዋል። 27 አዎ በደስታ ሊያደርጉት መልካም ፈቃዳቸው
ነበር፥ ለነገሩ የእነርሱ ባለዕዳዎች ናችው። አህዛብ ከእነርሱ መንፈሳዊ ነገርን ከተካፈሉ እነርሱ ደግሞ በቁሳዊ ነገር ሊያገለግሏቸው ይገባል። 28 ስለዚህም ይህን
ስጦታውን የማድረስ ተግባሬን ከፈጸምኩ በኋላ በእናንተ በኩል ወደ እስፔን አልፋለሁ። 29 ወደ እናንተ ስመጣ በክርስቶስ በረከት ተሞልቼ እንደምመጣ
አውቃለሁ። 30 እንግዲህ ወንድሞቼ ሆይ ስለኔ ወደ እግዚአብሔር በጸሎት አብራችሁኝ እንድትጋደሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ፣ በመንፈስ ቅዱስም ፍቅር
እለምናችኋለሁ። 31 በይሁዳ ካሉ የማይታዘዙ ሰዎች እንድጠበቅ አገልግሎቴም በኢየሩሳሌም ባሉ አማኞች ተቀባይነት እንዲያገኝ ጸልዩ። 32 በእግዚአብሔር
ፈቃድ ወደ እናንተ በደስታ መጥቼ አብሬያችሁ እንዳርፍ ጸልዩ። 33 የሠላም አምላክ ከሁላችሁም ጋር ይሁን። አሜን።

Romans 15:1

አያያዥ ሀሳብ፦
እዚህ ላይ ጳውሎስ ክርስቶስ እንዴት እንደኖረ በማስታወስ፣ አማኞች ለሌሎች ሊኖሩ እንደሚገባ የሚናገረውን ይህን ክፍል ይደመድመዋል።

እነሆ
ይህን ቃል በቋንቋችሁ ውስጥ በሙግት ውስጥ አዲስ ሃሳብን በሚያስተዋውቅ ቃል ተርጉሙት።

ብርቱዎች የሆንን እኛ
እዚህ ላይ “ብርቱ” የሚለው በእምነታቸው ብርቱ የሆኑ ሰዎችን ያመለክታል። እነርሱም እግዚአብሔር ምንም ዓይነት ምግብን እንዲበሉ እንደፈቀደ ያምናሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “በእምነታችን ብርቱ የሆንን እኛ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 15:3

ተብሎ እንደተጻፈው
እዚህ ላይ ጳውሎስ፣ ክርስቶስ (መሲሑ) ለእግዚአብሔር የሚናገርበትን አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ያነሳል። ይህን በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፦ “በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ መሲሑ ለእግዚአብሔር እንዲህ ሲል ተናግሯል …” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተን የሰደቡህ ሰዎች ስድብ እኔ ላይ ወደቀብኝ
እግዚአብሔርን የሰደቡት ሰዎች ስድብ በክርስቶስ ላይ ወደቀ።

አስቀድሞ የተጻፈው በሙሉ ለእኛ ትምህርት ተጽፏልና
ይህን በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፦ “ባለፉት ጊዜያት፣ ነቢያት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የጻፉት ሁሉም ነገር እኛን ለማስተማር የተጻፈ ነውና” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የኛ… እኛ
ጳውሎስ አንባቢዎቹንና ሌሎች አማኞችን ያካትታል። (አካታች “እኛ” የሚለውን ይመልከቱ)

ቃሉ በሚሰጠን ትዕግስትና ማበረታታት ተስፋ እንዲኖረን
እዚህ ላይ “ተስፋ እንዲኖረን” የሚለው አማኞች እግዚአብሔር የገባውን ቃል እንደሚፈጽም ማወቃቸውን ያመለክታል። የዚህን ትርጉም በትርጉምህ ውስጥ በግልጽ ማስቀመጥ ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፦ “በዚህ መንገድ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የገባውን ቃል በሙሉ እንደሚያደርግልን እያወቅን በተስፋ እንድንጠባበቅ ያበረታናል።” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 15:8

እላለሁ
ይህ ጳውሎስን ይወክላል (“እኔ” የሚለው አመልካች ጳውሎስን ይወክላል)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ክርስቶስ የመገረዝ አገልጋይ ሆኗል
እዚህ ላይ “መገረዝ” የሚለው አይሁድን የሚወክል ምትክ ስም ነው። ይህን በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፦ “ኢየሱስ ክርስቶስ የአይሁድ አገልጋይ ሆነ” (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የተስፋ ቃሉን ያጸና ዘንድ .... አሕዛብም እግዚአብሔርን ስለ ምሕረቱ እንዲያከብሩት
እነዚህ ክርስቶስ የመገረዝ አገልጋይ የሆነበት ሁለት ዓላማዎች ወይም ምክንያቶች ናቸው። አማራጭ ትርጉም፦ “የተስፋ ቃሉን ያረጋግጥ ዘንድ ... አሕዛብም ስለ ምሕረቱ እግዚአብሔርን እንዲያከብሩት”

ለአባቶች የሰጠውን የተስፋ ቃል
እዚህ ላይ “አባቶች” የሚለው የአይሑድ ሕዝቦችን አባቶች ያመለክታል። ይህንን በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ለአይሁድ ሕዝቦች አባቶች የሰጠውን የተስፋ ቃል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ተብሎ እንደተጻፈ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፦ “አንድ ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንዲህ ብሎ እንደጻፈው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ለስምህም ምስጋናን እዘምራለሁ
እዚህ ላይ “ለስምህ” የሚለው እግዚአብሔርን የሚወክል ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ለአንተ ምስጋናን እዘምራለሁ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 15:10

ደግሞም እንዲህ ይላል
“ደግሞም መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል”

ከሕዝቡ ጋር
ይህ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ያመለከታል። ይህን በትርጉሙ ውስጥ ግልጽ አድርጎ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አመስግኑ
“ጌታን አመስግኑ”

Romans 15:12

የእሴይ ሥር
እሴይ የንጉሥ ዳዊት የስጋ አባት ነበር። አማራጭ ትርጉም፦ “የእሴይ ዘር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ አሕዛብ ተስፋ ይኖራቸዋል
እዚህ ላይ “እርሱ” የሚለው የእሴይን ልጅ የሆነውን መሲሑን ያመለክታል። አይሁድ ያልሆኑ ሰዎችም ቃሉን እንዲፈጽም እርሱን ያምኑታል። አማራጭ ትርጉም፦ “አይሁድ ያልሆኑትም ቃል የገባውን እንዲፈጽም እርሱን ያምኑታል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 15:13

በደስታና በሰላም ይሙላችሁ
ጳውሎስ እዚህ ላይ ለንግግሩ አጽንዖት ለመስጠት ግነትን ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፦ “በታላቅ ደስታና ሰላም ይሙላችሁ” (ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 15:14

አያያዥ ሀሳብ፦
ጳውሎስ በሮም ያሉ አማኞች እግዚአብሔር እርሱን አሕዛብን ለመድረስ እንደመረጠው ያስታውሳቸዋል።

እኔ ራሴ ወንድሞቼ ሆይ ... ስለ እናንተ ተረድቻለሁ
ጳውሎስ በሮም ያሉት አማኞች አንዱ ሌላውን በመልካም ባሕሪያቸው እያከበሩ እንደሆነ አርግጠኛ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔ ራሴ እናንተ በሌሎች ዘንድ በመልካም አካሄድ እንደሄዳችሁ እርግጠኛ ነኝ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ወንድሞች
ይህ ማለት ሌሎች አማኞችን ያመለክታል፣ ወንዶችና ሴቶችንም ያካትታል።

በእውቀት ተሞልታችሁ
ጳውሎስ እዚህ ላይ ለንግግሩ አጽንዖት ለመስጠት ግነትን ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔርን ለመከተል በሚበቃ እውቀት ተሞልታችሁ” (ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እርስ በርሳችሁም ልትመካከሩ መቻላችሁ
እዚህ ላይ “ልትመካከሩ” የሚለው ማስተማርን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እርስ በርስ አንዱ ሌላውን ማስተማር መቻላችሁ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 15:15

በእግዚአብሔር የተሰጠኝ ጸጋ
ጳውሎስ ጸጋን እግዚአብሔር በአካል እንደሰጠው የሚዳሰስ ስጦታ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። ጳውሎስ ኢየሱስን ለመከተል ከመወሰኑ በፊት ብዙ አማኞችን ያሰቃየ ቢሆንም እግዚአብሔር ሐዋርያ እንዲሆን ሾሞታል። ይህን በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የአሕዛብ መስዋዕት ተቀባይ ይሆን ዘንድ
ጳውሎስ ወንጌል የመስበክ ስራውን ልክ እርሱ ካህን እንደሆነና ለእግዚአብሔር መስዋዕትን እንደሚያቀርብ አድርጎ ይስለዋል። አማራጭ ትርጉም፦ “አሕዛብ እግዚአብሔርን ሲታዝዙ እርሱን እንዲያስደስቱት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 15:17

ምንም ነገር ልናገር አልደፍርምና ... እነዚህ ነገሮች በሙሉ በቃልና በስራ፣ በምልክትና በድንቅ ነገር ኃይል፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይልም ተሰርተዋል
እዚህ ላይ ያለውን መንትያ አሉታዊ መግለጫ በአዎንታዊ መግለጫ መተርጎም ይቻላል። እዚህ ላይ “እነዚህ ነገሮች” የሚለው ክርስቶስ በጳውሎስ በኩል ያሳካቸውን ነገሮች ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “አሕዛብ እንዲታዘዙ፣ ክርስቶስ ብቻ በእኔ በኩል በቃሌና በስራዬ ፣ በምልክትና በድንቅ ነገር ኃይል በመንፈስ ቅዱስም ኃይል ያደረገውን ነገር እናገራለሁ” (መንትያ አሉታዎች እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ምልክትና ድንቅ ነገር
እነዚህ ሁለት ነገሮች ተመሳሳይ ትርጉምን የያዙ ሲሆን የተለያዩ ተዓምራትን ያመለክታሉ። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህ ከኢየሩሳሌም እስከ እልዋሪቆን ድረስ እየዞርኩ
ይህ ከኢየሩሳሌም ከተማ ከጣልያን ቅርብ ርቀት ላይ እስካለችው እስከ እልዋሪቆን ግዛት ድረስ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Romans 15:20

በዚህ መንገድ ፍላጎቴ ወንጌልን ማወጅ ነበር፣ ነገር ግን ክርስቶስ በሚታወቅበት ቦታ አይደለም
ጳውሎስ ወንጌልን መስበክ የሚፈልገው ስለ ክርስቶስ በጭራሽ ሰምተው ለማያውቁ ሰዎች ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በዚህም ምክንያት ሰዎች ስለ ክርስቶስ ሰምተው በማያውቁበት ቦታ የምስራቹን መስበክ እፈልጋለሁ።” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በሌላ ሰው መሰረት ላይ እንዳልገነባ
ጳውሎስ አገልግሎቱ በመሰረት ላይ ቤትን የመገንባት ዓይነት እንደሆነ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሌላ ሰው የጀመረውን ስራ መቀጠል እንዳይሆንብኝ። ሌላ ሰው በሰራው መሰረት ላይ ቤትን እንደሚገነባ ሰው መሆን አልፈልግም።” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ተብሎ እንደተጻፈ
እዚህ ላይ ጳውሎስ ኢሳይያስ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የጻፈውን ያነሳል። ይህን በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ፣ እንዲሁም ትርጉሙን በግልጽ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እየተከሰተ ያለው ኢሳይያስ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንደጻፈው ነው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ እርሱ ምንም ዜና ላልደረሳቸው
እዚህ ላይ ጳውሎስ “ዜናው” ወይም የክርስቶስ መልዕክት ሕያው እንደሆነና በራሱ እንደሚንቀሳቀስ አድርጎ ስሎታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ማንም ሰው ስለ እርሱ ዜናውን ላልነገራቸው ሰዎች” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 15:22

አያያዥ ሀሳብ፡-
ጳውሎስ በሮም ላሉ አማኞች እነርሱን ለመጎብኘት ስላለው የግል ሃሳብ ይነግራቸዋል፣ እንዲሁም አማኞቹን እንዲጸልዩ ይነግራቸዋል።

እንዲሁም ተከለከልሁ
ይህን በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፡- “ከለከሉኝ” ወይም “ሕዝቡ ከለከሉኝ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚህ በኋላ በነዚህ ቦታዎች ስፍራ የለኝም
ጳውሎስ እዚህ ላይ ለማለት የፈለገው በነዚህ ስፍራዎች ሰዎች ስለ ክርስቶስ ያልሰሙበት ቦታ የለም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በእነዚህ ቦታዎች ሰዎች ስለ ክርስቶስ ያልሰሙበት ስፍራ የለም” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 15:24

ስፔን
ይህ ጳውሎስ ሊጎበኘው የሚፈልግ ከሮም በስተሜን የሚገኝ የሮማ ግዛት ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል እና የማይታወቁትን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

ሳልፍ
“በሮም ሳልፍ” ወይም “በመንገድ ላይ ሳለሁ”

በመንገዴም እንድትረዱኝ
እዚህ ላይ ጳውሎስ ማለት የፈለገው በሮም ያሉት አማኞች እርሱ ወደ ስፔን በሚያደርገው ጉዞ የገንዘብ ድጋፍ እንዲያደርጉለት እንደሚፈልግ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በጉዞዬ እንድትረዱኝ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በአብሮነታችሁ ተደስቼ
“ከእናንተ ጋር ጊዜ በማሳለፌ ተደስቼ” ወይም “እናንተን በመጎብኘቴ ተደስቼ”

Romans 15:26

መቄዶንያና አካይያ ... ወድደዋልና
እዚህ ላይ “መቄዶንያ” እና “አካይያ” የሚሉት ቃላት በዚያ አካባቢ የሚኖሩትን ሕዝቦች የሚወክሉ ወካይ ስሞች ናቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “በመቄዶንያና በአካይያ ግዛቶች የሚኖሩ አማኞች ... ወድደዋልና” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

በእርግጥም ወድደዋል
“በመቄዶንያና በአካይያ የሚገኙ አማኞች (በመርዳታቸው) ደስተኞች ነበሩ”

Romans 15:28

የተሰበሰበው እንደደረሳቸው ካረጋገጥኩ በኋላ
ጳውሎስ እዚህ ላይ ወደ ኢየሩሳሌም እየወሰደ ያለውን የተሰበሰበውን ገንዘብ ልክ ለእነርሱ እንደተሰበሰበ እንደ ፍራፍሬ አድርጎ ይስለዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይህንን ስጦታ ለእነርሱ በአግባቡ አስረክቤ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እናንተ ስመጣ በክርስቶስ ሙላትና በረከት እንደምመጣ አውቃለሁ
ይህ ሃረግ ክርስቶስ ጳውሎስንና የሮሜ አማኞችን ይባርካል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ስጎበኛችሁም፣ ክርስቶስ አትረፍርፎ እንደሚባርከን አውቃለሁ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 15:30

እነሆ
ይህ ጳውሎስ ይተማመንባቸው ስለነበረው ስለ መልካም ነገሮች (ሮሜ 15:29) ማውራት አቁሞ ሊጋፈጣቸው ስላሉት ነገሮች ማውራት መጀመሩን የሚያሳይ ነው። ቋንቋችሁ ይሄንን የማሳያ መንገድ ካለው እዚህ ላይ ጥቅም ላይ አውሉት።

አነሳሳችኋለሁ
“አበረታታችኋለሁ”

ወንድሞች
ይህ ሌሎች ክርስቲያኖችን ያመለክታል፣ ሴቶችንና ወንዶችን ያካትታል

እንድትተጉ
“በርትታችሁ እንድትሰሩ” ወይም “እንድትታገሉ”

ከማይታዘዙት እድን ዘንድ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከማይታዘዙት እግዚአብሔር ያድነኝ ዘንድ” ወይም “የማይታዘዙት እንዳይጎዱኝ እግዚአብሔር ከእነርሱ ያድነኝ ዘንድ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በኢየሩሳሌም የሚኖረኝ አገልግሎት በአማኞች ዘንድ ተቀባይ እንዲሆን
እዚህ ላይ ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ያሉ አማኞች ከመቄዶንያና ከአካይያ አማኞች ይዞ የመጣውን ገንዘብ በደስታ እንዲቀበሉት ያለውን ፍላጎት ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፡- “የምወስድላቸውን ገንዘብ በኢየሩሳሌም ያሉ አማኞች በደስታ እንዲቀበሉኝ ጸልዩ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 15:33

ሰላም እንዲኖረን እንዲያደርግ እጸልያለሁ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰላም አምላክ
“የሰላም አምላክ” ማለት አማኞች ውስጣዊ ሰላምን እንዲኖራቸው የሚያደርግ አምላክ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ሁላችንም የውስጥ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **16**

1 በክንክራኦስ ያለችው ቤተክርስቲያን አገልጋይ የሆነችውን እህታችንን ፌበንን **2** በጌታ እንድትቀበሏት አደራ ሰጥቻችኋለሁ። ይህንንም ከአማኞች በሚጠበቅ መልኩ አድርጉት፣ የእናንተን እርዳታ በምትፈልግበት በማንኛውም ነገር ከጎኗ ቁሙ። ምክንያቱም እርሷ እራሷ እኔን ጨምሮ ብዙዎችን የምትረዳ ነች። **3** በክርስቶስ የአገልግሎቴ አጋሮች ለሆኑት ለአቂላና ለጵርስቅላ ሠላምታ አቅርቡልኝ፥ **4** እነርሱ ስለእኔ ህይወታቸውን ለአደጋ ያጋለጡ ናቸው። አመሰግናቸዋለሁ፥ እኔ ብቻ ሳልሆን የአህዛብ አብያተክርስቲያናትም ሁሉ ያመስግኗቸዋል። **5** በቤታቸው ላለች ቤተክርስቲያን ሠላምታ አቅርቡልኝ። በእስያ ለክርስቶስ የመጀምሪያው ፍሬዬ የሆነውን የምወደውን አጤኔጦንን ሠላም በሉልኝ። **6** ለእናንተ በሥራ ለደከመችው ለማሪያ ሠላምታ አቅርቡልኝ። **7** ዘመዶቼ ለሆኑትና አብረውኝ ታስረው ለነበሩት ለአንዲራኒቆንና ለዩልያን ሠላምታ አቅርቡልኝ። እነርሱ በክርስቶስ በመሆን የቀደሙኝና ከሐዋሪያት መካከል በመልካም የተመሰከረላቸው ናቸው። **8** በጌታ ለምወደው ለጵልያጦን ሠላምታ አቅርቡልኝ። **9** በክርስቶስ አብሮን የሚሠራውን ኢሩባኖንና የተወደደውን ስንጣክን ሠላም በሉልኝ። **10** በክርስቶስ መሆኑ ለተመሰከረለት ለኤጤሌን ሠላምታ አቅርቡልኝ። የአርስጣባሉን ቤተሰቦች ሠላም በሉልኝ። **11** ለዘመዴ ለሄሮድዮና ሠላምታ አቅርቡልኝ። ከንርቂሱ ቤተሰቦች መካከል በጌታ ላመኑት ሠላምታ አቅርቡልኝ። **12** በጌታ ሥራ ለሚደክሙት ለፕሮፊሞንና ለጢሮፊሞስ ሠላምታ አቅርቡልኝ። በጌታ ሥራ በብዙ የምትደክመውን የተወደደች ጠርሲዳን ሠላም በሉልኝ። **13** በጌታ ልተመረጠው ለሩፎን እና ለእርሱም ለእኔም እናት ለሆነችው ለእናቱ ሠላምታ አቅርቡልኝ። **14** አስቀራጡንን፥ አፍለሶንጳን፥ ሄሮሜንን፥ ጳጥሮባን፥ ሄርማንን እንዲሁም አብረዋቸው ያሉትን ወንድምች ሠላም በሉልኝ። **15** ለፍሊጎን፥ ለዩልያ፥ ለኔርያ ለእህቱም ለአልንጦን አብረዋቸውም ላሉት በጌታ ላመኑት ሁሉ ሠላምታ አቅርቡልኝ። **16** በተቀደሰ መሳሳም ሠላምታ ተለዋወጡ። የክርስቶስ አብያተክርስቲያናት ሁሉ ሠላምታ ያቀርቡላችኋል። **17** ወንድሞቼ ሆይ በመካከላችሁ የመለያየትንና የመሰናክል ምክንያት ስለሆኑት ሰዎች እንድታስቡ እለምናችኋለሁ። እነርሱ እናንተ ከተማራችሁት የወጣ ነገር ያስተምራሉና ከእነርሱ ተለዩ። **18** እንደነዚህ ያሉ ሰዎች የገዛ ሆዳቸውን እንጂ ክርስቶስን ጌታችንን አያገለግሉም። በለስላሳና በሚያባብል ቃላቸው የየዋሀንን ልብ ያታልላሉ። **19** የመታዘዛችሁ ምሳሌነታችሁ ለብዙዎች ደርሷል። ስለዚህም በእናንተ ደስ ይለኛል፥ ነገር ግን ለመልካም ነገር ጥበበኞች ለክፉ ነገር ደግሞ የዋሀን እንድትሆኑ እፈልጋለሁ። **20** የሠላም አምላክ ሠይጣንን በፍጥነት ከእግራችሁ በታች ይቀጠቅጠዋል። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሠላም ከሁላችሁ ጋር ይሁን። **21** የሥራ አጋሬ ጢሞቴዎስና ዘመዶቼ ለቂዮስ፥ኢያሶንና ሱሲጴጥሮስ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። **22** ይህን ደብዳቤ በእጄ የጻፍኩ እኔ ጤርጥዮስ ሰላምታ አቀርብላችኋለሁ። **23** እኔና ቤተክርስቲያንን በሙሉ በቤቱ ያስተናገደን ጋይዮስ ሰላምታ ያቀርብላችኋል። የከተማው ገንዘብ ያዥ ኤርስጦስ ወንድማችንም ቁአስጥሮስ ሰላም ብለዋችኋል። **25** እንግዲህ በወንጌሌ በኢየሱስ ክርስቶስም ስብከት ከቀድሞ ዘመን ጀምሮ ተሰውሮ በነበረውና **26** አሁን ግን በዘላለማዊ አምላክ ትዕዛዝ በአህዛብ ሁሉ መካከል በተገለጠውና የእምነት መታዘዝ እንዲገኝ በትንቢታዊ መጽሀፍት አማካኝነት በታወቀው ሚስጥር መሠረት ሊያቆማችሁ ለሚችለው **27** ብቻውን ጥበበኛ አምላክ ለሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ለዘላለም ክብር ይሁን። አሜን።

Romans 16:1

አያያዥ ሀሳብ፦
ከዚህ በኋላ ጳውሎስ በሮሜ ያሉት አማኞችን ብዙዎቹን ስማቸውን እየጠራ ሰላምታን ያቀርባል።

ፌበንን አደራ እላችኋለሁ
“ፌበንን እንድታከብሯት እፈልጋለሁ”

ፌበን
ይህ የአንዲት ሴት ስም ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል እና የማይታወቁትን ተርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

እኅታችንን
“እኅታችንን” የሚለው ቃል ውስጥ ያለው የባለቤት አመልካች “እኛ” ጳውሎስንና ሌሎች ሁሉንም አማኞች ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በክርስቶስ እህታችን” (አካታች “እኛ” የሚለውን ይመልከቱ)

ክንክራኦስ
ይህ በግሪክ የሚገኝ የወደብ ከተማ ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል እና የማይታወቁትን ተርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

በጌታ ስም ተቀበሏት
ጳውሎስ በሮሜ የሚገኙ አማኞች ፌበንን እንደ አጋር አማኝ እንዲቀበሏት ያበረታታቸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ “ተቀበሏት፣ ምክንያቱም ሁላችንም የጌታ ነንና“ (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለቅዱሳን በሚመጥን መንገድ
“አማኞች ሌሎች አማኞችን መቀበል ባለባቸው መንገድ”

አጠገቧ ቁሙ
ጳውሎስ የሮሜን አማኞች ለፌበን የሚያስፈልጋትን ነገር በሙሉ እንዲሰጧት ያበረታታቸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ “የሚያስፈልጋትን ሁሉ በመስጠት እርዷት” (ለስላሴ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለብዙዎች ለእኔም ጨምሮ ረዳት ነበረችና
“ብዙ ሰዎችን ረድታለች፣ እንዲሁም እኔንም ረድታኛለች”

Romans 16:3

ጵርስቅላ እና አቂላ
ጵርስቅላ የአቂላ ሚስት ነበረች። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አብረውኝ ለሚሰሩ
ከጳውሎስ ጋር “አብረው የሚሰሩት” ለሰዎች ስለ ኢየሱስ የሚሰብኩ ሰዎች ናቸው። አማራጭ ትርጉም፦ “ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ለሰዎች በመንገር አብረውኝ የሚሰሩ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 16:6

ማርያ
ይህ የአንዲት ሴት ስም ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

አንዲራኒቆን ... ጵልያጦን
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ዩልያን
ይህ ሊሆን የሚችለው 1. ዩልያ፥ የሴት ስም ወይም 2. ዩልያን፥ የወንድ ስም (ይህ የወንድ ስም የመሆን ዕድሉ ዝቅተኛ ነው) (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ከሐዋርያት ስመ ጥር የሆኑ
ይህን በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፡- “ሐዋርያቱ በደንብ ያውቋቸው የነበሩ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በጌታ ለምወደው
“የተወደደው ጓደኛዬ እንዲሁም አጋር አማኝ”

Romans 16:9

አፉባኖን ... ስንጥካን ... ኤጤሌን ... አርስጣባሉ ... ሄሮድዮና ... ንቀርሱ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

በክርስቶስ እምነቱ ለተረጋገጠለት
“የተረጋገጠለት” የሚለው ቃል ተፈትኖ ትክክለኛ መሆኑ የተረጋገጠን ሰው ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክርስቶስ እምነቱን ላረጋገጠለት”

በጌታ ላሉት
ይህ በኢየሱስ የሚታመኑን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “አማኞች የሆኑትን” ወይም “የጌታ የሆኑትን” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 16:12

ፕሮፊሞና ... ጢሮፊሞሳ ... ጠርሲዳ
እነዚህ የሴቶች ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል እና የማይታወቁትን ተርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ሩፎን ... አስቀሪጦን ... አፍለሶንጳ ... ሄሮሜን ... ጳጥሮባ ... ሄርማን
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል እና የማይታወቁትን ተርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

በጌታ የተመረጡ
ይህን በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፡- “ጌታ የመረጣቸው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 16:15

ፍሌጎን ... ኔርያ ... አልጦን
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል እና የማይታወቁትን ተርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ዩልያ
ይህ የአንዲት ሴት ስም ነው። ዩልያ የፍሌጎን ሚስት ልትሆን ትችላለች። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል እና የማይታወቁትን ተርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

የተቀደሰ አሳሳም
ለሌሎች አማኞች ፍቅርን የመግለጫ መንገድ ነው

የክርስቶስ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሰላምታን ያቀርቡላችኋል።
ጳውሎስ እዚህ ላይ በጠቅላላው ስለ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያናት ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “በዚህ አካባቢ ያሉ አብያተክርስቲያናት ውስጥ ያሉ አማኞች በሙሉ ሰላምታን ያቀርቡላችኋል” (ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 16:17

አያያዥ ሀሳብ፦
ጳውሎስ ለአማኞች ስለ አንድነትና ለእግዚአብሔር ስለመኖር አንድ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል።

ወንድሞች
ይህ ሌሎች ክርስቲያኖችን ሲያመለክት፣ ወንዶችና ሴቶችን ያካትታል

እንድታስቡ
“እንድትጠነቀቁ”

መከፋፈልንና ማሰናከያን የሚያደርጉ
ይህ የሚያመለክተው ክርክርን የሚፈጥሩ ሰዎችንና፣ ሌሎችን በኢየሱስ እንዳያምኑ ምክንያት የሚሆኑትን ሰዎች ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አማኞች እርስ በርስ እንዲከራከሩና በእግዚአብሔር እምነት እንዳይኖራቸው የሚያደርጉ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከተማራችሁት ትምህርት ወጥተው ሄደዋል
“እናንተ ከተማራችሁት እውነት ጋር የማይስማማ ትምህርት ያስተምራሉ”

ከእነርሱ ራቁ
“ራቁ” ማለት “አትስሟቸው” የሚለውን ትርጉም የያዘ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አታዳምጧቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለገዛ ሆዳቸው እንጂ
“ያገለግላሉ” የሚለው ቃል ከላይ ካለ ሐረግ አገባብ ትርጉሙን መረዳት ይቻላል። ይህ በተለይ አረፍተ ሃሳብ መገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይልቁንም የራሳችውን ሆድ ነው የሚያገለግሉት” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን ለገዛ ሆዳቸው
“ሆድ” የሚለው ቃል የአካላዊ ፍላጎቶችን የሚያሳይ ምትክ ስም ነው። የገዛ ሆዳቸውን ማገልገል ማለት ፍላጎቶቻቸውን ማግኘት ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን የራሳቸውን ራስ ወዳድ የሆኑ ፍላጎቶች ብቻ ማግኘት ነው የሚፈልጉት” (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በለስላሳና መልካም ንግግራቸው
“ለስላሳ” እና “መልካም” የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ጳውሎስ እነዚህ ሰዎች እንዴት አማኞችን እያታለሉ እንደሆነ አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፡- “መልካምና እውነት የሚመስሉ ነገሮችን በመናገር” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

የንጹሃንን ልብ ያታልላሉ
እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው የአንድን ሰው አእምሮ ወይም ውስጣዊ ማንነት የሚወክል ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ንጹሃን አማኞችን ያታልላሉ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ንጹሃን
ይህ ገር፣ ብዙ የማያውቁና የዋህ አማኞችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በየዋህነት የሚያምኗቸውን” ወይም “እነዚህ አስተማሪዎች እያታለሏቸው እንደሆነ የማያውቁትን”

Romans 16:19

የመታዘዛችሁ አርአያነት ለሁሉም ደርሷልና
እዚህ ላይ ጳውሎ ስለ ሮሜ አማኞች ታዛዥነት ስናገር ታዛዥነታቸው ሰው እንደሆነና ወደ ሌሎች ሰዎች የሚሄድ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ኢየሱስን እንዴት እንደምትታዘዙ ሁሉም ሰው ሰምቷልና” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰላም አምላክ ፈጥኖ ሰይጣንን ከእግራችሁ ስር ይቀጠቅጠዋል
“ከእግራችሁ ስር ይቀጠቅጠዋል” የሚለው ሐረግ በጠላት ላይ ያለን ሙሉ ድል መንሳት ይወክላል። እዚህ ላይ ጳውሎስ በሰይጣን ላይ ያለውን ድል የሮሜ አማኞች ጠላቶቻቸውን በእግራቸው ስር እንደሚቀጠቅጡ አድርጎ ይስለዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ፈጥኖም እግዚአብሔር ሰላምና በጠላትም ላይ ፍጹም ድልን ይሰጣችኋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉ ነገርም ለሆነው ንጹህ እንድትሆኑ
“ክፋትን ነገሮች የማትሰሩ እንድትሆኑ”

Romans 16:21

አያያዥ ሀሳብ፦
ጳውሎስ ከእርሱ ጋር ካሉት አማኞች ሰላምታን ያቀርባል።

ሉቂዮስ ኢያሶን ሱሲጴጥሮስ ጤርጥዮስ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ይህን መልእክት የጻፍኩ እኔ ጤርጥዮስ
ጤርጥዮስ ጳውሎስ የሚናገረውን በጽሑፍ ያሰፍር የነበረው ሰው ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 16:23

ጋይዮስ ኤርስጦስ ቁአስጥሮስ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

አስተናጋጅ
ይህ ጳውሎስና ሌሎች አማኞች ለአምልኮ የሚሰበሰቡበት ቤት ባለቤት የሆነውን ሰው ጋይዮስን ያመለክታል።

የግምጃ ቤት ሹም
ይህ ሰው የአንድ ቡድን ገንዘብ የሚይዝ ሰው ነው።

Romans 16:25

አያያዥ ሀሳብ፦
ጳውሎስ መልዕክቱን በበረከት ጸሎት ይዘጋል።

እንግዲህ
እዚህ ላይ “እንግዲህ” የሚለው ቃል የደብዳቤውን መጨረሻ ክፍል ያመለክታል። ይህን በራሳችሁ ቋንቋ መግለጽ የምትችሉ ከሆነ እሱን መጠቀም ይቻላል።

ሊያቆማችሁ የሚችለው
ጳውሎስ እዚህ ላይ ጠንካራ እምነት መኖርን ልክ ከመውደቅ ይልቅ እንደመቆም አድርጎ ይስለዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “እምነታችሁን ለማበርታት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ እኔ ወንጌልና እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ስብከት
“ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሰበክሁት እንደ የምስራቹ ቃል”

ለረጅም ጊዜ ተሰውሮ ቆይቶ መገለጥን ባገኘው ሚስጥር
ጳውሎስ እግዚአብሔር ቀድመው ተሰውረው የቆዩ ነገሮችን ለአማኞች እንደገለጠ ይናገራል። እነዚህ ነገሮች ሚስጥር እንደነበሩ አድርጎ ይናገራል። ይህን በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፡- “ምክንያቱም እግዚአብሔር ለእኛ ለአማኞች ለረጅም ጊዜ ሚስጥር ሆኖ የጠበቀውን ነገር ስለገለጠልን” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን አሁን በዘላለማዊው በእግዚአብሔር ትዕዛዝ በነቢያት ጽሁፎች ለሁሉም ሕዝቦች ተገልጧል፣ እንዲታወቅም ሆኗል
“ተገልጧል” እና “እንዲታወቅ ሆኗል” የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ጳውሎስ ሁለቱንም የሚጠቀመው አጽንዖት ለመስጠት ነው። እነዚህን ቃላት አንድ ላይ በማድረግ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፡- “አሁን ግን ዘላለማዊው እግዚአብሔር በነቢያቱ ጽሁፍ አማካይነት ለሕዝብ ሁሉ እንዲታወቅ አድርጓል” (ጥምር ቃል እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የእምነት መታዘዝን እንዲያመጣ
እዚህ ላይ “መታዘዝ” እና “እምነት” የሚሉት ቃላት ረቂቅ ስሞች ናቸው። “ታዛዥነት” እና “መታመን” የሚሉትን በትርጉምህ ላይ መጠቀም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፡- “ሕዝብ ሁሉ እግዚአብሔርን ስለሚታመኑት እንዲታዘዙት” (ረቂቅ ስሞች እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 16:27

ብቻውን ጠቢብ ለሆነው ... ለዘላለም ክብር ይሁን። አሜን
እዚህ ላይ “በክርስቶስ ኢየሱስ” የሚለው ኢየሱስ የሰራውን ስራ ያመለክታል። “ክብር” ይሁን ማለት እግዚአብሔርን ማመስገን ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ በሰራው ስራ ምክንያት፣ ብቻውን አምላክና ብቻውን ጥበበኛ የሆነውን እግዚአብሔርን ለዘላለም እናመሰግናለን። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: 1 Corinthians

1 Corinthians

ምዕራፍ 1

1 በእግዚአብሔር ፈቃድ ሐዋርያ ሊሆን በክርስቶስ ኢየሱስ የተጠራ ጳውሎስና ወንድማችን ሶስቴንስ በቆሮንቶስ ላለች ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን፤
በክርስቶስ ኢየሱስ ለተቀደሱት። 2 የእነርሱና የእኛ ጌታ የሆነውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በየስፍራው ከሚጠሩት ሁሉ ጋር ቅዱሳን ለመሆን
ለተጠሩት ደግሞ እንጽፍላቸዋለን። 3 ከአባታችን ከእግዚአብሔር ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን። 4 ክርስቶስ ኢየሱስ ከሰጣችሁ
ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሳ ሁልጊዜ ስለእናንተ አምላኬን አመሰግናለሁ። 5 በነገር ሁሉ፤በንግግርና በዕውቀት ሁሉ ባለጸጋ እንድትሆኑ አድርጎአችኋልና። 6
ስለክርስቶስ የተሰጠው ምስክርነት በመካከላችሁ እውነት ሆኖ እንደጸና ሁሉ ባለጸጎች አድርጎአችኋል። 7 ስለዚህ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መገለጥ
በጉጉት ስትጠባበቁ አንድም መንፈሳዊ ስጦታ አይጎድልባችሁም። 8 እርሱ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ያለ ነቀፋ እንድትሆኑ እስከ ፍጻሜ ድረስ
ያጸናችኋል። 9 ወደ ልጁ ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኅብረት የጠራችሁ እግዚአብሔር የታመነ ነው። 10 ስለዚህ ወንድሞችና እህቶች ሆይ፤ ሁላችሁም
በአንድ አሳብ እንድትስማሙ እንጂ በመካከላችሁ መለያየት እንዳይሆን በጌታችን በኢየሱስ ድርስቶስ ስም አሳስባችኋለሁ። እንዲሁም በአንድ ልብና በአንድ
ዓለማ የተባበራችሁ እንድትሆኑ አሳስባችኋለሁ። 11 በመካከላችሁ መከፋፈል እንደተፈጠረ የቀሎዔ ቤተ ሰዎች አስታውቀውኛል። 12 ይህን የምላችሁ፦
እያንዳንዳችሁ፦ "እኔ ከጳውሎስ ጋር ነኝ፥ ወይም ከአጵሎስ ጋር ነኝ፤ ወይም እኔ ከኬፋ ጋር ነኝ፤ ወይም እኔ ከክርቶስ ጋር ነኝ" ትላላችሁ። 13 ለመሆኑ ክርስቶስ
ተከፍሎአልን? ጳውሎስስ ስለ እናንተ ተሰቅሎአልን? ወይም የተጠመቃችሁት በጳውሎስስ ስም ነውን? 14 ከቀርስጶስና ከጋይዮስ በቀር ማናችሁንም
ስላላጠመቅሁ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። 15 ስለዚህ ማናችሁም በእኔ ስም እንደተጠመቃችሁ ለመናገር አትችሉም። (የእስጢፋኖስን ቤተ ሰብ ደግሞ
አጥምቄአለሁ። 16 ከዚህ ውጪ ሌላ ማንን አጥምቄ እንደሆነ አላውቅም።) 17 ክርስቶስ ወንጌልን እንድሰብክ እንጂ እንዳጥምቅ አላከኝም። በሰው ጥበብ
እንድሰብክ አልላከኝም፤ እንዲሁም የክርስቶስ መስቀል ኃይሉ ከንቱ መሆን ስለሌለበት በሰው የንግግር ጥበብ አልሰብክም ። 18 ስለመስቀሉ ያለው መልእክት
ለሚጠፉት ሞኝነት፤ ነገር ግን ለምንድን ለእኛ የእግዚአብሔር ኃይል ነው። 19 "የጥበበኖችን ጥበብ አጠፋለሁ፤ የአስተዋዮችንም ማስተዋል ከንቱ አደርጋለሁ"
ተብሎ ተጽፎአልና። 20 ጥበበኛ ሰው የት አለ? ፈለስፋስ የት አለ? የዚህ ዓለም መርማሪስ የት አለ? እግዚአብሔር የዚህን ዓለም ጥበብ ሞኝነት እንዲሆን
አላደረገምን? 21 ዓለም በጥበብዋ እግዚአብሔርን ስላላወቀች በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ሊያድን የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖአል። 22 አይሁድ
ታዓምራትን ይፈልጋሉ፤ የግሪክ ሰዎችም ጥበብን ይሻሉ። 23 እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን። ይህም ለአይሁድ ማሰናከያ ለግሪክ ሰዎችም
ሞኝነት ነው። 24 ነገር ግን እግዚአብሔር ለጠራቸው ለአይሁዶችም ሆነ ለግሪክ ሰዎች የእግዚአብሔር ኃይልና ጥበብ የሆነውን ክርስቶስን እንሰብካለን። 25
ምክንያቱም የእግዚአብሔር ሞኝነት የሚመስለው ነገር ከሰዎች ጥበብ ይበልጣል፤ እንዲሁም የእግዚአብሔር ድካም የሚመስለው ነገር ከሰዎች ብርታት
ይበልጣል። 26 ወንድሞችና እህቶች ሆይ፤ በእናንተ ያለውን የእግዚአብሔርን ጥሪ ተመልከቱ። ብዙዎቻችሁ በሰው መስፈርት ጥበበኞች አልነበራችሁም።
ብዙዎቻችሁ ኃያላን አልነበራችሁም፤ ብዙዎቻችሁም ከመሳፍንት አልነበራችሁም። 27 ነገር ግን እግዚአብሔር ጥበበኞችን ያሳፍር ዘንድ የዓለምን ሞኝ ነገር
መረጠ። ብርቱንም ነገር ለማሳፈር የዓለምን ደካማ ነገር መረጠ። 28 ዓለም እንደ ከበረ ነገር የምትቆጥረውን ከንቱ ለማድረግ እግዚአብሔ የዓለምን ምናምንቴ
ነገር መረጠ። የተናቀውንና ያልሆነውን ነገር መረጠ። 29 ይህን ያደረገው ማንም ሰው በእግዚአብሔር ፊት ለመመካት ምክንያት እንዳይኖረው ነው። 30
በክርስቶስ ኢየሱስ ለመሆን የበቃችሁት ከእግዚአብሔር ሥራ የተነሳ ነው፤ እርሱም ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበባችን፤ጽድቃችንና ቅድስናችን ቤዛችንም
ሆኖአልና። 31 እንግዲህ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ ፦"የሚመካ በጌታ ይመካ" ነው።

---

1 Corinthians 1:1

1 ቆሮንቶስ 1:1-3
ወንድማችን ሶስቴንስ ጳውሎስና የቆሮንቶስ ሰዎች ሶስቴንስን እንደሚያውቁ ይጠቁማል። ትኩረት፦ "ሶስቴንስ እናንተና እኔ የምናውቀው ወንድም።

ቅዱሳን ለመሆን የተጠሩት ሰዎች ትኩረት፦ «እግዚአብሔር ቅዱስ ሕዝብ እንዲሆኑ ጠርቶአቸዋል።»

የእነርሱና የእኛ ጌታ ኢየሱስ የጳውሎስና የቆሮንቶስ ሰዎች ጌታ ነው፤ እንዲሁም የሁሉም አብያተ ክርስቲያናት አንዱ ጌታ ነው። ለእናንተ «እናንተ» የሚለው ቃል በቆሮንቶስ ያሉትን ምእመናንን ያመለክታል።

1 Corinthians 1:4

1ቆሮንቶስ 1:4-6
ክርስቶስ ኢየሱስ የሰጣችሁ የእግዚአብሔር ጸጋ «በክርስቶስ ላላችሁ እግዚአብሔር የሰጣችሁ ጸጋ» ባለጸጋ አድርጎአችኋል ትርጉም ሊሆኑ የችሉ 1) «ክርስቶስ ባለጸጋ አድርጎአችኋል።» ወይም 2) «እግዚአብሔር ባለጸጋ አድርጎአችኋል።» በየስፍራው ባለጸጋ አድርጎአችኋል «በብዙ መንፈሳዊ በረከቶች ባለጸጋ አድርጎአችኋል» በንግግር ሁሉ እግዚአብሔር ለሌሎች ስለ እግዚአብሔር መልእክት በብዙ መንገድ እንድትናገሩ አስችሎአችኋል በዕውቀት ሁሉ እግዚአብሔር የእርሱን መልእክት በብዙ መንገድ እንድትረዱ አስችሎአችኋል። ስለ ክርስቶስ ምስክርነት «ስለ ክርስቶስ መልእክት» በመካከላችሁ እውነትን አረጋገጠ ትኩረት፦ « ሕይወታችሁን በግልጽ ለውጦአል።»

1 Corinthians 1:7

1 ቆሮንቶስ1:7-9
ስለዚህ «ከዚህ የተነሣ» ከመንፈሳዊ ስጦታ አልጎደለባችሁም «ማንኛውም መንፈሳዊ ስጦታ ይኑርባችሁ» የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መገለጥ አማራጭ ትርጉሞች 1) « እግዚአብሔር ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚገልጥበት ጊዜ።» 2) «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን በሚገልጥበት ጊዜ።» ነውር የሌለባችሁ ትሆናላችሁ እግዚአብሔር እናንተን የሚነቅፍበት ምክንያት ያለም ወደ ልጁ ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኅብረት የጠራችሁ እግዚአብሔር የታመነ ነው። እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አዲስ ሕይወት እንድትካፈሉ ጠርቶአችኋል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Corinthians 1:10

1 ቆሮንቶስ **1**:**10**-**11**
ሁላችሁ የምትስማሙበት «እርስ በርሳችሁ በስምምነት ትኖራላችሁ» በመካከላችሁ መከፋፈል እንዳይኖር «በመካከላችሁ በተለያየ ቡድን መከፋፈል የለባችሁም።» በአንድ አሳብና በአንድ ዓላማ የተሳሰራችሁ ሁኑ « በኅብረት ኑሩ» የቀሎዔ ሰዎች ይህ ቀሎዓ የተባለች ሴት የምትመራው ቤተ ሰብ፥ የቤተ ሰብ አባላት፥ አገልጋዮችና ሌሎችንም የሚያመለክተው ነው። በመካከላችሁ ክፍፍሎች እየተፈጠሩ ናቸው። «እርስ በርሳችሁ የምትጣላሉ ቡድኖች ናችሁ።»

1 Corinthians 1:12

1 ቆሮንቶስ **1**:**12**-**13**
እያንዳንዳችሁ ትላላችሁ ጳውሎስ በአጠቃላይ ስለ ክፍፍል እየገለጸ ነው። ክርስቶስ ተከፍሎአልን? ጳውሎስ ከአንዱ በቀር ክርስቶስ ያልተከፋፈለ የመሆኑን እውነት ለማስረዳት ይፈልጋል። «እናንት በምትፈጉበት ሁኔታ ክርስቶስን መከፋፈል አይቻልም።» ጳውሎስ ተሰቅሎአልን? ጳውሎስ የተሰቀለው ጳውሎስ ወይም አጵሎስ ሳይሆን ክርስቶስ ብቻ እንደሆን ለማስረዳት ይፈልጋል። «በመስቀል ላይ ጳውሎስን ለእናንተ ድነት አልሰቀሉትም።»

በጳውሎስ ስም ተጠመቃችሁን? ጳውሎስ ለማስረዳት የፈለገው ሁላችን በክርስቶስ ስም እንደተመቅን ነው። «ሰዎች በጳውሎስ ስም አላጠቁም።» (ተመልከት፦

1 Corinthians 1:14

1 ቆሮንቶስ **1**:**14**-**16**
እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ማንንም አለማጥመቁን ምን ያህል ትልቅ ሰው እንደሆን አጋኖ ይናገራል።

ቀርስጶስ የአይሁድ ምኩራብ አለቃ የነበረና ወደ ክርስትና የመጣ።

ጋይዮስ ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር አብሮ ተጉዞአል።

በስሜ ማናችሁም እንደተጠመቃችሁ የሚናገር ሰው እንዳይኖር ነበር «በኋላ ላይ ሰዎች እኔ እንዳጠመቅኋቸው አድርገው እንደይ ኩራሩብኝ ብዙ ሰዎችን በስሜ እንዳላጠምቅ ተከላክዬዋለሁ።»

የእስጢፋኖስ ቤተ ሰብ በእስጢፋኖስ ቤተ ሰብ ውስጥ ያሉ የቤተ ሰብ አባላትንና አገልጋዮችን የሚያሳይ ነው።

1 Corinthians 1:17

1 ቆሮንቶስ **1**:**17**
ክርስቶስ ለማጥመቅ አላከኝም ይህ ማለት ጥምቀት በጳውሎስ አገልግሎት ቅድሚያ የሚሰጠው አልነበረም። የክርስቶስ መስቀል ኃይል ከንቱ መሆን የለበትም ትኩረት፦ «የሰው ጥበብ የክርስቶስን መስቀል ኃይሉን ከንቱ ማድረግ ያለበትም።»

1 Corinthians 1:18

1 ቆሮንቶስ **1**:**18**-**19**
ስለ የመስቀል መልእክት «ስለ ስቅላት መስበክ» ወይም «ስለ ክርስቶስ በመስቀል ላይ መሞት መልእክት መስበክ ነው» (UDB) ሞኝነት ነው «ስሜት የማይሰጥ» ወይም «ከንቱ ነገር» ለሚሞቱ እዚህ ላይ «መሞት» ማለት የመንፈሳዊ ሞት ሂደትን የሚያሳይ ነው። ይህ የእግዚአብሔር ኃይል ነው «ይህ እግዚአብሔር በእኛ በኃይል የሚሠራውበት ነው።» የአስተዋዮችን ጥበብ ከንቱ አደርጋለሁ ትኩረት፦ «ዋቂ ሰዎችን ግራ እንዲጋቡ አደርጋለሁ» ወይም «የዐዋቂዎችን ዓላማ ሙሉ በሙሉ ከንቱ አደርጋለሁ።»

1 Corinthians 1:20

1 ቆሮንቶስ **1**:**20**-**21**
ጥበበኛ ሰው የት አለ? ፈላስፋስ የት አለ? የዚህ ዓለም መርማሪስ የት አለ? ጳውሎስ ሊገልጸው የፈለገው በእውነት ጥበበኛ የሆኑ ሰዎች የትም አይገኙም። ትኩረት፦ ከወንጌል ጥበብ ጋር ሲነጻጸር ጥበበኛ የሆኑ ሰዎች የሉም፤ ዐዋቂዎቹም የሉም። የዚህ ዓለም መርማሪዎቹም የሉም!" ዐዋቂ አንድ ሰው ከፍተኛ ዐውቀት እንዳለ የሚታወቅ የዚህ ዓለም መርማሪ አንድ ሰው ዐውቀት መኖሩን በክርክር ችሎታ የሚያሳምን እግዚአብሔር የዚህች ዓለም ጥበብን ሞኝነት አላደረገምን? እግዚአብሔር በዚህች ዓለም ጥበብ ላይ ያደረገውኔ ለምግለጽ የተጠቀመበት ጥያቄ ነው። ትኩረት፦ " እግዚአብሔር በርግጥ የዚህችን ዓለም ጥበብ ሞኝነት አድርጎአል" ወይም "እግዚአብሔር ያሰቡት የነበረው ሞኝነት እንደሆነ ለማሳየት ፈልጎአል። (UDB)

የሚያምኑ አማራጭ ትርጉሞች 1) «የሚያምኑ ሁሉ» (UDB) or 2) « እርሱን የሚያምኑ ሁሉ።»

1 Corinthians 1:22

1 ቆሮንቶስ **1**:**22**-**23**
እንሰብካለን «እኛ» የሚለው ቃል ጳውሎስንና ሌሎች ወንጌዋውያንን ይመለከታል። ክርስቶስ ተሰቅሎአል «ይህ በመስቀል ላይ ስለሞተው ክርስቶስ ነው።» የእንቅፋት ድንጋይ አንድ ሰው በመንገድ ላይ በድንጋይ እንቅፋት ሊሆን እንደሚሆንበት የክርስቶስ ስቅላት እንቅፋት ለአይሁድ እንቅፋት ሊሆን እንደቻለ ነው። «አይደለም» ትኩረት፦ «የሚቀበሉት አይደለም» ወይም «በጣም አስከፊ»

1 Corinthians 1:24

1 ቆሮንቶስ **1**:**24**-**25**
እግዚአብሔር ለመረጣቸው «እግዚአብሔር ለሚጠራቸው ሰዎች» ክርስቶስን እንሰብካለን «ስለክርስቶስ እናስተምራለን» ወይም «ስለ ክርስቶስ ለሰዎች ሁሉ እንናገራለን።» ክርስቶስ እንደ ኃይልና እንደ እግዚአብሔር ጥበብ ክርስቶስ እግዚአብሔር ኃይሉና ጥበቡን የሚገልጥለት ነው። የእግዚአብሔር ሞኝነት የእግዚአብሔር ድካም ይህ የእግዚአብሔርና የሰው ባሕርይ ንጽጽር ነው። የእግዚአብሔር ሞኝነት የሚመስል ወይም ድካም የሚመስል እንኳ ቢሆን ከሰው የመጨረሻ ከተሻለው ባሕርይ ጋር ሲነጻጸር የእግዚአብሔር ይበልጣል።

1 Corinthians 1:26

1 ቆሮንቶስ **1**:**26**-**27**
ለእናንተ የእግዚአብሔር ጥሪ «ቅዱሳን እንድትሆኑ እግዚአብሔር እንዴት እንደጠራችሁ» ከእናንተ ብዙዎች አልተመረጡም «ከእናንተ በጣም ጥቂቶች ብቻ»

የሰው ልማድ «የሰዎች ፍርድ" ወይም "ስለ መልካምነት የሰዎች አሳብ» ባለባት ሆኖ ስለ መወለድ «ቤተ ሰብህ አስፈላጊ ከመሆኑ የተነሣ የተለየ ነስ» ወይም «ንጉሳዊ» ጥበበኛን ለማሳፈር እግዚአብሔር የዚህ ዓለም ሞኝ ነገርን መረጠ የአይሁድ መሪዎች እነዚህ መሪዎች ከሌሎች ይልቅ ለእግዚአብሔር አስፈላጊ አይደለም ብለው የሚያምኑትን እግዚአብሔር ትሑታን ሰዎችን መረጠ።

1 Corinthians 1:28

1 ቆሮንቶስ **1**:**28**-**29**
ዝቅተኛና የተናቀ ምንድን ነው ዓለም የማትቀበላቸው ሰዎች ናቸው። ትኩረት፦ «ትሑታንና ተቀባይነት የሌላቸው ሰዎች ናቸው።» እንደ ምናምንቴ የሚቆጠሩ ሰዎች «ሁል ጊዜ ሰዎች ዋጋ እንደሌላቸው አድርገው የሚቆትሩአቸው» ዋጋ እንዳላቸው ተደርገው የሚያዙ ነገሮች «ሰዎች ዋጋ እንዳላቸው

የሚቆጥሩአቸው ነገሮች» ወይም «ሰዎች ገንዘብ ወይም ክብር ይገባቸዋል ብለው ያስቡ»

1 Corinthians 1:30

1 ቆሮንቶስ **1**:**30**-**31**
እግዚአብሔር ካደረገው የተነሣ ይህ የሚያሳየው ክርስቶስ በመስቀል ላይ ያደረገውን ሥራ ነው። በእኛ የእኛ ጳውሎስ «በእኛ» በሚለው የቆሮንቶስ ሰዎችን ይጨምራል፡

እንግዲህ እናንት በክርስቶስ ኢየሱስ ናችሁ «አሁን እናንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ድነትን ተቀብላችኋል» ክርስቶስ ኢየሱ ስለ እኛ የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው «ክርስቶስ አየሱስ እግዚአብሔር እንዴት ጥበበኛ እንደሆነ ግልጽ አደረገው»

የሚመካ በጌታ ይመካ «ሰው የሚመካ ከሆን ጌታ ምን ያህል ታላቅ በመሆኑ ይመካ»

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 2

1 ወንድሞችና እህቶች ሆይ፦ወደ እናንተ ስመጣ ስለ እግዚአብሔር የተሰወረውን የእውነት ምስጢር ሲሰብክላችሁ በሚያባብል የንግግር ችሎታ ወይም በላቅ
ጥበብ አልመጣሁም። 2 በመካከላችሁ ሳለሁ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀርና፥ እርሱም እንደተሰቀለ ሌላ እንዳላውቅ ወስኜ ነበርና። 3 ወደ እናንተ የመጣሁት
በድካምና በፍርሃት፤ እንዲሁም በብዙ መንቀጥቀጥ ነበር። 4 መልእክቴና ስብከቴም የመንፈስን ኃይል በመግለጥ እንጂ በሚያባብል የጥበብ ቃል
አልነበረም፤ 5 ይህም እምነታችሁ በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ ላይ እንዳይመሠረት ነው። 6 በእምነታቸው በሰሉት ሰዎች መካከል በጥበብ
እንናገራለን፤ ነገር ግን የምንናገረው የዚህን ዓለም ጥበብ ወይም ከጊዜ በኋላ የሚሻሩትን የዚህን ዓለም ገዢዎች ጥበብ አይደለም። 7 ይልቁን እግዚአብሔር
አስቀድሞ ከዘመናት በፊት ለክብራችን ያዘጃውን፥ ተሰውሮም የነበረውን የእግዚአብሔርን የጥበብ እውነት እንናገራለን። 8 የዚህም ዓልም ገዢዎች አንዳቸውም
ይህን ጥበብ አላወቁትም፤ በዚያን ጊዜ ይህን አውቀውስ ቢሆን ኖሮ የክብርን ጌታ ባልሰቀሉትም ነበር። 9 ነገር ግን፦ "ዓይን ያላየውን፤ ጆሮም ያልሰማውን፤
በሰውም ልብ ያልታሰበውን፤ እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀውን ነገር" ተብሎ ተጽፎአልና። 10 እግዚአብሔር በመንፈሱ አማካይነት የተሰወሩትን ነገሮች
ገልጦናን ። ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራል። በሰው ውስጥ ካለው ከእርሱ መንፈስ በቀር የሰውን
አሳብ የሚያውቅ ማን ነው? 11 እንዲሁም ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር የሚያውቅ ማንም የለም። 12 እኛ ግን ክእግዚአብሔር
በነፃ የተሰጠንን እንድናውቅ ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ የዓለምን መንፈስ አልተቀበለንም። 13 የሰው ጥበብ ሊያስተምር የማይችለውን ነገር ግን
የእግዚአብሔር መንፈስ የሚያስተምረውን ስለ እነዚህ ነገሮች በቃላት እንናገራለን። መንፈስ ቅዱስም መንፈሳዊውን ቃላት በመንፈሳዊ ጥበብ ይገልጥልናል። 14
የእግዚአብሔር መንፈስ የሌለው ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ስለሚሆንበት አይቀበለውም ። በመንፈስም የሚመረመር ስለሆነ ሊያውቀው
አይችልም። 15 የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት ሰው ሁሉን ይመረምራል፤ እርሱ ግን በማንም አይመረመርም። 16 "የጌታን አሳብ ማን አወቀው፤ ማንስ
ሊያስተምረው ይችላል?" እኛ ግን የክርስቶስ ልብ አለን።

---

1 Corinthians 2:1

1ቆሮንቶስ 2:1-2
በሚያባብል የንግግር ችሎታ ማሳመን በሚችለውና በሚስብ ንግግር ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ምንም ላለማወቅ ወስኜ ነበር ጳውሎስ ከሰው አስተሳሰብ ይልቅ በመስቀሉ ላይ አተኩሮአል። ትኩረት፦«ስለ ክርስቶስ ብቻ ለመናገር ወስኛ ነበር።»

1 Corinthians 2:3

1ቆሮንቶስ 2:3-5
ከእናንተ ጋር ነበርኩ «እኔ እናንተ ዘንድ ነበርኩ» በድካም አማጭ ትርጉሞች፦ 1) «የአካል ድካም» (UDB) or 2) «በሚገባ ሆኖ አለ መገኘት»
አሳማኝ ማሳመን ወይም አንድ ነገር ሰዎች እንዲያደርጉ ተጽእኖ ማድረግ ወይም እንድን ነገር ማመን እነርሱ የጳውሎስ መልእክትና የወንጌል ስብከት

1 Corinthians 2:6

1ቆሮንቶስ 2:6-7
ጥበብን መናገር «የጥበብን ቃል ተናገር» የበሰለ ትኩረት፦ «የበሰሉ አማኞች» ለክብራችን «የወደፊት ክብራችንን ለማረጋገጥ»

1 Corinthians 2:8

1ቆሮንቶስ 2:8-9
የክብሩ ጌታ «ኢየሱስ የከበረ ጌታ» ዓይን ያላየው ነገሮች፥ጆሮም ያልሰማ ነገሮች፥ በልብም ያልታሰቡ ነገሮች ሦስቱም ነገሮች የሚያሳዩት ማንም ሰው በሁሉ አካሉ ክፍሎች እግዚአብሔር ያዘጋጃቸውን ነገሮች እንደማያውቅ ለመግለጽ ነው። እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጃቸው ነገሮች ጌታ ለሚወዱት አስደናቂ ነገሮችን በሰማይ አዘጋጅቶአል።

1 Corinthians 2:10

1ቆሮንቶስ 2:10-11
እነዚህ ነገሮች ናቸው ስለ ኢየሱስና ስለ መስቀል ያሉ እውነቶች በሰው ውስጥ ያለውን አሳብ ከሰው መንፈስ በቀር ማን ያውቃል? ጳውሎስ ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ሰው የሚያስበውን ከራሱ ሰውየው በቀር ማንም አያውቅም። ትኩረት፦«ሰው የሚያስበውን ከሰው መንፈስ በቀር ማንም አያውቅም።»

1 Corinthians 2:12

1ቆሮንቶስ 2:12-13
እኛ ግን እዚህ «እ» ጳውሎስንና የእርሱን አድማጮችን ይጨምራል።

እግዚአብሔር በነጻ የሰጠን «እግዚአብሔር በነጻ ሰጠን» ወይም «እግዚአብሔር በነጻ ሰጥቶናል» መንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ ነገሮችን በመንፈሳዊ ጥበብ ይተረጉማል ቅዱስ መንፈስ የእግዚአብሔርን እውነት ለአማኞቹ በመንፈስ ቅዱስ በራሱ ቃላት ግንኙነት ያደርጋል እንዲሁም የራሱንም ጥበብ ይሰጣል።

1 Corinthians 2:14

1ቆሮንቶስ 2:14-16
መንፈሳዊ ያልሆነ ሰው ክርስቲያን ያልሆነ ሰው፥ መንፈስ ቅዱስን ያልተቀበለ ምክንያቱም በመንፈስ ስለሚመረመሩ «ምክንያቱም እነዚህን ነገሮች ለመረዳት የመንፈስ ቅዱስን ርዳታ ያስፈልጋል» መንፈሳዊ የሆነ ሰው ትኩረት፦ «መንፈስ ቅዱስን የተቀበለ አማኝ» የጌታን ልብ ማን አወቀው ማንስ ሊያስተምራው ይችላል? ጳውሎስ ይህን ጥያቄ የተጠቀመው የጌታን ልብ ማንም እንደማያውቀው ለማስረዳት ነው። ትኩረት፦ «የጌታን ልብ ማንም ሊያውቀው አይችልም። ስለዚህ ቀድሞኑ ስለማያውቀው ማንም ሊታስተምረው አይችልም።»

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 3

1 ወንድሞችና እህቶች ሆይ፤ እንደ ሥጋውያን፤ በክርስቶስም እንደ ሕፃናት እንጂ መንፈሳውያን እንደ ሆናችሁ ልናገራችሁ አልቻልሁም። 2 ገና ጠንካራ ምግብ
ለመብላት ስላልቻላችሁ ጠንካራ ምግብ ሳይሆን ወተት ጋትኋችሁ። እስከ አሁን ስንኳ ጠንካራ ምግብ ለመብላት ገና አልበቃችሁም። 3 ምክንያቱም ገና
ሥጋውያን ናችሁና። ቅናትና ክርክር ስለ ሚገኝባችሁ በሥጋ ፈቃድ እየኖራችሁ አይደላችሁምን? እንደ ሰውስ ልማድ እየተመላለሳችሁ አይደለምን? 4 አንዱ፦
"እኔ ጳውሎስን እከተላለሁ" እንዲሁም ሌላውም፦ "እኔ የአጵሎስ ተከታይ ነኝ" ሲል እንደ ሰዎች ልማድ መመላለሳችሁ አይደለምን? 5 ታዲያ አጵሎስ ማን
ነው? ጳውሎስስ ማን ነው? በእነርሱ እጅ ያመናችሁ እንደ ተሰጣቸው አገልጋዮች ናቸው። 6 እኔ ተክልሁ አጵሎስም አጠጣ፤ ግን ያሳደገው እግዚአብሔር ነው።
7 እንግዲህ የሚተክል ወይም የሚያጠጣ ምንም አይደለም። ነገር ግን የሚያሳድግ እግዚአብሔር ነው። 8 የሚተክልና የሚያጠጣ አንድ ናቸው። እንዲሁም
እያንዳንዱ እንደ ራሱ ድካም መሠረት የራሱን ደመወዝ ይቀበላል። 9 ምክንያቱም ከእግዚአብሔር ጋር አብረን የምንሠራ ነን። የእግዚአብሔር እርሻ፤
የእግዚአብሔርም ሕንፃ ናችሁ። ። 10 ከእግዚአብሔር በተሰጠኝ ጸጋ እንደ ዋና ሙያተኛ መሐንድስ መሠረትን ጠልሁ፤ ሌላውም ሰው በላዩ ያንጻል። እያንዳንዱ
ሰው ግን በእርሱ ላይ እንዴት እንደሚያንጽ ይጠንቀቅ። 11 ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልም፤ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።
12 ማንም ግን በዚህ መሠረት ላይ በወርቅ ቢሆን፤ በብር፤ በከበረ ድንጋይ፤ በእንጨት፤ በሣር ወይም በአገዳ ቢያንጽ፤ 13 የእያንዳንዱ ሥራ ይገለጣል፤ የቀን
ብርሃንም ይገልጠዋልና። የእያንዳንዱም ሥራ ጥራት እንዴት መሆኑን እሳቱ ይፈትነዋል። 14 አንድ ሰው ማንኛውንም ነገር ያነጸው ሥራ ቢጸናለት ሽልማቱን
ይቀበላል። ነገር ግን የማንም ሥራ የተቃጠለበት ከሆነ ይከስራል። 15 ነገር ግን እርሱ ራሱ ከእሳት እንደሚያመልጥ ሆኖ ይድናል ። 16 እናንተ የእግዚአብሔር
ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደሚኖርባችሁ አታውቁምን? 17 ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን
ያፈርሰዋል። የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ እንደሆነ እናንተም እናንተም ቅዱሳን ናችሁ። 18 ማንም ራሱን አያታልል። ከእናንተ መካከል ማንም በዚህ ዘመን
ጥበበኛ እንደሆነው ቢያስብ፤ ጥበበኛ ይሆን ዘንድ እንደ ሞኝ ራሱን ይቁጠር። 19 የዚህ ዓለም ጥበብ በእግዚአብሔር ፊት ሞኝነት ነውና። ምክንያቱም "እርሱ
ጥበበኞችን በተንኮላቸው ይይዛል" ተብሎ ተጽፎአል። 20 ደግሞም፦ "ጌታ የጥበበኞችን አሳብ ከንቱ እንደ ሆን ያውቃል" ተብሎ ተጽፎአል። 21 ስለዚህ
ማንም በሰው አይመካ። ነገር ሁሉ የእናንተ ነውና፤ 22 ጳውሎስ ቢሆን፥ ወይም አጵሎስ ቢሆን፥ ወይም ኬፋ ቢሆን፥ ወይም ዓለምም ቢሆን፥ወይም ሕይወት
ቢሆን፥ ወይም ሞት ቢሆን፥ ወይም ያለውም ቢሆን፥ ወይም የሚመጣውም ቢሆን 23 ሁሉ የእናንተ ነው፤ እናንተም የክርስቶስ ናችሁ፤ ክርስቶስም የእግዚአብሔር
ነው።

---

1 Corinthians 3:1

1ቆሮንቶስ **3**:**1**-**2**
መንፈሳዊ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚኖሩ ሰዎች ሥጋውያን ሰዎች የራሳቸውን ፍላጎት የሚከተሉ ሰዎች በክርስቶስ እንደ ሕፃናት የቅሮንቶስ ሰዎች በዕድሜአቸው ለመረዳት ገና እንደሆኑ ከሕፃናት ጋር ተነጻጽረዋል። ትኩረት፦ «በክርስቶስ በጣም ወጣት አማኞች» ተመልከት፦ ጠንካራ ምግብ ሳይሆን ወተት ጋትኩአችሁ የቆሮንቶስ ሰዎች ወተት እንደሚጠጡ ሕፃናት ሕፃናት ቀለል ያሉ ነገሮችን ብቻ መረዳት ይችላሉ። እንዳደጉና ጠንክር ያለ ምግብ ለመብላት እንደማይችሉ ሕፃናት ትላልቅ ነገሮችን ለመረዳት የበሰሉ አይችሉም። የበቃችሁ አይደላችሁም «ክርስቶስን ስለመከተል ከበድ ያሉ ትምህርቶችን ለመረዳት የበቃችሁ አይደላችሁም»

1 Corinthians 3:3

1ቆሮንቶስ **3**:**3**-**5**
እስካሁን ሥጋውያን ናችሁ እንደ ኃጢአተኛ መሆን ወይም እንደ ዓለማዊ ፍላጎት መመላለስ በሥጋ መስፈርት የምትመላለሱ አይደለምን? ጳውሎስ የቆሮንቶስን ሰዎች ስለ ኃጢአተኛ ባሕርያቸው ይገስጻቸዋል። ትኩረት፦ «በሥጋዊ ፍላጎት መስፈርት ስለምትመላለሱ ልታፍሩ ይገባል!» በሰው መስፈርት የምትመላለሱ አይደለምን? ጳውሎስ የቆሮንቶስን ሰዎች በሰው መስፈርት ስለሚመላለሱ ይገስጻቸዋል። ትኩረት፦ «የሰውን መስፈርት ስለምትከተሉ ልታፍሩ ይገባል።» እንደ ሰው የምትኖሩ አይደለምን? ትኩረት፦ «መንፈስ ቅዱስ የሌላቸው ሰዎች እንደሚኖሩ ስለምትኖሩ ልታፍሩ ይገባል።» አጵሎስ ማን ነው? ጳውሎስስ ማን ነው? ጳውሎስ እርሱና አጵሎስ የወንጌል ዋና ምንጭ እንዳይደሉና ስለዚህም ተከታዮች ሊኖሩአቸው እንደማይገባ ለማስረዳት ነው። ትኩረት፦ «አጵሎስ ወይም ጳውሎስ በማለት ቡድን መመሠረት ስሕተት ነው።» በእነርሱ እጅ ያመናችሁ የጌታ አገልጋዮች ናቸው ጳውሎስ የራሱን ጥያቄ እርሱና አጵሎስ የእግዚአብሔር አገልጋዮች መሆናቸውን እንዲህ ሲል ይመልሳል። ትኩረት፦«ጳውሎስና አጵሎስ የክርስቶስ ባሪያዎችና ክርስቶስን የተቀላችሁት እኛ ስላገለገልን ነው።» እያንዳንዳቸውን ጌታ እንደሰጣቸው ተግባር ያመናችሁ ትኩረት፦ ፡ «ፃመነን፥ ጌታ ተግባር የተሰጠን ሰዎች ብቻ ነን።»

1 Corinthians 3:6

1ቆሮንቶስ **3**:**6**-**7**
ተከለ የእግዚአብሔር ዕውቀት ለማደግ ዘር መተከል ስላለበት ንጽጽር ነው። ውኃ አጠጣ የተዘረ ዘር ውኃ እንደሚያስፈልጋው እምነትም ለማደግ ተጨማሪ ትምህርት ያስፈልጋል። ዕድገት እጽዋት እንደሚያድጉና ፍሬ እንደሚያፈሩ እምነትም በእግዚአብሔር ማደግና ሥር መስደድና ጠንካራ ይሆናል።

የሚተክል ምንም አይደለም፥ ነገር ግን እንዲያድግ የሚያደርገው እግዚአብሔር ነው ጳውሎስ እርሱ ወይም አጵሎስ ለአማኞች ዕድገት ኃላፊነት ያለባቸው ቢሆንም ይህን የሚያደርገው ግን እግዚአብሔር ነው።

1 Corinthians 3:8

1ቆሮንቶስ **3**:**8**-**9**
የሚተክልና የሚያጠጣ አንድ ናቸው መትከልና ማጠጣት ጳውሎስ የቆሮንቶስን ቤተ ክርስቲያን ለማገልገል ራሱንና አጵሎስን የሚያነጻጽርበት እንደ አንድ ሥራ ቆጥሮአል። ደመወዝ በሠራው ሥራ መሠረት ለሠራተኛ የሚከፈል ገንዘብ መጠን ነው። እኛ ይህ የሚያመለክተው ጳውሎስንና አጵሎስን ሲሆን የቆሮንቶስን ቤተ ክርስቲያን አመለከትም።

ከእግዚአብሔር ጋር አብረው የሚሠሩ ጳውሎስ ራሱንና አጵሎስን ከእግዚአብሔር ጋር የሚሠሩ ሠራተኞች እንደሆኑ ይቆጥራል። የእግዚአብሔር እርሻ እግዚአብሔር አንድ ሰው እርሻው ፍሬ እንዲያፈራ እንደሚንከባከብ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ጥንቃቄ ያደርጋል። የእግዚአብሔር ሕንፃ እግዚአብሔር አንድ ሰው ሕንፃ እንደሚያንጽ የቆሮንቶስን ቤተ ክርስቲያን ቀርጾ ፈጥሮአታል።

1 Corinthians 3:10

1ቆሮንቶስ **3**:**10**-**11**
ከእግዚአብሔር እንደተሰጠኝ ጸጋ «እግዚአብሔር እንድፈጽመው ሥራ በነፃ እንደሰጠኝ ጸጋ»

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

መሠረት ጠልኩ ጳውሎስ የእምነት ትምህርትና በክርስቶስ ያለውን ድነት ለሕንፃ መሠረት ከመጣል ጋር ተመሳሳይ ያደርገዋል።

ሌላው በላዩ ላይ የንጸል ሌላው ሠራተኛ እነዚህን አማኞች በመንፈሳዊ ርዳታ በቤተ ክርስቲያን ለማነጽ ይቀጥላል።

እያንዳንዱ ሰው ያድርግ ይህ የሚያመለክተው ባጠቃላይ የእግዚአብሔርን ሠራተኞችን ነው።ትኩረት፦ «እያንዳንዱ ሰው እግዚአብሔርን ያገልግል።» ከተመሠረተ በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልም ትኩረት፦ «ማንም ሊመሠርት የማይችለውን አንድን መሠረት ብቻ መሥርቻለሁ ወይም እኔ ጳውሎስ መሠረትን መሠረትሁ»

1 Corinthians 3:12

1ቆሮንቶስ **3**፡**12**-**13**
እንግዲህ ማንም በመሠረቱ ላይ በወርቅ ቢሆን፥ በብር፥ በከበረ ድንጋይ፥በእንጨት፥በሣር ወይም በአገዳ ቢያንጽ፤ ሕንፃ ለማነጽ የምንጠቀምባቸው የሕንፃ መሣሪያዎች ሰው በመንፈሳዊ ባሕርይና ተግባሮችን በሕይወት ዘመኑ ለመንፈሳዊ ዋጋ ያለው እንዲሆን እንደምንገነባ ዓይነት ይነጸጸራል። ትኩረት፦ «አንድ ሰው በውድና በጠንካራ ዕቃዎች ወይም በሚቃጠል ርካሽ ዕቃዎች ይገነባል» የከበረ ድንጋይ «ውድ የሆኑ ድንጋዮች» የቀኑ ብርሃን ሲገለጠው ሥራው ይገለጣል የቀን ብርሃን የሕንፃ ሠራተኞችን ጥረት እንደሚገለጥ የሰውንም የሥራ ጥረትና እንቅስቃሴ ጥራት የእግዚአብሔር ብርሃን መገኘት ይገልጠዋል።»

በእሳት ሲፈተን የእያንዳንዱ ሥራ ጥራት በእሳት ይፈተናል እሳት በሚገለጥበት ጊዜ የሕንፃውን ጥንካሬ ወይም መውደቅ ይታወቃል፤ እንዲሁም የእግዚአብሔር እሳት የሰውን ጥረትና እንቅስቃሴ ይፈትናል። ትኩረት፦ እሳቱ የሥራውን ጥራት ያሳያል።"

1 Corinthians 3:14

1ቆሮንቶስ **3**፡**14**-**15**
ይጸናል «ይቆያል» ወይም «ይቋቋማል» (UDB) ማንም ሰው ሥራው የተቃጠለበት ትኩረት፦ «የማንንም ሥራ እሳቱ ቢያጠፋ» ወይም «እሳቱ የማንንም ሥራ ቢያፈርስ» የማንም እርሱ ራሱ እነዚህ ቃላት የሚያሳየው «ሰው» ነው። ትኩረት፦ «ሰው» ወይም «እርሱ» (UDB) ኪሳራ ያጋጥመዋል ነገር ግን ራሱ ይድናል «በእሳቱ ተፈትኖ ካላለፈ ማንኛውም ሥራውንና ሽልማቱን ያጣል እግዚአብሔር ግን ያድነዋል።»

1 Corinthians 3:16

1ቆሮንቶስ **3**፡**16**-**17**
የእግዚአብሔር መንፈስ የሚኖርባችሁ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ አታውቁምን? ትኩረት፦ «የእግዚአብሔር መንፈስ የሚኖርባችሁ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ እንደማያውቅ ሆናችሁ ታደርጋላችሁ»

ማፍረስ «ማፍረስ» ወይም «ማጥፋት» እግዚአብሔር ያንን ሰው ያፈርሰዋል ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነው፤ ያውም እናንተ ናችሁ። ትኩረት፦ «እግዚአብሔር ያንን ሰው ያፈርሰዋል ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነው፤ እናንተም ቅዱሳን ናችሁ።»

1 Corinthians 3:18

1ቆሮንቶስ **3**፡**18**-**20**
ማንም ራሱን አያታልል በዚህ ዓለም ጥበበኛ የሆነ ማንም በውሸት ማመን የለበትም። በዚህ ዘመን «አሁን» ጥበበኛ ለመሆን «ሞኝ» ይሁን «የእግዚአብሔርን እውነተኛ ጥበብ ለማግኘት ዓለም የሚያስበው ሞኝነት እንደሆን ሰው መቀበል አለበት»

ጥበበኞችን በተንኮላቸው ይይዛቸዋል እግዚአብሔር ጥበበኛ እንደሆኑ የሚያስቡትን በራሳቸው ተንኮል ይይዛቸዋል። ጌታ የጥበበኞችን አሳብ ያውቃል ትኩረት፦ «ጌታ ጥበበኛ እንደሆኑ የሚያስቡ ሰዎች የሚያቅዱትን ያውቃል» ወይም «ጌታ የጥበበኞችን እቅድ ሁሉ አስቀድሞ ያውቃል» (UDB)

1 Corinthians 3:21

1ቆሮንቶስ **3**፡**21**-**23**
ማንም ሰው በሰው ላይ መመካት የለበትም! ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ምእመናን ትእዛዝ ይሰጣል። ትኩረት፦ «አንዱ መሪ ከሌላው እንዴት የተሻለ እንደሆነ መመካትን ያቁም።» ትምክት «ከመጠን በላይ ትዕቢትን መግለጥ» የቆሮንቶስ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስን ማምለክ ሲገባቸው ጳውሎስን ወይም አጵሎስን ከፍ ከፍ ያድርጉ ነበር። እናንተ የክርስቶስ ናችሁ፤ክርስቶስም የእግዚአብሔር ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 4

1 እንግዲህ ማንም ሰው እኛን የክርስቶስ አገልጋዮችና የእግዚአብሔር የተሰወረው ምሥጢር መጋቢዎች እንደሆነን ሊቆጥረን ይገባል። 2 በዚህ መሠረት
መጋቢዎች ታማኝ ሆነው መገኘት ይገባቸዋል። 3 ነገር ግን በእናንተ ወይም በየትኛውም ፍርድ ቤት መፈረድ ካለብኝ ለእኔ በጣም ትንሽ ነገር ነው። 4 እኔ በራሴ
እንኳ አልፈርድም። እኔ ምንም ክስ የለብኝም ግን ፍጹም ነኝ ማለቴ አይደለም። በእኔ የሚፈርድ ጌታ ነው። 5 ስለዚህ ጊዜ ሳይደርስ፥ ጌታ ከመምጣቱ በፊት
ስለምንም ነገር አትፍረዱ።እርሱም በጨለማ የተሰወረውን ወደ ብርሃን ያወጣል፤ የልብንም አሳብ ይገልጣል። በዚያን ጊዜ እያንዳንዱ ሰው የሚገባውን ምስጋና
ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቀበላል። 6 እንግዲህ ወንድሞችና እህቶች ሆይ፦ "ከተጻፈው አትለፍ" የሚለውን ትርጉሙ ከእኛ መማር እንድትችሉ ስለ እናንተ ስል
ለራሴና ለአጵሎስ እንደ ምሳሌ ተናገርሁ። ይህ ማናችሁም አንዳችሁ በሌላኛችሁ እንዳትታበዩ ነው። 7 በእናንተና በሌሎች መካከል ምን ልዩነት አለ? በነጻ
ያልተቀበልከውስ ምን አለህ? በነጻ የተቀበልከው ከሆንህ እንዳልተቀበልህ የምትመካ ስለ ምንድን ነው? 8 አሁን የምትፈልጉት ሁሉ አላችሁ! አሁንስ ባለ
ጠጎች ሆናችኋል! ከእኛ ተለይታችሁ መንገሥ ጀምራችኋል! በርግጥ እኛ ከእናንተ ጋር መንገሥ እንድንችል እናንተ ብትነግሡ በተመኘሁ ነበር። 9 እግዚአብሔር
እኛን ሐዋርያቱን ሞት እንደ ተፈረደባቸው ሰዎች ከሁሉ ይልቅ የኋለኞች ያደረገን ይመስለኛል። ለዓለም፥ ለመላእክትና ለሰዎች መታያ ሆነናልና። 10 እኛ ስለ
ክርስቶስ ሞኞች ነን፤ እናንተ ግን በክርስቶስ ጥበበኞች ናችሁ፤ እኛ ደካሞች ነን፤ እናንተ ግን ብርቱዎች ናችሁ እናንተ የከበራችሁ ናችሁ፤እኛ ግን የተዋረድን ነን።
11 እስከዚህ ሰዓት ድረስ እንራባለን፤ እንጥማለን፤ እንራቆታለን፤ ያለርኅራኄ እንደበደባለን፤ ራሳችንን የምናስጠጋበት ስለሌለን እንክራተታለን። 12 በገዛ እጃችን
እየሠራን እንደክማለን፤ ሲሰድቡን እንመርቃለን፤ ሲያሳድዱን እንታገሣለን። 13 ክፉ ሲናገሩን እንማልዳለን፤ እስከ አሁን ድረስ የዓለም ጥራጊ የሁሉም ጉድፍ
ሆነናል። 14 እነዚህን ነገሮች የጻፍኩላችሁ ላሳፍራችሁ ሳይሆን እንደ ተወደዱ ልጆቼ አድርጌ እንድትታርሙ ልገስጻችሁ ነው። 15 በክርስቶስ ብዙ እልፍ አዕላፋት
አሳዳጊዎች ቢኖሩአችሁ እንኳ ብዙ አባቶች የሉአችሁም። እኔ ግን በኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌል ልጆቼ ናችሁ። 16 እንግዲህ እኔን እንድትመስሉ እለምናችኋለሁ።
17 እንግዲህ የተወደደና ታማኝ የሆነውን በጌታ ልጄን ጢሞቲዎስን የላክሁላችሁ ለዚህ ነው ። እኔም በየስፍራውና በየአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እንደማስተምር፤
በክርስቶስ ያሉትን መንገዶቼ እርሱ ያሳስባችኋል። 18 አንዳንዶቻችሁ ግን ወደ እናንተ የማልመጣ መስሎአችሁ በትዕቢት የምትመላለሱ አላችሁ። 19 ነገር ግን
ጌታ ቢፈቅድ ፈጥኜ ወደ እናንተ እመጣለሁ። እነዚህ በትዕቢት የሚመላለሱት የሚናገሩትን ብቻ ሳይሆን ኃይላቸውንም ለማወቅ እሞክራለሁ። 20 ምክንያቱም
የእግዚአብሔር መንግሥት በኃይል ነው እንጂ በቃል ብቻ አይደለምና። ምን ትፈልጋላችሁ? 21 በበትር ወይስ በፍቅርና በትህትና መንፈስ እንድመጣባችሁ
ትፈልጋላችሁ?

---

1 Corinthians 4:1

1ቆሮንቶስ 4፥1-2
በዚህ መሠረት መጋቢዎች ትኩረት፦ «ከእነዚህ መጋቢዎች የተነሣ እኛ» መጋቢዎች ታማኝ ሆነው መገኘት ይገባቸዋል ትኩረት፦ « እንዲህ እንድንሆን ይገባል»

1 Corinthians 4:3

1ቆሮንቶስ 4፥3-4
እኔ በእናንተ መፍረዴ ለኔ ትንሽ ነገር ነው ጳውሎስ በሰውና በእግዚአብሔር ፍርድ መካከል ያለውን ልዩነት ያመዛዝናል። ከእግዚአብሔር እውነተኛ ፍርድ ጋር ሲመዛዘን የሰው ፍርድ የማይጠቅም ነው። የሚመሠረትብኝ ክስ እንዳለ አላውቅም ትኩረት፦ «ማንኛውንም ክስ አልሰማሁም» ይህ ማለት ግን እኔ ንጹሕ ነኝ አይደለም። እኔ ንጹሕ መሆኔን ወይም አለመሆኔን ጌታዬ ያውቃል።»

1 Corinthians 4:5

1ቆሮንቶውስ 4፥5
ስለዚህ አትፍረዱ ጌታ ሲመጣ ሰለሚፈርድ እኛ እንፍረድ ጌታ ከመምጣቱ በፊት የጌታ ዳግም መምጣትን ያመለክታል በጨለማ የተሠወረውን ወደ ብርሃን ያመጣል እንዲሁም የልብንም አሳብ ይገልጣል እግዚአብሔር የሰውን አሳብና ዓለማ ይገልጣል። በእግዚአብሔር ፊት የተሰወረ ነገር የለም። የልብ «የሰው ልብ»

1 Corinthians 4:6

1ቆሮንቶስ 4፥6-7
ስለ እናንተ «ስለ እናንተ በጎነት» ከተጻፈው በላይ አትለፍ «በቅዱሳት መጻሕፍት ከተጻፈው ውጪ አታድርግ» (TFT) በእናንተና በሌሎች መካከል ልዩነት ቢያዩ ጳውሎስ በጳውሎስ ወይም በአጵሎስ በማመናቸው የተሻሉ እንደሆኑ የሚያስቡትን የቆሮንቶስ ሰዎች ገሰጻቸው። ትኩረት፦«እናንተ በሌሎች ሰዎች ላይ የበላይ አይደላችሁም።» በነፃ ያልተቀበልካው ምን አለህ?
ጳውሎስ እግዚአብሔር በነፃ እንደሰጣቸው ይገልጻል። ትኩረት፦ «ማንኛውንም ያላችሁ ነገር ሁሉ እግዚአብሔር የሰጣችሁ ነው!»

የተቀበልከው ከሆንህ እንዳልተቀበልህ የምትመካ ስለ ምንድን ነው? ጳውሎስ በተቀበሉት ነገር በመመካታቸው ይገስጻል። ትኩረት፦ «ለመመካት መብት የላችሁም።» ወይም በምንም አትመኩ።»

1 Corinthians 4:8

1ቆሮንቶስ 4፥8-9
እግዚአብሔር እኛን ሐዋርያትን መታያ እድርጎ አስቀመጠን ጳውሎስ ሐዋርያቱን እግዚአብሔር እንዴት ለዓለም እንዲታዩ መታያ እንዳለደረገ ሁለት መንገዶችን ይገልጻል። እኛን ሐዋርያትን መታያ አደረገን እግዚአብሔር ሐዋርያቱን እስረኛ በመጨረሻ ለስቅለት ራሳቸውን ትሑት አድርገው እንደሚቀርቡ እንደ ሮማ ወታደራዊ ሰልፍ ገልጣቸው።

ለሞት እንደተፈረደባቸው ሰዎች እግዚአብሔር ሐዋርያትን ለስቅለት እንደቀረቡ ሰዎች አጋልጦአቸዋል።

ለመላእክቱና ለሰዎች ለመንፈሳውያንና ለሰው

1 Corinthians 4:10

1ቆሮንቶስ 4፥10-11
እኛ ስለ ክርስቶስ ሞኞች ነን እናንተ ግን በክርስቶስ ጥበበኞች ናችሁ ጳውሎስ የዓለምን አመለካከት ለማሳፈርና በክርስቶስ ለማመን የክርስትናን አመለካከት በተቃራኒ መንገድ ይጠቀማል። እኛ ደካሞች ነን እናንተ ግን ብርቱዎች ናችሁ ጳውሎስ የዓለምን አመለካከትንና በክርስቶስ ለማመን የክርስትና አመለካከትን በታቃራኒ መንገድ ይጠቀማል። እናንተ የከበራችሁ ናችሁ «የቆሮንቶስ ሰዎች በክብር ይዞአችኋል» እኛ የተዋረድን ነን «እኛን ሐዋርያቱን ሰዎች በውርደት ይዘውናል» እስከዚህ ሰዓት ትኩረት፦ «እስከዚህ ደረስ» ወይም «እስካሁን ድረስ» በጭካኔ/ ያለርኅራኄ ተደብድበዋል ትኩረት፦ «በአካላዊ ጉዳት ይቀጣል»

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Corinthians 4:12

1ቆሮንቶስ 4፥12-13
ሲሰድቡን እንመርቃለን «ሰዎች እኛን ሲሰድቡን እንመርቃቸዋለን»

ሲሳደቡ ትኩረት፦ «ሲሳደቡ» በሚቻለው፦ «ሲቃወሙ» ወይም «ሲረግሙን»(UDB) ሲያሳድዱን «ሰዎች እኛን ሲያሳድዱ» ክፉ ሲናገሩብን «ሰዎች ተገቢ ያልሆነውን ሲናገሩብ» በዚህ ዓለም የተጣልን ሆነናል « ሰዎች እኛን የዚህ ዓለም ጥራጊ አድርገው ቆጥረውናል»

1 Corinthians 4:14

1ቆሮንቶስ 4፥14-16
እናንተን ለማሳፈር ሳይሆን እንድትታረሙ ነው «እናንተን ላሳፍራችሁ ሳይሆን እንድትሻሸሉ ነው» ወይም «እንድታፍሩ እያደረግሁ ሳይሆን እናንተን ለማረም ነው» (UDB) ለማስተካከል "እንድትሻሸሉ» ወይም «የተሻላችሁ እንድትሆኑ» እንልፍ አእላፋት የሚያስተምሩአችሁ ይህ የአንድ ሰው መንፈሳዊ አባት አስፈላጊነት እነርሱንም የሚመሩአቸው የሰዎች የተጋነነ ቁጥር አጉልቶ ለማሳየት ነው። ሕፃናት አባት ጳውሎስ እነርሱን ወደ ክርስቶስ ስለ መራቸው ለቆሮንቶስ ሰዎች እንደ አባት ነው። ማሳሰብ «በብርቱ ማበረታታት» ወይም «በብርቱ ማሳሰብ»

1 Corinthians 4:17

1ቆሮንቶስ 4፥17-18
አሁን ይህ ዓለም የሚያሳየው ጳውሎስ እብሪተኛ የሆኑትን የቆሮንቶስ አማኞችን ባሕርይ ለመገሰጽ ርዕሱን መቀየሩ ነው።

1 Corinthians 4:19

1ቆሮንቶስ 4፥19-21
ወደ እናንተ እመጣለሁ «እናንተን እጎበኛለሁ» በቃል አይደለም ትኩረት፦ «በቃል የሚደረግ አይደለም» ወይም «በቃላት የምትናገሩት አይደለም» ምን ትፈልጋላችሁ ጳውሎስ የቆሮንቶስን ሰዎች ስላደረጉት ስሕተት እየገሰጻቸው የመጨረሻ ልመና ያቀርብላቸዋል። ትኩረት፦ «አሁን ምን እንዲሆነላችሁ እንደምትፈልጉ ንገሩኝ» በበትር ወይም በፍቅርና በትህትና መንፈስ ልምጣባችሁን? ጳውሎስ የቆሮንቶስን ሰዎች በሁለት ተቃራኒ አስተሳሰቦችን ያቀርብላቸዋል። ትኩረት፦ «ወደ እናንተ በጭካኔ ትምህርት ልምጣን? ወይም «በትህትና መንፈስ ፍቅርን ላሳያችሁን?»

ትህትና ትኩረት፦ «በርኅራኄ» ወይም «በትህትና»

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 5

1 በእናንተ መካከል ዝሙት እንዳለ ሰምተናል፤የዚያም ዓይነት ዝሙት በአሕዛብ መካከል እንኳ ተሰምቶ የማይታወቅ ነው። እንደሰማነው ከእናንተ አንዱ ከእንጀራ
እናቱ ጋር የሚተኛ አለ። 2 ስለዚህ በትዕቢት የምትመላለሱ አይደላችሁምን? በዚህም ልታዝኑ አይገባችሁምን? ይህን ያደረገ ሰው ከመካከላችሁ ሊወገድ
ይገባል። 3 እኔ በአካል ከእናንተ ጋር ባልሆንም በመንፈስ ከእናንተ ጋር አለሁ፤ከእናንተም ጋር እንዳለሁ ሆኜ ይህን ባደረገው ሰው ላይ በጌታችን በኢየሱስ
ክርስቶስ ስም አሁን ፈርጄበታለሁ። 4 እናንተ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በምትሰበሰቡበት ጊዜ መንፈሴም ከጌታችን ኢየሱስ ኃይል ጋር እዚያው
በመካከላችሁ አለ። 5 ይህ ሰው በጌታ በኢየሱስ ቀን ይድን ዘንድ፤ ለሥጋው ጥፋት ለሰይጣን እንዲሰጥ ፍርዴ ነው። 6 መመካታችሁ መልካም አይደለም።
ጥቂት እርሾ ሊጡን ሁሉ እንደሚያቦካ አታውቁምን? 7 እንግዲህ እርሾ የሌለ እንጀራ ሆናችሁ አዲሱን ሊጥ ትሆኑ ዘንድ ከአሮጌው እርሾ ራሳችሁን አንጹ።
ምክንያቱም የፋሲካችን በግ የሆነው ክርስቶስ ታርዶአል። 8 ስለዚህ በአሮጌ እርሾ በመጥፎ አስተሳሰብና በክፋት ሳይሆን በቅንነትና በእውነት በዓልን እርሾ
በሌለ ቂጣ እናድርግ። 9 ዝሙትን ከሚያደርጉ ሰዎች ጋር ኅብረት እንዳታደርጉ በመልእክቴ ጽፌላችሁ ነበር። 10 በምንም ነገር የዚህን ዓለም ዝሙት
ከሚያደርጉትን ወይም ገንዘብን ከሚመኙትን፥ ከነጣቂዎችንም፤ወይም ጣዖትን ከሚያመልኩትን ከማያምኑት አትተባበሩ። እንዲህ ቢሆን ኖሮ ከዓለም መውጣት
በተገባችሁ ነበር። 11 አሁን ግን በክርስቶስ ወንድሞች ወይም እህቶች ተብለው ከሚጠሩት ከማናቸውም ዝሙትን ከሚያደርግ ወይም ገንዘብን ከሚመኝ ወይም
ጣኦትን ከሚያመልክ ወይም ተሳዳቢ ወይም ሰካራም ወይም ነጣቂ ቢሆኑ ከእነርርሱ ጋር እንዳትተባበሩ እጽፍላችኋለሁ። እንደነዚህ ካሉት ጋር አብራችሁ እንኳን
አትብሉ። 12 ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ባሉ ሰዎች ላይ ለመፍረድ እንዴት እደፍራለሁ? በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባሉ ሰዎች ላይ እናንተ አትፈርዱምን? 13 ከቤተ
ክርስቲያን ውጭ ባሉቱ ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል። "ክፉውን ከመካከላችሁ አውጡት።"

---

1 Corinthians 5:1

1ቆሮንቶስ 5፥1-2
በአህዛብ ዘንድ እንኳን ተሰምቶ የማይታወቅ «አህዛብ እንኳን የማይፈቅዱት» የእንጀራ እናት የአባቱ ሚስት ግን የራሱ እናቱ አይደለችም። በዚህ ማፈር
የለባችሁምን? ይህ ፈሊጣዊ አዘል ጥያቄ ክርስቲያኖችን ለማሳዘን ጥቅም ላይ ውለዋል።) ይህን ያደረገ ሰው ከመካከላችሁ መወገድ አለበት «ይህን
ያደረገውን ከመካከላችሁ ማስወገድ አለባችሁ»

1 Corinthians 5:3

1ቆሮንቶስ 5፥3-5
በመንፈስ አብሮ መሆን ጳውሎስ በአሳቡ ከእነርሱ ጋር ነው። «በአሳቤ ከእናንተ ጋር ነኝ» በዚህ ሰው ላይ እኔ ፈጄበታለሁ «ይህ ሰው ጥፋተኛ ሆኖ
አግኝቻለሁ» በአንድ ላይ መሆን «መገነኘት» በጌታችን በኢየሱስ ስም ኢየሱስ ክርስቶስን ለማምለክ አንድ ላይ ለመሰብሰብ ፈሊጣዊ አነጋገር ይህን ሰው
ለሰይጣን አሳልፎ መስጠት ይህ የሚያመለክተው ሰውየውን ከእግዚአብሔር ሕዝብ ተለይቶ ከቤተ ክርስቲያን ውጪ በዓለም ውስጥ በሰይጣን ግዛት
ይኖራል። ለሥጋው ጥፋት ሰውየው ስለ ኅጢአቱ በአካላዊ ሕመም እግዚአብሔር ይቀጠዋል።

1 Corinthians 5:6

1ቆሮንቶስ 5፥6-8
መመካታችሁ መልካም አይደለም «መመካታችሁ መጥፎ ነው» ጥቂት እርሾ ሊጡን ሁሉ እንደሚያቦካ አታውቁምን? ጥቂት እርሾ እንጀራን ሁሉ
እንደሚያደርስ ሁሉ ጥቂት ኅጢአት የአማኞችን ኅብረት ሁሉ ሊያበለሽ ይችላል። መስዋዕት ሆኖአል «ጌታ እግዚአብሔር ክርስቶስ ኢየሱስን መስዋዕት አደረገው።» ክርስቶስ የፋሲካችን በግ ታርዶአል የፋሲካ በግ
የእስራኤልን ኅጢአት በእምነት እንደሚሸፍን የክርስቶስ ሞት በክርስቶስ ለሚያምኑት ኅጢአትን በክርስቶስ ለዘላለም ይሸፍናል።

1 Corinthians 5:9

1ቆሮንቶስ 5፥9-10
ዝሙትን የሚያደርጉ ሰዎች በክርስቶስ እንደሚያምኑ የሚያስመስሉ ግን በዚህ ሁኔታ የሚመላለሱትን የሚያመለክት ዝሙትን የሚያደሩ የዚህ ዓለም ሰዎች
በጌታ የማያምኑ በዝሙት ሕይወት ለመኖር ምርጫቸው ያደረጉ ስግብግብነት «ስግብግብ የሆኑ ሰዎች» ወይም «ማንኛውም ሰው ያለውን ሁሉን ነገር
የሚፈልጉ ሰዎች» ነጣቂዎች ይህ ማለት የሚያታልሉ ሰዎች ወይም የሌሎችን ገንዘብ ወይም ንብረት የሚያጭበረብሩ። ከእነርሱ መለየት ቢሆን ከዓለም
መውጣታችሁ ነበር በዓለም ከእንዲህ ዓይነት ተግባር ነፃ የሆነ ቦታ የለም። ትኩረት፦-«ከእነርሱ መለየት ቢሆን ከሁሉንም ሰው ማስወገድ ያስፈልግ
ነበር።»

1 Corinthians 5:11

1ቆሮንቶስ 5፥11-13
ማንም የተጠራ ማንም ሰው ራሱን በክርስቶስ አማኝ ብሎ የሚጠራ ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ባሉት ላይ እንዴት እፈርዳለሁ? ትኩረት፦ «የቤተ ክርስቲያን
ባልሆኑ ሰዎች ላይ እኔ አልፈድም።» በቤተ ክርስቲያን ባሉ ሰዎች እናንተ አትፈርዱምን? «በቤተ ክርስቲያን ባሉት ላይ እናንተ መፍረድ አለባችሁ»

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 6

1 ከእናንተ አንድ ሰው ከሌላ ሰው ጋር ክርክር ቢኖረው፤ በቅዱሳን ፊት ስለጉዳዩ ከመነጋገር ይልቅ በማያምን ዳኛ ፊት ለመቆም ወደ ፍርድ ቤት ለመሄድ ይደፍራልን? 2 ቅዱሳን በዓለም ላይ እንደሚፈርዱ አታውቁምን? በዓለም ላይ የምትፈርዱ ከሆነ፤ በትናንሽ ጉዳዮችን መፍረድ እንዴት ይሳናችኋል? 3 በመላእክት ላይ እንኳ እንደምንፈርድ አታውቁምን? እንግዲህ በዚህ ዓለም ሕይወት ጉዳዮች ላይ የበለጠ ለመፍረድ እንዴት አንችልም? 4 ለዕለታዊ ጠቃሚ ጉዳዮች ላይ መፍረድ ካለባችሁ በቤተ ክርስቲያን መካከል ለሚነሱ ክርክሮች የማያምኑ ሰዎችን እንዲፈርዱ ታስቀምጣላችሁን? 5 አሳፍራችሁ ዘንድ ይህን እላለሁ። እንደዚህ ነውን? በወንድሞችና እህቶች መካከል ክርክሮችን ሊፈታ የሚችል አንድ አስተዋይ ሰው በእናንተ ዘንድ አይገኝምን? 6 ነገር ግን አንዱ አማኝ ሌላውን አማኝ ለመክሰስ በማያምን ዳኛ ፊት ለመቆም ይሄዳልን? 7 እንግዲህ በክርስቲያኖች መካከል የእርስ በርስ ማንኛውም ክርክር ቢኖርባችሁ ለእናንተ ሽንፈት ነው። ብትበደሉ አይሻልምን? ብትታለሉስ እይሻልምን? 8 ነገር ግን እናንተ ወድሞቻችሁንና እህቶቻችሁን ትበድላላችሁ ታታልሉማላችሁ። 9 ዓመጸኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደማይወርሱ አታውቁምን? በሐሰት አታምኑ። ዝሙት አድራጊዎች ቢሆኑ፣ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ፥ ወይም አመዝሮች ወይም ግብረ ሶዶማውያኖች ቢሆኑ፤ ወይም ሌቦች፥ ወይም ስግብግቦች፤ ወይም ሰካራሞች፣ ወይም ተዳዳቢዎች፥ 10 ወይም ነጣቂዎች፥ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም። 11 ከእናንተም አንዳንዶቻችሁ እንዲሁ ነበራችሁ። ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል፥ ተቀድሳችኋል፤ ጸድቃችሁማል። 12 ሁሉ ተፈቅዶልኛል፤ነገር ግን ሁሉም የሚጠቅም አይደለም። ሁሉ ተፈቅዶልኛል ነገር ግን በእኔ ላይ ምንም ነገር አይሠለጥንብኝም። 13 "መብል ለሆድ ነው፤ ሆድም ለመብል ነው።" እግዚአብሔር ግን ይህንም ያንም ያጠፋቸዋል። ሥጋ ግን ለጌታ ነው እንጂ ለዝሙት አይደለም። ይልቁን ሥጋችንም ለጌታ ነው፤እንዲሁም ጌታ ለሥጋ ያዘጋጃል። 14 እግዚአብሔርም ደግሞ ጌታን አስነሣ እኛንም በኃይሉ ያስነሣናል።ሥጋችሁ የክርስቶስ ብልቶች እንደሆነ አታውቁምን? 15 እንግዲህ የክርስቶስን ብልቶች ወስጄ የሴተኛ አዳሪ ሴት ብልቶች ላድርጋቸውን? ሊሆን አይችልም። 16 ከሴተኛ አዳሪ ጋር የሚተባበር ከእርስዋ ጋር አንድ ሥጋ እንዲሆን አታውቁምን? "ሁለቱ አንድ ሥጋ ይሆናሉ" በእግዚአብሔር ቃል ተጽፎአል። 17 ከጌታ ጋር የሚተባበር ግን ከእርሱ ጋር አንድ መንፈስ ነው። 18 ከዝሙት ሽሹ። ሰው የሚያደርገው ሌላ ኃጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጭ ነው፤ ዝሙትን የሚያደርግ ሰው ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአትን ያድርጋል። 19 ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁትና በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? 20 በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም። ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።

---

1 Corinthians 6:1

1ቆሮንቶስ 6፥1-3
ክርክር ትኩረት፦ «አለመስማማት»ወይም «ሙጉት» ከአማኞች ይልቅ ወደ ማያምን ዳኛ ፊት ለመቆም ወደ መንግሥት ፍርድ ቤት ለመሄድ ይደፍራልን? ጳውሎስ ክርስቲያኖች በመካከላቸው አለመስማማት ቢኖር ራሳቸው መፍታት አለባቸው ይላል። ትኩረት፦«ክርስቲያን ባልንጀራችሁን በማያምን ዳኛ ፊት አትክሰስ። ክርስቲያን ባልንጀራዎች አለመስማማታቸውን ራሳቸው መካከል መፍታት አለባቸው።» መንግሥት ፍርድ ቤት መንግሥት በአካባቢ ባለው ጉዳዮችን የሚፈርድበትና ትክክል የሆነውን የሚወስንብት አማኞች በዓለም ላይ እንደሚፈርዱ አታውቁምን? ጳውሎስ ወደ ፊት በዓለም ላይ እንደሚፈረድ ያመለክታል። በዓለም ላይ የምትፈርዱ ከሆነ በትናንሽ ጉዳዮችን መፍረድ እንዴት ይሳናችኋል? ጳውሎስ ወደ ፊት በአጠቃላይ በዓለም ላይ የመፈረድ ኃላፊነትና ችሎታ እንደሚሰጥ ይናገራል፤ ስለዚህ በትናንሽ ጉዳዮች ላይ ራሳቸው መፍረድ አለባቸው። ትኩረት፦«ለወደ ፊት በዓለም ላይ ትፈርዳላችሁ ስለዚህ ይህን ጉዳይ መፍታት ትችላላችሁ።» . በመላእክት ላይ እንደምትፈርዱ አታውቁምን? «በመላእክት ላይ እንደምትፈዱ ታውቃላችሁ» እኛ ጳውሎስ ራሱንና የቆሮንቶስ ሰዎችን ይጨምራል። በዚህ ሕይወት ጉዳዮች ላይ የበለጠ መፍረድ እንደምንችል አታውቁምን? ትኩረት፦ «ምክንያቱም በመላእክት ላይ የመፍረድ ኃላፊነትና ችሎታ ስለተሰጠን በርግጠኝነት በሕይወት ጉዳዮች ላይ መፍረድ እንችላለን።»

1 Corinthians 6:4

1ቆሮንቶስ 6፥4-6
ለዕለታዊ ኑሮ የሚያስፈልገው ጉዳይ ላይ መፍረድ ካለባችሁ ትኩረት፦ «ስለ ዕለታዊ ህይወት ለመወሰን የተጠራችሁ ከሆነ» ወይም «በዚህ አስፈላጊ ሕይወት ላይ መፍታት ካለባችሁ» (UDB) እንዲህ ያሉ ጉዳዮችን ለምን ታስቀምጣላችሁ «እንዲህ ያሉ ጉዳዮችን መስጠት የለባችሁም» በቤተ ክርስቲያን የማያምኑ ሰዎች ጳውሎስ እነዚህን ነገሮች እንዴት እንደሚይዙ የቆሮንቶስ ሰዎችን ይገስጻቸዋል። አማራጭ ትርጉሞች 1)«እንዲያ ያሉትን ነገሮች ለመወሰን ተገቢ ያልሆኑትን አባላትን እንዲህ ያሉትን ጉዳዮች መስጠት አቁሙ» ወይም 2) «እንዲህ ያሉትን ጉዳዮች ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ላሉ ሰዎች መስጠት አቁሙ» ወይም 3) «በሌሎች አማኞች መልካም ሆኖ ላልተቆጠሩ አባላት እንኳን እንዲህ ያሉትን ጉዳዮችን መስጠት የለባችሁም።» ላሳፍራችሁ ትኩረት፦ «ለእናንተ ውርደት» ወይም «በዚህ ጉዳይ ላይ እንዴት እንደ ወደቃችሁ ለማሳየት» (UDB) በወንድሞችና እህቶች መካከል ያለ ክርክር ለመፍታት በመካከላችሁ አስተዋይ ሰው የለምን? ትኩረት፦ «በአማኞች መካከል ያለውን ክርክር የሚፈታ አንድ አስተዋይ ሰው ማግኘት ትችላላሁ።» ክርክር/ሙግት «ክርክር» ወይም «አለመስማማት» ነገር ግን እንዳለ ትኩረት፦ «ነገር ግን አሁን ባለው ሁኔታ» ወይም «ነገር ግን በዚህ ፈንታ» (UDB) አንዱ አማኝ ሌላውን ለመክሰስ በማያምን ዳኛ ፊት ለመቆም ወደ ፍርድ ቤት ይሄዳል ትኩረት፦ «እርስ በርሳቸው ክርክር ያለባቸው አማኞች የማያምን ዳኛ ስለ ጉዳያቸው እንዲፈርድላቸው ይጠትቃሉ» ይህ ጉዳይ ይቀርባል «ይህን ጉዳይ አማኝ ያቀርባል»

1 Corinthians 6:7

1ቆሮንቶስ 6፥7-8
ሽንፈት ትኩረት፦ «ውድቀት» ወይም «ኪሳራ» መበደል አይሻልምን? መታለል አይሻልምን? ትኩረት፦«ሌሎች ቢበድሉና ወደ ፍርድ ቤት ቢወሰዱና ቢያታልሉ ይሻላል» ማታለል ትኩረት፦ «ማሳሰት» ወይም «ማሳት» የራሳችሁ ወንድሞችና እህቶች ሁሉም በክርስቶስ የሆኑ አማኞች እርስ በርሳቸው ወንድሞችና እህቶች ናቸው። ትኩረት፦ «የራሳችሁ በእምነት ባልንጀሮች ናችሁ።»

1 Corinthians 6:9

1ቆሮንቶስ 6፥9-11
ይህን አታውቁምን? ጳውሎስ ይህን እውነት አስቀድሞ እንደሚያውቁ ያብራራል። ትኩረት፦«ይህን አስቅድማችሁ ታውቃላችሁ» አመፀኞች አይወርሱም «ጸድቃን ብቻ ይወርሳሉ» የእግዚአብሔርን መንግሥት ይወርሳሉ እግዚአብሔር እንደ ጸድቃን አይፈርድባቸውም፥ ወደ ዘላለም ሕይወት አይገቡም። ግብረ ሰዶማውያን ወንድ ከወንድ ጋር የሚተኙ ዝሙተኞች የግብረ ሰዶማዊ ልምምድ የሚያደርጉ ወንድ ሆኖ ከሌላ ወንድ ጋር የሚተኙ ሌቦች «ከሌሎች የሚሰርቁ ሰዎች» ወይም «ነጣቂዎች» ስግብግቦች ትኩረት፦ «ከሌሎቹ ይልቅ ተስገብግቦ ብዙ የሚወስዱ ሰዎች» አጨበርባሪዎች ትኩረት፦ «አታላዮች» ወይም «በእንርሱ ላይ እምነት ከጣሉባቸው ሰዎች የሚሰርቁ»(UDB) ታጥባችኋል እግዚአብሔር ንፁሕ አድርጎአችኋል ለእግዚአብሔር ተለይታችኋል/ተቀድሳችኋል ትኩረት፦ «እግዚአብሔር ለራሱ ቀድሶአችኋል» ወይም «እግዚአብሔር ቅዱሳን አድርጎአችኋል»

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ከእግዚአብሔር ጋር ጸድቃችኋል እግዚአብሔር ከራሱ ጋር ጻድቃን አድርጎአችኋል

1 Corinthians 6:12

1ቆሮንቶስ 6፥12-13
«ሁሉም ተፈቅዶልኛል» ትኩረት፦ «አንዳንዶች እንዲህ ይላሉ፥'ማንኛውንም ነገር ማድረግ እችላለሁ' ወይም «ማንኛውንም ነገር ለማድረግ ተፈቅዶልኛል» ነገር ግን ሁሉም አይጠቅመኝም «ነገር ግን ሁሉ ለእኔ መልካም አይደለም.» በማናቸውም አይግዛም/ማናቸውም አይሠለጥኑብኝም ትኩረት፦ «እነዚህ ነገሮች አንዳቸውም በእኔ ላይ ጌታ ሆነው አይሠለጥኑብኝም» «ምግብ ለሆድ ነው፥ሆድም ለምግብ ነው፤» ነገር ግን እግዚአብሔር ሁለቱንም ያጠፋቸዋል ትኩረት፦ «አንዳንዶች እንዲህ ይላሉ፥ 'ምግብ ለሆድ ነው፤ሆድም ለምግብ ነው' ነገር ግን እግዚአብሔር ምግብንም ሆድንም ያጠፋቸዋል» ሆድ የሚታይ አካል ያጠፋል «ማጥፋት»

1 Corinthians 6:14

1ቆሮንቶስ 6፥14-15
ጌታን አስነሣ ኢያሱስን አስነሥቶ ሕያው አደርገ የአካል ብልቶቻችሁ የክርስቶስ እንደሆኑ አታውቁምን? እጃችንና እግራችን የአካላችን ክፍሎች እንደ ሆኑ አካላችንም የክርስቶስ አካላት፥የቤተ ክርስቲያን ናቸው። ትኩረት፦ «አካላችሁ የክርስቶስ ነው»
የክርስቶስን አካል ወስጄ ከሴተኛ አዳሪ ጋር አንድ ላድርጋውን? ትኩረት፦«እናንተ የክርስቶስ አካል ናችሁ። የሴተኛ አዳሪ ጋር አንድ አላደርጋችሁም።»

ሊሆን አይችልም ትኩረት፦ «ይህ ሊሆን የሚገባ አይደለም!»

1 Corinthians 6:16

1ቆሮንቶስ 6፥16-17
ይህን አታውቁምን? «ይህን አስቀድማችሁ ታውቃላችሁ።» ጳውሎስ አስቀድሞ የሚያውቁትን እውነትየገልጥላቸዋል።

ነገር ግን ከጌታጋር አንድ ሆነ ከእርሱ ጋር አንድ መንፈስ ይሆናል ትኩራት፦ «አንድ ሰው ከጌታ ጋር አንድ የሆነ ከጌታ ጋር አንድ መንፈስ ይሆናል።»

1 Corinthians 6:18

1ቆሮንቶስ 6፥18
መሸሽ የአንድ ሰው በአካላዊ ሁኔታ መሸሸ ከመንፈሳዊ ሁኔታ ኀጢአትን ከመቃወም ጋር ሲነጻጸር ነው። ትኩረት፦ «ሸሽ» መተላልፍ «ማድረግ» ወይም «ማከናወን» «ሌላ ኀጢአት ከአካል ውጭ ይደረጋል» ነገር ግን ዝሙትን የሚያደርግ ግን በገዛ ሥጋው ነው የዝሙት ኀጢአት በሰው በራሱ አካል በሽታ መያዝ የሚችልበት ሲሆን፥ ነግር ግን ሌላ ኀጢአት በዚያው መንገድ አካልን አይጎደም።

1 Corinthians 6:19

`1ቆሮንቶስ 6፥19-20
አታውቁምን? «አስቀድማችሁ ታውቃላችሁ» ጳውሎስ ይህን እውነት አስቀድሞ እንድሚያቁ ያስረዳቸዋል። ሰውነታችሁ የእያንዳንዱ ክርስቲያን አካል የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ነው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ቤተ መቅደስ ለመለኮት የተለየ ነው እንዲሁም የመለኮትም ማደሪያ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ የአንድ ክርስቲያን አማኝ አካል እንደ ቤተ መቅደስ የመንፈስ ቅዱስ የሚገኝበት ነው። በዋጋ ተገዝታችኋል እግዚአብሔር ለቆሮንቶስ ሰዎች ከባርነት ነፃ እንዲወጡ ዋጋ ከፍሎላቸዋል። ትኩረት፦«እግዚአብሔር ለእናንተ ነፃነት ዋጋ ከፍሎላችኋል።» ስለዚህ ትኩረት፦ «እንግዲህ» ወይም «ይህ እውነት ስለሆን» ወይም «ከዚህ እውነት የተነሣ»

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 7

1 እንግዲህ ስለጻፋችሁኝ ነገር ሰው ከሴት ጋር አለመገናኘት መልካም ነው። **2** ነገር ግን ስለ ዝሙት ፈተና ምክንያት እንዳይሆን እያንዳንዱ ሰው የራሱ ሚስት ይኑረው፤ እንዲሁም ለእያንዳንዱ ሴት የራስዋ ባል ይኑራት። **3** ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላት፤ እንደዚሁም ደግሞ ሚስቲቱ ለባልዋ የሚገባትን ታድርግ። **4** ሚስት በገዛ ሰውነትዋ ላይ ሥልጣን ያላትም፤ ሥልጣን ለባልዋ ነው እንጂ፤ እንዲሁም ባል በገዛ ሰውነቱ ላይ ሥልጣን የለውም ሥልጣን ለሚስቱ ነው እንጂ። **5** በጸሎት ለመትጋት ተስማምታችሁ ለጊዜው ካልሆነ በቀር እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ። ራሳችሁን ስለ አለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈታተናችሁ ደግሞ አብራችሁ መሆን ትችላላችሁ። **6** ዳሩ ግን ይህን እንደ ፈቃድ እላለሁ እንጂ እንደ ትእዛዝ አይደለም። **7** ሰው ሁሉ እንደ እኔ ቢሆን እወዳለሁ። ነገር ግን እያንዳንዱ ሰው ለራሱ ከእግዚአብሔር የተቀበለ አንዱ አንድ ዓይነት ሌላው ሌላ ዓይነት ስጦታ አለው። **8** ላላገቡትና ባሎቻቸው ለሞተባቸው ሴቶች ግን እላለሁ፦ እንደ እኔ ሳያገቡ ቢኖሩ ለእነርሱ መልካም ነው። **9** ነገር ግን ራሳቸውን መግዛት የማይችሉ ከሆነ መጋባት ይሻላል። በምኞት ከመቃጠል ይልቅ መጋባት ይሻላቸዋልና። **10** ደግሞ የተጋቡትን እንዲ ብዬ አዛቸዋለሁ ይህንም እኔ ሳልሆን ጌታ ነው፦ "ሚስት ከባልዋ አትለይ፥ **11** ብትለይ ግን ሳታገባ ትኑር" ወይም "ከባልዋ ጋር ትታረቅ፥እንዲሁም" ባልም ሚስቱን አይፍታት።" **12** ነገር ግን ሌሎችንም ጌታ ሳይሆን እኔ እላለሁ፦ ማንም ያለመነች ሚስት ያለው ወንድም፥ ከእርሱ ጋር ለመኖር ብትስማማ አይፍታት፤ **13** እንዲሁም ያለመነ ባል ያላት ሚስትም ብትኖር፥ ከእርስዋ ጋር ለመኖር ቢስማማ አትፍታው። ያለመነች ሚስት በአማኙ ባልዋ ተቀድሳለችልና፤ **14** እንዲሁም ያለመነ ባል በአማኝ ሚስቱ ተቀድሶአል። አለዚያ ልጆቻቸውሁ ርኩሳን ይሆኑ ነበር፤ አሁን ግን የተቀደሱ ናቸው። **15** የማያምን የትዳር ጓደኛ ግን የሚለይ ከሆነ ይለይ። እንዲህ በሚመስል ነገር ወንድም ወይም እህት በቃል ኪዳን መታሰር የለባቸውም። እግዚአብሔር ግን በሰላም እንድንኖር ጠርቶናል። **16** አንቺ ሴት ባልሽን ታድኚ እንደ ሆንሽ ምን ታውቂአሽ? ወይስ አንተ ሰው ሚስትህን ታድናት እንደ ሆንህ ምን ታውቃለህ? **17** እያንዳንዱ ሰው እንደተጠራው ዓለማና ጌታ በሰጠው ሕይወት ብቻ ይመላለስ። ይህ ለአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የእኔ ድንጋጌ ነው። **18** ማንም ተገርዞ ወደ እምነት ተጠርቶአልን? ወደ አለመገረዝ መመለስ የለበትም። እንዲሁም ማንም ሳይገርዝ ወደ እምነት ተጠርቶአልን? መገረዝ የለበትም። **19** የእግአብሔርን ትእዛዛት መጠበቅ ነው እንጂ መገረዝ ወይም አለመገረዝ የሚያመጠው ችግር የለም። **20** እያንዳንዱ ሰው እግዚአብሔር ለእምነት በጠራበት ጊዜ እንደነበረ ይመላለስ። **21** እግዚአብሔር ሲጠራህ ባሪያ ነበርን? ይህ ለኀድህ አይገባም። ነፃ የምትወጣ ከሆንህ ተቀበለው። **22** አንድ ሰው በጌታ ባሪያ ሆኖ የተጠራ የጌታ ነፃ ሰው ነው፤ እንደዚሁም ነፃ ሆኖ ለእምነት የተጠራ የክርስቶስ ባሪያ ነው። **23** በዋጋ ተገዝታችልኋልና የሰው ባሪያ አትሁኑ። **24** ወድሞችና እህቶች ሆይ፤ እያንዳንዳችን በተጠራንበት እንደዚሁ ሆነን በእግዚአብሔር ዘንድ እንኑር። **25** ላላገቡት የጌታ ትእዛዝ የለኝም። ነገር ግን በጌታ ምሕረት እንደ ታመነ ሰው ሆኜ የራሴን ምክር እሰጣለሁ። **26** ስለዚህ ለችግር ጊዜ መፍትሔ እንዲሆን ሰው ሳያገባ መኖር ከቻለ መልካም ይመስለኛል። **27** በጋብቻ ቃል ኪዳን በሚስት ታስረሃልን? እንዲህ ከሆነ ከዚህ ነፃ ለመሆን አትሻ። በበጋብቻ በሚስት አልታሰርህ ወይም ያላገባህ ነህ? ሚስትን አትሻ። **28** ነገር ግን ካገባህ ኃጢአት አይሆንብህም። እንዲሁም ያላገባች ሴት ብታገባ ኃጢአት አይሆንባትም። ሆኖም ግን የሚያገቡ በኑሮአቸው ብዙ ችግር ይሆንባቸዋል፤ ከእንዲ ዓይነት ሕይወት እንድትርቁ እመኛለሁ። **29** ዳሩ ግን ወንድሞ ሆይ፤ ይህን እላለሁ፤ ዘመኑ አጭር ነው። ከእንግዲህ ወዲህ ሚስቶች ያሉአቸ እንደሌላቸው ይኑሩ። **30** የሚያላቅሱም እንደማያለቅሱ ይሁኑ፤ እንዲሁም የሚደሰቱ ደስታ እንደሌላቸው ይሁኑ፤ **31** ደግሞ ማንኛውንም ነገር የሚገዙ ምንም እንደሌላቸ ይሁኑ፤ በዚህች ዓለም የሚጠቀሙ በሙሉ እንደ ማይጠቀሙ ይሁኑ ምክንያቱም የዚች ዓለም አሠራር ሁሉ አላፊ ነውና። **32** ነገር ግን ያለ ጭንቀት እንድትኖሩ እወዳለሁ። ያላገባው ጌታን እንዴት ደስ እንደሚያሰኘው የጌታን ነገር ያስባል። **33** ያገባው ግን ሚስቱን እንዴት ደስ እንዲያሰኛት የዓለምን ነገር ያስባል፥ ልቡም ተከፍሎአልና። **34** ያላገባች ሴት ወይም ድንግል በሥጋና በመንፈስ እንዴትምትቀደስ የጌታን ነገር ታስባለች። ያገባች ሴት ግን ባልዋን እንዴት ደስ እንደምታሰኘው የዓለምን ነገር ታስባለች። **35** ሌላ ሸክም ለጭንባችሁ ሳይሆን ለራሳችሁ ጥቅም ይህን እላለሁ። ያለ ምንም ጉዳት በጌታ እንድትጸኑ ስለእውነት ይህን እላለሁ። **36** ዳሩ ግን ማንም ሰው ያጫትን ድንግል በአግባቡ ካልያዘ የእርስዋም ዕድሜ እየገፋ ከሄደ ሊያገባት ካሰበ ያግባት። ይህ ኃጢአት የለበትም። **37** ነገር ግን አንድ ሰው ላለማግባት ቢወስንና ስሜቱንም ለመቆጣጠር ከቻለ እርስዋን ባለማግባቱ መልካም ያደርጋል። **38** የእርሱንም እጮኛ የሚያገባት መልካም ያደርጋል፤እርስዋንም ለማግባት የማይመርጥ የበለጠ መልካም ያድርጋል። **39** አንዲት ሴት ባልዋ በሕይወት እስካለ ድረስ ከባልዋ ጋር የታሰረች ናት። ነገር ግን ባልዋ ቢሞት በጌታ የሆነውን ብቻ ለማግባት ነጻነት አላት። **40** እንደ እኔ ውሳኔ ግን ሳታገባ ብትኖር ደስተኛ ትሆናለች። እኔም የእግዚአብሔር መንፈስ ያለኝ ይመስለኛል።

---

1 Corinthians 7:1

1ቆሮንቶስ 7፥1-2
እንግዲህ ጳውሎስ በትምህርቱ አዲስ ርዕስ ያስተዋውቃል። ስለ ጻፋችሁልን ነገሮች የቆሮንቶስ ሰዎች ለጳውሎስ ለአንዳንድ ጥያቄዎች መልስ ፈልገው ደብዳቤ ጽፈውለት ነበር። ለሰው እዚህ ላይ ወንድ ወይም ሴት የትዳር ጓደኛ ይህ መልካም ነው ትኩረት፦ «ይህ ትክክልና ተቀባይነት ያለው ነው» ነገር ግን ስለ ዝሙት ምክንያት ፈተና ትኩረት፦ «ነገር ግን ሰዎች በዝሙት ፈተና ላይ እንዳይውድቁ» እያንዳንዱ ሰው የራሱ ሚስት ይኑረው እንዲሁም እያንዳንዷ ሴት ለራሷ ባል ይኑራት ብዙ ሚስት በሚያገቡ ማህበር ሰብ ግልጽ ለማድረግ፦«እያንዳንዱ ሰው አንድ ሚስት ሊኖረው ይገባል እንዲሁም እያንዳንዷ ሴት የራሷ ባል ሊኖራት ይገባል»

1 Corinthians 7:3

1ቆሮንቶስ 7፥3-4
ስለ ገብረ ሥጋ ግንኙነት መብት ሁለቱም ባልና ሚስት ከትዳር ጓደኛቸው ጋር ሁል ጊዜ አብሮ መተኛት ይገባል።

1 Corinthians 7:5

1ቆሮንቶስ 7፥5-7
አብራችሁ ለመተኛት እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ ትኩረት፦ «ከትዳር ጓደኛ ጋር አብራችሁ ለመተኛት እምቢ አትበሉ» ለጸሎት ራሳችሁ ለመትጋት ተስማምታችሁ በተለይም ለጸሎት ጊዜ ለመውሰድ ለተወሰኑ ቀናት አብሮ ሳይተኙ ለማሳለፍ ይወስናሉ። በአይሁድ እምነት አንድ ለሁለት ሳምንታት ይሆናል። ራሳችሁን ማትጋት «ራሳችሁን መስጠት» እንደ ገና አንድ ሁኑ ትኩረት፦ «እንደገና አንድ ላይ ተኙ» ራሳችሁን ለመግዛት ካለ መቻል የተነሣ መቆጣጠር* ትኩረት፦ «ምክንያቱም ከጥቂት ቀናት በኋላ የግብረ ሥጋ ፍላጎታችሁን ለመቆጠጠር ከባድ ይሆናል»

ይህን እንደ ፈቃድ እንጂ እንደ ትእዛዝ አይደለም ጳውሎስ የቆሮንቶስን ሰዎችን ለአጭር ጊዜ አብሮ ከመተኛት ለጸሎት መታቀብ ይችላሉ፤ነገር ግን ይህ የተለየ ጉዳይ ነው እንጂ የሚቀጥል መስፈርት አይደለም። እንደ እኔ ቢሆን ያላገቡ (አስቀድሞ ያገቡ ወይም ያላገቡ) እንደ ጳውሎስ ያሉ ነገር ግን እያንዳንዱ ከእግዚአብሔር የራሱ ስጦታ ይኑረው እንዲሁም ሌላውም እንደዚው ይሁን ትኩረት፦ «እግዚአብሔር ለአንድ ሰው ችሎታ ይሰጣል እንዲሁም ለሌላኛው ሰው ሌላ ችሎታ ይሰጣል»

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Corinthians 7:8

1ቆሮንቶስ 7፥8-9
ያላገባ «አሁን ያላገባ» ይህ ያላገቡትንና ቀደም ብሎ ያገቡትን ይጨምራል። መበለት ባል የሞተባት ሴት ይህ መልካም ነው «መልካም» የሚለው ቃል እዚህ ላይ ትክክልና ተቀባይነት ያለው የሚለውን ያመለክታል። ትኩረት፦«ይህ ትክክልና ተቀባይነት ያለው ነው።» መጋባት ባልና ሚስት መሆን

1 Corinthians 7:10

1ቆሮንቶስ 7፥10-11
ያገባ የትዳር ጓደኛ ያለው(ባልና ሚስት) መለየት የለባቸውም አብዘኛው የግሪክ ሰዎች ሕጋዊ ፍቺና እንዲሁ መለየትን አይለይም ነበር። «መለየት» ለአብዘኛው ባለ ትዳሮች ጋብቻ የማይቆይ እንደ ሆነ ማለት ነው። ከርሱ ጋር ታረቁ «ከባልዋ ጋር ያለውን ጉዳይ መፍታት አለባቸው እንዲሁም ወደ እርሱም ትመለስ» መፋታት የለባቸውም ይህ «መለየት የለባቸውም» ከሚለው ጋር ተመሳሳይ። (ከላይ ያለውን ማስታወሻ።) ሕጋዊ ፍቺ ወይም እንዲያው መለየት።

1 Corinthians 7:12

1ቆሮንቶስ 7፥112-14
ይዘት «ፈቃድ» ወይም«መርካት» የማያምን ባል የተለየ ነው «እግዚአብሔር ያላመነውን ባል» ያላመነት ሴት የተለች ናት «እግዚአብሔር ያላመነችን ሴት ለይቶአል»

እነርሱ የተለዩ ናቸው «እግዚአብሔር »እንርሱን ለይቶአቸዋል»

1 Corinthians 7:15

1ቆሮንቶስ 7፥15-16
በዚህ ዓይነት ጉዳይ ወንድሞች ወይም እህት ለቃል ኪዳናቸው የታሰሩ አይደለም «በዚህ ዓይነት ጉዳይ የአማኝ ባለትዳሮች ጋብቻ አስገዳጅነት የላቸውም።»

አንቺ ሴት ባልሽን ታድኚው እንደ ሆነ ምን ታውቂያለሽ? «የማያምን ባልሽን ታድኚው እንደ ሆነ ምን ታውቂያለሽ።»

አንተ ሰው ሚስትህን ታድናት እንደ ሆነ ምን ታውቃለህ «የማታምን ሚስትህን ታድናት እንደ ሆነ ምን ታውቃለህ።»

1 Corinthians 7:17

1ቆሮንቶስ 7፥17-19
እያንዳንዱ ሰው «እያንዳንዱ አማኝ» ይህ ለአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ትእዛዜ ነው ጳውሎስ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በዚህ ሁኔታ እንዲያደርጉ አማኞችን ያስተምራል። አንድ ሰው ሲጠራ ተገርዞአልን ጳውሎስ የተገረዙትን አንድ ሰው ወደ እምነት ሲጠራ ያልተገረዘ ነውን ጳውሎስ ያልተገረዙትን ይጠቅሳል። ትኩረት፦«ላልተገረዙት፤ እግዚአብሔር ለእምነት ሲጠራችሁ ያልተገረዛችሁ ነበርን።»

1 Corinthians 7:20

1ቆሮንቶስ 7፥20-24
በጥሪ እዚህ ላይ «ጥሪ» ወደ ሥራ ወይም የምትሳተፉበት ማኅበራዊ ደረጃን ያመለክታል። ትኩረት፦«እንደምታደርጉ ኑሩና ሥሩ።» (UDB) እግዚአብሔር ሲጠራችሁ ባርያ ነበራችሁን? ትኩረት፦ «እግዚአብሔር ለእምነት ሲጠራችሁ ባርያ ለነበራችሁ።» የጌታ ነፃ ሰዎች ይህን ነፃነት በእግዚአብሔር ይቅር ተብላችኋል ስለዚህ ከሰይጣንና ከኀጢአት ነፃ ሁኑ። በዋጋ ተገዝታችኋል ትኩረት፦ «ክርስቶስ ስለ እናንተ በመሞት ገዝቶአችኋል» ለእምነት በምንጠራበት ጊዜ «እግዚአብሔር እኛን ለእምነት በክርስቶስ ሲጠራን» እኛን --- እኛ ሁሉንም ክርስቲያኖችን ይመለከታል

1 Corinthians 7:25

1ቆሮንቶስ 7፥25-26
እንግዲህ ያላገቡትን በሚመለከት ከጌታ ትእዛዝ የለኝም ጳውሎስ ስለዚህ ሁኔታ የሚናገር የኢየሱስ ትምህርት እንደ ሌለ ይናገራል። ትኩረት፦ «ስላላገቡ ሰዎች ከጌታ ትእዛዝ የለኝም።» የእኔ አሳብ ጳውሎስ ስለ ጋብቻ እነዚህ አሳቦች የእርሱ እንደ ሆነ እንጂ በቀጥታ ከጌታ አለመሆኑን ያሳስባል። ስለዚህ ትኩረት፦ «እንግዲህ/ስለዚህ» ወይም «በዚህ ምክንያት» ለችግር ጊዜ መፍትሔ እንዲሆን ትኩረት፦ «የሚመጣ መከራ»

1 Corinthians 7:27

1ቆሮንቶስ 7፥27-28
ከአንዲት ሴት ጋር በጋብቻ ታስራችኋል ጳውሎስ ላገቡት ወንዶች ይናገራል። ትኩረት፦ «ያገባችሁ ከሆነ» ከዚህ ነፃ ለመሆን አትሻ ትኩረት፦ «ከጋብቻ ቃል ኪዳን ነፃ ለመሆን አትሞክሩ» ከሚስትህ ጋር በቃል ኪዳን ነፃ ወይም ያላገባህ ነህ? ጳውሎስ አሁን ላላገቡት ይናገራል። ትኩረት፦ «አሁን ያላገባህ ከሆንህ» ሚስት አትሻ ትኩረት፦ «ለማግባት አትፈልግ» መሰጠት «ተከናወነ» ወይም «ተሳትፎአል» ከእነርሱ ለመለየት እወዳለሁ ትኩረት፦ «ከእነርሱ ጋር እንድትሆን አልወድም»

1 Corinthians 7:29

1ቆሮንቶስ7፥29-31
ጊዜው አጭር ነው ትኩረት፦ «ጥቂት ጊዜ አለ» ወይም «ጊዜው ተጋባዶአል» ማልቀስ «መጮህ» ወይም «በእንባ ማዘን» ከዓለም ጋር የሚተባበሩ ትኩረት፦ «በየቀኑ ከማያምኑ ጋር የሚተባበሩ» ከዚህ ጋር ምንም እንደ ሌለ ትኩረት፦ «ከማያምኑ ጋር ምንም ግንኙነት እንደ ሌለ» የዚህ ዓለም አሠራር መጨረሻ ደርሷል ይህ ዓለም በሰይጣን ሥር ከመሆኑ የተነሣ ይህ ዓለም በአጭር ጊዜ ያልፋል።

1 Corinthians 7:32

1ቆሮንቶስ 7፥32-34
ከጭንቀት ነፃ መሆን ትኩረት፦ «ጸጥ ማለት» ወይም ያለ ጭንቀት» ስለ አንድ ነገር ትኩረት መስጠት «በአንድ ነገር ማተኮር» እርሱ ተከፍሏል ትኩረት፦ «እግዚአብሔርን ለማስደሰት እንዲሁም ሚስቱን ለማስደሰት ይፈልጋል»

1 Corinthians 7:35

1ቆሮንቶስ 7፥35
እጥረት «ሸክም» ወይም «ገደብ» ለዚህ ተሰጥቶ ሊሆን ይችላል «ትኩረት መስጠት ይችላል»

1 Corinthians 7:36

1ቆሮንቶስ 7፥36-38
አጠቃላይ መረጃ አንዳንድ ሰዎች ጳውሎስ ያላገቡ ሰዎች ለማግባት ስለሚፈልጉ ሴቶች እንደ ሚናገር ያስባሉ (see ULB and UDB። ሌሎች ደግሞ ጳውሎስ የሚናገረው ስላላገቡ ሴቶች አባቶች እንደ ሆነ ያስባሉ (በዚህ ማስታወሻ ያሉትን አማራጭ ትርጉሞችን ተመልከት)። በአክብሮት አለመያዝ «ቸር አለመሆን» ወይም «አለማክበር» እጮኛውን አማራጭ ትርጉሞች 1)«ሊያገባት ተስፋ የሰጣት ሴት» ወይም 2)«ድንግል የሆነች ልጃ ገረድ።» እጮኛ አንድ ሴት እና አንድ ወንድ ለጋብቻ የተስማሙበት ፍላጎቱ በጣም ከፍተኛ አማራጭ ትርጉሞች 1) ስለ ወሰባዊ ፍላጎቱ (UDB) ወይም 2) «ምክንያቱም ሴቷ ለማግባት የዕድሜ ብቁነት» ያግባት አማራጭ ትርጉሞች 1)«እጮኛውን ያግባት»(UDB) ወይም 2) «ሴት ልጁ ለጋብቻ ይፍቀድ» ላለማግባት ከወሰነ አማራጭ ትርጉሞች 1)«ለማግባት ፍላጎት እንደ ሌለ ከወሰነ» (UDB) ወይም 2) «እንድታገባ ሴት ልጁን የማይፈቅ ከሆነ» እርስዋን በለማግባቱ መልካም አደረገ አማራጭ ትርጉሞች 1) «እርስዋን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ላለማግባት የሚያደርገው ውሳኔ መልካም ነው» (UDB) ወይም
2)«ያላገባችውን እንዳታገባ ቢያቆያት መልካም ነው።» እጮኛውን ያገባል
አማራጭ ትርጉም፦ «ሴት ልጁ ለጋብቻ ይሰጣታል» ለማግባት አይመርጥም
አማራጭ ትርጉም፦ «ሴት ልጁን ለጋብቻ አይሰጥም»

1 Corinthians 7:39

1ቆሮንቶስ 7፥39-40
በሕይወት ካለ «እስከ ሞት ድረስ» የፈለገችውን ትኩረት፦ «ማንንም
የፈለገችውን» በጌታ ትኩረት፦ «አዲሱ ባል አማኝ ከሆነ» ፍርዴ
«የእግዚአብሔርን ቃል መረዳቴ» ደስተኛ የበለጠ ተስማምቶአል፤ የበለጠ
ደስተኛ እንዳለ ይኖራል ትኩረት፦ «ሳያገባ ይኖራል»

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 8

1 ለጣዖት ስለተሰዋ ሥጋ፦ "ሁላችንም ዕውቀት እንዳለን" እናውቃለን።ዕውቀት ያስታብያል፤ ፍቅር ግን ያንጻል። 2 አንድ ሰው አንድ ነገር እንደሚያውቅ ቢያስብ፥ ያ ሰው ፥እንደሚገባ እንደሚያውቅ ገና አለወቀም። 3 ነገር ግን ማንም ሰው እግዚአብሔርን ቢወድ እርሱም በእግዚአብሔር ዘንድ ይታወቃል። 4 እንግዲህ ለጣዖት የተሠዋውን ሥጋ ስለ መብላት በተመለከተ፦ "የዚህ ዓለም ጣዖት ከንቱ ነው፤" እና "ከአንዱም ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ አምላክ የለም" ይህንን እናውቃለን። 5 ብዙ "አማልክትና ጌቶች" እንዳሉ ሁሉ፥ ምንም እንኳ በሰማይና በምድር አማልክት የተባሉ ቢኖሩ ለእኛስ ነገር ሁሉ ከእርሱ የሆነ 6 እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ ብቻ አለን፤ እንዲሁም ነገር ሁሉም በእርሱ በኩል የሆነ እኛም በእርሱ በኩል የሆንን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ አለን። 7 ይሁን እንጂ ይህ ዕውቀት በሁሉም አይገኝም። በዚህ ፈንታ፥ አንዳንዶች ግን እስካሁን ድረስ ጣዖትን ማምለክ ስለ ለመዱ፦ ለጣዖት እንደ ተሠዋ አድርገው ይበላሉ። ሕሊናቸው ደካማ ስለ ሆነ ይረክሳሉ። 8 መብል ግን ወደ እግዚአብሔር አያደርሰንም። ስላልበላምንም አንረክስም፤ ወይም ስለበላንም የተሻለን አንሆንም። 9 ነገር ግን ይህ ነጻነታችሁ በእምነት ደካማ ለሆኑት ምክንያት ሆኖ መሰናከያ እንዳይሆን ተጠንቃቁ። 10 አንተ ዕውቀት ያለህ በጣዖት ቤት በማዕድ ተቀምጠህ ስትበላ አንድ ሰው ቢያይህ፤ በእምነቱ ያልጠነከረ ሰው ለጣዖት የተሠዋውን ለመብላት አይደፋፈርምን? 11 ስለ ጣዖት ባሕርይ በአንተ ዕውቀት የተነሣ ክርስቶስ የሞተላቸው ደካማ ወንድም ወይም እህት ይጠፋሉ። 12 ስለዚህም ወንድሞችንና እህቶችን ስትበድሉና ደካማ ሕሊናቸውንም ስታቆሽሹ ክርስቶስን ትበድላላችሁ። 13 ስለዚህም መብል ወንድሜንና እህቴን የሚያሰናክል ከሆን ወንድሜንና እህት እንዳላሰናክል ለዘላለ ከቶ ሥጋን አልበለም።

---

1 Corinthians 8:1

1ቆሮንቶስ 8፥1-3
እንግዲህ ስለ ጳውሎስ የቆሮንቶስ ሰዎች ወደ ጠየቁበት ጥያቄ መሸጋገሪያ እንዲሆን ይህን ሐረግ ይጠቀማል። ለጣዖት የተሠዋ አህዛብ ለአምልኮአቸው እህል፥ዓሣ፥ ወፍ፥ ወይም ሥጋ ለአማልክት ይሠዋሉ። ካህናቱም የመሥዋዕቱን ከፊል በመሠዊያ ላይ እንዲቃጠል ያደርጋሉ። ጳውሎስ የሚናገረው ለሚያመልኩት ወይም በገበያ ስለሚሸጠው ቀሪው ክፍል ነው። «ሁላችንም ዕውቀት እንዳለን» እናውቃለን ጳውሎስ አንዳንድ የቆሮንቶስ ሰዎች ካሉት ይህን ሐረግ ይጠቅሳል። ትኩረት፦ 'ሁላችን ዕውቀት አለን' ራሳችሁ እንደምትሉ «ሁላችን እናውቃለን።» ትዕቢት «አንድ ሰው ይታበያል» ወይም «አንድ ሰው ራሱን ከሌላ የተሻለ እንደሆን ያስባል» አንድ ነገር እንደሚያውቅ ያስባል «ማንኛውንም ነገር እንደሚያውቅ ያምናል» ይህ ሰው በእርሱ ዘንድ ይታወቃል «እግዚአብሔር ይህን ሰው ያውቃል» (ተመልከት፦)

1 Corinthians 8:4

1ቆሮንቶስ 8፥4-6
እናውቃለን «እኛ» ማለት ጳውሎስና የቆሮንቶስ ሰዎች የዚህ ዓለም «ጣዖት ምንም እንደ ሆን እናውቃለን» ጳውሎስ አንዳንድ የቆሮንቶስ ሰዎች ከተጠቀሙት ይህን ሐረግ ይጠቅሳል። ትኩረት፦ «ራሳችሁ እንደምትሉ፥'ጣዖት ኀይል እንደሌለ ወይም ለእኛ ትርጉም የለም' እንደምትሉ እናውቃለን» ጣዖታትና ጌቶች ጳውሎስ በብዙ ጣዖቶች አያምንም ነገር ግን አይዛብ በጣዖታት እንደሚያምኑ ያውቃል። እኛን ይህ «እኛን» የሚለው ጳውሎስና የቆሮንቶስ ሰዎችን ነው። ለእኛ አለን «እናምናለን»

1 Corinthians 8:7

`1ቆሮንቶስ 8፥7-8
እያንዳንዱ ሰው አንዳንዶች «ሁሉም ሰዎች» ከሁሉም ሰዎች የተወሰኑ ክፍሎች የተበላሹ «የጠፉ» ወይም «የተጎዱ»

1 Corinthians 8:8

`1ቆሮንቶስ 8፥8-10
ምግብ ወደ እግዚአብሔር አያደርስም «ምግብ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን አያስገኝም» ወይም «የምንበላው ምግብ እግዚአብሔርን ደስ አያሰኝም ደካማ የሆነ ሰው በእምነታቸው ብርቱ ያልሆኑ ለመብላት የሚደፍሩ «ለመብላት የበረታቱ»

1 Corinthians 8:11

1ቆሮንቶስ 8፥11-13
ደካማ ወንድም ወይም እህት ይጠፋሉ ወንድም ወይም እህት በእምነታቸው ያልበረቱ እምነታቸው ይፈተናል ወይም እምነታቸውን ያጣሉ። ስለዚህ «ከዚህ መጨረሻ መመሪያ የተነሣ» ምግብ ምክንያት ከሆነ «ምግብ ይህን የሚያስከትል» ወይም «ምግብ የሚያደፋፍር ከሆነ»

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 9

1 እኔ ነፃ አይደለሁም? እኔ ሐዋርያስ አይደለሁም? ጌታችን ኢየሱስን አላየሁትም? እናንተስ በጌታ የሥዬ ፍሬዎች አይደላችሁም? 2 ለሌሎች ሐዋርያ ባልሆን
እንኳ ቢያንስ ለእናንተ ሐዋርያ ነኝ። በጌታ ሐዋርያ ለመሆኔ እናንተ ማረጋገጫ ናችሁና። 3 ለሚጠይቁኝ መልሴ ይህ ነው። 4 እኛስ ለመብላትና ለመጠጣት
መብት የለንም? 5 እንደ ሌሎቹ ሐዋርያት፣ እንደ ጌታ ወንድሞች፣ እና እንደ ኬፋ፣ አማኝ የሆነች ሚስት ይዞ ለመሄድ መብት የለንም? 6 ወይስ የመሥራት ግዴታ
ያለብን እኔና በርናባስ ብቻ ነን? 7 በራሱ ወጪ በውትድርና የሚያገለግል ማን ነው? የወይን ተክል ተክሎ ከፍሬው የማይበላ ማን ነው? ወይስ ከሚጠብቀው
መንጋ ወተት የማይጠጣ ማን ነው? 8 እነዚህን ነገሮች የምናገረው በሰው ሥልጣን መሠረት ነው? ሕጉስ ይህን አይልም? 9 በሙሴ ሕግ፦ "የሚያበራየውን
በሬ፣አፉን አትሰር" ተብሎ ተጽፎአል። በእርግጥ እግዚአብሔር ስለ በሬዎች አስቦ ነው? 10 እየተናገረ ያለው ስለ እኛ አይደለም? የተጻፈው ስለ እኛ
ነው፣ምክንያቱም የሚያርስ በተስፋ ሊያርስ፣የሚያበራይም ከመከሩ ለመካፈል ተስፋ በማድረግ ሊያበራይ ይገባዋል። 11 በመካከላችሁ መንፈሳዊ ነገር ዘርተን
ከሆነ፣ከእናንተ ቁሳዊ ነገሮችን ብናጭድ ይበዛብናል? 12 ሌሎች ይህን መብት ከእናንተ የሚያገኙ ከሆነ፣እኛስ የበለጠ መብት የለንም? ሆኖም ግን ይህን
መብት ይገባናል አላልንም፣ይልቁንም ለክርስቶስ ወንጌል እንቅፋት እንዳንሆን ሁሉን ታገስን። 13 በመቅደስ የሚያገለግሉ ምግባቸውን ከመቅደስ እንደሚያገኙ
አታውቁም፣በመሠዊያው ላይ የሚያገልግሉስ መሠዊያው ላይ ከሚሠዋው እንደሚካፈሉ አታውቁም? 14 እንዲሁም ደግሞ ወንጌልን የሚያውጁ ከወንጌል
በሚገኝ እንዲኖሩ ጌታ አዟል። 15 እኔ ግን ከእነዚህ መብቶች አንዱንም ይገባኛል አላልሁም። ይህንንም የጻፍሁት አንዳች እንዲደረግልኝ አይደለም። ይህን
ትምክህቴን ማንም ከሚወስድብኝ ሞትን እመርጣለሁ። 16 ይህ ግዴታዬ ስለሆነ ወንጌል ብሰብክ የምታበይበት ምክንያት የለኝም፣ ወንጌልን ባልሰብክ ግን
ወየልኝ! 17 ይህን በፈቃደኝነት ባደርገው ግን ሽልማት አለኝ። በፈቃደኝነት ባላደርገው ግን በአደራ የተሰጠኝ ኃላፊነት አለብኝ። 18 ታዲያ ሽልማቴ ምንድነው?
በወንጌል ውስጥ ያለ ሙሉ መብቴን ትቼ ያለምንም ክፍያ ወንጌልን ስሰብክ ነው። 19 ምንም እንኳ ከሁሉም ነፃ ብሆንም፣ ብዙዎችን ለመማረክ
እንድችል፣የሁሉ አገልጋይ ሆንሁ። 20 አይሁድን ለመማረክ እንድችል፣ እንደ አይሁዳዊ ሆንሁ። ምንም እንኳ በሕግ ስር ባልሆንም፣ በሕግ ስር ያሉትን መማረክ
እንድችል፣ ከሕግ ስር እንዳለ ሰው ሆንሁ። 21 ከሕግ ውጭ ያሉትን መማረክ እንድችል፣እኔ ራሴ ከእግዚአብሔር ሕግ ውጭ ሳልሆን፣ ነገር ግን ከክርስቶስ ሕግ
ስር እያለሁ፣ ከሕግ ውጭ እንዳለ ሰው ሆንሁ። 22 ደካማውን መማረክ እንድችል፣እንደ ደካማ ሆንሁ። አንዳንዶችን ማዳን እንድችል፣ ለሰዎች ሁሉ ብዬ ሁሉን
ሆንሁ። 23 ይህን ሁሉ ያደረግሁት ከወንጌል በረከት መካፈል እንድችል፣ ስለ ወንጌል ብዬ ነው። 24 በሩጫ ውድድር የሚሳተፉ ሯጮች ሁሉ እንደሚሮጡ፣ ነገር
ግን ሽልማት የሚቀበል አንዱ ብቻ እንደሆነ አታውቁም? ስለዚህ ሽልማት ለማግኘት ሩጡ። 25 ለውድድር የሚዘጋጅ ሰው ሥልጠና ጊዜ ሁሉ ራሱን መቆጣጠር
ይለማመዳል። እነርሱ የሚጠፋውን ሽልማት ለማግኘት ይሮጣሉ፣ እኛ ግን የማይጠፋውን ሽልማት ለማግኘት እንሮጣለን። 26 ስለዚህም ያለ ዓላማ
አልሮጥም፣ወይም ንፋስ በቦክስ አልመታም። 27 ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ከውድድሩ ውጭ እንዳልሆን ሥጋዬን በመቆጣጠር አስገዛዋለሁ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **10**

1 ወንድሞች እና እህቶች፣ይህን እንድታውቁ እወዳለሁ፣አባቶቻችን ከዳመና በታች እና በባሕር ውስጥ አለፉ። **2** ሁሉም በዳመና እና በባሕር ውስጥ በሙሴ ተጠመቁ፣ **3** መንፈሳዊ ምግብ ተመገቡ፣ **4** ሁሉም አንድ ዓይነት መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ። እነርሱም ይከተላቸው ከነበረው መንፈሳዊ ዓለት ጠጡ፣ያም ዓለት ክርስቶስ ነበር። **5** ነገር ግን እግዚአብሔር በብዙዎች አልተደሰተምና ሬሳቸው ምድረ በዳ ውስጥ ወድቆ ቀረ። **6** እኛም እነርሱ እንዳደረጉት ክፉ ነገር እንዳንመኝ እነዚህ ነገሮች ምሳሌ እንዲሆኑልን ተጽፈውልናል። **7** "ሕዝቡ ሊበሉና ሊጠጡ ተቀመጡ፣በዝሙት ፍላጎት በመነሳሳት ሊጨፍሩ ተነሡ።" ተብሎ እንደተጻፈ፣ከእነርሱ አንዳንዶች እንዳደረጉት ጣዖት አምላኪዎች አትሁኑ። **8** ከእነርሱ ብዙዎች ዝሙት በመፈጸማቸው ምክንያት ሃያ ሦስት ሺ ሰዎች በአንድ ቀን እንደሞቱ፣እኛም ዝሙት አንፈጽም። **9** ከእነርሱም ብዙዎች ክርስቶስን እንደፈተኑት እና በእባብ እንደጠፉ፣እኛም ጌታን እንፈታተን። **10** በማጉረምረማቸው ምክንያት የሞት መልአክ እንዳጠፋቸው፣እኛም አናጉረምርም። **11** በእነርሱ ላይ የሆኑት እነኚህ ነገሮች ምሳሌ እንዲሆኑልን የተጻፈው፣ የዘመን ፍጻሜ ለደረሰብን ለእኛ ትምህርት እንዲሆንልን ነው። **12** ስለዚህ ማንም ቆሜአለሁ ብሎ የሚያስብ፣ እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ። **13** በሰው ሁሉ ላይ ከሚደርሰው በላይ የሆነ ፈተና አልደረሰባችሁም። ነገር ግን እግዚአብሔር ታማኝ ነውና ከምትችሉት በላይ እንድትፈተኑ አያደርግም። ይልቁን ፈተናውን መወጣት እንድትችሉ ከፈተናው ጋር ማምለጫ መንገዱንም ያዘጋጅላችኋል። **14** ስለዚህ ወዳጆቼ ሆይ፣ከጣዖት አምልኮ ሽሹ። **15** ይህን የምናገራችሁ አስተዋዮች በመሆናችሁ ነው፤የምለውን አመዛዝኑ። **16** የምንባርከው የበረከት ጽዋ፣የክርስቶስን ደም መካፈል አይደለም? የምንቆርሰው እንጀራ የክርስቶስን ሥጋ መካፈል አይደለም? **17** እንጀራው አንድ እንደሆነ፣ብዙዎች ሆነን ሳለ አንዱን እንጀራ በመካፈል አንድ አካል ነን። **18** የእስራኤልን ሕዝብ ተመልከቱ፦ ከመሥዋዕቱ የሚበሉ ከመሠዊያው ተካፋዮች አይደሉም? **19** ስለዚህ ምን እያልሁ ነው? ጣዖት ምንም አይደለም እያልሁ ነው? ወይስ ለጣዖት የተሠዋ ምግብ ምንም አይደለም ማለቴ ነው? **20** እያልሁ ያለሁት፣አሕዛብ የሚሠዋቸው ነገሮች፣ለአጋንንት እንጂ ለእግዚአብሔር አይደለም። ከአጋንንት ጋር ተካፋዮች እንድትሆኑ አልፈልግም! የጌታንም ጽዋ፣ የአጋንንትንም ጽዋ ልትጠጡ አትችሉም። **21** በጌታም ማዕድ፣ በአጋንንትም ማዕድ ኅብረት ልታደርጉ አትችሉም። **22** ይህን ብማድረግ ጌታን ለቅናት እናነሳሳዋለን? ከእርሱ የምንበረታ ነን? **23** "ሁሉም ነገር ተፈቅዷል፣" ነገር ግን ሁሉም ነገር የሚጠቅም አይደልም። "ሁሉም ነገር ተፈቅዷል፣" ነገር ግን ሁሉም ነገር ሰዎችን የሚያንጽ አይደለም። **24** ማንም ለራሱ መልካም የሆንውን ብቻ አያስብ። ይልቁን፣እያንዳንዱ ለሌሎች ሰዎች ሁሉ መልካም የሆነውን ይፈልግ። **25** በገበያ ቦታ የሚሸጥ ማንኛውንም ነገር፣የኅሊና ጥያቄ ሳታነሱ መብላት ትችላላችሁ። **26** "ምድርና በውስጧ ያለው ሁሉ የጌታ ነውና።" **27** አንድ አማኝ ያልሆነ ሰው ምግብ ቢጋብዛችሁና ግብዣውን ተቀብላችሁ መሄድ ብትፈልጉ፣ በፊታችሁ የቀረበላችሁን ማንኛውንም ነገር የኅሊና ጥያቄ ሳታነሱ ብሉ። **28** ነገር ግን እንድ ሰው፣"ይህ ምግብ ለጣዖት የተሠዋ ነው።" ብሎ ቢነግራችሁ አትብሉ። ይህን ማድረግ የሚገባችሁ፣ ለነገራችሁ ሰው እና ለኅሊና ስትሉ ነው። **29** ይህን ስል ስለ እናንተ ኅሊና ሳይሆን ስለ ሌላው ሰው ኅሊና ነው። ስለ ሌላው ኅሊና ሲባል ለምን በነፃነቴ ላይ ይፈረዳል? **30** ምግቡን በአክብሮት ከተቀበልሁ፣አመስግኜ ለበላሁት ነገር ለምን እሰደባልሁ? **31** ስለዚህ፣ስትበሉ እና ስትጠጡ፣ወይም በምታደርጉት ሁሉ፣ሁሉን ለጌታ ክብር አድርጉት። **32** ለአይሁዶች ወይም ለግሪኮች፣ እንዲሁም ለእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን መሰናከያ አታድርጉ። **33** እኔ ሰዎችን ሁሉ በሁሉ ነገር ደስ ለማሰኘት እንደምፈልግ ሁሉ እናንተም እንዲሁ አድርጉ። የራሴን ጥቅም ሳይሆን፣ለብዙዎች ጥቅም የሚሆነውን እፈልጋለሁ። ይህን የማደርገው ወደ ድነት እንዲመጡ ብዬ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **11**

1 እኔ ክርስቶስን እንደምመስል፣እናንተም እኔን ምሰሉ። **2** አሁን የማመሰግናችሁ በሁሉ ነገር ስለምታስቡኝ ነው። ለእናንተ ያስተላለፍኳቸውን ልምዶች ልክ እንደዚያው እንዳሉ አጥብቃችሁ በመያዛችሁ አመሰግናችኋለሁ። **3** ክርስቶስ የወንድ ሁሉ ራስ ፣ወንድ ደግሞ የሴት ራስ ፣ እግዚአብሔር የክርስቶስ ራስ እንደሆነ እንድትረዱ እፈልጋለሁ። **4** ራሱን ሸፍኖ የሚጸልይ ወይም ትንቢት የሚናገር ወንድ የእርሱ ራስ የሆነውን ክብር ያሳጣል። **5** ነገር ግን ራሷን ሳትሸፍን የምትጸልይ ወይም ትንቢት የምትናገር ሴት ራሷን ክብር ታሳጣለች። ይህን ማድረግ ልክ ጠጉሯን እንደመላጨት ነው። **6** ሴት ራሷን ካልሸፈነች፣ጠጉሯን አሳጥራ መቆረጥ ይኖርባታል። ሴት ጠጉሯን አሳጥራ መቆረጧ ወይም መላጭቷ አሳፋሪ ከሆነ፣ ራሷን ትሸፍን። **7** ወንድ ራሱን መሸፈን የለበትም፣ ምክንያቱም እርሱ የእግዚአብሔር መልክ እና ክብር ነውና። **8** ሴት ግን የወንድ ክብር ነች። ወንድ ከሴት አልተገኘምና። ይልቁንስ፣ሴት ከወንድ ተገኝታለች። **9** ወንድ ለሴት አልተፈጠረም፣ሴት ግን ለወንድ ተፈጥራለች። **10** ለዚህ ነው፣ ከመላእክቱ የተነሳ፣ ሴት በራሷ ላይ የሥልጣን ምልክት ሊኖራት የሚገባው። **11** የሆነ ሆኖ፣በጌታ ሴት ከወንድ፣ ወንድም ከሴት የተነጣጠሉ አይደሉም። **12** ሴት የተገኘችው ከወንድ እንደሆነ ሁሉ፣ወንድም የተገኘው ከሴት ነው። ሁሉም ነገር ደግሞ የተነኘው ከእግዚአብሔር ነው። **13** ራሳችሁ ፍረዱ፦ሴት ራሷን ሳትሸፈን ወደ እግዚአብሔር ብትጸልይ ተገቢ ነው? **14** ወንድስ ረጅም ጠጉር ቢኖረው አሳፋሪ እንደሆነ ተፈጥሮ ራሱ አያስተምራችሁም? **15** ሴት ግን ረጅም ጠጉር ቢኖራት ክብሯ እንደሆነ ተፈጥሮ ራሱ አያስተምራችሁም? ለእርሷ ጠጉር የተሰጣት እንደ መሸፈኛ ነውና። **16** ነገር ግን በዚህ ማንም ክርክር ሊያስነሳ ቢፈልግ፣እኛም ሆንን የእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት ከዚህ የተለየ ልምምድ የላቸውም። **17** በሚከተሉት መመሪያዎቼ ግን፣አላመሰግናችሁም። ምክንያቱም በምትሰበሰቡበት ጊዜ፣ ለተሻለ ነገር ሳይሆን እጅግ ለከፋ ነገር ትሰበሰባላችሁ። **18** በመጀመሪያ፣ በቤተክርስቲያን ስትሰበሰቡ በመካከላችሁ መከፋፈል እንዳለ ሰምቼአለሁ፣ ደግሞም ይህ እንደሚሆን በመጠኑም ቢሆን አምኜበታልሁ። **19** ምክንያቱም በእናንተ መካከል ተቀባይነትያላቸው እንዲለዩ የተለያዩ ቡድኖች መኖራቸው ግድ ነው። **20** በአንድነት በምትሰብሰቡበት ጊዜ፣የምትበሉት የጌታን ማዕድ አይደለምና። **21** በምትበሉበት ጊዜ፣ሌሎች ምግብ ከማግኘታቸው በፊት እያንዳንዱ ቀድሞ የየራሱን ምግብ ይበላል። አንዱ ተርቦ ሳለ ሌላው ይሰክራል። **22** የምትበሉበትና የምትጠጡበት ቤት የላችሁም? የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን በመናቅ ምንም የሌላቸውን ታዋርዳላችሁ? ምን ልበላችሁ? ታዲያ ላመስግናችሁ? ለዚህ አላምሰግናችሁም! **23** ከጌታ የተቀበልሁትን ለእናንተ አሳልፌ ሰጥቼአለሁ፣ ጌታ ኢየሱስ ታልፎ በተሰጠበት ምሽት፣እንጀራ አንሳ። **24** ካመሰገነ በኋላ ቆረሰውና፣"ለእናንተ የሆነ ሥጋዬ ይህ ነው፣ይህን እኔን ለማስታወስ አድርጉት፣" አለ። **25** እንዲሁም ከእራት በኋላ ጽዋን አንስቶ፣"ይህ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው።ይህን በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ እኔን ለማስታወስ አድርጉት።" **26** ይህን እንጀራ በበላችሁ እና ይህን ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ፣ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ታውጃላችሁ። **27** ስለዚህ ማንም፣ተገቢ ባልሆነ ሁኔታ የጌታን እንጀራ ቢበላ ወይም የጌታን ጽዋ ቢጠጣ፣ለጌታ ሥጋ እና ለጌታ ደም ተጠያቂ ይሆናል። **28** አንድ ሰው ራሱን ከመረመረ በኋላ እንጀራውን ይብላ ጽዋዉንም ይጠጣ። **29** የጌታ ሥጋ መሆኑን ሳይረዳ የሚበላ እና የሚጠጣ፣በራሱ ላይ ፍርድን ይበላል ይጠጣልም። **30** በመካከላችሁ ብዙዎች የታመሙ እና በሽተኞች የሆኑት ስለዚህ ነው፣ አንዳንዶችም ደግሞ ሞተዋል። **31** ነገር ግን ራሳችንን ብንመረምር አይፈረድብንም። **32** በጌታ ስንፈረድ ግን፣ከዓለም ጋር እንዳንኮነን እንገሠጻለን። **33** ስለዚህ፣ወንድሞቼ እና እህቶቼ፣ለመብላት ስትሰበሰቡ፣እርስ በርሳችሁ ተጠባበቁ። **34** ማንም የተራበ ቢኖር፣እቤቱ ይብላ፣እንዲያ ሲሆን ስትሰበሰቡ ለፍርድ አይሆንባችሁም። ስለ ጻፋችሁልኝ ሌሎች ነገሮች፣ስመጣ መመሪያዎችን እሰጣለሁ።

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **12**

1 ወንድሞች እና እህቶች መንፈሳዊ ስጦታዎችን በተመለከተ፣የማታውቁት ነገር እንዲኖር አልፈልግም። **2** አረማውያን በነበራችሁበት ወቅት፣መናገር እንኳ በማይችሉ ጣዖታት ወደማታውቁት መንገድ ተመርታችሁ እንደነበር ታውቃላችሁ። **3** ስለዚህ ማንም በእግዚአብሔር መንፈስ፣"ኢየሱስ የተረገመ ነው፣" የሚል እንደሌለ ሁሉ፤ እንዲሁም በእግዚአብሔር መንፈስ ካልሆነ በቀር፣"ኢየሱስ ጌታ ነው፣" ሊል የሚችል እንደሌለ እወቁ። **4** ልዩ ልዩ ስጦታዎች አሉ፣መንፈስ ቅዱስ ግን አንድ ነው። **5** አገልግሎቶች ልዩ ልዩ ናቸው፣ጌታ ግን አንድ ነው። **6** ልዩ ልዩ ሥራዎች አሉ፣ነገር ግን ለእያንዳንዱ ሰው ችሎታን የሚሰጥ አንዱ እግዚአብሔር ነው። **7** ደግሞም ለእያንዳንዱ መንፍስ ቅዱስን መግለጥ የተሰጠው ለሁሉም ጥቅም ሲባል ነው። **8** ለአንዱ የጥበብ ቃል በመንፈስ ቅዱስ ይሰጣል፣ለሌላው ደግሞ የእውቀት ቃል በዚያው መንፈስ ይሰጣል። **9** ለሌላው በዚያው መንፈስ እምነት ይሰጠዋል፣ለሌላው ደግሞ በዚያው መንፈስ የፈውስ ስጦታ ይሰጠዋል። **10** ለሌላው ደግሞ የኃይል ሥራዎች፣ለሌላው ትንቢት መናገር። ለሌላው ደግሞ መናፍስትን መለየት፣ለሌላው በልዩ ልዩ ልሳኖች መናገር፣እና ለሌላው ልሳኖችን የመተርጎም ስጦታ ይሰጠዋል። **11** ነገር ግን፣ለእያንዳንዳቸው እንደወደደ ልዩ ልዩ ስጦታዎችን በመስጠት በእነዚህ ሁሉ የሚሠራው ያው አንዱ መንፈስ ቅዱስ ነው። **12** አካል አንድ ሆኖ ሳለ ብዙ ብልቶች እንዳሉት ሁሉ፣ ሁሉም ብልቶች የአንዱ አካል ክፍል እንደሆኑ፣በክርስቶስም እንዲሁ ነው። **13** በአንድ መንፈስ በአንድ አካል እንደተጠመቅን፣አይሁድ ይሁኑ ግሪኮች፣ባሪያ ይሁን ነጻ፣ሁሉ ከአንዱ መንፈስ ጠጥተዋል። **14** አካል አንድ ብልት ብቻ ሳይሆን ብዙ ብልቶች አሉት። **15** እግር፣"እኔ እጅ አይደለሁም፣ስለዚህ የአካሉ ክፍል አይደለሁም፣" ቢል የአካሉ ክፍል መሆኑ አይቀርም። **16** ጆሮም ተነስቶ፣"ዓይን ስላይደለሁ፣የአካሉ ክፍል አይደለሁም፣" ቢል የአካሉ ክፍል ከመሆን አይቀነስም። አካል ሁሉ ዓይን ቢሆን፣ መስማት ወዴት ይሆናል? **17** አካል ሁሉ ጆሮ ቢሆን፣ማሽተት ወዴት ይሆናል? **18** እግዚአብሔር ግን እያንዳንዱን የአካል ክፍል እንደወደደ ሠርቶታል። **19** ሁሉም አንድ ብልት ቢሆኑ ኑሮ፣አካል ወዴት በሆነ ነበር? **20** አሁን ግን ብዙ ብልቶች ያሉት፣ አንድ አካል ነው። **21** ዓይን እጅን፣"አንተ አታስፈልገኝም፣" ሊል አይችልም። ራስም እግርን፣"አታስፈልገኝም፣" ሊል አይችልም። **22** ነገር ግን ዝቅተኛ ግምት የሚሰጣቸው ብልቶች አስፈላጊ ናቸው፣ **23** ዝቅተኛ ግምት የምንሰጣቸውን የሰውነት ክፍሎች ትልቅ ክብር እንሰጣቸዋለን፣እምናፍርባቸውን ብልቶች ደግሞ በአክብሮት እንይዛለን። **24** የማናፍርባቸውን ብልቶች ደግሞ በአክብሮት መያዝ አያስፈልገንም ምክንያቱም ቀድሞዉኑ ክብር አግኝተዋል። እግዚአብሔር ግን ብልቶችን ሁሉ በአንድነት በማያያዝ ክብር ላልተሰጣቸው የበለጠ ክብርን ሰጥቷል። **25** እግዚአብሔር እንዲህ ያደረገው በአካል ውስጥ መከፋፈል እንዳይኖርና ይልቁን ብልቶች በበለጠ ፍቅር እርስ በርሳቸው አንዳቸው ሌላቸውን እንዲከባከቡ ነው። **26** እናም አንዱ ብልት ሲሰቃይ ሁሉም ብልቶች አብረው ይሰቃያሉ። አንዱ ብልት ሲከብር፣ሁሉም ብልቶች አብረው ሐሴት ያደርጋሉ። **27** እንግዲህ እናንተ የክርስቶስ አካል ስትሆኑ እያንዳንዳችሁ የአካሉ ብልቶች ናችሁ። **28** እግዚአብሔርም በቤተክርስቲያን በመጀመሪያ ሐዋርያትን፣ሁለተኛ ነቢያትን፣ሦስተኛ አስተማሪዎችን፣ከዚያም ተአምራት ማድረግን፣በመቀጠል የፈውስ ስጦታዎችን፣እርዳታ የሚያደርጉትን፣ የአስተዳደር ሥራ የሚሠሩትን፣ እና ልዩ ልዩ ዓይነት ልሳኖችን የሚናገሩትን ሰጥቷል። **29** ታዲያ ሁላችን ሐዋርያት ነን? ሁላችንስ ነቢያት ነን? ወይስ ሁላችን አስተማሪዎች ነን? ሁላችን ተአምራቶችን እናደርጋለን? **30** ሁላችን የፈውስ ስጦታዎች አሉን? ሁላችን በልሳኖች እንናገራለን? ሁላችን ልሳኖችን እንተረጉማለን? **31** የሚበልጡትን ስጦታዎች በከፍተኛ ጉጉት ፈልጉ። እጅግ የሚበልጠውንም መንገድ አሳያችኋልሁ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **13**

1 በሰዎች እና በመላእክት ልሳኖች ብናገር፣ግን ፍቅር ከሌለኝ፣የሚንጫጫ ቃጭል ወይም የሚጮህ ታንቡር ነኝ። **2** የትንቢት ስጦታ ቢኖረኝ፣ የተሰወሩ እውነቶችን እና እውቀት ሁሉ ቢኖረኝ፣ተራሮችን ከስፍራቸው የሚያስወግድ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ፣ ፍቅር ከሌለኝ ግን ምንም የማይጠቅም ነኝ። **3** ድሆችን ለመመገብ ያለኝን ሁሉ ብሰጥ፣ ሰውነቴንም እንዲቃጠል ብሰጥ፣ፍቅር ከሌለኝ ግን ምንም አይጠቅመኝም። **4** ፍቅር ታጋሽና ደግ ነው። ፍቅር አይመቀኝም ደግሞም አይመካም። አይታበይም **5** ወይም ትህትና የጎደለው አይደለም። ራስ ወዳድ አይደለም። በቀላሉ አይበሳጭም፤ወይም በደልን አይቆጥርም። **6** ፍቅር በአመጽ ደስ አይሰኝም፣በእውነት ግን ደስ ይለዋል። **7** ፍቅር ሁሉን ይታገሳል፤ሁሉን ያምናል፤በሁሉም ድፍረት አለው በሁሉ ይጸናል። **8** ፍቅር ፍጻሜ የለውም። ትንቢቶች ያልፋሉ፤ልሳኖችም ቢሆኑ ያበቃሉ፤ዕውቀትም ቢሆን ጊዜ ያልፍበታል። **9** ከዕውቀት የተወሰነውን እናውቃልን፣ትንቢትም በከፊል እንተነቢያለን። **10** ነገር ግን ፍጹም የሆነው ሲመጣ፣ፍጹም ያልሆነው ወደ ፍጻሜ ይደርሳል። **11** ልጅ በነበርሁበት ጊዜ፣እንደ ልጅ እናገር ነበር፣እንደ ልጅም አስብ ነበር፣የመረዳት ችሎታዬም እንደ ልጅ ነበር። ጎልማሳ ስሆን ግን የልጅነት ነገሮችን አስወገድሁ። **12** አሁን በጨለማ ውስጥ ያለን ምስል በመስታዋት እንደሚያይ እንመለከታለን፣የዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን። አሁን ዕውቀትን በከፊል አውቃለሁ፣የዚያን ጊዜ ግን ልክ እኔ ሙሉ በሙሉ እንደምታወቀው ሙሉ በሙሉ አውቃለሁ። **13** ነገር ግን እምነት፣ ተስፋ፣ፍቅር እነዚህ ሦስቱ ግን ጸንተው ይኖራሉ። ከእነዚህ የሚበልጠው ፍቅር ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **14**

1 ፍቅርን ተከታተሉ ለመንፈሳዊ ስጦታዎችም ከፍተኛ ጉጉት ይኑራችሁ፣ **2** በተለይም ደግሞ ትንቢት የመናገር ስጦታን በብርቱ ፈልጉ። በልሳን የሚናገር ለሰው ሳይሆን ለእግዚአብሔር ይናገራል፣በመንፈስ የተሰወሩ ነገሮችን ይናገራልና ማንም አይረዳውም። **3** ትንቢት የሚናገር ግን ሰዎችን ለማነጽ፣ለማበረታታትና፣ ለማጽናናት፣ ይናገራል። **4** በልሳን የሚናገር ራሱን ያንጻል፣ትንቢት የሚናገር ግን ቤተክርስቲያንን ያንጻል። **5** እንግዲህ ሁላችሁም በልሳኖች ብትናገሩ ምኞቴ ነበር። ከዚያ ይበልጥ ትንቢት ብትናገሩ እወዳለሁ። በልሳን የተነገረውን የሚተረጉም ከሌለ፣ ቤተክርስቲያን እንድትታነጽ ልሳን ከሚናገር ይልቅ ትንቢት የሚናገር ይበልጣል። **6** ወንድሞች እና እህቶች፣ልሳን እየተናገርሁ ወደ እናንተ ብመጣ ምን እጠቅማችኋለሁ? በመገለጥ፣ወይም በእውቀት፣ወይም በትንቢት፣ወይም በማስተማር ካልሆነ ልጠቅማችሁ አልችልም። **7** ሕይወት የሌላቸው እንደ ዋሽንት ወይም ክራር ያሉ የሙዚቃ መሣሪያዎች መለየት የሚቻሉ ድምፆችን ካላወጡ፣አንድ ሰው የትኛው የሙዚቃ መሣሪያ እንደተጫወተ እንዴት ማወቅ ይችላል? **8** መለከት ሊለይ በማይቻል ድምፅ ቢነፋ፣አንድ ሰው ለጦርነት ለመዘጋጀት ጊዜው እንደሆነ እንዴት ሊያውቅ ይችላል? **9** እናንተንም በተመለከተ እንዲሁ ነው። ሊታወቅ የማይችል ንግግር ብትናገሩ አንድ ሰው ምን እንደተናገራችሁ እንዴት ሊያውቅ ይችላል? እናንተ ትናገራላችሁ ነገር ግን ማንም አይረዳችሁም። **10** በዓለም ውስጥ ብዙ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች እንዳሉ ጥርጥር የለውም፣ **11** አንዳቸውም ግን ትርጉም የሌላቸው አይደሉም። የአንድን ቋንቋ ትርጉም የማላውቅ ከሆን ለሚናገረው ሰው እንግዳ እሆንበታለሁ፣ተናጋሪውም እንግዳ ይሆንብኛል። **12** ለእናንተም እንዲሁ ነው። ለመንፈስ ቅዱስ መገለጦች ከፍተኛ ፍላጎት ስላላችሁ፣ቤተክርስቲያንን ለማነጽ ጉጉት ይኑራችሁ። **13** ስለዚህ በልሳን የሚናገር መተርጎም እንዲችል ይጸልይ። **14** በልሳን በምጸልይበት ጊዜ መንፈሴ ይጸልያል፣አእምሮዬ ግን ያለ ፍሬ ነው። **15** ታዲያ ምን ላድርግ? በመንፈሴም እጸልያልሁ፣በአእምሮዬም እጸልያለሁ። በመንፈሴ እዘምራለሁ፣በአእምሮዬም እዘምራለሁ። **16** እንደዚያ ካልሆነ ግን እግዚአብሔርን በመንፈሳችሁ ብታመሰግኑና ሌላው ሰው በምታመሰግኑበት ሰዓት ምን እያላችሁ እንደሆነ ካላወቀ እንዴት "አሜን" ይላል? **17** በእርግጠኝነት በሚገባ እያመሰገናችሁ ነው፣ሌላው ሰው ግን እየታነጸበት አይደለም። **18** ከሁላችሁም የበለጠ በልሳን ስለምናገር እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። **19** በቤተክርስቲያን ውስጥ ግን ሰዎችን ማስተማር እንድችል፥ በልሳን አሥር ሺ ቃላትን ከምናገር፣ በአእምሮዬ አምስት ቃላትን መናገር እመርጣለሁ። **20** ወንድሞች እና እህቶች፣በአስተሳሰባችሁ ልጆች አትሁኑ። ይልቁን ክፋትን በተመለከተ እንደ ሕፃናት ሁኑ። ነገር ግን በአስተሳሰባችሁ ይበልጥ የበሰላችሁ ሁኑ። **21** በሕጉ እንደተጻፈው፣"የማያውቁት ቋንቋ ባላቸው ሰዎችና እንግዳ በሆነ ንግግር ለዚህ ሕዝብ እናገራለሁ። እንደዚያም ሆኖ አይሰሙኝም፣" ይላል እግዚአብሔር። **22** ስለዚህ ልሳኖች ለአማኞች ሳይሆን አማኝ ላልሆኑ ሰዎች ምልክት ናቸው። ትንቢት መናገር ግን ለማያምኑ ሰዎች ሳይሆን ለአማኞች ምልክት ነው። **23** ስለዚህ፣ቤተክርስቲያን ውስጥ ያለ ሰው ሁሉ ቢሰበሰብ እና በልሳኖች በመናገር ላይ እያሉ ከውጭ ያሉና የማያምኑ ሰዎች ቢገቡ አብደዋል አይሉምን? **24** ነገር ግን ሁላችሁም ትንቢት እየተናገራችሁ ባለበት ሰዓት አማኝ ያልሆነ ወይም የውጭ ሰው ቢገባ በሚሰማው ነገር ሁሉ ኃጢአተኝነቱ ይሰማዋል። በሚነገረው ነገር ሁሉ ይፈረድበታል። **25** የልቡም ምስጢር ሁሉ ይገልጣል። ከዚህም የተነሳ፣ በግንባሩ ተደፍቶ እግዚአብሔርን ያመልካል። እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ነው! ብሎ ያውጃል። **26** ታዲያ ምን ይሁን፣ወንድሞች እና እህቶች? በአንድነት በምትሰበሰቡበት ጊዜ፣እያንዳንዳችሁ መዝሙር፣ትምህርት፣መገለጥ፣ልሳን፣ወይም ልሳን መተርጎም አላችሁ። የምታደርጉትን ሁሉ ቤተክርስቲያንን ለማንጽ አድርጉት። **27** ማንም በልሳን ቢናገር ሁለትም ሦስትም ብትሆኑ ተራ በተራ አድርጉት። ሌላው ሰው ደግሞ በልሳን የተነገረውን ይተርጉም። **28** የሚተረጉም ከሌለ ግን፣ሁሉም ሰው ድምፁን ሳያሰማ ለራሱ እና ለእግዚአብሔር ብቻ ይናገር። **29** ሁለት ወይም ሦስት ነቢያቶች በሚናገሩበት ጊዜ ሌሎች የሚነገረውን በመመርመር ያዳምጡ። **30** ነገር ግን በስብሰባው ውስጥ አንድ ሰው መረዳት ከመጣለት በመናገር ላይ ያለው ዝም ይበል። **31** ትንቢት ስትናገሩ ሁሉም ሰው እንዲበረታታ እያንዳንዳችሁ ተራ በተራ መናገር ትችላላችሁ። **32** የነቢያቶች መንፈስ ለነቢያት ይገዛል። **33** እግዚአብሔር የሰላም አምላክ እንጂ ግራ የመጋባት አምላክ አይደለም። በሁሉም የአማኞች አብያተክርስቲያናት ውስጥ፦ **34** ሴቶች በቤተክርስቲያን ውስጥ ዝም ይበሉ። እንዲናገሩ አይፈቀድላቸውም። ሕጉ ይህን ይላልና ይልቁንስ ይገዙ ። **35** ሊያውቁ የሚፈልጉት ነገር ቢኖር፣ባሎቻቸውን በቤት ውስጥ ይጠይቁ። ሴት በቤተክርስቲያን ውስጥ መናገሯ አሳፋሪ ነውና። **36** የእግዚአብሔር ቃል የመጣው ከእናንተ ነውን? ወይስ ወደ እናንተ ብቻ ደርሷልን? **37** ማንም ሰው ራሱን ነቢይ እንደሆነ ወይም መንፈሳዊ እንደሆነ ቢያስብ፣የጻፍሁላችሁ ነገሮች የጌታ ትዕዛዛት እንደሆኑ ሊያውቅ ይገባዋል። **38** ነገር ግን ማንም ይህን ባያውቅ እርሱም ዕውቅና አያግኝ። **39** እንግዲህ ወንድሞች እና እህቶች፣ትንቢትን መናገር በቅንነት ፈልጉ፣ ማንንም ልሳኖችን እንዳይናገር አትከልክሉ። **40** ነገር ግን ማንኛውም ነገር በመልካም ምግባር እና በሥርዓት ይደረግ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **15**

1 ወንድሞች እና እህቶች፣ ስላወጅሁላችሁ እና እናንተም ጸንታችሁ ስለቆማችሁበት ወንጌል አሳስብባችኋለሁ። **2** የሰበክሁላችሁን ቃል አጥብቃችሁ ብትይዙ፣በዚህ ወንጌል መዳን ይሆንላችኋል፣አለዚያ ግን ማመናችሁ ምንም ጥቅም የለውም። **3** ለእናንተ ያስተላለፉሁት በቀዳሚነት አስፈላጊ የሆነውን እና እኔም የተቀበልሁትን ነው፤ መጽሐፍት እንደሚሉት ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፣ **4** ተቀበረ፣ በሦስተኛውም ቀን ተነሳ፣መጽሐፍትም ይህን ያረጋግጣሉ። **5** ለኬፋ ታየ፣ከዚያም ለአሥራ ሁለቱ። **6** እንደገና ከአምስት መቶ ለሚበልጡ ወንድሞች እና እህቶች በአንድ ጊዜ ታየ። አብዛኛዎቹ እስካሁን ድረስ በሕይወት አሉ፣የተወሰኑት ደግሞ አንቀላፍተዋል። **7** ከዚያም ለያዕቆብ፣ደግሞም ለሐዋርያቱ ሁሉ ታየ። **8** ከሁሉም በኋላ፣ያለ ጊዜው እንደተወለደ ልጅ ለሆንሁት ለእኔ ታየ። **9** ከሐዋርያት ሁሉ የማንስ ነኝና። የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን አሳድጃለሁና ሐዋርያ ተብዬ ልጠራ አይገባኝም። **10** ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ የሆንሁትን ሆኜአለሁ፣በእኔ ውስጥ የነበረው ጸጋም በከንቱ አልነበረም። ይልቁን ከሁሉም በላይ ጠንክሬ ሠራሁ። ሆኖም ይህ የሆነው ከእኔ ሳይሆን ከእኔ ጋር ካለው የእግዚአብሔር ጸጋ የተነሳ ነው። **11** ስለዚህ እኔም ሆንሁ እነርሱ ስንሰብክላችሁ አመናችሁ። **12** አሁን ክርስቶስ ከሞት እንደተነሳ ከተሰበከ፣ከእናንተ አንዳንዶች ታዲያ እንዴት የሙታን ትንሣኤ የለም ይላሉ? **13** ሙታን ትንሣኤ ከሌለ እንግዲያው ክርስቶስም ከሙታን አልተነሳማ። **14** ክርስቶስም ካልተነሳ ስብከታችንም፣የእናንተም እምነት ዋጋ የሌለው ሆኗል። **15** እንግዲህ እኛም ስለ እግዚአብሔር የሐሰት ምስክሮች ሆነን ተገኝተናል፣ ምክንያቱም እርሱ ክርስቶስን ሳያስነሳ እኛ አስነስቶታል በማለታችን በእግዚአብሔር ላይ በሐሰት መስክረንበታል። **16** ሙታን ካልተነሱ፣ክርስቶስም አልተነሳም ማለት ነው። **17** ክርስቶስ ካልተነሳ ደግሞ፣ እምነታችሁ ምንም ዋጋ የለውምናም አሁንም በኃጢአታችሁ አላችሁ። **18** ስለዚህ በክርስቶስ ሆነው የሞቱ ደግሞ ጠፍተዋል ማለት ነው። **19** ክርስቶስ ተስፋ ያደረግነው ለዚህ ሕይወት ብቻ ከሆነ፣ከሰዎች ሁሉ ይልቅ የምናሳዝን ነን። **20** አሁን ግን ክርስቶስ ከሙታን ሁሉ በኩር ሆኖ ተነስቷል። **21** ሞት በአንድ ሰው በኩል እንደመጣ፣ የሙታን ትንሣኤም በአንድ ሰው በኩል መጥቷል። **22** በአዳም ሁሉም እንደሞቱ፣ሁሉም ደግሞ በክርስቶስ ሕያው ይሆናሉ። **23** ግን እያንዳንዱ በቅደም ተከተሉ መሠረት፦ ክርስቶስ በኩር፣ ቀጥሎ የክርስቶስ የሆኑት እርሱ ተመልሶ ሲመጣ ሕያዋን ይሆናሉ። **24** ከዚያም ክርስቶስ መንግሥቱን ለእግዚአብሔር አብ ሲያስረክብ ፍጻሜ ይሆናል። ይህም የሚሆነው ግዛትን ሁሉ፣ ሥልጣንን ሁሉ፣ እና ኃይልን ሁሉ ሲደመስስ ነው። **25** ጠላቶቹን ሁሉ ከእግሮቹ ስር እስኪያደርግ ድረስ ሊነግሥ ይገባዋል። **26** ሊደመሰስ የሚገባው የመጨረሻው ጠላት ሞት ነው። **27** "ሁሉን ከእግሮቹ በታች አደረገ።" ነገር ግን፣"ሁሉን አደረገ፣" ሲል፣ሁሉን እንዲገዛለት ያደረገውን እንደማይጨምር ግልጽ ነው። **28** ሁሉም ሲገዛለት፣ ልጁ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ለእርሱ ይገዛል። ይህ የሚሆነው እግዚአብሔር አብ ሁሉ በሁሉ እንዲሆን ነው። **29** አለበዚያ ግን ፤ ስለ ሙታን የሚጠመቁ ሰዎች ለምን ያደርጉታል? ሙታን ፈጽሞ የማይነሱ ከሆነ፣ስለምን ያጠምቁላቸዋል? **30** ስለምንስ በየሰዓቱ አደጋ ውስጥ እንወድቃለን? **31** ወንድሞች እና እህቶች፣ ስለ እናንተ በክርስቶስ ባለኝ ትምክህት ይህን እናገራለሁ፦ በየቀኑ እሞታለሁ ። **32** በሰው ዓይን ሲታይ፣ በኤፌሶን ከአውሬዎች ጋር መጋደሌ፣ ሙታን የማይነሱ ከሆነ ምን ይጠቅመኛል? "ነገ መሞታችን ስለማይቀር፣እንብላ፣ እንጠጣ።" **33** አትታለሁ፦ "መልካም ያልሆነ ግንኙነት መልካሙን ጠባይ ያበላሻል።" **34** ራሳችሁን ተቆጣጠሩ! የጽድቅ ሕይወት ኑሩ! ኃጢአት ማድረግን አትቅጠጥሉ። አንዳንዶቻችሁ ስለ እግዚአብሔር ዕውቀት የላችሁም። ይህን የምላችሁ ላሳፍራችሁ ነው። **35** አንዳንዶች ግን እንዲህ ይላሉ፣"ሙታን የሚነሱት እንዴት ነው? በምን ዓይነት አካል ይመጣሉ?" **36** ዕውቀት የጎደላችሁ ናችሁ! የዘራችሁት ዘር ካልሞተ አይበቅልም። **37** የዘራችሁት አካል ተምልሶ አይበቅልም፣ይልቁን ዘር ነው እንጂ። ስንዴ ወይም የተዘራውን ሌላ ዓይነት ዘር ሆኖ ይበቅላል። **38** እግዚአብሔር እንደወደደ አካልን ይሰጠዋል፣ለእያንዳንዱም ዘር የራሱን አካል ይሰጠዋል። **39** ሥጋ ሁሉ አንድ ዓይነት አይደለም። ይልቁን፣ የሰው ሥጋ አለ፣ እንዲሁም የእንሰሳት ሥጋ አለ፣ የአእዋፍት ሥጋም እንዲሁ፣ ዓሣም ደግሞ ሌላ ዓይነት ሥጋ አለው። **40** እንዲሁም ደግሞ ሰማያዊ አካልና ምድራዊ አካል አለ። ነገር ግን የሰማያዊ አካል ክብር አለ የምድራዊ አካል ክብር ደግሞ ሌላ ነው። **41** የፀሐይ ክብር አለ፣ የጨረቃ ክብር ደግሞ ሌላ ነው፣ ከዋክብት ደግሞ ሌላ ክብር አላቸው። የአንዱ ኮከብ ክብር ከሌላው ኮከብ ይለያል። **42** የሙታን ትንሣኤም ልክ እንደዚሁ ነው። የተዘራው የሚጠፋ ነው፣ የሚነሳው ደግሞ የማይጠፋ ነው። **43** ሲዘራ በውርደት ሲነሳ ግን በክብር ነው። ሲዘራ በድካም፣ሲነሳ ግን በኃይል ነው። **44** የተዘራው ፍጥረታዊ አካል፣የሚነሳው ግን መንፈሳዊ አካል ነው። ፍጥረታዊ አካል እንዳለ ሁሉ መንፈሳዊ አካልም አለ። **45** እንዲህም ተብሎ ተጽፎአል፣ "የመጀመሪያው አዳም ሕያው ነፍስ ሆነ።" የመጨረሻው አዳም ግን ሕይወት ሰጭ መንፈስ ሆነ። **46** መጀመሪያ የመጣው መንፈሳዊው ሳይሆን ፍጥረታዊው ነው፣ከዚያም መንፈሳዊው ተከተለ። **47** የመጀመሪያው ሰው ከምድር ሲሆን የተሠራውም ከአፈር ነው። ሁለተኛው ሰው ከሰማይ ነው። **48** አንዱ ከአፈር እንደተሠራ፣ከአፈር የተሠሩ ሁሉ እንዲሁ ናችው። እንዲሁም ከሰማይ እንደሆነው ሰው፣ ከሰማይ የሆኑትም እንዲሁ ናቸው። **49** ልክ እኛ ከአፈር የተሠራውን ሰው እንደምንመስል፣ እንዲሁ ደግሞ የሰማዩን ሰው መልክ እንይዛለን። **50** ወንድሞች እና እህቶች፣ አሁን እንዲህ እላለሁ፣ሥጋ እና ደም የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርስ አይችልም። እንዲሁም የሚጠፋው የማይጠፋውን ሊወርስ አይችልም። **51** ምስጢር የሆነ እውነት እነግራችኋለሁ፦ ሁላችን አንሞትም፣ግን ሁላችን እንለወጣለን። **52** የመጨረሻው መለከት ሲነፋ፣ዐይን ተጨፍኖ እስኪገለጥ ባለ ፍጥነት ድንገት እንለወጣለን። መለከቱ ሲነፋ፣ ሙታን የማይጠፋውን አካል ለብሰው ይነሳሉ፣ እኛም እንለወጣለን። **53** ይህ የሚጠፋው የማይጠፋውን ይለብሳል፣ ሟቹ ደግሞ የማይሞተውን ይለብሳል። **54** የሚጠፋው የማይጠፋውን ሲለብስ፣እና ይህ ሟች የሆነው የማይሞተውን ሲለብስ፣ እንዲህ ተብሎ የተጻፈው ይፈጸማል፣"ሞት በድል ተዋጠ።" **55** ሞት ሆይ ድል ማድረግህ የት አለ? ሞት ሆይ መንደፊያህ የት አለ?" **56** የሞት መንደፊያ ኃጢአት ነው፣ የኃጢአት ኃይል ደግሞ ሕጉ ነው። **57** ነገር ግን በጌታ በክርስቶስ ኢየሱስ ድል የሚሰጠን እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን! **58** ስለዚህ ውድ ወንድሞቼ እና እህቶቼ፣ የጸናችሁ እና የማትነቃነቁ ሁኑ። ሁልጊዜም የእግዚአብሔር ሥራ ይብዛላችሁ፣ምክንያቱም በጌታ የምትደክሙት ድካም በከንቱ አይደለም።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **16**

1 አሁን ደግሞ ለአማኞች የሚሰበሰበውን ገንዘብ በተመለከተ፣የገላትያ አብያተክርስቲያናትን እንዳዘዝሁት ሁሉ፣እናንተም እንደዚሁ አድርጉ። **2** እኔ ስመጣ ገንዘብ ከመሰብሰብ፣ በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን፣እያንዳንዳችሁ እንደቻላችሁት መጠን የተወሰነ ገንዘብ አጠራቅሙ። **3** ወደ እናንተ በደረስሁ ጊዜ በመረጣችሁት ሰው በኩል ከደብዳቤ ጋር መባችሁን ወደ እየሩሳሌም እልከዋለሁ። **4** የእኔም መሄድ አስፈለጊ ከሆነ ከእኔ ጋር ይሄዳሉ። **5** ነገር ግን ወደ መቄዶንያ መሄዴ ስለማይቀር፣ በመቄዶንያ በኩል ሳልፍ ወደ እናንተ እመጣለሁ። በምሄድበት ሁሉ ለጉዞዬ እንድትረዱኝ፣ **6** ምናልባትም ከእናንተ ጋር ልቆይና ክረምቱንም ከእናንተ ጋር ላሳልፍ እችላልሁ። **7** አሁን ግን ጊዜው ስለሚያጥር ላያችሁ አላስብም። ጌታ ቢፈቅድና ብመጣ ግን ከእናንተ ጋር ረዘም ላለ ጊዜ ለመቆየት ተስፋ አደርጋልሁ። **8** ግን በኤፌሶን እስከ በዓለ ኀምሳ ቀን ድረስ እቆያልሁ፣ **9** ሰፊ በር የተከፈተልኝ ቢሆንም ብዙ ተቃዋሚዎች አሉብኝ። **10** ጢሞቴዎስ ልክ እንደ እኔ የጌታን ሥራ የሚሠራ ነውና ወደ እናንተ ሲመጣ፣ያለ አንዳች ስጋት ከእናንተ ጋር እንዲቀመጥ አድርጉ። **11** ማንም አይናቀው። ወደ አኔ ሲመጣ በሰላም እንዲሄድም እርዱት። ምክንያቱም ከሌሎች ወንድሞች ጋር እንዲመጣ እጠብቃለሁ። **12** አጵሎስን በተመለከተ፣ከወንድሞች ጋር በመሆን እንዲጎበኛችሁ አበረታትቼው ነበር። አሁን ለመምጣት አልወሰነም፣ይሁን እንጂ ዕድሉን ሲያገኝ ይመጣል። **13** ተጠንቀቁ፣በእምነትም ጸንታችሁ ቁሙ፣ቆራጦች ሁኑ፣በርቱ። **14** የምታደርጉት ሁሉ በፍቅር ይሁን። **15** የእስጢፋኖስን ቤተሰቦች ታውቃላችሁ። እነርሱ በአካይያ የመጀመሪያ አማኞች እንደሆኑና አማኞችን ለማገልገል ራሳችውን እንደሰጡ ታውቃላችሁ። ወንድሞች እና እህቶች **16** እንደዚህ ላሉ ሰዎች፣ በሥራ እየረዱንና አብረውን እየደከሙ ላሉ ሰዎች ሁሉ እንድትገዙ አሳስባችኋለሁ። **17** በእስጢፋኖስ፣በፈርዶናጥስ፣ እና በአካይቆስ መምጣት ተደስቼአልሁ። የእናንተን በዚህ ያለመኖር ጉድለት ሞልተውልኛል። **18** የእኔን እና የእናንተን መንፈስ አድሰዋል። እንዲህ ላሉ ሰዎችን እውቅና ስጧቸው። **19** በእስያ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። አቂላና ጵርስቅላ፣ እንዲሁም በቤታቸው ያለችው ቤተክርስቲያን በጌታ ስም ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። **20** ወንድሞች እና እህቶች ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። በተቀደሰ አሳሳም እርስ በርሳችሁ ሰላምታ ተለዋወጡ። **21** እኔ ጳውሎስ፣ ይህን በእጄ ጽፌአለሁ። **22** ማንም ጌታን የማይወድ ቢኖር፣ የተረገመ ይሁን። ጌታ ሆይ ና! **23** የጌታ የኢየሱስ ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን። **24** በክርስቶስ ኢየሱስ ፍቅሬ ከሁላችሁ ጋር ይሁን።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: 2 Corinthians

2 Corinthians

ምዕራፍ 1

1 በእግዚአብሔር ፈቃድ የክርስቶስ ኢየሱስ ሐዋርያ የሆነ ጳውሎስ እና ወንድማችን ከሆነው ጢሞቲዎስ፥ በቆሮንቶስ ለምትገኝ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን
እንዲሁም በመላው አካይያ ላሉ አማኞች ሁሉ: 2 ከእግዚአብሔር ከአባታችን እንዲሁም ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋና ሰላም ለናንተ ይሁን። 3 የምህረት
አባት፥ የመፅናናት አምላክ እና በመከራችን ሁሉ የሚያፅናናን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ። 4 እግዚአብሔር በመከራችን ሁሉ
ያፅናናል፥እኛም ራሳችን በእርሱ በእግዚአብሔር በተፅናናንበት መፅናናት ልክ ሌሎችን ማፅናናት እንችላለን። 5 ምክንያቱም የክርስቶስ መከራ በእኛ ላይ
እንደበዛ፥ መፅናናታችንም በክርስቶስ በኩል እንዲሁ ይበዛልናል። 6 ነገር ግን መከራን ብንቀበል፥ስለናንተ መፅናናት እና ድነት ነው። ወይንም ደግሞ የእኛ
መፅናናት የእናንተም መፅናናት ማለት ነው፤ይህም እኛ በምንቀበለው መከራ እናንተም በተመሳሳይ መልኩ በትእግስት አብራችሁን ስለምትካፈሉ ነው። 7
በናንተም ያለን መታመን ፅኑ ነው፥በመከራችን እንደምትካፈሉ ሁሉ በመፅናናታችንን ደግሞ እንደምትካፈሉ እናውቃለን። 8 ወንድሞች ሆይ፥በእስያ ስለደረሰብን
መከራ እንድታውቁ እንወዳለን፤ በህይወት ለመኖር ተስፋ እስክንቆርጥ ድረስ ከአቅማችን በላይ ከብዶን ነበር። 9 በርግጥም ሞት ተፈርዶብን ነበር። ሆኖም ግን
ያ የደረሰብን መከራ ሙታንን በሚያስነሳ በእግዚአብሔር እንጂ በራሳችን እንዳንታመን አደረገን። 10 ከብርቱ ጥፋት አዳነን እንዲሁም ያድነናል። መታመናችንን
በእርሱ ላይ አድርገናል፤እርሱም ይታደገናል። 11 በእናንተም የፀሎት ድጋፍ አምላካችን ስራውን ይሰራል። በመቀጠልም በብዙዎች ፀሎት አማካኝነት ለእኛ
ስለተሰጠው ሞገስ በርካቶች ምስጋናን ያቀርባሉ። 12 የምንመካው በህሊናችን ምስክርነት ላይ ነው። ምክንያቱም በዚህ ዓለም ስንመላለስ የነበረው በንፁህ
ህሊና እና ከእግዚአብሔር በሚሰጥ ቅንነት ነበር። በተለይም ከናንተ ጋር የነበረን ግንኙነት የተመሰረተው በእግዚአብሔር ፀጋ ላይ እንጂ በምድራዊ ጥበብ ላይ
አልነበረም። 13 ልታነቡትና ልትረዱት የማትችሉትን አንዳችም ነገር አንዳልፃፍንላችሁ ተስፋ አደርጋለሁ፤ 14 እናንተም በከፊል እንደተረዳችሁን በጌታችን
በኢየሱስ ቀን እናንተ በእኛ እንደምትመኩ እኛም እንዲሁ በእናንተ እንመካለን። 15 ስለዚህ ርግጠኛ ስለነበርሁ፥ በመጀመሪያ ወደናንተ መምጣት ፈለግሁ፤ ይህ
ደግሞ በሁለቱም ጉብኝቶቼ ተጠቃሚዎች እንድትሆኑ ነው። 16 ወደ መቄዶንያ ስሄድ ልጎበኛችሁ ፤ከዚያ ደግሞ ክመቄዶንያ ስመለስ ላያችሁ፤በኋላ ግን
እናንተው ወደ ይሁዳ እንደምትልኩኝ አቅጄ ነበር። 17 ይህንን ሳስብ ታዲያ የወላወልኩ ይመስላችኋልን? ወይስ በአንድ ጊዜ እንደ ሰው መስፈርት "አዎን፥
አዎን" እና "አይደለም፥አይደለም" በማለት አቀድኩን? 18 ነገር ግን እግዚአብሔር የታመነ እንደሆነ፣ እኛም በሁለት ቃል "አዎን" እና "አይደለም" ብለን
አንናገርም። 19 ምክንያቱም በእናንተ መካከል በእኔ፥ በስልዋኖስ እና በጢሞቲዎስ የተሰበከው የእግዚአብሔር ልጅ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን በአንድ ጊዜ "አዎን"
እና "አይደለም" አልነበረም፥ይልቅስ ሁልጊዜም በእርሱ "አዎን" ነው። 20 በእርሱ የእግዚአብሔር ተስፋዎች ሁሉ "አዎን" ናቸው። ስለዚህ እኛም በእርሱ በኩል
ለእግዚአብሔር ክብር "አሜን" እንላለን። 21 እንግዲህ እኛንም ከእናንተ ጋር በክርስቶስ የሚያፀናን እንዲሁም የሾመን እግዚአብሔር ነው። 22 ለዚህም ወደፊት
ለሚሰጠን ዋስትና እንዲሆነን መንፈሱን በልባችን የሰጠን ማህተሙንም ያደረገብን እርሱ ነው። 23 ሆኖም ግን ወደ ቆሮንቶስ ያልመጣሁት እንዳላሳዝናችሁ
አስቤ እንደሆነ እግዚአብሔር ምስክሬ ነው። 24 እኛም እምነታችሁ ምን መምሰል እንዳለበት በናንተ ላይ ልናዝዝ ሳይሆን በእምነታችሁ ፀንታችሁ እንድትቆሙ
ለደስታችሁ የምንሰራ ነን።

---

2 Corinthians 1:1

2ኛ ቆሮንቶስ 1:1-2
ሐዋርያ የሆነ ጳውሎስ በቋንቋችሁ የዚህን ደብዳቤ ፀሐፊ ለማስተዋወቅ ምናልባት የተለየ መንገድ መንገድ መጠቀም ያስፈልጋችሁ ይሆናል። AT: "እኔ ጳውሎስ፥ ይህንን ደብዳቤ ፅፌያለሁ።" ወንድማችን በአዲስ ኪዳን፥ሐዋርያት ብዙውን ጊዜ ለክርስቲያን ወዳጆች "ወንድም" የሚል ቃል ይጠቀማሉ፥ምክንያቱም አማኞች ሁሉ በክርስቶስ እግዚአብሔር የሰማይ አባት በሆነበት የአንድ መንፈሳዊ ቤተሰብ አባላት ስለሆኑ ነው። አካይያ ይህ የሮም አውራጃ መጠሪያ ሲሆን በአሁኑ ዘመን ግሪክ ተብሎ የሚጠራው ደቡባዊ ክፍል ነው። ፀጋና ሰላም ለናንተ ይሁን "ለናንተ" የሚለው ቃል የሚያሳየው የቆሮንቶስ ቤተክርስትያንን ህዝብ እና በዚያ የሚገኙትን ክርስቲያኖች ነው። ይህ ጳውሎስ በደብዳቤዎቹ የሚጠቀመው የተለመደ ሰላምታ ነው።

2 Corinthians 1:3

2ኛ ቆሮንቶስ 1:3-4
አምላክና አባት "አምላክ የሆነው አባት" የምህረት አባት፥የመፅናናት ሁሉ አምላክ እነዚህ ሃረጎች አንድን ነገር በተመሳሳይ መንገዶች ይናገራሉ። "አባት" እና "አምላክ" የሚሉት ቃላት እግዚአብሔር "የሚሰጥ" ወይም "ምንጭ" መሆኑን የሚገልፁ ሲሆን ምክንያቱም እግዚአብሔር የነገሮች ሁሉ ምንጭ ስለሆነ ነው። AT: "የምህረት እና የመፅናናት ሁሉ ምንጭ" በመከራችን ሁሉ ያፅናናል እዚህ ላይ "እኛ" እና "የእኛ" የሚሉት ቆሮንቶሶችን ያጠቃልላል።

2 Corinthians 1:5

2ኛ ቆሮንቶስ 1:5-7
የክርስቶስ መከራ በእኛ ላይ እንደበዛ "ክርስቶስ ስለእኛ በብዙ መከራ እንደተቀበለ" ነገር ግን መከራን ብንቀበል ጳውሎስ ከቆሮንቶስ ሰዎች ውጪ እነርሱም የተቀበሉትን መከራ ይገልፃል። የእናንተ መፅናናት "መፅናናት ትለማመዳላችሁ"

2 Corinthians 1:8

2ኛ ቆሮንቶስ 1:8-10
እንድታውቁ እንወዳልን "እንድታውቁ እንፈልጋለን" ለመኖር ተስፋ እስክንቆርጥ "ተስፋ እስክንቆርጥ" የሚለው ቃል የሚያሳየው የሃዘን ስሜትን ነው። "በሃዘን መዋጥ" ከአቅማችን በላይ ከብዶን ጳውሎስ እና ጢሞቲዎስ የተሰማቸውን የሃዘን ስሜት የሚያነፃፅሩት ልክ መሸከም እንደሚገባቸው ከባድ ሸክም ነው። (See:

ሞት ተፈርዶብን ነበር ሞት ከተፈረደበት ሰው ጋር ነው። AT: "ሞት እንደተፈረደበት አይነት ሰው በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ነበርን"
በእግዚአብሔር እንጂ "እምነታችንን ልናደርግ" የሚሉት ቃላት ከዚህ ሃረግ ውስጥ ወጥተዋል። AT: "ነገር ግን እምነታችንን በእግዚአብሔር እንድናደርግ"
ሙታንን በሚያስነሳ "የሞተውን ወደ ህይወት እንደሚመልስ" ብርቱ ጥፋት

ጳውሎስ እና ጢሞቲዎስ የተሰማቸውን የሃዘን ስሜት የሚያነፃፅሩት ከብርቱ ጥፋት እና ከከፋ አደጋ ጋር ነው። (UDB) AT: "ተስፋ መቁረጥ።"

2 Corinthians 1:11

2ኛ ቆሮንቶስ 1:11
በእናንተም ድጋፍ እርሱ ስራውን ይሰራል "እናንተ የቆርንቶስ ሰዎች ሆይ፥እናንተ ለእኛ ስትፀልዩ እግዚአብሔር ደግሞ ከአደጋ ያድነናል።

2 Corinthians 1:12

2ኛ ቆሮንቶስ 2:12-14
በህሊናችን ምስክርነት ጳውሎስ እና ጢሞቲዎስ ለራሳችው ሃሳቦች እና ድርጊቶች የተሰጠው ማረጋገጫ። ምድራዊ ጥበብ "ሰዋዊ ጥበብ" ልታነቡትና ልትረዱት የማትችሉትን አንዳችም ነገር አንፅፍላችሁም AT: "የፃፍንላችሁን ሁሉ ልታነቡትም ሆነ ልትረዱት የምትችሉትን ነው። እንዲሁ በናንተ እንመካለን፡ ትኩረት፡ "እናንተ የመመካታችን ምክንያቶች ናችሁ"

2 Corinthians 1:15

2ኛ ቆሮንቶስ 1:15-16
ስለዚህ ርግጠኛ ስለነበርሁ ይህ ጳውሎስ ለቆሮንቶሶች አስቀድሞ የሰጠውን አስተያየት ያሳያል። ወደ ይሁዳ እንደምትልኩኝ "ወደ ይሁዳ በማደርገው ጉዞ እንደምታግዙኝ"

2 Corinthians 1:17

2ኛ ቆሮንቶስ 1:17-18
ይህንን ሳስብ የወላወልኩ ይመስላችኋልን? ጳውሎስና ጢሞቲዎስ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀሙት ውሳኔያቸው ትክክል እንደሆን ለማሳየት ነው። ትኩረት:"በዚህ መንገድ ሳስብ፥በውሳኔዬ እተማመናለሁ"

የወላወልኩ ይመስላችኋልን? "ርግጠኛ አልነበርሁምን?" ወይስ በአንድ ጊዜ እንደ ሰው መስፈርት "አዎን፥ አዎን" እና "አይደለም፥አይደለም" በማለት አቀድኩን? ጳውሎስ ለታማኝነቱ መከላከያ ያቀርባል። ትኩርት፡ "ነገሮችን የማቅደው እግዚአብሔር እንዳቅደው እንደሚፈልገው ነው። መልሴ እውነት እስከሆነ ድረስ ምላሼ አዎን ወይም አይደለም እላለሁ።"

2 Corinthians 1:19

2ኛ ቆሮንቶስ 1:19-20
የእግዚአብሔር ልጅ ይህ የኢየሱስ አስፈላጊ መጠሪያ ሲሆን ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት የሚገልፅ ነው። (ተመልከት፡

"አዎን" እና "አይደለም" አልነበረም ይህ ኢየሱስ እንዴት ጥያቄዎችን ይመልስ እንደነበር ነው። ትኩረት:"እዎን" እና "አይደለም" በማለት ሁለት መልስ አይመልስም ነበር። በእርሱ "አዎን" ናቸው "በእርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢየሱስ ክርስቶስን ነው።

2 Corinthians 1:21

2ኛ ቆሮንቶስ 2:21-22
ማህተሙን ያደረገብን "ማህተሙን" የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ማረጋግጫ ያመለክታል። ትኩረት፡ "ማረጋገጫ የሰጠን"

2 Corinthians 1:23

2ኛ ቆሮንቶስ 1:23-24
እግዚአብሔር ምስክሬ ነው "ምስክሬ ነው" የሚለው ሃረግ የሚያመለክተው አንድ ሰው ሙግቱን ለመርታት ሲል ያየውን ወይም የሰማውን ሲናገር ነው። ትኩረት፡ "የምናገረው ነገር እውነት መሆኑን እንዲያሳይ እግዚአብሔርን እጠይቃለሁ" በእምነታችሁ ፀንታችሁ እንድትቆሙ "እንድትቆሙ" የሚለው ቃል አንድ የማይለወጥ ነገርን ያሳያል። ትኩረት:"በእምነታችሁ ፀንታችሁ ኑሩ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 2

1 ስለዚህም በበኩሌ እንደገና ላስከፋችሁ ተመልሼ መምጣት አልፈለግሁም። 2 ባስከፋችሁ እንኳ ሊያስደስተኝ የሚችለው ያው ያስከፋሁት ሰው አይደለምን? 3 እንደፃፍኩላችሁ ወደ እናንተ በመጣሁ ጊዜ ደስ ሊያሰኙኝ የሚገባችው ሰዎች እንዳያሳዝኑኝ ነው። ስለሁላችሁም እርግጠኛ የምሆንበት በእኔ ያለ ደስታ በተመሳሳይ መልኩ በእናንተም ዘንድ ያለ መሆኑ ነው። 4 የፃፍኩላችሁም በታላቅ ጭንቀት፥ በልብ መናወጥ እንዲሁም በብዙ እንባ ነበር፥ ምክንያቱ ደግሞ ለናንተ ያለኝን ጥልቅ ፍቅር እንድታውቁ እንጂ እንዳላሳዝናችሁ ነው። 5 ማንም ያሳዘነ ሰው ቢኖር እኔን ብቻ ያሳዘነ ሳይሆን በተወሰነ መልኩ ሁላችሁንም ነው። 6 ለዚያም ሰው በብዙዎች የደረሰበት ቅጣት ይበቃዋል። 7 ግን ይህን ሰው በብዙ ሐዘን እንዳይዋጥ ከመቅጣት ይልቅ ይቅር ልትሉትና ልታፅናኑት ይገባል። 8 ስለዚህም ለዚህ ሰው ፍቅራችሁን በይፋ እንድታረጋግጡለት አደፋፍራችኋለሁ። 9 የፃፍኩላችሁ በሁሉ ነገር ታዛዦች መሆናችሁን እንድፈትንና እንዳውቅ ነው። 10 አንድን ሰው ይቅር ብትሉት፣ እኔም ያንን ሰው ይቅር እለዋለሁ። እኔ ይቅር የምለው አንዳች ነገር ቢኖር ይቅርታ የማደርግለት በክርስቶስ ፊት ስለ እናንተ ስል ነው። 11 ይህን የማደርገውም ሰይጣን እንዳያታልለን ነው። ምክንያቱም የርሱን እቅድ አንስተውምና። 12 ምንም እንኳ ወደ ጥሮአዳ ስመጣ የክርስቶስን ወንጌል ለመስበክ በጌታ በር ተከፍቶልኝ ነበር። ሆኖም ወንድሜን ቲቶን በዚያ ስላላገኘሁት በአዕምሮዬ አላረፍኩም ነበር። 13 ስለሆነም እነርሱን ትቼ ወደ መቄዶንያ ተመለስኩ። 14 ነገር ግን ሁልጊዜ በክርስቶስ በድል ለሚመራን፥ ጣፋጭ የእውቀት ሽታ በየስፍራውም ለሚናኘው ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን። 15 ምክንያቱም በሚድኑትና በሚጠፉት መካከል ለእግዚአብሔር የክርስቶስ ጣፋጭ ሽታ ነን። 16 ለሚጠፉት ሰዎች፥ለሞት የሚሆን የሞት ሽታ ስንሆን ለሚድኑት ደግሞ ለህይወት የሚሆን የህይወት ሽታ ነን። ለነዚህ ነገሮች የበቃ ማነው? 17 የእግዚአብሔርን ቃል ለትርፋቸው እንድሚነግዱበት እንደ ብዙዎች አይደለንም። በዚያ ፈንታ በክርስቶስ ሆነን በእግዚአብሔር ፊት፥ ከእግዚአብሔር እንደተላክን በቅን ልቦና እንናገራለን።

---

2 Corinthians 2:1

2ኛ ቆሮንቶስ 2:1-2
በበኩሌ "የወሰንኩት ራሴ ነኝ" ላስከፋችሁ ትኩረት: "የምታደርጉትን በብርቱ ተቃውሜያለሁ" ባስከፋችሁ እንኳ ሊያስደስተኝ የሚችለው ያው ያስከፋሁት ሰው አይደለምን? ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ደስ እንዳሰኙት ከነገራቸው በኋላ ቢጎዳቸው ግን ሁለቱንም የሚያስከፋ ያስታውቃቸዋል። ትኩረት: "ባስከፋችሁ ደስ ስለማትሰኙ እኔም አልደሰትም"

2 Corinthians 2:3

2ኛ ቆሮንቶስ 2:3-4
እንዳያሳዝኑኝ ነው ጳውሎስ እዚህ ጋር የስሜት ጉዳት ስላደረሱበት የተወሰኑ የቆሮንቶስ አማኞች ይናገራል። ትኩረት:"በእነርሱ ድርጊት እንዳልጎዳ" በታላቅ ጭንቀት፥ በልብ መናወጥ እንዲሁም በብዙ እንባ እነዚህ ሃረጋት የጳውሎስን ታላቅ ሃዘን ያሳያሉ፤ ይህንንም የፃፈው ለቆሮንቶስ ሰዎች ባለው ፍቅር በትልቅ ችግር ሆኖ ነው። ትኩረት: "ትልቅ ችግር ሊገጥመኝ የቻለው ታላቅ ሃዘን ስለገባኝ ሲሆን የዚህም መነሾ ለናንተ ካለኝ ሃላፊነት የተነሳ ነው።"

2 Corinthians 2:5

2ኛ ቆሮንቶስ 2:5-7
በተወሰነ መልኩ "በጥቂቱ" የደረሰበት ቅጣት "ያለበቂ ርህራሄ" ወይም "በበዛ ጭካኔ" በብዙ ሐዘን እንዳይዋጥ ይህ ማለት ለበዛ ሃዘን የበረታ የስሜት ምላሽ ያስፈልጋል ማለት ነው።

2 Corinthians 2:8

2ኛ ቆሮንቶስ 2:8-9
ፍቅራችሁን በይፋ እንድታረጋግጡለት ይህ ማለት ወደ አማኞች ህብረት ተመልሶ ሲመጣ አቀባበል ማድረግ ማለት ነው። ትኩረት:"በጋራ በምትሰበሰቡብት ጊዜ ቤተሰብ እንደምትወዱት ያህል አሁንም እንደምትወዱት አስታውቁ" በሁሉ ነገር ታዛዦች ይህ የሚያመለክተው ሁለቱንም ነገሮች ማለትም አንድን ሰው ለበደሉ መቅጣትና ከዚያም ይቅር ማለትን ነው። ትኩረት:"እንድታደርጉት እንዳስተማርኳችሁ በሁሉ ነገር ታዛዦች ናችሁ"

2 Corinthians 2:10

2ኛ ቆሮንቶስ 2:10-11
ይቅርታ የማደርግለት * ስለ እናንተ ስል ነው

ስሜት ሊስጡ የሚችሉት ትርጉሞች 1) "ከእኔ ውስጥ ከሚውጣው ፍቅር የተነሳ ይቅር ብዬዋለሁ" (UDB) ወይንም 2) "ለናንተ ጥቅም ይቅር ተብሏል።" ምክንያቱም የርሱን እቅድ አንስተውምና ትኩረት: "እቅዱን ስለምናውቅ ነው" (ተመልከት:

2 Corinthians 2:12

2ኛቆሮንቶስ 2:12-13
በር ተከፍቶልኝ ነበር የተከፈተ በር አንድን ሰው አልፎ እንዲራመድ እንደሚያደርገው ሁሉ ጳውሎስም በጥሮአዳ የወንጌልን መልዕክት እንዲያካፍል እድል አግኝቶ ነበር። ትኩረት: "እድልን ተስጥቶኝ ነበር" ወንድሜን ቲቶን ብዙውን ጊዜ ጳውሎስ በአገልግሎቱ ውስጥ የሚካፈሉትን ሌሎች ሰዎች በክርስቶስ ወንድም በማለት ይጠራል። እነርሱን ትቼ "ስለዚህም የጥሮአዳ ሰዎችን ትቼያቸው ሄድኩ"

2 Corinthians 2:14

2ኛ ቆሮንቶስ 2:14-15
በድል ለሚመራን ጳውሎስ ክርስቶስን ድልን እንደሚያቀዳጅ የጦር መሪ ይገልፀዋል። ትኩረት: "ድልን ይሰጠናል።" (ተመልከት: ጣፋጭ የእውቀት ሽታ "መልካም የእውቀት ሽታ።" ጳውሎስ "ጣፋጭ ሽታ" ሲል ደስ የሚያሰኝ እውቀትን ያመላክታል። ትኩረት:"አስደሳች እውቀት" የክርስቶስ ጣፋጭ ሽታ "መልካም የክርስቶስ ሽታ" ጳውሎስ "ጣፋጭ ሽታ" የሚለውን ሃርግ ሲጠቀም አስደሳች እውቀት የሚለውን እንዲያመለክት ነው። ትኩረት "የክርስቶስ አስደሳች እውቀት" (ተመልከት:

2 Corinthians 2:16

2ኛ ቆሮንቶስ 2:16-17
ለሞት የሚሆን የሞት ሽታ

ለህይወት የሚሆን የህይወት ሽታ "ሽታ" የሚለው ቃል የሚያሳየው ክርስቶስን ስለማወቅ ነው። በመንፈስ ህያው የሆኑ ሰዎች፥ የክርስቶስ እውቀት ልክ እንደ ጣፋጭ የመዓዛ ሽታ ነው። ትኩረት:"የህይወት እውቀት ሽታ ለህያዋን ሰዎች ነው" ለነዚህ ነገሮች የበቃ ማነው? ጳውሎስ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ክርስቶስን ማወቅ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ እንጂ ማንም የሚገባው ሆኖ

እንዳልሆነ ለማሳየት ነው። ትኩረት፡"እነዚህ ነገሮች የሚገባው እንድም ሰው የለም።"

"የምንናገረው በክርስቶስ ባለን እምነት ነው"

በቅን ልቦና "እውነተኛ ፍላጎቶች" በክርስቶስ* እንናገራለን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 3

1 ራሳችንን እንደገና ልናወድስ እንጀምራለንን? አንዳንድ ሰዎች እንደሚያደርጉት ለናንተም ሆነ ከእናንተ የድጋፍ ደብዳቤ ያስፈልገን ይሆን? አያስፈልገንም። 2 እናንተ ራሳችሁ በልባችን ላይ የተፃፋችሁ፥በሁሉም ሰዎች የምትታውቁ እና የምትነበቡ የድጋፍ ደብዳቤያችን ናችሁ። 3 በእኛ የቀረባችሁ የክርስቶስ መልዕክት ከመሆናችሁም በላይ በህያው የእግዚአብሔር መንፈስ እንጂ በቀለም ያልተፃፋችሁ፤በሰዎች የልብ ፅላት ላይ እንጂ በድንጋይ ፅላት ላይ ያልተቀረፃችሁ ናችሁ። 4 እንግዲህ በክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ላይ ይህ መታመን አለን። 5 ከእኛ የሆነ ብለን ልናስበው የምንችል አንዳች ችሎታ የለንም፤ነገር ግን ብቃታችን ከእግዚአብሔር ነው። 6 እርሱም የአዲስ ኪዳን አገልጋዮች አደረገን። ይህ ኪዳን የፊደል ሳይሆን የመንፈስ ነው። ምክንያቱም ፊደል ይገድላል፣ መንፈስ ግን ህይወትን ይሰጣል። 7 የእስራኤል ህዝብ ከፊቱ ክብር የተነሳ እያደር የሚደበዝዘውን የሙሴን ፊት መመልከት እስኪያቅታቸው ድረስ በፊደላት በድንጋይ ላይ የተቀረፀው የሞት አገልግሎት በክብር ከሆነ፤ 8 የመንፈስ አገልግሎት እጅግ በክብር አይልቅምን? 9 የኩነኔ አገልግሎት ክብር ከነበረው፥የፅድቅ አገልግሎት እንደምን በክብር ይብዛ! 10 በርግጥም ቀድሞ በክብር የነበረው ከሱ በሚበልጥ ክብር ተሸሯል። 11 አላፊው በክብር ከሆነ ፀንቶ የሚኖረው በክብር እንዴት ይበልጥ! 12 እንግዲያውስ እንዲህ ያለ ትምክህት ስላለን እጅግ በድፍረት እንናገራለን። 13 እኛ የእስራኤል ህዝቦች የሚያልፈውን ክብር ትኩር ብለው መመልከት እንዳልቻሉት፤ ፊቱን በመሸፈኛ እንደ ከለለው እንደ ሙሴ አይደለንም። 14 ሆኖም ግን አእምሮዋቸው ተሸፈነባቸው። እስከዛሬም አሮጌው ኪዳን ሲነበብ ያው መሸፈኛ ይኖራል፤ለገለጥም አይችልም፤ ምክንያቱም ሊወገድ የሚችለው በክርስቶስ ነው። 15 ሆኖም ግን እስከዛሬ ድረስ የሙሴ ህግ ሲነበብ በልባቸው ላይ መሸፈኛው ይኖራል። 16 ሰው ግን ወደ ጌታ መለስ ሲል ፥መሸፈኛው ይነሳል። 17 ጌታም መንፈስ ነው፤የጌታም መንፈስ ባለበት ነፃነት አለ። 18 እኛም ሁላችን ባልተሸፈነ ፊት የጌታን ክብር እያየን እርሱን ወደሚመስል ከአንድ ክብር ደረጃ ወደ ሌላ ክብር ደረጃ እንለወጣለን፤ይህም የሚሆነው መንፈስ ከሆነው ጌታ ነው።

---

2 Corinthians 3:1

2ኛ ቆሮንቶስ 3:1-3
ራሳችንን እንደገና ልናወድስ እንጀምራለንን? ጳውሎስ ይህን ሲናገር ራሳቸውን ከሌሎቹ የተሻሉ አድርገው እንደማይመለከቱ ለማስታውቅ ነው። ለናንተም ሆነ ከእናንተ የድጋፍ ደብዳቤ ያስፈልገን ይሆን? ጳውሎስ የሚለው ቆሮንቶሶች ስለ ጳውሎስም ሆነ ስለጢሞቲዎስ መልካም ስም አስቀድመው አውቀዋል። የድጋፍ ደብዳቤያችን ጳውሎስ እና ጢሞቲዎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ያላቸው ፍቅር ቤተ ክርስቲያን ጳውሎስ እና ጢሞቲዎስ የታመኑ መሆናቸውን ከሚያሳየው የድጋፍ ደብዳቤ ጋር ይንፃፀራል። በእኛ የቀረባችሁ የክርስቶስ መልዕክት ከመሆናችሁም በላይ በህያው የእግዚአብሔር መንፈስ እንጂ*፤በሰዎች የልብ ፅላት ላይ እንጂ ጳውሎስ እዚህ ጋር የሚናገረው በቆሮንቶስ ያሉ ሰዎች ልክ እንደ ደብዳቤ ስለ ምሳሌነታቸው የሚነገር ጳውሎስ እና ጢሞቲዎስም ያካፈሉት የክርስቶስ መልዕክትም በመንፈስ ቅዱስ ሃይል ለውጧቸው አሁን ምን አይነት ሰዎች እንደሆኑ ነው። በሰዎች የልብ ፅላት ላይ እንጂ በድንጋይ ፅላት ላይ ያልተቀረፃችሁ ናችሁ "ድንጋይ" የሚለው ቃል ለማይለወጥ ነገር ስዕላዊ መግለጫ ነው። "በሰዎች የልብ" የሚለው ሃረግ ጥቅም ላይ የዋለው ለስላሳ እና የሚለወጥ በመሆኑ ነው። ፅላት እነዚህ ጠፍጣፋ ለፅህፈት ስራ የሚያገለግሉ ከድንጋይ ወይም ከሸክ ላ የሚሰሩ ነገሮች ናቸው።

2 Corinthians 3:4

2ኛ ቆሮንቶስ 3:4-6
2ኛ ቆሮንቶስ 3:4-6

ይህ መታመን "ይህ" የሚለው ቃል ጳውሎስ እና ጢሞቲዎስ ክርስቶስን ማወቅ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ህዝብ ውስጥ ያመጣውን ለውጥ እንዴት እንደተገነዘቡት ያመለክታል። አንዳች ችሎታ፡ "በራሳችን ብቃት ያለን" ብቃታችን "የእኛ መስፈርት" የፊደል ሳይሆን የመንፈስ ጳውሎስ "ፊደል" የሚለውን ቃል ሲጠቀም የብሉይ ኪዳንን ህግጋት ለማመላከት ሲሆን በዚያም ፊደላት ቃልን የሚመሰርቱበት ነው። "የፊደል ኪዳን" የሚለው ሃረግ የብሉይ ኪዳን እያንዳንዱ ህግ ማለት ነው። ትኩረት፡ "ህግን በመታዘዝ ሳይሆን የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ በመቀበል ነው።" ፊደል ይገድላል ይህ ሃረግ የሚለው የብሉይ ኪዳንን ህግጋት በፍፁምነት ለመታዘዝ መሞከር ወደ መንፈሳዊ ሞት የሚመራ ውድቀት ያድርሳል።

2 Corinthians 3:7

2ኛ ቆሮንቶስ 3:7-8
የመንፈስ አገልግሎት እጅግ በክብር አይልቅምን? በመንፈስ ቅዱስ ውስጥ ያለው ክብር በሙሴ ህግ ውስጥ ካለው ክብር እጅግ ይበልጣል። ትኩረት፡"ምክንያቱም* የመንፈስ ቅዱስ ስራ የበለጠ ነውና።"

በፊደላት * የተቀረፀው

"በፊደላት የተቀረፀው" የሞት አገልግሎት * የመንፈስ አገልግሎት

ጳውሎስ "የ አገልግሎት" የሚለውን ሃረግ የሚጠቀመው እግዚአብሔር በህግ አማካኝነት የሰጠውን ሞት ወይም በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የሰጠውን ህይወት አመላካች ነው። ትኩረት፡ "ሞት የሚያስከትለው መንገድ * መንፈስ ቅዱስ መንገድ የሚመጣው።"

2 Corinthians 3:9

2ኛ ቆሮንቶስ 3:9-11
የኩነኔ አገልግሎት ይህ ሀረግ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠውን ህግ ነው። የሚያነጣጥረውም የሰውን ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ ሲሆን፥ውጤቱም የሰውን ልጅ ለሞት ፍርድ መዳረግ ነው። የፅድቅ አገልግሎት ይህ ሀረግ የሚያመለክተው በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት የተሰጠውን የይቅርታ መልዕክት ነው። የሞትን ፍርድ እንደሚያመጣው ህግ ሳይሆን ይቅርታን እና አዲስ ህይወትን ያስገኛል። በክብር ይብዛ የክርስቶስ የፅድቅ አገልግሎት ከህግ ክብር ይልቅ እጅጉን የከበረ ነው። በርግጥም ቀድሞ * የነበረው

"የነበረው" የሚለው ቃል የሙሴን ህግ አመላካች ነው። ይበልጥ "ያ የተሻለ ነው" አላፊው "ዓላማውን ፈፅሟል"

2 Corinthians 3:12

2ኛ ቆሮንቶስ 3:12-13
የሚያልፈውን ክብር፡ የእግዚአብሔር ክብር ብርሃን በሙሴ ፊት ላይ ነበርና ሙሴ እስራኤላውያን በፊቱ ላይ የሚደበዝዘውን ክብር እንሳያዩ ብሎ መሸፈኛ ፊቱ ላይ ያደርግ ነበር። ትኩረት፡ "ከሙሴ ፊት ላይ እየደበዘዘ የሚሄደው የእግዚአብሔር የክብሩ ብርሃን"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Corinthians 3:14

2ኛ ቆሮንቶስ 3:14-16
የእነርሱ "እስራኤላዊያን" ያው መሸፈኛ አይነርግብ ፊትን እንደሚሸፍን፥ጳውሎስም እዚህ ጋ መንፈሳዊ አይነርግብ አይሁድን የእግዚአብሔርን መልዕክት እንዳይረዱ እንደሚከለክላቸው ይናገራል። የሙሴ ህግ ሲነበብ ይህ በሙሴ አማካኝነት የተፃፉትን መፃህፍት ያመላክታል። ትኩረት፡ "የሙሴ ፅሁፎች በተነበቡ ጊዜ ሁሉ" (ተመልከት፡ ወደ ጌታ መለስ ሲል "መለስ" የሚለው ቃል የአስተሳሰብ ለውጥን የሚያመለክት ነው። ትኩረት፡ "ራሳቸውን ከማመን ጌታ ወደ ማመን መለወጥ" መሸፈኛው ይነሳል "መሸፈኛ" የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን መልዕክት መረዳት አለመቻልን ያሳያል። "ይነሳል" ሲልም በዚህ ጊዜ ደግሞ የመረዳት ችሎታ ይሰጣቸዋል ማለት ነው።

2 Corinthians 3:17

2ኛ ቆሮንቶስ 3:17-18
ባልተሸፈነ ፊት የጌታን ክብር እያየን የእንድ ሰው ፊት መሸፈኛ ሲነሳለት በግልፅ ማየት የሚችል ሲሆን መረዳት መቻልን ያመላክታል። "እያየን" የሚለው ቃል አንድን ነገር መረዳትን ያመለክታል። እርሱን ወደሚመስል ከጌታ ክብር ጋር የሚመሳሰል ክብር ወይንም የእግዚአብሔርን ክብር የሚያሳይ ነገር ከአንድ ክብር ደረጃ ወደ ሌላ ክብር ደረጃ "ከእንድ የክብር መጠን ወደ ሌላ የክብር መጠን"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 4

1 እንግዲህ፥ይህ አገልግሎት ስላለን እንዲሁም ምህረት እንደተቀበልን መጠን፥ ተስፋ አንቆርጥም። **2** በዚያ ፈንታ ግን አሳፋሪ እና ድብቅ የሆኑ መንገዶችን ክደናል። የተንኮል ህይወት አንኖርም፥የእግዚአብሔርንም ቃል ያለ አግባብ አንጠቀምበትም። እውነትንም እየተናገርን ራሳችንን ለሰው ሁሉ ህሊና በእግዚአብሔር ፊት እናቀርባለን። **3** ሆኖም ግን ወንጌላችን የተሸፈነ ቢሆን፥የተሸፈነው ለሚጠፉት ሰዎች ብቻ ነው። **4** በእነርሱ ሁኔታ ታዲያ የዚህ ዓለም አምላክ የማያምን አዕምሮዋቸውን አሳውሮታል። በዚህም የእግዚአብሔር መልክ የሆነውን የክርስቶስን የክብር ወንጌል ብርሃን እንዳያዩ አደረጋቸው። **5** ክርስቶስ ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ እንጂ ራሳችንን አንሰብክም፥እንዲሁም ስለ ኢየሱስ ስንል የእናንተ አገልጋዮች ነን። **6** ውስጥ ብርሃን ይብራ" ያለው ራሱ እግዚአብሔር ነው፤እናም በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት የእግዚአብሔር ክብር የእውቀት ብርሃን እንዲሰጠን በልባችን ውስጥ አበራልን። **7** ነገር ግን እጅግ ታላቅ የሆነው ሃይሉ ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ እንዳልሆነ ለማሳየት ይህ ሃብት በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን። **8** በሁሉ መንገድ መከራን እንቀበላለን፥ሆኖም በዚያ አንዋጥም። እናመነታለን ነገር ግን ተስፋ በማጣት አንረበሽም። **9** ቢሆንም ግን ተረስተን አንቀርም። **10** የኢየሱስ ህይወት በሰውነታችን እንዲገለጥ የእርሱን ሞት ሁልጊዜ በሰውነታችን እንሸከማለን። **11** ይህም የኢየሱስ ህይወት በሰብዓዊ ሰውነቶቻችን እንዲገለጥ እኛ ህያዋን የሆንን በየዕለቱ ስለ ኢየሱስ ምክንያት ለሞት ታልፈን እንሰጣለን። **12** በዚህም ምክንያት ሞቱ በእኛ፥ ህይወቱም በእናንተ ይሰራል። **13** ነገር ግን "አመንሁ ስለዚህም ተናገርሁ"ተብሎ እንደተፃፈ፡ ሁላችንም አንድ አይነት የእምነት መንፈስ አለን። ስለምናምንም እንናገራለን። **14** ጌታ ኢየሱስን ከሞት ያስነሳው እኛንም ከእርሱ ጋር ያስነሳናል። ከእናንተም ጋር ወደ ፊቱ እንዲያመጣን እናውቃለን። **15** የሚሆነው ለእናንተ ጥቅም ሲሆን ፀጋ ለብዙዎች ሲበዛ ለእግዚአብሔር ክብር የሚሆን ምስጋናም ይጨምራል። **16** ስለዚህም ተስፋ አንቆርጥም። ምንም እንኳ ውጫዊው ማንነታችን እየደከም ቢመጣም ውስጣዊው ማንነታችን ዕለት በየዕለት ይታደሳል። **17** ይህ ጊዜያዊ፣ ቀላል መከራችን መለኪያ ለሌለው፥ ለላቀው ዘላለማዊ ክብር የሚያዘጋጀን ነው። **18** የሚታዩትን ነገሮች ሳይሆን የማይታዩትን ነገሮች እንመለከታለን። የምናያቸው ነገሮች ጊዜያዊ ሲሆኑ የማይታዩት ነገሮች ግን ዘላለማዊ ናቸው።

---

2 Corinthians 4:1

2ኛ ቆሮንቶስ 4:1-2
እኛ፡ "እኛ" ለሚለው ለዚህ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉ 1) ጳውሎስ እና የአገልግሎት ቡድኑ ወይም 2) ጳውሎስ እና ሌሎች ሐዋርያቶች ወይም 3) ጳውሎስ እና የቆሮንቶስ አማኞች ይህ አገልግሎት ስላለን እንዲሁም ምህረት እንደተቀበልን፡ እነዚህ ሁለቱም ሃረጎች የሚያመላክቱት እግዚአብሔር እርሱን እንድንመስል በመለወጥ ምህረቱን በማሳየት እንዴት እንዳገለገለን ነው።
አሳፋሪ እና ድብቅ እነዚህ ሁለት ቃላት አንድ አሳብን ይገልፃሉ። ትኩረት፡ "ድብቅ አሳፋሪ" የተንኮል ህይወት፡ "በማታለል መኖር" የእግዚአብሔርንም ቃል ያለ አግባብ አንጠቀምበትም፡ ይህ ሃረግ አንድ አዎንታዊ ሃሳብ ለመግለፅ ሁለት አሉታዊ ሃሳቦችን ያነሳል። ትኩረት፡"የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል እንጠቀማለን። በእግዚአብሔር ፊት፡ እግዚአብሔር የፀሐፊውን እውነተኛነት የሚረዳበት ሁኔታ እግዚአብሔር እነርሱን ከሚያይበት ጋር ተመላክቷል።

2 Corinthians 4:3

2ኛ ቆሮንቶስ 4:3-4
ወንጌላችን የተሸፈነ ቢሆን፥የተሸፈነው * ብቻ ነው፡

"የተሸፈነው የሚለው ቃል ለመረዳት የማይቻል ማለት ነው። አንድ ነገር ከተሸፈነ ሊታይ የማይችል ነው ማለት ነው። የማይታይ ነገር መረዳት ከማይቻል ነገር ጋር እኩል ነው። የዚህ ዓለም አምላክ፡ ይህ ሃረግ የሚያመለክተው ሰይጣንን ነው። የእንግሊዝኛ ትርጉሞች ሃሰተኛ አማልክትን ለማመልከት ትንሹን "ጂ" ይጠቀማሉ። ኣሳውሮታል፡ ትኩረት፡"ከመረዳት ከለከላቸው" ብርሃን፡ "ብርሃን" የሚለው ቃል እውነትን ያመለክታል።

2 Corinthians 4:5

2ኛ ቆሮንቶስ 4:5-6
ክርስቶስ ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ እንጂ * የእናንተ አገልጋዮች ነን፡

ይህ የዕብራዊያን ፀሐፊ እንዲህ በማለት የፃፈውን ያሳያል። ትኩረት:"ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ እና ለጥቅማችሁ እንደምንሰራ እናውጃለን።" ስለ ኢየሱስ ስንል፡ ትኩረት፡ ለኢየሱስ ክብር ለማምጣት በጨለማ ውስጥ ብርሃን ይብራ፡ ብርሃን መረዳትን ያመላክታል። ትኩረት፡ "ሰዎች ከዚህ ቀደም ያላስተዋሉትን ሲያስተውሉ" አበራልን፡ "አበራልን" የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን የብሬሃን ፈጣሪነት እና መረዳትን ሰጪነት አመላካች ነው።" በልባችን ውስጥ፡ "ልብ የሚለው ቃል ሰው በራሱ እውነት ነው ብሎ የሚረዳውን ስፍራ አመላካች ነው። ትኩረት "ለእኛ"

2 Corinthians 4:7

2ኛ ቆሮንቶስ 4:7-10
ይህ ሃብት፡ ፀሐፊው በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ያለውን "የእግዚአብሔር እውቀት ክብር" ያመለክተናል።" በሸክላ ዕቃ፡ ፀሐፊው ይህንን ሃረግ የሚጠቀመው ለሰው ልጅ ሰውነት ነው። በሁሉ መንገድ መከራን እንቀበላለን፥ሆኖም በዚያ አንዋጥም። እናመነታለን ነገር ግን ተስፋ በማጣት አንረበሽም። ቢሆንም ግን ተረስተን አንቀርም፡ እነዚህ ሃረጋት የሚያመላክቱት በተግዳሮት ውስጥ ያለ ነገር ግን ያልተሸነፈ ሰውን ነው። የእርሱን ሞት ሁልጊዜ በሰውነታችን እንሸከማለን፡ "የኢየሱስ ሞት" የሚለው ሃረግ የሚያመለክተው ኢየሱስ ለሰው ልጆች ሃጢያት ማስተሰረያ የመሞቱን መረዳት ነው። ትኩረት፡ "ሁልጊዜ የኢየሱስን ሞት እውቀት በሰውነታችን እንሸከማለን።" የኢየሱስ ህይወት በሰውነታችን እንዲገለጥ፡ "በሰውነታችን" የሚለው ቃል አማኞች በኢየሱስ የሚኖሩትን አኗኗር የሚያሳይ ነው። (ተመልከት፡

2 Corinthians 4:11

x
2ኛ ቆሮንቶስ 4:11-12 እኛ ህያዋን የሆንን፡ ጳውሎስ በዚህ የሚያመለክተው በክርስቶስ አምኖ ጌታን የሚሰብክ ፥በሞት ያልተለየን ማንኛውንም ሰው ነው። ታልፈን እንሰጣለን፡ "አደጋ ውስጥ" የኢየሱስ ህይወት * እንዲገለጥ፤፡

ይህ ሃረግ ቀጣይ የሆነውን የኢየሱስ ህይወት የሚያመላክት እና ለዕብራውያን ፀሐፊም ምን ማለት እንደሆነ የሚያሳይ ሲሆን በተጨማሪም እምነታቸውን በክርስቶስ ጌታ ላይ በማድረጋቸው ምክንያት እስከ ሞት ድረስ አደጋ ውስጥ የከተቱትን አማኞች ያጠቃልላል። ትኩረት፡ "እምነታችን ኢየሱስ ከሞት እንደተነሳ እና የዘላለም ህይወት እንደሚሰጠን ይረጋገጥ ዘንድ ነው።" በሰብዓዊ ሰውነቶቻችን፡ በዚህ ማብራሪያ እንደሚታየው [2CO 4:10] ሞቱ በእኛ ይሰራል፡ ጳውሎስ ሞት ስራ እንደሚሰራ አድርጎ ያሳያል። ይህም ሞት የሚያስፈራቸው ሰዎች በሌሎች ላይ ግን አዎንታዊ ውጤት እንደሚኖራቸው ነው። ህይወቱም በእናንተ ይሰራል፡ ጳውሎስ ህይወት ስራ እንደሚሰራ አድርጎ ያሳያል። ይህም የዘላለም ህይወት እውቀት ሰዎች በአይሁድ እማኞች ኑሮ ላይ አዎንታዊ ውጤት እንደሚኖረው ነው። (ተመልከት፡

2 Corinthians 4:13

2ኛ ቆሮንቶስ 4:13-15
ሁላችንም አንድ አይነት፡ "ሁላችንም" የሚለው ቃል ጳውሎስን ፥ጢሞቲዎስን እና የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያንን ያመለክታል። አንድ አይነት የእምነት መንፈስ፡ "ተመሳሳይ የእምነት እሳቤ" "መንፈስ" የሚለው ቃል አንድ ሰው የሚያስብበትንና የሚወስንበትን መንገድ ያሳያል። ጳውሎስ እና ጢሞቲዎስ እያሉ ያሉት እግዚአብሔርን የመታመናቸው ዝንባሌ ከቆሮንቶሶች ጋር ተመሳሳይ ነው ማለት ነው። አመንሁ ስለዚህም ተናገርሁ፡ ይህ ቃል ከንጉስ ዳዊት የተጠቀሰ ነው። ከናንተም ጋር እንዲያመጣን፡ "እንዲያምጣን" የሚለው ቃል ውስጥ ቆሮንቶሶችን አይጨምርም። ምስጋና፡ መልካሙ አምላክ ያደረገውን ማሰብና ማመስገን

2 Corinthians 4:16

2ኛ ቆሮንቶስ 4:16-18
ስለዚህም ተስፋ አንቆርጥም፡ ትኩረት፡ "ስለዚህ እንበረታታለን" (ተመልከት፡ ውጫዊው ማንነታችን እየደከም ቢመጣም፡ ይህ ሃረግ የጳውሎስን እና የጢሞቲዎስ ውጫዊ ገፅታን ያሳያል። '"እየደከመ" የሚለው ቃል የሚያሳየው ጤናማ ገፅታ እያጣ የመጣን የአንድን ሰው ሁኔታ ነው። ውስጣዊው ማንነታችን ዕለት በየዕለት ይታደሳል፡ "ውስጣዊ" የሚለው ቃል የሰውን ማሰቢያ ውስጣዊ ማንነት አመላካች ነው። "ይታደሳል" የሚለውም ቃል እሳቤዎች እንደገና አዎንታዊ መልክ እንደሚይዙ ያሳያል። መለኪያ ለሌለው፥ ለላቀው ዘላለማዊ ክብር፡ ጳውሎስ እና ጢሞቲዎስ የሚጥብቃቸው ክብር ከእቅም በላይ ከሆነ ክብደት ጋር ተነፃፅሯል። ይህ በሌላ አባባል በስራቸው እጅግ ታላቅ ክብር እንደሚያግኙ ያሳያል። ትኩረት፡ "በሰማይ ለዘላለም በታላቅ ሁኔታ መክበር" (ተመልከት፡

የሚያዘጋጀን፡ ይህ ቃል የሚያመለክተው እንድ ሰው እንዲሆን የሚጠብቀውን ነው። ትኩረት፡ "መፈለግ" የምናያቸው ነገሮች፡ ይህ በህይውት ሳለን የሚገኙ ንብረቶች ናቸው። ትኩረት፡ "ንብረቶች" የማይታዩት ነገሮች፡ ይህ የሚያመለክተው በሰማይ ያለውን ሽልማት ነው። ትኩረት፡ "በሰማይ ያለ ታላቅ ብድራት" ቀደም ብሎ ከሚገኘው ሃረግ መገንዘብ እንደሚቻለው ጳውሎስና ጢሞቲዎስ የሚጠብቁት ይህንን ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 5

1 ምድራዊው መኖሪያችን ቢፈርስ እንኳ በሰማይ በሰው እጅ ያልተሰራ ዘላለማዊ ቤት በእግዚአብሔር እንደተሰራልን እናውቃለን። 2 ድንኳን ውስጥ ሆነን
እንቃትታለን፥ሰማያዊ መኖሪያችንንም ልንለብስ እንናፍቃለን። 3 ምክንያቱም ያን ለብሰን ስንገኝ ራቁታችንን ሆነን አንገኝም ። 4 በርግጥ በዚህ ድንኳን ውስጥ
ሆነን ከብዶን እንቃትታለን፤ምክንያቱ ደግሞ ሟች የሆነው ሰውነት በህይወት መዋጥ ስላለበት እኛም ለብሰን እንጂ ራቁታችንን መሆን አንፈልግም። 5 ወደ ፊት
ሊመጣ ላለው የመንፈሱን ዋስትና የሰጠን ለዚህም ያዘጋጀን እግዚአብሔር ነው። 6 እንግዲህ በሰውነታችን በዚህ ምድር በምንኖርበት ጊዜ በሰማይ ካለው ጌታ
ርቀን እንዳለን ይህን እርግጠኛ ሁኑ 7 ምክንያቱም በእምነት እንጂ በማየት አንመላለስምና። 8 ስለዚህ ይህ ድፍረት አለን፤ከሰውነታችን ተለይተን ከጌታ ጋር
በሰማይ ቤት መሆንን እንመርጣለን። 9 ስለሆነም በምድርም ብንሆን ወይም ከምድር ብንለይ ግባችን እርሱን ማስደሰት ነው። 10 እያንዳንዳችን በሰውነታችን
በዚህ ምድር ላይ የሰራነውን መልካምም ሆነ ክፉ እንቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት መቅረባችን ግድ ነው። 11 እንግዲህ ጌታን መፍራት
ምን ማለት እንደሆን ስለምናውቅ ሰዎችን ግድ እንላለን። ማንነታችን በእግዚአብሔር ፊት የተገለጠ ስለሆነ ለናንተም ህሊና ግልፅ እንደሚሆን ተስፋ አለኝ። 12
ራሳችንን ደግመን እንድታወድሱን አናቀርብላችሁም፥ ሆኖም በልብ ሳይሆን በውጫዊው መልክ ለሚመኩ መልስ መስጠት እንዲቻላችሁ እኛን ምክንያት
አድርጋችሁ እንድትመኩ እናስታውቃችኋለን። 13 እንደ እብድ ቢያረገን፥ ለእግዚአብሔር ነው፤እንደ ባለአዕምሮ ብንሆን ደግሞ ለእናንተ ስንል ነው። 14 የክርስቶስ
ፍቅር ግድ ይለናል፥ በዚህ ነገር እርግጠኞች ነን፡አንዱ ሰው ስለሁሉ ሞተ፥ ስለሆነም ሁሉም ሞቱ ማለት ነው። 15 በህይወት ያሉትም ስለእነርሱ ለሞተውና
ለተነሳው እንጂ ለራሳቸው እንዳይኖሩ ክርስቶስ ስለሁሉ ሞተ። 16 ስለዚህም ምክንያት ክርስቶስን ከዚህ ቀደም በሰዋዊ መንገድ አይተነው ቢሆን፥ካሁን ጀምሮ
ማንንም በሰዋዊ መስፈርት አንፈርድም። በማንም ላይ ከዚህ በኋል በዚህ መንገድ አንፈርድም። 17 ስለሆነም ማንም በክርስቶስ ውስጥ ቢሆን እርሱ አዲስ
ፍጥረት ነው። አሮጌ ነገሮች አልፈዋል። ተመልከቱ፥ ሁሉ አዲስ ሆኗል። 18 እነዚህ ነገሮች ሁሉ የሆኑት እኛን በክርስቶስ ከራሱ ጋር ባስታረቀንና የዕርቅ
አገልግሎት በሰጠን በእግዚአብሔር ነው። 19 እግዚአብሔርም በደላቸውን ሳይቆጥርባቸው ዓለሙን በክርስቶስ ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበር። እኛንም ለዚህ የዕርቅ
መልዕክት ታማኝ አድርጎ ሾመን። 20 ስለዚህም እግዚአብሔር በእኛ ሆኖ ልመናውን እንደሚያቀርብ፥ የክርስቶስ ተወካዮች ሆነን ተሹመናል። ከእናንተም ጋር
በመሆን ስለ ክርስቶስ "ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ!" ብለን ልመና እናቀርባለን። 21 እኛም በእርሱ የእግዚአብሔር ፅድቅ እንድንሆን ሃጢያት ሰርቶ የማያውቀውን
ክርስቶስን እግዚአብሔር የሃጢያት መስዋዕት አደረገው።

---

2 Corinthians 5:1

2ኛ ቆሮንቶስ 5:1-3
ምድራዊ መኖሪያችን፡ ሰብዓዊ ሰውነታችን መኖሪያችን ቢፈርስ፡ ሰብዓዊ ሰውነታችን ሲጠፋ በሰማይ በሰው እጅ ያልተሰራ ዘላለማዊ ቤት በእግዚአብሔር እንደተሰራልን እናውቃለን፡ እግዚአብሔር የምንኖርበትን አዲስ ዘላለማዊ አካል ይሰጠናል። ድንኳን ውስጥ ሆነን እንቃትታለን፡ ትኩረት፡"በዚህ ምድራዊ አካል ውስጥ ሆነን እንታገላለን"

ምክንያቱም ያን ለብሰን ስንገኝ ራቁታችንን ሆነን አንገኝም፡ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉ፡ 1) በእግዚአብሔር ፅድቅ እንሸፈናለን ወይም 2) እግዚአብሔር አዲስ አካልን ሰጥቶ ያለብሰናል።

2 Corinthians 5:4

2ኛ ቆሮንቶስ 5:4-5
በዚህ ድንኳን ውስጥ ሆነን፡ "በዚህ ምድራዊ አካል ውስጥ ሆነን" ከብዶን እንቃትታለን፡ ትኩረት፡ "ከሐጢያት ጋር እየታገልን" ራቁታችንን፡ ትኩረት፡ "ስንሞት" ለብሰን፡ ትኩረት፡ "በዘላለማዊ አካላችን ውስጥ ስንኖር" ሟች የሆነው ሰውነት በህይወት መዋጥ ስላለበት፡ ትኩረት፡"ምድራዊ የሆነው አካላችን ወደ አዲስ ሰማያዊ አካል ይለወጣል"

2 Corinthians 5:6

2ኛ ቆሮንቶስ 5:6-8
በሰውነታችን በዚህ ምድር በምንኖርበት ጊዜ፡ ትኩረት፡"በዚህ ምድራዊ ሰውነት በምንኖርበት ጊዜ" በሰማይ ካለው ጌታ ርቀን፡ ትኩረት፡ "ከጌታ ጋር በቤት አይደለንም" ወይም "በሰማይ ከጌታ ጋር አይደለንም" ከጌታ ጋር በሰማይ ቤት፡ ትኩረት፡"ከጌታ ጋር በሰማይ መኖር"

2 Corinthians 5:9

2ኛ ቆሮንቶስ 5:9-10
በምድርም ብንሆን ወይም ከምድር ብንለይ፡ ትኩረት፡"በምድራዊ እካል በምድር ወይም በሰማይ" በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት፡ "ለፍርድ በክርስቶስ ፊት መሆን" እንቀበል ዘንድ፡ ትኩረት፡"ሽልማትም ሆን ቅጣት ለመቀበል" በዚህ ምድር የሰራነውን፡ ትኩረት፡ "በዚህ ምድራዊ አካል የተሰራውን" መልካምም ሆነ ክፉ፡ "መልካምም ሆን ክፉ ቢሆኑ"

2 Corinthians 5:11

2ኛ ቆሮንቶስ 5:11-12
ጌታን መፍራት ምን ማለት እንደሆን ስለምናውቅ፡ ትኩረት፡ "እግዚአብሔር ሐጢያትን እንደሚጠላ እንደሚፈርድም አውቀን" ለናንተም ህሊና ግልፅ እንደሚሆን፡ ትኩረት፡ "እናንተም እንደዚሁ እንደምታውቁ" አናቀርብላችሁም፡ ጳውሎስ እዚህ ጋር ከቆሮንቶስ አማኞች ውጪ ያሉትን ሲያመላክት ነው።

2 Corinthians 5:13

2ኛ ቆሮንቶስ 5፤13-15
የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናል፡ "እኛን የሚያነሳሳን የክርስቶስ ፍቅር ነው" ስለሆነም ሁሉም ሞቱ፡ እኛ ሁላችን እንደሞትን ተቆጠርን። ለራሳቸው፡ ትኩረት፡"በሃጢያት ለሚገኝ ደስታ" ለተነሳው፡ "ደግሞም ለተነሳው"

2 Corinthians 5:16

2ኛ ቆሮንቶስ 5:16-17
ማንም በክርስቶስ ውስጥ ቢሆን፡ ትኩረት፡ "ማንም ክርስቶስን ቢያምን" አዲስ ፍጥረት ነው፡ ትኩረት፡ "አዲስ ባህሪ መያዝ" አሮጌ ነገሮች አልፈዋል፡ ትኩረት፡ "አሮጌው የአኗኗር መንገድ እና እስተሳሰብ ይጠፋል" ሁሉ አዲስ ሆኗል፡ ትኩረት፡ "አኗኗራችንና አስተሳሰባችን ክርስቶስን ከማወቃችን በፊት የነበረውን የማይመስል የተለየ ነው"

2 Corinthians 5:18

2ኛ ቆሮንቶስ 5:18-19
ባስታረቀንና፡ "በመለሰንና" "ባደሰን" የዕርቅ አገልግሎት፡ ሰዎችን ከክርስቶስ ጋር መልሶ የሚያገናኝ እና የሚያድስ አገልግሎት እግዚአብሔርም * ዓለሙን በክርስቶስ ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበር፡

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እግዚአብሔር በክርስቶስ መስቀል ሞት ሰዎችን ወደ ራሱ ይመልስ ነበር። እኛንም ለዚህ የዕርቅ መልዕክት ታማኝ አድርጎ ሾመን፡ እግዚአብሔር ለጳውሎስ መልዕክቱን እንዲያሰራጭ ብሎም ከእግዚአብሔር ጋር እንዲያድሱ ይፈልጋል።

2 Corinthians 5:20

2ኛ ቆሮንቶስ 5:20-21
ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ፡ ትኩረት፡"ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ" ክርስቶስን *የሃጢያት መስዋዕት፡ "እግዚአብሔር የክርስቶስን የመስቀል ሞት ተቀባይነት ያለው መስዋዕት አደረገው" እኛም በእርሱ የእግዚአብሔር ፅድቅ እንድንሆን፡ ትኩረት፡ "በእኛ ውስጥም የክርስቶስ ፅድቅ እንድንሆን"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 6

1 እንደዚሁም፥ አብሮ እንደሚሰራ የእግዚአብሔርን ፀጋ እንዲሁ እንዳትቀበሉ እለምናችኋለሁ። 2 ምክንያቱም እግዚአብሔር እንዲህ ብሏልና "በምቹ ጊዜ
ሰማሁህ በድነትም ቀን ረዳሁህ።" ልብ በሉ፥ ምቹ ጊዜም ሆነ የድነት ቀን አሁን ነው። 3 አገልግሎታችን እንዳይነቀፍ በማንም ፊት ማሰናከያ አናኖርም። 4 ከዚያ
ይልቅ፥ በድርጊቶቻችን ሁሉ የእግዚአብሔር አገልጋዮች መሆናችንን እናረጋግጣለን። ይህም በመፅናት፥በመከራ፥ በስቃይ፥በችግር 5 በመገረፍ፥ በእስራት፥ጥላቻ
በተሞላ አመፅ፥ ፥በከባድ ስራ ፥እንቅልፍ በማጣት፥በርሃብ፥ 6 በንፅህና፥በእውቀት፥በትዕግስት፥በርህራሄ፥በመንፈስ ቅዱስ፥በእውነተኛ ፍቅር፥ 7 በእውነት ቃል፥
በእግዚአብሔር ሃይል ማለትም ለቀኝ እና ለግራ ለሚሆን ለፅድቅ የጦር ዕቃ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ነን። 8 በክብርም ሆነ በውርደት፥ በሃሜትም ሆነ
በሙገሳ ውስጥ እንሰራለን። በሃሰት ብንከሰስም እውነተኞች ሆነን ተገኝተናል። 9 ያልታወቅን ሆነን ስንሰራ፥እንታወቃለን፤ የምንሞት ስንመስል ህያዋን ነን።
በጥፋታችን እንደሚቅጣ ሰው ብንሆንም፥ሞት አልተፈረደብንም። 10 እንደ ሃዘንተኞች ስንሰራ ሁልጊዜም ግን ደስተኞች ነን፤ ድሆች ስንሆን ብዙዎችን ባለፀጎች
እናደርጋለን፥ ምንም የሌለን ስንሆን፥ ሁሉም አለን። 11 የቆሮንቶስ ሰዎች ሆይ፥ ሁሉን ነገር በግልፅ ነግረናችኋል፥ልባችንንም ለእናንተ ከፍተንላችኋል። 12
ልባችሁ በራሳችሁ መሻት እንጂ በእኛ ምክንያት አልተዘጋም። 13 ተገቢ በሆነ ሁኔታ እኔም እንደ ልጆች እናገራችኋለሁ፤ልባችሁን ክፈቱልን። 14 ከማያምኑ ጋር
በማይሆን መንገድ በአንድ ላይ አትተሳሰሩ። ፅድቅ ከአመፀኝነት ጋር ምን መዛመድ አለው? ብርሃንስ ከጨለማ ጋር ምን ህብረት አለው? 15 ክርስቶስስ
ከቤልያር ጋር ምን ስምምነት አለው? የሚያምንስ ከማያምን ጋር ምን ድርሻ አለው? 16 የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስስ ከጣዖታት ጋር ምን ስምምነት አለው?
እግዚአብሔር "ከእነርሱም ጋር አድራለሁ፥በመካከላቸውም እመላለሳለሁ፤ አምላካቸው እሆናለሁ፥ እነርሱም ህዝብ ይሆኑኛል" ብሎ ስለተናገረ እኛ የህያው
እግዚአብሔር መቅደሶች ነን። 17 ስለዚህም "ከመካከላቸው ውጡ፤የተለያችሁም ሁኑ" ይላል ጌታ፥ "እርኩሱን አትንኩ፥እኔም እቀበላችኋለሁ። 18 አባት
እሆናችኋለሁ እናንተም ወንዶችና ሴቶች ልጆች ትሆኑኛላችሁ።" ብሏል ሁሉን የሚችል ጌታ።

---

2 Corinthians 6:1

2ኛ ቆሮንቶስ 6:1-3
አብሮ እንደሚሰራ፡ ትኩረት፡ "ከእግዚአብሔር ጋር አብሮ የሚሰራ" ጳውሎስ በተዘዋዋሪ መንገድ እርሱ እና ጢሞቲዎስ ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚሰሩ ያሳያል። የእግዚአብሔርን ፀጋ እንዲሁ እንዳትቀበሉ እለምናችኋለሁ፡ ጳውሎስ ቆሮንቶሶችን የእግዚአብሔር ፀጋ በኑሯቸው እንዲገለጥ ያበረታታቸዋል። ትኩረት፡ "እግዚአብሔር ፀጋውን እንዳሳያችሁ ሰዎች መኖራችሁን እርግጠኞች እንድትሆኑ አሳስባችኋለሁ።" በምቹ ጊዜ ሰማሁህ፡ ትኩረት፡"በትክክለኛው ጊዜ ሰማሁህ" ምቹ ጊዜም ሆነ የድነት ቀን አሁን ነው፡ ትኩረት፡"በርግጥም፥ትክክለኛው ጊዜ አሁን ነው፤የድነትም ቀን አሁን ነው" አገልግሎታችን እንዳይነቀፍ በማንም ፊት ማሰናከያ አናኖርም፡ ትኩረት፡ ማንንም ሊያሳስት በሚችል አይነት መንገድ አንኖርም ወይም በአገልግሎታችንም የሚያስት ነገር አናደርግም።"

2 Corinthians 6:4

2ኛ ቆሮንቶስ 6:4-7
በድርጊቶቻችን፡ ጳውሎስ እዚህ ጋ የሚያመለክተው ወደራሱ እና ጢሞቲዎስ ነው። በድርጊቶቻችን ሁሉ የእግዚአብሔር አገልጋዮች መሆናችንን እናረጋግጣለን፡ ትኩረት፡"የእግዚአብሔር አገልጋዮች መሆናችንን በአኗኗሯችን እና በንግግራችን እናረጋግጣለን" በእውነት ቃል፡ "እውነትን በታማኝነት በመስበክ" ለቀኝ እና ለግራ ለሚሆን ለፅድቅ የጦር ዕቃ ፡ ጳውሎስ ለሁሉም አይነት ሁኔታ በሚያስፈልግ መልኩ በመንፈሳዊ ሃይል በእግዚአብሔር እንደታጠቀ ያመለክታል።

2 Corinthians 6:8

2ኛ ቆሮንቶስ 6:8-10
እንሰራለን፡ "እንሰራለን" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን እና ጢሞቲዎስን ነው። በክብርም ሆነ በውርደት፡ እነዚህ ሰዎች የጳውሎስን አገልግሎት የሚመለከቱበትን ፅንፎች ያሳያል። በሃሜትም ሆነ በሙገሳ፡ እነዚህ ሰዎች ስልጳውሎስ አገልግሎት የሚናገሩትን ፅንፎች ያሳያል። የምንሞት ስንመስል ህያዋን ነን፡ ትኩረት፡"እንደምትመለከቱት፥የምንሞት ስንመስል ህያዋን ነን" ሁልጊዜም ግን ደስተኞች ነን፡ ትኩረት፡"መልካም ዜና በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ምክንያት ሁልጊዜ ደስ ይለናል" ምንም የሌለን ስንሆን፥ ሁሉም አለን፡ ትኩረት፡"ምንም ባይኖረንም የእግዚአብሔር ሃብት ግን አለን"

2 Corinthians 6:11

2ኛ ቆሮንቶስ 6:11-13
ሁሉን ነገር በግልፅ ነግረናችኋል፡ "በታማኝነት ነግረናችኋል" ልባችንንም ለእናንተ ከፍተንላችኋል፡ ትኩረት፡"በነፃ ፍቅራችንን አሳይተናችኋል" ልባችሁ * በእኛ ምክንያት አልተዘጋም፡

ትኩረት፡"በእኛ ዘንድ የፍቅር ጉድለት አላሳየንም" ልባችሁ በራሳችሁ መሻት እንጂ፡ ትኩረት፡ "ፍቅራችሁን በሆነ ምክንያት ዘግታችሁብናል" ተገቢ በሆነ ሁኔታ እኔም እንደ ልጆች እናገራችኋለሁ፤ልባችሁን ክፈቱልን፡ ትኩረት፡ "በቀላሉ በልጅ ቋንቋ ስንናገራችሁ፥ተገቢ የሚሆነው እናንተም ፍቅራችሁን ስታሳዩን ነው"

2 Corinthians 6:14

2ኛቆሮንቶስ 6:14-16
ከማያምኑ ጋር * በአንድ ላይ አትተሳሰሩ፡

ትኩረት፡"ከአማኞች ጋር ብቻ የምትተሳስሩ ሁኑ"

በአንድ ላይ፡ "በጋራ መቧደን" ወይም "የቅርብ ህብረት መፍጠር"

ብርሃንስ ከጨለማ ጋር ምን ህብረት አለው፡ ብርሃን ከጨለማ ጋር አብረው በጋራ መኖር አይችሉም። ብርሃን ሲኖር ፥ጨለማ ይሸሻል። (ተመልከት፡

ቤልያር፡ "ቤልያር" የዲያብሎስ ሌላ ስሙ ነው። የሚያምንስ ከማያምን ጋር ምን ድርሻ አለው፡ አማኞች ከማያምኑ ጋር ተመሳሳይ የሆነ እሴት የላቸውም። ትኩረት፡"አማኝ ከማያምን ጋር ምን አይነት እሴት ይኖረዋል"

የህያው እግዚአብሔር መቅደሶች ነን፡ ጳውሎስ ክርስቲያኖች ሁሉ የእግዚአብሔር መቅደስ ማደሪያዎች እንደሆኑ ያመለክታል። ትኩረት፡"በውስጣችን የሚኖር የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ አለን" (ተመልከት፡

2 Corinthians 6:17

2ኛቆሮንቶስ 6:17-18
እርኩሱን አትንኩ፡ የሙሴ ህግ አንድን ሰው ሊያረክሰው የሚችለው መንገድ መንካት እንደሆን ይደነግጋል። "ንፁህ የሆነውን ነገር ብቻ ንኩ" (ተመልከት፡

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

አባት እሆናችኋለሁ፡ ትኩረት፡"የተወደደ አባት ለልጆቹ እንክብካቤ
እንደሚያደርግ እናንተንም እንከባከባችኋለሁ" እናንተም ወንዶችና ሴቶች
ልጆች ትሆኑኛላችሁ፡ "እናንተም ልጆቼ ትሆናላችሁ" (ተመልከት፡

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 7

1 የተወደዳችሁ ሆይ፥ እነዚህ ተስፋዎች ስላሉን በእግዚአብሔር ፍርሃት ቅድስናን እየተከተልን ስጋችንን እና መንፈሳችንን ከሚያረክስ ከማናቸውም ነገር ራሳችንን
እናንፃ። **2** ለእኛ በልባችሁ ስፍራ ስጡን! ማንንም አልበደልንም፥ማንንም አልጎዳንም፥ ማንንም ለራሳችን ጥቅም አልበዘብዝንም። **3** ይህንን የምላችሁ
ልኮንናችሁ ብዬ አይደለም፤ምክንያቱም አብረን ለመሞትም ሆነ ለመኖር በልባችን ውስጥ አላችሁና ነው። **4** በእናንተም ታላቅ መታመን አለኝ፣ትምክህቴም
ናችሁ። በመከራዎቻችን እንኳ መፅናናት እና የተትረፈረፈ ደስታ ሞልቶኛል። **5** ወደ መቄዶንያ በመጣን ጊዜ ሰውነታችን እረፍት አልነበረውም። ይልቁንስ በውጭ
ግጭት እና በውስጥ ፍርሃት ስለነበረብን በሁሉ አቅጣጫ ተጨነቅን ። **6** ነገር ግን ተስፋ የቆረጡትን የሚያፅናና አምላክ በቲቶ መምጣት አፅናናን። **7** የእርሱ
መምጣት ብቻ ሳይሆን እናንተም እርሱን ያፅናናችሁት ማፅናናት እኛን አፅናናን። ለእኔም ያላችሁን ታላቅ ፍቅር፣ርህራሄ እና ጥልቅ ሃሳብ ሲነግረን በይበልጥ
ተደሰትሁ። **8** ምንም እንኳ በመልዕክቴ ባሳዝናችሁም ለምን ፃፍኩ ብዬ አልፀፀትም። ነገር ግን፥የምፀፀተው መልዕክቴ ለጥቂት ጊዜም እንዳሳዘናችሁ
ስለማውቅ ነው። **9** አሁን የምደሰትበት ምክንያት ስላዘናችሁ ሳይሆን ሃዘናችሁ ወደ ንስሃ ስለመራችሁ ነው። እግዚአብሔር የሚወደው አይነት ሃዘን
እየተለማመዳችሁ ስለሆነ በእኛ ምክንያት ያጣችሁት ነገር የለም። **10** እግዚአብሔር የሚወደው ሃዘን ፀፀት የሌለበት፥ ወደ ድነት የሚመራ ንስሃን ያመጣል።
ዓለማዊ ሃዘን ግን ሞትን ያመጣል። **11** እግዚአብሔር የሚወደው ሃዘን ምን አይነት ታላቅ ቁርጠኝነት እንዳመጣላችሁ እዩ። ይህም ታላቅ ቁርጠኝነት ምን ያህል
ንፁህ መሆናችሁን፥ ምን ያህል በሃጢያት ላይ እንድትቆጡ እንዳደረጋችሁ፥ ምን አይነት ናፍቆት እንዳሳደረባችሁ፥ ምን አይነት በጎ ቅንዓት እንደፈጠረባችሁ
፥ፍትህ እንድታደርጉም ምን አይነት ጥልቅ መሻት እንዳደረገላችሁ ተመልከቱ! በዚህ በኩል በሁሉም ንፁህ መሆናችሁን አስመስክራችኋል። **12** ምንም እንኳ
ብፅፍላችሁም የፃፍኩት ለክፉ አድራጊ ወይም በክፉ አድራጎቱ መከራ ለሚቀበል ሳይሆን ለእኛ ምን ያህል እንደምታስቡ በእግዚአብሔር ፊት እንዲታወቅ ነው።
13 በዚህ እንበረታታለን። እኛ ከመፅናናታችን በተጨማሪ በቲቶ ደስታ ሃሴት አድርገናል፤ መንፈሱ በሁላችሁ ምክንያት አርፏልና ነው። **14** ስለናንተ በመመካት
ለእርሱ ተናግሬ ነበር፣እናንተም አላሳፈራችሁኝም። በሌላ አንፃር ስለናንተ የተናገርነው ሁሉ እውነት ነበር፥ለቲቶም ስለናንተ የተናገርነው ሁሉ ትክክል መሆኑ
ተረጋግጧል። **15** እርሱም በፍርሃት እና በመንቀጥቀጥ ያደረጋችሁለትን አቀባበል እንዲሁም የሁላችሁንም መታዘዝ በሚያስብበት ጊዜ ለእናንተ ያለው ፍቅር
ታላቅ ነው። **16** በናንተ ሙሉ መታመን ስላለኝ፥ሃሴት አደርጋለሁ።

---

2 Corinthians 7:1

2ኛ ቆሮንቶስ 7:1
የተወደዳችሁ ሆይ፡ ጳውሎስ የሚያመለክተው የቆሮንቶስ ሰዎችን ነው። ራሳችንን እናንፃ፡ እዚህ ጋር ጳውሎስ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ከሚጎዳ ከየትኛውም አይነት ሃጢያት እንድንርቅ ይናገራል። በእግዚአብሔር ፍርሃት፡ በእግዚአብሔር ፊት ትሁታን መሆን።

2 Corinthians 7:2

2ኛ ቆሮንቶስ 7:2-4
በልባችሁ ስፍራ ስጡን፡ "በኑሮአችሁ ለእኛ ስፍራ ይኑራችሁ"

ይህንን የምላችሁ ልኮንናችሁ ብዬ አይደለም፡ ትኩረት፡ "አላሳጣችሁም" ምክንያቱም አብረን ለመሞትም ሆነ ለመኖር በልባችን ውስጥ አላችሁና፡ ትኩረት፡"ከናንተጋር ለመኖርም ሆነ ለመሞት የሚያስችል ፍቅር አለን" በመከራዎቻችን እንኳ፡ ትኩረት፡ "ከገጠመን ተግዳሮቶች በላይ"

2 Corinthians 7:5

2ኛ ቆሮንቶስ 7:5-7
ሰውነታችን እረፍት አልነበረውም፡ ትኩረት፡"በጣም ደክሞን ነበር" ወይም "ዝለን ነበር" በቲቶ መምጣት አፅናናን፡ ትኩረት፡"ከእናንተ ከቆሮንቶሶች ይዞ የመጣው የሚያበረታታ ዜና" ለእኔም ያላችሁን ታላቅ ፍቅር፣ርህራሄ እና ጥልቅ ሃሳብ ሲነግረን፡ ትኩረት፡"በእኔ በሆነብኝ ምክንያት ለእኔ ያላችሁን ፍቅር፣ርህራሄ እና ለደህንነቴ ያላችሁን ጥልቅ ሃላፊነት ነገረን።" በይበልጥ ተደሰትሁ፡ ትኩረት፡"በደስታ ተሞላሁ"

2 Corinthians 7:8

2ኛ ቆሮንቶስ 7:8-10
ምንም እንኳ በመልዕክቴ፡ ትኩረት፡"ከመልዕክቴ እንደተረዳሁት" ነገር ግን፥* ለጥቂት ጊዜም እንዳሳዘናችሁ፡

"ነገር ግን ያዘናችሁት ለጥቂት ጊዜ ነው" እግዚአብሔር የሚወደው አይነት ሃዘን እየተለማመዳችሁ፡ ትኩረት፡ ወደ ንስሃ የሚመራ እግዚአብሔር የሚወደው ሃዘን እግዚአብሔር የሚወደው ሃዘን ፀፀት የሌለበት፥ ወደ ድነት የሚመራ ንስሃን ያመጣል፡ "ከሃጢያት እንድንርቅ የሚያደርግ እግዚአብሔር የሚወደው ሃዘን" ዓለማዊ ሃዘን ግን ሞትን ያመጣል፡ ትኩረት፡"ዓለማዊ ሃዘን ግን ወደ መንፈሳዊ ሞት የሚመራ በመሆኑ ንስሃ የለውም።

2 Corinthians 7:11

2ኛ ቆሮንቶስ 7:11-12
ምን አይነት ታላቅ ቁርጠኝነት፡ "ታላቅ ቁርጠኝነትን መረዳት" እንዳመጣላችሁ እዩ። ይህም ታላቅ ቁርጠኝነት ምን ያህል ንፁህ መሆናችሁን፡ ትኩረት፡"ንፁህ መሆናችሁን ለማረጋግጥ፥ውስጣችሁ የማጣ ነገር አለ" ምን ያህል በሃጢያት ላይ እንድትቆጡ እንዳደረጋችሁ፡ "ቁጣችሁ በሃጢያት ላይ ታላቅ ነበር" እንድትቆጡ፡ "የእናንት ቁጣ" ናፍቆት፡ ትኩረት፡ ልታዩኝ በእጅግ ትፈልጉ ነበር" ቅንዓት፡ ትኩረት፡"ትክክለኛ የሆነውን ለማድረግ እጅግ ትጓጉ ነበር" ለእኛ ምን ያህል እንደምታስቡ በእግዚአብሔር ፊት እንዲታወቅ ነው፡ ትኩረት፡"እግዚአብሔርም ሆነ እኛ እንድምንገነዘበው ለእኛ ያላችሁ ስሜት መልካም ነበር"

2 Corinthians 7:13

2ኛ ቆሮንቶስ 7:13-14
በዚህ እንበረታታለን፡ ትኩረት፡ "እውነተኛ በሆነው ለእኛ ባላችሁ ታማኝነት እንበረታታለን" ስለናንተ በመመካት ለእርሱ ተናግሬ ነበር፡ "በእናንተ መመካቴን ለእርሱ አሳይቼዋለሁ" አላሳፈራችሁኝም፡ ትኩረት፡"አላሳዘናችሁኝም" ትክክል መሆኑ ተረጋግጧል፡ "እውነት መሆኑ ታይቷል"

2 Corinthians 7:15

2ኛ ቆሮንቶስ 7:15-16
ለእናንተ ያለው ፍቅር ታላቅ ነው፡ ትኩረት፡"ባሁኑ ጊዜ ቲቶ ከፊት ይልቅ ያስብላችኋል" በፍርሃት እና በመንቀጥቀጥ ያደረጋችሁለትን አቀባበል፡ ትኩረት፡"በፍርሃት እና በመንቀጥቀጥ አቀባበል አደረጋችሁለት እናም ታዘዛችሁት" ወይም "በታላቅ ክብር ተቀብላችሁ ታዘዛችሁት"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 8

1 ወንድሞችና እህቶች ሆይ ለመቄዶንያ ለአብያተ ክርስቲያናት ስለ ተሰጠው የእግዚአብሔር ጸጋ እንድታውቁ እንፈልጋለን 2 እጅግ የሚፈትናቸው መከራ
በደረሰባቸው ጊዜ የደስታቸው መብዛትና የደህንነታቸው አስከፊነት የልግስናቸውን መትረፍረፍ አብዝቷል። 3 የሚቻላቸውን ያህል ከሚቻላቸውም እንደ ሰጡ እኔ
እመሰክርላቸዋለው። በፈቃዳቸውም ለቅዱሳን በሚሰጠው በዚህ አገልግሎት የመሳተፍ ዕድል ይኖራቸው ዘንድ 4 እኛን በብዙ ልመና ለመኑን። 5 ይህም የሆነው
እኛ እንደጠበቅነው አይደለም ነገር ግን በመጀመሪያ ራሳቸውን በጌታ ከዚያም በእግዘአብሔር ፈቃድ ለእኛ ሰጡ። 6 ስለዚህ አስቀድሞ ከእናንተ ጋር የጀመረውን
ተግባር በእናንተ ዘንድ ያለውን ይህን የልግስና ስራ ከፍጻሜ እንዲደርስ ቲቶን ግድ ብለነው ነበር። 7 ነገር ግን እናንተ በሁሉም ነገር በእምነት፥ በንግግር
፣በዕውቀት በትጋት ሁሉ እንዲሁም ለእኛ ባላችሁ ፍቅር እንደሚልቁ በዚህ በበጎ ስራ ደግሞ የምትልቁ ሁኑ። 8 ከሌሎች ሰዎች ትጋት ጋር በማወዳደር
የፍቅራችሁን ቅንነት ለማረጋገጥ እንጂ ይህንን እንደ ትዕዛዝ አልልም እናንተ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ጸጋ ታውቃላችሁና። 9 በእርሱ ድኽነት እናንተ
ባለጠጎች ትሆኑ ዘንድ ፥ እርሱ ባለ ጠጋ ቢሆንም እንኳ ስለ እናንተ ደኸየ። 10 በዚህ ጉዳይ እናንተን ስለሚጠቅማችሁ ነገር ምክር እለግሳችኋለው። ከአንድ
ዓመት በፊት አንድን ነገር ለማድረግ መጀመር ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ልታደርጉት መሻት በውስጣችሁ ነበር። 11 አሁን ያንኑ ማድረጋችሁን ፈጽሙ። እንግዲህ
ልክ በዚያን ጊዜ ልታደርጉት ጉጉትና ጠንካራ ፍላጎት እንደ ነበራችሁ፣ወደ ፍጻሜ ልታመጡት ደግሞ ትችላላችሁ። 12 ይህን ስራ ለመስራት ጉጉት ካለ፣ አንድ
ሰው በሌለው ሳይሆን ባለው ነገር ላይ ተመስርቶ ሲሰራ መልካምና ተቀባይነት ያለው ነው። 13 ይህ ተግባር ሚዛናዊነት እንዲኖር ነው እንጂ ሌሎች
እንዲቀልላቸው እናንተም ሸክም እንዲበዛላችሁ አይደለም። 14 አሁን ያለው የእናንተ መትረፍ ለእነርሱ የሚያስፈልጋቸውን ይሞላል። ይህም ደግሞ ሚዛናዊነት
ይኖር ዘንድ የእነርሱ መትረፍረፍ የእናንተ ፍላጎት ደግሞ እንዲሞላ ነው። 15 እንዲህ ተብሎ እንደተጻፈ ፦ «ብዙ ያለው ምንም አልተረፈውም ፣ጥቂት ያለው ግን
ምንም አልጎደለውም።» 16 ነገር ግን እኔ ለእናንተ ያለኝን ቅን ሃሳብ በቲቶ ልብ ያኖረው እግዚአብሔር ይመስገን። 17 እርሱ ልመናችንን መቀበል ብቻ ሳይሆን ፣
ትጋትን በማሳየት በራሱ ፈቃድ ወደ እናንተ መጥቷልና። 18 ከእርሱ ጋርም ወንጌልን በማወጅ ስራው በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የተመሰገነውን ወንድም
ልከናል። 19 ይህ ብቻ አይደለም ነገር ግን ለራሱ ለጌታ ክብርና እኛ ለመረዳት ያለንን ጉጉት ለመግለጥ ይህን የጸጋ ስራ እንዲያከናውን አብሮን ይጓዝ ዘንድ
አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ መርጠውት ነበር። 20 ስለምንሰበስበው ስለዚህ የልግስና ስጦታ ማንም ትችት ለማቅረብ ምክንያት እንዳያገኝ እንጠነቀቃለን። 21
በጌታ ፊት ብቻ ሳይሆን ነገር ግን በሰዎች ፊት ደግሞ የከበረውን ነገር ለማድረግ እንተጋለን። 22 ብዙ ጊዜ ፈትነን በበርካታ ተግባራት ተነሳሽነት ያለው ሆኖ
ያገኘውን ፣አሁን ግን በእናንተ ላይ ትልቅ መታመን ምክንያት የበለጠ ትጋት የሚያሳየው ሌላ ወንድም ከእነርሱ ጋር እንልካለን። 23 ቲቶን በሚመለከት ግን ስለ
እናንተ ከእኔ ጋር የሚሰራ አጋሬ ነው። ወንድሞቻችንን በሚመለከት አብያተ ክርስቲያናት የላኳቸው የክርስቶስ ክብር ናቸው። 24 ስለዚህ ፍቅራችንን ፣ በሌሎች
አብያተ ክርስቲያናት ዘንድም ስለ እናንተ ለምን እንደ ተመካን ግለጡላቸው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **9**

1 ለቅዱሳን ስለ ሚሆነው አግልግሎት ለእናንተ ልጽፍላችሁ አያስፈልገኝም ። **2** ለመቄዶንያ ሰዎች ስለተመካሁት በውስጣችሁ ስላለው መሻት አውቃለው። በአካዶያ የሚነግሩት ካለፈው ዓመት ጀምሮ መዘጋጀትቱን ነገርኋቸው። የእናንተ ቅንዓት ብዙዎቻቸውን ለስራ አነሳስቷል። **3** እንግዲህ የተዘጋጃችሁ ትሆናላችሁ እንዳልኩት የተዘጋጃችሁ ትሆኑ ዘንድ፣ ስለ እናንተ መመካታችን ከንቱ እንዳይሆን ወድሞችን ልኬአለው። **4** ምናልባት አንዳቸው ከ እኔ ጋር ከሜቄዶንያ በመጡ፣ሳትዘጋጁ ቢያገኟችሁ ሁላችንም ሀፍረት ይሰማናል ነገር ግን በእናንተ ስለምተማመን ፣ ስለ እናንተ የምለው ምንም የለኝም። **5** ስለዚህ ወደ እናንተ እንዲመጡና እናንተ ተስፋ ለሰጣችሁት ስጦታ በቅድሚያ ዝግጅት እንዲያደርጉ ወንድሞችን መለመን አስፈላጊ እንደሆነ አሰብሁ። ይህም እንድትሰጡ ስለ ተገደዳችሁ ሳይሆን በነጻ እንደተሰጠ ስጦታ ዝግጁ ይሆን ዘንድ ነው። **6** ፍሬ ነገሩ ይህ ነው ፦ በጥቂት የሚዘራ በጥቂቱ ያጭዳል ፣ አትረፍርፎ የሚዘራ አትረፍርፎ ያጭዳል። **7** እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ ስትሰጡ በሐዘን ወይም በግድ አይደለም። **8** እግኢአብሔር ሁልጎዜ በነገር ሁሉ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ አግኝቷችሁ በብጎ ስራ ሁሉ ትበዙ ዘንድ ጸጋን ሁሉ ሊያበዛላችሁ ይችላል። **9** እንዲህ ተብሎ እንደተፃፈ «ሀብቱን በተነ ፣ለድሆችም አከፋፈለ።» **10** ለዘሪን ዘርን ለምግብ እንጀራን የሚሰጥ ፣የሚዘራ ዘርን ደግሞ ይሰጣል ያበዛውማል፣ ምርት ይጨምራል። **11** ለጋሶች እንድትሆኑ በሁሉም ረገድ መበልጸግ ትላላችሁ፣ ይህም በእኛ በኩል ለእግኢአብሔር ምስጋና ምክንያት ይሆናል። **12** ይህ የመስጠት አገልግሎት ለቅዱሳን ይሚያስፈልጋቸውን ሁሉ የሚሰጥ ብቻ አይደለምና፣ ነገር ግን ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ብዙ ምስጋና ደግሞ ይበዛል። **13** በዚህ አገልግሎት ተፈትናችሁ አልፋችኋል ደግሞም በክርስቶስ ወንጌል ምስክርነት በመታዘዛችሁ ፣እንዲሁም ለእነርሱና ለሁሉ ባደረጋችሁት የስጦታችሁ ልግስና እግዚአብሔርን ታከብራላችሁ። **14** በእናንተ ላይ ካለው እጅግ ታላቅ የእግዚአብሔር ጸጋ የተነሳ ስለ እናንተ ሲጸልዩ ይናፍቁአችኋል። **15** ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን!

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **10**

1 እኔ ራሴ ጳውሎስ ፣ በፊታችሁ ትሁት የሆንሁ በክርስቶስ ገርነትና የዋህነት እለምናችኃለሁ። **2** እንደ ስጋ ፈቃድ እንደምንኖር የሚያስቡትን በምቃወምበት ጊዜ ፣ ከእናንተ ጋር ሳለሁ መሆን እንደሚገባኝ በራስ በመተማመን የምደፍር መሆን የለብኝም ብዬ እለምናችኃለው ። **3** ምንም እንኳ በስጋ የምንመላለስ ብንሆን፣ እንደ ስጋ አንዋጋም። **4** የምንዋጋባቸው የጦር መሳሪያዎች ሥጋዊ አይደሉምና ይልቁንም ምሽጎችን ለመስበር መለኮታዊ ኃይል አለቸው ፥ አሳሳች የሆኑ ክርክሮችንም ያፈርሳሉ። **5** ደግሞም በእግዚአብሔር ዕውቀት ላይ የሚነሳውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን ፥ እንዲሁም ለክርስቶስ ለመታዘዝ ሀሳብን ሁሉ እንማርካለን። **6** መታዘዛችሁም በተፈጸመ ጊዜ ፣ ይለመታዘዝን ተግባር ሁሉ ለመቅጣት እንዘጋጃለን። **7** በግልጽ ከፊታችን ያለውን ተመልከቱ ፥ ማንም የክርስቶስ እንደሆነ ቢያምን ልክ እርሱ የክርስቶስ እንደሆነ እኛ ደግሞ እንዲሁ መሆናችንን ራሱ ያሰበው። **8** ሊያንጻችሁ እንጂ ሊያጠፋችሁ የይደለ ጌት ኣስለ ሰለ ሰጠው ስልጣናችን ጥቂት አብዝቼ ብመካም እንኳ፥ አላፍርም። **9** በመልዕክቶቼም ላስደነግጣችሁ አልፈልግም። **10** አንዳንድ ሰዎች ፥«መልእቶቹ ጠንከር ያሉና ኃይለኛ ናቸው፥ ነገር ግን በአካል ደካማ ነው፥ ንግግሩም ሊሰማ የሚገባ አይደለም»ይሉናል። **11** እንደነዚህ ያሉ ሰዎችን ስንርቅ በመልዕክት የምንለው፥እዚያ ስንሆን ከምናደርገው ጋር አንድ መሆኑን ይረዱ። **12** ራሳቸውን ከሚያመሰግኑ ጋር ራሳችንን እስከ ማስተያየት ወይም እስከ ማወዳደር ድረስ አንሔድም። ነገር ግን እነርሱ ራሳቸውን ከሌላ ጋር ሲመዝኑና ራሳቸውን እርስ በእርስ ሲያወዳድሩ ፥ ማስተዋል ተላቸውም። **13** ይሁን እንጂ እኛ ከልክ በላይ አንመካም፥ ነገር ግን ወደ እናንተ እንኳ እስክንደርስ እግዚአብሔር በወሰነልን ስራ እንሆናለን። **14** ወድ እናንተ ስንደርስ ከመጠን አላለፍንምንና በክርስቶስ ወንጌል ወደእናንተ ለመድረስ የመጀመሪያዎች ነበርን። **15** በሌሎች ድካም ከልክ ያለፈ አንመካም ፥ ነገር ግን ከእናንተ አካባቢ አልፎ እንኳ **16** ወንጌልን እንሰብክ ዘንድ እምነታችሁ ሲያድግ ስራችን እጅግ እንደሚስፋፋ ተስፋ እናደርጋለን ። በሌላ ስፍራ እየተሰራ ስላለው ሥራ አንመካም። **17** «ነገር ግን የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ።» **18** ጌታ የሚያመሰግነው እንጂ፣ ራሱን የሚያመሰግን ተፈትኖ የሚወጣ አይደለምና።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **11**

1 በጥቂት ሞኝነቴ ልትታገሱኝ ብትችሉ እመኝ ነበር፣ እናንተ ግን በእርግጥ ታግሳችሁኛል! **2** እኔ ስለ እናንተ እቀናለሁና እንደ አንዲት ንጽሕት ድንግል ለክርስቶስ ላቀችርባችሁ ለአንድ ባል ስላጨዋችሁ በእግዚአብሔር ቅንአት እቀናላችኃለው ። **3** ነገር ግን እባብ በተንኮሉ ሔዋንን እንዳታለላት ፣ ሐሳባችሁ ለክርስቶስ ካልችሁ ቅንና ንጹህ ታማኝነት መረን እንዳትወጡ ብዬ እፈራለው። **4** አንድሰው መጥቶ እኛ ከሰበክበው የተለየ ሌላ ኢየሱስ ቢያውጅላችሁ፣ ወይም ቀድሞ ከተቀበላችሁት የተለየ መንፈስ ብትቀበሉ ወይም እናንተ ከተቀበላችሁት የተለየ ወንጌል ቢደርሳችሁ ደህና ትታገሱታላችሁና። **5** ከነዚያ «ገናና ሐዋርያት» በጥቂቱ እንኳ የማንስ አይደለሁም ብዬ አስባለውና። **6** ነገር ግን በአነጋገር ያልሰለጠንሁ አይደለሁም። በሁሉም መንገድና በሁሉም ነገር ይህን አሳውቀናችኋል። **7** የእግዚአብሔርን ወንጌል በነፃ ስለሰበኩላችሁ፥ እናንተ ከፍ እንድትሉ እኔ ራሴን በማዋረዴ ኃጢያት ሰራሁን? **8** እናንተን ማገልገል እችል ዘንድ ከእነርሱ እርዳታ በመቀበል ሌሎችን አብያተ ክርስቲያናት«ጎዳሁ»። **9** አብሬአችሁ በሆንኩና በተቸገርሁ ጊዜም በማንም ላይ ሸክም አልሆንሁም። ከመቄዶንያ የመጡት ወንድሞች የሚያስፈልገኝን ሰጥተዋልና። በሁሉም ረገድ ለእናንተ ሸክም ከመሆን ተጠንቅቄአለሁ፣ይህን ማድረጌንም እቀጥላለው ። **10** የክርስቶስ እውነት በእኔ ውስጥ ያለ እንደ መሆኑ፣ ይህ የእኔ ትምህርት? **11** ለምንስ እንዲህ ይሆናል? ለማልወደችሁ ነውን? እንደምወዳችሁ እግዚአብሔር ያውቃል። እንደነዚህ ያሉ ሰዎችን ራሳቸውን እንደ ክርስቶስ ሐዋርያት በማስመሰል ሐሰተኞች ሐዋርያት፣ አታላይ ሰራተኞች ናቸውና ። **12** እኔን የሚነቅፉትንና እኛ የምናደርገውን እነርሱም እያደረጉ እንደ ሆነ እየተናገሩ የሚመኩበትን ምክንያት ለማሳጣት አሁን የሚደረገውን ወደ ፊትም አደርጋለሁ። **13** እንደ እነዚህ ያሉ ሰዎች ሐሰተኛ ሐዋርያትና አታላይ ሸራተኞች ናቸው። **14** ይህም የሚያስደንቅ አይደለም፣ ሰይጣን እንኳ ራሱን የብርሓን መልአክ በማስመሰሉ ርሱን ይለውጣልና። **15** የእርሱ አግልጋዮች ደግሞ የጽድቅ አገልጋዮች በማስመሰል ራሳቸውን ቢለውጡ እጅግ የሚያስደንቅ አይደለም። ዕጣ ፈንታቸውም እንደ ሥራቸው ይሆናል። **16** ደግሜ እላለሁ፦ እኔ ሞኝ እንደሆንሁ ማንም አያስብ ። ሞኝ እንደሆንሁ ብታስቡ ግን በጥቂቱ እመካ ዘንድ እንደ ሞኝ ተቀበሉኝ። **17** እንደዚህ ታምኜ በመመካት የምናገረው፣ ጌታ የፈቀደው አይደለም፣ እኔ ግን እንደ ሞኝ እናገራለው። **18** ብዙ ሰዎች በሥጋ ሰለሚመኩ፣ እኔም ደግሞ እመካለው። **19** እናንተ ብልሆች ሆናችሁ ሞኞችን በደስታ ትታገሣላችሁና! **20** ማንም ባሪያዎች ቢያደርጋችሁ፣ ማንም በመካከላችሁ መለያየትን ቢፈጥር፣ ማንም መጠቀሚያ ቢያደርጋችሁ፣ ማንም ቢቀማችሁ ፣ወይም ፊታችሁን በጥፊ ቢመታችሁ ትታገሱታላችሁና. **21** ይህንን ስናደርግ በጣም ደካሞች እንደ ነበርን እያፈርሁ እናገራለ። ሆኖም ማንም በሚመካበት ጊዜ ሁሉ እንደ ሞኝ እላለው፣ እኔ ደግሞ እመካለሁ። **22** እነርሱ ዕብራውያን ናቸውን? እኔ ደግሞ ነኝ እስራኤላውያን ናቸውን እኔ ደግሞ ነኝ። የአብርሃም ዘር ናቸውን? እኔ ደግሞ ነኝ። **23** የክርስቶስ አግልጋዮች ናቸውን? እኔ ደግሞ ነኝ (እንደ እብድ እናገራለው) እኔ እበልጣለሁ፣ በከባድ ሥራ አብዝቼ በመታሰር አብዝቼ፣ በመደብደብ ከልክ በላይ፣ ብዙ የሞት አደጋዎችን በመጋፈጥ ብዙ ጊዜ ሆንሁ። **24** አይሁድ «አንድ ሲጎድል አርባ ጅራፍ»አምስት ግዜ ገረፉኝ። **25** ሦስት ጊዜ በበትር ተመታሁ። አንድ ግዜ በድንጋይ ተወገርሁ። ሦስት ጊዜ የተሳፈርኩበት መርከብ ተሰበረ። አንድ ሌሊትና አንድ ቀን በባህር ላይ አሳለፍሁሁሁ፣ **26** በተደጋጋሚ በመንገድ ተጓዝሁ። በወንዞች አደጋ፣ በወንበዴዎች አደጋ በወገኖቼ በኩል አደጋ፣ በአሕዛብ በኩል አደጋ፣ በከተማ አደጋ በምድረ በዳ አደጋ፣ በባሕር አደጋ፣ በሐሰተኞች በኩል አደጋ ነበረብኝ። **27** በከባድ ስራና በችግር፣ እንቅልፍ ባጣሁባቸው ብዙ ሌሊቶች፣ በረሃብና በጥም ፣ እንዲሁም የሚበላ በማጣት፣በብርድባ በራቁትነት ነበርሁ። **28** ከሌላውም ሁሉ በተለይ ዕለት ዕለት የሚከብድብኝ ለአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ያለኝ ጭንቀት ነው። **29** ደካማ ምን ነው እኔስ አልደክምምን? ኃጢአት እንዲሠራ ሌላውን ያሰናከለ ማን ነው፣ እኔስ በውስጤ አልናደድምን?። **30** መመካት ካለብኝ፣ ድካሜን ስለሚያሳየው ነገር እመካለው። **31** እንደማልዋሽ፣ ለዘላለም የተመሰገነው የጌታ ኢየሱስ አምላክና አባት ያውቃል። **32** በደማስቆ ከንጉስ አርስጦስዮስ በታች የሆነ ገዢ እኔን ይዞ ለማሰር ከተማዋን እየጠበቀ ነበር፣ **33** ነገር ግን በቅጥሩ ባለ መስኮት በቅርጫት አወረዱኝ፣ ከእጆቹም አመለጥሁ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **12**

1 መመካት አለብኝ፤ ነገር ግን በመመካት ጥቅም አይገኝም። ከጌታ ወዳሉት ራዕዮችና መገለጦች ግን እሄዳለው። **2** በሥጋ ይሁን ወይም ከሥጋ ውጭ አላውቅም፤ እግዚአብሔር ግን ያውቃል። ከዐሥራ አራት ዓመታት በፊት በክርስቶስ የሆነ አንድ ሰው ወደ ሦስተኛ ሰማይ ተነጠቀ። እንደዚህ ያለውን ሰው ዐውቃለው። **3** በሥጋ ይሁን ወይም ከሥጋ ውጭ እኔ አላውቅም፣ እግዚአብሔ ግን ያውቃል፣ **4** ይህ ሰው ወደ ገነት ተነጠቀ፤ ማንኛውም ሰው የማይናገራቸው እጅግ የተቀደሰ ነገሮችን ሰማ። **5** እንደዚህ ስላለው ሰው እመካለው ስለራሴ ግን ከድካሜ በቀር አልመካም። **6** ልመካ ከፈለግሁ፣ ሞኝ አይደለሁም፣ እውነትን እናገራለሁና፤ ነገር ግን ማንም በእኔ ከታየው ወይም ከእኔ ከተሰማው ፣ **7** ወይም በመገልጦቹ ልዩ ባሕርይ ምክንያት የምበልጥ አድርጎ እንዳያስብ አልመካም።ስለዚህ እንዳልታበይ፣ እጅግ እንዳልኩራራ የሥጋ መውጊያ፣የሚነዘንዘኝ የሰይጣን መልዕክተኛ ተሰጠኝ። **8** መውጊያውን ከእኔ እንዲያነሣው ሦስት ጊዜ ጌታን ለመንሁ። **9** እርሱም፣ «ጸጋዬ ይበቃሃል ኃይል በድካም ይፈጸማልና» አለኝ። ስለሆነም የክርስቶስ ኃይል ያርፍብኝ ዘንድ አብዝቼ ስለ ድካሜ እመካለው። **10** ስለዚህ ስለ ክርስቶስ በድካም፣ በስድብ፣ በችግር፣ በስደት ፣ በጭንቀትም እርካታ ይሰማኛል በምደክምበት ጊዜ ሁሉ ብርቱ ነኝና። **11** ሞኝ ሆኜአለሁ! እንዲህ እንድሆን ያስገደዳችሁኝ እናንተ ናችሁ፣እናንተ እኔን ልታመሰግኑኝ ይገባችሁ ነበር፣ምክንያቱም እኔ ምንም ባልሆን እንኳ ከ«ገናና ሐዋርያት» የማንስ አልነበርሁም። **12** የአንድ ሐዋርያ እውነተኛ ምልክቶች በሁሉ ትዕግሥት፦ በምልክቶችና በድንቆች በብርቱ ተግባራትም በእናንተ መካከል ተደረጉ። **13** እኔ ሸክም ካልሆንሁባችሁ በቀር ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የምታንሱት እንዴት ነበር? ይህን ስሕትቴን ይቅር በሉኝ! **14** አስተውሉ! ለሦስተኛ ጊዜ ወደ እናንተ ለመምጣት ተዘጋጅቻለው፤ ሸክም አልሆንባችሁም፤ እናንተን እንጂ፣ የእናንተ የሆነውን አልፈልግም። ወላጆች ለልጆች እንጂ ልጆች ለወላጆች ገንዘብ አያስቀምጡምና። **15** እኔ እጅግ በጣምታልቅ በሆነ ደስታ ስለ ነፍሳችሁ እከፍላለው። እናንተን የበለጠ ብወዳችሁ፣ እኔ ከዚህ ያነሰ መወደድ አለብኝን? **16** ልክ እንደዚህ፣ እኔ አልከበድሁባችሁም፤ነገር ግን በጣም በተንኮልና በጥበብ ያታለልኃችሁ መሰላችሁ። **17** ወደ እናንተ በላክሁት በማንም ተጠቀምሁባችሁን? **18** ወደ እናንተ እንዲመጣ ቲቶን የግድ አልኩት ፤ ከእርሱ ጋርም ሌላውን ወንድም ላክሁት። ቲቶስ ተጠቀመባችሁን? በአንድ መንገድ አልተጓዝንምን? በአንድ ፈለግስ አልተራመድንምን? **19** በዚህ ጊዜ ሁሉ ለእናንተ ራሳችንን የምንከላከል ይመስላችኃልን? በእግዚአብሔር ፊት ስለእናንተ ድፍረት በክርስቶስ ብዙ ነገር እየተናገርን ነበር። **20** ስመጣ እንደምፈልገው ሆናችሁ አላገኛችሁምብዬ እፈራለው። እናንተም እንደምትፈልጉት ሆኜ አታግኙኝም ብዬ እፈራለው ምናልባት ክርክር፣ ቅንዓት፣ የቁጣ መግንፈል፣ራስ ወዳድነት ያለበት ምጅት፣ ሐሜት፣ ኩራትና ሁከት ይሆናሉ። **21** ተመልሼ ስመጣ፣ አምላኬ በፊታችሁ ዝቅ እንዳያደርገኝ ብዬ እፈራለው ፣ከዚህ በፊትም ኃጢያ ስለሠሩት፣ እንዲሁም ስለ ፈጸሙት ርኩሰትና ዝሙት መዳራትም ስለ ብዙዎቻቸው አዝናለው ብዬ እፈራለው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **13**

1 ወደ እናንተ ስመጣ ይህ ሦስተኛዬ ነው። «ክስ ሁሉ በሁለት ወይም በሦስት ምስክሮች መጽናት አለበት።» **2** ሁለተኛ ስመጣ በፊት ኃጢያት ለሰሩትና ለሌሎች ሁሉ ተናግሬአለው፥ አሁንም ደግሞ እላለው ተመልሼ ስመጣ እንዲሁ አላልፋቸውም። **3** ክርስቶስ በእኔ በኩል እየተናገረ ስለ መሆኑ ማስረጃ ስለምትሹ ይህን እነግራችሏለው። ክርስቶስ ስለ እናንተ አይደክምም፥ ይልቁንም እርሱ በእናንተ ኃይለኛ ነው። **4** እርሱ በድካም ተሰቅሏልና፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ኃይል ሕያው ነው። እኛ ደግሞ በእርሱ ደካሞች ነንና፤ ነገር ግን በመካከላችሁ ብለው የእግዚአብሔር ኀይል ሕያዋን ነን። **5** በእምነት መሆናችሁን ለማየት ራሳችሁን መርምሩ። ራሳችሁን ፈትኑ። ኢየሱስ ክርስቶስ በእናንተ እንደሚኖር አትገነዘቡምን? ተፈትናችሁ ካላለፋችሁ በቀር፣ እርሱ በእናንተ ይኖራል። **6** እኛ ግን ተፈትነን ያለፍን መሆናችንን እንደምታውቁ እተማመናለው። **7** እንግዲህ እናንተ ክፉ እንዳታደርጉ ወደ እግዚአብሔር እንጸልያለን፥ ይህንም የምናደርገው ፈተናውን ያለፍን መሰለን ለመታየት አይደለም፥ ነገር ግን ፈተናውን ያላለፍን ብንመስልም እንኳ፣ እናንተ ትክክል የሆነውን ታደርጉ ዘንድ እጸልያለው። **8** ስለ እውነት እንጂ የእውነት ተቃራኒ የሆነ ነገር መሥራት አንችልምና። **9** እኛ ደካሞች ሆነን እናንተ ብርቱዎች ስትሆኑ ደስ ይለናልና። እናንተ ፍጹማን እንድትሆኑ እንኛ ደግሞ እንጸልያለን። **10** ከእናንተ ርቄ እያለው እነዚህን ነገሮች ጻፍሁላችሁ፤ ከእናንተ ጋር ሳለው እናንተ ለማነጽ እንጂ ለማፍረስ ያይደለ ጌታ የሰጠኝ ሥልጣንን በመጠቀም እንዳላመናጭቃችሁ ንችው። **11** በመጨረሻ፣ ወንድሞችና እኅቶች፣ ደስ ይበላችሁ! ለተሐድሶ ሥሩ፤ተበረታቱ፤እርስ በርሳችሁ ተስማሙ፤በሰላም ኑሩ፤ የፍቅርና የሰላም አምልክም ከእናንተ ጋር ይሆናል። **12** በተቀደሰ አሳሳም ሰላም ተባባሉ። **13** ቅዱሳን ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። **14** የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣ፍቅር፣የመንፈስ ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Galatians

Galatians

ምዕራፍ 1

1 በሰው በኩል ወይም ከሰው ሳይሆን በክርስቶስ ኢየሱስ ደግሞም እርሱን ከሞት ባስነሳው በእግዚአብሔር አብ ሐዋርያ የሆንኩት ጳውሎስ **2** አብረውኝ ካሉ
ወንድሞች ጋር በገላትያ ለምትገኙ አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ **3** ከአባታችን ከእግዚአብሔር አብ ከጌታም ከኢየሱስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ **4** ይሁን፣እርሱ እንደ
አምላካችን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ከአሁኑ ክፉ ዘመን ያድነን ዘንድ እራሱን ስለ ኃጢአታችን ሰጥቶአልና **5** ለእርሱ ከዘላለም እስከዘላለም ክብር ይሁን።
አሜን! **6** ወደሌላ ወንጌል በዚህ ፍጥነት በመዞራችሁ እጅግ ተገርሜአለሁ። በክርስቶስ ጸጋ ከተጠራችሁ ከእርሱ ፊታችሁን ማዞራችሁ አስገርሞኛል። **7** ሌላ
ወንጌል የለም፣ ነገር ግን የሚያውኩዋችሁና የክርስቶስን ወንጌል ሊያጣምሙ የሚፈልጉ አንዳንድ ሰዎች አሉ። **8** ነገር ግን እኛም ሆንን የሰማይ መልአክ
አስቀድመን ከሰበክንላችሁ ሌላ ወንጌል ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን። **9** አስቀድመን እንዳልን እንደገና እላለሁ «ማንም ከተቀበላችሁት ወንጌል የተለየ
ወንጌል ቢሰብክላችሁ የተረገም ይሁን» **10** ለመሆኑ እኔ የምጥረው ከሰው ወይስ ከእግዚአብሔር ይሁንታን ለማግኘት ነው? ጥረቴ ሰውን ለማስደሰት ነው?
እስከአሁን ድረስ ሰውን ለማስደሰት እየጣርኩ ከሆነ እውነት እኔ የክርስቶስ አገልጋይ አይደለሁም። **11** ወንድሞች ሆይ የሰብኩላችሁ ወንጌል ከሰው እንዳልሆነ
እንድታውቁ እፈልጋለሁ። **12** ከጌታ ከኢየሱስ ከተሰጠኝ መገለጥ እንጂ ከሰው አልተቀበልኩትም ከሰውም አልተማርኩትም። **13** የይሁዲ እምነት ተከታይ
በነበርኩበት በቀድሞው ህይወቴ ወቅት እንዴት ቤተክርስቲያንን በአመፅ አሳድድና አጠፋ እንደነበረ ስለእኔ ሰምታችኋል። **14** በይሁዲነት ከአብዛኛዎቹ
አብረውኝ ከነበሩ አይሁዶች እየላቅሁ ነበር። ለአባቶቼም ወግ ከመጠን ያለፈ ቀናኢ ነበርኩ። **15** ነገር ግን እግዚአብሔር ገና በማህጸን ሳለሁ ሊመርጥኝ ወደደ፣
16 በአረማውያን መካከል አውጀው ዘንድ ልጁን በእኔ ለመግለፅ በጸጋው ጠራኝ። በጠራኝ ጊዜ ወዲያውኑ ከስጋና ከደም ጋር አልተማከርኩም **17** ፣ከእኔ
አስቀድመው ሃዋሪያት የሆኑት ወደሚገኙበት ወደ ኢየሩሳሌምም አልሄድኩም። ነገር ግን ወደ አረቢያ በኋላም ደግሞ ወደ መቄዶኒያ ተመለስኩ። **18** ከዚያም
ከሶስት አመት በኋላ ኬፋን ለመጠየቅ ወደኢየሩሳሌም ሄጄ ከእርሱ ጋር አስራአምስት ቀናት ቆየሁ። **19** ነገር ግን ከጌታ ወንድም ከያዕቆብ በስተቀር ሌሎች
ሃዋሪያትን አላገኘሁም። **20** በምፅፍላችሁ በእነዚህ ነገሮች በእግዚአብሔር ፊት እንዳልዋሸሁ እወቁ። **21** ቀጥሎም ወደ ሶሪያና ኪልቂያ አውራጃዎች ሄድኩኝ።
22 እስከዚያን ጊዜ ድረስ በይሁዳ ላሉት አብያተክርስቲያናት በአካል አልታወቅም ነበር፣ **23** ነገር ግን «ያ ቀድሞ ያሳድደን የነበረው ሰው አሁን ሊያጠፋው
ሲጥር የነበረውን እምነት እየሰበከ ነው» የሚል ወሬ ብቻ ይሰሙ ነበር፣ **24** ስለ እኔም እግዚአብሔርንም ያከብሩ ነበር።

Galatians 1:1

አያያዥ መግለጫ
ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ደብዳቤ በገላትያ አካባቢ ላሉት አብያተ ክርስቲያናት ጻፈ ።

አጠቃላይ መረጃ
በሌላ መንገድ ካልተገለጸ በቀር በዚህ ደብዳቤ ውስጥ “እርስዎ” እና “የእርስዎ” የሚሉት ሁሉም ምሳሌዎች የገላትያ እና ብዙ ናቸው ። (ይመልከቱ: የበለስ_ዮዎ)

ያስነሳው
"ኢየሱስ ክርስቶስን ያስነሳው"

አስነሳ
እዚህ ላይ ይህ ማለት የሞተ ሰው እንደገና ሕያው ይሆናል ማለት ነው ።

ወንድሞች
በክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ የአንድ ሰማያዊ ቤተሰብ አባላት ስለሆኑ ይህ ማለት ወንዶችም ሆኑ ሴቶችን ጨምሮ እዚህ ያሉ ክርስቲያኖችን ማለት ነው ። አት: “ወንድሞች እና እህቶች” (የበለስ_ቁጥር መግለጫዎችን ይመልከቱ)

Galatians 1:3

ስለእኛ ኃጢአት
ኃጢአቶች ቅጣትን ይወክላሉ ። አት: - “በኃጢአታችን ምክንያት የተገባንን ቅጣትን ለመውሰድ” (ይመልከቱ።

ከዚህ ክፉ ዘመን ነጻ እንዲያወጣን
እዚህ “ይህ… ዘመን” በስራ ላይ ያሉ ሀይሎችን ይወክላል። በዚህ ወቅት “በዓለም ላይ ከሚሠራው ከክፉ ኃይሎች ነፃ ያወጣናል” (ይመልከቱ ። የበለስ_ቁጥር)

አምላካችን እና አባታችን
ይህ የሚያመለክተው “እግዚአብሔር አባታችንን” ነው ። እርሱ አምላካችን እና አባታችን ነው ።

Galatians 1:6

አያያዥ መግለጫ
ጳውሎስ ይህንን ደብዳቤ የጻፈበትን ምክንያት ሲገልፅ ወንጌልን መረዳታቸውን እንዲቀጥሉ አሳስቧቸዋል ።

እደነቃለሁ
"ይገርመኛል" ወይንም "ደንግጫለሁ"። ይህንን እያደረጉ ስለሆነ ጳውሎስ አዝኗል።

ከእሱ በፍጥነት እየዞራችሁ ነው ... ወደ ተለየ ወንጌል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “በፍጥነት በእርሱ ላይ መታመን አቆምክዋል” ወይም 2) “ለእሱ ታማኝ መሆንን በፍጥነት አቆሙ” (ይመልከቱ ። የበለስ_ቁጥር ይመልከቱ)

የጠራችሁ እሱ
"እግዚአብሔር፣ የጠራችሁ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የጠራችሁ
እዚህ ማለት ይህ ማለት እግዚአብሔር ሰዎችን የእሱ ልጆች እንዲሆኑ ፣ እንዲያገለግሉት እና በኢየሱስ በኩል የመዳንን መልእክት እንዲሰብኩ ሾሞላቸዋል ወይም መረጣቸው ማለት ነው ።

በክርስቶስ ጸጋ
“በክርስቶስ ጸጋ ምክንያት” ወይም “በክርስቶስ ደግነት መስዋትነት”

ወደ ሌላ ወንጌል እየዞራችሁ ነው
"የተለየ ወንጌል እያመናችሁ ነው"

ሰዎች
ሰዎች

Galatians 1:8

ማወጅ አለበት
ይህ ያልተፈጠረ እና የማይከሰት አንድ ነገርን እየገለጸ ነው። አት: - “ያውጃል” ወይም “ማወጅ አለበት” (ይመልከቱ: የበለስ_አፖፖ)

ከአንዱ በስተቀር
“ከወንጌል የተለየ” ወይም “ከመልእክቱ የተለየ”

የተረገመ ይሁን
እግዚአብሔር ያንን ሰው ለዘላለም ይቀጣል ። ቋንቋዎ በሌላ ሰው ላይ የመርገም የተለመደ መንገድ ካለው ያንን መጠቀም አለብዎት።

አሁን የሰዎችን ወይንም የእግዚአብሔርን ይሁንታ የምፈልግ ነኝ? ሰዎችን ለማስደሰት ፈልጌአለሁ?
እነዚህ አጸያፊ ጥያቄዎች “አይሆንም” የሚል መልስ ይጠብቃሉ ። እኔ: - “የሰዎችን ሞገስ አልፈልግም ፣ ይልቁንም የእግዚአብሔርን ሞገስ እጠይቃለሁ ። ሰዎችን ለማስደሰት አልፈልግም ። (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)

ሰዎችን ለማስደሰት የምሞክር ከሆነ የክርስቶስ አገልጋይ አይደለሁም
ሁለቱም “ከሆነ” ሐረግ እና “ታዲያ” ሐረግ ከእውነት ተቃራኒ ናቸው ። እኔ አሁንም ሰዎችን ለማስደሰት አልሞከርኩም ፣ እኔ የክርስቶስ አገልጋይ ነኝ ወይም ደግሞ “አሁንም ሰዎችን ለማስደሰት እየሞከርኩ ከሆነ የክርስቶስ አገልጋይ ባልሆንኩ”

Galatians 1:11

አያያዥ መግለጫ
ጳውሎስ ወንጌልን ከሌሎች እንዳልተማረ ገል explainsል ። እሱ የተማረው ከኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ወንድሞች
በ1:1 ላይ እንዳለው ይተርጉሙት

የሰው ወንጌል አይደለም
ይህንን ሐረግ በመጠቀም ጳውሎስ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ሰው አይደለም ለማለት እየሞከረ አልነበረም ። ክርስቶስ ሰውም ሆነ እግዚአብሔር ስለሆነ ፣ እሱ ኃጢያተኛ ሰው አይደለም ። ጳውሎስ ወንጌሉ ከየት እንደመጣ እየጻፈ ነው ። እርሱ የመጣነው ከሌሎች ኃጢአተኛ የሰው ልጆች ነው ፣ ግን የመጣው ከኢየሱስ ክርስቶስ ነው ።

ይህ ለእኔ የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ነበር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ወንጌልን ገለጠኝ” ወይም 2) “ኢየሱስ ክርስቶስ ማን እንደ ሆነ አሳየኝ ።

Galatians 1:13

የቀድሞው ሕይወቴ
"በአንድ ጊዜ ባህሪ" ወይም "የቀደመው ህይወት" ወይም "የቀድሞው ኑሮ"

እቀጥላለሁ
ይህ ዘይቤ ጳውሎስ ፍጹም አይሁዳውያን ለመሆን ባላቸው ግብ ውስጥ በዕድሜው ከሌሎች አይሁዳውያን እንደሚቀድም ያሳያል ።

የእድሜዬ እኩዮች
እኔ እንደ እኔ ተመሳሳይ ዕድሜ ያሉ የአይሁድ ሰዎች ነበሩ ”

አባቶች
ቀደምት አባቶች

Galatians 1:15

በጸጋው የጠራኝን
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “እግዚአብሔር ቸር ነው ፣ እንዳገለግለው ጠራኝ” ወይም 2) “እርሱ በጸጋው በኩል ጠራኝ” ።

ልጁን በእኔ ውስጥ ለመግለጥ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ልጁን እንዳውቅ ይፈቅድልኛል” ወይም 2) “ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን በእኔ በኩል ዓለምን ለማሳየት” ነው ።

ልጁ
ይህ የእግዚአብሔር ልጅ ለኢየሱስ አስፈላጊ ርዕስ ነው ። (መመሪያዎችን ይመልከቱ) መመሪያዎች_ሶፍትዌር መመሪያዎች

አውጁት
“የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ አውጅ” ወይም “ስለ እግዚአብሔር ልጅ የሚገልጸውን ምሥራች ስበኩ”

ከስጋና ደም ጋር አልተማከርሁም
ይህ ከሌሎች ሰዎች ጋር መነጋገር ማለት አገላለፅ ነው ። አት: - “መልዕክቱን ለመረዳት ሰዎች እንዲረዱኝ ሰዎችን ጠይቅ” (የበለስ_ ቪዲዮም ተመልከት)

ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ
ወደ ኢየሩሳሌም ሂጂ ” ኢየሩሳሌም ለመድረስ ብዙ ኮረብታዎችን መውጣት አስፈላጊ ስለነበረች ከፍታ ኮረብታዎች አካባቢ ነች ፣ እናም ወደ ኢየሩሳሌም መጓዙ “ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚወጣ” መግለጹ የተለመደ ነበር ።

Galatians 1:18

ከያዕቆብ በስተቀር ሌላ ሐዋርያትን አላገኘሁም
ይህ ድርብ አሉታዊ አፅን emphasiት የሰጠው ጳውሎስ ያየው ሐዋርያው ያዕቆብ ብቻ መሆኑን ነው ። አት: - “እኔ ያየሁት ሌላ ሐዋርያ ያዕቆብ ብቻ ነበር” (የበለስ_ቁጥር አተያይ)

በእግዚአብሔር ፊት
ጳውሎስ የገላትያ ሰዎች ጳውሎስ ሙሉ በሙሉ ከባድ መሆኑን እና እግዚአብሔር የሚናገረውን እንደሚሰማ እና እውነቱን ካልተናገር እንደሚፈርድበት እንዲገነዘቡ ይፈልጋል።

ስለምጽፍላችሁ ነገር፣ በእግዚአብሔር ፊት አረጋግጥላችኋለሁ፣ እየዋሸሁ አይደለም
ጳውሎስ እውነቱን እየተናገረ መሆኑን ለማጉላት ድምጾችን ይጠቀማል ። አት: - “በጻፍኳቸው መልእክቶች ውስጥ አልዋሸም” ወይም “በጻፍኩላችሁ ነገር ውስጥ እውነቱን እነግራችኋለሁ” (ይመልከቱ ። የበለስ_ቁጥር ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Galatians 1:21

ክልሎች
“የአለም ክፍል”

እነሱ ሲናገሩ ብቻ ሰሙ
ግን እነሱ ሌሎች ስለ እኔ ሲናገሩ የሰሙትን ብቻ ያውቁ ነበር ”

በክርስቶስ ውስጥ ላሉት የይሁዳ አብያተ-ክርስቲያናት አሁንም በግል አልታወቅም
በይሁዳ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በክርስቶስ ውስጥ ካሉ ሰዎች ውስጥ ማንም አላገኘኝም ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 2

1 ከአስራ አራት ዓመት በኋላ ቲቶን ይዤ ከበርናባስ ጋር እንደገና ወደ ኢየሩሳሌም ሄድኩ። **2** የሄድኩበትም ምክንያት መሄድ እንዳለብኝ እግዚአብሔር ስላመለከተኝ ነበር። ሄጄም በአህዛብ መካከል እየሰበኩት ስላለው ወንጌል ነገርኳቸው፣ ነገር ግን በከንቱ እንዳልሮጥኩ ወይም እየሮጥኩ እንዳልሆን እርግጠኛ ለመሆን ይህን የተናገርኩት በሌሎቹ ዘንድ እንደ ዋና ለሚታሰቡት ብቻ ነበር። **3** ግሪካዊ የሆነው ሲላስ እንኳ እንዲገረዝ አልተገደደም። **4** ይህ ጉዳይ የተንሳው በክርስቶስ ያገኘነውን ነፃነት ለመሰለል ሾልከው በገቡ ውሸተኞች ወንድሞች ምክንያት ነበር። **5** የህግ ባሪያዎች ሊያደርጉን ይመኙ ነበር። ነገር ግን ለእናንተ ወንጌሉ ሳይለወጥ ይቆይላችሁ ዘንድ ለአንድ ሰዓት እንኳ ለሀሳባቸው አልተገዛንም። **6** ነገር ግን ሌሎች መሪዎች ናቸው ያልዋቸው ምንም አስተዋፅኦ አላደርጉልኝም። ማንም ይሁኑ ለእኔ ትርጉም አልነበረውም። ሆኖም ግን ልክ ጴጥሮስ ለተገረዙት ወንጌልን ለማድረስ አደራ እንደተሰጠው ሁሉ **7** እኔም ላልተገረዙት ወንጌልን ለማድረስ አደራ እንደተቀበልኩ አዩ፥ **8** ምክንያቱም ለተገረዙት ሃዋሪያ ይሆን ዘንድ በጴጥሮስ የሰራ እግዚአብሔር ላልተገረዙት ሃዋሪያ እሆን ዘንድ በእኔም ስለሚሰራ ነው። **9** እንደመሪዎች የሚታወቁት ያዕቆብ፥ኬፋና ዮሀንስ በእኔ ላይ ያለውን ፀጋ ባዩ ጊዜ እኛ ወደ አህዛብ እነርሱ ደግሞ ወደተገረዙት ይሄዱ ዘንድ የማህበራቸውም ተካፋዮች እንድንሆን ሙሉ መብት ሰጡን። **10** እኔ ለማድረግ የምናፍቀውን ድሆችን እንድናስብም አሳሰቡን። **11** ከዚያም ኬፋ ወደ አንጾኪያ በመጣ ጊዜ ሥራው ትክክል ስላልነበረ ፊት ለፊት ተቃወምኩት። **12** ምክንያቱም ከያዕቆብ ዘንድ ሰዎች ከመምጣታቸው በፊት ኬፋ ከአህዛብ ጋር ይበላ ነበር። ሰዎቹ በመጡ ጊዜ ግን እነኚህን የተገረዙ ሰዎች ፈርቶ ከአህዛብ ጋር መብላቱን አቆመ እንዲያውም ተለያቸው። **13** በርናባስ እንኳ በግብዝነታቸው እስኪሳብ ድረስ ሌሎቹም አይሁድ በኬፋ ግብዝነት ተካፋዮች ነበሩ። **14** ወንጌልን በሚፃረር መንገድ መሄዳቸውን ባየሁ ጊዜ ኬፋን በሁሉም ፊት «አንተ አይሁዳዊ ሆንህ በአህዛብ ስርአት የምትኖር ከሆነ አህዛብ በአይሁድ ስርአት እንዲኖሩ ለምን ታስገድዳቸዋልህ?» አልኩት። **15** እኛ«አህዛብ ኃጢአተኞች» ያልሆንን ነገር ግን በትውልድ አይሁዳዊ የሆንን በክርስቶስ ኢየሱስ ላይ ባለ እምነት እንጂ ማንም ህግን በመፈፀም እንደምይፀድቅ እናውቃለን። **16** በህግ ሥራ ማንም ሊፀድቅ ስለማይችል በህግ ሥራ ሳይሆን በክርስቶስ ኢየሱስ ባለ እምነት እንፀድቅ ዘንድ ወደ ክርስቶስ ኢየሱስ እምነት ተጠርተናል። **17** ነገር ግን እግዚአብሔር በክርስቶስ እንዲያፀድቀን እየፈለግን ሳለ ራሳችንን ኃጢአተኞች ሆነን እናገኛለን፥ **18** ታዲያ ክርስቶስ የኃጢአት አገልጋይ ሆነ ማለት ነው? በፍፁም አይደለም። **19** ምክንያቱም አውልቄ የጣልኩትን ህግን የመፈፀም ትምክህት እንደገና ብገነባ ራሴን ህግ ተላላፊ ሆኜ አገኘዋለሁ። በህግ በኩል ለህግ ሞቼአለሁ። **20** ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ። ከእንግዲህ የምኖረው እኔ አይደለሁም፥ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል። አሁን በሥጋ የምኖረው ኑሮ በወደደኝና እራሱን ስለ እኔ በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው። **21** የእግዚአብሔርን ፀጋ አላቃልልም፥ ህግን በመጠበቅ ፅድቅ የሚገኝ ቢሆን ኖሮ ክርስቶስ መሞቱ ከንቱ በሆነ ነበር።

Galatians 2:1

አያያዥ መግለጫ
ጳውሎስ ሐዋርያትን ሳይሆን ፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወንጌልን እንዴት እንደ ተማረ ታሪክ ማቅረቡን ቀጠለ ።

ወጣ
"ተጓዘ" ኢየሩሳላ በተራራማ አገር ውስጥ ትገኛለች ። በተጨማሪም አይሁዶች ኢየሩሳሌምን ወደ ሰማይ ቅርብ የሆነ ቦታ እንደሆነ አድርገው ይመለከቱት ነበር ፣ ስለዚህ ጳውሎስ በምሳሌያዊ ሁኔታ እየተናገረ ሊሆን ይችላል ፣ ወይም ወደ ኢየሩሳሌም ለመድረስ አስቸጋሪ የሆነውን ፣ ከፍ ያለ ፣ ጉዞውን የሚያንፀባርቅ ሊሆን ይችላል።

አስፈላጊ እንደሆኑ ተደርገው ይታያሉ
"በምእመናን መካከል በጣም አስፈላጊ መሪዎች"

እኔ እየሮጥኩ ወይም አልሮጥኩም በከንቱ ነበር
ጳውሎስ ለስራ እንደ ዘይቤ ሩጫ ይጠቀማል ፣ እናም እሱ የሠራው ሥራ ትርፋማ መሆኑን ለማጉላት ድርብ አሉታዊን ይጠቀማል። አት: - “ትርፋማ ሥራ ነበርኩ ፣ ወይም ሠራሁ ፣” (የበለስ_ቁጥር አሃዶች እና በለስ

በከንቱ
“ለትርፍ” ወይም “በከንቱ”

Galatians 2:3

መገረዝ
ይህ በንቃት ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “አንድ ሰው እንዲገረዘው ያድርጉት (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)

ሐሰተኛ ወንድሞች በድብቅ መጡ
“ክርስቲያን ነን የሚሉ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን መጡ ፣” ወይም “ክርስቲያን ነን የሚሉ ሰዎች በመካከላችን መጡ”

ነፃነትን ለመሰለል
ሰዎች በነፃነት እንዴት እንደሚኖሩ በድብቅ ይመልከቱ

ነፃነት
ነፃነት

ተመኙ
“እነዚህ ሰላዮች ይፈልጉ ነበር” ወይም “እነዚህ የሐሰት ወንድሞች ፈልገዋል”

ባሪያዎች እንድንሆን ያደርገናል
የሕግ ባሪያዎች እንድንሆን ያደርገናል ። ጳውሎስ እየተናገረ ያለው ህጉ ያዘዘውን የአይሁድን የአምልኮ ሥርዓት ለመከተል ስለ መገደድ ነው ። ይህን እየተናገረ ያለው ስለ ባርነት ነው ። በጣም አስፈላጊው የአምልኮ ሥርዓት ግርዘት ነበር ። አት: - “ህጉን እንድንታዘዝ ለማስገደድ” (የበለስ_ቁጥር እና የበለስ_ቁጥር ይመልከቱ)

ለራስህ አስገባ
“አስገባ” ወይም “አዳምጥ”

Galatians 2:6

ምንም አልጨምርም
እዚህ “እኔ” የሚለው ቃል ጳውሎስ የሚያስተምረውን ይወክላል ። አት: - "እኔ በም አስተምርበት ምንም ነገር አልጨምሩም" ወይም "በም አስተምርበት ምንም ነገር እንዳክል አልነገረኝም"

በተቃራኒው
“ይልቁን” ወይም “ይልቁን”

በአደራ ተሰጥቶኛል
ይህ በንቃት ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “እግዚአብሔር አመነኝ” (የበለስ_ቁጥር / ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Galatians 2:9

ቤተክርስቲያንን ገነባች
ሰዎች ስለ ኢየሱስ የሚያስተምሩት እና ሰዎች በኢየሱስ እንዲያምኑ ያመኑ ሰዎች ነበሩ ። (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)

የተሰጠኝ ጸጋ ይህ ነው
እግዚአብሔር ቸር እንደ ሆነልኝ አየሁ (የበለስ_ቁጥር ተመልከት)

የሕብረት ቀኝ እጅ ሰጠ
“ተቀባይነት ያለው… እንደ ባልደረባችን” ወይም “በክብር የተቀበሉት… በክብር” (ይመልከቱ ።

ቀኝ እጅ
"ቀኝ እጆቻቸው"

ድሆችን አስታውሱ
“ለችግረኞች ፍላጎቶች ይንከባከቡ” (ይመልከቱ ። የበለስ_ ቪዲዮም)

Galatians 2:11

በፊቱ ተቃወምኩት
“በፊቱ” የሚሉት ቃላት “ሊያይ እና ሊሰማኝ የሚችልበት ስፍራ” የሚል አገላለጽ ነው ። አት: - “በአካል ፊት ለፊት አጋጥቼዋለሁ” ወይም “በግለሰቡ በግለሰቡ ላይ ተከራክሬያለሁ”

ከዚህ በፊት
ከጊዜ ጋር በተያያዘ

ቆመ
ከእነሱ ጋር መብላት አቆመ ”

እነዚያን ይፈራው ነበር
እነዚህ መገረዝ የጠየቁት እነዚህ ሰዎች የሆነ ጥፋት እየፈጸመ እንደሆነ ይፈርዳል ብለው ፈራ ”ወይም“ እነዚህ ግርዛት የጠየቁት እነዚህ ሰዎች የሆነ ጥፋት በመፈጸማቸው ተጠያቂ እንደሚያደርጋቸው ፈርቶ ነበር ”(የበለስ_ቁጥር ን ይመልከቱ)

መገረዝ የሚፈልጉ ነበሩ
ክርስትናን የተቀበሉ አይሁዶች ግን በክርስቶስ የሚያምኑ በአይሁድ ወጎች መሠረት እንዲኖሩ የጠየቁ አይሁዶች

ራቅ
ከ “ራቁ” ወይም “ተቆጥበዋል”

Galatians 2:13

የወንጌልን እውነት አለመከተል
“እነሱ ወንጌልን እንደሚያምኑ ሰዎች አልነበሩም” ወይም “እነሱ ወንጌልን እንደማያምኑ ሆነው ይኖሩ ነበር”

አሕዛብ እንደ አይሁድ እንዲኖሩ እንዴት ማስገደድ ይችላሉ?
ይህ የአጻጻፍ ጥያቄ ተግሣጽ ነው እናም እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። AT: - “አሕዛብ ልክ እንደ አይሁዶች እንዲኖሩ ማስገደድ ስህተት ነዎት” ። “እርስዎ” የሚለው ቃል ጴጥሮስን የሚያመለክት ሲሆን ነጠላ ነው ። (ይመልከቱ: የበለስ_ቁልፍ እና በለስ_ዮዎ)

ኃይል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ቃላትን በመጠቀም ሀይል ወይም 2) ማሳመን (ዩ.አር.ቢ.) ናቸው።

Galatians 2:15

አያያዥ መግለጫ
ህጉን ለሚያውቁ አይሁዶች እንዲሁም ህጉን የማያውቁ አሕዛብ እንደሚድኑ ጳውሎስ ለአማኞች ይነግራቸዋል ህጉን ባለመጠበቅ ብቻ ።

የአህዛብ ኃጢያተኞች አይደሉም
“አይሁዶች የአህዛብ ወገን ብለው የሚጠሩት አይደለም”

እኛም በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እምነት መጣን
“በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል”

እኛ
ይህ ምናልባት የሚያመለክተው ጳውሎስንና ሌሎችን እንጂ ገላትያዎችን አይደለም። (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)

ሥጋ የለም
“ሥጋ” የሚለው ቃል ለሰውየው አጠቃላይ መግለጫ ነው ። አት: - “ማንም ሰው” (ይመልከቱ: የበለስ_ስኔክዶቼ)

Galatians 2:17

በክርስቶስ መጽደቅ እንፈልጋለን
“በክርስቶስ መጽደቅ” የሚለው ሐረግ ትክክለኛ ነው ምክንያቱም ከክርስቶስ ጋር አንድ ስለሆንን እና በክርስቶስ አማካይነት ጸድቀዋል ።

እኛም ኃጢአተኞች ሆነን ተገኝተናል
“ተገኝተዋል” የሚሉት ቃላት “እኛ በእርግጥ ኃጢአተኞች ነን” የሚል አፅን idት የሚሰጥ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው ። አት: - “እኛ ደግሞ በእርግጥ ኃጢአተኞች መሆናችንን እናውቃለን” (የበለስ_ ቪዲዮን ተመልከት)

በፍፁም አይደለም!
"በእርግጥ ይህ ያ እውነት አይደለም!" ይህ አገላለጽ ቀደም ባለው የአጻጻፍ ጥያቄ ላይ ጠንካራ ምላሽ የሚሰጥ አሉታዊ መልስ ይሰጣል “ክርስቶስ የኃጢአት አገልጋይ ሆኗል?” እዚህ ሊጠቀሙባቸው በሚችሉት ቋንቋዎ ተመሳሳይ መግለጫ ሊኖርዎት ይችላል ። (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)

Galatians 2:20

የእግዚአብሔር ልጅ
ይህ ለኢየሱስ አስፈላጊ ርዕስ ነው ። (መመሪያዎችን ይመልከቱ) መመሪያዎች_ሶፍትዌር መመሪያዎች

ወደ ጎን አላስቀመጥኩም
ፖል አዎንታዊውን ለማጉላት አሉታዊ ተናግሯል ። አት: - የ “ዋጋን አረጋግጣለሁ” የበለስ_ቁጥርቆች)

ጽድቅም ቢሆን ኖሮ... ክርስቶስ ይሞት ነበር
ጳውሎስ ከዚህ በፊት ያልነበረን ሁኔታ እየገለጸ ነው ። አት: - “ጽድቅ ግን አልተገኘም… ስለዚህ ክርስቶስ አልሞተም” (የበለስ_አፖን ተመልከት)

በሕጉ በኩል ጽድቅን ማግኘት ከቻለ
"አንድ ሰው ህጉን በመጠበቅ ጻድቅ ሊሆን ይችላል"

እንኪያስ ክርስቶስ በከንቱ ሞተ
በመሞቴ ምንም አላከናወንም ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 3

1 እናንተ ማስተዋል የጎደላችሁ የገላቲያ ሰዎች ማነው በክፉ ዓይኑ ያያችሁ፥ ክርስቶስ እንደተሰቀል ሆኖ በፊታችሁ ተስሎ አልነበረምን? **2** ይህን ብቻ ከእናንተ ማወቅ እፈልጋለሁ። መንፈስ ቅዱስን የተቀበላችሁት በህግ ሥራ ነው ወይስ የሰማችሁትን በማመናችሁ? **3** ይህን ያህል ሞኞች ናችሁ እንዴ፥ በመንፈስ ጀምራችሁ በሥጋ ትጨርሳላችሁ? **4** በእርግጥ ይህ ከንቱ ከተባለ ያን ሁሉ መከራ የተቀብላችሁት በከንቱ ነውን? **5** መንፈስ ቅዱስን የሰጣችሁና በመካከላችሁ ኃይለኛ ነገርን ያደረገው እርሱ ይህን ያደረገው በህግ ሥራ ነው ወይስ ከእምነት በሆነ እምነታችሁ ነው? **6** ልክ አብርሀም «እንዳመነና እምነቱ እንደ ፅድቅ እንደተቆጠረለት» **7** የሚያምኑ ሁሉ የአብርሀም ልጆች እንደሆኑ አስተውሉ። **8** ቅዱሳት መፅሀፍት እግዚአብሔር አህዛብን እንደሚያፀድቅ አስቀድመው አመልክተዋል። ወንጌል «አህዛብ ሁሉ በአንተ ይባረካሉ» ተብሎ በመጀመሪያ ለአብርሀም ተሰብኳል። **9** ስለዚህም የሚያምኑ እምነት ከነበረው ከአብርሀም ጋር የተባረኩ ናቸው። **10** «ህግን ሁሉ ይፈፅም ዘንድ ለህግ የማይታዘዝ ሁሉ የተረገመ ነው» ተብሎ ተፅፎአልና በህግ ስራ የሚታመን ሁሉ በእርግማን ስር ነው። **11** «ጻድቅ በእምነት ይኖራልና» እግዚአብሔር ማንንም በህግ እንደማያጸድቅ ግልጽ ነው። **12** ህግ ከእምነት የመነጨ አይደለም፥ ይልቁኑም «በህግ ውስጥ ያሉትን እነዚያን ነገሮች የሚያደርግ በህግ ይኖራል» **13** «በእንጨት ላይ የሚሰቀል የተረገመ ነው» ተብሎ በተጻፈው መሰረት እርሱ ስለኛ እርግማን በመሆን ከህግ እርግማን ዋጀን። **14** የዚህ ተግባር ዓላማ የመንፈስ ቅዱስን ተስፋ በእምነት እንቀበል ዘንድ በአብርሀም ላይ የነበረው በረከት በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል በአህዛብም ላይ እንዲሆን ነው። **15** የምናገረው በሰው ቋንቋ ነው። ልክ በሰዎች መካከል እንደተደረገ ውል ማንም ከዚህ ሊቀንስ ወይም ሊጨምር አይችልም። **16** እንግዲህ ተስፋዎቹ የተነገሩት ለአብርሀምና ለዘሩ ነው። ብዙ ሰዎችን እንደሚያመለክት «ለዘሮቹ» አላለም። ነገር ግን አንድ መሆኑን በሚገልጽ መልኩ«ለዘሩ» ብሎ ይናገራል። ያም ለዘሩ የተባለለት ክርስቶስ ነው። **17** እንግዲህ እንዲህ ልበል። አስቀድሞ በእግዚአብሔር የተረጋገጠው ቃል ኪዳን ተስፋ ከ430 ዓመት በኋላ በተሰጠ ህግ አልተሻረም። **18** ምክንያቱም ውርሱ በህግ የመጣ ቢሆን ኖሮ በተስፋ በኩል ባልመጣ ነበር፥ ነገር ግን እግዚአብሔር ለአብርሃም በተስፋ አማካኝነት ርስትን እንዲያው ሰጠው። **19** ታዲያ ህግ ለምን አስፈለገ? የአብርሃም ዘር ተስፋ ወደተሰጣቸው እስኪመጣ ድረስ በመተላለፍ ምክንያት ህግ ተሰጠ፤ ህጉ በመካከለኛ አማካኝነት በመላዕክት አማካኝነት ተግባራዊ ሆኗል። **20** መካከለኛ ሲል ከአንድ ሰው በላይ እንደሆነ ያመለክታል፥ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው። **21** ታዲያ ህግ የእግዚአብሔርን ተስፋ ይቃረናል ማለት ነው? በፍጹም አይደለም። ህይወትን ሊሰጥ የሚችል ህግ ተሰጥቶ ቢሆን ኖሮ በእርግጠኝነት ጽድቅ በህግ በኩል ይመጣ ነበር። **22** ነገር ግን ይልቁኑ መጽሀፍ ሁሉን ነገር ከኃጢአት በታች እስርኛ አድርጓል። ስለዚህም እኛን በክርስቶስ ኢየሱስ ለማዳን እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ ለሚያምኑ ተሰጠ። **23** ነገር ግን በክርስቶስ ማመን ከመምጣቱ በፊት እምነት እስከተገለጠበት ጊዜ ድረስ በህግ ታስረንና ታግደን ነበር። **24** ስለዚህ በእምነት እንድንጸድቅ ህግ ወደ ክርስቶስ ዘመን የሚያደርሰን ሞግዚት ሆነ። **25** አሁን እምነት ስለመጣ ከዚህ በኋላ በሞግዚት ሥር አይደለንም። **26** ምክንያቱም ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ። **27** በክርስቶስ ስም የተጠምቃችሁ ሁላችሁ ክርስቶስን ለብሳችሁታል። **28** ሁላችሁ በክርስቶስ አንድ ስለሆናችሁ በዚህ ጉዳይ በአይሁድና በግሪክ ሰዎች፥ በባሪያና ነጻ በሆነ፥በሴትና በወንድ መካከል ልዩነት የለም። **29** እንግዲህ የክርስቶስ ከሆናችሁ የአብርሀም ዘሮች እንደተስፋ ቃሉም ወራሾች ናችሁ።

Galatians 3:1

አጠቃላይ መግለጫ
ጳውሎስ በገላትያ የነበሩትን አማኞች የእግዚአብሔርን ህግ ባለመፈፀም ሳይሆን እግዚአብሔርን በእምነት መንፈስ ቅዱስ እንደሰጣቸው አስታውሷቸዋል ::

አጠቃላይ መረጃ
ጳውሎስ ገለልተኛ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ገላትያዎችን ገሥጻቸው ነበር ::

በአንተ ላይ አስማተኛ ያደረገ ማን ነው?
ጳውሎስ የገላትያ ሰዎች አንድ ሰው ፊደል እንዳስመሰላቸው የገለጹትን አስጨናቂ እና አፀያፊ ጥያቄን እየተጠቀመ ነው :: አንድ ሰው በእጃቸው ላይ አስማተኛ እንዳደረገ በእውነት አያምንም :: አት: - "አንድ ሰው አስማተኛ እንዳሳደረብዎት ታሳያላችሁ!" (ይመልከቱ: የበለስ እና የበለስ_ቁጥር)

ከአንተ ለመማር የምፈልገው ብቸኛው ነገር ይህ ነው
ይህ ከቁጥር 1 ድረስ አጠራጣሪ ሆኖ ይቀጥላል :: (ይመልከቱ: የበለስ_አሮን)

መንፈስን የተቀበለው በሕግ ሥራ ነው ወይስ የሰማችሁትን በማመን?
ይህንን የአጻጻፍ ጥያቄ ከቻሉ እንደ ጥያቄ ይተረጉሙ ፣ ምክንያቱም አንባቢው እዚህ ጥያቄ ይጠብቃል :: ደግሞም ፣ ለጥያቄው መልስ “የሰማችሁትን በማመን” ሳይሆን “ህጉ የሚናገረውን በማድረግ” መሆኑን አንባቢው ማወቋን ያረጋግጡ። AT: "መንፈስ ቅዱስን የተቀበለው ህጉ ያለውን ነገር በማድረግ ሳይሆን የሰማችሁትን በማመን ነው ::" (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)

እንዲህን የማታስተውሉ ናችሁ?
ይህ የተዛባ ጥያቄ ጳውሎስ የገላትያ ሰዎች ሞኞች መሆናቸው እንደተገረመ አልፎ ተርፎም እንደተናደደ ያሳያል :: አት: - "በጣም ሞኞች ናችሁ!" (UDB) (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)

በስጋ
“ሥጋ” የሚለው ቃል ጥረትን ለመግለጽ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። አት: - “በእራስዎ ጥረት” ወይም “በገዛ ሥራዎ”

Galatians 3:4

ብዙ ነገሮች በከንቱ መከራ ደርሶብዎታል ...?
ጳውሎስ የገላትያ ሰዎች በሚሰቃዩበት ወቅት የተወሰነ ጥቅም እንደሚያገኙ ያምን ዘንድ ይህን ጥያቄ ይጠቀም ነበር :: አት: - "በእርግጥ ብዙ ነገሮችን በከንቱ እየሠቃዩ እንደነበረ አላሰብኩም ...!" ወይም “በርግጥ ብዙ ነገሮችን ለመሠቃየት አንድ ጥሩ ዓላማ እንደነበረ አውቀዋል...!” (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)

ብዙ ነገሮች በከንቱ መከራ ደርሶብሃል
በክርስቶስ ላይ ባላቸው እምነት ምክንያት በሚቃወሟቸው ሰዎች ምክንያት እነዚህን ሁሉ መከራዎች እንደደረሱ በግልፅ ሊገለፅ ይችላል :: AT: "በክርስቶስ ያለዎት እምነት በእምነት ሲቃወሙህ ብዙ ብዙ መከራዎች ደርሶብሃል" ወይም "በክርስቶስ አምነሃል ፣ ክርስቶስን በሚቃወሙትም ብዙ መከራዎች ደርሶብሃል :: እምነትህ እና መከራ በከንቱ ነበር" (ተመልከት : የበለስ_ቁጥር)

በከንቱ
“ጥቅም የሌለው” ወይም “ጥሩ ነገር የማግኘት ተስፋ ሳይኖር”

በውኑ ከንቱ ነውን?
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ጳውሎስ ይህንን የተዛባ ጥያቄ ተጠቅሞ ልምዶቻቸው በከንቱ እንዳይሆኑ ለማስጠንቀቅ ነው ። አትቲ: - “በከንቱ ይሁን! ወይም “በኢየሱስ ክርስቶስ ማመንን ማቆም እና ሥቃያችሁ በከንቱ አይሁን” ወይም 2) ጳውሎስ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው መከራቸው በከንቱ እንዳልሆነ ያረጋግጥልናል ። አት: - በእርግጥ ይህ በከንቱ አልነበረም! (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)

እሱ ... የሚያደርገው በሕግ ሥራ ነው ወይ በእምነት በማዳመጥ?
ጳውሎስ የገላትያ ሰዎች ሰዎች መንፈስ ቅዱስን የሚቀበሉበትን መንገድ ለማስታወስ ሌላ የአጻጻፍ ጥያቄ ይጠይቃል ። አት: - እሱ ... የሕጉን ሥራ የሚሠራው በእምነት አይደለም ፤ ይህን የሚያደርገው በእምነት በመስማት ነው። (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)

በሕግ ሥራዎች
ይህ ህጉ የሚፈልገውን ሥራ የሚሠሩ ሰዎችን ይወክላል ። አት: - "ህጉን እንድናደርግ ያዘዘንን ታደርጋላችሁና"

በእምነት በመስማት ነው
ቋንቋዎ ሰዎች የሰሙትና ያመኑበት ነገር በግልፅ እንዲገለጽ ሊፈልግ ይችላል። አት: - “መልእክቱን ስለሰማችሁ እና በኢየሱስ ስለምታምኑ” ወይም “መልእክቱን ስላዳመጥክ እና በኢየሱስ ስለ ታምነሃል” (የበለስ_ቁጥር ን ይመልከቱ)

Galatians 3:6

አያያዥ መግለጫ
ጳውሎስ ፣ አብርሃም እንኳ በሕግ ሳይሆን በእምነት በእምነት ጽድቅን እንደተቀበለ የገላትያ አማኞችን ያስታውሳል ።

ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት
እግዚአብሔር የአብርሃምን በእግዚአብሔር ላይ እምነት እንዳለው አየ ፣ ስለሆነም እግዚአብሔር አብርሃምን እንደ ጻድቁ ተቆጥሯል ።

የእምነት ሰዎች
“እምነት ያላቸው” “እምነት” የሚለው ስም “ማመን” ከሚለው ግስ ጋር ሊገለጽ ይችላል ። አት: “የሚያምኑ” (የበለስ_ቁጥር ማስታወቂያዎችን ይመልከቱ)

የአብርሃም ልጆች
ይህ እግዚአብሔር ለአብርሃምን የሚመለከታቸው ሰዎችን ይወክላል ። አት: - “እንደ አብርሃም በተመሳሳይ ጻድቅ” (የበለስ_ማወቅን ይመልከቱ)

በመመልከት ላይ
እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባውን ቃል የገባላቸው እና ተስፋው በክርስቶስ በኩል ከመሆኑ በፊት የጻፉት ስለሆነ ፣ መጽሐፉ ከመፈጸሙ በፊት የወደፊቱን እንደሚያውቅ ሰው ነው ። አት: - “አስቀድሞ የተተነበየ” ወይም “ይህ ከመከሰቱ በፊት አየ” (ይመልከቱ።

በአንተ ውስጥ
“ባደረጋችሁት ነገር” (ዩ.አር.ቢ.) ወይም “ባረካችሁ” ። “እርስዎ” የሚለው ቃል አብርሃምን የሚያመለክት ሲሆን ነጠላ ነው ። (ይመልከቱ: የበለስ_ዮዎ)

ሕዝቦች ሁሉ
“በዓለም ውስጥ ያሉ ሁሉም ሰዎች-ቡድኖች” (UDB)። እግዚአብሔር ትኩረት እየሰጠ ያለው እርሱ የተመረጠውን ቡድን የአይሁድን ሕዝብ ብቻ አለመሆኑን ነው ። የመዳን እቅዱ ለአይሁድም እና አይሁድ ላልሆኑ ነበሩ ።

Galatians 3:10

በእሱ የሚታመኑ ሁሉ ... ሕጉ የተረገመ ነው
በእርግማን ሥር መሆን መርገምን ያመለክታል ። እዚህ የሚያመለክተው ዘላለማዊ ቅጣት መቀጣትን ነው ። “የሚተማመኑትን... ሕጉ የተረገመ ነው” ወይም “በሕግ ላይ የሚመኩትን ግን ለዘላለም ይቀጣቸዋል” (ይመልከቱ ።

አሁን ግልፅ ነው
ግልጽ የሆነው ነገር በግልጽ ሊገለፅ ይችላል ። በ “ቅዱሳት መጻሕፍት ግልጽ ናቸው” ወይም “ቅዱሳት መጻሕፍት በግልፅ ያስተምራሉ” (ይመልከቱ ። የበለስ_ቁጥር)

በእግዚአብሔር ፊት በሕግ የተጸደቀ ማንም የለም
ይህ ከነቃ ግስ ጋር ሊገለጽ ይችላል። አት: - “እግዚአብሔር ማንም በሕግ ጻድቅትን አያጸድቅም”

በእግዚአብሔር ፊት በሕግ የተጸደቀ ማንም የለም
ጳውሎስ ሕጉን ቢታዘዙ እግዚአብሔር እንደሚያጸድቃቸው ያላቸውን እምነት እያስተካከለ ነው ። አት: - “ሕጉን በመታዘዝ ማንም በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ አይደለንም” ወይም “እግዚአብሔር ሕጉን ስለታዘዙ ማንንም አያጸድቅም” (የበለስ_ቁጥር 3 ን ይመልከቱ)

ጻድቃን
ይህ ጻድቃንን ያመለክታል ። አት: - “ጻድቃንም ሰዎች” ወይም “እግዚአብሔር ጻድቃን አድርጎ የሚቆጥራቸው ሰዎች”

የሕግ ሥራዎች
"ህጉ ምን ማድረግ እንዳለበት"

በእነሱ መኖር አለበት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ሁሉንም መታዘዝ አለባቸው” (ዩ.አር.ቢ.) ወይም 2) “ሕጉ የሚፈልገውን ለማድረግ ባለው ችሎታ ይፈረድበታል” ።

Galatians 3:13

አያያዥ መግለጫ
ህጉን መጠበቅ አንድን ሰው ሊያድን እንደማይችል እና ህጉ ለአብርሃም በተሰጠ እምነት አዲስ ሁኔታ እንደማይጨምር ጳውሎስ በድጋሚ እነዚህን አማኞች ያስታውሳል ።

ከሕጉ እርግማን
“እርግማን” የሚለው ስም “እርግማን” ከሚለው ግስ ጋር ሊገለጽ ይችላል። አት: - “በሕጉ ምክንያት እንዳይረገም” ወይም “ህጉን ባለመታዘዙ የተረገመ”

ለእኛ እርግማን በመሆን
“እርግማን” የሚለው ስም “እርግማን” ከሚለው ግስ ጋር ሊገለጽ ይችላል። አት: - “ለእኛ በመረገምን” ወይም “በእኛ ፋንታ እግዚአብሔር ሲረገም” (የበለስ_ቁጥር መግለጫዎችን ይመልከቱ)

ከሕጉ እርግማን ... ለእኛ እርግማን ሆነ ... ሁሉም ሰው የተረገመ ነው
እዚህ ላይ የተረገመ እርግማን የተወገዘ መሆኑን ያሳያል ። አት: - “በሕግ ከመኮነን... በእኛ ፋንታ የተወገዘ... ሁሉም የተወገዘ ነው” (ይመልከቱ ። የበለስ_ቁጥር)

በዛፍ ላይ ተንጠልጥሏል
ጳውሎስ አድማጮቹ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ስለ ተሰቀለው እየተናገረ መሆኑን ይገነዘባሉ ።

ሊሆን ይችላል
ይሆናል

እኛ
“እኛ” የሚለው ቃል ደብዳቤውን የሚያነቡ ሰዎችን ያካትታል ። (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)

Galatians 3:15

ወንድሞች
ይህንን በ 1 1 ውስጥ ተርጉም ።

በሰዎች አነጋገር
“እንደ ሰው” ወይም “ብዙ ሰዎች ከሚረዱት”

አሁን
ይህ ቃል ጳውሎስ አጠቃላይ መርህ እንደገለጠ እና አሁን አንድ የተወሰነ ጉዳይ ለማስተዋወቅ መጀመሩን ያሳያል ።

ብዙዎችን ይጠቅሳል
"ብዙ ዘሮችን መጥቀስ"

ለዘሮችህ
“የአንተ” የሚለው ቃል ነጠላ ሲሆን የሚያመለክተው የተወሰነ የአብርሃም ዘር የሆነውን (እና ያ ዘር ደግሞ “ክርስቶስ” ተብሏል) ። ይመልከቱ: የበለስ_አዎ)

Galatians 3:17

ርስቱ በሕግ ቢሆንስ እንግዲያስ በተስፋ ቃል አይሆንም ፤ በተስፋ ቃል አይሆንም
ጳውሎስ እየተናገረ ያለው ውርስ የሚገኘው በተስፋ ቃል በኩል ብቻ መሆኑን ለማጉላት ስላልነበረ ሁኔታ ነው ። የ “የእግዚአብሔር ሕግን ማክበር ባለመቻላችን ርስታችን በተስፋው ቃል በኩል ሆኗል” (ይመልከቱ ። የበለስ_ሂፖ)

ውርስ
እግዚአብሔር ለአማኞች የገባውን ቃል መቀበል ከቤተሰብ አባል የርስት እና ሀብት ውርስ እና ዘላለማዊ በረከቶች እና ቤዛ እንደሆነ ተደርጎ ይገለጻል። (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)

Galatians 3:19

አያያዥ መግለጫ
ጳውሎስ በገላትያ ላሉት አማኞች እግዚአብሔር ህጉን ለምን እንደ ሰጣቸው ነግሯቸዋል ።

ታዲያ የሕጉ ዓላማ ምን ነበር?
ጳውሎስ ሊወያይበት የሚፈልገውን ቀጣዩን ርዕስ ለማስተዋወቅ አነጋገራዊ ጥያቄን ይጠቀማል ። እንደ መግለጫም ሊተረጎም ይችላል ። አት: - የሕጉ ዓላማ ምን እንደሆነ እነግርዎታለሁ ወይም “እግዚአብሔር ህጉን ለምን እንደሰጠ ልንገርዎ” (የበለስ_ቁጥር / ይመልከቱ)

ተጨምሯል
ይህ በንቃት ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “እግዚአብሔር አክሎታል” ወይም “እግዚአብሔር ህጉን ጨምሯል” (ይመልከቱ። የበለስ_ቁጥር / ይመልከቱ)

ሕጉ በመላእክት በኩል አስታራቂ ሆነ
ይህ በንቃት ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “እግዚአብሔር ሕጉን በመላእክት እገዛ አወጣ ፣ አስታራቂም ሥራ ላይ አደረገው” (ይመልከቱ። የበለስ_ቁጥር)

አስታራቂ
"የሚወክል"

አሁን አስታራቂ ከአንድ ሰው በላይ የሚናገር ሲሆን እግዚአብሔር አንድ ነው
እግዚአብሔር ያለ አስታራቂ እግዚአብሔር ለአብርሃም ተስፋውን ሰጠው ፣ ግን ሕጉን ለሙሴ ግን አስታራቂ ሰጠ ። በዚህ ምክንያት ፣ የጳውሎስ አንባቢዎች ሕጉ በሆነ መንገድ ቃል ኪዳኑን እንደማይፈጽም ያስቡ ይሆናል ። ጳውሎስ አንባቢዎቹ እዚህ ምን ሊያስቡበት እንደነበር እየገለጸ ነው ፣ በሚቀጥሉት ጥቅሶችም ይመልሳል ።

Galatians 3:21

አጠቃላይ መረጃ
በዚህ ክፍል ውስጥ “እኛ” የሚለው ቃል ሁሉንም ክርስቲያኖችን ያመለክታል ። (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)

ላይ
“መቃወም” ወይም “በግጭት ውስጥ”

ሕግ ተሰጥቶ ቢሆን ኖሮ ሕይወት ይሰጣል
ይህ በንቃት ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ፣ እና ቀልብ ስሙ “ሕይወት” የሚለው “የቀጥታ” ከሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። አት: - “እግዚአብሔር የሚጠብቁት በሕይወት እንዲኖሩ የሚያደርግ ሕግ ከሰጠ” (የበለስ_ቁጥር እና የበለስ_ቁጥር ማስታወቂያ)

ጽድቅ በሕጉ ይመጣ ነበር
ያንን ሕግ በመታዘዝ ጻድቅ ልንሆን ይችል ነበር ”

ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉንም ነገር በኃጢአት ታስረዋል ። በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እኛን ለማዳን የገባው ቃል ለሚያምኑት እንዲሰጥ እግዚአብሔር ይህን አደረገ
ሌሎች ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ሁላችንም ኃጢአትን ስለምንሠራ ፣ በክርስቶስ ሁሉንም ለሚያምኑ የገባውን ቃል ለእምነት ለሚያምኑ ይሰጣቸዋል ፣ ሁላችንም ኃጢአት ስለሠራን እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር በሕግ ቁጥጥር ስር አደረገ ። ኃጢአት ስለሠራን እግዚአብሔር እስር ቤት እንዳስገባ ሁሉ ሁሉንም ነገር ከሕግ የበላይነት በታች አስቀመጠ ። ይህንን ያደረገው በክርስቶስ ኢየሱስ ለሚያምኑ የገባውን ቃል ለሚያምኑ ሁሉ ለመስጠት ይፈልጋል ። . "

መጽሐፍት
ጳውሎስ ጥቅስ እንደ ሰው አድርጎ የሚናገር ሲሆን ጥቅስ የጻፈውን እግዚአብሔርን ይናገራል ። አት: - “እግዚአብሔር” (ይመልከቱ: የበለስ_ኔሽን)

Galatians 3:23

አያያዥ መግለጫ
ጳውሎስ አማኞች በሕጉ ሥር ባሪያዎች ሳይሆኑ በአምላክ ቤተሰብ ውስጥ ነፃ መሆናቸውን ጳውሎስ በገላትያ ላሉት ሰዎች አሳስቧቸዋል።

በሕግ እስረኞች ተይዘናል
ይህ በንቃት ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - ህጉ እስረኞችን ይይዘናል እናም እስር ቤት ነበርን አሊያም "ህጉ በእስር ቤት ውስጥ ያዙን" (ይመልከቱ ። የበለስ_ቁጥር)

በሕግ እስረኞች ተይዘናል
ሕጉ በቁጥጥር ስር የዋለን የእስረኞች ጠባቂ አካል ሕጉ የሚገዛንበት መንገድ ተገልጻል ። አት: - “ህጉ እንደ እስር ቤት ጠባቂ ሆኖ ይቆጣጠርን ነበር” (ይመልከቱ ። የበለስ_ቁጥር)

እምነት እስከ ተገለጠ ድረስ
ይህ በንቃት ቅርፅ ሊገለጽ ይችላል ፣ እና ይህ እምነት ያለበት ማን በግልጽ ሊገለፅ ይችላል። በዚህ: - “እግዚአብሔር በክርስቶስ የሚያምኑትን እንደሚያጸድቅ እስከገለጠ ድረስ” ወይም “በክርስቶስ የሚያምኑትን

እንደሚያጸድቅ እስኪያሳይ ድረስ” (የበለስ_ቁጥር እና የበለስ_ቁጥር ግልፅ) ይመልከቱ

አሳዳጊ
“ለልጅ የበላይነት” ከሚለው በላይ ይህ ብዙውን ጊዜ በወላጅ የተሰጡትን ህጎች እና ባህሪዎች የማስፈፀም ሃላፊነት የተሰጠው እና በልጁ ድርጊቶች ላይ ለወላጅ ሪፖርት የሚያደርግ አገልጋይ ነው ።

ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ
ክርስቶስ እስከመጣበት ጊዜ ድረስ

እንጸድቅ ዘንድ ይህ ነው
ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት ፣ እግዚአብሔር እኛን ለማፅደቅ አቅዶ ነበር ። ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ፣ እኛን ለማፅደቅ ያለውን ዕቅዱን ፈፅሟል ። ይህ በንቃት ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - "እኛ እግዚአብሔር ጻድቃችንን ያሳውቀን ነበር" (የበለስ_ቁጥር / ይመልከቱ)

Galatians 3:27

እናንተ. . . ራሳችሁን በክርስቶስን ለብሳችኋል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “እርስዎ... ልክ እንደ ክርስቶስ አንድ ዓይነት ሰው ሆነዋል” (UDB) ወይም 2) “እርስዎ... ልክ እንደ እግዚአብሔር ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ዓይነት ግንኙነት አለዎት” ። (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)

አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው ፣ ባሪያ ወይም ነፃ ፣ ወንድ ወይም ሴት የለም
እግዚአብሔር በአይሁድና በግሪክ ፣ በባሪያና በነጻ ፣ ወንድና ሴት መካከል ምንም ልዩነት የለውም ።

ወራሾች
እግዚአብሔር ቃል የገባላቸው ሰዎች ንብረትንና ሀብትን ከቤተሰብ አባል እንደሚወርሱ ተደርገው ይወሰዳሉ ። (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 4

1 ያን የምለው ህጻን ሳለ ምንም እንኳ ሁሉም የእርሱ ቢሆንም ወራሹ ከባሪያ አይለይም። 2 ነገር ግን አባቱ የወሰነልት ቀን እስኪደርስለት ድረስ
በተንከባካቢዎቹና በሞግዚቶቹ ስር ይቆያል። 3 እኛም ልጆች ሳለን በዚህ ዓለም ዋና ትምህርቶች እስራት ሥር ነበርን። 4 ነገር ግን በትክክለኛው ጊዜ
እግዚአብሔር በህግ ሥር ያሉትን 5 ነጻ እንዲያወጣና የልጅነትን መብት እንዲኖረን ከሴት የተወለደውንና በህግ ሥር የተወለደውን ልጁን ላከ። 6 ልጆች
ስለሆናችሁ «አባ አባት» እያለ የሚጣራውን የልጁን መንፈስ ወደ ልባችን ላከ። 7 በዚህም ምክንያት ከእንግዲህ ልጆች እንጂ ባሮች አይደላችሁም፥ ልጆች
ከሆናችሁ ደግሞ የእግዚአብሔር ወራሾች ናችሁ። 8 ነገር ግን እግዘአብሔርን በማታውቁበት በቀድሞው ዘመን በባህሪያቸው ፈጽሞ አማልክት ላልሆኑት
ተገዝታችሁ ኖራችሁ። 9 አሁን ግን እግዚአብሔርን አውቃችኋል ይልቁኑም በእግዚአብሔር ታውቃችኋል፥ ታዲያ እንዴት ወደ ደካማና ዋጋ ወደሌለው የዚህ ዓለም
ዋና ትምህርት ተመለሳችሁ።እንደገና ባሮች መሆን ትፈልጋላችሁ? 10 ልዩ ቀናትን፥አዳዲስ ጨረቃዎችን፥ ወራትና ዓመታትን ታመልካላችሁ። 11 ስለ እናንተ
የደከምኩት ድካም ከንቱ ሆኖብኝ እንዳይሆን ብዬ እፈራለሁ። 12 ወንድሞች ሆይ ልክ እኔ ለእናንተ እንደምሆነው እናንተም ለእኔ እንደዚያው እንድትሆኑ
እለምናችኋለሁ። 13 ምንም ክፉ አላደርጋችሁብኝም ነገር ግን ወንጌልን በመጀመሪያ በሰብኩላችሁ ጊዜ የሥጋ ህመም አሞኝ እንደነበረ ታውቃላችሁ። 14
በሥጋዬ ላይ የነበረው ለእናንተ ከባድ ፈተና ቢሆንም አልተጸየፋችሁኝም አልጣላችሁኝምም፥ ይልቁኑ እንደ እግዚአብሔር መልአክ ወይም ክርስቶስን
በተቀበላችሁብት አቀባበል ተቀበላችሁኝ። 15 አሁን ደስታችሁ በምንድነው? ዓይናችሁን እንኳ አውጥታችሁ ልትሰጡኝ ፈቃደኛ እንደነበራችሁ እኔ ራሴ ምስክር
ነኝ። 16 ታዲያ እውነትን ስለነገርኳችሁ የእናንተ ጠላት ሆንኩ ማለት ነው? 17 አጥበቀው ይፈልጓችኋል ነገር ግን ለመልካም አይደለም። እነርሱን እንድትከተሉ
ከእኔ ሊለዩዋችሁ ይፈልጋሉ። 18 እኔ ከእናንተ ጋር ስሆን ብቻ ሳይሆን ሁልጊዜ ለመልካም ነገር መትጋት ተገቢ ነው። 19 ጨቅላ ልጆቼ ሆይ ክርስቶስ
በውስጣችሁ እስኪቀረጽ ድረስ ስለእናንተ ምጥ ይዞኛል! 20 የእናንተ ነገር ግራ ስለገባኝ በመካከላችሁ ተገኝቼ በቁጣ ልናገራችሁ እመኛለሁ። 21 እስኪ እናንተ
በህግ ሥር ለመሆን የምትፈልጉ ንገሩኝ ህጉ ምን እንደሚል አልሰማችሁምን? 22 አብርሃም አንድ ባሪያ ከነበረች ሴት አንድ ደግሞ ነጻ ከነበረች ሴት የተወለዱ
ሁለት ልጆች እንደነበሩት ተጽፏል። 23 ነገር ግን ከባሪያይቱ የተወለደው በሥጋ ብቻ የተወለደ ነው፥ ከነጻይቱ የተወለደው ግን በተስፋ የተወለደ ነው። 24 እነዚህ
ነገሮች እንደ ምሳሌ ሊገለጹ ይችላሉ።እነኚህ ሴቶች እንደ ሁለቱ ቃል ኪዳኖች ናቸው፥ አንደኛዋ በሲና ተራራ የተሰጠውንና ባርነትን የወለደውን ታመለክታለች፥
እርሷም አጋር ናት። 25 እንግዲህ አጋር በአረቢያ ምድር የሚገኘው የሲና ተራራ ስትሆን ከልጆቿ ጋር በባርነት የምትኖረውን የአሁኗን ኢየሩሳሌምን ትወክላለች።
26 ነገር ግን እናታችን የሆነችው ላይኛይቱ ጽዮን ነጻ ነች። 27 ምክንያቱም እንዲህ ተብሎ ተጽፏል «አንቺ ያልወለድሽና መካን የሆንሽ ሴት ሀሴት አድርጊ፥አንቺ
መውለድን ያልተለማምድሽ ውጪና በደስታ ጩኺ፤ ባል ካላቱ ይልቅ የመካኗ ልጆች በዝተዋልና»። 28 እንግዲህ እናንተ ወንድሞቼ እንደ ይስሀቅ የተስፋ ልጆች
ናችሁ። 29 ነገር ግን እንደ ሥጋ ፈቃድ የተወለደው እንደ መንፈስ ፈቃድ የተወለደውን እንዳሳደደው አሁንም እየሆነ ያለው እንደዚያው ነው። 30 መጽሀፍ ስለዚህ
ነገር ምን ይላል«የባሪያይቱ ልጅ ከነጻይቱ ልጅ ጋር አይወርስምና ባሪያይቱንና ልጇን አስወጣ»። 31 ስለዚህ ወንድሞች ሆይ እኛ የነጻይቱ እንጂ የባሪያይቱ
ልጆች አይደለንም።

Galatians 4:1

አያያዥ መግለጫዎች
ጳውሎስ በሕጉ ሥር ያሉትን ለማዳን ክርስቶስ እንደመጣ ፣ እና ከእንግዲህ ልጆች ባሪያዎች እንዳልሆኑ አድርጎ ለገላትያ አማኞች ማሳሰብ ቀጥሏል ::

ከ ምንም የተለየ
"ተመሳሳይ"

አሳዳጊዎች
ለህፃናት ህጋዊ ኃላፊነት ያላቸው ሰዎች

ባለአደራዎች
ዋጋ ያላቸው እቃዎችን ደህንነት ለመጠበቅ ሌሎች ሰዎች የሚያምኗቸው ሰዎች

Galatians 4:3

አጠቃላይ መረጃ
እዚህ እኛ “እኛ” የሚለው ቃል የጳውሎስን አንባቢዎችንም ጨምሮ ሁሉንም ክርስቲያኖች ያመለክታል :: (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)

የዓለም መሠረታዊ መርሆዎች
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ የአለም ህጎችን ወይም የሞራል መርሆዎችን ይመለከታል ፣ ወይም 2) ይህ የሚያመለክተው አንዳንድ ሰዎች በምድር ላይ የሚሆነውን የሚቆጣጠሩትን መንፈሳዊ ሀይል ነው።

ማስመለስ
ጳውሎስ የጠፋውን ንብረት በመግዛት ወይም የባሪያን ነፃ በመግዛት ምሳሌያዊ ምሳሌ ተጠቅሞ በመስቀል ላይ በመሞት ኢየሱስ ለህዝቡ ኃጢአት የከፈለውን ምስል ያሳያል :: (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)

ልጅ
ይህ የእግዚአብሔር ልጅ ለኢየሱስ አስፈላጊ ርዕስ ነው :: (መመሪያዎችን ይመልከቱ) መመሪያዎች_ሶፍትዌር መመሪያዎች

Galatians 4:6

ልጆች ናችሁ... ከእንግዲህ ወዲህ ወንድ ልጅ አይደለሁም
እዚህ ላይ ጳውሎስ ቃሉን የተጠቀመበት ለወንድ ልጅ ነው ምክንያቱም ርዕሰ ጉዳዩ ውርስ ነው። በባህሉ እና በአንባቢዎቹ ዘንድ ፣ ውርስ በተለምዶ ፣ ግን ሁልጊዜ ለወንዶች ልጆች ያልፋል :: እሱ እዚህ የሴቶች ሕፃናትን አልገለጸም ወይም አልገለጸም ::

“አባ አባት ሆይ” ብሎ የሚጠራ የልጁን መንፈስ በልባችን ውስጥ ልኮታል ::
እግዚአብሔር አብ የእግዚአብሄርን ልጅ መንፈስ ወደ አማኞች ልብ ልኮታል :: እግዚአብሔር ሁል ጊዜ እንደሚወዳቸው ያውቃሉ ልክ እንደዚህ ደግ አባት ልጆቹን ይወዳል ::

የልጁን መንፈስ ወደ ልባችን ልከውናል
ልብ ለሚያሰበው እና ለሚሰማው ሰው ልብ ዘይቤ ነው :: አት: - "እንዴት ማሰብ እና እርምጃ መውሰድ እንዳለብን እንዲያሳይን የልጁን መንፈስ ልኮ ነበር" (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)

ልጁ
ይህ የእግዚአብሔር ልጅ ለኢየሱስ አስፈላጊ ርዕስ ነው ። (መመሪያዎችን ይመልከቱ) መመሪያዎች_ሶፍትዌር መመሪያዎች

የሚጠራችሁ
የሚጠራው መንፈስ ነው ።

አባ ፣ አባት
አንድ ትንሽ ልጅ አባቱን በጳውሎስ ቤት ቋንቋ ለአባቱ የሚናገርበት መንገድ ይህ ነው ፣ በገላትያ አንባቢዎች ቋንቋ ግን አይደለም ። የውጪ ቋንቋን ስሜት ለመጠበቅ ይህንን ቋንቋዎ “አባ” ከሚለው ጋር የሚመሳሰል ድምጽን ይተርጉሙ ።

ከእንግዲህ ወዲህ ባርያ አይደለህም... ደግሞም ወራሽ ነህ
ጳውሎስ አንባቢዎቹን አንድ ሰው እንደሆኑ አድርጎ እያነጋገራቸው ነው ፣ ስለዚህ “እርስዎ” እዚህ ነጠላ ነው ። (ይመልከቱ: የበለስ_ዮዎ)

ወራሽ
እግዚአብሔር ቃል የገባላቸው ሰዎች ንብረትንና ሀብትን ከቤተሰብ አባል እንደሚወርሱ ተደርገው ይወሰዳሉ ። (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)

Galatians 4:8

አያያዥ መግለጫ
ጳውሎስ የገላትያ አማኞችን በእምነት በእምነት ከመኖር ይልቅ እንደገና በእግዚአብሔር ሕጎች ስር እንደገና እንደሚሞክሩ አሳስቧቸዋል ።

አጠቃላይ መረጃ
ገለልተኛ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ገላትያዎችን መገሰሱን ቀጥሏል ።

የሆኑት
“እነዚያ እነዚያ” ወይም “እነዚያ መናፍስት”

በእግዚአብሔር ታውቀዋል
ይህ በንቃት ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “እግዚአብሔር ያውቅሃል” (የበለስ_ቁጥር / ተመልከት)

ወደ... መርሆዎች እንዴት ይመለሳሉ?
ይህ ከሁለቱም የአጻጻፍ ጥያቄዎች የመጀመሪያው ነው ። አት: - “ወደ... መርሆዎች” መመለስ የለብዎትም ። (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)

መሠረታዊ መርሆዎች
ይህንን ሐረግ በ 4:3 ውስጥ እንደተረጉሙት በተመሳሳይ መንገድ ይተርጉሙ ።

እንደገና እንደገና በባርነት መሆን ይፈልጋሉ?
ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። አት: - "እንደገና ባሪያዎች መሆን የለብዎትም!" ወይም እንደገና ባሪያዎች መሆን የሚፈልጉ ይመስላል። (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)

Galatians 4:10

ቀናት እና አዲስ ጨረቃዎችን ፣ ወቅቶችን እና አመታትን ይመለከታሉ
ጳውሎስ እየተናገረ ያለው የተወሰኑ ጊዜዎችን ለማክበር ጥንቃቄ እንዳላቸው በማሰብ ነው ፣ ይህም ያንን ማድረጉ በእግዚአብሔር ፊት ትክክለኛ ያደርገዋል ። አት: - “ቀኖችን ፣ አዲስ ጨረቃዎችን ፣ ወቅቶችን እና ዓመቶችን በጥንቃቄ ታከብራላችሁ”

ምናልባት በከንቱ ሊሆን ይችላል
«ምንም ላይጠቅሙ ይችሉ ነበር» ወይም «ምንም ዓይነት ተፅእኖ አልደረሰም»

Galatians 4:12

አያያዥ መግለጫ
ጳውሎስ የገላትያ አማኞችን አብሯቸው በነበረበት ጊዜ እንዴት በደግነት እንዴት እንደያዙቸው የሚያስታውስ ሲሆን አብሯቸው በማይኖርበት ጊዜ በእሱ መታመናቸውን እንዲቀጥሉ አበረታቷቸዋል ።

መለመን
እዚህ ማለት በጥብቅ መጠየቅ ወይም መሻር ማለት ነው ። ይህ ገንዘብን ወይም ምግብን ወይም ቁሳዊ ቁሳቁሶችን ለመጠየቅ የሚያገለግል ቃል አይደለም ።

ወንድሞች
በ1፡1 ላይ እንዳለው ተርጉሙት

ምንም ጥፋት አላደረገብኝም
ይህ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “መልካም አደረግከኝ” ወይም “እንደቻልሽ አደረግከኝ”

ምንም እንኳን አካላዊ ሁኔታዎ ሊፈተን ቢችልም
“በአካላዊ ህመም ብታየኝ ለእኔ ከባድ ቢሆንም”

መናቅ
እጅግ መጥላት

Galatians 4:17

እናንተን ለማሳመን
እነሱን እንዲቀላቀሉ ለማሳመን "

ለመከላከል
"እኛን እንዳያሳየን" ወይም "ለእኛ ታማኝ አለመሆንን እንዲያቆም"

ለእነሱ ቀንቻለሁ
“የምታደርጉትን ሁሉ ለማድረግ በቅናት”

Galatians 4:19

አያያዥ መግለጫ
ፀጋ እና ህግ አብረው ሊሠሩ እንደማይችሉ ጳውሎስ ለአማኞች ይነግራቸዋል ።

ልጆቼ
ይህ ለደቀመዛምርቶች ወይም ለተከታዮች ዘይቤ ነው ። አት: - “በእኔ ምክንያት እናንተ ደቀመዛሙርቶች ናችሁ” (የበለስ_ማይታፎርን ይመልከቱ)

ክርስቶስ በውስጣችሁ እስኪመሠረት ድረስ በእናንተ ላይ ገና በወሊድ ሥቃይ ውስጥ ነኝ
ጳውሎስ ልጅ መውለድን ለገላትያ ሰዎች አሳቢነት ለማሳየት እንደ ዘይቤ ነው ። AT: - “አንቺን መውለድ የምችል ሴት እንደሆንኩ ያህል ህመም ይሰማኛል እናም ክርስቶስ በእውነት እስከሚቆጣጠርዎ ድረስ በሥቃዬ እቀጥላለሁ” (የበለስ_አሜን)

Galatians 4:21

ንገሩኝ
"አንድ ጥያቄ መጠየቅ እፈልጋለሁ" ወይም "የሆነ ነገር ልነግርዎት እፈልጋለሁ"

ሕግን አትሰሙምን?
ጳውሎስ ቀጥሎ ምን እንደሚል እያስተዋወቅ ነው። አት: - "ህጉ በትክክል ምን እንደሚል መማር ያስፈልግዎታል" ወይም "ህጉ በትክክል ምን እንደሚል ልንገራችሁ" (የበለስ_ቁስለትን ይመልከቱ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Galatians 4:24

አያያዥ መግለጫ
ጳውሎስ አንድን እውነት ለመግለጽ ታሪክ ይጀምራል-ያ ሕግ እና ጸጋ አብረው ሊኖሩ አይችሉም ::

እነዚህ ነገሮች እንደ ምሳሌ ሊተረጎሙ ይችላሉ
ይህ የሁለቱ ልጆች ታሪክ እኔ አሁን የምነግራችሁን ስዕል ነው ”

እንደ ምሳሌ
“አመላካች” ማለት ሰዎች እና በውስጡ ያሉ ሌሎች ነገሮች የሚወክሉበት ታሪክ ነው :: በጳውሎስ ዘገባ ፣ በ 4 21 ውስጥ የተጠቀሱት ሁለቱ ሴቶች ሁለት ቃል ኪዳኖችን ይወክላሉ።

ሲና ተራራ
‹በሲና ተራራ› ሙሴ እዚያ ለነበሩ እስራኤላውያን የሰጠው ሕግ የሕግ ማሳያ ነው :: አት: - "ሙሴ ለእስራኤል ሕግን የሰጠበት በሲና ተራራ ላይ" (የበለስ_ስኔክዶቼን ይመልከቱ)

ባሪያዎች የሆኑ ልጆችን ትወልዳለች
ጳውሎስ ህጉን እንደ ሰው አድርጎ ይመለከታል። አት: - “በዚህ ቃል ኪዳን ስር ያሉ ሰዎች ሕጉን እንደሚታዘዙ ባሪያዎች ናቸው” (የበለስ_ቁጥር እና የበለስ_ቁጥር) ተመልከት

ይወክላል
"ስዕል ነው"

ከልጆ. ጋር በባርነት ውስጥ ናት
አጋር አጋርና ልጆችዋ ከእሷ ጋር ባሪያዎች ናቸው :: አት: - እንደ ኢየሩሳሌም እንደ ገዛ ባሪያ ናት ፣ ልጆችዋም ከእሷ ጋር ባሪያዎች ናቸው (ይመልከቱ :: የበለስ_ለታ)

Galatians 4:26

ነፃ
እዚህ “ነፃ” ማለት የታሰረ እንጂ ባርያ አይደለም።

ደስ ይበላችሁ
"ደስተኛ ሁኑ"

አንቺ መካን ያልሽ... አንቺ የማትሠቃይ
እዚህ “እርስዎ” መካን ሴትን ያመለክታል እና ነጠላ ነው። (ይመልከቱ: የበለስ_ዮዎ)

Galatians 4:28

ወንድሞች
በ1፡1 ላይ እንዳለው ተርጉሙት

የተስፋ ቃል ልጆች
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች ገላትያኖች የእግዚአብሔር ልጆች ሆነዋል 1) በእግዚአብሔር ቃል በማመን (UDB) ወይም 2) እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባውን ቃል ለመፈፀም ተዓምራትን ስለ ሠራ በመጀመሪያ በመጀመሪያ ለአብርሃም ወንድ ልጅን ከዚያም ገላትያንም የአብርሃምን ልጆች በመፍጠር እና ስለሆነም የእግዚአብሔር ልጆች ::

እንደ ሥጋ ፈቃድ
ይህ የሚያመለክተው አጋርን ሚስት አድርጎ በመውሰድ አብርሃም የእስማኤል አባት መሆንን ነው :: አት: - “በሰው ድርጊት” ወይም “ሰዎች በሠሩት ነገር ምክንያት” (ይመልከቱ።

እንደ መንፈስ ቅዱስ
“መንፈስ ቅዱስ በሆነ ነገር”

Galatians 4:30

ወንድሞች
በ1፡1 ላይ እንዳለው ይተርጉሙ

ከነፃይቱ ሴት ይልቅ
የቀሩትን ቃላት እዚህ ውስጥ መሞላት ይቻላል :: ግን ይልቁን እኛ የነፃይቱ ሴት ልጆች ነን ”(ይመልከቱ :: የበለስ_ሊሲስ)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 5

1 ክርስቶስ ነጻ ያወጣን በነጻነት እንድንኖር ነው ። ስለዚህ ጸንታችሁ ቁሙ፥ እንደገና በባርነት ቀንበር አትጠመዱ። **2** እኔ ጳውሎስ የምለውን ተመልከቱ ብትገረዙ ክርስቶስ በምንም ዓይነት መልኩ አይጠቅማችሁም። **3** የተገረዘ ሁሉ ህግን ሁሉ የመፈጸም ግዴታ አለበት ብዬ እንደገና እመሰክራለሁ። **4** በህግ ልትጸድቁ የምትደክሙ ሁላችሁ የእግዚአብሔር ጠላቶች ሆናችኋል፤ከጸጋም ርቃችኋል። **5** ምክንያቱም እኛ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የጽድቅን ዋስትና ስለምንጠብቅ ነው። **6** በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍቅር የሆነ እምነት እንጂ መገረዝም ሆነ አለመገረዝ ምንም ትርጉም የለውም። **7** በጥሩ ሁኔታ ትሮጡ ነበር። ታዲያ ለእውነት ከመታዘዝ ያስቆማችሁ ማነው? **8** ይህን እንድታደርጉ የሚያደርግ ጉትጎታ ከጠራችሁ የመጣ አይደለም። **9** ትንሽ እርሾ ሊጡን በሙሉ እንዲቦካ ያደርጋል። **10** በሌላ መልኩ እንደማታስቡ በጌታ እተማመንባችኋለሁ። ግራ የሚያጋባችሁ ማንም ይሁን ማን ፍርዱን ይቀበላል። **11** ወንድሞች ሆይ እስከአሁን ተገረዙ እያልኩ የምሰብክ ቢሆን ለምን እሰደድ ነበር? እንግዲያውስ የመስቀሉ እንቅፋት ይደመሰሳል። **12** የሚያስቷችሁ እራሳቸው ሄደው በተሰለቡ ብዬ እመኛለሁ። **13** ወንድሞች ሆይ እግዚአብሔር የጠራችሁ ለነጻነት ነው። ብቻ ነጻነታችሁን ለሥጋ ፈቃድ አትጠቀሙበት፥ በዚያ ፈንታ እርስ በእርሳችሁ በፍቅር አንዳችሁ አንዳችሁን አገልግሉ። **14** ምክንያቱም ህግ ሁሉ «ባልንጀራህን እንደራስህ ልትወድ ይገባል» **15** በሚለው ትዕዛዝ የተጠቀለለ ነው። **16** በመንፈስ ተመላለሱ የሥጋን ክፉ ምኞት አትፈጽሙ እላችኋለሁ። **17** ምክንያቱም ሥጋ ከመንፈስ ተቃራኒ መንፈስም ከሥጋ ተቃራኒ ነገር ይመኛሉና ነው። **18** እነዚህ እርስ በእርሳቸው ስለሚቀዋወሙ በውጤቱ እናንተ የምትፈልጉትን ለማድረግ አትችሉም። **19** እንግዲህ የሥጋ ስራዎች የተገለጡ ናቸው። እነዚህም አስቀድሜ እንዳስጠነቀኩዋችሁ **20** ዝሙት፣እርኩሰት፣ክፉ ምኞት፣ጣዖትን ማምለክ፣ምዋርት፣ጥል፣ክርክር፣ቅናት፣ በቁጣ መገንፈል፣አድመኛነት፣መለያየት፣ **21** መናፍቅነት፥ ምቀኝነት፥ መግደል፥ስካር፥ ዘፋኝነትና የመሳሰሉት ናቸው፥ ፥አስቀድሜ እንደነገርኳችሁ እነዚህን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም። **22** የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፣ ሠላም፣ ትዕግሥ፣ ቸርነት፥ መልካምነት፥ እምነት፥ **23** የውሃት፥ ራስን መግዛት ናቸው። ህግ እነዚህን አይቃወም። **24** የክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑት ሥጋን ከክፉ ስሜቱና መሻቱ ጋር ሰቅለውታል። **25** በመንፈስ የምንኖር ከሆነ በመንፈስ እንመላለስ። **26** አንታበይ፣ እርስ በእርሳችን ለክፉ አንነሳሳ፣ አንቀናና።

Galatians 5:1

አያያዥ መግለጫ
ሁሉም ሕጎች እንደ እኛ ጎረቤቶቻችንን በመውደድ የተሟላ በመሆኑ ክርስቶስ አማኞች በክርስቶስ ነፃነታቸውን እንዲጠቀሙ በማስታወስ ይህንን ምሳሌ ተጠቅሟል ።

ለነፃነት
በቀደሙት ቁጥሮች ላይ ከተገለፀው ባርነት በተቃራኒ ትርጉሙ “ነፃነት” ን ማጉላት አለበት ።

ለነፃነት ክርስቶስ ነፃ አወጣን
ክርስቶስ ነፃ ያወጣን ነፃ እንድንሆን ነው ።

ጸንታችሁ ቁሙ
እዚህ ላይ ቆመ ማለት ላለመቀጠል መወሰንን ያሳያል ። እንዴት እንደማይቀየሩ በግልፅ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “ሌላ ነገር ለሚያስተምሩ ሰዎች ክርክር አይስጡ” ወይም “ነፃ ለመሆን ቁርጥ ውሳኔ ያድርጉ” (የበለስ_ቁጥር እና የበለስ_ቁጥር ግልፅ) ይመልከቱ

እንደትገረዙ ብትፈቅዱ
ጳውሎስ ግርዘትን ለአይሁድ እምነት ምሳሌ አድርጎ ይጠቀማል። አት: - "ወደ የአይሁድ ሃይማኖት ብትመለሱ" (የበለስ_ቁጥር ተመልከት)

Galatians 5:3

መመስከር
“አውጁ” ወይም “ምስክርነት”

ለተገረዘ ሰው ሁሉ ይገረፋል
ጳውሎስ መገረዝ አይሁዳዊ ለመሆን እንደ ተመሳሳዩን ቃል ይጠቀማል። አት: - “አይሁዳዊ ለሆነ ሰው ሁሉ” (የበለስ_ቁጥር ተመልከት)

ግዴታ
“የታሰረ” ወይም “የታገደ” ወይም “የባርነት”

ከክርስቶስ ተለይተዋል
“ከክርስቶስ ጋር የነበረሽን ግንኙነት ጨርሰሻል”

በሕግ ልትጸድቁ የምትፈልጉ ከክርስቶስ ተለይታችሁ ከጸጋው ወድቃችኋል
እዚህ ላይ ጳውሎስ እዚህ ላይ እየተናገረ ነው ። በሕግ የተጠየቀውን ነገር ለማድረግ በመሞከር ማንም አይሁዳዊ ጻድቅ ሊሆን እንደማይችል በእውነት አስተምሯል ። አት: - “በሕግ የተጠየቀውን በማከናወን እናንተ ጻድቅ ትሆናላችሁ የምትሉ ሁሉ” ወይም “በሕግ ልትጸድቁ የምትፈልጉ” (ይመልከቱ ። የበለስ.

ከእንግዲህ ጸጋን አታገኝም
ያ ጸጋ ከየት እንደመጣ በግልፅ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “እግዚአብሔር አይራራዎትም” (የበለስ_ቁጥር ይመልከቱ)

Galatians 5:5

አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ላይ እኛ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስንና የክርስቲያኖችን ግርዘት የሚቃወሙትን ነው ። እሱ ምናልባት ገላትያዎችን ጨምሮ ሊሆን ይችላል። (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)

ለ
ይህም የሆነው ምክንያቱ

እኛ የጽድቅን ተስፋ በእምነት በጉጉት እንጠባበቃለን
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “እኛ ስለ እምነት የጽድቅ ተስፋ በእምነት እንጠብቃለን” ወይም 2) “በእምነት የሚመጣውን ትክክለኛውን የጽድቅ ተስፋ እንጠብቃለን” ።

እኛ የጽድቅን ተስፋ በጉጉት እንጠብቃለን
"እግዚአብሔር ሁልጊዜ ከራሱ ጋር እንዲያጸናን በትዕግሥት እና በትዕግሥት እየጠበቅን ነው ፣ እናም እርሱ እንደሚያደርገው እንጠብቃለን"

መገረዝ ወይም አለመገረዝ አይጠቅምም
እነዚህ አይሁዶች ወይም አይሁዳዊ ያልሆኑ መሆናቸው መገለጫዎች ናቸው ። አት: - “አይሁዳዊም ሆነም አይሁዳዊ አለመሆን” (ይመልከቱ ።

ፍቅር ግን በእምነት ብቻ ነው ፤
"ይልቁንም ሌሎችን በመውደድ የምናሳየው እግዚአብሔር በእርሱ ላይ ያለን እምነት ያሳስበዋል"

ማንኛውም ነገር ማለት ነው
የሚጠቅም ነው

እየሮጡ ነበር
“ኢየሱስ ያስተማረውን ተግባራዊ እያደረጉ ነው”

ይህ ማበረታቻ ከሚጠራችሁ አልወጣም
“ይህን እንድታደርግ ያሳመነሽ እግዚአብሔር አይደለም ፣ እርሱም የሚጠራው”

የሚጠራችሁ
የጠራቸው ምን እንደሆነ በግልጽ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “እናንተ የእሱ ሕዝብ እንድትሆኑ የሚጠራችሁ” (የበለስ_ቁጥር ይመልከቱ)

ማሳመን
አንድን ሰው ማሳመን ማለት ያመነውን እንዲለውጥ እና በተለየ መንገድ እርምጃ እንዲወስድ ማድረግ ነው ።

Galatians 5:9

ሌላ እይታ አይወስዱም
እኔ የምነግራችሁን ከነገርዎት የተለየ ነገር አያምኑም ”

የሚያስጨንቃችሁ ሰው ቅጣቱን ይከፍላል
የሚያስጨንቅህን እግዚአብሔር ይቀጣል "

የሚያውክህ
“እውነቱን እንድታውቁ ያደርጋችኋል” ወይም “በመካከላችሁ ችግር ያስነሳል”

ማንም ቢሆን
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች የሙሴን ሕግ መታዘዝ እንዳለባቸው የሚናገሩትን ሰዎች ስም አያውቅም ወይም 2) ጳውሎስ የገላትያ ሰዎች “ግራ የሚያጋቡ” ሀብታሞች መሆን አለመሆናቸውን እንዲገነዘቡ አልፈለገም ። ድሃ ወይም ትልቅ ወይም ትንሽ ወይም ሀይማኖት ወይም ሃይማኖተኛ ያልሆነ

Galatians 5:11

ወንድሞች ፣ እኔ አሁንም ስለ መገረዝ ብሰብክ አሁንም ለምን ስደት ይደርስብኛል?
ጳውሎስ ሰዎች እየሰደዱበት መሆኑን አፅን emphasizeት ለመስጠት የሌለበትን ሁኔታ እየገለጸ ነው ምክንያቱም ሰዎች አይሁድ መሆን አለባቸው ብለው እየሰበከ አይደለም ። ይህ በንቃት ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። AT: - “ወንድሞች ፣ እኔ ገና አይሁዳውያን ስደት እያደረሱብኝ ስለ መገረዝ እንዳልናገር ታውቃላችሁ ።” (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር እና በለስ_ማቶ)

ወንድሞች
በ1፡1 ላይ እንዳለው ተርጉሙት

እንደዚያ ከሆነ የመስቀል ዕንቅፋት ተወግዷል
ጳውሎስ ሰዎች በመስቀል ላይ ባከናወኑት ሥራ እግዚአብሔር ይቅር እንደሚል ስለሚሰብክ ሰዎች ስደት እንደሚያደርሱበት ለማጉላት በሌለበት ሁኔታ እየገለጸ ይገኛል ። (ይመልከቱ: የበለስ_ኪፖ)

እንደዚያ ከሆነ
“ሰዎች አሁንም አይሁዳውያን መሆን አለባቸው” እያልኩ ከሆነ

የመስቀሉ እንቅፋት ተወግዷል
ይህ በንቃት ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “ስለ መስቀሉ ማስተማር እንቅፋት የለውም” ወይም “የመስቀል ትምህርት ምንም ነገር የሚያሰናክል ነገር የለም” (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)

የመስቀሉ እንቅፋት ተወግዷል
ማሰናከል ኃጢያትን ይወክላል ፣ እና እንቅፋት ሰዎችን ወደ ኃጢአት የሚወስድ አንድ ነገርን ይወክላል። በዚህ ሁኔታ ኃጢያቱ በእግዚአብሔር ፊት ትክክል እንዲሆን ለማድረግ ፣ ሰዎች ለእኛ ኢየሱስ በመስቀል ላይ እንደሞተ ማመን ብቻ ያስፈልጋቸዋል የሚለውን አስተምህሮ እውነታውን አለመቀበል ነው ። አት: - “ሰዎች ስለ እውነት እንዲናገሩ የሚያደርጋቸው የመስቀል ትምህርት ተወግ "ል” ወይም “ኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞቱን አስመልክቶ ሰዎች ትምህርቱን እንዲተዉ የሚያደርጋቸው ምንም ነገር የለም” (የበለስ_ቁጥር እና የበለስ_ቁጥር ግልፅ)

ብልታቸውን ይቆረጡ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ቃል በቃል ፣ የወንዶች አካሎቻቸውን ለመቁረጥ ጃንደረቦች ወይም 2) ዘይቤያዊነት ፣ ከክርስቲያን ማኅበረሰብ ሙሉ በሙሉ ይርቃሉ ። (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)

Galatians 5:13

ለ
ጳውሎስ በ 5፡11 ውስጥ ለቃሉ የተናገረውን ምክንያት እየሰጠ ነው ።

ወደ ነፃነት ተጠርተዋል
ይህ በንቃት ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “እግዚአብሔር ወደ ነፃነት ጠራህ” (የበለስ_ቁጥር / ተመልከት)

ወደ ነፃነት ተጠርተዋል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ነፃ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ህዝቡ መረጠህ” ወይም 2) “ነፃ እንድትሆን እግዚአብሔር አዝዞሃል”

ወንድሞች
በ1፡1 ላይ እንዳለው ተርጉሙት

ለኃጢአተኛው ተፈጥሮ ዕድል
በእድሉ እና በኃጢያት ተፈጥሮ መካከል ያለው ግንኙነት ይበልጥ በግልፅ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “እንደ ኃጢያተኛ ተፈጥሮዎት ለመምሰል እድል ይሰጡዎታል” (ይመልከቱ። የበለስ_ቁጥር)

ሕግ ሁሉ በአንድ ቃል ይፈጸማል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “መላውን ሕግ በአንድ ትእዛዝ ብቻ መግለጽ ይችላሉ ፣ ይህ ነው” ወይም 2) “አንድን ትእዛዝ በመታዘዝ ፣ ሁሉንም ትእዛዛት ታደርጋላችሁ ፣ እና አንደኛው ትእዛዝ ይህ ነው።”

ጎረቤትህን እንደ ራስህ ውደድ
“እርስዎ” ፣ “የእርስዎ” እና “ራስዎ” የሚሉት ቃላት ሁሉም ነጠላ ናቸው ። (ይመልከቱ: የበለስ_ዮዎ)

Galatians 5:16

አያያዥ መግለጫ
ጳውሎስ ኃጢአት በኃጢያት ላይ ቁጥጥርን እንደሚሰጥ ጳውሎስ አብራርቷል ።

በመንፈስ ተመላለሱ
በእግር መሄድ የሕይወት ዘይቤ ነው ። አት-“ሕይወትዎን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይኑሩ” ወይም “ሕይወትዎን በመንፈስ ላይ በመመካት ኑሩ” (ይመልከቱ ። የበለስ_ቁጥር)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የኃጢያተኛ ተፈጥሮአዊ ፍላጎቶችን አታሟላም
“የአንድን ሰው ምኞቶች ማከናወን” የሚለው ሐረግ “አንድ ሰው የሚፈልገውን አድርግ” የሚል ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። አት: - “ኃጢአተኛ ተፈጥሮህ የሚፈልገውን አትፈጽምም” (የበለስ_ ቪዲዮን ተመልከት)

የኃጢያት ተፈጥሮ ምኞቶች
የኃጢያተኛው ተፈጥሮ ሰው ሆኖ ኃጢአት መሥራት እንደፈለገ ተደርጎ ተገልጻል። አት: - “በኃጢአተኛ ተፈጥሮህ ምን ማድረግ ትፈልጋለህ” ወይም “sinfulጢአት ስለሆንክ ምን ልታደርጋቸው ትፈልጋለህ?”

ከሕግ ስር አይደለም
'የሙሴን ሕግ የመታዘዝ ግዴታ አልነበረውም'

Galatians 5:19

የኃጢያት ተፈጥሮ ሥራዎች
“ሥራ” የሚለው የግሪክኛ ስም “እሱ” ከሚለው ግስ ጋር ሊተረጎም ይችላል። አት: - "የኃጢያት ተፈጥሮ ምን ያደርጋል"

የኃጢያት ተፈጥሮ ሥራዎች
የኃጢያተኛው ተፈጥሮ ነገሮችን የሚያደርግ የሚያደርግ ሰው ነው ተብሎ ተገልጻል። አት: - “ሰዎች በኃጢአታቸው ምክንያት የሚያደርጉት” ወይም “ሰዎች ኃጢአተኞች በመሆናቸው ምክንያት የሚያደርጉት” (ይመልከቱ። የበለስ_ከዋክብት)

መውርስ
ለአማኞች እግዚአብሔር ቃል የገባውን ቃል መቀበል ከቤተሰብ አባል ንብረትንና ሀብትን እንደሚወርስ ይገለጻል ። (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)

Galatians 5:22

የመንፈስ ፍሬ ፍቅር... ራስን መግዛት ነው
ቁጥጥር - ጳውሎስ ሰዎች በሌሎች ሰዎች ሊያዩት ለሚችሉት ዘይቤ እንደ ዘይቤ ይጠቀማል ። አት-መንፈስ ቅዱስ የሚቆጣጠራቸው ሰዎች ፍቅርን ይገልጣሉ ... እንደ ዛፍ ራስን መግዛትን ያፈራል "(ይመልከቱ ። የበለስ_ቁጥር) ።

የመንፈስ ፍሬ
"መንፈስ ምን ያፈራል"

የኃጢያተኛ ተፈጥሮውን በስሜቱ እና ፍላጎቱ ላይ ሰቀሉት
ጳውሎስ እንደ ሰው ስብዕና በኃጢያት ተፈጥሮአቸው ለመኖር ፈቃደኛ ያልሆኑ ክርስቲያኖችን ይናገራል ፣ እነሱ በመስቀል ላይ ስለገደሉት ። አት-“በመስቀል ላይ እንደገደሉት አድርገው ከኃጢያት ተፈጥሮው እና ፍላጎቱ ጋር ላለመመኘት እምቢ” (ይመልከቱ ። የበለስ_ቀፎ እና የበለስ_ቁጥር)

የኃጢያት ተፈጥሮ እና ፍላጎቶች እና ምኞቶች
የኃጢያት ተፈጥሮው ምኞት እና ምኞት ያለው ሰው እንደሆነ ተደርጎ ተገልጻል። አት: - “የኃጢአታቸው ተፈጥሮ ፣ እና በእሱ ምክንያት ለማድረግ በጣም የፈለጉት ነገር” (ይመልከቱ።

Galatians 5:25

በመንፈስ የምንኖር ከሆነ
"የእግዚአብሔር መንፈስ በሕይወት እንድንኖር አድርጎናል"

በመንፈስ ተመላለሱ
በየቀኑ "መራመድ" ዘይቤ ነው ። አት: - "እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን እና የምናከብርውን ነገር እናደርጋለን ፣ ስለሆነም መንፈስ ቅዱስ እንዲመራን ፍቀድልን" (የበለስ_ቁጥር ን ይመልከቱ)

እንፍቀድ
“አለብን”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 6

1 ወንድሞች ሆይ አንድ ሰው ስቶ ቢገኝ መንፈሳዊያን የሆናችሁ እናንት በጨዋነት መንፈስ ልታቀኑት ይገባል።ወደ ፈተና እንዳትገቡ ለራሳችሁም ተጠንቀቁ። 2 የእርስ በእርሳችሁን ሸክም በመሸካከም የክርስቶስን ህግ ፈጽሙ። 3 ምክንያቱም ማንም ምንም ሳይሆን ምንም እንደሆነ ቢያስብ ራሱን ያታልላል። 4 እያንዳንዱ ከሌላው ጋር ሳያነጻጽር የራሱን ሥራ ሊመዝን ይገባል፥ያን ጊዜ የሚመካበት ሊያገኝ ይችላል። 5 እያንዳንዱ የየራሱን ሸክም ይሸከማልና። 6 ቃሉን የሚማር ከመምህሩ ጋር ሁሉን ነገር ይካፈል ዘንድ ይገባዋል። 7 አትታለሉ እግዚአብሔር አይቀለድበትም።ሰው ምንም ነገር ቢዘራ ያንኑ ደግሞ ያጭዳል። 8 በሥጋው የሚዘራ ከሥጋው ውድቀትን ያጭዳል፤በመንፈስ የሚዘራ ግን ከመንፈስ የዘላለምን ህይወት ያጭዳል። 9 በተገቢው ጊዜ ፍሬውን እናጭዳለንና መልካምን ከመስራት አንቦዝን። 10 ስለዚህም ባገኘነው አጋጣሚ ሁሉ ለሰው ሁሉ በተለይም ለእምነት ቤተሰቦች መልካምን እናድርግ። 11 በገዛ እጅ ጽህፈቴ ምን ዓይነት ትልልቅ ቃላት እንደጻፍኩላችሁ ተመልከቱ። 12 እነዚያ በሥጋ መልካም መስለው የሚታዩ ስለክርስቶስ መስቀል መከራ ላለመቀበል ብለው እንድትገረዙ ያስገድዱዋችኋል።የተገረዙት እራሳቸው ህጉን አይጠብቁ፣ 13 ነገር ግን እናንተን እንድትገረዙ በማድረጋቸው ጉራ ለመንዛት እንድትገረዙ ይፈልጋሉ። 14 ዓለም ለእኔ ከተሰቀለበት እኔም ለዓለም ከተሰቀልኩበት ከክርስቶስ መስቀል በስተቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ። 15 አዲስ ፍጥረት መሆን እንጂ መገረዝም ሆነ አለመገረዝ ምንም አይጠቅምም። 16 በዚህ ሥርዓት ለሚሄዱ ሁሉ እንዲሁም የእግዚአብሔር ለሆነችው ለእስራኤል ሠላምና ምህረት ይሁን። 17 የክርስቶስን ምልክት በሥጋዬ ተሸክሜአለሁና ከእንግዲህ ማንም አይረብሸኝ። 18 ወንድሞች ሆይ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከመንፈሳችሁጋር ይሁን። አሜን!

Galatians 6:1

አያያዥ መግለጫ
ጳውሎስ አማኞችን ሌሎች አማኞችን እንዴት መያዝና እግዚአብሔር እንዴት ወሮታ እንደሚሰጥ አስተምሯቸዋል።

ወንድሞች
በ1:1 ላይ እንዳለው ተርጉሙት

አንድ ሰው
“አንድ ሰው” ወይም “ከመካከላችሁ ማንም”

በሆነ ኃጢአት ተይዟል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) አንድ ሰው በድርጊቱ ውስጥ የተገኘ ሰው ፣ “በኃጢያት ተገኝቷል ፣” ወይም 2) ያ ሰው ክፋትን ለማድረግ ሳይያስብ ኃጢአት ሠርቶ “እጅ ሰጠው ኃጢአት ሠርቷል” ።

እናንተ መንፈሳዊ የሆናችሁ
“ከእናንተ በመንፈስ የሚመሩ” ወይም “በመንፈስ መሪነት የምትኖሩ”

አቅኑት
"የበደለውን ሰው እርማት" ወይም "የበደለውን ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ወደ ትክክለኛው ዝምድና እንዲመለስ አጥብቀው ይመክሩ"

በገርነት መንፈስ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) መንፈስ እርማትን የሚሰጥ ወይም 2) “በገርነት” ወይም “በደግነት” የሚመራው መንፈስ ነው ።

ስለራስዎ ያስቡ
እነዚህ ቃላት ገላትያንን እያንዳንዳቸውን እንደሚናገር ለማጉላት ሁሉም አንድ ሰው እንደሆኑ አድርገው ይመለከቷቸዋል ። AT: - “ስለራሳችሁ አስቡ” ወይም “እያንዳንዳችሁን ፣ ስለ ራሳችሁ ጉዳይ ይጨነቁ” እላለሁ ።

እንደዚሁም እናንተ እንዳትፈተን ይሆናል
ይህ በንቃት ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “ስለሆነም ምንም ኃጢአት እንዳትሠሩ እንዳትፈታተኑ” (የበለስ_ቁጥር / ይመልከቱ)

Galatians 6:3

ለ
"ምክንያቱም።" ይህ የሚያሳየው የሚከተለው ቃል የገላትያ ሰዎች 1) “አንዱ የሌላውን ሸክም መሸከም” (6 1) ወይም 2) እነሱ ራሳቸው እንዳልተፈተኑ ተጠንቀቁ (6 1) ወይም 3) “እንዳይታለሉ” (5 1) ።

እሱ አንድ ነገር ነው
“እሱ በጣም አስፈላጊ የሆነ ሰው ነው” ወይም “እሱ ከሌላው ይበልጣል”

እርሱ ምንም አይደለም
እሱ እሱ አስፈላጊ አይደለም ወይም “እሱ ከሌሎቹ አይሻልም”

እያንዳንዳቸው ማድረግ አለባቸው
እያንዳንዱ ሰው የግድ መሆን አለበት

እያንዳንዱ የራሱን ሸክም ይይዛል
እያንዳንዱ ሰው የሚፈርደው በገዛ ሥራው ብቻ ነው ወይም “እያንዳንዱ ሰው ለገዛ ሥራው ብቻ ነው ተጠያቂው”

እያንዳንዱ ያደርጋል
እያንዳንዱ ሰው ያደርጋል

Galatians 6:6

እሱ
"ሰውየው"

ቃል
እዚህ ላይ ይህ ማለት እግዚአብሔር “በእግዚአብሔር ቃል” ወይም “በእውነት ቃል” ማለት እግዚአብሔር የተናገረው ወይም ያዘዘውን ሁሉ ማለት ነው ።

ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳል
መትከል በአንድ ዓይነት ውጤት የሚጠናቀቁ ነገሮችን ማድረጉን ይወክላል ፣ እናም መሰብሰብ አንድ ሰው ያደረገውን ውጤት ያሳያል ማለት ነው። አት: - “አንድ ገበሬ ማንኛውንም የተተከለውን ዘር ፍሬ እንደሚሰበስብ ሁሉ ፣ እያንዳንዱ ሰው የሚያደርገውን ማንኛውንም ነገር ያገኛል” (ይመልከቱ። የበለስ_ቁጥር)

ሰው ... የእሱ
እዚህ እዚህ ላይ ጳውሎስ ወንዶችን አልገለጸም ። "ሰው ... ያ ሰው"

ለእራሱ የኃጢያት ተፈጥሮ ዘሩ
እንደ ኃጢአተኛው ተፈጥሮው ዘር ይተክላሉ። በኃጢያት ተፈጥሮው ምክንያት ይህ ማድረግ የሚፈልገውን ማድረጉን ይወክላል። አት: - “በኃጢያት ተፈጥሮው እንደፈለገው እንደ ዘር ይተክላል” ወይም “በኃጢያቱ ተፈጥሮው ለማድረግ የሚፈልገውን ነገር ያደርጋል” (የበለስ_ቁጥር እና የበለስ_ቁጥር / ይመልከቱ)

በጥፋት ይሰበሰባሉ
“ላደረገው ነገር ቅጣትን ይቀበላል” (ይመልከቱ ። የበለስ_ቁጥር)

እጽዋት ለመንፈስ ፍሬ ይሰጣሉ
የእግዚአብሔር መንፈስ የወደደውን ያደርጋል “(የበለስ_ቁጥር ተመልከት)

ከመንፈስ የዘላለም ሕይወት ይሰበሰባሉ
ከእግዚአብሔር መንፈስ እንደ ሽልማት የዘላለም ሕይወት ይቀበላሉ ”

Galatians 6:9

መልካም በማድረግ መልካም አናደርግም
“መልካም ማድረጋችንን መቀጠል አለብን”

ጥሩ መሥራት
ለሌሎች ደህንነት ሲባል መልካም ማድረግ

በትክክለኛው ጊዜ
“በጊዜው” ወይም “እግዚአብሔር በመረጠው ጊዜ”

ስለዚህ
"በዚህ ምክንያት" ወይም "በዚህ ምክንያት"

በተለይም ... ለእነዚያ
“ከሁሉም በላይ ... ለእነዚያ” ወይም “በተለይም ... ለእነዚያ”

ከእምነት የሆኑ ቤተሰቦች ናቸው
"በእምነት በእምነት የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባላት የሆኑት"

Galatians 6:11

አያያዥ መግለጫ
ጳውሎስ ይህንን ደብዳቤ ሲዘጋ ፣ ሕጉ የማያድን እና የክርስቶስን መስቀል ማስታወስ እንዳለበት አንድ ተጨማሪ ማሳሰቢያ ሰጣቸው ።

ትልልቅ ፊደላት
ይህ ማለት ጳውሎስ አፅን wantsት ለመስጠት ይፈልጋል 1) የሚቀጥለውን መግለጫ ወይም 2) ይህ ደብዳቤ የመጣው ከእርሱ ነው ።

በገዛ እጄ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ምናልባት ጳውሎስ ምን እንደሚጽፍ የነገረውን ይህን ደብዳቤ አብዛኛው ሰው የፃፈው ረዳት ሳይኖረው አይቀርም ፣ ግን ጳውሎስ ራሱ የፃፋውን ይህን የመጨረሻውን ክፍል ጻፈ ወይም 2) ጳውሎስ መላውን ደብዳቤ ራሱ ጻፈ።

ጥሩ ስሜት ያሳድሩ
"ሌሎች ስለእነሱ እንዲያስቡ" ወይም “ሌሎች ጥሩ ሰዎች ናቸው ብለው እንዲያስቡ አድርጓቸዋል”

በስጋ
“በሚታይ ማስረጃ” ወይም “በእራሳቸው ጥረት”

ማስገድድ
"በኃይል" ወይም "በከፍተኛ ተጽዕኖ"

ስለ ክርስቶስ መስቀል እንዳይሰደዱ ብቻ ነው
አይሁዶች እንዳያሳድዱት "ክርስቶስ መስቀል ብቻውን ሰዎችን ያድናል"

መስቀሉ
እዚህ ላይ መስቀል በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ ክርስቶስ ለእኛ ያደረገውን ያሳያል ። አት: - “ኢየሱስ በመስቀል ላይ ያከናወነው ሥራ” ወይም “የኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ” (ይመልከቱ። የበለስ.

ይፈልጋሉ
እንድትገረዙ የሚጠይቁአችሁ ሰዎች

ስለ ሰውነታችሁ እንዲኩራሩ
"ህግን ለመጠበቅ በሚሞክሩ ሰዎች ላይ ስለጨምሩህ ይኮሩ ዘንድ"

Galatians 6:14

ነገር ግን ከመስቀል በስተቀር በምንም አልኩ
“ከመስቀል ውጭ በሌላ በየትኛውም ነገር መመካት አልፈልግም” ወይም “በመስቀል ብቻ ልኮራ”

ዓለም ለኔ ተሰቅሏል
ይህ በንቃት ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “ዓለምን እንደ ቀድሞው አስባለሁ” ወይም “ዓለምን በመስቀል ላይ እንደገደለው ወንጀለኛ አደርገዋለሁ” (የበለስ_ቁጥር / ይመልከቱ)

እኔ ለዓለም
ከዚህ በፊት ካለው ሐረግ ውስጥ “ተሰቅለዋል” የሚሉት ቃላት ተረድተዋል ። አት: - "እኔ ለዓለም ተሰቅዬአለሁ" (የበለስ_ሊሲስስ ይመልከቱ)

እኔ ለዓለም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ዓለም እንደ ቀድሞው እንደቆየችኝ” ወይም 2) “እግዚአብሔር በመስቀል ላይ እንደገደለው ወንጀለኛ ቆጠረችኝ”

ዓለም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የዓለም ሰዎች ፣ ለእግዚአብሄር ምንም ደንታ የሌላቸውም ወይም 2) ለእግዚአብሄር ምንም ግድየለሾች የሚያሳስባቸው ነገር አስፈላጊ ናቸው ።

ለማንኛውም ነገር ይቆጥራል
“ለእግዚአብሔር አስፈላጊ ነው”

አዲስ ፍጥረት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) አዲስ ክርስቶስ አማኝ ወይም 2) የአማኝ አዲስ ሕይወት።

ሰላምና ምሕረት በእስራኤል አምላክ ላይ ይሁን
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) አማኞች በአጠቃላይ የእግዚአብሔር እስራኤል ናቸው ወይም 2) “ሰላምና ምሕረት በአህዛብ አማኞችና በእግዚአብሔር እስራኤል ላይ ይሁን” 3) “ህጉን ለሚከተሉ እና ምህረት ሊሆኑ ይችላሉ ። በእግዚአብሔር እስራኤል ላይ ይሁን።

Galatians 6:17

ከ አሁን ጀምሮ
ይህ ደግሞ “በመጨረሻም” ወይም “ይህን ደብዳቤ እንደጨረስኩ” ማለት ይችላል ።

ማንም አያስቸግረኝ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች እንዳያስቸግሩት ፣ “ይህን እያዘዝኩህ ነው ፣ አትጨነቅ” ወይም 2) ጳውሎስ ሁሉንም ሰዎች እንዳያሳዝኑት ለገላትያኖች እየነገራቸው ነው ፣ “እኔ ነኝ ይህን ሁሉ ለሁሉም በማዘዝ “አታስጨንቁኝ ፣” ወይም 3) ጳውሎስ ምኞቱን እየገለጸ ነው ፣ “ማንም እንዲያስቸገረኝ አልፈልግም ።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ያስቸገረኝ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ስለእነዚህ ጉዳዮች ለእኔ ንገሩኝ” (ዩ.አር.ቢ.) ወይም 2) “ችግር ያመጣብኛል” ወይም “ጠንክሮ ስጠኝ” ።

እኔ የኢየሱስን ምልክቶች በሥጋዬ ተሸክሜአለሁና
እኔ የኢየሱስን አገልግሎት በማግኘቴ በሰውነቴ ውስጥ የተፈወሱ ቁስሎች አሉኝ ”ወይም“ እኔ የኢየሱስ በመሆኔ አሁንም እኔ በሰውነቴ ውስጥ የተፈወሰው የቁስል ምልክት አለኝ ።

ምልክቶች
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) በጦር ወታደር በወታደር ወይም በአገልጋይ በአደገኛ ሥራ ላይ ከደረሰባቸው ቁስል ቁስሎች ወይም 2) የባሪያ መለያ ምልክት የሆኑ ምልክቶች ።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከመንፈሳችሁ ጋር ይሁን
"ጌታ ኢየሱስ ለመንፈሳችሁ ደግ እንዲሆን እጸልያለሁ"

ወንድሞች
በ1፡1 ላይ እንዳለው ተርጉሙ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Ephesians

Ephesians

ምዕራፍ 1

1 በእግዚአብሔር ፈቃድ የክርስቶስ ኢየሱስ ሐዋርያ ከሆነው ከጳውሎስ፥ ለእግዚአብሔር ለተለዩት በክርስቶስ ኢየሱስ ለሚያምኑ በኤፌሶን ለሚኖሩ ቅዱሳን፤ 2 ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን። 3 በክርስቶስ ኢየሱስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባትና አምላክ ይባረክ። 4 እግዚአብሔር በክርስቶስ የምናምነውን እኛን ዓለም ከመፈጠሩ በፊት መርጦናል። ይህም በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን እንሆን ዘንድ ነው 5 እግዚአብሔር በፍቅር በኢየሱስ ክርስቶስ የራሱ ልጆች አድርጎ ሊቀበለን አስቀድሞ ወሰነን። ይህንንም የፈጸመው ሊያደርግ የፈለገውን ነገር ለማድረግ ደስ ስለተሰኘ ነበር። 6 ይህ ሁሉ የተፈጸመው በሚወደው ልጁ እንዲያው በነጻ ስለ ተሰጠን ክቡር ጸጋው እግዚአብሔር ይመሰገን ዘንድ ነው። 7 እንደ ጸጋው ባለጠግነት መጠን በሚወደው ልጁ ደም ቤዛነትን ይኸውም የሐጢአት ይቅርታን አገኘን። 8 ይህም ጸጋ በጥበብና በማስተዋል ሁሉ ተትረፍርፎ ተሰጠን። 9 በክርስቶስ በተገለጠው ፈቃዱ መሠረት እግዚአብሔር በዕቅዱ ውስጥ ያለውን የተሰወረውን እውነት እንድናውቅ አድርጎናል፤ 10 ዕቅዱን የሚፈጽምበት ጊዜ ሲድርስ በሰማይና በምድር ያሉትን ነገሮች ሁሉ በአንድ ላይ በክርስቶስ ስር ይጠቀልላል። 11 ሁሉንም ነገር እንደ ገዛ ፈቃዱ በሚያደርገው ዕቅድ መሠረት በክርስቶስ ተመረጥን፤ አስቀድሞም ተወሰንን 12 ይህም የሆነው በክርስቶስ በማመን ቀዳሚ የሆንነው እኛ ለክብሩ ምስጋና ይሆን ዘንድ እንድንኖር ነው። 13 ባመናችሁበትና እንደ ተሰጠው ተስፋ በመንፈስ ቅዱስ በታተማችሁበት በክርስቶስ አማካይነት የመዳናችሁ ወንጌል የሆነውን የእውነት ቃል የሰማችሁት በክርስቶስ ነው 14 ለክብሩ ምስጋና እንዲሆን ተስፋ የተደረገው ሀብት በእጅ እስገሚገባ ድረስ መንፈስ ቅዱስ የርስታችን ዋስትና የሚሆን መያዣ ነው። 15 ስለዚህ በጌታ ኢየሱስ ስላላችሁ እምነትና ለእርሱም ቅዱሳን ሁሉ ስላላችሁ ፍቅር ከሰማሁበት ጊዜ አንስቶ 16 ስለ እናንተ እግዚአብሔርን ማመስገንና እናንተንም በጸሎቴ ማስታወስ አላቋረጥሁም ። 17 የክብር አባት፥የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እርሱን ለማወቅ የሚያስችላችሁን የጥበብ እና የመገለጥ መንፈስ እንዲሰጣችሁ እጸልያለሁ፤ 18 የምጸልየውም የመጠራታችን አስተማማኝነት እና በእርሱ ቅዱሳን መካከል የርስቱ ክብር ባለጠግነት ምን እንደሆነ ታውቁ ዘንድ የልባችሁ ዐይኖች እንዲበሩ 19 እንዲሁም እንደ ኀይሉ ብርታት አሠራር በእኛ በምናምነው ውስጥ የሚሠራው የኀይሉ ታላቅነት ምን እንደሆነ እንድትረዱ ነው። 20 ይህም እግዚአብሔር ከሙታን ባስነሳውና በሰማያዊ ስፍራ በቀኙ እንዲቀመጥ ባደረገው ጊዜ በክርስቶስ ውስጥ የታየው ኀይል ነው። 21 ክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በአብ ቀኝ የተቀመጠውም ከማንኛውም ግዛት፥ ሥልጣን፥ኀይልና ጌትነት እንዲሁም በዚህ ዘመን ብቻ ሳይሆን በሚመጣውም ዘመን ቢሆን ሊሰየም ከሚችለው ስም ሁሉ በላይ ነው። 22 እግዚአብሔር ሁሉም ነገር በክርስቶስ እግር ሥር እንዲገዛ አድርጓል፤ እርሱንም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሁሉም ነገር ላይ ራስ አድርጎ ሾሞታል 23 ቤተ ክርስቲያንም ሁሉንም ነገር በሁሉም መንገድ የሚሞላው የእርሱ ሙላት የሆነች አካሉ ናት።

Ephesians 1:1

ኤፌሶን **1**:**1**-**2**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ጳውሎስ ይህን ደብዳቤ የሚከፍተው በእግዚአብሔር ፊት ያላቸውን የአማኞችን ደረጃ እና ደህንነት በመናገር ነው። በእግዚአብሔር ፈቃድ፡ "በእግዚአብሔር ፈቃድ" ወይም "በእግዚአብሔር ምርጫ" ለእግዚአብሔር ለተለዩት ትኩረት፡ "በግብረ ገብ ያለ ነቀፋ መሆን" ወይም "ቅዱሳን" በክርስቶስ ኢየሱስ ለሚያምኑ፡

Ephesians 1:3

ኤፌሶን **1**:**3**-**4**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባትና አምላክ ይባረክ፡ ትኩረት፡ "የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክና አባት እንባርከው" የባረከን፡ ትኩረት:"እግዚአብሔር ባርኮናልና" "ባረከን" የሚለው ቃል ጳውሎስን እና በኤፌሶን ያሉትን አማኞች ያጠቃልላል። በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ፡ ትኩረት:"ከእግዚአብሔር መንፈስ የሚመጣ በረከት ሁሉ" በክርስቶስ፡ "በክርስቶስ" እና ተመሳሳይ አገላለጦች ዘይቤያዊ አባባሎች ሲሆኑ በተደጋጋሚ በአዲስ ኪዳን ደብዳቤዎች ውስጥ የምናገኛቸው ናቸው። እንዚህ አባባሎችም በክርስቶስና እና በእርሱ በሚያምኑት መካከል ጠንካራ ግንኙነት የሚያሳዩ ናቸው። (ተመልከት፡ [[rc://*/tw/bible/kt/inchrist]]) ቅዱሳንና ነውር የሌለን እንሆን ዘንድ፡ ጳውሎስ በእግዚአብሔር ልንሆን የምንችላቸውን ሁለት ባህሪያት ያሳየናል።

Ephesians 1:5

ኤፌሶን **1**:**5**-**6**
እግዚአብሔር * የራሱ ልጆች አድርጎ ሊቀበለን አስቀድሞ ወሰነን፡

"ሊቀበለን" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን፥የኤፌሶንን ቤተክርስቲያን እና በክርስቶስ ውስጥ ያሉትን አማኞች ነው። ትኩረት:"እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ ልጆች አድርጎ ሊቀበለን ወሰነ" ልጆች አድርጎ ሊቀበለን፡ እዚህ ጋር"ልጆች አድርጎ ሊቀበለን" የሚለው ሃሳብ ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብነት መቀላቀልን አመልካች ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ፡ እግዚአብሔር አማኞችን ወደ ራሱ ቤተሰብ የሚያመጣው በኢየሱስ ክርስቶስ ስራ አማካኝነት ነው። ይህንንም የፈጸመው ሊያደርግ የፈለገውን ነገር ለማድረግ ደስ ስለተሰኘ ነበር፡ "የፈፀመው" እና "ሊያደርግ" የሚሉት ቃላት እግዚአብሔርን አመላካች ናቸው። በሚወደው በልጁ፡ "የእግዚአብሔር ውድ" ወይንም "ኢየሱስ ክርስቶስ"

Ephesians 1:7

ኤፌሶን **1**:**7**-**8**
በሚወደው ልጁ፡ "በእግዚአብሔር ውድ፥በኢየሱስ ክርስቶስ" ቤዛነትን*አገኘን "አገኘን" የሚለው ቃል ሁሉንም አማኞች ነው።

ፀጋ*ተትረፍርፎ፡ "የእግዚአብሔር ፀጋ ታላቅነት" ወይም "የእግዚአብሔር ፀጋ መትረፍረፍ" በጥበብና በማስተዋል ሁሉ፡ እግዚአብሔር ለአማኞች ታላቅ ጥበብ እና ማስተዋል ሰጥቷል። ትኩረት:"የበዛ ጥበብ እና ማስተዋል።"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ephesians 1:9

ኤፌሶን **1:9-10**
በፈቃዱ መሰረት፡ "እንደ እርሱ ደስታ" በክርስቶስ፡ "በክርስቶስ" እና ተመሳሳይ አገላለጦች ዘይቤያዊ አባባሎች ሲሆኑ በተደጋጋሚ በአዲስ ኪዳን ደብዳቤዎች ውስጥ የምናገኛቸው ናቸው። እንዚህ አባባሎችም በክርስቶስና እና በእርሱ በሚያምኑት መካከል ጠንካራ ግንኙነት የሚያሳዩ ናቸው። (ተመልከት፡ [[rc://*/tw/bible/kt/inchrist]]) በእቅዱ ውስጥ ያለውን፡ ትኩረት፡"ትክክለኛው ጊዜ ሲደርስ" ዕቅዱን የሚፈፅምበት ጊዜ ሲደርስ፡ ትኩረት፡"እርሱ እቅዱን ይፈፅማል"

Ephesians 1:11

ኤፌሶን **1:11-12**
ተመረጥን፡ "እግዚአብሔር የእርሱ ርስት እንሆን ዘንድ መረጠን" ወይም እግዚአብሔር የእርሱን ርስት እንቀበል ዘንድ መረጠን።" አስቀድሞም ተወሰንን፡ "ተወሰንን" የሚለው ቃል ጳውሎስን እና የአይሁድን በክርስቶስ አማኝ ህዝብ እንጂ አህዛብን በሚያደርገው ዕቅድ፡ "የእግዚአብሔር እቅድ" እንደ ገዛ ፈቃዱ በሚያደርገው ዕቅድ መሠረት፡ "የእግዚአብሔር ፈቃድ"

Ephesians 1:13

ኤፌሶን **1:13-14**
የእውነት ቃል የሰማችሁት በክርስቶስ ነው፡ ትኩረት፡"በክርስቶስ በማመናችሁ በእርሱ እንደዳናችሁ ሰማችሁ" በክርስቶስ አማካይነት የመዳናችሁ ወንጌል የሆነውን፡ ትኩረት፡"ክርስቶስ የመዳናችሁ ወንጌል ነው" ባመናችሁበትና፡ ትኩረት፡ "እናንተም በክርስቶስ አመናችሁ" በመንፈስ ቅዱስ በታተማችሁበት፡ ደብዳብ በሰም እንድሚታሸግ እና ማን እንድላከው ምልክት እንድሚደረግበት፥እግዚአብሔርም እንዲሁ በመንፈስ ቅዱስ አትሞ ባለቤትነቱን ያሳያል። ትኩረት፡ "እግዚአብሔር በተስፋው ቅዱስ መንፈስ አትሟችኋል" (ተመልከት፡ እንዲሁም

መንፈስ ቅዱስ የርስታችን ዋስትና የሚሆን መያዣ፡ እግዚአብሔር በትክክለኛው ጊዜ መንፈስ ቅዱስን የዘላለም ህይወት ተስፋ ስጦታ አድርጎ ሰጠን። ትኩረት፡"መንፈስ ቅዱስ ዋስትና ነው።" ተስፋ የተደረገው ሀብት በእጅ እስገሚገባ ድረስ፡ ትኩረት፡ "የርስታችንን ሃብት እስክናገኝ ድረስ" ወይንም "ርስታችንን እስክንቀበል ድረስ"

Ephesians 1:15

ኤፌሶን **1:15-16**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ጳውሎስ ለኤፌሶን አማኞች ከመፀለየም በላይ አማኞች በክርስቶስ ውስጥ ስላላቸው ሃይል ያመሰግናል። ስለዚህ፡ "በዚህ ምክንያት" ለእርሱም ቅዱሳን ሁሉ ስላላችሁ፡ "ለክርስቶስ ቅዱሳን ላላችሁ ፍቅር" ወይም "ለአማኞች ሁሉ ላላችሁ ፍቅር" እግዚአብሔርን ማመስገን*አላቋረጥሁም፡ ትኩረት፡"ማመስገኔን እቀጥላለሁ"

Ephesians 1:17

ኤፌሶን **1:17-18**
እርሱን ለማወቅ * የጥበብ እና የመገለጥ መንፈስ:

ትኩረት፡"የእርሱን መገለጥ መረዳት የሚያስችል መንፈሳዊ ጥበብ" የልባችሁ ዐይኖች እንዲበሩ፡ "የልባችሁ አይኖች እንዲበሩ" የሚለው ሃረግ የአንድን ሰው የማስተዋል ሁኔታ ይገልፃል። ትኩረት፡"ማስተዋልን አግኝታችሁ እንዲበራላችሁ"

የመጠራታችን ተስፋ፡ "የጥሪያችን ተስፋ" የርስቱ ክብር ባለጠግነት፡ "የርሱ የከበረ ርስት ባልጠግነት" ወይም "የከበረው ርስቱ ብዛት" በእርሱ ቅዱሳን፡ ይህ ሃሳብ ያለ ነቀፋ መሆንን፥መለየትን እና መቀደስን ያጠቃልላል።

Ephesians 1:19

ኤፌሶን **1:19-21**
የጎይሉ ታላቅነት ምን እንደሆነ፡ የእግዚአብሔር ሃይል ከሌሎች ሃይል ሁሉ ይበልጣል። እንደ ጎይሉ ብርታት አሠራር፡ ትኩረት፡"ለእኛ የሚሰራልን ታላቅ ሃይል" በቀኙ እንዲቀመጥ፡ "ክርስቶስን በእግዚአብሔር ቀኝ አስቀመጠው" ወይም "ክርስቶስ በክብር ስፍራ ተቀመጠ" ከማንኛውም ግዛት፥ ሥልጣን፥ጎይልና ጌትነት *በላይ፡ እነዚህ የተለያዩ የልዕለ ተፈጥሮ አካላትን ማለትም ሁለቱም የመላዕክትም ሆነ የዲያብሎስን ደረጃዎች ያሳያሉ። በዚህ ዘመን፡ "በዚህ ጊዜ" በሚመጣውም ዘመን፡ "ወደፊት"

Ephesians 1:22

ኤፌሶን **1:22-23**
እግዚአብሔር * እንዲገዛ አድርጓል፡

"እግዚአብሔር አስቀመጠለት" "እግዚአብሔር አደረገለት" (UDB) በክርስቶስ እግር ሥር፡ እዚህ ጋር "እግር" የክርስቶስን ጌትነት፥ስልጣን እና ሃይል ይወክላል።" በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሁሉም ነገር ላይ ራስ አድርጎ ሾሞታል፡ "ራስ" የሚያመለክተው መሪነትን ወይም ሃላፊነትን ነው። ትኩረት፡"በቤተክርስቲያን ውስጥ ባሉ ነገሮች ላይ ሁሉ ይገዛል" የእርሱ * አካሉ፡

ብዙውን ጊዜ የክርስቶስ አካል የሚለው ቤተክርስቲያንን ነው። በሁሉም መንገድ የሚሞላው የእርሱ ሙላት፡ ትኩረት፡"ክርስቶስ ለነገሮች ሁሉ ህይወት እንደሚሰጥ ቤተክርስቲያኑን በህይወት እና በሃይል ይሞላታል"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 2

1 እንግዲህ እናንተ ከበደላችሁና ከሓጢአታችሁ የተነሳ የሞታችሁ ነበራችሁ። 2 በዚያን ጊዜ የዚህን ዓለም ክፉ መንገድ በመከተል፥ በአየር ላይ ባሉት ኀይላት ላይ ገዥ ለሆነው እንዲሁም በማይታዘዙት ልጆች ላይ ለሚሠራው መንፈስ እየታዘዛችሁ ትኖሩ ነበር። 3 በአንድ ወቅት እኛ ሁላችን ለሥጋችን ክፉ ምኞት እየታዘዝንና ፈቃዱን እየፈጸምን፥ የአእምሮአችንንም ሐሳብ እየተከተልን በእነዚህ በማያምኑት ሰዎች መካከል እንኖር ነበር፤ በተፈጥሮአችንም እንደሌሎቹ የቁጣ ልጆች ነበርን። 4 ነገር ግን እግዚአብሔር ምሕረት በማድረግ ባለጠጋ ስለሆነ፥ ከወደደን ከታላቅ ፍቅሩ የተነሳ 5 በበደላችን ሙታን በነበርንበት ጊዜ እንኳ ከክርስቶስ ጋር አዲስ ሕይወት ሰጠን፤የዳናችሁትም በጸጋ ነው፤ 6 ከእርሱም ጋር አስነሳን፤በሰማያዊ ስፍራም ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር እንድንቀመጥ አደረገን። 7 ይህንንም ያደረገው፥በክርስቶስ ኢየሱስ በቸርነቱ የገለጠውን የጸጋው ባለጠግነት ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ በሚመጣው ዘመን ለእኛ ያሳይ ዘንድ ነው። 8 የዳናችሁት በእምነት አማካይነት በጸጋ ነውና ፤ ይህ ከእግዚአብሔር ያገኛችሁት ስጦታ እንጂ ከእናንተ የሆነ ነገር አይደለም። 9 ማንም ሰው እንዳይመካ በሥራ የተገኘ ነገር አይደለም 10 ምክንያቱም እግዚአብሔር ከዘመናት በፊት እንድንፈጽመው ያዘጋጀውን መልካም ሥራ ለመሥራት በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጠርን የእግዚአብሔር እጅ ሥራዎች ነን። 11 ስለዚህ በአንድ ወቅት በአካል ላይ በሰው እጅ የሚከናወነውን መገረዝ ስላገኙ «የተገረዙ» በሚባሉት ዘንድ «ያልተገረዙ» ተብላችሁ የምትጠሩ በትውልድ አሕዛብ የነበራችሁ እንደሆነ አስታውሱ። 12 በዚያን ጊዜ ከክርስቶስ ተለይታችሁ፥ የእስራኤል ወገን ከመሆን ርቃችሁ፥ለተስፋውም ኪዳን ባዕድ ሆናችሁ ያለ ተስፋ እና ያለ እግዚአብሔር በዓለም ላይ ትኖሩ እንደነበር ልብ በሉ። 13 ነገር ግን አሁን ከእግዚአብሔር ርቃችሁ የነበራችሁት በክርስቶስ ኢየሱስ በመሆን በክርስቶስ ደም አማካይነት ወደ እግዚአብሔር እንድትቀርቡ ተደርጋችኋል። 14 አይሁድንና አሕዛብን ሁለቱን አንድ ሕዝብ ያደረገ እርሱ ሰላማችን ነውና ፤ በሥጋውም እርስ በርስ የለያየንን የጥል ግድግዳ አፈረሰ። 15 ይኸውም ከሁለቱ ሕዝቦች አንድ አዲስ ሕዝብ በመፍጠር ሰላምን ያደርግ ዘንድ የትእዛዛትንና የሕግ ደንቦችን በሥጋው ሻረ። 16 ይህንንም ያደረገው በመስቀሉ አማካይነት በመካከላቸው የነበረውን ጠላትነት ገድሎ ሁለቱን ሕዝቦች አንድ አካል በማድረግ ከእግዚአብሔር ጋር ለማስታረቅ ነው። 17 ኢየሱስ መጥቶ ርቀው ለነበሩት እና ቀርበው ለነበሩት ለእነዚያ የምሥራቹን ወንጌል ሰበከ፤ ሰላሙንም አወጀ። 18 በኢየሱስ አማካይነት እኛ ሁለታችንም በአንድ መንፈስ ወደ አብ መቅረብ እንችላለንና። 19 ስለዚህ እናንተ አሕዛብ ከቅዱሳንና ከእግዚአብሔር ቤተ ሰብ አባላት ጋር የአንድ አገር ዜጎች ናችሁ እንጂ ከእንግዲህ መጻተኞችና እንግዶች አይደላችሁም። 20 እነዚህ በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ የተመሠረቱ ናቸው፤ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ራሱ ነው። 21 ቤተ ሰቡ የሆነው ሕንጻ ሁሉ በኢየሱስ ጎይል አንድ ላይ ተገጣጥሞ ለጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ለመሆን ያድጋል። 22 እናንተም እግዚአብሔር በመንፈሱ የሚኖርበት ሕንጻ እንድትሆኑ አብራችሁ በክርስቶስ እየታነጻችሁ ነው።

Ephesians 2:1

ኤፌሶን **2**:**1**-**3**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ጳውሎስ አማኞችን ስላለፈው ጊዜ ካስታወሳቸው በኋላ አሁን ደግሞ በእግዚአብሔር ፊት ያላቸውን ሁኔታ ይነግራቸዋል። ከበደላችሁና ከሓጢአታችሁ የተነሳ የሞታችሁ ነበራችሁ፡ የሞተ ሰው በአካሉ ምላሽ መስጠት ሃጢያተኛ ሰዎች እንዴት እግዚአብሔርን መታዘዝ እንደማይችሉ ያሳያል። ከበደላችሁና ከሓጢአታችሁ የተነሳ፡ ሁለቱም "በደል" እና "ሐጢያት" የሚሉት ቃላት የሚያሳዩት አንድ አይነት ነገር ነው። ጳውሎስ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው የሰዎችን ሃጢያት ታላቅነት ነው። እንኖር ነበር፤ ይህ ሰዎች ይኖሩ የነበሩበትን ባህሪ ያሳያል። ትኩረት:"ቀድሞ ትኖሩ ነበር።" በዚያን ጊዜ የዚህን ዓለም ክፉ መንገድ በመከተል፡ ሐዋርያት "ዓለም" የሚለውን ቃል የሚጠቀሙት ስግብግብነት የሞላበትን ብልሹ የዚህ ዓለም ሰዎችን ባህሪያት ለማሳየት ነው። ትኩረት:"በዚህ ዓለም ውስጥ እንደሚኖሩት አይነት ስዎች እሴት" ወይም የዚህን ጊዜያዊ ዓለም መርሆች በመከትል" በአየር ላይ ባሉት ኀይላት ላይ ገዥ ለሆነው፡ ይህ ዲያብሎስን ወይም ሰይጣንን ያመለክታል። ለሚሠራው መንፈስ፡ "ለሚሰራው መንፈስ" የሚለው ሃረግ ዲያብሎስ ወይም ሰይጣንን ያመለክታል። ለሥጋችን ክፉ ምኞት እየታዘዝንና ፈቃዱን እየፈጸምን፥ የአእምሮአችንንም ሐሳብ እየተከተልን፡ "ስጋ" እና "አዕምሮ" የሚሉት ቃላቶች መላው ሰውነትን ይወክላል። የቁጣ ልጆች፡ እግዚአብሔር የተቆጣቸው ሰዎች (ተመልከት:

Ephesians 2:4

ኤፌሶን **2**:**4**-**7**
እግዚአብሔር ምሕረት በማድረግ ባለጠጋ ስለሆነ፡ "እግዚአብሔር በምህረት የተትረፈረፈ ነው" ወይም "እግዚአብሔር ለእኛ እጅግ ሩህሩህ ነው" ከወደደን ከታላቅ ፍቅሩ የተነሳ፡ "ለእኛ ካለው ታላቅ ፍቅር የተነሳ" ወይም "እጅግ በጣም ስለሚወደን" በበደላችን ሙታን በነበርንበት ጊዜ እንኳ ከክርስቶስ ጋር አዲስ ሕይወት ሰጠን፡ ይህ የሚያሳየው የሞተ ሰው ከሞት ካልተነሳ በቀር ምላሽ መስጠት እንደማይችል፤ሃጢያተኛ ሰውም አዲስ መንፈሳዊ ህይወት ካልተቀበለ እግዚአብሔርን መታዘዝ አይችልም። በክርስቶስ ኢየሱስ፡ "በክርስቶስ ኢየሱስ" " እና ተመሳሳይ አገላለጦች ዘይቤያዊ አባባሎች ሲሆኑ በተደጋጋሚ በአዲስ ኪዳን ደብዳቤዎች ውስጥ የምናገኛቸው ናቸው። እነዚህ አባባሎችም በክርስቶስና እና በእርሱ በሚያምኑት መካከል ጠንካራ ግንኙነት የሚያሳዩ ናቸው። (ተመልከት፡ [[rc://*/tw/bible/kt/inchrist]]) በሚመጣው ዘመን፡ "ወደፊት"

Ephesians 2:8

ኤፌሶን **2**:**8**-**10**
የዳናችሁት በእምነት አማካይነት በጸጋ ነውና፡ የእግዚአብሔር ርህራሄ በኢየሱስ በማመን ብቻ ከፍርድ ልንድን የቻልንበት ሁኔታ ነው። ትኩረት:"በእርሱ በማመናችሁ ምክንያት እግዚአብሔር በፀጋው አዳነን።" የሆነ ነገር አይደለም፡ "የሆነ ነገር" የሚለው ሃረግ ወደ ኋላ "የዳናችሁት በእምነት አማካይነት በጸጋ ነውና" የሚለውን አመላካች ነው። በስራ የተገኘ አይደለም፡ ትኩረት:"ይህ መዳን በስራ አማካኝነት የተገኘ አይደለም" የእግዚአብሔር እጅ ሥራዎች ነን፡ "ነን" የሚለው ቃል ጳውሎስን እና በኤፌሶን ያሉትን አማኞች ሁሉ ነው። በክርስቶስ ኢየሱስ፡ "በክርስቶስ ኢየሱስ" " እና ተመሳሳይ አገላለጦች ዘይቤያዊ አባባሎች ሲሆኑ በተደጋጋሚ በአዲስ ኪዳን ደብዳቤዎች ውስጥ የምናገኛቸው ናቸው። እነዚህ አባባሎችም በክርስቶስና እና በእርሱ በሚያምኑት መካከል ጠንካራ ግንኙነት የሚያሳዩ ናቸው። (ተመልከት፡ [[rc://*/tw/bible/kt/inchrist]]) ለመስራት፡ ትኩረት፡ "መከተል" ወይም "ማድረግ"

Ephesians 2:11

ኤፌሶን **2**:**11**-**12**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ጳውሎስ እነዚህን አማኞች ሊያሳስባቸው የሚፈልገው ነገር አህዛብ እና አይሁድ በክርስቶስ እና በመስቀሉ አማካኝነት አንድ እንደሆኑ ነው። በትውልድ አሕዛብ፡ ከአይሁድ ህዝብ ውጪ የሆነውን ያመለክታል። ያልተገረዙ፡ ከአይሁድ ህዝብ ውጪ የሆኑት በህፃንነታቸው የማይገረዙ ስለነበር በአይሁዶች እግዚአብሔርን እንደማይከተሉ ይቆጠሩ ነበር። መገረዝ ፡ ይህ ቃል የአይሁድ ህዝብ 8 ቀን ከሆነው ወንድ ልጅ ጀምሮ የሚያደርጉትን ግዝረት ያመላክታል። ከክርስቶስ ተለይታችሁ፡ ትኩረት፡ "የማያምኑ" በሰው እጅ

የሚከናወነውን መገረዝ፡ ግዝረቱ የሚከናወነው በወንድ ህፃናት አካል ላይ ነው። የእስራኤል ወገን ፡ "የእስራኤል ማህበረሰብ" ለተስፋውም ኪዳን ባዕድ ሆናችሁ፡ ትኩረት፡ "የእግዚአብሔርን የተስፋ ኪዳን አታውቁም ነበር"

Ephesians 2:13

ኤፌሶን **2:13-16**
አሁን * በክርስቶስ ኢየሱስ በመሆን፡

ጳውሎስ የኤፌሶንን አማኞች በክርስቶስ ከማመናቸውና ካመኑ በኋላ ያለውን ልዩነት ያሳያቸዋል። (ተመልከት፡ [[rc://*/tw/bible/kt/inchrist]]) ከእግዚአብሔር ርቃችሁ የነበራችሁት * ወደ እግዚአብሔር እንድትቀርቡ ተደርጋችኋል፡

አማኞቹ ቀደም ብሎ በሐጢያታቸው ምክንያት ከእግዚአብሔር ተለይተው ነበር። አሁን ግን ኢየሱስ በደሙ አማካኝነት ወደ እግዚአብሔር አቅርቧቸዋል። እርሱ ሰላማችን ነውና፡ ትኩረት፡"ኢየሱስ ሰላሙን ሰጥቶናል" በሥጋውም፡ ትኩረት፡ "በመስቀል ሞት በመሞት" የጥል ግድግዳ፡ ትኩረት፡"የጥላቻ ግድግዳ" ወይም "ጤናማ ያልሆን እሳቤ" የለያየንን፡ ይሄ የሚያሳየው ጳውሎስንና የኤፌሶን ሰዎችን እንዲሁም አይሁድ አማኞችንና አህዛቦችን ነው። የትእዛዛትንና የሕግ ደንቦችን በሥጋው ሻረ፡ የኢየሱስ ደም አይሁድ እና አህዛብ በሰላም በእግዚአብሔር ፊት ይኖሩ ዘንድ የሙሴን ህግ ማሟላት ችሏል። አንድ አዲስ ሕዝብ፡ አንድ አዲስ ህዝብ፥የተዋጀ የሰው ዘር ሁለቱን ሕዝቦች* ለማስታረቅ፡

ትኩረት፡"አይሁድንም ሆነ አህዛብን በአንድ ላይ ለማምጣት" በመስቀሉ አማካይነት፡ ይህ በክርስቶስ በመስቀል ሞት አማካይነት ማለት ነው። (ተመልከት፡ በመስቀሉ አማካይነት* የነበረውን ጠላትነት ገድሎ፡

ኢየሱስ አይሁድ እና አህዛብ እርስ በእርሳቸው የሚኖራቸውን ጠላትነት አስወግዷል። እንደሙሴ ህግ እንደገና መኖር አያስፈልጋቸውም።

Ephesians 2:17

ኤፌሶን **2:17-18**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ጳውሎስ ለኤፌሶን አማኞች እያላቸው ያለው በአሁኑ ጊዜ ያሉት አማኞች ከሐዋርያት እና ከነቢያት ጋር አንድ በመሆናቸውም

የእግዚአብሔር መንፈስ ቤተ መቅደስ ሆነዋል። ሰላሙንም አወጀ፡ ትኩረት፡ "የሰላም ወንጌል አስታወቀ" ወይም "የሰላም ወንጌል አወጀ" ርቀው ለነበሩት፡ ይህ አህዛብን ወይም አይሁድ ያልሆኑትን አመልካች ነው። ቀርበው ለነበሩት፡ ይህ አይሁድን ያሳያል። በኢየሱስ አማካይነት እኛ ሁለታችንም * መቅረብ እንችላለንና፡

እዚህ ጋር "ሁለታችንም" የሚለው ጳውሎስን አማኝ አይሁድን እና አማኝ የሆኑትን አህዛብ ነው። በአንድ መንፈስ፡ ሁሉም አማኞች፥ አይሁድ እና አህዛብ ወደ እግዚአብሔር አብ መገኘት በዚያው አንድ መንፈስ መግባት ይችላሉ።

Ephesians 2:19

ኤፌሶን **2:19-22**
እናንተ አሕዛብ ከቅዱሳንና ከእግዚአብሔር ቤተ ሰብ አባላት ጋር የአንድ አገር ዜጎች ናችሁ እንጂ ከእንግዲህ መጻተኞችና እንግዶች አይደላችሁም፡ ልክ ዜጋ ያልነበር ዜጋ እንድሚሆነው ሁሉ ይህ የአህዛብን መንፈሳዊ ሁኔታ ከማመናቸው በፊት እና በኋላ ያለውን ሁኔታ ያሳያል። እንግዶች አይደላችሁም፡ "የውጭ አገር ሰዎች አይደላችሁም" መፃተኞች፡ "ዜጋ ያልሆናችሁ" መሠረት ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ቤተሰብ ከህንፃ ጋር ያስተያየዋል። ክርስቶስንም እንደ ማዕዘን ራስ ድንጋይ፥ሐዋርያትን እንደ መስረት እንዲሁም አማኞችን እንደ ውቅር። ቤተሰቡ የሆነው ሕንጻ ሁሉ በኢየሱስ ጎይል አንድ ላይ ተገጣጥሞ ለጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ለመሆን ያድጋል፡ ልክ ግንበኛ ድንጋዮቹን በቦታቸው እንደሚገጣጥማቸው፥ጳውሎስ የክርስቶስን ቤተሰብ አሁንም በህንፃ መመሰሉን ይቀጥላል። በእርሱ * በክርስቶስ

"በክርስቶስ ኢየሱስ" " እና ተመሳሳይ አገላለጦች ዘይቤያዊ አባባሎች ሲሆኑ በተደጋጋሚ በአዲስ ኪዳን ደብዳቤዎች ውስጥ የምናገኛቸው ናቸው። እነዚህ አባባሎችም በክርስቶስና እና በእርሱ በሚያምኑት መካከል ጠንካራ ግንኙነት የሚያሳዩ ናቸው። (ተመልከት፡ [[rc://*/tw/bible/kt/inchrist]]) እናንተም እግዚአብሔር በመንፈሱ የሚኖርበት ሕንጻ እንድትሆኑ፡ ይህ አማኞች እርስ በእርስ በመገጣጠም በመደበኛነት እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ሃይል እንዴት በመካከላቸው እንድሚኖር ይገልፃል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 3

1 በዚህ ምክንያት አሕዛብ ስለሆናችሁት ስለ እናንተ እኔ ጳውሎስ የክርስቶስ ኢየሱስ እስረኛ ሆኛለሁ። 2 ለእናንተ ጥቅም ሲባል ስለ ተሰጠኝ የእግዚአብሔር ጸጋ መጋቢነት ሰምታችኋል ብዬ አስባለሁ። 3 ቀደም ሲል እንደጻፍሁላችሁ እግዚአብሔር የተሰወረውን ምስጢር በመገለጥ እንዳውቅ አድርጓል። 4 ይህን በምታነቡበት ጊዜ ስለ ክርስቶስ ምስጢር እኔ ያለኝን መረዳት መገንዘብ ትችላላችሁ። 5 ምስጢሩም አሁን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ለሓዋርያቱ እና ለነቢያቱ የተገለጠው ያህል ባለፉት ዘመናት ለነበሩ ሰዎች አልተገለጠም ነበር። 6 ይህም ምስጢር አሕዛብ በወንጌል አማካይነት አብረው ወራሾች፥ አብረው የካሉ ብልቶች እንዲሁም በክርስቶስ በተገኘው ተስፋ አብረው ተካፋዮች መሆናቸው ነው። 7 እንደ እርሱ ጎይል አሠራር በተሰጠኝ በእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ አገልጋይ ሆኛለሁ። 8 ምንም እንኳ ከቅዱሳን ሁሉ ያነስሁ ብሆንም፥ የማይመረመረውን የክርስቶስ የባለጠግነት ወንጌል ለአሕዛብ እሰብክ ዘንድ ይህ ጸጋ ለእኔ ተሰጠኝ። 9 እንዲሁም የሁሉን ነገር ፈጣሪ በሆነው በእግዚአብሔር ላለፉት ዘመናት ተሰውሮ ስለነበረው ምስጢር የእግዚአብሔር ዕቅድ ምን እንደሆነ ለሁሉም አገልጥ ዘንድ ተሰጠኝ። 10 በዚህም ምክንያት በቤተ ክርስቲያን አማካይነት ብዙ ገጽታ ያለው የእግዚአብሔር ጥበብ በሰማያዊ ስፍራ ላሉት አለቆችና ባለ ሥልጣናት እንዲታወቅ ነው። 11 ይህም የሆነው በጌታችን በክርስቶስ ኢየሱስ በፈጸመው ዘላለማዊ ዕቅዱ መሠረት ነው። 12 በክርስቶስ በማመናችን በእርሱ ሆነን በድፍረትና በልበ ሙሉነት ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እንችላለንና። 13 ስለዚህ ክብራችሁ በሆነው ለእናንተ ስል በምቀበለው መከራ ተስፋ እንዳትቆርጡ አለምናችኋለሁ። 14 በዚህም ምክንያት በአብ ፊት እንበረከካለሁ፤ 15 እርሱም በሰማይና በምድር ላለ ቤተ ሰብ ሁሉ ስያሜ የሰጠ እና እነርሱንም የፈጠረ ነው። 16 የምጸልየውም ትጠነክሩ ዘንድ በውስጣችሁ በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት እንደ ክብሩ ባለጠግነት መጠን ጎይል እንዲሰጣችሁ ነው። 17 ይህም በእምነት ክርስቶስ በልባችሁ እንዲኖር፥ በፍቅሩ ሥር እንድትሰዱና እንድትታነጹ ነው፤ 18 ደግሞም የክርስቶስ ፍቅር ስፋቱ፥ርዝመቱ፥ከፍታውና ጥልቀቱ ምን ያህል እንደ ሆነ ከቅዱሳን ሁሉ ጋር መረዳት ትችሉ ዘንድ ነው። 19 እንዲሁም በእግዚአብሔር ፍጹም ሙላት ሁሉ ትሞሉ ዘንድ ፥ ከሰው ዕውቀት ሁሉ በላይ የሆነውን የክርስቶስን ታላቅ ፍቅር እንድታውቁ ነው። 20 እንግዲህ በእኛ ውስጥ እንደሚሠራው ሀይሉ መጠን ሁሉንም ነገር እኛ ከምንለምነው ወይም ከምናስበው በላይ እጅግ አብልጦ ማድረግ ለሚቻለው 21 በቤተ ክርስቲያንና በክርስቶስ ኢየሱስ በትውልዶች ሁሉ ከዘላለም እስከ ዘላለም ለእርሱ ክብር ይሁን፤አሜን።

Ephesians 3:1

ኤፌሶን 3:1-2
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ጳውሎስ ውድ ኋላ መለስ ብሎ የአይሁድንና የአህዛብን አንድ መሆን ካመላከት በኋላ አሁን ደግሞ አማኞች ቤተ መቅደስ የሆኑበትን የተሰወረ እውነት ያስታውቃል። በዚህ ምክንያት፡ "ለናንተ በተሰጠው ፀጋ ምክንያት" ለእናንተ ጥቅም ሲባል ስለ ተሰጠኝ የእግዚአብሔር ጸጋ መጋቢነት፡ "እግዚአብሔር ለናንተ የሰጠኝን የፀጋ ማስተዳደር ሃላፊነት"

Ephesians 3:3

ኤፌሶን 3:3-5
በመገለጥ እንዳውቅ አድርጓል፡ ትኩረት፡"እግዚአብሔር ገልጦልኛል" (ተመልከት፡

ቀደም ሲል እንደጻፍሁላችሁ፡ ጳውሎስ ለነዚህ ሰዎች ቀደም ብሎ አጠር ያለ ደብዳቤ የፃፈ ሲሆን፥የሚያመለክተውም እርሱን ነው። ስለ ክርስቶስ ምስጢር እኔ ያለኝን መረዳት፡ ትኩረት፡"ለዚህ ስውር እውነት ያለኝ መረዳት" ባለፉት ዘመናት ለነበሩ ሰዎች አልተገለጠም ነበር፡ ትኩረት፡"እግዚአብሔር ባለፉት ዘመናት ለነበሩት ሰዎች አላሳወቃቸውም ነበር።" ምስጢሩም አሁን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት* የተገለጠው፡

ትኩረት፡ "አሁን መንፈስ ቅዱስ ገልጦታል" ወይም "መንፈስ ቅዱስ አሁን እንዲታወቅ አድርጎታል"

Ephesians 3:6

ኤፌሶን 3:6-7
አሕዛብ በወንጌል አማካይነት አብረው ወራሾች፥ ይህ ጳውሎስ ቀደም ባሉት ቁጥሮች ለገልፃቸው የጀመረው ተሰውሮ የነበር እውነት ነው። ክርስቶስን የተቀበሉ አህዛብ ልክ እንድ አይሁድ አማኞች አንድ አይነት ርስት ይቀበላሉ። አብረው የአካሉ ብልቶች፡ ብዙውን ጊዜ ቤተክርስቲያን የክርስቶስ አካል ትባላለች። አገልጋይ ሆኛለሁ፡ "አሁን የእግዚአብሔር አገልጋይ የሆንሁት ወንጌልን ለማዳረስ ነው"

Ephesians 3:8

ኤፌሶን 3:8-9
ምንም እንኳ ከቅዱሳን ሁሉ ያነስሁ ብሆንም፥*ይህ ጸጋ ለእኔ ተሰጠኝ፡ ትኩረት፡ "ምንም እንኳ ከእግዚአብሔር ህዝብ በሙሉ የማይገባኝ ታናሽ ብሆንም፥እግዚአብሔር የፀጋውን ስጦታ ቸረኝ" ተሰውሮ ስለነበረው ምስጢር የእግዚአብሔር ዕቅድ ምን እንደሆነ ለሁሉም አገልጥ ዘንድ፡ "የእግዚአብሔርን ህዝብ በሙሉ ስለ እግዚአብሔር እቅድ አስታውቅ ዘንድ" የሁሉ ነገር ፈጣሪ በሆነው በእግዚአብሔር ላለፉት ዘመናት ተሰውሮ ስለነበረው ምስጢር የእግዚአብሔር ዕቅድ ምን እንደሆነ ለሁሉም አገልጥ ዘንድ፡ ትኩረት፡"እግዚአብሔር ሁሉን ከፈጠረ ጀምሮ ለረጅም ዘመን ጠብቆ ያቆየው"

Ephesians 3:10

ኤፌሶን፡3:10-11
ብዙ ገፅታ ያለው የእግዚአብሔር ጥበብ በሰማያዊ ስፍራ ላሉት አለቆችና ባለ ሥልጣናት እንዲታወቅ ነው፡ ገፅታ ያለው የእግዚአብሔር ጥበብ ትኩረት፡ "እግዚአብሔር ታላቅ የሆነ ጥበቡን በሰማይ ስፍራ ላሉ አለቆችና ስልጣናት የሚያስታውቀው በቤተ ክርስቲያን በኩል ነው" ብዙ ገፅታ ያለው የእግዚአብሔር ጥበብ፡ ገፅታ ያለው የእግዚአብሔር ጥበብ- የእግዚአብሔር ውስብስብ ጥበብ አለቆችና ባለ ሥልጣናት፡ እነዚህ ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ጳውሎስ ይህንን የተጠቀመው ማንኛውም መንፈሳዊ ፍጥረት የእግዚአብሔርን ጥበብ እንደሚያውቅ ነው። ዘላለማዊ ዕቅዱ፡ "በዘላለማዊ እቅዱ እየጠበቀ" ወይም "ከዘላለማዊ ዕቅዱ ጋር በሚስማማ" በጌታችን በክርስቶስ ኢየሱስ፡ በክርስቶስ አማካኝነት

Ephesians 3:12

ኤፌሶን 3:12-13
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ጳውሎስ ስለ መከራው እግዚአብሔርን ከማመስገኑም በላይ ስለኤፌሶን አማኞች ይፀልያል። በልበ ሙሉነት * መቅረብ፡

ትኩረት፡"ወደ እግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ ድፍረት ማግኘት" በክርስቶስ በማመናችን፡ በክርስቶስ በማመናችን ምክንያት

Ephesians 3:14

ኤፌሶን **3:14-16**
በዚህም ምክንያት፡ "እግዚአብሔር ይህንን ሁሉ የስራው ለናንተ ስለሆነ" በአብ ፊት እንበረከካለሁ፡ "በአብ ፊት ለፀሎት እንበረከካለሁ" ወይም "በአብ ፊት በትህትና እፀልያለሁ" በሰማይና በምድር ላለ ቤተ ሰብ ሁሉ ስያሜ የሰጠ፡ ስያሜ መስጠት ምናልባት የመፍጠርን ድርጊት ያመለክት ይሆናል። ትኩረት፡"በሰማይና በምድር ሁሉንም ቤተሰብ ስያሜ የሰጠ እና የፈጠረ" እንዲሰጣችሁ፡ እርሱ በፈቃዱ እንዲሰጣችሁ

Ephesians 3:17

ኤፌሶን **3:17-19**
በእምነት * በልባችሁ፡

"ልባችሁ" የሚለው የሰውን ነፍስ የሚያመላክት ሲሆን "በ" ደግሞ ማስተላለፊያውን መንገድ ያሳያል፤ይህም ክርስቶስ በአማኞች ልብ ውስጥ በእግዚአብሔር የእምነት ስጦታ አማካኝነት እንደሚኖር አመላካች ነው። በፍቅሩ ሥር እንድትሰዱና፡ ጳውሎስ እምነታቸውን ላይ ስሩን ዘርግቶ እንደተተከለ ዛፍ ወይንም በጥልቅ መሰረት ላይ እንደተገነባ ህንፃ ጋር ያመሳስለዋል። ትኩረት፡ "እንደ ዛፍ ስር ሰዳችሁ እንድትተከሉና እንደ ህንፃ በአለቱ ላይ እንድትገነቡ።"

ከቅዱሳን ሁሉ ጋር፡ "በክርስቶስ የሆኑት አማኞች ሁሉ" ወይም "ቅዱሳን ሁሉ" ከሰው ዕውቀት ሁሉ በላይ የሆነውን የክርስቶስን ታላቅ ፍቅር፡"በልምድ ልናውቀው ከምንችለው በላይ የሆነውን የክርስቶስ ፍቅር ልታውቁ ትችላችሁ"

Ephesians 3:20

ኤፌሶን **3:20-21**
ለእርሱ፡ "ለእግዚአብሔር" እጅግ አብልጦ፡ እኛ ከምንጠይቀው ወይም ከምንገምተው በላይ እግዚአብሔር ሊያደርግ ይችላል። እኛ ከምንለምነው ወይም ከምናስበው፡ "እኛ" የሚለው ቃል አማኞችን ሁሉ የሚያመለክት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 4

1 ስለዚህ የጌታ እስረኛ እንደመሆኔ በእግዚአብሔር ለተጠራችሁለት መጠራት የሚገባውን ሕይወት ትኖሩ ዘንድ እለምናችኋለሁ። 2 ይኸውም እርስ በርስ
በፍቅር ተቻችላችሁ በፍጹም ትሕትና፥በገርነትና በትዕግሥት እንድትኖሩ ነው። 3 በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ አስፈላጊውን ጥረት ሁሉ
አድርጉ። 4 በተጠራችሁ ጊዜ በአንድ ተስፋ እንደተጠራችሁ ሁሉ፥ አንድ አካል እና አንድ መንፈስ አለ፤ 5 አንድ ጌታ፥አንድ እምነት፥አንድ ጥምቀት አለ ፤ 6
ደግሞም ከሁሉ በላይ የሆነ፥በሁሉ የሚሠራ፥ በሁሉ የሚኖር ፥የሁሉም አባት የሆነ አንድ አምላክ አለ። 7 ክርስቶስ ስጦታ መጠን ለእያንዳንዳችን ጸጋ
ተሰጥቶናል 8 ይህም የእግዚአብሔር ቃል «ወደ ላይ በወጣ ጊዜ ምርኮኞችን ማረከ፤ለሰዎችም ስጦታ ሰጠ» በማለት እንደሚናገረው ነው። 9 «ወደ ላይ
ወጣ» ሲል ደግሞም «ወደ ምድር ጥልቅ ወረደ» ማለት ካልሆነ በቀር ሌላ ምን ሊያመለክት ይችላል? 10 ታች የወረደው ሁሉንም ይሞላ ዘንድ ከሰማያት ሁሉ
በላይ የወጣው ያው እርሱ ራሱ ነው። 11 ወንጌል ሰባኪዎችን፥እረኞችን እና አስተማሪዎችን ስጦታ አድርጎ የሰጠ ክርስቶስ ራሱ ነው። 12 ያደረገው የክርስቶስን
አካል ለማነጽና ለአገልግሎት ሥራ ቅዱሳንን ለማስታጠቅ ነው። 13 የሚሆነው ሁላችንም የእግዚአብሔርን ልጅ በማመን እና በማወቅ ወደ ሚገኘው አንድነት
እንዲሁም ወደ ክርስቶስ ሙላት ልክ እንዳደጉት ሰዎች ሙሉ ሰው ወደ መሆን ደረጃ እስከምንደርስ ድረስ ነው። 14 በሰዎች ረቂቅ ተንኮል እና ማታለል በተዘጋጀ
የትምህርት ነፋስ ወዲያና ወዲህ የምንነዳ ሕጻናት መሆን አይገባንም 15 ይልቁንም እውነትን በፍቅር የምንናገር እና ራስ ወደ ሆነው ወደ ክርስቶስ በሁሉም
መንገድ የምናድግ ሰዎች መሆን ይጠበቅብናል። 16 የአማኞችን አካል ሁሉ በሚያገናኘው ጅማት እየተያያዘና እየተጋጠመ፥እያንዳንዱም ክፍል የራሱን ተግባር
እያከናወነ በፍቅር ያድጋል። 17 እየለመንኋችሁ ይህን የምናገረው፥ ከእንግዲህ በአእምሮአቸው ከንቱነት እንደሚመላለሱት እንደ አሕዛብ እንዳትኖሩ ነው። 18
እነርሱም አእምሮአቸው ጨልሞአል፤ካለማወቃቸውና ከልባቸው ደንዳናነት የተነሳ ከእግዚአብሔር ሕይወት ርቀዋል፤ 19 ስግብግብነት ሁሉ ለሞላበት ቅጥ ላጣ
ብልግና ራሳቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል። 20 ግን ስለ ክርስቶስ የተማራችሁት እንደዚህ አይደለም። 21 እርሱ የሰማችሁ እና የተማራችሁ ከሆነም በርግጥ
የተማራችሁት ስለ ኢየሱስ የሚናገረውን እውነት ነው። 22 ክፉ ምኞት የጎደፈውን አስቀድሞ ትኖሩበት የነበረውን አሮጌውን ሰው ልታስወግዱ ይገባል። 23
በአእምሮአችሁ መንፈስ እንድትታደሱ 24 እውነተኛ በሆነው ጽድቅና ቅድስና በእግዚአብሔር የተፈጠረውን አዲሱን ሰው እንድትለብሱ ነው። 25 ውሸትን
አስወግዱ፤ ሁላችንም የአንድ አካል ብልቶች ስለሆንን «እያንዳንዱ ከባልንጀራው ጋር እውነትን ይነጋገር»። 26 «ተቆጡ፤ ነገር ግን ኀጢአት አትሥሩ»
በቁጣችሁ ጸሓይ እስከሚገባ ድረስ አትቆዩ፤ 27 ዕድል አትስጡት። 28 የነበረ ከእንግዲህ አይስረቅ፤ይልቁንም ለተቸገሩ ሰዎች ማካፈል ይችል ዘንድ በራሱ እጅ
በተገቢው ሁኔታ እየሠራ ለማግኘት ጥረት ማድረግ ይገባዋል። 29 ለማነጽ የሚያስፈልግ፥ ለሚሰሙትም ጸጋን የሚሰጥ ጠቃሚ ቃል እንጂ የማይረባ ቃል ከቶ
ከአፋችሁ አይውጣ። 30 ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ አታሳዝኑ። 31 ሁሉ፥ቁጣንና ንዴትን፥ጭቅጭቅንና ስድብን ከማንኛውም ዓይነት
ክፋት ጋር ከእናንተ ዘንድ አስወግዱ። 32 በርሳችሁ ቸሮች፥ ርኅሩሆች ሁኑ፤ ደግሞም እግዚአብሔር በክርስቶስ እንዲሁ ይቅር እንዳላችሁ እርስ በርሳችሁ ይቅር
ተባባሉ።

Ephesians 4:1

ኤፌሶን 4:1-3
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ጳውሎስ በፅሁፉ ለኤፌሶኖች በፃፈላችው፥የአማኞችን አንድነት በማጉላት እንደ አንደ አማኝ እንዴት መኖር እንዳለባቸው ያበረታታቸዋል። የጌታ እስረኛ፡ ትኩረት፡ "ጌታን ለማገልገል ባደረገው ምርጫ እንደ እንድ እስረኛ" ለተጠራችሁለት መጠራት የሚገባውን ሕይወት ትኖሩ ዘንድ፡ "ትኖሩ" የሚለው ቃል የኤፌሶን አማኞችን ያመላክታል። ትኩረት፡ "ለተጠራችሁለት ጥሪ የሚመጥን የሚገባ ማንነት እንዲኖችሁ አበረታታችኋለሁ" ይኸውም እርስ በርስ በፍቅር ተቻችላችሁ በፍጹም ትሕትና፥በገርነትና በትዕግሥት፡ ትኩረት፡"ትሁት፥ገር እና እርስ በእርሳችሁም የምትቀባበሉ መሆንን ተማሩ" በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ፡ "የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ በሰላም ለመኖር ጥረት አድርጉ"

Ephesians 4:4

ኤፌሶን 4:4-6
አንድ አካል፡ ብዙውን ጊዜ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ እካል በመባል ትታወቃለች። አንድ መንፈስ፡ "አንድ ቅዱስ መንፈስ ብቻ" (UDB) በተጠራችሁ ጊዜ በአንድ ተስፋ እንደተጠራችሁ፡ "እግዚአብሔር የጠራችሁ በተረጋገጥ ተስፋ ነው" (ተመለከት፡

የሁሉም አባት የሆነ፡ "የሁሉ ነገር አባት የሆነ በሁሉ ነገር ላይ በሁሉ ነገር በኩል በሁሉ ነገር ውስጥ"

Ephesians 4:7

ኤፌሶን 4:7-8
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ጳውሎስ ክርስቶስ ለአማኞች የሰጠው ስጦታዎች በቤተክርስቲያን ማለትም ለመላው የአማኞች እካል ጥቅም ነው። ለእያንዳንዳችን፡ ይህ ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን እና መላው የኤፌሶን አማኞችን ነው። ለእያንዳንዳችን ጸጋ ተሰጥቶናል፡ ትኩረት፡"እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን ስጦታን ሰጥቶናል" ወይም "እግዚአብሔር ለአማኝ ሁሉ ስጦታን ስጥቶታል"

ወደ ላይ በወጣ ጊዜ፡ "ክርስቶስ ወደ መንግስተ ሰማይ"

Ephesians 4:9

ኤፌሶን 4:9-10
ወደ ላይ ወጣ፡ "ክርስቶስ ወደ ላይ ሄደ" ወረደ፡ ወደታች ወረደ" ወይም "ክርስቶስም ወደ ታች መጣ" ወደ ምድር ጥልቅ ወረደ፡ ትርጉሞች ሊሆኑ የሚችሉ 1) "ወደ ታች የምድር አካባቢዎች" 2) ወደ ታች የምድር ክፍሎች ሁሉንም ይሞላ ዘንድ፡ "ሁሉንም ነገር ሙሉ በሙሉ እንዲሞላ" ወይም "ሁሉም በእርሱ ይሞላ ዘንድ"

Ephesians 4:11

ኤፌሶን 4:11=13
ስጦታ አድርጎ የሰጠ ክርስቶስ፡ "ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን ስጦታዎችን እንደዚህ አድርጎ ሰጠ"

ለአገልግሎት ሥራ፡ ትኩረት፡ "ሌሎችን ማገልገል" የክርስቶስን አካል ለማነጽና፡ ይህ በመንፈሳዊ ህይወት ማደግ፥ የሰውነት እንቅስቃሴ እያደረጉ ሰውነትን ከማበርታት ጋር ይነፃፀራል። ይህም የሚሆነው ሁላችንም

የእግዚአብሔርን ልጅ በማመን እና በማወቅ ወደ ሚገኘው አንድነት፡ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆን ማወቅ በእምነት ወደሚገኘው አንድነት ወይም ወደ አማኞች ብስለት ለመድረስ አስፈላጊ ነው። በማመን * ወደ ሚገኘው አንድነት፡

"በአንድነት በእምነት መጠንከር" የእግዚአብሔርን ልጅ፡ ይህ ለኢየሱስ አስፈላጊ መጠሪያ ነቅ። ሙሉ ሰው ወደ መሆን ደረጃ፡ "የበሰሉ አማኞች መሆን"

Ephesians 4:14

ኤፌሶን **4:14-16**
ከእንግዲህ፡ "ከዚህ በኋላ እንዲህ እናደርጋለን" የምንነዳ ሕጻናት፡ ይህ በመንፈሳዊ ህይወት ያላደጉትን አማኞች በህይወት ጥቂት ልምድ ካላቸው ህፃናት ጋር ተነፃፅሯል። የትምህርት ነፋስ ወዲያና ወዲህ የምንነዳ፡ ይህ ደግሞ አቅጣጫዋን በቅጡ የማታውቅ ጀልባ በነፋስ በምትገፋበት ጊዜ ያለውን ሁኔታ ከአንድ የስተትን ትምህርት ሰምቶ ከሚንቀሳቀስ ካልበሰለ አማኝ ጋር ያነፃፅረዋል። በሰዎች ረቂቅ ተንኮል እና ማታለል፡ "አማኞችን በሰላ ውሸት የሚያታልሉ ተንኮለኛ ሰዎች" ይልቁንም * የምንናገር፡

"ይሌቁንስ እንናገራለን" ራስ ወደ ሆነው አካል ሁሉ እየተያያዘና እየተጋጠመ ያድጋል፡

"ስለዚህም አማኞች እርስ በእርስ በፍቅር ለማደግ መደጋገፍ ይችላሉ"

Ephesians 4:17

ኤፌሶን **4:17-19**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ጳውሎስ እየነገራቸው ያለው በእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ እንደታተሙ አማኞች ማድረግ የሌለባቸውን ነው። በጌታ እየለመንኋችሁ ይህን የምናገረው፡ ትኩረት፡ "ስለዚህም በጌታ ሆኜ በእጅጉን አደፋፍራችኋለሁ። በአእምሮአቸው ከንቱነት እንደሚመላለሱት እንደ አሕዛብ እንዳትኖሩ ነው፡ ትኩረት፡"የማይረባ ሃሳብ እንደያዙ አህዛብ መኖርን አቁሙ" አእምሮአቸው ጨልሞአል፤ካለማወቃቸውና ከልባቸው ደንዳናነት የተነሳ ከእግዚአብሔር ሕይወት ርቀዋል፡ ትኩረት፡"ስለታወሩ እና ልባቸው ደንዳና ስለሆነ የእግዚአብሔርን ህይወት ሊለማመዱ አይችሉም" አእምሮአቸው ጨልሞአል፡ ጥርት ባለ መልኩ ማሰብም ሆን ማመዛዘን አይችሉም። ካለማወቃቸውና ከልባቸው ደንዳናነት የተነሳ ከእግዚአብሔር ሕይወት ርቀዋል፡ ትኩረት፡ "አለማወቃቸው ከእግዚአብሔር ህይወት ለይቷቸዋል" ወይም "እግዚአብሔርን ስለማያውቁ የእግዚአብሔርን ህይወት ሊለማመዱ አይችሉም" ከልባቸው ደንዳናነት፡ እግዚአብሔርን መስማትና ትምህርቱን መከተል እንቢ አሉ። ርኩሰትና ስግብግብነት ሁሉ ለሞላበት ቅጥ ላጣ ብልግና ራሳቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል፡ ትኩረት፡"ቅጥ ላጣ ፍላጎታቸውና ለራሳቸው ደስታ በክፉ ባህሪያቸው ኑሯቸውን አሳልፈው ሰጡ"

Ephesians 4:20

ኤፌሶን **4:20-22**
እናንተ ግን ስለ ክርስቶስ የተማራችሁት እንደዚህ አይደለም፡ ትኩረት፡ "ነገር ግን ክርስቶስን በዚህ መከተል አልተማራችሁም" ስለ እርሱ የሰማችሁ እና የተማራችሁ ከሆነም በርግጥ የተማራችሁት ስለ ኢየሱስ የሚናገረውን እውነት ነው፡ ትኩረት፡"ስለ ኢየሱስ ስለ ሰማችሁና ስለእርሱም እውነተኛውን ነገር ሰምታችኋልና" በሚያታልል ክፉ ምኞት የጎደፈውን አስቀድሞ ትኖሩበት የነበረውን አሮጌውን ሰው ልታስወግዱ ይገባል፡ ትኩረት፡"በክፉ ምኞት ተታልላችሁ ስትኖሩበት የነበረውን የድሮውን የተለመደ አኗኗር ዘዬ ማስወገድ ይገባችኋል" አሮጌውን ሰው ልታስወግዱ ይገባል፡ ልብስ አውልቃችሁ ወደዚያ እንደምታስወግዱት ሃጢያተኛ ባህሪያችሁን ልታስወግዱ ይገባል። ትኩረት፡"ባህሪያችሁን ልትለውጡ ይገባል" (ተመልከት፡

አስቀድሞ ትኖሩበት የነበረውን፡ ትኩረት፡"ከአሮጌው ባህሪ ጋር የሚስማማ ማንነት" ወይም "ከድሮው ማንነት ጋር የሚሄድ አይነት ፀባይ" በሚያታልል ክፉ ምኞት የጎደፈውን፡ ትኩረት፡"በውሸት የስጋ ምኞት እየባሰበት የሚሄድ"

Ephesians 4:23

ኤፌሶን **4:23-24**
እንድትታደሱ፡ ትኩረት፡"እንድትለወጡ" ወይም "እንድትታደሱ" አዲሱን ሰው እንድትለብሱ፡ አንድ ሰው አዲስን ልብስ ሲለብስ ፈፅሞ የተለየ እንደሚሆነው ሁሉ ያላመነ በክርስቶስ በማመን አዲስ ሰው ይሆናል።

Ephesians 4:25

ኤፌሶን **4:25-27**
ውሸትን አስወግዱ፡ ትኩረት፡"ሀሰት መናገርን ማቆም ይገባችኋል" እያንዳንዱ ከባልንጀራው ጋር እውነትን ይነጋገር፡ ትኩረት፡ "አማኞች ከጎረቤቶቻቸው ጋር እውነትን ሊነጋገሩ ይገባል" ሁላችንም የአንድ አካል ብልቶች ስለሆንን፡ "ሁላችንም የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባላት ነን"

ተቆጡ፤ነገር ግን ኀጢአት አትሥሩ፡ "ልትቆጡ ትችላላችሁ፥ሆኖም ሃጢያትን አትስሩ" በቁጣችሁ ጸሓይ እስከሚገባ ድረስ አትቆዩ፡ ትኩረት፡ "ምሽት ከመምጣቱ በፊት ሃጢያታችሁ ይብረድ" ወይም "ቀኑ ከመጠናቀቁ በፊት ቁጣችሁ ይቁም"

Ephesians 4:28

ኤፌሶን **4:28-30**
የማይረባ ቃል ከቶ ከአፋችሁ አይውጣ፡ "ከአፋችሁ መጥፎ ቋንቋ አይውጣ" ወይም "ክፉ ንግግር ከአፋችሁ አይውጣ" ሌሎችን ለማነጽ የሚያስፈልግ፡ "ይልቁንም ለአማኞች ብርታትን መስጠት የሚችል ጠቃሚ ቃላትን ተናገሩ" ለሚሰሙትም ጸጋን የሚሰጥ ጠቃሚ ቃል እንጂ፡ "በዚህ መንገድ ለሚያዳምጧችሁ ፀጋን መስጠት ይቻላችኋል" ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ አታሳዝኑ፡ ትኩረት፡"የእግዚአብሔርን ቅዱስ መንፈስ በመጥፎ ንግግራችሁ እንዲያዝን አታድርጉት" የታተማችሁበትን፡ ትኩረት፡ "ምክንያቱም እርሱ ስላተማችሁ"

Ephesians 4:31

ኤፌሶን **4:31-32**
መራራነት * ቁጣንና፡

"መራራነት" እና "ቁጣ" የሚሉት ቃላት ታላቅ መጠን ያለውን ቁጣ ያሳያሉ" ትኩረት፡"ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ቁጣ"

ጭቅጭቅንና ስድብን፡ "ጭቅጭቅ" የሚለው ቃል "የስደብ" ፀያፍ ደረጃ ነው። ትኩረት፡ "ፀያፍ የቃላት ናዳ" እርስ በርሳችሁ ቸሮች፥ ርኅሩሆች ሁኑ፡ ትኩረት፡"ይልቁንስ እርስ በእርሳችሁ ደጎችና ቸሮች መሆን ይገባችኋል" ወይም "በርህራሄ የተሞላችሁ ደጋጎች መሆን ይገባችኋል"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 5

1 እንግዲህ እንደ ተወደዱ የእርሱ ልጆች እግዚአብሔርን የምትመስሉ ሁኑ፤ 2 እንደ ወደደን፥ ራሱንም ስለ እኛ መልካም መዓዛ ያለው መባና መሥዋዕት አድርጎ
ለእግዚአብሔር እንዳቀረበ ሁሉ እናንተም በፍቅር ኑሩ። 3 የሚገባ ባለመሆኑ ዝሙት፥ማንኛውም ርኩሰትና ስስት በእናንተ ዘንድ ሊኖር አይገባም፤ 4 ጸያፍ
ንግግር፥ዋዛ ወይም ውርደትን የሚያስከትል ቀልድ ለእናንተ ስለማይገባ ከመካከላችሁ አስወግዱ፤ከዚህ ይልቅ የምታመሰግኑ ሁኑ። 5 አመንዝራ፥ርኩስ፥
ስግብግብ የሆነ ይኽውም ጣዖት አምላኪ ሰው በክርስቶስና በእግዚአብሔር መንግሥት ርስት እንደማይኖረው ርግጠኛ ልትሆኑ ይገባል። 6 ከንቱ በሆነ ንግግር
ማንም አያታላችሁ፤በእነዚህ ነገሮች ምክንያት የእግዚአብሔር ቁጣ በማይታዘዙት ልጆች ላይ ይመጣል 7 ስለዚህ የእነርሱ ተባባሪዎች አትሁኑ። 8 ወቅት ጨለማ
ነበራችሁና፤ አሁን ግን በክርስቶስ ብርሃን ናችሁ። ስለዚህ እንደ ብርሃን ልጆች ኑሩ። 9 ምክንያቱም ከብርሃኑ የሚገኘው ፍሬ መልካም ነገር ሁሉ፥ ጽድቅና እውነት
ነው 10 እንዲሁም ጌታን ደስ የሚያሰኝ ነገር ለማድረግ አስቡ፤ 11 ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ፤ይልቁን ልትገልጡት ይገባል። 12 በስውር ያደረጉትን
ነገር ለመግለጽ እንኳ አሳፋሪ ነውና። 13 በሚኖርበት ጊዜ ማንኛውም ነገር በግልጽ ይታያል። 14 ብርሃኑ በላዩ ላይ ስለሚያበራ ነው። ስለዚህ፥ «አንተ የምትተኛ
ንቃ፤ከሙታን ተነሳ፤ክርስቶስም ያበራልሃል» ተብሎ ተነግሯል። 15 ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን፥እንደ ጥበብኞች እንዴት እንደምትኖሩ ተጠንቀቁ። 16 ክፉዎች
ስለሆኑ ዘመኑን ዋጁ። 17 ፈቃድ ምን እንደሆነ አስተውሉ እንጂ ሞኞች አትሁኑ። 18 ሕይወታችሁን ለጥፋት ስለሚዳርግ፥በወይን ጠጅ አትስከሩ፤ይልቁንስ
በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ። 19 እርስ በርሳችሁ በመዝሙር፥በቅኔና በመንፈሳዊ ዝማሬ ተነጋገሩ፤ ጌታንም በልባችሁ አመስግኑ፤ለእርሱም ተቀኙ። 20 በጌታችን
በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ስለ ሁሉም ነገር ሁልጊዜ እግዚአብሔር አብን አመስግኑ 21 ክርስቶስን ለማክበር ስትሉ አንዳችሁ ለሌላችሁ ተገዙ። 22 ሚስቶች ሆይ!
ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ። 23 ክርስቶስ አካሉ ለሆነችውና አዳኟ ለሆናት ቤተ ክርስቲያን ራስ እንደ ሆነ ሁሉ ባልም የሚስቱ ራስ ነውና። 24 ቤተ
ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ ሁሉ ሚስቶችም በማንኛውም ነገር ለባሎቻቸው ሊገዙ ይገባል። 25 ባሎች ሆይ፤ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ስለ
እርስዋም ራሱን አሳልፎ እንደ ሰጠ፥ እናንተም ሚስቶቻችሁን ውደዱ። 26 ይህንንም ያደረገው በቃሉ አማካይነት በውሃ አጥቦ በማንጻት እንድትቀደስ፥ 27 ጉድፍ
ወይም የፊት መጨማደድ ወይም ይህን የመሰለ ሌላ ነገር ሳይታይባት ቅድስት የሆነችና ነውር የሌለባት ክብርት ቤተ ክርስቲያን አድርጎ ለራሱ ሊያቀርባት ነው።
28 ባሎች የገዛ ሥጋቸውን እንደሚወዱ ሚስቶቻቸውን መውደድ ይገባቸዋል። ሚስቱን የሚወድ ራሱን ይወዳል። 29 የራሱን ሥጋ የሚጠላ ማንም የለም፤
ይልቁን ይመግበዋል፤ ይንከባከበዋልም። ይህም ክርስቶስ ልክ ቤተ ክርስቲያንን እንደሚወድ ነው። 30 እኛ የእርሱ ብልቶች ነን። 31 ምክንያት ሰው አባቱንና
እናቱን ይተዋል፤ከሚስቱም ጋር አንድ ይሆናል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። 32 ታላቅ ምስጢር ነው፤ እኔም ይህን የምናገረው ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ
ክርስቲያኑ ነው። 33 ግን ከእናንተ እያንዳንዱ ደግሞ ሚስቱን እንደ ራሱ አድርጎ መውደድ ይገባዋል፤ ሚስትም ባልዋን ታክብር።

Ephesians 5:1

ኤፌሶን 5:1-2
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ እንግዲህ*እግዚአብሔርን የምትመስሉ ሁኑ፡ እንደ ተወደዱ የእርሱ ልጆች፡ በፍቅር ኑሩ፡ መልካም መዓዛ ያለው መባና መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር እንዳቀረበ፡

Ephesians 5:3

ኤፌሶን 5:3-4
ለቅዱሳን የሚገባ ባለመሆኑ ዝሙት፥ማንኛውም ርኩሰትና ስስት በእናንተ ዘንድ ሊኖር አይገባም፡ ማንኛውም ርኩሰትና፡ ስስት፡ በእናንተ ዘንድ ሊኖር አይገባም፡ ለቅዱሳን የሚገባ ባለመሆኑ ወይም ጸያፍ ንግግር፥ዋዛ ወይም ውርደትን የሚያስከትል ቀልድ ለእናንተ ስለማይገባ ከመካከላችሁ አስወግዱ፤ከዚህ ይልቅ የምታመሰግኑ ሁኑ፡

Ephesians 5:5

ኤፌሶን 5:5-7
ከንቱ በሆነ ንግግር ማንም አያታላችሁ፡ በእነዚህ ነገሮች ምክንያት የእግዚአብሔር ቁጣ በማይታዘዙት ልጆች ላይ ይመጣል፡ ስለዚህ የእነርሱ ተባባሪዎች አትሁኑ፡

Ephesians 5:8

ኤፌሶን 5:8-12
ባንድ ወቅት ጨለማ ነበራችሁና፡ አሁን ግን በክርስቶስ ብርሃን ናችሁ፡ ምክንያቱም ከብርሃኑ የሚገኘው ፍሬ መልካም ነገር ሁሉ፥ ጽድቅና እውነት ነው፡ ፍሬ ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ፡ ፍሬ ከሌለው ከጨለማ ሥራ፡ ይልቁን ልትገልጡት ይገባል፡

Ephesians 5:13

ኤፌሶን 5:13-14
ብርሃን በሚኖርበት ጊዜ ማንኛውም ነገር በግልጽ ይታያል፡ አንተ የምትተኛ ንቃ፤ከሙታን ተነሳ፡ ክርስቶስም ያበራልሃል፡

Ephesians 5:15

ኤፌሶን 5:15-17
እንግዲህ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን፥እንደ ጥበብኞች እንዴት እንደምትኖሩ ተጠንቀቁ፡ ዘመኑን ዋጁ፡ ቀኖቹ ክፉዎች ስለሆኑ፡

Ephesians 5:18

ኤፌሶን 5:18-21
በወይን ጠጅ አትስከሩ፡ ይልቁንስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፡ በመዝሙር፥በቅኔና በመንፈሳዊ ዝማሬ፡ ሁልጊዜ* አመስግኑ፡

ተገዙ፡

Ephesians 5:22

ኤፌሶን 5:22-24
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ አካሉ ለሆነችውና አዳኟ ለሆናት፡ ሚስቶችም በማንኛውም ነገር ለባሎቻቸው ሊገዙ ይገባል፡

Ephesians 5:25

ኤፌሶን 5:25-27
ሚስቶቻችሁን ውደዱ፡ ራሱን አሳልፎ እንደ ሰጠ * በውሃ አጥቦ በማንጻት እንድትቀደስ፡

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ስለ እርስዋም ራሱን አሳልፎ እንደ ሰጠ፡ በቃሉ አማካይነት በውሃ አጥቦ በማንጻት፡ ቤተ ክርስቲያን አድርጎ ለራሱ ሊያቀርባት ነው፡

Ephesians 5:28

ኤፌሶን **5:28-30**
የገዛ ሥጋቸውን እንደሚወዱ፡ ይልቁን ይመግበዋል፡ ምክንያቱም እኛ የእርሱ ብልቶች ነን።

Ephesians 5:31

ኤፌሶን **5:31-32**
በዚህም ምክንያት፡ ሚስቱን እንደ ራሱ አድርጎ መውደድ ይገባዋል፡ ሚስትም ባልዋን ታክብር፡

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 6

1 ልጆች ሆይ፤ በጌታ ለወላጆቻችሁ ታዘዙ፤ ይህ ተገቢ ነውና። 2 «አባትህንና እናትህን አክብር» በሚለው የመጀመሪያ ትእዛዝ ውስጥ ያለው ተስፋ 3 እንዲሆንልህ፥ ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝም» የሚል ነው። 4 እናንተም አባቶች ሆይ፤ ልጆቻችሁን አታስቆጡአቸው፤ ይልቁንስ በጌታ ሥርዓትና ምክር አሳድጓቸው። 5 ባሮች ሆይ፤ ለክርስቶስ እንደምትታዘዙት ለምድራዊ ጌቶቻችሁም በታላቅ አክብሮት፥ በመንቀጥቀጥና በልባችሁ ቅንነት ታዘዙ፤ 6 ለታይታ እነርሱን ደስ ለማሰኘት ብላችሁ ሳይሆን፥ እንደ ክርስቶስ አገልጋዮች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከልብ በመፈጸም ታዘዙአቸው። 7 ሰውን ሳይሆን ጌታን እንደምታገለግሉ እያሰባችሁ በደስታ አገልግሉ። 8 ባሪያም ይሁን ነጻ ሰው እያንዳንዱ ሰው ለሚያደርገው መልካም ነገር ከጌታ ሽልማት እንደሚቀበል ልብ በሉ። 9 እናንተም ጌቶች ሆይ፤ ለባሮቻችሁ እንዲሁ አድርጉላቸው፤ የእነርሱና የእናንተም ጌታ የሆነው እርሱ በሰማይ እንዳለና ለሰው ፊትም እንደማያዳላ ተረድታችሁ አታስፈራሯቸው። 10 በጌታና ብርቱ በሆነው ኀይሉ የበረታችሁ ሁኑ። 11 የዲያብሎስን ተንኮል አዘል ዕቅድ መቋቋም ትችሉ ዘንድ የእግዚአብሔርን የጦር ዕቃ ሁሉ ልበሱ። 12 ውጊያችን ከሥጋና ከደም ጋር ሳይሆን ከአለቆች፥ ከሥልጣናት፥ ከዚህ ከጨለማ ዓለም ገዦችና በሰማያዊ ስፍራ ካሉ ርኩሳን መናፍስት ጋር ነው። 13 በክፉ ቀን ክፉውን በመቃወም ጸንታችሁ ትቆሙ ዘንድ የእግዚአብሔርን የጦር ዕቃ ሁሉ ልበሱ፤ ጸንታችሁ ለመቆምም ማድረግ የምትችሉትን ሁሉ አድርጉ። 14 ወገባችሁን በእውነት ቀበቶ ታጥቃችሁ፥የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ ጸንታችሁ ቁሙ፤ 15 የሰላምን ወንጌል ለማወጅ እግሮቻችሁ በዚያ ተጫምተው ዝግጁ ይሁኑ 16 የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ማጥፋት ትችሉ ዘንድ ሁል ጊዜ የእምነትን ጋሻ አንሱ። 17 የመዳንን ራስ ቁር አድርጉ፤የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ፤ይህም የእግዚአብሔር ቃል ነው። 18 ዓይነት ጸሎትና ልመና ሁልጊዜ በመንፈስ በመጸለይና መልሱን ከእርሱ በመጠበቅ፥ ለቅዱሳንም ልመና በማቅረብ ትጉ። 19 ምስጢር በድፍረት ለመናገር አፌን በምከፍትበት ጊዜ ሁሉ ቃል ይሰጠኝ ዘንድ ለእኔም ጸልዩልኝ። 20 መናገር እንደሚገባኝ በድፍረት እናገር ዘንድ በሰንሰለት የታሰረ መልእክተኛ የሆንሁት ለዚሁ ነውና። 21 ሁኔታ እንዳለሁና ምን እያደረግሁ እንደምገኝ፥ የተወደደ ወንድምና በጌታ ታማኝ አገልጋይ የሆነው ቲኪቆስ ሁሉንም ነገር ይነግራችኋል። 22 ያለንበትን ሁኔታ እንድታውቁና እናንተንም እንዲያበረታታ በማለት ወደ እናንተ ልኬዋለሁ። 23 ከአብ፥ ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምና ፍቅር ከእምነት ጋር ለወንድሞች ይሁን። 24 ኢየሱስ ክርስቶስን በማይጠፋ ፍቅር ከሚወዱ ጋር ሁሉ ጸጋ ይሁን።

Ephesians 6:1

ኤፌሶን **6:1-3**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ልጆች ሆይ፤በጌታ ለወላጆቻችሁ ታዘዙ: መልካም እንዲሆንልህ፥ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝም:

Ephesians 6:4

ኤፌሶን **6:4**
እናንተም አባቶች ሆይ፤ልጆቻችሁን አታስቆጡአቸው: ይልቁንስ በጌታ ሥርዓትና ምክር አሳድጓቸው:

Ephesians 6:5

ኤፌሶን **6:5-8**
ባሪያዎች ሆይ *ታዘዙ: በታላቅ አክብሮት፥ በመንቀጥቀጥና: በመንቀጥቀጥና በልባችሁ ቅንነት ታዘዙ * እንደ ክርስቶስ አገልጋዮች:

እነርሱን ደስ ለማሰኘት ብላችሁ ሳይሆን፥ እንደ ክርስቶስ አገልጋዮች: እንደ ክርስቶስ አገልጋዮች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከልብ በመፈጸም ታዘዙአቸው:

Ephesians 6:9

ኤፌሶን **6:0**
እናንተም ጌቶች ሆይ፤ለባሮቻችሁ እንዲሁ አድርጉላቸው * አታስፈራሯቸው:

የእነርሱና የእናንተም ጌታ የሆነው እርሱ በሰማይ እንዳለና: ለሰው ፊትም እንደማያዳላ

Ephesians 6:10

ኤፌሶን **6:10-11**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: በጌታና ብርቱ በሆነው ኀይሉ የበረታችሁ ሁኑ: የዲያብሎስን ተንኮል አዘል ዕቅድ መቋቋም ትችሉ ዘንድ የእግዚአብሔርን የጦር ዕቃ ሁሉ ልበሱ:

Ephesians 6:12

ኤፌሶን **6:12-13**
ከሥጋና ከደም: የእግዚአብሔርን የጦር ዕቃ ሁሉ ልበሱ፤

Ephesians 6:14

ኤፌሶን **6:14-16**
በእውነት ቀበቶ: ቀበቶ ለአንድ ወታደር በሚገባ እንደሚይዝለት እውነትም ለአማኝ ነገሮችን አጥብቆ ይይዝለታል። የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ: ጥሩር የወታደርን ደረት እንደሚሸፍንለት የፅድቅ ስጦታም የአማኝን ልብ ይከልልለታል።

የሰላምን ወንጌል ለማወጅ እግሮቻችሁ በዚያ ተጫምተው ዝግጁ ይሁኑ: ወታደር ለእግሩ ጥሩ ጫማ መጫማት እንዳለበት ሁሉ አማኝም ጠንካራ የሆን የሰላም ወንጌል እውቀት ሊኖረው ይገባል። የእምነትን ጋሻ አንሱ: ወታደር ጠላትን ለመከላከል ጋሻውን እንደሚጠቀምበት ሁሉ እግዚአብሔር ለአማኝ የሚሰጠውም እምነት ከዲያብሎስ ጥቃት መከላከያ ነው። (ተመልከት: የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች:

Ephesians 6:17

ኤፌሶን **6:17-18**
እንዲሁም የመዳንን ራስ ቁር: በእግዚአብሔር የሚሰጥ ድነት የአማኝን አዕምሮ እንደ ራስ ቁር ሆኖ ይከላከላል። የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ፤ይህም የእግዚአብሔር ቃል ነው: ወታደር ሰይፍ መዝዞ ጠላትን ለማጥቃትና ለመከላከል እንደ ሚጠቀምበት ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ የሆነ የእግዚአብሔር ቃልም ለአማኝ ዲያብሎስን ማጥቂያ መሳሪያ ነው። በማንኛውም ዓይነት ጸሎትና ልመና ሁልጊዜ በመንፈስ በመጸለይና: ትኩረት: ስትፀልዩ እና የተወሰኑ ልመናዎችን ስታቀርቡ በመንፈስ ቅዱስ ሁልጊዜ የምትፀልዩ ሁኑ። ከእርሱ በመጠበቅ፥ ለቅዱሳንም ልመና በማቅረብ ትጉ: "ለአማኞች ሁሉ መደበኛ የሆነ ንቃት እና ፀሎት"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Ephesians 6:19

ኤፌሶን **6:19-20**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ጳውሎስ በእስር ሆኖ ወንጌል በድፍረት እንዲናገር እንዲፀልዩለት ይለምናል፥ለዚህም ደግሞ ቲኪቆስን ያደፋፍራቸው ዘንድ ይልከዋል። ከዚያም ክርስቶስን ለሚወዱ አማኞች ሁሉ በሰላምና በፀጋ ይባርካቸዋል። ቃል ይሰጠኝ ዘንድ፡ ትኩረት፡ "እግዚአብሔር ቃሉን እንዲሰጠኝ" ወይም "እግዚአብሔር መልዕክትን እንዲሰጠኝ" መናገር እንደሚገባኝ በድፍረት እናገር ዘንድ፡ ትኩረት፡ "በድፍረት ገለፃ እንዳደርግ" በሰንሰለት የታሰረ መልእክተኛ የሆንሁት ለዚሁ ነውና፡ ትኩረት፡ "የወንጌል ተወካይ በመሆኔ አሁን በእስር እገኛለሁ" በእስራቴም መናገር እንደሚገባኝ በድፍረት እናገር ዘንድ፡ ትኩረት፡ "የእግዚአብሔርን መልዕክት በድፍረት እንድናገር"

Ephesians 6:21

ኤፌሶን **6:21-22**
ምን እያደረግሁ እንደምገኝ፡ "የኔ ሁኔታ" ወይም "እኔ ያለሁበት ድባብ" ቲኪቆስ፡ ቲኪቆስ ከጳውሎስ ጋር ካሉት በርካታ ሰዎች መካከል አንዱ ነው። ያለንበትን ሁኔታ እንድታውቁና፡ ትኩረት፡ "ሁሉንም ነገሮች እንነግራችኋለን"

Ephesians 6:23

ኤፌሶን **6:23-24**
ማስታወሻ የለውም።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Philippians

Philippians

ምዕራፍ 1

1 የክርስቶስ ኢየሱስ አገልጋዮች ከሆኑት ከጳውሎስና ከጢሞቲዎስ፤ በክርስቶስ ኢየሱስ ቅዱሳን ለሆኑ በፊልጵስዩስ ከተማ ከእረኞችና ከዲያቆናት ጋር ለሚኖሩ
ሁሉ። 2 ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለአናንተ ይሁን። 3 ስለእናንተ በማስብበት ሁሉ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። 4
ስለ ሁላችሁም በምጸልይበት ጊዜ ሁሉ በደስታ እጸልያለሁ። 5 ከመጀመሪያ ጀምሮ እስካሁን ወንጌል በሚሰበክበት ሥራ ስላሳያችሁት ትብብራችሁ
እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። 6 ይህን መልካም ሥራ በእናንተ ውስጥ የጀመረው ኢየሱስ ክርስቶስ እስከሚመለስ ቀን ድረስ እንደሚፈጽም እርግጠኛ ነኝ። 7
እናንተ በልቤ ስላላችሁ ስለ ሁላችሁ እንዲህ ማሰብ ይኖርብኛል። በእስራቴና ስለ ወንጌል በመቆሜ ስለእርሱም በመመስከሬ ሁላችሁም በጸጋ ተባባሪዎች
ሆናችኋል። 8 በኢየሱስ ክርስቶስ ባለኝ ጥልቅ ፍቅር ሁላችሁንም እንድምናፍቃችሁ እግዚአብሔር ምስክሬ ነው። 9 ፍቅራችሁ በዕውቀትና በሙሉ መረዳት
የበለጠ እንዲበዘላችሁ እጸልያለሁ። 10 ይህን የምጸልይበት ምክንያት የተሻለውን ነገሮችን መርምራችሁ እንድታውቁ እንዲሁም ክርስቶስ ተመልሶ በሚመጣበት
ቀን ንጹኃንና ነውር የሌለባችሁ ሆናችሁ እንድትገኙ ነው። 11 ይህ ደግሞ ከኢየሱስ ክርስቶስ በሚገኘው የጽድቅ ፍሬ ተሞልታችሁ ለእግዚአብሔር ክብርና
ምስጋና እንዲሆን ነው። 12 ወንድሞች ሆይ፥በእኔ ላይ የደረሰው ሁሉ ወንጌል በጣም እንዲስፋፋ እንዳደረገ እንድታውቁ እወዳለሁ። 13 እኔም የታሰሁት
በክርስቶስ ምክንያት መሆኑን የቤተ መንግሥት ጠበቂዎችና ሌሎችም እዚያ ያሉት ሰዎች ሁሉ እንዲያውቁ ሆኖአል። 14 በእኔ መታሰር ምክንያት በጌታ
ወንድሞች ከሆኑት ብዙዎቹ የበለጠ ከቀድሞ ይልቅ የእግዚአብሔርን ቃል ያለ ፍርሃት ለመናገር ድፍረት አግኝተዋል። 15 በርግጥ አንዳንዶቹ የክርስቶስን
ወንጌል የሚሰብኩት በቅናትና በፉክክር መንፈስ ነው፤ሌሎቹ ግን ክርስቶስን የሚሰብኩት በቅን ልቡና ነው። 16 እነዚህ የእግዚአብሔርን ቃል በቅን ልቡና
የሚሰብኩት ከፍቅር የተነሳ ነው፤እነርሱም እኔ ስለወንጌል ቆሜ በመከራከርይ መታሰሬን ያውቃሉ። 17 እነዚያ ግን ስለ ክርስቶስ የሚሰብኩት በራስ ወዳድነትና
ቅንነት በሌለበት አስተሳሰብ ነው። በእስራቴም ላይ ተጨማሪ መከራ ሊያመጡብኝ አስበው ነው። 18 ታዲያ ምን ይደረግ? በርግጥ በዚህ ደስ
ይለኛል፤በማስመሰል ወይም በእውነት በሁሉም መንገድ ክርስቶስ ይሰበካል። 19 ምክንያቱም በእናንተ ጸሎትና በኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ርዳታ ነጻ
እንደምወጣ አውቃለሁ። 20 እንደማላፍርበት በሙሉ መተማመ እጠባበቃለሁ። ነገር ግን ዘወትር እንደማደርገውና በተለይም ዛሬም በሕይወት ብኖር ወይም
ብሞት ክርስቶስ በሰውነቴ ይከብራል ብዬ በድፍረት እናገራለሁ። 21 ስለዚህ ለእኔ ሕይወት ማለት በክርስቶስ መኖር ነው፤ ሞትም ማለት ማትፍረፍ ነው። 22
ነገር ግን በሥጋ መኖር ለእኔ የሥራ ፍሬ ቢሆን የትኛውን እንደምመርጥ አላውቅም። 23 ምክንያቱም በእነዚህ በሁለቱ አሳቦች መካከል ተወጥሬአለሁ። በአንድ
በኩል ከክርስቶስ ጋር መሆን ከሁሉ የሚበልጥ ነገር ስለሆነ ከዚህ ሕይወት ተለይቼ ከክርስቶስ ጋር መሆንን እፈልጋለሁ። 24 ሆኖም በሥጋ መኖሬ ለእናንተ
የበለጠ አስፈላጊ ነው። 25 እምነታችሁ እንዲያድግና ደስታን እንድታገኙ እንደምቆይና ከሁላችሁም ጋር እንደምቀጥል ስለዚህ ነገር እተማመናሉ። 26 በዚህ
ምክንያት እኔም እንደገና ወደ እናንተ ስመጣት ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ በእኔ ትመካላችሁ። 27 እንግዲህ ከሁሉም በላይ ሕይወታችሁ ለክርስቶስ ወንጌል
እንደሚገባ ይሁን፤ ይህም እኔ መጥቼ ባያችሁ ወይም ከእናንተ ብርቅ በአንድ መንፈስ ጸንታችሁ መቆማችሁንና ለወንጌልም እምነት በኅብረት መጋደላችሁን
እሰማ ዘንድ ነው። 28 ተቃዋሚዎቻችሁንም በምንም ነገር አትፍሩአቸው፤ ይህም ለእነርሱ የመጥፋታቸው ምልክት ሲሆን፤ ለእናንተ ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ
የሆነ የመዳናችሁ ምልክት ነው። 29 ምክንያቱም ከክርስቶስ የተነሳ ይህ የተሰጣችሁ አገልግሎት በእርሱ እንድታምኑ ብቻ ሳይሆን በእርሱ ምክንያት መከራ
እንድትቅበሉም ጭምር ነው። 30 ስለዚህ አሁን ከእኔ ጋር የመከራ ተካፋዮች ሆናችኋል፤ ይህም መከራ ከዚህ በፊት ደርሶብኝ ያያችሁትና አሁንም እየደረሰብኝ
መሆኑን የሰማችሁት ነው።

Philippians 1:1

ጳውሎስና ጢሞቲዎስ በቋንቋችሁ ደራሲዎችን ለማስተዋወቅ የተለየ መንገድ ካለ እዚህ ላይ ተጠቀሙበት። ትኩረት፡ ''ከጳውሎስና ጢሞቲዎስ'' ወይም ''እኛ ጳውሎስና ጢሞቲዎስ ይህን ደብዳቤ ጽፈናል።''
የክርስቶስ ኢየሱስ አገልጋዮች ''እኛየክርስቶስ ኢየሱስ አገልጋዮች ነን'')
በክርስቶስ ኢየሱስ ቅዱሳን ሆነው ለተለዩት ሁሉ ''በክርስቶስ ኢየሱስ አማኝ ለሆኑ ሁሉ'' ለእረኞችና ዲያቆናት ትኩረት፡''የቤተ ክርስቲያን መሪዎች'' ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን ይህ ለሌሎች በረከት እንዲሆንላቸሁ መመኘት የሚገለጽበት መንገድ ነው። ለእናንተ እዚህ ላይ ''እናንተ'' የሚያመለክተው በፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ አማኞችን ነው።

እግዚአብሔር አባታችን እዚህ ላይ''የእኛ'' የሚያመለክተው ምናልባት ጳውሎስንና ጢሞቲዎስን ጨምሮ በክርስቶስ አማኞችን ሁሉ እና የፊልጵስዩስ አማኞችን ነው።

Philippians 1:3

አመሰግናለሁ፤እጸልያለሁ፤ምስጋና አቀርባለሁ እዚህ ላይ
''እኔ'' ጳውሎስን ያመለክታል እናንተ እዚህ ላይ ''እናንተ'' የፊልጵስዩስ አማኞችን ያመለክታል። በወንጌል ስላላችሁ ኅብረት አመሰግናኋለሁ ጳውሎስ የፊልጵስዩስ ሰዎች ወንጌል በመስበካቸው እግዚአብሔርን ያመሰግናል። ትኩረት፡''ወንጌል በመስበካችሁ እግዚአብሔርን አመሰግናናለሁ'' ትምክህት አለኝ ''እርግጠኛ ነኝ'' በእናንተ የጀመረው ''የጀመረው እግዚአብሔር'' ይፈጽመዋል ''ይህን ለመፈጸም ይቀጥላል''

Philippians 1:7

ይህ ለእኔ ትክክል ነው ''ይህ ለእኔ ተገቢ ነው'' ወይም ''ይህ ለእኔ መልካም ነው።''
እናንተ በልቤ አላችሁ ትኩረት፡ ''በጣም እወዳችኋለሁ''

በጸጋው ተባባሪዎች ናችሁ ትኩረት፡''ከእኔ ጋር የጸጋ ተካፋዮች ሆናችኋል'' ወይም '' ከእኔ ጋር የጸጋው ተካፋዮች'' እግዚአብሔር ምስክሬ ነው ትኩረት፡ ''እግዚአብሔር ያውቃል'' ወይም '' እግዚአብሔር ይገበዋል'' በክርስቶስ ኢየሱስ ጥልቅ ፍቅር ይህ ሐረግ ''በጥልቅ ፍቅር'' የሚያመለክተው በውስጣችን ከስሜት ክፍል የሚወጣበት ቦታ ነው።''

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Philippians 1:9

የሚያገነኛው ዐረፍተ ነገር፡ ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ አማኞች እንደሚጸልይና ለጌታ መከራ መቀበል ደስታ እንዳለው ይናገራል።
እንዲበዘላችሁ ''ይተረፍላችኋል'' በዕውቀትና በሙሉ መረዳት ትኩረት፡''እግዚአብሔርን የሚያስደስተውን ባወቃችሁና በተርዳችሁ መጠን''

ይህን አደርጋለሁ ''ይህን እጸልያለሁ'' የተሻሉ ነገሮች ትኩረት፡'' በጣምእ ግዚአብሔርን የሚያስደስት ነገር'' ንጹኃንና ነውር የሌለባችሁ ''ንጹኃን" እና "ነውር የሌለባችሁ" የሚሉ ቃላት መሠረታዊ ነገሩ ተመሳሳይ ነው። ጳውሎስ የሞራል ንጽሕናን ለመግለጽ አንድ አድርጎ ያገናኘዋል''

በክርስቶስ ቀን ''በጌታ ቀን'' ወይም '' በፍርድ ቀን'' ትሞላላችሁ ትኩረት፡ '' ኢየሱስ ክርስቶስ የበለጠ እግዚአብሔርን እንድትታዘዙ ያደርጋችኋል''

በጽድቅ ፍሬዎች ትሞላላችሁ ይህ አማኞች እግዚአብሔርን ለመታዘዝ በዛፍ ላይ የሚያፈሩትን ፍሬ ያስተያያል።

ለእግዝዚአብሔር ክብርና ውዳሴ ይህ በተለየ ሁኔታ ሊተረጎም ይችላል። ትኩረት፡ ''እናንተ መልካም ያደረጋችሁትን ሰዎች አይተው እግዚአብሔርን እንዲያመሰግናሉ እንዲሁም ለእግዚአብሔር ክብር ይሰጣሉ።

Philippians 1:12

እንግዲህ እፈልጋለሁ
እዚህ ላይ ''እንግዲህ''የሚለው የደብዳቤውን አዲስ ክፍል ለማድረግ ጥቅም ላይ ውሎአል። ወንድሞች እዚህ ላይ ይህ ማለት ከሰማያዊው እግዚአብሔር ጋር በክርስቶስ ያመኑ ሁሉ አንድ መንፈሳዊ ቤተ ሰብ ስለሆኑ ወዶችንና ሴቶችን ጨምሮ ክርስቲያን ወዳጆችን ነው። በእኔ የሆኑ ነገሮች ጳውሎስ የሚናገረው በእስር ቤት የነበረበትን ጊዜ ነው። ትኩረት፡ "ይህን ሁሉ መከራ የተቀበልኩት የኢየሱስን ወንጌል እንድሰብክ በእስር ቤት የተጣልኩበት'' የቤተ መንግሥት ጠባቂዎች እንግዲህ በጌታ ወንድሞች የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራሉ ትኩረት፡ '' እኔ በመታሰሬ ምክንያት ብዙ በጌታ የሆኑ ወንድሞች የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራሉ'' በበለጠ ድፍረትና ያለ ፍርሃት ጳውሎስ የሚገልጸው በአዎንታዊና አሉታዊ ተመሳሳይ አሳብን በአደገኛ ሁኔታ ላይ ሆነው ወንጌልን በታላቅ ድፍረት መስበካቸውን ለመግለጽ ነው። ትኩረት፡ '' በታላቅ ድፍረትና ያለ ፍርሃት''

Philippians 1:15

አንዳንዶች ክርስቶስን ሰበኩ ትኩረት፡
''አንዳንድ ሰዎችስለ ክርስቶስ የምሥራች ይሰብካሉ በቅናትና በፉክክር ትኩረት፡ '' ሰዎች እኔን ለመስማት ባለመፈለጋቸው ችግር ለመፍጠር ይፈልጋሉ'' እንዲሁም ሌሎች ከቅን ልቦና ትኩረት፡ ''ነገር ግን ሌሎች ቸሮችና ለመርዳት በመፈለጋቸው አድርገውታል'' አንዳንዶች ''ሰዎቹ ለዚህ ተመድቤአለሁ ትኩረት፡ '' እግዚአብሔር መርጦኛል" ወንጌልን ለመደገፍ ትኩረት፡ "የኢየሱስ መልእክት እውነት መሆኑን ሁሉንም ለማስተማር'' "ነገር ሌሎች ክርስቶስን ይሰብካሉ" በቅናትና በቅን ልቦና። በእስራቴ በምቀበለው መከራ እየጨመሩብኝ ያስባሉ"

Philippians 1:18

x
እንግዲህ ምን ይደረግ ጳውሎስ አንዳንድ ሰዎች ስለ ክርስቶስ የሚሰብኩት አስፈላጊ አይደለም። ትኩረት፡ ''አይመለከተኝም'' በየትኛውም መንገድ በማስመሰል ወይም በእውነት ክርስቶስ ይሰበካል ትኩረት፡ ''ሰዎች ስለ ክርስቶስ እስከሰበኩ ድረስ በመልካም ወይም በመጥፎ ምክንያት ቢያደርጉትም ምንም አይደለም" በዚህ ሁሉ ደስ ይለኛል ትኩረት፡ ሰዎች ስለ ክርስቶስ በመስበካቸው ደስ ይለኛል" እደሰታለሁ "በዓል አደርጋለሁ'' ወይም ''እደሰታለሁ'' ይህ ለእኔ ነፃ መውጣትን ያመራልታል ትኩረት፡ '' እግዚአብሔር ከእስራቴ ነፃ ያወጣኛል" በእናንተ ጸሎትና በኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ርዳታ ትኩረት፡ "እናንተ ስለምትጸልዩና የኢሱስ ክርስቶስ መንፈስ እየረዳኝ ነው።" የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ትኩረት፡ "መንፈስ ቅዱስ"

Philippians 1:20

x
ይህ ትምክቴና በእርግጠኝነት የምጠብቀው ነው እዚህ ላይ"በትምክት የምጠብቀው" እና "በርግጠኝነት" የሚሉ ቃላት የሚናገሩት በመሠረቱ ተመሳሳይ ነው። ጳውሎስ የሚጠቀመው በተያያዘው የእርሱ አጠባበቅ ምን ያህል ጠንካራ እንደሆነ ለመግለጽ ነው። ትኩረት፡" እኔ ሙሉ ለሙሉ አምናለሁ"

ነገር ግን በሙሉ ድፍረት ሁልጊዜ እንደሚደረግና በተለይም በአሁኑ ጊዜ ትኩረት፡ "ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ ሁልጊዜ እንዳለኝ ሁሉ ሙሉ ድፍረት አለኝ።'' በሥጋዬ ለክርስቶስ ክብርን አመጣለሁ ጳውሎስ የራሱን ሕይወት ለማቅረብ አካላዊ "ሥጋ" ይጠቀማል። ትኩረት፡ "በማደርገው ሁሉ ክርስቶስን አከብራለሁ።

በሕይወቴ ወይም በሞቴ ትኩረት፡ "በሕይወት ብኖር ወይም ብሞት"

Philippians 1:22

ነገር ግን በሥጋ መኖር የሥራዬ ፍሬ ቢሆን
''ፍሬ'' የሚለው ቃል የጳውሎስ መልካም ውጤትን ያመለክታል። ትኩረት፡ '' ነገር ግን በሥጋ መኖሬ ሰዎች በክርስቶስ እንዲያምኑ ለማገዝ የበለጠ ዕድል ይሰጠኛል።'' በሥጋ መቆየቴ ለእናንተ የበለጠ አስፈላጊ ነው ትኩረት፡ ''በሥጋ መኖሬ ለእናንተ የበለጠ የሚረዳ ነው''

Philippians 1:25

x
ስለዚህ ነገር እርግጠኛ ከሆንሁ ''እርግጠኛ ከሆንሁ'' እንደምቆይ አውቃለሁ ''በሕይወት ለመኖር እንደምቀጥል አውቃለሁ'' ወይም ''መኖሬን እንደምቀጥል አውቃለሁ'' ከሁላችሁ ጋር መኖሬን እቀጥላለሁ ''ሁላችሁንም ማገልገሌን እቀጥላለሁ'' በዚህ ምክንያት እኔም እንደገና ወደ እናንተ ስመጣ ስለ ክርስቶስ በእኔ ትመካላችሁ ትኩረት፡ ''እንግዲህ እንደገና ወደ እናንት ስመጣ እኔ ስለ ክርስቶስ ስላደረግሁት በእኔ ትመካላችሁ ምክንያቱም'' ሕይወታችሁ እንደሚገባ ብቻ ይሁን ''ሕይወታችሁ እንደሚገባ ብቻ ኑሩ'' በአንድ መንፈስ በአንድ ነፍስ ጸንታችሁ ቁሙ፤ እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉሞችንና የህብረትን አስፈላጊነት ይገልጻሉ። ''ምንፈስ'' እና ''ነፍስ'' የሚሉ ቃላት አእምሮንና ስሜትን ይገልጻሉ። ትኩረት፡ '' ሁሉም የቅቆረጠ ተመሳሳይ ዓላማና አብሮ መሥራት ፍላጎት አላቸው''
ስለ ወንጌል እምነት ትኩረት፡ ''በወንጌል ላይ የተመሠረተ እምነትን ለማሠረጫት'' ወይም '' የምሥራቹ ቃል እንደሚያስተምረን ለመኖር ማመን'' (UDB)

Philippians 1:28

x
በአንዳች አትፍሩ ይህ ለፊጵስዩስ አማኞችትእዛዝ ነው።

ከሚቃወሙአችሁ ''በሚታደርጉት ነገር ላይ ከሚቃወሙአችሁ'' ለእነርሱ የመጥፋታችው ምልክት ለእኛ ግን ከእግዚአብሔር የሚሆን የመዳናችን ምልክት ነው ትኩረት፡''ምክንያቱም ድፍረታችሁ የሚያሳያቸው እግዚአብሔር እነርሱን እንደሚያጠፋቸው ነገር ግን እናንተን እንደሚያድናችሁ ነው''

በእኔ ያያችሁት መከራ ስለ ተቀበላችሁ አሁንም በእኔ እየተፈጸመ እንዳለ ሰምታችኋል ትኩረት፡ ''ይህም መከራ ከዚህ በፊት ደርሶንኝ ያያችሁትና አሁንም እየደረሰብኝ መሆኑን የሰማችሁት ነው።

ምዕራፍ 2

1 በክርስቶስ መበረታታት ካላችሁ፤ከፍቅሩም መጽናናት ካላችሁ፤የመንፈስም ኅብረት ካላችሁ፤እርስ በእርሳችሁም ደግነትና ርኅራኄ ካላችሁ። 2 ስለዚህ በአንድ
አሳብ፤ በፍቅር፤ በመንፈስ አንድነት፤በአንድ ዓላማ እየተስማማችሁ ደስታዬ እንዲፈጸም አድርጉት። 3 በራስ ወዳድነት ወይም በከንቱ ትምክህት ምንም
አታድርጉ፤ነገር ግን በዚህ ፈንታ ሌሎች ሰዎች ከእናንተ እንደሚሻሉ በትህትና ቁጠሩ። 4 እንዲሁም እያንዳንዳችሁ የራሳችሁን ጥቅም ብቻ ሳይሆን የሌላውንም
ሰው ጥቅም አስቡ። 5 በኢየሱስ ክርስቶስ የነበረ አሳብ በእናንተም ደግሞ ይኑር፤ 6 እርሱም የመለኮት ባሕር ነበረው፥ ነገር ግን ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር እኩል
የሚያደርጋውን የመለኮት ባሕይ እንደ ያዘ አልቆጠረም። ክብሩን ትቶ ራሱን ባዶ አደረገ። 7 የባሪያንም መልክ ያዘ፤ በሰው አምሳል ተገለጠ፤ እንደ ሰውም ሆኖ
በትህትና ራሱን ዝቅ አደረገ። 8 እንዲሁም እስከ ሞት፤ያውም እስከ መስቀል ሞት ድረስ ታዛዥ ሆነ። 9 ስለዚህም እግዚአብሔር ከሁሉ በላይ ከፍ ከፍ
አደረገው፤ ከስም ሁሉ በላይ የሆነ ስም ሰጠው። 10 በዚህም ምክንያት ጉልበት ሁሉ በሰማይና በምድር፤ ከምድርም በታች ሁሉ በኢየሱስ እግሮች በታች
እንዲንበረከኩ ነው። 11 አንደበትም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር እንዲሆን፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ነው ብሎ እንዲመሰክር ነው። 12 ስለዚህ ወዳጆቼ ሆይ፤
እኔ ከእናንተ ጋር በነበርኩበት ጊዜ ሁሉ እንደምትታዘዙ፥ይልቁንም አሁን ከእናንተ በራቅሁበት ጊዜ ይበልጥ ታዛዦች እንድትሆኑ ነው። 13 በፍርሃትና
በመንቀጥቀጥም መዳናችሁን ሥሩ። ምክንያቱም ለመልካምነቱ መፍቃዱንና ማድረግን በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነው። 14 ማናቸውንም ነገር
ሳታጉረምግሙና ሳትከራከሩ አድርጉ። 15 ይህን በማድረግ ነውርና ነቀፋ የሌለባችሁ ታማኝ የእግዚአብሔር ልጆች ትሆናላችሁ። በዚህ በጠማናና በመጥፎ
ትውልድ መካከል በዚህ ዓለም እንደ ደማቅ ብርሃን ታበራላችሁ። 16 ሕይወት የሚገኝበትን ቃል አጥብቃችሁ በምትይዙበት ጊዜ በከንቱ እንዳልሮጥሁና
በከንቱም እንዳልደከምሁ ክርስቶስ በሚመለስበት ቀን ለማክበር ምክንያት ሊኖረኝ ይችላል። 17 ነገር ግን ለእግዚአብሔር በእምነት በምታቀርቡት መሥዋዕትና
አገልግሎት ላይ የእኔም ሕይወት እንደ መሥዋዕት ሆኖ ቢቀርብ እንኳ ደስ ይለኛል። ከሁላችሁ ጋር ታላቅ ደስታ እደሰታለሁ። 18 እንዲሁም በተመሳሳይ ሁኔታ
እናንተም ከእኔ ጋር ደስተኞች ትሆናላችሁ። 19 ነገር ግን እናንተ እንዴት እየሠራችሁ እንዳላችሁ ሰምቼ እንድጽናና ጢሞቲዎስን ወደ እናንተ ፈጥኜ እንደምልክ
በጌታ በኢየሱስ ተስፋ አደርጋለሁ። 20 ስለ እናንተ ሁኔታ ከልብ የሚያስብ ከጢሞቲዎስ በስተቀር ሌላ ሰው የለኝም። 21 ሌሎቹ ግን የራሳቸውን ጥቅም ብቻ
ስለሚፈልጉ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ግድ የላቸውም። 22 ነገር ግን ጢሞቲዎስ ልጅ አባቱን እንደሚያገለግል ከእኔ ጋር ወንጌልን በማሠራጨት እንዳገለገለና
ስለታማኝነቱም የተመሰከረለት መሆኑን እናንተም ታውቃላችሁ። 23 ስለዚህ የእኔን ሁኔታ እንዳወቅሁ በፍጥነት ጢሞቲዎስን ወደ እናንተ እንደምልክላችሁ ተስፋ
አደርጋለሁ። 24 እንዲያውም እኔ ራሴ በቶሎ ወደ እናንተ እንደምመምጣት በጌታ እተማመናለሁ። 25 ነገር ግን ኤጳፍሮዲቱስን መልሼ ወደ እናንተ መላክ
አስፈላጊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። እርሱ እኔን በሚያስፈልገኝ ሁሉ እንዲረዳኝ ልካችሁት የነበረውን ወንድሜና ከእኔ ጋር የተሰለፈ ወታደርና የሥራ ባልደረባዬ ነው። 26
እርሱን ወደ እናንተ የምልከውም ሁላችሁንም ለማየት በመናፈቁና እናንተም መታመሙን በመስማታችሁ ስለ ተጨነቀ ነው። በእርግጥ በጠና ታሞ ለሞት ተቃርቦ
ነበር፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ምሕረት አደረገለት። 27 ከሕመሙ መዳኑ ለእርሱ ብቻ ሳይሆን ሐዘን በሐዘን ላይ እንዳይደረብብኝ ለእኔም ጭምር ነው። 28
ስለዚህ እናንተ እርሱን በማየት እንድትደሰቱና የእኔም ሐዘን እንዲቃለል እርሱን ወደ እናንተ ለመላክ ከፍተኛ ፍላጎት አድሮብኛል። 29 እንግዲህ ኤጳፍሮዲቱስን
በሙሉ ደስታ በጌታ ተቀበሉት። እንደ እርሱ ያሉትን ሰዎች አክብሩአቸው ። 30 በቅርብ ተገኝታችሁ ልታደርጉልኝ ያልቻላችሁትን በእናንተ ቦታ ሆኖ ሲያገለግለኝና
የሚያስፈልገኝን ለማሟላት ስለ ክርስቶስ ሥራ በማለት ለሕይወቱ ሳይሳሳ በማድረግ ለሞት ተቃርቦ ነበር።

Philippians 2:1

የሚያገናኝ ዐረፍተ ነገር ጳውሎስ አማኞችን ህብረትና ትህትና እንዲኖራቸው ይመክራቸዋል፤እንዲሁም የክርስቶስን ምሳሌ ያስታውሳቸዋል። ስለዚህ ምንም ቢሆን፤ ምንም ቢሆን፤ ምንም ቢሆን ጳውሎስ ''ቢሆን'' የሚለውን የዐረፍተ ነገር መመሠረቻ ቃል የሚጠቀመው እነዚህ ሁሉ የሚከሰቱ መሆናቸውን ለማመልከት ነው። ትኩረት፡ '' እስካለ ድረስ፤እስካለ ድረስ'' የመንፈስ ህብረት ''ከመንፈስ ጋር ህብረት'
x

Philippians 2:3

x
በራስ ወዳድነት ወይም በከንቱ ምኞት አንዳች አታድርጉ ትኩረት፡ ''ራሳችሁን ብቻ የሚያስደስት ወይም ከሌሎች ይልቅ የበለጠ አስፈላጊ እንደሆናችሁ የሚያደርጋችሁን ከቶ አታድርጉ።'' ለራሳችሁ ብቻ የሚያስፈልጋችሁን አትፈልጉ ትኩረት፡ '' ለራሳችሁ ብቻ የሚያስፈልጋችሁን አትመልከቱ።''

Philippians 2:5

x
በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ አሳብ በእናንተ ይሁን እዚህ ላይ ''አሳብ'' የአንድ ሰው ዝንባሌ ወይም እንዴት እንደሚያስቡ እንደሆነ ያመልክታል። ትኩረት፡ ''በክርስቶስ ኢየሱስ ያለ አሳብ በእናንተ ይኑራችሁ'' ወይም '' ነገሮችን ክርስቶስ ኢየሱስ በሚያስብበት መንገድ አስቡ''

Philippians 2:9

x
እግዚአብሔር ከሁሉ በላይ ከፍ አደረገው '' እግዚአብሔር ኢየሱስን ከሁሉ በላይ ከፍ አደረገው'' ከስሞች ሁሉ በላይ እዚህ ላይ ''ስም'' ማዕረግ ወይም ያመለክታል። ትኩረት፡ "ከማዕረግ ሁሉ በላይ" ወይም "ከክብርም ሁሉ በላይ"
ጉልበት ሁሉ እዚህ ላይ "ጉልበት" የሰው ሁለንተና ነው። ትኩረት፡ "እያንዳንዱ ሰው" ወይም "ማንኛውም ፍጥረት"

ከምድር በታች ይህ የሚያመለክተው ሰዎች ከሞቱ በኋላ የሚሄዱበት ቦታ፤ "ገሀነም" የሚጠራ፤እንዲሁም አጋንንት የሚኖሩበት ጨለማ/ጥልቅ ገደል ተብሎ የሚጠራ።" እዚህ ላይ "ምላስ" የሰው ሁለንተናን ያመለክታል። ትኩረት፡ "እያንዳንዱ ሰው" ወይም "እያንዳንዱ ፍጥረት"

Philippians 2:12

x
የሚያገናኝ ዐረፍተ ነገር፡ ጳውሎስ በሌሎች ፊት የክርስትና ሕይወት እንዴት እንደሚኖሩ የፊልጵስዩስ አማኞችን የበረታታል፤ የእርሱንም ምሳሌ ያስታውሳቸዋል። የተወደዳችሁ ትኩረት፡"በእምነት ውድ ወዳጆቼ" እኔ ባለሁበት ትኩረት፡"እኔ ከእናንተ ጋር በምሆንበት" እኔ በራቅሁበት ትኩረት፡ "ከእናንተ ዘንድ በሌለሁበት ጊዜ" መዳናችሁን ፈጽሙ ትኩረት፡ "እግዚአብሔርን መታዘዝ ቀጥሉ" በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ "ፍርሃትና መንቀጥቀጥ" የሚሉ ቃላት የሚናገሩት መሠረታዊ ነገሩ ተመሳሳይ ነው። ጳውሎስ በእግዚአብሔር ክብር እንዲኖር ለመግለጽ ይጠቀማል። ትኩረት፡

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

"ጥልቅ ክብር" ፍቃዱንና ማድረግን እግዚአብሔር የእርሱን ሥራ እንድንሠራ ያበረታተናል ያስችለንማል።

Philippians 2:14

x
ነውርና ነቀፋ የሌላችሁ ጳውሎስ ተመሳሳይ አሳብን በአዎንታዊና አሉታዊ ቃላትን በመጠቀም ይገልጻል። ትኩረት:"ፍጽም ንፁሐን" ያለ ነቀፋ ትኩረት:"ያለ ነውር" ወይም "ፍጹም" ብርሃን ታበራላችሁ ይህ እግዚአብሔርን በማያከብሩ ሰዎች መካከል እግዚአብሔርን እያከበሩ በጨለማ ብርሃን እያበሩ የሚኖሩ አማኞችን ያወዳድራል ።ትኩረት: "እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ ኑሩ" በዓለም ላይ እዚህ ላይ "ዓለም" እግዚአብሔርን የማያከብር እሴትና አስተሳሰብን ያሳያል። በጠማማና በመጥፎ እነዚህ ሁለት ቃላት ማለት በመሠረቱ ተመሳሳይ ነው። ጳውሎስ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ትውልዱ ምን ያህል ክፉ እንደሆነ ለመግለጽ ነው።ትኩረት:"ፍጹም ክፉ" ለክብር "ሐሴት ለማድረግ" ወይም "ለመደሰት" በክርስቶስ ቀን ይህ ኢየሱስ መንግሥትን ለማጽናትና ምድርን ለመግዛት በሚመጣበት ጊዜ መሆኑን ያመለክታል። ትኩረት: "ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ" በከንቱ አልሮጥም ወይም በከንቱ አልደክምም "በከንቱ መሮጥ" እና "በከንቱ መድከም" የሚሉ ሐረጎች እዚህ ላይ የሚሉት ተመሳሳይ ነገር ነው። ጳውሎስ ሰዎች በክርስቶስ እንዲያምኑ ያደረገው ምን ያህል ከባድ እንደሆን ለመግለጽ ነው። ትኩረት: "እንግዲህ የደከምሁት በከንቱ አይደለም"

Philippians 2:17

x
ነገር ግን የእኔ ሕይወት እንደ መሥዋዕት ሆኖ ቢቀረ እንኳ ደስ ይለኛል፤ ከሁላችሁ ጋር ታላቅ ደስ ይለኛል ጳውሎስ የራሱ ሞት ከብሉይ ኪዳን ወይን ወይም የወይራ ዘይት በእንስሳት መሥዋዕት ላይ ወይም አጠገብ መሥዋዕት አቅራቢ ለእግዚአብሔር እንደሚያፈስ ዓይነት ያወዳድራል። ጳውሎስ እያለ ያለው እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ከሆነ ለፊልጵስዩስ ሰዎች በደስታ ልሞት እንደሚገባ ነው። ትኩረት: "ነገር ግን ሮማውያን ሊሰቅሉኝ ቢወስኑ እንኳ የእኔ ሞት ለእናንተ እምነትና ደስታ የሚያደርግ ከሆነ የበለጠ እግዚአብሔርን የሚያስደስት ከሆነ እጅግ ደስ ይለኛል" በተመሳሳይ ሁኔታ ትኩረት: "በተመሳሳይ ሁኔታ" በታላቅ ደስታ ጋር መደሰት አለባችሁ "ከታላቅ ደስታ ጋር መደሰት" የሚለው ሐረግ ለመግለጽ ይጠቀማል። ትኩረት: "ከእኔ ጋር በታላቅ ደስታ እንድትደሰቱ እፈልጋለሁ"

Philippians 2:19

x
የሚያገናኝ ዐረፍተ ነገር: ጳውሎስ ጢሞቲዎስን እንደሚልክላቸው አሳብ እንዳለና ኤጳፍሮድጡን በልዩ ሁኔታ እንዲያስተናግዱ ይነግራል። ነገር ግን በጌታ ኢየሱስ እጠብቃለሁ ትኩረት: "ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ፈቃዱ ከሆነ እጠብቃለሁ" ስለ እነርሱ ሁሉ እዚህ ላይ "እነርሱ" የሚለው ቃል ጳውሎስ ወደ ፊልጵስዩስ ለመላክ መተማመን የማይችላቸው የሰዎች ቡድን ናቸው። ጳውሎስ ደግሞ መሄድ የነበረባቸው ነገር ግን ጳውሎስ መልእክታቸውን ለመፈጸም ያልታመነ፤ ከቡድኑ ጋር ደስተኛ አለመሆኑን እየገለጸ ነው።

Philippians 2:22

x
ጢሞቲዎስ ራሱን አረጋገጠ ትኩረት: "ጢሞቲዎስ ለኢየሱስ ነገሮች ጥንቃቄ መውሰድ አሳይቶአል"

ልጅ አባቱን እንደሚያገለግል እኔን አገለገለኝ ጳውሎስ የጢሞቲዎስን አገልግሎት ከእርሱ ጋር ልጅ አባቱን እንደሚያግልግል ያወዳድራል።

በወንጌል ሥርጭት ትኩረት:" ለሰዎች ስለ ወንጌል መንገር" በጌታ እታመናለሁ እኔ ራሴ ቶሎ እመጣለሁ ትኩረት: "የጌታ ፈቃድ ከሆነ ቶሎ እንደምመጣ እርግጠኛ ነኝ"

Philippians 2:25

x
ኤጳፍሮዲቱስን ይህ ሰው ጳውሎስን በእስር ቤት እንዲያገለግል የተላክ ነው። አብሮኝ የሚሠራና ወታደር እዚህ "ወታደር" ጦርነትን ከሚዋጋ ሰው መንፈሳዊ ጦርነት ከሚዋጋ አማኝ ጋር የሚነፃፀር ነው። ጳውሎስ አማኙ ወንጌልን ለማሰራጨት ከክፉ ጋር የሚያደርገው ትግል ለመግለጽ ነው። ትኩረት:"በእምነት ከእኛ ጋር አብሮ የሚሠራና የሚታገል" መልእክተኛና በሚያስፈልገኝ አገልጋይ ትኩረት: "መልእክቶቻችሁን ወደ እኔ የሚያመጣና በሚያስፈልገኝ የሚረዳኝ" በጥልቀት አዝኖአል፤ ከሁላችሁ ጋር ለመሆን ፈልጎአል ሐዘን ላይ ሐዘን ትኩረት:በእስር ላይ እያለሁ ሐዘን ላይ ሐዘንን ልጨምርብኝ ነበር"

Philippians 2:28

x
ኤጳፍሮዲቱስን ተቀበሉት "ኤጳፍሮዲቱስን ተቀበሉት" በጌታ ከሁሉ ደስታ ጋር ትኩረት: "በጌታ በእምነት አብሮ የሚሠራ" ወይም "ጌታ ኢሱስ ስለሚወደን ታላቅ ደስታ አለን"(UDB) የክርስቶስን ሥራ የሚሠራ ትኩረት:ለክርስቶስ መሥራት"(UDB) የሚያስፈልገኝን አዘጋጀ ትኩረት:"የሚያስፈልገኝን ያዘጋጃል"

ምዕራፍ 3

1 በጨረሻም ወንድሞቼ ሆይ፥ በጌታ ደስ ይበላችሁ። ከዚህ በፊት የጻፍኩላችሁን ተመሳሳይ ነግሮች አሁንም ደግሜ ብጽፍላችሁ አይታክተኝም። እነዚህ ነገሮች
እናንተን ከስሕተት ይጠብቃችኋል። 2 ከውሾች ተጠንቀቁ። ከክፉ ሠራተኞች ተጠንቀቁ፤ከሐሰተኞች መገረዝም ተጠንቀቁ። 3 እኛ በእግዚአብሔር መንፈስ
የምናመልክ፤ በሥጋም የማንታመን፤ በክርስቶስ ኢየሱስ የምንታመን የተገረዝን ነን። 4 በሥጋ ትምክሕት የሚያስፈልግ ቢሆን እኔ በብዙ ነገር ልመካ እችል
ነበረ። ማንም በሥጋ የሚመካበት አለኝ ብሎ የሚያስብ ሰው ቢኖር እኔ ከእርሱ የበለጠ የምመካበት ብዙ አለኝ። 5 እኔ በተወለድኩ በስምንተኛው ቀን
ተገርዤአለሁ፤ በትውልዴም ከብንያም ነገድ የሆንኩ እስራኤላዊ ነኝ፤ ከዚህም የተነሳ ጥርት ያልኩ ዕብራዊ ነኝ። የአይሁድን ሕግ ስለ መጠበቅም ቢሆን ፈሪሳዊ
ነበርኩ። 6 በቅንዓት ቤተ ክርስቲያን አሳድድ ነበር። ሕግን በመጠበቅ ስለ መጽደቅም ቢሆን ያለ ነቀፋ እኖር ነበር። 7 ነገር ግን ከዚህ በፊት ጠቃሚዎች ናቸው
ብዬ አምንባቸው የነበሩትን ነገሮች ሁሉ ስለ ክርስቶስ ብዬ ዋጋ እንደሌላቸው እንደ ከንቱ ነገሮች አድርጌ ቆጥሬአቸዋለሁ። 8 በርግጥ፥ ከሁሉ ይልቅ
ስለሚበልጥ ስለ ክርስቶስ ጌታዬ ዕውቀት ነገር ሁሉ ጉዳት እንዲሆን እቆጥራለሁ። ስለ እርሱም ሁሉን ነገር አጥቻለሁ። ክርስቶስንም ለማግኘትና በእርሱም
ለመገኘት ስል ሁሉን ነገር እንደ ቤት ጥራጊ እቆጥራለሁ። 9 እንግዲህ በሕግ ላይ የተመሠረተው የራሴ ጽድቅ የለኝም። በዚህ ፈንታ በክርስቶስ በኩል በሚገኝ
እምነት የእግዚአብሔር ጽድቅ አለኝ። 10 ይኸውም እርሱን የማወቅ ጽድቅ፤ የእርሱ የትንሣኤ ኃይልና የመከራው ተካፋይ የመሆንና በሞቱም ክርስቶስን
ለመምሰል ነው። 11 ደግሞም ከሙታን ትንሣኤን አገኝ ዘንድ ነው። 12 እነዚህን ነገሮች ገና አልጨበጥኩአቸውም ፤ ፍጹም ሆኜአለሁ ማለትም አልችልም። ነገር
ግን በክርስቶስ ኢየሱስ ያገኘሁትን አገኝ ዘንድ ወደ ፊት ጥረቴን እቀጥላለሁ። 13 ወንድሞች ሆይ፤እኔ ራሴ ገና እንደጨበጥኩ አልቆጥርም። ነገር ግን አንድ
ነገር አደርጋለሁ፤ ይኸውም በስተኋላዬ የነበረውን እየረሰሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እተጋለሉ። 14 እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ጠርቶ ሽልማቴን
ለማግኘት በፊት ወዳለው ግብ እሮጣለሁ። 15 ስለዚህ እኛ ብዙዎቻችን በመንፈሳዊ ሕይወት እንዳደጉ ሰዎች ነገሮችን ሁሉ ማሳብ ይኖርብናል። ደግሞ
በማንኛውም ነገር የተለያየ አስተሳሰብ ቢኖራችሁ እግዚአብሔር ሁሉንም ግልጥ ያደርግላችኋል። 16 ይሁን እንጂ በደረሰንበት በዚያው ሁኔታ እንመላለስ። 17
ወንድሞች ሆይ፥ የእኔን ምሳሌነት ተከተሉ፤ በእኛም ምሳሌነት የሚመላለሱትን ሁሉ ልብ ብላችሁ ተመልከቱ። 18 ከአሁን በፊት ብዙ ጊዜ እንደ ነገርኳችሁና
አሁንም እንባዬን እያፈሰስኩ እንደምነግራችሁ ሁሉ ብዙዎቹ በአካሄዳቸው የክርስቶስ መስቀል ጠላቶች ሆነዋል። 19 የእነርሱ አምላክ ሆዳቸው ነው፤ አሳፋሪ
የሆነ ነገርም ለእነርሱ ክብራቸው ነው፤ አሳባቸውም የሚያተኩረው በምድራዊ ነገር ላይ ነው ስለዚህ የእነርሱም መጨረሻ ጥፋት ነው፤ 20 ነገር ግን
የሚመጣውን አዳኝ ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን የምንጠብቅ የሰማይ መንግሥት ዜጎች ነን። 21 እርሱ ይህን የተዋረደውን ሰውነታችንን በመለወጥ የእርሱን
ክቡር ሰውነት እንዲመስል ያደርገዋል። ይህንንም የሚያደርገው ሁሉን በሥልጣኑ ሥር ለማድረግ በሚያስችለው ኃይል ነው።

Philippians 3:1

x
የሚያገናኝ ዐረፍተ ነገር፡ አብሮ የሚሠሩ አሮጌውን የአይሁድ ሕግ ለመከተል
የሚሞክሩትን የእምነት ወዳጆችን ለማስጠንቀቅ፤ ጳውሎስ የአማኞችን ስደት
ስለ ራሱ ምስክርነት ይሰጣል። በመጨራሻም፤ ወንድሞቼ ትኩረት፡
"ወንድሞቼ ሆይ፤ወደ ፊት ስለሚሆን፤ ወይም "ወድሞቼ ሆይ፤ስለሌሎች
ጉዳዮች" በጌታ ደስ ይበላችሁ ትኩረት፡ጌታ ስላደረጋቸው ሁሉ ደስ ይበላችሁ"
ከዚህ በፊት የጻፍኩላችሁን ተመሳሳይ ነገሮች አሁንም ደግሜ ብጽፍላችሁ
አይታክተኝም ትኩረት፡"አሁንም እነዚህን ተመሳሳይ ትምህርቶችን ብጽፍ ደስ
ይለኛል" እናንተን በሰላም ይጠብቁአችኋል እዚህ ላይ "እነርሱ" የሚለው
የጳውሎስን አስተምህርሆዎች ያሳያል። ትኩረት፡"እነዚህ ትምህርቶች ከስሕተት
ስለሚጠብቁአችሁ"

ተጠበቁ "ጥንቃቄ አድርጉ" ወይም "ተጠንቀቁ" ውሾች፤ክፉ አድራጊዎች፤
ከሐሰተኞች መገረዝ እነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች ተመሳሳይ ቡድን የሆኑ
የተለያዩ ሦስት መንገዶችን የሚገልጹ ናቸው። ውሾች "ውሾች" የሚለው ቃል
ከአይሁድ ውጪ የሆኑትን ሰዎችን ለመግልጽ አይሁዶች የተጠቀሙበት ነው።
ጳውሎስ የሐሰት አስተማሪዎችን እንደ ስድብ ከውሾች ጋር ያነጻጽራል።
በባሕላችሁ የረከሰ የተለየ እንስሳ ካለ ወይም እንደ ስድብ የሚቆጠር ካለ
በውሻ ፈንታ ይህን እንስሳ ልትጠቀሙ ትችላላችሁ። ሐሰተኛ መገረዝ
"መግረዝ" ማለት በአሰቃቂ ሁኔታ ማረድ ወይም መቁረጥ ማለት ነው።
ጳውሎስ የሐሰት አስተማሪዎችን ለመኮነን የግሪዛትን ድርጊት በተጋነነ ሁኔታ
ይገልጻል። የሐሰት አስተማሪዎች የሚሉት አንድ ሰው የተገዘ እንደሆነ ነው።
ስለዚህ እኛ እውነተኛ መገረዝ ጳውሎስ በአካል ያልተገረዙትን ነገር ግን
በመንፈሳዊ የተገረዙትን ማለትም በእምነት መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉትን
በክርስቶስ አማኝ የሆኑትን ለማሳየት ይህን ሐረግ ይጠቀማል። ትኩረት፡
"በእውነት የእግዚአብሔር ሕዝብ" በሥጋ መመካት የለም ትኩረት፡
"እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ሥጋችንን በመቁረጥ አትመኩ"

Philippians 3:4

x
እኔ ራሴ ትምክህት ልኖረኝ እችል ነበር። ፥ማንም ሰው በሥጋ ትምክህት አለኝ
ብሎ ቢያስብ እኔ እበልጠዋለሁ ይህ ለጳውሎስ ለማመን የማይቻል መላምት
ሁኔታ ነው። ጳውሎስ የሚለው እግዚአብሔር ሰዎችን በሠሩ ሥራ የሚያድን
ከሆነ እግዚአብሔር እርሱን ያድን ነበር። ትኩረት፡ "ማንም ሰው እግዚአብሔርን
ለማስደሰት በቂ ነገሮችን መሥራት የሚችል ቢሆን ኖሮ እኔ ነበርኩ" እኔ ራሴ
ጳውሎስ "እኔ ራሴ" የሚለውን የሚጠቀመው ትኩረት ለመስጠት ነው።
ትኩረት፡" በእርግጥ እኔ ነበርሁ" ተገርዤ ነበር ትኩረት፡ "ካህኑ ገርዞኝ ነበር"

ስምንተኛው ቀን "ከተወለድኩ ሰባት ቀኖች በኋላ" (UDB) ከዕብራዊ
ዕብራዊ "ዕብራዊው ልጅ ከዕብራዊ ወላጆች" ከሕግ አንፃር ፈሪሳዊ
ትኩረት፡"እንደ ፈሪሳዊ ሕግን በጠበቅ ፍጹም ነበርኩ"

Philippians 3:6

x
ቤተ ክርስቲያንን አሳድድ ነበርሁ ትኩረት፡"ክርስቲያኖችን ለመጉዳት በጣም
ቁርጠኛ ነበርኩ" ሕግን በመጠበቅ ያለ ነቀፋ ነበርኩ ትኩረት፡ " ሕግን
በመጠበቅ ፍጹም ነበርኩ" እንደ ከንቱ ቆጥሬለሁ ጳውሎስ የእርሱ የጽድቅ
ሥራዎች ሁሉ በክርስቶስ ፊት ከንቱ እንደሆነ ይደመድማል።

Philippians 3:8

x
በርግጥ "በርግጥም" ወይም "በእውነት" አሁን እቆጥራለሁ "አሁን"
የሚለው ቃል ጳውሎስ ፈሪሳዊ መሆኑን የተዋበትና በክርስቶስ አማኝ ከሆነበት
ጊዜ ጀምሮ መለወጡን ለማጉላት ነው" ትኩረት፡ "አሁን በክርስቶስ አምኛለሁ"
ሁሉን ነገር እንደ ጉዳት እቆጥራለህ ጳውሎስ ከክርስቶስ ሌላ በማንኛውም
ነገር መታመን ከንቱ እንደሆነ ይገልጻል። ትኩረት፡ "ማንኛውንም ነገር እንደ
ከንቱ እቆጥራለሁ" ከሁሉ ይልቅ ስለሚበልጠው ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ጌታዬ
ዕውቀት ትኩረት፡"የክርስቶስ ኢየሱስ ጌታዬ ዕውቀት ከሁሉ ይበልጣል" ስለ

እርሱ ሁሉ ነገር እንደ ጥራጊ እቆጥራለሁ ትኩረት:ከእርሱ የተነሣ ማንኛውንም ነገር በፈቃዴ ክጃለሁ" እንደ ቤት ጥራጊ እቆጥራለሁ ጳውሎስ አንድ ሰው የሚመካበት ነገር የሚጣል መሆኑን ያነጻጽራል። ምን ያህል ከንቱ እንደሆን ትኩረት ይሰጣራል። ትኩረት: "እንደ ጉድፍ አስባለሁ" ወይም "ፍጽም ከንቱ እንደሆኑ አስባለሁ" ስለዚህም ክርስቶስን አገኝ ዘንድ "ስለዚህ ክርስቶስ እንዲኖረኝ ብቻ" አሁን በእርሱ ተገኝቻለሁ "በእርሱ ተገኝቻለሁ" የሚለው ሐረግ ማለት ከእርሱ ጋር የቅርብ ግንኙነት ወይም ከክርስቶስ ጋር ህብረት መኖር ማለት ነው" ከሕግ የራሴ የሆነ ጽድቅ የለኝም ትኩረት:"በራሴ ሕግን በመታዘዝ እግዚአብሔርን ለማስደስት አልሞክርም" በዚህ ፈንታ አለኝ "ይልቁን ይህ አለኝ" ወይም "በቀጥታ ተቃራኒውአለኝ" ከእግዚአብሔር ያለኝ ጽድቅ በእምነት በክርስቶስ ያለኝ ነው ትኩረት: "እግዚአብሔር በክርስቶስ ባለኝ እምነት የተነሣ እግዚአብሔር ተቀብሎኛል" የትንሣኤው ኃይል ትኩረት:የእርሱ ኃይል ሕይወት እንደሚሰጥ አውቃለሁ" የእርሱ የመከራው ተካፋዮች "የመከራው ተካፋዮች" ሞቱን በሚመስል በክርስቶስ ተለውጫለሁ "መለወጥ" የሚለው ቃል ማለት አንድን ነገር በአንድ ነገር መለወጥ ማለት ነው።ኢየሱስ የሞተበት መንገድ የዘላለም ሕይወት አስገኘ። እንግዲህ ጳውሎስ የዘላለ ሕይወት ለማግኘ ሞቱ የኢየሱስን ሞት እንዲመስል ይፈልጋል። ትኩረት: "ክርስቶስ ሞቱን እንዲመስል ለውጦኛል" እንግዲህ እንደምንም ከሞት መነሳትን ለማመድ እንድችል ነው "እንደምንም" የሚለው ቃል ማለት ጳውሎስ በዚህ ዓለም ምን እንደሚሆን አያውቅም፤ ነገር ግን ምንም ቢሆን የዘላለ ሕይወት መሆኑ አይቀርም። ትኩረት: "እንግዲህ አሁን ምን ቢሆን ግድ የለም፤ ከሞትኩ በኋላ ወደ ሕይወት እመጣለሁ"

Philippians 3:12

x

የሚያገናኘው ዐረፍተ ነገር: ጳውሎስ ለአማኞች ለሚጠብቃቸው መንግሥተ ሰማያትና አዲስ ሕይወት የተነሣ የአሁኑን ሕይወት ምሳሌ እንዲከተሉ ያስጠነቀቃቸዋል። እነዚህን ነገሮች አግኝቻለሁ እነዚህ ክርስቶስን ማወቅ፤የትንሳኤውን ኃይል ማ ወቅ፤ መከራ ተካፋይ መሆንና ከክርስቶስ ጋር በሞቱና በትንሳኤው ሕብረት ማድረግን ይጨምራል። እንግዲህ አሁን ፍጹም አይደለሁም "እንግዲህ ገና ፍጹም አይደለሁም" ወይም "እንግዲህ ገና ብስለት የለኝም" ነገር ግን ወደ ፊት ጥረቴ እቀጥላለሁ "ነገር ግን ሙከራዬን እቀጥላለሁ"(UDB) እጨብጣለሁ "እነዚህን ነገሮች እቀበላለሁ" በክርስቶስ ኢየሱስ አግኝቻለሁ ትኩረት: "በዚህ ምክንያት ክርስቶስ የእርሱ የራስይ እንደሆንኩ ቆጥሮአል" ወንድሞች ሆይ፤ ጳውሎስ የፊልጵስዩስ አማኞችን ያመለክታል። ትኩረት: "የእምነት ወዳጆች" እኔ ራሴ ገና አልጨበጥኩትም ትኩረት: "እነዚህ ነገሮች ሁሉ ገና የእኔ መሆናቸው አልታወቀም" ከኋላዬ ያለውን እየረሰው ወደ ፊት ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ በእሽቅድድም እንደሚሮጥ ሰው ከኋላ ያለውን ሳይሆን ወደ ፊት በቀራው ላይ ትኩረት እንደሚደረግ ጳውሎስ የሚናገረው የእርሱ የሃይማኖታዊ ጽድቅ ሥራ ወደ ኋላ ትቶ በክርስቶስ በተዘጋጀው እንዲጨርሰው በፊቱ ባለው ሩጫ ትኩረት ማድረግ ነው። ትኩረት:"ቀድሞ ስለሥራሁት ግድ የለኝም" ግቡን ለመድረስ በክርስቶስ የእግዚአብሔርን ጥሪ ለማሸነፍ ወደ ፊት ጥረቴን እቀጥላለሁ ጳውሎስ እሽቅድድምን ለማሸነፍ እንደሚሮጥ ንጽጽሩን ይቀጥላል፤ ጳውሎስ ለማገልገልና ለክርስቶስ በመታዘዝ መመላለስን ትኩረት ያደርጋል። ትኩረት:" የእርሱ ለመሆንና ከሞትኩ በኋላ እግዚአብሔር ሲጠረኝ ወደ ራሱ ለመሄድ በክርስቶስ ማመኔን እቀጥላለሁ"

Philippians 3:15

x

ስለዚህ እንደ ባለአእምሮ እናስብ ጳውሎስ የእምነት ወዳጆችን እርሱ እንደ ጠቀሳቸው ፍላጎት እንዲኖሩ ይፈልጋል PHP 3:8-11። ትኩረት: "በእምነት እንደ ጠነከሩ ሆነው አንድ አሳብ እንዲያስቡ ሁላችንንም አማኞች አደፋፍራለሁ" እንደምታስቡ እዚህ ላይ "እናንት" የሚለው ቃል የሚያሳየው በተለየ ሁኔታ የሚያስቡ አማኞች ወይም ከጳውሎስ ጋር የማይስማሙትን ነው። እግዚአብሔር ደግሞ ለእናንተ ይገልጻል "እግዚአብሔር ደግሞ ግልጥ ያደርግላችኋል" በየትኛውም ደርጃ የደረስን ቢሆን በዚያው በደረስንበት ሁኔታ እንመላለስ ትኩረት:"ሁላችንም በተቀበልነው እውነት መሠረት በመታዘዝ እንቀጥል"

Philippians 3:17

x

ወንድሞች ሆይ፤ ተባበሩኝ ጳውሎስ የፊልጵስዩስ አማኞችን እንደ ራሱ ወንድሞቹ በቁጥር ይገልጻል። እኔን ምሰሉ "እኔ የማደርገውን አድርጉ" ወይም "እኔ እንደምኖር ኑሩ" በጥንቃቄ ጠብቁ "በጥንቃቄ ተመልከቱ" በምሳሌአችን ለሚመላለሱ "ቀድሞኑ እኔ እንደምኖር የሚኖሩ" ወይም "ቀድሞኑ እኔ እንደማደርገው የሚያደርጉ" ሁልጊዜ እንደ ነገርኩአችሁ "ብዙውን ጊዜ ነግሬአችኋለሁ" በእንባ እነግራችኋለሁ "በታላቅ ሐዘን እነግራችኋለሁ" ብዙዎች የክርስቶስ ጠላቶች ሆነው ይኖራሉ እዚህ ላይ "የክርስቶስ መስቀል" የክርስቶስን መከራና ሞትን ያመለክታሉ። ጠላቶቹ በክርስቶስ እናምናለን የሚሉና ነገር ግን የክርስቶስን መከራውን ለመቀበል ወይም ፤ለመሞት ፍቃደኛ የማይሆኑ። ትኩረት:ብዙ ሰዎች በኢየሱስ እንደሚያምኑ የሚናገሩ ነገር ግን ሥራቸው መከራ ሊቀበልና በመስቀል ላይ ለመሞት ፍቃደኛ የሆነው የክርስቶስ ጠላቶች ናቸው።" መጨራሻቸው ጥፋት ትኩረት: "እግዚአብሔር አንድ ቀን ያጠፈቸዋል" ሆዳቸው አምላካቸው እዚህ ላይ "ሆድ" የአንድ ሰው ለአካላዊ ምኞች ፍላጎቶችን ያመለክታል። ትኩረት: "እግዚአብሔርን ከመታዘዝ ይልቅ ምግብና ሌሎች ለአካል የሚያስፈልጉ ምኞችን ይፈልጋሉ" ክብራቸው በነውራቸው ትኩረት: "ውርደት በሚሆኑ ነገሮች ላይ የሚመኩ ናቸው" ስለ ምድራዊ ነገሮች ያስባሉ እዚህ ላይ "ምድራዊ" የሚያሳየው ማንኛውም ነገሮች ለአካል ምኞት የሚሰጡና ለእግዚአብሔር ክብር የማይሰጡ ነገሮችን ያመለክታል። ትኩረት: "የሚያስቡት ሁሉ እግዚአብሔርን ከሚያስደስተው ይልቅ ራሳቸውን የሚያስደስቱ ነገሮችን ነው"

Philippians 3:20

x

የእኛ፤እኛ ጳውሎስ "የእኛ" እና "እኛ" በማለት አድማጮችን ያካትታል። መኖሪያችን በሰማይ ነው "መኖሪያችን በሰማይ ነው" ወይም "እውነተኛ ቤታችን በሰማይ ነው" አዳኙን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ከምንጠባበቅበት "እኛ ከሰማይ ወደ ምድር የሚመለሰውን አዳኙን ጌታ አየሱስ ክርስቶስን እንጠባባቃለን" የተዋረደውን ሰውነታችንን ይለውጣል "የእኛን ደካማና ምድራዊ አካላችንን ይለውጣል" ክብሩን በሚመስል በተሠራው አካላት "አካሉን በሚመስል አካላት" ሁሉን ለመቆጣጠር በእርሱ ኃይል በተሠራው ትኩረት: "ሁሉን ነገር ለመቆጣጠር በሚጠቀምበት በተመሳሳይ ኃይል አካላችንን ይለውጣል"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 4

1 ስለዚህ ውድ ወንድሞቼ፤ ወዳጆቼም ሆይ፤ የምናፍቃችሁ፤ ደስታዬና አክሊሎቼ የሆናችሁ በዚህ መንገድ በጌታ ጸንታችሁ ቁሙ። 2 ኤዎድያና ሲንጢኪ እርስ
በርሳቸው በጌታ ተስማምተው እንዲኖሩ እለምናቸዋለሁ። 3 በርግጥ አንተም እዚያ ያለኸው የሥራ ባልደርባዬ እነዚህን ሴቶች እንድትረዳቸው እለምንሃለሁ።
እነርሱም ወንጌልን በማሰራጨት ከእኔና ከቅሌምንጦስ ጋር እንዲሁም ስማቸው በሕይወት መጽሐፍ ከተጻፉት ከሌሎች የሥራ ባልደረቦቼ ጋር ብዙ ተጋድለዋል።
4 ሁል ጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ ደግሜም እላለሁ ደስ ይበላችሁ። 5 ደግነታችሁ በሰዎች ሁሉ ዘንድ ይታወቅ። 6 ስለ ሁሉም ነገር በጸሎት፤ በልመናና
በምስጋና ለእግዚአብሔር አስታውቁ እንጂ ስለምንም ነገር አትጨነቁ። ጌታ ቅርብ ነውና። 7 ከማስተዋል በላይ የሆነው የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና
አሳችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል። 8 በመጨረሻም ወንድሞችሆይ፥ እውነት የሆነውን ሁሉ፤ ክቡር የሆነውን ሁሉ፤ ትክክል የሆነውን ሁሉ፤ንጹሕ የሆነውን
ሁሉ፤ ፍቅር የሆነውን ሁሉ፤ መልካም የሆነውን ሁሉ፤ በጎነት ቢሆን፤ ምስጋናም ቢሆን፤ እንደ እነዚህ ያሉትን ነገሮች ሁሉ አስቡ። 9 ከእኔ የተማራችሁትንና
የተቀበላችሁትን፤ የሰማችሁትንና ያያችሁትን ማናቸውንም ነገር አድርጉ። የሰላምም አምላክ ከእናንተ ጋር ይሆናል። 10 እንደገና በመጨረሻ ጊዜ ለእኔ ማሰብ
ስለ ጀመራችሁ በጌታ ታላቅ ደስታ ይሰማኛል። በርግጥ ከዚህ በፊት ስለ እኔ ያሰባችሁ ቢሆንም እኔን ለመርዳት ዕድሉን አላገኝችሁም ነበር። 11 ይህን የምለው
ለራሴ ጥቅም አይደለም። ምክንያቱም በሁሉም ሁኔታ ባለኝ ነገር መርካትን ተምሬአለሁ። 12 በማጣትም ሆነ በማግኘት እንዴት መኖር እንዳለብኝ ዐውቃለሁ።
በማንኛውም መንገድ የመጥገብንና የመራብን፤ የማግኘትንና የማጣትን ምሥጢር ተምሬአለሁ። 13 ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን ነገር ማድረግ
እችላለሁ። 14 ይሁን እንጂ፤ እናንተ የችግሬ ተካፋዮች በመሆናችሁ መልካም አድርጋችኋል። 15 እናንተ የፊልጵስዩስ ሰዎች የወንጌልን ተልዕኮ በጀመርኩበት
ጊዜ ከመቄዶንያ ስወጣ ከእናንተ በቀር በመስጠትም ሆን በመቀበል ከእኔ ጋር የተባበረ ሌላ ቤተ ክርስቲያን እንዳልነበረ ታውቃላችሁ። 16 በተሰሎንቄ
በነበርኩበት ጊዜም ቢሆን ከአንድ ጊዜ በላይ ለሚያስፈልገኝ ርዳታ ልካችሁልኛል። 17 ይህንንም ስል የእናንተን ስጦታ ለማግኘት በመፈለግ ሳይሆን
የልግሥናችሁ ፍሬ እንዲበዛላችሁ በመመኘት ነው። 18 ሁሉንም ነገር ተቀብያለሁ፤በዝቶልኛል፤ ሞልቶልኛልም። የላካችሁልኝን ስጦታ ከኤጳፍሮዲቱስ እጅ
ተቀብዬአለሁ። ይህም ስጦታ በመልካም መዓዛ እንደ ተሞላ መሥዋዕት እግዚአንሔር የሚቀበለውና ደስ የሚሰኝበት ነው። 19 ደግሞም አምላኬ እንደ ክብሩ
ባለጠግነቱ በክርስቶስ ኢየሱስ አማካይነት የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ይሰጣችኋል። 20 እንግዲህ ለአባታችንና ለአምላካችን ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ክብር
ይሁን፤ አሜን። 21 በክርስቶስ ኢየሱስ ለሆኑት ሁሉ ሰላምታ አቅርቡልኝ። ከእኔም ጋር ያሉት ወንድሞች ሰላምታ ያቀርቡላችሁኋል። 22 እዚህ ያሉት አማኞች ሁሉ
በተለይም የሮማ ቤተ መንግሥት ያሉ ሠራተኞች ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። 23 የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከመንፈሳችሁ ጋር ይሁን።

Philippians 4:1

x
የሚያገነኝ ዐረፍተ ነገር: ጳውሎስ በፊልጵስዩስ ለሚኖሩ አማኞች በህብረት ጉዳዮች ላይና አማኞች ከአንዳንድ ተጨባጭ መመሪዎች ጋር ለጌታ እንዴት እንደሚኖሩ መመሪያ መስጠቱን ይቀጥላል። ስለዚህ የምናፍቃችሁ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ትኩረት: "የእምነት ወዳጆቼ እወዳችኋለሁ እንዲሁም መጥቼ እናንተን ለጠየቅ ከፍተኛ ፍላጎት አለኝ" ደስታዬና አክሊሎቼ ጳውሎስ"ደስታ" የሚለውን ቃል የደስታው ምክንያት የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን እንደሆነች ለመግልጽ ይጠቀማል። "አክሊል" ከቅጠል የሚሠራና አንድ ሰው አንድ ጨወታ ሲያሸንፍ ለክብር ምልክት እንዲሆን በጭንቅላት ላይ የሚደፋ ነው። እዚህ ላይ "አክሊል" የሚለው ቃል የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ለጳውሎስ በእግዚአብሔር ፊት ክብርን አምጥቶአል። ትኩረት: "በኢየሱስ በማመናችሁ ምክንያት ደስታ ሆናችኋል እንዲሁም ለሥራዬ ሽልማቴና ክብሬ ናችሁ" የተወደዳችሁ ወዳጆቼ ሆይ፤በዚህ መንገድ ጸንታችሁ ትኩረት: "እንግዲህ ውድ ወዳጆቼ እኔ ባስተመኩአችሁ መንገድ ለጌታ መኖራችሁን ቀጥሉ" ከኤዎድያና ከሲንጢኪ ጋር አብሬ እያዘንኩ ነው በፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ጳውሎስን የረዱ አማኝ የነብሩ ሴቶች ናቸው።ትኩረት: " ኤዎዲያንና ሲንጢኪን እለምናቸዋለሁ" በጌታ በአንድ ልብ ሁኑ "በአንድ ልብ ሁኑ" የሚለው ሐረግ ተመሳሳይ አስተሳሰብ ወይም አመለካከት ማለት ነው። ትኩረት: "በአንድ ጌታ ስለምታምኑ እርስ በርሳችሁ ተስማሙ" በርግጥ እውነተኛ የሥራ ባልደረባዬ ደግሞ እያስተናገድኩ ነው እዚህ ላይ "እናንተ" የሚለው ቃል አስፈላጊ ነው። ጳውሎስ የሰው ስም አልጠቀሰም። ወንጌልን ለማሰራጨት ከጳውሎስ ጋር የሠራ አንድ ሰው የሚጠቅሰው "እውነተኛ የሥራ ባልደረባዬ" ብሎ ብቻ ይጠራል። ትኩረት: "አዎን፤ እውነተኛ የሥራ ባልደረባዬ ደግሞ እጠይቃለሁ" ከቄሌመጦስ ጋር ቄሌመንጦስ አማኝ የነበረውና በፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን የሚሠራ ነበር። ስማቸው በሕይወት መጽሐፍ ላይ ያላቸው ትኩረት: "ስማቸውን በሕይወት መጽሐፍ እግዚአብሔር የጻፋቸው"

Philippians 4:4

x
ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይበላችህ ደግሜ እላለሁ በጌታ ደስ ይበላችሁ ጳውሎስ የሚናገረው ለሁሉም ፊልጵስዩስ አማኞች ነው።ደስ የበለጠ ትኩረት ለመስጠት እንዴት አስፈላጊ እንደሆነ ይበላችሁ የሚለውን ትእዛዝ ይደግማል ። ትኩረት: "ጌታ ስላደረገላችሁ ነገር ደስ ይበላችሁ! እንደገና እነግራችኋለሁ ደስ ይበላችሁ!" ጌታ ቅርብ ነው አማራጭ ትርጉሞች 1)ጌታ ኢየሱስ ለአማኞቹ ቅርብ ነው ወይም2) ጌታ ኢየሱስ ወደ ምድር የሚመለስበት ቀን ቅርብ ነው። በሁሉ ነገር በጸሎት የሚያስፈልጋችሁን ጠይቁ አመስግኑም "የሚያስፈልጋችሁን እግዚአብሔርን በጸሎትና በምስጋና ጠይቁ" ከመረዳት የሚያልፈውን "ልንረዳው ከምንችለው በላይ" ልባችሁንና አሳባችሁን ይጠብቃል ይህ የእግዚአብሔር ሰላም እንደ ወታደር ስሜቶቻችንና አሳቦቻችንን ከጭንቀት የሚጠብቀውን ያቀርባል። ትኩረት: "እንደ ወታደር ስሜታችንና አሳባችንን ስለዚህ ዓለም መጨነቅ ይጠብቃችኋል"

Philippians 4:8

x
በመጨረሻ ይህ የደብዳቤውን ይህ ክፍል ያጠቃልላል። ጳውሎስ አማኞች ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም እንዲኖር እንዴት እንደሚኖሩ ማጠቃለያ እየሰጠ ነው። ወንዲሞች ሆይ እዚህ ላይ ይህ ማለት ክርስቲያን ወዳጆች፤ ወንዶችንና ሴቶችን ጨምሮ ከእግዚአብሔር ጋር እንደ ሰማያዊ አባታቸው ሁሉም አማኞች በክርስቶስ አንድ መንፈሳዊ ቤተ ሰብ አባላት ስለሆኑ ነው። ማንኛውም ነገሮች በፍቅር ነው "ማንኛውም ነገሮች የሚያስደስቱ ናቸው" ማንኛውም ነገሮች ከመልካም የሚነገር "ማንኛውም ነገሮች ሰዎች የሚያደንቁ" ወይም "ማንኛውም ነገሮች ሰዎች የሚያከብሩ" ትክክል ይሆነውን ሁሉ "በሞራል መልካም ከሆኑ" ማንኛውም ምስጋና ካላቸው "ለምስጋና ምክንያት ከሆኑ" እነዚህን ነገሮች አስቡ "ስለእነዚህ ነገሮች አስቡ" ከእኔ የተማራችሁትንና የተቀበላችሁትን የሰማችሁንና ያያችሁትን "እኔ ያስተማርኩአችሁንና ያሳየኋችሁትን"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Philippians 4:10

x
የሚያገነኘው ዐረፍተ ነገር፡ ጳውሎስ የሚናገረው በገንዘብ ስለ ደገፉት ሲሆን፤ እንድዲሁም በሰላምታና ምስጋና ይደመድማል። ከዚህ በፊት ስለ እኔ ያሰባችሁ ቢሆንም እኔን ለመርዳት ዕድሉን አላገኛችሁም ነበር። "ካሁን በፊት ስለ እኔ ታስቡ እንደነበረ አውቃለሁ፤ ነገር ግን ድጋፋችሁን ለመላክ ምክንያት አልነበራችሁም" የረካ መሆን "መርካት" ወይም " ደስተኛ መሆን" በሁሉም ሁኔታ "በየትኛውም ሁኔታ ቢሆን ግድ የለኝም" እንዴት እንደምኖር አውቃለሁ ትኩረት፡ "ትክክለኛ አስተሳሰብ እንዴት እንደሚኖረኝ አውቃለሁ" በአስፈላጊ ጊዜ "የሚያስፈልገኝ ሁሉ በማይኖረኝ ጊዜ" በሚበዛበት ጊዜ "ከሚያስፈልገኝ በላይ ሲሆረኝ" በመጥገብና በመራብ፤ በመብዛትና በሚያስፈልገኝ ጊዜ እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ነው። ጳውሎስ በማንኛውም ሁኔታ መርካትን እንዴት እንደተማረ ትኩረት ለመስጠት እነዚህን ሐረጎች ይጠቀማል። ኃይልን በሚሰጠኝ ሁሉ ማድረግ እችላለሁ "ሁሉን ማድረግ እችላለሁ ምክንያቱም ክርስቶስ ኃይልን ይሰጠኛል"

Philippians 4:14

x
በችግሬ ጊዜ "ነገሮች አስቸጋሪ በሚሆኑበት ጊዜ" የወንጌል ተልእኮ ይህ የሚያመለክተው ጳውሎስ ስለ ኢየሱስ ለመንገር ወደ ተለያዩ ከተሞች መጓዙን ነው። በመስጠትና በመቀበል ጉዳይ ላይ ከእናንተ በስተቀር የረዳኝ ቤተ ክርስቲያን የለም ትኩረት፡ "የእናንተ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ናችሁ ገንዘብ ወይም ርዳታ የሰጣችሁኝ" ፍሬአችሁ እንዲበዛላችሁ እፈልጋለሁ ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያን ስጦታ ለአንድ ሰው የበለጠ የሚጨምረው ብልጽግና እያነጻጸረ ነው።ጳውሎስ የፊልጵስዩስ ሰዎች መንፈሳዊ በረከት ለመቀበል ስለሚችሉ እንዲሰጡ ይፈልጋል"

Philippians 4:18

x
ሁሉም ነገር በብዛት አለኝል። ሞልቶልኛል ትኩረት፡ "ማንኛውም የሚያስፈልገኝና የሚተርፍ አለኝ" እነርሱም ጠፋጭ መዓዛ ያለው፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው መሥዋዕትና እግዚአብሔርን የሚያስደስት ነው። መልካም መዓዛ፤ ተቀባይነት ያለው እግዚአብሔርን የሚያደስት መሥዋዕት፤ጳውሎስ የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ስጦታን ከብሉይ ኪዳን መሥዋዕት ጋር እያነጻጸር ነው። ካህናት እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን መሥዋዕት ያቃጥላሉ። ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያን ስጦታ ታላቅ ዋጋ ያለ መሆኑን ትኩረት እየሰጠ ነው። ትኩረት፡ "እነዚህ ስጦታዎች እግዚአብሔርን የሚያስደስት እንደሆነ አረጋግጣለሁ" የሚያስፈልገውን ሁሉን ያዘጋጃል "የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ያዘጋጃል" በክርስቶስ ኢየሱስ እንደ ክብሩ ባለ ጠግነት ትኩረት፡ "በክርስቶስ ከክብሩ ባለጠግነት ይሰጣል" አሁን ለአላካችን "አሁን" የሚለው ቃል የመዝጊያ ጸሎትና የዚህ ደብዳቤ ክፍል መደምደሚያ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Colossians

Colossians

ምዕራፍ 1

1 በእግዚአብሔር ፈቃድ የክርስቶስ ኢየሱስ ሐዋርያ ከሆነው ከጳውሎስና ከወንድማችን ከጢሞቲዎስ፤ 2 በቆላስይስ ለሚኖሩ ለእግዚአብሔር ለተለዩና
በክርስቶስ ታማኝ ለሆኑ አማኞች፤ ከእግዚአብሔር ከአባታችን ጸጋና ሰላም ይሁንላችሁ። 3 ለእናንተ በምንጸልይበት ጊዜ ሁሉ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት
እግዚአብሔርን እናመሰግናለንን። 4 በክርስቶስ ኢየሱስ ስላላችሁ እምነትና ለእግዚአብሔር ለተለዩት ሁሉ ስላላችሁ ፍቅር ሰምተናል። 5 በሰማይ ከተጠበቀላችሁ
ከመታመነ ተስፋ የተነሣ ይህ እምነትና ፍቅር አላችሁ። ስለዚህም ተስፋ በወንጌል የእውነት ቃል አስቀድማችሁ ሰማችሁ፤ ይህም ወደ እናንት ደርሶአል። 6
ይህንም ወንጌል ከሰማችሁበትና የእግዚአብሔርን ጸጋ በእውነት ከተረዳችሁበት ቀን ጀምሮ በእናንተም ዘንድ እየሠራ እንዳለ ሁሉ በዓለም ዙሪያ ሁሉ ፍሬ
እያፈራና እያደገ ነው። 7 በእኛ ምትክ ለእናንተ የክርስቶስ ታማኝ አገልጋይ የሆነውና ከእኛም ጋር አብሮን ከሚያገለግል ከተወዳጁ ከኤጳፍራ ይህን ተምራችኋል።
8 ደግሞም በእግዚአብሔር መንፈስ ያላችሁን ፍቅር ነግሮናል። 9 ከዚህም ፍቅር የተነሣ ስለ እናንተ ከሰማንበት ቀን ጀምሮ ለእናንተ ከመጸለይ አላቋረጥንም።
በፈቃዱ ዕውቀት፣ በጥበብ ሁሉና በመንፈሳዊ ማስተዋል እንድትሞሉ እንጸልይላችኋለን። 10 ጌታን ደስ በሚያሰኝ መንገድ በሁሉም እንደሚገባ እንድትመላለሱ፤
በማናቸውንም መልካም ሥራ ፍሬ እንድታፈሩና በእግዚአብሔርም ዕውቀት እንድታድጉ እንጸልያለን። 11 በሁሉም ነገር እንድትጽኑና ትእግሥት እንዲኖራችሁ
፣ከኀይሉ ክብር የተነሣም በሁሉ ብርታትና ጥንካሬ እንዲኖራችሁ እንጸልያለን። 12 በብርሃን ከሚኖሩት አማኞች ጋር የርስቱ ተካፋይ እንድንሆን ላበቃን
ለእግዚአብሔር በደስታ ምስጋና ማቅረብ እንድትችሉ እንጸልያለን። 13 ከጨለማ ኀይል አዳነን፤ ወደ ተወደደውም ወደ ልጁ መንግሥት አሸጋገረን። 14 በልጁም
የኀጢአታችንን ይቅርታ፣ ድነትን አገኘን። 15 ልጁ የማይታየው አምላክ ምሳሌ ነው። እርሱ የፍጥረት ሁሉ በኩር ነው። 16 ምክንያቱም በሰማያትና በምድር፤
የሚታዩትና የማይታዩት ነገሮች ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋል። ዙፋናትም ሆኑ ኀይላት ወይም ግዛቶችች ወይም ሥልጣናት፤ሁሉም ነገር በእርሱና ለእርሱ
ተፈጥረዋል። 17 እርሱ ከሁሉ በፊት ነበረ፤ሁሉም ነገር የተያያዘው በእርሱ ነው። 18 እርሱ አካሉ ለሆነችው ቤተ ክርስቲያን ራስ ነው። እርሱ የሁሉም መገኛና
የሁሉም የመጀመሪያ፣ከሙታንም በኩር ነው። 19 በመሆኑም በሁሉም ነገሮች መካከል የመጀመሪያ ነው። በእርሱ የእግዚአብሔር ሙላቱ ሁሉ እንዲኖርና
እግዚአብሔር በልጁ በኩል ሁሉን ነገር 20 ከራሱ ጋር ያስታርቅ ዘንድ ስለ ወደደ ነው። እግዚአብሔር ልጁ በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደም በሰማያትም ሆነ
በምድር ያሉትን ነገሮች ሁሉ አስታረቀ። 21 እናንተም ቀድሞ ከእግዚአብሔር ርቃችሁ ነበር፤ በአሳባችሁና በክፉ ሥራችሁም ምክንያት ጠላቶች ነበራችሁ። 22
አሁን ግን ቅዱሳንና ንጹሓን፤ ነቀፋም የሌለባችሁ አድርጎ በፊቱ ሊያቀርባችሁ በልጁ ሞት እግዚአብሔር ከራሱ ጋር አስታረቃችሁ። ይህም በእርሱ
ተመሥርታችሁና ተደላድላችሁ በወንጌሉ ከተገኘው ተስፋ ሳትናወጡ 23 በእምነት ጸንታችሁ እንድትኖሩ ነው። ይህም ወንጌል እናንተ የሰማችሁትና ከሰማይ
በታች ላለ ፍጥረት ሁሉ ተሰብኮአል። እኔም ጳውሎስ አገልጋይ የሆንኩት ለዚህ ወንጌል ነው። 24 አሁን ስለ እናንተ በምቀበለው መከራ ደስ ይለኛል። አካሉ ስለ
ሆነችው ስለ ቤተ ክርስቲያንም ከክርስቶስ መከራ ከመካፈል የጎደለውን በሥጋዬ አሟላለሁ። 25 የእግዚአብሔርን ቃል በሙሉ ለእናንተ እንድገልጥ
ከእግዚአብሔር በተሰጠኝ ኀላፊነት ቃሉን ለመፈጸም የማገለግለው ይህችን ቤተ ክርስቲያን ነው። 26 ይህም ባለፉት ዘመናትና ትውልዶች ከሰው ልጆች ተሰውሮ
የቆየውና አሁን ግን እግዚአብሔር ለሚያምኑት ሁሉ የገለጠው ምስጢር ነው። 27 እግዚአብሔርም በእናንተ መካከል ለአሕዛብ ሊገልጥላቸው የፈለገው የዚህ
ምስጢር የክብር ብልጽግና ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ነው። ይህም ምሥጢር በተስፋ የምንጠባበቀው ክብር የሚገኝበት ክርስቶስ በእናንተ መካከል መሆኑ
ነው። 28 የምንሰብከው እርሱን ነው። እያንዳንዱን ሰው በክርስቶስ ፍጹም አድርገን ለማቅረብ ጥበብን ሁሉ በማስተማርና በመምክር ሰውን ሁሉ እንገስጻለን።
29 በውስጤ በኀይል በሚሠራው መሠረት በብርቱ እየታገልኩ እደክማለሁ።

Colossians 1:1

ቆላስያስ 1: 1-3
አጠቃላይ መረጃ: ይህ ወደ በቆላስያስ ለሚኖሩ አማኞች በጳውሎስ እና በጢሞቴዎስ አመካኝነት የተጻፈ ደብዳቤ ነው። በእግዚአብሔር ፈቃድ የክርስቶስ ኢየሱስ ሐዋርያ የሆነ "የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ለመሆን በእግዚአብሔር የተመረጠ" ወንድሞቻችን “እኛ” በሚለው ቃል ውስጥ ጳውሎስ ተደራሲያኑንም አካቷል።" ጸጋ ለእናንተ ይሁን ለሌላ ሰው ባርኮትን መስጠት ወይም ለሌላ ሰው መመኘት እናንተ በዚህ ሥፍራ ላይ “እናንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በቆላስያስ የሚገኙ ቅዱሳንን እና ታማኝ የሆኑ ወንድሞችን ነው። ስለእናነት ዘወትር እንጸልያለን አማራጭ ትርጉም: "ስለ እናንተ ሁል ጊዜ ከልባችን ሆነን እንጸልያለን።"

Colossians 1:4

ቆላስያስ 1: 4-6
አጠቃላይ መረጃ: በዚህ ሥፍራ ላይ “እናንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር አመልካች ሲሆን የሚመለክተው በቆላስያስ የሚገኙ አማኞችን ነው። ስለ እናንተ ሰምተናል በዚህ ሥፍራ ጳውሎስ “እኛ” የሚለው ቃል በመጠቀም አንባቢያኑን በውስጡ አላካተተም። በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያላችሁን እምነት "በኢየሱስ ክርስቶስ ያላችሁ እምነት" ለቅዱሳንም ሁሉ ስላላችሁ ፍቅር ሰምተን፥ "ለቅዱሳን ሁሉ ያላችሁን ፍቅር" (UDB) በሰማይ ከተዘጋጀላችሁ ተስፋን እንደሚታገኙ ካላችሁ ሙሉ እምነት የተነሣ "እግዚአብሔር በሰማይ ያስቀመጠላችሁን ተስፋ ላይ ካላችሁ እርግጠኝነት የተነሣ" እርግጠኛ ተስፋ "አጥብቃችሁ የያዛችሁት ተስፋ" ፍሬ ያፈራል እንዲሁም ያድጋል ይህ የተለያዩ ለምግብነት የሚሆኑ ነገሮችን ከሚያፈራ ዘፍ ወይም እጽዋጽ ጋር ተነጻጽሮ የቀረበ ሲሆን ሰዎችን የሚለውጠው ወንጌልም አድጎ ብዙ ሰዎች ባመኑት ቁጥር በዓለም ሁሉ ይሰራጫል። በዓለም ዙሪያ ሁሉ ወንጌል በሚታወቀው ዓለም ዙሪያ ሁሉ ይሰራጫል እንዲሁም ያድጋል። የእግዚአብሔር ጸጋ በእውነት "እውነተኛው የእግዚአብሔር ጸጋ" ወይም "እውነተኛው የእግዚአብሔር ሞገስ"

Colossians 1:7

ቆላስያስ 1: 7-8
ልክ ከኤጳፍራ እንደተማራችሁት ሁሉ "ልክ ኤጳፍራ እንዳስተማራችሁ ሁሉ" ወይም "ኤጳፍራ ያስተማራችሁን ሁሉ ሙሉ ለሙሉ በሚገባ እንደተረዳችሁት ሁሉ" ልክ እደዛው “እርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የወንጌል መልዕክት በቆላስያ ከተማ ውስጥ በሚገኙ አማኞች የዕለት ተዕለት ሕይወት ላይ ያመጣውን ውጤት የሚያመለክት ነው። እናንተ ተምራችኋል በቆላስያ ከተማ ይኖሩ የነበሩት አማኞች ይህንን ተምረዋል ኤጳፍራ ኤጳፍራ Epaphras በቆላስያ ከተማ ውስጥ ከነበሩ አማኞች ወንጌል የሰበከላቸው

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሰው ነው። ከተወደደ ከእኛም ጋር አብሮ ባሪያ ከሆነው ከኤጳፍራ እንዲህ ተማራችሁ፥ እርሱም ስለ እናንተ ታማኝ የክርስቶስ አገልጋይ ነው። ይህ ማለት ኤጳፍራ ጳውሎስ በእስር ቤት ባይሆን ኖሮ ልፈጽመው የሚችለው ነገር በማድረግ የክርስቶስን ሥራ የሠራ ሰው ነው ማለት ነው። አርሱ ለእኛ ገልጦልናል "ኤጳፍራ ለእኛ አስታውቆናል" በመንፈስ ስላልችሁ ፍቅር "ለአማኞች ፍቅር እንዲኖራችሁ መንፈስ ቅዱስ አቅም ሰጥቶአችዋለህ"

Colossians 1:9

ቆላስያስ **1**፡ **9-10**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ በክርስቶስ ስላላቸው እምነት እና በመንፈስ ስላላቸው ፍቅር ይጸልይላቸዋል። በዚህ ፍቅራችሁ ምክንያት "መንፈስ ቅዱስ ሌሎች አማኞችን መውደድ እንዲትችሉ ስላደረጋችሁ" ስለእናንተ ከሰማንበት ጊዜ አንስቶ "ኤጳፍራ ስለ እናንተ ለእኛ ከነገረበት ጊዜ አንስቶ" ሰምተናል ይህ የሚያመለክተው ጳውሎስ እና ጢሞቴዎስን እንጂ በቆላስያስ ከተማ የሚገኙ አማኞችን አይደለም። መጸለይ አላቋረጥንም "ብዙ ጊዜ እና ከልባችን ወደ እግዚአብሔር እንጸልያለን" የእርሱ ፈቃድ ምን እንደሆነ ታውቁና በዚህ ትሞሉ ዘንድ እንጠይቃለን "የእርሱን ፈቃድ ታደርጉ ዘንድ በእውቀት ሞላችሁ ዘንድ እግዚአብሔርን እንጠይቀዋለን" በጥበብ እነና መንፈሳዊ መረዳት ሁሉ "በመንፈስ ቅዱስ የሚሰጥ ጥበብ እና መረዳት" በሁሉም ነገር ለጌታ እንደሚገባ ትኖሩ ዘንድ "ጌታ በሚፈቅደው መንገድ መኖር ትችሉ ዘንድ ፍሬ እንዲታፈሩ ይህ ሀረግ ፍሬጣማ እጽዋትነን ከአማኝ መልካም ሥራ ጋር የሚያነጻጽር ነው። ልክ እጽዋት አድገው ፍሬ እደሚያፈሩ ሁሉ አማኞችም በእግዚአብሔር እውት ልያድጉ እና መልካም ሥራን ልሠሩ ይገባል።

Colossians 1:11

ቆላስያስ **1**፡ **11-12**
ስለ እናንተ እንጸልያለን በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል ጳውሎስን እና ጢሞቴዎስን የሚወክል እንጂ በቆላስያስ የሚገኙ አማኞችን የሚወክል አይደለም።

እንደ ክብሩ ጉልበት መጠን በኃይል ሁሉ እየበረታችሁ፥ "በታላቅ ክብሩ አማካኝነት በኃይሉ የበረታችሁ ሁኑ" በነገር ሁሉ ጽኑ እንዲሁም ትእግስት ኑራችሁ "ፈጽማችሁ ማመናችሁን አቁሙ እንዲሁም ትእግስት ይኑራችሁ" ለአብን በደስታ ምስጋናን እያቀረባችሁ "ለአብ በደስታ ምስጋናን እያቀረባችሁ" በቅዱሳንም ርስት በብርሃን እንድንካፈል ያበቃንን አማራጭ ትርጉም: "እንዲንካፈል ያበቃንን" እንድትበቁ ያደረጋችሁን በዚህ ሥፍራ ላይ ጳውሎስ ተደራሲያኑ የእግዚአብሔር ጸጋ ተካፋዮች መሆናቸው ላይ ትኩረት ያደርጋል። ይህ ማለት ግን እርሱ ይህንን ባርኮት በመውረስ ውስጥ ምንም ድርሻ የለኝም እያለ ግን አይደለም። ርስቱን ለመካፈል "ርስቱን ለመካፈል" በብርሃን "በክብሩ መገኘት ውስጥ" for the believers አማራጭ ትርጉም: "ቅዱሳን ለሆኑት" ወይም "ለልዩ ጥቅም የተመረጡት" ለእርሱ "ለአባት"

Colossians 1:13

ቆላስያስ **1**፡ **13-14**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ክርስቶስ በምን መንገድ ልቆ እንደሚገኝ ይናገራል። እርሱ አዳነን "እግዚአብሔር አባት አዳነን" አፈለሰን "አሸጋገረን።" በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል ጳውሎስን እና በቆላስያስ ከተማ የሚገኙ አማኞችን በውስጡ ያካትታል። በእርሱ ውድ ልጁ "የእግዚአብሔር አብ ተወዳጅ ልጁ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ" በገዛ ልጁ ቤዛነትን አገኘን "ልጁ ቤዛነትን ሰጠን" የኃጢአታችን ይቀርታን "ልጁ ኃጢአታችንን ይቅር አለን" ወይም "አብ በልጁ በኩል ኃጢአታችን ይቅር አለን"

Colossians 1:15

ቆላስያስ **1**፡ **15-17**
ልጁ የማይታየው አምላክ መልክ ነው ልጁ ኢየሱስ ምን እንደሚመስል በማወቅ እግዚአብሔር አብ ምን እንደሚመስል ማወቅ እንችላለን። ልጅ ይህ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው የኢየሱስ ወሳኝ ስም ነው። እርሱ በኩር ነው "ልጁ በኩር ነው።" ኢየሱስ በጣም ወሳኝ እና ልዩ የሆነ የእግዚአብሔር “ልጅ” ነው። “ልጅ” የሚለው ቃል ኢየሱስ ከአብ ጋር ያለውን ልዩ የሆነ ግንኙነት ያሳያል። ይህ በአብ እና በልጁ መካከል ያለው ግንኙነት በቋንቋችሁ ውስጥ “በልጅ” እና “አባት” የሚለውን ቃል ካልተጠቀማችሁ በስተቀር መረዳት አይቻል። ምክንያቱም ሁሉም ነገሮች የተፈጠሩት በእርሱ አማካኝነት ነው "ምክንያቱም ልጁ የተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ፈጥሯልና" ዙፋን ቢሆን ወይም ግዛት ወይም መንግስታት ወይም ሥልጣናት ሁሉም ነገሮች በእርሱ እና ለእርሱ ተፈጥረዋል ልጁ ሁሉን ነገር ለራሱ ፈጥረዋል ይህ ዙፋንን፣ ስልጣንን፣ ገዥዎችን እና ስልታናትን ያካትታል። እርሱ ከነገሮች ሁሉ በፊት ነው "እርሱ ከሁሉም ነገር በፊት ነበር" በእርሱ ሁሉም ነገር እርስ በእርሱ ተያይዟል "እርሱ ሁሉን ነገር አያይዟል" (UDB)

Colossians 1:18

ቆላስያስ **1**፡ **18-20**
እርሱ ራስ ነው "የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ራስ ነው" እርሱ አካሉ የሆነችው የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው። ይህ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ በቤተ ክርስቲያን ላይ ያለውን ሥልጣን ራስ በሰው አካል ጋር ካለው ጋር ያነጻጽራል። ልክ ራስ አካልን እንደሚገዛ እንዲሁም ዚየሱስ ቤተ ክርስቲያንን ይገዛል። የሥልጣን ሁሉ ምንጭ እርሱ ዋነኛ አለቃ ወይም መሥራች ነው። ኢየሱስ የቤተ ክርስቲያን ጀማሪ ነው። ከሙታን መከካከል በኩር ነው ኢየሱስ ሞተው ከሞት ወደ ሕይወት ከተመለሱት ሰዎች በኩር ነው፣ ከእንግዲህም ፈጽሞ እንደገና አይሞትም። ይህ የሆነበት ምክንያት እግዚአብሔር የእርሱ ሙላት በእርሱ ውስጥ አንዲኖር ስለፈቀደ ነው "እግዚአብሔር አብ እርሱ ያለው ነገር ሁሉ በክርስቶስ እንዲሆን ስለፈቀደ ነውቲ" በመስቀል ላይ በፈሰሰው የልጁ ደም በኩል “በኩል” ተብሎ የተተረጎመው ዋናው ቃል መሥመር ወይም መንገድ የሚል ሀሳብን በውስጡ ያዘለ ሲሆን እግዚአብሔር በመስቀል ላይ ሞቶ በፈሰሰው የኢየሱስ ደም በኩል ሰላምን እና እርቅን ማምጣቱን የሚያሳይ ነው። ልጅ ይህ የእግዚአብሔር ልጅ ለሆነው ለኢየሱስ ወሳኝ ስም ነው።

Colossians 1:21

ቆላስያስ **1**፡ **21-23**
እንዲሁም እናንተም ደግሞ "እንዲሁም በቆላስያስ ከተማ የሚትኖሩ አማኞችም ጭምር" ለእግዚአብሔት እንግዶች ነበራችሁ were strangers to God አማራጭ ትርጉም: "ከእግዚአብሔር የተለያችሁ ነበራችሁ" ወይም "እግዚአብሔር የተዋችሁ ነበራችሁ" በአእምሮዋችሁ እና በክፉ ተግባራችሁ የእግዚአብሔር ጠላቶች ነበራችሁ "ጠላቶቹ ነበራችሁ ምክንያቱም ክፉ ሀሳብን ስለምታስቡ እና ምክንያቱም ክፉ ተግባርን ስለምትፈጽሙ ነው።." (UDB) በክርስቶስ ሥጋ በሞቱ እግዚአብሔር እናንተን አስታረቀ እግዚአብሔር እናንተ ከኢየሱስ ጋር ስያስታርቃችሁ በመስቀል ላይ የተመለከተው ክርስቶስን ሳይሆን እናንተን ነው ይሁን እንጂ እናንተ ክርስቶስ ሲሞት እናንተም በመስቀል ላይ መሞታችሁን ተመልክቷል። እንከን የለሽ "ምንም እንከን ያሌለበት" ከነቀፋ ውጪ "ምንም ነቀፋ ያሌለበት" በራሱ ፊት "በእግዚአብሔር በራሱ ፊት" ጸንታችሁ ቆማችሁ "በቀጣይነት ጸንታችሁ ተተክላችሁ" ወይም "በቀጣይነት ቆማችሁ" በእምነት ጽንታችሁ "አለመናወጥ" ወይም "መጽናት" በወንጌል መተማመን "በወንጌል ተማምናችሁ" እኔ ጳውሎስ ባሪያ የሆንኩለት ከሰማይ በታች ለፍጥረታት ሁሉ የሰበኩትን ወንጌል "ሰዎች ወንጌልን ከሰማይ በታች ላሉ ፍጥረታት ሁሉ ሰብከዋል። እኔ ጳውሎስ የሚሰብከው እና እግዚአብሔር እንዳገለግል የተራሁት ይህ ተመሳሳይ ወንጌል ነው።"

Colossians 1:24

ቆላስያስ **1**፡ **24-27**
አሁን እኔ ደስ ይለኛል "እኔ ጳውሎስ አሁን ደስ ይለኛል" ለእናንተ ሲል የሚቀበለው መከራ "ስለ እናንተ ጥቅም ስለል መከራን እቀበላለሁ" (UDB) ስለ እናንተ "ለእናንተ የቆላስያስ አማኞች ሲባል" ስለ አካሉም ማለት ስለ ቤተ ክርስቲያን በሥጋዬ በክርስቶስ መከራ ውስጥ የጐደለውን እፈጽማለሁ። ጳውሎስ እየተናገረ ያለው ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም ሲል እየደረሰበት ያለውን ተቃውሞ እነና ስደት ነው። ጳውሎስ ገና አማኝ ሲሆን ይህ ከባድ የሆነ መከራ እንደሚደርስበት አስቀድሞ አሳይቶት ነበር። ቤተ ክርስቲያንን አገለግላለሁ "እኔ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን የሚስፈልጋትን ነገር

ለመሙላት እፈልጋለሁ" የእውነት ምስጢር "ሚስጥሩ" ለዘመናት ተሸሽጎ ነበር ይህ ከፍጥረት ጊዜ እንስቶ ጳውሎስ ለአሕዛብ ወንጌልን እስከ ሰበከበት ጊዜ ያለውን ዘመን ያመለክታል። ለአማኞች ተገልጧል አማራጭ ትርጉም: "ለእርሱ ተከታዮች ግልጽ ተደርጎላቸዋል።" ይህ አይሁድንና አሕዛብ ያካትታል። ለእነርሱም እግዚአብሔር በአሕዛብ ዘንድ ያለው የዚህ ምሥጢር ክብር ባለ ጠግነት ምን እንደ ሆነ ሊያስታውቅ ወደደ፥ እግዚአብሔር ለአሕዛብ ያለው ዕቅድ ምን ያኽል ግሩም እንደሆነ ማሳወቅ ፈለገ። ምሥጢሩም የክብር ተስፋ ያለው ክርስቶስ በእናንተ ዘንድ መሆኑ ነው። "ምሥጢሩም የእግዚብሔርነን ክብር ለወደፊት የመካፈላችሁ ርግጠኝነት ነው" (UDB)

Colossians 1:28

ቆላስያስ **1**: **28**-**29**
እና የሚነስበከው እርሱን ነው "ጳውሎስ እና ጢሞቴዎስ የሚሰብኩት ክርስቶስ ይህ ነው።" ሁሉንም ሰው እናስተጠነቅቃለን "ሰዎችን ሁሉ እናስጠነቅቃለን" ሰዎችን ሁሉ ማቅረብ እንችል ዘንድ "ሰዎችን ሁሉ ለእግዚአብሔር ማቅረብ እንችል ዘንድ" መፈጸም "መንፈሳዊ ብስለት" ስለዚህ እደክማለሁ "እኔ ጳውሎስ ስለዚህ ነገር እደክማለሁ" በእኔ በኃይል እንደሚሠራ እንደ አሠራሩ "በእኔ እንደሚሠራው የክርስቶስ ዓላማ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 2

1 ስለ እናንተና በሎዶቅያ ስላሉት ሰዎች እንዲሁም ፊቴን በሥጋ አይተውት ስለማያውቁ ስለ ብዙዎች ምን ያህል ብርቱ ትግል እንዳደረግሁ እንድታውቁ
እወዳለሁ። 2 ልባቸው ተጽናንቶና በፍቅር ተሳሰረው ፍጹም የሆነ የመረዳት ብልጽግና እንዲኖራቸውና የእግዚአብሔርን ምስጢር የሆነውን እውነት ክርስቶስን
እንዲያውቁ እታገላለሁ። 3 የጥበብና የዕውቀት ሀብት ሁሉ የተሰወረው በእርሱ ነው። 4 ይህን የምላችሁ ማንም በሚያታልል ንግግር እንዳያስታችሁ ነው። 5
በሥጋ ከእናንተ ጋር ባልሆን እንኳ በመንፈስ ከእናንተ ጋር ነኝ። የእናንተን መልካም ሥርዐትና በክርስቶስ ያላችሁን ጽኑ እምነት እያየሁ ደስ ይለኛል። 6 ጌታ ኢየሱስ
ክርስቶስን እንደ ተቀበላችሁት በእርሱ ተመላለሱ። 7 በእርሱም ተመሥርታችሁና ታንጻችሁ፤ እንደ ተማራችሁትም በእምነት ተደላድላችሁ ኑሩ፤ ምስጋናም
ይብዛላችሁ። 8 በክርስቶስ ላይ ባልተመሠረተ በሰው ሠራሽ ልማድና በዓለማዊ ነገሮች፥ በፍልስፍናና በከንቱ ሽንገላ ማንም እንዳይማርካችሁ ተጠንቀቁ። 9
የእግዚአብሔር ፍጹም ሙላት በእርሱ ይኖራልና። 10 በእርሱም ተሞልታችኋል። እርሱ የአለቅነትና የሥልጣን ሁሉ ራስ ነው። 11 በእርሱም ተገርዛችኋል፤ ይህም
መገረዛችሁ የሥጋዊ አካል በማስወገድ በሰው እጅ የተደረገ ሳይሆን በክርስቶስ የተደረገ ነው። 12 በተጠመቃችሁ ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ተቀበራችሁ፤በእርሱም
ክርስቶስን ከሞት ባስነሣው በእግዚአብሔር ኀይል በእምነት ተነሥታችኋል። 13 እናንተም በበደላችሁና በሥጋችሁ ባለመገረዝ ሙታን ሳላችሁ፤ እግዚአብሔር
ከክርስቶስ ጋር ሕያዋን አድርጎ መተላለፋችንንም ሁሉ ይቅር ብሎአል። 14 እርሱ ይከሰን የነበረውን የዕዳ ጽሑፍ ደመሰሰው። ሁሉንም በመስቀል ላይ ቸንክሮ
ከእኛ አስወገደው። 15 ኀይላትንና ባለሥልጣናትን በመስቀሉ ድል አድርጎ በይፋ እንዲጋለጡ አደረጋቸው። 16 እንግዲህ በመብል ወይም በመጠጥ ወይም
የበዓላትን ቀናት ወይም የወር መባቻን፤ ወይም ሰንበትን በማክበር ምክንያት ማንም አይፍረድባችሁ። 17 እነዚሁ ሁሉ ወደ ፊት ሊመጡ ላሉት ነገሮች እንደ ጥላ
ናቸው፤ እውነተኛው አካል ግን በክርስቶስ ነው። 18 አስመሳይ በሆነ ትሕትና የመላእክትን አምልኮ በመፈለግ ማንም ዋጋ እንዳያሳጣችሁ። እንዲህ ያለው ሰው
ስለሚያየው ነገር በሥጋዊ አስተሳሰቡ ይታበያል። 19 እርሱም ራስ ከሆነ ከክርስቶስ ጋር አልተያያዘም። በእግዚአብሔር በተሰጠው እድገት በመገጣጠሚያና
በጅማት አካልን በሙሉ አያይዞ የሚመግበውና ለአካል ሙሉ ዕድገት የሚሰጠው ራስ ነው። 20 ከክርስቶስ ጋር ከሞታችሁ፣ ለዓለማዊ ነገሮች እየታዘዛችሁ ስለ
ምን ትኖራላችሁ? ትእዛዞቹም፦ 21 «አትያዝ፤አትቅመስ፤ አትንካ!» የሚሉ ናቸው። 22 እነዚህ ሁሉ የሰው ትእዛዛትና ትምህርቶች ሥራ ላይ ከዋሉ በኋላ
የሚጠፉ ናቸው። 23 እነዚህ ትእዛዞች ሰው ሰራሽ «ጥበብ» አምልኮና የሐሰት ትሕትና ሰውነትንም በማጎሳቆል ላይ የሚያተኩሩ፤ ነገር ግን ሥጋዊ ስሜትን
በመቆጣጠር ረገድ ዋጋ ቢሶች ናቸው።

Colossians 2:1

ቆላስያስ 2፡ 1-3
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ በቆላስያስ እና በሎዶቂያ የሚገኙ አማኞች ክርስቶስ አምላክ እንደሆነ እና በአማኞች ውስጥ እንደሚኖር ተገንዝበው እርሱን በተቀበሉበት መቀበል መኖር እንዳለባቸው ማበረታታቱን ቀጥሏል። ስለዚህ ይህንን ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ "እኔ ጳውሎስ በቆላስያስ የሚትኖሩ አማኞች ይህንን ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ" እንዴት ያለ ትልቅ መጋደል እንዳለኝ ልታውቁ እወዳለሁና፤ የእርሱን ንጽሕና ለማሳደግ እና የወንጌል መረዳታቸውን ለመጨመር ጳውሎስ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል። በሎዶቅያ ላሉት ይህች ከተማ የቆላስያስ ከተማ ቅርብ የሆነች ከተማ ሲትሆን በዚህች ከተማ ውስጥመም ቤተ ክርስቲያን ነበረች፣ ጳውሎስም ለዚህች ከተማ ይጸልይላታል። ብዙዎች በሥጋ ፊቴን የማየት እድል አላገኙም "ብዙዎቹን በአካል አላገኘኋቸውም" ወይም "ብዙዎችነን ፈጽሞ ፊት ለፊት አግኝቼአቸው አላውቅም" ልባቸውም "ጳውሎስን በአካል አይተውት የማያውቁት ሁሉም አማኞች ልብ" ወደ አንድነት እንዲሰበሰብ በእውነተኛ ግንኙነት እንድቀራረቡ። አማራጭ ትርጉም: "እርስ በእርሳቸው እንዲተባበሩ" ወይም "እርስ በእርሳቸው እንዲቀራረቡ" ከመረዳት የሚመጣ መተማመን ይህ እነዚህ ነገሮች በማወቅ የሚገኝ መተማመን ማለት ነው። የእግዚአብሔር ምስጢር ይህ በእግዚአብሔር ስገለጥ ብቻ የሚታወቅ ነገር ነው። ይኼውም ክርስቶስ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔር የተገለጠ ምስጢር ነው። የጥበብ እና እውቀት የተደበቀ መዝገብ ታላቅ የጥበብ እና የእውቀት ሀብት ወይም ባለጠግነት ጥበብ እ እውቀት እነዚህ ቃላት በመሠረታዊ ሀሳባቸው ተመሳሳይ ናቸው። ጳውሎስ እነዚህ ቃላት በአንድነት የተጠቀመው ሁሉም መንፈሳዊ መረዳቶች ከክርስቶስ ዘንድ አንደሚመጡ አጽኖት ለመስጠት ነው። በእርሱ ናቸው “እርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ክርስቶስን ነው።

Colossians 2:4

ቆላስያስ 2፡ 4-5
ይህንን እላለሁ "እኔ ጳውሎስ ይህንን እላለሁ" እንዳያስታችሁ "እናንተ የቆላስያስ አማኞችን ወደ ተሳሳተ ሥፍራ ወይም ድምዳሜ እንዳይመራችሁ" በሚያሳምን ንግግር የሆነ ነገርንን እንዲታምኑ የሚያደርግ ንግግር ወይም አንድን ሀሳብ የሚታመን የሚያድረግ ንግግር ምንም እንኳ በሥጋ ከእናንተ ጋር ባልሆንም "በአካል ከእናንተ ጋር ባልሆንም" በመንፈስ ግን ከእናንተ ጋር ነኝ "ሁል ጊዜ ስለ እናንተ አስባለሁ" መልካም ሥርዓታችሁን ጳውሎስ ስለ አንድነታቸው እና ስለ እምነታቸው ጥንካሬ እንዲሁም በክርስቶስ ላይ ስላላቸው እምነት አመስግኖዋቸዋል።

Colossians 2:6

ቆላስያስ 2፡6-7
በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመላለሱ ይህ በተወሰነ የአኗኗር ዘይቤ ወይም መነንገድ መኖርን ለማመልከት ጥቅም ላይ የዋለ አገላለጽ ነው። እንደተቀበላችት "በቆላስያስ ከተማ ውስጥ ያሉ አማኞች ክርስቶስን እንደተቀበሉት" በእርሱ ጸንታችሁ ቁሙ፣ በእርሱ እደጉ በዚህ ሥፍራ ጳውሎስ ክርስትያኖች መኖር ያለባቸውን ሕይወት ለመግለጽ እና ስለ መንፈሳዊ ብስከለት ለመግለጽ ሁለት ምሳሌያዊ ነግግሮችን ይጠቀማል በእምነታችሁ ጽኑ "ሕይወታችሁን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ባላችሁ እምነት መሥርታችሁ ኑሩ" ምስጋና ይብዛላችሁ "እግዚአብሔርን በጣም አመስግኑት"

Colossians 2:8

ቆላስያስ 2፡ 8-9
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ አማኞች ወደ ቃላት እና ሌሎች ሕግጋት እንዳይመለሱ ያስጠነቅቃል ምክንያቱም አማኞች አሁን በክርስቶስ ካላቸው የእግዚአብሔር ሙላት ላይ ምንም የሚጨምሩት ነገር የላቸውምና። ይህንን ተመልከቱ "ጥንቃቄ አድርጉ" ወይም "ተጠንቀቁ" ፍልስፍና ስለ እግዚአብሔር እና ሕይውት ከእግዚአብሔር ቃል ያልወጣ ሃይማታዉ አስተምህሮዎች እና እምነቶች ባዶ ማታለል ይህ በክርስቶስ ወደ ሆነ ሕይወት የማይመሩ አሻች ሀሳቦችን ያመለክታል። ምንም ነገር አያፈሩም ባዶ ወይም ዋጋ ያሌላቸው ነገሮች ናቸው። እንደ ሰው ወግና እንደ ኃጢአት የሞላበት የዓም ሥርዓት የአይሁድ እና የአረማዊያን (አሕዛብ) የእምነት ሥርዓቶች፣ ሁለቱም ምንም ዋጋ የላቸውም። እንደ ክርስቶስ ትምህርት አይደሉም "እንደ ክርስቶስ ትምህርት አይደሉም" ወይም "በክርስቶስ ትምህርት ላይ የተመሠረቱ አይደሉም" ምክንያቱም የመለኮት ሙላት ሁሉ በአካሉ ውስጥ ይኖራል "ምክያቱም የእግዚአብሔር ሙሉ ባሕርይ በክርስቶስ አካል ውስጥ ይኖራል"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Colossians 2:10

ቆላስያስ **2**: **10**-**12**
በእርሱ "በኢየሱስ ክርስቶስ" እናንተ ናችሁ "እናንተ በቆላስያስ የሚትኖሩ አማኞች ናችሁ ፈጽሞ ሙሉ ሆናችኋል "ሙሉ ሆናችኋል" እግዚአብሔር ገርዞዋችኋል ይህ ምሳሌያዊ ንግግር ልክ በግርዛት ወቅት ሥጋ በቢላዋ ተቆርጦ እንደሚጣል ሁሉ እግዚአብሔር የአማኖችን ኃጢት ፈጽሞ አስወግዷል። ከእርሱ ጋር ተቀብራችኋል ይህ ምሳሌያዊ ንግግር ልክ አንድ ሰው ሲሞት አካሉ በምድር ውስጥ እንደሚቀበር ሁሉ እንዲሁም ድነትን ባገኛችሁበት ወቅት የድሮው ባሕርያችሁ በመቅጽበት እንዴት እንደሚወገድ የሚብራራ ነው። ከእርሱ ጋር ተነሥታችኋል ይህ ምሳሌያዊ ንግግር ልክ አንድ ሰው ከሞት ስነሳ አዲስ ህይወት እንደገና እንደሚኖረው ሁሉ አንድ አማኝ እንዴት አዲስ ባሕርይ እንደሚሰጠው ያመለክታል።

Colossians 2:13

ቆላስያስ **2**: **13**-**15**
ሙታን በሆናች ጊዜ "የቆላስያስ አማኞች በመንፈሳዊ ሞት ውስጥ በነበሩበት ጊዜ" በመተላለፋችሁ ሙታን ነበራችሁ እንዲሁም በሥጋችሁም ያልተገረዛችሁ ነበራችሁ በሁለት ነገሮቸ ሙታን ነበሩ: 1) በመንፈሳዊ ሕይወት ሙታን፣ ክርስቶስ የሚበድል ኃጢአት የሞላበትን ሕይወት ትኖሩ ነበር እና 2) እንደ ሙሴ ሕግ የተገረዛችሁ አልነበራችሁም። እርሱ እናንተን እንዲህ አደረጋችሁ "ኢየሱስ እናንተን የቆላስያስ አማኞችን እንዲህ እንዲትሆኑ አደረገ" መተላለፋችንን ሁሉ ይቅር አለን "ኢየሱስ ክርስቶስ አይዳዊያንን እና አሕዛብን ሁለቱን መተላለፋችንን ሁሉ ይቅር አለልን።" እናንተ ሙታን ነበራችሁ . . . ሕያዋን እንዲትሆኑ አደረገ ይህ ምሳሌዊ ንግግር ልክ የሞተ ሰው ወደ ሕይወት በአካል እንደሚመጣ ሁሉ እኛም እንዴት ኃጢአተኛ ከሆነ ሕይወት ወደ አዲስ መንፈሳዊ ሕይወት እንደመጣን ያሳያል። በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው፤

ይህ ምሳሌያዊ ንግግር እግዚአብሔር የእኛን ኃጢአት (እዳ) እና የእግዚአብሔርን ሕግ መተላለፋችን መሰረዙን በወረቀት ላይ የተጻፉ ዝርዝሮችን ከመሰረዝ ጋር እያነጻጸረ ያቀርባል። ድል በመንሣት በእርሱ እያዞራቸው በግልጥ አሳያቸው። በሮማዊያን ዘመን የሮም ወታደሮች ከጦርነት ሲመለሱ “የድል ጉዞ” ማድረግ የተለመደ ነገር ነው። በዚህ ወቅት በምርኮ የያዝዋቸውን ምርኮኞች እና የነጠቁትን ሀበት ያሳያሉ።

Colossians 2:16

ቆላስያስ **2**: **16**-**17**
ማንም አይፍረድባችሁ ጳውሎስ አማኞችን አሕዛቦች የሙሴን ሕግ መጠበቅ አለባቸው ከሚሉ አይዳዊያን ይጠበቁ ዘንድ ያስጠነቅቃቸዋል። በሚበላ ወይም በሚጠጣ ነገር የሙሴ ሕግ ምን መበላት እና መጠጣት እዳለበት የሚያሳይ ሕግ አለው። አማራጭ ትርጉም: AT: "በምትበሉት ወይም በምትጠጡት ነገር" የጾም ቀን ወይም አዲስ ጨረቃ ወይም ስለ ሰንበት የሙሴ ሕግ መከበር ያለባቸው፣ የአምልኮ ቀናት እና መስዋእት የሚቀርብበት ቀን መቼ እንደሆነ ይደነግጋል። እነዚህ ለሚመጣው ነገር ጥላ ናቸው “ጥላ” የአንድን ነገር ቅርጽ እና አጠቃላይ ሁኔታን ድብዝብዝ ባለ መንገድ የሚያሳይ ነው። በተማሳሳይ መልኩም እንደ ሙሴ ሕግ ያሉ ሃይማኖታዊ ትውፊቶች በኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጠውን እውነተኛውን ነገር በከፍል ብቻ የሚያሳዩ ናቸው።

Colossians 2:18

ቆላስያስ **2**: **18**-**19**
ዋጋችን ማንም ሰው እንዳይወስድባችሁ "ማንም ከሚያገኘው ዋጋ የተነሣ እንዳያታልላችሁ።" ይህ ምሳሌያዊ ንግግር የውሸት ትህትናን እና የመላእክት አምልኮን በቆላስያስ ከተማ ውስጥ የአማኞችን ድነት ለመስረቅ ከሚሞክር ሌባ ጋር ያነጻጽራል። አማራጭ ትርጉም: "ማንም የሌላ ሰውን ሽልማት እንዲሰርቅ አትፍቀዱለት።" የውሸት ትህትና "ትሁት ለመመስል የሚደረግ ጥረት።" ይህ ማለት በሌሎስ ሰዎች ፊት ትሁት ለመምሰል የተለያዩ ነገሮችን ማድረግ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም: “ራስን የካዱ መምሰል” በተለያዩ ነገሮች ከሚገባ በላይ መያዝ ይህ ማለት አእምሮን ሁል ጊዜ የሚዝ ወይም በሆነ ነገር በጣም መያዝን ያሳያል። አዲስ አስተሳሰብ ይህ ማለት እንደ መንፈሳዊ ሰው ሳይሆን ተፈጥሮአዊ ወይም ኃጢአተኛ ሰው ማሰብ ማለት ነው። አጥብቆ አይዝም "አጥብቆ አይዝም" ወይም "አይጠጋም፣" ልክ ልጅ ወደ ወላጆቹ እንደሚጠጋው ማለት ነው።

እንደዚህ ያለ ሰው ራስ ወደሚሆነው አይጠጋም፥ ከእርሱም አካል ሁሉ በጅማትና በማሰሪያ ምግብን እየተቀበለ እየተጋጠመም፥ እግዚአብሔር በሚሰጠው ማደግ ያድጋል።

ይህ ምሳሌያዊ ንግግር ክርስቶስ በቤተ ክርስቲያን ላይ ያለው ስልጣንን የሰው ልጅ ጭንቅለላት አካሉን ከሚቆጣጠርበት እና ከሚገዛበት መንገድ ጋር ያነጻጽራል።

Colossians 2:20

ቆላስያስ **2**: **20**-**23**
ከክርስቶስ ጋር ለዚህ ዓለም ኃጢአተኛ ሥርዓት ከሞትን ይህ ምሳሌያዊ ንግግር የሚያሳየው ልክ የሞተ ሰው የዚህ ዓለም አካላዊ ፍላጎቶች ታዲያ ለዚህ ዓለም እምነት ተገዝታችሁ ስለምን ትኖራላችሁ ጳውሎስ ይህን ጥያቄ የተጠቀመው የቆላስያስ አማኞች የዚህ ዓለምን የሐሰት የእምነት ሥርዓት መከተላቸውን ለመገሰጽ ነው።) ተገዝቶ መኖር "መገዛት" ወይም "መሰጠት" ወይም "መታዘዝ" መጥፋት "መበስበስ" እነዚህ ደንቦች በሰው የተዘጋጁ ሃይማኖታዊ “ጥበቦች” አሏቸው እንዲሁም ትሁታን ይመስላሉ አካላቸውንም ሃይማኖተኛ ለመምሰል ያጎሳቁላሉ። ሃይማኖትን በመፍጠር እና የሐሰት ትህትና እና አካላቸውም በሃይማኖት ስም በማጎሳቆል - "እነዚህ ህግጋት ከሰው ልጅ የእይታ አንጻር ጥበብ የሞላባቸው ይመስላሉ እንዲሁም አካላቸውን ያጎሳቁላሉ"

ማጎሳቆል "በከፍተኛ ሁኔታ መጉዳት" ወይም "ማሰቃየት" ነገር ግን ሥጋ ያለ ልክ እንዳይጠግብ ለመከልከል ምንም አይጠቅምም። "የሥጋን ፍላጎት መከተልን ለማስቆም ግን ምንም እገዛ አያደርጉም"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 3

1 እግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ከሞት ካስነሣችሁ፤ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያሉትን ነገሮች እሹ። **2** በላይ ስላሉት ነገሮች እንጂ በምድር ስላሉት ነገሮች አታስቡ። **3** ምክንያቱም ሞታችኋል፤ ሕይወታችሁንም እግዚአብሔር በክርስቶስ ውስጥ ሰውሮታልና። **4** ሕይወታችሁ የሆነ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ እናንተም ከእርሱ ጋር በክብር ትገለጣላችሁ። **5** ስለዚህ ምድራዊ ምኞቶቻችሁን ግደሉ፦ እነርሱም፦ ዝሙት፣ ርኩሰት፣ ፍትወት፣ ክፉ ምኞት፣ ስግብግብነትና ጣዖትን ማምለክ ናቸው። **6** በእነዚህም ነገሮች ምክንያት በማይታዘዙ ልጆች ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ይመጣባቸዋል። **7** እናንተም ራሳችሁ ከዚህ በፊት በማይታዘዙ ሰዎች መካከል ሳላችሁ እነዚህን ነገሮች እያደረጋችሁ ትመላለሱ ነበር። **8** አሁን ግን ቁጣን፤ ንዴትን፤ ተንኮልን፤ ስም ማጥፋትን ከእናንተ አስወግዱ፤ የሚያሳፍር ንግግርም ከአፋችሁ አይውጣ። **9** አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር አውልቃችሁ ስለ ጣላችሁ፣ አንዳችሁ በሌላው ላይ አትዋሹ። **10** የፈጠረውንም ምሳሌ እንዲመስል ዕውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችሁታል። **11** በዚህ ዕውቀት በግሪካዊና በአይሁዳዊ፣ በተገረዘና ባልተገረዘ፣ በሠለጠነና ባልሠለጠነ፣ በባሪያና በነጻ ሰው መካከል ልዩነት የለም፤ ክርስቶስ ግን ሁሉ ነው፤ በሁሉም ነው። **12** ስለዚህ እንደ እግዚአብሔር ምርጦች ቅዱሳንና የተወደዳችሁ ሆናችሁ ርኅራኄን፣ ቸርነትን፣ ትሕትናን፣ ገርነትን፣ ትዕግሥትን ልበሱ። **13** እርስ በርሳችሁ ታገሡ፤ እርስ በርሳችሁም ቸሮች ሆኑ። ከእናንተ አንዱ በሌላው ላይ ቅርታ ቢኖረው፣ ክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ። **14** በዚህ ሁሉ ላይ የፍጻሜ ማሰሪያ የሆነው ፍቅር ይኑራችሁ። **15** የአንድ አካል ክፍሎች ሆናችሁ የተጠራችሁት ለዚህ ሰላም ስለ ሆነ የክርስቶስ ሰላም በልባችሁ ይንገሥ፤ የምታመሰግኑም ሁኑ። **16** የክርስቶስ ቃል በሙላት ይኑርባችሁ። በጥበብ ሁሉ እርስ በርሳችሁ ተማማሩ፤ ተመካከሩ፤በመዝሙርና በውዳሴ፤ በመንፈሳዊ ዜማም እግዚአብሔርን ከልብ እያመሰገናችሁ ዘምሩ። **17** በእርሱ እግዚአብሔር አብን እያመሰገናችሁ በቃልም ሆነ በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት። **18** ሚስቶች ሆይ፥ ለጌታ እንደሚገባ ለባሎቻችሁ ታዘዙ። **19** ባሎች ሆይ፥ ሚስቶቻችሁን ውደዱ መራራም አትሁኑባቸው። **20** ልጆች ሆይ፥ ይህ ጌታን ደስ የሚያሰኝ በመሆኑ ለወላጆቻችሁ በሁሉ ነገር ታዘዙ። **21** አባቶች ሆይ፥ልጆቻችሁ ተስፋ እንዳይቆርጡ አታስመርሩአቸው። **22** አገልጋዮች ሆይ፥ ሰውን ለማስደሰትና ለታይታ ሳይሆን በቅን ልብ ጌታን በመፍራት ለምድራዊ ጌቶቻችሁ በሁሉ ነገር ታዘዙ። **23** የምታደርጉትን ሁሉ ለሰው እንደምታደርጉ ሳይሆን ለጌታ እንደምታደርጉ በሙሉ ልባችሁ አድርጉት። **24** ከጌታ ዘንድ እንደ ዋጋ የምትቀበሉት ርስት እንዳለ ታውቃላችሁና። **25** በዚህም የምታገለግሉት ጌታ ክርስቶስን ነው። በእግዚአብሔር ዘንድ አድልዎ ስለሌለ ክፉ የሚሠራ ማንም ስለ ክፉ ሥራው ቅጣቱን ይቀበላል።

Colossians 3:1

ቆላስያስ **3**: **1-4**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ከክርስቶስ ጋር አንድ በመሆናችሁ ምክንያት አማኞች ማድረግ የሌለባቸው ነገሮች አሉ በማለት ጳውሎስ አማኞች ያስጠነቅቃቸዋል። እግዚአብሔር እናንተን ከክርስቶስ ጋር ከሞት አስነስቷችኋል ልክ እግዚአብሔር ክርስቶስን ከሞት እንዳነሣው ሁሉ እግዚአብሔር በቆላስያስ ከተማ የሚገኙ አማኞችም ከሞት እንደተነሱ ይቆጥራል። አንስቶዋችኋል “እናንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በቆላስያስ ከተማ ውስጥ የሚኖሩ አማኞችን ነው። የላይኛውን ነገር "ሰማያዊውን ነገር" ወይም "መለኮታዊውን ነገር" በምድር ላይ ያለውን "ምድራዊውን ነገር" ወይም "የምድርን ነገር" እናንተ ሞታችኋልና ክርስቶስ በእርግጥ እንደሞተ እግዚአብሔር በቆላስያስ ከተማ ውስጥ የሚኖሩት አማኞችንም ከክርስቶስ ጋር እንደሞቱ አድርጎ ይቆጥራቸዋል። እግዚአብሔር ሸሽጎታል "እግዚአብሔር ሰውሮታል" ከእርሱ ጋር በክብሩ ውስጥ በዚህ ሥፍራ “እርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ክርስቶስን ነው።

Colossians 3:5

ቆላስያስ **3**: **5-6**
ስለዚህ ኃጢአተኛ መሻታችሁን ግደሉት። ይህ ልክ ክፉ ሰው እንዲሞት እንደሚደረግ ሁሉ ኃጢአተኛ መሻታችሁ ፈጽም እና ለመጨረሻ ጊዜ ማስወገድ ይኖርባችኋል። ንጹሕ ያልሆነ ነገር "ንጹሕ ያልሆነ ባሕርይ" መሻት "ጠንካራ የዝሙት ምኞት" እና ጣኦትን ለማምለክ መመኘት "እና ስግብግብነት፣ ይህ ልክ እንደ ጣኦትን ማምለክ ነው" ወይም "እና ስግብግብ አትሁኑ ምክንያቱም ይህ ጣኦትን ከማምለክ ጋር ተመሳሳይ ነውና" (UDB) ስለዚህም በእነዚህ ነገሮች ምክንያት በማይታዘዙ ልጆች ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ይመጣል። "እነዚህ ነገሮች በሚያደርጉ በማያምኑ ሰዎች ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ይመጣባቸዋል።" እናንተም ደግሞ ትኖሩባቸው በነበራችሁ ጊዜ፥ በፊት በእነዚህ ተመላለሳችሁ። "እነዚህ ነገሮች ትፈጽሙ በነበረበት ወቅት ትመላለሱ የነበረው እንዲህ ነበር። ቁጣ "ቅጣት" ንዴተ "ቁጣ" ክፉ ምኞቶች አማራጭ ትርጉም: "የልብ ክፋት፣ ሕይወት እና ባሕርይ" ስድቦች "እግዚአብሔርን መሳደብ" ወይም "እርኩሰት የሞላበት ቃል መናገር።" ይህ ሌሎች ሰዎችን ለመጉደት ሲባል የሚነገር ንግግርን ያመለክታል። አሳፋሪ፣ ሰዎችን የሚያሰናክል ንግግር አማራጭ ትርጉም: "ቆሻሻ ንግግር"

Colossians 3:9

ቆላስያስ **3**: **9-11**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ በአሕዛብ እና በአይሁድ፣ በባሮች እና በነጻ ሰዎች መካከል የነረው ግድግዳ ክርስቶስ እንዳፈረሰው በማስታወስ አማኞች እንዴት መኖር እንዳለባቸው ማስታወሱን ቀጥሏል። እናንተ ገፋችሁታል በዚህ ሥፍራ ላይ “እናንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በቆላስያስ ከተማ ውስጥ የሚኖሩ አማኞችን ነው። አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር ገፋችሁታልና፥ የፈጠረውንም ምሳሌ እንዲመስል እውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችሁታል፤ ይህ ምሳሌዊ ንግግር እግዚአብሔር የማይከብርበትን ባሕርይ አስወግድ እግዚአብሔር የሚከብርበትን ተግባር መፈጸም የጀመሩ ክርስትያኖች ቆሻሻ ልብስን አውልቆ አዲስ እና ንጹሕ ልብስከለበሰ ሰው ጋር ያነጻጽረዋለረ። የእርሱ መልክ ይህ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚወክል ነው። የእርሱ መልክ እውቀት ኢየሱስ ክርስቶስን ማወቅ እና መረዳት በዚያም የግሪክ ሰው አይሁዳዊም የተገረዘም ያልተገረዘም አረማዊም እስኩቴስም ባሪያም ጨዋ ሰውም መሆን አልተቻለም፥ ይህ ማለት እግዚአብሔር ሁሉንም ሰዎች ያለልዩነት ይመለከታቸዋል፣ በዘር፣ በሀገር ወይም በማህበረሰቡ ውስጥ ባላቸው ደረጃ ሳይሆን ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም: “ዘር፣ ሃይማኖት፣ ባሕል እና በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው ደረጃ የሚያመጣው ነገር የለም።” ክርስቶስ ሁሉ በሁሉ ነው ከክርስቶስ ሕልውና ውጪ የሚሆን ምንም ነገር የለም። አማራጭ ትርጉም: “ክርስቶስ በጣም አስፈላጊ ነው።”

Colossians 3:12

ቆላስያስ **3**: **12-14**
ልበሱት . . . የርህራሄን ልብ ሰው ልብስ እንደሚለብስ ሁሉ አማኞችም ለእያንዳንዳቸው በሚያሳዩት ባሕርይ ርህራሄን፣ ትህትናን ወዘተን መልበስ ይገባቸዋል። ስለዚህ ልበሱት በዚህ ሥፍራ ላይ "ስለዚህ" የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው ከዚህ በፊት በነበረው ውይይት ወይም በተሰጠው ትምህርት መሠረት መደረግ ያለበትን መተግባር ወይም ባሕርይ ለይቶ ለመናገር ነው። (ተመልከት: [[rc://*/ta/workbench/discourse/home]]) የእግዚአብሔር ምርጦች እንደመሆናችሁ - ቅዱስ እና የተወደደ "የእግዚአብሔር ቅዱሳን እና በእርሱ የተወደዳችሁ ምርጦቹ እንደመሆናችሁ። የርህራሄ ልብ፣ መልካምነት፣ ትህትና፣ ገርመት እና ትዕግስት "ርህራሄ. መልካምነት፣ ትህትና፣ ቅንነት እና ትዕግስት የውስት ማንነት ናቸው" ርሁሩ ልብ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

"የሚራራ ልብ" ወይም "ለሌሎች የሚያስብ ልብ" መልካምነት "መልካምነት" ወይም "ገርነት" ትህትና "የአእምሮ ትህትና" ወይም "የአእምሮ ገርነት" ቅንነት "ቅንነት።" ነፈስ ስሜትን ከመከተል ይልቅ ወደ እግዚአብሔር የሚጋድል ከሆነ ትዕግስት "መቻል" ወይም "መከራን መቀበል መቻል" እርስ በእርስ መቻቻል በመስማማት እና በፍቅር በአንድነት መሥራትለ። “እርስ በእርስ መስማማት” ወይም “እርስ በእርስ መቻቻል።” አንዱን ሌላኛውም መውቀስ "ሌላኛውን መውቀስ" ፍቅር ይኑራችሁ "ፍቅርን ደርቡ ይህ የፍጹምነት ማሠሪያ ነው "ይህ አንድ ልይ በትክክል የሚያያዝ ነው" ወይም "ይህ በአንድ ላይ ፍጹም በሆነ መልኩ በስምምነት የሚያሳስር ነው።"

Colossians 3:15

ቆላስያስ **3**፡ **15**-**17**
በልባችሁ ይግዛ "በልባችሁ ላይ ይንገሥ" በልባችሁ ውስጥ በዚህ ሥፍራ “እናንተ” የሚለው ቃል የሚየመለክተው የቆላስያስ አማኞች ነው። በእናንተ ይኖራል "በእናንተ ውስጥ ያድራል" ወይም "በእናንተ ውስጥ ይኖራል" እርስ በእርሳችሁ ተጠባበቁ "አንዳችሁ ለሌኛችሁ ተጠንቀቁ" በመዝሙር እና በምስጋና እንዲሁም በመንፈሳዊ መዝሙር "በሁሉም ዓይነት መዝሙሮች እግዚአብሔርን አመስግኑት" በልባችሁ አመስግኑ "የሚያመሰግን ልብ ይኑራችሁ" በእርሱ በኩል "በጌታ ኢየሱስ በኩል"

Colossians 3:18

ቆላስያስ **3**፡ **18**-**21**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ከዚያም ጳውሎስ አንዳንድ መመሪያዎችን ለሚስቶች፣ ለባሎች፣ ለሕጻናት፣ ለአባቶች፣ ለባሮች እና ለጌቶች ተገቢ የሆነ "ተገቢ ነው" ወይም "ትክክለኛ የሆነ" አታበሳጯቸው "ክፉ አትሁኑባቸው" ወይም "አትቆጦዋቸው" ይህ ጌታን የሚያስደስት ነገር ነው "ቤተሰቦቻችሁን የሚትታዘዙ ከሆነ ጌታ በዚህ ደስ ይለዋል" ልጆቻችሁን አታበሳጩ "ልጆቻችሁን አታስቆጡ" ወይም "ልጆቻችሁ እንዲበሳጩ አታድርጓቸው"

Colossians 3:22

ቆላስያስ **3**፡ **22**-**25**
ጌቶቻችሁን ታዘዙ በዚህ ሥፍራ “እናንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በቆላስያስ የሚገኙ አማኝ የሆኑ ባሮች የሚያመለክት ነው። ለታይታ አይሁን ጌቶቻችሁ ስመለከቷችሁ ብቻ አትታዘዙ። ሰዎችን የሚታስደስቱ ከጌታ ይልቅ በሌሎች ሰዎች ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት ሲሉ የተለያዩ ነገሮችን የሚያደርጉ አንዳንድ ሰዎች አሉ። (UDB) የሚታደርጉትን ነገር ሁሉ በዚህ ሥፍራ ላይ “እናንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ባሮችን ቢሆንም እናንተ ግን በቆላስያስ ከተማ ውስጥ የሚገኙትን ሁሉንም ክርስቲያኖች የሚያመለክት አድርጋችሁ ልትተረጉምት ትችላላችሁ። ከነፍስ "በሙሉ ልባችሁ" (UDB) ለጌታ ብላችሁ "ለጌታ ብላችሁ" (UDB) የርስት ብድራት "ጌታ ቃል የገባውን ነገር እንደሚወርስ ነው" (UDB) ጽድቅ ያልሆነ ነገር የሚያደርግ ይህ ማንኛውንም ትክክለኛ ያልሆነ ነገር (ሥነ-ምግባር፣ ማህበረሰባዎ ወይም አካላዊ) የሚያመለክት ነው። “ትክክል የማያደርግ ሰው” ወይም “ክፋትን የሚያደረግ ሰው”። ቅጣትን ይቀበላል አማራጭ ትርጉም: "ይቀጣል" ያለልዩነት "ያለምንም ማዳላት" ወይም "ምንም አድሎ አይደረግለትም"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 4

1 ጌቶች ሆይ፥ እናንተም በሰማይ ጌታ እንዳላችሁ ዐውቃችሁ ለአገልጋዮቻችሁ በትክክልና የሚገባቸውን ስጡአቸው። 2 በንቃት እግዚአብሔርን እያመሰገናችሁ
ሳታቋርጡ ጸልዩ። 3 የክርስቶስ ምሥጢር የሆነውን የቃሉን እውነት መናገር እንድንችል እግዚአብሔር በር እንዲከፍትልን ለእኛም ደግሞ በአንድ ልብ ጸልዩልን፤
ምክንያቱም እስር የሆንኩት ስለእርሱ ነውና። 4 እኔም እንደሚገባ ቃሉን መግለጥና መናገር እንድችል ጸልዩልኝ። 5 በውጪ ካሉት ጋር በጥበብ ተመላለሱ፤
ዘመኑንም ዋጁ። 6 ለእያንዳንዱ ሰው እንዴት መመለስ እንዳለባችሁ እንድታውቁ ንግግራችሁ ሁልጊዜ በጨው እንደ ተቀመመ በጸጋ ይሁን። 7 ቲኪቆስ መጥቶ
እኔ ስላለሁበት ሁኔታ ሁሉንም ነገር ይነግራችኋል። እርሱም ተወዳጅ ወንድም፤ ታማኝ አገልጋይና በጌታ ሥራም የአገልግሎት ባልደረባዬ ነው። 8 እርሱንም ወደ
እናንተ የላክሁበት ምክንያት ስለ እኛ ሁኔታ ትክክል የሆነውን እንዲነግራችሁና ልባችሁንም እንዲያጽናና ነው። 9 ከእርሱም ጋር የእናንተ ወገን የሆነውን
የታመነውንና የተወደደውን ወንድም አናሲሞስን ወደ እናንተ ልኬዋለሁ። እነርሱ በዚህ ስፍራ የተደረገውን ነገር ሁሉ ይነግሩአችኋል። 10 ከእኔም ጋር የታሰረው
አርስጥሮኮስም ሰላምታ ያቀርብላችኋል፤ አንድ ጊዜ፥ «ወደ እናንተ በሚመጣበት ጊዜ ተቀበሉት» ብዬ አሳስቤአችሁ የነበረው የበርናባስ የአጎት ልጅ ማርቆስም
ሰላምታ ያቀርብላችኋል። 11 ኢዮስጦስ ተብሎ የሚጠራው ኢያሱም ሰላምታ ያቀርብላችኋል። ከተገረዙ ወገኖች መካከል ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ከእኔ
ጋር አብረው የሚሠሩት ሰዎች እነዚህ ብቻ ናቸው፤ ለእኔም መጽናናት ሆነውኛል። 12 የእናንተ ወገን የሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ ኤጳፍራም ሰላምታ
ያቀርብላችኋል። እርሱም ፍጹም ጠንክራችሁና ሙሉ በሙሉ ተማምናችሁ በእግዚአብሔር ፈቃድ በሁሉ ጸንታችሁ እንድትቆሙ ዘወትር ስለ እናንተ በጸሎት
እየተጋ ነው። 13 ስለ እናንተ በሎዶቅያና በሂራጶሊስ ስላሉትም ሰዎች ተግቶ እንደሚሠራ እኔ ራሴ እመሰክርለታለሁ። 14 የተወደደው ሐኪም ሉቃስና ዴማስም
ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። 15 በሎዶቅያ ላሉት ወንድሞች ለንምፉና በቤትዋም ላለች ቤተ ክርስቲያን ሰላምታ አቅርቡልኝ ። 16 ይህን መልእክት እናንተ
ካነበባችሁ በኋላ በሎዶቅያ ሰዎች ዘንድ ባለችው ቤተ ክርስቲያን እንዲነበብ አድርጉ፤እናንተም ከሎዶቅያ የሚላክላችሁን መልእክት አንብቡ። 17 ለአርኪጳስም፥
«በጌታ አገልግሎት የተሰጠህን ሥራ በጥንቃቄ ፈጽም» ብላችሁ ንገሩልኝ። 18 ይህን ሰላምታ በገዛ እጄ የጻፍኩት እኔ ጳውሎስ ነኝ፤ በሰንሰለት ታስሬ እንዳለሁ
አስታውሱና ጸልዩልኝ። የእግዚአብሔር ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን።

Colossians 4:1

ቆላስስ **4**: **1**-**1**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ለግለሰቦች የሰጠውን መመሪያ ያጠናቀቀው ለጌቶች በመናገር ነው። ለአገልጋዮቻችሁ ስጡ በዚህ ክፍል ውስጥ “እናነተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በቆላስያስ የሚገኙ የባሪያ ባለቤት የሆነ አማኞችን ነው። በጽድቅ እና ቅንነት ይህ ባለቤቶቹ በጽድቅ እና ቅንነት በሞለበት መንገድ ለባሮቻቸው ያሳዩ ዘንድ የታዘዙት ነገርን የሚገልጽ ነው።፤ በሰማይ ያለው ጌታ እግዚአብሔር ጌታ መሆኑ የሚያሳየው 1) እግዚአብሔር የባሪያ ባለቤቶችች በምድር ላይ ያሉትን ባሮቻቸውን በያየዙበት መንገድ ነው ወይም 2) ምድራዊ ባሪዎቻችሁን በሚትንከባከቡበት መንገድ እግዚአብሔር፣ ጌታችሁ በተመሳሳይ መንገድ ይመልስላችኋል።

Colossians 4:2

ቆላስያስ **4**: **2**-**4**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ አማኞች እንዴት መኖር እና መናገር እንደሚገባቸው መመሪያ መስጠቱን ቀጥሏል። በጸሎት ጸንታችሁ ቀጥሉ "በታማኝነት መጸለያችሁን ቀጥሉ" ወይም "በቀጣይነት መጸለያቸሁን ቀጥሉ" በተጨማሪ ለእኛ በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን እና ጢሞቴዎስን ነው ነገር ግን የቆላስያስ አማኞች የሚያካትት አይደለም። እግዚአብሔር በር ይከፍታል አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር እድል ያዘጋጃል" የክርስቶስ ምስጢር ይህ ከክርስቶስ መምጣት በፊት ሰዎች በደንብ ያልተረዱትን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን የሚያመለክት ነው። በዚያ ቃል ምክንያት እኔ እስረኛ ነኝ "አሁን በእስር ቤት ያለሁት የኢየሱስ ክርስቶስን መልዕክት በመናገሬ ምክንያት ነው" ግልጽ አድርግ ዘንድ እና ልናገር እንደሚገባኝ ያህል መናር እችል ዘንድ ጸልዩልኝ። "የኢየሱስ ክርስቶስን መልዕክት ግልጽ በሆነ መልኩ መናር እችል ዘንድ ጸልዩልኝ።"

Colossians 4:5

ቆላስያስ **4**: **5**-**6**
በጥበብ ተመላለሱ። "ባሉት ዘንድ ጠቢባን ሁኑ" በውጭ ባሉቱ ዘንድ "አማኞች ባልሆኑት ዘንድ" ዘመኑን ዋጁ "በሚታደርጉት ነገር ጠቢባን ሁኑ" ቃላችሁ ሁል ጊዜ በጸጋ ይሆኑ። በጨው የተቀመመ ይሁን። አማራጭ ትርጉም: "ንግግራችሁ በጸጋ እና ሰዎችን የሚስብ ይሁን።" ለእነዚህ ነገሮች እንዴት ምላሽ መስጠት እንዳለብህ እወቅ "ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ከማንም ለሚመጣው ጥያቄ እንዴት መልስ መስጠት እንዳለብህ ማወቅ ይገባሃል"

Colossians 4:7

ቆላስያስ **4**: **7**-**9**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ለተወሰኑ ሰዎች ይሰጥ የነበረውን መመሪያ እንዲሁም ለግለሰቦች እና አማኞች ሰላምታ መስተላለፉን የሚበቃበት ክፍል ነው። ስለ እኔ ማወቅ የሚገባቸውን ነገር ለእናንተ ታውቋል "እኔ ላይ የሆነውን ነገር ሁሉ እነርሱ ይነግሯችኋል" (UDB) ለእናንተ ይገለጻል በዚህ ሥፍራ “እናንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የቆላስያስ አማኞችን ነው። አብሮን ባሪያ የሆነው "አብሮን የሚያገለግለው።" ምንም እንኳ ጳውሎስ ነጻ ሰው ቢሆንም ራሱን የክርስቶስ ባሪ አድርጎ ይመለከት ነበር እንዲሁም ቲኪቆስ አብሮን የሚያገለግል ነው። ስለእኛ ታውቁ ይሆናል በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስ እና ከእርስ ጋር የሚሠሩትን ሰዎችን ነው ነገር ግን ይህ በቆላስያስ የሚገኙ አማኞችን አያመለክትም። ልባችሁም እንዲጸና "እናንተን ለማበረታታት" አናሲሞስ አናሲሞስ በቆላስስ ከተማ ውስጥ የፊልሞን ባሪያ ነበር። ይህ ባሪያ ከፊልሞን ገንዘብ በመስረቅ ወደ ሮም ጠፍቶ የነበረ ሲሆን በዚያም በጳውሎስ አገልግሎት አማካኝነት ክርስቲያን ሆኗል። አሁን ከጳውሎስ ዘንድ የተጻፈውን ደብዳቤ ወደ ቆላስያስ ቤተ ክርስቲያን ይዘው የመጡት ቲኪቆስ እና አናሲሞስ ናቸው። ታማኝና ተወዳጅ ወንድም ጳውሎስ አናሲሞስን ክርስቲያን ወንድም እና የክርስቶስ ባሪያ ብሎ ይጠራዋል። ያስታውቃችኋልe " ቲኪቆስ እና አናሲሞስ ይነግሯችኋል" በዚህ የነበራቸውን ነገር ፈጽመዋል በቆላስያስ ከተማ ለሚገኙ አማኞች አሁን ጳውሎስ በሚኖርበት ሥፍራ እየተከናወነ ያለውን ነገር ይነግሯችኋል። በትውፊት ደረጃ ጳውሎስ በሮም በቤት እስር ወይም እስር ቤት እንደነበር ይነገራል።

Colossians 4:10

ቆላስያስ **4**: **10**-**11**
አርስጥሮኮስ ጳውሎስ ይህንን ደብዳቤ ለቆላስያስ ሰዎች ሲጽፍ በኤፌሶን ከጳውሎስ ጋር በእስር ነበረ። እርሱ ከመጣ "ማርቆስ ከመጣ" ኢየሱስ ተብሎ የሚጠራው ኢዮስጦስም ይህ ሰውም ከጳውሎስ ጋር አብሮ ይሠራ የነበረ ሰው ነው። ከተገረዙት መካከል አብረውኝ በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ የሚሠሩት እነዚህ ብቻ ናቸው። "እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ንጉሥ እንደሆነ ከእኔ ጋር ይሰብኩ የነበሩት ከአይዳዊያን አማኞች መካል እነዚህ ሦስት ሰዎች ብቻ ነበሩ" (UDB) ከተገረዙት መካከል እነነዚህ ብቻ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ናቸው "ከተገረዙት ሰዎች መካከል እነዚህ ሰዎች ኢዮስጦስም፣ ማርቆስ እና ኢየሱስ ብቻ ናቸው"

Colossians 4:12

ቆላስያስ **4**: **12**-**14**
ኤጳፍራ ኤጳፍራ በቆላስያስ ከተማ ውስጥ ላሉ ሰዎች ወንጌልን የሰበከ ሰው ነው። (ተመልከት COL 1:7) ከእናንተ የሆነው "ከእናንተ ከተማ የሆነው" ወይም "የከተማችሁ ሰው የሆነው" (UDB) የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ "የክርስቶስ ኢየሱስ የተሰጠ ደቀ መዝሙር" በጸሎት ሁል ጊዜ ስለ እናንተ ይጋደላል "በትጋት ስለ እናንተ ይጸልያል" ፈጽማችሁ በእርግጠኝነት በሙላት መቆም ትችሉ ዘንድ "በብስለት እና በመተማመን መቆም ትችሉ ዘንድ" ስለ እናንተ በትጋት እንደሚሠራ እኔ እመሰክራለሁ "ስለ እናንተ በትጋት እንደሚሠራ እኔ ራሴ ተመልክቻለሁ" (UDB) በሎዶቅያ ስላሉት በሎዶቅያ ከተማ ውስጥ ያለችው ቤተ ክርስቲያን። ሎዶቅያ በቆላስያስ አቅራቢያ የሚትገኝ ከተማ ናት። በኢያራ ስላሉት በኢያራ ከተማ ውስጥ ያለችው ቤተ ክርስቲያን። ዴማስ እርሱም ከጳውሎስ ጋር አብሮ ይሠራ የነበረ ሌላ ሰው ነው። ሰላም ብለዋችኋል "ሰላምታ አቅርበውላችኋል"

Colossians 4:15

ቆላስያስ **4**: **15**-**17**
ወንድሞችን ሰላም በሉልን "ለወንድሞች ሰሰላምታችንን አቅርቡልንል" በሎዶቅያ ላሉ በቆላስያስ ከተማ አቅራቢያ የሚትገኝ ከተማ ሲትሆን በዚህች ከተማ ውስይ ቤተ ክርስቲያን ነበር ንምፉ የተባለች ሴት ሲትሆን በቤቷ ውስጥ ቤተ ክርስቲያንነበር በሎዶቅያ ከተማ ውስጥ የሚገኘው ቤተ ክርስቲያን ንምፉ ተብላ በሚትጠራ ሴት ቤት ውስጥ ይካሄድ ነበር።አማራጭ ትርጉም: "ንምፉ እና በእርሷ ቤት ውስጥ የሚገናኙት የአማኝ ቡድኖች" (UDB) በእናንተ መካከል ይነበብ በዚህ ሥፍራ “እናንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በቆላስያስ ከተማ ውስጥ የሚገኙ አማኞች ነው። “ለአክሪጳም፦ በጌታ የተቀበልኸውን አገልግሎት እንድትፈጽሙው ተጠንቀቅ በሉልኝ።" ጳውሎስ አክሪጳን እግዚአብሔር የሰጠውን የሥራ ኃላፊነት በማስታወስ አክሪጳ ይህንን ኃላፊነት ለመወጣት በጌታ የተሰጠው አደራ እንዳለ ያስታውሰዋል።

Colossians 4:18

ቆላስያስ **4**: **18**-**18**
ኖት የለውም።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: 1 Thessalonians

1 Thessalonians

ምዕራፍ 1

1 ከጳውሎስ፣ ስልዋኖስና ጢሞቴዎስ በእግዚአብሔር አብና በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ላሉ ለተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን፤ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን! **2** በጸሎታቻን እያሳሰብን እግዚአብሔርን ሁልጊዜ ስለ ሁላችሁም እናመሰግናለን። **3** በእምነት ስለምትሠሩት ሥራ፣ በፍቅር ስለምትደክሙት ድካምና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ባላችሁ ተስፋ በመታመን ስለመጽናታችሁ በእግዚአብሔር በአባታችን ፊት ሳናቋርጥ እናስታውሳችኋለን። **4** በእግዚአብሔር የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ! መመረጣችሁን እናውቃለን፣ **5** ወንጌላችን በቃል ብቻ ወደ እናንተ አልመጣምና፥ ነገር ግን በኃይል፣ በመንፈስ ቅዱስና በብዙ መረዳትም እንጂ፥ ስለእናንተ ስንል በመካከላችሁ ደግሞ እንዴት እንደነበርን ታውቃላችሁ። **6** በብዙ መከራ ውስጥ ቃሉን ከመንፈስ ቅዱስ ደስታ ጋር ስትቀበሉት እኛንና ጌታን የምትመስሉ ሆናችሁ፣ **7** በመቄዶንያ ሁሉና በአካይያ ላሉ ለሚያምኑት ምሳሌ ሆናችሁላቸዋል። **8** የጌታ ቃል ከእናንተ ተነሥቶ በመቄዶንያና አካይያ ብቻ ሳይሆን ምንም መናገር እስከማያስፈልገን ድረስ በእግዚአብሔር ላይ ያላችሁ እምነት በሁሉ ሥፍራ ተወርቷል። **9** እኛን በሚመለከት እንዴት ያለ አቀባበል እንዳደረጋችሁልን፣ ሕያውና እውነተኛ የሆነውን አምላክ ታገለግሉ ዘንድ ከጣዖታት እንዴት ወደ እግዚአብሔር ዘወር **10** እንዳላችሁ፣ደግሞም ከሰማይ የሚመጣውን ልጁን፣ ያም ከሙታን ያስነሳውን፣ ሊመጣ ካለው ቁጣ የሚያድነንን ኢየሱስን እንደምትጠባበቁ እነርሱ ራሳቸው ይመሰክራሉ።

---

1 Thessalonians 1:1

1ኛ ተሰሎንቄ 1፡ 1-1
ጳውሎስ፣ ስልዋኖስ ጢሞቴዎስም ለቤተ ክርስቲያን UDB በግልጽ ይህንን ደብዳቤ የጻፈው ጳውሎስ መሆኑን ይናገራል። ሠላም ለእናንተ ይሁን በዚህ ሥፍራ “እናንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የተሰሎንቄ አማኞችን ነው።

1 Thessalonians 1:2

1ኛ ተሰሎንቄ 1፡ 2-3
እኛም ሁል ጊዜ ለእግዚአብሔር ምስጋናችንን እናቀርባለን አማራጭ ትርጉም: "እዘውትረን ለእግዚአብሔር ምስጋናን እናቀርባለን" ሁል ጊዜ እኛ በዚህ ሥፍራ “እኛ” የሚለው ቃል ጳውሎስን ስልዋኖስን እና ጢሞቴዎስን የሚወክል እንጂ በተሰሎንቄ ያሉ አማኞችን የሚወክል አይደለም። በጸሎታችን ስለ እናንተ እናሳስባለን "ስለ እናንተ እንጸልያለን" ያለማቋረጥ እናስባለን "ያለማቋረጥ እናስባለን" የእምነት ሥራ "የእምነት ሥራ" ወይም "በእግዚአብሔር የሚታምኑ ስለሆነ ለእርሱ ትሠራላችሁ" (UDB) የጠስፋችሁን መጽናት "በመተማመን መጽናታችሁን"

1 Thessalonians 1:4

1ኛ ተሰሎንቄ 1፡ 4-5
ወንድሞች "ወንድሞች" መጠራታችሁን እናውቃለን "በልዩ ሁኔታ ታገለግሉት ዘንድ እግዚአብሔር እንደመረጣችሁ እናውቃን" ወይም "የእርሱ ሕዝቦች እንሆን ዘንድ እግዚአብሔር እንደመረጣችሁ እናውቃለን" (UDB) እናውቃለን በዚህ ሥፍራ “እኛ” የሚለው ቃል ጳውሎስ፣ ስልዋኖስ እና ጢሞቴዎስን የሚያመለክት እንጂ በተሰሎንቄ ያሉትን አማኞችን የሚያመለክት አይደለም። ነገር ግን በኃይል፣ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት አማራጭ ትርጉሞች 1) "ጳውሎስ እና የእርሱ የሥራ አጋሮች በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካኝነት ወንጌልን በኃይል ይሰብካሉ።" ወይም 2) "ወንጌል በመንፈስ ቅዱስ ወቃሽ ኃይል አማካኝነት በአማኞች ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ የሚያመጣ ነው።" በላቀ ማረጋገጫ "በተመሳሳይ መልኩ" (UDB) ምን ዓይነት ሰዎች "እንዲህ ሲሆን እንዴት ባለ ሁኔታ መኖር እንዳለብን" (UDB)

1 Thessalonians 1:6

1ኛ ተሰሎንቄ 1፡ 6-7
እኛን መሳዮች ሆናችኋል መመስል ማለት መኮረጅ ወይም መከተል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም: “እኛ መስላችኋል”። በታላቅ መከራ "በታላቅ መከራ ወቅት" ወይም "በታላቅ ስደት ውስጥ" አካይ ይህች ከተማ በዘመኗ ግሪክ ውስጥ የነበረች ከተማ ናት።

1 Thessalonians 1:8

1ኛ ተሰሎንቄ 1፡ 8-10
ወጥተዋል "ወጥቶ ሄዷል" አካይ ይህች ከተማ በዘመኗ ግሪክ ውስጥ የነበረች ከተማ ናት።) በእያንዳንዱ ሥፍራ "በአከባቢው ሁሉ ባሉ የተለያዩ ቦታዎች" እነርሱ ራሳቸው ስለሆኑ ጳውሎስ በዚህ ሥፍራ ላይ እያመለከተ ያለው ስለ ተሰሎንቄ አማኞች የሰሙትን በዚያ አከባቢ የሚገኙ ቤተ ክርስቲያናትን ነው። እነርሱ ራሳቸው በዚህ ሥፍራ ላይ “እነርሱ ራሳቸው” ስለ ተሰሎንቄ አማኞች የሰሙትን ሰዎች አጽኖት ሰጥቶ ያመለክታል። ወደ እናንተ መግባታችን እንዴት እንደነበረ ስለ እኛ ይናገራሉና፤ "እንዴት ባለ መልኩ እኛን እንደተቀበላችሁ ታውቃላችሁ" (UDB) ልጆቹ ይህ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያሳይ ወሳኝ የሆነ ስም ነው። እርሱ ያስነሳው "እግዚአብሔር ከሞት ያስነሳው" እኛንም ያዳነን በዚህ ሥፍራ ላይ ጳውሎስ “እኛ” በሚለው ቃል ውስጥ የሚጽፍላቸውን ዓማኞች አካቷል።

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 2

1 ወንድሞች ሆይ! ወደ እናንተ መምጣታችን ፍሬቢስ እንዳልነበረ እናንተው እራሳችሁ ታውቃላችሁ፣ 2 ነገር ግን እንደምታውቁት ቀደም ሲል በፊልጵስዩስ
መከራና እንግልት ደረሰብን። በብዙ ተቃውሞ መካከል የእግዚአብሔርን ወንጌል ለእናንተ ለመንገር አምላካችን ድፍረት ሰጥቶናል። 3 የምንመክራችሁ ምክር
ከስሕተት ወይም ከእርኩሰት ወይም ከማታለል የመነጨ አይደለም፣ 4 ነገር ግን ወንጌልን በአደራ ይሰጠን ዘንድ እግዚአብሔር ታማኞች አድርጎ እንደቆጠረን
እንዲሁ ሰውን ሳይሆን ልባችንን የሚመረምረውን እርሱን ደስ ለማሰኘት እንናገራለን። 5 እናንተው እንደምታውቁት መቼም ቢሆን የሸንገላን ቃል አልተጠቀምንም፣
ገንዘባችሁን በመመኘት እንዳልሆነም እግዚአብሔር ምስክር ነው፣ 6 የክርስቶስ ሐዋርያት እንደመሆናችን ልንጠቀምባችሁ መብት ቢኖረንም እንኳን ከእናንተ
ወይም ከሌሎች ክብርን ከማንም ሰው አልፈለግንም። 7 ይልቁንም እናት የራስዋን ልጆች እንደምትንከባከብ በመካከላችሁ የዋሆች ሆንን። 8 ለእናንተ ካለን
ፍቅር የተነሳ የእግዚአብሔርን ወንጌል ብቻ ሳይሆን የራሳችንን ሕይወት እንኳን ጨምረን ብንካፈላችሁ ደስ ይለን ነበር፣ ምክንያቱም ለእኛ እጅግ የተወደዳችሁ
ሆናችኋልና። 9 ወንድሞች ሆይ! የእግዚአብሔርን ወንጌል በሰበክንላችሁ ጊዜ በማናችሁም ላይ ሸክም ላለመሆን ቀንና ሌሊት እንደሠራን ድካማችንንና
ጥረታችንን ታስታውሳላችሁ። 10 በእናንተ በምታምኑት መካከል እንዴት በቅድስና፣ በጽድቅና ነቀፋ በሌለበት ኑሮ ራሳችንን እንዳቀረብንላችሁ እግዚአብሔርና
እናንተም ጭምር ምስክሮች ናችሁ፣ 11 እናንተው እንደምታውቁት አባት ለራሱ ልጆች እንደሚያደርገው እያንዳንዳችሁን መከርናችሁ፣ አበረታታናችሁና 12
መሰከርንላችሁ፣ይኸውም ወደ ራሱ መንግሥትና ክብር ለጠራችሁ ለእግዚአብሔር እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ ነው። 13 በዚህ ምክንያት እኛ ደግሞ ሳናቋርጥ
እግዚአብሔርን እናመሰግናለን፣ የመልዕክቱን ቃል፣ የእግዚአብሔርን ቃል ከእኛ በሰማችሁ ጊዜ እንደ ሰው ቃል ሳይሆን፣ ነገር ግን እውነት እንደሆነ፣ በእናንተ
በምታምኑት ደግሞ እንደሚሠራ እንደ እግዚአብሔር ቃል ተቀበላችሁት። 14 እናንተም ወንድሞች ሆይ፣ በይሁዳ የሚኖሩ በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያምኑትን
የእግዚአብሔር አብያተክርስቲያናት የምትመስሉ ሆናችኋል፣ እነርሱ ከአይሁድ መከራ እንደደረሰባቸው እናንተ ደግሞ ከገዛ ራሳችሁ ሕዝብ ያንኑ መከራ
ተቀብላችኋልና፣ 15 አይሁድ ጌታ ኢየሱስንና ነቢያትን ገደሉ፣ እኛንም አሳደዱን፣ እነርሱ እግዚአብሔርን ደስ አያሰኙትም፥ ሰውን ሁሉ ይቃወማሉ። 16 ዘወትር
ኀጢአታቸውን ለማብዛትም ይድኑ ዘንድ ለአሕዛብ እንዳንናገር ይከለክሉናል። ቁጣው በላያቸው ላይ መጥቶባቸዋል። 17 ወንድሞች ሆይ፣ እኛ ለጥቂት ጊዜ
በልባችን ሳይሆን በአካል ተለይተናችሁ ነበር፣ በመሆኑም በነበረን ታላቅ ናፍቆት ፊታችሁን ለማየት የተቻለንን ያህል ጥረት አድርገናል፣ 18 ወደ እናንተ
ለመምጣት ፈልገን ነበር፣ እኔ ጳውሎስም ከአንድም ሁለት ጊዜ ሞከርኩኝ፣ ነገር ግን ሰይጣን አዘገየን። 19 ጌታችን ኢየሱስ በሚመጣበት ጊዜ በፊቱ ተስፋችን
ወይም ደስታችን ወይም የመክበራችን አክሊል እንደሌሎቹ ሁሉ እናንተ አይደላችሁምን? 20 ምክንያቱም እናንተ ክብራችንና ደስታችን ናችሁ።

---

1 Thessalonians 2:1

1ኛ ተሰሎንቄ **2**፡ **1-2**
እናንተ ራሳችሁ በዚህ ሥፍራ “እናንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በተሰሎንቄ የሚገኙ አማኞችን ነው።።
ወንድሞች በዚህ ሥፍራ ላይ ቃሉ ያለው ትርጉም ክርስቲያኖች ማለት ሲሆን ወንዶችን እና ሴቶችን ያካትታል። በክርስቶስ የሚያምኑ ሰዎች ሁሉ
እግዚአብሔር መንፈሳዊ አባታቸው የሆነ የአንድ መንፈሳዊ ቤተሰብ አባላት በመሆናቸው ምክንያት ነው። መምጣታችን በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው
ቃል ጳውሎስ፣ ስልዋኖስ እና ጢሞቴዎስን የሚያመለክት ነው። ይሁን እንጂ በተሰሎንቄ የነበሩትን አማኞች ግን አያመለክትም። ከንቱ አልነበረም "በጣም
ጠቃሚ ነበር" መከራን ተቀበልን እንዲሁም ተዋረድን ጳውሎስ በፊልጵስዮስ እያለ ተደብድቧል እንዲሁም ታሥሯል። አማራጭ ትርጉም: “ተንገላታን
እንዲሁም ተሰደብን።" ከብዙ ግጭቶች መካከል "ታላቅ ተቃውሞ ከደረሰብን በኋላ"

1 Thessalonians 2:3

1ኛ ተሰሎንቄ **2**፡**3-4**
ለእኛ ብርታት ይሆነን ዘንድ በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል ጳውሎስ፣ ስልዋኖስ እና ጢሞቴዎስን የሚያመለክት ነው። ከስሕተት ወይም ከርኩሰት
ወይም ከተንኰል አልነበረምና፤ "እውነተኛ፣ ንጹሕ እና ታማኝ" ልባችንን የሚመረምረው እግዚአብሔር "አእምሮዋችንን እና ሥራችንን የሚመረምረው
እግዚአብሔር"

1 Thessalonians 2:5

1ኛ ተሰሎንቄ **2**፡**5-6**
እኛ ስለሆንን በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል ጳውሎስ፣ ስልዋኖስ እና ጢሞቴዎስን የሚያመለክት ነው። ይሁን እንጂ በተሰሎንቄ የነበሩትን አማኞች
ግን አያመለክትም። በሚያማልል መልኩ ከቶ አልተናገርንም "የውሸት ሙገሳን ከቶ አልተናገርንም" ያመካኘን በመጐምጀት አልሠራንም፤ "ወይም በስስት
እናንተ የተለያዩ ነገሮችን ትሰጡን ዘንድ የተለያዩ ቃላትን አልተጠቀምንም"
የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ይገባናል ማለት እንችል ነበር "የተለያዩ ነገሮችን እንዲትሰጡን ልንጠይቅ እንችል ነበር"

1 Thessalonians 2:7

1ኛ ተሰሎንቄ **2**፡**7-9**
ልክ እናት ልጆቿን እንደሚታጽናና ልክ እናት በእርጋታ ልጇችን እንደምታጽናና እንዲሁም ጳውሎስ፣ ስልዋኖስ እና ጢሞቴዎስን ለተሰሎንቄ አማኞች ረጋ ባለ ሁኔታ አስረድተዋቸዋል። እንወዳችኋለን "ወደናችኋል" ለእኛ በጣም
የተወደዳችሁ ሆናችኋል "ለእናነት ከልባችን እንጠነቀቃለን" ወንድሞች በዚህ ሥፍራ ላይ ቃሉ ያለው ትርጉም ክርስቲያኖች ማለት ሲሆን ወንዶችን እና ሴቶችን ያካትታል። በክርስቶስ የሚያምኑ ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔር መንፈሳዊ
አባታቸው የሆነ የአንድ መንፈሳዊ ቤተሰብ አባላት በመሆናቸው ምክንያት ነው። ልፋታችን እና ድካማችን “ድካማችን” እና “ልፋታችን” የሚሉት ቃላት
በመሠረታዊነ ትርጉማቸው ተመሣሣይ ናቸው። ጳውሎስ እነዚህ ቃላት የተጠቀመው በእነርሱ መካከል ሳለ ጳውሎስ ምን ያኽል እንደደከመ ለማሳየት መው። አማራጭ ትርጉም: "ምን ያኽል በትጋት እንደሠራን።" በማናችሁም ላይ ሸክም እንዳንሆን ብለን ቀን ከሌት ሠራን "ከእናንተ ዘንድ እርዳታ እንዳንሻ
በማለት ለራሳችን የሚያስፈልገንን ነገር ሠረተን አገኘን።"

1 Thessalonians 2:10

1ኛ ተሰሎንቄ **2**፡**10-12**
ቅዱስ፣ ጻድቅ እና እንከን ያሌለበት ጳውሎስ እነዚህ በመሠረታዊ ትርጉማቸው ተመሳሳይ ቃላትን በዚህ ሥፍራ የተጠቀመበት ምክንያት በመካከላቸው ሳለ ጥሩ ባሕርይ እንደነበረው አጽኖት ሰጥቶ ለማሳየት ነው። አባት ከልጆቹ ጋር ጳውሎስ አባት ልጆቹ ምን ዓይነት ባሕርይ እንዲኖራቸው ከሚያስተምርበት መንገድ ጋር እያነጻጸረ አማኞች ለእግዚአብሔር እንደሚገባ ይኖሩ ዘንድ አማኞችን ያበረታታል። እየመከርንን እናጽናናችኋለን “መምከር” እና “ማጽናናት” የሚሉት ቃላት በመሠረታዊ ሀሳባቸው ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ቃላት ነው። ጳውሎስ እነዚህ ቃላት በዚህ ሥፍራ ላይ የተጠቀመው በተሰሎንቄ የሚኖሩ ክርስቲያኖችን ለማበረታታት ነው። አማራጭ ትርጉም: “እኛ አጥብቀን እናበረታታችኋለን”። ለራሱ መንግስት እና ክብር በዚህ ሥፍራ ላይ “ክብር” የሚለው ቃል “መንግስት” ለሚለው ቃል ምንነትን የሚገልጥ ነው። አማራጭ ትርጉም: “ለእርሱ ለራሱ በክብር የተሞላ መንግስት።"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Thessalonians 2:13

1ኛ ተሰሎንቄ 2፡ 13-13
በዚህም ምክንያት እኛም እግዚአብሔርን ሁል ጊዜ እናመሰግናለን "እግዚአብሔርን ሁል ጊዜ እናመሰግናን ምክንያቱም" እናንተ በተቀበላችሁ ጊዜ በተሰሰሎንቄ ይኖሩ የነበሩ አማኞች ጳውሎስ ያመታውን መልዕክት ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ መልዕክት አድርገው ተቀበሉት እንጂ ከራሱ በጳውሎስ ኃይል የመጣ አድርገው አላዩትም።

1 Thessalonians 2:14

1ኛ ተሰሎንቄ 2:14-16
ወንድሞች በዚህ ሥፍራ ላይ ይህ ቃል ክርስትያኖች የሚል ትርጉም አለው። ቤተ ክርስቲያናትን የሚትመስሉ ሁኑ የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች በአይሁድ መሪዎች ስደት የደረሰባቸው ሲሆን ልክ እንደዚሁም በተሰሎንቄ ያሉት አማኞች በተሰሎንቄ ከተማ በሚኖሩ ሰዎች ስደት ደርሶባቸዋ። "ቤተ ክርስቲያናትን መስላችኋል" ከገዛ ሀገራችን ሰዎች "ከሌሎች በተሰሎንቄ ከተማ ከሚኖሩ ሰዎች" እንዳንናገር ከለከሉን "እንዳንናገር ሊያስቆሙን ጥረት አደረጉ" ኃጢአታቸውን ይሞላ ዘንድ ሁል ጊዜ "በቀጣይነት ኃጢአት ያደርጉ ዘንድ" ቁጣ በእነርሱ ላይ መጥቶባቸዋል "የእግዚአብሔር ቅጣት በእነርሱ ላይ መጥቷል" ወይም "የእግዚአብሔር ቁጣ በእነርሱ ላይ መጥቷል"

1 Thessalonians 2:17

1ኛ ተሰሎንቄ 2፡ 17-20
ወንድሞች በዚህ ሥፍራ ቃሉ የሚያመለክተው ክርስትያኖችን ነው። በአካል፣ በልብ ሳይሆን "በአካል ነገር ግን ሁል ጊዜ ስለ እናንተ መጸለያችንን ቀጥለናል" ፍታችሁን ለማየት "እናንተን ለማየት" ወይም "ከእናንተ ጋር ለመሆን" እኔ ጳውሎስ እንደገና "እኔ ጳውሎስ ሁለት ጊዜ ያኸል ሞክሬያለሁ" እርሱ ሲመጣ ትምክታችን የሚሆነው ምንድ ነው? "ጌታችን ኢየሱስ ዳግም ሲመጣ ለወደፊት ትምክታችን፣ ሐሴት የሚናደርግበት እና የክብር አክልል የሚትሆኑን እናነት እና ሌሎች ናችሁ።"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 3

1 ስለዚህ ከዚያ በላይ ልንታገስ ባልተቻለን ጊዜ በአቴና ለብቻችን መቅረታችን መልካም እንደሆነ አሰብን። 2 በእምነታችሁ ያጸናችሁና ያበረታችሁ ዘንድ
ወንድማችንንና በክርስቶስ ወንጌል የእግዚአብሔር አገልጋይ የሆነውን ጢሞቴዎስን ላክንላችሁ፣ 3 ይህንን ያደረግነውም በእነዚህ መከራዎቻችሁ ማንም
እንዳይናወጥ ነው፣ ለዚህ እንደተመረጥን ራሳችሁ ታውቃላችሁና። 4 በእርግጥ ከእናንተ ጋር በነበርንበት ወቅት መከራ ልንቀበል እንዳለን አስቀድመን
ነግረናችሁ ነበር፣ እንደምታውቁት የሆነውም ይኸው ነው። 5 በዚህ ምክንያት ወደፊት ልታገስ ባቃተኝ ጊዜ ምናልባት ፈታኙ ፈትኗችሁ ልፋታችንም ከንቱ ሆኖ
እንዳይቀር ስለ እምነታችሁ አውቅ ዘንድ ላክሁት። 6 ጢሞቴዎስ ከእናንተ ዘንድ ተመልሶ ስለ እምነታችሁና ፍቅራችሁ የምሥራች ባመጣልን ጊዜ ሁልጊዜ
በመልካም እንደምታስታውሱንና እኛ ደግሞ ልናያችሁ እንደምንናፍቅ ሁሉ ልታዩን እንደምትናፍቁ ሲነግረን 7 በዚህ ምክንያት ወንድሞች ሆይ፣ በችግራችንና
በመከራችን ሁሉ በእናንተ እምነት ተጽናንተናል። 8 በጌታ ጸንታችሁ ብትቆሙ እኛ ደግሞ አሁን በሕይወት እንኖራለን። 9 በእናንተ ምክንያት በአምላካችን ፊት
ስላገኘነው ደስታ ሁሉ ስለ እናንተ ለእግዚአብሔር እንዴት ያለ ምስጋና ማቅረብ እንችል ይሆን? 10 ፊታችሁን ለማየትና በእምነታችሁ የሚጎድላችሁን ለመሙላት
ሌሊትና ቀን እጅግ አጥብቀን እንጸልያለን። 11 ራሱ አምላካችንና አባታችን፣ ጌታችንም ኢየሱስ ወደ እናንተ እንድንመጣ መንገዳችንን ያቅና፣ 12 እኛ ደግሞ
እንደምናፈቅራችሁ ጌታ ለእርስ በርሳችሁና ለሰው ሁሉ የሚሆን ፍቅራችሁን ያብዛ ያትረፍርፍም። 13 ጌታችን ኢየሱስ ከቅዱሳኑ ሁሉ ጋር ሲመጣ በአምላካችንና
በአባታችን ፊት ልባችሁን ነቀፋ በሌለበት ቅድስና ያጸና ዘንድ ይህንን ያድርግላችሁ።

---

1 Thessalonians 3:1

1ኛ ተሰሎንቄ **3**:**1**-**3**
ከእንግዲህ ልንሸከመው አንችልም በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል ጳውሎስ፣ ስልዋኖስ እና ጢሞቴዎስን የሚያመለክት ነው። ይሁን እንጂ በተሰሎንቄ የነበሩትን አማኞች ግን አያመለክትም። አማራጭ ትርጉም: "ከእንግዲህ ወዲህ ስለ እናንተ አንጨነቅም።" በአቴና ብቻችንን ልንቀር በጎ ፈቃዳችን ሆነ። "ስልዋኖስ እና አኔ በአቴና ወደ ኋላ ለመቅረት በጎፈቃዳችን ሆነ።" በጎ "ትክክለኛ" ወይም "ምክንያታዊ" አቴና ይህች በአሁና ግሪክ ውስጥ በአካያ ግዛት ውስጥ የሚትገኝ ከተማ ናት። ወንድማችንr "ክርስትያን ወንድማችን" ማንም ሰው እንዳይናወጥ "ማንም ሰው እንዳይረበሽ" ወይም "ማንም እንዳይደናገጥ" እኛ እንደተመረጥን "እኛ እንደተወሰንን"

1 Thessalonians 3:4

1ኛ ተሰሎንቄ **3**:**4**-**5**
እውነት አማራጭ ትርጉም: "በእርግጠኝነት" ወይም "ርግጡን" እኛ ከእናንተ ጋር ነን በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል ጳውሎስ፣ ስልዋኖስ እና ጢሞቴዎስን የሚያመለክት ነው። ይሁን እንጂ በተሰሎንቄ የነበሩትን አማኞች ግን አያመለክትም። አማራጭ ትርጉም: "ከእንግዲህ ወዲህ ስለ እናንተ አንጨነቅም።" መካራን መቀበል "በሌሎች ሰዎች መሰቃየት" እታገሥ ዘንድ ባልተቻለኝ ጊዜ በዚህ ሥፍራ ላይ “እኔ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን ነው። አማራጭ ትርጉም: “በአስቸኳይ ለማወቅ እፈልጋለሁ”። ላኩኝ "ጢሞቴዎስን ላኩኝ" በከንቱ "ጥቅም ላሌለው ነገር"

1 Thessalonians 3:6

1ኛ ተሰሎንቄ **3**:**6**-**7**
ወደ እኛ መጣ በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን ስልዋኖስ እና ጢሞቴዎስን እንደጂ በተሰሎንቄ የነበሩ አማኞችን አይደለም። ስለ እምነታችሁ መልካም ዜናን "ስለ እምነታችሁ መልካም ወሬ ይዞ መጥቷል" እናንተ ሁል ጊዜ መልካም ትዝታ አላችሁ "እናንተ ሁል ገዚ መልካም ትዝታ አላችሁ" ከእንግዲህ ወዲህ አታዩንም "ለታዩን ትፈልጋላችሁ" ወንድሞች በዚህ ሥፍራ “ወንድሞች” የሚለው ቃል ክርስትያኖች ማለት ነው። በእምነታችሁ በኩል "በክርስቶስ ባላችሁ እምነት በኩል" ወይም "በክርስቶስ ላይ ባላችሁ ቀጣይነት ያለው እምነት። በመከራችን እና በችግሮቻችን ሁሉ ውስጥ በዚህ ሥፍራ “መከራ” የሚለው ቃል በ”ችግር” ውስጥ ለመግባት ምክንያቱ ምንድ እንደሆነ ያብራራል። አማራጭ ትርጉም: "ሰዎች መከራን በእኛ ላይ በማምጣታቸው ምክንያት በተፈጠዉት ችግሮቻችን ውስጥ።"

1 Thessalonians 3:8

1ኛ ተሰሎንቄ **3**:**8**-**10**
አሁን በሕይወት እንኖራለን በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን ስልዋኖስ እና ጢሞቴዎስን እንደጂ በተሰሎንቄ የነበሩ አማኞችን አይደለም። አማራጭ ትርጉም: "በጣም ተበረታተናል።" እናንተ ጸንታችሁ ቁሙ አማራጭ ትርጉም: "እናንተ አብዝታችሁ ታመኑ" ከእናንተ የተነሣ ስለምንደሰተው ደስታ ሁሉ፥ ለእግዚአብሔር በእናንተ ምክንያት ምን ያህል ምስጋና እናስረክብ ዘንድ እንችላለን? ይህ ጥያቄ ምስጋንን የሚያሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም: "እግዚብሔር ስለእናንተ ስላደረገው ነገር እግዚአብሔር አመስግነን አንጠግብም! ወደ እግዚአብሔር ስንጸልይ ስለ እናነት በጣም ደስ ይለናል!" ሌሊት እና ቀን "Frequently" በጣም ከባድ "ከመጠን ይልቅ" ፊታችሁን ላይ "እናንተን ለመጎብኘት"

1 Thessalonians 3:11

1ኛ ተሰሎንቄ **3**:**11**-**13**
እግዚአብሔር አምላካችን ያድርግ "አምላካችን ይህንን ያድረግ ዘንድ እንጸልያለን" አምላካችን . . . ጌታችን ኢየሱስ ይህንን ያድረግ በዚህ ሥፍራ ላይ “የእኛ” የሚለው ቃል ሁሉንም አማኞችን የሚያመለክት ቃል ነው። አብ እራሱ በዚህ ሥፍራ ላይ “እራሱ” የሚለው ቃል ወደ ኃላ ኄዶ “አብ”ን የሚያመለክት ሲሆን ጠቀሜታውም አጽኖት ለመስጠት ነው። መንገዳችንን ያቅና በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን ስልዋኖስ እና ጢሞቴዎስን እንደጂ በተሰሎንቄ የነበሩ አማኞችን አይደለም። እኛም ይህንን እናደረጋለን በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን ስልዋኖስ እና ጢሞቴዎስን እንደጂ በተሰሎንቄ የነበሩ አማኞችን አይደለም። እርሱም ይህንን ያድርግ "እግዚአብሔር ይህንን እንዲያደረግ እንጸልያለን" በጌታችን በኢየሱስ መምጫ ጊዜ "ኢየሱስ ወደ ምድር ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ" ከእርሱ ቅዱሳን ሁሉ ጋር "የእርሱ ከሆኑት ሁሉ ጋር" (UDB)

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 4

1 በመጨረሻም ወንድሞች ሆይ፣ እንዴት መመላለስና እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት እንዳለባችሁ ከእኛ በተቀበላችሁት ትምህርት መሠረት አሁን እንደምትኖሩት
ሁሉ ከዚህም አብልጣችሁ እንድታደርጉ በጌታ በኢየሱስ እንመክራችኋለን እናደፋፍራችሁማለን። 2 በጌታ በኢየሱስ በኩል እንዴት ያለውን ትዕዛዝ እንደሰጠናችሁ
ታውቃላችሁና፤ 3 በቅድስና መኖራችሁ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፣ 4 ከእናንተ እያንዳንዱ ከዝሙት በመራቅ የራሱን አካል በቅድስናና በክብር ማግኘት
እንዳለበት ታውቃላችሁ፣ 5 እግዚአብሔርን እንደማያውቁ እንደ አሕዛብ የፍትወት ምኞት አይሁን፣ 6 በዚህ ጉዳይ ማንም አይተላለፍ ወንድሙንም አያታልል፣
ምክንያቱም አስቀድመን እንደነገርናችሁና እንዳስጠነቀቅናችሁ ጌታ ስለነዚህ ነገሮች ሁሉ የሚበቀል ነውና። 7 እግዚአብሔር ለቅድስና እንጂ ለእርኩሰት
አልጠራንም። 8 ስለዚህ ይህንን የማይቀበል ሰውን ሳይሆን የማይቀበለው ቅዱስ መንፈሱን የሰጣችሁን እግዚአብሔርን ነው። 9 የወንድማማች መዋደድን
በተመለከተ ማንም ሊጽፍላችሁ አያስፈልጋችሁም፣ እርስ በርስ ስለመዋደድ እናንተው ራሳችሁ ከእግዚአብሔር ተምራችኋልና። 10 በመቄዶንያ ላሉ ወንድሞች
ሁሉ ይህንን ታደርጋላችሁ፣ ይሁን እንጂ ወንድሞች ሆይ፣ ከዚህም አብልጣችሁ እንድታደርጉት ደግሞ እንመክራችኋለን። 11 ደግሞም ልክ እንዳዘዝናችሁ
በጸጥታ እንድትኖሩ፣ በራሳችሁ ጉዳይ ላይ እንድታተኩሩና በገዛ እጆቻችሁ እንድትሠሩ እንመክራችኋለን። 12 በማያምኑት ዘንድ በአግባብ እንድትመላለሱና
በኑሮአችሁ ምንም የሚጎድላችሁ እንዳይኖር ይህንን አድርጉ። 13 ወንድሞች ሆይ፣አንቀላፍተው ስላሉት ባለማወቃችሁ ስለወደፊቱ ተስፋ እንደሌላቸው እንደ
ሌሎች ሀዘናችሁ መሪር እንዲሆን አንፈልግም። 14 ኢየሱስ እንደሞተና እንደተነሳ ካመንን በእርሱ አምነው ያንቀላፉትን እግዚአብሔር ከኢየሱስ ጋር
ያመጣቸዋል። 15 በጌታ ቃል የምንነግራችሁ ይህንን ነው፣ ጌታ በሚመጣበት ጊዜ እኛ ሕያዋን ሆነን የቀረነው አስቀድመው ያንቀላፉትን በርግጥ አንቀድምም።
16 ጌታ ራሱ በታላቅ ድምፅ፣ በመላዕክት አለቃ ድምፅና በእግዚአብሔር መለከት ከሰማይ ይወርዳል፣ በክርስቶስ የሞቱትም አስቀድመው ይነሳሉ። 17 ከዚያም
እኛ ሕያዋን ሆነን የምንገኘው ጌታን በአየር ላይ ለመገናኘት ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፣ ሁልጊዜም ከጌታ ጋር እንሆናለን። 18 ስለዚህ እርስ በርሳችሁ
በእነዚህ ቃላት ተጽናኑ።

---

1 Thessalonians 4:1

1ኛ ተሰሎንቄ 4:1-2
ወንድሞች በዚህ ሥፍራ “ወንድሞች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ክርስትያኖችን ነው። እንመክራችኋለን እንዲሁም እንለምናችኋለን በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን ስልዋኖስ እና ጢሞቴዎስን እንደጂ በተሰሎንቄ የነበሩ አማኞችን አይደለም። በዚህ ሥፍራ ላይ “መምከር” እና “መለመን” የሚሉ ቃላት በመሠረታዊ ትርጉማቸው ተመሣሣይ ናቸው፡ ጳውሎስ በበዚህ ሥፍራ ላይ እነዚህ ቃት የተጠቀመው አጽኖት ለመስጠት እና ምን ያኽለወ አማኞችን ለማበረታታት እንደፈለገ ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም: "አብዝተን እናንተን እናበረተታችኋለን።" ከ . . . ዘንድ መመሪያ ወስዳችኋል "እናንተ በ . . . ተምራችኋል" ልትመላለሱ ይገባል በዚህ ሥፍራ “መመላለስ” የሚለው ቃል የአንድ ሰው አኗኗር መንገድን የሚያሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም: "እናት መኖር ይገባችኋል።"

1 Thessalonians 4:3

1ኛ ተሰሎንቄ 4:3-6
ከዝሙት እንዲትርቁ "ከዝሙት ተግባር ራቁ" እንዴት ማግኘት እንዳለባችሁ ታውቁ ዘንድ "እንዴት አብራችሁ መኖር እንደሚችሉ እንዲታውቁ" በፍተወት ምኞት "ትክክለኛ ያልሆነ የዝሙት ጥማት" ማንም "አንድም ሰው" ወይም "ዬትኛውም ሰው" መተላለፍ እና መበደል ይህ አንድን ሀሳብ በሁለት የተለያዩ መንገዶች መግለጽ ነው፡፤ አማራጭ ትርጉም: “መበደል”። ጌታ የሚበቀል ነው "ጌታ የሚተላለፉትን ይቀጣል እንዲሁም ለተበደሉት ይሟገትላቸዋል" እናንተን አስቀድሞ አስጠንቅቋችኋልና ተመስክሮላችኋል "አስቀድሞ ለእናነት ተነግሯችኋል እንዲሁም ከዚህ ነገር እንዲትቆጠቡ አበክሮ አስጠንቅቆዋችኋል"

1 Thessalonians 4:7

1ኛ ተሰሎንቄ 4:7-8
እግዚአብሔር ቅድስና እንጂ ለርኩሰት አልጠራንም "እግዚብሔር ፍጹም ንጹሐን እና ቅዱሳን እንዲንሆን ጠርቶናል" እግዚአብሔር አልጠራንም በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሁሉንም አማኞች ነው። ይህንን የማይቀበል ሰው "ይህንን ትምህርት የማይቀበል ማንኛውም ሰው" ወይም "ይንን ትምህርት ቸል የሚል ማንኛውም ሰው"

1 Thessalonians 4:9

1ኛ ተሰሎንቄ 4:9-12
የወንድማማች መዋደድ "ለአማኞች ያለ ፍቅር" እንዲሁ በመቄዶንያ ሁሉ ላሉት ወንድሞች ሁሉ ታደርጋላችሁና። "በመቅዶንያ ውስጥ ላሉት አማኞች ፍቅር ታሳያላችሁና።" ወንድሞች በዚህ ሥፍራ “ወንድሞች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ክርስቲያኖችን ነው። መነሳሳት "መከታተል" ወይም "ከልብ መጣር" የራሳችሁን ሥራ ሥሩ ይህ ማለት የሌላ ሰው ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ አትግቡ። አማራጭ ትርጉም: “የራሳችሁን ጉዳይ ብቻ ሥሩ”። በእጆቻችሁ ሥሩ "ለመኖር የሚያስፈልጋችሁን ለማግኘት የራሳችሁን ሥራ ሥሩ" በአግባቡ ተመላለሱ "በአክብሮት እና አግባብ ባለው መንገድ ነገሮች አከናውኑ" ተመልከት: ከእምነት ውጪ ያሉ ሰዎች "በክርስቶስ የማያምኑ ሰዎች" የሚያስፈልጋችሁ ነገር እንዳይኖር "አንዳች እንዳያስፈልጋችሁ"

1 Thessalonians 4:13

1ኛ ተሰሎንቄ 4:13-15
በተሳሳተ መንገድ እንዳትረዱት እንሻለን "በተገቢው መንገድ እንዲትገነዘቡን ዘንድ መሻታችን ነው" አንልግም በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን ስልዋኖስ እና ጢሞቴዎስን እንደጂ በተሰሎንቄ የነበሩ አማኞችን አይደለም። ወነወድሞች በዚህ ሥፍራ “ወንድሞች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ክርስትያኖችን ነው። ማንቀላፋት ይህ ቃል በዚህ ሥፍራ ያለው ትርጉም “መሞት” ማለት ነው። ማዘን የለባችሁም "ማልቀስ የለባችሁም" ተስፋ እንደሌላቸው እንደ ሌሎች ደግሞ እንዳታዝኑ፡ "እንደማያምኑ ሰዎች" የምናምን ከሆነ በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን እና የእርሱ ተደራሲያንን ነው። ከሞት እንደገና ተነሣ "ወደ ሕይወት እንደገና ተነሣ" እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉቱን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና። "እርሱ ተመልሶ ስመጣ በኢየሱስ አምነው የሞቱትን መልሶ ከሞት ያስነሳቸዋል።" ማቀላፋት ምሳሌያዊ ነግግር ሲሆን የሚያመለክተውም መሞትን ነው። ስለዚህም እንዲህ እንላለን በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን ስልዋኖስ እና ጢሞቴዎስን እንደጂ በተሰሎንቄ የነበሩ አማኞችን አይደለም። ጌታ ዳግም ሲመጣ "በክርስቶስ መምጫ ቀን" በእርግጥ አንቀድምም "ከእርሱ ፈጽሞ አንቀድምም"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Thessalonians 4:16

1ኛ ተሰሎንቄ **4**:**16**-**18**
ጌታ ራሱ ይወርዳል "ጌታ ራሱ ወደታች ይወርዳል" የመላእክት አለቃ "የመላእክት አለቃ" በክርስቶስ ሆነው የሞቱት በመጀመሪያ ይነሣሉ በዚህ ሥፍራ ይህ ቃል ያለው ትርጉም አካላዊ ሞትን የሚያመለክት ነው። "በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑት ነገር ግን የሞቱት ሰዎች በመጀመሪያ ከሞት ይነሣሉ" እኛ በሕይወት ያለን በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሁሉንም አማኞችን ነው። ከእነርሱ ጋር በዚህ ሥፍ “እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሞቱትን አማኞችን ነው። ጌታን በአየር ላይ ለመገናኘት በዳመና እነንነጠቃለን "ጌታን በሰማይ ለመገናኘት"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 5

1 ወንድሞች ሆይ፣ አሁን ስለ ጊዜያትና ዘመናት ሊጻፍላችሁ አያስፈልጋችሁም። 2 ሌባ በሌሊት እንደሚመጣ የጌታ ቀንም እንደዚያው እንደሆነ እናንተ ራሳችሁ በሚገባ ታውቃላችሁና። 3 እርጉዝን ሴት የምጥ ህመም እንደሚሆንባት ሁሉ “ሁሉ ሰላምና ደህና ነው” በሚሉበት በዚያን ጊዜ ድንገተኛ ጥፋት ይመጣባቸዋል፣ እነርሱም በምንም መንገድ አያመልጡም። 4 ወንድሞች ሆይ፣ እናንተ ግን ያ ቀን እንደ ሌባ ይመጣባችሁ ዘንድ በጨለማ አይደላችሁም። 5 ሁላችሁም የብርሃን ልጆች የቀንም ልጆች ናችሁና። እኛ የሌሊት ወይም የጨለማ ልጆች አይደለንም። 6 እንግዲያውስ ሌሎች እንደሚያደርጉት አናንቀላፋ፣ ነገር ግን እንንቃ በመጠንም እንኑር። 7 የሚያንቀላፉ በሌሊት ያንቀላፋሉ፣ የሚሰክሩትም በሌሊት ይሰክራሉና። 8 የብርሃን ልጆች እንደመሆናችን በመጠን እንኑር፣ የእምነትንና የፍቅርን ጥሩር፣ የድነታችንን ተስፋ እርግጠኝነትም እንደ ራስ ቁር እንልበስ። 9 በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ድነትን ልንቀበል እንጂ እግዚአብሔር ለቁጣ አልመደበንም፣ 10 የነቃን ወይም ያንቀላፋን ብንሆን ከእርሱ ጋር እንድንኖር ስለ እኛ ሞቶአልና። 11 ስለዚህ አሁን እንደምታደርጉት ሁሉ እርስ በርሳችሁ ተጽናኑ፣ አንዱም ሌላውን ያንጸው። 12 ወንድሞች ሆይ፣በመካከላችሁ በማገልገል የሚለፉትንና በጌታ የሚያስተዳድሯችሁን፣ የሚመክሯችሁንም እንድታከብሯቸው እንጠይቃችኋለን። 13 ደግሞም በሥራቸው ምክንያት ከፍ ያለ የፍቅር አክብሮት እንድታሳዩአቸው እንጠይቃችኋለን። እርስ በርሳችሁ በሰላም ኑሩ። 14 ወንድሞች ሆይ እንመክራችኋለን፣ ያለ ሥርዓት የሚመላለሱትን ገስጹአቸው፣ ድፍረት ያጡትን አበረታቱአቸው፣ ደካሞችን ደግፉአቸው፣ሰውን ሁሉ ታገሱ። 15 ማንም ስለተደረገበት ክፉ ነገር ለሌላው በክፉ እንዳይመልስ ተጠንቀቁ፣ ነገር ግን ለእርስ በርሳችሁና ለሰው ሁሉ መልካም የሆነውን ለማድረግ ሁልጊዜ ትጉ። 16 ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ፣ 17 ባለማቋረጥ ጸልዩ፣ 18 ስለ ሁሉም ነገር አመስግኑ፣ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ለእናንተ ነውና። 19 የመንፈስ ቅዱስን ሥራ አታዳፍኑ። 20 ትንቢትን አትናቁ። 21 ሁሉን መርምሩ፣ መልካም የሆነውን ያዙ፣ 22 ማንኛውንም ዓይነት ክፋት አስወግዱ። 23 የሰላም አምላክ ራሱ ፈጽሞ ይቀድሳችሁ፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ መላው መንፈሳችሁ፣ ነፍሳችሁና ሥጋችሁ ያለ ነቀፋ ይጠበቅ። 24 የጠራችሁ ታማኝ ነው፣ እርሱም ደግሞ ያደርገዋል። 25 ወንድሞች ሆይ፣ ስለ እኛ ደግሞ ጸልዩ። 26 ወንድሞችን ሁሉ በተቀደሰ አሳሳም ሰላም በሏቸው። 27 ይህ መልዕክት ለወንድሞች ሁሉ እንዲነበብ በጌታ አደራ እላችኋለሁ። 28 የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን።

---

1 Thessalonians 5:1

1ኛ ተሰሎንቄ 5:1-3
ጌዜውን እና ዘመኑን "ጌታ ኢየሱስ ተመልሶ የሚመጣበት ጊዜ" (UDB) ወንድሞች በዚህ ሥፍራ ላይ “ወንድሞች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ክርስቲያኖችን ነው። በግልጽ "በደንብ" ወይም "በእርግጥ" (UDB) እንደ ሌባ በምሽት ሌባ በምሽት ለመስረቅ በስትን ሰዓት እንደሚመጣ ማንም እንደማያውቅ ሁሉ ጌታም መቼ እንደሚመጣ አናውቅም። አማራጭ ትርጉም: "በድንገት።" እነርሱ እንዲህ ሲሉ "ሰዎች እንዲህ ባሏችሁ ጊዜ" ከዚያ ድንገተኛ ጥፋት ይሆናል "ከዚያም ያልተጠበቀ ጥፋት ይሆናል" ምጥ እርጉዝን እንደሚይዛት ልክ እርጉዝ ሴት በድንነት ምጥ እንደሚጀምራት እና እስክትወልድ ድረስ እንደማያቋርጥ እንደዚሁ ጥፋት ይመጣና ከዚህ ጥፋት ሰዎች አያመልጡም። (ተመልከት:

1 Thessalonians 5:4

1ኛ ተሰሎንቄ 5:4-7
እናንተ ወንድሞች ሆህ በጨለማ ውስጥ አይደላችሁም በዚህ ሥፍራ “ወንድሞች” የሚለው ቃል ክርስትያኖችን የሚያመለክት ነው። “የዚህ ክፋት የሞላበት ምድር፣ በጨለማ ውሰጥ አይደላችሁም።" ቀኑ እንደ ሌባ ይደርስባችሁ ዘንድ የጌታ መምጫ ቀን ሌባ ለመዝረፍ መምጣቱ እንደሚያስገርም አያስገርምም። "ሳትዘጋጁ እንዳይደርስባችሁ።" እናነት ሁላችሁ የብርሃን ልጆች ናችሁ...የጨለማ ልጆች አይደላችም በዚህ ሥፍራ ላይ “የብርሃን ልጆች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የክርስቶስን ተከታዮችን ነው። “የጨለማ ልጆች” የሚለው ቃል ደግሞ ዓምን የሚከተሉትን ሁሉ ነው። ሌሎች እንዳንቀላፉት አናንቀላፋ ጳውሎስ እንቅልፍን ኢየሱስ በዓለም ላይ ለመፍረድ ተመልሶ እንደሚመጣ ከማያውቁ ሰዎች ጋር ያነጻጽረዋል። "ኢየሱስ ዳግም እንደሚመጣ እንደማያቁ ሌሎች ሰዎች አንሁን።" መሆን በዚህ ክፍል ውስጥ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሁሉንም አማኞችን ነቅተን እንጠብቅ እንዲሁም በመጠን እንኑር በክርስቶስ አማኞች ስለ እርሱ ዳግም ምጻት ማወቅ እና ራሳቸውን በመግዛት መኖር ይገባቸዋል። የሚያንቀላፉት ሰዎች በምሽት ያንቀላፉ ሰዎች የሚተኙት በምሽት እንደሆነ ሁሉ እንዲሁም ምን እንደተፈጠረ እንደማያወቁ ሁሉ ዓለምም እንዲሁ ናት ክርስቶስ መቼ ተመልሶ እንደሚመጣ አታውቅም። የሚጠጡ ሰዎች ይህንን በምሽት ያደርጋሉ ጳውሎስ መጠጥ የሚጠጡ ሰዎች በምሽት ይህንን እንደሚድርጉ በምግለጽ እንዲሁም ሰዎች ክርስቶስ ዳግም እንደሚመጣ አለማወቃቸው ራሳቸውን ገዝተው እንዳይሩ ያደርጋል።

1 Thessalonians 5:8

1ኛ ተሰሎንቄ 5:8-11
የብርሃን ልጆች ይህ በክርስቶስ የሚምኑ ሰዎች መገለጫ ነው። አማራጭ ትርጉም: "በክርስቶስ የሚያምኑ" ወይም "የብርሃን ልጆች።" ራሳችንን እንግዛ "ራሳችንን በመግዛት እንኑር" ጥሩር ልበሱ ወታደር አካሉን ለመጠበቅ ጥሩር ይለብሳል። እንዲሁም በእመነት እና በፍቅር የሚኖር አማኝም መከላከያ ያገኛል። አማራጭ ትርጉም: “ራሳችንን እንጠብቅ።” የራስ ቁር ልክ የራስ ቁር የወታደሮችን ራስ ቅል ከአደጋ እንደሚጠብቅ ሁሉ የድነት ዋስትናም አማኞችነን ይጠብቃል። አማራጭ ትርጉም: “ይህንን እወቁ” ነቅተንም ይሁን አልቀላፈተን ቢሆን "በሕይወት ቢንኖር ወይም ቢንሞት" እርስ በእርሳችሁ ተናነጹ "እርስ በእርሳችሁ ተበረታቱ"

1 Thessalonians 5:12

1ኛ ተሰሎንቄ 5:12-14
ወንድሞች በዚህ ሥፍራ ላይ “ወንድሞች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው አማኞችን ነው።

በመካከላችሁ የሚደክሙትን በጌታም የሚገዙአችሁን የሚገሥጹአችሁንም ታውቁ ዘንድ ስለ ሥራቸውም በፍቅር ከመጠን ይልቅ ታከብሩአቸው ዘንድ እንለምናችኋለን። "በመሪነት ላይ ያሉ ሰዎችን አበረታቷቸው"

በጌታም የሚገዙአችሁን ይህ በአንድ አከባቢ ያሉ የአማኞች ቡድኖችን ለማገልገል በእግዚብሔር የተሾሙትን ሰዎችን ያመለክል። ስለ ሥራቸውም በፍቅር ከመጠን ይልቅ ታከብሩአቸው ዘንድ እንለምናችኋለን። አማራጭ ትርጉም: "ስለ ሥራቸው አክብሯቸው ምክንያቱም ትወዷቸዋላችሁና"

1 Thessalonians 5:15

1ኛ ተሰሎንቄ 5:15-18
ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ፤ ሳታቋርጡ ጸልዩ፤ በሁሉ አመስግኑ፤ ጳውሎስ አማኞች በነገር ሁሉ የሚያመሰግኑ አመለካከት እንዲኖራቸው፣ በትጋት እንዲጸልዩ እና በሁሉም ነገር አመስጋኞች ይሆኑ ዘንድ ያበረታታል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Thessalonians 5:19

1ኛ ተሰሎንቄ 5:19-22
ትንቢትን አትናቁ፤ "ትንቢት ይበቃል አትበሉ" ወይም "መንፈስ ቅዱስ ለአንድ ሰው የተናገረውን ነገር አትጥሉ" ሁሉን ነገር ፈትኑ "ሁሉም ትንቢቶች እውነት እና ከእግዚአብሔር መሆናቸውን እርግጠኞች ሁኑ"

1 Thessalonians 5:23

1ኛ ተሰሎንቄ 5: 23-24
ለራሱ ሁሉን ነገር ሙሉ ለሙሉ ሰጥቶዋ አማራጭ ትርጉም: "እናንተን ለይቷል" ወይም "ኃጢአት እንዳታድርጉ ለማድረግ እናንተን ከነቀፋ ውጪ ለማድረግ" (UDB) አጠቃላይ መንፈሳችሁን፣ ነፍሳችሁን እና አካላችሁን እነዚህ በንጽጽር የቀረቡት “መንፈስ፣ ነፍስ እና ሥጋ” የሚሉት ቃላት በመሠረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው የቀረቡበት ምክንያትም አጽኖት ለመስጠት ነው። ያለ ነቀፋ ፈጽመው ይጠበቁ። "ኃጢአት ከማደረግ ተቆጠቡ" የጠራችሁ እርሱ የታመነ ነው አማራጭ ትርጉም: "የጠራችሁ እርሱ የታመነ ነው" እርሱ ደግሞ ያደርገዋል "እርሱ ይረዳቿኋል"

1 Thessalonians 5:25

1ኛ ተሰሎንቄ 5: 25-28
ኖት የለውም ::

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: 2 Thessalonians

2 Thessalonians

ምዕራፍ 1

1 ከጳውሎስ፣ ስልዋኖስና ጢሞቴዎስ በእግዚአብሔር በአባታችን በጌታችንም በኢየሱስ ክርስቶስ ላሉ ለተሰሎንቄ ሰዎች ቤተክርስቲያን። **2** ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታችንም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን። **3** ወንድሞች ሆይ፣ ስለ እናንተ ሁልጊዜ ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረብ አለብን፣ ይህ ተገቢ ነውና፣ ምክንያቱም እምነታችሁ እጅግ እያደገ ነውና፣ የእያንዳንዳችሁ ፍቅርም ለሌሎች የሚተርፍ ሆኗል። **4** በመሆኑም በስደቶቻችሁና በመከራዎቻችሁ ሁሉ ስለ መጽናታችሁ ስለ ትዕግስታችሁና እምነታችሁ እኛ ራሳችን በእግዚአብሔር አብያተክርስቲያናት መካከል በልበ ሙሉነት እንመሰክራለን። **5** እናንተ ደግሞ መከራን ለምትቀበሉለት ለእግዚአብሔር መንግሥት ብቁ ሆናችሁ ትቆጠሩ ዘንድ ይህ የእግዚአብሔር ፍርድ ጻድቅ የመሆኑ ግልጽ ምልክት ነው። **6** መከራን ለሚያመጡባችሁ መከራን ይመልስላቸው ዘንድ ይህ በእግዚብሔር ፊት ቅን ፍርድ ነው፣ **7** ጌታችን ኢየሱስ ከኀይሉ መላዕክት ጋር ከሰማይ በሚገለጥበት ጊዜ ከእኛ ጋር መከራን ለተቀበላችሁት ደግሞ እረፍትን ይሰጣችኋል። **8** እግዚአብሔርን የማያውቁትንና ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የማይታዘዙትን ግን በሚነድ እሳት ይበቀላቸዋል። **9** ከጌታ ሀልዎትና ከኀይሉ ክብር ርቀው በዘላለም ጥፋት እየተቀጡ ይሰቃያሉ፣ **10** እርሱ በቅዱሳኑ ሊከበር በሚመጣበት በዚያን ቀን፣ ምስክርነታችንን አምናችኋልና በሚያምኑት ሁሉ ይገረምባቸዋል። **11** በዚህ ምክንያት እኛ ደግሞ አምላካችን ለጥሪአችሁ የተገባችሁ አድርጎ ይቆጥራችሁና መልካሙን ምኞታችሁንና ማናቸውንም የእምነት ሥራ በኀይል ይፈጽምላችሁ ዘንድ ባለማቋረጥ እንጸልይላችኋለን። **12** ይህም በአምላካችንና በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ምክንያት የጌታችን የኢየሱስ ስም በእናንተ እንዲከበርና እናንተም በእርሱ ትከብሩ ዘንድ ነው።

---

2 Thessalonians 1:1

2ኛ ተሰሎንቄ 1: 1-2
ስልዋኖስ "ስልዋኖስ " በላቲን ሲላስ ማለት ነው። " ይህ ሰው በሐዋሪያትሰ ሥራ መጽሐፍ ላይ ከጳውሎስ ጋር ጉዞ ያደረገው ሰው ነው። እናነተ በዚህ ቁጥር ላይ “እናንተ” የሚለው ቃለ በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ያሉ አማኞችን የሚያሳይ

2 Thessalonians 1:3

2ኛ ተሰሎንቄ 1:3-5
ግድ አለብን፤ ግድ አለብን “አለብን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን፣ ስልዋኖስንና ጢሞቲዮስን እንጂ የተሰሎንቄ አማኞችን አይደለም። ሁልጊዜ እግዚአብሔርን ልናመሰግን እግዚአብሔርን በተደጋጋሚ እናመሰግናለን ማለት ነው።
ስለእናነተ እዚህ ላይ “ስለእናንተ” የሚያመላክተው በተሰሎንቄ የሚገኙ አማኞችን ነው።

ወንድሞች ሆይ “ወንድሞች” ማለት ሌሎች አማኞችን ማለት ነው። እንደሚገባ ተገቢን ነገር ማድረግ በተገቢው ሁኔታ ማድረግ ወይም መልካምን ነገር ማድረግ ማለት ነው። እኛ ራሳችንን በዚህ ስፍራ “ራሳችንን” የሚለው ቃል ጳውሎስ ያለውን መመካት የሚያመለክት ነው። እርስ በርሳችሁ "ከሌሎች አማኞች ጋር ማለት ነው።" በስደታችሁና በመከራችሁ በመሰረቱ እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሳሳይ ናቸው። እነዚህ ሁለት ቃላት ጳውሎስ አጣምሮ የተጠቀመበት ምክንያት የሚያልፉበት መከራ ምን ያዕል የጸና እንደነበር ለማሳት ነው። ለእግዚአብሔር መንግሥት የምትበቁ ሆናችሁ ትቈጠሩ ዘንድ፥ አት AT: "በእግዚአብሔር መንግስት ዋጋ እንዳለው ተደርጋችሁ ትታሰቡ ዘንድ “(ተመልከት:

2 Thessalonians 1:6

2ኛ ተሰሎንቄ 1:6-8
በእግዚአብሔር ፊት በእርግጥ ጽድቅ ነውና "እግዚአብሔር ልክ ነው" ወይም "እግዚአብሔር ጻድቅ ነው " ዕረፍትን አት : "እግዚአብሔር እረፍትን ይመልስላችኃል።"

ከሥልጣኑ መላእክት "የእግዚአብሔር ኃያላን መልዕክተኞች "
በእሳት ነበልባል ሲገለጥ ይበቀላል "ጌታኢየሱስ በእሳት ነበልባል ይቀጣቸዋል " ወይም "በእሳት ነበልባል እረሱ ይቀጣቸዋል።" (UDB)

2 Thessalonians 1:9

2ኛ ተሰሎንቄ 1:9-10
ይቀጣሉ "ለወንጌል ያልታዘዙ ሰዎች ይቀጣሉ " በዚያም ቀን ሲመጣ "ኢየሱስ በጌታ ቀን ሲመጣ” በቅዱሳኑ ሊከብር፥ አትAT: "አማኞች ያከብሩታል " በሚያምኑት ሁሉ ዘንድ ሊገረም to be marveled at by all those who believed አትAT: "የሚያምኑት ሁሉ ይደነቃሉ” ወይም "በእርሱ የሚያምኑት ሁሉ በመገረም አብረውት ይቆማሉ።” /ተመልከት: አምናችኋልና በዚህ ቃል ውስጥ “እናንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የተሰሎንቄ አማኞችን ነው። (ተመልከት:

ስለ እንናነተ ሁል ጊዜ እንጸልያለን "ስለእናንተ ባለማቋረጥ እንጸልያለን” የሚጸልዩት ጳውሎስን፣ ስልዋኖስንና ጢሞቲዮስ ናቸው።

እናንተ “እናንተ” የሚለው ቃል በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ያሉ አማኞችን ያመለክታል። ለመጥራቱ እግዚአብሔር ሰዎች ልጆቹ፤ አገልጋዮቹና በኢየሱስ በኩል የተገለጠውን የድኅነት ወንጌል አብሳሪዎች እንዲሆኑ መምረጡ ወይም መሾሙን የሚያመለክት ነው። የበጎነትንም ፈቃድ ሁሉ "በምትፈልጉበት መንገድ ሁሉ በጎ ማድረግ እንድትችሉ” (UDB) የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ስም በእናንተ ዘንድ ሊከብር አትAT: "የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ስምን እንድታከብሩ" እናንተም በእርሱ ዘንድ ልትከብሩ፥ አት AT: "ኢየሱስ እንዲያከብራችሁ " እንደ አምላካችን ጸጋ፥ "በአምላካችን ጸጋ ምክንያት"

2 Thessalonians 1:11

1ኛ ተሰሎንቄ 1:11-12
ኖት የለውም።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 2

1 ወንድሞች ሆይ፣ አሁን የምንለምናችሁ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣትና ወደ እርሱ ስለመሰብሰባችን ነው፣ 2 ከእኛ የሆነ በሚመስል በመንፈስ፣ በቃል ወይም በደብዳቤ እነሆ የጌታ ቀን ሆኗል ብላችሁ በማመን በቀላሉ በአዕምሮአችሁ እንዳትናወጡ ወይም እንዳትደነግጡ እንለምናችኋለን። 3 በየትኛውም መንገድ ማንም አያስታችሁ። የመጨረሻው ክህደት ሳይመጣና የአመጽ ሰው እርሱም የጥፋት ልጅ ሳይገለጥ ያ ቀን አይመጣምና። 4 የሚቃወመውና አምላክ ከተባለው ወይም ከሚመለከው ሁሉ በላይ ራሱን ከፍ የሚያደርገው እርሱ ነው፣ በእግዚአብሔር ቤተመቅደስ እስኪቀመጥም ድረስ ራሱን እንደ አምላክ ያስተዋውቃል። 5 ከእናንተ ጋር በነበርኩበት ጊዜ ስለእነዚህ ነገሮች እንደነገርኳችሁ ትዝ አይላችሁምን? 6 በትክክለኛው ጊዜ ብቻ ይገለጥ ዘንድ አሁን የሚከለክለው ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ። 7 የአመጽ ምስጢር በሥራ ላይ ነው፣ ከመንገድ እስኪወገድ ድረስ አሁን የሚከለክለው አንድ ብቻ አለ። 8 ከዚያም ጌታ ኢየሱስ በአፉ እስትንፋስ የሚገድለውና በመምጣቱ መገለጥ የሚያጠፋው የአመጽ ሰው ይገለጣል። 9 የአመጽ ሰው አመጣጥ እንደ ሰይጣን አሰራር በኀይል ሁሉ፣ በምልክቶችና በሐሰተኛ ድንቆች፣ 10 ይድኑ ዘንድ የእውነትን ፍቅር ስላልተቀበሉ ለሚጠፉት በአመጽ ማታለል ሁሉ ነው። 11 በዚህ ምክንያት ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል፣ 12 ይኸውም እነዚያ እውነትን ያላመኑ ነገር ግን በአመጻ የተደሰቱ ሁሉ ይፈረድባቸው ዘንድ ነው። 13 ነገር ግን ስለ እናንተ በጌታ ስለተወደዳችሁት ወንድሞች ለእግዚአብሔር ሁልጊዜ ምስጋና ልናቀርብ ይገባናል፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ መቀደስና እውነትን በማመን ለድነት እንደ በኩራት መርጧችኋልና፣ 14 የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር እንድትካፈሉ በወንጌላችን ጠራችሁ። 15 እንግዲያውስ ወንድሞች ሆይ፣ ጸንታችሁ ቁሙ፣ በቃልም ሆነ ወይም በደብዳቤአችን የተማራችኋቸውን ልማዶች አጥብቃችሁ ያዙ። 16 አሁን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱና የወደደን፣ የዘላለምን መጽናናትና በጸጋው ተስፋ የምናደርግበትን መልካሙን መታመን የሰጠን እግዚአብሔር አባታችን፣ 17 በቃልና በመልካም ሥራ ሁሉ ልባችሁን ያጽናኑት፣ ያበርቷችሁም።

---

2 Thessalonians 2:1

2ኛ ተሰሎንቄ 2፡ 1-2
ነገር ግን፥ ጳውሎስ ይህን ቃል የተጠቀመው የጀመረውን ርዕሰ ጉዳን ለመቀየር ነው። እንለምናችኋለን በዚህ ቃል ውስጥ “እኛ” የሚለው የሚያመለክተው፤ ጳውሎስን፣ ስልዋኖስንና ጢሞቲዮስን ነው።አትAT: " እማጸናችኋለው" እናንተ “እናንተ” የሚለው ቃል በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ያሉ አማኞችን ያመለክታል። ወንድሞች ሆይ “ወንድሞች” ማለት ሌሎች አማኞችን ማለት ነው። . ከአእምሮአችሁ ቶሎ እንዳትናወጡ እንዳትደነግጡም AT: "እንዚህ ነገሮች በቀላሉ እንዳያውኳችሁ" በመንፈስ ወይም በቃል ወይም በመልእክት። "ከእኛ ዘንድ በወጣ ደብዳቤ ወይም በተነገረ ቃል" ከእኛ እንደሚመጣ ሌላ ሰው እንዳደርገው እንደተናገረኝ እንደማለት ነው። የጌታ ቀን ይህ ቀን ማለት በእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ላይ ያመጹና መሲሁን ባልተቀበሉ ላይ የመጨረሻው ፍርድ የሚሰጥበት ቀን ማለት ነው።

2 Thessalonians 2:3

2ኛ ተሰሎንቄ 2፡ 3-4
አያስታችሁ፤ “እናንተ” የሚለው ቃል በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ያሉ አማኞችን ያመለክታል። አይደርስምና "የጌታ ቀን አይመጣምና” የዓመፅ ሰው አትAT: " እና እግዚአብሔር የዓመጽ ሰውን ሳይገልጥ " የጥፋት ልጅ "የሚችለውን ነገር ሁሉ የሚያጠፋ” ወይም “አጥፊ” አምላክ ከተባለው ሁሉ፥ ሰዎችም ከሚያመልኩት ሁሉ አ/ት: "ሰዎች ነው እንደ አምላክ የሚያውቁትና የሚያመልከትን ነገር ሁሉ”(UDB) (ተመልከትSee:

2 Thessalonians 2:5

2ኛ ተሰሎንቄ 2፡ 5-7
ትዝ አይላችሁምን “እናንተ” የሚለው ቃል በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ያሉ አማኞችን ያመለክታል። አት : "እንደምታሳውሱ እርግጠኛ ነኝ።" ይህን እንዳልኋችሁ ከኢየሱስ ተመልሶ መምጣት ጋር፤ ከጌታ ቀን ጋር፤ እንዲሁም ከዓመጽ ሰው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ነገሮች የሚያመለክት ነው። በገዛ ራሱ ጊዜም ይገለጥ ዘንድ፥ አትAT: " እግዚአብሔር የዓመጽን ሰው ጊዜው ሲደርስ ይገልጠዋል።" የዓመፅ ምሥጢር በእግዚአብሔር ብቻ ለገለጥ የሚችልን የተሰወረን የእምነት ምስጢር ያመለክታል።

2 Thessalonians 2:8

2ኛ ተሰሎንቄ 2፡ 8-10
ዓመፀኛ ይገለጣል፤ አትAT: "እግዚአብሔ አመጸኛውን ይገልጠዋል" ወይም "እግዚአብሔ ሐሰተኛውን ክርስቶስን ይገልጠዋል" በአፉ መንፈስ የሚያጠፋው፥ "በሚናገረው ቃል ኃይል " ሲመጣም በመገለጡ የሚሽረው ኢየሱስ ተመልሶ በመምጣቱ የዓመጽን ሰው ያጠፋዋል። የእርሱ መምጣት እንደ ሰይጣን አሠራር ነው። እርሱ የተባለው የዓመጽ ሰው ሲሆን ሲመጣ ሰይጣን የዓመጽን ሰው ስልጣን እንዲኖረው፣ ምልክቶችንና ሐሰተኛ ድንቆች ማድረግ እንዲችል ያደርገዋል።

2 Thessalonians 2:11

2ኛ ተሰሎንቄ 2፡ 11-12
ስለዚህም ምክንያት፥ "ሰዎች እውነትን ባለመቅደዳቸው ምክንያት” ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል "እግዚአብሔር የዓመፅን ሰው እንዲያሳስታቸው ላከው ፍርድን እንዲቀበሉ፥ አትAT: "እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል።”
በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመፅ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ those who did not believe the truth but took pleasure in unrighteousness "እውነቱን ባለማመናቸው ምክንያት ዓመፁ ደስ አሰኛቸው።"

2 Thessalonians 2:13

2ኛ ተሰሎንቄ 2፡ 13-15
ነገር ግን፥ግን ጳውሎስ ይህን ቃል የተጠቀመው የጀመረውን ርዕሰ ጉዳን ለመቀየር ነው።

እግዚአብሔርን ልናመሰግን ግድ አለብን፥ " በተደጋጋሚ ልናመሰግን ይገባል " እኛ በዚህ ቃል ውስጥ “እኛ” የሚለው የሚያመለክተው፤ ጳውሎስን፣ ስልዋኖስንና ጢሞቲዮስን ነው። እናንተ “እናንተ” የሚለው ቃል በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ያሉ አማኞችን ያመለክታል። በጌታ የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ፥ AT: "for the Lord loves you, brothers" ወንድሞች ሆይ “ወንድሞች” ማለት ሌሎች አማኞችን ማለት ነው። ለመዳን እንደ በኩራት መርጦአችኋልና፤ "ከመጀመሪያዎቹ አማኞች መካከል እንድትሆኑ " (UDB) በመንፈስ መቀደስ "እግዚአብሔ የሚያድነንና የሚቀድሰን በመንፈሱ አማካኝነት ነው" (UDB)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እውነትንም በማመን "በእውነት መታመን" ወይም "በአውነት መተማመን " ወግ ያዙ ወግ ወይም ተውፊት የሚያመለክተው ጳውሎስ እና ሌሎች ሐዋሪያት ስለኢየሱስ ክርስቶስ ትክክለኛውን አውነት ያስተማሩትን ነው። አማራጭ ትርጉም: "አውነታውን አስታውሱ" የተማራችሁትንyou were taught አት AT: "ያስተማርናችሁን" (UDB) በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልእክታችን whether by word or by our letter "በአካል ከእናንተ ጋር ሆነን እንደነገርናችሁ ወይም በደብዳቤያችን እንደጻፍንላችኁ ቃል "

2 Thessalonians 2:16

2ኛ ተሰሎንቄ **2**፡ **16**-**17**
ግን ጳውሎስ ይህን ቃል የተጠቀመው የጀመረውን ርዕሰ ጉዳን ለመቀየር ነው። የወደደን.. የሰጠን የወደደን እና የሰጠን የሚለው ቃል አማኞችን ሁሉ የሚያመለክት ነው”. ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና በዚህ ስፍራ “ራሱ” የሚለው ቃል “ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሚለው ተጨማሪ መግለጫ ነው። " ልባችሁን ያጽናኑት “እናንተ” የሚለው ቃል በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ያሉ አማኞችን ያመለክታል።. "ያጽናናችሁ እና ያበርታችሁ”

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 3

1 በቀረውስ ወንድሞች ሆይ፣ በእናንተ ዘንድ ደግሞ እንደሚሆነው የጌታ ቃል በፍጥነት እንዲዳረስና እንዲከበር ስለ እኛ ጸልዩ፣ 2 ሁሉ እምነት ያላቸው
አይደሉምና ከአመጸኞችና ከክፉዎች ሰዎች እንድንድን ጸልዩልን። 3 ነገር ግን የሚያጸናችሁና ከክፉው የሚጠብቃችሁ ጌታ የታመነ ነው። 4 ያዘዝናችሁን ነገሮች
እንደጠበቃችሁና ወደፊትም እንደምትጠብቁ ስለ እናንተ በጌታ ታምነናል። 5 ጌታ ልባችሁን ወደ እግዚአብሔር ፍቅርና ወደ ክርስቶስ ጽናት ይምራው። 6
ወንድሞች ሆይ፣ ከእኛ እንደተቀበላችሁት ልማድ ሳይሆን ሥራ በመፍታት ከሚኖር ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዛችኋለን። 7
እንዴት ምሳሌነታችንን መከተል እንደሚኖርባችሁ እናንተው ታውቃላችሁ። በመካከላችሁ በስንፍና አልተመላለስንም፣ 8 ወይም ገንዘብ ሳንከፍል የማንንም
ምግብ አልበላንም። ከዚያ ይልቅ ከእናንተ በማንም ላይ ሸክም ላለመሆን በድካምና በጥረት ሌሊትና ቀን ሠራን። 9 ይህንን ያደረግነው እኛን ትመስሉ ዘንድ
ምሳሌ ልንሆንላችሁ ብለን እንጂ ሥልጣን ስላልነበረን አይደለም። 10 ከእናንተ ጋር በነበርንበት ጊዜ “ሊሠራ የማይወድ ማንም ቢኖር እርሱ መብላት የለበትም”
ብለን አዝዘናችሁ ነበር። 11 በመካከላችሁ ሥራ ፈት ሆነው የሚመላለሱ አንዳንዶች መኖራቸውን ሰምተናልና፤ ሥራ አይሠሩም ነገር ግን በሰው ጉዳይ ጣልቃ
ይገባሉ። 12 እንደነዚህ ያሉትን በጸጥታ እንዲሠሩና የራሳቸውን ምግብ እንዲበሉ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እናዛቸዋለን እንመክራቸዋለንም። 13 እናንተ ግን
ወንድሞች ሆይ፣ ትክክል የሆነውን ከማድረግ አትታክቱ። 14 በዚህ ደብዳቤ ውስጥ ያለውን ቃላችንን የማይታዘዝ ማንም ቢኖር ይህንን ሰው ልብ በሉት፣ ያፍርም
ዘንድ ከእርሱ ጋር ኅብረት አታድርጉ። 15 እንደ ወንድም ገስጹት እንጂ እንደ ጠላት አትቁጠሩት። 16 የሰላም ጌታ ራሱ ሁልጊዜ በሁሉ መንገድ ሰላምን
ይስጣችሁ። ጌታ ከሁላችሁም ጋር ይሁን። 17 እኔ ጳውሎስ፣ ሰላምታዬ እንዲህ ነው፣ በራሴ እጅ በምጽፋቸው ደብዳቤዎች ሁሉ ላይ ምልክቴ ይህ ነው። 18
የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን።

---

2 Thessalonians 3:1

2ኛ ተሰሎንቄ 3፡ 1-3
በቀረውስ ጳውሎስ ይህን ቃል የተጠቀመው የጀመረውን ርዕሰ ጉዳን ለመቀየር ነው። ወንድሞች ሆይ “ወንድሞች” ማለት ሌሎች አማኞችን ማለት ነው። ስለ እኛ ጸልዩ በዚህ ቃል ውስጥ “እኛ” የሚለው የሚያመለክተው፤ ጳውሎስን፣ ስልዋኖስንና ጢሞቲዮስን ነው እንጂ የተሰሎንቄ አማኞችን አያመላክትም። የጌታ ቃል እንዲሮጥ "እጅግ በጣም ብዙ ሰዎች ስለጌታ ኢየሱን የሚነገረውን የምስራች መልዕክት እንዲሰሙ" እንዲከበር "ስለጌታ ኢየሱን የሚነገረውን የምስራች መልዕክትን ሰዎች እንዲያከብሩት”

በእናንተም ዘንድ ደግሞ እንደሚሆን... የሚያጸናችሁ “እናንተ” የሚለው ቃል በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ያሉ አማኞችን ያመለክታል።. እንድንድን "እግዚአብሔር እንዲያድነን” ወይም “ እግዚአብሔር እንዲታደገን “ እምነትም ለሁሉ ስለማይሆን "ብዙ ሰዎች አማኞች አይደሉም" የሚያጸናችሁ "የሚያበረታችሁ " የሚያጸናችሁ "ያጠነክራችሁ"

2 Thessalonians 3:4

2ኛ ተሰሎንቄ 3፡ 4-5
ታምነናል በዚህ ቃል ውስጥ “እኛ” የሚለው የሚያመለክተው፤ ጳውሎስን፣ ስልዋኖስንና ጢሞቲዮስን ነው እንጂ የተሰሎንቄ አማኞችን አያመላክትም። በጌታ "ከጌታ ጋር ተባብረን " (UDB) ስለ "እንደ" እናንተ “እናንተ” የሚለው ቃል በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ያሉ አማኞችን ያመለክታል።. ልባችንን ያቅናው "አቅጣጫ ያሳያችሁ “ይምራችሁ”

2 Thessalonians 3:6

2ኛ ተሰሎንቄ 3፡ 6-9
በቀረውስ ጳውሎስ ይህን ቃል የተጠቀመው የጀመረውን ርዕሰ ጉዳን ለመቀየር ነው። . በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ። ጳውሎስ በጌታ ስም ማዘዙ ጌታ እንዲያደርግ የፈለገውን ነገር ማድረጉን ያመላክታል . እናዛችኋለን በዚህ ቃል ውስጥ “እኛ” የሚለው የሚያመለክተው፤ ጳውሎስን፣ ስልዋኖስንና ጢሞቲዮስን ነው እንጂ የተሰሎንቄ አማኞችን አያመላክትም። እናዛችኋለን “እናንተ” የሚለው ቃል በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ያሉ አማኞችን ያመለክታል። ወንድሞች ሆይ “ወንድሞች” ማለት ሌሎች አማኞችን ማለት ነው። ጌታችን `የኛ” የሚለው ቃል አማኞችን ሁሉ የሚያመለክት ነው”.. ያለ ሥርዓት ከሚሄድ "ሰነፍ እና ለመስራት ፈቃደኛ ያልሆነ " (UDB) እኛን ልትመስሉ "እኛ እንደምናደርገው የምታደርጉ " በድካምና በጥረት እየሠራን ድካም አስቸጋሪ ስራን በብዙ ልፋት መስራትን የሚያመላክት ሲሆን ጥረት ባልተመቻቸ ሁኔታ ውስጥ የሚሰራን ስራ AT: "በብዙ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ስራን ሰርተናል" ሌሊትና ቀን "በሌሊትን በቀን ግዜ” ሁል ግዜ ያለ ሥልጣን ስለ ሆንን አይደለም "በእርግጥ ስልጣን አለን። "

2 Thessalonians 3:10

2ኛ ተሰሎንቄ 3፡ 10-12
ጋር ሳለን በዚህ ቃል ውስጥ “እኛ” የሚለው የሚያመለክተው፤ ጳውሎስን፣ ስልዋኖስንና ጢሞቲዮስን ነው እንጂ የተሰሎንቄ አማኞችን አያመላክትም።) ከእናንተ “እናንተ” የሚለው ቃል በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ያሉ አማኞችን ያመለክታል።. ሊሠራ የማይወድ "መስራት የማይፈልግ ወይም “አንዳንድ ሰነፍ ሰዎች” በጸጥታ እየሠሩ "በእርጋት፤ ሰላማዊ በሆነ ሁኔታ፤ ሁከት በሌለበት መንገድ”

2 Thessalonians 3:13

2ኛ ተሰሎንቄ 3፡ 13-15
ግን፥ ጳውሎስ በትጉህ ሰራተኛ አማኞችና በሰንፍ ወይም ሊሰሩ በማይወዱ አማኞች መካከል ንጽጽር ለማድረግ የተጠቀመበት ቃል ነው። . እናንተ፣ ወንድሞች ሆይ፥ “እናንተ” የሚለው ቃል በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ያሉ አማኞችን ያመለክታል።. አትታክቱ። "ተስፋ አትቁረጡ ወይም “የጀመራችሁትን ነገር አታቁሙ”" or "do not stop" ከእርሱ ጋር አትተባበሩ።take note of him "በአደባባይ ለዩት፤ በግልጽ ተለዩት"

2 Thessalonians 3:16

2ኛ ተሰሎንቄ 3፡ 16-18
ኖት የለውም።

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: 1 Timothy

1 Timothy

ምዕራፍ 1

1 መታመኛችን በሆነው በክርስቶስ ኢየሱስ እና በአዳኛችን በእግዚአብሔር ትእዛዝ የክርስቶስ ኢየሱስ ሐዋርያ ጳውሎስ፣ 2 በእምነት እውነታኛ ልጁ ለሆነው፣
ለጢሞቴዎስ። ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታችንም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣ ምሕረትና ሰላም ለአንተ ይሁን። 3 ወደ መቄዶንያን በሄደኩ ጊዜ አንዳንድ ሰዎች
ልዩ ትምህርትን እናዳያስተምሩ፣ 4 በእምነት የሆነውን የእግዚአብሔርን እቅድ ለማያግዙ ለታሪኮችና መጨረሻ የሌላቸውን የትውልዶችን ሐረግ ለመቁጠር
ትኩረት ወደ መስጠት እንዳያዘነብሉ ታስጠነቅቃቸው ዘንድ በኤፌሶን እንድትቀመጥ አዘዝኩህ። 5 ነገር ግን የትእዛዙ ግብ ከንጹህ ልብ፣ ከመልካም ኅሊና እና
ከእውነተኛ እምነት የሚወጣ ፍቅር ነ|ው። 6 አንዳንድ ሰዎች ከእነዚህ ነገሮች ርቀው ወደ ባዶ ወሬ ዞረዋል። 7 የሕግ አስተማሪዎች ለመሆን ተመኝተዋል፤ ነገር
ግን የሚናገሩትንና መሆን አለበት የሚሉትን ነገር አያውቁትም። 8 ሆኖም ሕግ በትክክል ቢጠቀምበት መልካም እንደሆነ እናወቃለን። 9 እንዲሁም ሕግ ለጻድቅ
ሰው እንዳልተሠራ እናውቃለን፤ ነገር ግን ሕግ የተሰጠው፣ ሕገወጥ ለሆኑና ለአመጸኞች ሰዎች ፣ እግዚአብሔርን ለማይፈሩና ለኃጢአተኞች ፣ 10 ለአመንዝሮችና
ለግብረ ሰዶማውያን፣ ሰዎችን ባርያ አድርገው ለሚሸጡ፣ ለውሸተኞች፣ ለሐሰት ምስክሮች፣ ከእውነተኛው ትምህርት ርቀው ለሚገኙ ሰዎች ነው። 11 ይህ
እውነተኛ ትምህርት በተባረከው አምላካችን ለእኔ በአደራ የተሰጠው ወንጌል ነው። 12 ለዚህ አገልገሎት ታማኝ እንድሆን ያበቃኝንና የሾመኝን፣ ጌታችንን ኢየሱስ
ክርስቶስን አመሰግናለሁ። 13 ምንም እንኳ አስቀድሞ ተሳዳቢና አሳዳጅ ብሆንም፣ ባለማወቅና ባለማመን ስላደረግሁት ከጌታ ዘንድ ምሕረትን አግኝቼአለሁ።
14 ነገር ግን የጌታችንም ጸጋ በክርስቶስ ኢየሱስ ከእምነትና ከፍቅር ጋር ይበልጥ በዛ። 15 ‹‹ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም መጣ›› የሚለው መልዕክት ሁሉም ሊቀበሉት የተገባና አስተማማኝ ነው። እኔም ከእነዚህ ሁሉ የባስኩ ኃጢአተኛ ነኝ። 16 በዚህም ምክንያት ከኃጢአተኞች ዋነኛ
በምሆን በእኔ ክርስቶስ ኢየሱስ ትእግስቱን ሁሉ ሊያሳይ ምሕረትን አገኘሁ፤ ይህም የሆነው በእርሱ ለሚያምኑና የዘላለም ሕይወት ለሚያገኙ ምሳሌ እሆን ዘንድ
ነው። 17 ስለዚህ ለዘላለም ንጉሥ ፣ ለማይሞተው እና ለማይታየው፣ ብቻውን አምላክ ለሆነው፣ ክብርና ግርማ ለዘላለም ይሁን። አሜን። 18 ልጄ ጢሞቴዎስ
ሆይ፣ ስለ አንተ አስቀድሞ በተነገረው ትንቢት ተስማምቼ ይህን አዝሃለሁ፤ መልካሙን የእምነት ገድል ተጋደል፤ 19 ስለዚህም እምነትና መልካም ኅሊና ይኑርህ።
አንዳንድ ሰዎች እነዚህን ክደው መርከብ አለመሪ እንደሚጠፋ በእምነት ነገር ጠፍተዋል። 20 ከእነዚህም መካከል በእግዚአብሔር ላይ የስድብን ቃል
እንዳይናገሩ፣ ለሰይጣን አሳልፌ የሰጠኋቸው፣ ሄሜኔዎስ እና እስክንድሮስ ይገኙባቸዋል።

---

1 Timothy 1:1

1ኛ ጢሞቴዎስ **1**: **1-2**
ጳውሎስ "ከጳውሎስ" ወይም "እኔ ጳውሎስ1" በትዕዛዙ መሠረት "አንዳዘዘው ትዕዛዝ" ወይም "በልጣኑ መሠረት" እኛ . . . እኛ . . . እኛ በዚህ ሥፍራ ላይ ጳውሎስ ስለ ራሱ፣ ስለ ጢሞቴዎስ እና ምናልባት ሌሎች ሰዎችን ጨምሮ እየተናገረ ይሆናል። መድኀኒታችን እግዚአብሔር "ያዳነን እግዚአብሔር" ተስፋችን የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ "ተስፋችን የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ" ወይም "የሚንተማመንበት ኢየሱስ ክርስቶስ" ለጢሞቴዎስ "ይህ ደብዳቤ የተጻፈው ለጢሞቴዎስ ነው" እውነተኛ ልጅ ይህ ሀረግ በጳውሎስ እና በጢሞቴዎስ መካከል ያለውን ግንኙነት በአባት እና በልጅ መካከል ካለው ግንኙነት ጋር ያነጻጽራል። ጢሞቴዎስ የጳውሎስ እውነተኛ የጳውሎስ ልጅ ልጁ ባይሆንም ጢሞቴዎስ ለአባቱ የሚሰጠውን ተመሳሳይ አክብሮትን፣ ትዕዛዝን እና አገልግሎትን ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም: "እርሱ እንደ እውነተኛ ልጅ ነው" ጸጋ፣ ምሕረት እና ሠላም ከ . . . "ከ . . . ጸጋ፣ ምሕረት እና ሰላም በእናነተ ዘንድ ይሁን" ወይም "መልካምነት፣ ምሕረት እና ሠላም ከ . . . ይሁንላችሁ" እግዚአብሔር አባት "አባታችን የሆነው እግዚአብሔር" ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ጌታችን የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ"

1 Timothy 1:3

1ኛ ጢሞቴዎስ **1**: **3-4**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ጢሞቴዎስ ሕግን በተሳሳተ መንገድ መጠቀመን እነንዲቃወም እና ከእግዚአብሔር መልካም ትምህርት እንዲጠቀም ያበረታታዋል። እኔ አንተን እንደለመንኩህ "እንተ እንደለመንኩህ" ወይም "በስልጣን እንደተየኩህ" ወይም "እንደነገርኩህ" አንተ ነጠላ ቁጥር በኤፌሶን ቆየህ "በኤፌሶን ከተማ ውስጥ ቆየኸኝ" መጨረሻም ወደሌለው ወደ ትውልዶች ታሪክ እንዳያደምጡ "ወይም ከፍተኛ ትኩረት እንዳይሰጡ" ወይም "እንዳያደምጡ ልታዛቸው" ትውልዶች ታሪክ የትውልድ ሀረግ በአፍ የሚነገር ወይም የተጻፈ ወላጆች እና ዘሮች ዝርዝር ነው። ይህ በአይዳዊያን ባሕል ውስጥ በጣም ወሳኝ የሆነ ነገር ነው። ይህ አንድ ሰው በእስራኤል ሕዝብ ውስጥ በዬትኛው ነገድ ውስጥ እንደሆኑ ለማወቅ የሚረዳ በመሆኑ በአይሁድ ባሕል ውስጥ በጣም አስፈላጊ የሆነ ነገር ነው። ማቴዎስ 1 እና ሉቃስ 3 በጣም ጥሩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎች ናቸው። ክርክርን የሚያመጡ "ሰዎች በንዴት ተሞልተው እንዳይስማሙ የሚያደረግ" ሰዎች በእርግጠኝነት ማንም ልያውቃቸው የማይችለውን የተለያዩ ታሪኮችን እና ትውልዶችን ማዕከለ አድርገው ይከራከራሉ። የእዚአብሔርን ዕቅድ ከመርዳት ይልቅ "የእግዚአብሔርን ዕቅድ እንዲስፋፋ ከማድረግ ይልቅ" ወይም "ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣውን ነገር በእግባቡ ከማስተዳደር ይልቅ" በእምነት "በእመነት በመቀበል" ወይም "በእምነት የተሠራውን ነገር"

1 Timothy 1:5

1ኛ ጢሞቴዎስ **1**: **5-8**
የትዕዛዘቱ ግብ "የመመሪያው ግብ" ወይም "እኛ ሐዋርያት እንዲታደርጉት የነገርናችሁ ነገር" ትዕዛዝ ስርዓት። በዚህ ሥፍራ ላይ ይህ ቃል ያለው ትርጉም ብሉይ ኪዳን ወይም ዐሥርቱ ትዕዛዛትን አይደሉም ይልቁንም በ1:3 ላይ ፓውሎስ የሰጠውን ትዕዛዝ የሚያመለክት ነው። ፍቅር አማራጭ ትርጉም 1) የእግዚአብሔር ፍቅር (UDB) ወይም 2) ከባልንጀራ ያለህ ፍቅር። ከንጹሕ ፍቅር የተነሣ "ኃጢአት ላለማድረግ ካለ መሻት" መልካም ሕልና "ትክክለኛ ወይም የተሳሳተ ምርጫ የሚያደረግ ሕልና" በእውነት "ታማኝ" ወይም "እውነት" ወይም "ያለምንም ትምክት።" ሕግ በዚህ ሥፍራ ላይ ይህ ቃል የሚያመለክተው የሙሴን ሕግ ነው። ይሁን እንጂ አልተረዱትም "ምንም አንኳ ባይረዱትም" ወይም "ያልተረዱት ቢሆንም እንኳ" አስረግጠው የሚናገሩት ነገር "በጠንካራ ቃላት የሚናገሩት" ወይም "በእርግጠኝነት የሚናገሩት ነገር" ይሁን እንጂ "አሁን" ሕግ መልካም እንደሆነ እናውቃለን ሕግ ጠቃም እንደሆነ እንረዳለን" ወይም "ሕግ የሚጠቅም ነገር መሆኑን እንገነዘባለን" አንድ ሰው በሕግ ጥቅም ላይ ካዋለው "ምንም በአግባቢ የሚጠቀመው ከሆነ" ወይም "ለተቀመጠለት ዓላማ ማንም የሚጠቀመው ከሆነ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

1 Timothy 1:9

1ኛ ጢሞቴዎስ 1: 9-11
እናም ይህንን እናውቃለን "ይህንን እንረዳለን" ወይም "ይህንን ስለምንገነዘብ" ወይም "ይህንንም ስለምናውቅ" ለጻድቃን አልተሠራም "ለጻድቅ ሰው አልተሰጠም" ወይም "ለሚታዘዙት ሰዎች አልተሰጠም" ወይም "በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ለሆነ ሰው አልተሰጠም" እናቶቻቸውን እና አባቶቻቸውን ለገደሉት ሰዎች "አባቶቻቸውን እና እናቶቻቸውን ለገደሉ ሰዎች" ወይም "አባታቶቻቸው እና እናቶቻቸው ላይ አካላዊ ጉዳት ያደረሱ ሰዎች ግብረሰጋዊ ግንኙነት ግብረገብ የጊደላቸው ሰዎች ይህ በተባአት ጾታ የተገለጸ በሴቶች የሚካሄድ የሴተኛ አደርነትን የሚያሳይ ነው። በሌለ ሥፍራ ለእግዚአብሔር ታማኝ ያልሆኑ ሰዎችን ለመወከል በምሳሌነት ጥቅም ላይ ውሎ እናገኛለን ነገር ግን በዚህ ክፍል ውስጥ ያለው ትርጉም ከጋብቻ ውጪ ማንም ከሌላ ሰው ጋር ግብረስጋ ግንኙነት የፈጸመን ይወክላል። ከወንድ ጋርም ለሚተኙ፥ "ከሌላ ወንድ ጋር የሚተኙ ወንዶች።" ባሪያ አድራጊዎች "ሰዎችን እየሠረቁ ባሪያ አድርገው የሚሸጡ" ወይም "ሰዎችን ባሪያ አድርገው የሚሸጡ ሰዎች" የተባረከው የእግዚአብሔር ብሩክ ወንጌል "የተባረከው የእግዚአብሔር የሆነው ስለ ክብር የሆነው ወንጌል" ወይም "ስለ ክብር የሆነው ወንጌል እና የተባረከው አምላክ" ለእኔ አደራ እንደ ተሰጠኝ "እግዚአብሔር የሰጠኝ እና ተጠያቂ ያደረገኝ"

1 Timothy 1:12

1ኛ ጢሞቴዎስ 1: 12-14
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ባለፉት ጊዜያት እንዴት እንደሠራ በመናገር ጢሞቴዎስ ለእግዚአብሔር ታማኝ ይሆን ዘንድ ያበረታታዋል። እኔ አመሰግናለሁ "አመሰግናለሁ" ወይም "እኔ አመሰግናለሁ" ተማኝ አድርጎ ቆጥሮኛልና "ታማኝ አድርጎ ቆጥሮኝ" ወይም "ታማን እንደሆንኩ ቆጥሮ" በአገለግሎቱ ላይ ሾመኝ "እንዳገለግል ሾመኝ" ወይም "በአገልግሎት ላይ ሾመኝ" እኔን ከዚህ በፊት አሳዳጅ የነበርኩትን "በክርስቶስ ላይ ክፉ ክፉ ነገሮችን የተናገርኩትን ሰው" ወይም "እኔን ባለፉት ዘመናት ተሳዳቢ የነበርኩትን ሰው" አደገኛ ሰው "ሌሎች ሰዎችን የሚጎዳ ሰው።" ይህ ሌሎች ሰዎን የመጉዳት መብት አለኝ ብሎ የሚያምን ሰው ነው። ነገር ግን ሳላውቅ ባለማመን ስላደረግሁት ምህረትን አገኘሁ፥ አማራጭ ትርጉም: "በኢየሱስ የማላምን በመሆኔ ምክንያት እና የማደርገውን ነገር የማላውቅ በመሆነ ከኢየሱስ ዘንድ ምሕረትን አገኘሁ።" ምሕረትን አገኘሁ አማራጭ ትርጉም: "ኢየሱስ ምሕረት አሳየኝ" ወይም "ኢየሱስ ማረኝ" ነገር ግን ጸጋ "እና ጸጋ" ከእምነትና ከፍቅር ጋር አብልጦ በዛ። "በጣም በዛ" ወይም "ከበቂ በላይ ሆነ"

1 Timothy 1:15

1ኛ ጢሞቴዎስ 1: 15-17
ይህ መልእክት የታመነ ነው "ይህ ዓረፍተ ነገር እውነት ነው" ሁሉም ሰው ሊቀበለው የተገባ ነው "ያለምንም ጥርጥር መቀበል ይቻላል" ወይም "በሙሉ መተማመን ልቀበሉት የተገባ ነው" በመጀመሪያ ምሕረት ተሰጠኝ "በመጀመሪ እግዚአብሔር ምሕረቱን አሳየኝ" ወይም "በመጀመሪያ ከእግዚብሔር ዘንድ ምሕረትን አገኘሁ" ለዘመናት ንጉሥ የሆነ "ዘላለማዊ ንጉሥ" ወይም 'ለዘላለም ዋና ገዥ የሆነ" ክብር እና ምስጋና "እርሱ ልመሰገን እና ልከበር ይገባዋል" ወይም "ሰዎች ያክብሩት እነንዲሁም ምስጋነናን ያቅርቡለት"

1 Timothy 1:18

1ኛ ጢሞቴወስ 1: 18-20
በእናንተ ፊት ይህንን ትዕዛዝ አስምጫለሁ "ይህ እኔ የሰጠኋችሁ ትዕዛዝ" ወይም "ይህ ለእናንተ የሰጠሁት ትዕዛዝ" ልጅ ይህ “ወንድ ልጅ” ወይም “ሴት ልጅ” ከሚለው ቃል ይበልጥ ጠቅለል ያለ ሀሳብን በውስጡ ያዘለ ቃል ነው። ይሁን እንጂ በዚህኛውም መልኩ ከአባት ጋር ያለን ዝምድና የሚያሳይ ነው። ጳውሎስ ይህንን ለጢሞቴዎስ ያለውን ፍቅር ለማሳየት በምሳሌነት ተጥቅሞበታል። መልካም ጦርነት ተዋጋ "የአንተን ጥረት በሚጠይቅ ዋጋ ያለው ጦርነት ውስጥ ተሳትፎ አድርግ" ወይም "ጠላቶችህን ለማሸነፍ ጠንክረህ ሥራ።" ይህ ምሳሌያዊ ንግግር ያለው ትርጉም “ለጌታ ጠንክረህ ሥራ” (UDB)።

መርከብ አለ መሪ እንደሚጠፋ፥ በእምነት ነገር ጠፍተዋልና፤

ጳውሎስ የእመነት ሁኔታን ከድንጋይ ጋር እንደሚትላተም መረከብ በመመሠል ጽፏል። የዚህ ምሳሌያዊ ንግግር ትርጉሙ “በእምነታቸው ላይ የሆነ ነገር በጣም መጥፎ ነው” (UDB)። በእናንተ ቋንቋ ግልጽ ከሆነ ተመሳሳይ ምሳሌን መጠቀም ትችላለህ። መማር ይችላሉ "እግዚአብሔር ሊያስተምራቸው ይችላል"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 2

1 ስለዚህ ከሁሉ በፊት፣ ጸሎት፣ ምልጃና ምሥጋና ስለ ሰዎቸ ሁሉ እንዲደረግ እመክራለሁ፤ እግዚአብሔርን በመፍራትና በማክበር፣ 2 በጸጥታ ሕይወት ሰላማዊ ኑሮ እንድንኖር፣ ለነገሥታትና በሥልጣን ላይ ላሉ ሁሉ ጸልዩ። 3 ይህም በአዳኛችን በእግዚአብሔር ፊት መልካምና ተቀባይነት ያለው ነገር ነው። 4 እርሱ ሰዎች ሁሉ እንዲድኑና እውነትን ሁሉ ወደ ማውቅ እንዲደርሱ ይፈልጋልና። 5 አንድ እግዚአብሔር አለና፣ እንዲሁም በሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል፣ ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ አንድ መካከለኛ አለ፤ 6 እርሱም ለሁሉ ራሱን ቤዛ አድርጎ የሰጠ፣ በትክክለኛው ጊዜ የተገለጠ ምስክር ነው። 7 ለዚህም ዓላማ እኔ ራሴ፣ አወጅ ነጋሪና ሐዋርያ ሆኜአለሁ። እውነትን እናገራለሁ አልዋሸም፤ እኔ ለአሕዛብ የእምነትና የእውነት አስተማሪ ነኝ። 8 ስለዚህ፣ ወንዶች ሁሉ በየሥፍራው ያለ ጥርጥርና ያለ ቁጣ የተቀደሱ እጆቻቸውን እያነሱ እንዲጸልዩ እፈልጋለሁ። 9 እንደዚሁም፣ ሴቶች አግባብ ያለው አለባበስ ይኑራቸው፣ ራሳቸውን በመግዛት ረጋ እንዲሉ እንጂ ጸጉራቸውን በወርቅ ወይም በዕንቁ በመሥራት ወይም ውድ የሆኑ ልብሶችን በመልበስ ሊያጌጡ አይገባም። 10 ነገር ግን እግዚአብሔርን ለሚፈሩ ሴቶች አግባብ እንደሆነው፣ በመልካም ሥራ ተውበው ይታዩ። 11 ሴት በጸጥታና በመታዘዝ ትማር። 12 ሴት በጸጥታ እንድትኖር እንጂ፣ እንድታስተምርና በወንድ ላይ ሥልጣን እንዲኖራት አልፈቅድም። 13 አስቀድሞ አዳም ተፈጥሮአልና፣ ከዚያም ሔዋን። 14 አዳም አልተታለለም፣ ነገር ግን ሴቲቱ ሙሉ ለሙሉ በመተላለፍ ተታልላለች። 15 ሆኖም፣ በእምነትና በፍቅር፣ በቅድስናም በመልካም አዕምሮ ጸንታ ብትኖር፣ ልጆችን በመውለድ ትድናለች።

---

1 Timothy 2:1

1ኛ ጢሞቴዎስ **2**፡ **1**-**4**
አያየዥ ዓረፍተ ነገር: ጢሞቴዎስ ለሰዎች ሁሉ ይጸልይ ዘንድ ያበረታታዋል። በመጀመሪያ ደረጃ "ከሁሉ በበለጠ" ወይም "ከምንም ነገር በፊት" እለምንሃለሁ "እለምንሃለሁ" ወይም "እጠይቅሃለሁ" አክብሮት ሰዎች እኛን የሚያከብሩበት መንገድ። ይህ ቃል “መለኮትን ከመምሰል” ጋር ተያይዞ ሲመጣ ሰዎች እግዚአብሔርን የሚያከብሩበት እና የሚያመሰግኑበት መንገድ ነው።

1 Timothy 2:5

1ኛ ጢሞቴዎስ **2**፡ **5**-**7**
በእግዚአብሔር እና በሰው መካከል አንድ መካከለኛ አለ መካከለኛ በሁለት ባልተስማሙ አካላት መካከል የሠላም ድርድር እንዲኖር የሚያደርግ ነው። በዚህ ሥፍራ ላይ ይህ ኃጢአተኞች ከእግዚአብሔር ጋር ሠላም እንዲሆኑ ያግዛል። ራሱን ሰጠ "በፈቃደኝነት ሞተ" ቤዛነት "የነጻነት ዋጋ" ወይም "ነጻነትን ለማግኘት የሚከፍል ዋጋ" ምስክርነት በትክክለኛ ጊዜ "በትክክለኛ ሠዓት የእርሱ ምስክርነት" ወይም "በዚህ ሰዓት የምስክርነት ጊዜ" ለዚህ ዓላማ ሲባል "ለዚህ ሲባል" ወይም "በዚህ ምክንያት ሲባል" ወይም "ለዚህ ምስክርነት ሲባል አዋጅ ነጋሪ ሆንኩ "ሰባኪ ሆኜ ተሾምኩ" ወይም "ሰባኪ ለመሆን በክርስቶስ ተሾምኩ" እውነትን መናገር "እውነትን እናገራለሁ" ወይም "እኔ እውነትን እናገራለሁ" አልዋሸም "እኔ አልዋሸም" በእምነት እና በእውነት "ስለ እምነት እና እውነት" ወይም "ከእምነት እና እውነት ጋር"

1 Timothy 2:8

1ኛ ጢሞቴዎስ **2**፡ **8**-**10**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ስለ ሴቶች ልዩ የሆነ መመሪያዎችን ሰጥቷል። በሁሉም ሥፍራ ያሌ ሰዎች "በሁሉም ሥፍራ ያሉ ወንዶች" ወይም "በሁሉም ቦታ ያሉ ወንዶች" ማንሣት "መዘርጋት" ቅዱሳን እጆች "ለእግዚአብሔር የተለዩ እጆች።" ይህ ምሳሌያዊ ንግግር ኃጢአትን ያስወገደ ሰውን ያመለክታል። ከቁጣ እና ከመጠራጠር ውጪ "ቁጣን ከመግለጽ ውጪ እና ከሌሎች ጋር ከመጣላት ውጪ" ወይም "በሌሎች ላይ ከመቆጣት እና እግዚአብሔር ከመጠራጠር ውጪ" በትህትና "ለእነርሱ የተሳሳተ ትኩረት የሚሰጥ ምልክት በማያሳይ መልኩ" ወይም "ለሰዎች እና ለእግዚአብሔር ተገቢ ክብር በሚያሳይ መልኩ" በሽሩባ ሳይሆን "ጸጉራቸው ለማስዋብ ከፍተኛ ጥረት ከማድረግ ይልቅ።” working overly hard to make their hair look good." ሽሩባ መሠረት ሴት ልጅ ለጸጉሯ ትኩረት መስጠቷ የሚታይበት አንዱ መንገድ ብቻ ነው። በመልካም ሥራችን መልካምነቱን መግለጥ "መልካም ነገሮችን በማድረግ የእግዚአብሔር መሆናቸውን ማሳየት"

1 Timothy 2:11

1ኛ ጢሞቴዎስ **2**፡ **11**-**12**
አንድት ሴት ይህንን ልትማር ይገባታል "ሴት ልጅ ይህንን ትማር" ወይም "ሴት ልጅ ይህንን መማር ይኖርባታል" በዝምታ "በጸጥታ" ወይም "ጸጥ ባለ ባሕርይ" በነገር ሁሉ እየተገዛች "እግዚአብሔር ያዘዘውን ነገር ሁሉ ለመታዘዝ ዝግጁ እየሆነች" አንድት ሴት ይህንን እንድታደረግ አልፈቅደም "ሴት ልጅ ይህንን እንድታደረግ አልፈቅደም"

1 Timothy 2:13

1ኛ ጢሞቴዎስ **2**፡ **13**-**15**
በመጀመሪያ የተፈጠረው አዳም ነውቲ "እግዚአብሔር በመጀመሪያ የፈጠረው አዳምን ነው" ወይም "በእግዚአበብሔር በመጀመሪያ የተፈጠረው አዳም ነው" ከዚያ ሔዋን "ከዚያ ሔዋን ተፈጠረች" እንዲሁም የታለለው አዳም አልነበረም "በእባቡ የተታለለው አዳም አልነበረም" በመተላለፍ ፈጽመው ተሳሳቱ "ፈጽሞ በመተለሏ ምክንያት የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ተላለፉ።" የዚህ ንዑስ ዓረፍተ ነገር ዋና ነጥብ የእግዚአብሔር ሕግ የተላለፈችው ሔዋን እንጂ አዳም አይደለም። ልጅ በመውለድ ትድናለች "በተለመደው የሕይወት መንገድ ውስጥ እግዚአብሔር ደንነቷን ይጠብቃል። በዚህ መንገድ የቀጠለ እንደሆነ "በዚያው ከጸኑ" ወይም "በዚያ መንገድ መኖሩ ከቀጠሉ" በእምነትና በፍቅር በቅድስና "በኢየሱስ በማመን እና እርስ በእርስ በመዋደድ እና የቅድስና ሕይወትን በመኖር" ራሳቸውን እየገዙ "ራስን በመግዛት" ወይም "መልካም የሆነውን ነገር በማወቅ"

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 3

1 አንድ ሰው መሪነትን ቢፈልግ፣ መልካምን ሥራ ተመኝቶአል፣ የሚለው አባባል የታመነ ነው። 2 ስለዚህ መሪው ነቀፋ የሌለበት፣ የአንዲት ሚስት ባል፣ በመጠን
የሚኖር፣ አስተዋይ፣ ሥርዓት ያለው፣ እንግዳ ተቀባይ፣ ለማስተማር የሚበቃ፣ 3 የማይሰክር፣ የማይጨቃጨቅ፣ ነገር ግን፣ ለሌሎች የሚጠነቀቅ፣ ሰላማዊ፣
ገንዘብን የማያፈቅር መሆን አለበት። 4 ቤቱን በመልካም የሚያስተዳድርና ልጆቹም በሁሉም ረገድ የሚታዘዙለት ለሆን ይገባል፤ 5 ሰው የራሱን ቤት በመልካም
ማስተዳደር የማያውቅ ከሆነ ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን እንዴት ሊጠነቀቅ ይችላል? 6 ዲያብሎስ በትእቢት እንደወደቀ እንዳይወድቅ አዲስ አማኝ የቤተ
ክርስቲያን መሪ አይሁን፤ 7 በውጭ ባሉት ዘንድ መልካም ምስክርነት ያለው ሊሆን ይገባል፣ በመሆኑም በነቀፋ እና በዲያብሎስ ወጥመድ አይወድቅም። 8
ዲያቆናትም እንዲሁ፣ የተከበሩ፣ ቃላቸው አንድ የሆነ፣ ብዙ የወይን ጠጅ የማይጠጡ፣ የማይስገበገቡ መሆን አለባቸው። 9 በንጹህ ኅሊና የተገለጠውን የእምነት
እውነት ሊጠብቁ ይገባቸዋል። 10 አስቀድመው ይገምገሙ፣ ከዚያም ያለነቀፋ ሆነው ከተገኙ በዲቁና አገልግሎት ይሾሙ። 11 እንዲሁም ሴቶች የተከበሩ፣
የማያሙ፣ ልከኞችና በሁሉ ነገር የታመኑ ሊሆኑ ይገባቸዋል። 12 ዲያቆናት እያንዳንዳቸው የአንዲት ሚስት ባል መሆን አለባቸው፤ ቤታቸውንና ልጆቻቸውንም
በመልካም የሚያስተዳሩ ሊሆኑ ይገባል። 13 መልካም አገልግሎት የሚያበረክቱ እነርሱ በክርስቶስ ኢየሱስ ባላቸው እምነት ለራሳቸውእውነተኛ መሠረትና
ድፍረትን ያገኛሉ። 14 እነዚህን ነገሮች ስጽፍልህ ወደ አንተ በቅርቡ እንደምመጣ ተስፋ በማድረግ ነው። 15 ነገር ግን ብዘገይ፣ በእግዚአብሔር ቤት፣ ማለትም
የእውነት ዓምድና መሠረት በሆነው፣ በሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን እንዴት መኖር እንደሚገባህ ታውቅ ዘንድ እጽፍልሃለሁ። 16 እኛ ሁላችን በዚህ
እንስማማለን፦ ‹‹የተገለጠው እግዚአብሔርን የመምሰል ምስጢር ታላቅ ነው፣›› ይህም በሥጋ የተገለጠው፣ በመንፈስ የጸደቀው፣ በመላእክት የታየው፣
በሕዝቦች መካከል የታወጀው፣ በዓለም የታመነው፣ በክብር ወደ ሰማይ ያረገ ነው።

---

1 Timothy 3:1

1ኛ ጢሞቴዎስ 3፡ 1-3
አያያዥ ዓረፍ ነገር: ኤጲስ ቆጶስ ቤተ ክርስቲያን እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው እና እንዴት ነገሮችን ማከናወን እንዳለባት ጳውሎስ ልዩ የሆነ መመሪያ ይሰጣል። መልካም ሥራ "የተከበረ ሥራ" የአንድት ምስት ባል የኤጲስ ቆጶስ አንድ ምስት ብቻ ልኖረው ይገባል። ይህ ከዚህ ምስቶቻቸው የሞቱባቸው ወይም አግብተው የፈቱ ወይም ፈጽመው አግብተው የማያውቁ ሰዎችን ያካተት ወይም አያካትት የሚታወቅ ነገር የለም። ልከኛ "በልኩ ነገሮችን የሚያከናውን ሰው" ተቀባይነት ያለው ሰው "ጠበብ ያለውን ነገር የሚያስብ" ወይም "ጥሩ ፍርድ የሚያደርግ ሰው" ወይም "አመክኒዮዊ" ወይም "አመክኒዮ" ሥርዓት ያለው "ጥሩ ባሕርይ ያለው" እንግዳ ተቀባይ "መጻተኞች የሚቀበል" የመጠጥ ሱስ ያሌለበት "ሰካራም ያልሆነ" ወይም "ብዙ ወይን የማይጠጣ ሰው" የማይጨቃጨቅ "መደባደብ እና መከራከር የማይወድ ሰው" ገንዘብ የማይወድ የማይሰርቅ ወይም በቀጥተኛ መንገድ ወይም በማጭበርበር ወይም በትክክለኛ መንገድ ሠርቶ ገንዘብ የሚያገኝ ሰው ነገር ግን ለሰዎች ግድ የማይለው ሰው።

1 Timothy 3:4

1ኛ ጢሞቴዎስ 3፡ 4-5
ቤቱን በተገቢው መንገድ ማስተዳደር የሚችል እና ልጆቹም ተገቢውን ክብር የሚሰጧው ሰዎች። አማራጭ ትርጉሞች 1) ኤጲስ ቆጶስ ልጆቹ የሚታዘዙለት ሊሆን ይገባል እንዲሁም ሌሎች ሰዎችን የሚያከብሩ ልሆኖኑ ያገባል (UDB) ወይም 2) ኤጲስ ቆጶስ በአክብሮት የሚያስተዳድር ልሆን ይገባዋል። የራሱን ቤት የሚያስተዳድር "ቤተሰቡን የሚንከባከብ" ወይም "በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ ያሉ ሰዎችን በአግባቡ መምራት የሚችል" ከአክብሮት ሁሉ ጋር በዚህ ሥፍራ ላይ “ሁሉ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው “ሁሉንም ሰዎችን” ወይም “በሁሉም ጊዜ” ወይም “በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ”። አንድ ሰው እንዴት ነገሮችን ማከናወን እንዳለበት የማያውቅ ከሆነ "ምክንያቱም አንድ ሰው እንዴት ማከናውን እንዳለበት የማያውቅ ከሆነ" ወይም "አንድ ሰው ካልቻለ" ወይም "ነገር ግን አንድ ሰው የማችል መሆኑን ከታሰበ" እንዴት ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን መጠበቅ ይችላል አማራጭ ትርጉም: "የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዴት መጠበቅ ይችላል" ወይም "የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን መምራት አይችልም"

1 Timothy 3:6

1ኛ ጢሞቴዎስ 3፡ 6-7
አዲስ አማኝ ይሁን "አዲስ አማኝ ሊሆን አይገባም" ወይም "አማኝ ከሆነ ብዙ ጊዜ ያልሆነ ሰው መሆን የለበትም" ወይም "የበሰለ አማኝ ልሆን ይባዋል" በትዕቢት ተነፍቶ በዲያብሎስ ፍርድ እንዳይወድቅ፥ "እንደ ዳቢሎስ በትዕቢት ተሞልቶ እና እንደ ዳቢሎስ እንዳይፈረድበት" በውጪ ባሉት ዘንድ በጥሩ ምግባሩ የሚታወቅ ሊሆን ይገባዋል "በኢየሱስ የማያምኑ ሰዎች በጎነቱን የሚመሰክሩለት ሰው" ወይም "ከኢየሱስ የማያምኑ ሰዎች በጎነቱን የሚናገሩለት ሰው" (UDB) ከጸጋ እንዳይወድቅ "በራሱ ላይ ውርደትን እንዳያመጣ" ወይም "በእርሱ ላይ እንከን የሚፈልጉ ሰዎች ምንም ምክንያት ማግኘት እንዳይችሉ" እንዳይወድቅ ...በዳብሎሽ ወጥመድ ተጠልፎ "ዳብሎስ ጠልፎ እንዲጥላቸው እንዳይፈቅድላቸው።" ሴጣን ወጥመድን አዘጋጅቷል ወይም መጥመድ ሴጣን አማኞችን ሳያውቁ ኃጢአት እንዲያደርጉ የማታለያ መንገዱን ለማሳየት ምሳሌያዊ ንግግር ነው።

1 Timothy 3:8

1ኛ ጢሞቴዎስ 3፡ 8-10
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: የቤተ ክርስቲያን ዲያቆናት እና ምስቶቻቸው ምን ማድረግ እንዳለባቸው ጳውሎስ ልዩ የሆነ መመሪያዎቹን መስጠቱን ቀጠሏል። በተመሳሳይ መልኩም ዲያቆናት "ልክ እንደ ኤጵስ ቆጶሳት ሁሉ ዲያቆናትም" የተከበሩ ሊሆኑ ይገባል "በሰዎች ዘንድ የተከበሩ ሊሆኑ ይገባል" ሁለት አፍ ያላቸው መሆን የለባቸውም ሁለት አፍ የመሚናገሩ - "አንድ ነገር እየተናገሩ በሌላ በኩል ደግሞ ሌላ የሚሉ" ወይም "ለአንዱ ሰው አንድ ነገር ሌላ ሰው ደግሞ ሌላ የሚናገሩ"

ብዙ ወይን ጠጅ የማጠጡ "ወይን የመጠጣት ሱስ ያሌለባቸው" ወይም "ብዙ የወይን ጠጅ የማይጠጡ" ስስታሞች ያልሆኑ "ታማኝነትን በማጉደል ትርፍን የማይፈልጉ" የተገለጠውን የእምነት እውነት ልጠብቁ ይገባል "እግዚአብሔርን ለእኛ የገለጠውን እና እኛም የምናምነውም እውነተኛውን መልዕክት በማመን የሚቀጥሉ ሊሆን ይገባል።" ይህ ለተወሰነ ጊዜ ያለ እውነት ሲሆን ይህንን እውነት እግዚእሔት ለእርሱ አሳይቶዋቸዋል። በንጹሕ ሕልና "ስህተት አለማድረጋቸው በሚያውቅ ሕልና" ይህንን ማድረግ አለባቸው ...በመጀመሪያ የተፈቀደላቸው "ለአገልግሎቱ ብቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ መገምገም ይኖርባቸዋል" ወይም "በመጀመሪያ ብቁ መሆኑን ማሳየት ነው።" ያለነቀፋ ያልሆነ "ሰዎች ምንም ስህተት የማያገኙባው በመሆናቸው ምክንያት" ወይ "ያለነቀፋ በመሆናቸው ምክንት" ወይም "ምንም ስህተት ባለመስራታቸው ምክንያት"

1 Timothy 3:11

1ኛ ጢሞቴዎስ 3:11-13
ሴቶችም በተመሳሳይ መልኩ በዚህ ሥፍራ ላይ “ሴቶች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው አጠቃላይ ሴቶችን ቢሆንም በተለይ ግን የዲያቆናት ምስተፐች ወይም ሴት ዲያቆናትን የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም: "በተመሳሳይ መልኩም ምስቶችም መሥፈረት አላቸው" ወይም "ሴት ዲያቆናትም እንደ ወንድ ዲያቆናት መሥረት አላቸው።" ትክክለኛ ባሕርይ "በትክክል መፈጸም" የማይሳደቡ "ስለ ሌሎች ሰዎች ክፉ የሆነ ነገር የማይናገሩ" ልከኞች "ከመጠን በላይ የሆነ ነገርን የማደርጉ" የአንድ ምስት ባል የአንድ ምስ ባል። ይህ ምስት የሞተባቸውን፣ የተፋቱ ወይም ፈጽሞ ያለገቡ ወንዶችን ያመልክት አያመልክት ምንም የሚታወቅ ነገር የለም። ልጆቻቸውን እና ቤታቸውን በአግባቡ ማስተዳደር የሚችል "ልጆቻቸውን እና በቤታቸው ውስጥ ያሉትን ሌሎች ሰዎችን መንካከብ እና መመራት የሚችሉ።" እንዲህ ያሉ ሰዎች "እንዲህ ያሉ ሰዎች" ወይም "ኤዴስ ቆጶሶች፣ ዲያቆናት እና ሴት ዲቆናት” ወይም "የቤተ ክርስቲያን መሪ የሆኑ ሰዎች" ለራሳቸው የያገኛሉ "ለራሳቸው ይቀበላሉ" ወይም "ለራሳቸው ያተርፋሉ"

1 Timothy 3:14

1ኛ ጢሞቴዎስ 3: 14-15
እነዚህን ነገሮች ጽፌልሃለሁ "እነዚህም መመሪያዎችን ጽፌልሃለሁ" ወደ እናንት በቶሎ እመጣ ዘንድ ተስፋ አደርጋለሁ "ምንም እንኳ ወደ እናንተ በቶሎ እንድመጣ ተስፋ ባደርግም" ነገር ግን ከዘገየሁ "ይሁን እንጂ በቶሎ መምጣት ካልቻልኩኝ" ወይም "ይሁን እንጂ ወደ እናንተ ዘንድ በቶሎ እንዳልመጣ የተከለከልኩ እንደሆነ" . . . ዘንድ እጽፍልሃለሁ። "ለዚህ ዓላማ እጽፍልሃለሁ።" የእግዚአብሔር ቤት...በዚህ ልመራ ይገባዋል "የእግዚአብሔርን ቤተሰብ በዚህ መሠረት ልትመራው ይገባል" በእውነት ዓምድና መሠረት ይህ ምሳሌያዊ ንግግር እግዚአብሔር እውነቱን የገለጸበት ትልቅ፣ ጠንከራ መሠረትን ያሳያል። ይህ መሠረት የተለያዩ ክፍሎች፣ መሠረት እና ዓምድ አለው።

1 Timothy 3:16

1ኛ ጢሞቴዎስ 3: 16-16
በሥጋ "እንደ እውነተኛ የሰው ልጅ" እግዚአብሔርን የመምሰል ምስጥር ያለጥርጥር ታልቅ ነው "ስለ እምነታችን እግዚአብሔር የገለጠልን እውነት ትልቅ ነው" በመንፈስ የጸደቀ "ኢየሱስ ስለ ራሱ ማንነት የተናገረውን ነገር መንፈስ ቅዱስ አረጋግጧል" በአሕዛብ ሁሉ ዘንድ የተሰበከ "በተለያዩ ሀገራት ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ለሌሎች ሰዎች ስለ ኢየሱስ ተናግረዋል" በዓለም ሁሉ የታመነ "በዓለማችን የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች በኢየሱስ አምነዋል"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 4

1 አሁን ግን መንፈስ በመጨረሻ ዘመን አንዳንድ ሰዎች የራሳቸውን ኅሊና በውሸት በተሞላ ግብዝነት በማደንዘዝ፤ 2 ለሚያስቱ መናፍስትና ለአጋንንት ትምህርት
ትኩረት በመስጠት እምነትን ይክዳሉ በማለት በግልፅ ይናገራል። 3 እውነትን ለማወቅ የመጡትን አማኞች ከምሥጋና ጋር ከሚቀበሉትና እርስበርሳቸው
ከሚካፈሉት እግዚአብሔር ከፈጠረው ምግብ እንዲርቁ፣ ጋብቻንም እንዳያደርጉ ይከለክላሉ። 4 በእግዚአብሔር የተፈጠረው ሁሉ መልካም ነውና፤ በምሥጋና
የሚቀበሉት እንጂ የሚጣል የለውም። 5 በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት የተቀደሰ ነው። 6 እነዚህን ነገሮች ለወንድሞች ብታስረዳ፣ በእምነት ቃሎች እና
በተከተልከውም መልካም ትምህርት የምትመገብ የኢየሱስ ክርስቶስ መልካም አገልጋይ ትሆናለህ። 7 ራስህን እግዚአብሔርን ለመምሰል አሰልጥን እንጂ፣
አሮጊቶች የሚወዱአቸውን አለማዊ ተረቶችን አትቀበል። 8 የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ለጥቂት ነገር ይጠቅማል፣ ነገር ግን እግዚአብሔርን መምሰል ለአሁኑና
ለሚመጣውም ሕይወት ተስፋ ስላለው ለሁሉ ነገር ይጠቅማል። 9 ይህ መልእክት የታመነና ሁሉም ሊቀበሉት የተገባው ነው። 10 ለዚህም እንታገላለን
ጠንክረንም እንሠራለን፣ ይህም የሚሆነው ሰዎችን ሁሉ በተለይም የሚያምኑትን በሚያድን በሕያው እግዚአብሔር ስለምንታመን ነው። 11 እነዚህን ነገሮች
አውጅ አስተምርም። 12 ማንም ወጣትነትህን አይናቀው፣ ነገር ግን በዚህ ፈንታ፣ በቃልና በሥራ፣ በፍቅር፣ በእምነትና በንጽሕና የእምነት ምሳሌ ሁን። 13
እስክመጣ ድረስ፣ ማንበብህን፣ መምከርህን እና ማስተማርህን ቀጥል። 14 በትንቢት ከሽማግሌዎች የእጅ መጫን ጋር ለአንተ የተሰጠህን የጸጋ ስጦታ ቸል
አትበል። 15 ለእነዚህ ነገሮች ተጠንቀቅ፣ በእነርሱም ጽና፣ ይህን በማድረግህ ማደግህ በሁሉም ዘንድ ይገለጻል። 16 ለራስህ እና ለትምህርቱ ተጠንቀቅ፣
በእነዚህም ጽና ይህን ብታደርግ ራስህንም የሚሰሙህንም ታድናለህ።

---

1 Timothy 4:1

1ኛ ጢሞቴዎስ **4**፡ **1**-**2**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ መንፈስ እንደሚሆን የነገረውን ነገር እያስታወቀው ምን ምን ነገሮችን ማስተማር እንዳለበት በመናገር ያበረታታዋል። በኋላኛው ዘመን አማራጭ ትርጉሞች 1) ከጳውሎስ ዘመን በኋላ፣ "ለወደፊት" ወይም "በቀጣዩ ዘመን" ወይም 2) በጳውሎስ ዘመን "ከመጨረሻው በፊት ባለው ጊዜ ውስጥ" እምነት መተው "በኢየሱስ ማመን መተው" ወይም "አስቀድመው ከሚያምኑት ነገር መራቅ" እና ትኩረት መስጠት "እና ትኩረት መስጠት" ወይም "ትኩረት በመስጠታቸው ምክንያት" ወይም "ስያደምጡ ሳለ" አሳሳች መንፈስ እና የዳቢሎስ ትምህርቶች "ሰዎችን የሚያሳሰስት ትምህርት እና ዳቢሎስ የሚያስተምረው ትምህርት" በግብዝነት ውሸት "በግብዞች አማካኝነት በሚነገር ውሸት" በገዛ ሕሊናቸው እንደሚቃጠሉ ደንዝዘው፥ ይህ ምሳሌያዊ ንግግር የሚያሳየው አንድ ጌታ በባሪያዎቹ ወይም እንስሳቶቹ ቆዳ ላይ የእርሱ ባለቤትነት የሚያሳይ ምልክት በጋለ ብረት የሚየስቀምጥበት መንገድ ነው። አማራጭ ትርጉሞች 1) ማቃጠል የመለያ ምልክት ነው፣ "ግብዞች እንደሆኑ እያወቁ እንኳ ይህንን ያደርጋሉ፣" ወይም 2) ሕልናቸው ደንዝዟ፣ "ሕልናቸው እንድደነዝዝ በጋለ ብረት የተሰጠበሰ ይመስል።"

1 Timothy 4:3

1ኛ ጢሞቴዎስ **4**፡ **3**-**5**
ይህንን ያደርጋሉ "እነዚህ ሰዎች ይህንን ያደርጋሉ" መጋባትን ይከለክላሉ "አማኞች እንዳገቡ ይከለክላሉ" ወይም "አማኞች እንዳያገቡ ይከለክላሉ" ይከለክላሉ . . . ምግብ መቀበልን "ሰዎች ከምግብ ይርቁ ዘንድ ግድ ይላሉ" ወይም "ሰዎች ምግብ እንዳይበሉ ግድ ይላሉ" ወይም "ሰዎች የተወሰነ ዓይነት ምግብ እንዳይበሉ ይከለክላሉ።" በዚህ ሥፍራ ላይ "ሰዎች" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ምናልባት አማኞችን ነው (UDB)። እውነት ለማወቅ የሚመጡ አማኞች "እውነት የሚያውቁ አማኞች" ወይም "እውነትን ያወቁ አማኞች" ከምስጋና ጋር ይቀበሉ ዘንድ እግዚአብሔር ከፈጠረው መብል እንዲርቁ ያዝዛሉ። "እግዚአብሔርን ያመሰገንበትን ነገር አውጥተን አንጥልም" ወይም "በማመስገን የሚንበላው ማንኛውም ነገር የተመሰገነ ነው" በእግዚአብሔር ቃል እና ጸሎት ለእግዚአብሔር የተሰጠ ነው አማራጭ ትርጉም: "ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ እና ወደ እርሱ በመጸለይ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ነው" ወይም "በተገለጠው የእግዚአብሔር እውነት ጋር የሚስማማ ከሆነ በጸሎት ለእግዚአብሔር የተሰጠ ይሆናል።

1 Timothy 4:6

1ኛ ጢሞቴዎስ **4**፡ **6**-**8**
ይህንን ነገር በ. . . ፊት አኑሩት "ይህንን ሀሳብ በአማኞች አእምሮ ውስጥ አስቀምጡት" ወይም "አማኞች እነዚህ ቃላት ያስታውሱ ዘንድ አግዟቸው።" ሁሉም “የማስተማር” ሁደት እና “ቃል” በ 1TI 3:16 እስከ 1TI 4:5. ላይ የተጠቀሰውን ትምህርት የሚያመለክቱ ናቸው። ተገቢውን ምግብ ማግኘት "መሰልጠን" (UDB)። እግዚአብሔር ጢሞቴዎስ ይበልጥ ጠንካራ እንዲሆን አድርጎታል እንዲሁም እግዚአብሔርን የሚያስደስት ነገር እንዲያደርግ አስተምሮታል። የእምነት ቃላት "ሰዎች እንዲያምኑ የሚያደርጉ ቃላት" በአሮጊት ሴቶች የሚወደዱ ተራ ታሪኮች "ተራ የሆነ እና የአሮጊት ሴቶች ተረት ተረተ። በዚህ ሥፍራ ላይ “ታሪኮች” የሚለው ቃል በ [1TI 1:4] እግዚአብሔርን ለመምሰል ግን ራስህን አስለምድ። "ይበልጥ እግዚአብሔርን ለመምሰል ራሳችሁን አስለምዱ" ወይም "እግዚአብሔር በሚያስደስት መልኩ ነገሮችን ለማከናወን ራስህን አስለምድ" ወይም "እግዚአብሔርን መምሰልን ይበልጥ ራስግን አስለምድ" አካላዊ ለምምድ "አካላዊ ልምምድ" ለዚህ ሕይወት የሆነው ተስፋ ያዝ "ለዚህ ሕይወት ጠቃሚ ነው" ወይም "ይህንን ሕይወት የተሻለ ለማድረግ አጋዥ ነው"

1 Timothy 4:9

1ኛ ጢሞቴዎስ **4**፡ **9**-**10**
worth full acceptance "worthy of your complete belief" or "worthy of your full trust" ስለዚህ ምክንያት "ምክንያቱ ይህ ነው" እንታገላለን እንዲሁም ተግተን እንሠራለን በዚህ ሥፍራ ጥቅም ላይ የዋሉት “መታገል” እና “ተግቶ መሥራት” የሚሉት ቃላት በመሠረታዊ ትርጉማቸው ተመሳሳይ ናቸው። እነዚህ ቃላት ጳውሎስ በአንድነት የተጠቀማቸው ምን ያህል ተግተው በመስሥራት ላይ እንዳሉ ለማሳየት ነው። ሕያው በሆነ አምላክ ተስፋ ስለምናደረግ "ተስፋችንን በሕያው እግዚአብሔር ላይ እናደርጋለን" ወይም "ተስፋችንን በሕያው አምላክ ላይ እናደርጋለን" ነገር ግን በተለይም ለአማኞች "በተለይ ደግሞ አማኞች ለሆኑ ሰዎች እርሱ አዳኛቸው ነው"

1 Timothy 4:11

1ኛ ጢሞቴዎስ **4**፡ **11**-**13**
እነዚህ ነገሮች ስበከት እንዲሁም አስተምር "እነዚህን ነገሮች እዘዝ እንዲሁም አስተምር" ወይም "አሁን የነገርኩን ነገሮች እዘዝነ እንዲሁም አስተምር" ወጣት በመሆንን ምክንያት ማንም ሰው እንዳይንቅህ "ወጣት በመሆን ምክንያት ማንም ይህንን ያኸል ጠቃሚ አይደለም ብሎ እንዳያስብህ" ተግተህ አንብብ "ቅዱሳት መጻሕፍትን አንብብ" ወይም "በአደባባይ የእግዚአብሔር

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ቃል ማንበብህን ቀጥልበት" ሌሎችን አበረታታ "ሌሎች ሰዎች አበረታታ" ወይም "ሌሎች ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል በሕይወታቸው ተግባራዊ ያደርጉት ዘንድ አበረታታ"

1 Timothy 4:14

1ኛ ጢሞቴዎስ 4: 14-16
በአንተ ውስጥ ያለውን ስጦታ ቸል አትበለው "እግዚአብሔር የሰጠህን ስጦታ ተጠቀምበት" በትንቢት "የቤተ ክርስቲን መሪዎች የእግዚአብሔር ቃል በመናገር" ሽማግሌዎች እጃቸውን በመጫን ይህ የቤተ ክርስቲን መሪዎች እጆቻቸውን በጢሞቴዎስ ላይ በማድረግ እግዚአብሔር እንድሠራው ያዘዘውን ሥራ ማከናውን ይችል ዘንድ የጸለዩበት ሃይማኖታዊ ሥርዓት ነው። ስለእነዚህ ነገሮች አስብ፣ ኑራቸውም "እነዚህን ነገሮች ሁሉ አድርግ እንዲሁም በእነዚህም መሠረት ኑር" እድገተህ በሰዎች ሁሉ ዘንድ የተገለጠ ይሆን ዘንድ "ሌሎች ሰዎች እድገትህን መመልከት ይችሉ ዘንድ" ወይም "እነዚህ ነገሮች በማድረግ ያሳየኸውን እምርታ ሌሎች ሰዎች መመልከት ይችሉ ዘንድ" ስለራስህ ከፍተኛ ትኩረት ስጥ "በጥንቃቄ ነገሮችን አከናውን" ወይም "ባሕርይህን ተቆጣጠር" በእነዚህ ነገሮች ቀጥል "እነዚህ ነገሮችን ማድረግህን ቀጥልበት" ራስህን እና የሚያደምጡህን ታድናለህ "ራስህን እና የሚያደምጡህን ሰዎች የሐሰት መልዕክት ከመስማት እና የተሳሳተ ተግባር ከማድረግ ታድናለህ።" የሐሰት መልዕክት የሚያምኑ ሰዎች እና የተሳሳተ ተግባር የሚፈጽሙ ሳች በዚህ ምክንያት መከራ ይደርስባቸዋል። ጳውሎስ ጢሞቴዎስ እና የእርሱ ወዳጆች የስህተት ትምህርት በማመን እና የተሳሳተ ነገር በማድረግ መከራ እንዲያገኛቸው አይፈልግም።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 5

1 ሽማግሌ የሆነውን አትገስጸው፣ ነገር ግን እንደ አባት ለምነው፣ ወጣቶችን እንደ ወንድሞች፣ 2 አሮጊቶችን እንደ እናቶች፣ ቆነጃጅቶችን እንደ እኅቶች በሙሉ
ንጽሕና ለምናቸው። 3 በትክክል መበለት የሆኑትን አክብር፤ 4 ነገር ግን ባሏ የሞተባት ልጆችና የልጅ ልጆች ከሏት፣ እነርሱ ራሳቸው በቤታቸው አክብሮትን፣
ለወላጆቻቸው ብድራት መክፈልን ይማሩ፣ ይህ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ነገር ነው። 5 ነገር ግን እውነተኛ መበለት ሁሉን ነገር ትታ በእግዚአብሔር ታምና
ትኖራለች፣ ልመናዋን ሁል ጊዜ በእርሱ ፊት በማቅረብ ሌትና ቀን ትጠባበቃለች። 6 የሆነ ሆኖ፣ መቀማጠልን የምትወድ ሴት በሕይወትም ብትኖር የሞተች ነች።
7 ከወቀሳ የራቁ እንዲሆኑ እነዚህን ነገሮች ስበክ። 8 ነገር ግን ማንም ለዘመዶቹ የሚያስፈልጋቸውን የማይሰጥ፣ ይልቁንም ለገዛ ቤተሰቡ የማያስብ እምነትን
የካደ ከማያምን ሰው ይልቅ የከፋ ነው። 9 ባሏ የሞተባት ሴት በመዝገብ ለመጻፍ እድሜዋ ከስድሳ ማነስ የለበትም፣ የአንድ ባል ሚስትም መሆን አለባት። 10
ልጆቿን በሥርዓት የምታሳድግ፣ እንግዶችን የምትቀበል፣ ወይም የቅዱሳንን እግር በማጠብ፣ የተጨነቁትንም በማጽናናት፣ በመልካም ሥራ ሁሉ የተመሰከረላት
መሆን አለባት። 11 ወጣት መበለቶችን ግን እንደ መበለት አትመዝግባቸው፣ ምክንያቱም የክርስቶስ ተቃራኒ የሆነው ሥጋዊ ፍላጎታቸው ሲያይልባቸው
ለማግባት ይፈልጋሉና። 12 በዚህ ሁኔታ የቀድሞ እምነታቸውን ስለተዉ በደለኞች ናቸው። 13 ለሥራ ፈትነትም ስለሚጋለጡ ከቤት ወደ በት የሚዞሩ ይሆናሉ።
ሥራ ፈቶች መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ሐሜተኞችና በሰው ጉዳይ ጣልቃ እየገቡ የማይገባውን የሚናገሩ ይሆናሉ። 14 ስለዚህ ወጣት ሴቶች እንዲያገቡ እና
ልጆችን እንዲወልዱ ቤታቸውንም በመልካም እንዲያስተዳድሩ፣ ተቃዋሚውም ክፉ እንደምናደርግ የሚከስበትን ምክንያት እንዲያሳጡት እመክራለሁ። 15
አንዳንዶች ሰይጣንን ለመከተል ዞር ብለዋል። 16 መበለቶች ያሏት አንዲት የምታምን ሴት ብትኖር፣ ትርዳቸው፣ ስለሆነም የቤተ ክርስቲያን ሸክም ይቀልላታል
እውነተኞቹን መበለቶች ለመርዳት ትችላለች። 17 በመልካም የሚያስተዳድሩ መሪዎች በተለይም በቃሉ ስብከትና በማስተማር የሚተጉ እጥፍ ክብር
ይገባቸዋል። 18 የእግዚአብሔር ቃል ‹‹የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰር›› እንዲሁም ‹‹ለሠራተኛ ደመወዙ ይገባዋል›› ይላል። 19 ሁለት ወይም ሦስት
ምስክሮች ሳታገኝ በሽማግሌ ላይ ክስ አትቀበል። 20 ሁሉም ይማሩ ዘንድ አጥፊዎችን በሁሉ ፊት ገስጻሳቸው። 21 በእግዚአብሔር ፊት፣ በክርስቶስ ኢየሱስ
ፊት፣ በተመረጡትም መላእክት ፊት አዝዝሃለሁ፣ አንዳች አድልኦ ሳታደርግ እነዚህን ደንቦች ጠብቅ። 22 በማንም ላይ ቸኩለህ እጅህን አትጫን፣ ከማንም
ኃጢአት ጋር አትተባበር፣ ርስህን በንጽሕና መጠበቅ አለብህ። 23 በተደጋጋሚ ሆድህን ስለሚያምህ ጥቂት የወይን ጠጅ ጠጣ እንጂ ለወደፊቱ ውኃ ብቻ
አትጠጣ። 24 የአንዳንድ ሰዎች ኃጢአት በግልጽ የታወቀ ነው፣ ፍርድን ያስከትልባቸዋል፣ አንዳንዶች ግን ኋላ ይከተሉታል። 25 ልክ እንደዚሁ አንዳንድ መልካም
ሥራዎች የተገለጡ ናቸው፣ ነገር ግን ሌሎቹ በጊዜው የተገለጡ ባይሆንም እንኳ የተሰወሩ አይደሉም።

---

1 Timothy 5:1

1ኛ ጢሞቴዎስ 5:1-2
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ወንዶችን፣ ሴቶችን፣ መበልቶች እና ወጣት ሴቶችን በምን ዓይነት መንገድ ማስተናገድ እንዳለባት መናገሩን ቀጥሏል። አጠቃላይ መረጃ: ጳውሎስ እነዚህ ትዕዛዛት የሰጠው ጢሞቴዎስ ለተባለ አንድ ሰው ነው። በዚህ ሥፍራ ላይ “አንተ” የሚለው ቃል የተገለጸው በነጠላ ቁጥር ነው፤ ሽማግሌውን አትገስጸው "በሽማግሌ ላይ ጠንከር ያለ ቃል አትናገር" ይሁን እንጂ አባት እንደሚሆን ቆጥረህ አበረታታ "ነገር ግን አባትህ ሊሆን እንደሚችል በማሰብ አበረታታው" ከአክብሮት ጋር ወጣት ወንዶችንም ወንድሞችህ እንደሚሆኑ በማሰብ አበረታታቸው "ወጣት ወንዶችንም ወንድሞችህ ሊሆኑ እንደሚችሉ በማሰብ አበረታታቸው" ወይም "ወጣት ወንዶችን ልክ ወንድምህን በሚትንከባከብበት መንገድ ተንከባከባቸው፣" በሰላማዊ መንገድ። አሮጊት ሴቶችን እንደ እናት አበረታቷቸው "አሮጊት ሴቶችን ልክ እንደ እንናታችሁ ተንከቧከቧቸው" ወይም "አሮጊት ሴቶችን ልጅ እንደ እናራችሁ ተንከቧከቧቸው" ወጣት ሴቶችን ልጅ እንደ እህታችሁ "ወጣት ሴቶችን ልክ እህቶቻችሁን በምትቀርቡበት መንገድ ቅረቧቸው" ወይም "ለወጣት ሴቶችን ልክ ለእህቶቻችሁን የሚታደርጉትን እንክብካቤ አድርጉላቸው" በንጽሕና ሁሉ "በንጹህ ሀሳቦች እና ተግባራት" ወይም "በቅዱስ መንገድ"

1 Timothy 5:3

1ኛ ጢሞቴዎስ 5: 3-4
ክብር "አክብሯቸው እንዲሁም አስፈላጊውን ነገር ስጧቸው" ባልቴቶች፣ እውነተኛ ባልቴቶች "ባልቴቶች፣ በእርግጥም ባልቴት ለሆኑ" ወይም "ባልቴቶች፣ ማንም የሚያስፈልጋቸው የማያቀርብላቸው ባልቴቶች" ነገር ግን አንድት ባልቴት "ይሁን እንጂ ባልቴቷ" ልጆች "የእርሷ ልጆችን የሚሆኑ ካሏት" ወይም "እናቴ ብለው የሚጠሯት ልጆች ካሏት" የልጅ ልጆች "የእርሷ የልጅ ልጅ ናቸው የሚትላቸው ካሏት" ወይም "እናቴ ወይም አያቴ ብለው የሚጠሯት ካላት" በመጀመሪያ ለእነርሱ ፍቀዱላቸው በመጀመሪያ ደረጃ እነርሱ . . . ማድረግ ይኖርባቸዋል" ወይም "እነርሱ . . . ለማደረግ ቅድሚያ መስጠት ይኖርባቸዋል" አክብሮትን መስጠትን ተማር "ሃይማኖተኛ መሆናቸው ይታይ" ወይም "እግዚአብሔር መምሰላቸው ያሳዩ" ወይም "ሃይማኖታቸውን ያሳዩ" ወይም "ኃላፊነታቸውን መወጣትን ይለማመዱ" በገዛ ቤታቸው ውስጥ "ለራሳቸው ቤተሰብ" ወይም "በቤታቸው ውስጥ ለሚኖሩት ሰዎች" እንዲሁም ለወላጆቻቸው ብድራታቸውን ይክፈሉ "ለወላጆቻቸው መልሰው መክፈል ይችሉ ዘንድ" ወይም "ወላጆቻቸው በሰጧቸው መልካም ነገሮች ፈንታ እነርሱ ለወላጆቻቸው መልካም ነገርን ማድረግ ይችሉ ዘንድ" ምክንያቱ ይህ እግዚአብሔርን የሚያስደስት ነው "እነዚህ ነገሮች ስያደርጉ እግዚአብሔር በዚህ ደስ ይለዋል" ወይም "ይህ የማክበር ተግባር እግዚአብሔርን የሚስደስት ነው"

1 Timothy 5:5

1ኛ ጢሞቴዎስ 5:5-6
ይሁን እንጂ እውነተኛዋ በልታቴ ማንም የላትም "ይሁን እንጂ እውነተኛ ባልቴት የሆነች ሴት የሚያግዛት ቤተሰብ የላትም" ሁል ጊዜ በጥያቄ እና በጸሎት በእርሱ ፊት ትቀርባለች "በእግዚአብሔር ፊት ጥያቄዎቿን እና ጸሎቶቿን ይዛ ዘወትር ትቀርባለች" ጥያቄዎቿን እና ጸሎቷን እነዚህ ሁለት ቃላት ትርጉማቸው በመሠረቱ ተመሳሳይ ነው። እነዚህ ቃላት ጳውሎስ በዚህ ሥፍራ ላይ የተጠቀማቸው ባልቴቷ ምን ያህል እንደሚትጸልይ አጽኖት ለመስጠት ነው። ቀን እና ሌሊት አማራጭ ትርጉም: “ሁል ጊዜ”። ይሁን እንጂ "ነገር ግን" ሞተ የዚህ ምሳሌያዊ ንግግር ትርጉሙ ለእግዚአብሔር መልስ ለመስጠት አትችልም የሚል ነው። አማራጭ ትርጉም: "ልክ እንደ ሞተ ሰው ለእግዚአብሔር መልስ አትሰጥም።
ሕያው ይህ ሥጋዊ ሕይወትን ያመለክታል።

1 Timothy 5:7

1ኛ ጢሞቴዎስ 5: 7-8
እንዲሁም እነዚህን ነገሮች ስበክ "በተጨማሪም እነዚህን ነገሮች ስበክ" ወይም "በተጨማሪም እነዚህን ነገሮች በሥልጣን አስተምር።" ጢሞቴዎስ ራሱ የጳውሎስን ቃላት መታዘዝ ነበረበት—እንደሁም ሌሎችም የጳውሎስን ቃላት እንዲታዘዙ ማዘዝ አለበት። ያለነቀፋ መሆን ይችሉ ዘንድ "ማንም በእነርሱ ላይ ስህተት ማግኘት እዳይችል።" አማራጭ ትርጉሞች "እርሱ" 1) "እነዚህ ባልቴቶች እና ቤተሰቦቻቸው" (UDB) ወይም 2) "ቤተ ክርስቲያን።" በዚህ ሥፍራ ላይ የዐረፍተ ነገሩን ባለቤት “እነርሱ” በሚለው መተው መልካም ሳሆን አይቀርም። ለራሱ ዘመዶች አስፈላጊውን ነገር

የማያቀርብ ሰው "ዘመዶቹ የሚያስፈልጋቸውን ነገር የማይሰጣቸው ሰው" ወይም "የገዛ ዘመዱን የማይረዳ ሰው" ለሀዛ ቤተሰቦቹ "ለቤተሰቡ ሁሉ" ወይም "በቤቱ ውስጥ ላሉት ሰዎች" የራሱ የሆኑት በተሰቦች "ለቤተሰቦቹ" ወይም "በቤቱ ውስጥ የሚኖሩት ቤተሰቦቹ ለሆኑት ሰዎች" እምነትን ክዷል "የሚያደርገው ነገር ሃይማቱን የካደ ያስመስለዋል" ወይም "የሚያደርጋቸው ነገሮች እኛ ከምናምናቸው ነገሮች ተቃራኒ የሆኑትን ነው" ወይም "ቀድሞ ከሚያምናቸው ነገሮች ወደ ኋላ ተመልሷል" ከማያምኑትም የከፋ ነው "ይህ ሰው በኢየሱስ ከማያምኑት ሰዎች ይልቅ የከፋ ነው።" በኢየሱስ የማያምኑት ሰዎች እንኳ የገዛ ቤተሰቦቻቸውን ይንከባከባሉ፤ ስለዚህም ከአማኞች ደግም ከእነዚህ ይልቅ ምን ያኽል ማድረግ ይጠበቃል!

1 Timothy 5:9

1ኛ ጢሞቴዎስ **5**፡ **9-10**
ባልቴቶች ተብሎ የተመዘገቡት ይህ የሚያየው በጽሑፍም ይሁን ወይም አይሁን የባልቴቶች ስም ዝርዝርዝ ታውቋል ማለት ነው። ቤተክርስያንም ለእነዚህ ሴቶች የሚያስፈልገውን እንደ መጠለያ፣ ልብስ እና ምግብ ማቅረብ ይኖርባታል እንዲሁም እነዚህ ሴቶች ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል ራሳቸውን መስጠት ይጠበቅባቸዋል። ከስልዳ አመት በታች ያልሆነች ከስልሳ ዓመት በታች የሆነች ባልቴት ሴት እንደገና ማግባት ትችላለች ስለዚህም ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊውን ሁሉ እንክብካቤ ማድረግ ያለባት ከስልሳ ዓመት በላይ ለሆኑ ባልቴት ሴቶች ነው። የአንዲት ምስት ባል "ለባሏ ታማኝ የሆነች ሴት" በመልካም ተግባሮቿ የሚትታወቅ ልትሆን ይገባል ይህንንተከትሎ የሚመጡት ሀረጋት ሴትቱ ልትታወቅባቸው የሚገቡ መልካም ተግባራት ምን ምን ልመስሉ እንደሚችሉ ምሳሌ ይሆናል። እግር ማጠብ "ይህ እገዛ ለማደረግ የተለመደ ሥራ ነው።" በጭቃ እና አቧራ ውስጥ ስራመዱ የቆዩ ሰዎችን እግር ማጠብ ሌሎች ሰዎች የሚያስፈልጋቸውን ነገር የማድረግ እና ሕይወት ይበልጥ ተወዳጅ እንዲሆን የማድረግ ምሳሌ ነው። አማኞች "የእግዚአብሔር ቅዱስ ሕዝብ" መልካም ስራን ሁሉ የሚከታተሉ "is known for doing good works"

1 Timothy 5:11

1ኛ ጢሞቴዎስ **5**፡ **11-13**
ይሁን እንጂ ወጣት ባልቴቶችን በዚህ ውስጥ ማካተት የለባችሁም "በዚህ የባልቴቶች ዝርዝር ውስጥ ወጣት ሴቶችን ማካተት የለባችሁም።" ዝርዝሩ በውስጡ መያዝ ያለበት ቤተ ክርስቲያን ልታግዛቸው የሚገቡ ዕድሜያቸው ስልሳ እና ከስልሳ በላይ የሆኑ ባልቴቶችን ብቻ ነው። ክርስቶስን በሚቃወም አካላዊ ፍላጎች ይሸነፋሉ። "በፍተወት መሻት ምክንያት ከክርስቶስ ይርቃሉ" ወይም "መንፈሳዊ መሰጠታቸውን ከስሜታዊ መሻታቸው የተነሣ ይተውታል" የመጀመሪያውን መሰጠታቸውን ይተውታል "የመጀመሪያ መሰጣቸውን አይጠብቁም" ወይም "አስቀድመው እንደሚያደርጉ ቃል የገቡትን ነገር አይፈጽሚም" ቃል መግባት የባልቴቶቹ ስምምነት ቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች የሚታሟላ ከሆነ ቤተ ክርስቲያንን ለማገልግል ነው። ሐሜተኞች እነዚህ ስለ ሰዎች የግል ሕይወት ለሌሎች ሰዎች የሚወሩ ሰዎች ናቸው። ጣልቃ በመግባት እነዚህ በሌሎች ሰዎች ሕይወት ውስጥ ጣልቃ የሚገቡ ሰዎች ናቸው። መናገር የማይገባቸው ነገር "ለማንሳት እንኳ ተገቢ ያልሆኑ ነገሮችን"

1 Timothy 5:14

1ኛ ጢሞቴዎስ **5**፡ **14-16**
እኛን ለመክሰስ “እኛ” ለሚለው ቃል አማራጭ ትርጉሞች 1) ወጣት ሴቶች ወይም 2) ሐዋሪያው ጳውሎስን እና ወጣት ሴቶችን በበላይነት የሚያስተዳድሩ ሽማግሌዎች ወይም 3) ከወጣት ሴቶቹ ጋር አብረው የተቆጠሩት ሁሉም ክርስትያን አማኞች። አንዳንዶች ሰይጣንን እንዲከተሉ ፈቀቅ ብለዋልና። "ሴጣንን ለመከተል ከክርስቶስ መንገድ ፈቀቅ ብለዋልና። ዬትኛዋም አማኝ ሴት "ዬትኛዋም ክርስትያን ሴት" ወይም "በክርስቶስ የሚታምን ዬትኛዋም ሴት" ባልቴቶች ያሏቸው "በዘመዶቿ መካከል ባልቴት ያላት" እውተኛ ባልቴቶች "የሚያግዛቸው ማንም ሰው ያሌላቸው ሴቶች"

1 Timothy 5:17

1ኛ ጢሞቴዎስ **5**፡ **17-18**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: እንደገና ጳውሎስ ሽማግሌዎች (ኤጵስ ቆጳሳት)ን እንዴት መንከባከብ እንደሚገባ ይናራል። . . . እንደሚገባቸው ቁጠሩ አማራጭ ትርጉም: "አማኝ የሆናችሁ ሁላችሁ . . . ቁጠሩ።" እጥፍ ክብር አማራጭ ትርጉሞች 1) "ሁለቱንም ዓይነት ክብርለ አክብሮት እና ደሞዝ" ወይም 2) "ከሌሎች ሰዎች ይልቅ አክብሮት።" በመስበክና በማስተማር የሚደክሙት፥ "የእግዚአብሔርን ቃል የሚሰብኩ እና የሚያስተምሩት" የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰር ማሰሪያ በበሬ አፍ ላይ የሚታሰር ሲሆን በሬው ሥራውን በሚሠራበት ወቅት እንዳይበላ ያደርገዋል። በሬ እንደ ላም ያለ ትልቅ እንስሳ ነው። ሰብል ማበራየት እህሉን ከገለባው ለመለየጥ በታጨደ ሰብል ላይ መራመድ ወይም ከባድ ዕቃ ማንከባለል ነው። በሬዎች በሚያበራዩበት ወቅት ከገለባው እንዲበሉ ይፈቀድላቸዋል። ይገባዋል "ይገባዋል

1 Timothy 5:19

1ኛ ጢሞቴዎስ **5**፡ **19-20**
መቀበል "ማድመጥ" ወይም "መቀበል" ሁለት ወይም ሦስት "ቢያንስ ሁለት" ወይም "ሁለት ወይም ከዚያ በላይ" መገሠጽ "ገሰጸ" ወይም "አስተካከለ" ኃጢአተኞች ይህ ማንም እግዚአብሔር የማይታዘዝ ወይም የማያስደስትን ሥራን የሚሠራ ሰውን ያመለክታል። ይህ ምናልባት ያደረገውን ነገር ማንም ሰው ላያውቀው ይችላል። በሁሉም ፊት "ማንም ሰው በሚመለከተው ሥፍራ" ሌሎች ሰዎች ይፈሩ ዘንድ "ሌሎች ሰዎች ኃጢአትን ይፈሩ ዘንድ"

1 Timothy 5:21

1ኛ ጢሞቴዎስ **15**፡ **21-22**
አንተ ጳውሎስ ለአንድ ሰው፣ ለጢሞቴዎስ በመነናገር ላይ ሲሆን በዚህ ሥፍራ ላይ “አንተ” የሚለው ቃል የተገለጸው በነጠላ ቁጥር ነው። አስቀድሞ የተሰጠ ፍርድ "አስቀድሞ የተሰጠ ፍርድ" ወይም "ሁሉም ሰው በራሱ በኩል ስለተፈጠረው ነገር የሚናረውን ነገር ሳታደምጥ ውሳኔ መስጠት።" ጢሞቴዎስ እውነታው ምን እንደሆነ ማድመጥ ከዚያም የራሱን ፍርድ መስጠት ይጠበቅበታል። ከአድሎ ውጪ "ለሚትወደው ሰው ማዘንበል" ወይም "በወዳጅነት መሠረት።" ጢሞቴዎስ ፍርድን መስጠት ያለበት በሁኔታው ውስጥ የተሳተፉት እነማን ናቸው በሚል መሥፈረት ሳይሆን በእውነት መሠረት ላይ በመሆን ነው። እጅ በመጫን ይህ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሰዎች ላይ እጃቸውን ጭነው ወደ እግዚአብሔር በመጸለይ ይህህ ሰው እግዚብሔርን በሚያስደስት መንገድ ማገልገል እንዲችለል እግዚአብሔር ያስችለው ዘንድ የሚጸልዩበት ሥርዓት ነው። የሌላ ሰው ኃጢትን መካፈል "በሌላ ሰው ኃጢአት ውስጥ መካፈል።" የዚህ አማራጭ ትርጉሞች እነዚህ ናቸው 1) ጢሞቴዎስ አንድ ኃጢአት እንደሠራ የሚታወቅ ሰውን የቤተ ክርስቲያን ሠራተኛ እንዲሆን ከመረጠ እግዚብሔር በዚህ ሰው ኃጢአት ጢሞቴዎስን ተጠያቁ ያደርገዋል። ወይም 2) ሌሎች ሰዎች ስያደርጉ የተመለከተውን ኃጢአት ጢሞቴዎስ እርሱ ማድረግ የለበትም።

1 Timothy 5:23

1ኛ ጢሞቴዎስ **5**፡ **23-25**
አጠቃላይ መረጃ: በቁጥር 23 ላይ ለጢሞቴዎስ የተሰጠ የግል ማሳሰቢያ የገባ ይመስላል። ከዚያም በቁጥር 24 ላይ ጳውሎስ በቁጥር 22 ላይ መናገር የጀመረውን ነገር ይቀጥላል። ከእንግዲህ ወዲህ ውሃ መጠጣት የለብህም ወይም "ውሃ መጠጣት መቆም ይርብሃል፣" ውሃ ብቻ የሚጠጣ ሰው (UDB)። ጳውሎስ ውሃ መጠጣትን ሙሉ ለሙሉ ፈጽሞ አልከለከለም። ይሁን እንጂ ጳውሎስ ለጡሞቴዎስ የሰጠው አስተያየት ወይንን እንደ የሕክምና መዲሃኒት ይጠቀመው ዘንድ ነው። በዚያ አከባቢ የሚገኘው ውሃ ብዙ ጊዜ በሽታን ያስከትል ነበርና። ወደ ፍድ ከእነርሱ በፊት ይሄዳል "ኃጢአታቸው ከእርሱ ፊት ለፍርድ ይሄዳል።" እነዚህ አማራጭ ትርጉሞች ናቸው 1) ኃጢአታቸው የሚያሳየው ይህ ሰው እንደ ከዚህ በፊቱ ሁሉ እንደሆነ በመሆኑ ቤተ ክርስቲያን ይህ ሰው ምንም እንኳ የቤተ ክርስቲያን መሪ ቢሆንም

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ልትፈርድበት እንደሚገባ ነው።ወይም ወይም 2) ኃጢአታቸው እንደሚያሳየው ሰውዬው እንደ ከዚህ ቀደሙ በመሆኑ ምንያት ሰውዬው ጥፋተኝነቱ ይረጋገጥም አይረጋገጥም ቤተ ክርስቲያን ግን ውሳኔ ማስተላለፍ ይኖርባቸዋል። ወይም 3) ኃጢአታቸው የተረጋገጠ በመሆኑ እግዚአብሔር አሁን ይፈርድባቸዋል። ኋላ ላይ ሌሎች ይከተሏቸዋል "ይሁን እንጂ አንዳንድ ኃጢአቶች እነዚህን ሰዎች ይከተሏቸዋል።" አማራጭ ትርጉሞች 1) እስከ በኋላ ድረስ አንዳንድ ኃጢአቶችን ጢሞቴዎስ አያውቃቸውም ወይም 2) አንዳንድ ኃጢአቶችን ቤተ ክርስቲያን እስከ በኋላ ድረስ አታውቃቸውም፣ ወይም 3) አንዳንድ ኃጢአቶች እግዚአብሔር እስከ መጨረሻው ፍርድ ድረስ አይፈርድባቸዋም። መልካም በዚህ ሥፍራ ላይ “መልካም” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከእግዚብሔር ባሕርይ፣ ዓላማዎች እና ፈቃድ ጋር የሚስማማውን ነው። ሌሎቹም ቢሆኑ መሸሸግ አይችሉም አማራጭ ትርጉሞች፡ "ሌሎች መልካም ሥራዎችም ቢሆኑ ለወደፊት ይታወቃሉ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 6

1 የእግዚአብሔር ስምና ትምህርቱ እንዳይሰደብ ከቀንበር በታች ያሉ ባሪያዎች ለገዢዎቻቸው የሚገባቸውን ክብር ይስጡ። 2 አማኞች የሆኑ ገዢዎች ያሉአቸው ባሪያዎች፣ በእምነት ወንድሞቻቸው ስለሆኑ ገዢዎቻቸውን መናቅ የለባቸውም። ይልቁንም በመልካም ሥራቸው የሚጠቅሙ የተወደዱ ወንድሞች በመሆናቸው አብልጠው ያገልግሉአቸው። እነዚህን ነገሮች አስተምር ግለጽም። 3 ማንም ልዩ ትምህርትን ቢያስተምር፣ እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚረዳውን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል እና የእኛንም ጤናማ ቃል ባይቀበል፣ 4 በትእቢት ተነፍቶአል አንዳችም አያውቅም። ነገር ግን በክርክርና በቃል በመዋጋት የተለከፈ ነው፣ ከዚህም ምቀኝነት፣ ክርክር፣ መሳደብ፣ ክፉ አሳብና፣ እርስ በርስ መናደድም ይወጣሉ። 5 እነርሱም አእምሮአቸው የተበላሸባቸው ከእውነትም የራቁ እግዚአብሔርን መምሰል ጥቅም ማግኛ የሚመስላቸው ናቸው። 6 ባለው ለሚረካ ግን እግዚአብሔርን መምሰል እጅግ ማትረፊያ ነው። 7 ወደ ዓለም ምንም አላመጣንምና፣ አንዳችም ይዘን መሄድ አይቻለንም። 8 ምግብ እና ልብስ ካለን ያ ይበቃናል። 9 ባለጠጋ ለመሆን የሚመኙ በፈተና ውስጥ ይወድቃሉ፣ በወጥመድ፣ ሞኝነት በመሰሉ አያሌ ጎጂ ምኞቶች፣ እንዲሁም ሰዎችን በሚያሰጥሙና በሚያጠፉ በሌሎች ነገሮች ላይ ይወድቃሉ። 10 የገንዘብ ፍቅር የክፋት ሁሉ ሥር ነውና። አንዳንድ ሰዎች ይህን ሲመኙ ከእምነት ስተው ራሳቸውን በብዙ ሐዘን ጎዱ። 11 አንተ ግን፣ የእግዚአብሔር ሰው፣ ከእነዚህ ነገሮች ሽሽ። ጽድቅን፣ እግዚአብሔርን መምሰል፣ ታማኝነትን፣ ፍቅርን፣ ጽናትን እና ለሰዎች መጠንቀቅን ተከታተል። 12 መልካሙን የእምነት ገድል ተጋደል። የተጠራህለትን በብዙ ምሥክሮች ፊት ስለመልካምነቱ የመሰከርክለትን የዘላለምን ሕይወት ያዝ። 13 ሁሉን ነገር በፈጠረ፣ በእግዚአብሔር ፊት፣ በጴንጤናዊው በጲላጦስ ፊት እውነትን በመሰከረው፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት አዝዝሃለሁ፣ 14 ኢየሱስ ክርስቶስ እስኪገለጥ ድረስ ያለነቀፋ ሆነህ ትእዛዛቱን በፍጹምነት ጠብቅ። 15 እርሱም መገለጡን የተባረከውና፣ ብቻውን ኃያል የሆነው፣ የነገሥታት ንጉሥ፣ የጌቶችም ጌታ በወሰነው በትክክለኛው ጊዜ ያሳያል። 16 እርሱ ብቻ የማይሞት ነው፤ ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ውስጥ ይኖራል። ማንም ሰው አላየውም ሊያየውም አይችልም። ለእርሱ ክብር የዘላለምም ኃይል ይሁን። አሜን። 17 በአሁኑ ዘመን ሀብታሞች ለሆኑት እንዳይታበዩ ንገራቸው። ደስ እንዲለን እግዚአብሔር በሚሰጠን እውነተኛ ብልጥግና እንጂ እርግጠኛ ባልሆነው በዚህ ምድራዊ ባለጠግነት ተስፋ እንዳያደርጉ እዘዛቸው። 18 በመልካም ሥራ ባለጠጎች እንዲሆኑ፣ መልካም የሆነውን እንዲያደርጉ ለማካፈልም ፈቃደኞች እንዲሆኑ ንገራቸው። 19 በዚህ ሁኔታ በሚመጣው ዓለም ለራሳቸው መልካም መሠረትን ይጥላሉ፣ እውነተኛውንም ሕይወት ይይዛሉ። 20 ጢሞቴዎስ ሆይ፣ ለአንተ የተሰጠህን አደራ ጠብቅ። የማይረባውን ወሬ አስወግድ፣ በሐሰት እውቀት ከተባለ እርስ በርሱ ከሚጋጭ ነገር ጋር ከመከራከር ራቅ። 21 አንዳንድ ሰዎች ይህ እውቀት አለን በማለት ከእምነት ርቀዋል። ጸጋ ከአንተ ጋር ይሁን።

---

1 Timothy 6:1

1ኛ ጢሞቴዎስ **6**፡ **1**-**2**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ለባሮቹ እና ለጌቶቻቸው አንዳንድ ልዩ መመሪያዎችን መስጠቱትን ቀጥሮ እንዴት እግዚብሔር በመመስል መኖር እንደሚቻል መመሪያን ይሰጣል። ከቀንበር በታች ያሉቱ ባሪያዎች ይህ ባሪያን እንደ በሬ የሚመስል በመሆኑ በዚህ መልኩ ልተረጎም ይችላል። ይህንን ምሳሌያዊ ንግግር ለመተርጎም አስቸጋሪ ሊሆን ከቻለ ሳይተረጎም ሊያልፍ ይችላል። ይህ ክርስቲያን መሆንን በሚያለክት ምሳሌያዊ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። የእግዚአብሔር ስም እና ነትምህርቱ ይሰደባል "ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ያሉ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ስም እና ትምህርቱ አክብሮት ይናገሩ ዘንድ"

1 Timothy 6:3

1ኛ ጢሞቴዎስ **6**:**3**-**5**
አንድ ሰው ካስተማረ "ይህንን የሚያስተምር ማንኛውም ሰው" ወይም "ይህንን የሚያስተምሩ ሰዎች።" “የተለያዩ” ነገሮቸን የሚያስተምሩ ሰዎች እንዳሉ ጳውሎስ ታሳቢ ያደርጋል። የሆነ ሰው . . . እርሱ . . . እርሱ UDB ብዙ ቁጥር አመላካች ይጠቀማል "እንዳንድ ሰዎች . . . እንዲህ ያሉ ሰዎች . . . እነርሱ"፤ “የሚያስተምረው” “ማንኛውም ሰው” ወንድ ወይም ሴት፣ አንድ ሰው ወይም ብዙ ሰዎች። እነዚህ አማራጭ ትርጉሞች ሊያሳይ የሚችልን ቃል በቋንቋችሁ ካለ ተጠቀሙበት። በጭቅጭቅ ታሟል "ማድረግ የሚፈልገው ነገር ሁሉ መከራከር ነው" ወይም "ክርክረን ይፈልጋሉ።" እንዲህ ያሉ ሰዎች ክርክር ራሱን ይፈልጉታል እና መስማመማት የማይችሉበትን መንገድ ይፈልጋሉ። ቅንአት "ሌሎች ሰዎች ያላቸውን ነገር ለማግኘት ይፈልጋሉ" ክርክር "በአማኞች መካከል ያለ ክርክር" ስድብ "ሰዎች በሐሰት ስለ ሌሎች ሰዎች መጥፎ ነገርን ይናገራሉ" ክፉ ጥርጣሬተ ከእነርሱ ጋር የማይስማማ ማንኛውም ሰው በእነርሱ ላይ ክፉ ነገር ለማድረግ እየሞከረ እንደሆነ መናገር። ከሰዎች ጋር ሁል ጊዜ መጣላት "ከሁሉም ሰዎች ጋር መጣላት" የበሰበሰ አእምሮ "በመጥፎ ሀሳቦች ፈጽሞ የተበላሸ አእምሮ"

1 Timothy 6:6

1ኛ ጢሞቴዎስ **6**:**6**-**8**
ትልቅ ትርፍ ነው "ትልቅ ትርፍን ያስገኛል" ወይም "ለእኛ ብዙ መልካም ነገርን ያደርጋል" ወደ ዓለም ምንም ነገር አላመጣም "ስወለድ ወደ ዓለም ምንም ነገር ይዞ አልመጣም" እንዲሁም ምንም ወስደነው የሚንሄደው ነገር የለም "እንዲሁም ስንሞት ከዓለም ይዘነው የሚንሄደው ነገር የለም" ይህን እናድርግ "ይህንን ማድረግ አለብን"

1 Timothy 6:9

1ኛ ጢሞቴዎስ **6**፡ **9**-**10**
እንዳንወድቅ ይህ አንድ ሰው ሕይወቱን ወይም በአእምሮው የማሰብ ሂደቱን ማጣቱን የሚያመለክት ምሳሌያዊ ንግግር ነው። በፈተና እንዳይወድቅ "መቋቋም ከሚችለው በላይ ወደ ሆነ ፈተና እንዳይገባ" በወጥመድ ተይዞ . . . እንዳይወድቅ "በመጥመድ እንዳይያዝ።" ለራስ ጥቅም መሥራት አለመቻልን እና ጉዳት የሚያደርሱ ሰዎችን በመቃወም መሥራት አለመቻልን የሚያመለክት ምሳሌ ነው። በብዙ ሙኝነት በሞላባቸው እና ጉዳት በሚያደርሱ መሻት ውስጥ መውደቅ "ሞኝነት በሞላባቸው እና ጉዳት በሚያደርሱ ፍለጎቶች ቁጥጥር ሥር መሆን" ሰዎችን እንዲሰምጡ ማድረግ "ሰዎችን እንዲሠርጉ ወደ ታች መጎተት" ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ስለሆነ "ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር በመሆኑ ምክንያት" ለሚሹት ሰዎች "ገንዘብን ለሚሹ ሰዎች" ከእምነት ፈቀቅ ብለዋል "የእውነትን መንገድ ትተው ሄደዋል" ወይም "በእውነት ማመን ትተዋል" በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ። ይህ ምሳሌያዊ ንግግር ኃዘንን ከብላዋ ወየም ከጦር ጋር በማነጻጸር ያስቀምጣል።

1 Timothy 6:11

1ኛ ጢሞቴዎስ **6**፡ **11**-**12**
የእግዚአብሔር ሰው "የእግዚብሔር አገልጋይ" ወይም "የእግዚአብሔር የሆነ ሰው" ከእነዚህ ነገሮቸ ራቅ "እነዚህ ነገሮች አንተን ለመጉዳት እንደሚችሉ ነገሮች በማድረግ ከእነርሱ ራቅ።" የዚህ ነገር አማራጭ ተትርጉሞቹ 1) “ገንዘብን መውደድ" ፈልግ "ተከተ" ወይም "ተከታተል" ወይም "ይህን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ለማድረግ የሚትችለውን አድርግ" መልካምን ገድል ተጋደል...አጥብቀህ ያዝ...ሕይወት አንዳንዶች ይህንን ከክፍል የእስፖርታዊ ውድድር ጋር ተነጻጽሮ የቀረበ ምሳሌያዊ ንግግር አድርገው ይመለከቱታል። በዚህ ውድድር ውስጥም አሸናፊው ሽልማቱን “ለመያዝ” “ይጋደላል”። መያዝ . . . ሕይወት አንዳንዶች ይህንን ምሳሌያዊ ንግግር “መለካም ገድልን ተጋደል” ለሚለው ሌላ አማራጭ ንግግር እንደሆነ ይረዱታል። አማራጭ ትርጉም፡ "ሕይወትን ለማግኘት የሚታደርገውን ነገር ሁሉ አድርግ" ምስክርነት ስጥ "ምስክርነት ስጥ" ወይም "መስክር" በፊት "በመገኘቱ ውስጥ" መልካም የሆነውን ነገር "የሚታምነውን ነገር"

1 Timothy 6:13

1ኛ ጢሞቴዎስ **6**፡ **13**-**14**
በእግዚአብሔር ፊት "በእግዚብሔር መገኘት ውስጥ" ወይም "እግዚብሔር ምስክርህ ሆኖ" በክርስቶስ ፊት "በክርስቶስ መገኘት ፊት" ወይም "ክርስቶስ ምስክርህ ሆኖ" በጴንጤናዊው ጵላጦስ ፊት "በጴንጤናዊው ጵላጦስ ፊት" ከነቀፋ ውጪ የዚህ አማራጭ ትርጉሞች የሆኑት 1) እግዚአብሔር በጢሞቴዎስ ላይ ምንም ስሕተት አያገኝበትም (UDB) ወይም 2) ሌሎች ሰዎች በጢሞቴዎስ ላይ ምንም ስሕተት አያገኙበትም። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ "ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እስከሚገለጥበት ቀን ድረስ"

1 Timothy 6:15

1ኛ ጢሞቴዎስ **6**፡ **15**-**16**
በትክክለኛው ሰዓት "በትክክለኛው ጊዜ" (UDB) በተዘጋጀ "በተወሰነ" ወይም "በተመረጠ" የተባረከው "ሁሉንም በረከቶች በራሱ የያዘው" ወይም "ሁሉንም በረከቶች የሚሰጠው እግዚአብሔር።" ይህ የሚያመለክተው ኢየሱስን እንዲገለጥ የሚያደርገው እግዚአብሔር አባትን ነው።

1 Timothy 6:17

1ኛ ጢሞቴዎስ **6**፡ **17**-**19**
እርግጠኞች ያልሆኑ ባለጠጎች "ባለ ጠጎች የሆኑት የትዕቢትን ነገር እንዳያስቡ።" በዚህ ሥፍራ ላይ ይህ የሚያመለከተው ቁሳዊ የሆነ ነገር ነው። እውነተኛ ባለጠግነት "በእውነተኛ መንገድ ደስተኞች እንድንሆን የሚያደርገው።" በዚህ ስፍራ ላይ ይህ የሚያመለክተው ቁሳዊ ነገር የሚያለክት ነው ይሁን እንጂ ሰዎች በቁሳዊ ነገሮች አማካኝነት ለማግኘት የሚጥሯቸውን ፍቅርን ሐሴትን እና ሰላምን የሚወክል ነው። በመልካም ሥራ ባለጠጎች ሁኔ "ሌሎችን በተለያዩ መንገዶች በማገዝ አገልግሉ።" ቤተ ክርስቲያንንም መገንባት መሠረት ቤት በመሥራት ሂደት ውስጥ ልሠራ የሚገባው የመጀመሪያው ክፍል። ይህ የመጀመሪያው “እውነተኛ ባለጠግነት” መገለጫ ምሳሌ ነው እንዲሁም እግዚአብሔር ለለእርሱ ሕዝብ ለዘላለም የሚሰጠው “የእውነተኛ ሕይወት” ጅማሬ ነው። እውነተኛውን ሕይወት ያዝ ይህ በ 1TI 6:12 ላይ የተገለጸውን የእስፖርት ውድድር አሸናፊ የሚይዘውን ሽልማት የሚያሳይ ምሳሌያዊ ንግግርን የሚያሳይ ነው። በዚህ ሥፍራ ላይ “ሽልማት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሕይወትን ነው።

1 Timothy 6:20

1ኛ ጢሞቴዎስ **6**፡ **20**-**21**
ኖት የለውም።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: 2 Timothy

2 Timothy

ምዕራፍ 1

1 በእግዚአብሔር ፈቃድ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ለሆነው የሕይወት ተስፋ፣ የክርስቶስ ኢየሱስ ሐዋርያ የሆነው፣ጳውሎስ 2 ለተወደደው ልጄ፣ ለጢሞቴዎስ፣ ጸጋና
ምሕረት ሰላምም በእግዚአብሔር አባታችን፣ ቤታችንም በኢየሱስ ክርስቶስ ለአንተ ይሁን። 3 ሌትና ቀን በጸሎቴ ስለማስብህ፣ እንደ አባቶቼ አድርጌ በንጹህ ኅሊና
የማገለግለውን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፣ 4 እምባህን እያሰብኩ በደስታ እሞላ ዘንድ ላይህ እናፍቃለሁ፤ 5 ያለህንም እውነተኛ እምነት አስባለሁ፣ ይህም
እምነት አስቀድሞ በአያትህ በሎይድ በእናትህም በኤውንቄ ነበረባቸው፣ በአንተም እንዳለ ተረድቼአለሁ። 6 እግዚአብሔር የሰጠህን በአንተ ያለውን ስጦታ
እንድታነሣሣ ስለጆቼን በመጫኔ አሳስብሃለሁ። 7 እግዚአብሔር የኃይል እና የፍቅር ራስንም የመግዛት እንጂ፣ የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንም። 8 በጌታ እና
የእርሱ እስረኛ በሆንኩት በእኔም ምሥክርነት አትፈር፣ እንደ እግዚአብሔር ኃይል መጠን ስለ ወንጌል መከራን ተቀበል። 9 ከዘላለም ዘመናት በፊት በክርስቶስ
ኢየሱስ ያዳነን፣ በቅዱስም አጠራር የጠራን እግዚአብሔር ነው፤ ይህም የሆነው በራሱ እቅድና በጸጋው ነው እጂ በእኛ ሥራ አይደለም። 10 አሁን ግን
የእግዚአብሔር ማዳን፣ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ እና፣ ሞትን በማጥፋቱ እና የዘላለምን ሕይወት ወደ ብርሃን በማውጣቱ በወንጌሉ ተገልጦአል፣
11 ይህንንም ወንጌል ለማብሰር እኔ ሐዋርያ እና አስተማሪ ሆኜ ተሹሜአለሁ። 12 ስለዚህ ምክንያት እኔ መከራ እቀበላለሁ፣ ነገር ግን አላፍርበትም፣ ያመንኩትን
አውቃለሁና፤ የሰጠሁትን አደራ እስከዚያች ቀን ድረስ እንደሚጠብቅ ተረድቼአለሁ። 13 ከእኔ የሰማኸውን ጤናማ ቃል፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለ እምነትና ፍቅር
በምሳሌነት ጠብቅ። 14 በእኛ በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ አድርገህ በእግዚአብሔር የተሰጠህንም አደራ ጠብቅ። 15 በእስያ ያሉት ሁሉ ከእኔ ፈቀቅ እንዳሉ
ታውቃለህ፣ ከእነዚህም ጊሊጎስ እና ሄርሞጌኔስ ይገኙባቸዋል። 16 ጌታ ለኔሴሲፎሩ ቤተ ሰብ ምሕረትን ይስጣቸው፣ ብዙ ጊዜ አሳርፎኛልና፣ በሰንሰለቴም
አላፈረበትም። 17 ነገር ግን በሮም በነበረ ጊዜ፣ በብርቱ ፈልጎ አገኘኝ፣ 18 ጌታ በዚያች ቀን ምሕረትን እንዲያገኝ ይስጠው፣ በኤፌሶን ምንያህል እንደረዳኝ አንተ
በደኅና ታውቃለህ።

---

2 Timothy 1:1

2ኛ ጢሞቴዎስ 1: 1-2
ጳውሎስ "ከጳውስ" ወይም "እኔ ጳውሎስ ይህንን ደብዳቤ ጻፍኩላችሁ" በእግዚአብሔር ፈቃድ አማካኝነት "ከእግዚብሔር ፈቃድ የተነሣ" ወይም "እግዚአብሔር ይህንን ነገር በመፈለጉ ምክንያት።" ጳውሎስ ሐዋርያ የሆነው እግዚአብሔር ጳውሎስ ሐዋርያ እንዲሆን በመፈለጉ እንጂ ሰዎች ሐዋርያ እንዲሆ ስለመረጡት አይደለም። እንደ አማራጭ ትርጉሞች፡ 1) "ከ ጋር በመስማማት" ትርጉሙም እግዚአብሐየር ለኢየሱስ በገባው ቃለል መሠረት ኢየሱስ ሕይወትን ይሰጣል እንዲሁም ጳውሎስን ሐዋርያ አድርጓል ወይም 2) "ለዚህ ዓላማ ሲባል፣" ትርጉሙም እግዚአብሔር ጳውሎስን የሾመበጽ ምክንያት ጳውሎስ በኢየሱስ በኩል የሚገኘውን ሕይወት ለሌሎች ሰዎች ይናገር ዘንድ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ የሚገኘውን የሕይወት ተስፋ "በክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑ ሰዎች ሕያዋን እንደሚሆኑ እግዚአብሔር የተስፋ ቃልን ሰጥቷል።" የተወድህ ልጄ ሆይ "ውድ ልጄ ሆይ" ወይም "የተወደድከው ልጄ ሆይ" ወይም "የሚወድህ ልጄ ሆይ።" ጢሞቴዎስ ወደ ክርስቶስ የመጣው በጳውሎስ አማካኝነት ነው ስለዚህም ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ልክ እንደ ገዛ ልጁ አድርጎ ይመለከተው ነበር። ጸጋ፣ ምህረት እና ሰላም ከ . . . "ጸጋ፣ ምህረት እና ሰላም ለእናነት ከ . . . ዘንድ ይሁንላችሁ" ወይም "ከውስጥ መልካምነትን፣ ምህረትን እና ሰላምን ከ . . . ዘንድ ይሁንላችሁ" እግዚአብሔር አባት "አባታችን የሆነው እግዚአብሔር" እናም ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ "እንዲሁም ጌታችን ከሆነው ከክርስቶስ ኢየሱስ ዘንድ"

2 Timothy 1:3

2ኛ ጢሞቴዎስ 1: 3-5
ቀደምት አባቶቻችን እንዳገለገሉ እኔም አገለግላለሁ ጳውሎስ የሚያገለግለው ቀደምት አባቶቹ ያገለገሉትን እግዚአብሔርን ነው። “. . . እንደ ክርስትያን ኃላፊነትን የሚወጣው ከዚህ በፊት የኖሩት ቀደምት አባቶ ባደረጉት መልኩ ነው።" በንጹሕ ሕልና "በንጹሕ ሕልና።" በመጥፎ ሀሳብ የሚወዛገብ ሳይሆን ሁል ጊዜ ትክክለኛ ነገርን ለማድረግ ጥረት ያደርጋል። እኔ ሁል ጊዜ ስለ አንተ ሳስታውስ "ሁል ጊዜ ስለአንተ ሳስታውስ" ወይም 'ሁል ጊዜ ስለአንተ በማስታውስበት ወቅት" ምሽት እና አማራጭ ትርጉሞች 1) "በምሽት እና በቀን ስጸልይ" ወይም 2) "በቀን እና በሌልት አንተን ሳስታውስ ወይም 3) "በምሽት እና በዘን አንተን ለማየት ስጓጓ።" አንተን ለማየት ስጓጓ "አንተን ለማየት ከፍተኛ ፍላጎት ስለላለኝ" እንባህን እያስታወስኩ "ያሳለፍከውን መከራ ሁሉ እያስታወስኩ" በደስታ እሞላለሁ "ከፍኛ ደስታም ይሰማኛል" ወይም "በጣም ደስ ይለኛል" ይህንን እያስታወስኩ "ይህንን ስላምስታውስ" ወይም "ይህንን ባስታወስኩ ቁጥር" ወይም "ይህን በማስታወሴ ምክንያት" እውነተኛውን እምነትህ "እውነተኛ የሆነውን እምነትህን" ወይም "ማስመሰል ያሌለበትን እምነትህን።" ይህ እውነተኛ ወይም ምንም ውሸት ያሌለበትን እምነቱን የሚያመለክት ነው። እውነት...በመጀመሪያ በአያትህ ዘንድ የነበረውን . . . በአንተም ውስጥ ያለውን የጢሞቴዎስ ቅድመ አያት ለእግዚአብሔር የተሰጡ ነበሩ እናም ጳውሎስ የጢሞቴዎስን እምነት ከኤቱ እምነት ጋር ያነጻትራል።

2 Timothy 1:6

2ኛ ጢሞቲዎስ 1: 6-7
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ጢሞቴዎስ በኃይል፣ በፍቅር እና በደቀ መዝሙርነት እንዲኖር ያበረታታዋል። በተጨማሪም በጳውሎስ መታሠር እንዳያፍር ምክንያቱም የጳውሎስ መከራ በክርስቶስ በማመኑ ምክንያት ነው። ይህ ምክንያት ነው "በዚህ ምክንያት" ወይም "በኢየሱስ ላይ ባለህ እውነተና እምነት የተነሣ" ወይም "በኢየሱስ ላይ እውነተኛ እምነት ስላለህ" አስታውስሃለሁ "እኔ አስታውስሃለሁ" ወይም "እንደገና እነግርሃለሁ" እጅ በመጫን በአንተ ውስጥ ያለውን የእግዚብሔር ስጦታ አነሳሳለሁ ጳውሎስ በጢሞቴዎስ ላይ እጆቹን በመጫን በእርሱ ላይ ያለውን መንፈስ ቅዱስ እና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን አረጋግጧል። ጳውሎስ እየነገረው ያለው ነገር ለክርስቶስ በሚሠራበት ወቅት እነዚህን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች “እንደገና እንቀሰቅስ” ወይም “እንዲያነቃቃ” ነው። የከሰል እሳትን ማራገብ ወይም ማቀጣጠል የሚለው ምስላዊ ገለጻ በጢሞቴዎስ የተዘነጉ ወይም በጢሞቴዎስ ጥቅም ላይ እየዋሉ ያልሆኑ መንፈሳዊ ስጦታዎቹን መቀስቀስን ያመለክታሉ። ለእግዚአብሔር "በእግዚአብሔር ምክንያት" እግዚአብሔር የፍርሃትን መንፈስ አልሰጠንም ጳውሎስ ከእግዚአብሔር ዘንድ መንፈስን ተቀብሏል። በጢሞቴዎስ ላይ እጆቹን በሚጭንበት ጊዜ በጢሞቴዎስ ላይ ተመሳሳይ መንፈስ ያርፍበታል። ይህ መንፈስ ደግሞ እግዚአብሔር ወይም

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ሌሎች ሰዎችን እንዲፈራ አያደርገውም። ራስን የመግዛት መንፈስ አማራጭ ተትርጉሞች “የእግዚአብሔር መንፈስ ራሳችን የመግዛት መንፈስን ይሰጠናል" (UDB) ወይም 2) "የእግዚአብሔር መንፈስ በተሳሳተ መንገድ የሚሄዱ ሰዎችን እንድናስተካክል ያደርገናል።"

2 Timothy 1:8

2ኛ ጢሞቴዎስ **1**፡ **8**-**11**
ስለዚህ በዚህ አትፈር "ስለዚህ አትፍራ" ወይም "ስለዚህ በፍርሃት አትሞላ" ለወንጌል መከራን ተቀበል ጳውሎስ ትክክል ባልሆነ መልኩ መከራን እየተቀበለ ያለው በወንጌል ምክንያት ነው። ስለዚህም ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በተመሳሳይ መልኩ ለወንጌል መከራን ለመቀበል አትፍራ በማለት ይመክረዋል። እንደ እግዚአብሔር ኃይል "እግዚአብሔር እንዲያጠነክርህ ፍቀድለት" እንደ ሥራችን ሳይሆን "የምንድነው መልካም ራዎችን በሰራንበት መጠን አይደለም።" ወይም "እግዚአብሔር ያዳነን በሠራነው መልካም ሥራ መሠረት አይደለም" ወይም "ምንም እንኳ መጥፎ ስራዎችን የሠራን ቢንሆንም እንኳ እግዚአብሔር አድኖናል" እኛን ያዳነን ማን ነው . . . በእቅዱ መሰረት "እግዚአብሔር እኛን ለማዳን አቅዶ ዘሁን አዳነን" ወይም "እግዚአብሔር እኛን ለማዳን ወስኗል እነንዲሁም እንዲሁም እንዴት እንደሚያድነን ወስኖ አሁን እኛን አዳነን" ወይም "እኛን ማን አዳነን...በዕቅዱ መሠረት" ጊዜ ከመጀመሩ በፊት "ምድር ከመፈጠሯ በፊት" ወይም "ጊዜ ከመፈጠሩ በፊትn" ጊዜ ይህ ዓለማትን የሚያመለክት ምሳሌያዊ ንግግር ነው። የእግዚብሔር ድነት በአዳኛችን ኢየሱስ ክርስቶስ መገለጠ ምክንያት ተገልጧል። "እግዚአብሔር እኛን እንዴት እንዳዳነን አዳናችን መስሑን በመግለጥ አሳይቶናል።" ሞትን ያጠፋ "ሞት በእኛ ላይ የነረውን ኃይል የሰበረው" በወንጌል አማካኝነት ማብቂያ ያሌለውን ሕይወት ያመጣ "በወንጌል ስብከት አማካኝነት ማብቂ ስላሌለው ሕይወት ያስተማረ" እኔ ሰባኪ ሆኜ ተሾሙክ "መልዕከቱን እሰብክ ዘንድ እግዚአብሔር መረጠኝ"

2 Timothy 1:12

2ኛ ጢሞቴዎስ **1**፡ **12**-**14**
በዚህ ምክንያት አማራጭ ትርጉም: "ሐዋሪያ በመሆኔ ምንክንያት" እኔም እራሴ በእነዚህ ነገሮች መከራ ይደርስብኛል ጳውሎስ በዚህ ሥፍራ እያመለከተ ያለው የሚደርስበት እስራት ነው። አምኛለሁ "አምኛለሁ" በዚያ ቀን አማራጭ ትርጉም 1) ጌታ ዳግም በሚመጣበት ቀን ወይም 2) እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ በምፈርድበት ቀን። ከእኔ የሰማኸውን የእምነት መመሪያ ጠብቅ "ያስተማርኩህን ትክክለኛ ትምህርት ጠብቅ" ወይም "ምን እና እንዴት ማተማር እንዳለብህ ለማወቅ የእኔን ቃላት እና የማስተማሪያ ዘዴ ተጠቀም" እነዚያ መልካም ነገሮችን ይህ ወንጌልን በትክክለኛ መልኩ የመስበክ ሥራን ያመለክታል። ጠብቀው ሰዎችን ሥራውን ሊቃወሙ ስለሚችሉ ጢሞቴዎ ነቅቶ መጠበቅ ይኖርበታል፣ እንዲሁም ይህን ተግራቸውን እንዲያቆሙ ለማድረግ መጣር ይኖርበታል እንዲሁም የሚናገረውን ነገር እንዳጠፉበት መጠበቅ አለበት። በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት "መንፈስ ቅዱስ እንዲታደረግ የሚነግርህን ነገር ሁሉ እና እርሱን ብቻ አድርግ"

2 Timothy 1:15

2ኛ ጢሞቴዎስ **1**፡ **15**-**18**
ከእኔ ተለይተው ሄደዋል ስለታሠረ እና በወህኒ ቤት ስለተጣለ ትተውታል። በሰንሰለቴ አለፈረም ለሄኔሲፎሩ በጳውሎስ መታሠር አላፈረም ብዙ ጊዜም ወደ ወህኒ ቤት እየመጣ ይጠይቀው ነበረው። “ሠንሠለት” የመታሠር ምሳሌያዊ ንግግር ነው። ምህረትን ያገኝ ዘንድ ሰጠው . . . በዚያ ቀን ጳውሎስ ለሄኔሲፎሩ ፍርድ ሳይሆን ምህረትን እንዲቀበል ይመኛል። 1) ጌታ ዳግመኛ በሚመጣበት ቀን ወይም 2) እግዚብሔር ሰዎችን ላይ በምፈርድት ቀን።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 2

1 እንግዲህ ልጄ ሆይ በኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ጽጋ በርታ። 2 ከብዙ ምስክሮች ጋር ከእኔ የሰማኸውን፣ ሌሎችን ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ። 3 እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ መልካም ወታደር ሆነህ አብረኸኝ መከራ ተቀበል። 4 አለቃውን ማስደሰት የሚፈልግ ወታደር በምድራዊው ነገር ራሱን አያጠላልፍም። 5 ማንም በስፖርታዊ ውድድር የሚሳተፍ፣ በደንቡ መሠረት ካልተወዳደረ የድሉን አክሊል ሊያገኝ አይችልም። 6 በርትቶ የሚሠራው ገበሬ ምርቱን ከሚበሉት የመጀመሪያው ሊሆን ይገባል። 7 የምለውን ተመልከት ጌታም በነገር ሁሉ ማስተዋልን ይስጥህ። 8 በወንጌል መልእክቴ የገለጽኩትን፣ ከሙታን የተነሣውንና ከዳዊት ዘር የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን አስብ። 9 በዚህም ምክንያት እንደ ወንጀለኛ በመታሰር መከራ እቀበላለሁ፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል አይታሰርም። 10 ስለዚህ ስለተመረጡት ስል በሁሉ እጸናለሁ፣ እነርሱ በክርስቶስ ኢየሱስ የሆነውን መዳን ከዘላለማዊ ክብር ጋር ያገኙ ዘንድ። 11 እንዲህ የሚለው ቃል የታመነ ነው ‹‹ከእርሱ ጋር ከሞትን፣ ከእርሱ ጋር እንኖራለን። 12 ብንጸና ከእርሱ ጋር እንነግሣለን። ብንከዳው እርሱ ደግሞ ይክደናል። 13 ባናምነው እርሱ የታመነ ሆኖ ይኖራል፣ ራሱን ሊክድ አይችልምና። 14 እነዚህን ነገሮች አስታውሳቸው። በቃል እንዳይጣሉ በእግዚአብሔርም ዘንድ አስጠንቅቃቸው፣ይህ ምንም ጥቅም የሌለው የሚሰሙትንም የሚጎዳ ነው። 15 የእውነትን ቃል በትክክል የሚይዝ፣ የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ ራስህን በእግዚአብሔር ፊት ለማቅረብ ትጋ። 16 እግዚአብሔርን ከመምሰል የሚያርቅህን አለማዊ ተረቶችን አስወግድ። 17 ቃላቸው እንደ ቆላ ቁስል ነው፣ ከእነርሱም ሄሜኔዎስና ፊሊጦስ ይገኙባቸዋል፣ 18 እነዚህም ሰዎች ከእውነት ርቀው ትንሣኤ ሙታነ ካሁን ቀደም ሆናል ይላሉ፣ በዚህም የአንዳንዶችን እምነት ይገለብጣሉ። 19 ሆኖም፣ ‹‹ጌታ ለእርሱ የሆኑትን ያውቃል›› ደግሞም ‹‹የጌታን ስም የሚጠራ ከዓመፃ ይራቅ›› የሚለው ማኅተም ያለበት የእግዚአብሔር መሠረት ቆሞአል። 20 በሀብታም ቤት ውስጥ የሚገኙት የወርቅ እና የብር ዕቃዎች ብቻ አይደሉም ነገር ግን የእንጨት እና የሸክላ ዕቃዎችም ይገኛሉ፣ አንዳንዶቹ ለክብር ሌሎቹም ክብር ለማይሰጣቸው ሥራዎች ይውላሉ። 21 ማንም ከማያስከብር ሥራ ራሱን ቢያነጻ፣ የተከበረ ዕቃ፣ የተቀደሰ፣ ለጌታውም የሚጠቅም፣ ለማንኛውም መልካም ሥራ የተዘጋጀ ይሆናል። 22 ከወጣትነት ምኞት ራቅ፣ በንጹህ ልብ ጌታን ከሚጠሩ ጋር ጽድቅን፣ እምነትን፣ ፍቅርን፣ ሰላምን ተከታተል። 23 ነገር ግን ጠብን እንደሚያመጣ አውቀህ ከሰነፎችና ካልተማሩ ምርመራ ራቅ። 24 የጌታ አገልጋይ ሊጣላ አይገባውም፣ ከዚህ ይልቅ ለሁሉ የሚጠነቀቅ፣ ለማስተማርም የሚበቃ በትእግስትም የሚጸና፣ 25 በትህትናም ለሚቃወሙት ትምህርት የሚሰጥ ሊሆን ይገባዋል። እውነትን በማወቃቸው እግዚአብሔር ምናልባት ንስሐን ይሰጣቸው ይሆናልና፣ 26 እንዲሁም ለዲያብሎስ እና ለፈቃዱ ከተያዙበት ወጥመድ ተላቀው ወደ ኅሊናቸው ሊመለሱ ይችሉ ይሆናል።

---

2 Timothy 2:1

2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡ 1-2
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ የጢሞቴዎስን የክርስትና ሕይወት ከወታደር፣ ከገበሬ ሕይወት እና ከእስፖርተኛ ሕይወት ጋር በማነጻጸር ይጽፋል። በክርስቶስ ኢየሱስ ባለ ጸጋ በርታ አማራጭ ትርጉሞች 1) "እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት በሰጣችሁ ጸጋ አማካኝነት ያበርታችሁ" (UDB) ወይም 2) " በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ብቻ የሚገኘው ጸጋን በማወቅ ራሳችሁን አበርቱ፣" ከብዙ ምስክሮች መካከል "የእኔ ቃላት እውነት ስለመሆናቸው ብዙ ሰዎች ምስክር ናቸው" ታማኝ "ታማኝ"

2 Timothy 2:3

2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡ 3-5
ከእኔ ጋር መከራን ተቀበል አማራጭ ትርጉም 1) "እኔ መከራን እንደሚቀበል መከራን ታገስ" (UDB) ወይም 2) "በእኔ ከራ ውስጥ ተካፈሉ" በራሱ ሕይወት ውስጥ የተዋጠ ወታደር ተገቢውን አገልግሎት መስጠት አይችልም "በሕይወቱ የእለት ተዕለት ተግባራት ውስጥ ብቁ ተሳታፊ የሆነ ወታደር ተገቢውን አገልግሎት መስጠት አይችልም" ወይም "ወታደሮች በግዳጅ ላይ ሲሆኑ ሰዎች በእለት ተዕለት ኑሮዋቸው በሚያደርጉት ነገር ሀሳባቸው አይሰረቅም።" የክርስቶስ አገልጋዮች የሕይወት የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ለክርስቶስ እንዳይሠሩ ሀሳባቸውን ሊሰርቅ አይገባውም። እንዳይታነቅ ሌሎች ነገሮችን በመሥራታቸው ምክንያት ከማገልገል የሚከለክል ነገር በመረብ እንደመያዝ ነው።፤ ከፍተኛ ባለስልጣን "ወታደር እንዲሆን የመለመለው ሰው" አንድ እስፖርተኛ . . . በሕጉ መሠረት ውድድሩን ካላካሄደ ሽልማትን አያገኝም የክርስቶስ አገልጋይ ክርስቶስ አድርጉ ያለውን ነገር ማድረግ ይጠበቅበታል። በሕጉ መሠረት ነገሮችን ማከናወን ካልቻለ ሽልማትን ማግኘት አይችልም አማራጭ ትርጉም: "አሸናፊ ሆኖ ሽልማትን ማግኘት የሚችለው በሕጉ መሠረት ውድድሩን ከፈጸመ ብቻ ነው" አይሸለምም "ሽልማቱን አያገኝም" በሕጉ መሠረት ካተወዳደረ "በሕጉ መሠረት ውድድሩን ካላጠናቀቀ" ወይም "ሕጉን በትክክል ካልተከተለ"

2 Timothy 2:6

2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡ 6-7
ጠንካራ ሠራተኛ የሆነው ገበሬም የሰብሉን ከሚበሉት የመጀመሪ ሊሆን ይገባዋል ይህ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የነገረው ሦስተናው ምሳሌያዊ ንግግር ነው። አንባቢያን አንድ መገንዘብ ያለባቸው ነገር የክርስቶስ አገልጋዮች ታታሪ ሠራተኞች መሆን አለባቸው። አሁን ስለሚናገረው ነገር አስቡ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ስእላዊ ምሳሌዎችን በመጠቀም ይነግረዋል ነገር ግን የእነዚህ ምስሎች ትርጉም ምን እንደሆነ ግን አይነግረውም። ስለ ክርስቶስ አገልጋዮች አንዚህም ምሳሌዎች በመጠቀም ጳውሎስ እየተናገረ ያለው ምን እንደሆነ ጢሞቴዎስ ራሱ ፈልጎ እንዲያገኝ ይተወዋል። ለጌታ "በጌታ ምክንያት"

2 Timothy 2:8

2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡ 8-10
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ለክርስቶስ እንዴት መኖር እንደሚቻል፣ ለክርስቶስ እንዴት መከራን መቀበል እንደሚቻል እና ሌሎች ለክርስቶስ እንዴት መኖር እንዳለባቸው መመሪያዎችን ይሰጠዋል። በእኔ ወንጌል መልዕክት መሠረት "የእኔ ወንዴል መልዕክ እንደሚለው" እኔ መከራን የሚቀበልበት ምክንያት "እኔ መከራን የሚቀበልለት" በሠልሰለት የታሰርኩት "መታሠር" የእግዚአብሔር ቃል አይታሠርም "አይወሰንም" ወይም "አይታሠረም።" አማራጭ ትርጉም: "ሙሉ ነጻነት አለው" ለተመረጡት ሰዎች "እግዚአብሔር ለመረጣቸው ሰዎች" ድነትን ያገኙ ዘንድ "ድነትን እንዲያገኙ" ከዘላለም ክብር ጋር "እግዚብሔርን ለዘላለም እያመሰገኑ" ወይም "ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር ለዘላለም እያመለከቱ"

2 Timothy 2:11

2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡ 11-13
ይህ አባባል "እነዚህ ቃላት" ሞቷል በዚህ ሥፍራ ላይ ይህ ቃል ያለው ትርጉም አንድ ለራሱ የሞተን ሰው ያመለክታል። ለራሱ መሻት ያልተገዛን ሰው ያመለክታል። እኛ ታማኞችን ካልሆንን "እኛ ብንወድቅ እንኳ" ወይም "እግዚአብሔር እንድናደረግ የሚፈልገው ነገር የሚናምነው ነገር ባናደርግ እንኳ" ራሱን ሊክድ ፈጽሞ አይቻለውም "እርሱ እንደ ባሕርይው ልፈጽም

የግድ ነው" ወይም "ከእርሱ ባሕርይ ተቃራኒ የሆነ ነገርን ለማድረግ አይችልም"

2 Timothy 2:14

2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡ 14-15
እነርሱ አማራጭ ትርጉሞች: 1) "መምህራን" (UDB) ወይም 2) "የቤተ ክርስቲያን ሕዝቦች" በእግዚአብሔር ፊት "በእግዚአብሔር መገኘት ውስጥ" ወይም "እግዚአብሔር ይመለከትሃል እንዲሁም ይመለከታቸዋ።" በቃላት አትጣሉ "በቃላት ትርጉም ላይ አትከራከሩ" ወይም "በቃላት ላይ አትጣሉ" ወይም "በቃላት ትርጉምልዩበት ለሌሎች ሰዎችን አትጉዱ" ምንም ትርፍ የለውም "ለማንም ምንም ጥቅም የለውም" ወይም "ጥቅም የለውም" ማበላሸት የሕንጻ ማፍረስ ምሳሌ ነው። ጥሉን የተመለከቱ ሰዎች የክርስትያኖችን መልዕክት ማክበር ያቆማሉ። የሚያደምጡ ሰዎች "የሚያደምጡ ሰዎች" ራስህን በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ያለው ለማድረግ ትጋ "የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ፥ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ።" እንደ ሠራተኛ "ልክ እንደ ሠራተኛ" ወይም "እንደ ሠራተኛ" በትክክለኛ መንገድ "በትክክል በማብራራት"

2 Timothy 2:16

2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡ 16-18
ቃሉ ልክ እንደ ጋንግሪን ይሠራጫል "የሚናገሩት ነገር ልክ እንደ በሽታ ይሰራጫል።" ጋንግሪን በሰው ሰውነት ውስጥ በፍጥነት እንደሚሰራጭ እና አካሉን እንደሚያጠፋ ሁሉ እነዚህ ሰዎች የሚናገሩት ነገር ከሰው ወደ ሰው በቀላሉ በመሰራጨት የሰሙትን ሰዎች እምነት ላይ ጉዳት ያደርሳል። አማራጭ ትርጉም፡ "ቃላቸው በፍጥነት ይሰራጫል እንዲሁም ልክ እንደ ጋንግሪን ከፍተኛ ጉዳት ያሳድራል" ወይም "የሚሉትን ነገር ሰዎች በፍጥነት ይሰሙታል እንዲሁም በዚህ ንግግር ይጎዳሉ። ጋንግሪን የሞተ፣ የበሰበበሰ ሥጋ። ጋንግሪን በሰውነት ውስጥ እንዳይሰራጭ እና ሰውዬውን እዳይገድለው ማድረጊያ ብቸኛው መንገድ የተበከለውን የሰውነት ክፍል ቆርጦ መጣል ነው። ከእውነት ርቀዋል ይህ እነዚህን ትርጉሞች ሊኖሩት ይችላል 1) "ስለ እውነት ተሳስተዋል" ወይም "ስለ እውነት በስህተት ውስጥ ናቸው፣" ዒላዋን እንደ ሳተ ቀስት ወይም 2) "በእውነት ማመን አቁመዋል።" ትንሳዔ ...ሆኗልd "እግዚአብሔር የሞቱ አማኞችን ወደ ዘላለማዊ ሕይወተ አስነስቷቸዋል" የአንዳንዶችን እምነት ይገለብጣሉ "የአንዳንድ አማኞቸን እምነት ጥርጣሬ ውስጥ ይጥላሉ" ወይም "አንዳንድ አማኞች ማመናቸውን እንዲያቆሙ በማሳመን"

2 Timothy 2:19

2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡ 19-21
የእግዚአብሔር መሠረት አማራጭ ትርጉሞች 1) "እግዚአብሔር ከመጀመሪያው አንስቶ የመሠረታት ቤተ ክርስቲያን" ወይም 2) "ስለ እግዚአብሔር ያለ እውነት" (UDB) ወይም 3) "የእግዚአብሔር ታማኝነት።" የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ "በክርስቶስ እንደሚያምኑ የሚነገሩ ሰዎች" ከእምነት ተለይተው የወጡ አማራጭ ትርጉም 1) "ክፉ መሆንን ማቆም" ወይም 2) "ትክክለኛ ያልሆነ ነገር ማድረግን ማቆም።" መሣሪያዎች ይህ ሰዎች ምግብ ዌም መጠጥ በውስጡ የሚያስቀምጡባቸውን ጎድጓዳ ሳህኖች፣ ሳህኖች እና ድስቶች መጠሪያነት የሚውል አጠቃላይ ቃል ነው። በቋንቋችሁ ከዚህ ጋር ተመሳሰይ የሆኑ አጠቃላይ ቃል ካሌለ ያለውን ተጠቀሙ። ይህ ለሰዎች በዚህ ሥፍራ ላይ ጥቅም ላይ የዋለ ምሳሌያዊ ንግግር ነው። ለክብር . . . ውርደት አማራጭ ትርጉሞች 1) "ልዩ ሁኔታዎች ...በተለመዱት ጊዜያት" (UDB) ወይም 2) "መልካም የሆኑ ሰዎች የሚያከናውኗቸው የተለያዩ ተግባራት...መልካም የሆኑ ሰዎች በድብቅ የሚያከናውነዋቻ ተግባራት።" ራሱን ለውርደት ጥቅም ለላይ ከመዋል ያነጻል አማራጭ ትርጉሞች 1) "ራሱን ከወራዳ ሰዎች ይለያል" ወይም 2) "ራሱን ንጹሕ ያደርጋል።" የተከበተ ዕቃ "በልዩ ሁኔታዎች ጠቃሚ የሆኑ" ወይም "መልካም ሰዎች በአደባባይ ለሚያደርጓቸው ነገሮች የሚጠቅሙ"

2 Timothy 2:22

2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡ 22-23
ሸሽ . . . ተከተል እነዚህ ምሳሌያዎ ንግግሮች የሚያመለክቱት በተቻለው ፍጥነት መሮጥን ነው። መሸሽ የሚያመለክተው ከሚጎዳ ነገር ማምለጥን ነው፤ መከታተለ ደግሞ መልካም የሆነ ነገር ለማግኘት የሚደረግ ጥረትን ያመለክታል። (ተመልከት:.) ከወጣትን መሻቶች ሸሽ ልክ ሰዎች ጥቃት ሊያደርስባቸው ከሚችል እንስሳት እንደሚሸሽ ሁሉ “ወጣቶችን ከሚፈታቱ ነገሮች ሽሽ"። በቋንቋችሁ “መሻት” የሚለው ቃል በስም ማስቀመጥ የማይቸል ከሆነ “ወጣቶች አዘውትረው ለማድረግ ከሚፈልጓቸው ነገሮች መሸሽ” በማለት መተርጎም ትችላላችሁ። ጽድቅን ተከታተሉ "ጽድቅን መፈለግ" ጋር አማራጭ ትርጉሞች 1) "ከ . . . ጋር" ትርጉሙ “ጽድቅን በመፈለግ ሂደት ውስጥ ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር በመተባበር" ወይም 2) "ከ . . . ጋር ሆናችሁ" ትርጉሙ “ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ሰላም ለመሆን የሚትችሉትን ሁሉ አድርጉ።" እነርሱ ወወደ ጌታ የሚጠሩት "ክርስትያኖች" ወይም "የጌታ ሰዎች ብለው ራሳቸውን የሚጠሩት ሰዎች" ከንጹሕ ልብ "በንጹሕ መነሻ ሀሳብ" ወይም "ለመልካም ምክንያቶች" የሞኝ እና ያላዋቂ ጥያቄዎችን የሞኝ እና የማያውቁ ሰዎችን ጥያቄዎችን መልስ አትስጥ" ሞኞች ... ጥያቄዎች "ለእግዚአብሔር ምንም ክብር ያሌላቸው ዎች የሚጠይቋቸው ጥያቄዎች" የማያውቁ ሰዎች ጥያቄዎች "እውነትን ማወቅ የማይፈልጉ ሰዎች የሚጠይቋቸው ጥያቄዎች"

2 Timothy 2:24

2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡ 24-26
ትዕግስት "ታጋሽ" ወይም "ትሁት" ማስተማር "ማስተማሪ" ወይም "ትምህርት መስጠት" ወይም "ማስተካከል" ንሰሓ እንዲሰጣቸው "ከኃጢአታቸው እንዲመለሱ" ለእውነት እውቀት ሲባል "እውነትን ያውቁ ዘንድ" ወደ አእምሮዋቸው ይመለሱ ዘንድ "ከእንግዲህ ወዲህ ትክክለኛ ያልሆነ ነገርን እንዳያስቡ" ወይም "እንደገና ስለ እግዚአብሔር ማሰብ ይጀምሩ ዘንድ" የዳቢሎስ ወጥመድ ይህ ምሳሌያዊ ንግግር የሚያመለክተው በትክክለኛው መንገድ ሴጣንን እየተከተሉ ሳለ እግዚብሔትን የሚከተሉ ለሚመስላቸው ሰዎች ነው። ለእርሱ ፈቃድ ሲባል በእርሱ የተያዙ ሰዎች "የያዛቸው ሰዎች እና አሁን እርሱ የሚፈልገውን ነገር ሁሉ እንዲሠሩ የሚያደርጋቸው"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 3

1 ነገር ግን ይህን እወቅ፣ በመጨረሻዎቹ ቀናት አደገኛ ዘመን ይመጣል። 2 ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉ፣ ገንዘብን የሚወዱ፣ ትእቢተኞች፣
ትምክህተኞቸ፣ በእግዚአብሔር ላይ የስድብን ቃል የሚናገሩ፣ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፣ የማያመሰግኑ፣ ቅድስና የሌላቸው፣ 3 ተፈጥሮአዊ ፍቅር የሌላቸው፣
ሰላምን የማይፈጥሩ፣ ሐሜተኞች፣ ራሳቸውን የማይገዙ፣ አመጸኞች፣ መልካም የሆነውን የማይወዱ፣ 4 ከዳተኞች፣ ምክርን የማይሰሙ፣ በትእቢት የተነፉ፣
ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ። 5 እግዚአብሔርን የመምሰል መልክ አላቸው ነገር ግን ኃይሉን ይክዳሉ፣ ከእነዚህ ሰዎች ራቅ። 6 ከእነዚህም
አንዳንዶች በቤተ ሰብ ውስጥ ሾልከው እየገቡ በኃጢአት የሚገረሙትንና በልዩ ልዩ ምኞትም የሚነዱትን ሞኞችን ሴቶች ይማርካሉ። 7 እነዚህ ሴቶች ሁል ጊዜ
አዳዲስ ነገሮችን ለመማር ይሞክራሉ፣ ነገር ግን ፈጽሞ ወደ እውነት እውቀት ሊደርሱ አይችሉም። 8 ኢያኔስ እና ኢያንበሬስ ሙሴን እንደተቃወሙት፣ እነዚህ
የስህተት አስተማሪዎች እውነትን ይቃወማሉ። እነዚህ ሰዎች አዕምሮአቸው የተበላሸባቸው፣ የእምነታቸውም እውነተኝነት ያልተረጋገጠ ነው። 9 ዳሩ ግን የእነዚያ
የሁለቱ ሰዎች ሞኝነት እንደተጋለጠ፣ እነዚህም ሞኝነታቸው ይገለጣልና አይሳካላቸውም። 10 አንተ ግን ትምህርቴን፣ አካሄዴን፣ ዓላማዬን፣ እምነቴን፣ መጽናቴን፣
ፍቅሬን፣ ትእግስቴን፣ 11 ስደቴን፣ መከራዬን፣ በአንጾኪያ፣ በኢቆንዮን እና በልስጥራን የደረሰብኝን ሁሉ ተከትለሃል። ይህን ሁሉ ስደት በጽናት አልፌዋለሁ፣ ጌታም
ከሁሉ አዳነኝ። 12 በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔር እንደሚወደው ሊኖሩ የሚፈልጉ ሁሉ ይሰደዳሉ። 13 ከፉ ሰዎች እና አታላዮች በክፋት እየባሱ ሌሎችንም
እያሳቱና ራሳቸውም ችየሳቱ ይሄዳሉ። 14 አንተ ግን በተማርህበትና በምታምንበት ነገር ጸንተህ ኑር፣ ከማን እንደተማርከው ታውቃለህና። 15 ከሕፃንነትህ ጀምሮ
በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን ስለሚገኘው መዳን ጥበብ ሊሰጡህ ስለሚችሉት ቅዱሳት መጻሕፍት አውቀሃል። 16 በእግዚአብሔር የተገለጡ ቅዱሳት መጻሕፍት
ሁሉ ለመሠረተ እምነት፣ በእምነትም ለመጽናት፣ በጽድቅም ላለው ምክር ይጠቅማሉ፣ 17 በመሆኑም የእግዚአብሔር ሰው ለመልካም ሥራ የተዘጋጀ እና
የታጠቀ እንዲሆን ያደርጉታል።

---

2 Timothy 3:1

2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡ 1-4
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ በመጨረሻው ዘመን ሰዎች በእውነት ላይ ፊታቸውን እንደሚያዞሩ ጢሞቴዎስ እንዲያውቅ ፈልጓል እንዲሁም ስደት እንደሚመጣም እንዲያውቅ ፈልጓል ይሁን እንጂ በዚህ ሁሉ ውስጥ በእግዚአብሔር ቃል ላይ መደገፍ ይችላል። በአደገኛ ጊዜያት ይህ ክርስትያኖች አደገኛ ሁኔታ ውስጥ የሚሆኑባቸውን ቀናትን፣ ወራትን ወይም እንዲያውም ዓመታትን ሊያመለክት ይችላል። የእነርሱ ወዳጆች በዚህ ሥፍራ ላይ “ወዳጆች” የሚለው ቃል ትርጉሞ ወንድማዊ ፍቅር ወይም የጓደኛ ፍቅር ወይም የቤተሰብ አባላት ፍቅር ሊሆነ ይችላል፡ በተፈጥሮአዊ ሰው መካከል ያለ የጓደኛማቾች ወይም የዘመዳማቾች ፍቅርም ሊሆን ይችላል። ይህ ከእግዚአበብሔር ዘንድ የሚመታውን ዓይነት ፍቅር አይደለም። መመካት ስለ ራሱ በኩራት የሚናገር ሰው። ከተፈጥሮአዊ ፍቅር ውጪ "ቤተሰባቸውን የማይወዱ" የማይስማሙ "ከማንም ጋር የማይስማሙ" ወይም "ከመማንም ጋር በሰላም የማይኖሩ" ተሳዳቢቢዎች "በሐሰት የሚከሱ" ተደባዳቢዎች "ግልፍተኞች" ወይም "ሌሎች ሰዎችን የሚጎዳ ነገር ብዙ ጊዜ የሚያደርጉ" መልካም ነገር የማይወዱ "መልካ ነገር የሚጠሉ"

ከዳተኞች "የማይታመኑ" ችኩሎች "ከሌሎች ሰዎች እነርሱ የተሻሉ እንደሆኑ የሚያስቡ"

2 Timothy 3:5

2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡ 5-7
የአምልኮ መልክ ያላቸው "ሃይማኖተኛ የሚመስሉ" ወይም "ቅዱሳን የሚመስሉ " ወይም "መልካም የሚመስሉ" ኃይሉን ግን ክደዋል አማራጭ ትርጉሞች 1) "እግዚአብሔር በእውነት ሊሰጣቸው የሚፈልገውን ኃይል ለመቀበል ፈቃደኞች አይደሉም" (UDB) ወይም 2) "አለን ብለው የሚናገሩትን መልካምነት በሕይወታቸው ውስጥ አይታይም።" ከእነዚህ ራቅ "ራቅ" ሾልከው ከገቡት "ሾልከው ወደ . . . ከገቡት" ወደ ቤት አማራጭ ትርጉም 1) "ቤተሰብ" ወይም "በቤት ውስጥ የሚኖሩ ቤተሰብ" ወይም 2) “ቤት” ቁሳዊ (UDB). መማረክ "ተጽእኖ ለማድረግ ኃይል ያላቸው" ሞኝ ሴቶችን "በመንፈሳዊ ነገር ደካሞች የሆኑ ሴቶችን።" ይህ የሆነበት ምክንያት እግዚአብሔርን ለመምሰል ባለመስራታቸው ወይም ሥራ ፈቶች በመሆናቸው ምክንያት ወይም “በኃጢአት በመዋጣቸው” ምክንያት ሊሆን ይችላል። በኃጢአት የተዋጡት አማራጭ ትርጉሞች 1) "በብዙ ኃጢአት የተዋጡት" ወይም 2) "ብዙ ጊዜ ኃጢአት የሚያደርት ሰዎች።" ሀሳቢ ኃጢአት ለማድረግ ለማቆም አልቻሉም። በተለያዩ መሻቶች ተመርተው የተወሰዱት አማራጭ ትርጉም: "እነዚህ ሴቶች ሌሎች ብዙ መሻቶች አሏቸው ስለዚህም ክርስቶስን መታዝ አቁመዋል። ወይም "እነዚህ ሴቶች ክርስቶስን መታዘዝነአቁመዋል ይልቁንም ብዙ መሻታቸውን መከተል ጀምረዋል።" እውቀት የዚህ ቃል ትርጉሚ ስለ አንድ ሰው የሚታውቀው ያንን ሰው ለብዙ ጊዜ በጥንቃቄ ስትከታተለው ነው።

2 Timothy 3:8

2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡ 8-9
ኢያኔስና ኢያንበሬስም እነዚህ ሁለት ስሞች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙት በዚህ ሥፍራ ላይ ብቻ ነው። አንድ ትውፊት እነዚህ ሰዎች በዘጸአት 7-8 ውስጥ የተጠቀሱት ሙሴን የተቃወሙት ግብጻዊያን ምትሃተኞች እንደሆኑ ይናገራል። (ተመልከት:.) ተቃወሙት "ተቃወሙት" ስለዚህም "በተመሳሳይ መልኩም" እውነት "የኢየሱስ ወንጌል" በአእምሮ የተበከሉ "ከእንግዲህ በትክክል ማሰብ የማይችሉ" ከፊት ይልቅ "በተሻለ" ሞኝነት "የመረዳት ችግር" ወይም "ሞኝ" የታወቀ "በቀላሉ የሚታይ" ወይም "በቀላሉ የሚታወቅ"

2 Timothy 3:10

2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡ 10-13
ነገር ግን አንተ ተከታተላቸው "ይሁን እንጂ አንተ በጥንቃቄ ተመልከት" ትምህርት "መመሪያ" ተግባር "የሕይወት መንገድ" ዓላማ "መፍትሔ" ወይም "ውሳኔ" መከራን መቋቋም "ከሰዎች ጋር መታገስ" ትዕግስት አማራጭ ትርጉሞች 1) "ከባድ በሆነበት ጊዜ እንኳ ሳይቀር እግዚአብሔርን አገለግላለሁ" (UDB) ወይም 2) "በከባድ ሁኔታዎች ውስጥ እንኳ ትክክለኛ አመለካከትን እጠብቃለሁ።" መታደግ "መዳን" ፈለገ "መሻት" አታላዮች "ስለራሳቸው ሌሎች ሰዎችን የሚያሳስቱ ሰዎች" ወይም "ከሆኑት ውጪ ሌላ እንደሆኑ የሚያስመስሉ ሰዎች"

2 Timothy 3:14

2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡ 14-15
በተማሪከው ነገር ቀጥል "የተማርከውን ነገር አትርሳ።" ጠቢብ እንዲትሆን የሚያደርጉህ ቅዱሳት መጻሕፍት "የእግዚአብሔር ቃል የሚያስፈልግህን ሁሉ ጥበብ ይሰጡሃል" በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት የሚገኘውን ድነት "እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያለህን እምነት አንተን ለማዳን እንዲጠቀምበት።” ድነት አማራጭ ትርጉም 1) "እግዚአብሔር ዘላለማዊ ሕይወትን ይሰጥሃል" ወይም 2) "እግዚአብሔር በዚህች ሕይወት ውስጥ ካለ ሞኝነት ያድንሃል።"

2 Timothy 3:16

2ኛ ጢሞቴዎስ **3**፡ **16**-**17**
ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ በእግዚአብሔር እስትንፋስ የተጻፉ ናቸው "እግዚአብሔር ቅዱሳት መጽሐፍትን ሁሉ በመንፈሱ አማካኝነት ተናግሯቸዋል።" (UDB) ወይም "ቅዱሳት መጽሐፍት ሁሉ የእግዚአብሔር እስትንፋስ አለባቸው። ሰዎች ምን መጻፍ እንዳለባቸው እግዚአብሔር ነግሯቸዋል። ጠቃሚዎች ናቸው "ይጠቅማሉ" ወይም "ጠቃሚዎች ናቸው" ለተግሳጽ "ሰስህተትን ለማቅናት" ለማስተካከል "ስህተትን ለማስተካከል" ለማሰልጠን "ለማለማመድ" ወይም "ለማሳደግ" ሙሉ ሰው ለማድረግ "ለመሙላት"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 4

1 በእግዚአብሔር ፊት፣ በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ ባለው በክርስቶስ ኢየሱስ ፊት፣ በመገለጡና በመንግስቱ፣ አዝዝሃለሁ፣ **2** ቃሉን ስበክ ሲመችህም ሳይመችህም የተዘጋጀህ ሁን። እየታገስክና እያስተማርክ ዝለፍ፣ ገስጽ፣ ምከርም። **3** ሰዎች እውነተኛውን ትምህርት የማይታገሱበት ዘመን ይመጣል፣ ይልቁን፣ ለፍላጎታቸው የሚስማማቸውን የሚሰብኩአቸውን አስተማሪዎችን በዙሪያቸው ይሰበስባሉ። ይህም ጆሮቻቸውን የሚያሳክክላቸው ይሆናል። **4** ጆሮቻቸውን እውነትን ከመስማት ይመልሳሉ፣ ወደ ስህተትም ያዘነብላሉ። **5** አንተ ግን፣ በነገር ሁሉ የነቃህ ሁን፣ መከራን ተቀበል፣ የወንጌላዊነትን ሥራ አድርግ፣ አገልግሎትህንም ፈጽም። **6** እኔ እንደ መስዋዕት ልሰዋ ነው። የምሄድበትም ጊዜ ደርሶአል። **7** መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ፣ ሩጫውን ጨርሼአለሁ፣ እምነቱንም ጠብቄአለሁ። **8** የጽድቅም አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፣ ይህንንም ጻድቅ ፈራጅ፣ የሆነው ጌታ፣ በዚያን ቀን ለእኔ ያስረክባል፣ ለእኔ ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን መገለጡን ለሚወዱ ሁሉ ነው። **9** ወደ እኔ በቶሎ ልትመጣ ትጋ፣ **10** ዴማስ ትቶኛልና፣ ይህንንም ዓለም ወድዶ ወደ ተሰሎንቄ ሄዶአል። ቄርቂስ ወደ ገላትያ፣ ቲቶም ወደ ድልማጥያ ሄደዋል። **11** ሉቃስ ብቻ ከእኔ ጋር አለ። ማርቆስን ይዘኸው ና እርሱ በሥራው እጅግ ይጠቅመኛል። **12** ቲኪቆስን ወደ ኤፌሶን ልኬዋለሁ። **13** ስትመጣ በጢሮአዳ የተውኩትን ልብሴን፣ ይልቁንም በብራና የተጻፉትን መጻሕፍት ይዘህልኝ ና። **14** መዳብ አንጥረኛው አሌክሳንደር እጅግ ከፋብኝ። ጌታ ስለ ክፉ ሥራው ዋጋውን ይከፍለዋል። **15** አንተም ደግሞ ከእርሱ ተጠበቅ፣ ቃላችንን እጅግ ተቃውሞአልና። **16** በፊተኛው የፍርድ ቤት ክርክሬ ከአኔ ጋር ማንም አልቆመም፣ ነገር ግን ሁሉም ተዉኝ። ይህንንም አይቁጠርባቸው። **17** ነገር ግን፣ አሕዛብ ሁሉ እንዲሰሙት፣ የወንጌሉ ስብከት በእኔ እንዲፈጸም፣ ጌታ በአጠገቤ ቆሞ አበረታኝ፣ ከአንበሳም አፍ ዳንኩኝ። **18** ጌታ ከክፉ ሥራዎች ሁሉ አውጥቶኛል፣ ለሰማያዊውም መንግሥቱ ይጠብቀኛል። ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን። አሜን። **19** ለጵርስቅላና ለአቂላ ለሄኔሲፎሩ በተ ሰብ ሰላምታ አቅርብልኝ። **20** ኤርስጦስ በቆሮንቶስ ቀረ፣ ነገር ግን ጥሮፊሞስ ስለታመመ በሚሊጢን ተውኩት። **21** ከክረምት በፊት ልትመጣ ትጋ። ኤውግሎስና ጱዴስ፣ ሊኖስና ቅላውዲያም ወንድሞች ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡልሃል። **22** ጌታ ከመንፈስህ ጋር ይሁን። ጸጋ ከአንተ ጋር ይሁን። አሜን።

---

2 Timothy 4:1

2ኛ ጢሞቴዎስ **4**፡ **1**-**2**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ጢሞቴዎስ ታማኝ ሆነ እንዲቀጥል ያሳስበዋ እንዲሁም ጳውሎስ ለመሞት ዝግጁ እንደሆነ ያስረዳዋል። በእግዚአብሔር እና በክርስቶስ ኢየሱስ ፊት "በእግዚአብሔር እና በክርስቶስ ኢየሱስ መገኘት ውስጥ። እንዴት UDB ይህንን ዓረፍተ ነገር ጥቅም ላይ እንዳዋለው እና እንዳስተካከለው ተመልከት። ልፈረድ ያለው "በቅርቡ ለመፍረድ የሚመጣው" አጥብቀህ "ጠንከር አድርገህ" ወይም "ጫን ብለህ" ወይም "በእያንዳንዱ ቃል ትርጉም" ይህ ሳይሆን ሲቀር "ይህ ተስማሚ ሳይን ሲቀር" ዝለፍ "ሰዎች በደለኞች ሲሆኑ ንገራቸው" ወይም "ሰዎች የሰሩት ስህተት ምን እንደሆነ አስታውቃቸው" ገስጽ "አስጠንቅቅ" በጽናት አስተምር አማራጭ ትርጉሞች 1) ይህ ጢሞቴዎስ እንዴት ሰዎችን ያበረታታ እንደነበር ያሳያለል ወይም 2) ይህ ጢሞቴዎስ እንዴት ማስተማር እንዳለበት ያሳያል ወይ 3) ይህ ጢሞቴዎስ በመጨረሻው ዓረፍተ ነገር ውስጥ ሁሉን ነገር እንዴት ማድረግ እንዳለበት ያሳል። በጽናት "በትዕግስት" በጽናት ሁሉ "በታላቅ ጽናት" ወይም "በጣም በመታገስ"

2 Timothy 4:3

2ኛ ጢሞቴዎስ **4**፡ **3**-**5**
ጊዜ ይመጣልና "ለወደፊት . . . ጊዜ ይመጣልና" ሰዎች አውዱ እንደሚያሳየው እነዚህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ሰዎች ናቸው (UDB)። ትክክለኛ ትምህርት ይህ አጠቃላይ ቤተ ክርስቲያን እውነተኛ እና ትክክለኛ ብላ የሚትቀበለው ማለት ነው። ከእነርሱ ፍላጎት ጋር ተስማሚ የሆነ ትምህርትን ከሚያስተምህሩ መምህራን ጋር ይሆናሉ። በዚህ መልኩ ጆራቸውን ያኩላቸዋል። አማራጭ ትርጉሞች 1) ከግል ፍላጎታቸው የተነሣ ለመስማት የሚፈልጉትን ነገር በሚነግሯቸው መምህራን ዙሪያ ይሰበሰባሉ። ወይም 2) ከእነርሱ የግል ፍላጎት ጋር ከሚስማሙ መምህራን ዙሪያ ይሰበሰባሉ እነርሱም የሚፈልጉትን በጆሮዋቸው ይነግሯቸዋል። ለራሳቸው መሻት "የግል ፍላጎታው" ጆሮዋቸውን ያኩላቸዋል "እነዚህ መምህራን ጆሮዋቸውን ያኩላቸዋል።" "ጆሮዋቸውን ማከክ" ምሳሌያዊ አነጋገር ሲሆን የሚያሳየው መስማት የሚያስደስታቸውን ፣ ደስተኞች እንደሆኑ የሚያደርጋቸውን ነገር መናገር ማለት ነው። የወንጌላዊነት ሥራ ይህ ማለት ኢየሱስ ማን እንደሆነ፣ ለእነርሱ ምን እንዳደረገ እና ለእርሱ እንዴት መኖር እንዳለባቸው ለሰዎች መናገር ማለት ነው። አገልግሎት ስለ እግዚአብሔር እነርሱን በማስተማር እነርሱን በመንሳዊ ነገር ማገልገል ማለት ነው።

2 Timothy 4:6

2ኛ ጢሞቴዎስ **4**፡ **6**-**8**
ከአንተ የሚለይበት ጊዜ ተቃርቧል "በቅርቡ እሞታለሁ፣ ይህችንም ምድር ትቼ እሄዳለሁ" (UDB)። ጳውሎስ ከእንግዲህ በኋላ ለረጅም ጊዜ እንደማይኖረ አውቆዋል። ሩጫዬን በተገቢው ሁኔታ አጠናቅያለሁ ይህ የድብድብ፣ የትግል ወይም የቡጥ እስፖርታዊ ምሳሌ ነው። ጳውሎስ የሚችለውን ሁሉ አድርጓል። ይህ “የሚችለውን ሁሉ ጥረት አድርጌያለሁ” ወይም “ያቅሜን ያህለ አድርጌያለሁ” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ሩጫዬን ጨርሻለሁ ይህ ምሳሌያዊ ንግግር የሚያሳየው በሩጫ ውድድር ላይ የመጨረሻ መስመር ላይ መድረስን ከሕይወት ፍጻሜ ጋር በማነጻጸር ነው። አማራጭ ትርጉም: “ማድረግ የሚገባኝነት ነገር ጨርሼያለሁ። እምነትን ጠብቄያለሁ አማራጭ ትርጉሞች 1) "የሚናምነውን ነገር ከስህተት ጠብቄያለሁ" ወይም 2) "አገልግሎቴን በታማኝነት ጨርሼያለሁ" (UDB). የጽድቅ አክልል ለእኔ ተቀምጦልኛል አማራጭ ትርጉም: "የትድቅ አክልል ይሰጣኛል" የጽድቅ አክሊል አማራጭ ትርጉሞች 1) አክሊል እግዚአብሔር በትክክለኛ መንገድ ለኖሩ ሰዎች የሚሰጠው ሽልማት ነው። (UDB) ወይም 2) አክሊል ለጽድቅ ምሳሌ ነው። የውድድር ዳኛው ለአሸናፊው አክሊል እንደሚሰጠው ሁሉ ጳውሎስ ሕይወቱን አጠናቆ ሲሄድ እግዚአብሔር ጳውሎስን ጸድቅ ብሎ ይጠራዋል። አክሊል የሩጫ ውድድርን አሸንፈው ለሚገቡ ሮሯጮች የሚሰጥ ከወይራ ቅጠል የሚሠራ አክሊል ነው። በዚያ ቀን "ጌታ ዳግም በሚመጣት ቀን" ወይም "እግዚአብሔር ሕዝቡ ላይ በሚፈርድበት ቀን"

2 Timothy 4:9

2ኛ ጢሞቴዎስ **4**፡ **9**-**10**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: በመዝጊያውም ጳውሎስ ጢሞቴዎስ ወደ እርሱ ዘንድ እንዲመጣ ያበረታታዋል። እንዲሁም ሉቃስንም ከእርሱ ጋር ይዞት እንዲመጣ፣ ከጌታ ፊታቸውን ያዞሩ ሰዎችን ስም ዝርዝር ይነግራል በመጨረሻም ከጢሞቴዎስ ጋር ላሉት ሰዎች ሰላምታውን እንዲያቀርብለት ይጠይቀዋል። በፍጥነት "በተቻለ ፍጥነት" ምክንዬት ስለዚህ አሁን ያለችው ዓለም አማራጭ ትርጉሞች 1) የዚህ ዓለም ጊዜያዊ ነገር፣ "የዚህች ዓለም ምኞት እና ደስታ፣" ወይም 2) አሁን ያለው ሕይወት እና መሞት የሚሻለው። ዴማስ ከጳውሎስ ጋር ከቆየሁ ይገሉኛል ብሎ ፈርቶ ሊሆነ ይችላል።

ቄርቂስም ወደ ገላትያ ቲቶም ወደ ድልማጥያ ሄደዋል፤ እነዚህ ሁለት ሰዎች ጳውሎስን ትተውት ደዋል ነገር ግን ጳውሎስ እነዲህም ልክ እንደ ዴማስ “ይህንን ዓለም ወደዋል” እያለ አይደለም።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

2 Timothy 4:11

2ኛ ጢሞቴዎስ **4**፡ **11**-**13**
እርሱ በሥራ ለእኔ አጋዥ ነው አማራጭ ትርጉሞች 1) "በአገልግሎት ሊያግዘኝ ይችላል" ወይም 2) "እኔን በመርዳት ሊያገለግለኝ ይችላል።"

2 Timothy 4:14

2ኛ ጢሞቴዎስ **4**፡ **14**-**16**
በእኔ ላይ መጥፎ ነገር አድርጓል "ክፉ ነገር አድርጎብኛል" ወይም "ጎድቶኛል" አንተም ተጠንቀቀው "አንተም ቢትሆን እርሱን ልትጠነቀቅ ይገባሃል" ወይም "ከእርሱ ራስህን ጠብቅ" ወይም "ከእርሱ ራስህን ጠብቅ" እርሱ . . . እርሱ . . . እርሱ . . . እርሱ ሁሉም የሚያመለክቱት እስክንድሮስ ነው። የምንናገረውን እጅግ ተቃውሞአልና። "መልዕክታችንን ለመቃወም በከፍተኛ ሁኔታ ተነሥቷል" ወይም "መልዕክታችንን ይቃወማል" ከእኔ ጋር የቆመ አንዳችም ሰው የለም ሁሉም ትተውኝ ሄደዋል "ከእኔ ጋር የቆ ማንም ሰው የለም ይልቁንም ሁሉም ትተውኝ ሄደዋል።" ይህንም አይቀጠርባቸው፤ "እነዚህ አማኞች እኔን ለብቻዬ ትተውኝ በመሄዳቸው እግዚአብሔር እንዲቀጣቸው አልፈልግም"

2 Timothy 4:17

2ኛ ጢሞቴዎስ **4**፡**17**-**18**
ከእኔ ጋር ቁም "እኔን ለማገዝ ከእኔ ጋር ቁም" የስብከቱ ሥራ በእኔ እንዲፈጸም አሕዛብም ሁሉ እንዲሰሙት አማራጭ ትርጉሞች 1) ይህ እየሆነ ያለ ነገር ነው (UDB) ወይም 2)ይህ ለጳውሎስም ቢሆን ለወደፊት የሚሆን ነገር ነው፣ "ቃሉን ሙሉ ለሙሉ መናገር እችል ዘንድ እና አሕዛብ ሁሉ ይሰሙ ዘንድ።" ከአንበሳ አፍም ዳንሁ። ይህ አደጋ አካላዊ፣ መንፈሳዊ ወይም ሁለቱም ልሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡ "ከታላቅ አደጋ ተረፍኩኝ።"

2 Timothy 4:19

2ኛ ጢሞቴዎሰረ **4**፡ **19**-**22**
ኖት የለውም።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Titus

Titus

ምዕራፍ 1

1 የእግዚአብሔር ባሪያና፣የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ የሆነው ጳውሎስ፣ በእግዚአብሔር የተመረጡት ሰዎች እምነት እንዲጸና፣ እግዚአብሔርን ከመምሰል ጋር
የሚስማማውን የእውነት እውቀት ለማፅናት፣ **2** የማይዋሸ እግዚአብሔር፣ በተረጋገጠ ዘላለማዊ ሕይወት ከዘመናት በፊት ተስፋን ሰጠ፣ **3** እንደ መድሃኒታችን
እግዚአብሔር ትዕዛዝ፣ በትክክለኛው ጊዜ፣ ቃሉን ለእኔ አደራ በሰጠኝ መልዕክት ገለጠ። **4** የጋራችን በሆነ እምነት እውነተኛ ልጄ ለሆነ ለቲቶ። ከእግዚአብሔር
አብ፣ከመድሃኒታችን ክርስቶስ ኢየሱስ ፀጋ፣ምህረትና ሰላም ለአንተ ይሁን። **5** አንተን በቀርጤስ የተውኩበት ምክንያት፣ ያልተጠናቀቁትን ነገሮች
እንድታስተካክልና፣ በነገርኩህ መሠረት በየከተማው ሁሉ ሽማግሌዎችን እንድትሾም ነው። **6** የቤተክርስቲያን ሽማግሌ፣ ነቀፋ የሌለበት፣የአንዲት ሚስት ባል፣
ከክፍዎችና ካልታረሙ ጋር ስማቸው የማይነሳ ታማኝ ልጆች ያሉት ሊሆኑ ይገባዋል። **7** የቤተክርስቲያን ሽማግሌ የእግዚአብሔርን ቤት የሚያስተዳድር መሪ
ስለሆነ ነቀፋ የሌለበት፣ የማይጮህ፣ራሱን የሚገዛ ፣የማይቆጣ ፣ለወይን ጠጅ የማይገዛ፣ የማይጣላና ስስታም ያልሆነ ሊሆን ይገባል። **8** ነገር ግን እንግዳ
ተቀባይ፣ መልካምን የሚወድ፣ ጠንቃቃ፣ ጻድቅ፣ መንፈሳዊና ራሱን የሚገዛ መሆን አለበት። **9** በጤናማ ትምህርት ሌሎችን ለማበረታታት፣ የሚቃወሙትን
ለመገሠጽ እንዲችል እውነተኛውን ትምህር አጥብቆ መያዝ ይኖርበታል። **10** ሥርዓት የሌላቸው በተለይም ከተገረዙት ወገን የሆኑ ብዙዎች አሉ። ቃላቸው ከንቱ
ነው። ሰዎችን ያስታሉ፣ በተሳሳተ መንገድም ይመራሉ። **11** እነዚህን ዝም ማሰኘት ይገባል። ለነውረኛ ትርፍ ብለው ማስተማር የማይገባቸውን እያስተማሩ፣ መላ
ቤተሰብን ያፈርሳሉ። **12** ከነሱ ከራሳቸው ነብያት መካከል አንዱ፣ "የቀርጤስ ሰዎች ዘወትር ውሸተኞች፣ ክፉና አደገኛ አውሬዎች፣ ሰነፍ ሆዳሞች ናቸው"
ብሏል። **13** ይህም አባባል ትክክል ነው፣ ስለዚህ ጤነኛ እምነት እንዲኖራቸው አጥብቀህ ገሥጻቸው ። **14** ጊዜያቸውን በአይሁድ ተረትና፣ ከእውነት በራቁ
ሰዎች ትዕዛዛት ላይ አያባክኑ። **15** ንጹሆች ለሆኑት፣ ሁሉም ንጹህ ነው፣ ለርኩሶችና ለማያምኑ ግን ንጹህ የሆነ ምንም የለም። ይልቁን፣ አዕምሯቸውና ሃሳባቸው
እንኳ የረከሰ ነው። **16** እግዚአብሔር እንደሚውያቁ ይናገራሉ፣ በሥራቸው ግን ይክዱታል። የሚያስጸይፉ የማይታዘዙና፣ ለመልካም ስራም የማይበቁ ናቸው።

Titus 1:1

ቲቶ **1**፡ **1-3**
ጳውሎስ በአማርኛ ቋንቋ ጳውሎስ የሚለው ስም የሰፈረበት ምክንያት ጳውሎስ የመጽሐፉ ጸሐፊ መሆኑን ለማስተዋወቅ ነው። አት ፡ "ይህን ደብዳቤ የጻፍኩት፣እኔ፣ ጳውሎስ " የእግዚአብሔር ባሪያና የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ የሆንሁ በዚህ መስመር ውስጥ “የሆንሁ” የሚለው ሐረግ “እኔ ነኝ” ብሎ ብሎ ለማመላከት ነው። አት AT: "እኔ የእግዚአብሔር አገልጋይና እና የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋሪያ ነኝ” . እምነት እንዲሆንላቸው አትAT: "እንዲታነጹ ለማድረግ " በእግዚአብሔር ለተመረጡት "እግዚአብሔር የመረጣቸው ሰዎች " እንደ አምልኮት ያለውን እውነት "ከእግዚአብሔር ህግ ጋር የሚስማማ እውነት"ወይም "ለቅዱሳን ምልካም የሆነ እውነት " የማይዋሸ "በፍጹም ሐሰትን የማይናገር" ከዘላለም ዘመናት በፊት "ጊዜ ከመጀመሩ በፊት" በዘመኑም ጊዜ፣ "በተገቢው ጊዜA" ለእኔ አደራ በተሰጠኝ ስብከት አት “ቃሉን እንዳውጅ ለእኔ አደራ ተሰጥቶኝ ነበር" ወይም " እንድሰብክ ሀላፊነት ተሰጠኝ " መድኃኒታችን እግዚአብሔር "ያዳነን እግዚአብሔር " (UDB)

Titus 1:4

ቲቶ **1**፡ **4-5**
እውነተኛ ልጄ ቲቶ የጳውሎስ የስጋ ልጁነው ማለት አይደለም። አት ፡ "አንተ ለእኔ ልክ እንደ ልጄ ነህ " (UDB) በሃይማኖት ኅብረት our common faith አት " ሁለታችንንም በምንጋራው በክርስቶስ ላይ ባለን ተመሳሳይ እምነት "ወይም " ሁለታችንም በምናምነው ተመሳሳይ ትምህርት " ጸጋና ፤ምሕረት፤ ሰላምም ይሁን ይህ በጣም የተለመደ የሰላምታ አሰጣጥ ነው። አት: "ጸጋ፤ ምሕረት እና ሰላም ለእናንተ ይሁን" ወይም "መልካምነትን፤ ምሕረትን እና ሰላም በውስጣችሁ ሁኖ ተለማመዱት " ከመድኃኒታችንም ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ Christ Jesus our Savior "ያዳነን ክርስቶስ ኢየሱስ " ስለዚህ ምክንያት አት ፡ "ምክንያቱ ይህ ነው " በቀርጤስ ተውሁህ፤ አት "በቀርጤስ እንድትቆይ ነገርኩህ " የቀረውን እንድታደራጅ "መስተካከል የሚገባቸው ነገሮች አስተካክለህ እንድትጨርስ " ሽማግሌዎችን እንድትሾም ordain elders "ለሽማግሌዎች ሐላፊነትን እንድትሰጥ " (UDB) ወይም "ሽማግሌዎችን እንድትሰይም " ሽማግሌዎች በጥንቷ ቤተክርስቲያን ለአማኞች ጉባኤ መንፈሳዊ አመረር ይሰጡ የነበሩት ክርስቲያን ሽማግሌዎች ነበሩ።

Titus 1:6

ቲቶ **1**፡ **6-7**
የሽግግር ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ለቲቶ በቀርጤስ ደሴት ላይ በሚገኙ በሁሉም ከተሞች ውስጥ ሽማግሌዎችን እንዲሾም አዞታል አሁን ጳውሎስ ስለሚሾሙት ሽማግሌዎች መስፈርትን ይሰጣል የማይነቀፍ ሽማግሌ አትAT: "መልካም ስም ያለው” የአንዲት ሚስት ባል የሚሆን፥ የተለያዩ አብያተክርስቲያናት ከዚህ በፊት ሚስቱ ስለሞተችበት ሰው፤ ሚስቱን ስለፈታ እና በጭራሽ ያላገቡ ሰዎች ወደ አመራር ስለሚመጡበት ሁኔታ የተለያየ አቋም አላቸው። የሚያምኑም ልጆች ያሉት፥ አማራጭ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት 1) በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ልጆች ወይም 2) ታማኝ የሆኑ ልጆች የማይነቀፍ ሊሆን ይገባዋልና "የማይታወቅ " ወይም "ስሙ በዚህ መልክ የማይነሳ " ስለ አለመታዘዝ undisciplined "አመጸኛነት” ወይም "የእግዚአብሔርን ህግ የማይከተል" ሊሆን ይገባዋልና፤ አት: "ኤጲስ ቆጶስ በግድ መሆን ያለበትAn overseer must" እንደ እግዚአብሔር መጋቢ፥ "የእግዚአብሔር ባለአደራ" ወይም "ለእግዚአብሔር ቤት ላይ ሓላፊነት ያለበት" የማይሰክር "የመጠጥ ሱሰኛ ያልሆነ " ወይም "ሰካራም ያልሆነ " ወይም "ብዙ የወይን ጠጅ የማይጠጣ " የማይጨቃጨቅ፥ "ረብሸኛ ያልሆነ " ወይም " ጠብን የማይወድ " (UDB)

Titus 1:8

ቲቶ **1**፡ **8-9**
በጎ የሆነውን ነገር የሚወድ፥ "መልካም የሆኑ ነገሮችን የሚወድ " (UDB) ጠንቃቃ " የተሰጠ" ወይም "የተረዳ "ወይም "ጠንካራ ግንዛቤ ያለው " ሕይወት በሚገኝበት ትምህርት good teaching "እውነት የሆነ ትምህርት" ወይም "ትክክለኛ የሆነውን የሚያስተምር "

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Titus 1:10

ቲቶ 1: 10-11
የሸግግር ዓረፍተ ነገር: ትክክለኛውን አስተምህሮ የሚቃወ ሙ በመኖራቸው ምክንያት ጳውሎስ ቲቶ የእግዚአብሔርን ቃል የሚሰብክበትን እና ከሐሰት አስተማሪዎች የሚጠነቀቅበትን ምክንያት ይነግረዋል። ከተገረዙት ወገን የሚሆኑ those of the circumcision "የተገረዙ ሰዎች "ወይም " መገረዝን የሚፈጽሙ ሰዎች " ይህ አባባ፤ የተገረዙ አይዳዊያንን ያመላክታል። Their words are worthless "Their words do not benefit anyone" አፋቸውን መዝጋት ይገባል። "የሐሰት ትምህርታቸውን እንዳያስፋፉ ሊከለከሉ ይገባል።" ወይም or "በንግግራች በሌሎች ላይ ተጽዕኖ እንዳይፈጥሩ በግድ ልናቆማቸው ይገባል።" የማይገባውን እያስተማሩ "መማር የማይገባን ነገሮችን እያስተማሩ" ስለ ነውረኛ ረብ "ሰዎች ገንዘብ እንዲሰጦአቸው። ይህ አሳፋሪ ድሪጊት ነው" (UDB). ይህ የሚያመለክተው ሰዎች ተገቢ ያልሆነን ነገር በማድረግ ጥቅም ለማግኘት ሚፈልጉበት ሁኔታን ነው። ቤቶችን በሞላው ስለ ሚገለብጡ፥ "የቤተሰብን ሁኔታ የሚያበላሹ" አት : "የቤተሱቡን እምነት የሚያጠፉ"

Titus 1:12

ቲቶ 1: 12-13
ከእነርሱ አንዱ። One of them "ከቀርጤስ ሰዎች መካከል አንዱ የሆነ" ወይም "የቀርጤሳዊ የሆነ አንድ ሰው " የገዛ ራሳቸው ነቢይ የሆነ አት: "ሌሎች ሰዎች እንደ ነብይ የሚቆጥሩት ሰው " (UDB) የቀርጤስ ሰዎች ዘወትር ውሸተኞች፥ "ቀርጤሳዊያን ሁል ጊዜ ይዋሻሉ" ወይም "መዋሸት በፍጹም አያቆሙም " በአርግጥ ይህ ምን ያዕል ውሸተኞች መሆናቸውን ለማመላከት በማጋነን ሲቀርብ ነው። ክፉዎች አራዊት፥ ክዎች እና አውሬዎች የሚለው አገላለጥ ተምሳሌታዊ ሲሆን የቀርጤስ ሰዎችን ከአራት ጋር በማነጻጸር ያቀረበ ነው። በላተኞች፥ ሥራ ፈቶች lazy bellies "ሰነፍ በላተኞች" ወይም "ምንም የማይሰሩ ነገር ግን ብዙ የሚበሉ ናቸው " ሰው ስለሆዱ ያለው ግንዛቤ ማንነቱን እንደሚያሳይ የሚያስረዳ ምሳሌያዊ አባባል ነው። በብርቱ ውቀሳቸው። ልክ እንዳልሆኑ አበክረህ ንገራቸው። በሃይማኖት ጤናሞች እንዲሆኑh "ጤናማ እምነት እንዲኖራቸው" ወይም "እውነትን እንዲያምኑ " ወይም "እምነታቸው እውነት እንዲሆን "

Titus 1:14

ቲቶ 1: 14-14
ሳያዳምጡ፥ "ለመስማትጊዜሳያጠፉ" የአይሁድንተረትና ይህየአይሁዳዊያንየሐሰትትምህርትንያመለክታል። ፈቀቅየሚሉትን "አማኝነታቸውንያቆሙትን"

Titus 1:15

ቲቶ 1: 15-16
ሁሉለንጹሑችንጹሕነው፤ አት: "ንጹህለሆነሰውሁሉምነገርንጹህነው" ወይም "አንድሰውበውስጡንጹህከሆነየሚሰራውስራሁሉንጹህይሆናልIf someone is pure inside, everything they do will be pure." ለንጹሑች "ንጹህለሆኑሰዎች " ወይም "በእግዚአብሔርዘንድተቀባይነትላላቸው" ለርኩሳንናለማያምኑግንንጹሕየሆነምንምየለም፥ to those who are polluted and unbelieving, nothing is pure አትAT: "የተበላሸስንምግባርያላቸውእናመንጻትእንደሚችሉማያምኑማለትነው።" ረክሶአል "ተበላሽቶችል" ወይም "መገንዘብአይችልም" በሥራቸውይክዱታል "ተግባራቸውየሚገልጠውእርሱንእንደማያውቁትተግባራቸውይገልጠዋል።" የሚያስጸይፉናdetestable "አሳፋሪዎች" ለበጎሥራምሁሉየማይበቁ "ለየትኛውምመልካምተግባርየማይመጥኑመሆናቸውንያሳያሉ” ወይም"የትኛውንምመልካምተግባራመስራትእንደማይችሉያሳያሉ"

ሁሉ ለንጹሑች ንጹሕ ነው፤ አት: " ንጹህ ለሆነ ሰው ሁሉም ነገር ንጹህ ነው" ወይም "አንድ ሰው በውስጡ ንጹህ ከሆነ የሚሰራው ስራ ሁሉ ንጹህ ይሆናል " ለንጹሑች "ንጹህ ለሆኑ ሰዎች " ወይም "በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ላላቸው" ለርኩሳንና ለማያምኑ ግን ንጹሕ የሆነ ምንም የለም፥ አማራጭ ትርጉም (አት): "በስነምግበራቸው ችግር ያላቸውና ንጹ መሆን እንደሚችሉ የማምኑ"

ረክሶአል "ተበላሽቶአል"ወይም "መገንዘብ የማይችል" በሥራቸው ይክዱታል። "ተግባራቸው እርሱን እንደማያውቁት ያሳያል" የሚያስጸይፉdetestable "ማስጠሎ ምንም የማያምር " ለበጎ ሥራም ሁሉ የማይበቁ ስለ ሆኑ፥ prove to be unfit for any good work "ለበጎ ስራ የማይመጥኑ እንደሆነ አሳያቸው " ወይም "የትኛውንም መልካም ስራ መስራት ማይችሉ እንደሆነ አሳይ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 2

1 አንተ ግን፣ ከጤናማው ትምህርት ጋር የሚስማማውን ተናገር። 2 በእድሜ የገፋ ሰዎች ልከኞች፣ ጨዋዎች፣ ጠንቃቆች ጤናማ እምነት፣ ፍቅርና ጽናት ያላቸው ሊሆኑ ይገባችዋል። 3 በእድሜ የገፉ ሴቶችም እንዲሁ ጨዋዎችና፣ ከሃሜት የራቁ መሆን አለባቸው። ወይን ጠጅ ጠጪዎች መሆን አይገባቸውም። መልካም የሆነውን ማስተማር ይገባችዋል 4 ወጣት ሴቶችን በአስተሳሰባቸው ሚዛናዊ እንዲሆኑ እንዲያሳስቧቸው፣ የገዛ ባሎቻቸውና ልጆቻቸውን የሚወዱ፣ ጠንቃቃ እንዲሆኑ እንዲያበርቷቷቸው፣ 5 የእግዚአብሔር ቃል እንዳይሰደብ ንፁህ፣ መልካም የቤት አስተዳዳሪና፣ ለባሎቻቸውም የሚታዘዙ ይሁኑ። 6 በተመሳሳይ መንገድ፣ ወጣት ወንዶች ጠንቃቆች እንዲሆኑ አሳስባቸው። 7 በነገር ሁሉ ራስህን የመልካም ሥራ ምሳሌ አድርገህ ተገኝ፤ በትምህርትም ንጽህናን፣ ጨዋነት፣ የማይነቀፍ ጤናማ ቃላት ይኑርህ። 8 ስለ እኛ የሚናገረው ምንም ክፉ ነገር እንዳይኖር። የማይነቀፍ ስህተት የሌለበትን፣ ነገር ግን ሊቃወም የሚሞክረውን የሚያሳፍር ቃላትን ተናገር። 9 ባሪያዎች በሁሉም ነገር ለጌቶቻቸው ይታዘዙ። ጌቶቻቸውን ደስ ሊያሰኟቸው ይሞክሩ እንጂ፣ አይከራከሯቸው። 10 ስለ መድሃኒታችን እግዚአብሔር የምናስተምረው፣ በሁሉ መንገድ የሚማርክ እንዲሆን፣ ታማኝነትን ያሳዩ እንጂ አይስረቁ። 11 ሰዎችን ሁሉ ሊያድን የሚችለው የእግዚአብሔር ፀጋ ተገልጧል። 12 ይህም ፀጋ ሃጢዓተኝነትና ዓለማዊ ምኞትን እንድንክድና፣ በአሁኑ ዘመን በጥንቃቄ፣ በጽድቅና፣ እግዚአብሔርን በመምሰል እንድንኖር ያስለምደናል 13 ይህም የተባረከውን ተስፋችንን፣ የታላቁን አምላካችንና አዳኛችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ፣ ለመቀበል በደስታ እንድንጠባበቅ ነው። 14 ኢየሱስ ራሱን ለእኛ የሰጠው፣ ከዓመፅ ነፃ ሊያወጣንና ሊያነፃን፣ ገንዘቡና መልካምን ለማድረግ የሚናፍቅ ሕዝብ፣ ለራሱ ሊያደርገን፣ ዋጋ ለመክፈል ነው። 15 እነዚህን ነገሮች ተናገር፣ አበረታታ፣ በሙሉ ስልጣን ገስጽ፣ ማንም አይናቅህ።

Titus 2:1

ቲቶ 2፡ 1-2
የሽግግር ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ በዚህ ክፍል ላይ ቲቶ በእርሱ መጋቢነት ስር ያሉትን ኣዛውንቶች፤ አሮጊቶች፤ ወጣት ሴቶችና ባርያዎች ወይም ሰራተኞች እንደአማኝ እንዴት መኖር እንዳለባቸው የሚሰብክበትን ምክንያት ያስረዳዋለው። ነገር ግን አንተ አት አማራጭ ትርጉም "ነገር ግን አንተ,ቲቶ፣ ከሌሎች የሐሰት መምህራን አንጻር " ሕይወት ለሚገኝበት ትምህርት "ትክክለኛ አስተምህሮ " ወይም "ርቱዕ አስተምሮ " ራሳቸውን የሚገዙ፥ "ያልተሳከረ አህምሮ " ወይም "ራሳቸውን የሚቆጣጠሩ " ጭምቶችsensible "ራሱን የሚቆጣጠር" ወይም "ፍላጎቱን የሚገዛ " ጤናሞች "ትክክለኛ " በእምነት ጤናሞች "ጤናማ እምነት ያለው " ወይም "ትክክለኛ እምነት ያለው" ጤናሞች በፍቅር "በጤናማ ፍቅር " ጤናሞች በመጽናትም "ጽንአን " ወይም "ማይናወጡ" ወይም "የማይደክም"

Titus 2:3

ቲቶ 2፡ 3-5
እንዲሁም "በተመሳሳይ መንገድ " አማራጭ ትርጉም አት: "አዛውንቶቹን እንደመከርክ እንዲሁ አሮጊቶችን እዘዛቸው " አካሄዳቸው "ሁኔታቸው "ወይም "አኗኗራቸው " የማያሙ በዚህ ቁጥር ላይ ጥቅም ላይ የዋለው ቃል “ሰይጣን” ወይም “ሐሜተኛ” ወይም “ጠላት” ማለት ነው። ሌሎች ሰዎችን ለመጉዳት ክፋት የሚናገሩ ሰዎችን ያመለክታል። . ይምከሩአቸው "ማስተማር" ወይም "ሰነሰርዓት “ ወይም "ማበረታታት" በጎ የሆነውን ነገር "ጠቢባን " ንጹሐት አማራጭ ትርጉም "መልካምን የሚያስብ እና መልካምን የሚያደርግ" ወይም "ንጹሁ የሆነን ነገር የሚያስብ እና መልካምን የሚያደርግ" የእግዚአብሔር ቃል እንዳይሰደብ፥ "በዚህ ምክንያት የእግዚአብሔር መልዕክት ተቀባይነት እንዳያጣ " አማራጭ ትርጉም "በሴቶቹ ድርጊት ምክንያት ሌሎች ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንዳይተቹና እንዳይቃወሙ”

Titus 2:6

ቲቶ 2:6-8
እንዲሁ ይህ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ ሴቶችን ስለማሰልጠን አስፈላጊነት የተነገረውን የበፊቱን ቃል የሚያስተሰውስ ሲሆን በተመሳሳይ መንገድ ወንዶችን ማሰልጠን አስፈላጊ እንደሆነ ለማሳት ነው። ምከራቸው "ማስተማር" ወይም "ሰነሰርዓት “ ወይም "ማበረታታት" ራስህን አሳይ፤ present yourself አማራጭ ትርጉም "እንዲህ ልትሆን ይገባል" ወይም "ራስህን እንዲህ ልተሳይ ይገባል " መልካምን በማድረግህ ምሳሌ የሚሆን "ትክክለኛ ነገርን በማድረግ ምሳሌ መሆne መቻል " የሚቃወም ሰው ስለ እኛ የሚናገረውን መጥፎ ነገር ሲያጣ እንዲያፍር፥ ይህ ሐሳብ እንደ ጳውሎስ ግምት አንድ ሰው ቲቶን ቢቃወመው ውጤቱ ሐፍረት እንደሆነ ለማሳየት የተጠቀሰ ሲሆን ይህ ግን ገና ይሆናል ተብሎ የተገመተ እንጂ የተፈጸመ አይደለም።

Titus 2:9

ቲቶ 2፡ 9-10
ለገዛ ጌቶቻቸው "ግዢዎቻቸው " በሁሉምin everything "በሁሉም ሁኔታ ውስጥ ወይም "ዘወትር " ደስ እንዲያሰኙ፥ አማራጭ ትርጉም : "ገዢዎቻቸውን ደስ እንዲያሰኙ "ወይም "ገዢዎቸቸውን ማርካት እንዲችሉ " በጎ ታማኝነትን ሁሉ አማራጭ ትርጉም "በሁሉም ነገር ለገዢዎቻችሁ ተማኝ ሁኑ" ወይም "በገዢዎቻቸውን ለመታመን እንደበቁ የሚገልጡ " ስለ መድኃኒታችን ስለ እግዚአብሔር God our Savior "ያዳነን እግዚአብሔር " ያስመሰግኑ ዘንድ፥ ሰዎችን ወደ ነገሩ መሳብን ያመለክታል ሌሎችን ሰዎች ለመሳብ እንደተዋበ ስጦታ በሁሉ ነገር "በምታደርጉት ሁሉ "

Titus 2:11

ቲቶ 2፡ 11-13
11

12-13 ይህም ጸጋ፥ የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል እንድንኖር ያስተምረናል፤

የሽግግር ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ በዚህ ክፍል ላይ ቲቶን የጌታን ተመልሶ መምጣት እና ለእርሱ በክርስቶስ የተሰጠው ስልጣን እንዲያስተውስ ያበረታታዋል። ነገር ግን አንተ አት አማራጭ ትርጉም "ነገር ግን አንተ,ቲቶ፣ " ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና፤ አማራጭ ትርጉም "የሚያድነው የእግዚአብሔር ሁሉ ሰው እንዲያየው በግልጥ መጥቶአል። " ተገልጦአልና "ወደ ብርሃን መምጣት "ወይም "መታየት ቻለ " ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት ክደን፥ "ትክክለኛው ነገር ሚያስተምረን " አማራጭ ትርጉም "ፈተናዎችን ተቋሙአል መልካምን እንድናደር የሚያርገን" ዓለማዊን ምኞት "ስለዚህ ዓለም በሆነው ነገር” ወይም "ስለ ምድራዊ ነገር ያለ ጠንካራ ፍላጎት አይቻልም።" በአሁኑ ዘመን "በዚህ ምድር በምንኖርበት ግዜ " ወይም or "በዚህ ምድር ጊዜ " እየጠበቅን፥ "ለመቀበል እየጠብቅን " ክብር መገለጥ ይህ ቃል “መከሰትን” እና “ክብርን” አብሮ የያዘ ሲሆን “በክብር የሆነ መገለጥ” ማለት ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Titus 2:14

ቲቶ **2**፡ **14**
ስለ እኛ ነፍሱን ሰጥቶአል። "ስለ እኛ ለመሞት ራሱን አሳልፎ ሰጠ " ከዓመፅ ሁሉ እንዲቤዠን ፥ ይህ አገላለጥ ልክ ባሪያ አስፈላጊውን ክፍያ ከፍሎ ወይም ዓመታቱን ቆጥሮ ከጌታው ቁጥጥር ስር በህግ ተጠያቂ እንዳይሆን ነጻ እንደሚወጣ ሁሉ ከኃጢያ ነጻ መውጣታቸቸንን ያሳያል። ለራሱ እንዲያነጻ፥ "እንዲያነጻን" ገንዘቡም የሚሆነውን ሕዝብ አማራጭ ትርጉም "እንደ ውድ ሀብት የሚቆጠር መልካም ህዝብ " የሚቀናውን "በጣም ከፍተኛ ፍላጎት ያለው "

Titus 2:15

ቲቶ **2**፡ **15-15**
ይህን በሙሉ ሥልጣን ተናገርና ምከር አማራጭ ትርጉም "ሰሚዎችህ እንዚህ ነገሮች ማድረግ እንዲችሉ አስተምራቸው አበረታታቸው" በሙሉ ሥልጣን ገሥጽም፤ give correction with all authority "ይህን ነገር የማያድርጉትን በሙሉ ስልጣን አርማቸው " ማንም "ለማንም አትፍቀድ" አይናቅህ አማራጭ ትርጉም (አት)፡ "ቃልን ለመስማት እምቢ አይበል" ወይም "ማንም አላከብርህም አይበል"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 3

1 ለገዢዎችና ለባለሥልጣኖች እንዲገዙ፣ እንደታዘዟቸው፣ ለበጐ ሥራ ሁሉ የተዘጋጁ እንዲሆኑ፣ **2** ማንንም እንዳይሳደቡ፣ የሌሎችንም ፈቃድ እንዲያከብሩ እንጂ እንዳይከራከሩ፣ ለሁሉም ሰው ትህትን እንዲያሳዩ አሳስባቸው። **3** እኛም ቀድሞ የማናስተውልና የማንታዘዝ ነበርን። የሳትንና የተለያዩ ምኞቶቻችንና ፍላጐቶቻችን ባሪያዎች ነበርን። በክፋትና በምቀኝነት እንኖር ነበር። የተጠላንና እርስበርስ የምንጠላላ ነበርን። **4** ነገር ግን፣ የመድሃኒታችን የእግዚአብሔር ርህራሔና ለሰው ልጅ ያለው ፍቅር በተገለጠ ጊዜ፣ **5** ከምህረቱ የተነሳ፣ በአዲስ ልደት መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ መታድስ አዳነን እንጂ፣ በሠራነው የጽድቅ ሥራ ምክንያት አይደለም። **6** እግዚአብሔር በመድሃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል፣ አብዝቶ መንፈስ ቅዱስን አፈሰሰልን። **7** ይህም በፀጋው ፀደቅን፣ የዘላለም ህይወት ተስፋ ወራሾች እንድንሆን ነው። **8** እነዚህ ቃሎች የታመኑ ናቸው። በእግዚአብሔር የሚያምኑ እርሱ በፊታቸው ላኖረው መልካም ሥራ እንዲተጉ፣ እነዚህን ነገሮች በድፍረትት እንድትናገር እፈልጋለሁ። እነዚህ ነገሮች መልካምና ለሰዎች ሁሉ የሚጥቅሙ ናቸው። **9** ነገር ግን ከከንቱ ክርክር፣ ከዘር ቆጠራና በህግ ጉዳይ ከሚሆን ጸብና ግጭት ራቅ። እነዚህ ነገሮች፣ የማይገቡና የማይጠቅሙ ናቸው። **10** አንዴ ወይም ሁለቴ ካስጠነቀቅከው በኋላ፥ በመካከሃላችሁ መከፋፈል የሚፈጥረውን ሰው አስወግደው። **11** እንዲህ ዓይነቱ ሰው፣ ከእውነተኛው መንገድ የወጣ፣ ሃጢያት የሚያደርግና በራሱ የፈረደ እንደሆነ እወቅ። **12** አርጢሞንን ወይም ቲኪቆስን ወደ አንተ ስልክ፣ ክረምቱን ለማሳለፍ ወደ ወሰንኩበት ወደ ኒቆሊዎን ፈጥነህ ና። **13** የህግ ባለሞያውን፣ ዜማስንና አጵሎስን የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ሰጥተህ ቶሎ ላካቸው። **14** ወገኖቻችንም አለታዊ ፍላጎታቸውን ማግኛት እንዲችሉ ፍሬ ቢስም ሆነው እንዳይገኙ፣ መልካም ሥራ ማድረግን መማር አለባቸው። **15** ከኔ ጋር ያሉት ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡልሃል ። የሚወዱንን አማኞችን ሁሉ ሰላም በልልን። ፀጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን።አሜን።

Titus 3:1

ቲቶ 3፡ 1-2
የሽግግር ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ በዚህ ክፍል ላይ ቲቶ በእርሱ መጋቢነት ስር ያሉትን ሽማግሌዎች እና ሕዝብ እንዴት ማስተማር እናዳለበት ተከታታይ መመሪያ ይሰጠዋል። ኣሳስባቸው "በቤተክርስቲያን ላሉ ሰዎች በአጠቃላይ ከዚህ በፊት የሚያውቁትን ነገሮች ንገራቸው” ወይም "ሳታሰልስ አስታውሳቸው " የሚገዙና የሚታዘዙ፥እንዲሆኑ አት : "የፖለቲካ መሪዎች እና የመንግስት ባለስልጣናት የሚሉትን በማድረግ ታዘዙላቸው” ለገዦችና ለባለ ሥልጣኖች እንዚህ ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው የመንግሰትን ስልጣን የያዘን ሰው ሁሉ የሚያላክቱ ናቸው። ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጁ፥ "በየትኛውም አጋጣሚ የሚገኘውን ዕድል መልካምን ስራ ለመስራት የተዘጋጀ” ማንንም የማይሰድቡ፥ "ክፍ የማይናገር" ለሰው ሁሉ የዋህነትን ሁሉ የሚያሳዩ አት : "የዋህ "

Titus 3:3

ቲቶ 3፡ 3-3
የ "ምክንያቱም" አስቀድመን "ከዚህ ቀድሞ" ወይም "የሆነ ጊዜ “ ወይም "ከዚህ በፊት " የማናስተውል "ሞኞች" ወይ፣or "ማስተዋል የጎደለን" ለምኞትና ለልዩ ልዩ ተድላ እንደ ባሪያዎች የምንገዛ፥ ይህ ተምሳሌታዊ ንጽጽር ኃጢያታዊ ምኞታችን እንዴት እንደ ባሪያ ሊቆጣጠረን እንደሚችል የሚያሳ ነው። አት: "የኃጢያት መሻታችን ለተድላ ፍላጎታችን ባሪያ አድርጎናል" የምንስት አት: "የታለልን " ምኞት "ከፍተኛ ጉጉት" ወይም "መሻት " በክፋትና በምቀኝነት የምንኖር፥ አት: "ዘወትር ክፋትን የምንሰራና የሌላውን ሰው ምንመኝ ነበርን" የምንጣላ፥ እርስ በርሳችን የምንጠላላ ነበርን። "ለመጠላት የተገባን ነበርን" አት: "ሌሎች ሰዎችን እንዲጠሉን የምናደርግ ነበርን"

Titus 3:4

ቲቶ 3፡ 4-5
ነገር ግን የመድኃኒታችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ሰውን መውደዱ በተገለጠ ጊዜ፥ አት : መድኃኒታችን እግዚአብሔር ፍቅሩንና መልምነቱን ለሰዎች ባሳየ ጊዜ" ወደ ሰዎች "ለሰዎች " እንደ ምሕረቱ አዳነን እንጂ፥ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለ ነበረው ሥራ አይደለም፤ "አዳነን። ያዳነን እንደ እርሱ ምሕረት ነው እንጂ ስለመካም ስራችን አይደለም።” በ...አዳንን saved us through "ያዳነን....ዘዴ" ወይም "በ...አዳነን " ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና አት: " መንፈሳዊ በሆነ አዲስ ልደት ውስጣችንን ንጹህ አደረገልን" በመታደስ "አዲስ መሆን " አማራጭ ትርጉም "መንፈስ ቅዱስ አዲስ አደረገን "ወይም "መንፈስ ቅዱስ አዲስ ሰዎች አደረገን" እንደምሕረቱ "በምህረቱ መጠን ልክ " ወይም "ምሕረቱን በእኛ ላይ ስላበዛ"

Titus 3:6

ቲቶ 3፡ 6-7
አትርፎ "አትረፍርፎ " ወይም "ያለመሰሰት" ያን መንፈስም፥ በእኛ ላይ አፈሰሰው። ይህ ዘይቤያዊ አገላለጥ በካህናት ላይ ሲፈስ ከነበረው ዘይት ጋር ተቀራራቢነት አለው። አማራጭ ትርጉም: መንፈሱን ያለመሰሰት ሰጠንን" በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ "ኢየሱስ ባዳነን ጊዜ " በጸጋው ጸድቀን አማራጭ ትርጉም(አት): "በእግዚአብሔር ጻድቃን ተደርገናል" ወራሾች እንድንሆን፥ አማራጭ ትርጉም (አት): "እግዚአብሔር የመውረስ መብት ያላቸው ልጆች አደረገን” በዘላለም ሕይወት ተስፋ "አሁን የዘላለም ሕይወት እንዳለን በእርግጠኛነት እናውቃለን "

Titus 3:8

ቲቶ 3፡ 8-8
እግዚአብሔርንም የሚያምኑት እነዚህን አስረግጠህ እንድትናገር እፈቅዳለሁ። ይህ መልካምና ለሰዎች የሚጠቅም ነው፤ ቃሉ የታመነ ነው። ይህ የሚያመከለክተው በቀዳሚው ቁጥር ላይ እግዚአብሔር በኢየሱስ በኩል መንፈሱን እንደሰጠን የሚናገረውን ቁጥር ነው። በጥንቃቄ እንዲጸኑ፥ "ትኩረት እንዲያደርጉ"ወይም "በተደጋጋሚ እንዲያስቡበት " በመልካም ሥራ AT: "እግዚአብሔር እንዲሰጠሩ በሰጣቸው "

Titus 3:9

ቲቶ 3፡ 9-11
የሽግግር ዓረፍተ ነገር : ጳውሎስ በአማኞች መካከል ጠብ የሚፈጥሩነት ወይም የተለየ አስተያየት ያላቸውን ሰዎች እንዴት መያዝ እንዳለበት ወይም ማስወገድ እንዳለበት ለቲቶ ገለጻ ያደርግለታል። ነገር ግን But "ነገር ግን አንተ ቲቶ " ሞኝነት ካለው ምርመራ "አላስፈላጊ ሙግት " ጠብ "ጭቅጭቅ ሁከት " ስለ ሕግም "ስለሕግም " ራቅ አማራጭ ትርጉም : "አትነጋገር "ወይም "አብርሃቸው ጊዜን አታሳልፍ " ወይም "አስወግዳቸው" አንድ ጊዜ ሁለት ጊዜም ከገሠጽኸው በኋላ "ሰውየውን አንዴ ወይም ሁለቴ ካስጠየነቀቅከው በኃላ " እንዲህ ከሚመስል ሰው "ይህን የመስል ሰው " እንዲህ ከሚመስል ሰው ""ይህን የመስል ሰው "

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Titus 3:12

ቲቶ 3፡ 12-13
የሸግግር ዓረፍተ ነገር ፡ ጳውሎስ በአማኞች መካከል ጠብ የሚፈጥሩነት ወይም የተለየ አስተያየት ያላቸውን ሰዎች እንዴት መያዝ እንዳለበት ወይም ማስወገድ እንዳለበት ለቲቶ ገለጻ ያደርግለታል። ወደ አንተ ስልክ፥ "ከላኩልህ በኃላ " አርጢሞንን ወይም ቲኪቆስን ዜማስን

በዚያ ልከርም ቄርጬአለሁና። "ክረምቱን እቆያለው" ወደ እኔ እንድትመጣ ትጋ፤ "ፍጠንና ና” ወይም "ፈጥነህ ና" በጉዞአቸው ተግተህ እርዳ ። "ፍጠን" ወይም "ለመላክ አትዘግይ " ና አጵሎስን "እና አንዲሁም አጵሎስ ላከው"

Titus 3:14

ቲቶ 3፡ 14-14
በመልካም ሥራ እንዲጸኑ ይማሩ። "ባተሌ እና በመልም ስራ የተጠመዱ " ፍሬ ቢሶች ሆነው እንዳይቀሩ፥ አማራጭ ትርጉም

Titus 3:15

ቲቶ 3፡ 15-15
ኖት የለውም።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Philemon

Philemon

ምዕራፍ 1

1 ስለክርስቶስ ኢየሱስ እስረኛ የሆነው ጳውሎስ ከወንድማችን ከጢሞቴዎስ ጋር ለተወደደው ወንድማችንና የሥራ አጋራችን ለሆነው ለፊለሞና፣ 2 ለእህታችን
ለአፒፊያ፣አብሮን ወታደር ለሆነው ለአክሪፋ እንዲሁም በቤትህ ላለችው ቤተክርስቲያን፡ 3 ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሠላም
ለእናንተ ይሁን። 4 በጸሎቴ ሁሉ ስላንተ እያነሳሁ ሁልጊዜ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። 5 ምክንያቱም በጌታ በኢየሱስ ስላለህ እምነት ለቅዱሳንም ሁሉ
ስላለህ ፍቅር ሰምቻለሁ። 6 በክርስቶስ በኩል የመልካም ነገር ሁሉ እውቀት በእኛ ውስጥ ስላለ በእምነት ያለህ ተካፋይነት ውጤታማ እንዲሆን እጸልያለሁ። 7
ወንድሜ ሆይ፣ ለዚህም ምክንያቱ የቅዱሳን ሁሉ ልብ በአንተ በማረፉ ምክንያት በፍቅርህ በጣም ደስ ስላለኝና ስለተጽናናሁ ነው። 8 ስለዚህም ምንም እንኳ ምን
ማድረግ እንዳለብህ በክርስቶስ ለማዘዝ ድፍረት ቢኖረኝም 9 በዚህ ፈንታ እንደ ሽማግሌው አሁን ደግሞ ስለ ክርስቶስ እስረኛ እንደሆነው ጳውሎስ በፍቅር
እለምንሀለሁ። 10 ልመናዬ በእስርቤት አባት ስለሆንኩት ስለ ልጄ ኦኖሲሞስ ነው። 11 ምክንያቱም ቀድሞ ለአንተ የማይጠቅም አሁን ግን ለአንተም ለእኔም
ጠቃሚ በመሆኑ ነው። 12 የልቤ የሆነውን እርሱን ወደ አንተ ልኬዋለሁ። 13 በእኔ በኩልስ አንተን ወክሎ ስለ ወንጌል በእስር ቤት ያለሁትን ያገለግለኝ ዘንድ እኔ
ጋ ቢቀር እወድ ነበር። 14 ነገር ግን መልካም ሥራህ በግድ ሳይሆን በፈቃድህ ይሆን ዘንድ ያለ አንተ ፈቃድ ምንም ማድረግ አልፈለግሁም። 15 ለጥቂት ጊዜ
ከአንተ ተለይቶ የነበረው ምናልባት ለዘላለም የአንተ ይሆን ዘንድ ነው ። 16 ነገር ግን ከዚህ በኋላ ከባሪያ የተሻለ እንደተወደደ ወንድም እንጂ እንደባሪያ
አይደለም፥ በተለይ ለእኔ የተወደደ ከሆነ ለአንተማ በሥጋም በጌታም የበለጠ ይሆናል። 17 እንግዲህ እንደ አጋርህ ከቆጠርከኝ እንደኔ አድርገህ ተቀበለው። 18
ነገር ግን በምንም መልኩ አሳዝኖህ ቢሆን ወይም ዕዳ ቢኖርበት በእኔ ላይ ቁጠረው። 19 እኔ ጳውሎስ እኔ እከፍላለሁ ብዬ በገዛ እጄ ጽፌአለሁ።የገዛ
ህይወትህ እንኳ የኔ ነው ብዬህ አላውቅም። 20 አዎ ወንድሜ ሆይ እስኪ በጌታ ደስ ይበለኝ፥ ልቤም በክርስቶስ ይጽናና። 21 እንደምትታዘዘኝ በመተማመን
ካልኩህም በላይ እንደምታደርግ ስለማውቅ ጽፌልሀለሁ። 22 በነገራችን ላይ ከጸሎታችሁ የተነሳ ወደ እናንተ እንደምመጣ ተስፋ ስለማደርግ አንድ የእንግዳ
ክፍል አዘጋጅልኝ። 23 ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አብሮኝ የታሰረው ኤጳፍራ 24 እንዲሁም የሥራ አጋሮቼ ማርቆስ፣አርስጥሮኮስ፣ዴማስና ሉቃስ ሠላምታ
ያቀርቡልሀል። 25 የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከመንፈሳችሁ ጋር ይሁን። አሜን!

Philemon 1:1

ፊልሞን 1፡ 1-3
የክርስቶስ ኢየሱስ እስረኛ እና ጢሞቴዎስ ለፊልሞና በቋንቋችሁ የደብዳቤ ጸሐፊን ማስተዋወቂያ መንገድ ሊኖር ይችላል። አመራጭ ትርጉም: "በክርስቶስ ኢየሱስ እስረኛ የሆንኩት ጳውሎስ እና ወንድማችን ጢሞቴዎስ እና ይህንን ደብዳቤ ለፊልሞና ጽፈናል።" የክርስቶስ ኢየሱስ እስረኛ "ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በማስተማሩ ምክንያት እስረኛ የሆነው።" ኢየሱስን የማይወዱት ሰዎች ጳውሎስብ በእስር ቤት ውስጥ በማኖር ቀጥተውታለል። ወንድም በዚህ ሥፍራ ላይ ይህ ቃል ያለው ትርጉም ክርስትያን ማለት ነው። የተወደደው ወዳጃችን "ተወዳጁ ከእኛ ጋር አማኝ የሆነው" ወይም "የሚንወደው መንፈሳዊ ወንድማችን" የሥራአ አጋር "ልክ እንደ እኛ ወነንጌልን በማሠራጨት ሥራ የተጠመደው" እህታችን አፊያ ይህ ማለት "እንደ እና አማኝ የሆነችው አፊያ" ወይም "መንፈሳዊ እህታችን የሆነችው አፊያ" ለአርክጳ ይህ አንድ ሰው ስም ነው። ከእኛ ጋር የሚሠራ ሰው በዚህ ሥፍራ ላይ “ወታደር” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ወንጌልን በተለያዩ ሥፍራዎ ለማሠራጨት የሚጥርን ሰው ነው። አማራጭ ትርጉም: "ከእኛ ጋር መንፈሳዊ ውጊያን የሚዋጋ" ወይም "ከእኛ ጋር መንፈሳዊ ውጊያን የሚዋጋ ሰው።" በመኖሪያ ቤታችሁ ውስጥ የሚትሰበሰበው ቤተ ክርስቲያን "በአንተ ቤት ውስጥ የሚሰበሰቡት የአማኞች ቡድን" (UDB) ቤትህ ውስጥ በዚህ ሥፍራ ላይ “አንተ” የሚለው ቃል የተገለጸው በነጠላ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተው ፊልሞናን ነው። ጸጋ እና ሰላም ከአባታችን ከእግዚአብሔር እና ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ለእናነተ ይሁን "እግዚአብሔር አባታችን እና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋንና ሰላምን ለእናንተ ይስጣችሁ።” ይህ ባርኮት ነው። በዚህ ሥፍራ ላይ “እናንተ” የሚለው ቃል የተገለጸው በብዙ ቁጥር ሲሆን ጳውሎስ በዚህ ደብዳቤ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ቁጥሮች ላይ ሰላምታ የሰጣቸውን ሰዎችን ያመለክታልis is a blessing. The word "you" is plural and refers to all the people Paul greeted in verses 1 and 2.

Philemon 1:4

ፊልሞን 1፡ 4-7
እኔ ይህንን ደብዳቤ የጻፈው ጳውሎስ ነው። በዚህ ሥፍራ ላይ “እኔ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን ነው።፤ አንተ በዚህ ሥፍራ ላይ እና በዚህ ደብዳቤ ውስጥ በብዙ ሥፍራዎች ላይ “አንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ፊልሞንን ነው። በክርስቶስ የእኛ የሆነው የዚህ ትርጉም ሊሆን የሚችለው ከክርስቶስ የተነሣ እኛ አለን የሚል ይሆናል።" ልቦች በዚህ ሥፍራ ላይ “ልቦች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የአማኞችን ጽናት ነው። ወንድም ጳውሎስ ፊልሞንን “ወንድም” ብሎ ይጠራዋል ምክንያቱም ሁለቱም አማኞች በመሆናቸው ምክንያት ነው። ከዚህ በተጨመማሪም ምናልባት በሁለቱ መካከል ያለው ወዳጅነት አጽኖት መስጠት ፈልጎም ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም: "የተወደድከው ወንድም" ወይም "ውድ ወንድሜ።"

Philemon 1:8

ፊልሞን 1፡ 8-9
በክርስቶስ ያለን ድፍረት ሁሉ አማራጭ ትርጉሞች "ከክርስስ የተነሣ ያለን ሥልጣን" ወይም "ከክርስቶስ የተነሣ ያለን ብርታት።" አማራጭ ትርጉም: "የክርስቶስ ሐዋርያ በመሆነ ያለኝ ሥልጣን።" ይሁን እንጂ ከፍቅር የተነሣ አማራጭ ትርጉም 1) "የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንደሚትወድ ስለማውቅ" 2) "እኔን ስለምትወደኝ" ወይም 3) "አንተን ስለሚወድህ።"

Philemon 1:10

ፊልሞን 1፡ 10-13
ልጄ አናሲሞስ የእኔ ልጅ ስለሆነው አናሲሞስ ። ጳውሎስ ከአናሲሞስ ጋር የነበረውን ቅርብ ግንኙነት በአባት እና በለልጅ መካከል ካለው ግንኙነት ጋር ያነጻጽረዋል። አናሲሞስ የጳውሎስ ልጅ አይደለም። ይሁን እንጂ አናሲሞስ ሕይወትን ያገኘው ጳውሎስ ስለ ኢየሱስ ካስመተማረው በኋላ ነው፤ ጳውሎስም

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወደደው። አማራጭ ትርጉም: "ተወዳጁ ልጁ አናሲሞስ" ወይም "መንፈሳዊ ልጄ አናሲሞስ።" አናሲሞስ ይህ የአንድ ሰው ስም ነው። እኔ አባት የሆኑኩት አናሲሞስ የጳውሎስ ልጅ የሆነበት መንገድ ግልጽ ነው: "ስለ ክርስቶስ ሳስተምረው መንፈሳዊ ልጄ የሆነው እና አዲስ ሕይወትን የተቀበለው።" አማራጭ ትርጉም: "ለእኔ ልጅ የሆነው" ወይም "ለእኔ እንደ ልጅ የሆነው።" በእስራቴ በእስራቴ።" በዚያ ዘመን እስረኞች ብዙ ጊዜ በበሰንሰለት ይታሠሩ ነበር። ጳውሎስ አናሲሞስን ባስተመረበት ወቅት በእስር ቤት ነበር እንዲሁም ይህንንም ደብዳቤ በሚጽፍበት ወቅትም በእስር ላይ ነበር። በፊት የሚጠቅም አልነበረም ይህ እንደ አዲስ ዓረፈተ ነገር ተደርጎ ልተረጎም ይችላል። “ከዚህ በበፊት እርሱ ምንም የምጠቀም አልነበረም።” አሁን ግን የሚጠቅም ሆኗል "አሁን ግን ጠቃሚ ሆኗል።" ተርጓሚዎች በግሪጌ ማስታወሻ ላይ “ኦናሲሞስ የሚለው ቃል ትርጉም ጠቃሚ ማለት ነው” የሚለውን ማስቀመጥ ይችላሉ።" የእኔ ልብ የሆነውን ወደ አንተ መልሼ ልኬዋለሁ ጳውሎስ ይህንን ደብዳቤ የጻፈው ኦናሲሞስን ከመላኩ ጥቂት ቀደም ብሎ ሊሆን ይችላል። የልቤ የሆነውን በዚህ ሥፍራ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ተወዳጅ የሆነ ሰውን ነው። ጳውሎስ እየተናገረ ያለው ስለ ኦናሲሞስ ነው። አማራጭ ትርጉም: "ከልቤ የሚወደውን።" በእናንተ ፈንታ ሆኖ ያገለግለኝ ዘንድ "እናንተ በዚህ መሆን ስለማትችሉ እርሱ ለረዳኝ ይችላል።" አዲስ ዓረፈተ ነገር ተደርጎ ልተረጎም ይችላል። በእናንተ ፈንታ ልረዳኝ ይችላል።" እኔ በበሠንሰለት ታሥሬያለሁ አማራጭ ትርጉም: "በእስር እያለሁ" ወይም "በእስር ቤት ውስጥ ስላለሁ" ለወንጌል ሲባል አማራጭ ትርጉም: "ወንጌልም መስበክ ስላለብኝ።"

Philemon 1:14

ፊልሞን **1**፡ **14-16**
ይሁን እንጂ እናንተን ሳላማክር አንዳች ነገር ማድረግ አልፈልግም "ይሁን እንጂ እናንተ ሳትፈቅዱ እዚህ ላስቀረው አልፈለኩም" ወይም "ይሁን እንጂ እናንተ ከፈቀዳቹልኝ ብቻ በእኔ ዘንድ እንዲቆይ አደርገዋለሁ።" የአንተ . . . አንተ በዚህ ሥፍራ ላይ የተጠቀሱት ተውላጠ ስሞች በነጠላ ቁጥር ሲሆን የሚመለክቱት ፊልሞንን ነው። ስለዚህ የሚታደርገውን መልካም ነገር ሁሉ የሚታደርገው እኔ ስላሰገደድኩህ መሆን የለበትም አማራጭ ትርጉም: "ትክክለኛ የሆነውን ነገር አድርግ፣ እኔ ስላስገደድኩህ ኤደለም።" ነገር ግን አንተ ስለፈለከው እንጂ "ትክክለኛውን ነገር ለማድረግ አንተ ራሰህ ስለመረጥክ እንጂ" ምናልባት ከአንተ የተለየበት ምክንያት “እግዚአብሔር ኦናሲሞስ ከአንተ እንዲለይ ያደረገበት ምክንያት።" ምናልባት "ምንአልባት" ለተወሰነ ጊዜ "በእነዚህ ጊዜያት" ከባሪያ የተሻለ "ከባሪያ የተሻለ ጠቃሚ እንዲሆን" ተወዳጅ ወንድም "ውድ ወንድም" ወይም "በክርስቶስ ውድ የሆነ ወንድም" ለአንተ ድግሞ ከዚህ እንዴት አይበልጥ "ለአንተ ከዚህም በላይ ነው" በሰው እይታ ይህ በሰዎች መካከል የሚደረግ ግንኙነት በግልጽ ይቀመጣል: “እርሱ የአንተ ባርያ በመሆኑ ምክያት።" አማራጭ ትርጉም: "እንደ ሰው" ወይም "በሰውና ግንኙነትህ።" እንዲሁም በጌታ አማራጭ ትርጉም: "በጌታ ወንድምህ እንደመሆኑ መጠን" ወይም "የጌታ በመሆኑ ምክንያት።"

Philemon 1:17

ፊልሞን **1**፡ **17-20**
እኔን እንደ አጋርህ ከቆጠርከኝ "እኔን ለክርስቶስ አጋር ሠራተኛህ አድርገህ የሚታስበኝ ከሆነ" እዳውን በእኔ ላይ አድርገው አማራጭ ትርጉም: "የእርሱ እዳ በእኔ ላይ አድርገው" ወይም "ባለእዳው እኔ እንደሆንኩ ቁጠረው።" ይህን በገዛ አጆቼ የሚጽፍልህ እኔ ጳውሎስ ነኝ ጳውሎስ ይህንን ለፊልሞና የጻፈው የተጻፉት ነገሮች እውነት መሆናቸውን ለማረጋገጥ ነው። ጳውሎስ በእርግጥ ያለበትን እዳ ሁሉ ይከፍለዋል። አማራጭ ትርጉም: “እኔ ጳውሎስ ይህንን በገዛ እጆቼ ጻፍኩልህ።” ይህንን ለአንተ ማስታወስ የለብኝም "ይህንን ለአንተ ማስታወስ አይኖርብኝም" አማራጭ ትርጉም: "አንተ ታውቃለህ" ለእኔ የራስህ ደግሞ ብድር አለብህ "የገዛ ሕይውትን ብርድ ለእኔ አለብህ።" ፊልሞን የጳውሎስ ብድር እንዳለበት የሚያሳየው ኣረፍ ነገር እንዲህ በግለጽ ሊቀመጥ ይችላል: “ይህ እዳ አለበህም ምክንቱም ሕይወትህ ያደንኩህ እኔ ነኝ።” ወይም የራሰህ ሕይወት እንኳ የእኔ ነው ምክንቱም የዳንከው እኔ በነገርኩህ ነገር ነው።" ጳውሎስ በተዘዋዋሪ መንገድ እያለ ያለው ኦናሲሞስ ወይም ጳውሎስ እዳለ አለባቸው ማለት የለበትም ምክንቱም ኦናሲሞስ የጳውሎስ ብዙ እዳ አለበት። ልቤን አዲስልኝ ኦናሶሞስ ለጳውሎስ ያደረገው ነገር እንዲህ በግልጽ ሊቀመጥ ይችላል: "ኦናሲሞስን በመቀበል ልቤን አዲስልኝ።" አማራጭ ትርጉም: "ልቤ እንዲበሰት አድርግ" ወይም "ደስተኛ እንዲሆን አድርግ" ወይም "አጽናናኝ።"

Philemon 1:21

ፊልሞን **1**፡ **21-22**
ስለመታዘዝህ ከፍተኛ መተማመን አለኝ "ምክንያቱም ያዘዝኩን እነነደሚታደረግ እርግጠኛ ነኝ" የአንተ መታዘዝ...እጽፍልሃለሁ . . . ታደርገዋለህ ጳውሎስ ይህንን የጻፈው ለፊልሞና ነው። እያወቅሁ "አውቃለሁ" በተመሳሳይ መልኩ "እንዲሁም" ለእኔ ማረፊያ ሥፍራ አዘጋጅልኝ "በቤትህ ለእኔ ማረፊያ የሚሆን ሥፍራን አዘጋጅልን።" ጳውሎስ ፊልሞን ይህንን እንዲያደረግ ይጠይቀዋል። በእናንተ ጸሎት . . . ልጎበኛችሁ በዚህ ሥፍራ ላይ “እናንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ፊልሞንን እና በእርሱ ቤት ውስጥ የሚሰበሰቡ አማኞችን ነው። በጸሎታችሁ አማራጭ ትርጉም: "በጸሎታችሁ ምክንያት" ወይም "እናንተ ሁላችሁ ስለ እኔ በመጸለያችሁ ምክንያት።" በቶሎ ልጎበኛችሁ እችላለሁ "በእስር ያቆኙ ሰዎች ቶሎ በነጻ እንዲለቁኝ እግዚአብሔር ያደርጋል ከዚያም ወደ እናንተ መምጣት እችላለሁ።"

Philemon 1:23

ፊልሞን **1**፡ **23-25**
ኖት የለውም።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Hebrews

Hebrews

ምዕራፍ 1

1 ከረጅም ጊዜ በፊት በተለያዩ ዘመናትና በተለያዩ መንገዶች እግዚአብሔር በነቢያት በኩል ለአባቶቻችን ተናግሮ ነበር። **2** አሁን ግን የሁሉም ነገር ወራሽ ባደረገው፣ ዓለምንም በፈጠረበት በልጁ ተናገረን። **3** ልጁ የክብሩ ነጸብራቅ ነው፤ እርሱ በባሕርዩ ከእግዚአብሔር ጋር ፍጹም አንድ ነው፤ በሥልጣን ቃል ሁሉን ደግፎ ይዞአል። የሰዎችንም ኃጢአት ካነዳ በኃላ በሰማይ በግርማው ቀኝ ተቀምጧል። **4** እርሱ የወረሰው ስም ከሰማቸው እጅግ የላቀ በመሆኑ፣ ከመላእክትም የበለጠ ሆኖአል። **5** ለመሆኑ፣ ከመላክት መካከል፣ “አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ” ደግሞስ፣ “እኔ አባት እሆነዋለሁ፤ እርሱም ልጄ ይሆናል” ያለው ለማን ነው? **6** የበኩር ልጁን ወደ ዓለም ሲያስገባ እግዚአብሔር፣ “የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉ ይስገዱለት” ብሏል። **7** ስለ መላእክቱ ግን፣"መላዕክቱን ነፋሳት፥ አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል ያደርጋል" ይላል። **8** ስለ ልጁ ግን፣ “አምላክ ሆይ፣ዙፋንህ ከዘላለም እስከ ዘላለም ነው፤ የመንግሥትህም በትር የጽድቅ በትር ነው። **9** ጽድቅን ወደድህ፤ ዐመፅንም ጠላህ ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክህ፣ ከጓደኞችህ ይልቅ በደስታ ዘይት ቀባህ” ብሏል። **10** እንዲሁም፣ “ጌታ ሆይ፣ በመጀመሪያ ምድርን ፈጠርህ፤ ሰማያትም የእጅህ ሥራ ናቸው። **11** እነርሱ ይጠፋሉ፤ አንተ ግን ትኖራለህ። ሁሉም እንደ ልብስ ያረጃሉ። **12** እንደ መጎናጸፊያ ትጠቀልላቸዋለህ፤እንደ ልብስም ይለወጣሉ። **13** በየትኛውም ጊዜ ነበር እግዚአብሔር ከመላእክቱ ለአንዱ፣ “ጠላቶችህን ከእግርህ በታች እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ” ያለው? **14** ታድያ፣ መላእክት ሁሉ እኔን እንዲያመልኩና ድነት የሚወርሱትን ለመርዳት ተተላኩ መንፈሶች አይደሉምን?

Hebrews 1:1

ዕብራውያን **1**:**1**-**3**
ነጸብራቅ "ብርሃን" የእርሱ ባሕርያ ትክክለኛ መገለጫ አንድ ሰው ወደ ልጁ በመመልከት እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል ያያል። ቃሉ የእርሱ ኃይል "ኃይለኛ በሆነው ቃሉ" የኃጢአታንን መንጻት አስገኘ "ከኃጢአት እኛ ማንጻት ፈጸመ" እግዚአብሔር በልጁ አማካኝነት ለእኛ ተናገረን . . . ዓለማትን ሁሉ ፈጠረ የእግዚአብሔር ልጅ አምላክ ነው፣ አምላክ የሆነ ልጅ ነው። ልጁ ዓለማትን ፈጥሯል። ልጅ የእግዚአብሔር ልጅ የሚለው ስም ለኢየሱስ እጅግ ወሳኝ የሆነ የማዕረግ ስም ነው፣ የእርሱ ልጅ የእርሱ ክብር ማንጸባረቂያ፣ የእርሱ ባሕርይ መገለጫ . . . ሁሉን ነገር በእጁ ደግፎ የያዘ ልጁ የእግዚአብሔርን ክብር ያንጸባርቃል፣ የእግዚአብሔርን ባሕርይ እና መገለጫ ያሳያል እንዲሁም የፈጠረውን ፍጥረታት ሁሉ በእጆቹ ደግፎ ይይዛል ምክንያቱም እርሱ አምላክ ስለሆነ ነው።

Hebrews 1:4

ዕብራውያን **1**: **4**-**5**
እርሱ . . . ሆነ "ኢየሱስ . . . ሆነ" ከመላእክት መካከል እንዲህ ያለው ለማን ነው . . . አባት"? "እግዚአብሔር ከመላእክት መካከል ለአንዳቸውን እንዲህ አላለም . . . አባት።" ፈጽሞ እንዲህ ብሎ ያውቃልን "አባት የሆነው እግዚአብሔር ፈጽሞ እንዲህ ብሎ ያውቃልን" እንደገናም . . . ለእኔ "እንደገናም ከመላእክት መካከል ለአንዳቸውም ፈጽሞ እንዲህ አላለም . . . ለእኔ?" አንተ ልጄ ነህ ...እኔ አባት ሆኜሃለሁ . . . እኔ አባት እሆነዋለሁ . . . እርሱም ለእኔ ልጅ ይሆናል እግዚአብሔር አባት ከእግዚአብሔር ወልድ ጋር ያለው የተለየ ግንኙነት በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ኢየሱስ ከመወለዱ ብዙ መቶ ዓመታት በፊት ተገልጾ እናገኘዋለን።

Hebrews 1:6

ዕብራውያን **1**: **6**-**7**
በኹር በዚህ ሥፍራ ይህ ቃል የሚያመለክተው ኢየሱስን ነው። የእግዚአብሔር ልጅ የእግዚአብሔር በኹ ተብሎ ተጠርቷል። ምክንያቱም ከሌሎቹ ሁሉ በላይ አስፈላጊ ስለሆነ እና በሁሉም ላይ ሥልጣን ስላለው ነው። የእርሱ አገልጋዮች መላእክት መናፈስት . . . የእሳት ነበልባዮች አማራጭ ትርጉሞች፡ 1) እርሱን ልክ የሚያገለግሉትን መላእክት መናስፍስታትን እንደ እሳት መበልባል አድርጎ ፈጥሮዋቸዋል (UDB)፣ 2) ንፋስን እና የእሳት ነበልባን የእርሱ መልዕክተኞች አድርጎዋቸዋል።

Hebrews 1:8

ዕብራውያን **1**: **8**-**9**
ስለ ለልጁ እንዲህ ብሏል፣ "ዙፋንህ ከዘላለም እስከ ዘላለም ነው . . . ስለዚህም አምላክ፣ የአንተ አምላክ የእግዚብሔር ልጅ ለዘላለም ይገዛል። ስለልጁ እንዲህ አለ "ስለልጁ እግዚአብሔር እንዲህ ብሏል" ልጅ ይህ የእግዚአብሔር ልጅ ለሆነው ለኢየሱ በጣም ወሳኝ የማዕረግ ስም ነው። በትር መንግስት በንጉሥ ወይም ንግሥት ያላቸውን ስልጣን ለማሳየት በእጅ የሚያዝ ልዩ ዓይነት በተር ናት። ይበልጥ አንተን በደስታ ቅባት ቀባህ "ይበልጥ ደስታን ሰጠህ" የደስታ ቅባት አማራጭ ትርጉሞች 1) ሰዎች ደስታቸውን ለመግለጽ የሚቀቡት ልዩ መዓዛ ያለው ቅባት ወይም 2) ነገሥታ በሚነግሱበት ወቅት የሚቀቡት ቅባት ነው። በዚህም ሁኔታ ውስይ “ደስታ” የሚለው ቃል የሚመጣው እግዚአብሔር ከሚሰጠው ክብር ነው።

Hebrews 1:10

ዕብራውያን **1**: **10**-**12**
ያረጃሉ እያረጁ ይሄዳሉ ልብስ ልብስ ትጠቀልላቸዋለህ ያረጁ ልብሶችን መጠቀም ስታቆም የሚታደርጋቸውን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የሚውል ግሥን ተጠቀም። መጎናጸፊያ መጎናጸፊያ ወይም ከላይ የሚደረብ ልብስ

Hebrews 1:13

ዕብራውያን **1**: **13**-**14**
መርገጫ በሚትቀመጥበት ወቅት እግሮችህ የሚያርፉበት ሥፍራ ስለእነርሱ ለእነርሱ ሲባል ሁሉም መላእክት መናፈስት አይደሉምን አማራጭ ትርጉም: "ሁሉም መላእክት መናስፍት ናቸው"

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 2

1 ስለዚህ ከሰማነው ነገር እንዳንወሰድ፣ ስለ ሰማነው ነገር ይበልጥ መጠንቀቅ አለብን። **2** በመላእክት አማካይነት የመጣው መልእክት ጽኑ ከሆነና፣ ማንኛውም መተላለፍና ዐመፅ ተገቢውን ቅጣት የሚቀበል ከሆነ። **3** ታዲያ፣ይህንን ታላቅ መዳን ቸል ካልን እንዴት ማምለጥ እንችላለን? **4** እግዚአብሔርም ምልክቶችን፣ ድንቆችንና የተለያዩ ተአምራትን በማድረግ፣እንደ ፈቃዱ በታደሉት በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አማካይነት ምስክርነታቱን አጽንቶአል። **5** ይህ እየተናገርንለት ያለውን ወደ ፊት የሚመጣውን ዓለም እግዚአብሔር ለመላእክት አላስገዛም። **6** እንዲያውም በቅዱሳት መጻህፍት አንድ ሰው አንድ ስፍራ ሲናገር፣ **7** ሰውን ከመላእክት በጥቂት አሳነስኸው የክብርና የምስጋና ዘውድ ጫንህለት። [1]**8** ማንኛውንም ነገር ከእግሮቹ በታች አስገዛህለት” ብሏል። እግዚአብሔር ከእግሩ በታች ሲያስገዛለት ምንም ያላስገዛለት ነገር የለም። ነገር ግን በእሁኑ ጊዜ ሁሉም ነገር ተገዝቶለት ገና አናይም። **9** ይሁን እንጂ፣ ከመከራውና ከሞቱ የተነሣ ከመላእክቱ በጥቂቱ አንሶ የነበረውን ኢየሱስን፣ የክብርና የምስጋና ዘውድ ተጭኖለት እናያለን። በእግዚአብሔር ጸጋ እርሱ ለሰው ሁሉ ሞትን ቀምሷል። **10** ሁሉም በእርሱና ለእርሱ የሚኖር ብዙ ልጆችን ወደ ክብር ለማምጣት የድነታቸውን መሥራች በመከራው አማካይነት እግዚአብሔር ፍጹም ሊያደርገው ተገቢ ሆነ። **11** የሚቀድሰውም ሆነ የሚቀደሱት ሁለቱም ከአንዱ ምንጭ፣ ከእግዚአብሔር ናቸው። በዚህም ምክንያት የሚቀድሳቸው እርሱን ወንድሞቼ ብሎ ሊጠራቸው አላፈረም። **12** እንዲያውም፣ **13** እንዲሁም፣ “እኔ በእርሱ እታመናለሁ” ይላል። በተጨማሪ፣ “እነሆ እኔንና እግዚአብሔር የሰጠኝን ልጆች ተመልከቱ” ብሏል። **14** ስለዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ሁሉ በሥጋና ደም ስለሆኑ፣ በሞቱ አማካይነት ሞት ላይ ሥልጣን ያለውን ማለትም ዲያብሎስን ለመሻር ኢየሱስም እንደ እነርሱ ሥጋ ለብሶ። **15** ይህም የሆነው ዕድሜ ልካቸውን በሞት ፍርሃት ምክንያት ዕድሜ ልካቸውን ባርነት ውስጥ የነበሩትን ሁሉ ነጻ ለማውጣት ነው። **16** እርግጥም እየረዳቸው ያለው መላእክትን ሳይሆን፣ የአብርሃም ዘሮችን ነው። **17** ስለሆነም የእግዚአብሔር በሆነ ነገር ሁሉ መሓሪና ታማኝ ሊቀ ካህን ለመሆንና ለሰዎችም ሁሉ የኃጢአት ይቅርታን ለማስገኘኘት በሁሉም ረገድ ወንድሞችን መምሰሉ አስፈላጊ ሆነ። **18** ኢየሱስ ራሱ መከራ የተቀበለና የተፈተነ በመሆኑ፣ የሚፈተኑትን ሁሉ ሊረዳቸው ይችላል።

Footnotes

2:7 [1]አንዳንድ ቅጆች “...በእጆችህ ሥራ ሁሉ ላይ ሾምኸው” የሚል ይጨምራሉ።

Hebrews 2:1

ዕብራውያን **2**: **1**-**1**
ምናልባት እንዳንወሰድ "ስለዚህም እንዳንጠፋ"

Hebrews 2:2

ዕብራውያን **2**: **2**-**4**
ትክክለኝነቱ የተረጋገጠ እውነት መሆኑ የተረጋገጠ ማንኛውም መተላለፍ እና አለመታዘዝ የሚገባውን ቅጣት ይቀበላል አማራጭ ትርጉም: "ኃጢአት ያደረገ ማንኛውም ሰው እና የማይታዘዝ ሰው ሁሉ የሚገባውን ቅጣት ይቀበላል።" መተላለፍ እና አለመታዘዝ እነዚህ ሁለት ቃላት በመሠረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ማንኛውም አለለመታዘዝ ቅጣት እንደሚያስከትል አጽኖት ይሰጣል። መተው "ትኩረት አለመስጠት" ወይም "አለመቀበል" አከፋፈለ ሰጠ፣ መሰከረ እንደ እርሱ ፈቃድ "ፈጸም በሚፈልገው መልኩ"

Hebrews 2:5

ዕብራውያን **2**: **5**-**6**

Hebrews 2:7

ዕብራውያን **2**: **7**-**8**
የሰው ልጆች ሰዎች ለእርሱ አንዳች ነገር ሳያስገዛ አልተወም አማራጭ ትርጉም: "ሁሉን ነገር ለእርሱ አስገዛለት"

Hebrews 2:9

ዕብራውያን **2**: **9**-**10**
ከመለአክት አንሶ ሳለ . . . ክብር እና ምስጋና ይህንን በ HEB 2:7 ላይ በተረጎምከው መሠረት ተርጉመው። ልጆች በዚህ ሥፍራ ላይ ይህ ቃል የሚያመለክተው በክርስቶስ ያመኑ ሰዎችን ነው።

Hebrews 2:11

ዕብራውያን **2**: **11**-**12**
ወንድሞች ልላቸው ከተውንም አላፈረም "ወንድሞቹ ልላቸው ወዷል" ወንድሞች በዚህ ሥፍራ ይህ ቃል የሚያመለክተው ክርስትያን ወንድሞችን ነው። ይህም በክርስቶስ ያመኑት ሁሉ እግዚአብሔር ሰማያዊ አባታቸው የሆነ፤ የአንድ መንፈሳዊ ቤተሰብ አባላት ከመሆናቸው የተነሣ ነው።

Hebrews 2:13

ዕብራውያን **2**: **13**-**15**
እነንደገናም እንዲህ አለ አማራጭ ትርጉም: "እንደገናም ነቢይ በሌላ ቅዱስ መጽሐፍ ላይ ክርስቶስ ስለ እግዚአብሔር ያለውን እንዲህ ጽፎታል:" (UDB) የእግዚአብሔር ልጆች በዚህ ሥፍራ ላይ ይህ ቃል የሚያመለክተው መንፈሳዊ ልጆቹ የሆኑትን ሰወዎችን ነው። ለምሳሌ ያኽል፣ "የእግዚአብሔር ልጆች" የሚለው ቃል በኢየሱስ በማመን የእግዚአብሔር የሆኑትን ሰዎችን ነው። ሁሉም ሥጋንና ደምን ተካፍለዋል አማራጭ ትርጉም: "ሁሉም የሰው ልጆች ናቸውን" ሕይወታቸውን ሁሉ በባርነት ኖረዋል ይህ ሀረግ ምሳሌያዊ ነው። የሚያመለክተውም ሞትን በመፍራት ባርነት ውስጥ መኖራቸውን ነው።

Hebrews 2:16

ዕብራውያን **2**: **16**-**18**
አገኘ አማራጭ ትርጉም: "አገኘ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 3

1 ስለዚህ የሰማያዊ ጥሪ ተከፋዮች የሆናችሁ ቅዱሳን ወንድሞች የእምነታችንን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት የሆነውን ኢየሱስን አስቡ። **2** ሙሴ በእግዚአብሔር ቤት
ሁሉ ላይ ታማኝ እንደ ነበር ሁሉ፣ እርሱም ለሾመው ለእግዚአብሔር ታማኝ ነበር። **3** ቤቱን የሚሠራው ከራሱ ከቤቱ የበለጠ ክብር እንዳለው ሁሉ፣ ኢየሱስም
ከሙሴ ይልቅ የበለጠ ክብር እንደሚገባው ተቆጥሯል። **4** ማንኛውም ቤት ሠሪ አለው፤ ሁሉም ነገር የሠራ ግን እግዚአብሔር ነው። **5** ወደ ፊት መነገር
ለሚገባው ነገር ምስክር እንዲሆን፣ ሙሴም በእግዚአብሔር ቤት ሁሉ እንደ አገልጋይ ታማኝ ነበር። **6** ክርስቶስ ግን በእግዚአብሔር ቤት ሥልጣን ያለው ልጅ
ነው። የምንተማመንበትንና የመተማመናችንን ድፍረት አጥብቀን ብንይዝ ቤቱ ነን። **7** ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ፣ዛሬ ድምጹን ብትሰሙ **8** በምድረበዳ በፈተና ቀን
በአመጽ እንዳደረጋችሁት ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ። **9** ይህ የሆነው አባቶቻችሁ እኔን በመፈታተን ሲያምፁብኝና ዐርባ ዓመት ሙሉ ሥራዎቼን ባዩበት ጊዜ
ነበር። **10** ስለዚህ በዚያ ትውልድ ደስ አልተሰኘሁም። እንዲህም አልኩ፤ ልባቸው ሁል ጊዜ ይስታል መንገዴንም አላወቁም። **11** ስለዚህ በቁጣዬ፥ "ወደ እረፍቴ
አይገቡም" ብዬ ማልሁ። **12** ወንድሞች ሆይ ከእናንተ ማንም የማያምን ክፉና ከሕያው እግዚአብሔር ዘወር የሚል ልብ እንዳይኖረው ተጠንቀቁ። **13** ይልቁንስ
ከእናንተ ማንም በኃጢአት መታለል እልኸኛ እንዳይሆን ከዛሬ ጀምሮ በየዕለቱ እርስ በርሳችሁ ተበረታቱ። **14** ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ድረስ በእርሱ
ያለንን ድፍረት አጥብቀን ከያዝን ከክርስቶስ ጋር ተባባሪዎች እንሆናለን። **15** ስለዚህም፣ "ዛሬ ድምጹን ብትሰሙ በአመጽ ጊዜ እንደሆነው ልባችሁን እልከኛ
አታድርጉ" ተብሏል። **16** ለመሆኑ፣እነዚያ ድምፁን ሰምተው ያመፁት እነማን ነበሩ? ሙሴ እየመራ ከግብፅ ያወጣቸው ሁሉ አይደሉምን? **17** ለአርባ ዓመት
እግዚአብሔር የተቆጣባቸውስ እነማን ነበሩ? ኃጢአት ያደረጉና ሬሳቸው በበረሃ ወድቆ የቀረው አይደሉምን? **18** ደግሞስ እነዚያ ያልታዘዙት ካልሆኑ በቀር ወደ
ዕረፍቱ እንደማይገቡ እግዚአብሔር የማለባቸው እነማን ሊሆኑ ነው? **19** ባለማመናቸው ምክንያት ወደ ዕረፍቱ ሊገቡ እንዳልቻሉ እናያለን።

Hebrews 3:1

ዕብራውያን **3: 1-4**
ወንድሞች በዚህ ሥፍራ ላይ ይህ ቃል የሚያመለክተው ወንዶች እና ሴቶችን ያካተተ ክርስቲያኖችን ነው። ምክንያቱም በክርስቶስ የሆኑት እግዚአብሔር ሰማያዊ አባታቸው የሆኑ የአንድ መንፈሳዊ ቤተሰብ አባላት ናቸውና። የሃይማኖታችን አማራጭ ትርጉም: "እኛ የተቀበልነው" ወይም "እኛ ያመንበት"

Hebrews 3:5

ዕብራውያን **3: 5-6**
የእግዚአብሔር ቤት በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ያሉ ሰዎች ልጅ ይህ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው የኢየሱስ ወሳኝ ስም ነው። የምንደፍርበት የምንመካበት አማራጭ ትርጉም: "እኛ የምንመካበት ተስፋ አለን"

Hebrews 3:7

ዕብራውያን **3: 7-8**
አለመደሰት "ደስተኛ አለመሆን" በልባቸው ሁሉ ጊዜ ይኮበልላሉ አማራጭ ትርጉም: "ሁል ጊዜ እኔን ለመከተል አይፈልጉም" ወደ እረፍቴ አይገቡም "እኔ በሚገኝበት ሆነው እንዲያርፉ አልፈቅድላቸውም"

Hebrews 3:9

ዕብራዊያን **3:9-11**
ኖት የለውም።

Hebrews 3:12

ዕብራውያን **3: 12-13**
ወንድሞች በዚህ ሥፍራ ላይ ይህ ቃል የሚያመለክተው ወንዶች እና ሴቶችን ያካተተ ክርስቲያኖችን ነው። ምክንያቱም በክርስቶስ የሆኑት እግዚአብሔር ሰማያዊ አባታቸው የሆኑ የአንድ መንፈሳዊ ቤተሰብ አባላት ናቸውና። ከእናንተ በማንኛችሁም ውስጥ የማያምን ክፉ ልብ "ክፉ የሆነ፣ የማያምን ልብ በማናችሁም ውስጥ" ወይም "ማንኛችሁም ክፋትን እንዲታደርጉ የሚያደረግ የማያምን ልብ" ኮብላይ ልብ "እንድትኮበልሉ የሚያደርግ ልብ።" ሕያው አምላክ አማረጭ ትርጉም: 1) "በእርግጥ ሕያው የሆነ እውነተኛ አምላክ" ወይም 2) "ሕይወትን የሚሰጥ አምላክ።" ዛሬ ተብሎ ስጠራ ሳለ ዕድሉ እስካለ ድረስ ከእናንተ መካከል ማንም በኃጠአት ተታሎ ልቡን እንዳያደነድን አማራጭ ትርጉም: "እልከኛ እንዳይሆን፣ ሌሎች እንዲያስቱት እንዳይፈቅና ኃጢአት እንዳያደርግ" ወይም "ኃጢአትን አታድርግ፣ ራስህን አታታል እንዲሁም እለከኛ አትሁን"

Hebrews 3:14

ዕብራውያን **3: 14-15**
እኛም ሆነናልና ጸሐፊውና አንባቢያኑ ሁለቱም መተማመን ፍጹም የሆነ እምነት እስከ መጨረሻው ሞት ድምፁን "እግዚአብሔር" ወይም "እግዚአብሔር የተናገረውን" ልባችሁን አታደንድኑ፣እስራኤላዊያነ በአመፅ እንዳደረጉት ይህንን በ HEB 3:8 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከት።

Hebrews 3:16

ዕብራውያን **3: 16-19**
የእርሱ እረፍት የእግዚአብሔር ሕዝብ እግዚአብሔር የሰጣቸውን የተስፋ ቃላት ሁሉ ፍጻሜን አግኝቶ በመመልከት ሐሴት የሚያደርግበት እና መከራ ያሌለበት ሥፍራ ነው። እኛ ጸሐፊው እና አንባቢያኑ

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 4

1 ከእናንተ ማንም የእግዚአብሔር ዕረፍት ከሆነው ዘላቂ ተስፋ የሚጎድል እንዳይመስለው በጣም መጠንቀቅ አለብን። 2 ምክኒያቱም ለእስራኤላውያን እንደ
ተነገረ ሁሉ ለእኛም ስለ እግዚአብሔር ዕረፍት መልካም ዜና ተነግሮናል፤ ሆኖም፣ የሰሙትን መልእክት ሰሞዎቹ በእምነት ስላልተቀበሉት አልጠቀማቸውም። 3
“ወደ ዕረፍቴ አይገቡም፣ ብዬ በቁጣዬ ማልሁ” እንዳለው ሳይሆን እኛ ያመንን ግን ወደ ዕረፍቱ እንገባለን። የእርሱ ፍጥረት ሥራ ከዓለም መፈጠር ጀምሮ
የተጠናቀቀ ቢሆንም፣ 4 ስለ ሰባተኛ ቀን በማመልከት አንድ ቦታ “በሰባተኛው ቀን እግዚአብሔር ከሥራው ሁሉ ዐረፈ” ይላል። 5 ደግሞም፣ “ወደ ዕረፍቴ
አይገቡም” ይላል። 6 ወደ እግዚአብሔር ዕረፍት ለመግባት ለአንዳንዶች አሁንም የተጠበቀባቸው በመሆኑና ፣ መልካሙን ዜና ከሰሙት እስራኤላውያን ብዙዎቹ
ባለ መታዘዛቸው ምክንያት ወደ ዕረፍቱ ባለ መግባታቸው እግዚአብሔር በድጋሚ፣ 7 “ዛሬ” የተባለ ቀን ወስኖአል። 8 ኢያሱ አሳርፎአቸው ቢሆን ኖሮ፣
እግዚአብሔር ስለ ሌላ ቀን አይናገርም ነበር። 9 ስለዚህ ለእግዚአብሔር ሕዝብ አሁንም ቢሆን የሰንበት ዕረፍት ተጠብቆላቸዋል። 10 ምክንያቱም ወደ
እግዚአብሔር ዕረፍት የገባ ሰው እግዚአብሔር ከሥራው እንዳረፈ ሁሉ፣ እርሱም ከሥራው ያርፋል። 11 ስለዚህ ማንም የእነዚያን ሰዎች ዐመፅ ተከትሎ
እንዳይወድቅ ወደዚያ ዕረፍት ለመግባት እንናፍቅ። 12 የእግዚአብሔር ቃል ሕያው፣ የሚሠራና፣ ሁለት አፍ ካለው ሰይፍ ይልቅ፣ ስለታም ነው። ነፍስንና
መንፈስን፣ ጅማትንና ቅልጥምን እስኪለያይ ድረስ ይወጋል። የልብን ሐሳብና ውስጥን ይመረምራል። 13 ከእግዚአብሔር ፊት የሚሰወር ምንም ፍጥረት የለም።
እኛ ተጠያቂዎች በሆንንበት በእርሱ ዓይኖች ፊት ማንኛውም ነገር የተገለጠና የተራቆተ ነው። 14 እንግዲህ በሰማያት ያለፈ ታላቅ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር
ልጅ ኢየሱስ ስላለን፣ እምነታችንን አጥብቀን እንያዝ። 15 ነገር ግን እርሱ ከኃጢአት በቀር በማንኛውም ነገር እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ በድካማችን ሊራራልን
የማይችል ሊቀ ካህናት የለንምና። 16 ስለዚህ በሚያስፈልገን ጊዜ ምሕረትንና የሚረዳንን ጸጋ እንድንቀበል ወደ ጸጋው ዙፋን በድፍረት እንቅረብ።

Hebrews 4:1

ዕብራውያን 4: 1-2
ስለዚህ ምክንያም እግዚአብሔር በእርግጠኝነት የማይታዘዙትን ሰዎች ይቀጣልና (HEB 3:19) ከእናንተ መካከል ማንኛችሁም እግዚአብሔር ተስፋ ወደ ገባው የእግዚአብሔር እረፈት ሳይገባ እንዳይቀር አማራጭ ትርጉም: "ከእናንተ መካከል ማንንም እግዚአብሔር ወደ እርሱ አይገቡም ብሎ እንዳይናገር" ወይም "እግዚአብሔር ለሁላችሁም እርሱ ባለበት ያርፉ ዘንድ ተንግሯቸዋል" እንዲህ ማድረግ ይጠበቅብናል ጸሐፊው እና አንባቢያኑ ይህንን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ለእኛ ለጸሐፊዎቹ እና ለአንባቢያኑ በእምነት ከራሳቸው ጋር ሳያዋህዱ የሰሙት ሰዎች አማራጭ ትርጉም: "የኢየሱስን መልዕክት የሰሙት ነገር ግን ያላመኑት ሰዎች"

Hebrews 4:3

ዕብራውያን 4: 3-5
የፍጥረት ሥራው ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ተፈጽሟል። አማራጭ ትርጉም: "ዓለም ከመፈጠሩ በፊት እንኳ ዕቅዱ ሙሉ ለሙሉ ታውቋል።" ወደ እረፍቴ ፈጽሞ አይገቡም "እኔ ባለሁበት በዚያ አያርፉም"

Hebrews 4:6

ዕብራውያን 4: 6-7
አንዳንዶች ይገቡበት ዘንድ የእግዚአብሔር እረፍት ተጠብቆላቸዋል። "እግዚአብሔር አንዳንድ ሰዎች ከእርሱ ጋር ያርፉ ዘንድ ፈቅደቃል።" ድምፁ "እግዚአብሔር" ወይም "እግዚአብሔር እያለ ያለው" ልባችሁን አታደንድኑ ይህንን በ HEB 3:8 ላይ ምንም ብላችሁ እንደተረጎማችሁ ተመልከቱ።

Hebrews 4:8

ዕብራውያን 4: 8-11
ወደ እግዚአብሔር እረፍት የሚገቡት "እግዚአብሔር ባለበት ከእርሱ ጋር የሚያርፉት ሰዎች" ወደዚያ እረፍት ለመግባት እንትጋ "በተጨማሪ እግዚአብሔር በሚገኝበት ከእርሱ ጋር ለማረፍ ማድረግ የሚገባንን ነገር ሁሉ እናድረግ" እንትጋ "ፈቃደኞች እንሁን" ልክ አንደእነርሱ ባለመታዘዝ እንዳንወድቅ አማራጭ ትርጉም: "በተመሳሳይ መልኩ አለመታዘዝ" እነርሱ ያንን አደረጉ በበረሃ እስራኤላዊያን በእግዚአብሔር ላይ በማመጽ ያንንን አደረጉ

Hebrews 4:12

ዕብራውያን 4: 12-13
የእግዚአብሔር ቃል የእግዚአብሐየር ቃል ወይም እግዚአብሔር የተናገረው መልዕክት ሕያው እና የሚሠራ እግዚአብሔር ቃል ሕያው እንደሆነ፤ እንዲሁም ኃይል አለው። ከባለ ሁለት አፍ ሰይፍ ይልቅ አፍ ሰይፍ - የእግዚአብሔር ቃል ወደ ሰው ውስጥ ዘልቀው ይገባል።

የልብን ሀሳብ እና መነሻ ሀሰብ ያውቃል የእግዚአብሔር ቃል ድብቅ ሀሳባችንን እንኳ ሳይቀር ይገልጣል። and ሁሉ ነገር የተገለጸ ነው እንዲሁም በመጨረሻ ተጠያቂ በሚንሆንበት በእርሱ ፊት ሁሉ ነገር የተራቆተ ነው። "በአኗኗራችን መሠረት የሚፈርድብን እንዲሁም ሁሉንም ነገራችንን የሚመለከት እግዚአብሔር ነው።" የተራቆተ እና የተገለጠ ነው እነዚህ ሁለት ቃላት በመሠረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ አጽኖት የሚሰጡትን ከእግዚአብሔር ፊት ምንም የተሠወረ ነገር አለመኖሩን ነው።

Hebrews 4:14

ዕብራውያን 4: 14-16
ኢየሱስ የእግዚብሔር ልጅ፣ እምነታችንን አጥብቀን እንያዝ አማኞች “የእግዚአብሔር ልጅ” የሆነውን ኢየሱስን “አጥብቀው መያዝ” ይኖርባቸዋ። የእግዚአብሔር ልጅ ይህ የኢየሱስ እጅግ ወሳኝ የሆነ የማዕረግ ስም ነው። ለእኛ የማይራራ ሊቀ ካህን የለንም። "ያለን ሊቀ ካህን ለእኛ የሚራራ ነው።" እርሱ ኃጢአት የለበትም አማራጭ ትርጉም: "እርሱ ኃጢአት አላደረገም" የጸጋው ዙፋን አማራጭ ትርጉም: "ጸጋ የሚገኝበት የእግዚአብሔር ጸጋ" ወይም "ለጋስ የሆነው እግዚአብሔር በዙፋኑ ላይ ተቀምጧል።"

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 5

1 እያንዳንዱ ሊቀ ካህን ከሰዎች መካከል ይመረጣል፤ ለኃጢአት መሥዋዕትንና መባን ለማቅረብ እግዚአብሔርን በሚመለከት ጉዳይ እነርሱን በመወከል
ይሾማል። **2** እርሱ ራሱም በድካም ውስጥ ያለ በመሆኑ ዐላዋቂዎችንና ከመንገድ የሳቱትን ሊራራላቸው ሊቀበላቸው ይችላል። **3** ከዚህም የተነሣ ለሕዝቡ
ኃጢአት እንደሚያድርገው ሁሉ እርሱም ለገዛ ራሱ ኃጥአት መሥዋዕት ማቅረብ ይኖርበታል። **4** እንደ አሮን በእግዚአብሔር የተጠራ ካልሆነ በቀር ማንም ይህን
ክብር በራሱ አያገኘውም። **5** ክርስቶስ ራሱም ቢሆን ሊቀ ካህናት የመሆንን መብት በገዛ ራሱ አልወሰደም። ይልቁንም እግዚአብሔር ለእርሱ፣ **6** ይህም በሌላ
ቦታ፣ እግዚአብሔር፣እንደመልከጼዴቅ ሹመት አንተ ለዘላለም ካህን ነህ" ይላል። **7** ኢየሱስ ሰው ሆኖ በዚህ ምድር በነበረ ዘመን ፣ ከሞት ሊያድነው ወደሚችለው
አምላክ በታላቅ ጩኸትና በብዙ እንባ ጸሎትንና ልመናን አቀረበ። እግዚአብሔርን በመፍራቱም ጸሎቱ ተሰማለት። **8** ምንም እንኳ እርሱ ልጅ ቢሆንም፣
ከደረሰበት መከራ የተነሣ መታዘዝን ተማረ። **9** በዚህ ሁኔታ ሁሉ የዘላለም ድነት ምክንያት ሆነላቸው፤ **10** እግዚአብሔርም እንደ መልከጼዴቅ ሹመት ሊቀ
ካህናት አድርጎ ሾመው። **11** ስለ ኢየሱስ ብዙ የምንናገረው አለን፤ ሆኖም፣ ለመቀበል ዳተኞች ስለሆናችሁ፣ ለእናንተ ማስረዳት አዳጋች ነው። **12** እስከ አሁን
ድረስ መምህራን መሆን ሲገባችሁ፣ የእግዚአብሔርን ቃል መሠረታዊ መርሖዎች የሚያስተምራችሁ ሰው ገና ትፈልጋላችሁ። እናንተ የምትፈልጉት ወተት እንጂ፣
ጠንካራ ምግብ አይደለም። **13** ወተት ብቻ ሊጋት ማንኛውም ሰው ገና ሕፃን ስለሆነ የጽድቅ ትምህርት ልምምድ የለውም። **14** በሌላ በኩል ደግሞ ጠንካራ
ምግብ ግን መልካምንና ክፉውን መለየት ለተማሩና ትክክል የሆነውን ካልሆነው የመለየት ልምድ ላላቸው ትልልቅ ሰዎች ነው።

Hebrews 5:1

ዕብራውያን **5**:**1**-**3**
በእነርሱ ፈንታ ይፈጽማል አማራጭ ትርጉም: "እነርሱን ይወክላል" ይገባቃል አማራጭ ትርጉም: "ይጠበቅበታል"

Hebrews 5:4

ዕብራውያን **5**: **4**-**5**
ልጅ . . . አባት ይህ በኢያሱስ እና በእግዚአብሔር አባት መካል ያለውን ግንኙነት የሚያሳይ በጣም ወሳኝ የሆነ የማዕረግ ስም ነው።

Hebrews 5:6

ዕብራውያን **5**: **6**-**6**
እንደገናም እንዲህ አለ እግዚአብሔርም እንዲህ አለ (HEB 5:5)

Hebrews 5:7

ዕብራውያን **5**: **7**-**8**
በሥጋው ወራት አማራጭ ትርጉም: "በምድር ላይ ሲኖር ሳለ" ልጅ፣ በዚህ ሥፍራ ላይ ይህ ቃል የሚያመለክተው የሰው ልጅ ሆኖ ወደ ምድር የመጣውን የእግዚአብሔር ልጅ የሆነውን ኢየሱስን ነው።

Hebrews 5:9

ዕብራውያን **5**: **9**-**11**
ፈጸመ በዚህ ሥፍራ ላይ ይህ ቃል የሚያመለክተው "ማጠናቀቅን" ወይም "ሙሉ መሆንን" ነው። እናንተ ለማድመጥ የዘገያችሁ ናችሁ "እናንተ ለመረዳት የዘገያችሁ ናችሁ" ወይም "እናንተ ለማድመጥ ምንም ፍላጉት የላችሁም"

Hebrews 5:12

ዕብራውያን **5**: **12**-**14**
መርሆዎች በዚህ ሥፍራ ላይ ይህ ቃል ያለው ትርጉም መመረያ ወይም ውሳኔ ለመወሰን የሚረዳ መርህ ነው። ወተት መሠረታዊ የሆነ መንፈሳዊ እውነቶች ጠንካራ ምግብ "ጠንካራ መንፈሳዊ እውነቶች"

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 6

1 ስለዚህ ስለ ክርስቶስ መልእክት በመጀመሪያ የተረዳነውን ተወት በማድረግ ወደ ብስለት ልንሻገር ይገባናል እንጂ ከሞተ ሥራ ንስሐ መግባትንና
በእግዚአብሔር ማመንን፣ 2 ወይም ጥምቀቶችን፣እጆች መጫንን፣ የሙታን ትንሳኤን እንዲሁም የዘላለም ፍርድን ወደ ሚመለከት መሠረትን የመጣል ትምህርት
መመለስ አይገባንም። 3 እግዚአብሔር ከፈቀደ እነዚህንም እናደርጋለን 4 ይህንን የምናደርገው አንድ ጊዜ ብርሃን በርቶላቸው ሰማያዊውን ስጦታ
የተቀበሉትን፣ከመንፈስ ቅዱስ ተሳታፊዎች የነበሩትን፣ 5 መልካሙን የእግዚአብሔር ቃልና በመጪው ዘመን ሊመጣ ያለውን ኃይል ከቀመሱ በኋላ 6 የካዱትን
በንስሐ እንዲታደሱ ማድረግ የማይቻል በመሆኑ ነው። እነዚህ ለሕዝብ መሳለቂያ ይሆን ዘንድ ራሱን የእግዚአብሔርን ልጅ ራሳቸው እንደገና ይሰቅሉታል። 7
በእርሷ ላይ ብዙ ጊዜ የሚዘንበውን ዝናብ ተቀብላ ለደከሙባት የሚጠቅም ፍሬን የምታፈራ መሬት ከእግዚአብሔር በረከትን ትቀበላለች። 8 እሾህና አሜኬላ
የምታበቅል ከሆነች ግን ዋጋ ቢስና እርግማን የሚጠብቃት ትሆናለች፣ ፍጻሜዋም መቃጠል ይሆናል። 9 እንደዚህ የምንናገር ብንሆንም፣ ወዳጆች ሆይ፣
እናንተንና ድነታችሁን በሚመለከት ግን የተሻለ ነገር ስለ መኖሩ እርግጠኞች ነን። 10 ምክንያቱም ቅዱሳንን በማገልገላችሁና አሁንም እያገለገላችኋቸው
በመሆኑ ለስሙ ያላችሁን ፍቅር በማሳየት የሠራችሁትን ሥራ ይረሳ ዘንድ እግዚአብሔር ዓመፀኛ አይደለም። 11 በፍጹም የመተማመን ዋስትና እያንዳንዳችሁ
ይህንኑ ትጋት እስከመጨረሻ እንድታሳዩ በእጅጉ እንናፍቃለን። 12 ከእምነትና ከትዕግሥት የተነሣ የተስፋ ቃሉን የሚወርሱትን እንድትመስሉ እንጂ ቸልተኞች
እንድትሆኑ አንፈልግም። 13 ምክንያቱም እግዚአብሔር ለአብርሃም የተስፋ ቃል በገባለት ጊዜ ከራሱ በሚበልጥ በማንም ሊምል ስላልቻለ 14 “በእርግጥ
እባርክሃለሁ፣ ዝርያዎችህንም እጅጉን አበዛለሁ” በማለት በራሱ ምሎአልና። 15 በዚህ መንገድ በትዕግሥት ከጠበቀ በኋላ ተስፋ የተገባለትን ተቀበለ። 16
ሰዎች ከእነርሱ በሚበልጠው ይምላሉና፣ በመካከላቸው ለሚፈጠርውም ለማንኛውም ሙግት መሐላ የመጨረሻው ማጽኛ ነው። 17 የዓለማውን የማይለወጥ
ባሕርይ ለተስፋው ወራሾች ይበልጥ ግልጽ አድርጎ ለማሳየት እግዚአብሔር በወሰነ ጊዜ በመሃላ አጸናው። 18 ይህንን ያደረገው እግዚአብሔር ሊዋሽ
በማይችልባቸው ሁለት የማይለወጡ ነገሮች በፊታችን ያለውን መተማመኛ አጥብቀን ይዘን አምባ ፍለጋ ለሸሸን ለእኛ ብርቱ ድፍረት ይሆንልን ዘንድ ነው። 19
ከመጋረጃው በስተጀርባ ወዳለው ቅድስት የሚገባውና እኛ የያዝነው ይህ መተማመኛ፣ ሥጋት የሌለበትና አስተማማኝ የነፍሶቻችን መልሕቅ ነው። 20 በመልከ
ጼዴቅ ሥርዓት ለዘላለም ሊቀ ካህናት በመሆን ኢየሱስ ወደዚህ ስፍራ ለእኛ ቀዳሚ በመሆን ገብቷል።

Hebrews 6:1

ዕብራውያን **6**: **1**-**3**
ወደፊት መግፋት ይኖርብናል አማራጭ ትርጉም: "ወደፊት መገስገስ ይኖርብናል" እጆቻችንን በመጫን ይህ ዓይነቱ ልምምድ የሚደረገው አንድ ነው ለልዩ አገልግሎት ወይም ሥልጣን ለመለየት ነው።

Hebrews 6:4

ዕብራውያን **6**: **4**-**6**
ሰማያዊ ስጦታን የቀመሱ ይህ የሚያመለክተ እግዚአብሔር ያዳናቸውን አማኞችን ነው። የእግዚአብሔር መልካም ቃል የቀመሱትን ይህ የእግዚአብሔርን ቃል ራሳቸው አማኞችን የሚያመለክት ነው። የእግዚአብሔርን ልጅ ይሰቅሉታል ሰዎች ከእግዚአብሔር ፊታቸውን ሲያዞሩበት ልክ ኢየሱስን እንደሚሰቅሉት ነው። ወደቁ አማራጭ ትርጉም: "ከእግዚአብሔር ፊታቸውን አዙሩ"

Hebrews 6:7

ዕብራውያን **6**: **7**-**8**

Hebrews 6:9

ዕብራውያን **6**: **9**-**10**
እግዚአብሔር ይረሳ ዘንድ አመጸኛ አይደለም አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር ፍትሐዊ ነው እንዲሁም አይዘነጋም" HEB << | HEB >>

Hebrews 6:11

ዕብራውያን **6**:**11**-**12**
ታታርነት ጥንቃቄ የተሞላበት በትጋት መሥራት ዳተኛ ሰነፍ መመስል የሌላውን ሰው ባሕርይ ለመምሰል የሚደረግ ጥረት

Hebrews 6:13

ዕብራውያን **6**: **13**-**15**
እንዲህ ይላል እግዚአብሔር እንዲህ ይላል

Hebrews 6:16

ዕብራውያን **6**: **16**-**18**

Hebrews 6:19

ዕብራውያን **6**: **19**-**20**
እርግጥ እና ጽኑ መልሕቅ በዚህ ሥፍራ ላይ “እርግጥ” እና “ጽኑ” ተብለው የተተረጎሙት ቃላት በመሠረታዊ ትርጉማቸው ተመሳሳይ ሲሆኑ አጽኖት ሰጥተው የሚያሳዩት መልሕቁ ላይ ሙሉ ለሙሉ አስተማማኝ መሆኑን ነው። አማራጭ ትርጉም: "ፈጽም አስተማማኝ መሕልቅ" የነፍሳችን መሕልቅ መሕልቅ ጀልባ በውሃ ተንድታ እንዳትወሰድ እንደሚያደረግ ሁሉ ኢየሱስ በእግዚአብሔር መገኘት ውስጥ እንድንሆን ያደርገናል። ስለእኛ ቀዳሚ ነው "ስለ እኛ ሲል ቀድሞ የሄደ"

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 7

1 የሳሌም ንጉሥና የልዑል እግዚአብሔር ካህን የነበረው ይህ መልኬ ጼዴቅ የባረከው አብርሃምን ነገሥታቱን ድል አድርጎ ሲመለስ ነበር። **2** አብርሃምም ከማረጀው ከማንኛውም ነገር አንድ አሥረኛውን ለእርሱ ሰጠው። ‘መልኬ ጼዴቅ’ የሚለውም የስሙ ትርጉም ‘የጽድቅ ንጉሥ’ ደግሞም ‘የሳሌም ንጉ’ ማለትም ‘የሰላም ንጉሥ’ ማለት ነው። **3** እርሱ አባትም ሆነ እናት፣ የትውልድ ሐረግም ሆነ የጅማሬ ወይም የፍጻሜ አመን የሌለው ነው። ይልቁንም እንደ እግዚአብሔር ልጅ ሁሉ እርሱም ካህን ሆኖ ለዘላለም ይኖራል። **4** ይህ ሰው እንግዲህ ምን ያህል ታላቅ እንደነበረ አስቡ። አባታችን አብርሃም በጦርነት ካገኛቸው ምርጥ ነገሮች አንድ አሥረኛ የሚሆነውን ሰጥቶታል። **5** በእርግጥ የክህነቱን አገልግሎት የተቀበሉትም የሌዊ ዝርያዎች ከአብርሃም ዝርያ የተገኙ ቢሆኑም ከሕዝቡ ማለትም ከእስራኤላውያን ወገኖቻቸው አሥራትን ይሰበስቡ ዘንድ በሕጉ ታዘዋል። **6** ይሁን እንጂ የሌዊ ዝርያ ያልነበረው መልኬ ጼዴቅ የተስፋ ቃሎች ከነበሩት ከአብርሃም አሥራትን ተቀበለ፣ ባረከውም። **7** ታናሹ በታላቁ እንደሚባረክ የሚካድ ነገር አይደለም። **8** በአንድ በኩል ስናየው አሥራትን የሚቀበሉ ሰዎች አንድ ቀን ይሞታሉ በሌላ በኩል ስንመለከተው ግን ከአብርሃም አሥራትን የተቀበለው ሕያው ሆኖ እንደሚኖር ተገልጿል። **9** በሌላ አነጋገር አሥራትን ይቀበል የነበረው ሌዊ እንኳን በአብርሃም በኩል አሥራትን ሰጥቷል። **10** ምክንያቱም መልኬ ጼዴቅ አብርሃምን ባገኘው ጊዜ ሌዊ በቀደምት አባቱ በአብርሃም አብራክ ውስጥ ነበረና። **11** ሕዝቡ ሕጉን የተቀበሉት በዚህ ሥርዓት በነበሩ ጊዜ ነበርና ፍፁምና በሌዊ ክህነት ማግኘት የሚቻል ቢሆን ኖሮ በአሮን ሥርዓት ሳይሆን በመልከ ጼዴቅ ሥርዓት የሚሾም ሌላ ካህን ወደፊት ይነሳ ዘንድ ምን ያስፈልግ ነበር? **12** ክህነቱ የሚለውጥ ከሆነ ደግሞ ሕጉም መለወጥ ይገባዋል። **13** እነዚህ ነገሮች እየተነገሩለት ያለው ከወገኖቹ ከቶ ማንም በመሠዊያው ላይ አገልግሎ የማያውቅ የሌላ ነገድ ወገን ነውና። **14** እንግዲያውስ ጌታችን ካህናትን በሚመለከት ሙሴ ከቶውንም ምንም ካልተናገረለት ከይሁዳ ነገድ የመጣ መሆኑ ግልጽ ነው። **15** መልከ ጼዴቅን የመሰለ ሌላ ካህን ቢነሳ የምንለው ይበልጥ ግልጽ ይሆናል። **16** ይሄኛው ካህን ደግሞ ሰብዓዊ ዝርያን መሠረት በሚያደርገው ሕግ ሳይሆን የማይጠፋ የሕይወት ያይልን መሠረት ባደረገ ሕግ ካህን የሆነ ነው። **17** ቅዱሳት መጻሕርትም ስለ እርሱ እንዲህ ሲሉ ይመሰክራሉ፦ “በመልከ ጼዴቅ ሥርዓት አንተ ለዘላለም ካህን ነህ” **18** የቀደመው ትዕዛዝ ገለል የተደረገው ደካማና የማይጠቅም በመሆኑ ነውና። **19** ሕጉ ፍጹም ያደረገው ምንም ነገር አልነበረምና። ይሁን እንጂ ከዚህ በኃላ ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበት የተሻለ መተማመኛ አለ። **20** ይሄኛው የተሻለው መተማመኛ ግን ያለ መሃላ እውን አልሆነም፣ ምክንያቱም እነዚህ ሌሎቹ ካህናት ምንም መሃላ አልፈጸሙም። **21** “ጌታ ምሎአል ሃሳቡንም አይቀይርም፤ ‘አንተ ለዘላለም ካህን ነህ’” ተብሎ እንደተጻፈ። **22** በዚህም ደግሞ ኢየሱ ለሚሻል ኪዳን ዋስ ሆኖአል። **23** በእርግጥም ሞት ካህናቱን ለዘላለም ከማገልገል ያግዳቸዋል። እብንዱ ሌላውን እየተካ፣ ካህናት የሆኑት የበዙት ከዚህ የተነሣ ነው። **24** ኢየሱስ ግን ለዘላለም ስለሚኖር የእርሱ ክህነት የማይለወጥ ነው። **25** ስለዚይ ስለ እነርሱ ለማልድ ምን ጊዜም በሕይወት ስለሚኖር በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡትን ሙሉ በሙሉ ሊያድናቸው ይችላል። **26** እንደዚህ ያለው ማለትም ኃጢአትና ነቀፋ የሌለበት፣ ንጡሕ፣ ከኃጢአተኞች የተለየ ከሰማያትም በላይ ከፍ ያለ ሊቀ ካህን ሊኖረን ይገባል። **27** እርሱ ሊቀ ካህናቱ ሲያደርጉት እንደነበረው በመጀመሪያ ራሱ ለሠራቸው ኃጢአቶች ከዚያም ሕዝቡ ሁሉ ለፈፀሟቸው ኃጢአቶች በየቀኑ መሥዋዕቶችን ማቅረብ አያስፈልገውም። ራሱ አሳልፎ በሰጠ ጊዜ ይህንን ለአብዴና ለመጨረሻ ጊዜ አድርጎታል። **28** ሕጉ ድካም ያለባቸውን ሰዎች ሊቀ ካህናት አድርጎ ይሾማልና፣ ከሕጉ በኃላ የመጣው የመሐላው ቃል ግን ለዘላለም ፍጹም የተደረገውን ልጁን ሾሟልና።

Hebrews 7:1

ዕብራዊያን 7፡ 1-3
እርሱ አባት የለው መልከጼደቅ አባት የለውም የዘመን ጅማሬ ወይም የሕይወት ፍጻሜም የለውም መልከጼደቅ የተወለደበትን ወይም የሞተበትን ዘመን የሚያሳይ ምንም መረጃ የለም።

Hebrews 7:4

ዕብራውያን 7፡4-6
የክህነት አገልግሎት የተሰጣቸው ከሌዊ ወገን አማራጭ ትርጉም: "ካህናት የሚሆኑት ከሌዊ ወገን የሆኑት ናቸው።" የሌዊ ወገን የሆኑት ሁሉ ግን ካህናት አይሆኑም።

Hebrews 7:7

ዕብራውያን 7፡ 7-10
was in the private parts of his ancestor Abraham AT: "had not yet been born"

Hebrews 7:11

ዕብራውያን 7፡ 11-12
what further need was there for another priest to arise after the order of Melchizedek, and not be named after the order of Aaron? "no one would have needed another priest, one who was like Melchizedek and not like Aaron, to arise."

Hebrews 7:13

ዕብራውያን 7፡ 13-14

Hebrews 7:15

ዕብራውያን 7፡ 15-17
ከሰው ዘር ጋር ግንኙነት ያላቸው ሕጎች ክርስቶስ የሌዊ ወገን ሳይሆን ካህን መሆን ይችል ነበር። እንደ መልከ ጼደቅ ሹመት አማራጭ ትርጉም: "እንደ መልከ ጼደቅ"

Hebrews 7:18

ዕብራውያን 7፡ 18-19
ሕጉ ምንም ነገርን ፍጹም ማድረግ አይችልም ይህ የሚያሳየው ሕግ “ደካማ እና ጥቅም ያሌለው” መሆኑን ያሳያል፤ ስለዚህም “ልሻር” ይገባዋል። መቅረብ "ቅረቡ"

Hebrews 7:20

ዕብራውያን 7፡ 20-21
ይህ የተሻለው ማስተማመኛ በመሓላ ባይረጋገጥ ኖሮ ባልሆነም ነበር "የተሻለ መተማመን ይኖረን ዘንድ ዘንድ ሰው በመሓላ ማረጋገጥ ይኖርበታል” ወይም “. . . ክርስቶስ ካህን ሆኖ ለመሾም” አንተ ለዘላለም ካህን "አንተ ሁል ጊዜም ካህን ነህ እንዲሁም ካህን ትሆናለህ" (UDB)።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Hebrews 7:22

ዕብራውያን 7: 22-24
ማረጋገጫ "ማረጋገጫ" ወይም "ተስፋ" his priesthood is unchangeable "he will remain a high priest forever"

Hebrews 7:25

ዕብራውያን 7: 25-26
ሰማይ. ሰማይ፣ ሰማያዊ ስለዚህ "ክርስቶስ ለዘላለም ሊቀ ካህናችን ስለሆነ" በእርሱ በኩል "እርሱ ካደረገልን ነገር የተነሣ"

Hebrews 7:27

ዕብራውያን 7: 27-28
ምንም አያስፈልገውም "ክርስቶስ አያስፈልገውም" ሕጉ ይፈቅዳል "እግዚአብሔር በሕጉ በኩል በፈቀደው መሰረት" ከሕጉ በኋላ የመጣው የመሓላ ቃል ልጁን ሾመው። "ሕጉን ከሰጠ በኋላ እግዚአብሔር ማለ እንዲሁም ልጁን ሾመው" ፍጹም የሆነውን "እግዚአብሔርን ፈጽሞ የታዘዘውን እና ፍጹም የሆነውን" ራሱን መስዋእት አድርጎ ሰጠ . . . ለዘላለም ራሱን ፍጹም ያደረገውን ልጁን የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ራሱን ለዓለም ሁሉ ኃጢአት ብቸኛ ፍጹም መስዋእት አድርጎ ሰጠ። እግዚአብሔር ስለዓለም ሁሉ ኃጢአት ሌላ መስዋእትን አይቀበልም ነበር ምክንያቱም ፍጹም፣ ለሁሉም የሚሆን እና ቅዱስ የሆነ ሌላ መስዋእት ልኖር ስላማይችል ነው። እግዚአብሔር እራሱ መስዋእት መሆን ይገባው ነበር ስለዚህም የእግዚአብሔር ልጅ ዘላለማዊ የኃጢአት ይቅርታን ለማስገኘት ሲል ሕይወቱን አሳልፎ ሰጠ። ልጅ ይህ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው የኢየሱስ ወሳኝ የማዕረግ ስሙ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 8

1 እንግዲህ ልንናገር የፈለግነው ጉዳይ ዋና ነጥቡ ይሄ ነው፦ በሰማያት በልዑል እግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ የተቀመጠ ሊቀ ካህን አለን። 2 እርሱ እግዚአብሔር
በተከላት እውነተኛይቱ የማደሪያ ድንኳን፣ በተቀደሰው መቅደስ አገልጋይ የሆነ ነው እንጂ ማንኛውም ሟች ሰው አይደለም። 3 ማንኛውም ሊቅቀ ካህናት
የሚሾመው ስጦታዎችንና መሥዋዕቶችን ለማቅረብ በመሆኑ፣ የሚቀርብ ነገር ይዞ መገኘት አስፈላጊ ነው። 4 ታዲያ ክርስቶስ አሁን በምድር ላይ የሚኖር ቢሆን
በሕጉ መሠረት ስጦታዎችን የሚያቀርቡ ስላሉ እርሱ በፍጹም ካህን መሆን ባልቻለም ነበር። 5 የማደሪያ ድንኳኑን ለመሥራት በተነሣ ጊዜ እግዚአብሔር
ሙሴን”አስተውል፣ በተራራው ላይ ባየኸው ምሳሌ መሰረት ማንኛውንም ነገር እንድትሠራ” በማለት እንዳስጠነቀቀው ሁሉ እነርሱ የሰማያዊ ነገሮች ጥላና
ግልባጭ የሆኑ ነገሮችን የሚያገለግሉ ናቸው። 6 ነገር ግን በተሻለ ተስፋ ላይ የተመሠረተ የተሻለ ኪዳን መካከለኛው በመሆኑ ክርስቶስ አሁን የላቀ አገልግሎት
ተቀብሏል። 7 ያ የመጀመሪያው ኪዳን ነቀፋ ካልነበረው ሁለተኛ ኪዳን የሚፈለግበት ምንም ምክንያት አይኖርም ነበር። 8 እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ነቀፋ ባገኘ
ጊዜ እንደዚህ ብሎ ነበርና”አስተውሉ፣ ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት ዘመን ይመጣል” ይላል እግዚአብሔር። 9 “ከግብፅ
ምድር በእጆቼ መርቼ ባወጣኋቸው በዚያን ዘመን ከአባቶቻቸው ጋር እንደገባሁት እንደዚያ ቃል ኪዳን አይሆንም። በዚያ ኪዳኔ አልጸኑምና እኔም ችላ አልኳቸው”
ይላል እግዚአብሔር። 10 “ከእነዚያ ዘመናት በኋላ ከእስራኤል ቤት ጋር የምገባው ይህንን ኪዳን ነው፥ ‘ሕጌን በልቦናቸው አኖራለሁ፣ በልቦቻቸውም ላይ
እጽፈዋለሁ። አምላካቸው እሆናለሁ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ። 11 እያንዳንዱ ጎረቤቱን እያንዳንዱም ወንድሙን፥ ‘እግዚአብሔርን እወቅ እያለ አያስተምርም፣
እጅግ ታናሽ ከሆነው ጀምሮ እጅግ ታላቅ እስከሆነው ድረስ ሁሉም ያውቁኛልና። 12 በዓመፅ ለፈጸሟቸው ድርጊቶች ሁሉ ምሕረት አደርጋለሁና ኃጢአቶቻቸውንም
ከእንግዲህ አላስብምና” 13 ‘አዲስ’ በማለቱም የመጀመሪያው ኪዳን አስረጅቷል። አሮጌ ነው ብሎ የገለጸውም ሊወገድ ተቃርቧል።

Hebrews 8:1

ዕብራውያን **8**: **1**-**2**

Hebrews 8:3

ዕብራውያን **8**: **3**-**5**
ቅጂ እና ጥላ እነዚህ ቃላት በመሠረታዊ ትርጓመማቸው ተመሳሳይ ናቸው። አጽኖት ሰጥተው የሚያስተላልፉትም መልዕክት የመገናኛ ድንኳኑ በሰማይ ያለው የመገናኛ ድንኳን ምሳሌ መሆኑን ነው። አማራጭ ትርጉም: "ግልጽ ያልሆነ ምስል" ምሳሌ "ዲዛይን"

Hebrews 8:6

ዕብራውያን **8**: **6**-**7**
ክርስቶስ ተቀብሏል "እግዚአብሔር ለክርስቶስ ሰጥቶታል" ነቀፋ ያሌለበት ፍጹም

Hebrews 8:8

ዕብራውያን **8**: **8**-**9**
ተመልከት አማራጭ ትርጉም: "ተመልከት" ወይም "አድምጥ" ወይም "አሁን ልነግራችሁ ያለሁትን ነገር በጥንቃቄ አድምጡ።"

Hebrews 8:10

ዕብራውያን **8**: **10**-**10**

Hebrews 8:11

ዕብራውያን **8**: **11**-**12**

Hebrews 8:13

ዕብራውያን **8**: **13**-**13**

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 9

1 የመጀመሪያው ኪዳን ቢሆን በዚህ ምድር ለሚከናወነው አምልኮም ሆነ ለአምልኮ ደንቦች ስፍራ ነበረው። 2 በመገናኛው ድንኳን የተዘጋጀ ቅድስት የተባለ
ውጨኛ ክፍል ነበር። በዚህ ስፍራ መቅረዙ፣ ጠረጴዛውና የመንግስቱ መገለጫ ኅብስት ነበሩበት። 3 ከሁለተኛው መጋረጃም በስተጀርባ ቅድስተ ቅዱሳን የተባለ
ሌላ ክፍል ነበረ። 4 ዕጣን ለማጠን የሚሆን የወርቅ መሠዊያ ነበረው። ሙሉ በሙሉ በወርቅ የተለበጠ የኪዳን ታቦትም ነበረበት። በእርሱም ውስጥ መና
ያለበት የወርቅ መሶብ፣ ያቆጠቆጠች የአሮን በትርና የኪዳኑ የድንጋይ ጽላቶች ነበሩት። 5 በኪዳኑም ታቦት ላይ በስርየት መክደኛው ላ ያሰፈፉ የከበሩ የኩሩቤል
ምስሎች ነበሩ። ይሁን እንጂ ስለ እነዚህ ሁሉ አሁን በዝርዝር መግለጽ አንችልም። 6 እነዚህ ሁሉ ነገሮች ከተዘጋጁ በኃላ፣ ካህናቱ አገልግሎቶቻቸውን ለመፈጸም
በመደበኛነት በማደሪያው ድንኳን ውጫዊው ክፍል በኩል ይገባሉ። 7 ሊቀ ካህናቱ ግን በዓመት አንድ ጊዜ ወደ ሁለተኛው ክፍል ይገባል፣ በሚገባበትም ጊዜ
ለራሱና ሕዝቡም ባለማወቅ ለፈጸሟቸው በደሎች የደም መሥዋዕት ይዞ እንጂ እንደዚሁ አይደለም። 8 የመጀመሪያይቱ የመገናኛ ድንኳን በስፍራዋ ቆማ
እስካለች ድረስ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የሚያመራው መንገድ ገና እንዳልተገለጠ መንፈስ ቅዱስ በምሳሌ እያሳየ ነው። 9 ይህም ለአሁኑ ጊዜ ተምሳሌት ነው።
አሁን እየቀረቡ ያሉት ስጦታዎችም ይሁኑ መሥዋዕቶች የአምላኪውን ሕሊና ፍጹም ማድረግ የሚችሉ አይደሉም። 10 ከተለያዩ የመንፃት ሥርዓቶች ጋር የተያያዙ
ምግቦችና መጠጦች ብቻ ናቸው። እነዚህ ሁሉ አዲሱ ሥርዓት በሥራ ላይ እስኪውል ድረስ በሥጋዊ ደረጃ እንዲከበሩ የተሰጡ ሥርዓቶች ናቸው። 11 ክርስቶስ
በሰው እጆች በተሠራችው ሳይሆን ላቅ ባለችውና ይበልጥ ፍጹምና ቅድስት በመሆነችው፣ ከዚህም ከፍጥረታዊው ዓለም ባልሆነችው ድንኳን በኩል ለመጡት
መልካም ነገሮች ሊቀ ካህናት ሆኖ መጥቷል። 12 ክርስቶስ እጅግ ቅድስት ወደሆነችው ስፍራ አንድ ጊዜ ለሰዎች ሁሉ የገባውና የዘላለም ቤዛችንን ያስገኘልን
በፍየሎችና በጥጃዎች ደም ሳይሆን በራሱ ደም ነው። 13 የፍየሎችና የኮርማዎች ደም እንዲሁም የጊደሮች አመድ በሥርዓታዊ ደረጃ ንፁሕ ባልሆኑት ላይ
መረጨቱ የሚያጠራቸውና ሰውነቶቻቸውንም ንፁሕ የሚያደርገው ከሆነ፣ 14 ይልቁንም ነውር ሳይኖረው በዘላለማዊ መንፈስ ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበ
የክርስቶስ ደም ሕያው እግዚአብሔርን እናገለግል ዘንድ ሕሊናችንን ከሞተ ሥራ ምን ያህል ያነጻን ይሆን? 15 ከዚህም የተነሳ ክርስቶስ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ
ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት በእግዚአብሔር የተጠሩት ስለ ዘላለም ርስት የተሰጣቸውን የስፋ ቃል ይቀበሉ አንድ በመጀመሪያው ኪዳን ሥር ከነበረባቸው
የኃጢአት ቅጣት ነፃ እንዲወጡ የሞት ቅጣት ተፈጽሞ ስለነበረ ነው። 16 ይህም የሆነው አንድ ሰው ኑዛዜ እንደተወ ሲገለጽ ኑዛዜ የተወውን ሰው መሞት
ማረጋገጥ አስፈለጊ ነው። 17 ምክንያቱም ኑዛዜ የሚጸናው ሞት ተከስቶ ከሆነ ብቻ ነው፣ ተናዛዙ በሕይወት እስካለ ሊጸና አይችልምና። 18 እንደዚህም
በመሆኑ የመጀመሪያው ኪዳን እንኳን ያለ ደም አልጸናምና። 19 በሕጉ ውስጥ ያሉትን ማንኛቸውንም ትዕዛዛት ሙሴ ለሕዝቡ ሁሉ በሰጠ ጊዜ የጥጆችንና
የፍየሎችን ደም ከውሃ፣ ከቀይ የበግ ፀጉርና ከሂሶጵ ጋር ቀላቅሎ በራሱ በሕጉ መጽሐፍና በሕዝብ ሁሉ ላይ ይረጭ ነበርና። 20 ይህንንም ካደረገ በኃላ
“እግዚቸብሔር ለእናንተ ሕግጋቱን የሰጠበት የኪዳኑ ደም ይህ ነው” ይል ነበር። 21 በዚያው ዓይነት መንገድ ደሙን በመገናኛው ድንኳንና ለክህነት አገልግሎት
በሚውሉት ዕቃዎች ሁሉ ላይ ይረጭ ነበር። 22 ሕጉ በሚለውም መሠረት ሁሉም ነገር የሚነጻው በደም ነበር ማለት ይቻላል። ደምም ካልፈሰሰ በስተቀር
ይቅርታ የለም። 23 ስለሆነም በሰማይ ያሉት ነገሮች ግልባጮችም በእነዚህ የእንስሳት መሥዋዕቶች ይነጹ ዘንድ አስፈለጊ ነበር። ይሁን እንጂ ሰማያዊ የሆኑት
ነገሮች ራሳቸው እጅግ በተሻሉ መሥዋዕት መንጻት ይገባቸዋል። 24 ክርስቶስ በእጅ ወደተሠራው የእውነተኛውም ግልባጭ ብቻ ወደነበረው ቅድስተ ቅዱሳን
አልገባምና። ይልቁንም እርሱ የገባው እግዚአብሔር ባለበት ስለ እኛ አሁን እግዚአብሔር ፊት ወደሚቀርብበት ሰማይ በቀጥታ ገብቷል። 25 ወደዚያም የገባው
የሌላውን ደም ይዞ በየዓመቱ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን እንደሚገባው እንደ ሊቀ ካህናቱ በየጊዜው ራሱን ለማቅረብ አይደለም። 26 እንደዚያ ቢሆን ኖሮ ከዓለም
ጅማሬ አንስቶ ብዙ ጊዜ መከራ መቀበል ባስፈለገው ነበር። አሁን ግን ራሱን መሥዋዕት በማድረግ ኃጢአትን ለማስወገድ በዘመናት መጨረሻ የተገለጠው አንድ
ጊዜ ብቻ ነው። 27 እያንዳንዱ ሰው አንድ ጊዜ መሞት ከዚያ በኃላም ወደ ፍርድ መቅረብ እንደሚገባው ሁሉ 28 እንደዚሁም የብዙዎችን ኃጢአት ለማስወገድ
መሥዋዕት ሆኖ የቀረበው ክርስቶስ ኃጢአትን ለማስወገድ ዓላማ ሳይሆን በትዕግሥት ለሚጠባበቁት ድነትን ያስገኝላቸው ዘንድ ዳግመኛ ይገለጣል

Hebrews 9:1

ዕብራውያን **9**: **1-2**
የመጀመሪያው ኪዳን ይህንን በ HEB 8:7. ላይ በተረጎምከው መሠረት ተርጉመው። ደንቦች "ዝርዝር መመሪያዎች" ወይም "ሕግጋቶች" ወይም "አቅጣጫ ጠቋሚ ሕጎች" ስለዚህ ጸሐፊው በ HEB 8:7. ላይ የጀመረውን ሐተታ ቀጥሏል። ክፍል ተዘጋጅቷል "እስራኤላዊያን ክፍል አዘጋጅተው ነበር" በመስዋእት ህብስት "በእግዚአብሔር ፊት የሚቀርብ ህብስት" (UDB) ወይም "ካህናት በእግዚአብሔር ፊት የሚያቀርቡት ህብስት"

Hebrews 9:3

ዕብራውያን **9**: **3-5**
ከሁለተኛው ማጋረጃ በኋላ የመጀመሪያው መጋረጃ ከመገናኛ ድንኳኑ ውጨኛው ክፍል ውስጥ የሚገኝ ስለሆነ “ሁለተኛው መጋረጃ” “በቅዱስ ሥፍራው” እና “በቅድስተ ቅዱሳኑ” መካከል የሚገኝ ሥፍራ ነው። በውስጡም "በቃል ኪዳኑ ታቦት ውስጥም" አድገዋል "አብቧል" ወይም "በቅሏል" ወይም "አድገዋል" የድንጋይ ጽላት የተጻፈበት ጠፍጣፋ ድንጋይ። ምስል የሆነ ነገርን በመወከል የተቀረጸ ድንጋይ በላዩ ላይ የኩሩቤል ምስል ነበር "ክሩቤል በላዩ ላይ ነበር" ማስተሰሪያ ኪዳን የቃል ኪዳኑ ታቦት የላይኛው ክፍል

Hebrews 9:6

ዕብራውያን **9**: **6-7**
ይህ ነገር ከተዘጋጀ በኋላ አማራጭ ትርጉም: "ካህናቱ እነዚህ ነገሮች ካሰናዱ በኋላ" አዘጋጁ "አስቀድሞ ማዘጋጀት" ከመሰዋት በስቀር ምንም አልቀረም "ጉል ጊዜ ይሰው ነበር" ወይም "ሁል ጊዜ ይሰዋል"

Hebrews 9:8

ዕብራውያን **9**: **8-10**
መንገዱ . . . ገና አልተገለጠም ነበር "እግዚአብሔር መንገዱን ገና አልገለጠውም ነበር" ቅድስተ ቅዱሳኑ አማራጭ ትርጉሞች: 1) በምድር ላይ በመገናኛ ድንኳን ውስጥ የሚገኘው የውሰጠኛው ክፍል ወይም 2) በሰማይ የእግዚአብሔር መገኛ። የመጀመሪያው የመገናኛ ድንኳን አሁንም ድረስ ቆሞ ይገኛል አማራጭ ትርጉሞች: 1) "የመገናኛ ድንኳኑ ውጫዊው ክፍል አሁንም ድረስ ቆሞ ይገኛል ወይም 2) "የመስዋእት ሥርዓቱ ቀጥሏል" በምሳሌ ማብራሪያ "ምስል" በአሁኑ ወቅት "አሁን" የአምላኪውን ሕልና ፈጽሞ ለማንጻት አይችልም ነበር "የሚያመልከውን ሰው ከበደለኝነት ፈጽሞ ለማንጻት አይችልም ነበር" የመታጠብ ሥርዓት "ሕግጋት" ወይም "ምሳሌያዊ ተግባራት" ለሥጋ ሥርዓቶች "ለአካላዊ ሰውነት የሚሆኑ ሕግጋቶች" እነዚህ ሁሉ ሕግጋቶች ለሥጋ የተሰጡ ናቸው "እግዚአብሔር እነዚህ ሁሉ ሕግጋቶች የሰጠው ለሥጋ ነው" አዲስ ሥርዓት "አዲስ ኪዳን" (ULB)

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Hebrews 9:11

ዕብራውያን **9**፡ **11-12**
መልዕካም ነገሮች “አዲስ ሥርዓት” (HEB 9:8) ቅድስተ ቅዱሳን በሰማይ የእግዚአብሔር መገኘት

Hebrews 9:13

ዕብራውያን **9**፡ **13-15**
መርጫት ... አመድ ሥርዓታዊ መንገድ ንጹሕ ባልሆኑት ላይ ካህኑ ንጹሕ ባልሆኑት ሰዎች ላይ ትንሽ አመድ ይረጭባቸዋል። ለእግዚአብሔር እንከን ያለሌበትን መስዋእት በዘላለማዊ መንፈስ ያቀረበው፣ ሕያው የሆነውን እግዚአብሔር ማምለክ እንችል ዘንድ ሕልናችንን ከሞተ ሥራ ያነጻው የክርስቶስ ደም ግን ምን ያኽል የተሻለ ነው? "ክርስቶስ በዘላለማዊ መንፈስ አማካኝነት ራሱን ምንም ነቀፋ ያሌለበት መስዋእት አድርጎ ለእግዚብሔር አቅርቧል።" የክርስቶስ ደም ... ሕልናችንን ያነጻል ኢየሱስ ራሱን መስዋእት አድርጎ በማቅረቡ ምክንያት ለሰራነው ኃጢአት በደለኝነት ከእንግዲህ ሊሰማን አይገባም። ሕልናችንን የጸሐፊውን እና የአንበባቢው ሕልና ቅጣት "ፍርድ" በእግዚአብሔር የተጠሩት በእግዚአብሔር የተሾሙት ወይም የእርሱ ልጆች እንዲሆኑ የተመረጡት

Hebrews 9:16

ዕብራውያን **9**፡ **16-17**
ውርስ አንድ ሰው ስሞት ሌላኛው ሰው የእርሱን ንብረት እንዲወስድ የሚፈቅድለት የሕግ ወረቀት።

Hebrews 9:18

ዕብራዊያን **9**፡ **18-20**
ዕብራዊያን 9፡ 18-20 የመጀመሪያው ኪዳንም ቢሆን የተመሠረተው ያለ ደም አልነበረም "እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ኪዳንም ቢሆን የመሠረተው በደም ነበር" ደሙን ወስዶ ...ከውሃ ጋር...እና ይረጨዋል . . . ጥቅል መጽሐፍ. . . እና በሁሉም ሰዎች ላይ ካህኑ ሂሶጱን ወስዶ በደም እና ውሃ ውስጥ ይነክረውና በጥቅል መጽሐፉ ላይ እንዲሁም በሕዝቡ ላይ ይረጨዋል። ሂጾጵ ለመርጨት ሥርዓት ጥቅም ላይ የሚውል እፅዋት

Hebrews 9:21

ዕብራውያን **9**፡ **21-22**
መርጨት ይህንን በ HEB 9:19 ላይ ምን ብለህ እደተረጎምከው ተመልከት። መያዥያ ዕቃ "አንድ ነገር ለመያዝ የሚያገለግል ዕቃ" ወይም "ማጠራቀሚያ" የክህነት አገልግሎት "የካህናት ሥራ" ሁሉ ነገር በደም ይነጻል "ካህናት ሁሉን ነገር ለማንጻት ደምን ይጠቀማሉ" ዳም ሳይፈስ የኃጢአት ሥርዔት የለም "እግዚአብሔር የሰዎችን ኃጢአት ይቅር የሚለው ካህኑ መስዋእትን ካቀረበ እና ስለእነርሱ ካቀረበ ነው።"

Hebrews 9:23

ዕብራውያን **9**፡ **23-24**
የሰማዩ ቅጂ የሆነው በእነዚህ እንስሶች መስዋእት መንጻት ካለበት "ካህናት የሰማዩ ቅጂ የሆነውን ለማንጻት የእንስሳት መስዋእትን ልጠቀሙ ይገባል።" ሰማያዊው ነገር ራሱም በምበልጥ መስዋእት ልነጻ ይገባዋል። ምድራዊው ቅጂ ከሚነጻበት መስዋእት ይልቅ "ሰማያዊው ነገርንም እግዚአብሔር በጣም በተሻለ መስዋእት ልያነጻ ይገባዋል" እርሱ . . . በእግዚአብሔር ፊት ይቀርባል እርሱ . . . ወደ እግዚአብሔር መገኘት ይመጣል።

Hebrews 9:25

ዕብራውያን **9**፡ **25-26**
ወደዚያ አይሄድም "ወደ ሰማይ አይገባም" (UDB) ይህ እውነት ከሆነ "እርሱ ሁል ጊዜ መስዋእትን የሚያቀርብ ከሆነ" ከምድር ጅማሬ "እግዚአብሔር ዓለም ፈጠረ" እርሱ ገልጦታል አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር እርሱ ገልጦታል"

Hebrews 9:27

ዕብራውያን **9**፡ **27-28**
መስዋእት ሆኖ የቀረበው ክርስቶስ አማራጭ ትርጉም: "ራሱን መስዋእት አድርጎ ያቀረበው ክርስቶስ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **10**

1 ሕጉ ሊመጡ ላሉ መልካም ነገሮች ጥላ ብቻ እንጂ እውነተኛው አካል አይደለም። ሕጉ ካህናት ያለማቋረጥ በየዓመቱ በሚያቀርቧቸው በነዚያው መሥዋዕቶች ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡትን ከቶ ፍጹም ሊያደርጋቸው አይችልም። **2** ቢችል ኖሮ እነዚያ መሥዋዕቶች መቅረባቸው ይቀር አልነበረምን? እንደዚያ ቢሆን ኖሮ የሚያመልኩት አንድ ጊዜ ከኃጢአታቸው ከነጹ በኋላ ስለ ኃጢአታቸው የሚያስታውሱት ነገር ምንም አይኖርም ነበር። **3-4** ነገር ግን በእነዚያ መሥዋዕቶች ውስጥ በየዓመቱ የተፈጸሙትን ኃጢአቶች የሚያስታውስ ነገር አለ። ለዚህ ምክንያቱ የኮርማዎችና የበጎች ደም ኃጢአትን ማስወገድ ባለመቻሉ ነው። **5** ክርስቶስ ወደ ዓለም ሲመጣ፣ “አንተ መሥዋዕቶችን ወይም ስጦታዎችን አልፈለግህም። ይልቅ ለእኔ ሥጋን አዘጋጀህልኝ። **6** አንተ በሚቃጠል መባ ወይም በኃጢአት መሥዋዕት ደስ አልተሰኘህም። **7** ቀጥሎም፣ “እግዚአብሔር ሆይ በመጽሐፍ ስለ እኔ እንደተጻፈው እነሆ ፈቃድህን ለማድረግ እዚህ አለሁ” ብሏል። **8** ከላይ እንደተጠቀሰው፦“አንተ መሥዋዕቶችን፣ ስጦታዎችን ወይም ለኃጢአት የሚቃጠሉ ሙሉ መሥዋዕቶችን ማለትም በሕጉ መሠረት የሚቀርቡ መሥዋዕቶችን አልፈለግህ፣ በእነርሱም ደስ ስላልተሰኘህም” ብሏል። **9** ደግሞም፣ “እነሆ ፈቃድህን ለማድረግ እዚህ አለሁ” አለ። ሁለተኛውን ሥርዓት ለመትከል የመጀመሪያውን ሥርዓት ወደ ጎን ያደርገዋል። **10** በሁለተኛው ሥርዓት ለአንድ ጊዜና ለዘላለም በቀረበው በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ አማካኝነት በእግዚአብሔር ፈቃድ ተቀድሰናል። **11** በእርግጥ እያንዳንዱ ካህን ኃጢአትን ፈጽሞ ሊያስወግድ የማይችሉትን መሥዋዕቶች ለማቅረብ በየዕለቱ ለማገልገል ይቆማል። **12** ነገር ግን ክርስቶስ ለኃጢአት ሁሉ ለዘላለም የሚሆን አንድ መሥዋዕት ካቀረበ በኋላ፣ **13** ጠላቶቹ እስኪዋረዱና የእግሩ መረገጫ እስኪሆኑ ድረስ እየተጠባበቀ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጧል። **14** ይህም በአንድ መሥዋዕት የተቀደሱትን ለዘላለም ፍጹማን ስላደረጋቸው ነው። **15** ደግሞም መንፈስ ቅዱስ ለእኛ ይመሰክርልናል። ምክንያቱም በመጀመሪያ፣ **16** “ ከእነዚያ ቀኖች በኋላ ከእነርሱ ጋር የምገባው ቃልኪዳን ይህ ነው፦ ሕጎቼን በልባቸው ውስጥ አደርጋለሁ፣ ደግሞም በአእምሮአቸው ውስጥ እጽፈዋለሁ” ስላለ ነው። **17** ቀጥሎም፣ “ኃጢአታቸውንና ዓመጻቸውን ከእንግዲህ አላስበውም” አለ። **18** ለእነዚህ ነገሮች ይቅርታ በተረገበት በዚያ ለኃጢአት ከእንግዲህ ወዲያ መሥዋዕት አይቀርብም። **19** ስለዚህ ወንድሞች፣ በኢየሱስ ደም አማካኝነት ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የመግባት ድፍረት አለን። **20** ይህም በመጋረጃው ማለትም በሥጋው አማካኝነት ለእኛ የከፈተልን አዲስና ሕያው መንገድ ነው። **21** በእግዚአብሔር ቤት ታላቅ ካህን ስላለን፣ **22** ልባችን በመረጨት ከክፉ ኅሊና ሁሉ ነጽቶ፣ ሥጋችንም በንጹሕ ውኃ ታጥቦ ባገኘነው የእምነት ሙሉ ዋስትና በእውነተኛ ልብ እንቅረብ። **23** ተስፋን የሰጠ እግዚአብሔር ታማኝ ስለሆነ፣ አምነን የምንመሰክረውን ተስፋ ያለ ማወላወል አጥብቀን እንያዝ። **24** ለፍቅርና ለመልካም ሥራ እርስ በርስ እንዴት እንደምንነቃቃ እናስብ። **25** አንዳንዶቹ ልማድ እንዳደረጉት በአንድነት መሰብሰባችንን አንተው። በዚህ ፈንታ ቀኑ እየቀረበ መምጣቱን ስታዩ እርስ በርሳችሁ ይበልጥ ተበረታቱ። **26** የእውነትን እውቀት ከተቀበልን በኋላ ሆን ብለን ኃጢአት ማድረጋችንን የምንቀጥል ከሆንን፣ ከእንግዲህ ለኃጢአት የሚሆን መሥዋዕት አይኖርም። **27** ይልቅ የሚጠብቀን የሚያስፈራ ፍርድና የእግዚአብሔርን ጠላቶች ሊበላ ያለ ብርቱ እሳት ብቻ ነው። **28** የሙሴን ሕግ የናቀ ማናቸውም ሰው በሁለት ወይም በሦስት ምስክሮች ያለ ምንም ምሕረት ይሞታል። **29** ታዲያ የእግዚአብሔርን ልጅ የናቀ፣ የተቀደሰበትን የቃልኪዳኑን ደም እንደ እርኩስ የቆጠረ፣ የጸጋን መንፈስ የሰደበ ሰው ምን ያህል የባሰ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል? **30** “በቀል የእኔ ነው፤ እኔ ዋጋን እመልሳለሁ” ያለውን እናውቃለንና። ደግሞም፣ “ጌታ በሕዝቡ ይፈርዳል።” **31** በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ የሚያስፈራ ነገር ነው! **32** ነገር ግን ከበራላችሁ በኋላ በእንዴት ያለ ታላቅ ሥቃይ ውስጥ እንደታገሣችሁ እነዚያን የቀደሙ ወቅቶች አስታውሱ። **33** በስድብና በስደት ለሕዝብ መሳለቂያ ተዳርጋችኋል፣ ደግሞም በዚህ ዓይነቱ ሥቃይ ውስጥ ካለፉ ሰዎችም ጋር አብራችሁ ነበራችሁ። **34** ለእስረኞች ርኅራኄ አሳያችሁ፣ የተሻለና ዘላለማዊ ሀብት ለራሳችሁ እንዳላችሁ በመረዳትም የንብረታችሁን መነጠቅ በደስታ ተቀበላችሁ። **35** ስለዚህ ታላቅ ዋጋ ያለውን ድፍረታችሁን አትጣሉ። **36** ፈቃዱን ካደረጋችሁ በኋላ እግዚአብሔር ለእናንተ ተስፋ የገባውን ነገር ለመቀበል መታገሥ ያስፈልጋችኋል። **37** “በጣም በቅርብ ጊዜ ውስጥ የሚመጣው በእርግጥ ይመጣል፣ አይዘገይምም። **38** የእኔ የሆነው ጻድቅ ግን በእምነት ይኖራል። ወደኋላ ቢመለስ በእርሱ ደስ አይለኝም።” **39** እኛ ግን ለጥፋት ወደኋላ እንደሚያፈግፍጉት አይደለንም። ይልቅ እኛ ነፍሳቸውን ለማዳን ከሚያምኑት ነን።

Hebrews 10:1

ዕብራዊያን **10**፡ **1-4**
እነዚህ እውነታዎች አይደሉም "እውነት የሆነ ነገር አይደለም" ቅረቡ "ለማመልክ ኑ" (UDB) ወይም "ይበልጥ ቅረቡ" እነዚህ መስዋእቶች መሰዋታቸው በቀረ ነበር? "እነዚህ መስዋእት ማቅረብ በተው ነበር።" ማቆም "ማቆም" ሁኔታ "ሁኔታ" አንድ ጊዜ ከነጻ "እግዚአብሔር ያነጻው" ማወቅ "ሕልውናውን ማወቅ" የተሠራውን ኃጢአት ማስታወስ "እግዚአብሔር ሰዎች የሰሯቸውን ኃጢአት ያስታውሳል" ከዓመት ዓመት "በየዓመቱ" የኮርማ እና ፍየል ደም ኃጢአትን ፈጽሞ ለማስወገድ አይችልም። "የኮርማ እና የፍየል ደም ኃጢአትን ለማስወገድ አይችልም"

Hebrews 10:5

ዕብራውያን **10**፡ **5-7**
ሥጋን አዘጋጀኸልኝ "ለእኔ ሥጋን አዘጋጀኸልኝ"

Hebrews 10:8

ዕብራውያን **10**:**8-10**
ከዚህ በላይ እንደተገለጸው አማራጭ ትርጉም: "ከዚህ በላይ እንደጻፍኩት ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፡" መስዋእን፣ መባን ወይም የሚቃጠል መስዋእትን እነዚህ ቃላት በ HEB 10:5-6 ላይ በተረጎምካቸው መሠረት ተርጉማቸው። የሚቀርቡት መስዋእት አማራጭ ትርጉም: "እነርሱ' እነዚህ ሰዎች የሚያቀርቧቸውን ሁሉንም መስዋእት ናቸው።" ተመልከት "ከዚህ በመቀጠል ለሚናገረው ነገር ትኩረት ስጥ:" በእግዚአብሔር ፈቃድ መሠረት እኛም ለእግዚአብሔር ተሰጠን አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር ክርስቶስ ራሱን መስዋእት ያደረግ ዘንድ ፈቃዱ ነበር እንዲሁም በዚህ መስዋእት አማካኝነት እኛ ለእግዚአብሔር የተሰጠን ሆንን"

Hebrews 10:11

ዕብራውያን **10**፡ **11-14**
በእርግጥ ይህ HEB 10:1-4 ከዚያ ቀጥሎ ካለው ጋር ያያይዛል። ጠላቶቹ ተዋረዱ እንዲሁም የእግሩ መረገጫ ሆኑ "እግዚአብሔር የክርስቶስን ጠላቶች አዋረዳቸው እንዲሁም አሳፈራቸው።" አንድን ሰው በሌላ ሰው እግር በታች ማስቀመጥ የሚያሳፍር ነገር ነው። ለእግዚአብሔር የተሰጡት አማራጭ ትርጉሞች: "እግዚአብሔር ለራሱ ያዘጋጃቸው"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Hebrews 10:15

ዕብራውያን **10**: **15**-**16**
በመጀመሪያ በ HEB 10:17 ላይ ከተናገረው በፊት የተቀደሱት (HEB 10:14) ከእነዚህ ቀናት በኋላ "የመጀመሪያው ኪዳን ስጠናቀቅ"

Hebrews 10:17

ዕብራውያን **10**: **17**-**18**
ከዚያም በ HEB 10:16 ላይ ከተነገሩት በኋላ ያሉት ከእንግዲህ ወደህ ፈጽሞ አላስታውስም "ከእንግዲህ ወዲህ አላስታውሰውም" ኃጢአት እነና የሕግ አልባነት “ኃጢአት” እና “ሕግ አልባነት” የሚሉት ሁለት ቃልት በመሠረታዊ ሀሳባቸው ተመሳሳይ ናቸው። በአንድነትም አጽኖት የሚሰጡት የተፈጸመ ኃጢአትን ነው። ለእዚህ ነገሮች ይቅርታ የሚገኝበት ሥፍራ አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር እነዚህ ነገሮች ይቅር ሲል" ከእንግዲህ ለኃጢአት መስዋእትን አያቀርቡም አማራጭ ትርጉም: "ሰዎች ከእንግዲህ ለኃጢአት መስዋእትን አያቀርቡም"

Hebrews 10:19

ዕብራውያን **10**: **19**-**22**
ወንድሞች በዚህ ሥፍራ ይህ ቃል ክርስትያኖችን የሚያመለክት ሲሆን ወንዶችን እና ሴቶችን ያመለክታል። ምክንያም በክርስቶስ የሚምኑ አማኞች ሁሉ የአንድ መንፈሳዊ ቤተሰብ አባላት ናቸውን፣ እግዚአብሔርም ሰማያዊ አባታቸው ነው። ቅድስተ ቅዱሳን የእግዚአብሔር መገኘት አካሉ አማራጭ ትርጉም: "የእርሱ ሞት" በመጋረጃው በኩል በምድራዊ መ,ቤተ መቅዱስ ውስጥ ያለው መጋረጃ በሰዎች እና በእውነተኛው የእግዚአብሔር መገኘት መካከል የሚለይ ግድግዳ መኖሩን ያሳያል። የእግዚአብሔር እያንዳንዱ አማኝ ሙሉ ዋስትና ጠንካራ መተማመን ልብን በመርጨት ማንጻት አማራጭ ትርጉም: "በኢየሱስ ደም የተረጨ ደም ንጹሕ ይሆናል። መረጨረት ይህ በ HEB 9:19 ላይ ምን በማለት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

Hebrews 10:23

ዕብራውያን **10**: **23**-**25**
የምንተማመንበትን የተስፋ ቃለል አጥብቀን እንያዝ "የምንተማመንበትን ነገር ለሰዎች በቀጣይነት እንናገር ምክንያቱም እግዚአብሔር እንደሚፈጽም ቃል የገባውን ነገር እንደሚፈጽም እናምናለንና" መናወጥ "እርግጠኛ አለመሆን" ቀኑ ቀርቧል አማራጭ ትርጉም: "ኢየሱስ ተመልሶ የሚመጣት ቀን ቀርቧል"

Hebrews 10:26

ዕብራውያን **10**: **26**-**27**
ሆን ተብሎ "በሙሉ ስምምነት" ከእንግዲህ ወዲህ ለኃጢአት መስዋእ መሰዋት አያስፈልግም "እግዚአብሔር ኃጢአቱን ይቅር ይልለት ዘንድ ማንም ከእንግዲህ መስዋእትን አይሰዋም"

Hebrews 10:28

ዕብራውያን **10**: **28**-**29**
ሁለት ወይም ሦስት "2 ወይም 3" ማንኛውም ሰው ምን ያኽል ቅጣት ይባዋል ብላችሁ ታስባላችሁ . . . ጸጋ? አማራጭ ትርጉም: "ይህ በጣም ከባድ ቅጣት ነው። ይሁን እንጂ ይህ ቅጣት ለማንም ቢሆን በጣም ከባድ ነው . . . ጸጋ!" የእግዚአብሔር ልጅ አለመቀበል ይህ ቃል ክርስቶስ ማን እንደሆነ እና የሠራውን ሥራ አለመቀበልን የሚያሳይ ምስለላዊ ምሳሌ ነው።" የእግዚአብሔር ልጅ ይህ የኢየሱስ ወሳኝ የሆነ የማዕረግ ስም ነው። ለእግዚአብሔር በተሰጠበት ደሙ አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር ለራሱ በሰጠበት ደሙ" የጸጋ መንፈስ "ጸጋ የሚሰጠው የእግዚአብሔር መንፈስ"

Hebrews 10:30

ዕብራውያን **10**: **30**-**31**
እናውቃለን ጸሐፊው እና አንባቢኑ ይህን ያውቃሉ በእጆቹ ላይ ይወድቃሉ አማራጭ ትርጉም: "በሙሉ ፍርዱ ሥር ናቸው"

Hebrews 10:32

ዕብራውያን **10**: **32**-**34**
አንድ ጊዜ ከበራላችሁ በኋላ "እወነቱን ካወቃችሁ በኋላ" ሰዎች ልዘባበቱባችሁ እና ልሰድባችሁ ይችላሉ እንዲሁም ያሳድዷችኋል "ሰዎች በመሳደብ እና በአደባባይ እናንተን በማሳደድ ይዘባበቱባችኋል" እናንተ ራሳችሁ አንባቢያኑ እንደሚዘባበቱባቸው፣ እንደሚያሥሯቸው እና ንብረታቸውን እንደሚዘርፏቸው ሰዎች ሳይሆን

Hebrews 10:35

ዕብራውያን **10**: **35**-**37**
መጣል ምንም እርባና ወይም ጥቅም እንዳሌለው በቅርቡ "በቅርብ ጊዜ"

Hebrews 10:38

ዕብራውያም **10**: **38**-**39**
የእኔ ጻድቅ "የእኔ ተማኝ ተከታዮች"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **11**

1 እንግዲህ እምነት ሰው በተስፋ ለሚጠበቀው ነገር ማረጋገጫ ያልታየውም ነገርም አስረጅ ነው። **2** የቀድሞ አባቶቻችንም እምነታቸው የተረጋገጠው በዚሁ ነበር። **3** ፍጥርተ-ዓለሙ በእግዚአብሔር ትእዛዝ መፈጠሩን፣ የሚታየውም ከሚታዩት ነገሮች የተፈጠረ አለመሆኑን በእምነት እንረዳለን። **4** አቤል ከቃየል የበለጠ ተቀባይነት ያለውን መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ያቀረበው በእምነት ነበር። ጻድቅ እንደሆነ የተመሰከረለትም በዚህ ምክንያት ነበር። ስላቀረባቸው መሥዋዕቶች እግዚአብሔር መስክሮለታል። ቢሞትም እንኳ አሁንም ይናገራል። **5** ሄኖክ ሞትን ሳያይ ወደ ላይ የተወሰደው በእምነት ነበር። “እግዚአብሔር ስለወሰደው አልተገኘም።” ከመወሰዱ በፊት እግዚአብሔርን ደስ እንዳሰኘ ተነግሮለታና። **6** ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ምክንያቱም፣ ወደ እግዚአብሔር የሚመጣ፣ እግዚአብሔር እንዳለና እርሱን ለሚሹትም ዋጋን እንደሚሰጥ ማመን ስለሚገባው ነው። **7** ኖኅ ገና ስላልታዩ ነገሮች ከእግዚአብሔር ሲያስጠነቅቀው እግዚአብሔርን በመፍራት ቤተሰቡን የሚያድንበትን መርከብ የሠራው በእምነት ነበር። ይህን በማድረግ ዓለምን ኮንኖ በእምነት የሚገኘውን ጽድቅ ወራሽ ሆነ። **8** አብርሃም በተጠራ ጊዜ ርስትን ወደሚቀበልበት ቦታ ታዞ የሄደው በእምነት ነበር። የወጣው ወዴት እንደሚሄድ ሳያውቅ ነበር። **9** በተስፋው ምድር እንደ ባዕድ የኖረውም በእምነት ነበር። ያን ተስፋ ከእርሱ አብረው ከሚወርሱት እንደ ይስሐቅና እንደ ያዕቆብ በድንኳን ውስጥ ኖረ። **10** ይሄውም እግዚአብሔር መሠረት ያላትን፣ ያቀዳትንና ያነጻትን ከተማ ይጠባበቅ ስለነበር ነው። **11** አብርሃምና ሣራ እጅግ አርጅተው ሳሉ እንደሚወልዱ በተነገራቸው ጊዜ፣ ወንድ ልጅን እንደሚሰጣቸው ተስፋ የገባላቸውን እግዚአብሔር ታማኝ አድርገው ስለቆጠሩ ሣራ ለማርገዝ ኃይል ያገኘችው በእምነት ነበር። **12** በመሆኑም፣ ለሞት ከተቃረበ ከዚህ አንድ ሰው ቁጥር ስፍር የሌላቸው ዝርያዎች ተገኙ። እነርሱም በሰማይ እንዳሉ ከዋክብትና በባሕር ጠረፍ እንዳለ አሸዋ በዙ። **13** እነዚህ ሁሉ የተሰጧቸውን ተስፋዎች ሳይጨብጡ እምነታቸውን እንደጠበቁ ሞቱ። ይልቁንም እነዚህን ተስፋዎች ከሩቅ አይተው ስለተቀበሏቸው በምድር ላይ እንግዶችና መጻተኞች መሆናቸውን ተገነዘቡ። **14** እንደዚህ የሚሉ ሰዎች የራሳቸው የሆነ አገር እንዲሚሹ በግልጽ ያሳያሉ። **15** በእርግጥ ለቀው የመጡትን አገር ቢያሰቡ ኖሮ ለመመለስ ዕድሉ ነበራቸው። **16** አሁን ግን የሚፈልጉት የተሻለውን ሰማያዊ አገር ነው። ስለዚህም፣ እግዚአብሔር ከተማን ስላዘጋጀላቸው አምላካቸው ተብሎ ሊጠራ አያፍርም። **17** አብርሃም በተፈተነ ጊዜ ይስሐቅን ያቀረበው በእምነት ነበር። አዎን፣ **18** “ዝሮችህ የሚጠሩት በይስሐቅ ነው” የተባሉለትን ተስፋዎቹን በደስታ ስለተቀበለ አንድ ልጁን ለመሥዋዕት አቀረበ። **19** አብርሃም፣ እግዚአብሔር ይስሐቅን ከሞት ሊያስነሣ እንደሚችል አምኖ ነበር። ይስሐቅን ከሞት የመነሣት አምሳያ አድርጎ መልሶ ተቀበለው። **20** ይስሐቅ ገና ወደፊት የሚመጡትን ነገሮች አስቦ ያዕቆብንና ኤሳውን በእምነት ባረካቸው። **21** ያዕቆብ ፍጻሜው በተቃረበ ጊዜ፣ የዮሴፍን ልጆች እያንዳንዳቸውን የባረካቸውና በምርኩዙ አናት ተደግፎ የሰገደው በእምነት ነበር። **22** ዮሴፍ ለሞት ሲቃረብ የእስራኤል ልጆች ከግብጽ እንደሚወጡ የተናገረውና የእርሱን አጽሙን እንዲወስዱ ያዘዘው በእምነት ነበር። **23** ሙሴ ሲወለድ ወላጆቹ መልከ መልካም ሕፃን መሆኑን አይተው የንጉሡን ትእዛዝ ሳይፈሩ ለሦስት ወራት የደበቁት በእምነት ነበር። **24** ሙሴም ካደገ በኋላ የፈርዖን የልጅ ልጅ፣ እንዳይባል እምቢ ያለው በእምነት ነበር። **25** ለአጭር ጊዜ በኃጢአት ደስ ከመሰኘት ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራን መካፈልን መረጠ። **26** ዓይኖቹ ወደፊት የሚቀበለውን ዋጋ አተኩረው ስለተመለከቱ፣ በግብጽ ከሚገኝ ሀብት ይልቅ ክርስቶስን መከተል የሚያስከትልበትን ውርደት የላቀ ብልጽግና አድርጎ አሰበ። **27** ሙሴ ግብጽን ለቆ የወጣው በእምነት ነበር። የማይታየውን እርሱን ተመልክቶ በአቋሙ ስለጸና የንጉሡን ቁጣ አልፈራም። **28** ቀሳፊው የእስራኤልን የበኩር ልጆች እንዳይነካ ሙሴ የፋሲካ በዓልንና የደም ርጭት ሥርዓትን ያካሄደው በእምነት ነበር። **29** እስራኤላውያን በደረቅ መሬት ላይ እንደሚሄዱ ቀይ ባሕርን የተሻገሩት በእምነት ነበር። ግብጻውያን ይህን ለማድረግ በሞከሩ ጊዜ ተዋጡ። **30** የኢያሪኮ ግንብ በእምነት የወደቀው ለሰባት ቀናት ከተከበበ በኋላ ነበር። **31** ሴተኛ አዳሪዋ ረዓብ ሰላዮቹን ለደህንነታቸው ተጠንቅቃ ስለተቀበለቻቸው ከማይታዘዙት ጋር ያልጠፋችው በእምነት ነበር። **32-33** እንግዲህ ከዚህ የበለጠ ምን ልበል? በእምነት መንግሥታትን ድል ስላደረጉት፣ ፍትህን ስላስከበሩትና የተስፋ ቃሎችን ስለተቀበሉት ስለነጌዶዎን፣ ባርቅ፣ ሳምሶን፣ ዮፍታሄ፣ ዳዊት፣ ሳሙኤልና ነቢያት እንዳልናገር ጊዜ ያጥረኛል። **34** እነርሱ የአንበሶችን አፍ ዘጉ፣ የእሳትን ኃይል አጠፉ፣ ከሰይፍ ስለት አመለጡ፣ ከበሽታ ተፈወሱ፣ በጦርነት ኃያላን ሆኑ፥ የባዕድን ሠራዊት አባረሩ። **35** ሴቶች ሙታናቸው ከሞት ተነሡላቸው። ሌሎች የተሻለውን ትንሣኤ ያገኙ ዘንድ ከእስር መፈታታቸውን ለመቀበል እምቢ በማለት ተሠቃዩ። **36** የተቀሩት ደግሞ በስድብና በግርፋት፣ እንዲያውም በሰንሰለት በመታሰር ተሠቃዩ። **37** በድንጋይ ተወገሩ። በመጋዝ ለሁለት ተሰነጠቁ። በሰይፍ ተገደሉ። ይህ ዓለም ስላልተገባቸው **38** በምድረበዳ፣ በተራሮች፣ በዋሻዎችና በየጉድጓዱ እየተጎሳቆሉ፣ መከራ እየተቀበሉና ግፍ እየተፈጸመባቸው የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው በመንከራተት ዞሩ። **39** እነዚህ ሰዎች ሁሉ ስለ እምነታቸው በእግዚአብሔር ዘንድ የተመሰከረላቸው ቢሆኑም የተሰጣቸውን ተስፋ አልተቀበሉም። **40** እነርሱ ያለ እኛ ፍጹም ስለማይሆኑ እግዚአብሔር ለእኛ የተሻለውን ነገር አስቀድሞ ሰጠን።

Hebrews 11:1

ዕብራውያን **11**: **1-3**
እምነት አንድ ሰው በመተማመን በመጠበቅ ላይ ሳለ የሚኖረው እርግጠኝነት ነው "እምነት አንድ ሰው በመተማመን ለመጠባበቅ የሚሆነው መሠረት ነው" በመተማመን በዚህ ሥፍራ ላይ ይህ ቃል የሚያመለክተው እርግጠኛ የሆነውን የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል ነው። በተለይም ሁሉም አማኞች በኢየሱስ ክርስቶስ የሆኑት አማኞች አንድ ቀን በሰማይ ከእግዚአብሔር ጋር ለዘላለም እንደሚሆኑ ያላቸው እርግጠኝነት ነው። ስለዚህም በዚህ አማካኝነት "ምክንያቱም አሁን ለማይታየው ነገር እንደኳ እርግጠኞች ናቸው" አባቶቻችን በእምነታቸው አስተዋሉ "እግዚአብሔር አባቶቻችን ከእምነታቸው የተነሣ አረጋግጧል"

Hebrews 11:4

ዕብራውያን **11**: **4-4**
ይበልጥ ተገቢ ነው "የተሻለ" አቤል አሁንም ይናገራል አማራጭ ትርጉም: "አቤል በቀጣይነት እያስተማረን ያለው ነገር ምንድ ነው"

Hebrews 11:5

ዕብራውያን **11**: **5-6**
በእምነት ያዕቆብ ተነጠቀ፣ ሞትም አላገኘውም አማራጭ ትርጉም: "በእምነት ያዕቅብ አልሞተም ምክንያቱም እግዚአብሔር ወስዶታልና ሞትን አለየም "ሞት" እርሱ እግዚአብሔርን አስደስቶታል ተብሎ ስለእርሱ ተነግሮአል። አማራጭ ትርጉሞች: 1) "እግዚአብሔር ሔኖክ እንዳስደሰተው ተናግሯል" ወይም 2) "ሰዎች ሔኖክ እግዚአብሔርን እንዳስደሰተው ተናግሯል።" ከመወሰዱ በፊትም "እግዚአብሔር እርሱን ከመንጠቁ በፊት"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Hebrews 11:7

ዕብራውያን **11**: **7-7**
በእግዚአብሔር ማስጠንቀቂያ ስለተሰጣቸው አማራጭ ትርጉም: "ምክንያቱም እግዚአብሔር አስጠንቅቋቸዋል" ያልታዩ ነገሮች አማራጭ ትርጉም: "ከዚህ በፊት ማንም አይቶት የማያውቀው ነገር" ዓለም በዚያን ዘመን በዓለም ውስጥ ይኖሩ የነበሩት ሌሎች ሰዎች።

Hebrews 11:8

ዕብራውያን **11**: **8-10**
ወደ . . . ሄደ "ወደ . . . ለመሄድ ቤቱን ተወ" ወደ ተስፋይቱ ምድር "እግዚአብሔር ለእርሱ ቃል የገባው ምድር" አብረን ወራሾች "ከእርሱ ጋር ወራሾች ነን" አርክቴክት የሕንጻ ግንባታ ንድፍ የሚሠራ ሰው

Hebrews 11:11

ዕብራውያን **11**: **11-12**
የማርገዝ ኃይል "የማርገዝ በቃት" እግዚአብሔር . . . መቀበል "እግዚአብሔር . . እንደሆነ ማመን" ዘሮችን የማይቆጠሩ . . . በሰማይ እንዳለ ክዋክብት እና በሐይቅ ዳር እንዳለ አሸዋ በጣም ብዙ

Hebrews 11:13

ዕብራውያን **11**: **13-14**
ከርቀት ተመልከተው ተሳለሙት This phrase is comparing the prophet's understanding of future events to welcoming a traveler arriving from far away. AT: "having understood what God will do in the future" ተቀብለዋል "ተቀባይነት ማግኘት" ወይም "መቀበል" እንግዶች "መጻፈተኞች" ወይም "የውጪ ሰዎች" ሀገር ቤት "ሀገር"

Hebrews 11:15

ዕብራውያን **11**: **15-16**
በእርግጥ "በእርግጠኝነት" ወይም "በእግጥ" ወይም "ለዚህ ነገር ትኩረት ስጡ:" ሰማያዊው ሥፍራ "ሰማያዊው ሀገር" ወይም "በሰማይ ያለው ሀገር" እግዚአብሔርን አምላካቸው ብለው ለመጥራት አላፈሩም "እግዚአብሔር አምላካቸው ብለው ይጠሩት ዘንድ ፈቃደኛ ነው" ወይም "እግዚአብሔር ለሌሎች የእነርሱ አምላክ ብለው ይጠሩት ዘንድ ፈቃደኛ ነው"

Hebrews 11:17

ዕብራውያን **11**: **17-19**
መስዋእት ማቅረብ እንደ ስጦታ ወይም ለእግዚአብሔር መስዋእት ከልጅህ ከይሳቅ ዘር "የአንተ ዘሮች ተብለው የሚጠሩት የይሳቅ ልጆች ናቸው" እርሱን መልሰው ተቀበሉት "አብረሃም ይሳቅን መልሶ ተቀበለው"

Hebrews 11:20

ዕብራውያን **11**: **20-22**
ያዕቆብ አመለከ "ያዕቅብ እግዚብሔርን አመለከ" የእርሱ መጨረሻ "የእርሱ ሞት"

Hebrews 11:23

ዕብራውያን **11**: **23-26**
ሙሴ ከተወለደ በኋላ በወላጆቹ ለሦስት ወር ያኸል ሸሸጉት አማራጭ ትርጉም: "የሙሴ ወላጆች ሙሴ ከተወለደ በኋላ ለሦስት ወራት ያኸል ሸሸጉት" አደገ "ትልቅ ሰው ሆነ" የእግዚአብሔርን ሕዝብ ስቃይ ተካፈለ "ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ተሰቃየ" ክርስቶስን መከተል ያለው መከራ "ክርስቶስ የሚፈልገውን ነገር በማድረጉ ምክንያት ከሰዎች ዘንድ የሚደርስበት ነቀፋ" ወደፊት የሚያገኘውን ሽልማት ከፊቱ አተኩሮ እየተመለከተ "በሰማይ የሚያገኘውን ሽልማት እያሰበ"

Hebrews 11:27

ዕብራውያን **11**: **27-28**
እንዲህ አላደረገም . . . ጸንቶ አለፈ . . . አስቀድሞ ተመለከተ ሙሴ የማይታየውን እየተመለከተ "ያግዘው ዘንድ በእግዚአብሔር ላይ እየተደገፈ" የማይታይ "በዐይን ማየት የማይቻል"

Hebrews 11:29

ዕብራውያን **11**: **29-31**
አለፉ እስራኤላዊያን አለፉ ተዋጡ አማራጭ ትርጉም: "ውሃው ዋጣቸው" ወይም "ሰመጡ" ለሰባት ቀናት በዙሪያው ዞሩ አማራጭ ትርጉም: "እስራኤላዊያን ለሰባት ቀናት በዙሪያው ተሰልፈው ዞሩ" ለመሰለል የተላት ሰዎች በሰላም ተቀበለች አማራጭ ትርጉም: "ለመሰለል የተላኩትን ሰዎች ሸሸገቻቸው"

Hebrews 11:32

ዕብራውያን **11**: **32-34**
ከዚህ በተጨማሪ ምን ማለት እችላለሁ? አማራጭ ትርጉም: "ከዚህ በተጨማሪ በጣም ብዙ ምሳሌዎችን ማንሳት ይቻላል።" ጊዜ ያጥረኛል አማራጭ ትርጉም: "በዚ ጊዜ አይኖረኝም" ተቆጣጠሩት "አሸነፉ" የአንበሳውን አፍ ዘጋ . . . የእሳቱን ነበልባል ያጠፋ . . . ከሰይፍ የታደገ የእስራሴል ሕዝቦች ከሞት ያመለጡባቸው መንገዶች። አማራጭ ትርጉም: "አንበሶች አልበሏቸውም . . . እሳቱ አላቃጠላቸውመረ . . . ሰይፍ አላጠፋቸውም።" ተፈወሱ አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር ፈወሳቸው"

Hebrews 11:35

ዕብራውያን **11**: **35-38**
ሴቶች ሙታናቸውን በትንሳኤ ተቀበሉ "ሴቶች የሞተባቸውን ሰው እግዚአብሔር ከሞት አስነስቶ ሰጣቸው" ሌሎች ተገረፉ . . . ሌሎች መዘባበቻ ሆኑ እንዲሁም ተገረፉ . . . በደንጋይ ተወግረው ሞቱ . . .በመጋዝ ተሰንጥቀው ሞቱ . . . ሌሎስ በሰይፍ አንገታቸው ተቀላ አማራጭ ትርጉም: "ሌሎች በሰዎች ተገርፈው መከራን ተቀበሉ . . . ሌሎች በሰዎች መሳለቂያ ሆነው ተገረፉ . . . ሌሎች በደንጋይ ተወገሩ . . . ሌሎስ በመጋዝ ለሁለት ተሰንጥቀው ሞቱ . . . ሌሎች ተገደሉ።" መገረፍ ከፍተኛ ስቃይን መቀበል መለቀቃቸውን አልፈለጉም "ሰዎች ከእስር ይለቋቸው ዘንድ ክርስቶስን ለመካድ ፈቃደኞች አልበሩም" በሰንሰለት መታሰር እንኳ "ሰዎች በሰንሰለት አስረዋቸው በወህኒ ቤት ውስጥ ያኗሮዋቸው ነበር" ተዘዋወሩt "ከቦታ ቦታ ተጓዙ" ወይም "በሁሉም ጊዜ ኖሩ" ተቸገሩ "ምንም ነገር አልነበራቸውም" ወይም "ምንም አልነበራውም" ወይም "ደሃ"

Hebrews 11:39

ዕብራውያን **11**: **39-40**
ከእምነታቸው የተነሣ ምንም እንኳ እነዚህ ሰዎች ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ቢኖራቸውም ተስፋ የገባላቸው ነገር ግን አልተቀበሉም ነበር። አማራጭ ትርጉም: "ከእምነታቸው የተነሣ እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔር አክብሯቸዋል ይሁን እንጂ እግዚአብሔር የገባላቸውን የተስፋ ቃል እነርሱ አልተቀበሉትም።"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 12

1 እንደነዚህ ያሉ እጅግ ብዙ ምስክሮች ስላሉን፣ የሚከብደንን ነገር ሁሉና በቀላሉ የሚጠላልፈንን ኃጢአት አሽቀንጥረን እንጣል። ከፊታችን ያለውንም ሩጫ
በትዕግሥት እንሩጥ። 2 በእምነታችን ጀማሪና ፍጹም አድራጊ ኢየሱስ ላይ ዓይኖቻችን እንትከል። እርሱ ከፊቱ ስላለው ደስታ መስቀሉንና መስቀሉ
የሚያስከትለውን ውርደት ታግሦ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጧል። 3 እንዳትደክሙ ወይም ልባችሁ እንዳይዝል፣ ከኃጢአተኞች የተሰነዘረበትን እንዲህ
ያለውን የጥላቻ ንግግር የታገሠውን እርሱን አስቡ። 4 ደም እስከማፍሰስ ድረስ ኃጢአትን አልተቃወማችሁም፣ አልታገላችሁትምም። 5 ደግሞም እንደ ልጆች፡
“ልጄ ሆይ የጌታን ቅጣት አታቅልል፣ በሚቀጣህም ጊዜ ልብህ አይዛል። 6 ጌታ የሚወደውን ይገሥጻል፣ የሚቀበለውን ማንኛውንም ልጅ ይቀጣል" በማለት
የተናገራችሁን ማበረታቻ ምክር ረስታችኋል። 7 አባት በልጆቹ እንደሚደረግ እግዚአብሔርም በእናንተ ላይ ስለሚያደርግ፣ መከራን እንደ ተግሣጽ በመቁጠር
ታገሡ። ለመሆኑ አባቱ የማይቀጣው ልጅ ማን ነው? 8 ነገር ግን እኛ ሁላችን ከምንካፈለው ተግሣጽ ውጭ ከሆናችሁ፣ ዲቃሎች እንጂ ልጆች አይደላችሁም። 9
ከዚህም በላይ የሚቀጡን ምድራዊ አባቶች ነበሩን፤ እኛም እናከብራቸው ነበር። ይልቁንስ መንፈስ ለሆነው አባት እየታዘዝን መኖር የቱን ያህል ይገባናል? 10
በእርግጥ አባቶቻችን ለእነርሱ መልካም መስሎ እንደታያቸው ለጥቂት ጊዜ ይቀጡን ነበር፣ እግዚአብሔር ግን የእርሱን የቅድስናው ተካፋዮች እንድንሆን
ለጥቅማችን ያቀጣናል። 11 ቅጣት በወቅቱ የሚያም እንጂ አስደሳች አይደለም። ይሁን እንጂ፣ ለለመዱት በመጨረሻ ሰላማዊ የጽድቅ ፍሬን ያፈራል። 12
ስለዚህ የዛሉ እጆቻችሁን ወደ ላይ አንሡ፣ የደከሙ ጉልበቶቻችሁንም እንደገና አበርቱ፤ 13 የሚያነክስ ማንም ቢኖር እንዲፈወስ እንጂ እንዳይናጋ እግሮቻችሁ
የሚራመዱባቸውን መንገዶች ቀና አድርጉ። 14 ከሰው ሁሉ ጋር ሰላምን ተከታተሉ፣ ቅድስናንም ተከታተሉ፣ ያለ ቅድስና ማንም ጌታን ሊያይ አይችልም። 15
ማንም ከእግዚአብሔር ጸጋ እንዳይጎድል፣ መራራ ሥርም አድጎ እንዳያስጨንቅና ብዙዎችን እንዳይመርዝ ተጠንቀቁ። 16 ለአንድ መብል ብሎ ብኩርናውን
እንደሸጠ እንደ ኤሳው እግዚአብሔርን የማይፈራ፣ ወይም ሴሰኛ የሆነ ማንም እንዳይኖር ተጠንቀቁ። 17 ከዚያ በኋላ በረከትን ለመውረስ እያለቀሰ በትጋት
ቢፈልግም፣ ከአባቱ ዘንድ የይቅርታ እድል እንዳጣና እንደተጣለ ታውቃላችሁ። 18 የሚቃጠል እሳት፣ ጨለማ፣ ጭጋግና ማዕበል ወዳለበት በእጅ ሊነካ
ወደሚችል ተራራ ገና አልመጣችሁም። 19 የሰሙትም ሌላ ቃል እንዳይነገራቸው እስከሚለምኑ ወዳደረሳቸው ቃልን ወደሚያሰማ ድምጽ ወይም የመለከት
ጩኼት ገና አልመጣችሁም። 20 ይህም፣ “እንስሳም እንኳ ቢሆን ተራራውን ከነካ በድንጋይ ይወገር” ተብሎ የተሰጠውን ትእዛዝ ሊሸከሙት አልቻሉም። 21
ሙሴ፣ “እጅግ ስለፈራሁ እየተንቀጠቀጥሁ ነኝ” እስከሚል ድረስ ይህ ስፍራ አስፈሪ ነበር። 22 አሁን ግን፣ የሕያው እግዚአብሔር ከተማ ወደሆነችው ወደ
ጽዮን ተራራ፣ አእላፋት መላእክት በደስታ ወደሚያመልኩባት ሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም መጥታችኋል፤ 23 በሰማይ ወደሚገኙት የበኩራን ሁሉ ጉባኤ፣ የሁሉም
ፈራጅ ወደሆነው እግዚአብሔርና ፍጹም የተደረጉ የጻድቃን መንፈሶች ወዳሉበት መጥታችኋል፤ 24 የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ወደሆነው ኢየሱስና ከአቤል ደም
የተሻለውን ወደሚናገር ወደተረጨው ደም ደርሳችኋል። 25 የሚናገራችሁን እምቢ እንዳትሉ ተጠንቀቁ። እነርሱ በምድር ላይ ሆኖ ያስጠነቀቃቸውን እምቢ
በማለታቸው ካላመለጡ፣ በሰማይ ሆኖ ከሚያስጠነቅቀን በእርግጥ አናመልጥም። 26 በዚያን ጊዜ ድምጹ ምድርን አናወጠ። ነገር ግን፣ “አንድ ጊዜ ደግሜ
ምድርን ብቻ ሳይሆን ሰማያትንም አናውጣለሁ” በማለት አሁን ተስፋ ሰጥቷል። 27 “አንድ ጊዜ ደግሜ” የሚል ቃል፣ ያልተናወጡ ነገሮች መጽናታቸውን፣
የተናወጡት ማለትም የተፈጠሩት ነገሮች መወገዳቸውን ያመላክታል። 28 ስለዚህ፣ ሊናወጥ የማይችል መንግሥት ስለተቀብልን አምላካችንን እናመስግነው፣
ደግሞም እግዚአብሔርን ተቀባይነት ባለው በአክብሮትና በፍርሃት እናምልከው፣ 29 ምክንያቱም አምላካችን የሚባላ እሳት ነው።

Hebrews 12:1

ዕብራውያን **12**፡ **1**-**3**
እኛ . . . እኛ ጸሐፊው እና ተደራሲያኑ በታላቅ የዳመና ምስክሮች ተከበናል አማራጭ ትርጉሞች፡ "ይህን ይኸል ትልቅ የዳመና ምስክሮቹ በዙሪያችን አሉ" ወይም "ይህን የኸል ብዛት ያለው የምስክር እንደ ምሳሌ አሉልን።" ምስክር እነዚህ የብሉይ ኪዳን አማኞች “ሩጫቸውን” እየተመለከቱ የሚከብደንን ነገር ሁሉ እንደ ከባድ ልብስ ወይም ሸክም ሆኖ ሩጫችንን በአግባቡ እንዳንሮጥ የሚያደርገንንን በእግዚአብሔር እንዳንታመን እና እርሱን እንዳንታዘዝ የሚያደርገንን ማንኛውንም አመለካከት ወይም ባሕርይ። የሚያስችግረንን "ሩጫችንን አስቸጋሪ የሚያደርግን" ወይም "እግዚአብሔርን መታዘዝ አስቸጋሪ የሚያደርግን ነገር" ዐይናችንን . . . አድርገን "ወደፊት እየተመለከትን" ወይ "ስለእርሱ ብቻ እያሰብን" ጀማሪ እና ፈጸሚr አማራጭ ትርጉም: "ፈጣሪ እና ጨራሽ" ድካም ለረጅም ጊዜ እንደሮጠ ሰው መሮጥ ያቃተው ለረጅም ሰዓት ከመሮጡ የተነሣ መሮጥ ያቃተው

Hebrews 12:4

ዕብራውያን **12**፡ **4**-**6**
ኃጢአትን እስከ ደም ጠብታ ድረስ ገና አልተቃወማችሁትም ወይም አልተቋቁማችሁትም "ኃጢአትን ተቃውማችሁታል እንዲሁም ተቋቁማችሁታል ይሁን እንጂ ሌሎች ግን ይህንን ያደረጉት እስከ ደም ጠብታ ድረስ ነው።" resisted...to...blood "እስከ . . . ሞት . . መቋቋም።" ይህንን በማድረጉ የሚሞት እንኳ ቢሆን ትክክለኛውን ነገር ያደርጋል። ለእናንተ የማበረታቻ ትምህርት በብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ውስጥ የሚገኘው የሰለሞን ጽሑፍ በጌታ ቅጣት ውስጥ ሰዎች በሚሆኑበት ወቅት እንዴት መበረታተታች እንዳለባቸው ግንዛቤን እንዲያገኙ ይረዳል። የጌታን ተግሳጽ በቀላሉ አትውሰደው "ተግሳጹን በቁም ነገር ውሰደው" የጌታን ተግሳጽ "ጌታ ሲገስጽህ" ልብህ አይዛል "ተስፋ አትቁረጥ"

Hebrews 12:7

ዕብራውያን **12**፡ **7**-**8**
እንደ ተግሳጽ ሁሉ በመከራም ጽና አስቸጋሪ ጊዜያትን ልክ እንደ ተግሳጽ ጊዜያት አድረገህ ተመልከታቸው። ልጁን የማይገስጽ አባት ማን ነው? አማራጭ ትርጉም: "ማንኛውም አባት ልጆቹን ይገገስጻል" ሕጋዊ ያልሆኑ ልጆች ካልተጋቡ ወንድ እና ሴት የተወለዱ ልጆች

Hebrews 12:9

ዕብራውያን **12**፡ **9**-**11**
የመንፈስ አባት የመንፈሳችን እና ሌሎች መናፈስትንም የፈጠረው እግዚብሔር። የጽድቅ ፍሬ ልክ ዛፍ ፍራፍሬ እንደሚያፈራ ሁሉ ጽድቅም የተግሳጽ ውጤት ነው። በእርሱ ሰልጥኗል በተገሳጽ ተገርቷል

Hebrews 12:12

ዕብራውያን **12**፡ **12**-**13**
የዛለውን እጆቻችሁን አንሱ እንዲሁም የላላውን ጉልበታችሁን እደገና አጽኑ ተግዳሮት የገጠመው ሰው በሩጫ ብዛት እግሮቹ እና ጉልበቱ የዛለን ሯጭ ይመስላል። አማራጭ ትርጉም: "ልክ ሯጭ ሩጫውን ለማጠናቀቀው ስወስን አካሉን እንደሚያበረታው ሁሉ እናነት ራሳችሁን አበርቱ" ለእግሮቻችሁ ቀናን መንገድ አዘጋጁ እግዚአብሔርን መታዘዝ ልክ በቀና መንገድ እንደመጓዝ ነው። አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር እንዲታደርጉ የሚፈልገውን ነገረ አድርጉ"

ማቋረጥ የሚፈልግ ሰው አማራጭ ትርጉም: "ሩጫውን ማቋረጥ የሚፈልግ ማንም ሰው" በተሳሳተ አቅጣጫ አትጓዝ "ሌላ ሰው ተከትለህ በተሳሳተ መንገድ አትሂድ።" አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔርን የማያስከብሩ ነገር ግን ቀላል የሆኑ ነገሮችን ለማድረግ አትወስን።" ይልቁን በርታ "ይልቁንም ጠንካራ ሁን"

Hebrews 12:14

ዕብራውያን **12**: **14-17**
እንዲሁም ከቅድስና ውጪ ጌታ ማንም ልያየው አይችልም አማራጭ ትርጉም: "በተጨማሪም ለመቀደስ ጠንክረህ ሥራ ምክንያቱም ቅዱስ የሆኑ ሰዎች ብቻ ናቸው ጌታን ማየት የሚችሉት" በተጨማሪም ቅድስና "በተጨመማሪም ቅድስናን ተከታተል" ተጠንቀቅ . . . ማንም እንዳይቀር . . . መራራ ሥር እንዳይበቅል . . . ይህ እንዳይሆን አድረግ መሪዎች ከእነዚህ ሦስ ነገሮች ልጠበቁ ይገባል፡ “ማንም እንዳይገለል . . መራራ ሥር በልባቸውን እንዳይበበቅል . . . ይህ እንዳይሆን መጠንቀቅ ይገባቸዋል።" ከእግዚአብሔር ጸጋ እንዳይጎድሉ "አንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ጸጋ ተቀብለው ከዚያ ወደ ኃላ እንዳይመለሱ" መራራ ሥር ሌሎች ሰዎች ክፋት እንዲያደርጉ የሚያደርግ ሰው ሥርን በምግብ ውስጥ እንደሚያደረግ ሰው ነው ተተጠንቀቁ . . . ልክ ኤሳው አማራጭ ትርጉም: "ተጠንቀቁ . . . ከእናንተ መካል እነንደ ኤሳው። በእንባ አጽንት ቢፈልገውም "እያለቀሰ ከልቡ ቢፈልግ"

Hebrews 12:18

ዕብራውያን **12**: **18-21**
እናንተ አንባቢያን ትዕዛዛቱን መፈጸም አልቻሉም የሚትሸከመውን ሸከም እንደሚትቀበለው ሁሉ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መቀበል። አማራጭ ትርጉም: "እስራኤላዊያን የእግዚአብሔር ሕግ አልተቀበሉትም ነበር።"

Hebrews 12:22

ዕብራውያን **12**: **22-24**
እናንተ አንባቢያን መጥጣችኋል "ወደ . . . ደርሳችኋል" ዐሥር ሺህ መላእክት "ቁጥር ስፍር ወደላሌላቸው መላእክት" ፈራጁ አምላክ . . . ኢያሱስ መካከለኛው ኢያሱስ በፍርድ ቤት ውስጥ እንዳለ ጠበቃ የፈሰሰው የእርሱ ደም እንዴት ለሰዎች በደል ይቅርታ እንደሚሆን ያሳያል። ከአቤል ደም ይልቅ አብልጦ የሚናገር ደም ተርጭቷል "የተረጨው የኢየሱስ ደም ቃዬል ከገደለው ከአቤል ደም ይልቅ ትርጉም አለው።"

Hebrews 12:25

ዕብራውያን **12**: **25-26**
መናወጥ . . . መንቀጥቀጥ በምድር መንቀጥቀጥ ምክንያት የሚከሰትን የምድር መናወጥ እና የሐህንጻዎች መደርመስን ለማመልከት የሚውልን ቃል ተጠቀም። እናንተ አንባቢያን እነርሱ ማምለጥ ካልቻሉif they did not escape "የእስራኤል ሰዎች ይህንን ፍርድ ማለፍ ካልቻሉ" እኛ ጸሐፊዎች እና አንባቢያን የሚያስጠነቅቁትም . . . የተስፋ ቃል ገብቷል "እግዚአብሔር አስጠንቅቋለል . . . እግዚአብሔር የተስፋ ቃል ሰጥቷል"

Hebrews 12:27

ዕብራውያን **12**: **27-29**
ተናውጠዋል "መንቀጥቀጥ" እና "መናወጥ" የሚሉትን ቃላት በ HEB 12:26 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምካቸው ተመልከት። አመስጋኞች እንሁን "ምስጋናን እንስጥከ" አክብሮት እና አድናቆት ጋር "አክብሮት" እና "አድናቆት" የሚሉት ሁለት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉሞች ያሉት ሲሆን አጽኖት ሰጥተው የሚያስተላልፉት መልዕክት ታላቅ አክብሮት ነው። አማራጭ ትርጉም: "ከታላቅ አክብሮት ጋር" አምላካችን እግዚአብሔር የሚባላ እሳት ነው እግዚአብሔር ልክ እሳት ነገሮችን እንደሚያቃጥል ሁኔ ከእርሱ ዓላማ ጋር የሚቃረንን ማንኛውንም ነገር ለማፍረስ የሚያስችል ኃይል አለው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 13

1 በወንድማማችነት ፍቅር መዋደዳችሁን ቀጥሉ። 2 እንግዶችን መቀበል አትርሱ፣ አንዳንድ ሰዎች ይህን ሲያደርጉ ሳያውቁት መላእክትን አስተናግደዋል። 3 ከእነርሱ ጋር እንደታሰረ ሆናችሁ፣ በሰውነታችሁም እንደ እነርሱ መከራን እንደሚቀበል ሆናችሁ በእስራት ያሉትን አስቡ። 4 ጋብቻ በሁሉም ዘንድ የተከበረ መኝታውም ንጹሕ ይሁን፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር በሴሰኞችና በአመንዝራዎች ላይ ይፈርድባቸዋል። 5 አኗኗራችሁ ከገንዘብ ፍቅር የጸዳ ይሁን። እግዚአብሔር ራሱ፣ “እኔ ፈጽሞ አልተውህም፣ ደግሞም አልጥልህም” ስላለ፣ ባላችሁ ነገር ረክታችሁ ኑሩ። 6 ስለዚህ፣ “ጌታ ረዳቴ ነው፤ አልፈራም። ሰውስ ምን ሊያደርገኝ ይችላል?” ብለን በድፍረት እንናገራለን። 7 የእግዚአብሔርን ቃል የነገሯችሁን መሪዎቻችሁን አስቡ፣ የምግባራቸውንም ፍሬ ተመልከቱ፤ በእምነታቸውም ምሰሏቸው። 8 ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት፣ ዛሬና ለዘላለምም ያው ነው። 9 በልዩ ልዩ እንግዳ ትምህርቶች አትወሰዱ፣ ለሚከተሏቸው ሰዎች ፋይዳ የሌላቸውን የአመጋገብ ሥርዓቶች በመጠበቅ ሳይሆን ልብ በጸጋ ሲጸና መልካም ነው። 10 በመገናኛው ድንኳን የሚያገለግሉት ከእርሱ እንዲበሉ ያልተፈቀደላቸው መሠዊያ አለን። 11 ሊቀካህናቱ ለኃጢአት ስርየት የተሠዋውን የእንስሳት ደም ወደ ቅድስት ያመጣል፣ የእንስሳቱ ሥጋ ግን ከሰፈር ውጭ ይቃጠላል። 12 ደግሞም ኢየሱስ ሰዎችን በገዛ ደሙ ለመቀደስ ከከተማይቱ ቅጥር ውጭ መከራን ተቀበለ። 13 ስለዚህ እኛም እርሱ የተሸከመውን ውርደት ተሸክመን ከሰፈር ውጭ ወደርሱ እንሂድ። 14 በዚህ ምድር ምንም ዓይነት ዘላቂ ከተማ የለንም። ነገር ግን የምትመጣውን ከተማ እንጠብቃለን። 15 የስሙን ታላቅነት የሚናገሩ የከንፈሮቻችንን ፍሬ፣ ማለትም የምስጋና መሥዋዕቶችን ያለማቋረጥ በኢየሱስ በኩል ለእግዚአብሔር ማቅረብ ይገባናል። 16 ደግሞም መልካም ማድረግንና እርስ በርስ መረዳዳትን አትርሱ፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር የሚደሰተው እንደነዚህ ባሉ መሥዋዕቶች ነው። 17 ተጠያቂነት ስላለባቸው ለነፍሳችሁ እንክብካቤ ለሚያደርጉ ለመሪዎቻችሁ ታዘዙ፣ ተገዙላቸውም። ለእናንተ ስለማይጠቅም በሐዘን ሳይሆን በደስታ እንዲከባከቧችሁ ታዘዟቸው። 18 በሁሉም ነገር የከበረ ሕይወት ለመኖር የሚፈልግ ንጹሕ ኅሊና ስላለን ጸልዩልን። 19 ወደ እናንተ ቶሎ መመለስ እንድችል ይበልጥ ይህን እንድታደርጉ አበረታታችኋለሁ። 20-21 እንግዲህ በዘላለም ኪዳን ደም የበጎች ታላቅ እረኛ የሆነውን ጌታችን ኢየሱስን፣ ከሙታን ያስነሣው የሰላም አምላክ እግዚአብሔር፣በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት በእኛ ውስጥ የሚሠራውን፣ በእርሱ ፊት ደስ የሚያሰኘውን ፈቃዱን እንድታደርጉ በማናቸውም መልካም ነገር ያስታጥቃችሁ። ከዘላለም እስከ ዘላለም ለእርሱ ክብር ይሁን። አሜን። 22 ወንድሞች ሆይ፤ አሁን በዐጭሩ የጻፍሁላችሁን ማበረታቻ እንድትቀበሉ አደፋፍራችኋለሁ። 23 ወንድማችን ጢሞቴዎስ እንደተፈታ ዕወቁ፣ ቶሎ ከመጣም ከእርሱ ጋር አብሬ አያችኋለሁ። 24 ለመሪዎችና ለቅዱሳን ሁሉ ሰላምታ አቅርቡልኝ። በኢጣልያ ያሉት ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። 25 ጸጋ ከሁላችሁም ጋር ይሁን።

Hebrews 13:1

ዕብራውያን **13**፡ **1-2**
የወንድማማች ፍቅራችሁ ይቀጥል አማራጭ ትርጉም: "ሁል ጊዜ ለሌሎች አማኞች ልክ ለቤተሰባችሁ አባላት የሚታሳዩትን ዓይነት ፍቅር አሳዩ" አትዘንጉ አማራጭ ትርጉም: "ማስታወሳችሁን እርግጠኞች ሁኑ" እንግዶችን ተቀበሉ አማራጭ ትርጉም: "የማታውቋቸውን ሰዎች እንደ ጓደኞቻችሁ አድርጋችሁ ተቀበሉ"

Hebrews 13:3

ዕብራውያን **13**፡ **3-4**
ከእርሱ ጋር እንደሆናችሁ በመቁጠር . . . አካላችሁ ልክ እንደ እንደነርሱ እንደተጎሳቆለ በመቁጠር እነዚህ ሁለት ሀረጋት አማኞች የሌሎች ሰዎችን መከራ ልክ እንደ እንደነርሱ መከራ አድርገው ይቆጥሩት ዘነንድ የሚያበረታታ ነው። አማራጭ ትርጉም: "ከእነርሱ ጋር በእስር እንዳላችሁ እና መከራን እየተቀበላችሁ በመቁጠር" መኝታችሁ ንጹሕ ይሁን ይህ ማለት ባል እና ምስት በትዳራችሁ ውስጥ ያለውን ግንኙነት በማክበር ከሌሎች ሰዎች ጋር አይተኙ።

Hebrews 13:5

ዕብራውያን **13**፡ **5-6**
ያላችሁ ነገር ያርካችሁ "እግዚአብሔር የሰጣችሁ ነገር ያስደስታችሁ"

Hebrews 13:7

ዕብራውያን **13**፡ **7-8**
የተግባራቸው ውጤት አማራጭ ትርጉሞች: 1) "የኖሩበት መንገድ" ወይም 2) "ኖረው የሞቱበት መንገድ" ወይም "ዘመናቸውን ሁሉ የኖሩበት መንገድ" በኢየሱስ አምነው እስከመጨረሻው የኖሩት ኑሮ።

Hebrews 13:9

ዕብራውያን **13**፡ **9-11**
የተለያዩ እና እንግዳ ትምህርቶች "እኛ የነገርናችሁ ወንጌል ሳይሆን ብዙ እና የተለያዩ ትምህርቶች" ልባችን ስለምግብ በሚሰጡ ሕግጋት ሳይሆን በጸጋ መገንባጹ መልካም ነው አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር ለእኛ ምን ያኽል መልካም እነንደሆነ ስነናሰብ እንጠነክራለን ነገር ግን የምግብ ሕግጋትን በመጠበቅ አንጠነክርም" ለኃጢአት መስዋእት መሆን "እግዚአብሔር ኃጢአታችን ይቅር ይላን ዘንድ መስዋእት መሆን" ከቅጥር ውጪ ሰዎች ከሚኖሩበት አከባቢ ርቆ

Hebrews 13:12

ዕብራውያን **13**፡ **12-14**
ስለዚህ "በተመሳሳይ መልኩ" ወይም "መስዋእቱ ከቅጥር ውጪ የሚቃጠል በመሆኑ" (HEB 13:11) ስለዚህም እንሂድ "ስለዚህም ኢየሱስ ከከተማው መግቢያ ውጪ" ከቅጥሩ ውጪ ይህንን በ HEB 13:11 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት።

Hebrews 13:15

ዕብራውያን **13**፡ **15-17**
የከንፈሮቻችን ፍሬ የሆነውን ምሳጋና ይህ የአነጋር ዘይቤ ልክ ፍራፍሬ ዕጽዋት የሚያፈሩት ዋጋ ያለው ፍሬ እንደሆነ ሁሉ ምስጋና ከአንደበታችን የሚወጣ ዋጋ ያለው ነገር መሆኑን የሚያሳይ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Hebrews 13:18

ዕብራውያን **13**: **18**-**19**

Hebrews 13:20

ዕብራውያን **13**: **20**-**21**
በዘላለማዊ ኪዳን ደም አማራጭ ትርጉሞች: 1) "እግዚአብሔር ዘላለማዊ ኪዳኑን በደም አረጋግጦዋል" (UDB) ወይም 2) "በዘላለማዊ ኪዳን ደም" አማካኝነት ነው ኢየሱስ "ጌታችን" የሆነው ወይም 3) እግዚአብሔር ኢየሱስን “ከሞት” “መልሶ” ያመጣው "በደም . . . ኪዳን" ነው። እናንተን አስታጥቆ . . . በእኛ ውስጥ በመሥራት ደራሲው እና ተደራሲያኑ

Hebrews 13:22

ዕብራውያን **13**: **22**-**23**

Hebrews 13:24

ዕብራውያን **13**: **24**
ኖት የለውም።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: James

James

ምዕራፍ 1

1 በኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር እስረኛና አገልጋይ የሆነ ያዕቆብ በክርስቶስ ኢየሱስ ለሚያምኑና በመላው ዓለም ለተበተኑት ለአሥራ ሁለቱ ነገዶች ሰላም
ለእናንተ ይሁን። 2 ወንድሞቼ ሆይ፣ በልዩ ልዩ ፈተናዎች ውስጥ ማለፋችሁን እጅግ ደስ እንደሚያሰኝ ነገር ቍጠሩት። 3 በፈተና ውስጥ ሳላችሁ በእግዚአብሔር
ስታምኑ ይበልጥ ሌሎች ፈተናዎችን በትዕግሥት ለማሳለፍ የሚረዱዋችሁ መሆኑን ትረዳላችሁ። 4 ክርስቶስን በሁሉም መንገድ ትከተሉ ዘንድ እስከ
መጨረሻው በፈተና ጽኑ፤ ያንጊዜ መልካም ማድረግ አይከብዳችሁም። 5 ከእናንተ አንዱ ምን ማድረግ እንዳለበት ማወቅ ከፈለገ፣ በሚጠይቀው ላይ ሳይቈጣ
በልግሥና የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይጠይቅ። 6 እግዚአብሔርን ስትለምኑ፣ የምትጠይቁትን እንደሚሰጣችሁ እመኑ፤ መልስ እንደሚሰጣችሁና ሁልጊዜም
እንደሚረዳችሁ አትጠራጠሩ፤ የሚጠራጠሩ ሰዎች እግዚአብሔርን ሊከተሉት አይችሉም፤ መጠራጠር ልክ ተመልሶ እንደሚመጣ፣ ደግሞም በዚያው አቅጣጫ
መጓዝን እንደማይቀጥል የባሕር ማዕበል ያለ ነገር ነው። 7 በእርግጥ የሚጠራጠሩ ሰዎች የሚጠይቁትን ነገር ለመፈጸም እግዚአብሔር አንድ ነገር ሊያደርግ
እንደሚችል አያምኑም። 8 እነዚህ ሰዎች ኢየሱስን ለመከተል ወይም ላለመከተል ያልወሰኑ ናቸው፤ እነዚህም የሚናገሩትን ነገር የማያደርጉ ሰዎች ናቸው። 9 ድሀ
የሆኑ አማኞች እግዚአብሔር ስላከበራቸው ደስ ሊሰኙ ይገባል። 10 ባለጠጋ የሆኑ አማኞችም እግዚአብሔር ትሑታን ስላደረጋቸው ደስ ሊሰኙ ይገባል፤ ልክ
የበረሃ አበቦች እንደሚደርቁ ሁሉ፣ እነርሱም ሆኑ ሀብታቸው የሚያልፉ ናቸውና። 11 ፀሐይ በሚወጣ ጊዜ ሞቃታማ የሆነው ነፋስ ተክሎችን ያደርቃል፤ ደግሞም
አበቦችን በምድር ላይ እንዲወድቁም ሆነ በውበታቸው እንዳይቀጥሉ ያደርጋቸዋል። ባለ ጠጎች ልክ እንደሚሞቱ አበቦች ሁሉ ገንዘብን እየሰበሰቡ ሳሉ ይሞታሉ።
12 በመከራ የሚጸኑትን ሰዎች እግዚአብሔር ያከብራቸዋል፤ ለሚወድዱት ሁሉ ተስፋ እንደ ሰጠው ለዘላለም እንዲኖሩ በማድረግ ብድራታቸውን ይከፍላቸዋል።
13 በኃጢአት ስንፈተን እግዚአብሔር እየፈተነን ነው ብለን ልናስብ አይገባም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ክፉን እንድንሠራ አይፈልግምና፤ ክፉን እንዲያደርግ
ማንንም አይፈትንምና። 14 እያንዳንዱ ሰው የሚፈተነው በራሱ ክፉ ምኞት ሲታለልና ሲሳብ ነው። 15 ክፉ ምኞት ከተፀነሰ በኋላ ኀጢአት ይወለዳል፤
ኀጢአትም ካደገች በኋላ ሞት ይወለዳል። 16 የተወደዳችሁ ወንድሞቼ አትታለሉ። 17 ማንኛውም መልካምና ፍጹም ስጦታ እንደሚዘዋወር ጥላ
ከማይለዋወጠው ከላይ ከሰማይ ከብርሃናት አባት ይወርዳል። 18 በፍጥረታቱ መካከል እንደ በኵራት እንድንሆን እግዚአብሔር በእውነት ቃል ሕይወት
ሊሰጠን ወደደ። 19 የተወደዳችሁ ወንድሞቼ፣ ይህን ዕወቁ። ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ፣ ለመናገር የዘገዬ፣ ለመቆጣትም የዘገዬ ይሁን! 20 ምክንያቱም
የሰው ቍጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አያመጣም። 21 ስለዚህ ርኵሰትንና በየቦታው ሞልቶ ያለውን ክፋት አስወግዳችሁ ነፍሳችሁን ማዳን የሚችለውን
በውስጣችሁ የተተከለውን ቃል በትሕትና ተቀበሉ። 22 ለቃሉ ታዘዙ እንጂ፣ ሰሚዎች ብቻ በመሆን ራሳችሁን አታታልሉ። 23 ማንም ቃሉን እየሰማ ቃሉ የሚለውን
ባያደርግ፣ ፊቱን በመስታወት እንደሚያይ ሰው ይሆናል። 24 ፊቱን አይቶ ይሄዳል፤ ምን እንደሚመስል ግን ወዲያው ይረሳዋል። 25 ፍጹሙንና ነጻ የሚያወጣውን
ሕግ በጥንቃቄ የሚመለከትና የሚኖርበት እንጂ፣ ሰምቶ እንደሚረሳው ያልሆነ ሰው በሚያደርገው ሁሉ የተባረከ ይሆናል። 26 አንድ ሰው ሃይማኖተኛ ነኝ እያለ፣
አንደበቱን ግን ባይቆጣጠር፣ ልቡን ያስታል፤ ሃይማኖቱም ከንቱ ነው። 27 በእግዚአብሔር በአባታችን ፊት ንጹሕና ርኵሰት የሌለበት ሃይማኖት ይህ ነው፤ አባት
የሌላቸውንና መበለቶችን በችግራቸው መርዳት፤ በዓለም ካለ ርኵሰት ራስን መጠበቅ።

James 1:1

ያዕቆብ **1**፡ **1-3**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ከመክፈቻ ሠላምታው በኋላ ያዕቆብ የመከራ ዓላማ እምነትን ለመፈተን መሆኑን ለአማኞች ይነግራቸዋል። ያዕቆብ "እኔ ያዕቆብ።" ያዕቆብ የኢየሱስ በአንድ ወገን ወንድም ነው። የእግዚአብሔር እና የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ “እኔ” የሚለው ሀረግ በተዘዋዋሪ መልኩ የተገለጸ ነው። አማራጭ ትርጉም: "እኔ የእግዚአብሔር እና የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ ነኝ።" ለተበተኑት ዐሥራ ሁለት ነገዶች ያቆብ የጻፈው ከእስጥፋኖስ መወገር በኋላ በተነሣው ስደት ምክንያት ከይሁዳ ውጪ ባሉ የሮም ከተማዎች ውስጥ ለተበተኑት አይሁዳዊያን አማኞች ነው። ዐሥራ ሁለት ነገዶች ቁጥሮችን በመጸፍ ወጥነት ሊኖራችሁ ይገባል። ይህ “12 ነገዶች” ተብሎም ሊጻፍ ይችላል። ሠላምታ እንደ “ሄሎ” ወይም “መልካም ቀን” የመሳሰሉት መሠረታዊ የሠላምታ አሰጣጥ ነው። ወንድሞቼ ሆይ የተለያዩ መካራዎች ስደርስባችሁ ይህንን እንደ ደስታ ቁጠሩት "የተለያዩ መከራዎች ስደርሱባችሁ ወንድሞች ሆይ በዚህ ደስ ይበላችሁ።" የእምነታችሁ መፈተን ጽናትን እንደሚያመጣላችሁ በማወቅ "እግዚአብሔር እምነታችሁን ለማጠንከት መከራን እንደሚጠበቅ ሰለምታውቁ ነው።"

James 1:4

ያዕቆብ **1**፡ **4-5**
ጽናት ሥራውን እንዲፈጽም ፍቀዱለት በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ እንኳ በቀጣይነት ጸንተህ ቁም። አማራጭ ትርጉም: "በመከራህ ወቅት ጠንከር በል።" የአንተ . . . ይሆን ዘንድ "በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር እምነትህን ... ያደርግ ዘንድ" ፍጹም ሙሉ "ፍጹም ሙሉ" ምንም የማይጎድለው ይህ አሉታዊ ሀረግ ሲሆን በአወንታዊ መልኩ እንዲህ መገለጽ ይችላል: "ብዙ ያለው" ይህን ከሚሰጠው ከእግዚአብሔር ዘንድ ጠይቅ "ይህንን እግዚአብሔርን ጠይቀው። ይህንን የሚሰጠው እርሱ ነው።" ሳይነቅፍ በልግስና "ሳይነቅፍ" የሚለው ሀረግ አሉታዊ ነው፤ ይሁን እንጂ አዎንታዊ በሆነ መልኩ እንዲህ መገለጽ ይችላል፣ "በልግስና እና በደስታ።" ይህንን እርሱ ይሰጣል "እግዚአብሔር ይህን ይሰጣል" ወይም "እግዚአብሔር ጸሎትህን ይሰማል"

James 1:6

ያዕቆብ **1**፡ **6-8**
በምንም ሳይጠራጠር በእምነት “በምንም ሳይጠራጠር” የሚለው አሉታዊ ሀረግ ሲሆን አዎንታዊ በሆነ መልኩ እንዲህ ልገለጽ ይችላል፣ “እግዚአብሔር ለጸሎት መልስ በእርግጠኝነት ይሰጣል።” የሚጠራጠር ሰው ልጅ በባሕር ላይ እንዳለ ወጀብ በማዕበል ወዲህ እና ወዲያ የሚነዳ ነው ይህ የሚጠራጠር ሰውን በንፋስ በየጊዜው አቅጣጫውን ከሚቀያይር ውሃ ጋር ያነጻጽራል። አማራጭ ትርጉም: "የሚጠራጠር ሰው ሁል ጊዜ ወደኋላ እና

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ወደፊት በማመን እና ባለማመን መካል ይዋዥቃል።" ወይም "የሚጠራጠር ውስጥ ሁል ጊዜ የሚያምነውን ነገር ይለዋውጣል።" የእርሱ ጥያቄ "እርሱ የጠየቀው ምንድ ነው" ጌታን "ከጌታ" ሁለት ሀሳብ ላለው ሀሳብ ያለው ሰው - “ሁላት ሀሳብ ላለው” የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው አንድ ሰው አንድን ውሳኔ ለመወሰን ያላስቻለው ሀሳቦች ያሉትን ሰው ነው። አማራጭ ትርጉም: "ኢያሱስን መከተል ወይም መከተል እንዳሌለበት ለመወሰን አይችልም"

በመንገዱ ሁሉ የተረጋጋ አይሆንም "ስለምንም ነገር እርግጠኛ መሆን አይችልም"

James 1:9

ያዕቆብ **1:9-11**
ደሃ ወንድም "ብዙ ገንዘብ ያሌለው አማኝ" በቆመበት ክብር ይመካ "እግዚብሔር ክብር ስለሰጠው በዚህ ደስ ይበለው" ሀብታም የሆነው ወንድም "ብዙ ገንዘብ ያለው ወንድም" በእርሱ ትህትና ውስጥ የዚህ ሀረግ የተወሰነ ክፍል በተዘዋዋር መንገድ የተገለጸው ማለት “በውርደቱ ይመካ” የሚለው ተትቷል። አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር ትህትናን ስላስተማረው ደስ ይበለው።" ሀብታም ሰዎች በሥራቸው መካል ተፍተው ይቀራሉና "ሀብታም ሰው ተጨማሪ ገንዝብ ለማግኘት ተግቶ ስሠራ በዚያው ይሞታል"

James 1:12

ያዕቆብ **1:12-13**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ያዕቆብ የወደቁ አማኞችን ፈተናን እንደማያመጣ ያስታውሳቸዋል። ስለዚህም እንዴት ፈተናን ማስወገድ እንዳለባቸው ይነግራቸዋል። የተባረከ ሰው ነው "ደስተኛ ሰው ነው" በፈተና የሚጸና "መከራ ስመጣ በዚያ ውስጥ ጸንቶ የሚቆም ሰው" ፈተናውን የሚያልፍ "በመከራ ውስጥ ጸንቶ የሚቆም ሰው" እርሲ ይቀበላል "እግዚአብሔር ይሰጠዋል" የሕይወትን አክሊል ይቀበላል "የሕይወት አክሊል" እንደ ሽልማት የሚሰጠው የዘላለም ሕይወት ምሳሌያዊ ንግግር ነው። "የዘላለም ሕይወትን እንደ ሽልማት ይቀበላል" ይህ እግዚአብሔርን ለመውዱት የተስፋ ቃል ተሰጥቶዋቸዋል አማራጭ ትርጉም: "እርሱን ለምወዱት እግዚአብሔር የሕይወትን አክሊል እንደሚሰጣቸው የተስፋ ቃል ሰጥቶዋቸዋል።" በሚፈተንበት ጊዜ "ክፉ የሆነ ነገርን ለማድረግ ፍላጎት በውስጡ ስያድር" ይህ ፈተና ከእግዚአብሔር ነው “እግዚአብሔር ክፉ የሆነ ነገርን እንዳደረግ እያደረገኝ ነው” እግዚአብሔር በክፉ አይፈተን "እግዚአብሔር ክፉን ነገር ለማድረግ አይሻም" እግዚአብሔር ማንንም . . . አይፈትንም "እግዚአብሔር ሰዎች ክፋትን እንዲያደርጉ አይገፋፋም"

James 1:14

ያዕቆብ **1:14-16**
እያንዳንዱ ሰው የሚፈተነው በራሱ ክፉ መሻቶቹ ነው ክፋትን ለማድረግ መሻት በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ አለ። ይህ የስበዋል እንዲሁም ይጥለዋል "ይህ ይስበዋል እንዲሁም ወደሌላ አቅጣጫ ይመራዋል" ከዚህ በኋላ ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች፤ ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች። "ኃጢአታዊ ምኞች፣" "ኃጢአት፣" እና "ሞት" የሰው ልጅ ባሕርያት ናቸው። በዚህ ሥፍራ ላይ “ኃጢአታዊ ምኞች” የተገለጸው አንድት ሴት አንድን ወንድ ከእርሷ ጋር እንድተኛ ከሚታማልልበት መንግድ ጋር ተያይዞ ነው። "ኃጢአት" ልጃቸው ነው። "ሞት" ልጃቸው ሙሉ ለሙሉ ከደገ በኋላ የሚሆነው ውጤቱ ነው። በተጨማሪም ይህ ክፉ መሻት በመጀመሪያም ምን ያኽል ደስታን እንደሚሰጥ ያሳያል ነገር ግን ይህ ደስታ ወደ ኃጢአት ይለወጣል ከዚያም አካላዊ እና መንፈሳዊ ሞትን ያስከትላል። አትታለሉ "ማንም ሰው እንዳያታልላችሁ" ወይም "ራሳችሁን ማታለል አቁሙ" (UDB)

James 1:17

ያዕቆብ **1:17-18**
ማንኛውም መልካም የሆነ ስጦታ እና ፍጹም የሆነ ስጦታ እነዚህ ሁለት ሀረጋት በመሠረታዊ ትርጉማቸው ተመሳሳይ ናቸው። ያዕቆብ እነዚህ የተጠቀመው ያ ሰው ያለው ማንኛውም መልካም ነገር ሁሉ የመጣው ከእግዚአብሔር ዘንድ መሆኑን አጽኖት ሰጥቶ ለማሳየት ነው። ከላይ ነው "ከሰማይ ነው" ከብርሃን አባት በሰማይ ያሉትን ብርሃናት (ፀሐይ፣ ጨረቃ እና ክዋክብትን) የፈጠረው እግዚአብሔር ነው። እርሱ በብርሃን መለዋወጥ አይለዋወጥም ይህ የማይለወጠውን እግዚአብሔርን ለመግለጽ ቀጣይነት ካለው ብርሃን እና በሰማይ ላይ ከሚንቀሳቀሱት ሊሰጠን በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ያዕቆብን እና የእርሱ ተደራሲያንን ነው። ሕይወትን ሰጠን "መንፈሳዊ ሕይወትን ሰጠን።" (UDB) የእውነት ቃል "ወንጌል" ወይም "የኢየሱስ አስተምህሮ" እንደ በኩራት እንደ ሰብል በኩራት የእርሱ ተደራሲያን ከመጀመሪያዎቹ አማኞች መካከል መሆናቸውን ያዕቆብ አጽኖት ሰጥቶ በመግለጽ ለወደፊቱ በጣም ብዙ አማኞች እንደሚኖሩ ይገልጻል።

ከፍጥረታት መካከል "ከእርሱ ሕዝብ መካከል"

James 1:19

ያዕቆብ **1:19-21**
ይህንን ታውቃላችሁ አማራጭ ትርጉሞች 1) "ይህንን እወቁ" እንደ ትእዛዝ፣ ቀጥሎ ለሚጽፈው ነገር ከፍተኛ ትኩረት ስጡት ወይም 2) "እናንተ ይህንን ታውቁታላችሁ" እናንተ አስቀድማችሁ የሚታውቁትን ነገር አሁን ላታወሳችሁ ነው የሚል ዓረፍተ ነገር። ሁሉም ሰው ለመስማት የፈጠነ፣ ለማገር ደግሞ የዘገ ይሁን ሰዎች በመጀሪያ በጥንቃቄ ለማድመጥ ከዚያም የሚናገሩትን ነገር በጥንቃቄ መርጠው መናገር ይኖርባቸዋል። ለቁጣ የዘገዩ "በቀላዩ የማይቆጡ" የሰው ቁጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አይሠራም አንድ ሰው ሲቆጣ እግዚአብሔር በሚፈልገው መልኩ ነገሮችን ማከናወን ኤችልም። ርኩሰተን እና ክፋትን ሁሉ አስወግዳችሁ በዚህ ሥፍራ “ርኩሰትን እና ክፋትን” የሚለው ቃል ተመሣሣይ ትርጉም ያላቸወ ናቸው። እነዚህ ቃላት ያዕቆብ የተጠቀመባቸው ኃጢአት ምን ያኽል መጥፎ መሆኑን ለማሳየት መው። አማራጭ ትርጉም: "ማንኛውንም ዓይነት ኃጢአታዊ ባሕርይ ማድረግ አቁም። በትህትና "ያለትምክህት" ወይም "ያለ ጋጠወጥነት" በውስጥ የተተከለው ቃል ተቀበል “መትከል” የሚለው ቃል አንድን ነገር በሌላኛው ውስጥ አስገብቶ ማስቀመጥን ያመለክታል። ይህ የእግዚአብሔር ቃል በሰው ውስጥ መተከሉን ለማሳየት ጥቅም ላይ የዋለ ምሳሌ ነው። አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር ለአንተ የተናገረውን መልዕክት ታዘዝ።" ነፍስህን አድን በዚህ ሥፍራ ላይ “ነፍስ” የሚለው ቃል የሰውን ሁለንተና ታሳያለች። በተጨማሪም ሰውዩው የሚድነው ከምን እንደሆነ በግለጽ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም: "ከእግዚአብሔር ፍርድ ያድንሃል።"

James 1:22

ያዕቆብ **1:22-25**
ቃሉን ታዘዝ “የእግዚአብሔርን ቃል ታዘዝ” ወይም "እግዚአብሔር ለአንተ የላከውን ቃል ታዘዝ" የገዛ ራስህን አታታል "ራስህን አታታል" ወይም "ራስህን አታታል" ቃሉን የሚሰማ ነገር ግን የማያደርገው ማንኛውም ሰው ቢኖር እርሱ ተፈጥሮአዊ ፊቱን በመስታወት እንደሚመለከት ሰው ነው። Jያዕቆብ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቶ የማይታዘዝን ሰው ተፈጥሮአዊ ፊቱን በመስታወት አይቶ ምን እንደሚመሰል ከዘነጋ ሰው ጋር ያነጻጽረዋል። ተፈጥሮአዊ ፊቱን ተመልክቶ . . . ወዲያው የዘነጋ ፊቱን በመስታወት ተመልክቶ ወዲያ የተመለከተውን የሚረሳ ሰው የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቶ የሰማውን ከሚረሳ ሰው ጋር ተመሳሳይ ናቸው። ፍጹም ሕግ፣ የነጻነት ሕግ "ነጻነት የመከሰጥ ፍጹም ሕግ" የሰሙትን እንደሚረሱት ሰሚዎች ብቻ አትሁኑ "ሰምቶ ከዚያ እንደሚዘነጉት አትሁኑ" የሚያደርገው ይህ ሰው የተባረከ ነው አማራጭ ትርጉም: "ሕጉን በታዘዘ ቁጥር እግዚአብሔር ይህንን ሰው ይባርከዋል"

James 1:26

ያዕቆብ **1:26-27**
ራሱን ሃይማኖተኛ አድርጎ የሚቆጥረው ሰው "በትክክል እግዚብሔር እንደሚያመልክ የሚያስብ ሰው" አንደበቱ አማራጭ ትርጉም: "እርሱ የሚናገረው ነገር" ያታልላል "ማታለል" ወይም "መሸወድ" ወይም "ማሳሳት" የእረሱ ልብ በዚህ ሥፍራ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሰውን ሁለንተና ነው። አማራጭ ትርጉም: "እርሱ ራሱ።" ሃይማኖቱ ከንቱ ነው "አምልኮው ምንም ጥቅም የለውም" በአምላካችን እና በአባታችን ፊት ንጹሕ

እና ነውር ያሌለበት አምልኮ ይህ ነው አማራጭ ትርጉም፡ "ይህ እግዚአብሔር የሚቀበለው የሃይማኖት አይነት ነው" ንጹሕ እና ነውር የሌለው በዚህ ሥፍራ ላይ ያዕቆብ እውነተኛ ሃይማኖት ምን እንደሚመሰል አጽኖት ሰጥቶ ለመግለጽ ተመሳሳይ ሀሳብ ያላቸው ነገር ግን አንዱ በአውንታዊ ሌላኛው በአሉታዊ መልኩ የቀረቡ ቃላትን ተጠቅሟል።አማራጭ ትርጉም: "ፍጹም ንጹሕ።"

አባት የሌላቸው "አባት የሌላቸው ሰዎች" ወይም "ወላጆቻቸው የሞቱባቸው" ባልቴቶችን በመከራቸው ባላቸው በመሞቱ ምክንያት መከራ የደሰባቸው ሰዎች በዓለምም ከሚገኝ እድፍ ሰውነቱን መጠበቅ በዓለም ያለው ክፋት ኃጢአት እንድናደርግ እንዳያደርገን አለመፍቀድ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 2

1 ወንድሞች ሆይ፤ ለአንዳንዶች አድልዎ እያደረጋችሁ የክብር ጌታ የጌታችን አየሱስ ክርስቶስን እምነት እንከተላለን አትበሉ። 2 የወርቅ ቀለበት ያደረገና
የሚያማምሩ ልብሶች የለበሰ ወደ ስብሰባችሁ ሲገባና እንዲሁም አዳፋ ልብሶች የለበሰ ድኻ ቢገባ 3 ትኵረታችሁ የሚያማምሩ ልብሶች የለበሰው ሰው ላይ
ይሆንና፣ “እዚህ ደኅና ቦታ ላይ ተቀመጥ” ትሉታላችሁ፤ ድኻውን ግን፣ “እዚያ ቁም” ወይም “ከእግሬ በታች ተቀመጥ” ትሉታላችሁ 4 ታዲያ፣ በመካከላችሁ
አድልዎ ማድረጋችሁ አይደለምን፤ ደግሞስ በክፉ ዐሳብ የተያዛችሁ ፈራጆች መሆናችሁ አይደለምን? 5 የተወደዳችሁ ወንድሞች ስሙ፤ በእምነት ባለ ጸጋ
እንዲሆኑና፣ እርሱን ለሚወዱ ቃል የገባላቸውን መንግሥት እንዲወርሱ እግዚአብሔር የዚህ ዓለም ድኾችን አልመረጠምን? 6 እናንተ ግን ድኾችን አዋረዳችሁ!
የሚጨቁኗችሁ ባለ ጸጎች አይደሉምን? ወደ ፍርድ ቤት የሚጎትቱዋችሁስ እነርሱ አይደሉምን? 7 የተጠራችሁበትን መልካም ስም የሚሳደቡ ባለ ጸጎቹ
አይደሉምን? 8 ይሁን እንጂ፣ “ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ” ተብሎ እንደ ተጻፈው የከበረውን ሕግ ብትፈጽሙ መልካም ታደርጋላችሁ፤ 9 ለአንዳንዶች
አድልዎ ብታደርጉ ግን፣ ኃጢአት ትሠራላችሁ፤ እንደ ሕግ ተላላፊዎችም ትቆጠራላችሁ። 10 ምክንያቱም ሕጉን የሚፈጽም፣ በአንዱ ግን የሚሰናከል፣ ሕጉን ሁሉ
እንደ ተላለፈ ይቆጠራል! 11 “አታመንዝር” ያለው እግዚአብሔር፣ “አትግደልም” ብሎአልና። ባታመነዝር ሆኖም ግድያ ብትፈጽም፣ የእግዚአብሔርን ሕግ
ተላልፈሃል። 12 ስለዚህ ነጻ በሚያወጣው ሕግ እንደሚፈረድባቸው ሰዎች ተናገሩ፤ ደግሞም ታዘዙ። 13 ምክንያቱም ምሕረት በማያደርጉ፣ ምሕረት የሌለበት
ፍርድ ይመጣባቸዋል። ምሕረት ፍርድን ያሸንፋል! 14 ወንድሞቼ ሆይ፣ አንድ ሰው እምነት እንዳለው ቢናገር፣ ሥራ ግን ባይኖረው ምን ይጠቅማል? ያ እምነት
ሊያድነው ይችላልን? 15 አንድ ወንድም ወይም እኅት ልብስና የዕለት ምግብ ባይኖራቸው 16 ከእናንተ አንዱ፣ “በሰላም ሂዱ፤ አይብረዳችሁ፤ በደንብ ጥገቡ”
ቢላቸው፤ ለአካል የሚያስፈልጉ ነገሮችን ግን ባትሰጧቸው፣ ምን ይጠቅማል? 17 ሥራ የሌለው እምነትም እንዲሁ በራሱ የሞተ ነው። 18 ምናልባትም አንዱ፣
“አንተ እምነት አለህ እኔ ደግሞ ሥራ አለኝ” ሥራ የሌለው እምነትህን አሳየኝ፤ እኔም እምነቴን በሥራዬ አሳይሃለሁ ይል ይሆናል። 19 አንድ እግዚአብሔር መኖሩን
ታምናለህ፤ ትክክል ነህ። አጋንንትም ይህን ያምናሉ፤ በፍርሃትም ይንቀጠቀጣሉ። 20 አንተ ሞኝ፣ እምነት ያለ ሥራ ከንቱ መሆኑን ማወቅ ትፈልጋለህ? 21
አባታችን አብርሃም፣ ልጁ ይስሐቅን መሠዊያው ላይ ባቀረበ ጊዜ በሥራ ጸድቆ አልነበረምን? 22 እምነት በሥራው ታየ፤ በዚያው ሥራ እምነት ዓላማውን ፈጸመ።
23 “አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ፤ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት” የሚለው የመጽሐፍ ቃል ተፈጸመ። ስለዚህም አብርሃም የእግዚአብሔር ወዳጅ ተባለ። 24
ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን፣ በሥራ እንደሚጸድቅ ታያለህ። 25 በተመሳሳይ ሁኔታ ጋለሞታዪቱ ረዓብ መልእክተኞቹን ተቀብላ በሌላ መንገድ በሰደደቻቸው ጊዜ
በሥራ አልጸደቅችምን? 26 ከመንፈስ የተለዬ አካል ሙት እንደ ሆነ ሁሉ፣ ከሥራ የተለዬ እምነትም የሞተ ነው።

James 2:1

ያዕቆብ 2: 1-4
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ያዕቆብ ለተበተኑት አይሁዳዊያን አማኞች እንዴት እርስ በእርስ በመዋደድ መኖር እንደሚችሉ እንዲሁ አንድን ሰው ከሌላኛው አስበልጠው መውደድ እንዳሌለባቸው መናገሩን ቀጥሏል። ወንድሞቼ ያዕቆብ የመልዕክቱ ተደራሲያን አይሁዳዊያን አማኞች እንደሆነ ያስበል። አማራጭ ትርጉም: "አማኝ ወንድሞች" ወይም "በክርስቶስ ወንድሞቼ እና እህቶቼ የሆናችሁ።" ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል ያዕቆብን እና ሌሎች አማኞችን ያመለክታል። ለተወሰኑ ሰዎች አድሎ ማድረግ "ልዩ እንክብካቤ ማድረግ" ወይም "ለእርሱ መልካም መሆን" አንድ ሰው ይህንን ካደረገ ያዕቆብ በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ አማኞች ከድሆች ይልቅ ለሀብታሞች ይበልጥ ክብር የሚስተዋልባቸውን ሁኔታዎች በማንሳት ማብራራት ይጀምራል። የቀርቅ ቀለበት ያደረጉ እና መልካም ልብስ የለበሱ "እንደ ሀሰብታም ሰው የለበሱ" በዚህ ጥሩ ሥፍራ ተቀመጠ "በዚህ የክብር ሥፍራ ተቀመጥ" እዚያ ቁም "ክብር ወደሌለው መቀመጫ ሂድ" በእግሬ ፊት ተቀመጥ "ወደ ዝቅተኛ ቦታ ሂድ" በራሳችሁ መካከል ፍርድን እየሰጣችሁ አይደለምን እንዲሁም የሚትፈርዱት ደግሞ በክፉ ሀሳባችሁ አይደለምን ያዕቆብ ተደራሲያኑን ለማስተማር እና ለመገሰጽ ይህንን የመሳሳሉ ጥያቄዊ መንገድን ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም: "በራሳችሁ መካከል ፍርድን ትሰጣላች እንዲሁም በክፉ ሀሳባችም ፈራጆች ትሆናለችሁ።"

James 2:5

ያዕቆብ 2: 5-7
የተወደድክ ወንድሜ ሆይ አድምጠኝ ያዕቆብ አንባቢዎቹን ልክ እንደ ቤተሰብ ያበረታታቸዋል። “ውድ ወንድሞቼ ሆይ ትኩረት ሰጥታችሁ አድምጡኝ።" እግዚአብሔር አይመርጥምን በዚህ ሥፍራ ያዕቆብ አንባቢያኑን ለማበረታታት ጥያቄን ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉምለ “እግዚአብሔር ይመርጣል።" በእምነት ሀብታም ሁን "ብዙ እምነት ይኑርህ።" የምታመነው ነገር ምን እንደሆነ በግለጽ መታወቅ አለበት። አማራጭ ትርጉም: "በክርስቶስ ጠንካራ እምነት ይኑርህ።" የእግዚአብሔርን መንግስት ይወርሳሉ "ወደ መንግስተ ሰማያት ይገባሉ" እናንተ ግን . . . ይኑራችሁ በዚህ ሥፍራ ላይ ያዕቆብ ለአጠቃላይ ተደራሲያኑ እየተናገረ ነው። ድሆችን አያከብሩም "ለድሆች ዋጋ አይሰጡም" ወይም "ለድሆች ጥሩ እንክብካቤ አያደርጉም" ሃብታም ስላልሆኑ አይደለምን በዚህ ሥፍራ ላይ ያዕቆብ አንባቢያኑን ለመገሰጽ ጥያቄዎችን ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም: "ሃብታሞች ናቸው።" ሀብታም "ሀብታም ሰዎች" (UDB) የሚቃወማችሁ "የሚጨቁናችሁ" ወይም "በመጥፎ ሁኔታ የሚይዟችሁ" እነርሱ አይደሉምን በዚህ ሥፍራ ላይ ያዕቆብ አንባቢያኑን ለመገሰጽ ጥያቄዎችን ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም: "እነርሱ ናቸው።" ወደ ፍርድ ቤት የሚወስዷችሁ "በዳኞች ፊት እናንተን ለመክሰስ በኃይል የሚጎትቷችሁ" ሀብታሞች አይደሉምን በዚህ ሥፍራ ላይ ያዕቆብ አንባቢያኑን ለመገሰጽ ጥያቄዎችን ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም: "ሀብታሞች" ወይም "ሀብታም ሰዎች።" መልካም ስም "የክርስቶስ ስም"

James 2:8

ያዕቆብ 2: 8-9
ይህንን ካሟላችሁ በዚህ ሥፍራ ላይ “እናንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው አይሁዳዊን አማኞችን ነው። የንጉሡን ሕግን መፈጸም እግዚአብሔር በመጀመሪያ በብሉይ ኪዳናት መጽሐፍት ውስጥ የተጻፈውን የሙሴን ሕግጋት ሰጠ። አማራጭ ትርጉም: "የእግዚአብሔርን ሕግ መታዘዝ" ወይም "የታላቁ ንጉሣችንን ሕግጋ መታዘዝ።" ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ (አነጻጽር: ዘለዋዊያን LEV 19:18) ጎረቤቶቻችሁ "ሁሉም ሰዎች" ወይም "ሁሉም ሰው" መልካም አድርገዋል "አንተ መልካም አደረገሃል" ወይም "አንተ ትክክለኛ የሆነ ነገር አድርገሃል" አድሎ የሚታደርጉ ከሆነ "ልዩ የሆነ እንክብካቤን ማድረግ" ወይም "ክብርን ለመስጠት" ኃጢአትን ማድረግ ይህ ሕግን መተላለፍ ነው። አማራጭ ትርጉም: "ኃጢአትን ማድረግ" ኃጢአት፣ በሕግ የሕግን መስበሩ የተረጋገጠበት በዚህ ሥፍራ ላይ ሕግ የሰው ዳኛ ባሕርይ ተላብሷል። አማራጭ ትርጉም: "የእግዚአብሔር ሕግ በመስበር ኃጠአት እና በደለኛ መሆን።"

James 2:10

ያዕቆብ 2: 10-11
ለሚታዘዝ ሰው ሁሉ "ለምታዘዝ ሰው ሁሉ" ይሁን እንጂ ይሠናከሉበታል . . . በሕግ ሁሉ! መሰናክል አንድ ሰው ለመራመድ ሲል ተደናቅፎ መውደቅን

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ያሳያል። ከሕግ የተወሰነ ክፍል አለመታዘዝ ሁሉንም ሕግ ካለመታዘዝ ጋር አንድ ነው። አታድርግ “ማድረግ” ማለት የሆነ ነገርን መፈጸም ማለት ነው።

ባታመነዝርም፥ ነገር ግን ብትገድል፥ ሕግን ተላላፊ ሆነሃል። ምንም እንኳ ያዕቆብ ይህንን የጻፈው ለብዙ አይሁዊያን አማኞች ቢሆንም የተጠቀመባቸው ቃላት ግን ነጠለቀ ቁጥር ያላቸው በመሆናቸው ለእያንዳንዱ ግለሰብ የጻፈ እንዲመስል አድርጎ ነው የጻፈው። "እያንዳንዳችሁ"

James 2:12

ያዕቆብ **2**: **12-13**
ስለዚህ ተናገር እንዲሁም ታዘዝ ያዕቆብ ሰዎች ይህንን ያደርጉ ዘንድ ያዛል። "ስለዚህ መናገር እና መታዘዝ ይኖርባችኋል።" በነጻነት ሕግ ፍርድን ይቀበሉ ዘንድ እንዳላቸው ሰዎች "የጸነት ሕግ በቅርብ እንደሚፈርድባቸው የሚያውቁ ሰዎች" በሕግ አማካኝነት በዚህ ሥፍራ ላይ ሕግ የሰው ዳኛ ባሕርያት ተሰጥቶት እናገኛለን። የነጻነት ሕግ "እውነተኛ ነጻነትን የሚሰጠው ሕግ" ምሕረት በእርሱ ላይ ይነግሣል "ምሕረት ከ . . . ይበልጣል" ወይም "ምሕረት ያሸንፋል"

James 2:14

ያዕቆብ **2**: **14-17**
አያያዥ ኣረፍተ ነገር: ያዕቆብ በየሥፍራው የተበተኑ አማኞች ልክ አብረሃም እምነቱን በሥራ እንዳሳየ ሁሉ እነርሱም እምነታቸውን በሰዎች ፊት ያሳዩ ዘንድ ያበረታታቸዋል።. ወንድሞቼ ሆይ አንድ ሰው እምነት አለኝ ቢል ነገር ግን እምነቱን ሥራ ካሌለው ምን ይጠቅማል? ያዕቆብ ተደራሲያኑን ለማስተማር ጥያቄ ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፡ "አንድ ሰው እምነት አለኝ እያለ ነገር ግን እምነቱን በሥራ የማያሳይ ከሆነ ምንም ፋይዳ የለውም። አንድ ሰው እንዲህ ቢል ያዕቆብ የአንድ ሰው ንግግርን በመጥቀስ ይጽፋል። በዚህ ሥፍራ ላይ “እርሱ” የሚለው ቃል የተናገረውን ሰው ይወክላል። (ያ እምነት ልያድነው ይችላልን? ያዕቆብ ተደራሲያኑን ለማስተማር በዚህ ሥፍራ ላይ ጥያቄን ተጠቅሟል። አማራጭ ትርጉም: "እንዲህ አይነቱ እምነት አያድነውም።" አያድነውም "ከእግዚአብሔር ፍርድ ልያድነው አይችልም" ወንድምህ ከ . . . ይህ ምን ጥቅም አለው? ያዕቆብ ተደራሲያኑን ለማስተማር በዚህ ሥፍራ ላይ ጥያቄን ተጠቅሟል። አማራጭ ትርጉም: "ወንድምህ ከ . . . ፈጽሞ ጥሩ ነገር አይደለም።" ወንድም ወይም እህት "በክርስቶስ ወንድም ወይም እህት" ከእናንተ መካከል አንዱ እንዲህ ቢል "አንተ እንዲህ አልክ" ሙት ነው "ጥቅም የለውም"

James 2:18

ያዕቆብ **2**: **18-20**
ይሁን እንጂ አንድ ሰው እንዲህ ይላል ያዕቆብ በ2: 14-17 ላይ አንድ የእርሱን ትምህርት የሚቃወም ሰውን በምናቡ እየሳለ ምን ልል እንደሚችል ይናገራል። ያዕቆብ ይህንን ሰው "ሞኝ ሰው" በማለት በቁጥር 20 ይጠራዋል። የዚህ ምናባዊ ገለጻ ዋና ዓላማ በተደራሲያኑ ዘንድ ያለው ስለ እምነት እና ሥራ ያለውን አመለካከት ለማስተካከል ነው። እኔ ሥራ አለኝ እንዲሁም እኔ ሥራ አለኝ ያዕቀብ በእርሱ አስተምህሮ ዙሪያ አንዳንድ ሰዎች ሊያነሱ የሚችሉትን ተቃውሞ ይገልጻል። አማራጭ ትርጉም: "አንድ ሰው እምነት ካለው ይህ ተቀባይነት አለው እንዲሁም አንድ ሰው መልካም ሥራ ካለውም እንደዚያው።" እምነትህን አሳየኝ በዚህ ሥፍራ ላይ “እኔ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ያዕቆብን ነው። ዳብሎስም . . . ይንቀጠቀጣል "በፍርሃት ይንቀጠቀጣል" አንተ ሞኝ ሰው ሆይ እምነት ያለ ሥራ ምንም ዋጋ እንዳሌለው ማወቅ ትፈልጋለህን? ይህ ጥያቄ ያዕቆብን ለማድመጥ ፈቃደኛ ያልሆነ ሰውን ለመገሰጽ ጥቅም ላይ የዋለ ነው። አማራጭ ትርጉም: "አንተ ሞኝ! ያለ ሥራ የሆነ እምነት ጥቅም እንዳሌለው ባረጋግጥልህም ይህንን መስማት ግን አንተ ፈጽሞ አትፈልግም።"

James 2:21

ያዕቆብ **2**: **21-24**
አጠቃላይ መረጃ: እነዚህ አይሁድ አማኞች በመሆናቸው ምክንያት የአይሁዳዊያን አባት የሆነውን እና እግዚአብሔር በቃሉ አማካኝነት ከብዙ ዘመናት በፊት የነገራወቸውን የአብረሃምን ታሪክ ያውቃሉ። አባታችን አብረሃም የጸደቀው . . . አይደለምን ይህ ጥያቄ ጥቅም ላይ የዋለው በያዕቆብ ትምህርት ላይ ሞኙ ሰው በ [JAS 2:18] እምነት እንደለ ታያለህ በዚህ ሥፍራ ላይ “ታያለህ” የሚለው ቃል ምሳሌያዊ ነው። አማራጭ ትርጉም: “መረዳት።” በሥራ እምነቱ ዓላማውን ይፈጽማል "ሥራው እምነቱ ፍጹም ይሆናል" ቅዱሳት መጽሐፍት ተፈጸሙ አማራጭ ትርጉም: "ይህ በቅዱሳት መጻሕፍት የተገለጠው ነገር ተፈተመ።" ጽድቅ ሆኖ ተቀጠረለት "እግዚአብሔር እምነቱን ጽድቅ አድርጎ ቆጠረለት" ይህ የታየው በሥራቸው ነው ያዕቆብ እንደገና “እናንተ” የሚለውን የብዙ ቁጥር አመልካች ቃል ተደራሲያንን ተጠቅሟል። ሰው በሥራ ይጸድቃል "ሰው በሥራ እና እምነት ይጸድቃል"

James 2:25

ያዕቆብ **2**: **25-26**
በተመሳሳይ መልኩ ይህ ተመሳሳይ ሀሳብን መጀመሪያ መንገድ ነው። (ተመልከት: [[rc://*/ta/workbench/discourse/home]]) ጋለሞታይቱ ረሃብ የጽደቀችው በእምነት አይደለምን ያዕቆብ ተደራሲያኑን ለማስተማር ጥያቄን ተጠቅሟል። አማራጭ ትርጉም: "ጋለሞታይቱን ረሃብን ያጸደቃት ሥራዋ ነው።" ጋለሞታይቱ ረሃብ “ረሃብ” የተባለች ሴት ታሪክ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ተደራሲያኑ ይህንን ታሪክ ማወቅ እንዳለባቸው ያስባል። መልእክተኞች ከሌላ ቦታ ዜናዎችን የሚያመጡ ሰዎች። በሌላ መንገድ ሸኘቻቸው "ከከተማው እንዲያመጡ ረዳቻቸው" መንፈስ የተለየው አካል የሞተ እንደሆነ ሁሉ ከሥራ የተለየ እምነትም የሞተ ነው። በእምነታቸውን ሥራ የማይሠራ ሰው ልክ መንፈስ ያሌለው አካልን ይመስላል። ሁለቱም ሞተዋል እንዲሁም ጥቅም የላቸውም።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 3

1 ወንድሞቼ፣ እኛ የባሰውን ፍርድ እንደምንቀበል በመገንዘብ፣ ከእናንተ ብዙዎች አስተማሪዎች አትሁኑ። 2 ሁላችንም በብዙ መንገድ እንሰናከላለን። በንግግሩ
የማይሰናከል እርሱ ሰውነቱን ሁሉ መቆጣጠር የሚችል ፍጹም ሰው ነው። 3 ፈረሶች አፍ ውስጥ ልጓም ብናደርግ ይታዘዙልናል፤ መላ አካላቸውንም መቆጣጠር
እንችላለን። 4 ምንም እንኳ መርከቦች ግዙፍና በኃይለኛ ነፋስ የሚነዱ ቢሆኑም፣ የመርከቡ ነጂ በትንሽ መሪ ወደሚፈልገው አቅጣጫ እንደሚመራቸው
አስተውሉ። 5 እንዲሁም አንደበት ትንሽ የሰውነት ክፍል ሆኖ፣ በታላላቅ ነገሮች ይኵራራል። ጫካ የቱንም ያህል ሰፊ ቢሆን፣ በትንሽ እሳት ፍንጣሪ
እንደሚቃጠል ልብ አድርጉ! 6 አንደበትም እንዲሁ እሳት ነው፤ ሰውነትን ሁሉ የሚያረክስና የሕይወትንም መንገድ የሚያቃጥል፣ እርሱ ራሱም በገሃነም እሳት
የሚቃጠል ሰውነታችን ብልቶች መካከል ያለ ኃጢአተኛ ዓለም ነው። 7 ማንኛውም እንስሳ፣ ወፎች፣ በምድር የሚሳቡና ባሕር ውስጥ ያሉ ፍጥረቶች በሰው
ተገርተዋል፤ 8 ነገር ግን ከሰው መካከል ማንም አንደበትን መግራት አልቻለም፤ የሚገድል መርዝ የሞላበት ዕረፍት የለሽ ክፉ ነው። 9 በአንደበት ጌታና
አባታችንን እንባርካለን፤ በዚያው አንደበት በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩትን ሰዎች እንረግማለን። 10 ከአንድ አፍ በረከትና መርገም ይወጣል። ወንድሞቼ፣
እንዲህ መሆን የለበትም። 11 ከአንድ ምንጭ ጣፋጭና መራራ ውሃ ይወጣልን? 12 ወንድሞቼ፣ የበለስ ዛፍ ወይራን ወይስ ወይን በለስን ያበቅላልን?
እንዲሁም ከጨው ውሃ ንጹሕ ውሃ ሊገኝ አይችልም። 13 ከእናንተ መካከል ጥበበኛና አስተዋይ ማን ነው? ያ ሰው ከጥበብ በሚገኝ ትሕትና በሥራው መልካም
ሕይወትን ያሳይ። 14 በልባችሁ መራራ ቅናትና ራስ ወዳድ ምኞት ካለ ግን አትኩራሩ፤ በእውነትም ላይ አትዋሹ። 15 ይህ ከላይ የሚመጣ ጥበብ አይደለም፤
ይልቁንም ምድራዊ፣ መንፈሳዊ ያልሆንና አጋንንታዊም ነው። 16 ምክንያቱም ቅናትና ራስ ወዳድ ምኞት ባለበት ሁከትና ክፉ ሥራ ይኖራል። 17 ከላይ
የሚመጣው ጥበብ ግን በመጀመሪያ ንጹሕ ነው፤ ከዚያም ሰላም ወዳድ፣ ጨዋ፣ ደግ፣ ምሕረትና መልካም ፍሬ የሞላበት፣ ለሰዎች አድልዎ የማያደርግ ቅን ነው።
18 ሰላምን ለሚያደርጉ የጽድቅ ፍሬ በሰላም ይዘራል።

James 3:1

ያዕቆብ 3፡ 1-2
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ያዕቅብ እነዚህን አማኞችን ከሰዎች አፍ የሚወጡትን ቃላት መቆጣጠር የሚችለው ከእግዚአብሔር ዘንድ በሚመጣ ጥበብ ብቻ ነው። ብዙዎቻችሁ እንዲህ አይደላችሁም በዚህ ሥፍራ ላይ “እናንተ” የሚለው ቃል የሚያመልከትው የያዕቆብን ተደራሲያን ነው። ወንድሞቼ "አማኞች" ይህንን እወቁ "ስለዚህ ምክንያት" የባሰውን ፍርድ እንድንቀበል ታውቃላችሁና። አማራጭ ትርጉም: "ኃጢአትን በማደረጋችን ምንም ምክንያት የለንም ምክንያቱም ከሌሎች ሰዎች ይልቅ ቃሉን እናውቃለን ስለዚህም እግዚአብሔር ከሌሎች ሰዎች በላይ እኛን ይቀጣናል።" እንቀበላለን ያዕቆብ ራሱን ከእርሱ ጋር ቅዱሳት መጽሐፍትን ከሚያስተምሩት ሰዎች ጋር በማድረግ ይናገራል። ምንም እንኳ ይህንን ደብዳቤ የሚያነቡት ሰዎች አንዳንዶቹ የቅዱሳት መጽሐፍት አስተማሪዎች ይሆናሉ ብዙዎቹ ግን አይሆኑም። በሁሉን እንሰናከላለን ያዕቆብ ሁሉንም ተደራሲያኑን ወደ ማካተቱ ተመልሷል። በብዙ መንገድ እንሰናከላለን ይህ የአንድ ሰውን ግብረገባዊ ውድቀት አንድ ሰው በጎዘ ላይ ሳለ ከመውደቁ ጋር ያነጻጽራል። አማራጭ ትርጉም: "መወደቅ" ወይም "ኃጢአት።" በቃሉ አይሰናከሉም "በተናገረው ቃል ኃጢአትን ያደርጋሉ" እርሱ ፍጹም ሰው ነው "እርሱ መንፈሳዊ ብስለት ያለው ሰው ነው" አጠቃላይ አካሉን የሚቆጣጠር በዚህ ሥፍራ ላይ ያዕቆብ እያመለከተ ያለው ልቡን፣ ስሜቱን እና ተግባሩን ነው። አማራጭ ትርጉም: "ባሕርውን የሚቆጣጠር ሰው" ወይም "ተግባሩን የሚቆጣጠር ሰው።"

James 3:3

ያዕቆብ 3፡ 3-4
እነሆ፥ ፈረሶች ይታዘዙልን ዘንድ ልጓም በአፋቸው ውስጥ እናገባለን ያዕቆብ የሰውን ምላስ ከልጓም ጋር ያያይዛል። ልጓም ፈረስ በዬት አቅጣጫ መሄድ እንዳለበት ለመቆጣጠር በአፍ ውስጥ የሚገባ ትንሽ ብረት ነው። ይህ እንዴት ትንንሽ ነገሮች እንዴት በትልልቅ ነገሮች ላይ ኃይል እንዳለው ያሳያል። አሁን ከሆነ "ከሆነ" ወይም "ሲሆን" የፈረስ ሉጋም በፈረስ አፍ ውስጥ እንደሚገባ ሁሉ “ፈረስ” ዕቃ ወይም ሰዎችን ለመሸከም የሚውል ትልቅ እንስሳ ነው። አማራጭ ትርጉም: "የፈረስ ሉጋምን በፈረስ አፍ ውስጥ የሚናደርግ ከሆነ።" ያኛውን መረከብም ደግሞ ተመልከቱ . . . በትንሽ መሪ የሚቆም ከሆነ በቀመጠል ያዕቆብ የሰውን ምላስ ከመርከብ መሪ ጋር ያነጻጽራል። “መርከብ” በውሃ ላይ የሚንሳፈፍ ትልቅ ነገር ነው። “መሪ” በመርከቡ መጨረሻ አከባቢ የሚገኝ ከእንጨት ወይም ከብረት የሚሠራ የመርከብን አቅጣጫ ለመቆጣጠር የሚረዳ ነው። በዚህ ሥፍራ ላይም ያዕቆብ ከፈረስ ሉጓም ጋር ተመሳሳይ የሆነ ነጥብን ያስተላልፋል። ትንሽ ነገር ከትልቅ ነገር በላይ ኃይል ልኖረው ይገባል። በጣም ትልቅ ናቸው በዚህ ሥፍራ ላይ “እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው መርከቦችን ነው። በጠንካራ ንፋስ ይገፋል አማራጭ ትርጉም: "ጠንካራ ንፋስ ይገፋዋል" በትንሽ መሪ አማካኝነት ሹፌሩ ወደ ወደደው አቅጣጫ ይመራዋል። "ይህች ትንሽ ዕቃ መርከቡ የሚሄድበትን አቅታጫ ይወስናል።"

James 3:5

ያዕቆብ 3፡ 5-6
በተመሳሳይ መልኩም ይህ ቃል የፈረስ ልጓምን ከመርከብ መሪ ጋር ማነጻጸሩን ያሳያል። አማራጭ ትርጉም: "በተመሳሳይ መልኩም።" በታላላቅ ነገር ይመካል "አንድ ሰው በጣም ክፉ የሆኑ ነገሮችን ለመናገር ልጠቅምበት ይችላል" ይህ ምን ያኸል ትልቅ ነገር ነው "ምን ያኸል ትልቅ እንደሆነ አስቡ" ትልቅ ጫካ በትንሽ እሳት እንደሚቃጠል ሁሉ! አማራጭ ትርጉም: "ትንሽ የእሳት ነበልባል ብዙ ዛፎችን ማቃጠል ይችላል!" ምላስም ልክ እንደ እሳት ነው ልክ እሳት የሚቃጥላቸውን ነገሮች ሁሉ እንደሚስወግድ ሁሉ የሰውም አንደበት ሰዎችን በጣም ልጎዳ ይችላል። አማራጭ ትርጉም: "ምላስም ልክ እንደ እሳት ነው።" አንደበት በብልቶቻችን መካከል ዓመፀኛ ዓለም ሆኖአል፤ አማራጭ ትርጉም: "ይህ የአካላችን ትንሽዬ ክፍል ነው ይሁን እንጂ ብዙ ዓይነት ኃጢአቶችን ለመፈጸም ያስችላል።" ሥጋን ሁሉ ያሳድፋልና፥ ይህ እንደ አዲስ ዓረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ይህ ፈጽም እግዚአብሔር የማናስደስት ያደርገናል።" ወይም "ይህ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እንዳናገኝ ያደርገናል።" የፍጥረትንም የሕይወት ሩጫ ያቃጥላል፥ በዚህ ሥፍራ ፤ይ “የሕይወት ሩጫ” የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው የአንድ ሰውን አጠቃላይ ሕይወት ነው። አማራጭ ትርጉም: "የሰውን ሁለንተናዊ ሕይወት ሊያበላሽ ይችላል።" እንዲሁም በገሃነም እሳትም ይቃጠላል። በዚህ ሥፍራ ላይ “እርሱም” የሚለው ቃል ምላስን የሚያመለክት ነው። ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ስፍራ ላይ “ገሃነም” የሚለው ቃል የክፋትን ወይም ዳቢሎስን ያመለክታል። ይህ በቀጥታ እንዲህ ልተረጎም ይችላል። "ምክንያቱም ዳብሎስ ይህንን ለክፋቱ ይጠቀመዋል።"

James 3:7

ያዕቆብ 3፡ 7-8
የአራዊትና የወፎች የተንቀሳቃሾችና በባሕር ያለ የፍጥረት ወገን ሁሉ በሰው ይገራል፥ ደግሞ ተገርቶአል፤ በዚህ ሥፍራ ላይ “ሁሉንም ዓይነት” የሚለው ሀረግ ያለው ትርጉም “ብዙ ዓይነት” ነው፤ ይህ በቀጥታ እንዲህ ልተረጎም ይችላል: "ሰዎች ብዙ ዓይነት የዱር እንስሳትን፣ ወፎችም፣ ተሳቢ እንስሳትን እና የባሕር ውስጥ ፍጥረታትን መቆጣጠር ችሏል።" ተሳቢ እንስሳት እነዚህ በምድር ላይ እየተሳቡ የሚሄዱ የእንስሳት ዓይነቶች ናቸው። የባሕር ውስጥ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

እንስሳት እነዚህ በውሃ ውስጥ የሚኖሩ እንስሳትን ናቸው። ነገር ግን አንደበትን ሊገራ ማንም ሰው አይችልም በዚህ ሥፍራ ላይ “አንደበት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው አንድ ሰው የሚናገረውን ነገር ነው። የዚህ ሙሉ ትርጉሙ እንዲህ ልገለጽ ይችላል፡ "ከእግዚአብሔር እገዛ ውጭ ማንም ሰው ምላሱን ልቆጣጠር አይችልም።" የሚገድል መርዝ የሞላበት ወላዋይ ክፋት ነው። ይህ ሰዎችን በተሰበረ ቃል እንዴት ሌላ ሰውን እንደሚጎዱ የሚብራራ ነው። ይህ “ክፉ የሆነ ፍጥረት እንደማያንቀላፋ ነገር ግን ለማጥቃት ሁል ጊዜ ዝግጁ እንደሆነ ሁሉ” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል።"

James 3:9

ያዕቆብ **3**: **9-10**
በምላስ እኛ "ቃላትን ለመናገር ምላሳችንን እንጠቀማለን" በእርሱ እኛ "ቃላትን ለመናገር እንጠቀመዋለን" ሰዎችን እንረግምበታለን በሌሎች ሰዎች ላይ ክፋትን እንዲያደርግ እግዚአብሔርን እንጠይቃለን UDB) በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠሩትን አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር በገዛ መልኩ የፈጠራቸውን" ወንድሞቼ "ክርስትያኖች" እነዚህ ነገሮች ፈጽመው ሊሆኑ አይገባም "ይህ ትክክል ያልሆነ ነገር ነው"

James 3:11

ያዕቆብ **3**: **11-12**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ያዕቆብ ከአማኞች አንደበት የሚወጣው ቃል ባርኮት እና ርግማን መሆን እንዳሌለበት ከገለጸ በኋላ ይህንን ሀሳቡን ለመግለጽ ከተፈጠሮ የተለያዩ ምሳሌዎችን ያነሳል። ምንጭስ ከአንድ አፍ የሚጣፍጥንና የሚመርን ውኃ ያመነጫልን? ጳውሎስ የተፈጥሮን አመክኒዮዋዊ መንገድ ለአንባቢያኑ ለማስረዳት ይህንን ጥያቄ ተጠቅሟል። አማራጭ ትርጉም: "ምንጭ የሚጣፍጥ እና የሚመርን ውሃ አያመነጭም።" በለስ ወይራን ወይስ ወይን በለስን ልታፈራ ትችላለችን? ያዕቆብ የተፈጥሮን አመክኒዮአዊ መንገድ ለአንባቢያኑ ለማስረዳት ሌላ ሥዕላዊ ቃላትን ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም: "የበለስ ዘፍ የወይራ ፍሬን ልያፈራ አይችልም ወይም የወይራ ዘፍ የበለስ ፍሬን ሊያፈራ አይችልም።"

James 3:13

ያዕቆብ **3**: **13-14**
ከእናንተ ጥበበኛና አስተዋይ ማን ነው? በመልካም አንዋዋሩ ስራውን በጥበብ የዋህነት ያሳይ። ያዕቆብ ለተደራሲያኑ በጥያቄ መልክ ትክክለኛውን ባሕርይ ይገልጻል። “ጠበብ” እማ “አስተዋይ” የሚለው ቃል በዚህ ክፍል ውስጥ ያለው ትርጉም ተመሳሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም: "ጠብብ የሆነ ሰው እንዲህ ልሆን ይገባዋል።" መልካም ሕይወትን ያሳያል "መልካም ባሕርን ያሳያል" ወይም "ያሳይ" በመልካም አንዋዋሩ ስራውን በጥበብ የዋህነት ያሳይ። "ከእውነተና ጥበብ ከሞገኝ መልካ ሥራው እና ትህትናው ጋር" ነገር ግን መራራ ቅንዓትና አድመኛነት በልባችሁ ቢኖርባችሁ፥ “ልብ” የሚለው ቃል ስሜትን ወይም ሀሳብን ያሳያል። አማራጭ ትርጉም: "ከሌሎች ሰዎች ጋር ተካፈሉ እና ሁል ጊዜም ራሳችሁን መጀመሪያ አድርጉ።" አትመኩ በእውነትም ላይ አትዋሹ። "ስለዚህ ነገር አትዋሹ እንዲሁም ነገሮችን እንደ ጠቢብ ሰው አከናውኑ"

James 3:15

ያዕቆብ **3**: **15-18**
ይህ አይደለም በዚህ ሥፍራ ላይ "ይህ" የሚለው ቃል ከዚህ በፊት ባሉት ቁጥሮች ውስጥ የተብራራውን ጥበብ የጎደለውን ቅንአት እና ራስ ወደድ የሆነ መሻትን ያመለክታል። ከላይ የወረደ "ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ" ወይም "ከሰማይ የመጣ" ምድራዊ የሆነ በዚህ ስፍራ ላይ “ ምድራዊ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን የማያስከብር የሰዎችን እሴት እና ባሕርን ነው።" ኢ-መንፈሳዊ "ከመንፈስ ቅዱስ ያልሆነ" ወይን "መንፈሳዊ ያልሆነ" የአጋንንትም ነው፤ "ይሁን እንጂ ይህ ከዳቢሎስ ዘንድ ነው" ቅንዓትና አድመኛነት ባሉበት ስፍራ "ስለራሳቸው ብቻ የሚያስቡ እንጂ ስለሌሎች ሰዎች የማያስቡ ሰዎች ባሉበት ሥፍራ ሁሉ" ሁከት ይኖራል "በዚያ ሥርዓት አልበኝነት ይኖራል" ወይም "ወይም ቀውስ ይኖራል" ማንኛውም ክፉ ተግባር ሁሉ "ማንኛውም በኃጢአት የተሞላ ሥራ ሁሉ" ወይም "ማንኛውንም ዓይነት ክፉ ተግባራት" የመጀመሪያው ቅዱስ "የመጀመሪያው ቅዱስ" ከዚያም ሰላም- ፍቅር አፍቃሪ - "ከዚያም ሰላማዊ"

እንግዳ ተቀባይ ገር - "ትሁት" ወይም "አሳቢ"

እና በጎ ፍሬ የሞላበት ይህ መልካም ፍሬ የሞላበት ከመልካም ሥራ ጋር ተነጻጽሯል። አማራጭ ትርጉም: “መልካም ሥራዎች” ግብዝነት ያሌለበት "ታማኝ" ወይም "እውነተኛ"

የጽድቅም ፍሬ ሰላምን ለሚያደርጉት ሰዎች በሰላም ይዘራል።

ይህ በሕይወታችን ውስጥ ያለውን ሰላምን እና ድቅድን ከመዝራት እና መከረ ከመሰብሰብ ጋር ያነጻጽራል። አማራጭ ትርጉም: “በሰላም የሚኖሩት ሰዎች እግዚአብሔር ትክክል ነው ብሎ የተናገረውን ነገር ያደርጋሉ።"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 4

1 በእናንተ መከከል ያለው ፀብና ጭቅጭቅ ከየት የመጣ ነው? በውስጣችሁ ውጊያ ከገጠሙት ክፉ ምኞቶቻችሁ የመጣ አይደለምን? 2 የሌላችሁን
ትመኛላችሁ። ትገድላላችሁ፤ ማግኘት ያልቻላችሁትን በብርቱ ታሳድዳላችሁ። ትጣላላችሁ፤ ትዋጋላችሁ፤ ይሁን እንጂ፣ ከእግዚአብሔር ስለማትለምኑ አታገኙም።
3 ትለምናላችሁ ግን አትቀበሉም፤ ምክንያቱም ክፉ ምኞቶቻችሁን ለማሳካት ክፉ ነገሮችን ስለምትለምኑ ነው። 4 እናንት አመንዝሮች! የዓለም ወዳጅ መሆን፣
የእግዚአብሔር ጠላት መሆን እንደ ሆነ አታውቁም? ስለዚህ ማንም የዓለም ወዳጅ መሆን ቢፈልግ፣ የእግዚአብሔር ጠላት ይሆናል። 5 ወይስ እግዚአብሔር እኛ
ውስጥ ያኖረው መንፈስ ለእርሱ ብቻ እንድንሆን አብዝቶ ይቀናል የሚለው የመጽሐፍ ቃል በከንቱ የተነገረ ይመስላችኋል? 6 እግዚአብሔር ግን አብዝቶ ጸጋውን
ይሰጣል፤ መጽሐፍ፣ “እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፤ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል” የሚለው በዚህ ምክንያት ነው። 7 ስለዚህ፣ ራሳችሁን
ለእግዚአብሔር አስገዙ፤ ዲያብሎስን ተቃወሙት፤ እርሱም ከእናንተ ይሸሻል። 8 ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ፣ እርሱም ወደ እናንተ ይቀርባል። እናንተ ኃጢአተኞች
እጆቻችሁን አንጹ፤ እናንተ በሁለት ሐሳብ የምትዋልሉ ልባችሁን አጥሩ። 9 እዘኑ፤ አልቅሱ፤ ጩኹ! ሳቃችሁን ወደ ሐዘን፣ ደስታችሁን ወደ ትካዜ ለውጡ። 10
በጌታ ፊት ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ፤ እርሱም ከፍ ያደርጋችኋል። 11 ወንድሞች ሆይ፣ እርስ በርስ አትወነጃጀሉ። ወንድሙን የሚወነጅልና በወንድሙ ላይ የሚፈርድ
ሕጉ ላይ ክፉ ይናገራል፤ በእግዚአብሔርም ሕግ ላይ ይፈርዳል። ሕጉ ላይ የምትፈርዱ ከሆነ፣ ፈራጆች እንጂ፣ ሕጉን አድራጊዎች አይደላችሁም። 12 ሕጉን
የሰጠና በሕጉም የሚፈርድ፣ ማዳንም መግደልም የሚቻለው አንዱ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ታዲያ፣ በባልንጀራህ ላይ የምትፈርድ አንተ ማን ነህ? 13 “ዛሬ
ወይም ነገ ወደዚህ አገር እንሄዳለን፤ እዚያ አንድ ዓመት እንቆያለን፤ ነግደን እናተርፋለን” የምትሉ እናንተ ሰዎች ስሙ። 14 ነገ የሚሆነውን የሚያውቅ ማን ነው?
ሕይወታችሁስ ምንድን ነው? ጥቂት ጊዜ ታይቶ ኋላ እንደሚጠፋ ጭጋግ አይደላችሁምን? 15 ይልቁንም፣ “ጌታ ቢፈቅድ እንኖራለን፤ ይህን ወይም ያንን
እናደርጋለን” ማለት ይኖርባችኋል። 16 አሁን ግን በዕቅዶቻችሁ ትመካላችሁ። እንዲህ ያለው ትምክህት ሁሉ ክፉ ነው። 17 ስለዚህ መልካም የሆነውን ማድረግ
እንዳለበት እያወቀ ለማያደርግ ለዚያ ሰው ኃጢአት ይሆንበታል።

James 4:1

ያዕቆብ **4**፡ **1-3**
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ያዕቆብ እነዚህ አማኞችን ስለ ዓለማዊነታቸው እና ትህትና ማጣታቸው ይገስጽዋቸዋል፤ አንደበታቸውን ይጠብቁ እና እርስ በእርሳቸው በጥንቃቄ መነጋገር እንዳለባቸው ያበረታታቸዋል። አጠቃላይ መረጃ: በዚህ ክፍል ውስጥ “እራሳችሁ” የሚለው ቃል ውስጥ “እናንተ” እና እናንተ” የሚለው ቃል የብዙ ቁጥር አመልካች ቃል ሲሆን የሚያመለክተው ያዕቆብ የጻፈላቸውን አማኞችን ነው። በእናንተ ዘንድ ጦርና ጠብ ከወዴት ይመጣሉ? ያዕቆብ ተደራሲያንኑን ለማስተማር እና ለመገሰጽ ጥያቄን ተጠቅሟል። አማራጭ ትርጉም "እርስ በእርሳችሁ ሁል ጊዜ ለምን እንደሚትጣሉ አውቃለሁ።" ጠብ እና ክርክር “ጠብ” እና “ክርክር” የሚለው ቃል በመሠረታዊ ትርጉሙ ተመሳሳይ ነው። ያዕቆብ እነዚህ ሁለት ቃላትን በአንድነት የተጠቀመበት ምክንያት በሰዎች መካከል ያለውን ማንኛውንም አይነት ጠብ ለማመልከት ነው። በብልቶቻችሁ ውስጥ ከሚዋጉ ከእነዚህ ክፉ ምኞቶቻችሁ አይደሉምን? ያዕቆብ ይህንን ጥያቄ በዚህ ውስጥ የተጠቀመው ተደራሲያኑን ለመገሰጽ ነው። በእናንተ ቋንቋ ውስጥ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በዓረፍተ ነገር ቅርጽ ልጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም: "ከክፉ ምኞቶቻችሁ ውስጥ ይወጣሉ" ወይም "ከክፉ ምኞቶቻችሁ ስለምነሱ ነው።" ከሚዋጉ ከእነዚህ ክፉ ምኞቶቻችሁ ያዕቆብ “ክፉ ምኞትን” በሰውኛ መልኩ በመግለጽ አማኞችን በመቃወም የሚዋጋ ወታደር አድርጎ ያቀረበዋል። አማራጭ ትርጉም: “የሚትፈልጉት ክፋት ነው፣ ስለ ሌሎች አማኞች ፍላጎት ግድ አይላችሁም።” በአማኞች ወዳጆቻችሁ መካከል? "በአካሎቻችሁ።" አማራጭ ትርጉም 1) በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ በሚገኙ ምዕመናን መካከል ጥል አለ፣ አማራጭ 2) ጥሉ ውስጣዊ ነው ማለትም ክፉ እና መልካም ነገርን በማድረግ መካከል። ያልለህን ነገር ትመኛለህ "ሁል ጊዜ የሚትፈልገው ያሌለህን ነገር ነው።" ትገድላለህ፣ በብርቱም ትፈልጋለህ በዚህ ክፍል ውስጥ “ትገድላለህ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰዎች የሚፈልጉትን ነገር ለማግኘት እንዴት በከፋ ሁኔታ እንደሚሄዱ ያመለክታል። ይህ እንዲህ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል “ማግኘት የማትችሉትን ለማግኘት ስትሉ ሁሉንም ዓይነት ክፋቶችን ታደርጋላችሁ።” ትጣላላችሁ እንዲሁም ትዋጉማላችሁ “መጣላት” እና “መዋጋት” የሚሉት ቃላት በመሠረታዊ ትርጉማቸው ተመሳሳይ ናቸው። እነዚህ ቃላት ያዕቆብ የተጠቀማቸው ሰዎች እርስ በእርሳቸው ምን ያኸል እንደሚከራከሩ አጽኖት ሰጥተው ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም: "ሁል ጊዜ ትጣላላችሁ።" መጥፎ የሆኑ ነገሮችን ትለምናላችሁ "በመጥፎ ትጠይቃላችሁ።" አማራጭ ትርጉም 1) "በተሳሳተ መነሻ ሀሳብ ትጠይቃላችሁ፣ አመለካካታችሁ መጥፎ ነው።" ወይም 2) "ለተሳሳተ ዓላማ ወይም መጥፎ የሆኑ ነገሮችን ትጠይቃላችሁ።" ታጠፉታላችሁ "ታጠፏቸዋላችሁ"

James 4:4

ያዕቆብ **4**፡ **4-5**
እናንተ አመንዝሮች! ይህ እግዚአብሔርን የማይታዘዙ ሰዎችን ከባሏ ውጪ ከሌላ ሰው ጋር የሚትተኛ ምስትን ያነጻጽራል። አማራጭ ትርጉም: "እናንተ ከእግዚአብሔር ታማኞች አልሆናችሁም!" አታውቁምን . . . እግዚአብሔር? ያዕቆብ ተደራሲያኑን ለማስተማር ይህንን ጥያቄ ተጠቅሟል። አማራጭ ትርጉም: "እናንተ ታውቃላችሁ . . . እግዚአብሔር!" ከዓለም ጋር ወዳጅነት “ከዓለም ጋር ወዳጅነት” የሚለው ሀረግ ከዓለም እሴት ሥርዓት እና ባሕርይ ጋር ራስን ማመሳሰል ወይም መሳተፍ የሚያመለክት ነው። . ከዓለም ጋር መወዳጀት ከእግዚአብሔር ጋር መጣላት ነው የዓለም እሴት ሥርዓት አካል መሆን የእግዚአብሔር ጠላት መሆን ነው። አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር እንደማያከብሩ ሰዎች መኖር ልክ እግዚአብሔር እንደሚቃወም ሰው ነው።" ወይም ቅዱሳት መጻሕፍት ያለ ትርጉም ይመስሏችኋልን ያዕቆብ ተደራሲያኑን ለማረታታት ጥያቄን ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም: "ቅዱሳት መጻሕፍት እውነት ነው።" እርሱ በውስጣችን ያስቀመጠው መንፈስ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የሰው መንፈስን ለማመልከት “መንፈስ” ተጠቅመዋል። ቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ ቃሉ ያለው ትርጉም ይህም ሊሆን ይችላል። አንባቢያኑ የሚጠቀሟቸው ሌሎች ትርጉሞች ላይ ያለውን ቃል በትርጉምህ ውስጥ ተጠቀም።

James 4:6

ያዕቆብ **4**፡ **6-7**
ነገር ግን እግዚአብሔር ሌላ ተጨማሪ ጸጋ ይሰጣል ይህ ሀረግ እንዴት ከዚህ በፊት ካለው ጥቅስ ጋር እንደሚገናኝ ግልጽ ሆኖ መቀመጥ ይችላል: "ምንም እንኳ መንፈሳችን ማግኘት የማንችለውን ነገር የሚመኝ ቢሆን ራሳችንን ዝቅ ዝቅ ካደረግን እግዚአብሔር ከምኞታችን በላይ ጸጋን ይሰጠናል።" እግዚአብሔር ይቃወማል "እግዚአብሔር ይቃወማል" ትብተኛ "ትብተኞች ሰዎችን" ትሁት "ትሁታን ሰዎችን" ስለዚህ "በዚህ ምክንያት" ለእግዚአብሔር ራሳችሁን አስገዙ "ለእግዚአብሔር ራሳችሁን አስገዙ" ወይም "እግዚአብሔርን ታዘዙ" ራሳችሁን . . . እናንተ እነዚህ ተውላጠ ስሞች በብዙ ቁጥር የተጠቀሱ ሲሆኑ የሚያመለክቱትም የያዕቆብን ደራሲያንን ነው። ዳቢሎስን ተቃወሙት "ዳቢሎስን ተቃወሙት" ወይም "ዳቢሎስ የሚፈልጋቸውን ነገሮች አታድርጉ" እርሱም ከእናንተ ይሸሻል "ዳቢሎስ ከእናንተ ይሸሻል"

James 4:8

ያዕቆብ **4**: **8-10**
አጠቃላይ መረጃ: በዚህ ሥፍራ ላይ “እናንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ያዕቆብ የጻፈለቸው በተለያ ስፍራዎች ላይ ተበትነው ያሉትን አማኞችን ነው። እናንተ ኃጢአተኞች እጆቻችሁን አንጹ እንዲሁም እናንተ ወላዋዮች ልባችሁን አንጹ። ሀሳብ - “እጆቻችሁን አንጹ” የሚለው ሀረግ በሌላ አገላለጽ “ልባችሁን አንጹ” ተብሎ ተገልጾዋል። እንዲሁም “አናንተ ኃጢአተኞች” የሚለው ሀረግ “ወላዋዮች” በሚል ሌላ ሀረግ እንደገና ተጠቅሶ እናገኛለን።

እጆቻችሁን አንጹ የዚህ ሀገር አማራጭ ትርጉሞች እነዚህ ናቸው 1) አንድ ሰው ባሕርውን ወይም ተግባራቱን ማስተካከል ወይም 2) አንድ ሰው ኃጢአት ከሞላበት ባሕርይው ወይም ተግባራቱ ሲመለስ ወይም ንሰሓ ይግባ። አማራጭ ትርጉም: : "እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ መራመድ።" ልባችሁን አንጹ Here "hearts" refers to a person's thoughts and emotions. AT: "let your thoughts honor God." በሁለት ሀሳብ መወላወል በሁለት ሀሳብ መሆን - “በሁለት ሀሳብ ውስጥ መሆን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው አንድ ሰው በአእምሮው ውስጥ ያሉ ሀሳብ ሁለት ከመሆኑ የተነሳ ለመወሰን ስቸገር ነው። አማራጭ ትርጉም: "ባለ ሁለት ሀሳብ ሰዎች" ወይም "እግዚአብሔርን መታዘዝ እንዳለባቸው መወሰን ያልቻሉ ሰዎች።"

ኃዘን፣ ለቅሶ እና ማልቀስ “ኃዘን” እና “ለቅሶ” በመሠረታዊ ትርጉማቸው ተመሳሳይ ናቸው። በዚህ ስፍራ ላይ ያዕቆብ እነዚህ ቃላት በአንድ ላይ የተጠቀማቸው ሰዎች ከልባቸው ማዘን እንዳለባቸው አጽኖት ሰጥቶ ለማሳየት ነው። “ማልቀስ” የሚለው ቃል ደግሞ የሚያሳየው ሰዎች እያዘኑ መሆናቸውን ነው። " ሳቀቀችሁን ወደ ኃዘን እንዲሁም ደስታችሁ ወደ እንጉርጉሮ ለውጡት ይህ ተመሳሳይ የሆነ ሀሳብን አጽኖት ለመስጠት በተለያዩ መንገዶች ለመግለጽ ነው። አማራጭ ትርጉም: "በፍጥነት ሳቃችሁን አቁማችሁ እግዚብሔር ይቅርታ መለመን ጀምሩ። በጌታ ፊት ረሳችሁን አዋርዱ "በእግዚአብሔር ፊት ራሳችሁን አዋርዱ" እርሱ ያነሳችኋል አማራጭ ትርጉም: "እርሱ ያከብራችኋል።"

James 4:11

ያዕቆብ **4**: **11-12**
አጠቃላይ መረጃ: በዚህ ክፍል ውስጥ “እናንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ያዕቆብ የጻፈለቸውን አማኞችን ነው። ተቃውሞ መናገር "ስለእ . . . መጥፎ ነገር ማናገር" ወይም "መቃወም" ወንድሞች "አማኞች" ይሁን እንጂ እናንተ ፈራጆች ናችሁ አማራጭ ትርጉም: "ይሁን እንጂ የሚታደርጉት ነገር ልክ ሕግን እንደሚያወጣ ሰው ነው።" አንድ ሕግ አውጪ እና ፈረጃ እግዚአብሔር፣ አንድ "ሕግን ማውጣት የሚችል እና በሰዎች ላይ የሚፈርድ አንድ እግዚአብሔር አለ ምክንያቱም ይህንን ማድረግ የሚችል አንድ እርሱ ብቻ ነው።" በባልንጀሮቻችሁ ላይ እናንተ ለመፍረድ ማን ናችሁ? ያዕቆብ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው እነርሱን ለመገሰጽ ነው። አማራጭ ትርጉም: "እናንተ ሰዎች ብቻ ናችሁ ስለዚህም በሌሎች ሰዎች ላይ መፍረድ አትችሉም።"

James 4:13

ያዕቆብ **4**: **13-14**
እንዲህ የሚሉ ይኖራሉ አማራጭ ትርጉም: "ከእናንተ መካከል አንድ ሰው እንዲህ ሊል ይችላል" አንድ ዓመት ቆያለሁ አማራጭ ትርጉም: "ለአንድ ዓመት በዚያ እቆያለሁ" ነገ ምን እንደሚሆን ማን ያውቃል ያዕቆብ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው እነርሱን ለመገሰጽ ነው።. አማራጭ ትርጉም: "ነገ ምን እንደሚሆን ማንም ሰው አያውቅም።" ታዲያ ሕይወታችሁን ምንድናት ያዕቆብ ይህንን ጥያቄ በዚህ ሥፍራ ላይ የተጠቀመበት አካላዊ ሕይወት ይህንን ያኽል ጠቃሚ እንዳልሆነ ለማስተማር ነው። አማራጭ ትርጉም: "ስለ አካላዊ ሕይወታችሁ አስቡ።" እናንተ ለጥቂት ጊዜ ታይቶ አንደሚጠፋ ጤዛ ናችሁ ይህ አካላዊ ሕይወትን ለጥቂት ጊዜ ብቻ ታይቶ ወዲያው ከሚጠፋው ጤዛ ጋር ያነጻጽራል። አማራጭ ትርጉም: "የሚትኖሩት በጣም አጭር ለሆነ ዘመን ነው፤ መቼ እንደሚትሞቱ አታውቁም።

James 4:15

ያዕቆብ **4**: **15-17**
እንኖራለን በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል በቀጥታ ያዕቆብን ወይም የእርሱ ተደራሲያንን የሚያመለክት አይደለም ይልቁንም የያዕቆብ ተደራሲያን ምን ዓይነት ባሕርይ ሊኖራቸው እንደሚገባ የሚያሳይ ነው። ይህንን እና ያንን እናድርጋለን አማራጭ ትርጉም: "እና ለማድረግ ያቀድነውን ዕቅድ እንፈጽማለን" ለሚያውቀው ለእርሱ በዚህ ሥፍራ ላይ ያዕቆብ “ለእርሱ” በማለት ሲጽፍ ይህንን ማንንም ለማመልከት አልጻፈውም ይልቁንም መልካም ለማድረግ የሚፈለግ ነገር ግን የማያደርገን ሰው ለማመልከት ጽፎታል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 5

1 እንግዲህ እናንተ ሀብታሞች ስለሚመጡባችሁ ክፉ ነገሮች አልቅሱ ዋይ ዋይም በሉ። 2 ሀብታችሁ ሻግቶአል፤ ልብሳችሁንም ብል በልቶታል። 3 ወርቃችሁና
ብራችሁ ዝጎአል፤ ዝገቱም እናንተ ላይ ይመሰክራል፤ ሥጋችሁንም እንደ እሳት ይበላዋል። ለመጨረሻው ቀን ሀብታችሁን አከማችታችኋል። 4 ልብ በሉ፤
እርሻችሁን ላጨዱ ሠራተኞች ያልከፈላችሁት ደመወዝ ይጮኻል! የአጫጆቹም ጩኸት የሠራዊት ጌታ ጆሮ ደርሶአል። 5 በምድር ላይ በምቾትና በመንደላቀቅ
ኖራችኋል። ለዕርድ ቀን ልባችሁን አወፍራችኋል። 6 እናንተን ያልተቃወመውን ጻድቅ ሰው ኮንናችሁታል፤ ገድላችሁታል። 7 ስለዚህ ወንድሞች ሆይ፣
የመጀመሪያውና የኋለኛው ዝናብ እስኪመጣ ድረስ የምድርን ፍሬ በትዕግሥት እንደሚጠብቅ ገበሬ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ታገሡ። 8 እናንተም እንዲሁ ታገሡ፤
ልባችሁን አዘጋጁ፤ ምክንያቱም የጌታ መምጫ ቅርብ ነው። 9 ወንድሞች ሆይ፤ እንዳይፈረድባችሁ እርስ በርሳችሁ አታጉረምርሙ። ልብ በሉ፤ ፈራጁ በሩ ላይ
ቆሞአል። 10 በጌታ ስም የተናገሩ ነቢያትን መከራና ትዕግሥት እንደ ምሳሌ ውሰዱት። 11 ልብ በሉ፤ በትዕግሥት የጸኑትን፣ “የተባረኩ” እንላቸዋለን። ስለ
ኢዮብ ትዕግሥት ሰምታችኋል፤ ጌታ ለኢዮብ የነበረውንም ዓላማ ታውቃላችሁ፤ ጌታ እጅግ ሩኅሩኅና መሐሪ ነው። 12 ወንድሞቼ ሆይ፣ ከሁሉም በላይ አትማሉ፤
በሰማይም ሆነ በምድር ወይም በሌላ ነገር አትማሉ። ቃላችሁ “አዎን” ካላችሁ፣ “አዎን” ይሁን፤ “አይደለም” ካላችሁም፣ “አይደለም” ይሁን። 13 በእናንተ
መካከል መከራ የደረሰበት አለ? እርሱ ይጸልይ። ደስ ያለው አለ? እርሱ ይዘምር። 14 በእናንተ መካከል የታመመ አለ? የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን
ይጥራ፤ እነርሱም በጌታ ስም ዘይት እየቀቡ ይጸልዩለት፤ 15 የእምነት ጸሎት የታመመውን ሰው ይፈውሳል፤ ጌታም ያስነሣዋል። ኃጢአት አድርጎ ከሆነም
እግዚአብሔር ይቅር ይለዋል። 16 እንዲሁ ጌታ ከበሽታ ሊፈውስና ኃጢአትን ይቅር ሊል ስለሚችል ያደረጋችሁትን ኃጢአት በተመለከተ አንዳችሁ ለሌላችሁ
ተናዘዙ። ጻድቃን ሰዎች ከጸለዩና አንድ ነገር እንዲያደርግላቸው ጌታን አጥብቀው ከጠየቁት፣ እግዚአብሔር ይገለጣል፤ ደግሞም በእርግጠኝነት ያን ነገር
ያደርገዋል። 17 ነቢዩ ኤልያስ እንደኛው ያለ ሰው ቢሆንም፣ ዝናብ እንዳይዘንብ አጥብቆ ጸለየ። ለሦስት ዓመት ከስድስት ወራት ጊዜ ያህልም ዝናብ አልነበረም።
18 ከዚያም ዝናብ እንዲዘንብ እግዚአብሔርን እየለመነ ጸለየ፤ እግዚአብሔርም ዝናብን ላከ፣ ተክሎችም ዐደጉና ሰብልን ሰጡ። 19 ወንድሼና እኅቶቼ ሆይ፥
ከእናንተ አንዱ ዕውነተኛውን የእግዚአብሔርን ቃል መልእክት መታዘዝ ቢያቆም፣ ከእናንተ አንዱ ያደርገው ዘንድ እግዚአብሔር ለዚያ ሰው የነገረውን ነገር
በመንገር ሊያሳምነው ይገባል። 20 የሚያሳምነው ሰውም ኃጢአት እየሠራ የነበረውን ሰው ተናግሮ ስሕተት ከመሥራት እንዲመለስ ስላስቻለው፣ እግዚአብሔር
ያንን ሰው ከመንፈሳዊ ሞት ያድነዋል፤ ደግሞም ብዙ የሆኑት ኃጢአቶቹን ይቅር ይልለታል።

James 5:1

ያዕቆብ 5፡ 1-3
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ያዕቀብ አማኞች ስለ ደስታ እና ሀብት በጣም መጨነቅን አስመልክቶ ያስጠነቅቃቸዋል። እናንተ ሀብታም የሆናችሁ ሰዎች በዚህ ሥፍራ ላይ ያዕቆብ ሀብታም የሆኑ ነገር ግን እግዚአብሔርን የማያከብሩ ሰዎችን ይናገራል። አማራጭ ትርጉም: "እናንተ ሀብታም የሆናችሁ ሰዎች ነገር ግን እግዚአብሔርን የማታከብሩ።" በእናንተ ላይ ክፉ የሆነ ነገር መጥቶባችኋል አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር በሁሉም ሰዎች ላይ በሚፈርድበት ጊዜ ያኔ እናንተም ላይ አሰቃቂ ነገር ይመጣባችኋል" ሀብታችሁ ይበሰብሳል እንዲሁም ልብሳችሁ ብል ይበላዋል። ወርቅችሁ እና ብራችሁ ጥቅም አይኖረውም። ሀብታሁን እና ልብሳችሁ ይበላል። ወርቃችሁ እና ብራችሁ ጥቅም አይኖረውም - ያዕቆብ የእነዚህ ሀብታሞች ሀብት እና ልብስ ጠፍቷል እያለ አይደለም። ይልቁንም እነዚህ ነገሮች በአሁኑ ዘመን ምንም ዓይነት መነፈሳዊ እሴት ስላሌላቸው ለብዙ ጊዜ ከእነርሱ ጋር መቆየት አይችሉም። አማራጭ ትርጉም: "ዋጋ አላቸው እንዲሁም በጣም አስፈላጊ ናቸው ብላችሁ የሚታስቧቸው ነገሮች ሁሉ ምን ጥቅም የላቸውም እንነዲሁም ከእናንተ ጋር የሚቆዩት በጣም ለጥቂት ጊዜ ያኽል ብቻ ነው።"

መበስበሱ ራሱ ይመሰክርባችኋል በዚህ ሥፍራ ላይ “በእናንተ ላይ ይመስክራል” የሚለው ሀረግ የሚያሳየው አንድ ሰው ሕግን በመተላለፍ በዳኛ ፊት ሲቆም ሀብቱ ምንም የማይፈይድለት ሲሆን ነው። አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር እናንተ ላይ በሚፈርድበት ዕለት ሀብትህ የአንተ ከሳሽ ይሆናል።" ሥጋህን እንደ እሳት ይበላልe በዚህ ሥፍራ ላይ የተበለሻ ሀብት የሚለው ቃል ሁሉን ነገር ከሚያጠፋው እሳት ጋር ተነጻጽሮ ቀርቧል።ከዚህ በተጨማሪ “እሳት” የሚለው ቃል የእግዚአብሔር ፍርድ የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር አንተን ለመቀጣት ምክንያት ይሆኑታል።" ሀብትህን ለሌሎች ሰዎች አለማካፈል "ሀብትህን ሁሉ ለራስህ ብቻ በመያዝ ለሌሎች ሰዎች አለማካፈል" በመጨረሻው ዘመን ይህ ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔር በሰዎች ሁሉ ላይ የሚፈርድበት ጊዜ ከመድረሱ ጥቂት ጊዜ በፊት። አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር በአንተ ላይ ከመፍረዱ በፊት"

James 5:4

ያዕቆብ 5፡ 4-6
ለሠራተኞች ደምች መክፈል—ከማሳህ ላይ ሰብልህን ለሰበሰቡት ሰሰዎች ተገቢውን ክፍያ መክፍል በመጀመሪያ ትኩረት የተሰጠው ከዚህ በፊት ላልተከፈለ ክፍያ ወይም ደሞዝ ነው። አማራጭ ትርጉም: "በማሳህ ላይ ያለውን ሰብል እንዲሰበስብልህ ለቀጠርካቸው ሰዎች አስፈላጊውን ክፍያ አለመፈጸምህ ያስከስስሃል።" እንዲሁም ከማሳህ ላይ ሰብልህን የሰበሰቡልህ ሰዎች አማራጭ ትርጉም: "በማሳህ ላይ ያለውን ሰብል እንዲሰበስብልህ ለቀጠርካቸው ሰዎች አስፈላጊውን ክፍያ አልከፍልካቸውም እና እንድትከፍላቸው ወደ አንተ ይጮኻሉ" ወደ ሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ጆሮ ደርሰዋል አማራጭ ትርጉም: "በሰብል ማሳህ ላይ ቀጥረህ ስታሠራቸው የነበሩት ሰዎችን ለቅሶ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሐር ሰምቷል።" ልብህን ልክ ለመታደር እንደሚዘጋጀት አስብተሃል ይህ ስግብግብ እና ሁሉን ነገር ለራሱ ማድረግ የሚፍልግን ሀብታም እስኪደልብ እና ለምግብነት እኪታረድ ድረስ ሁሉን ነገር ከሚበላ በሬ ጋር ያነጻጽራል። አማራጭ ትርጉም: "ስግብግብነትህ ለትልቅ ዘላለማዊ ቅጣት የሚያዘጋጅህ ብቻ ይሆናል።" ጻድቅ ሳ "ትክክል የሆነውን ነገር የሚያደረግ ሰው" አይቋቋሚህም "አይቃወምህም"

James 5:7

ያዕቆብ 5፡ 7-8
1 ሽማግሌው በእውነት ለምወደውና ለተወደደው ጋይዮስ። 2 የተወደድክ ሆይ በነፍስህ እንደበለጸግህ በሁሉ ነገር እንድትበለጽግና በመልካም ጤንነት
እንድትሆን እጸልያለሁ። 3 ወንድሞች መጥተው በእውነት እንደምትሄድ ሲመሰክሩልኝ እጅግ ሀሴት አደረግሁኝ። 4 ልጆቼ በእውነት መንገድ እየሄዱ እንደሆነ
ከመስማት የበለጠ ደስታ የለኝም። 5 የተወደድክ ሆይ ለወንድሞችም ሆነ ለእንግዶች በምታድርገው ነገር ስላለህ ታማኝነት 6 ሁሉም በጉባኤ ፊት
ይመሰክሩልሀል።ለእግዚአብሔር እንደሚገባ በጉዞአቸው በመደገፍህ መልካም አድርገሀል። 7 ምክንያቱም ለተጠሩለት ስም አገልግሎት ሲወጡ ከአህዛብ
ምንም አልወሰዱም። 8 ስለዚህም የእውነት ማህበርተኞች እንሆን ዘንድ እንደነዚህ ያሉትን መርዳት ይገባናል። 9 ስለአንድ ጉዳይ ለቤተክርስቲያን ጽፌ ነበር ነገር
ግን በመካከላቸውአለቃ ሊሆን የሚወደው ዲዮትሪፈስ አይቀበለንም። 10 ስለዚህ በምመጣበት ጊዜ ያደረገውን ነገርና እንዴት ባሉ ክፉ ቃላት በእኛ ላይ
እንደተናገረ አልረሳም።ይህም አልበቃ ብሎት ወንድሞችን አይቀበልም ሊቀበሉ የሚፈልጉትንም ይከለክላቸዋል ከቤተክርስቲያንም ያስወጣቸዋል። 11
የተወደድክ ሆይ መልካሙን እንጂ ክፉን አትምሰል። መልካም የሚያደርግ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው። ክፉን የሚያደርግ ሁሉ እግዚአብሔርን አላየውም። 12
ለዲሜጥሮስ ሁሉም ይመሰክሩለታል እውነት እራሷም ትመሰክርለታልች። እኛም እንመሰክርለታለን የኛ ምስክርነት ደግሞ እውነት እንደሆነ ታውቃላችሁ። 13
የምጽፍልህ ብዙ ነገር ነበረኝ ነገር ግን በወረቀትና በቀለም ልጽፍልህ አልፈለግሁም። 14 ይልቁኑ ልጎበኝህ አስባለሁና በዚያን ጊዜ ፊት ለፊት እንነጋገራለን። 15
ሠላም ለአንተ ይሁን። ወገኖችሰላምታ ያቀርቡልሀል። በአንተ ዘንድ ላሉት ወገኖች በስማቸው እየጠራህ ሠላምታ አቅርብልኝ።

---

3 John 1:1

3ኛ ዮሐንስ 1፡ 1-4
ሽማግሌው r ሽማግሌው ይህ የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዝሙር የነበረውን ሐዋርያው ዮሐንስ የሚያመለክት ነው። ራሱን “ሽምግሌው” በማለት ይጠራል፡ ፤ ምክንያቱ አንድም በእድሜው ስላረጀ ወይም የቤተ ክርስቲያን መሪ በመሆኑ ሊሆን ይችላል። የጸሐፊው ስም በግልጽ መቀመጥ ይኖርበታል፡ “እኔ ሽማግሌው ዮሐንስ ይህንን ጽፌላችኋለሁ።" ለጋይዮስ ይህ ዮሐንስ ደብዳቤውን የጻፈለት አማኝ ነው። በእውነት የሚወደው አማራጭ ትርጉም: "በእውነት የሚወደው" (UDB) በሁሉ ነገር እንዲከናወነልክ እና ጤናማ እንድትሆን "በሁሉ ነገር መከናወንን ታገኝ ዘንድ እና ጤናማ ትሆን ዘንድ" ነፍስህ እንደተከናወነች ሁሉ "በመንፈሳዊ ነገር እንደተከናወነላቸው ሁሉ" ወንድሞች "አማኞች" አንተ በእውነት እንደምትሄድ ስለ እውነትህ ሲመሰክሩ እጅግ ደስ ብሎኛልና። h "በእግዚአብሔር እውነት መሠረት እየኖርክ መሆንህን ነግረውኛል" ከዚህ የሚበልጥ ደስታ ፈጽሞ የለኝም

ልጆቼ የሐንስ በኢየሱስ እንዲያምኑ ያስተማራቸውን ከልጆች ጋር ያነጻጽራቸዋል። ይህ የእርሱን ፍቅር እና ስለ እነርሱ ምን ያኽል ግድ እንደሚለው ያሳያል። አማራጭ ትርጉም: "የእኔ መንፈሳዊ ልጆች።"

3 John 1:5

3ኛ ዮሐንስ 1፡ 5-8
ወዳጆቼ ሆይ በዚህ ስፍራ ይህ ቃል የሚያሳየው አማኞች ምን ያህል የተወደዱ እንደሆኑ ነው። ስለ ፍቅር "ለእግዚብሔር ታማኝ መሆንን በተግባር አሳይተሃል" ወይም "ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነሃል" ለወንድሞች እና ለመጻተኞች ሥራ "አማኞችን እና የማታውቃቸውን ሰዎችም እርዳ/አግዝ" በቤተ ክርስቲያን ፊት ስለ ፍቅርህ መስክረዋል፤ ይህ በአዲስ ዓረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል፡ "በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ላሉ አመማኞች ምን ያኽል እንደወደድካቸው ተናግረዋል።" ለእግዚአብሔር እንደሚገባ አድርገህ በጉዞአቸው ብትረዳ መልካም ታደርጋለህ፤ "እግዚአብሔርን በሚያስከብር መልኩ በመንገዳቸው እባካችሁ ሸኙዋቸው" በወጡት ሰዎች ስም ምክንያት በዚህ ሥፍራ ላይ “ስም” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢየሱስን ነው። አማራጭ ትርጉም: “ስለ ኢየሱስ ለመናገር ወጥተዋል።" ከአሕዛብ አንዳች ሳይቀበሉ ስለ ስሙ ወጥተዋልና። በዚህ ሥፍራ ላይ “አሕዛብ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው አይሁዳዊ ያልሆነ ሰው ማለት አይደለም። በኢየሱስ የማያምን ሰው ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም: "ስለ ኢየሱስ ከሚናገሩ ሰዎች ምንም ነገር አልወሰዱም" ስለዚህ እኛ በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ዮሐንስን እና ሁሉንም አመማኞችን ያጠቃልላል። ለእውነት አጋር ሠራተኞች ነን "የእግዚአብሔርን እውነት ለሌሎች ሰዎች ይነናገሩ ዘንድ እናግዛቸዋለን"

3 John 1:9

3ኛ ዮሐንስ 1፡ 9-10
ማህበረ ምዕመናን ይህ ጋዮስን እና እግዚአብሔርን ለማምለክ የሚሰበሰቡ አማኞችን ያመለክታል። ዲዮጥራጢስ እርሱ የማህበረ ምዕመኑ አባል ነው። ከሁሉ አንደኛ መሆንን ይወዳል "የእነርሱ መሪ ሆኖ መታየትን ይወዳል" እኛን አይቀበልም በዚህ ስፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ዮሐንስን እና ከእርሱ ጋር ያሉትን ሰዎችን ነው። ጋዮስን ግን አያመለክትም። በእኛ ላይ በክፉ ቃል እየለፈለፈ የሚያደርገውን ሥራውን አሳስባለሁ፤ "እውነት ያልሆነ ነገር እየተናገረ በእኛ ላይ ብዙ ክፉ ነገሮችን ይናገራል" እርሱ ራሱ “እርሱ ራሱ” የሚለው ቃል እነዚህ ነገሮችን የሚያደርገውን ዲዮጥራጢስ ያመለክታል። ወንድሞችን አይቀበለም "ወንድሞችን አይቀበልም" እንዲሁም የሚፈልጉትንም ይከለክላል በዚህ ሀረግ ውስጥ የተተው ቃላት አሉ ነገር ግን ለመረዳት ግን እንቅፋት አይደሉም። አማራጭ ትርጉም: "ሌሎች አማኞችን የሚቀበሉ ሰዎችን ያስቆማል።" አውጢቶዋቸዋል "አባሮዋቸዋል።" በዚህ ሥፍራ ላይ “እነርሱ” የሚለው ቃል ሌሎች አማኞችን ለመቀበል ፈቃደኞች የሆኑ ሰዎችን ያመለክታል።

3 John 1:11

3ኛ ዮሐንስ 1፡ 11-12
ወዳጆቼ ሆይ በዚህ ሥፍራ ላይ ይህ ቃል የሚያመለክተው የተወደዱ አማኞችን ነው። ክፉን አትምሰሉ "ሰዎች የሚያደርጉትን ክፋት አትከተሉ" ይልቁንም መልካሙን በዚህ ሀረግ ውስጥ የተተው ቃላት አሉ ነገር ግን ለመረዳት አዳጋጅ አይደለም። አማራጭ ትርጉም: "ሰዎች የሚያደርጋዋቻን መልካም ነገሮችን ተከታተሉ።" ከእግዚአብሔር ነው "የእግዚአብሔር ነው" እግዚአብሔርን አላየውም አማራጭ ትርጉም: "የእግዚአብሔር አይደለም" ወይም "በእግዚአብሔር አያምንም" ለድሜጥሮስ ሁሉ ይመሰክሩለታል፥ አማራጭ ትርጉም: "ድሜጥሮስን የሚያውቁትን ሁሉም ክርስትያኖች ስለ እርሱ መልካምነት ይመሰክራሉ።" እንዲሁም እውነት እራሷም "እንዲሁም እውነት እራሷ ስለ እርሱ ትናገራለች።" በዚህ ሥፍራ ላይ “እውነት” የሚለው ቃል እንደሚናገር ሰው ሆና ቀርባለች። አማራጭ ትርጉም: "ስለ እርሱ

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የተናገሩት ነገር እውነት ነው።) እኛም ራሳችን እንመሰክራለን በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል ዮሐንስን እና ከእርሱ ጋር ያሉትን ሰዎች ይወክላል። ነገር ግን ጋዮስን አያካትትም። አማራጭ ትርጉም፡ "ስለ ለድሜጥሮስ እኛም ጭምር እንመሰክራለን።" ታውቃለህ በዚህ ሥፍራ ላይ “አንተ” የሚለው ቃል በነጠላ ቁጠትር የተቀመጠ ሲሆን ጋዮስን ያመለክታል።

3 John 1:13

3ኛ ዮሐንስ **1**፡ **13-15**
ኖት የለውም።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Jude

Jude

ምዕራፍ 1

1 የኢያሱስ ክርስቶስ አገልጋይ፥ የያዕቆብ ወንድም ይሁዳ፤ ለተጠሩት፥ በእግዚአብሔር አብ ለተወደዱትና በኢየሱስ ክርስቶስ ለተጠበቁት፤ 2 ምሕረት ለእናንተ
ይሁን፤ ሰላምና ፍቅርም ይብዛላችሁ። 3 ወዳጆች ሆይ፤ አብረን ስለምንካፈለው ድነት ልጽፍላችሁ ጥረት እያደረግሁ ሳለ፥ ለቅዱሳን አንዴና ለመጨረሻ
ስለተሰጠው እምነት ጸንታችሁ ትጋደሉ ዘንድ ለመምከር እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ። 4 ለፍርድ እንደሚዳረጉ ከብዙ ዘመን በፊት የተጻፈባቸው አንዳንድ
ሰዎች ሾልከው ወደ እናንተ ገብተዋልና። እነዚህ ሰዎች ፈሪሃ እግዚአብሔር የሌላቸው፥ የእግዚአብሔርን ጸጋ በሴሰኝነት የሚለውጡ፥ እርሱ ብቻ ገዣችንና ጌታችን
የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን የሚክዱ ናቸው። 5 ምንም እንኳ አስቀድማችሁ ሁሉን የምታውቁት ቢሆንም ጌታ አንድ ጊዜ ሕዝቡን ከግብጽ አውጥቶ እንደ
አዳናቸው በኋላ ግን ያላመኑትን እንዳጠፋቸው ላስታውሳችሁ እወዳለሁ። 6 እንዲሁም የነበራቸውን የሥልጣን ደረጃ ባለመጠበቅ ተገቢ የመኖሪያ ስፍራቸውን
የተውትን መላእክት እግዚአብሔር እስከ ታላቁ የፍርድ ቀን ድረስ በዘላለም እስራት በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ እንዲቆዩ አድርጓል። 7 እንዲሁም ሰዶምና ገሞራ
በዙሪያቸውም የነበሩት ከተሞች በተመሳሳይ ሁኔታ ራሳቸውን ለሴሰኝነትና ከተፈጥሮ ሥርዓት ውጪ ለሆነ ግብረ ሥጋ ግንኙነት አሳልፈው ሰጡ፤ እነርሱም
በዘላለም እሳት ተጥለው ለሚሰቃዩት ምሳሌ እንዲሆኑ ተደርገዋል። 8 በዚህ ሁኔታ እነዚህ ደግሞ በሚያልሙት ሕልማቸው የራሳቸውን ሥጋ ያረክሳሉ፤ሥልጣንን
ይቃወማሉ፤በሰማይ ክብር ያላቸውንም ይሳደባሉ። 9 የመላእክት አለቃ ሚካኤል እንኳ ዲያብሎስን በመቃወም ስለ ሙሴ ሥጋ በተከራከረው ጊዜ «ጌታ
ይገሥጽህ» አለው እንጂ በእርሱ ላይ ሊፈርድ ወይም አንዳች የስድብ ቃል ሊናገር አልደፈረም። 10 እነዚህ ሰዎች ግን የማያውቋቸውን ነገሮች ሁሉ ይሳደባሉ።
እነርሱም አእምሮ የሌላቸው እንስሳት እንደሚያደርጉት በደመ ነፍስ በሚያውቋቸው ነገሮች ይጠፋሉ። 11 ወዮላቸው፤ በቃየን መንገድ ሄደዋልና፤ለገንዘብ ሲሉ
በበለዓም ስህተት ውስጥ ወድቀዋልና፤በቆሬም ዐመፅ ጠፍተዋልና። 12 እነዚህ በፍቅር ግብዣችሁ ላይ አብረዋችሁ ሲጋበዙ ችግር የሚፈጥሩባችሁ ድብቅ
እንቅፋቶች ናቸው፤ ደግሞም ያለ ሃፍረት ራሳቸውን ብቻ የሚመግቡ እረኞች ናቸው። እነርሱም በነፋስ የሚነዱ ውሃ አልባ ደመናዎች ናቸው፤ በመከር ወራት ፍሬ
የማይገኝባቸው፥ ከሥራቸው የተነቀሉና ሁለት ጊዜ የሞቱ ዛፎች ናቸው። 13 የራሳቸውን የነውር አረፋ የሚደፍቁ የተቆጣ የባሕር ማዕበል፥ ድቅድቅ ጨለማም
ለዘላለም የተጠበቀላቸው ተንከራታች ከዋክብት ናቸው። 14 ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ ትውልድ የሆነው ሄኖክ ስለ እነዚህ ሰዎች እንዲህ በማለት ትንቢት
ተናግሯል፤ «እነሆ፤ ጌታ ከብዙ ሺህ ቅዱሳኑ ጋር ይመጣል። 15 የሚመጣውም በሰው ሁሉ ላይ ለመፍረድ እንዲሁም ዐመፀኞችንና ኀጢአተኞችን ክፋት
በተሞላበት ሁኔታ በፈጸሙት የዐመፅ ሥራቸውና በእግዚአብሔር ላይ በተናገሩት የስድብ ቃል ለመውቀስ ነው።» 16 እነዚህ የሚያጉረመርሙ፥ ሌላውን
የሚከሱ፥ የራሳቸውን ክፉ ምኞት የሚከተሉ፥ ጉራ የሚነዙና ጥቅም ለማግኘትም ሰዎችን የሚክቡ ናቸው። 17 እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ፤የጌታችን የኢየሱስ
ክርስቶስ ሐዋርያት አስቀድመው የተናገሩትን ቃል አስታውሱ 18 ለእናንተም ሲናገሩ፥«በመጨረሻው ዘመን የራሳቸውን ክፉ ምኞት የሚከተሉ ዘባኞች ይመጣሉ»
ብለዋል። 19 እነዚህ በሰዎች መካከል መለያየትን የሚፈጥሩ፥የሥጋን ምኞት የሚከተሉና መንፈስ ቅዱስ የሌላቸው ናቸው። 20 እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ፤እጅግ
ቅዱስ በሆነው እምነታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ ትጉ፤በመንፈስ ቅዱስም ጸልዩ። 21 በእግዚአብሔር ፍቅር ራሳችሁን ጠብቁ፤የዘላለም ሕይወትም ታገኙ ዘንድ
የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ምሕረት ፈልጉ። 22 ለሚጠራጠሩ ሰዎች ርኅራኄ አድርጉላቸው፤ 23 ከእሳት ነጥቃችሁ በማውጣት አንዳንዶችን አድኑ፤ ለሌሎች
ድግሞ በእርኩስ ሥጋ የተበከለውን ልብስ እንኳ እየጠላችሁ በፍርሃት ምህረት አሳዩአቸው። 24 እንግዲህ ከመውደቅ ሊጠብቃችሁ፥ ነቀፋ ሳይኖርባችሁ በታላቅ
ደስታ በክብሩ ፊት ሊያቀርባችሁ ለሚችለው 25 በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት አዳኛችን ለሆነው ብቸኛ አምላክ ከዘመናት ሁሉ በፊት፥ አሁንና እስከ
ዘላለም ድረስ ክብር፥ ግርማ፥ ኀይልና ሥልጣንም ይሁን፤ አሜን።

Jude 1:1

ይሁዳ 1፡ 1-2
ይሁዳ፣ አገልጋዩ ይሁዳ የያዕቆብ ወንድም ነው። አማራጭ ትርጉም: እኔ ይሁዳ ነኝ፣ የ . . . አገልጋይ።" እና ወንድሙ ያዕቆብ ያዕቆብ እና ይሁዳ የኢየሱስ በአንድ ወገን ወንድሞች ናቸው። በእግዚአብሔር አባት የተወደዱ "እግዚአብሔር አባት ይወዳችኋል ምሕረት ለአንተ ይሁን እንዲሁም ሰላምና ፍቅርም ይብዛላችሁ። በዚህ ሥፍራ ላይ “እናነተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ይህንን ደብዳቤ የተቀበሉት ሁሉንም ክረስትያኖች ነው። አማራጭ ትርጉም: "ምህረት፣ ሰላም እና ፍቅር አብዝቶ ይብዛላችሁ።"

Jude 1:3

ይሁዳ 1፡ 3-4
ለእናንተ ለመጻፍ ማንኛውንም ጥረት አደርጌያለሁ "ለእናንተ ለመጻፍ ጥሬያለሁ" የጋራ ድነታችን "ተመሳሳይ ድነትን ተጋርተናል" መጻፍ እንዳለብኝ "መጻፍ እንዳለበኝ አጥብቆ ተሰማኝ" ወይም "መጻፍ እንዳለብኝ በጣም ተሰምቶኛል" ፈጽሞ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ። "እውነተኛውን ትምህርት እንድትጠብቁ አበረታታለሁ" የተሰጠውን "እግዚአብሔር እውነተኛውን ትምህርት ሰጥቷል" አንዳንዶች ሰዎች ሾልከው ገብተዋልና፤ "አንዳንድ ሰዎች ሳይታወቅ ወደ አማኞች ዘንድ ሾልከው ገብተዋል" ከብዙ ጊዜ በፊት ለዚህ ፍርድ የተጻፉ "ከብዙ ዘመናት በፊት በእነዚህ ሰዎች ላይ እንደሚፈረድ ተጽፏል። " የአምላካችንን ጸጋ በሴሰኝነት ይለውጣሉ "እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔር ጸጋ አንድ ሰው በግብረስጋ ግንኙነት ኃጢአት እንዲቀጥል ይፈቅዳል በማለት ያስተምራሉ" ንጉሣችንንና ጌታችንንም ብቻውን ያለውን ኢየሱስ ክርስቶስን ይክዳሉ። ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ወይም ወደ እግዚአብሔር የሚወስድ መንገድ አይደለም ብለው ያስተምራሉ። ክደው አንድ ነገር ስህተት ነው ለማለት።

Jude 1:5

ይሁዳ 1፡ 5-6
ላሳስባችሁ እወዳለሁ "ላስታውሳችሁ እወዳለሁ" ሁሉን ነገር ታውቃላችሁ ይሁዳ በዚህ ሥፍራ ላይ እያመለከተ ያለው ስማሩ የነበሩትን የሙሴን መጽሐፍት ነው። አማራጭ ትርጉም: “የሙሴን መጽሐፍት አጠንቅቃችሁ ታውቃላችሁ።" ጌታ ከግብፅ አገር ሕዝቡን አድኖ "ጌታ ከብዙ ዘመናት በፊት እስራኤላዊያንን ከግብጽ ምድር ታድጎ" ይሁን እንጂ ከዚያ በኋላ "በኋላ ዘመናት ላይ" ወይም "አንዳንድ ነገሮች ከሆኑ በኋላ" የራሳቸውን አለቅነት "የራሳቸውን ስልጣን" ወይም "ለእነርሱ የተሰጣቸውን ኃላፊነት" ትክክለኛውን መኖሪያቸውን የተውትን "የተሰጣቸውን ሥፍራ የተውትን" እግዚአብሔር

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

በዘላለም እስራት ከጨለማ በታች እስከ ታላቁ ቀን ፍርድ ድረስ ጠብቆአቸዋል። "እግዚአብሔር እነዚህን መላእክት በጨለማ ውስጥ አስሮ አስቀምጦዋቸዋል" ታላቁ ቀን እግዚአብሔር በሰዎች ሁሉ ላይ የሚፍድበት ቀን

Jude 1:7

ይሁዳ 1፡ 7-8
በተሳሳይ መልኩም ራሳቸውን የሰጡትን መላእክት ክፉ መንገዳቸውን እንደተከተሉ ሁሉ ሶዶም እና ጎሞራም በዝሙት ኃጢአታቸውን ተከትለዋል። በዙሪያቸውም የነበሩ ከተማዎች በዘላለም እሳት እየተቀጡ ምሳሌ ሆነዋል። የሰዶም እና የጎሞራ መጥፋት እግዚአብሔርን የማይቀበሉ ሰዎች እድል ፈንታ ምን እንደሆነ የሚያሳይ ምሳሌ ነው። እነርሱም ደግሞ ተበክለዋል በዚህ ሥፍራ ላይ “እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔር ለመቀበል ፈቃደና ያልሆኑ ሰዎችን ነው። ልክ ቆሻሻን ወደ ውሃ ውስጥ መጣል ውሃውን እንዲሸት እንደሚያደርገው ሁሉ እነዚህም አካላቸውን በፍተወት በክለውታል። ስለ ተከበረው "ስለ ተከበረው የእግዚአብሔር መላእክ"

Jude 1:9

ይሁዳ 1፡ 9-11
ስለ ሥጋ ስከራከሩ ሳለ አካልን የሚወስደው ማን ነው ብለው በተከራከሩ ጊዜ። አማራጭ ትርጉም: "አካልን የሚወስደው ማን ነው ብለው ስከራከሩ ሳለ።" ሚካኤል ...እርሱን እንዲቃወም አልፈቀደለትም አማራጭ ትርጉም: "ሚካኤል...ዳቢሎስን መቃወምን ቀጥሎ ነበር" እርግማን ወይም የስድብ ቃላት "ጠንካራ ትችት ወይም ጸያፍ ቃላት" ይሁን እንጂ እነዚህ ሰዎች "እነዚህ ሰዎች" ከዚህ በፊት የተጠቀሱት ፈርሃ እግዚአብሔር ያሌላቸው ሰዎች ናቸው። እነዚህ ግን የማያውቁትን ሁሉ ይሳደባሉ፥ "ትርጉሙን የማያውቁትን ነገር ሁሉ ይሳደባሉ" የቃዬል መንገድ ቃዬል ወንድሙን አቤልን ገድሎታል። የበለአም ስህተት በለአም ለገንዘብ ሲል እስራኤልን ረግሞዋል። የቆሬ ልጆች አመጽ ቆሬ በሙሴ መሪነት እና በአሮን ካህንነት ላይ አምጸው ነበር።

Jude 1:12

ይሁዳ 1፡ 12-13
እነዚህ ናቸው በዚህ ሥፍራ ላይ “እነዚህ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ፈርሃ እግዚአብሐር ያሌላቸውን ሰዎችን ነው። በበገራ የደረቁ ፍሬ የማያፈሩ ዛፎች ናቸው በበጋ ወራት መጨረሻ ላይ አንዳንድ ዛፎች ፍሬ እንደማያፈሩ ሁሉ ፈርሃ እግዚአብሔር ያሌላቸው ሰዎችን ጽድቅ የሞላበት እምነት እና ሥራ የላቸውም። ፍሬ ያሌላቸው፣ ሁለት ጊዜ የሞቱ ልክ ሁለት ጊዜ እንደሞተ ዘፍ ፍሬ እንደማያፈራ ሁሉ ፈርሃ እግዚአብሔር ያሌለው ሰውም በውስጡ ምንም እሴት አይኖርም እንዲሁም በውስጡ ምንም ሕይወት የለም። ከነሥራቸው የተነቀሉ ልክ ከነሥራቸው የተነቀሉ ዛፎች ፈርሃ እግዚአብሔር ያሌላቸው ሰዎች የሕይወት ምንጭ ከሆነው ከእግዚአብሔር የተለዩ ናቸው። ጨካኝ የባሕር ማዕበል፥ የባሕር ማዕበል በንፈስ እንደሚንቀሳቀስ ሁሉ ፈርሃ እግዚአብሔር ያሌላቸው ሰዎችም የእምነት መሠረት ዬለቸውም እንዲሁም በተለያየ አቅጣጫ በቀላሉ ወዛወዛሉ። የገዛ ነውራቸውን አረፋ እየደፈቁ ንፋስ ማዕበሉን እየገፋ ቆሻሻ አረፋ እንደሚያስደፍቅ ሁሉ እነዚህ ሰዎችም በስህተት ትምህርታቸው እና ተግበራቸው አማካኝነት ረራሳቸውን ያዋርዳሉ። አማራጭ ትርጉም: "ማዕበል አረፋ እና ቆሻሻ እንደሚያወጣ ሁሉ እነዚህ ሰዎች በእፍረታቸው ሌሎች ሰዎችን ይበክላሉ። ድቅድቅ ጨለማ ለዘላለም የተጠበቀላቸው የሚንከራተቱ ከዋክብት ናቸው። ለመከታተል አስቸጋሪ እንደሆኑት በሰማይ ላይ እንደሚበሩት ክዋክብት እነዚህን ሰዎች መከተል የለባችሁም።

Jude 1:14

ይሁዳ 1፡ 14-16
እነዚህ ሰዎች...ሥራዎቻቸው ...እነርሱ ያላቸው ይህ የሚያመለክተው ፈርሃ እግዚአብሔር ያሌላቸው ሰዎች ነው። ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ የሆነ ሄኖክ ከአዳም ጀምሮ ያለው ሰባተኛው ትውልድ ድረስ። አንዳንድ ትርጉሞች አዳም መቆጠር አለመቆጠሩን አስመለክቶ ስድስተና ትውልድ ይላሉ። እነሆ ጌታ "ተመልከቱ ጌታ", ወይም "እነሆ ጌታ" ሁሉንም ከባባድ ነገሮችን "ሁሉንም ክፉ ቃላትን" የሚያንጎራጉሩና ኃጢአተኞች የማይታዘዝ ልብ ያላቸውe ሰዎች። የሚያንጎራጉሩና ይህንን ግልጽ ባልሆነ መንገድ ሲያደርጉ ኃጢአተኞች ደግሞ በግልጽ ያደርጉታል። በኩራት ሌሎች ሰዎች ይሰሟቸው ዘንድ ራሳቸውን የሚያሞግሱ ሰዎች።

Jude 1:17

ይሁዳ 1፡ 17-19
አንዲህ ይላችኋል "ሐዋርያው እንዲህ ይላችኋል" የራሳቸውን . . . ተከትለው ሄደዋል። እነርሱ እንዲህ ናቸው። በዚህ ሥፍራ ላይ ይሁዳ እያመለከተ ያለው ዘባች የሆኑ ሰዎችን ነው። ክፍፍልን ይፈጠትራሉ "በአማኞች መካከል መለያየትን የሚፈጥሩ ዘባቾች ናቸው" ስሜታዊያን ናቸው "ዘባቾቹ የፍተወት ፍላጎተቸውን ይከተላሉ"

Jude 1:20

ይሁዳ 1፡ 20-21
ራሳችሁን እያነጻችሁ ስትሄዱ እየጠነከራችሁ በሄዳችሁ እና ጤናማ አካልን እየገነባችሁ በሄዳችሁ ቁጥር አእምሮዋችሁ እየጎለበተ እና እደገ ይሄዳል። እንዲሁም በእግዚአብሔር እውቀትም በመንፈሳችሁ ታድጋላችሁ። ስትጠባበቁ... "ወደፊት የሚሆነውን በናፍቆት ስትጠባበቁ ሳለ"

Jude 1:22

ይሁዳ 1፡ 22-23
በጥርጣሬ ውስጥ ያሉ አንዳንድ ሰዎች "እግዚአብሔር አምላክ ለመሆኑ ገና ያላመኑ አንዳንድ ሰዎች" እነርሱ ከእሳት መንጭቆ በማውጣት "ወደ እሳት ባሕር ውስጥ እንዳይገቡ" እና በፍርሃት ማሩ "ለሌሎች ምህረትን አሳዩ ነገር ግን ልክ እንደ እነርሱ ኃጢአትን እንዳተታደርጉ ተጠንቀቁ።" በሥጋ የረከሰውን ልብስ እንኳ እየጠላችሁ "ልብሳቸውን እንኳ ጥሉ ምክንያቱም በኃጢአት ቆሻሻ ሆነዋል።" ሙሉ በሙሉ በኃጢአት ተበክለዋልና ንጹሕ አይደሉም።

Jude 1:24

ይሁዳ 1፡ 24-25
ኖት የለውም።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Book: Revelation

Revelation

ምዕራፍ 1

1 ይህ ፈጥኖ ሊሆን የሚገባውን ነገር ለአገልጋዮቹ እንዲያሳይ እግዚአብሔር ለኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው ራእይ ነው። እርሱም ይህን ራእይ መልአኩን ወደ አገልጋዩ ወደ ዮሐንስ በመላክ እንዲታወቅ አድርጓል። 2 ዮሐንስም የእግዚአብሔርን ቃል በሚመለከት ስላየው ማንኛውንም ነገር እና ክርስቶስን በሚመለከት ስለተሰጠው ምስክርነት ተናግሯል። 3 ዘመኑ ስለ ቀረበ ፥ የዚህን የትንቢት ቃል የሚያነብ የተባረከ ነው፤እንዲሁም የሚሰሙት ሁሉ በውስጡም የተጻፈው ን ነገር የሚፈጽሙ የተባረኩ ናቸው። 4 ከዮሐንስ፥በእስያ ላሉት ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት፤ካለው፥ከነበረው፥ወደፊትም ከሚመጣውና በዙፋኑ ፊት ካሉት ከሰባቱ መንፈሶች 5 እንዲሁም ታማኝ ምስክር፥ከሙታን በኩርና የምድር ነገሥታት ገዥ ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን። ለሚወደንና ከኀጢአታችንም በደሙ ነጻ ላወጣን፥ 6 አባቱ ለሆነው እግዚአብሔር መንግሥትና ካህናት እንሆን ዘንድ ላደረገን ለእርሱ ክብርና ኀይል ከዘላለም እስከ ዘላለም ይሁን፤አሜን። 7 እነሆ፤እርሱ በደመና ይመጣል፤የወጉትን ጨምሮ ዐይን ሁሉ ያየዋል። የምድርም ነገዶች ሁሉ በእርሱ ምክንያት ያለቅሳሉ፤እንደዚያም ይሆናል፤አሜን። 8 ጌታ እግዚአብሔር፥«አልፋና ኦሜጋ፥ ያለሁና የነበርሁ፥ወደፊትም የምመጣው ሁሉን ቻይ እኔ ነኝ» ይላል። 9 እኔ ከእናንተ ጋር በመከራው፥በመንግሥቱና በኢየሱስ በሚገኘው ትዕግሥት ተካፋይ የሆንሁ ወንድማችሁ ዮሐንስ፥ በእግዚአብሔር ቃልና በኢየሱስ ምስክርነት ምክንያት ፍጥሞ በምትባል ደሴት ነበርሁ። 10 በጌታም ቀን በመንፈስ ነበርሁ፤በኋላዬም የመለከትን ድምጽ የሚመስል ታላቅ ድምፅ ሰማሁ። 11 ድምፁም እንዲህ የሚል ነበር፤«የምታየውን በመጽሓፍ ጻፈው፤ ከዚያም በኤፌሶን፥ በሰምርኔስ፥ በጴርጋሞን፥ በትያጥሮን፥ በሰርዴስ፥ በፊላደልፍያና በሎዶቅያ ወዳሉት ወደ ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ላከው። 12 ይናገረኝ የነበረው የማን ድምፅ እንደ ሆነ ለማየት ዘወር አልሁ፤ ዘወር በምልበትም ጊዜ ሰባት የወርቅ መቅረዞችን አየሁ። 13 በመቅረዞቹም መካከል እስከ እግሩ ድረስ የሚደርስ ረጅም ልብስ የለበሰና ደረቱንም በወርቅ መታጠቂያ የታጠቀ የሰው ልጅ የሚመስለው ነበር። 14 ራሱና ጸጉሩ እንደ ነጭ የበግ ጸጉር ማለትም እንደ በረዶ ነጭ ነበሩ፤ዐይኖቹ የእሳት ነበልባል፥ 15 እግሮቹም በእቶን እሳት እንደ ነጠረ የጋለ ናስ፥ ድምፁም እንደ ብዙ ወራጅ ውኃ ድምፅ ነበር። 16 በቀኝ እጁ ሰባት ከዋክብት ይዞ ነበር፤ከአፉም በሁለት በኩል የተሳለ ስለታም ሰይፍ ይወጣ ነበር፤ፊቱም ጸሐይ በሙሉ ኀይልዋ ስታበራ የምታበራውን ያህል ያበራ ነበር። 17 ባየሁትም ጊዜ እንደ ሞተ ሰው ሆኜ በእግሩ ሥር ወደቅሁ፤ እርሱም ቀኝ እጁን በእኔ ላይ በመጫን እንዲህ አለኝ፤ «አትፍራ፤እኔ የመጀመሪያውና የመጨረሻው 18 ሕያውም ሆኜ የምኖር ነኝ። ሞቼ ነበር፤እነሆም ለዘላለም ሕያው ነኝ፤የሞትና የሲዖል መክፈቻም አለኝ። 19 ስለዚህ ያየኸውን፥አሁን ያለውን ሁኔታና ከዚህ በኋላ የሚሆነውን ነገር ጻፍ። 20 በቀኝ እጄ ያሉት አንተም ያየሃቸውን የሰባቱን ከዋክብትና የሰባቱን የወርቅ መቅረዞች ምስጢር በተመለከተ ትርጉሙ ይህ ነው፤ሰባቱ ከዋክብት የሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት መላእክት ሲሆኑ፥ ሰባቱ መቅረዞች ደግሞ ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው።

Revelation 1:1

ራዕይ 1፡ 1-3
የእርሱ አገልጋዮች በክርስቶስ አማኞች በቅርቡ ሊሆኑ ስላሉት ነገሮች አማራጭ ትርጉም: "በቅርቡ የሚሆኑ ነገሮች" አስታውቋል "ተነግሮዋል።" ጊዜ ቅርብ ነው አማራጭ ትርጉም: "መሆን የሚገባቸው ነገሮች ብቅርቡ ይሆናሉ"

Revelation 1:4

ራዕይ 1፡ 4-6
ሠላም ከሆነው ሠላም ይሁንላችሁ "ሠላም ከሆነ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሠላም ይሁንላችሁ" መናፍስት እነዚህ መናፈስት መላእክት መሆናቸው በተዘዋዋሪ መንገድ ተገልጸዋል ምክንያቱም እነዚህ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት የሚሆኑ ናቸውና። ነጻ ወጥተናል አማራጭ ትርጉም: "ነጻ አውጥቶናል" መግስት አድርጎናል "ለይቶን በእኛ ላይ መንገስ ጀምሯል"

Revelation 1:7

ራዕይ 1፡ 7-8
ዐይን ሁሉ አማራጭ ትርጉም: "ማንኛውም ሰው" ሰቀሉት ገደሉት ወጉት ቀዳዳ አበጁ አልፋ እና ኦሜጋ (ጅማሬ እና ፍጻሜ) እነዚህ የግሪክ ፊደላት መጀመሪያ እና መጨረሻ ናቸው። ትርጉሙም የሁሉ ነገር ጅማሬ እና ፍጻሜ እግዚአብሔር ነው፤ በመካከልም በሁሉም ላይ የሚገዘው እግዚአብሔር ነው ማለት ነው። አልፋ . . . ኦሜጋ ይህ በባሕሉ መሠረት መተርጎም ይኖርበታል። ለምሳሌ ያኽል አልፋ እና ኦሜጋ የሚሉት ቃላት የግሪክ ፊደላትን ለማያውቅ ሰው ምንም ዓይነት ትርጉም የላቸውም። ስለዚህም በቋንቋቸው ተስመሚ የሆኑ ቃላትን ፈልገው መተርጎም ይርባቸዋል።

Revelation 1:9

ራዕይ 1፡ 9-11
እናንተ . . . እናንተ በሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ያሉ አማኞች ከእናንተ ጋር በዚየሱስ ያለው መከራን እና መንግስትን በጽናት የሚካፈሉ "ከእናንተ ጋር የእግዚአብሔርን መንግስት የሚወርሱ። እንዲሁም የኢየሱስ ከመሆናችን የተነሣ ከእናንተ ጋር መከራን እና ስደተን በጽነናት የሚካፈል።" ከእግዚአብሔር ቃል የተነሣ "የእግዚአብሔርን ቃል በመናገሪ የተነሣ" በመንፈስ ይህ ማለት በእግዚአብሔር መንፈስ አማካኝነት። የጌታ ቀን በክርስቶስ የሆኑት አማኞች የሚያመልኩበት ቀን። የመለከት ድምፅ ያለው ክፈተኛ ድምፅ ድምፁ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሣ የመለከት ድምፅ ይመስላል። ሰምርኔስ፣ ጴርጋሞንም፣ ትያጥሮንም፣ ሰርዴስም፣ ፊልድልፍያም እና ሎዶቅያም እነዚህ በዘመኗ ቱሪክ አከባቢ በኢስያ ውስጥ የሚገኙ ከተሞች ስሞች ናቸው።

Revelation 1:12

ራዕይ 1፡ 12-13
ድምፁ በዚህ ሥፍራ ላይ “ድምፅ” የሚለው ቃል የሚናገረውን ሰው ይወክላል። ቀበቶ በመቀመጫ ዙሪያ ወይም በደረት ዙሪያ የሚታጠቁት ቁራጭ ጨርቅ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Revelation 1:14

ራዕይ **1**፡ **14**-**16**
ራሱ እና ጸጉሩ ልክ የበግ ጸጉር ይመስላል - እንደ በረዶ ነጭ ነው “እንደ ነጭ ነው” የሚለው በድጋሚ የተገለጸው ቃል ራሱ እና ጸጉሩ ምን ያኽል ነጭ እንደሆነ አጽኖት ለመስጠት ነው። ድምፁም እንደ ብዙ ውኃዎች ድምፅ ነበረ። ይህ ትልቅ ድምፅ ያለው፣ በፍጥነት የሚፈስ፣ ነጭ የወንዝ ውሃ የሚያሰማውን ድምፅ ነው።

Revelation 1:17

ራዕይ **1**፡ **17**-**18**
He placed his right hand on me አማራጭ ትርጉም: "በቀኝ እጆቹ ነካኝ" እኔ መጀመሪያ እና መጨረሻ ነኝ ይህ ለመኖር የመጀመሪያ መሆንን የሚያሳይ እና ለመኖር የመጨረሻ መሆንን የሚለው የሚያሳየው ዘላለማዊ ባሕርውን ነው።

Revelation 1:19

ራዕይ **1**፡ **19**-**20**
የወርቅ መቅረዞች ይህንን በ REV 1:12 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምክ ተመልከት። ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት See how you translated this in ይህንን በ REV 1:11 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምክ ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 2

1 “በኤፌሶን ወዳለው መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፤ ‘ሰባቱን ከዋክብት በቀኝ እጁ የያዘውና በሰባቱ የወርቅመቅረዞች መካከል የሚመላለሰው እንዲህ ይላል፤ 2 ‘ሥራህን፣ ትዕግሥትህንና ጽናትህን አውቃለሁ። ክፉ ሰዎችን መታገሥ አለመቻልህንም አውቃለሁ። ሐዋሪያት ሳይሆኑ “ሐዋሪያት ነን” የሚሉትን መርምረህ ሐሰተኞች ሆነው እንዳገኘሃቸውም አውቃለሁ።” 3 በትዕግሥት እንደ ጸናህ፥ስለ ስሜ ብዙ መከራ ቢደርስብህም እንዳልደከመህ አውቃለሁ። 4 ነገር ግን የምነቅፍብህ ነገር አለኝ፤ይኽውም የቀደመውን ፍቅርህን ትተሃል። 5 እንግዲህ ከወዴት እንደ ወደቅህ ለይተህ እወቅ፤ንስሓ ግባ፤ቀደም ሲል ታደርገው የነበረውንም ነገር አድርግ። ንስሓ ካልገባህ እመጣብሃለሁ፤መቅረዝህንም ከስፍራው አስወግዳለሁ። 6 ነገር ግን ይህ መልካም ነገር አለህ፤ እኔ የምጠላውን የኒቆላውያንን ሥራ ጠልተሃል። 7 ጆሮያለው መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያን የሚለውን ይስማ። ድል ለሚነሣው በእግዚአብሔር ገነት ካለው የሕይወት ዛፍ የመብላትን መብት እሰጠዋለሁ።” 8 «በሰምርኔስ ላለችው ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፤ "እነዚህ መጀመሪያም መጨረሻም የሆነው የእርሱ ቃሎች ናቸው፤ሞቶ የነበረው፥እንደ ገና ሕያው የሆነው እንዲህ ይላል፤ 9 '"መከራህንና ድኽነትህንም አውቃለሁ፤ነገር ግን ባለጠጋ ነህ፤የሰይጣን ማኅበር ሆነው እያለ፥አይሁድ ሳይሆኑ አይሁድ ነን ብለው የሚናገሩ ሰዎች የሚሳደቡትን ስድብ አውቃለሁ። 10 ወደ ፊት የሚደርስብህን መከራ አትፍራ። ተመልከት ከእናንተ አንዳንዶቹን እንድትፈተኑ ዲያብሎስ እስር ቤት ያስገባችኋል፤ ለአሥር ቀን መከራ ትቀበላላችሁ። እስከ ሞት ድረስ ታማኝ ሁን፤ እኔም የሕይወትን አክሊል እሰጥሃለሁ። 11 ጆሮ ያለው መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያን የሚለው ይስማ። ድል የሚነሻ በሁለተኛው ሞት አይጎዳም። 12 «በጴርጋሞን ላለው ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፤ "እነዚህ በሁለት በኩል የተሳለ ስለታም ሰይፍ ካለው የተነገሩ ቃሎች ናቸው፤እርሱም እንዲህ ይላል፤ 13 '"የሰይጣን ዙፋን ባለበት በዚያ እንደምትኖር አውቃለሁ፤ነገር ግን ስሜን አጥብቀህ ይዘሃል። ሰይጣን በሚኖርበት በእናንተ መካከል በተገደለው በታማኙ ምስክሬ በአንቲጳስ ዘመን እንኳ በእኔ ያለህን እምነት አልካድህም። 14 ነገር ግን የምነቅፍብህ ጥቂት ነገር አለኝ፤የእስራኤል ልጆች ለጣዖት የተሰዋ ምግብ እንዲበሉና እንዲሴስኑ በፊታቸው ማሰናከያ ያስቀምጥ ዘንድ ባላቅን የመከረው የበለዓምን ትምህርት አጥብቀው የሚከተሉ አንዳንድ ሰዎች በመካከልህ አሉ። 15 እንደዚሁም የኒቆላውያንን ትምህርት አጥብቀው የያዙ ሰዎች እንኳ በአንተ ዘንድ አሉ። 16 ስለዚህ ንስሓ ግባ፤አለበለዚያ ፈጥኜ እመጣብሃለሁ፤ከአፌም በሚወጣው ሰይፍ አዋጋቸዋለሁ። 17 ጆሮ ካለህ፥መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚናገረውን ስማ። ድል ለሚነሳ ከተሰወረው መና እሰጠዋለሁ፤እንደዚሁም ከሚቀበለው ሰው በስተቀር ማንም የማያውቀውን አዲስ ስም የተጻፈብትን ነጭ ድንጋይ እሰጠዋለሁ።> 18 በቲያጥሮን ወዳለው መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፤ “የእሰት ነበልባል የመሰሉ ዐይኖችና በእሳት ፍም የነጠረ ናስ የሚመስሉ እግሮች ያሉት የእግዚአብሔር ልጅ እንዲህ ይላል። 19 ሥራህን፣ ፍቅርህንና እምነትህን፣ አገልግሎትህንና በትዕግሥት መጽናትህን አውቃለሁ። አሁን በቅርቡ ያደረግኸው ቀድሞ ካደረግኸው የበለጠ መሆኑን አውቃለሁ።” 20 ነገር ግን የምነቅፍብህ አንድ ነገር አለኝ፤ራሷን ነቢይት ብላ የምትጠራውን ሴት ኤልዛቤልን ችላ ብለሃታል። ይህች ሴት በትምህርትዋ አገልጋዮቼ ሴሰኛ እንዲሆኑና ለጣዖት የተሰዋ ምግብ እንዲበሉ ታስታቸዋለች። 21 ንስሓ እንድትገባ ጊዜ ሰጥቻት ነበር ፤ይሁን እንጂ ከርኩሰትዋ ንስሓ ለመግባት ፈቃደኛ አልሆነችም። 22 እነሆ በሥቃይ አልጋ ላይ እጥላታለሁ፤ከእርስዋም ጋር የሚያመነዝሩት እርስዋ ከፈጸመችው ነገር ንስሓ ካልገቡ በስተቀር በከባድ ሥቃይ እንዲወድቁ አደርጋለሁ። 23 በሞት እቀጣለሁ፤በመሆኑም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የሰውን ሐሳብና ፍላጎትን የምመረምር እኔ እንደሆንሁ ያውቃሉ። ለእያንዳንዳችሁም እንደ ሥራችሁ እከፍላለሁ። 24 ዳሩ ግን ይህን ትምህርት ለማትከተሉ ሁሉ እንዲሁም አንዳንዶች የሰይጣን ጥልቅ ምስጢር ነው የሚሉትን ነገር ለማታውቁ በትያጥሮን ለምትኖሩ ለቀራችሁት ሌላ ሸክም አልጭንባችሁም።> 25 ሆኖም እስክመጣ ድርስ ያላችሁን ነገር አጸንታችሁ ጠብቁ። 26 ለሚነሣውና እስከ መጨረሻው እኔ የደረግሁትን ለሚያደርግ በሕዝቦች ላይ ሥልጣን እሰጠዋለሁ። 27 በብረት በትር ይገዛቸዋል፤ እንደ ሸክላም ዕቃ የደቃቸዋል። 28 እኔ ከአባቴ እንደ ተቀበልሁ የንጋትን ኮከብ እሰጠዋለሁ። 29 ጆሮ ያለው መንፈስ መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያን የሚለውን ይስማ።”

Revelation 2:1

ራዕይ 2፡ 1-2
ሐዋርያት ነን የሚሉትን አማራጭ ትርጉም: "ሐዋርያት ነን የሚሉ ሰዎች"

Revelation 2:3

ራዕ 2፡ 3-5
የመጀመሪያው ፍቅር ይህ ማለት "ለክርስቶስ ያላችሁ የመጀመሪያ ፍቅር::" መቅረዝህን እወስድሃለሁ እያንዳንዱ መቅረዝ ሰባቱን ቤተ ክርስቲያናትን ያመለክታል።

Revelation 2:6

ራዕይ 2፡ 6-7
ኒቆላውያንን ኒቆላ የሚባለውን ሰው ትምህርት የሚከተሉ ሰዎች:: ጆሮ ያለው ይስማ መንፈሰሳዊ ጆሮዎች:: ይህ ማለት እግዚብሔር ማድመጥ እና መልዕክቱን መረዳት የሚችል ሰው:: እንዲበላ እፈቅድለታለሁ "እንዲበሉ እፈቅድላቸዋለሁ"

Revelation 2:8

ራዕይ 2፡ 8-9
ስምርኔ ይህንንነ በ REV 1:11 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት:: መጀመሪያ እና መጨረሻ ይህንን በ REV 1:17 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት::

Revelation 2:10

ራዕይ 2፡ 10-11
ዳብሎስ አንዳንዶቻችሁን ወደ ወህኒ ቤት ልጥላቸው ነው አማራጭ ትርጉም: "ዳብሎስ አንዳንዶቻችሁን ወደ ወህኒ እንድትገቡ በቅርቡ ያደርጋል" ጆሮ ካላችሁ በ REV 2:7. ላይ በተረጎምከው መሠረት ተርጉም::

Revelation 2:12

ራዕይ 2፡ 12-13
በጴርጋሞንም ይህንን በ REV 1:11. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምክ ተመልከት:: አንቲጳስ ይህ የአንድ ሰው ስም ነው::

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Revelation 2:14

ራዕይ **2**፡ **14-15**
ባላቅ ይህ አንድ ንጉሥ ስም ነው። ባላቅን የእስራኤል ልጆች ፊት መሠናከያ ዓለተ እንዲያኖር ያስተማረ አማራጭ ትርጉም: "የእስራኤል ሕዝብ እንዴት ኃጢአት ማድረግ እንደሚችል ለባላቅ ያሳየው" ለጣኦት የተሰዋ ምግብን መብላት አማራጭ ትርጉም: "ለጣኦት የተሰዋ ምግብ እና ያንን መብላት" መሴሰን አማራጭ ትርጉም: "ፍትወታዊ ኃጢአት" ወይም "የግብረ ሥጋ ግንኙነት በማድረግ ኃጢአት መፈጸም"

Revelation 2:16

ራዕይ **2**፡ **16-17**
ይህንን የማታደርጉ ከሆነ እኔ "ንሰሓ የማትገቡ ከሆነ እኔ" ከአፌ በሚወጣው ሰይፍ ይህ በ REV 1:16. ላይ የተጠቀሰውን “ሰይፍ” ያመለክታል። የሚሰማ ጆሮ ያለው በ REV 2:7. ላይ ያለውን ትርጉም ተመልከት። ድል ለነሣው አማራጭ ትርጉም: "አሸናፉ ለሆነ ለማንኛውም ሰው"

Revelation 2:18

ራዕይ **2**፡ **18-19**
ትያጥሮን ይህንን በ REV 1:11. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። እነዚህ የእግዚአብሔር ልጅ ቃላት ናቸው። ከሞት የተነሣ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ካረገ ብዙ ዓመታት በኋላ አሁንም ለአማኞች በበመናገር ላይ ይገኛል። የእግዚአብሔር ልጅ ይህ ለኢየሱስ በጣም ወሳኝ የሆነ የማረግ ስም ነው።

Revelation 2:20

ራዕይ **2**፡ **20-21**
ይሁን እንጂ የምነቅፍ ነገር አለኝ ይህንን በ REV 2:4. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምክ ተመልከት።

Revelation 2:22

ራዕይ **2**፡ **22-23**
በአልጋ ላይ እጥላታለሁ አማራጭ ትርጉም: "ታማሚ እንዲትሆን አደርጋለሁ" ወይም "በበሽታ እቀጣታለሁ" ማመንዘር "ዝሙት መፈጸም" እርሷ ስላደረገችው ነገር እነርሱ ንሰሓ ገቡ አማራጭ ትርጉም: "እንደ እርሷ በመሆናቸው ንሰሓ ገቡ" ልጆቿን በሞት እገድላቸዋለሁ አማራጭ ትርጉም: "ልጆቿን እገድላቸዋለሁ" ሀሳብን እና መሻትን የሚመረምረው እኔ ነኝ አማራጭ ትርጉም: "ሀሳብን እና መሻትን እመረምራለሁ" ወይም "አእምሮን እና ልብን እመረምራለሁ"

Revelation 2:24

ራዕይ **2**፡ **24-25**
የሴጣንን ጥልቅ ነገር አማራጭ ትርጉም: "የሴጣንን የሐሰት ልምምድ" ወይም "የሴጣንን ውሸት" ወይም: እነዚህ መምህራን ምስጥ፣ አስገራም ልምምድ ብለው የሚናገሩት ሴጣን እንደነገራቸው የሚገልጹት ነገር ማለት ነው።

Revelation 2:26

ራዕይ **2**፡ **26-29**
ድል የነሣው አማራጭ ትርጉም: "ያሸነፈ ማንኛውም ሰው" እሰጠዋለሁ በዚህ ሥፍራ "እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ያሸነፈውን ሰው ነው። የማለደ ኮከብ ይህ የሚያመለክተው ከንጋት በፊት የሚትታይ ደማቅ ኮከብን ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 3

1 «በሰርዴስ ላለው ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፤ "ሰባቱን የእግዚአብሔር መንፈሶችና ሰባቱን ከዋክብት የያዘው እንዲህ በማለት
ይናገራል፤«ሥራህን ዐውቃለሁ፤ሕያው እንደሆንህ የሚገልጽ ዝነኛ ስም አለህ፤ነገር ግን ሞተሃል። 2 ሥራህን በእግዚአብሔር ፊት ፍጹም ሆኖ ስላላገኘሁት
ንቃ፤ሊሞቱ የተቃረቡትን የቀሩትን ነገሮች አጽና። 3 እንግዲህ ምን እንደተቀበልህና ምን እንደሰማህ አስታውስ፤ጠብቀው፤ንስሓም ግባ። ነገር ግን ባትነቃ ፥እንደ
ሌባ እመጣለሁ፤በምን ሰዓት እንደምመጣብህም አታውቅም። 4 ነገር ግን በሰርዴስ ልብሳቸውን ያላቆሸሹ ጥቂት ሰዎች አሉ። የተገባቸውም ስለ ሆነ፥ ነጭ
ልብሳቸውን ለብሰው ከእኔ ጋር ይሄዳሉ። 5 ድል የሚነሳ ነጭ ልብስ ይለብሳል፤ስሙን ከሕይወት መጽሐፍ ፈጽሞ አልደመስሰውም፤ይልቁን በአባቴና በመላእክቱ
ፊት ለስሙ እመሰክራለሁ። 6 ጆሮ ካለህም መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት ይሚናገረውን ስማ።» 7 «በፊላደልፍያ ላለው ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ
ጻፍ፤ የዳዊት መክፈቻ ያለው፥የሚከፍት እርሱ የከፈተውን ማንም የማይዘጋ፥የሚዘጋ እርሱ የዘጋውን ማንም ሊከፍት የማይችል ቅዱስና እውነተኛ የሆነው እርሱ
እንዲህ ይላል፤ 8 ሥራህን ዐውቃለሁ፤እነሆ፤ማንም ሊዘጋው የማይችል የተከፈተ በር በፊትህ አድርጌአለሁ። ዐቅምህ ትንሽ እንደሆነ አውቃለሁ፤ይሁን እንጂ ቃሌን
ጠብቀሃል፤ስሜንም አልካድህም። 9 እነሆ፤አይሁድ ሳይሆኑ አይሁድ ነን የሚሉት እነዚያ ከሰይጣን ማኅበር የሆኑት ውሸተኞች ናቸው። እነርሱንም እኔ እንደ
ወደድሁህ ያውቁ ዘንድ መጥተው በእግርህ እንዲወድቁ አደርጋለሁ። 10 በትዕግሥ እንድትጸና የሰጠሁህን ትእዛዜን ስለ ጠበቅህ ፥በምድር የሚኖሩትን ይፈትን
ዘንድ በዓለም ላይ ሁሉ ሊመጣ ካለው የፈተና ሰዓት እጠብቅሃለሁ። 11 በቶሎ እመጣለሁ፤አክሊልህን ማንም እዳይወስድብህ፥ያለህን አጥብቀህ ያዝ። 12
ድል የሚነሻውን በአባቴ ቤተ መቅደስ ዐምድ አደርገዋለሁ፤ ከዚያ በፍጹም አይወጣም። እርሱ ላይ የአምላኬን ከተማ ስም፣ ማለት ከሰማይ ከእግዚአብሔር
ዘንድ የምትወጣውን የአዲሲቱ ኢዩሳሌምን ስም ደግሞ አዲሱ ስሜን እጽፋለሁ። 13 ጆሮ ያለው መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያን የሚለውን የስማ።” 14
«በሎዶቅያ ላለው ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፤ "ይህም በእግዚአብሔር ፍጥረት ላይ ገዥ እንዲሁም እውነተኛና ታማኝ ምስክር ከሆነው ቃሉም
አሜን ከሆነው የተነገረ ነው፤ 15 ሥራህን አውቃለሁ፤በራድ ወይም ትኩስ አይደለህም። በራድ ወይም ትኩስ ብትሆን ኖሮ መልካም ይሆን ነበር። 16 እንግዲህ
ትኩስ ወይም በራድ ሳትሆን በመካከል ለብ ስላልህ ከአፌ ልተፋህ ነው። 17 «እኔ ሀብታም ነኝ፤ብዙ ገንዘብ አለኝ፤የጎደለኝ ምንም ነገር የለም» ትላለህ፤ነገር
ግን እጅግ ጎስቋላ፥ምስኪን፥ድኻ፥ዕውርና የተራቆትህ እንደሆንህ አታውቅም። 18 ሀብታም ትሆን ዘንድ በእሳት የተፈተነውን ወርቅ ከእኔ እንድትገዛ፥የራቁትነትህን
ሐፍረት ለመሸፈን ነጭ ልብስ እንድትለብስ፥አጥርተህ ለማየትም ዐይንህን እንድትኳል እመክርሃለሁ። 19 እኔ የምወዳቸውን እንዴት መኖር እንደሚገባቸው
ያውቁ ዘንድ እቀጣቸዋለሁ፤ አስተምራቸዋለሁም። ስለዚህ ትጋ፤ንስሓም ግባ። 20 እነሆ፤በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ። ማንም ድምጼን ሰምቶ ቢከፍትልኝ ወደ ቤቱ
እገባለሁ፤ከእርሱ ጋር እበላለሁ፤እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል። 21 እኔ ድል እንደነሳሁና በዙፋኑ ላይ ከአባቴ ጋር እንደተቀመጥሁ፥ድል ለሚነሳም በዙፋኔ ላይ ከእኔ
ጋር የመቀመጥን መብት እሰጠዋለሁ። 22 መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚናገረውን ጆሮ ያለው ይስማ።»

Revelation 3:1

ራዕይ 3፡1-2
ሰርዴስ ይህንን በ REV 1:11. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። ቃል "እነዚህ የ ቃል ናቸው" ሥራህ ፍጹም ሆኖ አላገኘሁትም "ያደረከው ነገር ሙሉ ሆኖ አላገኘሁትም"

Revelation 3:3

ራዕይ 3፡ 3-4
ንቃ ይህ የሚያመለክተው ትክክለኛ ነገር ለማድረግ መነሳትን ነው። እንደ ሌባ እመጣብሃለሁ ሌባ በማይታወቅ ሰዓት እንደሚመጣ ሁሉ ኢየሱስም ባልተጠበቀ ሰዓት ይመጣል። ልብሳቸውን ማቆሸሽ የለባቸውም ቆሻሻ ልብስ የሚያመለክተው በሕይወታቸው ውስጥ ያለውን ኃጢአት ነው። ነጭ መልበስ ነጭ ልብስ ንጹሕ ሕይወትን ያመለክታል።

Revelation 3:5

ራዕይ 3፡ 5-6
ድል የነሣው "ያሸነፈ ማንኛውም ሰው" ነጭ ልብስ መልበስ ነጭ ልብሽ ንጹሕ ሕይወትን ይወክላል። ጆሮ ያለው ይስማ . . . ቤተ ክርስቲያናት ይህንን በ REV 3:7. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት።

Revelation 3:7

ራዕይ 3፡ 7-8
ፊልድልፍያ ይህንን በ REV 1:11. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። የዳዊት ቁልፍ “ቁልፍ” መንፈሳዊ ስልጣንን ወይም ኃይልን ያመለክታል። የተከፈተ በር ይህ እግዚአብሔርን የማገልገል ዕድልን ይወክላል። ያልካዱት አማራጭ ትርጉም: "ያልካዱት" የእኔ ስም "እኔ"

Revelation 3:9

ራዕይ 3፡ 9-11
የሴጣን ምኩራብ . . . አይሁድ ሆነው ያልሆኑት ይህንን በ REV 2:9. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። መስገድ ይህ የአምልኮ ሳይሆን የመገዛት ምልክት ነው። በእግርህ ፊት "በአንተ ፊት" እነርሱን ለመፈተን "እነርሱን ለመፈተን" አጥብቀህ ያዝ "በማመን ቀጥል"

Revelation 3:12

ራዕይ 3፡ 12-13
ድል የነሣው አማራጭ ትርጉም: "ያሸነፈ ማንኛውም ሰው" በእኔ አምላክ ቤተ መቅደስ ውስጥ ያለ ምሰሶ “ምሰሶ” በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ ጠቃሚ እና ቋሚ የሆነን ነገር ይወክላል።

Revelation 3:14

ራዕይ 3፡ 14-16
ሎዶቅያ ይህንንን በ REV 1:11. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። የአሜን ቃላት ዮሐንስ ለኢየሱስ ክርስቶስ አሜን የሚል ሌላ ስም ይሰጠዋል። አማራጭ ትርጉም: "እነዚህ አሜን ተብሎ የሚጠራው ቃላት ናቸው።" በራድ ወይም ትኩ እነዚህ ሁለት የተለያዩ መንፈሳዊ ፍላጎት ጽንፎችን ያሳያሉ። “በራድ” መሆን ሙሉ ለሙሉ እግዚአብሔር መቃወም ሲሆን፣ “ትኩስ” መሆን ማለት ደግሞ እግዚአብሔርን ለማገልገል ከፍተኛ ቅናት ያለው ሰው መሆን ማለት ነው። ለብ ያለ "በጥቂቱ የሞቀ።" ይህ በተወሰነ ደረጃ መንፈሳዊ ፍላጎር ወይም እምነት ያለውን ሰው የሚያሳይ ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Revelation 3:17

ራዕይ **3**፡ **17**-**18**
ጐስቋላና ምስኪንም ድሀም ዕውርም የተራቆትህም እነዚህ ቃላት በጣም መጥፎ በሆነ መንፈሳዊ ሁኔታ ውስጥ ያለን ነገር ግን በመጥፎ ሁኔታ ውስጥ መሆናቸውን የማያውቁ ሰዎችን ያመለክታሉ። ባለ ጠጋ እንድትሆን ይህ በመንፈሳዊነት ንጹሕ መሆንን እና ከእግዚአብሔር ጋር መልካ ግንኙነት መኖርን ያመለክታል። ጥሩ ነጭ ልብስ ነጭ ልብስ መንፈሳዊ ንጽሕናን ይወክላል።

Revelation 3:19

ራዕይ **3**፡ **19**-**20**
ቅና ንሰሓም ግባ "በቁም ነገር ንሰሓ ግባ" እኔ በደጅ ቆሜ መዝጊያ በሩን አንኳኳለሁ “መዝጊያ በር” ክርስቶስ ልገባበት የሚፈልገውን ሕይወታችንን ወይም ነፈሳችንን ያመለክታል። ድምፄን ይሰማሌ “ድምፅ” የክርስቶስን ጥሪ ይወክላል። በሩን ክፈቱ ይህ ክርስቶስን ለመቀበል መወሰን እና ወደ ውስጥ እንዲገባ መጋዘበዝን ያመለክታል። ከእርሰሱ ጋር መብላት ይህ ግንኙነትን፣ ጓደኝነትን፣ ሕብረትን ያመልክታል።

Revelation 3:21

ራዕይ **3**፡ **21**-**22**
ድል የነሣው ይህንን በ REV 2:7 ላይ ምን ብለህ አንደተረጎምከው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም: "አሸናፊ የሆነ ማንኛውም ሰው።". በዙፋኔ ላይ ከእኔ ጋር ይቀመጣል። በዙፋን ላይ መቀመጥ ማለት መግዛት ማለት ነው። ጆሮ ያለው ይስማ ይህን በ REV 2:7. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 4

1 ከእነዚህ ነገሮች በኋላ እነሆ የተከፈተ በር በሰማይ አየሁ። እንደ መለከት ድምፅ ሆኖ ሲናገረኝ የነበረው የመጀመሪያው ድምፅ፥«ወደዚህ ና! ከእነዚህ ነገሮች
ሁሉ በኋላ የሚሆነውን አሳይሃለሁ።» አለ። 2 ወዲያው በመንፈስ ነበርሁ፤በሰማይ ዙፋን ተዘርግቶ አየሁ፤በዙፋኑም ላይ አንድ የተቀመጠ አካል ነበር። 3
በዙፋኑም ላይ ተቀምጦ የነበረው መልኩ የኢያስጲድንና የሰርዲኖን ዕንቁ ይመስል ነበር። በዙፋኑም ዙሪያ የመረግድ ዕንቁ የመሰለ ቀስተ ደመና ነበር። 4
በዙፋኑም ዙሪያ ሃያ አራት ዙፋኖች ነበሩ፤በእነዚህም ዙፋኖች ላይ ነጭ ልብስ የለበሱና በራሳቸውም ላይ የወርቅ አክሊል የደፉ ሃያ አራት ሽማግሌዎች
ተቀምጠው ነበር። 5 ከዙፋኑም የመብረቅ ብልጭታና የነጎድጓድ ድምፅ ወጣ። በዙፋኑም ፊት ሰባት መብራቶች ይበሩ ነበር፤እነዚህም ሰባቱ የእግዚአብሔር
መንፈሶች ናቸው። 6 እንደዚሁም በዙፋኑ ፊት እንደ መስተዋት እጅግ የጠራ ባሕር ነበር። በዙፋኑም ዙሪያ ሁሉ ከፊትና ከኋላ በዐይን የተሞሉ አራት ሕያዋን
ፍጡራን ነበሩ። 7 የመጀመሪያው ሕያው ፍጡር አንበሳ ሲመስል፥ሁለተኛው ሕያው ፍጡር ጥጃ ይመስል ነበር፤ሦስተኛው ሕያው ፍጡር የሰውን ፊት የሚመስል
ፊት ነበረው፤አራተኛው ሕያው ፍጡር ደግሞ የሚበር ንስር ይመስል ነበር። 8 አራቱም ሕያዋን ፍጡራን እያንዳንዳቸው ስድስት ክንፍ ነበራቸው፤ከላይና ከሥርም
በዐይኖች የተሞሉ ነበሩ። እነርሱም ቀንና ሌሊት፥ «ቅዱስ፥ቅዱስ፥ቅዱስ፥ በሁሉም ላይ የሚገዛ፥የነበረና ያለ፥ወደፊትም የሚመጣው ጌታ አምላክ» ማለትን
አያቋርጡም ነበር። 9 ሕያዋን ፍጡራኑም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠውና ከዘላለም እስከ ዘላለም ለሚኖረው ክብር፥ ሞገስና ምስጋና በሚሰጡበት ጊዜ፥ 10 ሃያ
አራቱ ሽማግሌዎች በዙፋኑ ላይ በተቀመጠው ፊት በግምባራቸው ተደፍተው ከዘላለም እስከ ዘላለም ለሚኖረው ሰገዱ፤አክሊላቸውንም በዙፋኑ ፊት
አስቀምጠው፥ 11 «ጌታችንና አምላካችን ሆይ፤አንተ ሁሉንም ነገር ስለፈጠርህ፥በፈቃድህ ስለፈጠርሃቸውና እንደዚያም ሆነው ስለተገኙ ክብር፥ሞገስ፥ኀይልም
ልትቀበል ይገባሃል።» ይሉ ነበር።

Revelation 4:1

ራዕይ 4፡ 1-3
ከእነዚህ ነገሮች በኋላ የሐንስ ኢየሱስ ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያት የተናገረውን ከሰማ በኋላ። (REV 2:1-3:22). በሰማይ ያለው ያ መዝጊያ በር ተከፈተ አማራጭ ትርጉም: "ወደ ሰማይ መግቢያ በር" የኢያስጲድንና የሰርዲኖን እነዚህ በመጠኑም ቢሆን ውድ ድንጋዮች ናቸው፡ ይሁን እንጂ ምን አይነት ቀለም እንዳላቸው ግን በእርግጠኝነት ማናገር አንችልም። ቀስተ ዳመና የጸሐይ ብርሃን ከኋላቸው ሆኖ ከፊታቸው ደግሞ ዝናብ ስዘንብ ሰዎች የሚመለከቱት ቀለማት ናቸው። መረግድ አረንጓዴ ቀለም ያለው በተወሰነ መልኩም ቢሆን ውድ የሆነ ድንጋይ ነው።

Revelation 4:4

ራዕይ 4፡ 4-5
የመብረቅ ብልጭታ በቋንቋችሄ የመብረቅ ብልጭታ መታየቱን ለማመልከት የሚያገለግል ቃልን ተጠቀሙ። መብረቅ እና የነጎድጓድ ድምፅ "እንደ ነጎድጓድ ያለ ድምፅ"

Revelation 4:6

ራዕይ 4፡ 6-6
ብርጭቆ ሙሉ ለሙሉ ግልጽ የሆነ ነገር፣ አማራጭ ትርጉም: "ብርጭቆ" ወይም "በረዶ።"

Revelation 4:7

ራዕይ 4፡ 7-8
የነበረ፣ ያለ እና የሚመጣው እግዚአብሔር ሁል ጊዜ የሚኖር ነው።

Revelation 4:9

ራዕይ 4፡ 9-11
ከዘላለምም እስከ ዘላለም በሕይወት ለሚኖረው “ከዘላለም እስከ ዘላለም” ማለት እርስ “ለዘላለም” ይኖራል ማለት ነው። ጌታችን እና አምላካችን ተናጋሪዎች እንጂ ሰሚዎች አይደሉም ሆነዋል እንዲሁም ተፈጠትረዋል “ሆነዋል” እና “ተፈጥረዋል” የሚለው ቃል ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን እግዚአብሔር ሁሉን ነገር እንደፈጠረ አጽኖት ሰጥተው የሚገልጹ ናቸው።

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 5

1 በዙፋኑም ላይ በተቀመጠው ቀኝ እጅ ከፊትና ከጀርባ የተጻፈበት በሰባትም ማኅተም የታሸገ ጥቅልል መጽሓፍ አየሁ። 2 አንድ ብርቱ መልአክ፥«መጽሓፉን
ሊከፍት፥ ማኅተሙን ሊፈታ የተገባው ማን ነው?» ብሎ በታላቅ ድምፅ ሲያውጅ አየሁ። 3 በሰማይ ቢሆን በምድር ወይም ከምድር በታች መጽሓፉን ሊከፍት
ወይም ሊያነብ ማንም አልቻለም። 4 መጽሓፉን ሊከፍት ወይም ሊያነብ የተገባው ማንም ስላልተገኘ፥አምርሬ አለቀስሁ። 5 ነገር ግን ከሽማግሌዎች
አንዱ፥«አታልቅስ፤እነሆ! ከዳዊት ሥር፥ከይሁዳ ነገድ የሆነው አንበሳ መጽሓፉን ይከፍትና ሰባቱንም ማኅተም ይፈታ ዘንድ ድል ነስቷል» አለኝ። 6 በዙፋኑና
በአራቱ ሕያዋን ፍጡራን መካከል እንዲሁም በሽማግሌዎች መካከል አንድ ታርዶ የነበረ የሚመስል በግ ቆሞ አየሁ። እርሱም ሰባት ቀንዶችና ሰባት ዐይኖች
ነበሩት፤እነዚህም በምድር ሁሉ ላይ የተላኩ ሰባቱ የእግዚአብሔር መንፈሶች ናቸው። 7 ሄዶም በዙፋን ላይ ከተቀመጠው ቀኝ እጅ ጥቅልል መጽሓፉን ወሰደ። 8
ጥቅልል መጽሓፉንም በሚወስድበት ጊዜ አራቱ ሕያዋን ፍጡራን እና ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች በበጉ ፊት በግምባራቸው ተደፉ፤ እያንዳንዳቸውም በገና እና
የቅዱሳን ጸሎት የሆነው ዕጣን የሞላበት የወርቅ ዕቃ ይዘው ነበር። 9 እነርሱም እንዲህ የሚል አዲስ ቅኔ ዘመሩ፤«መጽሓፉን ትወስድ እና ማኅተሞቹን ተፈታ
ዘንድ ይገባሃል፤ ታርደሃልና በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ፥ከቋንቋ ሁሉ፥ ከሕዝብና ከአገር ሁሉ ሰዎችን ዋጅተሃል። 10 አምላካችንን ያገለግሉ ዘንድ
መንግሥትና ካህናት አደረግሃቸው፤እነርሱም በምድር ላይ ይገዛሉ።» 11 ከዚያም በኋላ ስመለከት፥በዙፋኑ፥በሕያዋኑ ፍጡራን እና በሽማግሌዎች ዙሪያ የብዙ
መላእክት ድምፅ ሰማሁ፤ቁጥራቸውም ሁለት መቶ ሚሊዮን ነበር። 12 እነርሱም በታላቅ ድምፅ፥«የታረደው በግ ኀይልና ባለጠግነት፥ጥበብና ብርታት፥ምስጋና
እና ክብር ሊቀበል ይገባዋል።» አሉ። 13 በሰማይና በምድር፥ከምድር በታች እንዲሁም በባሕር ላይ ያለ ፍጥረት ሁሉ በእነርሱም ውስጥ ያለ ሁሉ
፥«ምስጋና፥ክብር፥ውዳሴ፥የመግዛትም ኀይል ከዘላለም እስከ ዘላለም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው እና ለበጉ ይሁን።» ሲሉ ሰማሁ፤ 14 አራቱ ሕያዋን
ፍጡራን፥«አሜን» አሉ፤ሽምግሌዎችም በግምባራቸው ተደፍተው ሰገዱ።

Revelation 5:1

ራዕይ 5፡ 1-2
ከዚያም ተመለከትኩ "እነዚህ ነገሮች ካየሁ በኋላ ይህንን አየሁ" በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው ይህ በ REV 4:2-3. ላይ ከተገለጸው ጋር “ተመሳሳይ ነው”። ሲያውጅ ከዚህ በመቀጠል ከቀረበው ጥያቄ ጋር የሚስማማ ቃልን ተጠቀም።

Revelation 5:3

ራዕይ 5፡ 3-5
በሰማይ ወይም በምድር ወይም ከምድር በታች "በዬትኛውም የተፈጠረ ሥፍራ" ወይም "በሁሉም ሥፍራ።" ይህ እግዚአብሔር እና መለአክቱ፣ ሰዎች የሚኖሩበት እና የሞቱት የሚኖሩበት ሥፍራ ነው። ተመልከት አማራጭ ትርጉም: "አድምጥ" ወይም "አሁን ልነገርህ ስላለሁት ነገር ትኩረት ሰጥተህ አድምጠኝ"

Revelation 5:6

ራዕይ 5፡ 6-7

Revelation 5:8

ራዕይ 5፡ 8-8
ወሰደው "በጉ ወሰደው" እያንዳንዳቸው አማራጭ ትርጉሞች 1) "እያንዳንዱ ሽማግሌዎች እና ሕያዋን ፍጥረታት" ወይም 2) "እያንዳንዱ ሽማግሌዎች።"

Revelation 5:9

ራዕይ 5፡ 9-10
አንተ ታርደሃልና አማራጭ ትርጉም: "አንተን አረደዋልና" ታርዷል በቋንቋችሁ ውስጥ ለመስዋእትነት የሚቀርቡ እንስሳትን መሰዋትን የሚያመለክት ቃል ካለ በዚህ ሥፍራ ይህን ቃል ለመቀበል ሞክሩ። ለእግዚአብሔር ሰዎችን ገዝተሃል። "ሰዎች የእግዚአብሔር መሆን ይችሉ ዘንድ አስፈላጊውን ዋጋ ከፍለሃል።" ገዝተሃል ይህ ሌላ ሰው የተከፈለውን ዋጋ ወስዷል የሚል ትርጉም ሊኖረው አይገባም። አማራጭት ትርጉም: “ዋጅተሃል” (DB)። ከነገድ፣ ከቋንቋ፣ ከሕዝብ እና ከሀገር ሁሉ ሰዎችን ለእግዚብሔር አማራጭ ትርጉም: "ሁሉንም ዓይነት ሰዎች" ወይም "ሰዎችን ከሁሉም ሥፍራ"

Revelation 5:11

ራዕይ 5፡ 11-12
200,000,000

Revelation 5:13

ራዕይ 5፡ 13-14
በሰማይ እና በምድር እንዲሁም ከምድር በታች ይህንን በ REV 5:3. ላይ ምን ብለህ እደተረጎምክ ተመለክት። በባሕር ላይ በጀልባዎች

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 6

1 ከዚህም በኋላ በጉ ከሰባቱ ማኅተሞች አንዱን ሲከፍት አየሁ፤ከአራቱ ሕያዋን ፍጡራን አንዱ እንደ ነጎድጓድ ባለ ድምፅ «ና!» ሲል ሰማሁ። 2 አየሁም ፤እነሆም አንድ ነጭ ፈረስ አየሁ፤ባላባዩ ላይ የተቀመጠውም ቀስት ይዞ ነበር፤አክሊልም ተሰጠው። እንደ ድል አድራጊ ሆኖ ድል ይነሳ ዘንድ ወጣ። 3 በጉ ሁለተኛውን ማኅተም በሚከፍትበት ጊዜ፥ሁለተኛው ሕያው ፍጡር«ና!» ሲል ሰማሁ። 4 ከዚያም ደማቅ ቀይ ፈረስ ወጣ፤በፈረሱም ላይ ለተቀመጠው ሰዎች እርስ በርስ ይተራረዱ ዘንድ ሰላምን ከምድር እንዲያስወግድ ሥልጣን ተሰጠው፤ትልቅ ሰይፍም ተሰጠው። 5 በጉ ሦስተኛውን ማኅተም በሚከፍትበት ጊዜ፥ ሦስተኛው ሕያው ፍጡር «ና!» ሲል ሰማሁ፤ ጥቁር ፈረስ አየሁ፤በፈረሱም ላይ የተቀመጠው በእጁ ሚዛን ይዞ ነበር። 6 ከአራቱ ሕያዋን ፍጡራን የመጣ የሚመስል ድምፅ፥«አንድ እርቦ ስንዴ በዲናር፥ሦስት እርቦ ገብስም በዲናር፤ ነገር ግን ዘይቱንና ወይኑን አትጉዳ» ሲል ሰማሁ። 7 በጉ አራተኛውን ማኅተም በሚከፍትበት ጊዜ የአራተኛው ሕያው ፍጡር ድምፅ «ና!» ሲል ሰማሁ። 8 ከዚያም በኋላ ግራጫ ፈረስ አየሁ፤በላዩም ላይ የተቀመጠው ስሙ ሞት ተብሎ ይጠራ ነበር፤ሲኦልም ይከተለው ነበር። ሞትና ሲኦልም የምድርን አንድ አራተኛ በሰይፍ፥በረሃብ፥ በበሽታ፥በዱር አራዊት እንዲገድሉ ሥልጣን ተሰጣቸው። 9 በጉ አምስተኛውን ማኅተም በሚከፍትበት ጊዜ ስለ እግዚአብሔር ቃልና በጽናት ስለ ጠበቁት ምስክርነት የተገደሉትን ሰዎች ነፍሶች ከመሠዊያው በታች አየሁ። 10 እነርሱም በታላቅ ድምፅ፥«በሁሉም ላይ የምትገዛ ቅዱስና እውነተኛ የሆንህ ጌታ አምላክ ሆይ፤በምድር በሚኖሩት ላይ የማትፈርደው፥ ደማችንስ የማትበቀለው እስከ መቼ ድረስ ነው?» በማለት ይጮኹ ነበር። 11 ከዚያም በኋላ ለእያንዳንዳቸው ነጭ ልብስ ተሰጣቸው፤እነርሱ እንደ ተገደሉ፥ ገና የሚገደሉ አገልጋይ ጓደኞቻቸው፥ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው ቁጥር እስኪሞላ ድረስ ለጥቂት ጊዜ እንዲታገሱ ተነገራቸው። 12 በጉ ስድስተኛውን ማኅተም በሚከፍትበት ጊዜ አየሁ፤ እነሆ ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ። ፀሐይም እንደ ጥቁር ጨርቅ ጠቆረች፤ ጨረቃም ሙሉ በሙሉ እንደ ደም ቀላች። 13 የበለስ ዛፍ ጎይለኛ ነፋስ በሚወዘውዛት ጊዜ በላይዋ ያለ ያልበሰለ ፍሬ እንደሚረግፍ ሁሉ የሰማይ ከዋክብት ወደ ምድር ረገፉ። 14 ሰማይም እንደ ብራና እየተጠቀለለ ተወገደ፤ እያንዳንዱ ተራራና ደሴት ከስፍራው ተነቀለ። 15 ከዚያም በኋላ የምድር ነገሥታት፥ታላላቅ ሰዎች፥ የጦር መኮንኖች፥ ሀብታሞች፥ብርቱዎች፥ ባሮችና ጌቶች ሁሉ በዋሻዎችና በተራሮች ዐለት ውስጥ ተሸሸጉ። 16 ለተራሮችና ለዐለቶችም እንዲህ ሲሉ ተናገሩ፤«በላያችን ላይ ውደቁ፤ በዙፋኑ ላይ ከተቀመጠው ፊት፥ከበጉም ቁጣ ሰውሩን 17 ታላቁ የቁጣቸው ቀን ስለ መጣ ማን መቆም ይችላል?»

Revelation 6:1

ራዕይ **6**፡ **1-2**
እኔ “እኔ” የሚለው ቃል በሁሉም ሥፍራዎች ላይ የሚያመለክተው ጸሐፊውም የሐንስ ነው። ሰባቱን ማህተሞት የፈታህ ከሰባቱ ማህተሞት መካከል በቁጥር አንድ ላይ የሚገኘውን የፈታህ

Revelation 6:3

ራዕይ **6**፡ **3-4**
ሁለተኛውን ማህተም የፈታህ በሁለት ቁጥር ላይ የሚገኘውን ማህተም የፈታህ
የቀይ ዳማ "ደማቅ ቀይ" ፈረስ ላይ ለተቀመጠው ፈቃድ ተሰጠው አማራጭ ትርጉም: "እግዚብሔር ፈረስ ላይ ለተቀመጠው ፈቃድ ሰጠው"

Revelation 6:5

ራዕይ **6**፡ **5-6**
ሦስተኛውን ማህተም ፈታ በሦስተና ተራ ቁጥር ላይ የሚገኘውን ማህተም ፈታ
እርቦ ስንዴ ይህ የመሥፈሪያ ዓይነት ሲሆን ከአንድ ሊተር ጋር ይስተካከላል።
አንድ ዲናር ይህ ገንዘብ የአንድ ቀን ሥራ ደሞዝ ጋር እኩል ነው።

Revelation 6:7

ራዕይ **6**፡ **7-8**

Revelation 6:9

ራዕይ **6**፡ **9-11**
ከእምነታቸው የተነሣ አማራጭ ትርጉም: "አጥበቀው ያምኑ ነበር" ወይም "በጣም ያምናሉ"

Revelation 6:12

ራዕይ **6**፡ **12-14**
ፀሐይም እንደ ማቅ ጠጉር ጥቁር ሆነ፥ ፀሐይ በጣም ጠቆረች።

Revelation 6:15

ራዕይ **6**፡ **15-17**
ጀነራሎች የጦር አዛዦችን የሚያመልክ ቃል ነው። በዋሻዎች ውስጥ ተሸሸጉ አማራጭ ትርጉም: "በተራሮች መካከል በሚገኙ ትልልቅ ዋሻዎች ውስጥ ተሸሸጉ" ወይም "በምድር ውስጥ በተቆፈሩ ምሽጎች ውስጥ ተሸሸጉ"
የእርሱን ፊት “እርሱ” የሚለው ተውላጠ ስም የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 7

1 ከዚህ በኋላ አራት መላእክት በአራቱም የምድር ማዕዘን ቆመው አየሁ፤ እነርሱም በምድር ቢሆን በባሕር ላይ ወይም በማንኛውም ዛፍ ላይ ፈጽሞ ነፋስ
እንዳይነፍስ አራቱን የምድር ነፋሳትን አጥብቀው ይከለክሉ ነበር። 2 የሕያው አምላክ ማኅተም የያዘ ሌላ መልአክ ከምስራቅ ሲመጣ አየሁ። እርሱም ምድርንና
ባሕርን ይጎዱ ዘንድ ሥልጣን ወደ ተሰጣቸው ወደ አራቱ መላእክት በታላቅ ድምፅ እየጮኽ፥ 3 «በአምላካችን አገልጋዮች ግምባር ላይ ማኅተም እስክናደርግ
ድረስ ምድርንም ሆነ ባሕርን ወይም ዛፎችን እንዳትጎዱ» አለ። 4 ከእስራኤል ሕዝብ ነገድ ሁሉ የታተሙት ሰዎች ቁጥር አንድ መቶ አርባ አራት ሺህ እንደ ሆነ
ሰማሁ። 5 ከይሁዳ ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ ፥ከሮቤል ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ ፥ከጋድ ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥ 6 ከአሴር ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥ ከንፍታሌም
ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ ፥ከምናሴ ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ 7 ከስምዖን ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ ፥ከሌዊ ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥ከይሳኮር ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥ 8
ከዛብሎን ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥ከዮሴፍ ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥ከብንያም ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ ታተሙ። 9 ከዚህ በኋላ ከሕዝብ፥ከነገድ፥ከወገንና ከቋንቋ
ሁሉ የመጡ ቁጥራቸው ማንም ሊቆጥረው የማይችል አጅግ ብዙ ሕዝብ ነጭ ልብስ ለብሰው፥ በእጃቸውም የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው በዙፋኑና በበጉ ፊት
ቆመው አየሁ። 10 በታላቅ ድምፅም «ማዳን፥ በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው የአምላካችንና የበጉ ነው!» እያሉ ይጮኹ ነበር። 11 መላእክቱም ሁሉ በዙፋኑ እና
በሽማግሌዎች ዙሪያ እንዲሁም በአራቱ ሕያዋን ፍጡራን ዙሪያ ቆመው ነበር፤እነርሱም በመሬት ላይ ወድቀው በዙፋኑም ፊት በግምባራቸው ተደፍተው
ለእግዚአብሔር እየሰገዱ፥ 12 «አሜን! ውዳሴ፥ ክብር፥ጥበብ፥ምስጋና፥ኀይልና ብርታትም ከዘላለም እስከ ዘላለም ለአምላካችን ይሁን፤አሜን» ይሉ ነበር። 13
ከዚያም በኋላ ከሽማግሌዎች አንዱ፥«እነዚህ ነጭ ልብስ የለበሱ እነማናቸው ከየትስ የመጡ ናቸው?» በማለት ጠየቀኝ፤ 14 እኔም «ጌታ ሆይ፥አንተ
ታውቃለህ» አልሁት። እርሱም እንዲህ አለኝ፤«እነዚህ በታላቁ መከራ ውስጥ አልፈው የመጡ ናቸው፤ልብሳቸውንም በበጉ ደም አጥበው በማንጻት ነጭ
አድርገዋል። 15 ክዚህም የተነሳ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት መሆን ችለዋል፤ እርሱንም በመቅደሱ ውስጥ ቀንና ሌሊት ያመልኩታል። በዙፋኑም ላይ
የተቀመጠው ድንኳኑን በእነርሱ ላይ ይዘረጋል። 16 እነርሱም ከእንግዲህ አይራቡም፤አይጠሙምም። ፀሐይ አያቃጥላቸውም፤ ሙቀትም አያሰቃያቸውም። 17
ምክንያቱም በዙፋኑ መካከል ያለው በጉ እረኛቸው ይሆናል፤ወደ ሕይወት ውኃ ምንጭ ይመራቸዋል፤እግዚአብሔር እንባንም ሁሉ ከዐይኖቻቸው ያብሳል።»

Revelation 7:1

ራዕይ 7፡ **1**-**3**

Revelation 7:4

ራዕይ 7፡ **4**-**6**
የታተመው አማራጭ ትርጉም: "የእግዚአብሔር ምልክት ያለባቸው ሰዎች" 12,000 ከእያንዳንዱ ነገድ ዐሥራ ሁለት ሺህ 144,000 ከእያንዳንዱ ነገር ዐሥራ ሁለት ሺህ በዐሥራ ሁሉት ቡድኖች ነበሩ። የእስራኤል ነገዶች ሁሉም በእስራኤል ውስጥ ዐሥራ ሁሉት ነገዶች የነበሩ ሲሆን እያንዳንዱን በያዕቆብ ልጆች ስም ተሰይሟል።

Revelation 7:7

ራዕይ 7፡ **7**-**8**

Revelation 7:9

ራዕይ 7፡ **9**-**10**
ከዙፋኑ ፊት ቆሙ እንዲሁም በበጉ ፊት ቆሙ "በዙፋኑ እና በበጉ ፊት ቆሙ" ነጭ ልብስ በዚህ ሥፍራ “ነጭ” ቀለም የሚያመለክተው ንጽሕናን ነው። ድነት የበጉ . . . ለሆኑትነው "በዘፉኑ ላይ የተቀመጠው አምላካችን እና በጉ አድኖናል" ወይም "ድነት በዙፋኑ ላይ ከተቀመጠው እና ከበጉ ዘንድ መትቶልናል"

Revelation 7:11

ራዕይ 7፡ **11**-**12**
መላእክት ሁሉ . . . ሕያዋን ፍጥረታት "በዙፋኑ ዙሪያ የቆሙት ሁሉም መላእክት እና ሽማግሌዎች እንዲሁም አራቱ ሕያዋን ፍጥረታት" አራቱ ሕያዋን ፍጥረታት እነዚህ በ REV 4:6-8. ላይ አስቀድመው የተጠቀሰሱት አራቱ ፍጥረታት ናቸው። ምሳጋና፣ ክብር . . . ለአምላካችን ይሁን "አምላካችን ምስጋና፣ ክብር፣ ትበብ፣ ምስጋና፣ አክብሮት እና ኃይል ሁሉ ይገባዋል" ከዘላለም እስከ ዘላለም እነዚህ ሁለት ቃላት በመሠረታዊ ሀሳባቸው ተመሳሳይ ሲሆን አጽኖት የሚሰጡት ሕያዋን ፍጥረታት ሁሉ ለዘላለም እግዚአብሔርን እንደሚያመልኩት ነው።

Revelation 7:13

ራዕይ 7፡ **13**-**14**
ልብሳቸውን አጥበዋል እንዲሁም በበጉ ደም ነጭ አድርገዋል “ነጭ” ቀለም የሚያመለክተው ንጽሕናን ሲሆን “ደም” ብዙ ጊዜ ነገሮችን ለማንጻት ጥቅም ላይ ከሚውለው ከውሃ ጋር ተነጻጽሮ ቀርቧል። ንጽሕና የሚገኘው “በመታጠብ” ነው ወይም በክርስቶስ ደም በመሸፈን ነው።

Revelation 7:15

ራዕይ 7፡ **15**-**17**
እነርሱ . . . እነርሱ . . . እነርሱ እነዚህ ሁሉ ተውላጠስሞች የሚመለክቱት በታላቁ መከራ ውስጥ ያለፉትን ሰዎችን ነው። ፀሐይ አታሸንፋቸውም ይህ ማለት ፀሐይ ከሙቀቷ የጠነሣ ከእንግዲህ ወዲህ አታሰቃያቸውም።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 8

1 በጉ ሰባተኛውን ማህተም በፈታ ጊዜ በሰማይ ለግማሽ ሰዓት ያህል ጸጥታ ሆነ፤ 2 ከዚያም በእግዚአብሄር ፊት የቆሙ ስባት መላዕክትን አየሁ፡፤ሰባት መለከቶችም ተሰጣቸው። 3 ሌላም መልኣክ መጣ፤በእጁም ከወርቅ የተሰራ ጥና ይዞ ነበር።እርሱም በመሰዊያው አጠገብ ቆሞ ነበር።በዙፋኑ ፊት ባለው በወርቅ በተሰራ መሰዊያ ላይ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር የሚያቀርበው ብዙ ዕጣን ተሰጠው። 4 የእጣኑ ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር ከመልኣኩ እጅ ወደ እግዚአብሄር ወጣ፤ 5 መልኣኩም ጥናውን ወስዶ ከመሰዊያው በወስድው እሳት ሞላው ከዚያም በኃላ ወደ ምድር ወረወረው፤የነጎድጓድ ድምጽ፤መብረቅ፤የምድር መናወጥም ሆነ። 6 ሰባት መለከቶችን የያዙ ስባት መላዕክት መለከቶቻቸውን ለመንፋት ተዘጋጁ። 7 የመጀመሪያውም መልኣክ መለከቱን ነፋ፤ደም የተቀላቀለበት እሳትና በረዶ ሆነ። ይህም ወደ ምድር ተጣለ፤ ከዚህም የተነሣ የምድርም አንድ ሦስተኛ ተቃጠለ፤ የዛፎችም አንድ ሦስተኛ ተቃጠለ፤ የለመለመ ሣር ሁሉ ተቃጠለ። 8 ሁለተኛውም መልኣክ መለከቱን ነፋ፤ በእሳት የሚቃጠል ትልቅ ተራራ የሚመስል ነገር ወደ ባህር ተጣለ፤ የባህር አንድ ሦስተኛ ወደ ደም ተለወጠ። 9 በባህር ውስጥ ካሉ ህያዋን ፍጥረታት አንድ ሦስተኛ ሞቱ፤ የመርከቦችም አንድ ሦስተኛ ተደመሰሱ። 10 ሦስተኛውም መልኣክ መለከቱን ነፋ፤ እንደ ችቦ የሚቃጠል ታላቅ ኮከብ ከሰማይ ወደቀ፤ የወደቀውም በወንዞች አንድ ሦስተኛ በውሃ ምንጮች ላይ ነው። 11 የኮከቡም ስም እሬቶ ይባላል። የውኖችም አንድ ሦስተኛ መራራ ሆነ። ከውሃው መራራነት የተነሳ ብዙ ሰዎች ሞቱ። 12 አራተኛውም መልኣክ መልከቱን ነፋ፤የፀሐይ አንድ ሦስተኛ፣ የጨረቃ አንድ ሦስተኛ የኮከቦች አንድ ሦስተኛ ተመታ። ስለዚህ የእነርሱ አንድ ሦስተኛ ጨለመ፤ በዚህም ምክንያት የቀን አንድ ሦስተኛና የሌሊት አንድ ሦስተኛው ያለ ብርሃን ሆነ። 13 እነሆ በሰማይ መካከል ሲበርር የነበር አንድ ንስር በታላቅ ድምጽ፤ ሦስቱ መላእክት የቀሩትን መለከቶች ስለሚነፉ «በምድር ላይ ለሚኖሩ ወዮላቸው! ወዮላቸው! ወዮላቸው!» ሲል ሰማሁ።

Revelation 8:1

ራዕይ **8**፡ **1-2**
ሰባት መለከቶች ተሰጣቸው አማራጭ ትርጉሞች: 1) እግዚአብሔር ሰባት መለከቶችን ሰጣቸው ወይም 2) በጉ ሰባት መለከቶችን ሰጣቸው።

Revelation 8:3

ራዕይ **8**፡ **3-5**

Revelation 8:6

ራዕይ **8**፡ **6-7**
ወደ ምድር ተወረወሩ አማራጭ ትርጉም: "መለላእኩ ወደ ምድር ወረወረው።" አንድ ሦስተኛው እጅ ተቃጠለ፣ አንድ ሦተኛው ዛፍ ተቃጠል እንዲሁም ሁሉም አረንጓዴ ሣሮች ተቃጠሉ አማራጭ ትርጉም: "የምድር አንድ ሦስተኛው ተቃጠለ፣ የዛፎች አንድ ሦስተኛ ተቃጠለ እንዲሁም አረንጓዴ ሣሮቹ ተቃጠሉ"

Revelation 8:8

ራዕይ **8**፡ **8-9**
በእሳት የሚቃጠል ታላቅ ተራራን የሚመስል ነገር በባሕር ተጣለ፤ "መላእኩ በእሳት የሚቃየል ታላቅ ተራራን የሚመስል ነገር በባሕር ተጣለ" የባሕርም ሲሶው ደም ሆነ በባሕርም ከሚኖሩ ሕይወት ካላቸው ፍጥረቶች ሲሶው ሞተ የመርከቦችም ሲሶው ጠፋ። አማራጭ ትርጉም: "የባሕር ሲሶው ደም እንዲሆን አደረገ፤ በባሕር ውስጥ ከሚኖሩት ሕያዋን ፍጥረታት መካከል ሲሶው ሞቱ እንዲም የመርከቦቹ ሲሶው ጠፋ።" ደም ሆነ አማራጭ ትርጉሞች: 1) "እንደ ደም ሆኑ" 2) literally "became blood."

Revelation 8:10

ራዕይ **8**፡**10-11**
እና እንደ ችቦም የሚቃጠል ታላቅ ኮከብ ከሰማይ ወደቀ፥ "እና እንደ ችቦ የሚቃጠል ታላቅ ኮከብ ከሰማይ ወደቀ።" የታላቁ ኮከብ እሳት ልክ የሚቃጠል ችቦ ጋር ተመሳሳይነት አለው። ችቦ በአንድ በኩል መንደድ የሚችል ብርሃን የሚሰጥ እንጨት። የኮከቡም ስም እሬቶ ነው የኮከቡ ስም “እሬቶ” የሆነው መራራ ጣዕም ካለው ተክል ተነስቶ ነው። እሬቶ በኮከብ የተመረዘ። አማራጭ ትርጉም: “መራራ”

Revelation 8:12

ራዕይ **8**፡ **12-12**
የፀሐይ ሲሶ ተመታ አማራጭ ትርጉም: "የፀሐይን ሲሶ ጨለማ ዋጠው"

Revelation 8:13

ራዕይ **8**፡ **13-13**
ሊነፉ ያላቸው የሦስቱ መላእክት መለከት ስለሚቀረው ድምፅ በምድር ላይ ለሚኖሩት ወዮላቸው፥ ወዮላቸው፥ ወዮላቸው ሲል ሰማሁ። አማራጭ ትርጉም: "የመለከት ድምፅ እሰስካሁን ያላሰሙት ሦስቱ መላእክት ማሰማት ልጀምሩ ስለሆነ"

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 9

1 አምስተኛውም መልአክ መለከቱን ነፋ፤ አንድን ኮከብ ከሰማይ ወደ ምድር ሲወድቅ አየሁ። ኮከቡም የጥልቁ ጕድጓድ መክፈቻ ተሰጠው፤ 2 እርሱም ጥልቅ
የሆነውን ጕድጓድ ከፈተው፤ ጢስም ከታላቅ ምድጃ እንደሚወጣ ጢስ ሆኖ ከጕድጓዱ ወጣ፤ ከጕድጓዱ በሚወጣው ጢስ ምክንያት ፀሐይና አየር ወደ
ጨለማነት ተለወጡ፤ 3 ከጢሱም ውስጥ አንበጣዎች በምድር ላይ ወጡ፤የምድር ጊንጦችን ኀይል የመሰለ ኀይል ተሰጣቸው፤ 4 የምድርንም ሣር ሆነ
ማናቸውንም የለመለመ ተክል ወይም ማናቸውንም ዛፍ እንዳይጎዱ ተነገራቸው። መጉዳት የነበረባቸው ግን በግንባራቸው ላይ የእግዚአብሔር ማህተም
የሌለባቸውን ሰዎች ብቻ ነው። 5 እነርሱንም ቢሆን ለአምስት ወር ለማሰቃየት ብቻ እንጂ የመግደል ሥልጣን አልተሰጣቸውም። የእነርሱም ስቃይ ጊንጥ ሰውን
ነድፎ እንደሚሰማው ስቃይ ዐይነት ነበር። 6 በእነዚያ ቀናት ሰዎች ሞትን ይፈልጋሉ፤ነገር ግን አያገኙትም። ለመሞት በብርቱ ይሻሉ፤ ነገር ግን ሞት ከእነርሱ
ይሸሻል። 7 አንበጦቹ ለጦርነት እንደ ተዘጋጁ ፈረሶች ነበሩ። በራሳቸውም ላይ የወርቅ አክሊል የመሰለ ነገር ነበር፤ ፊታቸውም የሰው ፊት ይመስል ነበር። 8
የሴቶች ጠጕር የሚመስል ጠጕር ነበራቸው። ጥርሳቸው የአንበሳ ጥርስ ይመስል ነበር። 9 የብረት ጥሩር የሚመስልጥሩር ነበራቸው፤ የክንፎቻቸውም ድምፅ
ወደ ጦርነት የሚጋልቡ ብዙ ፈረሶችና ሰረገሎች የሚያሰሙትን ድምፅ ይመስል ነበር። 10 እንደ ጊንጥ መንደፊያ ያለው ጅራት ነበራቸው። ሰዎችንም በጅራታቸው
ባለ መንደፊያ ለአምስት ወር ለመጉዳት ስልጣን ነበራቸው። 11 በእነርሱም ላይ የጥልቁ ጕድጓድ መልአክ የሆነ ንጉሥ ነበራቸው። ስሙም በዕብራይስጥ
አብዶን ሲሆን በግሪክ ደግሞ አጶሊዮን ይባላል፥ 12 የመጀመሪያው ወዮ አልፎአል፥ልብ በል! ከዚህ በኋላ ሌላ ሁለት ጥፋቶች ይመጣሉ። 13 ስድስተኛውም
መልአክ መለከቱን ነፋ፥ በእግዚአብሔር ፊት ካለው በወርቅ ከተሰራው መሰዊያ ከቀንዶቹ ድምጽ ሲወጣ ሰማሁ። 14 ድምፁም መለከት የያዘውን ስድስተኛውን
መልአክ፣ «በታላቁ ወንዝ በኤፍራጥስ የታሰሩትን አራቱን መላእክት ፍታቸው» አለው። 15 ለዚያ ሰዓትና ለዚያ ቀን ለዚያ ወርና ለዚያ ዓመት ተዘጋጅተው
የነበሩት አራት መላእክት የሰዎችን አንድ ሦስተኛ እንዲገድሉ ተፈቱ። 16 የፈረሰኛው ሰራዊት ብዛት ሁለት መቶ ሚሊዮን ነበር።ቊጥራቸውንም ሰማሁ። 17
ፈረሶቹና በፈረሶቹ ላይ የሚጋልቡ በራእይ ያየኋቸው በዚህ ዐይነት ነበር፥ በደረታቸው ላይ የነበረው ጥሩር እንደ እሳት ቀይ፣ እንደ ያክንት (ጥቁር ሰማያዊ)፣ እንደ
ዲንም ቢጫ ነበር፥ የፈረሶቹ ራስ የአንበሳ ራስ ይመስል ነበር። ከአፋቸው እሳትና ጢስ ዲንም ይወጣ ነበር። 18 በእነዚህ ሦስት መቅሰፍቶች ማለትም ከአፋቸው
በወጣው እሳት፤ ጢስና ዲን የሰዎች አንድ ሦስተኛ ተገደለ። 19 የፈረሶቹ ኃይል በአፋቸውና በጅራታቸው ነበር፥ ምክንያቱም ጅራታቸው እባብ ይመስላል፥ ራስ
አላቸው፥ ሰውን የሚጎዱትም በእርሱ ነበር። 20 በእነዚያ መቅሰፍቶች ከመሞት የተረፉት ሰዎች ከክፉ ሥራቸው ንስሓ አልገቡም፤ አጋንንትንና ከወር፣ ከብር፣
ከናስ፣ ከድንጋይና ከእንጨት የተሠሩ፣ ማየት ወይም መሄድ የማይችሉትን ጣዖታት ማምለክንም አልተዉም። 21 እንዲሁም ከነፍሰ ገዳይነት ወይም ከሟርት፥
ከሴሰኛነትና፥ ከሌብነት ንስሓ አልገቡም።

Revelation 9:1

ራዕይ **9**፡ **1-2**
ጉድጓድ በምድር ውስጥ ያለ ረጅም እና ጠባብ መንገድ ጥልቅ እና ማብቂያ ያሌለው አማራጭ ትርጉም: "መጨረሻ ያሌለው ጥልቅ" ትልቅ ጢስ ከእሳቱ ላይ የሚነሳ በጣም ረጅም ጢስ

Revelation 9:3

ራዕይ **9**፡ **3-4**
አንበጣዎች መንጋ በብዛት የሚበሩ ነፍት የምድርም ጊንጦች ሥልጣን እንዳላቸው ሥልጣን ተሰጣቸው። ጊንጦች የመያዝ እና ሌሎች እንስሳትን በመርዝ የመበከል ኃይል አላቸው። ጊንጦች ንቦች መርዛቸው ከኋላ እንደሆነ ሁሉ እነዚህም መርዛማ መውጊያ ያላቸውን ትንንሽ እንስሳቶች ናቸው። ግንባር ከዐይን በላይ በፊት ላይ የሚገኝ።

Revelation 9:5

ራዕይ **9**፡ **5-6**
እነርሱ አንበጣቹ (REV 9:03) እነዚያ ሰዎች አንበጣዎቹ የሚነድፏቸው ሰዎች ሰዎች ነገር ግን መግረፍ ብቻ "ሰዎች፤ እነርሱ የተሰጣቸው ፈቃድ የመግረፍ ብቻ በው" ፍላጎት መሻት

Revelation 9:7

ራዕይ **9**፡ **7-9**
አንበጣዎች አንበጣዎቹ የተገለጹት ሰዎች ከሚያውቋቸው ነገሮች ጋር በማነጻጸር ነው።

Revelation 9:10

ራዕይ **9**፡ **10-12**
ጥልቅ እና መጨረሻ ያሌለው ይህንን በ REV 9:1. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። አብዶን . . . አጶልዮን ሁለቱም “ጥፋት” የሚል ትርጉም አላቸው።

Revelation 9:13

ራዕይ **9**፡ **13-15**
በወርቅ ከተሠራ መሠዊያ ቀንዶች እነዚህ በመሰዊያው አናት ላይ በአራቱም ማዕዘኖች የሚገኙ የቀንድ ቅርጽ ያላቸው ነገሮች ናቸው።

Revelation 9:16

ራዕይ **9**፡ **16-17**
200,000,00 ይህንን በ REV 5:11. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት።

Revelation 9:18

ራዕይ **9**፡ **18-19**
ጭራቸው እንደ እባብ ነው የፈረሶቹ ጭራ ከእባብ ጋር ተነጻጽሮ ቀርቧል። አማራጭ ትርጉሞች፡ 1) "ጭራቸው የእባብን ራስ ይመስላል"

Revelation 9:20

ራዕይ **9**፡ **20-21**
በእነዚህም መቅሠፍቶች ያልተገደሉት የቀሩቱ ሰዎች "መቅጸፍቶቹ ያልገደሏቸው" ያዩ ወይም ይሰሙ ወይም ይሄዱ ዘንድ ለማይችሉ ጣኦታት። አማራጭ ትርጉሞች፡ "ሕያው ያልሆኑ ነገሮች"

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **10**

1 ከዚህ በኋላ ሌላ ብርቱ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ። እርሱም ደመናን የለበሰ ነበር። በራሱም ዙሪያ ቀስተ ደመና ነበር። ፊቱ እንደ ፀሐይ እግሮቹ እንደ እሳት ዐምድ ነበሩ፤ **2** የተከፈተ ትንሽ ጥቅል መጽሐፍ በእጁ ይዞ ነበር፤ ቀኝ እግሩን በባህር ላይ ግራውንም በምድር ላይ አደረገ። **3** ከዚያም እንደሚያገሳ አንበሳ በመሰለ ታላቅ ድምጽ ጮኸ፤ በጮኸ ጊዜ፣ ሰባቱም ነጎድጓዶች ድምፃቸውን አሰሙ ፤ **4** ሰባቱ ነድጓዶች በተናገሩ ድምፃቸውን ባሰሙ ጊዜ፣ እኔ ልጽፍ አሰብሁ። ነገር ግን «ሰባቱ ነጎድጓዶች የተናገሩትን በምስጢር ያዘው እንጂ አትጻፈው» የሚል ድምጽ ከሰማይ ሰማሁ። **5** ከዚያም በባህርና በምድር ላይ ቆሞ ያየሁት መልአክ ቀኝ እጁን ወደ ሰማይ አነሣና **6** ዘላለም በሚኖረው ሰማይንና በእርሱ ያሉትን፣ ምድርንና በእርስዋ ያሉትን፣ ባህርንና በርስዋ ያሉትን በፈጠረው አምላክ ስም ማለ። እንዲህም አለ፤«ከእንግዲህ ወዲህ አይዘገይም **7** ነገር ግን ሰባተኛው መልአክ መለከቱን በሚነፋበት ቀን ለአገልጋዮቹ ለነቢያት በገለጠላቸው መሰረት የእግዚአብሔር ምስጢር ይፈጸማል።» **8** ከሰማይ የሰማሁት ድምጽ፣«በባህርና በምድር ላይ የቆመው መልአክ በእጁ የያዘውንና የተፈታውን ጥቅል መጽሐፍ ሂድና ውሰድ» ብሎ እንደገና ሲናገረኝ ሰማሁት»። **9** ወደ መልአኩም ሄጄ «ትንሹን ጥቅል መጽሐፍ ስጠኝ?» አልሁት። እርሱም «ውሰድና ብላ በሆድህም ውስጥ መራራ ይሆናል፤ በአፍህ ግን እንደ ማር ይጣፍጣል»አለኝ። **10** እኔም ትንሹን ጥቅል መጽሐፍ ከመልአኩ እጅ ወስጄ በላሁት፤ በአፌ እንደ ማር ጣፈጠ፤ ከበላሁት በኋላ ግን ሆዴ መራራ ሆነ። **11** ከዚህም በኋላ «ስለብዙ ሕዝቦች፤ አገራት፤ ልዩ ልዩ ቋንቋ ስለሚናገሩ ሰዎችና ሰለ ነገሥታት እንደ ገና ትንቢት መናገር አለብህ» ተብሎ ተነገረኝ።

Revelation 10:1

ራዕይ **10**፡ **1-2**

Revelation 10:3

ራዕይ **10**፡ **3-4**

Revelation 10:5

ራዕይ **10**፡ **5-7**
ከዘላለምም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ሆኖ በሚኖረው በዚህ ሥፍራ ላይ “እርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው። በውስጡ ያሉትን ሁሉ ይህ ሦስት ጊዜ ያኸል ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን የሚመለክተውም በአየር፣ በባሕር ወይም በምድር ላይ የሚኖሩትን ሁሉንም እጽዋት፣ እንስሳት እና ሰዎችን ነው። ይፈጸማል "ይህ ልሆን ነው"

Revelation 10:8

ራዕይ **10**፡ **8-9**
እኔ ይህ የሚያመለክተው ዮሐንስን ነው። መራራ የዚህ ነገር ትርጉሙ የመጽሐፉ መልእክት የሚያበሳጭ ወይም አስደሳች አይሆንም።

Revelation 10:10

ራዕይ **10**፡ **10-11**

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **11**

1 ከዚያም ለመለኪያ የሚያገለግል አንድ ረዥም ዘንግ ተሰጠኝ፤እንዲህም ተባልሁ፣«ተነሥተህ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ፥ መሰዊያውንና በዚያ
የሚያመለኩትንም ቍጠር። **2** ከቤተመቅደሱ ውጭ ያለውን አደባባይ ግን ተወው፤ እርሱ ለአሕዛብ የተሰጠ ስለ ሆነ አትለካው፥አሕዛብ ቅድስቲቱን ከተማ አርባ
ሁለት ወራት ይረግጧታል። **3** ሁለቱ ምስክሮቼ ማቅ ለብሰው ለ1260 ቀን ትንቢት እንዲናገሩ ሥልጣን እሰጣቸዋለሁ።» **4** እነዚህም በምድር ጌታ ፊት የቆሙ
ሁለቱ የወይራ ዛፎችና ሁለቱ መቅረዞች ናቸው፤ **5** ማንም እነርሱን ሊጎዳ ቢፈልግ እሳት ከአፋቸው ወጥቶ ጠላቶቻቸውን ይበላል፤ እነርሱን ሊጎዳ የሚፈልግ ሁሉ
የሚሞተው በዚህ ዐይነት ነው፥ **6** እነዚህ ምስክሮች ትንቢት በሚናገሩባቸው ቀናት ዝናብ እንዳይዘንብ ሰማይን ለመዝጋት ሥልጣን አላቸው፥ እንዲሁም ውሆችን
ወደ ደም ለመለወጥና በሚፈልጉበትም ጊዜ ሁሉ በማንኛውም ዓይነት መቅሰፍት ምድርን ለመምታት ሥልጣን አላቸው፡ **7** ምስክርነታቸውን በጨረሱ ጊዜ
ከጥልቁ ጕድጓድ የሚወጣው አውሬ ከእነርሱ ጋር ይዋጋል፤ ያሸንፋቸዋል ይገድላቸውማል። **8** ሬሳቸውም በምሳሌያዊ አጠራር ሰዶም ወይም ግብጽ ተብላ
በምትጠራው በታላቂቱ ከተማ አደባባይ ይጋደማል፤ ከተማይቱም የእነርሱ ጌታ የተሰቀለባት ናት፤ **9** ከልዩ ልዩ ወገን፥ ነገድ፥ ከልዩ ልዩ ቋንቋና ሕዝብ የሆኑ ሰዎች
ሶስት ቀን ተኩል ሬሳቸውን ይመለከታሉ፥ ሬሳቸውም እንዳይቀበር ይከለክላሉ። **10** ሁለቱ ነቢያት የምድርን ሰዎች ሁሉ አስጨንቀው ስለ ነበር፣ በእነርሱ ሞት
በምድር የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ደስ ይላቸዋል፤ በደስታም በዓል ያደርጋሉ፤ ስጦታም ይለዋወጣሉ። **11** ነገር ግን ሦስት ቀን ተኩል ካለፈ በኋላ፣ የሕይወት
እስትንፋስ ከእግዚአብሔር መጥቶ ወደ ሬሳዎቹ ይገባል፤ በእግራቸውም ይቆማሉ፤ የሚመለከቷቸውም ሰዎች ታላቅ ፍርሃት ይወድቅባቸዋል። **12** ከዚህ በኋላ
ሁለቱ ነቢያት፣ «ወደዚህ ውጡ» የሚል ታላቅ ድምጽ ከሰማይ ሰሙ፤ ጠላቶቻቸውም እየተመለከቷቸው በደመና ወደ ሰማይ ወጡ። **13** በዚያኑ ሰዓት ታላቅ
የምድር መናወጥ ሆነ፤ የከተማይቱም አንድ ዐሥረኛ ወደመ። በምድር መናወጥም ምክንያት ሰባት ሺህ ሰዎች ሞቱ፤ ከሞት የተረፉትም እጅግ ፈሩ፤ለሰማይም
አምላክ ክብርን ሰጡ። **14** ሁለተኛው ወዮ አልፎአል፤ልብ በል! ሦስተኛው ወዮ ፈጥኖ ይመጣል። **15** ሰባተኛውም መልአክ መለከቱን ነፋ፤በሰማይም«የዓለም
መንግሥት የጌታ አምላካችንና የእርሱ ክርስቶስ ሆናለች፤ እርሱም ለዘላለም ይነግሣል» የሚል ታላቅ ድምጽ ሰማሁ። **16** በእግዚአብሔርም ፊት በዙፋኖቻቸው
ላይ የተቀመጡት ሃያ አራቱም ሽማግሌዎች በግምባራቸው ተደፍተው ለእግዚአብሔር ሰገዱ፤ **17** እነርሱም እንዲህ አሉ፣«ያለህና የነበርህ፣ ሁሉን የምትችል፣
ጌታ እግዚአብሔር ሆይ ትልቁን ሥልጣንህን በእጅህ አድርገህ ስለ ነገሥህ እናመሰግንሃለን። **18** አሕዛብ ተቆጡ፤ ነገር ግን የአንተም ቁጣ መጣ ።በሙታን ላይ
የምትፈርድበት ዘመንም መጣ፤ለአገልጋዮችህ፣ ለነቢያት፣ ለቅዱሳን፣ ስምህንም ለሚያከብሩት ለታናናሾችና ለታላላቆች ሽልማታቸውን የምትሰጥበት ጊዜ
እንዲሁም ምድርን ያጠፏትን የምታጠፋበት ጊዜ ደረሰ።» **19** በሰማይም ያለው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ተከፈተ፤የእርሱም የቃል ኪዳን ታቦት በቤተ
መቅደሱ ውስጥ ታየ። መብረቅ የመብረቅ ድምጽ፣ነጎድጓድም፣የምድር መናወጥና ታላቅም ማዕበል ሆነ።

Revelation 11:1

ራዕይ **11**፡ **1-2**
ለእኔ ተሰጠኝ . . . ተነገረኝ በዚህ ሥፍራ ላይ “እኔ” እና “ለእኔ” ዮሐንስን የሚያመልክት ነው። መርገጥ አንድ ነገር የማይጠቅም መሆኑን ለማሳየት በእርሱ ላይ መረማመድ። አርባ-ሁለት ወራት ሁለት ወራት - አማራጭ ትርጉም: "42 ወራት"

Revelation 11:3

ራዕይ **11**፡ **3-5**
እነዚህ ሁለት ምስክሮች ሁለቱ የወይራ ዛፎች እና ሁለቱ መቅረዞች ናቸው እነዚህ ሁለት ምስክሮች ከዚህ በፊት የተጠቀሱት ሁለቱ የወይራ ዛፎች እና ሁለቱ መቅረዞቸ ናቸው።

Revelation 11:6

ራዕይ **11**፡ **6-7**
ምድርን በሁሉም ዓይነት መቅሰፍቶች መምታት ይህ በምድር ላይ ሁሉንም ዓይነት አስቸጋሪ ነገሮችን እንዲከሰት የሚያድርጉትን ያመለክታል። ጥልቅ እና ማለቂያ ያሌለው “ማለቂያ ያሌለው” የሚለው ቃል ትርጉሙ መጨረሻ ያሌለው ማለት ነው። እነዚህ ሁለት ቃላት የትልቀቱን መጠን ለማሳየት ጥቅም ላይ የዋሉ ናቸው።

Revelation 11:8

ራዕይ **11**፡ **8-9**
ሦስት ከግማሽ ቀናት "3 ሙሉ ቀናት እና አንድ ግማሽ ቀን: ወይም"3.5 ቀናት" ወይም "3 1/2 ቀናት"

Revelation 11:10

ራዕይ **11**፡ **10-12**
ሦስት ከግማሽ ቀናት "3 ሙሉ ቀናት እና አንድ ግማሽ ቀን: ወይም"3.5 ቀናት" ወይም "3 1/2 ቀናት"

Revelation 11:13

ራዕይ **11**፡ **13-14**
ሰበባት ሺኅ ሰዎች "7,000 ሰዎች"

Revelation 11:15

ራዕይ **11**፡ **15-15**

Revelation 11:16

ራዕይ **11**፡ **16-17**
ሃያ - አራት ሽማግሌዎች አራት ሽማግሌዎች - "24 ሽማግሌዎች"

በግምባራቸው ተደፍተው የሰውነታቸው የፊት ክፍል “ፌታቸው” ተብሎ ይገለጻል።

Revelation 11:18

ራዕይ **11**፡ **18-18**
ቁጣህ . . . አገልጋዮችህ . . . ስምህ “አንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው። የማያስፈልግ "ዝቅተኛ" ወይም "ዝቅ ያለ" ወይም "በዝቅተኛ ሥፍራ ላይ ያለ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Revelation 11:19

ራዕይ 11፡ 19-19

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 12

1 በሰማይም ታላቅ ምልክት ታየ ፤ ፀሐይን የለበሰችና ጨረቃን ከእግሯ በታች ያደረገች፣ ዐሥራ ሁለት ከዋክብት ያሉት አክሊልም በራስዋ ላይ የደፋች አንዲት ሴት
ታየች። 2 እርስዋም ነፍሰ ጡር ነበረች፤ ምጥ ይዟትም ተጨንቃ ትጮህ ነበር፥ 3 እንዲሁም ሌላ ምልክት በሰማይ ታየ፤እነሆ፤ሰባት ራሶችና ዐሥር ቀንዶች
የነበሩት፤በራሶቹም ላይ ሰባት አክሊል የደፋ ትልቅ ቀይ ዘንዶ ታየ። 4 በጅራቱ የኮከቦችን አንድ ሦስተኛ ከሰማይ ስቦ ወደ ምድር ጣለ፤ዘንዶውም ሴቲቱ
በምትወልድበት ጊዜ ልጅዋን ለመዋጥ አስቦ ልትወልድ ወደ ተቃረበችው ሴት ፊት ቆመ። 5 ሴቲቱም ሕዝቦችን ሁሉ በብረት በትር የሚገዛ ወንድ ልጅ ወለደች።
ልጅዋ ግን ወደ እግዚአብሔርና ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ተወሰደ፤ 6 ሴቲቱም ወደ ምድረበዳ ሸሸታ ሄደች፤ በዚያም እግዚአብሔር ለ1260 ቀን በክብካቤ ተይዛ
እንድትጠበቅ አደረጋት። 7 በሰማይም ጦርነት ሆነ። ሚካኤልና መላእክቱ ከዘንዶው ጋር ተዋጉ፤ዘንዶውና መላእክቱ መልሰው ተዋጓቸው። 8 ነገር ግን ዘንዶው
የማሸነፍ ዐቅም አልነበረውም፤ከዚያም ወዲያ እርሱና መላእክቱ በሰማይ የነበራቸውን ስፍራ አጡ። 9 ታላቁም ዘንዶ ወደ ምድር ተጣለ፤ እርሱም ሰዎችን ሁሉ
የሚያስተው ዲያቢሎስ ወይም ሰይጣን ተብሎ የሚጠራው የቀደመው እባብ ነው።እርሱ ወደ ምድር ተጣለ፤ የእርሱም መላእክት ከእርሱ ጋር አብረው ተጣሉ።
10 ከዚህ በኋላ ታላቅ ድምፅ ከሰማይ እንዲህ ሲል ሰማሁ፤«አሁን ማዳንና ኃይል መንግሥትም የአምላካችን ሆኖአል፤ሥልጣንም የእርሱ ክርስቶስ
ሆኖአል።ምክንያቱም ወንድሞቻችንን በአምላካችን ፊት ቀንና ለሊት ሲከሳቸው የነበረ የወንድሞቻችን ከሳሽ ተጥሎአል። 11 እነርሱም በበጉ ደምና በተናገሩት
የምስክርነት ቃል ድል ነሡት፤ ለሕይወታቸው ሳይሳሱ ራሳቸውን ለሞት አሳልፈው ሰጥተዋልና። 12 ስለዚህ ሰማይና በውስጣቸው የምትኖሩ ሁሉ ደስ ይበላችሁ፤
ምድርና ባህር ግን ወዮላችሁ፤ ምክንያቱም ጥቂት ጊዜ እንደ ቀረው ዐውቆ ዲያቢሎስ በታላቅ ቊጣ ወደ እናንተ ወርዷል። 13 ዘንዶው ወደ ምድር እንደተጣለ
ባስተዋለ ጊዜ፤ ወንድ ልጅ የወለደችውን ሴት አሳደዳት፤ 14 ሴቲቱ ከእባቡ ፊት ርቃ ለዘመን፣ ለዘመናትና ለዘመንም እኩሌታ በክብካቤ ተጠብቃ ወደ
ምትኖርበት በምድረ በዳ ወደ ተዘጋጀላት ስፍራ በርራ እንድትሄድ ሁለት የታላቅ ንስር ክንፎች ተሰጧት። 15 እባቡ የወንዝ ውሃ የሚያህል ውሃ ከአፉ ተፍቶ ሴቲቱ
በጎርፍ እንድትወሰድ ብሎ በስተ ኋላዋ አፈሰሰ። 16 ነገር ግን ምድር አፍዋን ከፍታ ዘንዶው በአፉ ያፈሰሰውን ወንዝ በመዋጥ ረዳቻት። 17 ከዚያም ዘንዶው
በሴቲቱ ላይ ተቆጥቶ ከትሩፋን ዝርያዎችዋ ጋር ሊዋጋ ሄደ። እነርሱም የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁና ስለ ኢየሱስ በታማኝነት የሚመሰክሩት ናቸው። 18
ዘንዶውም በባህር ዳር ባለው አሸዋ ላይ ቆመ።

Revelation 12:1

ራዕይ **12**፡ **1-2**
በሰማይ ታላቅ ምልክት ታየ አማራጭ ትርጉም: "በሰማይ ታላቅ ምልክት ታየ" ወይም "እኔ፣ ዮሐንስ በሰማይ ታላቅ ምልክትን አየሁ" ፀሐይን የተጎናፀፈች አንድት ሴት አየሁ አማራጭ ትርጉም: "ፀሐይን የለበሰች ሴት" ዐሥራ ሁለት ክዋክብት "12 ክዋክብት"

Revelation 12:3

ራዕይ **12**፡ **3-4**
ዘንዶ ትልቅ፣ እንሽላልት የሚመስል አደገኛ ተሳቢ እንስሳ። ይህ ለአይሁዳዊያን የክፋት እና የተዘበራረቀ ነገር ምልከክት ነው።

Revelation 12:5

ራዕይ **12**፡ **5-6**
ልጇ ወደ እግዚአብሔር ተነጠቀ አማራጭ ትርጉም: "እግዚብሔር ልጇን ወደ ራሱ ወሰደው።"

Revelation 12:7

ራዕይ **12**፡ **7-9**
ዘንዶ ይህንን በ REV 12:3. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። በቁጥር 9 ላይ ዘንዶው “ዳቢሎስ ወይም ሴጣን” ተብሎ ተጠርቷል። ታላቁ ዘንዶ እና የእርሱ መላእክት. . . ወደ ምድር ተጣሉ አማራጭ ትርጉም: እግዚአብሔር ታላቁ ዘንዶን እና የእርሱን መላእክት ከሰማይ ወደ ምድር ጣላቸው።

Revelation 12:10

ራዕይ **12**፡ **10-10**
እኔ ይህ የሕንስን ያመለክታል። ቀን እና ማታ “ቀን እና ማታ” የሚሉት ቃላት ሁል ጊዜ ተጣምረው ጥቅም ላይ ውለዋል፤ እርሱም ሁል ጊዜ ወንድሞችን ይከሳቸዋል።

Revelation 12:11

ራዕይ **12**፡ **11-12**

Revelation 12:13

ራዕይ **12**፡ **13-14**
ዘንዶው ወደ ምድር መጣሉን አውቆ አማራጭ ትርጉም: "ዘንዶው እግዚአብሔር ከሰማይ ወደ ምድር እንደጣለው አውቆ" ዘንዶው ይህንን በ REV 12:3. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት።

Revelation 12:15

ራዕይ **12**፡ **15-18**
እባብ በ REV 12:9. መሠረት ይህ ከዘንዶው ጋር ተመሳሳይ ነው። እንደ ወንዝ አማራጭ ትርጉም: "በብዛት" ዘንዶ ይህንን በ REV 12:3. ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ምድሪቱም አፍዋን ከፍታ ዘንዶው ከአፉ ያፈሰሰውን ወንዝ ዋጠችው። አማራጭ ትርጉም: "በምድር ላይ ያለው ቀዳዳ ተከፍቶ ውሃ ወደ ቀዳዳው ውስጥ ፈሰሰ።"

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **13**

1 ከዚያም አንድ አውሬ ከባህር ሲወጣ አየሁ። እርሱም ዐስር ቀንዶችና ሰባት ራሶች ነበሩት። በቀንዶቹም ላይ አስር አክሊሎች ነበሩ፤ በራሶቹም ላይ እግዚአብሔርን የሚሰድብ ስሞች ነበሩት። **2** ያየሁትም አውሬ ነብር ይመስል ነበር፤ እግሮቹ የድብ እግሮች፤ አፉ የአንበሳ አፍ ይመስል ነበር። ይገዛም ዘንድ ዘንዶው የራሱን ኀይልና የራሱን ዙፋን ትልቅም ስልጣን ለአውሬው ሰጠው። **3** ከአውሬው ራሶቹ አንዱ ለሞት የሚያበቃ ቁስል እንደነበረው ሆኖ አየሁት፤ ነገር ግን ለሞት የሚያደርስው ቁስል ዳነ፤በዚህም ምክንያት ዓለም በሙሉ በመደነቅ አውሬውን ተከተለ። **4** አውሬውም ስልጣኑን በመስጠቱ ሁሉም ለዘንዶው ሰገዱለት «አውሬውን ማን ይመስለዋል? ከእርሱስ ጋር ማን ለዋጋ ይችላል?» እያሉ ለአውሬው ሰገዱለት። **5** አውሬውም የትዕቢትና የስድብ ቃል የሚናገርበት አፍ ተሰጠው፤ ለአርባ ሁለት ወራትም ስልጣኑን እንዲያሳይ ተፈቀደለት። **6** አውሬው አፉን ከፍቶ እግዚአብሔርን፤ የእግዚአብሔርን ስም፤ መኖሪያውንና በሰማይ የሚኖሩትን መሳደብ ጀምረ። **7** አውሬው ቅዱሳንን እንዲዋጋ ና፤ ድል እንዲነሳቸውም ስልጣን ተሰጠው። በነገድና በወገን በቃንቃና በህዝብ ሁሉ ላይ ስልጣን ተሰጠው። **8** ዓለም ሲፈጠር ጀምሮ ስሞቻቸው በታረደው በግ የህይወት መጽሀፍ ያልተጻፈ በዓለም ላይ የሚኖሩ ሰዎች ሁ ሉ ለአውሬው ይሰግዳሉ። **9** የሚሰማ ጆሮ ያለው ቢኖር ይስማ። **10** «የሚማረክ ማንም ቢኖር ወደ ምርኮ ይሄዳል፤ በሰይፍ የሚገደል ማንም ቢኖር በሰይፍ ይገደላል» እንግዲህ የቅዱሳን ትዕግስትና እምነት የሚታየው በዚህ ጊዜ ነው። **11** ከዚህም በኃላ ሌላ አውሬ ደግሞ ከምድር ሲውጣ አየሁ፤ የበግ ቀንዶች የሚመስሉ ሁለት ቀንዶች ነበሩት አነጋገሩም እንደ ዘንዶው ነበር። **12** የመጀመሪያውን አውሬ ስልጣን ሁሉ በመጀመሪያው አውሬ ፊት ሆኖ ይሰራበት ነበር፤ ምድርና በእርስዋ ላይ የሚኖሩት ሁሉ ለአውሬው እንዲሰግዱለት ያደርጋል፤ ይህም አውሬ ያ ለሞት የሚያድርስ ቁስል የዳነለት የመጀመሪያው አውሬ ነው። **13** እርሱም በሰዎች ፊት እሳትን ከሰማይ እስከማውረድ ድረስ ታላላቅ ምልክቶችን ያደርግ ነበር፤ **14** እንዲያደርግ በተፈቀደለት ተዓምራት በሰይፍ ቁስሎ የዳነውን የአውሬውን ምስል እንዲሰሩ በማዘዝ በምድር ላይ የሚኖሩትን ሰዎች ያስት ነበር። **15** እርሱም ምስሉ መናገር እንካ እስከሚችል ድረስ እስትንፋስ ለመስጠትና ለአውሬው የማይሰግዱትን መግደል ይችል ዘንድ ለማድረግ ስልጣን ተሰጠው። **16** እርሱም ታናናሾችም ሆኑ ታላላቆች፤ ሀብታሞችም ሆኑ ድኾች ጌቶችም ሆኑ አገልጋዮች ሁሉም በቀኝ እጃቸው ወይም በግምባራቸው ላይ ምልክት እንዲያደርጉ አስገደዳቸው። **17** የአውሬው ስም የሆነው ምልክት ወይም የስሙ ቁጥር የሌለው ማንም ሰው መግዛትም ሆን መሸጥ አይችልም ነበር። **18** ይህ ጥበብን የሚጠይቅ ነው።የሚያስተውል የአውሬውን ቁጥር ያስላው፤ ቁጥሩም የሰው ቁጥር ነው፤ የውሬውም ቁጥር 666 ነው፤

Revelation 13:1

ራዕይ **13**፡ **1-2**
ከዚያም ይህንን አየሁ በዚህ ሥፍራ ላይ “እኔ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ዮሐንስ ነው። ዘንዶ ይህንን በ REV 12:3. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት።

Revelation 13:3

ራዕይ **13**፡**3-4**
ይሁን እንጂ ያ ቁስል ተፈወሰ አማራጭ ትርጉም: "ይሁን እንጂ ቁልስሉ ተፈወሰ" አውሬውን ተከተሉ "ለአውሬው ታዘዙ" ዘንዶ ይህንን በ REV 12:3. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። እርሱን ተቃውሞ ማን መዋጋት ይችላል? አማራጭ ትርጉም: "አውሬንን ተቃውሞ ማንም ልዋጋ እና ልሸንፍ አይችልም!"

Revelation 13:5

ራዕይ **13**፡ **5-6**
ለአውሬው ተሰጠው . . . ተፈቀደለት "እግዚአብሔር ለአውሬው ሰጠው . . . እግዚብሔር ለአውሬው ፈቀደለት" አርባ -ሁለት ወራት ሁለት ወራት - "42 ወራት"

ስሙን እየተሳደበ "የእግዚአብሔርን ስም ወይም ባሕርይ እየተሳደበ"

Revelation 13:7

ራዕይ **13**፡ **7-8**
ስልጣን ለእርሱ ተሰጠው አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር ለአውሬው ስልጣን ሰጠው" ስሙ ያልተጻፈ ማንኛውም ሰው ሁሉ አማራጭ ትርጉም: "በጉ ስማቸውን ያልጻፋቸው ሰዎች ሁሉ" ወይም "ኢየሱስ ስማቸውን ያልጻፋቸው ሁሉ" በግ ይህ ኢየሱስን የሚያመለክት ነው። ይህንን በ REV 5:6. ላይ ምን ብለህ እደተረጎምከው ተመልከት። የታረደው አማራጭ ትርጉም: "ሰዎች ያረዱት"

Revelation 13:9

ራዕይ **13**፡ **9-10**
ጆሮ ያለው ይስማ ይህ ማለት የመስማት ችሎታ ያለው እና የእግዚአብሔርን መልዕክት መረዳት የሚችል ማለት ነው።

Revelation 13:11

ራዕይ **13**፡ **11-12**
ዘንዶው ይህንን በ REV 12:3. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። እና ምድርን እና በውስጧ የሚኖሩትን ሁሉ የፈጠረውን "እና በምድር ላይ ያሉትን ሁሉ የፈጠረውን" ለሞት የሚያበቃ ቁስል ያለበት ተፈወሰ አማራጭ ትርጉም: "ለሞት የሚያበቃ ቁስል ያለበት ተፈወሰ"

Revelation 13:13

ራዕይ **13**፡ **13-14**
ያድርጋል "በምድር ካይ ያለው አውሬ ይህንን ያደርጋል" በሰይፍ ቆስሎ የነበረው አማራጭ ትርጉም: "የሆነ ሰው በሰይፍ ያቆሰለው"

Revelation 13:15

ራዕይ **13**፡ **15-17**
ተፈቅዶለት ነበር አማራጭ ትርጉም: "እግዚአበብሔር ለአውሬው በምድር ላይ ፈቅዶለት ነበር" ለአውሬው ምስል ትንፋሽ እንዲሰጠው ተሰጠው። አማራጭ ትርጉም: "ለአውሬው ምስል ሕይወት ለመስጠት" ለአውሬው ምስል ለመስገድ ፈቃደኛ ያልሆኑት ሰዎች ሁሉ እንዲገደሉ አማራጭ ትርጉም: "አውሬውን ለማምለከት ፈቃደኛ ያልሆነ ማንኛውም ሰው እንዲገደል"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Revelation 13:18

ራዕይ **13**፡ **18**-**18**
የሰው ልጅ ቁጥር ነው አማራጭ ትርጉሞች 1) ቁጥሩ የሚያመለክተው
አንድን ሰው ነው ወይም 2) ቁጥሩ ሁሉንም የሰው ልጆች ይወክላል። 666
"ስድስት ስልሳ ስድት"

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 14

1 አየሁም እነሆ በጉ በጽዮን ተራራ በፊቴ ቆሞ ነበር። ከእርሱ ጋር የእርሱ ስምና የአባቱ ስም በግንባራቸው ላይ የተጻፈባቸው አንድ መቶ አርባ አራት ሺህ ነበሩ።
2 በሰማይ እንደ ብዙ ውኃ ድምጽና ና እንደታላቅ ነጎድጓድ ድምጽ የመሰለ ድምጽ ሰማሁ፤ የሰማሁትም ድምጽ በገና ደርዳሪዎች በገና እየደረደሩ የሚያሰሙትን
ድምጽ ይመስል ነበር። 3 እነርሱም በዙፋኑና በአራቱ እንስሶች በሽማግሌዎችም ፊት አዲስ መዝሙር ዘመሩ። ይህንም መዝሙር ከምድር ከተዋጁት ከአንድ
መቶ አርባ አራት ሺህ በቀር ማንም ሊማረው አልቻለም። 4 እነርሱም ራሳቸውን ከሴቶች ጋር ካላረከሱት ናቸው፤ ራሳቸውንም በግብረ ስጋ ግንኙነት ካለማርከስ
ጠብቀዋል። እነርሱ ናቸው በጉ ወደሚሄድበት ሁሉ የሚከተሉት እነዚህ ናቸው፤ እነርሱ ለእግዚአብሔርና ለበጉ በኩራት ለመሆን ከሰዎች መካከል የተዋጁ ናቸው።
5 በአንደበታቸውም ሀሰት ተናግረው አያውቁም። ነቀፋም የሌለባቸው ናቸው። 6 በምድር ላይ ለሚኖሩ ለህዝብ፤ ለነገድ፤ ለቃንቃና ለወገን ሁሉ ለማብሰር
ዘላለማዊውን የምስራች ቃል የያዘ ሌላ መልዓክ በሰማይ መካከል ሲበር አየሁ 7 እርሱም በታላቅ ድምጽ «እግዚአብሄርን ፍሩ፤ አክብሩትም። ምክንያቱም የእርሱ
የፍርድ ሰዓት ደርሳልና፤ ሰማይን፤ ምድርን፤ ባህርንና የውሃ ምንጮችን የፈጠረን አምላክ አምልኩ» አለ 8 ሌላም ሁለተኛ መልአክ «የዝሙትዋ ፍትወት የሆነውን
የሚያሰክር የወይን ጠጅ ለህዝቦች ሁሉ ያጠጣች ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች፤ ወደቀች» እያለ የመጀመሪያውን መልዓክ ተከተለው 9 ሌላ ሶስተኛ መለዓክ በታላቅ
ድምጽ እንዲህ እያለ ተከተላቸው «ለአውሬውና ለምስሉ ቢሰግዱ ምልክቱን በግምባሩ ወይም በእጁ ቢያደርግ፤ 10 የእግዚአብሔርን የቁጣ የወይን ጠጅ
ይጠጣል፤ ይህም የወይን ጠጅ ሳይበረዝ በቁጣው ጽዋ የተዘጋጀ ነው፤ ፅሚጠጣውም ሰው በቅዱሳን መላዕክት ፊትና በበጉ ፊት በእሳትና በዲን ይሰቃያል፤ 11
የስቃያቸውም ጢስ ከዘላለም እስከ ዘላለም ወደ ላይ ይወጣል፤ ለአውሬውና ለምስሉ የሚሰግዱ የስሙንም ምልክት ያደረጉ ሁሉ ቀንና ለሊት ዕረፍት የላቸውም።
12 የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የሚጠብቁና በኢየሱስ የሚያምኑማመኑ ቅዱሳን፤ ትዕግስታቸው የሚታየው እዚህ ላይ ነው። 13 ከሰማይም እንዲህ የሚል ድምጽ
ሰማሁ «ይህን ጻፍ ከእንግዲህ ወዲህ በጌታ ሆነው የሚሞቱ የተባረኩ ናቸው» መንፈስም አዎ ስራቸው ስለሚከተላቸው ከድካማቸው ያርፉሉ» ይላል 14
አየሁም እነሆ ነጭ ደመና ነበር በደመናውም ላይ የሰውን ልጅ የሚመስል ተቀምጦ ነበር። በራሱም ላይ የወርቅ አክሊል አድርጎአል፤ በእጁም ስለታም ማጭድ
ይዞአል። 15 ከዚህም በኃላ ሌላ መልአክ ከመቅደሱ ወጣ በደመና ላይ የተቀመጠውን በታላቅ ድምጽ «የምድር መከር ደርሶአል የአጨዳ ሰዓትም ቀርቦአል፤
ስለዚህ ማጭድህን ስደድ» አለው። 16 በደመናው ላይ የተቀመጠውም ማጭዱን ወደ ምድር ሰደደው ምድርም ታጨደች። 17 ሌላ መልዓክ ከሰማይ ባለው
መቅደስ ወጣ፤ እርሱም ስለታም ማጭድ ይዞ ነበር። 18 በእሳትም ላይ ስልጣን ያለው ሌላ መልዓክ ከመሰዊያው አጠገብ ወጣና ስለታም ማጭድ የያዘውን
መልዓክ በታላቅ ድምጽ «የዘለላዎቹ ፍሬዎች ስለበሰሉ የወይን ዘለላዎችን ሁሉ ከምድር ወይን ቁረጥ» አለው። 19 መልዓኩም ማጭዱን ወደ ምድር ሰደደው፤
የምድርንም ወይን ዘለላ ቆረጠ፤ ወደ ታላቁ ወደ እግዚአብሔር የቁጣ ወይን መጭመቂያ ውስጥ ጣለው። 20 ከከተማው ውጭ ባለው በወይን መጥመቂያም
ተጨመቀ ከመጭመቂያውም እስከ ፈረስ ልጋም ወደ ላይ ከፍ ያለና 300 ኪሎ ሜትር የሚደርስ ደም ወጥቶ ፈሰሰ።

Revelation 14:1

ራዕይ **14**፡ **1-2**
ተመለከትኩ በዚህ ሥፍራ ላይ “እኔ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ዮሐንስ ነው። በግ ይህ ኢየሱስን የሚያመለክት ነው። ይህንን በ REV 5:6. ላይ ምን ብለህ አንንደተረጎምከው ተመልከት። 144,000 ይህንን በ REV 7:4.ላይ ምን ብለህ አንንደተረጎምከው ተመልከት። ስሙና የአባቱ ስም በግምባራቸው የተጻፈላቸው አማራጭ ትርጉም: "በግንባራቸው ላይ የበጉ እና የአባቱ ስም የጻፉ ሰዎች።"

Revelation 14:3

ራዕይ **14**፡ **3-5**
ዘመሩ "144,000ዎቹ ዘመሩ" ከሴትቱ ጋር ራሳቸውን ያላረከሱት እነዚህ ናቸው አማራጭ ትርጉም: "144,000ዎቹ ድንግል በግብረገብ ንጹሕ እንደሆነች በመንፈሳዊነት ንጹሕ የሆኑት ሰዎች ናቸው። እነዚህ የሐሰት አማልክትን በማምለክ ራሳቸውን አላረከሱም።

Revelation 14:6

ራዕይ **14**፡ **6-7**

Revelation 14:8

ራዕይ **14**፡ **8-8**
ወደቀች፣ ወደቀች ይህ ቃል የተደጋገመው አጽኖት ለመስጠት ነው። ወደቀች . . . በራሷም ላይ ከፍተኛ ቁጣን አመጣች "በጣም ክፉ ከተማዎች

Revelation 14:9

ራዕይ **14**፡ **9-10**
የእግዚአብሔርን ቁጣ ወይን ይጠጣሉ በዚህ ሥፍራ ላይ “ወይን መጠጣት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ቁጣን መቀበልን ነው። የተዘጋጀውን አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር ያዘጋጀውን" የቁጣው ጽዋ ጽዋው በወይን የተሞላ ሲሆን ይህም የእግዚአብሔርን ቁጣ ይወክላል። ሳይቀላቀል መቀዳት ይህ በውሃ ያልተቀላቀለ ወይንን ያመለክታል። ይህ ማለት የእግዚአብሔር ቁጣ ሙሉ ለሙሉ እንደሚመጣባቸው ያሳያል። የእርሱ ቅዱስ መላእክት "የእግዚአብሔር ቅዱስ መላእክት"

Revelation 14:11

ራዕይ **14**፡ **11-12**
ከሥቃያቸው "ከቀጣይ ሕመማቸው"

Revelation 14:13

ራዕይ **14**፡ **13-13**
ሥራቸው ይከተላቸዋል አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር ስለሥራቸው ይሸልማቸዋልና"

Revelation 14:14

ራዕይ **14**፡ **14-16**
የሰው ልጅ የሚመስለው ይህንን በ REV 1:13. ላይ ምን ብለህ እደተረጎምከው ተመልከት። ማጭድህን አንሳ . . . ምድርም ታጨደች ይህ ምሳሌያዊ ንግግር በምድር ላይ ባሉት ሰዎች ሁሉ ላይ ያለውን የእግዚአብሔርን ፍርድ ያመለክታል። ማጭድ ሣር እና ወይን ለማጨድ ጥቅም ላይ የሚለው የተቆለመመ እና ስለታም ብረትን ያመለክታል። ከቤተ መቅዱስ ወጣ "ከሰማያዊው መቅደስ ወጣ" ምድር ታጨደች "ምድር አጨደ"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Revelation 14:17

ራዕይ **14**፡ **17**-**18**

Revelation 14:19

ራዕይ **14**፡ **19**-**20**
ታላቁ የወይን መጭመቂያ . . . ይህ ተመሳሳይ መያዥያ ዕቃን ያመለክታል።
ልጓም በፈረስ ጭንቅላት ላይ የሚታሠር እና የፈረስን አቅጣጫ ለመምራት
የሚገለግል ዕቃ 1,600 ምዕራፍ አንድ ምዕራፍ 185 ሜትሮች ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **15**

1 ከዚህም በኋላ ታላቅና ድንቅ ምልክት በሰማይ አየሁ፤ የእግዚአብሔር ቁጣ የሚፈጽምባቸው የመጨረሻዎቹን ሰባት መቅሰፍት የያዙትን ሰባት መላዕክት አየሁ **2** እኔም እሳት የተቀላቀለበት የሚመስል የመስተዋት ባህር አየሁ፤ አውሬውንና የአውሬውን ምስል የስሙንም ቁጥር ድል የነሱትን በባህሩ አጥገብ ቆመው ነበር። እግዚአብሔር የሰጣቸውንም በገና ይዘው ነበር። **3** እነርሱም የእግዚአብሔር አገልጋይ የሙሴን መዝሙርና የበጉን መዝሙር እንዲህ እያሉ ይዘምሩ ነበር «ሁሉን የምትችል ጌታ አምላክ ሆይ ስራህ ታላቅና አስደናቂ ነው። የእዝቦች ንጉስ ሆይ መንገድህ ትክክልና እውነት ነው። **4** ጌታ ሆይ አንተን የማይፈራና ስምህንም የማያከብር ማን ነው? ምክንያቱም አንተ ብቻ ቅዱስ ነህ የጽድቅ ስራህ ስለተገለጠ ሕዝቦች ሁሉ መጥተው በፊትህ ይሰግዳሉ።» **5** ከዚህም በኋላ አየሁ እነሆ የምስክር ድንኳን የሆንው ቅድስተ ቅዱሳን በሰማይ ተከፈተ። **6** ከቅድስተ ቅዱሳንም ሰባቱን መቅሰፍቶች የያዙት ሰባት መላዕክት ወጡ፤ የሚያንጸባርቅ ነጭ ልብስ ለብሰው ነበር። ደረታቸውንም በወርቅ መታጥቂያ ታጥቀው ነበር። **7** ከአራቱ ህያዋን ፍጡራን አንዱ ከዘላለም እስከ ዘላለም በሚኖረው አምላክ ቁጣ የተሞሉትን ሰባት የውርቅ ጽዋዎች ለሰባቱ መላዕክት ሰጣቸው። **8** ቅድስተ ቅዱሳኑም ከእግዚአብሔር ክብርና ኃይል የተነሳ በጢስ ተሞላ፤ ሰባቱ መላዕክት የያዙአቸው ስባት መቅሰፍቶች እስኪፈጽሙ ድረስ ማንም ወደ ቅዱሰተ ቅዱሳኑ መገባት አልቻሉም።

Revelation 15:1

ራዕይ **15**፡ **1**-**1**
ከዚያም አየሁ...ተፈጸመ በዚህ ሥፍራ ላይ ያለው 15:1 ከ15:2-16:21 ድረስ ያለው ማጠቃለያ ነው። ትልቅ እና አስገራሚ አማራጭ ትርጉም: "በጣም ያስገረመኝ ነገር" ከእነርሱ ጋር የእግዚአብሔር ቁጣ ተፈጸመ አማራጭ ትርጉም: "እነዚህ መቅሰፍቶች የእግዚአብሔርን ቁጣ ፈጸሙ።"

Revelation 15:2

ራዕይ **15**፡ **2**-**2**
ቁጥሩ የሚያመለክተው ስሙን ነው ይህ በ REV 13:18. ላይ የተጠቀሰውን ቁጥር እንደሚመለክት አንባቢያኑ ልገነዘቡ ይገባል።

Revelation 15:3

ራዕይ **15**፡ **3**-**4**
የጽድቅ ተግባርህ ታወቀ አማራጭ ትርጉም: "ሁሉም ሰው ያደረከውን የጽድቅ ሥራ ተመለከተ እንዲሁም ተገነዘበ።"

Revelation 15:5

ራዕይ **15**፡**5**-**6**
ከእነዚህ ነገሮች በኋላ "ሰዎች መዘመራቸውን ካጠናቀቁ በኋላ" ከተልባ እግር የተሠራ ልብስ ከላይ የሚለበስ የተብለጨለጨ ልብስ

Revelation 15:7

ራዕይ **15**፡ **7**-**8**
አራት ሕያዊያን ፍጥረታት ይህንን በ REV 4:6. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **16**

1 ሰባቱን መላእክት፣ “ሂዱና ሰባቱን የእግዚአብሔርን ቁጣ ጽዋዎች ምድር ላይ አፍስሱ” የሚል ታላቅ ድምፅ ከመቅደሱ ሲወጣ ሰማሁ። **2** የመጀመሪያው መልአክ ጽዋውን ምድር ላይ አፈሰሰ፤ የአውሬው ምልክት ባላቸውና ለምስሉ በሰገዱት አስከፊና የሚያሠቃይ ቁስል ወጣባቸው። **3** ሁለተኛው መልአክ ጽዋውን ባሕር ላይ አፈሰሰ፤ ባሕሩ እንደ ሞተ ሰው ደም ሆነ፤ ባሕር ውስጥ የነበረ ሕያው ፍጡር ሁሉ ሞተ። **4** ሦስተኛው መልአክ ጽዋውን ወንዞችና የውሃ ምንጮች ላይ አፈሰሰ እነርሱም ደም ሆኑ። **5** የውሃውም መልአክ፣ “ያለህና የነበርህ ቅዱስ ጌታ እንዲህ ስለ ፈረድህ ትክክል ነህ፣ **6** ምክንያቱም የቅዱሳንህና የነቢያትን ደም ስላፈሰሱ፣ ደም አጠጣሃቸው፤ ይህም የሚገባቸው ነው” ሲል ሰማሁ። **7** ከመሠዊያውም፣ “አዎን፣ ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ፍርድህ እውነትና ትክክል ነው” የሚል ድምፅ ወጣ። **8** አራተኛው መልአክ ጽዋውን ፀሐይ ላይ አፈሰሰ፤ ለእርሷም ሰዎችን በግለትዋ የማቃጠል ሥልጣን ተሰጣት። **9** ሰዎች በከባድ ሙቀቷ ተቃጠሉ፤ በእነዚህ መቅሠፍቶች ላይ ሥልጣን ያለውን የእግዚአብሔር ስም ሰደቡ። ንሰሐ አልገቡም፤ ክብርም አልሰጡትም። **10** አምስተኛው መልአክ ጽዋውን በአውሬው ዙፋን ላይ አፈሰሰ፤ የአውሬውም መንግሥት በጨለማ ተዋጠ። ከሥቃያቸውም የተነሣ ምላሳቸውን ያኝኩ ነበር። **11** ከሥቃያቸውና ከደረሰባቸው ቁስል የተነሣ የሰማይን አምላክ ተሳደቡ፤ ያም ሆኖ ግን ስላደረጉት ክፉ ሥራ ንስሐ ለመግባት ፈቃደኞች አልሆኑም። **12** ስድስተኛው መልአክ ጽዋውን ታላቁ ወንዝ ኤፍራጥስ ላይ አፈሰሰ፤ ከምሥራቅ ለመጡ ነገሥታት መንገድ ለማዘጋጀት የወንዙ ውሃ ደረቀ። **13** ከዘንዶው አፍና ከአውሬው አፍ እንዲሁም ከሐሰተኛው ነቢይ አፍ እንቁራሪት የሚመስሉ ሦስት ርኩሳን መናፍስት ስወጡ አየሁ። **14** እነዚህ ተአምራዊ ምልክቶች የሚያደርጉ የአጋንንት መናፍስት ናቸው። ሁሉን በሚገዛ አምላክ ታላቅ ቀን ለሚደረገው ጦርነት የዓለም መንግሥታችን ሁሉ ለመሰብሰብ ወደ ወጥተው ሄዱ። **15** “ልብ በሉ! እኔ እንደ ሌባ እመጣለሁ! ራቁቱን እንዳይገኝና ሰዎችም ሐፍረቱን እንዳያዩ ነቅቶ ልብሱን የሚጠብቅ የተባረከ ነው።” **16** መናፍስቱ ነገሥታቱን ሰብስበው በዕብራይስጥ አርማጌደን ወደሚባል ቦታ አመጧቸው። **17** ሰባተኛው መልአክ ጽዋውን አየር ላይ አፈሰሰ። በዚያን ጊዜ፣ “ተፈጸመ!” የሚል ታላቅ ድምፅ ከመቅደሱና ከዙፋኑ ወጣ። **18** ከዚያም የመብረቅ ብልጥታ፣ ሁካታ ነጎድጓድና ከባድ የመሬት መናወጥ ሆነ፤ የዚያ ዓይነት የምድር ነውጥ የሰው ልጅ ምድር ላይ መኖር ከጀመረ አንሥቶ ሆኖ የማያውቅ እጅግ ከባድ ነበር። **19** ታላቂቷ ከተማ ለሦስት ተከፈለች፤ የሕዝቦች ከተሞችም ተደመሰሱ። እግዚአብሔር ታላቂቱ ባቢሎንን አስታወሰ፤ ለዚያች ከተማም የብርቱ ቁጣው ወይን ጠጅ የሞላበት ጽዋ እንድትጠጣ ሰጣት። **20** ደሴቶች ሁሉ ጠፋ፤ ተራሮችም በቦታቸው አልተገኙም። **21** አንድ ታለንት የሚመዝን የበረዶ ድንጋይ ከሰማይ ወርዶ ሰዎች ላይ ወደቀ፤ መቅሠፍቱ እጅግ አሰቃቂ ከመሆኑ የተነሣ ሰዎች ስለ በረዶው ድንጋይ እግዚአብሔርን ተራገሙ።

Revelation 16:1

ራዕይ **16**፡ **1-1**
ሰማሁ ጸሐፊው ዮሐንስ (REV 1:9) ሰማ የእግዚአብሔርን ቁጣ ጽዋዎች በ REV 15:7. ተመሳሳይ ሀረጎችን ምን ብለህ እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

Revelation 16:2

ራዕይ **16**፡ **2-2**
ከጽዋው ውስጥ ፈሰሰ አማራጭ ትርጉም: "በጽዋው ውስጥ ያለውን ወይን ውስጥ አፈሰሰው" ወይም "በእርሱ ጽዋ ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔር ቁጣ አፈሰሰው" የሚያሳምም ቁስል "የሚያሳምም ቁስል።" ይህ ፈውስና ካላገኘ በእንፌክሽን ወይም ከጉዳ የመጣ ልሆን ይችላል። የአውሬው ምልክት ይህንን በ REV 13:17. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት።

Revelation 16:3

ራዕይ **16**፡ **3-3**
ከጽዋው ውስጥ አፈሰሰው ይህንን በ REV 16:2 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። ባሕሩ ይህ በዓለማችን ውስጥ የሚገኙ ጨዋማ የውሃ አካላትን ያመለክታል። የሞተ ሰው ደም የሚመስል ይህ ማለት ውሃው ቀይ፣ ወፍራም ሆኖ መጥፎ ጠረን እንዳለው ያሳያል።

Revelation 16:4

ራዕይ **16**፡**4-7**
ከጽዋው ውስጥ አፈሰሰው ይህንን በ REV 16:2 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። ወንዞች እና የውሃ ምንጮች ይህ ንጹሕ ውሃ የሚያመነጩ የውሃ አካላትን ያመለክታል። የውሃዎች መላእክ ይህ ሦስተኛውን መላእክ የሚመለክት ነው። እርሱ የእግዚአብሔር ቁጣ በወንዝ እና በውሃ ምንጮች ላይ እንዲያፈስ የተሾመ ነው። አንተ ጻድቅ ነህ በዚህ ሥፍራ ላይ "አንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው። ያለህና የነበርህ ተመሳሳይ ሀረጋትን በ REV 1:4. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምክ ተመልከት። የቅዱሳንህን እና የነቢትህን ደም አፍስሰዋል አማራጭ ትርጉም: "ክፉ ሰዎች ቅዱሳንን እና ነቢትን ገድለዋል።" ደም እንዲጠጡ ሰጠሃቸው እግዚአብሔር ለክፉ ሰዎች ወደ ደምነት የተቀየረ ውሃ ይጠጡ ዘንድ ሰጣቸው። ከመሰዊያው ላይ እንዲህ የሚል ምላሽ ሰማሁ አማራጭ ትርጉሞች 1) "ከመሰዊያው አጠገብ የነበረው መላእክ ስናገር ሰማሁት" ወይም 2) "ከመሰዊያው ሥር ያሉት የቅዱሳን ነፍሳት ስነናገሩ ሰማሁ"

Revelation 16:8

ራዕይ **16**፡ **8-9**
ከጽዋው ውስጥ አፈሰሰው ይህንን በ REV 16:2 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። ሰዎችን እንዲታቃጥል ፈቃድ ተሰጣት በዚህ ሥፍራ ላይ የሐንስ ፀሐይን በሰውና በመመሰል ይናገራል። አማራጭ ትርጉም: "ፀሐይ ሰዎችን ክፉኛ ታቃጥል" የእግዚአብሔርን ስም ተሳደቡ አማራጭ ትርጉም: "የእግዚአብሔርን ስም ተሳደቡ"

Revelation 16:10

ራዕይ **16**፡ **10-11**
ጽዋውን አፈሰሰ ይህንን በ REV 16:2. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። የአውሬው ዙፋን የአውሬው ኃይል ማዕከል፣ የመንግስቱ ዋና መቀመጫ ከተማ ሊሆን ይችላል። ፈሩ በአውሬው መንግስት ውስጥ ያሉ ሰዎች ፈሩ። ተሳደቡ "ረገሙ"

Revelation 16:12

ራዕይ **16**፡ **12-14**
እንቁራርት ይመስላል እንቅራሪት በውሃ አጠገብ የሚትኖር ትንሽ እንስሳ ናት። አይሁዳዊያን ንጹሕ እንስሳ አድርገው አይቆጥሯትም። አውሬው ይህንን በ REV 12:3. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Revelation 16:15

ራዕይ **16**፡ **15**-**16**
እኔ እንደ ሌባ እመጣለሁ ይህንን በ REV 3:3.ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። ይህን አሳፋሪ ሁኔታ ተመለከቱ በዚህ ሥፍራ ላይ “እነርሱ” የሚለው ቃል ሌሎች ሰዎችን ያመለክታል። በአንድነት ሰበሰቧቸው "የዳቢሎስ መናፈስት ነገስታትን እና ጦራቸውን በአንድነት ሰበሰቧቸው" ተብሎ ወደምጠራ ሥፍራ "ሰዎች ብለው ወደምጠሩት ሥፍራ" አርማንጌዶ ይህ የቦታ ስም ነው።

Revelation 16:17

ራዕይ **16**፡ **17**-**19**
ጽዋውን አፈሰሰ ይህንን በ REV 16:2. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምክ ተመልከት። ከዚያ ከቅድስተ ቅዱሳኑ እና ከዙፋኑን እንዲህ የሚል ድምጽ ወጣ ይህ ማለት በዙፋኑ ላይ የተቀመጠ አንድ ሰው ወይም በዙፋኑ አጠገብ የቆመ ሰው በከፍተኛ ድምጽ ተናገረ። ማን እንደተናገረ ግን በግልጽ አይታወቅም። ታላቅቷ ከተማ ተከፈለች አማራጭ ትርጉም: "የመሬት መንቀጥቀጥ ታላቅቷን ከተማ ከፈለት" ከዚያም እግዚአብሔር አስታወሳቸው "ከዚያም እግዚአብሔር አዘዘ" ወይም "ከዚያም እግዚአብሔር አመጣ" ወይም "ከዚያም እግዚአብሔር አጽኖት መስጠት ጀመረ።" አንባቢያኑ እግዚአብሔር የዘነጋውን ነገር አስታወሰ ብለው ማሰብ የለባቸውም። ለከተማይቱ በከፍተኛ ቁጣው የተሞላ የወይን ጽዋ ሰጣት እግዚአብሔር ሕዝቡን ክፉኛ ቀጣቸው እንዲሁም በጣም እንዲሰቃዩ አደረገ። ለከተማይቱ ጽዋ ሰጣት "ከተማይቱ ከጽዋው ትጠጣ ዘንድ አስገደዳት" ከ . . . የተዘጋጀ ወይን አማራጭ ትርጉም: " . . . የሚወክል ወይን"

Revelation 16:20

ራዕይ **16**፡ **20**-**21**
ታለንት ታለንት 34 ኪሎ ግራም ነው።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 17

1 ሰባቱን ጽዋዎች ይዘው ከነበሩት ሰባት መላእክት አንዱ ወደ እኔ መጥቶ እንዲህ አለኝ፤ “በብዙ ውሆች ላይ የተቀመጠችውን ታላቂቱ አመንዝራ የፍርድ ቅጣት
አሳይሃለሁ፤ 2 የምድር ነገሥታት ከእርሷ ጋር አመንዝረሃል፤ ከዝሙቷ ወይን ጠጅ የምድር ነዋሪዎች ሰክረዋል።” 3 መልአኩ በመንፈስ ወደ በረሐ ወሰዶኝ፣
የስድብ ስሞች በሞሉበት ቀይ አውሬ ላይ የተቀመጠች ሴት አየሁ። አወሬው ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶች ነበሩት። 4 ሴትዬዋ ሐምራዊና ቀይ ልብስ ለብሳ፣
በወርቅና በከበሩ ድንጋዮች እንዲሁም በዕንቁዎች አጊጣ ነበር። በእዛም ጸያፍ ነገሮችና የዝሙቷ ርኩሰት የሞላበት የወርቅ ጽዋ ይዛ ነበር። 5 ግንባሯም ላይ፣
“ታላቂቱ ባቢሎን፣ የአመንዝሮችና የምድር ጸያፍ ነገሮች እናት” የሚል ምስጢራዊ ትርጉም ያለው ስም ተጽፎ ነበር። 6 ሴትዬዋ በቅዱሳንና በኢየሱስ ሰማዕታት
ደም ሰክራ አየሁ። ባየኋት ጊዜ በጣም ተደነቅሁ። 7 መልአኩ ግን፣ “ለምን ትደነቃለህ? የሴትዮዋንና የተሸከማትን አውሬ (ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶች ያሉትን
አውሬ) ምንነት እነግርሃለሁ። 8 ያየኸው አውሬ ቀድሞ ነበረ፤ አሁን የለም፤ ሆኖም በኃላ ከጥልቁ ጉድጓድ ይመጣል። ከዚያም ወደ ጥፋት ይሄዳል። ዓለም
ከተፈጠረ ጀምሮ ሰማቸው በሕይወት መጽሐፍ ያልተጻፈ በምድር የሚኖሩ ሰዎች ቀድሞ የነበረውን፣ አሁን የሌለውን በኃላ ግን የሚመጣውን አውሬ ሲያዩ
ይደነቃሉ። 9 ይህ አስተዋይ አእምሮን የሚጠይቅ ጉዳይ ነው። ሰባቱ ራሶች ሴትዬዋ የተቀመጠችባቸው ሰባት ኮረብቶች ናቸው። 10 እነርሱም ሰባት ነገሥታት
ናቸው። አምስቱ ወድቀዋል፤ አንድሱ አሁንም አለ፤ ሌለው ገና አልመጣም፤ በሚመጣበት ጊዜ ግን ለአጭር ጊዜ መቆየት ይገባዋል። 11 ቀድሞ የነበረው አሁን
ግን የሌለው አውሬ ራሱ ስምንተኛው ንጉሥ ነው ሆኖም፣ ከሰባቱ አንዱም ነው ወደ ጥፋትም ይሄዳል። 12 ያዩኋቸው አሥር ቀንዶች ገና መንግሥት ያልተቀበሉ
አሥር ነገሥታት ናቸው፤ ነገር ግን ለአንድ ሰዓት ያህል ከአውሬው ጋር እንዲነግሡ ሥልጣን ይቀበላሉ። 13 እነዚህ ነገሥታት ተመሳሳይ ሐሳብ አላቸው፤ ኅይልና
ሥልጣናቸውን ሁሉ ለአውሬው ያስረክባሉ። 14 በጉን ይዋጋሉ። ይሁን እንጂ፣ በጉ የጌቶች ጌታ የነገሥታት ንጉሥ በመሆኑ እርሱ ያሸንፋቸዋል የተጠሩት፣
የተመረጡትና ታማኝ የሆኑት ከእርሱ ጋር ድል ይነሣሉ።” 15 መልአኩም፣ “አመንዝራዋ ተቀመጣባቸው የነበሩት ያየሃቸው ውሆች ሕዝቦችና ሰዎች፣ ወገኖችና
ቋንቋዎች ናቸው” አለኝ። 16 ያየሃቸው አሥር ቀንዶች ከአውሬው ጋር አንድ ላይ ሆነው አመንዝራዋን ይጠላሉ። ያጠፏታል፤ ራቁትዋን ያስቀሯታል፤ ሥጋዋን
ይበላሉ፤ ጨርሶ እስክትጠፋ በእሳት ያቃጥሏታል። 17 ምክንያቱም፣ የእግዚአብሔር ቃል እስኪፈጸም ድረስ ሥልጣናቸውን ለአውሬው ለመስጠት በመስማማት
ዕቅዱን እንዲፈጽሙ እግዚአብሔር ይህን ሐሳብ በልባቸው ውስጥ አኑሮአል። 18 ያይየሃት ሴት በምድር ነገሥታት ላይ የምትገባ ታላቂቱ ከተማ ናት።”

Revelation 17:1

ራዕይ **17**፡ **1-2**
በብዙ ውሃዎች ላይ የሚተቀመጠው ታላቅቷ ጋለሞታ መላእኩ እየተናገረ ያለው የሐንስ ገና ስላላያት ሴት ነው። ይህች ሴት በ REV 17:5 ላይ እና በ REV 17:18. ላይ የተገለተውን ከተማ የሚትወክል ናት። ታላቅቷ ጋለሞታ አማራጭ ትርጉም: "ሁሉም ሰው ስለእርሷ የሚያውቀው ጋለሞታ ሴት" ወይም "ሁሉም ሰው የሚጠላት ጋለሞታዋ ሴት።" በብዙ ውኃዎች ላይ "ብዙ የውኃ መውረጫዎች ባሉበት" ወይም "ብዙ ወንዞች አጠገብ" ወይም "በወንዞች እና በባህሮች አጠገብ"

Revelation 17:3

ራዕይ **17**፡ **3-5**
ውድ ድንጋዮች እና እንቁዎች አማራጭ ትርጉም: "ብዙ ዓይነት ውድ ድንጋዮች" እንቁዎች ለስላሳ፣ ጠንካራ እና ነጭ ጨሌ በግምባርዋም ምስጢር የሆነ ስም አማራጭ ትርጉም: "የሆነ ሰው በግንባሯ ላይ ይህንን ስም ጽፏል" . ታላቅቷ ባቢሎን አማራጭ ትርጉም: "እኔ ታላቅቷ ባቢሎን ነኝ"

Revelation 17:6

ራዕይ **17**፡ **6-7**
ከደም ጋር ጠጣችው ይህ ማለት በኢየሱስ የሚያምኑ ብዙ ሰዎችን ጎድታለች እንዲሁም ገድላለች። ለኢየሱስ ሰማእታት የሆኑ "ለሌሎች ሰዎች ስለኢየሱስ በመናገራቸው ምክንያት የሞቱት አማኞች" ስለምን ተደነቅህ? አማራጭ ትርጉም: "ልትደነቅ አይገባህም" ወይም "እነዚህን ነገሮች ልተገነዘባቸው ይገባል"

Revelation 17:8

ራዕይ **17**:**8-8**
is about to come up ከዝቅተኛ ሥፍራ ወደ ከፍተኛ ሥፍራ የመንቀሳቀስ ጉዳይ ነው ወደ ላይ የመምጣት ጉዳይ ነው ከዝቅተኛ ሥፍራ ወደ ከፍተና ሥፍራ የመውጣት ጉዳይ ነው ስማቸው ያልተጻፈ ሰዎች . . . ዓለም ሳይፈጠር በፊት "ስማቸውን እግዚአብሔር ያልጻፈሰዎች . . . ዓለም ከመፈጠሩ በፊት።" ይህ ልሆን ነው ይህ ልመጣ እና እንዲህ ሆኖ ሊቀር ነው

Revelation 17:9

ራዕይ **17**፡ **9-10**
ሴትቱ የተቀመጠችባቸው ሰባት ተራሮች በዚህ ሥፍራ ላይ “ተቀመጠች” የሚለው ቃል ትርጉሙ ሴትቱ በእነዚ ሥፍራዎች እና ሰዎች ላይ ሥልጣን ነበራት ማለት ነው። ሰባት ነገሥታት እነዚህ ነገሥታት አንዱ ሌላኛውን ይከታተላል። በተመሳሳይ ጊዜ የሚኖሩ አይደሉም። አንዱ ይኖራል "አሁን አነንዱ ንጉሥ ነው"

Revelation 17:11

ራዕይ **17**፡ **11-11**
ዘንዶው . . . ራሱ ስምነተኛው ንጉሥ ነው፤ ይሁን አንጂ ከእነዚያ ሰባት ነገሥታት መካከል አንዱ ነው። ዘንዶው ከሰባቱ እንደ አንዱ ሆኖ ነግሦዋል ወይም ይነግሣል ከዚያም እንደ ስምንተኛ ንጉስም ሆኖ ይነግሣል። አማራጭ ትርጉም: አስቀድሞ የኖረው ዘንዶ እና በሕይወት ያሌለው ስምንተኛው ንጉሥ ሆኖ ይነግሣል። ልክ እንደ ሰባቱ ነገሥታት ክፉ ይሆል ነገር ግን እግዚአብሔር በእርግጠኝነት ያጠፋዋል።

Revelation 17:12

ራዕይ **17**፡ **12-14**
ዐሥር ነገሥታት እነዚህ ነገሥታት ከዘንዶው ጋር በተመሳሳይ ጊዜያት የሚገዙ ናቸው። ለአንድ ሰዓት በቋንቋችሁ አንድን ቀን በሃያ አራት ሰዓታትን መከፋፈያ መንገድ ካሌለ በባሕላችሁ ውስጥ በአንድ ቀን ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትን ከፋፍላችሁ በምትገልጡበት መንገድ ይህንን መግለጽ ትችላላችሁ። በጉ ያሸንፋቸዋል . . . እንዲሁም ከእርሱ ጋርም የተጠሩት፣ የተመረጡት፣ ተማኞች የሆኑት "በጉ—እና ከእርሱ ጋር የተጠሩት፣ የተመረጡት እና ታማኝ የሆኑት-አብረው ያሸንፋሉ"

Revelation 17:15

ራዕይ **17**፡ **15-15**
የተመለከትከው ውሃ ገለሞታዋ ሴት የተቀመጠችበት ነው ይህንን በ REV 17:1. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎም ተመልከት። ሰዎች . . . ብዙ ሕዝብ . . . ቋንቋዎች እነዚህ ሁሉ ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ናቸው፤

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

የተዘረዘሩትም አጽኖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም: "በዓለም ውስጥ ያሉ ሰዎች ሁሉ።"

Revelation 17:16

ራዕይ **17**፡ **16**-**17**
ጥላቻ ይህንን በ REV 2:6. ላይ ያለውን በተረጎምክበት መንገድ ተርጉመው። ባዶዋንና ራቁትዋን አድርግ "ያላትን ሁሉ ስረቃት እና ባዶዋን አስቀራት" ሥጋዋንም ይበላሉ፥ በእሳትም ያቃጥሉአታል። እነዚህ ሁለት ንዑስ ዓረፍተ ነገሮች ያላቸው ትርጉም እርሷን ፈጽሞ ማጥፋት ነው። የእግዚአብሔር ቃ ፍጻሜን እስኪያገኝ ድረስ አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር ይሆናል ያለውን ነገር እስኪሆን ድረስ"

Revelation 17:18

ራዕይ **17**፡ **18**-**18**

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **18**

1 ከዚህ በኋላ ሌላ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ። ታላቅ ሥልጣንም ነበረው፤ ምድርም በክብሩ አበራች። **2** በታላቅ ድምፅም ጮኾ እንደኢህ አለ፤ “ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች፣ ወደቀች! የአጋንንት መኖሪያ፣ የርኩሳን መናፍስት ሁሉ ማደሪያ፣ የማንኛውም ርኩስና ጠያፍ ወፍ መጠጊያ ሆነች **3** ሕዝቦች ሁሉ ቁጣ በሚያመጣበት የዝሙቷ ወይን ጠጅ ሰክረዋል። የምድር ነገሥታት ከእርሷ ጋር አመንዝረዋል። የምድር ነጋዴዎች በምቾት ኑሮዋ በልጽገዋል።” **4** ሌላ ድምጽም ከሰማይ እንዲህ ሲል ሰማሁ፤ “ሕዝቤ ሆይ፣ በኃጢአትዋ እንዳትካፈሉ የማመጣበትንም መቅሠፍት እንዳትቀበሉ ከእርሷ ውጡ። **5** ኃጢአቷ እስከ ሰማይ ተከምሯል እግዚአብሔር ክፉ ሥራዋን አስታውሷል። **6** በሰጠችው መጠን ስጧት፤ ባደረገችው መጠን ዕጥፍ አድርጉባት እርሷ በቀካቀከችው ጽዋ መጠን፣ ዕጥፍ አድርጋችሁ ቀላቅሉባት። **7** እርሷ ራስዋን እንዳከበረችውና በምቾት በኖረችው መጠን፣ የዚያኑ ያህል ስቃይና ሐዘን ስጧት እርሷ በልቧ ‘እንደ ንግሥት ተቀምጫለሁ መበለትም አይደለሁም ሀዘንም አይደርስብኝም’ ብላለች። **8** ስለዚህ፣ መቅሠፍቶችዋ በእብንድ ቀን ይደርሱባታል፣ ሞት፣ ሐዘንና ረሐብ ይመጡባታል። በእሳት ትቃጠላለች፤ እርሷ ላይ የሚፈርድ ጌታ እግዚአብሔር ብርቱ ነው” **9** ከእርሷ ጋር ያመነዘሩና ቅጥ ያጣ ሕይወት የኖሩ፣ የቃጠሎዋ ጭስ ሲወጣ ሲያዩ ስለ እርሷ እየጮኹ ያለቅሳሉ። **10** ሥቃይዋንም በመፍራት በሩቅ ቆመው፣ “ታላቂቱ ከተማ፣ አንቺ ብርቱ ከተማ በአንድ ሰዓት ውስጥ ቅጣትሽ መጥቷልና ወየልሽ ወየልሽ” ይላሉ። **11** ከእንግዲህ ሸቀጧን የሚገዛ ስለማይኖር የምድር ነጋዴዎች ለእርሷ ያለቅሳሉ፤ ያዝኑላታል፤ **12** ሸቀጦችዋ ወርቅ፣ ብር፣ የከበረ ድንጋይ፣ ዕንቁ፣ ቀጭን ልብስ፣ ሐምራዊ ጨርቅ፣ ሐር ጨርቅ፣ ቀይ ጨርቅ፣ ማንኛውም ዓይነት ጣፋጭ ሽታ ያለው እንጨት፣ ማንኛውም ከዝሆን ጥርስ የተሠራ ዕቃ፣ ማንኛውም ከከበረ ድንጋይ የተሠራ ዕቃ፣ ነሐስ፣ ብረት፣ እብነ በረድ **13** ቀረፋ፣ ቅመም፣ የሚሸር እንጨት፣ ከርቤ፣ ዕጣን፣ ወይን ጠጅ፣ ዘይት፣ንጹሕ ዱቄት፣ ስንዴ፣ ከብቶች፣ በጎች፣ ፈረሶችና ሰረገሎች ባሪያዎችና የሰዎች ነፍሶች ናቸው። **14** አጥብቀሽ የተመኘሻቸው ነገሮች ከአንቺ አምልጠዋል። ምቾትና ውበትሽ ጠፍተዋል ከእንግዲህም አይገኙም። **15** በእርሷ የበለጸጉ እነዚህን ዕቃዎች የሚነግዱ ሰዎች ሥቃይዋን በመፍራት ከእርሷ ርቀው በመቆም በታላቅ ድምፅ ያለቅሳሉ **16** እንዲህም ይላሉ “ቀጭን ልብስ፣ ሐምራዊና ቀይ ልብስ ትለብስ ለነበች፤ በመርቅ፣ በከበረ ድንጋይና በዕንቁ ታጌጥ ለነበረች ታላቂቱ ከተማ ወዮ ወዮ!” **17** በእብንድ ሰዓት ያ ሀብት ሁሉ ጠፍቷል። የመርከብ አዛዦች ሁሉ፣ በመርከብ የሚጓዙ ሰዎች ሁሉ፣ መርከበኞችና በባሕር ላይ የሚሠሩ ሁሉ ርቀው ቆሙ። **18** ያቀጠሎዋን ጭስ ሲመለከቱ፣ “ ታላቂቱን ከተማ የሚመስላት ማነው?” እያሉ ጮኹ። **19** በራሳቸውም ላይ ዐመጽ ነስንሰው እያለቀሱና እያዘኑ፣ መርከቦች ያሏቸውና በእርሷ ሀብት የበለጸጉ ሁሉ ታላቂቱ ከተማ በአንድ ሰዓት ስለ ወደመች ወዮላት ወዮላት” አሉ። **20** “ ሰማይ ሆይ ደስ ይበልህ፤ እግዚአብሔር ስለ እናንተ እርሷ ላይ ፈርዷልና እናንት ቅዱሳን፣ ሐዋርያትና ነቢያት ደስ ይበላችሁ!” **21** ከዚያም አንድ ብርቱ መልአክ ታላቅ የወፍጮ ድንጋይ የሚመስልን ድንጋይ እንዲህ በማለት ወደ ባሕር ወረወሬ፣ “ታላቂቱ ከተማ ባቢሎን በዚህ ሁኔታ በኅይል ተገፍታ ወደ ባሕር ትጣላለች፤ ከእንግዲህ ወዲህ ጨርሶ አትታይም **22** የበገና ደርዳሪዎች፣ የሙዚቀኞች፣ የዋሽንትና መለኮት ነፊዎች ድምፅ ከእንዲህ በአንቺ አይሰማም። ማንኛውንም ዓይነት የጥበብ ሥራ የሚሠራ በአንቺ አይገኝም። የወፍጮ ድምፅም በአንቺ አይሰማም። **23** የመብራት ብርሃን፣ ከእንግዲህ በአንቺ አያበራም። የሙሽራውና የሙሽራይቱ ድምፅ ከእንግዲህ በአንቺ አይሰማም። ነጋዴዎችሽ የምድር ልዑላን ነበሩ ሕዝቦችን በመተትሽ አሳስተሻል። **24** የነቢያትና የቅዱሳን ደም፣ በዚህ ምድር የተገደሉ ሰዎች ሁሉ ደም በእርሷ ተገኝቷል።

Revelation 18:1

ራዕይ **18**፡ **1-3**
የተጠሉ ወፎች "አስጠሊታ ወፎች" ወይም "ደስ የማይሉ ወፎች" ለሁሉም ሕዝቦች "በሁሉም ሀገራት ውስጥ ላሉ ሕዝቦች" ወይኑን ጠጡ . . . ከእርሷ ጋር ኢ-ግብረገባዊ የወሰብ ግንኙነት ፈጸሙ "ከባቢሎን ከተማ ጋር ተባበሩ እንዲሁም በኃጢአቷም ተባበሩ" ያ የእርሷን ፍርድ አመጣ "ይህም የእግዚአብሔር ፍርድ በእርሷ ላይ አመጣ" ነጋዴ የተለያዩ ነገሮችን የሚሸጥ ሰው በተንደላቀቀ ኑሮው ኃይል "በእርሷ ደስታ ላይ በጣም ብዙ ብር ከማውጣቱ የተነሣ"

Revelation 18:4

ራዕይ **18**፡ **4-6**
ሌላ ድምፅ "ሌላ ሰው፣" ምናባትም ኢየሱስ ወይም እግዚአብሔር አስታወሰ ይህንን በ REV 16:19. ላይ “ማስታወስ” የሚለውን ቃል በተረጎምክብ ምንገድ ተርጉመው። ብድሯን ክፈለት ተናጋሪው ምናልባት ለመላእክቱ እየጠናገረ ይሆናል ወይም በ(REV 17:16) ለተጠቀሱት ለዐሥሩ ነገሥታት እየተናገረም ሊሆን ይችላል ወይም ለራሱ እየተናገረ ሊሆን ይችላል። እጥፍ ድርብ ደርቡባት አማራጭ ትርጉም: "ሁለት እጥፍ ጠንካራ አድርጉት"

Revelation 18:7

ራዕይ **18**፡ **7-8**
ራሷን አክብራለች . . . ስጧጽ . . እንዲህ ብላለች . . . እኔ . .. እኔ . . እኔ ፈጽሞ አላይም . . . መቅሰፍት ይበላታል አማራጭ ትርጉም: "የባብሎን ሕዝቦች ራሳቸውን አክብረዋል . . . እኛ . . . እና . . እኛ ፈጽሞ አናይም . . . መቅሰፍት ይበላቸዋ።" እንደ ንግስት እቀመጣለሁ፤ እኔ ባልቴት አይደሉም እርሷ በራሷ ስልጣን ገዥ ናት፤ በሌላ ሰው ላይ ፈጽሞ አትደገፍም (እንዲህ ታስባለች)። እርሷ በእሳት ትበላለች አማራጭ ትርጉም: "እሳት ፈጽሞ ያቃጥላታል"

Revelation 18:9

ራዕይ **18**፡ **9-10**
የግብረስጋ ግንኙነትን በተመለከተ ኢ-ግብረገባው ነገርን የፈጸመ ሰው እና ከእርሷ ጋር ከቁጥጥር ውጪ የሆነ ሰው ይህ ማለት ነገሥታቱ እና ሕዝቦቻቸው ኃጢአትን ሠርተዋል እንዲሁም የባቢሎን ሕዝቦች እንዳደረጉት ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ አምጸዋል። ወዮላችሁ፣ ወዮላችሁ የቃላት ድግግሞሹ የሚያሳየው አጽኖት መሰጠቱን ነው።

Revelation 18:11

ራዕይ **18**፡ **11-13**
ለእርሷ አልቅሱላት "ለባብሎን ሕዝብ አልቅሱለት" እምነ በረድ ሕንጻ ለመገንባት የሚያገለግል ድንጋይ ቅመማ ቅመም ለምግብ ጣዕም ለመስጠጥ የሚጨመር ቅመም

Revelation 18:14

ራዕይ **18**፡ **14-14**
አንዚ . . . ፍሬ በዚህ ሥፍራ ላይ “አንዚ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የባብሎንን ሕዝብ ነው። በሙሉ ኃይልሽ የተመኘሽውቸ "በጣም መፈለግ" እንደገና መገኘት የማይችል አማራጭ ትርጉም: "እንደገና የአንች ሊሆኑ አይችሉም"

Revelation 18:15

ራዕይ **18**፡ **15**-**17**
እና አስጌጠውት ነበር አማራጭ ትርጉም: "ራሳቸውን አስግጠው ነበር" ወይም "ለብሰው ነበር" ውድ ጌጣ ጌጦች "ውድ የሆነ ጌጦች" ወይም "ውድ ዋጋ ያላቸው ጌጦች" ዕንቁዎች ይህንን በ REV 17:4. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምክ ተመልከት።

Revelation 18:18

ራዕይ **18**:**18**-**20**
“የእርሷን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የባቢሎንም ከተማ ነው። ከተማይተዋ ታላቅ ከተማ ትመስላለችን? አማራጭ ትርጉም: "እንደ ባቢሎን ያላ ታላቅ ከተማ የለም።".

Revelation 18:21

ራዕይ **18**፡ **21**-**22**
የወፍጮ ድንጋይ እህል ለመፍጨት የሚሆን ትልቅ ክብ ድንጋይ። ታላቂቱ ከተማ ባቢሎን እንዲህ ተገፍታ ትወድቃለች ከእንግዲህም ወዲህ ከቶ አትገኝም። እግዚአብሔር ከተማይቱን ፈጽሞ ያጠፋታል። አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር ባቢሎን በኃይል ገፍቶ ይጥላታል እና ከቶም አትገኝም" በገና የሚመቱና የሚዘምሩም ድምፅ እንቢልታንና መለከትንም የሚነፉ ድምፅ ከእንግዲህ ወዲህ በአንቺ አማራጭ ትርጉም: "በከተማችሁ ውስጥ ማንም ከእንግዲህ የሙዝቃ ድምፅ እንደገና አይሰማም።" የእጅ ጥበብም ሁሉ አንድ ብልሃተኛ እንኳ ከእንግዲህ ወዲህ በአንቺ ውስጥ ከቶ አይገኝም፥ የወፍጮ ድምጽም ከእንግዲህ ወዲህ በአንቺ ውስጥ ከቶ አይሰማም፥ አማራጭ ትርጉም: "በከተማችሁ ውስጥ ከእንግዲህ ሠራተኞች አይታዩም ዌም አይሰሙም"

Revelation 18:23

ራዕይ **18**፡ **23**-**24**
የሙሽራና የሙሽራይቱም ድምጽ ከእንግዲህ ወዲህ በአንቺ ውስጥ ከቶ አይሰማም አማራጭ ትርጉም: "ማንም ከእንግዲህ የሙሽራ እና የሙሽራይቱን ደስታ የሞላበት ድምፅ አይሰማም።" ነጋዴዎችሽ የምድር መኳንንት ነበሩና "በሌሎች ከተሞች የሚኖሩ ሰዎች ነጋዴዎችሽን ያከብራሉ" እንዲሁም በአስማትሽም አሕዛብ ሁሉ ስተዋልና። አማራጭ ትርጉም: "እንዲሁም በአስማቶችሽ አሕዛብን ሁሉ አስተሻልና" በእርስዋም ውስጥ የነቢያትና የቅዱሳን ደም በምድርም የታረዱ ሁሉ ደም ተገኘባት። አማራጭ ትርጉም: "ነቢያትን እና ቅዱሳንን እንዲሁም በዓለም ውስጥ ያሉትን ሌሎች ሰዎችን በመግደል እግዚአብሔር በደለኛ አድርጎሻል።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 19

1 ከእነዚህ ነገሮች በኋላ የበዙ ሰዎች ድምፅ የሚመስል ታላቅ ድምፅ ከሰማይ ሰማሁ “ሃሌ ሉያ ማዳን፣ ክብርና ኃይል የአምላካችን ነው። 2 በዝሙቷ ምድርን
ያረከሰችውን ታላቂቱን አመንዝራ ስለ ፈረደባት ፍርዱ እውነትና ትክክል ነው። እርሷ ያፈሰሰችውን የአገልጋዮቹን ደም ተበቅሎአል። 3 በድጋሚ “ሃሌ ሉያ፤ ጢስዋ
ከዘላለም እስከ ዘላለም ከእርሷ ይወጣል” በማለት ተናገሩ። 4 ሃያ አራቱ ሽማግሌዎችና አራቱ ሕያዋን ፍጡራን በግንባራቸው ተደፍተው፣ “አሜን ሃሌ ሉያ!”
በማለት ዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ሰገዱ። 5 ከዚያ በኋላ፣ “ታናናሾችም ታላላቆችም እርሱን የምትፈሩ አገልጋዮቹ ሁሉ እግዚአብሔርን አመስግኑ!” የሚል ድምፅ
ከዙፋኑ ወጣ። 6 ከዚያም እንደ ብዙ ሕዝብ ድምፅ፣ እንደ ብዙ ውሆች ድምፅና የብርቱ ነጎድጓድ የሚመስል ድምፅ እንዲህ አለ፤ 7 ደስ ይበለን፤ ሐሤት
እናድርግ፤ የበጉ ሰርግ ስለ ደረሰ ሙሽራዋም ራስዋን ስላዘጋጀች፤ ደስ ይበለን፤ ሐሤት እናድርግ ፤ ክብርንም እንስጠው።” 8 ደማቅና ቀጭን ንጹሕ ልብስ
እንድትለብስ ገሰጣት። ቀጭኑ ልብስ የቅዱሳኑ የጽድቅ ሥራ ነው። 9 መልአኩም፣ “ወደ በጉ ሰርግ እንደመጡ የተጋበዙ ሰዎች የተባረኩ ናቸው ብለህ ጻፍ”
አለኝ። በተጨማሪም፣ “እነዚህ እውነተኛ የእግዚአብሔር ቃሎች ናቸው” አለኝ። 10 እኔም ልሰግድለት በእግሩ ሥር ተደፋሁ፤ እርሱ ግን፣ “እንዳታደርገው! እኔ ራሴ
ከአንተና ስለ ኢየሱስ የተሰጠውን ምስክር ከያዙ ወንድሞችህ ጋር አገልጋይ ነኝ። ልችእግዚአብሔር ስገድ፤ ስለ ኢየሱስ የተሰጠው ምስክር የትንቢት መንፈስ
ነውና” አልኝ። 11 ከዚያም ሰማይ ተከፍቶ አየሁ፤ እነሆም አንድ ነጭ ፈረስ ተመለከትኩ ፈረሱ ላይ የተቀመጠው ታማኝና እውነተኛ ይባላል። በጽድቅ ይፈርዳል፤
ይዋጋል። 12 ዐይኖቹ እንደ እሳት ነበልባል ናቸው፤ ራሱም ላይ ብዙ አክሊሎች ነበሩ። ከእርሱ በቀር ማንም የማያውቀው ስም እርሱ ላይ ተጽፎ ነበር። 13 ደም
የተነከረ ልብስ ለብሶ ነበር፤ ስሙ የእግዚአብሔር ቃል ተብሎ ይጠራል። 14 ቀጭን፣ ነጭና ንጹሕ ልብስ የለበሱ ሠራዊት በነጫጭ ፈረሶች ተቀምጠው
ይከተሉት ነበር። 15 ከአፉም ሕዝቦችን የሚመታበት የተሳለ ሰይፍ ይወጣ ነበር፤ በብረት በትር ይገዛቸዋል። ሁሉን የሚገዛ የእግዚአብሔርን ቁጣ የወይን ጠጅ
መጭመቂያ ይረግጣል። 16 ልብሱና ጭኑ ላይ፣ የነገሥታት ንጉሥ፣ የጌቶችም ጌታ የሚል ስም ተጽፎበት ነበር። 17 አንድ መልአክ ፀሐይ ላይ ቆሞ አየሁ።
እርሱም በታላቅ ድምፅ፣ “ኑ፣ ወደ ታላቁ የእግዚአብሔር ግብዣ ተሰብሰቡ። 18 መጥታችሁ የነገሥታትን፣ የጦር አዛዦችን፣ ሥጋ የጎያላንን ሥጋ፣ የፈረሰኞችንና
በላያቸው የተቀመጡትን ሥጋ፣ የጌቶችን የባሮችን፣ የታናናሾችንና የታላላቆችን ሥጋ፣ የሰዎችን ሁሉ ሥጋ ብሉ።” 19 አውሬውንና ከእርሱም ጋር የምድር
ነገሥታትንና ሰራዊታቸውን አየሁ። ፈረሱ ላይ ተቀምጦ ከነበረውና ከሰራዊቱ ጋር ውጊያ ለመግጠም ተዘጋጅተው ነበር። 20 እነሆ አውሬው ተያዘ፤ ከእነርሱም ጋር
በእርሱ ፊት ምልክቶችን የሚያደርገው ሐሰተኛ ነቢይ ተያዘ። በእነዚህ ምልክቶች አማካይነት የአውሬውን ምልክት የተቀበሉትንና ለምስሉ የሰገዱትን አሳሳተ።
ሁለቱም በዲን ወደሚቃጠለው የእሳት ባሕር በሕይወት እያሉ ተጣሉ። 21 የተቀሩትም ፈረስ ላይ ከተቀመጠው አፍ በሚወጣው ሰይፍ ተገደሉ። ወፎችም ሁሉ
ሥጋቸውን በልተው ጠገቡ።

Revelation 19:1

ራዕይ **19**፡ **1-2**
ሰማሁ በሥፍራ ላይ “እኔ” የሚለው ቃል ዮሐንስን ያመለክታል። ሃሌሉያ የዚህ ቃል ትርጉሙ “እግዚአብሔር ይመስገን” ወይም “እግዚብሔር እናመስግን” ማለት ነው። ታላቂቷ ጋለሞታ ይህ በምድር ላይ ያሉትን ሌሎች ሰዎችን የሚመሩትን፣ ትክክለኛ ያልሆኑ አምልክትን እንዲያመልኩ የሚያደርጉትን ክፉ ሰዎችን የሚያመለክት
በምድር ላይ የተበላሹት አማራጭ ትርጉም: "በምድር ላይ ያሉ ሰዎችን የሚያበላሹት"

Revelation 19:3

ራዕይ **19**፡ **3-4**
ሃሌሉያ ይህንን በ REV 19:1 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። ከእርሷ ከዘላለም እስከ ዘላለም ይወጣልr "ከጣኦት አምላኪዎች ከዘላለም እስከ ዘላለም።" አማራጭ ትርጉም: "ራሳቸውን ጋለሞታ ካደረጉት እና ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ መካራን ከሚቀበሉት" ሃያ አራት ሽምግሌዎች አራት ሽማግሌዎች - 24 ሽማግሌዎች

Revelation 19:5

ራዕይ **19**፡ **5-5**
አምላካችን እግዚአብሔር ይመስገን በዚህ ሥፍራ “የእኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ተናጋሪውን እና ሁሉንም የእግዚአብሔር አገልጋዮችን ነው። ሁለቱም አላስፈላጊዎች እና ኃይለኞች ናቸው ተናጋሪው እነዚህ ቃላት በአንድነት የተተቀመው ሁሉንም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማመልከት ነው።

Revelation 19:6

ራዕይ **19**፡ **6-6**
ሃሌሉያ ይህንን በ REV 19:1. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት።

Revelation 19:7

ራዕይ **19**፡ **7-8**
ደስ ይበልን በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሁሉንም የእግዚአብሔር አገልጋዮችን ነው። ክብርን ስጡት "ለእግዚአብሔር ክብርን ስጡ" ለበጉ ሠረግ ድግስ...ሙሽራይቱ ለእርሱ ራሷን አዘጋጅታለች ይህ የኢየሱስ እና የእርሱ ሕዝብ ለዘላለም አብረው ለመሆን መገናኘታቸውን ያመለክታል። በግ ይህንን በ REV 5:6. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት።

Revelation 19:9

ራዕይ **19**፡ **9-10**
የበጉ ሠረግ ድግስ የሠርጉ ድግስ የኢየሱስ እና የእርሱ ሕዝብ ለዘላለም መገናኘታቸውን ያመለክታል። በምድር ላይ ተደፋሁ በምድር ላይ መደፋት ማለት ፊትን ወወደ ምድር በማድረግ መደፋት ሲሆን አክብሮትን እና ለመገልገል ፈቃደኝነተን ያሳያል። በ19:3 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

Revelation 19:11

ራዕይ **19**፡ **11-13**
ከዚያም የተከፈተ ሰማይ አየሁ ይህ ምስል የአዲስ ራዕይ ጅማሬን ለማሳየት ጥቅም ላይ ውሏል። ይህንን ሀሳብ በ REV 4:1, REV 11:19, እና REV 15:5. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። በደም የተነከረ ልብስን ለበሷል አማራጭ ትርጉም: "በደም የተጨማለቀ ልብስ ለብሷል" ወይም "በደም የተነከረ ልብስ ለብሷል"

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Revelation 19:14

ራዕይ **19**፡ **14**-**16**
ከአፉ ስለታም ሰይፍ ይወጣል ይህንን ሀረግ በ REV 1:16. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። አሕዛብንም ይመታበት "አሕዛብን አጠፋ" ወይም "አሕዛብን በእርሱ ቁጥጥር ሥር አደረጓቸው" በብረት በተር ይገዛቸዋል ይህንን በ REV 12:5. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። በልብሱና በጭኑም የተጻፈበት፦ የነገሥታት ንጉሥና የጌታዎች ጌታ የሚል ስም አለው። አማራጭ ትርጉም: "በልብሱ ላይ እና በጭኑ ላይ ስም ተጽፎበታል"

Revelation 19:17

ራዕይ **19**፡ **17**-**18**
የጌታዎችንና የባሪያዎችንም የታናናሾችንና የታላላቆችንም መላእክት እነዚህ ቃለት የተጠቀሙትን በአንድነት ሁሉንም ሰዎች ለማመልከት ነው።

Revelation 19:19

ራዕይ **19**፡ **19**-**20**

Revelation 19:21

ራዕይ **19**፡ **21**-**21**
የተቀሩት "የተቀሩት የአውሬው ወታደሮች" ከአፉ የሚወጣቸው ሰይፍ በ REV 1:16. ላይ ያለውን ተመሳሳይ ሀረግ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ **20**

1 ከዚህ በኋላ የጥልቁ መክፈቻ ያለው አንድ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ፤ በእጁም ትልቅ ሰንሰለት ይዞ ነበር። **2** ዘንዶውን ይዞ ሺህ ዓመት አሰረው፤ ይህ ዘንዶ ዲያብሎስ ሰይጣን የተባለው የቀድሞው እባብ ነው። **3** ወደ ጥልቁ ጣለው፤ ዘግቶም በእርሱ ላይ ማኅተም አደረገበት። ይህን ያደረገው ሺህ ዓመቱ እስኮፈጸም ድረስ ከእንግዚህ ሕዝቦችን እንዳያሳስት ነው። ከዚያ በኋላ ለአጭር ጊዜ መፈታት ይኖርበታል። **4** ከዚያም ዙፋኖች አየሁ። ዙፋኖቹም ላይ የመፍረድ ሥልጣን የተሰጣቸው ተቀምጠው ነበር። ለኢየሱስና ለእግዚአብሔር ቃል ምስክር የተሰየፉ ሰዎችን ነፍሶችንም አየሁ። ለአውሬው ወይም ለምስሉ አልሰገዱም፤ ምልክቱም ግንባራቸው ወይም እጃቸው ላይ እንዲያርግ አልፈቀዱም። ከሞት ተነሥተው፣ ለሺህ ዓመት ከክርስቶስ ጋር ነገሡ። **5** የተቀሩት ሙታን ግን ሺሁ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ ከሞት አልተነሡም። ይህ የመጀመሪያው ትንሣኤ ነው። **6** በመጀመሪያው ትንሣኤ ድርሻ የሚኖራቸው ሁሉ የተባረኩና የተቀደሱ ናቸው! እነዚህን በመሳሰሉት ላይ ሁለተኛው ሞት ኅይል አይኖረውም። የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ካህናት ይሆናሉ፤ ከእርሱም ጋር ሺህ ዓመት ይነግሣሉ። **7** ሸው ዓመት ካበቃ በኋላ ሰይጣን ከእስራት ይፈታል። **8** በአራቱ የምድር ማእዘን ያሉ ሕዝቦች ማለትም ጎግና ማጎግን ወደ ጦርነት ለማምጣት እያሳተ ወደ ጦርነት ለማምጣት ይወጣል ቁጥራቸውም እንደ ባሕር አሸዋ ያህል እጅግ ብዙ ነው። **9** እነርሱም ወደ ምድር ሁሉ ሄደው የቅዱሳንን ሰፈር፣ እንዲሁም የተወደደችውን ከተማን ከበቡ። ሆኖም፣ እሳት ከሰማይ ወርዶ በላቸው። **10** እነርሱን ያሳሳተው ዲያብሎስ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወደ ተጣለበት በዲን ወደሚነደው የእሳት ባሕር ተጣሉ። ቀንና ሌሊት ከዘላለም እስከ ዘላለም ይሰቃያሉ። **11** ከዚያም አንድ ታላቅ ነጭ ዙፋንና በላዩ የተቀመጠውን አየሁ። ምድርና ሰማይ ከፊቱ ሸሹ፣ ሆኖም፣ መሄጃ ቦታ አልነበራቸውም። **12** በዙፋኑ ፊት መታን፣ ታላላቆችና ታናናሾች ቆመው አየሁ፤ መጽሕፍትም ተከፈቱ። ከዚያም የሕይወት መጽሐፍ የተባለ ሌላም መጽሐፍ ተከፈተ። መታንም መጻሕፍቱም ውስጥ በተመዘገበው መሠረት እንደ ሥራቸው ተፈረደባቸው **13** ባሕር ውስጡ ያሉ ሙታንን ሰጡ። ሞትና ሲኦል ውስጣቸው ያሉትን ሙታን ስጡ፤ ሙታንም እንደ ሥራቸው ተፈረደባቸው። **14** ሞትና ሲኦል ወደ እሳቱ ባሕር ተጣሉ። የእሳቱም ባሕር ሁለተኛው ሞት ነው። **15** ስሙ በሕይወት መጽሐፍ ያልተገኘ ሁሉ ወደ እሳቱ ባሕር ተጣለ።

Revelation 20:1

ራዕይ **20**፡ **1**-**3**
ከዚያም አየሁ በዚህ ሥፍራ “እኔ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ዮሐንስን ነው። ጥልቅ እና ማለቂያ ያሌለው መንገድ ይህንን በ REV 9:1. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። ዘንዶ ይህን በ REV 12:3. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። አንድ ሺህ ዓመታት "1,000 ዓመታት" ነጻ ልወጣ ይገባዋ አማራጭ ትርጉም: "እርሱን ነጻ ለማውጣት መላእክቱን ያዛል"

Revelation 20:4

ራዕይ **20**፡ **4**-**4**
የታረደው አማራጭ ትርጉም: "ራሶቻቸው የተቈረጡባቸውን ሰዎች ነፍሳት፥"

Revelation 20:5

ራዕይ **20**፡ **5**-**6**
ሌሎች የሞቱት "ሁሉም የሞቱት ሰዎች" አንድ ሺህ ዓመቱ አለቀ "1000 ዓመቱ አለቀ" እንደነዚህ ባሉት ላይ ሁለተኛው ሞት ኃይል የለውም በዚህ ሥፍራ ላይ ዮሐንስ “ሞትን” የገለጸው በሰውኛ ኃይል ያለው አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም: "እነዚህ ሰዎች ሁለተኛው ሞት አያገኛቸውም" ሁለተኛው ሞት ይህንን በ REV 2:11. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት።

Revelation 20:7

ራዕይ **20**፡ **7**-**8**
በመሬት አራቱ መዓዘናት ላይ ይህንን በ REV 7:1. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። ጎግ ማጎግ በነብይ ሕዝቄል ውስጥ የተጠቀሱት የእነዚህ ሰዎች ስም ሩቅ ያሉ ሀገራትን ለመወከል ጥቅም ላይ ውለዋል። በባሕር ዳርቻ እንዳለ አሸዋ ብዙ ይሆናሉ ይህ በሴጣን ሠራዊት መካል ትልቅ ቁጥር ያለው አንድነት መኖሩን አጽኖት ይሰጣል።

Revelation 20:9

ራዕይ **20**፡ **9**-**10**
ወጡ "የሴጣን ሠራዊት ወጡ" ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር ተጣለ፥ ይህንን በ REV 19:20. ላይም ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት።

Revelation 20:11

ራዕይ **20**፡ **11**-**12**
ምድር እና ሰማይ ከእርሱ መገኘት ፊት ሸሹ፤ ነገር ግን ልሸሸጉበት የሚችሉበት ሥፍራ አልነበራቸውም ዮሐንስ ምድር እና ሰማይን ከእግዚብሔር ፍርድ ፊት ለመሸሸ ጥረት የሚደርጉ አድርጎ ስሏቸዋል። ይህ ማለት የእግዚአብሔር መገኘት አሮጌውን ሰማይ እና ምድር ፈጽሞ ያጠፋል። ታናናሾችንና ታላላቆችን የሐንስ እነዚህ ቃላት በማዋሃድ ለመግለጽ ያሰበው የሞቱትን ሰዎች ሁሉ ነው። መጽሐፉ ተከፈተ አማራጭ ትርጉም: "እናም መጽሐፉ ተከፈተ"

Revelation 20:13

ራዕይ **20**፡ **13**-**15**
የሞቱት ተፈረደባቸው አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር የሞቱት ሰዎች ላይ ፈረደባቸው" ሁለተኛው ሞት ይህንን በ REV 2:11. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምክ ተመልከት።

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 21

1 ከዚህ በኋላ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር አየሁ፤ ምክንያቱም የመጀመሪያው ሰማይና የመጀመሪያው ምድር አልፈው ነበር፤ ባሕርም ከእንግዲህ አልተገኘም። 2 ቅድስቲቱ ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ለባልዋ እንዳጌጠች ሙሽራ ተዘጋጅታ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ። 3 ከዙፋኑም እንዲህ የሚል ታላዝ ድምፅ ሰማሁ፣ “እነሆ የእግዚአብሔር መኖሪያ ከሰዎች ጋር ነው፤ ከእነርሱ ጋር ይኖራል። እነርሱ ሕዝቡ ይሆናሉ፤ እግዚአብሔር ራሱም ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል። 4 እንባን ሁሉ ከዐይናቸው ያብሳል፤ ከእንግዲህ ሞት፣ ወይም ሐዘን፣ ወይም ለቅሶ ወይም ሕመም አይኖርም። ምክንያቱም የቀድሞ ነገሮች አልፈዋል። 5 በዙፋኑ የተቀመጠው፣ “እነሆ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ” አለ። “እነዚህ ቃሎች የታመኑና እውነተኛ ስለሆኑ ጻፍ” አለ። 6 ለእኔም እንዲህ አለኝ፤”እነዚህ ሁሉ ተፈጽመዋል እኔ አልፋና ዖሜጋ፣ የመጀመሪያውም የመጨረሻውም ነኝ። ለተጠማ ሰው ከሕይወት ውሃ ምንጭ እንዲጠጣ ያለ ዋጋ እሰጣለሁ። 7 ድል የነሣ እነዚህን ነገሮች ይወርሳል፤ አምላኩ እሆናለሁ፤ እርሱም ልጄ ይሆናል። 8 ነገር ግን የፈሪዎች፣ የእምነተ ቢሶች፣ የርኩሶች፣ የነፍስ ገዳዮች፣ የአመንዝራዎች፣ የሚርተኞች፣ የጦዖት አምላኪዎችና የሐሰተኞኦች ቦታቸው በዲን በሚቃጠለው እሳት ባሕር ውስጥ ይሆናል። ይህም ሁለተኛው ሞት ነው። 9 የመጨረሻዎቹ ሰባት መቅሠፍቶች የሞሉበትን ሰባት ድዋዎች ከያዙት ሰባት መላእክት አንዱ ወደ እኔ መጥቶ፣ “ወደዚህ ና፣ የበጉን ሚስት ሙሽራዋን አሳይሃለሁ” አለኝ። 10 ከዚያም ወደ አንድ ታላቅና ከፍ ወዳለ ተራራ በመንፈስ ወሰደኝና ቅዱሳቲቱ ከተማ ኢየሩሳሌም ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አሳየኝ። 11 ኢየሩሳሌም የእግዚአብሔር ክብር ነበራት፤ የብርሃንዋ ፀዳል እጅግ እንደከበረ ድንጋይ፣ እንደ አያሰጲድ ድንጋይ ጥርት ያለ ነበር። 12 አሥራ ሁለት በሮች ያሉት በጣም ታላቅ ረጅም ግምብ ነበራት በየበሮቹ አሥራ ሁለት መላእክት ነበሩ። በእነርሱም ላይ የአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ልጆች ስሞች ተጽፈው ነበር። 13 በምሥራቅ ሦስት በሮች፣ በሰሜን ሦስት በሮች፣ በደቡብ ሦስት በሮች፣ በምዕራብ ሦስት በሮች ነበሩ። 14 የከተማዋ ግምብ አሥራ ሁለት መሠረቶች ነበሩት፤ በእነርሱም ላይ የአሥራ ሁለቱ የበጉ ሐዋርያት ስሞች ተጽፈው ነበር። 15 ከእኔ ጋር ይነጋገር የነበረው መልአክ ከተማዋን፣ በሮቹንና ቅጥሮቹን የሚለካበት የወርቅ ዘንግ ነበረው። 16 ከተማዋ አራት ማእዘን ነበረች፤ ርዝመትና ስፋቱ ዕኩል ነበር። በመለኪያ ዘንጉ ሲለካ ርዝመቱ 12,000 ምዕራፍ ሆነ (ርዝመቱ፣ ስፋቱና ከፍታዋ ዕኩል ነበር)። 17 ቅጥሯን ስለካ ስፋቱ በሰው መለኪያ (ይህም የመላእክት መለኪያም ነው) 144 ክንድ ሆነ 18 ቅጥሩ ከኢያሰጲድ፣ ከተማዋም እንደ መስተዋት በጠራ ንጹሕ ወርቅ የተሠራች ነበረች። 19 የቅጥሩ መሠረቶች በከበሩ ድንጋዮች ያጌጡ ነበር። የመጀመሪያው ኢያሰጲድ፣ ሁለተኛው ሶንፔር፣ ሦስተኛው ኬልቄዶን፣ አራተኛው መረግድ 20 አምስተኛው ሰርደንክስ፣ ስድስተኛው ሰርድዮን፣ ሰባተኛው ክርስቲሎቤ፣ ስምንተኛው ቢረሌ፣ ዘጠነኛው ወራውሬ፣ አሥረኛው ክርስጵራስስ፣ አሥራ አንደኛው ያክንት፣ አሥራ ሁለተኛው አሜቴስ ቲኖስ ነበረ። 21 አሥራ ሁለቱም በሮች፣ አሥራ ሁለት ዕንቁዎች ነበሩ፤ እያንዳንዱ በር ከአንድ ዕንቁ የተሠራ ነበር። የየከተማዋ መንገዶች ጥርት እንዳለ መስተዋት ንጽሕ ወርቅ ነበሩ። 22 በከተማዋ ምንም መቅደስ አላየሁም፤ ምክንያቱም ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላክና በጉ መቅደሷ ነበሩ። 23 የእግዚአብሔር ክብር ስለሚያበራለት ከተማዋ የፀሐይ ወይም የጨረቃ ብርሃን አልነበራትም፤ ምክንያቱም በጉ ራሱ ብርሃንዋ ነው። 24 ሕዝቦችም በዚያች ከተማ ብርሃን ይመላለሳሉ። የምድር ነገሥታት ክብራቸውን ወደ እርሷ ያመጣሉ። 25 በሮቿ በቀን አይዘጉም፤ በዚያ ሌሊት የለም። 26 የመንግሥታትን ግርማና ክብር ወደ እርሷ ያመጣሉ 27 ርኩስ ነገር በፍጹም አይገባባትም። ጸያፍ ወይም አታላይ ወደዚያ አይገባም፤ ወደዚያ የሚገቡት ስሞቻቸው በበጉ የሕይወት መጽሐፍ የተጻፈ ብቻ ናቸው።

Revelation 21:1

ራዕይ **21**፡ **1**-**2**
አየሁ በዚህ ሥፍራ ላይ “እኔ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ዮሐንስ ነው። ልክ ሙሽሪት ለባሏ እንደሚትዋብ ሁሉ ይህ አዲስቷ ኢየሩሳሌም በጣም የተዋበች መሆኗን አጽኖት ሰጥቶ ያመለክታል።

Revelation 21:3

ራዕይ **21**፡ **3**-**4**

Revelation 21:5

ራዕይ **21**፡ **5**-**6**
አልፋ እና ኦሜጋ፣ መጀመሪያ እና መጨረሻ እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን አጽኖት ሰጥተው የሚያስተላልፉት መልዕክትም እግዚአብሔር ዘላለማዊ መሆኑነ ነው። . አልፋ እና ኦሜጋ ይህንን በ REV 1:8. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። የተተማ ቢኖር . . . የሕይወት ውሃ ይህ ማለት እግዚአብሔር ለሚፈልግ ሁሉ በነጻ የዘላለም ሕይወት ይሰጣል።

Revelation 21:7

ራዕይ **21**፡ **7**-**8**
የሚፈሩት "ትክክለኛ የሆነውን ነገር ለማድረግ በጣም የሚፈሩ ሰዎቸ" ርኩሳን "መጥፎ ነገር የሚያደርጉ ሰዎች" በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው፤ ይህንን በ REV 19:20. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። ሁለተኛው ሞት ይህን በ REV 2:11. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት።

Revelation 21:9

ራዕይ **21**፡ **9**-**10**
ሙሽራ፣ የበጉ ምስት በበዚህ ሥፍራ ላይ የጋብቻ ምስሉ የሚያመለክተው ኢሱስ ከሕዝቡ ጋር መሆኑን እና በእርሱ ቅዱስ ከተማ ለዘላለም እንደሚኖር ነው። በግ ይህንን በ REV 5:6. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። ከዚያም በመንፈስ ወሰደኝ ይህንን በ REV 17:3. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት።

Revelation 21:11

ራዕይ **21**፡ **11**-**13**
ኢየሩሳሌም "ሰማያዊዋ ኢየሩሳሌም" ወይም "አዲስቷ ኢየሩሳሌም" ብርጭቆ ይህንን በ REV 4:6. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢያሰጲድ ይህንን በ REV 4:3.ላይ ምን ብለህ እደተረጎምከው ተመልከት። ዐሥራ ሁለት በሮች "12 በሮች" ተጽፏል አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር ጽፎታል"

Revelation 21:14

ራዕይ **21**፡ **14**-**15**
በግ ይህ ኢየሱስን የሚያመለክት ነው። ይህንን በ REV 5:6. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Revelation 21:16

ራዕይ **21**፡ **16**-**17**
ምዕራፍ እስታዲዬም 185 ሜትሮች ነው። ክዩብs አንድ ክዩብ 46 ሴንቲሜተር ነው።

Revelation 21:18

ራዕይ **21**፡ **18**-**20**
ኢያሰጲድ፥ . . . ሰንፔር፥ . . . ኬልቄዶን፥ . . . መረግድ፥ እነዚህን በ REV 4:3. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምክ ተመልከት። አምስተኛው ሰርዶንክስ፥ ስድስተኛው ሰርድዮን፥ ሰባተኛው ክርስቲሎቤ፥ ስምንተኛው ቢረሌ፥ ዘጠነኛው ወራውሬ፥ አሥረኛው ክርስጶራስስ፥ አሥራ አንደኛው ያክንት፥ አሥራ ሁለተኛው አሜቴስጢኖስ ነበረ። እነዚህ ውድ ጌጣ ጌጦች ናቸው።

Revelation 21:21

ራዕይ **21**፡ **21**-**22**
ዕንቁዎች ይህንን በ REV 17:4. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከተ። ጌታ እግዚአብሔር . . . እና በጉ መቅደሳቸው ነው ቤተ መቅዱስ የእግዚአብሔርን መገኘት ይወክላል። ይህ ማለት አዲስቷ ኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ አያስፈልጋትም ማለት ነው ምክንያቱም እግዚአብሔር እና ቤተ መቅዱስ በዚያ ይኖራሉና።

Revelation 21:23

ራዕይ **21**፡ **23**-**25**
በጉ ብርሃን ነውና ይህ ማለት የኢየሱስ ክብር ለከተማይቱ ብርሃንም ይሆናል። ደጆቿ አይዘጉም አማራጭ ትርጉም: "ደጆቿን ማንመ አይዘጋቸውም"

Revelation 21:26

ራዕይ **21**፡ **26**-**27**
ንጹሕ ያልሆነ ምንም ነገረ ፈጽሞ አይገባባትም "ንጹሕ የሆነ ነገር ብቻ ነው ወደዚህች የሚገባው" ይሁን እንጂ በበበጉ የሕይወት መጽሐፍ ላይ ስማቸው የተጻፉት ብቻ አማራጭ ትርጉም: "ነገር ግን በጉ ስማቸውን በሕይወት መዝገብ ላይ ብቻ የጻፋቸው ብቻ" በጉ ይህን በ REV 5:6. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምክ ተመልክት።

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

ምዕራፍ 22

1 ከዚያም መልአኩ፣ እንደ መስተዋት የጠራውን የሆነውን የሕይወት ውሃ ወንዝ አሳየኝ። ወንዙም የሚወጣው ከእግዚአብሔርና ከበጉ ዙፋን ነበር 2 በከተማዋ
ዋና መንገድ መካከል ያልፍ ነበር። በወንዙ ግራና ቀኝ አሥራ ሁለት ወር ሙሉ አሥራ ሁለት ዓይነት ፍሬ የሚሰጥ የሕይወት ዛፍ ነበር። የዛፉ ቅጠሎች ሕዝቦችን
ሁሉ ይፈውሱ ነበር። 3 ከእንግዲህ ምንም ዐይነት መርገም አይሆንም። የእግዚአብሔርና የበጉ ዚፋን ከተማው ውስጥ ይሆናሉ፤ አገልጋዮቹም ያገለግሉታል። 4
ፊቱን ያያሉ፤ ስሙም ግንባሮቻቸው ላይ ይሆናል። 5 ከእንግዲህ ሌሊት አይሆንም፤ ጌታ አምላክ ስለሚያበራላቸው የመብራት ወይም የፀሐይ ብርሃን
አያስፈልጋቸውም። ከዘላለም እስከ ዘላለም ይነግሣሉ። 6 መልአኩም እንዲህ አለኝ፤ “እነዚህ ቃሎች የታመኑና እውነተኛ ናቸው። ጌታ፣ የነቢያት መናፍቅ አምላክ
ቶሎ መሆን ያለበትን ለአገልጋዮቹ እንዲያሳያቸው መልአኩን ላከ።” 7 “እነሆ፣ ቶሎ እመጣለሁ! ለዚህ መጽሐፍ የትንቢት ቃሎች የሚታአእ የተባረከ ነው። 8
እነዚህን ነገሮች የሰማሁና ያየሁ እኔ ዮሐንስ ነኝ። እነዚህን በሰማሁና ባይብሁ ጊዜ እነዚህን ነገሮች ላሳየኝ መልአክ ለመስገድ በፊቱ ተደፋሁ። 9 እርሱ ግን፣
“እንዳታደርገው! እኔ ራሴ ከወንድሞችህ ከነቢያት ጋር፣ ለዚህ መጽሐፍ ቃል ከሚታዘዙት ጋር አብሬ አገልጋይ ነኝ። ይልቅ ለእግዚአብሔር ስገድ አለኝ!” 10
እንዲህም አለኝ፤ ጊዜው በጣም ቅርብ ስለሆነ የዚህን መጽሐፍ የትንቢት ቃሎች በማኅተም አትዝጋው። 11 ዐመፀኛው ማመፁን ይቀጥል። ርኩሱም ርኩሰት
ማድረጉን ይቀጥል። ጻድቁም ጽድቅ የሆነውን ማድረጉን ይቀጥል። ቅዱስም ቅዱስ መሆን ይቀጥል። 12 “እነሆ፣ ቶሎ እመጣለሁ። ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው
የምከፍለው ዋጋ ከእኔ ዘንድ አለ። 13 እኔ አልፋና ዖሜጋ፣ ፊተኛውና ኋለኛው፤ የመጀመሪያውና የመጨረሻው ነኝ። 14 ከሕይወት ዛፍ ለመብላትና በበሮቿ ወደ
ከተማዋ ለመግባት መብት እንዲኖራቸው ልብሳቸውን የሚያጥቡ የተባረኩ ናቸው። 15 ውሾች፣ ጠንቋዮች፣ አመንዝራዎች፣ ነፍሰ ገዳዮች፣ ጣዖት አምላኪዎችና
ሐሰትን የሚወዱና የሚያደርጉ ግን በውጭ አሉ። 16 እኔ ኢየሱስ ለእናንተ እንዲመሰክር መልአኬን ወደ አብያተ ክርስቲያናት ላክሁ። እኔ የዳዊት ሥርጥ ዘር ነኝ፤
የሚያበራም የንጋት ኮከብ ነኝ።” 17 መንፈሱና ሙሽራይቱ፣ “ና!” ይላሉ፤ የሚሰማ ሁሉ፣ “ና!” ይበል። ማንም የተጠማ ቢኖር ይምጣ፣ የሚፈልግ የሕይወትን
ውሃ በነጻ ይውሰድ። 18 የዚህን መጽሐፍ ትንቢት ለሚሰሙ ሁሉ እኔ እመሰክራለሁ፣ ማንም ትንቢቱ ላይ ቢጨምር እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ የተጻፉትን
መቅሠፍቶች ይጨምርበታል። 19 ማንም ከዚህ መጽሐፍ ትንቢት ቢያጎድል እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ ከተጻፈው የሕይወት ዛፍና ቅድስት ከተማ ዕድሉን
ያጎልበታል። 20 ለእነዚህ ነገሮች የሚመሰክር እርሱ፣”አዎን! ቶሎ እመጣለሁ” አሜን! ጌታ ኢየሱስ ሆይ ና! ይላል። 21 የጌታ ኢየሱስ ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን

Revelation 22:1

ራዕይ **22**፡ **1-2**
አሳየኝ በበዚህ ሥፍራ ላይ “እኔ” የሚለው ቃል የሕንስ ያመለክታል። እንደ ብርጭቆ ንጹሕ ይህንን በ REV 4:6. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። በግ ይህንን REV 5:6.በ ላይ ምን ብለህ እደተረጎምከው ተመልከት። ዐሥራ ሁለት ዓይነት ፍራፍሬ "12ዓይነት ፍራፍሬ"

Revelation 22:3

ራዕይ **22**፡ **3-5**
አገልጋዮቹ እርሱን ያገለግላሉ “እርሱ” ለሚለው ቃል አማራጭ ትርጉሞች 1) እግዚብሔር አብን ያመለክታል ወይም 2) በጉ የሆነውን እግዚአብሔር ያመለክታል ዌም 3) አባት የሆነው እግዚአብሔርን እና በግ የሆነውን ሁለቱም በጋራአንድ ሆነው የሚገዙትን ያመለክታል።

Revelation 22:6

ራዕይ **22**፡ **6-7**
እነዚህ ቃላት የታመኑ እና እውነተኞች ናቸው ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነውን በ REV 21:5. ላይ የሚገኘውን ሀረግ ምን ብለህ እንደተረጎምክ ተመልከት። ተመልከት! እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ከዚህ ዓረፍተ ነገር በፊት ያለው የጥያቄ ምልክት በቁጥር 6 እና ቁጥር 7 ላይ የተናጋሪ ለውጥ መኖሩን ያመለክታል። በቁጥር 7 ላይ በ UDB. ላይ በተገለጸው መሠረት ተናጋሪው ኢየሱስ ነው።

Revelation 22:8

ራዕይ **22**፡ **8-9**
ስግደት ይህ በምድር ላይ መውደቅ እና መደፋትን ያመክታል። ይህ የአምልኮ ወሳኝ ክፍል ነው እንዲሁም አክብሮትን እና ለማገልገል ፈቃደኛ መሆንን ያሳያል።

Revelation 22:10

ራዕይ **22**፡ **10-11**
እንዲህ አለኝ "መልአኩ እንዲህ አለኝ"

Revelation 22:12

ራዕይ **22**፡ **12-13**
አልፋ እና ኦሜጋ፣ የመጀመሪያ እና መጨረሻ፣ ጅማሬ እና ፍጻሜ እነዚህ ሦስት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው ኢየሱስ ለዘላለም ኗሪ መሆኑን ያሳያል። . አልፋ እና ኦሜጋ ይህንን በ REV 1:8. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምክ ተመልከት። መጀመሪያ እና መጨረሻ ይህንን በ REV 1:17. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምክ ተመልከት። ጅማሬ እና ፍጻሜ ይህንን በ REV 21:6. ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምክ ተመልከት።

Revelation 22:14

ራዕይ **22**፡ **14-15**
ልብሳቸውን ያጠቡ . . . ከሕይወት ዛፍ ይበላሉ መንፈሳዊ ንጽሕና ያላቸው ሰዎች በዘላለም ሕይወት ፍሬ ይበላሉ። ከውጪ ይህ ማለት ከከተማ ውጪ ማለት ሲሆን ወደ ውስጥ ለመግባት አይፈቀድም ማለት ነው። ውሻዎች በዚያ ባሕል ውስጥ ውሻ ንጹሕ ያልሆነ እና የሚጠላ ነው። ይህ መጥፎ የሆኑ ሰዎችን ለመወከል የሚውል ቃል ነው።

Revelation 22:16

ራዕይ **22**፡ **16-16**
ለአናንተ ለመመሰክር በዚህ ሥፍራ ላይ “እናንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር አምልካች ቃል ነው። የዳዊት ሥፍ እና ዘር “ሥር” እና “ዘር” የሚሉት ቃላት በመሠረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ቃላት ናቸው። ሁሉም አጽኖት ሰጥተው የሚገልጹተ ኢየሱስ ከዳዊት ቤተሰብ የመጣ መሆኑን ነው። . ደማቅ የትዋት ኮከብ ይህ ጥዋት በማለዳ የሚትታየውን ደማቅ ኮከብ የሚያመለክት ነው። ይህም የቀን ብርሃን በቶሎ እንደሚወጣ አመልካች ነው። በተጨማሪም ይህ ኢየሱስ መስሑ መሆኑን ያሳያል።

Revelation 22:17

ራዕይ **22**፡ **17-17**
የተጠማ ቢኖር . . . የሕይወት ውሃ ይህ ማለት እግዚአብሔር የዘላለም ሕይወትን በእርግጥ ለሚፈልግ ሁሉ በነጻ ይሰጣል ማለት ነው።

Revelation 22:18

ራዕይ **22**፡ **18**-**19**
እመሰክራለሁ በዚህ ሥፍራ ላይ “እኔ1 የሚለው ቃል የሞመለክተው የሕንስን ነው። ማንም በእነዚህ ላይ ቢጨምር . . . ማንም ቢቀንስ ይህ በዚህ ትንቢት ላይ ለውጥ እንያደረግ ጠንካራ ማስጠንቀቂያ ነው። ስለዚህ መጽሐፍ የተጻፉ "በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የጻፍኳቸው"

Revelation 22:20

ራዕይ **22**፡ **20**-**21**
ኖት የለውም

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Language: Brazilian Português

Book: Genesis

Genesis

Capítulo 1

1 No princípio, Deus criou os céus e a terra. A terra era sem forma e vazia. **2** Havia escuridão sobre a face do abismo, e o Espírito de Deus Se movia sobre a superfície das águas. **3** Deus disse: "Haja luz". E houve luz. **4** E Deus viu que a luz era boa; então, separou a luz da escuridão. **5** Deus chamou a luz dia e chamou a escuridão noite. Houve manhã e anoitecer, o primeiro dia. **6** E Deus disse: "Que haja firmamento entre as águas, e haja separação entre águas e águas". **7** E Deus fez o firmamento e separou as águas que estavam debaixo do firmamento das águas que estavam em cima do firmamento. E assim aconteceu. **8** E Deus chamou o firmamento de céus. Houve manhã e anoitecer, o segundo dia. **9** E Deus disse: "Ajuntem-se as águas debaixo do céu, num só lugar, e apareça porção seca". E assim aconteceu. **10** Deus chamou a porção seca de terra e, ao ajuntamento das águas, de mares. E Deus viu que isso era bom. **11** E Deus disse: "Produza a terra vegetação, plantas que deem sementes e árvores frutíferas que deem frutos, conforme a sua espécie, cuja semente esteja no fruto". E assim aconteceu. **12** A terra produziu vegetação, plantas que davam semente, segundo a sua espécie, e árvores frutíferas cuja semente estava no seu fruto. E Deus viu que isso era bom. **13** Houve manhã e anoitecer, o terceiro dia. **14** Deus disse: "Haja luzeiros no firmamento dos céus para separar o dia da noite; que sirvam como sinais para estações, dias e anos. **15** Que sejam luzeiros no firmamento dos céus para iluminar a terra". E assim aconteceu. **16** Deus fez dois grandes luzeiros: o maior para governar o dia e o menor para governar a noite. Também fez as estrelas. **17** Deus os colocou no firmamento dos céus para iluminar a terra, **18** para governar o dia e a noite e separar a luz da escuridão. E Deus viu que isso era bom. **19** Houve manhã e anoitecer, o quarto dia. **20** Deus disse: "Que haja multidões de criaturas vivas nas águas, e que as aves voem por cima da terra, abaixo do firmamento dos céus". **21** Deus criou os grandes animais marinhos e todos os seres viventes que se movem e que povoam as águas, segundo as suas espécies; e todas as aves, segundo as suas espécieis. E Deus viu que isso era bom. **22** E Deus os abençoou, dizendo: "Sede frutíferos, multiplicai-vos e enchei as águas dos mares. Que as aves multipliquem-se na terra". **23** Houve manhã e anoitecer, o quinto dia. **24** E Deus disse: "Que a terra produza seres viventes, cada um de acordo com sua própria espécie: animais domésticos, animais selvagens e os demais seres vivos da terra; cada um de acordo com a sua própria espécie. E assim aconteceu". **25** Deus fez os animais selvagens da terra, conforme a sua espécie, os animais de criação, conforme a sua espécie, e os demais seres vivos da terra, conforme a sua espécie. Ele viu que isso era bom. **26** E disse Deus: "Façamos o homem à Nossa imagem, conforme a Nossa semelhança. Que ele exerça domínio sobre os peixes do mar, sobre as aves dos céus, sobre todos os animais de criação, sobre toda a terra e sobre todos os seres vivos que rastejam sobre a terra". [1]**27** Deus criou, então, o homem a Sua imagem, à imagem de Deus o criou; macho e fêmea Deus os criou. **28** Deus os abençoou e lhes disse: "Sede frutíferos e multiplicai-vos, enchei a terra e subjugai-a. Dominai sobre todos os peixes do mar, sobre as aves dos céus e sobre todo ser vivente que rasteja pela terra". **29** Deus disse: "Eis que vos tenho dado todas as plantas que dão semente que estão sobre a face de toda a terra e todas as árvores que dão frutos com semente; elas vos servirão de alimento. **30** Para todos os animais selvagens da terra, para todas as aves dos céus, para todos os seres vivos que rastejam pela terra, e para todas as criaturas que têm fôlego de vida, toda planta verde lhes será por alimento". E assim aconteceu. **31** E viu Deus tudo quanto fizera, e eis que isso era muito bom. Houve manhã e anoitecer, o sexto dia.

Footnotes

1:26 [1]Algumas cópias antigas trazem:

---

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Genesis 1:1

No princípio Deus criou os céus e a terra
"È sobre como Deus fez os céus e a terra no princípio." Essa declaração sumariza o resto do capítulo. Algumas linguagens a traduzem como "Ha muito tempo atrás Deus criou os céus e a terra." Traduzindo-a de uma forma que mostra que isso realmente ocorreu e que não é apenas uma historia comum.

No princípio
Se refere ao início do mundo e tudo nele.

Os céus e a terra
"O céu, a terra, e tudo neles".

Céus
Se refere ao céu.

Sem forma e vazia
Deus nao havia posto o mundo em ordem.

O abismo
"A água" ou "a água profunda" ou " a água vasta.

As águas
"a água" ou "a face das águas".

Genesis 1:3

"Que haja luz"
È um comando. Comandando que a luz deveria existir, Deus a fez existir Ver:

Deus viu a luz, e ela era boa
"Deus observou a luz e ficou grato por dela" "Bom" aqui significa "agradável" ou "adequado".

Separou a luz da escuridão
"Separou a luz da escuridão" ou "fez a luz em uma hora e a escuridão em outra." Se refere a Deus chamando a luz de dia e a escuridão de noite.

Passou a noite e a manhã, o primeiro dia
Deus fez essas coisas no primeiro dia que o universo existiu.

Dia e noite
Se refere ao dia completo. O esritor fala do dia todo como se ele fosse dividido em duas partes. Na cultura Judaica o dia começa quando o sol se põe.

Genesis 1:6

Que haja firmamento entre as águas, e haja separação entre águas e águas.
Essas são Ordens. Ordenando que o firmamento entre as águas deveria existir e que as águas deveriam se separar, Deus fez o firmamento separou as águas.

Entre as águas
"Na água".

Deus fez o firmamento e separou as águas
"Desta forma Deus fez o firmamento e separou as águas." Quando ele falou, aconteceu. Esta sentença explica o que Deus fez quando ele falou.

E assim foi
"Aconteceu dessa forma" ou "foi isso que aconteceu." O que Deus ordenou ocorreu da forma que ele disse que deveria. Essa frase aparece através do capítulo e tem o mesmo significado onde quer que apareça.

Dia e noite
Se refere ao dia completo. O escritor fala do dia todo como se ele fosse dividido em duas partes. Na cultura Judaica o dia começa quando o sol se põe. Veja como você traduziu em 1:3 (Ver: Merism)

O segundo dia
Se refere ao segundo dia que o universo existiu. Veja como você traduziu " O primeiro dia" em 1:3 e decida se você deveria traduzir este da mesma forma.

Genesis 1:9

"Que as águas debaixo do céu sejam juntamente unidas"
Pode ser traduzido como um verbo ativo. Isto é uma ordem.Ordenando que as águas se juntassem, Deus fez elas se juntarem. Tradução Alternativa(TA:) "Que as águas debaixo do céu sejam juntamente unidas" (UDB) ver and

E apareça porção seca
A água havia coberto a terra. Agora a água deveria se mover e alguma terra seria descoberta. É uma ordem. Ordenando que a porção seca deveria aparecer, Deus a fez aparecer. TA: "Que a terra fique visível" ou "Que a terra torne-se limpa" ou "Que a terra seja descoberta"

Porção seca
Se refere a terra que nao estava coberta com água. Não se refere a terra que estava muito seca para agricultura.

E assim foi
"Aconteceu dessa forma" ou "foi isso que aconteceu." O que Deus ordenou ocorreu da forma que ele disse que deveria. Essa frase aparece através do capítulo e tem o mesmo significado onde quer que apareça. Traduza isto como é em 1:6

terra
"terra" ou "solo"

Ele viu que era bom
Aqui se refere a terra e mar. Veja como você traduziu isso em 1:3

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

Genesis 1:11

Que a terra gere a vegetação
È uma ordem. Ordenando que a vegetação deveria ser gerada na terra, Deus a gerou. TA: "que a vegetação se gere na terra" ou "que a vegetação cresca na terra"

vegetação: plantas que deem sementes, árvores que dão frutos
"Vegetação, cada planta que deem sementes e árvores que dão frutos" ou "vegetação. Que elas sejam plantas que produzam sementes e árvores frutíferas que produzam frutos." "Vegetação" é usado aqui como um termo geral para todas as plantas e árvores.

plantas
São tipos de vegetação que tem hastes suaves, não hastes de madeira.

árvores que dão frutos, cada uma de acordo com seu próprio tipo
"Àrvores que dão frutos com sementes neles."

cada uma de acordo com seu próprio tipo
As sementes produzirão plantas e árvores que serão de acordo com as quais elas vieram. Desta forma as plantas e árvores irão "se reproduzir por sí só" (UDB)

E assim foi
"Aconteceu dessa forma" ou "foi isso que aconteceu." O que Deus ordenou ocorreu da forma que ele disse que deveria. Essa frase aparece através do capítulo e tem o mesmo significado onde quer que apareça. Traduza isso como está em 1:6

Deus viu que era bom
"Deus observou a vegetação, plantas e árvores. Veja como você traduziu isto em 1:9

Dia e noite
Se refere ao dia completo. O escritor fala do dia todo como se ele fosse dividido em duas partes. Na cultura Judaica o dia começa quando o sol se põe.Veja como você traduziu isto em 1:3(Ver: Merism)

o terceiro dia
Se refere ao terceiro dia que o universo existiu.O primeiro dia" em 1:3 e decida se você deveria traduzir este da mesma forma.

Genesis 1:14

Que haja luzes no céu
È uma ordem. Ordenando que a luz deveria existir, Deus a fez existir.

luzes no céu
"Coisas que brilham no céu" ou "coisas que dão luz no céu". Se refere ao sol, a lua e as estrelas.

no céu
"Na vastidão do céu" ou "no vasto espaço do céu"

para separar o dia da noite
"para dividir o dia da noite." Isso significa "para nos ajudar a dizer a diferença entre dia e noite." O sol significa que é hora do dia, e a lua e as estrelas que é hora da noite.

Que sirvam como sinais
È uma ordem. Ordenando que eles deveriam servir como sinais, Deus fez eles servirem de sinais. TA: "Que eles sirvam como sinais" ou "que eles mostrem"

sinais
Aqui significa algo que revela ou aponta alguma coisa.

estações
"Estações" se refere a tempos que estão marcados paras festivais ou coisas que as pessoas fazem

para estações, dias e anos
O sol, a lua, e as estrelas mostram a passagem do tempo. Isso nos permite saber quando é a hora para eventos que ocorrem semanalmente, mensalmente ou anualmente

Que haja luzes no céu para iluminar a terra
È uma ordem. Ordenando que deveria haver luz na terra, Deus o fez .

para iluminar a terra
"Para disseminar luz pela terra" ou "para iluminar a terra." A terra não tem luz própria mas ela reflete luz.

E assim foi
"Aconteceu dessa forma" ou "foi isso que aconteceu." O que Deus ordenou ocorreu da forma que ele disse que deveria. Essa frase aparece através do capítulo e tem o mesmo significado onde quer que apareça. Veja como você traduziu isso em 1:6

Genesis 1:16

Deus fez duas grandes luzes
"Desta forma Deus fez duas grandes luzes." Essa sentença explica o que Deus fez quando ele falou.

duas grandes luzes
"As duas luzer grandes" ou " as duas luzes brilhantes." As duas grandes luzes são o sol e a lua.

para governar o dia
"Para dirigir o dia como um ditador dirige um grupo de pessoas" ou " para marcar o tempo do dia"

Dia
se refere às horas do dia

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

a menor
"a luz pequena" ou "a luz menor".

no céu
"No paraíso" ou "no espaço aberto do céu".

separar a luz da escuridão
"dividir a luz da escuridão" ou "fazer a luz em uma hora e a escuridão em outra". Veja como foi traduzido em 1:3.

Deus viu que isso era bom
Aqui "isso" se refere ao sol, a lua e as estrelas. Veja como foi traduzido em 1:3.

noite e manhã
Isso se refere ao dia completo. O escritor fala do dia todo como se ele fosse dividido em duas partes. Na cultura judaica, um dia começa quando o sol se põe. Veja como foi traduzido em 1:3. (Veja: Merism)

o quarto dia
Isso se refere ao quarto dia da existência do universo. Veja como foi traduzido "o primeiro dia" em 1:3 e decida se você deveria traduzir isso da mesma maneira.

Genesis 1:20

Que haja multidões de criaturas vivas nas águas
Isso é uma ordem. Ordenando que seres vivos deveriam encher as águas, Deus as fez existir. Algumas linguagens podem possuir uma palavra que se refere a todos os tipos de peixes e animais marinhos. TA: "Que as águas sejam cheias de criaturas vivas" ou "Que todos os animais que andam vivam nos oceanos"

que as aves voem
É uma ordem. Ordenando que os pássaros deveriam voar, Deus os fez voar.

Aves
"Animais que voam" ou "coisas voadoras"

Por cima da terra
"O espaço vago do céu" ou "o céu"

Deus criou
"Desta forma Deus criou"

grandes animais aquáticos
"Grandes animais que vivem no mar"

segundo suas espécies
Coisas vivas da mesma "espécie" são como aqueles dos quais eles vieram.Veja como você traduziu "Espécie" em 1:11

Segundo suas espécies
"Cada ser voador que tenha asas." Se a palavra para pássaros é usada, pode ser mais natural em algumas linguagens simplesmente dizer "todos os pássaros" uma vez que todos os pássaros tem asas.

Deus viu que isso era bom
Aqui se refere a passários e os peixes. Veja como você traduziu isso em 1:3

Genesis 1:22

os abençoou
"Abençoou os animais que ele fez"

Sejais frutíferos e multiplicai-vos
Essa é a benção de Deus. Ele mandou os animais do mar produzirem mais animais do mar iguais a eles mesmos, então haveriam vários deles no mar. A palavra "multiplicar" explica como eles podem ser frutíferos".

multiplicai-vos
"aumentar grandemente em número" ou "ficar em maior número"

Que as aves multipliquem-se
È uma ordem. Ordenando que as aves deveriam se multiplicar, Deus as fez se multiplicar.

aves
"animais que voam" ou " coisas voadoras". Veja como você traduziu isso em 1:20

Passou noite e manhã
Se refere ao dia completo. O escritor fala do dia todo como se ele fosse dividido em duas partes. Na cultura Judaica o dia começa quando o sol se põe.Veja como você traduziu isso em 1:3 (veja:Merism)

o quinto dia
Deus fez essas coisas no quinto dia que o universo existiu. Veja como foi traduzido "o primeiro dia" em 1:3 e decida se você deveria traduzir isso da mesma maneira.

Genesis 1:24

Que a terra produza criaturas vivas
"Que a terra produza coisas vivas" ou "Que vários animais vivam na terra." È uma ordem. Ordenando que a terra deveria produzir criaturas vivas, Deus fez a terra produzir criaturas vivas. ver

cada uma de acordo com sua própria espécie
"Então que cada espécie de animal produzirá mais de sua própria espécie"

animais domésticos, criaturas rastejantes, e animais selvagens na terra
Isso mostra que Deus criou todas as espécies de animais. Se a sua linguagem tem outra forma de nomear grupos de animais, você pode usar esta forma nesses grupos.

generated on Sat Aug 12 21:42:18 2023

animais domésticos
"animais que as pessoas procuram"

criaturas rastejantes
"animais pequenos"

animais selvagens
"animais não domésticos" ou "animais perigosos"

E assim aconteceu
